WOLF LESLAU

# ENGLISH-AMHARIC CONTEXT DICTIONARY

To

CHARLOTTE

ELIANE SYLVIA

LISA MONIQUE LYNN CHRISTINE

*Every other author may aspire to praise; the lexicographer can only hope to escape reproach, and even this negative recompense has been granted to very few.*

SAMUEL JOHNSON
Preface to a Dictionary of the English language

# PREFACE

Amharic is the national language of Ethiopia. The scientific investigation of Amharic goes back to the 17th century, but little attention was given to furnishing the student with practical tools for the acquisition of the language.

The most recent English-Amharic dictionaries are those of C. H. Armbrüster, *Initia Amharica*, part II, 1910, and of C. H. Walker, *English-Amharic Dictionary*, 1928. Since these publications Amharic has developed considerably. The progress that Ethiopia has made in the field of education, the literary documents of the last fifty years, the technical needs for new expressions, the contact with the Western world, and the natural development within the language itself have contributed greatly not only to the enrichment of the language but also to numerous changes within the existing vocabulary. A few examples taken from Armbrüster's dictionary illustrate the changes in the expressions. Thus, 'address' is rendered in Armbruster by ምልክት in contrast with the present-day አድራሻ; 'bank' ግምጃ ፡ ቤት as against ባንክ; 'bicycle' የሰይጣን ፡ ፈረስ as against ቢሲክሌት; 'cigarette' በወረቀት ፡ የተጠቀለለ ፡ ትምባሆ (lit. 'tobacco that is wrapped in paper') as against ሲጃራ; 'coin' መሐለቅ as against ሳንቲም; 'doctor' ባለ ፡ መድኀኒት as against ሐኪም or ዶክተር; 'general' ደጃዝማች as against ጄኔራል; 'map' ያገር ፡ ሥዕል as against ካርታ; 'sea' የውኃ ፡ ባሕር as against ባሕር; 'story of a house' ደርብ as against ፎቅ, and many more.

Needless to say, in Armbruster's time there was no need for expressions such as 'United Nations, Trusteeship committee, Security Council, control tower, review of books, agenda, airlines, basketball, elevator', and so on. Moreover, the practical interest in Amharic has increased in the last few decades. If to all this we add the fact that at present English is the language of instruction in the high schools of Ethiopia as well as at the University, we can easily justify the urgent need for a modern English-Amharic dictionary.

The most useful approach to the understanding of English lexical items and to the translation process from English into Amharic appears to be to illustrate English words in context, that is, in a sentence showing the usage of the word, rather than simply to enumerate the various Amharic renderings of any given single English lexeme. This is particularly important wherever a single English lexeme varies in meaning according to the context of the sentence. A few examples bear out the point.

The English 'box' can be rendered by ሰንዱቅ ፡ ፓኮ and by በቡጢ ፡ መመታት. It is only the context that helps the reader to choose the appropriate Amharic expression. Thus, in the sentence, "Shall I put the shoes in a box?" ጫማዎቹን ፡ ሰንዱቅ ፡ ውስጥ ፡ ላድርጋቸውን, 'box' is rendered by ሰንዱቅ. In the sentence, "I have another box of cigars" ሌላ ፡ ፓኮ ፡ ሲጋራ ፡ አለኝ, 'box' is rendered by ፓኮ. Finally, in the sentence, "A box on the ear hurts" ጆሮ ፡ ላይ ፡ በቡጢ ፡ መመታት ፡ ያሳምማል, 'box' is rendered by በቡጢ ፡ መመታት.

Or, the English 'draw' can be rendered in Amharic by ሳበ ፡ ሣለ ፡ ቀዳ ፡ አወጣ ፡ ተጣጣለ ፡ አስገባ ፡

አተረፈ ፤ ማረከ ፤ መዘዘ, and probably by other expressions. Here again, only the context helps the reader to choose the appropriate expression. Thus, "The horses draw the wagon" ፈረሶቹ ፡ ሰረገላ ፡ ይስባሉ; "He drew a picture of his teacher" ያስተማሪውን ፡ ሥዕል ፡ ሣለ; "The boy drew water from the well" ልጁ ፡ ከጉድጓድ ፡ ውኃ ፡ ቀዳ; "He drew his hands from his pockets" እጆቹን ፡ ከኪሱ ፡ አወጣ; "They drew lots to see who should go first" መጀመሪያ ፡ ማን ፡ እንደሚሄድ ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉ; "You should draw fresh air into your lungs" ንጹሕ ፡ አየር ፡ ወደ ፡ ሳምባህ ፡ ማስገባት ፡ አለብህ; "His speech drew long applause" ንግግሩ ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ጭብጨባ ፡ አተረፈለት; "Her elegant dress drew the eyes of all onlookers" ያሸበረቀው ፡ ልብሷ ፡ የተመልካቾቹን ፡ ዓይን ፡ ሁሉ ፡ ማረከ; "He drew his sword and ran at the enemy" ጐራዴውን ፡ መዞ ፡ ወደ ፡ ጠላቱ ፡ ሮጠ.

The ambiguity of meaning applies to many English lexemes, and it therefore dictated the principle of using the lexeme in context.

The various meanings of the same English lexeme were taken from the existing English dictionaries. Sentences were chosen to illustrate the various meanings. Nevertheless, not all the meanings of the same lexeme were always considered, since to do so would have greatly increased the bulk of the dictionary. Occasionally, a sentence is limited to a specific situation. See, for example, 'incidence' where the sentence refers to 'a high incidence' only; or 'going, get going' is limited in reference to holding a conversation. The verb 'adulterate' (no. 2) refers only to adulteration of meat, but of course in Amharic for other kinds of food the verb 'adulterate' has to be translated differently.

In other situations, a main entry has to supplement a subentry or the other way around. Thus, in the entry 'inhospitable', the sentence of the subentry 'be inhospitable' refers only to the desert, but if the reader needs to translate 'be inhospitable' speaking of a host in relation to his guests, he must choose the translation of the main entry 'inhospitable' አስተናጋጅነት ፡ የጐደለው and convert the relative የጐደለ into the verb ጐደለ. Or, in the entry 'reasonable', it is evident that the subentry 'be reasonable' illustrated with the sentence "chicken is reasonable this week" refers to a specific situation. The translation of the verb 'be reasonable' in any other context is made possible by using any of the five adjectives translating 'reasonable' by the addition of ነው 'he is'.

There are sentences illustrating a lexeme in which the context does not seem to vary from the standpoint of English, but nevertheless require different Amharic translations. See the entry 'attitude', or 'uncover', nos. 3 and 4.

It is true that some lexemes have only one meaning and an illustrative sentence may not have been necessary. For other entries, the sentence may be considered superfluous since it is not meaningful, as "my father left for Harar" to illustrate the noun 'father' አባት. However, it is interesting to see that the same Amharic አባት is also used in the sentence "God is called Our Father," but in the sentence "I talked with Father Giyorgis about the church", 'father' is rendered by አባ.

For the sake of consistency I therefore thought it advisable to illustrate every word with a sentence. An additional reason for doing so was to provide the learner of Amharic as well as the Ethiopian student studying English with concrete illustrations.

An exception has been made for a few categories, such as the numerals (outside of the numerals 1 to 12 referring to time), certain animals, and a few isolated words.

## INFORMAL USAGE, SLANG

The English usage is mostly that of American English. Likewise, the orthography is that of American English.

Expressions that are considered informal in a dictionary such as "The Holt's Intermediate Dictionary of American English" are occasionally included. Thus, 'close call'; 'easy' in 'take it easy'; 'fancy' as in 'fancy rates,' and so on.

Slang expressions are not given.

## TECHNICAL EXPRESSIONS

Technical expressions in the fields of technology, mechanics or exact sciences are not included since normally Amharic would use the foreign word. Thus, 'electrodynamics, electron, helium, hydrogen, biopsy, biochemistry' will not be found in the dictionary. However, the everyday expressions dealing with electricity, cars, and telephone are included even though most of them are foreign loanwords.

## TRANSLATION

The translation of each sentence was checked with several translators. The main objective was to have a correct translation of the English sentence in idiomatic Amharic. Needless to say, because of stylistic preferences, various translators rendered the same sentence differently. Only one translation was chosen in order to keep the bulk of the dictionary within bounds.

For many words, Amharic offered only an approximate translation and thus the translation proved to be pale.

Since the main objective is a correct translation in idiomatic Amharic, stylistic and syntactic divergencies between the English sentences and the Amharic translations are inevitable. Only a few examples illustrate this point.

"He *banged* his fist *on* the table" ጠረጴዛውን ፡ በቡጢ ፡ መታው (English *bang on*, Amharic መታ with the direct object).

"*Under the guise of friendship*, he plotted treachery" ወዳጅ ፡ መስሎ ፡ ክሕደትን ፡ አሰበ (lit. "looking like a friend").

"Donations *are welcome*" እርዳታ ፡ እንቀበላለን (lit. "we accept help" or "donation").

"It is evident *that he cannot come*" ለመምጣት ፡ አለመቻሉ ፡ ግልጽ ፡ ነው (lit. "his not being able to come").

"*His brief* was printed in the newspaper" የሰጠው ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ በጋዜጣ ፡ ታተመ (lit. "the brief that he gave").

"Can you discriminate *good books from bad*?" መጥፎና ፡ ጥሩ ፡ መጽሐፎችን ፡ ለመለየት ፡ ትችላለህ? (lit. "bad and good books").

"You will be surprised *how he changed*" እንዴት ፡ እንደተለወጠ ፡ ብታይ ፡ ይገርምሃል (lit. "if you see how he changed").

"The boy's apology *conciliated the angry father*" የልጁ ፡ ይቅርታ ፡ መጠየቅ ፡ ያባቱን ፡ ንዴት ፡ አበረደ (lit. "appeased the father's anger").

"*What* is the frequency of the Addis Ababa station?" የአዲስ ፡ አበባ ፡ ሬዲዮ ፡ ጣቢያ ፡ ድግግሞሽ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው? (lit. "how much?)".

"*She is in the work* heart and soul" ሥራዋን ፡ ከልቧ ፡ ትሠራለች (lit. "she does her work").

"*He is* thirty years of age" ሠላሳ ፡ ዓመቱ ፡ ነው (lit. "his age is").

"She waited *at the street corner* for a bus" በመንገድ ፡ ዳር ፡ ቆማ ፡ አውቶቡስ ፡ ጠበቀች (lit. "standing at the street corner").

## GEEZ AS SOURCE OF NEW EXPRESSIONS

Geez morphological patterns as well as the Geez vocabulary are occasionally used for the creation of new expressions. Thus, the passive participle *qətul* is used in : ንኡስ ፡ ኮሚቴ 'subcommittee', ጽሑፍ 'article', እሙን 'axiom'.

Verbal nouns with *-ot*, *-o* : በጎ ፡ አድራጎት 'welfare', አድናቆት 'admiration', አክብሮት 'respect',

አኅጽሮተ ፡ ቃል (in the so-called construct state) 'abbreviation', አድልዎ 'bias', ኀልዮ 'theory', ተጋድሎ 'campaign', ተጽዕኖ 'influence', በአርምሞ ፡ ተቀበለ 'acquiesce'.

Geez construct state : ክፍለ ፡ አገር 'region', ክፍለ ፡ ዘመን 'century', ሥረ ፡ ነገር 'bottom of things', ከበረ ፡ በዓል 'celebration'. A reversed construct state, that is, the Amharic word order with the *-ä* of the Geez construct state : ውስጠ ፡ ደንብ 'bylaw', ውስጠ ፡ ኅሊና 'subconscience', ግብረ ፡ አበር 'accomplice', አንደበተ ፡ ርቱዕነት 'eloquence'.

With an adjective as second element : መሠረተ ፡ ቢስ 'baseless', መንፈሰ ፡ ርጉ 'calm', ዓይነ ፡ ስውር 'blind'.

## CALQUE TRANSLATIONS

With the spread of foreign languages, and particularly of English, it is to be expected that calque translations are being used in Amharic. Examples : 'weekend' የሳምንት ፡ መጨረሻ; 'cross-examination' መስቀለኛ ፡ ጥያቄ; 'slide rule' ተንሸራታች ፡ መሥመሪያ, and others.

Of particular interest is the usage of the verb ወሰደ 'take'. The example of ወምበር ፡ ውሰድ for 'take a seat!' is recognized by most Ethiopians as a calque and is frowned upon. The verb ወሰደ 'take' seems to be extended in usage, however, and it is at times difficult to decide whether we are faced with a calque translation or a correct Amharic expression. Thus, for instance, 'take' is idiomatically translated by ፈጀ in the sentence, "it took the firemen two hours to put out the blaze" ቃጠሎውን ፡ ለማጥፋት ፡ የእሳት ፡ አደጋው ፡ ሠራተኞች ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ፈጀባቸው. However, 'take' is rendered by ወሰደ in the sentence "the wound took a long time to heal" ቁስሉ ፡ እስኪሽር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወሰደ. The question arises whether this is a calque translation or whether it is idiomatic Amharic.

Another important question is the plural marker. Amharic does not normally use the plural marker. Thus, "there are many trees in this park" is normally rendered by በዚህ ፡ መናፈሻ ፡ ቦታ ፡ ብዙ ፡ ዛፍ ፡ አለ. There is, however, an increasing tendency to use the plural marker *-očč*, a tendency that is probably due to the influence of foreign languages. The above-mentioned sentence is translated by በዚህ ፡ መናፈሻ ፡ ቦታ ፡ ብዙ ፡ ዛፎች ፡ አሉ. Or, in the sentence "they raise fine cattle in this country" በዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ጥሩ ፡ ከብቶች ፡ ያረባሉ, 'cattle' has the plural marker. Whether the tendency to use the plural marker is due to the influence of a foreign language or whether it is a natural development within Amharic itself can be ascertained only by examining the writings of authors who are not familiar with a foreign language.

## CULTURE-BOUND TRANSLATIONS

Many English expressions cannot be translated into Amharic because the object or the institution does not exist in Ethiopian culture. Thus, there is no way of translating 'jury' or 'cheese' in Amharic, since the institution of jury does not exist in the legal system of Ethiopia, and Amharic አይብ is really not 'cheese'. The method adopted in the dictionary is to give an explanation in brackets (see 'ale, allergy, delta, galley'), or to use an existing loanword as in the case of 'cheese' rendered by ፎርማጆ, Italian 'formaggio', even though some loanwords are rarely used outside the confines of the literate class of Ethiopians.

Likewise complicated is the rendering of lexemes that are not equivalent in English and Amharic. This is the case of 'winter' and 'summer'. Neither the time nor the character of the continental winter or summer corresponds to the seasons in Ethiopia. The only recourse was to translate 'winter' by ክረምት (actually 'the rains' from July to September) and 'summer' by በጋ (actually 'the dry season').

It is due to the culture-bound phenomena that no literal translation can be given for certain English expressions. This is the case of 'temperate climate' in the sentence "we live in a *temperate climate*"

rendered by የምኖርበት ፡ ቦታ ፡ ወይና ፡ ደጋ ፡ ነው, but ወይና ፡ ደጋ (the intermediate region between highland and lowland) applies only to Ethiopia.

The sentence, "write the alphabet in *reverse* order" is rendered by ፊደሎቹን ፡ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በተራ ፡ ጻፋቸው because the Ethiopian student when studying the alphabet writes it from top to bottom.

The expression 'period' is translated by አራት ፡ ነጥብ 'four dots' in the sentence, "you forgot to put a *period* here" እዚህ ፡ አራት ፡ ነጥብ ፡ ማድረግ ፡ ረሳህ because Amharic uses four dots where English uses a period.

The sentence, "I did not get your *last name*" rendered by ያባትህ ፡ ስም ፡ አልሰማሁም means literally "I did not get your father's name" because the last name in Western culture is in reality the father's name in Ethiopian culture.

The expression 'hang out' is rendered by አሰጣ 'spread out on the ground' in the sentence "she was *hanging out* the wash when I came" ስመጣ ፡ የታጠበ ፡ ልብስ ፡ ታሰጣ ፡ ነበር because the Ethiopian woman spreads out the wash near the river instead of hanging it out. The verb ሰቀለ 'hang out' could probably be used in the sentence, but the verb አሰጣ 'spread out on the ground' is a more natural expression.

Another interesting lexeme inherent to Amharic is the verb 'borrow' or 'lend'. While English uses the same verb for borrowing money or objects, Amharic differentiates between borrowing money or grain (ተበደረ) and borrowing objects (ተዋሰ). The same differentiation is expressed for lending money or grain (አበደረ) and lending objects (አዋሰ).

English 'empress' expresses both the wife of an emperor or a woman who rules an empire. Amharic differentiates between the two meanings using እቴጌ for the wife of an emperor, and ንግሥተ ፡ ነገሥታት for a woman ruler. In the entry 'empress', in the first sentence the empress Menen was the wife of the emperor (therefore እቴጌ) whereas in the second sentence Zawditu was empress in her own right (therefore ንግሥተ ፡ ነገሥታት).

## LOANWORDS

The purist will probably object to the listing of loanwords in the dictionary. These loanwords are, however, normally used in the language and no systematic attempt has been made to replace them with Amharic expressions. There are about 300 loanwords in the dictionary from English, French and Italian.

## NEW EXPRESSIONS

There are many English lexemes for which there is no Amharic equivalent, mostly because they are culture-bound expressions. An attempt was made to create an Amharic equivalent, as in the case for 'dessert' ማጣጣሚያ; 'dressing (for salad)' ማጣፈጫ; 'lawn' የግቢ ፡ መስክ; 'oasis' የበረሃ ፡ ገነት, and others.

Other lexemes are ad-hoc creations, such as 'brochure' መግለጫ ፡ ጽሑፍ; 'leaflet' ጽሑፍ (also 'article in a newspaper'); 'diagram' ሥዕላዊ ፡ መግለጫ; 'dock' የመርከብ ፡ ማራገፊያ; 'drain' የእጣቢ ፡ መውረጃ, and others.

## ORTHOGRAPHY AND PUNCTUATION

An important decision had to be made in the domain of the orthography of Amharic. The Amharic alphabet has various letters representing originally only consonants, some of which have become iden-

tical in pronunciation. This is the case of አ and ዐ (letters that have lost their consonantal value and serve mainly when a word must be written with an initial vowel); ሀ, ሐ and ኀ pronounced *h*; ሠ and ሰ pronounced *s*; ጸ and ፀ pronounced *ṣ*. As a result of the identical pronunciation of these letters, there is lack of consistency in Amharic spelling. There are three possible solutions in dealing with Amharic spelling : 1, a radical reform of the alphabet; 2, the adoption of the commonly accepted orthography; and 3, the standardization of spelling through etymology.

In a radical reform of the alphabet, wherever there is a choice of two or three letters for the same pronunciation, one would have to adopt arbitrarily only one letter, regardless of the origin of the root. Thus, if in the case of አ and ዐ, one were to choose, say, the letter አ, one would have to write አሰረ 'imprison', አወቀ 'know', አይን 'eye', all with the አ, even though አወቀ goes back to Geez ዖቀ (with ዐ), and አይን likewise goes back to Geez ዐይን (cognate with Semitic *'ayn*). Similarly, if between ሠ and ሰ one were to choose ሰ, one would have to spell ተሳለ 'vow' and ተሳለ 'be painted' both with ሰ, even though etymologically ተሳለ 'vow' goes back to Geez ሰአለ, and ሣለ 'paint' goes back to Geez ሠዐለ. The same arbitrary principle would have to be applied to the other letters that have become identical in pronunciation. I did not feel that I could use this solution in a dictionary that is intended for use by Amharic speakers.

The orthography currently and commonly accepted is highly unsatisfactory. Indeed, not only different speakers of Amharic, but even the same speaker will spell indiscriminately እኅት and እሀት 'sister', ደኅና and ደህና 'well', ባህል and ባሕል 'culture', ሐቀኛ and ሀቀኛ 'just', ዐወቀ and አወቀ 'know', and so on. In this connection it is interesting to mention two authoritative dictionaries published by Ethiopian scholars. Abba Yohannəs Gäbrä Egzi'abəher (አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር) in his መዝገበ ፡ ቃላት ፤ ትግርኛ—አምሐርኛ (a Tigrinya-Amharic dictionary) spells the Amharic verbs አሰረ (p. 46), አደረ (p. 47), አሰፈ (p. 49), all with አ, whereas Kidanä Wäld Kəfle (ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ) in his መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ አዲስ (A Geez-Amharic dictionary) spells the same words with ዐ; thus, ዐሰረ (p. 470), ዐደረ (p. 473), and ዐሰፈ (p. 478). Incidentally the word for 'Amharic' is spelled አማርኛ (with አ) by Abba Yohannəs Gäbrä Egzi'abəher, but ዐማርኛ (with ዐ) by Käsate Bərhan Täsämma (ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ተሰማ) in his የዐማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት (Amharic-Amharic dictionary), p. 979. On the basis of this evidence it seems to me that it is not practical to follow the normally accepted spelling.

I decided to adopt the principle of standardization through etymologies even though this principle, too, presents certain pitfalls. In the case of አ and ዐ, Geez as well as Tigre and Tigrinya and the other Semitic languages could be used as guides for correct spelling. In the case of ሀ (*h*), ሐ (*ḥ*) or ኀ (*ḫ*), only Geez (and Arabic) could serve as a guide since Tigre and Tigrinya retain only ሀ *h* and ሐ *ḥ*, this last sound representing a merger of ሐ *ḥ* and ኀ *ḫ*. For ሠ and ሰ as well as for ጸ and ፀ, Geez alone could serve as source of information, since in both Tigre and Tigrinya ሠ and ሰ are represented as ሰ *s*, and ጸ and ፀ have merged into ጸ *ṣ*. It is on the basis of this principle that I adopted spellings such as ዐወቀ 'know' (Geez ዖቀ), ዐሥር 'ten' (G. ዐሥር), እኅት 'sister' (G. እኅት), ሦስት 'three' (G. ሠለስቱ), ሕንጻ 'building' (G. ሕንጸ), ሕፃን 'baby' (G. ሕፃን), እቃ 'things, baggage' (Tigrinya እቕሓ), ዕድል 'fortune, luck' (Tigrinya ዐደለ), and so on. Less generally accepted spellings are those of ዐጠፈ 'double', ዐጨደ 'mow', ዕንጨት 'wood', and ዓውሎ ፡ ነፋስ 'whirlwind', but here again the spelling with ዐ was adopted because these roots have an ዐ as first radical in Geez : ዐጠፈ ፤ ዐፀደ ፤ ዕፅ and ዐውሎ, respectively.

Special mention should be made of ሠራ 'work, do', and its derivatives ሥራ 'work' (noun), ሠራተኛ 'worker', መሣሪያ 'tool', all with ሠ. It is true that this root is the closest connected with Geez ሰርሐ 'labor, endeavor' (with ሰ), but it can also be connected with Geez ሠርዐ 'arrange, dispose' (with ሠ). If one adds to it the fact that the most frequently used Amharic spelling is ሠራ (with ሠ), I thought it advisable to spell it with ሠ.

The Amharic verb for 'to take a rest, to die' is spelled አረፈ (with አ) even though the root is ዐረፈ. The spelling with አ is justified since Amharic አረፈ comes from አዐረፈ becoming አረፈ, the አ of which is that of the prefixed morpheme of the አ-stem. The noun 'rest, vacation' is spelled, however, ዕረፍት (with ዐ) going back to its root.

Etymological spelling is also used in Arabic loanwords. Thus, ሒሳብ 'bill', Arabic حساب; ሐኪም 'doctor', Ar. حكيم; ዒላማ 'aim', Ar. عِلامة; ዓላማ 'object, purpose', Ar. عَلامة, and so on. It is likely that እቅድ 'plan' comes from Arabic عقد but since its origin is doubtful and it is normally written with እ, I adopted the spelling እቅድ.

The standardization of spelling through etymology is not intended to conflict with actual pronunciation of a lexeme. Thus, for instance, the verb 'he went out' is pronounced *wäṭṭa*, with *ṭ*, and is therefore written ወጣ (with ጣ), and not ወፃ as it would be if one adhered strictly to the origin of the verb, namely Geez ወፅአ. Also, the verb 'he is' is pronounced *allä*, with an initial *a*. It is therefore written አለ and not ሀለ as it would be if one adhered strictly to the etymology, namely Geez ሀለወ. The same consideration applies to 'new' *addis*, written አዲስ and not ሐዲስ as the etymology would have required.

In roots for which there is no corresponding Ethiopic or Semitic etymology, I have adopted አ for an initial vowel, ሀ for *h* (except in ውኃ 'water'), ሰ for *s*, and ጸ for *ṣ*.

A labiovelar with the vowel *ä* is often reduced in pronunciation and in writing to a velar followed by *o*. Generally, I kept the spelling with the labiovelar; thus ቈጠረ (and not ቆጠረ). This spelling is, however, not consistent.

In the verb forms of the 1.2.2. verbs in which the last two consonants are in contact I have adopted the spelling with one consonant; thus, መቶ (pronounced *mätto*) for መትቶ (from መታ).

In forms in which there is a meeting of the vowels *ä-a* I have normally adopted the system of eliding the vowel *ä*; thus, ያገር for የአገር. In entries, however, I also keep both vowels; thus, የአየር (see 'airlines'). In the meeting of the vowels *ä-ə* I have normally kept the two vowels; thus የእጅ (and not የጅ), but ስለሱ (and not ስለእሱ).

The conjunctions are not separated from the verbs; thus, ስለመጣ. The prepositions that have more than one letter are written separately; thus, ስለ ፡ ዝናብ. They are not separated from a pronoun; e.g. ስለሱ (for ስለእሱ), or occasionally in combination of nouns in which the የ of the first noun is omitted as in ስለህንዶች ፡ ኑሮ for ስለ ፡ (የ)ህንዶች ፡ ኑሮ.

The end of the Amharic sentence is not marked by ።. Only the question mark (?) is given wherever required, and occasionally the exclamation mark (!).

## PRONUNCIATION

No pronunciation is given for the English lexemes. The student will have to know that the pronunciation of 'entrance' (n.) is different from that of 'entrance' (v.). Only in exceptional cases where the same part of speech is pronounced in two different ways is there an indication for the pronunciation; see 'row' (n.) rhyming with 'low' or 'how'; or 'tear' (n.) rhyming with 'pear' or 'fear'.

As for the Amharic lexemes, it would have been highly desirable to indicate the gemination with a special symbol, but this would have increased the cost of the dictionary considerably.

## ENTRIES AND THEIR ARRANGEMENT

In the enumeration of entries, the verb is given before the noun.

Within each entry, the arrangement is alphabetical. Example : 'close, close down, close in, close in on, close out'. A word in parentheses does not count for alphabetic arrangement; therefore '(be) closed up' is not placed under 'be', but after 'close out'. In the subentries in which the word of the main entry is at the beginning, it is treated first. Thus, under the main entry 'near', the subentries 'near at hand, near here', are listed first. Only then follow the subentries in alphabetical order where 'near' is not the first word, as in 'as near as, come near, get near, nowhere near.'

An English entry is occasionally translated by two Amharic entries. In this case the symbol I is used to separate the equivalents; see 'anger' (vt.) አናደደ I አስቈጣ; 'abduct' ጠለፈ I አፍኖ ፡ ወሰደ. The second Amharic lexeme is either illustrated with a different sentence (as in the case of 'anger'), or is used in the same sentence. The second lexeme is then put in parentheses (as in the case of 'abduct').

Wherever there is only one meaning for the English entry, the Amharic equivalent follows immediately after the English entry (see 'ail'). If the English entry has more than one meaning, no Amharic equivalent follows the entry directly, but the Amharic equivalents are below the entry and are numbered according to the various meanings of the entry (see 'aim').

The English verb entry is normally rendered by the Amharic verb in the perfect, singular 3rd masculine; e.g. 'build' ሠራ, lit. 'he built'. The Amharic verb is cited in a verb form other than the perfect wherever the perfect is not used; see 'not bad' (under 'bad') ምንም ፡ አይል since in this idiom the verb is used only in the negative imperfect.

The Amharic verbs translating the English verbs with the prefix un- are also occasionally given in a verb form other than the perfect; see '(be) uninhabited'.

The 3rd person singular, masculine is also used if the Amharic entry is a gerundive or a relative imperfect translating an adjective. This is the case of 'late' (adv.) ዘግይቶ, but one of the cited sentences is 'she arrived late' ዘግይታ ፡ ደረሰች where the form is that of the 3rd person, singular, feminine. Or, 'favorite' (adj.) የሚወደው, lit. 'that he likes it', but the cited sentence is 'my favorite' የምወደው lit. 'that I like it', that is, the first person.

The Amharic impersonal verbs are cited in the perfect, singular, 3rd masculine followed by the object suffix pronoun of the singular, 3rd masculine in parentheses; thus '(be) thirsty' ጠማ(ው); 'understand' ገባ(ው).

An Amharic verb that is used with prepositional suffixes is cited with the prepositional suffixes in parentheses. Examples : 'rage' ባሰ(በት); 'rally (to)', 2. ደረሰ(በት).

While the Amharic verb entry is cited in the perfect, singular, 3rd masculine, the verb of the translated sentence can be used in any verb form. Thus, in 'base' (v.) መሠረተ, the verb of the translated sentence is likewise in the perfect (መሠረትከው); in 'backbite' (አማ), the verbal noun (ማማትን) is used in the Amharic sentence; and in 'benefit' (ጠቀመ), the imperfect (ይጠቅማል) is used.

Occasionally an active or a transitive verb is illustrated with a passive in the English sentence. In this case, the Amharic verb is cited in the active with its passive form in parentheses. Thus, for 'announce', no. 6, the sentence has the verb 'was announced'; the Amharic entry is therefore ነገረ (ተነገረ).

At other times, the cited English entry is in the passive rather than in the active; see '(be) imprinted', without the active 'imprint'. This procedure was adopted for cases where the passive usage is more frequent than the active usage. When an active form is required, the reader will then use the Amharic active verb of the cited verbs ተቀረጸ and ታተመ, that is ቀረጸ and አተመ.

Whenever a stative verb is expressed by 'be + adjective', it may occasionally have a special entry beside the adjective entry. Most often, however, this kind of verb has no special entry, but can easily be translated by using the cited Amharic adjective followed by ነው 'he is'. Thus, the adjectives 'curious, nasty, hollow' and others can serve as bases for the stative verbs ('be + adjective') by the addition of ነው 'he is' to the adjective : 'be nasty' አስጠያፊ ፡ ነው, or መጥፎ ፡ ነው.

The passive of an English verb is not cited as subentry since normally the passive is formed in Amharic by the ተ-stem. For instance, only 'betray' ከዳ is cited, since 'be betrayed' would normally be expressed by ተከዳ. However, in verbs in which the passive is not rendered in Amharic by the ተ-stem, but rather by the basic stem or by another root altogether, the English passive is cited as subentry. Examples : 'demolish' አወደመ (expressed by the አ-stem), but 'be demolished' ወደመ (expressed by the basic stem); or 'lift' አነሣ I ከፍ ፡ አደረገ, but 'be lifted' is translated by other roots (አበቃ I ተሰረዘ). See also 'affect' and 'be affected'; 'form' and 'be formed'.

Verbal nouns ending in -ing ('weeding') or abstracts (such as 'condemnation') are usually not cited, since they are expressed either by the Amharic verbal noun that can automatically be formed from the verb or by a verb form.

Phrasal or complemented verbs such as 'go in, throw away' are listed separately as subentries since the translation cannot be inferred from the main entry. More complicated is the question of a method for listing those verbs which are followed by a complement, but the combination is not a phrasal verb. Thus, for instance, 'deal with' in the sentence "how shall we deal with this problem?" is not a phrasal verb. This combination is, however, listed separately because the proper Amharic equivalent for 'deal with' could not be inferred from the equivalent of 'deal' followed by the Amharic preposition 'with'. Besides, the Amharic equivalents ተቋቋመ (no. 1) and ያዘ (no. 2) are not even used with a prepositional element, but are combined with the marker -ን of the direct object. Combinations of that kind are, therefore, listed separately. See also 'contribute' and 'contribute to'; 'bore into' (under 'bore'); 'zip through' (under 'zip').

A good illustration of separate listing of nonphrasal verbs is 'ask after' (as in "he asked after your health") or 'ask for' (as in "did anyone ask for me?"). It is true that in both these cases the verb 'ask' is translated ጠየቀ which is the translation of English 'ask'. However, since Amharic does not express 'ask after' or 'ask for' by a combination of ጠየቀ 'ask' with the prepositions 'after' or 'for', but by the direct complement, the separate listing seemed advisable.

Occasionally the preposition is put in parentheses, as in 'account (for)', 'adhere (to)', 'answer (for)', 'cut (through)', 'depend (on)'. A preposition placed in parentheses after the verb indicates that while the combination is not a phrasal verb, the preposition is required for the special meaning.

The Amharic key word does not always indicate the syntactic structure of the sentence which is conditioned by the key word. The reader should, therefore, read the whole sentence to familiarize himself with the function of the key word in the sentence. For instance, 'make believe' (under 'believe') አስመሰለ does not indicate that it requires the verb to be in the relative. Indeed, the sentence "the boys made believe they were fighting the enemy" is translated ልጆቹ ፡ ጠላትን ፡ የሚዋጉ ፡ አስመሰሉ (with the relative verb የሚዋጉ).

The functioning of the key word ያህል for 'about' (no. 4) is understood only through the whole sentence "this house is about as high as that tree" ይህ ፡ ቤት ፡ ያንን ፡ ዛፍ ፡ ያህል ፡ ይረዝማል where it becomes clear that the compared object 'that tree' has the suffix -ን (in ያንን).

Or, the position of ቢስ 'devoid of' after the noun in the construct state is evident only from the sentence "she is devoid of shame" እፍረተ ፡ ቢስ ፡ ናት.

## LABELS

An English verb is labeled transitive (vt.) or intransitive (vi.) according to the usage in the existing English dictionaries. A verb is considered transitive if it has a direct object; it is intransitive if it does not have a direct object. Thus, 'read' in the sentence "he reads a book" is transitive, but in the sentence "he reads well" it is intransitive.

The labels vt. and vi. are used only when the same verb can be either transitive or intransitive; see, for instance, 'clutter, read'.

Most normally an English transitive verb is translated by an Amharic transitive, and an English intransitive is translated by an Amharic intransitive. At times, however, this is not the case. An example of this is 'circle' (vt.) in "the moon circles the earth" translated ጨረቃ ፡ በመሬት ፡ ዙሪያ ፡ ትዞራለች (where ዞረ is used with the preposition and postposition በ - - - ዙሪያ). Or, 'bang at' (an intransitive usage) in "he banged at the door to be let in" is translated ለመግባት ፡ በሩን ፡ ደበደበ (that is, a transitive in Amharic).

The labels vt. (transitive) or vi. (intransitive) are not indicated for the Amharic verbs. It is through the translation that the reader will be able to deduce whether the Amharic verb has a transitive or intransitive usage.

The label n. (= noun) or v. (= verb) is used only for entries that could lend themselves to confusion when taken out of context. Thus, 'abuse' out of context can be either a noun or a verb. The label 'abuse' (v.), 'abuse' (n.) is therefore necessary. But there is no need for a part-of-speech label for 'accessory' or 'accommodate'.

## INFLECTED FORMS

Plural of nouns. The most frequently used plural marker -s, -es (dog-s, match-es) is not indicated. Any other plural marker is given in parentheses; thus 'calf (calves), child (children)'. Besides, the special plural form is found in the appropriate place with a reference to the singular; thus 'children, see child'.

Past tense. The most frequent marker for the past tense -ed is not indicated. Any form of the past tense that deviates from the regular form is given in parentheses; thus 'come (came), carry (carried), commit (committed)'. These forms of the past tense (except those of the 'carry' and 'commit' type) are also found in the appropriate places with the reference to the main entry; thus 'came, see come'.

## CROSS REFERENCES

The cross references are indicated as [See also...] placed at the end of the entry; see such entries as 'advance' [See also 'pacific']; or 'advantage' [See also 'operate']. The choice of placing a subentry under one or another main entry is arbitrary. For instance, 'make pacific advances' could have been entered under the main entry 'advance' rather than under 'pacific' where it is placed.

There are no cross references to the verbs 'get, keep, make, put, take' since they are frequently combined with other parts of speech. Nor are there cross references to the prepositions used in phrasal verbs, such as 'come in, come out, come by' and so on.

## SYMBOLS

The symbols used are : *, +, (=), and [ ].

The symbol *.

This symbol is used wherever there is no exact Amharic equivalent for the English entry. For instance, there is no precise Amharic equivalent for English 'afterthought'. The meaning of 'afterthought' can, however, be rendered in Amharic in a sentence such as "the idea came to me as an afterthought" ነገሩን ፡ የተገነዘብኩት ፡ ዘግይቼ ፡ ነው. It would, indeed, be misleading to translate the entry 'afterthought' by any of the Amharic lexemes in the above-mentioned sentence. It is the translation as a whole that renders the idea of 'afterthought'. Or, the idea of the noun 'adhesion' in the sentence ' adhesion of the intestine to the muscles requires surgery" አንጀት ፡ ከጡንቻ ፡ ጋር ፡ ሲጣበቅ ፡ ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ያስፈልጋል is undoubtedly understood in the verb form ሲጣበቅ 'when it adheres'. It would be misleading, however, to translate the noun adhesion by ሲጣበቅ. The symbol * is, therefore, used.

A sentence preceded by * is not necessarily the first sentence following the entry. For example, the first sentence following the entry 'advent' has the Amharic equivalent መምጣት, but in the second sentence 'since the advent' is translated by ከመጣ ፡ ወዲህ. It is the whole unit 'since the advent' that is translated and not the isolated word 'advent'. The sentence is, therefore, preceded by *.

When the English entry has neither an Amharic translation following it nor a *-sentence, it means that the key word equivalent is lengthy and is shown only in the translation. This is done in cases where the sentence that illustrates the entry contains only few additions to the entry. See, for instance, 'false alarm' (under 'alarm') illustrated with the sentence "it was a false alarm" የውሸት ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ፈጠሩት ፡ ነበር. I adopted this procedure for the sake of economy.

The symbol +.

This symbol indicates that the Amharic sentence has a different subject from that of the English sentence. This symbol is used if the difference in subjects affects the entry. This is the case in the so-called impersonal verb of Amharic; see, for instance, 'understand' no. 1 +ገባ(ው).

The subjects may differ between the English entry and its Amharic translation in many other verbs. Thus, for instance, 'be bored' (under 'bore') where the subject of the English sentence is the person whereas in the Amharic sentence the subject is the speech. See also 'absolve, be absolved'.

The symbol (=).

Occasionally a specific part of speech of the English entry is not rendered by the same part of speech in Amharic. In this case, the Amharic entry is preceded by the symbol (=). Examples : 'advance' no. 3 (= adv.); 'literal' no. 1 (= adv.); 'oddly' (= adj.).

This is likewise the case when an active verb of English is rendered by a passive; or when a passive of English is rendered by an active or transitive; or when an intransitive verb of English is rendered by a transitive verb in Amharic; see '(be) knocked down' (= tr.); 'lean over', vi. (= vt.); 'bark', vt. 2 (= passive).

For many sentences an equivalent part of speech could have been obtained by forcing the Amharic translation, but the more natural way of translating the English sentence was through a different part of speech in Amharic. The Amharic part of speech preceded by the symbol (=) was therefore kept.

Incidentally, the adverb (= adv.) in these cases refers not only to regular adverbs, as under 'vain' (= adv.) በከንቱ, but also to adverbial or circumstantial expressions, as under 'twofold' (= adv.) ሁለት ፡ እጅ; 'token' (= adv.) ለስሙ ፡ ያህል, or ለስሙ ፡ ትንሽ.

The bracket symbol [ ].

An English lexeme that has no equivalent in Amharic is explained by a definition. The definition is placed in brackets; see 'ale, allergy, delta, galley, jury', and so on.

## ABBREVIATIONS

| | | |
|---|---|---|
| act. | = | active |
| adj. | = | adjective |
| adv. | = | adverb |
| com. | = | common |
| conj. | = | conjunction |
| fem. | = | feminine |
| ger. | = | gerundive |
| intr. | = | intransitive |
| masc. | = | masculine |
| n. | = | noun |
| pl. | = | plural |
| prep. | = | preposition |
| pron. | = | pronoun |
| resp. | = | respect |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| sg. | = | singular | v. | = | verb |
| tr. | = | transitive | vi. | = | intransitive verb |
| trans. | = | transitive | vt. | = | transitive verb |

(zero) indicates that the English lexeme is not translated.

---

The motto at the head of the introduction is merely intended to express my own feelings while working for the last six years on the compilation of this dictionary. I am well aware of all the pitfalls inherent in a work of this kind. There undoubtedly are occasional inconsistencies in the arrangement of the subentries and even in the orthography. For some readers the material offered in this dictionary may be too abundant, for others too scanty. As for the translations themselves, in many cases other renderings could have been used. Notwithstanding the difficulties of all kinds and my own occasional hesitations, I thought that the time had come to put at the disposal of the student of Amharic as well as of the Ethiopian student learning English a dictionary that would prove helpful in furthering Amharic studies.

---

Many persons and institutions were involved in the preparation of the dictionary. The technical execution of the work was made possible through the financial support of the Office of Education of the Department of Health, Education and Welfare. Additional financial aid came from different parts of the University of California, Los Angeles, namely the Near Eastern Center, the African Studies Center, and the Committee on International and Comparative Studies. The printing expenses were partly covered by the Agency for International Development (AID) which purchased a certain number of copies and made them available for distribution to the Haile Sellassie University and to the Ethiopian Ministry of Education. The publication of the dictionary would not have been possible, however, without the enterprising spirit of the publisher Otto Harrassowitz. I wish to thank in particular Dr. Helmut Petzolt whose extraordinary attention to detail and sound advice in publication matters helped me in many stages of my work. The Imprimerie Orientaliste in Louvain was cooperative and very patient in accepting the many changes that I had to make as the printing went along.

Many Ethiopian students were involved in the translation of the sentences. I would like to mention in particular Tesfaye Shewaye and Girma Wolde Sellasie who were very helpful thanks to their excellent knowledge of Amharic and their perseverence. Abebe Bekele also helped me greatly in solving problems of language usage. I am especially grateful to my student Dr. Thomas Kane who participated in many stages of this work, including proofreading. His thorough familiarity with Amharic as well as his exceptional understanding of translation problems proved to be of considerable value from beginning to end.

I take once more the opportunity to express my profound admiration and my sincerest thanks to my teacher Marcel Cohen who initiated me into the study of Amharic and whose spirit guided me in my scientific endeavors.

The completion of this dictionary would not have been possible without the wholehearted cooperation, patience, understanding, sacrifice, and encouragement of my wife. My deepest gratitude goes to her.

Wolf Leslau

Los Angeles, December 1972

# A

**a**

1. (zero). A boy came. ልጅ ፡ መጣ
2. አንድ. A boy came. አንድ ፡ ልጅ ፡ መጣ

**aback, be taken ~** ደነቀ(ው)

I was taken aback by my friend's refusal to lend me money. ወዳጄ ፡ ገንዘብ ፡ አላበድርህም ፡ ሲለኝ ፡ ደነቀኝ

**abandon** (v.)

1. ተወ. He abandoned his efforts to achieve his goal. ከዓላማው ፡ ለመድረስ ፡ ያደርግ ፡ የነበረውን ፡ ጥረት ፡ ተወ
2. ጥሎ ፡ ሄደ. The man abandoned his family. ሰውዬው ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ ጥሎ ፡ ሄደ
3. ጥሎ ፡ ሸሸ. The captain gave the command to abandon ship. ካፒቴኑ ፡ ሰዎቹ ፡ መርከቡን ፡ ጥለው ፡ እንዲሸሹ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ

**abandon** (n.)

*The students cheered with abandon waving their arms and shouting. ተማሪዎቹ ፡ እጃቸውን ፡ በማወዛወዝና ፡ በመጮኽ ፡ በጋለ ፡ ስሜት ፡ ደስታቸውን ፡ ገለጹ

**abandoned** (adj.) የተጣለ

The abandoned child was begging in the streets. የተጣለው ፡ ልጅ ፡ በየመንገዱ ፡ ይለምን ፡ ነበር

**be abandoned** ቀረ

The prosecution will be abandoned if the stolen money is returned. የተሰረቀው ፡ ገንዘብ ፡ ከተመለሰ ፡ ክሱ ፡ ይቀራል

**abase** አዋረደ

A man who betrays his friends abases himself. ወዳጆቹን ፡ የሚከዳ ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ያዋርዳል

**abash** አሳፈረ

The rebuke abashed him. ነቀፌታው ፡ አሳፈረው

**be abashed** አፈረ

The little girl was abashed when she saw the room filled with strangers. ክፍሉ ፡ በእንግዳ ፡ ሰዎች ፡ ተሞልቶ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ልጅቷ ፡ አፈረች

**abate** (vt.) ቀነሰ

The city administration abated local taxes. የማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ የከተማውን ፡ ግብር ፡ ቀነሰ

**abate** (vi.) ተቀነሰ

The ship sailed when the storm abated. ማዕበሉ ፡ ሲቀንስ ፡ መርከቡ ፡ ተጓዘ

**abbreviate**

1. አሳጠረ. He likes to abbreviate long words. ረጃጅም ፡ ቃላትን ፡ ማሳጠር ፡ ይወዳል
2. አኅጽሮተ ፡ ቃል ፡ አደረገ. How do you abbreviate 'doctor'? ዶክተር ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንዴት ፡ አኅጽሮተ ፡ ቃል ፡ ታደርገዋለህ?

**abbreviation** አኅጽሮተ ፡ ቃል

'Dr.' is the abbreviation for 'doctor'. የዶክተር ፡ አኅጽሮተ ፡ ቃል ፡ ዶር ፡ ነው

**abdicate** ዙፋኑን ፡ ለቀቀ

Why did the king abdicate? ንጉሡ ፡ ለምን ፡ ዙፋናቸውን ፡ ለቀቁ?

**abdomen** ሆድ

The sick child's abdomen is swollen. የበሽተኛ ፡ ልጅ ፡ ሆድ ፡ አብጧል

**abdominal** የሆድ

Abdominal pains may be caused by eating too much. ከመጠን ፡ በላይ ፡ መብላት ፡ ለሆድ ፡ ሕመም ፡ መነሻ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

**abduct** ጠለፈ ፤ አፍኖ ፡ ወሰደ

The rebels abducted his daughter. ዐመፀኞቹ ፡ የሱን ፡ ልጅ ፡ ጠለፏት ፡ (አፍነው ፡ ወሰዷት)

**aberration** የአእምሮ ፡ ሁከት

He stole the watch in a moment of aberration. ሰዓቱን ፡ የሰረቀው ፡ የአእምሮ ፡ ሁከት ፡ ደርሶበት ፡ በነበረበት ፡ ወቅት ፡ ነው

*His speech was full of aberrations from the main subject. በንግግሩ ፡ ላይ ፡ ደጋግሞ ፡ ከዋናው ፡ አርእስት ፡ ይወጣ ፡ ነበር

**abet** (abetted) አደፋፈረ

Only one man stole the tire but his two friends abetted him. ጎማውን ፡ የሰረቀው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ቢሆንም ፡ ያደፋፈሩት ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ አሉ

**abeyance, be in ~** ቀዘቀዘ

His interest in stamps has been in abeyance for weeks. ቴምብር ፡ የመሰብሰብ ፡ ፍላጎቱ ፡ ለብዙ ፡ ሳምንታት ፡ ያህል ፡ ቀዝቅዞ ፡ ነበር

**hold in abeyance** በቀጠሮ ፡ አቆየ
The judge held the case in abeyance until additional witnesses appeared. ተጨማሪ ፡ ምስ ክሮች ፡ እስኪቀርቡ ፡ ድረስ ፡ ዳኛው ፡ ጉዳዩን ፡ በቀጠሮ ፡ አቆየው

**abhor** (abhorred) ጠላ
He abhorred cruelty to animals. በእንስሶች ፡ ላይ ፡ መጨከንን ፡ ጠላ

**abhorrence** ጥላቻ
I cannot hide my abhorrence for her. ለሷ ፡ ያለኝን ፡ ጥላቻ ፡ ልደብቀው ፡ አልችልም

**abhorrent** አስጠሊ
Treachery is abhorrent. ከሐዲነት ፡ አስጠሊ ፡ ነው

**abide** (abode, or abided), vt. ቻለ
I cannot abide loud noises. ጫጫታ ፡ አልች ልም

**abide** (vi.) አይቀርም
Even after disappointments hope still abides. ጉዳዮችን ፡ ባይሳካልንም ፡ እንኳ ፡ ተስፋ ፡ ማድ ረጋችን ፡ አይቀርም

**abide by**
1. አከበረ. You must abide by your promises. የገባኸውን ፡ ቃል ፡ ማክበር ፡ አለብህ
2. በ --- ጸና. I abide by what I said. ባልኩት ፡ እጸናለሁ

**abiding** ዘላቂ
He manifested abiding devotion to his country. ላገሩ ፡ ዘላቂ ፡ ፍቅርን ፡ አሳየ

**ability** (abilities)
1. ችሎታ. He has ability to swim like a fish. እንደ ፡ ዓሣ ፡ የመዋኘት ፡ ችሎታ ፡ አለው
He is a man of great abilities. ከፍ ፡ ያለ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው
2. ተሰጥዎ. Musical ability often shows itself early in life. የሙዚቃ ፡ ተሰጥዎ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በልጅነት ፡ ይታወቃል

**abject** አሰቃቂ
Abject poverty is visible in the beggar's tattered clothes. ከለማኙ ፡ ቡቱቶ ፡ ልብስ ፡ አሰቃቂ ፡ ድኽነት ፡ እንዳለበት ፡ ይታወቃል

**abjure** ካደ
He abjured his religion. ሃይማኖቱን ፡ ካደ

**(be) ablaze**
1. ተንቦገቦገ. The streets were ablaze with lights. ጐዳናዎቹ ፡ በመብራት ፡ ተንቦገቡገዋል
2. በእሳት ፡ ተያያዘ. The whole building was ablaze. ሕንጻው ፡ በሙሉ ፡ በእሳት ፡ ተያይዞ ፡ ነበር
3. ቱግ ፡ አለ. I was ablaze with anger when he kicked my dog. ውሻዬን ፡ በረገጠ ፡ ጊዜ ፡ በ ንዴት ፡ ቱግ ፡ አልኩ

**able**
1. ችሎታ ፡ ያለው. He is an able speaker. ችሎ ታ ፡ ያለው ፡ ተናጋሪ ፡ ነው
2. ብቁ. An able speech won the king's favor. የተደረገው ፡ ብቁ ፡ ንግግር ፡ የንጉሡን ፡ መልካም ፡ አስተያየት ፡ አስገኘ

**be able** ቻለ
Will you be able to come? ለመምጣት ፡ ትች ላለህ?

**able-bodied** የተሟላ ፡ ሰውነት ፡ ያለው
Only able-bodied men will be accepted into the army. ወደ ፡ ጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ ለመግባት ፡ የ ሚችሉ ፡ የተሟላ ፡ ሰውነት ፡ ያላቸው ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**ablution** መታጠብ
Ablution must be performed by Muslims before prayer. እስላሞች ፡ ከመጸለያቸው ፡ በፊ ት ፡ መታጠብ ፡ አለባቸው

**abnegate** ናቀ
He abnegated his family fortune and became a monk. የቤት ፡ ሰቡን ፡ ሀብት ፡ ንቆ ፡ መነኰሰ

**abnegation** (= adv.) ሥጋውን ፡ በድሎ
A hermit lives a life of abnegation. ባሕታዊ ፡ ሥጋውን ፡ በድሎ ፡ ይኖራል

**abnormal**
1. ከተፈጥሮ ፡ የተለየ. It is abnormal for a man to be seven feet tall. ያንድ ፡ ሰው ፡ ቁ መት ፡ ሰባት ፡ ጫማ ፡ መሆን ፡ ከተፈጥሮ ፡ የተ ለየ ፡ ነው
2. በአእምሮው ፡ ዝቅ ፡ ያለ. Abnormal children require special teaching. በአእምሮዋቸው ፡ ዝቅ ፡ ያሉ ፡ ልጆች ፡ ልዩ ፡ የማስተማር ፡ ዘዴ ፡ ያስፈል ጋቸዋል
3. ቅጥ ፡ ያጣ ፤ ያልተለመደ. His abnormal actions show that he has been drugged. ቅጥ ፡ ያጣው ፡ (ያልተለመደው) ፡ አኳኋኑ ፡ መድኀኒት ፡ መቅመሱን ፡ ያሳያል

**aboard, go ~** ተሳፈረ
We went aboard an hour before the boat sailed. መርከቧ ፡ ልትሄድ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሲቀ ራት ፡ ተሳፈርን

**all aboard** በመርከብ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩ ፡ ሁሉ
When the ship went under all aboard were drowned. መርከቢ ፡ ስትሰጥም ፡ በውስጧ ፡ የነበሩ ፡ ሁሉ ፡ ሰጠሙ

**all aboard!** ተሳፈሩ!
All aboard! The bus is about to leave. ተሳፈሩ! አውቶቡሱ ፡ ሊሄድ ፡ ነው

**abode** (n.) መኖሪያ
His abode is far away. መኖሪያው ፡ ሩቅ ፡ ነው

**abode,** see **abide**

**abolish** አስቀረ
He abolished slavery. ባርነትን ፡ አስቀረ

**abolition** ማጥፋት
The abolition of poverty was the main purpose of the bill. የሕጉ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ ድኽነትን ፡ ማጥፋት ፡ ነበር

**abominable**
1. አስከፊ. The weather this year is abominable. በዚህ ፡ ዓመት ፡ ያየሩ ፡ ጠባይ ፡ አስከፊ ፡ ነው
He finds this music abominable. ይህ ፡ ሙዚቃ ፡ አስከፊ ፡ ሆኖ ፡ ይሰማዋል
2. አሰቃቂ. The abominable cruelties of Nero are well known. የኔሮ ፡ አሰቃቂ ፡ ጭካኔ ፡ በሚገባ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**abominate** ጠላ
He abominates strict discipline. ጥብቅ ፡ ቁጥጥር ፡ ይጠላል

**abomination** (= adj.) አስከፊ
The man's cruelty is an abomination. የሰውየው ፡ ጭካኔ ፡ አስከፊ ፡ ነው

**aboriginal** የጥንት ፡ ሰዎች
Traces of aboriginal dwellings can still be seen. የጥንት ፡ ሰዎች ፡ መኖሪያዎች ፡ ርዝራዥ ፡ አሁንም ፡ ይታያል

**aboriginal inhabitant** የመጀመሪያ ፡ ነዋሪ
The aboriginal inhabitants of Ethiopia are the Agaus. የኢትዮጵያ ፡ የመጀመሪያ ፡ ነዋሪዎች ፡ አገዎች ፡ ናቸው

**aborigine** የመጀመሪያ ፡ ነዋሪ
The Agaus are the aborigines of Ethiopia. አገዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ነዋሪዎች ፡ ናቸው

**abort**
1. ጨነገፈ. When a pregnant cow is injured, it will abort. ከብድ ፡ የሆነች ፡ ላም ፡ ስትጐዳ ፡ ትጨነግፋለች
2. ከሸፈ. The attack aborted because of a breakdown in communication. ከመገናኛ ፡ ብልሽት ፡ የተነሣ ፡ የተደረገው ፡ ጥቃት ፡ ከሸፈ

**abortion** ፅንስን ፡ ማስወረድ
Is abortion a crime in Ethiopia? ፅንስን ፡ ማስወረድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀል ፡ ነው?

**abortive**
1. ሥር ፡ ያልሰደደ. An abortive case of smallpox will leave no scars. ሥር ፡ ያልሰደደ ፡ የፈንጣጣ ፡ በሽታ ፡ ጠባሳ ፡ አይተውም
2. ፍሬ ፡ ቢስ. The early attempts to fly were abortive. ቀደም ፡ ሲል ፡ ለመብረር ፡ የተደረጉት ፡ ሙከራዎች ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ሆነው ፡ ቀሩ

**abound** ሞላ
Animals abound in this forest. በዚህ ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ አራዊት ፡ ሞልቷል
The river abounds with fish. ወንዙ ፡ ውስጥ ፡ ዓሣ ፡ ሞልቷል

**about** (prep., adv.)
1. ስለ. They were talking about the war. ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ ያወሩ ፡ ነበር
What is it all about? ይህ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ምንድን ፡ ነው?
2. በ - - - ላይ. There is something queer about him. በሱ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ይታያል
3. አንድ. There were about thirty people present. አንድ ፡ ሠላሳ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ
4. ያህል. This house is about as high as that tree. ይህ ፡ ቤት ፡ ያንን ፡ ዛፍ ፡ ያህል ፡ ይረዝማል
5. በዚህ ፡ አካባቢ. Are there any wild animals about? በዚህ ፡ አካባቢ ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ አሉ?
6. በ - - - ዙሪያ. The dog capered about its master. ውሻው ፡ በጌታው ፡ ዙሪያ ፡ ቦረቀ
*John is adept at repairing things about the house. ጆን ፡ የቤት ፡ እቃዎች ፡ የመጠገን ፡ ችሎታ ፡ አለው
*He is about my age. በዕድሜ ፡ እኩያዬ ፡ ነው

**about face!** ቀኝ ፡ ኋላ ፡ ዙር!
The officer roared, "about face"! መኰንኑ ፡ ቀኝ ፡ ኋላ ፡ ዙር ፡ ብሎ ፡ አዘዘ

**be about** ለ + imperfect + ነው
The pail is about full. ባልዲው ፡ ሊሞላ ፡ ነው
Lunch is about ready. ምሳ ፡ ሊደርስ ፡ ነው

**be about the same** የተቀራረበ ፡ ነው ፤ የተመሳሰለ ፡ ነው
Is the weather in Addis Ababa better than in Harar? It is about the same. የአዲስ ፡ አ

በባ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ ከሐረር ፡ ይሻላል? የተቀራረበ ፡ (የተመሳሰለ) ፡ ነው
*It's about the same. ያው ፡ ነው

**be about to** ል + imperfect + ነው(ነበር)
He is about to leave. ሊሄድ ፡ ነው
I was about to send for you. ልልክብህ ፡ ነበር

**have about enough of** በቃ(ው)
+I have had just about enough of your arguments. ያንተ ፡ ጭቅጭቅ ፡ በቅቶኛል

**how about it?** ታዲያስ?
[See also 'somewhere, up, what']

**above** (prep.)
1. ከ - - - በላይ. They live above the store. ከሱቁ ፡ በላይ ፡ ይኖራሉ
The water came above our knees. ውኃው ፡ ከጉልበታችን ፡ በላይ ፡ ወጣ
The temperature was above 100 degrees. ሙቀቱ ፡ ከመቶ ፡ ዲግሪ ፡ በላይ ፡ ወጣ
His bravery was above all praise. ጀግንነቱ ፡ ከምስጋና ፡ በላይ ፡ ነበር
2. ከ. A father should not favor one child above the other. አባት ፡ አንዱን ፡ ልጅ ፡ ከንዱ ፡ ማበላለጥ ፡ የለበትም
*The book is above me. መጽሐፉ ፡ ከችሎታዬ ፡ በላይ ፡ ነው
*He is above suspicion. እሱ ፡ በፍጹም ፡ አይጠረጠርም

**above** (adv.) ከላይ
Seen from above, the lake looks like a mirror. ከላይ ፡ ሲታይ ፡ ሐይቁ ፡ መስተዋት ፡ ይመስላል
As mentioned above, the letter clarified the matter. ከላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ደብዳቤው ፡ ጉዳዩን ፡ አብራርቶታል
*The bookstore is just above. የመጻሕፍት ፡ መደብሩ ፡ ትንሽ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ነው

**above all** ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፤ ከሁሉም ፡ ይልቅ
Above all, remember to be on time! ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ በጊዜ ፡ መገኘትን ፡ አስታውስ
Above all, don't get discouraged! ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ተስፋ ፡ አትቍረጥ
[See also 'far, over']

**abrade**
1. ላጠ. The stone abrades the skin. ድንጋይ ፡ ቆዳ ፡ ይልጣል
2. (= pass.) ተላጠ. +The boy abraded the skin of his knee when he fell. ልጁ ፡ ወድቆ ፡ ጉልበቱ ፡ ተላጠ

**abrasion**
*Abrasions of the skin are painful. የተላጠ ፡ ቆዳ ፡ ያማል

**abreast** ወደ ፡ ጐን
The soldiers walked three abreast. ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ እየሆኑ ፡ ሄዱ

**keep abreast (of)**
1. በቅርብ ፡ ተከታተለ. He keeps abreast of scientific developments. የሳይንስን ፡ እድገት ፡ በቅርብ ፡ ይከታተላል
2. ከ --- ጋር ፡ ተራመደ. He keeps abreast of the times. ከጊዜው ፡ ጋር ፡ ይራመዳል

**abridge** አሳጠረ
The book was so long he had to abridge it. መጽሐፉ ፡ ረዥም ፡ ስለነበረ ፡ ማሳጠር ፡ ነበረበት

**abridged** (adj.) ያጠረ
This is an abridged version of David Copperfield. ይህ ፡ ያጠረው ፡ የዴቪድ ፡ ኩፐርፊልድ ፡ እትም ፡ ነው

**be abridged** ተነካ
The rights of citizens must not be abridged without proper cause. ያለ ፡ ተገቢ ፡ ምክንያት ፡ የሕዝብ ፡ መብት ፡ መነካት ፡ የለበትም

**abridgment**
* This book is an abridgment of a three-volume history. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ሦስት ፡ ጥራዝ ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍትን ፡ በማሳጠር ፡ የተጻፈ ፡ ነው

**abroad** ውጭ ፡ አገር
He studied three years abroad. ሦስት ፡ ዓመት ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ተማረ

**abrogate** ሻረ
The Emperor abrogated all laws permitting slavery. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ባርነትን ፡ የሚፈቅዱትን ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ሻሩ

**be abrogated** ፈረሰ
A binding contract cannot be abrogated by only one signatory. ጽኑ ፡ ውል ፡ ባንድ ፡ ፈራሚ ፡ ብቻ ፡ አይፈርስም

**abrupt**
1. ድንገተኛ. The road is full of abrupt turns. መንገዱ ፡ ድንገተኛ ፡ ጥምዝምዝ ፡ ይበዛበታል
We noticed an abrupt change in his attitude. በሁኔታው ፡ ድንገተኛ ፡ መለዋወጥ ፡ ተመለከትን
2. (= adv.) በድንገት. The abrupt awakening was caused by a noise. በድንገት ፡ የነቃው ፡ በጩኸት ፡ ምክንያት ፡ ነበር

*The road made an abrupt rise up the hill. መንገዱ ፡ ዳገቱ ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ በጣም ፡ አሻቅቦ ፡ ይወጣል

**abrupt manner**
He has a very abrupt manner. በጣም ፡ ግልፍተኛ ፡ ነው

**abruptly** እንደነገሩ
He treated me rather abruptly. እንደነገሩ ፡ አስተናገደኝ

**abscess** እባጭ
The doctor had to cut the abscess. ሐኪሙ ፡ እባጩን ፡ አፈረጠለት

**abscond, ~ with** ሰርቆ ፡ ኮበለለ
The clerk absconded with the store's money. ጸሐፊው ፡ የመደብሩን ፡ ገንዘብ ፡ ሰርቆ ፡ ኮበለለ

**absence** አለመኖር
The absence of water keeps plants from growing. የውኃ ፡ አለመኖር ፡ ዕፀዋትን ፡ እንዳያድጉ ፡ ያደርጋቸዋል
*In the absence of the director all work stopped. ዲሬክተሩ ፡ ስለቀሩ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ቆመ
*Please be my attorney during my absence. እኔ ፡ በሌለሁበት ፡ ጊዜ ፡ ነገረ ፡ ፈጂ ፡ ሁን
[See also 'leave']

**absent** (v.), ~ **oneself** ቀረ
Why did you absent yourself from school? ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ለምን ፡ ቀረህ?

**absent** (adj.) የቀረ
The absent members could not vote. የቀሩት ፡ አባሎች ፡ ድምፃቸውን ፡ ሊሰጡ ፡ አልቻሉም

**be absent**
1. ቀረ. Three members were absent because of illness. በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ሦስት ፡ አባሎች ፡ ቀርተው ፡ ነበር
2. አልተገኘም. Snow is absent in some countries. ባንዳንድ ፡ አገሮች ፡ በረዶ ፡ አይገኝም

**in an absent manner** ሳያስብ
She was daydreaming and answered in an absent manner. በሐሳብ ፡ ተውጣ ፡ ስለነበር ፡ ሳታስብ ፡ መልስ ፡ ሰጠች

**absentee**
1. የሚቀር ፡ ተማሪ. A careful teacher keeps track of absentees. ጠንቃቃ ፡ መምህር ፡ የሚቀሩትን ፡ ተማሪዎች ፡ ይቈጣጠራል
2. በመሬቱ ፡ ላይ ፡ የማይኖር. The problem of absentee landowners is a serious one in this country. በመሬታቸው ፡ ላይ ፡ የማይኖሩ ፡ ባለመሬቶች ፡ ሁኔታ ፡ ለዚህ ፡ አገር ፡ አሳሳቢ ፡ ችግር ፡ ፈጥሯል

**absently** በሌላ ፡ ሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ ተውጦ ፡ ሳለ
She absently nodded in response to the question. በሌላ ፡ ሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ ተውጣ ፡ ሳለች ፡ ለጥያቄው ፡ መልስ ፡ ራሷን ፡ ነቀነቀች

**absent-minded** ዝንጉ
He is always late to appointments because he is absent-minded. ዝንጉ ፡ ስለሆነ ፡ ሁልጊዜ ፡ ለቀጠሮ ፡ ዘግይቶ ፡ ይደርሳል

**absolute**
1. ፍጹም. That's the absolute truth. ይህ ፡ ፍጹም ፡ እውነት ፡ ነው
The dictator excercised absolute power. አምባ ፡ ገነኑ ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ ሥልጣን ፡ ገዛ
2. ፈላጭ ፡ ቈራጭ. He has been an absolute ruler. ፈላጭ ፡ ቈራጭ ፡ ገዢ ፡ ነበር
3. ፍጹም ፡ እርግጠኛ. It is an absolute fact. ፍጹም ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ነው
4. ገደብ ፡ የሌለው. The absolute authority of the director was burdensome for the teachers. ገደብ ፡ የሌለው ፡ የዲሬክተሩ ፡ ሥልጣን ፡ ለመምህራን ፡ ከባድ ፡ ነበር
5. ንጹሕ. Absolute alcohol has no water in it. ንጹሕ ፡ አልኮል ፡ ውኃ ፡ የለበትም

**absolutely**
1. በፍጹም. He is absolutely right. እሱ ፡ በፍጹም ፡ ልክ ፡ ነው
2. በጭራሽ (with negative verb). He is absolutely dishonest. በጭራሽ ፡ ታማኝ ፡ አይደለም
3. ሙሉ ፡ በሙሉ. Do you agree with me? Absolutely. ከኔ ፡ ጋር ፡ ትስማማለህ? ሙሉ ፡ በሙሉ

**absolution** ፍትሐት ፤ ፍታት
The priest performed absolution. ቄሱ ፡ ፍትሐት ፡ (ፍታት) ፡ አደረጉ

**give absolution** ፈታ
"Give me absolution", he said to the priest. ቄሱን ፡ ይፍቱኝ ፡ አላቸው

**pronounce absolution** ፍታት ፡ አሰማ
The priest pronounced absolution. ቄሱ ፡ ፍታት ፡ አሰሙ

**absolve**
1. ነጻ ፡ አደረገ. The judge absolved him of guilt in the accident. ባደጋ ፡ ከደረሰው ፡ ጥፋት ፡ ዳኛው ፡ ነጻ ፡ አደረገው
2. ሰረዘ(ለት). He absolved me from the promise I made. ገብቼለት ፡ የነበረውን ፡ ቃል ፡ ሰረዘልኝ

**be absolved ተሰረየ(ለት)**
+He was absolved from his sins. ኃጢአቱ ፣ ተሰረየለት

**absolve (someone) of his sins ፈታ**
The priest absolved him of his sins. ቄሱ ፣ ፈቱት

## absorb
1. መጠጠ. The sponge absorbed the water quickly. ሰፍነጉ ፣ ውኃውን ፣ ወዲያው ፣ መጠጠው
2. ያዘ. You cannot absorb all that material in a single lesson. ያንን ፣ ሁሉ ፣ ባንድ ፣ ትምህርት ፣ ልትይዘው ፣ አትችልም
3. ዋጠ. Large companies absorb smaller ones. ትልልቅ ፣ ኩባንያዎች ፣ ትንንሾቹን ፣ ይውጧቸዋል
4. ተቀበለ. The United States absorbed millions of immigrants. አሜሪካ ፣ በሚሊዮን ፣ የሚቈጠሩ ፣ ስደተኞች ፣ ተቀበለች
5. ቻለ. The company will absorb all the research costs. ኩባንያው ፣ የጥናቱን ፣ ወጪ ፣ ሁሉ ፣ ይችላል
6. ወሰደ(በት). This job absorbs all my time. ይህ ፣ ሥራ ፣ ጊዜዬን ፣ በሙሉ ፣ ይወስድብኛል
7. ማረከ. The circus absorbed the boy's attention. ሰርከሱ ፣ የልጁን ፣ መንፈስ ፣ ማረከው

**be absorbed ተመሰጠ**
He was so absorbed in his book, he did not hear me come in. በመጽሐፉ ፣ በጣም ፣ ተመስጦ ፣ ስለነበር ፣ ስገባ ፣ አልሰማኝም

## absorbent, ~ paper መምጠጫ ፣ ወረቀት
Absorbent paper is used to dry hands. መምጠጫ ፣ ወረቀት ፣ እጅን ፣ ለማድረቅ ፣ ያገለግላል

## absorbing የሚመስጥ
He told me an absorbing story. የሚመስጥ ፣ ታሪክ ፣ ነገረኝ

## abstain
1. ተቈጠበ ፤ ተጠበቀ. The doctor ordered him to abstain from meat. ሐኪሙ ፣ ከሥጋ ፣ እንዲቈጠብ ፣ አዘዘው
Athletes usually abstain from smoking. ስፖርተኞች ፣ አብዛኛውን ፣ ጊዜ ፣ ከማጨስ ፣ ይጠበቃሉ
2. ድምፅ ፣ አልሰጠም. Three nations voted for the proposal and two abstained. ሦስት ፣ አገሮች ፣ የቀረበውን ፣ ሐሳብ ፣ ሲደግፉ ፣ ሁለቱ ፣ ግን ፣ ድምፅ ፣ አልሰጡም

## abstention
1. መጠበቅ. His abstention from alcohol kept him healthy. ከአልኮል ፣ መጠበቁ ፣ በጤንነት ፣ አኖረው
2. ድምፅ ፣ አለመስጠት. The meeting adjourned after a vote of three for, two against and three abstentions. ሦስት ፣ በመደገፍ ፤ ሁለት ፣ በመቃወም ፤ ሦስት ፣ ድምፅ ፣ ባለመስጠት ፣ ስብሰባው ፣ ተበተነ

## abstinence መጠበቅ
Abstinence from liquor is good for health. ከሚያሰክር ፣ መጠጥ ፣ መጠበቅ ፣ ለጤንነት ፣ ይበጃል

## abstract (v.)
1. አወጣ. They abstract iron from ore by smelting it. አፈር ፣ በማቅለጥ ፣ ብረት ፣ ያወጣሉ
2. አሳጠረ. The student was asked to abstract the book. ተማሪው ፣ መጽሐፉን ፣ እንዲያሳጥር ፣ ተጠየቀ

## abstract (n.)
1. አኅጽሮተ ፣ ጽሑፍ. He published the full speech as well as the abstract of it. ንግግሩን ፣ በሙሉና ፣ አኅጽሮተ ፣ ጽሑፉን ፣ አሳተመ
2. የነገር ፣ ስም. Sweetness is an abstract; sugar is concrete. ጣፋጭነት ፣ የነገር ፣ ስም ፣ ነው ፤ ስኳር ፣ ግን ፣ የቆሳቍስ ፣ ስም ፣ ነው

**make an abstract አሳጥሮ ፣ ጻፈ**
He made an abstract of the book on Ethiopia. ስለ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የተጻፈውን ፣ መጽሐፍ ፣ አሳጥሮ ፣ ጻፈው

**abstract** (adj.)
1. ረቂቅ. Only advanced students can understand the abstract theory about the nature of the soul. ስለ ፣ ነፍስ ፣ ባሕርይ ፣ ረቂቅ ፣ አስተሳሰብ ፣ ሊረዱ ፣ የሚችሉ ፣ በትምህርታቸው ፣ የገፉ ፣ ተማሪዎች ፣ ብቻ ፣ ናቸው
2. የማይጨበጥ. That is an abstract question. ያ ፣ የማይጨበጥ ፣ ነገር ፣ ነው

## abstracted (adj.) የተመሰጠ
He gazed at me with an abstracted look. በተመሰጠ ፣ አስተያየት ፣ አትኩሮ ፣ ተመለከተኝ

## abstraction ረቂቅነት
The abstraction of philosophy contains the essence of human experience. የፍልስፍና ፣ ረቂቅነት ፣ የሰውን ፣ ልጅ ፣ ዕውቀት ፣ ፍሬ ፣ ነገር ፣ ይዟል
*In a moment of abstraction he grabbed the wrong hat. በሐሳብ ፣ ተውጦ ፣ ሳለ ፣ የሌላ ፣ ሰው ፣ ባርኔጣ ፣ ወሰደ

**abstruse**
1. የማይጨበጥ. What he said about the matter is abstruse. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ የተናገረው ፡ የማይጨበጥ ፡ ነው
2. ለመረዳት ፡ አዳጋች. +His ideas are abstruse. ሐሳቡን ፡ ለመረዳት ፡ አዳጋች ፡ ነው

**absurd** ዘበት
It is absurd to think I would steal. እኔ ፡ እሰርቃለሁ ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ ዘበት ፡ ነው

**absurdity** ጅልነት
It is an absurdity to wear shoes on your head. ጫማዎችን ፡ እራስ ፡ ላይ ፡ ማድረግ ፡ ጅልነት ፡ ነው

**abundance** ብዛት
The abundance of fish will develop the factory. የዓሣ ፡ ብዛት ፡ ፋብሪካውን ፡ ያደረጃል

**in abundance**
1. በገፍ. Food and drink in abundance are to be found here. መብልና ፡ መጠጥ ፡ እዚህ ፡ በገፍ ፡ ይገኛል
2. በድሎት. Since the end of the war they have lived in abundance. ጦርነቱ ፡ ካበቃ ፡ ወዲህ ፡ በድሎት ፡ ኖረዋል

**abundant**
1. የበለጸገ. Is Ethiopia abundant in minerals? ኢትዮጵያ ፡ በማዕድን ፡ የበለጸገች ፡ ናት?
2. ብዙ. We have abundant evidence to convict him. በሱ ፡ ላይ ፡ ለመፍረድ ፡ ብዙ ፡ መረጃ ፡ አለን

**abuse** (v.)
1. አጉሳቈለ. The mother abused her child. እናትዮዋ ፡ ልጇን ፡ አጉሳቈለች
2. ጐዳ. My brother abuses his eyes by reading in dim light. ወንድሜ ፡ በደብዛዛ ፡ ብርሃን ፡ በማንበብ ፡ ዓይኑን ፡ ይጐዳል
3. ያለ ፡ አግባብ ፡ ሠራ(በት). The manager abused his authority. ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ በሥልጣኑ ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ ሠራበት
4. አወከ. The demonstrators abused the speakers with their shouts. ሰላማዊ ፡ ሰልፈኞቹ ፡ ተናጋሪዎቹን ፡ በጩኸታቸው ፡ አወኳቸው
5. ሰደበ ፤ በከንቱ ፡ ጠራ. He sinned by abusing God's name.የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በመስደብ ፡ (በከንቱ ፡ በመጥራት) ፡ ኀጢአት ፡ ሠራ

**abuse each other** ተሰዳደበ
The candidates abused each other during the campaign. ተወዳዳሪዎቹ ፡ በውድድሩ ፡ ጊዜ ፡ ተሰዳደቡ

**abuse** (n.)
1. ስድብ. No one likes to listen to abuse. ስድብን ፡ መስማት ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ የለም
2. ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ አድራጎት. We hope to put an end to abuses. ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ አድራጎትን ፡ ለማስወገድ ፡ ተስፋ ፡ አለን
3. ያላግባብ ፡ መጠቀም. The abuse of power corrupts the official who does it. ሥልጣንን ፡ ያላግባብ ፡ መጠቀም ፡ ይህን ፡ የሚያደርገውን ፡ ባለሥልጣን ፡ ብልሹ ፡ ያደርገዋል
4. በ - - - መጠቀም. Abuses of public office such as taking bribes are punishable by law. ጉቦ ፡ መብላትን ፡ ለመሳሰሉት ፡ አድራጎቶች ፡ በመንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ መጠቀም ፡ በሕግ ፡ ያስቀጣል

**abusive** የዘለፋ
He showed me an abusive letter. የዘለፋ ፡ ደብዳቤ ፡ አሳየኝ

**abut** (abutted)
1. ተያያዘ. The two houses abut. ሁለቱ ፡ ቤቶች ፡ የተያያዙ ፡ ናቸው
2. ጐን ፡ ነው. The street abuts against the railroad. መንገዱ ፡ ከባቡሩ ፡ ሐዲድ ፡ ጐን ፡ ነው

**abysmal**
1. ከፍ ፡ ያለ. The people of this region live in abysmal poverty. የዚህ ፡ አካባቢ ፡ ሰዎች ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ
2. ወደር ፡ የሌለው. He showed abysmal ignorance of Ethiopian conditions. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሁኔታ ፡ ወደር ፡ የሌለው ፡ አላዋቂነት ፡ ታየበት

**abyss** ገደል
The bus crashed into the abyss. አውቶቡሱ ፡ ገደል ፡ ውስጥ ፡ ወድቆ ፡ ተሰባበረ

**acacia** ግራር

**academic**
1. የቀለም ፡ ትምህርት. We should have an institute that can grant academic degrees. ለቀለም ፡ ትምህርት ፡ ድግሪ ፡ የሚሰጥ ፡ ድርጅት ፡ እንዲኖረን ፡ ያሻል
2. ለአስተሳሰብ ፡ ብቻ ፡ የሚጠቅም. Whether or not to have a language academy is now an academic question. የቋንቋ ፡ አካዳሚ ፡ ይኑር ፡ አይኑር ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ባሁን ፡ ጊዜ ፡ ለአስተሳሰብ ፡ ብቻ ፡ የሚጠቅም ፡ ነው

**academic preparation** ትምህርት
He has sufficient academic preparation for the job. ለሥራው ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ትምህርት ፡ አለው
[See also 'year']

**academy** አካዳሚ
There is an urgent need for a language academy. የቋንቋ ፡ አካዳሚ ፡ ባስቸኳይ ፡ ያስፈልጋል

**accede, ~ to**
1. ተቀበለ. He acceded to my request. ጥያቄዬን ፡ ተቀበለ
2. ያዘ. He acceded to the chairmanship after the incumbent died. የቀድሞው ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ሲሞት ፡ እሱ ፡ ሊቀ ፡ መንበርነቱን ፡ ያዘ
3. ወረሰ. When the king died his son acceded to the throne. ንጉሡ ፡ ሲሞቱ ፡ ልጁ ፡ አልጋውን ፡ ወረሰ

**accelerate** (vt.)
1. ፍጥነት ፡ ጨመረ. The drivers accelerated the motor by stepping on the pedal. ነጂዎቹ ፡ ቤንዚን ፡ መስጫውን ፡ በመርገጥ ፡ የሞተሩን ፡ ፍጥነት ፡ ጨመሩ
2. አፋጠነ. Foreign aid is needed to accelerate Ethiopia's development. የኢትዮጵያን ፡ ልማት ፡ ለማፋጠን ፡ የውጭ ፡ እርዳታ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**accelerate** (vi.) ፍጥነት ፡ ጨመረ
The stone will accelerate as it rolls down the mountain. ድንጋዩ ፡ ተራራውን ፡ ሲወርድ ፡ ፍጥነት ፡ እየጨመረ ፡ ይሄዳል

**acceleration**
*Stepping on the gas pedal causes the acceleration of the car. ቤንዚን ፡ መስጫውን ፡ ብትረግጠው ፡ የመኪናው ፡ ፍጥነቱ ፡ ይጨምራል

**accent** (v.)
1. አነሣ. Accent the first syllable of this word! የዚህን ፡ ቃል ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍለ ፡ ቃል ፡ አንሣ
2. አጐላ. Her scarf accented her blue eyes. ያንገቷ ፡ ፎጣ ፡ ሰማያዊውን ፡ ዓይኖቿን ፡ አጐላቸው

**accent** (n.)
1. ቅናትና ፡ ድፋት. Where is the accent in this word? የዚህ ፡ ቃል ፡ ቅናትና ፡ ድፋት ፡ የት ፡ ላይ ፡ ነው?
2. ጭረት. The French alphabet uses different accents for the vowels. የፈረንሳይ ፡ ፊደል ፡ ለድምፅ ፡ አናባቢዎች ፡ በተለዩ ፡ ጭረቶች ፡ ይጠቀማል
3. አነጋገር. His foreign accent betrayed him. የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ አነጋገሩ ፡ አጋለጠው
*He still speaks with an accent. አነጋገሩ ፡ እንደ ፡ አገሩ ፡ ተወላጅ ፡ አይደለም

**accentuate** አጐላ
Her black hair accentuated the whiteness of her skin. ጥቁሩ ፡ ጸጉሯ ፡ የቆዳዋን ፡ ንጣት ፡ አጐላው

**be accentuated** ተመራ
The rhythm of the dance was accentuated by drum beats. የጭፈራው ፡ ውዝዋዜ ፡ የሚመራው ፡ በከበሮ ፡ ምት ፡ ነው

**accept**
1. ተቀበለ. Will you accept that position? ያንን ፡ ሥራ ፡ ትቀበላለህ?
She accepted the gift. ስጦታውን ፡ ተቀበለች
They accepted our invitation for dinner. ያደረግንላቸውን ፡ የእራት ፡ ግብዣ ፡ ተቀበሉ
2. እሺ ፡ አለ. He asked her to marry him, and she accepted. እንድታገባው ፡ ጠይቋት ፡ ነበር ፡ እሺ ፡ አለችው
3. አላመደ. The children immediately accepted their new classmate. ልጆቹ ፡ አዲሱን ፡ የክፍል ፡ ጓደኛቸውን ፡ ወዲያውኑ ፡ አላመዱት

**be accepted**
1. ለመግባት ፡ ቻለ. Only able-bodied men are accepted into the army. ወደ ፡ ጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ ለመግባት ፡ የሚችሉ ፡ የተሟላ ፡ ሰውነት ፡ ያላቸው ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ታመነ. It is now generally accepted that the world is round. ዛሬ ፡ ዓለም ፡ ክብነቷ ፡ በጠቅላላው ፡ ታምኗል
3. ተቀባይነት ፡ አገኘ. Einstein's theory was widely accepted. የአይንስታይን ፡ ዕንሰ ፡ ሐሳብ ፡ በሰፊው ፡ ተቀባይነት ፡ አገኘ

**acceptable** ተስማሚ
His behavior is acceptable. ጠባዩ ፡ ተስማሚ ፡ ነው

**be acceptable** ተቀባይነት ፡ አገኘ
The plan was acceptable to everyone. እቅዱ ፡ በሁሉም ፡ ተቀባይነት ፡ አገኘ

**acceptance**
1. መቀበል. Her acceptance of the flower they brought delighted the children. ያመጡላትን ፡ አበባ ፡ መቀበሏ ፡ ልጆቹን ፡ አስደሰታቸው
The acceptance of responsibilities is a sign of adulthood. ኀላፊነትን ፡ መቀበል ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ የመድረስ ፡ ምልክት ፡ ነው
2. ተቀባይነት. The invention found widespread acceptance. አዲስ ፡ የተፈለሰፈው ፡ ነገር ፡ ሰፊ ፡ ተቀባይነት ፡ አገኘ
*She was delighted by her acceptance into the club. የክበቡ ፡ አባል ፡ እንድትሆን ፡ ስለተቀበሏት ፡ ደስ ፡ አላት

**access** መድረስ
Access to the mountainous towns is often difficult because of poor roads. ከመንገዶች ፡ መጥፎነት ፡ የተነሣ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ተራራማ ፡ ወደ ፡ ሆኑ ፡ ከተማዎች ፡ መድረስ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**gain access** ሊገባ ፡ ቻለ ፤ ገባ
They gained access through a back window. ከኋር ፡ ባለው ፡ መስኮት ፡ ሊገቡ ፡ ቻሉ
The queue was too big and I couldn't gain access to the theater. ሰልፉ ፡ ስለበዛብኝ ፡ ቲያትር ፡ ሳልገባ ፡ ቀረሁ

**have access to**
1. ለመግባት ፡ ቻለ. All children have access to the library during the afternoon. ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ ለመግባት ፡ ይችላሉ
2. ለመቅረብ ፡ ቻለ. Only high officials have access to the Emperor. ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዘንድ ፡ ለመቅረብ ፡ የሚችሉት ፡ ከፍተኛ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ብቻ ፡ ናቸው
3. ለማየት ፡ ቻለ. He has access to the files. ዶሴዎቹን ፡ ለማየት ፡ ይችላል

**have an access of**
He had an access of coughing. ሳል ፡ ይዞታል

**accessible** በቀላሉ ፡ የሚደረስ
Debre Bizen is an accessible monastery. ደብረ ፡ ቢዘን ፡ በቀላሉ ፡ የሚደረስ ፡ ገዳም ፡ ነው
*A telephone should be put where it is accessible. ስልክ ፡ በቀላሉ ፡ ሊደረስበት ፡ በሚቻልበት ፡ ስፍራ ፡ መቀመጥ ፡ አለበት

**be accessible to** ተቀበለ
An open-minded person is accessible to reason. ሐሳበ ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የሌሎችን ፡ አስተሳሰብ ፡ ይቀበላል

**accession** መጨመር
The school was increased by the accession of fourteen new pupils. ዐሥራ ፡ አራት ፡ አዲስ ፡ ተማሪዎች ፡ በመጨመራቸው ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አደገ

**accession to the throne** የዙፋን ፡ አወራረስ
The constitution defines the accession to the throne. ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የዙፋንን ፡ አወራረስ ፡ ይደነግጋል

**accessory** (accessories)
1. ተጨማሪ ፡ እቃዎች. Duty has been imposed on automobile accessories. በመኪና ፡ ተጨማሪ ፡ እቃዎች ፡ ላይ ፡ ቀረጥ ፡ ተደርጎባቸዋል
2. ጌጣ ፡ ጌጥ. A woman likes her accessories to be of the same color as her dress. ሴት ፡ ጌጣ ፡ ጌጥ ፡ ከልብሷ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ቀለም ፡ ቢኖራቸው ፡ ትወዳለች

**accident**
1. አደጋ. When did the automobile accident happen? የመኪና ፡ አደጋ ፡ መቼ ፡ ደረሰ?
2. (= by accident) እንዳጋጣሚ. Our meeting was an accident. የተገናኘነው ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ነበር

**by accident** እንዳጋጣሚ
I found it out by accident. እንዳጋጣሚ ፡ ደረስኩበት
[See also 'overt, prevent']

**accidental** (= adv.)
1. ሳይታሰብ. An accidental discovery of oil was reported in the paper. ሳይታሰብ ፡ ዘይት ፡ መገኘቱ ፡ በጋዜጣ ፡ ተነገረ
2. በድንገት. Breaking her doll was accidental. አሻንጉሊቷን ፡ የሰበረው ፡ በድንገት ፡ ነው

**accidentally** በድንገት ፤ እንዳጋጣሚ
I dropped the plate accidentally. ሳሕኑን ፡ በድንገት ፡ ጣልኩት
I accidentally learned the truth. እውነቱን ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ደረስኩበት

**acclaim** (v.) የጋለ ፡ አድናቆቱን ፡ ገለጸ(ለት)
The crowd acclaimed the fireman for rescuing two people from the burning house. የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካዩ ፡ ከተቃጠለው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሁለት ፡ ሰዎች ፡ ሕይወት ፡ ስላተረፈ ፡ ሕዝቡ ፡ የጋለ ፡ አድናቆቱን ፡ ገለጸለት

**be acclaimed** ተባሎ ፡ ተጨበጨበ(ለት)
He was acclaimed winner of the race. እሱ ፡ የእሽቅድምድሙ ፡ አሸናፊ ፡ ተብሎ ፡ ተጨበጨበለት

**acclaim** (n.)
1. ጭብጨባና ፡ እልልታ. The Emperor was greeted with acclaim. ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ በጭብጨባና ፡ በእልልታ ፡ ተቀበሉዋቸው
2. ሆታ. The birth of the new nation was greeted with acclaim. ያዲሱን ፡ አገር ፡ መመሥረት ፡ በሆታ ፡ ተቀበሉት

**acclamation** አድናቆት
A shout of acclamation was heard when the winner was announced. አሸናፊው ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ የአድናቆት ፡ ጭብጨባ ፡ ተሰማ

**by acclamation** ድምፅ ፡ ሳይሰጥ ፡ በጭብጨባ
He was elected president by acclamation. ድምፅ ፡ ሳይሰጥ ፡ በጭብጨባ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሆኖ ፡ ተመረጠ

**acclimate** ለመደ
The dogs acclimated quickly to the colder country. ውሾቹ ፡ ብርዳሙን ፡ አገር ፡ በቶሎ ፡ ለመዱት

**acclimate oneself** ለመደ
Tom acclimated himself readily to the new town. ቶም ፡ አዲሱን ፡ ከተማ ፡ በፍጥነት ፡ ለመደ

**acclimatize** አለማመደ
They acclimatized the plants to the dry region. ዕፀዋትን ፡ ከደረቁ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ጋር ፡ አለማመዱ

**accommodate**
1. አስማማ. I will accommodate my plans to yours. የኔን ፡ እቅድ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ አስማማዋለሁ
2. አስቀመጠ. This table easily accommodates six people. ይህ ፡ ጠረጴዛ ፡ ስድስት ፡ ሰው ፡ ያለችግር ፡ ያስቀምጣል
3. አዘረጋ. The big bedroom will accommodate six beds. ትልቁ ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ ስድስት ፡ አልጋዎች ፡ ያዘረጋል
4. ረዳ. He accommodated his friend with money. ጓደኛውን ፡ በገንዘብ ፡ ረዳው
5. አገኘ(ለት). He wanted change for a quarter, but I could not accommodate him. ለስሙኒ ፡ ምንዛሬ ፡ ፈልጎ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ላገኝለት ፡ አልቻልኩም

**accommodate oneself** ራሱን ፡ አስማማ
He accommodated himself to the circumstances. ከሁኔታው ፡ ጋር ፡ ራሱን ፡ አስማማ

**accommodating** ፈቃደኛ
The man was accommodating enough to lend me a dollar. ሰውየው ፡ ብር ፡ ሊያበድረኝ ፡ ፈቃደኛ ፡ ነበር

**accommodation**
1. ማስማማት. The accommodation of old ideas to a new plan was possible. የድሮውን ፡ አስተሳሰብ ፡ ከአዲሱ ፡ እቅድ ፡ ጋር ፡ ማስማማት ፡ ተቻለ
2. ምቾት. The hotel has a restaurant for the accommodation of its guests. ሆቴሉ ፡ ለእንግዶች ፡ ምቾት ፡ የተዘጋጀ ፡ የምግብ ፡ ቤት ፡ አለው

**accommodations** ማረፊያ
They finally found accommodations in a small hotel. በመጨረሻ ፡ ካንዲት ፡ ትንሽ ፡ ሆቴል ፡ ውስጥ ፡ ማረፊያ ፡ አገኙ

**accompany** (accompanied)
1. ሸኘ. His friends accompanied him to the railroad station. ጓደኞቹ ፡ እስከ ፡ ባቡር ፡ ጣቢያ ፡ ድረስ ፡ ሸኙት
2. ተከትሎ ፡ መጣ. Evangelists accompanied the Spanish colonizers in South America. ወንጌላውያን ፡ የእስፓኝ ፡ አገር ፡ አቅኚዎችን ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ መጡ
3. ዐጀበ. The orchestra accompanied the singer. ኦርኬስትራው ፡ ዘፋኙን ፡ ዐጀበው
The nobility accompanied the Emperor to church. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲሄዱ ፡ መኳንንቱ ፡ ዐጀቧቸው
4. ተቀላቀለ(በት). Wind accompanied the rain. ነፋሱ ፡ ዝናብ ፡ ተቀላቅሎበት ፡ ነበር
*He accompanied his speech with gestures. ንግግር ፡ ሲያደርግ ፡ ከሰውነት ፡ እንቅስቃሴ ፡ ጭምር ፡ ነበር

**accomplice** ግብረ ፡ አበር
Who was his accomplice in this plot? በእድማው ፡ ግብረ ፡ አበሩ ፡ ማን ፡ ነበር?

**accomplish**
1. ፈጸመ. For one day he accomplished quite a lot. ባንድ ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ ፈጸመ
2. አከናወነ. Did he accomplish anything? Nothing to speak of. ያከናወነው ፡ ነገር ፡ አለ? የሚነገርለት ፡ አይደለም
3. ጨረሰ. With their work accomplished the boys went out to play. ልጆቹ ፡ ሥራቸውን ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ለመጫወት ፡ ሄዱ

**accomplished** (adj.) የወጣለት
He is an accomplished speaker of English. የወጣለት ፡ እንግሊዝኛ ፡ ተናጋሪ ፡ ነው

**accomplishment** ሥራ ፤ የሥራ ፡ ውጤት
His mother is proud of his accomplishments. እናቱ ፡ በሥራው ፡ ትኰራለች
These accomplishments are merely collateral to his primary goal. እነዚህ ፡ የሥራ ፡ ውጤቶች ፡ የዋናው ፡ ዓላማው ፡ ቅርንጫፎች ፡ ናቸው

**accord** (vt.)
1. አደረገ. They accorded him a warm welcome. ትልቅ ፡ አቀባበል ፡ አደረጉለት
2. ሰጠ. We accord praise to those who deserve it. ምስጋና ፡ ለሚገባቸው ፡ እንሰጣለን

**accord** (vi.) ተስማማ
His account of the accident accords with yours. ስለ ፡ አደጋው ፡ መድረስ ፡ እሱ ፡ የተናገረው ፡ አንተ ፡ ካልከው ፡ ጋር ፡ ይስማማል

**accord** (n.)

1. መግባባት. They acted in complete accord with him in releasing the prisoner. እስረኛውን ፡ ሲፈቱ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ በሙሉ ፡ መግባባት ፡ ነበር
2. ስምምነት. France and England reached an accord over certain tariffs. ፈረንሳይና ፡ እንግሊዝ ፡ ስለ ፡ አንዳንድ ፡ ቀረጦች ፡ ከስምምነት ፡ ደረሱ

**be in accord** ተስማማ

Their opinion of war was in accord with his. ስለ ፡ ጦርነት ፡ ያላቸው ፡ አስተሳሰብ ፡ እሱ ፡ ካለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ጋር ፡ ተስማማ

**of his own accord** በገዛ ፡ ፈቃዱ

He did it of his own accord. በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ አደረገው

**accordance, in ~ with**

1. እንደ + (noun). We tried to live in accordance with the customs of the country. እንደ ፡ አገሩ ፡ ልማድ ፡ ለመኖር ፡ ሞከርን
2. በ - - - መሠረት. In accordance with your request we are sending you three books. በጥያቄህ ፡ መሠረት ፡ ሦስት ፡ መጽሐፍ ፡ እንልክልሃለን

**according to**

1. እንደ + (noun). He will be punished according to the seriousness of his crimes. እንደ ፡ ወንጀሉ ፡ ከባድነት ፡ ይቀጣል
2. በ - - - መሠረት. Everything was carried out according to instructions. ሁሉም ፡ ነገር ፡ በመምሪያው ፡ መሠረት ፡ ተፈጸመ
3. በ - - - መጠን. He spends according to his income. የሚያወጣው ፡ በገቢው ፡ መጠን ፡ ነው
4. (= conj.) እንደ + (verb). According to the Bible, God created the earth in six days. መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንደሚለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ምድርን ፡ በስድስት ፡ ቀን ፡ ፈጠረ

**accordingly** በዚያ ፡ መሠረት ፤ እንደ ፡ ደንቡ

I have told you what to do, so act accordingly. ምን ፡ እንደምታደርግ ፡ ነግሬሃለሁ ፤ በዚያ ፡ መሠረት ፡ ሥራ

I have heard the evidence and will judge accordingly. መረጃውን ፡ ሰምቻለሁና ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ውሳኔውን ፡ እሰጣለሁ

*He felt unwell and, accordingly, left. ጤንነቱ ፡ ስለታወከ ፡ ሄደ

**accordion** አኮርዲዮን

He plays the accordion. አኮርዲዮን ፡ ይጫወታል

**accost**

1. አነጋገረ. A stranger accosted me. የማላውቀው ፡ ሰው ፡ አነጋገረኝ
2. ተማጠነ. A beggar accosted him begging for money. ለማኙ ፡ ገንዘብ ፡ ቢሰጠኝ ፡ ብሎ ፡ ተማጠነ

**account (for)**

1. ምክንያት ፡ ገለጸ. We must account for every dollar spent. እያንዳንዱ ፡ ብር ፡ የወጣበትን ፡ ምክንያት ፡ መግለጽ ፡ አለብን
2. ምክንያት ፡ ሰጠ. How do you account for that? ለዚያ ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ ትሰጣለህ?
3. ምክያት ፡ አለው. How do you account for your lateness? ለመዘግየትህ ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ አለህ?
4. ምክንያት ፡ ሆነ. His illness accounts for his actions. ላድራጎቱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ሕመሙ ፡ ነው
5. ኀላፊ ፡ ሆነ. You will have to account for your actions. በምታደርገው ፡ ነገር ፡ ኀላፊ ፡ መሆን ፡ ይኖርብሃል

*A dry spell accounted for the poor crops. አዝመራው ፡ የተበላሸው ፡ ከድርቀት ፡ የተነሣ ፡ ነው

**account** (n.)

1. መግለጫ. His account of the accident is not clear. ስለ ፡ አደጋው ፡ የሰጠው ፡ መግለጫ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም
2. ታሪክ. He gave a colored account of the battle. ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ ያቀረበው ፡ ታሪክ ፡ የተዛባ ፡ ነው
3. ተቀማጭ ፡ ሒሳብ. I have an account in this bank. እዚህ ፡ ባንክ ፡ ተቀማጭ ፡ ሒሳብ ፡ አለኝ
4. ሒሳብ. You will have to give an account of every penny you spend. ለያንዳንዷ ፡ ያወጣሃት ፡ ሳንቲም ፡ ሁሉ ፡ ሒሳብ ፡ ማቅረብ ፡ አለብህ
5. ምክንያት. I did not do it on this account. የሠራሁት ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም

*I have an account to settle with him. ከሱ ፡ ጋር ፡ እንተያያለን

**accounts** የሒሳብ ፡ መዝገብ

The company's accounts were in good order. የኩባንያው ፡ የሒሳብ ፡ መዝገብ ፡ በደንብ ፡ ነበር

**by all accounts** እንደሚባለው

It seems, by all accounts, that Ras Ali was a rival of King Theodore. እንደሚባለው ፡ ራስ ፡ ዓሊ ፡ የንጉሥ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ተቀናቃኝ ፡ የነበሩ ፡ ይመስላል

**call to account** ምክንያቱን ፡ እንዲነግረው ፡ ጠየቀው

He called his secretary to account when he found some money missing. ገንዘብ ፡ መጥፋቱን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ምክንያቱን ፡ እንዲነግረው ፡ ጸሓፊውን ፡ ጠየቀው

**of no account** ዋጋ ፡ ቢስ
His advice was of no account. የሱ ፡ ምክር ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ነበር

**on account** በዱቤ
She bought her furniture on account. የቤት ፡ እቃዋን ፡ የገዛችው ፡ በዱቤ ፡ ነው

**on (one's) account** ለሱ ፡ ብሎ ፤ ስለሱ
Don't go to any trouble on my account. ለኔ ፡ ብለህ ፡ (ስለኔ) ፡ ምንም ፡ አትቸገር

**on account of**
1. በ - - - ምክንያት. The game was postponed on account of rain. በዝናብ ፡ ምክንያት ፡ ጨዋታው ፡ ተላለፈ
2. በ - - - የተነሣ. On account of that, he was fired. በዚያ ፡ የተነሣ ፡ ከሥራ ፡ ተወገደ

**on no account** በምንም ፡ ምክንያት
On no account must you open this drawer. በምንም ፡ ምክንያት ፡ ይህንን ፡ መሳቢያ ፡ መክፈት ፡ የለብህም

**take into account**
1. አመዛዘነ. You have to take all the facts into account. ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ማመዛዘን ፡ አለብህ
2. ተመለከተ. The provisions of the law do not take this matter into account. የሕጉ ፡ አንቀጾች ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ አይመለከቱም
3. ግምት ፡ ውስጥ ፡ አደረገ. Before building a house he took into account the increased cost of materials. ቤት ፡ ከመሥራቱ ፡ በፊት ፡ የሕንጻ ፡ መሣሪያዎች ፡ መወደዳቸውን ፡ ግምት ፡ ውስጥ ፡ አደረገ

**take no account of** ችላ ፡ አለ
Take no account of his words. የሚናገረውን ፡ ችላ ፡ በለው

## (be) accountable for ኀላፊ ፡ ነው
Each person is accountable for his own work. እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ለሠራው ፡ ሥራ ፡ ኀላፊ ፡ ነው

## accountant ሒሳብ ፡ ዐዋቂ
Since I did not agree with my partner, we consulted an accountant. ከሽርኬ ፡ ጋር ፡ በሒሳብ ፡ ስላልተስማማን ፡ ሒሳብ ፡ ዐዋቂ ፡ አማከርን

## accredit
1. አምኖ ፡ ተቀበለ. The committee accredited Parker's report of the events. ፓርከር ፡ ስለ ፡ ሁኔታው ፡ የሰጠውን ፡ መግለጫ ፡ ደርጉ ፡ አምኖ ፡ ተቀበለው
2. ብሎ ፡ ተቀበለ. We accredit the invention of the telephone to Bell. ቤል ፡ ስልክን ፡ የፈለሰፈ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ተቀብለነዋል
3. የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡ ሰጥቶ ፡ ላከው. The minister accredited him as ambassador to England. ሚኒስትሩ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ አምባሳደር ፡ እንዲሆን ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡ ሰጥተው ፡ ላኩት
4. ተቀባይነት ፡ አገኘ. +The committee accredited the college. ኮሌጁ ፡ በደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነት ፡ አገኘ

## accretion የተጨመረ
The last part of the legend is a later accretion. የታሪኩ ፡ የመጨረሻ ፡ ክፍል ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ የተጨመረ ፡ ነው

**by accretion** በጥቃቅን ፡ አካሎች ፡ መዋሐድ
Some rocks are formed by accretion. አንዳንድ ፡ ቋጥኞች ፡ የሚሠሩት ፡ በጥቃቅን ፡ አካሎች ፡ መዋሐድ ፡ ነው

## accrue ጨመረ
Interest will accrue on my savings account. እባንክ ፡ ያለኝ ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘብ ፡ ወለዱ ፡ ይጨምራል
*Benefits accrue to society from better education. ከተሻለ ፡ ትምህርት ፡ የተነሣ ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ይጠቀማል

## accumulate (vt.)
1. አከማቸ. By working hard he accumulated a big fortune. ጠንክሮ ፡ በመሥራት ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ አከማችቷል
2. አጠራቀመ. He likes to accumulate money. ገንዘብ ፡ ማጠራቀም ፡ ይወዳል

**accumulate** (vi.) ተከማቸ ፤ ተጠራቀመ
If you don't sweep, dust will accumulate. ካልጠረግኸው ፡ አቧራ ፡ ይከማቻል
If earwax accumulates, it may hurt the ear. ኩክ ፡ በጆሮ ፡ ሲጠራቀም ፡ ሊጐዳው ፡ ይችላል

## accumulation
*The accumulation of knowledge is a result of reading. ዕውቀት ፡ የሚዳብረው ፡ ብዙ ፡ በማንበብ ፡ ነው
*His accumulation of old papers filled three trunks. ያጠራቀማቸው ፡ አሮጌ ፡ ወረቀቶች ፡ ሦስት ፡ ሣጥን ፡ ሞሉ

## accuracy ትክክለኛነት ፤ ትክክለኛ ፡ መሆን
I trust the accuracy of his story. የታሪኩን ፡ ትክክለኛነት ፡ አምናለሁ
The attestations of all witnesses were checked for accuracy. የምስክሮች ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ትክክለኛ ፡ ለመሆኑ ፡ ተመረመረ

## accurate ትክክለኛ
She is very accurate in her work. በሥራዋ ፡ በጣም ፡ ትክክለኛ ፡ ናት

Give me an accurate report of the accident! ስለ ፡ አደጋው ፡ ትክክለኛ ፡ መግለጫ ፡ ስጠኝ

**accurately** በትክክል
She described the accident accurately. አደጋ ውን ፡ እንዴት ፡ እንደደረሰ ፡ በትክክል ፡ ገለ ጸችው

**accursed** (adj.) የተረገመ
The poor man felt himself accursed. ድኻው ፡ ሰው ፡ የተረገመ ፡ መሆኑ ፡ ተሰማው

**accusation** ክስ
The man denied the accusation that he was a thief. ሰውዬው ፡ ሌባ ፡ ነህ ፡ ተብሎ ፡ የቀረበ በትን ፡ ክስ ፡ ካደ

**bring an accusation against** ከሰሰ
Why did he bring an accusation against him? ለምን ፡ ከሰሰው?

**lay an accusation against** ከሰሰ
He will lay an accusation of theft against the official. ሹሙን ፡ በሌብነት ፡ ይከሰዋል

**level an accusation** ክስ ፡ አቀረበ
He leveled an accusation against the governor. በአገረ ፡ ገዢው ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ አቀረበ

**accuse**
1. ከሰሰ. He accused him of theft. በሌብነት ፡ ከሰሰው
2. ወቀሰ. You can't accuse me of being lazy. ሰነፍ ፡ ነህ ፡ ብለህ ፡ ልትወቅሰኝ ፡ አትችልም

**accused** (n., adj.) ተከሳሽ
They brought the accused to court. ተከሳሹን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረቡት

**accuser** ከሳሽ
The judge gave an adverse decision to the accuser. ዳኛው ፡ ለከሳሹ ፡ የሚጐዳው ፡ ውሳኔ ፡ ሰጠ

**accustom** አለማመደ ፤ አስለመደ
He accustomed his hunting dog to the noise of a gun. የአደን ፡ ውሻውን ፡ ከጠመንጃ ፡ ጩ ኸት ፡ ጋር ፡ አለማመደው
The job accustomed him to meeting many people. ሥራው ፡ ከብዙ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ መገናኘ ትን ፡ አስለመደው

**accustomed** (adj.) የተለመደ
By Monday he was back in his accustomed place. ሰኞ ፡ ተመልሶ ፡ እተለመደው ፡ ቦታ ፡ ነ በር

**be accustomed** ለመደ
He was accustomed to hard work. ከባድ ፡ ሥ ራ ፡ መሥራትን ፡ የለመደ ፡ ነው

**get accustomed** ተላመደ
He couldn't get accustomed to the strict discipline. ጥብቅ ፡ ከሆነው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጋር ፡ ሊላመድ ፡ አልቻለም

**acerbity** ጐምዛዛነት
The acerbity of this fruit set my teeth on edge. የፍሬው ፡ ጐምዛዛነት ፡ ጥርሴን ፡ አደነዘዘው
*The acerbity of his words makes the students angry. መርዘኛ ፡ ንግግሩ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ያናድዳ ቸዋል

**ache** (v.)
1. አመመ(ው). My ear aches. ጆሮዬን ፡ ያመኛል
2. ጓጓ. He ached for his freedom. ለነጻነቱ ፡ ጓጓ

**ache all over** ሰውነቱ ፡ ጓጐለ
After riding the mule all day, he ached all over. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ በበቅሎ ፡ ስለተጓዘ ፡ ሰውነቱ ፡ ጓጐለ

**(one's) heart aches** ራራ
Her heart ached for the starving animals. ለተራቡ ፡ እንስሳት ፡ ራራች

**ache** (n.) ሕመም
This medicine relieves all aches. ይህ ፡ መድ ኃኒት ፡ ማንኛውንም ፡ ሕመም ፡ ያስታግሣል

**achieve**
1. ፈጸመ. He will never achieve anything. ምን ም ፡ ነገር ፡ ሊፈጽም ፡ አይችልም
2. ሠራ. I have achieved only half of what I hoped to do. ልሠራ ፡ ከምመኘው ፡ ገሚሱን ፡ ብቻ ፡ ሠርቻለሁ
3. አገኘ. He achieved distinction in mathematics. በሒሳብ ፡ ሊቅነትን ፡ አገኘ
4. ከግብ ፡ አደረሰ. He achieved his purpose. ዓላማውን ፡ ከግብ ፡ አደረሰ

**achievement**
1. ከፍተኛ ፡ ውጤት. Hoover Dam is an engineering achievement. የሁቨር ፡ ግድብ ፡ የሕንጸ ፡ ሥራ ፡ ከፍተኛ ፡ ውጤት ፡ ነው
2. የሥራ ፡ ክንውን. By his achievements, the president dignified his office. በሥራው ፡ ክ ንውን ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ሹመቱን ፡ አስከበረው
3. ማግኘት. The achievement of skill takes practice. ቅልጥፍና ፡ ለማግኘት ፡ ልምምድ ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል

**acid** (n.) አሲድ
The acid ate into the iron. አሲድ ፡ ብረቱን ፡ በላው

**acid** (adj.) ኮምጣጣ
A lemon is an acid fruit. ሎሚ ፡ ኮምጣጣ ፡ ፍሬ ፡ ነው

**acknowledge**
1. አረጋገጠ. This is to acknowledge receipt of your letter. ይህ ፡ የጻብጻቤህን ፡ መድረስ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ነው
2. ገለጸ. Please acknowledge receipt! መድረሱን ፡ ግለጽልኝ
3. አምኖ ፡ ተቀበለ. He acknowledged his own faults. የራሱን ፡ ጥፋት ፡ አምኖ ፡ ተቀበለ
4. ዐወቀ(ለት). The boys acknowledged him to be the best football player. ከተጫዋቾቹ ፡ ሁሉ ፡ ምርጥ ፡ ተጫዋች ፡ እሱ ፡ መሆኑን ፡ ልጆቹ ፡ ዐወቁለት

**acknowledgment**
1. ማረጋገጫ. A receipt is an acknowledgment that a bill has been paid. ደረሰኝ ፡ ገንዘብ ፡ ለመከፈሉ ፡ ማረጋገጫ ፡ ነው
2. ማሰብ. The company gave Mr. Parker a medal in acknowledgment of his long service. ኩባንያው ፡ የረዥም ፡ ጊዜ ፡ አገልግሎታቸውን ፡ በማሰብ ፡ ለሚስተር ፡ ፓርከር ፡ ሜዳይ ፡ ሸለማቸው

**acoustic** (adj.) የመስሚያ
Earphones are acoustic aids for deaf people. የጆሮ ፡ ማድመጫዎች ፡ ለደንቆሮዎች ፡ ለመስሚያ ፡ ረዳቶች ፡ ናቸው

**acoustics** ድምፅ ፡ መስጫ
The acoustics of the new hall are excellent. ያዲሱ ፡ አዳራሽ ፡ ድምፅ ፡ መስጫ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነው

**acquaint** ገለጸ(ለት)
I want to acquaint you with the facts of the case. የጉዳዩን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ልገልጽልህ ፡ እፈልጋለሁ

**acquaint oneself** ተረዳ
It will take me a week to acquaint myself with all the problems. ችግሩን ፡ በሙሉ ፡ ለመረዳት ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ይፈጅብኛል

**be acquainted (with)**
1. ተረዳ. Are you fully acquainted with the case? ጉዳዩን ፡ በደንብ ፡ ተረድተኸዋል?
2. ተዋወቀ. He is acquainted with my father. ካባቴ ፡ ጋር ፡ ይተዋወቃል
3. ተለማመደ. I am acquainted with the work. ሥራውን ፡ ተለማምጄዋለሁ

**get acquainted with each other** ተዋወቀ
You two should get acquainted with each other. ሁለታችሁ ፡ መተዋወቅ ፡ አለባችሁ
[See also 'intimately']

**acquaintance**
1. የሚያውቀው ፡ ሰው. An acquaintance of mine came to see me yesterday. አንድ ፡ የማውቀው ፡ ሰው ፡ ትናንት ፡ ሊጠይቀኝ ፡ መጣ
2. ጓደኝነት. We struck up an acquaintance while we were abroad. ውጭ ፡ አገር ፡ በነበርንበት ፡ ጊዜ ፡ ጓደኝነት ፡ መሠረትን

**be an acquaintance** (= know) ዐወቀ
He is an acquaintance, not a close friend. እውቀዋለሁ ፡ እንጂ ፡ የቅርብ ፡ ጓደኛዬ ፡ አይደለም

**have acquaintance with** ዐወቀ
He has some acquaintance with Amharic, but does not speak it fluently. አማርኛ ፡ በመጠኑ ፡ ያውቃል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አቀላጥፎ ፡ አይናገረውም

**make acquaintance** ተዋወቀ
I was very happy to make his acquaintance. ስለተዋወቅሁት ፡ ደስ ፡ ብሎኛል

**acquiesce in** በእርምጥ ፡ ተቀበለ
We acquiesced in their plans because we couldn't suggest a better one. የተሻለ ፡ ሐሳብ ፡ ለማቅረብ ፡ ስላልቻልን ፡ የነሱን ፡ እቅድ ፡ በእርምጥ ፡ ተቀበልነው

**acquire**
1. አገኘ. He acquired a good knowledge of Amharic. ጥሩ ፡ ያማርኛ ፡ ችሎታ ፡ አግኝቷል
He acquired considerable skill in football. በግር ፡ ኳስ ፡ ጨዋታ ፡ ከፍተኛ ፡ ችሎታ ፡ አገኘ
2. ቀሠመ. He has an inquisitive mind, and has acquired a lot of knowledge at an early age. ተመራማሪ ፡ አእምሮ ፡ ስላለው ፡ ገና ፡ በወጣትነቱ ፡ ብዙ ፡ ዕውቀት ፡ ቀሥሟል
3. ወረሰ. We acquired the house when our uncle died. አጎታችን ፡ ሲሞት ፡ ቤቱን ፡ ወረስን
[See also 'polish']

**acquirement** የገበየው ፡ ነገር
One of his recent acquirements is a knowledge of French. በቅርቡ ፡ ከገበያቸው ፡ ነገሮች ፡ የፈረንሳይ ፡ ቋንቋ ፡ መቻሉ ፡ አንዱ ፡ ነው

**acquisition** ማግኘት
Acquisition of skill in riding requires much effort. ፈረስ ፡ የመጋለብን ፡ ችሎታ ፡ ለማግኘት ፡ ብዙ ፡ ጥረት ፡ ይጠይቃል
*This land is a recent acquisition. ይህ ፡ መሬት ፡ በቅርብ ፡ የተገኘ ፡ ነው

**(be) acquisitive** (of)

1. ማግበስበስ ፡ ወደደ. A miser is acquisitive of money. ጨቅ ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ማግበስበስ ፡ ይወዳል

2. ቀሠመ. A great scholar is acquisitive of ideas. ታላቅ ፡ ሊቅ ፡ ሐሳብን ፡ ይቀሥማል

**acquit** (acquitted) በነጻ ፡ ለቀቀ

The judge acquitted him. ዳኛው ፡ በነጻ ፡ ለቀቀው

**acquit oneself well**

*The new player acquitted himself well in the football game. አዲሱ ፡ ተጫዋች ፡ የእግር ፡ ኳስ ፡ ጨዋታውን ፡ ጥሩ ፡ ተጫወተ

*He acquitted himself well in battle. ጦርነቱን ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ተዋጋ

**acquittal** በነጻ ፡ መለቀቅ

His acquittal was published in the newspaper. በነጻ ፡ መለቀቁ ፡ በጋዜጣ ፡ ተገለጸ

**acre** [የመሬት ፡ መለኪያ]

**acrid** አፍንጫ ፡ የሚከረክር

I smell acrid smoke from the burning rubber. አፍንጫ ፡ የሚከረክር ፡ የጎማ ፡ ሽታ ፡ ይሸተኛል

*The old man has an acrid disposition. ሽማግሌው ፡ ነጭናጫ ፡ ነው

**seem acrid** ከረከረ

Smoke seems acrid in your nose. ጢስ ፡ በአፍንጫ ፡ ከገባ ፡ ይከረክራል

**acrimonious** የሚያስመርር

He sent an acrimonious reply to my letter. ለጻፍኩለት ፡ ደብዳቤ ፡ የሚያስመርር ፡ መልስ ፡ ላከልኝ

**acrobat** [ቅልጥፍና ፡ የተመላበት ፡ ልዩ ፡ የሰውነት ፡ እንቅስቃሴ ፡ የሚያሳይ ፡ ሰው]

**across** (prep.)

1. ከ - - - ባሻገር. I looked across the room. ከክፍሉ ፡ ባሻገር ፡ ተመለከትሁ

2. ከ - - - ማዶ. He lives across the street. ከመንገዱ ፡ ማዶ ፡ ይኖራል

3. (= adv.) ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር. Draw a line across the sheet of paper. በወረቀቱ ፡ ላይ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ አሥምር

4. በ - - - አግድም. They stretched a rope across the path. በመንገዱ ፡ አግድም ፡ ገመድ ፡ ዘረጉ

5. በ - - - አቋርጦ. He hiked five miles across the desert. በምድረ ፡ በዳው ፡ አቋርጦ ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ ተጓዘ

6. በ - - - ላይ. They are going to construct a barrage across the river. በወንዙ ፡ ላይ ፡ ግድብ ፡ ሊገነቡ ፡ ነው

**across** (adv.) ከዳር ፡ እዳር

What is the distance across? ከዳር ፡ እዳር ፡ ርቀቱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው?

*The river is a half a mile across. ወንዙ ፡ የግማሽ ፡ ማይል ፡ ስፋት ፡ አለው

[See also 'come, just, pass, now, walk']

**act** (v.)

1. አደረገ. I will act on your advice. እንደመከርከኝ ፡ አደርጋለሁ

2. አስፈላጊውን ፡ አደረገ. He acted in time to save the house from burning down. ቤቱ ፡ እንዳይቃጠል ፡ በጊዜ ፡ አስፈላጊውን ፡ አደረገ

3. ሆነ. Don't act like a child. እንደ ፡ ሕፃን ፡ አትሁን

4. ሆኖ ፡ ተጫወተ. Who is acting Hamlet? ሀምሌትን ፡ ሆኖ ፡ የሚጫወተው ፡ ማነው?

5. ውሳኔ፡ሰጠ. I am required to act by tomorrow. እስከ ፡ ነገ ፡ ድረስ ፡ ውሳኔ ፡ እንድሰጥ ፡ ተጠይቄ ያለሁ

6. አስመሰለ. She is not really crying; she is only acting. የእውነት ፡ ልቅሶ ፡ አይደለም ፡ ማስመሰሏ ፡ ነው

*Please act your age. እባክህን ፡ ሥራህ ፡ በዕድሜህ ፡ ልክ ፡ ይሁን

*The boy acted badly in school. ልጁ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ አሳየ

**act as** በ + abstract + ሠራ

The student acted as interpreter for the Emperor. ተማሪው ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በአስተርጓሚነት ፡ ሠራ

**act for**

1. ወከለ. My lawyer acts for me in my absence. እኔ ፡ በሌለሁበት ፡ ጠበቃዬ ፡ ይወክለኛል

2. እንደራሱ ፡ ሆኖ ፡ ሠራ. He invested his lawyer with complete power to act for him. እንደራሱ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሠራ ፡ ለጠበቃው ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጠው

**act on** ተከትሎ ፡ ሠራ

He acted on his lawyer's advice. የጠበቃውን ፡ ምክር ፡ ተከትሎ ፡ ሠራ

**act out**

*Everyone roared when Henry acted out the episode with the teacher. ሄንሪ ፡ ከመምህሩ ፡ ጋር ፡ ድርጊቱን ፡ ያለ ፡ ንግግር ፡ በምልክት ፡ ብቻ ፡ ሲያሳይ ፡ ሁሉም ፡ ከት ፡ ብለው ፡ ሣቁ

**act up** ለቁጥጥር ፡ አስቸገረ

The children always act up in school the day

before a holiday. ተማሪዎቹ ፡ ለበዓላት ፡ ዋዜማ ፡ ለቁጥጥር ፡ ያስቸግራሉ

**act upon** ሠራ
This medicine acts upon the heart. ይህ ፡ መድኀኒት ፡ የሚሠራው ፡ በልብ ፡ ላይ ፡ ነው
[See also 'collusion, friendly, humble'].

**act** (n.)
1. ድርጊት. To hit a baby is a cruel act. ሕፃን ፡ መምታት ፡ የጭካኔ ፡ ድርጊት ፡ ነው
2. ገቢር. I do not want to miss the first act. የመጀመሪያው ፡ ገቢር ፡ እንዲያመልጠኝ ፡ አልፈልግም
3. የታወጀ ፡ ሕግ. By act of parliament demonstrations require a permit. በፓርላማ ፡ በታወጀ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ለሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ ፈቃድ ፡ ያስፈልጋል

**in the act of** ሲ + imperfect
The thief was caught in the act of stealing. ሌባው ፡ ሲሰርቅ ፡ እጅ ፡ ከፍንጅ ፡ ተያዘ

**acting** (n.)
1. ያሳየው ፡ ክፍል. The acting of the main performer was disappointing. ዋናው ፡ ተዋናይ ፡ ያሳየው ፡ ክፍል ፡ ቅር ፡ የሚያሰኝ ፡ ነበር
2. የማስመሰል ፡ ሥራ. His acting fooled nobody. የማስመሰል ፡ ሥራው ፡ ማንንም ፡ አላሞኘም

**acting** (adj.) ተጠባባቂ
He is acting minister in the Foreign Office. በውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ተጠባባቂ ፡ ሚኒስትር ፡ ነው

**action**
1. ድርጊት. The action takes place in a garden. ድርጊቱ ፡ የሚፈጸመው ፡ ባትክልት ፡ ስፍራ ፡ ነው
The adventure story was packed with action. የጀብዱ ፡ ታሪክ ፡ ድርጊት ፡ የበዛበት ፡ ነበር
2. ሥራ. Emperor Theodore was a man of action. አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የሥራ ፡ ሰው ፡ ነበሩ
3. ተግባር. To betray a friend is a base action. ጓደኛን ፡ መክዳት ፡ ጸያፍ ፡ ተግባር ፡ ነው
4. እርምጃ. Has any action been taken on my case? ስለኔ ፡ ጉዳይ ፡ የተወሰደ ፡ እርምጃ ፡ አለ?
5. ኀይል. The action of the water wore away the rocks. የውኃው ፡ ኀይል ፡ አለቶቹን ፡ ሸረሸራቸው
*He was killed in action. በጦር ፡ ሜዳ ፡ ሞተ

**actions** አድራጎት
His actions are hard to understand. አድራጎቱን ፡ ለመረዳት ፡ ያዳግታል

**be in action** ሠራ
The machine is not now in action. አሁን ፡ መኪናው ፡ አይሠራም

**be missing in action** በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ጠፋ
He is missing in action and presumed dead. በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ስለጠፋ ፡ ሞቷል ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል

**see action** ተዋጋ
The battalion saw action in Korea. ሻለቃው ፡ ጦር ፡ በኮሪያ ፡ ተዋግቷል

**activate** ቀሰቀሰ
The noise of the alarm activated the fire company. የማስጠንቀቂያው ፡ ደወል ፡ ጩኸት ፡ የእሳት ፡ አደጋውን ፡ ድርጅት ፡ ቀሰቀሰው

**active**
1. ሙሉ. Are you an active member? ሙሉ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ነህ?
2. ብርቱ. He is still very active for his age. በዚህ ፡ ዕድሜው ፡ አሁንም ፡ ብርቱ ፡ ነው
3. ንቁ. Children are more active in the morning than at night. ልጆች ፡ ከማታ ፡ ይልቅ ፡ ጧት ፡ የበለጠ ፡ ንቁ ፡ ናቸው
4. አድራጊ. "Eats" in "he eats bread" is an active verb. « እሱ ፡ ዳቦ ፡ ይበላል » ፡ በሚለው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ « ይበላል » ፡ አድራጊ ፡ ግስ ፡ ነው
*He leads an active life. ሁልጊዜ ፡ እንደሠራ ፡ ነው

**be active**
1. በትጋት ፡ ሠራ. Is he still active in this club? አሁንም ፡ በክበቡ ፡ ውስጥ ፡ በትጋት ፡ ይሠራል?
2. ተፋ. How long ago was Zuqwala an active volcano? ዝቋላ ፡ እሳተ ፡ ገሞራ ፡ ይተፋ ፡ የነበረው ፡ ከምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ነበር?

**take an active part** ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ተካፋይ ፡ ነው
He takes an active part in the government. በመንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ተካፋይ ፡ ነው

**actively** በሙሉ ፡ ልብ
He is actively interested in the project. በእቅዱ ፡ የሚካፈለው ፡ በሙሉ ፡ ልብ ፡ ነው

**activity**
1. እንቅስቃሴ. There is very little activity around here on Sundays. እሑድ ፡ እሑድ ፡ በዚህ ፡ አካባቢ ፡ ያለው ፡ እንቅስቃሴ ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው
He has to give up all physical activity for a while. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውንም ፡ አካላዊ ፡ እንቅስቃሴ ፡ መተው ፡ አለበት
2. የሥራ ፡ ኀይል. When a man is over 70, his time of full activity is usually past. አንድ ፡

ሰው ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ ካለፈው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሥራ ፡ ኀይሉ ፡ ይቀንሳል
3. ተግባር. A student who has too many activities does not have time to study. ብዙ ፡ ተግባሮችን ፡ የሚያከናውን ፡ ተማሪ ፡ ለጥናት ፡ ጊዜ ፡ የለውም
4. አድራጎት. The government was aware of the activities of enemy spies. መንግሥቱ ፡ የጠላት ፡ ሰላዮችን ፡ አድራጎት ፡ ያውቅ ፡ ነበር
*The committee is probing into his financial activities. ደርጉ ፡ ገንዘቡን ፡ ከምን ፡ ሥራ ፡ እንዳዋለው ፡ ይመረምራል
[See also 'feverish']

**actor** ተዋናይ
Charlie Chaplin is a good actor. ቻርሊ ፡ ቻፕሊን ፡ ጉበዝ ፡ ተዋናይ ፡ ነው

**actual**
1. እውነተኛ. The actual reason was an entirely different one. እውነተኛው ፡ ምክንያት ፡ ፍጹም ፡ ልዩ ፡ ነበር
2. ትክክለኛ. Can you give me the actual figures and not an estimate? ግምት ፡ ሳይሆን ፡ ትክክለኛውን ፡ ቁጥር ፡ ልትሰጠኝ ፡ ትችላለህ?
The actual state of affairs in the country is not known. ሀገሪቷ ፡ አሁን ፡ ያለችበት ፡ ትክክለኛ ፡ ሁኔታ ፡ አይታወቅም
3. የጊዜ. The teacher described the actual position of the moon. መምህሩ ፡ የጊዜውን ፡ የጨረቃ ፡ ሁኔታ ፡ አስረዳ

**actuality**
1. የጊዜው ፡ ሁኔታ. He had to adjust to the actualities of life. እንደጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ አለበት
2. እርግጥ ፡ ነገር. The actuality is worse than your suspicions. እርግጡ ፡ ነገር ፡ አንተ ፡ ከምትጠረጥረው ፡ ይከፋል

**become an actuality** በሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ
The plan never became an actuality. እቅዱ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሳይውል ፡ ቀረ

**in actuality** እርግጡን ፡ ለመናገር
In actuality, the battle never took place. እርግጡን ፡ ለመናገር ፡ ጦርነቱ ፡ ከቶ ፡ አልተደረገም

**actually**
1. በእውነት. Do you actually believe that story? ያንን ፡ ታሪክ ፡ በእውነት ፡ ታምናለህ?
2. (= adj.) እውነተኛ. The president rules in name only, as the party is actually in power. እውነተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የፖለቲካው ፡ ቡድን ፡ ሲሆን ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ የሚገዛው ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ ነው

**actuate** አንቀሳቀሰ
He actuated the pump by an electric motor. ፖምፑን ፡ በኮረንቲ ፡ ሞተር ፡ አንቀሳቀሰው

**be actuated** ተነሣሣ
She was actuated by love for her mother. የተነሣሣችው ፡ ለእናቷ ፡ ባላት ፡ ፍቅር ፡ ነው

**acumen** ብልህነት
His business acumen made him rich. ስለ ፡ ንግድ ፡ ያለው ፡ ብልህነት ፡ ሀብታም ፡ አደረገው

**acute**
1. ኀይለኛ. Dogs have an acute sense of smell. ውሾች ፡ ኀይለኛ ፡ የማሽተቻ ፡ ችሎታ ፡ አላቸው
2. አጣዳፊ. Aacute appendicitis prevented him from going on the trip. አጣዳፊ ፡ የትርፍ ፡ አንጀት ፡ ሕመም ፡ ከጉዞው ፡ አሰናከለው
3. ጽኑ. A bad tooth can cause acute pain. በሽተኛ ፡ ጥርስ ፡ ጽኑ ፡ ሕመም ፡ ሊያመጣ ፡ ይችላል
4. የሰላ. Some sounds are so acute that we cannot hear them. አንዳንድ ፡ ድምፆች ፡ በጣም ፡ የሰሉ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ ልንሰማቸው ፡ አንችልም
5. ከፍ ፡ ያለ. Due to the drought there was an acute shortage of vegetables. ከድርቀቱ ፡ የተነሣ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ያትክልት ፡ እጥረት ፡ ነበር
6. ንቁ. He is an acute observer of the political situation. በፖለቲካው ፡ ይዞታ ፡ ንቁ ፡ ተከታታይ ፡ ነው
7. ስል. An acute angle is less than 45 degrees. ስል ፡ ማእዘን ፡ ካርባ ፡ አምስት ፡ ዲግሪ ፡ በታች ፡ ነው

**be acute**
1. ጸና. If the pain becomes acute, call a doctor. ሕመሙ ፡ ከጸና ፡ ሐኪም ፡ ጥሩ
2. ከረረ. The political crisis became more acute. የፖለቲካው ፡ ብጥብጥ ፡ እየከረረ ፡ ሄደ

**(be) adamant** ንቅንቅ ፡ አይልም
Once he has made his decision he is adamant. አንዴ ፡ ውሳኔ ፡ ካደረገ ፡ ንቅንቅ ፡ አይልም

**Adam's apple** ማንቁርት
He scraped his Adam's apple on his collar. ማንቁርቱን ፡ በኮሌታው ፡ ላጠ

**adapt**
1. አራመደ. Schools should adapt their curriculum to modern needs. ትምህርት ፡ ቤቶች ፡

ሥርዓት ፡ ትምህርቱን ፡ ከዘመኑ ፡ ፍላጎት ፡ ጋር ፡ ማራመድ ፡ አለባቸው

*The ministry adapted the American textbook for use in Ethiopian schools. ሚኒስቴሩ ፡ የአሜሪካንን ፡ ማስተማሪያ ፡ መጽሐፍ ፡ በሚስማማ ፡ ዘዴ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ አደረገ

**adapt to** ለመደ

Most children adapt easily to new surroundings. ብዙ ፡ ልጆች ፡ አዲስ ፡ አካባቢን ፡ በቀላሉ ፡ ይለምዳሉ

**adapt oneself** ተላመደ ፤ ተስማማ

He adapts himself easily. በቀላሉ ፡ ይላመዳል

He adapts himself to new conditions. ከሚያጋጥሙት ፡ አዲስ ፡ ሁኔታዎች ፡ ይስማማል

## adaptable

1. እንዳስፈላጊነቱ ፡ ሊለዋወጥ ፡ የሚችል. Mother has an adaptable schedule. እናቴ ፡ እንዳስፈላጊነቱ ፡ ሊለዋወጥ ፡ የሚችል ፡ ፕሮግራም ፡ አላት
2. ከሁኔቱው ፡ ጋር ፡ የሚስማማ. She is an adaptable person. ከሁኔቱው ፡ ጋር ፡ የምትስማማ ፡ ሰው ፡ ናት

## add (vt.)

1. ጨመረ. You will have to add some sugar. ጥቂት ፡ ስኳር ፡ መጨመር ፡ አለብህ
Add it to my bill. በኔ ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ ጨምረው
2. ደመረ. He added 8 and 2. ስምንትና ፡ ሁለትን ፡ ደመረ
3. አከለ(በት). The committee added a rider to the bill. ደርጉ ፡ በሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ማሚያ ፡ አከለበት
4. ዘነቀ. They debased gold by adding copper. በወርቁ ፡ ላይ ፡ መዳብ ፡ በመዘነቅ ፡ አረከሱት
5. ቀላቀለ (ተቀላቀለ). Pigment is added to oil to make paint. ቀለም ፡ ለመሥራት ፡ ማቅለሚያው ፡ ከዘይት ፡ ጋር ፡ ይቀላቀላል

**add (vi.)**

1. ደመረ. They started learning to add and subtract. መደመርና ፡ መቀነስ ፡ መማር ፡ ጀመሩ
2. በተጨማሪ ፡ አለ. "I hope you will come early," he added. በተጨማሪ ፡ « ቀደም ፡ ብለህ ፡ እንደምትመጣ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ » ፡ አለው

**add to** አባሰ(በት)

His father's illness added to his troubles. ያባቱ ፡ ሕመም ፡ ችግሩን ፡ አባሰበት

**add up** ደመረ

Add up these figures! እነዚህን ፡ ቁጥሮች ፡ ደምር

**add up to** አመለከተ

The evidence adds up to a case of murder. መረጃው ፡ የነፍስ ፡ ግዳይ ፡ ወንጀል ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል

*How much does the bill add up to? ሒሳቡ ፡ በጠቅላላው ፡ ስንት ፡ ይሆናል?

[See also 'luster']

## addict ሱሰኛ

The cigarette addict finds it hard to stop smoking cigarettes. የሲጋራ ፡ ሱሰኛ ፡ ሲጃራ ፡ ማቆም ፡ ያስቸግረዋል

## (be) addicted to የ - - - ሱሰኛ ፡ ሆነ ፤ የ - - - ሱስ ፡ አለበት

He is addicted to smoking. የሲጃራ ፡ ሱሰኛ ፡ ሆኗል

He is addicted to strong drink. የመጠጥ ፡ ሱስ ፡ አለበት

## addiction አደገኛ ፡ የሆነ ፡ ሱስ

Opium is an addiction-causing drug. ኦፒዩም ፡ አደገኛ ፡ የሆነ ፡ ሱስ ፡ የሚያሲዝ ፡ መድኀኒት ፡ ነው

## addition

1. ድምር. Is my addition correct? ድምሬ ፡ ልክ ፡ ነው?
2. መደመር. Addition is taught in second grade. መደመር ፡ በሁለተኛ ፡ ክፍል ፡ ይሰጣል
3. መጨመር. The addition of flour will thicken the soup. ዱቄት ፡ መጨመር ፡ ሾርባን ፡ ያወፍራል
4. ቅጥያ. Workmen are building an addition to the house. ሠራተኞቹ ፡ የሕንጻውን ፡ ቅጥያ ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ ናቸው

**in addition** በተጨማሪ

In addition he asked for ten dollars. በተጨማሪ ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ ጠየቀ

**in addition to** ከ - - - ሌላ

In addition to his fixed salary he gets a commission. ከመደበኛ ፡ ደሞዙ ፡ ሌላ ፡ ኮሚስዮን ፡ ያገኛል

*He works in addition to going to school. እየሠራ ፡ ይማራል

## additional ተጨማሪ

An additional difficulty is the lack of money. ተጨማሪው ፡ ችግር ፡ የገንዘብ ፡ እጦት ፡ ነው

*For an additional dollar you get better quality. አንድ ፡ ብር ፡ ብትጨምር ፡ የተሻለ ፡ ዓይነት ፡ ታገኛለህ

**address** (v.)

1. አድራሻ ፡ ጻፈ. He addressed the letter to me. ደብዳቤውን ፡ በኔ ፡ አድራሻ ፡ ጻፈው
2. ንግግር ፡ አደረገ. Mr. Parker will now address the meeting. ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ አሁን ፡ ለጉባኤው ፡ ንግግር ፡ ያደርጋሉ
3. አቀረበ. I would like to address a question to the speaker. ለተናጋሪው ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ እፈልጋለሁ
4. ሰጠ. He addressed a warning to a friend. ላንድ ፡ ወዳጁ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሰጠ
5. አናገረ. I addressed him with respect. በአክብሮት ፡ አናገርኳቸው
6. ጠራ (ተጠራ). Protocol requires that dignitaries be addressed by their titles. ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ በማዕረግ ፡ ስማቸው ፡ እንዲጠሩ ፡ ፕሮቶኮል ፡ ያስገድዳል

*How do you address a mayor? የከንቲባ ፡ የክብር ፡ መጠሪያ ፡ ምንድነው?

**address oneself** ቆርጦ ፡ ተነሣ

He addressed himself to the task of doing his homework. የቤት ፡ ሥራውን ፡ ለመሥራት ፡ ቆርጦ ፡ ተነሣ

**be addressed**

*The letter is addressed to me. ደብዳቤው ፡ የተላከው ፡ በኔ ፡ አድራሻ ፡ ነው

**address** (n.)

1. አድራሻ. Do you want to write down my address? አድራሻዬን ፡ ለመጻፍ ፡ ትፈልጋለህ?
2. ንግግር. The Emperor delivered an important address. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ንግግር ፡ አደረጉ
3. ችሎታ. He managed this difficult affair with admirable address. አስቸጋሪውን ፡ ጉዳይ ፡ በሚያስደንቅ ፡ ችሎታ ፡ ፈጸመው
4. መልክ. A salesman should be a man of pleasant address. አሻሻጭ ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ አለበት

**adduce** ጠቀሰ

The lawyer adduced a decision in which the judge freed a man charged with robbery. ጠበቃው ፡ በፊት ፡ ዳኛው ፡ በዘረፋ ፡ የተከሰሰውን ፡ ሰው ፡ በነጻ ፡ የለቀቀበትን ፡ ውሳኔ ፡ ጠቀሰ

**(be) adept at** ችሎታ ፡ አለው

John is adept at repairing things about the house. ጆን ፡ የቤት ፡ እቃዎችን ፡ የመጠገን ፡ ችሎታ ፡ አለው

**adequacy** ብቁነት

We doubt the adequacy of his training. የትምህርቱን ፡ ብቁነት ፡ እንጠራጠራለን

**adequate**

1. በቂ. The lawyer presented adequate proof. ጠበቃው ፡ በቂ ፡ መረጃ ፡ አቀረበ
2. አጥጋቢ ፣ የተሟላ. His schooling is not adequate. ትምህርቱ ፡ አጥጋቢ ፣ (የተሟላ) ፡ አይደለም
3. ብቁ. Mr. Smith is adequate for the job. ሚስተር ፡ ስሚዝ ፡ ለሥራው ፡ ብቁ ፡ ነው

**adhere (to)**

1. ተጣበቀ. That scotch tape will adhere to anything. እስኮች ፡ ቴፕ ፡ ከምንም ፡ ነገር ፡ ጋር ፡ ይጣበቃል
2. አጥብቆ ፡ ተከተለ. He adhered to his plans. እቅዱን ፡ አጥብቆ ፡ ተከተለ
3. ተከተለ. Most people adhere to the church of their parents. አብዛኛዎቹ ፡ ሰዎች ፡ የወላጆቻቸውን ፡ ሃይማኖት ፡ ይከተላሉ

**adherence** ደጋፊነት

He declared his adherence to the cause of freedom. ለነጻነት ፡ ጉዳይ ፡ ደጋፊነቱን ፡ ገለጸ

**adherent** (n.) ደጋፊ

The adherents of the church party supported this plan. የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወገን ፡ ደጋፊዎች ፡ ይህንን ፡ እቅድ ፡ ደገፉ

**adherent** (adj.) የሚጣበቅ

Adherent materials should not be placed together. የሚጣበቁ ፡ ነገሮችን ፡ አንድነት ፡ ማኖር ፡ አይገባም

**adhesion**

*Adhesion of the intestine to the muscles requires surgery. አንጀት ፡ ከጡንቻ ፡ ጋር ፡ ሲጣበቅ ፡ ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ያስፈልጋል

**adhesive** (n.) ማጣበቂያ ፡ የሆነ ፡ ነገር

Glue is one of the many adhesives. ሙጫ ፡ ማጣበቂያ ፡ ከሆኑ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ነው

**adhesive tape** ፕላስተር

Give me some adhesive tape for my wound. ለቁስሌ ፡ የሚሆን ፡ ፕላስተር ፡ ስጠኝ

**adieus, make ~** ተሰናበተ

He made his adieus and left. ተሰናብቶ ፡ ሄደ

**adjacent** ቀጥሎ ፡ ያለው

The house adjacent to ours has been sold. ከኛ ፡ ቤት ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ቤት ፡ ተሸጧል

**be adjacent** ቀጥሎ ፡ ነው ፤ ተዋሰነ

The house is adjacent to the church. ቤቱ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ቀጥሎ ፡ ነው ፡ (ይዋሰናል)

**adjective** ቅጽል

The word 'heavy' is an adjective. « ከባድ » ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ቅጽል ፡ ነው

**adjoin** ተዋሰነ
My garden adjoins his. ያትክልት ፡ ስፍራዬ ፡ የሱን ፡ ያትክልት ፡ ስፍራ ፡ ይዋሰነዋል

**adjoining** የሚቀጥል
The adjoining room is empty. የሚቀጥለው ፡ ክፍል ፡ ባዶ ፡ ነው

**adjourn** (vt.)
1. ቀጠረ. The judge adjourned the court until the following day. ዳኛው ፡ ለሚቀጥለው ፡ ቀን ፡ ቀጠረ
2. በተነ. The chairman adjourned the meeting. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ስብሰባውን ፡ በተነ

**adjourn** (vi.)
1. ተበተነ. The meeting adjourned at 10 o'clock. ስብሰባው ፡ ባራት ፡ ሰዓት ፡ ተበተነ
2. ስብሰባው ፡ አበቃ. With the concordance of the membership we will adjourn. አባሎቹ ፡ ከተስማሙ ፡ ስብሰባው ፡ ያበቃል
3. ተለያየ. It was a strange proceeding when the senate adjourned without any decision. ሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ያለ ፡ ውሳኔ ፡ ሲለያይ ፡ ያልተለመደ ፡ ነገር ፡ ነበር

**be adjourned** አበቃ
The meeting is adjourned. ስብሰባው ፡ አበቃ

**(be) adjudged**
1. ተወሰነ. The boy's case was adjudged in juvenile court. የልጁ ፡ ጉዳይ ፡ በወጣት ፡ ጥፋተኞች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተወሰነ
2. በፍርድ ፡ ተሰጠ. The property was adjudged to the rightful owner. ንብረቱ ፡ በፍርድ ፡ ለእውነተኛው ፡ ባለሀብት ፡ ተሰጠ
3. ተፈረደ(በት). The accused man was adjudged guilty. ተከሳሹ ፡ ሰው ፡ ጥፋተኛ ፡ ነህ ፡ ተብሎ ፡ ተፈረደበት
4. ተገመተ. It was adjudged wise to avoid war. ጦርነት ፡ አለማንሣት ፡ የተሻለ ፡ ሆኖ ፡ ተገመተ

**adjudicate** በፍርድ ፡ አስወሰነ
It is better to adjudicate disputes than to settle them by fighting. ጠቡን ፡ በጥል ፡ ከመጨረስ ፡ ይልቅ ፡ በፍርድ ፡ ማስወሰን ፡ ይሻላል

**adjunct** ተጨማሪ ፡ እቃ
A radio is a common adjunct to an automobile. ሬዲዮ ፡ ለመኪና ፡ የተለመደ ፡ ተጨማሪ ፡ እቃ ፡ ነው

**adjure** ለመነ
I adjure you to tell the truth. እውነቱን ፡ እንድትናገር ፡ እለምንሃለሁ

**adjust** (vt.)
1. አስተካከለ. The manager will adjust your bill. ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ሒሳብህን ፡ ያስተካክልልሃል
You cannot see through the binoculars unless you adjust them first. በመጀመሪያ ፡ ካላስተካከልከው ፡ በአቅራቢው ፡ መነጽር ፡ ለማየት ፡ አትችልም
2. አስወገደ. The elders tried to adjust the differences in the quarrel. ሽማግሌዎቹ ፡ በጠቡ ፡ የተፈጠረውን ፡ አለመግባባት ፡ ለማስወገድ ፡ ሞከሩ

**adjust** (vi.) ራሱን ፡ አላመደ
His son adjusted to army life. የሱ ፡ ልጅ ፡ ራሱን ፡ ከወታደር ፡ ኑሮ ፡ ጋር ፡ አላመደ
*He has to adjust to the actualities of life. እንደጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ አለበት

**adjust oneself** ተላመደ
I cannot adjust myself to the climate here. ከዚህ ፡ ስፍራ ፡ አየር ፡ ጋር ፡ መላመድ ፡ አልችልም

**adjustment**
1. ማስተካከያ. Our radio has an adjustment so that we can make the tone loud or soft. የሬዲዮናችንን ፡ ድምፅ ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ የምናደርግበት ፡ ማስተካከያ ፡ አለው
2. የሚያቀራርብ ፡ ዘዴ. They worked out an adjustment of their conflicting ideas. የማይግባቡባቸውን ፡ ሐሳቦች ፡ የሚያቀራርብ ፡ ዘዴ ፡ ፈጠሩ

**make an adjustment** ተስማማ
Try to make some adjustment of your differences. በመካከላችሁ ፡ ስላለው ፡ አለመግባባት ፡ ለመስማማት ፡ ሞክሩ

**adjutant** ረዳት
The colonel's adjutant gave a report. የኮሎኔሉ ፡ ረዳት ፡ ሪፖርት ፡ አቀረበ

**administer**
1. አስተዳደረ. Who is administering his estate? ርስቱን ፡ የሚያስተዳድረው ፡ ማነው?
2. አስፈጸመ. Ethiopia has many good lawyers to administer justice. ኢትዮጵያ ፡ ፍትሕን ፡ የሚያስፈጽሙ ፡ ጥሩ ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ አሉዋት
3. ሰጠ. The nurse is entitled to administer drugs. ነርሷ ፡ መድኀኒት ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ አላት

**administration** አስተዳደር
The country is in need of good administration. አገሪቱ ፡ ጥሩ ፡ አስተዳደር ፡ ያስፈልጋታል

**administrative** ያስተዳደር
This is purely an administrative job. ይህ ፡ በሙሉ ፡ ያስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ነው

**administrative assistant** ረዳት ፡ አስተዳዳሪ
The administrative assistant has executive powers also. ረዳት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ትእዛዝ ፡ የመስጠትም ፡ ሥልጣን ፡ አለው

**administrator** አስተዳዳሪ
A good administrator treats the poor and the rich equally. ጥሩ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ድኻና ፡ ሀብታምን ፡ እኩል ፡ ያያል

**admirable** የሚያስደንቅ ፤ የሚደነቅ ፤ አስደናቂ
He performed many admirable deeds in the war. በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ጀብዱ ፡ ሠርቷል
His determination to go abroad to study is admirable. ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ ለመማር ፡ ያለው ፡ ቁርጥ ፡ አሳብ ፡ የሚደነቅ ፡ ነው
Since she has a goiter her admirable face is ruined. እንቅርት ፡ ስላወጣች ፡ አስደናቂ ፡ መልኳ ፡ ተበላሸ

**admiral** የባሕር ፡ ኀይል ፡ ዋና ፡ አዛዥ
The admiral's ship sank. የባሕር ፡ ኀይል ፡ ዋና ፡ አዛዡ ፡ መርከብ ፡ ሰመጠች

**admiration** አድናቆት
Your admiration is exaggerated. አድናቆትህ ፡ የተጋነነ ፡ ነው
*He is the object of everyone's admiration. እሱ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያደንቀው ፡ ነው

**admire** አደነቀ
I admire your patience. ትዕግሥትህን ፡ አደንቃለሁ

**admirer** የሚያደንቅ
She has many admirers. ብዙ ፡ የሚያደንቋት ፡ ሰዎች ፡ አሉ

**(be) admissible**
1. ተፈቀደ. This form of argument is not admissible. ይህ ፡ ዓይነት ፡ ክርክር ፡ አይፈቀድም
2. ተቀባይነት ፡ አለው. Hearsay is not admissible evidence. በስሚ ፡ ስሚ ፡ የተገኘ ፡ ወሬ ፡ ለማስረጃነት ፡ ተቀባይነት ፡ የለውም

**admission**
1. መግቢያ. Free admission is limited to certain days. ነጻ ፡ መግቢያ ፡ የሚፈቀደው ፡ ለተወሰኑ ፡ ቀኖች ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ማመን. His admission proved my innocence. የሱ ፡ ማመን ፡ የኔን ፡ ጥፋተኛ ፡ አለመሆን ፡ አረጋገጠ
*Admission to school is by examination only. ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚገባው ፡ በፈተና ፡ ብቻ ፡ ነው

**admit** (admitted)
1. አስገባ. The servant opened the door and admitted the guest. አሽከሩ ፡ በሩን ፡ ከፍቶ ፡ እንግዳውን ፡ አስገባ
2. አመነ. I admit that I was wrong. ስሕተተኛ ፡ መሆኔን ፡ አምናለሁ
3. ተቀበለ. Jordan does not admit any Israeli claims on her territory. ዮርዳኖስ ፡ እስራኤል ፡ በግዛቷ ፡ ውስጥ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ የምትለውን ፡ ሁሉ ፡ አትቀበልም
4. ያዘ. The harbor admits three ships. ወደቡ ፡ ሦስት ፡ መርከቦች ፡ ይይዛል
*His answer admits no reply. መልሱ ፡ ቁርጥ ፡ ያለ ፡ ነው

**be admitted**
1. እንዲገባ ፡ ተፈቀደ. Children under fifteen are not admitted. ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ ያሉ ፡ ሕፃናት ፡ እንዲገቡ ፡ አይፈቀድም
2. ታመነ. It is generally admitted that a good wife is necessary for success in life. በጠቅላላው ፡ ለተሳካ ፡ ኑሮ ፡ ጥሩ ፡ ሚስት ፡ ማስፈለጓ ፡ ታምኗል
3. (= active) አስገባ. Mention my name and you will be admitted. ስሜን ፡ ጥራ ፡ ያስገቡሃል
4. (= active) ተቀበለ. He was admitted to the club. የክበቡ ፡ አባል ፡ እንዲሆን ፡ ተቀበሉት
[See also 'bar']

**admittance** የመግባት ፡ ፈቃድ
He gained admittance to the park. ወደ ፡ መናፈሻው ፡ ስፍራ ፡ የመግባት ፡ ፈቃድ ፡ አገኘ

**admittedly**
*He was, admittedly, the thief. በእርግጥ ፡ ሌባው ፡ እሱ ፡ ነበር

**admixture** መቀላቀል
The admixture of foreign words makes the language hard to understand. የባዕድ ፡ ቃላት ፡ መቀላቀሉ ፡ ቋንቋውን ፡ ለመረዳት ፡ ያስቸግራል

**admonish**
1. ገሠጸ. The teacher admonished the boys for being lazy. አስተማሪው ፡ ልጆቹ ፡ ሰነፍ ፡ ስለሆኑ ፡ ገሠጻቸው
2. አስጠነቀቀ. The policeman admonished him not to drive too fast. ፖሊሱ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ እንዳይነዳ ፡ አስጠነቀቀው

**admonition** ተግሣጽ
The teacher's admonition to the student for his careless work was of no avail. አስተማሪ

ው ፡ ስለ ፡ ተማሪው ፡ የማይለሽ ፡ ሥራ ፡ የሰጠው ፡ ተማማጽ ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ነበር

**adobe (construction)** ከጡብ ፡ የተሠራ
The houses in this area are of adobe construction. የዚህ ፡ አካባቢ ፡ ቤቶች ፡ ከጡብ ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው

**adolescence** የጉልምስናና ፡ የኮረዳነት ፡ ጊዜ
Adolescence starts after childhood. የጉልምስናና ፡ የኮረዳነት ፡ ጊዜ ፡ ከሕፃንነት ፡ በኋላ ፡ ይጀመራል

**adolescent**
1. ጎረምሳ. He is still an adolescent. ገና ፡ ጎረምሳ ፡ ነው
2. ኮረዳ. She is still an adolescent. ገና ፡ ኮረዳ ፡ ነች

**adopt**
1. በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለ. The government adopted the present civil code several years ago. መንግሥቱ ፡ ያሁኑን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለ
2. ተቀበለ. The club adopted the motion by a vote of 20 to 5. ክበቡ ፡ የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ ሀያ ፡ በአምስት ፡ በሆነ ፡ ድምፅ ፡ ተቀበለው
3. በ - - - ተገለገለ. For the teaching of Amharic we adopted a new method. አማርኛ ፡ ለማስተማር ፡ ባዲስ ፡ ዘዴ ፡ ተገለገልን
4. መርጦ ፡ ያዘ. He adopted a new name when he became American. የአሜሪካዊነትን ፡ ዜግነት ፡ ሲያገኝ ፡ አዲስ ፡ ስም ፡ መርጦ ፡ ያዘ
5. በጉዲፈቻ ፡ ተቀበለ. My aunt has adopted a little boy. አክስቴ ፡ ትንሽ ፡ ልጅ ፡ በጉዲፈቻ ፡ ተቀበለች
[See also 'habit']

**adopted** (adj.) የጉዲፈቻ
It is an adopted child. የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ነው

**be adopted**
1. በሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ. A flexible policy was adopted. እንደ ፡ አስፈላጊነት ፡ የሚለዋወጥ ፡ ፖሊሲ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ
2. ተቀባይነት ፡ አገኘ. Christian practices have occasionally been adopted by members of other religions. አንዳንድ ፡ የክርስቲያን ፡ ምግባሮች ፡ በሌሎች ፡ እምነት ፡ ተከታዮች ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነት ፡ አግኝተዋል

**adoption**
1. ጉዲፈቻ. His adoption by the kind old man changed the boy's whole life. ደጉ ፡ ሽማግሌ ፡ ጉዲፈቻ ፡ ስላደረገው ፡ የልጁ ፡ መላ ፡ ሕይወት ፡ ተለወጠ
2. መቀበል. The teachers are talking about the adoption of a new course of study. አስተማሪዎቹ ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡ አዲስ ፡ መምሪያ ፡ ለመቀበል ፡ ይነጋገራሉ

**adoptive, ~ father** የጡት ፡ አባት
His adoptive father is very rich. የጡት ፡ አባቱ ፡ በጣም ፡ ሀብታም ፡ ነው

**adorable** ደስ ፡ የሚል
He is an adorable baby. ደስ ፡ የሚል ፡ ሕፃን ፡ ነው

**adoration** ማክበር
Adoration of the Virgin Mary is widespread in Ethiopia. ድንግል ፡ ማርያምን ፡ ማክበር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ የተለመደ ፡ ነው

**adore**
1. አፈቀረ. She adores her family. ቤተሰቧን ፡ ታፈቅራለች
2. ወደደ. The baby adores being tickled. ሕፃኑን ፡ ሲኰረኩሩት ፡ ይወዳል
3. አመለከ. In ancient times, Ethiopians adored idols. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በጣዖት ፡ ያመልኩ ፡ ነበር
4. ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ሰጠ. The followers of Gandhi adored him. የጋንዲ ፡ ተከታዮች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ይሰጡት ፡ ነበር

**adorn**
1. አስጌጠ. The municipality adorned the city before the return of the Emperor. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከመመለሳቸው ፡ በፊት ፡ መዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ከተማውን ፡ አስጌጠ
2. አሳመረ. Kindness adorns his character. ደግነት ፡ ጠባዩን ፡ ያሳምረዋል

**adornment** ማጌጫ
A flower was the only adornment on her dress. ልብሷ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ማጌጫ ፡ አበባ ፡ ብቻ ፡ ነበር
*She was busy with the adornment of the room the day before the party. የድግሱ ፡ ዋዜማ ፡ ለት ፡ ቤቱን ፡ ስታጌጥ ፡ ዋለች

**(be) adrift** ያለ ፡ መሪ ፡ ተንቀዋለለ ፤ ዋለለ
The boat was adrift in the ocean. ጀልባዋ ፡ ውቅያኖሱ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ መሪ ፡ ተንቀዋለለች
A derelict ship is adrift off the coast. ሰዎች ፡ የጣሏት ፡ መርከብ ፡ በጠረፉ ፡ አቅራቢያ ፡ ትዋልል ፡ ነበር

**adroit** ዘዴኛ
We admired the lawyer's adroit questioning of the witness. ጠበቃው ፡ ለምስክሩ ፡ ያቀረበውን ፡ ዘዴኛ ፡ አጠያየቅ ፡ አደነቅን

**adulate** ከመጠን ፡ በላይ ፡ አሞገሰ
Some young people adulate singers of popular songs. አንዳንድ ፡ ወጣቶች ፡ ዘመናዊ ፡ ዘፋኞችን ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ያሞግሷቸዋል

**adult** ዐዋቂ
There was milk for the children and coffee for the adults. ለልጆች ፡ ወተት ፡ ለዐዋቂዎች ፡ ቡና ፡ ነበር

**adulterate**
1. አቀጠነ. He adulterated the beer with water. ጠላውን ፡ በውኃ ፡ አቀጠነው
2. የማይረባ ፡ ሥጋ ፡ ተቀላቀለ. The company was fined for adulterating canned meat. ኩባንያው ፡ እታሸገው ፡ ሥጋ ፡ ውስጥ ፡ የማይረባ ፡ ሥጋ ፡ በመቀላቀሉ ፡ ተቀጣ

**adulterer** አመንዝረኛ
The adulterer was killed by the husband. አመንዝረኛው ፡ በባልየው ፡ ተገደለ

**adulteress** ዘማዊት ፡ ሴት ፤ ያመነዘረች ፡ ሴት
Adulteresses were stoned to death. ዘማዊያት ፡ ሴቶች ፡ (ያመነዘሩ ፡ ሴቶች) ፡ በድንጋይ ፡ ይወገሩ ፡ ነበር

**adultery** ዝሙት
The Bible condemns adultery. መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ዝሙትን ፡ ያወግዛል

**adulthood** አካለ ፡ መጠን ፡ መድረስ
The acceptance of responsibilities is a sign of adulthood. ኀላፊነትን ፡ መቀበል ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ የመድረስ ፡ ምልክት ፡ ነው

**advance** (vt.)
1. ወደ ፡ ፊት ፡ በመግፋት ፡ እንዲሄድ ፡ አደረገ. The general advanced his troops to the new position. ጄኔራሉ ፡ ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በመግፋት ፡ ወደ ፡ አዲሱ ፡ ግንባር ፡ እንዲሄዱ ፡ አደረገ
2. ቀደም ፡ አደረገ. The chairman advanced the time of the meeting. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ የስብሰባውን ፡ ጊዜ ፡ ቀደም ፡ አደረጉ
3. በቅድሚያ ፡ ሰጠ. Could you advance me some money? ትንሽ ፡ ገንዘብ ፡ በቅድሚያ ፡ ልትሰጠኝ ፡ ትችላለህ?
4. አበደረ. The banks often advance money to farmers. ባንኮቹ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለገበሬዎች ፡ ገንዘብ ፡ ያበድራሉ
5. አቀረበ. The plan he advanced was not good. ያቀረበው ፡ እቅድ ፡ ጥሩ ፡ አልነበረም
6. እንዲሰፍን ፡ አደረገ. The minister tried hard to advance the cause of peace. ሚኒስትሩ ፡ ሰላም ፡ እንዲሰፍን ፡ ለማድረግ ፡ ብዙ ፡ ደከመ
7. አዳበረ. His purpose was to advance his own interests rather than the company's. ዓላማው ፡ የራሱን ፡ እንጂ ፡ የኩባንያውን ፡ ፍላጎት ፡ ለማዳበር ፡ አልነበረም
8. አሳደገ. They advanced him from lieutenant to captain yesterday. ትላንትና ፡ ከመቶ ፡ አለቅነት ፡ ወደ ፡ ሻምበልነት ፡ አሳደጉት

**advance** (vi.)
1. ተጓዘ. We advanced twenty miles in one day. ባንድ ፡ ቀን ፡ ሀያ ፡ ማይል ፡ ተጓዝን
2. ጨመረ. Since the war, prices have continued to advance. ከጦርነቱ ፡ ወዲህ ፡ ዋጋ ፡ እየጨመረ ፡ ሄደ
3. ወደፊት ፡ ተራመደ. Has civilization advanced in our century? ሥልጣኔ ፡ በኛ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ወደፊት ፡ ተራምዷል?
4. ገፋ ፤ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፋ. The army advanced toward the enemy lines. ጦሩ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ግንባር ፡ ገፋ
The soldiers advanced under enemy fire. ወታደሮቹ ፡ የጠላትን ፡ ተኵስ ፡ ጥሰው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፉ

**be advanced** እንዲቀርብ ፡ ተደረገ
The date of the meeting was advanced from April to March. የስብሰባው ፡ ጊዜ ፡ ከሚያዝያ ፡ ወደ ፡ መጋቢት ፡ እንዲቀርብ ፡ ተደርጓል

**advance against** እየገፋ ፡ መጣ(በት)
The forces of the enemy advanced against us. የጠላት ፡ ኀይል ፡ እየገፋ ፡ መጣብን

**advance upon** ተጠጋ
He advanced upon me in a threatening manner. እያስፈራራ ፡ ተጠጋኝ

**advance** (n.)
1. መሻሻል. Great advances have been made in medicine during the last few years. ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በሕክምና ፡ ብዙ ፡ መሻሻል ፡ ተደርጓል
2. ገፍቶ ፡ መምጣት ፤ መግፋት. Nothing could stop the advance of the enemy. የጠላት ፡ ገፍቶ ፡ መምጣት ፡ (መግፋት) ፡ ምንም ፡ ሊያቆመው ፡ አልቻለም
3. (= adv.) በቅድሚያ. Can you give me an advance on my salary? ከደሞዜ ፡ በቅድሚያ ፡ ሊከፍሉኝ ፡ ይችላሉ?

**in advance** በቅድሚያ ፤ አስቀድሞ ፤ ቀደም ፡ ብሎ
Let me know in advance if you are coming. ትመጣ ፡ እንደሆነ ፡ በቅድሚያ ፡ አስታውቀኝ

After this, please let us know in advance. ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አስቀድመህ ፡ አስታውቀን

I arranged it in advance. ቀደም ፡ ብዬ ፡ አዘጋጀሁት

**in advance of** ከ - - - ቀድሞ

They walked on in advance of the king. ከንጉሡ ፡ ቀድመው ፡ ሄዱ

**(be) in advance of** ከ - - - ቀደመ

His ideas were in advance of the time. ሐሳቡ ፡ ከጊዜው ፡ የቀደመ ፡ ነበር

[See also 'pacific']

**advanced** (adj.)

1. ከፍተኛ. He is not smart enough to take advanced courses. ከፍተኛ ፡ ኮርስ ፡ ለመውሰድ ፡ ችሎታው ፡ አይፈቅድለትም
2. የገፋ. He is very advanced in years. በዕድሜ ፡ በጣም ፡ የገፋ ፡ ነው
3. በትምህርቱ ፡ የገፋ. Only advanced students can understand the abstract theory about the nature of the soul. ስለ ፡ ነፍስ ፡ ባሕርይ ፡ ረቂቅ ፡ አስተሳሰብ ፡ ሊረዱ ፡ የሚችሉ ፡ በትምህርታቸው ፡ የገፉ ፡ ተማሪዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው
4. ከጊዜው ፡ ቀድሞ ፡ የሄደ. He has advanced ideas. ከጊዜው ፡ ቀድሞ ፡ የሄደ ፡ ሐሳብ ፡ አለው

*Our army is in an advanced position. የኛ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ነው

**advancement**

1. የማዕረግ ፡ እድገት. The captain has hopes of advancement. ሻምበሉ ፡ የማዕረግ ፡ እድገት ፡ ለማግኘት ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋል
2. ማሻሻል. Advancement in school reform requires more teachers. የትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ይዞታ ፡ ለማሻሻል ፡ ተጨማሪ ፡ አስተማሪዎች ፡ ያስፈልጋሉ
3. ጭማሪ. Loyalty and hard work are what usually bring an advancement in pay. የደሞዝ ፡ ጭማሪ ፡ የሚያስገኙ ፡ ታማኝነትና ፡ ጠንክሮ ፡ መሥራት ፡ ናቸው

**advantage**

1. ጥቅም. This method has advantages and disadvantages. ይህ ፡ ዘዴ ፡ ጥቅምና ፡ ጉዳት ፡ አለው

This is to your advantage. ይህ ፡ ለራስህ ፡ ጥቅም ፡ ነው

2. ብልጫ. George had a good education and this gave him an advantage over his friend. ጆርጅ ፡ ጥሩ ፡ ትምህርት ፡ ነበረው ፤ ይህም ፡ ከጓደኛው ፡ ብልጫን ፡ አስገኘለት

**have an advantage** በተሻለ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነው

You have an advantage over me. ከኔ ፡ በተሻለ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነህ

**take advantage of** ሠራ(በት) ፤ ተጠቀመ(በት)

He takes advantage of every opportunity. የሚያጋጥመውን ፡ ዕድል ፡ ሁሉ ፡ ይሠራበታል ፡ (ይጠቀምበታል)

Don't let people take advantage of you! ሰዎች ፡ አይጠቀሙብህ

**to advantage** አሳምሮ

The draper will arrange your draperies to advantage. መጋረጃ ፡ ሠራተኛው ፡ መጋረጃዎችህን ፡ አሳምሮ ፡ ይሠራልሃል

[See also 'operate']

**advantageous**

1. የሚጠቅም. He is in an advantageous position. የሚጠቅመው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው
2. ምቹ. This advantageous position commands three roads. ይህ ፡ ምቹ ፡ ስፍራ ፡ ሦስት ፡ መንገዶችን ፡ ለመቆጣጠር ፡ ያስችላል

**advent** መምጣት

The advent of spring is a joyful occasion. የጸደይ ፡ መምጣት ፡ የሚያስደስት ፡ ወቅት ፡ ነው

*Since the advent of modern medicine, diseases have been reduced. ዘመናዊ ፡ ሕክምና ፡ ከመጣ ፡ ወዲህ ፡ በሽታ ፡ ተቀነሰ

**Advent of Christ** ምጽአት

The exact day of the Advent of Christ is not known. የምጽአት ፡ ትክክለኛ ፡ ቀን ፡ አይታወቅም

**adventitious** ተጨማሪ

The exciting life of the author gives the book an adventitious interest. የደራሲው ፡ አስገራሚ ፡ ኑሮ ፡ ለመጽሐፉ ፡ ተጨማሪ ፡ አድናቆት ፡ ይሰጠዋል

**adventure**

1. ጀብዱ. The soldier told the tale of his adventures. ወታደሩ ፡ የጀብዱውን ፡ ወሬ ፡ አወራ
2. አጋጣሚ. The title of the book is " Adventure in the Forest ". የመጽሐፉ ፡ አርእስት ፡ « በጫካ ፡ ውስጥ ፡ የደረሰ ፡ አጋጣሚ » ፡ የሚል ፡ ነው
3. ያጋጠመው ፡ ነገር. He regaled me with stories of his adventures. ያጋጠሙትን ፡ ነገሮች ፡ ታሪክ ፡ በማጫወት ፡ አስደሰተኝ

**adventurer**

1. የጀብዱ ፡ ሰው. The traveler to Africa is a great adventurer. ወደ ፡ አፍሪካ ፡ የሚጓዘው ፡ ሰው ፡ ታላቅ ፡ የጀብዱ ፡ ሰው ፡ ነው

2. ጮሌ. The adventurer looked for an unmarried girl whose father was rich. ጮሌው ፡ ያልተዳረች ፡ የባለጸጋ ፡ ልጅ ፡ ፈለገ

**adventurous**
1. ጀብዱ ፡ የበዛበት. An expedition to the North Pole is an adventurous undertaking. ወደ ፡ ሰሜናዊው ፡ ዋልታ ፡ መጓዝ ፡ ጀብዱ ፡ የበዛበት ፡ ድርጊት ፡ ነው
2. ደፋር. The adventurous explorer was applauded by the listeners. ለደፋሩ ፡ አሳሽ ፡ አድማጮቹ ፡ አጨበጨቡለት

**adverb** ተውሳከ ፡ ግስ
The word 'now' is an adverb. « አሁን » ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ተውሳከ ፡ ግስ ፡ ነው

**adversary**
1. ባላጋራ. He is my most dangerous adversary. በጣም ፡ አደገኛ ፡ ባላጋራዬ ፡ እሱ ፡ ነው
2. ጠላት. The United States and Japan were adversaries in World War II. በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ አሜሪካንና ፡ ጃፓን ፡ ጠላቶች ፡ ነበሩ
3. ተጋጣሚ. Which school is our adversary in the football game? በእግር ፡ ኳስ ፡ ጨዋታ ፡ የኛ ፡ ተጋጣሚ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የትኛው ፡ ነው?

**adverse**
1. የሚጎዳ. The judge gave an adverse decision to the plaintiff. ዳኛው ፡ ለከሳሹ ፡ የሚጎዳው ፡ ውሳኔ ፡ ሰጠ
2. ያልተቃና. He struggled against adverse circumstances. ካልተቃና ፡ ሁናቴ ፡ ጋር ፡ ታገለ
3. ጥላቻ ፡ ያዘለ. His adverse criticism discouraged me. ጥላቻ ፡ ያዘለው ፡ ነቀፋው ፡ ተስፋ ፡ አስቈረጠኝ
4. ከፊት ፡ ለፊት ፡ የመጣ. An adverse wind delayed the boat. ከፊት ፡ ለፊት ፡ የመጣ ፡ ነፋስ ፡ መርከቧን ፡ አዘገያት

**adversity** መከራ
He knew many days of adversity. ብዙ ፡ የመከራ ፡ ቀኖችን ፡ አሳልፏል

**advertise**
1. አስታወቀ. He advertised for a servant in the Sunday paper. በእሑድ ፡ ጋዜጣ ፡ አሽከር ፡ መፈለጉን ፡ አስታወቀ
The mayor advertised the hours of the public meeting. ከንቲባው ፡ ሕዝባዊ ፡ ስብሰባ ፡ የሚያደርግባቸውን ፡ ሰዓቶች ፡ አስታወቀ
2. የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ አወጣ. Stores that wish to sell things advertise in a newspaper. እቃ ፡ ለመሸጥ ፡ የሚፈልጉ ፡ መደብሮች ፡ በጋዜጣ ፡ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ያወጣሉ

**advertisement**
1. ማስታወቂያ. I saw your advertisement for employing teachers. አስተማሪዎች ፡ ለመቅጠር ፡ ያወጣኸውን ፡ ማስታወቂያ ፡ አየሁ
2. የንግድ ፡ ማስታወቂያ. I saw your advertisement on the special sale. ልዩ ፡ ሽያጭ ፡ እንደምታደርግ ፡ በንግድ ፡ ማስታወቂያው ፡ ላይ ፡ አየሁ

**advertising**
1. ማስታወቂያ ፡ ማስነገር. Advertising on television is very expensive. በቴሌቪዥን ፡ ማስታወቂያ ፡ ማስነገር ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ ነው
2. የማስታወቂያ ፡ ሥራ. John found a career in advertising as an illustrator. ዮሐንስ ፡ በማስታወቂያ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ በሠዓሊነት ፡ ቋሚ ፡ ሥራ ፡ አገኘ

**advice** ምክር
My advice is to leave immediately. ምክሬ ፡ አሁኑኑ ፡ እንድትሄድ ፡ ነው

**advisable** የሚሻል
I think it advisable to stay home today. ዛሬ ፡ ቤት ፡ መዋል ፡ የሚሻል ፡ ይመስለኛል
It is advisable to cross streets only at corners. መንገዶችን ፡ መታጠፊያቸው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ማቋረጥ ፡ የሚሻል ፡ ይመስለኛል

**advise**
1. መከረ. What do you advise me to do? ምን ፡ እንዳደርግ ፡ ትመክረኛለህ?
He advised me against it. እንዳላደርገው ፡ መከረኝ
2. አስታወቀ. Please advise us when the merchandise arrives. ሸቀጡ ፡ ሲደርስ ፡ እባክህን ፡ አስታውቀን

**be advised** ተነገረ(ው)
He was advised of the latest developments. በቅርቡ ፡ ስለደረሱት ፡ ነገሮች ፡ ይነገረው ፡ ነበር
[See also 'ill']

**advisedly** ሆን ፡ ብሎ
He used the word advisedly. ቃሉን ፡ የተጠቀመበት ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ነው

**advisor** አማካሪ
My legal advisor is away on business. የሕግ ፡ አማካሪዬ ፡ በሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሄዷል

**advisory** አማካሪ
He is a member of the advisory board. የአማካሪው ፡ ቦርድ ፡ አባል ፡ ነው

**advocate** (v.)

1. ሰበከ. He advocates Amharic as a medium of instruction for secondary schools. የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ባማርኛ ፡ እንዲሰጥ ፡ ይሰብካል

2. አጥብቆ ፡ ደገፈ. He advocates education at the age of six. በስድስት ፡ ዓመት ፡ ትምህርት ፡ መጀመርን ፡ አጥብቆ ፡ ይደግፋል

3. ተከራከረ. Parties of the right advocate free trade. የቀኝ ፡ ክፍል ፡ ፓርቲዎች ፡ ለነጻ ፡ ንግድ ፡ ይከራከራሉ

**advocate** (n.)

1. ጠበቃ. He is studying to become an advocate. ጠበቃ ፡ ለመሆን ፡ ይማራል

2. ተከራካሪ. Mahatma Gandhi was an advocate of passive resistance. ማሃትማ ፡ ጋንዲ ፡ የሰላማዊ ፡ ተቃውሞ ፡ ተከራካሪ ፡ ነበር

**advocated** (adj.) የተጠየቀ

A reform long advocated by the younger generation was finally adopted. በወጣት ፡ ትውልድ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ የተጠየቀው ፡ መሻሻል ፡ በመጨረሻ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ

**adze** መጥረቢያ

In olden days they made boards with an adze. በድሮ ፡ ጊዜ ፡ ሳንቃ ፡ የሚጠረበው ፡ በመጥረቢያ ፡ ነበር

**aerate** አናፈሰ

This device aerates the room. ይህ ፡ መሣሪያ ፡ ክፍሉን ፡ ያናፍሳል

**aesthetics** የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ጥናት

**aether** [ከህዋው ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የሚገኝ ፡ የጠፈር ፡ ክፍል]

**afar** ሩቅ

I saw him from afar. ከሩቅ ፡ አየሁት

**affable**

1. ትሑት. He is affable with everybody. ለሁሉ ፡ ሰው ፡ ትሑት ፡ ነው

2. አስደሳች. His smile is affable. ፈገግታው ፡ አስደሳች ፡ ነው

**affair**

1. ጉዳይ. I don't meddle in his affairs. በሱ ፡ ጉዳይ ፡ አልገባም

2. ነገር. Their wedding was the most brilliant affair of the season. በወቅቱ ፡ ከተደረጉት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ደምቆ ፡ የታየው ፡ የነሱ ፡ ሰርግ ፡ ነበር

[See also 'state']

**affect**

1. አቃወሰ. That cold climate affected his health. ቀዝቃዛው ፡ አየር ፡ ጤናውን ፡ አቃወሰው

2. ጐዳ. War affects a nation's external trade. ጦርነት ፡ የሀገርን ፡ የውጭ ፡ ንግድ ፡ ይጐዳል

Cold doesn't affect him at all. ብርድ ፡ ፈጽሞ ፡ አይጐዳውም

3. አጠፋ. The disease must run its course; there is no medicine which affects it. የሚያጠፋው ፡ መድኀኒት ፡ ስለሌለ ፡ በሽታው ፡ እንደገባ ፡ ይውጣ

4. ተጽዕኖ ፡ አለው. Edison's inventions have greatly affected modern civilization. የኤድስን ፡ ፍልሰፋዎች ፡ በዘመናዊው ፡ ሥልጣኔ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተጽዕኖ ፡ አላቸው

5. ተሰማ(ው). His wife's death affected him deeply. የሚስቱ ፡ ሞት ፡ በጥልቅ ፡ ተሰምቶታል

6. ወደደ. He affects loud neckties. ደማቅ ፡ ከራቫቶችን ፡ ይወዳል

*He affected not to hear me. ሰምቶኝ ፡ ያልሰማ ፡ መሰለ

**be affected**

1. ተነካ. The lung was affected by tuberculosis. ሳንባው ፡ በሳንባ ፡ ነቀርሳ ፡ ተነክቷል

The stable foundation of this house was not affected by the earthquake. ጽኑ ፡ የሆነው ፡ የዚህ ፡ ቤት ፡ መሠረት ፡ በመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ አልተነካም

2. ታመመ. If the epidemic is unchecked, thousands more will be affected. በሽታውን ፡ ካልተቈጣጠሩት ፡ ሌሎች ፡ በሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ይታመማሉ

**affectation** ልምሰል ፡ ባይ ፡ ሁኔታ

Her little affectations annoyed me. ልምሰል ፡ ባይ ፡ ሁኔታዋ ፡ አበሳጨኝ

**affected** (adj.) የራሱ ፡ ያልሆነ

He has affected manners. የራሱ ፡ ያልሆነ ፡ ጠባይ ፡ ይዟል

**affection** ፍቅር

He hopes to win her affection. ፍቅሯን ፡ ለማግኘት ፡ ይመኛል

The affection of a mother for her children is well described in this book. እናት ፡ ለልጆቿ ፡ ያላት ፡ ፍቅር ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በሚገባ ፡ ተገልጿል

[See also 'crave, starving']

**affectionate**

1. ሰው ፡ የሚወድ. She is an affectionate child. ሰው ፡ የምትወድ ፡ ልጅ ፡ ናት

2. ተወዳጅ. She has an affectionate nature. ተወዳጅ ፡ ባሕርይ ፡ አላት

**(be) affianced** አጨ
He was affianced at an early age. ገና ፡ በልጅነቱ ፡ አጨ

**affiliate** (v.) ተቀላቀለ
He refused to affiliate with a political party. ከፖለቲካ ፡ ቡድን ፡ ጋር ፡ ለመቀላቀል ፡ አልፈለገም

**be affiliated with** የ - - - ጥገኛ ፡ ነው
The college is affiliated with the university. ኮሌጁ ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ጥገኛ ፡ ነው

**affiliation** ዝምድና
The affiliation of the two languages is shown by the many words they have in common. የሁለቱ ፡ ቋንቋዎች ፡ ዝምድና ፡ የሚታወቀው ፡ በጋራ ፡ ባሏቸው ፡ ብዙ ፡ ቃላት ፡ ነው

**affinity**
1. መቀራረብ. There is close affinity between those two tribes. በእነዚያ ፡ ሁለት ፡ ነገዶች ፡ መሀከል ፡ ጥብቅ ፡ መቀራረብ ፡ አለ
2. ተሰጥዎ. He has an affinity for languages. የቋንቋ ፡ ተሰጥዎ ፡ አለው

**affirm**
1. አረጋገጠ. He affirmed his loyalty to his country. ላገሩ ፡ ያለውን ፡ ታማኝነት ፡ አረጋገጠ
He affirmed that he was not guilty. ጥፋተኛ ፡ አለመሆኑን ፡ አረጋገጠ
2. አጸደቀ. The higher court affirmed the lower court's decision. ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ውሳኔ ፡ አጸደቀ

**affirmative** የአዎንታ
An affirmative answer is indicated by nodding the head. የአዎንታ ፡ መልስ ፡ እራስን ፡ ደፋ ፡ ቀና ፡ በማድረግ ፡ ይገለጻል
*John was on the affirmative side of the debate. ጆን ፡ በክርክሩ ፡ ላይ ፡ ሐሳቡን ፡ ከደገፉት ፡ ወገን ፡ ነበር

**affix** (v.)
1. አኖረ. I affixed my signature to the letter. ደብዳቤው ፡ ላይ ፡ ፊርማዬን ፡ አኖርኩኝ
2. ለጠፈ. Affix a label to the jar! ገንቦው ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ ለጥፍበት

**afflict**
1. በጣም ፡ ጐዳ. War has long afflicted mankind. ጦርነት ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሰውን ፡ በጣም ፡ ጐድቶታል
2. አጠቃ. Starvation afflicts India from time to time. ረኃብ ፡ ህንድን ፡ በየጊዜው ፡ ያጠቃታል

**be afflicted**
1. ተመረዘ. Is Congo afflicted by sleeping sickness? ኮንጎ ፡ በእንቅልፍ ፡ በሽታ ፡ ተመርዛለች?
2. ተሠቃየ. Farmers are constantly afflicted by locusts. ገበሬዎች ፡ በየጊዜው ፡ በአንበጣ ፡ ይሠቃያሉ
3. ተጐዳ. The world was afflicted by the financial crisis which began in 1929. በ፲፱፻፳፱ ፡ በጀመረው ፡ የገንዘብ ፡ ችግር ፡ ዓለም ፡ ተጐድቶ ፡ ነበር
4. (= active) አጠቃ. +Hararge is often afflicted by drought. ሐረርጌን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ድርቅ ፡ ያጠቃዋል

**affliction**
1. የመከራ ፡ ጊዜ. She was brave in her affliction. በመከራዋ ፡ ጊዜ ፡ ታጋሽ ፡ ነበረች
2. መቅሠፍት. Some diseases are terrible afflictions. አንዳንድ ፡ በሽታዎች ፡ ከፉ ፡ መቅሠፍቶች ፡ ናቸው
3. ሥቃይ. The affliction caused by this disease was considerable. በዚህ ፡ በሽታ ፡ የተነሣ ፡ የደረሰው ፡ ሥቃይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው

**affluence**
1. ሀብት. Affluence will not guarantee happiness. ሀብት ፡ ደስታን ፡ ለማስገኘት ፡ ዋስትና ፡ አይደለም
2. በገፍ ፡ መኖር. The affluence of minerals made the country wealthy. የማዕድን ፡ በገፍ ፡ መኖር ፡ ሀገሪቱን ፡ አበለጸጋት

**live in affluence** ኑሮው ፡ ተሟላ
The people of this country live in affluence. የዚህ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ኑሮዋቸው ፡ የተሟላ ፡ ነው

**affluent** (n.) ጅረት
The affluents of the Awash River are dry in December. ወደ ፡ አዋሽ ፡ ወንዝ ፡ የሚፈሱ ፡ ጅረቶች ፡ በታኅሣሥ ፡ ይደርቃሉ

**affluent** (adj.)
1. ባለጸጋ. The minister was an affluent man. ሚኒስትሩ ፡ ባለጸጋ ፡ ሰው ፡ ነበሩ
2. የጥጋብ. Affluent times followed the end of the war. ጦርነቱ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ የጥጋብ ፡ ዘመን ፡ መጣ

**afford**
1. ሰጠ. Reading affords pleasure. ማንበብ ፡ ደስታን ፡ ይሰጣል

2. አስገኘ. His own garden affords vegetables for the family. የራሱ ፡ ያትክልት ፡ ስፍራ ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ አትክልት ፡ ያስገኝለታል

**can afford** ቻለ

Can you afford now to buy a car? አሁን ፡ መኪና ፡ ለመግዛት ፡ ትችላለህ?

**cannot afford**

1. አይፈቅድም. A busy man cannot afford delay. ሥራ ፡ የሚበዛበት ፡ ሰው ፡ መዘግየትን ፡ አይፈቅድም

2. ከዐቅሙ ፡ በላይ ፡ ነው. I cannot afford that. ያ ፡ ከዐቅሜ ፡ በላይ ፡ ነው

3. ዐቅሙ ፡ አይፈቅድለትም. I cannot afford to buy a car now. አሁን ፡ መኪና ፡ ለመግዛት ፡ ዐቅሜ ፡ አይፈቅድልኝም

[See also 'pleasure']

**afforest** ደን ፡ አለበሰ

The government is trying to afforest the area around the capital. በመናገሻ ፡ ከተማ ፡ አካባቢ ፡ ያለውን ፡ ስፍራ ፡ ደን ፡ ለማልበስ ፡ መንግሥቱ ፡ በመጣር ፡ ላይ ፡ ነው

**affranchise** አርነት ፡ አወጣ

Lincoln is famous for affranchising the slaves in America. በአሜሪካ ፡ ሊንኮልን ፡ ባሮችን ፡ አርነት ፡ በማውጣቱ ፡ የታወቀ ፡ ሆኗል

**affront** (v.) አዋረደ

He affronted me by walking out in the middle of the speech. በንግግሬ ፡ መሀል ፡ ተነሥቶ ፡ በመውጣት ፡ አዋረደኝ

**affront** (n.) ውርደት

We cannot take this affront. ይህንን ፡ ውርደት ፡ አንቀበለውም

**afield** በየሜዳ

The hunting dogs are afield looking for rabbits. አዳኞቹ ፡ ውሾች ፡ ጥንቸል ፡ ፍለጋ ፡ በየሜዳ ፡ ናቸው

**far afield** ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር

The traveler wandered far afield. መንገደኛው ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ሄደ

*To discuss that topic takes us too far afield. በዚያ ፡ ጉዳይ ፡ እንጋገር ፡ ከአርእስቱ ፡ ብዙ ፡ ያወጣናል

**(be) afire** በእሳት ፡ ተያያዘ

The house is afire. ቤቱ ፡ በእሳት ፡ ተያይዟል

**set afire** አቀጣጠለ

A spark set the house afire. የእሳት ፡ ፍንጣሪ ፡ ቤቱን ፡ አቀጣጠለው

**(be) aflame** በእሳት ፡ ተቀጣጠለ

The house was aflame by the time I got there. እኔ ፡ እዚያ ፡ በደረስኩ ፡ ጊዜ ፡ ቤቱ ፡ በእሳት ፡ ተቀጣጥሎ ፡ ነበር

**(be) afloat**

1. ተንሳፈፈ. The logs are afloat. ግንዶቹ ፡ በመንሳፈፍ ፡ ላይ ፡ ናቸው

2. ነፈሰ. There were many rumors afloat. ብዙ ፡ ጭምጭምታ ፡ ይነፍስ ፡ ነበር

**get afloat** አንሳፈፈ

We could not get the ship afloat. መርከቡን ፡ ልናንሳፍፈው ፡ አልቻልንም

**afoot** በእግር

Afoot it is two hours, but by car it is ten minutes. በእግር ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ይወስዳል ፤ በመኪና ፡ ግን ፡ ዐሥር ፡ ደቂቃ ፡ ብቻ ፡ ነው

**be afoot** ተቀሰቀሰ

Trouble was afoot. ረብሻ ፡ ተቀስቅሶ ፡ ነበር

**aforementioned** ከላይ ፡ የተጠቀሰ

The aforementioned students can leave. ከላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ተማሪዎች ፡ ሊሄዱ ፡ ይችላሉ

**(be) afoul** ተተበተበ

We cannot use the rope because it is afoul. ገመዱ ፡ የተተበተበ ፡ ስለሆነ ፡ ልንጠቀምበት ፡ አንችልም

**run afoul**

*He ran afoul of the law. ሕጉን ፡ ጥሶ ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ

**(be) afraid**

1. ፈራ. He is not afraid of anyone. ማንንም ፡ አይፈራም

I was afraid of hurting her feelings. እስቀይማታለሁ ፡ ብዬ ፡ ፈርቻለሁ

2. መሰለ(ው). I am afraid it is too late. ጊዜው ፡ የዘገየ ፡ ይመስለኛል

I'm afraid I can't help you. ልረዳህ ፡ የምችል ፡ አይመስለኝም

**after** (prep. adv.)

1. ከ - - - በኋላ. Can you call me up after supper? ከራት ፡ በኋላ ፡ ልትደውልልኝ ፡ ትችላለህ?

He fell sick on Tuesday, and died two days after. ማክሰኞ ፡ ታመመና ፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሞተ

2. ስለ. Your aunts asked after you. አክስቶችህ ፡ ስላንተ ፡ ጠየቁ

3. (= conj.) ብ + (imperfect). After all her suffering she is still cheerful. ያ ፡ ሁሉ ፡ መጉሳቆል ፡ ቢደርስባትም ፡ አሁንም ፡ ደስተኛ ፡ ትመስላለች

4. (= conj.) ስ + (imperfect). After the rude way she acted who could like her? እንዲህ ፡ ስትባልግ ፡ ታይታ ፡ ማን ፡ ይወዳታል?
*He wrote a fable after the manner of Aesop. የኤዞፕን ፡ አጻጻፍ ፡ በመከተል ፡ አንድ ፡ ተረት ፡ ጻፈ
*He closed the door after him when he left the room. በሩን ፡ ዘግቶ ፡ ወጣ
*He failed his exams after all that studying. ያንን ፡ ያህል ፡ አጥንቶ ፡ ፈተናውን ፡ ወደቀ
*The brazen girl told lie after lie. ኀፍረተ ፡ ቢሷ ፡ ልጅ ፡ ደጋግማ ፡ ዋሸች

**after** (conj.)
1. እንደ + (verb.). I answered immediately after I received his letter. ደብዳቤው ፡ እንደ ደረሰኝ ፡ ወዲያውኑ ፡ መልስ ፡ ጻፍኩ
2. ከ + verb + በኋላ. He left after we ate. ከበላን ፡ በኋላ ፡ ሄደ

**after all**
1. ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፤ የሆነ ፡ ሆኖ. After all, he failed his exams. ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ፈተናውን ፡ ወደቀ
You are right, after all. የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ልክ ፡ ነህ
2. መቼም. What can I do? After all, he is my friend. ምን ፡ ላድርግ ፤ መቼም ፡ ወዳጄ ፡ ነው
It appears the best after all. መቼም ፡ ከሁሉም ፡ የተሻለ ፡ ይመስላል

**after that** ከዚያ ፡ በኋላ
After that, there was nothing else to do. ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ ሌላ ፡ የሚደረግ ፡ ነገር ፡ አልነበረም

**after this** ከዚህ ፡ በኋላ
After this, please let us know in advance. ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አስቀድመህ ፡ አስታውቀን

**be after**
1. ተከታተለ. The police are after him. ፖሊሶች ፡ ይከታተሉታል
2. ፈለገ. It is quite plain that he is after her money. ገንዘቧን ፡ መፈለጉ ፡ ግልጽ ፡ ነው
[See also 'ever, long, one, shortly, soon']

## afterbirth የእንግዴ ፡ ልጅ
The afterbirth was buried outside the hut. የእንግዴ ፡ ልጁ ፡ ከጎጆው ፡ ውጭ ፡ ተቀበረ

## afternoon ከሰዓት ፡ በኋላ
He goes home every afternoon at three. ሁል ጊዜ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይሄዳል

**this afternoon** ዛሬ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ
Can you come this afternoon? ዛሬ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ልትመጣ ፡ ትችላለህ?
[See also 'late']

## afterthought
*The idea came to me as an afterthought. ነገሩን ፡ የተገነዘብኩት ፡ ዘግይቼ ፡ ነው

## afterwards በኋላ
I will talk to you afterwards. በኋላ ፡ አነጋግርሃለሁ

**shortly afterwards** ወዲያው
He came at ten and I left shortly afterwards. ባራት ፡ ሰዓት ፡ መጣ ፡ እኔም ፡ ወዲያው ፡ ሄድኩ

## again
1. እንደገና. I will tell him again. እንደገና ፡ እነግረዋለሁ
Do you think she will marry again? እንደገና ፡ የምታገባ ፡ ይመስልሃል?
2. ከዚህም ፡ በላይ. Again, I must say that he is very honest. ከዚህም ፡ በላይ ፡ በጣም ፡ ታማኝ ፡ መሆኑን ፡ መግለጽ ፡ እፈልጋለሁ
*It might rain and again it might not. ሊዘንብም ፡ ላይዘንብም ፡ ይችላል

**again and again** ደጋግሞ
I told him again and again. ደጋግሜ ፡ ነገርኩት

**do again** ደገመ
Don't do that again! ይህንን ፡ እንዳትደግም
[See also 'happen, never, now, once, over, time']

## against
1. ከ - - - አንጻር. The sailor tried to row against the tide. መርከበኛው ፡ ከሞገዱ ፡ አንጻር ፡ ለመቅዘፍ ፡ ሞከረ
2. በ - - - ላይ. He had charms recited against his opponent. በባለጋራው ፡ ላይ ፡ አስማት ፡ አስደገመበት
3. በመቃወም. He voted against the proposal. የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ በመቃወም ፡ ድምፅ ፡ ሰጠ
4. ለመውጋት. The Ethiopians went to war against the invaders. ኢትዮጵያውያን ፡ ወራሪውን ፡ ለመውጋት ፡ ተነሡ
5. (= adj.) የሚከለክል. Is there a law against begging in this country? እዚህ ፡ አገር ፡ ልመናን ፡ የሚከለክል ፡ ሕግ ፡ አለ?
6. ለመከላከል. The parliament took energetic measures against crime. ምክር ፡ ቤቱ ፡ ወንጀልን ፡ ለመከላከል ፡ ጥብቅ ፡ እርምጃ ፡ ወሰደ
7. ያለ. He was named chairman against his

will. ያለ ፡ ውዴታው ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ እንዲሆን ፡ ተመረጠ
*He saved money against difficult times. ለችግር ፡ ጊዜ ፡ በማሰብ ፡ ገንዘብ ፡ ቈጥቦ ፡ አስቀመጠ

**be against** ተቃወመ
Are you for or against it? ትደግፈዋለህ ፡ ወይስ ፡ ትቃወመዋለህ?
The police are against student agitation. ፖሊሶች ፡ የተማሪዎችን ፡ መነሣሣት ፡ ይቃወማሉ
[See also 'time, up']

**age** (vt.) አሸመገለ
Fear aged him overnight. ፍርሃት ፡ ባንዴ ፡ አሸመገለው

**age** (vi.)
1. አረጀ. He has aged a great deal lately. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ በጣም ፡ አርጅቷል
2. በሰለ. This mead ages well. ይህ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ደኅና ፡ የበሰለ ፡ ነው

**age** (n.)
1. ዕድሜ. State age and occupation! ዕድሜህንና ፡ ሥራህን ፡ ግለጽ
He is about my age. በዕድሜ ፡ እኩያዬ ፡ ነው
2. ዓመት. He is thirty years of age. ሠላሳ ፡ ዓመቱ ፡ ነው
3. እርጅና. His back was bent with age. በእርጅና ፡ ምክንያት ፡ ጐብጧል
4. የዕድሜ ፡ መግፋት. Because of his age he stays at home. ከዕድሜያቸው ፡ መግፋት ፡ የተነሣ ፡ እቤት ፡ ውለዋል
5. የጊዜ ፡ ብዛት. The bread turned black with age. ዳቦው ፡ ከጊዜው ፡ ብዛት ፡ ጠቈረ
6. ማርጀት. The boards of the floor were cracked with age. የወለሉ ፡ ሳንቃዎች ፡ ከማርጀታቸው ፡ የተነሣ ፡ ተሰነጣጥቀዋል
7. ዘመን. This is the age of invention. ይህ ፡ የፍልሰፋ ፡ ዘመን ፡ ነው
8. የቆየ ፡ መሆን. Its age heightens the value of the painting. የቆየ ፡ መሆኑ ፡ የሥዕሉን ፡ ዋጋ ፡ ያስወድደዋል

**be of age** ለዐቅመ ፡ አዳም ፡ ደረሰ
He will enter the priesthood when he is of age. ለዐቅመ ፡ አዳም ፡ ሲደርስ ፡ ይቀስሳል

**come of age** ለአካለ ፡ መጠን ፡ ደረሰ
He will come of age next year. በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ለአካለ ፡ መጠን ፡ ይደርሳል

**in ages** ለብዙ ፡ ዘመናት
We have not seen them in ages. ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ አላየናቸውም
[See also 'early, old, tender']

**aged** (adj.) የበሰለ
Do you like aged wine? የበሰለ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ትወዳለህ?
*A boy aged ten came to see me. ያሥር ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ሊጠይቀኝ ፡ መጣ

**aged man** ሽማግሌ
The aged man was wrinkled and bent. ሽማግሌው ፡ ቆዳቸው ፡ ከመሸብሸቡም ፡ በላይ ፡ ጐብጠዋል

**aged woman** አሮጊት
The aged woman was wrinkled and bent. አሮጊቷ ፡ ቆዳቸው ፡ ከመሸብሸቡም ፡ በላይ ፡ ጐብጠዋል

**agency**
1. ድርጅት. Employment agencies help workers find jobs. የአስቀጣሪ ፡ ድርጅቶች ፡ ሠራተኞች ፡ ሥራ ፡ እንዲያገኙ ፡ ይረዳሉ
2. ወኪል. The company has an agency in Addis Ababa. ኩባንያው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ወኪል ፡ አለው
3. አማካይነት. Sand is made from rocks by the agency of water. አሸዋ ፡ ከቋጥኞች ፡ የሚሠራው ፡ በውኃ ፡ አማካይነት ፡ ነው
[See also 'employment']

**agenda** አጀንዳ
The secretary read the agenda of the meeting. ጸሐፊው ፡ የስብሰባውን ፡ አጀንዳ ፡ አነበበ

**agent**
1. ወኪል. Your agent has already called on me. ወኪልህ ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ ጠይቆኛል
2. አነሣሽ. Agents are fomenting rebellion in outlying districts. አነሣሾች ፡ ሩቅ ፡ ባሉት ፡ አውራጃዎች ፡ ውስጥ ፡ ብጥብጥ ፡ ያነሣሣሉ
3. መገልገያ. Heat and electricity are important agents in the life of today. በዛሬው ፡ ኑሮ ፡ ኮረንቲና ፡ ሙቀት ፡ ጠቃሚ ፡ መገልገያዎች ፡ ናቸው

**agglomerate** (v.) አደባለቀ
He agglomerated rocks and clay to make a kind of brick. ድንጋይና ፡ ሸክላ ፡ በማደባለቅ ፡ የጡብ ፡ ዓይነት ፡ ሠራ

**agglomeration, ~ of**
1. ዕጅብ ፡ ያሉ. An agglomeration of houses could be seen in the distance. በሩቅ ፡ ዕጅብ ፡ ያሉ ፡ ቤቶች ፡ ይታዩ ፡ ነበር
2. የተውጣጣ. His plan is an agglomeration of other people's ideas. የሱ ፡ እቅድ ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ሐሳብ ፡ የተውጣጣ ፡ ነው

LAPSLEY / BROOKS FOUNDATION, INC.
1701 N. GREENVILLE AVE. ST. 810
RICHARDSON, TEXAS 75081, USA



**agglutinate** ተገጣጠመ
The word-particles agglutinate to form long words. የቃል ፡ ንኡስ ፡ ክፍሎች ፡ ተገጣጥመው ፡ ረጃጅም ፡ ቃላትን ፡ ይፈጥራሉ

**agglutination** መዋሐድ
The agglutination of asphalt and gravel solidifies the highway. የሬንጅና ፡ የጠጠር ፡ መዋሐድ ፡ ጎዳናውን ፡ ያጠነክረዋል

**aggrandize** አሳደገ
He aggrandized himself at the expense of others. በሌሎች ፡ ትከሻ ፡ ራሱን ፡ አሳደገ

**aggravate**
1. አበሳጨ. His tardiness aggravates me. የሱ ፡ ዳተኝነት ፡ ያበሳጨኛል
2. አባሰ(በት). +He aggravated his sprained ankle by walking. መራመዱ ፡ ወለም ፡ ያለውን ፡ ቁርጭምጭሚቱን ፡ አባሰበት

**aggravation** ብስጭት
I got nothing but aggravation. ከብስጭት ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ አላገኘሁም

**cause an aggravation** አባባሰ
The treatment caused an aggravation of the pain. ሕክምናው ፡ ሕመሙን ፡ አባባሰው

**aggregate** (vt.)
1. አቀላቀለ. Farmers should aggregate small fields into one large field. ገበሬዎች ፡ ትንንሽ ፡ ማሳዎችን ፡ በማቀላቀል ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ማሳ ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው
2. አጠቃለለ. He aggregated his holdings into one company. ንብረቱን ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ኩባንያ ፡ አጠቃለለ

**aggregate** (n.) ጠቅላላ ፡ ድምር
The aggregate of all his debts is a hundred dollars. ያለበት ፡ ዕዳ ፡ ጠቅላላ ፡ ድምሩ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ነው

**aggression**
1. የጠብ ፡ አጫሪነት. Haile Sellassie the First accused Italy of aggression. ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኢጣልያንን ፡ በጠብ ፡ አጫሪነት ፡ ከሰሷት
2. ጠብ ፡ ማጫር. Aggression is condemned by the United Nations. ጠብ ፡ ማጫር ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የተወገዘ ፡ ነው

**aggressive**
1. ጠብ ፡ ጫሪ. An aggressive country is always ready to start a war. ጠብ ፡ ጫሪ ፡ አገር ፡ ጦርነት ፡ ለመጀመር ፡ ምንግዜም ፡ ዝግጁ ፡ ነው
2. ጠበኛ. Nobody likes an aggressive boy. ማንም ፡ ሰው ፡ ጠበኛ ፡ ልጅ ፡ አይወድም
3. ጥብቅ. The police are making an aggressive campaign against crime. ፖሊሶች ፡ ወንጀልን ፡ ለመከላከል ፡ ጥብቅ ፡ ትግል ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ናቸው

**aggressor** ጠብ ፡ አጫሪ ፤ አጥቂ
The aggressor was Italy, the victim, Ethiopia. ጠብ ፡ አጫሪዋ ፡ ኢጣልያን ፡ ስትሆን ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ የወደቀችው ፡ ደሞ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነበረች
As restitution, the aggressor government gave ten million dollars. አጥቂው ፡ መንግሥት ፡ ዐሥር ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ ካሳ ፡ ከፈለ

**aggrieved, feel ~** ቅር ፡ ተሰኘ
He felt aggrieved when I was promoted. እኔ ፡ የደረጃ ፡ እድገት ፡ ባገኘሁ ፡ ጊዜ ፡ ቅር ፡ ተሰኘ

**(be) aghast** ክው ፡ ብሎ ፡ ደነገጠ
He was aghast at the damage the wind had caused. ነፋሱ ፡ ያደረሰውን ፡ ጥፋት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ክው ፡ ብሎ ፡ ደነገጠ

**stand aghast** ክው ፡ አለ
He stood aghast at the horrible sight. አሰቃቂውን ፡ ነገር ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ክው ፡ አለ

**agile**
1. ቀልጣፋ. A basketball player has to be agile. የቅርጫት ፡ ኳስ ፡ ተጫዋች ፡ ቀልጣፋ ፡ መሆን ፡ አለበት
2. ንቁ. You need an agile mind to solve the problem. ለችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ ለማስገኘት ፡ ንቁ ፡ አእምሮ ፡ ያስፈልግሃል

**agitate**
1. አነሣሣ. Foreign agents were sent to agitate the people. ሕዝቡን ፡ ለማነሣሣት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ አነሣሾች ፡ ተልከው ፡ ነበር
2. አሸበረ. The news that his enemy was promoted agitated him. የጠላቱ ፡ መሾም ፡ ወሬ ፡ አሸበረው
3. አናወጸ. The wind agitated the lake. ነፋሱ ፡ ሐይቁን ፡ አናወጸው
4. አማሰለ. The maid agitated the soup. ገረዲቱ ፡ ሾርባውን ፡ አማሰለችው

**agitation**
1. መነሣሣት. The police are against student agitation. ፖሊሶች ፡ የተማሪዎችን ፡ መነሣሣት ፡ ይቃወማሉ
2. የመንፈስ ፡ መረበሽ. His agitation wouldn't let him sleep. የመንፈሱ ፡ መረበሽ ፡ እንቅልፍ ፡ ነሣው

3. መናወጥ. The agitation of air causes the dust to rise. ያየሩ ፡ መናወጥ ፡ አቧራውን ፡ ያነሣ
ዋል

**be in a state of agitation** ተሸበረ
She was in a state of agitation due to her recent bereavement. በቅርቡ ፡ በደረሰባት ፡ የዘ
መድ ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ ተሸብራ ፡ ነበር

**(be) aglow** አበራ
His face was aglow with pleasure. ፊቱ ፡ በደ
ስታ ፡ ያበራ ፡ ነበር

**ago**
1. ከ - - - በፊት. I was there two months ago. ከሁለት ፡ ወር ፡ በፊት ፡ እዚያ ፡ ነበርኩ
2. የዛሬ. The club began two years ago. ክበቡ ፡ የዛሬ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ተቋቋመ
[See also 'how, long, moment, week, while']

**agonize** (vt.) አስጨነቀ
His decision agonized him for weeks. ያደረ
ገው ፡ ውሳኔ ፡ ለብዙ ፡ ሳምንቶች ፡ አስጨነቀው

**agonize** (vi.) ተጨነቀ
Even though he was right, he agonized over the decision for weeks. ምንም ፡ እንኳን ፡ ት
ክክል ፡ ቢሆን ፡ ባደረገው ፡ ውሳኔ ፡ ለብዙ ፡ ሳም
ንት ፡ ተጨነቀ

**agony** (agonies)
1. ጣረ ፡ ሞት. His agony lasted hours. ጣረ ፡
ሞቱ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆየ
2. ሥቃይ. An earache is an agony. የጆሮ ፡ ሕ
መም ፡ ሥቃይ ፡ ነው
3. አሰቃቂ ፡ ሁኔታ. The viper bit her and she died in agony. እፉኝት ፡ ነድፏት ፡ ባሰቃቂ ፡
ሁኔታ ፡ ሞተች

**be in agony** ተሠቃየ
He was in an agony of remorse. በጸጸት ፡ ይሠ
ቃይ ፡ ነበር

**suffer agonies** ክፉኛ ፡ ተሠቃየ
I suffered agonies with that headache. በራስ ፡
ምታት ፡ ክፉኛ ፡ ተሠቃየሁ

**agrarian** የእርሻ
Our agrarian laws are very strict. የእርሻ ፡ ሕገጋ
ታችን ፡ በጣም ፡ ጥብቅ ፡ ናቸው

**agree**
1. ተስማማ. He agreed to accompany us.
ሊሸኘን ፡ ተስማማ
We agreed on a price. ስለ ፡ ዋጋው ፡ ተስማ
ማን
The verb agrees with the subject in person and gender. ግስ ፡ በመደብና ፡ በጾታ ፡ ከባለቤ
ት ፡ ጋር ፡ ይስማማል
2. አለ. I agree that he is the ablest of us.
ከሁላችንም ፡ በችሎታ ፡ የሚበልጥ ፡ ነው ፡ እላለሁ

**agree with one** ተስማማ
This food doesn't agree with me. ይህ ፡ ምግ
ብ ፡ አይስማማኝም

**happen to agree** ተስማማ
I don't happen to agree with you. ካንተ ፡ ጋ
ር ፡ አልስማማም

**agreeable**
1. አስደሳች. She has an agreeable disposition.
አስደሳች ፡ ባሕሪይ ፡ አላት
2. ተስማሚ. They played music agreeable to the occasion. ለጊዜው ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ሙ
ዚቃ ፡ ተጫወቱ

**(be) agreeable (to)** ተስማማ
Is he agreeable to our suggestion? እሱ ፡ ባቀ
ረብነው ፡ ሐሳብ ፡ ይስማማል?

**agreement**
1. ስምምነት. The agreement has to be ratified by the Senate. ስምምነቱ ፡ በሕግ ፡ መወሰኛ ፡ መ
ጽደቅ ፡ አለበት
2. መስማማት. Agreement between the verb and the noun is required in Amharic. ባማርኛ ፡
በግስና ፡ በስም ፡ መሀከል ፡ መስማማት ፡ ተፈ
ላጊ ፡ ነው
3. ተመሳሳይነት. There was complete agreement between the stories of the two witnesses.
በሁለቱ ፡ ምስክሮች ፡ ቃል ፡ መሀከል ፡ ፍጹም ፡
ተመሳሳይነት ፡ ነበር

**be in agreement** ተስማማ
We are all in agreement on that. ሁላችንም ፡
በዚህ ፡ እንስማማለን

**come to an agreement** ተስማማ
We came to an agreement on this point.
በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ተስማማን

**conclude an agreement** ስምምነት ፡ አደረገ
The two nations concluded a trade agreement.
ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ የንግድ ፡ ስምምነት ፡ አደረጉ

**agricultural** የእርሻ
The farmers used modern agricultural methods.
ገበሬዎቹ ፡ በዘመናዊ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ ተጠቀሙ

**agriculture**
1. ግብርና. What is the state of Ethiopian agriculture? የኢትዮጵያ ፡ ግብርና ፡ ይዞታ ፡ እ
ንዴት ፡ ነው?

2. የእርሻ ፡ ተግባር. There is not much agriculture in this region. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ብዙ ፡ የእርሻ ፡ ተግባር ፡ የለም

**Ministry of Agriculture** እርሻ ፡ ሚኒስቴር
Inquire at the Ministry of Agriculture! እርሻ ፡ ሚኒስቴርን ፡ ጠይቅ

**aground, run ~** መሬት ፡ ያዘ
The ship ran aground in the shallow waters. መርከቧ ፡ ጥልቀት ፡ በሌለው ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ መሬት ፡ ያዘች

**ahead**
1. ወደፊት. There are rough times ahead. ወደፊት ፡ የችግር ፡ ጊዜ ፡ አለ
2. በቅድሚያ. I want to send my baggage on ahead. ጓዜን ፡ በቅድሚያ ፡ ለመላክ ፡ እፈልጋለሁ

**ahead of**
1. ቀደም ፡ ብሎ. He sits three rows ahead of us. ከኛ ፡ ሦስት ፡ ተርታ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ተቀምጧል
2. ቀድሞ. He got here ahead of me. ከኔ ፡ ቀድሞ ፡ እዚህ ፡ ደረሰ

**be far ahead** ቀደመ
His scientific discoveries were far ahead of the times. በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ጥናት ፡ ያገኛቸው ፡ ነገሮች ፡ ከጊዜው ፡ የቀደሙ ፡ ነበሩ

**be ahead** መራ
Who is ahead in the election race now? የምርጫውን ፡ ውድድር ፡ የሚመራው ፡ ማነው?

**be ahead of**
1. ቀደመ. Are you next? No, he is ahead of me. ያንተ ፡ ተራ ፡ ነው? የለም ፡ እሱ ፡ ይቀድመኛል
2. ላቀ. He is ahead of everybody. ሁሉንም ፡ ይልቃል

**be way ahead**
1. ገፋ. I am way ahead in my work. በሥራዬ ፡ ገፍቻለሁ
2. ብዙ ፡ ቀደመ. Hurry up, the others are way ahead of us already. ፈጠን ፡ በል ፤ ሌሎቹ ፡ ብዙ ፡ ቀድመውናል

**get ahead** ተሳካ(ለት)
+My uncle got ahead in business. የኔ ፡ አጎት ፡ የንግድ ፡ ሥራው ፡ ተሳካለት
[See also 'go, straight, time']

**aid** (v.) ረዳ
Can I aid you in any way? ልረዳህ ፡ የምችልበት ፡ መንገድ ፡ አለ?

**aid** (n.)
1. እርዳታ. Tanzania is seeking only economic aid. ታንዛኒያ ፡ የምትፈልገው ፡ የኢኮኖሚ ፡ እርዳታ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ረዳት. He is a nurse's aide. የነርስ ፡ ረዳት ፡ ነው

**come to (someone's) aid** ደረሰ(ለት)
When I was losing the fight, he came to my aid. በድብድብ ፡ ልሸነፍ ፡ ስል ፡ ደረሰልኝ
[See also 'first aid']

**ail** ነካ
What ails the man? ሰውየውን ፡ ምን ፡ ነካው?

**ailing** በሽተኛ
He has an ailing mother. በሽተኛ ፡ እናት ፡ አሉት

**be ailing** አመመ(ው)
She is always ailing. ሁልጊዜ ፡ ያማታል

**ailment** ሕመም
There is no remedy for his ailment. የሱ ፡ ሕመም ፡ መድኃኒት ፡ የለውም

**aim** (v.)
1. አነጣጠረ. Aim higher! Your bullet hit below the target. ከፍ ፡ ብለህ ፡ አነጣጥር ፤ ጥይትህ ፡ ከዒላማው ፡ በታች ፡ ነው ፡ የመታው
2. አሰበ. He aims to become a doctor. ሐኪም ፡ ለመሆን ፡ ያስባል
3. ተጣጣረ. She aimed to please her teacher. አስተማሪዋን ፡ ለማስደሰት ፡ ተጣጣረች

**be aimed at**
1. ተሰነዘረ. He fended off the blow which was aimed at his head. ለራሱ ፡ የተሰነዘረውን ፡ ምት ፡ ተከላከለ
The President's speech was aimed at men of his party. የፕሬዚዳንቱ ፡ ንግግር ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ የፖለቲካ ፡ ቡድን ፡ የተሰነዘረ ፡ ነበር
2. ታሰበ. That was aimed at me. የታሰበው ፡ ለኔ ፡ ነበር

**aim** (n.)
1. ማነጣጠር. Is your aim good? ጥሩ ፡ ማነጣጠር ፡ ትችላለህ?
2. ዒላማ. He has missed his aim. ዒላማውን ፡ ስቷል
3. ዓላማ. His aim is to become a good doctor. ዓላማው ፡ ጥሩ ፡ ሐኪም ፡ ለመሆን ፡ ነው

**take aim** አነጣጠረ
He took careful aim and fired at the fleeing convict. ደኅና ፡ አድርጎ ፡ አነጣጠረና ፡ ይሸሽ ፡ በነበረው ፡ ወንጀለኛ ፡ ላይ ፡ ተኰሰ

**aimless (pursuits)** ዋዛ ፡ ፈዛዛ
He spent his life in aimless pursuits. ዕድሜውን ፡ በዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ አሳለፈው

**aimlessly** ያላንዳች ፡ ዓላማ
The child was running about aimlessly. ልጁ ፡ ያላንዳች ፡ ዓላማ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይሮጥ ፡ ነበር

**air** (v.) አናፈሰ
Would you please air the room while I am out. እኔ ፡ ስወጣ ፡ ክፍሉን ፡ አናፍሰው

**air one's grievances** ቅሬታውን ፡ ሁሉ ፡ ገለጸ
He aired his grievances when he met with the minister. ከሚኒስትሩ ፡ ጋር ፡ በተገናኘ ፡ ጊዜ ፡ ቅሬታውን ፡ ሁሉ ፡ ገለጸ

**air** (n.)
1. አየር. The air in this room is bad. በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ አየር ፡ መጥፎ ፡ ነው
Birds fly in the air. ወፎች ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ ይበራሉ
2. ሁኔታ. The famous man has an air of mystery. ዝነኛው ፡ ሰው ፡ ስውር ፡ የሆነ ፡ ሁኔታ ፡ አለው
The air was charged with excitement. ሁኔታው ፡ የጋለ ፡ ስሜት ፡ የሞላበት ፡ ነበር
3. መልክ. The hotel has an air of luxury. ሆቴሉ ፡ የድሎት ፡ መልክ ፡ አለው
4. ዜማ. This is an old English air. ይህ ፡ የጥንት ፡ የእንግሊዝ ፡ ዜማ ፡ ነው

**airs** ፊሊጥ
John's city airs annoyed his friends at home. የጆን ፡ የከተማ ፡ ፊሊጥ ፡ እቤት ፡ የሚገኙትን ፡ ወዳጆቹን ፡ አበሳጫቸው

**air** (adj.) ያየር
The order of the day was to be alert for air attack. ዕለታዊው ፡ ትእዛዝ ፡ ላየር ፡ ጥቃት ፡ ዝግጁ ፡ ሁኑ ፡ የሚል ፡ ነበር

**give oneself airs** ልታይ ፡ ልታይ ፡ አለ
She has few friends because she gives herself such airs. ልታይ ፡ ልታይ ፡ ማለትን ፡ ስለምታበዛ ፡ ጓደኞቿ ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ናቸው

**go off the air** ተቋረጠ
Because of a power failure, the station went off the air. በኤሌክትሪክ ፡ ጉድለት ፡ የተነሣ ፡ ጣቢያው ፡ ተቋረጠ

**(be) in the air** ነፈሰ
There are rumors in the air that he will become President. እሱ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ ጭምጭምታ ፡ ይነፍሳል

**let in fresh air!** ይንፈስበት
This room is stuffy; open a window and let in fresh air! ይህ ፡ ክፍል ፡ ታፍኗል ፤ መስኮቱን ፡ ክፈተውና ፡ ይንፈስበት

**let the air out of** አስተነፈሰ
He let the air out of the tire. ጎማውን ፡ አስተነፈሰው

**put on airs** ጉራ ፡ ነዛ
Yours friends will laugh if you put on airs. ጉራ ፡ ስትነዛ ፡ ጓደኞችህ ፡ ይሥቁብሃል

**take the air** ተናፈሰ
Let's go into the garden and take the air! ባትክልቱ ፡ ቦታ ፡ እንናፈስ

**(be) up in the air** በውጥን ፡ ነው
My plans are still up in the air. ሐሳቤ ፡ ገና ፡ በውጥን ፡ ነው
[See also 'current, freight, fresh, importance, open']

**airborne** አየር ፡ ወለድ
Airborne troops occupied the town. አየር ፡ ወለድ ፡ ወታደሮች ፡ ከተማውን ፡ ያዙት

**aircraft** አውሮፕላን
Aircraft must land on level hard ground. አውሮፕላኖች ፡ ደልዳላ ፡ በሆነ ፡ ጠንካራ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ማረፍ ፡ አለባቸው

**airfield** አውሮፕላን ፡ ማቢያ
We will meet at the airfield. አውሮፕላን ፡ ማቢያው ፡ እንገናኛለን

**air force** የአየር ፡ ኀይል
The Ethiopian air force is strong. የኢትዮጵያ ፡ የአየር ፡ ኀይል ፡ ኀይለኛ ፡ ነው

**airing, give an ~**
1. አናፈሰ. They gave their winter clothes an airing. የክረምት ፡ ልብሳቸውን ፡ አናፈሱት
2. ለሕዝብ ፡ ነዛ. The newspapers gave the scandal an airing. ጋዜጣዎች ፡ የተደረገውን ፡ አሳፋሪ ፡ ነገር ፡ ለሕዝብ ፡ ነዙት

**air letter** የአየር ፡ መልእክት
I received an air letter today. ዛሬ ፡ የአየር ፡ መልእክት ፡ ደረሰኝ

**airlines** የአየር ፡ መንገድ
Ethiopian Airlines goes to Athens. የኢትዮጵያ ፡ የአየር ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ አቴን ፡ ይበራል

**airmail** የአየር ፡ መልእክት
What are the rates for airmail? የአየር ፡ መልእክት ፡ ዋጋው ፡ ስንት ፡ ነው?

**airmail letter** በአየር ፡ የተላከ ፡ ደብዳቤ ፤ የአየር ፡ ፖስታ ፡ ደብዳቤ

I received an airmail letter today. ዛሬ ፡ በአየር ፡ የተላከ ፡ ደብዳቤ ፡ ደረሰኝ

**air-minded**
*Ethiopia is air-minded now. ኢትዮጵያ ፡ አሁን ፡ የአየር ፡ መንገድ ፡ ጥቅም ፡ ገብቷታል

**airplane** አይሮፕላን ፤ አውሮፕላን
How long does it take by airplane? በአውሮፕላን ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ይፈጃል?

**airport** የአውሮፕላን ፡ ማረፊያ
The airport of Addis Ababa is new. ያዲስ ፡ አበባ ፡ የአውሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ አዲስ ፡ ነው

**air raid** የአየር ፡ ወረራ
The people were told to seek shelter when there is an air raid. የአየር ፡ ወረራ ፡ ሲመጣ ፡ ሕዝቡ ፡ ተገን ፡ እንዲይዝ ፡ ተነገረው

**(be) airsick** አጥወለወለ(ው)
I am airsick in this small plane. በዚች ፡ ትንሽ ፡ አውሮፕላን ፡ ውስጥ ፡ ያጥወለውለኛል

**(be) airtight** አየር ፡ አይዘልቀውም
Is the box airtight? ሣጥኑ ፡ አየር ፡ አይዘልቀውም?
*We have an airtight case against him. በዚህ ፡ ሰውዬ ፡ ላይ ፡ መውጫ ፡ የሚያሳጣው ፡ ክስ ፡ አለን

**airy**
1. ነፋስ ፡ የሚገባው. He wants an airy room on the second floor. በሁለተኛው ፡ ፎቅ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ነፋስ ፡ የሚገባው ፡ ክፍል ፡ ይፈልጋል
2. ከንቱ. His airy schemes always ended unhappily. ከንቱ ፡ እቅዱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ሳይሳካ ፡ ይቀራል

**aisle** መተላለፊያ
The aisle in this cinema is narrow. የዚህ ፡ ሲኒማ ፡ ቤት ፡ መተላለፊያ ፡ ጠባብ ፡ ነው

**(be) ajar** ገርበብ ፡ አለ
The door was ajar. መዝጊያው ፡ ገርበብ ፡ ብሎ ፡ ነበር

**(be) akin**
1. ተመሳሳይ ፡ ነው. Most boys are akin in their love of sports. አብዛኛዎቹ ፡ ልጆች ፡ ስለ ፡ ስፖርት ፡ ባላቸው ፡ ፍቅር ፡ ተመሳሳይ ፡ ናቸው
2. ተዛመደ. The man is an old friend of mine but is not akin to me. ሰውየው ፡ የብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጓደኛዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አይዛመደኝም
Pity is often akin to love. ርኅራኄ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከመውደድ ፡ ጋር ፡ የተዛመደ ፡ ነው

**alacrity, with ~**
1. ነቃ ፡ ብሎ. Although the man is very old, he still moves around with alacrity. ምንም ፡ እንኳን ፡ ሰውየው ፡ በጣም ፡ ያረጀ ፡ ቢሆንም ፡ አሁንም ፡ ነቃ ፡ ብሎ ፡ ይዘዋወራል
2. በፍጥነት ፤ ያላንዳች ፡ ማመንታት. He accepted the invitation with alacrity. ግሬውን ፡ በፍጥነት ፡ (ያላንዳች ፡ ማመንታት) ፡ ተቀበለ

**alarm** (vt.) አሸበረ ፤ አስደነገጠ
The news of war alarmed everybody. የጦርነቱ ፡ ወሬ ፡ ሁሉንም ፡ አሸበረ
The clatter of the mob in the street alarmed me. በመንገድ ፡ ላይ ፡ የሕዝቡ ፡ ውካታ ፡ አስደነገጠኝ

**be alarmed**
1. ደነገጠ. Don't be alarmed if you see a car coming. መኪና ፡ ሲመጣ ፡ ስታይ ፡ አትደንግጥ
2. ተሸበረ. Everybody was alarmed at the news that war might break out. ጦርነት ፡ ይነሣ ፡ ይሆናል ፡ በሚለው ፡ ወሬ ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ተሸብሯል

**alarm** (n.)
1. ድንጋጤ. Everyone drew back in alarm when they saw the snake. እባቡን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ በድንጋጤ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈጉ
2. የሰዓት ፡ ደወል. Set the alarm for six! የሰዓቱን ፡ ደወል ፡ በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ እንዲደውል ፡ሙላው
3. የማስጠንቀቂያ ፡ ደወል. The noise of the alarm activated the fire company. የማስጠንቀቂያው ፡ ደወል ፡ ጩኸት ፡ የእሳት ፡ አደጋውን ፡ ድርጅት ፡ ቀሰቀሰው

**alarm clock** የሚደውል ፡ ሰዓት
Set the alarm clock for six! የሚደውል ፡ ሰዓቱን ፡ በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ እንዲደውል ፡ አስተካክለው

**false alarm**
It was a false alarm. የውሸት ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ጩኸት ፡ ነበር

**sound the alarm** ያደጋ ፡ ድምፅ ፡ አሰማ
Sound the alarm! The building is on fire. ያደጋ ፡ ድምፅ ፡ አሰማ ፤ ሕንጻው ፡ ተያይዟል
[See also 'flurry']

**alarming** አሳሳቢ
The report of the world news was alarming. የዓለም ፡ ወሬ ፡ መግለጫው ፡ አሳሳቢ ፡ ነበር

**alarmingly** በሚያሰጋ ፡ ሁኔታ
The fire is alarmingly close. እሳቱ ፡ በሚያሰጋ ፡ ሁኔታ ፡ ተቃርቧል

**alas!** ወይኔ
Alas! I have no more money. ወይኔ ! ምንም ፡ ገንዘብ ፡ አልተረፈኝም

**albeit** ምንም ፡ እንኳን ፡ ብ + imperfect
Albeit he has failed twice he is not discouraged. ምንም ፡ እንኳን ፡ ሁለቴ ፡ ቢወድቅም ፡ ተስፋ ፡ አልቈረጠም

**album** የፎቶግራፍ ፡ ማኖሪያ
He gave her a photograph album for a present. የፎቶግራፍ ፡ ማኖሪያ ፡ ስጦታ ፡ አደረገላት

**alchemy** [በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ የኬሚስትሪ ፡ ብጤ]

**alcohol**
1. አልኮል. Alcohol is the principal ingredient of beer. አልኮል ፡ ዋናው ፡ የጠላ ፡ ክፍል ፡ ነው
2. የሚያሰክር ፡ መጠጥ. Drinking too much alcohol depraves a person's character. የሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ በብዛት ፡ መጠጣት ፡ የሰውን ፡ ጠባይ ፡ ያበላሻል

**alcoholic** (n.) የአልኮል ፡ ሱሰኛ
Alcoholics must be treated by a doctor. የአልኮል ፡ ሱሰኞች ፡ በሐኪም ፡ መታከም ፡ አለባቸው

**alcoholic** (adj.) አልኮልነት ፡ ያለው
How is the strength of alcoholic beverages measured? አልኮልነት ፡ ያላቸው ፡ መጠጦች ፡ ኀይላቸው ፡ የሚለካው ፡ እንዴት ፡ ነው?

**alcove** ጓዳ
The cupboard is kept in an alcove in the dining room. ቁም ፡ ሣጥኑ ፡ በምግብ ፡ ቤቱ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ ጓዳ ፡ ተቀምጧል

**ale** [የቢራ ፡ ዓይነት]

**alert** (v.) አስጠነቀቀ
He alerted the guards that a visitor was coming. እንግዳ ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡ ዘበኞቹን ፡ አስጠነቀቃቸው
The commander alerted the troops before the enemy attack. ጠላት ፡ ከማጥቃቱ ፡ በፊት ፡ አዛዡ ፡ ወታደሮቹን ፡ አስጠነቀቃቸው

**alert** (n.) ማስጠንቀቂያ
He received the alert in the afternoon. ማስጠንቀቂያው ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ደረሰው

**be on the alert** ንቁ ፡ ሆነ
A soldier must be on the alert. ወታደር ፡ ንቁ ፡ መሆን ፡ አለበት

**alert** (adj.)
1. ንቁ. He is an alert fellow. ንቁ ፡ ሰው ፡ ነው
A good hunting dog is alert to every sound in the field. ጥሩ ፡ የአደን ፡ ውሻ ፡ሜዳው ፡ ውስጥ ፡ ለሚሰማው ፡ ለማንኛውም ፡ ድምፅ ፡ ንቁ ፡ ነው
2. ዝግጁ. The order of the day was to be alert for air attack. ዕለታዊው ፡ ትእዛዝ ፡ ለአየር ፡ ጥቃት ፡ ዝግጁ ፡ ሁኑ ፡ የሚል ፡ ነበር

**algebra** አልጀብራ
Algebra is a form of mathematics. አልጀብራ ፡ የሒሳብ ፡ ዓይነት ፡ ነው

**alias** የሐሰት ፡ ስም
The spy's real name was Harrison, but he sometimes went under the alias of Johnson. የሰላዩ ፡ እውነተኛ ፡ ስም ፡ ሀሪሰን ፡ ነበረ ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ጆንሰን ፡ በሚል ፡ የሐሰት ፡ ስም ፡ ይጠቀም ፡ ነበር

**alibi** [ወንጀል ፡ ተፈጸመበት ፡ በተባለው ፡ ስፍራ ፡ አልነበርኩም ፡ ማለት]

**alien** (n.) የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፤ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ
All aliens must register. የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ (ተወላጆች) ፡ ሁሉ ፡ መመዝገብ ፡ አለባቸው

**alien** (adj.) ባዕድ
A refusal to support one's parents is alien to Ethiopian culture. ወላጆችን ፡ አለመጦር ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ባህል ፡ ባዕድ ፡ ነው

**alienate**
1. አለያየ. His wife alienated him from his friends. ሚስቱ ፡ ከወዳጆቹ ፡ አለያየችው
2. አራቀ. He has alienated his entire family. ቤተ ፡ ሰቡን ፡ በሙሉ ፡ አርቋል

**alight** (v.)
1. አረፈ. The plane alighted. አውሮፕላኑ ፡ አረፈ
The bird alighted on the ground. ወፏ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አረፈች
2. ወረደ. I ran up to him when he alighted from the plane. ከአውሮፕላኑ ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ ሮጬ ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ ዘንድ ፡ ሄድኩ

**(be) alight**
1. ፈካ. His bright face was alight with happiness. ብሩህ ፡ ፊቱ ፡ በደስታ ፡ ፈካ
2. ተንበለበለ. The fire is alight in the hearth. እሳቱ ፡ ምድጃው ፡ ውስጥ ፡ ተንበለበለ

**align** (vt.)
1. አሰለፈ. The officer aligned the soldiers. መኰንኑ ፡ ወታደሮቹን ፡ አሰለፈ
2. ደረደረ. We aligned the chairs along the wall. ወንበሮቹን ፡ በግድግዳው ፡ ጥግ ፡ ደረደርን

**align** (vi.)
1. ተሰለፈ. The troops aligned. ወታደሮቹ ፡ ተሰለፉ
2. ባንድ ፡ መሥመር ፡ ላይ ፡ ተገኘ. This wheel aligns with the other. ይህ ፡ ጎማ ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ ባንድ ፡ መሥመር ፡ ላይ ፡ ይገኛል

**align oneself** ተሰለፈ
Ethiopia aligned herself with the majority on that vote. በዚያ ፡ ጉዳይ ፡ ድምፅ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከብዛኛው ፡ ጋር ፡ ተሰለፈች

**be aligned** ተባበረ
Germany was aligned with Japan in World War II. በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጀርመን ፡ ከጃፓን ፡ ጋር ፡ ተባበረች

**alike**
1. እኩል. This law applies to men and women alike. ይህ ፡ ሕግ ፡ ለወንዶችም ፡ ለሴቶችም ፡ እኩል ፡ ይጸናል
2. አንድ. All music is alike to him. ለሱ ፡ ሁሉም ፡ ዓይነት ፡ ሙዚቃ ፡ አንድ ፡ ነው

**be alike** ተመሳሰለ
These seats are all alike. እነዚህ ፡ መቀመጫዎች ፡ ሁሉ ፡ ይመሳሰላሉ

**treat alike** ባንድ ፡ ዓይን ፡ አየ
We treat all our customers alike. ሁሉንም ፡ ደንበኞቻችንን ፡ ባንድ ፡ ዓይን ፡ እናያቸዋለን

**aliment** ምግብ
Bread, milk, and fish are aliments. ዳቦ ፤ ወተትና ፡ ዓሣ ፡ ምግብ ፡ ናቸው

**alimentary** የአንጀት
Alimentary disturbances ruined his health. የአንጀት ፡ በሽታ ፡ ጤንነቱን ፡ አበላሸው

**alimentary tract** የሆድ ፡ የምግብ ፡ መተላለፊያ
The alimentary tract is subject to diseases. የሆድ ፡ የምግብ ፡ መተላለፊያ ፡ በበሽታ ፡ ሊጠቃ ፡ ይችላል

**alimentation** አመጋገብ
Proper alimentation is important for maintaining health. ጤንነትን ፡ ለመጠበቅ ፡ ተገቢ ፡ አመጋገብ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**alimony** አበል
After the divorce he had to pay alimony to his wife. ከተፋቱ ፡ በኋላ ፡ ለሚስቱ ፡ አበል ፡ መክፈል ፡ ነበረበት

**alive**
1. በሕይወት ፡ ያለ. Who is the greatest man alive? በሕይወት ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ታላቁ ፡ ማን ፡ ነው ?
2. ከነሕይወቱ. Get him dead or alive! ሬሳውን ፤ ሆነ ፡ ከነሕይወቱ ፡ አምጣልኝ
3. ንቁ. John is one of the most alive boys we know. ጆን ፡ ከምናውቃቸው ፡ በጣም ፡ ንቁ ፡ ከሆኑት ፡ ልጆች ፡ አንዱ ፡ ነው

**be alive**
1. በሕይወቱ ፡ አለ. Is he still alive? አሁንም ፡ በሕይወቱ ፡ አለ ?
2. ኖረ. Being dead is better for me than being alive. ለኔ ፡ ከመኖር ፡ ይልቅ ፡ መሞት ፡ ይሻለኛል

**be alive (to)**
1. ዐወቀ. He was alive to the danger of the situation. ስለ ፡ ሁኔታው ፡ አደገኛነት ፡ ያውቅ ፡ ነበር
2. አላለፈም. He is alive to his opportunities. የመጣለትን ፡ ዕድል ፡ አያልፈውም

**be alive with** ተሞላ
The streets were alive with people. መንገዶቹ ፡ በሕዝብ ፡ ተሞልተው ፡ ነበር
*The room is alive with bugs. ክፍሉ ፡ ትኋን ፡ ብቻ ፡ ነው

**keep alive** (vt.) አቆየ
His revengeful actions kept the quarrel alive for years. የበቀል ፡ ተግባሩ ፡ ጠባቸውን ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ አቆይቷል

**keep alive** (vi.) በሕይወት ፡ ቆየ
It is a miracle they kept alive. በሕይወት ፡ መቆየታቸው ፡ ተአምር ፡ ነው

**all** (n., adj.)
1. ሁሉ. He wanted all or nothing. ሁሉን ፡ ካልሆነ ፡ አልፈልግም ፡ አለ
That upsets all my plans. ያ ፡ እቅዴን ፡ ሁሉ ፡ ያቃውሰዋል
2. ሁል + (suffix pronouns). Did you all go? ሁላችሁም ፡ ሄዳችሁ ፡ ነበር ?
3. መላው. Last year, all Ethiopia celebrated the 25th Anniversary of the Restoration. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ መላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሃያ ፡ አምስተኛውን ፡ የነጻነት ፡ በዓል ፡ አከበረ
4. ማንኛው. He has to give up all physical activity for a while. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውንም ፡ አካላዊ ፡ እንቅስቃሴ ፡ መተው ፡ አለበት
5. (= adv.) በሙሉ. My son has appropriated all my ties. ልጄ ፡ ክራቫቶቼን ፡ በሙሉ ፡ ወሰደብኛል

**all** (adv.)
1. በፍጹም. He is all wrong. እሱ ፡ በፍጹም ፡ ተሳስቷል
2. በሚገባ. The men were all ready to start their next job. ሰዎቹ ፡ የሚቀጥለውን ፡ ሥራቸውን ፡ ለመጀመር ፡ በሚገባ ፡ ተዘጋጅተው ፡ ነበር

*If that is all there is to it, I will do it. እንዲህ፡ ከሆነማ ፡ እሠራዋለሁ
*That is all I needed. የፈለግሁት ፡ ይህን ፡ ብቻ ፡ ነው
*The prisoner denied all connection with the crime. እስረኛው ፡ ስለ ፡ ወንጀሉ ፡ ምንም ፡ አላውቅም ፡ ሲል ፡ ካደ

**all along**
1. ምንጊዜም. We knew it all along. ምንጊዜም ፡ እናውቀው ፡ ነበር
2. ሁልጊዜ. We have suspected him all along. ሁልጊዜ ፡ እንደተጠራጠርነው ፡ ነበር
3. ከመጀመሪያ ፡ ጀምሮ. He knew all along that it was a lie. ውሸት ፡ መሆኑን ፡ ከመጀመሪያ ፡ ጀምሮ ፡ ያውቅ ፡ ነበር
*There were trees all along the road. በየመንገዱ ፡ ዛፎች ፡ ነበሩ

**all at once** በድንገት
All at once the wind came up. ነፋስ ፡ በድንገት ፡ መጣ

**all but**
*He all but collapsed. ለመውደቅ ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር

**(be) all for** ፈቃደኛ ፡ ነው
I am all for accepting the prize. ሽልማቱን ፡ ለመቀበል ፡ ፈቃደኛ ፡ ነኝ

**all in all** በጠቅላላው
All in all, he is not a bad fellow. በጠቅላላው ፡ መጥፎ ፡ ሰው ፡ አይደለም

**all kinds of** ማናቸውም ፡ ዓይነት
They sell all kinds of electrical appliances. ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ የኤሌክትሪክ ፡ መሣሪያ ፡ ይሸጣሉ

**all of** ሁል + suffix pronouns
They asked all of us to the party. ሁላችንንም ፡ ለድግሱ ፡ ጋበዙን

**all over** (prep. adv.)
1. በሙሉ ፤ በመላው. He traveled all over the country. አገሩን ፡ በሙሉ ፡ ዞረ
Her brilliance as a piano player was known all over the world. በፒያኖ ፡ ተጫዋችነት ፡ ያላት ፡ ቅልጥፍና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የታወቀ ፡ ነበረ
2. በ - - - ላይ ፡ በሙሉ. He left bread crumbs all over the table. በጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ በሙሉ ፡ ፍርፋሪ ፡ አስቀረ
3. ሁለመናውን. I am aching all over. ሁለመናዬን ፡ ያመኛል
4. መላ ፡ ሰውነቱ. He trembled all over. መላ ፡ ሰውነቱ ፡ ተንቀጠቀጠ

**(be) all over** አለቀ
It is all over. You may go home now. አልቋል ፤ ቤትህ ፡ ለመሄድ ፡ ትችላለህ
*Once the police discovered his identity it was all over with him. ፖሊሶቹ ፡ እሱ ፡ መሆኑን ፡ ካወቁ ፡ የሱ ፡ ነገር ፡ አበቃ ፡ ማለት ፡ ነው

**all that**
1. እስከዚህ. It is not all that bad. እስከዚህ ፡ መጥፎ ፡ አይደለም
2. ይህን ፡ ያህል. It is not all that cold. ይህን ፡ ያህል ፡ ብርድ ፡ አይደለም

**all the better**
*If that's so, all the better. እንዲህ ፡ ከሆነማ ፡ እንዲያውም ፡ የተሻለ ፡ ነው

**all the same**
1. ያው. That's all the same to me. ለኔ ፡ ያው ፡ ነው
2. ቢሆንም. All the same, I want to see it. ቢሆንም ፡ ላየው ፡ እፈልጋለሁ
*His remark was well-meant, but insulting all the same. አስተያየት ፡ የሰጠው ፡ በቅን ፡ መንፈስ ፡ ቢሆንም ፡ ስድብ ፡ መሆኑ ፡ አልቀረም

**as ... as all that** ይህን ፡ ያህል
It is not as difficult as all that. ይህን ፡ ያህል ፡ አስቸጋሪ ፡ አይደለም

**from all over** ከየቦታው
They came from all over. ከየቦታው ፡ መጡ

**in all** በጠቅላላው
How many are there in all? በጠቅላላው ፡ ስንት ፡ አሉ ?

**once and for all** የመጨረሻውን ፡ ነው
I am telling you once and for all, stop it. የምነግርህ ፡ የመጨረሻውን ፡ ነው ፤ ተው
[See also 'after, almost, around, at, for, gone, line, not, once, one, time']

## all-around
1. ሁለ ፡ ገብ ፡ የሆነ. The all-around athlete earned three Olympic gold medals. ሁለ ፡ ገብ ፡ የሆነ ፡ እስፖርተኛ ፡ ሦስት ፡ የኦሊምፒክ ፡ ወርቅ ፡ ኒሻን ፡ አገኘ
2. (= adv.) ፈጽሞ. Our attempt to get control of the meeting was an all-around failure. ስብሰባውን ፡ ለመቈጣጠር ፡ ያደረግነው ፡ ሙከራ ፡ ፈጽሞ ፡ ሳይሳካ ፡ ቀረ

## allay
1. አቃለለ. The doctor allayed his fears. ሐኪሙ ፡ ፍርሃቱን ፡ አቃለለለት
2. አስታገሠ. These pills should allay any pain.

እነዚህ ፡ ኪኒኖች ፡ ማንኛቸውንም ፡ ዓይነት ፡ ሕመም ፡ ያስታግሣሉ

**all clear** ያየር ፡ ወረራ ፡ ማብቃት ፡ ምልክት
The all clear was given at 8 o'clock. ያየር ፡ ወረራው ፡ ማብቃት ፡ ምልክት ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ተሰጠ

**allegation** ቃል ፤ ነገር
The lawyer's allegation was no proof. የጠበቃው ፡ ቃል ፡ ማስረጃ ፡ አልነበረም
He made so many wild allegations that no one will believe him. ብዙ ፡ ከእውነት ፡ የራቁ ፡ ነገሮች ፡ ደረሱ ፡ ስለሚል ፡ ማንም ፡ አያምነውም

**allege** አለ
The man alleges that his watch has been stolen. ሰውዬው ፡ ሰዓቴ ፡ ተሰረቀብኝ ፡ ይላል
He alleged that he had closed the door when he left. ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ ቤቱን ፡ ዘግቼያለሁ ፡ አለ

**alleged** (adj.) የተባለ
The alleged theft never really happened. የተባለው ፡ ስርቆት ፡ በእርግጥ ፡ አልደረሰም

**allegiance**
1. ታማኝነት. In America students pledge allegiance to the flag every morning. የአሜሪካ ፡ ተማሮች ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ለሰንደቅ ፡ ዓላማቸው ፡ ታማኝነታቸውን ፡ ይገልጻሉ
2. ታማኝ ፡ መሆን. The soldiers pledged allegiance to their country. ወታደሮቹ ፡ ላገራቸው ፡ ታማኞች ፡ መሆናቸውን ፡ ገለጹ

**oath of allegiance**
He took his oath of allegiance. ላገሩ ፡ የታማኝነት ፡ መሐላ ፡ ማለ
[See also 'pledge']

**allegory** ምሳሌ
He sought to explain it by means of an allegory. በምሳሌ ፡ አድርጎ ፡ ለመግለጽ ፡ ሞከረ

**allergy** [የሰውነት ፡ አንዳንድ ፡ ምግቦችንና ፡ መድኃኒቶችን ፡ አለመቀበል]

**alleviate**
1. አስታገሠ. He takes aspirin to alleviate the pain. ሥቃዩን ፡ ለማስታገሥ ፡ አስፒሪን ፡ ይውጣል
2. አቃለለ. Food was distributed to alleviate the distress of the starving people. የረኀብተኞቹን ፡ ሰዎች ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ ምግብ ፡ ታደለ

**alley** ጠባብ ፡ መንገድ
There are many alleys in Addis Ababa. አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጠባብ ፡ መንገዶች ፡ አሉ

**alliance** ኅብረት ፤ ስምምነት
The two clans have an alliance. ሁለቱ ፡ ጐሳዎች ፡ ኅብረት ፡ አላቸው
This line of policy seeks security through military alliances. የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ፖሊሲ ፡ ጸጥታን ፡ በወታደራዊ ፡ ስምምነት ፡ ለማስገኘት ፡ የሚፈልግ ፡ ነው

**allied** (adj.)
1. የጦር ፡ ጓደኛ. The allied nations won both World Wars. የጦር ፡ ጓደኞች ፡ መንግሥታት ፡ ሁለቱንም ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ድል ፡ አደረጉ
2. የሚዛመድ. The dog and the wolf are allied animals. ውሻና ፡ ተኩላ ፡ የሚዛመዱ ፡ እንስሳት ፡ ናቸው

**be allied**
1. ተባበረ. This newspaper is allied with three others. ይህ ፡ ጋዜጣ ፡ ከሌሎች ፡ ሦስት ፡ ጋዜጦች ፡ ጋር ፡ የተባበረ ፡ ነው
2. ተስማማ. The conservatives and the clergy were allied on the question of church schools. ለውጥ ፡ የማይፈልጉትና ፡ ቀሳውስቱ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ጉዳይ ፡ ተስማምተው ፡ ነበር

**allocate** ደለደለ
He allocated the money fairly. ገንዘቡን ፡ በተገቢ ፡ አኳኋን ፡ ደለደለ

**allot** (allotted)
1. መደበ. He allotted ten million dollars for education. ዐሥር ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ ለትምህርት ፡ መደበ
2. ሰጠ. The teacher allotted work to each student. አስተማሪው ፡ ለያንዳንዱ ፡ ተማሪ ፡ ሥራ ፡ ሰጠ
3. ከፋፈለ (ተከፋፈለ). The profits have all been allotted. ትርፉ ፡ በሙሉ ፡ ተከፋፍሏል

**all-out**
1. ሰፊ. An all-out effort is needed to wipe out illiteracy. መሀይምነትን ፡ ለማጥፋት ፡ ሰፊ ፡ ጥረት ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል
2. ያልተቈጠበ. He made an all-out effort to climb the wall. ግድግዳውን ፡ ለመውጣት ፡ ያልተቈጠበ ፡ ጥረት ፡ አደረገ

**allow**
1. ፈቀደ. How much time will he allow him for completing the work? ሥራውን ፡ ለመጨረስ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይፈቅድለታል?

2. **አስቻለ**. The precision of this instrument allows us to measure very small things. የዚህ ፡ መሣሪያ ፡ ትክክለኛነት ፡ በጣም ፡ ጥቃቅን ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ለመለካት ፡ ያስችለናል

3. **መደበ**. How much should I allow for traveling expenses? ለመጓጓዣ ፡ ወጪ ፡ ስንት ፡ መመደብ ፡ አለብኝ ?

4. **ተቀበለ**. The International Court of Justice allowed the Ethiopian claim. የዓለም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥያቄ ፡ ተቀበለ

5. **ሰጠ**. He does not allow himself a minute's rest. ለራሱ ፡ ያንድ ፡ ደቂቃ ፡ ዕረፍት ፡ አይሰጥም

**allow for አሰፈ**

This teacher is very stern. He does not allow for mistakes. ይህ ፡ መምህር ፡ በጣም ፡ ጥብቅ ፡ ነው ። ስሕተትን ፡ አያልፍም

*The dress was made larger to allow for shrinking. ልብሱ ፡ ሲኰማተር ፡ እንዳይጠብ ፡ በማለት ፡ ለቀቅ ፡ ተደርጎ ፡ ተሰፋ

## allowance

1. **አበል**. How much travel allowance do you get from your company? ከኩባንያህ ፡ የምታገኘው ፡ የጉዞ ፡ አበል ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?

2. **ልዩ ፡ ወጪ**. How much allowance do you get a week? በሳምንት ፡ ልዩ ፡ ወጪ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ታገኛለህ ?

**make allowance for**

1. **ግምት ፡ ውስጥ ፡ አስገባ**. Indeed, we must make allowance for his youth. ልጅነቱን ፡ ግምት ፡ ውስጥ ፡ ማስገባት ፡ አለብን

2. **አስተያየት ፡ አደረገ**. We made allowance for Jack's inexperience. ለጃክ ፡ የልምምድ ፡ እጦት ፡ አስተያየት ፡ አደረግን

**no allowance መግባት ፡ ክልክል ፡ ነው**

No allowance except for authorized personnel. ከተፈቀደላቸው ፡ ሠራተኞች ፡ በስተቀር ፡ መግባት ፡ ክልክል ፡ ነው

## allowed, not ~ ክልክል

The boss served notice that smoking is not allowed. አለቅዬው ፡ ማጨስ ፡ ክልክል ፡ መሆኑን ፡ አስታወቀ

## alloy ቅይጥ

This is not pure gold; it is an alloy. ይህ ፡ ንጹሕ ፡ ወርቅ ፡ አይደለም ። ጥቂት ፡ ቅይጥ ፡ አለበት

## all right

1. **አጥጋቢ**. His work is all right. ሥራው ፡ አጥጋቢ ፡ ነው

2. **እሺ**. He said, "All right, I will do it". እሺ ። እሠራዋለሁ ፡ አለ

3. **ደኅና**. Don't worry; it will be all right. አትጨነቅ ። ደኅና ፡ ይሆናል

4. **በደኅና**. I hope the books arrived all right. መጽሐፎቹ ፡ በደኅና ፡ እንደደረሱ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ

*Is that all right with you? በዚህ ፡ ትስማማለህ?

## all-round በሙሉ ፡ የተዋጣለት

He's an all-round sportsman. በሙሉ ፡ የተዋጣለት ፡ እስፖርተኛ ፡ ነው

## allude አነሣ

Don't allude to his wife's death when you see him. ስታገኘው ፡ የሚስቱን ፡ ሞት ፡ አታንሣበት

## allure ስሜት ፡ ሳበ

The sea allures him. ባሕር ፡ ስሜቱን ፡ ይስበዋል

## allusion የሚነካ ፡ ነገር

There were certain allusions to me in his words. ከተናገረው ፡ ውስጥ ፡ እኔን ፡ የሚነካ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ነበር

**make allusions አነሣ**

Don't make allusions to his wife's death. የሚስቱን ፡ ሞት ፡ አታንሣበት

## ally v. (allied), ~ oneself ተባበረ

Our country will ally itself with another to protect its people. አገራችን ፡ ሕዝቧን ፡ ለመከላከል ፡ ስትል ፡ ከሌላ ፡ አገር ፡ ጋር ፡ ትተባበራለች

## ally n. (allies) ጓደኛ ። የጦር ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ጓደኛ

We need to find an ally if we are going to win. እንድናሸንፍ ፡ ከፈለግን ፡ ጓደኛ ፡ ማግኘት ፡ አለብን

France and England were allies in the war. በጦርነቱ ፡ እንግሊዝና ፡ ፈረንሳይ ፡ የጦር ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ጓደኞች ፡ ነበሩ

## almighty ኀያል

He prayed to almighty God to save him. ኀያሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲያድነው ፡ ጸለየ

## almond ለውዝ

## almost

1. **ል + imperfect + ነበር**. He slipped and almost fell. አዳልጦት ፡ ሊወድቅ ፡ ነበር

2. **ል + imperfect + ምንም ፡ አልቀረም**. The smoke almost suffocated me. ጢሱ ፡ ሊያፍነኝ ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር

*I almost said that he was a liar. እሱ ፡ ዋሾ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ቃጣኝ

**be almost** ምንም ፡ ያህል ፡ አልቀረም
It is almost time to start. ለመጀመር ፡ ጊዜው ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልቀረም
[See also 'alone, nothing']

## alms ምጽዋት
The hands of the beggar were outstretched for alms. ለማኙ ፡ ምጽዋት ፡ ለመቀበል ፡ እጁን ፡ ዘረጋ

## (be) aloft ሰማይ ፡ ላይ ፡ ነበረ
The planes were aloft at the time of the air raid. ያየር ፡ ወረራ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ አይሮፕላኖቹ ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ ነበሩ

## alone
1. ብቻ. We are not alone in thinking that the situation is grave. ሁኔታው ፡ አስጊ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ የምናምን ፡ እኛ ፡ ብቻ ፡ አይደለንም
2. ብቻ + (suffix pronouns). Do you live alone? ብቻህን ፡ ትኖራለህ ?
Meat alone is not the best food for children. ሥጋ ፡ ብቻውን ፡ ለልጆች ፡ የተሻለ ፡ ምግብ ፡ አይደለም

**almost all alone** ተነጥሎ
The house stands on the mountainside almost all alone. ቤቱ ፡ ተነጥሎ ፡ በተራራው ፡ ጥጋት ፡ ላይ ፡ ይገኛል

**stand alone** ወደር ፡ የለውም
He stands alone among the scholars on Ethiopia. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሚያውቁት ፡ ሊቃውንት ፡ መካከል ፡ ወደር ፡ የለውም
[See also 'leave, let']

## along
1. በ - - - ዳር. We walked along the shore. በባሕሩ ፡ ዳር ፡ ተራመድን
2. በ - - - መሠረት. Along the lines just noted, I suggest we start the new project. አሁን ፡ በተገለጹት ፡ ሐሳቦች ፡ መሠረት ፡ አዲስ ፡ እቅድ ፡ እንድንጀምር ፡ አሳስባለሁ
3. በ - - - ጥግ. We aligned the chairs along the wall. ወንበሮቹን ፡ በግድግዳው ፡ ጥግ ፡ ደረደርን
*We walked along the road for a mile or so. መንገዱን ፡ ይዘን ፡ አንድ ፡ ማይል ፡ ያህል ፡ ተጓዝን

**along with** ከ - - - ጋር
He planned the project along with his associates. እቅዱን ፡ ከሽርካዎቹ ፡ ጋር ፡ አዘጋጀ

**somewhere along** በ - - - ላይ
Somewhere along the journey I lost my hat. በመንገዴ ፡ ላይ ፡ ባርኔጣዬ ፡ ጠፋብኝ
[See also 'all, come, get, go, line, move, take']

## alongside
1. ከ - - - ጐን ፤ ጐን. This tree will grow alongside the eucalyptus tree. ይህ ፡ ዛፍ ፡ ከባሕር ፡ ዛፍ ፡ ጐን ፡ ያድጋል
He parked his car alongside the building. መኪናውን ፡ ሕንጻው ፡ ጐን ፡ አቆመ
2. በ - - - ዳርቻ. There is a bank of earth alongside the street. በመንገዱ ፡ ዳርቻ ፡ ያፈር ፡ ክምር ፡ አለ

## (be) aloof
*Because of her shyness, she has the reputation of being aloof. ዓይን ፡ አፋር ፡ ስለሆነች ፡ በገለልተኛነቷ ፡ የታወቀች ፡ ናት

**hold aloof** ፈንጠር ፡ ብሎ ፡ ቆመ
He held aloof from the crowd. ከሕዝቡ ፡ ፈንጠር ፡ ብሎ ፡ ቆመ

**stand aloof**
1. ዝም ፡ ብሎ ፡ በገለልተኛነት ፡ ቆየ. Their leaders stood aloof throughout the crisis. በችግሩ ፡ ጊዜ ፡ መሪዎቻቸው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ በገለልተኝነት ፡ ቆዩ
2. ተገሎ ፡ ቆመ. One boy stood aloof from the others. አንድ ፡ ልጅ ፡ ከሌሎቹ ፡ ተገሎ ፡ ቆመ

## aloud
1. ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ. You may whisper in the library but do not talk aloud. ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ውስጥ ፡ ልታንሾካሹኩ ፡ ትችላላችሁ ፤ ግን ፡ ድምፃችሁን ፡ ከፍ ፡ አድርጋችሁ ፡ አትነጋገሩ
2. ጮክ ፡ ብሎ. He read the story aloud. ታሪኩን ፡ ጮክ ፡ ብሎ ፡ አነበበ

## alphabet ፊደል
The Amharic alphabet is different from the Arabic alphabet. ያማርኛ ፡ ፊደል ፡ ከዐረብኛ ፡ ፊደል ፡ የተለየ ፡ ነው

## alphabetical የፊደል
Put the names in alphabetical order. ስሞቹን ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ አስገባቸው

## alphabetize በፊደል ፡ ተራ ፡ አደረገ
Please alphabetize this list of names for me. ይህን ፡ የስም ፡ ዝርዝር ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ አድርግልኝ

**already**
1. አስቀድሞ. I have already eaten. አስቀድሜ ፡ በልቻለሁ
When he asked for permission to use the car he had already used it. መኪናዋን ፡ ለመውሰድ ፡ ሲጠይቅ ፡ አስቀድሞ ፡ ተጠቅሞባት ፡ ነበር
2. ቀደም ፡ ሲል. Your agent has already called on me. ወኪልህ ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ ጠይቆኛል
3. ከዚህ ፡ ቀደም. I've burned my fingers once already. ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተሳስቻለሁ
4. ድሮ. We have already used up our canned food. የቆርቆሮ ፡ ምግባችንን ፡ ድሮ ፡ ጨረስነው
5. ገና ፡ ድሮ. Is it ten o'clock already? ገና ፡ ድሮ ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ሞላ ?

**also** —ም
May I have some of that also? ከዚያም ፡ ትንሽ ፡ ልውሰድ ?
[See also 'not']

**altar**
1. መሠዊያ. The priest placed the Bible on the altar. ቄሱ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱሱን ፡ መሠዊያው ፡ ላይ ፡ አኖረው
2. የመሥዋዕት ፡ ማቅረቢያ ፡ ቦታ. Moses went up to the altar. ሙሴ ፡ ወደ ፡ መሥዋዕት ፡ ማቅረቢያው ፡ ቦታ ፡ ወጣ

**alter** ለወጠ
The death of the President altered the country's history. የፕሬዚዳንቱ ፡ ሞት ፡ የአገሪቱን ፡ ታሪክ ፡ ለወጠው

**have altered** አስቀየረ
I will have to have the collar of this shirt altered. የዚህን ፡ ሸሚዝ ፡ ኮሌታ ፡ ማስቀየር ፡ አለብኝ
*I will have my pants altered. ሱሪው ፡ እንዲስተካከልልኝ ፡ እፈልጋለሁ

**alteration**
1. ለውጥ. Not much alteration is visible in the village. በመንደሪቷ ፡ ውስጥ ፡ ብዙም ፡ ለውጥ ፡ አይታይም
2. ማስተካከያ. No charge for alteration. ለማስተካከያ ፡ አይከፈልም

**altercate** ተጨቃጨቀ
They altercated in the Senate for days on end. በሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ ተጨቃጨቁ

**altercation** ንትርክ
The altercation between the two drivers led to blows. የሁለቱ ፡ መኪና ፡ ነጂዎች ፡ ንትርክ ፡ ከዱላ ፡ አደረሳቸው

**have an altercation** ተጨቃጨቀ
The two teams had an altercation over the umpire's decision. ሁለቱ ፡ ቡድኖች ፡ ስለ ፡ አሚዋቹ ፡ ውሳኔ ፡ ተጨቃጨቁ

**alternate** (vt.)
1. አፈራረቀ. He alternates work with pleasure. መሥራትና ፡ መደሰትን ፡ ያፈራርቃል
2. እያፈራረቀ + (verb). Most modern farmers alternate wheat with barley. አብዛኞቹ ፡ ዘመናውያን ፡ ገበሬዎች ፡ ስንዴና ፡ ገብስ ፡ እያፈራረቁ ፡ ይዘራሉ

**alternate** (vi.)
1. ተፈራረቀ. Hot days alternate with cool days in Addis Ababa. አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ሞቃትና ፡ ቀዝቃዛ ፡ ቀናት ፡ ይፈራረቃሉ
2. (= adv.) በተራ ፡ በተራ. Mary and her sister will alternate in setting the table. ሜሪና ፡ እኅቷ ፡ በተራ ፡ በተራ ፡ ጠረጴዛውን ፡ ያዘጋጃሉ

**alternate** (n.) ምትክ
An alternate was sent in his place. በሱ ፡ ቦታ ፡ ምትክ ፡ ተላከ

**alternate** (adj.)
1. ተፈራራቂ. Tom and Harry do work on alternate days. ቶምና ፡ ሃሪ ፡ በተፈራራቂ ፡ ቀን ፡ ይሠራሉ
2. የተፈራረቁ. The skirt has alternate stripes of blue and yellow. ቀሚሱ ፡ የተፈራረቁ ፡ ሰማያዊና ፡ ቢጫ ፡ መሥመሮች ፡ አሉት

**alternation** ማፈራረቅ
Alternation of crops prevents damage to the soil. ሰብልን ፡ ማፈራረቅ ፡ አፈርን ፡ ከጉዳት ፡ ይጠብቃል

**alternative** (n.) ሌላ ፡ አማራጭ
Is there no alternative to what you propose? ላቀረብከው ፡ ሐሳብ ፡ ሌላ ፡ አማራጭ ፡ የለውም ?

**have the alternative** ምርጫ ፡ አለው
You have the alternative of riding or walking. በፈረስ ፡ ወይም ፡ በእግርህ ፡ የመሄድ ፡ ምርጫ ፡ አለህ

**alternative** (adj.) አማራጭ
There are several alternative routes from New York to Chicago. ከኒውዮርክ ፡ ወደ ፡ ቺካጎ ፡ የሚወስዱ ፡ ብዙ ፡ አማራጭ ፡ መንገዶች ፡ አሉ

**alternatively** እያፈራረቁ
One must run and rest alternatively to cover a long distance quickly. አንድ ፡ ረዥም ፡ ጉዳናን ፡ በፍጥነት ፡ ለማቋረጥ ፡ እያፈራረቁ ፡ መሮጥና ፡ ማረፍ ፡ ያስፈልጋል

**although** ብ + imperfect + ም ፤ ብ + imperfect + ም ፡ እንኳ
I will be there, although I have very little time. ያለኝ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ ቢሆንም ፡ ከዚያ ፡ እገኛለሁ
I don't know him well, although he lives next door. ጐረቤቴ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ብዙ ፡ አላውቀውም

**altitude** ከፍታ ፤ ተራራማነት
It is difficult to breathe at this altitude. በዚህ ፡ ከፍታ ፡ ለመተንፈስ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
Ethiopia's tropical climate is modified by the altitude. የኢትዮጵያ ፡ ሞቃት ፡ ያየር ፡ ንብረት ፡ ባገሪቱ ፡ ተራራማነት ፡ ቀዝቀዝ ፡ ይላል

**high altitude** ከፍታ
Because of the high altitude he showed signs of distress. ከከፍታው ፡ የተነሣ ፡ የመሠቃየት ፡ ምልክት ፡ ታየበት

**altogether**
1. በጠቅላላው. Altogether there are thirty books. በጠቅላላው ፡ ሠላሳ ፡ መጽሐፎች ፡ አሉ
2. በፍጹም. He is altogether innocent of the charge. እሱ ፡ ከቀረበበት ፡ ክስ ፡ በፍጹም ፡ ንጹሕ ፡ ነው
I don't altogether agree with him. ከሱ ፡ ጋር ፡ በፍጹም ፡ አልስማማም

**altruism** ለሌሎች ፡ ጥቅም ፡ ማሰብ
Altruism is the opposite of egoism. ለሌሎች ፡ ጥቅም ፡ ማሰብ ፡ ራስን ፡ የመውደድ ፡ ተቃራኒ ፡ ነው

**alumnus** የቀድሞ ፡ ምሩቅ
An alumnus of our school became the principal. የትምህርት ፡ ቤታችን ፡ የቀድሞ ፡ ምሩቅ ፡ የሥራ ፡ መሪ ፡ ሆነ

**always**
1. ሁልጊዜ ፤ ሁሌ. I am not always at home on Sundays. እሑድ ፡ እሑድ ፡ ሁልጊዜ ፡ (ሁሌ) ፡ እቤት ፡ አልገኝም
2. ምንጊዜም. I am always glad to oblige you. ልታዘዝህ ፡ ምንጊዜም ፡ ፈቃደኛ ፡ ነኝ
3. ዘወትር. The scar will always be visible and will never disappear. ጠባሳ ፡ ምንጊዜም ፡ ስለማይጠፋ ፡ ዘወትር ፡ ይታያል

**amalgamate** ተቀላቀለ
The two companies amalgamated to form one big company. ሁለቱ ፡ ኩባንያዎች ፡ ተቀላቅለው ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ኩባንያ ፡ ሆኑ

**amalgamation** ድብልቅ
Our nation is an amalgamation of many different races. ሀገራችን ፡ የብዙ ፡ ጐሳዎች ፡ ድብልቅ ፡ ናት

**amass** አከማቸ
The miser amassed a fortune for himself. ጨቁ ፡ ለራሱ ፡ ሀብት ፡ አከማቸ

**amateur** አማተር
She is an amateur painter. አማተር ፡ ሠዓሊ ፡ ናት

**amaze** አስደነቀ
Your ignorance in money matters amazes me. ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ጉዳይ ፡ አለማወቅህ ፡ ያስደንቀኛል

**be amazed** ተደነቀ
I was amazed at his indifference. በግዴለሽነቱ ፡ ተደንቄ ፡ ነበር

**amazement** መገረም
He looked at me in amazement. በመገረም ፡ ተመለከተኝ
*To my amazement, he came to see me. መምጣቱ ፡ ገረመኝ

**amazing** የሚያስደንቅ
Ethiopia has made amazing progress. ኢትዮጵያ ፡ የሚያስደንቅ ፡ እርምጃ ፡ አድርጋለች

**be amazing** አስደነቀ ፤ ገረመ
It is amazing how fast he learned Amharic. አማርኛ ፡ እንዴት ፡ በፍጥነት ፡ እንደተማረ ፡ ያስደንቃል ፡ (ይገርማል)

**ambassador** አምባሳደር
The Brazilian ambassador came to Addis Ababa. የብራዚል ፡ አምባሳደር ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጡ

**amber** ብሩህ ፡ ቢጫ
The glass has an amber color. መስተዋቱ ፡ ብሩህ ፡ ቢጫ ፡ ቀለም ፡ አለው

**ambiguity** አሻሚነት
His statement is full of ambiguity. የሰጠው ፡ መግለጫ ፡ አሻሚነት ፡ ይበዛዋል

**ambiguous**
1. አሻሚ. His statements on financial problems are ambiguous. ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ችግር ፡ የሰጠው ፡ መግለጫ ፡ አሻሚ ፡ ነው
2. ግራ ፡ የሚያገባ. He was left in an ambiguous position by his friend's failure to appear and help him. ወዳጁ ፡ መጥቶ ፡ ሳይረዳው ፡ በመቅረቱ ፡ ግራ ፡ በሚያገባ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ወደቀ

**ambition**
1. ምኞት. His ambition is to become prime minister. ምኞቱ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ለመሆን ፡ ነው
2. ፍላጎት. He has plenty of drive and ambition. ብዙ ፡ ትጋትና ፡ ፍላጎት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**ambitious**
1. ጉጉ. The student is ambitious for knowledge. ተማሪው ፡ ለዕውቀት ፡ ጉጉ ፡ ነው
2. በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ. He has an ambitious plan for building a plane. አውሮፕላን ፡ ለመሥራት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እቅድ ፡ አለው
3. ከፍተኛ. He has an ambitious program for eliminating the slums. ደሳሳ ፡ ጎጆ ፡ ያለበትን ፡ ሰፈር ፡ ለማስወገድ ፡ ከፍተኛ ፡ እቅድ ፡ አለው

**be ambitious** በጣም ፡ ተመኘ
John is ambitious to get through high school in two years. ጆን ፡ ሁለተኛ ፡ ደረጃን ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ለመጨረስ ፡ በጣም ፡ ይመኛል

**ambivalence** ማመንታት
His ambivalence made the final decision of the committee impossible. ማመንታቱ ፡ ደርጉ ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ እንዳይሰጥ ፡ አደረገው

**(be) ambivalent**
*She is ambivalent about going to the party. ወደ ፡ ፓርቲው ፡ መሄድ ፡ አለመሄዷን ፡ አልቈረጠችም

**amble**
1. ተንጐራደደ. The tardy students ambled into the classroom. ዳተኞቹ ፡ ተማሪዎች ፡ እየተንጐራደዱ ፡ ወደ ፡ ክፍል ፡ ገቡ
2. አዘገመ. The mule ambled along the rocky path. በቅሎዋ ፡ በኰረኰንቹ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ አዘገመች

**ambulance** አምቡላንስ
This man is hurt. Call an ambulance! ይህ ፡ ሰው ፡ ተጐድቷል ። አምቡላንስ ፡ ይጠራ

**ambush** (v.) አድፍጦ ፡ ወጋ
The Viet Cong ambushed another government patrol. ቪዬት ፡ ኮንጎች ፡ ሌላ ፡ የመንግሥቱን ፡ ጠር ፡ ጓድ ፡ አድፍጠው ፡ ወጉ

**ambush** (n.) ያደፈጠበት ፡ ቦታ ። ደፈጣ
They lured the enemy into an ambush. ጠላትን ፡ አታለው ፡ ካደፈጡበት ፡ ቦታ ፡ አስገቡት
They were killed in an ambush. በደፈጣ ፡ ተገደሉ

**lay in ambush** አድፍጦ ፡ ቆየ
The soldiers lay in ambush for many hours. ወታደሮቹ ፡ ለብዙ ፡ ሰዓቶች ፡ አድፍጠው ፡ ቆዩ

**place in ambush** እንዲያደፍጥ ፡ አደረገ
The general placed his troops in ambush in the woods. ጄኔራሉ ፡ ወታደሮቹ ፡ ጫካው ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ እንዲያደፍጡ ፡ አደረገ

**ameliorate** (vt.) አሻሻለ
He promulgated laws to ameliorate living conditions. የኑሮን ፡ ሁኔታ ፡ ለማሻሻል ፡ ሕግ ፡ አወጣ
The agency is trying to ameliorate the conditions of starving farmers. ድርጅቱ ፡ በረኃብ ፡ የሚሠቃዩትን ፡ ገበሬዎች ፡ ሁኔታ ፡ ለማሻሻል ፡ በመጣጣር ፡ ላይ ፡ ነው

**ameliorate** (vi.) ተሻሻለ
Our living conditions will ameliorate soon. የኑሯችን ፡ ሁኔታ ፡ በቅርቡ ፡ ይሻሻላል

**amen** አሜን
At the end of the prayer everybody said "amen". ከጸሎቱ ፡ በኋላ ፡ ሁሉም ፡ ሰው ፡ አሜን ፡ አለ

**(be) amenable** ተጠያቂ ፡ ሆነ
People living in a country are amenable to its laws. ባንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝቦች ፡ በሕጋቸው ፡ ተጠያቂ ፡ ይሆናሉ
*A reasonable person is amenable to persuasion. አስተዋይን ፡ ሰው ፡ ለማግባባት ፡ ይቻላል

**amend** አሻሻለ
They intend to amend the constitution. ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ለማሻሻል ፡ ያስባሉ

**amendment** የማሻሻያ ፡ ሐሳብ
He proposed an amendment to the constitution. ለሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የማሻሻያ ፡ ሐሳብ ፡ አቀረበ

**amends** ካሳ
The court ordered that amends be made to the woman. ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለሴትዮዋ ፡ ካሳ ፡ እንዲከፈል ፡ አዘዘ

**make amends for** ሸፈነ(ለት)
His letter makes amends for his rudeness. የጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ብልግናውን ፡ ይሸፍንለታል

**amenity** ተስማሚነት
The amenity of Addis Ababa's climate will attract tourists. ያዲስ ፡ አበባ ፡ ያየር ፡ ንብረት ፡ ተስማሚነት ፡ አገር ፡ ጎብኚዎችን ፡ ይስባል

**America** አሜሪካ

**American** አሜሪካዊ ፤ አሜሪካን

**Amharic** አማርኛ
Amharic is the national language of Ethiopia. አማርኛ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ብሔራዊ ፣ ቋንቋ ፣ ነው

**amiable** ተወዳጅ
He is an amiable person and everyone knows him. ተወዳጅ ፣ ሰው ፣ ስለሆነ ፣ ማንም ፣ ያውቀዋል

**amicable**
1. የወዳጅነት. They had an amicable discussion. የወዳጅነት ፣ ውይይት ፣ አደረጉ
2. የሰላም. Instead of fighting the two nations settled their quarrels in an amicable way. ሁለቱ ፣ አገሮች ፣ በመካከላቸው ፣ ስላለው ፣ አለመግባባት ፣ በጠብ ፣ ሳይሆን ፣ በሰላም ፣ መንገድ ፣ ከስምምነት ፣ ደረሱ

**amid, amidst** በ - - - መሀል
Only one column stood amid(st) the ruins. በፍራሹ ፣ መሃል ፣ አንድ ፣ ዐምድ ፣ ብቻ ፣ ቆሟል

**amiss**
1. (= n.) ጉድለት. The doctor examined him and found nothing amiss. ሐኪሙ ፣ መርምሮት ፣ ምንም ፣ ጉድለት ፣ አላገኘበትም
2. (= n.) ያልሆነ ፣ ነገር ፣ መሆን. On entering his house he at once perceived that something was amiss. ቤቱ ፣ ውስጥ ፣ ሲገባ ፣ አንድ ፣ ያልሆነ ፣ ነገር ፣ መሆኑ ፣ ወዲያውኑ ፣ ገባው

**feel amiss** ቅር ፣ አለ(ው)
Don't feel amiss if I criticize your work. ሥራህን ፣ ብነቅፍ ፣ ቅር ፣ አይበልህ

**go amiss** ጥፋት ፣ አደረገ
She certainly went amiss in quitting school. ትምህርቷን ፣ በማቋረጧ ፣ ጥፋት ፣ አድርጋለች

**take it amiss** ቅር ፣ አለ(ው)
Don't take it amiss if I criticize your work. ሥራህን ፣ ብነቅፍ ፣ ቅር ፣ አይበልህ

**amity** ወዳጅነት
The United States and Canada have lived in amity for many years. አሜሪካና ፣ ካናዳ ፣ ለብዙ ፣ ዓመታት ፣ በወዳጅነት ፣ ኖረዋል

**ammunition**
1. ጥይት. The soldiers ran out of ammunition. ወታደሮቹ ፣ ጥይት ፣ አለቀባቸው
2. መሣሪያ. The discovery gave him ammunition in his campaign. አዲስ ፣ ያገኘው ፣ ነገር ፣ ለውድድሩ ፣ መሣሪያ ፣ ሆነው

**amnesia** [በአንጎል ፣ መጐዳት ፣ ምክንያት ፣ የሚመጣ ፣ የማስታወስን ፣ ኀይል ፣ የሚያሳጣ ፣ ሕመም]

**amnesty** ምሕረት
The Emperor declared an amnesty for the rebels. ንጉሠ ፣ ነገሥቱ ፣ ለአጋሚዶቹ ፣ ምሕረት ፣ የሚያደርጉላቸው ፣ መሆናቸውን ፣ አስታወቁ

**amoeba** አሜባ

**among**
1. በ--- መሀከል. Don't be afraid to express your opinion. You are among friends. ሐሳብህን ፣ ለመግለጽ ፣ አትፍራ ፤ በወዳጅ ፣ መሀከል ፣ ነህ
2. መሃል. There were many nice people among them. እነሱ ፣ መሃል ፣ ብዙ ፣ ጥሩ ፣ ሰዎች ፣ ነበሩ
3. ከ - - - ውስጥ. You are only one among the many who need help. እርዳታ ፣ ከሚያስፈልጋቸው ፣ ከብዙዎቹ ፣ ውስጥ ፣ አንዱ ፣ ነህ
4. በ - - - ዘንድ. He is popular among the masses. በሕዝቡ ፣ ዘንድ ፣ የተወደደ ፣ ነው
5. በ - - - ዙሪያ. Bees droned among the flowers. ንቦች ፣ ባበባው ፣ ዙሪያ ፣ አንበነቡ
*London is among the largest cities of the world. ለንደን ፣ ከዓለም ፣ ታላላቅ ፣ ከተሞች ፣ አንዷ ፣ ነች

**among them** ለጋራ
They had less than ten dollars among them. ለጋራ ፣ ከሥር ፣ ብር ፣ የሚያንስ ፣ ነበራቸው

**among -selves**
1. በመካከል + (suffix pronoun). We decided it among ourselves. በመካከላችን ፣ ወሰንን
2. እርስ ፣ በርስ + (suffix pronoun). They don't even agree among themselves. እርስ ፣ በርሳቸው ፣ እንኳን ፣ አይስማሙም
[See also 'other']

**amongst** ከ - - - መሀከል
I found the paper amongst my notebooks. ወረቀቱን ፣ ከደብተሮቼ ፣ መሀከል ፣ አገኘሁት

**amoral** ግብረ ፣ ገብነት ፣ የጐደለው ፣ ሰው
The killer is completely amoral. ነፍስ ፣ ገዳዩ ፣ ፍጹም ፣ ግብረ ፣ ገብነት ፣ የጐደለው ፣ ሰው ፣ ነው

**amorous** ፍቅርን ፣ የሚገልጽ
His amorous behavior pleased her. ፍቅርን ፣ የሚገልጸው ፣ ሁኔታው ፣ አስደሰታት

**become amorous** በፍቅር ፣ ተማረከ
One look at her and he became amorous. አንዴ ፣ አይቷት ፣ በፍቅር ፣ ተማረከ

**amorphous** ቅርጽ ፣ ቢስ
The amorphous clay became a vase. ቅርጽ ፣ ቢስ ፣ የነበረው ፣ ሸክላ ፣ ጽዋ ፣ ሆነ

**amortize** እየከፈለ ፣ ጨረሰ
He amortized the loan over a ten-year period.

ብድሩን ፡ ባሥር ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ እየከፈለ ፡ ጨረሰ

**amount** (v.), ~ **to**

1. ሆነ. His debts amount to 50 dollars. ዕዳው ፡ ኀምሳ ፡ ብር ፡ ይሆናል
How much does the bill amount to? ሒሳቡ ፡ ስንት ፡ ይሆናል?
2. ተቈጠረ. Riding on the bus without paying amounts to cheating. በአውቶቡስ ፡ ሳይከፍሉ ፡ መሄድ ፡ ከማጭበርበር ፡ ይቈጠራል

**does not amount to much** እምብዛም ፡ ነው
His knowledge of Amharic doesn't amount to much. የሱ ፡ ያማርኛ ፡ ችሎታ ፡ እምብዛም ፡ ነው

**amount** (n.)

1. መጠን. What is the amount? መጠኑ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው?
2. ዋጋ. I paid the full amount. ሙሉ ፡ ዋጋውን ፡ ከፈልኩ
3. ብዛት. The amount of evidence against him is great. በሱ ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ የመረጃ ፡ ብዛት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው

**no amount of** ምንም ፡ ያህል + negative verb
No amount of discipline could lessen his exuberance. የተነቃቃውን ፡ መንፈሱን ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ቁጥጥር ፡ አይቀንሰውም

**the whole amount** ሁሉ
I ordered 50 pens for the class and I need the whole amount right away. ለክፍሉ ፡ ኀምሳ ፡ ብዕር ፡ አዝዤ ፡ ነበር ፡ ሁሉንም ፡ አሁኑኑ ፡ እፈልጋለሁ
[See also 'inordinate, like']

**amphibious** በየብስም ፡ በውኃም ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር
The frog is an amphibious animal. እንቁራሪት ፡ በየብስም ፡ በውኃም ፡ ውስጥ ፡ የምትኖር ፡ ናት

**ample**

1. በቂ. Five dollars will be ample for my needs. ለፍላጎቴ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ በቂ ፡ ነው
2. ሰፊ. The ample room held all the furniture. ሰፊው ፡ ክፍል ፡ የቤት ፡ እቃውን ፡ በሞላ ፡ ያዘ

**ample supply of** በቂ
Take an ample supply of food for a day's journey! ላንድ ፡ ቀን ፡ ጉዞ ፡ በቂ ፡ ምግብ ፡ ያዝ

**amplifier** ድምፅ ፡ ማጉያ
The amplifier broke down in the middle of his speech. በንግግሩ ፡ መሀከል ፡ ድምፅ ፡ ማጉያው ፡ ተበላሸ

**amplify**

1. አጐላ. He used a loudspeaker to amplify his voice. ድምፁን ፡ ለማጐላት ፡ በድምፅ ፡ ማጉያው ፡ ተጠቀመ
2. አብራራ. Will you please amplify that statement. የተናገርከውን ፡ እስቲ ፡ አብራራ
3. በሚገባ ፡ ዘረዘረ. The preacher amplified on the theme. ሰባኪው ፡ አርእስቱን ፡ በሚገባ ፡ ዘረዘረ

**amplitude** ከፍተኛነት
The amplitude of his generosity is the subject of many songs. የለጋስነቱ ፡ ከፍተኛነት ፡ የብዙ ፡ ዘፈኖች ፡ አርእስት ፡ ነው

**amply**
*You will be amply rewarded. ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ይከፈልሃል
*They were amply supplied with food. በቂ ፡ ምግብ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ነበር

**amputate** ቈረጠ
The doctor amputated his leg. ሐኪሙ ፡ እግሩን ፡ ቈረጠው

**amulet** ክታብ
She hung an amulet around her neck. አንገቷ ፡ ላይ ፡ ክታብ ፡ አንጠለጠለች

**amuse**

1. አስደሰተ. That amuses me very much. ይህ ፡ በጣም ፡ ያስደስተኛል
2. አሣቀ. His foolish mistakes amused all of us. የማይረባ ፡ ስሕተቱ ፡ ሁላችንንም ፡ አሣቀን

**amuse oneself** ራሱን ፡ አስደሰተ
The students amused themselves by imitating the teacher. ተማሪዎቹ ፡ መምህሩን ፡ በመቀለድ ፡ እየመሰሉ ፡ ራሳቸውን ፡ አስደሰቱ

**amused** (adj.)

1. የተደሰተ. The amused spectators applauded the play. የተደሰቱት ፡ ተመልካቾች ፡ ቲያትሩን ፡ በጭብጨባ ፡ አደነቁ
2. ደስታ ፡ የመላበት. The child listened to the story with an amused smile. ልጁ ፡ ታሪኩን ፡ ደስታ ፡ በመላበት ፡ ፈገግታ ፡ አዳመጠ

**amusement**

1. ጨዋታ. He did it only for amusement. ያደረገው ፡ ለጨዋታ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ደስታ ፡ መደሰት. With amusement, the child watched the kitten chasing its tail. የድመቷ ፡ ግልገል ፡ ጭራዋን ፡ ለመያዝ ፡ ስታሳድድ ፡ ልጁ ፡ በደስታ ፡ ተመለከተ

He looked at me in amusement. በመደሰት ፡
ተመለከተኝ
3. መደሰቻ. There is not much amusement
in this village. በዚህ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ብ
ዙ ፡ መደሰቻ ፡ የለም

**amusing**
1. የሚያስደስት. My friend told me an amusing
story. ጓደኛዬ ፡ የሚያስደስት ፡ ወሬ ፡ አወራልኝ
2. አሥቂኝ. The man's certainty was amusing
for we could see that he was wrong. የተሳሳ
ተ ፡ መሆኑን ፡ ስለምናውቅ ፡ የሰውየው ፡ እርግ
ጠኛ ፡ ነኝ ፡ ማለት ፡ አሥቂኝ ፡ ነበር

**an**
1. አንድ. Is there an apple for me? አንድ ፡ ፖ
ም ፡ ላገኝ ፡ እችላለሁ ?
2. (zero). Is there an apple for me? ፖም ፡ ላገ
ኝ ፡ እችላለሁ ?

**anachronism** ጊዜውን ፡ የሳተ
It would be an anachronism to speak of
George Washington riding in an automobile.
ጆርጅ ፡ ዋሽንግተን ፡ በመኪና ፡ ሄደ ፡ ብሎ ፡ መ
ናገር ፡ ጊዜውን ፡ የሳተ ፡ ይሆናል

**analogous** (= n.) ተመሳሳይነት
A bird's wing and a human arm are analogous.
የወፍ ፡ ክንፍና ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ተመሳሳይነት ፡ አላ
ቸው

**analogy** ማመሳሰል
The analogy between your problem and mine
surprises me. ያንተና ፡ የኔን ፡ ችግር ፡ ማመሳሰ
ል ፡ አስደንቆኛል

**draw an analogy between** አመሳሰለ
The teacher drew an analogy between the
heart and the pump. አስተማሪው ፡ ልብንና ፡
ፖምፕን ፡ አመሳሰለ

**analysis**
1. ትንተና. He gave a thorough analysis of the
political situation. ስለ ፡ ፖለቲካው ፡ ሁኔታ ፡
የተሟላ ፡ ትንተና ፡ አቀረበ
2. ምርመራ. The analysis of the water proved
that it was poisonous. ምርመራው ፡ ውኃው ፡ መ
ርዝ ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጠ

**analyst** ተንታኝ
His detachment makes him a good political
analyst. ገለልተኛነቱ ፡ ጥሩ ፡ የፖለቲካ ፡ ሁኔታ ፡
ተንታኝ ፡ አድርጎታል

**analyze**
1. ተነተነ. The teacher analyzed the cause of
our failure. አስተማሪው ፡ የወደቅንበትን ፡ ምክን
ያት ፡ ተነተነ
2. መረመረ. The students analyzed the poem.
ተማሪዎቹ ፡ ግጥሙን ፡ መረመሩ

**anarchy** ግርግር
After the death of the king anarchy broke out.
ከንጉሡ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ግርግር ፡ ተከተለ

**anathema** ውግዘት
The priest's anathema was removed when the
governor promised to obey. አገረ ፡ ገዢው ፡ ለ
መታዘዝ ፡ ቃል ፡ ስለገባ ፡ የቄሱ ፡ ውግዘት ፡ ተሻረ

**anatomy**
1. አናቶሚ. Anatomy shows how the body is
constructed. አናቶሚ ፡ ሰውነት ፡ እንዴት ፡ እንደ
ተገነባ ፡ ያስረዳል
2. የሰውነት ፡ አሠራር. The anatomy of an earth-
worm is much simpler than that of an animal.
የትል ፡ የሰውነት ፡ አሠራር ፡ ከእንስሳት ፡ የቀለለ ፡
ነው

**ancestor** ቅድመ ፡ አያት ፤ አያት ፡ ቅድመ ፡ አያ
ት ፤ አባት
Our ancestors were warriors. ቅድመ ፡ አያቶ
ቻችን ፡ (አባቶቻችን) ፡ ጦረኞች ፡ ነበሩ
Kinship is based on a common ancestor.
ለዝምድና ፡ መሠረት ፡ የሚሆነው ፡ አንድ ፡ አያት ፡
ቅድመ ፡ አያት ፡ ነው
*Scientists say that the ancestor of man
was the ape. ሳይንቲስቶች ፡ ሰው ፡ የመጣው ፡ ከ
ዝንጀሮ ፡ ነው ፡ ይላሉ

**ancestral** የዘር
They still have ancestral properties in this
province. በዚህ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ አ
ሁንም ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ አላቸው

**ancestral home** የትውልድ ፡ አገር
The ancestral home of the Emperor's family
is in Shoa. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የትውልድ ፡ አ
ገር ፡ ሸዋ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**ancestral trait** የዘር
Curly hair is an ancestral trait in that family.
በዚህ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡ ከርዳዳ ፡ ጸጉር ፡ የዘ
ር ፡ ነው

**ancestry** ቅድመ ፡ አያቶች
Many of the early settlers in America had
English ancestry. ቀደም ፡ ሲል ፡ አሜሪካ ፡ ላ
ይ ፡ ከሰፈሩት ፡ ሰዎች ፡ የብዙዎቹ ፡ ቅድመ ፡ አ
ያቶች ፡ እንግሊዞች ፡ ናቸው

**anchor** (vt.) መልሕቅ ፡ ጣለ
The sailors anchored the boat. መርከበኞቹ ፡
የጀልባውን ፡ መልሕቅ ፡ ጣሉ

**anchor** (vi.) ገባ
The ocean liner anchored at Massawa at noon. መርከቧ ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ ምፅዋ ፡ ገባች

**anchor** (n.) መልሕቅ
The sailors dropped the anchor. መርከበኞቹ ፡ መልሕቁን ፡ ጣሉ

**lay at anchor** መልሕቁን ፡ ጥሎ ፡ ቆመ
The ship lay at anchor in the port. መርከቡ ፡ መልሕቁን ፡ ጥሎ ፡ ወደቡ ፡ ላይ ፡ ቆሟል

**anchorite** ባሕታዊ
The anchorite lived alone in the desert. ባሕታዊው ፡ ምድረ ፡ በዳው ፡ ውስጥ ፡ ብቻውን ፡ ኖረ

**ancient** (n.) የድሮ ፡ ሰው
The ancients considered the flight of birds as an omen of good fortune. የድሮ ፡ ሰዎች ፡ ወፎች ፡ ሲበሩ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ገድ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያምኑ ፡ ነበር

**ancient** (adj.)
1. አሮጌ. Why did you invest so much money in that ancient building? ለዚህ ፡ አሮጌ ፡ ሕንጻ ፡ ይህንን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ ለምን ፡ አወጣህ ?
2. ጥንታዊ. I am very interested in ancient art. ጥንታዊ ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ በጣም ፡ ያስደስተኛል
3. የጥንት. Ancient man used to live in caverns. የጥንት ፡ ሰው ፡ በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ይኖር ፡ ነበር
4. ከጥንት ፡ የመጣ. Marriage is an ancient institution. ጋብቻ ፡ ከጥንት ፡ የመጣ ፡ ልማድ ፡ ነው
[See also 'vintage']

**and**
1. (zero.) I brought salt and pepper from the market. ከገበያ ፡ ጨው ፡ በርበሬ ፡ አመጣሁ
2. -ና. I brought salt, pepper and butter. ጨው ፡ በርበሬና ፡ ቅቤ ፡ አመጣሁ
3. -ም. I brought salt, pepper and butter. ጨው ፡ በርበሬ ፡ ቅቤም ፡ አመጣሁ
4. ተ—. We travelled day and night. ሌት ፡ ተቀን ፡ ተጓዝን

**and so forth**
1. ሌሎችም. All my uncles, aunts, and so forth were there. አጎቶቼም ፡ አክስቶቼም ፡ ሌሎችም ፡ እዚያ ፡ ነበሩ
2. እንዲያ ፡ የመሳሰሉት ፡ ነገሮች. They were singing, dancing, and so forth. ይዘምሩ ፤ ይደንሱ ፡ እንዲያ ፡ የመሳሰሉትን ፡ ነገሮች ፡ ያደርጉ ፡ ነበር

**and so on** እነኚህን ፡ የመሳሰሉት
I need paper, ink, and so on. ወረቀት ፡ ቀለምና ፡ እነኚህን ፡ የመሳሰሉት ፡ ያስፈልገኛል
[See also 'then']

**anecdote** ተረት
He told anecdotes to the children. ለሕፃናቱ ፡ ተረት ፡ ነገራቸው

**anesthetic** የሚያስተኛ ፡ መድኀኒት
The amount of anesthetic they gave you was according to your strength. የሚያስተኛውን ፡ መድኀኒት ፡ የሰጡህ ፡ በዐቅምህ ፡ መጠን ፡ ነው

**anew**
1. እንደገና. She had to learn to walk anew after the accident. ከደጋው ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ መራመድን ፡ መልመድ ፡ ነበረባት
2. ባዲስ ፡ መልክ. The architect planned the building anew. መሀንዲሱ ፡ ሕንጻውን ፡ የነደፈው ፡ ባዲስ ፡ መልክ ፡ ነው

**angel** መልአክ
The angel told Mary that she would have a son. መልአኩ ፡ ማርያምን ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ እንደምትወልድ ፡ አበሰራት

**angelic** መልአካዊ
His angelic appearance astonished everybody. መልአካዊ ፡ መልኩ ፡ ሁሉንም ፡ አስደነቀ

**anger** (vt.) አናደደ ፤ አስቈጣ
The nasty remark angered her. አስጠያፊው ፡ አስተያየት ፡ አናደዳት
His boorish manners angered the host. የባልገና ፡ ሁናቴው ፡ ባለቤቱን ፡ አስቈጣው

**anger** (vi.) ተናደደ
He angers easily. በቀላሉ ፡ ይናደዳል

**anger** (n.) ንዴት
Let your anger cool before you do anything. እስቲ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ከማድረግህ ፡ በፊት ፡ ንዴትህ ፡ ይብረድልህ

**rouse (one's) anger** አስቈጣ
The insult roused his anger. ስድቡ ፡ አስቈጣው

**angle** (v.)
1. ሊያግባባው ፡ ሞከረ. She angled for an invitation to his party by flattering him. እሱን ፡ በመደለል ፡ ወደ ፡ ግብዣ ፡ እንዲጠራት ፡ ልታግባባው ፡ ሞከረች
2. [በመንጠቆና ፡ በሲባጎ ፡ ዓሣ ፡ አጠመደ]

**angle** (n.) ማእዘን
The two walls form an angle. ሁለቱ ፡ ግድግዳዎች ፡ በማእዘን ፡ ይጋጠማሉ

**from all angles** ከሁሉም ፡ አቅጣጫ
He considered the matter from all angles. ጉዳዩን ፡ ከሁሉም ፡ አቅጣጫ ፡ ተመለከተው
[See also 'obtuse']

**angry**

1. የቁጣ. She gave me an angry reply. የቁጣ ፡ መልስ ፡ ሰጠችኝ

He spoke to me in an angry voice. በቁጣ ፡ ቃል ፡ ተናገረኝ

2. የተናደደ. The angry child dashed a cup to the floor. የተናደደው ፡ ልጅ ፡ ሲኒውን ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ወረወረው

**(be, become, wax) angry**

1. ተናደደ. What are you angry about? ለምንድ ነው ፡ የተናደድከው ?

He began to wax angry. መናደድ ፡ ጀመረ

2. ተቈጣ. The merchant became angry with the boys for breaking the window. ነጋዴው ፡ ል ጆቹ ፡ መስኮቱን ፡ ስለሰበሩ ፡ ተቈጣቸው

**feel angry** ተናደደ

He feels angry whenever he sees her. ባያት ፡ ቁጥር ፡ ይናደዳል

[See also 'dart']

**anguish** ጭንቀት

She was in anguish until she knew that her husband's life had been saved. የባሏን ፡ ሕይወ ት ፡ መትረፍ ፡ እስከታውቅ ፡ ድረስ ፡ በጭንቀት ፡ ላይ ፡ ነበረች

**angular** ማእዘናዊ

The machine has an angular shape. መኪናው ፡ ማእዘናዊ ፡ ቅርጽ ፡ አለው

**animadversion** ነቀፌታ

He softened his animadversions on his rival's character. ስለ ፡ ተወዳዳሪው ፡ ጠባይ ፡ ያለውን ፡ ነቀፌታ ፡ ለስለስ ፡ አደረገው

**animal**

1. እንስሳ (pl. እንስሳት). He heard an animal moving in the bushes. አንድ ፡ እንስሳ ፡ በቁጥ ቋጦው ፡ ውስጥ ፡ ሲንቀሳቀስ ፡ ተሰማው

There are many animals in this country. በዚ ሀ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ እንስሳት ፡ አሉ

2. አውሬ. Lions are carnivorous animals. አንበሶች ፡ ሥጋ ፡ በል ፡ አውሬዎች ፡ ናቸው

**wild animals** የዱር ፡ አራዊት

There are no more wild animals left. የቀሩ ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ የሉም

[See also 'pack, stuff']

**animate** (v.)

1. አፈካ. A smile animated her face. ፈገግታ ፡ ፊ ትዋን ፡ አፈካው

2. ገፋፋ. Love for her mother animated her work. ሥራውን ፡ እንድትሠራ ፡ የገፋፋት ፡ የና ቷ ፡ ፍቅር ፡ ነው

3. ሕይወት ፡ ሰጠ. People believe that the soul animates the body. ሰዎች ፡ ለአካል ፡ ሕይወትን ፡ የምትሰጥ ፡ ነፍስ ፡ ናት ፡ ብለው ፡ ያምናሉ

4. ድምቀት ፡ ሰጠ. The speaker's arguments animated the discussion. የተናጋሪው ፡ ክርክር ፡ ለ ውይይቱ ፡ ድምቀት ፡ ሰጠው

**animate** (adj.) ሕይወታዊ

Zoology deals with animate things. ዞዎሎጂ ፡ ስለ ፡ ሕይወታዊ ፡ ፍጥረቶች ፡ ጥናት ፡ ነው

**animated** (adj.) የተሟሟቀ

The animated discussion pleased us all. የተሟሟቀው ፡ ውይይት ፡ ሁላችንንም ፡ አስደሰተን

**be animated**

1. ተነሸጠ. The soldiers were animated by their captain's speech. ወታደሮቹ ፡ በሻምበሉ ፡ ንግግር ፡ ተነሸጡ

2. ተንቀሳቀሰ. Windmills are animated by the wind. የነፋስ ፡ ወፍጮዎች ፡ የሚንቀሳቀሱት ፡ በ ነፋስ ፡ ኀይል ፡ ነው

**animation** የጋለ ፡ ስሜት

He spoke with animation about his plans for the city. ስለ ፡ ከተማው ፡ ያለውን ፡ እቅድ ፡ በ ጋለ ፡ ስሜት ፡ ተናገረ

**animosity** ጥላቻ

He could not hide his animosity toward his neighbors. ለጎረቤቶቹ ፡ ያለውን ፡ ጥላቻ ፡ ሊደብቅ ፡ አልቻለም

**ankle** ቁርጭምጭሚት

Did she sprain her ankle? ቁርጭምጭሚቷን ፡ ወ ለም ፡ አላት ?

**anklet** አምባር

The woman wore a silver anklet. ሴትዮዋ ፡ ከ ብር ፡ የተሠራ ፡ አምባር ፡ አድርጋለች

**annals** ዜና ፡ ታሪክ

The annals of Ethiopia were written in Geez. የኢትዮጵያ ፡ ዜና ፡ ታሪክ ፡ የተጻፈው ፡ በግዕዝ ፡ ነው

**annex** (v.) ቀላቀለ

The enemy annexed the conquered territory to their country. ወራሪዎቹ ፡ ያስገበሩትን ፡ አገር ፡ ካገራቸው ፡ ጋር ፡ ቀላቀሉ

**annex** (n.) ቅጥያ ፤ ተጨማሪ ፡ ሕንጻ

They built an annex to the library. ለቤተ ፡ መ ጻሕፍቱ ፡ ቅጥያ ፡ (ተጨማሪ ፡ ሕንጻ) ፡ ሠሩ

**annexation** መቀላቀል

The annexation of Texas enlarged the United States. የቴክሳስ ፡ መቀላቀል ፡ የአሜሪካንን ፡ ግ ዛት ፡ አሰፋው

**annihilate** ድምጥማጡን ፡ አጠፋ
Caesar annihilated the enemy army. ቄሳር ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ ድምጥማጡን ፡ አጠፋ

**anniversary**
1. በዓል. They are celebrating their thirtieth marriage anniversary. ሠላሳኛውን ፡ ዓመት ፡ የጋብቻ ፡ በዓላቸውን ፡ ያከብራሉ
2. የዓመት ፡ በዓል. Your birthday is an anniversary. የተወለድክበት ፡ ቀን ፡ የዓመት ፡ በዓል ፡ ነው

**Anniversary of Restoration** የነጻነት ፡ በዓል
Last year, all Ethiopia celebrated the 25th Anniversary of the Restoration. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ መላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሃያ ፡ አምስተኛውን ፡ የነጻነት ፡ በዓል ፡ አከበረ

**annotate** ማብራሪያ ፡ ጻፈ
He annotated Shakespeare's plays. ሼክስፒር ፡ ለጻፋቸው ፡ ቲያትሮች ፡ ማብራሪያ ፡ ጻፈ

**announce**
1. አስታወቀ. They just announced that on the radio. ያንን ፡ በሬድዮ ፡ ልክ ፡ አሁን ፡ አስታወቁ
2. ገለጸ. They announced their engagement last night. መተጫጨታቸውን ፡ ትናንትና ፡ ማታ ፡ ገለጹ
3. ዐወጀ. The Emperor announced that full authority would be given to the prime minister. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ለጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ እንደሚሰጥ ፡ ዐወጁ
4. ጠራ. The servant announced the names of the visitors as they came in. አሽከሩ ፡ እንግዶቹ ፡ ሲገቡ ፡ ስማቸውን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ይጠራ ፡ ነበር
5. አበሰረ. The trumpet blared, announcing the king's arrival. የንጉሡን ፡ መምጣት ፡ ለማብሰር ፡ ጥሩምባው ፡ አምባረቀ
6. ነገረ (ተነገረ). The capitulation of the enemy was announced this morning. የጠላት ፡ እጅ ፡ መስጠት ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ ተነገረ

**announcement** መግለጫ ፤ ማስታወቂያ
The announcements of deaths, marriages, and births are published daily by the newspaper. ዜና ፡ ዕረፍትን ፤ ጋብቻን ፤ ልደትን ፡ የሚገልጹት ፡ መግለጫዎች ፡ (ማስታወቂያዎች) ፡ በየዕለቱ ፡ በጋዜጣው ፡ ላይ ፡ ይወጣሉ

**announcer** ተናጋሪ ፤ ማስታወቂያ ፡ ተናጋሪ
The radio announcer confused the dates of the two events. ሬዲዮ ፡ ተናጋሪው ፡ የሁለቱን ፡ ሁኔታዎች ፡ ቀናት ፡ አማታ
The announcer spoke in a low voice. ማስታወቂያ ፡ ተናጋሪው ፡ ድምፁን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ተናገረ

**annoy** አበሳጨ
Was that drunk annoying you? ያ ፡ ሰካራም ፡ ያበሳጭህ ፡ ነበር ?

**be annoyed**
1. ተበሳጨ. He was annoyed to hear that the plane would be delayed. አውሮፕላኑ ፡ መዘግየቱን ፡ ሲሰማ ፡ ተበሳጨ
2. ተናደደ. He was annoyed with his servant because his dinner was cold. እራቱ ፡ በመቀዝቀዙ ፡ በአሽከሩ ፡ ተናዶ ፡ ነበር

**annoyance** ማወክ
The annoyance of mosquitos kept her awake. የወባ ፡ ትንኞች ፡ ማወክ ፡ አላስተኛ ፡ አላት

**annual** (n.) ዓመታዊ ፡ መጽሔት
The institute publishes an annual. ድርጅቱ ፡ ዓመታዊ ፡ መጽሔት ፡ ያዘጋጃል

**annual** (adj.)
1. ዓመታዊ. This is an annual banquet. ይህ ፡ ዓመታዊ ፡ ግብዣ ፡ ነው
2. በያመቱ ፡ አንዴ ፡ የሚገኝ. Corn and beans are annual plants. በቆሎና ፡ ባቄላ ፡ በያመቱ ፡ አንዴ ፡ የሚገኙ ፡ ዕፀዋት ፡ ናቸው

**annually** በያመቱ
Annually, he receives ten thousand dollars. በያመቱ ፡ ዐሥር ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ይቀበላል

**annuity** (annuities) አበል
An annuity is paid to all wounded patriots. ለቈሰሉት ፡ አርበኞች ፡ ሁሉ ፡ አበል ፡ ይከፈላቸዋል

**annul** (annulled) ሻረ
The judge annulled the land contract of the two people. ዳኛው ፡ የሁለቱን ፡ ሰዎች ፡ የመሬት ፡ ውል ፡ ሻረ

**annunciate,** see **announce**

**annunciation** የምስራች
The Archangel Gabriel made the annunciation to Mary. ሊቀ ፡ መልአኩ ፡ ገብርኤል ፡ ለማርያም ፡ የምስራች ፡ ነገራት

**anoint** ቀባ
The coronation is concluded when the patriarch anoints the Emperor. የዘውድ ፡ መጫን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ፓትሪያርኩ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ሲቀባው ፡ ይፈጸማል

He anointed the sunburned places with salve. ፀሐይ ፡ ያቃጠለውን ፡ ስፍራ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ቅባት ፡ ቀባው

**anomalous** ያልተለመደ
Rain in the desert is an anomalous occurrence. በምድረ ፡ በዳ ፡ ዝናብ ፡ ያልተለመደ ፡ ነው

**anomaly** ያልተለመደ ፡ ነገር
A heavy downpour in the desert is an anomaly. በምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ ከባድ ፡ ዝናብ ፡ መጣል ፡ ያልተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው

**anonymous** ስም ፡ ያልተጻፈበት
He sent them an anonymous letter. ስም ፡ ያልተጻፈበት ፡ ደብዳቤ ፡ ላከላቸው

**be anonymous**
*The author of the story is anonymous. የታሪኩ ፡ ጸሐፊ ፡ ስም ፡ አይታወቅም

**another** (adj.) ሌላ
I would like another book. ሌላ ፡ መጽሐፍ ፡ እፈልጋለሁ

**another** (pron.) ሌላ
I don't like this book; give me another. ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ አልፈልገውም ፤ ሌላ ፡ ስጠኝ

**in another** ከ - - - በኋላ
Where will Ethiopia be in another ten years? ኢትዮጵያ ፡ ካሥር ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የት ፡ ትደርሳለች ?
In another ten minutes, I will be through. ካሥር ፡ ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ እጨርሳለሁ

**one another** (is expressed by the stem of reciprocity). They saw one another frequently. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይገናኙ ፡ ነበር

**answer** (v.)
1. መለሰ. He answered the question satisfactorily. ጥያቄውን ፡ በሚያስደስት ፡ አኳኋን ፡ መለሰ
2. መልስ ፡ ሰጠ. The student answered the teacher. ተማሪው ፡ ላስተማሪው ፡ መልስ ፡ ሰጠ
3. አለ. He answered that he knew nothing. ምንም ፡ አላውቅም ፡ አለ
4. ሞላ(ለት). Will this answer your needs? ይህ ፡ ፍላጎትህን ፡ ይሞላልሃል ?
5. አረካ. Will this answer your purpose? ይህ ፡ ፍላጎትህን ፡ ያረካልሃል ?
*She answered the knock on the door. በሩ ፡ ስለተንኳኳ ፡ ሄዳ ፡ ከፈተች
*The maid went to answer the telephone. ገረዲቱ ፡ ስልኩን ፡ ለማንሣት ፡ ሄደች

**answer back** መለሰ(ለት)
The father punished his son for answering him back. ልጁ ፡ ስለመለሰለት ፡ አባትዬው ፡ ቀጣው

**answer (for)**
1. በኀላፊነት ፡ ተጠየቀ(በት). You will have to answer for your mistakes. ለጥፋትህ ፡ በኀላፊነት ፡ ትጠየቅበታለህ
2. መልስ ፡ ሰጠ. She was called before the bar to answer for her crimes. ለተከሰሰችበት ፡ ወንጀል ፡ መልስ ፡ እንድትሰጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተጠራች
3. እንደ - - - አገለገለ. A piece of paper answered for a tablecloth. የወረቀት ፡ ቁራጭ ፡ እንደ ፡ ጠረጴዛ ፡ ልብስ ፡ አገለገለ

**answer (to)** ተስማማ
The house answers to your description. ቤቱ ፡ ካንተ ፡ ገለጻ ፡ ጋር ፡ ይስማማል
[See also 'call, duty']

**answer** (n.) መልስ
Have you had an answer to your letter? ለደብዳቤህ ፡ መልስ ፡ አገኘህ ?
What is the correct answer to this problem? ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ ትክክለኛው ፡ መልስ ፡ ምንድነው ?

**in answer to** በ - - - መሠረት
The doctor came in answer to my call. በጥሪዬ ፡ መሠረት ፡ ሐኪሙ ፡ መጣ
[See also 'guess']

**ant** ጉንዳን
The ants invaded the food. ጉንዳን ፡ ምግቡን ፡ ወረረው

**antagonism** ጥላቻ
The antagonism between the two villages led to murder. በሁለቱ ፡ መንደሮች ፡ መሀከል ፡ ያለው ፡ ጥላቻ ፡ እስከ ፡ መጋደል ፡ አደረሳቸው

**antagonize** የጥላቻ ፡ መንፈስ ፡ አሳደረበት
Her rudeness antagonizes everyone she meets. ብልግናዋ ፡ ያገኘቻቸውን ፡ ሁሉ ፡ የጥላቻ ፡ መንፈስ ፡ ያሳድርባቸዋል

**Antarctic** አንታርክቲክ
The Antarctic is always covered with ice. አንታርክቲክ ፡ ሁልጊዜ ፡ በበረዶ ፡ እንደተሸፈነ ፡ ነው

**antecede** ከ - - - በፊት ፡ ኖረ
Shakespeare anteceded Milton. ሼክስፒር ፡ የኖረው ፡ ከሚልተን ፡ በፊት ፡ ነው

**antecedent** ከ - - -በፊት
The witness told of an event antecedent to

the robbery. ምስክሩ ፡ ከዘረፋው ፡ በፊት ፡ ስለተደረገው ፡ ነገር ፡ ተናገረ

**antecedents**
1. ቅድመ ፡ አያቶች. His antecedents once lived on the Red Sea coast. ቅድመ ፡ አያቶቹ ፡ ከዘመናት ፡ በፊት ፡ ቀይ ፡ ባሕር ፡ ጻርቻ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር
2. የሕይወት ፡ ታሪክ. No one knows the antecedents of the mysterious stranger. የዚህን ፡ እንግዳ ፡ ሰው ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ የሚያውቅ ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ የለም

**antedate**
1. ጊዜ ፡ አስቀደመ. You antedate a check written on May 3rd if you put May 1st on it. ግንቦት ፡ ሦስት ፡ የተጻፈውን ፡ ግንቦት ፡ አንድ ፡ ብለህ ፡ ብትጽፍበት ፡ የቼኩን ፡ ጊዜ ፡ ታስቀድማለህ
2. በመሠራት ፡ ቀደመ. Automobiles antedate airplanes. መኪና ፡ በመሠራት ፡ ከአይሮፕላን ፡ ይቀድማል

**antelope** ድኩላ

**antenna** አንቴና
The antenna is placed on the roof. አንቴናው ፡ ጣሪያው ፡ ላይ ፡ ተደርጓል

**anterior, ~ part** (= adv.) ከወደፊቱ
The anterior part of a fish contains the head. የዓሣ ፡ ራሱ ፡ የሚገኘው ፡ ከወደፊቱ ፡ ነው

**be anterior** ቀደመ
The American Revolution was anterior to the French Revolution. የአሜሪካን ፡ ብጥብጥ ፡ ከፈረንሳይ ፡ ብጥብጥ ፡ ቀደመ

**anthem, national ~** የሕዝብ ፡ መዝሙር
The national anthem of Ethiopia is sung on many occasions. የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ መዝሙር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይዘመራል

**anthology** [የግጥም ፤ የታሪክ ፡ የቅኔና ፡ የሌሎችም ፡ ጽሑፎች ፡ ስብስብ]

**anticipate** (vt.)
1. ተስፋ ፡ አደረገ. She anticipates great pleasure from her visit to Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ጉብኝቷ ፡ ብዙ ፡ እንደምትደሰት ፡ ተስፋ ፡ ታደርጋለች
2. ቀደመ. The Chinese anticipated our discovery of gunpowder. እኛ ፡ ባሩድ ፡ ከመሥራታችን ፡ በፊት ፡ ቻይናዎች ፡ ቀድመውን ፡ ነበር
3. ሳይጠይቀው ፡ አረካ. He tries to anticipate all my needs. ፍላጎቴን ፡ ሁሉ ፡ ሳልጠይቀው ፡ ሊያረካ ፡ ይሞክራል
4. አስቀድሞ ፡ ዐወቀ. Our interlocutors anticipate much of what we say. በውይይቱ ፡ አብረውን ፡ ተከፋይ ፡ የነበሩት ፡ የምንለውን ፡ አስቀድመው ፡ ያውቃሉ

**anticipate** (vi.) አሰበ
The attendance was greater than we anticipated. የተገኘው ፡ ሕዝብ ፡ ካሰብነው ፡ በላይ ፡ ነበር

**anticipation** መጠባበቅ
Anticipation of the battle made the soldiers nervous. ጦርነቱን ፡ መጠባበቅ ፡ ወታደሮቹን ፡ አቅነጠነጣቸው

**in anticipation** በመገመት
He cut more wood than usual in anticipation of a long winter. የሚመጣው ፡ ክረምት ፡ ረዥም ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ በመገመት ፡ ከወትሮው ፡ የበለጠ ፡ ዕንጨት ፡ ቈረጠ

**antidote** ማርከሻ
Milk is an antidote for some poisons. ወተት ፡ ላንዳንድ ፡ መርዞች ፡ ማርከሻ ፡ ነው

**antipathy** ጥላቻ
The old man's antipathy to tobacco is well known. ሽማግሌው ፡ ለትምባሆ ፡ ያላቸው ፡ ጥላቻ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**antipodes**
1. ተነጻጻሪ ፡ ቦታ. The North and South poles are antipodes. የሰሜንና ፡ የደቡብ ፡ ዋልታዎች ፡ ተነጻጻሪ ፡ ቦታዎች ፡ ናቸው
2. ተቃራኒ. Love and hate are antipodes. ፍቅርና ፡ ጥላቻ ፡ ተቃራኒ ፡ ናቸው

**antiquated** ጊዜ ፡ ያለፈበት
Most science books written twenty years ago are now antiquated. ከሃያ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የተጻፉት ፡ አብዛኞዎቹ ፡ የሳይንስ ፡ መጻሕፍት ፡ ባሁኑ ፡ ወቅት ፡ ጊዜ ፡ ያለፈባቸው ፡ ናቸው

**antique** (adj.) የጥንት
I bought an antique vase. የጥንት ፡ ማሰሮ ፡ ገዛሁ

**antiquity** (antiquities)
1. የጥንት ፡ ጊዜ. Adulis was a port famous in antiquity. አዱሊስ ፡ በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ዝነኛ ፡ ወደብ ፡ ነበረች
2. ጥንታዊነት. The Tourist Office has several posters showing Ethiopia's antiquities. የቱሪስት ፡ ድርጅት ፡ ብዙ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥንታዊነት ፡ የሚገልጹ ፡ ሥዕላዊ ፡ መግለጫዎች ፡ አሉት

**antithesis** ተቃራኒ
Hate is the antithesis of love. ጥላቻ ፡ የፍቅር ፡ ተቃራኒ ፡ ነው

**antler** ቀንድ
The antlers of the oryx were placed on the walls of the hunter's home. የአውራሪስ ፡ ቀንዶች ፡ አዳኙ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ ተሰቅለዋል

**antonym** ተቃራኒ
"Hot" is the antonym of "cold". « ሙቅ » ፡ የ « ቀዝቃዛ » ፡ ተቃራኒ ፡ ነው

**anus** ፍንጢጣ
Diarrhea made his anus sore. ተቅማጥ ፡ ፍንጢጣውን ፡ አቁሰለው

**anvil** መስፍ
The blacksmith held the heated metal on the anvil. ቀጥቃጩ ፡ የጋለውን ፡ ብረት ፡ መስፉ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠው

**anxiety**
1. ስጋት. We waited in anxiety for news of his safe arrival. በደኅና ፡ መግባቱን ፡ ለመስማት ፡ በስጋት ፡ እንጠባበቅ ፡ ነበር
2. ጉጉት. Her anxiety about succeeding led her to work hard. ከዓላማዋ ፡ ለመድረስ ፡ ያላት ፡ ጉጉት ፡ ጠንክራ ፡ እንድትሠራ ፡ ገፋፋት

**anxious** የተሸበረ
The anxious person was walking up and down. የተሸበረው ፡ ሰው ፡ ወደላይና ፡ ወደታች ፡ ይመላለስ ፡ ነበር

**be anxious**
1. ጓጓ. I am anxious to see the new book. አዲሱን ፡ መጽሐፍ ፡ ለማየት ፡ ጓጉቻለሁ
2. ሰጋ. He is anxious about his future. ስለ ፡ ወደፊት ፡ ኑሮው ፡ ይሰጋል
He became anxious when his daughter failed to come home on time. ልጁ ፡ በጊዜ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ባለመግባቷ ፡ ሰጋ

**any**
1. ማንም. Any mechanic can fix that. ያንን ፡ ማንም ፡ ሜካኒክ ፡ ሊገጥመው ፡ ይችላል
2. ምንም. Barren soil will not grow any wheat. ጭንጫ ፡ መሬት ፡ ምንም ፡ ስንዴ ፡ አያበቅልም
3. ማንኛውም. That boy can wriggle out of any difficulty. ያ ፡ ልጅ ፡ ከማንኛውም ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ በዘዴ ፡ ሊያመልጥ ፡ ይችላል
4. ማናቸውም ፡ ሌላ. Any job is better than this one. ከዚህ ፡ ሥራ ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ይሻላል
5. አንዳች. We did the work without any difficulty. ሥራውን ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ ፈጸምን
6. (zero). Did you find any books there? እዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ አገኘህ ?
Come any day you like. በፈለግህበት ፡ ቀን ፡ ና

**any more**
1. ከእንግዲህ. He cannot bear any more pain. ከእንግዲህ ፡ ምንም ፡ ሕመም ፡ ሊታገሥ ፡ አይችልም
2. ሌላ. Have you any more pepper? ሌላ ፡ በርበሬ ፡ አለህ?

**any other** ሌላ
Have you any other question? ሌላ ፡ ጥያቄ ፡ አለህ ?

**any place** የትም
You will find a radio any place you go. የትም ፡ ብትሄድ ፡ ሬዲዮ ፡ ታገኛለህ

**not ... any** (adj.) ምንም
I don't have any bread. ምንም ፡ ዳቦ ፡ የለኝም

**not ... any** (pron.) ምንም
Keep the cake! I don't want any. ኬኩን ፡ ላንተ ፡ አድርገው ፤ ምንም ፡ አልፈልግም
[See also 'better, man, minute, moment']

**anybody**
1. ሰው. Will anybody be at the station to meet me? እኔን ፡ ለመቀበል ፡ እጣቢያው ፡ የሚገኝ ፡ ሰው ፡ ይኖራል ?
2. ማንኛውም ፡ ሰው. Anybody can do that. ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሊሠራው ፡ ይችላል

**not ...... anybody** ማንም
I don't know anybody here. እዚህ ፡ ማንንም ፡ አላውቅም
[See also 'else']

**anyhow**
1. ሆኖም. I said no, but he did it anyhow. እኔ ፡ አይሆንም ፡ አልኩኝ ፤ ሆኖም ፡ አደረገው
2. እንደምንም ፡ ብሎ. You will have to make your way through this crowd anyhow. እንደምንም ፡ ብለህ ፡ በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ማለፍ ፡ አለብህ
3. ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ. I would have gone anyhow. ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ እሄድ ፡ ነበር

**anyone** ሰው
If anyone needs help, send him to me. እርዳታ ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ወደኔ ፡ ላከው

**anything**
1. አንዳች. Did he say anything? አንዳች ፡ ነገር ፡ ተናገረ ?
2. ነገር. Is there anything left over? የተረፈ ፡ ነገር ፡ አለ ?

3. ምንም ፡ ነገር. I am so hungry I will eat anything. በጣም ፡ ስለራበኝ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ እበላለሁ
4. ምናምን. Is there anything for me here? እዚህ ፡ ለኔ ፡ ምናምን ፡ አለ ?
5. የፈለገውን. You could buy anything at the bazaar. ከመደብሩ ፡ የፈለግከውን ፡ መግዛት ፡ ትችላለህ

**anything else** ሌላ ፡ ነገር
Would you like anything else? ሌላ ፡ የምትፈልገው ፡ ነገር ፡ አለ ?

**not ... anything** ምንም
I can't do anything in this case. እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ ምንም ፡ ማድረግ ፡ አልችልም

**not for anything** ለምንም ፡ ነገር ፡ ብሎ
I wouldn't do that for anything. ለምንም ፡ ነገር ፡ ብዬ ፡ ያንን ፡ አላደርገውም

**anyway**
1. ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ. This may or may not be true, but we will look into it anyway. ይህ ፡ እውነት ፡ ሊሆንም ፡ ላይሆንም ፡ ይችላል ፤ ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ነገሩን ፡ እናጣራለን
2. የሆነ ፡ ሆኖ. She did not want to come anyway. የሆነ ፡ ሆኖ ፡ መምጣት ፡ አልፈለገችም
3. በየትኛውም ፡ አንጻር. The answer is wrong anyway you look at it. በየትኛውም ፡ አንጻር ፡ ብትመለከተው ፡ መልሱ ፡ ስሕተት ፡ ነው
4. እንደ + (verb). He does his work anyway he likes. ሥራውን ፡ እንዳሻው ፡ ይሠራል
*Sooner or later, you'll have to buy a car anyway. ውሎም ፡ አድሮም ፡ ቢሆን ፡ መኪና ፡ መግዛት ፡ ይኖርብሃል

**anywhere** የትም
I don't want to go anywhere tonight. ዛሬ ፡ ማታ ፡ የትም ፡ ለመሄድ ፡ አልፈልግም
*I'll go anywhere you like. የፈለግህበት ፡ እሄዳለሁ
[See also 'else']

**apart**
1. ተለያይተው. They live apart. ተለያይተው ፡ ይኖራሉ
2. በ - - - ልዩነት. The eruptions of the volcano came about one hour apart. የእሳተ ፡ ገሞራው ፡ መፈንዳት ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ልዩነት ፡ ይደርስ ፡ ነበር
3. ለየብቻው. They viewed each idea apart. እያንዳንዱን ፡ ሐሳብ ፡ ለየብቻው ፡ መረመሩት

**be apart**
1. ተራራቀ. The two houses are a mile apart. ሁለቱ ፡ ቤቶች ፡ አንድ ፡ ማይል ፡ ይራራቃሉ
2. ተበላለጠ. We are four years apart in age. በዕድሜ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ እንበላለጣለን

**apart from** ከ - - - በስተቀር
Apart from newspapers, he reads very little. ከጋዜጦች ፡ በስተቀር ፡ ብዙም ፡ አያነብ
The book interested me apart from the plot. ከታሪኩ ፡ በስተቀር ፡ መጽሐፉ ፡ በጠቅላላው ፡ አስደስቶኛል
[See also 'fall, keep, take, tell']

**apartment** አፓርተማ
Our apartment has three rooms. አፓርተማችን ፡ ባለሦስት ፡ ክፍል ፡ ነው

**apathy** ግዴለሽነት
After his father's death, he displayed apathy. አባቱ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ግዴለሽነት ፡ ይታይበት ፡ ነበር

**ape** ጦጣ
Apes ate up the grain. ጦጣ ፡ እህል ፡ ጨረሰ

**aperture** ቀዳዳ
A window is an aperture for letting in air and light. መስኮት ፡ አየርና ፡ ብርሃን ፡ ማስገቢያ ፡ ቀዳዳ ፡ ነው

**apex** ከፍተኛ ፡ ደረጃ
The apex of Mussolini's reign was the conquest of Ethiopia. የሙሶሊኒ ፡ የግዛት ፡ ዘመን ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የደረሰው ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረ ፡ ጊዜ ፡ ነበር

**aphorism** እውነትን ፡ የሚገልጽ ፡ ምሳሌ
A collection of aphorisms is found at the end of the book. በመጽሐፉ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ እውነትን ፡ የሚገልጽ ፡ ምሳሌ ፡ አለ

**apiece**
*The apples are five cents apiece. የእያንዳንዱ ፡ ፖም ፡ ዋጋ ፡ አምስት ፡ ሳንቲም ፡ ነው
*We ate an orange apiece. እያንዳንዳችን ፡ አንዳንድ ፡ ብርቱካን ፡ በላን

**apologize** ይቅርታ ፡ ጠየቀ ፤ ይቅርታ ፡ ለመነ
He apologized for being so bold as to speak to the general. ጄኔራሉን ፡ ደፍሮ ፡ በመናገሩ ፡ ይቅርታ ፡ ጠየቀ
She lost her temper and apologized in the same breath. ተቈጥታ ፡ ያኔውኑ ፡ ይቅርታ ፡ ለመነች
*I apologize for troubling you. ስለ ፡ አስቸገርኩህ ፡ ይቅርታ ፡ አድርግልኝ

**apology** ይቅርታ ፡ መጠየቅ ፤ ይቅርታ
The boy's apology conciliated his angry father.

የልጁ ፡ ይቅርታ ፡ መጠየቅ ፡ ያባቱን ፡ ንዴት ፡ አበረደው
You owe me an apology for being late. በመዘግየትህ ፡ ይቅርታ ፡ ልትጠይቀኝ ፡ ይገባል

**apoplexy** የሚጥል ፡ በሽታ
He had an attack of apoplexy and cannot go to work. የሚጥል ፡ በሽታ ፡ ተነሥቶበት ፡ ስለነበር ፡ ሥራ ፡ ሊሄድ ፡ አይችልም

**apostate** ሃይማኖት ፡ የከዳ ፡ ሰው
The apostate from Islam later became a famous churchman. የእስላምን ፡ ሃይማኖት ፡ የከዳው ፡ ሰው ፡ በኋላ ፡ የታወቀ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካህን ፡ ሆነ

**apostle** ሐዋርያ
Jesus had twelve apostles. ኢየሱስ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሐዋርያት ፡ ነበሩት

**apothecary** መድኃኒት ፡ ቀማሚ
The apothecary gave me the wrong prescription. መድኃኒት ፡ ቀማሚው ፡ ለኔ ፡ የማይገባውን ፡ መድኃኒት ፡ ሰጠኝ

**apotheosis**
1. [በጥንት ፡ ሮማውያን ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ ሲሞት ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ መመልከት]
2. ምሳሌ. To her husband, she was the apotheosis of womanhood. በባልዋ ፡ ዘንድ ፡ እሷ ፡ የሴት ፡ ምሳሌ ፡ ናት

**appall** አስደነገጠ
This news appalled us. ይህ ፡ ወሬ ፡ አስደነገጠን

**be appalled** ተሸበረ
We were appalled at the thought of another war. ሌላ ፡ ጦርነት ፡ ይነሣል ፡ ብለን ፡ በማሰብ ፡ እንሸበር ፡ ነበር

**appalling**
1. የሚያሰቅቅ. I saw an appalling accident in the street. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ የሚያሰቅቅ ፡ አደጋ ፡ አየሁ
2. የሚያሳዝን. There was an appalling number of victims after the earthquake. ከመሬት ፡ መንቀጥቀጡ ፡ በኋላ ፡ የሚያሳዝኑ ፡ ብዙ ፡ የተጐዱ ፡ ነበሩ

**apparatus** መሣሪያ
An apparatus made of bowls and pipes is used in making arack. እንስራና ፡ መሳቢያ ፡ ካለው ፡ መሣሪያ ፡ አረቄ ፡ ለማውጣት ፡ ይጠቅማል

**apparel** ልብስ
His apparel was splattered with mud. ልብሱ ፡ ላይ ፡ ጭቃ ፡ ተፈናጥቆበት ፡ ነበር

**apparent** ግልጽ
It is apparent that he did not understand the question. ጥያቄውን ፡ እንዳልተረዳው ፡ ግልጽ ፡ ነው
*In spite of his apparent desire to do good, he fails to help the poor. መልካም ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ፍላጎት ፡ ያለው ፡ ቢመስልም ፡ ድኾችን ፡ ሲረዳ ፡ አይታይም
*His apparent sincerity fooled us. ታማኝ ፡ መምሰሉ ፡ አታለለን

**be apparent** ታየ
His contempt for her was apparent in his face. እሷን ፡ መናቁ ፡ በፊቱ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**make apparent** በግልጽ ፡ አመለከተ
His poorly written letter makes it apparent that he would not get the job. መጥፎ ፡ የደብዳቤ ፡ አጻጻፉ ፡ ሥራውን ፡ እንደማያገኝ ፡ በግልጽ ፡ ያመለክታል

**apparently**
1. የ + perfect (affirmative, negative) + ይመስላል. These stones have apparently fallen from the mountain tops. እነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ ከተራራው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ተንከባለው ፡ የወደቁ ፡ ይመስላሉ
He has apparently not changed his mind. ሐሳቡን ፡ ያልለወጠ ፡ ይመስላል
2. (relative imperfect) + ይመስላል (or አይመስልም). He will apparently reduce taxes. ግብር ፡ የሚቀንስ ፡ ይመስላል
Apparently, he will not come today. ዛሬ ፡ የሚመጣ ፡ አይመስልም

**apparition** ጣረሞት — ghost
He does not believe in apparitions. በጣረሞት ፡ አያምንም

**appeal** (vt.) ይግባኝ ፡ አለ
The lawyer decided to appeal the case. ጠበቃው ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ ወሰነ

**appeal** (vi.)
1. ለመነ. The prisoner appealed to the judge for mercy. እስረኛው ፡ ዳኛውን ፡ ምሕረት ፡ ለመነ
The Red Cross appeals to philanthropy. ቀይ ፡ መስቀል ፡ የበጎ ፡ አድራጊዎችን ፡ እርዳታ ፡ ይለምናል
2. ሳበ. This book appeals to university students. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ተማሪዎችን ፡ ይስባል
3. ደስ ፡ አለ. Blue and red appeal to me, but I do not like white. ሰማያዊና ፡ ቀይ ፡ ቀለማት ፡ ደስ ፡ ይሉኛል ፤ ነጭ ፡ ግን ፡ አልወድም

4. ማረከ. This sensuous music appeals to women. ይህ ፡ ሕዋሳትን ፡ የሚያነሣሣ ፡ሙዚቃ ፡ ሴቶችን ፡ ይማርካል
5. የሚመለከት ፡ ነገር ፡ ጻፈ. Many newspapers appeal to the crowd. ብዙ ፡ ጋዜጦች ፡ ተራውን ፡ ሕዝብ ፡ የሚመለከት ፡ ነገር ፡ ይጽፋሉ
6. ስሜት ፡ ሰጠ. It does not appeal to me at all. በፍጹም ፡ ስሜት ፡ አይሰጠኝም
*Appeal to his conscience! ኅሊናውን ፡ እንዲነካው ፡ አድርገህ ፡ ንገረው
[See also 'conscience']

**appeal** (n.)
1. ይግባኝ. The appeal was denied. ይግባኙ ፡ ተከለከለ
2. አቤቱታ. The students presented an appeal to the president of the university. ተማሪዎቹ ፡ ለ ዩኒቨርሲቲው ፡ ፕሬዚዳንት ፡ አቤቱታ ፡ አቀረቡ
3. መጠየቅ. My appeal to her pity met with no response. እንድታዝንልኝ ፡ መጠየቄ ፡ ምንም ፡ ፍሬ ፡ አልሰጠም
4. ስሜት ፡ መቀስቀስ. He wound up his speech with an appeal to everyone's patriotism. የሁሉንም ፡ የሀገር ፡ ፍቅር ፡ ስሜት ፡ በመቀስቀስ ፡ ንግግሩን ፡ ደመደመ

**appear**
1. ብቅ ፡ አለ. He appeared at the last minute. በመጨረሻዋ ፡ ደቂቃ ፡ ብቅ ፡ አለ
2. ታየ. When we reached the top of the hill, the town appeared below us. ከኮረብታው ፡ ጫፍ ፡ በደረስን ፡ ጊዜ ፡ ከተማው ፡ ከበታቻችን ፡ ታየን
3. መጣ. He promised to be here at four, but did not appear until six. በዐሥር ፡ ሰዓት ፡ እመጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ አልመጣም
4. ቀረበ. The defendant failed to appear in court. ተከሳሹ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሳይቀርብ ፡ ቀረ
5. ወጣ. This paper appears every Thursday. ይህ ፡ ጋዜጣ ፡ ኀሙስ ፡ ኀሙስ ፡ ይወጣል
6. መሰለ. He appears to be very sick. በጣም ፡ የታመመ ፡ ይመስላል
It appears to me that the program is a failure. እንደኔ ፡ ፕሮግራሙ ፡ ውድቅ ፡ የሆነ ፡ ይመስለኛል

**appear as** ሆኖ ፡ ሠራ
He appeared as the king in the play. በቲያትሩ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ሆኖ ፡ ሠራ

**appearance**
1. መልክ. I never judge by appearance. ፍጹም ፡ በመልክ ፡ አልገምትም
2. መልክና ፡ አለባበስ. You have to pay more attention to your appearance. ለመልክህና ፡ ለአለባበስህ ፡ የበለጠ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ አለብህ
3. ሰውነት. A man in your position has to be careful of his appearance. ባንተ ፡ ሁኔታ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ለሰውነቱ ፡ መጠንቀቅ ፡ አለበት
4. ብቅ ፡ ማለት. His sudden appearance startled her. ድንገት ፡ ብቅ ፡ ማለቱ ፡ አስደነገጣት
5. መታየት. It is his first appearance on the stage. ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ መታየቱ ፡ ነው

**give the appearance of** (relative tense) + ተመስሎ ፡ ታየ
Mary gives the appearance of being busy, but she gets little done. ሜሪ ፡ የምትጣደፍ ፡ መስላ ፡ ትታያለች ፤ ግን ፡ ሥራ ፡ ጠብ ፡ አይልላትም

**keep up appearances** ሁኔታ ፡ ጠበቀ
Keep up appearances while you are looking for a new job. አዲስ ፡ ሥራ ፡ ስትፈልግ ፡ ሁኔታህን ፡ ጠብቅ

**outward appearance** መልክ
The outward appearance of things can be deceptive. መልክ ፡ አሳሳች ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

**make an appearance** ብቅ ፡ አለ
At least make an appearance! ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ብቅ ፡ በል

**put in an appearance** ብቅ ፡ አለ
I do not want to go to the party, but I had better put in an appearance. ወደ ፡ ግብዣው ፡ ስፍራ ፡ ለመሄድ ፡ አልፈልግም ፤ ግን ፡ ብቅ ፡ ብል ፡ ይሻለኛል

**to all appearances**
*He was, to all appearances, dead. እንደሚታየው ፡ የሞተ ፡ ይመስላል
[See also 'majestic']

**appease**
1. አበረደ. He tried to appease his anger by offering him money. ገንዘብ ፡ በመስጠት ፡ ቁጣውን ፡ ለማብረድ ፡ ሞከረ
2. ፍላጎት ፡ አረካ. Chamberlain appeased Hitler at Munich. ቻምበርሌን ፡ ሙኒክ ፡ ላይ ፡ የሂትለርን ፡ ፍላጎት ፡ አረካ
[See also 'hunger']

**appellation** አጠራር
The appellation "Habasha" is not liked by Ethiopians. ሐበሻ ፡ የሚለው ፡ አጠራር ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ አይወደድም

**append** አያያዘ
He appended his photograph to his letter of

application. ከማመልከቻው ፡ ጋር ፡ ፎቶግራፉን ፡ አያያዘ

**appendage** ቅጥል ፡ አካል
The tail of a cat is an appendage. የድመት ፡ ጭራ ፡ ቅጥል ፡ አካል ፡ ነው

**appendicitis** የትርፍ ፡ አንጀት ፡ በሽታ
Appendicitis requires a surgical operation. የትርፍ ፡ አንጀት ፡ በሽታ ፡ ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ያስፈልገዋል

**appendix**
1. ትርፍ ፡ አንጀት. His appendix is inflamed. ትርፍ ፡ አንጀቱን ፡ አሞታል
2. ተጨማሪ ፡ መግለጫ. The appendix of this book deals with the genealogy of the kings. የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጨማሪ ፡ መግለጫ ፡ ስለ ፡ ነገሥታቱ ፡ የዘር ፡ ግንድ ፡ ይናገራል

**appertain** ተመለከተ
These are the duties that appertain to your office. ይህ ፡ ያንተን ፡ የሥራ ፡ ክፍል ፡ የሚመለከት ፡ ኀላፊነት ፡ ነው

**appetite**
1. የምግብ ፡ ፍላጎት. Our boy has a good appetite. ልጃችን ፡ ጥሩ ፡ የምግብ ፡ ፍላጎት ፡ አለው
2. ፍላጎት. The lively boys have a great appetite for amusement. ንቁዎቹ ፡ ልጆች ፡ ከፍተኛ ፡ የጨዋታ ፡ ፍላጎት ፡ አላቸው

**have an appetite** ራበ(ው)
After a walk, I have a sharp appetite. ከሽርሽር ፡ በኋላ ፡ በጣም ፡ ይርበኛል
[See also 'hearty, sharpen, spoil, stimulate, whet']

**applaud**
1. አጨበጨበ ፤ በጭብጨባ ፡ አደነቀ. When he finished speaking, the crowd applauded. ንግግሩን ፡ ሲጨርስ ፡ ሕዝቡ ፡ አጨበጨበ ፡ (በጭብጨባ ፡ አደነቀ)
2. አደነቀ. I applaud your courage. ጉብዝናህን ፡ አደንቃለሁ

**applause** ጭብጨባ
He was greeted by applause. በጭብጨባ ፡ ተቀበሉት

**bring applause** ጭብጨባን ፡ አተረፈ
The speaker's measured words brought applause. ተናጋሪው ፡ መርጦ ፡ የተናገራቸው ፡ ቃላት ፡ ጭብጨባን ፡ አተረፉ

**apple** ቱፋሕ ፤ ፖም

**appliance** መሣሪያ
They sell all kinds of electrical appliances. ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ የኤሌክትሪክ ፡ መሣሪያ ፡ ይሸጣሉ

**(be) applicable** ሠራ
The rule is not applicable in this case. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ደንብ ፡ አይሠራም

**applicant** አመልካች
There were many applicants for the job. ለሥራው ፡ ብዙ ፡ አመልካቾች ፡ ነበሩ

**application**
1. ማመልከቻ. Fill out this application blank! ይህን ፡ ማመልከቻ ፡ ፎርም ፡ ሙላ
2. መጠቀም. The application of the penal code to this case is incorrect. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መጠቀም ፡ ስሕተት ፡ ነው
3. በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል. Serious difficulties may arise from the application of this law. ይህን ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ሊፈጥር ፡ ይችላል
4. አሠራር. The application of what you know will help you to solve new problems. የምታውቀው ፡ አሠራር ፡ ላዳዲስ ፡ ችግሮች ፡ መፍትሔ ፡ ለማግኘት ፡ ይረዳሃል
5. ጥረት. If you show application to your studies, you will succeed. ለትምህርትህ ፡ ጥረት ፡ ብታደርግ ፡ ይሳካልሃል
6. መትጋት. By application to his work, he got a better job. በሥራው ፡ ላይ ፡ በመትጋቱ ፡ የተሻለ ፡ ሥራ ፡ አገኘ
7. የሚቀባ ፡ መድኃኒት. This application is made of various ointments. የሚቀባ ፡ መድኃኒት ፡ የሚሠራው ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅባቶች ፡ ነው

**letter of application** ማመልከቻ
He appended his photograph to his letter of application. ከማመልከቻው ፡ ጋር ፡ ፎቶግራፉን ፡ አያያዘ

**make an application** አመለከተ
We made an application to the court for an investigation. ምርመራ ፡ እንዲደረግ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አመለከትን

**applied** (adj.) ተግባራዊ
He published a textbook of applied mathematics. ተግባራዊ ፡ የሒሳብ ፡ መጽሐፍ ፡ አሳተመ

**apply** (applied), vt.
1. ሠራ. I had to apply all my strength. ባለኝ ፡ ዐቅም ፡ ሁሉ ፡ መሥራት ፡ ነበረብኝ

2. አሰረ. The nurse applied a bandage to the wound. ነርሷ ፡ ቁስሉን ፡ በፋሻ ፡ አሰረች
3. ተጠቀመ(በት). You have applied this rule incorrectly. ይህን ፡ ደንብ ፡ በስሕተት ፡ ተጠቅመህበታል
4. በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለ. He knows the rule, but does not know how to apply it. ደንቡን ፡ ያውቀዋል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንዴት ፡ እንደሚያውለው ፡ አያውቅም
5. ቀባ. He applied iodine to the cut on his arm. ክንዱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ቁስል ፡ አዮዲን ፡ ቀባው

**apply** (vi.)
1. አመለከተ. I would like to apply for a job. ሥራ ፡ እንዲሰጠኝ ፡ ላመለክት ፡ እፈልጋለሁ
2. ተመለከተ. What I have just said applies especially to you. አሁን ፡ የተናገርኩት ፡ በተለይ ፡ አንተን ፡ ይመለከታል
3. ጸና. This law applies to men and women alike. ይህ ፡ ሕግ ፡ ለወንዶችም ፡ ለሴቶችም ፡ እኩል ፡ ይጸናል
4. አግባብነት ፡ አለው The rule does not apply here. ሕጉ ፡ እዚህ ፡ አግባብነት ፡ የለውም

**apply oneself** ጥረቱን ፡ ሁሉ ፡ አዋለ
He applied himself to the task of getting rid of the slums. ጥረቱን ፡ ሁሉ ፡ የከተማውን ፡ ቆሻሻ ፡ ክፍል ፡ ለማጥፋት ፡ አዋለ
[See also 'brake']

## appoint
1. ሾመ. The Emperor appointed him judge. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዳኛ ፡ አድርገው ፡ ሾሙት
2. መረጠ. The teacher appointed me to score for both sides. አስተማሪው ፡ ለሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ እንድቈጥር ፡ መረጠኝ
3. ወሰነ. Appoint a time for the meeting! ለስብሰባው ፡ ጊዜ ፡ ወስን

## appointed (adj.) የተወሰነ
The time appointed for the meeting was 8 o'clock. ለስብሰባው ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ነበር

## appointee የተሾመ ፡ ሰው
The official gazette contains a list of the names of new appointees. ነጋሪት ፡ ጋዜጣው ፡ አዲስ ፡ የተሾሙትን ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ ይዟል

## appointment
1. ቀጠሮ. Did you make an appointment with the doctor? ከሐኪሙ ፡ ጋር ፡ ቀጠሮ ፡ አደረግህ?
2. ሹመት. The Emperor made several appointments to the office of judge today. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዛሬ ፡ ብዙ ፡ የዳኝነት ፡ ሹመት ፡ ሰጡ
He got a good appointment in a business firm. ባንድ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ ደኅና ፡ ሹመት ፡ አገኘ

## apportion አከፋፈለ
He apportioned the profits among the partners. ትርፉን ፡ ለማኅበርተኞቹ ፡ አከፋፈለ

## appraisal የገመተ
His appraisal of the damage was less than fifty dollars. የደረሰውን ፡ ጥፋት ፡ የገመተው ፡ ከኀምሳ ፡ ብር ፡ ያነሰ ፡ አድርጎ ፡ ነው

**make an appraisal** ገመተ
He made an appraisal of the deceased's estate. የሟቹን ፡ ንብረት ፡ ገመተ

## appraise
1. አመዛዘነ. The teacher appraises the ability of his pupils. አስተማሪው ፡ የተማሪዎቹን ፡ ችሎታ ፡ ያመዛዝናል
2. ገመተ. He appraised the property for taxation. ለግብር ፡ አከፋፈል ፡ እንዲመች ፡ ንብረቱን ፡ ገመተ

## appreciable ጉልህ
There is an appreciable difference in the results of the students who study and those who do not study. በሚያጠኑና ፡ በማያጠኑ ፡ ተማሪዎች ፡ ውጤት ፡ መካከል ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ልዩነት ፡ አለ

## appreciate (vt.)
1. ወደደ. We appreciate a holiday after a year of hard work. ካንድ ፡ ዓመት ፡ ከባድ ፡ የሥራ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ዕረፍት ፡ ቢሰጠን ፡ እንወዳለን
2. ዋጋ ፡ ሰጠ. He does not seem to appreciate what I have done for him. ላደረግሁለት ፡ ነገር ፡ ዋጋ ፡ የሚሰጠው ፡ አይመስለኝም
3. በጣም ፡ ደስ ፡ አለ(ው). I would appreciate it, if you could come. ብትመጣ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለኛል
4. አደነቀ. A frivolous person will not appreciate a thoughtful book. አስተሳሰቡ ፡ ቀላል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ጥልቅ ፡ መጽሐፍ ፡ አያደንቅም
5. አመሰገነ. I appreciate your kindness. ስለ ፡ ደግነትህ ፡ አመሰግንሃለሁ
6. አስወደደ. New buildings appreciate the value of land. አዳዲስ ፡ ሕንጻዎች ፡ የመሬትን ፡ ዋጋ ፡ ያስወድዳሉ
7. ተገነዘበ. Everyone can appreciate the danger of war. ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ጦርነት ፡ የሚያስከትለውን ፡ አደጋ ፡ ሊገነዘብ ፡ ይችላል
8. ተሰማ(ው). A musician can appreciate any differences in sound. ሙዚቀኛ ፡ በድምፅ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ማንኛቸውም ፡ ዓይነት ፡ ልዩነት ፡ ይሰማዋል

**appreciate** (vi.) ዋጋ ፡ ጨመረ
This land will appreciate as soon as good roads are built. ደኅና ፡ መንገዶች ፡ በተሠሩ ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ መሬት ፡ ዋጋ ፡ ይጨምራል

**appreciation**
1. ምስጋና. I do not expect any appreciation. ምንም ፡ ምስጋና ፡ አልጠባበቅም
2. አድናቆት. The children's concerts foster an appreciation of music. የሕፃናት ፡ ኮንሰርት ፡ የሙዚቃን ፡ አድናቆት ፡ ያነቃቃል
3. ስሜት. She has no appreciation for art. ለኪነ ፡ ጥበብ ፡ ምንም ፡ ስሜት ፡ የላትም

**appreciative**
1. አመስጋኝ. She does not seem very appreciative of the kindness done for her. ለተደረገላት ፡ ውለታ ፡ አመስጋኝ ፡ አትመስልም
2. ሐሳቡን ፡ ተቀባይ. The appreciative audience cheered. ሐሳቡን ፡ ተቀባይ ፡ የሆኑት ፡ አድማጮች ፡ አጨበጨቡ

**apprehend**
1. ያዘ. The police apprehended the thief. ፖሊሱ ፡ ሌባውን ፡ ያዘው
2. ተረዳ(ው). +He fully apprehended what he read. ያነበበውን ፡ በሙሉ ፡ ተረዳው
[See also 'danger']

**apprehension**
1. መያዝ. The apprehension of the thief was announced over the radio. የሌባው ፡ መያዝ ፡ በሬዲዮ ፡ ተነገረ
2. ማወቅ. Apprehension of the fundamental principles of health is essential. መሠረታዊ ፡ የጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ዘዴን ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
3. ፍርሃት. The roar of the hurricane filled us with apprehension. የዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ጩኸት ፡ ፍርሃት ፡ አሳደረብን

**be filled with apprehension** በጣም ፡ ሰጋ
He was filled with apprehension about the exam. ስለ ፡ ፈተናው ፡ በጣም ፡ ሰግቶ ፡ ነበር

**have a clear apprehension of** የመረዳት ፡ ችሎታ ፡ አለው
He has a clear apprehension of arithmetic. ሒሳብን ፡ የመረዳት ፡ ችሎታ ፡ አለው

**(be) apprehensive** ሰጋ
John was apprehensive about his test marks. ጆን ፡ ስለ ፡ ፈተናው ፡ ውጤት ፡ ይሰጋ ፡ ነበር

**apprentice** ተለማማጅ
He is an apprentice in masonry. እሱ ፡ የግምበኝነት ፡ ሥራ ፡ ተለማማጅ ፡ ነው

**apprise** አስጠነቀቀ
I apprised him of the danger. ስለ ፡ አደጋው ፡ አስጠነቀቅሁት

**approach** (vt.)
1. ጠየቀ. How shall I approach my boss about a raise? አለቃዬን ፡ ስለ ፡ ደሞዝ ፡ ጭማሪ ፡ እንዴት ፡ ልጠይቀው?
2. አነጋገረ. Who shall I approach about it? ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ማንን ፡ ላነጋግር?
Have you approached your father about letting you have a bicycle? ቢስክሌት ፡ እንዲገዙልህ ፡ አባትህን ፡ አነጋገርካቸው?
3. አደረገ. How would you approach the problem? ችግሩን ፡ እንዴት ፡ ታደርገዋለህ ?
4. (= intr.) ተቀራረበ. The painter used a green paint that approached what he wanted. ቀለም ፡ ቀቢው ፡ እሱ ፡ ከሚፈልገው ፡ ጋር ፡ የሚቀራረብ ፡ አረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ ቀባ
5. ደረሰ(በት). As a poet, he hardly approaches Keats. በገጣሚነት ፡ ኪትስን ፡ አይደርስበትም

**approach** (vi.)
1. ቀረበ. They approached cautiously. በጥንቃቄ ፡ ቀረቡ
2. መጣ. We cast about for something to do during the approaching vacation. ለሚመጣው ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ የምንሠራውን ፡ ለማግኘት ፡ አወጣን ፡ አወረድን

**approach** (n.)
1. መቃረብ. The enemy fled at our approach. በመቃረባችን ፡ ጠላት ፡ ሸሸ
2. ዘዴ. He invented a new approach to the study of language. ለቋንቋ ፡ ጥናት ፡ አዲስ ፡ ዘዴ ፡ ፈጠረ
3. አቋም. Our director has a straightforward approach to the problem. ዲሬክተራችን ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ የማያወላውል ፡ አቋም ፡ አላቸው
4. የሚወስድ ፡ መንገድ. The approaches to the bridge are under repair. ወደ ፡ ድልድዩ ፡ የሚወስዱት ፡ መንገዶች ፡ በመጠገን ፡ ላይ ፡ ናቸው

**approbation** ድጋፍ
Our plans have the teacher's approbation. እቅዳችን ፡ ያስተማሪውን ፡ ድጋፍ ፡ አግኝቷል

**appropriate** (v.)
1. መደበ. The city has appropriated fifty thousand dollars for a new library. ከተማይቱ ፡ ላዲስ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ኀምሳ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ መድባለች
2. ወሰደ(በት). My son has appropriated all my ties. ልጄ ፡ ክራቫቶቼን ፡ በሙሉ ፡ ወሰደብኝ

3. ለራሱ ፡ ወሰደ. He appropriated the most comfortable chair in the room. ከፍሉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ምቹ ፡ የሆነውን ፡ ወንበር ፡ ለራሱ ፡ ወሰደ
4. ከለለ. The government appropriated land for a military base. መንግሥቱ ፡ ለጦር ፡ ሰፈር ፡ የሚሆን ፡ ቦታ ፡ ከለለ

**appropriate** (adj.) ተገቢ
The remark is quite appropriate. አስተያየቱ ፡ በእውነት ፡ ተገቢ ፡ ነው

**approval**
1. ፈቃድ. You will need your parents' approval. የወላጆችህ ፡ ፈቃድ ፡ ያስፈልግሃል
2. አድናቆት. The audience showed its approval by applauding. አድማጩ ፡ አድናቆቱን ፡ በጭብጨባ ፡ ገለጸ
3. መስማማት. He misconstrued her silence as approval. ዝምታዋን ፡ እንደ ፡ መስማማት ፡ አድርጎ ፡ በስሕተት ፡ ተረዳው
*This plan has the teacher's approval. ይህ ፡ እቅድ ፡ ባስተማሪው ፡ ተደግፏል

**on approval**
*They sent me the book on approval. ባይስማማኝ ፡ ልመልስ ፡ ፈቅደው ፡ መጽሐፉን ፡ ላኩልኝ
[See also 'meet']

**approve**
1. አጸደቀ. The senate approved the treaty. የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ስምምነቱን ፡ አጸደቀ
2. አመሰገነ. The teacher looked at John's work and approved it. አስተማሪው ፡ የጆንን ፡ ሥራ ፡ አይቶ ፡ አመሰገነው
3. ደገፈ. Do you approve of kissing in public? በአደባባይ ፡ መሳሳምን ፡ ትደግፋለህ ?
4. ፈቀደ(ለት). He approved his request for additional money. የጠየቀውን ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ፈቀደለት
5. ተስማማ. Her father approved of her marriage. አባቷ ፡ በጋብቻዋ ፡ ተስማማ

**be approved** ተቀባይነት ፡ አገኘ ፤ ተቀበለ
Your application will have to go through the proper channels before it is approved. ማመልከቻህ ፡ ተቀባይነት ፡ ከማግኘቱ ፡ (ከመቀበሉ) ፡ በፊት ፡ በተገቢዎቹ ፡ ክፍሎች ፡ በኩል ፡ መምጣት ፡ አለበት

**approving** የመስማማት
The speaker was answered by a chorus of approving shouts. ሕዝቡ ፡ በኅብረት ፡ በመጮኸ ፡ ለተናጋሪው ፡ የመስማማት ፡ መልስ ፡ ሰጠው

**approvingly** በመስማማት
She nodded approvingly. በመስማማት ፡ ራሷን ፡ ደፋ ፡ ቀና ፡ አደረገች

**approximate** (v.)
1. ተቃረበ. The translation approximates the original. ትርጉሙ ፡ ከዋናው ፡ ይቃረባል
2. ያህል ፡ ነበር. The crowd approximated a thousand people. ሕዝቡ ፡ ዐሥር ፡ ሺ ፡ ያህል ፡ ነበር

**approximate** (adj.)
1. (= adv.) በግምት. The approximate time of the trip is ten hours. የጉዞው ፡ ጊዜ ፡ በግምት ፡ ዐሥር ፡ ሰዓት ፡ ነው
2. (= adv.) ከሞላ ፡ ጐደል. The approximate length of the room is eight feet. የክፍሉ ፡ ርዝመት ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ስምንት ፡ ጫማ ፡ ያህል ፡ ይሆናል
The painting is an approximate copy of one by Rembrandt. ሥዕሉ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ሬምብራንት ፡ የሠራው ፡ ሥዕል ፡ ግልባጭ ፡ ነው

**approximately**
1. ያህል. He will stay abroad approximately a month. አንድ ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ይቆያል
2. በግምት. Addis Ababa is approximately midway between Asmara and Nairobi. በግምት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለአሥመራና ፡ ለናይሮቢ ፡ አማካይ ፡ ስፍራ ፡ ናት

**approximation** ግምት
About 93,000,000 miles is an approximation of the distance of the earth from the sun. ከመሬት ፡ እስከ ፡ ፀሐይ ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ ግምት ፡ 93,000,000 ማይል ፡ ያህል ፡ ነው

**appurtenances** ተጨማሪ
He showed me the house and all appurtenances, such as the garage and the servants' quarters. ቤቱንና ፡ እንዲሁም ፡ የመኪና ፡ ማቆሚያ ፡ ቤቱን ፤ ያሽከር ፡ ቤቱን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ተጨማሪ ፡ ሁሉ ፡ አሳየኝ

**April** ሚያዝያ

**apron** ሽርጥ
She wears an apron when she cooks. ምግብ ፡ ስትሠራ ፡ ሽርጥ ፡ ታሸርጣለች

**tied to someone's apron strings**
He is still tied to his mother's apron strings. ገና ፡ ከእናቱ ፡ ጉያ ፡ አልወጣም

**apropos of** ስለ - - - ነገር
Apropos of your vacation, what will you do? ስለ ፡ ዕረፍትህ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ልታደርግ ፡ አሰበሃል ?

**apt**
1. ንቁ. He is a very apt pupil. እሱ ፡ በጣም ፡ ንቁ ፡ ተማሪ ፡ ነው
2. ተገቢ. That is a very apt remark. በጣም ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ አስተያየት ፡ ነው

**be apt to**
1. ሰ + negative imperfect + አይቀርም. A careless person is apt to make mistakes. ግዴለሽ ፡ ሰው ፡ ስሕተት ፡ ሳይሠራ ፡ አይቀርም
2. imperfect + ይሆናል. He is apt to come in the middle of the night. በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ላይ ፡ ይመጣ ፡ ይሆናል

**aptitude** ስጦታ
He has an aptitude for foreign languages. የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋዎች ፡ ለመማር ፡ ስጦታ ፡ አለው

**aqueduct** [ውኃ ፡ ካንድ ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ የሚወሰድበት ፡ ትልቅ ፡ ቧምቧ ፡ ወይንም ፡ ቦይ]

**Arab** ዐረብ

**Arabia** የዐረብ ፡ አገር

**Arabic** ዐረብኛ
Arabic is close to Geez. ዐረብኛ ፡ ለግዕዝ ፡ ይቀርባል

**(be) arable** ለእርሻ ፡ ሆነ
The land in this region is arable. የዚህ ፡ አካባቢ ፡ መሬት ፡ ለእርሻ ፡ ይሆናል

**arbiter** አስታራቂ
He was chosen arbiter for the border problem. ስለ ፡ ወሰኑ ፡ ጉዳይ ፡ አስታራቂ ፡ ሆኖ ፡ ተመረጠ

**arbitrary**
1. የተገመደለ. A good judge does not make arbitrary decisions. ጥሩ ፡ ዳኛ ፡ የተገመደለ ፡ ፍርድ ፡ አይሰጥም
2. በፈቃዱ ፡ የሚገዛ. He is an intelligent, but arbitrary ruler. ብልህ ፡ ነው ፤ ግን ፡ በፈቃዱ ፡ የሚገዛ ፡ ገዢ ፡ ነው

**arbitrate** አስታረቀ
The judge is going to arbitrate the dispute. ዳኛው ፡ ጠቡን ፡ ሊያስታርቅ ፡ ነው

**arbitrate between** አስማማ
The committee will arbitrate between the company and the striking workmen. ደርጉ ፡ ኩባንያውንና ፡ ሥራ ፡ ያቆሙትን ፡ ሠራተኞች ፡ ያስማማል

**arbitrator** አስታራቂ
The quarrel was resolved by an arbitrator. ጥሉ ፡ ባስታራቂ ፡ መፍትሔ ፡ አገኘ

**arc** ቅስት
The fortification is in the shape of an arc. ምሽጉ ፡ በቅስት ፡ ቅርጽ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**arcade** [በምሰሶ ፡ የተደገፉ ፡ ተቀጣጣይ ፡ ቅስቶች]

**arch** (n.) ቅስት
The city erected a triumphal arch in his honor. ከተማዋ ፡ ስለ ፡ ክብሩ ፡ የድል ፡ ቅስት ፡ አቆመችለት

**arch** (adj.) ቀንደኛ
The arch rebel was Patrick Henry. ቀንደኛው ፡ ዐመፀኛ ፡ ፓትሪክ ፡ ሄንሪ ፡ ነበር

**archaic** የጥንት
There are many archaic words in Amharic. ባማርኛ ፡ ብዙ ፡ የጥንት ፡ ቃላት ፡ አሉ

**archangel** ሊቀ ፡ መልአክ
The archangel Gabriel made the annunciation to Mary. ሊቀ ፡ መልአኩ ፡ ገብርኤል ፡ ለማርያም ፡ የምስራቹን ፡ ነገራት

**archbishop** ሊቀ ፡ ጳጳስ
The archbishop gave the blessing. ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ቡራኬ ፡ ሰጡ

**archeology** አርኬዎሎጂ

**archipelago** ተጐራባች ፡ ደሴቶች

**architect**
1. ፕላን ፡ የነደፈ. Who is the architect of this building? የዚህን ፡ ሕንጻ ፡ ፕላን ፡ የነደፈ ፡ ማን ፡ ነው ?
2. መሀንዲስ. Is Afework the architect of Africa Hall? አፈወርቅ ፡ የአፍሪካ ፡ አዳራሽ ፡ መሀንዲስ ፡ ነው ?

**architecture**
1. የሕንጻ ፡ ጥበብ. The university has a school of architecture. ዩኒቨርሲቲው ፡ የሕንጻ ፡ ጥበብ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አለው
2. የሕንጻ ፡ አሠራር. Some people think that the architecture of this castle is Portuguese. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የዚህ ፡ ግንብ ፡ የሕንጻ ፡ አሠራር ፡ የፖርቱጋሎች ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያስባሉ
3. የሕንጻ ፡ አሠራር ፡ ዘዴ. Greek architecture made use of columns. የግሪኮች ፡ የሕንጻ ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ በምሰሶ ፡ በመጠቀም ፡ ነበር

**archive(s)** መዝገብ ፡ ቤት
He filed the document in the Foreign Ministry's archives. ሰነዱን ፡ ከውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ አኖረው

**archway** የቅስት ፡ በር
The archway by the palace was decorated with flags. ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሚያስገባው ፡ የቅስት ፡ በር ፡ በሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ተጊጦ.ል

**Arctic** አርክቲክ
The Arctic is always cold. አርክቲክ ፡ ሁልጊዜ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ነው

**ardent**
1. ጽኑ. He is an ardent defender of human liberty. ጽኑ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ ተከራካሪ ፡ ነው
2. ኀይለኛ. He is an ardent nationalist. ኀይለኛ ፡ የሀገር ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው
*She is an ardent lover of music. ለሙዚቃ ፡ የጋለ ፡ ፍቅር ፡ አላት

**ardor** የጋለ ፡ ስሜት
He expressed his ardor for knowledge in a beautiful poem. ለዕውቀት ፡ ያለውን ፡ የጋለ ፡ ስሜት ፡ በውብ ፡ ግጥም ፡ ገለጸ

**arduous**
1. ብርቱ. He gained strength by arduous exercise. ብርቱ ፡ እንቅስቃሴ ፡ በማድረግ ፡ ጉልበት ፡ ጨመረ
2. በጣም ፡ ከባድ. The arduous lesson made him spend many hours at work. በጣም ፡ ከባዱ ፡ ትምህርት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጥናት ፡ ላይ ፡ እንዲያጠፋ ፡ አደረገው

**area**
1. ስፋት. The area of this room is 150 square meters. የዚህ ፡ ክፍል ፡ ስፋት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ካሬ ፡ ሜትር ፡ ነው
2. አካባቢ. The area around Addis Ababa is densely populated. ያዲስ ፡ አበባ ፡ አካባቢ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አለበት
3. ስፍራ. Bananas grow in tropical areas. ሙዝ ፡ በሞቃት ፡ ስፍራዎች ፡ ይበቅላል
*His major area of study is history. በተለይ ፡ የሚያጠናው ፡ ታሪክ ፡ ነው
[See also 'rural, urban']

**arena** [ዙሪያውን ፡ የታጠረ ፡ የትግል ፡ መወዳደሪያ ፡ ቦታ]

**argot** ልዩ ፡ ንግግር
The argot of thieves is meaningless to other people. የሌቦች ፡ ልዩ ፡ ንግግር ፡ ለሌሎች ፡ ትርጉም ፡ አይሰጥም

**argue**
1. ተጨቃጨቀ. He argued with his sister about who should wash the dishes. ሳሕኖቹን ፡ ማን ፡ እንደሚያጥብ ፡ ከእኅቱ ፡ ጋር ፡ ተጨቃጨቀ
2. ተከራከረ. One side argued for a larger army, and the other argued against it. አንዱ ፡ ወገን ፡ ትልቅ ፡ ጦር ፡ ሰራዊት ፡ እንዲኖረው ፡ ሲከራከር ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ በመቃወም ፡ ተከራከረ
I argued that it would save a lot of time. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያተርፍልናል ፡ ብዬ ፡ ተከራከርኩ
3. ተሟገተ. He argued his case before the court. በጉዳዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ተሟገተ

**argue into** አግባባ
The boy couldn't argue his father into buying him a new bicycle. ልጁ ፡ አባቱ ፡ አዲስ ፡ ቢስክሌት ፡ እንዲገዙለት ፡ ሊያግባባቸው ፡ አልቻለም

**argument**
1. ክርክር ፤ ጭቅጭቅ. I don't want any argument from you. ካንተ ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ክርክር ፡ (ጭቅጭቅ) ፡ አልፈልግም
This form of argument is not admissible. ይህ ፡ ዓይነት ፡ ክርክር ፡ አይፈቀድም
2. የመከላከያ ፡ ምክንያት. Cancer is a strong argument against smoking. ማጨስን ፡ ለመቃወም ፡ የካንሰር ፡ በሽታ ፡ ብርቱ ፡ የመከላከያ ፡ ምክንያት ፡ ነው
3. ሐሳብ. That is an argument in his favor. ያ ፡ እሱን ፡ የሚደግፍ ፡ ሐሳብ ፡ ነው
4. መረጃ. The lawyer presented an ineffective argument. ጠበቃው ፡ አጥጋቢ ፡ ያልሆነ ፡ መረጃ ፡ አቀረበ

**have an argument** ተጣላ
He is in a bad temper because he had an argument with his wife. ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ስለ ተጣላ ፡ በጣም ፡ ተናዶ ፡ ነበር

**argumentative** ተጨቃጫቂ
It is difficult to get along with an argumentative person. ከተጨቃጫቂ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ለመግባባት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**arid**
1. ደረቅ. The soil in this region is arid. በዚህ ፡ አካባቢ ፡ አፈሩ ፡ ደረቅ ፡ ነው
2. የማያስደስት. Geography is for him an arid subject. ጂኦግራፊ ፡ ለሱ ፡ የማያስደስት ፡ ትምህርት ፡ ነው

**aridity** ድርቀት
The aridity of the climate is bad for the skin. የአየሩ ፡ ንብረት ፡ ድርቀት ፡ ለቆዳ ፡ መጥፎ ፡ ነው

**arise** (arose, arisen)

1. ተነሣ. They all arose at the same time. ሁሉም ፡ ባንድነት ፡ ተነሡ
2. ተፈጠረ. The border problem arose some time ago. የድንበሩ ፡ ችግር ፡ ከተፈጠረ ፡ ቆየት ፡ ብሏል
3. አጋጠመ. As soon as the opportunity arises, I will start work. ዕድል ፡ እንዳጋጠመኝ ፡ ሥራውን ፡ እጀምራለሁ

**arisen**, see **arise**

**aristocracy**

1. መኳንንት. The priests form the aristocracy in some countries. ካህናት ፡ ባንዳንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ከመኳንንት ፡ ክፍል ፡ ይደመራሉ
2. መሳፍንት. The aristocracy has begun to be interested in land reform. መሳፍንቱ ፡ ስለ ፡ መሬት ፡ ይዞታ ፡ መሻሻል ፡ መደገፍ ፡ ጀምረዋል

**aristocrat** ባላባት

Many aristocrats lost their life during the French Revolution. በፈረንሳይ ፡ መሠረታዊ ፡ ለውጥ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ባላባቶች ፡ ሕይወታቸውን ፡ አጡ

**aristocratic**

1. የጌትነት. His pose was aristocratic. ሁኔታው ፡ የጌትነት ፡ ነበር
2. የእመቤትነት. Her pose was aristocratic. ሁኔታዋ ፡ የእመቤትነት ፡ ነበር

**arithmetic** ሒሳብ

They begin teaching arithmetic in the second grade. ሒሳብ ፡ ማስተማር ፡ ከሁለተኛ ፡ ክፍል ፡ ይጀምራሉ

**ark** መርከብ ፤ ሐመር

Noah made an ark for the flood. ኖኅ ፡ በጥፋት ፡ ውኃ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ መርከብ ፡ (ሐመር) ፡ ሠራ

**Ark of the Covenant** የኪዳን ፡ ታቦት

The stone tablets are kept in the Ark of the Covenant. ጽላቶቹ ፡ በኪዳን ፡ ታቦት ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣሉ

**arm** (vt.) አስታጠቀ

The Chinese armed the guerillas with modern weapons. ቻይናውያን ፡ የደፈጣ ፡ ተዋጊዎቹን ፡ ዘመናዊ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ አስታጠቋቸው

**arm** (vi.) ታጠቀ

The country armed for war. አገሪቱ ፡ ለጦርነት ፡ ታጠቀች

**arm** (n.)

1. እጅ. He has lost an arm. እጁን ፡ ተቈርጧል
2. ብብት. Can you carry the package under your arm? ጥቅሉን ፡ በብብትህ ፡ ሥር ፡ ልትይዘው ፡ ትችላለህ?
3. መደገፊያ. The arms of this chair are low. የዚህ ፡ ወንበር ፡ መደገፊያዎች ፡ ዝቅ ፡ ያሉ ፡ ናቸው

**arm in arm** እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተያይዘው

He walked arm in arm with her. እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተያይዘው ፡ ከሷ ፡ ጋር ፡ ሄዱ

**carry in one's arms** አቀፈ

She was carrying a child in her arms. ሕፃን ፡ ታቅፋ ፡ ነበር

**have on one's arm** አንጠለጠለ

She had a basket on her arm. ቅርጫት ፡ አንጠልጥላ ፡ ነበር

**hold in one's arms** ታቀፈ

She held the baby in her arms. ሕፃኑን ፡ ታቀፈችው

**put one's arm around** አቀፈ

He put his arm around her waist. ወገቧን ፡ አቀፈ

**take one in his arms** አቀፈ

He took her into his arms and kissed her. አቅፎ ፡ ሳማት

**with open arms** በደስታ

He welcomed her with open arms. በደስታ ፡ ተቀበላት

[See also 'enfold, fold, give, length, link, lock, open']

**armada** የጦር ፡ መርከብ ፡ ጓድ

The enemy armada is passing by our coast. የጠላት ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ ጓድ ፡ በባሕራችን ፡ ዳርቻ ፡ እያለፈ ፡ ነው

**armament** የጦር ፡ መሣሪያ

The Ethiopian army acquired modern armaments. የኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ ዘመናዊ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ አግኝቷል

**armband** ጉሜ

He wore an armband made of silver. ከብር ፡ የተሠራ ፡ ጉሜ ፡ ክንዱ ፡ ላይ ፡ አድርጓል

**armchair** ምቹ ፡ ወምበር

He relaxed in an armchair. ምቹ ፡ ወምበር ፡ ላይ ፡ ተዝናና

**armed** (adj.) የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የያዘ

The police caught an armed robber. ፖሊሱ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የያዘውን ፡ ቀማኛ ፡ ያዘው

*Each lawyer came to court armed with facts. እያንዳንዱ ፡ ጠበቃ ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ይዞ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀረበ

**be armed**

1. የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ያዘ. Were the robbers armed? ቀማኞቹ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዘው ፡ ነበር ?
2. ተከላከለ. He was armed against the cold with a heavy coat. ኀይለኛውን ፡ ብርድ ፡ በወፍራም ፡ ኮት ፡ ተከላከለው
[See also 'tooth']

**armed forces** የጦር ፡ ኀይሎች
The armed forces of our country have good training. ያገራችን ፡ ጦር ፡ ኀይሎች ፡ በደምብ ፡ ሠልጥነዋል

**armful (of)** እቅፍ ፡ ሙሉ
He brought in an armful of books for me to read. እቅፍ ፡ ሙሉ ፡ መጽሐፍ ፡ እንዳነብ ፡ አመጣልኝ

**armistice** የጦር ፡ ማቆም ፡ ስምምነት
The Americans did not violate the armistice. አሜሪካኖች ፡ የጦር ፡ ማቆም ፡ ስምምነቱን ፡ አልጣሱም

**armor** [በውጊያ ፡ ጊዜ ፡ ከጦርና ፡ ከጐራዴ ፡ ሰውነትን ፡ ለመከላከል ፡ የሚለበስ ፡ የብረት ፡ ልብስ]

**armory** የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ግምጃ ፡ ቤት
The armory was raided by the rebels. የጦር ፡ መሣሪያው ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ በአጋሚዶዎች ፡ ተዘረፈ

**armpit** ብብት
He has hair growing in his armpit. ብብቱ ፡ ውስጥ ፡ ጸጉር ፡ በቅሏል

**arms** መሣሪያ ፤ የጦር ፡ መሣሪያ
Everyone who could carry arms was drafted. መሣሪያ ፡ ለመያዝ ፡ የሚችል ፡ ሁሉ ፡ ተመለመለ
All arms have to be turned over to the police. ማንኛውም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ለፖሊስ ፡ መረከብ ፡ አለበት

**bear arms** የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ያዘ
A grown man is allowed to bear arms. አካለ ፡ መጠን ፡ የደረሰ ፡ ሰው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እንዲይዝ ፡ ይፈቀድለታል

**take up arms** የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ ተነሣ
They took up arms to defend their country. ሀገራቸውን ፡ ለመከላከል ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዘው ፡ ተነሡ

**(be) under arms** ለጦርነት ፡ ታጠቀ
All men were under arms. ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለጦርነት ፡ ታጥቀው ፡ ነበር

**(be) up in arms** በንዴት ፡ ጦፈ
He was up in arms when he learned the news. ወሬውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በንዴት ፡ ጦፈ

**army**

1. ጦር ፤ የጦር ፡ ሰራዊት. The defeated army had to lay down arms. ድል ፡ የተመታው ፡ ጦር ፡ መሣሪያውን ፡ ማስረከብ ፡ ነበረበት
He fought in the Italian army. በኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ ሰራዊት ፡ ውስጥ ፡ ተዋጋ
2. የምድር ፡ ጦር. Did you serve in the army or in the navy? ያገለገልከው ፡ በምድር ፡ ጦር ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ በባሕር ፡ ኀይል ?
3. ወታደርነት. I am joining the army. ወታደርነት ፡ መግባቴ ፡ ነው
4. መዓት. An army of children ran down the street. የሕፃናት ፡ መዓት ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ሮጡ

**aroma** ሽታ
The aroma of coffee is very pleasant. የቡና ፡ ሽታ ፡ በጣም ፡ አስደሳች ፡ ነው

**arose,** see **arise**

**around** (prep., adv.)

1. በ - - - ዙሪያ. The earth moves around the sun. መሬት ፡ በፀሐይ ፡ ዙሪያ ፡ ትዞራለች
They were sitting around the table. በጠረጴዛው ፡ ዙሪያ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር
2. እዚህ. Is there anybody around? እዚህ ፡ ሰው ፡ አለ ?
3. በ - - - ላይ. He tied the rope around the tree. ገመዱን ፡ በዛፉ ፡ ላይ ፡ አሰረው
4. ዙሪያውን. The tree was 40 inches around. ዛፉ ፡ ዙሪያውን ፡ አርባ ፡ ኢንች ፡ ነበር
5. ላይ. She lives right around the corner. ቤቷ ፡ ልክ ፡ መታጠፊያው ፡ ላይ ፡ ነው
6. ያህል. I have around 20 dollars. ሃያ ፡ ብር ፡ ያህል ፡ አለኝ
7. ገደማ. He is around forty years old. ዕድሜው ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ገደማ ፡ ነው
*Is there enough coffee to go around? ለሁሉም ፡ የሚዳረስ ፡ ቡና ፡ ይገኛል ?

**around here** በዚህ ፡ አካባቢ ፤ እዚህ
There is very little activity around here on Sundays. እሑድ ፡ እሑድ ፡ በዚህ ፡ አካባቢ ፡ (እዚህ) ፡ እንቅስቃሴው ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው

**all around**

1. ዙሪያውን. His land is fenced all around. የሱ ፡ መሬት ፡ ዙሪያውን ፡ ታጥሯል
2. በያለበት. There are mailboxes all around the city. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ በያለበት ፡ የፖስታ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ሣጥኖች ፡ አሉ

**be around** በቶሎ ፡ ደረሰ
An unfailing friend will always be around in time of need. እውነተኛ ፡ ወዳጅ ፡ በችግር ፡ ጊዜ ፡ በቶሎ ፡ ይደርሳል

**be around again** ደረሰ
Christmas will soon be around again. ገና ፡ በቅርቡ ፡ ይደርሳል

**have (a coat) around** ጣል ፡ አደረገ
She had a coat around her shoulders. ትከሻዋ ፡ ላይ ፡ ኮት ፡ ጣል ፡ አድርጋ ፡ ነበር

**somewhere around here** እዚሁ ፡ አካባቢ
He lives somewhere around here. እዚሁ ፡ አካባቢ ፡ ይኖራል

**with someone around**
*Don't use bad language with children around. ልጆች ፡ ባሉበት ፡ የብልግና ፡ ቃላት ፡ አትናገር
[See also 'circle, clock, up']

**arouse**
1. ቀሰቀሰ. The mother aroused her son early. እናትዮዋ ፡ ልጇን ፡ በማለዳ ፡ ቀሰቀሰችው
The hunter aroused the wild beast to anger. አዳኙ ፡ ያውሬውን ፡ ንዴት ፡ ቀሰቀሰበት
2. አሳደረ(በት). Her strange behavior aroused my suspicion. ያልተለመደ ፡ ሁኔታዋ ፡ ጥርጣሬ ፡ አሳደረብኝ
[See also 'ire']

**arraign** ከፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረበ
The prosecutor arraigned the tramp on a charge of stealing. ሕግ ፡ አስከባሪው ፡ በሌብነት ፡ ወንጀል ፡ ከሶ ፡ ዱርዬውን ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረበው

**arrange**
1. አዘጋጀ. I arranged it in advance. ቀደም ፡ ብዬ ፡ አዘጋጀሁት
The maid arranged the table for dinner. ገረዲቷ ፡ ጠረጴዛውን ፡ ለእራት ፡ አዘጋጀች
2. አደረገ. I have arranged to meet him at 5 o'clock. በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ እንድንገናኝ ፡ አድርጌያለሁ
3. ደረደረ. Who arranged the books? መጽሐፎቹን ፡ ማን ፡ ደረደረ ?
4. ደለደለ (ተደለደለ). The classes are arranged according to subject. ክፍሎቹ ፡ የተደለደሉት ፡ በትምህርት ፡ ዓይነት ፡ መሠረት ፡ ነው
5. ከ - - - ጋር ፡ አስማማ. He arranged the piano music for the violin. የፒያኖውን ፡ሙዚቃ ፡ ከቫዮሊን ፡ ጋር ፡ አስማማው
6. ወሰነ. The parents sent an old man to act as go-between in arranging an appointment. ወላጆች ፡ ቀጠሮውን ፡ ለመወሰን ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ አማጭ ፡ ላኩ
[See also 'match']

**arranged** (adj.) የታቀደ
The meeting arranged for tomorrow was postponed. ለነገ ፡ የታቀደው ፡ ስብሰባ ፡ ተላለፈ

**arrangement** ማደራጀት
The arrangement of the furniture in our new house took a long time. ባዲሱ ፡ ቤታችን ፡ ውስጥ ፡ የእቃው ፡ ማደራጀት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፈጀ

**make arrangements** ዝግጅት ፡ አደረገ
They made all the necessary arrangements to leave the following morning. በማግሥቱ ፡ ጧት ፡ ለመሄድ ፡ አስፈላጊውን ፡ ዝግጅት ፡ ሁሉ ፡ አደረጉ

**array** (v.) አደራጀ
The general arrayed his troops for the battle. ጀኔራሉ ፡ ወታደሮቹን ፡ ለጦርነት ፡ አደራጀ

**be arrayed** አሸበረቀ
She was arrayed like a queen. እንደ ፡ ንግሥት ፡ አሸብርቃ ፡ ነበር

**array** (n.)
1. ሰልፍ. The troops were formed in battle array. ወታደሮቹ ፡ በጦርነት ፡ ሰልፍ ፡ ተዘጋጁ
2. እቃዎች. The array of silver on the table was quite beautiful. በጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ ከብር ፡ የተሠሩ ፡ እቃዎች ፡ ያምሩ ፡ ነበር

**array of** ብዙ
We were impressed by the array of scholars who came to the meeting. ለስብሰባው ፡ ብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ መምጣታቸው ፡ አስደነቀን

**arrears**
*The arrears of his debt are well over a thousand dollars. ካንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ የበለጠ ፡ የመክፈያ ፡ ጊዜ ፡ የተላለፈበት ፡ ዕዳ ፡ አለበት

**arrest** (v.)
1. ያዘ. The policeman arrested the thief. ፖሊሱ ፡ ሌባውን ፡ ያዘው
2. ማረከ. The bright colors of the flag arrested the children's attention. ደማቆቹ ፡ የባንዲራው ፡ ቀለሞች ፡ የልጆቹን ፡ ስሜት ፡ ማረኩ
3. አቆመ. Filling a tooth arrests decay. የጥርስን ፡ ቀዳዳ ፡ ማስሞላት ፡ መበስበስን ፡ ያቆማል
[See also 'growth']

**arrest** (n.) መታሰር ፤ መያዝ
The arrest of the director was announced

in the papers. የዲሬክተሩ ፡ መታሰር ፡ (መያዝ) ፡ በጋዜጣ ፡ ተገለጸ

**be under arrest** ተያዘ
You are under arrest because you ran through a red light. የትራፊክ ፡ መብራት ፡ ስለጣስክ ፡ ተይዘሃል

**make an arrest** ያዘ
The police made two arrests. ፖሊሶች ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ያዙ

## arrival
1. መድረስ. We waited for the arrival of news. የዜናውን ፡ መድረስ ፡ ተጠባበቅን
2. መድረሻ. The bulletin lists departures and arrivals of all buses. ማስታወቂያው ፡ የአውቶቡሶቹን ፡ ሁሉ ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ ይዘረዝራል
3. የመድረሻ ፡ ጊዜ. He timed his arrival to coincide with the President's visit. ከፕሬዚዳንቱ ፡ ጉብኝት ፡ ጋራ ፡ እንዲገጣጠምለት ፡ አድርጎ ፡ የመድረሻውን ፡ ጊዜ ፡ መጠነ
4. መምጣት. His arrival caused a lot of excitement. የሱ ፡ መምጣት ፡ ብዙ ፡ ግርግር ፡ ፈጠረ

**arrivals** እንግዶች
There are several new arrivals at the hotel. በሆቴሉ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ አዲስ ፡ እንግዶች ፡ አሉ

**ensure the arrival** አደረሰ
This money will ensure your safe arrival in Addis Ababa. ይህ ፡ ገንዘብ ፡ እስከ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በደምብ ፡ ያደርስሃል
[See also 'new, tardy']

## arrive
1. ደረሰ. When will the teacher arrive tomorrow? ነገ ፡ አስተማሪው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ይደርሳል ?
Did they arrive at a decision? ከንድ ፡ ውሳኔ ፡ ደረሱ ?
2. ተሳካ(ለት). After years of hard work he finally arrived. ከብዙ ፡ ዓመት ፡ ልፋት ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ተሳካለት

## arrogance እብሪት ፤ ትዕቢት
His arrogance comes out in every speech he makes. በሚያደርገው ፡ ንግግር ፡ ሁሉ ፡ እብሪት ፡ (ትዕቢት) ፡ ይታይበታል

## arrogant እብሪተኛ ፤ ትዕቢተኛ
Mussolini was a very arrogant dictator. ሙሶሊኒ ፡ በጣም ፡ እብሪተኛ ፡ (ትዕቢተኛ) ፡ አምባገነን ፡ ነበር

## arrogate (to oneself) በራሱ ፡ እጅ ፡ አደረገ
The governor arrogated to himself the power to punish violators of the law. ሕግ ፡ ተላላፊዎችን ፡ የመቅጣቱን ፡ ሥልጣን ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ በራሱ ፡ እጅ ፡ አደረገው

## arrow
1. ወስፈንጥር. Hold the arrow against the bow when you shoot. ስትወረውር ፡ ወስፈንጥሩን ፡ ከቀስቱ ፡ ላይ ፡ አስደግፈህ ፡ ያዘው
2. ቀስት. The arrow points north. ቀስቱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ያመለክታል

## arsenal
1. የመሣሪያ ፡ ፋብሪካ. Our arsenal makes only rifles and pistols. የመሣሪያ ፡ ፋብሪካችን ፡ የሚሠራው ፡ ጠመንጃዎችንና ፡ ሽጉጦችን ፡ ብቻ ፡ ነው
2. የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ግምጃ ፡ ቤት. Only a few rifles were left in the arsenal. በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ግምጃ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂት ፡ ጠመንጃዎች ፡ ብቻ ፡ ይገኛሉ

## arson የቤት ፡ ማቃጠል ፡ ወንጀል
The two young men were accused of arson. ሁለቱ ፡ ወጣቶች ፡ በቤት ፡ ማቃጠል ፡ ወንጀል ፡ ተከሰሱ

## art
1. ኪነ ፡ ጥበብ. He knows a lot about art. ስለ ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ ብዙ ፡ ያውቃል
This building contains many works of art. በዚህ ፡ ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ሥራዎች ፡ አሉ
2. ጥበብ. The public speaker cultivates the art of pleasing his audience. ተናጋሪው ፡ ያድማጮችን ፡ ማስደሰቻ ፡ ጥበብ ፡ ያጐለምሳል
3. ዘዴ. He has the art of making friends. ወዳጅ ፡ የማፍሪያት ፡ ዘዴ ፡ አለው
4. ብልሃት. The witch deceived the girl by her art. ጠንቋይቱ ፡ ልጃገረዲቱን ፡ በብልሃቷ ፡ አታለለቻት

## artery (arteries)
1. ደም ፡ ቅዳ. It is dangerous if an artery is cut. ደም ፡ ቅዳ ፡ ከተበጠሰ ፡ አደገኛ ፡ ነው
2. ዋና ፡ መንገድ. Churchill Road is one of the main arteries of Addis Ababa. የቸርቺል ፡ ጐዳና ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ዋና ፡ መንገዶች ፡ አንዱ ፡ ነው

## artful የማጭበርበር
The cheat uses artful tricks to get people's money away from them. አታላይ ፡ የሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመውሰድ ፡ በማጭበርበር ፡ ዘዴ ፡ ይጠቀማል
*The Japanese excel in artful arrangements of flowers. ጃፓኖች ፡ አበባ ፡ በመደርደር ፡ ጥበብ ፡ ከማንም ፡ ይልቃሉ

**article**

1. እቃ. Many valuable articles were stolen. ብዙ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ እቃዎች ፡ ተሰረቁ
2. አንቀጽ. I am not clear on article 3. አንቀጽ ፡ ሦስት ፡ በግልጽ ፡ አልገባኝም
3. ጽሑፍ. There was an interesting article about it in the newspaper. ስለሱ ፡ አንድ ፡ የሚያስደስት ፡ ጽሑፍ ፡ በጋዜጣው ፡ ላይ ፡ ተጽፎ ፡ ነበር
4. መስተአምር. In English the definite article is more often used than in Amharic. ካማርኛ ፡ ይልቅ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ የተወሰነ ፡ መስተአምር ፡ ይበልጡን ፡ ጊዜ ፡ ይነገራል

[See also 'definite, indefinite, leading, toilet']

**articulate** (vt.) በግልጽ ፡ ተናገረ
Don't mumble; articulate your words! አታጕረምርም ፤ በግልጽ ፡ ተናገር

**articulate** (vi.) ተጋጠመ
The arm articulates with the body at the shoulder. ክንድ ፡ ከሰውነት ፡ ጋር ፡ የሚጋጠመው ፡ ትከሻ ፡ ላይ ፡ ነው

**articulate** (adj.) ታጣፊ
The legs are articulate limbs. እግሮች ፡ ታጣፊ ፡ አካላት ፡ ናቸው
*He is a very articulate speaker. ቃላት ፡ መርጦ ፡ የመናገር ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**use articulate speech** ለይቶ ፡ ተናገረ
A baby cries but does not use articulate speech. ሕፃን ፡ ያለቅሳል ፡ እንጂ ፡ ለይቶ ፡ አይናገርም

**artifact** ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ነገር
Artifacts made of flint were found by the river. ከባልጩት ፡ የተሠሩ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ነገሮች ፡ በወንዝ ፡ ዳር ፡ ተገኙ

**artifice**

1. ዘዴ. He makes use of the artifice of flattery. በድለላ ፡ ዘዴ ፡ ይጠቀማል
2. ጥበብ. She displayed a great deal of artifice in decorating her new apartment. አዲሱን ፡ አፓርተማዋን ፡ በከፍተኛ ፡ ጥበብ ፡ አጌጠችው
3. (= adv.) ካንገት ፡ በላይ. His sincerity toward other people is an artifice. ለሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ቅን ፡ የሚመስለው ፡ ካንገት ፡ በላይ ፡ ነው

**artificial**

1. ሰው ፡ ሠራሽ. Are those flowers artificial? እነዚያ ፡ አበቦች ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ናቸው ?
2. ከልብ ፡ ያልሆነ. She has an artificial smile. ከልብ ፡ ያልሆነ ፡ ፈገግታ ፡ አላት

**artillery** (n.)

1. ከባድ ፡ መሣሪያ. Our artillery was effective in destroying the city. ከባድ ፡ መሣሪያችን ፡ ከተማውን ፡ ለማጥፋት ፡ ቻለ
2. መድፈኞች. The artillery is usually some distance behind the lines. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ መድፈኞች ፡ ከጦር ፡ ግንባር ፡ በኋላ ፡ ራቅ ፡ ይላሉ

**heavy artillery** ከባድ ፡ መሣሪያ
The Russians favored the use of heavy artillery. መስኮባውያን ፡ በከባድ ፡ መሣሪያ ፡ መጠቀምን ፡ መረጡ

**artillery** (adj.) የመድፍ
The artillery fire leveled the town. የመድፍ ፡ ተኩስ ፡ ከተማውን ፡ አወደመው

**artisan**

1. ጥበበኛ. The weavers of the toga are good artisans. ሸማኔዎች ፡ ጥሩ ፡ ጥበበኞች ፡ ናቸው
2. ባለ ፡ እጅ. The silversmith is a good artisan. ብር ፡ አፍሳሹ ፡ ጥሩ ፡ ባለ ፡ እጅ ፡ ነው

**artist**

1. አርቲስት. This artist is famous for his statues. ይህ ፡ አርቲስት ፡ በሠራቸው ፡ ሐውልቶች ፡ ዝነኛ ፡ ሆኗል
2. የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ሰው. There is an artist colony near our home. እኛ ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ሰዎች ፡ መንደር ፡ አለ
3. ሠዓሊ. Afework Tekle is Ethiopia's most famous artist. አፈወርቅ ፡ ተክሌ ፡ የታወቀ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሠዓሊ ፡ ነው
4. ሊቅ. He is an artist on the harp. እሱ ፡ የበገና ፡ ሊቅ ፡ ነው

**artistic** (= abstract) ጥበበኛነት
Her artistic arrangement of flowers was admired by everybody. አበባ ፡ የመደርደር ፡ ጥበበኛነቷ ፡ በሁሉም ፡ ተደነቀ

**as** (conj., prep.)

1. ስ + (imperfect). Did you see anyone as you came in? ስትገባ ፡ ሰው ፡ አይተሃል ?
2. እንደ. I regard it as important. እንደ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ አድርጌ ፡ እቈጥረዋለሁ

He is late as usual. እንደተለመደው ፡ ዘግይቷል
Try to act as a brave man would. ደፋር ፡ ሰው ፡ እንደሚያደርገው ፡ ለመሥራት ፡ ሞክር

2. ስለ + (verb). As he is leaving tomorrow, we must hurry. ነገ ፡ ስለሚሄድ ፡ መፋጠን ፡ አለብን
3. ምንም ፡ እንኳ ፡ ብ + (imperfect). Dark as it was we could still see the sign. ምንም ፡

እንኳ ፡ ጭለማ ፡ ቢሆን ፡ ምልክቱን ፡ ማየት ፡ እንችል ፡ ነበር

4. ብ + imperfect + ም. Much as I like you, I will not marry you. በጣም ፡ ብወድሽም ፡ አላገባሽም

Young as I am, I have experienced life. ወጣት ፡ ብሆንም ፡ ኑሮን ፡ ቀምሼዋለሁ

5. በ + (abstract). He serves as gardener and as chauffeur. ባታክልተኛነትና ፡ በሹፌርነት ፡ ያገለግላል

*We left the house by the same door as we had entered. በገባንበት ፡ በር ፡ ተመልሰን ፡ ወጣን

**as a** በ + abstract

As a child, he lived in Ethiopia. በልጅነቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ኖረ

As a poet, he hardly approaches Keats. በገጣሚነት ፡ ኪትስን ፡ አይደርስበትም

**as ...... as** እንደ

Is it as difficult as you say it is? አንተ ፡ እንደ ምትለው ፡ ከባድ ፡ ነው ?

*I want a box twice as large as this. ከዚህ ፡ በ ዕጥፍ ፡ ከፍ ፡ የሚል ፡ ሣጥን ፡ እፈልጋለሁ

**as for** በ - - - በኩል

As for him, it is all right. በሱ ፡ በኩል ፡ ደኅና ፡ ነው

*As for you, I never want to see you again. አንተን ፡ ግን ፡ ዳግመኛ ፡ ላይህ ፡ ፈጽሞ ፡ አልፈቅድም

**as if**

*He acts as if it were very important. ትልቅ ፡ ያስመስለዋል

*He talks as if he had been there. እዚያ ፡ እንደነበረ ፡ ሆኖ ፡ ያወራል

**as to** - ን ፡ እንደሆነ

As to your brother, I will see him later. ወንድምህን ፡ እንደሆነ ፡ በኋላ ፡ እጠይቀዋለሁ

[See also 'even, far, long, much, often, see, so, soon, such, though, yet']

## ascend

1. ወጣ. The path ascends the mountain. የእግር ፡ መንገዱ ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ይወጣል

2. ተቀመጠ. Yohannes the Second ascended the throne. ዳግማዊ ፡ ዮሐንስ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀመጡ

## ascendancy ግዛት

The Roman ascendancy in England lasted for centuries. ሮማውያን ፡ በእንግሊዞች ፡ ላይ ፡ የነበራቸው ፡ ግዛት ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ ቆየ

**gain ascendancy over** አሸነፈ

The soldier gained ascendancy over fear. ወታደሩ ፡ ፍርሃትን ፡ አሸነፈ

## ascendant (n.), be in the ~

1. እያየለ ፡ ሄደ. His rivals were in the ascendant, and he lost his position. ተወዳዳሪዎቹ ፡ እያየሉ ፡ ስለሄዱ ፡ ሥልጣኑን ፡ አጣ

2. እየደረጀ ፡ ሄደ His fortunes are in the ascendant. ሀብቱ ፡ እየደረጀ ፡ ሄደ

**ascendant** (adj.) በማደግ ፡ ላይ ፡ ያለ

The prime minister visited the ascendant nations of West Africa. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ የምዕራብ ፡ አፍሪካ ፡ አገሮችን ፡ ጐበኙ

## ascension

1. መውጣት. The ascension of the mountain requires much effort. ተራራውን ፡ መውጣት ፡ ብዙ ፡ ጥረት ፡ ይጠይቃል

2. ዕርገት. Christ's ascension is a church holiday. የክርስቶስ ፡ ዕርገት ፡ የሃይማኖት ፡ በዓል ፡ ነው

## ascent

1. መውጣት. The ascent of Mt. Everest is difficult. የኤቨረስትን ፡ ተራራ ፡ መውጣት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

2. መመንጠቅ. The sudden ascent of the elevator made me dizzy. የአሳንሱሩ ፡ በድንገት ፡ መመንጠቅ ፡ አዞረኝ

## ascertain

1. አረጋገጠ. He tried to ascertain the truth of the matter. የነገሩን ፡ እውነተኛነት ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሞከረ

2. አጣራ. Ascertain what really happened! የደረሰውን ፡ ነገር ፡ አጣራ

## ascetic (n.) መናኝ

Ascetics prefer to live in the desert. መናኞች ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ ይመርጣሉ

**ascetic** (adj.)

1. የባሕታዊ. His mode of life is very ascetic. የኑሮው ፡ ሁኔታ ፡ የባሕታዊ ፡ ነው

2. የብቃት. The monks live ascetic lives. መነኩሴዎች ፡ የብቃት ፡ ኑሮ ፡ ይኖራሉ

## ascribe to

1. ከ - - - የተነሣ ፡ ነው ፡ አለ. The police ascribed the automobile accident to fast driving. ፖሊሶቹ ፡ አደጋው ፡ የደረሰው ፡ በፍጥነት ፡ ከመንዳት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ አሉ

2. በ - - - ምክንያት ፡ ነው ፡ አለ. She ascribed

her success to hard work. የውጤቷ ፡ መቃናት ፡ በከባድ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ አለች

*The alphabet is usually ascribed to the Phoenicians. ፊደሉን ፡ የፈጠሩት ፡ ፊንቄያውያን ፡ ናቸው ፡ ይባላል

**ash(es)** አመድ

Don't drop cigarette ashes on the floor. በወለሉ ፡ ላይ ፡ የሲጃራ ፡ አመድ ፡ አታራግፍ

The floor was covered with ashes. ወለሉ ፡ አመድ ፡ ብቻ ፡ ነበር

**be burned to ashes** አመድ ፡ ሆነ

The house was burned to ashes. ቤቱ ፡ አመድ ፡ ሆነ

[See also 'smother']

**(be) ashamed** አፈረ

The boy was ashamed of his tears. ልጁ ፡ በማልቀሱ ፡ አፈረ

**be ashamed of oneself** አፈረ

You needn't be ashamed of yourself. You have done well in your exam. የምታፍርበት ፡ ነገር ፡ የለም ፤ ፈተናህን ፡ ጥሩ ፡ ሠርተሃል

**ashore** ወደ ፡ ዳርቻ

He jumped overboard and swam ashore. ከመርከብ ፡ ዘሎ ፡ ወደ ፡ ዳርቻ ፡ ዋኘ

**be ashore** ከመርከብ ፡ ወረደ

The captain has been ashore for two hours. ካፒቴኑ ፡ ለሁለት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ከመርከብ ፡ ወርዶ ፡ ነበር

**go ashore** ወደ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ሄደ

We were not allowed to go ashore. ወደ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ እንድንሄድ ፡ አልተፈቀደልንም

**ashtray** መተርኮሻ

The ashtray is full of ashes. (የሲጃራ) ፡ መተርኮሻው ፡ አመድ ፡ ብቻ ፡ ነው

**Asia** እስያ

**aside** ቀርቶ

All joking aside, I want my money. ቀልዱ ፡ ቀርቶ ፡ ገንዘቤን ፡ እፈልጋለሁ

**aside from**

1. ከ - - - በስተቀር. Aside from this there is nothing else we can do. ከዚህ ፡ በስተቀር ፡ ልናደርግ ፡ የምንችለው ፡ ነገር ፡ የለም

2. ከ - - - ሌላ. Aside from that there is not much to it. ከዚያ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የቀረው ፡ ነገር ፡ የለም

**ask** ጠየቀ

Ask at the ticket office! ቲኬት ፡ መሸጫው ፡ ቢሮ ፡ ጠይቅ

May I ask a question? ጥያቄ ፡ ልጠይቅ ?

He asked a favor of me. ውለታ ፡ እንዳደርግለት ፡ ጠየቀኝ

**ask after** ጠየቀ

He asked after your health. ጤንነትሽን ፡ ጠየቀ

**ask for**

1. ጠየቀ. He asked for permission to go home. ወደ ፡ ቤት ፡ ለመሄድ ፡ ፈቃድ ፡ ጠየቀ

2. ፈለገ. Did anyone ask for me? የፈለገኝ ፡ ሰው ፡ አለ ?

**ask in**

*Mr. Parker is at the door. Shall we ask him in?ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ እደጅ ፡ ናቸው ፤ ይግቡ ፡ እንበላቸው ?

**ask of**

1. ጠየቀ. I only ask of you that you clean up the room. የምጠይቅህ ፡ ክፍሉን ፡ እንድታጸዳ ፡ ብቻ ፡ ነው

2. አስቸገረ. Have I asked too much of you? ብዙ ፡ አስቸገርኩህ ?

[See also 'excuse, extension, hand, marriage']

**askance, look ~** በጥርጣሬ ፡ ተመለከተ

The students look askance at the plan for voting. ድምፅ ፡ ስለ ፡ መስጠታቸው ፡ ያለውን ፡ እቅድ ፡ ተማሪዎቹ ፡ በጥርጣሬ ፡ ይመለከቱታል

**(be) askew** ተጣመመ ፤ ተንጋደደ

His hat is askew. ባርኔጣው ፡ ተንጋዷል ፡ (ተጣሟል)

**(be) asleep**

1. ተኛ. I must have been asleep when you came to visit me. ልትጠይቀኝ ፡ በመጣህ ፡ ጊዜ ፡ ተኝቼ ፡ ይሆናል

2. (foot) ደነዘዘ(ው). My foot tingles when it is asleep. እግሬን ፡ ሲደነዝዘኝ ፡ ይወረኛል

**fall asleep** አንቀላፋ ፤ ተኛ ፤ እንቅልፍ ፡ ያዘው

He fell asleep during the sermon. በስብከቱ ፡ ጊዜ ፡ አንቀላፋ

I simply couldn't fall asleep. ምንም ፡ ልተኛ ፡ አልቻልኩም

I fell asleep while driving my car. መኪና ፡ ስነዳ ፡ እንቅልፍ ፡ ያዘኝ

**(be) fast asleep** ድብን ፡ ያለ ፡ እንቅልፍ ፡ ወሰደው

He did not hear the burglar because he was fast asleep. ድብን ፡ ያለ ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዶት ፡ ስለነበረ ፡ ቤት ፡ ሰርሳሪው ፡ ሲገባ ፡ አልሰማውም

**lay asleep** ተኛ

A drunken man lay asleep in the doorway. የሰከረ ፡ ሰው ፡ ደጃፉ ፡ ላይ ፡ ተኛ

[See also 'sound']

**aspect**
1. ሞገስ. The judge has a solemn aspect. ዳኛው ፡ ረጋ ፡ ያለ ፡ ሞገስ ፡ አለው
2. ሁኔታ. The aspect of the countryside is extremely attractive. የባላገሩ ፡ ሁኔታ ፡ እጅግ ፡ ማራኪ ፡ ነው
3. አሠራር. This house has a southern aspect. ይህ ፡ ቤት ፡ የደቡብ ፡ አሠራር ፡ አለው
*The Emperor is a man of dignified aspect. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ አላቸው
**every aspect** ከሁሉም ፡ አንጻር
We have considered every aspect of the problem. ጉዳዩን ፡ ከሁሉም ፡ አንጻር ፡ ተመልክ ተነዋል

**asperity** ኀይለ ፡ ቃል
He answered his critics with asperity. የሚነቅ ፉትን ፡ ሰዎች ፡ በኀይለ ፡ ቃል ፡ መለሰላቸው

**asperse** አማ
A true friend will not asperse his comrade. እውነተኛ ፡ ወዳጅ ፡ ጓደኛውን ፡ አያማም

**aspersion** ሐሜት
Such vehement aspersions cannot be ignored. እንዲህ ፡ ያለ ፡ ከባድ ፡ ሐሜት ፡ የሚታለፍ ፡ አ ይደለም
**cast aspersions on** አጐደፈ
He cast aspersions on my reputation. ዝናዬ ን ፡ አጐደፈ

**asphalt** አስፋልት ፤ ሬንጅ
The road is paved with asphalt. መንገዱ ፡ አ ስፋልት ፡ (ሬንጅ) ፡ ተነጥፎል

**(be) aspirant for** ፈለገ ፤ ተመኘ
There are many aspirants for the position of mayor. የከንቲባነትን ፡ ሥልጣን ፡ የሚፈል ጉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አሉ
Some students were aspirants for a scholarship. አንዳንድ ፡ ተማሪዎች ፡ የነጻ ፡ ትምህርት ፡ ለማ ግኘት ፡ ይመኙ ፡ ነበር

**(be) aspirated** ትንፋሽ ፡ ተሰማ
The 'h' in 'home' is aspirated. «ሆም» ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ «ህ» ፡ ሲነበብ ፡ ትንፋሽ ፡ ይሰማል

**aspiration** ምኞት
He has aspirations to be a doctor. ሐኪም ፡ ለመሆን ፡ ምኞት ፡ አለው

**aspire**
1. ተመኘ. Many young people aspire to be doctors. ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ ሐኪም ፡ ለመሆን ፡ ይ መኛሉ
2. ጓጓ. Most writers aspire after fame. አብዛኞ ቹ ፡ ደራሲያን ፡ ለዝና ፡ ይጓጓሉ

**ass**
1. አህያ. He loaded the ass before going to market. ገበያ ፡ ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ አህያውን ፡ ጫነ
He insulted him by calling him an ass. አህያ ፡ ነህ ፡ ብሎ ፡ ሰደበው
2. ቂጥ. He gave him a kick in the ass. ቂጡን ፡ ረገጠው

**assail**
1. በኀይል ፡ አጠቃ. The enemy assailed the castle. ጠላት ፡ ግንቡን ፡ በኀይል ፡ አጠቃው
2. አጣደፈ. The student assailed me with questions. ተማሪው ፡ በጥያቄ ፡ አጣደፈኝ

**assailant** ደብዳቢ
The injured man did not know his assailant. የቈሰለው ፡ ሰውዬ ፡ ደብዳቢውን ፡ አላወቀውም

**assassin** ነፍስ ፡ ገዳይ
The assassin escaped. ነፍስ ፡ ገዳዩ ፡ አመለጠ

**assassinate** ገደለ
His former friends assassinated him. የቀድሞ ፡ ጓደኞቹ ፡ ገደሉት

**assault** (v.) ደበደበ
That man assaulted me. ያ ፡ ሰው ፡ ደበደበኝ

**assault** (n.)
1. ጥቃት. The assault was repulsed with heavy losses. ጥቃቱ ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ሊ መለስ ፡ ቻለ
2. ድብደባ. He was charged with assault. በድብደባ ፡ ተከሰሰ

**assemblage** መሰብሰብ
He was responsible for the assemblage of facts. መረጃዎችን ፡ ለመሰብሰብ ፡ ኀላፊ ፡ ነበር
*This is an assemblage of important people. ይህ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ የሚገኙበት ፡ ነው

**assemble** (vt.)
1. ሰበሰበ. He assembled the pupils in the auditorium. ተማሪዎቹን ፡ በአዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ ሰ በሰባቸው
2. አገጣጠመ. He assembles cars imported from abroad. ከውጭ ፡ የመጡ ፡ መኪናዎችን ፡ ያገ ጣጥማል
**assemble** (vi.) ተሰበሰበ
The pupils assembled in the auditorium. ተማ ሪዎቹ ፡ በአዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ተሰበሰቡ

**assembling** (= verb) ሲያገጣጥም
In the factory we saw the assembling of the parts which make up an automobile. በፋብሪካው ፡ ውስጥ ፡ የመኪና ፡ ክፍሎችን ፡ ሲያገጣጥሙ ፡ አየን

**assembly**
1. ስብሰባ. He spoke at the lawyers' assembly. ለጠበቆች ፡ ስብሰባ ፡ ንግግር ፡ አደረገ
2. ጉባኤ. The U.N. General Assembly meets tomorrow. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ነገ ፡ ይሰበሰባል
3. ሸንጎ. The assembly of elders meets at the governor's palace. የአበው ፡ ሸንጎ ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ግቢ ፡ ይደረጋል

**assent** (v.) እሺ ፡ አለ
She assented to my request. የጠየቅኋትን ፡ እሺ ፡ አለችኝ

**assent** (n.) ስምምነት
The governor's assent is needed before the bill becomes law. ረቂቁ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ያገረ ፡ ገዢው ፡ ስምምነት ፡ ያስፈልጋል

**give the assent** ተስማማ
He gave his assent to her marriage. በጋብቻዋ ፡ ተስማማ

**assert**
1. ተከራከረ. The lawyer asserted that his client was innocent. ጠበቃው ፡ ነገርተኛው ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለም ፡ ሲል ፡ ተከራከረ
2. አረጋገጠ. By revolting, the colonies asserted their right to govern themselves. በገዢዎቻቸው ፡ ላይ ፡ በመነሣት ፡ ቅኝ ፡ ግዛቶች ፡ ራሳቸውን ፡ ለማስተዳደር ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ አረጋገጡ

**assertion** የተናገረ
His assertion is questionable. የተናገረውን ፡ ለመቀበል ፡ ያዳግታል

**assess**
1. ገመተ. The official assessed the house at $10,000. ባለሥልጣኑ ፡ ቤቱን ፡ በዐሥር ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ገመተው
2. ቈረጠ. The club assessed each member 20 dollars. ክበቡ ፡ በያንዳንዱ ፡ አባል ፡ ላይ ፡ ሃያ ፡ ብር ፡ ቈረጠ

**asset**
1. ጸጋ. Good health is a great asset. ጥሩ ፡ ጤንነት ፡ ታላቅ ፡ ጸጋ ፡ ነው
2. ጠቃሚ. Ability to get along with people is an asset in business. ከሰዎች ፡ ጋር ፡ የመግባባት ፡ ችሎታ ፡ ለንግድ ፡ ሥራ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው

**assets** ንብረት
The bank's assets amount to a million dollars. የባንኩ ፡ ንብረት ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ ነው

**assiduity** ትጋት
His assiduity was noticed by all. የሱ ፡ ትጋት ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**assiduous** ትጉ
He is assiduous in his work. በሥራው ፡ ትጉ ፡ ነው

**assign**
1. መደበ(ተመደበ). He assigned two men to guard the prisoner. እስረኛውን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ መደበ
These rooms have been assigned to us. እነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ ለኛ ፡ ተመድበዋል
2. ወሰነ(ተወሰነ). Has a day been assigned for the trial? ጉዳዩ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚታይበት ፡ ቀን ፡ ተወስኗል ?
3. ደለደለ. They assigned all the new children to the various classes. አዳዲሶቹን ፡ ልጆች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ ደለደሏቸው
4. እንዲያዘጋጅ ፡ አዘዘው. The teacher assigned us two lessons for Monday. አስተማሪው ፡ ለሰኞ ፡ ሁለት ፡ ትምህርት ፡ እንድናዘጋጅ ፡ አዘዘን
5. አዛወረ. Mr. Jones assigned his home and farm to his creditors. ሚስተር ፡ ጆንስ ፡ ቤቱን ፡ እርሻውን ፡ ለአበዳሪዎች ፡ አዛወረ
6. ሰጠ(ተሰጠ). He performed the task assigned him with diligence. የተሰጠውን ፡ ሥራ ፡ በትጋት ፡ ፈጸመ

**assignment**
1. ድልድል. The assignment of the various jobs is taken care of by the foreman. ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ የሚደረገው ፡ ድልድል ፡ በአሠሪው ፡ ይከሄዳል
2. ሥራ. The boss gave me an interesting assignment. አለቃው ፡ የሚያስደስት ፡ ሥራ ፡ ሰጠኝ
3. የተመደበለት ፡ ሥራ. He used a subterfuge to get out of the assignment. ከተመደበለት ፡ ሥራ ፡ ለማምለጥ ፡ ብልሃት ፡ ፈጠረ

**assimilate** (vt.)
1. ቀሠመ. He assimilated the customs of his new country. ያዲሱን ፡ አገር ፡ ልማድ ፡ ቀሠመ
2. (= pass.) ከሰውነቱ ፡ ተዋሐደ. We assimilate some kinds of food more easily than others.

አንዳንድ ፡ ምግቦች ፡ ከሌሎቹ ፡ ይልቅ ፡ ከሰውነ ታችን ፡ በቀላሉ ፡ ይዋሐዳሉ
3. ያዘ. The girl reads so much that she does not assimilate it all. ልጅቷ ፡ ብዙ ፡ ከማንበ ቧ ፡ የተነሣ ፡ ሁሉንም ፡ ልትይዝ ፡ አልቻለችም
4. መጠጠ. Plants assimilate nourishment through their roots. ዕፀዋት ፡ ምግባቸውን ፡ በሥሮቻቸ ው ፡ ይመጣሉ

**assimilate** (vi.) ተቀላቀለ
Swedes assimilate readily in this country. ስዊድኖች ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ በቀላሉ ፡ ይቀላቀላሉ

**assist** (vt.) ረዳ
Who assisted you in preparing this report? ይህንን ፡ ሪፖርት ፡ ስታዘጋጅ ፡ የረዳህ ፡ ማነው ?
He assisted the old lady in crossing the street. አሮጊቷ ፡ መንገዱን ፡ ስታቋርጥ ፡ ረዳት

**assist** (vi.) ተገኘ
The father assisted at the birth of the child. ሕፃኑ ፡ ሲወለድ ፡ አባትዬው ፡ እዚያው ፡ ተገኝቶ ፡ ነ በር

**assistance** እርዳታ
He did it without any assistance. ያለ ፡ ምንም ፡ እርዳታ ፡ ሠራው

**assistant** (n., adj.) ረዳት
My assistants are available if you need them. ረዳቶቼን ፡ ከፈለግሃቸው ፡ ሊረዱህ ፡ ይችላሉ
He is assistant manager. ረዳት ፡ ሥራ ፡ አስኪያ ጅ ፡ ነው

**associate** (vt.)
1. አዛመደ. We associate Egypt with the Nile. ግብጽን ፡ ከዐባይ ፡ ጋር ፡ እናዛምዳለን
2. (= passive) በሐሳቡ ፡ ተያያዘ. In America we associate Christmas with giving presents. በአ ሜሪካ ፡ የገና ፡ በዓል ፡ በሐሳባችን ፡ ስጦታ ፡ ከመ ስጠት ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው

**associate oneself** ራሱን ፡ አስገባ
I don't wish to associate myself with what has been said. በተባለው ፡ ነገር ፡ ራሴን ፡ ላስገ ባ ፡ አልፈልግም

**associate** (vi.)
1. ተጐዳኘ. He went wrong as a result of associating with criminals. ከወንጀለኞቹ ፡ ጋር ፡ ከመጐዳኘቱ ፡ የተነሣ ፡ ተበላሸ
2. ግንኙነት ፡ ነበረው. We didn't associate with them very much. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ግን ኙነት ፡ አልነበረንም
3. ግንኙነት ፡ አደረገ. He has always associated with political groups. ሁልጊዜ ፡ ከፖለቲካ ፡ ማ ኅበሮች ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ አድርጓል

**associate** (n.) ተባባሪ ፤ ሸርካ
He was an associate of mine during the summer months. በበጋው ፡ ወራቶች ፡ ተባባሪዬ ፡ ነበር
He planned the project along with his associates. እቅዱን ፡ ከሸርካዎቹ ፡ ጋር ፡ አዘጋጀ

**associate** (adj.) ተባባሪ
He is associate editor of the school paper. የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ መጽሔት ፡ ተባባሪ ፡ አዘ ጋጅ ፡ እሱ ፡ ነው

**association**
1. ማኅበር. I don't think I will join the association. የማኅበሩ ፡ አባል ፡ የምሆን ፡ አይመስለኝም
2. ግንኙነት. I benefited much from my association with him. ከሱ ፡ ጋር ፡ ባለኝ ፡ ግንኙነት ፡ በጣም ፡ ተጠቀምኩ
3. ኅብረት. The United States is an entity rather than an association of states. አሜሪካ ፡ አንድነት ፡ ያላት ፡ አገር ፡ እንጂ ፡ የሀገሮች ፡ ኅብ ረት ፡ አይደለችም
4. መዋል. His association with the embezzler blemished his reputation. ከአደራ ፡ በሊታው ፡ ጋር ፡ መዋሉ ፡ ዝናውን ፡ አጐደፈው
5. ትዝታ. The city brings many pleasant associations to my mind. ከተማዋን ፡ ሳይ ፡ ብዙ ፡ የሚያስደስቱ ፡ ትዝታዎች ፡ ይታወሱኛል

**assort** ለየ
Assort these buttons according to size. እነዚህን ፡ አዝራሮች ፡ እንደየመጠናቸው ፡ ለያቸው

**assorted,** adj. (= adv.) በያይነቱ
A box of assorted biscuits costs five dollars. አንድ ፡ ሣጥን ፡ ብስኩት ፡ በያይነቱ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ያወጣል

**assortment, ~ of** ልዩ ፡ ልዩ
This shop has a good assortment of merchandise to choose from. ይህ ፡ ሱቅ ፡ ለመምረ ጥ ፡ የሚያስችል ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሸቀጣ ፡ ሸ ቀጦች ፡ አሉት

**assuage**
1. አጽናና. Her kind words assuaged my grief. የተናገረችኝ ፡ መልካም ፡ ቃል ፡ ከሐዘኔ ፡ አጽናናኝ
2. አበረደ. Nothing will assuage his anger. ቁጣውን ፡ ምንም ፡ አያበርደውም

**assume**
1. ገመተ. He is not such a fool as you assume him to be. አንተ ፡ እንደምትገምተው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ቂል ፡ አይደለም
The maid did not come for a week; I therefore

assume that she quit. ገረዲቷ ፡ ሳንድ ፡ ሳም
ንት ፡ ስላልመጣች ፡ ሥራውን ፡ ለቃለች ፡ ብዬ ፡
እገምታለሁ
2. የሚል ፡ ግምት ፡ ያዘ. You assume his innocence before hearing the evidence. ማስረጃው
ን ፡ ከመስማትህ ፡ በፊት ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፡ የሚል ፡
ግምት ፡ ትይዛለህ
3. መስሎ ፡ ታየ. He assumed a humble manner.
ትሕትና ፡ ያለው ፡ መስሎ ፡ ታየ
4. አስመሰለ. He assumed ignorance of the law.
ሕጉን ፡ የማያውቅ ፡ አስመሰለ
5. ያዘ. He assumed the direction of the office.
የቢሮ ፡ ሥራውን ፡ አመራር ፡ ያዘ
6. ተቀበለ. I cannot assume any responsibility for that. ለዚያ ፡ ምንም ፡ ኀላፊነት ፡ ልቀበል ፡
አልችልም
[See also 'throne']

**assumed** ሌላ
The writer concealed his identity under an assumed name. ጸሓፊው ፡ ማንነቱን ፡ በሌላ ፡
ስም ፡ ሸፈነው
*He is living under an assumed name. ስሙን ፡
ለውጦ ፡ ይኖራል

**assuming that** ከገመተ ፡ በኋላ
Assuming that he had stolen the money we called the police. ገንዘቡን ፡ ሰርቋል ፡ ብለን ፡
ከገመትን ፡ በኋላ ፡ ፖሊስ ፡ ጠራን

**assumption** ግምት
Their assumption that the war could end soon was wrong. ጦርነቱ ፡ ቶሎ ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል ፡
የሚለው ፡ ግምታቸው ፡ ስሕተት ፡ ነበር

**assurance**
1. እምነት. I have full assurance of his honesty.
ስለ ፡ ታማኝነቱ ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ አለኝ
2. ሙሉ ፡ እምነት. He answered all the questions with assurance. ጥያቄዎቹን ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡
እምነት ፡ መለሰ
3. ማረጋገጫ. The flood victims received assurances of government aid. የውኃ ፡ መጥለቅለ
ቅ ፡ አደጋ ፡ የደረሰባቸው ፡ ሰዎች ፡ ከመንግ
ሥት ፡ እርዳታ ፡ እንደሚደርሳቸው ፡ ማረጋገጫ ፡
ተሰጣቸው
4. በራስ ፡ መተማመን. The young lawyer lacks assurance. ወጣቱ ፡ ጠበቃ ፡ በራስ ፡ መተማ
መን ፡ ይጐድለዋል

**give assurance** አረጋገጠ(ለት)
Mother gave me her assurance that I could go to the movies. እናቴ ፡ ወደ ፡ ሲኒማ ፡ እንደ
ምሄድ ፡ አረጋገጠችልኝ

**have one's assurance** (= active) አረጋገጠ(ለት)
I have his assurance that he will pay on time.
በጊዜው ፡ የሚከፍል ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጦልኛል

**assure** አረጋገጠ
He assured us that he would be there. እዚህ ፡
እንደሚገኝ ፡ አረጋገጠልን
Nothing can assure lasting happiness. የዘለዓለ
ም ፡ ደስታን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም

**assure oneself** አረጋገጠ
The man assured himself that the bridge was safe before crossing it. ከመሻገሩ ፡ በፊት ፡ ሰ
ውየው ፡ ድልድዩ ፡ ጥብቅ ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጠ

**assured** (adj.)
1. በራስ ፡ የመተማመን. The speaker's assured manner impressed me greatly. የተናጋሪው ፡
በራስ ፡ የመተማመን ፡ ሁኔታ ፡ በጣም ፡ ነካኝ
2. የማያቋርጥ. He has an assured income of 500 dollars a month. በየወሩ ፡ የማያቋርጥ ፡ አ
ምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ገቢ ፡ አለው

**be assured** አመኑ
You may be assured that your son is safe.
ልጅህ ፡ ደኅና ፡ መሆኑን ፡ እመን

**rest assured!** አትጠራጠር
Rest assured that I will be there! እዚያ ፡ እንደ
ምገኝ ፡ አትጠራጠር

**asterisk** የኮከብ ፡ ምልክት
Put an asterisk after all foreign words!
ከባዕድ ፡ ቃላት ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ የኮከብ ፡ ምልክት ፡
አድርግ

**astern** ከመርከብ ፡ ኋላ
Another ship anchored close astern. አንድ ፡
መርከብ ፡ ከሌላዋ ፡ መርከብ ፡ ኋላ ፡ መልሕቅ ፡
ጣለ

**asthma** አስማ

**(be) astir** ተሟሟቀ
The town is astir with visitors. ከተማይቱ ፡ ባ
ገር ፡ ጐብኚዎች ፡ ተሟሙቃለች

**astonish** አስደነቀ
The gift of ten dollars astonished the little boy.
የዐሥር ፡ ብር ፡ስጦታ ፡ ትንሹን ፡ ልጅ ፡ አስደነቀው

**be astonished** በጣም ፡ ተገረመ
I am astonished that he did not come.
ባለመምጣቱ ፡ በጣም ፡ ተገረምኩ

**astonishment** አድናቆት
He expressed astonishment at the invention.
በፍልሰፋው ፡ አድናቆቱን ፡ ገለጸ

**astound**
1. እጅግ ፡ አስገረመ. The Americans' landing on the moon astounded us. የአሜሪካኖች ፡ ጨረቃ ፡ ላይ ፡ ማረፍ ፡ እጅግ ፡ አስገረመን
2. አስደነገጠ. The news of Kennedy's murder astounded everybody. የኬኔዲ ፡ መገደል ፡ ዜና ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አስደነገጠ

**(be) astray** ባከነ
Her thoughts are astray. አሳቧ ፡ የባከነ ፡ ነው

**go astray** ጠፋ
We are looking for the cows that have gone astray. የጠፉትን ፡ ላሞች ፡ በመፈለግ ፡ ላይ ፡ ነን

**lead astray** አሳሳተ
The similarity between the two situations led him astray. የሁለቱ ፡ ሁኔታዎች ፡ መመሳሰል ፡ አሳሳተው

**(be) led astray** ማገጠ
The boy was led astray by bad companions. ልጁ ፡ ከመጥፎ ፡ ጓደኞዎች ፡ ገጥሞ ፡ ማገጠ

**astride, sit ~** አንፈራጦ ፡ ተቀመጠ
He sat astride the log. አንፈራጦ ፡ ግንዱ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ

**astrology** አስትሮሎጂ ፤ ኮከብ ፡ ቈጠራ
Magic and astrology are occult arts. ጥንቈላና ፡ ኮከብ ፡ ቈጠራ ፡ (አስትሮሎጂ) ፡ ስውር ፡ ጥበቦች ፡ ናቸው

**astronomer** የከዋክብት ፡ መርማሪ
An astronomer observes the stars. የከዋክብት ፡ መርማሪ ፡ ከዋክብትን ፡ ይመረምራል

**astronomy** አስትሮኖሚ

**astute** ብልጥ
He is an astute merchant. ብልጥ ፡ ነጋዴ ፡ ነው

**asunder,** see **drive, split**

**asylum** ጥገኝነት
The rebel found asylum in the neighboring country. ዐመፀኛው ፡ በጐረቤት ፡ አገር ፡ ጥገኝነት ፡ አገኘ

**at**
1. በ. He came at three o'clock. በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ መጣ
He could read and write at the age of four. በአራት ፡ ዓመቱ ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ ይችል ፡ ነበር
I was astonished at the size of the city. በከተማው ፡ ትልቅነት ፡ ተደንቄ ፡ ነበር
2. እ. I met him at the station. እጣቢያው ፡ አገኘሁት
I will be at home. እቤት ፡ እገኛለሁ
3. እ - - - ላይ ፤ በ - - - ላይ. I will wait for you at the entrance. እመግቢያው ፡ ላይ ፡ እጠብቅሃለሁ
The bus stops at the next corner. አውቶቡሱ ፡ በሚቀጥለው ፡ መታጠፊያ ፡ ላይ ፡ ይቆማል
4. ከ. We have not arrived at a decision yet. ገና ፡ ከውሳኔ ፡ አልደረስንም
5. ለ. At the moment I have no permanent address. ለጊዜው ፡ ቋሚ ፡ አድራሻ ፡ የለኝም
6. ዘንድ. We were at the tailor's. ልብስ ፡ ሰፊው ፡ ዘንድ ፡ ነበርን
7. (zero). It happened at night. የሆነው ፡ ሌሊት ፡ ነው
The children are at school. ልጆቹ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ናቸው

**at all**
1. ምንም + (negative verb). I do not have any money at all. ምንም ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም
2. በፍጹም + (negative verb). He has no patience at all. በፍጹም ፡ ትዕግሥት ፡ የለውም
3. ምናልባት. If you are at all worried, you shouldn't send your child to that place. ምናልባት ፡ የምትሰጋ ፡ ከሆነ ፡ ልጅህን ፡ ወደዚያ ፡ ቦታ ፡ መላክ ፡ የለብህም
[See also 'cost, first, last, least, most, once, time, will']

**ate,** see **eat**

**atheist** [እግዚአብሔር ፡ መኖሩን ፡ የማያምን]

**athlete** ስፖርተኛ ፤ እስፖርተኛ
The best athlete received a prize. ምርጡ ፡ ስፖርተኛ ፡ ሽልማት ፡ አገኘ

**atlas** አትላስ

**atmosphere**
1. ሀዋ. The atmosphere is now a subject of careful study. ሀዋው ፡ አሁን ፡ በጥንቃቄ ፡ በመጠናት ፡ ላይ ፡ ነው
2. ሁኔታ. The atmosphere of the room is pleasant. የክፍሉ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስደስት ፡ ነው
[See also 'tranquil']

**atmospheric** የአየር
Meteorology instructs us about atmospheric changes. የአየር ፡ ጠባይ ፡ ትምህርት ፡ ስለአየር ፡ መለዋወጥ ፡ ያስረዳል

**atom** አቶም

**atone**
1. ንስሐ ፡ ገባ. How can I atone for my sin? ከኀጢአቴ ፡ እንዴት ፡ ንስሐ ፡ ልገባ ፡ እችላለሁ ?

2. አረመ. How can I atone for my bad behavior? መጥፎ ፡ አድራጎቴን ፡ እንደምን ፡ ላርመው ?

**atrocious** አሰቃቂ
The murderer committed an atrocious crime. ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ የሠራው ፡ ወንጀል ፡ አሰቃቂ ፡ ነው

**atrocity** (atrocities) ግፍ
The atrocities of the enemy are revealed in this book. የጠላት ፡ ግፍ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጿል

**atrophy** መመንመን
Paralysis of the arm resulted in atrophy of the muscles. የክንዱ ፡ መሰለል ፡ የጡንቻዎችን ፡ መመንመን ፡ አስከተለ

**attach**
1. አያያዘ. He attached a sample of cloth to the letter. ከደብዳቤውም ፡ ጋር ፡ የጨርቁን ፡ ናሙና ፡ አያያዘው
2. መደበ (ተመደበ). He was attached to the Imperial Bodyguard for awhile. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በክብር ፡ ዘበኛ ፡ ውስጥ ፡ ተመድቦ ፡ ነበር
3. በሕግ ፡ አስያዘ. We had to attach Mr. Parker's salary to collect what he owed us. ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ ላይ ፡ ያለንን ፡ ገንዘብ ፡ ለማስከፈል ፡ ደሞዙን ፡ በሕግ ፡ ማስያዝ ፡ ነበረብን
4. ሰጠ. You attach too much importance to it. ከሚያስፈልገው ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ትሰጠዋለህ

**be attached to** ወደደ
I am very much attached to that child. ያንን ፡ ልጅ ፡ በጣም ፡ እወደዋለሁ

**attach oneself** ተጐዳኘ
He attached himself to a political party. ካንድ ፡ የፖለቲካ ፡ ቡድን ፡ ጋራ ፡ ተጐዳኘ

**attachment**
1. መፈቃቀር. The two had a strong attachment for each other. ሁለቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መፈቃቀር ፡ ነበራቸው
2. ግንኙነት. She is promiscuous, so don't form any attachment with her. ልክስክስ ፡ ሴት ፡ ስለሆነች ፡ ከሷ ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ግንኙነት ፡ አታድርግ

**attack** (v.)
1. ደበደበ ፤ ተናነቀ ፤ መታ(ተመታ). The thieves attacked him and robbed him. ሌቦቹ ፡ ደብድበው ፡ ዘረፉት
He justified his shooting the criminal by saying that the man attacked him. ወንጀለኛውን ፡ በጥይት ፡ የገደለው ፡ ስለተናነቀው ፡ መሆኑን ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ አቀረበ
He was attacked from behind. ከኋላው ፡ ተመታ
2. አጠቃ. The enemy attacked at dawn. ጠላት ፡ ንጋት ፡ ላይ ፡ አጠቃ
Measles is a disease which attacks children. ኩፍኝ ፡ ልጆችን ፡ የሚያጠቃ ፡ በሽታ ፡ ነው
The dog attacked the cat. ውሻው ፡ ድመቲቱን ፡ አጠቃት
3. ወረረ. The disorderly mob attacked the President's residence. ቅጥ ፡ ያጣ ፡ ሕዝብ ፡ የፕሬዚዳንቱን ፡ ቤት ፡ ወረረ
4. አነቀ. The leopard crouched ready to attack. ነብሩ ፡ ሊያንቅ ፡ አድፍጧል
5. ተተናኰለ(በት). Some insects attacked our garden plants. አንዳንድ ፡ ነፍሳት ፡ አትክልቶቻችንን ፡ ተተናኰሉብን
6. በኀይል ፡ ነቀፈ ፤ ዘለፈ (ተዘለፈ). The newspaper attacked the senator's speech. ጋዜጣው ፡ የሕግ ፡ መወሰኛውን ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባል ፡ ንግግር ፡ በኀይል ፡ ነቀፈ
He was violently attacked in the newspapers. በጋዜጣው ፡ ክፉኛ ፡ ተዘለፈ
7. አጣደፈ. The hungry boy attacked his dinner as soon as it was served. የተራበው ፡ ልጅ ፡ እራቱ ፡ እንደቀረበለት ፡ ወዲያው ፡ አጣደፈው

**attack** (n.)
1. ማጥቃት. In the attack many soldiers were killed. በማጥቃቱ ፡ ወቅት ፡ ብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ተገደሉ
2. መውጋት. The German attack on Russia is considered a blunder. የጀርመን ፡ መስኮብን ፡ መውጋት ፡ እንደ ፡ ከፍተኛ ፡ ስሕተት ፡ ይቈጠራል
3. ውጊያ. The general massed his troops for an attack. ጀኔራሉ ፡ ወታደሮቹን ፡ ለውጊያ ፡ አንድነት ፡ ሰበሰበ
4. ወረራ. The soldiers resisted courageously the enemy's attack. ወታደሮቹ ፡ የጠላትን ፡ ወረራ ፡ በጀግንነት ፡ ተቋቋሙ
*He had another attack yesterday. ትላንትና ፡ ሕመሙ ፡ ተነሥቶ ፡ ነበር

**have an attack of** ተነሣ(በት)
He had an attack of fever. ወባው ፡ ተነሥቶበት ፡ ነበር

**attain**
1. አገኘ. He attained first prize. ያንደኛነትን ፡ ሽልማት ፡ አገኘ
2. ከ - - - ደረሰ. He tried hard to attain his goal. ከግቡ ፡ ለመድረስ ፡ በጣም ፡ ተጣጣረ
He attained the mountain peak after five hours

of climbing. አምስት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ከተንዘ ፡ በኋላ ፡ ከተራራው ፡ ጫፍ ፡ ደረሰ
3. ሆነው ፤ ሞላው. Grandfather attained the age of 90. ወንድ ፡ አያቴ ፡ ዘጠና ፡ ዓመት ፡ ሆናቸው ፡ (ሞላቸው)

**attainment** ማግኘት
The attainment of complete happiness is the goal of some religions. ያንዳንድ ፡ ሃይማኖት ፡ ዓላማ ፡ ፍጹም ፡ ደስታን ፡ ማግኘት ፡ ነው

**attempt** (v.) ሞከረ
Don't attempt too much at one time. ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ አትሞክር

**attempt** (n.) ሙከራ
They failed in their attempt to climb the mountain. ተራራውን ፡ ለመውጣት ፡ ያደረጉት ፡ ሙከራ ፡ ሳይሳካላቸው ፡ ቀረ
An attempt was made on Sukarno's life several times. ሱካርኖን ፡ ለመግደል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሙከራ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር

**make an attempt** ሞከረ ፤ ደከመ
At least make an attempt to pass your exam. ቢያንስ ፡ ፈተናውን ፡ ለማለፍ ፡ ሞክር
I made vain attempts to reach him by telephone. በስልክ ፡ ላነጋግረው ፡ በከንቱ ፡ ደከምኩ

**attend**
1. ተገኘ. His inability to speak English puts him at a disadvantage when he attends conferences. የርሱ ፡ እንግሊዝኛ ፡ መናገር ፡ ያለመቻሉ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ሲገኝ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ይጥለዋል
2. ተማረ. I attend business school. ንግድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እማራለሁ
3. ተካፈለ. He attended a seminar in economics. በሀብተ ፡ ምጣኔ ፡ ትምህርታዊ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ተካፍሏል
4. አከመ. What doctor attended you? ያከመህ ፡ ሐኪም ፡ ማነው ?
5. አስታመመ. Three nurses attended the patient. ሦስት ፡ ነርሶች ፡ በሽተኛውን ፡ አስታመሙት
6. አገለገለ. She has many servants attending her. ብዙ ፡ የሚያገለግሏት ፡ አሽከሮች ፡ አሏት
7. ዐጀበ. A company of nobles attended the king. ብዙ ፡ ባላባቶች ፡ ንጉሡን ፡ ዐጀቡ

**attend to**
1. አከበረ. The child attended to his mother's warning. ልጁ ፡ እናቱ ፡ የሰጠችውን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ አከበረ
2. ልብ ፡ ብሎ ፡ ተለማመደ. Attend to your music if you want to play well. ጥሩ ፡ አድርገህ ፡ ለመጫወት ፡ ብትፈልግ ፡ ሙዚቃህን ፡ ልብ ፡ ብለህ ፡ ተለማመድ
3. ፈጸመ. I still have some things to attend to. ገና ፡ የምፈጽማቸው ፡ ጥቂት ፡ ጉዳዮች ፡ አሉኝ

**attendance**
1. መገኘት. Attendance is compulsory. መገኘት ፡ ግዴታ ፡ ነው
2. በትምህርት ፡ ቀን ፡ መገኘት. Attendance in school is compulsory. በትምህርት ፡ ቀን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መገኘት ፡ ግዴታ ፡ ነው
3. የተገኘ ፡ ሕዝብ. The attendance at the last three meetings has been very poor. ባለፉት ፡ ሦስት ፡ ስብሰባዎች ፡ ላይ ፡ የተገኘው ፡ ሕዝብ ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነበር

**be in attendance**
1. አይታጣም. There is always a mechanic in attendance in the garage. ምንግዜም ፡ ከጋራዡ ፡ መካኒክ ፡ አይታጣም
2. ጠበቀ. The nurse is in attendance. ነርሷ ፡ ትጠብቀዋለች

**take attendance** ስም ፡ ጠራ
The teacher takes attendance every day. አስተማሪው ፡ በየቀኑ ፡ ስም ፡ ይጠራል

**attendant** (n.)
1. ተከታይ. The prince accompanied by his attendants came to our country. ልዑሉ ፡ ከተከታዮቹ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ መጣ
2. ጠባቂ. The attendant at the zoo is sick today. የአራዊቶቹ ፡ ማኖሪያ ፡ ጠባቂ ፡ ዛሬ ፡ ታሟል

**gas station attendant** ቤንዚን ፡ ቀጂው
The gas station attendant spilled some gasoline. ቤንዚን ፡ ቀጂው ፡ ቤንዚን ፡ አፈሰሰ

**attendant** (adj.)
*The war and its attendant evils are described in this book. ጦርነት ፡ ያስከተላቸው ፡ ጠንቆች ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጿል

**attention**
1. ስሜት ፤ መንፈስ. The bright colors of the flag arrested the children's attention. ደማቆቹ ፡ የባንዴራው ፡ ቀለሞች ፡ የልጆቹን ፡ ስሜት ፡ (መንፈስ) ፡ ማረኩት
2. ፍላጎት. The advertisement will capture the attention of the buyers. የንግድ ፡ ማስታወቂያው ፡ የገዢዎቹን ፡ ፍላጎት ፡ ይማርካል
3. የሰው ፡ ዓይን ፡ ልቦና. The speaker was the focus of attention. ተናጋሪው ፡ የሰው ፡ ዓይን ፡ ልቦና ፡ ማረፊያ ፡ ነበር
4. ሐሳብ. Some people's attention is easily

diverted. ያንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ሐሳብ ፡ በቀላሉ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ይመራል
5. ተመልካች. A pretty girl gets more attention than an ugly one. ቆንጆ ፡ ልጃገረድ ፡ ከፉንጋ ፡ ይልቅ ፡ ብዙ ፡ ተመልካች ፡ ታገኛለች
*Attention please! እባካችሁ ፡ አዳምጡ !
*No attention was given to my advice. ምክሬ ፡ ተቀባይ ፡ አላገኘም

**Attention! (military command)** ተጠንቀቅ!

**attentions** መታሰቢያዎች
The soldiers were grateful for letters, packages, and other attentions from home. ወታደሮቹ ፡ ለተላኩላቸው ፡ ደብዳቤዎች ፤ እቃዎችና ፡ ሌሎች ፡ መታሰቢያዎች ፡ አመሰገኑ

**attract attention** ሐሳቡን ፡ ሳበው
Any moving object attracts my attention. የሚንቀሳቀስ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሐሳቤን ፡ ይስብዋል
*Can you bring in the dishes without attracting attention? ሰዎች ፡ ሳያዩህ ፡ ሳሕኑን ፡ ልታመጣ ፡ ትችላለህ ?
*I tried to attract his attention. ወደኔ ፡ እንዲያስተውል ፡ ለማድረግ ፡ ሞከርኩ

**bring to the attention** አስታወቀ
Any change of residence must be brought to the attention of the police. አድራሻ ፡ በተለወጠ ፡ ጊዜ ፡ ለፖሊስ ፡ ማስታወቅ ፡ ያስፈልጋል

**call attention to**
1. አሳሰበ. I have called attention to that repeatedly. ስለ ፡ እሱ ፡ ደጋግሜ ፡ ደጋግሜ ፡ አሳስቤ ፡ ነበር
2. አመለከተ. He called my attention to the cat trying to catch the mouse. ድመቷ ፡ አይጢን ፡ ለመያዝ ፡ ስትሞክር ፡ አመለከተኝ
*I called his attention to it. እንዲያስብበት ፡ ነገርኩት

**catch one's attention** እንዲመለከተው ፡ ምልክት ፡ ሰጠ
She looked away when I tried to catch her attention. እንድትመለከተኝ ፡ ምልክት ፡ ለመስጠት ፡ ስሞክር ፡ ፊቷን ፡ ዘወር ፡ አደረገችብኝ

**draw attention to** አስገነዘበ
He drew my attention to my mistake. ስሕተቴን ፡ አስገነዘበኝ

**get the attention**
1. እንዲከታተለው ፡ አደረገ. A teacher must know how to get the attention of his pupils. አንድ ፡ መምህር ፡ ተማሪዎቹ ፡ እንዲከታተሉት ፡ ማድረግን ፡ ማወቅ ፡ አለበት
2. ሐሳቡን ፡ ማረከ. She jogged his elbow to get his attention. ሐሳቡን ፡ ለመማረክ ፡ ክርኑን ፡ ነካ ፡ አደረገችው

**pay attention**
1. ልብ ፡ ብሎ ፡ አዳመጠ. Please pay attention to the teacher. አስተማሪውን ፡ ልብ ፡ ብላችሁ ፡ አዳምጡ
2. ሰማ. Don't pay attention to anything he says! እሱ ፡ የሚለውን ፡ አትስማ
3. ተጠንቅቆ ፡ ሠራ. Pay attention to what you are doing, or you will hurt yourself. የምትሠራውን ፡ ነገር ፡ ተጠንቅቀህ ፡ ሥራ ፤ ያለበለዚያ ፡ ራስህን ፡ ትጐዳለህ
4. ጥንቃቄ ፡ አደረገ. You have to pay more attention to your appearance. ለመልክህና ፡ ላለባበስህ ፡ ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ አለብህ

**not pay attention**
1. ችላ ፡ አለ. Don't pay attention to it! ችላ ፡ በለው
2. ከምንም ፡ አልቈጠረም. The warriors paid no attention to their captives' entreaties for mercy. ምርኮኞቻቸው ፡ ምሕረት ፡ እንዲያደርጉላቸው ፡ ያቀረቡትን ፡ ልመና ፡ አርበኞቹ ፡ ከምንም ፡ አልቈጠሩም
3. ዞር ፡ ብሎም ፡ አላየው. The passing crowd paid no attention to the sick child. ተላላፊው ፡ ሕዝብ ፡ በሽተኛውን ፡ ልጅ ፡ ዞር ፡ ብሎም ፡ አላየው

**show attention** አሰበ(ለት)
The boy shows his mother much attention. ልጁ ፡ ለእናቱ ፡ በጣም ፡ ያስብላታል
[See also 'center, concentrate, focus, snap, turn']

**attentive** ትጉ ፤ ልባም
The attentive student learns his lessons quickly. ትጉ ፡ (ልባሙ) ፡ ተማሪ ፡ ትምህርቱን ፡ በፍጥነት ፡ ይማራል

**be attentive to (guests)** በሚገባ ፡ አስተናገደ
The girl was attentive to her mother's guests. ልጅቷ ፡ የእናቷን ፡ እንግዶች ፡ በሚገባ ፡ ታስተናግድ ፡ ነበር

**attentively, listen ~** ልብ ፡ ብሎ ፡ አዳመጠ ፤ በንቃት ፡ አዳመጠ
The teacher listened to the student's story attentively. አስተማሪው ፡ የተማሪውን ፡ ታሪክ ፡ ልብ ፡ ብሎ ፡ አዳመጠ
The children listened attentively. ልጆቹ ፡ በንቃት ፡ አዳመጡ

**attenuate** (vt.)
1. አወከ. The harsh climate of the desert

attenuates the health of those residing there. የበረሃው ፡ ኀይለኛ ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፡ እዚያ ፡ የሚ ኖሩትን ፡ ሰዎች ፡ ጤና ፡ ያውካል
2. (= intr.) መነመነ. +Stretching attenuates a rubberband. ላስቲክ ፡ ሲሳብ ፡ ይመነምናል

**be attenuated**
1. ተዳከመ. The power of the kings became much attenuated in recent times. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ የነገሥታት ፡ ኀይል ፡ በጣም ፡ ተ ዳከመ
2. መነመነ. His body was attenuated by disease. ሰውነቱ ፡ በበሽታ ፡ መንምኖ ፡ ነበር

**attest (to)**
1. መሰከረ. Your work attests to your ability. ሥራህ ፡ ችሎታህን ፡ ይመሰክራል
2. አረጋገጠ. The auditor attested to the correctness of the account. ተቈጣጣሪው ፡ የሒሳቡን ፡ ት ክክለኛነት ፡ አረጋገጠ

**attestation** ቃል
The attestations of all witnesses are checked for accuracy. የምስክሮቹ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ትክክለኛ ፡ ለመሆኑ ፡ ተመረመረ

**attic** [ጣሪያው ፡ ሥር ፡ ያለው ፡ ቦታ]

**attire** (n.) ልብስ
He came to church in inappropriate attire. የማይገባ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያ ን ፡ መጣ

**(be) attired** ለበሰ
The queen is attired in red. ንግሥቲቱ ፡ ቀይ ፡ በ ቀይ ፡ ለብሰዋል

**attitude**
1. ጠባይ. His unfriendly attitude discourages visitors. ሰው ፡ ያለመውደድ ፡ ጠባዩ ፡ ጐብኚዎችን ፡ ያባርራል
2. ሁኔታ. I don't like his attitude. ሁኔታውን ፡ አልወደውም
3. አስተያየት. What is your attitude toward cheating? ስለ ፡ ማታለል ፡ ያለህ ፡ አስተያየት ፡ ምንድነው ?
4. አኳኋን. He stood there in a threatening attitude. በሚያስፈራ ፡ አኳኋን ፡ እዚያ ፡ ቆመ
5. መንፈስ. We must maintain a firm attitude. ቈራጥ ፡ መንፈስ ፡ ይዘን ፡ መቆየት ፡ አለብን
6. አመል. That attitude is characteristic of her. ያ ፡ አመል ፡ የርሷ ፡ ዓይነተኛ ፡ ጠባይዋ ፡ ነው

**attorney**
1. ጠበቃ. The company's attorney failed to show up at the hearing. የኩባንያው ፡ ጠበቃ ፡ በ ቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ሳይቀርብ ፡ ቀረ
2. ነገረ ፡ ፈጅ. Please be my attorney during my absence. እባክህን ፡ እኔ ፡ በሌለሁበት ፡ ጊዜ ፡ ነ ገረ ፡ ፈጄ ፡ ሁን

**attorney for the prosecution** ሕግ ፡ አስከባሪ
The attorney for the prosecution hopes to get a conviction. ሕግ ፡ አስከባሪው ፡ በተከሳሹ ፡ ላ ይ ፡ ለማስፈረድ ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋል

**attorney general** ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ
The attorney general asked the judge to acquit the defendant. ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ተከሳ ሹ ፡ በነጻ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ዳኛውን ፡ ጠየቀ

**defense attorney** የተከሳሽ ፡ ጠበቃ
The defense attorney is a famous lawyer. የተከሳሹ ፡ ጠበቃ ፡ ዝነኛ ፡ ጠበቃ ፡ ነው

**attract**
1. ማረከ. The glamour of the East has always attracted me. የምሥራቅ ፡ ውበት ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ እንደማረከኝ ፡ ነው
2. ሳበ. What is attracting the flies here? እዚህ ፡ ዝንቦችን ፡ የሚስብ ፡ ምንድነው ?
A magnet attracts iron. ማግኔት ፡ ብረት ፡ ይስባል
[See also 'attention']

**attraction** የሚማርክ
Her dancing was the big attraction in the show. በትርኢይቱ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ የሚማርከው ፡ የሷ ፡ ዳንስ ፡ ነበር

**have an attraction for** አጓጓ
Money has a great attraction for him. ገንዘብ ፡ በጣም ፡ ያጓጓዋል

**attractive**
1. የሚያምር ፤ የሚማርክ. He married a very attractive girl. በጣም ፡ የምታምር ፡ ልጅ ፡ አገባ
This film star is very attractive. ይህች ፡ ፊልም ፡ ተጫዋቾ ፡ በጣም ፡ የምትማርክ ፡ ናት
2. ማራኪ. The girl's voice is attractive. የልጅቷ ፡ ድምፅ ፡ ማራኪ ፡ ነው
3. የሚያጓጓ. He made me a very attractive offer. የሚያጓጓ ፡ ድርድር ፡ አቀረበልኝ

**be attractive** አስደሰተ
The layout of the streets is quite attractive. የመንገዱ ፡ አቀያየስ ፡ በጣም ፡ ያስደስታል

**make attractive** አሳመረ
Typography makes the printed page more attractive. እትም ፡ ጽሑፉን ፡ የያዘውን ፡ ገጽ ፡ በይበልጥ ፡ ያሳምራል

**attractiveness** ውበት
The municipality is in charge of the city's

attractiveness. ለከተማው ፡ ውበት ፡ ኀላፊ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ነው

**attribute** (v.)
*He attributes his success to hard work. የሥራውን ፡ መሳካት ፡ በትጋቱ ፡ ያገኘሁት ፡ ነው ፡ ይላል
*He attributed intelligence to his colleagues. የሥራ ፡ ጓደኞቹ ፡ ዐዋቂዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ይናገራል

**attribute** (n.)
1. ባሕርይ. Mercy is an attribute of God. ምሕረት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሕርይ ፡ ነው
2. መለዮ. The crown is an attribute of royalty. ዘውድ ፡ የንጉሥነት ፡ መለዮ ፡ ነው

**attrition** ማዳከም
The long siege turned into a war of attrition. ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ የተደረገው ፡ መከበብ ፡ እንደ ፡ ማዳከም ፡ ጦርነት ፡ ሆነ

**by attrition** ሲበላ
Metal becomes weak by attrition. ብረት ፡ ሲበላ ፡ ደካማ ፡ ይሆናል

**(be) attuned to** ለመደ
His ears were attuned to the noise of the big city. ጆሮው ፡ የትልቁን ፡ ከተማ ፡ ውካታና ፡ ጫጫታ ፡ ለምዶታል

**auction** ሐራጅ
His property was sold at auction. ንብረቱ ፡ በሐራጅ ፡ ተሸጠ

**audacious** ደፋር
The audacious boy rushed into the burning building to rescue the child. ደፋሩ ፡ ልጅ ፡ ሕፃኑን ፡ ለማትረፍ ፡ የተቀጣጠለው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሮጦ ፡ ገባ

**audacity** ድፍረት
His audacity to ask me for money shocked me. እኔን ፡ ገንዘብ ፡ ሲጠይቅ ፡ ድፍረቱ ፡ አስደነገጠኝ

**audible** የሚሰማ
He spoke in a scarcely audible voice. በችግር ፡ በሚሰማ ፡ ድምፅ ፡ ተናገረ

**audience**
1. የተሰበሰበ ፡ ሕዝብ. The audience was asked to remain seated. የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ እተቀመጠበት ፡ እንዲቆይ ፡ ተጠየቀ
2. ተመልካች. The television audience in Ethiopia is still very small. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አሁንም ፡ የቴሌቪዥን ፡ ተመልካች ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነው
3. መገናኘት. People were waiting in the hall for an audience with the governor. ከገዢው ፡ ጋር ፡ ለመገናኘት ፡ ሰዎች ፡ በመተላለፊያው ፡ ላይ ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበር
*Today I had an audience with the minister. ዛሬ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ተቀብለው ፡ አነጋገሩኝ

**give an audience** በቆይታ ፡ ሰማ
The committee will give you an audience to hear the plan. እቅድህን ፡ ለማዳመጥ ፡ ደርጉ ፡ በቆይታ ፡ ይሰማሃል

**grant an audience** ተቀብሎ ፡ አነጋገረው
The Emperor granted him an audience. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ተቀብለው ፡ አነጋገሩት

**auditor**
1. አድማጭ. The auditors sat in back of the hall. አድማጮቹ ፡ አዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ከበስተኋላ ፡ ተቀመጡ
2. ተቈጣጣሪ. The auditor checked the account. ተቈጣጣሪው ፡ ሒሳቡን ፡ መረመረ

**auditorium** (የጉባኤ) አዳራሽ
The auditorium in which the celebration was to be held was small. በዓሉ ፡ የሚፈጸምበት ፡ የጉባኤው ፡ አዳራሽ ፡ ትንሽ ፡ ነበር

**augment**
1. ጨመረ. The boss failed to augment my pay. አለቃዬ ፡ ደሞዜን ፡ ሳይጨምርልኝ ፡ ቀረ
2. አሳደገ. He augmented his income by writing speeches. ንግግር ፡ በመጻፍ ፡ ገቢውን ፡ አሳደገ

**augur** ተስፋ ፡ አመለከተ
Everything augurs success. ሁሉም ፡ ነገር ፡ የመሳካትን ፡ ተስፋ ፡ ያመለክታል

**august** ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ያለው
Ras Imru is an august personage. ራስ ፡ እምሩ ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ያላቸው ፡ ሰው ፡ ናቸው

**August** ነሐሴ

**aunt** አክስት

**aura** መንፈስ
An aura of holiness surrounded the saint. ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ በጻድቁ ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**aureole** የብርሃን ፡ አክሊል
The aureoles are always painted in gold. የብርሃን ፡ አክሊል ፡ ሁልጊዜ ፡ ወርቅማ ፡ ቀለም ፡ ይቀባል

**auspices** ድጋፍ
He traveled abroad under the government's

auspices. በመንግሥት ፡ ድጋፍ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሄደ

**auspicious** ተስፋ ፡ የሚሰጥ
Our team made an auspicious beginning by winning the first game. ቡድናችን ፡ የመጀመሪያውን ፡ ግጥሚያ ፡ በማሸነፍ ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጥ ፡ አጀማመር ፡ አሳየ

**austere**
1. ምቾት ፡ የለሽ. The austere life of the first pioneers was remarkable. የቀደምቶቹ ፡ ሰፋሪዎች ፡ ምቾት ፡ የለሽ ፡ ኑሮ ፡ የሚደነቅ ፡ ነበር
2. ጥብቅ. He is an austere person. ጥብቅ ፡ ሰው ፡ ነው
3. ኮስታራ. The austere look on the judge's face frightened the criminal. የዳኛው ፡ ኮስታራ ፡ አስተያየት ፡ ወንጀለኛውን ፡ አስደነገጠው

**austerity** ድሎት ፡ የለሽ ፡ መሆን
Austerity is characteristic of monasteries. የገዳም ፡ ኑሮ ፡ ድሎት ፡ የለሽ ፡ መሆን ፡ የተለመደ ፡ ነው

**regime of austerity** ችግር ፡ የበዛበት ፡ ኑሮ
Because of the war, they had a regime of austerity. ከጦርነቱ ፡ የተነሣ ፡ ችግር ፡ የበዛበት ፡ ኑሮ ፡ አጋጠማቸው

**authentic**
1. እውነተኛ. This is an authentic signature. ይህ ፡ እውነተኛ ፡ ፊርማ ፡ ነው
2. የሚታመን. I heard an authentic account of the wreck given by one of the ship's officers. ስለ ፡ መርከቡ ፡ አሰባበር ፡ ከመርከቡ ፡ መኰንኖች ፡ አንዱ ፡ የሰጠውን ፡ የሚታመን ፡ መግለጫ ፡ ሰማሁ

**authenticate**
1. እውነተኛነት ፡ አረጋገጠ. The art historian authenticated the painting. የሥዕል ፡ ታሪክ ፡ ዐዋቂው ፡ የሥዕሉን ፡ እውነተኛነት ፡ አረጋገጠ
2. አጸደቀ. The court authenticated his claim to the property. ሀብቱ ፡ ይገባኛል ፡ ማለቱን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አጸደቀለት

**author**
1. ደራሲ. He always wanted to be an author. ዘወትር ፡ ደራሲ ፡ መሆን ፡ ይመኝ ፡ ነበር
2. አመንጪ. Are you the author of this scheme? የዚህ ፡ ውጥን ፡ አመንጪ ፡ አንተ ፡ ነህ ?

**authoritarian** ፈላጭ ፡ ቈራጭ
South Africa has a authoritarian regime. ደቡብ ፡ አፍሪካ ፡ ፈላጭ ፡ ቈራጭ ፡ የሆነ ፡ መንግሥት ፡ አለው

**authoritative**
1. የሚታመን. The news came from an authoritative source. ዜናው ፡ የተገኘው ፡ ከሚታመን ፡ ምንጭ ፡ ነው
2. የአዛዥነት. The officer spoke to the crew in an authoritative tone. መኰንኑ ፡ ሠራተኞቹን ፡ በአዛዥነት ፡ ቃል ፡ ተናገራቸው

**authority** (authorities)
1. ሥልጣን. Do you have the authority to sign this contract for him? ይህንን ፡ ውል ፡ ልትፈርምለት ፡ ሥልጣን ፡ አለህ ?
2. የታመነ ፡ መረጃ. What is your authority for this statement? ለዚህ ፡ ቃል ፡ የታመነ ፡ መረጃህ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
3. ምንጭ. I have it on good authority that the minister will resign. ከታመነ ፡ ምንጭ ፡ እንደ ሰማሁት ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሥራውን ፡ በፈቃዱ ፡ ይለቃል
4. ምስክር. This dictionary is the best authority for English words. ለእንግሊዝኛ ፡ ቃላት ፡ ይህ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ምስክር ፡ ነው
5. ያጠና ፡ ሊቅ ፤ ዐዋቂ. He is an authority on labor problems. በሠራተኞች ፡ ችግር ፡ ያጠና ፡ ሊቅ ፡ ነው
Everyone recognizes him to be an authority on Ethiopia. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዐዋቂ ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ ይቀበለዋል

**authorities** ባለሥልጣን
Apply to the proper authorities. ለተገቢው ፡ ባለሥልጣን ፡ አመልክት

**authorization** ሥልጣን
We need authorization before we can act. ለማድረግ ፡ ከመቻላችን ፡ በፊት ፡ ሥልጣን ፡ እንዲሰጠን ፡ ያስፈልጋል
He had no authorization to sign my name. በኔ ፡ ስም ፡ ለመፈረም ፡ ሥልጣን ፡ አልነበረውም

**authorize**
1. ፈቀደ. The board authorized the spending of 10 million dollars for schools. ቦርዱ ፡ ዐሥር ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ ለትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ወጪ ፡ እንዲሆን ፡ ፈቀደ
The dictionary authorizes the two spellings of this word. መዝገበ ፡ ቃላቱ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ያለውን ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ አጻጻፍ ፡ ይፈቅዳል
2. ሥልጣን ፡ ሰጠ. The President has authorized him to sign the treaty. ውሉን ፡ እንዲፈርም ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶታል

**authorized personnel** የተፈቀደላቸው ፡ ሠራተኞች
Only authorized personnel may enter this office. የተፈቀደላቸው ፡ ሠራተኞች ፡ ብቻ ፡ እዚህ ፡ ቢሮ ፡ መግባት ፡ ይችላሉ

**authorship**
*The authorship of this book is uncertain. የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ደራሲ ፡ አልታወቀም

**auto** መኪና

**autobiography** የራስ ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ
The teacher asked the student to write his autobiography. አስተማሪው ፡ ተማሪው ፡ የራሱ ን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ እንዲጽፍ ፡ ጠየቀው

**autocrat**
*The kings in the Middle Ages were autocrats. በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ንጉሦች ፡ ገደብ ፡ የሌለው ፡ ሥልጣን ፡ ነበራቸው

**autograph** (v.) ስሙን ፡ ጻፈ
The film star autographed his picture. የፊል ም ፡ ኮከቡ ፡ ስሙን ፡ በፎቶግራፍ ፡ ላይ ፡ ጻፈ

**automatic**
1. አቶማቲክ. This is an automatic device that turns the heat on and off. ይህ ፡ ዐውቆ ፡ ሙቀት ፡ የሚሰጥና ፡ የሚያጠፋ ፡ አቶማቲክ ፡ መሣሪያ ፡ ነው
2. ያለ ፡ ባለቤቱ ፡ ቁጥጥር ፡ የሚደርስ. Breathing and swallowing are usually automatic. መተን ፈስና ፡ መዋጥ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ባለቤቱ ፡ ቁጥጥር ፡ የሚደርሱ ፡ ናቸው

**automobile** አውቶሞቢል ፤ መኪና

**autonomous**
1. ነጻ. An autonomous nation chooses its own ruler. ነጻ ፡ አገር ፡ የራሱን ፡ መሪ ፡ ይመርጣል
2. ራሱን ፡ ችሎ ፡ የሚተዳደር. This department is autonomous; it appoints its own officials. ይህ ፡ ክፍል ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ የሚተዳደር ፡ ስለሆ ነ ፡ የራሱን ፡ ሹማምንት ፡ ይሾማል

**autonomy** የራስን ፡ አገዛዝ ፡ ነጻነት
This country gained autonomy last year. ይህ ፡ አገር ፡ የራስን ፡ አገዛዝ ፡ ነጻነት ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ አገኘ

**autumn** መከር
In Europe, autumn lasts from September to December. በአውሮፓ ፡ መከር ፡ ከመስከረም ፡ እስከ ፡ ታኅሣሥ ፡ ይቆያል

**auxiliary** ረዳት
The general sent auxiliary troops to the front. ጄኔራሉ ፡ ረዳት ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ ግንባር ፡ ላከ

**avail** (v.) ጠቀመ
Money will not avail you after you are dead. ከሞትክ ፡ በኋላ ፡ ገንዘብህ ፡ አይጠቅምህም

**avail oneself of** ሠራ(በት)
You should avail yourself of every opportunity to speak Amharic. አማርኛ ፡ ለመናገር ፡ የሚያ ጋጥምህን ፡ ዕድል ፡ ሁሉ ፡ ልትሠራበት ፡ ይገባል

**avail** (n.) ጥቅም
Of what avail is it to study Chinese? የቻይና ን ፡ ቋንቋ ፡ ማጥናት ፡ ምን ፡ ጥቅም ፡ አለው ?

**of no avail** ፍሬ ፡ ቢስ
His efforts were of no avail. ድካሙ ፡ ፍሬ ፡ ቢ ስ ፡ ነበር

**to no avail** በከንቱ
The hunters pursued the quarry to no avail. አዳኞቹ ፡ የሚያድኑትን ፡ እንስሳ ፡ በከንቱ ፡ ሲያ ሳድዱ ፡ ዋሉ

**available** (adj.) የተገኘ
After the fire, every available car was used to take the injured to the hospital. ከቃጠሎው ፡ በኋላ ፡ የተጐዱትን ፡ ሰዎች ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ለማድረስ ፡ የተገኘው ፡ መኪና ፡ በሙሉ ፡ ተሠ ራበት

**be available** ተገኘ
When will the doctor be available? ሐኪሙ ፡ መ ቼ ፡ ይገኛል ?
The dress is available in three colors. ልብሱ ፡ በሦስት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ ይገኛል

**avalanche**
1. ናዳ. An avalanche of rocks blocked the highway. የድንጋይ ፡ ናዳ ፡ መንገዱን ፡ ዘጋው
2. ተንሸራታች ፡ የበረዶ ፡ ክምር. An avalanche destroyed the village in the Alps. አልፕስ ፡ መሀከል ፡ የምትገኘውን ፡ መንደር ፡ ተንሸራታች ፡ የበረዶ ፡ ክምር ፡ አወደማት

**avarice** ንፉግነት
His avarice helped him get rich. የሱ ፡ ንፉግነ ት ፡ ባለጸጋ ፡ ለመሆን ፡ ረዳው

**avaricious** ጨቅ
The avaricious old man gave no money to the poor. ጨቁ ፡ ሽማግሌ ፡ ለድኻ ፡ ገንዘብ ፡ አ ልሰጠም

**avenge** ተበቀለ
He avenged his father's death. ያባቱን ፡ ደም ፡ ተበቀለ

**avenge oneself on** ተበቀለ
He avenged himself on the enemy. ጠላቱን ፡ ተበቀለ

**avenger** ደም ፡ መላሽ
The avenger was a member of the family. ደም ፡ መላሹ ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ አንዱ ፡ ነበር

**avenue**
1. ጐዳና. Churchill Avenue is the main street in Addis Ababa. የቸርቺል ፡ ጐዳና ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ዋና ፡ መንገድ ፡ ነው
2. በር. Hard work is a sure avenue to success. ጠንክሮ ፡ መሥራት ፡ የተረጋገጠ ፡ የእድገት ፡ በር ፡ ነው
Books are avenues to knowledge. መጻሕፍት ፡ የዕውቀት ፡ በር ፡ ናቸው

**average** (v.)
*The rainfall averages 30 inches a year. የዝናቡ ፡ ማእከላዊ ፡ መጠን ፡ ባመት ፡ ሠላሳ ፡ ኢንች ፡ ነው
*He averages sixty dollars a week. የሳምንት ፡ ማእከላዊ ፡ ገቢው ፡ ሥልሳ ፡ ብር ፡ ነው
*He averages six hours' work a day. በየቀኑ ፡ የሚሠራው፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ነው
*The cost of our lunches averages one dollar a week. ለምሳችን ፡ በሳምንት ፡ የምናወጣው ፡ አማካይ ፡ ሒሳብ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ነው

**average** (n., adj.)
1. አማካይ. The average of 4, 5, and 9, is 6. የአራት ፤ የአምስት ፤ የዘጠኝ ፡ አማካይ ፡ ስድስት ፡ ነው
2. መካከለኛ. The average daily temperature was 30°. የቀኑ ፡ መካከለኛ ፡ ሙቀት ፡ 30° ነበር
3. ማእከላዊ. Your work is below the average. ሥራህ ፡ ከማእከለዊ ፡ በታች ፡ ነው
4. መጠነኛ. He is above average height. ከመጠነኛ ፡ ቁመት ፡ በላይ ፡ ነው

**on an average** ከሞላ ፡ ጐደል
It rains on an average of once a week. ከሞላ ፡ ጐደል ፡ በሳምንት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይዘንባል

**on the average** በማእከለዊ ፡ ሲታሰብ
On the average, I go to the movies once a week. በማእከላዊ ፡ ሲታሰብ ፡ በሳምንት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሲኒማ ፡ እሄዳለሁ

**(be) averse (to)** ጠላ
He is averse to hard work. ከባድ ፡ ሥራ ፡ ይጠላል

**aversion** ጥላቻ
His aversion to poetry is well known. ለግጥም ፡ ያለው ፡ ጥላቻ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**have an aversion to** ጠላ
He has a strong aversion to eating pork. ያሳማ ፡ ሥጋ ፡ መብላት ፡ በጣም ፡ ይጠላል

**avert** ዞር ፡ አደረገ
She averted her eyes from the wreck. በግጭቱ ፡ ከተሰባበረው ፡ ነገር ፡ ዓይኗን ፡ ዞር ፡ አደረገች

**avert an accident** ከአደጋ ፡ ዳነ
He averted an accident by applying the brakes. ፍሬኑን ፡ በመያዝ ፡ ከአደጋው ፡ ዳነ

**aviation** ያየር ፡ ማመላለሻ
Aviation is important for Ethiopian commerce. ያየር ፡ ማመላለሻ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**avid** ጉጉ
He is an avid reader. ጉጉ ፡ አንባቢ ፡ ነው

**be avid** ተስገበገበ
The merchant was avid for gold. ነጋዴው ፡ ለወርቅ ፡ ይስገበገባል

**avocation**
*Mr. Brown is a lawyer, but writing stories is his avocation. ሚስተር ፡ ብራውን ፡ ጠበቃ ፡ ነው ፡ ግን ፡ ታሪክ ፡ መጻፍ ፡ ከመደበኛው ፡ ሥራው ፡ ውጭ ፡ የሚሠራው ፡ ነው

**avoid**
1. ሸሸ. He took a devious route to avoid busy streets. የተጨናነቀ ፡ መንገድ ፡ ለመሸሽ ፡ በዙሪያ ፡ መንገድ ፡ ሄደ
Why is he avoiding me? ለምን ፡ ይሸሸኛል ?
2. አስወገደ. Avoid that by all means! በምንም ፡ አኳኋን ፡ ያንን ፡ አስወግደው
3. ከ - - - ራቀ. This peaceful tribe tries to avoid war. ይህ ፡ ሰላማዊ ፡ ነገድ ፡ ከጦርነት ፡ ለመራቅ ፡ ይሞክራል

**be avoided** ተወገደ
The main part of his speech was that the danger of war must be avoided. የንግግሩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ጦርነት ፡ የሚያመጣው ፡ አደጋ ፡ መወገድ ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ ነው

**avoidance** መጠበቅ
The surest way of keeping slim is avoidance of fattening food. ለመቅጠን ፡ ዋናው ፡ ዘዴ ፡ ከሚያወፍር ፡ ምግብ ፡ መጠበቅ ፡ ነው

**avouch** አረጋገጠ
The spectators avouched that the man was injured. ተመልካቾቹ ፡ ሰውዬው ፡ መቍሰሉን ፡ አረጋገጡ

**avow** አመነ
He avowed that he could not think. ሊያስብ ፡ አለመቻሉን ፡ አመነ

**avowed** (adj.)
*His avowed intention was to rob the bank. ባንኩን ፡ ለመዝረፍ ፡ ዓላማ ፡ እንዳለው ፡ በግልጽ ፡ ተናገረ

**await**
1. ተጠባበቀ. We await your reply. መልስህን ፡
እንጠባበቃለን
2. ጠበቀ. Many pleasures await you. ብዙ ፡ ደ
ስታ ፡ ይጠብቅሃል

**awake** (awoke), vt. ቀሰቀሰ
The story I heard awoke my interest. የሰማሁት ፡
ታሪክ ፡ ፍላጎቴን ፡ ቀሰቀሰው
The photo awoke old memories. ፎቶግራፉ ፡ የ
ጥንት ፡ ትዝታዬን ፡ ቀሰቀሰው

**awake** (vi.) ነቃ
I awoke at seven o'clock. ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ነቃሁ

**awake, be (become)** እንቅልፉ ፡ ለቀቀው.
Are you awake? Let's go on a walk! እንቅል
ፍህ ፡ ለቀቀህ? ተነሥ ፡ እንሽራሽር

**be (become) awake to**
1. ንቁ ፡ ነው. He was awake to danger. ለአ
ደጋ ፡ ንቁ ፡ ነበር
2. ደረሰ(በት). He became awake to the fact that
his girl was seeing someone else. ወዳጁ ፡ ከሌላ ፡
ሰው ፡ ጋር ፡ ወዳጅነት ፡ እንደጀመረች ፡ ደረሰበት

**keep awake** (vt.)
1. እንቅልፍ ፡ ነሣው. The cannonade kept us
awake all night. የመድፉ ፡ እሩምታ ፡ ሌሊቱን ፡ በ
ሙሉ ፡ እንቅልፍ ፡ ነሣን
2. አላስተኛ ፡ አለው. The annoyance of mosqui-
tos kept her awake. የወባ ፡ ትንኞች ፡ ማወክ ፡
አላስተኛ ፡ አላት

**keep awake** (vi.) ነቅቶ ፡ ቆየ
She willed to keep awake. ነቅታ ፡ ለመቆየት ፡
ቈረጠች

**stay awake** ነቅቶ ፡ ቆየ
He needs the stimulation coffee gives him to
stay awake. ነቅቶ ፡ እንዲቆይ ፡ የቡና ፡ ማነቃቂ
ያ ፡ ያስፈልገዋል

**awaken** ቀሰቀሰ
The noise awakened me. ጩኸት ፡ ቀሰቀሰኝ

**awakening**
1. (= verb) የነቃው. The abrupt awakening
was caused by a noise. በድንገት ፡ የነቃው ፡
በጩኸት ፡ ምክንያት ፡ ነበር
2. መንቃት. Their awakening to danger saved
their lives. ለአደጋ ፡ መንቃታቸው ፡ ሕይወታ
ቸውን ፡ አዳነ

**award** (v.)
1. ሸለመ. He awarded him first prize. ያንደኛ
ነት ፡ ሽልማት ፡ ሸለመው
2. ቈረጠ(ለት). The judge awarded him 50
dollars as damages. ዳኛው ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ካሳ ፡
ቈረጠለት

**award** (n.) ሽልማት
He received the Haile Sellassie award. የቀዳማ
ዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴን ፡ ሽልማት ፡ ተቀበለ
[See also 'presentation']

**(be) aware** ተገነዘበ
I was aware how deeply he felt the death of
his mother. የእናቱ ፡ ሞት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እ
ንደተሰማው ፡ ተገንዝቤ ፡ ነበር

**be aware of** ዐወቀ
The government was aware of the activities
of enemy spies. መንግሥቱ ፡ የጠላት ፡ ሰላዮችን ፡
አድራጎት ፡ ያውቅ ፡ ነበር
[See also 'fully']

**(be) awash** (= trans.) ውኃ ፡ አጥለቀለቀው
+The street was awash after the sudden down-
pour. በድንገት ፡ ኀይለኛ ፡ ዝናም ፡ በመጣሉ ፡
መንገዱን ፡ ውኃ ፡ አጥለቀለቀው

**(be) away**
1. ከዚህ ፡ ተለየ. I shall be away for some time.
ላጭር ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ እለያለሁ
2. ውጭ ፡ ሄደ. I shall be away from Ethiopia
for five months. ላምስት ፡ ወር ፡ ከኢትዮጵያ ፡
ውጭ ፡ እሄዳለሁ
3. ሄደ. She is away on vacation. ለዕረፍት ፡ ሄ
ዳለች
4. ራቀ. The sea is two miles away. ባሕሩ ፡ ሁ
ለት ፡ ማይል ፡ ይርቃል
*When his best friend is away, he never fails to
backbite him. የቅርብ ፡ ወዳጁ ፡ በሌለበት ፡ እሱ
ን ፡ ማማቱን ፡ ፈጽሞ ፡ አይተውም

**awe** (v.) አስደነቀ
The majesty of the mountains awed us.
የተራራው ፡ ሞገስ ፡ አስደነቀን

**awe** (n.) አክብሮታዊ ፡ ፍርሃት
The sight of the Emperor filled him with awe.
ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ አክብሮታዊ ፡ ፍ
ርሃት ፡ ያዘው

**feeling of awe** አድናቆት
The glory of the sunset filled his heart with a
feeling of awe. የፀሐይ ፡ ጥልቀት ፡ ውበት ፡ ል
ቡን ፡ በአድናቆት ፡ ሞላው

**awesome** አስፈሪ
A great fire is an awesome sight. ትልቅ ፡ ቃጠ
ሎ ፡ አስፈሪ ፡ ትርእይት ፡ ነው

**(be) awe-struck** ተደነቀ
He was awe-struck at the size of the building. የሕንጻውን ፡ ትልቅነት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ተደነቀ

**awful**
1. በጣም ፡ የሚያስቅቅ. I saw the accident and it was awful. አደጋውን ፡ አየሁት ፤ በጣም ፡ የሚያስቅቅ ፡ ነበር
2. አሰቃቂ. He died an awful death. አሰቃቂ ፡ አሟሟት ፡ ሞተ
3. መጥፎ. What awful handwriting you have! ምን ፡ ዓይነት ፡ መጥፎ ፡ የእጅ ፡ ጽሕፈት ፡ አለህ !
4. የባሰበት. He is an awful liar. የባሰበት ፡ ውሸታም ፡ ነው
5. አስጠሊ. I wouldn't wish that awful job on my worst enemy. ያን ፡ አስጠሊ ፡ ሥራ ፡ ለክፉ ፡ ጠላቴም ፡ አልመኘው
6. ልክ ፡ የሌለው. That was an awful mix-up. ያ ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ ምስቅልቅል ፡ ነበር

**awfully**
1. ክፉኛ. I am awfully tired. ክፉኛ ፡ ደክሞኛል
2. በጣም. I am awfully sorry that I hurt your feelings. ስላስቀየምኩህ ፡ በጣም ፡ አዝናለሁ

**behave awfully**
She behaved awfully all evening. የማይገባ ፡ ጠባይ ፡ ስታሳይ ፡ አመሸች

**awhile** ለጥቂት ፡ ጊዜ
He was here awhile this afternoon. ዛሬ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እዚህ ፡ ነበር

**awkward**
1. ገልጃጃ. Is he so awkward in everything he does? በሚሠራው ፡ ሁሉ ፡ እንደዚህ ፡ ገልጃጃ ፡ ነው ?
2. የማይመች. The meeting was at nine which is an awkward time for some people. ስብሰባው ፡ ለሕዝብ ፡ በማይመች ፡ ጊዜ ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ ነበር
3. ግራ ፡ ቢስ. This bottle has an awkward shape. ይህ ፡ ጠርሙስ ፡ ግራ ፡ ቢስ ፡ የሆነ ፡ ቅርጽ ፡ አለው
4. ወልካፋ. He has an awkward gait. አረማመዱ ፡ ወልካፋ ፡ ነው
5. የሚያሳፍር. His unfortunate remark was followed by an awkward pause. ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ አስተያየቱ ፡ የሚያሳፍር ፡ ዝምታን ፡ አስከተለ
*The child is still awkward with his knife and fork. ሕፃኑ ፡ በቢላዋና ፡ በሹካ ፡ አያያዝ ፡ ገና ፡ አልሠለጠነም

**awl** ወስፌ
The shoemaker needs an awl for his work. ጫማ ፡ ሰፊው ፡ ለሥራው ፡ ወስፌ ፡ ያስፈልገዋል

**awning** ግርዶሽ
The awning keeps the sun off the porch. ግርዶሹ ፡ በረንዳው ፡ ላይ ፡ ፀሐይ ፡ እንዳይወጣ ፡ ይከላከላል

**awoke**, see **awake**

**awry, blow ~** አንጋደደ
The wind blew her hat awry. ነፋስ ፡ ባርኔጣዋን ፡ አንጋደደባት

**go awry** ተበላሸ
Our plans went awry. እቅዳችን ፡ ተበላሸ

**ax** መጥረቢያ
He split the wood with the ax. እሱ ፡ ዕንጨቱን ፡ በመጥረቢያ ፡ ፈለጠ

**axiom** እሙን ፤ ጽድቅ
It is an axiom that no one lives forever. ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ለዘላለም ፡ እንደማይኖር ፡ እሙን ፡ (ጽድቅ) ፡ ነው

**axis** ዘንግ ፤ እንዝርት
The world whirls on its axis. ዓለም ፡ በዘንጓ ፡ (በእንዝርቷ) ፡ ላይ ፡ ትሽከረከራለች

**azure** የጠራ
The azure sky had only one cloud. የጠራው ፡ ሰማይ ፡ አንዲት ፡ ደመና ፡ ብቻ ፡ ነበረበት

## B

**babble** (v.) ተኮላተፈ
The baby babbled all day long. ሕፃኑ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሲኮላተፍ ፡ ዋለ

**babble** (n.) ጉርምርምታ
The babble of the stream was very soothing. የወንዙ ፡ ጉርምርምታ ፡ የመንፈስ ፡ እርካታ ፡ ይሰጥ ፡ ነበር

**babies,** see **baby**

**baboon** ዝንጀሮ
The baboons destroy grain. ዝንጀሮ ፡ እህል ፡ ያጠፋል

**baby** (babied), v. እንከባከበ
We all babied father when he was sick. አባታችን ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ ሁላችንም ፡ እንከባከብ ነው

**baby** (babies), n.
1. ሕፃን. The baby is crying. ሕፃኑ ፡ ያለቅሳል
2. የመጨረሻ ፡ ልጅ. Which one of you is the baby of the family? የመጨረሻ ፡ ልጅ ፡ ማንኛችሁ ፡ ናችሁ ?

**baby bird** የወፍ ፡ ጫጩት
The baby bird was attacked by a horde of ants. የወፏን ፡ ጫጩት ፡ የጉንዳን ፡ መዓት ፡ ወረራት
[See also 'change, deliver, newborn baby, nipple']

**babyhood** ሕፃንነት
The boy had no illness during his babyhood. ልጁ ፡ በሕፃንነቱ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ ሕመም ፡ አልነበረውም

**babyish** የሕፃንነት
He outgrew his babyish habits. ስላደገ ፡ የሕፃንነት ፡ ጠባዩን ፡ ትቷል

**bachelor** ወንደ ፡ ላጤ
Even though he is thirty years old, he is still a bachelor. ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ቢሆነውም ፡ አሁንም ፡ ወንደ ፡ ላጤ ፡ ነው

**bachelor's degree** የቢ ፡ ኤ ፡ ዲግሪ
He received his bachelor's degree from the University of California. የቢ ፡ ኤ ፡ ዲግሪ ፡ ያገኘው ፡ ከካሊፎርንያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ነው

**back** (v.)
1. ከ - - - ጀርባ ፡ ነው. Our garden backs theirs. የኛ ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ ከነሱ ፡ ጀርባ ፡ ነው
2. ደገፈ. He backs his friends in every argument. በማንኛውም ፡ ክርክር ፡ ወዳጆቹን ፡ ይደግፋል

**back away**
*Protocol requires backing away from the Emperor's presence. በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊት ፡ ሳትዞር ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንድትሄድ ፡ ፕሮቶኮል ፡ ይጠይቃል

**back down**
1. ተወ. After threatening to hit me, he backed down. ሊመታኝ ፡ ከዛተ ፡ በኋላ ፡ ተወው
2. ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈገ. He claimed that he could fix the engine, but backed down when asked to do it. ሞተሩን ፡ ልጠግነው ፡ እችላለሁ ፡ ብሎ ፡ ነበር ፤ እንዲሠራው ፡ ቢጠየቅ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈገ

**back out** (vt.) ወደ ፡ ኋላ ፡ ነድቶ ፡ አወጣ
He backed his car out of the garage. ወደ ፡ ኋላ ፡ ነድቶ ፡ መኪናውን ፡ ከጋራዥ ፡ አወጣ

**back out** (vi.)
1. አፈገፈገ ፤ ወደ ፡ ኋላ ፡ አለ. He promised to help, but backed out at the last minute. ለመርዳት ፡ ቃል ፡ ገብቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ደቂቃ ፡ አፈገፈገ ፡ (ወደ ፡ ኋላ ፡ አለ)
2. እጁን ፡ አወጣ. He tried to back out of the agreement he signed. ከፈረመው ፡ ውል ፡ እጁን ፡ ለማውጣት ፡ ሞከረ

**back up a bit** ወደ ፡ ኋላ ፡ ሄደት ፡ አለ
Back up a bit; I can't get by. ትንሽ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሄደት ፡ በል ፤ ላልፍ ፡ አልችልም

**back** (n.)
1. ጀርባ. My back aches. ጀርባዬን ፡ ያመኛል
He wrote something in the back of the book. በመጽሐፉ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ጻፈ
2. መደገፊያ. He hung his sweater on the back of the chair. ሹራቡን ፡ በወንበሩ ፡ መደገፊያ ፡ ላይ ፡ ሰቀለው

**back of hand**
He has a scar on the back of his hand. እጁ ፡ ላይ ፡ ጠባሳ ፡ አለው

**back of head** ማጅራት
You cannot see the back of your head. ማጅራትህን ፡ ለማየት ፡ አትችልም

**back of knife** የቢላዋ ፡ ደንደስ
You cannot cut anything with the back of the knife. በቢላዋው ፡ ደንደስ ፡ ምንም ፡ ልትቆርጥበት ፡ አትችልም

**back to back** ጀርባ ፡ ለጀርባ
They sat back to back. ጀርባ ፡ ለጀርባ ፡ ተቀመጡ

**behind one's back**
1. በሌለበት. She slandered me behind my back. በሌለሁበት ፡ አማችኝ
2. ከሱ ፡ ደብቆ. They did it behind my back. ከኔ ፡ ደብቀው ፡ አደረጉት
3. የፊጥኝ. His hands were tied behind his back. እጁ ፡ የፊጥኝ ፡ ታስሮ ፡ ነበር

**in back of the house** ከቤቱ ፡ ጓሮ
There is a garden in back of the house. ከቤቱ ፡ ጓሮ ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ አለ

**in the back**
1. ከ--- ኋላ. He put it in the back of the car. ከመኪናው ፡ ኋላ ፡ አስቀመጠው
2. ከ - - - በስተኋላ. She put the wardrobe in the back of the room. ሰንዱቁን ፡ ከክፍሉ ፡ በስተኋላ ፡ አደረገች

**take on one's back** አዘለ
She took the child on her back. ልጅዋን ፡ አዘለችው

**turn one's back on**
1. ዝም ፡ ብሎ ፡ አለፈ. He is unable to turn his back on any suffering creature. በሥቃይ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ማንኛቸውንም ፡ ፍጡር ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ማለፍ ፡ አይሆንለትም
2. ፊቱን ፡ አዞረ (በት). He refused to turn his back on his friend when he got in trouble. ጓደኛው ፡ ችግር ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ፊቱን ፡ አላዞረበትም
[See also 'bend, carry, flat, go, hump, pat, resistance, run down, seat, talk']

## back (adj.)
1. የኋላ. The back wheel of the bicycle came off. የቢስክሌቷ ፡ የኋላ ፡ ጎማ ፡ ወለቀ
2. በስተጀርባ ፡ ያለ. The back rooms are dark. በስተጀርባ ፡ ያሉት ፡ ክፍሎች ፡ ጨለማ ፡ ናቸው
3. ከጓሮ ፡ ያለ. They gained access through a back window. ከጓሮ ፡ ባለው ፡ መስኮት ፡ ሊገቡ ፡ ቻሉ
4. ያለፈ. Send me all the back numbers of your newspaper. የጋዜጣችሁን ፡ ያለፉትን ፡ እትሞች ፡ ሁሉ ፡ ላክልኝ
5. እላፊ. He received 500 dollars in back pay. አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ እላፊ ፡ ደሞዝ ፡ ተቀበለ

**back** (adv.) ድሮ
They met in Addis Ababa back in 1946. ድሮ ፡ በ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ.ም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ተገናኝተው ፡ ነበር

**back and forth** ወዲያ ፡ ወዲህ
The pendulum swings back and forth. የግድግዳው ፡ ሰዓት ፡ እጀታ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይወዛወዛል

**be back** ተመለሰ
He is not back yet. ገና ፡ አልተመለሰም
[See also 'there']

## backache የጀርባ ፡ ሕመም
Backache is his chief complaint. በጣም ፡ የሚያማርረው ፡ የጀርባ ፡ ሕመሙ ፡ ነው

## backbite አማ
When his best friend is away, he never fails to backbite him. የቅርብ ፡ ወዳጁ ፡ በሌለበት ፡ እሱን ፡ ማማቱን ፡ ፈጽሞ ፡ አይተውም

## backbone አከርካሪ
His backbone was broken when he fell. በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ አከርካሪው ፡ ተሰበረ

**it takes backbone** ቆራጥነት ፡ ይጠይቃል
It takes backbone to stand up to such a big man. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ለመቋቋም ፡ ቆራጥነት ፡ ይጠይቃል

## backdoor የጓሮ ፡ በር
They exited through the backdoor. በጓሮ ፡ በር ፡ ወጡ

## background
1. መደብ. The stars of the American flag are sewn on a blue background. የአሜሪካን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ኮከቦች ፡ የተሰፉት ፡ በሰማያዊ ፡ መደብ ፡ ላይ ፡ ነው
2. መነሻ. This book tells about the background of the last war. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ስላለፈው ፡ ጦርነት ፡ መነሻ ፡ ይናገራል
3. ልምምድ. She has a good background for office work. ለቢሮ ፡ ሥራ ፡ ጥሩ ፡ ልምምድ ፡ አላት
4. ችሎታ. His background includes courses in French and German. ችሎታው ፡ ፈረንሳይኛና ፡ ጀርመንኛን ፡ ያጠቃልላል

**in the background** ከ - - - በስተጀርባ
There were mountains in the background of the picture. ከሥዕሉ ፡ በስተጀርባ ፡ ተራሮች ፡ ነበሩ

**keep in the background** (vt.) አገለለ
He always keeps his young son in the back-

ground. እሱ ፡ ትንሹን ፡ ልጁን ፡ ሁልጊዜ ፡ እንዳገ
ለለው ፡ ነው

**stay in the background** የማይታይበት ፡ ቦታ ፡ ያዘ ፤
ወደ ፡ ኋላ ፡ ሆነ
The mayor's wife tried to stay in the back-
ground. የከንቲባው ፡ ሚስት ፡ የማትታይበት ፡
ቦታ ፡ ለመያዝ ፡ (ወደ ፡ ኋላ ፡ ለመሆን) ፡ ሞከረች

**backhanded** የለበጣ
He likes to makes backhanded compliments.
የለበጣ ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብ ፡ ይወዳል

**backing** ድጋፍ
He has the backing of the president. የፕሬዚዳን
ቱ ፡ ድጋፍ ፡ አለው

**backlog**
*There is a large backlog of unfilled orders.
ብዙ ፡ ያልተሟላ ፡ የሥራ ፡ ውዝፍ ፡ አለ

**back rest** መደገፊያ
The back rest of the chair is broken. የወንበሩ ፡
መደገፊያ ፡ ተሰብሯል

**back seat, take a ~** በታች ፡ ሆነ
He will take a back seat to no one. ከማንም ፡
በታች ፡ ሊሆን ፡ አይፈልግም

**backward** (adj.)
1. የአእምሮ ፡ ብስለት ፡ የሚጐድለው. Backward
children need a special kind of schooling. የ
አእምሮ ፡ ብስለት ፡ ለሚጐድላቸው ፡ ልጆች ፡ የተለ
የ ፡ የማስተማር ፡ ዘዴ ፡ ያስፈልጋቸዋል
2. (= adv.) ወደ ፡ ኋላ. The backward movement
of the car was halted by a wall. መኪናዋ ፡ ወደ ፡
ኋላ ፡ ስትሄድ ፡ ግንብ ፡ አቆማት

**be backward** ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀረ
The people there are very backward. የዚያ ፡
አገር ፡ ሰዎች ፡ በጣም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርተዋል

**backward** (adv.) ወደ ፡ ኋላ
He walked backward, and then he tripped.
ወደ ፡ ኋላ ፡ ከተራመደ ፡ በኋላ ፡ ተደናቀፈ

**backwardness**
*An inclement ruler contributes to the back-
wardness of a country. ጨቋኝ ፡ ገዢ ፡ አገር
ን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ያስቀራል

**backwards**
1. ወደ ፡ ኋላ. Can you say the alphabet back-
wards and forwards? ፊደሉን ፡ ወደ ፡ ኋላና ፡
ወደ ፡ ፊት ፡ ልትለው ፡ ትችላለህ ?
2. የእንግልል. He fell backwards. የእንግልል ፡
ወደቀ

**backwards and forwards** ጠንቅቆ ፡ ከዳር ፡ እስ
ከ ፡ ዳር
He knows his lines backwards and forwards.
ትምህርቱን ፡ ጠንቅቆ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ያውቃል
[See also 'bend, lean']

**backyard** ጓሮ
There was no grass in the backyard. እጓሮው ፡
ምንም ፡ ሣር ፡ አልነበረም

**bacteria** ረቂቃን ፡ ነፍሳት
Bacteria causes milk to sour. ረቂቃን ፡ ነፍሳ
ት ፡ ወተትን ፡ ያኰመጥጣሉ

**bad**
1. ክፉ. He heard the bad news over the radio.
ክፉውን ፡ ወሬ ፡ ከሬድዮ ፡ ሰማ
2. ኀይለኛ. I have a bad cold. ኀይለኛ ፡ ጉንፋን ፡
ይዞኛል
3. መጥፎ. There is a bad smell here. እዚህ ፡ መ
ጥፎ ፡ ሽታ ፡ አለ
That's not a bad idea. ያ ፡ መጥፎ ፡ ሐሳብ ፡
አይደለም
The boy was led astray by bad companions.
ልጁ ፡ ከመጥፎ ፡ ጓደኞዎች ፡ ገጥሞ ፡ ማገጠ
4. በሽተኛ. A bad tooth can cause acute pain.
በሽተኛ ፡ ጥርስ ፡ ጽኑ ፡ ሕመም ፡ ሊያመጣ ፡
ይችላል
Bad eyesight handicaps him. ዓይኑ ፡ በሽተኛ ፡
መሆኑ ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆኖበታል
5. ጐጂ. Reading in poor light is bad for the
eyes. በደብዛዛ ፡ መብራት ፡ ማንበብ ፡ ለዓይን ፡ ጐጂ ፡
ነው
6. የተበላሸ. He is tempting fate by driving
with a bad tire. በተበላሸ ፡ ጎማ ፡ በመንዳት ፡ በ
ገዛ ፡ እጁ ፡ አደጋ ፡ ይጐትታል
7. ጸያፍ. He uses bad language all the time.
ሁልጊዜ ፡ ጸያፍ ፡ አነጋገር ፡ ይናገራል
8. ያልተጣራ. Please excuse my bad Amharic.
ስላልተጣራው ፡ አማርኛዬ ፡ ይቅርታ ፡ አድርግ
ልኝ
9. ባለጌ. If you are bad in school, you'll go to
bed without supper. በትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡
ባለጌ ፡ ከሆንክ ፡ እራት ፡ አይሰጥህም
10. አጉል. He came at a bad time. በአጉል ፡ ጊ
ዜ ፡ መጣ
11. የበሰበሰ. This bad apple upset his stomach.
የበሰበሰው ፡ ቱፋ ፡ ሆዱን ፡ አሳመመው
12. ዋጋ ፡ ቢስ. He was arrested for passing
bad checks. ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ቼክ ፡ ስለሰጠ ፡ ተያዘ

**bad weather** የአየር ፡ መጥፎነት
Do you contemplate any difficulty because of

bad weather? በአየሩ ፡ መጥፎነት ፡ ችግር ፡ ይደር ሳል ፡ ብለህ ፡ ትገምታለህ?

**be bad** ከፋ

The locusts are bad this year. አንበጣ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ከፍቷል

**call someone a bad name** ሰደበ

He called me a bad name because he was mad at me. በጣም ፡ ተናዶብኝ ፡ ስለነበረ ፡ ሰደበኝ

**feel bad**

1. ጤንነት ፡ አልተሰማውም. I feel bad today. Perhaps I shouldn't have drunk so much yesterday. ዛሬ ፡ ጤንነት ፡ አይሰማኝም ፤ ትናንት ፡ ብዙ ፡ ባልጠጣ ፡ ይሻለኝ ፡ ነበር

2. አዘነ. I feel bad about your loss. ስለደረሰብ ህ ፡ ጉዳት ፡ አዝናለሁ

**go bad** ተበላሸ

Fish and meat soon go bad in hot weather. ዓሣና ፡ ሥጋ ፡ በሙቀት ፡ አየር ፡ ውስጥ ፡ ቶሎ ፡ ይበላሻሉ

**go from bad to worse** የባሰውን ፡ እየተበላሸ ፡ ሄደ

His business is going from bad to worse. ንግዱ ፡ የባሰውን ፡ እየተበላሸ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ነው

**not bad** ምንም ፡ አይል

How are you? Not bad. እንደምን ፡ ነህ ? ም ንም ፡ አልል

**too bad**

*Too bad that you couldn't come. ለመምጣ ት ፡ አለመቻልህ ፡ ያሳዝናል

[See also 'grace, half, humor, language, luck, manners, mood, repair, shape, taste, temper, term, worse']

## bad blood ጥላቻ

There is bad blood between the two families. በሁለቱ ፡ ቤተሰብ ፡ መካከል ፡ ጥላቻ ፡ አለ

## bade, see bid

## badge አርማ

The policeman wears a badge on his arm. ፖሊሱ ፡ እክንዱ ፡ ላይ ፡ አርማ ፡ አድርጓል

## badger አበሳጨ

They badgered the speaker with interruptions. ንግግሩን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በማቋረጥ ፡ ተናጋሪውን ፡ አበሳጩት

## badly

1. ከፋኛ. This team was badly beaten in football. ይህ ፡ ቡድን ፡ በእግር ፡ ኳስ ፡ ከፋኛ ፡ ተ ሸንፎ ፡ ነበር

2. መጥፎ ፡ አድርጎ. The barber cut my hair badly. ጸጉር ፡ አስተካካዩ ፡ ጸጉሬን ፡ መጥፎ ፡ አድርጎ ፡ ቈረጠኝ

3. በመጥፎ ፡ አኳኋን. He sent me a badly written letter. በመጥፎ ፡ አኳኋን ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፡ ላከልኝ

4. በጣም. She wants it badly. በጣም ፡ ትፈልገዋ ለች

5. በኀይል. The soldier sank to the ground, badly wounded. ወታደሩ ፡ በኀይል ፡ ስለቈሰለ ፡ ተዝለፍልፎ ፡ ወደቀ

*Badly cooked food bloated his stomach. በደንብ ፡ ያልበሰለው ፡ ምግብ ፡ ሆዱን ፡ ነፋው

*The car runs badly. መኪናዋ ፡ በደንብ ፡ አት ሄድም

**be badly off** ተቸገረ ፤ ቸገረ(ው)

They are not so badly off; they still have money in the bank. ይህንን ፡ ያህል ፡ አልተቸ ገሩም ፤ አሁንም ፡ እባንክ ፡ ገንዘብ ፡ አላቸው

They are badly off this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ በጣም ፡ ቸግሯቸዋል

**take badly** ልቡን ፡ ነካ(ው)

+He took his loss badly. የደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ልቡን ፡ ነካው

[See also 'behave, treat, use']

## (be) bad-mannered መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ አሳየ

He is generally bad-mannered with his employees. በጠቅላላው ፡ በሠራተኞቹ ፡ ላይ ፡ መጥ ፎ ፡ ጠባይ ፡ ያሳያል

## bad-tempered ቁጡ

He is a bad-tempered old man. ቁጡ ፡ ሽማግሌ ፡ ነው

## baffle ግራ ፡ አገባ

This algebra problem baffled me. ይህ ፡ የአልጀ ብራ ፡ ጥያቄ ፡ ግራ ፡ አገባኝ

## bag (bagged), v. ጐረበ

The trousers bagged at the knees. ሱሪው ፡ እጉ ልበቱ ፡ ላይ ፡ ጐርቧል

## bag (n.)

1. ቦርሳ. She took some change out of her bag. ከቦርሳዋ ፡ ውስጥ ፡ ዝርዝር ፡ ገንዘብ ፡ አወጣች

2. ከረጢት. Put these oranges in (to) a bag. እነዚህን ፡ ብርቱካኖች ፡ እከረጢት ፡ ውስጥ ፡ አ ድርጋቸው

3. ዶንያ ፤ ጆንያ. The bags of wheat were piled on the dock. የስንዴ ፡ ዶንያዎች ፡ በመርከብ ፡ ማ ራገፊያ ፡ ተከምረው ፡ ነበር

4. ስልቻ. Farmers bring grist to the mill in large bags. ገበሬዎች ፡ በትልልቅ ፡ ስልቻዎች ፡ የሚፈጭ ፡ እህል ፡ ወፍጮ ፡ ቤት ፡ ያመጣሉ

**bag and baggage** ጓዝ

He packed up bag and baggage and left. ጓዙን ፡ ጠቅልሎ ፡ ሄደ

**baggage** ጓዝ ፤ ሻንጣዎች

I want to send my baggage on ahead. ጓዜን ፡ በቅድሚያ ፡ ለመላክ ፡ እፈልጋለሁ

He put his baggage in a cart. ሻንጣዎቹን ፡ ጋሪው ፡ ላይ ፡ ጫነ

[See also 'bag']

**(be) baggy** ሰፋ ፡ አለ

His trousers are baggy. ሱሪው ፡ ሰፋ ፡ ብሏል

**bail** ዋስትና ፤ የገንዘብ ፡ ዋስ

The judge released him on 2,000 dollars bail. ዳኛው ፡ በሁለት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ዋስትና ፡ ለቀቀው

Since the trial will not be held until next month, he's out on bail. ጉዳዩ ፡ እስከሚመጣው ፡ ወር ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለማይታይ ፡ በገንዘብ ፡ ዋስ ፡ ተለቋል

**bail out**

1. ውኃውን ፡ አፈሰሰ. The sailors bailed out the boat. መርከበኛው ፡ ከጀልባው ፡ ውስጥ ፡ ውኃውን ፡ አፈሰሰ

2. ዋስ ፡ ሆኖ ፡ አስፈታ. His friends bailed him out. ወዳጆቹ ፡ ዋስ ፡ ሆነው ፡ አስፈቱት

**bait** (n.) መሳቢያ ፡ ምግብ ፤ ማታለያ ፡ ምግብ

Bait is placed on the fishhook. ዓሣ ፡ ለመያዝ ፡ መንጠቆ ፡ ላይ ፡ መሳቢያ ፡ ምግብ ፡ ይደረጋል

He catches fish with bait. በመንጠቆው ፡ ላይ ፡ ማታለያ ፡ ምግብ ፡ አድርጎ ፡ ዓሣ ፡ ያጠምዳል

**bake**

1. ጋገረ. She knows how to bake good bread. ጥሩ ፡ ዳቦ ፡ መጋገር ፡ ታውቃለች

2. ጠበሰ. She baked the clay in fire to make a pot. ማሰሮ ፡ ለመሥራት ፡ ሸክላውን ፡ በእሳት ፡ ጠበሰችው

**baker** ዳቦ ፡ ጋጋሪ

This baker has good bread. ይህ ፡ ዳቦ ፡ ጋጋሪ ፡ ጥሩ ፡ ዳቦ ፡ አለው

**bakery** ዳቦ ፡ መጋገሪያ ፡ ቤት

The bakery is closed on Sunday. ዳቦ ፡ መጋገሪያው ፡ ቤት ፡ እሑድ ፡ ለት ፡ ዝግ ፡ ነው

**balance** (vt.)

1. አስተካከለ ፤ አቃና. The government balanced the budget this year. መንግሥቱ ፡ ዘንድሮ ፡ ባጀቱን ፡ አስተካከለ ፡ (አቃና)

2. ቀጥ ፡ አድርጎ ፡ አቆመ. Can you balance a stick on your head? በጭንቅላትህ ፡ ላይ ፡ ዘንግ ፡ ቀጥ ፡ አድርገህ ፡ ማቆም ፡ ትችላለህ ?

3. አወዳደረ. She balanced a trip to the mountain against the chance of a summer job. ወደ ፡ ተራራው ፡ ለሽርሽር ፡ መውጣትንና ፡ የክረምት ፡ ሥራ ፡ የማግኘትን ፡ ዕድል ፡ አወዳደረች

4. አካካሰ(ለት). His kind act balances his rough manner. የደግነት ፡ ሥራው ፡ ባለጌ ፡ ጠባዩን ፡ ያካክስለታል

**balance** (vi.)

1. ልክ ፡ መጣ. Does the account balance? ሒሳቡ ፡ ልክ ፡ ይመጣል ?

2. ትክክል ፡ ነው. These scales balance. እነዚህ ፡ ሚዛኖች ፡ ትክክል ፡ ናቸው

3. ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ. The dancer balanced on her toes. ዳንሰኛዋ ፡ ቀጥ ፡ ብላ ፡ በጥፍሯ ፡ ቆመች

**balance** (n.)

1. ሚዛን. He weighed the gold on a balance. ወርቁን ፡ በሚዛን ፡ መዘነው

He found it hard to keep his balance in the strong wind. በከባዱ ፡ ነፋስ ፡ ውስጥ ፡ ሚዛኑን ፡ መጠበቅ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆነበት

2. የመንፈስ ፡ እርጋታ. His balance kept him from doing anything foolish. የመንፈሱ ፡ እርጋታ ፡ እንዳችም ፡ የማይረባ ፡ ነገር ፡ እንዳያደርግ ፡ ረዳው

3. ቀሪ. Pay one third down, and the balance in a month. ሲሶውን ፡ አሁን ፡ ክፈል ፡ ቀሪውን ፡ ደግሞ ፡ ባንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ክፈል

4. የተረፈ ፡ ጊዜ. I will be away for the balance of the week. ለተረፈው ፡ የሳምንት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ እሄዳለሁ

**keep one's balance** ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ

A small child has to learn to keep its balance before it can walk. ሕፃን ፡ ልጅ ፡ መራመድ ፡ ከመቻሉ ፡ በፊት ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ መቆም ፡ መልመድ ፡ አለበት

**lose one's balance** ሚዛኑን ፡ ሳተ

He lost his balance and fell. ሚዛኑን ፡ ስቶ ፡ ወደቀ

**recover (one's) balance**

He recovered his balance immediately. ከተንገደገደ ፡ በኋላ ፡ ወዲያውኑ ፡ ቀጥ ፡ አለ

[See also 'hang']

**balanced** (adj.) የተደላደለ

A stable currency is necessary for a balanced

economy. ለተደላደለ ፡ ኢኮኖሚ ፡ የማይለዋወጥ ፡ ገንዘብ ፡ ያስፈልጋል

**balcony**
1. ሰገነት. I have an apartment with a balcony. ሰገነት ፡ ያለው ፡ አፓርትማ ፡ አለኝ
2. ፎቅ. We had seats in the first balcony. በመጀመሪያው ፡ ፎቅ ፡ መቀመጫ ፡ ነበረን

**bald**
1. መላጣ. He has a bald head. ራሱ ፡ መላጣ ፡ ነው
2. ራሰ ፡ በራ. He is bald, and yet he is still young. ራሰ ፡ በራ ፡ ቢሆንም ፡ ገና ፡ ልጅ ፡ ነው
3. ገላጣ. The mountaintop was bald. የተራራው ፡ ጫፍ ፡ ገላጣ ፡ ነበር

**be bald** ተመለጠ
He was bald at thirty. በሠላሳ ፡ ዓመቱ ፡ ተመልጦ ፡ ነበር

**the bald truth is** እቅጩን ፡ ለመናገር
The bald truth is that he is a thief. እቅጩን ፡ ለመናገር ፡ እሱ ፡ ሌባ ፡ ነው

**bale** (v.) አሰረ
They baled the currency in large bundles. ገንዘቡን ፡ በትልልቅ ፡ ጥቅል ፡ አሰሩት

**bale** (n.) ጥቅል
They compressed the cotton into bales. ጥጡን ፡ አምቀው ፡ በጥቅል ፡ አሰሩት

**baleful** ክፉ
The wicked witch gave the child a baleful glance. እርጉሟ ፡ አስማተኛ ፡ ልጁን ፡ በክፉ ፡ ዓይን ፡ ተመለከተችው

**balk** (vt.)
1. አጉል ፡ አደረገ(በት). A heavy rain balked our plans for a hike. ኀይለኛ ፡ ዝናብ ፡ ለሽርሽር ፡ የነበረንን ፡ እቅድ ፡ አጉል ፡ አደረገብን
2. አከሸፈ(በት). The police balked the robber's plans. ፖሊሶቹ ፡ የሌባውን ፡ እቅድ ፡ አከሸፉበት

**balk** (vi.)
1. ለግሞ ፡ ቆመ. The mule balked, and nothing could make her move. በቅሎዋ ፡ ለግማ ፡ ስለ ቆመች ፡ ምንም ፡ ሊያስኬዳት ፡ አልቻለም
2. ሳይስማማ ፡ ቀረ. When tax reform was proposed, the committee balked. ታክስ ፡ እንዲሻሻል ፡ ሐሳብ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ደርጉ ፡ ሳይስማማ ፡ ቀረ

**ball**
1. ኳስ. They played ball all afternoon. ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ኳስ ፡ ሲጫወቱ ፡ ዋሉ
2. የዳንስ ፡ ምሽት. He attended the ball given by the minister. ሚኒስትሩ ፡ ባዘጋጁት ፡ የዳንስ ፡ ምሽት ፡ ላይ ፡ ተገኘ
3. ጥቅል. I want a ball of yarn. አንድ ፡ ጥቅል ፡ ክር ፡ እፈልጋለሁ

**carry the ball** ኀላፊነት ፡ ተሸከመ
You can always count on him to carry the ball in an emergency. ምን ፡ ጊዜም ፡ በአስቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ ኀላፊነት ፡ እንደሚሸከም ፡ ልትተማመንበት ፡ ትችላለህ
[See also 'roll']

**ballad** አወዳሽ ፡ ግጥም
The ballad commemorates the king's victory. አወዳሹ ፡ ግጥም ፡ የንጉሡ ፡ የድል ፡ መታሰቢያ ፡ ነው

**ballast** ምንጣፍ
A ballast of heavy stones keeps the rails in place. የኰረት ፡ ድንጋይ ፡ ምንጣፍ ፡ ሐዲዱ ፡ ከቦታው ፡ እንዳይነቃነቅ ፡ አርቆ ፡ ይይዘዋል

**balloon** ፊኛ
The child likes to play with his balloon. ሕፃኑ ፡ በፊኛ ፡ መጫወት ፡ ይወዳል

**ballot** (n.) የምርጫ ፡ ወረቀት ፤ ድምፅ
Have all the ballots been counted? የምርጫው ፡ ወረቀት ፡ ሁሉ ፡ ተቈጥሯል ?
How many ballots were cast for their candidates? ለተመራጮቻቸው ፡ ስንት ፡ ድምፅ ፡ ተሰጠ ?

**take a ballot** በወረቀት ፡ ድምፅ ፡ ሰጠ
Let's take a ballot to decide this question. ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ ለመወሰን ፡ በወረቀት ፡ ድምፅ ፡ እንስጥ

**balm**
1. መድኃኒት ፡ የሆነ ፡ ቅባት. She put balm on the wound. ቁስሉ ፡ ላይ ፡ መድኃኒት ፡ የሆነ ፡ ቅባት ፡ አደረገችበት
2. ማስታገሻ. Sleep was a balm to his troubles. እንቅልፍ ፡ የችግሩ ፡ ማስታገሻ ፡ ነበር

**balmy** ለስላሳ
The balmy weather is good for his health. ለስላሳ ፡ አየር ፡ ለጤንነቱ ፡ ይስማማዋል

**bamboo** ሸምበቆ
Bamboo grows in Ethiopia. ሸምበቆ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይበቅላል
[See also 'shoot']

**ban** (v.) ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ እንዳይገባ ፡ ከለከለ ፤ አገደ

The government banned the book. መንግሥት ፡ መጽሐፉ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ እንዳይገባ ፡ ከለከለ ፡ (or መንግሥት ፡ መጽሐፉን ፡ አገደው)

**ban** (n.) እገዳ
The ban on importation of automobiles was lifted. መኪናዎች ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ እንዳይገቡ ፡ የተደረገው ፡ እገዳ ፡ ተሻረ
The court decision lifts the ban on the book. የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ የመጽሐፉን ፡ እገዳ ፡ ያነሣለታል

**banal** ተራ
She made a banal remark. ተራ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠች

**banana** ሙዝ

**band** (v.), ~ **together** ተባበረ
The people banded together to fight the enemy. ሕዝቡ ፡ ጠላትን ፡ ለመውጋት ፡ ተባበረ

**band** (n.)
1. ጥምጣም. I need a new band for this hat. ለዚህ ፡ ባርኔጣ ፡ አዲስ ፡ ጥምጣም ፡ እፈልጋለሁ
2. ከፈፍ. The white plate has a blue band around the edge. ነጩ ፡ ሳሕን ፡ ዙርያውን ፡ ሰማያዊ ፡ ከፈፍ ፡ አለው
3. ማሰሪያ. I bought a black band for my watch. ለሰዓቴ ፡ ጥቁር ፡ ማሰሪያ ፡ ገዛሁ
4. እስር. A tight armband will interfere with circulation of the blood. የጠበቀ ፡ የክንድ ፡ ላይ ፡ እስር ፡ የደምን ፡ መዘዋወር ፡ ያውካል
5. የሙዚቃ ፡ ጓድ. The band played all evening. የሙዚቃው ፡ ጓድ ፡ ምሽቱን ፡ በሙሉ ፡ ተጫወተ
6. ጓድ. A band of robbers attacked the travelers. የሽፍቶች ፡ ጓድ ፡ መንገደኞቹን ፡ አጠቃቸው

**iron band** የብረት ፡ ሐዲድ
The iron bands around the barrel broke. በበርሚሉ ፡ ዙሪያ ፡ ያለው ፡ የብረት ፡ ሐዲድ ፡ ተሰበረ
[See also 'decorative']

**bandage** (v.) አሰረ ፤ በፋሻ ፡ አሰረ (ታሰረ)
I am going to the hospital to have the nurse bandage my cut finger. የተቈረጠውን ፡ ጣቴን ፡ አስታማሚዋ ፡ እንድታስርልኝ ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ እሄዳለሁ
The injury was local; so his leg was bandaged, and he went home. ጉዳቱ ፡ የደረሰው ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ እግሩ ፡ በፋሻ ፡ ታስሮ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ

**bandage** (n.) ፋሻ
The bandage is narrow. ፋሻው ፡ ቀጭን ፡ ነው

**bandit** ሽፍታ
Jesse James was a famous bandit. ጀሲ ፡ ጀምስ ፡ ዝነኛ ፡ ሽፍታ ፡ ነበር

**banditry** ውንብድና
Where there is no law, banditry is common. ሕግ ፡ ከሌለ ፡ ውንብድና ፡ ይበዛል

**bane, be a** ~ ጥፋት ፡ አመጣ
Wild animals were the bane of the mountain village. ተራራው ፡ ላይ ፡ ላለችው ፡ መንደር ፡ ጥፋት ፡ የሚያመጡ ፡ አውሬዎች ፡ ነበሩ

**bang** (vt.)
1. አናጋ. Don't bang the door! መዝጊያውን ፡ አታናጋው
2. ወቃ. He banged the book down on the table. መጽሐፉን ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ወቃው
3. መታ. He banged his fist on the table. ጠረጴዛውን ፡ በጡጫ ፡ መታው
4. አጋጨ. I banged my elbow. ክርኔን ፡ አጋጨሁት

**bang** (vi.) ጓው ፡ ብሎ ፡ ተዘጋ
A stop for the door keeps it from banging. መዝጊያ ፡ መግቻ ፡ ከተበጀለት ፡ ጓው ፡ ብሎ ፡ ከመዘጋት ፡ ያድነዋል

**bang at** ደበደበ
He banged at the door to be let in. ለመግባት ፡ በሩን ፡ ደበደበ

**bang** (n.) ድምፅ
The bang of a gun could be heard from a distance. የጠመንጃው ፡ ድምፅ ፡ ከሩቅ ፡ ይሰማ ፡ ነበር

**with a bang**
1. ድው ፡ ብሎ. The box fell down with a bang. ሣጥኑ ፡ ድው ፡ ብሎ ፡ ወደቀ
2. እናግቶ. He always shuts the door with a bang. ሁልጊዜ ፡ በሩን ፡ እናግቶ ፡ ይዘጋዋል

**banish**
1. አጋዘ (ተጋዘ). He was banished to the remotest province. በጣም ፡ ሩቅ ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ተጋዘ
2. አስወገደ (ለት). The doctor's talk banished his fear of illness. የሐኪሙ ፡ ንግግር ፡ ስለ ፡ በሽታ ፡ የነበረውን ፡ ፍርሀት ፡ አስወገደለት

**bank** (v.) ቈለለ
The wind banked the snow against the doorstep. ነፋሱ ፡ በረዶውን ፡ ደረጃው ፡ ላይ ፡ ቈለለው

**bank** (n.)
1. ባንክ. I keep my money in the bank. ገንዘቤን ፡ እባንክ ፡ አስቀምጣለሁ
2. የወንዝ ፡ ዳርቻ. He swam to the nearest bank. ቀረብ ፡ ወዳለው ፡ የወንዝ ፡ ዳርቻ ፡ ዋኘ
3. ቁልል. There is a bank of earth alongside the street. በመንገዱ ፡ ዳርቻ ፡ የአፈር ፡ ቁልል ፡ አለ
*The ship ran aground on the sand bank. በባሕር ፡ ውስጥ ፡ በሚገኝ ፡ አሸዋማ ፡ ጉብታ ፡ መርከቧ ፡ መሬት ፡ ያዘች
*The water rose until it was level with the bank. ወንዙ ፡ እስከ ፡ አፍ ፡ ደገፉ ፡ ሞልቷል

**make a bank of earth** አፈር ፡ ቈለለ
The engineers made a bank of earth across the road to keep out the cars. መኪናዎቹን ፡ ለማገድ ፡ መሀንዲሶቹ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ አፈር ፡ ቈለሉ
[See also 'farther, flow, overflow']

**bankbook** የባንክ ፡ የሒሳብ ፡ ደብተር
He lost his bankbook and cannot withdraw money. የባንክ ፡ የሒሳብ ፡ ደብተሩን ፡ ስለጣለ ፡ ገንዘብ ፡ ሊያወጣ ፡ አይችልም

**banker** ባለ ፡ ባንክ
Foreign bankers are permitted to have banks in Ethiopia. የውጭ ፡ አገር ፡ ባለ ፡ ባንኮች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ባንክ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ይፈቀድላቸዋል

**bank note** ገንዘብ ፤ ብር
The government brought out new bank notes recently. መንግሥት ፡ በቅርብ ፡ አዲስ ፡ ገንዘብ ፡ (ብር) ፡ አትሞ ፡ አወጣ

**bankrupt** (v.) አከሰረ
They are underselling us in order to bankrupt us. እኛን ፡ ለማክሰር ፡ በዝቅተኛ ፡ ዋጋ ፡ ይሸጣሉ

**bankrupt** (adj.) የከሰረ
A bankrupt firm is not solvent. የከሰረ ፡ ድርጅት ፡ ዕዳውን ፡ ሊከፍል ፡ አይችልም

**be (become) bankrupt** ከሰረ
He became bankrupt through too many business expenses. የንግድ ፡ ሥራው ፡ ወጪ ፡ ስለበዛበት ፡ ከሰረ

**bankruptcy**
1. መክሰር. Their bankruptcy reduced them to begging. መክሰራቸው ፡ ከልመና ፡ አደረሳቸው
2. የንግድ ፡ ኪሳራ. There were ten bankruptcies last year. ዓምና ፡ ዐሥር ፡ የንግድ ፡ ኪሳራ ፡ ደርሶ ፡ ነበር

**go into bankruptcy** ከሰረ
The firm went into bankruptcy. የንግዱ ፡ ድርጅት ፡ ከሰረ

**banner**
1. የጽሑፍ ፡ ሰሌዳ. The students carried a banner with "We want better schools" written on it. ተማሪዎቹ ፡ « የተሻለ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንፈልጋለን » ፡ የሚል ፡ የጽሑፍ ፡ ሰሌዳ ፡ ይዘው ፡ ተሰለፉ
2. ሰንደቅ ፡ ዓላማ. The banners were waving in the breeze. ሰንደቅ ፡ ዓላማዎቹ ፡ በነፋስ ፡ ይውለበለቡ ፡ ነበር

**banquet** የእራት ፡ ግብዣ
The Emperor gave a banquet in honor of his guests. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ለእንግዶቹ ፡ ክብር ፡ የእራት ፡ ግብዣ ፡ አደረጉ
[See also 'wedding']

**banter** ፌዝ
The boy's banter made the girls laugh. የልጁ ፡ ፌዝ ፡ ልጃገረዶቹን ፡ አሣቃቸው

**baptism** ክርስትና
The baptism was performed in the new church. ክርስትናው ፡ የተፈጸመው ፡ ባዲሱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ነበር

**baptize**
1. አጠመቀ. The priest baptized the child. ቄሱ ፡ ሕፃኑን ፡ አጠመቀው
2. የክርስትና ፡ ስም ፡ ሰየመ. They baptized their son, John. የልጃቸውን ፡ የክርስትና ፡ ስም ፡ ጆን ፡ ብለው ፡ ሰየሙት

**be baptized** ክርስትና ፡ ተነሣ
She was baptized when she was a month old. በወሯ ፡ ክርስትና ፡ ተነሣች

**bar** (barred), v.
1. ቀረቀረ. He forgot to bar the gate. በሩን ፡ መቀርቀር ፡ ረሳ
2. ዘጋ. A fallen tree barred our way. አንድ ፡ የወደቀ ፡ ዛፍ ፡ መንገዳችንን ፡ ዘጋው
3. ከለከለ. The director barred smoking in the classroom. ዲሬክተሩ ፡ እክፍል ፡ ውስጥ ፡ ማጨስን ፡ ከለከለ

**bar** (n.)
1. የብረት ፡ ዘንግ. The bars in the window show that it is a jail. በመስኮት ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ የብረት ፡ ዘንጎች ፡ የእስር ፡ ቤት ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታሉ
2. ቡና ፡ ቤት. Let's meet in the bar in an hour! ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ እቡና ፡ ቤት ፡ እንገናኝ

3. ፍርድ ፡ ቤት. She was called before the bar to answer for her crimes. ለተከሰሰችበት ፡ ወንጀል ፡ መልስ ፡ እንድትሰጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተጠራች
4. መሰናከል. Poor health may be a bar to success in life. የጤና ፡ ማጣት ፡ ለኑሮ ፡ መሳካት ፡ መሰናከል ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

**be a bar**
1. አገደ. Foreign birth is a bar to becoming President. ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ መወለድ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከመሆን ፡ ያግዳል
2. ከለከለ. Disparity in ages is no bar to marriage. በዕድሜ ፡ አለመመጣጠን ፡ ጋብቻ ፡ አይከለክልም

**be admitted to the bar** በጥብቅና ፡ እንዲሠራ ፡ ተፈቀደለት
After passing his law examination, the young man was admitted to the bar. የሕግ ፡ ፈተናውን ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ወጣቱ ፡ ሰው ፡ በጥብቅና ፡ እንዲሠራ ፡ ተፈቀደለት
[See also 'soap']

**barbarian** (adj.) ያረመኔዎች
To emasculate is a barbarian custom. መስለብ ፡ ያረመኔዎች ፡ ልማድ ፡ ነው

**barbarous** የጭቆና
The barbarous treatment of prisoners was described in the newspaper. የእስረኞች ፡ የጭቆና ፡ አያያዝ ፡ በጋዜጣው ፡ ላይ ፡ ተገለጸ

**barbed wire** ባለሾህ ፡ ሽቦ
The soldiers placed a barrier of barbed wire across the road. ወታደሮቹ ፡ የባለሾህ ፡ ሽቦ ፡ ማገጃ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ሠሩ

**barber** ጸጉር ፡ አስተካካይ
The barber cut my hair badly. ጸጉር ፡ አስተካካዩ ፡ ጸጉሬን ፡ መጥፎ ፡ አድርጎ ፡ ቈረጠኝ

**barber shop** የጸጉር ፡ ማስተካከያ ፡ ቤት
The barber shops are closed on Sunday. የጸጉር ፡ ማስተካከያ ፡ ቤቶች ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ ይዘጋሉ

**bare** (v.), ~ **the head** ባርኔጣ ፡ አነሣ
When the flag passed, the men bared their heads. ሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ ሲያልፍ ፡ ሰዎቹ ፡ ባርኔጣቸውን ፡ አነሡ

**bare** (adj.)
1. ባዶ. You should not run around in your bare feet! በባዶ ፡ እግርህ ፡ መዘዋወር ፡ አይገባህም
He lived in a bare, little house. ትንሽ ፡ ባዶ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ኖረ
He fought the enemy with bare hands. ከጠላት ፡ ጋር ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ ተዋጋ
2. (ዕ)ራቁት. In hot countries, men and women go around bare to the waist. በሞቃት ፡ አገሮች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ከወገባቸው ፡ በላይ ፡ ዕራቁታቸውን ፡ ይሄዳሉ
3. አነስተኛ. He was elected by a bare majority. የተመረጠው ፡ በአነስተኛ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ነው
4. ገላጣ. The top of the hill was bare. የጋራው ፡ ጫፍ ፡ ገላጣ ፡ ነበር
5. የተራቈተ. The Ethiopian landscape in the north is very bare. የሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመሬት ፡ አቀማመጥ ፡ የተራቈተ ፡ ነው
*The room was bare of furniture. ክፍሉ ፡ የቤት ፡ እቃ ፡ አልነበረውም
*The trees are still bare. ዛፎቹ ፡ ገና ፡ ቅጠል ፡ የላቸውም
*These are the bare facts. እቅጩ ፡ ያለው ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው
*His pay affords him only the bare necessities of life. ደሞዙ ፡ ከእጅ ፡ ወደ ፡ አፍ ፡ አያልፍም

**bare of goods** ባዶ
The store is now completely bare of goods. መደብሩ ፡ አሁን ፡ ባዶ ፡ ነው

**be bare of** የለበትም
The chicken yard is bare of grass. የዶሮዎቹ ፡ ቦታ ፡ ሣር ፡ የለበትም

**lay bare** ገለጠ ፤ ገፈፈ
The doctor laid the burned flesh bare with his scalpel. ዶክተሩ ፡ የተቃጠለውን ፡ ሥጋ ፡ በሰላ ፡ ቢላዋ ፡ ገለጠው ፡ (ገፈፈው)

**look bare** ተራቈተ
The walls look so bare. ግድግዳዎቹ ፡ የተራቈቱ ፡ ናቸው

**bareback** ሌጣ(ውን)
He rode the horse bareback. ፈረሱን ፡ ሌጣውን ፡ ጋለበው

**barefisted** በባዶ ፡ እጅ
The two boys fought barefisted. ሁለቱ ፡ ልጆች ፡ በባዶ ፡ እጃቸው ፡ ተደባደቡ

**barefoot** ባዶ ፡ እግሩን
Children, don't run around barefoot! ልጆች ፤ ባዶ ፡ እግራችሁን ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ አትዘዋወሩ !

**barehanded** ባዶ ፡ እጁን
Don't pick up that hot pan barehanded! ያን ፡ የጋለ ፡ መጥበሻ ፡ ባዶ ፡ እጅህን ፡ አታንሣው

**barely**
1. ላመል. The ship is barely visible. መርከቡ ፡ ላመል ፡ ይታያል

2. እንደምንም ፡ ብሎ. He barely managed it. እንደምንም ፡ ብሎ ፡ ሆነለት
3. ግልጥ ፡ አድርጎ. They gave the facts to him barely. ትክክለኛውን ፡ ነገር ፡ ግልጥ ፡ አድርገው ፡ ነገሩት
4. ለትንሽ. He barely escaped being beaten by the mob. ከሕዝቡ ፡ ድብደባ ፡ ለትንሽ ፡ አመለጠ
*This room is barely furnished. ክፍሉ ፡ ያለው ፡ እቃ ፡ እምብዛም ፡ ነው
*He is barely ten. ዕድሜ ፡ ዓመት ፡ ሊሞላው ፡ ነው
[See also 'crawl']

**bargain** (v.) ተከራከረ
I bargained with him about the sale of his house. ስለ ፡ ቤቱ ፡ ሽያጭ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ተከራከረን ፡ ነበር

**bargain for**
*We had more trouble with the old car than we bargained for. በአሮጌዋ ፡ መኪና ፡ ምክንያት ፡ ካሰብነው ፡ በላይ ፡ ችግር ፡ ገጠመን

**bargain** (n.)
1. ጥሩ ፡ ግዢ. This book is a bargain. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ጥሩ ፡ ግዢ ፡ ነው
2. ግዢ. The guarantee was part and parcel of the bargain. ዋስትናው ፡ የግዢው ፡ መሠረታዊ ፡ ክፍል ፡ ነበር
3. ስምምነት. According to our bargain, you were to pay half this month. እንደ ፡ ስምምነታችን ፡ ግማሹን ፡ በዚህ ፡ ወር ፡ ትከፍለኝ ፡ ነበር

**drive a (good) bargain**
He drove a good bargain at the store. ተከራክሮ ፡ ከሱቁ ፡ ገዛ

**in the bargain** -ም
The new houskeeper proves to be a fine cook in the bargain. አዲሷ ፡ ቀላቢት ፡ ጥሩ ፡ ወጥ ፡ ቤትም ፡ ናት

**make a bargain** ተስማማ
Let's make a bargain to help each other with our chores! ሥራችን ፡ ለመረዳዳት ፡ እንስማማ

**strike a bargain** ተስማማ
He struck a bargain that each one was to pay half. እያንዳንዱ ፡ ግማሽ ፡ እንዲከፍል ፡ ተስማማ
[See also 'seal']

**barge** የጭነት ፡ መርከብ
The barge which was transporting stones sank in the river. ድንጋይ ፡ ተሸክሞ ፡ የነበረው ፡ የጭነት ፡ መርከብ ፡ ወንዙ ፡ ውስጥ ፡ ሰጠመ

**bark** (vt.)
1. ላጠ. The farmers barked the trees in order to dry them. ገበሬዎቹ ፡ ዛፎቹ ፡ እንዲደርቁ ፡ ላጡዋቸው
2. (= passive) ተላላጠ. +I fell down the steps and barked my shins. ከደረጃው ፡ ላይ ፡ በወደቅሁ ፡ ጊዜ ፡ ቅልጥሜ ፡ ተላላጠ

**bark** (vi.) ጮኸ
The dog barked loudly. ውሻው ፡ በኀይል ፡ ጮኸ

**bark commands** በጩኸት ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ
The officer barked commands at the soldiers. መኰንኑ ፡ ለወታደሮቹ ፡ በጩኸት ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ

**bark** (n.)
1. ቅርፊት ፤ ልጣጭ. Those sycamore trees have a thin bark. እነዚያ ፡ ወርካዎች ፡ ስስ ፡ ቅርፊት ፡ አላቸው
The bark of some trees is used for making paper. ያንዳንድ ፡ ዛፎች ፡ ልጣጭ ፡ (ቅርፊት) ፡ ወረቀት ፡ ለመሥራት ፡ ያገለግላል
2. ጩኸት. A bark of a dog could be heard from afar. የውሻ ፡ ጩኸት ፡ ከሩቅ ፡ ሊሰማ ፡ ይችላል

**take off the bark** ላጠ
Take off the bark before you bring in that log. ያንን ፡ ግንድ ፡ ከማግባትህ ፡ በፊት ፡ ላጠው

**barkeeper** የቡና ፡ ቤት ፡ ባለቤት
The barkeeper is a rich man. የቡና ፡ ቤቱ ፡ ባለቤት ፡ ሀብታም ፡ ሰው ፡ ነው

**barley** ገብስ
I like beer made with barley. የገብስ ፡ ጠላ ፡ እወዳለሁ

**barn** [የእህልና ፡ የከብት ፡ ማስቀመጫ ፡ ቤት]

**barracks** ሰፈር
The soldiers' barracks are built of concrete. የወታደሮቹ ፡ ሰፈር ፡ ከድንጋይና ፡ ከሲሚንቶ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**barrage**
1. ግድብ. They are going to construct a barrage across the river. በወንዙ ፡ ላይ ፡ ግድብ ፡ ሊገነቡ ፡ ነው
2. ከባድ ፡ ተኩስ. The enemy barrage began at dawn. ጠላት ፡ ንጋት ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ተኩስ ፡ ከፈተ

**barrel**
1. በርሚል ፤ በርሜል. We drank a whole barrel of beer. አንድ ፡ ሙሉ ፡ በርሜል ፡ ቢራ ፡ ጠጣን
2. አፍ. The barrels of the cannon shone in the sunlight. የመድፉ ፡ አፍ ፡ በፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ አንጸባረቀ
[See also 'lock']

**barren**

1. መካን. He sold his barren mare. መካን ፡ ባዝራውን ፡ ሸጠ
His wife is barren. ሚስቱ ፡ መካን ፡ ነች
2. ባዶና ፡ ጠፍ. Above the three thousand meter line, everything was barren. ከሦስት ፡ ሺ ፡ ሜትር ፡ ከፍታ ፡ በላይ ፡ የነበረው ፡ ባዶና ፡ ጠፍ ፡ ነበር
3. ባዶ. The Red Sea coastline is barren. የቀይ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ባዶ ፡ ነው
4. ጭንጫ. Barren soil will not grow any wheat. ጭንጫ ፡ መሬት ፡ ምንም ፡ ስንዴ ፡ አያበቅልም

**barricade** (v.) ዘጋ
She barricaded the door with a chair. መዝጊያውን ፡ በወንበር ፡ ዘጋችው

**barricade** (n.)

1. መከታ. They quickly made a barricade to keep back the enemy. ጠላትን ፡ ለመከላከል ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ መከታ ፡ አበጁ
2. መንገድ ፡ መዝጊያ. The barricade was placed there temporarily, not permanently. መንገድ ፡ መዝጊያው ፡ የተቀመጠው ፡ ለጊዜው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለዘለቄታ ፡ አይደለም
3. መሰናክል. The students erected a barricade to keep out the police. ፖሊሶቹን ፡ ለመከላከል ፡ ተማሪዎቹ ፡ መሰናክል ፡ ሠሩ

**barrier**

1. ማገጃ. The soldiers placed a barrier of barbed wire across the road. ወታደሮቹ ፡ የባለሾህ ፡ ሽቦ ፡ ማገጃ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ሠሩ
2. ገደብ. The enemy was strongly entrenched on the other side of the barrier. ጠላት ፡ በገደቡ ፡ አሻገር ፡ በደምብ ፡ መሽጎ ፡ ነበር
3. መሰናክል. The Sahara Desert has been a barrier to trade. የሰሐራ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ለንግድ ፡ መሰናክል ፡ ሆኖ ፡ ነበር

**barring** (prep.) ካልደረሰ ፡ በስተቀር
Barring accidents, the train will reach Chicago at 12:00 o'clock. አደጋ ፡ ካልደረሰ ፡ በስተቀር ፡ ባቡሩ ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ ቺካጎ ፡ ይደርሳል

**barter** (v.) ለወጠ
Indians used to barter furs for guns. ህንዶች ፡ የአውሬ ፡ ጸጉር ፡ በጠመንጃ ፡ ይለውጡ ፡ ነበር

**barter** (n.) የእቃ ፡ መለዋወጥ ፡ ንግድ
Barter was practiced before money was introduced. ገንዘብ ፡ ከመሠራቱ ፡ በፊት ፡ የእቃ ፡ መለዋወጥ ፡ ንግድ ፡ ይሠራበት ፡ ነበር

**base** (v.) መሠረተ
On what did you base your figures? የቁጥር ፡ ዝርዝርህን ፡ ምን ፡ ላይ ፡ መሠረትከው ?

**be based** ተመደበ
The division is based at Fort Benning. ክፍለ ፡ ጦሩ ፡ ፎርት ፡ ቤኒንግ ፡ ተመድቧል
The tax is based upon income. ግብሩ ፡ የተመደበው ፡ እንደ ፡ ገቢው ፡ ብዛት ፡ ነው

**base** (n.)

1. መሠረት. The base of the statue was still standing. የሐውልቱ ፡ መሠረት ፡ አሁንም ፡ ቆሞ ፡ ነበር
2. ሰፈር. The government appropriated land for a military base. መንግሥቱ ፡ ለጦር ፡ ሰፈር ፡ የሚሆን ፡ ቦታ ፡ ከለለ
3. መደበኛ ፡ ቅመም. Pepper is the base of this stew. በርበሬ ፡ የዚህ ፡ ወጥ ፡ መደበኛ ፡ ቅመም ፡ ነው

**base** (adj.)

1. ጸያፍ. To betray a friend is a base action. ጓደኛን ፡ መክዳት ፡ ጸያፍ ፡ ተግባር ፡ ነው
2. ተራ. Iron and lead are base metals. ብረትና ፡ እርሳስ ፡ ተራ ፡ ብረቶች ፡ ናቸው
3. (= n.) ወራዳ ፡ ነገር. No needful service is to be looked at as base. ማንኛቸውም ፡ ዓይነት ፡ አስፈላጊ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ወራዳ ፡ ነገር ፡ መታየት ፡ የለበትም

**baseless** መሠረተ ፡ ቢስ
This is a baseless accusation. ይህ ፡ መሠረተ ፡ ቢስ ፡ ክስ ፡ ነው

**basement** ምድር ፡ ቤት
The basement was flooded by the rain. ምድር ፡ ቤቱ ፡ በዝናም ፡ ተጥለቀለቀ

**bashful** ዓይናፋር
She is bashful in company. ከሰው ፡ ጋር ፡ ስትሆን ፡ ዓይናፋር ፡ ነች

**basic**

1. መሠረታዊ. One of the basic difficulties of Ethiopian agriculture is land tenure. ከኢትዮጵያ ፡ የርሻ ፡ መሠረታዊ ፡ ችግሮች ፡ አንዱ ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ነው
2. ዋና. He quoted his basic reasons for the decision. ለውሳኔው ፡ ዋና ፡ ምክንያቶቹን ፡ ጠቀሰ

**basically** በመሠረቱ
He is basically honest. በመሠረቱ ፡ ታማኝ ፡ ነው

**basin**
1. ጐድጓዳ ፡ ሳሕን. He washed his hands in a metal basin. እጆቹን ፡ ከብረት ፡ በተሠራ ፡ ጐ ድጓዳ ፡ ሳሕን ፡ ውስጥ ፡ ታጠበ
2. ሸለቆ. The Awash river basin is being developed for agriculture. የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ለእ ርሻ ፡ ሥራ ፡ በመልማት ፡ ላይ ፡ ነው

**basis**
1. መሠረት. We cannot continue on this basis. በዚህ ፡ መሠረት ፡ ልንቀጥል ፡ አንችልም
2. ማስረጃ. What basis do you have for that statement? ለዚህ ፡ አባባልህ ፡ ምን ፡ ማስረጃ ፡ አለህ?
3. መደበኛ ፡ ቅመም. The basis of this medicine is oil. የመድኃኒቱ ፡ መደበኛ ፡ ቅመም ፡ ዘይት ፡ ነው

**bask** ሞቀ
He likes to bask in the sun. ፀሐይ ፡ መሞቅ ፡ ይ ወዳል

**basket** ቅርጫት
Put the laundry in the basket! የሚታጠበውን ፡ ልብስ ፡ እቅርጫቱ ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጥ

**basketball** የቅርጫት ፡ ኳስ
He likes to play basketball. የቅርጫት ፡ ኳስ ፡ መጫወት ፡ ይወዳል

**bass** [ወፍራምና ፡ ጎርናና ፡ የወንድ ፡ ድምፅ]

**bassinet** የሕፃን ፡ ቅርጫት
The baby sleeps in a bassinet. ሕፃኑ ፡ በሕፃን ፡ ቅርጫት ፡ ውስጥ ፡ ይተኛል

**bastard** ዲቃላ
He is said to be the prince's bastard. እሱ ፡ የል ዑሉ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ፡ ይባላል

**baste** ወሰወሰ
The tailor basted the hem before he sewed it permanently. ልብስ ፡ ሰፊው ፡ ጠርዙን ፡ ከመስ ፋቱ ፡ በፊት ፡ ወሰወሰው

**bat** (batted), v. ለጋ
He batted the ball over the fence. ኳሷን ፡ ባጥ ሩ ፡ ላይ ፡ አሻግሮ ፡ ለጋት
**not bat an eye** ዓይኑን ፡ እንኳን ፡ አልሰበረም
The prisoner did not bat an eye when accused of murder. እስረኛው ፡ በነፍስ ፡ ገዳይነት ፡ ሲወ ነጀል ፡ ዓይኑን ፡ እንኳን ፡ አልሰበረም

**bat** (n.)
1. የሌሊት ፡ ወፍ. The bats flew about to catch insects. የሌሊት ፡ ወፎች ፡ ነፍሳት ፡ ለመያዝ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ በረሩ
2. መምቻ. He hit the ball so hard that the bat broke. ኳሷን ፡ በኀይል ፡ ስለመታ ፡ መምቻው ፡ ተሰበረ

**batch**
1. ክምችት. What happened to the batch of papers on my desk? ከጠረጴዛዬ ፡ ላይ ፡ የነበ ረው ፡ የወረቀት ፡ ክምችት ፡ የት ፡ ደረሰ?
2. ቡድን. A new batch of Peace Corps volunteers arrived today. አዲስ ፡ የሰላም ፡ ጓድ ፡ ቡድን ፡ ዛሬ ፡ ገባ
*She made another batch of cookies. ሌላ ፡ ብስ ኩት ፡ ሠራች

**bath** የገላ ፡ መታጠቢያ ፤ የገላ ፡ መታጠቢያ ፡ ውኃ
Have you a room with bath? የገላ ፡ መታጠ ቢያ ፡ ያለው ፡ ክፍል ፡ አለህ?
Your hot bath is ready now. የገላህ ፡ መታጠቢ ያ ፡ ሙቅ ፡ ውኃ ፡ ተዘጋጅቷል
**take a bath** ገላ ፡ ታጠበ
Take a bath after work! ሥራህን ፡ ከጨረስክ ፡ በኋላ ፡ ገላህን ፡ ታጠብ!

**bathe** (vt.) አጠበ
Bathe the baby in lukewarm water! ሕፃኑን ፡ ለ ብ ፡ ባለ ፡ ውኃ ፡ እጠብ
He bathed his wound in alcohol. ቁስሉን ፡ በ አልኮል ፡ አጠበው
**bathe** (vi.) ገላ ፡ ታጠበ
I couldn't bathe this morning because the water was cold. ዛሬ ፡ ጧት ፡ ውኃው ፡ ቀዝቃዛ ፡ ስለነበረ ፡ ገላዬን ፡ ልታጠብ ፡ አልቻልኩም
**be bathed** ተጥለቀለቀ
The valley was bathed in sunlight. ሸለቆው ፡ በፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ተጥለቅልቋል
**go bathing** ዋኘ
We went bathing every day. በየቀኑ ፡ እንዋኝ ፡ ነበር

**bathing suit** የዋና ፡ ልብስ
Put on your bathing suit and go for a swim! የዋና ፡ ልብስህን ፡ ልበስና ፡ ወደ ፡ ዋና ፡ ሂድ

**bathrobe** የመታጠቢያ ፡ ልብስ
I need a new bathrobe. አዲስ ፡ የመታጠቢያ ፡ ልብስ ፡ ያስፈልገኛል

**bathroom** የመታጠቢያ ፡ ቤት
The bathroom is large and new. የመታጠቢያ ፡ ቤቱ ፡ ሰፊና ፡ አዲስ ፡ ነው

**bathub** የገላ ፡ መታጠቢያ ፡ ገንዳ ፤ የመታጠቢ ያ ፡ ገንዳ ፤ ባኞ
Do they have a bathtub or a shower? ያላቸ

ው ፡ የገላ ፡ መታጠቢያ ፡ ገንዳ ፡ (ባኞ) ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ የቁም ፡ መታጠቢያ ?
Watch out that the bathtub does not run over! የመታጠቢያው ፡ ገንዳ ፡ ሞልቶ ፡ እንዳይፈስ ፡ ተጠንቀቅ

**battalion** ሻለቃ
The battalion saw action in Korea. ሻለቃው ፡ በኮርያ ፡ ተዋግቷል

**batter** (v.) ገረፈ
The waves battered the rocks on the shore. ማዕበሉ ፡ ባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ የነበሩትን ፡ ቋጥኞች ፡ ገረፈ

**batter at** በኀይል ፡ ደበደበ
The firemen battered at the front door. የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካዮቹ ፡ የፊት ፡ ለፊቱን ፡ በር ፡ በኀይል ፡ ደበደቡት

**batter down** ሰባበረ
The firemen battered down the door. የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካዮቹ ፡ መዝጊያውን ፡ ሰባበሩት

**batter** (n.) ሊጥ
The cake is made from batter. ብስኩቱ ፡ የተጋገረው ፡ ከሊጥ ፡ ነው

**battery**
1. ባትሪ. My car has to have a new battery. መኪናዬ ፡ አዲስ ፡ ባትሪ ፡ ያስፈልጋታል
2. የመድፈኛ ፡ ባትሪ. Four batteries began firing on the enemy. አራት ፡ የመድፈኛ ፡ ባትሪዎች ፡ ጠላት ፡ ላይ ፡ ተኩስ ፡ ከፈቱ

**a battery of** ብዙ
A battery of microphones surrounded the mayor. በከንቲባው ፡ ዙሪያ ፡ ብዙ ፡ የድምፅ ፡ ማጉያ ፡ ነበር

**battle** (v.)
1. ታገለ. The little ship battled against the storm. ትንሿ ፡ መርከብ ፡ ከማዕበል ፡ ጋር ፡ ታገለች
2. ተጋደለ. They battled for freedom for many years. ለነጻነት ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ተጋደሉ

**battle** (n.)
1. ጦርነት. The Egyptians were defeated in the battle of Gura in 1875. በ፲፰፻፸፭ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በጉራ ፡ ጦርነት ፡ ግብጾች ፡ ድል ፡ ሆኑ
2. ውጊያ. He heard the sounds of battle from a distance. የውጊያ ፡ ድምፅ ፡ ከሩቅ ፡ ሰማ
3. ተጋድሎ. The battle for freedom lasted several years. የነጻነት ፡ ተጋድሎ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ዓመታት ፡ ወሰደ

**battle cry** ቀረርቶ
The battle cry of the patriots frightened the enemy. ያርበኞቹ ፡ ቀረርቶ ፡ ጠላትን ፡ አስበረገገው
[See also 'lose']

**battlefield** የጦር ፡ ሜዳ ፤ የጦርነት ፡ ሜዳ
The battlefield was littered with corpses. የጦር ፡ ሜዳው ፡ (የጦርነት ፡ ሜዳው) ፡ በሬሳ ፡ ተርከፍክፎ ፡ ነበር

**battleship** የጦር ፡ መርከብ
The navy has six battleships in commission. የባሕር ፡ ኀይል ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ስድስት ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ አሉት

**bawl** ስቅቅ ፡ ብሎ ፡ አለቀሰ
The child bawled because it could not find its mother. ልጁ ፡ እናቱን ፡ ስላጣ ፡ ስቅቅ ፡ ብሎ ፡ አለቀሰ

**bawl one's wares** እየጮኸ ፡ ገዢ ፡ እንዳለ ፡ ጠየቀ
The peddler bawled his wares in the street. ሱቅ ፡ በደረቴው ፡ በየመንገዱ ፡ እየጮኸ ፡ ገዢ ፡ እንዳለ ፡ ጠየቀ

**bawl out** ወረደ(በት)
Your father will bawl you out when he sees this mess. ይህንን ፡ ዝርክርክ ፡ ነገር ፡ ሲያይ ፡ አባትህ ፡ ይወርድብሃል

**bay** (n.) የባሕር ፡ ሰላጤ
Massawa is located on the shore of a wide bay. ምፅዋ ፡ ሰፊ ፡ በሆነ ፡ የባሕር ፡ ሰላጤ ፡ ዳርቻ ፡ ትገኛለች

**bay** (adj.) ዳማ
The farmer bought a bay horse. ገበሬው ፡ ዳማ ፡ ፈረስ ፡ ገዛ

**bayonet** ሳንጃ
The soldiers fixed their bayonets on their rifles. ወታደሮቹ ፡ ሳንጃቸውን ፡ ጠመንጃቸው ፡ ላይ ፡ ሰኩ

**bay window** [ወደ ፡ ውጭ ፡ ያጋደለ ፡ መስኮት]

**bazaar** መደብር
You could buy anything at the bazaar. ከመደብሩ ፡ የፈለግኸውን ፡ መግዛት ፡ ትችል ፡ ነበር

**be**, see **is**, **was**

**beach** የባሕር ፡ ዳርቻ
They built a fire on the beach. በባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ እሳት ፡ አነደዱ

**beacon** የወደብ ፡ መብራት
The beacon showed the ship where the port was. የወደቡ ፡ መብራት ፡ ወደቡ ፡ ያለበትን ፡ ለመርከቡ ፡ አመለከተ

**bead**
1. ዶቃ. Beads are used for making necklaces. ዶቃ ፡ ያንገት ፡ ጌጥ ፡ ይሠራበታል
2. ነጠብጣብ. Beads of sweat showed on his forehead. የላብ ፡ ነጠብጣብ ፡ ግንባሩ ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**beak** አፍ
This bird has a yellow beak. ይች ፡ ወፍ ፡ ቢጫ ፡ አፍ ፡ አላት

**beam** (v.) ፊቱ ፡ አበራ
She was beaming with joy. በደስታ ፡ ብዛት ፡ ፊቷ ፡ ያበራ ፡ ነበር

**beam** (n.)
1. አውታር. The beams of the bridge are rotten through and through. የድልድዩ ፡ አውታሮች ፡ ጨርሰው ፡ በስብሰዋል
The roof was supported by steel beams. ጣሪያው ፡ የተደገፈው ፡ በብረት ፡ አውታሮች ፡ ነበር
2. ርብራብ. The steel beams are riveted together. የብረት ፡ ርብራቦች ፡ በሪቬት ፡ ተያይዘዋል
3. ጠርብ. Drill a hole in the beam! ጠርቡን ፡ ብሳው
4. ጮራ. The searchlight sent a beam of light into the sky. ባውዛው ፡ የብርሃን ፡ ጮራ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ፈነጠቀ

**beam of plow** ሞፈር
The beam of the plow broke. ሞፈሩ ፡ ተሰብሯል

**bean** ባቄላ
Beans are sown in the highlands. በደጋ ፡ ባቄላ ፡ ይዘራል
[See also 'coffee bean']

**bear** (bore, borne), vt.
1. ወለደ(ተወለደ). She is too old to bear children. ስላረጀች ፡ አትወልድም
Where were you born? የተወለድከው ፡ የት ፡ ነው ?
2. ተሸከመ. The donkey bore a very heavy load. አህያው ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ጭነት ፡ ተሸከመ
3. ቻለ. He has to bear the whole burden himself. ሸክሙን ፡ ሁሉ ፡ እራሱ ፡ መቻል ፡ አለበት
I cannot bear to look at him. በዓይኔ ፡ ላየው ፡ አልችልም
4. ታገሠ. He cannot bear any more pain. ከእንግዲህ ፡ ምንም ፡ ሕመም ፡ ሊታገሥ ፡ አይችልም
5. አዘለ. The letter bears good news. ደብዳቤው ፡ ጥሩ ፡ ወሬ ፡ አዝሏል
The document bore the Emperor's signature. ሰነዱ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ፊርማ ፡ አዝሏል
6. አስገኘ. The money bears 5 per cent interest. ገንዘቡ ፡ አምስት ፡ በመቶ ፡ ወለድ ፡ ያስገኛል
7. አፈራ. This tree bears fine apples. ይህ ፡ ዛፍ ፡ ጥሩ ፡ ቱፋዎች ፡ ያፈራል
8. አለ(ው). The director bears a good name. ዲሬክተሩ ፡ ጥሩ ፡ ስም ፡ አላቸው

**bear** (vi.)
*His claim to the land does not bear close examination. በጥንቃቄ ፡ ሲመረመር ፡ መሬቱ ፡ ይገባኛል ፡ ማለቱ ፡ መሠረት ፡ የለውም

**bear down** ወጣ(በት)
The car bore down on him. መኪናው ፡ ሊወጣበት ፡ ነበር

**bear on**
1. ተመለከተ. What you say may be true, but it does not bear on this problem. አንተ ፡ የምትለው ፡ እውነት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ አይመለከትም
2. ተጫነ. Her sorrow bears heavily on her. ሐዘን ፡ በጣም ፡ ተጭኗታል

**bear oneself** ራሱን ፡ ተቈጣጠረ
The soldier bore himself well during the battle. በውጊያው ፡ ጊዜ ፡ ወታደሩ ፡ ራሱን ፡ በሚገባ ፡ ተቈጣጠረ

**bear (one) out** ምስክር ፡ ሆነ(ለት)
Call up my friend. He will bear me out in what I say. ጓደኛዬን ፡ ጥራው ፡ ላልኩት ፡ ምስክር ፡ ይሆነኛል

**bear to (the right)** ቀኝ ፡ ያዘ
When you reach the top of the hill, bear to the right! ኮረብታው ፡ ጫፍ ፡ ስትደርስ ፡ ቀኝህን ፡ ያዝ

**bear up** ራሱን ፡ ተቈጣጠረ
She bore up well during the crisis. በችግሩ ፡ ወቅት ፡ ራሷን ፡ በሚገባ ፡ ተቈጣጠረች

**bear upon** ነካ
These are matters which bear upon the community. እነዚህ ፡ ሕዝቡን ፡ የሚነኩ ፡ ጉዳዮች ፡ ናቸው

**bear with** ታገሠ
Please bear with me a little longer! እባክህን ፡ ትንሽ ፡ ታገሠኝ
[See also 'arm, cross, fruit, grudge, mind, pressure, relation, witness']

**bear** (n.) ድብ
In Europe, there are white bears. በአውሮፓ ፡
ነጭ ፡ ድብ ፡ አለ

**(be) bearable** ሊታገሡት ፡ የሚቻል
His ache was bearable enough. ሕመሙ ፡ ሊ
ታገሡት ፡ የሚቻል ፡ ነበር

**beard** ጢም
I am growing a beard. ጢሜን ፡ አሳድጋለሁ

**bearded** ጢማም
This bearded man is my uncle. ይህ ፡ ጢማም ፡
ሰውዬ ፡ አጎቴ ፡ ነው

**bearing**
1. አቋም. A soldier should have a military bearing. ወታደር ፡ የውትድርና ፡ አቋም ፡ እንዲኖ
ረው ፡ ያሻል
2. ዛላ. She has a queenly bearing. የንግሥት ፡
ዛላ ፡ አላት
3. ግንኙነት. His foolish questions have no bearing on the problem. ያቀረባቸው ፡ የማይ
ረቡ ፡ ጥያቄዎች ፡ ከችግሩ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡
የላቸውም

**bearings** አቅጣጫ
The ship lost her bearings in the fog. በጭጋ
ግ ፡ ውስጥ ፡ መርከቧ ፡ አቅጣጫዋን ፡ ሳተች

**dignified bearing** ግርማ ፡ ሞገስ
His dignified bearing is admired by all. ግርማ ፡
ሞገሱ ፡ በሁሉ ፡ የተደነቀ ፡ ነው

**have bearing on** ተመለከተ
This has no bearing on the subject. ይህ ፡ ጉዳዩ
ን ፡ አይመለከትም

**bearish** የባለጌ
His bearish behavior made him many enemies.
የባለጌ ፡ ጠባዩ ፡ ብዙ ፡ ጠላት ፡ አፈራበት

**beast** አውሬ ፤ አረመኔ
He hates that beast of a supervisor. ያንን ፡ አ
ውሬ ፡ (አረመኔ) ፡ ተቈጣጣሪ ፡ አይወደውም

**wild beast** አውሬ
The wild beast attacked the hunters. አውሬ
ው ፡ አዳኞቹን ፡ ተተናኰላቸው

**beasts** አራዊት
There are tracks of many kinds of beasts in the mud. ጭቃው ፡ ውስጥ ፡ የብዙ ፡ ዓይነት ፡ አ
ራዊት ፡ ፈለግ ፡ አለ
[See also 'burden']

**beastly** የአውሬነት
The murder of the child was a beastly crime.
የሕፃኑ ፡ መገደል ፡ የአውሬነት ፡ ተግባር ፡ ነበር

**beat** (vt.)
1. ደበደበ. The robbers beat the man and robbed him. ቀማኞቹ ፡ ሰውዬውን ፡ ደብድበው ፡
ዘረፉት
2. መታ. He was beating a drum. ከበሮ ፡ ይ
መታ ፡ ነበር
He was beating the dog with a stick. ውሻው
ን ፡ በዱላ ፡ ይመታው ፡ ነበር
3. ናጠ. She beat the milk until it foamed.
አረፋ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ ወተቱን ፡ ናጠችው
4. አሸነፈ. We beat them in today's game.
በዛሬው ፡ ጨዋታ ፡ አሸነፍናቸው
5. አስናቀ. Nothing can beat horse riding as a sport. በስፖርት ፡ ረገድ ፡ ግልቢያን ፡ የሚያስን
ቅ ፡ የለም
6. አሰሰ. The men beat the woods in search of the lost child. የጠፋውን ፡ ልጅ ፡ ፍለጋ ፡ ሰ
ዎች ፡ ጫካውን ፡ አሰሱ
*I saw the wallet first, but he beat me to it.
የኪስ ፡ ቦርሳውን ፡ መጀመሪያ ፡ አይቸው ፡ ነበር ፡
ነገር ፡ ግን ፡ እሱ ፡ ቀድሞኝ ፡ አነሣው

**beat** (vi.) መታ
His heart began to beat faster. ልቡ ፡ በኀይል ፡
ይመታ ፡ ጀመር

**beat against**
1. መታ. The rain was beating against the windows. ዝናቡ ፡ መስኮቱን ፡ መታው
2. አማታ. The bird beat its wings against the cage. ወፏ ፡ ክንፎቿን ፡ ከወፍ ፡ ጎጆው ፡ ጋር ፡
አማታች

**beat around the bush** ዳር ፡ ዳር ፡ አለ
He did not answer my question, but beat around the bush. ጥያቄዬን ፡ አልመለሰም ፡ ነ
ገር ፡ ግን ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ አለ

**(be) beaten back**
The attack was beaten back. ወረራውን ፡ ለመ
መለስ ፡ ተቻለ

**(be) beaten down** (= tr.) ጨፈጨፈ
+The wheat was beaten down by the rain.
ዝናብ ፡ ስንዴውን ፡ ጨፈጨፈው

**beat off** አባረረ
He tried to beat off the bees that were stinging him. ይነድፉት ፡ የነበሩትን ፡ ንቦች ፡ ለማባረር ፡ ሞከረ

**(be) beaten off** መለሱት
The enemy's attack was beaten off. የጠላትን ፡
ድንገተኛ ፡ ጥቃት ፡ መለሱት

**beat up** ደበደበ
He beat him up because he insulted his mother.
እናቱን ፡ ስለሰደበበት ፡ ደበደበው
[See also 'hot, path, pulp, retreat, time, wood']

**beat** (n.) ድለቃ
The beat of the drum was heard from a distance. የከበሮው ፡ ድለቃ ፡ ከሩቅ ፡ ይሰማ ፡ ነበር
*The policeman's beat is around Churchill Avenue. ፖሊሱ ፡ የሚዘዋወረው ፡ በቸርችል ፡ ጐዳና ፡ አካባቢ ፡ ነው
[See also 'heartbeat']

**beating** ድብደባ
Beating is forbidden in school. ድብደባ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ተከልክሏል

**suffer a beating** ተሸነፈ
The team suffered a beating last Sunday. ቡድኑ ፡ ባለፈው ፡ እሑድ ፡ ተሸነፈ

**take a beating** ተደበደበ
The thieves took a beating. ሌቦቹ ፡ ተደበደቡ

**Beatitude** ብጹዕ
His Beatitude Abuna Kerellos died some years ago. ብጹዕ ፡ አቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ አረፉ

**beautiful**
1. ቆንጆ. She is a beautiful girl. ቆንጆ ፡ ልጃገረድ ፡ ነች
2. ውብ. The necklace is made of beautiful pearls. ድሪው ፡ ከውብ ፡ ሉል ፡ የተሠራ ፡ ነው
He expressed his ardor for knowledge in a beautiful poem. ለዕውቀት ፡ ያለውን ፡ የጋለ ፡ ስሜት ፡ በውብ ፡ ግጥም ፡ ገለጸ
3. የደመቀ. The ceremony of the coronation is very beautiful. የዘውዱ ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ በጣም ፡ የደመቀ ፡ ነው
4. የሚያምር. The ceremonial costumes were beautiful. የክብረ ፡ በዓል ፡ ልብሶች ፡ የሚያምሩ ፡ ነበሩ
5. ጥሩ. What a beautiful day! እንዴት ፡ ያለ ፡ ጥሩ ፡ ቀን ፡ ነው !

**make beautiful** አሳመረ
The priest's melodious voice makes the service beautiful. የቄሱ ፡ ለዛ ፡ ያለው ፡ ድምፅ ፡ ቅዳሴውን ፡ ያሳምራል

**beautifully** አሳምሮ
She plays the flute beautifully. ዋሽንት ፡ አሳምራ ፡ ትጫወታለች

**beautify** (beautified) አስጌጠ
She beautified the room with flowers. ክፍሉን ፡ በአበባ ፡ አስጌጠችው

**beautify oneself** አምሮ ፡ ታየ
Women have always used cosmetics to beautify themselves. ሴቶች ፡ አምሮ ፡ ለመታየት ፡ ሁል ጊዜ ፡ በመኳኳያ ፡ ይጠቀሙ ፡ ነበር

**beauty** (beauties)
1. ቁንጅና. Her beauty beguiled us. ቁንጅናዋ ፡ ማረከን
Beauty is only skin-deep. ቁንጅና ፡ ብቻ ፡ አይበቃም
2. ውበት. The necklace enhanced her beauty. ሐብሉ ፡ በውበቷ ፡ ላይ ፡ ውበት ፡ ጨመረላት
We are always finding new beauties in his poetry. በቅኔው ፡ ሁልጊዜ ፡ አዲስ ፡ ውበት ፡ እናገኝበታለን
3. (= adj.) ቆንጆ. She is really a beauty. በእውነት ፡ በጣም ፡ ቆንጆ ፡ ናት
[See also 'personal']

**beauty parlor** የቁንጅና ፡ ሳሎን
She goes to the beauty parlor once a week. ወደ ፡ ቁንጅና ፡ ሳሎን ፡ በሳምንት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ትሄዳለች

**became,** see **become**

**because**
1. ስለ + (perfect). He didn't come because he was sick. ስለታመመ ፡ አልመጣም
2. ስለ + (relative imperfect). Because my brother is coming from the country, I will go to see him. ወንድሜ ፡ ካገር ፡ ቤት ፡ ስለሚመጣ ፡ ላየው ፡ እሄዳለሁ

**because of**
1. ለሱ ፡ ብሎ. I did it because of her. ለሷ ፡ ብዬ ፡ አደረግሁት
2. ስለሱ ፡ ብሎ. I don't want you to do it just because of me. ስለኔ ፡ ብለህ ፡ እንድታደርገው ፡ አልፈልግም
3. ከ - - - የተነሣ. Because of his age, he stays at home. ከዕድሜያቸው ፡ መግፋት ፡ የተነሣ ፡ እቤት ፡ ውለዋል
4. (= conj.) ስለ. Because of the high price, I did not buy it. ዋጋው ፡ ውድ ፡ ስለሆነ ፡ አልገዛሁትም

**beckon** ጠቀሰ
She beckoned to me to follow. እንድከተላት ፡ ጠቀሰችኝ

**become** (became)
1. ሆነ. A lamb becomes a sheep. ጠቦት ፡ በግ ፡ ይሆናል
Flour becomes dough. ዱቄት ፡ ሊጥ ፡ ይሆናል
2. ተገባ(ው). He uses language which does not become a man of his education. በሱ ፡ ት

ምህርት ፡ ደረጃ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሊናገር ፡ የማይ ገባውን ፡ ይናገራል
3. አማረ(በት). A white dress becomes her. ነጭ ፡ ልብስ ፡ ያምርባታል
*What became of him? የት ፡ ደረሰ?

**becoming**
*She has a becoming smile. የፈካ ፡ ፈገግታ ፡ አላት

**be becoming** ተስማማ
This dress is very becoming to you. ይህ ፡ ቀሚ ስ ፡ በጣም ፡ ይስማማሻል

**bed** (n.)
1. አልጋ. I want a room with two beds. ባለሁለት ፡ አልጋ ፡ ክፍል ፡ እፈልጋለሁ
2. መውረጃ. In the dry season the bed of the river is completely dry. በበጋ ፡ ወራት ፡ የወ ንዙ ፡ መውረጃ ፡ በፍጹም ፡ ይደርቃል
3. መደብ. He has a bed of flowers in front of his house. ከቤቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የአበባ ፡ መ ደብ ፡ አለው

**get to bed** ተኛ
We did not get to bed until 2 A.M. እስከ ፡ ሌ ሊቱ ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ አልተኛንም ፡ ነበር

**go to bed** ተኛ
I went to bed late. አምሽቼ ፡ ተኛሁ
The doctor thinks I had better go to bed. ሐኪሙ ፡ ብተኛ ፡ የሚሻል ፡ መሆኑን ፡ ያምናል

**lie in bed** ተኛ
Don't lie in bed all morning! ጧቱን ፡ሙሉ ፡ ተኝተህ ፡ አታርፍድ

**make the bed** አልጋ ፡ አነጠፈ
The maid made my bed. ገረዲቷ ፡ አልጋዬ ን ፡ አነጠፈች

**put to bed** አስተኛ
The mother put the children to bed late in the evening. እናቲቱ ፡ ልጆቹን ፡ መሸት ፡ ሲል ፡ አ ስተኛቻቸው

**send to bed** አስተኛ
The mother sent the children to bed early. እናቲቱ ፡ ልጆቹን ፡ በጊዜ ፡ አስተኛች

**stay in bed** ተኛ
The doctor recommended that she stay in bed. ሐኪሙ ፡ እንድትተኛ ፡ አዘዘ
[See also 'change, double bed, flower, head, hustle, tuck, turn']

**bed** (v.), ~ **down** አደረ
We will bed down here in the woods. እዚህ ፡ ጫ ካ ፡ ውስጥ ፡ እናድራለን

**bedazzle**
1. ዓይኑን ፡ አጥበረበረው. The glare of the searchlight bedazzled him. የባውዛው ፡ ብርሃ ን ፡ ዓይኑን ፡ አጥበረበረው
2. ማረከ. She bedazzled the audience with her charm. ተመልካቾቹን ፡ በውበቷ ፡ ማረከቻቸው

**bedbug** ትኋን
Spray powder to kill the bedbugs! ትኋኑን ፡ ለ ማጥፋት ፡ መድኀኒት ፡ እርጪው

**bedding**
1. የአልጋ ፡ ልብስ. You better air the bedding today. ዛሬ ፡ የአልጋ ፡ ልብሱን ፡ ብታናፍሺ ው ፡ ጥሩ ፡ ነው
2. መኝታ. Straw is used as bedding for horses. ገለባ ፡ ለፈረሶች ፡ መኝታ ፡ ያገለግላል

**bedlam** የግርግር ፡ ቦታ
The streets were a bedlam during the riot. በብጥብጥ ፡ ጊዜ ፡ መንገዶች ፡ ሁሉ ፡ የግርግር ፡ ቦታ ፡ ነበሩ

**Bedouin** በረኸኛ ፡ ዐረብ
The Bedouins live in the Sahara Desert. በረኸኞቹ ፡ ዐረቦች ፡ ሰሐራ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ውስ ጥ ፡ ይኖራሉ

**(be) bedraggled** ተጨማለቀ
My dress was bedraggled when I came in from the rain. ዝናም ፡ መቶኝ ፡ ስገባ ፡ ልብሴ ፡ ተጨ ማልቆ ፡ ነበር

**bedridden** ያልጋ ፡ ቁራኛ
She takes care of her bedridden mother. ያልጋ ፡ ቁራኛ ፡ እናቷን ፡ ታስታምማለች

**be bedridden** ከአልጋ ፡ ተቈራኘ
Because my mother is very old, she is bedridden. እናቴ ፡ በጣም ፡ ስላረጀች ፡ ከአልጋ ፡ ተቈራኝታለች

**bedroom** መኝታ ፡ ቤት
Go to the bedroom and bring me my coat! መኝታ ፡ ቤት ፡ ሂድና ፡ ኮቴን ፡ አምጣልኝ

**bedside, by the** ~ በ --- አልጋ ፡ አጠገብ
The nurse sat by the sick woman's bedside. አስታማሚዋ ፡ በበሽተኛዋ ፡ ሴት ፡ አልጋ ፡ አጠገ ብ ፡ ተቀመጠች

**bedspread** የአልጋ ፡ ልብስ
The bedspread is red. የአልጋ ፡ ልብሱ ፡ ቀይ ፡ ነው

**bedspring** የአልጋ ፡ ሽቦ
The bedsprings are not very good any more. የአልጋው ፡ ሽቦ ፡ ከእንግዲህ ፡ አይጠቅምም

**bedtime, at ~** ሊተኛ ፡ ሲል
I drink warm milk at bedtime. ልተኛ ፡ ስል ፡ የፈላ ፡ ወተት ፡ እጠጣለሁ

**bee** ንብ
There aren't many bees in my beehive. በኔ ፡ ቀፎ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ንብ ፡ የለም
**queen bee** የንብ ፡ አውራ
When the queen bee leaves, the bees disperse. የንብ ፡ አውራ ፡ ሲወጣ ፡ ንቦች ፡ ይበተናሉ

**beef** የበሬ ፡ ሥጋ
The doctor told me not to eat beef. ሐኪሙ ፡ የበሬ ፡ ሥጋ ፡ አትብላ ፡ አለኝ

**beehive** ቀፎ
I shall smoke out my beehive tonight. ዛሬ ፡ ማታ ፡ ቀፎዬን ፡ አጥናለሁ

**been,** see **be**

**beer**
1. (native) ጠላ. My sister brews good beer. የኔ ፡ እኅት ፡ ጥሩ ፡ ጠላ ፡ ትጠምቃለች
2. ቢራ. I would like a glass of beer. አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ቢራ ፡ እፈልጋለሁ

**beeswax** ሰም
We sometimes make candles from beeswax. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከሰም ፡ ጧፍ ፡ እናበጃለን

**beetle** ጥንዚዛ
The beetles have eaten all the leaves. ጥንዚዛዎች ፡ ቅጠሉን ፡ ሁሉ ፡ በልተውታል

**befall** (befell) አጋጠመ
Whatever befalls them, they are ready to meet it. የሚያጋጥማቸውን ፡ ሁሉ ፡ ሊቋቋሙት ፡ ተዘጋጅተዋል

**befell,** see **befall**

**befit** ተስማማ
You must wear a dress to befit the occasion. ለጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ የሚስማማ ፡ ልብስ ፡ መልበስ ፡ አለብህ

**before** (prep.)
1. ከ - - - በፊት. I will be there before two. ከስምንት ፡ ሰዓት ፡ በፊት ፡ እዚያ ፡ እገኛለሁ
2. (= conj.) ሳ + (negative imperfect). The telegram should be here before evening. ሳይመሽ ፡ ቴሌግራሙ ፡ እዚህ ፡ መድረስ ፡ አለበት
3. (= adv.) ፊት ፡ ለፊት. She stopped before the gate. እዋናው ፡ በር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ቆመች
*The question before us is very complicated. የቀረበልን ፡ ጉዳይ ፡ በጣም ፡ የተወሳሰበ ፡ ነው

**before** (conj.)
1. (= prep.) ከ + verbal noun + በፊት (or አስቀድሞ)
Clean the house before he comes! ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ ቤቱን ፡ አጽዳ
That happened before Ethiopia was christianized. ኢትዮጵያ ፡ የክርስትናን ፡ ሃይማኖት ፡ ከመቀበሏ ፡ አስቀድሞ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ነው
2. ሳ + (negative imperfect). Sweep the carpet before the guests come! እንግዶቹ ፡ ሳይመጡ ፡ ስጋጃውን ፡ ጥረገው
3. ከ + imperfect + ይልቅ. I would starve before I surrender. እጄን ፡ ከምሰጥ ፡ ይልቅ ፡ በረኃብ ፡ ልሙት
**before** (adv.) ከዚህ ፡ በፊት ፤ ከዚህ ፡ ቀደም
I have seen that film before. ያንን ፡ ፊልም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ አይቼዋለሁ
I have never been there before. ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እዚያ ፡ ሄጄ ፡ አላውቅም
**before long** በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፤ በቅርቡ ፤ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ
Before long, he will be able to help you. በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሊረዳህ ፡ ይችላል
Before long, we will have saved up a hundred dollars. በቅርቡ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ እናጠራቅማለን
I will see you before long. ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ እንገናኛለን
[See also 'ever, night, shortly, yesterday']

**beforehand** አስቀድሞ
I knew it beforehand. አስቀድሜ ፡ አውቄዋለሁ

**befriend** ጓደኛ ፡ ሆነ
He befriended the new student. ካዲሱ ፡ ተማሪ ፡ ጋር ፡ ጓደኛ ፡ ሆነ

**beg** ለመነ
They begged me to help them. እንድረዳቸው ፡ ለመኑኝ
The children begged for coins. ልጆቹ ፡ ፍራንክ ፡ ለመኑ
*I beg to differ with you; the situation is not that way at all. ይቅርታ ፡ አድርግልኝና ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ አልስማማም ፤ ሁኔታው ፡ በፍጹም ፡ እንደዚያ ፡ አይደለም
*I beg your pardon! ይቅርታ
**beg off** ወደ ፡ ኋላ ፡ አለ
He was assigned to help us, but he had begged off. እኛን ፡ እንዲረዳ ፡ ተመድቦ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አለ
[See also 'question']

**began,** see **begin**

**beget** (begot)

1. ወለደ. Abraham begot Isaac. አብርሃም ፡ ይስሐቅን ፡ ወለደ
2. አስከተለ. Idleness begets crime. ሥራ ፡ ፈትነት ፡ ወንጀልን ፡ ያስከትላል

**beggar** ለማኝ

There is a beggar at the door. ለማኝ ፡ እበር ፡ ቆሟል

**begging** ልመና

Their bankruptcy reduced them to begging. መክሰራቸው ፡ ከልመና ፡ አደረሳቸው

**begin** (began, begun), vt.

1. ጀመረ. She began work on the project right away. የታቀደውን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ወዲያው ፡ ጀመረች
2. አቋቋመ. Two friends began the club three years ago. ሁለት ፡ ጓደኛሞች ፡ ክበቡን ፡ የዛሬ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ አቋቋሙት

**begin** (vi.)

1. ተጀመረ. Life began many million years ago. ሕይወት ፡ የተጀመረው ፡ ከብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ነው
2. ጀመረ ፤ ተነሣ. Where shall I begin? የት ፡ ልጀምር ? (or ከየት ፡ ልነሣ ?)
3. ተቋቋመ. The club began two years ago. ክበቡ ፡ የዛሬ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ተቋቋመ

**begin to** ሊ + imperfect + ነው

It's beginning to rain. ሊዘንብ ፡ ነው

**to begin with**

1. መጀመሪያ ፡ ነገር. To begin with, we have not enough money. መጀመሪያ ፡ ነገር ፣ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ የለንም
2. ከሁሉ ፡ በፊት. To begin with, I want a competent man to have the job. ከሁሉ ፡ በፊት ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሥራውን ፡ እንዲይዝ ፡ እፈልጋለሁ

**beginner** ጀማሪ

He is still a beginner. ገና ፡ ጀማሪ ፡ ነው

**beginning**

1. የመጀመሪያ. This is only the beginning; the worst is yet to come. ይህ ፡ የመጀመሪያው ፡ ነው ፤ ገና ፡ የባሰ ፡ ይመጣል
2. የመጀመሪያ ፡ ክፍል. I missed the beginning of the race. የውድድሩን ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ አላየሁትም
3. አጀማመር. Our team made an auspicious beginning by winning the first game. ቡድናችን ፡ የመጀመሪያውን ፡ ግጥሚያ ፡ በማሸነፍ ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጥ ፡ አጀማመር ፡ አሳየ

**begot**, see **beget**

**begrudge**

1. ቀና. I don't begrudge him the honor. በክብሩ ፡ አልቀናበትም
2. ቆጨ(ው). +I begrudged the money it cost me. ያወጣሁት ፡ ገንዘብ ፡ ቆጨኝ

**beguile**

1. አታለለ. They beguiled the enemy into an ambush. ጠላትን ፡ አታለው ፡ ካደፈጡበት ፡ ቦታ ፡ አስገቡት
2. ማረከ. Her beauty beguiled us. ቁንጅናዋ ፡ ማረከን
3. አስደሰተ. He beguiled us with stories. ተረቶች ፡ እያወቶ ፡ አስደሰተን

**begun**, see **begin**

**behalf, on ~ of** ስለ ፤ በ --- ስም ፡ ሆኖ

He worked for weeks on behalf of the organization. ስለ ፡ ድርጅቱ ፡ ለብዙ ፡ ሳምንት ፡ ሠራ

I want to thank you on behalf of our organization. በድርጅታችን ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ላመሰግናችሁ ፡ እፈልጋለሁ

**on one's behalf** ስለ

He intervened in the dispute on my behalf. ስለኔ ፡ በክርክር ፡ ውስጥ ፡ ጣልቃ ፡ ገባ

His friends intervened with the minister on his behalf. ጓደኞቹ ፡ ስለሱ ፡ ሚኒስትሩን ፡ አማለዱት

**behave**

1. መልካም ፡ ምግባር ፡ ፈጸመ. Did you behave today? ዛሬ ፡ መልካም ፡ ምግባር ፡ ፈጽመሃል ?
2. ጠባዩን ፡ አሳመረ. On my honor, I will do my best to behave. በተቻለኝ ፡ መጠን ፡ ጠባዬን ፡ ለማሳመር ፡ ቃል ፡ እገባለሁ
3. ሠራ. How does your car behave in heavy traffic? መኪና ፡ በበዛበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ መኪናህ ፡ እንዴት ፡ ትሠራለች ?

He behaves like a fool. እንደቂል ፡ ይሠራል

*He doesn't know how to behave. መልካም ፡ ጠባይ ፡ ይጐድለዋል

*Behave yourself! አትባልግ

**behave oneself badly** መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ አሳየ

The little boy behaves himself badly in school. ትንሹ ፡ ልጅ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ ያሳያል

**behave well** አደበ

She behaves well in company. ሰው ፡ ሲኖር ፡ ታድባለች

[See also 'awfully, naturally, normally, shamefully']

**behavior**

1. ጠባይ. He was commended for his good behavior. ስለ ፡ መልካም ፡ ጠባዩ ፡ ተመሰገነ
2. አድራጎት. Account to me for your behavior! ለአድራጎትህ ፡ ምክንያት ፡ ስጠኝ
3. ሁኔታ. His amorous behavior pleased her. ፍቅርን ፡ የሚገልጽ ፡ ሁኔታው ፡ አስደሰታት
[See also 'indecent, presumptuous, rough']

**(be) beheaded** አንገቱን ፡ ተቈረጠ

In the England of former days, a pretender to the throne was often beheaded. ድሮ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ በሐሰት ፡ ዙፋኑ ፡ ይገባኛል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ አንገቱን ፡ ይቈረጥ ፡ ነበር

**behest** ማግባባት

At the behest of friends, he decided to take a rest. በወዳጆች ፡ ማግባባት ፡ የተነሣ ፡ ዕረፍት ፡ ለማድረግ ፡ ወሰነ

**behind**

1. ከ - - - ኋላ ፤ ከኋላ ፤ ከ - - - በስተኋላ. The boy was hiding behind the tree. ልጁ ፡ ከዛፍ ፡ ኋላ ፡ ተደብቆ ፡ ነበር
The dog was running behind the car. ውሻው ፡ ከመኪናው ፡ ኋላ ፡ ይሮጥ ፡ ነበር
He sits behind me. ከኋላዬ ፡ ይቀመጣል
The bridesmaid walked behind the bride. ደንገጡሯ ፡ ከሙሽራዋ ፡ በስተኋላ ፡ ትሄድ ፡ ነበር
2. ሥር. He hid behind a bush. ቁጥቋጦ ፡ ሥር ፡ ተደበቀ

**be behind**

1. ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀረ. Mary is behind the others in her sewing. ሜሪ ፡ በልብስ ፡ ስፌት ፡ ከሌሎቹ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርታለች
My watch is ten minutes behind. ሰዓቴ ፡ ዐሥር ፡ ደቂቃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርታለች
2. ዘገየ. The mailman is behind his usual time today. ፖስተኛው ፡ ዛሬ ፡ ያለወትሮው ፡ ዘግይቷል
3. ደገፈ. The Congress was behind the President on the last bill. በመጨረሻው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ላይ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ፕሬዚዳንቱን ፡ ደገፉቸው

**behind the house** በጓሮ ፡ በኩል

There is a garage behind the house. በጓሮ ፡ በኩል ፡ የመኪና ፡ ማቆምያ ፡ አለ

**from behind** ከኋላው

He was attacked from behind. ከኋላው ፡ ተመታ
[See also 'back, leave, time']

**behold** (beheld) አየ

At last, they beheld the Promised Land. በመጨረሻ ፡ ቅድስት ፡ አገርን ፡ አዩ

**behold!** ይኸውልህ

And, behold, three soldiers appeared! ይኸውልህ ፤ ሦስት ፡ ወታደሮች ፡ ብቅ ፡ አሉ

**(be) beholden to** ውለታው ፡ ተሰማው

I am beholden to you for your advice. ስለ ፡ ሰጠኸኝ ፡ ምክር ፡ ውለታህ ፡ ይሰማኛል

**behoove, it behooves**

1. ተገቢ ፡ ነው. It behooves a child to obey his parents. ልጅ ፡ ለወላጆቹ ፡ መታዘዝ ፡ ተገቢ ፡ ነው
2. ኖረ(በት). It behooves you to work if you want to keep this job. ይህንን ፡ ሥራ ፡ ይዘህ ፡ ለመቆየት ፡ ከፈለግህ ፡ መሥራት ፡ ይኖርብሃል

**being**

1. ፍጡር. Men, women, and children are human beings. ወንዶች ፡ ሴቶችና ፡ ልጆች ፡ ሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ ናቸው
2. ህልውና. God's being is beyond the comprehension of man. የእግዚአብሔር ፡ ህልውና ፡ ከሰው ፡ ዕውቀት ፡ በላይ ፡ ነው
3. ሁኔታ. Her whole being thrilled to the beauty of the music. መላው ፡ ሁኔታዋ ፡ በሙዚቃው ፡ ውበት ፡ ተመሰጠ

**come into being** ተቋቋመ

The Boy Scouts came into being in 1908. እስካውት ፡ በ፲፱፻፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ተቋቋመ
[See also 'human']

**belabor**

1. መላልሶ ፡ አነሣ. He kept belaboring the point after we had agreed. ከተስማማንበትም ፡ በኋላ ፡ ጉዳዩን ፡ መላልሶ ፡ ማንሣቱን ፡ አላቋረጠም
2. አጣደፈ. They belabored the candidate with questions. ተወዳዳሪውን ፡ በጥያቄ ፡ አጣደፉት

**belated** የዘገየ

The belated letter arrived at last. የዘገየው ፡ ደብዳቤ ፡ በመጨረሻ ፡ ደረሰ

**belch**

1. አገሣ. Every time he eats, he belches. በበላ ፡ ቁጥር ፡ ያገሣል
2. ተፋ. The volcano was belching smoke and ashes. እሳተ ፡ ገሞራው ፡ ጭስና ፡ አመድ ፡ ይተፋ ፡ ነበር

**beleaguer** ከበበ

The enemy beleaguered the city. ጠላት ፡ ከተማውን ፡ ከበበ

**belie**

1. ሸፈነ. His appearance belies his feelings. መልኩ ፡ ስሜቱን ፡ ይሸፍነዋል.

2. እውነት ፡ አለመሆኑን ፡ አሳየ. His cruelty belies his statements. ጭካኔው ፡ ቃሉ ፡ እውነት ፡ አለመሆኑን ፡ ያሳያል

**belief** እምነት

My belief in him was seriously shaken. በሱ ፡ ላይ ፡ ያለኝ ፡ እምነት ፡ በጣም ፡ ተቀንሷል

He never expresses his religious beliefs. ስላለው ፡ የሃይማኖት ፡ እምነት ፡ ገልጾ ፡ አያውቅም

[See also 'superstition']

**believe**

1. አመነ. He believes in God. በእግዚአብሔር ፡ ያምናል

He believes in a lot of exercise. በብዙ ፡ የሰውነት ፡ እንቅስቃሴ ፡ ያምናል

2. መሰለ(ው). Will they come tomorrow? No, I do not believe so. ነገ ፡ ይመጣሉ ? አይመስለኝም

3. ገመተ. They believed him to be insane. እብድ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ገመቱ

**make believe**

1. አስመሰለ. The boys made believe they were fighting the enemy. ልጆቹ ፡ ጠላትን ፡ የሚዋጉ ፡ አስመሰሉ

2. መስሎ ፡ ታየ. The girl liked to make believe she was a queen. ልጃገረዲቷ ፡ ንግሥት ፡ መስላ ፡ መታየትን ፡ ትወድ ፡ ነበር

**believer** አማኝ

The faith of the believers was shaken by the capture of the holy city. የቅድስት ፡ ከተማ ፡ መያዝ ፡ ያማኞቹን ፡ መንፈስ ፡ አናጋው

**believing, convert into ~** አሳመነ

Can I convert you into believing that the earth is round? መሬት ፡ ክብ ፡ መሆኗን ፡ ላሳምንህ ፡ እችላለሁ ?

**belittle** አንኳሰሰ ፤ አንቋሸሸ

When I found out he was a Frenchman, I felt like a fool for belittling his country. ፈረንሳዊ ፡ መሆኑን ፡ ካወቅሁ ፡ በኋላ ፡ አገሩን ፡ በማንኳሰሴ ፡ አፈርኩ

He constantly belittles my efforts to write better. ጽሕፈቴን ፡ ለማሻሻል ፡ የማደርገውን ፡ ጥረት ፡ ሁልጊዜ ፡ ያንቋሽሻል

**bell**

1. ደወል. The bell doesn't work. ደወሉ ፡ አይሠራም

2. ቃጭል. The cat has a bell on its collar. ድመቷ ፡ አንገቷ ፡ ላይ ፡ ቃጭል ፡ አላት

**ring a bell** ትዝ ፡ አለ(ው)

His name rings a bell. ስሙ ፡ ትዝ ፡ ይለኛል

**bellicose** የጠበኛነት

He has a bellicose disposition. የጠበኛነት ፡ ጠባይ ፡ አለው

**belligerence** ጠብ ፡ መፈለግ

I cannot understand his belligerence about such a trivial matter. እንዲህ ፡ ላለ ፡ ለማይረባ ፡ ነገር ፡ ጠብ ፡ መፈለጉ ፡ አይገባኝም

**state of belligerence** ጠብ

A state of belligerence exists between the two countries. በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ጠብ ፡ አለ

**belligerent** ጠብ ፡ ወዳድ

Some nations seem more belligerent than others. አንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ከሌሎች ፡ ይልቅ ፡ ጠብ ፡ ወዳድ ፡ ይመስላሉ

**bellow** (v.) አጓራ

The ox bellowed when the farmer hit it. ገበሬው ፡ በመታው ፡ ጊዜ ፡ በሬው ፡ አጓራ

**bellows** (n.) ወናፍ

Use the bellows to make the fire hotter. እሳቱን ፡ ለማንደድ ፡ በወናፍ ፡ ተጠቀም

**belly** (v.) ተነፋ

The sails bellied in the wind. ሸራው ፡ በነፋሱ ፡ ተነፋ

**belly** (n.) ሆድ

He kicked him in the belly. ሆዱ ፡ ላይ ፡ ረገጠው

**bellyache** የቁርጠት ፡ ሕመም

His bellyache prevented him from going to school. የቁርጠት ፡ ሕመም ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከመሄድ ፡ አስቀረው

**belong**

1. የ + noun (or pronoun) + ነው. Does this book belong to you? ይህ ፡ ያንተ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ?

2. ግንኙነት ፡ ነበረው. He never belonged to any political movement. ከምንም ፡ ዓይነት ፡ የፖለቲካ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ አልነበረውም

*He too belongs to our club. እሱም ፡ የክበባችን ፡ አባል ፡ ነው

*You don't belong here. እዚህ ፡ መሆን ፡ አይገባህም

*This book belongs on the top shelf. ይህ ፡

**bend over** ጐንበስ ፡ አለ
He bent over to pick up his wallet. ቦርሳውን ፡ ለማንሣት ፡ ጐንበስ ፡ አለ

**bend over backwards** የሚቻለውን ፡ ሁሉ ፡ አደረገ
She bent over backwards to make sure that he was always pleased. ደስ ፡ እንዲለው ፡ የሚቻላትን ፡ ሁሉ ፡ አደረገች

**be bent**
1. (= active) ደፋ. +Her head was bent over the books. መጻሕፍቱ ፡ ላይ ፡ ራሷን ፡ ደፍታ ፡ ነበር
2. ጣረ. He was bent on mastering Amharic. አማርኛ ፡ በደምብ ፡ አጣርቶ ፡ ለማወቅ ፡ ጣረ

**(one's) back is bent** ጐበጠ
The farmer's back was bent from years of toil. ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ ልፋት ፡ የተነሣ ፡ ገበሬው ፡ ጐብጧል
[See also 'effort']

**bend** (n.) ጠምዛዛ ፡ ቦታ
The bend in the road was straightened recently. መንገዱ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጠምዛዛ ፡ ቦታ ፡ በቅርቡ ፡ ተቃና
*There is a sharp bend in the road here. እዚህ ፡ ቦታ ፡ መንገዱ ፡ በድንገት ፡ ዕጥፍ ፡ ይላል

**bended, on ~ knee** ተንበርክኮ
He begged for mercy on bended knee. ተንበርክኮ ፡ ምሕረት ፡ ለመነ

**beneath** (prep.) ከ - - - ሥር ፤ በ - - - ሥር
I put it beneath all the other papers. ከሌሎቹ ፡ ወረቀቶች ፡ ሁሉ ፡ ሥር ፡ አስቀመጥኩት
He was buried beneath the tree. ከዛፉ ፡ ሥር ፡ ተቀበረ
He walked beneath the canopy of flowery trees. በአበባማ ፡ ዛፎች ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ተራመደ

**beneath** (adv.) ከታች ፤ ከበታች
What you drop will fall upon the step beneath. የምትጥለው ፡ ነገር ፡ ከታች ፡ በሚገኘው ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ይወድቃል
The fortress commands the plain beneath. ምሽጉ ፡ ከበታች ፡ ያለውን ፡ ሜዳ ፡ ለመቈጣጠር ፡ ያስችላል
*The work was beneath him. ሥራው ፡ ካለው ፡ ችሎታ ፡ በጣም ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ነበር
[See also 'dignity']

**benediction** ቡራኬ
The benediction is part of the church services. ቡራኬ ፡ ከቅዳሴ ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ፡ ነው
He received benediction. ቡራኬ ፡ ተቀበለ

**give benediction** ባረከ
Since the man is a good Christian, the priest gave him benediction. ሰውዬው ፡ ጥሩ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለሆነ ፡ ቄሱ ፡ ባረኩት

**benefactor** ደጋፊ ፤ ረዳት
He was the benefactor of many artists. የብዙ ፡ አርቲስቶች ፡ ደጋፊ ፡ ነበር
He is rightly called our benefactor. ረዳታችን ፡ ተብሎ ፡ የተጠራው ፡ በሚገባ ፡ ነው

**beneficence** ችሮታ
His beneficence relieved the poor. ችሮታው ፡ ችግረኞችን ፡ ረዳቸው

**beneficial** ጠቃሚ
Fresh air is beneficial to health. ንጹሕ ፡ አየር ፡ ለጤንነት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው

**be beneficial** ጠቀመ
I hope your holiday will be beneficial to you. የዕረፍት ፡ ጊዜህ ፡ እንደሚጠቅምህ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ

**beneficiary** (beneficiaries) ተጠቃሚ ፤ ተቀባይ
My brother was the beneficiary of the insurance policy. ወንድሜ ፡ የሕይወት ፡ ዋስትናው ፡ ተጠቃሚ ፡ (ተቀባይ) ፡ ነበር
All the children are beneficiaries of the new playground. ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ አዲስ ፡ በተሠራው ፡ የመጫወቻ ፡ ሜዳ ፡ ተጠቃሚዎች ፡ ናቸው

**benefit** (vt.) ጠቀመ
Rest will benefit a sick person. ዕረፍት ፡ ማድረግ ፡ ለበሽተኛ ፡ ይጠቅማል

**benefit** (vi.) ተጠቀመ(በት)
He benefited from his past experiences. በፊት ፡ የደረሰበት ፡ ነገር ፡ ትምህርት ፡ ስለሆነው ፡ ተጠቀመበት

**benefit** (n.)
1. ጥቅም. I do not expect to get any benefit out of it. ከዚህ ፡ ነገር ፡ የምጠባበቀው ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ የለኝም
2. ብልጽግና. Benefits accrue to society from better education. ከተሻለ ፡ ትምህርት ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ብልጽግና ፡ ያገኛል
3. አገልግሎት. Does your insurance policy include medical benefits? የሕይወት ፡ ዋስትናህ ፡ የሕክምና ፡ አገልግሎትን ፡ ይጨምራል ?
4. ወሮታ. My new friend showered many benefits upon me. አዲሱ ፡ ወዳጄ ፡ ብዙ ፡ ወሮታ ፡ አደረገልኝ
5. በጎ ፡ አድራጎት. Tonight's show is a benefit for crippled children. ከዛሬው ፡ ምሽት ፡ ትርእይት ፡ የሚገኘው ፡ ገቢ ፡ የሚውለው ፡ አካለ ፡ ስንኩል ፡ ለሆኑ ፡ ልጆች ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ነው

**be of benefit** ጠቀመ
The trip was not of much benefit to us. ጉዞው ፤ ምንም ፤ ያህል ፤ አልጠቀመንም

**for the benefit of**
1. ሲል. Speak louder for the benefit of those in the rear. ኋላ ፤ ላሉት ፤ ስትል ፤ ጮክ ፤ ብለህ ፤ ተናገር
2. እርዳታ ፤ ለመሰብሰብ. She is holding a great fete for the benefit of the hospital. ለሐኪም ፤ ቤቱ ፤ እርዳታ ፤ ለመሰብሰብ ፤ ታላቅ ፤ ግብዣ ፤ ታደርጋለች

**give the benefit of the doubt**
*He gave him the benefit of the doubt, and so released him. ነገሩ ፤ አጠራጣሪ ፤ ስለሆነ ፤ ካልተረጋገጠበት ፤ በማለት ፤ ለቀቀው

**benevolence** ቅንነት
His benevolence led him to work for the church. ቅንነቱ ፤ ቤተ ፤ ክርስቲያንን ፤ እንዲያገለግል ፤ አደረገው

**benevolent**
1. በጎ ፤ አድራጊ. A benevolent person will always give money to the poor. በጎ ፤ አድራጊ ፤ ሰው ፤ ሁልጊዜ ፤ ለድኻ ፤ ይመጸውታል
2. የደግነት. His benevolent smile showed me that he forgave me. የደግነት ፤ ፈገግታውን ፤ ባየሁ ፤ ጊዜ ፤ ይቅርታ ፤ እንዳደረገልኝ ፤ ዐወቅሁ

**benign**
1. ተስማሚ. The sick child was taken to Harar because of its benign climate. አየሩ ፤ ተስማሚ ፤ ስለሆነ ፤ በሽተኛው ፤ ልጅ ፤ ወደ ፤ ሐረር ፤ ተወሰደ
2. የደግነት. He has a benign smile. የደግነት ፤ ፈገግታ ፤ አለው

**bent,** see **bend**

**bent** (n.) ተሰጥዎ
He has a bent for painting. የሥዕል ፤ ተሰጥዎ ፤ አለው

**benumb** አደነዘዘ
The cold benumbed my fingers. ብርዱ ፤ ጣቶቼን ፤ አደነዘዛቸው

**be benumbed** ደነዘዘ
My fingers were benumbed by cold. ጣቶቼ ፤ በብርድ ፤ ምክንያት ፤ ደንዝዘው ፤ ነበር

**bequeath** አወረሰ
He bequeathed me his gold watch. የወርቅ ፤ ሰዓቱን ፤ አወረሰኝ
The artist bequeathed his talent to his son. አርቲስቱ ፤ ችሎታውን ፤ ለልጁ ፤ አወረሰ

**bequest**
1. ውርስ. Henry received a bequest of 500 dollars from his aunt. ሄንሪ ፤ ከክስቱ ፤ ያምስት ፤ መቶ ፤ ብር ፤ ውርስ ፤ አገኘ
2. ኑዛዜ. His philanthropic bequests have created museums and libraries. በሱ ፤ የችሮታ ፤ ኑዛዜዎች ፤ ቤተ ፤ መዘክሮችና ፤ ቤተ ፤ መጻሕፍቶች ፤ ተሠርተዋል

**make a bequest** ንብረት ፤ አወረሰ
He made a munificent bequest to the university. ለዩኒቨርሲቲው ፤ ታላቅ ፤ ንብረት ፤ አወረሰ

**berate** ገሠጸ
The mother berated her child for his rudeness. እናትዮዋ ፤ ልጅዋን ፤ ስለ ፤ ብልግናው ፤ ገሠጸችው

**bereave (of)** አሳጣ
The accident bereaved him of his entire family. አደጋው ፤ መላ ፤ ቤተ ፤ ሰቡን ፤ አሳጣው

**bereaved** (adj.) noun + የሞተበት
The bereaved mother showed little sign of affliction. ልጅዋ ፤ የሞተባት ፤ እናት ፤ እንዳችም ፤ የሥቃይ ፤ ምልክት ፤ አላሳየችም

**be bereaved** በጣም ፤ አዘነ
He was bereaved by his mother's death. በእናቱ ፤ ሞት ፤ የተነሣ ፤ በጣም ፤ አዝኖ ፤ ነበር

**bereavement** የዘመድ ፤ ሞት
She was in a state of agitation due to her recent bereavement. በቅርቡ ፤ በደረሰባት ፤ የዘመድ ፤ ሞት ፤ ምክንያት ፤ ተሸብራ ፤ ነበር

**berry** ፍሬ
The shrub has small red berries. ቁጥቋጦው ፤ ትንንሽ ፤ ቀያይ ፤ ፍሬዎች ፤ ይዟል

**berserk, go** ~ መላ ፤ ቅጡ ፤ አጣ
He went berserk at the terrible news. አሰቃቂውን ፤ ወሬ ፤ በሰማ ፤ ጊዜ ፤ መላ ፤ ቅጡ ፤ አጣ

**berth** (የ)መኝታ ፤ ክፍል
I found a stranger in my berth on the train. ባቡሩ ፤ ውስጥ ፤ ባለው ፤ መኝታ ፤ ክፍሌ ፤ ውስጥ ፤ እንግዳ ፤ ሰው ፤ አገኘሁ

**beseech** (besought) ለመነ
The prisoner besought the judge to be merciful. እስረኛው ፤ ዳኛው ፤ እንዲራራለት ፤ ለመነ

**beseem** ይገባዋል
It hardly beseems you always to quarrel with your sister. ሁልጊዜ ፤ ከእኅትህ ፤ ጋር ፤ መጣላት ፤ አይገባህም

**beset**
1. በዛ(በት). Danger beset his path. መንገዱ ፡ አደጋ ፡ የበዛበት ፡ ነው
2. አዋከበ. Many doubts beset him. ብዙ ፡ ጥርጣሬ ፡ አዋከበው

**be beset**
1. ተወረረ. In the swamp, we were beset by mosquitos. በረግረጉ ፡ ስፍራ ፡ በወባ ፡ ትንኝ ፡ ተወረርን
2. ተዋጠ. This task is beset with difficulties. ይህ ፡ ሥራ ፡ በጣጣ ፡ የተዋጠ ፡ ነው
3. (= act.) አጠቃ. Since there was a drought last year, we were beset by famine. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ድርቅ ፡ ስለነበረ ፡ ረኃብ ፡ አጥቅቶናል

**beside** (prep.)
1. ከ --- ጐን ። ጐን. Please put this trunk beside the other one. ይህንን ፡ ሰንዱቅ ፡ ከሌላው ፡ ጐን ፡ አኑረው
Who is that standing beside your father? ያ ፡ አባትህ ፡ ጐን ፡ የቆመው ፡ ማን ፡ ነው ?
2. በ --- አጠገብ. She would like to live beside the sea. በባሕሩ ፡ አጠገብ ፡ ለመኖር ፡ ትፈልጋለች
3. ዳር. The cat lay stretched out beside the fire in contentment. ድመቲቷ ፡ ረክታ ፡ እሳት ፡ ዳር ፡ ተዘራለች
4. በ --- ፊት ፡ ለፊት. The teacher put a check beside the correct answer. በትክክለኛው ፡ መልስ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አስተማሪው ፡ ምልክት ፡ አደረገ
5. ከ --- ውጭ. That's beside the point. ይህ ፡ ከነገሩ ፡ ውጭ ፡ ነው
*Mary seems dull beside her sister. ሜሪን ፡ ከእኅቷ ፡ ጋር ፡ ሲያወዳድሯት ፡ ለዛ ፡ ቢስ ፡ ትመስላለች

**beside oneself**
*He was beside himself with rage. በንዴት ፡ ራሱን ፡ ስቶ ፡ ነበር
[See also 'mark, question']

**besides** (prep.)
1. ከ --- ሌላ. I have three other hats besides this one. ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ሦስት ፡ ባርኔጣ ፡ አለኝ
Besides his wages, he gets tips. ከደሞዙ ፡ ሌላ ፡ ጉርሻ ፡ ያገኛል
2. ከ --- በስተቀር. We spoke of no one besides you. ካንተ ፡ በስተቀር ፡ ስለ ፡ ማንም ፡ አላወራንም
**besides** (adv.)
1. ከዚያም ፡ ሌላ. We will have games and dancing and food besides. እንጫወታለን ፡ እንደንሳለን ። ከዚያም ፡ ሌላ ፡ እንበላለን
2. ከዚያም ፡ በላይ ። ከዚህም ፡ በላይ. It is too late to go for a walk. Besides, it is starting to rain. ሽርሽር ፡ ለመሄድ ፡ ዘግይቷል ። ከዚያም ፡ በላይ ፡ ሊዘንብ ፡ ነው
He is a good worker, and besides, everybody likes him. እሱ ፡ ጥሩ ፡ ሠራተኛ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይወደዋል

**besiege** ከበበ
The English besieged Emperor Theodore at Magdala. እንግሊዞች ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ መቅደላ ፡ ላይ ፡ ከበቧቸው

**be besieged with**
*During the flood, the Red Cross was besieged with calls for help. በጐርፍ ፡ ጊዜ ፡ የቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ የእርዳታ ፡ ጥያቄ ፡ ጐረፈለት

**besmirch** አጐደፈ
The newspaper besmirched the director's good name. ጋዜጣው ፡ የዲሬክተሩን ፡ መልካም ፡ ስም ፡ አጐደፈ

**besought,** see **beseech**

**bespeak** አሳየ
His good manners bespeak a good upbringing. መልካም ፡ ጠባዩ ፡ ጥሩ ፡ አስተዳደግ ፡ እንዳለው ፡ ያሳያል

**best** (n.) ምርጥ
We want only the best. ምርጥ ፡ የሆነውን ፡ ብቻ ፡ እንፈልጋለን
**best** (adj.)
1. ምርጥ. The boys acknowledged him to be the best football player. ከተጫዋቾቹ ፡ ሁሉ ፡ ምርጥ ፡ ተጫዋች ፡ እሱ ፡ መሆኑን ፡ ልጆች ፡ ዐወቁለት
2. የቅርብ. He betrayed his best friend. የቅርብ ፡ ወዳጁን ፡ ከዳው
3. የበለጠ. This is the best beer I have ever tasted. ከቀመስኩት ፡ ቢራ ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ የበለጠ ፡ ነው
4. ከሁሉ ፡ የተሻለ. The best student was appointed monitor of his class. ከሁሉ ፡ የተሻለው ፡ ተማሪ ፡ የክፍል ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ ተመረጠ
**best** (adv.)
1. ይበልጥ ። የበለጠ. I work best in the morning. ይበልጥ ፡ የምሠራው ፡ ጧት ፡ ነው
I can illustrate this best by an example. ይህን ፡ በምሳሌ ፡ የበለጠ ፡ ላብራራው ፡ እችላለሁ
2. ከሁሉ ፡ አብልጦ. I like this book best. ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ከሁሉ ፡ አብልጬ ፡ እወደዋለሁ
3. ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ አሳምሮ. Who reads best? ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ አሳምሮ ፡ የሚያነብ ፡ ማነው ?

4. በጣም. I like it best this way. በጣም ፡ የምወደው ፡ እንዲህ ፡ ሲሆን ፡ ነው

**best of** ምርጥ

I have had the best of teachers. ምርጥ ፡ አስተማሪዎች ፡ ነበሩኝ

**(the) best part of an hour** አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል

Driving to work takes the best part of an hour. ወደ ፡ ሥራ ፡ በመኪና ፡ መሄድ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ይወስዳል

**at best** ግፋ ፡ ቢል

The book, at best, will sell 1,000 copies. ግፋ ፡ ቢል ፡ ካንድ ፡ ሺህ ፡ መጽሐፍ ፡ በላይ ፡ አይሸጥም

**for the best**

*Let's hope for the best. የተሻለ ፡ ይመጣል ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ እናድርግ

*Don't cry; it is all for the best. አታልቅስ ፤ መጨረሻው ፡ ያምራል

**get the best of someone**

1. አታለለ. We have to be careful that he does not get the best of us. እንዳያታልለን ፡ መጠንቀቅ ፡ አለብን

2. በክርክር ፡ ረታ. I got the best of my teachers. አስተማሪዎቼን ፡ በክርክር ፡ እረታ ፡ ነበር

**had best**

*You had best phone your father to tell him where you are going. የት ፡ እንደምትሄድ ፡ ላባትህ ፡ ብትደውል ፡ መልካም ፡ ነው

**make the best of something** የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ተጠቀመበት

We do not like our new house, but we will have to make the best of it. አዲሱን ፡ ቤታችንን ፡ አንወደውም ፤ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የተቻለንን ፡ ያህል ፡ እንጠቀምበታለን

**one's best** የተቻለው ፤ በተቻለው ፡ መጠን

I'll try to do my best. የተቻለኝን ፡ ለማድረግ ፡ እሞክራለሁ

On my honor, I will do my best to behave. በተቻለኝ ፡ መጠን ፡ ጠባዬን ፡ ለማሳመር ፡ ቃል ፡ እገባለሁ

**to the best of**

Answer to the best of your knowledge. የምታውቀውን ፡ ያህል ፡ መልስ

[See also 'bet, do, far, knowledge, level, next, none, second, seller, suit, very']

**bestial** የአውሬነት

The fighting was carried out with bestial cruelty. ውጊያው ፡ የተደረገው ፡ የአውሬነት ፡ ጭካኔ ፡ በተመላበት ፡ ሁኔታ ፡ ነበር

**best man** ሚዜ

After the woman quarreled with her husband and went off, the best man brought her back. ሴትዮዋ ፡ ከባሏ ፡ ጋር ፡ ተጣልታ ፡ ሄዳ ፡ ሚዜዋ ፡ መልሶ ፡ አመጣት

**bestow**

1. ሸለመ. The Emperor bestowed a medal on him. ጃንሆይ ፡ ሜዳይ ፡ ሸለሙት

2. ሰጠ. The rich man bestowed thousands of dollars on libraries. ባለጸጋው ፡ ብዙ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ለቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ሰጠ

**bet** (v.)

1. ተወራረደ. I bet five dollars on the black horse. ጥቁሩ ፡ ፈረስ ፡ በግልቢያ ፡ ያሸንፋል ፡ ብዬ ፡ ባምስት ፡ ብር ፡ እወራረዳለሁ

2. እርግጠኛ ፡ ነው. I will bet she is never going to pay him. እንደማትከፍለው ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ

**bet** (n.) ውርርድ

When are you going to pay up that bet? ያንን ፡ ውርርድ ፡ የምትከፍለው ፡ መቼ ፡ ነው ?

**make a bet** ተወራረደ

Let's make a bet about who will finish first! ማን ፡ ቀድሞ ፡ እንደሚጨርስ ፡ እንወራረድ

**your best bet** የሚያዋጣህ

Your best bet is to try for a scholarship here. የሚያዋጣህ ፡ እዚህ ፡ ነጻ ፡ ትምህርት ፡ ለማግኘት ፡ መሞከር ፡ ነው

**betray**

1. ከዳ. He betrayed his best friend. የቅርብ ፡ ወዳጁን ፡ ከዳው

2. አጠፋ. She has betrayed my confidence. በሷ ፡ ላይ ፡ የነበረኝን ፡ እምነት ፡ አጠፋችው

3. (= pass.) ታወቀ(በት). The boy's face betrayed the fact that he had been eating chocolate. ቸኮላት ፡ ይበላ ፡ እንደነበረ ፡ ከልጁ ፡ ፊት ፡ ታወቀበት

4. ገለጸ(በት). His mistakes betrayed his lack of education. የፈጸማቸው ፡ ስሕተቶች ፡ አለመማሩን ፡ ገለጹበት

5. አጋለጠ(በት). His foreign accent betrayed him. የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ አነጋገሩ ፡ አጋለጠበት

**betrayal**

1. ክዳት. She reproached him for his betrayal in bitter words. ስለ ፡ ክዳቱ ፡ አምርራ ፡ ተናገረችው

2. ማጉደል. A broken promise is a betrayal of trust. ቃልን ፡ ማጠፍ ፡ እምነትን ፡ ማጉደል ፡ ነው

**betroth** አሳጨ
The father betrothed his daughter to his
friend's son. አባትዬው ፡ ሴት ፡ ልጇን ፡ ለጓደኛ
ው ፡ ልጅ ፡ አሳጨ

**be betrothed**
1. ተሟጨ. Mary and John are now betrothed.
ሜሪና ፡ ጆን ፡ አሁን ፡ ተሟጭተዋል
2. ታጨ. His daughter was betrothed to a doctor.
ሴት ፡ ልጁ ፡ ለሐኪም ፡ ታጨች

**betrothal** ማጨት
His betrothal was announced in the newspaper.
ማጨቱ ፡ በጋዜጣ ፡ ተገለጸ

**better** (adj.) የተሻለ
Don't you have a better room? የተሻለ ፡ ክፍ
ል ፡ የለህም ?

**better** (adv.) የተሻለ ፡ አድርጎ
They did it better after a little practice. ከጥቂ
ት ፡ ልምምድ ፡ በኋላ ፡ የተሻለ ፡ አድርገው ፡ ሠሩት
*You ought to know better than to play with
matches. በክብሪት ፡ መቀለድ ፡ ጥሩ ፡ አለመሆ
ኑን ፡ ማወቅ ፡ ይገባሃል

**better than** ከ - - - የተሻለ
He is a better man than his brother. ከወንድሙ ፡
የተሻለ ፡ ሰው ፡ ነው

**be any better** ተሻለ(ው)
Is your father any better? አባትህ ፡ ተሻላቸው ?

**be better** ተሻለ(ው)
The sick child is better today. ሕመምተኛው ፡
ልጅ ፡ ዛሬ ፡ ተሽሎታል

**be better off** ተሻለ(ው)
Because of his asthma, he would be better off
in a different climate. ለአስማው ፡ አየር ፡ ቢ
ለውጥ ፡ ይሻለው ፡ ነበር

**be better off if** ብ + imperfect + ይሻላል
This house is too small; we will be better off
if we move. ይህ ፡ ቤት ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው ።
ቤት ፡ ብንቀይር ፡ ይሻላል

**change for the better** ተሻሻለ
His work has changed for the better. ሥራው ፡
ተሻሽሏል

**feel better** ተሻለ(ው)
Do you feel better? ተሽሎሃል ?

**get the better of someone**
1. አሸነፈ. Fright got the better of him.
ፍርሃት ፡ አሸነፈው
2. አሞኘ ። አታለለ. He will try to get the better
of you in every business deal you have with
him. ከርሱ ፡ ጋር ፡ በምታደርገው ፡ በማንኛው
ም ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሊያሞኝህ ፡ (ሊያታልልህ) ፡
ይሞክራል
3. ተጠቀመ. I got the better of him in the
swap. በልውውጡ ፡ እኔ ፡ ተጠቀምኩ

**had better**
*You had better return before dark or you
will get lost. ሳይጨልም ፡ ብትመለስ ፡ ይሻላል ።
አለዚያ ፡ ትጠፋለህ

**have the better of one** ከ - - - ተሻለ
He had the better of me in that argument.
በዚያ ፡ ክርክር ፡ እርሱ ፡ ከኔ ፡ የተሻለ ፡ ነበር

**the better**
*The better I know him, the more I like him.
እያወቅሁት ፡ ስሄድ ፡ ይበልጥ ፡ እወደው ፡ ጀመር
*The sooner the better. ቶሎ ፡ ቢሆን ፡ ይሻላል

**the better part of the day** ከግማሽ ፡ ቀን ፡ በላይ
It takes the better part of the day to get there.
እዚያ ፡ ለመድረስ ፡ ከግማሽ ፡ ቀን ፡ በላይ ፡ ይወ
ስዳል
[See also 'all, think']

**better** (v.) አሻሻለ
The government is trying to better the farmers'
conditions. መንግሥቱ ፡ የገበሬዎችን ፡ ሁኔታ ፡
ለማሻሻል ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነው

**betterment** መሻሻል
He labored for the betterment of mankind.
ስለ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ መሻሻል ፡ ብዙ ፡ ደክሟል

**between** በ - - - መካከል
The car was caught between two trees. መኪና
ዋ ፡ በሁለት ፡ ዛፎች ፡ መካከል ፡ ተቀረቀረች

**between ... and**
1. በ - - - ና ፡ በ - - - መካከል. The relation
between teacher and pupil is friendly. ባስተማ
ሪና ፡ በተማሪ ፡ መካከል ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙ
ነት ፡ አለ
We will meet between six and seven. በዐሥ
ራ ፡ ሁለትና ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ መካከል ፡ እንገ
ናኛለን
2. በ - - - ና ፡ በ -. Between teaching and writing,
my time is completely taken up. ጊዜዬ ፡ በሙ
ሉ ፡ በማስተማርና ፡ መጽሐፍ ፡ በመጻፍ ፡ ያል
ፋል
3. ከ - - - እስከ. He earned between ten and
fifteen dollars. ከዐሥር ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡
ብር ፡ ያገኝ ፡ ነበር
4. ወይም. It is between five and six miles to
Bethlehem from here. ከዚህ ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ልሔ
ም ፡ አምስት ፡ ወይም ፡ ስድስት ፡ ማይል ፡ ነው

*This plane flies between Addis Ababa and Dire Dawa. ይህ ፡ አውሮፕላን ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ድሬ ፡ ዳዋ ፡ ይበራል

**between you and me**
*This is just between you and me. ይህ ፡ በሁለታችን ፡ መካከል ፡ ይቅር
*Between you and me, it is his own fault. በኔና ፡ ባንተ ፡ ይቅርና ፡ ጥፋቱ ፡ የራሱ ፡ ነው

**between us (you, them)** ባንድነት ፤ ለጋራ
They caught twelve fish between them. ባንድነት ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓሣ ፡ ያዙ
They have only one dollar between them. ለጋራ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ አላቸው
We shall finish the job between us. ሥራውን ፡ ለጋራ ፡ እንጨርሰዋለን

**in between** እ - - - ውስጥ
He found a letter in between the pages of his book. እመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ አገኘ

**beverage** መጠጥ
Beverages are sold in this store. እዚህ ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ መጠጥ ፡ ይሸጣል

**bewail** አለቀሰ
He bewailed the loss of his son in battle. ልጁ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ በመሞቱ ፡ አለቀሰ

**beware** ተጠነቀቀ
Beware of dogs! ከውሾች ፡ ተጠንቀቅ !

**bewilder** ግራ ፡ አጋባ
The unfamiliar streets of the city bewildered me. የማላውቃቸው ፡ የከተማ ፡ መንገዶች ፡ ግራ ፡ አጋቡኝ

**bewitch**
1. መተት ፡ አደረገበት. The old woman bewitched the cows so they gave no milk. አሮጊቷ ፡ ላሞቹ ፡ ወተት ፡ እንዳይሰጡ ፡ መተት ፡ አደረገችባቸው
2. አፈዘዘ. They used magic to bewitch their enemies. ጠላቶቻቸውን ፡ በአስማት ፡ ያፈዙ ፡ ነበር
3. አነሆለለ. Her beauty bewitched the audience. ቁንጅናዋ ፡ ተመልካቾቹን ፡ አነሆለለ

**beyond** (prep.)
1. ከ - - - ባሻገር. The house is right beyond the hospital. ቤቱ ፡ ልክ ፡ ከሆስፒታሉ ፡ ባሻገር ፡ ነው
2. ከ - - - በስተቀር. He has no income beyond his pension. ከጡረታ ፡ አበል ፡ በስተቀር ፡ ገቢ ፡ የለውም
3. ከ - - - በላይ. I will pay nothing beyond the stated price. ከተወሰነው ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ ምንም ፡ አልከፍልም
She is living beyond her means. የምትኖረው ፡ ከቅሟ ፡ በላይ ፡ ነው
God is beyond the bounds of human knowledge. እግዚአብሔር ፡ ከሰብአዊ ፡ ዕውቀት ፡ ጽንፍ ፡ በላይ ፡ ነው
4. አልፎ. The road forks beyond the village. መንገዱ ፡ መንደሩን ፡ አልፎ ፡ ይከፈላል
*Your work is beyond praise. ለሥራህ ፡ ምስጋና ፡ ሲያንሰው ፡ ነው
*He is beyond help. ምንም ፡ እርዳታ ፡ ሊደረግለት ፡ አይቻልም

**beyond** (adv.) ወዲያ ፡ ማዶ
Beyond were the hills. ጋራዎቹ ፡ ወዲያ ፡ ማዶ ፡ ነበሩ

**be beyond one** ሊገባው ፡ አልቻለም
It's beyond me how he manages to keep from being fired. ከሥራ ፡ እንዴት ፡ እንደማይወጣ ፡ ሊገባኝ ፡ አልቻለም
[See also 'description, dispute, doubt, measure, number, question']

**bias** አድልዎ
His judgements are always without bias. የሱ ፡ ዳኝነት ፡ ሁልጊዜ ፡ ያለ ፡ አድልዎ ፡ ነው

**(be) biased** አደላ
A mother is often biased where her children are concerned. እናት ፡ ሁልጊዜ ፡ ለልጆቿ ፡ ታደላለች

**Bible** መጽሐፍ ፡ ቅዱስ
The Bible was originally written in Hebrew. መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በመጀመሪያ ፡ የተጻፈው ፡ በዕብራይስጥ ፡ ነው

**bibliography** [አንድን ፡ አርእስት ፡ የሚመለከቱ ፡ መጽሐፎች ፡ ወይም ፡ ጽሑፎች ፡ ዝርዝር]

**biceps** የክንድ ፡ ጡንቻ
His biceps show he is very strong. የክንዱ ፡ ጡንቻ ፡ ጠንካራነቱን ፡ ያመለክታል

**bicycle** (n.) ቢሲክሌት ፤ ቢስኪሌት
My bicycle needs fixing. ቢሲክሌቱ ፡ ጥገና ፡ ያስፈልጋታል

**bicycle** (v.) በቢሲክሌት ፡ ተንሸራሸረ
We went bicycling last Sunday. ባለፈው ፡ እሑድ ፡ በቢሲክሌት ፡ ተንሸራሸርን

**bid** (bade, or bid)
1. ጠራ. The king bade the nobles to a feast. ንጉሡ ፡ መኳንንቱን ፡ ግብር ፡ ጠሯቸው

2. ተጫረተ. I bid ten dollars for the bicycle. ቢሲክሌቱን ፡ በዐሥር ፡ ብር ፡ ተጫረትኩ
3. አዘዘ. The captain bade us halt. ሻምበሉ ፡ እንድንቆም ፡ አዘዘን

**bid fair** መሰለ
The winter bids fair to be a cold one. ክረምቱ ፡ የሚበርድ ፡ ይመስላል

**bid farewell** ተሰናበተ
He bade his friends farewell. ጓደኞቹን ፡ ተሰናበታቸው

**bid** (n.) የጨረታ ፡ ዋጋ
Companies are invited to submit bids for building an annex to Africa Hall. ለአፍሪካ ፡ አዳራሽ ፡ ተጨማሪ ፡ ሕንጻ ፡ ለመሥራት ፡ ኩባንያዎች ፡ የጨረታ ፡ ዋጋቸውን ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ተጠይቀዋል

**bide, ~ one's time** አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ጠበቀ ፤ ታግሦ ፡ ቆየ
He bided his time until his rival was absent. ተወዳዳሪው ፡ የሚቀርበትን ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ጠበቀ
He bided his time until the minister went abroad. ሚኒስትሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እስኪሄድ ፡ ድረስ ፡ ታግሦ ፡ ቆየ

**biennial** በየሁለቱ ፡ ዓመት ፡ የሚደረግ
The biennial meeting of our society was held in Washington. በየሁለቱ ፡ ዓመት ፡ የሚደረገው ፡ የማኅበራችን ፡ ስብሰባ ፡ በዋሽንግተን ፡ ተደረገ

**bier** ርብራብ
The coffin was placed on a bier in front of the church. አስከሬኑ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በርብራብ ፡ ላይ ፡ አርፎ ፡ ነበር

**bifurcate** ተለያየ
The road bifurcates at Dire Dawa. መንገዱ ፡ ድሬ ፡ ዳዋ ፡ ላይ ፡ ይለያያል

**big**
1. ትልቅ (ትልልቅ, with plural). They live in a big house. ትልቅ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ
Her children are big now. ልጆቿ ፡ አሁን ፡ ትልልቆች ፡ ሆነዋል
2. ታላቅ. The day he entered college was a big day in his life. ኮሌጅ ፡ የገባበት ፡ ቀን ፡ በሕይወቱ ፡ ታላቅ ፡ ዕለት ፡ ነበር
3. የታወቀ. Her father is a big lawyer. አባቷ ፡ የታወቁ ፡ ጠበቃ ፡ ናቸው

**as big as** የሚያህል
The hungry boy ate a slab of cheese as big as his hand. የራበው ፡ ልጅ ፡ እጁን ፡ የሚያህል ፡ ቁራጭ ፡ ፎርማጆ ፡ በላ

[See also 'great, hand, selection, shot, splash, this']

**bigamy** [ሁለት ፡ ሚስቶች ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ማግባት]

**bigot** [የራሱ ፡ ያልሆነ ፡ ማንኛቸውንም ፡ ዓይነት ፡ ሐሳብ ፡ የማይቀበል]

**bilateral** የጋራ
Sweden and Ethiopia signed a bilateral agreement. ስዊድንና ፡ ኢትዮጵያ ፡ የጋራ ፡ ውል ፡ ተፈራረሙ

**bile** አሞት
He mixed pepper with bile. በርበሬውን ፡ በአሞት ፡ ለወሰው

**(be) bilingual** ሁለት ፡ ቋንቋ ፡ ተናገረ
Many Ethiopians are bilingual. ብዙ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሁለት ፡ ቋንቋ ፡ ይናገራሉ

**bill** (v.) ሒሳብ ፡ ላከ
Please bill me without delay. ሳትዘገይ ፡ ሒሳቡን ፡ ላክልኝ

**bill** (n.)
1. ሒሳብ. The garage bill was high. የጋራዡ ፡ ሒሳብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነበር
2. የሒሳብ ፡ ደረሰኝ. I handed her a sheaf of bills. አንድ ፡ ክምር ፡ የሒሳብ ፡ ደረሰኝ ፡ አስረከብኳት
3. የሒሳብ ፡ መክፈያ. His bill became delinquent. የሒሳቡ ፡ መክፈያ ፡ ጊዜው ፡ ተላልፏል
4. ብር ፤ ገንዘብ. The government has put new bills into circulation. መንግሥት ፡ አዲስ ፡ ብር ፡ (ገንዘብ) ፡ አውጥቷል
Give me a ten dollar bill! አንድ ፡ ባለ ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ ስጠኝ
5. የሕግ ፡ ረቂቅ. The senator submitted a bill authorizing the construction of a new business school. የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ አባል ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ የንግድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲሠራ ፡ የሚለውን ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ አቀረበ
6. ማስታወቂያ. Post no bills! ማስታወቂያዎችን ፡ አትለጥፍ
7. አፍ. The bird has a large bill. ወፏ ፡ ትልቅ ፡ አፍ ፡ አላት

**foot the bill** ወጪውን ፡ ከፈለ
Who is going to foot the bill for all this? ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ወጪውን ፡ የሚከፍል ፡ ማነው ?

**small bills** ዝርዝር ፡ ብር
Give me some small bills, please. ዝርዝር ፡ ብር ፡ ስጠኝ

**billboard** የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስሌዳ
The billboard advertised radios. የንግድ ፡ ማስታወቂያው ፡ ስሌዳ ፡ ላይ ፡ የሬዲዮ ፡ ማስታወቂያ ፡ ተለጥፎበታል

**billion** ሺ ፡ ሚሊዮን

**bill of fare** የምግብ ፡ ዝርዝር
The bill of fare lists only Ethiopian food. የምግብ ፡ ዝርዝር ፡ የሚያመለክተው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ምግብ ፡ ብቻ ፡ ነው

**bimonthly** (adj.) በየሁለት ፡ ወሩ ፡ የሚታተም
A bimonthly magazine comes out six times a year. በየሁለት ፡ ወሩ ፡ የሚታተም ፡ መጽሔት ፡ ባመት ፡ ስድስት ፡ ጊዜ ፡ ይወጣል

**bimonthly** (adv.) በወር ፡ ሁለቴ
The magazine appears bimonthly. መጽሔቱ ፡ በወር ፡ ሁለቴ ፡ ይወጣል

**bind** (bound)
1. አሰረ. She bound her hair with a ribbon. ጸጉሯን ፡ በሪበን ፡ አሰረች
2. አስተሳሰረ. Deep friendship binds these two peoples. ጥልቅ ፡ ወዳጅነት ፡ እነዚህን ፡ ሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ ያስተሳስራል
3. ለወሰ (ተለወሰ). Stones bound together with asphalt make good roads. በአስፋልት ፡ የተለወሰ ፡ ኮረት ፡ ለመንገድ ፡ ሥራ ፡ ጥሩ ፡ ነው
4. ወደረ. He bound the cow's legs for milking. ወተት ፡ ለማለብ ፡ የላሟን ፡ እግር ፡ ወደረ
5. (= intr.) ጸና. The contract binds him for twelve years. ውሉ ፡ ለዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ይጸናል
6. አቈራኘ. What binds you to your job? ከሥራህ ፡ ጋር ፡ ያቈራኘህ ፡ ምንድነው ?
7. ጠረዘ. The bookbinder bound the magazines. ጠራዡ ፡ መጽሔቶቹን ፡ ጠረዘ

**be bound** ተገደደ
The witness is bound by oath to tell the truth. ምስክሩ ፡ እውነቱን ፡ እንዲናገር ፡ በመሓላ ፡ ይገደዳል
[See also 'honor']

**binder** ጠራዥ
The newspapers are at the binder's. ጋዜጦቹ ፡ ጠራዡ ፡ ዘንድ ፡ ናቸው

**bindery** የመጠረዣ ፡ ክፍል
The newspapers are still in the bindery. ጋዜጦቹ ፡ አሁንም ፡ እመጠረዣው ፡ ክፍል ፡ ይገኛሉ

**binding** (n.) ጥራዝ
The book has lost its binding. የመጽሐፉ ፡ ጥራዝ ፡ ተገንጥሏል

**binding** (adj.) ጽኑ
A binding contract cannot be abrogated by only one signatory. ጽኑ ፡ ውል ፡ ባንድ ፡ ፈራሚ ፡ ብቻ ፡ አይፈርስም

**be binding** ተከበረ
This agreement is binding on both contracting parties. ይህ ፡ ውል ፡ በሁለቱም ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ይከበራል

**binoculars** አቅራቢ ፡ መነጽር
You cannot see through the binoculars unless you adjust them. ካላስተካከልከው ፡ አቅራቢ ፡ መነጽሩ ፡ ውስጥ ፡ ለማየት ፡ አትችልም

**biography** የሕይወት ፡ ታሪክ
This book contains the biography of Abraham Lincoln. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የአብርሃም ፡ ሊንኮልን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ይዟል

**biology** ባዮሎጂ

**bird** ወፍ
There are many birds in this garden. በዚህ ፡ አትክልት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ወፎች ፡ አሉ
[See also 'baby']

**birth**
1. መወለድ. They announced the birth of their child. የልጃቸውን ፡ መወለድ ፡ አስታወቁ
2. ትውልድ. What is your place of birth? የትውልድ ፡ አገርህ ፡ የት ፡ ነው ?
Are you American by birth? በትውልድ ፡ አሜሪካዊ ፡ ነህ ?
3. መመሥረት. The birth of the new nation was greeted with acclaim. ያዲሱን ፡ አገር ፡ መመሥረት ፡ በሆታ ፡ ተቀበሉት

**give birth to** ወለደ
She gave birth to a boy. ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች
[See also 'humble, low, mean']

**birthday** የልደት ፡ ቀን
When is your birthday? የልደት ፡ ቀንህ ፡ መቼ ፡ ነው ?
[See also 'happy']

**birthday party** የልደት ፡ በዓል ፡ ድግስ
His birthday party was attended by many people. በልደት ፡ በዓሉ ፡ ድግስ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተገኙ

**birthmark, have a ~** ማርያም ፡ ሳመችው
He has a birthmark on his arm. ክንዱ ፡ ላይ ፡ ማርያም ፡ ስማዋለች

**birthplace** የተወለደበት ፡ ስፍራ
Write down your birthplace in the application! በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ የተወለድክበትን ፡ ስፍራ ፡ ጻፍ
*Philadelphia is the birthplace of the Constitution of the United States. ፊላዴልፊያ ፡ የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መጀመሪያ ፡ የተጻፈባት ፡ ከተማ ፡ ናት

**birth rate** የሚወለዱት ፡ ቁጥር
The birth rate increases while the death rate decreases. የሚወለዱት ፡ ቁጥር ፡ ሲጨምር ፡ የሚሞቱት ፡ እያነሰ ፡ ይሄዳል

**biscuit** ብስኩት
This biscuit is too hard for me to eat. እንዳልበላው ፡ ይህ ፡ ብስኩት ፡ በጣም ፡ ደረቅ ፡ ነው

**bishop** ጳጳስ

**bit** (v.), see **bite**

**bit** (n.) ልባብ
This bridle does not have a bit. ልጓሙ ፡ ልባብ ፡ የለውም

**bit, a ~** ትንሽ
She is feeling a bit tired. ትንሽ ፡ ደክም ፡ ብሏታል
**bit by bit** ትንሽ ፡ በትንሽ
We learned the story bit by bit. ነገሩን ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ ሰማነው
**bits of** ከዚያም ፡ ከዚህም ፤ ጥቃቅን
He is out picking up bits of information. ከዚያም ፡ ከዚህም ፡ ወሬ ፡ ለመለቃቀም ፡ ወጥቷል
They pieced together bits of information to discover the cause of the explosion. የፈንጂውን ፡ ምክንያት ፡ ለማግኘት ፡ የተገኙትን ፡ ጥቃቅን ፡ ማስረጃዎች ፡ አጠናቀሩ
**a bit more** ትንሽ
Can't you wait a bit more? ትንሽ ፡ ልትቆይ ፡ አትችልም ?
**a bit of** ቁራሽ
There is not a bit of bread in the house. እቤት ፡ ውስጥ ፡ ቁራሽ ፡ እንጀራም ፡ የለ
**a bit too......** ትንሽ ፤ ጥቂት
The tea is a bit too strong. ሻዩ ፡ ትንሽ ፡ ወፈር ፡ ብሏል
The bread is a bit too old to eat. ለመብል ፡ ዳቦው ፡ ጥቂት ፡ ቆየት ፡ ያለ ፡ ነው
**not a bit** ትንሽም + negative verb
He was not a bit angry. ትንሽም ፡ አልተናደደም ፡ ነበር
**not a bit of** ምንም + negative verb
That does not make a bit of difference. ይህ ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ አያመጣም
**not one bit** በጭራሽ + negative verb
Are you tired? Not one bit. ደክሞሃል ? በጭራሽ ፡ አልደከመኝም
**quite a bit** በጣም
The uncertainty of my position worries me quite a bit. የሥራዬ ፡ ነገር ፡ የማያስተማምን ፡ መሆኑ ፡ በጣም ፡ ያሳስበኛል
[See also 'blow, dash, every, old, smash']

**bitch** ሴት ፡ ውሻ

**bite** (bit, bitten), vt.
1. ነከሰ. Our dog will bite any thief who enters our house. ውሻችን ፡ ቤታችን ፡ ውስጥ ፡ የሚገባውን ፡ ሌባ ፡ ይነክሳል
The mosquitos bit me all last night. የወባ ፡ ትንኝ ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ሲነክሰኝ ፡ አደረ
2. አቃጠለ ፤ ፈጀ. Pepper bites the tongue. በርበሬ ፡ ምላስ ፡ ያቃጥላል ፡ (ይፈጃል)
3. ገመጠ. She bit the apple. ቱፋውን ፡ ገመጠችው
4. በላ. The small boy bites his fingernails. ትንሹ ፡ ልጅ ፡ የጣት ፡ ጥፍሮቹን ፡ ይበላል
5. ገረፈ. The cold wind bit our faces. ብርዳሙ ፡ ነፋስ ፡ ፊታችንን ፡ ገረፈው
**bite** (vi.) ተናከሰ (in the imperfect)
Does your dog bite? ውሻህ ፡ ይናከሳል ?
**bite into** ገመጠ
He bit into the apple. ቱፋውን ፡ ገመጠው
**bite off**
1. ገመጠ. He bit off a piece of bread. ቁራሽ ፡ ዳቦ ፡ ገመጠ
2. ቈረጠ. The leopard bit off his arm. ነብር ፡ እጁን ፡ ቈረጠው
[See also 'lip']

**bite** (n.)
1. ንክሻ. The dog bite became infected. የውሻው ፡ ንክሻ ፡ መርዝ ፡ ሆነ
2. ጉርሻ. Carefully chew each bite! እያንዳንዱን ፡ ጉርሻ ፡ ደኅና ፡ አድርገህ ፡ አኝክ
**a bite** ምንም ፡ ምግብ
We haven't a bite left. ምንም ፡ ምግብ ፡ አልተረፈንም
**have a bite** እህል ፡ ቀመሰ
Have a bite with me! ከኔ ፡ ጋር ፡ እህል ፡ ቅመስ

**biting** (adj.)
1. የሚጋረፍ. He went outside into the cold,

biting wind. ወደሚጋረፈው ፣ ብርዳማ ፣ ነፋስ ፣ ወጣ
2. አጥንት ፣ የሚነካ. He made a biting remark. አጥንት ፣ የሚነካ ፣ ነገር ፣ ተናገረ

**bitter**
1. መራራ. Bitter grass is sometimes used as medicine. መራራ ፣ ሣር ፣ አንዳንዴ ፣ ለመድኀኒት ፣ ይጠቅማል
2. የመረረ. He surrendered himself to bitter grief. በመረረ ፣ ሐዘን ፣ ተዋጠ
3. የሚያንገፈግፍ. He has had some bitter experiences. በኑሮው ፣ አንዳንድ ፣ የሚያንገፈግፉ ፣ ነገሮች ፣ አጋጥመውታል
4. አሰቃቂ. They suffered bitter hardships during the war. በጦርነቱ ፣ ጊዜ ፣ አሰቃቂ ፣ መከራ ፣ ደረሰባቸው
5. ክፉ. They exchanged bitter words. ክፉ ፣ ቃል ፣ ተነጋገሩ
*She reproached him for his betrayal in bitter words. ስለ ፣ ክዳቱ ፣ አምርራ ፣ ተናገረችው
*They are bitter enemies. እሳትና ፣ ጭድ ፣ ናቸው

**bitter** (adv.)
1. ክፉኛ. It was bitter cold. ክፉኛ ፣ ይበርድ ፣ ነበር
2. (= adj.) የሚሸነቍጥ. The night was bitter cold. ሌሊቱ ፣ የሚሸነቍጥ ፣ ብርድ ፣ ነበረው

**be bitter about** ተመረረ
He was very bitter about losing the job. ሥራውን ፣ በማጣቱ ፣ በጣም ፣ ተመረረ

**taste bitter** መረረ
This medicine tastes bitter. ይህ ፣ መድኀኒት ፣ ይመራል

**to the bitter end** እስከ ፣ መጨረሻው
They fought to the bitter end. እስከ ፣ መጨረሻው ፣ ተዋጉ

**bitterly** ተማርሮ ፤ አምርሮ
He complained to me bitterly. ተማርሮ ፣ ነገረኝ
He cried bitterly. አምርሮ ፣ አለቀሰ

**bitterness** መመረር
His hateful remarks reveal his bitterness toward his teacher. ጥላቻ ፣ የተመላበት ፣ አስተያየቱ ፣ ባስተማሪው ፣ መመረሩን ፣ ያሳያል

**biweekly**
This paper is a biweekly. ይህ ፣ ጋዜጣ ፣ በሳምንት ፣ ሁለቴ ፣ ይወጣል

**bizarre** ግራ ፣ የሆነ
His behavior is bizarre. ግራ ፣ የሆነ ፣ ጠባይ ፣ አለው

**black** (v.), ~ **out** ራሱን ፣ ሳተ
A person who is on a high mountain will black out if he works hard. ከፍተኛ ፣ ተራራ ፣ ላይ ፣ የሚገኝ ፣ ሰው ፣ ሥራ ፣ ቢያበዛ ፣ ራሱን ፣ ይስታል

**black** (n.) ጥቁር
The blacks in the United States are struggling for a better life. የአሜሪካ ፣ ጥቁሮች ፣ የተሻለ ፣ ኑሮ ፣ እንዲኖራቸው ፣ በመታገል ፣ ላይ ፣ ናቸው

**black** (adj.)
1. ጥቁር. His hair is black. ጠጉሩ ፣ ጥቁር ፣ ነው
2. የጠቈረ. The black clouds forebode a storm. የጠቈረው ፣ ደመና ፣ ኀይለኛ ፣ ዝናም ፣ መምጣቱን ፣ ያመለክታል

**be black** ጨለመ
The room was black at night. ሌሊት ፣ ክፍሉ ፣ ጨልሞ ፣ ነበር

**turn black** ጠቈረ
The bread turned black with age. ዳቦው ፣ ከጊዜ ፣ ብዛት ፣ ጠቈረ
[See also 'magic, mark']

**blackboard** ጥቁር ፣ ሰሌዳ
Write it on the blackboard! ጥቁሩ ፣ ሰሌዳ ፣ ላይ ፣ ጻፈው

**blacken** (vt.)
1. አጠቈረ. Soot blackens kettles. ጥላሸት ፣ ጆበናን ፣ ያጠቍራል
2. አጎደፈ. This article blackened the director's reputation. ይህ ፣ ጽሑፍ ፣ የዲሬክተሩን ፣ ዝና ፣ አጎደፈ

**blacken** (vi.) ጠቈረ
The sky blackened. ሰማዩ ፣ ጠቈረ

**(be) blacklisted** በቅጣት ፣ መዝገብ ፣ ተመዘገበ
This actor was blacklisted because of his political ideas. ይህ ፣ ተዋናይ ፣ ስለ ፣ ፖለቲካ ፣ አስተሳሰቡ ፣ በቅጣት ፣ መዝገብ ፣ ተመዘገበ

**blackmail** (v.)
*He used pictures to blackmail his boss. ያለቃውን ፣ መጥፎ ፣ ፎቶግራፍ ፣ ለሰው ፣ አሳያለሁ ፣ እያለ ፣ በማስፈራራት ፣ ገንዘብ ፣ ተቀበለ

**blackout** የከተማ ፣ መጨለም
The blackout lasted until the enemy airplanes left. የከተማው ፣ መጨለም ፣ የጠላት ፣ አውሮፕላኖች ፣ እስኪሄዱ ፣ ድረስ ፣ ቆየ

**blacksmith** ቀጥቃጭ
The blacksmith works with metal. ቀጥቃጭ ፣ ብረታ ፣ ብረት ፣ ይሠራል

**bladder** ፊኛ
Rattles are made of dried pig bladders and peas. የሚቅጨለጨል ፡ መጫወቻ ፡ ከደረቀ ፡ የ አሳማ ፡ ፊኛና ፡ ከባቄላ ፡ ይሠራል

**blade**
1. ስለት. I need a knife with two blades. ባለ ፡ ሁለት ፡ ስለት ፡ ቢላዋ ፡ እፈልጋለሁ
2. ምላጭ. These blades do not fit my razor. እነዚህ ፡ ምላጮች ፡ ለመላጫዬ ፡ አይሆኑም
3. ቅጠል. The wind waved the blades of grass. ነፋሱ ፡ የሣሩን ፡ ቅጠል ፡ አውለበለበው
[See also 'razor']

**blame** (v.)
1. ወቀሰ ፤ ነቀፈ. Under those circumstances, I could hardly blame her. በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ምንም ፡ ልወቅሳት ፡ (ልነቅፋት) ፡ አልችልም
2. አመካኘ. Bad workmen often blame their tools for their mistakes. መጥፎ ፡ ሠራተኞች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ስሕተታቸውን ፡ በመሣሪያቸው ፡ ያ መካኛሉ
3. ላከከ. He tried to save face by blaming the accident on me. አደጋውን ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ በመላ ከክ ፡ ራሱን ፡ ሊያወጣ ፡ ሞከረ
*He blamed us for the accident. ላደጋው ፡ መድ ረስ ፡ ጥፋተኛ ፡ አደረገን

**blame** (n.) ወቀሳ
The letter was full of blame. ደብዳቤው ፡ ወቀ ሳ ፡ የበዛበት ፡ ነበር

**put the blame on** ወቀሰ
Don't put the blame on me! እኔን ፡ አትውቀሰኝ

**share the blame** ተወቃሾች ፡ ናቸው
We must all share the blame for this deplorable condition. ለዚህ ፡ አስከፊ ፡ ሁኔታ ፡ ሁላችንም ፡ ተ ወቃሾች ፡ ነን

**take the blame** ተወቀሰ
He took the blame for their mistake. በነሱ ፡ ጥ ፋት ፡ እሱ ፡ ተወቀሰ

**blameless** እንከን ፡ የሌለበት
The teacher praised him for his blameless conduct. ጠባዩ ፡ እንከን ፡ ስለሌለበት ፡ መምህሩ ፡ አ መሰገነው

**bland**
1. ቅመም ፡ የሌለው. I do not like bland food. ቅመም ፡ የሌለው ፡ ምግብ ፡ አልወድም
2. ለስላሳ. His bland manner won him many friends. ለስላሳ ፡ ጠባዩ ፡ ብዙ ፡ ጓደኞች ፡ አፈራ ለት
3. ፈዛዛ. He is a bland young man who does not seem interested in anything. ምንም ፡ ነገር ፡ የማያስደስተው ፡ ፈዛዛ ፡ ልጅ ፡ ነው

**blandish** አባበለ
They blandished the guard into letting them through the gate. በሩን ፡ እንዲያሳልፋቸው ፡ ዘ በኛውን ፡ አባበሉት

**blank** (n.)
1. ፎርም. Would you help me to fill out this blank? ይህንን ፡ ፎርም ፡ መሙላት ፡ ትረዳኛለህ ?
2. ባዶ ፡ ቦታ. Fill in all the blanks. ባዶውን ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ሙላ
3. የውሸት ፡ ጥይት. The bullets that he fired were blanks. የተኰሳቸው ፡ የውሸት ፡ ጥይቶች ፡ ነበሩ
*My mind is a complete blank. ምንም ፡ ነገር ፡ አላስታውስም

**blank** (adj.) ባዶ
The envelope contained only a blank sheet of paper. ኤንቬሎፑ ፡ ባዶ ፡ ወረቀት ፡ ብቻ ፡ ይዟል
*There was a blank look on his face. ከፊቱ ፡ ም ንም ፡ ለመረዳት ፡ አይቻልም ፡ ነበር

**blanket**
1. ብርድ ፡ ልብስ. Take another blanket, and you won't be cold. ሌላ ፡ ብርድ ፡ ልብስ ፡ ብትጨ ምር ፡ አይበርድህም
2. ከምር. A blanket of snow covered the ground. የበረዶ ፡ ከምር ፡ መሬቱን ፡ ሸፈነው

**blare** (v.)
1. ጮክ ፡ ብሎ ፡ ነገረ. He blared his instructions at the workers. መምሪያውን ፡ ለሠራተኞቹ ፡ ጮ ክ ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው
2. አምባረቀ. The trumpet blared announcing the king's arrival. የንጉሡን ፡ መምጣት ፡ ለማ ብሰር ፡ ጥሩምባው ፡ አምባረቀ

**blare** (n.) ጩኸት
The blare of the radio made conversation impossible. የሬዲዮው ፡ ጩኸት ፡ ለመጨዋወት ፡ አላስቻለም

**blaspheme** ስም ፡ አጐደፈ ፤ ስም ፡ በከንቱ ፡ አነሣ
The drunken man blasphemed God. የሰከረው ፡ ሰውዬ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ አጐደፈ ፡ (በከ ንቱ ፡ አነሣ)

**blasphemy** የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በከንቱ ፡ ማን ሣት
Blasphemy is prohibited in some religions. የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በከንቱ ፡ ማንሣት ፡ ባንዳንድ ፡ ሃይማኖቶች ፡ የተከለከለ ፡ ነው

**blast** (vt.)

1. ፈንጂ ፡ በማፈንዳት ፡ አወጣ. They blasted a tunnel through the mountain. ፈንጂ ፡ በማፈን
ዳት ፡ በተራራው ፡ ውስጥ ፡ መተላለፊያ ፡ አወጡ
2. በኀይል ፡ ነፋ. He blasted his horn irritably at every car in his way. በብስጭት ፡ መንገዱ ፡ ላ
ይ ፡ ባጋጠሙት ፡ መኪናዎች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡
የመኪናውን ፡ ጥሩምባ ፡ በኀይል ፡ ነፋ
3. አጨናገፈ(በት). Failure in the exam blasted his hopes for college. በፈተና ፡ መውደቁ ፡ ኮሌጅ ፡
ለመግባት ፡ የነበረውን ፡ ተስፋ ፡ አጨናገፈበት
4. ድምጥማጡን ፡ አጠፋ. Heavy artillery blasted the enemy off the hill. ከባድ ፡ መድፍ ፡ ጠላቱ
ን ፡ ከተራራው ፡ ላይ ፡ ድምጥማጡን ፡ አጠፋው
5. ፈረካከሶ ፡ አስወገደ. They blasted the fallen rocks off the road with dynamite. የወደቁትን ፡
ቋጥኞች ፡ በድማሚት ፡ ፈረካክሰው ፡ ከመንገዱ ፡
ላይ ፡ አስወገዱ

**be blasting** በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ ነበረ
They turned down the microphone because his voice was blasting. ድምፁ ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡
ስለነበረ ፡ የድምፅ ፡ ማጉያውን ፡ ቀነሱት

**blast** (n.)

1. የፈንጂ ፡ ጩኸት ፤ የፈንጂ ፡ ድምፅ. You could hear the blast for miles. የፈንጂው ፡ ጩኸት ፡ ከ
ሩቅ ፡ ይሰማል
He was deafened by the blast. በፈንጂው ፡ ድ
ምፅ ፡ ደነቆረ
2. የፈንጂ ፡ ኀይል. The blast pushed out the window. የፈንጂው ፡ ኀይል ፡ መስኮቱን ፡ ነቅሎ ፡
አወጣው
*One blast of the siren was enough to clear the streets. ሳይረኑ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢጮህ ፡ መን
ገዱን ፡ ባዶ ፡ አስቀረው

**a blast of** (= adj.) በጣም ፡ የሚጋረፍ
When the window was opened, a blast of hot air entered the room. መስኮቱ ፡ ሲከፈት ፡ በ
ጣም ፡ የሚጋረፍ ፡ ሞቃት ፡ አየር ፡ ወደ ፡ ክፍሉ ፡
ውስጥ ፡ ገባ

**full blast** ሙሉ ፡ በሙሉ
The factory is going full blast. ፋብሪካው ፡ ሙ
ሉ ፡ በሙሉ ፡ ይሠራል

**blatant**

1. ለፍላፊ. The blatant children were quieted by the teacher. ለፍላፊዎቹን ፡ ልጆች ፡ አስተማ
ሪው ፡ ጸጥ ፡ አደረጋቸው
2. ጉልህ. The student made a blatant error in simple addition. ተማሪው ፡ በቀላል ፡ ድም
ር ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ስሕተት ፡ አደረገ

**blaze** (v.)

1. አበራ. Their faces blazed with joy. ፊታቸው ፡
በደስታ ፡ አበራ
2. ተንቀለቀለ. There was a fire blazing in the hearth. እሳቱ ፡ በምድጃው ፡ ውስጥ ፡ ይንቀለቀ
ል ፡ ነበር
3. አሸበረቀ. On Christmas eve, the big house blazed with lights. ለልደት ፡ ዋዜማ ፡ ትልቁ ፡
ቤት ፡ በመብራት ፡ አሸብርቆ ፡ ነበር

**blaze a trail** የጥበብ ፡ ፋና ፡ አፈለቀ
Pasteur blazed a trail which other researchers followed. ፓስተር ፡ ያፈለቀውን ፡ የጥበብ ፡ ፋ
ና ፡ ሌሎች ፡ ተመራማሪዎች ፡ ተከተሉት
*He blazed a trail through the forest. በ
ጫካ ፡ ውስጥ ፡ ያለፈበትን ፡ መንገድ ፡ ለማመልከ
ት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በየዛፉ ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡
ጭረት ፡ አደረገ

**blaze up** እሳት ፡ ለበሰ
He blazed up at the insult. ስለተሰደበ ፡ እሳት ፡
ለበሰ

**blaze** (n.)

1. ቃጠሎ. It took the firemen two hours to put out the blaze. ቃጠሎውን ፡ ለማጥፋት ፡ የእ
ሳት ፡ አደጋው ፡ ሠራተኞች ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ፈጀ
ባቸው
2. የሚነድ ፡ እሳት. We could see the blaze across the beach. ከጠረፉ ፡ ማዶ ፡ የሚነድ ፡ እሳት ፡
ይታየን ፡ ነበር
3. ምልክት. The hunter made a blaze on the tree with his knife. አዳኙ ፡ ዛፉ ፡ ላይ ፡ በሰን
ጢው ፡ ምልክት ፡ አደረገ

**make a blaze of color** ድምቀት ፡ ሰጠ
The flowers made a blaze of color in our garden. አበቦቹ ፡ ላትክልት ፡ ቦታችን ፡ ድምቀ
ት ፡ ሰጡ

**blazing** ጠራራ
We had to stand for half an hour in the blazing sun. ጠራራው ፡ ፀሐይ ፡ ላይ ፡ ግማሽ ፡ ሰዓት ፡ መ
ቆም ፡ ግድ ፡ ሆነብን

**blazon** ነዛ
Big posters blazoned the wonders of the coming circus. ትልልቅ ፡ ሥዕላዊ ፡ መግለጫዎ
ች ፡ የመጪውን ፡ ሰርከስ ፡ አስደናቂነት ፡ ነዙት

**bleach** [ፀሐይ ፡ ላይ ፡ በማድረግ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡
ኬሚካል ፡ በመጨመር ፡ ማንጣት]

**bleak**

1. ቀፋፊ. I did not go out because of the bleak

weather. ቀኑ ፡ ቀፋፊ ፡ ስለነበረ ፡ ከቤትም ፡ አልወጣሁ

2. ገላጣ. The rocky peaks of high mountains are bleak. ድንጋያማ ፡ የሆኑት ፡ የከፍተኛ ፡ ተራራዎች ፡ ጫፎች ፡ ገላጣ ፡ ናቸው

3. ብዙ ፡ የሚያስደስት ፡ አልነበረም. Life was bleak for unmarried women in those days. በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ላላገቡ ፡ ሴቶች ፡ ኑሮ ፡ ብዙ ፡ የሚያስደስት ፡ አልነበረም

**(be) bleary** ፈዘዘ
His eyes were bleary from lack of sleep. ከእንቅልፍ ፡ እጦት ፡ የተነሣ ፡ ዓይኖቹ ፡ ፈዘዋል

**bleat** ባ ፡ አለ
The sheep bleated piteously. በጎቹ ፡ በሚያሳዝን ፡ ሁኔታ ፡ ባ ፡ አሉ

**bled,** see **bleed**

**bleed** (bled), vt. አገመ
In earlier times, doctors bled people to make them feel well. በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ሐኪሞች ፡ ሰዎች ፡ እንዲሻላቸው ፡ በማለት ፡ ያግሟቸው ፡ ነበር

**bleed** (vi.)
1. ደማ. If you cut your finger, it will bleed. ጣትህን ፡ ብትቈርጥ ፡ ይደማል
2. ደም ፡ አፈሰሰ. They fought and bled for freedom. ለነጻነት ፡ በመዋጋት ፡ ደማቸውን ፡ አፈሰሱ
*My heart bleeds for him. ከልቤ ፡ አዝንለታለሁ

**(one's) nose is bleeding** ነሰረ(ው)
Since my nose is bleeding, I don't want to sit in the sun. ስለሚነስረኝ ፡ ፀሐይ ፡ ላይ ፡ መቀመጥ ፡ አልፈልግም

**blemish** (v.) አጐደፈ
His association with the embezzler blemished his reputation. ከአደራ ፡ በሊታ ፡ ጋር ፡ መዋሉ ፡ ዝናውን ፡ አጐደፈው

**be blemished**
*The book is blemished by those long descriptions. መጽሐፉን ፡ የተንዛዙት ፡ ማብራሪያዎች ፡ አበላሽተውታል

**blemish** (n.)
1. ጉድለት. This manuscript has too many blemishes to be worth anything. ይህ ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ ብዙ ፡ ጉድለቶች ፡ ስላሉበት ፡ ዋጋ ፡ የለውም
2. እንከን. His reputation is without blemish. ዝናው ፡ እንከን ፡ አይገኝበትም

**blend** (vt.) ቀየጠ
The grocer blends Ethiopian coffee with another kind of coffee. የምግብ ፡ ሸቀጥ ፡ ነጋዴው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቡና ፡ ከሌላ ፡ ዓይነት ፡ ቡና ፡ ጋር ፡ ይቀይጣል

**blend** (vi.) ኅብር ፡ ሰጠ
These colors don't blend. እነዚህ ፡ ቀለሞች ፡ ኅብር ፡ አይሰጡም

**blend together**
1. ቀላቀለ. The painter blended two kinds of color together. ሠዓሊው ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ቀለሞች ፡ ቀላቀለ
2. አዋሕዶ ፡ ያዘ. The rainbow blended two kinds of color together. ቀስተ ፡ ደመና ፡ ሁለት ፡ ቀለሞች ፡ አዋሕዶ ፡ ይዟል

**blend** (n.) ቅይጥ
Harari music is a blend of Ethiopian and Arab music. የሐረር ፡ ዘፈን ፡ የኢትዮጵያና ፡ የዐረብ ፡ ሙዚቃ ፡ ቅይጥ ፡ ነው

**bless**
1. ባረከ. The priest blessed the people. ቄሱ ፡ ሕዝቡን ፡ ባረኩ
2. መረቀ. The father blessed his son before he went to America. ልጁ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ አባትዬው ፡ መረቀው
3. አመሰገነ. We bless Thy holy name. የተቀደሰ ፡ ስምህን ፡ እናመሰግናለን
4. ዐደለ. Fortune blessed him with a good disposition. ዕድል ፡ ከመልካም ፡ ጠባይ ፡ ጋር ፡ ዐድሎታል
*May you always be blessed with good health! ጥሩ ፡ ጤንነትን ፡ ይስጥህ

**blessed** (adj.)
1. ቅዱስ (fem. ቅድስት). Pray to the Blessed Virgin for success! እንዲቀናህ ፡ ለቅድስት ፡ ማርያም ፡ ጸልይ
2. የተባረከ. Mary is blessed among women. ማርያም ፡ ከሴቶች ፡ የተባረከች ፡ ናት

**blessing**
1. ቡራኬ. The priest's blessing was said in Geez. ቄሱ ፡ ቡራኬ ፡ የሰጡት ፡ በግዕዝ ፡ ነበር
2. መታደል. It was really a blessing that she came. የሷ ፡ መምጣት ፡ በእውነት ፡ መታደል ፡ ነው
*You have my blessing. ይባርክህ

**cast blessings** ባረከ
The priest cast blessings upon the sick persons. ቄሱ ፡ የታመሙትን ፡ ሰዎች ፡ ባረኩ

**give blessing** መረቀ
The elders give their blessings to the children. ሽማግሌዎች ፡ ልጆችን ፡ ይመርቃሉ

**say the blessing** ምስጋና ፡ አቀረበ
He said the blessing before he ate supper. እራቱን ፡ ከመብላቱ ፡ በፊት ፡ ምስጋና ፡ አቀ ረበ

**blew,** see **blow**

**blight** መቅሠፍት
War is the blight of mankind. ጦርነት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መቅሠፍት ፡ ነው

**blind** (vt.)
1. አሳወረ. The disease blinded him. በሽታው ፡ አሳወረው
2. አጥበረበረ. The sun is blinding me. ፀሐዩ ፡ አጥበረበረኝ
3. ዓይኑን ፡ ከለለው. A bright light blinded him for a moment. ብሩህ ፡ ብርሃን ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዓይኑን ፡ ከለለው
4. ራሱን ፡ አሳተው. Anger blinded him. ንዴት ፡ ራሱን ፡ አሳተው

**blind** (n.) መጋረጃ
Close the blinds because the sun's rays are too hot. የፀሐይዋ ፡ ጨረር ፡ በጣም ፡ ስለሚሞቅ ፡ መጋረጃውን ፡ ዝጋው

**blind** (adj.)
1. ዓይነ ፡ ስውር ፤ ዕውር. This man is blind; help him cross the street! ሰውዬው ፡ ዓይነ ፡ ስ ውር ፡ (ዕውር) ፡ ስለሆነ ፡ መንገዱን ፡ አሻግረው
2. የማይታይ. A blind curve on a highway is dangerous. በመንገድ ፡ ላይ ፡ የማይታይ ፡ መጠም ዘዝ ፡ አደገኛ ፡ ነው
3. (= adv.) በጭፍን. She has blind faith in his talent. የሱን ፡ ችሎታ ፡ በጭፍን ፡ ታምናለች

**blind man** ዓይነ ፡ ስውር
We helped the blind man across the street. ዓይነ ፡ ስውሩን ፡ መንገድ ፡ አሻገርነው

**be blind** ዓይን ፡ የለውም
Love is blind. ፍቅር ፡ ዓይን ፡ የለውም

**be blind in one eye** አንድ ፡ ዓይና ፡ ሆነ
He is blind in one eye, and cannot drive in heavy traffic. አንድ ፡ ዓይና ፡ ስለሆነ ፡ ትራፊክ ፡ በሚበዛበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ሊነዳ ፡ አይችልም

**be blind to**
*Mothers are sometimes blind to their children's faults. እናቶች ፡ አንዳንዶ ፡ የልጆቻቸው ፡ ጥፋት ፡ አይታያቸውም

**become blind** ታወረ
In his old age, he became blind. በስተርጅናው ፡ ታወረ

**go blind** ታወረ
I hope he is not going blind. እንደማይታወር ፡ ተስፋ ፡ አለኝ

**blind alley** መውጫ ፡ የሌለው ፡ ቀጭን ፡ መንገድ
He was trapped by thieves in a blind alley. መውጫ ፡ እሌለው ፡ ቀጭን ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ሌ ቦች ፡ ያዙት

**blindfold** ዓይን ፡ ሸፈነ
The robbers blindfolded the storekeeper. ዘራፊዎቹ ፡ ባለ ፡ ሱቁን ፡ ዓይኑን ፡ ሸፈኑት

**blindly** ዓይኑን ፡ ጨፍኖ
The younger child follows his brother blindly. ትንሹ ፡ ልጅ ፡ ዓይኑን ፡ ጨፍኖ ፡ ታላቁን ፡ ይከተ ተላል

**blindness** ዕውርነት
Do not make any reference to his blindness! ስለ ፡ ዕውርነቱ ፡ ምንም ፡ አታንሣ

**blink**
1. አርገበገበ. Blinking one's eyes when someone threatens to hit you in the face is a reflex action. አንድ ፡ ሰው ፡ ሊመታህ ፡ ሲቃጣ ፡ ዓይን ን ፡ ማርገብገብ ፡ ያለ ፡ ባለቤቱ ፡ ቁጥጥር ፡ የሚደረ ግ ፡ ነው
2. ብልጭ ፡ ድርግም ፡ አደረገ. He blinked his flashlight to signal he was ready. መዘጋጀቱን ፡ ለማሳወቅ ፡ ባትሪውን ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ አ ደረገ

**bliss** ተድላና ፡ ደስታ
After they got married, they lived in bliss. ከተጋቡ ፡ በኋላ ፡ በተድላና ፡ በደስታ ፡ ኖሩ

**blissful** አስደሳች
He announced the blissful event of his child's birth. የልጁን ፡ መወለድ ፡ አስደሳች ፡ ዜና ፡ አስ ታወቀ

**blister**
*The blister on his foot hurt him. ውኃ ፡ የቋጠ ረው ፡ እግሩ ፡ አመመው

**have a blister**
*He has a blister on his foot. እግሩ ፡ ውኃ ፡ ቋጠረ

**blithe, ~ heart** ፍልቅልቅነት
Everyone loved her for her blithe heart. በፍልቅልቅነቷ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደዳት

**blizzard** [ነፋስ ፡ የተቀላቀለበት ፡ በጣም ፡ ከፍ ተኛ ፡ ቅዝቃዜና ፡ ኀይለኛነት ፡ ያለው ፡ በረዶ]

**bloat** ነፋ
Badly cooked food bloated his stomach. በደንብ ፡ ያልበሰለው ፡ ምግብ ፡ ሆዱን ፡ ነፋው

**block** (v.)
1. ዘጋ. When I tried to get by him, he blocked my path. ባጠገቡ ፡ ለማለፍ ፡ ስሞክር ፡ መንገዱን ፡ ዘጋብኝ
2. አገደ(ታገደ). Their forward march was blocked by a river. የነርሱ ፡ ግስጋሴ ፡ ባንድ ፡ ወንዝ ፡ ታግዶ ፡ ነበር
3. ደፈነ(ተደፈነ). The irrigation canal was blocked with mud. የመስኖው ፡ ቦይ ፡ በጭቃ ፡ ተደፍኖ ፡ ነበር
4. ከለለ. A large pillar blocked my view of the stage. አንድ ፡ ትልቅ ፡ ዓምድ ፡ መድረኩን ፡ እንዳላይ ፡ ከለለኝ

**block** (n.)
1. ግንድ. The butcher cut up his meat on a large block of wood. ሥጋ ፡ ሻጩ ፡ ሥጋውን ፡ በትልቅ ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ቈራረጠው
2. ግእዘን. What do you plan to do with those blocks of wood? የዕንጨት ፡ ግእዘኖቹን ፡ ምን ፡ ታደርግባቸዋለህ ?
3. [አራት ፡ መንገዶች ፡ የሚያካልሉት ፡ የከተማ ፡ ክፍል]
*The block in the pipe was caused by someone stuffing it with cotton. ቧምቧው ፡ የተደፈነው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ጥጥ ፡ ስለወተፈው ፡ ነው

**block of stone** ጥርብ ፡ ድንጋይ
The pyramids were made of blocks of stone. ፒራሚዶች ፡ የተሠሩት ፡ ከጥርብ ፡ ድንጋይ ፡ ነው

**blockade** (= to block) መዝጋት
A complete blockade of this harbor would require many ships. ይህንን ፡ ወደብ ፡ በፍጹም ፡ ለመዝጋት ፡ ብዙ ፡ መርከቦች ፡ ያስፈልጋሉ

**declare a blockade** የበሮች ፡ መዘጋት ፡ አስታወቀ
The Egyptians declared a blockade of Israel. ግብጻውያን ፡ የእስራኤልን ፡ በሮች ፡ መዘጋታቸውን ፡ አስታወቁ (or ግብጻውያን ፡ የእስራኤል ፡ መርከቦች ፡ በወደቦቻቸው ፡ እንዳያልፉ ፡ ከለከሉ)

**blond** ነጣ ፡ ያለ
She has blond hair. ነጣ ፡ ያለ ፡ ጸጉር ፡ አላት

**blood**
1. ደም. There was much blood shed in the riot. በረብሻው ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ የደም ፡ መፋሰስ ፡ ነበረ
2. ዘር. They are of the same blood. ዘራቸው ፡ አንድ ፡ ነው
Love of the sea runs in his blood. ባሕርን ፡ መውደድ ፡ ከዘሩ ፡ ነው
*Blood is thicker than water. ከባዕድ ፡ ዘመድ ፡ ይሻላል

**blood pressure** የደም ፡ ኀይል
His blood pressure is low. የደሙ ፡ ኀይል ፡ ተቀንሷል
*My blood pressure is high. የደም ፡ ብዛት ፡ አለብኝ

**draw blood** አደማ
He struck at me with a knife and drew blood. በቢላዋ ፡ ወግቶ ፡ አደማኝ

**in cold blood** በግፍ ፤ በጭካኔ
They were murdered in cold blood. በግፍ ፡ (በጭካኔ) ፡ ተገደሉ

**give one's blood** ደሙን ፡ አፈሰሰ
The soldiers gave their blood for their country. ወታደሮቹ ፡ ደማቸውን ፡ ላገራቸው ፡ አፈሰሱ
[See also 'bad blood, clot, cold, flesh, stream, sweat']

**blood bath** የደም ፡ መፋሰስ
The blood bath that followed the French Revolution was terrible. ከፈረንሳይ ፡ መሠረታዊ ፡ ለውጥ ፡ በኋላ ፡ የተደረገው ፡ ደም ፡ መፋሰስ ፡ አሰቃቂ ፡ ነበር

**bloodless** ደም ፡ ያልፈሰሰበት
This was a bloodless victory. ደም ፡ ያልፈሰሰበት ፡ ድል ፡ ነበር

**bloodless cheeks** የፊት ፡ መገርጣት
To judge from her bloodless cheeks, she must be sick. ከፊቷ ፡ መገርጣት ፡ እንደሚታየው ፡ ሳትታመም ፡ አትቀርም

**blood money** የደም ፡ ዋጋ ፤ ጉማ
He refused to accept the blood money. የደም ፡ ዋጋ ፡ (ጉማ) ፡ አልቀበልም ፡ አለ

**blood relative** የሥጋ ፡ ዘመድ
Only blood relatives were invited to the wedding. ሰርግ ፡ የተጠሩት ፡ የሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**bloodshed** የደም ፡ መፋሰስ
The riot resulted in bloodshed. ብጥብጡ ፡ የደም ፡ መፋሰስን ፡ አስከተለ

**bloodstream** የደም ፡ ሥር
The doctor injected the medicine into the bloodstream. ሐኪሙ ፡ በደም ፡ ሥሩ ፡ መርፌ ፡ ወጋው

**bloodthirsty** ደም ፡ የተጠማ
A bunch of bloodthirsty bandits captured them. ደም ፡ የተጠማ ፡ የሽፍቶች ፡ ጓድ ፡ ያዛቸው

**blood vessel** የደም ፡ ሥር
He cut a blood vessel in his arm. የክንዱን ፡ የደም ፡ ሥር ፡ ቈረጠው

**bloody**
1. ደም ፡ የተነከረ. He denied killing the man, even though the bloody knife was still in his hand. ደም ፡ የተነከረ ፡ ጩቤ ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ቢታይም ፡ ሰውዬውን ፡ መግደሉን ፡ ካደ
2. ደም ፡ የሚያፋስስ. The shooting triggered a bloody riot. ተኵሱ ፡ ደም ፡ የሚያፋስስ ፡ ብጥብጥ ፡ አስነሣ
3. በደም ፡ የተበከለ. The bloody corpses made me shudder. በደም ፡ የተበከሉትን ፡ ሬሳዎች ፡ ማየት ፡ ዘገነነኝ

**be bloody** በደም ፡ ተበከለ
His handkerchief was all bloody. መሐረቡ ፡ በደም ፡ ተበክሎ ፡ ነበር

**bloom** (v.)
1. አበበ. The roses bloomed all summer. ጽጌረዳዎቹ ፡ በጋውን ፡ ሙሉ ፡ እንዳበቡ ፡ ነበሩ
2. አማረ(በት). The children bloomed at camp this summer. ልጆቹ ፡ በዚህ ፡ በጋ ፡ በነበሩበት ፡ የመዝነኛ ፡ ቦታ ፡ አማረባቸው

**bloom** (n.) እምቡጥ
The rose has a bloom that can easily be damaged. ጽጌረዳ ፡ በቀላሉ ፡ ሊጐዳ ፡ የሚችል ፡ እምቡጥ ፡ አለው

**bloom of youth** የአበብነት ፡ ጊዜ
She was in the bloom of youth. በአበብነት ፡ ጊዜዋ ፡ ነበረች

**be in full bloom** ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ አበበ
The apple trees are in full bloom. የቱፋው ፡ ዛፎች ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ አብበዋል

**blossom** (v.)
1. አበበ. The trees in our garden are about to blossom. ባትክልት ፡ ቦታችን ፡ ያሉት ፡ ዛፎች ፡ ሊያብቡ ፡ ነው
2. ፈካ. These yellow flowers blossom on the slope of the mountain. እነዚህ ፡ ቢጫ ፡ አበባዎች ፡ ከተራራው ፡ ቁልቁለት ፡ ላይ ፡ ይፈካሉ

**blossom** (n.) አበባ
The blossoms are falling off the tree. አበቦቹ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ እየረገፉ ፡ ናቸው

**blot** (v.)
1. አመጠጠ. Blot the signature before you fold the letter. ደብዳቤውን ፡ ከማጠፍህ ፡ በፊት ፡ ፊርማውን ፡ አምጥጠው
2. ቀለም ፡ አነጠበ. His pen slipped and blotted the paper in two places. ብዕሩ ፡ አምልጦት ፡ ወረቀቱን ፡ ሁለት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ቀለም ፡ አነጠበበት

**blot out** ጋረደ
Clouds blotted out the moonlight. የጨረቃዋን ፡ ብርሃን ፡ ደመና ፡ ጋረደው

**be blotted out** ጠፋ
Many words in this letter have been blotted out. ከዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ቃላት ፡ ጠፍተዋል

**blot up** አመጠጠ
Take a blotter and blot up the ink! ቀለሙን ፡ በቀለም ፡ ማምጠጫ ፡ አምጠው

**blot** (n.) ጥፋት
She has been haunted by a blot on her past. የድሮ ፡ ጥፋቷ ፡ ጸጸቱ ፡ ያሠቃያታል
*The page is full of blots. ገጹ ፡ ብዙ ፡ ቀለም ፡ ተንጠባጥቦበታል

**blotter** የቀለም ፡ ማምጠጫ
Take a blotter, and blot up the ink! ቀለሙን ፡ በቀለም ፡ ማምጠጫ ፡ አምጠው

**blotting paper** ማምጠጫ ፡ ወረቀት
Blotting paper takes up ink. ማምጠጫ ፡ ወረቀት ፡ ቀለም ፡ ይመጣል

**blouse** ሸሚዝ
Do you need any elastic for the blouse? ለሸሚዝሽ ፡ ላስቲክ ፡ ትፈልጊያለሽ ?

**blow** (blew, blown), vt.
1. ነፋ. The herald angel blew his horn three times. አብሳሪው ፡ መልአክ ፡ መለከቱን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ነፋ
The police blew his whistle three times. ፖሊሱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ፊሽካውን ፡ ነፋ
2. አሰማ. The driver blew his horn three times. ነጂው ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ጥሩምባውን ፡ አሰማ
3. አራገፈ. Blow the dust off the books! አቧራውን ፡ ከመጽሐፉ ፡ ላይ ፡ አራግፍ

**blow** (vi.)
1. ነፈሰ. A strong wind was blowing. ብርቱ ፡ ነፋስ ፡ ይነፍስ ፡ ነበር
2. ጮኸ. The siren blew just as we reached the hospital. ልክ ፡ ሆስፒታል ፡ ስንደርስ ፡ ሳይረን ፡ ጮኸ
3. በነነ(በት). The dust blew into my face

through the open window. በክፍቱ ፡ መስኮት ፡ በኩል ፡ አቧራ ፡ ፊቴ ፡ ላይ ፡ በነነብኝ
4. ተቃጠለ. A fuse blew as we sat down to dinner. ልክ ፡ ለእራት ፡ ቁጭ ፡ ስንል ፡ ባልበላው ፡ ተቃጠለ
5. ገባ. The dust blew into the house. አቧራው ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገባ

**blow away**
*The paper blew away. ወረቀቱን ፡ ነፋስ ፡ ወሰደው

**blow down** ገነጣጠለ ፤ ገነዳደሰ
The storm blew the trees down. ነፋስ ፡ ዛፎቹን ፡ ገነጣጠላቸው ፡ (ገነዳደሳቸው)

**blow in** ነፈሰ
The house was half-buried by the dust that had blown in from the desert. ቤቱ ፡ ከበረኻው ፡ በነፈሰው ፡ አቧራ ፡ በከፊል ፡ ተቀብሮ ፡ ነበር

**blow off** (vt.)
1. ከራሱ ፡ ላይ ፡ ወሰደ. The wind blew off my hat. ነፋሱ ፡ ባርኔጣዬን ፡ ከራሴ ፡ ላይ ፡ ወሰደው
2. በታተነ. The hand grenade blew off his head. የእጅ ፡ ቦምብ ፡ ጭንቅላቱን ፡ በታተነው
3. ገነጣጠለ. The gale blew off the roofs of some of the huts. ዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ያንዳንድ ፡ ቤቶችን ፡ ጣሪያ ፡ ገነጣጠላ

**blow off** (vi.) ነፋስ ፡ ወሰደበት
+My hat suddenly blew off. ባርኔጣዬን ፡ ነፋስ ፡ በድንገት ፡ ወሰደብኝ

**blow on**
1. ተነፈሰ(በት). Blow on your hands to warm them! እጆችህን ፡ ለማሞቅ ፡ ተንፍስባቸው
2. እፍ ፡ እፍ ፡ አለ. The child blew on the hot soup. ልጁ ፡ ትኩሱን ፡ ሾርባ ፡ እፍ ፡ እፍ ፡ አለው

**blow open** (vt.)
1. በፈንጂ ፡ ከፈተ. The thief blew open the safe. ሌባው ፡ ካዝናውን ፡ በፈንጂ ፡ ከፈተው
2. በረገደ. The wind blew the door open. በሩን ፡ ነፋስ ፡ በረገደው

**blow open** (vi.) ተበረገደ
The door blew open and scared me. በሩ ፡ ተበርግዶ ፡ አስደነገጠኝ

**blow out** (vt.) አጠፋ
The wind blew the candle out. ነፋሱ ፡ ሻማውን ፡ አጠፋው

**blow out** (vi.)
1. ጠፋ. The light blew out. መብራቱ ፡ ጠፋ
2. ፈነዳ. The old tire blew out. አሮጌው ፡ ጎማ ፡ ፈነዳ
3. ተቃጠለ. The fuse blew out. ባልበላው ፡ ተቃጠለ

**blow (itself) out** እያደር ፡ በረደ
The storm has blown itself out. ኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ እያደር ፡ በረደ

**blow over** አለፈ
The storm will blow over soon. ማዕበሉ ፡ ቶሎ ፡ ያልፋል

**blow to bits** ብትንትኑን ፡ አወጣ
A mine blew the ship to bits. ድማሚት ፡ መርከቡን ፡ ብትንትኑን ፡ አወጣው

**blow up** (vt.)
1. በደማሚት ፡ አፈራረሰ ፤ በፈንጂ ፡ አፈራረሰ ፤ አፈነዳ. The enemy has blown up all bridges. ጠላት ፡ ድልድዮችን ፡ ሁሉ ፡ በደማሚት ፡ አፈራረሳቸው ፡ (በፈንጂ ፡ አፈራረሳቸው, or አፈነዳቸው)
2. አጠፋ. The charge is enough to blow us all up. ፈንጂው ፡ ሁላችንንም ፡ ለማጥፋት ፡ በቂ ፡ ኀይል ፡ አለው
3. ነፋ. Blow up my tires, please. ጎማዎቼን ፡ ንፋልኝ

**blow up** (vi.)
1. ፈነዳ. The powder plant blew up. የባሩዱ ፡ ፋብሪካ ፡ ፈነዳ
2. በንዴት ፡ ጦፈ. When he heard he had not been promoted, he blew up. የደረጃ ፡ እድገት ፡ አለማግኘቱን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በንዴት ፡ ጦፈ
[See also 'horn, nose, wind']

**blow** (n.)
1. ምት. The power of his blow split the wooden door. የምቱ ፡ ኀይል ፡ የዕንጨቱን ፡ መዝጊያ ፡ ሰነጣጠቀው
2. ቡጢ. The boxer was laid prostrate by the blow. ቡጢኛው ፡ በቡጢ ፡ ተዘረረ
3. ጉዳት. His losing his car was a hard blow. መኪናውን ፡ ማጣቱ ፡ ትልቅ ፡ ጉዳት ፡ ነበር

**at one blow** ባንድ ፡ ጊዜ
The entire province fell to the enemy at one blow. መላው ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ወደቀ

**come to blows** ተደባደበ
The enemies came to blows. ጥለኞቹ ፡ ተደባደቡ

**deal a (hard) blow**
1. አወለቀ. He dealt me a hard blow on the chin. አገጩን ፡ አወለቀኝ
2. አናጋ. The President's death dealt the country's politics a blow. የፕሬዚዳንቱ ፡ ሞት ፡ የሀገሪቱን ፡ ፖለቲካ ፡ አናጋው

**exchange blows** ተደባደበ
They almost came to the point of exchanging blows. ሊደባደቡ ፡ ምንም ፡ አልቀራቸውም ፡ ነበር

**(begin to) exchange blows** ዱላ ፡ ጀመሩ
The two men argued and began to exchange blows. ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ ተጨቃጭቀው ፡ ዱላ ፡ ጀመሩ

**get a blow** ተመታ
He got a blow on the head. ራሱ ፡ ላይ ፡ ተመታ

**launch a blow** ቡጢ ፡ ሰነዘረ(በት)
He launched a blow at my chin. በአገጬ ፡ ላይ ፡ ቡጢ ፡ ሰነዘረብኝ

**lay on heavy blows** ደበደበ
He laid on heavy blows with a short club. በቆመጥ ፡ ደበደበው

**lead to blows** ከዱላ ፡ አደረሰ
The altercation between the two drivers led to blows. የሁለት ፡ መኪና ፡ ነጂዎች ፡ ንትርክ ፡ ከዱላ ፡ አደረሳቸው

**strike a blow** አደጋ ፡ ጣለ
Our army struck a swift blow at the enemy. ጦራችን ፡ በጠላት ፡ ላይ ፡ ድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ ጣለ

**(without) striking a blow** ያለ ፡ አንዳች ፡ ተቃውሞ
The fortress was taken without striking a blow. ምሽጉ ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ተቃውሞ ፡ ተያዘ

**suffer a blow** ፈረሰ
The solidity of their friendship suffered a blow. የጠበቀ ፡ ወዳጅነታቸው ፡ ፈረሰ
[See also 'vital']

**blowout, have a ~** ጎማ ፡ ፈነዳበት
We had a blowout on the way home. ወደ ፡ ቤት ፡ ስንሄድ ፡ ጎማ ፡ ፈነዳብን

**blowup** የጋለ ፡ ጭቅጭቅ
The blowup caused angry feelings among the members of the committee. የጋለው ፡ ጭቅጭቅ ፡ በደርጉ ፡ አባሎች ፡ መካከል ፡ ቅሬታን ፡ ፈጠረ

**blubber** (v.) ተነፋረቀ
Stop blubbering and tell me what's wrong! መነፋረቁን ፡ ትተህ ፡ ምን ፡ እንደሆንክ ፡ ንገረኝ

**blue**
1. ሰማያዊ. The cat has beautiful blue eyes. ድመቲቷ ፡ ሰማያዊ ፡ የሆኑ ፡ ቆንጆ ፡ ዓይኖች ፡ አሏት
2. የተከዘ. He was lonely and blue. ብቸኛና ፡ የተከዘ ፡ ነበር

**out of the blue**
*He arrived out of the blue. ከዚህ ፡ መጣ ፡ ሳይባል ፡ ከች ፡ አለ
[See also 'moon']

**blueprint** ንድፍ
The blueprint of the building was drawn up by an engineer. የሕንጻው ፡ ንድፍ ፡ የተሠራው ፡ በመሀንዲስ ፡ ነበር

**bluff** (v.)
1. አታለለ. He bluffed the guard into admitting him. ዘበኛውን ፡ አታሎ ፡ እንዲያስገባው ፡ አደረገ
2. አሞኘ. The guerrillas bluffed the enemy into thinking they were being attacked by a huge army. አጋሚዶዎቹ ፡ ጠላታቸውን ፡ በትልቅ ፡ ጦር ፡ የተጠቃ ፡ በማስመሰል ፡ አሞኙት

**bluff** (n.) ቀጥ ፡ ያለ ፡ ገደል
Caves are seen in the face of the bluff. ቀጥ ፡ ባለው ፡ ገደል ፡ ላይ ፡ ዋሻዎች ፡ ይታያሉ

**bluff, is only a ~** እንዲያው ፡ ለአፉ ፡ ነው
His threat to fire you is only a bluff. ከሥራ ፡ ሊያስወጣህ ፡ የዛተብህ ፡ እንዲያው ፡ ለአፉ ፡ ነው

**be all a bluff** የፈጠረው ፡ ወሬ ፡ ነው
Her story was all a bluff to get money from us. የነገረችን ፡ ታሪክ ፡ ከኛ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ስትል ፡ የፈጠረችው ፡ ወሬ ፡ ነው

**blunder** (v.) ተሳሳተ
She blundered and failed to write down the names of all the people. ተሳስታ ፡ የሰዎቹን ፡ ስም ፡ በሙሉ ፡ ሳትጽፍ ፡ ቀረች

**blunder into** በስሕተት ፡ ገባ
Without my glasses, I blundered into the wrong room. መነጽሬን ፡ ሳላደርግ ፡ ቀርቼ ፡ በስሕተት ፡ ሌላ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ገባሁ

**blunder** (n.) ከፍተኛ ፡ ስሕተት ፤ ስሕተት
The German attack on Russia is considered a blunder. የጀርመን ፡ መስኮብን ፡ መውጋት ፡ እንደ ፡ ከፍተኛ ፡ ስሕተት ፡ ይቈጠራል
I made an awful blunder when I spoke to the minister thinking that he was a secretary. ጸሓፊ ፡ መስሎኝ ፡ ከሚኒስትሩ ፡ ጋር ፡ ስነጋገር ፡ ትልቅ ፡ ስሕተት ፡ አደረግሁ

**blunt**
1. ደነዝ. This knife is blunt. ይህ ፡ ቢላዋ ፡ ደነዝ ፡ ነው
2. ዱልዱም. The pencil is blunt; please sharpen it! እርሳሱ ፡ ዱልዱም ፡ ስለሆነ ፡ ቅረጸው
3. ፍርጥ ፡ ያለ. He thinks blunt speech proves he is honest. ፍርጥ ፡ ያለው ፡ አነጋገሩ ፡ ታማኝ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ መስሎታል

**become (be) blunt**
1. ደነዘ. The ax became blunt from cutting

too much wood. ብዙ ፡ ዕንጨት ፡ ስለተቈረጠበት ፡ መጥረቢያው ፡ ደነዘ
2. ዶለዶመ. The spear is blunt because it struck a stone. ጦሩ ፡ ድንጋይ ፡ ስለወጋ ፡ ዶልዱሟል

**bluntly** ፍርጥ ፡ አድርጎ
He told me the truth very bluntly. እውነቱን ፡ ፍርጥ ፡ አድርጎ ፡ ነገረኝ

**blur** (blurred)
1. ከለለ. Mist blurred the hill. ጭጋግ ፡ ኮረብታውን ፡ ከለለው
2. አደበዘዘ. He blurred the page in two places. ገጹን ፡ ሁለት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ አደበዘዘው

**blurred** (adj.) ደብዛዛ
The print was blurred. ሕትመቱ ፡ ደብዛዛ ፡ ነበር
**be blurred** (= tr.) አቀረረ
+Her eyes were blurred with tears. ዓይኗ ፡ እንባ ፡ አቅርሮ ፡ ነበር

**blurt out** ዘከዘከ
He rushed in and blurted out the news. ሮጦ ፡ ገብቶ ፡ ወሬውን ፡ ዘከዘከ

**blush** (v.) አፈረ ፤ ፊቱ ፡ ፍም ፡ መሰለ
She blushes easily when she is in company. ከሰው ፡ ጋር ፡ ስትሆን ፡ ቶሎ ፡ ታፍራለች
She blushed with shame. በእፍረት ፡ ፊቷ ፡ ፍም ፡ መሰለ

**blush** (n.), **at first ~** መጀመሪያ ፡ ሲታይ
At first blush, the plan appeared very simple. መጀመሪያ ፡ ሲታይ ፡ እቅዱ ፡ ቀላል ፡ ይመስል ፡ ነበር

**bluster** ደነፋ
When the police arrested him, the motorist began to bluster. ፖሊሶች ፡ ሲይዙት ፡ መኪና ፡ ነጂው ፡ መደንፋት ፡ ጀመረ

**boar, wild ~** ከርከሮ
They went hunting wild boar in the mountains. ከርከሮ ፡ ሊያድኑ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጡ

**board** (vt.) ተሳፈረ
We boarded the train in Washington. ባቡር ፡ የተሳፈርነው ፡ ዋሽንግተን ፡ ነው
**board** (vi.) ተዳብሎ ፡ ኖረ
She is boarding with us. ከኛ ፡ ጋር ፡ ተዳብላ ፡ ትኖራለች
**board up** ዕንጨት ፡ አደረገበት
Did you board up the window? መስኮቱ ፡ ላይ ፡ ዕንጨት ፡ አደረግህበት ?

**board** (n.)
1. ሳንቃ. The boards of the floor were cracked with age. የወለሉ ፡ ሳንቃዎች ፡ ከማርጀታቸው ፡ የተነሣ ፡ ተሰነጣጥቀዋል
2. ሰሌዳ. Please nail the board to the wall! ሰሌዳውን ፡ ግድግዳው ፡ ላይ ፡ በምስማር ፡ ምታው
3. ጥቁር ፡ ሰሌዳ. Write it on the board! ጥቁር ፡ ሰሌዳው ፡ ላይ ፡ ጻፈው
4. ቦርድ. He was elected to the Water and Power Board. ለውኃና ፡ መብራት ፡ ቦርድ ፡ አባልነት ፡ ተመረጠ
**be on board** ተሳፈረ
Is everybody on board? ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተሳፍሯል ?
[See also 'cutting, room']

**boarder** አዳሪ
Do you take boarders? አዳሪዎች ፡ ትቀበላላችሁ ?

**boarding**
*In this town, many people make a living by boarding students. በዚህ ፡ ከተማ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተማሪዎችን ፡ ገንዘብ ፡ እያስከፈሉ ፡ በማኖር ፡ ይተዳደራሉ

**boarding house** ምግብና ፡ መኝታ ፡ የሚገኝበት ፡ ስፍራ
Do you know of a nice boarding house? ጥሩ ፡ ምግብና ፡ መኝታ ፡ የሚገኝበት ፡ ስፍራ ፡ ታውቃለህ ?

**boarding pass** የመሳፈሪያ ፡ ቅጽ
Have your boarding pass ready! የመሳፈሪያ ፡ ቅጻችሁን ፡ አዘጋጁ

**boarding school** አዳሪ ፡ ትምህርት ፡ ቤት
He goes to a boarding school. አዳሪ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይማራል

**boast** (v.)
1. ፎከረ. The enemy boasted that he would never be defeated. ጠላት ፡ ምንጊዜም ፡ አልሸነፍም ፡ ብሎ ፡ ፎከረ
2. ጉራ ፡ ነዛ. He boasted that he never failed an exam. ፈተና ፡ ከቶ ፡ ወድቄ ፡ አላውቅም ፡ በማለት ፡ ጉራውን ፡ ነዛ
3. ኰራ. Our town boasts many fine parks. ከተማችን ፡ ባሏት ፡ ብዙ ፡ የሚያማምሩ ፡ የመናፈሻ ፡ ስፍራዎች ፡ ትኰራለች

**boast** (n.) ጉራ
His boast bored everyone. ጉራው ፡ ሁሉን ፡ አሰለቸ

**(be) boastful** ጉራውን ፡ ነዛ
Yohannes was boastful of his strength. ዮሐንስ ፡ ስለ ፡ ጥንካሬው ፡ ጉራውን ፡ ይነዛ ፡ ነበር

**boasting** ፉከራ
In the past, victory in battle was followed by boasting before the king. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ በጦርነት ፡ ድል ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ማሳረጊያው ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ፉከራ ፡ በማድረግ ፡ ነበር

**boat**
1. መርከብ. This boat goes to Australia. ይህ ፡ መርከብ ፡ ወደ ፡ አውስትራሊያ ፡ ይሄዳል
The boat trip will take five days. የመርከቡ ፡ ጉዞ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ይፈጃል
2. ጀልባ. We went fishing in his boat. በሱ ፡ ጀልባ ፡ ዓሣ ፡ ለማጥመድ ፡ ሄድን

**boating** በጀልባ ፡ መሄድ
Boating is discontinued in winter. በጀልባ ፡ መሄድ ፡ በክረምት ፡ ይቋረጣል

**bode** ምልክት ፡ ነበረ
The frequent mishaps boded disaster. የተደጋገሙት ፡ አደጋዎች ፡ የመዓት ፡ ምልክቶች ፡ ነበሩ

**bodies**, see **body**

**bodily** (adj.) የሰውነት
Bodily pains are a sign of old age. የሰውነት ፡ ሕመም ፡ የእርጅና ፡ ምልክት ፡ ነው

**bodily** (adv.)
1. በጉልበት. He was dragged away bodily. በጉልበት ፡ ተጎተተ
2. ባንድነት. The audience rose bodily to cheer the hero. አድማጩ ፡ ጀግናውን ፡ ለማድነቅ ፡ ባንድነት ፡ ብድግ ፡ አለ
*The tornado picked him up bodily and threw him against the wall. ኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ አንሥቶ ፡ ከግድግዳው ፡ አላጋው

**body** (bodies)
1. ሰውነት. He has a large body. ግዙፍ ፡ ሰውነት ፡ አለው
2. ሬሳ ፤ አስከሬን. They took the body to the cemetery. ሬሳውን ፡ (አስከሬኑን) ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ወሰዱት
3. አካል. A lake is a body of water. ሐይቅ ፡ አንድ ፡ የውኃ ፡ አካል ፡ ነው
The human body consists of many cells. የሰው ፡ አካል ፡ የተሠራው ፡ ከብዙ ፡ ሴል ፡ ነው
Chemistry teaches us about solid and liquid bodies. ኬሚስትሪ ፡ ስለ ፡ ጥጥርና ፡ ፈሳሽ ፡ አካሎች ፡ ያስተምረናል
4. ጓድ. A large body of singers sang at the church. ትልቅ ፡ የዘማሪዎች ፡ ጓድ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ዘመረ
5. ዋና ፡ ክፍል. The body of the book contains all the essential facts. የመጽሐፉ ፡ ዋና ፡ ክፍል ፡ ተፈላጊዎቹን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ በሙሉ ፡ አዝሏል
6. ክፍል. The legislative body makes the laws for the country. ሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ ለሀገሪቷ ፡ ሕጎችን ፡ ይደነግጋል
7. ምግብነት. Thick soup has more body than thin soup. ወፍራም ፡ ሾርባ ፡ ከቀጭን ፡ ሾርባ ፡ የበለጠ ፡ ምግብነት ፡ አለው

**(the) body of the people** አብዛኛው ፡ ሕዝብ
The body of the people favor the President's policy. አብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ የፕሬዚዳንቱን ፡ ፖሊሲ ፡ ይደግፋል

**in a body** ባንድነት
They left the hall in a body. ባንድነት ፡ ከዳራሹ ፡ ወጡ

**keep body and soul together**
*He hardly eats enough to keep body and soul together. ነፍስ ፡ እንድትሰነብት ፡ ብቻ ፡ ይበላል
[See also 'exercise, foreign, legislative, lifeless']

**bodyguard** ዐጃቢ
The rich trader was told to take a bodyguard with him when he went on a trip. ሀብታሙ ፡ ነጋዴ ፡ በሚጓዝበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ዐጃቢ ፡ እንዲይዝ ፡ ተነገረው

**Imperial Bodyguard** የክብር ፡ ዘበኛ
The Imperial Bodyguard protects the Emperor. የክብር ፡ ዘበኛ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ይጠብቃል

**bog down**
1. ሰመጠ. The car bogged down in the mud. መኪናው ፡ እጭቃው ፡ ውስጥ ፡ ሰመጠ
2. ተጓተተ. Negotiations bogged down due to disagreement. ካለመግባባት ፡ የተነሣ ፡ የስምምነቱ ፡ ንግግር ፡ ተጓተተ

**bogus** የሐሰት
They were condemned for making bogus money. የሐሰት ፡ ገንዘብ ፡ ስላወጡ ፡ ተፈረደባቸው

**boil** (vt.)
1. አፈላ. Please boil the water! ውኃውን ፡ አፍላው
2. ቀቀለ. Please boil the eggs two minutes! እንቁላሉን ፡ ለሁለት ፡ ደቂቃ ፡ ቀቅለው

**boil** (vi.) ፈላ
The water is boiling. ውኃው ፡ እየፈላ ፡ ነው
The kettle is boiling, so come and make coffee. ጀበናው ፡ ፈላ ፤ ነይ ፡ ቡና ፡ ጨምሪበት
*He was boiling with rage. ደሙ ፡ ፈልቶ ፡ ነበር

**boil away** ፈልቶ ፡ አለቀ
The water has boiled away. ውኃው ፡ ፈልቶ ፡ አልቋል

**boil down**
*It all boils down to this: He won't come. እቅጩ፡ ፡ እሱ ፡ አይመጣም
*After I talked to the secretary, I knew that it all boiled down to the fact that I was wrong. ጸሐፊዋን ፡ ካነጋገርኳት ፡ በኋላ ፡ በጭራሽ ፡ መሳሳቴን ፡ ተገነዘብኩ

**(be) boiled down**
*The water was boiled down to obtain salt. ጨው ፡ ለማውጣት ፡ ውኃው ፡ ተኖ ፡ እስኪያልቅ ፡ ተፈላ

**boil over** ገነፈለ
The milk boiled over. ወተቱ ፡ ገነፈለ

**make (one) boil over** (= boil over) በንዴት ፡ ጦፈ
Any mention of the incident makes her boil over. ሁኔታው ፡ በተነሣ ፡ ቁጥር ፡ በንዴት ፡ ትጦፋለች

**put on to boil** ጣደ
Put the kettle on to boil. ጀበናውን ፡ ጣደው

**boil** (n.) ብጉንጅ
He has a boil on his neck. አንገቱ ፡ ላይ ፡ ብጉንጅ ፡ ወጥቶበታል

**boiler** የማፈያ ፡ ጋን
The intake of each boiler is 300 gallons an hour. የማፈያ ፡ ጋን ፡ በሰዓት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ጋሎን ፡ ሊይዝ ፡ ይችላል

**boiling, be ~ hot** ገረረ
The sun was boiling hot. ፀሐይዋ ፡ እየገረረች ፡ ትሄድ ፡ ነበር

**boisterous** ሁካታ ፡ የበዛበት
The boisterous party lasted until midnight. ሁካታ ፡ የበዛበት ፡ ግብዣ ፡ እስከ ፡ እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ድረስ ፡ ቆየ

**bold**
1. ደፋር. The bold explorer saw the whole country. ደፋሩ ፡ አሳሽ ፡ አገሪቷን ፡ በሞላ ፡ አያት
2. ስድ ፡ አደግ. The bold little boy mocked us as we passed. ስድ ፡ አደጉ ፡ ትንሽ ፡ ልጅ ፡ ስናልፍ ፡ አላገጠብን
3. ቀጥ ፡ ያለ. Bold cliffs fronted the sea. ቀጥ ፡ ያሉ ፡ ገደሎች ፡ ከባሕሩ ፡ ዳር ፡ ይታያሉ
4. የድፍረት. That was a bold statement. የድፍረት ፡ አነጋገር ፡ ነበር
*He apologized for being so bold as to speak to the general. ጄኔራሉን ፡ ደፍሮ ፡ በመናገሩ ፡ ይቅርታ ፡ ጠየቀ

**boldness** ደፋርነት
Boldness in women is not admired. የሴቶች ፡ ደፋርነት ፡ አይደነቅም

**bolt** (vt.) ቀረቀረ
After the farmer put the cattle in the pen, he bolted the gate. ገበሬው ፡ ከብቶቹን ፡ ከበረት ፡ ካስገባቸው ፡ በኋላ ፡ በሩን ፡ ቀረቀረው

**bolt** (vi.) ደነበረ ፤ ሽመጠጠ
Suddenly, the horse bolted. ፈረሱ ፡ ድንገት ፡ ደነበረ ፡ (ሽመጠጠ)

**be bolted** በቡሎን ፡ ተያያዘ
The plates were welded together, not bolted. ጠፍጣፎቹ ፡ ብረቶች ፡ ተበይደዋል ፡ እንጂ ፡ በቡሎን ፡ አልተያያዙም

**bolt** (n.) አናት ፤ መያዣ
The nut came off the bolt. ቡሎኑ ፡ ከአናቱ ፡ (ከመያዣው) ፡ በኩል ፡ ወለቀ

**bomb** (v.) በቦምብ ፡ ደበደበ
The planes bombed the factory again during the night. አውሮፕላኖቹ ፡ ፋብሪካውን ፡ እንደገና ፡ ሌሊት ፡ በቦምብ ፡ ደበደቡ

**bomb** (n.) ቦምብ
The whole district has been destroyed by bombs. ቀበሌው ፡ በሙሉ ፡ በቦምብ ፡ ወደመ

**set off a bomb** ቦምብ ፡ አፈነዳ
They set off a bomb in the street. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ቦምብ ፡ አፈነዱ

**bombard** በቦምብ ፡ ደበደበ
The artillery bombarded the enemy all day. መድፈኞቹ ፡ ጠላትን ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ በቦምብ ፡ ደበደቡት

**bombard with** አወረደ(በት)
The audience bombarded him with questions. አድማጮቹ ፡ ጥያቄ ፡ አወረዱበት

**bombardment** የቦምብ ፡ ድብደባ
He went mad during the bombardment. በቦምብ ፡ ድብደባው ፡ ጊዜ ፡ ናላው ፡ ዞረ

**bombast** ጉራ
His bombast impresses the boss, but not his colleagues. ጉራው ፡ አለቃውን ፡ እንጂ ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቹን ፡ አያስደንቅም

**bombing** የቦምብ ፡ ድብደባ ፤ ቦምብ ፡ መጣል
The bombing reduced Germany to chaos. የቦምቡ ፡ ድብደባ ፡ ጀርመንን ፡ አተራመሰ

Indiscriminate bombing results in many civilian casualties. እጅ ፡ እንዳመጣ ፡ ቦምብ ፡ መጣል ፡ ብዙ ፡ ሲቪሎችን ፡ ይገድላል

**bond**
1. ሰንሰለት. The prisoner broke his bonds and escaped. እስረኛው ፡ ሰንሰለቱን ፡ በጥሶ ፡ አመለጠ
2. ግንኙነት. The treaty strengthened the bond between the two nations. ውሉ ፡ የሁለቱን ፡ አገሮች ፡ ግንኙነት ፡ አጠነከረ
3. መንፈስ. There is a bond of loyalty between the Emperor and the patriots. በጃንሆይና ፡ በአርበኞቹ ፡ መካከል ፡ የታማኝነት ፡ መንፈስ ፡ አለ
4. ቦንድ. He bought government bonds. የመንግሥት ፡ ቦንድ ፡ ገዛ

**bondage** ባርነት
The Jews were held in bondage in Egypt. አይሁዶች ፡ በግብጽ ፡ ውስጥ ፡ በባርነት ፡ ተይዘው ፡ ነበር

**bondman** ገባር
A bondman could not own land in old England. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ገባር ፡ ርስት ፡ አይኖረውም

**bone** (v.), ~ **up** ከላለሰ
I have to bone up on my history for the exam. ለታሪክ ፡ ፈተና ፡ መከላለስ ፡ አለብኝ

**bone** (n.) አጥንት
Give the dog a bone! ለውሻው ፡ አጥንት ፡ ስጠው
I feel chilled to the bone. ብርዱ ፡ እስከ ፡ አጥንቴ ፡ ተሰማኝ

**have a bone to pick with someone**
I have a bone to pick with you. የምገልጽልህ ፡ ቅሬታ ፡ አለኝ

**make no bones about**
He made no bones about his intentions. ሐሳቡን ፡ ያላንዳች ፡ ቅሬታ ፡ ገለጸ

**bonfire**
1. ደመራ. The children made a bonfire for the Mesqel holiday. ልጆቹ ፡ ለመስቀል ፡ ደመራ ፡ አበሩ
2. ትልቅ ፡ እሳት. They built a bonfire on the beach to attract the attention of passing ships. አላፊ ፡ መርከቦች ፡ እንዲያዩዋቸው ፡ በባሕር ፡ ዳርቻ ፡ ትልቅ ፡ እሳት ፡ አነደዱ

**bonus** ጉርሻ
The company gave every worker a bonus. ኩባንያው ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሠራተኛ ፡ ጉርሻ ፡ ሰጠ

**bony** አጥንታም
The skull is a bony structure. የራስ ፡ ቅል ፡ አጥንታም ፡ አካል ፡ ነው

**boo** በጩኸት ፡ ተቃወመ
The audience booed his lamentable violin playing. የማይረባውን ፡ የቪዮሊን ፡ ምቱን ፡ አድማጮቹ ፡ በጩኸት ፡ ተቃወሙት

**book** (v.)
1. መዘገበ. The police booked him on a charge of drunken driving. ፖሊሱ ፡ ሰክሮ ፡ በመንዳት ፡ ጥፋት ፡ መዘገበው
2. ያዘ. How many seats did you book for the theater? ለቴያትሩ ፡ ስንት ፡ መቀመጫዎች ፡ ያዝክ ?

**book** (n.) መጽሐፍ
There are many pictures in this book. እዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሥዕሎች ፡ አሉ

**according to the book**
*The solution was not according to the book, but it served the purpose. የችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ ደንቡን ፡ ባይከተልም ፡ ለጉዳዩ ፡ ተስማምቷል

**keep books** መዝገብ ፡ ያዘ
The accountant keeps my books. የሒሳብ ፡ ዐዋቂው ፡ መዝገቤን ፡ ይይዝልኛል

**bookbinder** መጽሐፍ ፡ ጠራዥ
The bookbinder will repair your book cover. መጽሐፍ ፡ ጠራዡ ፡ የመጽሐፍህን ፡ ሽፋን ፡ ይጠግንልሃል

**bookcase** የመጽሐፍ ፡ ሣጥን
The bookcase is small, and I cannot place in it all my books. የመጽሐፉ ፡ ሣጥን ፡ ትንሽ ፡ ስለሆነ ፡ መጽሐፌን ፡ በሙሉ ፡ ላስቀምጥበት ፡ አልችልም

**bookish** የመጽሐፍ ፡ ቀበኛ
A bookish child does not like football. የመጽሐፍ ፡ ቀበኛ ፡ የሆነው ፡ ልጅ ፡ የእግር ፡ ኳስ ፡ አይወድም

**bookkeeper** ሒሳብ ፡ ያዥ
The bookkeeper found a shortage when he checked the accounts. ሒሳብ ፡ ያዡው ፡ ሒሳቡን ፡ ተቈጣጥሮ ፡ ጉድለት ፡ አገኘበት

**booklet** ትንሽ ፡ መጽሐፍ
The booklet you gave me has a paper cover. የሰጠኸኝ ፡ ትንሽ ፡ መጽሐፍ ፡ ልባሱ ፡ የወረቀት ፡ ነው

**bookshelf** የመጽሐፍ ፡ መደርደሪያ
My bookshelf is wide. የመጽሐፍ ፡ መደርደሪያዬ ፡ ሰፊ ፡ ነው

**bookstore** የመጽሐፍ ፡ መደብር
You may be able to get it in a second-hand bookstore. ከአሮጌ ፡ መጽሐፍ ፡ መደብር ፡ ታገኘው ፡ ይሆናል

**bookworm** የመጽሐፍ ፡ ቀበኛ ፤ የመጽሐፍ ፡ ቁራኛ
Since he is a bookworm, he got the highest grade in the exam. የመጽሐፍ ፡ ቀበኛ ፡ (ቁራኛ) ፡ በመሆኑ ፡ በፈተና ፡ አንደኛ ፡ ወጣ

**boom** (v.)
1. አጓራ. At the announcement of victory, cannons boomed. የድል ፡ ዜና ፡ በተገለጸ ፡ ጊዜ ፡ መድፎች ፡ አጓሩ
2. ተስፋፋ ፤ ተሟሟቀ. After the war, business boomed. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ንግድ ፡ ተስፋፋ ፡ (ተሟሟቀ)

**boom out** ጐላ ፡ ብሎ ፡ ተሰማ
The big man's voice boomed out above the rest. የግዙፉ ፡ ሰውዬ ፡ ድምፅ ፡ ከሌሎቹ ፡ ጐላ ፡ ብሎ ፡ ተሰማ

**boom** (n.)
1. ድንፋታ. He could hear the boom of the cannon. የመድፋን ፡ ድንፋታ ፡ ለመስማት ፡ ቻለ
2. መሟሟቅ. The business boom lasted five years. የንግዱ ፡ መሟሟቅ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ቆየ

**boon, be a ~** በጣም ፡ ጠቀመ
Those warm stockings were a boon to me in the cold weather. እነዚያ ፡ የሚሞቁ ፡ የእግር ፡ ሹራቦች ፡ በዚያ ፡ ብርዳማ ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ ጠቀሙኝ

**boor** ስድ ፡ አደግ
The boor talked only about himself. ስድ ፡ አደጉ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ አወራ

**boorish** የብልግና
His boorish manners angered the host. የብልግና ፡ ሁናቴው ፡ ባለቤቱን ፡ አስቈጣው

**boost** (v.)
1. ወደ ፡ ላይ ፡ ገፋ. If you boost me, I can climb that tree. ወደ ፡ ላይ ፡ ብትገፋኝ ፡ ያንን ፡ ዛፍ ፡ እወጣለሁ
2. ከፍ ፡ አደረገ(ለት). The award boosted his confidence. የተደረገለት ፡ ሽልማት ፡ በራሱ ፡ ያለውን ፡ እምነት ፡ ከፍ ፡ አደረገለት
3. አስወደደ. The drought has boosted the prices of grain. ድርቁ ፡ የእህልን ፡ ዋጋ ፡ አስወደደው

**boost** (n.) ጭማሪ
The newspapers announced the tremendous boost in food prices. ጋዜጦች ፡ በምግብ ፡ ሸቀጥ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ የዋጋ ፡ ጭማሪ ፡ መደረጉን ፡ ገለጹ

**give a boost** ወደ ፡ ላይ ፡ ገፋ
Give me a boost so I can climb over this wall. በዚህ ፡ ግንብ ፡ አጥር ፡ ላይ ፡ መዝለል ፡ እንድችል ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ግፋኝ

**boot, high ~** ቦት ፡ ጫማ
When I go fishing, I wear high boots. ዓሣ ፡ ለማጥመድ ፡ ስሄድ ፡ ቦት ፡ ጫማ ፡ አደርጋለሁ

**lick someone's boots** ተለማመጠ
The private refused to lick the lieutenant's boots to get a raise in rank. ወታደሩ ፡ ለሹመት ፡ እድገት ፡ ሲል ፡ መቶ ፡ አለቃውን ፡ መለማመጥ ፡ አሻፈረኝ ፡ አለ

**booth**
1. ዳስ. There were many booths at the fair. ኤግዚቢሽኑ ፡ ብዙ ፡ ዳሶች ፡ ነበሩት
2. ጎጆ. There is no telephone booth in this city. በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ የስልክ ፡ ጎጆ ፡ የለም

**booty** ምርኮ
They shared the booty after the battle. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ምርኮውን ፡ ተከፋፈሉ

**border** (v.) ተዋሰነ
His land borders mine. መሬቱ ፡ የኔን ፡ ይዋሰናል

**border on** የ - - - ያህል ፡ ነበር
His remark bordered on insult. የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ የስድብ ፡ ያህል ፡ ነበር

**be bordered**
1. ተዋሰነ. The garden is bordered by a stream. ያትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ካንድ ፡ ትንሽ ፡ ወንዝ ፡ ይዋሰናል
Ethiopia is bordered on the south by Kenya. ኢትዮጵያ ፡ በስተደቡብ ፡ ከኬንያ ፡ ትዋሰናለች
2. ተከፈፈ. The dress is bordered with lace. ቀሚሱ ፡ በጥለት ፡ የተከፈፈ ፡ ነው

**border** (n.)
1. ጠረፍ. When do we reach the border? ከጠረፉ ፡ መቼ ፡ እንደርሳለን ?
2. ወሰን ፤ ድንበር. He was chosen arbiter for the border problem. ስለ ፡ ወሰኑ ፡ (ስለ ፡ ድንበሩ) ፡ ጉዳይ ፡ አስታራቂ ፡ ሆኖ ፡ ተመረጠ
3. ዳር. We camped on the border of a lake. ባንድ ፡ ሐይቅ ፡ ዳር ፡ ሰፈርን
4. ጠርዝ. The border of this rug is getting frayed. የዚህ ፡ ምንጣፍ ፡ ጠርዝ ፡ እየተዘረዘረ ፡ ነው

*There is a border of flowers around the lawn. በአጥር ፡ ግቢው ፡ መስክ ፡ ዙሪያ ፡ አበባዎች ፡ አሉ

**border post** (የ)ጠረፍ ፡ ጣቢያ
He fell from grace and was exiled to a border post. ከባለሟልነቱ ፡ ወርዶ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ጠረፍ ፡ ጣቢያ ፡ ተጋዘ

**share a common border** ተዋሰነ
Ethiopia and Sudan share a common border. ኢትዮጵያና ፡ ሱዳን ፡ ይዋሰናሉ
[See also 'zone']

**borderline** ድንበር
The borderline is not marked on the map. ድንበሩ ፡ በካርታው ፡ ላይ ፡ አልተመለከተም
*He has a borderline case of mental illness. ወደ ፡ እብደት ፡ የተቃረበ ፡ የአእምሮ ፡ ሕመም ፡ አለበት

**bore,** see **bear**

**bore** (v.)
1. አሰለቸ. His speech bored me. ንግግሩ ፡ አሰለቸኝ
He bored me stiff. በጣም ፡ አሰለቸኝ
2. ሰረሰረ. They bored through the rocks. ቋጥኙን ፡ ሰረሰሩ
3. ቈፈረ. They plan to bore a tunnel through the mountains. በተራራው ፡ ውስጥ ፡ መሿለኪያ ፡ ለመቈፈር ፡ ያስባሉ

**be bored** (= bore) አሰለቸ
+I am terribly bored by his speech. የሱ ፡ ንግግር ፡ በጣም ፡ አሰልችቶኛል

**bore a hole through** በሳ
We will have to bore a hole through the wall. ግድግዳውን ፡ መብሳት ፡ አለብን

**bore into** ሰርስሮ ፡ ገባ ፤ ሰረሰረ
This kind of worm bores into the wood. የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ትል ፡ ዕንጨቱን ፡ ሰርስሮ ፡ ይገባል
The drill bored into the ground. መሰርሰሪያው ፡ መሬቱን ፡ ሰረሰረው

**bore one's way through** ሰርስሮ ፡ ሄደ
A mole has bored its way through the earth. ፍልፈል ፡ መሬቱን ፡ ሰርስሮ ፡ ሄደ
[See also 'death']

**bore** (n.) አሰልቺ
It is a bore to have to wash dishes three times a day. በቀን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሳሕን ፡ ማጠብ ፡ አሰልቺ ፡ ነው

**boredom** መሰልቸት
The little children wriggled in their seats from boredom. ትንንሾቹ ፡ ልጆች ፡ ከመሰልቸት ፡ የተነሣ ፡ መቀመጥ ፡ አቅቷቸው ፡ ተቍነጠነጡ

**born,** see **bear**

**born,** adj. (= adv.) በተፈጥሮ
Yohannes is a born poet. ዮሐንስ ፡ በተፈጥሮው ፡ ገጣሚ ፡ ነው

**borrow**
1. ተበደረ. He borrowed a lot of money from him. ከሱ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ተበደረ
2. ተዋሰ. She borrowed the book from him. መጽሐፉን ፡ ከሱ ፡ ተዋሰች
3. ወሰደ. Rome borrowed many ideas from Greece. ሮማ ፡ ከግሪክ ፡ ብዙ ፡ ዕውቀት ፡ ወሰደች

**bosom**
1. ጡት. The dress barely covered her bosom. ቀሚሱ ፡ ላመል ፡ ጡቷን ፡ ሸፍኖታል
2. ደረት. Rest your head on my bosom! ራስሽን ፡ ደረቴ ፡ ላይ ፡ አስደግፊው
3. ልብ. My bosom swells with joy. ልቤ ፡ በደስታ ፡ ተሞልቷል

**bosom friend** የልብ ፡ ወዳጅ
Bosom friends share secrets. የልብ ፡ ወዳጆች ፡ ምስጢር ፡ ይካፈላሉ

**in the bosom of** እ - - - መሀከል
He did not mention it even in the bosom of his family. እቤተ ፡ ሰቡ ፡ መሀከል ፡ እንኳን ፡ አልጠቀሰውም

**boss** (v.) አዘዘ
The captain bosses the crew. ካፒቴኑ ፡ መርከበኞቹን ፡ ያዛል

**boss** (n.) አለቃ
Who is the boss in this house? በዚህ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አለቃው ፡ ማነው ?

**botany** ያዝርእትና ፡ ያትክልት ፡ ጥናት

**both** ሁለቱም ፤ ሁለት + suffix pronouns
Both brothers are in the army. ሁለቱም ፡ ወንድማማቾች ፡ ወታደሮች ፡ ናቸው
Do you like swimming or horseback riding? I like to do both equally well. የምትወደው ፡ ዋና ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ግልቢያ ? ሁለቱንም ፡ ማድረግ ፡ እኩል ፡ እወዳለሁ
We both visited him. ሁለታችንም ፡ ጠየቅነው

**both a ... and a ...** -ም ፡ - - -ም
He is both a soldier and a poet. ወታደርም ፡ ባለቅኔም ፡ ነው

**both of** ሁለት + suffix pronouns
Both of us were going to the movie. ሁለታችን
ም ፡ ወደ ፡ ሲኒማ ፡ እንሄድ ፡ ነበር

**bother** (vt.)
1. አስቸገረ. Does the smoke bother you?
ጢሱ ፡ ያስቸግርሃል ?
2. ነዘነዘ. Don't bother him when he is in
bad humor. ቅር ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ አትነዝንዘው
3. ወቀሰ. His conscience bothered him. ኅሊና
ው ፡ ወቀሰው
4. ነካ. You look so sad. What is bothering
you? ያዘንክ ፡ ትመስላለህ ፤ ምን ፡ ነካህ ?

**bother** (vi.) ተቸገረ
I cannot bother with her now; I am too busy.
አሁን ፡ ሥራ ፡ ስለበዛብኝ ፡ ስለሷ ፡ ልቸገር ፡ አል
ችልም

**bother** (n.)
1. ችግር. We had a lot of bother in getting
here because of the fog. በጭጋጉ ፡ ምክንያት ፡
እዚህ ፡ ለመድረስ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ገጠመን
2. አስቸጋሪ. He is just a bother. እርሱ ፡ አስቸ
ጋሪ ፡ ነው
*It's no bother at all. ምንም ፡ አያሳስብም

**be a bother** አስቸገረ
Flies are a great bother. ዝንቦች ፡ በጣም ፡ ያ
ስቸግሩኛል

**go to any bother** ተቸገረ ፤ ተጨነቀ
Please don't go to any bother on my account!
ስለኔ ፡ ምንም ፡ አትጨነቅ ፡ (አትቸገር)

**bothersome** አሳሳቢ
The bothersome problem did not let me sleep.
አሳሳቢው ፡ ጉዳይ ፡ እንቅልፍ ፡ አላስወሰድ ፡
አለኝ

**bottle** ጠርሙስ

**bottleneck, be a ~** ጭንቅንቅ ፡ ፈጠረ
This narrow street is a bottleneck during
rush hours. መኪና ፡ በሚበዛበት ፡ ጊዜ ፡ ይህች ፡
ጠባብ ፡ መንገድ ፡ ጭንቅንቅ ፡ ትፈጥራለች

**bottom** (n.)
1. ሥረ ፡ ነገር. We have to get to the bottom
of this affair. የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ሥረ ፡ ነገር ፡ መረ
ዳት ፡ አለብን
2. መሬት. The lake is so deep, a swimmer
cannot touch the bottom. ሐይቁ ፡ ጥልቅ ፡ በመ
ሆኑ ፡ ዋናተኛ ፡ መሬቱን ፡ ሊነካ ፡ አይችልም
3. ቂጥ. She spanked the child on its bottom.
ልጁን ፡ ቂጡ ፡ ላይ ፡ መታችው
4. መነሻ. I'd like to know what is at the bottom
of all this. የዚህን ፡ ሁሉ ፡ መነሻ ፡ ለማወቅ ፡
እፈልጋለሁ

**(the) bottoms of** የውስጥ
The bottoms of the feet are ticklish. የውስጥ ፡
እግር ፡ ይሰቀጥጣል

**at bottom** በመሠረቱ
They knew at bottom that they were wrong.
በመሠረቱ ፡ መሳሳታቸውን ፡ ያውቁ ፡ ነበር

**at the bottom of** ሥር ፤ እ - - - ሥር
The road branches at the bottom of the hill.
መንገዱ ፡ ጋራው ፡ ሥር ፡ ሲደርስ ፡ ይከፋፈላል
He found it at the bottom of the trunk.
እሣጥኑ ፡ ሥር ፡ አገኘው

**from top to bottom** ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፤ ከ
ጻር ፡ እስከ ፡ ጻር
The house was searched from top to bottom.
ቤቱ ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ (ከጻር ፡ እስከ ፡ ጻር) ፡
ተበረበረ

**on the bottom of** ከ - - - ሥር
The green book is on the bottom of the pile.
አረንጓዴው ፡ መጽሐፍ ፡ ከመጽሐፉ ፡ ቁልል ፡
ሥር ፡ ነው

**bottom** (adj.)
1. የመጨረሻ ፡ ዝቅተኛ. What is your bottom
price? የመጨረሻ ፡ ዝቅተኛ ፡ ዋጋህ ፡ ስንት ፡ ነ
ው ?
2. ሥረኛ. Put the book on the bottom shelf!
መጽሐፉን ፡ ሥረኛው ፡ መደርደሪያ ፡ ላይ ፡ አስቀምጥ
3. የታችኛ. The bottom drawer of the bureau is
stuck. የጠረጴዛው ፡ የታችኛው ፡ መሳቢያ ፡ ነክሷል
[See also 'rock']

**bough** ቅርንጫፍ
He sawed the broken bough off the tree.
የተሰባበረውን ፡ ቅርንጫፍ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ በመጋዝ ፡
ቈረጠው

**bought**, see **buy**

**boulder** ትልቅ ፡ ቋጥኝ
The falling boulder pulverized all the stones
it fell on. ትልቁ ፡ ቋጥኝ ፡ የወደቀባቸውን ፡ ድን
ጋዮች ፡ ሁሉ ፡ አደቀቃቸው

**boulevard** [በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሰፊ ፡ መን
ገድ]

**bounce** (vt.) አነጠረ
The boy bounced the ball on the sidewalk.
ልጁ ፡ በእግር ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ኳሱን ፡ አነጠረ

**bounce** (vi.)
1. ነጠረ. This ball doesn't bounce. ይህ ፡ ኳስ ፡ አይነጥርም
2. ፈነደቀ. His heart bounced with joy. ልቡ ፡ በደስታ ፡ ፈነደቀ

**bounce into** ዘሎ ፡ ገባ
The boy bounced into the room. ልጁ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ዘሎ ፡ ገባ

**bounce out** ተፈትልኮ ፡ ወጣ
She bounced out of the room. ከክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተፈትልካ ፡ ወጣች

**bounce up and down** ዘለለ
The baby likes to bounce up and down on the bed. ሕፃኗ ፡ አልጋዋ ፡ ላይ ፡ መዝለል ፡ ትወዳለች

**bounce** (n.), **in one ~** ፈንጠር ፡ ብሎ
In one bounce, he was at the door. ፈንጠር ፡ ብሎ ፡ ከበር ፡ ደረሰ

**bound,** see **bind**

**bound** (vt.) አዋሰነ
A highway bounds the farm on the west. እርሻው ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ያዋስነዋል

**bound** (vi.)
1. ተዋሰነ. Canada bounds on the United States. ካናዳ ፡ ከዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ትዋሰናለች
2. ቦረቀ. The deer bounds through the woods. አጋዘኑ ፡ ጫካው ፡ ውስጥ ፡ ይቦርቃል

**be bounded** ተዋሰነ
Ethiopia is bounded on the west by Sudan. ኢትዮጵያ ፡ በምዕራብ ፡ ከሱዳን ፡ ትዋሰናለች

**bound** (n.)
1. ጽንፍ. God is beyond the bounds of human knowledge. እግዚአብሔር ፡ ከሰብአዊ ፡ ዕውቀት ፡ ጽንፍ ፡ በላይ ፡ ነው
2. መጠን ፤ ወሰን. His pride knows no bounds. ኩራቱ ፡ መጠን ፡ የለውም
His gratitude knew no bounds. ምስጋናው ፡ ወሰን ፡ የለውም
3. ክልል. He drives a car only within the bounds of his estate. በግል ፡ መሬቱ ፡ ክልል ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ መኪና ፡ ይነዳል
4. ዝላይ. He jumped over the fence with one bound. ባንድ ፡ ዝላይ ፡ አጥሩን ፡ አለፈ
*Keep your hopes within bounds! ለተስፋህ ፡ ልጓም ፡ አብጅለት
[See also 'leap']

**bound** (adj.), **be ~ for** ሄደ
That boat is bound for America. ያ ፡ መርከብ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ የሚሄድ ፡ ነው

**be all bound up**
*He's all bound up in his work. በሥራው ፡ ተውጧል

**it was bound to happen** መድረሱ ፡ አልቀረም
It was bound to happen sooner or later. ውሎ ፡ አድሮ ፡ መድረሱ ፡ አልቀረም
[See also 'outward']

**boundary** ድንበር ፤ ወሰን
A pile of stones marks the boundary between the two fields. የሁለቱ ፡ ማሳዎች ፡ ድንበር ፡ የድንጋይ ፡ ክምር ፡ ነው
The commission delineated the boundaries of Somalia. ኮሚስዮኑ ፡ የሱማሊያን ፡ ወሰን ፡ ከለለ

**have a boundary** ተዋሰነ
Ethiopia has a boundary with the Sudan in the west. ኢትዮጵያ ፡ በምዕራብ ፡ ከሱዳን ፡ ትዋሰናለች

**boundless** ወሰን ፡ የሌለው
He is a man of boundless energy. ወሰን ፡ የሌለው ፡ ጉልበት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**be boundless** ወሰን ፡ አልነበረውም
The jubilance of the crowd was boundless. የሕዝቡ ፡ ፈንጠዝያ ፡ ወሰን ፡ አልነበረውም

**bounteous** የተትረፈረፈ
Bounteous presents were distributed to the poor. የተትረፈረፈ ፡ ስጦታ ፡ ለድሆች ፡ ተከፋፈለ

**bountiful** ለጋስ
My bountiful friend helped me greatly. ለጋሱ ፡ ወዳጄ ፡ በጣም ፡ ረዳኝ

**a bountiful supply of** (= adv.) በገፍ
We have a bountiful supply of tomatoes. ቲማቲም ፡ በገፍ ፡ አለን

**bounty**
1. ችሮታ. This hospital is supported by the bounty of one man. ሆስፒታሉ ፡ የሚካሄደው ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ችሮታ ፡ ነው
2. ቸርነት. Through God's bounty, we were saved. በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ዳንን
3. ጉርሻ. They paid a bounty for each viper killed. ለተገደለው ፡ ለያንዳንዱ ፡ መርዘኛ ፡ እባብ ፡ ጉርሻ ፡ ሰጡ

**bouquet** እቅፍ
Where did you get that beautiful bouquet of

roses? ያን፡ ቆንጆ ፡ የጽጌረዳ ፡ እቅፍ ፡ ከየት ፡ አገኘህ ?

**bout** ውድድር ፤ ግጥሚያ
He watched a wrestling bout. የትግል ፡ ውድድር ፡ ተመለከተ
Those are the two boxers who will appear in the main bout. በዋናው ፡ ግጥሚያ ፡ ላይ ፡ የሚታዩ ፡ ሁለቱ ፡ ቡጢኞች ፡ እነዚያ ፡ ናቸው

**a long bout of** የረዥም ፡ ጊዜ
A long bout of illness left him weak and without money. የረዥም ፡ ጊዜ ፡ ሕመሙ ፡ ደካማና ፡ ድኻ ፡ አድርጎ ፡ አስቀረው

**bow** (v.) እጅ ፡ ነሣ
The singer bowed and left the stage. ዘፋኙ ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ከመድረኩ ፡ ላይ ፡ ሄደ

**bow down** ሰገደ
They bowed down to the idol. ለጣዖቱ ፡ ሰገዱ

**bow (one's) head**
1. ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አደረገ . They bowed their heads in prayer. ለጸሎት ፡ ራሳቸውን ፡ ዝቅ ፡ አደረጉ
2. እጅ ፡ ነሣ. I bowed my head to her, and she bowed hers in return. እጅ ፡ ስነሣት ፡ እሷም ፡ በፀጸፋው ፡ መለሰችልኝ
3. አንገቱን ፡ ሰበረ. The girl was shy and bowed her head. ልጅቷ ፡ ስላፈረች ፡ አንገቷን ፡ ሰበረች
4. አጎበጠ. Age has bowed his head. እርጅና ፡ አጕብጦታል

**bow to**
1. ፈጸመ. He bowed to his father's wishes. ያባቱን ፡ ፈቃድ ፡ ፈጸመ
2. ተቀበለ. We must bow to necessity. አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮችን ፡ መቀበል ፡ አለብን

**bow,** n. (rhymes with 'row')
1. ቀስት. Boys like to play with bows and arrows. ልጆች ፡ በቀስትና ፡ በወስፈንጥር ፡ መጫወት ፡ ይወዳሉ
2. ደጋን. His back was curved like a bow. ጀርባው ፡ እንደ ፡ ደጋን ፡ ጐብጧል
3. የቢራቢሮ ፡ ቅርጽ. She tied her ribbon in a bow. ሪባኑን ፡ በቢራቢሮ ፡ ቅርጽ ፡ አሰረችው

**bow,** n. (rhymes with 'cow') የፊት ፡ ለፊት ፡ ክፍል
The ship's bow was damaged when it struck a rock. የመርከቧ ፡ የፊት ፡ ለፊት ፡ ክፍል ፡ በድንጋይ ፡ ስለተመታ ፡ ተጐዳ

**make a bow** እጅ ፡ ነሣ
He made a low bow. ለጥ ፡ ብሎ ፡ እጅ ፡ ነሣ

**bowel** አንጀት
Only a dog eats the bowels. አንጀት ፡ የሚበላ ፡ ውሻ ፡ ብቻ ፡ ነው

**bowl** ጐድጓዳ ፡ ሳሕን
Put these oranges into a bowl! እነዚህን ፡ ብርቱካኖች ፡ እጐድጓዳ ፡ ሳሕን ፡ ወስጥ ፡ አስቀምጥ

**bowstring** የቀስት ፡ መሳቢያ ፤ የቀስት ፡ መወጠሪያ
The bowstring is made from the sinews of an ox. የቀስቱ ፡ መሳቢያ ፡ (መወጠሪያ) ፡ የተሠራው ፡ ከበሬ ፡ ጅማት ፡ ነው

**box** (v.)
1. በሣጥን ፡ አስገባ. He boxed the books before he shipped them. መጽሐፎቹን ፡ በመርከብ ፡ ከመላኩ ፡ በፊት ፡ በሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አስገባቸው
2. በቡጢ ፡ መታ. Do you know how to box? በቡጢ ፡ መምታት ፡ ታውቃለህ ?

**box** (n.)
1. ሰንዱቅ. Shall I put the shoes in a box? ጫማዎቹን ፡ ሰንዱቅ ፡ ውስጥ ፡ ላድርጋቸው ?
2. ፓኮ. I have another box of cigars. ሌላ ፡ ፓኮ ፡ ሲጋራ ፡ አለኝ
Give me a box of matches. አንድ ፡ ፓኮ ፡ ክብሪት ፡ ስጠኝ
3. በቡጢ ፡ መመታት. A box on the ear hurts. ጆሮ ፡ ላይ ፡ በቡጢ ፡ መመታት ፡ ያሳምማል

**(letter) box** ፖስታ ፡ ሣጥን
Would you drop the letter in the box for me? ይህንን ፡ ደብዳቤ ፡ ፖስታ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ትጥልልኛለህ ?

**boxer** ቡጢኛ
The boxer was badly hurt in the last fight. በመጨረሻው ፡ ግጥሚያ ፡ ላይ ፡ ቡጢኛው ፡ ክፉኛ ፡ ተጐዳ

**box office** ቲኬት ፡ መሸጫ
I bought three tickets at the box office. ከቲኬት ፡ መሸጫ ፡ ሦስት ፡ ቲኬት ፡ ገዛሁ

**boy**
1. ወንድ. The school is for boys only. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የወንዶች ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ልጅ. How old is your boy? ልጅህ ፡ ስንት ፡ ዓመቱ ፡ ነው ?
[See also 'office boy, paper boy']

**boycott** (v.)
1. ተካፋይ ፡ ከመሆን ፡ ተቈጠበ. The Arabs boycotted the meetings. ዐረቦች ፡ የስብሰባው ፡ ተካፋዮች ፡ ከመሆን ፡ ተቈጠቡ

2. ላይገዛ ፡ ተስማማ. The town boycotted the store because of the unclean conditions. ስለመ
ደብሩ ፡ ንጽሕና ፡ ጉድለት ፡ የከተማው ፡ ሕዝ
ብ ፡ ከመደብሩ ፡ ላይገዛ ፡ ተስማማ

**boycott** (n.) አድማ
The boycott was lifted. አድማው ፡ አበቃ

**boyfriend** የከንፈር ፡ ወዳጅ
She has a nice boyfriend. ጥሩ ፡ የከንፈር ፡ ወዳ
ጅ ፡ አላት

**boyhood** ልጅነት
I learned to swim in my boyhood. ዋና ፡ በልጅ
ነቴ ፡ ተማርኩ

**boyish** የልጅ
He has a boyish face. የልጅ ፡ መልክ ፡ አለው

**brace** (v.)
1. አነቃቃ. The cool, fresh air will brace you. ቀዝቃዛው ፡ ንጹሕ ፡ አየር ፡ ያነቃቃሃል
2. ድጋፍ ፡ አደረገ(በት). He braced the wall to withstand the wind. ነፋሱን ፡ እንዲቋቋም ፡ ግ
ድግዳውን ፡ ድጋፍ ፡ አደረገበት

**brace oneself** ተዘጋጀ
Brace yourself for some bad news! ክፉ ፡ ወ
ሬ ፡ ልነግርህ ፡ ነውና ፡ ተዘጋጅ

**brace** (n.) መደገፊያ
He put an extra brace under the shelf. ከመደር
ደሪያው ፡ ሥር ፡ ትርፍ ፡ መደገፊያ ፡ አስቀመጠ

**bracelet** አምባር
The bracelet is pure gold. አምባሩ ፡ ንጹሕ ፡ ወርቅ ፡ ነው

**bracket**
1. መደገፊያ. The bracket holds the shelf against the wall. መደገፊያው ፡ መደርደሪያውን ፡ ከግድግ
ዳ ፡ ጋር ፡ ይይዘዋል
2. ቅንፍ. Brackets are not used in Amharic. አማርኛ ፡ በቅንፍ ፡ አይጠቀምም

**brackish** ጨው ፡ ጨው ፡ የሚል
There is a brackish spring in the desert. በምድረ ፡ በዳው ፡ ጨው ፡ ጨው ፡ የሚል ፡ ምን
ጭ ፡ አለ

**brag** (bragged) ጉራ ፡ ነዛ
Does he always brag that way? ሁልጊዜ ፡ እን
ደዚያ ፡ ጉራውን ፡ ይነዛል ?

**braggart** ጉረኛ ፡ ሰው
The braggart told of his brave deeds in the war. ጉረኛው ፡ ሰው ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ስለፈጸማቸው ፡ የጀግንነት ፡ ሙያዎች ፡ አወራ

**braid** (v.) አሸመ ፤ ጐነጐነ
She braids her hair every evening. ጸጉሯን ፡ ማ
ታ ፡ ማታ ፡ ታሽማለች ፡ (ትጐነጕናለች)

**braid** (n.)
1. ሹሩባ. She redoes her braids every month. ሹሩባዋን ፡ በየወሩ ፡ ትሠራዋለች
2. ጉንጉን. The king's uniform was resplendent in gold braid and medals. የንጉሡ ፡ የወታደ
ር ፡ ልብስ ፡ በወርቅ ፡ ጉንጉንና ፡ በኒሻኖች ፡ አ
ጊጧል

**braided**
*She wears her hair braided. ሹሩባ ፡ ትሠራለች

**brain** አንጐል
The bullet had penetrated his brain. ጥይቱ ፡ አ
ንጐሉን ፡ ነክቶታል
He hasn't a brain in his head. አንጐል ፡ የለውም

**brains** አእምሮ
Nature endowed her with both beauty and brains. ተፈጥሮ ፡ ውበትና ፡ አእምሮ ፡ ዐድሏታል
[See also 'rack']

**braise** በመጠኑ ፡ ጠበሰ
She braised the chicken for the dinner. ለእራት ፡ ዶሮውን ፡ በመጠኑ ፡ ጠበሰችው

**brake** (v.) ፍሬን ፡ ያዘ
The driver braked suddenly, so I crashed into him. ነጂው ፡ በድንገት ፡ ፍሬን ፡ ስለያዘ ፡ ገጨሁት

**brake** (n.) ፍሬን
The brake doesn't work. ፍሬኑ ፡ አይሠራም

**apply the brakes** ፍሬን ፡ ያዘ
He did not apply the brakes in time. ፍሬኑን ፡ በጊዜው ፡ አልያዘም

**put on the brake** ፍሬን ፡ ያዘ
He put on the brake, and the car slowed down to a stop. ፍሬኑን ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፡ መኪናው ፡ ዝግ ፡
ብሎ ፡ ቆመ

**branch** (v.) ተከፋፈለ
The road branches at the bottom of the hill. መንገዱ ፡ ጋራው ፡ ሥር ፡ ሲደርስ ፡ ይከፋፈላል

**branch off** ተለያየ ፤ ተገነጠለ
The road branches off here. መንገዱ ፡ እዚህ ፡
ይለያያል
This road branches off to Harar. ይህ ፡ መንገ
ድ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ የሚገነጠል ፡ ነው

**branch out**
1. ተሰራጨ. A successful business will soon branch out over the country. የተሳካ ፡ የንግድ ፡

ሥራ ፡ በቅርቡ ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ይሰራጫል
2. የንግድ ፡ ሥራ ፡ አስፋፋ. My uncle is thinking of branching out by opening another hotel in the city. አጐቴ ፡ ሌላ ፡ ሆቴል ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ በመክፈት ፡ የንግድ ፡ ሥራውን ፡ ሊያስፋፋ ፡ ያስባል

**branch** (n.)
1. ቅርንጫፍ. The wind broke off several branches. ነፋሱ ፡ ብዙ ፡ ቅርንጫፎችን ፡ ገነጣጠለ Our firm has a branch in Harar. ኩባንያችን ፡ ሐረር ፡ ቅርንጫፍ ፡ አለው
His education encompasses many branches of knowledge. የሱ ፡ ትምህርት ፡ ብዙ ፡ የዕውቀት ፡ ቅርንጫፎች ፡ ያጠቃልላል
2. ክፍል. Chemistry is a branch of science. ኬሚስትሪ ፡ የሳይንስ ፡ ትምህርት ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ነው
[See also 'collateral']

**brand** (v.)
1. ለምልክት ፡ ተኰሰ (ተተኰሰ). Have the new horses been branded yet? አዲሶቹ ፡ ፈረሶች ፡ ገና ፡ ለምልክት ፡ አልተተኰሱም ?
2. ቈጠረ (ተቈጠረ). He was branded as a traitor. እንደ ፡ ከሐዲ ፡ ተቈጠረ

**brand** (n.)
1. ዓይነት. What brand do you smoke? ምን ፡ ዓይነት ፡ ሲጃራ ፡ ታጨሳለህ ?
2. በመተኰስ ፡ የሚደረግ ፡ ምልክት. Brands are put on cattle to show who owns them. ከብቶችን ፡ በመተኰስ ፡ የሚደረጉት ፡ ምልክቶች ፡ ባለቤቱ ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ለማሳወቅ ፡ ነው

**brandish** አቈመዘመዘ
The soldier brandished the sword at his enemy. ወታደሩ ፡ ጎራዴውን ፡ በጠላት ፡ ላይ ፡ አቈመዘመዘው

**brand-new** ፍጹም ፡ አዲስ
My car is brand-new. የኔ ፡ መኪና ፡ ፍጹም ፡ አዲስ ፡ ናት

**brash** የብልግና
The student was punished for his brash behavior. ተማሪው ፡ በብልግና ፡ ጠባዩ ፡ ተቀጣ
*The student gave a brash answer without thinking. ተማሪው ፡ አፉ ፡ እንዳመጣለት ፡ መለሰ

**brass** ነሐስ
Brass is used for bells. ነሐስ ፡ ለደወል ፡ ያገለግላል

**brat** ቀበጥ
His younger brother is a brat. ታናሽ ፡ ወንድሙ ፡ ቀበጥ ፡ ነው

**brave** (v.)
1. ተቋቋመ. He braved the king's anger. የንጉሡን ፡ ቊጣ ፡ ተቋቋመ
2. በቈራጥነት ፡ ተጋፈጠ. He braved death on the battlefield many times. በጦር ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ሞትን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ በቈራጥነት ፡ ተጋፈጠ

**brave** (adj.)
1. ጀግና. His father was a brave warrior. አባቱ ፡ ጀግና ፡ ጦረኛ ፡ ነበሩ
2. የጀግንነት. The braggart told of his brave deeds in the war. ጉረኛው ፡ ሰው ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ስለፈጸማቸው ፡ የጀግንነት ፡ ሥራዎች ፡ አወራ
3. ደፋር. He is a brave boy; hyenas do not frighten him. ደፋር ፡ ልጅ ፡ ነው ፤ ጅቦች ፡ አያስደነግጡትም
4. ታጋሽ. She was brave in her affliction. በመከራዋ ፡ ጊዜ ፡ ታጋሽ ፡ ነበረች
*It was brave of him to enter the burning building. ከሚነደው ፡ ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ መግባቱ ፡ ጀግንነት ፡ ነበር

**brave act** ጀብዱ
His brave act redeemed his faults. ጀብዱው ፡ ጥፋቱን ፡ ሰረዘለት

**bravely** ከፍ ፡ ባለ ፡ ጉብዝና
Our troops held their ground bravely. ወታደሮቻችን ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጉብዝና ፡ ቦታቸውን ፡ ሳያስነኩ ፡ ቆዩ

**bravery** ጀግንነት
The general decorated four soldiers for bravery. ጀኔራሉ ፡ አራት ፡ ወታደሮችን ፡ ስለ ፡ ጀግንነታቸው ፡ ሸለሟቸው

**bravo!** ጎሽ
Bravo! You did a good job, Kathy. ካቲ ፡ ጎሽ ! ጥሩ ፡ ሥራ ፡ ሠራሽ !

**brawl** (v.) ተራበሸ
The youngsters brawled in the street at midnight. በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ ወጣቶች ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ይረብሹ ፡ ነበር

**brawl** (n.) ረብሻ ፤ ጥል
They were arrested because of a brawl. በረብሻ ፡ ምክንያት ፡ ተያዙ
Several men were wounded in the brawl. በጥሉ ፡ ጊዜ ፡ አያሌ ፡ ሰዎች ፡ ቈሰሉ

**bray** አናፋ
The donkey brayed all night. አህያው ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ አናፋ

**brazen**

1. ከነሐስ ፡ የተሠራ. The brazen door handles need to be polished. ከነሐስ ፡ የተሠራው ፡ የመዝጊያው ፡ እጀታ ፡ መጠረግ ፡ ያስፈልገዋል
2. ኀፍረተ ፡ ቢስ. The brazen girl told lie after lie. ኀፍረተ ፡ ቢሷ ፡ ልጅ ፡ ደጋግማ ፡ ዋሸች

**brazier** [የከሰል ፡ ማንደጃ ፡ ብረት]

**breach** (v.) ጣሰ
The enemy's fierce attack finally breached our lines. የጋለው ፡ የጠላት ፡ ማጥቃት ፡ በመጨረሻው ፡ ማንባራችንን ፡ ጣሰ

**breach** (n.)
1. ጉድባ. There is a breach in the hedge. ቁጥቋጦው ፡ ውስጥ ፡ ጉድባ ፡ አለ
2. ቅሬታ. There was never a breach between the two friends. በሁለቱ ፡ ጓደኞች ፡ መሀከል ፡ ቅሬታ ፡ ተፈጥሮ ፡ አያውቅም

**breach of duty** ኀላፊነትን ፡ መዘንጋት
For me, to leave work today would be a breach of duty. ዛሬ ፡ ከሥራ ፡ መቅረት ፡ ኀላፊነትን ፡ መዘንጋት ፡ ሆኖ ፡ ይሰማኛል

**breach of rules** ሕግ ፡ መጣስ
His smoking was considered a breach of the rules. ማጨሱ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ መጣስ ፡ ተቈጥሮ ፡ ነበር

**make a breach in** ገመሰ
The cannon made a breach in the wall. መድፉ ፡ ግድግዳውን ፡ ገመሰው

**bread**
1. እንጀራ. Ethiopian bread looks nothing like American bread. የኢትዮጵያ ፡ እንጀራ ፡ ከአሜሪካን ፡ ዳቦ ፡ ጋር ፡ በምንም ፡ አይመሳሰልም
2. ዳቦ. Please slice the bread. ዳቦውን ፡ ቈራርሰው

**bread crumbs** ፍርፋሪ
He left bread crumbs all over the table. በጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ በሙሉ ፡ ፍርፋሪ ፡ አስቀረ

**earn one's bread**
*How does he earn his bread? ምን ፡ ሠርቶ ፡ ይበላል ?

**loaf of bread** ዳቦ
We need two loaves of bread. ሁለት ፡ ዳቦ ፡ ያስፈልገናል
[See also 'cut']

**breadth** ስፋት
The breadth of this room is ten feet. የዚህ ፡ ክፍል ፡ ስፋት ፡ ዐሥር ፡ ጫማ ፡ ነው
*A tolerant person usually has breadth of mind. ቻይ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አእምሮ ፡ ሰፊ ፡ ነው

**break** (broke, broken), vt.
1. ሰበረ. The boys have broken the window. ልጆቹ ፡ መስኮቱን ፡ ሰበሩ
Bombing broke the enemy's resistance. የቦምብ ፡ ድብደባ ፡ የጠላትን ፡ የመከላከል ፡ ኀይል ፡ ሰበረው
The runner broke the old record. ሯጩ ፡ የቀድሞውን ፡ ክብረ ፡ ወሰን ፡ ሰበረ
2. (part of body) ተሰበረ. I broke my leg. እግሬን ፡ ተሰበርኩ
3. በጠሰ. He broke the string. ሲባጎውን ፡ በጠሰው
The prisoner broke his bonds and escaped. እስረኛው ፡ ሰንሰለቱን ፡ በጥሶ ፡ አመለጠ
4. ቀነሰ. The thick hedge breaks the force of the wind. ጥቅጥቅ ፡ ያለው ፡ የቁጥቋጦ ፡ አጥር ፡ የነፋሱን ፡ ኀይል ፡ ይቀንሰዋል
5. ተወ ፤ አስወገደ. He broke the habit of smoking. ሲጋራ ፡ የማጨስ ፡ ልምዱን ፡ ተወ ፡ (አስወገደ)
6. አፈረሰ. The company refused to break the contract. ኩባንያው ፡ ውሉን ፡ አላፈርስም ፡ አለ
Why do you always break your appointments with me? ለምን ፡ ሁልጊዜ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ያለህን ፡ ቀጠሮ ፡ ታፈርሳለህ ?
7. ጣሰ. He has broken the law. ሕጉን ፡ ጥሷል
8. ዐጠፈ. He won't break his word. ቃሉን ፡ አያጥፍም
9. አጣራ. The police needed only a week to break that case. ያንን ፡ ጉዳይ ፡ ለማጣራት ፡ ፖሊሶች ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ብቻ ፡ ወሰደባቸው
10. ገለጸ. They will break the story tomorrow. ጉዳዩን ፡ ነገ ፡ ይገልጹታል
11. ገራ. You have to break a horse before you can ride it. ፈረስን ፡ ከመጋለብህ ፡ በፊት ፡ መግራት ፡ አለብህ
12. አወከ. The braying of the donkey broke the silence. የአህያ ፡ ማናፋት ፡ ጸጥታውን ፡ አወከ

**break** (vi.)
1. ተሰበረ. Glass breaks easily. መስታወት ፡ በቀላሉ ፡ ይሰበራል
2. ተበጠሰ. He pulled too hard, and the string broke. በጣም ፡ ስለሳበው ፡ ገመዱ ፡ ተበጠሰ
3. ገለጠ. The clouds broke, and the sun shone through. ደመናው ፡ ገለጠና ፡ ፀሐይዋ ፡ ትታይ ፡ ጀመር
4. (= tr.) አፈረጠ. The blister broke when he pricked it. ውኃ ፡ የቋጠረውን ፡ እጁን ፡ በመርፌ ፡ ወግቶ ፡ አፈረጠው

5. ከሰረ. When the bank broke, most people lost their money. ባንኩ ፡ ሲከስር ፡ አብዛኞቹ ፡ ሰዎች ፡ ገንዘባቸውን ፡ አጡ
6. ተቈራረጠ. I broke with my old friend when he failed to keep his word. ቃሉን ፡ ስላላከበረ ፡ ከቆየ ፡ ጓደኛዬ ፡ ጋር ፡ ተቈራረጥኩ
*The woman's heart broke when her husband died. ሴትዮዋ ፡ ባሏ ፡ ስለሞተ ፡ ከባድ ፡ ሐዘን ፡ ደረሰባት

**break away** ተፈተለከ
The runners broke away before the signal gun was fired. ምልክቱ ፡ ሳይተኰስ ፡ ሯጮቹ ፡ ተፈተለኩ

**break down** (vt.) ሰበረ
The vehemence of his attack broke down the door. የምቱ ፡ ኀይለኛነት ፡ መዝጊያውን ፡ ሰበረ

**break down** (vi.)
1. ተበላሸ. The machine broke down this morning. መኪናው ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ ተበላሸ
2. ተደረመሰ. The bridge broke down during the flood. በጐርፍ ፡ ጊዜ ፡ ድልድዩ ፡ ተደረመሰ
3. ተሰበረ. The loaded truck broke down. ጭነት ፡ የበዛበት ፡ መኪና ፡ ተሰበረ
4. ከው ፡ አለ. He broke down when he heard the news. ወሬውን ፡ ሲሰማ ፡ ከው ፡ አለ
*The thief denied stealing it, but broke down under questioning and admitted it. ሌባው ፡ መስረቁን ፡ ካደ ፤ ግን ፡ በጥብቅ ፡ ሲመረመር ፡ ተስፋ ፡ ቈርጦ ፡ እውነቱን ፡ አወጣ

**break even**
1. ሳፈ ፡ ለሳፈ ፡ ተለያዩ. They played cards all evening and broke even. ካርታ ፡ ሲጫወቱ ፡ አምሽተው ፡ ሳፈ ፡ ለሳፈ ፡ ተለያዩ
2. ትርፍም ፡ ኪሳራም ፡ የለበት. He is just breaking even and can now start a new business. ትርፍም ፡ ኪሳራም ፡ ስለሌለበት ፡ አሁን ፡ አዲስ ፡ ንግድ ፡ ሊጀምር ፡ ይችላል

**break in** (vt.) አሠለጠነ
I will have to break in another beginner. አዲስ ፡ ጀማሪ ፡ ማሠልጠን ፡ አለብኝ

**break in** (vi.)
1. ጣልቃ ፡ ገባ. Don't break in on the conversation when elders talk. ሽማግሌዎች ፡ ሲጫወቱ ፡ ጣልቃ ፡ አትግባ
2. ቤቱን ፡ ሰበረ. Someone broke in and made off with all our money. አንድ ፡ ሰው ፡ ቤታችንን ፡ ሰብሮ ፡ ንብረታችንን ፡ ዘረፈን

**break into**
1. ሰብሮ ፡ ገባ. Last night thieves broke into our neighbor's house. ትላንትና ፡ ሌሊት ፡ ሌቦች ፡ የጐረቤታችንን ፡ ቤት ፡ ሰብረው ፡ ገቡ
2. ጥልቅ ፡ አለ. He broke into the conversation at a crucial moment. በጭውውቱ ፡ አፍላ ፡ ላይ ፡ ጥልቅ ፡ አለ

**break (the) news** ዜና ፡ ነገረ
We will have to break the news to him gently. ዜናውን ፡ በእርጋታ ፡ ልንነግረው ፡ ይገባል

**break (the) news of one's death** አረዳ
Since he is ill, let us not break the news of his wife's death to him soon. ስለታመመ ፡ የሚስቱን ፡ ሞት ፡ ቶሎ ፡ አናርዳው

**break (oneself) of the habit of** ተወ
I am trying to break myself of the habit of smoking. ሲጃራ ፡ ለመተው ፡ እታገላለሁ

**break off** (vt.)
1. አቋረጠ. They have broken off relations. ግንኙነታቸውን ፡ አቋርጠዋል
2. ገነጠለ. The storm broke off the top of our big tree. ዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ የትልቁን ፡ ዛፋችን ፡ ጫፍ ፡ ገነጠለው
3. ሰበረ. He broke off the handle. እጀታውን ፡ ሰበረው

**break off** (vi.)
1. ተገነጠለ. The branch broke off in the storm. ቅርንጫፉ ፡ በዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ተገነጠለ
2. ንግግሩን ፡ አቆመ. He broke off in the middle of a sentence. ዐረፍተ ፡ ነገሩን ፡ ሳይጨርስ ፡ ንግግሩን ፡ አቆመ
3. (a piece) ተሸረፈ. +A piece broke off my cup. ሲኒዬ ፡ ተሸረፈ

**break off a piece (of bread)** ቈረሰ
He broke off a piece of bread and ate it. ከዳቦው ፡ ላይ ፡ ቈርሶ ፡ በላ

**break open** (vi.) ሰብሮ ፡ ከፈተ
The thief broke open the cashbox. ሌባው ፡ የገንዘቡን ፡ ካዝና ፡ ሰብሮ ፡ ከፈተው

**break open** (vi.) በመሰበሩ ፡ ተከፈተ
When the box fell, it broke open. ሣጥኑ ፡ ሲወድቅ ፡ በመሰበሩ ፡ ተከፈተ

**break out**
1. ተነሣ. The fire broke out toward midnight. እሳቱ ፡ በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ ገደማ ፡ ተነሣ
The war broke out last year. ጦርነቱ ፡ ዓምና ፡ ተነሣ
2. ገባ. Measles broke out in Harar. ሐረር ፡ ኩፍኝ ፡ ገብቷል
3. አመለጠ. He broke out of prison. ከእስር ፡ ቤት ፡ አመለጠ
4. በድንገት ፡ ተለወጠ. The discussion broke out into a fight. ውይይቱ ፡ በድንገት ፡ ወደ ፡ ድብድብ ፡ ተለወጠ

5. ተከተለ. After the death of the king, anarchy broke out. ከንጉሡ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ግርግር ፡ ተከተለ

**break through**
1. ጥሶ ፡ ወጣ. The cattle have broken through the fence. ከብቶች ፡ አጥሩን ፡ ጥሰው ፡ ወጡ
2. ጥሶ ፡ ሄደ. The hunters broke through the underbrush. አዳኞቹ ፡ ቁጥቋጦውን ፡ ጥሰው ፡ ሄዱ

**break up** (vt.)
1. ሰባበረ. He broke up the boxes for firewood. ሣጥኖቹን ፡ ለማገዶ ፡ ሰባበራቸው
2. በተነ. The opposition tried to break up the meeting. የተቃዋሚው ፡ ወገን ፡ ስብሰባውን ፡ ለመበተን ፡ ሞከረ
3. ከሰከሰ. The farmer broke up the clods of earth with a pickaxe. ገበሬው ፡ ጓሉን ፡ በዶማ ፡ ከሰከሰው

**break up** (vi.)
1. ተበተነ. The meeting broke up in confusion. ስብሰባው ፡ በብጥብጥ ፡ ተበተነ
2. ፈረሰ. Their marriage broke up last year. ጋብቻቸው ፡ ዓምና ፡ ፈረሰ
3. ተቈራረጠ. After this, the two friends broke up. ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱ ፡ ጓደኞሞች ፡ ተቈራረጡ

**the day broke** ጐሕ ፡ ቀደደ
Day was beginning to break when we left. ስንሄድ ፡ ጐሕ ፡ መቅደድ ፡ ጀምሮ ፡ ነበር
[See also 'engagement, ground, heart, laughter, loose, peace, piece, resistance, wind']

**break** (n.)
1. ዕረፍት ፤ ፋታ. He spoke all day without a break. ቀኑን ፡ በሙሉ ፡ ያለ ፡ ዕረፍት ፡ ተናገረ
This morning I have been doing this work without a break. ዛሬ ፡ ጧት ፡ ይህንኑ ፡ ሥራ ፡ ያላንዳች ፡ ፋታ ፡ እሠራ ፡ ነበር
2. ግንኙነት ፡ መቋረጥ. A break between the two countries can no longer be avoided. በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መኻል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ መቋረጥ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሊወገድ ፡ አይችልም
3. (= verb.). There was a break in the window. መስኮቱ ፡ ተሰንጥቆ ፡ ነበር

**give a break** ዕድል ፡ ሰጠ
He did not do too well on his examination, but let's give him a break and let him pass. በፈተናው ፡ ጥሩ ፡ አልሠራም ፡ ግን ፡ ዕድል ፡ እንስጠውና ፡ ይለፍ

**take a break** ዕረፍት ፡ አደረገ
Let's take a five-minute break at three! በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ ያምስት ፡ ደቂቃ ፡ ዕረፍት ፡ እናድርግ

**breakable** ተሰባሪ
This glass is breakable. ይህ ፡ ብርጭቆ ፡ ተሰባሪ ፡ ነው

**breakage** የተሰበሩ ፡ እቃዎች
The insurance company had to pay a lot of money for the breakage. የኢንሹራንስ ፡ ኩባንያው ፡ ለተሰበሩት ፡ እቃዎች ፡ ብዙ ፡ መክፈል ፡ ነበረበት
*Shipping crates have to be carefully made to prevent breakage. እቃዎች ፡ እንዳይሰበሩ ፡ የሚላኩባቸው ፡ ሣጥኖች ፡ በጥንቃቄ ፡ መሠራት ፡ አለባቸው

**breakdown**
1. ብልሽት. A breakdown of the machinery stopped production. የመኪናው ፡ ብልሽት ፡ የሥራውን ፡ ውጤት ፡ አቆመው
The attack aborted because of a breakdown in communication. ከመገናኛ ፡ ብልሽት ፡ የተነሣ ፡ የተደረገው ፡ ጥቃት ፡ ከሸፈ
2. የአእምሮ ፡ ሁከት. He had a breakdown due to strain. ከጭንቀት ፡ የተነሣ ፡ የአእምሮ ፡ ሁከት ፡ ደረሰበት

**make a breakdown**
*The boss asked me to make a breakdown of the time I spent on the job. አለቃዬ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የቆየሁበትን ፡ ጊዜ ፡ በየሥራው ፡ ዓይነት ፡ እንድዘረዝር ፡ ጠየቀኝ

**breakfast** ቁርስ
I eat breakfast at 8 o'clock. ቁርስ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ እበላለሁ

**breakup** መለያየት
The breakup between the two friends was due to an argument. የሁለቱ ፡ ጓደኞሞች ፡ መለያየት ፡ የመጣው ፡ በክርክሩ ፡ ምክንያት ፡ ነው

**breast**
1. ደረት. When her son died, she wept and beat her breast. ልጇ ፡ ሲሞት ፡ ደረቷን ፡ እየመታች ፡ አለቀሰች
2. ጡት. Her dress slipped, revealing gently rounded breasts. ቀሚሷ ፡ ሲወርድ ፡ ሙልሙል ፡ ያሉት ፡ ጡቶቿ ፡ ታዩ

**breast stroke** የደረት ፡ ቀዘፋ
He uses the breast stroke in swimming. በደረት ፡ ቀዘፋ ፡ ይዋኛል

**breath** ትንፋሽ
His breath came in gasps. ትንፋሹ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ አለ
Hold your breath! ትንፋሽህን ፡ ዋጥ ፡ አድርገህ ፡ ያዘው !

**catch one's breath**
I have to catch my breath first. መጀመሪያ ፡ ትንፋሼ ፡ ይመለስ

**draw a breath**
Draw a deep breath! በኀይል ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ትንፋሽ ፡ ሳብ

**hold one's breath** ነፍሱ ፡ ተጨነቀች
We held our breath while we watched the man climbing the tall building. ሰውዬው ፡ ረጂም ፡ ሕንጻ ፡ ላይ ፡ ሲወጣ ፡ ስንመለከት ፡ ነፍሳችን ፡ ተጨነቀች

**in a breath** ከመቅጽበት
It all happened in a breath. ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሆነው ፡ ከመቅጽበት ፡ ነው

**in the same breath** ያኔውኑ
She lost her temper and apologized in the same breath. ተቈጥታ ፡ ያኔውኑ ፡ ይቅርታ ፡ ለመነች

**(be) out of breath** ትንፋሽ ፡ አጠረው ፤ ትንፋሹ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ አለ
I am out of breath from running. ከመሮጤ ፡ የተነሣ ፡ ትንፋሽ ፡ አጥሮኛል
The portly gentlemen was out of breath from climbing the steps. ወፍራሙ ፡ ሰውዬ ፡ ደረጃውን ፡ ሲወጣ ፡ ትንፋሹ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ አለ

**take a breath** ትንፋሽ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ሳበ
The nurse said to the patient "take a deep breath"! ነርሷ ፡ በሽተኛውን ፡ በኀይል ፡ ትንፋሽህን ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ሳብ ፡ አለችው

**under one's breath** በሆዱ
He muttered a curse under his breath. በሆዱ ፡ ተሳደበ

## breathe
1. ተነፈሰ. He is breathing regularly. በደንብ ፡ ይተነፍሳል
2. ተንፈስ ፡ አለ. I can breathe easier now that the work is done. ሥራው ፡ ስላለቀ ፡ ተንፈስ ፡ ልል ፡ እችላለሁ

**breathe again** እፎይ ፡ አለ
Now that he is gone, we can breathe again. አሁን ፡ ስለሄደ ፡ እፎይ ፡ ለማለት ፡ እንችላለን

**breathe hard** ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰ
She was breathing hard from the long climb up the hill. ረዥሙን ፡ ዳገት ፡ በመውጣቷ ፡ ቁና ፡ ቁና ፡ ትተነፍስ ፡ ነበር

**not breathe a word**
Don't breathe a word of this to anyone! ይህንን ፡ ለማንም ፡ አትተንፍስ

## breathing መተንፈስ
Breathing is more difficult at very high altitudes. ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ለመተንፈስ ፡ ያስቸግራል

## (be) breathless ትንፋሽ ፡ አጠረ(ው)
The spectators were breathless with excitement. ተመልካቾቹ ፡ ከደስታ ፡ የተነሣ ፡ ትንፋሽ ፡ አጠራቸው

**leave one breathless** ትንፋሹን ፡ ቈረጠው
The climb left him breathless. ዳገቱን ፡ መውጣት ፡ ትንፋሹን ፡ ቈረጠው

## (be) breathtaking ልብ ፡ አጠፋ
The view from the mountain top is breathtaking. ከተራራው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ ትዕይንት ፡ ልብ ፡ ያጠፋል

## bred, see breed

## breeches ጠባብ ፡ ሱሪ
His breeches were torn in the seat. ጠባብ ፡ ሱሪው ፡ መቀመጫው ፡ ላይ ፡ ተቀዷል

## breed (bred), vt.
1. አረባ. My uncle breeds horses. አጐቴ ፡ ፈረስ ፡ ያረባል
2. አመጣ. Dirt breeds disease. ቆሻሻ ፡ በሽታ ፡ ያመጣል
3. አስከተለ. War breeds misery and ruin. ጦርነት ፡ ችግርና ፡ ጥፋትን ፡ ያስከትላል

**breed** (vi.)
1. ተፈለፈለ. Birds breed in the spring. ወፎች ፡ በጸደይ ፡ ወራት ፡ ይፈለፈላሉ
2. ረባ. Cattle breed in the spring. የቀንድ ፡ ከብት ፡ የሚረባው ፡ በጸደይ ፡ ነው
3. ተራባ. Rabbits breed rapidly. ጥንቸሎች ፡ በፍጥነት ፡ ይራባሉ
*He was born and bred a gentleman. ትውልዱም ፡ አስተዳደጉም ፡ የጨዋ ፡ ነው

## breed (n.) ዘር
Fertile cattle are needed to improve the breed. ዘሩን ፡ ለማሻሻል ፡ ወላድ ፡ የቀንድ ፡ ከብት ፡ ያስፈልጋል
*She comes from a fine breed of people. ከመልካም ፡ ዘር ፡ ትወለዳለች

## breeding
1. አስተዳደግ. His manners show good breeding. ጠባዩ ፡ ጥሩ ፡ አስተዳደጉን ፡ ያሳያል

2. ጥሩ ፡ አስተዳደግ. You can tell when a girl has breeding. ጥሩ ፡ አስተዳደግ ፡ ያላትን ፡ ልጅ ፡ ለ ማወቅ ፡ ትችላለህ
3. ማርባት. Careful breeding of livestock will improve the meat. ከብቶችን ፡ በጥንቃቄ ፡ ማር ባት ፡ የተሻለ ፡ ሥጋ ፡ ያስገኛል

**breeding ground** መርቢያ
This marshland is a breeding ground for mosquitos. ይህ ፡ ረግረግ ፡ ስፍራ ፡ የወባ ፡ ትንኝ ፡ መርቢያ ፡ ነው

**man of breeding** የጨዋ ፡ ልጅ
His uncle is a man of breeding. አጎቱ ፡ የጨ ዋ ፡ ልጅ ፡ ነው

**brethren,** see **brother**

**breeze** የነፋስ ፡ ሽውታ ፤ ለስላሳ ፡ ነፋስ
The breeze ruffled her hair. የነፋሱ ፡ ሽውታ ፡ (ለስላሳው ፡ ነፋስ) ፡ ጸጉሯን ፡ በታተነው
[See also 'fly, whip']

**brevity** ማጠር
Thanks to the brevity of his speech, the meeting was soon over. ከንግግሩ ፡ ማጠር ፡ የተነሣ ፡ ስ ብሰባው ፡ በቶሎ ፡ አለቀ

**brew**
1. ጠመቀ. We brew our own beer. የራሳችንን ፡ ጠላ ፡ እንጠምቃለን
2. ጠነሰሰ. Children are good at brewing mischief. ልጆቹ ፡ ነገር ፡ መጠንሰስ ፡ ይሆንላቸዋል

**be brewing** ተጠነሰሰ
There is trouble brewing between them. በመሀከላቸው ፡ ችግር ፡ ተጠንስሷል

**brewery** የቢራ ፡ ፋብሪካ
He has an interest in the brewery. በቢራ ፡ ፋ ብሪካ ፡ ውስጥ ፡ ጥቅም ፡ አለው

**bribe** (v.) በጉቦ ፡ ደለለ ፤ ጉቦ ፡ ሰጠ ፤ በገንዘ ብ ፡ አባበለ
You cannot bribe him. በጉቦ ፡ ልትደልለው ፡ አትችልም
He bribed the guard by giving him a gold watch. ለዘበኛው ፡ ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ ሰዓት ፡ ጉቦ ፡ ሰጠው
It is difficult to bribe an incorruptible witness. ሊታለል ፡ የማይችልን ፡ ምስክር ፡ በገንዘብ ፡ ማ ባበል ፡ አይቻልም

**bribe** (n.) ጉቦ
He was caught accepting a bribe. ጉቦ ፡ ሲቀበ ል ፡ ተያዘ

**take bribes** ጉቦ ፡ በላ
Taking bribes is punishable by law. ጉቦ ፡ መ ብላት ፡ በሕግ ፡ ያስቀጣል

**bribery** ጉቦ ፡ መብላት
Bribery has corrupted many a judge. ጉቦ ፡ መ ብላት ፡ ብዙ ፡ ዳኞችን ፡ በክሏቸዋል

**brick** ጡብ
Their house is built of red bricks. ቤታቸው ፡ የተሠራው ፡ በቀይ ፡ ጡብ ፡ ነው

**bricklayer** ጡብ ፡ ገንቢ
A bricklayer gets a good salary. ጡብ ፡ ገንቢ ፡ ጥሩ ፡ ደሞዝ ፡ ያገኛል

**bricklaying** ግንብ ፡ አሠራር
That is a skillful piece of bricklaying. ይህ ፡ ጥበብ ፡ ያለበት ፡ ግንብ ፡ አሠራር ፡ ነው

**bridal** የሙሽራ
Her bridal gown was red. የሙሽራ ፡ ልብሷ ፡ ቀይ ፡ ነበር

**bride** ሙሽራ
The bride wore white, and the bridegroom wore a dark suit. ሙሽራዋ ፡ ነጭ ፡ ሙሽራው ፡ ጥቁ ር ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ ነበር

**bridegroom** ሙሽራ
The bridegroom wore a dark suit. ሙሽራው ፡ ጥቁር ፡ ሙሉ ፡ ልብስ ፡ ለብሷል

**bride price** [ሙሽራው ፡ ወይም ፡ ቤተሰቡ ፡ ለ ሙሽራይቱ ፡ ቤተሰቦች ፡ የሚያበረክታቸው ፡ የገንዘብ ፡ ወይም ፡ የእቃ ፡ ስጦታ]

**bridesmaid** ደንገጡር
The bridesmaid walked behind the bride. ደንገጡሯ ፡ ከሙሽራዋ ፡ በስተኋላ ፡ ትሄድ ፡ ነበር

**bridge** (v.)
1. ድልድይ ፡ ሠራ. The engineers bridged the river. መሀንዲሶቹ ፡ በወንዙ ፡ ላይ ፡ ድልድይ ፡ ሠሩ
2. ተጋደመ. A log bridged the brook. ግንዱ ፡ ምንጩ ፡ ላይ ፡ ተጋደመ
3. አስወገደ. Politeness will bridge many difficulties. ትሕትና ፡ ብዙ ፡ ችግሮችን ፡ ያስወ ግዳል

**bridge** (n.) ድልድይ
There is a bridge a mile from here. ከዚህ ፡ አን ድ ፡ ማይል ፡ ርቆ ፡ ድልድይ ፡ ይገኛል

**burn his bridges**
*He burned his bridges behind him. ወደ ፡ ኋላ ፡ ሊመለስ ፡ የሚችልበትን ፡ መንገድ ፡ አበላሸ

**bridgehead** [ከዋናው ፡ ዘማች ፡ ቀደም ፡ በሚሄድ ፡ ጓድ ፡ በጠላት ፡ ጠረፍ ፡ ላይ ፡ የሚሠራ ፡ የጦር ፡ አቋም]

**bridle** (v.)
1. ለጐመ. He bridled the mule. በቅሎዋን ፡ ለጐመ
2. ገታ. You must bridle your anger. ንዴትህን ፡ መግታት ፡ አለብህ

**bridle** (n.) ልጓም
The Ethiopian bridle hurts the mule. የኢትዮጵያ ፡ ልጓም ፡ በቅሎ ፡ ይጐዳል

**brief** (v.) የመምሪያ ፡ መግለጫ ፡ ሰጠ
The captain briefed the soldiers. ሻምበሉ ፡ ለወታደሮቹ ፡ የመምሪያ ፡ መግለጫ ፡ ሰጣቸው

**brief** (n.) አጭር ፡ መግለጫ
His brief was printed in the newspaper. የሰጠው ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ በጋዜጣ ፡ ታተመ

**brief** (adj.) አጭር
His speech was brief but to the point. ንግግሩ ፡ አጭርና ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ነበር

**be brief** ንግግሩን ፡ አሳጠረ
Please be brief; we have to leave in a few minutes. ንግግርህን ፡ አሳጥረው ፤ ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በኋላ ፡ መሄድ ፡ አለብን

**in brief** ባጭሩ
In brief, our plan is this. ባጭሩ ፡ እቅዳችን ፡ ይህ ፡ ነው

**briefcase** ቦርሳ
There were important papers in my briefcase. ቦርሳዬ ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ጉዳዮች ፡ የያዙ ፡ ወረቀቶች ፡ ነበሩ

**brigade** ብርጌድ
The brigade is stationed on the border. ብርጌዱ ፡ ወሰን ፡ ላይ ፡ ተመደበ
[See also 'fire brigade']

**brigand** ቀማኛ
The brigand eluded the police and escaped. ቀማኛው ፡ ፖሊሱን ፡ አታሎ ፡ አመለጠ

**bright**
1. ደማቅ. She likes to wear bright colors. ደማቅ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ ልብስ ፡ መልበስ ፡ ትወዳለች
2. ብሩህ. Sunshine is bright. የፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ብሩህ ፡ ነው
His bright face was alight with happiness. ብሩህ ፡ ፊቱ ፡ በደስታ ፡ ፈካ
3. በግ ፡ ያለ. I like a bright fire. በግ ፡ ያለ ፡ እሳት ፡ እወዳለሁ
4. ንጹሕ. The bright water trickled through his fingers. ከእጁ ፡ ላይ ፡ ንጹሕ ፡ ውኃ ፡ ይንጠባጠብ ፡ ነበር
5. ጥሩ. He has a bright future. ወደፊት ፡ ጥሩ ፡ ዕድል ፡ አለው
6. አስደሳች. She always has a bright smile. ሁልጊዜ ፡ አስደሳች ፡ ፈገግታ ፡ አላት
7. ብልህ. That was a bright idea. ብልህ ፡ የሆነ ፡ ሐሳብ ፡ ነበረ
He is a bright boy. ብልህ ፡ ልጅ ፡ ነው
*Rub the silver cup to a bright polish! የብር ፡ ዋንጫውን ፡ እስኪያንጸባርቅ ፡ ወልውለው

**brighten** (vt.)
1. አደመቀ. Flowers brighten a room. አበቦች ፡ ክፍልን ፡ ያደምቃሉ
2. ደስተኛ ፡ አደረገ. Her smile has brightened my day. ፈገግታዋ ፡ ቀኑን ፡ በሙሉ ፡ ደስተኛ ፡ አደረገኝ

**brighten** (vi.)
1. ጠራ. The sky brightened. ሰማዩ ፡ ጠራ
2. ፈካ. Her face brightened. ፊቷ ፡ ፈካ

**brightness** ድምቀት
The flowers lend brightness to the room. አበቦች ፡ ለክፍሉ ፡ ድምቀት ፡ ይሰጣሉ

**brilliance**
1. ማንጸባረቅ. The brilliance of a diamond makes it desirable. የዕንቁ ፡ ማንጸባረቅ ፡ ተፈላጊ ፡ ያደርገዋል
2. ቅልጥፍና. Her brilliance as a pianist was known all over the world. በፒያኖ ፡ ተጫዋችነት ፡ ያላት ፡ ቅልጥፍና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የታወቀ ፡ ነው
3. ብልህነት. His brilliance put his teacher in the shade. በብልህነቱ ፡ መምህሩን ፡ አስናቀ

**brilliant**
1. ደማቅ. You can tell his paintings by the brilliant colors. የርሱን ፡ ሥዕሎች ፡ በደማቅ ፡ ቀለሞች ፡ ለመለየት ፡ ትችላለህ
2. የሚያንጸባርቅ. The brilliant jewels were admired by all. የሚያንጸባርቁት ፡ ጌጣ ፡ ጌጥ ፡ በሁሉም ፡ ተደንቀዋል
3. ድንቅ. He is a brilliant speaker. ድንቅ ፡ ተናጋሪ ፡ ነው
4. ብልህ. He is the most brilliant man I know. ከማውቃቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ብልህ ፡ ነው
5. ጐበዝ. He is a brilliant scholar. ጐበዝ ፡ ምሁር ፡ ነው
6. አስደናቂ. The musician gave a brilliant per-

formance last night. ሙዚቀኛው ፡ ትናንት ፡ ምሽት ፡ አስደናቂ ፡ ትርእይት ፡ አሳየ
7. ደምቆ ፡ የታየ. Their wedding was the most brilliant affair of the season. በወቅቱ ፡ ከተደረጉት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ደምቆ ፡ የታየው ፡ የነሱ ፡ ሰርግ ፡ ነበር

**brim**
1. አፍ. The glass is filled to the brim. ብርጭቆው ፡ እስከ ፡ አፉ ፡ ሞልቷል
2. ክፈፍ. The brim of his hat is worn out. የባርኔጣው ፡ ክፈፍ ፡ አልቋል

**bring** (brought)
1. አመጣ. Bring me a glass of water, please. አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ውኃ ፡ አምጣልኝ
What brings you to this town? እዚህ ፡ ከተማ ፡ ምን ፡ እግር ፡ አመጣህ ?
2. ይዞ ፡ መጣ. May I bring a friend with me? ጓደኛዬን ፡ ይዤ ፡ ልምጣ ?
3. አስከተለ. Spring brings birds and flowers. ጸደይ ፡ ወፎችንና ፡ አበቦችን ፡ ያስከትላል
4. አወጣ. These cars will bring a good price. እነዚህ ፡ መኪናዎች ፡ ጥሩ ፡ ዋጋ ፡ ያወጣሉ
5. አስገኘ. Loyalty and hard work are what usually bring an advancement in pay. የደሞዝ ፡ ጭማሪ ፡ የሚያስገኙ ፡ ታማኝነትና ፡ ጠንክሮ ፡ መሥራት ፡ ናቸው
6. አተረፈ. Edison's inventions brought him glory. የኤዲሰን ፡ ፍልሰፋዎች ፡ ክብር ፡ አተረፉለት
*What will the future bring? ወደፊት ፡ ምን ፡ ይመጣ ፡ ይሆን ?

**bring about**
1. አመጣ. The war brought about a change in living standards. ጦርነቱ ፡ በኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ለውጥ ፡ አመጣ
2. አስከተለ. The disappearance of the airplane brought about a search of the area. የአውሮፕላኑ ፡ መጥፋት ፡ በቀበሌው ፡ ፍለጋ ፡ አስከተለ
3. ፈጠረ. Equality between men and women is hard to bring about. በወንዶችና ፡ በሴቶች ፡ መካከል ፡ እኩልነት ፡ ለመፍጠር ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**bring along** ይዞ ፡ መጣ
He brought along his entire staff. ሠራተኞቹን ፡ በሙሉ ፡ ይዞ ፡ መጣ

**bring (someone) around to** አግባብቶ ፡ አሳመነ
He brought me around to his point of view. አግባብቶኝ ፡ በሐሳቡ ፡ አሳመነኝ

**bring back** መለሰ
Please bring the book back! መጽሐፉን ፡ መልስ

**bring down**
1. አወረደ. I also brought down the big box. ትልቁንም ፡ ሣጥን ፡ አወረድኩት
2. ከሥልጣን ፡ አወረደ. The strike brought down the new government. አድማው ፡ አዲሱን ፡ መንግሥት ፡ ከሥልጣን ፡ አወረደው
3. ቀነሰ. I won't buy that lamp unless you bring down the price. ዋጋውን ፡ ካልቀነስክ ፡ መብራቱን ፡ አልገዛህም
4. ተኩሶ ፡ ጣለ. The hunter brought down a mountain goat. አዳኙ ፡ የሚዳ ፡ ፍየሉን ፡ ተኩሶ ፡ ጣለው

**bring face to face**
He brought the enemies face to face. ጠበኞቹን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አጋጠማቸው

**bring forth** አተረፈ(ለት)
His idea brought forth a storm of applause. ያቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ የቀለጠ ፡ ጭብጨባ ፡ አተረፈለት

**bring in**
1. አስገኘ. The dance brought in a hundred dollars. ዳንሱ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ አስገኘ
2. አገባ. Take off the bark before you bring in that log! ያንን ፡ ግንድ ፡ ከማግባትህ ፡ በፊት ፡ ላጠው
3. አመጣ. A camel caravan brings salt in from the desert. የግመል ፡ ግትልትል ፡ ከምድረ ፡ በዳው ፡ ጨው ፡ ያመጣል
4. አቀረበ. She brought his supper in on a tray. እራቱን ፡ በዝርግ ፡ ሳሕን ፡ አቀረበችለት
5. ሳበ. The school's prominence in science brings in many students. የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በሳይንስ ፡ መታወቅ ፡ ብዙ ፡ ተማሪዎችን ፡ ይስባል

**bring on**
1. አስከተለ. This incident will surely bring on a disturbance. ይህ ፡ ጉዳይ ፡ በእርግጥ ፡ ብጥብጥ ፡ ያስከትላል
2. አሳደረ(በት). His smoking cigarettes brought on an attack of coughing. ሲጃራ ፡ ማጨሱ ፡ የሳል ፡ በሽታ ፡ አሳደረበት

**bring out**
1. አወጣ. They are bringing out a new edition of his work. የመጽሐፉን ፡ አዲስ ፡ እትም ፡ ያወጣሉ
2. አውጥቶ ፡ አመጣ. Can't you bring the ball out? ኳሱን ፡ አውጥተህ ፡ ማምጣት ፡ አትችልም ?
*The holiday brought out large crowds. ለበዓሉ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተሰበሰበ

**bring to** ነፍስ ፡ አዘራው
Cold water brought her to. ቀዝቃዛ ፡ ውኃ ፡ ነፍስ ፡ አዘራት

**(not) bring (himself) to አቃተው**
They could not bring themselves to believe the news. ወሬውን ፡ ለማመን ፡ አቃታቸው

**(bring under), be brought under ቀረበ**
The various points were brought under three different chapters. ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑት ፡ ጉዳዮች ፡ በሦስት ፡ የተለያዩ ፡ ምዕራፎች ፡ ቀርበው ፡ ነበር

**bring up**
1. አሳደገ. Her aunt brought her up. አክስቷ ፡ አሳደገቻት
2. አነሣ. I will bring it up at the next meeting. በሚቀጥለው ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ አነሣዋለሁ

**bring with it አስከተለ**
Old age brings many diseases with it. እርጅና ፡ ብዙ ፡ ሕመም ፡ ያስከትላል
[See also 'accusation, attention, control, discredit, head, home, house, life, line, mind, naught, order, pressure']

## brink
1. ጠርዝ. He went to the brink of the well. ወደ ፡ ውኃው ፡ ጉድጓድ ፡ ጠርዝ ፡ ሄደ
2. አፋፍ. The country is on the brink of war. አገሪቱ ፡ በጦርነት ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ትገኛለች

## brisk
1. ፈጠን ፡ ያለ. A brisk walk brings him home from school in ten minutes. ፈጠን ፡ ባለ ፡ እርምጃ ፡ በዐሥር ፡ ደቂቃ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ እቤቱ ፡ ይደርሳል
2. የሚያነቃቃ. A brisk wind was blowing. የሚያነቃቃ ፡ ነፋስ ፡ ይነፍስ ፡ ነበር
*He took a brisk walk. ራመድ ፡ ራመድ ፡ ብሎ ፡ ተንሸራሸረ

## bristle
1. ተገጠገጠ. +The line of soldiers bristled with bayonets. በወታደሮቹ ፡ ሰልፍ ፡ ላይ ፡ ሳንጃ ፡ ተገጥግጦ ፡ ነበር
2. ቆመ. The cat's hair bristled when the dog barked. ውሻው ፡ ሲጮህ ፡ የድመቷ ፡ ጸጉር ፡ ቆመ
3. ደሙ ፡ ፈላ. He bristled at the insult. ስለ ፡ ተሰደበ ፡ ደሙ ፡ ፈላ

## brittle በቀላሉ ፡ የሚሰበር
Beware, the glass is brittle. ተጠንቀቅ ፤ መስታወቱ ፡ በቀላሉ ፡ የሚሰበር ፡ ነው

## broach (v.)
1. አነሣ. How do you broach an unpleasant subject? ስለማያስደስት ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ ታነሣለህ ?
2. ነድሎ ፡ ከፈተ. He broached a barrel of wine. የጠጁን ፡ በርሜል ፡ ነድሎ ፡ ከፈተው

## broad
1. ሰፊ. He has broad shoulders. ሰፊ ፡ ትከሻ ፡ አለው (or, ደረቱ ፡ ሰፊ ፡ ነው)
His broad education prepared him well for the job. ሰፊ ፡ የሆነው ፡ ትምህርቱ ፡ ለሥራው ፡ በሚገባ ፡ አዘጋጀው
He has a broad view of the situation. ስለ ፡ ሁኔታው ፡ ሰፊ ፡ አስተያየት ፡ አለው
2. ለጥ ፡ ያለ. The broad expanse of the plain was dotted with trees. ለጥ ፡ ያለው ፡ ሜዳ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ዛፎች ፡ ተተክለውበታል

**broad outline ጠቅላላ ፡ ማብራሪያ**
Give the broad outlines of today's lesson. ስለ ፡ ዛሬው ፡ ትምህርት ፡ ጠቅላላ ፡ ማብራሪያ ፡ ስጥ

**in broad daylight ቀን ፡ በቀን**
It happened in broad daylight. ቀን ፡ በቀን ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ነው

**to broad daylight ካረፈደ ፡ በኋላ**
He awoke to broad daylight. ካረፈደ ፡ በኋላ ፡ ተነሣ
[See also 'jump']

## broadcast (v.)
1. በራዲዮ ፡ አስተላለፈ. They will broadcast directly from London. በራዲዮ ፡ በቀጥታ ፡ ከለንደን ፡ ያስተላልፋሉ
2. አሰማ. The radio broadcast a speech filled with menace. ዛቻ ፡ የተሞላበት ፡ ንግግር ፡ ራዲዮኑ ፡ አሰማ
3. አሰራጨ. Don't broadcast the secret! ምስጢሩን ፡ አታሰራጭ

## broadcast (n.)
1. የራዲዮ ፡ ፕሮግራም. The broadcast was called off for technical reasons. በቴክኒክ ፡ ጉድለት ፡ ምክንያት ፡ የራዲዮ ፡ ፕሮግራም ፡ ቀረ
2. በራዲዮ ፡ የተነገረ. Did you listen to the broadcast? በራዲዮ ፡ የተነገረውን ፡ ሰማህ ?

## broaden (vt.)
1. አሰፋ. The municipality is broadening the new street. ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ አዲሱን ፡ መንገድ ፡ በማስፋት ፡ ላይ ፡ ነው
2. አበለጸገ. Reading broadens our understanding. ማንበብ ፡ ዕውቀታችንን ፡ ያበለጽገዋል

**broaden (vi.) ሰፋ**
The river broadens at its mouth. ወንዙ ፡ በመግቢያው ፡ ላይ ፡ ይሰፋል

**(be) broad-minded** አስተያየቱ ፡ ሰፊ ፡ ነው
He is a broad-minded person, and people ask him for advice. አስተያየቱ ፡ ሰፊ ፡ ስለሆ ነ ፡ ሰዎች ፡ ምክር ፡ ይጠይቁታል

**broadside** በጐን
The ship drifted broadside toward the shore. መርከቧ ፡ በጐን ፡ ወደ ፡ ዳርቻ ፡ ተንሳፈፈች

**brocade** የረቀቀ ፡ ጉንጉን
The royal regalia is made of velvet and gold brocade. የንጉሥ ፡ ነገሥቱ ፡ የክብር ፡ ልብስ ፡ ከአ ጥላስና ፡ ከረቀቀ ፡ የወርቅ ፡ ጉንጉን ፡ የተሠራ ፡ ነው

**brochure** መግለጫ ፡ ጽሑፍ
They published a brochure for the exhibition. ለኤግዝቢሽኑ ፡ መግለጫ ፡ ጽሑፍ ፡ አሳተሙ

**broil** (vt.) ጠበሰ
He broiled the meat. ሥጋውን ፡ ጠበሰ

**broil** (vi.) ተቃጠለ
You will broil if you stay in the sun. ፀሐይ ፡ ላ ይ ፡ ብትቆይ ፡ ትቃጠላለህ

**broke,** see **break**

**(be) broke** ባዶ ፡ ኪሱን ፡ ነው
I am broke again, and it is only the day after payday. ልደታ ፡ ካለፈች ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ባዶ ፡ ኪሴን ፡ ነኝ

**be dead broke** ባዶ ፡ እጁን ፡ ነው
It is the end of the month, and I am dead broke. የወሩ ፡ ማለቂያ ፡ ስለሆነ ፡ ባዶ ፡ እጄን ፡ ነኝ

**go broke** ከሰረ
He went broke gambling. በቁማር ፡ ከሰረ

**leave broke** ባዶ ፡ እጁን ፡ አስቀረው
A siege of illness left him broke, የረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሕመም ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ አስቀረው
[See also 'stone-broke']

**broken,** see **break**

**broken** (adj.)
1. የተሰባበረ ፤ ሰባራ. The broken glass ruined my tires. የተሰባበረው ፡ መስታወት ፡ ጎማዬን ፡ አበላ ሸብኝ
The broken glass gashed his arm. ሰባራ ፡ ጠር ሙስ ፡ ክንዱን ፡ ቈረጠው
2. የተለያየ ፤ የፈረሰ. A united family is healthier than a broken one. ከተለያየ ፡ (ከፈረሰ) ፡ ቤት ፡ ሰብ ፡ በፍቅር ፡ የቆየው ፡ ይሻላል
3. ያልተጣራ. The foreigner speaks broken Amharic. የውጭ ፡ አገሩ ፡ ሰው ፡ ያልተጣራ ፡ አማር ኛ ፡ ይናገራል

*A broken promise is a betrayal of trust. ቃልን ፡ ማጠፍ ፡ እምነትን ፡ ማጕደል ፡ ነው
*His broken health was due to age. ጤንነቱ ፡ የ ተቃወሰው ፡ በእርጅና ፡ ምክንያት ፡ ነው

**be broken** ተሰበረ
His backbone was broken when he fell. በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ አከርካሪው ፡ ተሰበረ
His spirit was broken by his wife's death. ሚስቱ ፡ ስለሞተች ፡ ቅስሙ ፡ ተሰብሯል

**be broken down** ፈረሰ
This detour is necessary because the bridge is broken down. ድልድዩ ፡ ስለፈረሰ ፡ ዙሮ ፡ መሄድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**(be) broken-hearted** ሐዘን ፡ ተጫነው
She was broken-hearted over her son's death. በልጇ ፡ መሞት ፡ ምክንያት ፡ ሐዘን ፡ ተጭኗታል

**bronze** ነሐስ
The cross is made of bronze. መስቀሉ ፡ ከነሐ ስ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**brood** (vt.)
1. ታቀፈ. The hen is still brooding her eggs, but they will hatch soon. ዶሮዋ ፡ አሁንም ፡ እንደታቀፈች ፡ ነች ፤ ግን ፡ በቅርቡ ፡ ትፈለፍላለች
2. በአእምሮው ፡ ውስጥ ፡ ነበር. +For years he brooded vengeance. ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ የቂም ፡ በቀል ፡ ሐሳብ ፡ በአእምሮው ፡ ውስጥ ፡ ነበር

**brood** (vi.) በሐዘን ፡ ተከዘ
He brooded all day long over his misfortune. በመጥፎ ፡ ዕድሉ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ በሐዘን ፡ ሲ ተከዝ ፡ ዋለ

**brood** (n.) ጫጩቶች
The mother hen walked about followed by her brood. እናቲቱ ፡ ዶሮ ፡ ጫጩቶቿ ፡ ተከትለዋት ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ትል ፡ ነበር

**brook** ጅረት
The brook dries up in the summer. ጅረቱ ፡ በ በጋ ፡ ይደርቃል

**broom** መጥረጊያ
The woman got angry and hit the child with the broom. ሴትዮዋ ፡ ተናዳ ፡ ልጅዋን ፡ በመጥረ ጊያ ፡ መታችው

**broth** ሾርባ ፤ መረቅ
A hot cup of broth on a cold day tastes fine. በብርድ ፡ ቀን ፡ ትኩስ ፡ ሾርባ ፡ ተስማሚ ፡ ነው
Meaty broth is given to sick people. ሥጋ ፡ የ በዛበት ፡ መረቅ ፡ ለበሽተኞች ፡ ይሰጣል

**brother** (pl. brothers, brethren) ወንድም
My younger brother is in the tenth grade. ታናሽ ፡ ወንድሜ ፡ ዓሥረኛ ፡ ክፍል ፡ ነው

**brotherhood**
1. ወንድማማችነት. The YMCA tries to promote the brotherhood of man. ወ. ወ. ክ. ማ. የሰዎችን ፡ ወንድማማችነት ፡ ለማስፋፋት ፡ ይጥራል
2. ያንድነት ፡ ማኅበር. The railroad workers belong to a brotherhood. የባቡሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ያንድነት ፡ ማኅበር ፡ አላቸው

**brother-in-law** ዋርሳ (wife's brother); አማች ፤ አማት (husband's brother)

**brotherly** የወንድማማችነት
There was a brotherly feeling among the boys in the class. በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ልጆች ፡ መሀከል ፡ የወንድማማችነት ፡ መንፈስ ፡ ነበረ

**brought,** see **bring**

**brow** ግንባር
He wiped the sweat off his brow. ላቡን ፡ ከግንባሩ ፡ ላይ ፡ ጠረገ

**browbeat**
Don't try to browbeat me! በመደንፋትና ፡ ፊትህን ፡ በማጥቆር ፡ ልታስፈራራኝ ፡ አትሞክር

**brown** ቡናማ ፤ ቡና ፡ ዓይነት
His hair and eyes are brown. የጸጉሩና ፡ የዓይኖቹ ፡ ቀለም ፡ ቡናማ ፡ ነው
The brown cloth is flecked with green. ቡና ፡ ዓይነት ፡ ልብሷ ፡ አረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ ብሎበታል
[See also 'dark']

**browse**
1. ጋጠ. The cattle browse in the field. ከብቶቹ ፡ በሜዳ ፡ ላይ ፡ ይግጣሉ
2. ተመለካከተ. He likes to browse among the books. መጽሐፎች ፡ መመለካከት ፡ ይወዳል

**bruin** ድብ

**bruise** (v.)
1. ሰንበር ፡ አወጣ. The boy bruised his knee. ልጁ ፡ ጉልበቱ ፡ ላይ ፡ ሰንበር ፡ አወጣ
2. አበለዘ. The gun's recoil bruised his shoulder. የጠመንጃው ፡ እርግጫ ፡ ትከሻውን ፡ አበለዘው
3. ጐዳ. His harsh words bruised her feelings. የተናገራት ፡ ኀይለኛ ፡ ቃል ፡ ስሜቷን ፡ ጐዳው
The stirrup bruised the horse's flank. የፈረሱን ፡ ሽንጥ ፡ እርካብ ፡ ጐድቶታል

**bruise** (n.) ሰንበር
He had a bruise on his left foot. ግራ ፡ እግሩ ፡ ላይ ፡ ሰንበር ፡ ነበረው

**brunt** ከፍተኛ ፡ ኀይል
The island town bore the brunt of the storm. የደሴቷ ፡ ከተማ ፡ የማዕበሉ ፡ ከፍተኛ ፡ ኀይል ፡ ደረሰባት

**brush** (v.)
1. ቦረሸ. I brush my hair every morning. ጧት ፡ ጧት ፡ ጸጉሬን ፡ እቦርሻለሁ
Please brush my coat! ኮቴን ፡ ቦርሽልኝ
2. አራገፈ. Brush the dust off my coat! አቧራውን ፡ ከኮቴ ፡ ላይ ፡ አራግፈው
3. ፋቀ. I have to brush my teeth. ጥርሴን ፡ መፋቅ ፡ አለብኝ
4. አበሰ. The leaves of the tree brushed my face as I walked through the forest. በጫካው ፡ ውስጥ ፡ ስሄድ ፡ የዛፉ ፡ ቅጠሎች ፡ ፊቴን ፡ አበሱት
5. ጠረገ. The child brushed the tears from his eyes. ልጁ ፡ እንባውን ፡ ከይኖቹ ፡ ላይ ፡ ጠረገ

**brush aside** ከምንም ፡ አልቈጠረም
He brushed my excuses aside. የሰጠሁትን ፡ ምክንያት ፡ ከምንም ፡ አልቈጠረም

**brush lightly against** ዳሰሰ
The leaves brushed lightly against his face. ቅጠሎቹ ፡ ፊቱን ፡ ዳሰሱት

**brush up on** ከላለሰ
I am brushing up on my Amharic. አማርኛዬን ፡ በመከላለስ ፡ ላይ ፡ ነኝ

**brush** (n.)
1. ብሩሽ. You can use this brush for your shoes. በዚህ ፡ ብሩሽ ፡ ጫማህን ፡ ልትቦርሽበት ፡ ትችላለህ
2. ጥሻ. Much of this land is covered with brush. የዚህ ፡ መሬት ፡ አብዛኛው ፡ ክፍል ፡ በጥሻ ፡ ተሸፍኗል
3. አነስ ፡ ያለ ፡ ግጭት. The troops had a brush with the enemy. ጦሩ ፡ ከጠላት ፡ ጋር ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ ግጭት ፡ አደረገ

**brusque** ቁርጥ ፡ ያለ
His answer to our request was a brusque "no". ለጥያቄያችን ፡ የሰጠን ፡ መልስ ፡ አይሆንም ፡ የሚል ፡ ቁርጥ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ነበር

**brutal**
1. ጨካኝ. He is a brutal ruler who has his own people bombed. የገዛ ፡ ሕዝቡን ፡ በቦምብ ፡ የሚያስደበድብ ፡ ጨካኝ ፡ መሪ ፡ ነው

2. የጭካኔ. He acted in a brutal way. የጭካኔ ፡ አሠራር ፡ አሳየ

**brutality** ጭካኔ
The brutality of the punishment shocked the onlookers. ቅጣቱ ፡ ሲሰጥ ፡ የነበረው ፡ ጭካኔ ፡ ተመልካቾችን ፡ አሰቀቃቸው
Some tribes wage war with brutality. አንዳንድ ፡ ጐሳዎች ፡ በጭካኔ ፡ ይዋጋሉ

**brutalize** አውሬ ፡ አደረገ
War tends to brutalize men. ጦርነት ፡ ሰውን ፡ አውሬ ፡ ያደርገዋል

**brute**
1. አውሬ. He is a brute. እርሱ ፡ አውሬ ፡ ነው
2. አዳጋች. Man has struggled long against the brute forces of nature. ሰው ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ ካዳጋች ፡ የተፈጥሮ ፡ ኀይል ፡ ጋር ፡ ታግሏል

**bubble** (v.) ተፍለቀለቀ
The water is beginning to bubble. ውኃው ፡ መፍለቅለቅ ፡ ጀመረ

**bubble over** ፈነደቀ
The last time I saw her she was bubbling over with enthusiasm. ከዚህ ፡ በፊት ፡ ሳያት ፡ በጋለ ፡ ስሜት ፡ ትፈነድቅ ፡ ነበር

**bubble with**
*His mind bubbles with plans and ideas. ብዙ ፡ ሐሳቦችና ፡ እቅዶች ፡ ከአእምሮው ፡ ውስጥ ፡ ይመነጫሉ

**bubble** (n.) አረፋ
You could see the bubbles rise to the surface. አረፋ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሲወጣ ፡ ይታያል

**buck** (v.) ተቃወመ
The mayor bucked at the school director's suggestion. ከንቲባው ፡ የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ዲሬክተር ፡ ሐሳብ ፡ ተቃወመ

**make buck** ነቀነቀ
The turbulent air made the plane buck. የተናወጸው ፡ አየር ፡ አውሮፕላኑን ፡ ነቀነቀው

**buck,** n. [ወንድ ፡ አጋዘን ፤ ወይም ፡ ወንድ ፡ ጥንቸል ፤ ወይም ፡ ወንድ ፡ የሜዳ ፡ ፍየል]

**bucking** እንጣጥ ፡ የሚል
The bucking horse unseated him. እንጣጥ ፡ የሚለው ፡ ፈረስ ፡ ከኮርቻው ፡ ላይ ፡ ጣለው

**bucket** ባልዲ
He carried the water in a bucket to put out the fire. እሳቱን ፡ ለማጥፋት ፡ በባልዲ ፡ ውኃ ፡ አመጣ

**buckle** (vt.) ቈለፈ
I cannot buckle the strap. የጠፍሩን ፡ ዘለበት ፡ ልቈልፍ ፡ አልችልም
I cannot buckle my belt. ቀበቶዬን ፡ ልቈልፍ ፡ አልችልም

**buckle** (vi.) ተሰረጐደ
The bridge buckled under the weight of the heavy truck. ከመኪናው ፡ ክብደት ፡ የተነሣ ፡ ድልድዩ ፡ ተሰረጐደ

**buckle down** አእምሮውን ፡ ለሥራ ፡ ሰበሰበ
He was by nature a daydreamer and found it hard to buckle down. በተፈጥሮው ፡ ሐሳቡ ፡ የሚባክን ፡ ስለሆነ ፡ አእምሮውን ፡ ለሥራ ፡ መሰብሰብ ፡ አቃተው
*It's about time we buckled down to work. ታጥቀን ፡ የምንሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ነው

**buckle to** ተያያዘ
She buckled to the housework. የቤቱን ፡ ሥራ ፡ ተያያዘችው

**buckle under** እሺ ፡ አለ
He refused to take the medicine, but buckled under when the doctor told him to. መድኀኒቱን ፡ አልውጥም ፡ ብሎ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ዶክተሩ ፡ እንዲውጥ ፡ ቢነግረው ፡ እሺ ፡ አለ

**buckle** (n.) ዘለበት
The buckle came off my belt. ዘለበቱ ፡ ከቀበቶዬ ፡ ላይ ፡ ወለቀ

**bud** (budded), v. እምቡጥ ፡ ያዘ
The rose bush has budded. ጽጌረዳው ፡ እምቡጥ ፡ ይዟል

**bud** (n.) እምቡጥ
The frost killed all the buds. ውርጩ ፡ እምቡጦቹን ፡ ሁሉ ፡ አጠፋቸው

**buddy** የቅርብ ፡ ጓደኛ
He was my buddy all through my school years. ትምህርት ፡ ቤት ፡ በነበርኩበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የቅርብ ፡ ጓደኛዬ ፡ ነበር

**budge** (vt.) አነቃነቀ
The stone was so heavy that the child could not budge it. ድንጋዩ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ስለነበረ ፡ ልጁ ፡ ሊያነቃንቀው ፡ አልቻለም

**budge** (vi.)
1. ተንቀሳቀሰ. The mule would not budge. በቅሎዋ ፡ አልንቀሳቀስ ፡ አለች
2. ሐሳቡን ፡ ለወጠ. Once her father had said "no", he wouldn't budge. አባቷ ፡ አንዴ ፡ አይሆንም ፡ ካለ ፡ ሐሳቡን ፡ አይለውጥም

**budget** (v.)
*You will have to learn to budget your salary. ደሞዝህን ፡ እንዴት ፡ እንደምታወጣ ፡ መመደብ ፡ መልመድ ፡ አለብህ

**budget** (n.) ባጀት ፤ ወጪና ፡ ገቢ
The ministry's new budget exceeded the funds allowed it last year. የሚኒስቴሩ ፡ አዲስ ፡ ባጀት ፡ ዓምና ፡ ከተፈቀደለት ፡ በለጠ
Balancing my budget is hopeless. ወጪና ፡ ገቢዬን ፡ ማቃናት ፡ አይሆንለኝም

**buff**
1. [ለስላሳ ፡ የሆነ ፡ ከጎሽ ፡ ቆዳ ፡ የተሠራ ፡ ጠንካራ ፡ ቆዳ]
2. [ደብዛዛ ፡ ቢጫ]

**buffalo** ጎሽ
The buffalo and the ox look alike. ጎሽና ፡ በሬ ፡ ይመሳሰላሉ

**buffer** የግጭት ፡ መከላከያ
The buffer in front of the car prevented any damage from happening. በመኪናው ፡ ፊት ፡ ያለው ፡ የግጭት ፡ መከላከያ ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስ ፡ ተከላከለ

**buffet** (v.) አንገላታ
The waves buffeted him. ማዕበሉ ፡ አንገላታው

**buffet** (n.) መደርደሪያ
The dishes are in the buffet. ሳሕኖቹ ፡ በመደርደሪያ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው

**bug** (n.)
1. ትል. The leaves were covered with bugs. ቅጠሎቹ ፡ በትል ፡ ተወረው ፡ ነበር
2. ትኋን. The mattress was full of bugs. ፍራሹ ፡ ትኋን ፡ ሞልቶበታል

**buggy** [አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ የሚይዝ ፡ ጋሪ]

**bugle** [ከነሐስ ፡ የተሠራ ፡ ዋሽንት ፡ የሚመስል ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ]

**build** (built)
1. ሠራ. Our neighbor is building a new house. ጐረቤታችን ፡ አዲስ ፡ ቤት ፡ እየሠራ ፡ ነው
2. አቋቋመ. They built a factory for canning meat. ሥጋ ፡ በቆርቆሮ ፡ የሚያሽግ ፡ ፋብሪካ ፡ አቋቋሙ
3. መሠረተ. Don't build your future on dreams! የወደፊት ፡ ዕድልህን ፡ በከንቱ ፡ ምኞት ፡ ላይ ፡ አትመሥርት

**build up**
1. አዳበረ. He built up the business. ንግዱን ፡ አዳበረ
2. አደራጀ. This country is building up its army to counter the threat of invasion. ይህች ፡ አገር ፡ ወረራን ፡ ለመቋቋም ፡ ጦሯን ፡ እያደራጀች ፡ ነች
3. አተረፈ. The firm has built up a wide reputation for fair dealing. ድርጅቱ ፡ ተገቢ ፡ ለሆነ ፡ ገበያው ፡ ከፍተኛ ፡ ዝናን ፡ አትርፏል

**(be) built up** ተከተመ
The area near the airport is being built up. በአውሮፕላን ፡ ማቢያው ፡ አጠገብ ፡ ያለው ፡ ስፍራ ፡ በመከተም ፡ ላይ ፡ ነው
[See also 'slightly']

**builder**
1. የሠራ. The builder of these churches is well known. እነዚህን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የሠራው ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ነው
2. ገንቢ. The builders were pinched by a shortage of good lumber. በጥሩ ፡ ዕንጨት ፡ እጥረት ፡ ምክንያት ፡ ገንቢዎቹ ፡ ተቸገሩ

**building** ሕንጻ
Both offices are in one building. ሁለቱም ፡ ቢሮዎች ፡ ባንድ ፡ ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው

**build-up** ማደርጀት
The build-up of the nation's heavy industry is vital. የሀገሪቱ ፡ ከባድ ፡ ኢንዱስትሪዎችን ፡ ማደርጀት ፡ እጅግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**built,** see **build.**

**bulb**
1. አምፑል. This bulb is burnt out. ይህ ፡ አምፑል ፡ ተቃጥሏል
2. ራስ. He planted some onion bulbs yesterday. የሽንኩርት ፡ ራስ ፡ ትናንትና ፡ ተከለ

**bulge** (vt.) አሳበጠ
The apples bulged his pockets. ቱፋዎቹ ፡ ኪሱን ፡ አሳበጡት

**bulge** (vi.) ተወጠረ
His schoolbag bulged with books. የትምህርት ፡ ቤት ፡ ቦርሳው ፡ በመጻሕፍት ፡ ተወጥሯል

**bulge** (n.)
*What is that bulge in your pocket? ያ ፡ ኪስህን ፡ ያሳበጠው ፡ ነገር ፡ ምንድነው ?

**bulk**
1. አብዛኛ. The bulk of my salary goes for rent and food. ከደሞዜ ፡ አብዛኛው ፡ የሚውለው ፡ ለቤት ፡ ኪራይና ፡ ለምግብ ፡ ነው
2. አብዛኛ ፡ ክፍል. The ocean covers the bulk of the earth's surface. ውቅያኖስ ፡ የመሬትን ፡ አብዛኛውን ፡ ክፍል ፡ ይሸፍነዋል
3. መጠን. The carton was hard to carry because of its bulk. ካርቶኑ ፡ ከመጠኑ ፡ የተነሣ ፡ ለመሸከም ፡ አዳጋች ፡ ነበር
4. ግዙፍነት. The bulk of the elephant does not prevent him from walking fast. ዝሆንን ፡ ግዙፍነቱ ፡ በፍጥነት ፡ ከመሄድ ፡ አያግደውም

**bulky**
1. መጠኑ ፡ ትልቅ ፡ የሆነ. It is hard to carry this bulky package. ይህን ፡ መጠኑ ፡ ትልቅ ፡ የሆነ ፡ ጥቅል ፡ መሸከም ፡ አዳጋች ፡ ነው
2. በጣም ፡ ግዙፍ. Since the man is bulky, the mule can't carry him. ሰውዬው ፡ በጣም ፡ ግዙፍ ፡ ስለሆነ ፡ በቅሎዋ ፡ መሸከም ፡ አቃታት

**bull** (n.) ኮርማ
The bull is more expensive than the ox. ኮርማ ፡ ከበሬ ፡ ይበልጥ ፡ ውድ ፡ ነው

**bull** (adj.) ወንድ
A bull elephant rampaged through the jungle. አንድ ፡ ወንድ ፡ ዝሆን ፡ በጫካው ፡ ውስጥ ፡ ይራወጥ ፡ ነበር

**bulldozer** ቡልዶዘር

**bullet** ጥይት
The bullet lodged in his shoulder. ጥይቱ ፡ ትከሻው ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ቀረ
[See also 'shoot, stray']

**bulletin**
1. መግለጫ. During the President's illness, a medical bulletin was issued daily. ፕሬዚዳንቱ ፡ በታመሙ ፡ ጊዜ ፡ የጤንነታቸው ፡ መግለጫ ፡ በየቀኑ ፡ ይወጣ ፡ ነበር
2. ማስታወቂያ. The bulletin lists departures and arrivals of all buses. ማስታወቂያው ፡ የአውቶቡሶቹን ፡ ሁሉ ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ ይዘረዝራል
3. መጽሔት. Our club publishes a bulletin each month. ክበባችን ፡ በየወሩ ፡ መጽሔት ፡ ያዘጋጃል

**bulletin board** ማስታወቂያ ፡ ሰሌዳ
Put the notice on the bulletin board! ማስታወቂያውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰሌዳው ፡ ላይ ፡ ለጥፈው

**bulletproof** ጥይት ፡ የማይዘልቀው
The car had bulletproof windows. መኪናው ፡ ጥይት ፡ የማይዘልቀው ፡ መስኮት ፡ አለው

**bullheaded** አሳበ ፡ ግትር
He is so bullheaded, he never gives in. በጣም ፡ አሳበ ፡ ግትር ፡ ስለሆነ ፡ ያለውን ፡ በፍጹም ፡ አይለቅም

**bully** (bullied) አንጣበረ
He is always bullying his employees. ሠራተኞቹን ፡ ሁልጊዜ ፡ ያንጣብራቸዋል

**bulwark**
1. ግድብ. A bulwark of sand and stone keeps the water out. የአሸዋና ፡ የድንጋይ ፡ ግድብ ፡ ውኃ ፡ እንዳይገባ ፡ ይከላከላል
2. ጋሻ. Freedom of speech is one of the bulwarks of democracy. የንግግር ፡ ነጻነት ፡ የዴሞክራሲ ፡ ጋሻ ፡ ነው

**bump** (vt.)
1. ገጨት ፡ አደረገ. The bus bumped the car ahead of it. አውቶቡሱ ፡ ከፊቱ ፡ የነበረችውን ፡ መኪና ፡ ገጨት ፡ አደረጋት
2. ጣለ. The cat bumped the vase off the shelf. ድመቷ ፡ ያበባ ፡ ማስቀመጫውን ፡ ከመደርደሪያው ፡ ላይ ፡ ጣለችው
3. አወረደ. The voters bumped the senator and elected his rival. መራጮቹ ፡ አማካሪውን ፡ አውርደው ፡ ተቀናቃኙን ፡ መረጡት

**bump** (vi.) ተጋጨ
He bumped into the chair in the dark. በጨለማ ፡ ከወንበሩ ፡ ጋር ፡ ተጋጨ

**bump along** ተንገጫገጨ
The bus bumped along the unpaved road. አውቶቡሱ ፡ ባልተነጠፈው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ተንገጫገጨ

**bump (into)** አጋጠመ(ው).
+Guess whom I bumped into yesterday? ትናንትና ፡ ማንን ፡ እንዳጋጠመኝ ፡ ታውቃለህ ?

**bump** (n.)
1. ጉብታ. The car went over a bump. መኪናው ፡ በጉብታ ፡ ላይ ፡ አለፈ
2. እብጠት. There is a palpable bump on his head. በራሱ ፡ ላይ ፡ ሊዳሰስ ፡ የሚችል ፡ እብጠት ፡ አለ

**bumper** ፈረፋንጎ
The bumpers of the two cars were locked together. የሁለቱ ፡ መኪናዎች ፡ ፈረፋንጎ ፡ ተቈላለፈ

**bumpy**
1. አባጣ ፡ ጐርባጣ. We drove for an hour over a bumpy road. በአባጣ ፡ ጐርባጣ ፡ መንገድ ፡ ላንድ ፡ ሰዓት ፡ በመኪና ፡ ሄድን

2. ተለዋዋጭ. Bumpy air made the passengers uncomfortable. ተለዋዋጭ ፡ አየር ፡ የአይሮፕላኑን ፡ ተሳፋሪዎች ፡ አቅለሸለሻቸው

**bunch**

1. ጭብጥ. Let me have a bunch of radishes, please! አንድ ፡ ጭብጥ ፡ ቀይ ፡ ሥር ፡ ስጠኝ
2. ዘለላ. The woman sold me a bunch of bananas. ሴትዮዋ ፡ አንድ ፡ ዘለላ ፡ ሙዝ ፡ ሸጠችልኝ

**a whole bunch of** ብዙ
A whole bunch of us is going on the picnic. ብዙ ፡ ሆነን ፡ ወደ ፡ ሽርሽር ፡ እንሄዳለን

**bundle** (v.)

1. አጨቀ ፤ አጐረ. We bundled all our clothes into one suitcase. ልብሳችንን ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ሻንጣ ፡ አጨቅነው ፡ (አጐርነው)
2. አሰረ. Bundle the newspapers for the trash man! ቆሻሻ ፡ ለሚያነሣው ፡ ሰውዬ ፡ ጋዜጣውን ፡ አሰርለት

**bundle (one) off**
1. አጣድፎ ፡ ወሰደ. They bundled me off to the hospital against my will. አጣድፈው ፡ ያለፈቃዴ ፡ ወደ ፡ ሆስፒታል ፡ ወሰዱኝ
2. አቻኩሎ ፡ ላከ. They bundled her off to the country. አቻኩለው ፡ ወደ ፡ ባላገር ፡ ላኳት

**bundle up** ጠቀለለ
The mother bundled up the child in a towel. እናትዮዋ ፡ ሕፃኑን ፡ በፎጣ ፡ ጠቀለለችው

**bundle** (n.) ጥቅል
Is that bundle too heavy for you? ያ ፡ ጥቅል ፡ በጣም ፡ ይከብድሃል ?

**make up in bundles** አንድ ፡ ላይ ፡ እያደረገ ፡ አሰረ
Make these books up in bundles for shipping! በመርከብ ፡ እንዲላኩ ፡ እነዚህን ፡ መጻሕፍት ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ እያደረግህ ፡ እሰራቸው
[See also 'compact']

**bungalow** አነስተኛ ፡ ቤት
The bungalow does not hold more than twenty people. አነስተኛው ፡ ቤት ፡ ከሃያ ፡ ሰው ፡ በላይ ፡ አይዝም

**bunk** ቆጥ ፡ ቢጤ
The soldiers sleep in bunks. ወታደሮቹ ፡ ቆጥ ፡ ቢጤ ፡ ላይ ፡ ይተኛሉ

**bunker** መከለያ ፡ ምሽግ
The soldiers built two bunkers yesterday. ወታደሮቹ ፡ ትናንትና ፡ ሁለት ፡ መከለያ ፡ ምሽጎች ፡ ሠሩ

**buoy** [በባሕር ፡ ውስጥ ፡ አደጋን ፡ የሚያመለክት ፡ ነገር]

**buoyancy**

1. የመንሳፈፍ ፡ ኀይል. Wood has more buoyancy than iron. ዕንጨት ፡ ከብረት ፡ የበለጠ ፡ የመንሳፈፍ ፡ ኀይል ፡ አለው
2. የደስተኛነት ፡ መንፈስ. She lost her buoyancy due to the death of her son. በልጅዋ ፡ መሞት ፡ ምክንያት ፡ የደስተኛነት ፡ መንፈሷ ፡ ጠፋ

**buoyant** (= n.) ተንሳፋፊ ፡ ነገር
Wood and cork are buoyant. ዕንጨትና ፡ ቡሽ ፡ ተንሳፋፊ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው

**be buoyant** የደስታ ፡ መንፈስ ፡ አለው
Children are usually more buoyant than old people. ሕፃናት ፡ ከሽማግሌዎች ፡ የበለጠ ፡ የደስታ ፡ መንፈስ ፡ አላቸው

**burden** (v.)

1. ጫነ ፤ ጫነ(በት). They burdened the mule with many pots. በቅሎውን ፡ ብዙ ፡ ማሰሮ ፡ ጫኑበት
He burdened me with the responsibility of cleaning up this mess. ይህን ፡ ዝብርቅርቅ ፡ ነገር ፡ እንዳስተካክል ፡ ኀላፊነት ፡ ጫነብኝ
2. አስቸገረ. I do not want to burden you with that. በዚህ ፡ እንዳስቸግርህ ፡ አልፈልግም

**burden** (n.)

1. ሸክም. The porter carried the burden on his shoulders. ኩሊው ፡ ሸክሙን ፡ በትከሻው ፡ ላይ ፡ ተሸከመ
I would like to accept your invitation to stay, but I don't want to be a burden to you. ካንተ ፡ ጋር ፡ እንድቆይ ፡ ያደረግህልኝን ፡ ግብዣ ፡ መቀበል ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ ግን ፡ ሸክም ፡ ልሆንብህ ፡ አልፈልግም
2. ቀንበር. To support my family became a great burden for me. ቤተ ፡ ሰቦቼን ፡ ማስተዳደር ፡ ትልቅ ፡ ቀንበር ፡ ሆነብኝ
3. ዋና ፡ ፍሬ ፡ ነገር. The value of peace was the burden of the President's speech. ከፕሬዚዳንቱ ፡ ንግግር ፡ ዋናው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ የሰላም ፡ ጥቅም ፡ ነበር

**beast of burden** የጭነት ፡ ከብት
Donkeys, camels, and packhorses are beasts of burden. አህዮች ፤ ግመሎችና ፡ አጋሰሶች ፡ የጭነት ፡ ከብቶች ፡ ናቸው

**burdensome** ከባድ
The President's duties are burdensome. የፕሬዚዳንት ፡ ተግባሮች ፡ ከባድ ፡ ናቸው

**bureau**

1. ቢሮ. The travel bureau is closed today. የጉዞው ፡ ቢሮ ፡ ዛሬ ፡ ዝግ ፡ ነው
2. ጠረጴዛ. The bottom drawer of the bureau is stuck. የጠረጴዛው ፡ የታችኛው ፡ መሳቢያ ፡ ነክሷል

**burglar** ሰርሳሪ ፡ ሌባ ፤ የቤት ፡ ሰርሳሪ
He surprised the burglar in the act of entering his house. ሰርሳሪ ፡ ሌባ ፡ (የቤት ፡ ሰርሳሪ) ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ሲገባ ፡ ደረሰበት

**burglary** ቤት ፡ ሰብሮ ፡ የመግባት ፡ ወንጀል
Several cases of burglary were reported last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ብዙ ፡ ቤት ፡ ሰብሮ ፡ የመግባት ፡ ወንጀል ፡ መፈጸሙ ፡ ተነግሯል

**burial**

1. ቀብር. Burial of the body will take place next Thursday. ቀብሩ ፡ የሚመጣው ፡ ኀሙስ ፡ ይፈጸማል
2. መቅበር. The Egyptians embalmed their dead before burial. ግብጻዊያን ፡ ሙታንን ፡ ከመቅበራቸው ፡ በፊት ፡ እንዳይፈርሱ ፡ መድኀኒት ፡ አደረጉባቸው

**burial grounds** የመቃብር ፡ ቦታ
Burial grounds are within the church compound. የመቃብር ፡ ቦታ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጥር ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል

**buried** የተደበቀ
The sailor's story conjured up scenes of buried treasures. የመርከበኛው ፡ ታሪክ ፡ የተደበቀ ፡ ሀብት ፡ መኖሩን ፡ በሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ ፈጠረ

**be half-buried** በከፊል ፡ ተቀበረ
The house was half-buried by the dust which had blown in from the desert. ቤቱ ፡ ከበረኻው ፡ በነፈሰው ፡ አቧራ ፡ በከፊል ፡ ተቀብሮ ፡ ነበር

**burly** ጠብደል
Truck drivers are often burly men. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከባድ ፡ መኪና ፡ ነጂዎች ፡ ጠብደሎች ፡ ናቸው

**burn** (burned, or burnt), vt.

1. አቃጠለ ፤ ፈጀ. They burned their old papers. አሮጌ ፡ ወረቀታቸውን ፡ አቃጠሉ
Pepper burnt his throat. በርበሬ ፡ ጉሮሮውን ፡ አቃጠለው ፡ (ፈጀው)
The coffee is very hot, so don't let it burn your mouth. ቡናው ፡ በጣም ፡ ትኩስ ፡ በመሆኑ ፡ እንዳይፈጅህ
2. አበራ. People used to burn candles for light. ሰዎች ፡ ብርሃን ፡ ለማግኘት ፡ ሻማ ፡ ያበሩ ፡ ነበር
3. አያያዘ. He burned coal to heat the room. ክፍሉን ፡ ለማሞቅ ፡ ከሰል ፡ አያያዘ
*This train burns coal instead of oil. ይህ ፡ ባቡር ፡ በዘይት ፡ ፈንታ ፡ በከሰል ፡ ይሄዳል

**burn** (vi.)

1. ነደደ. The wood burns well. ዕንጨቱ ፡ በደንብ ፡ ይነዳል
2. በራ. All the lights in the room were burning. በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ መብራቶች ፡ ሁሉ ፡ ይበሩ ፡ ነበር
3. ተቃጠለ. The house is still burning. ቤቱ ፡ አሁንም ፡ እየተቃጠለ ፡ ነው
4. ጋለ. The pavement burns in the noon sun. በቀትር ፡ ጊዜ ፡ የእግር ፡ መንገዱ ፡ ይግላል
5. ጐረና. If you had stirred the soup, it wouldn't have burned. ሾርባውን ፡ ብታማስለው ፡ ኖሮ ፡ ባልጐረና ፡ ነበር
6. ተፋጀ. His forehead burns with fever. ግንባሩ ፡ በትኩሳት ፡ ምክንያት ፡ ይፋጃል
7. ተዋጠ. He is burning with enthusiasm. በጋለ ፡ ስሜት ፡ ተውጧል
*I'm burning with curiosity. ለማወቅ ፡ እጅግ ፡ ጓጉቻለሁ

**be burned** ጨሰ
The incense is burned in a censer. ዕጣኑ ፡ በጥና ፡ ይጨሳል

**burn down** (vt.) አቃጠለ
They extorted money from him by threatening to burn down his house. ቤቱን ፡ ለማቃጠል ፡ በማስፈራራት ፡ ገንዘብ ፡ አስከፈሉት

**burn down** (vi.)

1. ተቃጥሎ ፡ ወደመ. The building was burned down. ሕንጻው ፡ ተቃጥሎ ፡ ወደመ
2. በረደ. The fire has burned down. እሳቱ ፡ በርዷል

**burn (one's) fingers** ተሳሳተ
I've burned my fingers once already. ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተሳስቻለሁ

**burn oneself** ተቃጠለ
Look out, you will burn yourself. ተጠንቀቅ ፤ ትቃጠላለህ

**burn out** ጠፋ
The fire burned out for lack of wood. ዕንጨት ፡ ስለሌለ ፡ እሳቱ ፡ ጠፋ

**(be) burned out** ተቃጠለ
This bulb is burned out. ይህ ፡ አምፑል ፡ ተቃጥሏል

**burn up** ተቃጠለ
His books burned up in the fire. መጽሐፎቹ ፡ በእሳት ፡ ተቃጠሉ

**taste burnt** ጐረና
The rice tastes burnt. ሩዙ ፡ ጐርንቷል
[See also 'ash, bridge, sulphur']

**burn** (n.) ቃጠሎ ፤ የተቃጠለ ፡ ሰውነት
This is a serious burn. ይህ ፡ ከባድ ፡ ቃጠሎ ፡ ነው
Put some salve on your burn! የተቃጠለው ፡ ሰውነትህ ፡ ላይ ፡ ቅባት ፡ አድርግበት
*There is a burn on my hand where the fire touched me. እሳቱ ፡ ያቃጠለኝ ፡ ቦታ ፡ ቈስሏል

**burned** ያረረ
A sickening odor of burned flesh pervaded the room. የሚያቅለሸልሽ ፡ ያረረ ፡ ሥጋ ፡ ሽታ ፡ ክፍሉን ፡ ሞላው

**burning** የሚነድ
It was brave of him to enter the burning building. ከሚነደው ፡ ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ ጀግንነት ፡ ነበር
**be burning hot** አቃጠለ
The sun is burning hot today. ዛሬ ፡ ፀሐዩ ፡ ያቃጥላል

**burnt,** see **burn**

**burp** አገሣ
After drinking the milk, the baby burped. ሕፃኑ ፡ ወተት ፡ ከጠጣ ፡ በኋላ ፡ አገሣ

**burrow** (v.) ቈፈረ
The mole burrowed a hole in the garden. ፍልፈሏ ፡ አትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ጉድጓድ ፡ ቈፈረች
**burrow (in)**
1. በረበረ. He was burrowing in an old trunk. አሮጌውን ፡ ሣጥን ፡ ይበረብር ፡ ነበር
2. ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ፈለገ. She burrowed in the library for a book about Indian life. ስለህንዶች ፡ ኑሮ ፡ የሚገልጽ ፡ መጽሐፍ ፡ ለማግኘት ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ውስጥ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ፈለገች
**burrow (into)** ቈፍሮ ፡ ገባ
The obscure sound is made by termites which have burrowed into the wall. ግልጽ ፡ ያልሆነው ፡ ድምፅ ፡ ግድግዳውን ፡ ቈፍረው ፡ ከገቡት ፡ ምስጦች ፡ የሚመጣ ፡ ነው
**burrow out of sight** መሬቱን ፡ ምሶ ፡ ገባ
The mole quickly burrowed out of sight. ፍልፈሏ ፡ ባንዴ ፡ መሬቱን ፡ ምሳ ፡ ገባች

**burrow** (n.) ጉድጓድ ፤ ጐሬ
The rabbit hid in his burrow. ጥንቸሉ ፡ ጉድጓድ ፡ (ጐሬ) ፡ ውስጥ ፡ ተደበቀ

**burst** (vt.)
1. በጠሰ ፤ ሰበረ. The prisoner burst his chains. እስረኛው ፡ እግር ፡ ብረቱን ፡ በጠሰው ፡ (ሰበረው)
2. አፈነዳ. He burst the balloon with a pin. ፊኛውን ፡ በወረቀት ፡ መርፌ ፡ አፈነዳው
**burst** (vi.) ፈነዳ
The water pipe burst. የውኃው ፡ ቧምቧ ፡ ፈነዳ
The water tank burst when the bullet hit it. የውኃው ፡ በርሚል ፡ በጥይት ፡ ሲመታ ፡ ፈነዳ
**burst forth** ገነፈለ
With the latest insult, his pent-up rage burst forth. በቅርቡ ፡ በደረሰበት ፡ ስድብ ፡ ታፍኖ ፡ የነበረው ፡ ቊጣው ፡ ገነፈለ
**burst (into)** ዘሎ ፡ ገባ
He burst into the room. ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ዘሎ ፡ ገባ
*She burst into tears. ስቅ ፡ ብላ ፡ አለቀሰች
**burst into flames** በግ ፡ ብሎ ፡ ተያያዘ
The paper burst into flames. ወረቀቱ ፡ በግ ፡ ብሎ ፡ ተያያዘ
**burst open** ሰብሮ ፡ ከፈተ
We had to burst open the door. በሩን ፡ ሰብረን ፡ መክፈት ፡ ግድ ፡ ሆነብን
**burst out**
She burst out crying. ተንሰቅስቃ ፡ አለቀሰች
**burst (through)** ተፈትልኮ ፡ ወጣ
He burst through the doorway. በበሩ ፡ ተፈትልኮ ፡ ወጣ
**burst (with)**
1. ፈነዳ. The granaries were bursting with grain. ጐተራው ፡ በእህል ፡ ብዛት ፡ ሊፈነዳ ፡ ነበር
2. ፈነደቀ. The people were bursting with joy. ሰዎች ፡ በደስታ ፡ ይፈነድቁ ፡ ነበር

**burst** (n.) ካካታ
We heard from afar a burst of laughter. ከሩቅ ፡ የሣቅ ፡ ካካታ ፡ ሰማን

**bursting, be ~ with**
1. እጭቅ ፡ አለ. +The house was bursting with people. ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ሕዝብ ፡ እጭቅ ፡ ብሎ ፡ ነበር
2. ሊሞት ፡ ነው. She is bursting with curiosity. በማወቅ ፡ ጉጉት ፡ ልትሞት ፡ ነው
**to the bursting point** እስኪፈነዳ ፡ ድረስ
The balloon was distended to the bursting point. ፊኛው ፡ እስኪፈነዳ ፡ ድረስ ፡ ተነፍቶ ፡ ነበር

**bury** (buried) ቀበረ (ተቀበረ)
They buried the corpse in the church compound. ሬሳውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ቀበሩ

My passport was buried under the other papers. የይለፍ ፡ ወረቀቴ ፡ ከሌሎች ፡ ወረቀቶች ፡ ሥር ፡ ተቀብሯል

**bury oneself (in)** ተመሰጠ
He buried himself in a book. መጽሐፍ ፡ በማንበብ ፡ ተመሰጠ

**bus** አውቶቡስ
It is better for you to go by bus. በአውቶቡስ ፡ ብትሄድ ፡ ይሻልሃል

**bush**
1. ቁጥቋጦ. He hid behind a bush. ቁጥቋጦ ፡ ሥር ፡ ተደበቀ
2. ደን. The hunting party was lost in the bush. የአደኑ ፡ ጓድ ፡ ደኑ ፡ ውስጥ ፡ ጠፋ

**beat around the bush** ዳር ፡ ዳር ፡ አለ
Stop beating around the bush; get down to the subject! ዳር ፡ ዳር ፡ አትበል ፤ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ተናገር

**bushel** [እህል ፤ ፍራ ፡ ፍሬና ፡ አታክልት ፡ የሚለ ኩበት ፡ መስፈሪያ]

**bushy**
1. ዕጅብ ፡ ያለ. He has bushy eyebrows. ዕጅብ ፡ ያለ ፡ ሽፋል ፡ አለው
2. ደን ፡ የለበሰ. The bushy land shelters small animals. ደን ፡ የለበሰው ፡ መሬት ፡ ትናንሽ ፡ እንስሳትን ፡ ያስጠጋል

**business**
1. ንግድ. Business is good. ንግዱ ፡ ጥሩ ፡ ነው
They sold their business for a million dollars. ንግዳቸውን ፡ ባንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ ሸጡ
2. የንግድ ፡ ሥራ. Ability to get along with people is an asset in business. ከሰዎች ፡ ጋር ፡ የመግባባት ፡ ችሎታ ፡ ለንግድ ፡ ሥራ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው
3. ጉዳይ. Let's settle this business right away! ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ አሁኑኑ ፡ እንፈጽም
Don't meddle in other people's business! በሌላው ፡ ሰው ፡ ጉዳይ ፡ አትግባ
Mind your own business! ለራስህ ፡ ጉዳይ ፡ አስብ
4. ሥራ. What business is he in? ሥራው ፡ ምንድነው ?
He knows his business. ሥራውን ፡ ያውቃል
5. የሥራ ፡ ጉዳይ. I have to see him on business. ለሥራ ፡ ጉዳይ ፡ እሱን ፡ ማግኘት ፡ አለብኝ
6. ተግባር. It isn't my business to tell him that. ይህንን ፡ ለሱ ፡ መንገር ፡ የኔ ፡ ተግባር ፡ አይደለም
7. መብት. You have no business coming into this house. እዚህ ፡ ቤት ፡ ለመምጣት ፡ መብት ፡ የለህም
*That's none of your business! አያገባህም

**get down to business** ወደ ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ ተመለሰ
They finally got down to business and signed the contract. በመጨረሻ ፡ ወደ ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ ተመልሰው ፡ ውሉን ፡ ተፈራረሙ

**go into business** ንግድ ፡ አቋቋመ
She has gone into business for herself. የራሷን ፡ ንግድ ፡ አቋቁማለች
[See also 'export, mean, talk, venture']

**businesslike** ቀልጣፋ
He is businesslike in all his dealings. በአድራጎቱ ፡ ሁሉ ፡ ቀልጣፋ ፡ ነው

**businessman** ነጋዴ
He is a good businessman. ጥሩ ፡ ነጋዴ ፡ ነው

**bus stop** አውቶቡስ ፡ መቆሚያ
A shelter was built at the bus stop. አውቶቡስ ፡ መቆሚያ ፡ ላይ ፡ መጠለያ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር

**bust** (v.) ሰበረ
He busted the chair. ወንበሩን ፡ ሰበረው

**bust up** አፈረሰ
They tried to bust up the meeting. ስብሰባውን ፡ ለማፍረስ ፡ ሞከሩ

**bust** (n.)
1. ደረት. The seamstress measured her bust. ልብስ ፡ ሰፊዋ ፡ ደረቷን ፡ ለካችው
2. ከወገብ ፡ በላይ ፡ የተሠራ ፡ ሐውልት. A bust of Ras Makonnen is in the hallway. በመተላለፊያው ፡ ውስጥ ፡ ከወገብ ፡ በላይ ፡ የተሠራ ፡ የራስ ፡ መኰንን ፡ ሐውልት ፡ ይገኛል

**bustle**
1. ሽርጉድ ፡ አለ. He bustled about the room. ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ሽርጉድ ፡ አለ
2. ጉድ ፡ ጉድ ፡ አለ. She bustled about the kitchen preparing food for her guests. ለእንግዶቿ ፡ ምግብ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ማድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ጉድ ፡ ጉድ ፡ አለች
3. ደራ. In the afternoon, the market is bustling. ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ገበያ ፡ ደርቷል

**bustle with** በዛበት
The office bustled with activity. መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ግርግር ፡ በዝቶበት ፡ ነበር
[See also 'hustle and bustle']

**busy**
1. ሥራ ፡ የሚበዛበት. A busy man does not waste his time. ሥራ ፡ የሚበዛበት ፡ ሰው ፡ ጊዜውን ፡ አያባክንም
His secretary left him in the lurch at the

peak of the busy season. ጸሐፊዋ ፡ ሥራ ፡ በሚበዛበት ፡ ጊዜ ፡ ትታው ፡ ሄደች
2. የተጨናነቀ ፤ ተዘዋዋሪ ፡ የሚበዛበት ፤ ትራፊክ ፡ የሚበዛበት ፤ ተመላላሽ ፡ የሚበዛበት. He took a devious route to avoid busy streets. የተጨናነቀውን ፡ መንገድ ፡ ለመሸሽ ፡ በዙሪያ ፡ መንገድ ፡ ሄደ
They live on a busy street. ተዘዋዋሪ ፡ የሚበዛበት ፡ (ትራፊክ ፡ የሚበዛበት, or ተመላላሽ ፡ የሚበዛበት) ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ይኖራሉ

**be busy**
1. ሥራ ፡ በዛ(በት). He couldn't see any visitors because he was busy. ሥራ ፡ ስለበዛበት ፡ ባለጉዳዮችን ፡ ሊያነጋግር ፡ አልቻለም
2. ሥራ ፡ ያዘ. Don't disturb me! I am busy right now. አታስቸግረኝ ፤ አሁን ፡ ሥራ ፡ ይዤያለሁ
3. በሥራ ፡ ተጠመደ. The doctors were busy in the promotion of a health campaign. ሐኪሞች ፡ የጤና ፡ ጥበቃን ፡ ዘመቻ ፡ ለማስፋፋት ፡ በሥራ ፡ ተጠምደው ፡ ነበር
4. ሥራ ፡ ሠራ. The students are busy at their desks. ተማሪዎቹ ፡ በየተቀመጡበት ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ ናቸው
5. ተጣደፈ. She was busy decorating the room before the party. ከድግሱ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ክፍሉን ፡ በማጌጥ ፡ ሥራ ፡ ትጣደፍ ፡ ነበር
6. ተያዘ. The line is busy. መሥመሩ ፡ ተይዟል
7. ብዙ ፡ ገበያ ፡ አለው. The shops are always busy just before the holiday. ከበዓሉ ፡ በፊት ፡ መደብሮቹ ፡ ሁልጊዜ ፡ ብዙ ፡ ገበያ ፡ አላቸው

**busy oneself** ጊዜውን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ አሳለፈ
He busied himself with compiling a dictionary. መዝገበ ፡ ቃላት ፡ በማዘጋጀት ፡ ጊዜውን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ አሳለፈ

**be too busy** ሥራ ፡ በዛበት
I am even too busy to read the paper. ሥራ ፡ ስለሚበዛብኝ ፡ ጋዜጣ ፡ እንኳ ፡ ለማንበብ ፡ ጊዜ ፡ የለኝም

**be very busy** ሥራ ፡ በዛ(በት)
We are very busy at the office. እቢሮ ፡ ሥራ ፡ ይበዛብናል

## busybody ሁልገብ
He is a real busybody. ሁልገብ ፡ ነው

## but (conj.)
1. ነገር ፡ ግን. We can go with you, but we will have to come back early. ካንተ ፡ ጋር ፡ ለመሄድ ፡ እንችላለን ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ መመለስ ፡ አለብን
2. እንጂ. I did not mean you, but your friend. ጓደኛሀን ፡ እንጂ ፡ አንተን ፡ ማለቴ ፡ አይደለም
3. የሆነ ፡ ሆኖ. We don't like our new house, but we will have to make the best of it. አዲሱን ፡ ቤታችንን ፡ አንወደውም ፤ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የተቻለንን ፡ ያህል ፡ እንጠቀምበታለን
*I don't doubt but that he will do it. እንደሚሠራው ፡ አልጠራጠርም

**but** (prep.) ከ - - - በስተቀር
Nobody was there but me. ከኔ ፡ በስተቀር ፡ ማንም ፡ እዚያ ፡ አልነበረም
All but one were saved. ካንዱ ፡ በስተቀር ፡ ሁሉም ፡ ዳኑ

**but** (adv.)
1. ገና. He is but a child. ገና ፡ ሕፃን ፡ ነው
2. ብቻ. He has written us but once since he left. ከሄደ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ጽፎልናል
There is but one God. አንድ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ ነው

**but then** ታዲያ
But then I won't have any money. ምንም ፡ ገንዘብ ፡ አይቀረኝም ፡ ታዲያ
*The suit is expensive, but then it fits you well. ዋጋው ፡ ውድ ፡ ቢሆንም ፡ ልብሱ ፡ በጣም ፡ ተስማምቶሃል
[See also 'all, not, nothing']

## butcher (v.)
1. አረደ. He butchered an ox and ten chickens for his daughter's wedding. ለልጁ ፡ ሰርግ ፡ አንድ ፡ በሬና ፡ ዐሥር ፡ ዶሮ ፡ አረደ
2. ፈጀ. The army butchered the helpless civilians. ጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ መከላከያ ፡ የሌላቸውን ፡ ሲቪሎች ፡ ፈጀ

## butcher (n.)
1. ሉካንዳ ፡ ነጋዴ. His father is a butcher. አባቱ ፡ ሉካንዳ ፡ ነጋዴ ፡ ነው
2. ሥጋ ፡ ሻጭ. The butcher sliced off a piece of meat. ሥጋ ፡ ሻጩ ፡ ትንሽ ፡ ሥጋ ፡ ቈረጠ

## butcher shop ሉካንዳ
Try that butcher shop! እዚያኛው ፡ ሉካንዳ ፡ ጠይቅ

## butler [ዋና ፡ የቤት ፡ አሽከር]

## butt (v.) አጋጨ
The goat kept butting its head against the fence. ፍየሉ ፡ ራሱን ፡ ካጥሩ ፡ ጋር ፡ እየደጋገመ ፡ አጋጨ

## butt (n.)
1. ቁራጭ. He threw the cigarette butt away. የሲጋራውን ፡ ቁራጭ ፡ ወረወረ

2. ሰደፍ. The rifle butt is held in the hand. የጠመንጃ ፡ ሰደፍ ፡ በእጅ ፡ ይያዛል

**the butt of (one's) jokes** የሱ ፡ መሳለቂያ
The fat boy was the butt of their jokes. ወፍራሙ ፡ ልጅ ፡ የነሱ ፡ መሳለቂያ ፡ ነበር

**butter** (v.)
1. ቅቤ ፡ ቀባ. Please butter my bread! ዳቦዬን ፡ ቅቤ ፡ ቀባልኝ
2. በቅቤ ፡ አሰሰ. The cook buttered the pan. ወጥ ፡ ቤቷ ፡ መጥበሻውን ፡ በቅቤ ፡ አሰሰች

**butter** (n.) ቅቤ
Stew made with butter tastes good. በቅቤ ፡ የተሠራ ፡ ወጥ ፡ ይጣፍጣል
[See also 'sweet']

**butterfly** ቢራቢሮ
There are many butterflies in the rainy season. በክረምት ፡ ወራት ፡ ቢራቢሮች ፡ ይበዛሉ

**buttermilk** አሬራ
Buttermilk is made from milk. አሬራ ፡ ከወተት ፡ ይገኛል

**buttock** ቂጥ
There was a scar on his buttocks. ቂጡ ፡ ላይ ፡ ጠባሳ ፡ ነበረበት

**button** (v.) ቈለፈ
He buttoned his coat. ኮቱን ፡ ቈለፈ

**button** (n.)
1. አዝራር ፤ ቁልፍ. She sewed the shirt button on for me. ሸሚዜ ፡ ላይ ፡ አዝራር ፡ (ቁልፍ) ፡ ተከለችልኝ
2. መደወያ. When he pressed the button, the doorbell rang. መደወያውን ፡ ሲጫን ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ የበሩ ፡ ደወል ፡ ጮኸ
3. መጥሪያ. Please press lightly on the button! መጥሪያውን ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ ተጫነው

**buttonhole** የቁልፍ ፡ ቀዳዳ
Please sew up this torn buttonhole! የተቀደደውን ፡ የቁልፍ ፡ ቀዳዳ ፡ ዘምዝም

**buttress** መደገፊያ
The buttress keeps the wall from falling down. መደገፊያው ፡ ግድግዳው ፡ እንዳይወድቅ ፡ ይጠብቃል

**buxom** ዳሌያም
Only women are called buxom. ዳሌያም ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ ብቻ ፡ ናት

**buy** (bought)
1. ገዛ. The mother bought sugar cane for her children. እናትዮዋ ፡ ለልጆቿ ፡ ሸንኮር ፡ አገዳ ፡ ገዛችላቸው
Ten dollars will buy a lot of meat and beer. ዐሥር ፡ ብር ፡ ብዙ ፡ ሥጋና ፡ ቢራ ፡ ይገዛል
2. ሸመተ. He bought grain in the market. ከገበያ ፡ እህል ፡ ሸመተ
3. ጉቦ ፡ ሰጠ(ተሰጠ). It was charged that the judge had been bought. ለዳኛው ፡ ጉቦ ፡ ተሰጥቷል ፡ ተባለ

**buy off** በገንዘብ ፡ ደለለ
The official bought off those who might expose him. ባለሥልጣኑ ፡ የሚያጋልጡትን ፡ ሰዎች ፡ በገንዘብ ፡ ደለላቸው

**buy up** በሙሉ ፡ ገዛ
He bought up all the books from the bookstore. እመደብሩ ፡ የሚገኙትን ፡ መጻሕፍት ፡ በሙሉ ፡ ገዛ
[See also 'spree']

**buy** (n.) ግዢ
You paid only 300 dollars for your car. That was a good buy. ለመኪናህ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ አወጣህ ፤ ጥሩ ፡ ግዢ ፡ ነበር

**buyer** ገዢ
This advertisement is calculated to attract the buyers' attention. ይህ ፡ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ የገዢዎችን ፡ ስሜት ፡ እንዲማርክ ፡ ሆኖ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነው

**buzz** (v.)
1. ጥዝ ፡ አለ. The bee buzzes. ንቧ ፡ ጥዝ ፡ ትላለች
2. ጭው ፡ አለ(በት). My ears buzz because of the altitude. ከከፍታው ፡ የተነሣ ፡ ጆሮዬ ፡ ጭው ፡ አለብኝ
3. ጮኸ. Buzzing flies are a great irritation to me. የሚጮኹ ፡ ዝንቦች ፡ በጣም ፡ ያናድዱኛል
4. ተነዛ. The town buzzed with the news. ከተማው ፡ በወሬ ፡ ተነዛ

**buzz** (n.) ድምፅ
The buzz of a mosquito kept me awake. የወባ ፡ ትንኙ ፡ ድምፅ ፡ እንቅልፍ ፡ ነሣኝ
The buzz of whispers stopped when the teacher entered the room. የሹክሹክታው ፡ ድምፅ ፡ አስተማሪው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ እንደገባ ፡ ቆመ

**give a buzz** ደወለ(ለት)
When I find out, I'll give you a buzz. ነገሩን ፡ ሳውቅ ፡ እደውልልሃለሁ

**buzzard** ጥንብ ፡ አንሣ
We counted four buzzards in the air. ሰማይ ፡ ላይ ፡ አራት ፡ ጥንብ ፡ አንሣ ፡ ቈጠርን

**by**

1. በ. I will send it to you by rail. በባቡር ፡ እልክልሃለሁ
We came by car. በመኪና ፡ መጣን
That is done by machine. እሱ ፡ የተሠራው ፡ በመኪና ፡ ነው
We like to travel by night. በሌሊት ፡ መጓዝ ፡ እንወዳለን
By my watch, it is five o'clock. በኔ ፡ ሰዓት ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ነው
He ought to be here by this time. በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እዚህ ፡ መገኘት ፡ አለበት
The apples sell by the kilo. ቱፋ ፡ በኪሎ ፡ ይሸጣል
The room was 10 feet by 12 feet. ክፍሉ ፡ ዐሥር ፡ በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ጫማ ፡ ነው
They came into the room two by two. ሁለት ፡ በሁለት ፡ ወደ ፡ ክፍል ፡ ገቡ
Closed by order of the police. በፖሊስ ፡ ትእዛዝ ፡ የተዘጋ
I just know him by name. የማውቀው ፡ በስሙ ፡ ብቻ ፡ ነው
This book was written by a Frenchman. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተደረሰው ፡ ባንድ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ነው
He is paid by the hour. የሚከፈለው ፡ በሰዓት ፡ ነው
2. በ - - - ዳር. Artifacts made of flint were found by the river. ከባልጩት ፡ የተሠሩ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ነገሮች ፡ በወንዙ ፡ ዳር ፡ ተገኙ
3. በ - - - መሠረት. By act of parliament, demonstrations require a permit. በፓርላማ ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ ፈቃድ ፡ ያስፈልገዋል
4. በ - - - ዘንድ. He is beloved by all. በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ነው
5. በ - - - እጅ. The collaborator was shot by the patriots. ግብረ ፡ አበሩ ፡ በአርበኞቹ ፡ እጅ ፡ በጥይት ፡ ተገደለ
6. አጠገብ. The garden is by the house. ያትክልቱ ፡ ስፍራ ፡ ቤቱ ፡ አጠገብ ፡ ነው
7. እስከ. Can you finish the work by tomorrow? እስከ ፡ ነገ ፡ ሥራውን ፡ ልትጨርስ ፡ ትችላለህ ?
8. ከ - - - በፊት. Be back by ten o'clock! ከአራት ፡ ሰዓት ፡ በፊት ፡ ተመለስ
9. በ - - - በኩል. I go by the post office on my way to school. ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ስሄድ ፡ በፖስታ ፡ ቤቱ ፡ በኩል ፡ አልፋለሁ
10. እጐን. Come and sit by me! ና ፡ እጐኔ ፡ ተቀመጥ

**by and by** እያደር (እያደረ)
You will get used to it by and by. እያደር ፡ ትለምደዋለህ
You will see that it is not true by and by. እውነት ፡ ያለመሆኑን ፡ እያደረ ፡ ትረዳለህ

**by and large** ከሞላ ፡ ጎደል ፤ በጠቅላላው
By and large, the results were satisfactory. ከሞላ ፡ ጎደል ፡ (በጠቅላላው) ፡ ውጤቱ ፡ አጥጋቢ ፡ ነበር

**by oneself** ብቻውን
He did that by himself. ያንን ፡ ብቻውን ፡ ሠራው

**by that**
*What do you understand by that? ይህ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ይመስልሃል ?
*What do you mean by that? እንዲህ ፡ ስትል ፡ ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ?
[See also 'heart, now, then, way']

**bygone** የቀድሞ
The ancient Romans lived in bygone days. የጥንት ፡ ሮማውያን ፡ የኖሩት ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ነበር

**bygones** ያለፈው
Let bygones be bygones, and begin again! ያለፈው ፡ እንዳለፈ ፡ ይቅርና ፡ እንደገና ፡ እንጀምር

**bygone era** ያለፉት ፡ ዘመናት
Throwing rice at the bride is a carry-over from a bygone era. ሩዝ ፡ ሙሽራይቱ ፡ ላይ ፡ መበተን ፡ ካለፉት ፡ ዘመናት ፡ የቆየ ፡ ባህል ፡ ነው

**bylaw** ውስጠ ፡ ደንብ
The chairman read the bylaws before the meeting. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ የማኅበሩን ፡ ውስጠ ፡ ደንብ ፡ ከስብሰባው ፡ በፊት ፡ አነበቡ

**bypass** (v.)
1. በ - - - ጎን ፡ አለፈ. The cars bypass the city. መኪናዎቹ ፡ በከተማው ፡ ጎን ፡ ያልፋሉ
2. ዘሎ ፡ ወደ ፡ በላይ ፡ ሄደ. I am his supervisor, but he bypasses me in matters of importance. ተቈጣጣሪው ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ግን ፡ ከፍተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ሲያጋጥመው ፡ እኔን ፡ ዘሎ ፡ ወደ ፡ በላይ ፡ ይሄዳል

**by-product**
*This is a by-product of refining oil. ይህ ፡ ዘይት ፡ በሚጣራበት ፡ ጊዜ ፡ በደባልነት ፡ የሚገኝ ፡ ነው

**bystander** ተመልካች
The bystanders gathered around the injured man. ተመልካቾቹ ፡ በተጎዳው ፡ ሰው ፡ ዙሪያ ፡ ተሰበሰቡ

## C

**cab** ታክሲ
The doorman hailed a passing cab. በረኛው ፡ አላፊውን ፡ ታክሲ ፡ ጠራ

**cabal** አድማ
The students who had formed a cabal were expelled from school. አድማ ፡ ያደረጉት ፡ ተማሪዎች ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ተወገዱ

**cabbage** ጐመን
Buy some cabbage for me at the market! ከገበያ ፡ ጐመን ፡ ግዢልኝ

**cabin** ጎጆ ፤ ክፍል
They lived in a log cabin. በዕንጨት ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ ኖሩ
I had a cabin by myself. በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የግል ፡ ክፍል ፡ ነበረኝ

**cabinet**
1. ቁም ፡ ሣጥን. We keep our good dishes in the small cabinet. ጥሩዎቹን ፡ ሳሕኖቻችንን ፡ ትንሹ ፡ ቁም ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ እናኖራለን
2. ካቢኔ. The cabinet met with the President yesterday. ካቢኔው ፡ ትላንትና ፡ ከፕሬዚዳንቱ ፡ ጋር ፡ ተገናኘ

**cabinet meeting** የሚኒስትሮች ፡ ጉባኤ
The prime minister presides over most cabinet meetings. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አብዛኛውን ፡ የሚኒስትሮች ፡ ጉባኤ ፡ በሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ይመራል

**cable** (v.) ቴሌግራም ፡ አደረገ
Cable immediately when you arrive! ወዲያው ፡ እንደደረስክ ፡ ቴሌግራም ፡ አድርግ

**cable** (n.)
1. በጣም ፡ ወፍራም ፡ የሆነ ፡ ሽቦ. The bridge is supported by cables. ድልድዩ ፡ በጣም ፡ ወፍራም ፡ በሆነ ፡ ሽቦ ፡ ተይዟል
2. ሽቦ. The cable is covered with copper plating. ሽቦው ፡ የመዳብ ፡ ሽፋን ፡ አለው
3. ቴሌግራም. I want to send a cable to Addis Ababa. ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ቴሌግራም ፡ ለመላክ ፡ እፈልጋለሁ

**cacao** ካካዎ

**cache** የተደበቀበት ፡ ቦታ
They discovered a cache of food. ምግብ ፡ እተደበቀበት ፡ ቦታ ፡ አገኙ

**cackle** አስካካ
The hen laid an egg and cackled. ዶሮዋ ፡ እንቁላል ፡ ጣለችና ፡ አስካካች

**cactus** የባሕር ፡ ቁልቋል

**cadaver** ሬሳ
The cadaver was buried by the police. ሬሳው ፡ በፖሊሶች ፡ ተቀበረ

**cadaverous** የጣረሞት
The old woman's cadaverous face frightened the children. የአሮጊቷ ፡ የጣረሞት ፡ መልክ ፡ ልጆቹን ፡ አስደነገጣቸው

**cadence** ምት
The cadence of waves breaking on the shore is pleasant to the ears. ሞገዱ ፡ የባሕሩን ፡ ዳርቻ ፡ ሲገርፍ ፡ የሚሰማው ፡ ምት ፡ ያስደስታል

**cadence of speech** አነጋገር
The cadence of her speech shows she is from Sweden. ካነጋገሯ ፡ የስዊድን ፡ ተወላጅ ፡ መሆኗ ፡ ይታወቃል

**cadet** እጩ ፡ መኰንን
The air force cadets are in Debre Zeit. የአየር ፡ ኀይል ፡ እጩ ፡ መኰንኖች ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ናቸው

**café** ቡና ፡ ቤት
There is a good café at the airport. በአይሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ጥሩ ፡ ቡና ፡ ቤት ፡ አለ

**cage**
1. የሽቦ ፡ ቤት. The lion was in a strong cage. አንበሳው ፡ በጠንካራ ፡ የሽቦ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ነበር
2. የወፍ ፡ ጎጆ. He keeps a songbird in a cage. ዘማሪ ፡ ወፍን ፡ በወፍ ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ ያኖራል

**cagey** ዘዴኛ
The cagey politician would not answer the questions directly. ዘዴኛው ፡ የፖለቲካ ፡ ሰው ፡ ጥያቄዎቹን ፡ በቀጥታ ፡ አይመልስም ፡ ነበር

**cajole** ደለለ
She cajoled the child with candy. ልጁን ፡ በከረሜላ ፡ ደለለችው
He cajoled me into signing the note. ደልሎ ፡ ወረቀቱን ፡ አስፈረመኝ

**cake** ኬክ ፤ ብስኩት
I like cake after lunch. ከምሳ ፡ በኋላ ፡ ኬክ ፡ (ብስኩት) ፡ እወዳለሁ
[See also 'soap']

**calamitous** አሰቃቂ
The calamitous journey ended in the death of the entire family. አሰቃቂው ፡ ጉዞ ፡ የቤተ ፡ ሰቡን ፡ ሁሉ ፡ እልቂት ፡ አስከተለ

**calamity**
1. አደጋ. The bus accident was the worst calamity in years. የአውቶቡሱ ፡ አደጋ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ከደረሱት ፡ አደጋዎች ፡ ሁሉ ፡ የከፋ ፡ ነበር
2. መቅሠፍት. War is always a calamity for a country. ጦርነት ፡ ለአገሪቷ ፡ ሁሌ ፡ መቅሠፍ ት ፡ ነው
3. ስጋት. Dire calamity threatened the town when the water was cut off. ውኃው ፡ በተቋረጠ ፡ ጊዜ ፡ ከተማዋ ፡ አደገኛ ፡ ስጋት ፡ ላይ ፡ ወደቀች

**calculate**
1. አሰላ. It is difficult to calculate the costs. ወጪውን ፡ ለማስላት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
We calculated the day of the week on which Christmas will fall. ገና ፡ ከሳምንቱ ፡ በየትኛው ፡ ቀን ፡ እንደሚውል ፡ አሰላን
2. አሰበ. Pilots have to calculate the drift of the wind when they fly. አውሮፕላን ፡ ነጂዎ ች ፡ በሚበሩበት ፡ ጊዜ ፡ የነፋሱን ፡ አቅጣጫ ፡ ማሰብ ፡ አለባቸው

**be calculated to**
1. ታስቦ ፡ ተሰነዘረ. His remarks were calculated to inspire confidence. አስተያየቱ ፡ እምነት ን ፡ እንዲያሳድር ፡ ታስቦ ፡ የተሰነዘረ ፡ ነበር
2. ሆኖ ፡ ተዘጋጀ. This advertisement is calculated to attract the buyers' attention. ይህ ፡ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ የገዢዎችን ፡ ስ ሜት ፡ እንዲማርክ ፡ ሆኖ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነው

**calculation** ሒሳብ
Keep quiet or you will throw me off in my calculation. ዝም ፡ በል ፡ ያለዚያ ፡ ሒሳቡን ፡ ታሳስተኛለህ

**calendar**
1. የቀን ፡ መቍጠሪያ. I have noted it on my calendar. በቀን ፡ መቍጠሪያው ፡ ላይ ፡ ማስታ ወሻ ፡ አድርጌያለሁ
2. የቀን ፡ አቈጣጠር. The Muslim calendar differs from the Christian one. የእስላም ፡ የ ቀን ፡ አቈጣጠር ፡ ከክርስቲያን ፡ የተለየ ፡ ነው
3. አጀንዳ. The judge proceeded to hear the next case on the calendar. ዳኛው ፡ ከአጀንዳው ፡ ላይ ፡ የሚቀጥለውን ፡ ጉዳይ ፡ መስማት ፡ ጀመሩ

**calf** (calves)
1. ጥጃ. Cows and calves were grazing in the field. ላሞችና ፡ ጥጆች ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ይግጡ ፡ ነበር
2. ባት. The bullet hit him in the calf. ጥይቱ ፡ ባቱ ፡ ላይ ፡ መታው

**caliber**
1. የአፈሙዝ ፡ ስፋት. The caliber of the gun is 50 millimeters. የጠመንጃው ፡ አፈሙዝ ፡ ስፋት ፡ አ ምሳ ፡ ሚሊሜትር ፡ ነው
2. ችሎታ. My uncle is a man of high caliber. አጎቴ ፡ የላቀ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**calico** [ርካሽ ፡ ቀለማዊ ፡ ጌጣጌጥ ፡ ያሉት ፡ ከጥጥ ፡ የተሠራ ፡ ጨርቅ]

**calk** በቅጥራን ፡ መረገ (ተመረገ)
Boats are calked to make them watertight. ጀልባዎች ፡ ውኃ ፡ እንዳይገባቸው ፡ በቅጥራን ፡ ይ መረጋሉ

**call** (vt.)
1. ጠራ (ተጠራ). I called him, but he did not hear me. ጠርቼው ፡ ነበር ፡ ግን ፡ አልሰማኝም
Call a doctor! ሐኪም ፡ ጥራ
Has my name been called yet? ስሜ ፡ ገና ፡ አልተ ጠራም ?
2. አለ. What do you call this in Amharic? ይህንን ፡ በማርኛ ፡ ምን ፡ ትለዋለህ ?
3. ደወለ(ለት). Call me when you arrive! ስትደርስ ፡ ደውልልኝ
4. ቀጠረ (ተቀጠረ). The conference was called for Monday. ስብሰባው ፡ ለሰኞ ፡ ተቀጥሯል
5. ሰየመ. They called the baby John. ሕፃኑን ፡ ጆን ፡ ብለው ፡ ሰየሙት

**call** (vi.)
1. ጠራ. The child called, but no one heard him. ልጁ ፡ ቢጠራ ፡ ማንም ፡ አልሰማውም
2. ለጉብኝት ፡ ብቅ ፡ አለ. The minister called, but did not stay long. ሚኒስትሩ ፡ ለጉብኝት ፡ ብ ቅ ፡ ብለው ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ አልቆዩም

**(be) called away** ተጠርቶ ፡ ሄደ
The doctor is not in. He was called away on an emergency. ሐኪሙ ፡ የለም ፤ በድንገተኛ ፡ ምክንያት ፡ ተጠርቶ ፡ ሄዷል

**call back** መልሶ ፡ ጠራ
The President called him back from Asia. ፕሬዚዳንቱ ፡ ከእስያ ፡ መልሶ ፡ ጠራው

**call for**
1. ጠየቀ. The conference called for solidarity between the two nations. ጉባኤው ፡ በሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ አንድነት ፡ እንዲመሠረት ፡ ጠየቀ
2. ወሰደ. I have to call for my laundry. አጣቢ ፡ ቤት ፡ ያለውን ፡ ልብሴን ፡ መውሰድ ፡ አለብኝ
3. ብቅ ፡ ብሎ ፡ አየ. Will you call for me at the hotel? ወደ ፡ ሆቴል ፡ ብቅ ፡ ብለህ ፡ አታየኝም ?
*The riot called for an explanation. የዚህ ፡ ረብሻ ፡ ምክንያት ፡ መታወቅ ፡ አለበት

**call for help** እሪ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ
I called for help when I was robbed. በተዘረፍኩ ፡ ጊዜ ፡ እሪ ፡ ብዬ ፡ ጮኽኩ

**call forth** ሰጠ
The circumstances of her childhood called forth her courage and resolve. የልጅነት ፡ ሁኔታዋ ፡ ጉብዝናንና ፡ ቁራጥነትን ፡ ሰጣት

**call in**
1. ጠራ. We had to call in a specialist. ልዩ ፡ ዐዋቂ ፡ መጥራት ፡ ግድ ፡ ሆነብን
2. አስገባ. Call him in! አስገባው

**(be) called in** እንዲመለስ ፡ ተደረገ
All old bank notes are being called in. አሮጌ ፡ ብር ፡ ሁሉ ፡ እንዲመለስ ፡ በመደረግ ፡ ላይ ፡ ነው

**call (one) names** ሰደበ
He got mad and called me names. ተናዶ ፡ ሰደበኝ

**call off** ሰረዘ
They called off the program because of rain. በዝናቡ ፡ ምክንያት ፡ ፕሮግራማቸውን ፡ ሰረዙት
*Please call your dog off; he is bothering me. ውሻህ ፡ አስቸገረኝ ፤ እስቲ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ጥራው

**(be) called off** ቀረ
The broadcast was called off for technical reasons. በቴክኒክ ፡ ጉድለት ፡ ምክንያት ፡ የራዲዮ ፡ ፕሮግራም ፡ ቀረ

**call on**
1. ጠየቀ. Why doesn't the teacher call on me? አስተማሪው ፡ ለምን ፡ እኔን ፡ አይጠይቀኝም ?
Call on my friend when you visit Addis Ababa. አዲስ ፡ አበባ ፡ ስትሄድ ፡ ጓደኛዬን ፡ ጠይቀው
2. እንዲጠቀምበት ፡ አደረገው. The danger called on his energy. አደጋው ፡ በሙሉ ፡ ኀይሉ ፡ እንዲጠቀምበት ፡ አደረገው

**call (something) one's own**
*We have nothing that we can call our own. የኛ ፡ ነው ፡ የምንለው ፡ ምንም ፡ የለንም

**call out**
1. አዘዘ. The President called out the army to restore order. ፕሬዚዳንቱ ፡ ጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ ጸጥታ ፡ እንዲያስከብር ፡ አዘዘ
2. ጮክ ፡ ብሎ ፡ አነበበ. The secretary called out the answers. ጸሐፊዋ ፡ መልሱን ፡ ጮክ ፡ ብላ ፡ አነበበች

**call together** ሰበሰበ
The leader called his men together. መሪው ፡ ሰዎቹን ፡ ሰበሰባቸው

**call up**
1. ደወለ(ለት). I will call you up tomorrow. ነገ ፡ እደውልልሃለሁ
2. አዘመተ. If war breaks out, the Ministry of Defense will call up many civilians. ጦርነት ፡ ቢነሣ ፡ የመከላከያ ፡ ሚኒስቴር ፡ ብዙ ፡ ሲቪሎችን ፡ ያዘምታል
[See also 'attention, bad, colors, dirty, mind, name, order, question']

**call** (n.) ጥሪ
Did you get your telephone call from New York? ከኒውዮርክ ፡ የተደወለልህ ፡ የስልክ ፡ ጥሪ ፡ ደረሰህ ?
*The students gathered at the call of the teacher. አስተማሪው ፡ ሲጠራቸው ፡ ተማሪዎቹ ፡ ተሰበሰቡ
*Were there any calls for me? ስልክ ፡ የደወለልኝ ፡ ነበር ?
*He answered the call of his country. አገሪቱ ፡ የፈለገችበትን ፡ ግዳጅ ፡ ፈጸመ
*A busy man has many calls on his time. ሥራ ፡ የሚበዛበት ፡ ሰው ፡ ጊዜውን ፡ የሚወስድበት ፡ ጉዳይ ፡ ብዙ ፡ ነው

**call for**
1. ጠያቂ. There is no call for raincoats in the dry season. በበጋ ፡ ወራት ፡ የዝናብ ፡ ልብስ ፡ ጠያቂ ፡ የለውም
2. ምክንያት. There was no call for you to laugh at us. የምትሥቅብን ፡ ምንም ፡ ምክንያት ፡ አልነበረም

**call for help** ኡኡታ
He heard a call for help. ኡኡታ ፡ ሰማ

**answer the call** ዐዋጅ ፡ ተቀበለ
The manhood of the nation answered the call to defend the country. አገሪቱን ፡ ከወራሪ ፡ ለመከላከል ፡ የተደረገውን ፡ ዐዋጅ ፡ ወንዶች ፡ ሁሉ ፡ ተቀበሉት

**be on call** ተረኛ ፡ ነው
The doctor was on call all night. ሐኪሙ ፡ ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ ተረኛ ፡ ነበር

**pay a call** ጠየቀ
I have to pay a call on the governor. አገረ ፡ ገዢውን ፡ መጠየቅ ፡ አለብኝ

**within call**
*Remain within call while I am ill. በሕመሜ ፡ ጊዜ ፡ ልትጠራ ፡ ከምትችልበት ፡ አካባቢ ፡ ቆይ
[See also 'close call, duty, roll call, telephone']

**calligrapher** ቁም ፡ ጸሐፊ
A calligrapher is not paid much nowadays. ቁም ፡ ጸሐፊ ፡ ባሁን ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ አይከፈለውም

**calligraphy** የቁም ፡ ጽሕፈት
Not many people know calligraphy. የቁም ፡ ጽሕፈት ፡ የሚችሉ ፡ ብዙ ፡ አይደሉም

**calling**
1. ዝንባሌ. He has a calling for a military career. የወታደርነት ፡ ዝንባሌ ፡ አለው
2. ሙያ. It is important to find the right calling. ተስማሚውን ፡ ሙያ ፡ ማግኘት ፡ ያስፈልግሃል

**callous** ርኅሩኄ ፡ የሌለው
Only a callous person can see suffering without trying to relieve it. ሰው ፡ መከራ ፡ ሲደርስበት ፡ አይቶ ፡ ለመርዳት ፡ ሳይሞክር ፡ የሚያልፍ ፡ ርኅሩኄ ፡ የሌለው ፡ ብቻ ፡ ነው

**be callous** መጅ ፡ አበቀለ
My hands are callous from work. እጄ ፡ በሥራ ፡ ምክንያት ፡ መጅ ፡ አብቅሏል

**callus** መጅ
Toil left his hands covered with calluses. ብርቱ ፡ ሥራ ፡ እጁን ፡ መጅ ፡ ብቻ ፡ አድርጎታል

**calm** (vt.)
1. አረጋጋ. We tried to calm the frightened animals. የደነበሩትን ፡ እንስሳት ፡ ማረጋጋት ፡ ሞከርን
2. አበረደ. The cashier tried to calm the furious woman. ገንዘብ ፡ ተቀባዩ ፡ የተናደደችውን ፡ ሴት ፡ ሊያበርድ ፡ ሞከረ

**calm** (vi.) ጸጥ ፡ አለ
After the heavy storm, the sea calmed. ከኀይለኛ ፡ ማዕበል ፡ በኋላ ፡ ባሕሩ ፡ ጸጥ ፡ አለ

**calm down** (vt.) አረጋጋ
Try to calm him down! እሱን ፡ ለማረጋጋት ፡ ሞክር

**calm down** (vi.)
1. ጸጥ ፡ አለ. The wind has calmed down. ነፋሱ ፡ ጸጥ ፡ ብሏል
2. ረጋ ፡ አለ. Little by little he calmed down. እያደር ፡ ረጋ ፡ አለ

**calm oneself** ረጋ ፡ አለ
Calm yourself; the dentist won't hurt you. ረጋ ፡ በል ፡ የጥርሱ ፡ ሐኪም ፡ አይጐዳህም

**calm** (n.) ጸጥታ
Calm prevails in the country. ባገሪቷ ፡ ላይ ፡ ጸጥታ ፡ ሰፍኗል

**calm** (adj.) የረጋ
They rowed a boat on the calm sea. በረጋው ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ጀልባ ፡ ቀዘፉ
Although she was frightened, she answered with a calm voice. ምንም ፡ እንኳን ፡ ብትደነግጥ ፡ በረጋ ፡ ድምፅ ፡ መለሰች

**be calm**
1. ጸጥ ፡ አለ. The sea is calm again. ባሕሩ ፡ እንደገና ፡ ጸጥ ፡ ብሏል
2. መንፈሰ ፡ ርጉ ፡ ነው. He is calm in the presence of danger. አደጋ ፡ ባጋጠመው ፡ ጊዜ ፡ መንፈሰ ፡ ርጉ ፡ ነው

**keep calm** ጸጥ ፡ አለ
Keep calm! The doctor is coming. ጸጥ ፡ በል ፤ ሐኪሙ ፡ እየመጣ ፡ ነው

**calmly** በጥሞና
She took the news calmly. ዜናውን ፡ በጥሞና ፡ ተቀበለች

**calumniate** አማ
He calumniates his friend behind his back. ወዳጁን ፡ በሌለበት ፡ ያማዋል

**calumny** ሐሜት
His charges are nothing but baseless calumny. የርሱ ፡ ማሳጣት ፡ መሠረት ፡ቢስ ፡ የሆነ ፡ ሐሜት ፡ ነው

**calve** ወለደ
The cow is pregnant and will calve soon. ላሚ ፡ እርጉዝ ፡ ናት ፡ በቅርብ ፡ ትወልዳለች

**calves,** see **calf**

**came,** see **come**

**camel** ግመል
The camel is an animal of the desert. ግመል ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ እንስሳ ፡ ናት

**camera** ካሜራ
I bought a camera in Japan. ከጃፓን ፡ ካሜራ ፡ ገዛሁ

**camouflage** (v.)
*They camouflage their guns with green paint.

ጠመንጃቸው ፡ ተለይቶ ፡ እንዳይታወቅ ፡ አረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ ይቀቡታል

**camouflage** (n.)
[አካባቢውን ፡ የሚመስል ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ በመልበስ ፡ እንዳይታወቅ ፡ ማድረግ]

**camp** (v.) ሰፈረ
We camped in the woods. እጫካው ፡ ውስጥ ፡ ሰፈርን

**camp** (n.)
1. የጦር ፡ ሰፈር. At what camp did you get your training? በየትኛው ፡ የጦር ፡ ሰፈር ፡ ሠለጠንክ ?
2. መዝናኛ ፡ ሰፈር. He shipped his children off to camp. ልጆቹን ፡ ወደ ፡ መዝናኛ ፡ ሰፈር ፡ ላካቸው
3. ወገን. The students were split into two camps with regard to their school's rules. ተማሪዎቹ ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ቤታቸው ፡ ሕግ ፡ ሁኔታ ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ተከፍለዋል

**live in a camp** ድንኳን ፡ ተክሎ ፡ ኖረ
Many people live in a camp near a lake in the summer. በበጋ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ድንኳን ፡ ተክለው ፡ ሐይቅ ፡ አጠገብ ፡ ይኖራሉ

**campaign** (v.) ዘመቻ ፡ አደረገ
The students campaigned for their candidate's election. ተማሪዎቹ ፡ ለተመራጫቸው ፡ ዘመቻ ፡ አደረጉለት

**campaign** (n.)
1. ዘመቻ. He took part in the African campaign. በአፍሪካ ፡ ዘመቻ ፡ ተካፍሏል
2. ውድድር. American presidential campaigns last several months. የአሜሪካ ፡ የፕሬዚዳንትነት ፡ ውድድር ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ ይወስዳል
3. ተጋድሎ. Ethiopia issued stamps commemorating the U.N. campaign against hunger. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ረኀብን ፡ ለማስወገድ ፡ ለሚያደርገው ፡ ተጋድሎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመታሰቢያ ፡ ቴምብር ፡ አወጣች
4. ትግል. The police are making an aggressive campaign against crime. ፖሊሶቹ ፡ ወንጀልን ፡ ለመከላከል ፡ ጥብቅ ፡ ትግል ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ናቸው
5. ጥረት. The campaign to raise money for the college brought in a thousand dollars. ለኮሌጁ ፡ ገንዘብ ፡ ለመሰብሰብ ፡ የተደረገው ፡ ጥረት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ አስገኘ
[See also 'literacy, wage']

**campaigner** ተሟጋች
He is a strenuous compaigner for literacy. ለጉልማሶች ፡ ትምህርት ፡ ብርቱ ፡ ተሟጋች ፡ ነው

**campfire** [ሽርሽር ፡ ሲኬድ ፡ የሚሰፈርበት ፡ ቦታ ፡ ለምግብ ፡ መሥሪያም ፡ ሆነ ፡ ዙሪያውን ፡ ተሰብስቦ ፡ ለመጫወት ፡ የሚነድ ፡ እሳት]

**campus** ምድረ ፡ ግቢ
The campus of the Haile Sellassie University is large. የቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ምድረ ፡ ግቢ ፡ ሰፊ ፡ ነው

**can** (canned) በቆርቆሮ ፡ አሸገ
They built a factory for canning meat. ሥጋ ፡ በቆርቆሮ ፡ የሚያሽግ ፡ ፋብሪካ ፡ አቋቋሙ

**can** (could) ቻለ
Anyone can cross the street here. እዚህ ፡ ጋ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ መንገዱን ፡ ለማቋረጥ ፡ ይችላል
Once she could sing beautifully. ድሮ ፡ ጥሩ ፡ አድርጋ ፡ መዘመር ፡ ትችል ፡ ነበር

**can** (n.) ጣሳ
Give me a can of peas! አንድ ፡ ጣሳ ፡ አተር ፡ ስጠኝ

**canal** ቦይ
The irrigation canal was blocked with mud. የመስኖው ፡ ቦይ ፡ በጭቃ ፡ ተደፍኖ ፡ ነበር
The Suez Canal is blocked at present. ባሁን ፡ ጊዜ ፡ የስዌዝ ፡ ቦይ ፡ ተዘግቷል
[See also 'drainage']

**canalize**
1. በቦይ ፡ አገናኘ. They canalized the two creeks and the small lake. ሁለቱን ፡ ጅረቶችና ፡ ትንሹን ፡ ሐይቅ ፡ በቦይ ፡ አገናኙ
2. ወደ ፡ አንድ ፡ አቅጣጫ ፡ እንዲመራ ፡ አደረገ. The war canalized their efforts. ጦርነቱ ፡ ጥረታቸው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ አቅጣጫ ፡ እንዲመራ ፡ አደረገ

**cancel**
1. አፈረሰ. I had to cancel my doctor's appointment. ከሐኪሙ ፡ ጋር ፡ የነበረኝን ፡ ቀጠሮ ፡ ማፍረስ ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ
2. ሰረዘ. The post office cancels the stamp on a letter that is mailed. ፖስታ ፡ ቤቱ ፡ በተላከ ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ ቴምብር ፡ ይሰርዛል
He canceled his order for the books. መጽሐፎቹ ፡ እንዲላኩለት ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ሰረዘ
3. ተወ. I would like to cancel my room reservation. እንዲያዝልኝ ፡ የጠየቅሁትን ፡ ክፍል ፡ ለመተው ፡ እፈልጋለሁ
4. ማረ. He canceled the rest of my debt. የቀረብኝን ፡ ዕዳ ፡ ማረኝ

**be canceled** ቀረ
Today's meeting is canceled. የዛሬው ፡ ስብሰባ ፡ ቀርቷል

**cancer** የነቀርሳ ፡ በሽታ
Cancer is a strong argument against smoking. ማጨስን ፡ ለማስተው ፡ የነቀርሳ ፡ በሽታ ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ ነው

**candid** ቅን
Give me your candid opinion! ቅን ፡ ሐሳብህን ፡ ንገረኝ

**be candid** እውነቱን ፡ ተናገረ
I like a man none the worse for being candid. እውነቱን ፡ ስለተናገረ ፡ አንድን ፡ ሰው ፡ አልጠላውም

**candidacy** እጩ ፡ ተወዳዳሪ ፡ መሆን
John announced his candidacy for the senate. ጆን ፡ በሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባልነት ፡ እጩ ፡ ተወዳዳሪ ፡ መሆኑን ፡ ገለጸ

**candidate**
1. ተወዳዳሪ. We have three candidates for the position. ለቦታው ፡ ሦስት ፡ ተወዳዳሪዎች ፡ አሉን
2. ተመራጭ. How many ballots were cast for their candidates? ለተመራጮቻቸው ፡ ስንት ፡ ድምፅ ፡ ተሰጠ ?

**candle** ሻማ
When the electricity went off, we bought candles. ኮረንቲ ፡ ሲጠፋ ፡ ሻማ ፡ ገዛን

**candlelight** ሻማ
We dined by candlelight. በሻማ ፡ እራት ፡ በላን

**candlestick** የሻማ ፡ መቆሚያ
The candlestick is made of brass. የሻማው ፡ መቆሚያ ፡ ከነሐስ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**candy** ከረሜላ
Children like chocolate candy more than other kinds of candy. ሕፃናት ፡ ከሌላ ፡ ከረሜላ ፡ ይልቅ ፡ የቸኮላታ ፡ ከረሜላ ፡ ይወዳሉ

**cane** (v.) በበትር ፡ መታ
He caned the dog, but the dog did not budge. ውሻውን ፡ በበትር ፡ መታው ፡ ግን ፡ ውሻው ፡ አልተንቀሳቀሰም

**cane** (n.) ከዘራ
The old man was leaning on a black cane. ሽማግሌው ፡ ጥቁር ፡ ከዘራ ፡ ተደግፈው ፡ ነበር
[See also 'sugar cane']

**canine** የክራንቻ
Wolves and foxes are canine animals. ተኩላዎችና ፡ ቀበሮዎች ፡ የክራንቻ ፡ እንስሳት ፡ ናቸው

**canine tooth** ክራንቻ
The child lost his canine tooth. ሕፃኑ ፡ ክራንቻውን ፡ ነቀለ

**canker** [የአፍ ፡ ቁስል]

**canned** (adj.) የቆርቆሮ ፤ የታሸገ
We have already used up our canned food. የቆርቆሮ ፡ ምግባችንን ፡ ድሮ ፡ ጨረስነው
The company was fined for adulterating canned meat. ኩባንያው ፡ እታሸገው ፡ ሥጋ ፡ ውስጥ ፡ የማይረባ ፡ ሥጋ ፡ በመቀላቀሉ ፡ ተቀጣ

**cannibal** የሰው ፡ ሥጋ ፡ የሚበላ ፡ ሰው
Cannibals eat people whom they capture in wars. የሰው ፡ ሥጋ ፡ የሚበሉ ፡ ሰዎች ፡ በጦርነት ፡ የማረኳቸውን ፡ ሰዎች ፡ ይበሏቸዋል

**canning** በጣሳ ፡ ማሸግ
Canning makes the preservation of food possible. በጣሳ ፡ ማሸግ ፡ ምግብን ፡ ሳይበላሽ ፡ ለማኖር ፡ ያስችላል

**cannon** መድፍ
The Ethiopians captured many cannons from the Italians. ኢትዮጵያውያን ፡ ከኢጣልያን ፡ ብዙ ፡ መድፎች ፡ ማረኩ

**cannonade** የመድፍ ፡ እሩምታ
The cannonade kept us awake all night. የመድፉ ፡ እሩምታ ፡ ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ እንቅልፍ ፡ ነሣን

**canny** ብልጥ
He is canny where money is concerned. የገንዘብ ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፡ ብልጥ ፡ ይሆናል

**canoe** ታንኳ
The canoe sank in the river. ታንኳው ፡ ወንዙ ፡ ውስጥ ፡ ሰጠመ

**canon**
1. ሕግ. The church canon regarding marriage is often violated. ጋብቻን ፡ የሚመለከተው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይጣሳል
2. ደንብ. His remarks violated all canons of good taste. አስተያየቱ ፡ የተገቢነትን ፡ ደንብ ፡ ሁሉ ፡ ጣሰ

**can opener** የቆርቆሮ ፡ መክፈቻ
I need a can opener to open the can. ለዚህ ፡ ቆርቆሮ ፡ የቆርቆሮ ፡ መክፈቻ ፡ እፈልጋለሁ

**canopy**
1. አጐበር. The newly married couple sat under the canopy. ሙሽሮቹ ፡ አጐበር ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠዋል
2. ጥላ. He walked beneath a canopy of flowery trees. በአበባማ ፡ ዛፎች ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ተራመደ

**cant** የራሱ ፡ መነጋገሪያ
The thieves have their own cant. ሌቦቹ ፡ የራሳቸው ፡ መነጋገሪያ ፡ አላቸው

**canteen**
1. ኰዳ. I could tell by the gurgle that there was some water in the canteen. በኰዳው ፡ ውስጥ ፡ ውኃ ፡ እንዳለ ፡ በማንቦጫጫ ፡ ላውቅ ፡ ቻልኩ
2. መዝናኛ ፡ ቤት. The officers have their own canteen. መኰንኖቹ ፡ የራሳቸው ፡ መዝናኛ ፡ ቤት ፡ አላቸው

**canter**
*He cantered across the field. በዝግተኛ ፡ ግልቢያ ፡ ሜዳውን ፡ አቋረጠ

**canticle** መዝሙር
The most famous canticle is the Song of Solomon. ከሁሉም ፡ የታወቀ ፡ መዝሙር ፡ የሰሎሞን ፡ መሓልየ ፡ መሓልይ ፡ ነው

**canton** ግዛት
The Swiss cantons confederated to form a union. የስዊዝ ፡ ግዛቶች ፡ አንድ ፡ የኅብረት ፡ መንግሥት ፡ ለማቋቋም ፡ ተባበሩ

**canvas** (n.) ሸራ
Tents of canvas were given to the refugees. ስደተኞቹ ፡ የሸራ ፡ ድንኳን ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ነበር

**canvass** (vt.)
1. መረመረ. John canvassed the papers hunting for 'help wanted' ads. ጆን ፡ የሥራ ፡ ፈላጊዎችን ፡ ማስታወቂያ ፡ በመፈለግ ፡ ጋዜጣዎችን ፡ መረመረ
2. አሰሰ. Salesmen canvassed the whole city for subscriptions. ደንበኛ ፡ ለማግኘት ፡ አሻሻጮች ፡ ከተማውን ፡ አሰሱት

**canvass** (vi.) በየመንገዱ ፡ ተዘዋወረ
The students canvassed for their political candidate. ለነሱ ፡ እጩ ፡ ተወዳዳሪ ፡ ድምፅ ፡ ለማግኘት ፡ ተማሪዎቹ ፡ በየመንገዱ ፡ ተዘዋወሩ

**canyon** ገደላማ ፡ ሸለቆ
There are many canyons in Godjam. በጐጃም ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ገደላማ ፡ ሸለቆዎች ፡ አሉ

**cap** (capped), v.
1. ሸፈነ. Snow capped the hills. በረዶ ፡ ጋራዎችን ፡ ሸፈነ
2. ወተፈ. The storekeeper capped the bottle. ባለመደብሩ ፡ ጠርሙሱን ፡ ወተፈ
3. ሊደርስበት ፡ ቻለ. The other runners could not cap John's winning time. ሌሎች ፡ ሯጮች ፡ ጆን ፡ ያሸነፈበትን ፡ ጊዜ ፡ ሊደርሱበት ፡ አልቻሉም

**cap** (n.)
1. ቆብ. He is wearing a cap. ቆብ ፡ አድርጓል
2. ክዳን. I have lost the cap of my fountain pen. የብዕሬ ፡ ክዳን ፡ ጠፋብኝ
[See also 'feather']

**capability** ችሎታ
The boy shows much capability for learning. ልጁ ፡ ለመማር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችሎታ ፡ አለው

**capable** ችሎታ ፡ ያለው
Many capable doctors work in this hospital. ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ብዙ ፡ ሐኪሞች ፡ በዚህ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ይሠራሉ
*He is quite capable of telling a lie. ለመዋሸት ፡ ግድ ፡ የለውም

**be capable of** ተቻለ
This novel is capable of many interpretations. ይህ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ድርሰት ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ሊፈታ ፡ ይቻላል

**capacity**
1. ሥልጣን. What is his capacity in that office? በዚያ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሥልጣኑ ፡ ምንድነው ?
I am here in the capacity of guardian. እዚህ ፡ የምገኘው ፡ በሞግዚትነት ፡ ሥልጣኔ ፡ ነው
2. ችሎታ. He has a great capacity for learning. እሱ ፡ ትልቅ ፡ የመማር ፡ ችሎታ ፡ አለው
This book is beyond the capacity of third graders. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከሦስተኛ ፡ ክፍል ፡ ልጆች ፡ ችሎታ ፡ በላይ ፡ ነው

**be crowded to capacity** ጢም ፡ አለ
The hall was crowded to capacity. አዳራሹ ፡ ጢም ፡ ብሎ ፡ ነበር

**be filled to capacity** ጢም ፡ አለ
The theater was filled to capacity. የቲያትር ፡ ቤቱ ፡ አዳራሽ ፡ ጢም ፡ ብሎ ፡ ነበር

**have a capacity of** ያዘ
The tank has a capacity of one hundred gallons. በርሚሉ ፡ መቶ ፡ ጋሎን ፡ ይይዛል
[See also 'crowded']

**cape**
1. ካባ. All the dignitaries wear capes. ሹማምን
ቱ ፡ በሙሉ ፡ ካባ ፡ ይለብሳሉ
2. ርእሰ ፡ ምድር. The ship reached the cape
safely. መርከቧ ፡ በደኅና ፡ ርእሰ ፡ ምድር ፡ ደረ
ሰች

**caper** ቦረቀ
The dog capered about its master. ውሻው ፡ በ
ጌታው ፡ ዙሪያ ፡ ቦረቀ

**capital** (n.)
1. ዋና ፡ ከተማ ፤ መናገሻ ፡ ከተማ. Mogadishu
is the capital of Somalia. ሞቃዲሾ ፡ የሱማሊያ ፡
ዋና ፡ ከተማ ፡ ነው
Addis Ababa is the capital of Ethiopia.
አዲስ ፡ አበባ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡
(ዋና ፡ ከተማ) ፡ ነው
2. ዋና ፡ ገንዘብ. He doubled his capital in two
years. ዋና ፡ ገንዘቡን ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ዕጥፍ ፡
አደረገው
3. ትልቅ ፡ ፊደል. Begin every line with a capital!
እያንዳንዱን ፡ መሥመር ፡ በትልቅ ፡ ፊደል ፡ ጀምር

**make capital** ተጠቀመ
He made capital of his father's fame to get the
job. ሥራውን ፡ ለማግኘት ፡ ባባቱ ፡ ዝና ፡ ተ
ጠቀመ

**capital** (adj.) ዓቢይ
These are the capital points in our discussion.
እነዚህ ፡ የውይይታችን ፡ ዓቢይ ፡ ጉዳዮች ፡ ናቸው

**capital crime** በሞት ፡ የሚያስቀጣ ፡ ወንጀል
Murder is a capital crime in most countries.
ነፍስ ፡ ግዳይ ፡ በአብዛኞዎቹ ፡ አገሮች ፡ በሞት ፡ የ
ሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ ነው

**capitalism** ካፒታሊዝም
Communists are against capitalism. ኮሚኒስቶ
ች ፡ ካፒታሊዝምን ፡ ይቃወማሉ

**capitalize** (vt.)
1. መደበ. They capitalized the firm at $100,000.
ለንግድ ፡ ማስፋፊያ ፡ የሚሆን ፡ $100,000 መደቡ
2. በትልቁ ፡ ጻፈ. Capitalize the first letter of the
sentence! የዐረፍተ ፡ ነገሩን ፡ የመጀመሪያ ፡ ፊደል ፡
በትልቁ ፡ ጻፍ

**capitalize** (vi.) ተጠቀመ
He capitalized on his adversary's mistake.
በባላጋራው ፡ ስሕተት ፡ ተጠቀመ

**capital letter** ትልቅ ፡ ፊደል
Begin every line with a capital letter! እያንዳንዱ
ን ፡ መሥመር ፡ በትልቅ ፡ ፊደል ፡ ጀምር

**capital punishment** ወንጀለኛን ፡ በሞት ፡ መ
ቅጣት ፤ የይሙት ፡ በቃ ፡ ፍርድ
Capital punishment is no longer in existence
in England. በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ወንጀለኛን ፡ በ
ሞት ፡ መቅጣት ፡ ቀርቷል
Capital punishment was approved. የይሙት ፡ በ
ቃ ፡ ፍርድ ፡ ጸናበት

**capitol** ቤተ ፡ መንግሥት
The cupola of the capitol was sheathed with
copper. የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ቁብታ ፡ በመዳብ ፡
ተሸፍኗል

**capitulate** እጅ ፡ ሰጠ
The Italians capitulated to the Ethiopians in
1941. ጣሊያኖች ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡
እጃቸውን ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ሰጡ

**capitulation** እጅ ፡ መስጠት
The capitulation of the enemy was announced
this morning. የጠላት ፡ እጅ ፡ መስጠት ፡ ዛሬ ፡
ጧት ፡ ተነገረ

**caprice**
*Her refusal to go is a mere caprice. አልሄድ
ም ፡ ያለችው ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ነው

**(be) capricious** ሐሳቡን ፡ በየጊዜው ፡ ለዋወጠ
A spoiled child is often capricious. ሞልቃቃ ፡
ልጅ ፡ በደንብ ፡ ስላላደገ ፡ ሐሳቡን ፡ በየጊዜው ፡
ይለዋውጣል

**capsize** ተገለበጠ
The boat capsized because of the strong wind.
በኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ምክንያት ፡ ጀልባው ፡ ተገለበጠ

**capsule** ከምሱር
The powder is contained in a capsule. ባሩድ ፡
በከምሱር ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣል

**captain**
1. ሻምበል. The captain was taken prisoner
with his soldiers. ሻምበሉ ፡ ከወታደሮቹ ፡ ጋር ፡
ተማረከ
2. አምበል. Who is captain of the team?
የቡድኑ ፡ አምበል ፡ ማን ፡ ነው ?
3. ካፒቴን. The captain managed to land the
plane despite its broken wing. የአውሮፕላኑ ፡
ክንፍ ፡ ቢሰበርም ፡ ካፒቴኑ ፡ አውሮፕላኑን ፡
ለማሳረፍ ፡ ቻለ
The captain of the ship is very brave. የመርከቡ ፡
ካፒቴን ፡ በጣም ፡ ደፋር ፡ ነው

**caption** መግለጫ ፡ ጽሑፍ
Pictures in newspapers have captions explain-

ing them. በጋዜጣ ፡ ላይ ፡ የሚወጡ ፡ ሥዕሎች ፡
ከግርጌያቸው ፡ መግለጫ ፡ ጽሑፍ ፡ አላቸው

**captivate** ማረከ
He captivated the audience with his wonderful
voice. ግሩም ፡ በሆነ ፡ ድምፁ ፡ አድማጩን ፡ ማ
ረከ

**captive** ምርኮኛ
He was a captive of the Italians. የኢጣልያኖች ፡
ምርኮኛ ፡ ነበር

**be captive** ተማረከ
He was captive to her beauty. በውበቷ ፡ ተ
ማረከ

**captivity** ምርኮኛነት ፤ ምርኮ
The prisoners lived in captivity many years.
እስረኞቹ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ በምርኮኛነት ፡ ኖሩ
He redeemed his friend from captivity.
ገንዘብ ፡ ከፍሎ ፡ ጓደኛውን ፡ ከምርኮ ፡ ነጻ ፡ አወ
ጣው

**capture** (v.)
1. ማረከ. They captured a general and his
entire staff. አንድ ፡ ጄኔራል ፡ ከአባሎቹ ፡ ጋር ፡
ማረኩ
The advertisement will capture the attention
of the buyers. ማስታወቂያው ፡ የገዢዎቹን ፡ ፍ
ላጎት ፡ ይማርካል
2. ያዘ. We captured butterflies with a net.
ቢራቢሮዎችን ፡ በመረብ ፡ ያዝን
[See also 'defy']

**capture** (n.) መያዝ
The capture of the spy is certain. የሰላዩ ፡ መ
ያዝ ፡ እርግጠኛ ፡ ነው

**car** መኪና
My elder brother bought a new car. ታላቅ ፡
ወንድሜ ፡ አዲስ ፡ መኪና ፡ ገዛ

**caramel** ከረሜላ
The child likes caramels. ልጁ ፡ ከረሜላ ፡ ይወ
ዳል

**caravan**
1. ጉዞ. The traders' caravan was robbed while
traveling through the desert. የነጋዴዎቹ ፡ ጉዞ ፡
በበረሃ ፡ አቋርጦ ፡ ሲያልፍ ፡ በወንበዴዎች ፡ ተዘረፈ
2. ግትልትል. A camel caravan brings salt in
from the desert. የግመል ፡ ግትልትል ፡ ከምድረ ፡
በዳው ፡ ጨው ፡ ያመጣል

**carbon paper** የካርቦን ፡ ወረቀት
Use good carbon paper for the copy! ለግልባ
ጩ ፡ በጥሩ ፡ የካርቦን ፡ ወረቀት ፡ ተጠቀም

**carcass** ጥንብ ፤ ጥምብ
The vulture devoured the carcass. ጥንብ ፡ አን
ሣ ፡ ጥንቡን ፡ (ጥምቡን) ፡ በላ

**card** (v.) ነደፈ
The woman carded cotton for spinning.
ሴትዮዋ ፡ ጥጡን ፡ ለመፍተል ፡ ነደፈችው

**card** (n.)
1. ካርታ. They played cards all evening.
ካርታ ፡ ሲጫወቱ ፡ አመሹ
2. ካርድ. I will send her a card when I go to
Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ስሄድ ፡ ካርድ ፡ እልክላ
ታለሁ
3. ያድራሻ ፡ ወረቀት. Here is my card. Call
me when you need me! ያድራሻዬ ፡ ወረቀት ፡
ይኸውና ፤ ሲያስፈልግህ ፡ ደውልልኝ
4. መታወቂያ ፡ ወረቀት. I don't have my member-
ship card on me. የአባልነት ፡ መታወቂያ ፡ ወረቀ
ቴን ፡ አልያዝኩም
[See also 'identification, playing card']

**cardboard** ካርቶን
Use thick cardboard for the package! ለመጠቅለ
ያው ፡ በወፍራም ፡ ካርቶን ፡ ተጠቀም

**cardiac** የልብ
He died of a cardiac disease. ከልብ ፡ በሽታ ፡
የተነሣ ፡ ሞተ

**cardinal** ዓቢይ
Honesty is his cardinal quality. ሐቀኝነት ፡ ዓቢ
ይ ፡ ጠባዩ ፡ ነው

**cardinal number** ተራ ፡ ቁጥር
'Five' is a cardinal number, but 'fifth' is an
ordinal number. አምስት ፡ ተራ ፡ ቁጥር ፤ አምስተ
ኛ ፡ ግን ፡ መደበኛ ፡ ቁጥር ፡ ነው

**cardinal point** ዋነኛ ፡ አቅጣጫ
The cardinal points are east, west, north and
south. ዋነኞቹ ፡ አቅጣጫዎች ፡ ምሥራቅ ፤ ም
ዕራብ ፤ ሰሜንና ፡ ደቡብ ፡ ናቸው

**care** (v.) ፈለገ
Do you care to come along? ለመምጣት ፡ ትፈ
ልጋለህ ?
*What do I care? ምን ፡ ጨነቀኝ ? (ምን ፡ ቸገረ
ኝ ?)
*I do not care for him very much. ለሱ ፡ እጅግ
ም ፡ ነኝ

**care about** ወደደ
He cares about music. ሙዚቃ ፡ ይወዳል

**care for**
1. ጠበቀ (ተጠበቀ). My sister is caring for the

children today. እኅቱ ፡ ዛሬ ፡ ልጆቹን ፡ ትጠብቃለች
This garden is well cared for. ይህ ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ በደንብ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው
2. ፈለገ. Do you care for sugar in your coffee? ቡናህ ፡ ውስጥ ፡ ስኳር ፡ እንዲጨመርልህ ፡ ትፈልጋለህ ?

**(be) cared for** ጥንቃቄ ፡ ተደረገ(ለት)
Feeble-minded children are cared for in a special home. አእምሮ ፡ ደካማ ፡ ልጆች ፡ በልዩ ፡ ማሳደጊያ ፡ ቤት ፡ ጥንቃቄ ፡ ይደረግላቸዋል

**for all I care** ደንታ ፡ የለኝም
You can go alone to the dance for all I care. ወደ ፡ ዳንሱ ፡ ስፍራ ፡ ብቻህን ፡ ብትሄድ ፡ ደንታ ፡ የለኝም

**not care** ግድ ፡ የለውም
I don't care what he thinks. እሱ ፡ ስለሚያስበው ፡ ግድ ፡ የለኝም
He doesn't care for television. ለቴሌቪዥን ፡ ግድ ፡ የለውም
I don't care to go to the movies. ለሲኒማ ፡ ግድ ፡ የለኝም

**care** (n.)
1. ጥንቃቄ. The work is done with care. ሥራው ፡ በጥንቃቄ ፡ ተሠራ
I put a lot of care into that. ለዚህ ፡ ብዙ ፡ ጥንቃቄ ፡ አድርጌበታለሁ
2. ጥንቃቄ ፡ ማድረግ. Regular care of the teeth is important. ለጥርስ ፡ የዘወትር ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
3. መከባከብ. The care of a baby claims much of a mother's time. ሕፃኑን ፡ መከባከብ ፡ የእናቱን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይወስዳል
4. ተግባር. The keeping of the records is in the care of the secretary of the club. መዝገብ ፡ መያዝ ፡ የክበቡ ፡ ጸሐፊ ፡ ተግባር ፡ ነው
5. ስጋት. He is rich and free from cares of every kind. ሀብታም ፡ ነውና ፡ ከማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ስጋት ፡ ነጻ ፡ የሆነ ፡ ነው
6. ሐሳብ. Care has made him look ten years older. ሐሳብ ፡ ከዕድሜው ፡ በዐሥር ፡ ዓመት ፡ ያረጀ ፡ አስመስሎታል
7. ጭንቀት. Music was his refuge from his many cares. ከብዙ ፡ ጭንቀቱ ፡ የሚላቀቀው ፡ በሙዚቃ ፡ ነው

**commend to one's care** አደራ ፡ ሰጠ
She commended the child to her aunt's care. ልጁን ፡ ላክስቷ ፡ አደራ ፡ ሰጠች
*I commend you to God's care. እግዚአብሔር ፡ ይጠብቅህ

**commit oneself to one's care** ተማመነ
He committed himself to the doctor's care. ሐኪሙን ፡ ተማመነ

**have care (for)** አሰበ
A mother has care for her baby's health. እናት ፡ ለሕፃኗ ፡ ጤንነት ፡ ታስባለች

**in care of** በ - - - በኩል
Send me the letter in care of the university! ደብዳቤ ፡ በዩኒቨርሲቲው ፡ በኩል ፡ ላክልኝ

**in one's care** ለ - - - አደራ
May I leave my valuables in your care? ውድ ፡ የሆኑትን ፡ እቃዎቼን ፡ ላንተ ፡ አደራ ፡ ልተው?
*The baby was left in her sister's care. እኅቷ ፡ ሕፃኗን ፡ እንድትጠብቅ ፡ ተደረገ

**take care** ተጠነቀቀ
I took care not to mention anything. ምንም ፡ እንዳልናገር ፡ ተጠነቀቅሁ

**take care of**
1. ጠበቀ(ለት) ፤ ጠበቀ. Don't worry; I will take care of your children. አታስብ ፤ ልጆችህን ፡ እኔ ፡ እጠብቅልሃለሁ
Take care of my money for me! ገንዘቤን ፡ ጠብቅልኝ
Mother charged her with taking care of the baby. እናታችን ፡ ሕፃኗን ፡ እንድትጠብቅ ፡ አዘዘቻት
2. አጠናቀቀ. Before I can leave for Ethiopia, I still have a few things to take care of. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ የማጠናቅቃቸው ፡ ነገሮች ፡ አሉኝ
3. ተጠነቀቀ. He takes care of his clothes. ለልብሱ ፡ ይጠነቀቃል
4. አከናወነ. The office boy takes care of minor things. ተላላኪው ፡ ጥቃቅን ፡ ሥራዎችን ፡ ያከናውናል
5. አስታመመ. Who will take care of me when I get sick? ስታመም ፡ ማን ፡ ያስታምመኛል ?
*We'll take care of everything. ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ እኛ ፡ አለን

**take care of oneself** ራሱን ፡ ጠበቀ
You have to take better care of yourself. ራስህን ፡ ይበልጥ ፡ መጠበቅ ፡ አለብህ

**(be) under the care of**
1. በ - - - ሥር ፡ ተዳደረ. This library is under the care of the Ministry of Education. ይህ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚተዳደረው ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥር ፡ ነው
2. በ - - - ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው. He is still under the doctor's care. አሁንም ፡ በዶክተር ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው

[See also 'confide, consign, maternal, recommend, trust']

**careen** አጋደለ
The ship careened in the strong wind. በኀይለ
ኛው ፡ ነፋስ ፡ ምክንያት ፡ መርከቧ ፡ አጋደለች

**career**
1. ሥራ. Her career is more important to her than her marriage. ለርሷ ፡ ከትዳሯ ፡ ይልቅ ፡
ሥራዋ ፡ ይበልጥባታል
2. ቋሚ ፡ ሥራ. John found a career in advertising as an illustrator. ዮሐንስ ፡ በማስታወቂ
ያ ፡ ሥራ ፡ በሠዐሊነት ፡ ቋሚ ፡ ሥራ ፡ አገኘ
3. የሕይወት ፡ ታሪክ. We can learn much by reading about the careers of great men.
የታላላቅ ፡ ሰዎችን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ በማንበ
ብ ፡ ብዙ ፡ ልንማር ፡ እንችላለን

**carefree** የግዴለሽ
He leads a carefree life. የግዴለሽ ፡ ኑሮ ፡ ይ
ኖራል

**careful**
1. ጥንቁቅ. She is a careful secretary. ጥንቁቅ ፡
ጸሐፊ ፡ ናት
2. በጥንቃቄ ፡ የተሠራ. This is a careful piece of work. ይህ ፡ ሥራ ፡ በጥንቃቄ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**be careful** ተጠነቀቀ
Be careful not to break this dish. ይህንን ፡ ሳ
ሕን ፡ እንዳትሰብረው ፡ ተጠንቀቅ

**carefully**
1. በጥንቃቄ. They lifted the stretcher carefully.
ቃሬዛውን ፡ በጥንቃቄ ፡ አነሡት
2. ደኅና ፡ አድርጎ. Chew each bite carefully!
እያንዳንዱን ፡ጉርሻ ፡ ደኅና ፡ አድርገህ ፡ እኘክ

**careless**
1. ግዴለሽ ፤ ግድየለሽ. A careless driver is a danger to the public. ግዴለሽ ፡ ነጂ ፡ ለሕዝቡ ፡
አደገኛ ፡ ነው
She has become careless lately. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡
ወዲህ ፡ ግድየለሽ ፡ ሆናለች
2. የቸልታ. The police charged the accident to careless driving. ፖሊሶቹ ፡ ያደጋው ፡ መነሾ ፡ በ
ቸልታ ፡ መንዳት ፡ ነው ፡ አሉ

**be careless** ግድ ፡ የለውም
He is careless with his money. ለገንዘብ ፡ ግድ ፡
የለውም

**carelessly**
1. በግድ ፡ የለሽነት. Don't throw your things down so carelessly! እቃህን ፡ በግድ ፡ የለሽነት ፡
አታዝረክርከው
2. እንደነገሩ. The student ran carelessly through his homework. ተማሪው ፡ እንደነገሩ ፡ በጥድፊያ ፡
የቤት ፡ ሥራውን ፡ ጨረሰ

**carelessness**
1. ግድ ፡ የለሽነት. This is another instance of his carelessness. ለሱ ፡ ግድ ፡ የለሽነት ፡ ይህ ፡ ሌላ
ው ፡ ማስረጃ ፡ ነው
2. ቸልተኝነት. Carelessness is the real cause of the accident. ያደጋው ፡ እርግጠኛ ፡ መነሻ ፡ ቸል
ተኝነት ፡ ነው
3. ጠንቃቃ ፡ አለመሆን. His carelessness neutralized his efforts. ጠንቃቃ ፡ አለመሆኑ ፡ ጥረቱን ፡
ፍሬ ፡ ቢስ ፡ አደረገው

**caress** ደባበሰ
She caressed her baby. ልጇን ፡ ደባበሰቻት

**caretaker** (n.) ቤት ፡ ጠባቂ
He left a caretaker in his house when he went abroad. ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሲሄድ ፡ ቤት ፡
ጠባቂ ፡ ትቶ ፡ ሄደ

**caretaker** (adj.) ጊዜያዊ
A caretaker government took over until the elections. ምርጫ ፡ እስኪደረግ ፡ ድረስ ፡ ጊዜያ
ዊ ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ያዘ

**carfare** መሳፈሪያ
Do you have your carfare ready? መሳፈሪያ ፡
አለህ ?

**cargo** ጭነት
Since the cargo is heavy, the boat cannot move fast. ጭነቱ ፡ ከባድ ፡ ስለሆነ ፡ መርከቡ ፡ በፍጥነ
ት ፡ ሊሄድ ፡ አይችልም

**caricature** አሥቂኝ ፡ ሥዕል
A caricature of the enemy was published in the newspaper. የጠላት ፡ አሥቂኝ ፡ ሥዕል ፡ በጋዜ
ጣው ፡ ወጥቷል

**caries** መበስበስ
Tooth cavities are caused by caries. ጥርሶች ፡
የሚቦረቦሩት ፡ ከመበስበስ ፡ የተነሣ ፡ ነው

**carnage** እልቂት
The carnage continued until dawn. እልቂቱ ፡ እ
ስከ ፡ ንጋቱ ፡ ቆየ

**carnal** የሥጋ
Gluttony and drunkenness have been called carnal vices. ሆዳምነትና ፡ ጠጭነት ፡ የሥጋ ፡ መ
ጥፎ ፡ ምግባሮች ፡ ይባላሉ

**carnival** ካርኒቫል

**carnivore** ሥጋ ፡ በል
The lion is a carnivore. አንበሳ ፡ ሥጋ ፡ በል ፡ ነው

**carnivorous** ሥጋ ፡ በል
Lions are carnivorous animals. አንበሶች ፡ ሥጋ ፡ በል ፡ እውሬዎች ፡ ናቸው

**carol** የልደት ፡ መዝሙር
We sing carols at Christmas time. ለገና ፡ የልደት ፡ መዝሙር ፡ እንዘምራለን

**carouse** ረበሸ
They caroused all night long. ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ሲረብሹ ፡ አደሩ

**carpenter** አናጢ
The carpenter is fixing the broken stairs. አናጢው ፡ የተሰበሩትን ፡ ደረጃዎች ፡ እየጠገነ ፡ ነው

**carpentry** የአናጢነት ፡ ሙያ
The artist has a sideline in carpentry. ሠዓሊው ፡ ከሥራው ፡ ሌላ ፡ የአናጢነት ፡ ሙያ ፡ ያከናውናል

**carpet** v. (= pass.) ስጋጃ ፡ ተነጠፈበት
They carpeted the stairs for the Emperor's arrival. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ስለሚመጡ ፡ ደረጃው ፡ ሁሉ ፡ ስጋጃ ፡ ተነጠፈበት

**carpet** (n.) ስጋጃ
Sweep the carpet before the guests come! እንግዶቹ ፡ ሳይመጡ ፡ ስጋጃውን ፡ ጥረገው

**carriage**
1. ሰረገላ. His Majesty rode in a carriage during the coronation. ጃንሆይ ፡ በዘውዱ ፡ በዓል ፡ ጊዜ ፡ በሰረገላ ፡ ተጓዙ
2. ዛላ. She has a queenly carriage. የንግሥት ፡ ዛላ ፡ አላት

**carrier** የሚያመጣ
A carrier of bad news is never welcome. መጥፎ ፡ ወሬን ፡ የሚያመጣ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ በደስታ ፡ የሚቀበለው ፡ የለም

**be a carrier** አስተላለፈ
Flies are carriers of several diseases. ዝንቦች ፡ ብዙ ፡ በሽታዎችን ፡ ያስተላልፋሉ

**carrion** ጥምብ ፤ ጥንብ
Vultures eat only carrion. ጥምብ ፡ አንሣ ፡ ጥምብ ፡ (ጥንብ) ፡ ብቻ ፡ ይበላል

**carrot** ካሮት

**carry** (carried), vt.
1. ተሸከመ. He will carry your bag for you. እሱ ፡ ሻንጣህን ፡ ይሸከምልሃል
He carried the gun on his shoulders. ጠመንጃውን ፡ በትከሻው ፡ ላይ ፡ ተሸከመ
2. ያዘ. Do you always carry an umbrella? ሁልጊዜ ፡ ዣንጥላ ፡ ትይዛለህ ?
The elevator cannot carry more than 10 persons. አሳንሰሩ ፡ ከዐሥር ፡ ሰው ፡ የበለጠ ፡ አይዝም
3. አጓጓዘ. Freighters carry our products to foreign countries. የጭነት ፡ መርከቦች ፡ የንግድ ፡ እቃችንን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ያጓጉዛሉ
4. ሸጠ. He carries the best line of shoes in town. በከተማው ፡ የሚገኙትን ፡ ምርጥ ፡ ዓይነት ፡ ጫማዎች ፡ ይሸጣል
5. አዘለ. The letter carried a threat. ደብዳቤው ፡ ማስፈራሪያ ፡ ያዘለ ፡ ነው
6. አዳረሰ. He carried the news to everyone in the village. ለመንደሩ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወሬውን ፡ አዳረሰ
7. አሳለፎ ፡ ሰጠ. The treacherous soldier carried reports to the enemy. ከዳተኛው ፡ ወታደር ፡ ለጠላት ፡ ሪፖርት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ
8. አስተላለፈ. Air carries sound. አየር ፡ ድምፅ ፡ ያስተላልፋል
9. አሸነፈ ፤ ረታ. Our side carried the election for club president. የኛ ፡ ወገን ፡ የክበቡን ፡ የፕሬዚዳንትነት ፡ ምርጫ ፡ አሸነፈ
John easily carried the argument. ጆን ፡ ክርክሩን ፡ በቀላሉ ፡ አሸነፈ ፡ (ረታ)
10. በቃ(ው). This money will carry us for about a week. ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ለሳምንት ፡ ያህል ፡ ይበቃናል
*That crime carries the death penalty. ያ ፡ ወንጀል ፡ በሞት ፡ ያስቀጣል

**carry** (vi.) ተሰማ
Her voice carried to the back of the room. ድምጿ ፡ እስከ ፡ ክፍሉ ፡ ጀርባ ፡ ተሰማ

**be carried** ተቀባይነት ፡ አገኘ
The motion was carried. ሐሳቡ ፡ ተቀባይነት ፡ አገኘ

**carry away** ወሰደ
The rushing water carried away the bridge. ጐርፉ ፡ ድልድዩን ፡ ወሰደው

**(be) carried away** ተነሣሣ
The crowd was carried away by the speech. የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ በንግግሩ ፡ ተነሣሣ

**carry off**
1. ወሰደ. The police caught the spy and

carried him off to prison. ፖሊሶቹ ፡ ሰላዩን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ወሰዱት
2. ፈጀ. The disease carried off thousands. በሽታው ፡ ብዙ ፡ ሺ ፡ ሰው ፡ ፈጀ

**carry on** ቀጠለ
His son carries on the business. የሱ ፡ ልጅ ፡ ንግዱን ፡ ይቀጥላል

**carry on the back** አዘለ
She was carrying the baby on her back. ሕፃኑን ፡ አዝላ ፡ ነበር

**carry oneself**
*She carries herself beautifully, like a queen. ዛላዋ ፡ እንደ ፡ ንግሥት ፡ ያማረ ፡ ነው

**carry out**
1. ፈጸመ ፤ አከናወነ. They carried out the orders. ትእዛዙን ፡ ፈጸሙ ፡ (አከናወኑ)
2. ከግቡ ፡ አደረሰ. We will try to carry out your plan. እቅድህን ፡ ከግቡ ፡ ለማድረስ ፡ እንሞክራለን

**(be) carried out** ተካሄደ
The war in Vietnam is carried out by guerillas. የቪየትናም ፡ ጦርነት ፡ የሚካሄደው ፡ በደፈጣ ፡ ተዋጊዎች ፡ ነው

**(be) carried over** ተላለፈ
The last item on the agenda was carried over to the next meeting. በአጀንዳው ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ የመጨረሻው ፡ ሐሳብ ፡ ለሚቀጥለው ፡ ስብሰባ ፡ ተላለፈ

**carry the day** ውድድሩን ፡ አሸነፈ
The new party carried the day. አዲሱ ፡ ፓርቲ ፡ ውድድሩን ፡ አሸነፈ

**carry weight**
1. ቁም ፡ ነገር ፡ አለው. His opinion carries great weight. አስተያየቱ ፡ ትልቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ነው
2. ዋጋ ፡ አለው. That argument does not carry much weight. ክርክሩ ፡ አምብዛም ፡ ዋጋ ፡ የለውም
[See also 'art, ball, conversation, piggyback']

**carry-over** የቆየ ፡ ባህል
Throwing rice at the bride is a carry-over from a bygone era. ሩዝ ፡ ሙሽራይቱ ፡ ላይ ፡ መበተን ፡ ካለፉት ፡ ዘመናት ፡ የቆየ ፡ ባህል ፡ ነው

**cart** ጋሪ ፤ ተሳቢ
He put his baggage in a cart. ሻንጣዎቹን ፡ ጋሪው ፡ ላይ ፡ ጫነ
He trundles his cart behind him wherever he goes. በሄደበት ፡ ሁሉ ፡ ተሳቢውን ፡ እየጐተተ ፡ ይሄዳል

**cartography** የካርታ ፡ ሥራ
Cartography helps to delineate the borders of territories. የካርታ ፡ ሥራ ፡ የግዛትን ፡ ድንበር ፡ ለመለያ ፡ ይጠቅማል

**carton** የካርቱን ፡ ሣጥን
Please bring me ten cartons from the stationery! ከጽሕፈት ፡ መሣሪያ ፡ መደብር ፡ ዐሥር ፡ የካርቱን ፡ ሣጥን ፡ አምጣልኝ

**cartoon** [በጋዜጦች ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ስለ ፡ ታወቁ ፡ ሰዎችና ፡ ስለ ፡ ጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ በሐሰ ፡ መልክ ፡ የሚናገር ፡ ሥዕል]

**cartridge** ጥይት
He put a cartridge in his gun. ጠመንጃውን ፡ ጥይት ፡ አጐረሰ

**cartridge belt** ዝናር
Soldiers used to wear cartridge belts. ወታደሮች ፡ ዝናር ፡ ይታጠቁ ፡ ነበር

**empty cartridge** ቀለሀ
The battlefield was full of empty cartridges. በጦርነቱ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ቀለሀ ፡ ሞልቶ ፡ ነበር

**carve**
1. ቀረጸ. He carved his initials in the bark of the tree. የስሙን ፡ የመጀመሪያ ፡ ፊደሎች ፡ እዛፉ ፡ ቅርፊት ፡ ላይ ፡ ቀረጸ
2. ፋቀ. Is the knife fine enough to carve well? ቢላዋው ፡ ለመፋቂያ ፡ በጣም ፡ ስል ፡ ነው?
3. መተረ. The cook carved the meat at the table. ወጥ ፡ ቤቷ ፡ ሥጋውን ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ መተረች
4. ወቀረ (ተወቀረ). For the grain to be ground thoroughly, the upper and nether millstones have to be carved. እህል ፡ በደንብ ፡ መፍጨት ፡ እንዲቻል ፡ ወፍጮና ፡ መጁ ፡ መወቀር ፡ አለበት

**carve out** በራሱ ፡ አቋቋመ
He carved out a career in business. በራሱ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ አቋቋመ

**cascade** ትንሽ ፡ ፏፏቴ
There is a cascade near the road. በመንገዱ ፡ አጠገብ ፡ ትንሽ ፡ ፏፏቴ ፡ አለ

**case**
1. ሣጥን. Leave the bottles in the case! ጠርሙሶቹን ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ተዋቸው
2. ማኅደር. I need a case for my glasses. ለመነጽሬ ፡ ማኅደር ፡ እፈልጋለሁ
3. ጉዳይ. I read about the case in the newspapers. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ከጋዜጣ ፡ ላይ ፡ አነበብኩ
When will the case come before the court? ጉዳዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቼ ፡ ይቀርባል ?

4. ክርክር. The lawyer stated the case briefly. ጠበቃው ፡ ክርክሩን ፡ ባጭሩ ፡ አቀረበ
5. ምክንያት. He presented a strong case against the proposed law. የቀረበውን ፡ ሕግ ፡ የሚቃወም ፡ አጥጋቢ ፡ ምክንያት ፡ አቀረበ
*This is not the case. እንዲህ ፡ አይደለም
*There were five new cases of malaria. ወባ ፡ በቅርቡ ፡ የያዛቸው ፡ አምስት ፡ በሽተኞች ፡ ነበሩ

**if that is the case** እንዲህ ፡ ከሆነ
If that is the case, you'll have to work much harder. እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ በጣም ፡ ጠንክረህ ፡ መሥራት ፡ ይኖርብሃል

**in any case**
1. ለማንኛውም. I will call in any case. ለማንኛውም ፡ ስልክ ፡ እደውላለሁ
2. ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ. In any case, there won't be any necessity for you to come. ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ መምጣት ፡ አያስፈልግህም

**in case** ምናልባት ፡ ብ + imperfect.
Wait for me in case I am late. ምናልባት ፡ ብዘገይ ፡ ጠብቀኝ

**in case of**
1. የ + perfect + እንደሆነ. In case of illness, please notify my family! የታመምኩ ፡ እንደሆነ ፡ ለዘመዶቼ ፡ ንገር
2. ብ + (imperfect). In case of fire, call the fire department! ቃጠሎ ፡ ቢነሣ ፡ ለእሳት ፡ አደጋ ፡ ክፍል ፡ ደውል

**in no case** በምንም ፡ ምክንያት
He should in no case be allowed to get up until he has completely recovered from his illness. ፈጽሞ ፡ እስኪድን ፡ ድረስ ፡ በምንም ፡ ምክንያት ፡ ካልጋው ፡ እንዳይነሣ ፡ መከልከል ፡ ነው

**in this case** እንደዚህ ፡ ከሆነ
I can't do anything in this case. እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ ምንም ፡ ማድረግ ፡ አልችልም

**lose the case** ተረታ
He lost the case he brought against his uncle. ባጎቱ ፡ ላይ ፡ ባቀረበው ፡ ክስ ፡ ተረታ

**this was not the case** እውነት ፡ አልነበረም
He said he had done the work, but this was not the case. ሥራውን ፡ ሠርቻለሁ ፡ ብሎ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እውነት ፡ አልነበረም
[See also 'emergency, test']

**casement** [የመስኮት ፡ ጠርዝ]

**cash** (v.) መነዘረ
Can you cash a check for me? ቼኬን ፡ ልትመነዝርልኝ ፡ ትችላለህ ?
He cashed a bond at the bank. ቦንዱን ፡ ባንክ ፡ ሄዶ ፡ መነዘረ

**cash** (n.)
1. ጥሬ ፡ ገንዘብ. I have no cash with me. በጄ ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም
2. እጅ ፡ በጅ. I will pay cash. እጅ ፡ በጅ ፡ እከፍላለሁ

**cash payment** እጅ ፡ በጅ ፡ መክፈል
Redemption of articles is done through cash payment. እቃዎች ፡ የሚመለሱት ፡ እጅ ፡ በጅ, ፡ በመክፈል ፡ ነው

**for cash** እጅ ፡ በጅ ፡ ለሚከፈል
We sell only for cash. የምንሸጠው ፡ እጅ ፡ በጅ ፡ ለሚከፈል ፡ ብቻ ፡ ነው

**hard cash** ጥሬ ፡ ገንዘብ
He sold his house for hard cash. ቤቱን ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ሸጠው
[See also 'petty cash']

**cashbox** የገንዘብ ፡ ካዝና
The thief broke open the cashbox. ሌባው ፡ የገንዘቡን ፡ ካዝና ፡ ሰብሮ ፡ ከፈተው

**cashier** ገንዘብ ፡ ተቀባይ
Women are often cashiers. ገንዘብ ፡ ተቀባይ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ሴቶች ፡ ናቸው

**casing** ሽፋን
The casing protects the wires from the rain. ሽፋኑ ፡ ሽቦውን ፡ ከዝናም ፡ ይከላከለዋል

**metal casing** ብረት ፡ ቧንቧ
The electric wires are enclosed in a metal casing. የኮረንቲ ፡ ሽቦዎች ፡ ብረት ፡ ቧንቧ ፡ ውስጥ ፡ ተቀብረዋል

**cask** [ከዕንጨት ፡ የተሠራ ፡ በርሚል]

**casket**
1. ትንሽ ፡ ሣጥን. He kept his jewels in a casket. ጌጣጌጡን ፡ በትንሽ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አኖረ
2. የሬሳ ፡ ሣጥን. The body was put in a wooden casket. አስከሬኑ ፡ በንጨት ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ተደረገ

**casserole** ድስት
He put the casserole on the table. ድስቱን ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠ

**cast** (cast), v.
1. ጣለ. They cast lots to see who would go first. በመጀመሪያ ፡ ማን ፡ እንደሚሄድ ፡ ለማወቅ ፡ ዕጣ ፡ ጣሉ
The fisherman cast his net into the sea. ዓሣ ፡ አጥማጁ ፡ መረቡን ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ጣለ

2. አደላደለ. The director will cast the new play next week. ሥራ ፡ መሪው ፡ በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ አዲሱን ፡ ጨዋታ ፡ ያደላድላል
3. ቀረጸ. He cast a statue of the Emperor in bronze. የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ሐውልት ፡ ከ መዳብ ፡ ቀረጸ

**cast about (for)**
1. ለማግኘት ፡ ሞከረ. He cast about for a new job. አዲስ ፡ ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ ሞከረ
2. ለማግኘት ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ. We cast about for something to do during the approaching vacation. ለሚመጣው ፡ የዕረፍት ፡ ጊ ዜ ፡ የምንሠራውን ፡ ለማግኘት ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አልን

**cast aside** ጣለ
He cast aside his torn clothes. የተቀዳደደ ፡ ል ብሶቹን ፡ ጣለ

**cast away**
1. ተወ. He cast away his humble habits when he became an officer. መኰንን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ተ ራ ፡ ጠባዩን ፡ ተወ
2. በተነ. He will cast away this money just as he has done in the past. ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳደረገው ፡ ሁሉ ፡ ገንዘቡን ፡ ይበትናል

**(be) cast down**
1. ተደረመሰ. The columns of the building were cast down by an earthquake. የሕንጻው ፡ ምሰ ሶዎች ፡ በመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ተደረመሱ
2. ትካዜ ፡ አደረ(በት). I was cast down when I failed the test. ፈተናውን ፡ ስወድቅ ፡ ትካዜ ፡ አደረብኝ

**cast in** አንድ ፡ አደረገ
He cast in his lot with the gangsters. ዕድሉን ፡ ከወንበዴዎች ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አደረገ

**cast off** ጣለ ፤ ወዲያ ፡ ጣለ
The snake cast off its skin. እባቡ ፡ ቅርፊቱን ፡ ጣለ
He cast off his shoes. ጫማውን ፡ ወዲያ ፡ ጣለ
[See also 'aspersion, blessing, chill, eye, glance, spell, vote']

**cast** (n.)
1. ጀሶ. How long must you keep your broken arm in a cast? የተሰበረውን ፡ ክንድህን ፡ ለስ ንት ፡ ጊዜ ፡ በጀሶ ፡ እንደታሰረ ፡ ማቆየት ፡ ይ ኖርብሃል ?
2. ተጫዋቾች. A party is to be given for the cast. ለተጫዋቾቹ ፡ ግብዣ ፡ ሊደረግ ፡ ነው

**plaster cast** ጀሶ
All his members were covered by a plaster cast. እጅና ፡ እግሩ ፡ ሳይቀር ፡ በጀሶ ፡ ተሸፍኗል

**castaway** መርከቡ ፡ የተሰበረበት ፡ ሰው
The castaway was rescued years later. መርከ ቡ ፡ የተሰበረበት ፡ ሰውዬ ፡ ከዓመታት ፡ በኋ ላ ፡ ደረሱለት

**caste** ጎብረተ ፡ ሰብአዊ ፡ ክፍል
In India, there are many castes. በህንድ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ኅብረተ ፡ ሰብአዊ ፡ ክፍሎች ፡ አሉ

**castigate** ከፉኛ ፡ ነቀፈ (ተነቀፈ)
He was castigated by the newspaper. በጋዜጣው ፡ ክፉኛ ፡ ተነቀፈ

**cast iron** ብረት
Cast iron is used for making stoves. ብረት ፡ ምድጃ ፡ ለመሥሪያ ፡ ያገለግላል

**castle** ግንብ
Have you seen the castles in Gondar? ጐንደ ር ፡ ያሉትን ፡ ግንቦች ፡ አይተሃቸዋል ?

**castor bean** የጉሎ ፡ ፍሬ
This company will extract oil from castor beans. ይህ ፡ ኩባንያ ፡ ዘይት ፡ ከጉሎ ፡ ፍሬ ፡ ያወጣል

**castrate**
1. አኰላሸ. He castrated the goat and the ox. ፍየሉንና ፡ በሬውን ፡ አኰላሻቸው
2. ሰለበ. Slavers used to castrate boys so that they could serve as harem guards. ባሪያ ፡ ፈንጋዮች ፡ ወንዶች ፡ ባሮች ፡ የዕቁባት ፡ ጠባ ቂዎች ፡ እንዲሆኑ ፡ ይሰልቧቸው ፡ ነበር

**casual**
1. የግዴለሽነት. He has a casual attitude toward study. ስለ ፡ ትምህርት ፡ የግዴለሽነት ፡ ጠባይ ፡ አለው
2. (= adv.) ድንገት. A casual meeting on the street began our long friendship. በመንገድ ፡ ላ ይ ፡ ድንገት ፡ የተገናኘነው ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ ወዳጅነታችን ፡ ምክንያት ፡ ሆነ
*It was just a casual remark. እፍ ፡ እንዳመ ጣ ፡ የተነገረ ፡ አስተያየት ፡ ነበር
*He is only a casual acquaintance. ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያለኝ ፡ መተዋወቅ ፡ የጠበቀ ፡ አይደለም
[See also 'glance']

**casually** አፉ ፡ እንዳመጣለት
He said it to me quite casually. አፉ ፡ እንዳ መጣለት ፡ ነገረኝ
*I know him casually. መተዋወቃችን ፡ እምብዛ ም ፡ ነው

**casualty** (casualties)
1. ባደጋው ፡ የተጐዳ. The casualties ran into

the thousands. ባደጋው ፡ የተጐዱት ፡ በሺ ፡ ይቈጠሩ ፡ ነበር
2. የደረሰበት ፡ ጉዳት. Our casualties in Africa were small. በአፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ የደረሰብን ፡ ጉዳት ፡ አነስተኛ ፡ ነበር

**cat** ድመት
The cat hunts mice. ድመቷ ፡ አይጦችን ፡ ታድናለች
*He let the cat out of the bag. ምስጢር ፡ አባከነ

**cataclysm** መቅሠፍት
He prophesied a cataclysm for the evil city. ኀጢአተኛው ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ መቅሠፍት ፡ ይወርዳል ፡ ብሎ ፡ ተነበየ

**catacomb** [የመቃብር ፡ ዋሻ]

**catafalque** [በቀብር ፡ ሥርዓት ፡ ጊዜ ፡ ሬሳ ፡ የሚያርፍበት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነገር]

**catalog** (v.) መዘገበ
He cataloged all the books in the library. በመጻሕፍት ፡ ቤቱ ፡ ያሉትን ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ መዘገባቸው

**catalog** (n.) ዝርዝር
He received the catalog of books yesterday. ትናንት ፡ የመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ አገኘ
He received the catalog showing the latest kinds of guns. በቅርቡ ፡ የወጡትን ፡ ጠመንጃዎች ፡ የሚያሳይ ፡ ዝርዝር ፡ አገኘ

**cataract** ፏፏቴ
The cataract falling down the mountainside is quite attractive. ከተራራው ፡ ላይ ፡ የሚወርደው ፡ ፏፏቴ ፡ በጣም ፡ ያስደስታል

**catarrh** ጉንፋን
He suffers from a violent catarrh. ክፉ ፡ ጉንፋን ፡ ይዞታል

**catastrophe** መቅሠፍት
The earthquake which took place in Japan was a great catastrophe. በጃፓን ፡ የደረሰው ፡ የመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ታላቅ ፡ መቅሠፍት ፡ ነበር

**catch** (caught)
1. ያዘ. We caught many birds. ብዙ ፡ ወፎች ፡ ያዝን
The police caught the thief. ፖሊሱ ፡ ሌባውን ፡ ያዘው
I did not catch his name. Would you please repeat it? ስሙን ፡ አልያዝኩም ፤ እስቲ ፡ ድገመው
2. ያዘ(ው). +Put a warm coat on; you will catch cold. የሚሞቅ ፡ ኮት ፡ ልበስ ፤ ጉንፋን ፡ ይይዝሃል
3. ያዘ(በት). +He caught his jacket on a nail. ጃኬቱን ፡ ምስማር ፡ ያዘበት
4. ቀለበ. He caught the ball which was thrown to him. የተወረወረውን ፡ ኳስ ፡ ቀለበ
5. ደረሰ(በት). I caught the boy stealing fruit from my garden. ልጁ ፡ ከትክልት ፡ ቦታዬ ፡ ፍሬ ፡ ፍሬ ፡ ሲሰርቅ ፡ ደረስኩበት
I caught him just as he was leaving the house. ልክ ፡ ከቤቱ ፡ ሲወጣ ፡ ደረስኩበት
6. ተጋባ(በት). +I caught the measles from him. ኩፍኝ ፡ ከሱ ፡ ተጋባብኝ
7. ማረከ. The neckties in the window caught my eye. እመስኮቱ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ከራቫቶች ፡ ዓይኔን ፡ ማረኩት
8. ከረተፈ. +I caught my finger in the door. በሩ ፡ ጣቴን ፡ ከረተፈኝ
9. ጠለፈ. +My sleeve caught on the doorknob. የመዝጊያው ፡ እጀታ ፡ እጅጌዬን ፡ ጠለፈው
10. አጠመደ. The fish that I caught were flopping around in the bottom of the boat. ያጠመድኳቸው ፡ ዓሣዎች ፡ ጀልባው ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ ይንፈራፈሩ ፡ ነበር
11. ገባ(ው). I didn't quite catch your meaning. ምን ፡ ማለትህ ፡ እንደሆነ ፡ በደንብ ፡ አልገባኝም
12. አጣደፈ. The teacher caught the student off guard with a question. አስተማሪው ፡ ተማሪውን ፡ ሳያስበው ፡ በጥያቄ ፡ አጣደፈው
13. ተሳፈረ ፤ ሄደ. I will catch the plane for Addis Ababa at nine. በሦስት ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በሚሄደው ፡ አውሮፕላን ፡ እሳፈራለሁ
I have to catch the five o'clock train. በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓቱ ፡ ባቡር ፡ መሄድ ፡ አለብኝ
14. ደረሰ. Is there any chance of catching the train? ባቡሩ ፡ ሳይሄድ ፡ ለመድረስ ፡ ተስፋ ፡ አለ ?

**be caught** ተቀረቀረ
The car was caught between two trees. መኪናዋ ፡ በሁለት ፡ ዛፎች ፡ መካከል ፡ ተቀረቀረች

**catch at** ወዲያውኑ ፡ ተቀበለ
He caught at the chance to get free tickets. ነጻ ፡ ቲኬት ፡ የማግኘትን ፡ ዕድል ፡ ወዲያውኑ ፡ ተቀበለ

**catch hold of** ያዘ
Catch hold of the other end! ሌላውን ፡ ጫፍ ፡ ያዘው

**catch on**
1. ገባ(ው). +He catches on quickly. ቶሎ ፡ ይገባዋል

2. እየተወደደ ፡ ሄደ. That new song is beginning to catch on. አዲሱ ፡ ዘፈን ፡ እየተወደደ ፡ ሄደ

**catch oneself** ራሱን ፡ ገታ
He caught himself before he said the wrong thing. የተሳሳተ ፡ ነገር ፡ ከመናገሩ ፡ በፊት ፡ ራሱን ፡ ገታ

**catch up with** ደረሰ(በት)
He made a sustained effort to catch up with me. ሊደርስብኝ ፡ የማያቋርጥ ፡ ጥረት ፡ አደረገ
*Try to catch up in your work by working weekends. እሑድና ፡ ቅዳሜ ፡ በመሥራት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረህበትን ፡ ለማሟላት ፡ ሞክር
*Leaves were caught up in the wind. ቅጠሎቹን ፡ ነፋስ ፡ ወሰዳቸው
[See also 'breath, cold, fire, glimpse, short, sight']

**catch** (n.) ተንኰል
There is a catch in it somewhere. አንድ ፡ ተንኰል ፡ አለበት
*The fisherman brought home a large catch. ዓሣ ፡ አጥማጁ ፡ ብዙ ፡ ዓሣ ፡ ይዞ ፡ ገባ

**catchall** ብዙ ፡ ሐሳቦችን ፡ ያዘለ ፡ ቃል
The word 'freedom' is often used as a catchall. ነጻነት ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ብዙ ፡ ሐሳቦችን ፡ ያዘለ ፡ ነው

**catching** ተላላፊ ፡ በሽታ
Measles is catching ኩፍኝ ፡ ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ ነው
*Her laughter is catching. የሷ ፡ ሣቅ ፡ ሌሎችን ፡ ያሥቃል

**catchword** መላልሶ ፡ የሚያሰማው ፡ ቃል
'Graft' was the catchword of the demonstrators. ጉቦ ፡ ሰላማዊ ፡ ሰልፈኞች ፡ መላልሰው ፡ የሚያሰሙት ፡ ቃል ፡ ነበር

**catchy** የሚያስደስት
He sang a catchy tune. የሚያስደስት ፡ ዜማ ፡ አዜመ

**catechism** [በጥያቄ ፡ መልስ ፡ መልክ ፡ የተዘጋጀ ፡ የሃይማኖት ፡ ማስተማሪያ ፡ መጽሐፍ]

**categorical** ቁርጥ ፡ ያለ
His reply was categorical. መልሱ ፡ ቁርጥ ፡ ያለ ፡ ነበር

**category** (categories) ክፍል
He divided the subject into categories. አርእስቱን ፡ በየክፍሉ ፡ መደበው

**cater** ምግብና ፡ አገልግሎት ፡ ሰጠ
He caters large parties and weddings. ለትልልቅ ፡ ድግስና ፡ ሰርግ ፡ ምግብና ፡ አገልግሎት ፡ ይሰጣል

**cater to**
1. ለመሳብ ፡ ጣረ. This store caters to young people. ይህ ፡ መደብር ፡ ወጣቶችን ፡ ለመሳብ ፡ ይጥራል
2. ለማስደሰት ፡ ጣረ. The new magazine caters to boys by printing stories about airplanes. አዲሱ ፡ መጽሔት ፡ ስለ ፡ አውሮፕላኖች ፡ ታሪክ ፡ በመጻፍ ፡ ልጆችን ፡ ለማስደሰት ፡ ይጥራል

**caterpillar** አባ ፡ ጨጓሬ

**cathedral** ካቴድራል
This cathedral commemorates the Emperor's victory. ይህ ፡ ካቴድራል ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ድል ፡ መታሰቢያ ፡ ነው

**Catholic** ካቶሊክ
There are not many Catholics in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ካቶሊኮች ፡ የሉም

**cattle**
1. ከብት. They raise fine cattle in this country. እዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ጥሩ ፡ ከብቶች ፡ ያረባሉ
2. የቀንድ ፡ ከብት. All cattle eat grass. የቀንድ ፡ ከብት ፡ ሁሉ ፡ ሣር ፡ ይበላል
[See also 'range']

**cattleman** ከብት ፡ አርቢ
The occupancy of the land by farmers was opposed by the cattlemen. መሬቱ ፡ ባራሾች ፡ መያዙን ፡ ከብት ፡ አርቢዎች ፡ ተቃውመው ፡ ነበር

**caught,** see **catch**

**cause** (v.)
1. አ-stem, አስ-stem. He causes her a lot of grief. ብዙ ፡ ያሳዝናታል
2. አመጣ. What caused the accident? አደጋውን ፡ ያመጣው ፡ ምንድነው ?
3. አስከተለ. It is my contention that poverty causes crime. ድኽነት ፡ ወንጀልን ፡ ያስከትላል ፡ ብዬ ፡ አምናለሁ
4. ፈጠረ. The news caused a furor. ወሬው ፡ ሽብር ፡ ፈጠረ
*What causes malaria? የወባ ፡ መነሾው ፡ ምንድነው ?

**cause** (n.)
1. ምክንያት. What is the cause of the delay? የተዘገየበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድነው ?
2. ተጋድሎ. World peace is a cause she works for. ተጋድሎ ፡ የምታደርገው ፡ የዓለምን ፡ ሰላም ፡ ለማግኘት ፡ ነው
3. ዓላማ. He died for a good cause. የሞተው ፡ ለጥሩ ፡ ዓላማ ፡ ነው

4. መነሻ. We cannot stop war until we get rid of the causes of war. የጦርነትን ፡ መነሻዎች ፡ ካላስወገድን ፡ ጦርነትን ፡ ልናስወግድ ፡ አንችልም
5. ጉዳይ. He declared his adherence to the cause of freedom. ለነጻነት ፡ ጉዳይ ፡ ደጋፊነቱን ፡ ገለጸ

**be the cause of** አስከተለ
Parents' lack of firmness is the cause of much trouble today. ዛሬ ፡ የወላጆች ፡ ጥብቅ ፡ አለመሆን ፡ ብዙ ፡ ጠንቅ ፡ ያስከትላል
[See also 'immediate']

**caustic** የሚከነክን
He made caustic remarks about my proposal. ስለ ፡ አቀረብኩት ፡ ሐሳብ ፡ የሚከነክን ፡ አስተያየት ፡ ሰጠ

**cauterize** ተኰሰ
He cauterized the wound with a hot iron. ቁስሉን ፡ በጋለ ፡ ብረት ፡ ተኰሰው

**caution** (v.) አስጠነቀቀ
I cautioned him against being late. እንዳይዘገይ ፡ አስጠነቀቅሁት

**caution** (n.) ጥንቃቄ
The path is slippery; you had better proceed with caution. መንገዱ ፡ ስለሚያዳልጥ ፡ በጥንቃቄ ፡ ብትራመድ ፡ ይሻላል

**caution sign** የማስጠንቀቂያ ፡ ምልክት
The traffic signal showing a palm facing the road is a caution sign. በመንገድ ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ መዳፍን ፡ የሚያሳይ ፡ የትራፊክ ፡ ምልክት ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ምልክት ፡ ነው

**cautious** ጥንቁቅ
He is a cautious driver. ጥንቁቅ ፡ ነጂ ፡ ነው

**cautiously** በጥንቃቄ
They approached cautiously. በጥንቃቄ ፡ ቀረቡ

**cavalry** ፈረሰኛ
The cavalry attacked first. ፈረሰኛው ፡ በቅድሚያ ፡ አጠቃ

**cavalryman** ፈረሰኛ
His equestrian training helped him become the best cavalryman. በፈረሰኛነት ፡ መሠልጠኑ ፡ ምርጥ ፡ ፈረሰኛ ፡ ለመሆን ፡ ረዳው

**cave** (v.), ~ **in** ተደረመሰ
Look out! The wall is caving in. ተጠንቀቅ ፤ ግድግዳው ፡ ሊደረመስ ፡ ነው

**cave** (n.) ዋሻ
He hid in a cave. ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ተደበቀ

**cavern** ዋሻ
Ancient man used to live in caverns. የጥንት ፡ ሰው ፡ በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ይኖር ፡ ነበር

**cavernous** ዋሻ ፡ የበዛበት
The cavernous mountain is a good hiding place for the outlaws. ዋሻ ፡ የበዛበት ፡ ተራራ ፡ ለሽፍቶች ፡ ጥሩ ፡ መደበቂያ ፡ ቦታ ፡ ነው

**cavity** የተቦረቦረ ፡ ጥርስ
The dentist filled the cavity. የጥርስ ፡ ሐኪሙ ፡ የተቦረቦረውን ፡ ጥርስ ፡ ሞላ
*The abdominal cavity contains the stomach and the intestines. በሆድ ፡ እቃው ፡ ውስጥ ፡ ጨጓራና ፡ አንጀት ፡ ይገኛሉ

**cease** (vt.) አቆመ
The factory ceased making bicycles. ፋብሪካው ፡ ቢሲክሌት ፡ መሥራት ፡ አቆመ

**cease** (vi.)
1. አበቃ. The Aksumite empire ceased to exist in the 10th century. የአክሱም ፡ መንግሥት ፡ በዓሥረኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ አበቃ
2. ተቋረጠ. The music ceased suddenly. ሙዚቃው ፡ በድንገት ፡ ተቋረጠ

**cease fire** የተኩስ ፡ ማቆም ፡ ስምምነት
The cease fire was violated by both sides. የተኩስ ፡ ማቆሙ ፡ ስምምነት ፡ በሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ተጣሰ

**ceaseless** የማያቋርጥ
A brook's ceaseless murmur is enjoyable. የማያቋርጠው ፡ የጅረቷ ፡ ጉርምርምታ ፡ አስደሳች ፡ ነው

**cedar** ጥድ
The room is paneled in cedar. ግድግዳው ፡ በጥድ ፡ ተለብዷል

**cede** ለቀቀ
They refused to cede their land. መሬታቸውን ፡ አንለቅም ፡ አሉ

**ceiling**
1. ቢላፎን. The ceiling is low. ቢላፎኑ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ነው
2. ጣሪያ. The government imposed a ceiling on prices. መንግሥት ፡ የዋጋ ፡ ጣሪያ ፡ ወሰነ

**celebrate**
1. አከበረ. We are celebrating his birthday tomorrow. የሱን ፡ የልደት ፡ ቀን ፡ ነገ ፡ እናከብራለን
2. አሞገሰ. We celebrate the names of great men. የታላላቅ ፡ ሰዎችን ፡ ስም ፡ እናሞግሳለን

3. ተደሰተ. The salesman clinched the sale and went out to celebrate. አሻሻጩ ፡ የንግዱን ፡ ጉዳይ ፡ ፈጽሞ ፡ ሊደሰት ፡ ሄደ

*The newspaper celebrated the end of the war in red headlines. ጋዜጣው ፡ የጦርነቱን ፡ ፍጻሜ ፡ በቀይ ፡ ቀለም ፡ ጻፈው

[See also 'Mass']

**celebrated** (adj.) ዝነኛ

Longfellow was a celebrated author. ሎንግፌሎ ፡ ዝነኛ ፡ ደራሲ ፡ ነበር

**celebration**

1. የበዓል ፡ አከባበር ፤ ክብረ ፡ በዓል. The celebration took place yesterday. የበዓሉ ፡ አከባበር ፡ ትላንትና ፡ ተከናወነ

The streets were illuminated for the celebration. ለክብረ ፡ በዓሉ ፡ መንገዶቹ ፡ አሸብርቀው ፡ ነበር

2. ሥነ ፡ ሥርዓት. They commemorated the victory with a special celebration. የድሉን ፡ በዓል ፡ በልዩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አከበሩ

**celebrity** ዝነኛ ፡ ሰው ፤ ስመ ፡ ጥር

Mark Twain was a celebrity. ማርክ ፡ ትዌን ፡ ዝነኛ ፡ ሰው ፡ (ስመ ፡ ጥር) ፡ ነበር

**celestial**

1. የሰማይ. The stars are celestial bodies. ከዋክብቶች ፡ የሰማይ ፡ አካሎች ፡ ናቸው

2. መንግሥተ ፡ ሰማያዊ. The couple enjoyed celestial happiness. ባልና ፡ ሚስቱ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያዊ ፡ ደስታ ፡ አገኙ

**celibacy** ብሕትውና

The monks live in celibacy. መነኰሳት ፡ በብሕትውና ፡ ይኖራሉ

**celibate** ድንግል (pl. ደናግል)

The celibates live in a monastery. ደናግሉ ፡ የሚኖሩት ፡ በገዳም ፡ ውስጥ ፡ ነው

**cell**

1. ክፍል. Take the prisoner to his cell! እስረኛውን ፡ ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ውሰደው

2. ሴል. The human body consists of many cells. የሰው ፡ አካል ፡ የተሠራው ፡ ከብዙ ፡ ሴል ፡ ነው

3. ቡድን. The underground movement is divided into cells. በድብቅ ፡ የሚደረገው ፡ እንቅስቃሴ ፡ በቡድን ፡ የተከፋፈለ ፡ ነው

**cellar** ምድር ፡ ቤት

They shut the boy up in the cellar. ልጁን ፡ ምድር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ዘጉበት

**cello** [ትልቅ ፡ መሰንቆ ፡ መሳይ ፡ መሣሪያ]

**cement** (v.)

1. በሙጫ ፡ አያያዘ. The housewife cemented the broken plate. የቤት ፡ እመቤቷ ፡ የተሰበረውን ፡ ሳሕን ፡ በሙጫ ፡ አያያዘችው

2. ሲሚንቶ ፡ አለበሰ. They cemented the floor of their house. የቤታቸውን ፡ ወለል ፡ ሲሚንቶ ፡ አለበሱት

3. አጠነከረ. Time cements friendship. ጊዜ ፡ ጓደኝነትን ፡ ያጠነክራል

**cement** (n.) ሲሚንቶ

The cement hardened. ሲሚንቶው ፡ ደረቀ

**cemetery** መካነ ፡ መቃብር

The cemetery is near the church. መካነ ፡ መቃብሩ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አጠገብ ፡ ነው

**censer** ጥና

The incense is burned in a censer. ዕጣኑ ፡ በጥና ፡ ይጨሳል

**censor** (v.) መረመረ (ተመረመረ)

The article was censored before it was printed. ጽሑፉ ፡ ከመታተሙ ፡ በፊት ፡ ተመርምሮ ፡ ነበር

**censor** (n.) የሳንሱር ፡ ሹም

The censor banned the book. የሳንሱሩ ፡ ሹም ፡ መጽሐፉን ፡ አገደው

**censure** (v.) ገሠጸ

The man he worked for censured him for being late. ስለዘገየ ፡ አሠሪው ፡ ገሠጸው

**censure** (n.) ተግሣጽ

Censure is sometimes harder to bear than punishment. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከቅጣት ፡ ይልቅ ፡ ተግሣጽ ፡ ይከብዳል

**census** የሕዝብ ፡ ቈጠራ

The last census was made five years ago. ያለፈው ፡ የሕዝብ ፡ ቈጠራ ፡ ካምስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ተደረገ

**cent** ሳንቲም

An Ethiopian dollar has a hundred cents. አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ መቶ ፡ ሳንቲም ፡ ነው

**centenary** መቶኛ ፡ ዓመት ፡ በዓል

The university celebrates its centenary this year. ዩኒቨርሲቲው ፡ መቶኛ ፡ ዓመት ፡ በዓሉን ፡ ዘንድሮ ፡ ያከብራል

**centennial** መቶኛ ፡ ዓመት

Our nation celebrated its centennial in 1880.

አገራችን ፡ መቶኛውን ፡ ዓመት ፡ በ፲፱፻፺፪ ፡ ዓ.ም. አከበረች

**center** (v.)

1. መኻል ፡ አዋለ. Try to center the design on the page! ጌጡን ፡ ወረቀቱ ፡ መኻል ፡ ለማዋል ፡ ሞክር

2. አሳረፈ. We centered all our attention on the baby. ሐሳባችንን ፡ ሁሉ ፡ በሕፃኑ ፡ ላይ ፡ አሳረፍን

**center on** በተለይ ፡ ተመለከተ

+He centered his novel on the war. መጽሐፉ ፡ በተለይ ፡ ጦርነቱን ፡ የሚመለከት ፡ ነው

**be centered (on)** አረፈ

All his thoughts were centered on her. ሐሳቡ ፡ ሁሉ ፡ በእሷ ፡ ላይ ፡ አርፏል

**center** (n.)

1. መኻል. The center of the city is occupied by shops. በመኻል ፡ ከተማ ፡ ብዙ ፡ ሱቆች ፡ አሉ

2. እምብርት. New York City is a center of trade. የኒው ፡ ዮርክ ፡ ከተማ ፡ የንግድ ፡ እምብርት ፡ ናት

3. ክፍል. The university has a center for African Studies. ዩኒቨርሲቲው ፡ የአፍሪካ ፡ ጥናት ፡ ክፍል ፡ አለው

**center of attention**

*She is the center of attention. የሰው ፡ ሁሉ ፡ ዓይን ፡ ማረፊያ ፡ ነች

**in the center** እ - - - መኻል ፤ መካከል

The table is standing in the center of the room. ጠረጴዛው ፡ እክፍሉ ፡ መኻል ፡ ቆሟል

The house that is in the center of the village is very big. መንደሩ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ቤት ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ነው

**centigrade** ሴንቲግሬድ

**centigram** ሴንቲግራም

**centimeter** ሴንቲሜትር

**central**

1. ማእከላዊ. We chose a central meeting place. የምንገናኝበትን ፡ ማእከላዊ ፡ ስፍራ ፡ መረጥን

2. ዋና. The father is the central character in the novel. በታሪኩ ፡ ውስጥ ፡ አባትየው ፡ ዋናው ፡ ባለታሪክ ፡ ነው

**central idea** ፍሬ ፡ ነገር

The central idea of the book is not very clear. የመጽሐፉ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ግልጽ ፡ አይደለም

**central part of** መኻል

The central part of the city is occupied by shops. በመኻል ፡ ከተማው ፡ ብዙ ፡ ሱቆች ፡ አሉ

**centralize** ባንድ ፡ አስተዳደር ፡ ሥር ፡ አጠቃለለ

The mayor centralized the school system. ከንቲባው ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ባንድ ፡ አስተዳደር ፡ ሥር ፡ አጠቃለለ

**century** ክፍለ ፡ ዘመን ፤ መቶ ፡ ዓመት

Airplanes were invented during this century. አውሮፕላኖች ፡ የተፈለሰፉት ፡ በዚህ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ነው

America was discovered five centuries ago. አሜሪካ ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ተገኘች

**for centuries** ለብዙ ፡ ዘመናት

The Roman ascendancy in England lasted for centuries. ሮማውያን ፡ በእንግሊዞች ፡ ላይ ፡ የነበራቸው ፡ ግዛት ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ ቆየ

**cereal**

1. እህል. Wheat is a cereal; so are barley and millet. ስንዴ ፡ እህል ፡ ነው ፤ ገብስና ፡ ጤፍም ፡ እንዲሁ

2. ከጥሬ ፡ ጥሬ ፡ የተሠራ ፡ ምግብ. He eats cereal every day. ሁል ፡ ቀን ፡ ከጥሬ ፡ ጥሬ ፡ የተሠራ ፡ ምግብ ፡ ይበላል

**cerebral** የአንጎል

Cerebral nerves are located in the neck. የአንጎል ፡ ጅማቶች ፡ የሚገኙት ፡ አንገት ፡ ውስጥ ፡ ነው

**ceremonial**

1. የክብረ ፡ በዓል. The ceremonial costumes were beautiful. የክብረ ፡ በዓሉ ፡ ልብሶች ፡ የሚያምሩ ፡ ነበሩ

2. ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ያለው. The inauguration of the airport was a ceremonial occasion. የአውሮፕላን ፡ ጣቢያው ፡ ምረቃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ያለው ፡ በዓል ፡ ነበር

**ceremonious** (= adv.) በአክብሮት

He made a ceremonious bow to the Emperor. ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ በአክብሮት ፡ እጅ ፡ ነሣ

*He greeted his rival with a ceremonious display of friendship. ተቃዋሚውን ፡ ለይስሙላ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ አነጋገረው

**ceremony**

1. ሥነ ፡ ሥርዓት. The ceremony of the opening of the parliament was celebrated properly. የምክር ፡ ቤቱ ፡ አከፋፈት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በደንብ ፡ ተከበረ

There is no need for ceremony between friends. በጓደኞች ፡ መካከል ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ መከ ተል ፡ አያሻም
2. አከባበር. The ceremony of the coronation is very beautiful. የዘውዱ ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ በ ጣም ፡ የደመቀ ፡ ነው

**certain**
1. አንዳንድ. Certain people, whom I'd rather not name, ... አንዳንድ ፡ ስማቸውን ፡ ለመጥቀስ ፡ የማልፈልገው ፡ ሰዎች - - -
2. አንድ. A certain person whom I met yesterday told me so. ትላንትና ፡ ያገኘሁት ፡ አንድ ፡ ሰውዬ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገረኝ
There is a certain shyness in her manner. አንድ ፡ ያይናፋርነት ፡ ጠባይ ፡ አለባት
3. እርግጠኛ. One thing is certain ... አንድ ፡ ነ ገር ፡ እርግጠኛ ፡ ነው
He is certain to come. ለመምጣት ፡ እርግጠኛ ፡ ነው
4. እሙን. His eventual success is certain. በመጨረሻ ፡ እንደሚቀናው ፡ እሙን ፡ ነው
5. የተወሰነ. At a certain hour, all the stores will close. በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ መደብሮች ፡ ሁሉ ፡ ይዘጋሉ
*You will face certain death if you drink that impure water. ያን ፡ ያልተጣራ ፡ ውኃ ፡ ብትጠጣ ፡ መሞትህ ፡ አያጠራጥርም

**for certain** በእርግጥ
I know for certain that he will pass the exam. ፈተናውን ፡ እንደሚያልፍ ፡ በእርግጥ ፡ አውቃለሁ

**make certain** አረጋገጠ
I think there is a plane at eight, but you ought to make certain. በሁለት ፡ ሰዓት ፡ አውሮፕላን ፡ ያለ ፡ ይመስለኛል ፡ ግን ፡ ማረጋገጥ ፡ ይገባሃል
[See also 'dead, degree, extent']

**certainly**
1. ፍጹም ፤ በፍጹም. She is certainly right. ፍጹ ም ፡ ልክ ፡ ነች
Now I certainly won't do it. በፍጹም ፡ አልሠራ ውም
2. እውነትም. Your boy has certainly grown a lot. እውነትም ፡ ልጅህ ፡ በጣም ፡ አድጓል
3. እንዴታ. Will you pass me the sugar, please. Certainly! ስኳሩን ፡ ታቀብለኝ ፤ እንዴታ !
[See also 'most']

**certainty** (certainties)
1. የማይቀር. Death and taxes are certainties. ሞትና ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ የማይቀሩ ፡ ናቸው
2. እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ ማለት. The man's certainty was amusing for we could see that he was wrong. የተሳሳተ ፡ መሆኑን ፡ ስለምናውቅ ፡ የሰ ውየው ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ ማለት ፡ አሥቂኝ ፡ ነበር

**with any certainty** በእርግጥ
I cannot say with any certainty where I will be next week. በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ የት ፡ እንደምሆን ፡ በእርግጥ ፡ ለመናገር ፡ አልችልም

**certificate** የምስክር ፡ ወረቀት
He needs a doctor's certificate. ከሐኪም ፡ የ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ ማግኘት ፡ አለበት
[See also 'gift certificate']

**certify** (certified)
1. አረጋገጠ. I certified that this is his book. ይህ ፡ የሱ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሆነ ፡ አረጋገጥኩ
2. መሰከረ. This diploma certifies that you have completed high school. ይህ ፡ ዲፕሎማ ፡ የሁለ ተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ መፈጸምህን ፡ ይመሰ ክራል

**certitude** ፍጹምነት
Our belief in God lacks the certitude of our fathers' belief. እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያለን ፡ እምነት ፡ አባቶቻችን ፡ የነበራቸውን ፡ ፍጹምነ ት ፡ ይጐድለዋል

**cessation**
*During the summer, there is a cessation of work. በበጋ ፡ ወራት ፡ ሥራ ፡ ይቋረጣል

**chafe**
1. እየፈገፈገ ፡ አሳመመ. A stiff collar may chafe your neck. ደረቅ ፡ ኮሌታ ፡ አንገትህን ፡ እየፈ ገፈገ ፡ ሊያሳምምህ ፡ ይችላል
2. አፋጨ. She chafed her cold hands. እጇን ፡ ስለበረዳት ፡ አፋጨች

**chaff** (v.) ቀለደ(በት)
The boys chaffed him about his mistakes in speaking English. እንግሊዝኛ ፡ ሲናገር ፡ በሚያ ደርገው ፡ ስሕተት ፡ ልጆቹ ፡ ቀለዱበት

**chaff** (n.) ገለባ
The wind blew the chaff from the grain. ነፋሱ ፡ እህሉን ፡ ከገለባው ፡ ለየው
His opinions are mere chaff. ሐሳቡ ፡ ገለባ ፡ ነው

**chagrin** (v.) ቅር ፡ አሰኘ
The rejection of his proposal chagrined him deeply. ያቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ተቀባይነት ፡ ማጣቱ ፡ ቅር ፡ አሰኘው

**be chagrined** ቅር ፡ ተሰኘ
He was chagrined when he did not get the prize. ሽልማቱን ፡ ባጣ ፡ ጊዜ ፡ ቅር ፡ ተሰኘ

**chagrin** (n.) ቅሬታ
He didn't win the prize, and his chagrin was apparent. ሽልማቱን ፡ ስላላገኘ ፡ ቅሬታው ፡ ግልጽ ፡ ነበር

**chain** (v.) በሰንሰለት ፡ አሰረ
Have you chained the dog? ውሻውን ፡ በሰንሰለት ፡ አሰረኸዋል ?

**be chained (to)** ተቈራኘ
My brother is chained to his job. ወንድሜ ፡ ከ ሥራው ፡ ጋር ፡ ተቈራኝቷል

**chain** (n.)
1. ሰንሰለት. They put a chain around his hands. እጁን ፡ በሰንሰለት ፡ አሰሩት
2. እግር ፡ ብረት. The prisoner burst his chains. እስረኛው ፡ እግር ፡ ብረቱን ፡ በጠሰው
3. ሐብል. She wore a golden chain around her neck. ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ ሐብል ፡ አጥልቃ ፡ ነበር
4. ማሰሪያ. He was unable to detach the watch from the chain. ሰዓቱን ፡ ከማሰሪያው ፡ ለመለያየት ፡ አልቻለም ፡ ነበር

**chains** እስራት
He lived all his life in chains. ሕይወቱን ፡ በሙሉ ፡ በእስራት ፡ ኖረ

**chain of events** ተከታታዮች ፡ ድርጊቶች
The chain of events started with the Emperor's arrival. ተከታታዮቹ ፡ ድርጊቶች ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደደረሱ ፡ ተጀመሩ
[See also 'mountain chain']

**chair** (v.) በሊቀ ፡ መንበርነት ፡ መራ
The teacher chaired the meeting. አስተማሪው ፡ ስብሰባውን ፡ በሊቀ ፡ መንበርነት ፡ መራ

**chair** (n.) ወምበር ፤ ወንበር
The chair has four legs. ወንበሩ ፡ አራት ፡ እግር ፡ አለው
They created a chair for Ethiopian history. የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ለማስተማር ፡ አዲስ ፡ ወንበር ፡ አቋቋሙ

**take the chair** ስፍራውን ፡ ያዘ
When the chairman took the chair, everybody was quiet. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ስፍራቸውን ፡ ሲይዙ ፡ ሁሉም ፡ ጸጥ ፡ አለ
[See also 'back, easy chair']

**chairman** ሊቀ ፡ መንበር
He is the chairman of the Trusteeship Committee. የሞግዚት ፡ አስተዳደሩ ፡ ኮሚቴ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ነው

**chairmanship** ሊቀ ፡ መንበርነት
He acceded to the chairmanship after the incumbent died. የቀድሞው ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ሲሞት ፡ እሱ ፡ ሊቀ ፡ መንበርነቱን ፡ ያዘ

**chaise longue** ረዥም ፡ ፎቴ
He sat on a chaise longue. በረዥም ፡ ፎቴ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ

**chalice** ጽዋ
They found a golden chalice in this church. የወርቅ ፡ ጽዋ ፡ እዚህ ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ አገኙ

**chalk** ጠመኔ
The teacher writes with chalk. አስተማሪው ፡ በጠመኔ ፡ ይጽፋል

**challenge** (v.)
1. አልተቀበለም. South Africa has challenged the U.N. decision. ደቡብ ፡ አፍሪካ ፡ የተባበሩትን ፡ መንግሥታት ፡ ውሳኔ ፡ አልተቀበለችም
I challenge your way of thinking. ሐሳብህን ፡ አልቀበልም
2. ፍላጎት ፡ ቀሰቀሰ. Science challenges today's young people. ሳይንስ ፡ የዘመኑን ፡ ወጣቶች ፡ ፍላጎት ፡ ይቀሰቅሳል
3. ተጠራጠረ. I challenge the wisdom of his decision. የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ጥልቅነት ፡ እጠራጠራለሁ
4. ተፎካከረ. He challenged him to come out and fight. ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጥተው ፡ እንዲዋጣላቸው ፡ ተፎካከረው
*I challenge anyone to race me. በሩጫ ፡ ማንም ፡ ይምጣልኝ

**challenge** (n.) የግጥሚያ ፡ ጥሪ
Our team accepted their challenge. ቡድናችን ፡ የግጥሚያ ፡ ጥሪያቸውን ፡ ተቀበለ
*This job offers many challenges to an intelligent man. ይሀ ፡ ሥራ ፡ የአስተዋይነትና ፡ የአእምሮ ፡ ንቃትን ፡ ይጠይቃል

**chamber**
1. ክፍል. The Congress of the United States has two chambers — the Senate and the House of Representatives. የአሜሪካን ፡ የምክር ፡ ቤት ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ አሉት ፤ የሕግ ፡ መወሰኛና ፡ የሕግ ፡ መምሪያ
2. የእንግዳ ፡ መቀበያ ፡ አዳራሽ. The Emperor meets with important guests in a large chamber.

ንትሠ ፣ ነገሥቱ ፣ ትልቅ ፣ የእንግዳ ፣ መቀበያ ፣ አ ዳራሽ ፣ ውስጥ ፣ የታወቁ ፣ እንግዶችን ፣ ይቀበላሉ
3. (የ)ግል ፣ ክፍል. She retired to her chambers. ወደ ፣ ግል ፣ ክፍሏ ፣ ገባች
4. ጋን. The bullet is stuck in the chamber of the gun. ጥይቱ ፣ ጠመንጃው ፣ ጋን ፣ ውስጥ ፣ ተቀረቀረ

**chameleon** እስስት

**chamois** [ፍየል ፣ የምታህል ፣ ድኩላ]

**champion** (v.) ተጋደለ
He championed freedom of speech. ለንግግር ፣ ነጻነት ፣ ተጋደለ

**champion** (n.)
1. ሻምፒዮን ፤ የሁሉ ፣ ረቺ ፣ የሆነ. The tennis champion won all the games. የቴኒስ ፣ ሻምፒ ዮኑ ፣ ግጥሚያውን ፣ ሁሉ ፣ አሸነፈ
The champion won by a knockout in the tenth round. የሁሉ ፣ ረቺ ፣ የሆነው ፣ በዐሥረኛው ፣ ዙር ፣ ላይ ፣ በመዘረር ፣ አሸነፈ
2. ተጋዳይ. He is a great champion of peace. ታላቅ ፣ የሰላም ፣ ተጋዳይ ፣ ነው

**champion** (adj.) ወደር ፣ የሌለው ፤ ተወዳዳሪ ፣ የ ሌለው
He is a champion football player. ወደር ፣ የሌለ ው ፣ (ተወዳዳሪ ፣ የሌለው) ፣ የእግር ፣ ኳስ ፣ ተጫ ዋች ፣ ነው

**championship** እንደኛነት ፤ አሸናፊነት
Our school won the championship in football. ትምህርት ፣ ቤታችን ፣ በእግር ፣ ኳስ ፣ እንደኛነትን ፣ (አሸናፊነትን) ፣ አገኘ

**chance** (v.)
*We chanced to meet. ባጋጣሚ ፣ ተገናኘን

**chance on**
1. በድንገት ፣ አጋጠመ(ው). He chanced on the book he wanted. የፈለገውን ፣ መጽሐፍ ፣ በድንገት ፣ አጋጠመው
2. በድንገት ፣ አየ. She chanced on a rare kind of mushroom on her walk through the woods. በጫካው ፣ ውስጥ ፣ ስትሄድ ፣ በድንገት ፣ ልዩ ፣ ዓይነት ፣ እንጉዳይ ፣ አየች

**chance** (n.)
1. ዕድል. This was the chance he had been waiting for. ሲጠባበቀው ፣ የነበረው ፣ ዕድል ፣ ይ ህ ፣ ነበር
2. ተስፋ. Is there any chance of catching the train? ባቡሩ ፣ ሳይሄድ ፣ ለመድረስ ፣ ተስፋ ፣ አለ ?
3. ዕጣ. Do you want to buy a chance for the Literacy Campaign? ለተምሮ ፣ ማስተማር ፣ ፕሮግራም ፣ ዕጣ ፣ ለመግዛት ፣ ትፈልጋለህ ?
*The chances are that the train hasn't left yet. ምናልባት ፣ ባቡሩ ፣ ገና ፣ አልተነሣ ፣ ይሆናል

**by chance** እንዳጋጣሚ ፤ እንዳመጣለት
I met him by chance. እንዳጋጣሚ ፣ አገኘሁት
He works by a system, not by chance. የሚሠራው ፣ በሥርዓት ፣ እንጂ ፣ እንዳመጣለት ፣ አይደለም

**have a chance** ዕድል ፣ ገጠመ(ው)
I had a chance to go to California. ወደ ፣ ካሊ ፎርኒያ ፣ ለመሄድ ፣ ዕድል ፣ ገጥሞኝ ፣ ነበር

**take a chance**
1. ዕድል ፣ ሞከረ. The movie may be closed but should we take a chance and go? ሲኒማው ፣ ተ ዘግቶ ፣ ይሆናል ፣ ግን ፣ ዕድላችንን ፣ እንሞክር ?
2. ባወጣ ፣ ያውጣው ፣ አለ. He took a chance when he swam the river. ወንዙን ፣ ዋኝቶ ፣ ለመ ሻገር ፣ የገባው ፣ ባወጣ ፣ ያውጣው ፣ ብሎ ፣ ነው
[See also 'happy, sheer, stand']

**change** (vt.)
1. ለወጠ. We may have to change our plans. እቅዳችንን ፣ መለወጥ ፣ ይኖርብን ፣ ይሆናል
He changed his money before going to Addis Ababa. ወደ ፣ አዲስ ፣ አበባ ፣ ከመምጣቱ ፣ በፊ ት ፣ ገንዘቡን ፣ ለወጠ
2. ቀየረ (ተቀየረ). The linen is changed every week. ያልጋ ፣ ልብስ ፣ በየሳምንቱ ፣ ይቀየራል
3. መነዘረ. Can you change a ten-dollar bill for me? ዐሥር ፣ ብር ፣ ልትመነዝርልኝ ፣ ትች ላለህ ?

**change** (vi.)
1. ተለወጠ. The weather is going to change. ያየሩ ፣ ጠባይ ፣ ሊለወጥ ፣ ነው
You will be surprised how he has changed. ምን ፣ ያህል ፣ እንደተለወጠ ፣ ብታይ ፣ ይገርም ሃል
2. ልብስ ፣ ቀየረ. It will take her five minutes to change. ልብሷን ፣ ለመቀየር ፣ አምስት ፣ ደቂቃ ፣ ይፈጅባታል
3. ሌላ ፣ ባቡር ፣ ተሳፈረ. We have to change at the next station. እሚቀጥለው ፣ ጣቢያ ፣ ሌ ላ ፣ ባቡር ፣ መሳፈር ፣ አለብን

**change (the) bed** አንሶላ ፣ ቀየረ
Mother changes the bed every Monday. እናታችን ፣ ሰኞ ፣ ሰኞ ፣ አንሶላ ፣ ትቀይራለች

**change (the) baby** የሕፃን ፣ ልብስ ፣ ለወጠ
The nurse changes the baby several times a day. ነርሷ ፣ በቀን ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ የሕፃኗን ፣ ልብስ ፣ ትለውጣለች

**change to**
The rainy season changed to autumn. ክረምት ፡ ሲወጣ ፡ ጥቢ ፡ ይተካል
[See also 'better, hard']

**change** (n.)
1. ለውጥ. I am for a change in the administration. ባስተዳደሩ ፡ ውስጥ ፡ ለውጥ ፡ እንዲደረግ ፡ እደግፋለሁ
2. የተለወጠ ፡ ነገር. Have there been any changes in my absence? እኔ ፡ በሌለሁበት ፡ የተለወጠ ፡ ነገር ፡ ኖሯል ?
3. መልስ. I have no money now; I will give you your change tomorrow. አሁን ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም ፤ መልስህን ፡ ነገ ፡ እሰጥሃለሁ
4. ምንዛሪ. Can you give me change for five dollars? ያምስት ፡ ብር ፡ ምንዛሪ ፡ ልትሰጠኝ ፡ ትችላለህ ?
5. ዝርዝር ፡ ገንዘብ. She took some change out of her bag. ከቦርሳዋ ፡ ውስጥ ፡ ዝርዝር ፡ ገንዘብ ፡ አወጣች

**for a change** ለለውጥ ፡ ያህል
For a change, I would like to go to the movies tonight. ለለውጥ ፡ ያህል ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ ወደ ፡ ሲኒማ ፡ መሄድ ፡ እፈልጋለሁ

**undergo changes** ተለወጠ
American society has undergone many changes. የአሜሪካን ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ብዙ ፡ ተለውጧል
[See also 'heart']

**channel** (v.)
1. አስተላለፈ. The secretary channeled the information to the director. ጸሐፊዋ ፡ መረጃውን ፡ ለዲሬክተሩ ፡ አስተላለፈች
2. አዘነበለ. +The student channeled his interest into studying law. የተማሪው ፡ ፍላጎት ፡ ወደ ፡ ሕግ ፡ አዘነበለ

**channel one's way** ቦረቦረ
The river had channeled its way through the rocks. ወንዙ ፡ በድንጋዮቹ ፡ መሀከል ፡ ቦረቦረ

**channel** (n.)
1. ሰላጤ ፤ የባሕር ፡ ወሽመጥ. The two lakes are joined by a narrow channel. ሁለቱ ፡ ሐይቆች ፡ በጠባብ ፡ ሰላጤ ፡ (በባሕር ፡ ወሽመጥ) ፡ ይገናኛሉ
2. አቅጣጫ. He hoped to direct the conversation to a new channel. ጭውውቱን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ ሊመራው ፡ ፈለገ

**channels**
1. ክፍል. Your application will have to go through the proper channels before it is approved. ማመልከቻህ ፡ ተቀባይነት ፡ ከማግኘቱ ፡ በፊት ፡ በተገቢዎቹ ፡ ክፍሎች ፡ በኩል ፡ መምጣት ፡ አለበት
2. መንገድ. The information came through secret channels. መረጃው ፡ የመጣው ፡ በምስጢር ፡ መንገዶች ፡ በኩል ፡ ነው

**chant** (v.) ዘመረ
The crowd chanted softly. ሕዝቡ ፡ በቀስታ ፡ ዘመረ

**chant** (n.) ዜማ
I recorded the priests' chant. የቄሱን ፡ ዜማ ፡ ቀረጽኩ

**chaos**
1. ፍርስርስ. The chaos left by the bombing has only recently been cleared up. በቦምቡ ፡ መፈንዳት ፡ ምክንያት ፡ የደረሰው ፡ ፍርስርስ ፡ የተወገደው ፡ በቅርብ ፡ ነው
2. ትርምስምስ. The city was in chaos after the hurricane. ከዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ በኋላ ፡ ከተማው ፡ ትርምስምስ ፡ ውስጥ ፡ ነበር

**reduce to chaos** አሸበረ
The bombings reduced Germany to chaos. የቦምቡ ፡ ድብደባ ፡ ጀርመንን ፡ አሸበረ

**chaotic, ~ condition** ምስቅልቅል
The room was in a chaotic condition. ክፍሉ ፡ ምስቅልቅሉ ፡ ወጥቶ ፡ ነበር

**chaotic mass** ዝባዝንኬ
There was a chaotic mass of books and papers on his desk. የመጻሕፍትና ፡ የወረቀት ፡ ዝባዝንኬ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ነበር

**chap** (chapped), vt.
1. ሰነጣጠቀ. The summer heat chapped the ground. የበጋው ፡ ሙቀት ፡ መሬቱን ፡ ሰነጣጠቀው
2. አቈረፈደ. Cold chaps the skin. ብርድ ፡ ቆዳን ፡ ያቈረፍዳል

**chap** (vi.) ቈረፈደ
My skin chaps in cold weather. በብርድ ፡ ጊዜ ፡ ቆዳዬ ፡ ይቈረፍዳል

**chapel** የጸሎት ፡ ቤት
The minister has his own chapel. ሚኒስትሩ ፡ የራሳቸው ፡ ጸሎት ፡ ቤት ፡ አላቸው

**chaplain** ቄስ
The chaplain, who went on a mission with the soldiers, gave the blessing. ከወታደሮቹ ፡ ጋር ፡ የዘመቱት ፡ ቄስ ፡ ቡራኬ ፡ ሰጡ

**chaplet** መቍጠሪያ
This chaplet is made of beads of various colors. ይህ ፡ መቍጠሪያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ ካሉ ዋቸው ፡ ዶቃዎች ፡ የተሠራ ፡ ነው

**chapped** (adj.) የተሰነጣጠቀ
He smeared butter on his chapped hand. የተሰነጣጠቀው ፡ እጁን ፡ ቅቤ ፡ ቀባው

**chapter**
1. ምዕራፍ. Did you read the last chapter of this book? የዚህን ፡ መጽሐፍ ፡ የመጨረሻውን ፡ ምዕራፍ ፡ አንብበሃል ?
That is a closed chapter in my life. ያ ፡ በሕይወቴ ፡ ውስጥ ፡ የተፈጸመ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው
2. ቅርንጫፍ. The Los Angeles chapter of the American Red Cross celebrated its tenth anniversary. ሎስ ፡ አንጀለስ ፡ የሚገኘው ፡ የቀይ ፡ መስቀል ፡ ቅርንጫፍ ፡ ዐሥረኛ ፡ ዓመቱን ፡ አከበረ

**chapter and verse** አንድ ፡ ባንድ
The deacon knows the New Testament chapter and verse. ዲያቆኑ ፡ አዲስ ፡ ኪዳንን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ያውቃል

**char** (charred) አሳረረ
The woman charred the meat by cooking it too close to the flames. ሴትዮዋ ፡ እሳት ፡ አብዝታ ፡ ሥጋውን ፡ አሳረረችው

**character**
1. ጠባይ. I have misjudged his character. ጠባዩን ፡ በተሳሳተ ፡ አስተያየት ፡ ገመትኩ
2. ባለ ፡ ታሪክ. How many characters are there in the play? በቲያትሩ ፡ ውስጥ ፡ስንት፡ ባለ ፡ ታሪኮች ፡ አሉ ?
3. ፊደል (pl. ፊደላት). Ethiopian characters are difficult to read. የኢትዮጵያን ፡ ፊደላት ፡ ማንበብ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
4. ዓይነት. What is the character of the plan you suggest? የምታቀርበው ፡ እቅድ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ?
5. ተፈጥሮ. The trees of those islands are of a particular character. በዚያ ፡ ደሴት ፡ ያሉት ፡ ዛፎች ፡ የተለየ ፡ ተፈጥሮ ፡ አላቸው
6. መንፈስ ፡ ጠንካራነት. It takes character to endure calumny. ሐሜትን ፡ ለመቋቋም ፡ መንፈስ ፡ ጠንካራነትን ፡ ይጠይቃል
7. ሰው. He is a strange character. ጠባዩ ፡ የማይገባ ፡ ሰው ፡ ነው
*My uncle is quite a character. አጎቴ ፡ ጠባዩ ፡ ከሰው ፡ የተለየ ፡ ነው

**in character with**
*Such behavior does not seem to be in character with what I know of him. የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጠባይ ፡ እኔ ፡ ከማውቀው ፡ ሁኔታው ፡ የተለየ ፡ ነው
[See also 'virtuous']

**characteristic** (n.)
1. መለያ. He has all the characteristics of a scholar. ማንኛውንም ፡ የምሁርን ፡ መለያ ፡ ይዟል
2. ባሕርይ. Arrogance is a characteristic of a rude person. ትዕቢት ፡ የባለጌ ፡ ባሕርይ ፡ ነው

**characteristic** (adj.)
1. የተለመደ. She received me with her characteristic kindness. በተለመደው ፡ ደግነቷ ፡ ተቀበለችኝ
2. ዓይነተኛ ፡ ጠባይ. That attitude is characteristic of her. ያ ፡ አመል ፡ የርሷ ፡ ዓይነተኛ ፡ ጠባይዋ ፡ ነው
3. ዓይነተኛ. Yellow and green are characteristic colors of September. ብጫና ፡ አረንጓዴ ፡ የመስከረም ፡ ዓይነተኛ ፡ ቀለሞች ፡ ናቸው
4. የሚለይበት. Nationalism is one of the characteristic features of our age. ብሔራዊ ፡ ስሜት ፡ ጊዜያችን ፡ ከሚለይባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ አንዱ ፡ ነው
5. የተለየ. Bananas have their own characteristic smell. ሙዝ ፡ የተለየ ፡ የራሱ ፡ ሽታ ፡ አለው

**characterize**
1. ገመተ. I would characterize our teacher as a very kindly person. አስተማሪያችን ፡ በጣም ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ እገምታለሁ
2. ሁኔታውን ፡ ገልጾ ፡ አስረዳ. He characterized her in a few words. ሁኔታዋን ፡ ባጭሩ ፡ ገልጾ ፡ አስረዳ
3. (= pass.) ታወቀ. Short lines characterize his poetry. የሱ ፡ ግጥም ፡ ባጭር ፡ ሐረጉ ፡ ይታወቃል

**be characterized** ከሌሎች ፡ ተለየ
The camel is characterized by the hump on its back. ግመል ፡ ከሌሎች ፡ የምትለየው ፡ በሻኛዋ ፡ ነው

**charcoal** ከሰል
It is customary to burn charcoal in the city. ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ከሰል ፡ ማንደድ ፡ የተለመደ ፡ ነው

**charge** (vt.)
1. ጠየቀ ፤ አስከፈለ. We charge only fair prices here. እዚህ ፡ መጠነኛ ፡ ዋጋ ፡ ብቻ ፡ እንጠይቃለን
He charged me a triple price for the book. ለመጽሐፉ ፡ ሦስት ፡ ዕጥፍ ፡ ዋጋ ፡ አስከፈለኝ
2. አዘዘ (ታዘዘ). Mother charged her with taking

care of the baby. እናታችን ፡ ሕፃኗን ፡ እንድ ትጠብቅ ፡ አዘዘቻት

The minister was charged with carrying a personal message to the Emperor. ሚኒስትሩ ፡ የግል ፡ መልእክት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እንዲያደርስ ፡ ታዘዘ

3\. አሳደደ. The bull charged him, but he climbed a tree and escaped. ወይፈኑ ፡ አሳደደው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዛፉ ፡ ላይ ፡ ወጣና ፡ አመለጠ

4\. አጠቃ. The soldiers charged the enemy. ወታደሮቹ ፡ ጠላትን ፡ አጠቁ

5\. ሞላ. Please charge my battery! ባትሪዬን ፡ ሙላልኝ

6\. ከሰሰ. They charged him with theft. በሌብነት ፡ ከሰሱት

*The police charged the accident to careless driving. ፖሊሶች ፡ ያደጋው ፡ መነሾ ፡ በቸልታ ፡ መንዳት ፡ ነው ፡ አሉ

*If you have no cash, this store will charge your purchase. ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ከሌለህ ፡ ይህ ፡ መደብር ፡ ዱቤውን ፡ መዝግቦ ፡ ይሸጥልሃል

**charge** (vi.) ተፈተለከ

The boy charged through the door. ልጁ ፡ በበሩ ፡ ተፈተለከ

**be charged** ተከሰሰ

The driver was charged with speeding. ነጂው ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ በመንዳት ፡ ተከሰሰ

*His mind was charged with important matters. በአእምሮው ፡ ብዙ ፡ ትልልቅ ፡ ጉዳዮች ፡ ይዟል

**charge for** አለ

What do you charge for these shoes? እነዚህን ፡ ጫማዎች ፡ ስንት ፡ ትላለህ ?

**charge with** የ - - - ኀላፊነት ፡ ጣለ

The law charges policemen with keeping law and order. ሕጉ ፡ ሕግንና ፡ ጸጥታን ፡ የማስከበር ፡ ኀላፊነትን ፡ በፖሊሶች ፡ ላይ ፡ ይጥላል

**(be) charged with**

1\. (= active) አዘለ. He spoke to her in words charged with longing and love. ናፍቆትና ፡ ፍቅር ፡ ባዘለ ፡ አኳኋን ፡ አነጋገራት

2\. ሞላ(በት). The air was charged with excitement. ሁኔታው ፡ የጋለ ፡ ስሜት ፡ የሞላበት ፡ ነበር

## charge (n.)

1\. ፈንጂ. The charge is enough to blow us all up. ፈንጂው ፡ ሁላችንንም ፡ ለማጥፋት ፡ በቂ ፡ ኀይል ፡ አለው

2\. ትእዛዝ. The officer's charge to the men to keep watch was disregarded. መኰንኑ ፡ ለወታደሮቹ ፡ የሰጡት ፡ የጥበቃ ፡ ትእዛዝ ፡ ችላ ፡ ተባለ

3\. ክስ. What were the charges against him? በሱ ፡ ላይ ፡ የቀረቡት ፡ ክሶች ፡ ምን ፡ ነበሩ ?

4\. ማሳጣት. His charges are nothing but calumny. የሱ ፡ ማሳጣት ፡ ሐሜት ፡ ብቻ ፡ ነው

5\. ማጥቃት. After a fierce charge, our soldiers drove the enemy from the hilltop. ከኀይለኛ ፡ ማጥቃት ፡ በኋላ ፡ ወታደሮቻችን ፡ ጠላትን ፡ ከኮረብታው ፡ ጫፍ ፡ አባረሩ

6\. ሸክም. I hope you will never be a charge on your parents. ምንም ፡ ጊዜ ፡ ለወላጆችህ ፡ ሸክም ፡ እንደማትሆን ፡ ተስፋ ፡ አለኝ

7\. ዋጋ. I won't pay these excessive charges. ይህንን ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ዋጋ ፡ አልከፍልም

8\. ኀላፊነት. He took complete charge of the library. የቤተ ፡ መጻሕፍቱን ፡ ሙሉ ፡ ኀላፊነት ፡ ወሰደ

9\. ኪሳራ. The improvements were made at the tenant's own charge. ቤቱ ፡ የታደሰው ፡ በተከራዩው ፡ ኪሳራ ፡ ነው

*There is no charge for alteration. ለማስተካከያ ፡ አይከፈልም

**be in charge** ኀላፊ ፡ ነው

Who is in charge of this section? የዚህ ፡ ክፍል ፡ ኀላፊ ፡ ማን ፡ ነው ?

**be in one's charge** አደራ ፡ ተሰጠ

The baby was in Mary's charge. ሕፃኑ ፡ ለሜሪ ፡ አደራ ፡ ተሰጥቶ ፡ ነበር

**free of charge**

1\. በነጻ. We will mail it to you free of charge. በፖስታ ፡ በነጻ ፡ እንልክልሃለን

2\. ያለቅጥያ ፡ ዋጋ. This store delivers free of charge. ይህ ፡ መደብር ፡ ያለቅጥያ ፡ ዋጋ ፡ እቃ ፡ እቤት ፡ ድረስ ፡ ያመጣል

**on a charge of** በ - - - ተከሶ

The tramp was arraigned on a charge of stealing. በረንዳ ፡ አዳሪው ፡ በሌብነት ፡ ተከሶ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀረበ

**prefer charges** ከሰሰ

He preferred charges against the driver of the car that hit him. የገጨውን ፡ መኪና ፡ ነጂ ፡ ከሰሰው

**take charge of**

1\. ኀላፊ ፡ ሆነ. He is taking charge of the new branch. ያዲሱ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ኀላፊ ፡ ሊሆን ፡ ነው

2\. ኀላፊነት ፡ ወሰደ. When father died, she took the charge of caring for the family. አባታችን ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ የቤተ ፡ ሰቡን ፡ የመደገፍ ፡ ኀላፊነት ፡ እሷ ፡ ወሰደች

3. በእጅ ፡ አደረገ. The military took charge of the village. ሰራዊቱ ፡ መንደሪቱን ፡ በእጁ ፡ አደ ረገ

**chariot** ሰረገላ ፤ ጋሪ
The Romans used chariots for fighting and racing. ሮማውያን ፡ ለጦርነትና ፡ ለእሽቅድድም ፡ በሰረገላ ፡ ይጠቀሙ ፡ ነበር
The invention of chariots was a forerunner of the automobile. የጋሪ ፡ መፈልሰፍ ፡ ከአውቶሞ ቢል ፡ ቀደምትነት ፡ ነበረው

**charitable**
1. የበጎ ፡ አድራጎት. Homes for old people are often charitable institutions. ያረጁ ፡ ሰዎች ፡ መኖሪያዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የበጎ ፡ አድራጎ ት ፡ ድርጅቶች ፡ ናቸው
2. በጎ ፡ አድራጊ. He is charitable to all the needy persons. ለተቸገሩ ፡ ሁሉ ፡ በጎ ፡ አድራጊ ፡ ነው
*It was charitable of you to overlook my mistakes. ስሕተቴን ፡ ያለፍከኝ ፡ በበጎ ፡ ምኞት ህ ፡ ነው

**be charitable** ችሮታ ፡ አደረገ
He wished he had the means to be more charitable. የበለጠ ፡ ችሮታ ፡ ለማድረግ ፡ የሚች ልበትን ፡ ዘዴ ፡ ቢያገኝ ፡ ተመኘ

**charity** (charities)
1. ምጽዋት ፤ ችሮታ ፤ እርዳታ. Even though she is very poor, she is too proud to accept charity. በጣም ፡ ድኻ ፡ ብትሆንም ፡ ምጽዋት ፡ (ችሮታ ፤ እር ዳታ) ፡ ለመቀበል ፡ በጣም ፡ ኩሩ ፡ ናት
2. ልግስና. Charity begins at home. ልግስና ፡ ከቤት ፡ ይጀምራል
3. የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት. He left his estate to one of the charities. ንብረቱን ፡ ላን ድ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ትቶ ፡ ሞተ
4. በጎ ፡ አድራጎት. They contributed unlike sums to charity. ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ የተለያየ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጡ

**give to charity** ቸረ
He is too stonehearted to give any money to charity. ለሰው ፡ የማያዝን ፡ ስለሆነ ፡ ገንዘብ ፡ አይቸርም

**out of charity** አዝኖለት
She looked so poor that we fed her out of charity. በጣም ፡ የተቸገረች ፡ መስላ ፡ ስላየና ት ፡ አዝነንላት ፡ ምግብ ፡ ሰጠናት

**charm** (v.) ማረከ
His friendliness charmed the audience. የሱ ፡ የወዳጅነት ፡ አቀራረብ ፡ አድማጮቹን ፡ ማረከ

**be charmed** በጣም ፡ ተደሰተ
We were charmed by the play. በቲያትሩ ፡ በጣ ም ፡ ተደስተን ፡ ነበር

**charm** (n.)
1. ውበት. He fell victim to her charms. በውበቷ ፡ ተማረከ
2. ደግምነት. The reason so many men are seen talking to her is because she has a lot of charm. ይህን ፡ ያህል ፡ የሚያጫውታት ፡ ሰ ው ፡ የበዛው ፡ ደግምነት ፡ ስላላት ፡ ነው
3. ለዛ. Our grandmother did not lose her charm for us as she grew old. አያታችን ፡ በዕድ ሜ ፡ እየገፉ ፡ ቢሄዱም ፡ ለዛቸውን ፡ አላጡብንም
4. ክታብ. He wore a charm around his neck to ward off the evil eye. ከቡዳ ፡ ለመከላከል ፡ አንገቱ ፡ ላይ ፡ ክታብ ፡ አስሯል

**charms** አስማት
He had charms recited against his opponent. በባለጋራው ፡ ላይ ፡ አስማት ፡ አስደገመበት

**have charm** የደስ ፡ ደስ ፡ አለው
She has a lot of charm, and everyone likes her. የደስ ፡ ደስ ፡ ስላላት ፡ ሁሉም ፡ ይወዳታል

**have great charm for** ማረከ
Paris has great charm for tourists. ፓሪስ ፡ አገ ር ፡ ጎብኚዎችን ፡ ትማርካለች
[See also 'lucky']

**charming** ደስ ፡ የሚል ፤ የደስ ፡ ደስ ፡ ያለው
She has a charming smile. ደስ ፡ የሚል ፡ ፈገግ ታ ፡ አላት
His sister is a very charming person. እኅቱ ፡ የደ ስ ፡ ደስ ፡ ያላት ፡ ሰው ፡ ናት

**chart** ካርታ ፤ ሰሌዳ
He marked the enemy positions on a chart. ጠላት ፡ ያለበትን ፡ ሰፍራ ፡ በካርታ ፡ (በሰሌዳ) ፡ ላይ ፡ አመለከተ

**charter** (v.) ተኰናተረ
We chartered a bus to Harar. ወደ ፡ ሐረር ፡ የሚ ሄድ ፡ አውቶቡስ ፡ ተኰናተርን

**charter** (n.) ሕግ ፡ መሠረት
We must respect the charter of the United Nations. የተባበሩትን ፡ መንግሥታት ፡ ሕግ ፡ መ ሠረት ፡ ማክበር ፡ አለብን

**charwoman** የቀን ፡ ሠራተኛ
The charwoman comes twice a week. የቀን ፡ ሠ ራተኛዋ ፡ በሳምንት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ትመጣለች

**chase** (vt.)
1. አሳደደ. Dogs like to chase rabbits. ውሾች ፡ ጥንቸሎችን ፡ ማሳደድ ፡ ይወዳሉ

2. አባረረ. I chased him out of the house. ከቤቱ ፡ አባረርኩት

3. ያዘ. The two children dropped behind the group to chase butterflies. ቢራቢሮዎችን ፡ ለመ ያዝ ፡ ሁለቱ ፡ ሕፃናት ፡ ከቡድኑ ፡ ተለይተው ፡ ኋላ ፡ ቀሩ

4. ተከታተለ. He chased her for three years before she consented to marry him. ልታገባው ፡ ከመፍቀዷ ፡ በፊት ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ተከታተላት

**chase** (vi.) ተሯሯጠ
I have chased all over town looking for you. አንተን ፡ ፍለጋ ፡ በከተማው ፡ በሙሉ ፡ ተሯሯጥሁ

**chase away** ወዲያ ፡ አባረረ
Chase the dog away! ውሻውን ፡ ወዲያ ፡ አባርረው

**chase** (n.) ማሳደድ
After a long chase, they caught the thief. ከብዙ ፡ ማሳደድ ፡ በኋላ ፡ ሌባውን ፡ ያዙት

**give chase** ማባረር ፡ ቀጠለ
The hunt began, and the dog gave chase. አደኑ ፡ ተጀምሮ ፡ ውሻው ፡ ማባረር ፡ ቀጠለ

**chasm**
1. ገደል. The chasm was too wide to jump across. ገደሉ ፡ ሰፊ ፡ ስለነበረ ፡ በዝላይ ፡ ሊታለፍ ፡ አይቻልም
2. መቃቃር. The chasm between England and the American colonies resulted in the Revolutionary War. በእንግሊዝና ፡ በአሜሪካን ፡ ቅኝ ፡ ግዛቶች ፡ መሀከል ፡ የነበረው ፡ መቃቃር ፡ ከጦርነት ፡ አደረሳቸው

**chaste** ንጽሕት
Saint Mary is chaste. ቅድስት ፡ ማርያም ፡ ንጽሕት ፡ ናት

**remain chaste** በድንግልና ፡ ቆየች
Custom prescribes that a woman remain chaste until marriage. ሴት ፡ ልጅ ፡ እስከካገባች ፡ ድረስ ፡ በድንግልና ፡ እንድትቆይ ፡ ባህላዊ ፡ ግዴታ ፡ ነው

**chasten**
1. ቀጣ. The teacher chastened the disobedient child. አስተማሪው ፡ የማይታዘዘውን ፡ ልጅ ፡ ቀጣው
2. ቀነሰ. Age has chastened his violent temper. እርጅና ፡ ግልፍተኛነቱን ፡ ቀንሶታል

**chastise** ቀጣ
The father chastised his son. አባትየው ፡ ልጁን ፡ ቀጣ

**chastity** ድንግልና
Monks must make a vow of chastity and poverty. መነኮሳዎች ፡ በድንግልናና ፡ በድኽነት ፡ እንኖራለን ፡ ብለው ፡ መማል ፡ አለባቸው

**chat** (chatted) , v. ተጫወተ ፤ አወጋ ፤ አወራ
We chatted all evening. ስንጫወት ፡ (ስናወጋ ፤ ስናወራ) ፡ አመሸን

**chat** (n.) ጭውውት
We had a nice chat. ጥሩ ፡ ጭውውት ፡ አደረግን

**chatter** (v.)
1. ለፈለፈ. They chattered incessantly. ያለማቋረጥ ፡ ለፈለፉ
2. ተንገጫገጨ. My teeth are chattering. ጥርሴ ፡ ይንገጫገጫል

**chatter** (n.) ልፍለፋ
His chatter bored me. ልፍለፋው ፡ አሰለቸኝ

**chatterbox** ለፍላፊ
She is a dreadful chatterbox. ክፉ ፡ ለፍላፊ ፡ ነች

**chatty** ለፍላፊ
I get all the gossip from my chatty neighbor. ወሬውን ፡ ሁሉ ፡ ከለፍላፊው ፡ ጐረቤቴ ፡ እሰማለሁ

**chauffeur** ሾፌር
The chauffeur did not bring the car on time. ሾፌሩ ፡ መኪናውን ፡ በጊዜ ፡ አላመጣም

**cheap** (adj.)
1. ርካሽ. Fruit is very cheap here. እዚህ ፡ ፍራፍሬ ፡ በጣም ፡ ርካሽ ፡ ነው
2. ቈጥቋጣ. He is too cheap to buy her a new dress. ቈጥቋጣ ፡ ስለሆነ ፡ አዲስ ፡ ልብስ ፡ አይገዛላትም
3. አልባሌ. She looks cheap in those clothes. ያንን ፡ ልብስ ፡ ስትለብስ ፡ አልባሌ ፡ ትመስላለች
4. በርካሽ ፡ የሚሸጥ. She always buys her clothes in a cheap store. ሁልጊዜ ፡ ልብስ ፡ የምትገዛው ፡ በርካሽ ፡ ከሚሸጥ ፡ መደብር ፡ ነው
5. መናኛ. The radio is made of cheap parts that will wear out. ራዲዮኑ ፡ የተሠራው ፡ በቀላሉ ፡ ከሚያልቁ ፡ መናኛ ፡ እቃዎች ፡ ነው

**cheap** (adv.) በርካሽ ፡ ዋጋ
He is selling his car cheap. መኪናውን ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ ይሸጣል

**cheapen**
1. አበላሸ. She cheapened her dress by adding a fringe to it. ልብሷ ፡ ላይ ፡ ጥለት ፡ ቀጥላ ፡ አበላሸችው

2. ዝቅተኛ ፡ ግምት ፡ አሰጠ. Constant swearing cheapened him. ስድብ ፡ ካፉ ፡ ስለማይጠፋ ፡ ዝቅተኛ ፡ ግምት ፡ አሰጠው

**cheat** (vt.) አታለለ
He cheated me in the agreement I made with him. ከሱ ፡ ጋር ፡ ባደረግሁት ፡ ስምምነት ፡ አታሎኛል

**cheat** (vi.) አጭበረበረ ፤ ሰረቀ
He is always cheating in exams. ሁልጊዜ ፡ ፈተና ፡ ላይ ፡ ያጭበረብራል ፡ (ይሰርቃል)

**cheat someone out of** አጭበርብሮ ፡ ወሰደበት
He cheated him out of all his money. ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ አጭበርብሮ ፡ ወሰደበት

**cheat** (n.)
1. አታላይ. They all know he is a cheat and a liar. አታላይና ፡ ውሸታም ፡ መሆኑን ፡ ሁሉም ፡ ያውቃሉ
2. (= adj.) ማታለል ፡ የበዛበት. The game was a cheat and cost him $50. ማታለል ፡ የበዛበት ፡ ቁማር ፡ ስለሆነ ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ አጠፋ

**cheater** አታላይ
Cheaters will be punished. አታላዮች ፡ ይቀጣሉ

**cheating** ማጭበርበር ፤ ቅጥፈት ፤ ማታለል
The student compromised his good name by cheating. ተማሪው ፡ በማጭበርበር ፡ ጥሩ ፡ ስሙን ፡ አጠፋው
Cheating got him into a mess. ቅጥፈት ፡ ጣጣ ፡ ውስጥ ፡ ከተተው
What is your attitude toward cheating? ስለማታለል ፡ ያለህ ፡ አስተያየት ፡ ምንድነው ?

**check** (vt.)
1. መረመረ. Will you please check the bill once more? ሒሳቡን ፡ ደግመህ ፡ መርምረው
2. ምልክት ፡ አደረገ(በት). The teacher checked the correct answers. መምህሩ ፡ ትክክል ፡ የሆኑትን ፡ መልሶች ፡ ምልክት ፡ አደረገባቸው
3. አጣራ. Check the figures carefully! ሒሳቡን ፡ በጥንቃቄ ፡ አጣራ
The Bible concordance is very useful in checking words. የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የቃላት ፡ ዝርዝር ፡ ቃላትን ፡ ለማጣራት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው
4. አየ(ለት). Please check the oil! እባክህ ፡ ዘይቱን ፡ እይልኝ
5. አስቀመጠ. Check your hat and coat here! ባርኔጣህንና ፡ ኮትህን ፡ እዚህ ፡ አስቀምጥ
6. አገደ. We have checked the enemy's advance. ጠላት ፡ ወደኛ ፡ የሚያደርገውን ፡ መግፋት ፡ አግደነዋል
The vaccine checked the spread of the disease. ክትባቱ ፡ በሽታው ፡ እንዳይሰራጭ ፡ አገደ
7. ገታ. I advise you to check your anger. ንዴትህን ፡ እንድትገታ ፡ እመክርሃለሁ

**check** (vi.) ተስማማ
Our figures check with his. የኛ ፡ ሒሳብ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ይስማማል

**check in** ገባ
When did he check in at the hotel? ከሆቴሉ ፡ የገባው ፡ መቼ ፡ ነው ?

**check off** ምልክት ፡ አደረገ
He checked off the items as they were called out. የእቃዎቹ ፡ ስም ፡ ሲጠራ ፡ ምልክት ፡ አደረገ

**check (on)**
1. አጣራ. We have to check on his statement. ቃሉን ፡ ማጣራት ፡ አለብን
2. ተቈጣጠረ. Don't forget to check on his work! የሚሠራውን ፡ መቈጣጠር ፡ ችላ ፡ እንዳትል

**check out** ለቆ ፡ ወጣ
You have to check out by 10 A.M. እስከ ፡ ጧቱ ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ለቀህ ፡ መውጣት ፡ አለብህ

**check through** በቀጥታ ፡ ላከ
I will check my bags through to Chicago. ሻንጣዎቼን ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ቺካጎ ፡ እልካለሁ

**check** (n.)
1. ቼክ. I will send you a check tomorrow. ነገ ፡ ቼክ ፡ እልክልሃለሁ
2. ሒሳብ. When we finished eating, I asked the waiter for the check. በልተን ፡ ስናበቃ ፡ ሠራተኛው ፡ ሒሳብ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ጠየቅሁት
3. ምልክት. The teacher put a check beside the correct answer. በትክክለኛው ፡ መልስ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አስተማሪው ፡ ምልክት ፡ አደረገ
4. ቲኬት. Show your trunk check when you want your trunk. ሣጥንህን ፡ ለመውሰድ ፡ ስትፈልግ ፡ የሣጥንህን ፡ ቲኬት ፡ አሳይ
5. መቈጣጠሪያ. The increase of duty is an effective check on imports. የቀረጥ ፡ መጨመር ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የሚገቡ ፡ ነገሮችን ፡ ለመቈጣጠሪያ ፡ ጥሩ ፡ ዘዴ ፡ ነው
6. አራት ፡ ማእዘን ፡ ቅርጽ. The checks in this dress are big. በዚህ ፡ ቀሚስ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ ቅርጾች ፡ ትልልቅ ፡ ናቸው
*High tariffs act as a check to trade. ከፍተኛ ፡ ቀረጥ ፡ ንግድን ፡ ያዳክማል

**make a quick check** በፍጥነት ፡ ፈተሸ
We made a quick check, but found nothing missing. በፍጥነት ፡ ፈትሸን ፡ ምንም ፡ የጐደለ ፡ ነገር ፡ አላገኘንም

**put a check to** አቆመ
We must put a check to so much tardiness. ይህን ፡ ዘግይቶ ፡ መምጣት ፡ ማቆም ፡ አለብን

**checkbook** የቼክ ፡ ደብተር
As it happens, I have my checkbook with me. እንዲጋጣሚ ፡ የቼክ ፡ ደብተር ፡ ይዣለሁ

**checkered**
1. ልዩ ፡ ልዩ. Winston Churchill enjoyed a checkered career. ዊንስተን ፡ ቸርችል ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራ ፡ ዘርፍ ፡ ተካፍለዋል
2. አራት ፡ ማእዘን ፡ ቅርጽ ፡ ያለበት. This checkered fabric is attractive. ይህ ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ ቅርጽ ፡ ያለበት ፡ ጨርቅ ፡ ያምራል

**checkers** ዳማ
Do you play checkers? ዳማ ፡ ትጫወታለህ ?

**checkup** ምርመራ
I went to the doctor for a checkup. ለምርመራ ፡ ወደ ፡ ዶክተሩ ፡ ሄድኩ

**cheek** ጉንጭ
My cheek is all swollen. ጉንጬ ፡ በጣም ፡ አብጧል
[See also 'bloodless']

**cheer** (vt.)
1. በእልልታና ፡ በጭብጨባ ፡ ተቀበለ. The exuberant crowd cheered the Emperor. በደስታ ፡ የተሞላው ፡ ሕዝብ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ በእልልታና ፡ በጭብጨባ ፡ ተቀበሏቸው
2. በደስታ ፡ አጨበጨበ(ለት). The crowd cheered the speaker. ሰዎቹ ፡ ተናጋሪውን ፡ በደስታ ፡ አጨበጨቡለት
3. አደነቀ. The audience rose bodily to cheer the hero. አድማጩ ፡ ጀግናውን ፡ ለማድነቅ ፡ ባንድነት ፡ ብድግ ፡ አለ
4. (= intr.) ተደሰተ. It cheered the old woman to have us visit her. አሮጊቷ ፡ እኛ ፡ ስለጠየቅናቸው ፡ በጣም ፡ ተደሰቱ

**cheer** (vi.)
1. በደስታ ፡ ጮኸ. The crowd cheered. የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ በደስታ ፡ ጮኸ
2. ደስታውን ፡ ገለጸ. The students cheered with abandon waving their arms. እጃቸውን ፡ በማወዛወዝ ፡ ተማሪዎቹ ፡ በኃለ ፡ ስሜት ፡ ደስታቸውን ፡ ገለጹ

**cheer on** አደፋፈረ
She cheered him on when he was about to give up. ተስፋ ፡ ሊቈርጥ ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ አደፋፈረችው

**cheer up** (vt.) አጽናና ፤ አበረታታ
We visit her often to cheer her up. ለማጽናናት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንጠይቃታለን
His periodic visits cheered up the ill. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሊጠይቃቸው ፡ መሄዱ ፡ ሕመምተኞቹን ፡ አበረታታ

**cheer up** (vi.) ተጽናና ፤ ደስ ፡ አለ(ው)
He cheered up at once when I promised to help him. እንደምረዳው ፡ ተስፋ ፡ ስሰጠው ፡ ወዲያው ፡ ተጽናና ፡ (ደስ ፡ አለው)

**cheer up!** አይዞህ
Cheer up, he will be back soon! አይዞህ ፤ ቶሎ ፡ ይመለሳል !

**cheer** (n.) ደስታ
The song brings cheer to my heart. መዝሙሩ ፡ ልቤን ፡ በደስታ ፡ ይሞላዋል

**cheers**
1. የደስታ ፡ ጩኸት. We could hear the cheers from quite a distance. የደስታውን ፡ ጩኸት ፡ ከሩቅ ፡ እንሰማ ፡ ነበር
2. እልልታና ፡ ጭብጨባ. The crowd greeted the President with cheers. የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ፕሬዚዳንቱን ፡ በእልልታና ፡ በጭብጨባ ፡ ተቀበለው
3. ማበረታታት. The cheers of the crowd reanimated the losing team. የተመልካቾቹ ፡ ማበረታታት ፡ ለተሸናፊው ፡ ቡድን ፡ አዲስ ፡ ኀይል ፡ ሰጠው

**be of good cheer!** በርታ
Be of good cheer! Things could be much worse. በርታ ! የባሰ ፡ ነገር ፡ ሊመጣም ፡ ይችላል

**cheerful**
1. አስደሳች. This sunny room is cheerful. ይህች ፡ ፀሐይ ፡ የሚገባት ፡ ክፍል ፡ አስደሳች ፡ ናት
2. ፍልቅልቅ ፤ ደስተኛ. She is a smiling, cheerful girl. ፈገግ ፡ የምትል ፡ ፍልቅልቅ ፡ ልጅ ፡ ናት
After all her suffering, she is still cheerful. ያ ፡ ሁሉ ፡ መንሳቀል ፡ ቢደርስባትም ፡ አሁንም ፡ ደስተኛ ፡ ትመስላለች

**be cheerful** ደስ ፡ አለ(ው)
He heard good news today and is very cheerful. አስደሳች ፡ ወሬ ፡ ስለሰማ ፡ ዛሬ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎታል
[See also 'disposition']

**cheerless** ቀፋፊ
It was a cheerless day, dark and rainy. ጭለማና ፡ የሚዘንም ፡ ቀፋፊ ፡ ቀን ፡ ነበር

**cheery** አስደሳች
Sunshine and the singing of birds are cheery.

የፀሐይ ፡ ብርሃንና ፡ የወፎች ፡ ዝማሬ ፡ አስደሳ ች ፡ ናቸው

**cheese** አይብ ፤ ፎርማጆ
The farm sells a lot of cheese. የርሻው ፡ ማቤ ያ ፡ ብዙ ፡ አይብ ፡ (ፎርማጆ) ፡ ይሸጣል

**chemical** የኬሚካል ፡ ቅመም
The two chemicals interact. ሁለቱ ፡ የኬሚካል ፡ ቅመሞች ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ተጽዕኖ ፡ አለው

**chemistry** ኬሚስትሪ

**cherish**
1. ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ሰጠ. Our grandmother cherishes her childhood memories. አያታችን ፡ የል ጅነት ፡ ጊዜ ፡ ትዝታዋን ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ት ሰጠዋለች
2. አንከባከበ. A mother cherishes her baby. እናት ፡ ልጇን ፡ ታንከባክባለች

**cherish the hope** በተስፋ ፡ ጠበቀ
The old woman cherished the hope of her son's return. አሮጊቷ ፡ የልጇን ፡ መመለስ ፡ በተስፋ ፡ ጠበቀች

**cherry** [የፍሬ ፡ ዓይነት]

**cherub** ኪሩቤል
A cherub is one of the holy angels. ኪሩቤ ል ፡ ከቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡ ነው

**chess** ሰንጠረዥ
I like to play chess. ሰንጠረዥ ፡ መጫወት ፡ እወ ዳለሁ

**game of chess** ሰንጠረዥ
Would you like to play a game of chess? ሰንጠረዥ ፡ እንጫወት ?

**chest**
1. ደረት. He was hit in the chest by a bullet. ደረቱ ፡ በጥይት ፡ ተመታ
2. ሰንዱቅ. Put the tools in the chest! መሣሪያዎ ቹን ፡ በሰንዱቅ ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጥ

**chestnut** [የለውዝ ፡ ዓይነት]

**chest of drawers** ባለመሳቢያ ፡ ቁም ፡ ሣጥን
He placed the chest of drawers in the hall. ባለመሳቢያ ፡ ቁም ፡ ሣጥኑን ፡ መተላለፊያው ፡ መሃል ፡ አደረገው

**chew**
1. አኘከ. Chew your food well! ምግብህን ፡ ደኅ ና ፡ አድርገህ ፡ አኝክ
2. አላመጠ. Girls like to chew chewing gum. ልጃገረዶች ፡ መስቲካ ፡ ማላመጥ ፡ ይወዳሉ

**chew cud** አመነዠከ
A donkey does not chew the cud. አህያ ፡ አ ያመነዥክም

**chew a hole in** በጥርሱ ፡ በሳ
The puppy chewed a hole in my slipper. ቡችላዋ ፡ ነጠላ ፡ ጫማዬን ፡ በጥርሷ ፡ በሳችው

**chew over in one's mind** አውጥቶ ፡ አውርዶ ፡ አሰበ(በት)
He chewed the problem over in his mind. ጉዳዩን ፡ አውጥቶ ፡ አውርዶ ፡ አሰበበት

**chewing gum** መስቲካ
Don't stick your chewing gum on my seat! መስቲካህን ፡ ከመቀመጫዬ ፡ ላይ ፡ አትለጥፍ

**chick** ጫጩት
The hawk carried away the chick. ጭልፊት ፡ ጫጩት ፡ ወሰደ

**chicken** ዶሮ
They eat a lot of chickens at Easter. የፋሲካ ፡ ለት ፡ ብዙ ፡ ዶሮ ፡ ይበላሉ

**chicken pox** ኩፍኝ
The child has chicken pox. ሕፃኑ ፡ ኩፍኝ ፡ ይዞታል

**chickpea** ሽምብራ

**chide** ገሠጸ
The teacher chided him for being late. ስለዘገየ ፡ አስተማሪው ፡ ገሠጸው

**chief** (n.)
1. አለቃ. The village chiefs assembled to listen to a lecture. ንግግር ፡ ለመስማት ፡ የመ ንደሩ ፡ አለቆች ፡ ተሰበሰቡ
2. ሹም. The various chiefs in the department will discuss the plan. የልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎቻች ን ፡ ሹሞች ፡ ስለ ፡ እቅዱ ፡ ይወያያሉ
3. መሪ. You have to get permission from the chief of the tribe to pass through this land. በዚህ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አቋርጠህ ፡ ለማለፍ ፡ የ ጐሳውን ፡ መሪ ፡ ማስፈቀድ ፡ አለብህ

**chief** (adj.)
1. ዋና. What are the chief exports of Ethiopia? ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የምትልካቸ ው ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነገሮች ፡ ምን ፡ ምን ፡ ናቸው ?
2. የበላይ. They constituted him chief advisor. የበላይ ፡ አማካሪ ፡ አድርገው ፡ ሾሙት
3. ታላቅ. He is the chief poet of our time. በጊዜያችን ፡ ታላቁ ፡ ባለቅኔ ፡ እሱ ፡ ነው

**in chief** ዋና
The editor-in-chief writes the leading article. ዋናው ፡ አዘጋጅ ፡ ዓቢዩን ፡ ጽሑፍ ፡ ይጽፋል

**chiefly**
1. አብዛኛው. Candy is made chiefly of sugar. ከረሜላ ፡ የሚሠራው ፡ አብዛኛው ፡ ከስኳር ፡ ነው
2. በተለይ. We visited Washington chiefly to see the White House. ዋሽንግተንን ፡ የጐበኘነው ፡ በተለይ ፡ ዋይት ፡ ሃውስን ፡ ለማየት ፡ ነው

**child** (children) ልጅ
They took the child along on the trip. ልጁን ፡ ይዘው ፡ ተጓዙ
*I have been used to it ever since I was a child. ከልጅነቴ ፡ ጀምሬ ፡ የለመድኩት ፡ ነው

**be with child** አረገዘች
The woman is obviously with child. ሴትዮዋ ፡ በእርግጥ ፡ አርግዛለች
[See also 'conceive, heavy, illegitimate, only, problem']

**childbearing** ልጅ ፡ መውለጃ
Her childbearing period is over. ልጅ ፡ መውለጃዋ ፡ ዘመን ፡ አልፏል

**childbed** አራስ ፡ ቤት
She will be in childbed for several days. ለብዙ ፡ ቀናት ፡ አራስ ፡ ቤት ፡ ትቆያለች

**childbirth**
1. ልጅ ፡ መውለድ. Childbirth is painful for women. ልጅ ፡ መውለድ ፡ ለሴቶች ፡ ሥቃይ ፡ ነው
2. ምጥ. His wife had a difficult childbirth. ባለቤቱ ፡ ምጥ ፡ ጸንቶባት ፡ ነበር

**in childbirth** ልጅ ፡ የሚወለድበት ፡ ጊዜ
In childbirth, women pray for Mary's help. ልጅ ፡ የሚወለድበት ፡ ጊዜ ፡ ሴቶች ፡ ማርያምን ፡ እርዳታ ፡ ይለምናሉ

**childhood** የልጅነት ፡ ጊዜ ፤ ልጅነት
I spent my childhood in the country. የልጅነት ፡ ጊዜዬን ፡ ባገር ፡ ቤት ፡ አሳለፍኩት
I have a dreary recollection of my childhood. የልጅነት ፡ ትዝታዬ ፡ የማያስደስት ፡ ነው

**childish** ሕፃን ፤ እንደ ፡ ሕፃን
He is an adult with a childish manner. ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ሕፃን ፡ ነው
Don't be so childish! እንደ ፡ ሕፃን ፡ አትሁን

**be childish** ሕፃን ፡ መሆን ፡ ነው
Crying for things you cannot get is childish. ማግኘት ፡ ለማትችለው ፡ ነገር ፡ ማልቀስ ፡ ሕፃን ፡ መሆን ፡ ነው

**childlike** እንደ ፡ ሕፃን
His childlike frankness wins the heart of everybody. እንደ ፡ ሕፃን ፡ የዋህ ፡ መሆኑ ፡ የማንኛቸውንም ፡ ሰው ፡ ልብ ፡ ይማርካል

**children**, see **child**

**child welfare** የሕፃናት ፡ በጎ ፡ አድራጎት
I am interested in child welfare. ለሕፃናት ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ስሜት ፡ አለኝ

**chill** (vt.)
1. አቀዘቀዘ. Please chill the fruit! ፍራፍሬውን ፡ አቀዝቅዘው
The wind chilled her. ነፋሱ ፡ አቀዘቀዛት
2. አስቈረጠ. The news chilled his hopes. ዜናው ፡ ተስፋውን ፡ አስቈረጠው

**chill** (vi.) ቀዘቀዘ
The earth chills when the sun sets. ፀሐይ ፡ ስትጠልቅ ፡ መሬት ፡ ትቀዘቅዛለች

**chill** (n.) ብርድ
He suffers from recurrent chills and fever. ብርድና ፡ ትኩሳት ፡ እያገረሸ ፡ ያስቸግረዋል
The chill of the evening is not good for your health. የምሽት ፡ ብርድ ፡ ለጤንነት ፡ ጥሩ ፡ አይደለም

**cast a chill**
*His entrance cast a chill over everyone in the room. በሱ ፡ መምጣት ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ መንፈስ ፡ ቀዘቀዘ

**get a chill**
I got a chill. ብርድ ፡ ብርድ ፡ አለኝ

**chilly** ቀዝቃዛ
I dislike chilly rooms. ቀዝቃዛ ፡ ክፍል ፡ እጠላለሁ
We were given a chilly reception. ቀዝቃዛ ፡ አቀባበል ፡ አደረጉልን

**be chilly** በረደ
It is chilly outside. ውጪ ፡ ይበርዳል

**chime** (v.) ጮኸ
The bells chimed at noon. በቀትር ፡ ላይ ፡ ደወል ፡ ጮኸ

**chime in** ተስማማ
The new building will not chime in with the surrounding architecture. አዲሱ ፡ ሕንጻ ፡ ባካባቢው ፡ ካሉት ፡ ጋር ፡ አይስማማም
*As the other men were talking, Mr. Jones kept chiming in with his comments. ሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ በሚነጋገሩበት ፡ ጊዜ ፡ ሚስተር ፡ ጆንስ ፡ ጣልቃ ፡ እየገባ ፡ አስተያየት ፡ ይሰጥ ፡ ነበር

**chimerical**
*He has chimerical schemes for getting rich. ሀብታም ፡ ለመሆን ፡ የማይደረስበት ፡ እቅድ ፡ አለው

**chimney** የጪስ ፡ ማውጫ
This house has a chimney. ይህ ፡ ቤት ፡ የጪስ ፡ ማውጫ ፡ አለው

**chimpanzee** [የዝንጀሮ ፡ ዓይነት]

**chin** አገጭ
He has a beard on his chin. ከአገጩ ፡ ላይ ፡ ጢም ፡ አለው
**chin up!** አይዞህ
Chin up! Things will get better. አይዞህ ፤ ሁሉም ፡ ነገር ፡ እየተሻሻለ ፡ ይሄዳል

**China** ቻይና
China has a great many people. ቻይና ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አላት

**china** የሸክላ ፡ ሳሕን
China is made from white clay. የሸክላ ፡ ሳሕን ፡ የሚሠራው ፡ ከነጭ ፡ ሸክላ ፡ ነው

**Chinese** (n.)
1. ቻይናዊ. There are few Chinese in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂት ፡ ቻይናውያን ፡ አሉ
2. ቻይንኛ. Chinese is a difficult language. ቻይንኛ ፡ ከባድ ፡ ቋንቋ ፡ ነው

**Chinese** (adj.) የቻይና
Chinese civilization differs from ours. የቻይና ፡ ባህል ፡ ከኛ ፡ ይለያል

**chink** ክፍት ፡ ቦታ
They sealed the chinks between the logs. ከግንዶቹ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ በጭቃ ፡ ደፈኑት

**chip** (chipped), vt. ሸረፈ
The maid chipped the edge of the bottle. ገረዲቱ ፡ የጠርሙሱን ፡ አፍ ፡ ሸረፈችው
He chipped a piece of stone off the statue. ከሐውልቱ ፡ ላይ ፡ ድንጋይ ፡ ሸረፈ
**chip** (vi.) ተሸራረፈ
The cups chip if they are not handled carefully. በጥንቃቄ ፡ ካልተያዙ ፡ ሲኒዎቹ ፡ ይሸራረፋሉ
**chip in** አዋጣ
We all chipped in to buy her a present. ስጦታ ፡ ልንገዛላት ፡ ሁላችንም ፡ አዋጣን

**chip** (n.)
1. ስብርባሪ. The chips of the cup fell to the floor. የሲኒው ፡ ስብርባሪ ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ወደቀ
2. ፍቅፋቂ. The ground is covered with wood chips. መሬቱ ፡ በዕንጨት ፡ ፍቅፋቂ ፡ ተሸፍኗል
**have a chip** ተሸረፈ
This glass has a chip. ይህ ፡ ብርጭቆ ፡ ተሸርፏል
**have a chip on one's shoulder** ነጭናጫ ፡ ሆነ
She always has a chip on her shoulder, so nobody wants to be with her. ነጭናጫ ፡ ስለ ሆነች ፡ ማንም ፡ ሊቀርባት ፡ አይፈልግም
**when the chips are down** ቁርጠኛው ፡ ጊዜ ፡ ሲመጣ
When the chips are down, he proves to be a loyal friend. ቁርጠኛው ፡ ጊዜ ፡ ሲመጣ ፡ ታማኝ ፡ ጓደኝነቱ ፡ አያጠራጥርም

**chirp** ጭውጭው ፡ አለ
The birds chirp toward evening. ወደ ፡ ማታ ፡ ጊዜ ፡ ወፎች ፡ ጭውጭው ፡ ይላሉ

**chisel** (v.) ቀረጸ
He chiseled a statue from the stone. ከድንጋዩ ፡ ሐውልት ፡ ቀረጸ

**chisel** (n.) መሮ
He made a hole in the board with a chisel. ሳንቃውን ፡ በመሮ ፡ በሳው

**chit-chat** ተራ ፡ ወሬ
The discussion was nothing important, just chit-chat. ንግግሩ ፡ ምንም ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ አልነበረውም ፤ ተራ ፡ ወሬ ፡ ነበር

**chock-full**
*He had a briefcase chock-full of papers. ወረቀት ፡ የታጨቀበት ፡ ቦርሳ ፡ ነበረው

**chocolate** ቸኮላታ
Is this chocolate sweet or bitter? ይህ ፡ ቸኮላታ ፡ ጣፋጭ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ መራራ ?

**choice**
1. ምርጫ. There is a wide choice of colors. ብዙ ፡ የቀለም ፡ ዓይነት ፡ ምርጫ ፡ አለ
You made a good choice in picking that new man. ያንን ፡ አዲሱን ፡ ሰውዬ ፡ በመምረጥህ ፡ ጥሩ ፡ ምርጫ ፡ አድርገሃል
2. የሚመረጥ. These flowers are the choice of my garden. እነዚህ ፡ አበባዎች ፡ ከትክልት ፡ ስፍራዬ ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ የሚመረጡ ፡ ናቸው
3. አመራረጥ. Her mother takes a dim view of her choice of clothes. እናቲቱ ፡ ስለ ፡ ልጅቷ ፡ ልብስ ፡ አመራረጥ ፡ ቅር ፡ ትሰኛለች
4. (= to choose) መምረጥ. I will leave the choice of a movie to you. ሲኒማውን ፡ መምረጡን ፡ ላንተ ፡ እተዋለሁ
**fine choice of** ምርጥ ፡ የሆነ
This restaurant has a fine choice of wines. ይህ ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ ምርጥ ፡ የሆነ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ አለው

**have no choice about**
*The child has no choice about going to school. ልጁ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ ግዴታው ፡ ነው

**make a choice** መረጠ
You made a good choice. ጥሩ ፡ መርጠሃል

**choicest** ምርጥ
The choicest food had the highest price. ምርጡ ፡ ምግብ ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ነበረው

**choir** የመዝሙር ፡ ጓድ
He sings in the choir. በመዝሙሩ ፡ ጓድ ፡ ውስጥ ፡ ይዘምራል

**in a choir** በኅብረት
The priests sing in a choir. ካህናቱ ፡ በኅብረት ፡ ያዜማሉ

**choke** (vt.)
1. አነቀ. My shirt is choking me because its collar is tight. ሸሚዜ ፡ አንገቱ ፡ ጠባብ ፡ ስለሆነ ፡ ያንቀኛል
2. አዳፈነ. Too much wood will choke a fire. ዕንጨት ፡ ሲበዛ ፡ እሳቱን ፡ ያዳፍነዋል
3. አፈነ. The thick smoke choked the firemen. ጥቅጥቅ ፡ ያለው ፡ ጢስ ፡ የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካዮችን ፡ አፈናቸው

**choke** (vi.)
1. ታነቀ. The boy choked with laughter. ልጁ ፡ በሣቅ ፡ ታነቀ
2. (= tr.) አነቀ. +I choked on a piece of meat. የሥጋ ፡ ቁራጭ ፡ አነቀኝ

**be choked** ሞላ
The storeroom was choked with furniture, luggage and boxes. የእቃ ፡ ቤቱን ፡ የቤት ፡ እቃ ፤ ሻንጣና ፡ ሣጥን ፡ ሞልቶታል

**choke back** ዋጠ
She choked back the tears. እንባዋን ፡ ዋጠችው

**choke to death** አንቆ ፡ ገደለ
He choked the dog to death. ውሻውን ፡ አንቆ ፡ ገደለው

**cholera** [የወረርሽኝ ፡ በሽታ ፡ ዓይነት]

**choose** (chose, chosen)
1. መረጠ. I chose the books carefully. መጽሐፎቹን ፡ በጥንቃቄ ፡ መረጥኩ
They chose him for their leader. መሪያቸው ፡ እንዲሆን ፡ መረጡት
2. ፈለገ. She did not choose to go with us. ከኛ ፡ ጋር ፡ ለመሄድ ፡ አልፈለገችም
3. አሻ(ው). +Do as you choose! እንዳሻህ ፡ አድርግ

**choosy** መራጭ
Don't be so choosy! እጅግ ፡ መራጭ ፡ አትሁን

**chop** (chopped)
1. ፈለጠ ፤ ቈረጠ. Did you chop some wood? ጥቂት ፡ ዕንጨት ፡ ፈለጥህ ? (ቈረጥህ?)
2. ከተፈ. The cook chopped some meat for the stew. ወጥ ፡ ቤቱ ፡ ለወጥ ፡ ሥጋ ፡ ከተፈ

**chop down** ቈረጠ
They chopped the dead tree down. የደረቀውን ፡ ዛፍ ፡ ቈረጡት

**chop off** ቈረጠ
Be careful you don't chop your finger off. ጣትህን ፡ እንዳትቈርጥ ፡ ተጠንቀቅ

**chop up** ከተፈ (ተከተፈ)
Meat is often chopped up before it is cooked. ሥጋ ፡ ከመቀቀሉ ፡ በፊት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ይከተፋል

**chopped meat** ክትፎ
Chopped meat is the dish I like best. በጣም ፡ የምወደው ፡ ምግብ ፡ ክትፎ ፡ ነው

**choppy** ተለዋዋጭ
A choppy wind is not good for small boats. ተለዋዋጭ ፡ ነፋስ ፡ ለትናንሽ ፡ ጀልባዎች ፡ አይመችም

**make choppy** አናወጠ
A strong wind made the lake choppy. ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ሐይቁን ፡ አናወጠው

**choral** (= adv.) በኅብረት
Choral singing is characteristic of worship in some churches. በኅብረት ፡ መዘመር ፡ ያንዳንድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ልማድ ፡ ነው

**chord**
*His story struck a chord of pity in the listeners. ታሪኩ ፡ ያድማጮቹን ፡ ልብ ፡ ነካ

**chore**
1. የሚያስለች ፡ ሥራ. Scrubbing frying pans is a chore for her. መጥበሻዎችን ፡ መፈተግ ፡ ለሷ ፡ የሚያስለች ፡ ሥራ ፡ ነው
2. የዘወትር ፡ ሥራ. All the children had to do their chores. ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ የዘወትር ፡ ሥራቸውን ፡ መሥራት ፡ ነበረባቸው
3. ሥራ. Let's make a bargain to help each with our chores! በሥራችን ፡ ለመረዳዳት ፡ እንስማማ

**chorus**
1. የመዝሙር ፡ ጓድ. They formed a chorus in the school. በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የመዝሙር ፡ ጓድ ፡ አቋቋሙ
2. ባንድነት ፡ መጮኽ. The speaker was answered by a chorus of approving shouts.

ሕዝቡ ፡ ባንድነት ፡ በመጮኽ ፡ ለተናጋሪው ፡
የመስማማት ፡ መልስ ፡ ሰጠው

**chose,** see **choose**

**chosen,** see **choose**

**chrestomathy** [ከሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ የተውጣጡ ፡
ጽሑፎች]

**christen**
1. አጠመቀ. The priest christened four children
last Sunday. ባለፈው ፡ እሑድ ፡ ቄሱ ፡ አራት ፡
ልጆች ፡ አጠመቀ
2. የክርስትና ፡ ስም ፡ አለ. We christened our
baby, Yohannes. የልጃችንን ፡ የክርስትና ፡ ስም ፡
ዮሐንስ ፡ አልነው
3. ሰየመ. They christened the farm "Stony
Brook". እርሻቸውን ፡ ስቶኒ ፡ ብሩክ ፡ ብለው ፡
ሰየሙት

**christening** ክርስትና
The baby's christening will be next Sunday.
የሕፃኑ ፡ ክርስትና ፡ በሚቀጥለው ፡ እሑድ ፡ ነው

**Christian** ክርስቲያን
Christians used to be known for their charity.
ክርስቲያኖች ፡ በልግስናቸው ፡ የታወቁ ፡ ነበሩ

**Christianity** ክርስትና
Christianity was introduced to Ethiopia in the
fourth century. ባራተኛው ፡ መቶ ፡ ክፍለ ፡ ዘመ
ን ፡ ክርስትና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገባ

**(be) Christianized** የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ተ
ቀበለ
That happened before Ethiopia was Christian-
ized. ኢትዮጵያ ፡ የክርስትናን ፡ ሃይማኖት ፡ ከ
መቀበሏ ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ነው

**Christmas** ገና
Christmas is celebrated in Ethiopia in January.
በኢትዮጵያ ፡ ገና ፡ የሚከበረው ፡ በታኅሣሥ ፡ ነው
[See also 'merry']

**chronic**
1. ልማደኛ. She is a chronic complainer.
ልማደኛ ፡ ነዝናዣ ፡ ነች
2. ሥር ፡ የሰደደ. He has a chronic cough.
ሥር ፡ የሰደደ ፡ ሳል ፡ አለበት

**chronicle** ዜና ፡ መዋዕል
A chronicle is a kind of history. ዜና ፡ መዋዕል ፡
የታሪክ ፡ ዓይነት ፡ ነው

**chronology**
*The teacher explained to the students the
chronology of events leading to the French
Revolution. መምህሩ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳይ ፡ መሠረ
ታዊ ፡ ለውጥ ፡ ያመሩትን ፡ ተከታታይ ፡ ሁኔታ
ዎች ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ለተማሪዎቹ ፡ አስ
ረዳ

**(be) chubby** ፋፋ
The baby was chubby. ሕፃኑ ፡ የፋፋ ፡ ነበር

**chuckle** ሣቅ ፡ አለ
He chuckled over the joke. በቀልዱ ፡ ሣቅ ፡ አለ

**chug** ድምፅ
You could hear the chug of an engine. የሞተሩ
ን ፡ ድምፅ ፡ ለመስማት ፡ ይቻላል

**chunk**
1. ቁራጭ. The dog found a chunk of meat.
ውሻው ፡ የሥጋ ፡ ቁራጭ ፡ አገኘ
2. ስባሪ. I found a chunk of stone stuck in
my tire. የድንጋይ ፡ ስባሪ ፡ ጎማዬ ፡ ላይ ፡ ተሰክ
ቶ ፡ አገኘሁ

**church**
1. ቤተ ፡ ክርስትያን. We went to church on Sun-
day. እሑድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄድን
2. ደብር (pl. አድባር). This priest is new to our
church. ይህ ፡ ቄስ ፡ ለደብራችን ፡ እንግዳ ፡ ነው
3. ሃይማኖት. Most people adhere to the church
of their parents. አብዛኛዎቹ ፡ ሰዎች ፡ የወላጆ
ቻቸውን ፡ ሃይማኖት ፡ ይከተላሉ
4. የሃይማኖት ፡ ድርጅት. A missionary goes
wherever the church sends him. ተጓዥ ፡ ሰባኪ ፡
የሃይማኖቱ ፡ ድርጅት ፡ እላከው ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡
ይሄዳል
5. የሃይማኖት ፡ ወገን. The two churches have
been incorporated into one. ሁለቱ ፡ የሃይማኖት ፡
ወገኖች ፡ ተዋሕደዋል
6. ቅዳሴ. What time does church begin?
ቅዳሴ ፡ በስንት ፡ ይገባል ?

**church** (adj.) የቤተ ፡ ክህነት
The conservatives and the clergy were allied
on the question of church schools. ለውጥ ፡ የ
ማይፈልጉትና ፡ ቀሳውስቱ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡
ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ጉዳይ ፡ ተስማምተው ፡ ነበር

**go to church** ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሳመ
They go to church every Sunday. እሑድ ፡ እሑ
ድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይስማሉ

**marry in church** በተክሊል ፡ አገባ
Were you married in church? ያገባኸው ፡ በተ
ክሊል ፡ ነው ?
[See also 'rite, service']

**churchman** የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካህን
The apostate from Islam later became a famous churchman. የእስላም ፡ ሃይማኖትን ፡ የከዳው ፡ ሰው ፡ በኋላ ፡ የታወቀ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካህን ፡ ሆነ

**churchyard** የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግቢ
There is a cemetery in the churchyard. በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ መካን ፡ መቃብር ፡ አለ

**churn** (v.) ናጠ
Churn the milk to make butter! ቅቤ ፡ እንዲወጣው ፡ ወተቱን ፡ ናጠው

**churn** (n.) መናጫ
Butter is beginning to form in the churn. በመናጫው ፡ ውስጥ ፡ ቅቤ ፡ መውጣት ፡ በመጀመር ፡ ላይ ፡ ነው

**cider** የቱፋ ፡ ጭማቂ

**cigar** ሲጋር

**cigarette** ሲጃራ

**cigarette holder** ፒፓ
She uses a cigarette holder when she smokes. እርሷ ፡ ስታጨስ ፡ በፒፓ ፡ ትጠቀማለች

**cinder** አመድ
The wood was burned to a cinder. ዕንጨቱ ፡ አመድ ፡ እስኪሆን ፡ ነደደ

**cinema** ሲኒማ
I'll go to the cinema. ወደ ፡ ሲኒማ ፡ እሄዳለሁ

**cinnamon** ቀረፋ
Cinnamon is used to flavor food. ቀረፋ ፡ ለምግብ ፡ ማጣፈጫ ፡ ይጠቅማል

**circa** ገደማ
Mohammed was born circa 570 A.D. መሐመድ ፡ የተወለደው ፡ ፭፻፸ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ገደማ ፡ ነው

**circle** (vt.)
1. በ --- ዙሪያ ፡ መሥመር ፡ አሠመረ. Circle the correct answer on the exam paper! በፈተናው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ በትክክለኛው ፡ መልስ ፡ ዙሪያ ፡ መሥመር ፡ አሥምር
2. (= intr.) ዞረ. The moon circles the earth. ጨረቃ ፡ በመሬት ፡ ዙሪያ ፡ ትዞራለች
3. ከበበ. The enemy circles the hill. ጠላት ፡ ኮረብታውን ፡ ከቦታል
4. በ --- ዙሪያ ፡ አለፈ. He circled Chicago to save an hour's driving time. ያንድ ፡ ሰዓት ፡ መንገድ ፡ ለማዳን ፡ በቺካጎ ፡ ዙሪያ ፡ አለፈ

**circle** (vi.)
1. ዞረ. The plane circled a half hour before landing. አውሮፕላኑ ፡ ከማረፉ ፡ በፊት ፡ ግማሽ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ዞረ
2. በማንጃበብ ፡ ዞረ. The airplane is circling over the town. አውሮፕላኑ ፡ በከተማው ፡ ላይ ፡ በማንጃበብ ፡ ይዞራል

**circle** (n.) ክበብ
He drew a circle in the sand. በአሸዋው ፡ ላይ ፡ ክበብ ፡ ሣለ
*He has a wide circle of friends. ወዳጆቹ ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ናቸው

**circles**
*Diplomatic circles agree that war with China must be avoided. ከቻይና ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ እንዳይነሣ ፡ መጠንቀቅ ፡ እንደሚገባ ፡ የፖለቲካ ፡ ሰዎች ፡ ይስማማሉ

**around in a circle** ዙሪያውን
We drove around in a circle. ዙሪያውን ፡ ነዳን
[See also 'commercial circle, inner, narrow, vicious']

**circuit**
1. ዙሪያ. The circuit of the city walls is three miles. የከተማው ፡ ግምብ ፡ ዙሪያ ፡ ሦስት ፡ ማይል ፡ ነው
2. ዑደት. Every year, the earth completes its circuit of the sun. መሬት ፡ በፀሐይ ፡ ዙሪያ ፡ የምታደርገውን ፡ ዑደት ፡ ለመጨረስ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ይፈጅባታል
3. መሥመር. The telephone circuit was broken during the storm. የስልኩ ፡ መሥመር ፡ በማዕበሉ ፡ ወቅት ፡ ተበጠሰ

**circular**
1. ክብ. Ancient coins were not circular in shape. የጥንት ፡ ገንዘቦች ፡ ቅርጻቸው ፡ ክብ ፡ አልነበረም
2. የሚጠመዛዘዝ. A circular stairway leads up to the balcony. የሚጠመዛዘዘው ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ሰገነቱ ፡ ያወጣል
3. ዙሪያ ፡ ጥምጥም. Circular arguments are ineffective. ዙሪያ ፡ ጥምጥም ፡ ክርክሮች ፡ ውጤት ፡ አይሰጡም

**circular letter** ሰርኩላር
All departments received a circular letter today. ሁሉም ፡ ክፍሎች ፡ ዛሬ ፡ ሰርኩላር ፡ ደረሳቸው

**circular motion** መዞር
The circular motion of the earth is still not completely understood. የመሬት ፡ መዞር ፡ ገና ፡ ተጣርቶ ፡ አልታወቀም

**circulate** (vt.)

1. አሰራጨ. He circulated the news of the holiday. የዓመት ፡ በዓሉን ፡ ወሬ ፡ አሰራጨ
2. አስተላለፈ. He circulated the letter among the students. ደብዳቤውን ፡ ለተማሪዎች ፡ አስተላለፈ
He circulated counterfeit money and got caught. የሐሰት ፡ ገንዘብ ፡ አስተላልፎ ፡ ተያዘ

**circulate** (vi.)
1. ተዘዋወረ. This causes the blood to circulate faster. ይህ ፡ ደም ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ እንዲዘዋወር ፡ ያደርጋል
2. ተሰራጨ. Bad news circulates quickly. መጥፎ ፡ ወሬ ፡ በፍጥነት ፡ ይሰራጫል
3. ነፈሰ. There is a strange rumor circulating. እንግዳ ፡ የሆነ ፡ ጭምጭምታ ፡ ይነፍሳል
*She circulated among her guests. እንግዶቿን ፡ እየተዘዋወረች ፡ አስተናገደች

**circulation**
1. መዘዋወር. Open windows increase the circulation of air. የመስኮቶች ፡ ክፍት ፡ መሆን ፡ የአየር ፡ መዘዋወርን ፡ ይጨምራል
A tight armband interferes with circulation of the blood. የጠበቀ ፡ የክንድ ፡ ላይ ፡ እስር ፡ የደምን ፡ መዘዋወር ፡ ያውካል
2. አንባቢዎች. Our paper has a circulation of a hundred thousand. ጋዜጣችን ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ አንባቢዎች ፡ አሉት
*He suffers from poor circulation. ደሙ ፡ በደንብ ፡ ስለማይዘዋወር ፡ ያመዋል

**put into circulation** አወጣ
The government has put new bills into circulation. መንግሥት ፡ አዲስ ፡ ገንዘብ ፡ አውጥቷል

**(be) withdrawn from circulation**
This book has been withdrawn from circulation. መጽሐፉ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዳይደርስ ፡ ተከልክሏል

**circumcise** ገረዘ (ተገረዘ)
The man circumcised the boy. ሰውዬው ፡ ሕፃኑን ፡ ገረዘ
Girls are also circumcised in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ልጃገረዶችም ፡ ይገረዛሉ

**circumcision** ግርዘት ፤ ግዝረት
Circumcision has been practiced in Ethiopia since ancient times. ግርዘት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የተለመደ ፡ ነው

**circumference** ዙሪያ
The circumference of our swimming pool is 70 feet. የመዋኛ ፡ ቦታችን ፡ ዙሪያው ፡ ሰባ ፡ ጫማ ፡ ነው

**circumlocution** ዙሪያ ፡ ጥምጥም ፡ ንግግር
He used circumlocution to avoid using some words. ባንዳንድ ፡ ቃላት ፡ እንዳይጠቀም ፡ በማለት ፡ ዙሪያ ፡ ጥምጥም ፡ ንግግር ፡ ይናገር ፡ ነበር

**circumnavigate** በ - - - ዙሪያ ፡ ተጓዘ
This ship circumnavigates the earth. ይህ ፡ መርከብ ፡ በዓለም ፡ ዙሪያ ፡ ይጓዛል

**circumscribe**
1. ወሰነ (ተወሰነ). The father circumscribed the activities of his daughter. አባትዬው ፡ ልጅቷ ፡ ማድረግ ፡ የሚገባትን ፡ ወሰነ
A prisoner's activities are circumscribed. የእስረኛው ፡ ተግባሮች ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው
2. ነደፈ. The teacher circumscribed the city on the map. መምህሩ ፡ ከተማይቱን ፡ ካርታ ፡ ላይ ፡ ነደፈ

**circumspect** ጥንቁቅ
A judge must be circumspect when he makes a judgment. ዳኛ ፡ ፍርድ ፡ ሲሰጥ ፡ ጥንቁቅ ፡ መሆን ፡ አለበት

**circumstance**
1. ነገር. There is one important circumstance you haven't mentioned. ያልጠቀስከው ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ አለ
Weather and other circumstances permitting, we sail on Monday. አየሩና ፡ ሌላውም ፡ ነገር ፡ ከተስማማን ፡ ሰኞ ፡ በመርከብ ፡ እንነሣለን
2. ሁኔታ. Under those circumstances, I could hardly blame her. በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ምንም ፡ ልወቅሳት ፡ አልችልም
3. አኳኋን. The rich man is in good circumstances. ሀብታሙ ፡ ሰው ፡ በጥሩ ፡ አኳኋን ፡ ይኖራል
4. አጋጣሚ. His arrival is a fortunate circumstance. የሱ ፡ መድረስ ፡ መልካም ፡ አጋጣሚ ፡ ነው
5. ጥቃቅን ፡ ጉዳዮች. The author dwells on circumstances rather than essentials. ደራሲው ፡ መሠረታዊ ፡ ከሆኑት ፡ ይልቅ ፡ በጥቃቅን ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ሐተታ ፡ ያበዛል

**under no circumstances** በምንም ፡ ምክንያት ፤ በምንም ፡ ዓይነት
Under no circumstances should you go to see him. በምንም ፡ ምክንያት ፡ (በምንም ፡ ዓይነት) ፡ ሄደህ ፡ እሱን ፡ መገናኘት ፡ የለብህም

**under the circumstances** አሁን ፡ ባለው ፡ ሁኔታ
Under the circumstances, there is little hope

for an early settlement. አሁን ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ በቅርቡ ፡ ዕርቅ ፡ የማድረግ ፡ ተስፋ ፡ እጅግም ፡ ነው

**circumstantial**

1. አጋጣሚ. Minor details are circumstantial compared with the main facts. ከዋናው ፡ ጉዳይ ፡ ጋር ፡ ሲመዛዘኑ ፡ ዝርዝሮቹ ፡ ነገሮች ፡ አጋጣሚዎች ፡ ናቸው
2. ሰፊ. The policeman gave a circumstantial report of the accident. ፖሊሱ ፡ ስለደረሰው ፡ አደጋ ፡ ሁኔታ ፡ ሰፊ ፡ ሪፖርት ፡ አቀረበ

**circumstantiate** አረጋገጠ
He produced documents to circumstantiate his statement. ቃሉን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሰነድ ፡ አቀረበ

**circumvent**

1. በዘዴ ፡ አመለጠ. Some people try to circumvent the law. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከሕግ ፡ በዘዴ ፡ ለማምለጥ ፡ ይሞክራሉ
2. በዘዴ ፡ አከሸፈ. The colonel circumvented the plan of the enemy to blow up the bridge. ጠላት ፡ ድልድይ ፡ በፈንጂ ፡ ለማፍረስ ፡ የነበረውን ፡ እቅድ ፡ ኮሎኔሉ ፡ በዘዴ ፡ አከሸፈው
3. በዘዴ ፡ አለፈ. The speaker carefully circumvented the real issue. ተናጋሪው ፡ በልዩ ፡ ዘዴ ፡ ዋናውን ፡ ነገር ፡ አለፈው

**circus** ሰርከስ

**cistern** የውኃ ፡ ማጠራቀሚያ
The cisterns of the city were dry. የከተማው ፡ የውኃ ፡ ማጠራቀሚያዎች ፡ ደርቀዋል

**citadel** ምሽግ
The enemy conquered the citadel. ጠላት ፡ ምሽጉን ፡ ያዘ

**citation**

1. ጥቅስ. Citations from Scriptures are used in sermons. ከቅዱሳን ፡ መጻሕፍት ፡ የተወሰዱ ፡ ጥቅሶች ፡ በስብከት ፡ ላይ ፡ ይነገራሉ
2. የምስጋና ፡ ወረቀት. He received a citation from the President for bravery in war. በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ላሳየው ፡ ጀግንነት ፡ ከፕሬዚዳንቱ ፡ የምስጋና ፡ ወረቀት ፡ ተቀበለ
3. መጥሪያ. A traffic ticket for speeding is a citation. ከመጠን ፡ በላይ ፡ በመንዳት ፡ ምክንያት ፡ ከትራፊክ ፡ የሚሰጠው ፡ ካርኒ ፡ መጥሪያ ፡ ነው

**cite** ጠቀሰ
He cited the Bible to prove his statement. ያለውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ጠቀሰ
The lawyer cited another case similar to the one being tried. ጠበቃው ፡ አሁን ፡ ከሚታየው ፡ ነገር ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰል ፡ ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ጠቀሰ

**be cited (for)**

1. ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርብ ፡ ታዘዘ. He was cited for bad brakes. የተበላሸ ፡ ፍሬን ፡ አለው ፡ በመባል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርብ ፡ ታዟል
2. ስሙ ፡ በክብር ፡ ተጠራ. The soldier was cited for bravery. ወታደሩ ፡ ስለ ፡ ጀግንነት ፡ ስሙ ፡ በክብር ፡ ተጠራ

**citizen**

1. ዜጋ. I am an American citizen. እኔ ፡ የአሜሪካ ፡ ዜጋ ፡ ነኝ
2. የሀገሪቱ ፡ ነዋሪ. The observance of the law is required by all citizens. የሀገሪቱ ፡ ነዋሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ሕግን ፡ እንዲያከብሩ ፡ ይገደዳሉ

**citizenship** ዜግነት
One must fulfill the obligations of citizenship. ማንም ፡ ሰው ፡ የዜግነትን ፡ ግዴታ ፡ መፈጸም ፡ አለበት

**citron** [የሎሚ ፡ ዓይነት]

**city** ከተማ
The municipality is in charge of the city's attractiveness. ለከተማው ፡ ውበት ፡ ኀላፊ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ነው

**city hall** ማዘጋጃ ፡ ቤት
City hall has given bids for construction of a hospital. ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ሆስፒታል ፡ ለማሠራት ፡ ጨረታ ፡ አውጥቷል

**civet** ዝባድ
Civet is very expensive. ዝባድ ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ ነው

**civet cat** ጥርኝ
It is forbidden to kill civet cats. ጥርኝ ፡ መግደል ፡ ተከልክሏል

**civic**

1. ሕዝባዊ ፤ የዜግነት. Obeying the law and paying taxes are civic duties. ሕግን ፡ ማክበርና ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ ሕዝባዊ ፡ ግዴታዎች ፡ ናቸው
They understood their civic duties. የዜግነት ፡ ተግባራቸውን ፡ ተገነዘቡ
2. የከተማ. The mayor is making great efforts for civic beauty. ከንቲባው ፡ ለከተማው ፡ ውበት ፡ በጣም ፡ ያስባል

**civil**

1. ሕዝባዊ. Civil liberties are guaranteed by the constitution. ሕዝባዊ ፡ መብቶች ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው

2. ሲቪል. Post offices are part of the civil service of the government. የፖስታ ፡ አስተዳደር ፡ የሲቪል ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ነው
3. ትሑት. He is always civil to everyone he meets. ለሚያገኛቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ትሑት ፡ ነው

**civil rights** የሰው ፡ ልጆች ፡ መብት
He is in the forefront of the civil rights movement. ስለ ፡ ሰው ፡ ልጆች ፡ መብት ፡ በሚደረገው ፡ ንቅናቄ ፡ እሱ ፡ ግምባር ፡ ቀደም ፡ ነው
[See also 'marriage, service']

**civil code** የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ
The present civil code was adopted several years ago. ያሁኑ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ

**civilian** (n.) ሲቪል
There were civilians and soldiers in the crowd. በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ሲቪሎችና ፡ ወታደሮች ፡ ነበሩ

**civilian** (adj.) የሲቪል
Was he wearing civilian clothes? የለበሰው ፡ የሲቪል ፡ ልብስ ፡ ነበር ?

**civility** ትሕትና
He treats his customers with civility. ደንበኞቹን ፡ በትሕትና ፡ ያስተናግዳል

**civilization**
1. ሥልጣኔ. The civilization of mankind has taken thousands of years to reach its present level. የሰው ፡ ልጅ ፡ ሥልጣኔ ፡ አሁን ፡ ካለበት ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ ብዙ ፡ ሺ ፡ ዓመታት ፡ ወስዷል
2. ባህል. Chinese civilization differs from ours. የቻይና ፡ ባህል ፡ ከኛ ፡ ይለያል
3. ምቾት ፡ ያለበት ፡ ኑሮ. After a week in the woods, the scouts looked forward to civilization again. እስካውቶች ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ምቾት ፡ ወዳለበት ፡ ኑሮ ፡ ለመመለስ ፡ ጓጉ

**civilize** አሠለጠነ
School helps to civilize people. ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሕዝብን ፡ ለማሠልጠን ፡ ይረዳል

**civilized** (adj.)
1. የሠለጠነ. The civilized world must fight ignorance. የሠለጠነው ፡ ዓለም ፡ ድንቁርናን ፡ ማጥፋት ፡ አለበት
2. መልካም. Civilized behavior is found in all countries. መልካም ፡ ጠባይ ፡ በየአገሩ ፡ ይገኛል

**civil law** የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ
Loans are decided by civil law. የገንዘብ ፡ ብድር ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ይወሰናል

**civil servant** የመንግሥት ፡ ሠራተኛ
Civil servants retire at sixty-five. የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በስድሳ ፡ አምስት ፡ ዓመታቸው ፡ ጡረታ ፡ ይገባሉ

**civil war** የርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት
The country was torn by civil war. አገሪቱ ፡ በርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ተገነጣጥላ ፡ ነበር

**clack** (v.)
1. አጋጨ. He clacked the cup against the saucer. ሲኒውን ፡ ከማስቀመጫው ፡ ጋር ፡ አጋጨው
2. ቋ ፡ ቋ ፡ አለ. Her heels clacked on the pavement. ተረከዟ ፡ አስፋልቱ ፡ ላይ ፡ ቋ ፡ ቋ ፡ አለ

**(be) clad** ለበሰ
He was clad in red. ቀይ ፡ ልብስ ፡ ለብሷል

**claim** (v.)
1. ፈለገ. I claim my share. ድርሻዬን ፡ እፈልጋለሁ
2. ጠየቀ. Where do I claim my baggage? ሻንጣዬን ፡ የት ፡ ልጠይቅ ?
3. የኔ ፡ ነው ፡ አለ. Does anyone claim the pencil? እርሳሱ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ አለ ?
4. አለ. She claims to know the man. ሰውዬውን ፡ አውቀዋለሁ ፡ ትላለች
5. ወሰደ. The care of the baby claims much of mother's time. ሕፃኑን ፡ መከባከብ ፡ የእናቱን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይወስዳል
*This matter claims our attention. ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ ልናስብበት ፡ ይገባናል

**claim** (n.)
1. ይገባኛል ፡ የተባለ. He refuted the claim. ይገባኛል ፡ የተባለውን ፡ አስተባበለ
2. ይገባኛል ፡ ማለት. He relinquished his claim to the throne. ዙፋኑ ፡ ይገባኛል ፡ ማለትን ፡ ተወ
3. የሚለው ፡ ነገር. Can you make good your claim? የምትላቸውን ፡ ነገሮች ፡ ልታረጋግጥ ፡ ትችላለህ ?
4. መብት. He forbore his claim. መብቱን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ
5. ጥያቄ. The International Court of Justice allowed the Ethiopian claim. የዓለም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥያቄ ፡ ተቀበለ

**file a claim**
1. ክስ ፡ አቀረበ. He filed a claim in order to recover damages to his car. በመኪናው ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ካሳ ፡ ለማግኘት ፡ ክስ ፡ አቀረበ
2. ይገባኛል ፡ ሲል ፡ አመለከተ. The farmer filed a claim for a piece of land. ገበሬው ፡ መሬቱ ፡ ይገባኛል ፡ ሲል ፡ አመለከተ

**have a claim on**
*She has a claim on us because she is my mother's sister. አክስታችን ፡ ስለሆነች ፡ ከኛ ፡ ሊ ታገኝ ፡ የሚገባት ፡ ድርሻ ፡ አለ

**lay claim**
1. ይገባኛል ፡ አለ ፤ የኔ ፡ ነው ፡ አለ. A distant relative laid claim to the estate. የሩቅ ፡ ዘመ ድ ፡ ርስቱ ፡ ይገባኛል ፡ አለ
I lay no claim to that. ያ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ አላል ኩም
2. አለ. I have never laid claim to being an expert in geography. የጂኦግራፊ ፡ ዐዋቂ ፡ ነኝ ፡ ብዬ ፡ አላውቅም

**make a claim to** የኔ ፡ ነው ፡ አለ
She makes a claim to the pencil. እርሳሱ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ትላለች

**make no claim to**
*He made no claim to being an expert in history. የታሪክ ፡ ዐዋቂ ፡ ነኝ ፡ የማለት ፡ ስሜት ፡ አላሳየም
[See also 'satisfy, stake')

**claimant** ይገባኛል ፡ ባይ
He is a claimant in the affair. በጉዳዩ ፡ ይገባኛ ል ፡ ባይ ፡ ነው

**clamber up** በከባድ ፡ ትግል ፡ ወጣ
The boys clambered up the cliff. ልጆቹ ፡ ገደሉ ን ፡ በከባድ ፡ ትግል ፡ ወጡ

**clamor** (v.) በጩኸት ፡ አሰማ
They clamored their demands at the meeting. ፍላጎታቸውን ፡ በስብሰባው ፡ ላይ ፡ በጩኸት ፡ አሰሙ

**clamor for**
1. ብሎ ፡ ጮኸ. The foolish people clamored for war. ሞኞች ፡ ሰዎች ፡ ጦር ፡ አምጣ ፡ ብለው ፡ ጮኹ
2. ብሎ ፡ ተንጫነጨ. The child clamored for his breakfast. ልጁ ፡ ቁርስ ፡ ስጡኝ ፡ ብሎ ፡ ተንጫነጨ

**clamor** (n.)
1. ሁከት. There was a clamor in the market place. ገበያው ፡ ውስጥ ፡ ሁከት ፡ ነበር
2. ጩኸት. The clamor of the dissenting members broke up the meeting. የተቃዋሚዎቹ ፡ ጩ ኸት ፡ ስብሰባውን ፡ በተነው
3. የተገለጸ ፡ ስሜት. The senators could not ignore the clamor against higher taxation. የታክስን ፡ መጨመር ፡ በመቃወም ፡ የተገለጸውን ፡ ስሜት ፡ አማካሪዎቹ ፡ ችላ ፡ ሊሉት ፡ አልቻሉም

**set up a clamor** ተንጫጫ
The eager children set up a clamor to get into the movie house. ለማየት ፡ የጓጉት ፡ ል ጆች ፡ ወደ ፡ ሲኒማ ፡ ቤት ፡ ለመግባት ፡ ይንጫጩ ፡ ነበር

**clamp** የብረት ፡ ማጣበቂያ
He held the two pieces of wood together with a clamp. ሁለቱን ፡ ዕንጨቶች ፡ በብረት ፡ ማጣበቂያ ፡ አያያዛቸው

**clan** ወገን
This clan descends from a common ancestor. ይህ ፡ ወገን ፡ ካንድ ፡ ቅድማያት ፡ ይወለዳል

**clandestine** የምስጢር
They held a clandestine meeting. የምስጢር ፡ ስብሰባ ፡ አደረጉ

**clank** ተቃጨለ
His fetters clanked when he moved. ሲንቀሳቀስ ፡ የእግር ፡ ብረቱ ፡ ተቃጨለ

**clap** (clapped), vt.
1. አጨበጨበ. He clapped his hands to summon the servant. አሽከሩን ፡ ለመጥራት ፡ አጨበጨበ
2. መታ ፡ መታ ፡ አደረገ. He clapped his friend on the back. ወዳጁን ፡ ጀርባው ፡ ላይ ፡ መታ ፡ መታ ፡ አደረገው

**clap** (vi.)
1. አጨበጨበ. The audience clapped for five minutes after the play was over. ቲያትሩ ፡ ከተ ፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ተመልካቹ ፡ ለአምስት ፡ ደቂ ቃ ፡ አጨበጨበ
2. ተንኳኳ. The shutters clapped in the wind. የሳንቃ ፡ መከለያ ፡ በነፋስ ፡ ተንኳኳ

**clarify** (clarified), vt.
1. አብራራ. He tried to clarify his statement. ንግግሩን ፡ ለማብራራት ፡ ሞከረ
2. አጣራ. She washed her hands in preparation for clarifying the hydromel. ብርዙን ፡ ለማጣራ ት ፡ እጇን ፡ ታጠበች

**clarify (vi.)** ግልጽ ፡ ሆነ
He was certain that the political situation would eventually clarify. የፖለቲካው ፡ ሁኔታ ፡ እያደር ፡ ግልጽ ፡ እንደሚሆን ፡ እርግጠኛ ፡ ነበር

**clarinet** [ዋሽንት ፡ ብጤ ፡ መሣሪያ]

**clarity** (= adj.) ግልጽ
His clarity of speech makes him a good teacher. ግልጽ ፡ አነጋገሩ ፡ ጥሩ ፡ መምህር ፡ ያደርገዋል

**with clarity** ግልጽ ፡ ሆኖ
The problem was presented with clarity, and

everyone understood it. ጉዳዩ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ስለቀረበ ፡ ሁሉም ፡ ሰው ፡ ተረዳው

**clash** (vt.)
1. አጋጨ. In her haste, she clashed the pan against the stove. ቸኩላ ፡ መጥበሻውን ፡ ከምድጃው ፡ ጋር ፡ አጋጨችው
2. አፋጨ. They clashed their swords. ጐራዴዎቻቸውን ፡ አፋጩ።

**clash** (vi.)
1. ተጋጨ. The armies clashed on the plain. ሰራዊቶቹ ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ተጋጩ።
The employee clashed with his boss over salary. ሠራተኛው ፡ በደሞዝ ፡ ምክንያት ፡ ከለቃው ፡ ጋር ፡ ተጋጨ
2. ተቃረነ. Their stories of the accident completely clashed. ስለ ፡ አደጋው ፡ የቀረቡት ፡ መግለጫዎች ፡ ፍጹም ፡ የሚቃረኑ ፡ ነበሩ

**clash with** አልተስማማም
The color of the curtains clashes with the carpet. የመጋረጃው ፡ ቀለም ፡ ከስጋጃው ፡ ቀለም ፡ ጋር ፡ አይስማማም

**clash** (n.)
1. ግጭት. The clash between the workers and the factory owner led to a strike. በሠራተኞቹና ፡ በፋብሪካው ፡ ባለቤት ፡ መካከል ፡ የተነሣው ፡ ግጭት ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ማቆም ፡ አደረሰ
There was a border clash yesterday. ትላንትና ፡ የወሰን ፡ ግጭት ፡ ነበረ
2. ድምፅ. The automobiles collided with a terrible clash. መኪናዎቹ ፡ ሲጋጩ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ ተሰማ

**clasp** (v.)
1. ያዘ. He clasped a knife in his hand. ጩቤ ፡ በእጁ ፡ ይዟል
2. አቀፈ. She clasped the child to her bosom. ሕፃኑን ፡ ደረቷ ፡ ላይ ፡ አቀፈችው

**clasp hands** እጅ ፡ ለጅ ፡ ተጨባበጡ
They clasped hands as a sign of friendship. ለወዳጅነታቸው ፡ ምልክት ፡ እጅ ፡ ለጅ ፡ ተጨባበጡ

**clasp** (n.) መያዣ
He rummaged through his drawers looking for a tie clasp. የከራቫት ፡ መያዣውን ፡ ለመፈለግ ፡ መሳቢያዎችን ፡ በረበረ

**give a clasp**
*He gave my hand a warm clasp. ሞቅ ፡ ያለ ፡ አጨባበጥ ፡ ጨበጠኝ

**class** (v.) መደበ
He classed Churchill among the world's greatest men. ቸርችልን ፡ ከዓለም ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ መደባቸው

**class** (n.)
1. ትምህርት. Classes begin in September. ትምህርት ፡ የሚጀመረው ፡ በመስከረም ፡ ነው
2. የክፍል ፡ ጊዜ. My first class starts at eight-thirty. የመጀመሪያ ፡ የክፍል ፡ ጊዜዬ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ይጀምራል
3. የትምህርት ፡ ዓይነት. How many classes did you have the first semester? በመጀመሪያው ፡ የትምህርት ፡ ዘመን ፡ አጋማሽ ፡ ስንት ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ ነበሩህ ?
4. ተማሪዎች. The class had arrived on time for the lecture. ተማሪዎቹ ፡ ንግግሩን ፡ ለማዳመጥ ፡ በጊዜው ፡ ደረሱ
5. ማዕረግ. We went second class. በሁለተኛ ፡ ማዕረግ ፡ ተሳፈርን
6. የኅብረ ፡ ሰብ ፡ ክፍል. In America there is a strong middle class. በአሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ መካከለኛ ፡ ገቢ ፡ ያለው ፡ ኀይለኛ ፡ የኅብረ ፡ ሰብ ፡ ክፍል ፡ አለ
7. ፍጹምነት. She is a good performer, but she lacks class. ጥሩ ፡ ተዋናይ ፡ ናት ፡ ሆኖም ፡ ፍጹምነት ፡ ይጐድላታል
*Ras Imru has a high standing among the educated class of Ethiopians. ራስ ፡ እምሩ ፡ በተማሩት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ ትልቅ ፡ ግምት ፡ አላቸው

**hold class** አስተማረ
It is to no purpose to hold class the day before Christmas. ለልደት ፡ ዋዜማ ፡ ለማስተማር ፡ መሞከር ፡ እንዲያው ፡ ነው

**take a class (in)** ክፍል ፡ ገባ
I am taking a class in English. እንግሊዝኛ ፡ ክፍል ፡ እገባለሁ

**classic** ዓይነተኛ
The building is a classic example of modern architecture. ሕንጻው ፡ ለዘመናዊ ፡ የሕንጻ ፡ አሠራር ፡ ዓይነተኛ ፡ ምሳሌ ፡ ነው

**classical** የጥንት ፡ ሮምና ፡ ግሪክ
This is a map of the classical world. ይህ ፡ የጥንት ፡ ሮምና ፡ ግሪክ ፡ ካርታ ፡ ነው

**classical language** የሚጻፍበት ፡ ቋንቋ
The speech was written in the vernacular and not the classical form of the language. ንግግሩ ፡ የተጻፈው ፡ ሁልጊዜ ፡ በሚነገርበት ፡ ቋንቋ ፡ እንጂ ፡ በሚጻፍበት ፡ ቋንቋ ፡ አልነበረም

**classics** [የጥንት ፡ ሮማውያንና ፡ ግሪኮች ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ]

**classification** ድልድል
The classification now in use requires revision. አሁን ፡ የሚሠራበት ፡ ድልድል ፡ መሻሻል ፡ ያስፈልገዋል

**classify** (classified)
1. ለየየ. He classified the objects according to size, weight, and color. እቃዎቹን ፡ እንደየመጠናቸው ፡ እንደየክብደታቸው ፡ እንደየቀለማቸው ፡ ለያያቸው
2. መደበ. He classified the students according to their ability. ተማሪዎቹን ፡ እንደየችሎታቸው ፡ መደባቸው
3. በምስጢር ፡ ያዘ. The government classified the report on the new plane. መንግሥት ፡ ስለ ፡ አዲሱ ፡ አውሮፕላን ፡ ያለውን ፡ መግለጫ ፡ በምስጢር ፡ ያዘ

**classmate** የክፍል ፡ ጓደኛ
He surpasses his classmates in strength and skill. በጥንካሬና ፡ በችሎታ ፡ የክፍል ፡ ጓደኞቹን ፡ ይልቃል

**classroom** ክፍል
The teacher is still in the classroom. አስተማሪው ፡ እስካሁን ፡ እክፍል ፡ ነው

**clatter** (vt.) አንኳኳ
The cook is in the kitchen clattering the pots and pans. ወጥ ፡ ቤቷ ፡ ማድቤት ፡ ውስጥ ፡ ማሰሮዎቹንና ፡ መጥበሻዎቹን ፡ ታንኳኳለች

**clatter** (vi.)
1. ተንገጫገጨ. The bus clattered down the bumpy road. አውቶቡሱ ፡ በአባጣ ፡ ጐርባጣ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ይንገጫገጫል
2. ለፈለፈ. She clattered on and on about her children. ስለ ፡ ልጆቿ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ለፈለፈች
3. (= tr.) አርገበገበ. +The shutters clattered in the wind. የሳንቃ ፡ መከለያዎችን ፡ ነፋሱ ፡ አርገበገባቸው
4. ተቅጨለጨለ. When I run, the coins clatter in my pocket. ስሮጥ ፡ እኪሴ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ፍራንክ ፡ ይቅጨለጨላል

**clatter** (n.) ውካታ
The clatter of the mob in the streets alarmed us. በመንገድ ፡ ላይ ፡ የሕዝቡ ፡ ውካታ ፡ አስደነገጠን

**clause**
1. አንቀጽ. There is a clause in my contract which allows me a month's vacation. በውለታዬ ፡ ውስጥ ፡ ያንድ ፡ ወር ፡ ዕረፍት ፡ የሚፈቅድልኝ ፡ አንቀጽ ፡ አለ
2. ሐረግ. The main clause has the verb at the end. ዓቢይ ፡ ሐረግ ፡ ግሱ ፡ ከመጨረሻ ፡ ላይ ፡ ነው

**clavicle** ብራኳ
The clavicle joins the shoulder to the backbone. ብራኳ ፡ ትከሻንና ፡ አከርካሪትን ፡ ያያይዛል

**claw** (v.) በጥፍር ፡ ያዘ
The cat clawed the mouse. ድመቷ ፡ አይጡን ፡ በጥፍር ፡ ያዘች

**claw** (n.) ጥፍር
The hawk had a mouse in its claws. ጭልፊቷ ፡ አይጢን ፡ በጥፍሯ ፡ ይዛታለች

**clay** ሸክላ ፤ ጭቃ
The pot is made of clay. እንስራው ፡ ከሸክላ ፡ የተሠራ ፡ ነው
He worked the clay into a vase. ጭቃውን ፡ የአበባ ፡ ማስቀመጫ ፡ እንዲሆን ፡ ሠራው

**clean** (vt.)
1. ጠረገ. Has the maid cleaned the room yet? ገረዲቷ ፡ ገና ፡ ክፍሉን ፡ አልጠረገችም ?
I have got to clean my shoes. ጫማዬን ፡ መጥረግ ፡ አለብኝ
2. ወለወለ. We still have to clean the windows. ገና ፡ መስኮቶቹን ፡ መወልወል ፡ አለብን
3. አጸዳ. Clean the house before he comes! ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ ቤቱን ፡ አጽጂ
4. ፋቀ. I have to clean my teeth. ጥርሴን ፡ መፋቅ ፡ አለብኝ

**clean** (vi.) ተጸዳ
This kind of fabric cleans easily. ይህ ፡ ዓይነት ፡ ጨርቅ ፡ በቀላሉ ፡ ይጸዳል

**clean out**
1. በረበረ. He cleaned out his pockets, but could not find the ticket stub. ኪሶቹን ፡ በረበረ ፡ ግን ፡ የካርኒውን ፡ ጉራጅ ፡ ሊያገኝ ፡ አልቻለም
2. ጨረሰ. He had cleaned out his savings. ያጠራቀመውን ፡ ገንዘብ ፡ ጨረሰ

**(be) cleaned out** ተጋባ
This drawer has to be cleaned out. ይህ ፡ መሳቢያ ፡ መጋባት ፡ አለበት

**clean up** (vt.)
1. አጸዳ. The maid cleaned up the house. ገረዲቱ ፡ ቤቱን ፡ አጸዳች
2. አስተካከለ. He burdened me with the responsibility of cleaning up this mess. ይህን ፡ ዝ

ብርቅርቅ ፡ ነገር ፡ እንዳስተካክል ፡ ኀላፊነት ፡ ጫነብኝ

**clean up** (vi.) ተጸዳዳ
I would like to clean up before dinner. ከራት ፡ በፊት ፡ መጸዳዳት ፡ እፈልጋለሁ
[See also 'house']

**clean** (adj.)
1. ንጹሕ ፤ ጽዱ. This plate is not clean. ይህ ፡ ሳሕን ፡ ንጹሕ ፡ (ጽዱ) ፡ አይደለም
Give me a clean sheet of paper! ንጹሕ ፡ ወረቀት ፡ ስጠኝ
The saint has a clean heart. ጻድቁ ፡ ንጹሕ ፡ ልብ ፡ አለው
2. የተስተካከለ. Her face has clean features. ፊቷ ፡ የተስተካከለ ፡ ቅርጽ ፡ አለው
3. (= adv.) በደምብ. A sharp knife makes a clean cut. ስል ፡ ቢላዋ ፡ በደምብ ፡ ይቈርጣል
*The younger people often make a clean break with tradition. ወጣቶች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከባህል ፡ ፈጽሞ ፡ ይወጣሉ

**jump clean** ሳይነካ ፡ ዘለለ.
The horse jumped clean over the fence. ፈረሱ ፡ አጥሩን ፡ ሳይነካ ፡ ዘለለ

**slice clean** በቀላሉ ፡ ቈረጠ ፡ ዘለቀ
The sharp knife sliced clean through the meat. ስለታሙ ፡ ቢላዋ ፡ ሥጋውን ፡ በቀላሉ ፡ ቈረጠ ፡ ዘለቀው

**wash clean** ታጥቦ ፡ ጠራ
This shirt will never wash clean. ይህ ፡ ሸሚዝ ፡ ምንጊዜም ፡ ታጥቦ ፡ አይጠራም
[See also 'lick, slate']

**clean-cut** ሰልካካ
Her clean-cut features make her an artist's model. መልኳ ፡ ሰልካካ ፡ ስለሆነ ፡ ሠዓሊዎች ፡ ሞዴል ፡ አድርገዋታል

**cleaner**
1. የልብስ ፡ ንጽሕና ፡ መስጫ. Do you know a good cleaner around here? በዚህ ፡ አካባቢ ፡ ጥሩ ፡ የልብስ ፡ ንጽሕና ፡ መስጫ ፡ ታውቃለህ ?
2. ልብስ ፡ አጣቢ. The cleaner said he couldn't get the spot off my coat. ልብስ ፡ አጣቢው ፡ ኮቴ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጠብታ ፡ ለማስለቀቅ ፡ አልቻልኩም ፡ አለ

**cleaning** መጽዳት
The house needs a good cleaning. ቤቱ ፡ በደንብ ፡ መጽዳት ፡ ያስፈልገዋል

**cleanliness** ንጽሕና
Cleanliness is good for health. ንጽሕና ፡ ለጤና ፡ ጥሩ ፡ ነው

**cleanly** መጸዳዳት ፡ የሚወድ
A cat is a cleanly animal. ድመት ፡ መጸዳዳት ፡ የምትወድ ፡ እንስሳ ፡ ናት

**cleanness** ንጹሕ ፡ መሆን
The cleanness of the boy's room pleased his mother. የልጁ ፡ ክፍል ፡ ንጹሕ ፡ መሆኑ ፡ እናቱን ፡ አስደሰታት

**cleanse** ታጠበ
Cleanse your hands before dinner! ከእራት ፡ በፊት ፡ እጆችህን ፡ ታጠብ

**cleanser** ማጽጃ
They used to use sand as a cleanser. ለማጽጃ ፡ በአሸዋ ፡ ይጠቀሙ ፡ ነበር

**clear** (vt.)
1. ጠረገ. His son cleared the snow from the sidewalk. ልጁ ፡ ከእግረኛው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በረዶውን ፡ ጠረገ
2. አስወገደ. The fan cleared the smoke from the room. ማራገቢያው ፡ ከክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ጢሱን ፡ አስወገደ
3. አስመረመረ. Did you clear customs? እቃህን ፡ በጉምሩክ ፡ ሠራተኞች ፡ አስመርምረሃል ?
4. ባዶ ፡ አስቀረ. One blast of the siren was enough to clear the streets. ሳይረኑ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢጮኽ ፡ መንገዱን ፡ ባዶ ፡ አስቀረው
5. አለፈ. Her serve is so weak that the ball hardly clears the net. አለጋጓ ፡ በጣም ፡ ደካማ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ኳሱ ፡ መረቡን ፡ ላመል ፡ ያልፋል
6. ሳይነካው ፡ አለፈ. The plane barely cleared the trees. አውሮፕላኑ ፡ ሲነሣ ፡ ዛፎቹን ፡ ለጥቂት ፡ ሳይነካቸው ፡ አለፈ
7. አስወጣ. They cleared the courtroom of photographers. ፎቶግራፍ ፡ አንሺዎችን ፡ ሁሉ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ አስወጡ
8. አጋባ. The child cleared his plate. ልጁ ፡ ሳሕኑን ፡ አጋባው
9. መነጠረ. The settlers made a stubborn effort to clear the forest. ሰፋሪዎቹ ፡ ጫካውን ፡ ለመመንጠር ፡ ከባድ ፡ ጥረት ፡ አደረጉ
10. ነጻ ፡ ለቀቀ. The verdict cleared the accused men. ፍርዱ ፡ ተከሳሾቹን ፡ ነጻ ፡ ለቀቃቸው
11. አጣራ. She clears the water by means of a filter. በማጥለያ ፡ ውኃውን ፡ ታጣራለች
12. ተሻገረ. He cleared the ditch with one leap. ቦዩን ፡ ባንድ ፡ ዝላይ ፡ ተሻገረው
13. አተረፈ. He cleared $5,000 on the sale. ከሽያጩ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ አተረፈ
14. (= intr.) ጸደቀ. +The bill cleared the Senate.

የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ በሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጸደቀ
*You must clear your plan with the chairman. እንዳችም ፡ ነገር ፡ ከማድረግህ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ እቅድህ ፡ ከሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ፈቃድ ፡ ተቀበል

**clear** (vi.) አባራ
It rained, and then it cleared. ዘንበና ፡ አባራ

**clear away** (vt.)
1. አነሣ. Ask her to clear away the dishes. ሳሕኑን ፡ እንድታነሣ ፡ ንገራት
2. መነጠረ (ተመነጠረ). Most of Ethiopia's forests have been cleared away. አብዛኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ደን ፡ ተመንጥሯል

**clear away** (vi.) ገፈፈ
When the smoke cleared away, we saw that the house was in ruins. ጭሱ ፡ ሲገፍ ፡ ቤቱ ፡ መደምሰሱን ፡ አየን

**clear of trees** መነጠረ
The farmer will clear the land of trees. ገበሬው ፡ መሬቱን ፡ ይመነጥራል

**clear out** (vt.) አጋባ
Please clear out this closet! ይህንን ፡ ቁም ፡ ሣጥን ፡ አጋባው

**clear out** (vi.) ሸሸ
The police are after you; you'd better clear out. ፖሊሶች ፡ ይከታተሉሃል ፤ ብትሸሽ ፡ ይሻልሃል

**clear (the) table**
Did you clear the table? ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ እቃ ፡ አነሣሣኸው ? (or ገበታውን ፡ አነሣህ ?)

**clear (the) throat** ጉሮሮውን ፡ አጠራ
He cleared his throat several times before he could speak. ከመናገሩ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጉሮሮውን ፡ አጠራ

**clear up** (vt.)
1. አስወገደ. They are trying to clear up the misunderstanding between Poland and Czechoslovakia. በፖላንድና ፡ በቼኮዝሎቫኪያ ፡ መካከል ፡ የተፈጠረውን ፡ አለመግባባት ፡ ለማስወገድ ፡ በመጣር ፡ ላይ ፡ ናቸው
2. በግልጽ ፡ አቀረበ. He changed the report in order to clear up the essential points. ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ጉዳዮች ፡ በግልጽ ፡ ለማቅረብ ፡ ሪፖርቱን ፡ ለወጠው

**clear up** (vi.)
1. ጠራ. The weather has cleared up. ሰማዩ ፡ ጠርቷል
2. አባራ. We can go out when it clears up. ሲያባራ ፡ ልንወጣ ፡ እንችላለን
3. ዳነ(ለት). His wound finally cleared up. በመጨረሻ ፡ ቁስሉ ፡ ዳነለት

**(be) cleared up**
1. ተጣራ. Several matters remain to be cleared up. ብዙ ፡ መጣራት ፡ ያለባቸው ፡ ነገሮች ፡ አሉ
2. ተወገደ. The chaos left by the bombing has only recently been cleared up. በቦምቡ ፡ መፈንዳት ፡ ምክንያት ፡ የደረሰው ፡ ፍርስርስ ፡ የተወገደው ፡ በቅርቡ ፡ ነው

**clear** (adj.)
1. ጥሩ. The water is deep and clear. ውኃው ፡ ጥልቅና ፡ ጥሩ ፡ ነው
2. የጠራ. His voice is very clear over the radio. ድምፁ ፡ በራዲዮን ፡ ሲሰማ ፡ የጠራ ፡ ነው
It is a clear day; let us go on a picnic! ዛሬ ፡ የጠራ ፡ ቀን ፡ ነው ፤ ሽርሽር ፡ እንሂድ
3. ግልጽ. He made a clear statement on the accident. ስለደረሰው ፡ አደጋ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ መግለጫ ፡ ሰጠ
He has a clear voice, and everyone understands him. ድምፁ ፡ ግልጽ ፡ ስለሆነ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ይሰማዋል
*Is the road clear up ahead? ከፊታችን ፡ ያለው ፡ መንገድ ፡ ያሳልፋል ?

**clear** (adv.) በትክክል
The bullet passed clear through the target. ጥይቱ ፡ በትክክል ፡ በዒላማው ፡ ውስጥ ፡ አለፈ

**clear weather** ብራ
We have had clear weather all week. ሳምንቱን ፡ በሙሉ ፡ ብራ ፡ ነበር

**be clear**
1. ታወቀ. It is clear that it is going to rain. እንደሚዘንብ ፡ የታወቀ ነው
2. በግልጽ ፡ ታወቀ. The cause of the last war may never be clear. ያለፈው ፡ ጦርነት ፡ መነሻ ፡ ምክንያቶች ፡ ምንጊዜም ፡ በግልጽ ፡ አይታወቁም
3. ተገላገለ. I wish I were clear of that encumbrance. ከዚያ ፡ ችግር ፡ ብገላገል ፡ እወድ ፡ ነበር
*It is clear from the letter that he is not satisfied. አለመደሰቱን ፡ ደብዳቤው ፡ በግልጽ ፡ ያስረዳል

**be clear about** እርግጠኛ ፡ ነው
I am not quite clear about what you expect me to do. ምን ፡ አድርግ ፡ እንደምትለኝ ፡ እርግጠኛ ፡ አይደለሁም

**be clear on** ገባ(ው)
I am not clear on the speaker's proposal. ተናጋሪው ፡ ያቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ አልገባኝም

**go clear through** በስቶ ፡ ገባ
The bullet went clear through the door. ጥይቱ ፡ መዝጊያውን ፡ በስቶ ፡ ገባ

**(be) in the clear**
*He is now in the clear with the police. አሁን ፡ ከፖሊሶች ፡ ጥርጣሬ ፡ አምልጧል

**keep clear**
*It is hard to keep the desert roads clear of sand. የበረሃውን ፡ መንገዶች ፡ በአሸዋ ፡ ከመሸፈን ፡ ለመከላከል ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**make clear** ገለጸ
Make it clear to him that we will not submit to his demands. የሚጠይቀውን ፡ የማንፈጽም ፡ መሆናችንን ፡ ግለጽለት
[See also 'apprehension, perception, see, sky, steer']

**clearance**
1. ፈቃድ. The plane received clearance from the control tower. አውሮፕላኑ ፡ ከመቈጣጠሪያ ፡ ጣቢያ ፡ ፈቃድ ፡ አገኘ
2. ባዶ ፡ ቦታ. There is not much clearance between the top of the car and the bridge. በመኪናው ፡ አናትና ፡ በድልድዩ ፡ መሀከል ፡ ብዙ ፡ ባዶ ፡ ቦታ ፡ የለም
3. ገላጣ ፡ ቦታ. The house stands in a clearance among the trees. ቤቱ ፡ በዛፎች ፡ መካከል ፡ በሚገኘው ፡ ገላጣ ፡ ቦታ ፡ ነው

**clearance sale** የማጣሪያ ፡ ሽያጭ
They announced a clearance sale this month. በዚህ ፡ ወር ፡ የማጣሪያ ፡ ሽያጭ ፡ መኖሩን ፡ አስታወቁ

**clear-cut**
1. የተረጋገጠ. He has clear-cut ideas about his work. ስለሚሠራው ፡ ሥራ ፡ የተረጋገጠ ፡ ሐሳብ ፡ አለው
2. በቂ. His sale of secrets was a clear-cut example of treachery. ምስጢራዊ ፡ ሰነዶችን ፡ መሸጡ ፡ ለከዳተኝነት ፡ በቂ ፡ ምሳሌ ፡ ነበር
3. ሰልካካ. His face has clear-cut features. ሰልካካ ፡ ፊት ፡ አለው

**clearing** የተመነጠረ ፡ መሬት ፤ ምንጥር
The clearing is now overgrown with bushes. የተመነጠረው ፡ መሬት ፡ (ምንጥሩ) ፡ አሁን ፡ ቁጥቋጦ ፡ ለብሷል

**clearly**
1. በግልጽ ፤ ግልጽ ፡ አድርጎ. The student enunciates his words clearly. ተማሪው ፡ ቃላቱን ፡ በግልጽ ፡ ይናገራል
Please speak clearly! ግልጽ ፡ አድርገህ ፡ ተናገር
2. ፈጽሞ. It is clearly out of question to drop the case. ክሱን ፡ ለመተው ፡ ፈጽሞ ፡ የማይታሰብ ፡ ነው
[See also 'question']

**cleat** ፌሮ
Some shoes have cleats to keep people from slipping. አንዳንድ ፡ ጫማዎች ፡ ሰው ፡ እንዳያንሸራትቱ ፡ ሲባል ፡ ፌሮ ፡ አላቸው

**cleavage** አለመግባባት
There is a cleavage between the two countries concerning duties. በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መሀከል ፡ ስለ ፡ ቀረጥ ፡ አንድ ፡ አለመግባባት ፡ አለ

**cleave** (cleft, or cleaved)
1. ፈለጠ. This knife is sharp enough to cleave a man's head. ይህ ፡ ቢላዋ ፡ የሰው ፡ ጭንቅላት ፡ ለመፍለጥ ፡ በቂ ፡ ስለት ፡ አለው
2. ሰነጠቀ. His blow cleft the log in two. የሱ ፡ ምት ፡ ግንዱን ፡ እሁለት ፡ ሰነጠቀው
The lightning cleft the tree. መብረቁ ፡ ዛፉን ፡ ሰነጠቀው

**cleave a path through** መንጥሮ ፡ መንገድ ፡ አበጀ
The boy scouts cleaved a path through the wilderness. እስካውቶቹ ፡ ጫካውን ፡ መንጥረው ፡ መንገድ ፡ አበጁ

**cleave (to)** ጸና
He cleaves to his belief, and nothing can change his mind. በእምነቱ ፡ ስለሚጸና ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ሐሳቡን ፡ ሊያስለውጠው ፡ አይችልም

**cleaver** [ስለት ፡ ያለው ፡ ባለ ፡ አጭር ፡ እጀታ ፡ መሣሪያ]

**cleft,** see **cleave**

**clemency** ርኅራኄ
The judge showed clemency toward the young prisoner. ዳኛው ፡ ለወጣቱ ፡ እስረኛ ፡ ርኅራኄ ፡ አሳዩ

**clement**
1. ርኅሩኅ. I have never seen a person as clement as my teacher. እንደ ፡ አስተማሪዬ ፡ ርኅሩኅ ፡ ሰው ፡ አላየሁም
2. መልካም. The weather in Harar is clement. የሐረር ፡ አየር ፡ መልካም ፡ ነው

**clench**
1. ጨበጠ. He clenched his fist and shook it in my face. እጁን ፡ ጨብጦ ፡ እየወዘወዘ ፡ ዛተብኝ

2. ነከሰ. He clenched his teeth in pain. በሕመሙ ፡ የተነሣ ፡ ጥርሱን ፡ ነከሰ

**clergy** ቤተ ፡ ክህነት ፤ ካህናት
The clergy makes laws for the faith. ቤተ ፡ ክህነት ፡ የሃይማኖትን ፡ ሕጎች ፡ ትደነግጋለች
The laity and the clergy agreed to hold a counsel. ምእመናኑና ፡ ካህናቱ ፡ ስብሰባ ፡ ለማድረግ ፡ ተስማሙ

**clergyman** ካህን (pl. ካህናት)
Only clergymen are allowed to enter the sanctuary. መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገቡ ፡ የሚፈቀድላቸው ፡ ካህናት ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**clerical** የጸሐፊዎች
Filing is a clerical task. መዝገብ ፡ አያያዝ ፡ የጸሐፊዎች ፡ ሥራ ፡ ነው
**clerical robes** ልብሰ ፡ ተክህኖ
The priest wears clerical robes in the church. ቄሱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ይለብሳል

**clerk**
1. ጸሐፊ. He is a clerk in a big office. ያንድ ፡ ትልቅ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጸሐፊ ፡ ነው
2. ሻጭ. The clerks in this store are very friendly. የዚህ ፡ መደብር ፡ ሻጮች ፡ ሰው ፡ ወዳጆች ፡ ናቸው

**clever**
1. ብልጥ. He is a clever speaker. ብልጥ ፡ ተናጋሪ ፡ ነው
2. ጮሌ. He is a clever businessman. ጮሌ ፡ ነጋዴ ፡ ነው
3. ብልህ. He is a clever man. እሱ ፡ ብልህ ፡ ሰው ፡ ነው
4. ጎበዝ. This student is clever in arithmetic. ይህ ፡ ተማሪ ፡ በቁጥር ፡ ጎበዝ ፡ ነው
5. በዘዴ ፡ የተፈጠረ. These pearls are clever imitations. እነዚህ ፡ ዕንቁዎች ፡ በዘዴ ፡ የተፈጠሩ ፡ ሰው ፡ ሠራሾች ፡ ናቸው
*I wish I were clever enough to make my own clothes. የገዛ ፡ ልብሴን ፡ የመስፋት ፡ ችሎታ ፡ በኖረኝ

**cleverly** በሥርዓት
The plan is cleverly conceived. ፕላኑ ፡ በሥርዓት ፡ የታቀደ ፡ ነው

**click** (vt.) አቃጨለ
He clicked the metal pieces. የብረቱን ፡ ቁራጮች ፡ አቃጨለ
**click** (vi.)
1. ተቀራረበ. They get along in public, but their personalities don't really click. ባደባባይ ፡ ይስማማሉ ፤ እንደ ፡ እውነቱ ፡ ግን ፡ ባሕርያቸው ፡ አይቀራረብም
2. ቂብ ፡ ቂብ ፡ አለ. I heard her heels clicking on the sidewalk. በግረኛ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ስትራመድ ፡ የጫማዋ ፡ ተረከዝ ፡ ቂብ ፡ ቂብ ፡ ሲል ፡ ሰማሁ
**click one's heel**
He clicked his heels and saluted. ጫማዎቹን ፡ አጋጭቶ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠ

**click** (n.) መቃጨል
I could hear the click of the key in the lock. የቁልፉን ፡ መቃጨል ፡ በመቈለፊያው ፡ ጋን ፡ ውስጥ ፡ እሰማ ፡ ነበር

**client**
1. የሚሟገትለት ፡ ሰው. The lawyer presented coherent arguments in favor of his client. ጠበቃው ፡ የሚሟገትለትን ፡ ሰው ፡ የሚደግፍ ፡ የተጣራ ፡ ክርክር ፡ አቀረበ
2. ደንበኛ. The clients of this shop are mostly town people. የዚህ ፡ ሱቅ ፡ ደንበኞች ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የከተማ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው
This lawyer has many clients. ይህ ፡ ጠበቃ ፡ ብዙ ፡ ደንበኞች ፡ አሉት

**cliff** ገደል
There is a high cliff on the mountainside. ከተራራው ፡ ጎን ፡ አንድ ፡ ረዢም ፡ ገደል ፡ አለ

**climate** አየር
The climate here is colder than I expected. እዚህ ፡ አየሩ ፡ ካሰብኩት ፡ በላይ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ነው
**climate of opinion** መንፈስ
There is a favorable climate of opinion among the students. በተማሪዎቹ ፡ መካከል ፡ ስምምነታቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ መንፈስ ፡ አለ
[See also 'temperate']

**climatic** ያየር
Climatic conditions prevent settlement in this region. በዚህ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ለመኖር ፡ ያየሩ ፡ ሁኔታ ፡ አይፈቅድም

**climax** (v.)
*His election climaxed a brilliant career. መመረጡ ፡ የእድገቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ነበር

**climax** (n.)
1. ማከተሚያ. The victory was a climax to a week of fighting. ድሉ ፡ ያንድ ፡ ሳምንት ፡ ውጊያ ፡ ማከተሚያ ፡ ነበር
2. ከፍተኛ ፡ ክፍል. The climax of the play

was the prisoner's escape. የትርእይቱ ፣ ከፍተኛ ፣ ክፍል ፣ የእስረኛው ፣ ማምለጥ ፣ ነበር

**climb** (vt.) ወጣ
The boys climbed the tree. ልጆቹ ፣ ዛፉ ፣ ላይ ፣ ወጡ
I do not like to climb stairs. ደረጃ ፣ መውጣት ፣ አልወድም

**climb** (vi.)
1. ወደ ፣ ላይ ፣ መጠቀ. The plane began to climb rapidly. አውሮፕላኑ ፣ በፍጥነት ፣ ወደ ፣ ላይ ፣ ይመጥቅ ፣ ጀመር
2. ተጓዘ. We had been climbing for hours, but we had not reached the top of the mountain. ይኸው ፣ ለብዙ ፣ ጊዜ ፣ ስንጓዝ ፣ ገና ፣ ተራራው ፣ ጫፍ ፣ አልደረስንም
3. ደረሰ. From a lowly beginning he climbed to occupy the highest position in the country. ከዝቅተኛ ፣ ደረጃ ፣ ተነሥቶ ፣ ባገሪቱ ፣ ውስጥ ፣ ከከፍተኛው ፣ ደረጃ ፣ ደረሰ
4. ተወደደ. After the war, the prices climbed. ከጦርነቱ ፣ በኋላ ፣ የእቃ ፣ ዋጋ ፣ ተወደደ

**climb (down)** ወረደ
The boy climbed down the ladder. ልጁ ፣ ከመሰላሉ ፣ ወረደ

**climb (over)** ዘለለ
The thief climbed over the wall and escaped. ሌባው ፣ በግምቡ ፣ ላይ ፣ ዘሎ ፣ አመለጠ

**climb (up)** ወጣ
Can you climb up a ladder? መሰላል ፣ ላይ ፣ መውጣት ፣ ትችላለህ ?

**climb** (n.) አቀበትን ፣ መውጣት
Our climb took two hours. አቀበቱን ፣ መውጣት ፣ ሁለት ፣ ሰዓት ፣ ወሰደብን

**clinch**
1. አጠበቀ. He clinched the barrel with a band of metal. በርሜሉን ፣ በብንዳ ፣ አጠበቀው
2. ፈጸመ. The salesman clinched the deal and went out to celebrate. አሻሻጩ ፣ የንግዱን ፣ ጉዳይ ፣ ፈጽሞ ፣ ሊደሰት ፣ ሄደ

**cling** (clung), ~ **to**
1. አጥብቆ ፣ ተከተለ. We cling to the belief of our fathers. ያባቶቻችንን ፣ እምነት ፣ አጥብቀን ፣ እንከተላለን
2. አጥብቆ ፣ ያዘ. Despite the unfavorable returns, the candidate clung to the belief that he would be elected. ምንም ፣ እንኳ ፣ የገባው ፣ የምርጫው ፣ ውጤት ፣ የማይደግፈው ፣ ቢሆንም ፣ ተወዳዳሪው ፣ እመረጣለሁ ፣ የሚል ፣ እምነቱን ፣ አጥብቆ ፣ ያዘ
3. ተጠመጠመ. The child clung to its mother. ሕፃኑ ፣ እናቱ ፣ ላይ ፣ ተጠመጠመ
4. ተጣበቀ. The wet paper clung to the glass. እርጥቡ ፣ ወረቀት ፣ መስታወቱ ፣ ላይ ፣ ተጣበቀ

**cling to each other** ተቃቀፉ
The children clung to each other in the dark. በጭለማው ፣ ውስጥ ፣ ልጆቹ ፣ ተቃቀፉ

**clinic** ክሊኒክ
The government opened a new clinic in the city. መንግሥቱ ፣ በከተማው ፣ ውስጥ ፣ አዲስ ፣ ክሊኒክ ፣ ከፈተ

**clink** አቃጨለ
He clinked the key against the penknife in his pocket. በኪሱ ፣ ውስጥ ፣ ቁልፉንና ፣ ሰንጢውን ፣ አቃጨለ

**clip** (clipped), v.
1. ቈረጠ. Don't clip my hair too short! ጸጉሬን ፣ በጣም ፣ አሳጥረህ ፣ አትቍረጠው
2. ቀዶ ፣ አወጣ. I clipped this article out of a magazine. ይህን ፣ ጽሑፍ ፣ ከመጽሔት ፣ ውስጥ ፣ ቀድጄ ፣ አወጣሁት
3. አሳጠረ. We clipped a week off our visit to return home earlier. ቀደም ፣ ብለን ፣ ወደ ፣ ቤት ፣ ለመመለስ ፣ አስበን ፣ ጉብኝታችንን ፣ ባንድ ፣ ሳምንት ፣ አሳጠርነው

**clip together** አያያዘ
Clip these papers together! እነዚህን ፣ ወረቀቶች ፣ አያይዛቸው

**clip** (n.) አግራፍ
He fastened the sheets of paper together with a clip. ወረቀቶቹን ፣ ባግራፍ ፣ አያያዛቸው

**clippers** መቀስ
The farmer used clippers for trimming hedges. ገበሬው ፣ ቁጥቋጦውን ፣ በመቀስ ፣ አስተካከለ

**barber's clippers** የጸጉር ፣ ማስተካከያ
The barber's clippers are dull. የጸጉር ፣ ማስተካከያው ፣ ደንዟል

**clipping** ቁራጭ
I enclosed the newspaper clipping you wanted. የፈለግኸውን ፣ የጋዜጣ ፣ ቁራጭ ፣ አያይዤ ፣ ልኬልሃለሁ

**cloak** (v.) ሸፈነ
Fog cloaks the city buildings. ጭጋግ ፣ የከተማውን ፣ ሕንጻዎች ፣ ይሸፍናል

**cloak** (n.) ካባ
He wore a blue cloak. ሰማያዊ ፣ ካባ ፣ ለብሷል

**drop a cloak over** ሸፈነ
The fog dropped a cloak over the city. ጉሙ ፡ ከተማውን ፡ ሸፍኖታል

**(be) cloaked (in)**
1. ደረበ. She arrived at the theater cloaked in black velvet. ጥቁር ፡ አጥላስ ፡ ደርባ ፡ ወደ ፡ ቴያትር ፡ ቤቱ ፡ መጣች
2. ተያዘ. The mission was cloaked in mystery. መልእክቱ ፡ በምስጢር ፡ ተያዘ

**clock** ሰዓት
We set our clock by the radio. ሰዓቱን ፡ በራዲዮን ፡ አስተካከልን
**around the clock** ሌት ፡ ተቀን ፤ ሃያ ፡ አራት ፡ ሰዓት
The factory works around the clock. ፋብሪካው ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ (ሃያ ፡ አራት ፡ ሰዓት) ፡ ይሠራል
[See also 'alarm, pendulum, set, work']

**clockwise** ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ
Turn the screw clockwise! ቅርንፉዱን ፡ ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ አዙረው

**clod** ጓል
The farmer broke up the clods of earth with a pickaxe. ገበሬው ፡ ጓሉን ፡ በዶማ ፡ ከሰከሰው

**clog** (clogged)
1. ደፈነ. Leaves clogged the waterpipe. ቅጠላ ፡ ቅጠል ፡ የውኃውን ፡ ቧምቧ ፡ ደፈነው
2. ሞላ. Cars clogged the highway. አውራውን ፡ መንገድ ፡ መኪና ፡ ሞላው

**cloister** ገዳም
There are beautiful cloisters in Italy. በኢጣልያ ፡ ውስጥ ፡ የሚያምሩ ፡ ገዳሞች ፡ አሉ

**close** (vt.)
1. ዘጋ. Please close the door! እባክህ ፡ በሩን ፡ ዝጋው
2. ጨፈነ. Close your eyes, and the smoke won't bother you. ዓይንህን ፡ ብትጨፍን ፡ ጭሱ ፡ አያስቸግርህም
3. ደመደመ. They closed the debate in the morning. ክርክሩን ፡ ጧት ፡ ደመደሙት
4. አጠጋጋ. The captain closed the ranks of the troops. ሻምበሉ ፡ ሰልፈኞቹን ፡ አጠጋጋቸው

**close** (vi.)
1. ተዘጋ. The box wouldn't close properly. ሣጥኑ ፡ በደንብ ፡ አይዘጋም
2. አበቃ. The meeting closed after the Emperor's speech. ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ንግግር ፡ በኋላ ፡ ስብሰባው ፡ አበቃ

**close down** ተዘጋ
The factory closed down because of a lack of workers. ፋብሪካው ፡ ሠራተኞች ፡ ስላጣ ፡ ተዘጋ
**close in** እየቀረበ ፡ መጣ ፤ ተቃረበ
The fog closed in from the sea. ጉሙ ፡ ከወደ ፡ ባሕር ፡ እየቀረበ ፡ መጣ
His pursuers closed in rapidly. አባራሪዎቹ ፡ በፍጥነት ፡ ተቃረቡት
**close in on** ከበበ
Police closed in on the rebels from all sides. ፖሊሶቹ ፡ ሽፍቶቹን ፡ ከያቅጣጫው ፡ ከበቧቸው
**close out** እቃውን ፡ በርካሽ ፡ አጣራ
He had to leave town, and therefore closed out. ከተማውን ፡ መልቀቅ ፡ ስለነበረበት ፡ እቃውን ፡ በርካሽ ፡ አጣራ
**(be) closed up** ተዘጋ
When I came to the shop, it was closed up. ወደ ፡ ሱቅ ፡ ስመጣ ፡ ተዘግቶ ፡ ነበር

**close** (n.), **at the ~ of** ሲያልቅ
I will see you at the close of the meeting. ስብሰባው ፡ ሲያልቅ ፡ እንገናኛለን
**from close up** ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ሲያዩት
From close up, it looks entirely different. ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ሲያዩት ፡ በፍጹም ፡ ልዩ ፡ ይመስላል

**close** (adj., adv.)
1. የቅርብ. He is a close friend of mine. የቅርብ ፡ ጓደኛዬ ፡ ነው
2. በጣም ፡ ተቀራራቢ. It was a close race; the two horses were only inches apart. በጣም ፡ ተቀራራቢ ፡ እሽቅድምድም ፡ ስለነበረ ፡ ሁለቱ ፡ ፈረሶች ፡ ባንዲት ፡ ሴኮንድ ፡ ተቀዳደሙ
3. ጥብቅ. The matter requires close investigation. ጉዳዩ ፡ ጥብቅ ፡ ምርመራ ፡ ያስፈልገዋል
4. (= adv.) ደኅና ፡ አድርጎ. Pay close attention! ደኅና ፡ አድርገህ ፡ አስተውል
5. (= adv.) በቅርቡ. He was a close observer of the war situation. የጦርነቱን ፡ ሁኔታ ፡ በቅርቡ ፡ የሚከታተል ፡ እሱ ፡ ነበር
6. (= adv.) ባጭሩ. Recruits receive a close haircut. ምልምል ፡ ወታደሮች ፡ ጸጉራቸውን ፡ ባጭሩ ፡ ያስተካክላሉ
**close behind** ጠጋ ፡ ብሎ
Follow close behind! ጠጋ ፡ ብለህ ፡ ተከተል
**close by**
1. እዚህ ፡ አካባቢ. Is there a restaurant close by? እዚህ ፡ አካባቢ ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ ይገኛል ?
2. አጠገብ. The house stands close by the river. ቤቱ ፡ ወንዙ ፡ አጠገብ ፡ ነው

**close (to) አጠገብ**
The hotel is close to the station. ሆቴሉ ፡ ባቡር ፡ ጣቢያ ፡ አጠገብ ፡ ነው

**(be) close with one's money**
She is close with her money. ንፉግ ፡ ናት

**be close ተቃረበ**
The fire is alarmingly close. እሳቱ ፡ በሚያሰጋ ፡ ሁኔታ ፡ ተቃርቧል

**be close to ሊሆን ፡ ነው**
It is close to five o'clock. ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሊሆን ፡ ነው

**be very close**
1. በጣም ፡ ቅርብ ፡ ነው. The restaurant is very close. ምግብ ፡ ቤቱ ፡ በጣም ፡ ቅርብ ፡ ነው
2. ታፈነ. The air is very close in this room. እዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ አየሩ ፡ ታፍኗል

**put close together አጠጋግቶ ፡ አስቀመጠ**
He put the chairs close together. ወንበሮቹን ፡ አጠጋግቶ ፡ አስቀመጣቸው

**stand close ጠጋ ፡ ብሎ ፡ ቆመ**
Stand close to the wall! ወደ ፡ ግድግዳው ፡ ጠጋ ፡ ብለህ ፡ ቁም
[See also 'drive, proximity, pull up, range, vicinity']

## close call, be a ~ ለጥቂት ፡ አመለጠ
It was a close call; the heavy rock fell and grazed my elbow. ድንጋዩ ፡ ክንዴን ፡ ብቻ ፡ ጨርፎኝ ፡ በማለፉ ፡ ለጥቂት ፡ አመለጥኩ

## (be) closed
1. ዝግ ፡ ሆነ. The museum is closed Sundays. እሑድ ፡ እሑድ ፡ ቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ዝግ ፡ ነው
2. ተፈጸመ. The deal was closed this morning. ውሉ ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ ተፈጸመ

## closefisted ጨቅ
The closefisted old man gave no money for his son to go to school. ጨቁ ፡ ሽማግሌ ፡ ለልጁ ፡ መማሪያ ፡ ምንም ፡ ገንዘብ ፡ አልሰጠውም

## closely
1. በደምብ. Listen to me closely! በደምብ ፡ አዳምጠኝ
2. በውል. Look at it closely! በውል ፡ ተመልከተው
3. በቅርቡ. The doctor followed the child's development closely. ሐኪሙ ፡ የልጁን ፡ እድገት ፡ በቅርቡ ፡ ተከታተለ
4. በጥብቅ. His movements were closely watched. መግቢያ ፡ መውጫውን ፡ በጥብቅ ፡ ይከታተሉ ፡ ነበር
5. በጣም. Cousins are closely related. የአክስትና ፡ የአጎት ፡ ልጆች ፡ በጣም ፡ የተቀራረቡ ፡ ናቸው

## close quarters, at ~ ቅርብ ፡ ለቅርብ ፡ ሆነው
They fought at close quarters. ቅርብ ፡ ለቅርብ ፡ ሆነው ፡ ተዋጉ

**in close quarters ተጨናንቀው**
The prisoners live in close quarters because the prison is small. እስር ፡ ቤቱ ፡ ትንሽ ፡ ስለ ሆነ ፡ እስረኞቹ ፡ ተጨናንቀው ፡ ይኖራሉ

## closer, on ~ examination በደምብ ፡ ሲመረመር
On closer examination, the wound turned out to be superficial. በደምብ ፡ ሲመረመር ፡ ቁስሉ ፡ ቀላል ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

## closet ቁም ፡ ሣጥን
The closet is full of clothes. ቁም ፡ ሣጥኑ ፡ ልብስ ፡ ሞልቶበታል

## (be) closeted with
*He was closeted with his lawyers for over an hour. ከጠበቆቹ ፡ ጋራ ፡ በግል ፡ ለመመካከር ፡ ካንድ ፡ ሰዓት ፡ በላይ ፡ ፈጀበት

## clot (v.) ረጋ
His blood takes a long time to clot. የሱ ፡ ደም ፡ ለመርጋት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይወስዳል

## clot (n.), blood ~ የደም ፡ መርጋት
He died of a blood clot. ከደም ፡ መርጋት ፡ የተነሣ ፡ ሞተ

## cloth
1. ጨርቅ. Use a clean cloth for dusting! በንጹሕ ፡ ጨርቅ ፡ ወልውል
2. ሸራ. Leather shoes usually outlast those made of cloth. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የቆዳ ፡ ጫማ ፡ ከሸራ ፡ ጫማ ፡ ይበረክታል
[See also 'spread, stitch']

## clothe አለበሰ
St. Takla Haymanot clothed the naked and fed the poor. አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የታረዙውን ፡ አለበሱ ፡ የተራበውን ፡ አበሉ
The sun clothes the earth with light. ፀሐይ ፡ ምድርን ፡ ብርሃን ፡ ታለብሳለች

## clothes ልብስ
I want these clothes cleaned and pressed. እነዚህ ፡ ልብሶች ፡ እንዲጠረጉና ፡ እንዲተኰሱ ፡ እፈልጋለሁ
[See also 'ragged, tattered']

## clothes hanger የልብስ ፡ መስቀያ
A clothes hanger made of wire breaks easily.

ከሽቦ ፡ የተሠራ ፡ የልብስ ፡ መስቀያ ፡ በቀላሉ ፡
ይሰበራል

**cloud** (vt.)
1. ሸፈነ. The smoke from the fire clouded the sun from view. ከእሳቱ ፡ የሚወጣው ፡ ጭስ ፡ ፀሐይዋን ፡ ሸፈናት
2. አጠቈረ. Grief clouded his face. ሐዘን ፡ ፊቱ
ን ፡ አጥቍሮታል
3. አድበሰበሰ. Don't cloud the issue with unnecessary details! በማያስፈልግ ፡ ዝርዝር ፡ ጉዳ
ዩን ፡ አታድበስብስ

**cloud** (vi.) ጠቈረ
Her face clouded with worry. ፊቷ ፡ በሐሳብ ፡ ጠቈረ

**be clouded over** በደመና ፡ ተሸፈነ
When I woke up, I found the sky was clouded over. ስነቃ ፡ ሰማዩ ፡ በደመና ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር

**cloud up**
Just after we started, the sky clouded up. እንደጀመርን ፡ ደመና ፡ ሆነ

**cloud** (n.) ደመና
The sun has disappeared behind the clouds. ፀሐይዋን ፡ ደመና ፡ ጋረዳት

**cloud of locusts** ያንበጣ ፡ መንጋ
A cloud of locusts covered the sky. ያንበጣ ፡ መንጋ ፡ ሰማዩን ፡ ሸፈነው

**be up in the clouds** ከንቱ ፡ ነው
Her schemes are usually up in the clouds. በጠቅላላው ፡ አቅዷ ፡ ከንቱ ፡ ነው
[See also 'threatening']

**cloudburst** ዶፍ
I rarely witnessed a cloudburst in the dry season. ዶፍ ፡ በበጋ ፡ እምብዛም ፡ አላየሁም

**cloudy**
1. ደመናማ. Since it is cloudy today we can't go for a walk. ዛሬ ፡ ደመናማ ፡ ስለሆነ ፡ ለ
መንሸራሸር ፡ አንችልም
2. የደፈረሰ. He could not see through the cloudy liquid. በደፈረሰው ፡ ፈሳሽ ፡ ውስጥ ፡ ም
ንም ፡ ሊያይ ፡ አልቻለም

**clove** (n.) ቅርንፉድ

**clove,** see **cleave**

**cloven** የተሰነጠቀ
The cow has a cloven hoof. ላም ፡ የተሰነጠቀ ፡ ሰኰና ፡ አላት

**cloven-hoofed** የተሰነጠቀ ፡ ሰኰና ፡ ያለው
Cloven-hoofed animals may be eaten in Ethiopia. የተሰነጠቀ ፡ ሰኰና ፡ ያላቸው ፡ እንስሳ
ት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይበላሉ

**clover** [የሣር ፡ ዓይነት]

**clown** አሥቂኝ ፡ ተዋናይ ፤ ተራቢ
This circus has many clowns. ይህ ፡ ሰርከስ ፡ ብዙ ፡ አሥቂኝ ፡ ተዋንያን ፡ (ተራቢዎች) ፡ አሉት

**club** (clubbed), v. መታ
The robber clubbed his victim and ran off. ቀማኛው ፡ ሰውዬውን ፡ መቶ ፡ ሮጠ

**club together** አዋጣ
The children clubbed together to buy their mother a present. ለእናታቸው ፡ ስጦታ ፡ ለመ
ግዛት ፡ ልጆቹ ፡ አዋጡ

**club** (n.)
1. ዱላ. The policeman had to use his club. ፖሊሱ ፡ በዱላ ፡ መምታት ፡ ግድ ፡ ነበረበት
2. ክበብ. Are you a member of the club? የክበቡ ፡ አባል ፡ ነህ ?

**clubfooted** እግረ ፡ ቆልማማ
The child was born clubfooted. ልጁ ፡ እግረ ፡ ቆልማማ ፡ ሆኖ ፡ ተወለደ

**cluck** (v.) አስካካ
The hens clucked as they searched for food. ዶሮዎቹ ፡ እያስካኩ ፡ ምግብ ፡ ፍለጋ ፡ ጫሩ

**cluck** (n.) ማስካካት
The cluck of the hen woke me up. የዶሮዋ ፡ ማ
ስካካት ፡ ቀሰቀሰኝ

**clue** ፍንጭ
The footprints were a clue. የእግሩ ፡ ዱካ ፡ ፍን
ጭ ፡ ነበር

**clump (of)** ዕጅብ ፡ ያሉ
A clump of trees conceals the house from view. ዕጅብ ፡ ያሉት ፡ ዛፎች ፡ ቤቱን ፡ ይከልሉታል

**clump along** እየተጐተተ ፡ ሄደ
The lame man clumped along. ሽባው ፡ ሰው
ዬ ፡ እየተጐተተ ፡ ሄደ

**clumsy** ገልጃጃ
The clumsy boy bumped into all the furniture. ገልጃጃው ፡ ልጅ ፡ እቤት ፡ ካለው ፡ እቃ ፡ ሁሉ ፡ ተጋጨ

**be clumsy** ቅልጥፍና ፡ ጐደለው
He is well-intentioned but clumsy. ቅን ፡ ነው ፡ ግን ፡ ቅልጥፍና ፡ ይጐድለዋል

**clung,** see **cling**

**cluster (of)**
1. ችብችብ ፡ ያሉ. A cluster of houses was seen from far. ከሩቅ ፡ ችብችብ ፡ ያሉ ፡ ቤቶች ፡ ታዩ
2. የተሰበሰቡ. There was a cluster of tourists at the gate. በመግቢያው ፡ ላይ ፡ የተሰበሰቡ ፡ አገር ፡ ጐብኚዎች ፡ ነበሩ

**in clusters** ዕጅብ ፡ ብሎ
This flower usually grows in clusters. ይህ ፡ አበባ ፡ የሚያድገው ፡ ዕጅብ ፡ ብሎ ፡ ነው

**cluster around** ከበበ
Many people clustered around the accident victim. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አደጋው ፡ የደረሰበትን ፡ ሰው ፡ ከበቡት

**clutch** (v.) ጨበጠ
The child clutched my hand. ልጁ ፡ እጄን ፡ ጨበጠኝ

**clutch (at)** ለመያዝ ፡ ሞከረ
He clutched at the rope, but missed it. ገመዱን ፡ ለመያዝ ፡ ሞከር ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ሳተ

**clutch** (n.) ፍሬሲዮን
Let out the clutch slowly, or the car will stop. ፍሬሲዮኑን ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ ልቀቅ ፤ አለበለዚያ ፡ መኪናው ፡ ይቆማል
*Quick shooting saved the hunter from the bear's clutches. ፈጥኖ ፡ መተኰሱ ፡ አዳኙን ፡ ከድብ ፡ አዳነው

**into the clutches of** ‑‑‑ እጅ
They fell into the clutches of the moneylenders. ገንዘብ ፡ አበዳሪዎች ፡ እጅ ፡ ወደቁ

**clutter** (v.) ቅጥ ፡ አሳጣ
Heaps of books cluttered her room. የመጻሕፍት ፡ ቁልል ፡ ክፍሏን ፡ ቅጥ ፡ አሳጣው

**be cluttered** ተዝረከረከ
His desk was cluttered with old papers. ጠረጴዛው ፡ ብዙ ፡ አሮጌ ፡ ወረቀት ፡ ተዝረከርኮበታል

**clutter** (n.) ምስቅልቅል
Please tidy up the clutter in your room! የክፍልህን ፡ ምስቅልቅል ፡ አስተካክል

**coach**
1. ሰረገላ. When Queen Elizabeth visited Ethiopia, His Imperial Majesty came to meet her in a coach. ንግሥት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሲጐበኙ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ በሰረገላ ፡ ተቀበሏቸው
2. አሠልጣኝ. The coach of this team is very good. የዚህ ፡ ቡድን ፡ አሠልጣኝ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነው

**coagulate** ረጋ
The milk coagulated in the bottle. ወተቱ ፡ በጠርሙሱ ፡ ውስጥ ፡ ረጋ

**coal**
1. ከሰል. Put some coal on the fire! እሳቱን ፡ ከሰል ፡ ጨምርበት
2. የድንጋይ ፡ ከሰል. Coal and salt are minerals. የድንጋይ ፡ ከሰልና ፡ ጨው ፡ ማዕድኖች ፡ ናቸው

**live coals** የከሰል ፡ ፍም
There are still live coals in the fire. እሳቱ ፡ ውስጥ ፡ የከሰል ፡ ፍም ፡ ገና ፡ አለ

**coalesce** ተባበረ
The thirteen colonies coalesced to form a nation. ዐሥራ ፡ ሦስቱ ፡ የቅኝ ፡ ግዛቶች ፡ አንድ ፡ አገር ፡ ለመመሥረት ፡ ተባበሩ

**coalition** ኅብረት
The clergy and the nobility formed a coalition. ካህናቱና ፡ መኳንንቱ ፡ ኅብረትን ፡ መሠረቱ

**coarse**
1. ከርዳዳ. He used some coarse cloth to make a bag. በከርዳዳ ፡ ጨርቅ ፡ ከረጢት ፡ ሰፋ
2. ሻካራ. This cloth is too coarse for me. ይህ ፡ ጨርቅ ፡ በጣም ፡ ሻካራ ፡ ይሆንብኛል
The table is coarse and is not suitable for writing. ጠረጴዛው ፡ ሻካራ ፡ ስለሆነ ፡ ለጽሕፈት ፡ አይመችም
3. ደቃቅ ፡ ያልሆነ. The beach is covered with coarse sand. የባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ደቃቅ ፡ ባልሆነ ፡ አሸዋ ፡ የተሸፈነ ፡ ነው
4. ያልታረመ. His coarse language angered the teacher. ያልታረመ ፡ አነጋገሩ ፡ መምህሩን ፡ አስቈጣው
*His manners are coarse. ባለጌ ፡ ነው

**coarsely, grind ~** ገረደፈ
She ground the barley coarsely. ገብሱን ፡ ገረደፈችው

**coast** (n.) ጠረፍ ፤ የባሕር ፡ ጠረፍ ፤ የባሕር ፡ ዳርቻ
We approached the coast at night. ከጠረፉ ፡ ሌሊት ፡ ደረስን
On the map, the coast has a jagged outline. በካርታ ፡ ሲታይ ፡ የባሕሩ ፡ ጠረፍ ፡ (የባሕሩ ፡ ዳርቻ) ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ ነው

**coast** (v.)
*The old car coasted down the hill. አሮጌው ፡ መኪና ፡ ሞተሩ ፡ ጠፍቶ ፡ ቁልቁለቱን ፡ ወረደ

**coast along** ጠረፍ ፡ ጠረፉን ፡ ተጓዘ
We coasted along South America on our trip

last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ጉዟችን ፡ ደቡብ ፡ አሜሪካን ፡ ጠረፍ ፡ ጠረፉን ፡ ተጓዝን

**coastal** በየባሕር ፡ ዳሩ ፡ የሚገኝ
The conversion of the coastal tribes to Islam occurred in the 19th century. በየባሕር ፡ ዳሩ ፡ የሚገኙት ፡ ጐሳዎች ፡ ወደ ፡ እስልምና ፡ ሃይማኖት ፡ የተለወጡት ፡ በዐሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ነው

**coastline** ጠረፍ
The Red Sea coastline is barren. የቀይ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ የተራቈተ ፡ ነው

**coat** (v.) ቀባ
He coated the wall with paint. ግድግዳውን ፡ ቀለም ፡ ቀባው

**coat** (n.)
1. ኮት. What is the difference between a coat and overcoat? ኮትና ፡ ካፖርት ፡ ልዩነታቸው ፡ ምንድነው ?
2. ጸጉር. The leopard has a sleek coat. ነብር ፡ ለስላሳ ፡ ጸጉር ፡ አለው
*Our house has three coats of paint. ቤታችን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ተደጋግሞ ፡ ተቀብቷል

**coating** ቅባት
We must put a protective coating over the drawing. በሥዕሉ ፡ ላይ ፡ መከላከያ ፡ ቅባት ፡ ማድረግ ፡ አለብን

**coat of arms** ጋሻው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አርማ
His coat of arms shows he is descended from a king. ጋሻው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አርማ ፡ የንጉሥ ፡ ዘር ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳል

**coat of mail** የብረት ፡ ልብስ
A coat of mail protects one against sword cuts. የብረት ፡ ልብስ ፡ ከጐራዴ ፡ ስለት ፡ ይጠብቃል

**coax**
1. አባበለ. He tried to coax the child to come with him. ልጁ ፡ አብሮት ፡ እንዲመጣ ፡ ሊያባብለው ፡ ሞከረ
2. ተለማመጠ. She coaxed her father to let her go to the dance. ወደ ፡ ዳንሱ ፡ እንድትሄድ ፡ አባቷ ፡ እንዲፈቅድላት ፡ ተለማመጠችው
3. አደፋፈረ. He tried to coax me to take the medicine. መድኃኒቱን ፡ እንድጠጣ ፡ ሊያደፋፍረኝ ፡ ሞከረ

**cobbler** ጫማ ፡ ሰፊ
Let's take the shoes to the cobbler's! ጫማዎቹን ፡ ጫማ ፡ ሰፊ ፡ ዘንድ ፡ እንውሰድ

**cobra** [በአፍሪካ ፡ ወይም ፡ በእስያ ፡ የሚገኝ ፡ መርዛም ፡ እባብ]

**cobweb** የሸረሪት ፡ ድር
The flies were caught in a cobweb. ዝምቦቹ ፡ በሸረሪት ፡ ድር ፡ ተያዙ

**cock** (v.) አቀባበለ
He cocked the gun and threatened to shoot. ጠመንጃውን ፡ አቀባብሎ ፡ ለመተኰስ ፡ ቃጣ

**cock** (n.) አውራ ፡ ዶሮ
The cock crowed at dawn. አውራ ፡ ዶሮው ፡ ጐሕ ፡ ሲቀድ ፡ ጮኸ

**cockroach** በረሮ

**(be) cocksure**
*He would not be so cocksure were his father not the boss. አባቱ ፡ አለቃ ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ በአፉ ፡ ሙሉ ፡ አይናገርም ፡ ነበር

**(be) cocky** ትምክሕቱ ፡ ከፍ ፡ አለ
Jim was very cocky about his chance of winning first prize. ጂም ፡ ያንደኛነትን ፡ ሽልማት ፡ ለማግኘት ፡ ትምክሕቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነበር

**coconut** [የዘንባባ ፡ ገውዝ]

**coddle** አሞላቀቀ
If you coddle your child he will not grow up to be manly. ልጅህን ፡ ካሞላቀቅኸው ፡ ጐበዝ ፡ ሆኖ ፡ አያድግም

**code**
1. ደንብ. You must observe the code of the school. የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ደንብ ፡ ማክበር ፡ አለብህ
A traffic code contains rules for driving. የትራፊክ ፡ ደንብ ፡ ያነዳድን ፡ ሥርዓት ፡ ይይዛል
2. የምስጢር ፡ ጽሑፍ. He found a message written in code. በምስጢር ፡ ጽሑፍ ፡ የተጻፈ ፡ መልእክት ፡ አገኘ
3. ልዩ ፡ ማስታወሻ. The code on the label shows the date of manufacture. በንግድ ፡ እቃው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ልዩ ፡ ማስታወሻ ፡ እቃው ፡ የተሠራበትን ፡ ጊዜ ፡ ያመለክታል

**codex** (codices) የጥንት ፡ ጽሑፍ
The monastery owns many codices. ገዳሙ ፡ ብዙ ፡ የጥንት ፡ ጽሑፎች ፡ አሉት

**codify** (codified) በጽሑፍ ፡ አሰፈረ
Justinian codified Roman law in the sixth century. ጁስቲንያን ፡ የሮማውን ፡ ሕግ ፡ በስድስተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በጽሑፍ ፡ አሰፈረ

**co-ed** ልጃገረድ
There are more boys than co-eds at the college. በኮሌጅ ፡ ውስጥ ፡ ከልጃገረዶች ፡ ይልቅ ፡ ወንዶች ፡ ይበዛሉ

**coerce** አስገደደ
He coerced the prisoner into confessing. እስረኛውን ፡ እንዲያምን ፡ አስገደደው

**coexist** አብሮ ፡ በሰላም ፡ ኖሩ
Nations must learn to coexist. መንግሥታት ፡ አብሮ ፡ በሰላም ፡ መኖርን ፡ መልመድ ፡ አለባቸው

**coffee** ቡና
I drink coffee every morning. ጧት ፡ ጧት ፡ ቡና ፡ እጠጣለሁ

**coffee bean** ቡና
Coffee beans are dried before they are shipped. ቡና ፡ ለገበያ ፡ በመርከብ ፡ ከመላኩ ፡ በፊት ፡ እንዲደረቅ ፡ ይደረጋል

**coffee grounds** የቡና ፡ አተላ
Empty the coffee grounds in the garbage pail! ቆሻሻ ፡ ማጠራቀሚያው ፡ ባልዲ ፡ ውስጥ ፡ የቡናውን ፡ አተላ ፡ አፍሰው

**coffeehouse** ቡና ፡ ቤት
There are no coffeehouses in this village. በዚህ ፡ መንደር ፡ ምንም ፡ ቡና ፡ ቤቶች ፡ የሉም

**coffee pot** ጀበና
Coffee pots are sold at the market. ጀበና ፡ አገበያ ፡ ውስጥ ፡ ይሸጣል

**coffer** ሣጥን
She put the coffer under the bed. ሣጥኗን ፡ ከልጋዋ ፡ ሥር ፡ አስቀመጠች

**coffin** የሬሳ ፡ ሣጥን ፤ ሬሳ
Kennedy's body was put in a bronze coffin. የኬኔዲ ፡ አስከሬን ፡ ከነሐስ ፡ በተሠራ ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አረፈ
Sorrowful relatives followed the coffin. ያዘኑት ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ ሬሳውን ፡ ተከተሉት
*When the coffin was lowered into the grave, his sister cried. ግብአተ ፡ መሬት ፡ ሲደረግ ፡ እኅቱ ፡ አለቀሰች

**cogent** አጥጋቢ
He found no cogent reason to change his mind. ሐሳቡን ፡ ለመለወጥ ፡ አጥጋቢ ፡ ምክንያት ፡ አላገኘም

**cogitate** በጥብቅ ፡ ተመራመረ
The senators cogitated about the problem. እማካሪዎቹ ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ በጥብቅ ፡ ተመራመሩ

**cognate** የሚዛመድ
Amharic and Arabic are cognate languages. አማርኛና ፡ ዐረብኛ ፡ የሚዛመዱ ፡ ቋንቋዎች ፡ ናቸው

**cognizance** ዕውቀት
He has a wide cognizance of the habits of animals. ስለ ፡ እንስሳት ፡ ጠባይ ፡ ሰፊ ፡ ዕውቀት ፡ አለው

**take cognizance of** ተረዳ
Take cognizance of what happened and act accordingly! የተደረገውን ፡ ነገር ፡ በሚገባ ፡ ከተረዳህ ፡ በኋላ ፡ በዚያው ፡ መሠረት ፡ ሥራ

**(be) cognizant of** ዐወቀ
The general was cognizant of the movements of the enemy. ጄኔራሉ ፡ የጠላትን ፡ እንቅስቃሴ ፡ ያውቅ ፡ ነበር

**coherence** ቅንብር
His composition lacks coherence. ድርሰቱ ፡ ቅንብር ፡ ይጐድለዋል

**coherent**
1. የተሳካ. A sentence that is not coherent is hard to understand. ያልተሳካ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገርን ፡ ለመረዳት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. የተጣራ. The lawyer presented coherent arguments in favor of his client. ጠበቃው ፡ የሚሟገትለትን ፡ ሰው ፡ የሚደግፍ ፡ የተጣራ ፡ ክርክር ፡ አቀረበ

**coherently** አስተካክሎ
She cannot talk coherently any more. ከእንግዲህ ፡ አስተካክላ ፡ መናገር ፡ አትችልም

**cohesion** የመጣበቅ ፡ ኀይል
Wet sand has more cohesion than dry sand. እርጥብ ፡ አሸዋ ፡ ከደረቅ ፡ አሸዋ ፡ ይልቅ ፡ የመጣበቅ ፡ ኀይል ፡ አለው

**cohesive** የሚጣበቅ
Clay is cohesive, but gravel is not. ሸክላ ፡ የሚጣበቅ ፡ ሲሆን ፡ ጠጠር ፡ ግን ፡ አይደለም

**cohort** ጓድ
The enemy's cohorts were struck by a plague. የጠላት ፡ ጓዶች ፡ በወረርሽኝ ፡ ተጐድተው ፡ ነበር

**coil** (vt.) ጠመጠመ
The sailor coiled the rope on the deck of the ship. መርከበኛው ፡ ገመዱን ፡ በመርከቡ ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ጠመጠመው

**coil** (vi.)
1. ተጠማዘዘ. The river coils through the valley. ወንዙ ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ይጠማዘዛል

2. ተጥመለመለ. The snake coiled, ready to strike. ለመንከስ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ እባቡ ፡ ተጥመለመለ

**coil up** ጠመጠመ
He coiled up the wire. ሽቦውን ፡ ጠመጠመው

**coin** (v.)
1. አተመ. The mint is coining pennies. ገንዘብ ፡ መሥሪያው ፡ ሳንቲሞች ፡ በማተም ፡ ላይ ፡ ነው
2. ፈጠረ. He coined a word for his invention. ለፈለሰፈው ፡ ነገር ፡ ቃል ፡ ፈጠረለት

**coin** (n.) ፍራንክ ፤ ገንዘብ
He gave me a handful of Ethiopian coins. አንድ ፡ እፍኝ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍራንክ ፡ ሰጠኝ
Ancient coins were not circular in shape. የጥንት ፡ ገንዘቦች ፡ ቅርጻቸው ፡ ክብ ፡ አልነበረም
[See also 'toss']

**coincide**
1. አንድ ፡ ሆነ. Jesus' birth coincided with the appearance of a bright star in the sky. ኢየሱስ ፡ ሲወለድና ፡ አንዲት ፡ ብሩህ ፡ ኮከብ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ስትታይ ፡ አንድ ፡ ሆነ
2. ተስማማ. The two stories did not coincide. ሁለቱ ፡ ታሪኮች ፡ አልተስማሙም
3. ተጋጠመ. Our vacations coincided. የዕረፍት ፡ ጊዜያችን ፡ ተጋጠመ

**coincidence** አጋጣሚ
What a strange coincidence! ምንኛ ፡ ድንቅ ፡ አጋጣሚ ፡ ነው !
[See also 'lucky']

**(be) coincident** ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ገባ
Winter in the United States is coincident with summer in Australia. የአሜሪካን ፡ ክረምትና ፡ የአውስትራልያ ፡ በጋ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ይገባሉ

**coincidental, purely** ~ እንዳጋጣሚ
It was purely coincidental that we met this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ የተገናኘነው ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ነበረ

**cold** (n.)
1. ብርድ. I cannot stand this cold. ይህንን ፡ ብርድ ፡ አልችለውም
2. ቅዝቃዜ. Heat is the converse of cold. ሙቀት ፡ የቅዝቃዜ ፡ ተቃራኒ ፡ ነው
3. ጉንፋን. You have given me a bad cold. ክፉ ፡ ጉንፋን ፡ አጋብተህብኛል

**catch a cold** ጉንፋን ፡ ያዘ(ው)
We all caught colds during the winter. በክረምት ፡ ወራት ፡ ሁላችንም ፡ ጉንፋን ፡ ያዘን

**common cold** ጉንፋን
The scientist isolated the virus of the common cold. ሳይንቲስቱ ፡ የጉንፋኑን ፡ ቫይረስ ፡ ከሌሎቹ ፡ ለየው

**get a cold** ጉንፋን ፡ ያዘ(ው)
I have got a bad cold and cannot go to school. ክፉ ፡ ጉንፋን ፡ ስለያዘኝ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ልሄድ ፡ አልችልም

**have a cold** ጉንፋን ፡ ያዘ(ው)
He has a bad cold and cannot go to school. ኀይለኛ ፡ ጉንፋን ፡ ስለያዘው ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሊሄድ ፡ አይችልም

**cold** (adj.)
1. በራድ. I like to drink cold coffee in the afternoon. ቀን ፡ በራድ ፡ ቡና ፡ መጠጣት ፡ እወዳለሁ
2. ቀዝቃዛ. Give me a glass of cold water! አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ውኃ ፡ ስጠኝ
3. ብርዳም. The cold wind bit our faces. ብርዳሙ ፡ ነፋስ ፡ ፊታችንን ፡ መታን
4. የብርድ. A hot cup of broth on a cold day tastes fine. በብርድ ፡ ቀን ፡ ትኩስ ፡ ሾርባ ፡ ተስማሚ ፡ ነው
5. ብርዳማ. November is a cold month. ኅዳር ፡ ብርዳማ ፡ ወር ፡ ነው
6. ብርድ ፡ የመታው. He massaged his cold fingers. ብርድ ፡ የመታቸውን ፡ ጣቶቹን ፡ አሸ
7. (= adv.) እንደነገሩ. They gave us a cold greeting. እንደነገሩ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጡን

**be cold**
1. ቀዘቀዘ. The water is not cold enough. ውኃው ፡ የሚፈለገውን ፡ ያህል ፡ አልቀዘቀዘም
2. በረደ. The coffee was cold, so I drank it at once. ቡናው ፡ ስለበረደ ፡ ባንዴ ፡ ጠጣሁት
3. በረደ(ው). I am cold. Give me a blanket! ስለበረደኝ ፡ ብርድ ፡ ልብስ ፡ ስጠኝ

**feel cold** ቀዘቀዘ
The air feels cold. አየሩ ፡ ይቀዘቅዛል

**get cold feet** ፈራ
He promised to speak to my boss about my promotion, but he got cold feet and backed out. ስለ ፡ ሹመቴ ፡ አለቃዬን ፡ ሊያነጋግርልኝ ፡ ቃል ፡ ገብቶ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ፈርቶ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አለ

**in cold blood** በጭካኔ ፤ በግፍ
They shot him down in cold blood. በጭካኔ ፡ (በግፍ) ፡ ገደሉት

**out in the cold**
*When the new manager came, John found himself out in the cold. አዲሱ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሲመጣ ፡ ጆን ፡ ከሥራው ፡ ተፈናቀለ

**turn cold** አየሩ ፡ ቀዝቀዝ ፡ አለ
It turned cold at night. ማታ ፡ አየሩ ፡ ቀዝቀዝ ፡ ብሎ ፡ ነበር
[See also 'shoulder, throw']

**cold-blooded** ጨካኝ ፤ አረመኔ
The cold-blooded criminal killed an unarmed man. ጨካኙ ፡ (አረመኔው) ፡ ወንጀለኛ ፡ መሣሪያ ፡ ያልያዘ ፡ ሰው ፡ ገደለ

**colder** ብርዳማ
The dogs acclimated quickly to the colder country. ውሾቹ ፡ ብርዳማውን ፡ አገር ፡ በቶሎ ፡ ለመዱት

**get colder** በረደ
The nights are getting colder. ሌሊቱ ፡ እየበረደ ፡ ይሄድ ፡ ጀመር

**colic** ያንጀት ፡ ሕመም
The baby had an attack of colic. ሕፃኑ ፡ ያንጀት ፡ ሕመም ፡ ይዞት ፡ ነበር

**collaborate**
1. አበረ. During the war, a small number of people collaborated with the enemy. በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ከጠላት ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ነበር
2. አብሮት ፡ ጻፈ. I collaborated with him on a book. አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ አብሬው ፡ ጻፍኩ

**collaborator** ግብረ ፡ አበር
The collaborator was shot by the patriots. ግብረ ፡ አበሩ ፡ ባርበኞቹ ፡ እጅ ፡ በጥይት ፡ ተገደለ

**collapse** (v.)
1. ተናደ ፤ ፈረሰ. If the foundation is not sound, the house will collapse. መሠረቱ ፡ ጠንካራ ፡ ካልሆነ ፡ ቤቱ ፡ ይናዳል ፡ (ይፈርሳል)
2. ፈራረሰ. The earth shook and many buildings collapsed. መሬቱ ፡ በመንቀጥቀጡ ፡ ብዙ ፡ ሕንጻዎች ፡ ፈራረሱ
3. ተደረመሰ. The bridge suddenly collapsed. ድልድዩ ፡ በድንገት ፡ ተደረመሰ
4. ወደቀ. If you cut the tent ropes, the tent will collapse. የድንኳኑን ፡ አውታሮች ፡ ብትበጥስ ፡ ድንኳኑ ፡ ይወድቃል
5. ተዝለፍልፎ ፡ ወደቀ. He collapsed in the middle of the street. እመሃል ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ተዝለፍልፎ ፡ ወደቀ
6. ተጨናገፈ. Our plans will collapse if we don't get some help. እርዳታ ፡ ካላገኘን ፡ ሐሳባችን ፡ ይጨናገፋል
7. ታጠፈ. This table collapses. ይህ ፡ ጠረጴዛ ፡ ይታጠፋል

**collapse** (n.) ውድቀት
Let us presume that economic collapse is imminent. የኤኮኖሚ ፡ ውድቀት ፡ የማይቀር ፡ ነው ፡ እንበል
Corruption will bring about the collapse of justice. እምነትን ፡ ማጉደል ፡ የፍትሕን ፡ ውድቀት ፡ ያስከትላል

**collar**
1. ኮሌታ. He sewed a button to the collar of the shirt. በሸሚዙ ፡ ኮሌታ ፡ ላይ ፡ አዝራር ፡ ተከለ
2. ዘለበት. The dog's collar broke. የውሻው ፡ ዘለበት ፡ ተበጠሰ
3. አንገት. The cat has a bell on its collar. ድመቷ ፡ አንገቷ ፡ ላይ ፡ ቃጭል ፡ አላት
[See also 'seize, white']

**collateral** (n.) መያዣ
The bank requires collateral on loans. ባንኩ ፡ ብድር ፡ ለመስጠት ፡ መያዣ ፡ ይጠይቃል

**collateral** (adj.)
1. ከ - - - ጎን ፡ የሚገኝ. The collateral wing of the library collapsed. ከቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ጎን ፡ የሚገኘው ፡ ቅጥያ ፡ ክፍል ፡ ፈረሰ
2. (= n.) ቅርንጫፍ. These accomplishments are merely collateral to his primary goal. እነዚህ ፡ የሥራ ፡ ውጤቶች ፡ የዋናው ፡ ዓላማው ፡ ቅርንጫፎች ፡ ናቸው

**collateral branch**
*He is not a direct descendant; he is from a collateral branch. የዋናው ፡ ግንድ ፡ ተወላጅ ፡ አይደለም ፤ ቅርንጫፍ ፡ ተወላጅ ፡ ነው

**colleague** የሥራ ፡ ጓደኛ
My colleagues refused to work with me. የሥራ ፡ ጓደኞቼ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ አንሠራም ፡ አሉ

**collect** (vt.)
1. ሰበሰበ. Did you collect all the notebooks? ደብተሮቹን ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰብክ ?
2. (ገንዘብ) ፡ አስከፈለ. The company is trying to collect the money for the furniture he bought. የቤት ፡ እቃ ፡ የገዛበትን ፡ ገንዘብ ፡ ለማስከፈል ፡ ኩባንያው ፡ በመጣር ፡ ላይ ፡ ነው
3. አንድ ፡ ቦታ ፡ አደረገ. He collected his thoughts in order to think up a solution. ስለ ፡ መፍትሔ ፡ ለማሰብ ፡ ሐሳቡን ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ አደረገ
4. ወሰደ. I went to the office to collect my mail. ደብዳቤ ፡ ለመውሰድ ፡ እቢሮ ፡ ሄጄ ፡ ነበር

**collect** (vi.)
1. ተሰበሰበ. A crowd collected in the square. ብዙ ፡ ሰው ፡ ባደባባዩ ፡ ተሰበሰበ
2. ተጠራቀመ. Lint collects in the pockets of the suit. ኪስ ፡ ውስጥ ፡ የከርና ፡ የጨርቅ ፡ ብናኝ ፡ ይጠራቀማል

**collected, remain calm and ~** በርጋታ ፡ ቆየ
Despite all the furor around him, John remained calm and collected. ብዙ ፡ ሁከት ፡ ቢከበውም ፡ ጆን ፡ በርጋታ ፡ ቆየ

**collection**
1. የሰበሰበው. This volume makes my collection complete. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የሰበሰብኩትን ፡ ያሟላልኛል
2. ስብስብ. He has a collection of curious old coins. ልዩ ፡ ዓይነት ፡ የድሮ ፡ ገንዘቦች ፡ ስብስብ ፡ አለው
3. አሰባሰብ. The government is trying to remedy the deficiencies in the collection of taxes. በግብር ፡ አሰባሰብ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ጉድለት ፡ መንግሥት ፡ ለማሻሻል ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነው
*The library's collection of books is kept in a large room. መጻሕፍት ፡ ቤቱ ፡ ያጠራቀማቸው ፡ መጻሕፍት ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ
*The library has a famous collection of books on America. መጻሕፍት ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፡ አሜሪካ ፡ የተጻፉ ፡ የታወቁ ፡ መጽሐፎች ፡ አሉት

**take up a collection** ገንዘብ ፡ ሰበሰበ
They took up a collection after the concert. ከኮንሰርቱ ፡ በኋላ ፡ ገንዘብ ፡ ሰበሰቡ

**collective**
1. የጋራ. Collective security is important for Ethiopia. የጋራ ፡ ጸጥታ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው
2. (= adv.) የጋርዮሽ. The state is promoting collective ownership of coffee-cleaning facilities. መንግሥቱ ፡ የቡና ፡ ማጣሪያ ፡ እቃዎች ፡ የጋርዮሽ ፡ እንዲሠራባቸው ፡ ያበረታታል
[See also 'security']

**collectively** በጅምላ
Consider these points, first severally and then collectively. እነዚህን ፡ ጉዳዮች ፡ መጀመሪያ ፡ በዝርዝር ፤ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ በጅምላ ፡ ተመልከታቸው

**collective noun** የጥቅል ፡ ስም
"Army" and "crowd" are collective nouns. ጦር ፡ ሰራዊትና ፡ ሕዝብ ፡ የጥቅል ፡ ስሞች ፡ ናቸው

**college** ኮሌጅ
Many students have graduated from this college. ከዚህ ፡ ኮሌጅ ፡ ብዙ ፡ ተማሪዎች ፡ ተመረቁ

**collide**
1. ተጋጨ. The car collided with a bus. መኪናው ፡ ከአውቶቡስ ፡ ጋር ፡ ተጋጨ
The cars collided with a terrible crash. መኪናዎቹ ፡ ሲጋጩ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ ተሰማ
2. ተለያየ. Our ideas collide on this matter. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አሳባችን ፡ ይለያያል

**collision (የመኪና) ፡ ግጭት**
There was a collision on Churchill St. last night. ትናንት ፡ ሌሊት ፡ በቸርቺል ፡ ጐዳና ፡ የመኪና ፡ ግጭት ፡ ነበር

**colloquial expression** የመንደር ፡ አነጋገር
There are many colloquial expressions in Afework's books. የአፈወርቅ ፡ መጻሕፍት ፡ ብዙ ፡ የመንደር ፡ አነጋገር ፡ ይገኝባቸዋል

**collusion, work in ~** ግብረ ፡ አበር ፡ ሆነ
The cashier has worked in collusion with the thief. ገንዘብ ፡ ተቀባዩ ፡ ከሌባው ፡ ጋር ፡ ግብረ ፡ አበር ፡ ሆኗል

**act in collusion** አሴረ(በት)
Some of his employees were acting in collusion to rob him. አንዳንድ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ሊሰርቁት ፡ ያሴሩበት ፡ ነበር

**colon**
1. ድርብ ፡ ሰረዝ. The colon is used for punctuation. ድርብ ፡ ሰረዝ ፡ ሥርዐተ ፡ ነጥብ ፡ ነው
2. ትልቅ ፡ አንጀት. The surgeon will operate on his colon. ሐኪሙ ፡ ትልቅ ፡ አንጀቱን ፡ ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ያደርጋል

**colonel** ኮሎኔል
He is a colonel in the army. በጦር ፡ ሰራዊት ፡ ውስጥ ፡ ኮሎኔል ፡ ነው

**colonial** የቅኝ ፡ ገዢዎች
The colonial government oppressed the natives. የቅኝ ፡ ገዢዎች ፡ መንግሥት ፡ አገሬውን ፡ ጨቁነው

**colonialism** ቅኝ ፡ አገዛዝ
The subject matter of this book is colonialism. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈው ፡ ስለ ፡ ቅኝ ፡ አገዛዝ ፡ ነው

**colonization** የቅኝ ፡ አገዛዝ
Colonization was widespread in Africa in the 19th century. በዐሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የቅኝ ፡ አገዛዝ ፡ በአፍሪካ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ነበር

**colonize**
1. በብዛት ፡ አሰፈረ. They hope to colonize the area with farmers. ቀበሌው ፡ ላይ ፡ ገበሬዎችን ፡ በብዛት ፡ ለማስፈር ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋሉ
2. ቅኝ ፡ ግዛት ፡ አደረገ. Italy colonized Somalia in the 19th century. ጣልያን ፡ በዐሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ሶማሌን ፡ ቅኝ ፡ ግዛት ፡ አደረገቻት

**colonizer** ቅኝ ፡ ገዢ
Evangelists accompanied the Spanish colonizers in South America. ወንጌላውያን ፡ የእስፓኝ ፡ ቅኝ ፡ ገዢዎችን ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ መጡ

**colonnade** [በተወሰነ ፡ ርቀት ፡ የተደረደሩ ፡ ዓምዶች]

**colony** (colonies)
1. ቅኝ ፡ ግዛት. Mauritius is a British colony. ሞሪሽስ ፡ የእንግሊዝ ፡ ቅኝ ፡ ግዛት ፡ ነች
2. መንደር. There is an artist colony near our house. ከኛ ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ሰዎች ፡ መንደር ፡ አለ
*There is a considerable American colony in Paris. በርከት ፡ ያሉ ፡ አሜሪካኖች ፡ ፓሪስ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ

**color** (v.)
1. ከለር ፡ ቀባ. The child colored the picture with crayons. ልጁ ፡ ሥዕሉን ፡ ከለር ፡ ቀባው
He colored the illustrations in the book. በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ሥዕሎች ፡ ከለር ፡ ቀባቸው
2. አከሰለ. The fever colored her cheeks. ትኩሳቱ ፡ ጉንጮቿን ፡ አከሰለው
3. አዛባ. The dishonest general colored his report of the battle. አታላዩ ፡ ጀኔራል ፡ ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ የሰጠውን ፡ መግለጫ ፡ አዛባው

**color** (n.)
1. ቀለም. I do not like any of these colors. ከነዚህ ፡ ቀለማት ፡ አንዱንም ፡ አልወድም
2. የተለየ ፡ ውበት. His gift for description adds color to his stories. ለመግለጽ ፡ ያለው ፡ ተሰጥዎ ፡ ለሚነግራቸው ፡ ታሪኮች ፡ የተለየ ፡ ውበት ፡ ይሰጣቸዋል
*She has a lovely color. ደማም ፡ ናት
**call** (n.) **to the colors** የክተት ፡ ሰራዊት ፡ ዐዋጅ
The call to the colors was answered by Ethiopians of all ages. የክተት ፡ ሰራዊቱን ፡ ዐዋጅ ፡ ትንሽ ፡ ትልቁ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ተቀበለው
**call** (v.) **to the colors** ለዘመቻ ፡ ጠራው
His country called him to the colors. አገሩ ፡ ለዘመቻ ፡ ጠራው
**good color** የደም ፡ ግባት
Her good color indicates robust health. የደም ፡ ግባቷ ፡ ሙሉ ፡ ጤንነቷን ፡ ያሳያል
[See also 'blaze, flying colors, salute']

**colored** (adj.)
1. ባለ ፡ ቀለም. Have you any colored shirts? I don't like to wear white ones. ባለ ፡ ቀለም ፡ ሸሚዝ ፡ አለህ ? ነጭ ፡ ሸሚዝ ፡ መልበስ ፡ አልወድም
2. የተዛባ. His account of the battle was colored. ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ ያቀረበው ፡ ታሪክ ፡ የተዛባ ፡ ነበር
**colored people** ነጭ ፡ ያልሆኑ
There is still discrimination against colored people. አሁንም ፡ ገና ፡ ነጭ ፡ ባልሆኑ ፡ ላይ ፡ የቀለም ፡ ልዩነት ፡ ይደረጋል
[See also 'print']

**colorful**
1. የሚያምር. This room has a colorful wallpaper. ይህ ፡ ክፍል ፡ የሚያምር ፡ የግድግዳ ፡ ወረቀት ፡ አለው
2. ጌጥ ፡ የበዛበት. The dress of the 18th century was colorful. የዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዘመን ፡ ልብስ ፡ ጌጥ ፡ የበዛበት ፡ ነበር
3. የሚያስደንቅ. He told us a colorful story of life in the jungle. ስለ ፡ ጫካ ፡ ኑሮ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ታሪክ ፡ አጫወተን

**coloring** ቀለም
The picture's coloring looks fine. የሥዕሉ ፡ ቀለም ፡ ደኅና ፡ ይመስላል

**colorless** ድርቅ ፡ ያለ
The journalist gave a colorless description of the parade. ጋዜጠኛው ፡ ስለ ፡ ሰልፉ ፡ ድርቅ ፡ ያለ ፡ መግለጫ ፡ ሰጠ
**be colorless** ቀለም ፡ የለውም
Pure water is colorless. ንጹሕ ፡ ውኃ ፡ ቀለም ፡ የለውም

**colossal** በጣም ፡ ትልቅ
Tokyo is a colossal city. ቶኪዮ ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ከተማ ፡ ናት

**colt** የፈረስ ፡ ውርንጭላ ፤ የፈረስ ፡ ግልገል
The colt runs around in the field. የፈረሷ ፡ ውርንጭላ ፡ (ግልገል) ፡ ሜዳ ፡ ውስጥ ፡ ትፈነጫለች

**column**
1. ዓምድ. You can recognize the house by its

white columns. ቤቱን ፡ በነጫጭ ፡ ዓምዶቹ ፡ ልትለየው ፡ ትችላለህ
The article is in the third column on the first page. ጽሑፉ ፡ በመጀመሪያው ፡ ገጽ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓምድ ፡ ላይ ፡ ነው
2. ረድፍ. He summed up a long column of figures. በረድፍ ፡ የተደረደሩ ፡ ብዙ ፡ ቁጥሮችን ፡ ደመረ

**coma, be in a ~** በሕመም ፡ ራሱን ፡ አያውቅም
He has been in a coma for the last two days. ባለፉት ፡ ሁለት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ በሕመም ፡ ራሱን ፡ አያውቅም ፡ ነበር

**comb** (v.)
1. አበጠረ. Did your mother comb your hair? እናትህ ፡ ጸጉርህን ፡ አበጠረችልህ ?
2. አሰሰ. The police combed the whole city. ፖሊሶቹ ፡ ከተማውን ፡ በሞላ ፡ አሰሱት

**comb** (n.)
1. ማበጠሪያ. Where can I buy a comb? ማበጠሪያ ፡ የት ፡ ልገዛ ፡ እችላለሁ ?
2. ሚዶ. He bought a beautiful Ethiopian comb. ጥሩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሚዶ ፡ ገዛ

**combat** (v.)
1. ተከላከለ. Vaccines help to combat disease. ክትባት ፡ በሽታን ፡ ለመከላከል ፡ ይረዳል
2. አጠፋ. The whole village turned out to combat the fire. መንደሩ ፡ ሁሉ ፡ እሳቱን ፡ ለማጥፋት ፡ ወጣ
3. ተቋቋመ. The U.N. tries to combat militarism. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ በጦር ፡ ኀይል ፡ መጠቀምን ፡ ለመቋቋም ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነው

**combat** (n.) ውጊያ
He was wounded in combat. በውጊያው ፡ ላይ ፡ ቈሰለ

**be in combat** ተዋጋ
Our soldiers have never been in combat. ወታደሮቻችን ፡ ተዋግተውም ፡ አያውቁ

**combative** የጠበኛነት
He displayed a combative attitude. የጠበኛነት ፡ ስሜት ፡ አሳየ

**combination** ኅብር
How do you like the combination of red and gray? የቀይና ፡ የግራጫ ፡ ኅብር ፡ ደስ ፡ ይልሃል ?
*The college is supported by a combination of private money and government money. ኮሌጁ ፡ የሚካሄደው ፡ በግልና ፡ በመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ መዋጮ ፡ ነው

**combine**
1. አጣመረ. Can't you combine the two sentences? ሁለቱን ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ልታጣምራቸው ፡ አትችልም ?
2. ቀላቀለ. He never combines pleasure with business. እሱ ፡ ከቶ ፡ ሥራን ፡ ከደስታ ፡ ጋር ፡ አይቀላቅልም
3. አቀላቀለ. She combined the ingredients to make the stew. ወጥ ፡ ለመሥራት ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ነገሮች ፡ አቀላቀለች
4. አንድ ፡ ላይ ፡ አደረገ. If we combine all our money, we will be able to buy a car. ገንዘባችንን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ብናደርገው ፡ መኪና ፡ ልንገዛ ፡ እንችላለን
5. አስተባበረ. They combined their efforts to pull the car out of the ditch. መኪናውን ፡ ከጉድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ለመጐተት ፡ ጉልበታቸውን ፡ አስተባበሩ

**combine against** በ - - - ላይ ፡ አደመ(በት)
The employees combined against the new boss. ሠራተኞቹ ፡ ባዲሱ ፡ አለቃ ፡ ላይ ፡ አደሙበት

**combined** ተደምሮው
This country produces more coffee than all other countries combined. ይህ ፡ አገር ፡ ሌሎቹ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ተደምረው ፡ ከሚያመርቱት ፡ የበለጠ ፡ ቡና ፡ ያመርታል

**with combined efforts** በመተባበር
With combined efforts, we will be able to do it. በመተባበር ፡ ልንሠራው ፡ እንችላለን

**combustible** ነዳጅ
Wood is combustible. ዕንጨት ፡ ነዳጅ ፡ ነው

**combustion** መቃጠል
Once the combustion of gasoline begins, the process is irreversible. ቤንዚን ፡ አንዴ ፡ መቃጠል ፡ ከጀመረ ፡ ሊመለስ ፡ አይችልም

**come** (came)
1. መጣ. When does he come to town? ወደ ፡ ከተማ ፡ መቼ ፡ ይመጣል ?
Let there come what may! የመጣ ፡ ይምጣ
2. ደረሰ. When your turn comes, speak up! ተራህ ፡ ሲደርስ ፡ በደንብ ፡ ተናገር
3. ዋለ. That holiday comes on a Monday. ያ ፡ በዓል ፡ ሰኞ ፡ ላይ ፡ ይውላል
*He comes from a poor family. ትውልዱ ፡ ከድኻ ፡ ቤተሰብ ፡ ነው
*This cloth comes only in two colors. ይህ ፡ ጨርቅ ፡ ቀለሙ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ብቻ ፡ ነው
*That's what comes of being careless. የግዴለሽነት ፡ ውጤቱ ፡ ይህ ፡ ነው

*When it comes to making a decision, he has to ask his wife for help. ውሳኔ ፡ ማድረግ ፡ ቢያስፈልገው ፡ ሚስቱን ፡ እርዳታ ፡ መጠየቅ ፡ ግድ ፡ ይሆንበታል

**come about** ሊሆን ፡ ቻለ
How did all this come about? ይህ ፡ ሁሉ ፡ እንዴት ፡ ሊሆን ፡ ቻለ ?

**come across**
1. አቋርጦ ፡ መጣ. We came across the mountains by car. ተራራውን ፡ በመኪና ፡ አቋርጠን ፡ መጣን
2. አገኘ. I came across my friend's name in this book. የጓደኛዬን ፡ ስም ፡ እዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ አገኘሁ
3. አጋጠመ(ው). +We came across hard words in this book. እዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከባድ ፡ ቃላት ፡ አጋጠሙን
*His speech came across effectively. ንግግሩ ፡ መሬት ፡ ጠብ ፡ አይልም

**come along**
1. አብሮት ፡ መጣ ፤ ከሱ ፡ ጋር ፡ መጣ. Do you want to come along? አብረኸን ፡ ልትመጣ ፡ ትፈልጋለህ ?
We tried to prevail on him to come along. ከኛ ፡ ጋር ፡ እንዲመጣ ፡ ልናግባባው ፡ ሞከርን
2. ተካሄደ. How is your work coming along? ሥራህ ፡ እንዴት ፡ ይካሄዳል ?

**come apart**
1. ተለያየ. The chair is coming apart already. ወንበሩ ፡ ካሁኑ ፡ መለያየት ፡ ጀምሯል
2. ወላለቀ. The bus came apart. አውቶቡሱ ፡ ወላለቀ

**come around**
1. ወደዚህ ፡ አካባቢ ፡ መጣ. He comes around about 2:00 o'clock. በስምንት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ወደዚህ ፡ አካባቢ ፡ ይመጣል
2. ብቅ ፡ አለ ፤ ጎራ ፡ አለ. Why don't you come around some evening? አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ለምን ፡ ብቅ ፡ አትልም ?
Please come around at six! በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ጎራ ፡ በል
3. ተስማማ. After our argument, she finally came around. ከተነጋገርንበት ፡ በኋላ ፡ ተስማማች

**come around to**
1. በ - - - ተስማማ. He finally came around to my view. የኋላ ፡ ኋላ ፡ በኔ ፡ ሐሳብ ፡ ተስማማ
2. እሺ ፡ አለ. He came around to our demands. የጠየቅነውን ፡ እሺ ፡ አለን ፡ (or እሺ ፡ አሰኘነው)

**come at** ተጋበዘ(በት)
He came at me with a knife. በጩቤ ፡ ተጋበዘብኝ

**come back** ተመለሰ
He came back to Ethiopia a changed man. ልዩ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመለሰ

**come before**
1. ቀደመ. Ladies come before gentlemen. ወይዛዝርት ፡ ከመኳንንት ፡ ይቀድማሉ
2. ቀረበ. The complaint will come before the U.N. Assembly next week. አቤቱታው ፡ ለተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ ይቀርባል

**come between** አጣላ
Love of money came between the two brothers. ሁለቱን ፡ ወንድማማቾች ፡ ገንዘብ ፡ አጣላቸው
*Don't let a quarrel come between us! እንዳንጣላ

**come by**
1. በዚህ ፡ መጣ. Did you see anyone come by? ሰው ፡ በዚህ ፡ ሲመጣ ፡ አይተሃል ?
2. አገኘ. He came by his wealth honestly. ሀብቱን ፡ ያገኘው ፡ በንጹሕ ፡ መንገድ ፡ ነው

**come down**
1. ወረደ. Can you come down for a moment? ላንድ ፡ አፍታ ፡ ልትወርድ ፡ ትችላለህ ?
2. ቀነሰ. We cannot come down a penny on this price. ከዚህ ፡ ዋጋ ፡ ሳንቲም ፡ አንቀንስም
3. ተደረመሰ. He was present when the building came down. ሕንጻው ፡ ሲደረመስ ፡ እዚያው ፡ ነበረ

**come down with** ያዘ(ው)
He came down with a bad cold. መጥፎ ፡ ጉንፋን ፡ ያዘው

**come forward** ቀረበ
Will anyone come forward as a candidate? ለእጩነት ፡ የሚቀርብ ፡ አለ ?

**come in**
1. ገባ. He came in at nine o'clock. በሦስት ፡ ሰዓት ፡ ገባ
The money owed us is slowly coming in. ያበደርነው ፡ ገንዘብ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየገባ ፡ ነው
2. መጣ. One day he came in to see me. አንድ ፡ ቀን ፡ ሊጠይቀኝ ፡ መጣ

**come inside** ገባ
Why don't you come inside? ለምን ፡ አትገባም ?

**come into** ወረሰ
He came into a large fortune at the age of twenty. በሃያ ፡ ዓመቱ ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ ወረሰ

**come into one's own**
1. ሥልጣኑን ፡ ያዘ. After the king's death, the prince came into his own. ከንጉሡ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ልዑሉ ፡ ሥልጣን ፡ ያዘ

2. ራሱን ፡ ቻለ. He came into his own after his father died. አባቱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ራሱን ፡ ቻለ

**come now!** ተው ፡ እባክህ !
Come now, you don't really mean that! ተው ፡ እባክህ ፤ ካንጀትህ ፡ አይደለም

**come of** (= tr.) ውጤት ፡ አገኘ
Nothing came of his attempt to simplify English spelling. የእንግሊዝኛን ፡ የቃላት ፡ አጻጻፍ ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ የተደረገው ፡ ሙከራ ፡ ውጤት ፡ አላገኘም

**come off**
1. ተበጠሰ. The button has come off. አዝራሩ ፡ ተበጥሷል
2. ወለቀ. One leg of the table has come off. አንደኛው ፡ የጠረጴዛው ፡ እግር ፡ ወልቋል
The handle came off. እጀታው ፡ ወለቀ
3. ተዋጣ(ለት). His speech came off satisfactorily. ንግግሩ ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ ተዋጣለት
4. ተፈጸመ. The contest came off on the day fixed. ውድድሩ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ተፈጸመ

**come on** ጀመረ
The film will be coming on in a few minutes. ፊልሙ ፡ በጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ ውስጥ ፡ ይጀምራል

**come on!**
1. ቶሎ ፡ በል. Come on! It's getting late. ቶሎ ፡ በል ፤ መምሸቱ ፡ ነው
2. ና ፡ እስቲ. Come on; let's race to the end of the road! ና ፡ እስቲ ፤ መንገዱ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ እንሽቀዳደም

**come on something** አገኘ
He came on a cabin while wandering through the woods. ጫካው ፡ ውስጥ ፡ ሲዘዋወር ፡ አንዲት ፡ ጎጆ ፡ አገኘ

**come on with** ያዘ(ው)
+How are you coming on with your new job? አዲሱ ፡ ሥራህ ፡ እንዴት ፡ ይዞሃል ?

**come out**
1. ብቅ ፡ አለ. Can you come out for a moment? አንዳፍታ ፡ ብቅ ፡ ልትል ፡ ትችላለህ ?
2. ወጣ ፡ አለ. Why don't you come out to the country with us? ወደ ፡ ባላገር ፡ አብረኸን ፡ ለምን ፡ ወጣ ፡ አትልም ?
3. ወጣ. He came out of the house. ከቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ወጣ
A bimonthly magazine comes out six times a year. በየሁለት ፡ ወሩ ፡ የሚታተም ፡ መጽሔት ፡ ባመት ፡ ስድስት ፡ ጊዜ ፡ ይወጣል
4. ታትሞ ፡ ወጣ. My book has just come out. የጻፍኩት ፡ መጽሐፍ ፡ ልክ ፡ አሁን ፡ ታትሞ ፡ ወጣ
5. ለቀቀ. The stain won't come out. እድፉ ፡ አይለቅም
6. ተሰማ. When the news came out, everyone was surprised to hear of his demotion. የመሻሩ ፡ ወሬ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ተደነቀ
7. ታየ. His arrogance comes out in every speech he makes. በሚያደርገው ፡ ንግግር ፡ ሁሉ ፡ እብሪቱ ፡ ይታይበታል

**(it) comes out** ታወቀ
Now it comes out that I was right. ልክ ፡ መሆኔ ፡ አሁን ፡ ታወቀ

**come out against** ተቃወመ
The President has come out against changing the constitution. ፕሬዚዳንቱ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ መለወጥ ፡ ተቃወመ

**come out with** አወጣ
The publisher is coming out with a revised edition of the textbook. መጽሐፍ ፡ አታሚው ፡ የመማሪያውን ፡ መጽሐፍ ፡ አዲስ ፡ እትም ፡ ሊያወጣ ፡ ነው

**come over**
1. መጣ. Some friends are coming over to see us this evening. ዛሬ ፡ ማታ ፡ ጥቂት ፡ ወዳጆቻችን ፡ ሊጠይቁን ፡ ይመጣሉ
2. ብቅ ፡ አለ. Come over and see me sometime! አንድ ፡ ቀን ፡ ብቅ ፡ ብለህ ፡ ጠይቀኝ
*He will never come over to our side. ከቶ ፡ ከኛ ፡ ወገን ፡ አይሰለፍም

**come over one** ነካው
I can't imagine what has come over her. ምን ፡ እንደነካት ፡ ላውቅ ፡ አልቻልም

**come (through)**
1. አለፈ. Does the bus come through here? አውቶቡሱ ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ያልፋል ?
2. አየ. He has come through two world wars. ሁለት ፡ የዓለም ፡ ጦርነቶችን ፡ አይቷል

**come (to)**
1. ነፍስ ፡ ዘራ ፤ ነፍሱን ፡ ዐወቀ ፤ ነፍሱ ፡ ተመለሰ. After a few minutes she came to. ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በኋላ ፡ ነፍስ ፡ ዘራች ፡ (ነፍሷ ፡ ተመለሰ)
When he came to, he found himself in the hospital. ነፍሱን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ ሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው
2. ደረሰ. The dress comes to her knees. ቀሚሱ ፡ ከጉልበቷ ፡ ይደርሳል
3. ነው. The bill comes to two dollars. ሒሳቡ ፡ ሁለት ፡ ብር ፡ ነው
4. (= tr.) አገኘ. +They promised no harm would come to us. ጉዳት ፡ እንደማያገኘን ፡ አረጋገጡልን

**come to pass**
*It came to pass that she married a prince. ልዑል ፡ እንድታገባ ፡ ሆነ

**come true** ተፈጸመ(ለት)
His fondest wish came true. በጣም ፡ የጓጓለ ት ፡ ምኞቱ ፡ ተፈጸመለት

**come (under)** በ - - - ሥር ፡ ተገኘ
What regulation does this come under? ይህ ፡ የሚገኘው ፡ በየትኛው ፡ ደምብ ፡ ሥር ፡ ነው ?
*The company came under the control of a new management. ኩባንያውን ፡ አዲስ ፡ ባለንብረ ት ፡ ተረከበው
*We came under heavy fire from the enemy. ከጠላት ፡ የተተኮሰ ፡ እሩምታ ፡ ወረደብን

**come up**
1. መጣ. Won't you come up for a cup of coffee? መጥተህ ፡ ቡና ፡ አትጠጣም ?
2. ወጣ. The water came up to my waist during that heavy rain. በዚያ ፡ በከባዱ ፡ ዝናብ ፡ ጊዜ ፡ ውኃው ፡ ወገቤ ፡ ድረስ ፡ ወጣ
When the sun comes up, the dew disappears. ፀሐይ ፡ ስትወጣ ፡ ጤዛ ፡ ይረግፋል
3. ደረሰ. She only comes up to my shoulder. በቁመት ፡ ትከሻዬ ፡ ጋ ፡ ትደርሳለች
4. በቀለ. The wheat is beginning to come up. ስንዴው ፡ መብቀል ፡ ጀምሯል
5. ተነሣ. Did the matter come up at the meeting? ጉዳዩ ፡ በስብሰባው ፡ ላይ ፡ ተነሥቶ ፡ ነ በር ?
6. ተፈጠረ. This problem comes up every day. ይህ ፡ ችግር ፡ በየቀኑ ፡ ይፈጠራል
7. አጋጠመ(ው). I can't go with you. Something has come up. ካንተ ፡ ጋር ፡ ልሄድ ፡ አልችልም ፤ አንድ ፡ ነገር ፡ አጋጥሞኛል

**come up to** ተስተካከለ ፤ ታከለ
He does not come up to her in skill. በሙያ ፡ አይስተካከላትም ፡ (አይታከላትም)
*It doesn't come up to my expectations. ያሰብኩትን ፡ ያህል ፡ አይደለም

**come up with** አቀረበ
He came up with a new idea. አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ አ ቀረበ

**come upon** ደረሰ(በት)
I came upon the solution by accident. መፍትሔ ውን ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ደረስኩበት
The police came upon the thieves while they were stealing the money. ሌቦቹ ፡ ገንዘብ ፡ ሲ ሰርቁ ፡ ፖሊስ ፡ ደረሰባቸው

**how come ?**
*How come she is still here? እስካሁን ፡ እንዴ ት ፡ እዚህ ፡ ቆየች ?
[See also many nouns combined with 'come']

## comedy ኮሜዲ
The comedy attracted a large audience. ኮሜዲው ፡ ብዙ ፡ ተመልካች ፡ ሳበ

## comely
1. የደስ ፡ ደስ ፡ ያላት. She is a comely woman. የደስ ፡ ደስ ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ ናት
2. መልካም. Her comely behavior won his love. መልካም ፡ ሁኔታዋ ፡ እንዲወዳት ፡ አደረ ገው

## comestible ምግብ
He imported French comestibles. የፈረንሳይን ፡ ምግቦች ፡ አስመጣ

## (be) comestible የሚበላ ፡ ነው
Some mushrooms are comestible. አንዳንድ ፡ እ ንጉዳዮች ፡ የሚበሉ ፡ ናቸው

## comet ጅራታም ፡ ኮከብ
A bright comet crossed the sky. ብሩህ ፡ ጅራታም ፡ ኮከብ ፡ ሰማዩን ፡ አቋረጠ

## comfort (v.) አጽናና
He stroked her arm to comfort her. ለማጽናናት ፡ ክንዷን ፡ ዳበሳት
This news will comfort you. ይህ ፡ ወሬ ፡ ያጽ ናናሃል

## comfort (n.)
1. ምቾት. They lacked many comforts. ብዙ ፡ ምቾት ፡ አላገኙም
2. መጽናኛ. My sister is a great comfort to me. እኅቴ ፡ ለኔ ፡ ትልቅ ፡ መጽናኛዬ ፡ ናት
3. ደስታ. Good health is a source of comfort. መልካም ፡ ጤንነት ፡ የደስታ ፡ ምንጭ ፡ ነው

**give comfort** አጽናና
Your kind words give me comfort in a difficult time. መልካም፡ ንግግርህ ፡ በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ አጽ ናንቶኛል

**see to the comfort of** ተከባከበ
The hostess personally saw to the comfort of her guests. እመቤቲቱ ፡ ራሳቸው ፡ እንግዶቹን ፡ ተከባከቡ

## comfortable ምቹ
This chair is not very comfortable. ይህ ፡ ወን በር ፡ በጣም ፡ ምቹ ፡ አይደለም
*Make yourself comfortable! እንግዳ ፡ አትሁን

**be comfortable ተመቸ(ው)**
The baby is not comfortable. Let him down from your shoulder! ሕፃኑ ፡ አልተመቸውም ፤ ከ ትከሻህ ፡ ላይ ፡ አውርደው

**feel comfortable ተዝናና**
I don't feel comfortable in the same room with her. ከሷ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ስሆን ፡ አልዝናናም

## comfortably
*We are comfortably established in our new home. አዲሱ ፡ ቤታችን ፡ ተስማምቶናል

## comic አሥቂኝ
A clown is a comic actor. ተራቢ ፡ አሥቂኝ ፡ ተ ዋናይ ፡ ነው

## comical አሥቂኝ
The most comical things always happen to him. ሁልጊዜ ፡ በጣም ፡ አሥቂኝ ፡ ነገሮች ፡ ይደ ርሱበታል

## comma ንኡስ ፡ ሰረዝ
When nouns follow one another they are separated by a comma. ስሞች ፡ ተከታትለው ፡ ሲገቡ ፡ በንኡስ ፡ ሰረዝ ፡ ይለያሉ

## command (v.)
1. **አዘዘ**. He commanded the soldiers to advance. ወታደሮቹን ፡ ወደፊት ፡ እንዲገፉ ፡ አዘዘ
The captain commands his ship. ካፒቴኑ ፡ መ ርከቡን ፡ ያዛል
2. **ለመቈጣጠር ፡ አስቻለ**. This advantageous position commands three roads. ይህ ፡ ምቹ ፡ ስ ፍራ ፡ ሦስት ፡ መንገዶችን ፡ ለመቈጣጠር ፡ ያስችላል
3. **አለው** (for subordinate *ይኖር-). He cannot command so large a sum of money. ይህን ፡ ያ ህል ፡ አያሌ ፡ ገንዘብ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም
4. **ተሰጠ(ው)**. +He commands much respect for his attitude. ለሁኔታው ፡ ብዙ ፡ ክብር ፡ ይሰጠ ዋል
5. **አስተዳደረ**. The Pharaoh commanded 10,000 slaves. ፈርዖኑ ፡ ዐሥር ፡ ሺህ ፡ ባሪዎች ፡ ያስተዳ ድር ፡ ነበር
[See also 'respect']

## command (n.) ትእዛዝ
Why was my command not carried out? ትእዛዜ ፡ ለምን ፡ አልተፈጸመም ?
*I am at your command. ታዛዥዎ ፡ ነኝ

**be in command አዛዥ ፡ ነው**
Who is in command here? እዚህ ፡ አዛዡ ፡ ማን ፡ ነው ?

**be placed in command አዛዥ ፡ ተደረገ**
He was placed in command of the army. የጦር ፡ ሰራዊት ፡ አዛዥ ፡ ተደረገ

**have a command of ቻለ**
Does he have a good command of English? እንግሊዝኛ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ይችላል ?

**take command of**
1. **አዛዥነት ፡ ወሰደ**. When the major was killed, the captain took command of the regiment. ሻለቃው ፡ በተገደለ ፡ ጊዜ ፡ ሻምበሉ ፡ የጦሩን ፡ አዛዥነት ፡ ወሰደ
2. **ኀላፊነት ፡ ወሰደ**. He took command of the task of feeding refugees. ስደተኞቹን ፡ የመመገ ብ ፡ ኀላፊነት ፡ ወሰደ
[See also 'bark, second']

## commander አዛዥ
He is a commander of the First Regiment. ያንደኛ ፡ ረጂማ ፡ አዛዥ ፡ ነው

## commander in chief ዋና ፡ አዛዥ
The commander in chief will visit the battalion. ዋናው ፡ አዛዡ ፡ ሻለቃውን ፡ ይጐበኛሉ

## commanding officer አዛዥ ፡ መኰንን
The commanding officer set an eight o'clock curfew. አዛዡ ፡ መኰንን ፡ ከሁለት ፡ ሰዓት ፡ ጀ ምሮ ፡ የሰዓት ፡ እላፊ ፡ ወሰነ

## commandment
1. **ትእዛዝ**. He violated the commandments of the church. የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ትእዛዝ ፡ አፈ ረሰ
2. **ቃላተ ፡ አሪት**. Moses received the Ten Commandments from God. ሙሴ ፡ ዐሠርቱ ፡ ቃላ ተ ፡ አሪትን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተቀበለ

## commemorate
1. **አስታወሰ**. Christmas commemorates Christ's birth. ገና ፡ የክርስቶስን ፡ መወለድ ፡ ያስታውሳል
2. **አከበረ**. They commemorated the victory with a special celebration. የድሉን ፡ በዓል ፡ በ ልዩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አከበሩ
3. **መታሰቢያ ፡ ነው**. This cathedral commemorates the Emperor's victory. ይህ ፡ ካቴድራ ል ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ድል ፡ መታሰቢያ ፡ ነው

## commemoration መታሰቢያ
The commemoration of the former king is next Sunday. የቀድሞው ፡ ንጉሥ ፡ መታሰቢያ ፡ በሚቀጥለው ፡ እሑድ ፡ ነው

**in commemoration of ለ - - - መታሰቢያ**
A hospital is being built in commemoration of

the princess. ለልዕልቲቱ ፡ መታሰቢያ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ ነው

**commemorative**

*A commemorative monument will be erected for the king. ለንጉሡ ፡ መታሰቢያ ፡ ሐውልት ፡ ይሠራል

**commence** ጀመረ

We will commence work tomorrow. ነገ ፡ ሥራ ፡ እንጀምራለን

**commencement**

1. የሚጀመርበት ፡ ቀን. The commencement for construction was postponed for another time. የሕንጻው ፡ ሥራ ፡ የሚጀመርበት ፡ ቀን ፡ ለሌላ ፡ ጊዜ ፡ ተላልፏል

2. የምረቃ ፡ በዓል. The commencement will be celebrated at the end of the school year. በትምህርት ፡ ዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ የምረቃው ፡ በዓል ፡ ይከበራል

**commend**

1. አመሰገነ. The general commended the troops for their bravery. ጄኔራሉ ፡ ወታደሮቹን ፡ ስለ ፡ ጀግንነታቸው ፡ አመሰገነ

2. ሰላምታ ፡ አቀረበ (ለት). Please commend me to your aunt! እባክህን ፡ ላክስትህ ፡ ሰላምታዬን ፡ አቅርብልኝ

[See also 'care']

**commensurate** ተመጣጣኝ ፤ የተመጣጠነ

Was the pay you received commensurate with the work you did? ታገኝ ፡ የነበረው ፡ ደሞዝ ፡ ከሠራኸው ፡ ጋር ፡ ተመጣጣኝ ፡ ነበር ?

His punishment is commensurate with the crime. ቅጣቱ ፡ ከወንጀሉ ፡ ጋር ፡ የተመጣጠነ ፡ ነው

**comment** (v.)

1. ተቸ. He commented on the situation of Ethiopia at length. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሁኔታ ፡ በሰፊው ፡ ተቸ

2. አስተያየት ፡ ሰጠ. Everyone commented on her new hat. ሰው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ አዲሱ ፡ ባርኔጣዋ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠ

**comment** (n.)

1. አስተያየት. Did he make any comments? አስተያየት ፡ ሰጥቷል ?

2. ትችት. The teacher's comments on the essay helped us to understand it. አስተማሪው ፡ የሰጠው ፡ ትችት ፡ ድርሰቱን ፡ ለመረዳት ፡ አስቻለን

3. የሚነካ. The play is a comment on modern society. ቲያትሩ ፡ ዘመናዊ ፡ ኅብረተ ፡ ሰብን ፡ የሚነካ ፡ ነው

**commentary**

1. ሐተታ. His commentary on Ethiopia was well received. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሰጠው ፡ ሐተታ ፡ ተቀባይነት ፡ አገኘ

The teacher told the students to read the commentary on the Gospel of St. John. ተማሪዎቹ ፡ ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ የተሰጠውን ፡ ሐተታ ፡ እንዲያነቡ ፡ አስተማሪው ፡ ነገራቸው

2. ትርጓሜ. Some Bibles have commentaries that give much information. አንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱሶች ፡ ብዙ ፡ ዕውቀት ፡ የሚሰጥ ፡ ትርጓሜ ፡ አላቸው

**commentator** ሐተታ ፡ ሰጪ

The commentator on this radio station is my friend. የዚህ ፡ ራዲዮ ፡ ጣቢያ ፡ ሐተታ ፡ ሰጪ ፡ ወዳጄ ፡ ነው

**commerce** ንግድ

Ethiopia's commerce has doubled in recent years. በቅርብ ፡ ዓመታት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ ዕጥፍ ፡ ሆኗል

**commercial**

1. የንግድ. Commercial laws are regularly issued by the government. የንግድ ፡ ደንቦች ፡ በየጊዜው ፡ በመንግሥት ፡ ይወጣሉ

2. ገንዘብን ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት. His attitude toward theater is very commercial. ስለ ፡ ቲያትር ፡ ያለው ፡ አስተያየት ፡ ገንዘብን ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት ፡ ነው

**in commercial circles** በነጋዴዎች ፡ ዘንድ

He is well known in commercial circles. በነጋዴዎች ፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ነው

**commiserate** ሐዘን ፡ ገለጸ(ለት)

He commiserated with his friend on his misfortunes. ወዳጁ ፡ ለደረሰበት ፡ መከራ ፡ ሐዘኑን ፡ ገለጸለት

**commission** (v.)

1. ወከለ. He commissioned him to buy books in Ethiopia. ከኢትዮጵያ ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲገዛለት ፡ ወከለው

2. ተዋዋለ. The owners commissioned a painting for the building's lobby. ባለቤቶቹ ፡ በሕንጻው ፡ መተላለፊያ ፡ ላይ ፡ ሥዕል ፡ ለማሣል ፡ ከሠዓሊ ፡ ጋር ፡ ተዋዋሉ

**commission** (n.)

1. **ተግባር**. Mr. John's commission was to send the students home. የሚስተር ፡ ጆን ፡ ተግባር ፡ ተማሪዎቹን ፡ ወደየቤታቸው ፡ መላክ ፡ ነበር
2. **ኮሚሲዮን**. The President appointed a commission to find out why food costs so much. ፕሬዚዳንቱ ፡ ምግብ ፡ የተወደደበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚያጠና ፡ ኮሚሲዮን ፡ አቋቋመ
He receives 10 percent commission on all orders he gets. ከሚያስመጣው ፡ እቃ ፡ ከመቶ ፡ ዐሥር ፡ ኮሚሲዮን ፡ ያገኛል
3. **ማዕረግ**. He received his commission as an officer from the Emperor. የመኰንንነቱን ፡ ማዕረግ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ተቀበለ
4. **መፈጸም**. People are punished for the commission of crimes. ሰዎች ፡ ወንጀል ፡ በመፈጸማቸው ፡ ይቀጣሉ

**be out of commission** አይሠራም
My car is out of commission. መኪናዬ ፡ አይሠራም

**in commission** በሥራ ፡ ላይ ፡ ያለ
The navy has six battleships in commission. የባሕር ፡ ኀይል ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ስድስት ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ አሉት

**put in commission** እንዲሠራ ፡ አደረገ
A great deal of work will be necessary to put this radio in commission again. ይህ ፡ ሬዲዮ ፡ እንዲሠራ ፡ ለማድረግ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ያስፈልገዋል

**commit** (committed)

1. **ፈጸመ**. Who committed the crime? ወንጀሉን ፡ ማን ፡ ፈጸመ ?
2. **አስገባ**. The judge committed the thief to prison. ዳኛው ፡ ሌባውን ፡ እስር ፡ ቤት ፡ አስገባው
3. **ላከ**. The commander has committed all his troops to the front lines. አዛዡ ፡ ወታደሮቹን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ጦሩ ፡ ግንባር ፡ ላካቸው

**commit oneself** ቃል ፡ ገባ
He has committed himself to supporting his mother's children. የናቱን ፡ ልጆች ፡ ለመርዳት ፡ ቃል ፡ ገብቷል
[See also 'care, excess, murder, suicide']

**commitment** አሳቢነት
His commitment to his job prevents him from taking a leave. ለሥራው ፡ ያለው ፡ አሳቢነት ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ እንዲወስድ ፡ አይፈቅድለትም

**make a commitment** ቃል ፡ ገባ
We made a commitment to work at the hospital on Saturdays. ቅዳሜ ፡ ቅዳሜ ፡ ሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ ለመሥራት ፡ ቃል ፡ ገባን

**committee** ደርግ ፤ ኮሚቴ
The committee studied the matter. ደርጉ ፡ (ኮሚቴው) ፡ ጉዳዩን ፡ አጠና

**commodity** (commodities)

1. **የገቢ ፡ ምንጭ**. Coffee is an important commodity for Ethiopia. ቡና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጠቃሚ ፡ የገቢ ፡ ምንጭ ፡ ነው
2. **እቃ**. The price of coffee and other commodities is regulated by the government. የቡናና ፡ የሌሎች ፡ እቃዎች ፡ ዋጋ ፡ በመንግሥት ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው

**common**

1. **የተለመደ**. Is that a common practice? ይህ ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው ?
2. **ተራ**. This is the age of the common man. ይህ ፡ የተራ ፡ ሰው ፡ ዘመን ፡ ነው
3. **የጋራ**. These two countries have common interests. ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ የጋራ ፡ ጥቅም ፡ አላቸው
4. **አንድ ፡ ዓይነት**. The two nations have a common language. ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ቋንቋ ፡ አላቸው
5. **አንድ**. This clan descends from a common ancestor. ይህ ፡ ወገን ፡ ከአንድ ፡ ቅድማያት ፡ ይወርዳል
6. **የተሰራጨ**. Gonorrhea is a common venereal disease. ጨብጦ ፡ የተሰራጨ ፡ የአባል ፡ ዘር ፡ በሽታ ፡ ነው
7. **ጥሬ**. She is very common. በጣም ፡ ጥሬ ፡ ናት
8. **ያልታረመ**. She has common manners. ያልታረመ ፡ ሁኔታ ፡ ይታይባታል
*He has the common good at heart. ለሁሉ ፡ አሳቢ ፡ ነው

**common knowledge** የታወቀ ፡ ነገር
It is common knowledge that he lies. መዋሸቱ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ነው

**be common**

1. **ተገኘ**. Bananas are common in many parts of the world. ሙዝ ፡ በብዙ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ ይገኛል
2. **በዛ**. Where there is no law, banditry is common. ሕግ ፡ ከሌለ ፡ ውንብድና ፡ ይበዛል

**have in common** አንድ ፡ ነው ፤ በጋራ ፡ አለው
She has much in common with her friend. በብዙ ፡ ነገር ፡ ከጓደኛዋ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ናት
The affiliation of the two languages is shown by the many words they have in common. የሁለቱ ፡ ቋንቋዎች ፡ ዝምድና ፡ የሚታወቀው ፡ በጋራ ፡ ባሏቸው ፡ ብዙ ፡ ቃላት ፡ ነው

*We've nothing in common. የሚያገናኘን ፡ ነገር ፡ የለም

**in common with**

*In common with educated people, he likes poetry. እንደተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ቅኔን ፡ ይወዳል
[See also 'border, consent, ground']

**commoner** ማንም ፡ ሰው

There are precedents for a commoner becoming a king. ማንም ፡ ሰው ፡ ንጉሥ ፡ ለመሆን ፡ እንደሚችል ፡ የሚያሳዩ ፡ ምሳሌዎች ፡ አሉ

**common gender** የወል ፡ ጾታ

Some names of animals are nouns of common gender. አንዳንድ ፡ የእንስሳ ፡ ስም ፡ የወል ፡ ጾታ ፡ አላቸው

**commonly**

1. አብዛኛውን ፡ ጊዜ. Arithmetic is commonly taught in elementary schools. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ሒሳብ ፡ ባንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ይሰጣል
2. ብዙውን ፡ ጊዜ. Boys commonly enjoy sports. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ እስፖርት ፡ ይወዳሉ

**common noun** የወል ፡ ስም

A common noun has a singular and a plural. የወል ፡ ስም ፡ የነጠላና ፡ ብዙ ፡ ቁጥር ፡ አለው

**commonplace** የተለመደ ፡ ነገር

Today television is a commonplace. ዛሬ ፡ ቴሌቪዥን ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው

**common sense** የተፈጥሮ ፡ ዕውቀት

Why don't you use your common sense in handling your child? ስለ ፡ ልጅህ ፡ አያያዝ ፡ ለምን ፡ የተፈጥሮ ፡ ዕውቀትህን ፡ አትሠራበትም ?

**commonwealth**

1. [ነጻነት ፡ ያላቸው ፡ አገሮች ፡ በገዛ ፡ ፈቃዳቸውና ፡ ፍላጎታቸው ፡ ለንግድና ፡ ለሌላም ፡ የጋራ ፡ ጉዳይ ፡ ኅብረትን ፡ የፈጠሩ ፡ አገሮች]
2. ሬፑብሊክ. After the king of Greece was deposed, the country became a commonwealth. የግሪክ ፡ ንጉሥ ፡ ከዙፋን ፡ ከተወገዱ ፡ በኋላ ፡ አገሪቱ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ሆነች

**commotion**

1. ሽብር. The news caused a commotion. ወሬው ፡ ሽብር ፡ አስከተለ
2. ሁከት. There was a terrific commotion in the street. መንገዱ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሁከት ፡ ነበር

**communal**

1. ጠቅላላ. Communal punishment was used against the village so that it would turn over the criminal. ወንጀለኛውን ፡ እንዲያወጡ ፡ በመንደሩ ፡ ላይ ፡ ጠቅላላ ፡ ቅጣት ፡ ተወሰነ
2. የጋራ. Communal ownership of land is practiced in northern Ethiopia. በሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ የጋራ ፡ ነው

**lead a communal life** በስብስብ ፡ ኖረ

Members of the Mormon community still lead a communal life. የሞርሞን ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ አሁንም ፡ በስብስብ ፡ ይኖራሉ

**communal labor** ጅጊ

Communal labor is widely practiced in Ethiopia. ጅጊ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በሰፊው ፡ የተለመደ ፡ ነው

**commune** (v.) ግንኙነት ፡ አለው

It was thought that witches communed with the devil. ጠንቋዮች ፡ ከሰይጣን ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ አላቸው ፡ እየተባለ ፡ ይታመን ፡ ነበር

**communicable** ተላላፊ

Measles is a communicable disease. ኩፍኝ ፡ ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ ነው

**communicate** (vt.)

1. አስተላለፈ. Flies communicate many diseases. ዝምብ ፡ ብዙ ፡ በሽታ ፡ ታስተላልፋለች
The messenger communicated the general's instructions to the men. ተላላኪው ፡ የጄኔራሉን ፡ ትእዛዝ ፡ ለወታደሮቹ ፡ አስተላለፈ
2. አቀረበ. I asked my sister to communicate my greetings to you. እኅቴ ፡ ሰላምታዬን ፡ እንድታቀርብልኝ ፡ ጠይቄያት ፡ ነበር

**communicate** (vi.)

1. ተገናኘ. You can communicate with most parts of the world by telephone. ከአብዛኛው ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ በስልክ ፡ ለመገናኘት ፡ ይቻላል
2. የሚያገናኝ ፡ በር ፡ አለው. The living room communicates with the dining room. ሳሎኑ ፡ ከምግብ ፡ ቤቱ ፡ ጋር ፡ የሚያገናኝ ፡ በር ፡ አለው
3. ተግባባ. They communicate easily. በቀላሉ ፡ ይግባባሉ

**communicate with each other** ተገናኙ

They communicate with each other every day. በየቀኑ ፡ ይገናኛሉ

**communication**

1. ግንኙነት. All communication with Asmara has been stopped by the rains. በዝናቡ ፡ የተነ

ሣ ፡ ከአሥመራ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ሁሉ ፡ ተቋርጧል

We're not in communication with them. ከነሱ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የለንም

2. መተላለፊያ. There is no communication between the two rooms. በሁለቱ ፡ ክፍሎች ፡ መሀከል ፡ መተላለፊያ ፡ የለም

3. (= to communicate) ማሰራጨት. The communication of news by radio has only been possible in the last century. ዜናዎችን ፡ በራዲዮ ፡ ማሰራጨት ፡ የተቻለው ፡ ካለፈው ፡ ምእተ ፡ ዘመን ፡ ወዲህ ፡ ነው

4. መገናኛ. Radio is a medium of communication. ራዲዮ ፡ የመገናኛ ፡ ዘዴ ፡ ነው

5. ንግግር. I gather from your communication that .... ከንግግርህ ፡ እንደተረዳሁት - - -

6. መልእክት. This communication is confidential. ይህ ፡ መልእክት ፡ ምስጢር ፡ ነው

7. መተላለፍ. Do not spit in public, since it leads to the communication of disease. የበሽታ ፡ መተላለፍን ፡ ስለሚያስከትል ፡ ባደባባይ ፡ ምራቅህን ፡ አትትፋ

*Among the deaf and dumb, communication is carried on by means of the finger alphabet. ደንቆሮና ፡ ድዳ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሐሳብ ፡ የሚለዋወጡት ፡ በጣታቸው ፡ በሚሰጡት ፡ ምልክት ፡ ነው

**Ministry of Communication and Public Works** የሥራና ፡ የመገናኛ ፡ ሚኒስቴር

The Ministry of Communication and Public Works has charge of the telephone service. የሥራና ፡ የመገናኛ ፡ ሚኒስቴር ፡ የስልክ ፡ አገልግሎት ፡ ኀላፊነት ፡ ተጥሎበታል

## communion

1. መተሳሰር. The close communion between friends helps in overcoming difficulties. የወዳጆች ፡ መተሳሰር ፡ ችግሮችን ፡ ለማስወገድ ፡ ይረዳል

2. ቁርባን. Communion is given only on Sunday. ቁርባን ፡ የሚሰጠው ፡ እሑድ ፡ ብቻ ፡ ነው

**receive communion** ቈረበ

He received communion last Sunday. ያለፈው ፡ እሑድ ፡ ቈረበ

## communiqué መግለጫ

The two leaders signed a joint communiqué. ሁለቱ ፡ መሪዎች ፡ የጋራ ፡ መግለጫ ፡ ተፈራረሙ

## Communist ኮሚኒስት

The Communists took over the government. ኮሚኒስቶቹ ፡ መንግሥቱን ፡ ገለበጡት

## community

1. መንደር. How many families are living in this community? በዚህ ፡ መንደር ፡ ስንት ፡ ቤተሰቦች ፡ ይኖራሉ ?

2. ሕዝብ. These are matters which bear upon the community. እነዚህ ፡ ሕዝቡን ፡ የሚነኩ ፡ ጉዳዮች ፡ ናቸው

3. ኮሚኒቲ. The European community in Addis Ababa organized a Christmas party. ባዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኘው ፡ የአውሮፓውያን ፡ ኮሚኒቲ ፡ አንድ ፡ የልደት ፡ በዓል ፡ ግብዣ ፡ አዘጋጅቷል

4. (= adj.) ተመሳሳይ. Community of interests causes people to work together. ተመሳሳይ ፡ ጥቅም ፡ ሰዎችን ፡ በመተባበር ፡ እንዲሠሩ ፡ ያደርጋል

## commute (vt.) አሻሻለ(ለት) ፤ ቀነሰ(ለት)

The Emperor commuted his death sentence to life imprisonment. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሞት ፡ ፍርዱን ፡ ወደ ፡ ዕድሜ ፡ ይፍታህ ፡ አሻሻሉለት ፡ (ቀነሱለት)

**commute** (vi.) ተመላለሰ

He commutes between Debre Zeit and Addis Ababa. ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ይመላለሳል

## compact

1. የተጠቀጠቀ. It is a very compact bag. በጣም ፡ የተጠቀጠቀ ፡ ከረጢት ፡ ነው

2. ጥብቅ ፡ ያለ. A compact package requires less paper for wrapping. ጥብቅ ፡ ያለ ፡ ጥቅል ፡ ለመጠቅለል ፡ ያነሰ ፡ ወረቀት ፡ ይፈጃል

3. የጠጠረ. This soil is too compact for growing anything. ይህ ፡ አፈር ፡ በጣም ፡ የጠጠረ ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ለማብቀል ፡ አይቻልም

4. አጥር ፡ ምጥን ፡ ያለ. The report the president gave of his trip was compact. ስለ ፡ ጉብኝቱ ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ የሰጠው ፡ መግለጫ ፡ አጥር ፡ ምጥን ፡ ያለ ፡ ነበር

**in a compact bundle** እጭቅ ፡ ብሎ

His books were tied in a compact bundle. መጽሐፎቹ ፡ እጭቅ ፡ ብለው ፡ ተጠፍረዋል

## companion

1. ጓደኛ. He was my close companion all through school. ትምህርት ፡ ቤት ፡ በነበርንበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የቅርብ ፡ ጓደኛዬ ፡ ነበር

Where is the companion to this glove? የዚህ ፡ የጓንቲ ፡ ጓደኛ ፡ የት ፡ አለ?

2. የጉዞ ፡ ጓደኛ. We were companions on the journey to America. ወደ ፡ አሜሪካ ፡ ስንሄድ ፡ የጉዞ ፡ ጓደኞች ፡ ነበርን

**companionship** ከሱ ፡ ጋር ፡ መሆን
He enjoys the companionship of his dog. የውሻው ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ መሆን ፡ ያስደስተዋል

**company** (companies)
1. ጓድ. She guided a company of tourists. አንድ ፡ ያገር ፡ ጐብኝዎች ፡ ጓድ ፡ አስጐበኘች
2. ጓደኞች. We are known by the company we keep. አብረን ፡ በምንውለው ፡ ጓደኞቻችን ፡ እንገመታለን
3. እንግዶች. Are you expecting company this evening? ዛሬ ፡ ማታ ፡ እንግዶች ፡ አሉብህ ?
4. የሱ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ መሆን. His company has been a great consolation to me. የሱ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ መሆን ፡ ትልቅ ፡ መጽናኛ ፡ ሆኖኛል
5. አብረውት ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች. His exposure of his anger shocked the company. ቁጣውን ፡ አለመደበቁ ፡ አብረውት ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ አስደነገጣቸው
6. ሻምበል. I served in his company. በሻምበሉ ፡ ውስጥ ፡ አገልግያለሁ
7. ኩባንያ. What company do you represent? የየትኛው ፡ ኩባንያ ፡ ወኪል ፡ ነህ ?

**in company** ሰው ፡ ሲኖር
She behaves well in company. ሰው ፡ ሲኖር ፡ ታድባለች

**(be) in company** ከሰው ፡ ጋር ፡ ሆነ
She blushes easily when she is in company. ከሰው ፡ ጋር ፡ ስትሆን ፡ ቶሎ ፡ ታፍራለች

**keep company** ጓደኛ ፡ አበጀ
Don't keep bad company! መጥፎ ፡ ጓደኛ ፡ አታብጅ

**keep someone company**
1. አጫወተ. Keep me company for a while! ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አጫውተኝ
2. አብሮት ፡ ቆየ. My wife kept Mrs. Belaynesh company while her husband was out of town. የወይዘሮ ፡ በላይነሽ ፡ ባል ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ የኔ ፡ ሚስት ፡ አብራት ፡ ቆየች

**part company** ተለየ ፤ ተለያየ
I was sorry to part company with such a pleasant fellow. እንደዚህ ፡ ደስ ፡ ከሚል ፡ ሰው ፡ ስለይ ፡ በጣም ፡ አዝኜ ፡ ነበር
They disagreed violently and parted company. ተጣልተው ፡ ተለያዩ

**part company with** በሐሳብ ፡ ተለየ
On this question, I must part company with you. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በሐሳብ ፡ ካንተ ፡ ሳልለይ ፡ አልቀርም

**comparable**
1. ተነጻጻሪ. A fire is comparable with the sun: both give light and heat. እሳት ፡ ከፀሐይ ፡ ጋር ፡ ተነጻጻሪ ፡ ነው ፤ ሁለቱም ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀት ፡ ይሰጣሉ
2. የሚመዛዘን. The present world situation is in no way comparable to the situation in 1930. ያሁኑ ፡ የዓለም ፡ ሁኔታ ፡ ከ፲፱፻፳፪ው ፡ ዓ. ም. ሁኔታ ፡ ጋር ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ የሚመዛዘን ፡ አይደለም

**comparative** (n.) የማነጻጸር ፡ ደረጃ
Amharic has no special form of the adjective to express the comparative. አማርኛ ፡ የቅጽልን ፡ የማነጻጸር ፡ ደረጃ ፡ ለመግለጽ ፡ የተለየ ፡ ዘዴ ፡ የለውም

**comparative** (adj.)
1. (= adv.) በመጠኑ. Screens give us comparative freedom from flies. መጋረጃዎች ፡ ዝንቦችን ፡ በመጠኑ ፡ ይከላከላሉ
2. (= adv.) በማወዳደር. I am making a comparative study of the weights of boys and girls. የወንዶችና ፡ የሴቶችን ፡ ክብደት ፡ በማወዳደር ፡ ጥናት ፡ አደርጋለሁ

**comparatively**
1. ከሌላው ፡ ጋር ፡ ሲታይ. It was comparatively easy. ከሌላው ፡ ጋር ፡ ሲታይ ፡ ቀላል ፡ ነበር
2. ከሌላው ፡ ስናመዛዝን. Cotton goods are comparatively inexpensive. ከሌሎች ፡ ሸቀጣ ፡ ሸቀጥ ፡ ስናመዛዝነው ፡ ከጥጥ ፡ የተሠሩ ፡ እቃዎች ፡ ርካሽ ፡ ናቸው

**compare** (vt.)
1. አነጻጸረ. Compare the two translations, and tell me which is better! ሁለቱን ፡ ትርጉሞች ፡ አነጻጽረህ ፡ የትኛው ፡ እንደሚሻል ፡ ንገረኝ
2. አመሳሰለ. Poets compare sleep with death. ባለቅኔዎች ፡ እንቅልፍን ፡ ከሞት ፡ ጋር ፡ ያመሳስሉታል

**compare** (vi.) ተወዳደረ
Artificial light cannot compare with daylight for general use. ለጠቅላላ ፡ አገልግሎት ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ብርሃን ፡ ከፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ጋር ፡ አይወዳደርም
[See also 'note']

**comparing** ማነጻጸር
Comparing France with the United States is not a good comparison. ፈረንሳይን ፡ ከአሜሪካ ፡ ጋር ፡ ማነጻጸር ፡ ጥሩ ፡ ማነጻጸር ፡ አይደለም

**comparison** ማነጻጸር ፤ ማወዳደር
The teacher's comparison of the heart to a

pump helped the students to understand its function. አስተማሪው ፡ ልቡን ፡ ከፖምፕ ፡ ጋር ፡ ማነጻጸሩ ፡ (ማወዳደሩ) ፡ ተማሪዎቹ ፡ አሠራሩን ፡ እንዲገነዘቡት ፡ ጠቀማቸው

**in comparison** ሲነጻጸር ፤ ሲመዛዘን
The tallest buildings in London are small in comparison with the buildings in New York. በለንደን ፡ የሚገኙት ፡ ረጃጅም ፡ የሚባሉት ፡ ሕንጻዎች ፡ ኒው ፡ ዮርክ ፡ ከሚገኙት ፡ ሕንጻዎች ፡ ጋር ፡ ሲነጻጸሩ ፡ አጫጭሮች ፡ ናቸው
This parish is small in comparison with others. ይህ ፡ ደብር ፡ ከሌሎች ፡ ጋር ፡ ሲመዛዘን ፡ አነስተኛ ፡ ነው

**compartment**
1. ክፍል. All compartments in this car are crowded. እዚህ ፡ ፋርጎ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ክፍሎች ፡ ሁሉ ፡ ተጣበዋል
2. ስፍራ. The document was hidden in a secret compartment. ሰነዱ ፡ በምስጢራዊ ፡ ስፍራ ፡ ተደብቆ ፡ ነበር

**compass** (v.)
1. (= pass.) ተከለለ. +An old stone wall compasses his property. ንብረቱ ፡ በቆየ ፡ የድንጋይ ፡ ካብ ፡ ተከልሏል
2. ገመተ. His mind couldn't compass the extent of the disaster. ያደጋውን ፡ ከፍተኛነት ፡ አእምሮው ፡ ሊገምት ፡ አልቻለም

**compass** (n.)
1. ኮምፓስ. You need a compass to draw circles with. ክበብ ፡ ለመሥራት ፡ ኮምፓስ ፡ ያስፈልግሃል
If you are traveling in the forest, you should take a compass. በጫካ ፡ ውስጥ ፡ የምትጓዝ ፡ ከሆነ ፡ ኮምፓስ ፡ መያዝ ፡ አለብህ
2. ክልል. A prisoner must remain within the compass of the prison walls. እስረኛ ፡ በወህኒ ፡ ቤቱ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ አለበት

**stay within the compass** ከ - - አልወጣም
Her actions stayed within the compass of propriety. ሁኔታዋ ፡ ሁሉ ፡ ከተገቢነት ፡ ያልወጣ ፡ ነበር

**compassion** ከፍ ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ
He was filled with compassion for the refugees. ለስደተኞቹ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ ተሰማው

**arouse compassion** አሳዘነ
The meager face of the beggar aroused his compassion. የተጐሳቈለው ፡ የለማኙ ፡ ፊት ፡ አሳዘነው

**compassionate** ርኅሩኅ
He is compassionate toward the needy. ሰውየው ፡ ለተቸገረ ፡ ሁሉ ፡ ርኅሩኅ ፡ ነው

**compatible**
1. የሚስማሙ. They are the most compatible couple I know. እንደዚህ ፡ የሚስማሙ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አላየሁም
2. ተስማሚ. This lamp is compatible with the style of the room. ይህ ፡ ፋኖስ ፡ ከዚህ ፡ ክፍል ፡ አሠራር ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ ነው

**compatriot** ያገር ፡ ልጅ
I try to help him because he is my compatriot. ያገሬ ፡ ልጅ ፡ ስለሆነ ፡ ልረዳው ፡ እሞክራለሁ

**compel** (compelled) አስገደደ
You compel me to take this step. ይህንን ፡ እርምጃ ፡ እንድወስድ ፡ ታስገድደኛለህ
[See also 'obedience']

**compensate**
1. ካሰ. Italy compensated Ethiopia for wartime damage. በጦርነቱ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኢጣልያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ካሰች
2. ተጨማሪ ፡ ሒሳብ ፡ ከፈለ. This company compensates its employees for overtime. ይህ ፡ ኩባንያ ፡ ሰዓት ፡ እላፊ ፡ ለሚሠሩት ፡ ተጨማሪ ፡ ሒሳብ ፡ ይከፍላል
3.አስተካከለ. Glasses compensate for weak eyes. መነጽር ፡ ደካማ ፡ ዓይኖችን ፡ ያስተካክላል

**compensation**
1. ካሳ. He received compensation for his injuries. ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ካሳ ፡ ተቀበለ
2. ዋጋ. He receives adequate compensation for the work he does. ለሚሠራው ፡ ሥራ ፡ በቂ ፡ ዋጋ ፡ ይከፈለዋል

**compete**
1. ተወዳደረ. Of course I can't compete with you. እርግጥ ፡ ነው ፤ ካንተ ፡ ጋር ፡ ልወዳደር ፡ አልችልም
2. ተካፋይ ፡ ነው. Are you competing in the contest? ውድድሩ ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ ነህ ?

**competence** ብቁነት
He is without competence for that job. ለዚህ ፡ ሥራ ፡ ብቁነት ፡ የሌለው ፡ ነው

**competent**
1. ችሎታ ፡ ያለው. It is necessary to have a competent leader. ችሎታ ፡ ያለው ፡ መሪ ፡ ያስፈልጋል
2. ጐበዝ. He is a very competent businessman. እሱ ፡ በጣም ፡ ጐበዝ ፡ ነጋዴ ፡ ነው

**competition**

1. ውድድር. Competition is a necessary part of trade. ውድድር ፡ ለንግድ ፡ ከሚያስፈልጉት ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ነው

The swimming competition will be held on Saturday. የዋናው ፡ ውድድር ፡ ቅዳሜ ፡ ይደረጋል

2. መወዳደር. They are in competition with each other. እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በመወዳደር ፡ ላይ ፡ ናቸው

**competitive**

1. ውድድር ፡ ያለበት. Football is a competitive sport. የእግር ፡ ኳስ ፡ ውድድር ፡ ያለበት ፡ ጨዋታ ፡ ነው

2. የማወዳደሪያ. A competitive examination for the job will be held on January 10th. ለሥራው ፡ የማወዳደሪያ ፡ ፈተና ፡ ጥር ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ይሰጣል

**competitor** የንግድ ፡ ተወዳዳሪ

My competitor sells at lower prices than me. የንግድ ፡ ተወዳዳሪዬ ፡ እኔ ፡ ከምሸጠው ፡ ዋጋ ፡ ባነሰ ፡ ይሸጣል

**compile**

1. አዘጋጀ. He compiled an Amharic dictionary. አንድ ፡ አማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ አዘጋጀ

2. መዘገበ. He compiled all the figures asked for by the tax inspector. የታክስ ፡ ተቈጣጣሪው ፡ የጠየቀውን ፡ ሒሳብ ፡ ሁሉ ፡ መዘገበ

**complacent** በራሱ ፡ መደሰቱን ፡ የሚያመለክት

The winner's complacent smile annoyed some people. አሸናፊው ፡ በራሱ ፡ መደሰቱን ፡ የሚያመለክት ፡ ፈገግታው ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎችን ፡ አበሳጫቸው

**be complacent** ረካ

He is quite complacent about his work. በሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ረገድ ፡ በጣም ፡ ረክቷል

**complain**

1. አማረረ. Why don't you do something instead of complaining all the time? ዘወትር ፡ ከማማረር ፡ ለምን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አታደርጉም ?

2. ተማረረ. She complains of severe pains. ባሰቃቂ ፡ ሕመም ፡ ትማረራለች

3. አመለከተ. We complained to the manager about the noise. ስለ ፡ ጫጫታ ፡ ለሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ አመለከትን

4. አቤቱታ ፡ አቀረበ ፤ አቤት ፡ አለ. It won't do you much good to complain. አቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ ብዙ ፡ አይጠቅምህም

Sir! I came to complain. ጌታዬ ፤ አቤት ፡ ልል ፡ መጥቻለሁ

5. ተነጫነጨ. Nothing satisfies her; she is always complaining. ምንም ፡ ነገር ፡ አይጥማትም ፤ ሁልጊዜ ፡ ትነጫነጫለች

**complaint**

1. ክስ. The court dismissed the complaint after a hearing. ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳዩን ፡ ካዳመጠ ፡ በኋላ ፡ ክሱን ፡ ሰረዘ

2. ቅሬታ ፤ ስሞታ. Do you have any complaints? ቅሬታ ፡ አለህ ?

Your complaint is unjustified. ስሞታህ ፡ መሠረት ፡ የለውም

3. አቤቱታ. His boss rejected his complaint. አለቃው ፡ አቤቱታውን ፡ አልተቀበለውም

4. ንዝንዝ. I am tired of your everlasting complaints. ማለቂያ ፡ የሌለው ፡ ንዝንዝህ ፡ አሰልችቶኛል

*Backache is his chief complaint. በጣም ፡ የሚያማርረው ፡ የጀርባ ፡ ሕመም ፡ ነው

*The doctor asked her the nature of the complaint. ሐኪሙ ፡ ምኗን ፡ እንዳመማት ፡ ጠየቃት

**complement** (v.) አሟላ

They complement each other well. አንዱ ፡ ሌላውን ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ያሟላዋል

**complement** (n.) ማሟያ

In a race horse, endurance is the complement of speed. በፈረስ ፡ ግልቢያ ፡ ድካም ፡ መቻል ፡ የፍጥነት ፡ ማሟያ ፡ ነው

*The ship now has its full complement of men. መርከቧ ፡ የተመደበላትን ፡ ያህል ፡ ሰው ፡ አግኝታለች

**(be) complementary to** አሟላ

These two books are complementary to each other. እነዚህ ፡ ሁለት ፡ መጽሐፎች ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ ያሟላል

**complete** (v.)

1. ፈጸመ ፤ ጨረሰ. Did you complete your work? ሥራህን ፡ ፈጸምክ ? (ጨረስክ ?)

2. አሟላ. I need several stamps to complete my collection. የሰበሰብኩትን ፡ ለማሟላት ፡ ብዙ ፡ ቴምብሮች ፡ ያስፈልጉኛል

**complete** (adj.)

1. ፍጹም. It was a complete surprise to me. ለኔ ፡ ነገሩ ፡ ፍጹም ፡ ያላሰብኩት ፡ ነበር

2. ሙሉ. They acted in complete accord with him in releasing the prisoners. እስረኞውን ፡ ሲፈቱ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ በሙሉ ፡ መግባባት ፡ ነበር

3. (= adv.) በሙሉ ፡ ልብ. She has complete confidence in the doctor. ሐኪሙን ፡ በሙሉ ፡ ልቧ ፡ ታምነዋለች

4. (= adv.) በጠቅላላው. The complete trip will take two months. በጠቅላላው ፡ ጉዞው ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ይፈጃል
*This is a complete edition of Shakespeare's plays. ይህ ፡ የሼክስፒርን ፡ ድራማዎች ፡ በሙሉ ፡ የያዘ ፡ ነው

**be complete** ተፈጸመ
When will the project be complete? እቅዱ ፡ መቼ ፡ ይፈጸማል ?

**make complete** አሟላ
This volume makes my collection complete. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የሰበሰብኩትን ፡ ያሟላልኛል
[See also 'oblivion']

## completely
1. ፈጽሞ. I admit I was completely wrong about him. ስለሱ ፡ ያለኝ ፡ አስተሳሰብ ፡ ፈጽሞ ፡ የተሳሳተ ፡ መሆኑን ፡ አምናለሁ
2. በሙሉ. My time is completely engaged. ጊዜዬ ፡ በሙሉ ፡ ተይዟል
3. ጨርሶ. He is completely out of his mind. ጨርሶ ፡ አእምሮውን ፡ ስቷል

## completion
1. ፍጻሜ. His last book represented the completion of his literary achievement. የመጨረሻ ፡ መጽሐፉ ፡ የጽሑፍ ፡ ችሎታውን ፡ ፍጻሜ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው
2. (= to complete) መጨረስ. The completion of the job will require another month. ሥራውን ፡ ለመጨረስ ፡ ገና ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ያስፈልገዋል
*After the completion of the job, the workmen went home. ሥራውን ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄዱ

## complex (adj.)
1. የተወሳሰበ. Democracy is a complex form of government. ዲሞክራሲ ፡ የተወሳሰበ ፡ አገዛዝ ፡ ነው
2. የተዘበራረቀ. The directions for reaching the house were so complex that we couldn't understand them. እቤቱ ፡ ለመድረስ ፡ መከተል ፡ ያለብን ፡ ያቅጣጫ ፡ መምሪያ ፡ የተዘበራረቀ ፡ ስለሆነ ፡ ልንረዳው ፡ አልቻልንም
3. ረቂቅ. An X-ray machine is complex. የራጂ ፡ መሣሪያ ፡ ረቂቅ ፡ ነው

## complexion
1. መልክ ፤ የፊት ፡ ቆዳ. Her complexion was a lovely, dark brown. መልኳ ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ጠይም ፡ ነበር
His complexion is spotty. የፊቱ ፡ ቆዳ ፡ ጠቃጠቆ ፡ አለው
2. አኳኋን. The complexion of our lives is changed by modern machines. የኑሯችን ፡ አኳኋን ፡ በዘመናዊ ፡ መሣሪያዎች ፡ ምክንያት ፡ ተለወጠ
[See also 'fresh']

## complexity ውስብስብነት
He was puzzled by the complexity of the problem. በፕሮብሌሙ ፡ ውስብስብነት ፡ ግራ ፡ ገብቶት ፡ ነበር

## compliance (with)
1. ማሟላት. Compliance with his father's demands is distasteful to him. ያባቱን ፡ ፍላጎት ፡ ማሟላት ፡ ይጠላል
2. ማክበር. Compliance with the law is necessary for peace. ሕግን ፡ ማክበር ፡ ለሰላም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**in compliance with** በ - - - መሠረት
I am writing to the director in compliance with your orders. በትእዛዝህ ፡ መሠረት ፡ ለዲሬክተሩ ፡ መጻፌ ፡ ነው

## (be) compliant ታዘዘ
Japanese women are compliant toward their husbands. የጃፓን ፡ ሴቶች ፡ ለባሎቻቸው ፡ ይታዘዛሉ

## complicate
1. አማታ. Don't complicate matters any more than they are! ነገሩን ፡ በይበልጥ ፡ አታማታ
2. አባሰ(በት). The bad weather complicated his illness. መጥፎው ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ በሽታውን ፡ አባሰበት

## complicated (adj.) ውስብስብ ፤ የተወሳሰበ
The procedures to follow in applying for a visa are complicated. ቪዛ ፡ ለማውጣት ፡ የምንከተለው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውስብስብ ፡ ነው
I don't know how to operate this complicated machine. ይህን ፡ የተወሳሰበ ፡ መሣሪያ ፡ ማንቀሳቀስ ፡ አላውቅም

**be complicated** ባሰ
His headaches were complicated by eye trouble. ራስ ፡ ምታቱ ፡ በዓይን ፡ ሕመም ፡ ምክንያት ፡ የባሰ ፡ ሆነ

## complication
*The complication of little rules makes this game hard to learn. የተወሳሰቡ ፡ ጥቃቅን ፡ ደንቦች ፡ ጨዋታውን ፡ ለመማር ፡ አስቸጋሪ ፡ ያደርጉታል

## complicity አባሪ ፡ መሆን ፤ ግብረ ፡ አበርነት
Complicity in a crime will be punished the

same way as commission of the crime itself. በወንጀል ፡ ሥራ ፡ አባሪ ፡ መሆን ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ዋናው ፡ ወንጀል ፡ ያስቀጣል
He was charged with complicity in the theft. በሌብነት ፡ ግብረ ፡ አበርነት ፡ ተከሰሰ

**compliment** (v.) አመሰገነ
He complimented me on my cooking. ስለ ፡ ምግብ ፡ አሠራሬ ፡ አመሰገነኝ

**compliment** (n.) ምስጋና
Thanks for the compliment! ስለ ፡ ምስጋናህ ፡ እግዜር ፡ ይስጥልኝ

**compliments** ሰላምታ
Take this with my compliments to your mother! ይህን ፡ ከሰላምታዬ ፡ ጋር ፡ ለእናትህ ፡ ውሰድልኝ

**pay a compliment** አሞገሰ
Pay a compliment to your boss if you want him to like you. አለቃህ ፡ እንዲወድህ ፡ ከፈለግህ ፡ አሞግሰው

**complimentary**
1. የሚያሞግስ. She made complimentary remarks on the new house. ስለ ፡ አዲሱ ፡ ቤት ፡ የሚያሞግስ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠች
2. ነጻ. I received two complimentary tickets for the theater. ለቲያትሩ ፡ ሁለት ፡ ነጻ ፡ ቲኬቶች ፡ አገኘሁ

**comply** (complied) እሺ ፡ አለ
They asked him to leave, and he complied. እንዲሄድ ፡ አዘዘውት ፡ እሺ ፡ አለ

**comply with** ፈጸመ
We regret that we cannot comply with your request. የጠየቅኸውን ፡ ለመፈጸም ፡ ባለመቻላችን ፡ በጣም ፡ እናዝናለን

**component, ~ part** አካል (pl. አካላት)
The blade and handle are the component parts of a knife. ስለትና ፡ እጀታ ፡ የቢላዋ ፡ አካላት ፡ ናቸው

**comport (with)** ተመጣጠነ
His remarks did not comport with the seriousness of the matter. አስተያየቱና ፡ የጉዳዩ ፡ አሳሳቢነት ፡ አይመጣጠኑም

**comport oneself**
*He comported himself properly. የሚገባ ፡ ጠባይ ፡ አሳየ

**compose**
1. ደረሰ. He has composed much poetry in Geez. ብዙ ፡ ግጥም ፡ በግዕዝ ፡ ደርሷል
He composed that symphony during the war. ሲምፎኒውን ፡ የደረሰው ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ነው
2. አጠናቀረ. He composed his speech from many research notes. ንግግሩን ፡ ከብዙ ፡ የምርመራ ፡ ማስታወሻዎች ፡ አጠናቀረ
3. አረጋጋ. He composed his thoughts. ሐሳቡን ፡ አረጋጋው

**compose oneself** ረጋ ፡ አለ
Stop crying and compose yourself! ማለቃቀሱን ፡ ትተሽ ፡ ረጋ ፡ በይ

**(be) composed**
1. ተቀነባበረ. The figures in the painting are well composed. በሥዕሉ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ምስሎች ፡ በሚገባ ፡ የተቀነባበሩ ፡ ናቸው
2. ተሠራ. This fabric is composed of wool and silk. ይህ ፡ ጨርቅ ፡ የተሠራው ፡ ከሱፍና ፡ ከሐር ፡ ነው

**be composed of** አለው
This book is composed of three main parts. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ሦስት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ክፍሎች ፡ አሉት

**remain composed** ረጋ ፡ አለ
He remained composed during the whole trial. ነገሩ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚታይበት ፡ ጊዜ ፡ ረጋ ፡ ብሎ ፡ ነበር

**composer** የሙዚቃ ፡ ደራሲ
Beethoven was a famous composer. ቤቶቨን ፡ ዝነኛ ፡ የሙዚቃ ፡ ደራሲ ፡ ነበር

**composite** የተውጣጣ
The photographer made a composite picture by putting together parts of several others. ፎቶግራፍ ፡ አንሺው ፡ ከብዙ ፡ ሌሎች ፡ ፎቶግራፎች ፡ የተውጣጣ ፡ አንድ ፡ ፎቶግራፍ ፡ አወጣ

**composition**
1. ድርሰት. Have you done your English composition? የእንግሊዝኛ ፡ ድርሰትህን ፡ ጽፈሃል ?
2. የደረሰው ፡ ሙዚቃ. The orchestra is going to play his compositions tonight. ኦርኬስትራው ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ እሱ ፡ የደረሰውን ፡ ሙዚቃ ፡ ይጫወታል
3. ድብልቅ. The metal is a composition of copper and lead. ብረቱ ፡ የመዳብና ፡ የእርሳስ ፡ ድብልቅ ፡ ይገኝበታል
*Scientists are studying the composition of the soil. የሳይንስ ፡ ሊቆች ፡ አፈሩ ፡ ከምን ፡ ከምን ፡ እንደተሠራ ፡ በማጥናት ፡ ላይ ፡ ናቸው

**composure** እርጋታ
The insult failed to ruffle his composure. ስድቡ ፡ እርጋታውን ፡ አላናወጸውም

**keep (one's) composure** ረጋ ፡ አለ
He kept his composure in the crisis. በብጥብጡ ፡ ጊዜ ፡ ረጋ ፡ ብሎ ፡ ነበር

**compound** (v.) ቀየጠ
He compounded a beverage from several fruit juices. ከብዙ ፡ ፍራፍሬዎች ፡ ጭማቂ ፡ አንድ ፡ መጠጥ ፡ ቀየጠ
The pharmacist compounds medicine. መድኃኒት ፡ ቀማሚው ፡ መድኃኒት ፡ ይቀይጣል
**be compounded** በዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ተደመረ
Your bank deposit's interest will be compounded quarterly. ከባንክ ፡ ቤት ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘብህ ፡ የሚገኘው ፡ ትርፍ ፡ በየሦስት ፡ ወሩ ፡ በዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ይደመራል
*The misery of loneliness was now compounded by his poverty. ድኽነት ፡ የብቸኝነት ፡ ሥቃዩን ፡ አባሰበት

**compound** (n.)
1. ምድረ ፡ ግቢ. The school compound was crowded with students. የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ምድረ ፡ ግቢ ፡ በተማሪዎች ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ ነበር
2. ውሑድ. Split up a compound into its elements! አንድን ፡ ውሑድ ፡ በየጥንተ ፡ ንጥሩ ፡ አለያየው
3. ድብልቅ. The soil is a compound of clay and sand. አፈሩ ፡ የሸክላና ፡ የአሸዋ ፡ ድብልቅ ፡ ነው

**comprehend**
1. ገባ(ው). +He does not comprehend the meaning of the play. የትያትሩ ፡ ትርጉም ፡ አይገባውም
2. ያዘ. Science comprehends the study of physics, chemistry and biology. ሳይንስ ፡ የፊዚክስ ፤ የኬሚስትሪና ፡ የባዮሎጂን ፡ ጥናት ፡ ይይዛል

**(be) comprehensible** የሚገባ ፡ ነው
Yesterday's lecture on electricity was comprehensible. ትናንት ፡ ስለ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ የተሰጠው ፡ ንግግር ፡ የሚገባ ፡ ነበር

**comprehension** የመረዳት ፡ ችሎታ ፤ ዕውቀት
Arithmetic is beyond the comprehension of a child. ሒሳብ ፡ ከልጁ ፡ የመረዳት ፡ ችሎታ ፡ በላይ ፡ ነው
God is beyond the comprehension of man. የእግዚአብሔር ፡ ህልውና ፡ ከሰው ፡ ዕውቀት ፡ በላይ ፡ ነው

**comprehensive**
1. አጠቃላይ. The term's work ended with a comprehensive review. የተርሙ ፡ ሥራ ፡ ባጠቃላይ ፡ ክለሳ ፡ ተፈጸመ
2. ሰፊ. A comprehensive mind can grasp everything. ሰፊ ፡ አእምሮ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ይይዛል

**compress** (v.)
1. አመቀ. They compressed the cotton into bales. ጥጡን ፡ አምቀው ፡ ጥቅል ፡ አደረጉት
2. በቦንዳ ፡ አሰረ. They compressed the cotton before shipping. ጥጡን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ከመላካቸው ፡ በፊት ፡ በቦንዳ ፡ አሰሩት
3. ጨመቀ. He compressed the beans to obtain the oil. ዘይት ፡ ለማውጣት ፡ የጉሎውን ፡ ዘይት ፡ ጨመቀ
4. አጠቃለለ. He compresses a great deal of meaning into a few words. በጥቂት ፡ ቃላት ፡ ብዙ ፡ ሐሳብ ፡ ያጠቃልላል

**compress** (n.) ጨርቅ
He put a cold compress on his head. እርጥብ ፡ ጨርቅ ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ አደረገ

**comprise**
1. ያዘ. The Soviet Union comprises several republics. የሶቪዬት ፡ ኅብረት ፡ ብዙ ፡ ሬፑብሊኮችን ፡ ይይዛል
2. ተገኘ(በት). +The committee comprises men of widely different views. ደርጉ ፡ የተለያዩ ፡ አስተያየቶች ፡ ያሏቸው ፡ ሰዎች ፡ ይገኙበታል

**compromise** (vt.) አጠፋ
The student compromised his good name by cheating. ተማሪው ፡ በማጭበርበር ፡ ጥሩ ፡ ስሙን ፡ አጠፋው
**compromise** (vi.)
1. ግልግል ፡ አደረገ. The two parties could not accept each other's views but compromised. ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ የያንዳንዳቸውን ፡ ሐሳብ ፡ ባይቀበሉም ፡ ግልግል ፡ አደረጉ
2. ከስምምነት ፡ ደረሰ. They compromised on the amount of salary to be paid. ስለሚከፈለው ፡ ደሞዝ ፡ ከስምምነት ፡ ደረሱ
3. ንቅንቅ ፡ አላለም. He never compromises with his principles. ከሚያምንበት ፡ ነገር ፡ ንቅንቅ ፡ አይልም

**compromise** (n.)
1. ከእኔ ፡ ይቅር ፡ ከእኔ ፡ ይቅር ፡ የሚል ፡ ስምምነት. A compromise is never fully satisfactory to both parties. ከእኔ ፡ ይቅር ፡ ከእኔ ፡ ይቅር ፡ የሚል ፡ ስምምነት ፡ ለሁለቱም ፡ ወገን ፡ አያስደስትም
2. አስታራቂ ፡ ሐሳብ. The strike was settled by a compromise. አድማው ፡ ባስታራቂ ፡ ሐሳብ ፡ ቆመ

*We had to accept a compromise between cheaper and more expensive material. ከርካሹና ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ ከሆነው ፡ እቃ ፡ መካከለኛ ፡ የሆነውን ፡ መቀበል ፡ ነበረብን

**compulsion** ግዳጅ
A defeated country usually signs a treaty of peace under compulsion. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የተሸነፈ ፡ አገር ፡ የሰላም ፡ስምምነት ፡ የሚፈርመው ፡ በግዳጅ ፡ ነው

**compulsory** ግዴታ
Attendance in school is compulsory. በትምህርት ፡ ቀን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መገኘት ፡ ግዴታ ፡ ነው

**compulsory education** የመማር ፡ ግዴታ
Compulsory education has not yet been introduced into Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የመማር ፡ ግዴታ ፡ ገና ፡ አልተጀመረም

**compunctions, have ~** ተጸጸተ
He had no compunctions about being late. በመዘግየቱ ፡ አይጸጸትም

**compute** አሰበ ፡ ደረሰ(በት)
He computed his losses at $50. ኪሳራው ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ መሆኑን ፡ አስቦ ፡ ደረሰበት

**comrade** ጓደኛ
They were faithful comrades to the last. እስከ ፡ መጨረሻ ፡ የታመኑ ፡ ጓደኞች ፡ ነበሩ

**con** አሉታ
The two debating teams argued the questions pro and con. ሁለቱ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ የነገሩን ፡ አዎንታና ፡ አሉታ ፡ ተከራከሩበት

**concave** ጐድጐድ ፡ ያለ
The palm of the hand is slightly concave. መዳፍ ፡ ትንሽ ፡ ጐድጐድ ፡ ያለ ፡ ነው

**conceal**
1. ደበቀ ፤ ሸሸገ. She could not conceal her curiosity. ጉጉቷን ፡ ልትደብቀው ፡ (ልትሸሽገው) ፡ አልቻለችም
2. ሸፈነ (ተሸፈነ). The trees were concealed by a very heavy mist. ዛፎቹ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ባለ ፡ ጉም ፡ ተሸፍነው ፡ ነበር

**conceal oneself** ተሸሸገ ፤ ተደበቀ
She concealed herself behind a tree. ከዛፉ ፡ በስተኋላ ፡ ተሸሸገች ፡ (ተደበቀች)

**conceal from view** ከለለ
A clump of trees concealed the house from view. ዕጅብ ፡ ያሉ ፡ ዛፎች ፡ ቤቱን ፡ ከለሉት

**concealment**
1. መደበቅ. The concealment of facts by a witness is a criminal offense. የምስክር ፡ እውነተኛን ፡ ነገር ፡ መደበቅ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ ነው
2. የተደበቀ(በት). He came out of concealment for brief periods of time. ከተደበቀበት ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜያት ፡ ብቻ ፡ ወጣ

**concede**
1. አመነ. You must concede that I have tried hard. በጣም ፡ መሞከሬን ፡ ማመን ፡ አለብህ
2. ሰጠ. He conceded us the right to walk through his land. በመሬቱ ፡ ላይ ፡ የመተላለፍ ፡ መብት ፡ ሰጠን
3. መሸነፉን ፡ አመነ. The candidate conceded early in the evening. ተወዳዳሪው ፡ መሸነፉን ፡ ማታ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ አመነ

**conceit** እብሪት
The film star was puffed up with conceit. የፊልሙ ፡ ኮከብ ፡ በእብሪት ፡ ተወጥራለች

**conceited** ትዕቢተኛ
He is a conceited fool. የጅል ፡ ትዕቢተኛ ፡ ነው

**conceivable**
1. የሚቻል. We take every conceivable precaution against fire. እሳትን ፡ ለመከላከል ፡ የሚቻለንን ፡ ጥንቃቄ ፡ ሁሉ ፡ እናደርጋለን
2. የሚታሰብ. But that isn't conceivable. ግን ፡ ያ ፡ የማይታሰብ ፡ ነው

**conceive**
1. አሰበ. I cannot conceive of her doing such a thing. እሷ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ታደርጋለች ፡ ብዬ ፡ አላስብም
2. ተረዳ. It is difficult to conceive how this motor works. ይህ ፡ ሞተር ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠራ ፡ መረዳት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**be conceived**
1. ተነገረ. The warning was conceived in the plainest language. ማስጠንቀቂያው ፡ የተነገረው ፡ በግልጽ ፡ አነጋገር ፡ ነበረ
2. ታቀደ. The plan is cleverly conceived. እቅዱ ፡ በሥርዓት ፡ የታቀደ ፡ ነው

**conceive a child** ፀነሰች
She conceived a child twelve months after she married. ባገባች ፡ በዐሥራ ፡ ሁለተኛ ፡ ወሯ ፡ ፀነሰች

**conceive the idea** አሰበ
Who first conceived the idea of using steam to drive vehicles? መኪናዎችን ፡ በእንፋሎት ፡

ኀይል ፡ መንዳትን ፡ መጀመሪያ ፡ ያሰበ ፡ ማን ፡ ነው ?

**concentrate** (vt.)

1. ሰበሰበ. The general concentrated his troops to attack the enemy. ጄኔራሉ ፡ ጠላትን ፡ ለማጥቃት ፡ ወታደሮቹን ፡ ሰበሰበ
2. አወፈረ. You can concentrate orange juice by removing water. ውኃውን ፡ በመቀነስ ፡ የብርቱካኑን ፡ ጭማቂ ፡ ልታወፍረው ፡ ትችላለህ
3. አጠነከረ. The soldiers concentrated their fire on a single enemy position. ወታደሮቹ ፡ ተኩሳቸውን ፡ ባንድ ፡ የጠላት ፡ ስፍራ ፡ ብቻ ፡ አጠነከሩ
4. በሙሉ ፡ አዋለ. The student concentrated his attention on the problem. ተማሪው ፡ ሐሳቡን ፡ በሙሉ ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ አዋለ

**concentrate** (vi.)

1. ተሰበሰበ. The crowd concentrated near the gate. ሕዝቡ ፡ መግቢያው ፡ አጠገብ ፡ ተሰበሰበ
2. አጥብቆ ፡ ተመለከተ. We will have to concentrate on the first part. የመጀመሪያውን ፡ ክፍል ፡ አጥብቀን ፡ መመልከት ፡ አለብን

**be concentrated** ተከማቸ

The most important industries are concentrated in the north. ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ የተከማቹት ፡ በሰሜን ፡ ነው

**concentration**

1. መከማቸት. The concentration of enemy troops along the border worried the population. የጠላት ፡ ጦር ፡ በድንበሩ ፡ ላይ ፡ መከማቸት ፡ ሕዝቡን ፡ አሳሰበው
2. ማስተዋል. Chess is a game that requires concentration. ሰንጠረዥ ፡ ማስተዋልን ፡ የሚጠይቅ ፡ ጨዋታ ፡ ነው

**concept** ሐሳብ

He has no concept of hard work. ስለ ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ ምንም ፡ ሐሳብ ፡ የለውም

**conception**

1. ንድፍ. The architect presented a fine conception of the building. መሃንዲሱ ፡ ለሕንጻው ፡ የሚሆን ፡ ረቂቅ ፡ ንድፍ ፡ አቀረበ
2. ማመንጨት. He will get credit for the conception of the plan. ሐሳቡን ፡ በማመንጨቱ ፡ ምስጋና ፡ ይሰጠዋል

*The conception of the United Nations was in 1945. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የተፀነሰው ፡ በ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ.ም. ነበር

**have no conception of** ፈጽሞ ፡ አያውቅም

He has no conception of what we are doing. ምን ፡ እንደምንሠራ ፡ ፈጽሞ ፡ አያውቅም

**concern** (v.)

1. ተመለከተ. This concerns you. ይህ ፡ አንተን ፡ የሚመለከት ፡ ነው
2. አሳሰበ. His poor health concerns me. ጤና ፡ ማጣቱ ፡ ያሳስበኛል

**concern oneself**

1. ደከመ. He concerns himself with obtaining jobs for the refugees. ለስደተኞቹ ፡ ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ ይደክማል
2. ሐሳቡን ፡ አዋለ. He concerns himself with such trivialities. በማይረቡ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ሐሳቡን ፡ ያውላል

**be concerned** (= concern) ተመለከተ

+Where the children are concerned, the mother is always ready to do whatever is necessary. ልጆቹን ፡ በሚመለከት ፡ ነገር ፡ እናትዮው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ለማድረግ ፡ ሁልጊዜ ፡ ዝግጁ ፡ ናቸው

**be concerned (about, with)**

1. አሰበ. We are concerned about their safety. ስለ ፡ ደኅንነታቸው ፡ እናስባለን
2. ተቸገረ. I am not concerned with the details. ስለ ፡ ዝርዝሩ ፡ ሁኔታ ፡ አልቸገርም

**as far as he is concerned** በ - - - በኩል

As far as he is concerned, it is all right. በሱ ፡ በኩል ፡ ግድ ፡ የለም

**concern** (n.)

1. ዓላማ. Our primary concern is the transport of troops. ዋናው ፡ ዓላማችን ፡ ወታደሮችን ፡ ማጓጓዝ ፡ ነው
2. ሥራ. Revision of the new bill is the chief concern of Congress this week. በዚህ ፡ ሳምንት ፡ የምክር ፡ ቤት ፡ ዋና ፡ ሥራ ፡ አዲሱን ፡ ሕግ ፡ ማሻሻል ፡ ነው
3. ጭንቀት. The mother's concern for her child kept her awake all night. እናቲቱ ፡ ስለ ፡ ልጇ ፡ ያደረባት ፡ ጭንቀት ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ እንቅልፍ ፡ ነሣት
4. የሚያሳስብ ፤ ሐሳብ. There is no reason for concern. የሚያሳስብ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለ

Her family was her paramount concern. ዋና ፡ ሐሳቧ ፡ ለቤተሰቦቿ ፡ ነበር

5. ድርጅት. How long have you been with this concern? በዚህ ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ቆየህ ?

*She said it was no concern of mine. አያገባህም ፡ አለችኝ

**have concern** አሰበ
The mayor has great concern for civic beauty. ከንቲባው ፡ ለከተማው ፡ ውበት ፡ ብዙ ፡ ያስባል

**show concern** ተጨነቀ
The phlegmatic fellow showed no concern about the coming hurricane. ግዴለሹ ፡ ሰው ፡ ስለሚመጣው ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ምንም ፡ አልተጨነቀም

**concerning** ስለ
Nothing was said concerning vacation. ስለ ፡ ዕረፍት ፡ ምንም ፡ የተነገረ ፡ ነገር ፡ የለም

**concert** የሙዚቃ ፡ ትርኢይት
How did you like the concert? የሙዚቃውን ፡ ትርኢይት ፡ ወደድከው ?

**in concert** በኅብረት
They acted in concert. በኅብረት ፡ ሠሩ

**concerted** የተባበረ
Their concerted efforts resulted in victory. የተባበረው ፡ ጥረታቸው ፡ ድልን ፡ አስገኘ

**concession**
1. ፈቃድ. The Ethiopian government gave the Sinclair Oil Company a concession to explore for oil. የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ለሲንክሌር ፡ ኩባንያ ፡ ነዳጅ ፡ ዘይት ፡ የሚገኝበትን ፡ ስፍራ ፡ እንዲፈልግ ፡ ፈቃድ ፡ ሰጠ
2. ምሕረት. He consolidated his position with the nobility by granting them tax concessions. ለመኳንንቱ ፡ የግብር ፡ ምሕረት ፡ እያደረገላቸው ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ አጠነከረ
3. ማመን. His concession that he had made a hasty decision was all we wanted to hear. እንድናውቅ ፡ የፈለግነው ፡ የችኰላ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠቱን ፡ ማመኑን ፡ ብቻ ፡ ነው
4. ከእኔ ፡ ይቅር ፡ ከእኔ ፡ ይቅር ፡ ማለት. The quarrel was settled by concessions. ጠቡ ፡ ከእኔ ፡ ይቅር ፡ ከእኔ ፡ ይቅር ፡ በማለት ፡ ተወገደ

**as a concession to** ለማርካት
As a concession to popular feeling, the government reduced the tax. የሕዝቡን ፡ ስሜት ፡ ለማርካት ፡ መንግሥቱ ፡ ግብሩን ፡ ቀነሰ

**make concessions** ለቀቀ ፤ ለቀቅ ፡ አደረገ ፤ ተወ
I had to make some concessions to get them to agree to my plan. በኔ ፡ እቅድ ፡ እንዲስማሙ ፡ አንዳንድ ፡ ጉዳዮችን ፡ ለቀቅ ፡ ማድረግ ፡ (መልቀቅ ፤ መተው) ፡ ነበረብኝ

**make reciprocal concessions** አንዳንድ ፡ ነገሮችን ፡ ለመተው ፡ ተስማሙ
Both sides made reciprocal concessions in order to settle the border problem. የወሰን ፡ ችግራቸውን ፡ ለማስወገድ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮችን ፡ ለመተው ፡ ተስማሙ

**conciliate**
1. አስታረቀ. He tried to conciliate the two parties in the dispute. ሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ ለማስታረቅ ፡ ሞከረ
2. አባበለ. She conciliated her cook with a present. ስጦታ ፡ በመስጠት ፡ ወጥ ፡ ቤቷን ፡ አባበለች
3. አበረደ. The boy's apology conciliated his angry father. የልጁ ፡ ይቅርታ ፡ መጠየቅ ፡ ያባቱን ፡ ንዴት ፡ አበረደው

**conciliation**
1. ስምምነት. Conciliation between the workers and the company proved hard to obtain. በኩባንያውና ፡ በሠራተኞቹ ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ ማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆነ
2. ዕርቅ. Conciliation involved payment of damages to the worker by the company. በዕርቁ ፡ መሠረት ፡ ኩባንያው ፡ ለሠራተኛው ፡ ካሳ ፡ መክፈል ፡ ነበረበት

**conciliator** አስታራቂ
A conciliator must be able to understand the opposing viewpoints. አስታራቂ ፡ የሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ ሐሳብ ፡ ለመረዳት ፡ መቻል ፡ አለበት

**conciliatory** አስታራቂ
His conciliatory remarks were very welcome after so much disagreement. ከብዙ ፡ አለመስማማት ፡ በኋላ ፡ አስታራቂ ፡ ሐሳቡን ፡ በመልካም ፡ ተቀበሉት

**concise** አጥር ፡ ምጥን ፡ ያለ
He made a concise remark. አጥር ፡ ምጥን ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠ

**conclave** የቆይታ ፡ ስብሰባ
A political conclave was held to select a new prime minister. አዲስ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ለመምረጥ ፡ የቆይታ ፡ የፖለቲካ ፡ ስብሰባ ፡ ተደረገ

**conclude** (vt.)
1. ደመደመ. He concluded his speech with a prayer. ንግግሩን ፡ በጸሎት ፡ ደመደመ
They concluded the deal with a handshake. ውሉን ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ በመጨባበጥ ፡ ደመደሙ
2. ፈጸመ(ተፈጸመ). The coronation is concluded when the patriarch anoints the Emperor. የዘ

ውድ ፡ መጫን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ፓትሪያርኩ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥቱን ፡ ሲቀባው ፡ ይፈጸማል
3. ተገነዘበ. From the tracks we saw, we concluded that the animal must be a deer. አውሬው ፡ አጋዘን ፡ መሆኑን ፡ ባየነው ፡ ፋና ፡ ተገነዘብን
4. ወደማለት ፡ ደረሰ. After study, I concluded that Amharic is a difficult language. ከምርምር ፡ በኋላ ፡ አማርኛ ፡ ከባድ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ፡ ወደማለት ፡ ደረስኩ
5. ገለጸ. At the end of his speech, he concluded that all problems were solved. በንግግሩ ፡ መጨረሻ ፡ ችግሮች ፡ ሁሉ ፡ መፍትሔ ፡ ማግኘታቸውን ፡ ገለጸ

**conclude** (vi.) ተደመደመ
The book concluded with a warning to alcoholics. መጽሐፉ ፡ የተደመደመው ፡ ለአልኮል ፡ ሱሰኞች ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ በመስጠት ፡ ነው
*What do you conclude from his remark? ከንግግሩ ፡ ምን ፡ አሳብ ፡ ያለው ፡ ይመስልሃል ?
[See also 'agreement']

**conclusion**
1. ውሳኔ. They failed to reach a conclusion on building a new bridge. አንድ ፡ አዲስ ፡ ድልድይ ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ ጉዳይ ፡ ከውሳኔ ፡ መድረስ ፡ አቃታቸው
The conclusion of the treaty was announced in the newspapers. የስምምነቱ ፡ ውሳኔ ፡ በጋዜጣ ፡ ተገለጸ
2. መጨረሻ. At the conclusion of his speech, he suggested that support be given to the government. በንግግሩ ፡ መጨረሻ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ድጋፍ ፡ መስጠት ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ አቀረበ

**draw a conclusion** ተገነዘበ
What conclusion am I to draw from his speech? ከሱ ፡ ንግግር ፡ ምን ፡ ልገነዘብ ፡ እችላለሁ ?

**in conclusion** በመጨረሻ
In conclusion, I should like to state that .... በመጨረሻ ፡ ልናገር ፡ የምፈልገው ---

**jump to conclusions**
Don't jump to conclusions! ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ አትቸኩል

**conclusive** የማያጠራጥር
The evidence against the burglar is conclusive. በቤት ፡ ሰርሳሪው ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ መረጃ ፡ የማያጠራጥር ፡ ነው

**concoct** አዘጋጀ
The cook concocted a new recipe. ወጥ ፡ ቤቷ ፡ አዲስ ፡ የምግብ ፡ መምሪያ ፡ አዘጋጀች

**concomitant** አብሮ ፡ የሚሄድ
Happiness is not always a concomitant of wealth. ደስታና ፡ ብልጽግና ፡ ዘወትር ፡ አብረው ፡ የሚሄዱ ፡ አይደሉም

**concord** ስምምነት
These two nations live in concord. እነዚህ ፡ ሁለት ፡ አገሮች ፡ በስምምነት ፡ ይኖራሉ

**concordance** የቃላት ፡ ዝርዝር
The Bible concordance is very useful in checking words. የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የቃላት ፡ ዝርዝር ፡ ቃላትን ፡ ለማጣራት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው

**in concordance with** በ --- መሠረት
I must act in concordance with the rules. በሕጉ ፡ መሠረት ፡ መሥራት ፡ አለብኝ

**with the concordance of** ከተስማሙ
With the concordance of the membership, we will adjourn. አባሎች ፡ ከተስማሙ ፡ ስብሰባው ፡ ያበቃል

**concourse** የሕዝብ ፡ መተላለፊያ
A concourse is being built beneath the bus station. ከአውቶቡሱ ፡ ጣቢያ ፡ ሥር ፡ የሕዝብ ፡ መተላለፊያ ፡ እየተሠራ ፡ ነው

**concrete** (n.) ሲሚንቶ
The bridge is built of concrete. ድልድዩ ፡ የተሠራው ፡ ከሲሚንቶ ፡ ነው

**concrete** (adj.)
1. የተጨበጠ. Give me a concrete example. የተጨበጠ ፡ ምሳሌ ፡ ስጠኝ
2. የቁሳቁስ. "Sugar" and "salt" are concrete nouns. ስኳርና ፡ ጨው ፡ የቁሳቁስ ፡ ስሞች ፡ ናቸው

**concubine** ዕቁባት
His wife and his concubine quarreled. ሚስቱና ፡ ዕቁባቱ ፡ ተጣሉ

**concur** (concurred)
1. ተስማማ. All the judges concurred in the decision. ዳኞቹ ፡ በሙሉ ፡ በውሳኔው ፡ ተስማሙ
2. ተጋጠመ. Careful planning and good luck concurred to bring about victory. በጥንቃቄ ፡ የተደረገ ፡ እቅድና ፡ ጥሩ ፡ ዕድል ፡ ስለተጋጠሙ ፡ ድል ፡ ተገኘ

**concurrence**
1. መገናኘት. The concurrence of three large highways causes traffic jams. የሦስቱ ፡ ታላላቅ ፡ አውራ ፡ መንገዶች ፡ መገናኘት ፡ የትራፊክ ፡ መጨናነቅ ፡ ይፈጥራል

2. ስምምነት. The concurrence of the committee was unanimous. የደርጉ ፡ ስምምነት ፡ በሙሉ ፡ ባንድ ፡ ድምፅ ፡ የተደገፈ ፡ ነበር

**concurrent**
1. አንድነት ፡ የተደረገ. The concurrent attacks by land and sea defeated the enemy. በየብስና ፡ በባሕር ፡ አንድነት ፡ የተደረገው ፡ ማጥቃት ፡ ጠላትን ፡ ሊያሸንፍ ፡ ቻለ
2. (= noun) መመሳሰል. The concurrent views of different observers show that the minister was in the wrong. የልዩ ፡ ልዩ ፡ ተመልካቾች ፡ አስተያየት ፡ መመሳሰል ፡ ሚኒስትሩ ፡ የተሳሳተ ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል
**be concurrent with** ተደራረበ(በት)
His illness was concurrent with his financial troubles. ሕመሙና ፡ የገንዘብ ፡ ማጣቱ ፡ ተደራረቡበት

**concurrently** ባንድ ፡ ጊዜ
His novel appeared concurrently with the play. የልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፉ ፡ ከቴያትሩ ፡ ጋር ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ወጣ

**concussion**
1. ጉዳት. Because of the car accident, he suffered a concussion of the brain. በመኪና ፡ አደጋ ፡ ምክንያት ፡ ያንጐል ፡ ጉዳት ፡ ደረሰበት
2. መናጋት. The concussion caused by the explosion broke many windows. በፈንጂው ፡ ምክንያት ፡ የደረሰው ፡ መናጋት ፡ ብዙ ፡ መስኮቶች ፡ ሰባበረ

**condemn**
1. ፈረደ(በት). The judge condemned him to life imprisonment. ዳኛው ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ እስራት ፡ ፈረደበት
2. ነቀፈ. The newspapers condemned foreign agents for the latest disturbances. በቅርቡ ፡ በተፈጸመው ፡ ብጥብጥ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ አነሣሾች ፡ ተካፋይ ፡ በመሆናቸው ፡ ጋዜጦቹ ፡ ነቀፏቸው
3. አወገዘ. The church condemns corrupt morals. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውድቅ ፡ ግብረ ፡ ገብነትን ፡ ታወግዛለች
4. አሳልፎ ፡ ሰጠ. Poverty condemned him to a life of toil. ድኽነት ፡ ለመከራ ፡ ኑሮ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው
5. ከሕዝብ ፡ ወሰደ. The government has had to condemn much land for new highway construction. መንግሥቱ ፡ ብዙ ፡ መሬትን ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ ሥራ ፡ ከሕዝብ ፡ መውሰድ ፡ ነበረበት
6. ለመኖሪያ ፡ አይገባም ፡ አለ. The municipality condemned the slum dwellings. ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ደሳሳ ፡ ጎጆዎች ፡ ለመኖሪያ ፡ አይገቡም ፡ አለ
**be condemned**
1. እንዲፈርስ ፡ ታዟል. This building has been condemned. ይህ ፡ ሕንጻ ፡ እንዲፈርስ ፡ ታዟል
2. አይስማማም ፡ ተባለ. The meat was condemned as unfit for consumption because it was full of worms. ሥጋው ፡ ትል ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ለመብል ፡ አይስማማም ፡ ተባለ
**be condemned to hell** ተኰነነ
The sinner was condemned to hell. ኃጢአተኛው ፡ ተኰነነ

**condensation** የውኃ ፡ መጤዝ
Condensation causes windows to become cloudy. የውኃ ፡ መጤዝ ፡ መስኮቶቹን ፡ ጉም ፡ ያለብሳቸዋል
**make a condensation of** አሳጠረ
Would you make a condensation of the report? መግለጫውን ፡ ታሳጥረዋለህ ?

**condense** አሳጠረ
The newspaper condensed the long speech to a paragraph. ጋዜጣው ፡ ረጅሙን ፡ ንግግር ፡ ባንድ ፡ አንቀጽ ፡ አሳጠረው
**condense to water** አጤዘ
Steam condenses to water when it touches a cold surface. እንፋሎት ፡ ቀዝቃዛ ፡ አካል ፡ ሲነካ ፡ ያጤዛል
**be condensed** ረጋ
Milk is condensed by evaporation. ወተት ፡ የሚረጋው ፡ ውኃው ፡ በመትነኑ ፡ ነው

**condescend** ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አደረገ
The king condescended to eat with the people. ንጉሡ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ በመብላት ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አደረገ

**condiment** ቅመም
Pepper is a useful condiment. በርበሬ ፡ ጠቃሚ ፡ ቅመም ፡ ነው

**condition** (v.) የ - - - መሠረት ፡ ነው
Ability and effort condition success. ችሎታና ፡ ጥረት ፡ የመሳካት ፡ መሠረት ፡ ናቸው
**condition to (= be conditioned to)** ለመደ
+His boyhood conditioned him to hardship. በልጅነቱ ፡ ችግርን ፡ ለምዷል
**be conditioned** ተመሠረተ
The gift to the boy is conditioned on his good behavior. ለልጁ ፡ የሚሰጠው ፡ ስጦታ ፡ ልጁ ፡ በሚያሳየው ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው

**condition** (n.)

1. ሁኔታ. The rug is in good condition. ስጋጃው ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነው
Social conditions have changed tremendously in recent years. የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሁኔታዎች ፡ በቅርብ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ተለውጠዋል
I'm in no condition to go mountain climbing. ተራራ ፡ ለመውጣት ፡ በሚያስችል ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ አይደለሁም
2. አኳኋን. He keeps his things in good condition. እቃውን ፡ በጥሩ ፡ አኳኋን ፡ ይይዛል
3. አካሄድ. He tries to reform the working conditions in the factory. በፋብሪካው ፡ ውስጥ ፡ የሥራውን ፡ አካሄድ ፡ ለማሻሻል ፡ ይሞክራል
4. አስፈላጊ ፡ ነገር. Ability is one of the conditions for success in life. ችሎታ ፡ ለኑሮ ፡ መሳካት ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆኑት ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ነው
5. ግዴታ. This contract has seven conditions. ይህ ፡ ውል ፡ ሰባት ፡ ግዴታዎች ፡ አሉት
I have one condition to make before I will accept. ከመቀበሌ ፡ በፊት ፡ ላቀርበው ፡ የምፈልገው ፡ አንድ ፡ ግዴታ ፡ አለ

**keep in good condition** በደንብ ፡ ያዘ
He keeps his things in good condition. እቃዎቹን ፡ በደንብ ፡ ይይዛል

**on any condition** ምንም ፡ ቢሆን
I won't go on any condition. ምንም ፡ ቢሆን ፡ አልሄድም

**on condition that**
*I will go on condition that you will too. እኔ ፡ የምሄደው ፡ አንተም ፡ የምትሄድ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ነው

**on one condition** ባንድ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ብቻ
I will accept the offer on one condition. የቀረበልኝን ፡ የምቀበለው ፡ ባንድ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ ነው
[See also 'humble, insanitary, living, unsettled']

**(be) conditional** ተመሠረተ
My promise to help you is conditional upon your good behavior. ልረዳህ ፡ የሰጠሁህ ፡ ተስፋ ፡ በምታሳየው ፡ መልካም ፡ ባሕርይ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው

**condole** አጽናና
He condoled him on his loss. በደረሰበት ፡ ችግር ፡ አጽናናው

**condolence** የሐዘን ፡ መግለጫ
The Emperor expressed his condolences in a telegram. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሐዘን ፡ መግለጫቸውን ፡ በቴሌግራም ፡ ገለጹ

**condone**
1. ችላ ፡ ብሎ ፡ አለፈ. I cannot condone your rudeness. ብልግናህን ፡ ችላ ፡ ብዬ ፡ አላልፈውም
2. ፈቀደ. Church dogma does not condone divorce. የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ መፋታትን ፡ አይፈቅድም

**conduce** በጀ
Exercise conduces health. ጅምናስቲክ ፡ ለጤንነት ፡ ይበጃል

**(be) conducive** ረዳ
Good food and exercise are conducive to a long life. ጥሩ ፡ ምግብና ፡ ጅምናስቲክ ፡ ረዥም ፡ ዕድሜ ፡ ለማግኘት ፡ ይረዳሉ

**conduct** (v.)
1. አካሄደ. He conducts his business affairs very badly. ንግዱን ፡ በመጥፎ ፡ ሁኔታ ፡ ያካሄዳል
2. አስጎበኘ. He conducted the visitors around the museum. ጐብኚዎቹን ፡ ቤተ ፡ መዘክሩን ፡ አዙሮ ፡ አስጎበኘ
3. ኤሌክትሪክ ፡ አስተላለፈ. Copper conducts better than any other material. ከሌሎች ፡ ብረታ ብረቶች ፡ ይልቅ ፡ መዳብ ፡ በተሻለ ፡ አኳኋን ፡ ኤሌክትሪክ ፡ ያስተላልፋል
4. መራ. Who is conducting the symphony tonight? ዛሬ ፡ ማታ ፡ ሲምፎኒውን ፡ የሚመራ ፡ ማን ፡ ነው ?
The usher conducted the people to their seats. አስተናባሪ ፡ ሰዎቹን ፡ ወደየመቀመጫቸው ፡ መራቸው

**conduct oneself** ራሱን ፡ ተቈጣጠረ
He conducted himself well during the cross-examination. በመስቀለኛው ፡ ጥያቄ ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ በደንብ ፡ ተቈጣጠረ
*She conducts herself like a lady. ሁኔታዋ ፡ እንደ ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ነው

**conduct** (n.)
1. አመል. Your conduct is disgraceful. አመልህ ፡ ያሳፍራል
2. ጠባይ. The teacher praised him for his blameless conduct. ጠባዩ ፡ እንከን ፡ ስለሌለበት ፡ መምህሩ ፡ አመሰገነው
3. ተግባር. The Medical Association discourages unprofessional conduct among its members. የሕክምና ፡ ማኅበር ፡ አባሎቹ ፡ ለሙያ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ተግባር ፡ እንዳይፈጽሙ ፡ ይከለክላል
[See also 'safe conduct']

**conductor**
1. ቲኬት ፡ ቈራጭ. Did the conductor punch your ticket? ቲኬት ፡ ቈራጩ ፡ ቲኬትህን ፡ በሳ ?
2. መሪ. Who is the conductor of the orchestra? የሙዚቃ ፡ ጓድ ፡ መሪ ፡ ማነው ?
3. አስተላላፊ. Copper is a good conductor of electricity. መዳብ ፡ ጥሩ ፡ የኤሌክትሪክ ፡ አስተላላፊ ፡ ነው

**cone** [ከታች ፡ ሰፋ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ጣሪያ ፡ ሾለል ፡ ብሎ ፡ የሚወጣ]

**Confederacy** [ለእርስ ፡ በርስ ፡ መረዳዳት ፡ የመንግሥት ፡ ኅብረት]

**confederate** (v.) ተባበረ
The Swiss cantons confederated to form a union. የስዊዝ ፡ ግዛቶች ፡ አንድ ፡ የኅብረት ፡ መንግሥት ፡ ለማቋቋም ፡ ተባበሩ

**confederate** (n.) ግብረ ፡ አበር
The thief was arrested, but his confederate escaped. ሌባው ፡ ተያዘ ፡ ግብረ ፡ አበሩ ፡ ግን ፡ አመለጠ

**confer** (conferred), vt. ሰጠ
The university conferred the degree of Ph.D. on him. ዩኒቨርሲቲው ፡ የፍልስፍና ፡ ዶክተርነትን ፡ ሰጠው

**confer** (vi.) ተመካከረ
The criminal conferred with his lawyer. ወንጀለኛው ፡ ከጠበቃው ፡ ጋር ፡ ተመካከረ

**conference** ስብሰባ
He had a conference with the mayor. ከከንቲባው ፡ ጋር ፡ ስብሰባ ፡ ነበረው

**hold a conference** ስብሰባ ፡ አደረገ
He held a conference on housing at city hall. ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ጉዳይ ፡ ስብሰባ ፡ አደረገ

**confess** (vt.)
1. ንስሐ ፡ አስገባ. The priest confessed my sister. ቄሱ ፡ እኅቴን ፡ ንስሐ ፡ አስገቧት
2. አመነ. I have to confess that I have not read the book yet. መጽሐፉን ፡ ገና ፡ አለማንበቤን ፡ ማመን ፡ አለብኝ
3. ገለጸ. She confessed her secrets to her friends. ምስጢሯን ፡ ለጓደኞቿ ፡ ገለጸች
The soldiers confessed allegiance to their country. ወታደሮቹ ፡ ላገራቸው ፡ ታማኞች ፡ መሆናቸውን ፡ ገለጹ

**confess** (vi.)
1. ኀጢአት ፡ ተናዘዘ. My sister confesses every month. እኅቴ ፡ በየወሩ ፡ ኀጢአቷን ፡ ትናዘዛለች
2. አመነ. The defendant confessed. ተከሳሹ ፡ አመነ

**confession**
1. ንስሐ. The priest is ready to hear confession in English. ቄሱ ፡ ንስሓውን ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ለመስማት ፡ ተዘጋጅተዋል
2. የእምነት ፡ ቃል. In his confession, the thief incriminated two others. በሰጠው ፡ የእምነት ፡ ቃል ፡ ሌባው ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ አወጣ

**go to confession** ንስሐ ፡ ገባ
She goes to confession regularly. ያለማቋረጥ ፡ ንስሐ ፡ ትገባለች

**make a confession** አመነ ፤ ተናዘዘ
The criminal made a full confession. ወንጀለኛው ፡ ጥፋቱን ፡ በሙሉ ፡ አመነ ፡ (ተናዘዘ)
[See also 'extort, extract, wring']

**confessor** የንስሐ ፡ አባት ፤ የነፍስ ፡ አባት
This priest is my confessor. እኚህ ፡ ቄስ ፡ የንስሐ ፡ (የነፍስ) ፡ አባቴ ፡ ናቸው

**confidant** (n.) ምስጢረኛ
He tells all his secrets to his confidant. ምስጢሩን ፡ ሁሉ ፡ ለምስጢረኛው ፡ ይናገራል

**confide**
1. አካፈለ. She regularly confides her troubles to her friend. ችግሯን ፡ በየጊዜው ፡ ለጓደኛዋ ፡ ታካፍላለች
2. ሰጠ. She confides her baby to the nursery while she is at work. ሥራ ፡ ስትሄድ ፡ ልጇን ፡ ለሕፃናት ፡ ማሳደጊያ ፡ ትሰጣለች

**confide in** ተማመነ
He confides in his father. ባባቱ ፡ ይተማመናል

**confide to the care** አደራ ፡ ሰጠ
They confided the children to the care of their aunt. ልጆቹን ፡ ላክስታቸው ፡ አደራ ፡ ሰጧቸው

**confidence**
1. እምነት ፤ በራሱ ፡ ያለው ፡ እምነት. Nothing can shake his confidence. እምነቱን ፡ ምንም ፡ ሊያነቃንቀው ፡ አይችልም
The award boosted his confidence. የተደረገለት ፡ ሽልማት ፡ በራሱ ፡ ያለውን ፡ እምነት ፡ ከፍ ፡ አደረገለት
I have confidence in him. በሱ ፡ ላይ ፡ እምነት ፡ አለኝ
2. ሙሉ ፡ ልብ. He described the situation with

such confidence that the audience believed him completely. ሁኔታውን ፡ በሙሉ ፡ ልብ ፡ ስለገለጸ ፡ አዳማጮቹ ፡ ሁሉ ፡ አመኑት
3. ምስጢር. I listened to her confidences for half an hour. የነገረችኝን ፡ ምስጢር ፡ ለግማሽ ፡ ሰዓት ፡ አዳመጥኩ
He told me that in confidence. በምስጢር ፡ ነገረኝ

**gain one's confidence** (= have confidence in) ተማመነ(በት)
+He has gained my confidence because he has always been so honest. ሁልጊዜ ፡ ታማኝ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘሁት ፡ እተማመንበታለሁ
[See also 'strict']

**confident** (adj.) እርግጠኛ
We are confident of victory. እንደምናሸንፍ ፡ እርግጠኞች ፡ ነን

**be confident** ተማመነ
I am confident that everything will turn out all right. ሁሉም ፡ ነገር ፡ እንደሚቃና ፡ እተማመናለሁ

**confident manner** ልበ ፡ ሙሉነት ፤ በራስ ፡ የመተማመን ፡ ጠባይ
His confident manner gained him popularity. ልበ ፡ ሙሉነቱ ፡ ተወዳጅነትን ፡ አተረፈለት
His confident manner dispelled our fears. በራስ ፡ የመተማመን ፡ ጠባዩ ፡ ፍርሃታችንን ፡ አስወገደልን

**confidential**
1. ልዩ. A confidential secretary should be discreet. ልዩ ፡ ጸሐፊ ፡ ጥንቁቅ ፡ መሆን ፡ አለበት
2. ምስጢራዊ. The confidential report was distributed only to the ministers. ምስጢራዊው ፡ ሪፖርት ፡ ለሚኒስትሮቹ ፡ ብቻ ፡ ታደለ

**become confidential** ምስጢር ፡ አጫወተ
Don't become too confidential with strangers! ብዙ ፡ ላላወቅሃቸው ፡ ምስጢርህን ፡ አታጫውት

**confine** (v.)
1. ወሰነ. Please confine your talk to five minutes! ንግግርህን ፡ ባምስት ፡ ደቂቃ ፡ ወስን
2. አገደ. The banks could not confine the swollen river. የወንዙ ፡ ዳርቻዎች ፡ የሞላውን ፡ ውኃ ፡ ሊያግዱ ፡ አልቻሉም
3. አዋለ. Illness confines him to his room. ሕመም ፡ እቤት ፡ ያውለዋል

**confine oneself** ተወሰነ
I wish the speaker would confine himself to the subject. ተናጋሪው ፡ በንግግሩ ፡ እርእስት ፡ ቢወሰን ፡ ጥሩ ፡ ነበር

**be confined to prison** ታሰረ
He was confined to prison for two years. ሁለት ፡ ዓመት ፡ ታሰረ

**be confined to the house** ከቤት ፡ አልወጣም
She is confined to the house by her duties. ሥራ ፡ ስለሚበዛባት ፡ ከቤት ፡ አትወጣም

**confinement**
1. ታፍኖ ፡ መዋል. Confinement in a small room is bad for one's health. በትንሽ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ታፍኖ ፡ መዋል ፡ ለጤንነት ፡ መጥፎ ፡ ነው
2. እስራት. His confinement lasted two years. እስራቱ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ቆየ

**confinement in prison** እስራት
He was sentenced to three years' confinement in prison. የሦስት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ተፈረደበት

**solitary confinement** ገለልተኛ ፡ የሆነ ፡ ክፍል
The rebel was put in solitary confinement. ወንበዴው ፡ ገለልተኛ ፡ በሆነ ፡ ክፍል ፡ ታሰረል

**confines** ክልል
These people have never been beyond the confines of their valley. እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ከሸለቆዋቸው ፡ ክልል ፡ ወጥተው ፡ አያውቁም
*God is beyond the confines of human knowledge. እግዚአብሔር ፡ የሰው ፡ ዕውቀት ፡ ከሚደርስበት ፡ በላይ ፡ ነው

**confirm**
1. አጠነከረ. That only confirms my faith in him. ያ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ያለኝን ፡ እምነት ፡ ያጠነክረዋል
2. እውነት ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጠ. He confirmed the news we heard over the radio. በሬዲዮ ፡ የሰማነውን ፡ ወሬ ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጠ
3. አጸደቀ. The Senate confirmed the treaty. የሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ስምምነቱን ፡ አጸደቀው

**be confirmed** ሙሉ ፡ የሃይማኖት ፡ አባል ፡ ነው
She was baptized when she was a month old and confirmed when she was 13. በወሯ ፡ ክርስትና ፡ ተነሥታ ፡ በ፲፫ ዓመቷ ፡ ሙሉ ፡ የሃይማኖት ፡ አባል ፡ ሆነች

**confirmation**
1. እርግጠኛነት. We are waiting for confirmation of the news. የወሬውን ፡ እርግጠኛነት ፡ በመጠባበቅ ፡ ላይ ፡ ነን
2. ማረጋገጫ. This is a confirmation of your discovery. ይህ ፡ አንተ ፡ ላገኘኸው ፡ ማረጋገጫ ፡ ነው

3. የክርስትና ፡ መቀበል ፡ በዓል. Confirmation was celebrated in St. Mary's Church. የክርስትና ፡ መቀበል ፡ በዓል ፡ በቅድስት ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተከበረ

**confirmed** (adj.) የቈረጠ
He is a confirmed bachelor. የቈረጠ ፡ ወንደ ፡ ላጤ ፡ ነው

**confiscate**
1. ወረሰ. The government confiscated the smuggled goods. መንግሥት ፡ ቀረጥ ፡ ያልተከፈለባቸውን ፡ እቃዎች ፡ ወረሰ
2. ውርስ ፡ አደረገ. They confiscated everything, even personal property. የግል ፡ ንብረት ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ውርስ ፡ አደረጉ

**conflagration** የእሳት ፡ ቃጠሎ
A conflagration destroyed most of the city. የእሳት ፡ ቃጠሎ ፡ የከተማውን ፡ አብዛኛውን ፡ ክፍል ፡ አወደመው

**conflict** (v.)
1. አልተስማማም. Their account of the accident conflicts with ours. ስለ ፡ አደጋው ፡ የሰጡት ፡ መግለጫ ፡ እኛ ፡ ከሰጠነው ፡ ጋር ፡ አይስማማም
2. ተጋጨ. According to my schedule, the French class conflicts with my Amharic class. በኔ ፡ የጊዜ ፡ ሰሌዳ ፡ መሠረት ፡ የፈረንሳይኛና ፡ ያማርኛ ፡ ክፍሎች ፡ ይጋጫሉ

**conflict** (n.)
1. ትግል. It is the eternal conflict between good and evil. በክፉና ፡ በበጎ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ትግል ፡ ነው
2. ልዩነት. There is a conflict of opinion between students and professors. በተማሪዎችና ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ መምህራን ፡ መካከል ፡ ያሳብ ፡ ልዩነት ፡ አለ
3. አለመስማማት. The workers adopted a policy of obstruction due to their conflict with the boss. ካሠሪያቸው ፡ ጋር ፡ ባለመስማማታቸው ፡ የተነሣ ፡ ሠራተኞቹ ፡ በማሰናከያ ፡ ዘዴ ፡ ተጠቀሙ
4. ጠብ. This incident can create a global conflict. ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ጠብ ፡ ሊፈጥር ፡ ይችላል
5. ውጊያ ፤ ግጭት. The army is stockpiling fuel for any future conflict. የጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ ወደፊት ፡ ለሚመጣው ፡ ውጊያ ፡ (ግጭት) ፡ ነዳጅ ፡ ያጠራቅማል

**conflict of opinion** አለመግባባት
The conflict of opinion between students and professors led the students to strike. በተማሪዎችና ፡ ባስተማሪዎች ፡ አለመግባባት ፡ ምክንያት ፡ ተማሪዎቹ ፡ ክፍል ፡ አንገባም ፡ አሉ

**conflicting** ተቃራኒ
I have heard two conflicting reports. ሁለት ፡ ተቃራኒ ፡ ሪፖርቶች ፡ ሰምቻለሁ

**confluence** መገናኛ
The town was built at the confluence of two rivers. ከተማው ፡ የተሠራው ፡ በሁለቱ ፡ ወንዞች ፡ መገናኛ ፡ አጠገብ ፡ ነው

**confluent** ጅረት
This confluent is completely full in the rainy months. ጅረቱ ፡ በክረምት ፡ ወራት ፡ ጢም ፡ ብሎ ፡ ይሞላል

**conform** (vt.) አስማማ
The stranger conformed his ways to ours. እንግዳው ፡ ሰው ፡ አኗኗሩን ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ አስማማ

**conform** (vi.)
1. ተስማማ. Her dress conforms to the times. ልብሷ ፡ ከጊዜው ፡ ጋር ፡ ይስማማል
2. ተከተለ. You must conform to the rules. ደንቦቹን ፡ መከተል ፡ አለብህ

**conformity**
1. መስማማት. Conformity of opinion is sometimes necessary in deciding important matters. አንዳንድ ፡ አስፈላጊ ፡ ጉዳዮችን ፡ ለመወሰን ፡ የሐሳብ ፡ መስማማት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ያስፈልጋል
2. ባንድ ፡ አስተሳሰብ ፡ መመራት. Strict conformity often prevents original thought. ጽኑ ፡ የሆነ ፡ ባንድ ፡ አስተሳሰብ ፡ መመራት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ከማፍለቅ ፡ ያግዳል

**in conformity with** በ - - - መሠረት
In conformity with your request, I am sending you the necessary forms. በጥያቄህ ፡ መሠረት ፡ ተፈላጊዎቹን ፡ ፎርሞች ፡ ልኬልሃለሁ
*He lives in conformity with the law. ሕግን ፡ አክብሮ ፡ ይኖራል

**confound**
1. አማታ. Their demands confounded the situation even more. ያቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ ሁኔታውን ፡ የባሰ ፡ አማታው
2. አለየም ፤ አሳሳተ. He confounds dreams with reality. ሕልምንና ፡ እውነትን ፡ አይለይም ፡ (ያሳስታል)
3. አስገረመ. The news of his appointment as governor confounded me. አገረ ፡ ገዢ ፡ ሆኖ ፡ መሾሙ ፡ አስገረመኝ

**(be) confounded** ተደነቀ
I was confounded to hear that he had become

a professor. ፕሮፌሰር ፣ መሆኑን ፣ በመስማቴ ፣
ተደንቄ ፣ ነበር

**confront**

1. ገጠመ. The difficulties that confronted us
have been overcome. የገጠሙንን ፣ ችግሮች ፣
አሸንፈናል
2. ተጋጠመ. Our army confronted the enemy
with great bravery. ሰራዊታችን ፣ በታላቅ ፣ ጀ
ግንነት ፣ ጠላትን ፣ ተጋጠመው
*The lawyer confronted the prisoner with the
forged check. ጠበቃው ፣ እስረኛውን ፣ አጭበርብ
ረሃል ፣ በመባል ፣ የተከሰሰበትን ፣ ቼክ ፣ አሳየው

**confront each other** ተፋጠጠ
Egypt and Israel confront each other across
the Suez Canal. ግብጽና ፣ እስራኤል ፣ ከስዌ
ዝ ፣ በይ ፣ ባሻገር ፣ ተፋጠዋል

**confront with the need** አስገደደ
This situation confronts me with the need to
make a quick decision. ይህ ፣ ሁኔታ ፣ የተፋጠ
ነ ፣ ውሳኔ ፣ ላይ ፣ እንድደርስ ፣ ያስገድደኛል

**be confronted** ፊት ፣ ለፊት ፣ ተጋጠመ
The prisoner was confronted by his ac-
cusers. እስረኛው ፣ ከከሳሾቹ ፣ ጋር ፣ ፊት ፣ ለፊ
ት ፣ ተጋጠመ

**confuse**

1. አደናገረ. His talk confused me. ንግግሩ ፣ አ
ደናገረኝ
2. አመሳቀለ. Don't confuse the papers on
his desk! ጠረጴዛው ፣ ላይ ፣ ያለውን ፣ ወረቀት ፣ አ
ታመሳቅልበት
3. አማታ. The radio announcer confused the
dates of the two events. ሬዲዮ ፣ ተናጋሪው ፣
የሁለቱን ፣ ሁኔታዎች ፣ ቀናት ፣ አማታ
*He must have confused me with someone else.
ሌላ ፣ ሰው ፣ መስዬው ፣ ነበር

**confusion**

1. መደናገር. There was confusion in the room
when the fire broke out. ቃጠሎው ፣ በተነሣ ፣
ጊዜ ፣ ክፍሉ ፣ ውስጥ ፣ መደናገር ፣ ነበር
2. ትርምስምስ. There was an inordinate amount
of confusion on registration day. በምዝገባ ፣ ቀ
ን ፣ ከልክ ፣ ያለፈ ፣ ትርምስምስ ፣ ነበር
3. ግርግር. He escaped in the confusion.
በግርግሩ ፣ መሃል ፣ አመለጠ
4. ሽብር. The army retreated in confusion.
ወታደሩ ፣ በሽብር ፣ አፈገፈገ
5. ብጥብጥ. The meeting broke up in confusion.
ስብሰባው ፣ በብጥብጥ ፣ ተበተነ
6. ግፈር. I couldn't hide my confusion.
ግፈሬን ፣ ለመደበቅ ፣ አልቻልኩም

**confute, ~ the claim** አስተባበለ
The student confuted the claim that he cheated
in the examination. ተማሪው ፣ በፈተና ፣ ማጭ
በርበሩን ፣ አስተባበለ

**congeal** ረጋ
The blood around the wound congealed.
በቁስሉ ፣ አካባቢ ፣ ያለው ፣ ደም ፣ ረጋ

**congenial**

1. መሰል. He has a congenial roommate.
መሰል ፣ የክፍል ፣ ጓደኛ ፣ አለው
2. ተወዳጅ. People like to visit his house
because he is a congenial host. ተወዳጅ ፣ አስ
ተናጋጅ ፣ ስለሆነ ፣ ሰዎች ፣ እቤቱ ፣ መሄድ ፣ ይ
ወዳሉ
3. የሚስማማ. He has found a congenial job.
የሚስማማውን ፣ ሥራ ፣ አገኘ

**congest** አገደ
Parades congest traffic. ሰልፍ ፣ የመኪና ፣ መ
ዘዋወርን ፣ ያግዳል

**(be) congested** ተጨናነቀ
The streets of Addis Ababa are congested
with traffic. የአዲስ ፣ አበባ ፣ መንገዶች ፣ በእ
ግረኞችና ፣ በተሽከርካሪዎች ፣ ተጨናንቀዋል

**cause to become congested** ደፈነ
A cold causes the nose to become congested.
ጉንፋን ፣ አፍንጫን ፣ ይደፍናል

**congestion** መጨናነቅ
Traffic congestion is caused by the narrow
roads. በጠባቦች ፣ መንገዶች ፣ ምክንያት ፣ የመ
ኪናዎች ፣ መጨናነቅ ፣ ይደርሳል

**congestion of the lungs** የሳንባ ፣ መታፈን
He died from a congestion of the lungs.
በሳንባው ፣ መታፈን ፣ ምክንያት ፣ ሞተ

**conglomerate** ተጠረቃቀመ
Pebbles have conglomerated into rocks in the
course of millions of years. ጠጠሮች ፣ በ
ሚሊዮን ፣ ዓመታት ፣ ውስጥ ፣ ተጠረቃቅመው ፣
አለት ፣ ይሆናሉ

**conglomeration** ጥርቃሚ
This is a conglomeration of useless facts.
ይህ ፣ ፍሬ ፣ ቢስ ፣ የሆነ ፣ ነገር ፣ ጥርቃሚ ፣ ነው

**congratulate** እንኳን ፣ ደስ ፣ ያለህ ፣ አለ
We congratulated him on his success. ስለተሳ
ካለት ፣ እንኳን ፣ ደስ ፣ ያለህ ፣ አልነው
*May I congratulate you on your birthday?
ስለ ፣ ልደት ፣ በዓልህ ፣ እንኳን ፣ ደስ ፣ ያለህ

**congratulation** የደስታ ፡ መግለጫ
Let's send congratulations to the winner! ላሸናፊው ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ እንላክለት

**congratulations!** እንኳን ፡ ደስ ፡ ያለህ
Congratulations on your appointment! ስለ ፡ ተሾምክ ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ ያለህ !
*Our heartiest congratulations! ከልብ ፡ የሆነ ፡ ደስታችንን ፡ እንገልጻለን

**congregate** ተሰበሰበ
Don't congregate in the hall! በመተላለፊያው ፡ ላይ ፡ አትሰብሰቡ

**congregation**
1. ጉባኤ. The Protestant congregation meets in the American Embassy. የፕሮቴስታንት ፡ ጉባኤ ፡ በአሜሪካን ፡ ኤምባሲ ፡ ውስጥ ፡ ይሰበሰባል
2. ክምችት. There was a congregation of bees around the beehive. በቀፎው ፡ አካባቢ ፡ የንብ ፡ ክምችት ፡ ነበር

**Congress** ምክር ፡ ቤት
The Congress discusses the matter of land taxes. ምክር ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፡ መሬት ፡ ግብር ፡ ይነጋገራል

**congress** ስብሰባ
The congress of Ethiopian Studies was held in Addis Ababa. የኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ ስብሰባ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ተደረገ

**(be) congruent** ተስማማ
The plan to expand the school system is congruent with our aims. ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ለማስፋፋት ፡ ያለው ፡ እቅድ ፡ ካለን ፡ ዓላማ ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፡ ነው

**congruous** ተስማሚ
The plan is congruous to the needs of the school. እቅዱ ፡ ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ፍላጎት ፡ ተስማሚ ፡ ነው

**conical** ሾጣጣ
Fujiyama has a conical shape. ፉጂያማ ፡ የተባለው ፡ የጃፓን ፡ ተራራ ፡ ሾጣጣ ፡ ቅርጽ ፡ አለው

**conifer** [ቅጠለ ፡ ቀጫጭን ፡ ዛፍ]

**conjecture** (v.) በግምት ፡ ተናገረ
Columbus conjectured that the earth was round. ኮሎምበስ ፡ መሬት ፡ ክብ ፡ መሆኗን ፡ በግምት ፡ ተናገረ

**conjecture** (n.) ይሆናል
This book is based on conjecture rather than research. መጽሐፉ ፡ የተመሠረተው ፡ በይሆናል ፡ እንጂ ፡ በምርምር ፡ ላይ ፡ አይደለም

**conjugal** የጋብቻ
The husband failed to perform his conjugal duties. ባልዬው ፡ የጋብቻ ፡ ተግባሩን ፡ ሳያከናውን ፡ ቀረ
*Their conjugal happiness is exemplary. በትዳራቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ደስታ ፡ አርአያነት ፡ ያለው ፡ ነው

**conjugate** አረባ
Please conjugate this verb in the past! ይህንን ፡ ግስ ፡ በአላፊ ፡ ጊዜ ፡ አርባ

**conjugation** አረባብ
The conjugation of the Amharic verb is different from that of the Arabic verb. ያማርኛ ፡ ግስ ፡ አረባብ ፡ ከዐረብኛ ፡ ግስ ፡ አረባብ ፡ የተለየ ፡ ነው

**conjunction**
1. መጣመር. The conjunction of fog and rain made driving impossible. የጭጋግና ፡ የዝናብ ፡ መጣመር ፡ መኪና ፡ ለመንዳት ፡ አላስቻለም
2. መስተፃምር. The word 'but' is a conjunction. ነገር ፡ ግን ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ መስተፃምር ፡ ነው

**in conjunction with** ከ -- ጋር ፡ ተጨምሮ
High winds, in conjunction with rain, made travel difficult. ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ከዝናብ ፡ ጋር ፡ ተጨምሮ ፡ ጉዞውን ፡ አስቸጋሪ ፡ አደረገው

**conjunctivitis** የዓይን ፡ ማዝ ፡ ሕመም
The children suffer from conjunctivitis. ልጆቹ ፡ የዓይን ፡ ማዝ ፡ ሕመም ፡ አለባቸው

**conjure**
1. በመተት ፡ አወጣ. The magician conjured a rabbit out of a hat. አስማተኛው ፡ በመተቱ ፡ ጥንቸል ፡ ከባርኔጣው ፡ ውስጥ ፡ አወጣ
2. ለመነ. I conjure you not to betray your country. አገርህን ፡ እንዳትከዳ ፡ እለምንሃለሁ

**conjure up**
1. ጐተተ. The sorcerer conjured up an evil spirit. ጠንቋዩ ፡ ሰይጣን ፡ ጐተተ
2. በሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ ፈጠረ. The sailor's story conjured up scenes of buried treasures. የመርከበኛው ፡ ታሪክ ፡ የተደበቀ ፡ ሀብት ፡ መኖሩን ፡ በሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ ፈጠረ

**connect** (vt.)
1. አገናኘ. Operator, please connect me with the main office! ማዞሪያ ፤ ከዋናው ፡ ቢሮ ፡ ጋር ፡ አገናኘኝ ፡
A bus line connects the two towns. ሁለቱን ፡ ከተማዎች ፡ አውቶቡስ ፡ ያገናኛቸዋል

2. ቀጠለ. The telephone company connected my telephone today. የቴሌፎን ፡ ኩባንያው ፡ ዛሬ ፡ ስልክ ፡ ቀጠለልኝ
3. ግንኙነት ፡ ያለው ፡ መሰለው. Do you connect Bill's silence with Mary's arrival? የቢል ፡ ዝምታ ፡ ማለት ፡ ከሜሪ ፡ መምጣት ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ይመስልሃል ?

**connect** (vi.) ተገናኘ
The two rooms connect. ሁለቱ ፡ ክፍሎች ፡ ይገናኛሉ

**be connected**
*The two towns are connected by train. በሁለቱ ፡ ከተሞች ፡ መካከል ፡ ባቡር ፡ ይመላለሳል

**be connected (with)** ግንኙነት ፡ አለው
He is connected with several firms. ከብዙ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ አለው
*Mr. Parker has been connected with this firm since 1918. ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ ከ፲፱፻፲ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ በዚህ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ሠርቷል

**connection**
1. መገናኛ. The connections with that town are very poor. ከዚህ ፡ ከተማ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ መገናኛ ፡ ጥሩ ፡ አይደለም
2. ግንኙነት. The two governments sundered diplomatic connections. ሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ግንኙነታቸውን ፡ አቋረጡ
3. (= to connect) ማስቀጠል. The connection of our telephone took two days. ስልካችንን ፡ ለማስቀጠል ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ፈጀ
4. ማመላለሻ. I missed my connection in Dire Dawa. ከድሬ ፡ ደዋ ፡ ወዲያ ፡ የሚወስደኝ ፡ ማመላለሻ ፡ አመለጠኝ
*He has some important connections. ወገን ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**be a connection of** ተዛመደ
She is a connection of ours by marriage. በጋብቻ ፡ ትዛመደናለች

**get a connection** ተገናኘ
Because of bad weather, it is difficult to get a connection on the telephone. ያየሩ ፡ ሁኔታ ፡ ስለተበላሸ ፡ በስልክ ፡ ለመገናኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**in connection with** ከ - - ጋር ፡ የተያያዘ
I have an idea in connection with your last remark. በመጨረሻ ፡ ካልከው ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ አንድ ፡ ሐሳብ ፡ አለኝ

**in this connection** ከዚህ ፡ ጋር ፡ በማያያዝ
In this connection he told him that it would not do. ከዚህ ፡ ጋር ፡ በማያያዝ ፡ እንደማያዋጣ ፡ ነገረው

**in what connection?** በምን ፡ መነሻ
In what connection did he mention it? በምን ፡ መነሻ ፡ ጠቀሰው?

**make connections** መጓጓዣ ፡ ለወጠ
You make connections at the next station. በሚቀጥለው ፡ ጣቢያ ፡ መጓጓዣ ፡ ትለውጣለህ

**connivance** መስማማት
The robbery was done with the connivance of the police. ስርቆቱ ፡ የተፈጸመው ፡ ከፖሊስ ፡ ጋር ፡ በመስማማት ፡ ነበር

**connive** ተመሳጠረ
The general connived with the enemies of his country. ጄኔራሉ ፡ ከሀገሩ ፡ ጠላቶች ፡ ጋር ፡ ተመሳጠረ

**connive at** ሸፋፈነ
Some policemen connive at gambling. አንዳንድ ፡ ፖሊሶች ፡ የቁማርን ፡ ወንጀል ፡ ይሸፋፍናሉ

**connote** አሳሰበ
The word "equator" often connotes heat. የምድር ፡ መቀነት ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ሙቀትን ፡ ያሳስባል

**conquer**
1. ገዛ. He wanted to conquer the whole world. ዓለምን ፡ በሙሉ ፡ ለመግዛት ፡ ፈለገ
2. ያዘ. The Italians wanted to conquer Ethiopia. ኢጣልያኖች ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመያዝ ፡ ፈለጉ
3. አሸነፈ. He conquered the habit of smoking. የሲጋራ ፡ ማጤስ ፡ ሱስን ፡ አሸነፈ
The soldiers sequestered food from the people they conquered. ወታደሮቹ ፡ ካሸነፏቸው ፡ ሰዎች ፡ ምግብ ፡ ዘረፉ

**conqueror** ድል ፡ አድራጊ
The conqueror was given a warm reception. ድል ፡ አድራጊው ፡ የጋለ ፡ አቀባበል ፡ ተደረገለት

**conquest**
1. ድል ፡ ማድረግ. The enemy's conquest split the country in two. የጠላት ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ አገሪቱን ፡ ለሁለት ፡ ከፈላት
2. መያዝ. The conquest of Mexico by the Spanish is described in this book. የእስፓኞች ፡ ሜክሲኮን ፡ መያዝ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጿል

**conscience** ኅሊና
I have a clear conscience. ንጹሕ ፡ ኅሊና ፡ አለኝ

**appeal to someone's conscience**
*He appealed to his conscience in the hope of getting the money back. ገንዘቡን ፡ ይመልስለት ፡ ዘንድ ፡ ለኅሊናው ፡ እንዲሰማው ፡ አድርጎ ፡ ነገረው

**have something on one's conscience**
*She behaves as if she had something on her conscience. ጥፋት ፡ እንዳጠፋ ፡ ሰው ፡ ትሆናለች
[See also 'guilty']

**conscientious**
1. በጥንቃቄ ፡ የተሠራ. Conscientious work gives good results. በጥንቃቄ ፡ የተሠራ ፡ ሥራ ፡ ውጤቱ ፡ ያምራል
2. ትጉህ. The conscientious student received the teacher's praise. ትጉሁ ፡ ተማሪ ፡ ካስተማሪው ፡ ምስጋና ፡ አገኘ

**conscious** (= adv.) ሆን ፡ ብሎ
He made a conscious effort to be kind. ደግ ፡ ለመሆን ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ጥረት ፡ አደረገ

**be conscious** ራሱን ፡ ዐወቀ
Doctor, is he conscious? ሐኪም ፡ ሆይ ፤ ራሱን ፡ ያውቃል ?

**be conscious of** ዐወቀ
She wasn't conscious of his presence in the room. እሱ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ መኖሩን ፡ አላወቀችም ፡ ነበር

**consciousness**
1. ሐሳብ. The memory of the event was gone from his consciousness. ነገሩ ፡ ከሐሳቡ ፡ ጠፍቷል
2. አእምሮ. Gradually, the sound of the bell penetrated the sleeping man's consciousness. የደወሉ ፡ ድምፅ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ የተኛውን ፡ ሰው ፡ አእምሮ ፡ ዘለቀ
*A consciousness of impending danger kept him awake. አደጋ ፡ ሊደርስበት ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ስላወቀ ፡ እንቅልፍ ፡ አጣ

**lose consciousness** ነፍሱን ፡ ሳተ ፤ ሕይወቱን ፡ ሳተ
She lost consciousness due to the extreme heat. ከኀይለኛው ፡ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ነፍሷን ፡ (ሕይወቷን) ፡ ሳተች

**recover consciousness** ነፍስ ፡ ዘራ ፤ ነፍሱን ፡ ዐወቀ
She just now recovered consciousness. አሁን ፡ ገና ፡ ነፍስ ፡ ዘራች ፡ (ነፍሷን ፡ ዐወቀች)

**regain consciousness** ራሱን ፡ ዐወቀ ፤ ነፍስ ፡ ዘራ
After two hours, he regained consciousness. ከሁለት ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ራሱን ፡ ዐወቀ ፡ (ነፍስ ፡ ዘራ)

**(not) regain consciousness** ሕይወቱን ፡ ሳተ
The injured man did not regain consciousness for two hours. የተጐዳው ፡ ሰው ፡ ለሁለት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ሕይወቱን ፡ ስቶ ፡ ነበር

**conscript** ምልምል
Conscripts are trained in marching before they are sent to their various units. ምልምሎች ፡ ወደየተመደቡባቸው ፡ ክፍሎቻቸው ፡ በፊት ፡ ሰልፍ ፡ ይማራሉ

**conscription** በግዴታ ፡ መመልመል
Conscription is necessary in time of war. በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ በግዴታ ፡ መመልመል ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**consecrate**
1. አዋለ. He consecrated his life to the service of the church. ሕይወቱን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎት ፡ አዋለ
2. ስለት ፡ ሰጠ. She consecrated her child to the service of the church. ልጇን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንዲያገለግል ፡ ስለት ፡ ሰጠች

**be consecrated**
*A church is consecrated to worship. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለጸሎት ፡ የተወሰነ ፡ ቅዱስ ፡ ቦታ ፡ ነው

**consecration** የምረቃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት
The consecration of the church took place last Sunday. የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የምረቃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተደረገው ፡ ባለፈው ፡ እሑድ ፡ ነበር

**consecutive**
1. ተከታታይ. Monday, Tuesday, and Wednesday are consecutive days. ሰኞ ፡ ማክሰኞና ፡ ረቡዕ ፡ ተከታታይ ፡ ቀኖች ፡ ናቸው
2. (= adv.) መደዳውን. He came on three consecutive days. ሦስት ፡ ቀን ፡ መደዳውን ፡ መጣ

**consensus** ስምምነት
The consensus was against the war. ስምምነቱ ፡ ጦርነቱን ፡ የሚቃወም ፡ ነበር

**consent** (v.)
1. ተስማማ. He consented to stay. ለመቆየት ፡ ተስማማ
2. ፈቀደ. Ann's father would not consent to her marrying a foreigner. የአን ፡ አባት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ እንድታገባ ፡ አይፈቅድም
3. እሺ ፡ አለ. When I asked her whether she would marry me, she consented. እንድንጋባ ፡ ብጠይቃት ፡ እሺ ፡ አለች

**consent** (n.)

1. ፈቃድ. This was done without my consent. ይህ ፡ የተደረገው ፡ ያለኔ ፡ ፈቃድ ፡ ነው

2. መስማማት. Silence often implies consent. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ዝምታ ፡ መስማማትን ፡ ያመለክታል

**by common consent** በ - - - ሁሉ ፡ ስምምነት

By common consent of the class, he was chosen president. በተማሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ስምምነት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሆኖ ፡ ተመረጠ

**by general consent** ባንድ ፡ ድምፅ

He was chosen chairman by general consent. ባንድ ፡ ድምፅ ፡ ለሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ተመረጠ

[See also 'yield']

**consequence** የሚያስከትለው ፡ ውጤት

I am afraid of the consequences. የፈራሁት ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ ነው

*You must take the consequences of your action. በሥራህ ፡ ሳቢያ ፡ የመጣውን ፡ ነገር ፡ መቀበል ፡ አለብህ

*The consequence of his fall was a broken leg. መውደቁ ፡ የቅልጥሙን ፡ መሰበር ፡ አስከተለ

**in consequence of** በ - - - ምክንያት

An investigation was initiated in consequence of the disaster. ባደጋው ፡ ምክንያት ፡ ምርመራ ፡ እንዲጀመር ፡ ተደረገ

**it is of no consequence** ዋጋ ፡ የለውም

That he still has the title of president is of no consequence. የፕሬዚዳንቱን ፡ ማዕረግ ፡ መያዙ ፡ ዋጋ ፡ የለውም

**of no consequence** እዚህ ፡ ግባ ፡ የማይባል

He is a person of no consequence. እዚህ ፡ ግባ ፡ የማይባል ፡ ሰው ፡ ነው

**consequent** ያስከተለ

The storm and consequent flood caused great danger. ማዕበሉና ፡ ያስከተለው ፡ ጐርፍ ፡ ትልቅ ፡ አደጋ ፡ አደረሰ

*His long illness and consequent absence puts him far behind in his work. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ታሞ ፡ ከሥራ ፡ መቅረቱ ፡ ሥራውን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ጐተተበት

**consequently**

*He failed to come on time; consequently, the meeting broke up without settling anything. በሰዓቱ ፡ ሳይመጣ ፡ ስለቀረ ፡ ጉባኤው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ሳይወስን ፡ ተበተነ

**conservation** ጥበቃ

The conservation of forests is important to our country. የደን ፡ ጥበቃ ፡ ለሀገራችን ፡ ጠቃሚ ፡ ነው

**conservative** ወደ ፡ ትክክለኛው ፡ የሚቃረብ

He gave me a conservative estimate of costs. ወደ ፡ ትክክለኛው ፡ የሚቃረብ ፡ የዋጋ ፡ ግምት ፡ ሰጠኝ

**be conservative** የቆየ ፡ ልማድን ፡ ማክበር ፡ ወደደ

Old people are usually more conservative than young people. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከወጣቶች ፡ ይልቅ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የቆየ ፡ ልማድን ፡ ማክበር ፡ ይወዳሉ

**conserve** (v.)

1. እንዳይጠፉ ፡ ጠበቀ. Scientific farming conserves the soil. ዘመናዊ ፡ እርሻ ፡ አፈር ፡ እንዳይጠፉ ፡ ይጠብቃል

2. ቈጠበ. He tried to conserve his strength for the big test the following day. ጉልበቱን ፡ በበነጋው ፡ ለሚደረገው ፡ ትልቅ ፡ ፈተና ፡ ለመቆጠብ ፡ ሞከረ

**conserve** (n.) በቆርቆሮ ፡ የታሸገ

Since we have no fresh fruit we use a lot of conserves. ትኩስ ፡ ፍራ ፡ ፍሬ ፡ ስለሌለን ፡ በቆርቆሮ ፡ የታሸገውን ፡ በብዛት ፡ እንጠቀምበታለን

**consider**

1. ከቁም ፡ ነገር ፡ ቈጠረ. He never considers the feelings of others. የሌሎችን ፡ ስሜት ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ አይቈጥርም

2. ቈጠረ. I consider him an able chemist. ችሎታ ፡ ያለው ፡ ኬሚስት ፡ አድርጌ ፡ እቈጥረዋለሁ

3. ተመለከተ. We have to consider his age. ዕድሜውን ፡ መመልከት ፡ አለብን

4. አሰበ. You should consider the traffic and start early. የመኪናውን ፡ ብዛት ፡ አስበህ ፡ በጊዜ ፡ መነሣት ፡ አለብህ

Will you accept my offer to work with me? I will consider it. ከኔ ፡ ጋር ፡ እንድትሠራ ፡ ያቀረብኩልህን ፡ ሐሳብ ፡ ትቀበላለህ ? አስብበታለሁ

5. እንደ - - - አየ. He considers him his foe. እንደጠላቱ ፡ ያየዋል

6. አመዛዘነ. He wants to consider the pros and cons before he makes up his mind. ሐሳቡን ፡ ከመቍረጡ ፡ በፊት ፡ ጥቅሙንና ፡ ጉዳቱን ፡ ሊያመዛዝን ፡ ይፈልጋል

*I consider the story improbable. ታሪኩ ፡ የሚሆን ፡ አይመስለኝም

**be considered**

1. ተባለ. This nation is considered to be aggressive. ይህ ፡ መንግሥት ፡ ጠብ ፡ ጫሪ ፡ ነው ፡ ይባላል

2. ተቈጠረ. Pride was considered a sin by the churchmen. በካህናት ፡ ዘንድ ፡ ኩራት ፡ እንደ ፡ ኀጢአት ፡ ይቈጠር ፡ ነበር

**considerable**

1. በዛ ፡ ያለ. That is a considerable sum. በዛ ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ ነው
2. ብዙ. It took considerable effort. ብዙ ፡ ጥረትን ፡ ጠየቀ
3. ብዙ ፤ ረጂም. The distance between Harar and Addis Ababa is considerable. በሐረርና ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ ብዙ ፡ (ረጂም) ፡ ነው
4. ከፍተኛ. He acquired considerable skill in football. በግር ፡ ኳስ ፡ ጨዋታ ፡ ከፍተኛ ፡ ችሎታ ፡ አገኘ
*There is a considerable American colony in Paris. በርከት ፡ ያሉ ፡ አሜሪካኖች ፡ ፓሪስ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ

**considerably** በጣም
The boy was considerably older than he looked. ልጁ ፡ መልኩ ፡ ከሚያሳየው ፡ በላይ ፡ ዕድሜው ፡ በጣም ፡ ገፋ ፡ ያለ ፡ ነው

**considerate** ለሰው ፡ አሳቢ
My boss is very considerate. አለቃዬ ፡ በጣም ፡ ለሰው ፡ አሳቢ ፡ ነው

**consideration**

1. ማሰብ. Giving a correct answer requires consideration. ትክክለኛ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ማሰብ ፡ ያስፈልጋል
2. አሳቢነት. The girl's consideration for her mother is in contrast with her brother's rudeness. የልጂቱ ፡ ለእናቷ ፡ አሳቢነትና ፡ የወንድሟ ፡ ብልግና ፡ ይፃረራሉ
*Time is an important consideration in this case. በዚህ ፡ ረገድ ፡ የጊዜ ፡ ነገር ፡ ሊታሰብበት ፡ የሚገባ ፡ ነው

**give consideration** ተመለከተ
I will give your project full consideration. እቅድህን ፡ በሚገባ ፡ እመለከተዋለሁ

**in consideration of**
1. ስለ. In consideration of his services, he received an award. ስለ ፡ አገልግሎቱ ፡ ሽልማት ፡ ተሰጠው
2. በመመልከት. In consideration of his age, the judge ordered the boy released from jail. የዕድሜውን ፡ ማነስ ፡ በመመልከት ፡ ልጁ ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ እንዲለቀቅ ፡ ዳኛው ፡ አዘዙ

**not have consideration** ግድ ፡ የለውም
He has no consideration for anybody. ለማንም ፡ ግድ ፡ የለውም

**show no consideration** ምንም ፡ ግድ ፡ የለውም
They show no consideration for his feelings. ስለ ፡ ስሜቱ ፡ ምንም ፡ ግድ ፡ የላቸውም

**take into consideration**
1. አስተያየት ፡ አደረገ. When grading the papers, the teacher took the student's long illness into consideration. መምህሩ ፡ ወረቀቶቹን ፡ ሲያርም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ለታመመው ፡ ተማሪ ፡ አስተያየት ፡ አደረገ
2. ተመለከተ. When you criticize his manners, you should take into consideration the fact that he is foreign. ጠባዩን ፡ ስትነቅፍ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ መመልከት ፡ አለብህ
3. ስለሱ ፡ አሰበ. Then too, we must take him into consideration. ከዚያም ፡ በላይ ፡ ስለሱ ፡ ማሰብ ፡ አለብን

**treat with consideration** በሚገባ ፡ ያዘ
One should treat one's mate with consideration. አንድ ፡ ሰው ፡ የትዳር ፡ ጓደኛውን ፡ በሚገባ ፡ መያዝ ፡ አለበት

**(be) under consideration** በመጠናት ፡ ላይ ፡ ነው
Three plans are under consideration. ሦስት ፡ እቅዶች ፡ በመጠናት ፡ ላይ ፡ ናቸው

**considered** (adj.), ~ **opinion**
*My considered opinion is that the project will never succeed. ተመራምሬ ፡ እንደደረስኩበት ፡ እቅዱ ፡ ምንጊዜም ፡ ከፍሬ ፡ አይደርስም

**considering** ሲታሰብ
He did well considering his lack of preparation. አለመዘጋጀቱ ፡ ሲታሰብ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ አግኝቷል

**consign**

1. ላከ. We consign the goods to Asmara by air. እቃውን ፡ በአየር ፡ ወደ ፡ አሥመራ ፡ እንልካለን
2. መደበ. He consigned two hours daily to studying Amharic. አማርኛ ፡ ለማጥናት ፡ በየቀኑ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ መደበ
3. አደራ ፡ ሰጠ. They consigned her to a guardian. ለአሳዳጊ ፡ አደራ ፡ ሰጧት

**consign to one's care** አደራ ፡ ሰጠ
He consigned his child to his uncle's care. ልጁን ፡ ላጎቱ ፡ አደራ ፡ ሰጠ

**consign to one's use** እንዲጠቀምበት ፡ አደረገ
The host consigned this room to our use. ባለቤቱ ፡ ይህንን ፡ ክፍል ፡ እንድንጠቀምበት ፡ አደረገ

**consignment**
*He received a consignment of Swiss merchandise. የተላኩትን ፡ የስዊስ ፡ እቃዎች ፡ ተቀበለ
*The trucker lost a consignment of pots.

ሹፌሩ ፡ መኪናው ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ ሸክላዎች ፡ ጠፉበት

**large consignment of** ብዙ
He sent me a large consignment of books. ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ላከልኝ

**consist**
1. ተሠራ. The human body consists of many cells. የሰው ፡ አካል ፡ የተሠራው ፡ ከብዙ ፡ ሴል ፡ ነው
2. ነበረ (past; ነው for the present; negative past አልነበረም; negative present አይደለም). The lunch consisted of fish, vegetables, and coffee. ምሳው ፡ ዓሣ ፤ አትክልትና ፡ ቡና ፡ ነበር
Wisdom does not consist only in knowing facts. ጥበብ ፡ እውነተኛ ፡ ነገርን ፡ ማወቅ ፡ ብቻ ፡ አይደለም
3. ተገኘ. Cooperation consists in working together. መረዳዳት ፡ አብሮ ፡ ከመሥራት ፡ ይገኛል
*A week consists of seven days. በሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ሰባት ፡ ቀኖች ፡ አሉ

**consistency** ሐሳበ ፡ ጽኑነት
Consistency should guide conduct. ሐሳበ ፡ ጽኑነት ፡ መመሪያ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል
*There is not always consistency between words and action. ንግግርና ፡ ተግባር ፡ ሁልጊዜ ፡ አብረው ፡ አይሄዱም
*His behavior is marked by consistency. የማይለዋወጥ ፡ ጠባይ ፡ አለው

**increase the consistency** አወፈረ
Flour is added to soup to increase its consistency. ሙቅን ፡ ለማወፈር ፡ዱቄት ፡ ይጨመራል

**consistent**
1. ዘላቂ. He is a consistent friend of Ethiopia. የኢትዮጵያ ፡ ዘላቂ ፡ ወዳጅ ፡ ነው
2. ሐሳበ ፡ ጽኑ. What a consistent person says today agrees with what he said yesterday. ሐሳበ ፡ ጽኑ ፡ ሰው ፡ ዛሬ ፡ የሚናገረውና ፡ ትናንት ፡ የተናገረው ፡ ይስማማሉ

**consistent with each other** ተደጋጋፊዎች
The ideas in his various speeches are consistent with each other. በየጊዜው ፡ በሚያደርጋቸው ፡ ንግግሮች ፡ ውስጥ ፡ የሚገልጻቸው ፡ ሐሳቦች ፡ ተደጋጋፊዎች ፡ ናቸው

**be consistent (with)** ተስማማ
What you said today is not consistent with what happened last week. ዛሬ ፡ የተናገርከው ፡ ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ከሆነው ፡ ነገር ፡ ጋር ፡ አይስማማም

Driving on the right is consistent with the law of most countries. በቀኝ ፡ መንዳት ፡ ከብዙ ፡ አገሮች ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ይስማማል

**consolation** መጽናኛ
Your company has been a great consolation to me. ያንተ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ መሆን ፡ ትልቅ ፡ መጽናኛ ፡ ሆኖኛል

**console** አጽናና
He consoled the widow for the loss of her husband. ሴትዮዋን ፡ ስለ ፡ ባሏ ፡ ሞት ፡ አጽናናት

**consolidate** (vt.)
1. አዳበረ. The company consolidated its gains. ኩባንያው ፡ ትርፉን ፡ አዳበረ
2. አጠነከረ. He consolidated his position with the nobility by granting them tax concessions. ለመኳንንቱ ፡ የግብር ፡ ምሕረት ፡ እያደረገላቸው ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ አጠነከረ
3. አጠቃለለ. He must consolidate scattered land holdings. የተበታተነውን ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ማጠቃለል ፡ አለበት
4. አዋሐደ. They consolidated their three companies. ሦስቱን ፡ ኩባንያዎቻቸውን ፡ አዋሐዱ

**consolidate** (vi.) ተዋሐደ
The two airlines consolidated. ሁለቱ ፡ የአየር ፡ መንገዶች ፡ ተዋሐዱ

**consonant** (n.) ድምፅ ፡ ሰጪ ፤ ተነባቢ
Some Amharic consonants are not easy to pronounce. አንዳንድ ፡ አማርኛ ፡ ድምፅ ፡ ሰጮች ፡ (ተነባቦች) ፡ በቀላሉ ፡ አይነበቡም

**(be) consonant** ተስማማ
His actions are consonant with his principles. አድራጎቱ ፡ ከእምነቱ ፡ ጋር ፡ የተስማማ ፡ ነው

**consort** (v.) ዋለ
Do not consort with thieves! ከሌቦች ፡ ጋር ፡ አትዋል

**consort** (n.) ባል
The consort of the empress has no authority over the government. የንግሥቲቱ ፡ ባል ፡ በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ሥልጣን ፡ የለውም

**conspicuous**
1. ዓይነተኛ. Lincoln is a conspicuous example of a poor boy who succeeded. ሊንከልን ፡ የተሳካላቸው ፡ ድኾች ፡ ልጆች ፡ ዓይነተኛ ፡ ምሳሌ ፡ ነው
2. ጉልህ. Traffic signs should be conspicuous. የትራፊክ ፡ ምልክቶች ፡ ጉልህ ፡ መሆን ፡ አለባቸው

**be conspicuous** ጐልቶ ፡ ታየ
She was conspicuous in her red dress. ቀይ ፡ ልብስ ፡ በመልበሷ ፡ ጐልታ ፡ ትታያለች

**conspiracy** አድማ ፤ ሴራ
The conspiracy to overthrow the government was discovered in time. መንግሥቱን ፡ ለመገልበጥ ፡ የተደረገው ፡ አድማ ፡ በጊዜ ፡ ተደረሰበት
I don't want to be a party to any conspiracy. በምንም ፡ ዓይነት ፡ ሴራ ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ ልሆን ፡ አልፈልግም

**conspire**
1. አደመ. The army conspired against the government. የጦር ፡ ኀይሉ ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ አደመ
2. አሴረ. His enemies conspired to ruin him. ጠላቶቹ ፡ ሊያጠፉት ፡ አሴሩ
3. ተሟላ. All things conspired to make her birthday a happy one. የልደት ፡ በዓሏን ፡ የደስታ ፡ ዕለት ፡ ለማድረግ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ተሟላ

**constancy** ቅንነት
He serves with constancy and devotion. በቅንነትና ፡ በታማኝነት ፡ ያገለግላል
*We admire the constancy of Columbus in believing the earth was round. መሬት ፡ ክብ ፡ ናት ፡ የሚለውን ፡ የኮለምበስን ፡ ጠንካራ ፡ እምነት ፡ እናደንቃለን

**constant**
1. የማያቋርጥ. The constant noise is getting on my nerves. የማያቋርጠው ፡ ጫጫታ ፡ ያበሳጨኛል
2. ያልተቈጠበ. Constant encouragement helped the crippled child to walk again. ያልተቈጠበ ፡ ማደፋፈር ፡ ሽባውን ፡ ልጅ ፡ እንደገና ፡ እንዲራመድ ፡ ረዳው
3. የዘወትር. His constant criticism flustered her. የዘወትር ፡ ነቀፋው ፡ ግራ ፡ አጋባት
4. (= adv.) አዘውትሮ ፤ አሁንም ፡ አሁንም. He harassed me with constant requests for money. አዘውትሮ ፡ (አሁንም ፡ አሁንም) ፡ ገንዘብ ፡ እየጠየቀ ፡ ነዘነዘኝ
5. ጽኑ. He is constant in his devotion to his country. ላገሩ ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፡ ጽኑ ፡ ነው
6. ታማኝ. A constant friend helps you when you need help. ታማኝ ፡ ጓደኛ ፡ ለችግርህ ፡ ይደርስልሃል
7. አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሆነ. The soldier walked at a constant pace. ወታደሩ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ በሆነ ፡ እርምጃ ፡ ሄደ

**constantly**
1. ሳያቋርጥ. The phone has been ringing constantly. ስልኩ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ይደውል ፡ ነበር
2. በየጊዜው. Farmers are constantly afflicted by locusts. ገበሬዎች ፡ በየጊዜው ፡ በአንበጣ ፡ ይሠቃያሉ
3. ሁልጊዜ. He constantly belittles my efforts to write better. ጽሕፈቴን ፡ ለማሻሻል ፡ የማደርገውን ፡ ጥረት ፡ ሁልጊዜ ፡ ያንቋሽሻል

**constellation** ኅብረ ፡ ኮከብ
The Great Bear is a constellation. ትልቁ ፡ ድብ ፡ አንድ ፡ ኅብረ ፡ ኮከብ ፡ ነው

**consternation** ድንጋጤ
The consternation he felt during the earthquake was beyond description. በመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ጊዜ ፡ የደረሰበት ፡ ድንጋጤ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይችልም
*To my consternation, my wallet has disappeared. ቦርሳዬ ፡ ሲጠፋ ፡ ክው ፡ አልኩ

**be in consternation** ተጨነቀ
All the women of the village were in consternation. የመንደሩ ፡ ሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ተጨንቀው ፡ ነበር

**constipate** ሆድ ፡ አደረቀ
Chocolate often constipates. ቸኮላት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ሆድ ፡ ያደርቃል

**constipation** ሆድ ፡ ድርቀት
His constipation bothers him seriously. ሆድ ፡ ድርቀቱ ፡ በኀይል ፡ ያስቸግረዋል

**constituent** የተመረጠበት ፡ ቀበሌ
The congressman received many letters from his constituents. የምክር ፡ ቤቱ ፡ አባል ፡ ከተመረጠበት ፡ ቀበሌ ፡ ብዙ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ይደርሱታል
*Sugar is one of the constituents of candy. ከረሜላ ፡ ከሚሠራባቸው ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ስኳር ፡ ነው

**constitute**
1. ሾመ. They constituted him chief advisor. የበላይ ፡ አማካሪ ፡ አድርገው ፡ ሾሙት
2. ሆነ. Twelve months constitute a year. ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ወሮች ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ይሆናሉ
3. ተቈጠረ. Being seen at the scene of the crime does not constitute guilt. ወንጀሉ ፡ ከተፈጸመበት ፡ ቦታ ፡ መታየት ፡ ከወንጀል ፡ አይቈጠርም

**be constituted** ተቋቋመ
Courts are constituted by law to give justice. ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ፍትሕ ፡ እንዲሠሩ ፡ በሕግ ፡ የተቋቋሙ ፡ ናቸው

**constitution**
1. ሕገ ፡ መንግሥት. The constitution of the United States went into effect in 1789. የአሜሪ

ካ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በ፲፱፻፳፫ ዓመተ ፡ ምሕረ ት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ

2. የመተዳደሪያ ፡ ደንብ. The structure of the organization is explained in its constitution. የድርጅቱ ፡ አቋም ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ውስ ጥ ፡ ተገልጿል

3. መቋቋም. The delegates recommended the constitution of a peace commission. መልእክተ ኞቹ ፡ የሰላም ፡ ኮሚሲዮን ፡ መቋቋምን ፡ ደገፉ

4. ሰውነት. He has a very strong constitution. ብርቱ ፡ ሰውነት ፡ አለው

*The physical constitution of the moon is now known. የጨረቃ ፡ አካል ፡ ምን ፡ ምን ፡ እንዳለበ ት ፡ አሁን ፡ ታውቋል

**draw up a constitution** ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አ ረቀቀ

The committee drew up a constitution for the country. ደርጉ ፡ ለአገሪቷ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አረቀቀ

[See also 'strong']

## constitutional

1. የሰውነት. A constitutional weakness makes him susceptible to colds. የሰውነቱ ፡ ደካማነት ፡ ለብርድ ፡ በሽታ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጠዋል

2. በሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተፈቀደ. Freedom of speech is one of our constitutional rights. የንግ ግር ፡ ነጻነት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከተፈቀዱል ን ፡ መብቶች ፡ አንዱ ፡ ነው

## constrain

1. አስገደደ. One must not constrain a child to eat. ሕፃናትን ፡ በግድ ፡ እንዲበሉ ፡ ማስገደድ ፡ አይገባም

2. ገታ. You have to constrain your temper. ንዴትህን ፡ መግታት ፡ አለብህ

**constrain the growth** አቀጨጨ

Cold weather constrained the plant's growth. ቀዝቃዛ ፡ አየር ፡ አትክልቱን ፡ አቀጨጨው

## constraint ግዴታ

He kept silent under constraint. በግዴታ ፡ ጸ ጥ ፡ አለ

**show constraint** አደበ

The boys were usually noisy, but they showed constraint when visitors came. ልጆቹ ፡ አብዛኛ ውን ፡ ጊዜ ፡ ይንጫጩ ፡ ነበር ፤ እንግዶች ፡ በ መጡ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ አደቡ

## constrict አገደ

He tied a rope around his arm to constrict the blood vessels. ደም ፡ ሥሮችን ፡ ለማገድ ፡ ክንዱን ፡ በገመድ ፡ አሰረ

## constriction ጥበት

A constriction in the neck of the bottle kept the water from pouring out. የጠርሙስ ፡ አን ገት ፡ ጥበት ፡ ውኃው ፡ እንዳይፈስ ፡ አገደው

## construct

1. ሠራ. They plan to construct a building on this site. በዚህ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሕንጻ ፡ ለመሥራት ፡ ያስባሉ

2. ገነባ. They are going to construct a barrage across the river. በወንዙ ፡ ላይ ፡ ግ ድብ ፡ ሊገነቡ ፡ ነው

## construction

1. ሕንጻ. That new construction is a bank. ያ ፡ አዲሱ ፡ ሕንጻ ፡ ባንክ ፡ ነው

2. መሠራት. Construction of highways is important to Ethiopia. የአውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ መ ሠራት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

The bridge is still under construction. ድልድ ዩ ፡ ገና ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ ነው

3. ሥራ. The construction of the building was stopped for budgetary reasons. የሕንጻው ፡ ሥ ራ ፡ በባጀት ፡ ምክንያት ፡ ተቋረጠ

4. አሠራር. The construction of this building is modern. የዚህ ፡ ሕንጻ ፡ አሠራር ፡ ዘመናዊ ፡ ነው

## constructive ጠቃሚ

He engages in constructive activity. ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ይሰማራል

## construe

1. ገመተ. He construed from her expression that she was furious. ካስተያየቷ ፡ የተቈጣች ፡ መሆኗን ፡ ገመተ

2. ተረጐመ. Different lawyers may construe the same law differently. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጠበቃዎች ፡ አንዱን ፡ ሕግ ፡ በተለያየ ፡ መንገድ ፡ ይተረጕሙ ት ፡ ይሆናል

## consul ቆንሲል

The Emperor received the British consul. ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የእንግሊዝን ፡ ቆ ንሲል ፡ አነጋገሩ

## consulate ቆንስላ

Were you at the American consulate? ከአሜሪካ ኑ ፡ ቆንስላ ፡ ዘንድ ፡ ነበርክ ?

## consult (vt.)

1. አማከረ. You should have consulted us. እኛን ፡ ማማከር ፡ ነበረብህ

2. ከ - - - ጋር ፡ ተመካከረ. He consulted his

lawyer about the case. ስለ ፡ ነገሩ ፡ ከጠበቃው ፡ ጋር ፡ ተመካከረ
3. ምክር ፡ ጠየቀ (ተጠየቀ). He is consulted regarding such problems because of his long experience. የረጅም ፡ ጊዜ ፡ ልምድ ፡ ስላለው ፡ እነዚህን ፡ ስለመሳሰሉ ፡ ጉዳዮች ፡ ምክር ፡ ይጠየቃል
4. ወደ - - - ዘንድ ፡ ሄደ. If your coughing continues, consult a doctor. ሳልህ ፡ ከጠናብህ ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ዘንድ ፡ ሂድ
5. ተመለከተ. When in doubt about the meaning of a word, consult a dictionary. ስላንድ ፡ ቃል ፡ ትርጉም ፡ በተጠራጠርክ ፡ ጊዜ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ተመልከት

**consult** (vi.) ተመካከረ
The doctors consulted before operating. ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ከማድረጋቸው ፡ በፊት ፡ ዶክተሮች ፡ ተመካከሩ

**consultation** ምክር
The three doctors held a consultation to decide whether an operation was necessary. ሦስቱ ፡ ሐኪሞች ፡ ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ያስፈልግ ፡ እንደሆን ፡ ለመወሰን ፡ ምክር ፡ አደረጉ

**consume**
1. አጋየ. The flames soon consumed the wooden huts. ነበልባሉ ፡ ጎጆዎቹን ፡ ወዲያውኑ ፡ አጋያቸው
2. ጨረሰ. We consumed a lot of food on our hike. ለሽርሽር ፡ በሄድን ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ምግብ ፡ ጨረስን
He soon consumed his fortune. ሃብቱን ፡ ወዲያውኑ ፡ ጨረሰ
3. ጠጣ. My car consumes a lot of gas. መኪናዬ ፡ ብዙ ፡ ቤንዚን ፡ ይጠጣል
4. አዋለ. A student consumes much of his time in studying. ተማሪ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜውን ፡ የሚያውለው ፡ ለጥናት ፡ ነው
5. አጠፋ (በት). The meetings consume much of my time. ስብሰባዎቹ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያጠፉብኛል

**be consumed**
1. አለቀ. The copious supply of beer was soon consumed. በገፍ ፡ የቀረበው ፡ ቢራ ፡ ወዲያውኑ ፡ አለቀ
2. ተዋጠ. She was consumed with curiosity. በማወቅ ፡ ፍላጎት ፡ ተውጣለች

**consuming, be time** ~ ጊዜ ፡ ይፈጃል
Preparing reports is time consuming. ሪፖርት ፡ ማዘጋጀት ፡ ጊዜ ፡ ይፈጃል

**(be) consummated** አበቃ
His ambition was consummated when he won the first prize. ያንደኝነት ፡ ሽልማቱን ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ምኞቱ ፡ አበቃ

**consumption** መብል
The meat is unfit for consumption because it is full of worms. ሥጋው ፡ ትል ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ለመብል ፡ አይስማማም
*Consumption of cotton cloth has increased 50 per cent. ከጥጥ ፡ የተሠሩ ፡ ልብሶችን ፡ መልበስ ፡ ኀምሳ ፡ በመቶ ፡ ጨምሯል
*The consumption of coal is much greater in winter than in summer. ከበጋ ፡ ጊዜ ፡ ይልቅ ፡ በክረምት ፡ ጊዜ ፡ የሚነደው ፡ ከሰል ፡ ይበልጣል

**for consumption**
*This food is for our consumption on the trip. ይህ ፡ ምግብ ፡ በጉዞዋችን ፡ ወቅት ፡ የምንመገበው ፡ ነው

**contact** (v.)
1. ጠየቀ. I will contact you as soon as I arrive. እንደደረስኩ ፡ እጠይቅሃለሁ
2. ተገናኘ. I will contact you by mail or by telephone. በደብዳቤ ፡ ወይም ፡ በስልክ ፡ እንገናኛለን

**contact** (n.) ግንኙነት
Contact with the main office is maintained by radio. ከዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የሚደረገው ፡ በሬዲዮ ፡ ነው

**be in contact** ተጋጠመ
Our troops are in contact with the enemy. ወታደሮቻችን ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ ተጋጥመውታል

**by the contact** ሲገናኝ
The light is turned on by the contact of the switch with the wire. መብራቱ ፡ የሚበራው ፡ ማብሪያና ፡ ማጥፊያው ፡ ከሽቦው ፡ ጋር ፡ ሲገናኝ ፡ ነው

**come in contact** ነካ
When the mirror came in contact with the hot iron, it split. የጋለው ፡ ብረት ፡ መስታወቱን ፡ ሲነካው ፡ መስታወቱ ፡ ተሰነጠቀ

**come into contact** ግንኙነት ፡ አደረገ
He has never come into contact with foreigners. ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ግንኙነት ፡ አድርጎ ፡ አያውቅም

**make contact** ግንኙነት ፡ አደረገ
The food salesman made contact with the grocers in all parts of the city. ምግብ ፡ አሻሻጩ ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ ምግብ ፡ ሻጮች ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ አደረገ
[See also 'immediate']

**contagion** ተላላፊ ፡ በሽታ
To avoid contagion, the water must be purified. ተላላፊ ፡ በሽታን ፡ ለማስወገድ ፡ ውኃን ፡ ማጣራት ፡ ያስፈልጋል

**contagious** ተላላፊ
There are several contagious diseases in this country. በዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ተላላፊ ፡ በሽታዎች ፡ አሉ

**be contagious** ተጋባ
Yawning is contagious. ማዛጋት ፡ ይጋባል

**contain**
1. አለ(በት). That trunk contains clothing. ያ ፡ ሰንዱቅ ፡ ልብስ ፡ አለበት
2. ያዘ. A kiloliter contains a thousand liters. አንድ ፡ ኪሎሊትር ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ሊትር ፡ ይይዛል
This book contains a biography of Abraham Lincoln. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የአብርሃም ፡ ሊንከልንን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ይዟል
3. ነው. A pound contains 16 ounces. አንድ ፡ ፓውንድ ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ አውንስ ፡ ነው
4. አዘለ. The body of the book contains all the essential facts. የመጽሐፉ ፡ ዋና ፡ ክፍል ፡ ተፈላጊዎችን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ በሙሉ ፡ አዝሏል
5. ገታ. He contained his anger. ንዴቱን ፡ ገታው
6. እንዳይስፋፋ ፡ አገደ. The Western powers hope to contain Russian military strength. የምዕራብ ፡ ኀያላን ፡ መንግሥታት ፡ የሩሲያን ፡ የጦር ፡ ኀይል ፡ እንዳይስፋፋ ፡ ለማገድ ፡ ይጥራሉ

**be contained** ተቀመጠ
The powder is contained in a capsule. ባሩዱ ፡ ከምሱር ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣል

**container**
1. ማስቀመጫ. He used old bottles and boxes as containers for his food. አሮጌ ፡ ጠርሙሶችንና ፡ ሣጥኖችን ፡ ለምግብ ፡ ማስቀመጫ ፡ አዋለ
2. ማጠራቀሚያ. Place refuse in a container! ቈሻሻውን ፡ ማጠራቀሚያው ፡ ውስጥ ፡ ጣለው

**contaminate**
1. መረዘ. Flies contaminate food. ዝምቦች ፡ ምግብን ፡ ይመርዛሉ
2. በከለ. The villagers contaminated the well with sewage. መንደርተኞቹ ፡ የውኃውን ፡ ጉድጓድ ፡ በቆሻሻ ፡ በከሉት

**contemplate**
1. አሰበ. She was contemplating a visit to Addis Ababa. አዲስ ፡ አበባን ፡ ለመጐብኘት ፡ ታስብ ፡ ነበር
2. አሰላሰለ. He was contemplating his future. ስለወደፊት ፡ ኑሮው ፡ ያሰላስል ፡ ነበር
The traveler contemplated the beauty of the desert. መንገደኛው ፡ የምድረ ፡ በዳውን ፡ ውበት ፡ አሰላሰለ
3. ገመተ. Do you contemplate any difficulty because of bad weather? ባየሩ ፡ መጥፎነት ፡ ችግር ፡ ይደርሳል ፡ ብለህ ፡ ትገምታለህ ?

**contemplation** አሳብ
He was sunk in contemplation. ባሳብ ፡ ተውጦ ፡ ነበር

**contemporaneous**
*The lives of Thomas Jefferson and John Adams were contemporaneous. ቶማስ ፡ ጀፈርሶንና ፡ ጆን ፡ አዳምስ ፡ ያንድ ፡ ዘመን ፡ ነዋሪዎች ፡ ነበሩ

**contemporary** (n.)
1. ባንድ ፡ ዘመን ፡ የኖረ. He was a contemporary of Washington. እሱ ፡ ከዋሽንግተን ፡ ጋር ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ የኖረ ፡ ነበር
2. በጊዜው ፡ የነበረ ፡ ሰው. Menelik towered above his contemporaries. ምኒልክ ፡ በዘመናቸው ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ልቀው ፡ ይታዩ ፡ ነበር

**contemporary** (adj.)
1. ዘመናዊ. I like contemporary furniture. ዘመናዊ ፡ የቤት ፡ እቃ ፡ እወዳለሁ
2. የጊዜ. He gave a lecture on contemporary events. ስለጊዜው ፡ ሁኔታዎች ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**contempt**
1. (= verbal noun) መናቅ. His contempt for her was apparent in his face. እሷን ፡ መናቁ ፡ በፊቱ ፡ ይታይ ፡ ነበር
2. (= verbal noun) መጋፋት. He was fined for contempt of court. ፍርድ ፡ ቤትን ፡ በመጋፋቱ ፡ መቀጮ ፡ ተወሰነበት

**contemptible** የሚናቅ
Cowards and cheats are contemptible. ቡከኖችና ፡ አታላዮች ፡ የሚናቁ ፡ ናቸው

**contemptuous** የንቀት
She gave him a contemptuous look. በንቀት ፡ ዓይን ፡ ተመለከተችው

**contend** (vt.) ተከራከረ
Columbus contended that the earth was round. ኮለምበስ ፡ ዓለም ፡ ክብ ፡ ናት ፡ ሲል ፡ ተከራከረ

**contend** (vi.) ተወዳደረ
They were contending for the first prize.

ያንደኝነትን ፡ ሽልማት ፡ ለማግኘት ፡ ይወዳደሩ ፡ ነበር

**contend with** ተቋቋመ
The first settlers had to contend with sickness. የመጀመሪያዎቹ ፡ ሰፋሪዎች ፡ በሽታን ፡ መቋቋም ፡ ነበረባቸው

**content** (v.)
1. ጣመ. Nothing contents her; she is always complaining. ምንም ፡ ነገር ፡ አይጥማትም ፤ ሁልጊዜ ፡ ትነጫነጫለች
2. ደስ ፡ አለ(ው). Will it content you if I let you have the ball tomorrow? ነገ ፡ ኳሱን ፡ ብተውልህ ፡ ደስ ፡ ይልሃል ?

**content oneself** ራሱን ፡ አረካ
I must content myself with reading about travel. ስለ ፡ ጉዞ ፡ በማንበብ ፡ ራሴን ፡ ማርካት ፡ አለብኝ

**(be) content** ተደሰተ
Are you content at your present salary? ባሁኑ ፡ ደሞዝህ ፡ ተደስተሃል ?

**content** (n.)
1. ይዘታ. The alcoholic content is negligible. የአልኮል ፡ ይዘታው ፡ እምብዛም ፡ ነው
2. ፍሬ ፡ ነገር. The content of his speech was good, but not the form. ከአቀራረቡ ፡ በስተቀር ፡ የንግግሩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ጥሩ ፡ ነበር

**contents** ያለው ፡ ነገር ፤ ያለው ፡ እቃ
Dissolve the contents of this package in one glass of water! እዚህ ፡ ባኮ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ባንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ውኃ ፡ አሟሟው
The contents of your trunk have to be examined. ከሣጥንህ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ እቃ ፡ መታየት ፡ አለበት

**table of contents** የመጽሐፍ ፡ ማውጫ
The table of contents is printed on the first page. የመጽሐፉ ፡ ማውጫ ፡ በመጀመሪያው ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ታትሟል
[See also 'heart']

**contented** በቃኝ ፡ ባይ
A contented person is happy with what he has. በቃኝ ፡ ባይ ፡ ባለው ፡ ይደሰታል

**contentedly** ተደስቶ
The cat purred contentedly on my lap. ድመቷ ፡ ተደስታ ፡ በጭኔ ፡ ላይ ፡ ተኝታ ፡ ታንኳርፍ ፡ ነበር

**contention**
1. ጠብ. This is not a time for contention. ይህ ፡ የጠብ ፡ ጊዜ ፡ አይደለም
2. አስተያየት. Columbus' contention that the earth was round turned out to be correct. መሬት ፡ ክብ ፡ ናት ፡ የሚለው ፡ የኮሎምበስ ፡ አስተያየት ፡ እውነት ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

**it is my contention** ብዬ ፡ አምናለሁ
It is my contention that poverty causes crime. ድኽነት ፡ ወንጀልን ፡ ያስከትላል ፡ ብዬ ፡ አምናለሁ

**contentment** መደሰት
Her contentment was apparent in her smile. መደሰቷ ፡ በፈገግታዋ ፡ ይታወቅ ፡ ነበር

**in contentment** ረክቶ
The cat lay stretched out beside the fire in contentment. ድመቲቷ ፡ ረክታ ፡ እሳቱ ፡ ጻር ፡ ተዘረረች

**contest** (v.)
1. ተከራከረ(በት). They are contesting the will. በኑዛዜው ፡ ይከራከሩበታል
They contested his right to speak. ለመናገር ፡ መብት ፡ እንዳለው ፡ ተከራከሩ
2. ተጋደለ. The soldiers contested every inch of ground. ወታደሮቹ ፡ ለያንዳንዷ ፡ ስንዝር ፡ መሬት ፡ ተጋደሉ

**contest** (n.)
1. ውድድር ፤ ግጥሚያ. Who won the contest? ውድድሩን ፡ ማን ፡ አሸነፈ ?
At last the fatal day for the contest arrived. በመጨረሻ ፡ ቁርጠኛው ፡ የግጥሚያ ፡ ቀን ፡ ደረሰ
2. መፎካከሪያ. Games and debates are contests. ጨዋታና ፡ ክርክር ፡ መፎካከሪያ ፡ ናቸው

**contestant** ተወዳዳሪ
The contestants shake hands before a fight begins. ተወዳዳሪዎቹ ፡ ከመጋጠማቸው ፡ በፊት ፡ የእጅ ፡ ሰላምታ ፡ ይለዋወጣሉ

**context** አገባብ
Words can be understood best in context. ቃላት ፡ ትርጉማቸው ፡ በሚገባ ፡ የሚታወቀው ፡ ባገባብ ፡ ነው

**contiguous** የተጠጋጋ
The two contiguous houses were destroyed by fire. ሁለቱ ፡ የተጠጋጉ ፡ ቤቶች ፡ በእሳት ፡ ተደመሰሱ

**continence** ራስን ፡ መግታት
Continence is a desirable quality. ራስን ፡ መግታት ፡ ተፈላጊ ፡ ባሕርይ ፡ ነው

**continent** (n.) አህጉር (pl. አህጉራት)
Africa is an old continent. አፍሪካ ፡ ጥንታዊት ፡ አህጉር ፡ ናት

The Roman empire stretched over continents. የሮም ፡ ግዛት ፡ በአህጉራት ፡ ላይ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ነበር

**continent** (adj.), **remain ~** ገታ
A monk is expected to remain continent with regard to sex. መነኩሴ ፡ ፍትወተ ፡ ሥጋን ፡ እንዲገታ ፡ ይጠበቃል

**contingency** (contingencies)
*We sent the supplies for contingencies. ለድንገተኛ ፡ አደጋዎች ፡ መጠባበቂያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሥንቅና ፡ ትጥቅ ፡ ላክን

**contingent** ድንገተኛ
The traveler set aside $5.00 a day for contingent expenses. መንገደኛው ፡ ለድንገተኛ ፡ ወጪ ፡ ለዕለት ፡ አምስት ፡ ብር ፡ መደበ

**be contingent (on)**
1. ተወሰነ. Her coming is contingent on the weather. መምጣት ፡ አለመምጣቷ ፡ ባየሩ ፡ ጠባይ ፡ ይወሰናል
2. ተመሠረተ. His promotion is contingent on his passing the final test. በሹመት ፡ ማደጉ ፡ የመጨረሻውን ፡ ፈተና ፡ በማለፉ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው

**continual** የማያቋርጥ
The continual noise is getting on my nerves. የማያቋርጠው ፡ ጩኸት ፡ ያበሳጨኛል

**continually** ያለማቋረጥ ፤ ብዙ ፡ ጊዜ
The line was continually busy. የስልኩ ፡ መሥመር ፡ ያለማቋረጥ ፡ ተይዞ ፡ ነበር
His speech was continually interrupted by rude exclamations. ንግግሩ ፡ በብልግና ፡ ጩኸት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተቋርጦ ፡ ነበር

**continuance** መቀጠል
His continuance in school depends on his health. ትምህርቱን ፡ መቀጠሉ ፡ ጤንነቱን ፡ የሚጠይቅ ፡ ነገር ፡ ነው
*His lawyer asked for a continuance of the trial. ጠበቃው ፡ ጉዳዩ ፡ በቀጠሮ ፡ እንዲተላለፍ ፡ አመለከተ

**continuation** (= to continue) መቀጠል
Continuation of my work was hard after I had been ill for a month. ላንድ ፡ ወር ፡ ከታመምኩ ፡ በኋላ ፡ ሥራዬን ፡ መቀጠል ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆኖብኝ ፡ ነበር

**continue**
1. ቀጠለ. We will continue with our work. ሥራችንን ፡ እንቀጥላለን
I hope this hot weather will not continue. ይህ ፡ ሙቀት ፡ እንደማይቀጥል ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ
To be continued. ይቀጥላል
2. ቆየ. The king's reign continued for twenty years. የንጉሡ ፡ የግዛት ፡ ዘመን ፡ ለሀያ ፡ ዓመት ፡ ቆየ
3. ዘለቀ. How far does this road continue? ይህ ፡ መንገድ ፡ እስከየት ፡ ይዘልቃል?
I want to continue on to Nairobi. እስከ ፡ ናይሮቢ ፡ ለመዝለቅ ፡ እፈልጋለሁ

**continued,** adj. (= adv.) ብዙ ፡ ጊዜ ፤ አከታትሎ
Continued failures dampened their enthusiasm. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሳይሳካላቸው ፡ መቅረቱ ፡ መንፈሳቸውን ፡ አቀዘቀዘው
The boy's failure was due to continued disregard of his studies. የልጁ ፡ መውደቅ ፡ ጥናቱን ፡ አከታትሎ ፡ ችላ ፡ ከማለቱ ፡ የመጣ ፡ ነው

**continuous** የማያቋርጥ
Where does that continuous noise come from? ያ ፡ የማያቋርጥ ፡ ድምፅ ፡ የሚመጣው ፡ ከየት ፡ ነው ?

**continuously** ያለማቋረጥ
The phone has been ringing continuously. ስልኩ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ይደውል ፡ ነበር

**contort** አጨማደደ
The clown contorted his face. ተራቢው ፡ ፊቱን ፡ አጨማደደ

**contour** ቅርጽ
The contour of the mountain can be seen from afar. የተራራው ፡ ቅርጽ ፡ ከሩቅ ፡ ይታያል

**contraband** የኰንትሮባንድ ፡ እቃ ፤ ያልተቀረጠበት ፡ እቃ
The guards make a rigorous search for contraband. ዘበኞቹ ፡ የኰንትሮባንድ ፡ እቃ ፡ እንዳይገባ ፡ ጥብቅ ፡ ፍተሻ ፡ ያደርጋሉ
The smugglers were caught with contraband on them. የኰንትሮባንድ ፡ ነጋዴዎች ፡ ያልተቀረጠበት ፡ እቃ ፡ እንደያዙ ፡ ተያዙ

**contract** (vt.)
1. አሳጠረ. In talking, we often contract words. ስንነጋገር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቃላትን ፡ እናሳጥራለን
2. አኰማተረ. Heat expands; cold contracts. ሙቀት ፡ ያስፋፋል ፤ ቅዝቃዜ ፡ ያኰማትራል
3. ያዘ(ው). +I contracted tuberculosis. የሳምባ ፡ ነቀርሳ ፡ ይዞኛል

**contract** (vi.)
1. ተኰናተረ. They have contracted to put up

the building in five months. ሕንጻውን ፡ ባምስት ፡ ወር ፡ ለመጨረስ ፡ ተኮናትረዋል
2. ለመደ. Bad habits are easy to contract and hard to get rid of. መጥፎ ፡ ልማዶችን ፡ መልመድ ፡ ቀላል ፡ ሲሆን ፡ መላቀቁ ፡ ግን ፡ ያስቸግራል

**be contracted** አጠረ
The Amharic word for God "Egziabeher" is often contracted to "Egzer". እግዚአብሔር ፡ የሚለው ፡ ያማርኛ ፡ ቃል ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እግዜር ፡ በመባል ፡ ያጥራል

**contract** (n.) ውል
I refuse to sign that contract. ውሉን ፡ አልፈርምም

**contracting** ተዋዋይ
This agreement is binding on both contracting parties. ይህ ፡ ውል ፡ ሁለቱንም ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ያስገድዳል

**contractor** ሥራ ፡ ተቋራጭ
The minister was accused of taking graft from the contractors. ሚኒስትሩ ፡ ከሥራ ፡ ተቋራጮች ፡ ጉቦ ፡ በመውሰድ ፡ ተከሶ ፡ ነበር

**contradict** (vt.)
1. አፈረሰ. He contradicted his own story. ራሱ ፡ የተናገረውን ፡ አፈረሰ
2. ተቃረነ. The facts contradict the theory. እውነተኛው ፡ ነገር ፡ የቀረበውን ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳብ ፡ ይቃረናል

**contradict** (vi.) ተቃወመ
Don't contradict me when I present a good suggestion. ጥሩ ፡ ሐሳብ ፡ በማቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ አትቃወመኝ

**contradiction**
1. የሚቃወም ፡ አስተያየት. He hates any contradiction of his views. ሐሳቡን ፡ የሚቃወም ፡ አስተያየት ፡ አይወድም
2. መቃረን. There is no contradiction between my words and my actions. በምለውና ፡ በማደርገው ፡ መካከል ፡ መቃረን ፡ የለም

**contradictory** የሚፃረር
We heard the most contradictory reports on it. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ በጣም ፡ የሚፃረሩ ፡ ሪፖርቶች ፡ ሰማን

**contrary**
1. ተቃራኒ. Hot and cold are contrary terms. ሙቀትና ፡ ቀዝቃዛ ፡ ተቃራኒ ፡ ቃላት ፡ ናቸው
2. ግርምቢጥ. The contrary boy refused to do what was suggested. ግርምቢጡ ፡ ልጅ ፡ የተነገረውን ፡ አልሠራም ፡ አለ

**on the contrary**
*The economic situation appears to be quite good. On the contrary, it couldn't be worse. የኤኮኖሚው ፡ ሁኔታ ፡ ጥሩ ፡ ይመስላል ። በዚህ ፡ አንጻር ፡ ምንም ፡ የባሰ ፡ ነገር ፡ አይሆንም

**to the contrary**
*We will come on Tuesday unless you write us to the contrary. አትምጡ ፡ ብለህ ፡ ካልጻፍክልን ፡ በስተቀር ፡ ማክሰኞ ፡ እንመጣለን
[See also 'expectation']

**contrast** (vt.) አነጻጸረ
He contrasted the programs of the two parties. የሁለቱንም ፡ ወገን ፡ ፕሮግራም ፡ አነጻጸረ

**contrast** (vi.) ተለያየ
His actions contrasted sharply with his words. የሚያደርገውና ፡ የሚናገረው ፡ ፈጽሞ ፡ የተለያየ ፡ ነገር ፡ ነው
*The black and the gold contrast well in that design. በዚህ ፡ ጌጥ ፡ የጥቁርና ፡ የወርቅማው ፡ ቀለማት ፡ ልዩነት ፡ ጕልቶ ፡ ይታያል

**contrast** (n.) ልዩነት
There is a big contrast between the two brothers. በሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ መሀከል ፡ ትልቅ ፡ ልዩነት ፡ አለ

**be in contrast** ተፃረረ
The girl's consideration for her mother was in contrast with her brother's rudeness. የልጂቱ ፡ ለእናቷ ፡ አሳቢነትና ፡ የወንድሟ ፡ ብልግና ፡ ይፃረራሉ

**contribute**
1. አዋጣ. How much money did you contribute to the organization? ለድርጅቱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ አዋጣህ ?
2. ጽሑፍ ፡ አቀረበ. He contributes to the local paper. ለቀበሌው ፡ ጋዜጣ ፡ ጽሑፍ ፡ ያቀርባል
3. ተጨማሪ ፡ ምክንያት ፡ ሆነ. Poor food contributed to the child's illness. ለልጁ ፡ ሕመም ፡ መጥፎው ፡ ምግብ ፡ ተጨማሪ ፡ ምክንያት ፡ ሆነ

**contribute to**
1. ረዳ. Your efforts have contributed to my success. ጥረትህ ፡ እንዲሳካልኝ ፡ ለማድረግ ፡ ረድቶኛል
2. አባሰ. This noise just contributes to the confusion. ይህ ፡ ጩኸት ፡ ሁከቱን ፡ ያብሰዋል

**contribution**
1. መዋጮ. We received your contribution with thanks. መዋጮህን ፡ ከምስጋና ፡ ጋር ፡ ተቀብለነዋል

2. ስጦታ. The contributions of some liberal donors assured the construction of the hospital.
ያንዳንድ ፡ ለጋስ ፡ በጎ ፡ አድራጊዎች ፡ ስጦታ ፡
ሆስፒታሉ ፡ እንዲሠራ ፡ ምክንያት ፡ ሆነ
3. ጽሑፍ. The newspaper is short of contributions to the May issue. ጋዜጣው ፡ ለግንቦቱ ፡
እትም ፡ ጽሑፎች ፡ አጥረውታል
4. ያቀረበው ፡ ሐሳብ. His contributions to the discussion were well received. ለውይይቱ ፡ ያቀ
ረበው ፡ ሐሳብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተቀባይነት ፡ አገኘ

**contrite** ጸጸት ፡ የሞላበት
He wrote an apology in contrite words.
ጸጸት ፡ በሞላበት ፡ አነጋገር ፡ የይቅርታ ፡ ደብ
ዳቤ ፡ ጻፈ

**contrive** (vt.) ፈጠረ
The engineer contrived a new engine. መሀንዲ
ሱ ፡ አዲስ ፡ ሞተር ፡ ፈጠረ

**contrive** (vi.) እንደምንም ፡ ብሎ ፡ ቻለ
I will contrive to be there by ten o'clock.
ባራት ፡ ሰዓት ፡ እንደምንም ፡ ብዬ ፡ እዚያ ፡
ለመድረስ ፡ እችላለሁ

**control** (controlled)
1. በጅ ፡ ያዘ. He controls sixty percent of the business. ከንግዱ ፡ ከመቶ ፡ ስድሳውን ፡ በጁ ፡ ይ
ዟል
2. ተቈጣጠረ. A captain controls his ship and its crew. ካፒቴኑ ፡ መርከቡንና ፡ መርከበኞቹን ፡
ይቈጣጠራል
Efforts are made to control the disease.
በሽታን ፡ ለመቈጣጠር ፡ ጥረት ፡ ይደረጋል
3. ገታ. It is hard to control one's anger.
ንዴትን ፡ መግታት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**control oneself** ራሱን ፡ ገታ
Though I tried hard to control myself, I could not. ራሴን ፡ ለመግታት ፡ ጥረት ፡ ባደር
ግም ፡ አልተሳካልኝ

**be controlled** በ - - - ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው
The railway is government controlled. የባቡሩ ፡
ሐዲድ ፡ በመንግሥት ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው

**control** (n.) ቁጥጥር
Government controls have increased in recent years. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ የመንግሥት ፡ ቁ
ጥጥር ፡ እየጨመረ ፡ ሄዷል
The children are getting beyond my control.
ልጆቹ ፡ ለቁጥጥር ፡ አስቸግረውኛል

**be under control** በ - - - ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው
A child is under his parents' control. ልጁ ፡
በወላጆቹ ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው
The police moved into the riot area, and now everything is under control. ፖሊስ ፡ ወደ ፡ ሁ
ከቱ ፡ ስፍራ ፡ ስለሄደ ፡ አሁን ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡
በቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው

**bring under control** ጸጥ ፡ አደረገ
The police brought the riot under control.
ፖሊሶቹ ፡ ሁከቱን ፡ ጸጥ ፡ አደረጉት

**get control of** ተቈጣጠረ
The attempt to get control of the meeting was a failure. ስብሰባውን ፡ ለመቈጣጠር ፡ የተደ
ረገው ፡ ሙከራ ፡ ፈጽሞ ፡ ሳይሳካ ፡ ቀረ

**keep under control** ተቈጣጠረ
A stern teacher is needed to keep the students under control. ተማሪዎችን ፡ ለመቈጣጠር ፡ ጥ
ብቅ ፡ አስተማሪ ፡ ያስፈልጋል

**controller** ተቈጣጣሪ
The controller checked the accounts and found no errors. ተቈጣጣሪው ፡ ሒሳቡን ፡ ተቈጣጥሮ ፡
ምንም ፡ ጉድለት ፡ አላገኘም

**controversial** አከራካሪ
The exact location of the border is a controversial matter. የወሰኑ ፡ ትክክለኛ ፡ ቦታ ፡ አ
ከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ ነው
You won't get anywhere by writing such controversial reports. ይህንን ፡ የመሰለ ፡ አከራ
ካሪ ፡ ጽሑፍ ፡ መጻፍ ፡ አያዋጣህም

**controversy** (controversies)
1. ሙግት. The controversy concerning the war took a long time. ጦርነቱን ፡ የሚመለከተ
ው ፡ ሙግት ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ወሰደ
2. ዋና ፡ የመከራከሪያ ፡ ምክንያት. The religious controversy centered around the nature of Christ. የሃይማኖቱ ፡ ዋና ፡ የመከራከሪያ ፡ ምክ
ንያት ፡ የክርስቶስ ፡ ባሕርይ ፡ ነው
3. ንትርክ. The director declared his position in the controversy. ዲሬክተሩ ፡ በንትርኩ ፡ ጊ
ዜ ፡ የሚያምንበትን ፡ ሐሳብ ፡ ገለጸ
4. አለመግባባት. They decided to settle the controversy once and for all. አለመግባባታቸው
ን ፡ ለዘለቄታው ፡ ውሳኔ ፡ ሊሰጡት ፡ ተስማሙ

**contumacious** የማይታዘዝ
The contumacious child was expelled from school. የማይታዘዘው ፡ ልጅ ፡ ከትምህርት ፡ ቤ
ት ፡ ወጣ

**convalesce** አገገመ
He is in Florida to convalesce. ለማገገም ፡ ወ
ደ ፡ ፍሎሪዳ ፡ ሄደ

**convalescent** ገመምተኛ
He is still a convalescent and cannot partake in sports. እሱ ፡ አሁንም ፡ ገመምተኛ ፡ ስለሆነ ፡ በእስፖርት ፡ ሊካፈል ፡ አይችልም

**convene** (vt.) ሰበሰበ
The President convened the Congress for a special session. ፕሬዚዳንቱ ፡ የምክር ፡ ቤቱን ፡ ለልዩ ፡ ጉባኤ ፡ ሰበሰበ

**convene** (vi.) ተሰበሰበ
The Parliament convenes next week. የምክር ፡ ቤቱ ፡ በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ ይሰበሰባል

**convenience** (n.) ምቾት
Our new apartment has every modern convenience. አዲሱ ፡ አፓርተማችን ፡ ማንኛውም ፡ ዘመናዊ ፡ ምቾት ፡ አለው

**at one's convenience** በሚመችው
I will come any day at your convenience. በማንኛውም ፡ በሚመችህ ፡ ቀን ፡ እመጣለሁ

**at one's earliest convenience**
Call me at your earliest convenience! ቶሎ ፡ ባመችህ ፡ ጊዜ ፡ ደውልልኝ

**for convenience** እንዲመቸው
I keep the book near my desk for convenience. እንዲመቸኝ ፡ መጽሐፉን ፡ ጠረጴዛዬ ፡ አጠገብ ፡ አስቀምጠዋለሁ

**convenient** ምቹ ፤ ያመቸ
The bus service here is very convenient. እዚህ ፡ የአውቶቡሱ ፡ አገልግሎት ፡ በጣም ፡ ምቹ ፡ ነው
Their house is convenient to all transportation. ቤታቸው ፡ ለማንኛውም ፡ መጓጓዣ ፡ ያመቸ ፡ ነው

**be convenient** ተመቸ
It is very convenient for me to take the bus. በአውቶቡስ ፡ መሄዱ ፡ ለኔ ፡ በጣም ፡ ይመቸኛል

**conveniently** በሚያመች ፡ ሁኔታ
The book was conveniently arranged according to subject matter. መጽሐፉ ፡ በሚያመች ፡ ሁኔታ ፡ በየአርእስቱ ፡ ተዘጋጅቷል
*The hotel is conveniently located for travelers. ሆቴሉ ፡ ለመንገደኞች ፡ አማካይ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው

**convent** የሴቶች ፡ ገዳም
There is a convent on the top of the mountain. በተራራው ፡ ላይ ፡ የሴቶች ፡ ገዳም ፡ አለ

**convention**
1. ስብሰባ. Were you at the convention last year? ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ስብሰባው ፡ ላይ ፡ ነበርክ ?
2. ስምምነት. There is an international convention for the treatment of prisoners of war. ስለጦር ፡ ምርኮኞች ፡ አያያዝ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ስምምነት ፡ አለ
3. ባህል. Does convention in your country forbid women to smoke? ያገራችሁ ፡ ባህል ፡ ሴቶች ፡ እንዳያጨሱ ፡ ይከለክላል ?
4. ልማድ. His actions mock convention. አድራጎቱ ፡ ልማድን ፡ ያፌርሳል

**conventional**
1. የተለመደ. I prefer the conventional method. የተለመደውን ፡ መንገድ ፡ እመርጣለሁ
2. ልማድ ፡ አክባሪ. She is very conventional and does not like modern ways of dress. ልማድ ፡ አክባሪ ፡ ስለሆነች ፡ ዘመናዊ ፡ አለባበስን ፡ አትወድም

**converge**
1. ተገናኘ. The four roads converge at one point. አራቱ ፡ መንገዶች ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ይገናኛሉ
2. ከያለበት ፡ ጐረፈ. The crowds converged on the stadium. ሕዝቡ ፡ ከያለበት ፡ ወደ ፡ እስታዲዮሙ ፡ ጐረፈ

**(be) conversant with** ዐወቀ
He is conversant with Ethiopian history. የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ያውቃል

**conversation** ወሬ ፤ ጭውውት
His conversation was all about his family problems. ወሬው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ቤተሰቡ ፡ ችግር ፡ ነበር
Conversation tends to slow down work. ወሬ ፡ ሥራን ፡ ይጐትታል
He hoped to direct the conversation to a new channel. ጭውውቱን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ ሊመራው ፡ ሞከረ

**carry on a conversation** ተጨዋወተ
It is hard to carry on a conversation in a crowded room. ሕዝብ ፡ በበዛበት ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ መጨዋወት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**have a conversation** ተነጋገረ
I had a long conversation with the boss. ከለቃዩው ፡ ጋር ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ ተነጋግሬያለሁ

**conversational** ለንግግር ፡ የሚረዳ
The students study conversational Amharic. ተማሪዎቹ ፡ ለንግግር ፡ የሚረዳቸው ፡ አማርኛ ፡ ይማራሉ

**converse** (v.) ተወያየ ፤ ተጨዋወተ
We conversed about the language problem for a long time. ስለ ፡ ቋንቋው ፡ ችግር ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ተወያየን

We conversed about our childhood. ስለ ፡ ልጅነታችን ፡ ጊዜ ፡ ተጫዋወትን

**converse** (n.) ተቃራኒ
Heat is the converse of cold. ሙቀት ፡ የቅዝቃዜ ፡ ተቃራኒ ፡ ነው

**conversion**
1. መለወጥ. The Israelis are setting up a plant for the conversion of salt water into potable water. እስራኤላውያን ፡ የባሕርን ፡ ውኃ ፡ ወደ ፡ መጠጥ ፡ ውኃ ፡ ለመለወጥ ፡ ፋብሪካ ፡ በማቆም ፡ ላይ ፡ ናቸው
2. መመንዘር. Conversion of Ethiopian money into foreign money must be done at the National Bank. የኢትዮጵያን ፡ ብር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ ለመመንዘር ፡ የሚቻለው ፡ በብሔራዊ ፡ ባንክ ፡ ነው
*The conversion of the coastal tribes to Islam occurred in the nineteenth century. በየባሕር ፡ ዳሩ ፡ የሚገኙት ፡ ጐሳዎች ፡ ወደ ፡ እስልምና ፡ ሃይማኖት ፡ የተለወጡት ፡ በዐሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ነው
*The conversion of Ethiopia to Christianity took place in the 4th century A.D. ኢትዮጵያ ፡ ባራተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ክርስትናን ፡ ተቀበለች

**convert** (v.)
1. መነዘረ. He tried to convert Ethiopian dollars into Swiss francs. የኢትዮጵያን ፡ ብር ፡ ወደ ፡ ስዊዝ ፡ ፍራንክ ፡ ሊመነዝር ፡ ሞከረ
2. ለወጠ. These machines convert cotton into cloth. እነዚህ ፡ መሣሪያዎች ፡ ጥጥን ፡ ወደ ፡ ልብስ ፡ ይለውጡታል
3. አሳመነ. Missionaries are trying to convert the pagans. ሚስዮናውያን ፡ አረመኔዎችን ፡ ለማሳመን ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ናቸው
[See also 'believing']

**convert** (n.) አዲስ ፡ ሃይማኖት ፡ የተቀበለ ፡ ሰው
The converts swore to destroy their idols. አዲስ ፡ ሃይማኖት ፡ የተቀበሉት ፡ ሰዎች ፡ ጣዖቶቻቸውን ፡ ሊያጠፉ ፡ ማሉ

**become a convert to** ተቀበለ
He became a convert to the Christian faith. የክርስትናን ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀበለ

**convex** [እንደ ፡ ኳስ ፡ አካል ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ያበጠ]

**convey**
1. አጓጓዘ. The train conveys passengers. ባቡሩ ፡ ሰው ፡ ያጓጉዛል
2. አቀረበ. He conveyed my greetings to his relatives. ሰላምታዬን ፡ ለዘመዶቹ ፡ አቀረበልኝ
3. አሳየ. Her expression conveys her disappointment. ፊቷ ፡ ቅሬታዋን ፡ ያሳያል
4. አስተላለፈ. The old farmer conveyed his farm to his son. ሽማግሌው ፡ ገበሬ ፡ ማሳውን ፡ ለልጁ ፡ አስተላለፈ

**conveyance**
1. ማስተላለፍ. Books are for the conveyance of ideas. መጻሕፍት ፡ ሐሳብን ፡ ለማስተላለፍ ፡ ይረዳሉ
2. ማመላለሻ. Railroad trains and buses are public conveyances. ባቡሮችና ፡ አውቶቡሶች ፡ የሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ ናቸው

**convict** (v.)
1. ፈረደ(በት). The judge convicted him of murder. ዳኛው ፡ በነፍስ ፡ ግዳይ ፡ ወንጀል ፡ ፈረደበት
2. አስፈረደ(በት). These new facts will be enough to convict him. ይህ ፡ አዲስ ፡ ማስረጃ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ለማስፈረድ ፡ በቂ ፡ ይሆናል

**be convicted** ተፈረደ(በት)
He was convicted of murder. በነፍስ ፡ ገዳይነት ፡ ተፈረደበት

**convict** (n.) ወንጀለኛ ፤ የተፈረደበት ፡ ወንጀለኛ
Three convicts escaped. ሦስት ፡ ወንጀለኞች ፡ አመለጡ
They caught the fugitive convict. የኮበለለውን ፡ የተፈረደበትን ፡ ወንጀለኛ ፡ ያዙት

**conviction** እምነት ፤ የጸና ፡ እምነት
I hope you will hold to your conviction. በእምነትህ ፡ እንደምትጸና ፡ ተስፋ ፡ አለኝ
His statement lacked conviction. የሱ ፡ ቃል ፡ የጸና ፡ እምነት ፡ ጐደለው
*The conviction of the embezzler was announced in the newspaper. አጭበርባሪው ፡ እንደተፈረደበት ፡ በጋዜጣ ፡ ተገለጸ

**convince** አሳመነ
I had a hard time convincing her. እሷን ፡ ለማሳመን ፡ በጣም ፡ ደከምኩ

**be convinced** አመነ ፤ ተማመነ
Many are convinced that smoking has a great deal to do with lung cancer. የሳንባ ፡ ነቀርሳ ፡ ሲጃራ ፡ ከማጨስ ፡ የሚመጣ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ብዙዎች ፡ ያምናሉ
I am convinced of his honesty. በታማኝነቱ ፡ እተማመናለሁ

**convincing** አጥጋቢ
The illumination of his theory was not con-

vincing. ስለ ፡ ቲዮሪው ፡ የሰጠው ፡ ማብራሪያ ፡ አጥጋቢ ፡ አልነበረም

**convivial** የደስ ፡ ደስ
A convivial gathering was held when I returned from my trip. ከጉዞዬ ፡ ስመለስ ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ግብዣ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር

**convocation** ስብሰባ
There was a convocation of clergymen in Aksum. በአክሱም ፡ የካህናት ፡ ስብሰባ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር

**convoke** ስብሰባ ፡ ጠራ
The President convoked the Congress. ፕሬዚዳንቱ ፡ ምክር ፡ ቤቱን ፡ ስብሰባ ፡ ጠራ

**convoy** የታጀበ ፡ የመርከቦች ፡ ጓድ
The convoy was attacked by submarines. የታጀበው ፡ የመርከቦች ፡ ጓድ ፡ በሰርጓጅ ፡ መርከብ ፡ ተጠቃ

**truck convoy** የታጀቡ ፡ መኪናዎች
The truck convoy was attacked in the desert. የታጀቡት ፡ መኪናዎች ፡ በረሃው ፡ ውስጥ ፡ አደጋ ፡ ተጣለባቸው

**convulse** በሣቅ ፡ ፈጀ
The comedian convulsed the audience. አጫዋቹ ፡ ተመልካቾቹን ፡ በሣቅ ፡ ፈጃቸው

**be convulsed**
1. ተንቀጠቀጠ ፤ ተንዘፈዘፈ. The patient was convulsed with pain. በሽተኛው ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ተንቀጠቀጠ ፡ (ተንዘፈዘፈ)
2. ተንከተከተ. When the audience heard the joke, they were convulsed with laughter. ተመልካቾቹ ፡ ቀልዱን ፡ ሲሰሙ ፡ በሣቅ ፡ ተንከተከቱ

**convulsion** መንቀጥቀጥ ፤ መንዘፍዘፍ
The child's convulsions filled me with fear. የሕፃኑ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ (መንዘፍዘፍ) ፡ ፍርሃት ፡ አሳደረብኝ

**cook** (vt.) አበሰለ
He cooked the meat in an oven. ሥጋውን ፡ በምድጃ ፡ አበሰለው

**cook** (vi.)
1. ምግብ ፡ ሠራ. She cooks well. ጥሩ ፡ ምግብ ፡ ትሠራለች
2. ምግብ ፡ አዘጋጀ. We don't have time to cook tonight. ዛሬ ፡ ማታ ፡ ምግባችንን ፡ ለማዘጋጀት ፡ ጊዜ ፡ የለንም

**be cooked** ተቀቀለ
Meat is often chopped up before it is cooked. ሥጋ ፡ ከመቀቀሉ ፡ በፊት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ይከተፋል

**cook** (n.) ወጥ ፡ ቤት
She is the best cook we ever had. ከነበሩን ፡ ወጥ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ ትበልጣለች

**cookie** ብስኩት
The child likes cookies. ልጁ ፡ ብስኩት ፡ ይወዳል

**cooking** ወጥ ፡ ቤትነት ፤ ምግብ ፡ አሠራር
She prides herself on her good cooking. በጥሩ ፡ ወጥ ፡ ቤትነቷ ፡ ትኮራበታለች
He complimented me on my cooking. ስለ ፡ ምግብ ፡ አሠራሬ ፡ አመሰገነኝ

**cool** (vt.)
1. አቀዘቀዘ. She blew on the soup to cool it. ሾርባውን ፡ ለማቀዝቀዝ ፡ እፍ ፡ አለችው
2. (= intr.) ከ --- በረድ ፡ አለ. The father advised his son to cool his anger. አባትዬው ፡ ልጁ ፡ ከቁጣው ፡ በረድ ፡ እንዲል ፡ መከረው

**cool** (vi.) ቀዘቀዘ
The soup is cooling. ሾርባው ፡ እየቀዘቀዘ ፡ ነው

**cool** (adj.)
1. ቀዝቀዝ ፡ ያለ. Keep it in a cool place! ቀዝቀዝ ፡ ያለ ፡ ስፍራ ፡ አኑረው
2. ቀዝቃዛ. Hot days alternate with cool days in Addis Ababa. አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ሞቃትና ፡ ቀዝቃዛ ፡ ቀናት ፡ ይፈራረቃሉ
3. የቀዘቀዘ. They gave the visitor a cool reception. ለጎብኚው ፡ የቀዘቀዘ ፡ አቀባበል ፡ አደረጉለት

**be cool**
1. በረደ. The coffee is not cool yet. ቡናው ፡ ገና ፡ አልበረደም
2. ረጋ ፡ ያለ. He is cool in the face of danger. ባደጋ ፡ ጊዜ ፡ ረጋ ፡ ያለ ፡ ነው
3. በረደ(ው). I'm cool, but open the window if you feel hot. እኔ ፡ በርዶኛል ፤ ሆኖም ፡ አንተ ፡ ከሞቀህ ፡ መስኮቱን ፡ ልትከፍት ፡ ትችላለህ

**it gets pretty cool** ቀዝቀዝ ፡ አለ
It gets pretty cool here in the evening. ማታ ፡ ማታ ፡ እዚህ ፡ ቀዝቀዝ ፡ ይላል

**coop** (n.) ባለሽቦ ፡ ቆጥ
The chicken is in a coop. ዶሮዋ ፡ ባለሽቦ ፡ ቆጥ ፡ ውስጥ ፡ ናት

**coop** (v.), ~ **up** ዘጋ(በት)
They cooped him up in a tiny room. ትንሽ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ዘጉበት

**cooperate**
1. ተግባብቶ ፡ ሠራ. He tried to cooperate with his co-workers. ከሥራ ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ተግባብቶ ፡ ለመሥራት ፡ ሞከረ
2. ተባበረ. The people in the village cooperated in building a bridge. የመንደሩ ፡ ሕዝብ ፡ ድልድይ ፡ ለመሥራት ፡ ተባበረ

**cooperation**
1. እርዳታ. Can we count on your cooperation? ባንተ ፡ እርዳታ ፡ እምነት ፡ ልንጥል ፡ እንችላለን ?
2. ትብብር. The cooperation of the two communities became greater over the years. የሁለቱ ፡ ቀበሌዎች ፡ ነዋሪዎች ፡ ትብብር ፡ እያደር ፡ ጠነከረ
*The cooperation of the two communities resulted in the building of a bridge. ሁለቱ ፡ መንደሮች ፡ ተባብረው ፡ ድልድይ ፡ ሠሩ

**cooperative** (n.) የኅብረት ፡ ድርጅት
The farmers market their grain through cooperatives. ገበሬዎቹ ፡ እህላቸውን ፡ በኅብረት ፡ ድርጅት ፡ በኩል ፡ ይሸጣሉ

**(be) cooperative** ረዳ
The librarian was most cooperative when I was looking for the book. መጽሐፉን ፡ ስፈልግ ፡ የመጻሕፍት ፡ ቤቱ ፡ ሠራተኛ ፡ በጣም ፡ ረዳኝ

**coordinate** (v.)
1. አስተባበረ. It is necessary to coordinate economic and social policies. የኤኮኖሚንና ፡ የኅብረተ ፡ ሰብን ፡ ዓላማዎች ፡ ማስተባበር ፡ ያስፈልጋል
2. አስተካከለ. Let's coordinate our watches so we will have the same time. ጊዜያችን ፡ እንዳይለያይብን ፡ ሰዓታችንን ፡ እናስተካክል

**coordinate** (n.) ጥቅስ
What are the map coordinates of Washington? የዋሽንግተን ፡ የካርታ ፡ ጥቅሶች ፡ ምን ፡ ናቸው ?

**cope, ~ with**
1. አረካ. One clerk could not cope with their demands. አንድ ፡ ሻጭ ፡ ፍላጎታቸውን ፡ ሊያረካላቸው ፡ አልቻለም
2. ተቋቋመ. I will try to cope with his rudeness. ብልግናውን ፡ እቋቋመዋለሁ

**copious** በርከት ፡ ያለ
He kept copious notes of the meetings. ስለ ፡ ስብሰባው ፡ ቃለ ፡ ጉባኤ ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ማስታወሻ ፡ ያዘ

**copious supply of** በገፍ ፡ የቀረበ
The copious supply of beer was soon consumed. በገፍ ፡ የቀረበው ፡ ቢራ ፡ ወዲያውኑ ፡ አለቀ

**copper** መዳብ
The pipe is made of copper. ቧምቧው ፡ ከመዳብ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**copy** (copied), v.
1. ገለበጠ. Copy the letter exactly! ደብዳቤውን ፡ በትክክል ፡ ገልብጥ
2. ቀዳ. He copies his mother's way of talking. የናቱን ፡ ያነጋገር ፡ ፈሊጥ ፡ ይቀዳል

**copy down** አሰፈረ
He copied down the notes in his notebook. ማስታወሻዎቹን ፡ በደብተሩ ፡ ላይ ፡ አሰፈረ

**copy** (copies), n.
1. ግልባጭ. I made a copy of the letter. የደብዳቤውን ፡ ግልባጭ ፡ ጻፍኩ
2. ቅጂ. The copies of the examination are in the blue folder. የፈተናው ፡ ቅጂዎች ፡ ሰማያዊው ፡ ማኅደር ፡ ውስጥ ፡ ናቸው
*Send me a copy of his book. ከሱ ፡ መጽሐፍ ፡ አንዱን ፡ ላክልኝ

**coral** (n.) የተከማቸ ፡ ዛጐል
Coral grows on the ocean floor. የተከማቸ ፡ ዛጐል ፡ በውቅያኖስ ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ ያድጋል

**coral** (adj.) የዛጐል
She wears a coral necklace. የዛጐል ፡ ሐብል ፡ ታደርጋለች

**cord** ሲባጎ
I haven't enough cord to tie up the package. ጥቅሉን ፡ የማስርበት ፡ በቂ ፡ ሲባጎ ፡ የለኝም
[See also 'umbilical cord']

**cordial** ልባዊ
The host gave us a cordial welcome. ባለቤቱ ፡ ልባዊ ፡ አቀባበል ፡ አደረገልን

**cordiality**
1. ትሕትና. The clerk's cordiality pleased all the customers. የሻጩ ፡ ትሕትና ፡ ደንበኞቹን ፡ ሁሉ ፡ አስደሰታቸው
2. (= adj.) ልባዊ ፡ የሆነ. The cordiality of his welcome pleased me. ልባዊ ፡ የሆነው ፡ አቀባበል ፡ አስደሰተኝ

**cordially** በጋለ ፡ ስሜት
He shook my hand cordially. በጋለ ፡ ስሜት ፡ ጨበጠኝ

**cordon** ጓድ
A cordon of police protected the bank. አንድ ፡ የፖሊስ ፡ ጓድ ፡ ባንኩን ፡ ጠበቀ

**core**
1. ውስጥ. The core of the apple was rotten. ቱፋው ፡ ውስጡ ፡ በስብሷል
2. ፍሬ ፡ ነገር. Let's get to the core of the subject! ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ እንነጋገር
**to the core** በሙሉ
This apple is rotten to the core. ይህ ፡ ቱፋ ፡ በሙሉ ፡ በስብሷል

**cork** (v.) ወተፈ
Don't forget to cork the bottle! ጠርሙሱን ፡ መወተፍ ፡ አትዘንጋ

**cork** (n.) ቡሽ
The cork of the bottle came out and the liquor spilled. የጠርሙሱ ፡ ቡሽ ፡ ተነቅሎ ፡ አረቄው ፡ ፈሰሰ

**corkscrew** የጠርሙስ ፡ መክፈቻ
I bought a corkscrew at the market. የጠርሙስ ፡ መክፈቻ ፡ ከገበያ ፡ ገዛሁ

**corn**
1. በቆሎ. A lot of corn is produced in America. በአሜሪካ ፡ በቆሎ ፡ በብዛት ፡ ይመረታል
2. እህል. Fields of corn are a common sight in the Ethiopian highlands. በኢትዮጵያ ፡ ደጋዎች ፡ የእህል ፡ ማሳዎች ፡ በብዛት ፡ ይታያሉ
3. መጅ. He removed a large corn from my toe. ከእግሬ ፡ ጣት ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ መጅ ፡ ቀረፈልኝ
[See also 'ear, parched']

**corner** (v.) ማምለጫ ፡ አሳጣ
The cat cornered the mouse. ድመቷ ፡ አይጧን ፡ ማምለጫ ፡ አሳጣቻት

**corner** (n.)
1. ጥግ ፤ ሥርቻ. The man you want is sitting in the corner. የምትፈልገው ፡ ሰውዬ ፡ ከጥጉ ፡ ተቀምጧል
The cat hid in an obscure corner of the room. ድመቷ ፡ ካንድ ፡ ከማይታይ ፡ ሥርቻ ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ ተደበቀች
2. መታጠፊያ. It is advisable to cross streets only at corners. መንገዶችን ፡ መታጠፊያቸው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ማቋረጥ ፡ የሚሻል ፡ ይመስለኛል
3. አካባቢ. He likes to read in a quiet corner of the house. እቤቱ ፡ ጸጥ ፡ ባለ ፡ አካባቢ ፡ ማንበብ ፡ ይወዳል
4. ዳር. She waited at the street corner for a bus. በመንገድ ፡ ዳር ፡ ቆማ ፡ አውቶቡስ ፡ ጠበቀች
5. ጠርዝ. He struck his arm on the corner of a box. የሣጥን ፡ ጠርዝ ፡ ክንዱን ፡ መታው
**around the corner** እዚህ ፡ ቅርብ
They live around the corner. እዚህ ፡ ቅርብ ፡ ይኖራሉ
**in all corners of the world** ከጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ
People have searched in all corners of the world for gold. ሰዎች ፡ ወርቅ ፡ ፍለጋ ፡ ከጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ ተጕዘዋል
[See also 'turn']

**cornerstone**
1. የመሠረት ፡ ድንጋይ. The President laid the cornerstone of the new university building. ፕሬዚዳንቱ ፡ ያዲሱን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ሕንጻ ፡ የመሠረት ፡ ድንጋይ ፡ አኖሩ
2. መሠረት. Thrift is a cornerstone of wealth. ቁጠባ ፡ የብልጽግና ፡ መሠረት ፡ ነው

**cornmeal** የበቆሎ ፡ ዱቄት
Cornmeal is used in making bread. የበቆሎ ፡ ዱቄት ፡ ዳቦ ፡ ይሆናል

**corollary** ውጤት
Good health is a corollary of having good habits. ጥሩ ፡ ጤና ፡ የጥሩ ፡ ልማድ ፡ ውጤት ፡ ነው

**coronation**
1. የዘውድ ፡ በዓል. I was not invited to His Majesty's coronation. ለግርማዊነታቸው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ አልተጠራሁም ፡ ነበር
2. የዘውድ ፡ መጫን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት. The coronation is concluded when the patriarch anoints the Emperor. የዘውድ ፡ መጫን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ፓትርያርኩ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥቱን ፡ ሲቀባው ፡ ይፈጸማል

**corporal** (n.) የዐሥር ፡ አለቃ
The corporal was demoted for insubordination. የዐሥር ፡ አለቃው ፡ ባለመታዘዙ ፡ ከማዕረጉ ፡ ዝቅ ፡ ተደረገ

**corporal punishment** በአካል ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ቅጣት
Corporal punishment deters delinquency among the young. በአካል ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ቅጣት ፡ ወጣቶችን ፡ ከጥፋት ፡ ያርቃል

**corporation** ማኅበር
They formed a corporation to sell steel goods. የብረታ ፡ ብረት ፡ እቃ ፡ ለመሸጥ ፡ ማኅበር ፡ አቋቋሙ

**corps** ጓድ
He established a corps of engineers to supervise highway construction. የአውራ ፡ ጐዳናን ፡ ሥራ ፡ ለመቈጣጠር ፡ የመሀንዲሶች ፡ ጓድ ፡ አቋቋመ
[See also 'peace']

**corpse**
1. ሬሳ. After a man dies, the old men wash the corpse. ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሬሳውን ፡ ያጥባሉ
2. አስከሬን. The grieving relatives placed the corpse in a beautiful coffin. ሐዘንተኞቹ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ አስከሬኑን ፡ በሚያምር ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አኖሩት

**corpulent** ወፍራም
Who is the corpulent old man? ይህ ፡ ወፍራም ፡ ሽማግሌ ፡ ማን ፡ ነው ?

**corral** በረት
The cattle are kept in a corral during the night. የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ ሌሊት ፡ በረት ፡ ውስጥ ፡ ያድራሉ

**correct** (v.)
1. አረመ. Please correct the mistakes in Amharic! ያማርኛ ፡ ስሕተቶችን ፡ አርም
2. ቀጣ. You ought not to correct your children for their bad manners in public. ስለ ፡ መጥፎ ፡ ምግባራቸው ፡ ልጆችህን ፡ ባደባባይ ፡ መቅጣት ፡ አይገባህም
3. ስሕተት ፡ አረመ. I had a hard time correcting her. ስሕተቷን ፡ ሳርም ፡ በጣም ፡ ተቸገርኩ
4. አስተካከለ. I corrected my watch by the radio. ሰዓቴን ፡ በሬዲዮው ፡ አስተካከልኩ

**be corrected** ተቃና
His deficient knowledge of algebra must be corrected before the exam. በቂ ፡ ያልሆነው ፡ የአልጀብራ ፡ ችሎታው ፡ ከፈተናው ፡ በፊት ፡ መቃናት ፡ አለበት

**correct** (adj.)
1. ትክክለኛ. Is this the correct address? ይህ ፡ ትክክለኛው ፡ አድራሻ ፡ ነው ?
2. ልክ. Is my addition correct? ድምሬ ፡ ልክ ፡ ነው ?
3. መልካም. His correct manners are admired by all. መልካም ፡ ጠባዩ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የተደነቀ ፡ ነው
[See also 'stand']

**correction** እርማት
Please make the necessary corrections! አስፈላጊውን ፡ እርማት ፡ አድርግ

**correctness** ትክክለኛነት
The auditor attested to the correctness of the account. ተቈጣጣሪው ፡ የሒሳቡን ፡ ትክክለኛነት ፡ አረጋገጠ

**correlate** አዛመደ
The student correlated his knowledge of history with his knowledge of geography. ተማሪው ፡ የታሪክንና ፡ የመልክአ ፡ ምድር ፡ ትምህርቱን ፡ አዛመዳቸው

**correlation** ግንኙነት
There is a correlation between climate and vegetation. ባየሩ ፡ ጠባይና ፡ በዕፀዋት ፡ መካከል ፡ ግንኙነት ፡ አለ

**correspond**
1. ተመሳሰለ. The translation does not correspond to the original. ትርጉሙ ፡ ከዋናው ፡ ጽሑፍ ፡ ጋር ፡ አይመሳሰልም
2. ተስማማ. Her hat and shoes correspond with her white dress. ባርኔጣዋና ፡ ጫማዎቿ ፡ ከነጭ ፡ ልብሷ ፡ ጋር ፡ ይስማማሉ
3. ደብዳቤ ፡ ተላላከ. Menelik corresponded with the Emperor John about an Italian invasion. አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ከአፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ኢጣልያኖች ፡ ወረራ ፡ ደብዳቤ ፡ ተላላኩ

**correspond with each other** ተጻጻፈ
We have been corresponding with each other for six years. ስድስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ስንጻጻፍ ፡ ነበር

**correspondence**
1. ተመሳሳይነት. There is not much correspondence between their ideas and ours. በኛና ፡ በነሱ ፡ ሐሳብ ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ ተመሳሳይነት ፡ የለም
2. የደብዳቤ ፡ መጻጻፍ ፡ ጉዳይ. My job is to take care of the correspondence. የኔ ፡ ሥራ ፡ የደብዳቤ ፡ መጻጻፍን ፡ ጉዳይ ፡ ማከናወን ፡ ነው
*He carries on a wide correspondence. ከብዙ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ይጻጻፋል

**correspondent** ዜና ፡ አጠናቃሪ
He is a correspondent for the Times. የታይምስ ፡ ዜና ፡ አጠናቃሪ ፡ ነው

**be correspondents** ተጻጻፉ
She and I have been regular correspondents for over a year. እርሷና ፡ እኔ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ እንጻጻፍ ፡ ነበር

**corridor** መተላለፊያ
Large cupboards were set up in the corridor.

ትልልቅ ፡ ቁም ፡ ሣጥኖች ፡ ከመተላለፊያው ፡ ላይ ፡ ተደርድረዋል

**corroborate** አረጋገጠ
The facts corroborate his account of the accident. የደረሰው ፡ ነገር ፡ እሱ ፡ ስለ ፡ አደጋው ፡ የተናገረውን ፡ ያረጋግጣል

**corrode** ተበላ ፤ ዛገ
Iron corrodes easily. ብረት ፡ በቀላሉ ፡ ይበላል ፡ (ይዝጋል)

**corrosive** የመብላት
The corrosive action of the salt water ruined his watch. የጨውማው ፡ ውኃ ፡ የመብላት ፡ ኀይል ፡ ሰዓቱን ፡ አበላሸበት

**corrugate** ወጣ ፡ ገባ ፡ አድርጎ ፡ አጐባበጠ
They corrugated the cardboard to pack merchandise. ሸቀጡን ፡ ሊከቱበት ፡ ካርቶኑን ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ አድርገው ፡ አጐባበጡት

**corrugated iron** ቆርቆሮ
In Ethiopia, they use corrugated iron to cover the roof. በኢትዮጵያ ፡ ጣሪያ ፡ ለመሸፈን ፡ በቆርቆሮ ፡ ይጠቀማሉ

**corrupt** (v.)
1. አበላሸ. Love of money has corrupted his ideals. የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ ዓላማውን ፡ አበላሽቶበታል
2. ምግባረ ፡ ከንቱ ፡ አደረገ. The abuse of power corrupts the official who practices it. ሥልጣን ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ መጠቀም ፡ ይህን ፡ የሚያደርገውን ፡ ባለሥልጣን ፡ ምግባረ ፡ ከንቱ ፡ ያደርገዋል
3. በከለ. Bribery has corrupted many a judge. ጉቦ ፡ መብላት ፡ ብዙ ፡ ዳኞችን ፡ በክሎዋቸዋል

**corrupt** (adj.)
1. ምግባረ ፡ ብልሹ. The corrupt judge should be removed from office. ምግባረ ፡ ብልሹ ፡ ዳኛ ፡ ከሥራው ፡ መነቀል ፡ አለበት
2. የተበላሸ. They tried to overthrow the corrupt government. የተበላሸውን ፡ መንግሥት ፡ ለመገልበጥ ፡ ሞከሩ
3. ውድቅ. The church condemns corrupt morals. ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ውድቅ ፡ ግብረ ፡ ገብነትን ፡ ታወግዛለች
4. የተዛባ. The text of this book is corrupt. የዚህ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቃል ፡ የተዛባ ፡ ነው

**corruption**
1. ብልሽት ፤ መበላሸት ፤ የባለሥልጣኖች ፡ ምግባረ ፡ ቢስነት. We must put an end to corruption. ብልሽትን ፡ (መበላሸት, or የባለሥልጣኖች ፡ ምግባረ ፡ ቢስነት) ፡ ፈጽመን ፡ ማቆም ፡ አለብን
2. እምነትን ፡ ማጉደል. Corruption will bring about the collapse of justice. እምነትን ፡ ማጉደል ፡ የፍትሕን ፡ ውድቀት ፡ ያስከትላል
3. ውድቅ ፡ ግብረ ፡ ገብነት. The church condemns corruption. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውድቅ ፡ ግብረ ፡ ገብነትን ፡ ታወግዛለች

**cortege, funeral** ~ የቀብር ፡ ጉዞ ፤ ለቀስተኛ
The funeral cortege moved slowly down the street. የቀብሩ ፡ ጉዞ ፡ መንገዱን ፡ ይዞ ፡ አዘገመ
The funeral cortege walked with measured steps. ለቀስተኛው ፡ በተመጠነ ፡ የዝግታ ፡ እርምጃ ፡ ተጓዘ

**corvée** ሠራተኛን ፡ ያለዋጋ ፡ ማስገደድ
Corvée was used to build the roads until recently. እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ መንገድ ፡ የሚሠራው ፡ ሠራተኛን ፡ ያለዋጋ ፡ በማስገደድ ፡ ነበር

**cosmetic** መኳኳያ
Women have always used cosmetics to beautify themselves. ሴቶች ፡ አምሮ ፡ ለመታየት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በመኳኳያ ፡ ይጠቀማሉ

**cost** (cost), v.
1. አወጣ. How much does it cost? ምን ፡ ያህል ፡ ያወጣል ?
2. አስወጣ. The accident will cost him a pretty sum. አደጋው ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ ያስወጣዋል
3. ፈጀ. Making war costs vast sums of money. ጦርነት ፡ ማድረግ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ይፈጃል
The battle cost many lives. ጦርነቱ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ፈጀ
4. ጠየቀ. Renting pack animals will cost a lot of money. የጭነት ፡ ከብት ፡ መከራየት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ይጠይቃል
5. አሳልፎ ፡ ሰጠ. It cost him his life to save his son. ልጁን ፡ ለማዳን ፡ ሕይወቱን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ

**cost** (n.)
1. ወጪ. The cost of living is rising. የኑሮ ፡ ወጪ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ነው
2. ዋጋ. The cost of this hat is $10. የዚህ ፡ ባርኔጣ ፡ ዋጋ ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ ነው
3. ጉዳት. The victory was won at a frightful cost. ድሉ ፡ የተገኘው ፡ አሰቃቂ ፡ ጉዳት ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ነው

**at the cost of**
*The fox escaped from the trap at the cost of a leg. ቀበሮው ፡ ከወጥመዱ ፡ ሲያመልጥ ፡ እግሩ ፡ ተቈርጦ ፡ ቀረ

**at all costs** በምንም ፡ ዓይነት ፤ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ

He wants it at all costs. በምንም ፡ ዓይነት ፡ እሱን ፡ ነገር ፡ ማግኘት ፡ ይፈልጋል
We must get it at all costs. በምንም ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ ፡ ማግኘት ፡ አለብን

**high (increased) cost of living** የኑሮ ፡ ውድነት
The high cost of living means nothing to some people. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የኑሮን ፡ ውድነት ፡ ከምንም ፡ አይቈጥሩም

**increased cost** መወደድ
Before building a house he took into account the increased cost of materials. ቤት ፡ ከመሥራቱ ፡ በፊት ፡ የሕንጻ ፡ መሣሪያዎች ፡ መወደዳቸውን ፡ ግምት ፡ ውስጥ ፡ አደረገ
[See also 'dear, living']

**costly** ውድ
She wears a costly necklace. ውድ ፡ ሐብል ፡ ታደርጋለች

**costume** ልብስ
The actors wore historical costumes. ተዋንያኑ ፡ የጥንት ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ ነበር

**cot** ሸራ ፡ አልጋ
During his stay in the country he slept on a cot. ባላገር ፡ በቈየበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሸራ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ይተኛ ፡ ነበር

**cottage** ጎጆ
They have a small cottage on the lake. ሐይቁ ፡ አጠገብ ፡ አነስተኛ ፡ ጎጆ ፡ አላቸው

**cotton** ጥጥ
Cotton grows in warm countries. ጥጥ ፡ ሞቃት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ይበቅላል
You will find some cotton in the medicine chest. መድኃኒቱ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ትንሽ ፡ ጥጥ ፡ ታገኛለህ

**couch** (v.) ገለጸ
Poets couch their ideas in beautiful language. ገጣሚዎች ፡ ሐሳባቸውን ፡ በውብ ፡ ቃላት ፡ ይገልጻሉ

**couch** (n.) መከዳ
The nobility of old had couches in their houses. የጥንት ፡ መኳንንት ፡ በየቤታቸው ፡ መከዳ ፡ ነበራቸው

**cough** (v.) ሳለ
The baby has been coughing all night. ሕፃኑ ፡ ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ ሲስል ፡ አደረ

**cough** (n.) ሳል
His cough is due to tobacco smoke and not a cold. ሳሉ ፡ ከትምባሆ ፡ ጭስ ፡ የተነሣ ፡ እንጂ ፡ ጉንፋን ፡ አይደለም

**coughing, fit of ~** አጣዳፊ ፡ ሳል
He had a fit of coughing. አጣዳፊ ፡ ሳል ፡ ይዞት ፡ ነበር
[See also 'seizure']

**could**, see **can**

**council** ኮሚቴ ፤ ምክር ፡ ቤት
The teachers' council recommended a raise. ያስተማሪዎች ፡ ኮሚቴ ፡ የደሞዝ ፡ ጭማሪ ፡ እንዲደረግ ፡ አሳሰበ
The council slashed the mayor's budget. ምክር ፡ ቤቱ ፡ ከንቲባው ፡ ያቀረበውን ፡ ባጀት ፡ ጐመደበት

**Regency Council** የዘውድ ፡ አማካሪዎች
In the event of the Emperor's death, a Regency Council will take over until the Crown Prince reaches maturity. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሲሞቱ ፡ አልጋ ፡ ወራሹ ፡ ላቅመ ፡ አዳም ፡ እስኪደርስ ፡ የዘውድ ፡ አማካሪዎች ፡ ሥልጣን ፡ ይይዛሉ

**hold a council** ተመካከረ
The rebels held a council to decide what to do with the prisoners. ሽፍቶቹ ፡ እስረኞቹ ፡ ምን ፡ እንደሚደረጉ ፡ ለመወሰን ፡ ተመካከሩ

**counsel** (v.) መከረ
He counseled us to leave early. ቀደም ፡ ብለን ፡ እንድንሄድ ፡ መከረን

**counsel** (n.)
1. ምክር. Let me give you some good counsel! ጥሩ ፡ ምክር ፡ ልስጥህ
2. ጠበቃ. They could afford the best counsel. ምርጥ ፡ ጠበቃ ፡ ሊገዙ ፡ ይችሉ ፡ ነበር

**hold a counsel** ስብሰባ ፡ አደረገ
The laity and the clergy agreed to hold a counsel. ምእመናኑና ፡ ካህናቱ ፡ ስብሰባ ፡ ለማድረግ ፡ ተስማሙ

**take counsel** ተመካከረ
They took counsel together before deciding to invest all their money. ያላቸውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ከመወሰናቸው ፡ በፊት ፡ ተመካከሩ

**counselor**
1. ጠበቃ. He engaged a counselor to defend his case. ጉዳዩን ፡ እንዲከራከርለት ፡ ጠበቃ ፡ ገዛ
2. አማካሪ. The prime minister is the king's counselor. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የንጉሡ ፡ አማካሪ ፡ ነው

3. ተቈጣጣሪ. He is a counselor at a boys' camp. በወንዶች ፡ ልጆች ፡ መዝናኛ ፡ ሰፈር ፡ ተቈጣጣሪ ፡ ነው

**count** (vt.) ቈጠረ
Please count your change! መልስህን ፡ ቍጠር

**count** (vi.)
1. ቈጠረ. Can you count from one to twenty in Amharic? ካንድ ፡ እስከ ፡ ሀያ ፡ ባማርኛ ፡ ልት ቈጥር ፡ ትችላለህ ?
2. ተቈጠረ. This one is broken, so it doesn't count as a whole one. ይኸኛው ፡ ስለተሰበረ ፡ እንደ ፡ ሙሉ ፡ አይቈጠርም
3. ዋጋ ፡ አለው. Every moment counts. እያንዳን ዷ ፡ ደቂቃ ፡ ዋጋ ፡ አላት
4. ታየ. It's not the quantity but the quality that counts. የሚታየው ፡ ብዛቱ ፡ ሳይሆን ፡ ዓይነ ቱ ፡ ነው

**count among**
*You count among my best friends. አንተ ፡ ከ ልብ ፡ ወዳጆቼ ፡ አንዱ ፡ ነህ

**count (one) in** ጨመረ
Count me in if you want to know how many are going. የሚሄዱት ፡ ስንት ፡ እንደሆኑ ፡ ለ ማወቅ ፡ ትፈልግ ፡ እንደሆነ ፡ እኔንም ፡ ጨምረኝ

**count off** ለብቻ ፡ ቈጠረ
He counted off a hundred books. መቶ ፡ መጻሕ ፍት ፡ ለብቻ ፡ ቈጠረ

**count (on)**
1. ተማመነ(በት). You can count on each and every one of us. በያንዳንዳችን ፡ ልትተማመንብ ን ፡ ትችላለህ
You can always count on him to lend you money. ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ገንዘብ ፡ እንደሚያ በድርህ ፡ ልትተማመንበት ፡ ትችላለህ
2. አሰበ. You had better not count on an increase in your salary this year. በዚህ ፡ ዓመ ት ፡ የደሞዝ ፡ ጭማሪ ፡ አገኛለሁ ፡ ብለህ ፡ ባታ ስብ ፡ ይሻላል
3. እምነት ፡ ጣለ. Can we count on your help? ባንተ ፡ እርዳታ ፡ እምነት ፡ ልንጥል ፡ እንችላለን ?

**count oneself** ራሱን ፡ ቈጠረ
He counted himself lucky to have survived the crash. ከአደጋው ፡ ስለዳነ ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ ዕ ድለኛ ፡ ቈጠረ

**count (me) out!** አትጨምረኝ
If you are planning to go there, count me out! እዚያ ፡ ለመሄድ ፡ የምታስብ ፡ ከሆነ ፡ እኔን ፡ አ ትጨምረኝ
[See also 'nose']

**count** (n.)
1. ቈጠራ. The count has not yet been taken. ገና ፡ ቈጠራው ፡ አልተደረገም
2. ወንጀል. He has been found guilty on two counts. በሁለት ፡ ወንጀል ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

**take count of** አጠና ፤ ዐወቀ
Before going on a trip, you should take count of the weather conditions. ጉዞ ፡ ከመነሣትህ ፡ በ ፊት ፡ ያየሩን ፡ ሁኔታ ፡ ማጥናት ፡ (ማወቅ) ፡ አ ለብህ

**countenance** ፊት
His angry countenance frightened us all. ቍጡ ፡ ፊቱ ፡ ሁላችንንም ፡ አስደነገጠን

**noble countenance** ግርማ ፡ ሞገስ
The king has a noble countenance. ንጉሡ ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ አለው

**counter** (v.) ተቋቋመ
This country is building up its army to counter the threat of invasion. ይህች ፡ አገር ፡ ወረራ ን ፡ ለመቋቋም ፡ ጦሯን ፡ እያደራጀች ፡ ነች

**counter** (n.)
1. ቲኬት ፡ መሸጫ ፡ ቦታ. He was standing at the counter buying a ticket. ቲኬት ፡ መሸ ጫው ፡ ቦታ ፡ ቲኬት ፡ ለመግዛት ፡ ቆሞ ፡ ነበር
2. ባንክ. Let's have a drink at the counter! ባንኮው ፡ ላይ ፡ እንጠጣ

**under the counter** በድብቅ
The banned book was sold under the counter. የተከለከለው ፡ መጽሐፍ ፡ በድብቅ ፡ ይሸጥ ፡ ነበር

**counter (to)** ከ --- ውጭ
He acted counter to his promise. ከተናገረው ፡ ውጭ ፡ ፈጸመ
*He acted counter to orders. የታዘዘውን ፡ ነገር ፡ ተቃራኒ ፡ ሠራ

**counteract** ተከላከለ
A hot bath and a hot drink will sometimes counteract a chill. በሙቅ ፡ ውኃ ፡ መታጠብ ና ፡ ሙቅ ፡ ነገር ፡ መጠጣት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብርድን ፡ ይከላከላል

**counterattack** (v.) አጸፋውን ፡ መለሰ
The enemy counterattacked our position last night. ጠላት ፡ ትላንት ፡ ማታ ፡ ይዞታችንን ፡ አጸ ፋውን ፡ መለሰ

**counterbalance** መቋቋሚያ
Religion is a counterbalance to fear. ሃይማኖት ፡ የፍርሃት ፡ መቋቋሚያ ፡ ነው

**counterfeit** (v.) አስመሰሉ ፣ የውሸት ፣ ብር ፣ ሠራ
He was sent to prison for counterfeiting five dollar bills. ባለ ፣ አምስት ፣ ብር ፣ አስመስሎ ፣ የ ውሸት ፣ ብር ፣ ስለሠራ ፣ እስር ፣ ቤት ፣ ገባ

**counterfeit** (adj.) የውሸት
On inspection, the coin proved to be counterfeit. ሲመረመር ፣ ፍራንኩ ፣ የውሸት ፣ ሆኖ ፣ ተ ገኘ

**counterpart**
1. ተነጻጻሪ. An admiral in the navy is the counterpart of a general in the army. የባሕር ፣ ኀይል ፣ አድሚራል ፣ ከጦር ፣ ሰራዊት ፣ ጄኔራል ፣ ጋር ፣ ተነጻጻሪ ፣ ነው
2. ተቃራኒ. Night is the counterpart of day. ሌሊት ፣ የቀን ፣ ተቃራኒ ፣ ነው

**counting** ከ - - - ጋር
Counting the children, there are fifteen of us. ከልጆቹ ፣ ጋር ፣ ዐሥራ ፣ አምስት ፣ ነን

**countless** ቁጥር ፣ የሌለው
There are countless mistakes in his composition. በድርሰቱ ፣ ውስጥ ፣ ቁጥር ፣ የሌለው ፣ ስሕ ተት ፣ አለ

**country** (countries)
1. አገር. I have seen many countries. ብዙ ፣ አገሮች ፣ አይቻለሁ
I have never been out of the country. ከገር ፣ ወጥቼ ፣ አላውቅም
We drove through wooded country on our way home. ወደ ፣ ቤታችን ፣ ስንመለስ ፣ ጫካማ ፣ አገር ፣ አቋረጥን
2. ሕዝብ. The country will vote tomorrow. ሕዝቡ ፣ ነገ ፣ ድምፁን ፣ ይሰጣል
3. ባላገር. My aunt lives in the country and I live in the city. አክስቴ ፣ ባላገር ፣ ትኖራለች ፤ እ ኔ ፣ ግን ፣ ከተማ ፣ ውስጥ ፣ እኖራለሁ

**country** (adj.) ያገር ፣ ቤት
He likes country food. ያገር ፣ ቤት ፣ ምግብ ፣ ይወዳል
[See also 'native country']

**countryfolk** ያገር ፣ ቤት ፣ ሰዎች
Countryfolk still know traditional dances. ያገር ፣ ቤት ፣ ሰዎች ፣ አሁንም ፣ የባህል ፣ ጨዋታን ፣ ይጫወታሉ

**countryman**
1. ባላገር. He looks like a countryman to me. ለኔ ፣ እሱ ፣ ባላገር ፣ ይመስለኛል
2. ያገር ፣ ሰው. He is a countryman of mine. ያገሬ ፣ ሰው ፣ ነው
[See also 'fellow']

**countryside** ባላገር ፤ ገጠር
Pure air is found in the countryside rather than in the city. ከከተማ ፣ ይልቅ ፣ ባላገር ፣ (ገጠር) ፣ ውስጥ ፣ ንጹሕ ፣ አየር ፣ ይገኛል

**coup**
1. አድማ. The coup against the king failed. ንጉሡን ፣ ለመገልበጥ ፣ የተደረገው ፣ አድማ ፣ ሳይሳካ ፣ ቀረ
2. ተግባር. His getting the news to his newspaper before the others was a brilliant coup. ወሬውን ፣ ከሌሎቹ ፣ ቀድሞ ፣ ለራሱ ፣ ጋዜጣ ፣ ማድረሱ ፣ ድንቅ ፣ ተግባር ፣ ነበር

**couple** (v.), ~ **together** አቀጣጠለ ፤ አቈላለፈ
He coupled the two cars together. ሁለቱን ፣ ፉርጎዎች ፣ አቀጣጠላቸው ፣ (አቈላለፋቸው)

**couple** (n.)
1. ባልና ፣ ሚስት. I am living with an elderly couple. የምኖረው ፣ በዕድሜ ፣ ከገፉ ፣ ባልና ፣ ሚ ስት ፣ ጋር ፣ ነው
2. ሙሽሮች. The priest joins the couple in marriage. ቄሱ ፣ ሙሽሮቹን ፣ በጋብቻ ፣ ያስተሳስራል
3. ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ ጥንድ ፣ ጥንድ ፣ ሆነው. On the dance floor, many couples were dancing. በዳንሱ ፣ ክፍል ፣ ውስጥ ፣ ወንዶችና ፣ ሴቶች ፣ ጥንድ ፣ ጥንድ ፣ ሆነው ፣ ይደንሱ ፣ ነበር

**a couple of** አንድ ፣ ሁለት
I have only a couple of dollars with me. የያዝኩት ፣ አንድ ፣ ሁለት ፣ ብር ፣ ብቻ ፣ ነው

**newly married couple** ሙሽሮች
The newly married couple sat under the canopy. ሙሽሮቹ ፣ አጐበር ፣ ውስጥ ፣ ተቀምጠዋል

**couplet** ሁለት ፣ ቤት
The poem was written in couplets. ግጥሙ ፣ በ ሁለት ፣ በሁለት ፣ ቤት ፣ የተጻፈ ፣ ነበር

**coupon** ቲኬት
You can get coffee here with a coupon. እዚህ ፣ በቲኬት ፣ ቡና ፣ ልታገኝ ፣ ትችላለህ

**courage** ጀግንነት ፤ ጕብዝና
The soldier was rewarded for his courage. ወታደሩ ፣ ስለ ፣ ጀግንነቱ ፣ ተሸለመ
I applaud your courage. ጕብዝናህን ፣ አደንቃለሁ

**lose courage** ሐሞቱ ፣ ፈሰሰ
When he saw how many opponents he had

to face, he lost courage. የተወዳዳሪዎቹን ፡ ብዛት ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ሐሞቱ ፡ ፈሰሰ

**take courage!** አይዞህ ፡ በርታ

Take courage, things will get better! አይዞህ ፡ በርታ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ይሻሻላል

[See also 'evaporate, fail, infuse, master']

**courageous** ጀግና

He is a courageous soldier. ጀግና ፡ ወታደር ፡ ነው

**courier** መልእክተኛ

Government dispatches were sent by couriers. የመንግሥት ፡ ደብዳቤዎች ፡ በመልእክተኞች ፡ እጅ ፡ ይላኩ ፡ ነበር

**course**

1. አቅጣጫ. The river has changed its course. ወንዙ ፡ አቅጣጫውን ፡ ለውጧል
2. ዘዴ. The only sensible course was to go home. ጥሩ ፡ መስሎ ፡ የታየኝ ፡ ዘዴ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ ብቻ ፡ ነበር
3. ሜዳ. The golf course is large. የጎልፍ ፡ ሜዳ ፡ ሰፊ ፡ ነው
4. መሥመር. The plane is taking a straight course. አውሮፕላኑ ፡ ቀጥታ ፡ መሥመር ፡ ይዟል
5. ዓይነት ፡ ምግብ. The dinner had four courses. እራት ፡ ላይ ፡ አራት ፡ ዓይነት ፡ ምግብ ፡ በላን
6. ዓይነት ፡ ትምህርት. What courses did you take in college? ኮሌጅ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ትምህርቶች ፡ አጠናህ ?

**course of events** የጊዜው ፡ ሁኔታ

He has been following the course of events since the end of winter. ክረምቱ ፡ ከወጣ ፡ ጀምሮ ፡ የጊዜውን ፡ ሁኔታ ፡ ይከታተል ፡ ነበር

**as a matter of course** እንደተለመደው

No need to ask him, he will come as a matter of course. እሱን ፡ መጠየቅ ፡ አያስፈልግም ፤ እንደተለመደው ፡ ይመጣል

**in due course** ጊዜ ፡ ሲደርስ ፤ በጊዜው

You will be notified in due course. ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ ይነገረሃል

I will speak about that in due course. ስለዚህ ፡ በጊዜው ፡ እናገራለሁ

**in the course of**

1. በ - - - ውስጥ. I heard from him twice in the course of the year. በዓመት ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ጻፈልኝ
2. በ - - - ላይ. In the course of the conversation, he learned that he was to be promoted. በጨዋታው ፡ ላይ ፡ የማዕረግ ፡ እድገት ፡ የሚያገኝ ፡ መሆኑን ፡ ሰማ

**of course**

1. እንዴታ. Of course I know what you mean! እንዴታ ፤ ምን ፡ ማለትህ ፡ እንደሆነ ፡ አውቃለሁ
2. እርግጥ ፡ ነው. Of course I cannot compete with you. እርግጥ ፡ ነው ፤ ከንተ ፡ ጋር ፡ ልወዳደር ፡ አልችልም
3. መቼም. Extra services are charged for, of course. መቼም ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ ይከፈላል

**(must) run its course** እንደገባ ፡ ይውጣ

The disease must run its course; there is no medicine which affects it. የሚያጠፋው ፡ መድኀኒት ፡ ስለሌለ ፡ በሽታው ፡ እንደገባ ፡ ይውጣ

**take a course in** ተማረ

I am taking a course in French. ፈረንሳይኛ ፡ እማራለሁ

**take its course** ሥርዓት ፡ ተከተለ

The law must take its course. ሕጉ ፡ ሥርዓቱን ፡ መከተል ፡ አለበት

[See also 'race course, study']

**court** (v.)

1. አሽኮረመመ. He has been courting her for quite some time. ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ ያሽኮረምማት ፡ ነበር
2. አግባባ. A good politician will always court the voters. ዐዋቂ ፡ የፖለቲካ ፡ ሰው ፡ ሁልጊዜ ፡ መራጮችን ፡ ያግባባል

**court danger** አደጋን ፡ ተጋፈጠ

It is foolish to court danger. አደጋን ፡ መጋፈጥ ፡ ጅልነት ፡ ነው

**court disaster** መከራ ፡ ጠራ

He courts disaster by reckless driving. ከመጠን ፡ በላይ ፡ ስለሚነዳ ፡ መከራን ፡ ይጠራል

**court favor** ደጅ ፡ ጠና

He has been courting the minister's favor in the hope of getting a job. ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ ሚኒስትሩን ፡ ደጅ ፡ ይጠና ፡ ነበር

**court** (n.)

1. ፍርድ ፡ ቤት. The court found him guilty. ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆኑን ፡ ወሰነበት
2. ችሎት. The king held court yesterday. ንጉሡ ፡ ትናንት ፡ ችሎት ፡ አስቻለ
3. ግቢ. The ambassador has not yet been received at the court. አምባሳደሩ ፡ ገና ፡ እግቢ ፡ ሄዶ ፡ እጅ ፡ አልነሣም
4. ቤተ ፡ መንግሥት. The court went into mourning when Prince Sahle Sellassie died. ልዑል ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ሲሞቱ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በሐዘን ፡ ላይ ፡ ነበር
5. አጥር ፡ ግቢ. There are many trees in our

court. አጥር ፡ ግቢያችን ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ዛፎች ፡ አሉ
6. ሜዳ. The tennis court is private. የቴኒሱ ፡ ሜዳ ፡ የግል ፡ ነው

**bring to court** ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረበ
They brought the accused to court. ተከሳሹን ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረቡት

**be thrown out of court** ተሰረዘ
The case was thrown out of court for lack of evidence. መረጃ ፡ በመታጣቱ ፡ ክሱ ፡ ተሰረዘ

**courteous** (= noun) የትሕትና ፡ ተግባር
It is courteous to help an old lady. ባልቴት ፡ መርዳት ፡ የትሕትና ፡ ተግባር ፡ ነው

**be courteous** ትሕትና ፡ አሳየ
He could at least have been courteous. የቀረው ፡ ቢቀር ፡ ትሕትና ፡ ማሳየት ፡ ይገባው ፡ ነበር

**courtesy**
1. ይሉኝታ. I have to go out of courtesy. ለይሉኝታ ፡ ስል ፡ መሄድ ፡ አለብኝ
2. መልካም ፡ እርዳታ. The costumes for the play are by courtesy of the museum. ለትያትሩ ፡ መሥሪያ ፡ የዋሉት ፡ ልብሶች ፡ በሙዚየሙ ፡ መልካም ፡ እርዳታ ፡ የተገኙ ፡ ናቸው
*Thank you for the courtesy of writing to me. አከብረሀ ፡ ስለጻፍክልኝ ፡ አመሰግንሃለሁ

**courthouse** ፍርድ ፡ ቤት
The courthouse is built of red brick. ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከቀይ ፡ ጡብ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**courtier** የክብር ፡ ተከታይ ፤ ባለሟል
The king arrived with his courtiers. ንጉሡ ፡ ከክብር ፡ ተከታዮቹ ፡ ጋር ፡ መጣ
His irreverent attitude towards the king annoyed the courtiers. በንጉሡ ፡ ፊት ፡ አክብሮት ፡ የጐደለው ፡ ምግባሩ ፡ ባለሟሎቹን ፡ አናደደ

**court-martial** የወታደር ፡ ፍርድ ፡ ቤት
The deserter received a court-martial. ከዳተኛው ፡ ወታደር ፡ ከወታደር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀረበ

**courtroom** ፍርድ ፡ ቤት
The courtroom was full of people. ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሕዝብ ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር

**courtyard** አጥር ፡ ግቢ
The courtyard has a small garden in it. አጥር ፡ ግቢው ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ አለ

**cousin** ያክስት ፡ ልጅ ፤ ያጐት ፡ ልጅ
My cousin remained unmarried. ያክስቴ ፡ ልጅ ፡ (ያጐቴ ፡ ልጅ) ፡ ቆማ ፡ ቀረች

**cove** [ከባሕር ፡ ሰላጤ ፡ መለስ ፡ ያለ ፡ ውኃው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ገባ ፡ ያለበት ፡ የባሕር ፡ አካል]

**covenant** ቃል ፡ ኪዳን
God made a covenant with Israel. እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገባ
[See also 'ark']

**cover** (v.)
1. ከደነ. He covered the roof with straw. ጣሪያውን ፡ ሣር ፡ ክዳን ፡ ከደነው
The maid covered the pot. ገረዲቱ ፡ ማሰሮውን ፡ ከደነችው
2. ሸፈነ. Snow covered the fields. በረዶ ፡ ሜዳውን ፡ ሸፍኖታል
In Ethiopia, they use corrugated iron to cover the roof. በኢትዮጵያ ፡ ጣሪያ ፡ ለመሸፈን ፡ በቆርቆሮ ፡ ይጠቀማሉ
3. አለበሰ. Use this cloth to cover the table! ጠረጴዛውን ፡ ይህን ፡ ጨርቅ ፡ አልብሰው
4. አጠቃለለ. The lectures covered the subject thoroughly. የተሰጡት ፡ ንግግሮች ፡ ትምህርቱን ፡ በሚገባ ፡ አጠቃለሉ
5. አጠናቀቀ. Have you covered everything that is important in that book? በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ አጠናቅቀኻልን?
6. አጠናቀረ. He covered the fire for the newspaper. ስለ ፡ ቃጠሎው ፡ ለጋዜጣው ፡ ዜና ፡ አጠናቀረ
7. ሸፋፈነ. Do not try to cover a mistake! ስሕተትህን ፡ ለመሸፋፈን ፡ አትሞክር
8. ተጓዘ. The camel covers sixty-five miles a day. ግመሏ ፡ በቀን ፡ ስድሳ ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ ትጓዛለች
9. ዘለቀ ፤ አቋረጠ. We covered the distance in three hours. መንገዱን ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ ዘለቅነው ፡ (አቋረጥነው)
10. ሄደ. We had to cover the rest of the way on foot. የቀረውን ፡ መንገድ ፡ በእግራችን ፡ መሄድ ፡ ነበረብን
11. አዳረሰ. The hunters fanned out to cover the whole field. አዳኞቹ ፡ ሜዳውን ፡ በሙሉ ፡ ለማዳረስ ፡ ተበታተኑ
12. ሰረረ. The stallion covered the mare. ፈረሱ ፡ ባዝራዋን ፡ ሰረራት

**be covered**
1. ተዋጠ. Because of the heat, his face was covered with sweat. ከሙቀቱ ፡ የተነሣ ፡ ፊቱ ፡ በላብ ፡ ተውጦ ፡ ነበር
2. (= tr.) ተመለከተ. +Is this case covered by the rule? ሕጉ ፡ ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ ይመለከተዋል ?

*The check is covered. ቼኩ ፡ የሚያዘውን ፡ ያህል ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘብ ፡ አለው

**cover oneself up** ለበሰ
It is cold outside; cover yourself up well! ውጪ ፡ ይበርዳል ፤ ደኅና ፡ አድርገህ ፡ ልበስ

**cover oneself with** ተጐናጸፈ
This hero covered himself with glory in the last war. ይህ ፡ ጀግና ፡ ባለፈው ፡ ጦርነት ፡ ከብርንና ፡ ዝነኛነትን ፡ ተጐናጸፈ

**cover over**
1. ደፈነ. They covered over the hole in the road with asphalt. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጉድጓድ ፡ ባስፋልት ፡ ደፈኑት
2.ሸፈነ. They covered the picture over with cloth so that it couldn't be seen. እንዳይታይ ፡ በማለት ፡ ሥዕሉን ፡ በጨርቅ ፡ ሸፈኑት

**cover up** ደበቀ
How can we cover up our tracks? ዱካችንን ፡ እንዴት ፡ መደበቅ ፡ እንችላለን ?

**cover up for** የ - - - ተግባር ፡ ሸፋፈነ
The commission tried to cover up for the corrupt judge. ኮሚሽኑ ፡ የብልሹውን ፡ ዳኛ ፡ ተግባር ፡ ለመሸፋፈን ፡ ሞከረ

**(be) covered with** ለበሰ
Everything is covered with dust. ሁሉ ፡ ነገር ፡ አቧራ ፡ ለብሷል
[See also 'ground, insurance, mildew']

**cover** (n.)
1. የሚደረብ ፡ ልብስ. I did not have enough covers last night. ትላንትና ፡ ሌሊት ፡ በቂ ፡ የሚደረብ ፡ ልብስ ፡ አልነበረኝም
2. እፊያ. When the water boils, remove the cover from the pan. ውኃው ፡ ሲፈላ ፡ እፊያውን ፡ ከድስቱ ፡ ላይ ፡ አንሺ
3. ክዳን. Where are the covers for these boxes? የነዚህ ፡ ሣጥኖች ፡ ክዳኖች ፡ የት ፡ አሉ ?
4. ሽፋን ፤ ልባስ. Who has torn off the cover of this book? የዚህን ፡ መጽሐፍ ፡ ሽፋን ፡ (ልባስ) ፡ የቀደደ ፡ ማን ፡ ነው ?
5. ተገን. The land was bare, and provided no cover for the troops. መሬቱ ፡ ገላጣ ፡ ስለነበረ ፡ ወታደሮቹ ፡ ተገን ፡ አልነበራቸውም

**from cover to cover** ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር
I read this book from cover to cover. ይህንን ፡ መጽሐፍ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ አነበብኩት

**remain under cover** ተደበቀ
He remained under cover until the police left. ፖሊሶቹ ፡ እስኪሄዱ ፡ ድረስ ፡ ተደበቀ

**take cover**
1. ተጠለለ. It is raining; take cover quickly! ይዘንባል ፤ ቶሎ ፡ ተጠለል
2. ጥግ ፡ ያዘ. When the soldiers heard gunfire, they took cover. ወታደሮቹ ፡ የጠመንጃ ፡ ተኩስ ፡ ሲሰሙ ፡ ጥግ ፡ ያዙ

**under cover** በምስጢር
Arrangements for the escape were made under cover. ለማምለጥ ፡ የተደረገው ፡ ዝግጅት ፡ በምስጢር ፡ ተያዘ

**coverage** ጥንቅር
The television coverage of the coronation was excellent. ቴሌቪዥኑ ፡ ስለ ፡ ዘውድ ፡ በዓሉ ፡ አከባበር ፡ ያቀረበው ፡ ጥንቅር ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነበር

**covering** ልባስ
This rug is a bed covering. ይህ ፡ ምንጣፍ ፡ ያልጋ ፡ ልባስ ፡ ነው
The exterior covering is made of iron. የውጪው ፡ ልባስ ፡ ከብረት ፡ የተሠራ ፡ ነው

**covert, take a ~ glance at** ሰረቅ ፡ አድርጎ ፡ ተመለከተ
I took a covert glance at the note. ማስታወሻውን ፡ ሰረቅ ፡ አድርጌ ፡ ተመለከትኩ

**covet** ተመኘ
Do not covet your friend's wife! የጓደኛህን ፡ ሚስት ፡ አትመኝ
The boys coveted his new hat. ልጆቹ ፡ አዲሱን ፡ ባርኔጣውን ፡ ተመኙት

**cow** ላም
The man breeds cows. ሰውየው ፡ ላም ፡ ያረባል

**coward** ፈሪ ፤ ቡከን
Don't be such a coward! እንደዚህ ፡ ፈሪ ፡ አትሁን
Cowards and cheats are contemptible. ቡከኖችና ፡ አታላዮች ፡ የሚናቁ ፡ ናቸው

**cowardice** ፈሪነት
They laughed at his cowardice. በፈሪነቱ ፡ ሣቁበት

**cowardly**
1. ፈሪ. The cowardly soldier was censured by his superiors. ፈሪው ፡ ወታደር ፡ ባለቆቹ ፡ ተነቀፈ
2. የፈሪነት. He was blamed for his cowardly act. ስለፈሪነት ፡ ተግባሩ ፡ ተገሠጸ

**cower** ተወሸቀ
The whipped dog cowered under the table. የተገረፈው ፡ ውሻ ፡ ጠረጴዛው ፡ ሥር ፡ ተወሸቀ

**cowherd** እረኛ
Two cowherds were guarding the cows. ሁለት ፡ እረኞች ፡ ላሞቹን ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር

**co-worker** የሥራ ፡ ጓደኛ
He tried to cooperate with his co-workers. ከሥራ ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ተግባብቶ ፡ ለመሥራት ፡ ሞከረ

**coy** ዓይን ፡ አፋር
A coy girl will not have many friends. ዓይን ፡ አፋር ፡ ልጃገረድ ፡ ብዙ ፡ ጓደኞች ፡ አይኖሯትም

**cozy**
1. የሞቀ. They have a very cozy home. በጣም ፡ የሞቀ ፡ ቤት ፡ አላቸው
2. ደስ ፡ የሚል. It was cozy sitting around the fire. ተቀምጦ ፡ እሳት ፡ መሞቁ ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ነበር

**crab** ሸርጣን
Crabs are found only in salt water. ሸርጣን ፡ ጨው ፡ ባለበት ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ይገኛል

**crack** (vt.)
1. ሰነጠቀ. You have cracked the window. መስኮቱን ፡ ሰንጥቀኸዋል
2. ፈረከሰ. I will crack the nuts. ገውዙን ፡ እፈረክሰዋለሁ
3. አጮኸ. The driver cracked the whip over the horses. ባለጋሪው ፡ ፈረሶቹ ፡ ላይ ፡ አለንጋ ፡ አጮኸባቸው

**crack** (vi.)
1. ተሰነጠቀ. The glass cracked when I poured the hot water in. የፈላ ፡ ውኃ ፡ ብጨምርበት ፡ ብርጭቆው ፡ ተሰነጠቀ
2. የሚሰነጥቅ ፡ ድምፅ ፡ አሰማ. Thunder rolled and lightning cracked. ነጐድጓዱ ፡ ባጕረመረመ ፡ ጊዜ ፡ መብረቁ ፡ የሚሰነጥቅ ፡ ድምፅ ፡ አሰማ
3. ሰለለ. His voice cracked. ድምፁ ፡ ሰለለ
4. ጮኸ. The whip cracked. ጅራፉ ፡ ጮኸ
5. ቅርሽም ፡ አለ. The branch cracked under the weight of the ice. በረዶው ፡ ስለከበደው ፡ ቅርንጫፉ ፡ ቅርሽም ፡ አለ

**crack down** ጥብቅ ፡ ቁጥጥር ፡ አደረገ
The authorities are cracking down on illegal gambling activities. ባለሥልጣኖቹ ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ቁማርን ፡ ለማጥፋት ፡ ጥብቅ ፡ ቁጥጥር ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ናቸው

**crack up** ራሱን ፡ ሳተ
She was in danger of cracking up under the strain. ከጭንቀቷ ፡ የተነሣ ፡ ራሷን ፡ እንዳትስት ፡ ያሰጋታል

**crack** (n.)
1. ንቃቃት. The cracks in the wall have to be filled. የግድግዳው ፡ ንቃቃት ፡ መደፈን ፡ አለበት
2. ቀዳዳ. I could see it through a crack in the fence. ባጥሩ ፡ ቀዳዳ ፡ ለማየት ፡ ቻልኩ
3. ስንጥቅ. There is a crack in the plate. ሳሕኑ ፡ ስንጥቅ ፡ አለው
4. ጩኸት. I thought I heard the crack of a rifle. የጠመንጃ ፡ ጩኸት ፡ የሰማሁ ፡ መሰለኝ
[See also 'dawn']

**cracker** ብስኩት
Children like crackers. ሕፃናት ፡ ብስኩት ፡ ይወዳሉ

**cradle**
1. የሕፃን ፡ አልጋ. She rocked the baby in the cradle. ሕፃኑን ፡ በሕፃን ፡ አልጋው ፡ ላይ ፡ ናጠችው
2. ልደት. They have insurance from the cradle to the grave. ከልደት ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ የሕይወት ፡ ዋስትና ፡ አላቸው
3. ምንጭ. Boston is the cradle of the American Revolution. ቦስተን ፡ ያሜሪካ ፡ የነጻነት ፡ ንቅናቄ ፡ ምንጭ ፡ ነች

**craft**
1. ሙያ. He learned the mason's craft. የግምበኝነት ፡ ሙያ ፡ ተማረ
2. ጥበብ. The carpenter fitted the bits of wood together with craft. አናጢው ፡ በጥበቡ ፡ የዕንጨት ፡ ቁርጥራጮችን ፡ አገጣጠመ
3. ዘዴ. By craft he got all the money from them. በዘዴው ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ከነርሱ ፡ ወሰደ

**craftsman** ባለ ፡ እጅ
There are not many craftsmen in this country. እዚህ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ባለ ፡ እጅ ፡ የለም

**craftsmanship** ጥበበኛነት
His handiwork shows craftsmanship. የእጅ ፡ ሥራው ፡ ጥበበኛነትን ፡ ያመለክታል

**crafty** ተንኮለኛ
He is a very crafty person, so don't make any deals with him. በጣም ፡ ተንኮለኛ ፡ ሰው ፡ ነውና ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ውል ፡ አታድርግ

**cram** (crammed), vt. አጨቀ
He crammed everything into one trunk. ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ባንድ ፡ ሣጥን ፡ አጨቀ

**cram** (vi.) ሸመደደ
It is better to study regularly than to cram at

the last minute. በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ከመሸምደ ድ ፡ ይልቅ ፡ በየጊዜው ፡ ማጥናት ፡ ይሻላል

**cramp** (v.) አሸመቀቀ
Fear cramped his stomach. ፍርሃት ፡ ሰውነቱን ፡ አሸመቀቀው

**cramp** (n.)
*The cramp in his leg prevented him from crossing the river. እግሩ ፡ ስለተሸመቀቀ ፡ ወንዙ ን ፡ ማቋረጥ ፡ አዳገቶት ፡ ነበር

**have a cramp** ሸመቀቀ(ው)
I have a cramp in my leg. እግሬን ፡ ይሸመቅ ቀኛል

**cramped** (adj.) የተጣበበ
He lived in cramped quarters. በተጣበበ ፡ ክፍ ል ፡ ኖረ

**crank** (v.) በማኑቬላ ፡ ተጠቀመ
He cranked the car to get it started. ሞተሩን ፡ ለማስነሣት ፡ በማኑቬላ ፡ ተጠቀመ

**crank** (n.)
1. ማኑቬላ. We need a crank to start this motor. ሞተሩን ፡ ለማስነሣት ፡ ማኑቬላ ፡ ያስፈልገናል
2. ወፈፌ. The President received many letters from cranks. ፕሬዚዳንቱ ፡ ከወፈፌዎች ፡ ብዙ ፡ ደብዳቤ ፡ ተቀበለ

**cranky** ነጭናጫ
The cranky child cried constantly. ነጭናጫው ፡ ልጅ ፡ ያለማቋረጥ ፡ አለቀሰ

**crash** (vt.) ጥሶ ፡ ገባ
The boys crashed the gate at the football game. ልጆቹ ፡ በኳስ ፡ ጨዋታው ፡ ጊዜ ፡ በሩን ፡ ጥሰው ፡ ገቡ

**crash** (vi.)
1. ተሰበረ. The beam is going to crash soon. አውታሩ ፡ በቅርብ ፡ ሊሰበር ፡ ነው
2. ወድቆ ፡ ተሰባበረ. One plane crashed. አንድ ፡ አውሮፕላን ፡ ወድቆ ፡ ተሰባበረ
3. በጣም ፡ ጮኸ. The thunder crashed. መብረ ቁ ፡ በጣም ፡ ጮኸ
4. ተጋጨ. Two cars crashed. ሁለቱ ፡ መኪናዎ ች ፡ ተጋጩ
5. ተንከታከተ. The vase crashed to the floor. ያበባ ፡ ማስቀመጫው ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ተንከታከተ

**crash into**
1. ገጨ. The driver braked suddenly, so I crashed into him. ነጂው ፡ በድንገት ፡ ፍሬን ፡ ስለያዘ ፡ ገጨሁት
2. ከ - - - ጋር ፡ ተላተመ. The bus crashed into a tree. አውቶቡሱ ፡ ከዛፍ ፡ ጋር ፡ ተላተመ
3. ወደ - - - ወድቆ ፡ ተሰባበረ. The bus crashed into the abyss. አውቶቡሱ ፡ ገደል ፡ ውስጥ ፡ ወ ድቆ ፡ ተሰባበረ

**crash through** ሰብሮ ፡ ገባ
A rock crashed through the window. ድንጋይ ፡ መስኮቱን ፡ ሰብሮ ፡ ገባ
[See also 'powder']

**crash** (n.)
1. ግጭት. Was anyone hurt in the crash? በግጭቱ ፡ የተጐዳ ፡ ሰው ፡ ነበር ?
2. ወድቆ ፡ መሰባበር. The plane crash was shocking news. የአውሮፕላኑ ፡ ወድቆ ፡ መሰባበ ር ፡ ዜና ፡ አስቃቂ ፡ ነበር
3. መጋጨት. The crash of dishes woke me up. የሳሕኖቹ ፡ መጋጨት ፡ አነቃኝ
4. ውድቀት. This year there was a big business crash. በዚህ ፡ ዓመት ፡ ትልቅ ፡ የንግድ ፡ ውድቀ ት ፡ ነበር

**loud crash** (= verb) ቋ ፡ አለ
The pitcher fell down with a loud crash. እንስራው ፡ ሲወድቅ ፡ ቋ ፡ አለ

**crass**
1. ፍጹም. His crass ignorance shows lack of education. ፍጹም ፡ ድንቁርናው ፡ አለመማሩን ፡ ያሳያል
2. የብልግና. His crass joking annoyed everybody. የብልግና ፡ ቀልዱ ፡ ሁሉንም ፡ አበሳጨ

**crate** ሣጥን
A crate full of oranges has come. አንድ ፡ ሣጥ ን ፡ ብርቱካን ፡ መጣ

**crater** የእሳተ ፡ ገሞራ ፡ አናት
The volcano has a lake in its crater. እሳተ ፡ ገሞራው ፡ አናት ፡ ላይ ፡ ሐይቅ ፡ አለ

**crave**
1. ወደደ. He craves chocolate more than anything. ከማንኛውም ፡ ነገር ፡ ቸኮላታ ፡ አብል ጦ ፡ ይወዳል
2. ለመነ. He craved a favor of the king. ንጉሡ ፡ አንድ ፡ ወሮታ ፡ እንዲያደርግለት ፡ ለመነ

**crave affection** ጓጓ
The child craved his mother's affection. ልጁ ፡ ለእናቱ ፡ ጓጓ

**craving** (n.) ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉጉት
He has a craving for sweets. ለከረሜላ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉጉት ፡ አለው

**crawl** (v.)
1. ዳኸ. Her child is beginning to crawl. ልጇ ፡ መዳኸ ፡ ጀምሯል

2. ተሳበ. The snake crawled across the ground. እባቡ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ተሳበ
3. በደረቱ ፡ እየተሳበ ፡ ገባ. The dog has crawled under the table. ውሻው ፡ በደረቱ ፡ እየተሳበ ፡ ጠረጴዛው ፡ ሥር ፡ ገባ
4. ተሸመቀቀ. My flesh crawled when I saw a big snake. ትልቅ ፡ እባብ ፡ ባየሁ ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቴ ፡ ተሸመቀቀ
5. ተጐተተ ፤ ተጐተተ(በት). The work crawled. ሥራው ፡ ተጐተተ
Time crawled that day. በዚያን ፡ ቀን ፡ ጊዜው ፡ ተጐተተብኝ
6. ዝግ ፡ አለ. Traffic barely crawls during the rush hour. በሥራ ፡ መውጫ ፡ ሰዓት ፡ መኪና ፡ ስለሚበዛ ፡ ጉዞ ፡ በጣም ፡ ዝግ ፡ ይላል
7. ተወረረ. The place was crawling with ants. በታው ፡ በጉንዳን ፡ ተወሯል

**crawl** (n.), **at a ~** ዝግ ፡ ብሎ
Traffic was moving at a crawl. መኪናዎቹ ፡ በጣም ፡ ዝግ ፡ ብለው ፡ ይሄዱ ፡ ነበር

**crayon** ከለር
He draws best with crayons. በከለር ፡ የበለጠ ፡ ይሥላል

**craze** ፈሊጥ
Dancing the twist is the latest craze. ትዊስትን ፡ መደነስ ፡ የጊዜው ፡ ፈሊጥ ፡ ነው

**crazy**
1. እብድ. The crazy boy was taken to the hospital. እብዱ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሆስፒታል ፡ ተወሰደ
2. የማይረባ. That is a crazy idea. የማይረባ ፡ ሐሳብ ፡ ነው

**be crazy** አበደ
Are you crazy? I would never do such a thing. አብደሃል ? እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ልሠራ ፡ አልችልም

**be crazy about**
I'm crazy about bananas. ለሙዝ ፡ ነፍሴ ፡ ይወጣል

**drive (someone) crazy** አሳበደ
You will drive me crazy yet. አንተ ፡ ሳታሳብደኝ ፡ አትቀርም

**go crazy** (= tr.) አሳበደ
+I am going crazy because of the gnats. እነዚህ ፡ ትንኞች ፡ ሊያሳብዱኝ ፡ ነው

**creak**
1. ሲጢጥ ፡ አለ. The door creaks terribly. በሩ ፡ በጣም ፡ ሲጢጥ ፡ ይላል
2. ተንቋቋ. The stairs are creaking. ደረጃው ፡ ይንቋቋል

**cream**
1. [ከፍተኛ ፡ ቅባትነት ፡ ያለው ፡ የወተት ፡ አናት]
2. ወተት. Do you take cream with your coffee? ቡና ፡ የምትጠጣው ፡ ከወተት ፡ ጋር ፡ ነው ?
3. ቅባት. That cream smells good. ያ ፡ ቅባት ፡ ጥሩ ፡ ሽታ ፡ አለው
4. ምርጥ. This tobacco is the cream of the crop. ይህ ፡ ትምባሆ ፡ ከተመረተው ፡ ሁሉ ፡ ምርጥ ፡ ነው

**crease** (vt.) አጨማደደ
Sitting in that position will crease your trousers. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ አቀማመጥ ፡ ሱሪህን ፡ ያጨማድዳል

**crease** (vi.) ተጨማደደ
The dress creased in the suitcase. ቀሚሱ ፡ ሻንጣው ፡ ውስጥ ፡ ስለተቀመጠ ፡ ተጨማደደ

**create**
1. ፈጠረ. God created man in his own image. እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ በአምሳሉ ፡ ፈጠረው
We have to create a position for him. ለሱ ፡ የሚሆን ፡ ሥራ ፡ መፍጠር ፡ አለብን
The students created a disturbance. ተማሪዎቹ ፡ ረብሻ ፡ ፈጠሩ
2. አስከተለ. This incident can create a global conflict. ይህ ፡ ግጭት ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ጥል ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል
3. ቀሰቀሰ. The incident created a lot of excitement. ድርጊቱ ፡ የብዙውን ፡ ስሜት ፡ ቀሰቀሰ

**creation**
1. ፍጥረት. The creation of the world was accomplished in six days. ፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ በስድስት ፡ ቀን ፡ ተከናወነ
Let all creation praise the Lord! ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመስግን
2. ድርሰት. Shakespeare's plays are great creations. የሼክስፒር ፡ ድራማዎች ፡ ግሩም ፡ ድርሰቶች ፡ ናቸው
3. ሥራ. At the art show, the creations of the various students were on display. በኪነ ፡ ጥበብ ፡ ትርእይት ፡ ላይ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ተማሪዎች ፡ ሥራዎች ፡ ታዩ

**creative** የፈጠራ ፡ ችሎታ ፡ ያለው
Sculptors are creative artists. ቅርጽ ፡ አውጪዎች ፡ የፈጠራ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ አርቲስቶች ፡ ናቸው

**creator** ፈጣሪ
He worships his creator in every way. በማንኛውም ፡ ሁኔታ ፡ ፈጣሪውን ፡ ያመልካል

**creature**

1. ፍጥረት. We do not know what kind of creature may inhabit Mars. በማርስ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ፍጥረት ፡ እንደሚኖር ፡ አናውቅም
2. ፍጡር. He is unable to turn his back on any suffering creature. በሥቃይ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ማንኛውንም ፡ ፍጡር ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ማለፍ ፡ አይሆንለትም
3. ሰው. She is a charming creature. ደስ ፡ የምትል ፡ ሰው ፡ ናት

**poor creature** የእግዜር ፡ ድኻ
The poor creatures are hungry. የእግዜር ፡ ድኾች ፡ ተርበዋል

**credentials**

1. የሹመት ፡ ደብዳቤ. The ambassador presented his credentials to the Emperor. አምባሳደሩ ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አቀረቡ
2. መረጃ. Only those with proper credentials are admitted. ተገቢ ፡ መረጃ ፡ ብቻ ፡ ያላቸው ፡ ይገባሉ

**credible** የሚታመን ፤ ሊታመን ፡ የሚቻል
His story sounds credible. ታሪኩ ፡ የሚታመን ፡ ይመስላል
It hardly seems credible. እምብዛም ፡ ሊታመን ፡ የሚቻል ፡ አይመስልም

**credit** (v.)

1. አመነ. You cannot credit those reports. እነዚያን ፡ ሪፖርቶች ፡ ልታምናቸው ፡ አትችልም
2. በሱ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ አስገባ. We will credit you with this amount. ይህንን ፡ ባንተ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ እናስገባዋለን

*We credit Edison with many inventions. ብዙዎች ፡ ፍልስፍናዎች ፡ የኤዲሰን ፡ ናቸው ፡ እንላለን

**be credited (with)**

1. ተባለ. In former times, many herbs were credited with healing powers. በድሮ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ዕፀዋት ፡ የፈዋሽነት ፡ ኀይል ፡ አላቸው ፡ ይባል ፡ ነበር
2. ተመሰገነ. The heroic woman was credited with saving the lives of many children. የብዙ ፡ ልጆችን ፡ ሕይወት ፡ በማትረፏ ፡ ጀግናዋ ፡ ሴት ፡ ተመሰገነች

**credit** (n.)

1. ብድር. The bank refused further credit to the firm. ባንኩ ፡ ለንግዱ ፡ ድርጅት ፡ ሌላ ፡ ብድር ፡ ከለከለ
2. ዱቤ. We can buy the furniture on credit. የቤት ፡ እቃውን ፡ በዱቤ ፡ መግዛት ፡ እንችላለን
3. ክብር. This hero is a credit to his country. ይህ ፡ ጀግና ፡ ላገሩ ፡ ክብር ፡ ነው
4. ዝና. This new book will not add to his credit. ይህ ፡ አዲስ ፡ መጽሐፍ ፡ ምንም ፡ ዝና ፡ አያተርፍለትም
5. ጥሩ ፡ ስም. If you pay your bills, your credit will be good. ያለብህን ፡ ሒሳብ ፡ በጊዜው ፡ ብትከፍል ፡ በገንዘብ ፡ በኩል ፡ ጥሩ ፡ ስም ፡ ታተርፋለህ
6. ክሬዲት. A semester course is worth three credits. በሰሚስተር ፡ የሚሰጥ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነት ፡ ሦስት ፡ ክሬዲት ፡ አለው

*Credit for raising the most money in the drive goes to the third grade. በተደረገው ፡ መዋጮ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ስላስገኙ ፡ ሦስተኛ ፡ ክፍሎች ፡ ይመሰገናሉ

**get (the) credit**

1. ተመሰገነ. I did the work and he got the credit. እኔ ፡ በሠራሁት ፡ እሱ ፡ ተመሰገነ
2. ምስጋና ፡ ተሰጠ. He will get credit for the conception of the plan. ሐሳቡን ፡ በማመንጨቱ ፡ ምስጋና ፡ ይሰጠዋል
3. ተቈጠረ(ለት). Will you get credit for these courses in college? እነዚህ ፡ ትምህርቶች ፡ በኮሌጅ ፡ ይቈጠሩልሃል ?

**give credit for** አመሰገነ(በት)
There is one thing you have got to give him credit for. እሱን ፡ ልታመሰግንበት ፡ የሚገባ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ

**outstanding credit** ዕዳ
He has an outstanding credit of $50. አምሳ ፡ ብር ፡ ዕዳ ፡ አለበት

**place credit** አመነ
I place full credit in what the boy says. ልጁ ፡ የሚለውን ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ አምናለሁ

**reflect credit on** አስመሰገነ
His son's behavior reflects credit on the father. የልጁ ፡ ጠባይ ፡ አባቱን ፡ ያስመሰግነዋል

**take credit (for)** ተመሰገነ
He likes to take credit for what somebody else has done. ሌላ ፡ ሰው ፡ በሠራው ፡ እሱ ፡ መመስገን ፡ ይወዳል

**(be) to one's credit** አስመሰገነው
It is to his credit that he admitted his guilt and took the punishment. ጥፋቱን ፡ አምኖ ፡ ቅጣቱን ፡ መቀበሉ ፡ የሚያስመሰግነው ፡ ነው

**creditor** ባለ ፡ ዕዳ ፤ አበዳሪ
He settled with his creditors. ከባለ ፡ ዕዳዎቹ ፡ (ከበዳሪዎቹ) ፡ ጋር ፡ ተስማማ

**credulous** ተታላይ
She was so credulous that the other children could fool her easily. ተታላይ ፡ ስለሆነች ፡ ልጆቹ ፡ በቀላሉ ፡ ሊያሞኙዋት ፡ ይችላሉ

**creed** እምነት
The French creed is "Liberty, Equality, Fraternity". የፈረንሳይ ፡ እምነት ፡ « እኩልነት ፤ ነጻነት ፤ ወንድማማችነት » ፡ ነው

**creek** ጅረት
This creek is dry in the dry season. ይህ ፡ ጅረት ፡ በበጋ ፡ ይደርቃል

**creep** (crept)
1. ዳኸ. Our baby learned to creep before it learned to walk. ልጃችን ፡ መራመድ ፡ ከመቻሉ ፡ በፊት ፡ መዳኸ ፡ ለመደ
2. ተሳበ. The vines crept over the castle walls. ሐረጉ ፡ ግንቡ ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ ተሳበ
3. ሄደ. There is a bedbug creeping on the wall. ትኋን ፡ ግድግዳው ፡ ላይ ፡ ትሄዳለች

**creep silently** እያደባ ፡ ተሳበ
The cat crept silently toward the bird. ድመቷ ፡ ወደ ፡ ወፏ ፡ እያደባች ፡ ተሳበች

**creep up** ቀስ ፡ ብሎ ፡ አጨለገ
We crept up and peeked over the wall. ቀስ ፡ ብለን ፡ ባጥሩ ፡ ላይ ፡ አጮልገን ፡ ተመለከትን

**make one's flesh creep** ሰውነቱ ፡ ተሰቀቀ
It made my flesh creep to hear her moan. ስታለቅስ ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቴ ፡ ተሰቀቀ
[See also 'stealthy']

**cremate, ~ the dead** ሬሳ ፡ አቃጠለ
It is not customary in this country to cremate the dead. እዚህ ፡ አገር ፡ ሬሳ ፡ ማቃጠል ፡ የተለመደ ፡ አይደለም

**crept,** see **creep**

**crescent, ~ of** ግማሽ
We could see the crescent of the moon behind the trees. በዛፉ ፡ ውስጥ ፡ ግማሽ ፡ ጨረቃ ፡ ትታየናለች

**crest** ጉትቻ
This bird has a red crest. ይቺ ፡ ወፍ ፡ ቀይ ፡ ጉትቻ ፡ አላት

**(be) crestfallen** ኩምሽሽ ፡ አለ
The players were crestfallen at losing the game. ተጫዋቾቹ ፡ ስለተሸነፉ ፡ ኩምሽሽ ፡ አሉ

**crevasse** ጉድባ
While mountain climbing he fell into a crevasse. ተራራ ፡ ሲወጣ ፡ ሳለ ፡ ጉድባ ፡ ውስጥ ፡ ገባ

**crevice** ስንጥቅ
Give me some plaster to plug up this crevice! ይህን ፡ ስንጥቅ ፡ የምደፍንበት ፡ ጭቃ ፡ ስጠኝ

**crew**
1. ሠራተኞች. All of the plane crew are Ethiopians. የአውሮፕላኑ ፡ ሠራተኞች ፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ናቸው
2. መርከበኞች. The entire crew was saved when the ship sank. መርከቡ ፡ ሲሰምጥ ፡ መርከበኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ዳኑ

**crib**
1. የሕፃን ፡ አልጋ. This crib is too small for our boy. ይህ ፡ የሕፃን ፡ አልጋ ፡ ለልጃችን ፡ አንሶታል
2. ጐተራ. He took all of the corn out of the crib. በቆሎውን ፡ ሁሉ ፡ ከጐተራው ፡ አወጣ

**cricket** ፌንጣ
The cricket eats grass. ፌንጣ ፡ ሣር ፡ ይበላል

**crime**
1. ወንጀል. Auto thefts and similar crimes are on the increase. የመኪና ፡ ስርቆትና ፡ ተመሳሳይ ፡ ወንጀሎች ፡ በመጨመር ፡ ላይ ፡ ናቸው
2. ጥፋት. It would be a crime to throw that away. ይህንንስ ፡ መጣል ፡ ጥፋት ፡ ነው
[See also 'partner, wave']

**commit a crime** ወንጀል ፡ ሠራ ፤ ወነጀለ
Because he committed a crime, he went to jail. ወንጀል ፡ ስለሠራ ፡ (ስለወነጀለ) ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ገባ

**criminal** (n.) ወንጀለኛ
He looks like a criminal. ወንጀለኛ ፡ ይመስላል

**criminal** (adj.) የወንጀለኛ
Arson is considered a criminal act. ቤት ፡ ማቃጠል ፡ የወንጀለኛ ፡ ሥራ ፡ ነው

**criminal act** የወንጀለኛ ፡ ሥራ ፤ ወንጀል
A criminal act harms society. የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ይጐዳል
Arson is considered a criminal act. ቤት ፡ ማቃጠል ፡ እንደ ፡ ወንጀል ፡ ይቈጠራል

**criminal law** የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ
Criminal law defines the different kinds of crimes. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወንጀሎችን ፡ ይወስናል

**criminal offense** የሚያስቀጣ ፡ ወንጀል
The concealment of facts by a witness is a criminal offense. የምስክር ፡ እውነተኛን ፡ ነገር ፡ መደበቅ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ ነው

**cringe** ተሸማቀቀ
The dog cringed at the sight of the whip. ውሻው ፡ አለንጋውን ፡ ሲያይ ፡ ተሸማቀቀ

**crinkle** አጨማደደ
Try not to crinkle the paper! ወረቀቱን ፡ እንዳታጨማድድ ፡ ተጠንቀቅ

**cripple** (v.)
1. አካለ ፡ ጐደሎ ፡ አደረገ. The accident crippled him. አደጋው ፡ አካለ ፡ ጐደሎ ፡ አደረገው
2. አሰናከለ. The strike crippled the steel industry. የሠራተኞች ፡ ሥራ ፡ ማቆም ፡ የብረታ ፡ ብረት ፡ ኢንዱስትሪውን ፡ አሰናከለ

**cripple** (n.) አካለ ፡ ስንኩል
The cripple is an object of charity. አካለ ፡ ስንኩሉ ፡ ተመጽዋች ፡ ነው

**crippled** ሽባ
The beggar held out a crippled hand. ለማኙ ፡ ሽባ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ለመነ

Constant encouragement helped the crippled child to walk again. ያልተቈጠበ ፡ ማደፋፈር ፡ ሽባውን ፡ ልጅ ፡ እንደገና ፡ እንዲራመድ ፡ ረዳው

**be crippled**
1. አካለ ፡ ጐደሎ ፡ ሆነ. He will be crippled for life. ዕድሜ ፡ ልኩን ፡ አካለ ፡ ጐደሎ ፡ ይሆናል
2. ተሰናከለ. The ship was crippled by the storm. መርከቧ ፡ በማዕበሉ ፡ ምክንያት ፡ ተሰናከለች

**crisis**
1. አስጊ ፡ ሁኔታ. Doctor, has he passed the crisis? ሐኪም ፡ ሆይ ! ከአስጊው ፡ ሁኔታ ፡ አምልጧል ?
2. አስጊ ፡ ወቅት ፤ ብጥብጥ. She bore up well during the crisis. በአስጊ ፡ ወቅት ፡ ራሷን ፡ በሚገባ ፡ ተቈጣጠረች
He kept his composure in the crisis. በብጥብጡ ፡ ጊዜ ፡ ረጋ ፡ ብሎ ፡ ነበር
3. ችግር. The world was afflicted by the financial crisis which began in 1929. በ፲፱፻፳፪ ፡ በጀመረው ፡ የገንዘብ ፡ ችግር ፡ ዓለም ፡ ተጐድቶ ፡ ነበር
4. ጠንቅ. The border incident precipitated a crisis in international relations. የድንበሩ ፡ ግጭት ፡ በዓለም ፡ ግንኙነት ፡ ላይ ፡ ጠንቅ ፡ አስከተለ

**crisp**
1. ጉልህ. He has a crisp way of speaking. ሲነጋገር ፡ ድምፁ ፡ ጉልህ ፡ ነው
2. ድርቅ ፡ ያለ. His crisp manner of speaking is offensive to some people. ድርቅ ፡ ያለው ፡ አነጋገሩ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎችን ፡ ያስቀይማል

**be crisp**
1. ኩርሽም ፡ ኩርሽም ፡ አለ The bread is crisp. ዳቦው ፡ ኩርሽም ፡ ኩርሽም ፡ ይላል
2. አነቃቃ. The air is crisp today. ዛሬ ፡ አየሩ ፡ ያነቃቃል

**crisscross** እያቈራረጠ ፡ አለፈ
Railroad tracks crisscross the valley. ሐዲዱ ፡ ሸለቆውን ፡ እያቈራረጠ ፡ ያልፋል

**criterion** መመዘኛ
A student's grades are not always the best criterion of his ability. ማርክ ፡ ብቻ ፡ የተማሪ ፡ ጠቅላላ ፡ ችሎታ ፡ መመዘኛ ፡ አይደለም

**critic**
1. ተቺ. Johnson is an art critic. ጆንሰን ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ተቺ ፡ ነው
2. ነቃፊ. She was such a constant critic that the other girls did not like her. ዘወትር ፡ ነቃፊ ፡ ስለሆነች ፡ ሌሎቹ ፡ ልጃገረዶች ፡ አይወዷትም ፡ ነበር
*The director is a poor critic of men. ዲሬክተሩ ፡ ሰው ፡ መገመት ፡ አይችልም

**critical**
1. ጥልቅ. His critical analysis of the economic situation was approved by all. ስለ ፡ ኤኮኖሚው ፡ ሁኔታ ፡ ያደረገውን ፡ ጥልቅ ፡ ምርመራ ፡ ሁሉም ፡ ተቀበሉት
2. አስጊ. His condition is critical. ሁኔታው ፡ አስጊ ፡ ነው
3. አሳሳቢ. This is a critical situation which could lead to war. ይህ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ሊያደርስ ፡ የሚችል ፡ አሳሳቢ ፡ ሁኔታ ፡ ነው
4. ዋነኛ. This was a critical step in the experiment. በሙከራው ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ዋነኛው ፡ ደረጃ ፡ ነበር

**critical opinion** ትችት
I would like to hear your critical opinion. የምትሰጠውን ፡ ትችት ፡ ለመስማት ፡ እፈልጋለሁ

**be critical of** ነቀፈ
He is critical of my efforts. ጥረቴን ፡ ሁሉ ፡ ይነቅፋል

**criticism**
1. ትችት. His criticisms are always negative. የሱ ፡ ትችት ፡ ሁልጊዜ ፡ ጉድለትን ፡ የሚያመለክት ፡ ነው
2. ነቀፌታ. He cannot stand criticism. ነቀፌታ ፡ አይወድም
3. ነቀፋ. His adverse criticism discouraged me. ጥላቻ ፡ ያዘለው ፡ ነቀፋው ፡ ተስፋ ፡ አስቈረጠኝ
[See also 'target']

**criticize**
1. ነቀፈ. The inspector criticized the un-

sanitary conditions of the kitchen. ተቈጣጣሪው ፡ የማድቤቱን ፡ የንጽሕና ፡ ጉድለት ፡ ነቀፈ
2. ገሠጸ(ተገሠጸ). The faint-hearted soldier was criticized by his superior. ፈሪው ፡ ወታደር ፡ በ አለቃው ፡ ተገሠጸ
3. መዘነ(ለት). It helps a music student to have an expert criticize his playing. ጨዋታውን ፡ የ ሚመዝንለት ፡ ዐዋቂ ፡ ሰው ፡ ማግኘት ፡ የሙዚቃ ፡ ተማሪን ፡ ይረዳዋል

**croak** ጮኸ
Frogs and ravens croak. እንቁራሪቶችና ፡ ቁራዎ ች ፡ ይጮኻሉ

**crocodile** አዞ
There are many crocodiles in the Nile. በዐባይ ፡ ወንዝ ፡ ውስጥ ፡ አዞ ፡ ሞልቷል

**crook**
1. ቈልማማ ፡ ዱላ. The shepherd's crook was broken. የእረኛው ፡ ቈልማማ ፡ ዱላ ፡ ተሰበረ
2. መጠምዘዣ. A crook in the stream causes floods during heavy rains. በከባድ ፡ ዝናብ ፡ ጊ ዜ ፡ የወንዙ ፡ መጠምዘዣ ፡ የውኃ ፡ መጥለቅለቅ ን ፡ ያስከትላል
3. አጭበርባሪ. This person is a crook. ይህ ፡ ሰው ፡ አጭበርባሪ ፡ ነው
[See also 'hook']

**crooked**
1. ጠማማ. This needle is crooked. ይህ ፡ መርፌ ፡ ጠማማ ፡ ነው
2. አጭበርባሪ. All the merchants in this section of the market are crooked. በዚህ ፡ ተራ ፡ ያሉ ፡ ነጋዴዎች ፡ ሁሉ ፡ አጭበርባሪዎች ፡ ናቸው
3. (= adv.) አዛንፎ. An inept carpenter made these stairs crooked. ሙያ ፡ የሌለው ፡ አናጺ ፡ እ ነዚህን ፡ ደረጃዎች ፡ አዛንፎ ፡ ሠራቸው

**be (become) crooked** ተጣመመ
The *nails* became crooked due to the intense heat. ከኀይለኛው ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ምስማሮቹ ፡ ተጣመሙ

**croon (softly) to** እሹሩሩ ፡ አለ
The woman crooned softly to her crying child. ሴትዮዋ ፡ የሚያለቅሰውን ፡ ልጇን ፡ እሹሩሩ ፡ አ ለችው

**crop** (cropped), v.
1. ጋጠ. The sheep have cropped the grass. በጎቹ ፡ ሣሩን ፡ ግጠውታል
2. አሳጠረ. The farmer cropped the tail of the horse. ገበሬው ፡ የፈረሱን ፡ ጭራ ፡ አሳጠረው

**crop up** ተፈጠረ
Many new problems are sure to crop up. ብዙ ፡ አዲስ ፡ ችግሮች ፡ እንደሚፈጠሩ ፡ አይጠረ ጠርም

**crop** (n.)
1. ሰብል. The farmers expect a good crop this year. ገበሬዎቹ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ጥሩ ፡ ሰብል ፡ ለማ ግኘት ፡ ይጠባበቃሉ
2. ምርት. The tenant farmers get a percentage of the crop. ጭሰኞቹ ፡ ከምርቱ ፡ ከመቶ ፡ የተ ወሰነ ፡ እጅ ፡ ይደርሳቸዋል
*A crop of new writers is coming up. አዳዲስ ፡ ደራሲያን ፡ በመፍለቅ ፡ ላይ ፡ ናቸው

**cross** (vt.)
1. ተሻገረ. He crossed the river in a boat. ወንዙን ፡ በጀልባ ፡ ተሻገረ
2. አቋረጠ. Cross the street at the green signal! አረንጓዴ ፡ መብራት ፡ ሲበራ ፡ መንገዱን ፡ አቋርጥ
When do we cross the border? ወሰኑን ፡ የምና ቋርጠው ፡ መቼ ፡ ነው ?
3. አጣመረ. He crossed his arms over his breast. እጆቹን ፡ በደረቱ ፡ ላይ ፡ አጣመረ
4. ደራረበ. He sat down and crossed his legs. ተቀምጦ ፡ እግሮቹን ፡ ደራረበ
5. ሐሳቡን ፡ አልተቀበለውም. If anyone crosses him, he gets very angry. ሐሳቡን ፡ ያልተቀበሉ ት ፡ እንደሆነ ፡ በጣም ፡ ይናደዳል

**cross** (vi.)
1. ተገናኘ. The two principal avenues cross over there. ሁለቱ ፡ አውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ የሚገና ኙት ፡ እዚያ ፡ ነው
2. መንገድ ፡ አቋረጠ. Remember to look both ways before crossing. መንገድ ፡ ከማቋረጥህ ፡ በፊት ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ መመልከትን ፡ አትዘንጋ
3. በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተላለፈ. My letter to her and hers to me crossed. እኔ ፡ የጻፍኩላትና ፡ እ ሷ ፡ የጻፈችልኝ ፡ ደብዳቤ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተላለፈ

**cross oneself** አማተበ
The priest crossed himself when he met with peril. ቄሱ ፡ አደጋ ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ አማተበ

**cross out** ሰረዘ
Cross out the items that you do not want. የማትፈልጋቸውን ፡ ነገሮች ፡ ሰርዛቸው
[See also 'mind']

**cross** (n.)
1. መስቀል. Do you see the church with the big cross on the steeple? ጉልላቱ ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ መስቀል ፡ ያለበት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይታይ ሃል ?

2. ዲቃላ. The mule is a cross between a horse and a donkey. በቅሎ ፡ የፈረስና ፡ የአህያ ፡ ዲቃላ ፡ ናት
3. የተዳቀለ. This fruit is a cross between an orange and a tangerine. ይህ ፡ ፍሬ ፡ ከመንደሪንና ፡ ከብርቱካን ፡ የተዳቀለ ፡ ነው

**bear one's cross** መከራን ፡ ተቀበለ
A patient person bears his cross without complaining. ታጋሹ ፡ ሰው ፡ መከራን ፡ ያለማማረር ፡ ይቀበላል

**make a cross on** በጣቱ ፡ ፈረመ
The illiterate person made a cross on the contract. መሃይሙ ፡ ውሉን ፡ በጣቱ ፡ ፈረመ

**make the sign of the cross** አማተበ
He made the sign of the cross before entering the church. ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ አማተበ

**(be) cross** ተበሳጨ
He is cross today because he had an argument with his wife. ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ስለተጨቃጨቀ ፡ ዛሬ ፡ ተበሳጭቷል

**cross-country** ያገር ፡ አቋራጭ
There will be a cross-country race next Sunday. በሚቀጥለው ፡ እሑድ ፡ ያገር ፡ አቋራጭ ፡ የሩጫ ፡ ውድድር ፡ ይደረጋል

**crosscut** አቋራጭ
He took a crosscut through the woods. በጫካው ፡ ውስጥ ፡ የሚያልፈውን ፡ አቋራጭ ፡ ተከተለ

**cross-examination** መስቀለኛ ፡ ጥያቄ
He conducted himself well during the cross-examination. በመስቀለኛው ፡ ጥያቄ ፡ ጊዜ ፡ መልካም ፡ ምግባር ፡ አሳየ

**cross-examine** መስቀለኛ ፡ ጥያቄ ፡ ጠየቀ
The lawyers cross-examined the accused. ጠበቃዎቹ ፡ ተከሳሹን ፡ መስቀለኛ ፡ ጥያቄ ፡ ጠየቁት

**cross-eyed** ሸውራራ
The child is so cross-eyed it is hard for him to see properly. ልጁ ፡ በጣም ፡ ሸውራራ ፡ ስለሆነ ፡ ለማየት ፡ ይቸገር ፡ ነበር

**crossfire, in the ~** በተታኰሱበት ፡ ጊዜ
An innocent man was killed in the crossfire. በተታኰሱበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ንጹሕ ፡ ሰው ፡ ሞተ

**crossing**
1. ማቋረጫ. There is no traffic light at this crossing. እዚህ ፡ ማቋረጫ ፡ ላይ ፡ የትራፊክ ፡ መብራት ፡ የለም
2. መተላለፊያ. Troops have been stationed at the border crossing. በወሰኑ ፡ መተላለፊያ ፡ ላይ ፡ ወታደሮች ፡ ተመድበው ፡ ነበር
*Did you have a good crossing? ደኅና ፡ ተሻገርክ ?

**crossroad** መስቀለኛ ፡ መንገድ ፤ የመንገዶች ፡ መገናኛ
You will find a sign on that crossroad. በዚ ፡ መስቀለኛ ፡ መንገድ ፡ (የመንገዶች ፡ መገናኛ) ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ ታገኛለህ

**cross section**
*The newspaper polled a cross section of the city voters. ጋዜጣው ፡ በከተማው ፡ ከሚገኙት ፡ መራጮች ፡ ከእያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ስለ ፡ ድምፅ ፡ መስጠት ፡ ጉዳይ ፡ ጠየቀ

**crosswalk** ማቋረጫ ፡ ስፍራ
Cars are to stop for pedestrians at a crosswalk. በማቋረጫ ፡ ስፍራ ፡ መኪናዎች ፡ ለእግረኞች ፡ መቆም ፡ አለባቸው

**crosswise, be placed ~** ተመሳቀለ
The sticks were placed crosswise and then tied together. ዕንጨቶቹ ፡ እየተመሳቀሉ ፡ ታሰሩ

**crouch**
1. አደፈጠ. The leopard crouched ready to attack. ነብሩ ፡ ሊያንቅ ፡ አድፍጧል
2. ቁጢጥ ፡ አለ. The child crouched at the foot of the wall. ልጁ ፡ ግድግዳው ፡ ሥር ፡ ቁጢጥ ፡ ብሏል

**crouch low** አደፈጠ
The raiders crouched low in the bushes. ቀማኞቹ ፡ ጥሻው ፡ ውስጥ ፡ አደፈጡ

**crow** (v.) ጮኸ
I woke up when the cock crowed. ዶሮ ፡ ሲጮኽ ፡ ነቃሁ

**crow** (n.) ቁራ
The crow caws every morning. ቁራ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ይጮኻል

**crowbar** የብረት ፡ መፈልቀቂያ
I had to pry open the box with a crowbar. ሣጥኑን ፡ በብረት ፡ መፈልቀቂያ ፡ ሰብሬ ፡ መክፈት ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ

**crowd** (vt.)
1. አጠበበ. Let's not crowd the room with furniture! ቤቱን ፡ በቤት ፡ እቃ ፡ አናጥበው

2. አመቀ. He crowded the toys into the box. አሻንጉሊቶቹን ፡ እሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አመቃቸው
3. ሞላ. People crowded the beaches. ሰዎች ፡ የባሕሩን ፡ ጠረፍ ፡ ሞሉት

**crowd** (vi.)
1. በብዛት ፡ ተሰበሰበ. People crowded to see the show. ትርኢይቱን ፡ ለመመልከት ፡ ሰዎች ፡ በብዛት ፡ ተሰበሰቡ
2. ታጐረ. We all crowded into the bus. ሁላችንም ፡ አውቶቡሱ ፡ ውስጥ ፡ ታጐርን

**crowd around** ከበበ ፤ በብዛት ፡ ከበበ
The pupils crowded around the teacher to ask questions. ተማሪዎቹ ፡ ጥያቄ ፡ ለመጠየቅ ፡ አስተማሪውን ፡ ከበቡት ፡ (በብዛት ፡ ከበቡት)

**crowd** (n.)
1. የተሰበሰበ ፡ ሕዝብ. Have you seen the crowd in front of the theater? ከቲያትሩ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የተሰበሰበውን ፡ ሕዝብ ፡ አይተሃል ?
2. ሕዝብ. There was a large crowd at the market. እገበያው ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ነበር
3. የሕዝብ ፡ ጭንቅንቅ. We were nearly crushed in the crowd. በሕዝቡ ፡ ጭንቅንቅ ፡ ልንሰባበር ፡ ነበር
4. ተራ ፡ ሕዝብ. Many newspapers appeal to the crowd. ብዙ ፡ ጋዜጦች ፡ ተራውን ፡ ሕዝብ ፡ የሚመለከት ፡ ነገር ፡ ይጽፋሉ
5. መሰሎች. He and his crowd went to the dance. እርሱና ፡ መሰሎቹ ፡ ወደ ፡ ዳንሱ ፡ ሄዱ

**crowded** (adj.)
1. ጥቅጥቅ ፡ ያለ. It is difficult to drive along crowded streets. ጥቅጥቅ ፡ ባለ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ መንዳት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. ሕዝብ ፡ የበዛበት. It is hard to carry on a conversation in a crowded room. ሕዝብ ፡ በበዛበት ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ መጨዋወት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**be crowded**
1. ተጣበበ. All compartments in this car are crowded. እዚህ ፡ ፉርጎ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ክፍሎች ፡ ሁሉ ፡ ተጣበዋል
2. ተጨናነቀ. The polling booths were crowded with people. የድምፅ ፡ መስጫዎቹ ፡ ጣቢያዎች ፡ በሕዝብ ፡ ተጨናንቀው ፡ ነበር
[See also 'capacity']

**crown** (v.)
1. ዘውድ ፡ ጫነ(ለት). The patriarch crowned him king. ፓትሪያርኩ ፡ ዘውድ ፡ ጫኑለት
2. (= intr.) ጉብ ፡ አለ. A fort crowns the hill. ምሽጉ ፡ ኮረብታው ፡ ላይ ፡ ጉብ ፡ ብሏል
3. ከፍ ፡ አደረገ(ለት). The Nobel Prize crowned his career as an author. የኖቤልን ፡ ሽልማት ፡ መቀበሉ ፡ የደራሲነት ፡ ሙያውን ፡ ከፍ ፡ አደረገለት
*Success crowned his efforts. ጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ተሳካለት

**be crowned** ዘውድ ፡ ጫነ
The sovereigns of Ethiopia used to be crowned in Axum. ድሮ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውድ ፡ የሚጭኑት ፡ አክሱም ፡ ነበር

**be crowned with success** የተሳካ ፡ ውጤት ፡ አገኘ
His efforts were crowned with success. ድካሙ ፡ ሁሉ ፡ የተሳካ ፡ ውጤት ፡ አገኘ

**crown** (n.) ዘውድ
This crown is made of silver. ይህ ፡ ዘውድ ፡ የተሠራው ፡ ከብር ፡ ነው

**crown of the head** አናት
He struck him on the crown of the head. አናቱ ፡ ላይ ፡ መታው
[See also 'succeed']

**Crown Prince** አልጋ ፡ ወራሽ
The Crown Prince will succeed his father on the throne. አልጋ ፡ ወራሹ ፡ ያባቱን ፡ ዙፋን ፡ ይወርሳል

**crucial** ቁርጥ ፡ የሚለይበት
This was a crucial battle. ይህ ፡ ቁርጥ ፡ የሚለይበት ፡ ውጊያ ፡ ነበር

**crucial moment** አፍላ
He broke into the conversation at a crucial moment. በጭውውቱ ፡ አፍላ ፡ ላይ ፡ ጥልቅ ፡ አለ

**crucible** [የወርቅና ፡ የብር ፡ ማቅለጫ ፡ ጉድጓዳ ፡ ሸክላ]

**crucifix** ስቅለትን ፡ የሚያሳይ ፡ ቅርጽ
There was a crucifix on the church wall. እቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ ስቅለትን ፡ የሚያሳይ ፡ ቅርጽ ፡ ነበር

**Crucifixion** ስቅለት
A picture of the Crucifixion was given to our church. የስቅለቱ ፡ ሥዕል ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ተሰጠ

**crucify** (crucified)
1. ሰቀለ. His enemies crucified Jesus on Golgotha. ጠላቶቹ ፡ ኢየሱስን ፡ ጎልጎታ ፡ ላይ ፡ ሰቀሉት
2. አሠቃየ. The mob crucified him for failing to solve the country's problems. ያገሪቱን ፡ ችግር ፡ ለማስወገድ ፡ ስላልቻለ ፡ ሕዝቡ ፡ አሠቃየው

**crude**

1. ባለጌ. He is a rather crude person. ባለጌ ፡ መሳይ ፡ ሰው ፡ ነው

2. ያልተጣራ. Ethiopia has to import crude oil from abroad. ኢትዮጵያ ፡ ያልተጣራ ፡ ዘይት ፡ ከውጭ ፡ ማስመጣት ፡ አለባት

3.ያልተሻሻለ. An eye for an eye is a crude principle of justice. « ዓይን ፡ ያጠፋ ፡ ዓይኑ ፡ ይጠፋል » ፡ የሚለው ፡ ያልተሻሻለ ፡ የፍትሕ ፡ ሥርዓት ፡ ነው

4. ረቂቅነት ፡ የጐደለው. The ancient inhabitants made crude paintings on the walls of the caves. የቀድሞ ፡ ሰዎች ፡ ረቂቅነት ፡ የጐደላቸው ፡ ሥዕሎች ፡ በዋሻዎች ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ ሣሉ

**cruel**

1. ጨካኝ. How can you be so cruel? እንዴት ፡ እንደዚህ ፡ ጨካኝ ፡ ትሆናለህ ?

2. የጭካኔ. To hit a baby is a cruel act. ሕፃን ፡ መምታት ፡ የጭካኔ ፡ ድርጊት ፡ ነው

3. አሰቃቂ. The cruel war left thousands dead. አሰቃቂው ፡ ጦርነት ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ፈጀ

**cruelty** (cruelties)

1. ጭካኔ. Cruelty was customary in the prison camps. በእስረኞች ፡ ሰፈር ፡ ውስጥ ፡ ጭካኔ ፡ የተለመደ ፡ ነበር

2. የጭካኔ ፡ ተግባር ፡ መፈጸም. Cruelty to children is now forbidden by law. በሕፃናት ፡ ላይ ፡ የጭካኔ ፡ ተግባር ፡ መፈጸም ፡ ዛሬ ፡ በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ ነው

3. መጨከን. Cruelty to animals in a perverse act. በእንስሳት ፡ መጨከን ፡ ኀጢአት ፡ ነው

**cruise** (v.) ተዘዋወረ

The police car cruised through the park. የፖሊስ ፡ መኪና ፡ መናፈሻው ፡ ውስጥ ፡ ተዘዋወረ

**cruise** (n.) የመርከብ ፡ ሽርሽር

I still think about the cruise we made last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ያደረግነው ፡ የመርከብ ፡ ሽርሽር ፡ እስካሁን ፡ ትዝ ፡ ይለኛል

**go for a cruise** በጀልባ ፡ ተንሸራሸረ

We went for a cruise on the lake last summer. ባለፈው ፡ በጋ ፡ በሐይቁ ፡ ላይ ፡ በጀልባ ፡ ተንሸራሸርን

**crumb** ፍርፋሪ

Sweep up the crumbs! ፍርፋሪውን ፡ ጥረግ
[See also 'bread']

**crumble** (vt.) ፈረፈረ

He crumbled his bread, and put it in his soup. ዳቦውን ፡ ፈርፍሮ ፡ በሾርባው ፡ ውስጥ ፡ ጨመረው

**crumble** (vi.) ተናደ

The wall crumbled after the heavy rain. ግድግዳው ፡ በኀይለኛው ፡ ዝናብ ፡ ተናደ

*The general's hopes crumbled as his soldiers retreated. ወታደሮቹ ፡ ወደኋላ ፡ ቢያፈገፍጉ ፡ ጄኔራሉ ፡ ተስፋውን ፡ ቈረጠ

**crumple** ጨባበጠ

He crumpled the paper, and tossed it away. ወረቀቱን ፡ ጨባብጦ ፡ ወረወረው

**crunch** (vt.) ቈረጣጠመ

The dog was crunching the bones. ውሻው ፡ አጥንት ፡ ይቈረጣጥም ፡ ነበር

**crunch** (vi.)

1. ተንኮሻኮሸ. The dry grass and leaves crunched under our feet. ደረቅ ፡ ሣርና ፡ ቅጠል ፡ ስንረግጠው ፡ ተንኮሻኮሸ

2. ከሽ ፡ ከሽ ፡ አለ. The broken glass crunched under our feet. የመስታወቱ ፡ ስባሪ ፡ ስንረግጠው ፡ ከሽ ፡ ከሽ ፡ አለ
[See also 'bread']

**crusade** (v.) ታገለ

He crusaded for better housing. ለተሻለ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ታገለ

**Crusade** (n.) የመስቀል ፡ ጦርነት

There were several Crusades in the Middle Ages. በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ የመስቀል ፡ ጦርነቶች ፡ ነበሩ

**crusade** ተጋድሎ

Everyone was asked to join the crusade against cancer. ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ካንሰርን ፡ ለማጥፋት ፡ ተጋድሎ ፡ እንዲያደርግ ፡ ተጠይቆ ፡ ነበር

**crush** (v.)

1. አጨማደደ. You are crushing my hat. ባርኔጣዬን ፡ አጨማደድኸው

2. ጨፈለቀ. They crushed the castor beans to obtain castor oil. የጉሎ ፡ ዘይት ፡ ለማውጣት ፡ የጉሎ ፡ ፍሬዎችን ፡ ጨፈለቁ

3. ተጫነ. Don't crush this box! It has flowers in it. ይህን ፡ ሣጥን ፡ እንዳትጫነው ፤ ውስጡ ፡ አበባ ፡ አለበት

4. ፈጨ. This machine crushes rocks. ይህ ፡ መኪና ፡ ድንጋይ ፡ ይፈጫል

5. ደቈሰ. The maid is crushing salt. ገረዲቱ ፡ ጨው ፡ ትደቍሳለች

6. ደመሰሰ. The ruler crushed the rebellion. ገዢው ፡ ዐመፁን ፡ ደመሰሰ

**crush one's spirit** ቅስሙን ፡ ሰበረው

Losing the job crushed his spirit. ከሥራ ፡ መውጣቱ ፡ ቅስሙን ፡ ሰበረው

**be crushed**
1. ተሰባበረ. We were nearly crushed in the crowd. በሕዝብ ፡ ጭንቅንቅ ፡ ልንሰባበር ፡ ነበር
2. ተፈረካከሰ. The flimsy boat was crushed like an eggshell. ደቃቃዋ ፡ ጀልባ ፡ እንደ ፡ እንቁላል ፡ ቅርፊት ፡ ተፈረካከሰች
3. (= act.) ቅስሙን ፡ ሰበረው +He was crushed by the news. ወሬው ፡ ቅስሙን ፡ ሰበረው
[See also 'powder']

**crush** (n.) ግፊያ
There was a frightful crush at the gate. በበሩ ፡ ላይ ፡ ኀይለኛ ፡ ግፊያ ፡ ነበር

**crushing**
*Menelik won a crushing victory against the Italians at Aduwa. ምኒልክ ፡ ጣልያንን ፡ አድዋ ፡ ላይ ፡ እንደማያንሰራራ ፡ አድርገው ፡ አሸነፉት
*The enemy suffered a crushing defeat. ጠላት ፡ እንደማያንሰራራ ፡ ሆኖ ፡ ተሸነፈ

**crust** ቅርፊት
I cannot eat the crust of the bread. የዳቦውን ፡ ቅርፊት ፡ ልበላ ፡ አልችልም
When the metal cools a crust forms at the top. የጋለ ፡ ብረት ፡ ሲቀዘቅዝ ፡ ቅርፊት ፡ ያበጃል

**crutch** ምርኩዝ
He has to walk on crutches. በምርኩዝ ፡ መሄድ ፡ አለበት

**crux** ዋና ፡ ነገር ፤ ፍሬ ፡ ነገር
The crux of the matter is this. የጉዳዩ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው
The crux of the matter is that we can't afford a new car. ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ አዲስ ፡ መኪና ፡ ለመግዛት ፡ አለመቻላችን ፡ ነው

**cry** (cried)
1. አለቀሰ. She cried when she heard the news. ወሬውን ፡ ስትሰማ ፡ አለቀሰች
The baby cried all night. ልጁ ፡ ሲያለቅስ ፡ አደረ
2. ጮኸ. "Help, help," she cried. ኡ ! ኡ ! ብላ ፡ ጮኸች
*Peddlers cry their wares in the street to sell them. እቃ ፡ አዟሪዎች ፡ የሚሸጧቸውን ፡ የእቃዎችን ፡ ስም ፡ እየጠሩ ፡ ይዞራሉ

**cry for** ለመነ
The starving people cried to their chief for bread. ረኀብተኞቹ ፡ አለቃቸውን ፡ ምግብ ፡ ለመኑት

**cry (one's) head off**
The child cried his head off. ልጁ ፡ እሪ ፡ ብሎ ፡ አለቀሰ

**cry out**
1. ጮኸ. He cried out in pain. በሥቃይ ፡ ጮኸ
2. ተጣራ. She saw her father and cried out, "Papa"! አባቷን ፡ አይታ ፡ አባባ ፡ ብላ ፡ ተጣራች
[See also 'heart, shoulder']

**cry** (n.) ጩኸት
Then we heard a loud cry. ቀጥሎም ፡ ትልቅ ፡ ጩኸት ፡ ሰማን
*Have a good cry! አልቅስና ፡ ይውጣልህ
*This is a far cry from what we expected. ይህ ፡ እኛ ፡ ከፈለግነው ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ ጉዳይ ፡ ነው

**cry for help** ኡኡታ
He heard a cry for help in the distance. ከሩቅ ፡ ቦታ ፡ ኡኡታ ፡ ሰማ
[See also 'battle, head']

**crying** (n.) ለቅሶ
Stop your crying! ለቅሶህን ፡ አቁም

**crystal** [ከፍተኛ ፡ ጥራት ፡ ያለው ፡ መስተዋት ፡ የሚመስል ፡ ድንጋይ]

**crystallize** አጠናቀቀ
He crystallized his plans. ፕላኑን ፡ አጠናቀቀ

**cub** ግልገል
The hunter found five lion cubs. አዳኙ ፡ አምስት ፡ ያንበሳ ፡ ግልገል ፡ አገኘ

**cube**
1. [ስድስት ፡ ጐን ፡ ያለው ፡ ቅርጽ]
2. እንኳር. Give me a cube of sugar! አንድ ፡ እንኳር ፡ ስኳር ፡ ስጠኝ
3. ቁራጭ. He made a pair of dice out of two cubes of wood. ከሁለት ፡ የዕንጨት ፡ ቁራጮች ፡ ሁለት ፡ ዳይስ ፡ ሠራ

**cubic** ኩብ
The tank contains a hundred cubic meters of water. በርሜሉ ፡ መቶ ፡ ሜትር ፡ ኩብ ፡ ውኃ ፡ ይይዛል

**cubicle** ትንሽ ፡ ክፍል
He went into a telephone cubicle. ወደ ፡ ትንሽ ፡ የስልክ ፡ ክፍል ፡ ገባ

**cubit** ክንድ
A cubit is half a meter. አንድ ፡ ክንድ ፡ የሜትር ፡ ግማሽ ፡ ነው

**cucumber** የፈረንጅ ፡ ዱባ

**cud** ምንዣጊ
The cow's cud consisted of grass. የላሚቱ ፡ ምንዣጊ ፡ ሣር ፡ ነበር
[See also 'chew']

**cuddle**
1. እንከባከበ ፡ አቀፈ. The mother cuddled the sick child. እናቲቱ ፡ የታመመውን ፡ ልጅ ፡ እንከባ ክባ ፡ አቀፈችው
2. እቅፍ ፡ አደረገ. She cuddled her baby in her arms. ልጇን ፡ በክንዷ ፡ እቅፍ ፡ አደረገችው
**cuddle up** ኩርምት ፡ ብሎ ፡ ተኛ
The children cuddled up under the blankets. ልጆቹ ፡ በብርድ ፡ ልብሱ ፡ ውስጥ ፡ ኩርምት ፡ ብ ለው ፡ ተኙ

**cudgel** ቆመጥ
His cudgel cracked when he struck the man with it. ሰውየውን ፡ ሲመታበት ፡ ቆመጡ ፡ ተሰነጠቀ

**cue** ምልክት
I will give you the cue when to start. መቼ ፡ እን ደምትጀምር ፡ ምልክት ፡ እሰጥሃለሁ

**cuff** (v.) አጮለ
The father cuffed his son for his impudence. ልጁ ፡ ስለባለገ ፡ አባትየው ፡ አጮለው

**cuff** (n.) የእጅጌ ፡ ክፈፍ
His shirt was torn at the cuffs. የሸሚዙ ፡ እጅጌ ፡ ክፈፍ ፡ ተቀደደ

**cufflink** የእጅጌ ፡ ቁልፍ
I lost one of my cufflinks. አንደኛው ፡ የእጅጌ ዬ ፡ ቁልፍ ፡ ጠፋብኝ

**cull** መርጦ ፡ አወጣ
The lawyer culled important facts from the mass of evidence. ጠበቃው ፡ ካገኘው ፡ ብዙ ፡ መረጃ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ መርጦ ፡ አወጣ

**culminate** ተደመደመ
The tower culminated in a cupola. ግምቡ ፡ በ ቁብታ ፡ ተደምድሟል
*His career culminated in the presidency. የሥራው ፡ ደረጃ ፡ መጨረሻ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ መ ሆን ፡ ነበር

**culprit** ወንጀለኛ
I am on the culprit's trail. የወንጀለኛውን ፡ ፋ ና ፡ ደርሼበታለሁ

**cult** አምልኮ
The cult of Apollo was widespread. የአፖሎ ፡ አምልኮ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ነበር

**cultivate**
1. አለማ. The farmers cultivate fruit trees. ገበሬዎቹ ፡ የፍሬ ፡ አትክልት ፡ ያለማሉ
2. ኰተኰተ. She cultivated roses in her garden. ጽጌረዳ ፡ ባትክልት ፡ ቦታዋ ፡ ኰተኰተች
3. አዳበረ. He cultivates his mind by reading. አእምሮውን ፡ በማንበብ ፡ ያዳብራል
4. ለመወዳጀት ፡ ጣረ. He cultivated the important people so that he could get a better job. የተሻለ ፡ ሥራ ፡ እንዲያገኝ ፡ ከታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ለመወዳጀት ፡ ጣረ
5. አጐለመሰ. The public speaker cultivates the art of pleasing his audience. ተናጋሪው ፡ ያድ ማጮቹን ፡ ማስደሰቻ ፡ ጥበብ ፡ ያጐለምሳል

**cultivated** (adj.) የታረሰ
Cultivated land is scarce in the desert. የታረሰ ፡ መሬት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ ብርቅ ፡ ነው

**cultivation** ማረስ
Better cultivation of soil will result in better crops. መሬትን ፡ በተሻለ ፡ ሁኔታ ፡ ማረስ ፡ የተ ሻለ ፡ እህል ፡ ያስገኛል

**cultivator** አራሽ
The cultivator must protect the soil from erosion. አራሹ ፡ አፈሩን ፡ ከመሬት ፡ መሸርሸር ፡ መከላከል ፡ አለበት

**cultural** የባህል
There is a cultural similarity between Japan and China. በጃፓንና ፡ በቻይና ፡ መካከል ፡ የባ ህል ፡ መመሳሰል ፡ አለ

**culture**
1. ባህል. Universities should be the centers of culture. ዩኒቨርሲቲዎች ፡ የባህል ፡ እምብር ቶች ፡ መሆን ፡ አለባቸው
2. (Physical) መዳበር; (of mind) መጐልመስ. Physical culture is important, but we must not forget the culture of the mind. የሰውነት ፡ መዳበር ፡ ጠቃሚ ፡ ቢሆንም ፡ የአእምሮን ፡ መ ጐልመስም ፡ አስፈላጊነት ፡ መርሳት ፡ አይገባንም
3. መትከል. The culture of cotton was only recently introduced to Ethiopia. ጥጥ ፡ መትከ ል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የተጀመረው ፡ በቅር ብ ፡ ጊዜ ፡ ነው

**cultured** ጨዋ
She is a cultured woman. ጨዋ ፡ ሴት ፡ ናት

**(be) cumbersome** አይመችም ፤ ለመያዝ ፡ አ ይመችም
It is cumbersome to carry this package. ይህ ፡ ጥቅል ፡ ለመያዝ ፡ አይመችም
Old-fashioned weapons were cumbersome. የድሮ ፡ ጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ለመያዝ ፡ የማይመ ቹ ፡ ነበሩ

**cumin** ከሙን
Cumin serves to flavor sauce. ከሙን ፡ ወጥ ፡ ለማጣፈጥ ፡ ይጠቅማል

**cumulative** በየጊዜው ፡ የተጠራቀመ
Only cumulative effort can solve the land problem. ለመሬት ፡ ይዞታ ፡ ችግር ፡ መፍትሔ ፡ የሚገኘው ፡ በየጊዜው ፡ በተጠራቀመ ፡ ጥረት ፡ ብቻ ፡ ነው

**be cumulative** እየጠነከረ ፡ ሄደ
The evidence against him has been cumulative. በርሱ ፡ ላይ ፡ የሚቀርበው ፡ መረጃ ፡ እየጠነከረ ፡ ሄደ

**cunning**
1. ብልጥ. He is too cunning for anyone to be able to deceive him. ብልጥ ፡ ስለሆነ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊያታልለው ፡ አይችልም
2. የሚያስደስት. Kittens and babies are cunning. ድመቶችና ፡ ሕፃናት ፡ የሚያስደስቱ ፡ ናቸው
*He is a cunning old fox. ጭራው ፡ የማይያዝ ፡ ሙሌ ፡ ነው

**cup** (cupped), v.
1. አገመ. In rural Ethiopia, they cup people to cure headaches. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በየ ባላገሩ ፡ ራስ ፡ ምታትን ፡ ለማዳን ፡ ያግማሉ
2. አጐድጕዶ ፡ ጠበቀ. She cupped her hands to catch the ball. ኳሱን ፡ ለመያዝ ፡ እጆቿን ፡ አጐድጕዳ ፡ ጠበቀች

**cup** (n.)
1. ሲኒ. She served coffee in a cup. ቡናውን ፡ በሲኒ ፡ አቀረበች
2. ዋንጫ. The Ethiopian team won the Africa Cup. የኢትዮጵያ ፡ ቡድን ፡ የአፍሪካን ፡ ዋንጫ ፡ አገኘ

**horn cup** ዋንጫ
In former days, Ethiopians preferred to drink mead from a horn cup. በድሮ ፡ ጊዜ ፡ ኢት ዮጵያውያን ፡ ጠጅ ፡ በዋንጫ ፡ መጠጣት ፡ ይወ ዱ ፡ ነበር

**cupboard** ቁም ፡ ሣጥን
We put our dishes in the cupboard. ሳሕኖቻች ንን ፡ ቁም ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ እናስቀምጣለን

**cupidity** ሥሥት
His cupidity made it possible for the swindlers to cheat him. ሥሥቱ ፡ ለአታላዮች ፡ መንገድ ፡ ሰጣቸው

**cupola** ቁብታ
The cupola on the capitol is sheeted with copper. የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ቁብታ ፡ በመዳብ ፡ ተለብጧል

**cupping glass** ዋገምት
A cupping glass is used to draw blood. ዋገም ት ፡ ደም ፡ ለመምጠጫ ፡ ያገለግላል

**(be) curable** ማዳን ፡ ተቻለ
Pneumonia is easily curable today. የሳንባን ፡ በ ሽታ ፡ ዛሬ ፡ በቀላሉ ፡ ማዳን ፡ ይቻላል

**curator** ኀላፊ
The curator of the museum knows much about pictures. የቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ኀላፊ ፡ ስለ ፡ ሥዕሎች ፡ ብዙ ፡ ያውቃል

**curb** (v.) ገታ
You will have to learn to curb your temper. ንዴትህን ፡ መግታት ፡ መልመድ ፡ አለብህ

**curb** (n.) የመንገድ ፡ ጠርዝ
The curb was so high that the child could not step up. የመንገዱ ፡ ጠርዝ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለ ሆነ ፡ ልጁ ፡ መውጣት ፡ አቃተው

**at the curb** መንገዱ ፡ ጥግ
He stood at the curb while waiting for the bus. መንገዱ ፡ ጥግ ፡ ቆሞ ፡ አውቶቡስ ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር

**put a curb on** ገታ
You have to put a curb on extravagant spending. ገንዘብ ፡ ማባከንህን ፡ መግታት ፡ አለ ብህ

**curd** እርጎ
Curd is used in making cheese. እርጎ ፡ አይብ ፡ ለማውጣት ፡ ይጠቅማል

**curdle** ረጋ
The milk curdled in the sun. ወተቱ ፡ ፀሐይ ፡ ው ስጥ ፡ ረጋ

**cure** (v.)
1. አዳነ. This medicine will cure your cough. ይህ ፡ መድኃኒት ፡ ሳልህን ፡ ያድንልሃል
2. ፈወሰ. The holy water cured him. ጠበሉ ፡ ከ በሽታው ፡ ፈወሰው
3. አጠፋ. The government tried to cure unrest at home by making war abroad. መንግሥቱ ፡ ከ ገር ፡ ውጭ ፡ ጦርነት ፡ በማድረግ ፡ ባገር ፡ ውስ ጥ ፡ ያለውን ፡ ሁከት ፡ ለማጥፋት ፡ ሞከረ
4. ተወ. He finally cured his fear of the dark. በመጨረሻ ፡ ጭለማ ፡ መፍራቱን ፡ ተወ

**cure of** እንድ + negative imperfect + ገፋፋ
Low grades cured me of neglecting my homework. የትምህርቴ ፡ ውጤት ፡ ዝቅተኛ ፡ መሆን ፡ የቤት ፡ ሥራዬን ፡ ችላ ፡ እንዳልል ፡ ገፋፋኝ

**be cured** ዳነ
He is completely cured. ፈጽሞ ፡ ድኗል

**cure** (n.)
1. መድኀኒት. There is no cure for cancer.
ካንሰር ፡ መድኀኒት ፡ የለውም
2. የሚፈውስ. This treatment is a painless cure
for tuberculosis. ይህ ፡ ሕክምና ፡ ከሳንባ ፡ ነቀ
ርሳ ፡ ያለ ፡ ምንም ፡ ሥቃይ ፡ የሚፈውስ ፡ ነው
3. መዳን. His cure took six weeks. ለመዳን ፡
ስድስት ፡ ሳምንት ፡ ፈጀበት
4. መፍትሔ. The cure for ignorance lies in
education. የድንቁርና ፡ መፍትሔ ፡ ትምህርት ፡
ነው

**curfew** የሰዓት ፡ እላፊ
The commanding officer set an eight o'clock
curfew. አዛገዡ ፡ መኰንን ፡ ከሁለት ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ
ሮ ፡ የሰዓት ፡ እላፊ ፡ ወሰነ

**curiosity** (curiosities)
1. ጉጉት. He yielded to curiosity and opened
the letter addressed to his father. ጉጉት ፡ ገፋ
ፍቶት ፡ ላባቱ ፡ የተጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ ከፈተው
2. የማወቅ ፡ ፍላጎት. She was consumed with
curiosity. በማወቅ ፡ ፍላጎት ፡ ተውጣለች
3. ብርቅ. A fire engine pulled by horses is
now a curiosity. በዛሬ ፡ ጊዜ ፡ በፈረስ ፡ የሚጐ
ተት ፡ የእሳት ፡ አደጋ ፡ መከላከያ ፡ ሰረገላ ፡ ብርቅ ፡
ነው
*She is bursting with curiosity. ጓጉታ ፡ (በማወ
ቅ ፡ ጉጉት) ፡ ልትሞት ፡ ነው

**curious**
1. ጉጉ. Don't be so curious! እንዲህ ፡ ጉጉ ፡ አ
ትሁን
2. ልዩ. What a curious looking car this is!
ይህ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ መኪና ፡ ነው
3. ልዩ ፡ ዓይነት ፡ የሆነ. He has a collection
of curious old coins. ልዩ ፡ ዓይነት ፡ የሆነ ፡ የድ
ሮ ፡ ገንዘቦች ፡ ስብስብ ፡ አለው

**be curious**
1. ጓጓ. I am curious to know what the answer
will be. መልሱ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ጓጉ
ቻለሁ
2. ለማወቅ ፡ ጓጓ. Small children are curious and
they ask many questions. ትንንሽ ፡ ልጆች ፡ ለ
ማወቅ ፡ ስለሚጓጉ ፡ ብዙ ፡ ጥያቄዎች ፡ ይጠ
ይቃሉ

**curl** (vt.) ጠቀለለ
She curls her hair every morning. ሁልጊዜ ፡ ጧ
ት ፡ ጸጉሯን ፡ ትጠቀልላለች

**curl** (vi.)
1. ተጥመለመለ. Her hair curls naturally. ጸጉሯ ፡
በተፈጥሮው ፡ ይጥመለመላል
2. ተሸባለለ. The parchment curled in the
intense heat. ከኀይለኛው ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ብ
ራናው ፡ ተሸባለለ

**curl up** ጥምልምል ፡ አለ
The dog curled up and went to sleep. ውሻው ፡
ጥምልምል ፡ ብሎ ፡ ተኛ

**curl** (n.) ጥቅል ፡ ጸጉር
The girl's curls hung down to her shoulders.
የልጃገረዲቱ ፡ ጥቅል ፡ ጸጉር ፡ ትከሻዋ ፡ ላይ ፡ ተ
ኝቷል

**curly** ከርዳዳ
Curly hair is an ancestral trait in that family.
በዚህ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡ ከርዳዳ ፡ ጸጉር ፡ የዘር ፡
ነው

**currency** (currencies) ገንዘብ
A stable currency is absolutely necessary.
ዋጋው ፡ የማይለዋወጥ ፡ ገንዘብ ፡ ፍጹም ፡ አስ
ፈላጊ ፡ ነው
*Belief in witchcraft has wide currency in
certain countries. ጥንቆላ ፡ ባንዳንድ ፡ አገሮች ፡
በሰፊው ፡ ይታመንበታል

**current** (n.)
1. ፈረሰኛ ፡ ውኃ ፤ ገስጋሽ ፡ ውኃ. The current
carried away two people. ፈረሰኛው ፡ ውኃ ፡ (ገስ
ጋሹ ፡ ውኃ) ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ወሰደ
2. አዝማሚያ. Newspapers influence the current
of public opinion. ጋዜጦች ፡ በሕዝብ ፡ አስተያየ
ት ፡ አዝማሚያ ፡ ላይ ፡ ተጽዕኖ ፡ አላቸው
*He swam against the current. አሸቅቦ ፡ ዋኘ

**current of air** አየር
A cold current of air came into the room
through the open window. በተከፈተው ፡ መስኮ
ት ፡ ቀዝቃዛ ፡ አየር ፡ ገባ
[See also 'electric']

**current** (adj.)
1. ያሁኑ. The bill for the current month was
small. ያሁኑ ፡ ወር ፡ ሒሳብ ፡ አነስተኛ ፡ ነበር
I read that in the current issue of "Life". ያንን ፡
ያነበብኩት ፡ ባሁኑ ፡ የላይፍ ፡ መጽሔት ፡ እት
ም ፡ ላይ ፡ ነው
2. በጊዜ ፡ ያለ. Read the newspapers to keep
track of current events! በጊዜው ፡ ያለውን ፡ ሁኔ
ታ ፡ ለመከታተል ፡ ጋዜጣ ፡ አንብብ

**be current** ተነዛ
A rumor of an invasion was widely current.
የወረራ ፡ ወሬ ፡ በሰፊው ፡ ተነዝቶ ፡ ነበር

**no longer be current** ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አይሠራበትም
The use of Maria Theresa dollars is no longer current in Ethiopia. የማርትሬዛ ፡ ብር ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አይሠራበትም

**currently**
1. ባሁኑ ፡ ጊዜ. He is currently working on the project. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እቅዱን ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ነው
2. ሰሞኑን. There is a good film currently being shown at the nearby theater. በአቅራቢያው ፡ ባለው ፡ ቲያትር ፡ ቤት ፡ ሰሞኑን ፡ በመታየት ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ጥሩ ፡ ፊልም ፡ አለ

**curriculum** ሥርዓተ ፡ ትምህርት
Music and French are included in our curriculum. ሥርዓተ ፡ ትምህርታችን ፡ ውስጥ ፡ ሙዚቃና ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ይገኙበታል

**curry** [ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅመማት ፡ የተዘጋጀ ፡ ሩዝን ፡ ለማጣፈጥ ፡ የሚያገለግል ፡ ቅመም]

**curse** (vt.)
1. ረገመ. He cursed us in God's and Mary's names. የእግዚአብሔርንና ፡ የማርያምን ፡ ስም ፡ ጠርቶ ፡ ረገመን
2. ቁጣውን ፡ አወረደ(በት). God cursed the builders of the tower of Babel. የባቢሎንን ፡ ግንብ ፡ የገነቡትን ፡ እግዜር ፡ ቁጣውን ፡ አወረደባቸው

**curse** (vi.) ተሳደበ
The teacher told the boy not to curse. መምህሩ ፡ ልጁ ፡ እንዳይሳደብ ፡ ነገረው

**be cursed** መቅሠፍት ፡ ወረደበት
This country was cursed for centuries with floods. ይህች ፡ አገር ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ የውኃ ፡ መጥለቅለቅ ፡ መቅሠፍት ፡ ወርዶባት ፡ ነበር

**curse** (n.)
1. እርግማን. His curse did not frighten me. እርግማኑ ፡ አላስደነገጠኝም
2. መቅሠፍት. Locusts are a curse in this part of Ethiopia. አንበጣ ፡ ለዚህኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍል ፡ መቅሠፍት ፡ ነው
*He muttered a curse under his breath. በሆዱ ፡ ተራገመ

**cursive** የተቀጣጠለ
The Ethiopian alphabet has no cursive handwriting. የኢትዮጵያ ፡ ፊደል ፡ የተቀጣጠለ ፡ አጻጻፍ ፡ የለውም

**cursory** (= adv.) በችኮላ
Even a cursory reading of the letter showed many errors. ደብዳቤውን ፡ በችኮላ ፡ በማንበብ ፡ እንኳን ፡ ብዙ ፡ ስሕተት ፡ ተገኘ

**curt** ድርቅ ፡ ያለ
He gave him a curt answer. ድርቅ ፡ ያለ ፡ መልስ ፡ ሰጠው

**curtail**
1. ቈረጠ(በት). The government curtailed the student's stipend because he wasn't studying enough. ተማሪው ፡ የሚገባውን ፡ ያህል ፡ ስላላጠና ፡ መንግሥቱ ፡ ቀለቡን ፡ ቈረጠበት
2. ቀነሰ. The ministry curtailed the supply of free books to the students. ሚኒስቴሩ ፡ ለተማሪዎች ፡ በነጻ ፡ መጽሐፍ ፡ መስጠቱን ፡ ቀነሰ

**curtain** መጋረጃ
I want curtains for the windows. ለመስኮቶቹ ፡ መጋረጃ ፡ እፈልጋለሁ

**curtain off** ጋረደ
He took two sheets and curtained off a space in the corner. ሁለት ፡ አንሶላዎች ፡ ወስዶና ፡ ጥጉን ፡ ጋረደ

**curtsy** እጅ ፡ ነሣ
Women will curtsy when they meet the Emperor. ሴቶች ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ እጅ ፡ ይነሣሉ

**curve** (v.) ታጠፈ
The road curves to the right. መንገዱ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ይታጠፋል

**curve around** ዞረ
The road curves around the town. መንገዱ ፡ ከተማውን ፡ ይዞረዋል

**be curved** ጐበጠ
His back is curved like a bow. ጀርባው ፡ እንደ ፡ ደጋን ፡ ጐብጧል

**curve** (n.) መጠምዘዣ
Watch out for the curves in the road! በጐዳናው ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ መጠምዘዣዎች ፡ ጠንቀቅ ፡ በሉባቸው

**cushion** ትራስ
We need some cushions for the sofa. ለሶፋው ፡ ትራስ ፡ ያስፈልገናል

**custodian** ጠባቂ
The custodian of the museum showed us around. የቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ጠባቂ ፡ አስጐበኘን

**custody** የማሳደግ ፡ ኀላፊነት
The custody of the child is given to the father

in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የልጅ ፡ ማሳደግን ፡ ኀላፊነት ፡ የሚወስድ ፡ አባት ፡ ነው

**be held in custody** በ - - - እጅ ፡ ተገኘ
The car is held in the custody of the police. መኪናዋ ፡ በፖሊስ ፡ እጅ ፡ ትገኛለች

**take into custody** ማረፊያ ፡ ቤት ፡ አቆየ
The police took a suspect into custody. ፖሊሱ ፡ ተጠርጣሪውን ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ አቆየው

**(be) taken into custody** በ - - - ጥበቃ ፡ ሥር ፡ እንዲሆን ፡ ተደረገ
The traitor was taken into custody by the police. ከሐዲው ፡ በፖሊስ ፡ ጥበቃ ፡ ሥር ፡ እንዲሆን ፡ ተደረገ

## custom ልማድ
Eating raw meat is an old Ethiopian custom. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ጥሬ ፡ ሥጋ ፡ መብላት ፡ የቆየ ፡ ልማድ ፡ ነው
Social customs vary in different countries. የሕዝብ ፡ ልማዶች ፡ እንደየሀገሩ ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው

**customs**
1. ጉምሩክ. When do we pass the customs inspection? የጉምሩክን ፡ ምርመራ ፡ የምናልፈው ፡ መቼ ፡ ነው?
2. ቀረጥ. Do we have to pay customs on this? ለዚህ ፡ ቀረጥ ፡ መክፈል ፡ አለብን ?

**custom** (adj.) በልኩ ፡ የተሰፋ
He wears only custom clothes. በልኩ ፡ የተሰፋ ፡ ልብስ ፡ ብቻ ፡ ይለብሳል

## (be) customary ተለመደ
It is not customary in this country to cremate the dead. በዚህ ፡ አገር ፡ሬሳ ፡ ማቃጠል ፡ የተለመደ ፡ አይደለም

## customer ደንበኛ
He is a regular customer of mine. የሁል ፡ ጊዜ ፡ ደንበኛዬ ፡ ነው

## customhouse የጉምሩክ ፡ ቤት
The government built a new customhouse. መንግሥቱ ፡ አዲስ ፡ የጉምሩክ ፡ ቤት ፡ አሠራ

## cut (vt.)
1. ቈረጠ. He cut his nails with a scissor. ጥፍሩን ፡ በመቀስ ፡ ቈረጠ
He cut wood for the fire. ለማገዶ ፡ ዕንጨት ፡ ቈረጠ
2. ዐጨደ. He cut a load of hay last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ አንድ ፡ ሸክም ፡ ሣር ፡ ዐጨደ
3. ቀነሰ. The company will cut the cost of merchandise next week. ኩባንያው ፡ በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ የሸቀጦችን ፡ ዋጋ ፡ ይቀንሳል
4. ከ - - - ቀረ. The lazy student cut three classes in history. ሰነፉ ፡ ልጅ ፡ ከታሪክ ፡ ክፍል ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ቀረ
5. ቀጨ. The quarrel cut the ties of friendship. ጠቡ ፡ ጓደኝነታቸውን ፡ ቀጨው
6. አስቀረ. She had to cut two songs from her program. ከፕሮግራሟ ፡ ሁለት ፡ ዘፈኖች ፡ ማስቀረት ፡ ነበረባት
7. አስተካከለ. The barber cut my hair. ጸጉር ፡ ቈራጩ ፡ ጸጉሬን ፡ አስተካከለኝ

**cut** (vi.)
1. ቈረጠ. This knife doesn't cut well. ይህ ፡ ቢላዋ ፡ በደንብ ፡ አይቈርጥም
2. ተቈረጠ. This meat cuts easily. ይህ ፡ ሥጋ ፡ በቀላሉ ፡ ይቈረጣል
3. ተፈለጠ. The wood cuts easily. ዕንጨቱ ፡ በቀላሉ ፡ ይፈለጣል

**cut across** አቋረጠ
He cut across the field.ሜዳውን ፡ አቋረጠ

**cut away** ቈረጠ
He cut away the burned flesh on my arm. ክንዴ ፡ ላይ ፡ የተቃጠለውን ፡ ሥጋዬን ፡ ቈረጠው

**cut back** አስተካከለ
They cut back the stick until it could be fitted in the hole. ከቀዳዳው ፡ እንዲገባ ፡ ለማድረግ ፡ የብትሩን ፡ ጫፍ ፡ አስተካከሉት

**cut back on** ቀነሰ
They cut back on expenses in order to save money. ገንዘብ ፡ ለመቈጠብ ፡ ወጪያቸውን ፡ ቀነሱ

**cut bread** ቈረሰ
Will you cut the bread, please? ዳቦውን ፡ ቍረሰው

**cut down** ቈረጠ
He cut down a tree with an ax. ዛፍ ፡ በመጥረቢያ ፡ ቈረጠ

**(be) cut down** ተቀጨ
He was cut down in the prime of life by cancer. በሕይወቱ ፡ አፍላ ፡ በካንሰር ፡ ተቀጨ

**cut down on** ቀነሰ
We will have to cut down on our expenses. ወጪያችንን ፡ መቀነስ ፡ አለብን

**cut in** ጥልቅ ፡ አለ
He likes to cut in when people talk. ሰው ፡ ሲያወራ ፡ ጥልቅ ፡ ማለት ፡ ይወዳል

**cut in ahead of**
*Accidents are often caused by drivers who cut in ahead of one. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አደጋ ፡ የሚደርሰው ፡ በድንገት ፡ ከጐን ፡ ወጥቶ ፡ ድቅን ፡ በሚሉ ፡ ነጂዎች ፡ ምክንያት ፡ ነው

**cut in half** እሁለት ፡ ከፈለ
He cut the apple in half. ቱፋውን ፡ እሁለት ፡ ከፈለው

**cut into**
1. ቈረጠ. He cut into the cake with a large knife. ኬኩን ፡ በቢላዋ ፡ ቈረጠ
2. አደከመ. The guerrilla raids cut into the enemy's strength. የደፈጣ ፡ ተዋጊዎቹ ፡ የጠላትን ፡ ኀይል ፡ አደከሙት

**cut into strips**
1. ዘለዘለ. They cut meat into strips and dried them. ሥጋውን ፡ ዘልዝለው ፡ ቋንጣ ፡ አደረጉት
2. በቀጫጭኑ ፡ ቈራረጠ. He cut the paper into strips. ወረቀቱን ፡ በቀጫጭኑ ፡ ቈራረጠው

**cut off**
1. ቈረጠ. Cut it off at the end! ጫፉ ፡ ላይ ፡ ቍረጠው
2. ቀነጠበ. He cut off a piece of his cigar and chewed it. ሲጋሩን ፡ ቀንጥቦ ፡ አኘከው
3. ነጠለ. They cut off the vanguard from the main body of the troops. አዝማቾቹን ፡ ጦር ፡ ከዋናው ፡ ጦር ፡ ነጠሉት

**(be) cut off** መሥመር ፡ ተቋረጠ
+I was cut off while talking to him on the phone. በቴሌፎን ፡ በማነጋግረው ፡ ጊዜ ፡ መሥመሩ ፡ ተቋረጠ

**cut open**
1. ቀደደ. He cut the chicken open and removed its gizzard. የዶሮዋን ፡ ሆድ ፡ ቀዶ ፡ መቋደሻዋን ፡ አወጣ
2. አፈረጠ. We will have to cut the blister open. ውኃ ፡ የቋጠረውን ፡ ማፍረጥ ፡ አለብን

**cut out**
1. ተወ. He cut out drinking. መጠጥ ፡ ተወ
2. ቈርጦ ፡ አወጣ. I will cut out the picture. ሥዕሉን ፡ ቈርጬ ፡ አወጣዋለሁ

**(be) cut out** ተፈለፈለ
The churches of Lalibela are cut out of solid rock. የላሊበላ ፡ አድባራት ፡ ካንድ ፡ ቋጥኝ ፡ የተፈለፈሉ ፡ ናቸው
*He is not cut out to be a teacher. አስተማሪ ፡ ለመሆን ፡ ተሰጥዎ ፡ የለውም

**cut (through)**
1. አቋረጠ. He cut through the woods to get home. በጫካው ፡ መካከል ፡ አቋርጦ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ
2. ቈረጠ. He cut through the wood with a saw. ግንዱን ፡ በመጋዝ ፡ ቈረጠው
3. አልፎ ፡ ቀደደ. You have cut through the lining. አልፈህ ፡ ገበሩን ፡ ቀደኸዋል

**cut up**
1. ቈረጠ. Cut it up in four pieces! ከአራት ፡ ቍረጠው
2. ገነጣጠለ. The maid cut the chicken up to make the chicken sauce. ገረዲቱ ፡ ወጥ ፡ ለመሥራት ፡ ዶሮዋን ፡ ገነጣጠለች
[See also 'groove, loose, short, throat, tooth']

**cut** (n.)
1. ቊስል. The cut is nearly healed. ቊስሉ ፡ ሊድን ፡ ምንም ፡ አልቀረውም
2. የተቈረጠ. He held out his hand and showed me the cut. እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ የተቈረጠውን ፡ አሳየኝ
3. (= to cut) መቀነስ. A cut in expenditures is necessary if we are to avoid bankruptcy. እንዳንከስር ፡ ከተፈለገ ፡ ወጪያችንን ፡ መቀነስ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**cutbacks, make ~**
*Many factories made cutbacks when their orders were canceled. ብዙ ፡ ፋብሪካዎች ፡ ሽያጭ ፡ ሲቀንስ ፡ የሚሠሩዋቸውን ፡ እቃዎች ፡ ብዛት ፡ ቀነሱ

**cute** የደስ ፡ ደስ ፡ ያለው
She is a cute little girl. የደስ ፡ ደስ ፡ ያላት ፡ ልጃገረድ ፡ ነች

**cutlery** የእቃ ፡ መቈራረጫ ፡ መሣሪያ
The best cutlery is made in Germany. ምርጥ ፡ የሆኑት ፡ የእቃ ፡ መቈራረጫ ፡ መሣሪያዎች ፡ የሚሠሩት ፡ ጀርመን ፡ አገር ፡ ነው

**cutlet** ኮተለቴ
I like my cutlet well done. ኮተለቴ ፡ የምወደው ፡ በስል ፡ ሲል ፡ ነው

**cutoff**
1. አቋራጭ. Let's take the cutoff to Harar! ወደ ፡ ሐረር ፡ የሚወስደውን ፡ አቋራጭ ፡ እንያዝ
2. መፈጸሚያ. The cutoff date for this project is in two weeks. በሁለት ፡ ሳምንት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የዚህ ፡ ፕሮጄክት ፡ መፈጸሚያ ፡ ይሆናል

**cutting** የሚነካ
He prefaced his speech with some cutting

remarks about the principal. በንግግሩ ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ ዲሬክተሩን ፡ የሚነካ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠ

**cutting board** መክተፊያ
They slice the meat on a cutting board. ሥጋውን ፡ መክተፊያ ፡ ላይ ፡ ይከትፋሉ

**cutting edge** ስለት
Be careful of the cutting edge of the knife! የቢላዋውን ፡ ስለት ፡ ተጠንቀቅ

**cycle** ዑደት
The epoch is reckoned in cycles of 52 years. ዘመኑ ፡ በየአምሳ ፡ ሁለት ፡ ዑደት ፡ ይቀመራል
*There is a cycle of stories about the adventures of King Arthur. ስለ ፡ ንጉሥ ፡ አርቱር ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ብዙ ፡ ተከታታይ ፡ ታሪኮች ፡ ተጽፈዋል

**cynical** ተጠራጣሪ
He is a very cynical person. እሱ ፡ በጣም ፡ ተጠራጣሪ ፡ ሰው ፡ ነው

**cypress** [ጥድ ፡ የሚመስል ፡ ዛፍ]

## D

**dab** (dabbed) ቀባባ
The girl dabbed her face with powder. ልጃገረዲቱ ፡ ፊቷን ፡ በፑድር ፡ ቀባባች

**dabble**
*My brother dabbles at painting. ወንድሜ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሥዕል ፡ ይሥላል

**daddy** አባባ
Children often address their father as daddy. ልጆች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አባታቸውን ፡ አባባ ፡ እያሉ ፡ ይጠራሉ

**dagger** ጩቤ
The man was killed with a dagger. ሰውዬው ፡ የተገደለው ፡ በጩቤ ፡ ነው

**daily** (n.) በየቀኑ ፡ የሚታተም ፡ ጋዜጣ
There are three dailies in this city. በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ በየቀኑ ፡ የሚታተሙ ፡ ሦስት ፡ ጋዜጦች ፡ አሉ

**daily** (adj.)
1. የዕለት. The "Los Angeles Times" is a daily newspaper. ሎስ ፡ አንጀለስ ፡ ታይምስ ፡ የዕለት ፡ ጋዜጣ ፡ ነው
2. (= adv.) በየቀኑ. That is a daily occurrence around here. ይህ ፡ እዚህ ፡ በየቀኑ ፡ የሚደረግ ፡ ነው

**daily** (adv.)
1. በቀን. The mail is delivered twice daily. ደብዳቤ ፡ በቀን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ይታደላል
2. በየዕለት. The announcements of deaths and marriages are published daily by the newspaper. ዜና ፡ ዕረፍትን ፡ ጋብቻን ፡ የሚገልጹት ፡ መግለጫዎች ፡ በየዕለቱ ፡ በጋዜጣው ፡ ላይ ፡ ይወጣሉ

**dainty**
1. ለስላሳ. She was dressed in a thin, dainty dress of blue. ስስና ፡ ለስላሳ ፡ የሆነ ፡ ሰማያዊ ፡ ቀሚስ ፡ ለብሳ ፡ ነበር
2. በጣም ፡ ቅምጥል. She is dainty about her eating. ስትበላ ፡ በጣም ፡ ቅምጥል ፡ ናት

**dairy farm** የከብት ፡ ርቢ ፡ ማቢያ
They started a dairy farm in Debre Zeit. በደብረ ፡ ዘይት ፡ የከብት ፡ ርቢ ፡ ማቢያ ፡ አቋቋሙ

**dais** የዙፋን ፡ መቀመጫ ፡ ስፍራ
The Emperor was sitting on a dais with a lion by his side. ንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ አንበሳውን ፡ አጠገባቸው ፡ አድርገው ፡ በዙፋን ፡ መቀመጫ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር

**dally, ~ away** አባከነ
He dallied away the afternoon. ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ያለውን ፡ ጊዜ ፡ አባከነ

**dam** (dammed), v. ገደበ
They dammed the river with rocks and clay. ወንዙን ፡ በድንጋይና ፡ በሸክላ ፡ ገደቡ

**dam** (n.) ግድብ
The dam is broken. ግድቡ ፡ ፈርሷል

**damage** (v.) አበላሸ
The storm damaged the roof. ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ጣሪያውን ፡ አበላሸው

**damage** (n.) ጉዳት ፤ ጥፋት
How much damage has been done? ምን ፡ ያህል ፡ ጉዳት ፡ ደረሰ ?
His appraisal of the damage was less than fifty dollars. የደረሰውን ፡ ጥፋት ፡ የገመተው ፡ ከኀምሳ ፡ ብር ፡ ያነሰ ፡ አድርጎ ፡ ነው

**damages** ካሳ ፤ ያጠፋ
He had to pay damages in the automobile accident. ላደረሰው ፡ የአውቶሞቢል ፡ አደጋ ፡ ካሳ ፡ (ያጠፋውን) ፡ መክፈል ፡ ነበረበት

**damn**
1. ኰነነ(ተኰነነ). Verily I say to you: the transgressors of God's law will be damned. እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ የሚጥስ ፡ ይኰነናል
2. ፈረደ(በት). God damned the Sodomites to everlasting punishment. እግዚአብሔር ፡ በሰዶማውያን ፡ ላይ ፡ የዘለዓለም ፡ ቅጣት ፡ ፈረደባቸው
3. አጥላላ. All critics damned the play. ተችዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ጨዋታውን ፡ አጥላሉ

**damnation**
*The priest preached concerning the damnation of sinners. ቄሱ ፡ ኀጢአተኞች ፡ እንዲኰነኑ ፡ አስተማሩ

**damned** (adj.) የተኰነነ
The wailing of the damned souls is well described in this poem. የተኰነኑት ፡ ነፍሳት ፡ ጩኸት ፡ በዚህ ፡ ግጥም ፡ በደንብ ፡ ተገልጿል

**damp** (v.)
1. አቀዘቀዘ. Continued failures damped their enthusiasm. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሳይሳካላቸው ፡ መቅረቱ ፡ መንፈሳቸውን ፡ አቀዘቀዘው
2. ዋጠ. The many rugs in the room damped the sound. በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ብዙ ፡ ስጋጃዎች ፡ ድምፁን ፡ ዋጡት

**damp** (adj.) እርጥብ
He wiped the window with a damp cloth. መስኮቱን ፡ በእርጥብ ፡ ጨርቅ ፡ ወለወለው

**get damp** ተወረዘ
Everything gets damp in the cellar. በምድር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይወረዛል

**dampen**
1. ውኃ ፡ አርከፈከፈ. She dampened the clothes before ironing them. ከመተኰሷ ፡ በፊት ፡ ልብሱን ፡ ውኃ ፡ አርከፈከፈችበት
2. አራሰ. The child dampened the handkerchief with his tears. ልጁ ፡ መሐረቡን ፡ በእንባው ፡ አራሰው
3. አቀዘቀዘ(በት). He dampened their joy by telling them of the money that they would have to pay. ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ እንዳለባቸው ፡ ነግሮ ፡ ደስታቸውን ፡ አቀዘቀዘባቸው

**dampness** ርጥበት
The dampness of the climate decayed the books. ያየሩ ፡ ርጥበት ፡ መጽሐፎቹን ፡ አወረዛቸው

**dance** (v.)
1. ደነሰ. They danced until midnight. እስከ ፡ እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ደነሱ
2. ጨፈረ. The villagers danced to celebrate the marriage. መንደረኞቹ ፡ ጋብቻውን ፡ ለማክበር ፡ ጨፈሩ

**dance** (n.)
1. ዘፈን. We are going to see the dances put on by the Ethiopian Patriotic Association. በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ያገር ፡ ፍቅር ፡ ማኅበር ፡ የተዘጋጀውን ፡ ዘፈን ፡ ልናይ ፡ እንሄዳለን
2. ዳንስ. He invited his girl friend to the dance. ወዳጁን ፡ ለዳንስ ፡ ጋበዛት

**dancer** ደናሽ
He is a good dancer. ጥሩ ፡ ደናሽ ፡ ነው

**dancing** ዳንስ
Her dancing was the big attraction in the show. በትርኢይቱ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ የሚማርከው ፡ የሷ ፡ ዳንስ ፡ ነበር

**dandle** ሽቅብ ፡ ሽቅብ ፡ አደረገ
The mother dandled the baby on her knees. እናትየው ፡ ልጇን ፡ በጉልበቷ ፡ ላይ ፡ አድርጋ ፡ ሽቅብ ፡ ሽቅብ ፡ አደረገችው

**dandy** [ስለ ፡ አለባበሱ ፡ ስለ ፡ መልኩ ፡ በጣም ፡ የሚጠነቀቅ ፡ ሰው]

**danger**
1. አደጋ. The doctor says she is out of danger now. ሐኪሙ ፡ ከእንግዲህ ፡ ካደጋ ፡ መትረፏን ፡ ተናገረ
Caution! Danger! ተጠንቀቅ ፤ አደጋ ፡ አለ
2. አደገኛነት. He was alive to the danger of the situation. ስለ ፡ ሁኔታው ፡ አደገኛነት ፡ ያውቅ ፡ ነበር
3. (= adj.) አደገኛ. A careless driver is a danger to the public. ግዴለሽ ፡ ነጂ ፡ ለሕዝቡ ፡ አደገኛ ፡ ነው

**apprehend danger** በረገገ
A guilty man apprehends danger in every sound. ወንጀለኛ ፡ ከሽ ፡ ባለ ፡ ቁጥር ፡ ይበረግጋል

**be in danger of** አሰጋ(ው)
He is in danger of losing his job. ሥራውን ፡ እንዳያጣ ፡ ያሰጋዋል
[See also 'court']

**dangerous**
1. አደገኛ. Is it dangerous to swim here? እዚህ ፡ መዋኘት ፡ አደገኛ ፡ ነው ?
2. አስጊ. This disease is dangerous for babies. ይህ ፡ በሽታ ፡ ለሕፃናት ፡ አስጊ ፡ ነው

**dangle** (vt.) አወዛወዘ
The boy dangled his legs over the edge of the rock. ልጁ ፡ ቋጥኙ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ እግሮቹን ፡ አወዛወዘ

**dangle** (vi.) ተንጠልጥሎ ፡ ተወዛወዘ
We found his corpse dangling at the end of a rope. ሬሳው ፡ በገመድ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ሲወዛወዝ ፡ አገኘነው
*He dangled the promise of promotion before his eyes. የማዕረግ ፡ እድገት ፡ ተስፋ ፡ አጓጓው

**dank** ለዛዛ
The dank air of the swamps is bad for your health. በረግረጉ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ለዛዛ ፡ አየር ፡ ለጤና ፡ ጠንቅ ፡ ነው

**dapple** ዥጉርጉር
A dapple horse makes a handsome mount. ዥጉርጉር ፡ ፈረስ ፡ የኮርቻ ፡ ክብት ፡ ይወጣዋል

**dare**
1. ደፈረ. I did not dare leave the baby alone. ሕፃኑን ፡ ብቻውን ፡ ትቼ ፡ ለመሄድ ፡ አልደፈርኩም
He dared to tell his boss the idea was no good. አሳቡ ፡ ጥሩ ፡ አለመሆኑን ፡ ላለቃው ፡ ደፍሮ ፡ ተናገረ
2. ተዳፈረ. He will dare any danger. ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ይዳፈራል
3. በድፍረት ፡ ተናገረ. He exposed his chest and dared the enemy to shoot him. ደረቱን ፡ ገልብጦ ፡ ጠላቱን ፡ ተኰስ ፡ እያለ ፡ በድፍረት ፡ ተናገረ
**dare someone** አደፋፈረ
He dared me to jump over the stream. ወንዙን ፡ ዘልዬ ፡ እንድሻገር ፡ አደፋፈረኝ

**dark** (n.)
1. ጨለማ. The road is hard to find in the dark. ጨለማ ፡ ውስጥ ፡ መንገዱን ፡ ማግኘት ፡ ያስቸግራል
2. ማታ. He works from dawn to dark. ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ይሠራል
3. መምሸት. The workers tried hard to finish before dark. ሠራተኞቹ ፡ ከመምሸቱ ፡ በፊት ፡ ለመጨረስ ፡ በጣም ፡ ጣሩ
*Don't keep me in the dark! ገልጸህ ፡ ንገረኝ
**dark** (adj.)
1. ጥቁር. His skin is very dark. መልኩ ፡ በጣም ፡ ጥቁር ፡ ነው
2. ጨለማ. A night without a moon is dark. ጨረቃ ፡ የሌለችበት ፡ ሌሊት ፡ ጨለማ ፡ ነው
I couldn't find a thing in this dark room. እዚህ ፡ ጨለማ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ላገኝ ፡ አልቻልኩም
3. ጭልም ፡ ያለ. We had to go through a dark passage. ጭልም ፡ ባለ ፡ መተላለፊያ ፡ ማለፍ ፡ ነበረብን
4. ጠቈርቈር ፡ ያለ. It is a somber room with dark furniture. በክፍሉ ፡ ያለው ፡ የቤት ፡ እቃ ፡ ጠቈርቈር ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ ክፍሉ ፡ ይከብዳል
5. ጭለማ. Things looked dark for him. ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ጭለማ ፡ ሆነበት
6. ያልደመቀ. I don't like dark colors. ያልደመቀ ፡ ቀለም ፡ አልወድም
**dark brown** ጠይም
Her complexion was a lovely dark brown. መልኳ ፡ ጠይምና ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ነበር
**get dark, grow dark** ጨለመ
In summer it gets dark late. በበጋ ፡ ዘግይቶ ፡ ይጨልማል
It began to grow dark. መጨለም ፡ ጀመረ
**(be) in the dark** አልተነገረውም
As usual, he was in the dark about our plans. እንደተለመደው ፡ እቅዳችን ፡ አልተነገረውም ፡ ነበር

**darken**
1. አጨለመ. He darkened the room to develop his photos. ፎቶውን ፡ ለማጠብ ፡ ክፍሉን ፡ አጨለመ
2. ሸፈነ. Clouds darkened the sun. ደመና ፡ ፀሐይዋን ፡ ሸፈናት
3. አጠቈረ. The sun darkens the skin. ፀሐዩ ፡ ቆዳን ፡ ያጠቍራል
4. ኳለ. She darkened her eyelashes. ቅንድቧን ፡ ኳለች

**darkness** ጨለማ
Darkness is absence of light. ጨለማ ፡ የብርሃን ፡ አለመኖር ፡ ነው
**be in darkness** ጨለመ
The room was in darkness. ክፍሉ ፡ ጨልሞ ፡ ነበር

**darling** ብርቅ
He is his mother's darling. ለናቱ ፡ ብርቅ ፡ ነው
*My darling children! የምወዳችሁ ፡ ልጆቼ !

**darn** ጠቀመ
Did you darn my socks? እግር ፡ ሹራቤን ፡ ጠቀምሽ ?

**dart, ~ a glance**
He darted a glance at me. ዓይኑን ፡ ጣል ፡ አደረገብኝ
**dart after** ተከትሎ ፡ ተፈተለከ
The dog darted after the rabbit. ውሻው ፡ ጥንቸሏን ፡ ተከትሎ ፡ ተፈተለከ
**dart an angry glance at** ገላመጠ
She darted an angry glance at her sister. እኅቷን ፡ ገላመጠቻት
**dart away** ሸመጠጠ
The deer saw us and darted away. አጋዘኑ ፡ ሲያየን ፡ ሸመጠጠ

**dash** (vt.)
1. አላጋ. The waves dashed the boat against the rocks. ሞገዱ ፡ ጀልባውን ፡ ከአለት ፡ ጋር ፡ አላጋው
2. ደፋ. We dashed water over him. በላዩ ፡ ላይ ፡ ውኃ ፡ ደፋንበት
3. ከሰከሰ. The angry child dashed a cup to the floor. የተናደደው ፡ ልጅ ፡ ሲኒውን ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ከሰከሰው
**dash** (vi.)
1. ተጣደፈ. When he dashed across the street,

he almost got killed by a car. መንገዱን ፡ በመጣደፍ ፡ ሲያቋርጥ ፡ መኪናው ፡ ሊገድለው ፡ ነበር
2. ተፈተለከ. He dashed to safety. ራሱን ፡ ለማዳን ፡ ሲል ፡ ተፈተለከ

**dash by** ተፈትልኮ ፡ አለፈ
They dashed by in a car. በመኪና ፡ ተፈትልከው ፡ አለፉ

**dash (one's) hopes** ተስፋ ፡ አስቈረጠው
The boss dashed my hopes for promotion. አለቃዬ ፡ ለእድገት ፡ ያለኝን ፡ ተስፋ ፡ አስቈረጠኝ

**dash off** (vt.) በጥድፊያ ፡ ጽፎ ፡ ላከ
He dashed off a letter to the director. ለሥራ ፡ መሪው ፡ በጥድፊያ ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎ ፡ ላከ

**dash off** (vi.) ተንደርድሮ ፡ ወጣ
Before I could answer, he dashed off. መልስ ፡ ከመስጠቴ ፡ በፊት ፡ ተንደርድሮ ፡ ወጣ

**dash to bits** ከሰከሰ
He dashed the bowl to bits on a rock. ጐድጓዳውን ፡ ሳሕን ፡ ከድንጋይ ፡ አጋጭቶ ፡ ከሰከሰው

## dash (n.)

1. ጭረት. Put a dash after the first word! ከመጀመሪያው ፡ ቃል ፡ በኋላ ፡ ጭረት ፡ አድርግ
2. ድምቀት. Mary always adds dash to a party. ሜሪ ፡ ሁልጊዜ ፡ ለፓርቲው ፡ ድምቀት ፡ ትሰጠዋለች

**a dash of** ትንሽ
Put a dash of salt in the salad! ሰላጣው ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ ጨው ፡ አድርግበት

**make a dash** በርግጎ ፡ ሮጠ
At the cry "Fire!", they all made a dash for the door. እሳት ፡ የሚል ፡ ጩኸት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ በርግገው ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ ሮጡ

## dashing ያሸበረቀ

She wears a dashing costume. ያሸበረቀ ፡ ልብስ ፡ ለብሳለች

## date (v.)

1. ቀኑን ፡ ጻፈ. Do not forget to date your letters! በደብዳቤዎቹ ፡ ላይ ፡ ቀኑን ፡ መጻፍ ፡ አትርሳ
2. ዕድሜ ፡ ዐወቀ ፤ ዕድሜ ፡ ተናገረ. He dated the tree by counting the rings in its trunk. የዛፉን ፡ ክብ ፡ መሥመር ፡ በመመልከት ፡ የዛፉን ፡ ዕድሜ ፡ ዐወቀ
Can you date that castle? የዚያን ፡ ግንብ ፡ ዕድሜ ፡ ልትናገር ፡ ትችላለህ ?
3. ተወዳጀ. Our relations are somewhat strained because he found out I am dating his worst enemy's sister. በጣም ፡ ጠላቱ ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ እኅት ፡ ጋር ፡ መወዳጀቴን ፡ ስላወቀ ፡ ጓደኛነታችን ፡ ሻክሯል
*The oldest house in town dates from the 17th century. በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ ጥንታዊነት ፡ ያለው ፡ ያሥራ ፡ ሰባተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ሕንጻ ፡ ነው
*The letter is dated June 6th. ደብዳቤው ፡ የተጻፈበት ፡ ቀን ፡ ሰኔ ፡ ስድስት ፡ ይላል

## date (n.)

1. ቀን. What is the date today? ዛሬ ፡ ቀኑ ፡ ስንት ፡ ነው ?
The date of Lincoln's birthday was February 12, 1809. ሊንከልን ፡ የተወለደበት ፡ ቀን ፡ የካቲት ፡ ፲፪ ፲፰፻፱ ዓ. ም. ነው
2. ጊዜ. The date of the meeting was advanced from April to March. የስብሰባው ፡ ጊዜ ፡ ከሚያዝያ ፡ ወደ ፡ መጋቢት ፡ እንዲቀርብ ፡ ተደርጓል
3. ዘመን. At that date, there were no airplanes. በዚያ ፡ ዘመን ፡ አውሮፕላኖች ፡ አልነበሩም
4. ቀጠሮ. I have a date for lunch today. ዛሬ ፡ የምሳ ፡ ቀጠሮ ፡ አለብኝ
5. ተምር. How much are dates by the pound? አንድ ፡ ፓውንድ ፡ ተምር ፡ ስንት ፡ ነው ?

**be out of date** ቀኑ ፡ አለፈ(በት)
Short skirts are out of date. አጭር ፡ ቀሚስ ፡ ቀኑ ፡ አልፎበታል

**to date** እስከዛሬ ፤ እስካሁን
We have not heard from him to date. እስከዛሬ ፡ (እስካሁን) ፡ ከሱ ፡ ምንም ፡ የሰማነው ፡ ነገር ፡ የለም

## daub ቀባ

She daubed salve on his burnt finger. የተቃጠለውን ፡ ጣቱን ፡ ቅባት ፡ ቀባችለት

## daughter ሴት ፡ ልጅ

He has two sons and three daughters. ሁለት ፡ ወንዶች ፡ ልጆችና ፡ ሦስት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ አሉት

## daughter-in-law የልጅ ፡ ሚስት

My daughter-in-law comes to visit me once a month. የልጄ ፡ ሚስት ፡ በወር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እየመጣች ፡ ትጠይቀኛለች

## daunt ተስፋ ፡ አስቈረጠ

Even the risk of death did not daunt him. የሞት ፡ አደጋ ፡ የሚያጋጥመው ፡ መሆኑን ፡ ማወቁ ፡ እንኳን ፡ ተስፋ ፡ አላስቈረጠውም

## dawn (v.)

1. ነጋ. The day was just dawning when we left. እኛ ፡ በሄድን ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ መንጋቱ ፡ ነበር
2. ተጀመረ. A new era of peace is dawning. አዲስ ፡ የሰላም ፡ ዘመን ፡ መጀመሩ ፡ ነው

**dawn on** ተገለጸ(ለት)
It finally dawned on me what he meant. ምን ፡ ማለቱ ፡ እንደሆነ ፡ አድሮ ፡ ተገለጸልኝ

**dawn** (n.)
1. ንጋት. Don't come before dawn! ከንጋት ፡ በፊት ፡ እንዳትመጣ
2. ጧት. He works from dawn to dark. ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ይሠራል
3. መክፈቻ. The invention of the airplane marked the dawn of a new age. የአውሮፕላን ፡ መፈልሰፍ ፡ ያዲስ ፡ ዘመን ፡ መክፈቻ ፡ ሆነ

**dawn of history**
*Man lived in caves before the dawn of history. ታሪክ ፡ ከመታወቁ ፡ በፊት ፡ ሰው ፡ በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ይኖር ፡ ነበር

**at dawn** ጐሕ ፡ ሲቀድ
We had to get up at dawn. ጐሕ ፡ ሲቀድ ፡ መነሣት ፡ አለብን

**at the crack of dawn** ጐሕ ፡ ሲቀድ
We got up at the crack of dawn. ጐሕ ፡ ሲቀድ ፡ ተነሣን

**day**
1. ቀን. I will finish the book in three days. መጽሐፉን ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ እጨርሰዋለሁ
He has been sleeping all day. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ተኝቶ ፡ ዋለ
2. ዕለት. The day he entered college was a big day in his life. ኮሌጅ ፡ የገባበት ፡ ቀን ፡ በሕይወቱ ፡ ታላቅ ፡ ዕለት ፡ ነበር
3. ጊዜ. He was the best writer of his day. በጊዜው ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ጸሐፊ ፡ ነበር
*Let's call it a day! ለዛሬ ፡ ይብቃን
*Colonialism has had its day. የቅኝ ፡ አገዛዝ ፡ ዘመን ፡ አልፎበታል

**day after day** በነጋ ፡ በጠባ ፤ በየቀኑ
Day after day, he tells us the same story. በነጋ ፡ በጠባ ፡ ያንኑ ፡ ታሪክ ፡ ደጋግሞ ፡ ይነግረናል
Day after day, he returned to the same place. በየቀኑ ፡ እዚያ ፡ ቦታ ፡ ተመላለሰ

**(the) day before** ከትናንትና ፡ ወዲያ
It had rained the day before. ከትናንትና ፡ ወዲያ ፡ ዘንቦ ፡ ነበር

**day by day** ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፤ በየቀኑ
Day by day, his condition is improving. ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ (በየቀኑ) ፡ ሁኔታው ፡ እየተሻለ ፡ ይሄዳል

**day in, day out** ነጋ ፡ ጠባ
They fed us beans day in, day out. ነጋ ፡ ጠባ ፡ ባቄላ ፡ ያበሉን ፡ ነበር

**day off** የዕረፍት ፡ ቀን
Sunday is the government workers' day off. ለመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ እሑድ ፡ የዕረፍት ፡ ቀን ፡ ነው

**by the day**
1. ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን. He gets fresher by the day. ብልግናው ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ እየባሰ ፡ ይሄዳል
2. በቀን ፡ ሒሳብ. You can rent this room by the day. ይህን ፡ ክፍል ፡ በቀን ፡ ሒሳብ ፡ ልትከራይ ፡ ትችላለህ

**(the) following day** በበነጋው ፤ በማግሥቱ
He tried to conserve his strength for the big test the following day. ጉልበቱን ፡ በበነጋው ፡ ለሚደረገው ፡ ትልቅ ፡ ፈተና ፡ ለመቈጠብ ፡ ፈለገ
The following day it rained. በማግሥቱ ፡ ዘነበ

**for days on end** ለብዙ ፡ ቀናት
They altercated in the senate for days on end. በሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ ተጨቃጨቁ

**from day to day** ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን
It is getting worse from day to day. ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ እየባሰ ፡ ይሄዳል

**one of these days** አንድ ፡ ቀን
I will drop by your house one of these days. አንድ ፡ ቀን ፡ እቤትህ ፡ ብቅ ፡ እላለሁ

**some day** አንድ ፡ ቀን
Some day I will visit you. አንድ ፡ ቀን ፡ እጠይቅሃለሁ

**the other day** በቀደም ፡ ለት
I met him the other day. በቀደም ፡ ለት ፡ አገኘሁት

**these days**ሰሞኑን
Prices are very high these days. ሰሞኑን ፡ ዋጋ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ብሏል

**this day** በዛሬው ፡ ቀን
Where were you this day last year? ባለፈው ፡ ዓመት ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ የት ፡ ነበርክ ?
[See also 'all, better, break, carry, few, fine, former, next, night, one, other, preceding, rainy, reckoning, registration, same, spend, tomorrow, very, yesterday']

**daybreak, at ~**
1. ማለዳ. He always gets up at daybreak. ሁልጊዜ ፡ ማለዳ ፡ ይነሣል
2. ጐሕ ፡ ሲቀድ. We reached the city at daybreak. ጐሕ ፡ ሲቀድ ፡ ከከተማው ፡ ደረስን

**daydream**
1. በሐሳብ ፡ ባክኖ. Too many students daydream

when the teacher is talking. አስተማሪው ፡ ሲናገር ፡ ብዙ ፡ ተማሪዎች ፡ በሐሳብ ፡ ይባክናሉ
2. በሐሳብ ፡ ተናወዘ. A faraway look in her eyes showed that she was daydreaming. ዝም ፡ ብላ ፡ አትኩራ ፡ ማየቷ ፡ በሐሳብ ፡ መናወዝ ፡ ያመለክታል

**daylight** የቀን ፡ ብርሃን
The light of a lamp is not as good as daylight. የፋኖስ ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ቀን ፡ ብርሃን ፡ አይሆንም

**at daylight** ጐሕ ፡ ሲቀድ
He was up at daylight. ጐሕ ፡ ሲቀድ ፡ ተነሥቶ ፡ ነበር

**before daylight** ፀሐይ ፡ ሳትወጣ
He started on his road before daylight. ፀሐይ ፡ ሳትወጣ ፡ መንገዱን ፡ ጀመረ
[See also 'broad']

**day student** ተመላላሽ ፡ ተማሪ
He is a day student at the Menilek School. በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተመላላሽ ፡ ተማሪ ፡ ነው

**daze**
1. አፈዘዘ. A blow on his head dazed him so that he could not find his way home. ራሱን ፡ የተመታው ፡ ስላፈዘዘው ፡ ቤቱ ፡ መድረስ ፡ አቅቶት ፡ ነበር
2. አደነዘዘ. The news of his friend's death dazed him. የጓደኛው ፡ ሞት ፡ አደነዘዘው

**be dazed** ፈዘዘ
His meaningless gestures showed that he was dazed by the blow. ትርጉም ፡ የሌለው ፡ እንቅስቃሴው ፡ በምቱ ፡ የፈዘዘ ፡ መሆኑን ፡ አመለከተ

**dazzle**
1. አጭበረበረ. Looking straight into the sun dazzled his eyes. ወደ ፡ ፀሐዩ ፡ ሲመለከት ፡ ዓይኑን ፡ አጭበረበረው
2. አስደነቀ. Her singing dazzled us. ዘፈኗ ፡ አስደነቀን

**deacon** ዲያቆን
The deacon serves in the church. ዲያቆን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ያገለግላል

**dead** (n.) ሙት (pl. ሙታን)
They buried the dead. ሙታንን ፡ ቀበሩ

**in the dead of the night** በውድቅት
It happened in the dead of night. የሆነው ፡ በውድቅት ፡ ነው

**dead** (adj.)
1. የሞተ. A dead person was found behind the hotel. አንድ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ በሆቴሉ ፡ ጀርባ ፡ ተገኘ
Latin is a dead language. ላቲን ፡ የሞተ ፡ ቋንቋ ፡ ነው
2. የደረቀ. The dead leaves swished in the wind. የደረቁትን ፡ ቅጠሎች ፡ ነፋሱ ፡ አንኮሻኮሻቸው
3. ፍጹም. After his speech, a dead silence ensued. ከሱ ፡ ንግግር ፡ በኋላ ፡ ፍጹም ፡ ጸጥታ ፡ ነበር
4. በጣም ፡ ቀዝቃዛ. The party was dead so I went home early. ፓርቲው ፡ በጣም ፡ ቀዝቃዛ ፡ ስለነበር ፡ በጊዜ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ሄድኩ

**dead matter** በድን
A rock is dead matter. ቋጥኝ ፡ በድን ፡ ነው

**dead** (adv.), ~ **certain** ፍጹም ፡ እርግጠኛ
I am dead certain that I put it here. እዚህ ፡ እንዳስቀመጥኩት ፡ ፍጹም ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ

**be dead tired** ሙትት ፡ ብሎ ፡ ደከመ
He is dead tired after his long trip. ከረዥሙ ፡ ጉዞ ፡ በኋላ ፡ ሙትት ፡ ብሎ ፡ ደክሞ ፡ ነበር

**be dead**
1. ሞተ. His father is dead. አባቱ ፡ ሞተዋል
2. ጠፋ. The fire is dead. እሳቱ ፡ ጠፍቷል
3. ደረቀ. The flowers in my garden are dead. ባትክልት ፡ ቦታዬ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ አበባዎች ፡ ደርቀዋል

**be (a) dead season** ቀዘቀዘ
Summer is often a dead season except in businesses. በበጋ ፡ ጊዜ ፡ ከንግድ ፡ በስተቀር ፡ ሁሉም ፡ የቀዘቀዘ ፡ ነው

**be half dead**
1. በድን ፡ ሆነ. He was half dead with fright. በድንጋጤ ፡ በድን ፡ ሆነ
2. ሙትት ፡ አለ. The beggar was half dead from hunger. ለማኙ ፡ በረኀብ ፡ ሙትት ፡ ብሎ ፡ ነበር

**be pretty dead** ሞተ
That meeting was pretty dead. ያ ፡ ስብሰባ ፡ የሞተ ፡ ነበር

**become a dead letter** ዋጋ ፡ አጣ
After the legal reforms, this law became a dead letter. ሕጎች ፡ ከተሻሻሉ ፡ ወዲህ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ዋጋ ፡ አጣ

**fall dead** ሙትት ፡ አለ
I worked all day and fell dead with exhaustion. ስሠራ ፡ ውዬ ፡ በድካም ፡ ሙትት ፡ አልኩ
*The hunter fired, and the lion fell dead at his feet. አዳኙ ፡ ተኰሰ ፡ አንበሳውን ፡ ጣለው

**go dead** ተቋረጠ
During the storm, the telephone suddenly went dead. በማዕበሉ ፡ ጊዜ ፡ ስልኩ ፡ በድንገት ፡ ተቋረጠ
[See also 'broke, earnest, faint, strike']

## deaden
1. አደነዘዘ. The drug deadened his pain. መድኃኒቱ ፡ ሥቃዩን ፡ አደነዘዘለት
2. ቀነሰ. Heavy curtains will deaden street noises. ወፍራም ፡ መጋረጃ ፡ ከመንገዱ ፡ የሚመጣውን ፡ ድምፅ ፡ ይቀንሳል

## dead end መውጫ ፡ የሌለው
There are many dead end streets in this city. እዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ መውጫ ፡ የሌላቸው ፡ መንገዶች ፡ አሉ

## deadline የመጨረሻ ፡ ቀን
The teacher gave the student a deadline for the composition. አስተማሪው ፡ ተማሪው ፡ ድርሰቱን ፡ የሚያቀርብበትን ፡ የመጨረሻ ፡ ቀን ፡ ወሰነ

## deadlock
*Employers and strikers were at a deadlock. ሠራተኞቹም ፡ አሠሪዎቹም ፡ አንበገርም ፡ አሉ

## deadly (adj.)
1. የሚገድል. Typhus used to be a deadly disease. ተስቦ ፡ የሚገድል ፡ በሽታ ፡ ነበር
2. የተማረረ. The deadly enemies have a fierce hatred for each other. በተማረሩ ፡ ባላጋራዎች ፡ መካከል ፡ የከረረ ፡ ጥላቻ ፡ አለ
3. የቀዘቀዘ. The dinner party was absolutely deadly. የእራት ፡ ግብዣው ፡ በጣም ፡ የቀዘቀዘ ፡ ነበር
*Her deadly pallor frightened us. እንደሬሳ ፡ መገርጣቷ ፡ አስደነገጠን

**deadly** (adv.)
He is deadly serious. የምሩን ፡ ነው

## deadwood
1. ጭራሮ. The children are gathering deadwood for the fire. ልጆቹ ፡ ለማገዶ ፡ ጭራሮ ፡ ይለቅማሉ
2. ዋጋ ፡ የሌለው. He cut the deadwood from his staff of advisors. ከማካሪዎቹ ፡ መካከል ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውን ፡ ቀነሰ

## deaf ደንቆሮ
He is completely deaf. ፍጹም ፡ ደንቆሮ ፡ ነው

**deaf-mute** ደንቆሮና ፡ ድዳ
Her child is a deaf-mute. ልጅዋ ፡ ደንቆሮና ፡ ድዳ ፡ ነው

**be deaf to** አልሰማም
He was deaf to warning of danger. ስለ ፡ አደጋ ፡ የሚሰጠውን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ አልሰማም

**turn a deaf ear**
*He turned a deaf ear to my request. ጥያቄ ፡ ሳቀርብለት ፡ የዝሆን ፡ ጆሮ ፡ ይስጠኝ ፡ አለ

## deafen አደነቈረ
The noise is deafening. ጩኸቱ ፡ ያደነቍራል

**be deafened** ደነቈረ
He was deafened by the blast. በፈንጂው ፡ ድምፅ ፡ ደነቈረ

## deafness ድንቁርና
Deafness is a disability for a musician. ድንቁርና ፡ ሙዚቀኛን ፡ ያሰናክላል

## deal (dealt), v.
1. ተገናኘ. He deals directly with the company. ከኩባንያው ፡ ጋር ፡ በቀጥታ ፡ ይገናኛል
2. ተናገረ ፤ አወሳ. History deals with the past. ታሪክ ፡ ስላለፈ ፡ ነገር ፡ ይናገራል
This book deals with the Italian invasion. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ ጣልያን ፡ ወረራ ፡ ያወሳል
3. ተግባባ. That man is easy to deal with. ከዚህ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ መግባባት ፡ ቀላል ፡ ነው
4. ግንኙነት ፡ አደረገ. He is diplomatic in dealing with people. ከሰው ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ሲያደርግ ፡ ዘዴኛ ፡ ነው
5. ገጠመ. Don't deal with him; he is very foxy. በጣም ፡ ተንኰለኛ ፡ ስለሆነ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ አትግጠም
6. መፍትሔ ፡ አገኘ. Only an expert knows how to deal with that problem. ለችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ የሚያገኘው ፡ በሥራው ፡ የሠለጠነ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው

**deal in**
1. ሸጠ. This garage deals in gasoline, oil, and tires. ይህ ፡ ጋራዥ ፡ ቤንዚን ፤ ዘይትና ፡ ጎማ ፡ ይሸጣል
2. ነገደ. My uncle deals in coffee. አጐቴ ፡ ቡና ፡ ይነግዳል

**deal out** አከፋፈለ
The Red Cross dealt out food to the hungry soldiers. ቀይ ፡ መስቀል ፡ ለተራቡት ፡ ወታደሮች ፡ ምግብ ፡ አከፋፈለ

**deal with**
1. ተቋቋመ ፤ ገባ(በት) How shall we deal with this problem? ይህን ፡ ችግር ፡ እንዴት ፡ እንቋቋመው?
Deal with that problem yourself! ጉዳዩን ፡ አንተ ፡ ራስህ ፡ ግባበት
2. ያዘ. The husband dealt fairly with his wife. ባልየው ፡ ሴትዮዋን ፡ በሚገባ ፡ ይዟታል
3. መረመረ. He is dealing with the first question.

የመጀመሪያውን ፡ ጉዳይ ፡ በመመርመር ፡ ላይ ፡ ነው

**deal with a problem** ተጠቀመ
How shall we deal with the problem of bringing water to the city? ወደ ፡ ከተማ ፡ ውኃ ፡ ለማስገባት ፡ በምን ፡ ዘዴ ፡ እንጠቀም ?
[See also 'blow']

## deal (n.)
1. መገበያየት. He made a lot of money on that deal. በዚህ ፡ መገበያየት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አተረፈ
2. ውል. They concluded the deal with a handshake. ውሉ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተጨባበጡ
He is a very crafty person, so don't make any deals with him. በጣም ፡ ተንኰለኛ ፡ ስለሆነ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ውል ፡ አታድርግ
3. ሥራ. He will try to get the better of you in every business deal you have with him. ከሱ ፡ ጋር ፡ በምታደርገው ፡ በማንኛውም ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሊያሞኝህ ፡ ይሞክራል
4. የንግድ ፡ ጉዳይ. The salesman clinched the deal and went out to celebrate. አሻሻጩ ፡ የንግዱን ፡ ጉዳይ ፡ ፈጽሞ ፡ ሊደሰት ፡ ወጣ ፡ አለ
*Well, it's a deal. መልካም ፤ ተስማማን

**a good deal** ብዙ
He smokes a good deal. ብዙ ፡ ያጨሳል

**a great deal**
1. ብዙ. I have worked a great deal on that thing. በዚህ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ደክሜበታለሁ
2. በጣም. He has aged a great deal lately. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ በጣም ፡ አርጅቷል

**give a good deal** በቀላል ፡ ዋጋ ፡ ሸጠ
If you buy this radio now, I can give you a good deal. ይህን ፡ ሬዲዮ ፡ አሁን ፡ ብትገዛ ፡ በቀላል ፡ ዋጋ ፡ እሸጥልሃለሁ

## dealer ነጋዴ
The automobile dealer sold two cars today. የአውቶሞቢሉ ፡ ነጋዴ ፡ ዛሬ ፡ ሁለት ፡ መኪናዎች ፡ ሸጠ
[See also 'retail']

## dealings
1. ይዞታ. His commercial dealings are being investigated by the ministry. የንግድ ፡ ይዞታው ፡ በሚኒስቴሩ ፡ በመመርመር ፡ ላይ ፡ ነው
2. አድራጎት. He is businesslike in all his dealings. ባድራጎቱ ፡ ሁሉ ፡ ቀልጣፋ ፡ ነው

## dear
1. ተወዳጅ. What a dear, little child he was! እንዴት ፡ ያለ ፡ ተወዳጅ ፡ ልጅ ፡ ነበር
2. ውድ. Ivory is very dear these days. ዛሬ ፡ የዝሆን ፡ ጥርስ ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ ነው
He is a dear friend of mine. ውድ ፡ ጓደኛዬ ፡ ነው
3. ከፍተኛ. This was a dear price to pay for our independence. ይህ ፡ ለነጻነታችን ፡ የከፈልነው ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ነበር

**be dear to someone**
*His sister is very dear to him. እኅቱን ፡ በጣም ፡ ይወዳታል

**oh dear!**
1. ወየው. "Oh dear! I will be late today", she said. « ወየው ፤ ዛሬም ፡ ልዘገይ ፡ ነው » ፡ አለች
2. ዐጀብ. "Oh dear! I will be late today", he said. « ዐጀብ ፤ ዛሬም ፡ ልዘገይ ፡ ነው » ፡ አለ

## dearest ልባዊ
His dearest wish is to go to Ethiopia. ልባዊ ፡ ፍላጎቱ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሄድ ፡ ነው

## dearly በጣም
He loved her dearly even though she was not his mother. ምንም ፡ እንኳ ፡ እናቱ ፡ ባትሆንም ፡ በጣም ፡ ይወዳት ፡ ነበር
He would dearly love to get his money back. ገንዘቡ ፡ ቢመለስለት ፡ በጣም ፡ ይወድ ፡ ነበር
He had to pay dearly for his mistake. በጥፋቱ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ደረሰበት

**cost (one) dearly** ጉዳት ፡ ላይ ፡ ጣለው
That mistake will cost you dearly. ጥፋትህ ፡ ጉዳት ፡ ላይ ፡ ይጥልሃል

## dearth እጥረት
There was dearth of food after the war. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ የምግብ ፡ እጥረት ፡ ነበር

## death
1. ሞት. His father's death saddened him greatly. ያባቱ ፡ ሞት ፡ በጣም ፡ አሳዘነው
2. መሞት. His death was announced in the newspapers. መሞቱ ፡ በጋዜጣ ፡ ተገለጸ
3. አሟሟት. The mystery of his death is unsolvable. ያሟሟቱን ፡ ምስጢር ፡ ሊደረስበት ፡ አይቻልም
4. ሕይወት ፡ መጥፋት. Hitler is responsible for the death of millions. በሚሊዮን ፡ ለሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ሕይወት ፡ መጥፋት ፡ ተጠያቂ ፡ ሂትለር ፡ ነው
5. እልቂት. The calamitous journey ended in

the deaths of the entire family. አሰቃቂው ፡ ጉዞ ፡ የቤተ ፡ ሰቡን ፡ ሁሉ ፡ እልቂት ፡ አስከተለ
6. ዜና ፡ ዕረፍት. The newspaper has a column in which deaths are reported. ጋዜጣው ፡ ዜና ፡ ዕረፍት ፡ የሚገለጽበት ፡ ዓምድ ፡ አለው
7. ፍጻሜ. The last war marked the death of the empire. ያለፈው ፡ ጦርነት ፡ የመንግሥቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ
*Don't work yourself to death! ነፍስህ ፡ እስ ክትወጣ ፡ ድረስ ፡ አትሥራ

**(be) bored to death** ሰለቸ(ው)
+She was bored to death by the lecture. ንግግሩ ፡ በጣም ፡ ሰልችቷት ፡ ነበር

**meet one's death** ሞተ
The policeman met his death in the line of duty. ፖሊሱ ፡ በተግባሩ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ሞተ

**put to death** ገደለ ፤ በጥይት ፡ ደበደበ(ተደበደበ)
The soldiers put the traitor to death. ወታደሮ ቹ ፡ ከሓዲውን ፡ ገደሉት
The sergeant was put to death this morning. ያምሳ ፡ አለቃው ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ በጥይት ፡ ተደበደበ

**sentence to death** የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረደበት
He pleaded for mercy, but the judge sentenced him to death. ምሕረት ፡ እንዲደረግለት ፡ ለመነ ፡ ግን ፡ ዳኛው ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረደበት
[See also 'break, choke, sentence, starve, stone, violent']

## deathbed
*On his deathbed, he sent for his son. ሲያጣጥ ር ፡ ልጁን ፡ አስጠራ

## death penalty የሞት ፡ ፍርድ
His death penalty was revoked by the Emperor. የሞት ፡ ፍርዱ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ተሻረ

## death throes ጣረሞት
The old man was in his death throes when I arrived. እኔ ፡ ስደርስ ፡ ሽማግሌው ፡ በጣረሞት ፡ ላይ ፡ ነበር

## debark ከመርከብ ፡ ወረደ
The troops debarked in the dark. ወታደሮቹ ፡ በጨለማ ፡ ከመርከብ ፡ ወረዱ

## debase አረከሰ
They debased gold by adding copper. በወርቁ ፡ ላይ ፡ መዳብ ፡ በመዘነቅ ፡ አረከሱት

**debase oneself** ራሱን ፡ አዋረደ
He debased himself by cheating. በማጭበርበር ፡ ራሱን ፡ አዋረደ

## debatable የሚያከራክር
The effect of tobacco on health is a debatable question. ትምባሆ ፡ በጤንነት ፡ ላይ ፡ የሚያደ ርሰው ፡ ጉዳት ፡ የሚያከራክር ፡ ነው

## debate (v.)
1. ተከራከረ(በት). They debated the question for hours. ጉዳዩን ፡ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ ተከራከሩበት
2. መረመረ. The mayor debated the property owners' demands. ከንቲባው ፡ የባለ ፡ ንብረቶች ን ፡ ጥያቄ ፡ መረመረ

**debate with oneself** አመነታ
I debated with myself whether or not to go. ልሂድ ፡ ልቅር ፡ በማለት ፡ አመነታሁ

## debate (n.) ክርክር
The debate went on for hours. ክርክሩ ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ፈጀ

## debating team የክርክር ፡ ቡድን
The debating team came off with flying colors. የክርክሩ ፡ ቡድን ፡ ድልን ፡ ተቀዳጀ

## debauch አበላሸ
The life of the big city debauches the youth. የከተማ ፡ ኑሮ ፡ ወጣቶችን ፡ ያበላሻል

## debilitate አደከመ
A humid climate debilitates one who is not used to it. እርጥበት ፡ ያለው ፡ ያየር ፡ ንብረ ት ፡ ላለመደው ፡ ሰው ፡ ያደክማል

## debit (v.)
*Please debit Mr. Jones' account for $5.00! በሚስተር ፡ ጆንስ ፡ የዱቤ ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ አም ስት ፡ ብር ፡ ጨምርበት

## debris ፍርስራሽ
The street was covered with debris from the explosion. መንገዱ ፡ ከፈንጂው ፡ የተነሣ ፡ በ ፍርስራሽ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር

## debt
1. ዕዳ. Is he still in debt? አሁንም ፡ ዕዳ ፡ አለበት ? He is up to his ears in debt. እስከ ፡ አንገቱ ፡ ድረስ ፡ በዕዳ ፡ ተውጧል
2. ውለታ. My debt to him for advice is not easy to repay. ላካፈለኝ ፡ ምክር ፡ ውለታውን ፡ በቀላሉ ፡ ልከፍለው ፡ አልችልም

**keep in debt** ዕዳ ፡ ውስጥ ፡ ከተተ
His extravagance kept him always in debt. ገንዘብ ፡ አባካኝነቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ዕዳ ፡ ውስጥ ፡ እንደከተተው ፡ ነው

**make debts** ዕዳ ፡ ገባ
He dishonored his family by making debts. ዕዳ ፡ በመግባት ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ አዋረደ
[See also 'honor, run']

**debtor**

1. ባለዕዳ. He is a debtor of mine. የኔ ፡ ባለዕዳ ፡ ነው
2. ተበዳሪ. The creditor exacted full payment from his debtor. አበዳሪው ፡ ተበዳሪውን ፡ በሙሉ ፡ እንዲከፍል ፡ አስገደደው

**decade** ዐሥር ፡ ዓመታት

Addis Ababa developed greatly in the last decade. ባለፉት ፡ ዐሥር ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በጣም ፡ ተስፋፍታለች

**decadence** ውድቀት

The decadence of morals was one of the causes of the fall of Rome. የሮም ፡ መውደቅ ፡ ምክንያቶች ፡ ከሆኑት ፡ አንዱ ፡ የሞራል ፡ ውድቀት ፡ ነበር

**decant** አጠለለ

Decant the wine into each of the glasses! ወይኑን ፡ በያንዳንዱ ፡ ብርጭቆ ፡ አጥለው

**decapitate** ቀላ

The soldiers decapitated the defeated prince. ወታደሮቹ ፡ ድል ፡ የሆነውን ፡ መስፍን ፡ ቀሉት

**decay** (vt.)

1. አበሰበሰ. A hot climate decays fruit. ሞቃት ፡ አየር ፡ ፍሬ ፡ ያበሰብሳል
2. አወረዘ. The dampness of the climate decayed the books. ያየሩ ፡ ርጥበት ፡ መጽሐፎችን ፡ አወረዛቸው

**decay** (vi.)

1. በሰበሰ. Old fruits and vegetables decay. የቆዩ ፡ ፍሬዎችና ፡ ቅጠላ ፡ ቅጠሎች ፡ ይበሰብሳሉ
2. እየተዳከመ ፡ ሄደ. After the Muslim states reached the limit of their glory, they decayed. የእስላም ፡ መንግሥታት ፡ ከከፍተኛው ፡ ክብራቸው ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፡ እየተዳከሙ ፡ ሄዱ

**decay** (n.)

1. መበስበስ. Decay set in rapidly after the animal was killed. እንስሳው ፡ እንደተገደለ ፡ መበስበስ ፡ ጀመረ
2. መበላሸት. The decay of the international situation worries us. የዓለም ፡ ሁኔታ ፡ መበላሸት ፡ አሳስቦናል

**decease** መሞት

The decease of his uncle saddened us. የአጎቱ ፡ መሞት ፡ አሳዘነን

**upon the decease** ሲሞት

He will inherit the estate upon the decease of his uncle. አጎቱ ፡ ሲሞት ፡ ርስቱን ፡ ይወርሳል

**deceased** ሟች

The names of the deceased have not yet been reported. የሟቾቹ ፡ ስም ፡ እስካሁን ፡ አልተገለጸም

**be deceased** ሞተ

His father is deceased. አባቱ ፡ ሞቷል

**deceit** ማታለል

She is incapable of deceit. ማታለል ፡ አይሆንላትም

**deceitful** አታላይ

A deceitful person cannot keep friends for long. አታላይ ፡ ሰው ፡ የብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጓደኞች ፡ ሊኖሩት ፡ አይችልም

**deceive** አታለለ

When he sold me a gold watch, he deceived me. ሰዓቱ ፡ የወርቅ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሲሸጥልኝ ፡ አታለለኝ

His wife is deceiving him. ሚስቱ ፡ ታታልለዋለች

**decelerate** ፍጥነቱን ፡ ቀነሰ

The plane decelerated just before landing. ከማረፉ ፡ ጥቂት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ አውሮፕላኑ ፡ ፍጥነቱን ፡ ቀነሰ

**December** ታኅሣሥ

**decency, common ~** መልካም ፡ ምግባር

Common decency requires a healthy man to try to support his family. መልካም ፡ ምግባር ፡ አንድ ፡ ደኅና ፡ ሰው ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ ለማስተዳደር ፡ እንዲሞክር ፡ ያስገድደዋል

**decent**

1. ደኅና. Put on some decent clothes before you visit your friends! ጓደኞችህ ፡ ዘንድ ፡ ከመሄድህ ፡ በፊት ፡ ደኅና ፡ ልብስ ፡ ልበስ

He is a decent fellow. ደኅና ፡ ሰው ፡ ነው

2. ጨዋ. He gives the impression of being a decent fellow. ጨዋ ፡ ልጅ ፡ መስሎ ፡ ይታያል
3. የረባ. I haven't eaten a decent meal in weeks. ለብዙ ፡ ሳምንት ፡ የረባ ፡ ምግብ ፡ አልበላሁም
4. ተገቢ. The old lady says that it is not decent to wear short skirts. አሮጊቷ ፡ አጭር ፡ ቀሚስ ፡ መልበስ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ፡ ትላለች
5. በቂ. He gets decent marks at school. በትምህርት ፡ ቤት ፡ በቂ ፡ ውጤት ፡ ያገኛል
6. መልካም. He comes from a decent home. ከመልካም ፡ ቤተሰብ ፡ ይወለዳል
7. አሳፋሪ ፡ ያልሆነ. Make sure the jokes you tell are decent! የምትናገረው ፡ ቀልዶች ፡ አሳፋሪ ፡ ላለመሆናቸው ፡ እርግጠኛ ፡ ሁን

**deception**
1. ማጭበርበር. He stood there shamefaced when his deception was discovered. ማጭበርበሩ ፡ በተነቃበት ፡ ጊዜ ፡ በእፍረት ፡ ተገትሮ ፡ ቀረ
2. የማታለል ፡ ሥራ ፡ መሆን. He discovered the deception too late. የማታለል ፡ ሥራ ፡ መሆኑን ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ ዐወቀ

**deceptive** አሳሳች
The outward appearance of things can be deceptive. መልክ ፡ አሳሳች ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

**decide**
1. ቈረጠ. I decided to stay. ለመቆየት ፡ ቈረጥኩ
2. ወሰነ. It is not easy to decide that question. ነገሩን ፡ መወሰን ፡ ቀላል ፡ አይደለም
3. ከፍጻሜ ፡ አደረሰ. That one battle decided the course of the war. ያቺ ፡ ውጊያ ፡ ጦርነቱን ፡ ከፍጻሜ ፡ አደረሰችው
4. ፍርድ ፡ ሰጠ ፤ በየነ. The judge decided the case this morning. ዳኛው ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ ለነገሩ ፡ ፍርድ ፡ ሰጠ ፡ (ነገሩን ፡ በየነ)

**decide against** ፈረደ(በት)
The judge decided the case against him. ዳኛው ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ፈረደበት

**decide in favor of** ፈረደ(ለት)
The judge decided the case in favor of the plaintiff. ዳኛው ፡ ለከሳሹ ፡ ፈረደለት

**decide on** መረጠ
She finally decided on the blue dress. በመጨረሻ ፡ ሰማያዊውን ፡ ልብስ ፡ መረጠች

**decided** (adj.)
1. የማያጠራጥር. There is a decided difference between the two. በሁለቱ ፡ መሀከል ፡ የማያጠራጥር ፡ ልዩነት ፡ አለ
2. ከፍ ፡ ያለ. His height gave him a decided advantage. ቁመቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመብለጥ ፡ ዕድል ፡ አስገኘለት
3. ቁርጥ. He has very decided ideas on the subject. በጉዳዩ ፡ ቁርጥ ፡ ያለ ፡ ሐሳብ ፡ አለው

**decidedly** መቶ ፡ በመቶ
Her work is decidedly better than his. ሥራዋ ፡ መቶ ፡ በመቶ ፡ ከሱ ፡ የተሻለ ፡ ነው

**decimal system** ያሥራት ፡ አቈጣጠር
Ten is the base of the decimal system. ዐሥር ፡ ያሥራት ፡ አቈጣጠር ፡ መሠረት ፡ ነው

**decimate** አብዛኛውን ፡ ክፍል ፡ አጠፋ
War has decimated the tribe. ጦርነት ፡ የጎሳውን ፡ አብዛኛውን ፡ ክፍል ፡ አጥፍቶታል

**decipher**
1. አነበበ. It is difficult to decipher his handwriting. የእጅ ፡ ጽሕፈቱን ፡ ለማንበብ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. ፈታ. He was able to decipher the secret message. ምስጢራዊ ፡ መልእክቱን ፡ ለመፍታት ፡ ቻለ

**decision** ውሳኔ
At last, he has come to a decision. በመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ አድርጓል
The judge studies all sides of the question before he makes a decision. ውሳኔ ፡ ከማስተላለፉ ፡ በፊት ፡ ዳኛው ፡ ነገሩን ፡ በብዙ ፡ አንጻር ፡ ይመለከተዋል

**hand down a decision** ፍርድ ፡ ፈረደ
The judge handed down an unfavorable decision. ዳኛው ፡ የማይስማማ ፡ ፍርድ ፡ ፈረደ

**man of decision** ቁርጠኛ ፡ ሰው
A man of decision makes up his mind what to do and then does it. ቁርጠኛ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ እንደሚያደርግ ፡ ወጥኖ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያውለዋል
[See also 'judicial']

**decisive**
1. ማብቂያ. The battle of Stalingrad was decisive in bringing about the ultimate defeat of the Germans. እስታሊንግራድ ፡ የተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ጀርመኖችን ፡ ድል ፡ በማስነሣት ፡ ለጦርነቱ ፡ ማብቂያ ፡ ሆነ
2. ቁርጥ ፡ ያለ. He spoke with a decisive tone of voice. ቁርጥ ፡ ባለ ፡ አነጋገር ፡ ተናገረ

**decisive manner** ቈራጥነት
The general was known by his decisive manner. ጀኔራሉ ፡ በቈራጥነት ፡ የታወቀ ፡ ነበር

**deck** የመርከብ ፡ መድረክ ፤ የመርከብ ፡ ወለል
The upper deck is reserved for first-class passengers. የመርከቡ ፡ የላይኛው ፡ መድረክ ፡ ለአንደኛ ፡ ማዕረግ ፡ ተሳፋሪዎች ፡ ተይዟል
The sailor coiled the rope on the deck of the ship. መርከበኛው ፡ ገመዱን ፡ በመርከቡ ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ጠመጠመው

**declaim**
1. እየተቀናጣ ፡ ተናገረ. He likes to declaim all the time. ሁልጊዜ ፡ እየተቀናጣ ፡ መናገር ፡ ይወዳል
2. በጋለ ፡ ስሜት ፡ አቀረበ. He declaimed his speech before a large audience. ንግግሩን ፡ ለአድማጮቹ ፡ በጋለ ፡ ስሜት ፡ አቀረበ

**declaration**

1. **ዐዋጅ ፡ መታወጅ**. The declaration of a state of emergency caused great excitement. ያስቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ ዐዋጅ ፡ መታወጅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መደናገጥ ፡ ፈጠረ
2. **መግለጫ**. They made a joint declaration of policy. የፖሊሲውን ፡ የጋራ ፡ መግለጫ ፡ አወጡ
3. **ሰነድ**. The law requires all travelers to hand in a customs declaration. ሕጉ ፡ መንገደኞች ፡ ሁሉ ፡ እቃ ፡ የሚያስፈትሹበት ፡ የጉምሩክ ፡ ሰነድ ፡ እንዲያሳዩ ፡ ይጠይቃል

**declare**

1. **ዐወጀ**. They declared war on us. ጦርነት ፡ ዐወጁብን
2. **አለ**. The accused man declared that he was not guilty. ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ አለ
3. **አስመዘገበ**. Do I have to declare the tobacco at customs? ትምባሆውን ፡ እጉምሩክ ፡ ማስመዝገብ ፡ አለብኝ ?
4. **ገለጸ**. The director declared his position in the controversy. ዲሬክተሩ ፡ በክርክሩ ፡ ጊዜ ፡ የሚያምንበትን ፡ ሐሳብ ፡ ገለጸ
[See also 'blockade']

**declension** **እርባታ**

The declension of a Latin noun is quite difficult. የላቲን ፡ የስም ፡ እርባታ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**decline** (vt.)

1. **አልተቀበለም**. They had to decline his invitation. ጥሪውን ፡ አለመቀበል ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው
2. **አልፈቀደም (አልተፈቀደም)**. He declined to discuss his plans with the reporter. ስለ ፡ እቅዱ ፡ ከዜና ፡ አጠናቃሪው ፡ ጋር ፡ ለመነጋገር ፡ አልፈቀደም
Request declined. የተጠየቀው ፡ አልተፈቀደም
3. **አረባ**. The teacher asked me to decline three nouns. ሦስት ፡ ስሞች ፡ እንዳረባ ፡ አስተማሪው ፡ ጠየቀኝ

**decline** (vi.)

1. **ቀነሰ**. His strength is declining rapidly. ጉልበቱ ፡ በፍጥነት ፡ እየቀነሰ ፡ ይሄዳል
2. **አቈለቈለ**. The hill declines to a fertile valley. ኮረብታው ፡ ወደ ፡ ለምለም ፡ ሸለቆ ፡ ያቈለቍላል
3. **ወደቀ**. Critics declare that morality is declining in this country. ተቺዎች ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ሞራል ፡ በመውደቅ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ይላሉ
4. **ሳይቀበል ፡ ቀረ**. We sent him an invitation, but he declined. ያደረግንለትን ፡ ጥሪ ፡ ሳይቀበል ፡ ቀረ
5. **አዘቀዘቀ**. The sun declined in the skies. ፀሐይዋ ፡ አዘቀዘቀች
6. **ዝቅ ፡ አለ**. The rating of this hotel has declined. የዚህ ፡ ሆቴል ፡ ደረጃ ፡ ዝቅ ፡ ብሏል

**decline** (n.) **ማነስ**

The decline in exports transmuted the economic life of the country. ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚላከው ፡ እቃ ፡ ማነስ ፡ ያገሪቱን ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሁኔታ ፡ ለወጠው
*The decline of the Roman Empire was due to many causes. የሮም ፡ መንግሥት ፡ የደከመው ፡ በብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ ነበር

**be on the decline**

1. **ዝቅ ፡ እያለ ፡ ሄደ**. Ivory sales are on the decline. የዝሆን ፡ ጥርስ ፡ ሽያጭ ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ሄዷል
2. **እየበረደ ፡ ሄደ**. The epidemic is on the decline. ተላላፊው ፡ በሽታ ፡ እየበረደ ፡ ሄደ

**there is a decline in** **ወረድ ፡ አለ**

There is a decline in prices. ዋጋ ፡ ወረድ ፡ ብሏል

**declivity, extreme ~** **ቀጥ ፡ ማለት**

The extreme declivity of the mountain makes climbing impossible. የተራራው ፡ ቀጥ ፡ ማለት ፡ ለመውጣት ፡ ያዳግታል

**decode**

*He learned to decode while assigned to the embassy. አምባሲው ፡ ውስጥ ፡ ሲሠራ ፡ በልዩ ፡ ምልክት ፡ የሚጻፈውን ፡ መልእክት ፡ መፍታት ፡ ተማረ

**decompose** (vt.) **ለያየ**

Heat decomposes certain chemical compounds. ሙቀት ፡ አንዳንድ ፡ የኬሚካል ፡ ውሑዶችን ፡ ይለያያቸዋል

**decompose** (vi.)

1. **ፈረሰ**. The flesh had decomposed, leaving only the bones. ሥጋው ፡ ፈርሶ ፡ አጥንቶቹ ፡ ብቻ ፡ ቀርተዋል
2. **ተለያየ**. The compound decomposes when it is exposed to sunlight. ውሑዱ ፡ ፀሐይ ፡ ሲመታው ፡ ይለያያል

**decomposition**

*Lead is the result of the decomposition of uranium. እርሳስ ፡ ዩራንየም ፡ ሲለያይ ፡ የሚገኝ ፡ ማዕድን ፡ ነው

**decorate**

1. **አስጌጠ ፤ አጌጠ**. They decorated the church with flowers. ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ በአበባ ፡ አስጌጡት
The gay young people were singing as they decorated the hall. ደስ ፡ ያላቸው ፡ ወጣቶች ፡ አዳራሹን ፡ በሚያጌጡበት ፡ ጊዜ ፡ ይዘፍኑ ፡ ነበር
2. **ሸለመ**. The general decorated four soldiers for bravery. ጄኔራሉ ፡ አራት ፡ ወታደሮችን ፡ ስለ ፡ ጀግንነታቸው ፡ ሸለማቸው

**decoration**

1. **ጌጥ**. The girl wore some sort of decoration on her dress. ልጃገረዲቱ ፡ በቀሚሷ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ጌጥ ፡ አድርጋለች
2. **ሽልማት**. What did he get the decoration for? ሽልማቱን ፡ በምን ፡ አገኘ ?

**decorations ጌጣጌጥ**

The decorations are not pretty. ጌጣጌጡ ፡ አያምርም

**decorative, ~ design ጌጥ**

This fabric has an interesting decorative design. ይህ ፡ ጨርቅ ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ጌጥ ፡ አለው

**decorative band ጥለት**

A decorative band is sewn to the edge of the cloth. በልብሱ ፡ ላይ ፡ ጥለት ፡ ተደርጎበታል

**decorator የቤት ፡ እቃ ፡ የሚያደራጅ**

The decorator will arrange your furniture to advantage. የቤት ፡ እቃ ፡ የሚያደራጀው ፡ የቤት ፡ እቃህን ፡ አሳምሮ ፡ ይደረድርልሃል

**decorous የጨዋ**

Only decorous behavior is suitable in the Emperor's presence. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ባሉበት ፡ ቦታ ፡ የጨዋ ፡ ምግባር ፡ ማሳየት ፡ ተገቢ ፡ ነው

**decoy** [ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ወፍ ፡ ወይም ፡ እንስሳ ፡ ወፎችን ፡ ወይም ፡ እንስሳዎችን ፡ ወጥመድ ፡ ወዳለበት ፡ ቦታ ፡ የምትስብ]

**decrease** (vt.) **ቀነሰ**

Decrease the dose of the medicine as you feel better! እየተሻለህ ፡ ሲሄድ ፡ የምትወስደውን ፡ መድኃኒት ፡ መጠን ፡ ቀንስ

**decrease** (vi.)

1. **ተቀነሰ**. Your hunger decreases as you eat. ስትበላ ፡ ረኀብህ ፡ እየተቀነሰ ፡ ይሄዳል
2. **አነሰ**. The birth rate increases while the death rate decreases. የሚወለዱቱ ፡ ቁጥር ፡ ሲጨምር ፡ የሚሞቱቱ ፡ እያነሰ ፡ ይሄዳል

**decrease** (n.) **መቀነስ**

Statistics show a decrease in the death rate in the last few years. እስታቲስቲክ ፡ ባለፉት ፡ ጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የሚሞቱ ፡ ሰዎችን ፡ ቁጥር ፡ መቀነስ ፡ ያሳያል

**there is a decrease ቀነሰ**

Toward night, there was a decrease of heat. ወደ ፡ ማታ ፡ የፀሐይ ፡ ሙቀት ፡ ይቀንስ ፡ ጀመር

**decree** (v.) **ደነገገ**

The government decreed that foreigners may not own land. መንግሥቱ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ መሬት ፡ እንዳይገዙ ፡ ደነገገ
*Fate decreed otherwise. ዕድል ፡ አይሁን ፡ ብሎታል

**decree** (n.) **ድንጋጌ**

The decree goes into effect tomorrow. ድንጋጌው ፡ ከነገ ፡ ጀምሮ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላል

**issue a decree ዐወጀ**

The Emperor issued a decree requiring all men over 45 to join the militia. ከአርባ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ ሁሉ ፡ ብሔራዊ ፡ ጦር ፡ እንዲገባ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዐወጁ
[See also 'legislative']

**decrepit ድቅቅ ፡ ያለ**

He is old and decrepit. ድቅቅ ፡ ያለ ፡ ሽማግሌ ፡ ነው

**decry** (decried)

1. **አቃለለ**. He decried the value of learning. የትምህርትን ፡ ዋጋ ፡ አቃለለ
2. **አወገዘ**. The minister decried gambling in all its forms. ማንኛውንም ፡ ዓይነት ፡ የቁማር ፡ ጨዋታ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አወገዙ

**dedicate**

1. **መርቆ ፡ ከፈተ**. The Emperor will dedicate the new airport. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አዲሱን ፡ የአውሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ መርቀው ፡ ይከፍታሉ
2. **መረቀ**. The patriarch will dedicate the new church. ፓትሪያርኩ ፡ አዲሱን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይመርቃሉ
3. **መደበ**. The ancient Greeks dedicated many shrines to their gods. ጥንታውያን ፡ ግሪኮች ፡ ላማልክታቸው ፡ ብዙ ፡ ቅዱሳን ፡ ስፍራዎች ፡ መድበው ፡ ነበር
4. **አዋለ**. He dedicated his life to the service of God. ሕይወቱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አገልግሎት ፡ አዋለ
5. **መታሰቢያ ፡ አደረገ**. The author dedicated his book to his wife. ደራሲው ፡ መጽሐፉን ፡ ለሚስቱ ፡ መታሰቢያ ፡ አደረገ

**deduce ተረዳ**

I deduce from your remarks that you disagree

with me. ከኔ ፡ ጋር ፡ አለመስማማትህን ፡ ካነጋገር
ህ ፡ እረዳለሁ

**deduct**

1. ቀነሰ. Deduct ten percent! ከመቶ ፡ ዐሥሩ
ን ፡ ቀንስ

2. አነሣ. Once you deduct your expenses, there is nothing left. ወጪህን ፡ ካነሣህለት ፡
ምንም ፡ አይተርፍ

**deduction**

1. ቅናሽ. After deductions from taxes, there was not much left. ለግብር ፡ ቅናሽ ፡ ከተደረገ ፡
በኋላ ፡ ብዙ ፡ አልተረፈውም

2. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮችን ፡ መመርመር. Detectives in stories solve crimes by deduction. የወንጀል ፡
መርማሪዎች ፡ በልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡
ለወንጀል ፡ መፍትሔ ፡ የሚያገኙት ፡ ልዩ ፡ ል
ዩ ፡ ነገሮችን ፡ በመመርመር ፡ ነው

*A deduction will be made for unexplained absences. ባልታወቀ ፡ ምክንያት ፡ ሲቀር ፡ ደሞዝ ፡
ይቀነስበታል

**deed**

1. ሥራ. Deeds are better than words. ከወሬ ፡
ሥራ ፡ ይሻላል

His deeds have glorified his name. የሠራው ፡
ሥራዎች ፡ ዝና ፡ አተረፉለት

2. ሙያ. The braggart told of his brave deeds in the war. ጉረኛው ፡ ሰው ፡ በጦርነቱ ፡
ላይ ፡ ስለፈጸማቸው ፡ የጀግንነት ፡ ሙያ ፡ አወራ

3. ጀብዱ. He performed many admirable deeds in the war. በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የሚያስደንቅ ፡
ጀብዱ ፡ ሠርቷል

4. ስመርስት. After I paid the owner, he gave me the deed to the land. ለባለንብረቱ ፡ ገንዘቡ
ን ፡ ከከፈልኩት ፡ በኋላ ፡ ስመርስቱን ፡ አዛወረ
ልኝ

[See also 'epic']

**deem** አመነ

He deemed it his duty to help. መርዳት ፡ ተ
ግባሩ ፡ መሆኑን ፡ አመነ

**deep** (adj.)

1. ጥልቅ. A deep lake is never covered with snow. ጥልቅ ፡ ሐይቅ ፡ በበረዶ ፡ ተሸፍኖ ፡ አያውቅም

2. ጎድጓዳ. The river flows through a deep gorge. ወንዙ ፡ በጎድጓዳ ፡ ገደልማ ፡ የወንዝ ፡ ሸለ
ቆ ፡ ውስጥ ፡ ይፈሳል

3. ወፍራም. He has a very deep voice. በጣም ፡
ወፍራም ፡ ድምፅ ፡ አለው

4. ጥብቅ. It is such a deep secret, I cannot find out anything about it. ጥብቅ ፡ ምስጢር ፡ ስለሆ
ነ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ለማወቅ ፡ አልችልም

5. ከባድ. The child was in such a deep sleep, he did not hear the noise. ሕፃኑ ፡ ከባድ ፡ እንቅ
ልፍ ፡ ስለወሰደው ፡ ጫጫታው ፡ አልተሰማውም ፡
ነበር

6. ደማቅ. I would like a deep red skirt. ደማቅ ፡
ቀይ ፡ ቀሚስ ፡ እፈልጋለሁ

7. የጎን ፡ ስፋት ፡ ያለው. This deep shelf is not suitable for my books. ይህ ፡ የጎን ፡ ስፋት ፡ ያ
ለው ፡ መደርደሪያ ፡ ለመጽሐፎቼ ፡ አይስማማም

**be deep (in)** ተዋጠ

He was deep in debt. በዕዳ ፡ ተውጦ ፡ ነበር

He is deep in thought all day long. ቀኑን ፡ ሙ
ሉ ፡ በሐሳብ ፡ እንደተዋጠ ፡ ነው

**be in deep water** መድረሻ ፡ ጠፋ(ው)

He has been in deep water ever since he stole the watch. ሰዓቱን ፡ ከሰረቀ ፡ ጀምሮ ፡ መድረሻ ፡
ጠፍቶታል

**deep** (adv.) ጠለቅ ፡ አድርጎ

The men dug deep before they found water.
ውኃ ፡ ከማግኘታቸው ፡ በፊት ፡ ጠለቅ ፡ አድርገው ፡
ቈፈሩ

*He studied deep into the night. ሲያጠና ፡ በ
ጣም ፡ አመሸ

[See also 'sleep']

**deepen** አርቆ ፡ ቈፈረ

They deepened the shallow pool. ቅርቡን ፡ ኩ
ሬ ፡ አርቀው ፡ ቈፈሩት

**deeply** በጥልቅ

His wife's death affected him deeply. የሚስቱ ፡
ሞት ፡ በጥልቅ ፡ ተሰምቶታል

**be deeply (in)** ተዋጠ

The tenant was deeply in debt. ጭሰኛው ፡ በዕዳ ፡
ተውጧል

**deer** አጋዘን

There are deer in this forest. በዚህ ፡ ጫካ ፡ ውስ
ጥ ፡ አጋዘን ፡ አለ

**deface** አበላሸ

They defaced the wall with ink. ግድግዳውን ፡
በቀለም ፡ አበላሹት

**defame** ስም ፡ አጠፋ

This article defames the candidates. ይህ ፡ ጽ
ሑፍ ፡ የተወዳዳሪዎቹን ፡ ስም ፡ ያጠፋል

**default** (v.) ሳያከብር ፡ ቀረ

He defaulted his contract. ውሉን ፡ ሳያከብር ፡
ቀረ

**default in** አቋረጠ
He defaulted in his payments on the loan. ብድር ፣ መክፈሉን ፣ አቋረጠ

**default** (n.), **be in ~** አስተላለፈ
He was in default by two payments. ክፍያውን ፣ ሁለት ፣ ጊዜ ፣ አስተላለፈ

**by default** በመቅረቱ
When the other team did not arrive, we won the game by default. ሌላው ፣ ቡድን ፣ ሳይመጣ ፣ በመቅረቱ ፣ እኛ ፣ አሸነፍን

**by sheer default** በግዴለሽነት
They lost their best client by sheer default. በግዴለሽነት ፣ ዋና ፣ ደንበኛቸውን ፣ አጡ

**defeat** (v.)
1. ድል ፣ አደረገ. King Theodore defeated Ras Ali more than once. አፄ ፣ ቴዎድሮስ ፣ ራስ ፣ ዓሊን ፣ ከአንዴም ፣ ሁለቴ ፣ በላይ ፡ ድል ፣ አድርገዋቸዋል
2. ድል ፣ ነሣ. The heavenly host will defeat the devils. የሰማይ ፣ መላእክት ፣ ሰይጣናትን ፣ ድል ፣ ይነሡዋቸዋል
3. አሸነፈ. The candidate defeated his opponent in the election. ተወዳዳሪው ፣ በምርጫው ፣ ባለጋራውን ፣ አሸነፈ
4. ውድቅ ፣ አደረገ. The conservatives joined forces with the clergy to defeat our plan. ሙሉና ፣ ፈጣን ፣ ለውጥ ፣ የማይፈልጉት ፣ የኛን ፣ እቅድ ፣ ውድቅ ፣ ለማድረግ ፣ ከካህናት ፣ ጋር ፣ ተባበሩ

**defeat** (n.)
1. ድል ፣ መሆን. The defeat of the enemy was announced over the radio. የጠላት ፣ ድል ፣ መሆን ፣ በሬድዮ ፣ ተነገረ
2. መሸነፍ. The coach was dejected after the defeat of his team. አሠልጣኙ ፣ በቡድኑ ፣ መሸነፍ ፣ ከባድ ፣ ሐዘን ፣ ወደቀበት

**suffer a defeat** ተሸነፈ
The enemy suffered a crushing defeat. ጠላት ፣ እንደማያንሰራራ ፣ ሆኖ ፣ ተሸነፈ

**defeated** (adj.) ድል ፣ የተመታ ፤ ድል ፣ የሆነ ፤ የተሸነፈ
The defeated army had to lay down arms. ድል ፣ የተመታው ፣ (ድል ፣ የሆነው ፤ የተሸነፈው) ፣ ጦር ፣ መሣሪያውን ፣ ማስረከብ ፣ ነበረበት

**be defeated**
1. ድል ፣ ሆነ. Ras Ali was defeated more than once. ራስ ፣ ዓሊ ፣ ከአንዴም ፣ ሁለቴ ፣ በላይ ፣ ድል ፣ ሆነው ፣ ነበር
2. ውድቅ ፣ ሆነ. The motion was defeated. ሐሳቡ ፣ ውድቅ ፣ ሆነ
3. ዋጋ ፣ ቢስ ፣ ሆነ. All our hopes were defeated. ተስፋችን ፣ ሁሉ ፣ ዋጋ ፣ ቢስ ፣ ሆነ

**defecate**
1. ቀዘነ. The child defecated on his bed. ልጁ ፣ እመኝታው ፣ ላይ ፣ ቀዘነ
2. እዳሪ ፣ ወጣ. The man defecated near the house. ሰውዬው ፣ እቤቱ ፣ አጠገብ ፣ እዳሪ ፣ ወጣ
3. ሜዳ ፣ ወጣች. The woman defecated near the house. ሴትዮዋ ፣ እቤቱ ፣ አጠገብ ፣ ሜዳ ፣ ወጣች

**defect** (v.) ከድቶ ፣ ገባ
Several of our people defected to the enemy. ከኛ ፣ ሰዎች ፣ አያሌዎቹ ፣ ከድተው ፣ ለጠላት ፣ ገቡ

**defect** (n.)
1. ጉድለት. There is a defect in this radio somewhere. ሬዲዮኑ ፣ አንድ ፣ ጉድለት ፣ አለው
Our system of education suffers from many defects. የትምህርት ፣ አሰጣጣችን ፣ ዘዴ ፣ ብዙ ፣ ጉድለት ፣ አለበት
2. እንከን. Her beauty is without defect. ለውበቷ ፣ እንከን ፣ አይወጣለትም

**defection** መኮብለል
His defection to East Germany was regarded as treasonable. ወደ ፣ ምሥራቅ ፣ ጀርመን ፣ መኮብለሉ ፣ ከከዳተኛነት ፣ ተቈጠረበት

**defective** የተበላሸ
This machine is defective and will not work. ይህ ፣ መኪና ፣ የተበላሸ ፣ ስለሆነ ፣ አይሠራም

**defector** ከዳተኛ
The defector sought refuge in a friendly embassy. ከዳተኛው ፣ በወዳጅ ፣ ኤምባሲ ፣ ውስጥ ፣ ጥገኝነት ፣ ጠየቀ

**defend**
1. ተከላከለ. The Ethiopians defended their land against the invader. ኢትዮጵያውያኖች ፣ አገራቸውን ፣ ከወራሪው ፣ ተከላከሉ
2. አስከበረ. Ethiopia will defend her territorial integrity. ኢትዮጵያ ፣ የግዛቶቿን ፣ አንድነት ፣ ታስከብራለች
3. ጠበቀ. The President takes the pledge to defend the constitution. ፕሬዚዳንቱ ፣ ሕገ ፣ መንግሥቱን ፣ ለመጠበቅ ፣ ቃል ፣ ይገባል
4. አስረዳ. He made a long speech defending his ideas. ሐሳቡን ፣ ለማስረዳት ፣ ረጅም ፣ ንግግር ፣ አደረገ

5. ተከራከረ(ለት). You will need a lawyer to defend you. የሚከራከርልህ ፡ ጠበቃ ፡ ያስፈልግ ሃል
6. በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሰጠ. Can you defend your absence? ለምን ፡ እንደቀረህ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ትሰጣለህ ?
*Can you defend your rudeness? ለምን ፡ ባለ ግህ ?

**defendant** ተከሳሽ
I am the defendant in this case. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ተ ከሳሹ ፡ እኔ ፡ ነኝ

**defender** ተከራካሪ
He is an ardent defender of human liberty. ጽኑ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ ተከራካሪ ፡ ነው

**defense**
1. ተከላካይ ፤ ምሽግ. Since the defenses were weak, the enemy was able to cross the border. ተከላካዮቹ ፡ ደከም ፡ ያሉ ፡ ስለነበሩ ፡ ጠላት ፡ ወሰኑን ፡ አልፎ ፡ ለመግባት ፡ ቻለ
Shock troops swarmed over our defenses. መቺ ፡ ኀይል ፡ ምሽጎቻችንን ፡ ወረሩት
2. መከላከያ. Vaccination is the best defense against smallpox. ክትባት ፡ ለፈንጣጣ ፡ ዋና ፡ መከላከያ ፡ ነው
What can you say in your defense? ምን ፡ መከላከያ ፡ አለህ ?
3. (= verbal noun) መከላከል. The civilians helped in the defense of their country. ሲቪሎቹ ፡ ሀገራቸውን ፡ በመከላከል ፡ ረዱ
4. የሚደግፍ ፡ ንግግር. He delivered a defense of the new taxation. አዲሱን ፡ ታክስ ፡ የሚደግ ፍ ፡ ንግግር ፡ አደረገ
5. (= verbal noun) ማስከበር. They fought in defense of liberty. ነጻነትን ፡ ለማስከበር ፡ ተዋጉ

**Ministry of Defense** የመከላከያ ፡ ሚኒስቴር
The Ministry of Defense is located in a new building. የመከላከያ ፡ ሚኒስቴር ፡ የሚገኘው ፡ ባ ንድ ፡ አዲስ ፡ ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ ነው
[See also 'attorney, speak']

**(be) defenseless** ራሱን ፡ ለመከላከል ፡ አይችልም
A baby is defenseless. ሕፃን ፡ ልጅ ፡ ራሱን ፡ ለ መከላከል ፡ አይችልም

**defensible** ሊከላከል ፡ የሚችልበት
The troops were placed in a defensible position. ሰራዊቱ ፡ ሊከላከል ፡ የሚችልበትን ፡ ስፍራ ፡ ያዘ

**defensive** (n.) መከላከል
The army is on the defensive. ሰራዊቱ ፡ በመ ከላከል ፡ ላይ ፡ ነው

**defensive** (adj.) የመከላከያ
The prime minister announced the purchase of defensive weapons. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የመከላከያ ፡ መሣሪያዎች ፡ መግዛታቸውን ፡ አስ ታወቁ

**defensive measure** መከላከያ
These fortifications are a defensive measure. እነዚህ ፡ ምሽጎች ፡ መከላከያ ፡ ናቸው

**defer** (deferred), vt. አስተላለፈ
I deferred my trip for a week. ጉዞዬን ፡ ላንድ ፡ ሳምንት ፡ አስተላለፍኩት
We defer questions of this kind to him. ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ጉዳይ ፡ ለሱ ፡ እናስተላልፋለን

**defer** (vi.) ተመራ
He always defers to his wife's wishes. ሁልጊዜ ፡ በሚስቱ ፡ ሐሳብ ፡ ይመራል

**be deferred**
1. ተላለፈ. The meeting was deferred to a later date. ስብሰባው ፡ ለሌላ ፡ ቀን ፡ ተላለፈ
2. ጊዜ ፡ ተሰጠ. For how long have you been deferred? ጊዜ ፡ የተሰጠህ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ?

**deference** አክብሮት
He always treats his elders with deference. ሁልጊዜም ፡ ታላላቆቹን ፡ በአክብሮት ፡ ይመለከታል

**defiance**
1. አለመበገር. Defiance of the enemy is an Ethiopian characteristic. ለጠላት ፡ አለመበገር ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ባሕርይ ፡ ነው
2. ከቁም ፡ ነገር ፡ አለመቍጠር. His complete defiance of danger was astonishing. አደጋን ፡ ፈ ጽሞ ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ አለመቍጠሩ ፡ የሚያስገር ም ፡ ነበር
3. መጣስ. His taking his men across the river was in defiance of orders. ወታደሮቹን ፡ ይዞ ፡ ወ ንዙን ፡ ማቋረጡ ፡ ትእዛዝን ፡ በመጣስ ፡ ነበር

**in defiance of** ቢሆንም
In defiance of the rainstorm, there was a big audience. ኀይለኛ ፡ ዝናብ ፡ ቢሆንም ፡ ብዙ ፡ አዳ ማጮች ፡ ነበሩ
*The boys climbed the cliff in defiance of all common sense. ልጆቹ ፡ ዓይናቸውን ፡ ጨፍነው ፡ አቀበቱን ፡ ወጡ

**defiant** እምቢተኛ
The father punished his son, but he remained just as defiant as before. አባትዬው ፡ ልጁን ፡ ቢቀጣውም ፡ እንደበፊቱ ፡ እምቢተኛ ፡ ሆኖ ፡ ቀረ

**remain defiant** አልበገርም ፡ አለ
Though he ran out of ammunition, the soldier

remained defiant. ምንም ፡ እንኳን ፡ ጥይት ፡ ቢ ያልቅበት ፡ ወታደሩ ፡ አልበገርም ፡ አለ

**deficiency**
1. እጥረት. We suffered from a deficiency of food. የምግብ ፡ እጥረት ፡ ችግር ፡ ደረሰብን
2. ጉድለት. The government is trying to remedy the deficiencies in the collection of taxes. በግብር ፡ አሰባሰብ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ጉድለት ፡ መንግሥት ፡ ለማሻሻል ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነው
**there is a deficiency of** ጐደለ
There is a deficiency of $50 in our club funds. ከክበባችን ፡ ገንዘብ ፡ ኃምሳ ፡ ብር ፡ ጐድሏል

**deficient** በቂ ፡ ያልሆነ
His deficient knowledge of algebra must be corrected before the exam. በቂ ፡ ያልሆነው ፡ የአልጀብራ ፡ ችሎታው ፡ ከፈተናው ፡ በፊት ፡ መ ቃናት ፡ አለበት
**be deficient in** ጐደለ
This bread is deficient in vitamins. ይህ ፡ ዳቦ ፡ ቪታሚን ፡ ይጐድለዋል
**mentally deficient** አእምሮው ፡ ደካማ ፡ የሆነ
A mentally deficient person lacks normal intelligence. አእምሮው ፡ ደካማ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ብ ልህነት ፡ ይጐድለዋል

**deficit**
1. እጥረት. There was a large deficit in the budget. ከፍ ፡ ያለ ፡ የባጀት ፡ እጥረት ፡ ነበር
2. ኪሳራ. We suffered a great deficit because the Suez Canal was closed. የስዌዝ ፡ በይ ፡ ስ ለተዘጋ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ኪሳራ ፡ ደረሰብን

**defile** (vt.)
1. አረከሰ. The barbarians defiled the church by using it as a stable. አረመኔዎቹ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያኑን ፡ ጋጥ ፡ አድርገው ፡ አረከሱት
2. በከለ. The refuse defiled the rivers. ቆሻ ሻው ፡ ወንዞቹን ፡ በከለ
**defile** (vi.) በሰልፍ ፡ ሄደ
The soldiers defiled to the barracks. ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ሰፈራቸው ፡ በሰልፍ ፡ ሄዱ

**define**
1. ወሰነ. Criminal law defines the different kinds of crimes. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወንጀሎችን ፡ ይወስናል
2. አስረዳ. Please listen while I define your duties. ተግባርህን ፡ ሳስረዳህ ፡ አዳምጠኝ
3. ፍች ፡ ሰጠ. Can you define the word "democracy"? ዲሞክራሲ ፡ የተባለውን ፡ ቃል ፡ ፍች ፡ ልትሰጥ ፡ ትችላለህ ?
4. ደነገገ. The constitution defines the succession to the throne. ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የዙፋኑ ን ፡ አወራረስ ፡ ይደነግጋል
5. ከለለ. The treaty defined the borders of the two countries. ውሉ ፡ የሁለቱን ፡ አገሮች ፡ ወሰን ፡ ከለለ
**be defined** ታየ
The tree is sharply defined in outline because the sky is light and the tree is dark. ሰማዩ ፡ ብሩህ ፡ ዛፉ ፡ ግን ፡ ጠቊር ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ ቅር ጹ ፡ ጐልቶ ፡ ይታያል

**definite**
1. ቊርጠኛ ፤ ቊርጥ ፤ የተቈረጠ. I want a definite answer. ቊርጠኛ ፡ መልስ ፡ እፈልጋለሁ
Give me a definite decision before Friday. ከዓርብ ፡ በፊት ፡ ቊርጥ ፡ ውሳኔ ፡ ንገረኝ
Mind now, this is not a definite promise. ልብ ፡ አድርግ ፤ ይህ ፡ የተቈረጠ ፡ ቃል ፡ አይደለም
2. የተወሰነ. I need a definite amount of money before starting the business. ንግዱን ፡ ከመጀመሬ ፡ በፊት ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ያስፈ ልገኛል
3. እርግጥ. Is it definite that he will take the job? ሥራውን ፡ እንደሚይዝ ፡ እርግጥ ፡ ነው ?
4. (= adv.) በተለይ. Have you anyone definite in mind for the job? ለሥራው ፡ በተለይ ፡ ያሰብከ ው ፡ ሰው ፡ አለ ?

**definite article** የተወሰነ ፡ መስተአምር
In English, the definite article is used more often than in Amharic. ካማርኛ ፡ ይልቅ ፡ በ እንግሊዝኛ ፡ የተወሰነ ፡ መስተአምር ፡ ይበልጡን ፡ ጊዜ ፡ ይነገራል

**definitely** በእርግጥ
I am definitely coming. በእርግጥ ፡ እመጣለሁ

**definition** ፍች
Look up the definition of "jet" in the dictionary! የጄትን ፡ ፍች ፡ በመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ው ስጥ ፡ ተመልከት
*The definition of the mayor's duties is prescribed by law. የከንቲባው ፡ ሥልጣን ፡ በሕ ግ ፡ ተወስኗል

**definitive**
1. (= adv.) በግልጽ. He clarified his stand with a definitive statement. አቋሙን ፡ በግልጽ ፡ አስረዳ
2. (= noun) ማሳረጊያ. He published the definitive biography of George Washington. የጆርጅ ፡ ዋሽንግተንን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ማሳረጊያ ፡ አ ሳተመ

*He made me a definitive offer of the job. ሥራውን ፡ እንደሚሰጠኝ ፡ አረጋገጠልኝ

**deflate**
1. አስተነፈሰ. The little boy deflated the tires of my car. ትንሹ ፡ ልጅ ፡ የመኪናዬን ፡ ጎማ ዎች ፡ አስተነፈሰብኝ
2. ዝቅ ፡ አደረገ. The rebuke deflated him. ግሣ ጼው ፡ ዝቅ ፡ አደረገው

**deflect** በሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ አስኬደ
A spectator deflected the ball. ከተመልካቾች ፡ አንዱ ፡ ኳሷን ፡ በሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ አስኬደ

**deform**
1. አበላሸ. The accident deformed his face. አደጋው ፡ ፊቱን ፡ አበላሸው
2. አጠፋ. Anger deformed his face. ንዴት ፡ መልኩን ፡ አጠፋው
3. አንሻፈፈ. Shoes that are too tight deform the feet. ጠባብ ፡ ጫማ ፡ እግር ፡ ያንሻፍፋል
4. አካለ ፡ ጐደሎ ፡ አደረገ. In cases where the drug was taken during pregnancy, it deformed the infants. በእርግዝና ፡ ጊዜ ፡ የሚወሰድ ፡ መድ ኃኒት ፡ ሕፃኑን ፡ አካለ ፡ ጐደሎ ፡ ያደርገዋል

**be deformed** ጠማማ ፡ ሆነ
The boy's foot is deformed, and so he cannot play games. የልጁ ፡ እግር ፡ ጠማማ ፡ ስለሆነ ፡ ሊጫወት ፡ አይችልም

**deformity** አካለ ፡ ጐደሎነት
His deformity prevented him from playing games. አካለ ፡ ጐደሎነቱ ፡ ስፖርት ፡ እንዳይጫ ወት ፡ አደረገው

**defraud** አጭበረበረ
The seller must not defraud the buyer. ሻጭ ፡ ገዢን ፡ ማጭበርበር ፡ የለበትም

**defray** ቻለ
Each passenger must defray his own expenses. እያንዳንዱ ፡ መንገደኛ ፡ የራሱን ፡ ወጪ ፡ መቻ ል ፡ አለበት

**deft** ቀልጣፋ
The fingers of a pianist must be deft. የፒያኖ ፡ ተጫዋች ፡ ጣቶቹ ፡ ቀልጣፋ ፡ መሆን ፡ አለባቸው

**(be) defunct** በሥራ ፡ ላይ ፡ አልዋለም
The treaty has been defunct for the last three years. ካለፈው ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ውሉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አልዋለም

**defy** (defied)
1. ጣሰ. If you defy the law, you will be punished. ሕጉን ፡ ብትጥስ ፡ ትቀጣለህ
2. ትእዛዙን ፡ ጣሰ. Despite threats, he continued to defy me. ባስፈራራውም ፡ እንኳን ፡ ትእዛዜን ፡ ከመጣስ ፡ አልተቈጠበም (or ትእ ዛዜን ፡ መጣሱን ፡ አልተወም)
3. ከቁም ፡ ነገር ፡ ሳይጥፈው ፡ ቀረ. The Ethiopians defied the Italian order to surrender. ኢት ዮጵያውያን ፡ እጃችሁን ፡ ስጡ ፡ የሚለውን ፡ የጣ ሊያንን ፡ ትእዛዝ ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ ሳይጥፉት ፡ ቀሩ
4. ተቃወመ. The boy defied his father's authority. ልጁ ፡ ያባቱን ፡ ትእዛዝ ፡ ተቃወመ
5. ተቋቋመ. His obstinate fever defied the doctor's attempt to cure it. የማይበገረው ፡ ትኩሳ ቱ ፡ ሐኪሙ ፡ ለማዳን ፡ ያደረገውን ፡ሙከራ ፡ ሁ ሉ ፡ ተቋቋመ
*They defied him to jump off the bridge. ከድልድዩ ፡ እዘላለሁ ፡ ቢል ፡ አታደርገው ፡ ብለ ው ፡ ገፋፉት
*The door defied all attempts to open it. በሩ ፡ በምንም ፡ መንገድ ፡ አልበገር ፡ አለ

**defy capture** አይበገርም
This strong fort defies capture. ይህ ፡ ጥብቅ ፡ ምሽግ ፡ አይበገርም

**degenerate** (v.) ተበላሸ
The morale of the soldiers degenerated, and they were unable to fight. የወታደሮቹ ፡ ሞራል ፡ ስለተበላሸ ፡ ለመዋጋት ፡ አልቻሉም

**(be) degenerate** መንፈስ ፡ ደካማ ፡ ሆነ
He denied that the young men of his generation were degenerate. የዘመኑ ፡ ወጣቶች ፡ መንፈስ ፡ ደካማ ፡ ናቸው ፡ የሚለውን ፡ አስተያየት ፡ አስተባበለ

**degrade** ዝቅ ፡ አደረገ
The appointment the minister received degraded him. የተሰጠው ፡ ሹመት ፡ ሚኒስትሩን ፡ ዝቅ ፡ አደረገው

**degree**
1. ደረጃ. Ras is a title of high degree. ራስ ፡ ከ ፍተኛ ፡ የማዕረግ ፡ ደረጃ ፡ ነው
His work has reached a high degree of excellence. ሥራው ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ደርሷል
3. ሁኔታ ፤ አኳኋን. Each of us, in varying degrees, has learned this for himself. እያንዳንዳችን ፡ በ ተለያየ ፡ ሁኔታ ፡ (አኳኋን) ፡ ይህን ፡ ለየራሳችን ፡ አጥንተነዋል
4. ዲግሪ. He received his degree at the University of California. ዲግሪውን ፡ ከካሊፎርኒያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አገኘ
Last night, the temperature dropped ten degrees. ትላንትና ፡ ማታ ፡ ያየሩ ፡ ሙቀት ፡ ባሥ ር ፡ ዲግሪ ፡ ዝቅ ፡ አለ

**by degrees** ቀስ ፡ በቀስ
By degrees, the lake gets warm enough to swim in. ቀስ ፡ በቀስ ፡ ሐይቁ ፡ ለዋና ፡ እስኪመች ፡ ድረስ ፡ ይሞቃል

**to a certain degree** በመጠኑ
To a certain degree, he is responsible. በመጠኑ ፡ እሱ ፡ ኀላፊ ፡ ነው

**to what degree** ምን ፡ ያህል
To what degree are you interested in reading? ማንበብ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ደስ ፡ ይልሃል ?

**deify** (deified) አመለከ
The Romans deified their emperors. ሮማውያን ፡ ንጉሦቻቸውን ፡ ያመልኩ ፡ ነበር

**deign**
*The governor deigned to grant us an audience. ገዢው ፡ እኛኑ ፡ መስሎ ፡ አነጋገረን
*He passed by without deigning to look at me. ክብሩን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲል ፡ ዘወር ፡ ብሎም ፡ ሳያየኝ ፡ አለፈ
*Would you deign to have dinner with us? ከኛ ፡ ጋር ፡ እራት ፡ ለመብላት ፡ ፈቃድዎ ፡ ቢሆን ?

**deity** (deities)
1. አምላክ (pl. አማልክት) ፤ ጣዖት. This book describes the deities of ancient Greece. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የጥንት ፡ ግሪክን ፡ አማልክት ፡ ያስረዳል
Many ancient peoples worshipped the sun as a deity. ብዙ ፡ የጥንት ፡ ሰዎች ፡ ፀሐይን ፡ እንደ ፡ ጣዖት ፡ ያመልኩ ፡ ነበር
2. አምላክነት. The deity of Christ is recognized by the Christians. የክርስቶስን ፡ አምላክነት ፡ ክርስቲያኖች ፡ ተቀብለውታል

**deject** ተስፋ ፡ አስቈረጠ
Such news dejects me. እንዲህ ፡ ያለ ፡ ወሬ ፡ ተስፋ ፡ ያስቈርጠኛል

**(be) dejected** ከባድ ፡ ሐዘን ፡ ወደቀ(በት)
The coach was dejected after the defeat of his team. አሠልጣኙ ፡ በቡድኑ ፡ መሸነፍ ፡ ከባድ ፡ ሐዘን ፡ ወደቀበት

**look dejected** ያዘነ ፡ ይመስላል
Why is she looking so dejected? ለምን ፡ እንደዚህ ፡ ያዘነች ፡ ትመስላለች ?

**delay** (vt.)
1. አስተላለፈ. We are going to delay the trip for a week. ጉዞውን ፡ ላንድ ፡ ሳምንት ፡ ልናስተላልፈው ፡ ነው
2. አዘገየ. The accident delayed him. አደጋው ፡ አዘገየው

**be delayed** ዘገየ
The trip was delayed because of fog. ጉዞው ፡ በጭጋጉ ፡ ምክንያት ፡ ዘገየ

**delay** (n.) መዘግየት
What is causing his delay? የመዘግየቱ ፡ ምክንያት ፡ ምንድን ፡ ነው ?

**be subject to delay** ተዘገየ
The planes are subject to delay when there is fog. ጭጋግ ፡ ሲሆን ፡ አውሮፕላኖች ፡ ይዘገያሉ

**without delay** ሳይዘገይ
Do it without delay! ሳትዘገይ ፡ አድርገው

**delegate** (v.)
1. ወከለ. He delegated the authority to his son during his absence. ባልነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ሥልጣኑን ፡ ለልጁ ፡ ወከለ
The children delegated her to buy the flowers. አበባውን ፡ እንድትገዛላቸው ፡ ልጆቹ ፡ ወከሏት
2. ላከ. He delegated his son to represent him at the conference. በስብሰባው ፡ ላይ ፡ እንዲወክለው ፡ ልጁን ፡ ላከው

**delegate** (n.) መልእክተኛ
The delegates will arrive tomorrow. መልእክተኞቹ ፡ ነገ ፡ ይገባሉ

**delegation**
1. መልእክተኞች. Will you receive this delegation? እነዚህን ፡ መልእክተኞች ፡ ትቀበላላችሁ ?
2. (= to delegate) ማከፋፈል. The delegation of duties to others is part of an executive's job. ኀላፊነትን ፡ ማከፋፈል ፡ የባለሥልጣን ፡ ተግባር ፡ ነው

**delete** ሰረዘ
The censor deleted several words. ሳንሱሩ ፡ ብዙ ፡ ቃላት ፡ ሰረዘ

**deleterious, have a ~ effect on** ጐዳ
Smoking has a deleterious effect on one's health. ማጨስ ፡ የሰውን ፡ ጤና ፡ ይጐዳል

**deliberate** (v.)
1. ተመካከረ. We were deliberating what to do. ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚገባ ፡ በመመካከር ፡ ላይ ፡ ነበርን
2. አሰላሰለ. I was deliberating where to put up my new picture. አዲሱን ፡ ሥዕሌን ፡ የት ፡ እንደምሰቅል ፡ አሰላስል ፡ ነበር

**deliberate** (adj.)
1. ጥንቁቅ. A minister should be deliberate in his speeches. ሚኒስትር ፡ በንግግሩ ፡ ጥንቁቅ ፡ መሆን ፡ አለበት

2. ሆን ፡ ብሎ ፡ የተደረገ. His excuse was a deliberate lie. የሰጠው ፡ ምክንያት ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ የተደረገ ፡ ውሸት ፡ ነበር
*The old man walked with deliberate steps. ሽማግሌው ፡ እየመጠነ ፡ ተራመደ

**deliberately** ሆን ፡ ብሎ ፤ ዐውቆ
I do not think he did it deliberately. ሆን ፡ ብሎ ፡ (ዐውቆ) ፡ የሠራው ፡ አይመስለኝም

**deliberation**
1. ውይይት. After much deliberation, they passed the bill. ከብዙ ፡ ውይይት ፡ በኋላ ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ አጸደቁት
2. ማውጣትና ፡ ማውረድ. The judge gave his decision after long deliberation. ዳኛው ፡ ከብዙ ፡ ማውጣትና ፡ ማውረድ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ሰጠ
3. ጥንቃቄ. The hunter aimed his gun with great deliberation. አዳኙ ፡ ጠመንጃውን ፡ በብዙ ፡ ጥንቃቄ ፡ አነጣጠረ

**delicacy** (delicacies)
1. ኰሳሳነት. The child's delicacy was a constant worry to his mother. እናቱ ፡ በልጁ ፡ ኰሳሳነት ፡ ያለማቋረጥ ፡ ትጨነቅ ፡ ነበር
2. ልስላሴ. The delicacy of a flower allows it to be easily damaged. አበባ ፡ በቀላሉ ፡ ሊጐዳ ፡ የሚችለው ፡ ልስላሴ ፡ ስላለው ፡ ነው
*The delicacy of a baby's skin makes it pleasant to touch. የሕፃን ፡ ገላ ፡ ለስላሳ ፡ ስለሆነ ፡ ሲዳስሱት ፡ ደስ ፡ ይላል

**delicate**
1. ሰልከክ ፡ ያለ. She has delicate features. ሰልከክ ፡ ያለ ፡ መልክ ፡ አላት
2. ብስክስክ. A spider's web is very delicate. የሸረሪት ፡ ድር ፡ በጣም ፡ ብስክስክ ፡ ነው
**be delicate** በቋፍ ፡ ላይ ፡ ነው
The international situation is delicate at present. ባሁን ፡ ጊዜ ፡ የዓለም ፡ ሁኔታ ፡ በቋፍ ፡ ላይ ፡ ነው
*Her health is very delicate. ታማሚ ፡ ናት

**delicious** ጣፋጭ
This is delicious candy. ይህ ፡ ጣፋጭ ፡ ከረሜላ ፡ ነው
**be delicious** በጣም ፡ ጣፈጠ
Just taste this! It's delicious. እስቲ ፡ ቅመሰው ፤ በጣም ፡ ይጣፍጣል

**delight** (vt.) አስደሰተ
Toys delight a child. አሻንጉሊቶች ፡ ሕፃንን ፡ ያስደስታሉ

**delight** (vi.) ተሰኘ
We delighted in our good fortune. በመልካም ፡ ዕድላችን ፡ ተሰኘን
**be delighted** ደስ ፡ አለ(ው)
I was delighted to see him. እሱን ፡ በማየቴ ፡ ደስ ፡ አለኝ

**delight** (n.) ደስታ
The boys were grinning with delight. ልጆቹ ፡ በደስታ ፡ ፈገግ ፡ ብለው ፡ ነበር
*To his great delight, he passed the exams. ፈተናውን ፡ በማለፉ ፡ ፈነጠዘ

**delightful** አስደሳች
We have had a delightful evening. አስደሳች ፡ ምሽት ፡ አሳለፍን

**delimit** ወሰነ
The chairman delimited the topic for discussion. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ የንግግሩን ፡ አርእስት ፡ ወሰነ

**delineate**
1. ከለለ. The commission delineated the boundaries of Somalia. ኮሚሲዮኑ ፡ የሱማሊያን ፡ ወሰን ፡ ከለለ
2. አስረዳ. He delineated the plan with great care. እቅዱን ፡ በከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ አስረዳ

**delinquency** (delinquencies) ወንጀል ፤ ጥፋት
Juvenile delinquency is widespread at present. በዛሬ ፡ ጊዜ ፡ የወጣት ፡ ልጆች ፡ ወንጀል ፡ ተስፋፍቷል
Corporal punishment deters delinquency among the young. ከአካል ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ቅጣት ፡ ወጣቶችን ፡ ከጥፋት ፡ ያርቃል
*His property was seized because of delinquency in paying taxes. ታክስ ፡ ሳይከፍል ፡ በመቅረቱ ፡ ንብረቱ ፡ ተያዘበት

**delinquent** (n.) ዱርዬ
The boy became a delinquent as a result of associating with bad companions. ልጁ ፡ ከመጥፎ ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ በመዋሉ ፡ ዱርዬ ፡ ሆነ
**delinquent** (adj.) ተግባሩን ፡ የማይፈጽም
Delinquent parents deserve punishment. የወላጅነት ፡ ተግባራቸውን ፡ የማይፈጽሙ ፡ ወላጆች ፡ ቅጣት ፡ ይገባቸዋል
*The owner lost his house when it was sold for delinquent taxes. ባለቤቱ ፡ ያለበትን ፡ ውዝፍ ፡ ግብር ፡ ሳይከፍል ፡ በመቅረቱ ፡ ቤቱ ፡ ተሸጠ
**become delinquent** ጊዜው ፡ ተላለፈ
His bill became delinquent. የሒሳቡ ፡ መክፈያ ፡ ጊዜው ፡ ተላልፏል

**(become) delirious**

1. አቃዠ(ው). The patient's temperature went up, and he became delirious. በሽተኛው ፡ ትኩሳቱ ፡ ስለበዛ ፡ ያቃዠዋል

2. የሚያደርገውን ፡ አጣ. She was delirious with joy. በደስታ ፡ ብዛት ፡ የምታደርገውን ፡ አጣች

**deliver**

1. አደረሰ. Please deliver these packages to my hotel. እነዚህን ፡ ጥቅሎች ፡ እሆቴሌ ፡ አድርስልኝ

2. ላከ (ተላከ). That will be delivered to you. ያ ፡ ላንተ ፡ ይላክልሃል

3. እቃ ፡ እቤት ፡ ድረስ ፡ አመጣ. This store delivers free of charge. ይህ ፡ መደብር ፡ ያለቅጥያ ፡ ዋጋ ፡ እቃ ፡ እቤት ፡ ድረስ ፡ ያመጣል

4. ዐደለ. The postman delivers letters. ፖስተኛው ፡ ደብዳቤዎችን ፡ ያድላል

5. አስተላለፈ. The telephone is an expedient way to deliver messages. መልእክትን ፡ ለማስተላለፍ ፡ ስልክ ፡ ምቹ ፡ የሆነ ፡ መንገድ ፡ ነው

6. ሰወረ. May God deliver us from all evil! እግዚአብሔር ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይሰውረን

7. ገላገለ. Deliver me from such tiresome people! እንደዚህ ፡ ካሉ ፡ ከሚሰለቹ ፡ ሰዎች ፡ ገላግለኝ

8. አሳልፎ ፡ ሰጠ. They delivered the fortress to the enemy only after a long siege. ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከተከበቡ ፡ በኋላ ፡ ምሽጉን ፡ ለጠላት ፡ አሳልፈው ፡ ሰጡ

9. ተገላገለ. She delivered exactly when the doctor had predicted she would. ዶክተሩ ፡ ትገላገላለች ፡ ባለው ፡ ሰዓት ፡ ተገላገለች

**deliver the baby** ሴትዮዋን ፡ አዋለደች

The midwife delivered the baby this morning. አዋላጇ ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ ሴትዮዋን ፡ አዋለደች

**be delivered** አርነት ፡ ወጣ

After many efforts, they were delivered from bondage. ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጥረት ፡ በኋላ ፡ ከባርነት ፡ አርነት ፡ ወጡ

[See also 'slavery, talk']

**delivery**

1. አቀራረብ. The delivery of his speech was admired by all. የንግግሩ ፡ አቀራረብ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ ተደነቀ

2. (= verb) ታደለ. There will be no delivery of mail on Sundays or holidays. እሑድ ፡ ወይም ፡ በበዓል ፡ ቀን ፡ ደብዳቤ ፡ አይታደልም

3. (= verb) አስረከበ. I will pay you on delivery. ስታስረክበኝ ፡ እከፍልሃለሁ

4. (= verb) ከፈለ. The captive was released after the delivery of his ransom. ምርኮኛው ፡ ቤዛውን ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ተለቀቀ

**delta** [ወንዝ ፡ ከውቅያኖስ ፡ ጋር ፡ በሚገናኝበት ፡ በደለል ፡ መከማቸት ፡ ምክንያት ፡ የሚፈጠር ፡ መሬት]

**delude oneself** ራሱን ፡ አሞኘ

He deludes himself with false hope. በከንቱ ፡ ተስፋ ፡ ራሱን ፡ ያሞኛል

**delude one into**

*His conceit deluded him into believing he was important. በእብሪቱ ፡ ተደልሎ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ ከማለት ፡ ደረሰ

**deluge** (v.) አጥለቀለቀ

The rain deluged the village. ዝናም ፡ መንደሩን ፡ አጥለቀለቀው

**deluge with** አወረደ(በት)

The audience deluged him with questions. አዳማጮቹ ፡ የጥያቄ ፡ መዓት ፡ አወረዱበት

**deluge** (n.)

1. ጐርፍ. A deluge flooded the city. ጐርፍ ፡ ከተማውን ፡ አጥለቀለቀው

2. የጥፋት ፡ ውኃ. After the deluge, Noah's ark came to rest on Mt. Ararat. ከጥፋት ፡ ውኃ ፡ በኋላ ፡ የኖኅ ፡ መርከብ ፡ በአራራት ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ቆመች

3. መዓት. A deluge of questions followed his talk. ከንግግሩ ፡ በኋላ ፡ የጥያቄ ፡ መዓት ፡ ወረደበት

**(be) deluged** (= deluge) ጐረፈ(በት)

+He was deluged with letters protesting his decision to close the school. ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ለመዝጋት ፡ ያደረገውን ፡ ውሳኔ ፡ የሚቃወሙ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ጐረፉበት

**delusion** ከንቱ ፡ ስሜት

His delusions of grandeur led him to disappointment. ከንቱ ፡ የትልቅነት ፡ ስሜቱ ፡ ከብስጭት ፡ ላይ ፡ ጣለው

**have a delusion** ዘላበደ

The insane man had a delusion that he was king. እብዱ ፡ ሰው ፡ ንጉሥ ፡ ነኝ ፡ እያለ ፡ ይዘላብድ ፡ ነበር

**delve** አጥብቆ ፡ ፈለገ

The scholar delved in many libraries for facts. ምሁሩ ፡ መረጃዎችን ፡ ለማግኘት ፡ ብዙ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ አጥብቆ ፡ ፈለገ

**demand** (v.)

1. ጠየቀ. He is demanding more money. ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ይጠይቃል

This work demands great patience. ይህ ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ ትዕግሥት ፡ ይጠይቃል
2. ወሰደ(በት). His business demanded his full time. ሥራው ፡ ጊዜውን ፡ በሙሉ ፡ ወሰደበት
3. አስገደደ. He demands that I tell him everything. ሁሉንም ፡ ነገር ፡ እንድነግረው ፡ ያስገድደኛል

**demand** (n.)
1. ፍላጎት. The library cannot supply the demand for books. ቤተ ፡ መጽሐፍቱ ፡ ለመጻሕፍት ፡ ያለውን ፡ ፍላጎት ፡ ሊያረካ ፡ አይችልም
2. ተፈላጊነት. There is a great demand for teachers in this country. በዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የመምህራን ፡ ተፈላጊነት ፡ ከፍተኛ ፡ ነው
3. የእቃ ፡ ተፈላጊነት. Value is relative to demand. ዋጋው ፡ እንደ ፡ እቃው ፡ ተፈላጊነት ፡ ነው
4. የሚጠይቀው ፡ ነገር. He is moderate in his demands. የሚጠይቀው ፡ ነገር ፡ መጠነኛ ፡ ነው
5. ይገባኛል ፡ የሚለው. The demands of the client could not be met. ደንበኛው ፡ ይገባኛል ፡ የሚለውን ፡ ለመፈጸም ፡ አይቻልም

**be in demand** ተፈለገ
He is in great demand as a speaker. በንግግር ፡ ዐዋቂነቱ ፡ በጣም ፡ የሚፈለግ ፡ ሰው ፡ ነው

**make demands on** ወሰደ(በት)
This job makes great demands on my time. ይህ ፡ ሥራ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜዬን ፡ ይወስድብኛል

**on demand** በተጠየቀ ፡ ጊዜ
Show this identification card on demand! ይህን ፡ መታወቂያ ፡ ወረቀት ፡ በተጠየቅህ ፡ ጊዜ ፡ አሳይ

**demarcate**
1. ከለለ. The surveyors demarcated the boundary between Ethiopia and Somalia. መሃንዲሶቹ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሱማሊያ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ወሰን ፡ ከለሉ
2. ተከለለ. I demarcated my land from his. መሬቴን ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ተከለልኩ

**demean** አቃለለ
You demean yourself by telling a lie. ውሸት ፡ በመናገር ፡ ራስህን ፡ ታቃልላለህ
*He demeans himself like a boor. የስድ ፡ አደግ ፡ ጠባይ ፡ አለው

**demented** እብድ
He is a poor, demented creature. እሱ ፡ ምስኪን ፡ እብድ ፡ ነው

**demilitarize** ከወታደር ፡ ነጻ ፡ አደረገ
The treaty will demilitarize a broad zone between the two countries. ስምምነቱ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ የሚገኘውን ፡ ሰፊ ፡ ስፍራ ፡ ከወታደር ፡ ነጻ ፡ ያደርጋል

**demise**
1. መጥፋት. The demise of ancient Rome did not mean the end of the Latin language. የሮም ፡ መጥፋት ፡ የላቲን ፡ ቋንቋ ፡ ማብቂያ ፡ አልነበረም
2. መሞቻ. Smoking will hasten the day of your demise. ማጨስ ፡ የመሞቻህን ፡ ቀን ፡ ያቀርበዋል

**demobilize** በተነ
After the war, the minister demobilized the troops. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ጦሩን ፡ በተነ

**democracy** (democracies) ዲሞክራሲ
Democracy allows people to share in choosing their leaders. ዲሞክራሲ ፡ ሕዝቡ ፡ መሪውን ፡ እንዲመርጥ ፡ ይፈቅድለታል

**demolish**
1. አወደመ. The explosion demolished the house. ፈንጂው ፡ ቤቱን ፡ አወደመው
2. ውድቅ ፡ አደረገ. The results of his research demolished many theories. የምርምሩ ፡ ውጤት ፡ ብዙ ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳቦችን ፡ ውድቅ ፡ አደረገ

**be demolished** ወደመ
Our hopes were demolished by his refusal. እምቢ ፡ በማለቱ ፡ ተስፋችን ፡ ወደመ

**demon** መንፈስ (pl.መናፍስት) ፤ ጋኔን
I do not believe in demons. በመናፍስት ፡ (በጋኔን) ፡ አላምንም

**demonstrate** (vt.)
1. አስረዳ. How would you demonstrate that the world is round? ዓለም ፡ ክብ ፡ መሆኗን ፡ እንዴት ፡ ታስረዳለህ ?
2. አሳየ. I will now demonstrate how the machine works. አሁን ፡ መሣሪያው ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠራ ፡ አሳያለሁ
He demonstrated his courage by his actions in battle. ጦርነቱ ፡ ላይ ፡ በፈጸመው ፡ ተግባር ፡ ጀግንነቱን ፡ አሳየ

**demonstrate** (vi.) ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ አደረገ
The students demonstrated against the war in Vietnam. ተማሪዎቹ ፡ የቪየትናምን ፡ ጦርነት ፡ በመቃወም ፡ ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ አደረጉ

**demonstration**
1. መግለጫ. A kiss is a demonstration of affection. መሳም ፡ የፍቅር ፡ መግለጫ ፡ ነው

2. ማስረጃ. The experiment was a clear demonstration that wood needs oxygen to burn. ዕንጨት ፡ ለመንደድ ፡ ኦክሲጂን ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ሙከራው ፡ ግልጽ ፡ ማስረጃ ፡ ነበር
3. ሰላማዊ ፡ ሰልፍ. The demonstration caused a riot. ሰላማዊው ፡ ሰልፍ ፡ ረብሻ ፡ አስነሣ

**give a demonstration** እንዴት ፡ እንደሚሠራ ፡ አሳየ
The salesman gave her a demonstration of the sewing machine. አሻሻጩ ፡ የስፌት ፡ መኪናው ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠራ ፡ አሳያት
[See also 'stage']

**demonstrative**
1. በጋለ ፡ ስሜቱ ፡ ያቀረበው. The girl's demonstrative greeting embarrassed her shy brother. በጋለ ፡ ስሜት ፡ ያቀረበችው ፡ ሰላምታ ፡ ዓይን ፡ አፋር ፡ ወንድሟን ፡ አሳፈረው
2. አመልካች. "This" and "that" are demonstrative pronouns. ይህና ፡ ያ ፡ አመልካች ፡ ተውላጠ ፡ ስሞች ፡ ናቸው

**demonstrator** ሰላማዊ ፡ ሰልፈኛ
The demonstrators abused the speakers with their shouting. ሰላማዊ ፡ ሰልፈኞቹ ፡ ተናጋሪዎችን ፡ በጩኸታቸው ፡ አወኳቸው

**demoralize**
1. አበላሸ. Habit-forming drugs demoralize people's character. ሱስ ፡ የሚያስይዙ ፡ መድኃኒቶች ፡ የሰዎችን ፡ ጠባይ ፡ ያበላሻሉ
2. ሞራል ፡ ሰበረ. An attack on the rear guard demoralized the army. የደጀኑ ፡ መጠቃት ፡ የጦሩን ፡ ሞራል ፡ ሰበረው

**demote** ዝቅ ፡ አደረገ ፤ ሻረ
He demoted him to director. ወደ ፡ ዲሬክተርነት ፡ ማዕረግ ፡ ዝቅ ፡ አደረገው
The Emperor demoted the prime minister. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩን ፡ ሻረው

**be demoted** ማዕረጉን ፡ ተገፈፈ
The corporal was demoted for insubordination. ዐሥር ፡ አለቃው ፡ ባለመታዘዙ ፡ ማዕረጉን ፡ ተገፈፈ

**demotion** በደረጃ ፡ ዝቅ ፡ መደረግ ፤ መሻር
His demotion was announced in the paper. በደረጃ ፡ ዝቅ ፡ መደረጉ ፡ በጋዜጣ ፡ ተገለጸ
When the news came out, everyone was surprised to hear of his demotion. የመሻሩ ፡ ወሬ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ተደነቀ

**demur** (demurred) አቅማማ
He demurs when he should act at once. ያኔውኑ ፡ መፈጸም ፡ ሲገባው ፡ ያቅማማል

**demure** ትሑት
Her demure behavior made her admired by all. ትሑት ፡ ጠባይዋ ፡ የሁሉን ፡ አድናቆት ፡ አትርፎላታል

**den**
1. [ትንሽና ፡ ምቹ ፡ የሆነች ፡ ለማንበቢያና ፡ ለመሥሪያ ፡ የምታገለግል ፡ ክፍል]
2. ዋሻ ፤ ጐሬ. Why venture into the lion's den? ያንበሳውን ፡ ዋሻ ፡ (ጐሬ) ፡ ምን ፡ አዳፈረን ?
They discovered a den of thieves. የሌባ ፡ ዋሻ ፡ አገኙ
3. ጉድጓድ. He found a den of foxes behind his house. ከቤቱ ፡ ጓሮ ፡ አንድ ፡ የቀበሮ ፡ ጉድጓድ ፡ አገኘ

**denial**
1. ማስተባበያ. The government issued a denial regarding the arrest of the ambassador. ስለ ፡ አምባሳደሩ ፡ መታሰር ፡ መንግሥት ፡ ማስተባበያ ፡ አወጣ
2. መካድ. I refuse to believe his denial that he did not take the money. ገንዘቡን ፡ አልወሰድኩም ፡ ብሎ ፡ መካዱን ፡ አልቀበለውም
3. አለመቀበል. His denial of our request seemed very rude. ጥያቄያችንን ፡ አለመቀበሉ ፡ ብልግና ፡ መሰለ

**denigrate** አጠፋ
He denigrated his opponent's good reputation. የተቃዋሚውን ፡ መልካም ፡ ስም ፡ አጠፋ

**denomination**
1. የሃይማኖት ፡ ወገን. The Protestant denomination includes the Presbyterians and Baptists. የፕሮቴስታንት ፡ የሃይማኖት ፡ ወገን ፡ ፕረስቢቴርያንና ፡ ባፕቲስትን ፡ ያጠቃልላል
2. ዋጋ ፤ ልኩን ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ. On the reverse of the coin, the denomination is stamped. በፍራንኩ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ዋጋው ፡ (ልኩን ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ) ፡ ታትሟል

**denote**
1. አመለከተ. An S.O.S. signal denotes distress. ኤስ ፡ ኦ ፡ ኤስ ፡ ምልክት ፡ ችግርን ፡ ያመለክታል
2. ማለት ፡ ነው. The word "stool" denotes a small chair without a back. « ብርጩማ » ፡ መደገፊያ ፡ የሌለው ፡ ትንሽ ፡ ወምበር ፡ ማለት ፡ ነው

**denounce**
1. አወገዘ. The minister denounced gambling. ሚኒስትሩ ፡ ቁማርን ፡ አወገዙ
2. ነቀፈ. He made a fiery speech denouncing

fascism. የፋሽስትን ፡ እምነት ፡ በመንቀፍ ፡ ጎይ ለኛ ፡ ንግግር ፡ አደረገ
3. በመንገር ፡ አጋለጠ. He denounced his own brother to the police as a spy. ወንድሙ ፡ ሰላ ይ ፡ መሆኑን ፡ ለፖሊስ ፡ በመንገር ፡ አጋለጠው

**dense** ጥቅጥቅ ፡ ያለ
We drove through a dense fog. ጥቅጥቅ ፡ ባለ ው ፡ ጭጋግ ፡ ውስጥ ፡ ነዳን

**densely**
*This area is densely populated. ይህ ፡ ቀበሌ ፡ በ ጣም ፡ ሕዝብ ፡ ይበዛዋል

**density** ጥቅጥቅ ፡ ማለት
The density of the forest prevented us from seeing more than a little way ahead. የጫካው ፡ ጥቅጥቅ ፡ ማለት ፡ ራቅ ፡ አድርገን ፡ እንዳናይ ፡ ከለከለን

**dent** (v.) ጠረመሰ
The impact dented the fender of the automobile. ግጭቱ ፡ የመኪናውን ፡ ፈረፋንን ፡ ጠረ መሰው

**be dented** ተሰረጎደ
That table was dented in moving. ጠረጴዛው ፡ ሲጓጓዝ ፡ ተሰረጎደ

**dent** (n.), **make (dents) in** አጎደጎደ
Bullets had made dents in the steel helmet. ጥይት ፡ የብረት ፡ ባርኔጣውን ፡ አጎድጉዶታል

**not make a dent** ነገሬም ፡ አላለው
The doctor told him to stop smoking, but it didn't make a dent. ሐኪሙ ፡ ሲጃራ ፡ ማጨስ ፡ እንዲያቆም ፡ ቢነግረው ፡ ነገሬም ፡ አላለው

**dental** የጥርስ
There is no dental clinic in this village. በዚህ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ የጥርስ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ የለም

**dentist** (የ)ጥርስ ፡ ሐኪም
I took my sister to the dentist because she had a toothache. እኅቴ ፡ ጥርሷን ፡ ስላመማት ፡ ወደ ፡ ጥርስ ፡ ሐኪም ፡ ወሰድኳት

**denude** ባዶውን ፡ አስቀረው
The storm completely denuded the trees. ኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ ዛፎቹን ፡ ባዶዋቸውን ፡ አስ ቀራቸው

**denunciation** (= to denounce) ማሳጣት
The candidate's denunciation of his opponent consisted of insults and lies. እጩው ፡ ተወዳዳሪ ፡ ተቀናቃኙን ፡ ለማሳጣት ፡ የሰነዘረው ፡ ሁሉ ፡ ስድብ ና ፡ ውሸት ፡ ነበር

**deny** (denied)
1. ካደ. He denied his own signature. የገዛ ፡ ራሱን ፡ ፊርማ ፡ ካደ
The prisoner denied the charges against him. እስረኛው ፡ የተከሰሰበትን ፡ ወንጀል ፡ ካደ
2. አልተቀበለም. The guard denied his request. ዘበኛው ፡ ጥያቄውን ፡ አልተቀበለውም
3. አስተባበለ. He denied that the young men of his generation were degenerate. የዘመኑ ፡ ወ ጣቶች ፡ መንፈስ ፡ ደካማ ፡ ናቸው ፡ የሚለውን ፡ አስተያየት ፡ አስተባበለ
4. ነፈገ. He denied them the opportunity to go to college. ኮሌጅ ፡ የመግባትን ፡ ዕድል ፡ ነፈጋቸው

**be denied** ተከለከለ
The appeal was denied. ይግባኙ ፡ ተከለከለ

**depart**
1. ሄደ. He will depart in a short time. በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ይሄዳል
2. ተለየ. The new method departs from the old in several respects. አዲሱ ፡ ዘዴ ፡ ከድሮው ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ይለያል

**depart from** ለወጠ
He departed from his usual way of working. የተለመደ ፡ የአሠራር ፡ ዘዴውን ፡ ለወጠ

**departed** (n.) ሟች
After a person dies, it is customary for the priest to pray for the soul of the departed. አንድ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ቄስ ፡ ለሟቹ ፡ ነ ፍስ ፡ መጸለዩ ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው

**department** ክፍል
In which department of the store does he work? በመደብሩ ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ ይሠራል ?
*That sort of thing is not in my department. እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ እኔን ፡ አይመለከትም

**department store** መደብር
The department store is closed. መደብሩ ፡ ተ ዘግቷል

**departure**
1. መሄድ. His departure was unexpected. መሄዱ ፡ ያልታሰበ ፡ ነበር
2. መነሻ. The bulletin lists the arrivals and departures of all buses. ማስታወቂያው ፡ የአውቶ ቡሶቹን ፡ ሁሉ ፡ መድረሻና ፡ መነሻ ፡ ይዘረዝራል

**be a departure from** ከ - - የወጣ ፡ ነው
To bury the dead the same day they died is a departure from our old customs. ሙታንን ፡ የ ዕለቱ ፡ ዕለት ፡ መቅበር ፡ ከጥንት ፡ ልማድ ፡ የወ ጣ ፡ ነው

**depend (on)**

1. ተማመነ. Can I depend on this airport schedule or is it an old one? በዚህ ፡ የአውሮፕላን ፡ ፕሮግራም ፡ ልተማመን ፡ እችላለሁ ፡ ወይስ ፡ የቆየ ፡ ነው ?

I depend on my friend to help me. ጓደኛዬ ፡ እንደሚረዳኝ ፡ እተማመንበታለሁ

2. ተመሠረተ. A man's dignity depends on his character. የሰው ፡ ልጅ ፡ ክብሩ ፡ በጠባዩ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው

*Good health depends on good food. መልካም ፡ ምግብ ፡ የመልካም ፡ ጤንነት ፡ መሠረት ፡ ነው

*That depends on the circumstances. እንደ ፡ ሁኔታው ፡ ነው

**it all depends** እንደ ፡ ሁኔታው ፡ ነው

I may go to Ethiopia or I may not; it all depends. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እሄድ ፡ ወይም ፡ አልሄድ ፡ ይሆናል ፤ እንደ ፡ ሁኔታው ፡ ነው

**dependable** ታማኝ

A dependable friend will help you in time of difficulty. ታማኝ ፡ ጓደኛ ፡ በችግር ፡ ጊዜ ፡ ይረዳሃል

**dependency** (dependencies) ጥገኛ

The Virgin Islands is a dependency of the United States. የቨርጂን ፡ ደሴቶች ፡ የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ጥገኛ ፡ ናት

**(be) dependent on**

1. ተመሠረተ. A farmer's success is dependent on having the right kind of weather for his crops. ያንድ ፡ ገበሬ ፡ የሰብል ፡ ማማር ፡ በተስማሚ ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው

2. በ - - ትከሻ ፡ ላይ ፡ ኖረ. A child is dependent on its parents for food and clothing. ልጅ ፡ ልብሱንና ፡ ምግቡን ፡ ለማግኘት ፡ በወላጆቹ ፡ ትከሻ ፡ ላይ ፡ መኖር ፡ አለበት

3. የሱን ፡ እጅ ፡ እያየ ፡ ኖረ. I'm financially dependent on him. በገንዘብ ፡ በኩል ፡ የሱን ፡ እጅ ፡ እያየሁ ፡ እኖራለሁ

4. ተወሰነ. Our trip is dependent on the weather. ጉዟችን ፡ የሚወሰነው ፡ ባየሩ ፡ ሁኔታ ፡ ነው

**depict**

1. ገለጸ. The book depicted life in Tibet. መጽሐፉ ፡ በቲቤት ፡ ያለውን ፡ ኑሮ ፡ ገለጸ

2. አሳየ. The big painting depicts Christ's crucifixion. ትልቁ ፡ ሥዕል ፡ የክርስቶስን ፡ ስቅለት ፡ ያሳያል

**deplete** ጨረሰ

Illness depleted his strength. ሕመም ፡ ጉልበቱን ፡ ጨረሰው

A disease depleted the lake of fish. በሽታ ፡ የሐይቁን ፡ ዓሣ ፡ ጨረሰ

**be depleted** በጣም ፡ ተቀነሰ

Our resources in men have been depleted by war. የሰው ፡ ኀይላችን ፡ በጦርነት ፡ በጣም ፡ ተቀንሷል

**deplorable**

1. አሳዛኝ. This was a deplorable accident. ይህ ፡ አሳዛኝ ፡ አደጋ ፡ ነበር

2. የሚያስጠላ. This room is in deplorable order. ይህ ፡ ክፍል ፡ በሚያስጠላ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነው

You have deplorable manners. የሚያስጠላ ፡ ጠባይ ፡ አለብህ

3. አስከፊ. We must all share the blame for this deplorable condition. ለዚህ ፡ አስከፊ ፡ ሁኔታ ፡ ሁላችንም ፡ ተወቃሾች ፡ ነን

**deplore**

1. አዘነ. We deplore the accident. ስለ ፡ አደጋው ፡ እናዝናለን

2. የተሰማውን ፡ ቅሬታ ፡ ገለጸ. The government deplored the mass demonstrations. ስለተደረገው ፡ ትልቅ ፡ ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ መንግሥቱ ፡ የተሰማውን ፡ ቅሬታ ፡ ገለጸ

**deploy** በየወገኑ ፡ አሰማራ

The general deployed the troops for a charge. ጄኔራሉ ፡ ጠላትን ፡ ለማጥቃት ፡ እንዲመች ፡ ወታደሮቹን ፡ በየወገኑ ፡ አሰማራ

**depopulate** የ - - - ሕዝብ ፡ ማብዛት ፡ ጨረሰ

A plague almost depopulated Europe in the Middle Ages. በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ወረርሽኝ ፡ ያውሮፓን ፡ ሕዝብ ፡ ማብዛት ፡ ሊጨርሰው ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር

**deport** ካገር ፡ አስወጣ

The government deported the spy. መንግሥቱ ፡ ሰላዩን ፡ ካገር ፡ አስወጣው

**deport oneself**

*John deports himself like a gentleman. ዮሐንስ ፡ የጨዋ ፡ ጠባይ ፡ አለው

**depose**

1. የምስክርነት ፡ ቃሉን ፡ ሰጠ. He deposed that he had seen the prisoner on the day of the murder. የነፍስ ፡ ግዳዩ ፡ በተፈጸመ ፡ ዕለት ፡ እስረኛውን ፡ አይቼዋለሁ ፡ ብሎ ፡ የምስክርነት ፡ ቃሉን ፡ ሰጠ

2. ከዙፋን ፡ አወረደ. In Greece, the radical party deposed the king. በግሪክ ፡ አገር ፡ ፍጹም ፡ ለውጥ ፡ ፈላጊው ፡ ክፍል ፡ ንጉሡን ፡ ከዙፋን ፡ አወረደው

3. ከሥልጣን ፡ አወረደ. The people deposed the dictator. ሕዝቡ ፡ አምባ ፡ ገነኑን ፡ ከሥልጣኑ ፡ አወረደው

**deposit** (v.)

1. አስቀመጠ. He deposited the books on the desk. መጽሐፎቹን ፡ በጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ አስቀመጠ
I will have to deposit some money at the bank. ጥቂት ፡ ገንዘብ ፡ እባንክ ፡ ማስቀመጥ ፡ አለብኝ
2. አከማቸ ፤ ከመረ. The flood deposited a layer of mud in the streets. ጐርፉ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ደለል ፡ አከማቸ ፡ (ከመረ)

**deposit** (n.)

1. መያዣ. I had to pay five cents deposit for the bottle. ለጠርሙሱ ፡ መያዣ ፡ አምስት ፡ ሳንቲም ፡ መክፈል ፡ ነበረብኝ
2. ዝቃጭ. There are mineral deposits in the Congo. በኮንጎ ፡ የማዕድን ፡ ዝቃጭ ፡ አለ
*A deposit of jewels was stolen from the hotel safe. ሆቴሉ ፡ ካዝና ፡ ውስጥ ፡ የተቀመጠው ፡ አልማዝ ፡ ተሰረቀ
*Potash is obtained from deposits in the desert. ፖታሽ ፡ ከበረሃ ፡ ውስጥ ፡ ተከማችቶ ፡ ይገኛል

**date of deposit** ገንዘብ ፡ የተቀመጠበት ፡ ጊዜ
Interest is reckoned from the date of deposit. ወለዱ ፡ የሚታሰበው ፡ ገንዘቡ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ጊዜ ፡ እንሥቶ ፡ ነው

**make a deposit** አስቀመጠ
I still have to make a deposit at the bank. አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ገንዘብ ፡ እባንክ ፡ ማስቀመጥ ፡ አለብኝ
[See also 'mud']

**deposition** በጽሑፍ ፡ ያቀረበ ፡ የምስክርነት ፡ ቃል.
His deposition was not accepted by the judge. በጽሑፍ ፡ ያቀረበውን ፡ የምስክርነት ፡ ቃሉን ፡ ዳኛው ፡ አልተቀበለውም

**give a deposition** ቃሉን ፡ በጽሑፍ ፡ ሰጠ
He could not attend the trial, so he gave a deposition. ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ ስላልቻለ ፡ ቃሉን ፡ በጽሑፍ ፡ ሰጠ

**depository** ማስቀመጫ
The hotel's depository for valuables is located behind the reception desk. ሆቴሉ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የውድ ፡ እቃዎች ፡ ማስቀመጫ ፡ እንግዳ ፡ መቀበያው ፡ ጠረጴዛ ፡ ኋላ ፡ ነው

**depot** ግምጃ ፡ ቤት
A depot for automatic weapons is next to the police station. የአውቶማቲክ ፡ መሣሪያዎች ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ከፖሊስ ፡ ጣቢያው ፡ ቀጥሎ ፡ ነው

**deprave** አበላሸ
Drinking too much alcohol depraves a person's character. የሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ በብዛት ፡ መጠጣት ፡ የሰውን ፡ ጠባይ ፡ ያበላሻል

**depraved** ነውረኛ
The newspaper reported on the depraved criminal. ጋዜጣው ፡ ስለ ፡ ነውረኛው ፡ ወንጀለኛ ፡ አተተ

**deprecate** አንኳሰሰ
Some people deprecate modern art. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ዘመናዊ ፡ ሥዕልን ፡ ያንኳስሳሉ

**depreciate** (vt.) ዝቅ ፡ አደረገ
The government depreciated its currency. መንግሥት ፡ የሀገሪቱን ፡ የገንዘብ ፡ ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ አደረገ

**depreciate** (vi.) ዋጋው ፡ ቀነሰ
A house depreciates rapidly if not kept in repair. ቤት ፡ በየጊዜው ፡ ካልታደሰ ፡ ዋጋው ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ይቀንሳል

**depreciate in value** ዋጋውን ፡ ቀነሰ
Money depreciates in value every year. በየዓመቱ ፡ ገንዘብ ፡ ዋጋውን ፡ ይቀንሳል

**depress**

1. ቅር ፡ አሰኘ ፤ አሳዘነ. His letters always depress me. ደብዳቤው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ቅር ፡ ያሰኘኛል
The news he received today depressed him. ዛሬ ፡ የሰማው ፡ ወሬ ፡ አሳዘነው
2. ተጫነ. Depress the gas pedal slowly! የቤንዚን ፡ መስጫውን ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ ተጫነው
3. አቀዘቀዘ. High tariffs have depressed world trade. ከፍተኛ ፡ ቀረጥ ፡ የዓለምን ፡ ንግድ ፡ አቀዝቅዞታል
4. አዘበጠ. The heavy trucks depressed the road. ከባዶቹ ፡ መኪናዎች ፡ መንገዱን ፡ አዘበጡት

**(be) depressed** አዘነ
He has been very depressed. በጣም ፡ አዝኖ ፡ ነበር

**depressing** አስከፊ
His very presence is depressing. እዚህ ፡ መገኘቱ ፡ ብቻ ፡ አስከፊ ፡ ነው

**depression**

1. ጉድጓድ. After the rain, every depression in the road was filled with water. ከዝናብ ፡ በኋላ ፡ በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ጉድጓዶች ፡ ሁሉ ፡ ውኃ ፡ ቋጥረው ፡ ነበር
2. ስርጉድ ፡ ስፍራ. Lake Assal is located in

a large depression in the Rift Valley. የአሳል ፡ ሐይቅ ፡ በታላቁ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኝ ፡ ስርጉድ ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ነው
3. ክፉ ፡ ቀን. We lost all our money in the depression. ገንዘባችንን ፡ ሁሉ ፡ በክፉ ፡ ቀን ፡ ጨረስን

**a fit of depression** ብስጭት ፤ ተስፋ ፡ መቍረጥ
He committed suicide in a fit of depression. ከብስጭት ፡ የተነሣ ፡ (ተስፋ ፡ በመቍረጥ) ፡ ራሱን ፡ ገደለ

**cause a depression** አዘበጠ
The heavy weight of sand caused a depression in the roof of the house. ያሸዋው ፡ ክብደት ፡ የቤቱን ፡ ጣራ ፡ አዘበጠው

## deprive
1. ከለከለ. I wouldn't want to deprive you of your cigarettes. ሲጃራህን ፡ ልከለክልህ ፡ አልፈልግም
2. አስቀረ(በት). I hope this won't deprive me of your company. ያንቺን ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ መሆን ፡ እንደማያስቀርብኝ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ
3. ዘጋ(በት). The world deprived Ethiopia of her chance to export coffee. ዓለም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ቡና ፡ ለመላክ ፡ ያላትን ፡ ዕድል ፡ ዘጋባት

**be deprived of**
1. ተገፈፈ. They were deprived of all their rights. መብታቸውን ፡ ሁሉ ፡ ተገፈዋል
2. ተነጠቀ. The student was deprived of his books and couldn't study. ተማሪው ፡ መጽሐፎቹን ፡ ሁሉ ፡ ስለተነጠቀ ፡ ሊያጠና ፡ አልቻለም

## depth ጥልቀት
The depth of this lake has never been measured. የዚህ ፡ ሐይቅ ፡ ጥልቀት ፡ ተለክቶም ፡ አያውቅ
*The depth of his love led him to commit suicide when his wife died. ለሚስቱ ፡ የነበረው ፡ ፍቅር ፡ የጠለቀ ፡ ስለነበር ፡ በሞተች ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ ገደለ

**from the depth of my heart** ከልብ
I thank you from the depth of my heart. ከልብ ፡ አመሰግንሃለሁ

**in depth** በጥልቅ
He made a survey in depth of the economic situation. የኤኮኖሚውን ፡ ሁኔታ ፡ በጥልቅ ፡ መረመረ

## deputation እንደራሴ
Our neighborhood sent a deputation to the mayor to ask for street repairs. ሰፈራችን ፡ መንገዶቹ ፡ እንዲጠገኑ ፡ ወደ ፡ ከንቲባው ፡ እንደራሴ ፡ ላከ

## deputy (deputies) ምክትል
I am the chief here and he is my deputy. ዋናው ፡ ሹም ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ እሱ ፡ ደግሞ ፡ ምክትሌ ፡ ነው

**deputy minister** ምክትል ፡ ሚኒስትር
The deputy minister of agriculture will visit our school. የእርሻ ፡ ምክትል ፡ ሚኒስትር ፡ ትምህርት ፡ ቤታችንን ፡ ይጐበኛል

## derail (vt.) የሐዲዱን ፡ አቅጣጫ ፡ ለወጠ
The enemy derailed the train. ጠላት ፡ የሐዲዱን ፡ አቅጣጫ ፡ ለወጠው

**be derailed** ሐዲዱን ፡ ለቆ ፡ ወጣ
The switch was left open, and the train was derailed. የሐዲዱ ፡ መዝጊያ ፡ ክፍት ፡ ስለነበር ፡ ባቡሩ ፡ ሐዲዱን ፡ ለቆ ፡ ወጣ

## derange አናወጠ
The war deranged his mind. ጦርነቱ ፡ አእምሮውን ፡ አናወጠው

## derangement
1. መቃወስ. The derangement of the schedule is caused by the hijacking. የፕሮግራሙ ፡ መቃወስ ፡ የደረሰው ፡ በአውሮፕላኑ ፡ መጠለፍ ፡ የተነሣ ፡ ነው
2. የአእምሮ ፡ መናወጥ. His derangement is caused by the death of his wife. የአእምሮው ፡ መናወጥ ፡ ከሚስቱ ፡ መሞት ፡ የተነሣ ፡ ነው

## derelict
1. ቸልተኛ. He is always derelict in his duty and you cannot rely on him. ሁልጊዜ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ቸልተኛ ፡ ስለሆነ ፡ ልትተማመንበት ፡ አትችልም
2. ሰዎች ፡ የጣሉት. A derelict ship is adrift off the coast. ሰዎች ፡ የጣሏት ፡ መርከብ ፡ በጠረፉ ፡ አቅራቢያ ፡ ትዋልል ፡ ነበር

## deride አፌዘ
The boys derided him for his vanity. በግብዝነቱ ፡ ልጆቹ ፡ አፌዙበት

## derision ፌዝ
Children dread the derision of their playmates. ልጆች ፡ በጓደኞቻቸው ፡ ፌዝ ፡ በጣም ፡ ይፈራሉ

## derivation, ~ of words ሥርወ ፡ ቃላት
This dictionary gives the derivation of words. ይህ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሥርወ ፡ ቃላትን ፡ ይገልጻል
*This is a tune of Turkish derivation. ይህ ፡ ዜማ ፡ የመነጨው ፡ ከቱርክ ፡ ነው

**derive** አገኘ

He has not derived much benefit from his studies. ከትምህርቱ ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ አላገኘም
*From which root do you derive this verb? የግሡ ፡ ሥር ፡ ምንድነው ?

**be derived** ተወረሰ

Many Amharic words are derived from Geez. ብዙ ፡ ያማርኛ ፡ ቃላት ፡ የተወረሱት ፡ ከግዕዝ ፡ ነው

**derogatory** የሚነካ

He made remarks that are derogatory to my reputation. ስሜን ፡ የሚነካ ፡ ነገር ፡ ተናገረ

**make derogatory remarks** አንቋሾ ፡ ተናገረ

He made derogatory remarks about the quality of the food. ስለ ፡ ምግቡ ፡ አንቋሾ ፡ ተናገረ

**descend**

1. ወረደ. He descended the mountain. ተራራውን ፡ ወረደ
2. ፈሰሰ. The river descends to the sea. ወንዙ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ይፈሳል
3. ተንከባሎ ፡ ወረደ. These stones have apparently descended from the mountain tops. እነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ ከተራራው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ተንከባለው ፡ የወረዱ ፡ ይመስላሉ
4. ዝቅ ፡ አለ. Prices have descended during the past month. ባለፈው ፡ ወር ፡ የእቃዎች ፡ ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ነበር
5. ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ መጣ. This custom descends from the ancient Greeks. ይህ ፡ ልማድ ፡ ከጥንታውያን ፡ ግሪኮች ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፡ ነው
6. ተላለፈ. This house will descend to my son. ይህ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ልጄ ፡ ይተላለፋል

**descend to** ራሱን ፡ አቀለለ

He would never descend to cheating. በማታለል ፡ ራሱን ፡ አያቀልም

**descend upon** ወረረ

The bandits descended upon the village at night. ሽፍቶቹ ፡ መንደሩን ፡ ሌሊት ፡ ወረሩት

**descendant** ተወላጅ

He is not a direct descendant. የዋናው ፡ ግንድ ፡ ተወላጅ ፡ አይደለም
*He is a descendant of the royal family. የነገሥታት ፡ ዘር ፡ አለው

**be a descendant** ተወለደ

That man is a direct descendant of Emperor Menilek. ያ ፡ ሰው ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በቀጥታ ፡ ይወለዳል

**descent**

1. ቁልቁለት. He climbed down a steep descent. ቀጥ ፡ ያለውን ፡ ቁልቁለት ፡ ወረደ
2. ዘር. He is of French descent. ዘሩ ፡ ፈረንሳይ ፡ ነው
*Going downhill, our descent was rapid. ቁልቁል ፡ ስንወርድ ፡ መንገዳችን ፡ ፈጣን ፡ ነበር
*There is a sharp descent in the price of corn. የእህል ፡ ዋጋ ፡ ባንዴ ፡ ወረደ

**describe**

1. ገለጸ. He described the events of last week accurately. ያለፈውን ፡ ሳምንት ፡ ሁኔታ ፡ በትክክል ፡ ገለጸ
2. አስረዳ. The teacher described the actual position of the moon. መምህሩ ፡ የጊዜውን ፡ የጨረቃ ፡ ሁኔታ ፡ አስረዳ
3. ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሆነ ፡ ነገረ. She described her coat so well that I found it right away. ካፖርቷ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሆነ ፡ በደንብ ፡ ስለነገረችኝ ፡ ወዲያው ፡ አገኘሁት
4. ሠራ. He described a circle in the air. አየር ፡ ላይ ፡ ክብ ፡ ሠራ

**describe oneself**

*He described himself as a doctor. ሐኪም ፡ ነኝ ፡ አለ

**description**

1. መግለጫ. Can you give me a detailed description? ዝርዝር ፡ መግለጫ ፡ ልትሰጠኝ ፡ ትችላለህ ?
2. ገለጸ. The house answers to your description. ቤቱ ፡ ካንተ ፡ ገለጸ ፡ ጋር ፡ ይስማማል
3. ዓይነት. I like food of every description. ማንኛውንም ፡ ዓይነት ፡ ምግብ ፡ እወዳለሁ

**be beyond description** ይህ ፡ ነው ፡ አይባልም ፤ ይህ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይችልም

The shame she felt was beyond description. የተሰማት ፡ እፍረት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አይባልም ፡ (ይህ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይችልም)

**desecrate** አረከሰ

Young criminals desecrated the cemetery. ወጣት ፡ ወንጀለኞች ፡ የመቃብሩን ፡ ቦታ ፡ አረከሱት

**desert** (vt.)

1. ለቀቀ. A good soldier never deserts his post. ታማኝ ፡ ወታደር ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የተመደበበትን ፡ ስፍራ ፡ አይለቅም
2. ጥሎ ፡ ሄደ. He deserted his wife and children. ሚስቱንና ፡ ልጆቹን ፡ ጥሎ ፡ ሄደ

**desert** (vi.) ከዳ

The soldiers deserted in droves. ወታደሮቹ ፡ በብዛት ፡ ከዱ

**desert** (n.) ምድረ ፡ በዳ
They crossed the desert in twenty days.
ምድረ ፡ በዳውን ፡ በሀያ ፡ ቀን ፡ አቋረጡ

**desert** (adj.) በረሃማ ፡ የሆነ ፤ ምድረ ፡ በዳ ፡ የሆነ
Pirates used to maroon people on desert
islands. የባሕር ፡ ሽፍቶች ፡ ሰዎችን ፡ በረሃማ ፡ በ
ሆነ ፡ (ምድረ ፡ በዳ ፡ በሆነ) ፡ ደሴት ፡ ላይ ፡ እየወ
ሰዱ ፡ ያለ ፡ መመለሻ ፡ ይለቋቸው ፡ ነበር

**desert(s)** ዋጋ
The criminal got his just deserts. ወንጀለኛው ፡
የሚገባውን ፡ ዋጋ ፡ አገኘ

**deserted** ሰው ፡ የሌለበት
After a long march, they came to a deserted
village. ከብዙ ፡ ጉዞ ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ የሌለበት ፡ መ
ንደር ፡ ደረሱ

**be deserted**
1. ጭር ፡ አለ. At midnight, the streets are
deserted. በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ መንገዶች ፡ ጭር ፡ ይላሉ
2. ተለቀቀ. The village was hurriedly deserted
because bandits were in the area. በሰፈሩ ፡ ሽ
ፍታ ፡ ስለነበረ ፡ መንደሩ ፡ በፍጥነት ፡ ተለቀቀ
[See also 'desolate']

**deserter** ከዳተኛ ፤ ከዳተኛ ፡ ወታደር
The deserter was shot by a firing squad.
ከዳተኛው ፡ (ከዳተኛው ፡ ወታደር) ፡ በጥይት ፡
ተደበደበ

**desertion** መክዳት
Desertion from the army is punishable by
death. ከጦር ፡ ሰራዊት ፡ መክዳት ፡ በሞት ፡ ያ
ስቀጣል
*The wife sued her husband for desertion.
ሚስትየዋ ፡ ባሏ ፡ ጥሏት ፡ ስለሄደ ፡ ከሰሰችው

**deserve** ይገባዋል
Such a good worker deserves better pay.
እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጠንካራ ፡ ሠራተኛ ፡ የበለጠ ፡
ደሞዝ ፡ መከፈል ፡ ይገባዋል

**design** (v.)
1. ነደፈ. The engineer designed a beautiful
bridge. መሃንዲሱ ፡ ጥሩ ፡ የድልድይ ፡ ንድፍ ፡ ነደፈ
2. ሞድ ፡ አወጣ. She designs her own clothes.
ለልብሷ ፡ ሞዱን ፡ ራሷ ፡ ታወጣለች
3. አጨ. His parents designed him for the
ministry. ወላጆቹ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገል
ግሎት ፡ አጩት
4. አቀደ. The prisoner designed an intricate
escape. እስረኛው ፡ የተራቀቀ ፡ የማምለጫ ፡ ዘ
ዴ ፡ አቀደ

**design** (n.)
1. ቅርጽ. This cross has a very intricate design.
ይህ ፡ መስቀል ፡ በጣም ፡ ረቂቅ ፡ ቅርጽ ፡ አለው
2. ጌጥ. Try to center the design on the page!
ጌጡን ፡ ወረቀቱ ፡ መሃል ፡ ለማዋል ፡ ሞክር
3. አሠራር. The building seats 10,000 people,
but is poor in design. ሕንጻው ፡ ዐሥር ፡ ሺህ ፡
ሰው ፡ ይይዛል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አሠራሩ ፡ ጥሩ ፡ አ
ይደለም
4. ዓላማ. My enemy's design is to get my job.
የባለጋራዬ ፡ ዓላማ ፡ ሥራዬን ፡ ለመንጠቅ ፡ ነው

**by design** ዐውቆ
Whether by accident or design, he overturned
the lamp. ሳያውቅ ፡ ይሁን ፡ ዐውቆ ፡ ኩራዙን ፡
ደፋው

**have designs on**
*I suspect that he has designs on my job.
ሥራዬን ፡ ለመንጠቅ ፡ ሐሳብ ፡ እንዳለው ፡ እጠ
ረጥራለሁ

**School of Design** የንድፍ ፡ ትምህርት ፡ ቤት
This college has a School of Design. ይህ ፡ ኮሌ
ጅ ፡ የንድፍ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አለው
[See also 'decorative']

**designate**
1. ሠየመ. He designated the director to be his
successor. ሥራ ፡ መሪውን ፡ በሱ ፡ ቦታ ፡ እንዲተ
ካ ፡ ሠየመ
2. አሳየ. His insignia designates his rank.
ምልክቱ ፡ ማዕረጉን ፡ ያሳያል

**be designated** ተላከ
This shipment is designated for Ethiopia.
ይህ ፡ በመርከብ ፡ የሚጓዝ ፡ እቃ ፡ ወደ ፡ ኢትዮ
ጵያ ፡ የሚላክ ፡ ነው

**designer** ሞዴል ፡ አውጪ
My brother is a dress designer. ወንድሜ ፡ የል
ብስ ፡ ሞዴል ፡ አውጪ ፡ ነው

**designing** ሞዴል
She studies dress designing at the school.
በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የልብስ ፡ ሞዴል ፡
ትማራለች

**desirable**
1. ተፈላጊ. A change would be very desirable.
ለውጥ ፡ እጅግ ፡ ተፈላጊ ፡ ይሆናል
2. የሚመች. This is a very desirable site for a
hotel. ይህ ፡ ለሆቴል ፡ በጣም ፡ የሚመች ፡ ስፍ
ራ ፡ ነው
3. ደስ ፡ የሚል. This is a very desirable apart-
ment. ይህ ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ አፓርትማ ፡ ነው

**desire** (v.) ተመኘ
We all desire happiness and health. ሁላችንም ፡ ደስታና ፡ ጤና ፡ እንዲኖረን ፡ እንመኛለን

**desire** (n.)
1. ፍላጎት. My desires are easily satisfied. ፍላጎቴ ፡ በቀላሉ ፡ ይረካል
2. ምኞት. He has no desire to see his family. ቤተሰቡን ፡ ለማየት ፡ ምንም ፡ ምኞት ፡ የለውም
*Since he got his heart's desire he has lived happily ever after. የልቡ ፡ ከደረሰለት ፡ በኋላ ፡ በ ደስታ ፡ ኖረ

**desired** (adj.) የተፈለገ
His speech produced the desired effect. ንግግሩ ፡ የተፈለገውን ፡ ውጤት ፡ አስገኘ
*His performance of his duties leaves much to be desired. የሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ብዙ ፡ እንከ ን ፡ አለበት

**(be) desirous of** ተመኘ
He is desirous of going to Ethiopia. ወደ ፡ ኢ ትዮጵያ ፡ ለመሄድ ፡ ይመኛል

**desist** ተወ
He was told to desist from smoking. ሲጋራ ፡ እንዲተው ፡ ተነግሮት ፡ ነበር

**desk** ዴስክ
This desk is too small for me. ይህ ፡ ዴስክ ፡ በ ጣም ፡ ያንሰኛል
[See also 'reception']

**desolate** (v.) አጠፋ
The invading army desolated the countryside. ወራሪው ፡ ጦር ፡ ባላገሩን ፡ አጠፋ

**be desolated** በሐዘን ፡ ተዋጠ
He was desolated to learn that she would not marry him. እንደማታገባው ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ በ ሐዘን ፡ ተዋጠ

**desolate** (adj.) በዳ
The surface of the moon is desolate. የጨረቃ ፡ ገጽ ፡ በዳ ፡ ነው

**be desolate** በጣም ፡ ያስጠላል
This must be a desolate place in winter. በክረምት ፡ ይህ ፡ ቦታ ፡ በጣም ፡ ያስጠላል
*Lalibela is a desolate place in the rainy season. በክረምት ፡ ወራት ፡ ላሊበላ ፡ የተወረረ ፡ ነው ፡ የሚመስለው

**desolate and deserted** በዳ
The village lay desolate and deserted. መንደሩ ፡ በዳ ፡ ቀርቷል

**look desolate** ከፋ(ው)
The ragged, hungry child looked desolate. ቡትቶ ፡ የለበሰውና ፡ የተራበው ፡ ልጅ ፡ ከፍቶት ፡ ነበር

**despair** (v.) ተስፋ ፡ ቈረጠ
The doctors despaired of saving his life. ሐኪሞቹ ፡ ሕይወቱን ፡ ለማዳን ፡ የነበራቸውን ፡ ተስፋ ፡ ቈረጡ

**despair** (n.) ተስፋ ፡ መቍረጥ
In her despair, she jumped out of the window. ተስፋ ፡ ከመቍረጧ ፡ የተነሣ ፡ በመስኮት ፡ ዘለለች

**be filled with despair** ተስፋ ፡ ቈረጠ
He was filled with despair when he saw the exam. ፈተናውን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ተስፋውን ፡ ቈ ረጠ

**be the despair of** አስመረረ
The naughty girl was the despair of her parents. ባለጌዋ ፡ ልጅ ፡ ወላጆቿን ፡ አስመርራ ፡ ነበር

**surrender oneself to despair** ተስፋ ፡ ቈረጠ
He surrendered himself to despair and took his own life. ተስፋ ፡ በመቍረጡ ፡ የገዛ ፡ ሕይ ወቱን ፡ አሳለፈ

**despatch,** see **dispatch**

**desperate**
1. ተስፋ ፡ የሚያስቈርጥ. The state of the country is desperate. ያገሪቷ ፡ ሁኔታ ፡ ተስፋ ፡ የሚያ ስቈርጥ ፡ ነው
2. የሚያሳዝን. She is in a desperate situation. እሷ ፡ በሚያሳዝን ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነች
*An escaped prisoner is likely to be a desperate man. ያመለጠ ፡ እስረኛ ፡ ተስፋ ፡ በመቍረጥ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ከማድረግ ፡ አይመለስም

**desperate act** ተስፋ ፡ የመቍረጥ ፡ ድርጊት
Suicide is a desperate act. ራስን ፡ መግደል ፡ ተስፋ ፡ የመቍረጥ ፡ ድርጊት ፡ ነው

**desperation, in ~** ተስፋ ፡ ቈርጦ
In desperation, he jumped out of the window when he saw the stairs were on fire. ደረጃው ፡ በእሳት ፡ ተያይዞ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ተስፋ ፡ ቈርጦ ፡ በመስኮት ፡ ዘሎ ፡ ወጣ

**despicable** የሚናቅ
Cowards and liars are despicable. ፈሪዎችና ፡ ዋሾዎች ፡ የሚናቁ ፡ ናቸው

**despise** ናቀ
He despises manual labor. የሞያተኝነት ፡ ሥራ ፡ ይንቃል

**despite**
1. ብ + imperfect + ም. Despite my threats, he continued to defy me. ባስፈራራውም ፡ ትእዛዜን ፡ መጣሱን ፡ ቀጠለ
2. ምንም ፡ እንኳ ፡ ብ + (imperfect). The boys went for a walk despite the storm. ምንም ፡ እንኳ ፡ ኀይለኛ ፡ ዝናብ ፡ ቢዘንብ ፡ ልጆቹ ፡ ለሽርሽር ፡ ወጡ

**despoil** በዘበዘ
The robbers despoiled the house. ቀማኞቹ ፡ ቤቱን ፡ በዘበዙት

**(be) despondent** አዝኖ ፡ ተከዘ
He was despondent over his wife's poor health. ስለ ፡ ሚስቱ ፡ ጤና ፡ ማጣት ፡ አዝኖ ፡ ተክዞ ፡ ነበር

**despot** ግን ፡ አለብኝ ፡ ባይ
In ancient times, many rulers were despots. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ገዢዎች ፡ ማን ፡ አለብኝ ፡ ባዮች ፡ ነበሩ

**dessert** ማጣጣሚያ
Dessert is my favorite part of a meal. ማጣጣሚያ ፡ ከምግብ ፡ ሁሉ ፡ አብልጬ ፡ እወዳለሁ

**destination**
1. ያሰበበት ፡ ቦታ. When do we reach our destination? ካሰብንበት ፡ ቦታ ፡ መቼ ፡ እንደርሳለን ?
2. (የጉዞ) ፡ መድረሻ. Our destination is Addis Ababa. የጉዟዋችን ፡ መድረሻ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ነው
3. የተባለበት ፡ ቦታ. The company will rush packages to any destination. ኩባንያው ፡ ወደተባለበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ጥቅሎችን ፡ በፍጥነት ፡ ይልካል
*What is the destination of the letter? ደብዳቤው ፡ የሚላከው ፡ የት ፡ ነው ?

**destine**
*Family tradition destined him for the medical profession. የሐኪምነት ፡ ሥራ ፡ የዘራቸው ፡ በመሆኑ ፡ እሱም ፡ ሐኪም ፡ ሆነ

**be destined**
1. ተመረጠ. He was destined from birth to become a soldier. እርሱ ፡ ጥንቱን ፡ ሲወለድ ፡ ለወታደርነት ፡ የተመረጠ ፡ ነው
2. አመራ. We are destined for home. የምናመራው ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ነው
*My letter was destined never to reach him. እንደ ፡ ዕድል ፡ ሆኖ ፡ ደብዳቤዬ ፡ ሳይደርሰው ፡ ቀረ

**destiny** (destinies)
1. ዕጣ ፤ ዕድል. It was his destiny to die in a foreign country. በባዕድ ፡ አገር ፡ መሞት ፡ ዕጣው ፡ (ዕድሉ) ፡ ሆነ
2. ዓላማ. Ethiopia's destiny may be to bring peace to Africa. የኢትዮጵያ ፡ ዓላማ ፡ ለአፍሪካ ፡ ሰላም ፡ ለማስገኘት ፡ ይሆናል

**destitute** ምስኪን
Destitute families may apply for government aid. ምስኪን ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ መንግሥት ፡ እርዳታ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ያመለክታሉ

**be destitute of** የለውም
Due to his shyness he is destitute of friends. በዓይናፋርነቱ ፡ የተነሣ ፡ ጓደኛ ፡ የለውም

**be left destitute** ችግር ፡ ላይ ፡ ወደቀ
When Mr. Jones died, his family was left destitute. ሚስተር ፡ ጆንስ ፡ ሲሞት ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ወደቁ

**destroy**
1. አጠፋ. The fighting destroyed many villages. ውጊያው ፡ ብዙ ፡ መንደሮችን ፡ አጠፋ
2. አበላሸ. Don't destroy that box; it may be useful later. ያንን ፡ ሳጥን ፡ አታበላሸው ፤ ወደፊት ፡ ይጠቅምህ ፡ ይሆናል

**be destroyed**
1. አለቀ. Ten divisions were destroyed. ዐሥር ፡ ክፍለ ፡ ጦሮች ፡ አለቁ
2. ተደመሰሰ. The two contiguous houses were destroyed by the fire. ሁለቱ ፡ የተጠጋጉ ፡ ቤቶች ፡ በእሳት ፡ ተደመሰሱ
3. ተቃጠለ. All my papers were destroyed in the fire. ወረቀቶቼ ፡ በሙሉ ፡ በእሳት ፡ ተቃጠሉ
4. ወደመ. All the records were destroyed. መዝገቦቹ ፡ ሁሉ ፡ ወድመዋል
5. ተበጣጠሰ. The tenuous web of the spider was destroyed in no time. ቀጭኑ ፡ የሸረሪት ፡ ድር ፡ ባንዳፍታ ፡ ተበጣጠሰ
6. (= act.) ፉርሽ ፡ አደረገ(በት). +His tenuous argument was soon destroyed by his opponent. መሠረተ ፡ ቢስ ፡ ምክንያቱን ፡ ተከራካሪው ፡ ፉርሽ ፡ አደረገበት

**destroyer** ደምሳሽ
The convoy was protected by several destroyers. የመርከቦች ፡ ጓድ ፡ በብዙ ፡ ደምሳሾች ፡ ታጅቦ ፡ ነበር

**destruction** ጥፋት
The fire caused a lot of destruction. እሳቱ ፡ ብዙ ፡ ጥፋት ፡ አደረሰ

**destructive** ጥፋት ፡ የሚያደርስ
Termites are destructive insects. ምስጦች ፡ ጥፋት ፡ የሚያደርሱ ፡ ተባዮች ፡ ናቸው

**desuetude, fall into ~** ከጥቅም፡ውጭ፡ሆነ
Many words once commonly used have fallen into desuetude. አንዳንድ ፡ ቃላት ፡ ብዙ ፡ ጊ ዜ ፡ ከተገለገልንባቸው ፡ በኋላ ፡ ከጥቅም ፡ ውጭ ፡ ይሆናሉ

**desultory** (= adv.) ያለ ፡ ዓላማ
The careful study of a few books is better than the desultory reading of many. ብዙ ፡ መጻሕፍ ት ፡ ያለ ፡ ዓላማ ፡ ከማንበብ ፡ ጥቂቶችን ፡ በጥን ቃቄ ፡ ማጥናት ፡ ይበልጣል

**be desultory** የተወሰነ ፡ ዓላማ ፡ አልነበረውም
Their talk at lunch was desultory. የምሳ ፡ ጊዜ ፡ ጭውውታቸው ፡ የተወሰነ ፡ ዓላማ ፡ አልነበረ ውም

**detach**
1. በጠሰ. The tailor detached the button from my coat. ልብስ ፡ ሰፊው ፡ ቁልፉን ፡ ከኮቴ ፡ ላ ይ ፡ በጠሰው
2. ገነጠለ. Shall I detach the stub? የቲኬቱን ፡ ጉር ድ ፡ ልገንጥለው ?
3. አለያየ. He was unable to detach the watch from the chain. ሰዓቱን ፡ ከማሰሪያው ፡ ለማለያ የት ፡ አልቻለም ፡ ነበር
4. መደበ. The officer detached ten men to guard the railroad station. ሹሙ ፡ የባቡር ፡ ጣቢያውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ከጓዱ ፡ ዐሥር ፡ ሰዎች ፡ መደበ

**detached** (adj.)
1. ለብቻው ፡ የተሠራ. These houses have detached garages. እነዚህ ፡ ቤቶች ፡ ለብቻቸው ፡ የተሠ ሩ ፡ የመኪና ፡ ቤቶች ፡ አሏቸው
2. ገለልተኛ. He has a detached view of the political campaign. ስለ ፡ ፖለቲካ ፡ ውድድር ፡ ገለ ልተኛ ፡ አስተያየት ፡ አለው

**detachment**
1. ክፍል. A detachment of troops was stationed by the railway station. አንዱ ፡ የጦር ፡ ክፍል ፡ በ ባቡሩ ፡ ጣቢያ ፡ ተመድቦ ፡ ነበር
2. ገለልተኛነት. His detachment makes him a good political analyst. ገለልተኛነቱ ፡ ጥሩ ፡ የ ፖለቲካ ፡ ሁኔታ ፡ ተንታኝ ፡ አድርጎታል

**with detachment** በግዴለሽነት ፤ ዝም ፡ ብሎ
He observed the train wreck with detachment. የተሰባበረውን ፡ ባቡር ፡ በግዴለሽነት ፡ (ዝም ፡ ብ ሎ) ፡ ተመለከተ

**detail** (v.)
1. ዘረዘረ. The travelers detailed to us all the wonders they had seen in their travels. መንገደ ኞቹ ፡ በጉዞዋቸው ፡ ላይ ፡ ያጋጠማቸውን ፡ አስ ደናቂ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ዘረዘሩልን
The salesman detailed all expenses in his report. አሻሻጩ፡በሰጠው፡መግለጫ፡ውስጥ፡ወ ጭውን ፡ ሁሉ ፡ ዘረዘረ
2. መደበ. He detailed two men for guard duty. ለዘብ ፡ ጥበቃ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ መደበ

**detail** (n.)
1. ማብራሪያ. Today's paper gives further details. የዛሬው ፡ ጋዜጣ ፡ ተጨማሪ ፡ ማብራሪያ ፡ ይሰጣል
2. ዝርዝር ፤ ዝርዝር ፡ ሁኔታ. I do not want to go into details. ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ልገባ ፡ አልፈልግም
He described the incident in detail. ድርጊቱን ፡ በዝርዝር ፡ ገለጸ
I am not concerned with the details. ስለ ፡ ዝር ዝሩ ፡ ሁኔታ ፡ አልቸገርም
3. (= adj.) ጥቃቅን ፡ የሆነ. She does not enjoy the details of housekeeping. ጥቃቅን ፡ የሆነውን ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ደስ ፡ አይላትም

**in detail** በዝርዝር
He told me the story in detail. ነገሩን ፡ በ ዝርዝር ፡ ነገረኝ

**detailed** (adj.) ዝርዝር
He gave me a detailed report on the battle. ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ፡ አቀረበልኝ

**detain**
1. አቆየ. The police detained him for questioning. ፖሊሶቹ ፡ ለጥያቄ ፡ አቆዩት
2. አዘገየ. An urgent matter detained the doctor. አስቸኳይ ፡ ጉዳይ ፡ ሐኪሙን ፡ አዘገየው

**detect** አገኘ
The expert detected a flaw in the painting. ዐዋቂው ፡ ሥዕሉ ፡ ላይ ፡ ጉድለት ፡ አገኘበት
He was unable to detect any signs of life. ሕይወት ፡ ያላቸው ፡ ነገሮች ፡ ለመኖራቸው ፡ ፍን ጭ ፡ ለማግኘት ፡ አልቻለም ፡ ነበር

**detect an odor** ሽታ ፡ ሸተተ(ው)
Could you detect any odor in this room? በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሽታ ፡ አይሸ ትህም ?

**detective** ወንጀል ፡ መርማሪ
The detectives reasoned that the murderer was a man. ወንጀል ፡ መርማሪዎቹ ፡ ገዳዩ ፡ ወን ድ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ብለው ፡ አሰቡ

**detention**
*The disobedient pupil was punished by detention after school. የማይታዘዘው ፡ ተማሪ ፡

ከትምህርት ፡ በኋላ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እንዲቆይ ፡ ተደረገ

**deter** (deterred)

1. አራቀ. Punishment does not deter anybody from committing a crime. ቅጣት ፡ ሁሉን ፡ ሰው ፡ ወንጀልን ፡ ከመፈጸም ፡ አያርቅም
2. አገደ. The extreme heat deterred us from going on a picnic. ኀይለኛው ፡ ሙቀት ፡ ሽርሽር ፡ ከመሄድ ፡ አገደን

**deteriorate** ተበላሸ

This material deteriorates quickly in a hot climate. ይህ ፡ እቃ ፡ በሞቃት ፡ አየር ፡ ውስጥ ፡ ፈጥኖ ፡ ይበላሻል

The relations between the two countries are deteriorating. በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መሀከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ እየተበላሸ ፡ ሄደ

**determinant** ዋና ፡ ነገር

Cost is often a determinant in choosing a college. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ኮሌጅን ፡ ለመምረጥ ፡ ገንዘብ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ነው

**determination**

1. ቈራጥነት. He showed great determination. ከፍ ፡ ያለ ፡ ቈራጥነትን ፡ አሳየ
2. ቁርጥ ፡ ሐሳብ. His determination to learn English is admirable. እንግሊዝኛ ፡ ለመማር ፡ ያለው ፡ ቁርጥ ፡ ሐሳብ ፡ የሚደነቅ ፡ ነው
3. (= to determine) መወሰን. The determination of the name for the club took hours. የክበቡን ፡ ሥያሜ ፡ መወሰን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፈጀ

[See also 'grim']

**determine**

1. ወሰነ (ተወሰነ). His future has not yet been determined, but he may study medicine. የወደፊት ፡ ዕድሉ ፡ ገና ፡ ባይወሰንም ፡ ሕክምና ፡ ያጠና ፡ ይሆናል
2. ዐወቀ. Can you determine the meaning of this Amharic word? የዚህን ፡ ያማርኛ ፡ ቃል ፡ ትርጉም ፡ ልታውቅ ፡ ትችላለህ ?
3. ቈረጠ. He determined to become the best student in his class. በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ምርጥ ፡ ተማሪ ፡ ለመሆን ፡ ቈረጠ
4. ገፋፋ. What determined you to accept the offer? ያቀረበልህን ፡ እንድትቀበል ፡ ምን ፡ ገፋፋህ ?

**determined** (adj.) ሐሳበ ፡ ቈራጥ

A determined person will achieve his goal. ሐሳበ ፡ ቈራጥ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ከዓላማው ፡ ይደርሳል

**be determined** ቈረጠ

She is determined to have her way. የፈለገችውን ፡ ለመሥራት ፡ ቈርጣለች

**deterrent, serve as a ~** አራቀ

Fear of punishment may serve as a deterrent from crime. የቅጣት ፡ ፍራቻ ፡ ወንጀልን ፡ ከመፈጸም ፡ ያርቅ ፡ ይሆናል

*The iron gates are a deterrent to burglary. የብረት ፡ መዝጊያዎች ፡ ሌቦችን ፡ ይከላከላሉ

**detest** ጠላ

I detest liars. ውሸታም ፡ እጠላለሁ

**detestable** አስከፊ

To kill an unarmed man is a detestable crime. መሣሪያ ፡ ያልያዘ ፡ ሰውን ፡ መግደል ፡ አስከፊ ፡ ሥራ ፡ ነው

**dethrone** ከዙፋን ፡ አወረደ

In Greece, the army dethroned the king. በግሪክ ፡ አገር ፡ ጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ ንጉሡን ፡ ከዙፋን ፡ አወረደ

**detonation** የፈንጂ ፡ ድምፅ

The detonation woke me. የፈንጂው ፡ ድምፅ ፡ ቀሰቀሰኝ

**detour** (n.) ዙሮ ፡ መሄድ

This detour is necessary because the bridge is broken down. ድልድዩ ፡ ስለፈረሰ ፡ ዙሮ ፡ መሄድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**make a detour**

*He made a detour to see the lake. ሐይቁን ፡ ለማየት ፡ ዋናውን ፡ መንገድ ፡ ትቶ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ሄደ

**(be) detoured** በሌላ ፡ መንገድ ፡ እንዲዞር ፡ ተደረገ

Traffic was detoured because of the automobile accident. በመኪናው ፡ አደጋ ፡ ምክንያት ፡ መኪናዎች ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ እንዲዞሩ ፡ ተደረገ

**detract** ቀነሰ(በት)

His vanity detracts from his merit. ግብዝነቱ ፡ መልካም ፡ ተግባሩን ፡ ይቀንስበታል

**detriment** ጉዳ

Overeating is a detriment to health. አብዝቶ ፡ መብላት ፡ ለጤንነት ፡ ጉዳ ፡ ነው

*I know nothing to his detriment. ስሙ ፡ በክፉ ፡ ሲነሣ ፡ ሰምቼም ፡ አላውቅ

*No one can tell lies without detriment to his character. ማንም ፡ ሰው ፡ ስሙን ፡ ሳያጒድፍ ፡ ሊዋሽ ፡ አይችልም

**to the detriment of** እስከሚጐዳው ፡ ድረስ
*He works long hours to the detriment of his health. ጤንነቱን ፡ እስከሚጐዳው ፡ ድረስ ፡ ለረ ዢም ፡ ጊዜያት ፡ ይሠራል

**(be) detrimental to** ሊጐዳ ፡ ይችላል
Smoking may be detrimental to your health. ማጨስ ፡ ጤንነትን ፡ ሊጐዳ ፡ ይችላል

**devaluation** የገንዘብ ፡ ዋጋ ፡ መቀነስ
The business world was surprised by the devaluation. በገንዘቡ ፡ ዋጋ ፡ መቀነስ ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ሁሉ ፡ ተሸበሩ

**devalue** ዝቅ ፡ አደረገ
The government decided to devalue the dollar. መንግሥት ፡ የብርን ፡ ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ ለማድረግ ፡ ወሰነ

**devastate**
1. **አወደመ**. The locusts devastated the growing crops. አንበጣ ፡ ቡቃያውን ፡ አወደመው
2. **አጠፋ**. The bandits devastated many villages. ሽፍቶቹ ፡ ብዙ ፡ መንደር ፡ አጠፉ

**develop** (vt.)
1. **አስፋፋ**. The government is interested in developing education. መንግሥት ፡ ትምህርትን ፡ ለማስፋፋት ፡ ፍላጎት ፡ አለው
Gradually we developed our plan for the club. ቀስ ፡ በቀስ ፡ የክበባችንን ፡ እቅድ ፡ አስፋፋን
2. **አበለጸገ**. Our mandate allows us to do all we can to develop the country. የተጣለብን ፡ አደራ ፡ ሀገሪቷን ፡ ለማበልጸግ ፡ የተቻለንን ፡ ሁሉ ፡ እንድናደርግ ፡ ይፈቅድልናል
3. **አዳበረ**. Swimming will develop many different muscles. ዋና ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጡንቻ ዎችን ፡ ያዳብራል
We must develop our natural resources. የተፈጥሮ ፡ ሀብታችንን ፡ ማዳበር ፡ አለብን
4. **አለማ**. Landowners must develop their land. ባለመሬቶች ፡ መሬታቸውን ፡ ማልማት ፡ አለባቸው
5. **አበጀ**. You should try to develop the reading habit. የማንበብ ፡ ልማድ ፡ እንድታበጅ ፡ ያስፈልግሃል
6. **ያዘ**. The boy is developing a fine personality. ልጁ ፡ ጥሩ ፡ ጠባይ ፡ ይዟል
7. **አጠበ**. Would you develop this film for me? ይህንን ፡ ፊልም ፡ ልታጥብልኝ ፡ ትችላለህ ?
*He developed a cough. ሳል ፡ አደረበት

**develop** (vi.)
1. **በቀለ**. Plants develop from seeds. ዕፀዋት ፡ ከዘር ፡ ይበቅላሉ
2. **በለጸገ**. The country developed under his guidance. አገሪቱ ፡ በሱ ፡ መሪነት ፡ በለጸገች
3. **ተስፋፋ**. Addis Ababa developed greatly in the last decade. ባለፉት ፡ ዐሥር ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በጣም ፡ ተስፋፍታለች
4. **አደገ**. The boy is developing nicely. ልጁ ፡ ደኅና ፡ ያድጋል
5. **ተፈጠረ**. Trouble has developed between the two countries. በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ መቃቃር ፡ ተፈጥሯል

**develop into** ለመሆን ፡ በቃ
London developed into one of the world's largest ports. ለንደን ፡ በዓለም ፡ እጅግ ፡ ታላላቅ ፡ ከሚባሉት ፡ ወደቦች ፡ አንዷ ፡ ለመሆን ፡ በቃች

**developing** በማደግ ፡ ላይ ፡ ያለ
There are many developing countries in Africa. አፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ አገሮች ፡ አሉ

**development**
1. **እድገት**. This plan fosters community development. ይህ ፡ እቅድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብ ፡ እድገትን ፡ ያበረታታል
2. (= to develop) **ማስፋፋት**. He is engaged in the development of his business. ንግዱን ፡ ማስፋፋት ፡ ይዟል
3. **ልማት**. This land is ripe for development. ይህ ፡ መሬት ፡ ለልማት ፡ የተመቸ ፡ ነው
4. **አስተዳደግ**. The doctor followed the child's development closely. ሐኪሙ ፡ የልጁን ፡ አስተዳደግ ፡ በቅርቡ ፡ ተከታተለ

**developments** የተፈጠረ ፡ ሁኔታ ፤ የደረሱ ፡ ነገሮች
Do you know the latest developments in the Vietnam problem? በቅርቡ ፡ ስለ ፡ ቬየትናም ፡ ጉዳይ ፡ የተፈጠረ ፡ ሁኔታ ፡ ታውቃለህ ?
He was advised of the latest developments. በቅርቡ ፡ ስለደረሱት ፡ ነገሮች ፡ ተነገረው

**deviate** ራቀ
His stories always deviate from the truth. ሁልጊዜ ፡ እሱ ፡ የሚናገራቸው ፡ ነገሮች ፡ ከእውነት ፡ የራቁ ፡ ናቸው

**device**
1. **ዘዴ**. The device was intended to throw the police off his trail. ዘዴው ፡ ፖሊሱን ፡ ከፍለጋው ፡ ለማሳሳት ፡ ነበር
2. **መሣሪያ**. That is an ingenious device. ያ ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ የሆነ ፡ መሣሪያ ፡ ነው

**devil** ሰይጣን
Many people believe in the existence of the devil. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰይጣን ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ያምናሉ

**poor devil** ምስኪን
The poor devil kept losing jobs through no fault of his own. ምስኪኑ ፡ የራሱ ፡ ባልሆነ ፡ ጥፋት ፡ ከሥራ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወጣ

**devious** ቅን ፡ ያልሆነ
The devious ways of the tourist guides made them distrusted. አገር ፡ አስጐብኝዎች ፡ ሁኔታቸው ፡ ቅን ፡ ስላልነበረ ፡ ጐብኝዎቹን ፡ አጠራጠራቸው
**take a devious route** በዙሪያ ፡ መንገድ ፡ ሄደ
He took a devious route to avoid busy streets. ትራፊክ ፡ የበዛባቸውን ፡ መንገዶች ፡ ለመሸሽ ፡ በዙሪያ ፡ መንገድ ፡ ሄደ
**devious ways** ተንኰል
He got rich by devious ways. በተንኰል ፡ ከበረ

**devise** ፈጠረ
The boys devised a scheme for earning money during vacation. ልጆቹ ፡ በዕረፍት ፡ ጊዜያቸው ፡ ገንዘብ ፡ የሚያገኙበትን ፡ ዘዴ ፡ ፈጠሩ
**devise a plan** አቀደ
They devised a plan for cheating the government. መንግሥቱን ፡ ለማጭበርበር ፡ አቀዱ

**devoid of** ቢስ
She is devoid of shame. እፍረተ ፡ ቢስ ፡ ናት
The plan was devoid of results. እቅዱ ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ነበር

**devolve (on)** በሱ ፡ ላይ ፡ ተጣለ
The responsibility for managing the office devolved on me. የቢሮው ፡ ሥራ ፡ ኀላፊነት ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ተጣለ

**devote** አዋለ
He devoted all his spare time to his studies. ያለውን ፡ ትርፍ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ለጥናት ፡ አዋለ
*A mother devotes herself to her children. እናት ፡ ሙሉ ፡ ጊዜዋን ፡ ልጆቿን ፡ በማንከባከብ ፡ ታሳልፋለች

**devoted** (adj.) ታማኝ
He is a devoted friend. ታማኝ ፡ ጓደኛ ፡ ነው
**be devoted to**
1. ብቻ ፡ ተመደበ. The 'Ethiopia Observer' is devoted to Ethiopian studies. ኢትዮጵያ ፡ ኦብሰርቨር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለሚመለከቱ ፡ ጥናቶች ፡ ብቻ ፡ የተመደበ ፡ ነው
2. ተወሰነ. The entire program was devoted to reading poetry. ፕሮግራሙ ፡ በሙሉ ፡ ግጥም ፡ ለማንበቢያ ፡ ተወስኖ ፡ ነበር
3. ወደደ. He is very devoted to his mother. እናቱን ፡ በጣም ፡ ይወዳል

**devotion**
1. ፍቅር. A mother's devotion is to her children. የእናት ፡ ፍቅሯ ፡ ለልጆቿ ፡ ነው
Her devotion to the club made her attend every meeting. ለክበቡ ፡ ያላት ፡ ፍቅር ፡ በየጊዜው ፡ በሚደረገው ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ እንድትገኝ ፡ አደረጋት
The monks show their devotion in constant prayer to God. መነኰሳት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያላቸውን ፡ ፍቅር ፡ በማያቋርጥ ፡ ጸሎት ፡ ይገልጻሉ
2. መውደድ. He manifested his exclusive devotion to his work. በሙሉ ፡ ልብ ፡ ሥራውን ፡ መውደዱን ፡ አሳየ
3. ታማኝነት. He serves with constancy and devotion. በቅንነትና ፡ በታማኝነት ፡ ያገለግላል
4. መልካም ፡ አገልግሎት. The Emperor met with the senators and praised them for their devotion to Ethiopia. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎችን ፡ አስጠርተው ፡ ላገራቸው ፡ ላደረጉት ፡ መልካም ፡ አገልግሎት ፡ አመሰገኑዋቸው

**devotional** መንፈሳዊ
Monks lead a devotional life. መነኰሳት ፡ መንፈሳዊ ፡ ኑሮ ፡ ይኖራሉ

**devour**
1. በላ. The lion devoured the sheep. አንበሳው ፡ በጉን ፡ በላ
2. ጐሰጐሰ. He devoured his dinner in a few minutes. እራቱን ፡ በጥቂት ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ጐሰጐሰው
3. አመነመነ. Anxiety devoured him. ሥጋት ፡ አመነመነው
4. አደመጠ. She devoured the gossip eagerly. ወሬውን ፡ በጉጉት ፡ አደመጠችው
5. በጉጉት ፡ አነበበ. The students devoured the new book. ተማሪዎቹ ፡ አዲሱን ፡ መጽሐፍ ፡ በጉጉት ፡ አነበቡት

**devout**
1. ለእግዚአብሔር ፡ ያደረ. That priest is a devout man. ካህኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያደረ ፡ ነው
2. መንፈሳዊ. This book describes the devout life of the saints. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የቅዱሳኑን ፡ መንፈሳዊ ፡ ኑሮ ፡ ይገልጻል
3. ታማኝ. The devout followers of Gandhi crowded around his grave. የጋንዲ ፡ ታማኝ ፡ ተከታታዮች ፡ መቃብሩን ፡ በብዛት ፡ ከበው ፡ ነበር
4. እውነተኛ. He is a devout Christian and a good man. እውነተኛ ፡ ክርስቲያንና ፡ ጥሩ ፡ ሰው ፡ ነው

**dew** ጤዛ
The grass was wet with dew. ሣሩን ፡ ጤዛ ፡ አርጥቦት ፡ ነበር

**dexterity**
1. ቅልጥፍና. He handles his sword with dexterity. ጐራዴውን ፡ በቅልጥፍና ፡ ይይዛል
2. ብልሃት. He handles the matter with dexterity. ጉዳዩን ፡ በብልሃት ፡ ያከሂዳል

**dexterous** ጥበበኛ
A dexterous basket weaver makes any sort of basket. ጥበበኛው ፡ ቅርጫት ፡ ሠሪ ፡ ማንኛው ንም ፡ ዓይነት ፡ ቅርጫት ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል

**diabolic** የሰይጣን
This was a diabolic scheme. ይህ ፡ የሰይጣን ፡ ሥራ ፡ ነበር

**diadem** የራስ ፡ ወርቅ
Her diadem is made of diamonds. የራስ ፡ ወር ቋ ፡ ከአልማዝ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**diagnose** ለይቶ ፡ ዐወቀ
The doctor diagnosed the illness as measles. ሐኪሙ ፡ በሽታው ፡ ኩፍኝ ፡ መሆኑን ፡ ለይቶ ፡ ዐ ወቀ

**diagnosis**
1. የምርመራ ፡ ውጤት. The doctor's diagnosis of the disease was correct. የሐኪሙ ፡ የበሽታ ው ፡ ምርመራ ፡ ውጤት ፡ ልክ ፡ ነበር
2. ምርመራ. A diagnosis of the elections shows the workers voted for the one man only. የምርጫው ፡ ምርመራ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ላን ዱ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ድምፅ ፡ መስጠታቸውን ፡ አስ ረዳ

**diagonal** ሰያፍ
A diagonal line runs from one corner of the box to the other. ሰያፍ ፡ መሥመር ፡ ከሣጥኑ ፡ አንደኛው ፡ ጫፍ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ይሄዳል

**diagram** ሥዕላዊ ፡ መግለጫ
This diagram will show you how to make a boat. ይህ ፡ ሥዕላዊ ፡ መግለጫ ፡ ጀልባ ፡ እንዴ ት ፡ እንደሚሠራ ፡ ያሳይሃል

**dial** (v.) ደወለ
She dialed the wrong number. የተሳሳተ ፡ ቁ ጥር ፡ ደወለች

**dial** (n.) መቁጠሪያ
The dial on my watch is dirty. የሰዓቴ ፡ መቁ ጠሪያ ፡ ቆሻሻ ፡ ነው
* Telephones with dials are a recent invention. በቁጥር ፡ የሚደወሉ ፡ ስልኮች ፡ የቅርብ ፡ ፍ ልሰፋ ፡ ናቸው

**dialect** ያነጋገር ፡ ዘዬ ፤ የቋንቋ ፡ ስልት
Italian has many dialects. የጣልያን ፡ ቋንቋ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ያነጋገር ፡ ዘዬ ፡ አለው
This dialect is equally removed from German and English. ይህ ፡ የቋንቋ ፡ ስልት ፡ ከጀርመን ኛ ፡ የሚለየውን ፡ ያህል ፡ ከእንግሊዝኛም ፡ ይለያል

**dialogue**
1. ውይይት. The two men engaged in a long dialogue concerning the rights of man. ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ ረጅም ፡ ውይ ይት ፡ አደረጉ
2. ጭውውት. The two actors engaged in a long dialogue. ሁለቱ ፡ ተዋንያን ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ጭው ውት ፡ አደረጉ

**diameter** የክበብ ፡ አጋማሽ ፡ መሥመር
Measure the diameter with a ruler! የክበቡን ፡ አጋማሽ ፡ መሥመር ፡ በማሥመሪያ ፡ ለካ
*The diameter of this tree trunk is 50 inches. ይህ ፡ ግንድ ፡ መሀል ፡ ለመሀል ፡ ስፋቱ ፡ አምሳ ፡ ኢንች ፡ ነው

**diamond** አልማዝ
She wears a diamond ring on holidays. በበዓላት ፡ ቀን ፡ ያልማዝ ፡ ቀለበት ፡ ታደር ጋለች

**diarrhea** ተቅማጥ
Eating green bananas gave him diarrhea. ጥሬ ፡ ሙዝ ፡ መብላት ፡ ተቅማጥ ፡ ለቀቀበት

**diary** (diaries) የየቀን ፡ ማስታወሻ
The diary was written in Amharic. የየቀኑ ፡ ማ ስታወሻ ፡ የተጻፈው ፡ ባማርኛ ፡ ነበር

**dice** [ትንሽ ፡ ኩቦች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከጐናቸው ፡ ላይ ፡ ከአንድ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ነጠብጣብ ፡ ያላ ቸው]

**dicker** ተከራከረ
They dickered for hours over some of the finer points of the contract. ውሉን ፡ በሚመለከቱ ፡ ጥቃቅን ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ለብዙ ፡ ሰዓቶች ፡ ተከራከሩ

**dictate**
1. በቃል ፡ አጻፈ ፤ አጸፈ. The teacher dictated two pages to the class. አስተማሪው ፡ የክፍሉን ፡ ተማሪዎች ፡ ሁለት ፡ ገጽ ፡ በቃል ፡ አጻፈ
I cannot keep up with you when you dictate

so fast. እንደዚህ ፡ ፈጥነህ ፡ ስታጽፈኝ ፡ ልከታተልህ ፡ አልችልም
2. ፍላጎቱን ፡ እንዲያሟላው ፡ አስገደደ. Big nations dictate to little ones. ታላላቅ ፡ መንግሥታት ፡ ታናናሾቹን ፡ ፍላጎታቸውን ፡ እንዲያሟላላቸው ፡ ያስገድዳሉ
* The victor dictates the terms to the defeated enemy. ድል ፡ አድራጊው ፡ ድል ፡ የተመታው ፡ ጠላት ፡ ሳይፈቅድ ፡ የዕርቁን ፡ ድርድር ፡ ይወስናል

**dictation** የቃል ፡ ጽሕፈት
The pupils wrote at the teacher's dictation. መምህሩ ፡ ተማሪዎቹን ፡ የቃል ፡ ጽሕፈት ፡ አጻፋቸው

**dictator** አምባ ፡ ገነን
Mussolini was a dictator. ሙሶሊኒ ፡ አምባ ፡ ገነን ፡ ነበር

**diction** አነጋገር
An actor must have clear diction. አንድ ፡ ተዋናይ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ አነጋገር ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈልጋል
*The diction of everyday talk is different from that of the essay. የተራ ፡ ንግግርና ፡ የድርሰት ፡ አጻጻፍ ፡ ስልት ፡ የተለዩ ፡ ናቸው

**dictionary** (dictionaries) መዝገበ ፡ ቃላት
He is compiling an Amharic dictionary. ያማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ያዘጋጃል

**did,** see **do**

**didactic** ትምህርት ፡ አዘል
Many of Aesop's fables are didactic. ብዙዎቹ ፡ የኤሶፕ ፡ ተረቶች ፡ ትምህርት ፡ አዘል ፡ ናቸው

**die**
1. ሞተ ፤ አረፈ. My mother died yesterday. እናቴ ፡ ትላንትና ፡ ሞተች
He died by his own hand. በገዛ ፡ እጁ ፡ ሞተ
He died this morning at two o'clock. ዛሬ ፡ ጧት ፡ በስምንት ፡ ሰዓት ፡ አረፈ
2. አከተመ. The League of Nations died in 1935. የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ በ፲፱፻፳፯ ዓ. ም. አከተመ
3. ደረቀ. The tree is dying. ዛፉ ፡ እየደረቀ ፡ ነው
4. ባንዴ ፡ በረደ. His sudden anger died. ድንገተኛ ፡ ንዴቱ ፡ ባንዴ ፡ በረደ
5. ጠፋ. The motor died. ሞተሩ ፡ ጠፋ
6. በጣም ፡ ጓጓ. I am dying to find out what he said about me. ስለኔ ፡ ምን ፡ እንዳለ ፡ ለማወቅ ፡ በጣም ፡ ጓጉቻለሁ
*What did he die of? ምን ፡ ገደለው?

**die away**
1. ጠፋ. The sounds of the music died away. የሙዚቃው ፡ ድምፅ ፡ ጠፋ
2. እየጠፋ ፡ ሄደ. The noise of the train died away in the distance. ባቡሩ ፡ ሲርቅ ፡ ጩኸቱ ፡ እየጠፋ ፡ ሄደ

**die down**
1. ጠፋ. We let the fire die down. እሳቱ ፡ እንዲጠፋ ፡ ዝም ፡ አልነው
The excitement will die down in a few days. ሽብሩ ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ይጠፋል
2. በረደ. The wind died down. ነፋሱ ፡ በርዷል

**die for** ለ --- መሥዋዕት ፡ ሆነ
The Emperor spoke in praise of the soldiers who died for Ethiopia. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መሥዋዕት ፡ የሆኑትን ፡ ወታደሮች ፡ በሞገስ ፡ ተናገሩ

**die off** አለቀ
The old inhabitants are dying off. የዱሮ ፡ ነዋሪዎች ፡ እያለቁ ፡ ናቸው

**die out**
1. ቀረ. This old custom is gradually dying out. ይህ ፡ የጥንት ፡ ልማድ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየቀረ ፡ ሄዷል
2. መነገሩ ፡ ቀረ. Latin died out a long time ago. የላቲን ፡ ቋንቋ ፡ መነገሩ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ቀርቷል

**die-hard** ለውጥ ፡ የማይፈልግ
The die-hards will never accept the new regime. ለውጥ ፡ የማይፈልጉት ፡ አዲሱን ፡ መንግሥት ፡ በፍጹም ፡ አይቀበሉም

**diet** (v.)
*Are you still dieting? አሁንም ፡ የምትመገበው ፡ የተወሰነ ፡ ምግብ ፡ ነው?

**diet** (n.) ምግብ
For weeks our diet consisted of nothing but fish. ለብዙ ፡ ሳምንቶች ፡ ምግባችን ፡ ዓሣ ፡ ብቻ ፡ ነበር
Poor diet dwarfed the children. በቂ ፡ አልሚነት ፡ የሌለው ፡ ምግብ ፡ ልጆቹን ፡ አቀረቆዘ
*He subsisted on a diet of bananas. ሙዝ ፡ እየበላ ፡ በሕይወት ፡ ቆየ
*No cake for me, I'm on a diet. እኔ ፡ ኬክ ፡ አልበላም ፤ ምግብ ፡ በመቈጠብ ፡ ላይ ፡ ነኝ
[See also 'starvation']

**differ**
1. ተለያየ. Opinions differ here. በዚህ ፡ ላይ ፡ የሰው ፡ አስተያየት ፡ ይለያያል

2. አልተገናኘም. They differ in every respect. በምንም ፡ ነገር ፡ አይገናኙም
3. አልተስማማም. I beg to differ with you. Ethiopia was never conquered by the Muslims. ይቅርታ ፡ አድርግልኝና ፡ በምትለው ፡ አልስማ ማም ፤ ኢትዮጵያ ፡ በእስላሞች ፡ ፈጽሞ ፡ ድል ፡ ሆና ፡ አታውቅም

**difference**
1. ልዩነት. Can you explain the difference to me? ልዩነቱን ፡ ልታስረዳኝ ፡ ትችላለህ ?
It makes no difference when you come. ምንም ፡ ጊዜ ፡ ብትመጣ ፡ ልዩነት ፡ አያመጣም
The difference between seven and eleven is four. በሰባትና ፡ በዐሥራ ፡ አንድ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ አራት ፡ ነው
2. አለመግባባት. Try to make some adjustments of your differences! በመካከላችሁ ፡ ስላለው ፡ አለመግባባት ፡ ለመስማማት ፡ ሞክሩ
**have a difference**
1. ተከራከረ. The children had a difference over a name for the new puppy. ልጆቹ ፡ ስለ ፡ አዲሱ ፡ ቡችላ ፡ ስም ፡ ይከራከሩ ፡ ነበር
2. ተለያየ. They had a serious difference of opinion. በሐሳብ ፡ በጣም ፡ ይለያዩ ፡ ነበር
**make a difference** ሊወስን ፡ ቻለ
What you eat for breakfast makes a difference in how you feel all day long. ለቁርስ ፡ የምትበላው ፡ የቀኑን ፡ ውሎህን ፡ ሊወስነው ፡ ይችላል

**different**
1. ሌላ. That's a different matter. ያ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ነው
2. የተለያየ. I called three different times, but he was out. በሦስት ፡ የተለያዩ ፡ ጊዜያት ፡ ብደውልለትም ፡ ላገኘው ፡ አልቻልኩም
**be different** ተለያየ
The two brothers are very different. ሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ በጣም ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው

**differentiate** (vt.) ለየ
What differentiates the polar bear from other bears? የዋልታ ፡ ድብን ፡ ከሌሎች ፡ ድቦች ፡ ምን ፡ ይለያቸዋል ?
**differentiate** (vi.)
1. ልዩነት ፡ ዐወቀ. Only an expert could differentiate between the original painting and the copy. በዋናውና ፡ በቅጂው ፡ ሥዕል ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ሊያውቅ ፡ የሚችለው ፡ በሥራው ፡ የሠለጠነ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. (= passive) ተለየ. +He cannot differentiate between Amharic and Tigrinya; they sound so much alike to him. ድምፃቸው ፡ በጣም ፡ ስለሚመሳሰሉበት ፡ አማርኛና ፡ ትግርኛ ፡ አይለይም

**differently** በተለያየ ፡ መንገድ
Different lawyers may construe the same law differently. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጠበቃዎች ፡ አንዱን ፡ ሕግ ፡ በተለያየ ፡ መንገድ ፡ ይተረጉሙት ፡ ይሆናል
*I think differently about it. ስለዚህ ፡ ያለኝ ፡ አስተያየት ፡ የተለየ ፡ ነው

**difficult**
1. ከባድ ፤ አስቸጋሪ. Amharic is a difficult language. አማርኛ ፡ ከባድ ፡ (አስቸጋሪ) ፡ ቋንቋ ፡ ነው
There are many difficult pupils in this class. እዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ አስቸጋሪ ፡ ተማሪዎች ፡ አሉ
2. ክፉ. My boss is a difficult employer. አለቃዬ ፡ ክፉ ፡ አሠሪ ፡ ነው
3. የመከራ. Your kind words give me comfort in a difficult time. መልካም ፡ ቃላትህ ፡ በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ አጽናንተውኛል
**be difficult** አስቸገረ
It is difficult to understand what he means. የሚለውን ፡ ነገር ፡ ለመረዳት ፡ ያስቸግራል
**have a difficult time** ችግር ፡ አለበት
Left-handed people have a difficult time learning to write. ግራኝ ፡ ሰዎች ፡ ጽሕፈት ፡ ሲማሩ ፡ ችግር ፡ አለባቸው

**difficulty** (difficulties)
1. ችግር. He overcame all difficulties. ሁሉንም ፡ ችግሮች ፡ አሸነፈ
The difficulty of learning Amharic is considerable. አማርኛን ፡ ለመማር ፡ ያለው ፡ ችግር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው
2. አስቸጋሪ ፡ ነገር. This task is beset with difficulties. ይህ ፡ ሥራ ፡ ባስቸጋሪ ፡ ነገሮች ፡ የተዋጠ ፡ ነው
3. ክብደት. The difficulty of the job was greater than we thought it would be. የሥራው ፡ ክብደት ፡ ካሰብነው ፡ በላይ ፡ ነበር
**make difficulties** አስቸገረ
Study your lesson thoroughly and don't make any difficulties! ጥናትህን ፡ በጥንቃቄ ፡ አጥና ፤ አታስቸግር

**diffidence** እፍረት
Her diffidence makes her hard to talk with. እፍረት ፡ ስለምታበዛ ፡ ማነጋገር ፡ ያስቸግራል

**diffident** በራሱ ፡ ያለመተማመን
His diffident manner makes him a poor

teacher. በራሱ ፡ ያለመተማመን ፡ ጠባዩ ፡ ደካማ ፡ አስተማሪ ፡ አድርጎታል

**diffuse** (vt.) አስፋፋ
The Jesuits diffused learning throughout South America. ኢየሱሳውያን ፡ በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ ትምህርትን ፡ አስፋፉ

**diffuse** (vi.) ተሰራጨ
The dye diffused slowly through the water. ማቅለሚያው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ በውኃው ፡ ውስጥ ፡ ተሰራጨ

**diffuse** (adj.)
*This lamp gives diffuse light. ይህ ፡ መብራት ፡ ደብዘዝ ፡ ያለ ፡ ብርሃን ፡ ያሰራጫል

**dig** (dug) ቈፈረ
He dug a ditch around the field. በመስኩ ፡ ዙሪያ ፡ ቦይ ፡ ቈፈረ
The farmer's wife digs potatoes. የገበሬው ፡ ሚስት ፡ ድንች ፡ ትቈፍራለች

**(be) dug in** መሸገ
The enemy was dug in on the top of the hill. ጠላት ፡ በኮረብታው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ መሽጎ ፡ ነበር

**dig into** ከ --- አወጣ
I'm afraid we will have to dig into our reserves. ከተቀማጫችን ፡ ማውጣት ፡ ያለብን ፡ ይመስለኛል

**dig out**
1. ቈፍሮ ፡ አወጣ. They dug him out of the well after it collapsed. ከተደረመሰ ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ቈፍረው ፡ አወጡት
2. ፈልፍሎ ፡ አወጣ. He dug the bullet out of the board. ጥይቱን ፡ ከሳንቃው ፡ ውስጥ ፡ ፈልፍሎ ፡ አወጣ

**dig through** በረበረ
He dug through the pile of letters. የደብዳቤውን ፡ ክምር ፡ በረበረው

**dig up**
1. ቈፈረ. He dug up land for a new garden. ላዲስ ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ መሬት ፡ ቈፈረ
2. ነቀለ. We will have to dig up the rose bush. የጽጌረዳውን ፡ ቁጥቋጦ ፡ መንቀል ፡ አለብን
3. ቈፍሮ ፡ አወጣ. Dig up the taproot of the tree! የዛፉን ፡ ዋና ፡ ሥር ፡ ቈፍረህ ፡ አውጣው
4. ሰበሰበ. The students were digging up information in the library. ተማሪዎቹ ፡ በቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ መረጃ ፡ ይሰበስቡ ፡ ነበር

**(be) dug up** ተቈፍሮ ፡ ወጣ
An old statue was dug up in Aksum last month. ባለፈው ፡ ወር ፡ ካክሱም ፡ የጥንት ፡ ሐውልት ፡ ተቈፍሮ ፡ ወጣ
[See also 'spur']

**digest** (vt.)
1. አዋሐደ. The function of the stomach is to digest food. የጨጓራ ፡ ተግባር ፡ ምግብ ፡ ማዋሐድ ፡ ነው
2. ቀሠመ. Have you digested everything that is important in that book? በዚያ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ቀሥመሃል ?

**digest** (vi.)
1. (= trans.) ፈጨ. Nuts are hard to digest. ጨጓራ ፡ ለውዝን ፡ በቀላሉ ፡ ሊፈጭ ፡ አይችልም
2. ከሰውነት ፡ ጋራ ፡ ተዋሐደ. Cabbage is hard to digest. ጐመን ፡ ከሰውነት ፡ ጋር ፡ ቶሎ ፡ አይዋሐድም
*The victuals offered us by the natives were hard to digest. ሀገሬዎቹ ፡ ያቀረቡልን ፡ ምግብ ፡ አልንሸራሸር ፡ አለን

**digest** (n.) አጭር ፡ መግለጫ
A news digest is printed by the embassy. አጭር ፡ የዜና ፡ መግለጫ ፡ በኤምባሲው ፡ ታትሞ ፡ ወጥቷል

**digestion** የምግብ ፡ መንሸራሸር
A short rest after a meal helps digestion. ከምግብ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ዕረፍት ፡ ማድረግ ፡ ለምግብ ፡ መንሸራሸር ፡ ይረዳል

**digit** [ከዜሮ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ያለው ፡ ማንኛውም ፡ ቁጥር]

**dignified** (adj.) ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ያለው
His father was a dignified old gentleman. አባቱ ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ያላቸው ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ነበሩ
[See also 'bearing']

**dignify** (dignified) አስከበረ
By his achievements, the President dignified his office. በሥራው ፡ ክንውን ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ሹመቱን ፡ አስከበረው

**dignitary** (dignitaries)
1. ባለ ፡ ሥልጣን. The church dignitaries were dressed in blue and gold. የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ ሰማያዊና ፡ ወርቅማ ፡ ልብስ ፡ ለብሰዋል
2. ታላቅ ፡ ሰው. The police parted the crowd to let the dignitaries pass. ታላላቆች ፡ ሰዎች ፡ እንዲያልፉ ፡ ፖሊሶች ፡ ሕዝቡን ፡ ገለል ፡ አደረጉት
3. ሹም (pl. ሹማምንት). All the dignitaries wear capes. ሹማምንቱ ፡ በሙሉ ፡ ካባ ፡ ይለብሳሉ

**dignity**
1. ክብር. A man's dignity depends on his

character. የሰው ፡ ልጅ ፡ ክብሩ ፡ በጠባዩ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው

2. ማዕረግ. He may attain the dignity of the presidency. የፕሬዚዳንትነትን ፡ ማዕረግ ፡ ያገኝ ፡ ይሆናል

**be beneath one's dignity** ክብሩን ፡ ቀነሰ

It would be beneath my dignity to notice his insults. የሱን ፡ ስድብ ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ መጣፍ ፡ ክብሬን ፡ ይቀንሳል

**digress** ወጣ

He often digresses from the main subject. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከዋናው ፡ አርእስት ፡ ይወጣል

**dike** ግድብ

They stemmed the flood with dikes. ጐርፉን ፡ በግድብ ፡ አገዱት

**dilapidated** የወደቀ

This is a dilapidated old house. ይህ ፡ የወደቀ ፡ አሮጌ ፡ ቤት ፡ ነው

**dilate** ሰፋ

The pupils of the cat's eyes dilate in the dark. የድመት ፡ የዓይን ፡ ብሌን ፡ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ይሰፋል

**dilemma** የሁለት ፡ ክፉ ፡ ምርጫ

He faced the dilemma with courage. የሁለት ፡ ክፉ ፡ ምርጫውን ፡ በድፍረት ፡ ተቋቋመ

**diligence** ትጋት

He performed his task with diligence. ሥራውን ፡ በትጋት ፡ አከናወነ

**diligent** ትጉህ ፤ ትጉ

He is a diligent student. ትጉህ ፡ (ትጉ) ፡ ተማሪ ፡ ነው

**dilute (with water)** አቀጠነ

The cook diluted wine with water. ወጥ ፡ ቤቱ ፡ ወይኑን ፡ አቀጠነው

**be diluted** ተዳከመ

The force of his writing is diluted by the use of too many words. ያጻጻፉ ፡ ኀይል ፡ በቃላት ፡ ብዛት ፡ ተዳከመ

**dilution** ውኃ ፡ መቀላቀል

Dilution of milk is forbidden by law. በወተት ፡ ውስጥ ፡ ውኃ ፡ መቀላቀል ፡ በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ ነው

**dim** (dimmed), v. ቀነሰ

The car didn't dim its lights. መኪናው ፡ መብራቱን ፡ አልቀነሰም

**dim** (adj.) ደብዛዛ

I saw a dim figure in the shadows. በጥላው ፡ ውስጥ ፡ ደብዛዛ ፡ የሰው ፡ ቅርጽ ፡ ታየኝ

I couldn't see anything in that dim light. በደብዛዛው ፡ መብራት ፡ ምንም ፡ ለማየት ፡ አልቻልኩም

**get dim** ደከመ

His eyesight is getting dim. የዓይኑ ፡ ብርሃን ፡ እየደከመ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ነው

**take a dim view**

1. ቅር ፡ ተሰኘ. Her mother takes a dim view of her choice of clothes. እናቲቱ ፡ ስለ ፡ ልጅቷ ፡ ልብስ ፡ አመራረጥ ፡ ቅር ፡ ትሰኛለች

2. ዝቅተኛ ፡ አስተያየት ፡ አለው. My father takes a dim view of my business activities. አባቴ ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ሥራዬ ፡ ዝቅተኛ ፡ አስተያየት ፡ አለው

**dimension** ወርድና ፡ ስፋት

What are the dimensions of this room? የዚህ ፡ ክፍል ፡ ወርድና ፡ ስፋቱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?

**of great dimensions** በጣም ፡ ትልቅ

The temple is a building of great dimensions. የመቅደሱ ፡ ሕንጻ ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ነው

**of vast dimensions** በጣም ፡ ሰፊ ፡ ያለ

A project of vast dimensions like building a railroad system costs a lot of money. የባቡር ፡ ሐዲድን ፡ መዘርጋት ፡ የመሰለ ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ ያለ ፡ እቅድ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ይጠይቃል

**diminish** (vt.) ቀነሰ

The war diminished the country's wealth. ጦርነቱ ፡ ያገሪቱን ፡ ሀብት ፡ ቀነሰው

**diminish** (vi.) ተቀነሰ

Our food supplies are diminishing daily. ቀለባችን ፡ በየቀኑ ፡ እየተቀነሰ ፡ ይሄዳል

**diminution**

*His diminution of strength is due to increasing age. ጉልበቱ ፡ የተዳከመው ፡ ከዕድሜ ፡ መግፋት ፡ የተነሣ ፡ ነው

*The diminution of our respect for him was caused by his careless talk. ለሱ ፡ የነበረን ፡ አክብሮት ፡ በግዴለሽ ፡ ንግግሩ ፡ መነመነ

**diminutive** (n.) አነስተኛ ፡ የሆነ ፡ ነገር

Amharic occasionally uses the feminine for the diminutive. አንዳንዴ ፡ ባማርኛ ፡ አነስተኛ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡ በአንስታይ ፡ ጾታ ፡ ይጠራሉ

**diminutive** (adj.) ጥቃቅን

The doll's house contains diminutive furniture. ያሻንጉሊት ፡ ቤት ፡ ጥቃቅን ፡ እቃዎች ፡ ይይዛል

**dimple** ጉድጉድ ፡ ያለ ፡ ምልክት
She has dimples in her cheeks. ጉንጯ ፡ ላይ ፡ ጉድጉድ ፡ ያለ ፡ ምልክት ፡ አለ

**din** (dinned), v. አስተጋባ
The thunder dinned in his ears. ነጐድጓዱ ፡ ጆሮው ፡ ላይ ፡ አስተጋባ

**din** (n.) ጋጋታ
The din of the traffic does not let me sleep. የመኪናው ፡ ጋጋታ ፡ እንቅልፍ ፡ ነሣኝ

**dine** እራት ፡ በላ
Our parents are dining with us tonight. ወላጆቻችን ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ እራት ፡ ይበላሉ

**dine out** እውጭ ፡ በላ
We always dine out on Saturdays. ቅዳሜ ፡ ቅዳሜ ፡ ሁልጊዜ ፡ እውጭ ፡ እንበላለን

**dingy** ቆሸሽ ፡ ያለ
His dingy house is a disgrace to the neighborhood. ቆሸሽ ፡ ያለው ፡ ቤቱ ፡ ለሰፈሩ ፡ አሳፋሪ ፡ ነው

**dining room** ምግብ ፡ ቤት
Bring another chair into the dining room! እምግብ ፡ ቤት ፡ ሌላ ፡ ወንበር ፡ አምጣ

**dinner**
1. እራት. We eat dinner most often at six o'clock. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እራት ፡ የምንበላው ፡ በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ነው
2. የራት ፡ ግብዣ. The Emperor is giving a dinner in the ambassador's honor. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ስለ ፡ አምባሳደሩ ፡ ክብር ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ያደርጋሉ

**have dinner** እራት ፡ በላ
As long as you are here, have dinner with us! እዚህ ፡ ካለህ ፡ እራት ፡ አብረኸን ፡ ብላ

**take to dinner** እራት ፡ ጋበዘ
He wants to take me to dinner. እራት ፡ ሊጋብዘኝ ፡ ይፈልጋል
[See also 'formal, invite']

**dip** (dipped), vt.
1. አጠለቀ. He dipped the bucket into the lake. ባልዲውን ፡ ሐይቁ ፡ ውስጥ ፡ አጠለቀ
2. ቀዳ. The servant dipped water from a spring. ገረዲቱ ፡ ውኃ ፡ ከምንጭ ፡ ቀዳች
3. አጠቀሰ. Dip the bread into the stew! ዳቦሀን ፡ በወጡ ፡ አጥቅሰው
4. ነከረ. She dipped her head into the water. ራሷን ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ነከረች

**dip** (vi.)
1. ጠልቆ ፡ ወጣ. The birds dipped into the ocean. ወፎች ፡ ውቅያኖስ ፡ ውስጥ ፡ ጠልቀው ፡ ወጡ
2. ዘቀጠ. Be careful! The road dips here. ተጠንቀቅ ፤ እዚህ ፡ ጋ ፡ መንገዱ ፡ ይዘቀጣል
3. አወጣ. I have to dip into my savings. ካጠራቀምኩት ፡ ገንዘብ ፡ ማውጣት ፡ አለብኝ

**dip for**
*She dipped into the jar for an olive. የወይራ ፡ ፍሬ ፡ ለማውጣት ፡ እጇን ፡ ማሰሮ ፡ ውስጥ ፡ ከተተች

**dip out** ጨለፈ
He dipped out the stew into the dishes. ወጡን ፡ በሳሕኖቹ ፡ ላይ ፡ ጨለፈ

**diphtheria** [ተላላፊ ፡ የጉሮሮ ፡ በሽታ]

**diploma** የምስክር ፡ ወረቀት
He received his diploma for teaching English. እንግሊዝኛ ፡ የማስተማር ፡ የምስክር ፡ ወረቀቱን ፡ ተቀበለ

**diplomacy** ዲፕሎማሲ
Diplomacy requires many skills. ዲፕሎማሲ ፡ ብዙ ፡ ጥበብን ፡ ይጠይቃል

**diplomat** ዲፕሎማት
Many graduates of the School of Law become diplomats. ከሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚመረቁ ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ ዲፕሎማት ፡ ይሆናሉ

**diplomatic** ዘዴኛ
He is diplomatic in dealing with people. ከሰው ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ሲያደርግ ፡ ዘዴኛ ፡ ነው

**diplomatic corps** ኮር ፡ ዲፕሎማቲክ
He belongs to the diplomatic corps. የኮር ፡ ዲፕሎማቲክ ፡ አባል ፡ ነው

**dire** አደገኛ
Dire calamity threatened the town when the water was cut off. ውኃው ፡ በተቋረጠ ፡ ጊዜ ፡ ከተማዋ ፡ አደገኛ ፡ ስጋት ፡ ላይ ፡ ወደቀች
*He was in dire need of help. እርዳታ ፡ ከፉኛ ፡ ያስፈልገው ፡ ነበር

**direct** (v.)
1. አሳየ. Can you direct me to the post office? ፖስታ ፡ ቤቱን ፡ ልታሳየኝ ፡ ትችላለህ ?
2. መራ. Who directed the orchestra at yesterday's concert? በትላንቱ ፡ የሙዚቃ ፡ በዓል ፡ ላይ ፡ ሙዚቀኞቹን ፡ ይመራ ፡ የነበረው ፡ ማን ፡ ነበር ?
He directed the company through a difficult

time. ኩባንያውን ፡ ባስቸጋሪ ፡ ጊዜያት ፡ ሁሉ ፡ መራ

3. አቀረበ ፤ ሰነዘረ. The chairman directed his remarks to two of the committee members. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ አስተያየቱን ፡ ለሁለቱ ፡ የደርጉ ፡ አባሎች ፡ አቀረበ

He directed his remarks to all of us. አስተያየቱን ፡ ለሁላችንም ፡ ሰነዘረ

4. ተቈጣጠረ. There was no one to direct the workmen. ሠራተኞቹን ፡ የሚቈጣጠር ፡ ሰው ፡ አልነበረም

5. አስተላለፈ. A policeman is directing the traffic. ፖሊሱ ፡ ትራፊኩን ፡ ያስተላልፋል

6. አዘዘ. The captain directed his men to advance. ሻምበሉ ፡ ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንዲያመሩ ፡ አዘዘ

7. ጻፈ. Shall I direct the letter to his home address? ደብዳቤውን ፡ በቤቱ ፡ አድራሻ ፡ ልጻፈው ?

8. አዋለ. We should direct our efforts to useful ends. ጥረታችንን ፡ ሁሉ ፡ ለመልካም ፡ ተግባር ፡ ማዋል ፡ አለብን

**direct** (adj.)

1. ቀጥታ. There is no direct route. ቀጥታ ፡ መንገድ ፡ የለም

2. ቀጥተኛ. He made a direct answer to the charges brought against him. ለቀረበበት ፡ ክስ ፡ ቀጥተኛ ፡ መልስ ፡ ሰጠ

3. የግልጽነት. I like his direct manner. የግልጽነት ፡ ጠባዩ ፡ ያስደስተኛል

4. ሙሉ. He took direct charge of the library. የቤተ ፡ መጻሕፍቱን ፡ ሙሉ ፡ ኀላፊነት ፡ ወሰደ

5. (= adv.) በቀጥታ. That man is a direct descendant of Emperor Menelik. ያ ፡ ሰው ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በቀጥታ ፡ ይወለዳል

*It is the direct opposite of what we expected. እኛ ፡ ካሰብነው ፡ ጋር ፡ ፈጽሞ ፡ አይስማማም

*War will be a direct result of such political action. የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ የፖለቲካ ፡ ጉዳይ ፡ ጦርነት ፡ ማስከተሉ ፡ አይቀርም

**direction**

1. አቅጣጫ. The water splashes in all directions. ውኃው ፡ በሁሉ ፡ አቅጣጫ ፡ ይሰራጫል

2. የሚወስድ ፡ መንገድ. Can you give me directions to the lake? ወደ ፡ ሐይቁ ፡ የሚወስደኝን ፡ መንገድ ፡ ትነግረኛለህ ?

3. መሪነት. They have made great progress under his direction. በሱ ፡ መሪነት ፡ ታላቅ ፡ መሻሻል ፡ አደረጉ

4. ተቈጣጣሪነት. He did the work under my direction. ሥራውን ፡ በኔ ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ ሠራ

5. መመሪያ. Follow the enclosed directions! ተያይዞ ፡ የሚገኘውን ፡ መመሪያ ፡ ተከተል

6. እንጻር. This town shows improvement in many directions. ይህ ፡ ከተማ ፡ በብዙ ፡ እንጻር ፡ መሻሻል ፡ አድርጓል

**in all directions** በያለበት

The water splashes in all directions. ውኃው ፡ በያለበት ፡ ይረጫል

**in .... direction** በ - - በኩል

In which direction did he go? በየት ፡ በኩል ፡ ሄደ ?

[See also 'whichever, wrong']

**directive** መምሪያ

The newspaper published the President's new directives on education. ጋዜጣው ፡ የፕሬዚዳንቱን ፡ አዲስ ፡ የትምህርት ፡ መምሪያ ፡ አትሞ ፡ አወጣ

**directly** በቀጥታ

Let's go directly to the hotel! በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ሆቴል ፡ እንሂድ

**directly opposite** ፊት ፡ ለፊት

Our house is directly opposite the store. ቤታችን ፡ ከሱቁ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ነው

**direct object,** see **object**

**director** ዲሬክተር

He is the director of our company. የኛ ፡ ኩባንያ ፡ ዲሬክተር ፡ ነው

**directory** የስም ፡ ማውጫ

The University of California publishes a directory every year. የካሊፎርኒያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ በያመቱ ፡ የስም ፡ ማውጫ ፡ እያተመ ፡ ያወጣል

[See also 'telephone']

**direful** ሟርተኛ

The direful croak of the raven perturbed him. የቁራው ፡ ሟርተኛ ፡ ድምፅ ፡ ረበሸው

**dirge** ሙሾ

The mourners' dirge could be heard from far away. ያልቃሾች ፡ ሙሾ ፡ ከሩቅ ፡ ይሰማ ፡ ነበር

**dirt**

1. ቆሻሻ. How can I get the dirt off the walls? ቆሻሻውን ፡ ከግድግዳው ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ልጠርገው ፡ እችላለሁ ?

2. እድፍ. How can I get the dirt off my shirt? እድፉን ፡ ከሸሚዜ ፡ እንዴት ፡ ላስለቅቀው ?

[See also 'smear']

**dirty** (v.) አቆሸሸ
Don't dirty your shoes! ጫማህን ፡ አታቆሽሽ

**dirty** (adj.)
1. ቆሻሻ. The floor is dirty. ወለሉ ፡ ቆሻሻ ፡ ነው
2. የብልግና. He likes to tell dirty jokes. የብልግና ፡ ቀልዶች ፡ ማውራት ፡ ይወዳል
*She gave me a dirty look. በጥላቻ ፡ ተመለከተችኝ

**be dirty** ቆሸሸ ፤ አደፈ
Your shirt is dirty. ሸሚዝህ ፡ ቆሽሿል (አድፏል)

**be in a dirty state** ቆሽሾ ፡ አለ
The house was in a dirty state. ቤቱ ፡ ቆሽሾ ፡ ብሎ ፡ ነበር
[See also 'mark, trick']

**disability** ጉድለት
His greatest disability is his constant stammering. የርሱ ፡ ትልቁ ፡ ጉድለቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ መንተባተቡ ፡ ነው
The disability of the plan is that it requires too many engineers. የእቅዱ ፡ ጉድለት ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ መሃንዲሶች ፡ መጠየቁ ፡ ነው

**be a disability for** አሰናከለ
Deafness is a disability for a musician. ደንቆሮነት ፡ ሙዚቀኛን ፡ ያሰናክላል

**disable** ከሥራ ፡ ውጭ ፡ አደረገ
The injury to his knee disabled him for many weeks. የጉልበቱ ፡ መጐዳት ፡ ለብዙ ፡ ሳምንታት ፡ ከሥራው ፡ ውጭ ፡ አደረገው

**disabled** (adj.) አካለ ፡ ስንኩል
The disabled soldiers received a pension from the government. አካለ ፡ ስንኩል ፡ ወታደሮች ፡ ከመንግሥት ፡ ጡረታ ፡ አገኙ

**disabuse (of)** አስተወ
I disabused him of the idea that he could graduate after one year. ካንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የመመረቅ ፡ አሳቡን ፡ አስተውኩት

**disabuse oneself of** ከአእምሮው ፡ አስወገደ
You must disabuse yourself of that notion. ያንን ፡ ሐሳብህን ፡ ከአእምሮህ ፡ ማስወገድ ፡ አለብህ

**disadvantage** ጉዳት
It is a disadvantage to be small when you are standing in a crowd. አጭር ፡ የመሆን ፡ ጉዳቱ ፡ የሚታወቀው ፡ በብዙ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ሲቆም ፡ ነው

**be at a disadvantage** በበለጠ ፡ ተቸገረ
A person who is not Ethiopian is at a disadvantage in learning Amharic. ኢትዮጵያዊ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ አማርኛ ፡ ለመማር ፡ በበለጠ ፡ ይቸገራል

**be to one's disadvantage** የማይመች ፡ ነው
This arrangement is to his disadvantage. ይህ ፡ ዝግጅት ፡ ለሱ ፡ የማይመች ፡ ነው

**put at a disadvantage** አስቸገረ
His inability to speak English puts him at a disadvantage when he attends conferences. እንግሊዝኛ ፡ መናገር ፡ አለመቻሉ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ሲገኝ ፡ ያስቸግረዋል

**(be) disadvantageous (to)** የሚጐዳ ፡ ነው
The terms of the treaty are disadvantageous to our country. የስምምነቱ ፡ አንቀጾች ፡ ሀገራችንን ፡ የሚጐዱ ፡ ናቸው

**disaffected** (adj.) ቅሬታ ፡ የገባው
The disaffected sailors talked of mutiny. ቅሬታ ፡ የገባቸው ፡ መርከበኞች ፡ ሊያሴሩ ፡ አሰቡ

**disagree** አልተስማማም
I disagree with the method. በዘዴው ፡ አልስማማም
Grapes disagree with me. የወይን ፡ ፍሬ ፡ አይስማማኝም

**disagree violently** ተጣላ
They disagreed violently and parted company. ተጣልተው ፡ ተለያዩ

**disagreeable** ደስ ፡ የማይል
He has a disagreeable voice. ደስ ፡ የማይል ፡ ድምፅ ፡ አለው

**disagreement** አለመግባባት ፤ አለመስማማት
The meeting ended in complete disagreement. ስብሰባው ፡ በፍጹም ፡ አለመግባባት ፡ ተበተነ
His conciliatory remarks were very welcome after so much disagreement. ከብዙ ፡ አለመስማማት ፡ በኋላ ፡ አስታራቂ ፡ ሐሳቡን ፡ በመልካም ፡ ተቀበሉት

**disallow** ዋጋ ፡ አልሰጠም
The ministry disallowed the report of the committee. ሚኒስቴሩ ፡ ለደርጉ ፡ ሪፖርት ፡ ዋጋ ፡ አልሰጠም

**(be) disallowed** አልተቀበሉትም
The request for a new trial was disallowed. ጉዳዩ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደገና ፡ እንዲታይ ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ አልተቀበሉትም

**disappear** ጠፋ
He disappeared in the crowd. በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ጠፋ

The scar will always be visible and will never disappear. ጠባሳው ፡ ምንግዜም ፡ ስለማይጠፋ ፡ ዘወትር ፡ ይታያል
The light suddenly disappeared. ብርሃኑ ፡ በድንገት ፡ ጠፋ

**disappearance** መጥፋት
The disappearance of the airplane brought about a search of the area. የአውሮፕላኑ ፡ መጥፋት ፡ በቀበሌው ፡ ፍለጋ ፡ አስከተለ

**disappoint** ቅር ፡ አሰኘ
His conduct disappointed us. ጠባዩ ፡ ቅር ፡ አሰኘን

**be disappointed** ቅር ፡ አለ(ው)
I was very much disappointed when he did not come. ሳይመጣ ፡ በመቅረቱ ፡ በጣም ፡ ቅር ፡ አለኝ

**disappointment**
1. ቅሬታ. He spoke openly of his disappointment. ስለተሰማው ፡ ቅሬታ ፡ በግልጽ ፡ ተናገረ
2. ብስጭት. His delusions of grandeur led him to disappointments. ከንቱ ፡ የትልቅነት ፡ ስሜት ፡ ከብስጭት ፡ ላይ ፡ ጣለው
*Even after disappointments hope still abides. ጉዳያችን ፡ ባይሳካልንም ፡ እንኳ ፡ ተስፋ ፡ ማድረጋችን ፡ አይቀርም

**be a disappointment** አሳዘነ
Her lazy son was a disappointment to her. ሰነፍ ፡ ልጇ ፡ በጣም ፡ ያሳዝናት ፡ ነበር

**disapproval**
1. በነገሩ ፡ አለመስማማት. He shook his head in disapproval. በነገሩ ፡ ባለመስማማት ፡ ራሱን ፡ ነቀነቀ
2. ትዝብት. The elders observed the doings of the young people with disapproval. ሽማግሌዎች ፡ የወጣቶችን ፡ ድርጊት ፡ በትዝብት ፡ ተመለከቱ
3. ተቃውሞ. A frown is often an intimation of disapproval. ፊትን ፡ መቋጠር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የተቃውሞ ፡ ምልክት ፡ ነው

**meet with disapproval** ተነቀፈ
His remarks met with general disapproval. የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ በሁሉም ፡ ተነቀፈ

**disapprove**
1. ተቃወመ. Does he disapprove of people kissing in public? የሰዎችን ፡ ባደባባይ ፡ መሳሳም ፡ ይቃወማል ?
2. አልተስማማ(በትም). The higher judge disapproved the verdict. ከፍተኛው ፡ ዳኛ ፡ በፍርዱ ፡ አልተስማማበትም
3. አልተቀበለም. The committee disapproved his request for a scholarship. ዶርጉ ፡ የነጻ ፡ ትምህርት ፡ እንዲሰጠው ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ አልተቀበለውም
4. ነቀፈ. The teacher disapproved of the students' florid writing. መምህሩ ፡ የተማሪዎቹን ፡ የተቀባባ ፡ ጽሑፍ ፡ ነቀፈ
5. አጥላላ. The mother disapproved of her daughter's garish earrings. ልጅቷ ፡ ያደረገችውን ፡ ብልጭልጭ ፡ ጉትቻ ፡ እናትየዋ ፡ አጥላላችባት

**disarm**
1. የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ቀነሰ. It is difficult to persuade the great powers to disarm. ኀያላን ፡ መንግሥታት ፡ የጦር ፡ መሣሪያን ፡ እንዲቀንሱ ፡ ማግባባት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. መሣሪያውን ፡ ገፈፈው. The police captured the bandit and disarmed him. ፖሊሱ ፡ ሽፍታውን ፡ ይዞ ፡ መሣሪያውን ፡ ገፈፈው
3. አበረደ. The speaker's frankness disarmed the angry mob. ተናጋሪው ፡ ፍርጥ ፡ አድርጎ ፡ እውነቱን ፡ መናገሩ ፡ የተናደደውን ፡ ሕዝብ ፡ አበረደው
*His smile disarmed us. ፈገግታው ፡ እንድናቀርበው ፡ አደረገን

**be disarmed** መሣሪያውን ፡ ተገፈፈ
The prisoners were quickly disarmed. እስረኞቹ ፡ መሣሪያቸውን ፡ ወዲያውኑ ፡ ተገፈፉ

**disarmament** የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ቅነሳ
The great powers are going to hold a disarmament conference. ኀያላን ፡ መንግሥታት ፡ ስለ ፡ ጦር ፡ መሣሪያ ፡ ቅነሳ ፡ ስብሰባ ፡ ሊያደርጉ ፡ ነው

**disarray** ትርምስ
The meeting ended in disarray. ስብሰባው ፡ በትርምስ ፡ ተፈጸመ

**disaster**
1.መቅሠፍት. The last earthquake was the greatest disaster in years. ያለፈው ፡ የመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ በብዙ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ከደረሱት ፡ ሁሉ ፡ ኀይለኛ ፡ መቅሠፍት ፡ ነበር
2. ጥፋት. I have a premonition of disaster. ጥፋት ፡ እንደሚደርስ ፡ ተሰማኝ
3. መዓት. The frequent mishaps boded disaster. የተደጋገሙት ፡ አደጋዎች ፡ የመዓት ፡ ምልክቶች ፡ ነበሩ
4. አደጋ. How will he recoup after such a disaster? ከእንደዚያ ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ በኋላ ፡ እንዴት ፡ ያንሰራራል ?
[See also 'court']

**disastrous**
1. አሰቃቂ ፤ አደገኛ. A disastrous accident

occurred on the highway. በአውራ ፡ ጐዳናው ፡ ላይ ፡ አሰቃቂ ፡ አደጋ ፡ ደረሰ
A disastrous flood destroyed the fields. አደገኛ ፡ ጐርፍ ፡ እርሻውን ፡ አጠፋው
2. አጥፊ. His guidance of foreign policy proved disastrous. የውጭ ፡ አገር ፡ ፖሊሲ ፡ አመራሩ ፡ አጥፊ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

**prove disastrous to** ጠንቅ ፡ ነው
The rain and cold proved disastrous to his health. ዝናብና ፡ ብርድ ፡ ለጤንነቱ ፡ ጠንቅ ፡ ናቸው

**disavow** አስተባበለ
He disavowed any share in the plot. በአድማው ፡ ውስጥ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ተካፋይ ፡ እንዳልነበረ ፡ አስተባበለ

**disband** (vt.) አፈረሰ
The principal disbanded all clubs in our school. ሥራ ፡ መሪው ፡ በትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ክበቦች ፡ ሁሉ ፡ አፈረሰ

**disband** (vi.) ተበተነ ፤ ፈረሰ
The troops disbanded at the end of the parade. ወታደሮቹ ፡ ሰልፉ ፡ እንዳለቀ ፡ ተበተኑ
The disunity of the members resulted in the club's disbanding. ያባሎቹ ፡ አለመስማማት ፡ ክበቡን ፡ ከመፍረስ ፡ አደረሰው

**be disbanded** ተበተነ
The army was disbanded at the end of the war. በጦርነቱ ፡ መጨረሻ ፡ ሰራዊቱ ፡ ተበተነ

**disbelieve** አላመነም
His mother disbelieved his story. እናቱ ፡ የሰጠውን ፡ ምክንያት ፡ አላመነችውም

**disburse** ከፈለ
The treasurer disburses their salaries. ገንዘብ ፡ ያዡ ፡ ደሞዛቸውን ፡ ይከፍላል

**discard** ጣለ
He discarded his winter clothes. የክረምት ፡ ልብሱን ፡ ጣለ

**discern**
1. ለየ. It is often difficult to discern the truth of what we are told. ከተነገርነው ፡ ውስጥ ፡ እውነቱን ፡ መለየት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያዳግተናል
2. አየ. He discerned the figure of a man in the distance. ከሩቅ ፡ የሰው ፡ ቅርጽ ፡ አየ
3. ተረዳ. I discerned his plan to gain the presidency. ዓላማው ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ለመሆን ፡ እንደሆነ ፡ ተረዳሁ

**discerning**
*His wife has a discerning taste in clothes. ሚስቱ ፡ የልብስ ፡ መምረጥ ፡ ችሎታ ፡ አላት
*He is a discerning critic of French poetry. የፈረንሳይን ፡ ግጥም ፡ በረቂቅ ፡ ሁኔታ ፡ ይተቻል

**discharge** (vt.)
1. አራገፈ. The ship discharged its cargo at Massawa. መርከቡ ፡ ጭነቱን ፡ ምፅዋ ፡ ላይ ፡ አራገፈ
2. አከናወነ. He discharged his duties promptly. ሥራውን ፡ በሚገባ ፡ አከናወነ
3. እንዲወጣ ፡ አዘዘው. The doctor discharged the patient from the hospital. ሐኪሙ ፡ በሽተኛውን ፡ ከሐኪም ፡ ቤት ፡ እንዲወጣ ፡ አዘዘው
4. ከሥራ ፡ አስወጣ. The factory discharged many workers. ፋብሪካው ፡ ብዙ ፡ ሠራተኞች ፡ ከሥራ ፡ አስወጣ
5. ረፈተ. The commanding officer discharged him from the army. አዛዡ ፡ መኰንን ፡ ከወታደርነት ፡ ረፈተው
6. ከፈለ. I have discharged all my debts. ያለብኝን ፡ ዕዳ ፡ በሙሉ ፡ ከፍያለሁ

**discharge** (vi.)
1. ፈሰሰ. The stream discharges into the lake. ወንዙ ፡ ሐይቁ ፡ ውስጥ ፡ ይፈሳል
2. ባረቀ. The gun discharged when he dropped it on the floor. ጠመንጃውን ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ በጣለው ፡ ጊዜ ፡ ባረቀ

**be discharged**
1. ተለቀቀ. The accused man was found not guilty and was discharged. ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ባለመገኘቱ ፡ ተለቀቀ
2. ተረፈተ. He was discharged from the army when he completed his service. አገልግሎቱን ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ከጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ ተረፈተ

**discharge** (n.)
1. መተኰስ. The discharge of the gun startled us. የጠመንጃው ፡ መተኰስ ፡ አስደነገጠን
2. የመሰናበቻ ፡ ደብዳቤ. He received his discharge from the army. ከጦር ፡ ሰራዊት ፡ የመሰናበቻ ፡ ደብዳቤ ፡ ተቀበለ
3. ድምፅ. The dynamite discharge could be heard for a mile. የድማሚቱ ፡ ድምፅ ፡ ከሩቅ ፡ ይሰማ ፡ ነበር
4. (= to discharge) ማራገፍ. The discharge of this cargo will not take long. ጭነቱን ፡ ማራገፍ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይፈጅም
*An official should be honest in the discharge of his duties. ባለሥልጣን ፡ ሥራውን ፡ በሚያከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ ታማኝ ፡ መሆን ፡ አለበት

**disciple** ደቀ ፡ መዝሙር
John was a disciple of Christ. ዮሐንስ ፡ የክርስቶስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነበር

He is a disciple of Freud. የፍሮይድ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነው

**disciplinary** የቅጣት
Disciplinary measures will be taken against unruly students. ባዋኪ ፡ ተማሪዎች ፡ ላይ ፡ የቅጣት ፡ እርምጃዎች ፡ ይወሰዳሉ

**discipline** (v.) ቀጣ
He disciplined the students for their unruly behavior. ተማሪዎቹን ፡ ከሥርዓት ፡ ውጭ ፡ ስለሆነው ፡ ተግባራቸው ፡ ቀጣቸው
*A good officer must know how to discipline men. ጥሩ ፡ መኰንን ፡ ወታደሮቹን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲያከብሩ ፡ ማድረግን ፡ ማወቅ ፡ አለበት

**discipline** (n.)
1. ሥነ ፡ ሥርዓት. He insists on strict discipline. ጥብቅ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይኑር ፡ ይላል
2. መለማመጃ. Question and answer work is a good discipline for learning a language. ጥያቄና ፡ መልስ ፡ ቋንቋን ፡ ለመማር ፡ ጥሩ ፡ መለማመጃ ፡ ነው
3. ትምህርት. Mathematics and astronomy are related disciplines. ሒሳብና ፡ አስትሮኖሚ ፡ የተቀራረቡ ፡ ትምህርቶች ፡ ናቸው

**enforce discipline** ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ አስከበረ
The police took steps to enforce discipline. ፖሊስ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ ለማስከበር ፡ እርምጃ ፡ ወሰደ

**disclaim**
*He disclaimed all knowledge of the affair. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ምንም ፡ አላውቅም ፡ አለ
*He disclaimed all responsibility for the accident. ባደጋው ፡ ምንም ፡ የሚያስጠይቀኝ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ አለ

**disclose**
1. አወጣ(በት). He disclosed my secret to my worst enemy. ምስጢሬን ፡ ለዋናው ፡ ጠላቴ ፡ አወጣብኝ
2. ገለጸ(ተገለጸ). It was disclosed today that the visitor would arrive by plane. እንግዳው ፡ በአውሮፕላን ፡ እንደሚገቡ ፡ ዛሬ ፡ ተገለጸ

**disclosure** (= to be disclosed) መገለጽ
The disclosure of the epidemic frightened many. የተላላፊ ፡ በሽታ ፡ መግባት ፡ መገለጽ ፡ ብዙዎችን ፡ አስደነገጣቸው

**discolor** ቀለም ፡ አበላሸ
The fire had discolored the building. እሳቱ ፡ የሕንጻውን ፡ ቀለም ፡ አበላሽቶታል

**discomfit** በጣም ፡ አበሳጨ
The warning that whiskey was bad for them greatly discomfited the drinkers. ዊስኪ ፡ መጥፎ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ጠጪዎችን ፡ በጣም ፡ አበሳጫቸው

**discomfort**
1. መጉሳቈል. Discomfort is incidental to travel by mule. በበቅሎ ፡ ስትጓዝ ፡ መጉሳቈል ፡ የማይቀር ፡ ነው
2. ሥቃይ. The discomfort caused by the disease was hard to bear. በሽታው ፡ ያስከተለው ፡ ሥቃይ ፡ ሊታገሡት ፡ የሚያዳግት ፡ ነበር

**disconcert** አደናገረ
Arresting the innocent man disconcerted the policeman. የንጹሑ ፡ ሰው ፡ መያዝ ፡ ፖሊሱን ፡ አደናገረው

**disconnect**
1. ነቀለ. He disconnected the radio and took it from the room. ራዲዮኑን ፡ ነቅሎ ፡ ከክፍሉ ፡ ወሰደው
2. ቈረጠ. The company disconnected the telephone. ኩባንያው ፡ ስልኩን ፡ ቈረጠ

**disconnected** (adj.) ያልተያያዘ
The injured man could give only a disconnected account of the accident. የቈሰለው ፡ ሰውዬ ፡ ስለ ፡ አደጋው ፡ ሁናቴ ፡ የሰጠው ፡ መግለጫ ፡ ያልተያያዘ ፡ ነበር

**discontent** ቅሬታ ፤ ሕዝባዊ ፡ ቅሬታ
There was an expression of discontent on her face. የቅሬታ ፡ ምልክት ፡ በፊቷ ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ ነበር
Many countries seethe with discontent. ብዙ ፡ አገሮች ፡ በሕዝባዊ ፡ ቅሬታ ፡ ተፋፍመዋል

**(be) discontented** ቅር ፡ አለ(ው)
He is discontented with his job. በሥራው ፡ ቅር ፡ ብሎታል

**discontinue** (vt.) አቋረጠ
Due to illness he discontinued his work. በበሽታው ፡ ምክንያት ፡ ሥራውን ፡ አቋረጠ

**discontinue** (vi.) ተቋረጠ
Trade will discontinue if custom dues are raised. ቀረጥ ፡ ሲጨመር ፡ ንግድ ፡ ይቋረጣል

**discord**
1. ብጥብጥ. What has brought discord into the family? በቤተሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ብጥብጥ ፡ ያስከተለው ፡ ምንድነው ?

2. አለመስማማት. Discord among nations may lead to war. ያገሮች ፡ አለመስማማት ፡ ጦርነት ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል
3. አለመቀነባበር. The discord in modern music startles many people. የዘመናዊ ፡ ሙዚቃ ፡ አለመቀነባበር ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያደናግራል

**discordant** የሚጋጩ
Many discordant views were expressed. ብዙ ፡ የሚጋጩ ፡ ሐሳቦች ፡ ቀርበው ፡ ነበር
**be discordant** ደስ ፡ የማይል ፡ ድምፅ ፡ አለው
Many automobile horns are discordant. ብዙ ፡ የአውቶሞቢል ፡ ጥሩምባዎች ፡ ደስ ፡ የማይል ፡ ድምፅ ፡ አላቸው

**discount** (v.)
1. በሙሉ ፡ አምኖ ፡ አልተቀበለም. You have to discount occasionally what you read in the newspaper. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ የምታነበውን ፡ በሙሉ ፡ አምነህ ፡ አትቀበለው
2. ከቁጥር ፡ አላገባም. Even if we discount the irrelevant materials, the thesis remains mediocre. የማይረባውን ፡ ጉዳይ ፡ እንኳ ፡ ከቁጥር ፡ ባናገባ ፡ ጽሑፉ ፡ ከምንም ፡ አይቈጠር
3. ቅናሽ ፡ አደረገ. The stores discount all bills paid within 30 days. ሱቆች ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ለሚከፈሉ ፡ ሒሳቦች ፡ ቅናሽ ፡ ያደርጋሉ

**discount** (n.) ቅናሽ
Can you get a discount on these books? ለነዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ ቅናሽ ፡ ልታገኝ ፡ ትችላለህ ?

**discourage** (vt.)
1. መፈለጉን ፡ እንዲተው ፡ አደረገ. We tried to discourage him from climbing the mountain without a guide. ተራራውን ፡ ያለ ፡ መሪ ፡ ለመውጣት ፡ መፈለጉን ፡ እንዲተው ፡ ለማድረግ ፡ ሞከርን
2. ተስፋ ፡ አስቈረጠ. Repeated failures discouraged him. ደጋግሞ ፡ መውደቁ ፡ ተስፋ ፡ አስቈረጠው
3. አባረረ. His unfriendly attitude discourages visitors. ሰው ፡ ያለመውደድ ፡ ጠባዩ ፡ ጐብኝዎችን ፡ ያባርራል
**discourage** (vi.) ተስፋ ፡ ቈረጠ
Some people discourage easily. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በቀላሉ ፡ ተስፋ ፡ ይቈርጣሉ

**discouraged, get (be) ~** ተስፋ ፡ ቈረጠ
He gets discouraged easily. በቀላሉ ፡ ተስፋ ፡ ይቈርጣል
Albeit he has failed twice, he is not discouraged. ምንም ፡ እንኳን ፡ ሁለቴ ፡ ቢወድቅም ፡ ተስፋ ፡ አልቈረጠም

**discouragement, be a ~** ተስፋ ፡ አስቈረጠ
Lack of money is a big discouragement. ገንዘብ ፡ ማጣት ፡ ተስፋ ፡ ያስቈርጣል
**in his discouragement** ተስፋ ፡ ቈርጦ
In his discouragement he committed suicide. ተስፋ ፡ ቈርጦ ፡ ራሱን ፡ ገደለ

**(be) discouraging** ተስፋ ፡ አስቈረጠ
The results are very discouraging. ውጤቱ ፡ በጣም ፡ ተስፋ ፡ ያስቈርጣል

**discourse** (v.) ሰፊ ፡ ንግግር ፡ አደረገ
He discoursed all day on economics. ቀኑን ፡ በሙሉ ፡ ስለ ፡ ኢኮኖሚክስ ፡ ሰፊ ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**discourse** (n.) ንግግር
He gave a long discourse on how to grow tomatoes. ቲማቲም ፡ እንዴት ፡ ለማብቀል ፡ እንደሚቻል ፡ ረጅም ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**discourteous** ባለጌ
The discourteous salesman was dismissed. ባለጌው ፡ አሻሻጭ ፡ ከሥራ ፡ ተባረረ
**be discourteous** ድፍረት ፡ ነው
It was discourteous of you to arrive late. ዘግይተህ ፡ መምጣትህ ፡ ድፍረት ፡ ነው

**discover**
1. ፈጠረ. He discovered a new teaching method. አዲስ ፡ የማስተማር ፡ ዘዴ ፡ ፈጠረ
2. ተገነዘበ. We suddenly discovered it was too late to catch the train. በባቡሩ ፡ ለመሳፈር ፡ ጊዜው ፡ እንደተላለፈ ፡ በድንገት ፡ ተገነዘብን
3. አገኘ. He discovered the thief hiding under the bed. ሰውዬው ፡ ሌባውን ፡ አልጋው ፡ ሥር ፡ ተደብቆ ፡ አገኘው
Columbus discovered America in 1492. ኮሎምበስ ፡ አሜሪካን ፡ በ፲፬፻፺፪ ዓ. ም. አገኘ
4. ዐወቀ. He discovered the deception too late. የማታለል ፡ ሥራ ፡ መሆኑን ፡ ጊዜው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ዐወቀ
5. ደረሰ(በት). The enemy discovered our plans. ጠላት ፡ እቅዳችንን ፡ ደረሰበት

**discovery** (discoveries)
1. መገኘት. The discovery of gold is exciting news. የወርቅ ፡ መገኘት ፡ የሚያስደስት ፡ ወሬ ፡ ነው
2. አዲስ ፡ የተደረሰበት ፡ ነገር. The discovery gave him ammunition in his campaign. አዲስ ፡ የተደረሰበት ፡ ነገር ፡ ለውድድሩ ፡ መሣሪያ ፡ ሆነው
3.ያገኘው ፡ ነገር. His scientific discoveries were

far ahead of his time. በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ጥናት ፡ ያገኛቸው ፡ ነገሮች ፡ ከጊዜው ፡ የቀደሙ ፡ ነበሩ
4. ፍልሰፋ. He made a discovery that startled the world. ዓለምን ፡ ያስገረመ ፡ ፍልሰፋ ፡ አደረገ
*The thief passed the day in fear of discovery. ሌባው ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ አሁን ፡ ካሁን ፡ ተያዝኩ ፡ እያለ ፡ ሲበረግግ ፡ ዋለ

**make a discovery** ፈለሰፈ
He made an important discovery. ታላቅ ፡ ነገር ፡ ፈለሰፈ

## discredit (v.)
1. ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ አስገመተ. His behavior will discredit him with the public. ጠባዩ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ያስገምተዋል
2. ከንቱ ፡ አደረገ. He tries to discredit the belief in the evil eye. የቡዳን ፡ እምነት ፡ ከንቱ ፡ ለማድረግ ፡ ይሞክራል
3. አልተቀበለም. I discredit all those stories. ወሬዎቹን ፡ ሁሉ ፡ አልቀበልም
4. (= be discredited) ስሙ ፡ ጠፋ. Losing three battles discredited the general. በሦስት ፡ ጦር ፡ ሜዳዎች ፡ ላይ ፡ ድል ፡ በመሆኑ ፡ ጄኔራሉ ፡ ስሙ ፡ ጠፋ
*The lawyer discredited the witness by showing that he had been bribed. ጠበቃው ፡ ምስክሩ ፡ ጉቦ ፡ መብላቱን ፡ ገልጾ ፡ የሰጠው ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ የማይታመን ፡ መሆኑን ፡ አስረዳ

**be discredited** ዋጋ ፡ አጣ
His theory has been discredited by all scientists. ፅንሰ ፡ ሐሳቡ ፡ በሁሉም ፡ ሊቃውንት ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ አጣ

## discredit (n.), bring ~ ስም ፡ አጕደፈ
If you continue to act this way, you will bring discredit on yourself. አድራጎትህን ፡ እንደዚህ ፡ የምትቀጥል ፡ ከሆነ ፡ ስምህን ፡ ታጐድፋለህ

**bring into discredit** ከንቱ ፡ አደረገ
Science brings old beliefs into discredit. ሳይንስ ፡ የቆዩ ፡ እምነቶችን ፡ ከንቱ ፡ ያደርጋቸዋል

**be a discredit to** አዋራጅ ፡ ሆነ
The boy was a discredit to his family. ልጁ ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ አዋራጅ ፡ ሆነ

## discreet ጥንቁቅ
The ambassador must be discreet in dealing with foreigners. አምባሳደሩ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ሲያደርግ ፡ ጥንቁቅ ፡ መሆን ፡ አለበት

**be discreet** ምስጢር ፡ ጳጠረ
He is not very discreet, so don't tell him anything. ምስጢር ፡ አይቋጥርምና ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አትንገረው

## discrepancy ልዩነት
There was a great discrepancy between the two accounts of the accident. ስለ ፡ አደጋው ፡ በተሰጡት ፡ በሁለቱ ፡ መግለጫዎች ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ ልዩነት ፡ ነበር

## discretion
*Making final plans was left to the President's discretion. የመጨረሻ ፡ ውሳኔዎች ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ እንደመሰለው ፡ እንዲፈጽም ፡ ተደረገ

**show discretion** አመዛዘነ
You must show more discretion in choosing your friends. ጓደኞችህን ፡ ስትመርጥ ፡ ማመዛዘን ፡ አለብህ

## discriminate
1. ለየ. Can you discriminate good books from bad? መጥፎና ፡ ጥሩ ፡ መጽሐፎችን ፡ ለመለየት ፡ ትችላለህ ?
2. አደላ. The law does not discriminate against anyone. ሕጉ ፡ ለማንም ፡ አያደላም
He discriminates in favor of his relatives. ለዘመዶቹ ፡ ያደላል

**discriminate against**
* He discrimintates against foreigners. የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎችን ፡ ከወገኖቹ ፡ በተለየ ፡ ዓይን ፡ ይመለከታቸዋል

## discrimination
1. የዘር ፡ ልዩነት ፤ የቀለም ፡ ልዩነት. Discrimination is widespread in South Africa. በደቡብ ፡ አፍሪካ ፡ የዘር ፡ ልዩነት ፡ (የቀለም ፡ ልዩነት) ፡ በሰፊው ፡ አለ
2. ምርጫ. Some people do not show much discrimination in their choice of friends. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ጓደኛ ፡ ሲያበጁ ፡ ምንም ፡ ምርጫ ፡ አያደርጉም
3. ማስተዋል. She chose her dresses with great discrimination. ልብሷን ፡ በታላቅ ፡ ማስተዋል ፡ መረጠች

**without discrimination** ሳያማርጥ
Do not buy clothes without discrimination! ሳታማርጥ ፡ ልብስ ፡ አትግዛ

## discuss
1. ተነጋገረ. Discuss the matter with him! ነገሩን ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ተነጋገርበት
2. ተወያየ. He discussed his problem with a friend. ችግሩን ፡ ከጓደኛው ፡ ጋር ፡ ተወያየ

**discussion**
1. ውይይት. The discussion was about the best way to reduce crime. ውይይቱ ፡ ወንጀልን ፡ ለመቀነስ ፡ ስላለው ፡ ምርጥ ፡ ዘዴ ፡ ነበር
2. ክርክር. Parliamentary discussion on the budget lasted several days. በምክር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ባጀቱ ፡ የተደረገው ፡ ክርክር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፈጀ

**disdain** (v.)
1. ናቀ. Great men should disdain flattery. ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ከንቱ ፡ ውዳሴን ፡ መናቅ ፡ አለባቸው
He disdained my offer to help. ለመርዳት ፡ ያቀረብኩትን ፡ ሐሳብ ፡ ናቀብኝ
2. ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ተመለከተ. The honest official disdained the offer of a bribe. ታማኙ ፡ ሹም ፡ ጉቦ ፡ መቀበልን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ተመለከተ

**disdain** (n.) ንቀት
He greeted the servants with disdain. ላሽከሮቹ ፡ በንቀት ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠ

**disdainful, ~ attitude** ሰውን ፡ የመናቅ ፡ ጠባይ
His disdainful attitude made him many enemies. ሰውን ፡ የመናቅ ፡ ጠባዩ ፡ ብዙ ፡ ጠላት ፡ አፈራበት

**disease** በሽታ
This disease is contagious. ይህ ፡ በሽታ ፡ ተላላፊ ፡ ነው

**diseased** በሽተኛ
The diseased leg had to be amputated. በሽተኛው ፡ እግሩ ፡ መቈረጥ ፡ ነበረበት

**be diseased** በሽታ ፡ አለበት
The meat is diseased. Do not eat it! ሥጋው ፡ በሽታ ፡ ስላለበት ፡ እንዳትበላው

**disembark** (vt.) አወረደ
They disembarked the passengers in New York. ተሳፋሪዎቹን ፡ ኒውዮርክ ፡ ላይ ፡ አወረረዷቸው

**disembark** (vi.) ወረደ
The passengers disembarked at Bole airport. መንገደኞቹ ፡ በቦሌ ፡ ያውሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ወረዱ

**disembody** (disembodied) ከሥጋ ፡ ለየ
Death disembodies the soul. ሞት ፡ ነፍስን ፡ ከሥጋ ፡ ይለያል

**disenchant** (= be disenchanted) ቅር ፡ ተሰኘ
We admired him at first, but his dishonesty soon disenchanted us. በመጀመሪያ ፡ አደነቅነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ታማኝ ፡ ሆኖ ፡ ስላላገኘነው ፡ ወዲያውኑ ፡ ቅር ፡ ተሰኘን

**be disenchanted**
*Anyone who thinks it never rains in Mexico will be disenchanted by a visit there. ሜክሲኮ ፡ ዝናብ ፡ ፈጽሞ ፡ አይዘንብም ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ እዚያ ፡ ቢሄድ ፡ መሳሳቱን ፡ ይረዳዋል

**disengage** አላቀቀ
The mother disengaged her hands from that of the sleeping child. እናትዮዋ ፡ እጇቿን ፡ ከተኛው ፡ ሕፃን ፡ አላቀቀች

**disentangle**
1. ፈታ. It took hours to disentangle the vines. ሐረጉን ፡ ለመፍታት ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ወሰደ
2. የ - - - ውል ፡ አገኘ. It took him several hours to disentangle the rope. የገመዱን ፡ ውል ፡ ለማግኘት ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ፈጀበት
3. ለየ. It is hard to disentangle truth from falsehood. እውነትን ፡ ከሐሰት ፡ መለየት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**disfavor**
*He viewed my plans with disfavor. እቅዴን ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀረ
*The minister incurred the king's disfavor. ሚኒስትሩ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ አጣ

**disfigure** አጠፋ
The scar disfigured his face. ጠባሳው ፡ መልኩን ፡ አጠፋው

**disgorge** ተፋ
The volcano disgorged fire and smoke. እሳተ ፡ ገሞራው ፡ እሳትና ፡ ጭስ ፡ ተፋ

**disgrace** (v.) አሳፈረ
He disgraced his mother by being rude to her guests. በእንግዶች ፡ ፊት ፡ በመባለግ ፡ እናቱን ፡ አሳፈረ

**be disgraced** ተዋረደ
He was disgraced because he intrigued with the enemy. ከጠላት ፡ ጋር ፡ ስለተመሳጠረ ፡ ተዋረደ

**disgrace** (n.)
1. አሳፋሪ ፤ ነውር. These slums are a disgrace to the city. እነዚህ ፡ ውዳቂ ፡ ቤቶች ፡ ለከተማይቱ ፡ አሳፋሪዎች ፡ (ነውር) ፡ ናቸው
2. ኀፍረት. His marriage was considered a disgrace for the family. የሱ ፡ ጋብቻ ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ እንደ ፡ ኀፍረት ፡ ተቈጠረ
3. ውርደት. His disgrace became publicly known. ውርደቱ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ታወቀ

**be in disgrace** ውርደት ፡ ላይ ፡ ወደቀ
He told a lie and is now in disgrace. ውሸት ፡ ተናግሮ ፡ አሁን ፡ ውርደት ፡ ላይ ፡ ወድቋል

**fall into disgrace**
*He has fallen into disgrace with the Emperor. ንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊት ፡ ነሡት

**disgraceful** የሚያሳፍር
It is disgraceful the way he drinks. ጠጪነቱ ፡ በጣም ፡ የሚያሳፍር ፡ ነው

**disguise** (v.) ደበቀ
He disguised his sorrow with a smiling face. ሐዘኑን ፡ በፈገግታ ፡ ደበቀው
*He disguised his handwriting. ጽሕፈቱ ፡ እንዳ ይታወቅ ፡ አድርጎ ፡ ጻፈ

**disguise oneself as** መስሎ ፡ ታየ
The spy disguised himself as an old man. ሰላዩ ፡ ሽማግሌ ፡ መስሎ ፡ ታየ

**be disguised as**
*This is a door, but it is disguised as a bookcase. ይህ ፡ በር ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የመጻሕፍት ፡ መ ደርደሪያ ፡ እንዲመስል ፡ ሆኖ ፡ ተሠርቷል

**disguise** (n.) ማሳሳቻ ፡ መልክ
I did not recognize him in his disguise. በማሳሳ ቻ ፡ መልኩ ፡ ልለየው ፡ አልቻልኩም

**put on a disguise** ማንነቱን ፡ ሰወረ
He put on a disguise so the police would not recognize him. ፖሊስ ፡ ለይቶ ፡ እንዳያውቀው ፡ ማንነቱን ፡ ሰወረ

**disgust** (v.) አስጠላ
His conduct disgusts me. ጠባዩ ፡ ያስጠላኛል

**disgust** (n.) ጽያፌ
The smell of garbage filled her with disgust. የቆሻሻው ፡ ግማት ፡ ጽያፌ ፡ አሳደረባት

**fill with disgust** አስጸየፈ ፤ ጽያፌ ፡ አሳደረ(በት)
The sight of garbage filled her with disgust. ቆሻሻ ፡ ማየቱ ፡ አስጸየፋት ፡ (ጽያፌ ፡ አሳደረባት)

**in disgust** ተከፍቶ
He turned away in disgust. ተከፍቶ ፡ ዞር ፡ አለ

**disgusting** ጺያፍ
The old man thought that the sight of lovers kissing in public was disgusting. ሽማግሌው ፡ ሰው ፡ የፍቅረኞቹ ፡ ባደባባይ ፡ መሳሳም ፡ ጺያ ፍ ፡ መሰለው

**be disgusting** (= trans.) አስጠላ
The disorder of the boys' room was disgusting. የልጆቹ ፡ ክፍል ፡ መዝረክረክ ፡ ያስጠላ ፡ ነበር

**dish** (n.)
1. ሳሕን. We will have to buy dishes. ሳሕን ፡ መግዛት ፡ አለብን
I would like a dish of ice cream. አንድ ፡ ሳሕን ፡ አይስክሬም ፡ እፈልጋለሁ
2. ምግብ. Chopped meat is the dish I like best. በጣም ፡ የምወደው ፡ ምግብ ፡ ክትፎ ፡ ነው

**do the dishes** ሳሕኖች ፡ አጸዳ
We have to do the dishes now. ሳሕኖቹን ፡ አ ሁን ፡ ማጽዳት ፡ አለብን

**dish** (v.), ~ **out** አቀረበ
She dished out food to the hungry children. ለተራቡት ፡ ልጆች ፡ ምግብ ፡ አቀረበችላቸው

**dishearten** ተስፋ ፡ አስቈረጠ
A long drought disheartens a farmer. ረዘም ፡ ያ ለ ፡ ድርቀት ፡ ገበሬን ፡ ተስፋ ፡ ያስቈርጣል

**be disheartened** ተስፋ ፡ ቈረጠ
Don't be disheartened by this one failure! አንዴ ፡ ብቻ ፡ ስላልተሳካልህ ፡ ተስፋ ፡ አትቍረጥ

**disheveled** (= be disheveled) ተመሰቃቀለ
Her disheveled hair was due to the strong wind. ጸጉሯ ፡ የተመሰቃቀለው ፡ ከኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ የተነሣ ፡ ነው

**dishonest**
1. ሸፋጭ. He is very dishonest in business. በንግድ ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ ሸፋጭ ፡ ነው
2. አታላይ. The dishonest general colored his report of the battle. አታላዩ ፡ ጀኔራል ፡ ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ የሰጠውን ፡ መግለጫ ፡ አዛባው
3. እምነት ፡ ጐደሎ. Don't lend yourself to such dishonest plans! እንደዚህ ፡ ባለ ፡ እምነት ፡ ጐደሎ ፡ አቅድ ፡ ውስጥ ፡ አትግባ
4. የማይታመን. We found him to be dishonest. የማይታመን ፡ ሆኖ ፡ አገኘነው

**dishonest dealings** ማጭበርበር
He heaped up riches by dishonest dealings. በማጭበርበር ፡ ሀብት ፡ አከማቸ

**dishonesty** ታማኝ ፡ ያለመሆን
His dishonesty makes him unsuitable for the treasurer's job. ታማኝ ፡ ያለመሆኑ ፡ ለገንዘብ ፡ ያዥነቱ ፡ ሥራ ፡ ተገቢ ፡ አያደርገውም

**dishonor** (v.) አዋረደ
He dishonored his family by incurring debts. ዕዳ ፡ በመግባት ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ አዋረደ

**dishonor** (n.) ውርደት
He prefers death to dishonor. ከውርደት ፡ ሞ ትን ፡ ይመርጣል

**dishonorable** አሳፋሪ
Dishonorable conduct will be punished by dismissal. አሳፋሪ ፡ ምግባር ፡ ከሥራ ፡ ያስወጣል

**(be) disillusioned** እንዳሰበው ፡ ሳይሆን ፡ ቀረ
They had thought that the new colony would be a paradise, but they were soon disillusioned. አዲሱ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ገነት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አስበው ፡ ነበር ፡ ግን ፡ እንዳሰቡት ፡ ሳይሆን ፡ ቀረ

**disincline**
*Your rudeness disinclined me to grant you your request. ብልግናህ ፡ የጠየቅኸውን ፡ እንዳ ልፈጽምልህ ፡ አድርጎኛል

**(be) disinclined** ዝንባሌ ፡ ጉደለ(ው)
A lazy person is disinclined to work. ሰነፍ ፡ ሰ ው ፡ የሥራ ፡ ዝንባሌ ፡ ይጉድለዋል

**disinfect** መድኃኒት ፡ ረጨ
They disinfected the house after the child had typhus. ልጁ ፡ ተስቦ ፡ ከያዘው ፡ በኋላ ፡ ቤቱ ን ፡ መድኃኒት ፡ ረጩበት

**disinherit** ምንም ፡ አላወረሰ ፤ ከውርስ ፡ ነቀለ
They read the will and found he had disinherited everybody. ኑዛዜውን ፡ ካነበቡ ፡ በኋላ ፡ ለቤተሰቦቹ ፡ ምንም ፡ አለማውረሱን ፡ ተረዱ
His father threatened to disinherit him. አባቱ ፡ ከውርስ ፡ እነቅልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ አስፈራራው

**disintegrate** (vt.) ገነጣጠለ
The explosion disintegrated the airplane. ፈንጂው ፡ አውሮፕላኑን ፡ ገነጣጠለው

**disintegrate** (vi.)
1. ተፈረካከሰ. Rocks disintegrate because of frost and rain. አለት ፡ ከውርጭና ፡ ከዝናብ ፡ የተነሣ ፡ ይፈረካከሳል
2. ተበታተከ. The blanket disintegrated in the washing machine. ብርድ ፡ ልብሱ ፡ በማጠቢያ ው ፡ መኪና ፡ ውስጥ ፡ ተበታተከ

**(be) disinterested**
1. አላደላም. A judge should be disinterested. ዳኛ ፡ የማያደላ ፡ መሆን ፡ አለበት
2. ያላንዳች ፡ ምክንያት ፡ ነበረ. His giving me money was not altogether disinterested. ለኔ ፡ ገንዘብ ፡ መስጠቱ ፡ ያላንዳች ፡ ምክንያ ት ፡ አልነበረም

**disjoin** (vt.)
1. ለየብቻ ፡ ሠራ. It is better to disjoin the buildings than to build them in a row. ሕንጻው ን ፡ አያይዞ ፡ ከመሥራት ፡ ይልቅ ፡ ለየብቻ ፡ መ ሥራት ፡ የተሻለ ፡ ነው
2. አላቀቀ. The electrician disjoined the wires to make repairs. ኤሌክትሪክ ፡ ሠራተኛው ፡ ጥገ ና ፡ ለማድረግ ፡ ሽቦዎቹን ፡ አላቀቃቸው

**disjoin** (vi.) ተለያየ
The scientist watched the two cells disjoin. ሳይንቲስቱ ፡ ሁለቱ ፡ ሴሎች ፡ ሲለያዩ ፡ ተመለከተ

**disjoint** ገነጣጠለ
The cook disjointed the chicken and put it in the pot. የወጥ ፡ ቤቱ ፡ ዶሮውን ፡ ገነጣጥ ሎ ፡ ድስት ፡ ውስጥ ፡ ጨመረው

**disjointed** (adj.) ያልተያያዘ
The boy's speech was mumbled and disjointed. የልጁ ፡ አነጋገር ፡ ማጉመትመት ፡ የመላበትና ፡ ያልተያያዘ ፡ ነበር

**disk**
1. [ጠፍጣፋ ፡ ቀጭን ፡ እንደ ፡ ሳንቲም ፡ ቅርጽ ፡ ያለው ፡ ክብ ፡ ነገር]
2. ሸክላ. A disk was placed on the record player. ሸክላው ፡ በሸክላ ፡ ማጫወቻው ፡ ላይ ፡ ተደርጓል

**dislike** (v.)
1. ጠላ. I dislike that fellow. ያንን ፡ ሰው ፡ እጠ ላዋለሁ
2. አልወደደም. I dislike getting up early. በጧት ፡ መነሣት ፡ አልወድም
3. አስከፋ. +We disliked his untoward rudeness to the stranger. በእንግዳው ፡ ላይ ፡ የፈጸመው ፡ የማይገባ ፡ ብልግና ፡ አስከፋን

**dislike** (n.) ጥላቻ
I cannot conceal my dislike for him. ለርሱ ፡ ያለኝን ፡ ጥላቻ ፡ ልደብቀው ፡ አልችልም

**have a dislike of** ጠላ
I have a dislike of fog. ጉም ፡ እጠላለሁ

**take a dislike to** ጠላ
He took a dislike to her after he knew her better. በይበልጥ ፡ እያወቃት ፡ ሲሄድ ፡ ጠላት
*He took a dislike to me. ውቃቢው ፡ አልወደደ ኝም

**dislocate**
1. አናጋ. The earthquake dislocated several buildings. የመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ብዙ ፡ ሕንጻዎ ችን ፡ አናጋ
2. (= intr.) ወለቀ. +He dislocated his shoulder playing football. ኳስ ፡ ሲጫወት ፡ ትከሻው ፡ ወለቀ
3. ወለም ፡ አለ(ው). +I dislocated my wrist when trying to lift the heavy box. ከባዱን ፡ ሣጥን ፡ አ ነሣለሁ ፡ ብዬ ፡ የጁን ፡ አንጓ ፡ ወለም ፡ አለኝ

**dislodge**
1. ፈነቃቀለ. The earthquake dislodged many rocks. የመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ብዙ ፡ ቋጥኞችን ፡ ፈነቃቀለ
2. አስለቀቀ. Heavy gunfire dislodged the enemy from the fort. ከባድ ፡ ተኩስ ፡ ጠላትን ፡ ከምሽጉ ፡ አስለቀቀው

**disloyal** ታማኝነት ፡ የጐደለ(ው)
The ruler exiled the disloyal official to the provinces. ታማኝነት ፡ የጐደለውን ፡ ሹም ፡ ገዢው ፡ ወደ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ አጋዙት

**be disloyal** ቅን ፡ አገልጋይ ፡ አልነበረም
The head of the municipality was disloyal to the governor. የማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ላገረ ፡ ገዢው ፡ ቅን ፡ አገልጋይ ፡ አልነበረም

**disloyalty**
*The traitor was shot for disloyalty to the country. ከሐዲው ፡ አገሩን ፡ ስለከዳ ፡ በጥይት ፡ ተደበደበ

**dismal**
1. ቀፋፊ. This dismal weather oppresses me. ይህ ፡ ቀፋፊ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ ይጫጫነኛል
2. የማይረባ. Our team played a dismal game. ቡድናችን ፡ የማይረባ ፡ ጨዋታ ፡ ተጫወተ

**feel dismal** ቀዛዛ ፡ አለ
He feels dismal because of the cold. በጉንፋኑ ፡ ምክንያት ፡ ቀዛዛ ፡ ብሏል

**dismantle**
1. ለያየ. They dismantled the bookcases in order to move them. ለማጓጓዝ ፡ እንዲመች ፡ የመጻሕፍት ፡ መደርደሪያዎቹን ፡ ለያዩዋቸው
2. አወላለቀ. They dismantled the machine and shipped it in pieces. መኪናውን ፡ አወላልቀው ፡ እቃውን ፡ ላኩት

**dismay** (v.) አስጨነቀ
The thought that she might fail the history test dismayed her. የታሪኩን ፡ ፈተና ፡ የመውደቅ ፡ ሐሳብ ፡ አስጨነቃት

**be dismayed** ተደናገጠ
They were dismayed to hear the enemy was near. ጠላት ፡ መቃረቡን ፡ በመስማታቸው ፡ ተደናገጡ

**dismay** (n.) ተስፋ ፡ መቍረጥ
Her dismay was visible in her face. ተስፋ ፡ መቍረጧ ፡ ፊቷ ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**fill with dismay** ቅስሙን ፡ ሰበረው
The doctor's report filled her with dismay. የዶክተሩ ፡ ሪፖርት ፡ ቅስሟን ፡ ሰበረው

**(be) filled with dismay** በጣም ፡ ተሰቀቀ
The mother was filled with dismay when her son confessed that he had robbed a store. ልጇ ፡ ሱቁን ፡ መዝረፉን ፡ ባመነ ፡ ጊዜ ፡ እናቱ ፡ በጣም ፡ ተሰቀቀች

**in dismay** ድንግጥ ፡ ብሎ
He looked at me in dismay. ድንግጥ ፡ ብሎ ፡ ተመለከተኝ

**dismiss**
1. አሰናበተ. The teacher dismissed the class when the bell rang. ደወሉ ፡ ሲደወል ፡ አስተማሪው ፡ የክፍሉን ፡ ተማሪዎች ፡ አሰናበተ
2. ከሥራ ፡ አስወጣ ፤ ከሥራ ፡ አባረረ. We dismissed the maid because her cooking was so poor. የወጥ ፡ አሠራር ፡ ችሎታዋ ፡ አነስተኛ ፡ ስለሆነ ፡ ገረዳችንን ፡ ከሥራ ፡ አስወጣናት ፡ (አባረርናት)
3. ሰረዘ. The court dismissed the complaint after a hearing. ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳዩን ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ክሱን ፡ ሰረዘ
4. ችላ ፡ አለ. Dismiss your troubles and be happy! ነገሩን ፡ ችላ ፡ ብለህ ፡ ተደሰት
5. ተወ. He dismissed the matter with a shrug of the shoulders. ጉዳዩን ፡ ንቆ ፡ ተወው

**be dismissed**
1. ከሥራ ፡ ወጣ ፤ ከሥራ ፡ ተባረረ. She was dismissed after two weeks. ከሁለት ፡ ሳምንት ፡ በኋላ ፡ ከሥራ ፡ ወጣች ፡ (ከሥራ ፡ ተባረረች)
2. ተለቀቀ. The noise is due to the children's being dismissed from school. ሁካታው ፡ ልጆች ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ስለተለቀቁ ፡ ነው

**dismissal**
1. ከሥራ ፡ መሰናበት. His loose conduct was grounds for his dismissal. ልክስክስ ፡ ምግባሩ ፡ ከሥራ ፡ ለመሰናበቱ ፡ ምክንያት ፡ ሆነ
2. ከሥራ ፡ መወገድ. The news of the minister's dismissal was disseminated by radio. የሚኒስትሩ ፡ ከሥራ ፡ መወገድ ፡ ዜና ፡ በሬዲዮ ፡ ተነገረ

**dismount** (vt.)
1. ፈታታ. The watchmaker dismounted the watch. ሰዓት ፡ ሠሪው ፡ ሰዓቱን ፡ ፈታታው
2. አወረደ. The mechanic dismounted the motor to work on it. ሜካኒኩ ፡ ሞተሩን ፡ አውርዶ ፡ ሠራ

**dismount** (vi.) ወረደ
He dismounted from his mule. ከበቅሎው ፡ ወረደ

**disobedience** አለመታዘዝ
Disobedience cannot be allowed in the army.

አለመታዘዝ ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ አይ
ፈቀድም

**disobedient** እምቢተኛ ፤ የማይታዘዝ
The disobedient child was punished. እምቢተ
ኛው ፡ (የማይታዘዘው) ፡ ልጅ ፡ ተቀጣ

**disobey**
1. አልታዘዝም ፡ አለ. The child is rude and disobeys. ልጁ ፡ ባለጌ ፡ ስለሆነ ፡ አልታዘዝም ፡ አለ
2. ከ - - ቃል ፡ ወጣ. The child disobeyed his father. ልጁ ፡ ከአባቱ ፡ ቃል ፡ ወጣ
3. ጣሰ. The soldier disobeyed the order to stop. ወታደሩ ፡ ቁም ፡ የሚለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ጣሰ

**disoblige** ሊረዳው ፡ አልቻለም
I hate to disoblige you, but I must leave now. ልረዳህ ፡ ስለማልችል ፡ አዝናለሁ ፤ ግን ፡ አሁን ፡
መሄድ ፡ አለብኝ

**disorder**
1. መዝረክረክ. The disorder of the boys' room was disgusting. የልጆቹ ፡ ክፍል ፡ መዝረክረክ ፡
ያስጠላ ፡ ነበር
2. ትርምስምስ. Great disorder is common when children play. ልጆች ፡ ሲጫወቱ ፡ ትል
ቅ ፡ ትርምስምስ ፡ የተለመደ ፡ ነው
3. ረብሻ. Troops were called in to suppress the disorders in the capital. በዋናው ፡ ከተማ ፡
ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ ረብሻ ፡ ለማቆም ፡ ወታደሮ
ች ፡ ተጠርተው ፡ ነበር
4. ሕመም. My uncle suffers from a heart disorder. አጐቴ ፡ የልብ ፡ ሕመም ፡ አለበት

**leave in great disorder** አመሰቃቅሎ ፡ ሄደ
The boarding student left the room in great disorder. አዳሪው ፡ ተማሪ ፡ ክፍሉን ፡ አመሰቃቅ
ሎት ፡ ሄደ

**disorderly**
1. ቅጥ ፡ ያጣ. The disorderly mob attacked the President's residence. ቅጥ ፡ ያጣ ፡ ሕዝብ ፡
የፕሬዚዳንቱን ፡ ቤት ፡ ወረረ
2. የተመሰቃቀለ. His desk is very disorderly.
ጠረጴዛው ፡ በጣም ፡ የተመሰቃቀለ ፡ ነው
3. የተተራመሰ. The proceedings of the meeting were disorderly. ስብሰባው ፡ የተተራመሰ ፡ ነበር

**disorganize** አቃወሰ
Fog disorganized the airplane schedule. ጉሙ ፡
የአውሮፕላኑን ፡ ፕሮግራም ፡ አቃወሰ

**disorganized** (adj.) ዝርክርክ
A systematic person can do more work than a disorganized person. ሥርዓት ፡ ተከትሎ ፡ የሚ
ሠራ ፡ ሰው ፡ ከዝርክርክ ፡ ሰው ፡ ይልቅ ፡ ይበልጥ ፡
ሊሠራ ፡ ይችላል

**be disorganized** ሥርዓት ፡ አጣ
His work is disorganized, so he never gets anything done. ሥራው ፡ ሥርዓት ፡ ያጣ ፡ ስለ
ሆነ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አያከናውንም

**disorient** ግራ ፡ አጋባ
The shock of the accident disoriented him.
ያደጋው ፡ ድንጋጤ ፡ ግራ ፡ አጋባው

**disown** ካደ
The boy was so wicked that his father disowned him. ልጁ ፡ በጣም ፡ ክፉ ፡ ስለነበረ ፡ አባ
ቱ ፡ ካደው

**disparage** አንኳሰሰ
The candidate disparaged his rival. እጩ ፡ ተ
ወዳዳሪው ፡ ተቃዋሚውን ፡ አንኳሰሰ

**disparity** አለመመጣጠን
Disparity in ages is no bar to marriage.
የዕድሜ ፡ አለመመጣጠን ፡ ጋብቻ ፡ አይከለክልም

**(be) dispassionate** ለስሜት ፡ አልተገዛም
A judge should be dispassionate. ዳኛ ፡ ለስሜቱ ፡
የማይገዛ ፡ መሆን ፡ አለበት

**dispatch** (v.)
1. በፍጥነት ፡ ላከ ፤ ሰደደ. Please dispatch these letters! እነዚህን ፡ ደብዳቤዎች ፡ በፍጥነት ፡ ላክ
He dispatched the letter through the embassy.
በኤምባሲ ፡ በኩል ፡ ደብዳቤውን ፡ ሰደደለት
2. ፈጸመ. He dispatched the business deal.
የንግዱን ፡ ጉዳይ ፡ ፈጸመ

**be dispatched** ተገደለ
The bandit was dispatched with a sword.
ሽፍታው ፡ በጐራዴ ፡ ተገደለ

**dispatch** (n.)
1. ደብዳቤ. Our office received a dispatch from the President today. መሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ ዛሬ ፡
ከፕሬዚዳንቱ ፡ ደብዳቤ ፡ ደረሰው
2. ቅልጥፍና. This boy works with dispatch.
ይህ ፡ ልጅ ፡ በቅልጥፍና ፡ ይሠራል

**dispel** (dispelled)
1. በተነ. The wind soon dispelled the fog.
ነፋሱ ፡ ጭጋጉን ፡ ወዲያውኑ ፡ በተነው
2. አስወገደ. His confident manner dispelled our fears. በራስ ፡ የመተማመን ፡ ጠባዩ ፡ ፍር
ሃታችንን ፡ አስወገደልን

**dispensable**
*Luxuries are dispensable. ያለቅንጦት ፡ እቃዎ
ች ፡ ለመኖር ፡ ይቻላል

**dispensary** (dispensaries) የሕክምና ፡ ክፍል
I am going to the dispensary to have the nurse bandage my cut finger. የተቈረጠውን ፡ ጣቴን ፡ አስታማሚዋ ፡ እንድታስርልኝ ፡ ወደ ፡ ሕክምና ፡ ክፍል ፡ እሄዳለሁ

**dispense** ዐደለ
They dispensed the clothing to needy refugees. ለተቸገሩ ፡ ስደተኞች ፡ ልብስ ፡ ዐደሉ
The druggist dispenses medicine. መድኃኒት ፡ ቀማሚው ፡ መድኃኒት ፡ ያድላል

**dispense with**
1. አባረረ. The storekeeper dispensed with the lazy clerk. የሱቁ ፡ ባለቤት ፡ ሰነፉን ፡ ሻጭ ፡ አባረረው
2. አቋረጠ. He is not well enough to dispense with the doctor's care. ሕክምናውን ፡ እንዳያቋርጥ ፡ ገና ፡ አልተሻለውም
[See also 'justice']

**disperse** (vt.) በታተነ
The police dispersed the crowd. ፖሊሶቹ ፡ ሕዝቡን ፡ በታተኑ

**disperse** (vi.) ተበታተነ
The crowd dispersed when the troops arrived. ወታደሮቹ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ተበታተነ

**displace**
1. ያለቦታው ፡ አኖረ. Did you displace my eyeglasses again? መነጽሬን ፡ እንደገና ፡ ያለቦታው ፡ አኖርከው ?
2. ተካ. The automobile has displaced the horse. አውቶሞቢል ፡ ፈረስን ፡ ተክቷል

**be displaced** ተፈነቃቀለ
The telephone poles were displaced by the earthquake. የስልክ ፡ ዕንጨቶች ፡ በመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ የተነሣ ፡ ተፈነቃቅለው ፡ ነበር
*The minister was displaced by his rival. ተቀናቃኙ ፡ የሚኒስትሩን ፡ ቦታ ፡ ወሰደ

**display** (v.)
1. አሳየ. He displayed great courage. ታላቅ ፡ ጀግንነት ፡ አሳየ
The salesman pattered on while displaying his wares. አሻሻጩ ፡ የሚሸጡትን ፡ እቃዎች ፡ እያሳየ ፡ ቀባጠረ
2. (= passive) ተደርድሮ ፡ ታየ. +The store displays boys' suits in the window. የልጆች ፡ ልብስ ፡ በሱቁ ፡ መስኮት ፡ ውስጥ ፡ ተደርድሮ ፡ ይታያል
3. (= passive) ተሰቀለ. +All the houses displayed flags. በየቤቱ ፡ ባንዲራ ፡ ተሰቅሎ ፡ ነበር
4. (= passive) ታየ(በት). +After his father's death, he displayed apathy. አባቱ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ግዴለሽነት ፡ ይታይበት ፡ ነበር

**be displayed** ለሕዝብ ፡ እንዲታይ ፡ ተደረገ
The goods were displayed in the shop. ሸቀጣ ፡ ሸቀጡ ፡ በሱቁ ፡ ውስጥ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲታይ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር

**display** (n.)
1. መታየት. The paintings are on display at the museum. ሥዕሎቹ ፡ በቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ውስጥ ፡ በመታየት ፡ ላይ ፡ ናቸው
2. ትዕይንት. Last week, there was a display of paintings depicting the life of the Chinese. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ የቻይናን ፡ ኑሮ ፡ የሚገልጽ ፡ የሥዕል ፡ ትዕይንት ፡ ነበር
3. ድርድር. There was a profuse display of flowers in her room. በክፍሏ ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ያበባ ፡ ድርድር ፡ ነበር

**be on display** ታየ
At the art show, the works of the various students were on display. በኪነ ፡ ጥበብ ፡ ትርኢይት ፡ ላይ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ተማሪዎች ፡ ሥራዎች ፡ ታዩ

**displease** አስከፋ ፤ ደስ ፡ አላሰኘም
His behavior displeases me. ጠባዩ ፡ ያስከፋኛል
He dropped a remark which displeased me. ያስከፋኝን ፡ (ደስ ፡ ያላሰኘኝን) ፡ አስተያየት ፡ ጣል ፡ አደረገ

**displeasure** አለመደሰት ፤ ቅሬታ
A frown marked her displeasure. አለመደሰቷ ፡ (ቅሬታዋ) ፡ ግምባሯን ፡ ከመቋጠሯ ፡ ታወቀ

**disposal** (= to dispose)
1. ማስወገድ. Garbage disposal is a major problem for large cities. ለታላላቅ ፡ ከተማዎች ፡ ቆሻሻ ፡ ማንሣት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ነው
2. መገላገል. Disposal of the car requires finding someone who is interested in it. ከመኪናው ፡ ለመገላገል ፡ ፈላጊ ፡ ሰው ፡ ማግኘት ፡ ያሻል
3. መደርደር. The disposal of the chairs around the sides of the room left plenty of space in the middle. በክፍሉ ፡ ጥግ ፡ ዙሪያ ፡ የወምበሮች ፡ መደርደር ፡ በመኻል ፡ ብዙ ፡ ቦታ ፡ አስገኘ
*His will arranged for the disposal of his property after his death. ኑዛዜው ፡ ከርሱ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ሀብቱ ፡ እንዴት ፡ እንደሚከፈል ፡ ወሰነ

**have (be) at one's disposal**
*He has a car at his disposal. በፈለገበት ፡ ጊዜ ፡ መኪና ፡ ያገኛል
*I'm at your disposal. ልረዳህ ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ

## dispose
1. ገፋፋ. The good pay and short hours disposed him to take the new job. ጥሩ ፡ ደሞዝና ፡ አጭር ፡ የሥራ ፡ ጊዜ ፡ አዲሱን ፡ ሥራ ፡ እንዲቀበል ፡ ገፋፋው
2. አቆመ. He disposed the cars in a single line. መኪናዎቹን ፡ በተርታ ፡ አቆማቸው
*Getting your feet wet disposes you to catching cold. በዝናብ ፡ ጊዜ ፡ እግርህን ፡ ውኃ ፡ ቢነካህ ፡ ለጉንፋን ፡ ትጋለጣለህ

**dispose of**
1. ስፍራ ፡ አስያዘ. They will leave as soon as they dispose of their furniture. የቤቱን ፡ እቃ ፡ ስፍራ ፡ እንዳስያዙ ፡ ይሄዳሉ
2. ጣለ. Where can I dispose of this? ይህንን ፡ የት ፡ ልጣለው ?
3. ሸጠ. Because of the gasoline shortage, we had to dispose of our car. በቤንዚኑ ፡ እጥረት ፡ ምክንያት ፡ መኪናችንን ፡ መሸጥ ፡ ግድ ፡ ሆነብን
4. አከሸፈ. We disposed of all his arguments. ክርክሩን ፡ ሁሉ ፡ አከሸፍነው

## disposed (adj.)
*He is kindly disposed toward you. በደግ ፡ ዓይን ፡ ያይሃል

## disposition
1. ባሕርይ ፣ ጠባይ. Mary has a sunny disposition. ሜሪ ፡ ባሕርየ ፡ (ጠባየ) ፡ መልካም ፡ ናት
2. ወዳጅነት. His disposition to argue made him many enemies. ጭቅጭቅ ፡ ወዳጅነቱ ፡ ብዙ ፡ ጠላቶች ፡ አተረፈለት
3. አመዳደብ. The general approved the disposition of the troops. ጄኔራሉ ፡ የወታደሮቹን ፡ አመዳደብ ፡ አጸደቁ
4. አቀማመጥ. The disposition of the chairs in the room has been changed. በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ የወምበሮች ፡ አቀማመጥ ፡ ተለውጧል

**have a disposition for** መረጠ
He has a disposition for quiet places. ጸጥ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ይመርጣል

**of cheerful disposition** ፍልቅልቅ
She is always of cheerful disposition. ምን ፡ ጊዜም ፡ ፍልቅልቅ ፡ ናት
[See also 'sunny']

## dispossess አስለቀቀ
The landlord dispossessed the family of their apartment. የቤቱ ፡ ጌታ ፡ ተከራዮቹን ፡ አስለቀቃቸው

**be dispossessed of** ተነጠቀ
The landowners were dispossessed of their land. ባለመሬቶቹ ፡ መሬታቸውን ፡ ተነጠቁ

## disproportion አለመመጣጠን
The disproportion in their salaries caused resentment. የደሞዛቸው ፡ አለመመጣጠን ፡ ቅሬታ ፡ አሳደረባቸው

## disprove ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጠ
Columbus disproved the theory that the earth was flat. መሬት ፡ ዝርግ ፡ ናት ፡ የሚለውን ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳብ ፡ ኮለምበስ ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጠ

**be disproved** ውሸት ፡ መሆኑ ፡ ተደረሰበት
His fraudulent claim to be a nephew of the minister was soon disproved. የሚኒስትሩ ፡ የእኅት ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ የሚለው ፡ የሐሰት ፡ ወሬ ፡ ወዲያው ፡ ውሸት ፡ መሆኑ ፡ ተደረሰበት

## dispute (vt.) አልተቀበለም
They disputed his authority. ሥልጣኑን ፡ አልተቀበሉትም

**dispute (vi.)** ተጨቃጨቀ
They were disputing whether to start at once or wait. በፍጥነት ፡ ከመጀመርና ፡ ከመቆየት ፡ የቱ ፡ እንደሚሻል ፡ ይጨቃጨቁ ፡ ነበር
Some people like to dispute. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ መጨቃጨቅ ፡ ይወዳሉ
*The soldiers disputed every inch of ground when the enemy attacked. ወታደሮቹ ፡ ጠላት ፡ በገጠማቸው ፡ ጊዜ ፡ አንዲት ፡ ቅንጣት ፡ መሬት ፡ እንኳ ፡ አንለቅ ፡ አሉ

**be disputed** አከራካሪ ፡ ነበር
The election results were disputed. የምርጫው ፡ ውጤት ፡ አከራካሪ ፡ ነበር

## dispute (n.) ክርክር ፣ ጠብ
The dispute is about the ownership of this land. ክርክሩ ፡ ስለዚህ ፡ መሬት ፡ ባለቤትነት ፡ ነው
There were many religious disputes in this country at one time. አንድ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ የሃይማኖት ፡ ክርክር ፡ ነበር
The judge is going to arbitrate the dispute. ዳኛው ፡ ጠቡን ፡ ሊያስታርቅ ፡ ነው

**beyond dispute** አያከራክርም
This book is beyond dispute the best book on the subject. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በዚህ ፡ አርእስት ፡ ላይ ፡ ከተጻፉት ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ መሆኑ ፡ አያከራክርም

## disqualify (disqualified)
1. እንድ + negative imperfect + ከለከለ. The

Constitution disqualifies a foreign-born person from becoming President. ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ እንዳይሆን ፡ ይከለክላል

2. አስቀረ. His eyesight disqualified him from participating in the Olympic Games. የዓይኑ ፡ መታወክ ፡ በኦሊምፒክ ፡ ጨዋታዎች ፡ ከመካፈል ፡ አስቀረው

**disqualify oneself** ራሱን ፡ አገለለ

The judge disqualified himself for this particular case. በተለይ ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ እንዳይመለከት ፡ ዳኛው ፡ ራሱን ፡ አገለለ

**disquiet** (v.) ዕረፍት ፡ ነሣ

Rumors of a war disquieted the general. የጦርነቱ ፡ መምጣት ፡ ጭምጭምታ ፡ ጄኔራሉን ፡ ዕረፍት ፡ ነሣው

**disquiet** (n.) መሸበር

A feeling of disquiet spread through the waiting crowd. ተጠባባቂውን ፡ ሕዝብ ፡ የመሸበር ፡ መንፈስ ፡ አደረበት

**disregard** (v.) ችላ ፡ አለ

We cannot disregard the teacher's objections. የመምህሩን ፡ ተቃውሞ ፡ ችላ ፡ ልንለው ፡ አንችልም

**disregard** (n.)

1. ችላ ፡ ማለት. The boy's failure was due to continued disregard of his studies. የልጁ ፡ መውደቅ ፡ ጥናቱን ፡ አከታትሎ ፡ ችላ ፡ ከማለቱ ፡ የመጣ ፡ ነው

2. ግዴለሽ ፡ መሆን. His disregard of my feelings annoys me. ለስሜቴ ፡ ግዴለሽ ፡ መሆኑ ፡ ቅር ፡ ያሰኘኛል

**disreputable** ተግባረ ፡ ልክስክስ ፡ የሆነ

Not all disreputable people are in jail. እስር ፡ ቤት ፡ የገቡት ፡ ተግባረ ፡ ልክስክስ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አይደሉም

**disrepute, be in ~** ስሙ ፡ በጥሩ ፡ አይነሣም

Imperialism is now in disrepute. ኢምፔሪያሊዝም ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ስሙ ፡ በጥሩ ፡ አይነሣም

**disrespect, show ~ to** አንጓጠጠ

We must not show disrespect to our elders. ታላላቆቻችንን ፡ ማንጓጠጥ ፡ አይገባንም

**disrespectful**

1. የብልግና. His disrespectful attitude toward his elders was considered shameful. ለታላላቆቹ ፡ የሚያሳየው ፡ የብልግና ፡ ጠባዩ ፡ አሳፋሪ ፡ ነበር

2. ባለጌ. The children are disrespectful. ልጆቹ ፡ ባለጌ ፡ ናቸው

**disrobe** (vt.) ልብስ ፡ አወለቀ(ለት)

The mother disrobed the child. እናትዮዋ ፡ የልጁን ፡ ልብስ ፡ አወለቀችለት

**disrobe** (vi.) ልብስ ፡ አወለቀ

He slowly disrobed. በቀስታ ፡ ልብሱን ፡ አወለቀ

**disrupt**

1. አፋለሰ. These quarrels will disrupt the unity of our association. እንዲህ ፡ ያለው ፡ ጭቅጭቅ ፡ የማኅበራችንን ፡ አንድነት ፡ ያፋልሳል

2. አናወጠ(ተናወጠ) ፤ አምቦጫረቀ. The rock fell into the lake and disrupted the smooth surface of the water. አለቱ ፡ ከሐይቁ ፡ ውስጥ ፡ ሲወድቅ ፡ የረጋውን ፡ ውኃ ፡ አናወጠው ፡ (አምቦጫረቀው)

The unity of Nigeria was disrupted by enemy agents. የናይጄርያ ፡ አንድነት ፡ በአነሣሾች ፡ ተናውጦ ፡ ነበር

3. በጠበጠ. The news disrupted the conference. ወሬው ፡ ስብሰባውን ፡ በጠበጠው

**dissatisfy** (dissatisfied) ቅር ፡ አሰኘ

The color of the house dissatisfied her. የቤቱ ፡ ቀለም ፡ ቅር ፡ አሰኛት

**be dissatisfied**

1. ቅር ፡ ተሰኘ. He is dissatisfied with his salary. በደሞዙ ፡ ቅር ፡ ተሰኝቷል

2. ቅር ፡ አለ(ው). You look dissatisfied. ቅር ፡ ያለህ ፡ ትመስላለህ

**dissect**

1. ሰነጠቀ. The biology class dissected frogs last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ የባዮሎጂ ፡ ተማሪዎች ፡ እንቁራሪት ፡ ሰነጠቁ

2. በዝርዝር ፡ አጠና. The senators dissected the budget report. የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ የባጀቱን ፡ ራፖር ፡ በዝርዝር ፡ አጠኑ

**dissemble** ሸፈነ

She dissembled her anger with a smile. ንዴቷን ፡ በፈገግታ ፡ ሸፈነች

**disseminate** አሰራጨ

Missionaries disseminate Christian belief all over the world. የወንጌል ፡ ሰባኪዎች ፡ የክርስቲያንን ፡ እምነት ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ያሰራጫሉ

**be disseminated** ተነገረ

The news of the minister's dismissal was disseminated by radio. የሚኒስትሩ ፡ ከሥራ ፡ መወገድ ፡ ዜና ፡ በሬዲዮ ፡ ተነገረ

**dissension** ጠብ

The border dispute caused lasting dissension. የወሰኑ ፡ ጠብ ፡ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ ንትርክ ፡ አስከተለ

**dissent** (v.)
1. ተቃወመ. I strongly dissent from what the last speaker said. የመጨረሻው ፡ ተናጋሪ ፡ ያለውን ፡ አጥብቄ ፡ እቃወማለሁ
2. አልተስማማ(በትም). Several of us dissented from the majority report. አብዛኛው ፡ ያቀረበውን ፡ ሪፖርት ፡ ብዙዎቻችን ፡ አልተስማማንበትም

**dissent** (n.) አለመስማማት
He expressed his dissent when asked if he agreed with the speaker. ከተናጋሪው ፡ ጋር ፡ ይስማማ ፡ እንደሆን ፡ ቢጠየቅ ፡ አለመስማማቱን ፡ ገለጸ

**dissertation** ለዶክተርነት ፡ ዲግሪ ፡ ያዘጋጀ ፡ ጽሑፍ
He finally finished his dissertation last week. በመጨረሻው ፡ ለዶክተርነት ፡ ዲግሪ ፡ ያዘጋጀውን ፡ ጽሑፍ ፡ ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ፈጸመ

**disservice, do a ~**
*I would be doing you a disservice if I solved the problem for you. ያንን ፡ ጥያቄ ፡ ብሠራልህ ፡ እጐዳሃለሁ ፡ እንጂ ፡ አልጠቅምህም

**dissident** (n.) ተቃዋሚ
He purged his cabinet of dissidents. ከካቢኔው ፡ ውስጥ ፡ ተቃዋሚዎቹን ፡ ሁሉ ፡ አስወገደ

**dissident** (adj.) የተቃውሞ
A dissident voice was heard in the audience. ከአድማጩ ፡ ሕዝብ ፡ የተቃውሞ ፡ ድምፅ ፡ ተሰማ

**dissimilar** የተለያየ
Henry and John have dissimilar tasks. ሄንሪና ፡ ጆን ፡ የተለያዩ ፡ ሥራዎች ፡ አሉዋቸው

**dissimilarity** አለመስማማት
The dissimilarity of the two brothers' character is surprising. የሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ ጠባይ ፡ አለመስማማት ፡ የሚደንቅ ፡ ነው

**dissimulate** ደበቀ
He cannot dissimulate his true feelings. እውነተኛውን ፡ ስሜቱን ፡ ሊደብቅ ፡ አይችልም

**dissipate** (vt.)
1. በታተነ. The wind quickly dissipated the smoke. ነፋሱ ፡ ጭሱን ፡ ወዲያው ፡ በታተነው
2. አባከነ. He dissipated his entire fortune. ሀብቱን ፡ በሙሉ ፡ አባከነ

**dissipate** (vi.) ተበተነ
The fog dissipated by noon. ጭጋጉ ፡ ቀትር ፡ ላይ ፡ ተበተነ

**dissipated** (adj.) ብኩን
He leads a dissipated life. ብኩን ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል

**dissociate** ለየ
It is difficult to dissociate imperialism from exploitation. ኢምፔርያሊዝምን ፡ ከጭቆና ፡ ለመለየት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**dissociate oneself** ራሱን ፡ አወጣ
I wish to dissociate myself from what has just been said. አሁን ፡ ከተባለው ፡ ነገር ፡ ራሴን ፡ ለማውጣት ፡ እፈልጋለሁ

**(be) dissoluble** ሟሟ
Salt is easily dissoluble in water. ጨው ፡ በቀላሉ ፡ በውኃ ፡ ይሟሟል

**dissolute** የወራዳነት
He leads a dissolute life. የወራዳነት ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል

**dissolution** ማፍረስ
The partners arranged for the dissolution of their partnership. ሽሪኮቹ ፡ ሽርክናቸውን ፡ ለማፍረስ ፡ ተስማሙ

**dissolve** (vt.)
1. አሟሟ. Water dissolves salt. ውኃ ፡ ጨውን ፡ ያሟሟል
Dissolve the contents of the package in one liter of water! ፓኮው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ባንድ ፡ ሊትር ፡ ውኃ ፡ አሟሟው
2. አፈረሰ. They dissolved their partnership. ሽርክናቸውን ፡ አፈረሱ

**dissolve** (vi.)
1. ሟሟ. Salt dissolves in water. ጨው ፡ በውኃ ፡ ይሟሟል
2. ፈረሰ. The partnership dissolved after many arguments. ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጭቅጭቅ ፡ በኋላ ፡ ሽርክናው ፡ ፈረሰ

**dissonance** ያልተቀናበረ ፡ ዜማ
The dissonance caused by an inexperienced harp player is unpleasant. በቂ ፡ ልምድ ፡ የሌለው ፡ በገና ፡ ተጫዋች ፡ ያቀረበው ፡ ያልተቀናበረ ፡ ዜማ ፡ አያስደስትም

**dissuade from** እንድ + negative imperfect + መከረ
He dissuaded his friend from marrying that girl. ባልንጀራውን ፡ ያችን ፡ ልጅ ፡ እንዳያገባ ፡ መከረው

**distaff** ማዳወሪያ
The cotton is wound around the distaff. ጥጡ ፡ በማዳወሪያው ፡ ላይ ፡ ይጠመጠማል

**distance**
1. ርቀት. The distance between Harar and

Addis Ababa is considerable. በሐረርና ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ ረጂም ፡ ነው

2. መንገድ. We can cover the distance in three hours. መንገዱን ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ ልንዘልቅ ፡ እንችላለን

*He knows how to keep his distance. ደረጃውን ፡ ያውቃል

*The noise of the train died away in the distance. ባቡሩ ፡ ሲርቅ ፡ ድምፁ ፡ እየጠፋ ፡ ሄደ

**from a distance** ከሩቅ

You can see the house from a distance. ቤቱ ፡ ከሩቅ ፡ ይታያል

## distant

1. ሩቅ. We visited distant places. ሩቅ ፡ ስፍራዎችን ፡ ጐበኘን

2. የሩቅ. She is a distant relative of mine. የሩቅ ፡ ዘመዴ ፡ ነች

**distant past** የጥንት ፡ ጊዜ

These animals lived in the distant past. እነዚህ ፡ እንስሳት ፡ በጥንት ፡ ጊዜ ፡ የነበሩ ፡ ናቸው

**be distant** ራቀ

The school is three miles distant from here. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ ሦስት ፡ ማይል ፡ ይርቃል

*John has been very distant since our argument. ከክርክራችን ፡ ወዲህ ፡ ጆን ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ አይደለም

**act distant**

*She acted very distant toward him. ፊት ፡ ነሣችው

## distaste ጥላቻ

His distaste of hard study is well known. ጠንክሮ ፡ የማጥናት ፡ ጥላቻው ፡ የታወቀ ፡ ነው

**have a distaste for** ጠላ

He has a distaste for hard work. ከባድ ፡ ሥራን ፡ ይጠላል

## distasteful የሚያንገሸግሽ

This is a distasteful medicine. ይህ ፡ የሚያንገሸግሽ ፡ መድኃኒት ፡ ነው

**be distasteful to** ጠላ

Compliance with his father's demand is distasteful to him. ያባቱን ፡ ፍላጎት ፡ ማሟላት ፡ ይጠላል

## distemper [ትኩሳትና ፡ ድካም ፡ ያለበት ፡ የቡችሎች ፡ በሽታ]

## distend ወጠረ

He distended the skin over the frame for drying. ቆዳው ፡ እንዲደርቅ ፡ በመወጠሪያው ፡ ላይ ፡ ወጠረ

**be distended** ተነፋ

The balloon was distended to the bursting point. ፊኛው ፡ እስኪፈነዳ ፡ ድረስ ፡ ተነፍቶ ፡ ነበር

## distill

1. አነጠረ. You have to distill ocean water for drinking. የውቅያኖስን ፡ ውኃ ፡ ከመጠጣትህ ፡ በፊት ፡ ማንጠር ፡ አለብህ

2. አወጣ. They distill alcohol from grain. አረቄ ፡ ከእህል ፡ ያወጣሉ

## distinct

1. ጉልህ. There is a distinct difference between the two. በሁለቱ ፡ መኻል ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ልዩነት ፡ አለ

2. የተለያየ. These are two distinct kinds of animals. እነዚህ ፡ ሁለት ፡ እንስሳት ፡ በዘር ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው

3. ልዩ ፡ ልዩ. His sermon was divided into three distinct parts. ስብከቱ ፡ በሦስት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ ተከፍሎ ፡ ነበር

4. የተለየ. His praise is a distinct honor. ሙገሳው ፡ የተለየ ፡ ክብር ፡ ነው

5. እየቅል. The twin brothers have distinct personalities. መንትዮቹ ፡ ጠባያቸው ፡ እየቅል ፡ ነው

**keep distinct from one another** ለየ

Keep the two ideas distinct from one another! ሁለቱን ፡ ሐሳቦች ፡ ለይ

## distinction

1. ልዩነት. The Emperor shook hands with everybody, without distinction of rank. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የማዕረግ ፡ ልዩነት ፡ ሳያደርጉ ፡ የሁሉንም ፡ እጅ ፡ ጨበጡ

The distinctions of birth are less important now than formerly. የትውልድ ፡ ልዩነት ፡ ከጥንት ፡ ይልቅ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ እየቀረ ፡ ሄዷል

2. ክብር. To be awarded a Ph.D. is a distinction few attain. የፍልስፍና ፡ ዶክተርነትን ፡ የመቀበል ፡ ክብር ፡ የሚያገኙ ፡ ጥቂት ፡ ናቸው

3. ሊቅነት. He achieved distinction in mathematics. በሒሳብ ፡ ሊቅነትን ፡ አገኘ

*A governor should be a man of character and distinction. አንድ ፡ ገዢ ፡ ሐሳበ ፡ ጽኑና ፡ ችሎታው ፡ የተመሰከረለት ፡ መሆን ፡ አለበት

*His distinction of sounds is excellent. ድምፅ ፡ ሲለይ ፡ ግሩም ፡ ነው

## distinctive ልዩ

The Imperial Bodyguard wears a distinctive

uniform. የክብር ፡ ዘበኛ ፡ ልዩ ፡ የደንብ ፡ ልብስ ፡ ይለብሳል

**distinctively** ግልጽ ፡ አድርጎ
He speaks distinctively. እርሱ ፡ ግልጽ ፡ አድርጎ ፡ ይናገራል

**distinctly** ግልጽ ፡ አድርጎ
I told him distinctly not to come. እንዳይመጣ ፡ ግልጽ ፡ አድርጌ ፡ ነገርኩት

**distinguish** ለየ
I can't distinguish the colors. ቀለሞቹን ፡ ልለይ ፡ አልችልም
It is hard to distinguish her from her sister. እሷን ፡ ከእኅቷ ፡ ለመለየት ፡ በጣም ፡ ያስቸግራል

**distinguish between** ለየ
Can you distinguish between the two? ሁለቱን ፡ ልትለይ ፡ ትችላለህ ?

**distinguish oneself** ራሱን ፡ አሳወቀ
He distinguished himself by his courage. በጀግንነቱ ፡ ራሱን ፡ አሳወቀ

**distinguished** (adj.) የታወቀ
He is a distinguished scholar. የታወቀ ፡ ምሁር ፡ ነው

**distort**
1. አጣመመ. The mirror distorted his face. መስታወቱ ፡ የፊቱን ፡ ቅርጽ ፡ አጣመመው
2. አኰማተረ. Rage distorted his face. ንዴት ፡ ፊቱን ፡ አኰማተረው
3. አዛባ. Why did you distort the meaning of my words? የቃላቴን ፡ ትርጉም ፡ ለምን ፡ አዛባኸው ?

**distract** (vt.)
1. ጣመ. I am bored with television, but reading distracts me. ቴሌቪዥን ፡ ሰልችቶኛል ፤ ማንበብ ፡ ግን ፡ ይጥመኛል
2. ሐሳቡን ፡ አዛባ. He is very single-minded and impossible to distract. የተወሰነ ፡ ዓላማ ፡ ስላለው ፡ ሐሳቡን ፡ ለማዛባት ፡ ያስቸግራል

**distract (from)**
1. ሐሳቡን ፡ ሳበ. The television program distracts me from reading. በማነብበት ፡ ጊዜ ፡ የቴሌቪዥን ፡ ፕሮግራም ፡ ሐሳቤን ፡ ይስበዋል
2. ከለከለ. The noise in the street distracted me from reading. መንገዱ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጫጫታ ፡ ማንበብ ፡ ከለከለኝ

**distraction**
1. ሐሳብ ፡ የሚስብ ፡ ነገር ፤ ሐሳብ ፡ የሚበትን ፡ ነገር. Television is a distraction when you are also trying to read. ሰው ፡ በሚያነብበት ፡ ጊዜ ፡ ቴሌቪዥን ፡ ፕሮግራም ፡ መኖሩ ፡ ሐሳብ ፡ የሚስብ ፡ (የሚበትን) ፡ ነገር ፡ ነው
2. መንፈሱን ፡ ማደስ. Alice needs some distraction after her examination. አሊስ ፡ ከፈተናዋ ፡ በኋላ ፡ መንፈሷን ፡ ማደስ ፡ ያስፈልጋታል
3. የጊዜ ፡ ማሳለፊያ ፡ ቦታ. There are not enough distractions in a small village to keep life from being dull. በትንሽ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ኑሮ ፡ እንዳይሰለች ፡ የሚያደርጉ ፡ በቂ ፡ የጊዜ ፡ ማሳለፊያ ፡ ቦታዎች ፡ የሉም
*In his distraction after the accident, he forgot his name. ከደጋው ፡ በኋላ ፡ ስለተደናገጠ ፡ ስሙን ፡ ዘነጋ

**distraught** የተጨነቀ
The lost child's distraught mother cried all night long. የተጨነቀችው ፡ የጠፋው ፡ ልጅ ፡ እናት ፡ ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ ስታለቅስ ፡ አደረች

**distress** (v.) አስጨነቀ
The sudden illness of her son distressed Mrs. Parker. የልጇ ፡ ድንገተኛ ፡ ሕመም ፡ ሚሲስ ፡ ፓርከርን ፡ አስጨነቃት

**be distressed** አዘነ
I am distressed to hear of your wife's death. የሚስትህን ፡ ሞት ፡ በመስማቴ ፡ አዝናለሁ

**distress** (n.)
1. ችግር ፤ ጉዳት. He caused his mother much distress. ለእናቱ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ፈጠረባት
The Red Cross did everything to relieve the distress. ቀይ ፡ መስቀል ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ የደረሰውን ፡ ችግር ፡ (ጉዳት) ፡ ለማቃለል ፡ ሞከረ
2. መሠቃየት. Because of the high altitude he showed signs of distress. ከከፍታው ፡ የተነሣ ፡ የመሠቃየት ፡ ምልክት ፡ ታየበት
3. ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥቃይ. The Olympic runner showed signs of distress toward the end of the race. እውድድሩ ፡ ማለቂያ ፡ ላይ ፡ የኦሊምፒኩ ፡ ሯጭ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሥቃይ ፡ ምልክት ፡ ታየበት

**show distress** ተሠቃየ
The traveler in the desert showed distress when he ran out of water. የበረሃው ፡ መንገደኛ ፡ ውኃው ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ ተሠቃየ

**distressing** አሳዛኝ
His ignorance of political affairs is distressing. ስለ ፡ ፖለቲካ ፡ ሁኔታዎች ፡ ምንም ፡ አለማወቁ ፡ አሳዛኝ ፡ ነው

**distribute**
1. አከፋፈለ. The mother distributed the toys

among the children. እናትየዋ ፡ አሻንጉሊቶቹን ፡ ለልጆቹ ፡ አከፋፈለች
2. ዐደለ. There is a special clerk who distributes the mail. ደብዳቤዎችን ፡ የሚያድል ፡ ልዩ ፡ ጸሐፊ ፡ አለ
3. ነሰነሰ. The farmer distributed ashes in front of the house. ገበሬው ፡ ከቤቱ ፡ ደጃፍ ፡ አመድ ፡ ነሰነሰ

**distribution**
1. አከፋፈል. They did not agree on the distribution of the profits. በትርፉ ፡ አከፋፈል ፡ ላይ ፡ አልተስማሙም
2. የማከፋፈል ፡ ሥራ. The distribution of food and clothing to the needy took place yesterday. ምግብና ፡ ልብስ ፡ ለችግረኞች ፡ የማከፋፈሉ ፡ ሥራ ፡ ትናንት ፡ ተከናወነ
3. ድልድል. The distribution of our troops is a military secret. የወታደሮቻችን ፡ ድልድል ፡ የጦር ፡ ኀይል ፡ ምስጢር ፡ ነው
*What is the distribution of eucalyptus trees in the world? በዓለም ፡ ላይ ፡ የባሕር ፡ ዛፍ ፡ የት ፡ የት ፡ ይገኛል ?
*The distribution of our school paper is now 1000. አሁን ፡ የትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ጋዜጣ ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ አንባቢዎች ፡ አሉት
**for distribution** ለሕዝብ ፡ እንዲታይ
The censor released the film for distribution. ሳንሱሩ ፡ ፊልሙን ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲታይ ፡ አሳለፈው
**have wide distribution** በብዙ ፡ ቦታ ፡ ይገኛል
This tree has wide distribution in Ethiopia. ይህ ፡ ዛፍ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ይገኛል

**district**
1. አውራጃ. He governed his district with an iron hand. አውራጃውን ፡ ቀጥቅጦ ፡ ገዛ
2. ቀበሌ. This is a very poor district. ይህ ፡ በጣም ፡ ችግር ፡ የበዛበት ፡ ቀበሌ ፡ ነው
3. ወረዳ. The city is divided into two districts. ከተማው ፡ በሁለት ፡ ወረዳ ፡ ተከፍሏል
[See also 'remote']

**district attorney** የአውራጃው ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ
The district attorney is in the courtroom. የአውራጃው ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው

**distrust** (v.)
1. አላመነም. I distrust him because he often lied to me. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስለዋሸ ፡ አላምነውም
2. ተጠራጠረ. The child distrusted the stranger's offer. ልጁ ፡ የእንግዳውን ፡ ስጦታ ፡ ተጠራጠረ

**distrust** (n.) ጥርጣሬ
He looked at the friendly stranger with distrust. የወዳጅነት ፡ መልክ ፡ የሚያሳየውን ፡ እንግዳ ፡ በጥርጣሬ ፡ ተመለከተ

**distrustful** ተጠራጣሪ
A distrustful dog is the best watchdog. ተጠራጣሪ ፡ ውሻ ፡ ጥሩ ፡ ጠባቂ ፡ ነው
**be distrustful of** ተጠራጠረ
I was distrustful of his motives. ዓላማውን ፡ ተጠራጥሬ ፡ ነበር

**disturb**
1. አወከ. Don't disturb the others! ሌሎቹን ፡ አታውክ
The noise of the birds disturbs me. የወፎች ፡ ጫጫታ ፡ ያውከኛል
2. አሳሰበ. That rumor disturbed us. ወሬው ፡ አሳሰበን
The sharp drop in prices disturbed the farmers. የእህል ፡ ዋጋ ፡ በድንገት ፡ በጣም ፡ ዝቅ ፡ ማለቱ ፡ ገበሬዎቹን ፡ አሳሰባቸው
3. ረበሸ. Do not disturb the baby! He is asleep. ሕፃኑን ፡ አትረብሸው ፤ ተኝቷል
4. አመሰቃቀለ. Someone has disturbed my papers. ወረቀቴን ፡ ሰው ፡ አመሰቃቅሎታል
**disturb oneself** ተቸገረ
Please don't disturb yourself! I will take care of it. አትቸገር ፤ እኔ ፡ እሠራዋለሁ
**be disturbed** ተሸበረ
I am disturbed at that news. በዚያ ፡ ወሬ ፡ ተሸብሬያለሁ

**disturbance**
1. ሁከት. There were several political disturbances in Greece last year. በግሪክ ፡ አገር ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ አያሌ ፡ የፖለቲካ ፡ ሁከት ፡ ነበረ
2. ግርግር ፤ ረብሻ. There is a disturbance at the corner. መጠምዘዣው ፡ ላይ ፡ ግርግር ፡ (ረብሻ) ፡ አለ
3. ችግር. The radio can be a disturbance when one studies. በጥናት ፡ ጊዜ ፡ ሬዲዮው ፡ ችግር ፡ ሊፈጥር ፡ ይችላል
4. ጭንቀት. Her disturbance was plain to see. ጭንቀቷ ፡ በግልጽ ፡ ይታይ ፡ ነበር
*The disturbance of the construction schedule was due to bad weather. የሕንጻው ፡ ሥራ ፡ ፕሮግራም ፡ የተቃወሰው ፡ በመጥፎ ፡ አየር ፡ ምክንያት ፡ ነው

**disturbed, ~ mind**
He has a disturbed mind. ንክ ፡ ነው
**mentally disturbed** አእምሮው ፡ የታወከ
Therapy was given the mentally disturbed man.

አእምሮው ፡ ታውኮ ፡ የነበረው ፡ ሰውዬ ፡ ሕክምና ፡ ተደረገለት

**disunite** ከፋፈለ
He tried to disunite the students. ተማሪዎቹን ፡ ሊከፋፍል ፡ ሞከረ

**disunity** አለመስማማት
The disunity of the members resulted in the club's disbanding. የአባሎቹ ፡ አለመስማማት ፡ ክበቡን ፡ ከመፍረስ ፡ አደረሰው

**disuse**
*The old tools were rusted from disuse. አሮጌዎቹ ፡ መሣሪያዎች ፡ ስላልተሠራባቸው ፡ ዝገዋል

**fall into disuse** ቀረ
Many customs have fallen into disuse. ብዙ ፡ ልማዶች ፡ ቀርተዋል

**ditch** (v.) ቦይ ፡ ቈፈረ
The farmer ditched the garden for drainage. ገበሬው ፡ ለውኃ ፡ መውረጃ ፡ ባትክልት ፡ ዙሪያ ፡ ቦይ ፡ ቈፈረ

**ditch** (n.) ጉድጓድ
The car got stuck in the ditch. መኪናዋ ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ተቀረቀረች

**dive** (dived, or dove)
1. ዘለለ. He dived from the bridge and rescued the drowning child. ከድልድዩ ፡ ዘሎ ፡ ሊሰጥም ፡ የነበረውን ፡ ልጅ ፡ አዳነ
2. ጉብ ፡ አለ. I will dive into my homework right after dinner. ከራት ፡ በኋላ ፡ በቀጥታ ፡ ጥናቴ ፡ ላይ ፡ ጉብ ፡ እላለሁ
*Can you dive? ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ዘለህ ፡ በአናትህ ፡ መግባት ፡ ትችላለህ ?

**diverge**
1. ተገነጠለ. Our paths diverge before we reach the village. መንደሩ ፡ ከመድረሳችን ፡ በፊት ፡ መንገዶቻችን ፡ ይገነጠላሉ
2. ተለያየ. Our opinions diverge on politics. በፖለቲካ ፡ አስተሳሰባችን ፡ ይለያያል

**divergence** ልዩነት
There are several divergences of opinion on the subject. ስለ ፡ ነገሩ ፡ ብዙ ፡ የሐሳብ ፡ ልዩነት ፡ አለ

**divers** የተለያዩ
He has lived in divers places in the world. በዓለም ፡ ውስጥ ፡ በተለያዩ ፡ ቦታዎች ፡ ኖሯል

**diverse** ብዙ ፡ የተለያዩ
There are diverse languages spoken in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የተለያዩ ፡ ቋንቋዎች ፡ ይነገራሉ

**diversify** (diversified) አለዋወጠ
Farmers diversify crops to keep the soil healthy. አፈሩን ፡ በሚገባ ፡ ለመያዝ ፡ ገበሬዎች ፡ ሰብሉን ፡ ያለዋውጣሉ

**diversion**
1. አቅጣጫ ፡ መለወጥ. Diversion of the river is necessary for irrigation. የወንዙን ፡ አቅጣጫ ፡ መለወጥ ፡ ለመስኖ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
2. ጊዜውን ፡ የሚያሳልፍበት ፡ ጨዋታ. Chess is his favorite diversion. ሰንጠረዥ ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ጊዜውን ፡ የሚያሳልፍበት ፡ ጨዋታ ፡ ነው
*A diversion was created by a surprise attack from another point. ካልታሰበ ፡ አቅጣጫ ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡ ጠላትን ፡ አደናገሩት

**diversity**
1. የሐሳብ ፡ ልዩነት. Their diversity did not prevent them from being friends. ያላቸው ፡ የሐሳብ ፡ ልዩነት ፡ ጓደኝነታቸውን ፡ አልቀነሰውም
2. የ - - ዓይነት ፡ ብዛት. The diversity of food on the table made it hard for him to choose. በጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ የምግብ ፡ ዓይነት ፡ ብዛት ፡ ለምርጫው ፡ አስቸገረው

**diversity of** የተለያየ
Diversity of opinion is good for a society. የተለያየ ፡ አስተያየት ፡ ለኅብረ ፡ ሰብ ፡ ጥሩ ፡ ነው

**divert**
1. አዋለ. Ethiopia will divert the Awash into a canal. ኢትዮጵያ ፡ የአዋሽን ፡ ውኃ ፡ ለመስኖ ፡ ታውለዋለች
2. አስደሰተ. The movie diverted us. ፊልሙ ፡ አስደሰተን

**divert (one's) attention** መንፈሱን ፡ ማረከ
The band diverted our attention from the game. የሙዚቃው ፡ ጓድ ፡ ከጨዋታው ፡ ላይ ፡ መንፈሳችንን ፡ ማረከው

**be diverted**
1. ወደ ፡ ሌላ ፡ ተመራ. Some people's attention is easily diverted. ያንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ መንፈስ ፡ በቀላሉ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ይመራል
2. በሌላ ፡ መንገድ ፡ ዞሮ ፡ ሄደ. Traffic was diverted while the highway was repaired. አውራ ፡ ጎዳናው ፡ በሚጠገንበት ፡ ጊዜ ፡ መኪናዎች ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ዞረው ፡ ይሄዱ ፡ ነበር

**(be) divested of** ተገፈፈ
He was divested of his rank and privileges. ማዕረጉንና ፡ ልዩ ፡ መብቱን ፡ ተገፎ ፡ ነበር

**divide** (vt.)
1. ተካፈለ. My partner and I divided the profits. ሸርካዬና ፡ እኔ ፡ ትርፉን ፡ ተካፈልን
2. አካፈለ. Divide the total by four! ድምሩን ፡ ለአራት ፡ አካፍለው
3. ለየ. A high fence divides their farm from ours. ረጅም ፡ አጥር ፡ እርሻቸውን ፡ ከእርሻችን ፡ ይለየዋል
4. (= pass.) በሐሳብ ፡ ተከፋፈለ. +The issue divided the committee members. በጉዳዩ ፡ የደርጉ ፡ አባሎች ፡ በሐሳብ ፡ ተከፋፈሉ

**divide** (vi.)
1. መንታ ፡ ሆነ. At the end of the village the road divides. እመንደሩ ፡ መጨረሻ ፡ መንገዱ ፡ መንታ ፡ ይሆናል
2. ከሁለት ፡ ተከፈለ. The river divides near the sea. ወንዙ ፡ ባሕሩ ፡ አጠገብ ፡ ከሁለት ፡ ይከፈላል

**be divided**
1. ተከፈለ. The book is divided into two parts. መጽሐፉ ፡ በሁለት ፡ ክፍል ፡ ተከፍሏል
2. ተከፋፈለ. The land was divided among the peasants. መሬቱ ፡ ለገበሬዎች ፡ ተከፋፈለ
3. ተለያየ. Opinions are divided on that question. በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ የተሰጡት ፡ አስተያየቶች ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው

**dividend** [የኩባንያ ፡ የትርፍ ፡ ክፍያ]

**divider** መከፋፈያ
They used wardrobes as a room divider. ቁም ፡ ሣጥኑን ፡ የክፍል ፡ መከፋፈያ ፡ አደረጉት

**divination** ጥንቆላ
Divination was practiced in olden times to foretell the future. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ጥንቆላን ፡ እንደ ፡ ትንቢት ፡ ይቈጥሩት ፡ ነበር

**divine** (v.)
1. ተነበየ. The prophet divined the end of the world. ትንቢተኛው ፡ የዓለምን ፡ ፍጻሜ ፡ ተነበየ
2. ገባ(ው). He divined the purpose of her visit from the way she looked. የመጣችበት ፡ ዓላማ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ከአስተያየቷ ፡ ገባው

**divine** (adj.) ግሩም
What divine weather! ምንኛ ፡ ግሩም ፡ አየር ፡ ነው !

**divine kingdom** መንግሥት ፡ ሰማያት
The divine kingdom is the reward of the virtuous in many religions. ለብዙ ፡ ሃይማኖቶች ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መግቢያ ፡ የደግ ፡ አድራጊዎች ፡ ዋጋ ፡ ነው

**divine right** የቅብዓ ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን
King Charles claimed to rule by divine right. ንጉሡ ፡ ቻርለስ ፡ በቅብዓ ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ እገዛለሁ ፡ ይል ፡ ነበር

**divine scripture** ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት
Divine scripture tells us how to obtain salvation. ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ድኅነት ፡ የምናገኝበትን ፡ መንገድ ፡ ይነግሩናል

**divine worship** ለአምልኮት ፡ ስግደት
In olden days, divine worship was often performed outdoors. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ለአምልኮት ፡ ስግደት ፡ ከቤት ፡ ውጭ ፡ ይደረግ ፡ ነበር

**divinity** መለኮትነት
Most Christians believe in the divinity of Christ. አብዛኛው ፡ ክርስቲያን ፡ በክርስቶስ ፡ መለኮትነት ፡ ያምናል

**divisible** ተካፋይ
The number 6 is divisible by 2 and 3. ስድስት ፡ በሁለትና ፡ በሦስት ፡ ተካፋይ ፡ ነው

**division**
1. ክፍል. My brother works in the testing division. ወንድሜ ፡ በፈተና ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ይሠራል
2. ድንበር. This hedge forms the division between his land and mine. ይህ ፡ የጢሻ ፡ አጥር ፡ የኔና ፡ የሱ ፡ መሬት ፡ ድንበር ፡ ነው
3. ልዩነት. Divisions between social classes are not so great as formerly. በኅብረተ ፡ሰቡ ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ ልዩነቶች ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ የበዙ ፡ አይደሉም
4. ማካፈል. Children find it hard to learn division. ማካፈልን ፡ መማር ፡ ለሕፃናት ፡ ያስቸግራል
5. አከፋፈል. The division of profits among the partners was equitable. የባለጥቅሞቹ ፡ የትርፍ ፡ አከፋፈል ፡ ተገቢ ፡ ነበር
6. ክፍለ ፡ ጦር. Ten divisions were destroyed. ዐሥር ፡ ክፍለ ፡ ጦሮች ፡ ወደሙ

**divorce** (v.)
1. ፈታ. She divorced her husband several years ago. ባሏን ፡ ከፈታች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆናት
2. አፋታ. The priest divorced the couple. ቄሱ ፡ ባልና ፡ ሚስቶቹን ፡ አፋታቸው

**be divorced from** ፈታ
He's divorced from his wife. ሚስቱን ፡ ፈቷል

*His plan is divorced from reality. እቅዱ ፡
የሕልም ፡ እንጀራ ፡ ነው

**divorce** (n.)
1. ፍች. Some homes are broken by divorce.
አንዳንድ ፡ ትዳር ፡ በፍች ፡ ይፈርሳል
2. መፋታት. Church dogma does not condone
divorce. የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ መፋታት
ን ፡ አይፈቅድም
*In America, there is a complete divorce of
government and religion. በአሜሪካ ፡ ፖለቲካና ፡
ሃይማኖት ፡ በፍጹም ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው

**get a divorce** ፈታ
She wants to get a divorce. ለመፍታት ፡ ትፈ
ልጋለች

**divorced** (adj.) ፈት
She is a divorced woman. ፈት ፡ ናት
He is a divorced man. ፈት ፡ ነው

**divulge**
1. አወጣ. We hope he will not divulge the
secret. ምስጢሩን ፡ እንደማያወጣ ፡ ተስፋ ፡ አለን
2. ገለጸ. He wouldn't divulge his name to
the police. ስሙን ፡ ለፖሊስ ፡ ለመግለጽ ፡ ፈቃ
ደኛ ፡ አልነበረም

**dizzy** ጭው ፡ ያለ
The airplane climbed to a dizzy height. አውሮ
ፕላኑ ፡ ጭው ፡ ያለ ፡ ከፍታ ፡ ላይ ፡ ደረሰ

**feel dizzy**
1. ተጫጫነ(ው). I feel dizzy and want to lie down.
ስለተጫጫነኝ ፡ ጋደም ፡ ማለት ፡ እፈልጋለሁ
2. ጭው ፡ አለ(በት). He felt dizzy when he stood
on the edge of the precipice. ገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ላ
ይ ፡ ሲቆም ፡ ጭው ፡ አለበት

**make dizzy** አዞረ
The sudden ascent of the elevator made me
dizzy. የአሰንሰሩ ፡ መመንጠቅ ፡ አዞረኝ
[See also 'sensation']

**do** (did, done)
1. ሠራ. What are you doing this afternoon?
ዛሬ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ ትሠራለህ ?
What does he do for a living? ምን ፡ ሠርቶ ፡ ይ
በላል ?
2. አደረገ. They cannot do a thing to him.
ምንም ፡ ሊያደርጉት ፡ አይችሉም
What can I do? After all, he is my friend.
ምን ፡ ላድርግ ፤ መቼም ፡ ጓደኛዬ ፡ ነው
3. አለ. How do you do? እንደምን ፡ አለህ ?
4. ሆነ. The corn is doing well this year. በቆሎ
ው ፡ ዘንድሮ ፡ ጥሩ ፡ ሆኗል
See there, that won't do at all. ስማ ፤ ይህ ፡ ፈ
ጽሞ ፡ የማይሆን ፡ ነገር ፡ ነው
5. ኖረ. We can't do without water. ያለ ፡ ውኃ ፡
ልንኖር ፡ አንችልም
6. በቃ. This roast has to do for four people.
ይህ ፡ ጥብስ ፡ ለአራት ፡ ሰው ፡ መብቃት ፡ አለበት
That will do for now. ላሁን ፡ ይበቃል
7. አዋጣ. This won't do, my friend. ወዳጄ ፤
ይህ ፡ አያዋጣም
8. አዘጋጀ (ተዘጋጀ). My room hasn't been done
yet. ክፍሌ ፡ ገና ፡ አልተዘጋጀም
9. አጠና. I have to do my Amharic tonight.
ያማርኛ ፡ ትምህርቴን ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ ማጥናት ፡
አለብኝ
*He's doing very well at school. ትምህርቱን ፡ በ
ትጋት ፡ ይከታተላል
*What can I do for you? ምን ፡ ልታዘዝ ?

**do away with**
1. አስወገደ. They plan to do away with most
of the requirements. አስፈላጊ ፡ ከሚባሉት ፡ ነ
ገሮች ፡ ብዙዎቹን ፡ ለማስወገድ ፡ ያቅዳሉ
2. አጠፋ. He did away with himself. ራሱን ፡ አጠፋ
3. ገደለ. He was accused of doing away with
his wealthy uncle. ሀብታም ፡ አጐቱን ፡ ገድሎሃ
ል ፡ ተብሎ ፡ ተከሷል
4. ሰረዘ. Parliament voted to do away with
several tax laws. ፓርለማ ፡ ብዙዎቹን ፡ የቀረጥ ፡
ሕጎች ፡ ለመሰረዝ ፡ ተስማማ

**(be) done away with** ጠፋ
Bribery should be done away with. ጉቦ ፡
መጥፋት ፡ አለበት

**do (one's) best** የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ሞከረ
I'll do my best to have it ready on time.
በጊዜው ፡ እንዲደርስ ፡ የተቻለኝን ፡ ያህል ፡ እሞ
ክራለሁ

**do by** ያዘ
He has done well by his family. ቤተ ፡ ሰ
ቦቹን ፡ በሚገባ ፡ ይዟል

**do good** ጠቀመ.
A vacation will do you a lot of good. ዕረፍት ፡
በጣም ፡ ይጠቅምሃል
It won't do you much good to complain.
ማማረር ፡ ምንም ፡ አይጠቅምህም

**do with**
*I could do with more leisure time. የበለጠ ፡
የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ባገኝ ፡ እወዳለሁ
*What did you do with my umbrella? ጃንጥላዬ
ን ፡ የት ፡ አደረስከው ?

**do without** ችላ ፡ አለ
She did without necessities to be able to pay

for her daughter's piano lessons. የሚያስፈልጋትን ፡ ሁሉ ፡ ችላ ፡ ብላ ፡ ለልጇ ፡ ፒያኖ ፡ ማስተማሪያ ፡ ከፈለች
*Can you do without this pencil for a while? እርሳስህን ፡ እንዴ ፡ ልሠራበት ፡ እችላለሁ ?

**have to do (with)** መዋዋል ፡ አለበት
A lawyer has to do with all sorts of people. ጠበቃ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ መዋዋል ፡ አለበት
*Many are convinced that smoking has a great deal to do with lung cancer. የሳንባ ፡ ነቀርሳ ፡ ሲጃራ ፡ ከማጨስ ፡ የሚመጣ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ብዙዎች ፡ ያምናሉ

**not have to do (with)** ምንም ፡ ግንኙነት ፡ የለው
That has nothing to do with the question. እሱ ፡ ከጥያቄው ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ግንኙነት ፡ የለው
[See also 'dish, well']

**docile** ታዛዥ
The docile dog wagged his tail. ታዛዡ ፡ ውሻ ፡ ጅራቱን ፡ ቈላ

**dock** (vt.)
1. ከወደብ ፡ አሳረፈ ፤ ወደ ፡ ወደብ ፡ አስገባ. The captain docked his boat at three o'clock. ካፒቴኑ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ መርከቡን ፡ ከወደብ ፡ አሳረፋት
A tugboat is used to dock large ships. ጐታች ፡ ጀልባ ፡ ትልልቅ ፡ መርከቦችን ፡ ወደ ፡ ወደብ ፡ ለማስገባት ፡ ያገለግላል
2. ቈረጠ. The company docks the men's wages if they come late to work. ኩባንያው ፡ ሠራተኞች ፡ ዘግይተው ፡ ሲመጡ ፡ ደሞዛቸውን ፡ ይቈርጣል

**dock** (vi.) ከወደብ ፡ ደረሰ
The ship docked three hours late. መርከቡ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ዘግይቶ ፡ ከወደቡ ፡ ደረሰ

**dock** (n.)
1. [በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የተከሳሹ ፡ መቆሚያ]
2. የመርከብ ፡ ማራገፊያ ፤ የመርከብ ፡ መቆሚያ. The bags of wheat were piled on the dock. የስንዴ ፡ ዶንያዎች ፡ በመርከብ ፡ ማራገፊያ ፡ ተከምረው ፡ ነበር
The dock was built last year. የመርከብ ፡ መቆሚያው ፡ ዓምና ፡ ተሠራ

**doctor** (v.) አከመ
He doctors his children himself. ልጆቹን ፡ ራሱ ፡ ያከማል

**doctor** (n.) ሐኪም ፤ ዶክተር
How many doctors are there in Addis Ababa? አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ስንት ፡ ሐኪሞች ፡ አሉ ?
[See also 'witch doctor']

**doctrine**
1. ሕግ. The doctrines of the church are very rigid. የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሕግ ፡ በጣም ፡ ጥብቅ ፡ ነው
2. እምነት. Many theologians criticized the unsound doctrine. ብዙ ፡ የሃይማኖት ፡ ሊቃውንት ፡ መሠረት ፡ የሌለውን ፡ እምነት ፡ ነቀፉ

**document** (v.) በማስረጃ ፡ አረጋገጠ
He documented all instances in which the judge took a bribe. ዳኛው ፡ ጉቦ ፡ የተቀበለበትን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በማስረጃ ፡ አረጋገጠ

**document** (n.) ሰነድ
A birth certificate is a document of importance. የልደት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ሰነድ ፡ ነው

**documentary** የጽሑፍ
Give me documentary proof of your accusation! ለምን ፡ እንደከሰስከኝ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ አቅርብልኝ

**documentation** መረጃዎች
Documentation is required in order to obtain a passport. የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ ለማግኘት ፡ መረጃዎች ፡ ማቅረብ ፡ ያስፈልጋል

**dodge** (vt.) አድበሰበሰ
The lawyer dodged the issue. ጠበቃው ፡ ጭብጡን ፡ አድበሰበሰው

**dodge** (vi.) ዞር ፡ ብሎ ፡ አሳለፈ
He dodged cleverly when I threw my shoe at him. ጫማዬን ፡ ስወረውርበት ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ አሳለፈው

**dog** (n.) ውሻ
Beware of the dog! ውሻውን ፡ ተጠንቀቅ

**be dog tired** ክፉኛ ፡ ደከመ
They were dog tired after the excursion. ከሽርሽሩ ፡ በኋላ ፡ ክፉኛ ፡ ደክመው ፡ ነበር

**go to the dogs** በጣም ፡ ወደቀ
The country is going to the dogs. አገሪቷ ፡ በጣም ፡ ወደቀች

**lead a dog's life** የብስጭት ፡ ኑሮ ፡ ኖረ
Ever since he left home, he has led a dog's life. ከቤቱ ፡ ከወጣ ፡ ጀምሮ ፡ የብስጭት ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል

**dog** (dogged), v. በጥብቅ ፡ ተከታተለ
The police dogged the suspected thief. ፖሊሱ ፡ የተጠረጠረውን ፡ ሌባ ፡ በጥብቅ ፡ ተከታተለው

**dogged** (adj.)
*His dogged effort helped him to win the race. ሙሉ ፡ ጥረት ፡ ማድረጉ ፡ በሩጫው ፡ ላይ ፡ እንዲያሸንፍ ፡ ረዳው

**dogged determination** ጠንካራ ፡ መንፈስ
His success is in good part ascribable to dogged determination. ካሰበው ፡ መድረሱ ፡ አብዛኛው ፡ ከጠንካራ ፡ መንፈሱ ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል

**dogma** ሕግ
Church dogma does not condone divorce. የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ መፋታትን ፡ አይፈቅድም

**dogmatic**
*The professor is very dogmatic. ፕሮፌሶሩ ፡ እኔ ፡ ያልኩት ፡ ይሁን ፡ ባይ ፡ ነው

**doings** አድራጎት ፤ ድርጊት
His doings are the subject of neighborhood gossip. አድራጎቶቹ ፡ ሁሉ ፡ የቡና ፡ መጠጫ ፡ ሆነዋል
The elders observed the doings of the young people with disapproval. ሽማግሌዎች ፡ የወጣቶችን ፡ ድርጊት ፡ በትዝብት ፡ ተመለከቱ

**dole, ~ out** ዐደለ
He doled out some food to the poor. ለድኾች ፡ ምግብ ፡ ዐደለ

**doleful** አሳዛኝ
We could hear the doleful wail of the woman. የሴትዮዋን ፡ አሳዛኝ ፡ ለቅሶ ፡ እንሰማ ፡ ነበር

**doll** አሻንጉሊት
Girls like to play with dolls. ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በአሻንጉሊት ፡ መጫወት ፡ ይወዳሉ

**dollar** ብር
An Ethiopian dollar has a hundred cents. አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ መቶ ፡ ሳንቲም ፡ ነው

**dolorous** አሳዛኝ
She uttered a dolorous cry. አሳዛኝ ፡ ለቅሶ ፡ አሰማች

**dolphin** [ከዓሣ ፡ ነባሪ ፡ የተዛመደ ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ እንስሳ]

**domain**
1. ርስት. The merchant has a large domain. ነጋዴው ፡ ሰፊ ፡ ርስት ፡ አለው
2. ግዛት. The domain of the Emir of Harar was located in southeastern Ethiopia. የሐረር ፡ አሚር ፡ ግዛት ፡ በደቡብ ፡ ምሥራቅ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይገኝ ፡ ነበር
*This application does not fall in my domain. ይህ ፡ ማመልከቻ ፡ እኔን ፡ አይመለከትም

**in the domain of** በ - - - ረገድ
Edison was a leader in the domain of invention. ኤዲሰን ፡ በፍልስፍና ፡ ረገድ ፡ መሪ ፡ ነበር

**dome** ጉልላት
The dome of the church is painted blue. የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ጉልላት ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ ተቀብቷል

**domestic**
1. የቤት. Horses, cows and sheep are domestic animals. ፈረሶች ፡ ላሞችና ፡ በጎች ፡ የቤት ፡ እንስሶች ፡ ናቸው
2. የቤት ፡ ውስጥ. He has many domestic problems. ብዙ ፡ የቤት ፡ ውስጥ ፡ ችግር ፡ አለበት
3. የሀገር ፡ ውስጥ. The newspaper publishes both domestic and foreign news. ጋዜጣው ፡ የሀገር ፡ ውስጥና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜናዎች ፡ ያወጣል
4. ባገር ፡ ውስጥ ፡ የተሠራ. Those are all domestic products. እነዚህ ፡ እቃዎች ፡ ሁሉ ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው
*She has always been very domestic. የጓዳ ፡ ሰው ፡ ነች

**domesticate** አላመደ ፤ ለማዳ ፡ አደረገ
Some people try to domesticate lions. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ አንበሳን ፡ ለማላመድ ፡ ይሞክራሉ
Man domesticated cattle thousands of years ago. ሰው ፡ ከብዙ ፡ ሺህ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የቀንድ ፡ ከብቶችን ፡ ለማዳ ፡ አደረገ

**domicile** መኖሪያ
He makes his domicile in Addis Ababa. መኖሪያውን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ አድርጓል

**dominant**
1. ከሌላው ፡ የሚልቅ. Red is the dominant color in his paintings. በሥዕሉ ፡ ውስጥ ፡ ከሌላው ፡ ቀለማት ፡ የሚልቀው ፡ ቀይ ፡ ነው
2. ጐልቶ ፡ የሚታይ. Ethiopia is the dominant state in the Horn of Africa. ኢትዮጵያ ፡ በአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ጐልታ ፡ የምትታይ ፡ አገር ፡ ነች
3. ዋና. Corn is the dominant crop in the region. በቆሎ ፡ የቀበሌው ፡ ዋና ፡ እህል ፡ ነው

**be dominant** ሰፈነ
The feudal system was dominant in the Middle Ages. በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ የባላባት ፡ አገዛዝ ፡ ሰፍኖ ፡ ነበር

**dominate**
1. ገዛ. The strong usually dominate the weak. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ብርቱ ፡ ደካማን ፡ ይገዛል
2. ተጫነ. His weak character allows everyone to dominate him. ደካማ ፡ መንፈሱ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲጫነን ፡ ያደርገዋል
3. ከሁሉም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ታየ. The mountain dominates the harbor. ወደቡ ፡ አጠገብ ፡ ያለው ፡ ተራራ ፡ ከሁሉም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ይታያል

**domination** አገዛዝ
Fascist domination lasted only six years. የፋሽስት ፡ አገዛዝ ፡ ለስድስት ፡ ዓመታት ፡ ብቻ ፡ ቆየ

**domineer** ጨቈነ
Big boys sometimes domineer over their small sisters. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ትልልቅ ፡ ልጆች ፡ ታናሽ ፡ እኅቶቻቸውን ፡ ይጨቊናሉ

**domineering** ኀይለኛ
A domineering mother can emasculate her sons. ኀይለኛ ፡ እናት ፡ የወንዶች ፡ ልጆቿን ፡ የወንድነት ፡ ወኔያቸውን ፡ ልትገድል ፡ ትችላለች

**dominion**
1. ግዛት. The dominions of the king were enlarged by military campaigns. የንጉሡ ፡ ግዛቶች ፡ በወታደር ፡ ኀይል ፡ ተስፋፍተው ፡ ነበር
2. የበላይነት. He struggled to escape the dominion of others. የሌሎችን ፡ የበላይነት ፡ ለመሸሽ ፡ ታገለ

**have dominion over** ገዛ
The Romans had dominion over a large part of the world. ሮማውያን ፡ ብዙውን ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ ይገዙ ፡ ነበር

**don** (donned) ለበሰ
The judge donned his robe. ዳኛው ፡ ካባውን ፡ ለበሰ

**donate**
1. እርዳታ ፡ ሰጠ. He donated ten dollars to the Red Cross. ለቀይ ፡ መስቀል ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ እርዳታ ፡ ሰጠ
2. ረዳ. I donated a dollar. አንድ ፡ ብር ፡ ረዳሁ

**donation** እርዳታ
Donations are welcome. እርዳታ ፡ እንቀበላለን

**(be) done** (see also 'do')
1. አለቀ. When the work is done you can go. ሥራው ፡ ሲያልቅ ፡ ልትሄድ ፡ ትችላለህ
2. በሰለ. In ten minutes the meat will be done. ባሥር ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ሥጋው ፡ ይበስላል
3. (= active) ጨረሰ. +All my lessons are done. ጥናቴን ፡ ሁሉ ፡ ጨርሻለሁ
*That sort of thing isn't done. እንዲህ ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ አይገባም

**well done** በሰል ፡ ሲል
I like my cutlet well done. ኮተሌት ፡ የምወደው ፡ በሰል ፡ ሲል ፡ ነው

**donkey** አህያ
Country people know how to load a donkey. የባላገር ፡ ሰዎች ፡ አህያ ፡ መጫን ፡ ያውቃሉ

**he donkey** ወይል ፡ አህያ
Is that donkey a he or a she? ያ ፡ አህያ ፡ ወይል ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ እናቲት ?

**she donkey** እናቲት ፡ አህያ
Is a she donkey stronger than a he donkey? እናቲት ፡ አህያ ፡ ከወይል ፡ አህያ ፡ ትጠነክራለች ?

**donor**
1. የለገሰ. The donor of the blood is not known. ደም ፡ የለገሰው ፡ አይታወቅም
2. የሰጠ. The donor of this land is a rich man. ይህን ፡ መሬት ፡ የሰጠው ፡ ሀብታም ፡ ነው

**doodle** ሥዕል ፡ ቢጤ ፡ ጫጫረ
He doodled during the whole lecture. በትምህርቱ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ሥዕል ፡ ቢጤ ፡ ይጫጭር ፡ ነበር

**doom** (v.)
1. ፈረደ(በት). The judge doomed him to lifelong imprisonment. ዳኛው ፡ ዕድሜ ፡ ይፍታህ ፡ ፈረዱበት
2. አጠፋ. The weather doomed our hopes of a picnic. ያየሩ ፡ ጠባይ ፡ ለሽርሽር ፡ የነበረን ፡ ተስፋ ፡ አጠፋው

**doom to fail**
*The prospect was doomed to fail. የሥራው ፡ ውጥን ፡ ጥንቱን ፡ የማይሳካ ፡ ነበር

**doom** (n.) ክፉ ፡ ቀን
The fortune teller prognosticated doom. ኮከብ ፡ ቈጣሪው ፡ ክፉ ፡ ቀን ፡ ይመጣል ፡ አለ

**march to one's doom** ወደ ፡ ሞቱ ፡ አመራ
The soldiers marched to their doom. ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ሞታቸው ፡ አመሩ

**meet one's doom** የሞት ፡ ጽዋውን ፡ ቀመሰ
He met his doom on the battlefield. በጦር ፡ ሜዳ ፡ የሞት ፡ ጽዋውን ፡ ቀመሰ

**door** መዝጊያ ፤ በር
He locks the door every night. ማታ ፡ ማታ ፡ መዝጊያውን ፡ (በሩን) ፡ ይቈልፋል

**lay the blame at someone's door**
*The blame for delinquency may be laid at the door of careless parents. የወጣት ፡ ጥፋተኞች ፡ ተጠያቂዎች ፡ ግዴለሽ ፡ ወላጆች ፡ ናቸው

**from door to door** ከቤት ፡ ቤት
The peddler sold his wares from door to door.

ሱቅ ፡ በደረቴው ፡ እቃዎችን ፡ ከቤት ፡ ቤት ፡ እያዞረ ፡ ሸጠ

**next door**
*Who lives next door to you? ጐረቤትህ ፡ ማን ፡ ነው ?

**out of doors** ደጅ ፤ ውጭ
Did you ever sleep out of doors? ደጅ ፡ አድረህ ፡ ታውቃለህ ?
It is too cold to sit out of doors. ውጭ ፡ ለመቀመጥ ፡ በጣም ፡ ብርድ ፡ ነው

**show someone the door** አስወጣ
If he becomes insulting, show him the door. የሚሳደብ ፡ ከሆነ ፡ አስወጣው
[See also 'next']

**doorbell** የበር ፡ ደወል
When he pressed the button, the doorbell rang. መደወያውን ፡ ሲጫን ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ የበሩ ፡ ደወል ፡ ጮኸ

**doorman** በረኛ
A doorman stands outside the main entrance of the hotel. በረኛው ፡ ከሆቴሉ ፡ ዋና ፡ መግቢያ ፡ ውጭ ፡ ይቆማል

**doorsill** ደፍ
He stood on the doorsill a moment. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ደፉ ፡ ላይ ፡ ቆመ

**doorstep** ደጃፍ
The doorstep was covered with mud where people had wiped their feet. ሰዎች ፡ እግራቸውን ፡ ስለጠረጉበት ፡ ደጃፉ ፡ ጨቅይቶ ፡ ነበር

**doorway** ደጃፍ ፤ በራፍ
He fell over the dog sleeping in the doorway. ደጃፍ ፡ ላይ ፡ እተኛው ፡ ውሻ ፡ ላይ ፡ ወደቀ
Please don't stand in the doorway! በራፍ ፡ ላይ ፡ አትቁም !

**(be) dormant**
1. ተከተተ. Bears are dormant during the winter. ድቦች ፡ በክረምት ፡ ወራት ፡ ይከተታሉ
2. አላደገም. Some plants are dormant in the winter. አንዳንድ ፡ ዕፀዋቶች ፡ በክረምት ፡ አያድጉም
3. ፈንድቶ ፡ አያውቅም. This volcano has been dormant for the last hundred years. ባለፉት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ እሳተ ፡ ገሞራ ፡ ፈንድቶ ፡ አያውቅም

**dormer** [በጣሪያ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ ብሎ ፡ የተሠራ ፡ መስኮት]

**dormitory** መኝታ ፡ ቤት
The university has three student dormitories. ዩኒቨርሲቲው ፡ ሦስት ፡ የተማሪ ፡ መኝታ ፡ ቤቶች ፡ አሉት

**dorsal** የጀርባ
The fish has lateral fins as well as dorsal ones. ዓሣው ፡ የጐን ፡ ክንፍና ፡ የጀርባ ፡ ክንፍ ፡ አለው

**dosage** መጠን
The usual dosage is 1/2 teaspoon every 4 hours. የተለመደው ፡ መጠን ፡ በየአራቱ ፡ ሰዓት ፡ ግማሽ ፡ የሻይ ፡ ማንኪያ ፡ ነው

**dose** መጠን
Decrease the dose of the medicine as you feel better! እየተሻለህ ፡ ሲሄድ ፡ የምትወስደውን ፡ መድኃኒት ፡ መጠን ፡ ቀንስ
*The bottle contains six doses. ጠርሙሱ ፡ ለስድስት ፡ ጊዜ ፡ የሚሆን ፡ መድኃኒት ፡ አለበት

**dossier** ፋይል
The police keep dossiers on many criminals. ፖሊሶች ፡ የብዙ ፡ ወንጀለኞች ፡ ፋይል ፡ አላቸው

**dot** (dotted), v. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ታየ
Flowers dotted the hillside. በተራራው ፡ ወገብ ፡ ላይ ፡ አበባዎች ፡ አልፈው ፡ አልፈው ፡ ይታዩ ፡ ነበር

**dot** (n.)
1. ጠቃጠቆ. Wear your dress with the blue dots! ባለ ፡ ሰማያዊ ፡ ጠቃጠቆ ፡ ቀሚስሽን ፡ ልበሺ
2. ነጥብ. In Amharic, words are separated by two dots. ባማርኛ ፡ ቃላት ፡ የሚለዩት ፡ በሁለት ፡ ነጥብ ፡ ነው

**on the dot** ልክ
I will see you at three on the dot. ልክ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ እንገናኛለን

**right on the dot** ልክ ፡ በሰዓቱ
He came right on the dot. ልክ ፡ በሰዓቱ ፡ መጣ

**dotted** (adj.) የነጠብጣብ
Sign on the dotted line! በነጠብጣቡ ፡ መሥመር ፡ ላይ ፡ ፈርም

**double** (vt.)
1. ዕጥፍ ፡ አደረገ. He has doubled his capital in two years. ዋና ፡ ገንዘቡን ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ዕጥፍ ፡ አደረገው
2. (= intr.) ዕጥፍ ፡ ሆነበት. + His partner is ill, so he has to double his work. ሸርካው ፡ ስለ ታመመ ፡ ሥራው ፡ ዕጥፍ ፡ ሆኖበታል
3. ዕጥፍ ፡ አቀረበ. He doubled my bid. ያቀረብኩትን ፡ ጨረታ ፡ ዕጥፍ ፡ አቀረበ

4. ዐጠፈ. The child doubled a piece of paper. ልጁ ፡ ወረቀቱን ፡ ዐጠፈ

5. (= intr.) ዞሮ ፡ ሄደ. The ship doubled Cape Horn. መርከቧ ፡ በኬፕ ፡ ሆርን ፡ ዞራ ፡ ሄደች

**double** (vi.)

1. ዕጥፍ ፡ ሆነ. Prices have doubled this last year. ዓምና ፡ የገበያው ፡ ዋጋ ፡ ዕጥፍ ፡ ሆኖ ፡ ነበር

2. አገለገለ. The living room doubles as a dining area. ሳሎኑ ፡ እንደ ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ ያገለግላል

*The cook doubles as a chauffeur. ሰውዬው ፡ ወጥ ፡ ቤትም ፡ ሹፌርም ፡ ነው

**double for** ተካ

He doubles for the main actor. ዋናውን ፡ ተዋናይ ፡ የሚተካ ፡ ነው

**double over** ተሸማቀቀ ፤ ተኰራመተ

The child doubled over with pain. ሕፃኑ ፡ በሕመም ፡ ተሸማቀቀ ፡ (ተኰራመተ)

**double up**

1. ተኰራመተ ፤ ተሸማቀቀ. He doubled up in pain. በሕመም ፡ ተኰራመተ ፡ (ተሸማቀቀ)

2. ለሁለት ፡ ለሁለት ፡ ተኛ. We had to double up because there weren't enough beds to go around. በቂ ፡ አልጋ ፡ ስላልነበረ ፡ ለሁለት ፡ ለሁለት ፡ መተኛት ፡ ግድ ፡ ሆነብን

3. ተዳበለ. Because of a room shortage, we had to double up. ክፍል ፡ ስላነሰ ፡ መዳበል ፡ ነበረብን

**double** (n.)

1. ዕጥፍ. Ten is the double of five. ዐሥር ፡ ያምስት ፡ ዕጥፍ ፡ ነው

2. መንትያ. He could be your double, he looks so much like you. አንተን ፡ በጣም ፡ ስለሚመስል ፡ መንትያህ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

**double** (adj.)

1. ሁለት. Every language has words that have double meanings. ማንኛውም ፡ ቋንቋ ፡ ሁለት ፡ ፍች ፡ ያላቸው ፡ ቃላት ፡ አሉት

This sofa serves a double purpose. ይህ ፡ ሶፋ ፡ ሁለት ፡ ጥቅም ፡ አለው

May I have a double portion of rice? ሁለት ፡ ድርሻ ፡ ሩዝ ፡ ላገኝ ፡ እችላለሁ ?

2. መንታ. The conference room is closed off from the corridor by double doors. የስብሰባው ፡ አዳራሽ ፡ ከመተላለፊያው ፡ የሚለየው ፡ በመንታ ፡ መዝጊያዎች ፡ ነው

*It is double the size of mine. የኔን ፡ ሁለት ፡ ይሆናል

[See also 'time']

**double bed** የፋሚሊ ፡ አልጋ

Yesterday I bought a double bed. ትናንትና ፡ የፋሚሊ ፡ አልጋ ፡ ገዛሁ

**double-cross** አጭበረበረ

He double-crossed his partner in that deal. በዚህ ፡ ሥራ ፡ ሽርካውን ፡ አጭበረበረው

**double-faced** አታላይ

She is double-faced, so don't trust her. አታላይ ፡ ስለሆነች ፡ አትመናት

**double-talk**

*Everything he says is double-talk. የንግግሩ ፡ ትርጉም ፡ ሁሉ ፡ አሻሚ ፡ ነው

**doubly**

*You have to be doubly careful on this bad road. በዚህ ፡ መጥፎ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ አለብህ

**doubt** (v.) ተጠራጠረ

I doubt if the story is true. ታሪኩ ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ እጠራጠራለሁ

Do you think he will come? I doubt it. የሚመጣ ፡ ይመስልሃል ? እጠራጠራለሁ

**doubt** (n.) ጥርጥር ፤ ጥርጣሬ

Without a doubt, he is the best man for the job. ያላንዳች ፡ ጥርጥር ፡ (ጥርጣሬ) ፡ ለሥራው ፡ እሱ ፡ ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ ተገቢ ፡ ነው

*There is no room for doubt. ምንም ፡ የሚያጠራጥር ፡ ነገር ፡ የለም

**be in doubt**

1. አጠራጠረ. The result is still in doubt. ውጤቱ ፡ አሁንም ፡ የሚያጠራጥር ፡ ነው

2. ተጠራጠረ. When in doubt about the meaning of a word, consult the dictionary. ስላንድ ፡ ቃል ፡ ትርጉም ፡ በተጠራጠርክ ፡ ጊዜ ፡ መዝገበ ፡ ቃላትን ፡ ተመልከት

3. አልተጣራም. The guilt of the accused is in doubt. የተከሳሹ ፡ ጥፋት ፡ አልተጣራም

**beyond doubt** ያለ ፡ ጥርጥር

Beyond doubt, he is the greatest writer we have. ያለን ፡ ትልቅ ፡ ደራሲ ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ እሱ ፡ ነው

**have any doubts** የሚጠራጠርበት ፡ ነገር ፡ አለ

Do you have any doubts about marrying her? እሷን ፡ ለማግባት ፡ የምትጠራጠርበት ፡ ነገር ፡ አለ ?

**no doubt** አይጠረጠርም

No doubt the train will be late. ባቡሩ ፡ እንደሚዘገይ ፡ አይጠረጠርም

**not a shadow of a doubt**

There is not a shadow of a doubt about it. ስለሱ ፡ ምንም ፡ አያጠራጥርም

**throw doubt on** ጥርጣሬ ፡ ላይ ፡ ጣለ
This witness throws doubt on the honesty of the accused. ይህ ፡ ምስክር ፡ የተከሳሹን ፡ ታማኝነት ፡ ጥርጣሬ ፡ ላይ ፡ ይጥላል
[See also 'benefit, room']

**doubtful** አጠራጣሪ
The weather looks very doubtful. ያየሩ ፡ ሁኔታ ፡ በጣም ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው
**be doubtful** ተጠራጠረ
I am still doubtful about it. አሁንም ፡ በነገሩ ፡ እጠራጠራለሁ
*It's doubtful that he will get well. መዳኑ ፡ ያጠራጥራል

**doubtless** ያለ ፡ ጥርጥር
That is doubtless true. ያለ ፡ ጥርጥር ፡ እውነት ፡ ነው

**dough** ሊጥ
Yeast acts on the dough and makes it rise. እርሾ ፡ ሊጡን ፡ ያቦካውና ፡ ኩፍ ፡ እንዲል ፡ ያደርገዋል

**dour**
*The judge's dour expression made the defendant tremble. የዳኛው ፡ ፊቱን ፡ ማኰሳተር ፡ ተከሳሹን ፡ አርበደበደው

**douse**
1. ውኃ ፡ ረጨ. He doused me with the hose. በውኃ ፡ ማጠጫው ፡ ላስቲክ ፡ ውኃ ፡ ረጨኝ
2. ነከረ. The blacksmith doused the hot metal in water. ቀጥቃጩ ፡ የጋለውን ፡ ብረት ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ነከረ

**dove** ርግብ፤ እርግብ
One can domesticate a dove. ርግብን ፡ (እርግብን) ፡ ማላመድ ፡ ይቻላል

**dove,** see **dive**

**dovetail** ስምም ፡ ወርቅ ፡ ሆነ
Our plans dovetailed neatly. ሐሳባችን ፡ ስምም ፡ ወርቅ ፡ ሆነ

**down** (v.)
1. ጅው ፡ አደረገ. He downed his beer and ran outside. ቢራውን ፡ ጅው ፡ አድርጎ ፡ ሮጦ ፡ ወጣ
2. ጣለ. He downed his opponent in the third round. ባላጋራውን ፡ በሦስተኛው ፡ ዙር ፡ ላይ ፡ ጣለው

**down** (adv.) ታች
Down in the valley, the fog still lingers. እታች ፡ ሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ጉም ፡ አሁንም ፡ አልጠፋም
Did you look down there? እዚያ ፡ ታች ፡ አየህ ?
*Down with him! ገደል ፡ ይግባ
**down to** እስከ
He wrote the history of Ethiopia from the beginning down to our times. ከሥር ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ጻፈ
**be down**
1. ተበጠሰ. After the storm, all the telephone lines were down. ከኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ በኋላ ፡ የስልኩ ፡ መሥመር ፡ ሁሉ ፡ ተበጥሶ ፡ ነበር
2. ተጣለ. The curtain is down. መጋረጃው ፡ ተጥሏል
**be down with**
*He is down with a cold. ጉንፋን ፡ አስተኝቶታል
[See also 'go, hill']

**(be) downcast** አዘነ
The team was downcast over the loss of the game. ጨዋታውን ፡ ሳያሸንፍ ፡ ስለቀረ ፡ ቡድኑ ፡ አዝኖ ፡ ነበር
**look downcast** ፊቱ ፡ ላይ ፡ ሐዘን ፡ ተነበበ
She looked downcast when I told her she flunked. መውደቋን ፡ በነገርኋት ፡ ጊዜ ፡ ፊቷ ፡ ላይ ፡ ሐዘን ፡ ይነበብ ፡ ነበር
**stand with downcast eyes** አንገቱን ፡ አቀረቀረ
Ashamed of his mistakes, he stood with downcast eyes. በስሕተቱ ፡ አፍሮ ፡ አንገቱን ፡ አቀረቀረ

**downfall** ውድቀት
Heavy drinking caused his downfall. አብዝቶ ፡ መጠጣት ፡ ከውድቀት ፡ አደረሰው

**downgrade** (v.)
1. ከሥልጣን ፡ ዝቅ ፡ አደረገ. He downgraded the employees for their insubordination. ሠራተኞቹ ፡ አንታዘዝ ፡ ስላሉ ፡ ከሥልጣን ፡ ዝቅ ፡ አደረጋቸው
2. አንኳሰሰ. He downgraded the importance of the conference. የስብሰባውን ፡ ጠቃሚነት ፡ አንኳሰሰ

**downgrade** (n.), **be on the ~** ዝቅ ፡ እያለ ፡ ሄደ
His reputation has been on the downgrade since his last book. የመጨረሻውን ፡ መጽሐፉን ፡ ከጻፈ ፡ ወዲህ ፡ ዝናው ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ሄዷል

**downhearted** የተከዘ
He looks downhearted. የተከዘ ፡ ይመስላል

**downhill, go ~**
1. ቁልቁል ፡ ወረደ. Going downhill, our descent

was rapid. ቁልቁል ፡ ስንወርድ ፡ መንገዳችን ፡ ፈጣን ፡ ነበር
The road goes downhill. መንገዱ ፡ ቁልቁል ፡ ይወርዳል
2. ኑሮው ፡ ዝቅ ፡ አለ. He has been going downhill since he lost his job. ከሥራው ፡ ከወጣ ፡ ጀምሮ ፡ ኑሮው ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ሄዷል

**down payment** የመጀመሪያ ፡ ክፍያ
In all probability, you will have to make a down payment first. የመጀመሪያ ፡ ክፍያ ፡ መክፈል ፡ ሳይኖርብህ ፡ አይቀርም

**downpour** ዶፍ ፤ ኀይለኛ ፡ ዝናም ፡ መጣል
We were caught in the downpour. ዶፍ ፡ ወረደብን
The street was awash after the sudden downpour. በድንገት ፡ ኀይለኛ ፡ ዝናም ፡ በመጣሉ ፡ መንገዱን ፡ ውኃ ፡ አጥለቀለቀው

**downright**
1. ፍጹም. He gave a downright foolish answer. ፍጹም ፡ የማይረባ ፡ መልስ ፡ ሰጠ
2. ቁርጥ ፡ ያለ. His downright answer surprised the boss. ቁርጥ ፡ ያለው ፡ መልሱ ፡ አለቃውን ፡ አስደነቀው

**downstairs** (adv.)
1. እምድር ፡ ቤት. I will be waiting downstairs. እምድር ፡ ቤት ፡ እጠብቅሃለሁ
2. ከደረጃ. He tripped and fell downstairs. ተደናቅፎ ፡ ከደረጃ ፡ ወደቀ
*He ran downstairs. ደረጃውን ፡ ሩጦ ፡ ወረደ
**downstairs** (adj.) የምድር ፡ ቤት
The downstairs rooms are dark. የምድር ፡ ቤቱ ፡ ክፍሎች ፡ ጨለማ ፡ ናቸው

**downstream, float ~**
The logs floated downstream. ግንዶቹ ፡ በወንዙ ፡ ላይ ፡ ተንሳፈው ፡ ወረዱ

**down-to-earth**
He is a down-to-earth fellow. እሱ ፡ በተጨበጠ ፡ ነገር ፡ የሚመራ ፡ ሰው ፡ ነው

**downtown** መኻል ፡ ከተማ
Let's go downtown! ወደ ፡ መኻል ፡ ከተማ ፡ እንሂድ

**downward** ቁልቁል
The kite glided downward. ወላንዳው ፡ ቁልቁል ፡ አዥገመገመ
*This custom has been handed downward through the ages. ይህ ፡ ልማድ ፡ ከአያት ፡ ከቅድመ ፡ አያት ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፡ ነው
[See also 'flight']

**downwards, face ~** ደፍቶ
He left the pictures face downwards on the table. ሥዕሎቹን ፡ በጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ደፍቶ ፡ አስቀመጣቸው

**dowry** ጥሎሽ
In certain countries, the bride's father gives a dowry to the bride. በንዳንድ ፡ አገሮች ፡ የሙሽራይቱ ፡ አባት ፡ ለሙሽራይቱ ፡ ጥሎሽ ፡ ይሰጣል

**doze** አንቀላፋ
I was dozing while the man gave the speech. ሰውዬው ፡ ንግግር ፡ ሲያደርግ ፡ አንቀላፋ ፡ ነበር
**doze off** ሸለብ ፡ አደረገ(ው)
He dozed off after supper. ከራት ፡ በኋላ ፡ ሸለብ ፡ አደረገው

**dozen**
1. ደርዘን. Please give me a dozen eggs! አንድ ፡ ደርዘን ፡ እንቁላል ፡ ስጠኝ
2. ብዙ. I have dozens of reasons not to go to the office today. ዛሬ ፡ ወደ ፡ ቢሮ ፡ የማልሄድበት ፡ ብዙ ፡ ምክንያት ፡ አለኝ

**drab**
1. ረጋ ፡ ሠራሽ. The drab clothes of the country people show that they are poor. ያገር ፡ ቤት ፡ ሰዎች ፡ የሚለብሷቸው ፡ ረጋ ፡ ሠራሽ ፡ ልብሶች ፡ ሰዎቹ ፡ ድኻ ፡ መሆናቸውን ፡ ያሳያል
2. የማይጥም. He leads a drab existence. የማይጥም ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል

**draft** (v.)
1. አረቀቀ. The legislators must draft and submit bills. ሕግ ፡ አውጪዎች ፡ ሕግ ፡ አርቅቀው ፡ ማቅረብ ፡ አለባቸው
2. ያለ ፡ ፈቃዱ ፡ መረጠ. They drafted him to act as chairman. ለሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ያለ ፡ ፈቃዱ ፡ መረጡት
3. መለመለ. The army drafted him last month. ባለፈው ፡ ወር ፡ ለወታደርነት ፡ መለመሉት
**be drafted** ለወታደርነት ፡ ተመለመለ
He was drafted last month. ባለፈው ፡ ወር ፡ ለወታደርነት ፡ ተመለመለ

**draft** (n.)
1. ነፋስ. I cannot stand the draft in this room. የዚህን ፡ ቤት ፡ ነፋስ ፡ አልችልም
2. ረቂቅ. The first draft of his speech is ready. የንግግሩ ፡ የመጀመሪያ ፡ ረቂቅ ፡ ተዘጋጅቷል
3. ሐዋላ. He gave a draft for $1,000. ላንድ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ሐዋላ ፡ ሰጠ
4. ለወታደርነት ፡ በግዴታ ፡ መመልመል. The draft is certainly necessary in wartime. በጦር

ነት ፡ ጊዜ ፡ ለወታደርነት ፡ በግዴታ ፡ መመል
መል ፡ በርግጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**drafty**
This is a drafty room. ይህ ፡ ከሁለት ፡ አቅጣጫ ፡ ነፋስ ፡ የሚገባበት ፡ ክፍል ፡ ነው

**drag** (dragged), vt.
1. ጐተተ. His clothes were torn when the police dragged him. ፖሊሱ ፡ ሲጐትተው ፡ ልብሱ ፡ ተ ቀደደ
2. እየገፋ ፡ ወሰደ. He dragged the bicycle home because it had a flat tire. የቢስክሌቱ ፡ ጎማ ፡ ስለተነፈሰበት ፡ እየገፋ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወሰዳት

**drag** (vi.)
1. ተጐተተ. Her skirt is dragging on the floor. ቀሚሷ ፡ በወለሉ ፡ ላይ ፡ ይጐተታል
2. ረዘመ. Time drags when you do not have anything to do. የምትሠራው ፡ ስታጣ ፡ ጊዜው ፡ ይረዝማል

**drag on**
1. ተጓተተ. The meeting dragged on for three hours. ስብሰባው ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ተጓተተ
2. ረዘመ. The days just dragged on. ቀኑ ፡ ረዘመ

**drag oneself**
*He could hardly drag himself to work. ወደ ፡ ሥራ ፡ ለመሄድ ፡ እግሩን ፡ እንኳ ፡ ማንሣት ፡ አቃተው

**drag** (n.) ዕንቅፋት
A lazy, complaining boy is a drag on the team. ሰነፍና ፡ ነጭናጫ ፡ ልጅ ፡ ለቡድኑ ፡ ዕንቅፋት ፡ ነው

**dragnet** ተጐታች ፡ መረብ
Fish were caught in the dragnet. ዓሣዎቹ ፡ በተ ጐታች ፡ መረብ ፡ ተያዙ

**drain** (vt.)
1. አደረቀ. They are draining the marsh to build houses there. ቤት ፡ ለመሥራት ፡ ረግረጉ ን ፡ በማድረቅ ፡ ላይ ፡ ናቸው
2. ውኃ ፡ ለቀቀ. The mother drained the bathtub. እናትዮዋ ፡ መታጠቢያው ፡ ገንዳ ፡ ውስጥ ፡ የነበ ረውን ፡ ውኃ ፡ ለቀቀችው
*War drains a country of its people and money. ጦርነት ፡ ያንድን ፡ አገር ፡ ሕዝብና ፡ ገንዘብ ፡ ይጨር ሳል

**drain** (vi.)
1. ፈሰሰ. The river drains into the ocean. ወንዙ ፡ ወደ ፡ ውቅያኖሱ ፡ ይፈሳል
2. ጠፈፈ. She left her dishes to drain. ሳሕኖቹ ፡ እንዲጠፉ ፡ ደረደረቻቸው

**drain off** ወረደ
The water doesn't drain off. ውኃው ፡ አይወር ድም
[See also 'energy']

**drain** (n.) የእጣቢ ፡ መውረጃ
The drain is stopped up again. የእጣቢው ፡ መው ረጃ ፡ እንደገና ፡ ተደፈነ

**be a (great) drain on**
1. ጨረሰ. Working too hard is a drain on your strength. ብዙ ፡ መሥራት ፡ ጉልበት ፡ ይጨርሳል
2. አራቆተ. Military expenditures have been a great drain on the country's treasury. ለጦር ፡ ኀይል ፡ የሚደረገው ፡ ወጪ ፡ ያገሪቷን ፡ ግም ጃ ፡ ቤት ፡ አራቆተ

**drainage**
1. የውኃ ፡ መውረጃ. Adequate drainage is maintained by a series of ditches. በቂ ፡ የውኃ ፡ መ ውረጃ ፡ በርከት ፡ ባሉ ፡ ቦዮች ፡ ይሟላል
2. (= to drain) ማድረቅ. The drainage of swamps improves the land. ረግረጎችን ፡ ማድረ ቅ ፡ መሬት ፡ ያሻሽላል

**drainage canal** የቆሻሻ ፡ መውረጃ ፡ ቦይ
There are not enough drainage canals in this city. በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ በቂ ፡ የቆሻሻ ፡ መ ውረጃ ፡ ቦዮች ፡ የሉም

**drama**
1. ቴያትር. This author wrote many dramas. ይህ ፡ ደራሲ ፡ ብዙ ፡ ቴያትሮችን ፡ ደርሷል
2. ታሪክ. The history of America is a thrilling drama. የአሜሪካ ፡ ታሪክ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ታሪ ክ ፡ ነው

**dramatic**
1. የድራማ. His dramatic writings have been printed in one book. የድራማ ፡ ጽሑፎቹ ፡ ባ ንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ታትመው ፡ ወጥተው ፡ ነበር
2. አስደናቂ. These are dramatic changes in the international situation. እነዚህ ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ አስደናቂ ፡ ለውጦች ፡ ናቸው

**dramatize**
1. በድራማ ፡ መልክ ፡ አወጣ. They dramatized the life of Edison in a movie. የኤዲሰንን ፡ የሕ ይወት ፡ ታሪክ ፡ በድራማ ፡ መልክ ፡ በፊልም ፡ አ ወጡት
2. አሳምሮ ፡ ገለጸ. The newspaper dramatized the wedding. ጋዜጣው ፡ የሰርጉን ፡ ዜና ፡ አሳ ምሮ ፡ ገለጸ
3. አጋነነ. She dramatizes all her illnesses. ሕመሟን ፡ ሁሉ ፡ ታጋንናለች

**drank,** see **drink**

**drape** (v.)

1. አለበሰ. He draped the wall with flags. ግድግዳውን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ አለበሰው
2. ሸፈነ. The woman draped cloth over the furniture to protect it from dust. ሴትዮዋ ፡ አቧራ ፡ እንዳይለብስ ፡ እቃውን ፡ ጨርቅ ፡ ሸፈነችው
3. ጋረደ. They draped the window with a heavy cloth. መስኮታቸውን ፡ በወፍራም ፡ ጨርቅ ፡ ጋረዱ
4. ሸነሸነ. The seamstress draped the skirt around the customer's waist. ልብስ ፡ ሰፊዋ ፡ ቀሚሱን ፡ በደንበኛዋ ፡ ወገብ ፡ ልክ ፡ ሸነሸነች

**drape around oneself**
She draped the cloth around herself. ነጠላዋን ፡ አጣፋች

**drape** (n.) ወፍራም ፡ መጋረጃ
She bought white drapes for her living room windows. ለሳሎኑ ፡ መስኮቶች ፡ ነጭ ፡ ወፍራም ፡ መጋረጃ ፡ ገዛች

**drastic** ጥብቅ
The government took drastic measures to stop inflation. የገንዘብን ፡ መርከስ ፡ ለመከላከል ፡ መንግሥት ፡ ጥብቅ ፡ እርምጃ ፡ ወሰደ

**draw** (drew, drawn), vt.

1. ሳበ. The horses draw the wagon. ፈረሶች ፡ ሰረገላ ፡ ይስባሉ
2. ሣለ. He drew a picture of his teacher. ያስተማሪውን ፡ ሥዕል ፡ ሣለ
3. አሠመረ. He drew a straight line. ቀጥተኛ ፡ መሥመር ፡ አሠመረ
4. ቀዳ. The boy drew water from the well. ልጁ ፡ ከጉድጓድ ፡ ውኃ ፡ ቀዳ
5. አወጣ. He drew his hands from his pocket. እጆቹን ፡ ከኪሱ ፡ አወጣ
He drew a lot of money from the bank. ከባንክ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አወጣ
6. አገኘ. He draws a large salary. ብዙ ፡ ደሞዝ ፡ ያገኛል
7. ተጣጣለ. They drew lots to see who should go first. መጀመሪያ ፡ ማን ፡ እንደሚሄድ ፡ ለማወቅ ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉ
8. አስገባ. You should draw fresh air into your lungs. ትኩስ ፡ አየር ፡ ወደ ፡ ሳንባህ ፡ ማስገባት ፡ አለብህ
9. ጣለ. She draws the curtains when there is too much sunshine. ብዙ ፡ የፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ሲኖር ፡ መጋረጃውን ፡ ትጥላለች
10. አተረፈ(ለት). His speech drew long applause. ንግግሩ ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ጭብጨባ ፡ አተረፈለት
11. ማረከ. Her elegant dress drew the eye of all onlookers. ያሸበረቀው ፡ ልብሷ ፡ የተመልካቾቹን ፡ ዓይን ፡ ሁሉ ፡ ማረከ
12. መዘዘ. He drew his sword and ran at his enemy. ጐራዴውን ፡ መዞ ፡ ወደ ፡ ጠላቱ ፡ ሮጠ
*The movie is sure to draw a big crowd. ሲኒማውን ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እንደሚያየው ፡ እርግጠኛ ፡ ነው
*His lecture drew a large audience. የሱን ፡ ንግግር ፡ ለማዳመጥ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ተሰበሰበ

**draw** (vi.)

1. ተቃረበ. The train is just drawing into the station. ባቡሩ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ጣቢያው ፡ ተቃርቧል
In the spring of 1945, the war was drawing to a close. በ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ.ም. በጸደይ ፡ ወራት ፡ ጦርነቱ ፡ ወደ ፡ ማለቅ ፡ ተቃርቦ ፡ ነበር
2. ሣለ. He draws best with crayons. በከለር ፡ የበለጠ ፡ ይሥላል

**draw ahead of** ቀደመ
The black horse drew ahead of the others. ጥቁሩ ፡ ፈረስ ፡ ሌሎቹን ፡ ፈረሶች ፡ ቀደማቸው

**draw back** ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈገ
Everyone drew back in alarm when they saw the snake. እባቡን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ በድንጋጤ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈጉ

**draw in** አስገባ ፤ ሰበሰበ
The cat drew in his claws. ድመቷ ፡ ጥፍሮቿን ፡ አስገባች (ሰበሰበች)
*He looked out for a minute and then drew in his head. አንገቱን ፡ ብቅ ፡ አድርጎ ፡ መለሰ

**(be) drawn into** ገባ
I have been drawn into this argument against my will. ያለ ፡ ፈቃዴ ፡ እዚህ ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ ገባሁ

**draw near**

1. ተጠጋ. We drew near the fire to get warm. እንዲሞቀን ፡ ወደ ፡ እሳቱ ፡ ተጠጋን
2. ተቃረበ. Christmas is drawing near. ገና ፡ እየተቃረበ ፡ ነው

**draw nigh** ተቃረበ
The time draws nigh. ጊዜው ፡ ተቃረበ

**draw on oneself** አተረፈ(ለት)
Your action drew praise on you. ሥራህ ፡ ምስጋና ፡ አተረፈልህ

**draw out** አወጣ
I will have to draw out fifty dollars from the bank. ከባንክ ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ማውጣት ፡ አለብኝ

**(be) drawn out** ተጓተተ
The battle was drawn out over several days. ጦርነቱ ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ ያህል ፡ ተጓተተ

**(be) drawn to**
*She didn't feel drawn to him. ምንም ፡ አልማ ረከት

**draw up** (vt.)
1. አስጠጋ. Draw your chair up to the table! ወምበርህን ፡ ወደ ፡ ጠረጴዛው ፡ አስጠጋ
2. አወጣ ፤ አዘጋጀ. Who drew up the program? ፕሮግራሙን ፡ ማን ፡ አወጣ ፡ (አዘጋጀ) ?
3. ነደፈ. Who drew up the plan for the house? የቤቱን ፡ ፕላን ፡ ማን ፡ ነደፈው ?

**draw up** (vi.) ተቃረበ
A taxi is drawing up. ታክሲ ፡ እየተቃረበ ፡ ነው

**(be) drawn up**
1. ተሰለፈ. The troops were drawn up for inspection. ወታደሮቹ ፡ ለቁጥጥር ፡ ተሰልፈው ፡ ነበር
2. ተዋዋለ. Mercantile law specifies how contracts must be drawn up. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ውል ፡ መዋዋል ፡ እንዴት ፡ እንደሚገባ ፡ ይወስናል
[See also 'analogy, attention, blood, breath, conclusion, constitution, horn, line, parallel, tears']

**drawback** ትልቅ ፡ ዕንቅፋት
It is a drawback not to have books when you are a student. ተማሪ ፡ ሆነህ ፡ መጽሐፍ ፡ ማጣ ት ፡ ትልቅ ፡ ዕንቅፋት ፡ ነው

**drawer** መሳቢያ
My passport is in the top drawer. የይለፍ ፡ ወረ ቀቴ ፡ በላይኛው ፡ መሳቢያ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል

**drawing** ሥዕል
Have you seen Tekle's drawings? የተክሌን ፡ ሥ ዕሎች ፡ አይተሃል ?
[See also 'linear']

**drawl** ጐተተ
Because he drawls his words, it is difficult to understand him. ቃላትን ፡ ስለሚጐትት ፡ የሚለ ውን ፡ ለመከታተል ፡ አዳጋች ፡ ነው

**drawn out** ረዘም ፡ ያለ
There was a drawn out discussion about the draft. ስለ ፡ ረቂቁ ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ውይይት ፡ ነበረ

**dread** (v.)
1. አልወደደም. I dread going to the dentist. ጥርስ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ አልወድም
2. ፈራ. There are few people who do not dread death. ሞትን ፡ የማይፈሩ ፡ ጥቂት ፡ ሰ ዎች ፡ ናቸው

**dread** (n.) ስጋት
He lives in constant dread of poverty. የድኽነት ፡ ስጋት ፡ አድሮበታል

**have a dread of** በጣም ፡ ፈራ
I have a dread of doctors. ሐኪም ፡ በጣም ፡ እፈራለሁ

**dreadful**
1. የሚያስጠላ. She wears dreadful clothes. የሚያስጠላ ፡ ልብስ ፡ ትለብሳለች
2. አሰቃቂ. There was a dreadful accident on the road. መንገዱ ፡ ላይ ፡ አሰቃቂ ፡ አደጋ ፡ ደ ርሶ ፡ ነበር
3. ክፉ. She is a dreadful chatterbox. ክፉ ፡ ለፍላፊ ፡ ነች

**dreadfully** በጣም
It is dreadfully late. በጣም ፡ መሽቷል

**dream** (dreamed, or dreamt), v.
1. አለመ. Last night, I dreamed that I was in the sea. ትናንትና ፡ ማታ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ መ ሆኔን ፡ አለምኩ
2. ጨርሶ ፡ አሰበ. I wouldn't dream of doing it. አደርገዋለሁ ፡ ብዬ ፡ ጨርሶ ፡ አላስብም

**dream up** አወጣ
They dreamed up the most impossible plan. ፍጹም ፡ የማይሆን ፡ እቅድ ፡ አወጡ

**dream** (n.)
1. ሕልም. I had a funny dream last night. ትናንትና ፡ ማታ ፡ አንድ ፡ የሚያስገርም ፡ ሕል ም ፡ አየሁ
2. ከንቱ ፡ ምኞት. Don't build your future on dreams! የወደፊት ፡ ዕድልህን ፡ በከንቱ ፡ ምኞ ት ፡ ላይ ፡ አትመሥርት
*His dream is to buy a house. ሌትም ፡ ሆነ ፡ ቀ ን ፡ የሚያልመው ፡ ቤት ፡ ለመግዛት ፡ ነው
[See also 'nourish']

**dreamy** ሕልም ፡ የበዛበት
Dreamy sleep is not restful. ሕልም ፡ የበዛበት ፡ ሌሊት ፡ ዕረፍት ፡ ይነሣል

**dreary**
1. ቀፋፊ. It was an awfully dreary day. በጣም ፡ ቀፋፊ ፡ ቀን ፡ ነበር
2. የማያስደስት. I have a dreary recollection of my childhood. የልጅነት ፡ ትዝታዬ ፡ የማያስ ደስት ፡ ነው

**dregs**
1. አተላ. He dumped the coffee dregs on the ground. የቡናውን ፡ አተላ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ደ ፋው

2. አምቡላ. He stirred up the dregs by shaking the bottle of mead. የጠጁን ፣ ጠርሙስ ፣ በመነቅነቅ ፣ አምቡላውን ፣ ቀሰቀሰው

**drench** አራሰ
The heavy rain drenched the earth. ኀይለኛው ፣ ዝናም ፣ መሬቱን ፣ አራሰ

**be drenched** በሰበሰ
He was drenched by the rain. በዝናቡ ፣ በሰበሰ

**dress** (vt.)
1. አለበሰ. Mother is just dressing the baby. እናቱ ፣ አሁን ፣ ሕፃኑን ፣ በማልበስ ፣ ላይ ፣ ናት
2. ልብስ ፣ ገዛ. How much does it cost him to dress his family? ለቤተ ፣ ሰቡ ፣ ልብስ ፣ ለመግዛት ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ይፈጅበታል ?
3. አሰረ. Did you dress the wound properly? ቁስሉን ፣ በደንብ ፣ አሰርከው ?
4. ሠራ. She dresses her hair in the traditional manner. ጸጉሯን ፣ የምትሠራው ፣ እንደ ፣ ድሮ ፣ ልማድ ፣ ነው

**dress** (vi.) ለበሰ
He dresses very quickly. በፍጥነት ፣ ይለብሳል

**dress down** ገሠጸ
The officer dressed the men down for their untidy appearance. መኰንኑ ፣ ሰዎቹ ፣ ሁኔታቸው ፣ ስላልተጣጸው ፣ ገሠጻቸው

**dress oneself up as**
The children dressed themselves up as clowns. ሕፃናቱ ፣ የኮሚክ ፣ ልብስ ፣ ለበሱ

**be dressed**
1. ለባበሰ. If you are dressed, let's go for a walk! ከለባበስክ ፣ ሽርሽር ፣ እንሂድ
2. ተጌጠ. The store windows were dressed for Christmas. ለገና ፣ የሱቁ ፣ መስኮቶች ፣ ተጊጠው ፣ ነበር

**be all dressed up** ሽክ ፣ አለ
Look at him, all dressed up! እየው ! ሽክ ፣ ብሏል

**be well-dressed** ሽክ ፣ አለ
He's always well-dressed. ሁል ፣ ጊዜ ፣ ሽክ ፣ ይላል

**get dressed** ለበሰ
I just have to take a shower and get dressed. ገላዬን ፣ ታጥቤ ፣ መልበስ ፣ አለብኝ

**dress** (n.)
1. ልብስ. The dress of the 18th century was colorful. የዐሥራ ፣ ስምንተኛው ፣ ዘመን ፣ ልብስ ፣ ጌጥ ፣ የበዛበት ፣ ነበር
The Ethiopian national dress is called "shamma". የኢትዮጵያ ፣ ብሔራዊ ፣ ልብስ ፣ ሸማ ፣ ነው
2. ቀሚስ. She wants to buy a new dress. አዲስ ፣ ቀሚስ ፣ ለመግዛት ፣ ትፈልጋለች

**dresser**
1. ባለ ፣ መስታወት ፣ ኮመዲኖ. He bought a dresser for the bedroom. ለመኝታ ፣ ክፍሉ ፣ ባለ ፣ መስታወት ፣ ኮመዲኖ ፣ ገዛ
2. ረዳት ፣ አስታማሚ. They train dressers in the Empress Zawditu Hospital. በንግሥት ፣ ዘውዲቱ ፣ ሆስፒታል ፣ ውስጥ ፣ ረዳት ፣ አስታማሚዎች ፣ ይሠለጥናሉ

**dressing**
1. የቁስል ፣ ፋሻ. The nurse changes his dressing every morning. አስታማሚዋ ፣ የቁስሉን ፣ ፋሻ ፣ ጧት ፣ ጧት ፣ ትለውጥለታለች
2. ማጣፈጫ. Mary put the salad dressing in the refrigerator. ሜሪ ፣ የሰላጣውን ፣ ማጣፈጫ ፣ ከማቀዝቀዣው ፣ ውስጥ ፣ አኖረችው

**dressmaker** ልብስ ፣ ሰፊ
There are good dressmakers at the market. ገቢያ ፣ ውስጥ ፣ ጥሩ ፣ ልብስ ፣ ሰፊዎች ፣ አሉ

**dressy** ያጌጠ
These shoes are too dressy for school. እነዚህ ፣ ጫማዎች ፣ በጣም ፣ ያጌጡ ፣ ስለሆኑ ፣ ለትምህርት ፣ ቤት ፣ አይሆኑም

**drew,** see **draw**

**dribble**
1. ተንጠባጠበ. The water is dribbling on the floor from that broken cup. ከተሰበረው ፣ ሲኒ ፣ ውስጥ ፣ ውኃው ፣ ወለሉ ፣ ላይ ፣ ይንጠባጠባል
2. ለሀጩ ፣ ተዝረከረከ. A baby dribbles when it's teething. ሕፃን ፣ ጥርስ ፣ ሲያወጣ ፣ ለሀጩ ፣ ይዝረከረካል

**dried** (adj.) ደረቅ
Buy me a pound of dried apples! አንድ ፣ ፓውንድ ፣ ደረቅ ፣ ቱፋሕ ፣ ግዛልኝ

**drift** (v.)
1. ተንሳፈፈ. We saw some logs drifting down the river. ግንዶች ፣ በወንዙ ፣ ላይ ፣ እየተንሳፈፉ ፣ ሲወርዱ ፣ አየን
2. ወደማይሆን ፣ ስፍራ ፣ ሄደ. A boat drifts if it is not steered. ጀልባ ፣ ካልተቀዘፈ ፣ ወደማይሆን ፣ ስፍራ ፣ ይሄዳል
3. ተበተነ. Sand has drifted across the road. አሸዋ ፣ በመንገዱ ፣ ላይ ፣ ተበትኗል
4. ዋለለ. Some people have a purpose in life; others just drift. አንዳንድ ፣ ሰዎች ፣ ለኑሯቸው ፣ ዓላማ ፣ አላቸው ፤ ሌሎች ፣ ግን ፣ ዝም ፣ ብለው ፣ ይዋልላሉ

Clouds drift across the sky. ደመና ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ይዋልላል
5. ባከነ. His thoughts drifted. ሐሳቡ ፡ ባከነ

**drift across** አቋርጦ ፡ ሄደ
The smoke has drifted across the railroad tracks. ጢሱ ፡ ሐዲዱን ፡ አቋርጦ ፡ ሄደ

**drift** (n.)
1. አቅጣጫ. Pilots have to calculate the drift of the wind. አውሮፕላን ፡ ነጂዎች ፡ የነፋስን ፡ አቅጣጫ ፡ ማሰብ ፡ አለባቸው
2. አዝማሚያ. Explain that again; I don't get the drift of your words. ያን ፡ እንደገና ፡ አብራራው ፤ የንግግርህን ፡ አዝማሚያ ፡ አልተረዳሁትም
The drift of opinion was against war. ያስተያየቱ ፡ አዝማሚያ ፡ ጦርነትን ፡ የሚቃወም ፡ ነበር

**drill** (v.) ልምምድ ፡ አደረገ
The soldiers drill every day. ወታደሮቹ ፡ በየቀኑ ፡ ልምምድ ፡ ያደርጋሉ

**be drilled in** የ - - - ልምምድ ፡ አደረገ
We were drilled in arithmetic. የቁጥር ፡ ልምምድ ፡ አድርገናል

**drill a hole in** በሳ
Drill a hole in the beam! አውራጁን ፡ ብሳው

**drill** (n.)
1. መሰርሰሪያ. The mechanic needs another drill. ሚካኒኩ ፡ ሌላ ፡ መሰርሰሪያ ፡ ያስፈልገዋል
2. ልምምድ ፡ ማድረግ. Drill forms an important part of learning Amharic. ልምምድ ፡ ማድረግ ፡ አማርኛን ፡ ለመማር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**drink** (drank, drunk), v. ጠጣ
Drink plenty of water! ብዙ ፡ ውኃ ፡ ጠጣ
He doesn't gamble, but he drinks. ቁማር ፡ አይጫወትም ፤ ግን ፡ ይጠጣል

**drink a toast** ጽዋ ፡ አነሣ
We drink a toast to your health. ለጤንነትህ ፡ ጽዋችንን ፡ እናነሣለን

**drink up** መጠጠ
The plants drank up the water I poured on them. ተክሎቹ ፡ ያጠጣኋቸውን ፡ ውኃ ፡ መጠጡት
[See also 'health']

**drink** (n.)
1. መጠጥ. What kind of drinks do you have? ምን ፡ ዓይነት ፡ መጠጥ ፡ አለህ ?
Drink was his downfall. ያጠፋው ፡ መጠጥ ፡ ነበር
2. ጠጭነት. She drove me to drink by her constant nagging. በማያቋርጥ ፡ ንዝንዟ ፡ ከጠጭነት ፡ አደረሰችኝ

**drink of water** የሚጠጣ ፡ ውኃ
May I have a drink of water? የሚጠጣ ፡ ውኃ ፡ ትሰጠኝ ?

**take a drink** ጠጣ
He takes a drink every now and then. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይጠጣል
[See also 'round, strong']

**drinker** ጠጪ
My uncle is a heavy drinker. አጎቴ ፡ ኀይለኛ ፡ ጠጪ ፡ ነው

**drinking horn** ዋንጫ
They still use drinking horns in some parts of Ethiopia. አሁንም ፡ ባንዳንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ በዋንጫ ፡ ይጠጣል

**drip** (dripped) ተንጠባጠበ
The rain has soaked through the roof and dripped on our heads. ጣሪያው ፡ አፍስሶ ፡ ዝናብ ፡ እራሳችን ፡ ላይ ፡ ተንጠባጠበ

**be dripping**
1. አንጠባጠበ. The pump is dripping. ቧንቧው ፡ ያንጠባጥባል
2. ችፍ ፡ አለ. +His forehead was dripping with sweat. ግምባሩ ፡ ላይ ፡ ላብ ፡ ችፍ ፡ ብሏል

**be dripping wet** ልብሱ ፡ በሰበሰ
When he got home, he was dripping wet. እቤት ፡ ሲደርስ ፡ ልብሱ ፡ በስብሶ ፡ ነበር

**drive** (drove, driven), vt.
1. ነዳ. Drive the cattle over to the left! ከብቶቹን ፡ በግራ ፡ በኩል ፡ ንዳቸው
Can you drive a truck? የጭነት ፡ መኪና ፡ ልትነዳ ፡ ትችላለህ ?
2. በመኪና ፡ አደረሰ. He drove me to the station. ከጣቢያው ፡ በመኪና ፡ አደረሰኝ
3. ገፋፋ. Hunger drove him to stealing. ራብ ፡ እንዲሰርቅ ፡ ገፋፋው
4. አደረሰ. She drove me to drink by her constant nagging. በማያቋርጥ ፡ ንዝንዟ ፡ ከጠጭነት ፡ አደረሰችኝ
5. አጣደፈ. The men said the boss drove them too hard. ሠራተኞቹ ፡ አሠሪው ፡ በጣም ፡ ያጣድፈናል ፡ አሉ

**drive** (vi.)
1. መኪና ፡ ነዳ. Do you know how to drive? መኪና ፡ መንዳት ፡ ትችላለህ?
2. በመኪና ፡ ደረሰ. He drove into the station just on time. በመኪናው ፡ ልክ ፡ በሰዓቱ ፡ ከጣቢያው ፡ ደረሰ

**(be) driven asunder** ተለያየ
They were driven asunder by the war. በጦርነቱ ፡ ምክንያት ፡ ተለያዩ

**drive at**
*What is he driving at? ምን ፡ ማለቱ ፡ ነው ?

**drive away** አባረረ
Drive the dog away! ውሻውን ፡ አባርረው

**drive back** ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲመለስ ፡ አደረገ
We drove back the attacking army. አጥቂውን ፡ ጠላት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲመለስ ፡ አደረግነው

**drive (from)**
1. አስለቀቀ. After a fierce charge, our soldiers drove the enemy from the hilltop. ጠንከረው ፡ ካጠቁ ፡ በኋላ ፡ ወታደሮቻችን ፡ ጠላትን ፡ የኮረብታውን ፡ ጫፍ ፡ አስለቀቁት
2. አባረረ. A repellent smell drove us from the room. አንድ ፡ መጥፎ ፡ ሽታ ፡ ከክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ አባረረን

**drive in** (vt.) መታ ፤ አስገባ
Drive the nail in! ምስማሩን ፡ ምታው
He drove in the nail with one stroke of the hammer. ምስማሩን ፡ ባንድ ፡ በመዶሻ ፡ ምት ፡ አስገባው

**drive off** አባረረ
The soldiers fought in hand to hand combat and drove off the enemy. ወታደሮቹ ፡ በጨበጣ ፡ ተዋግተው ፡ ጠላትን ፡ አባረሩ

**drive out** (vt.) አስለቀቀ
They drove the enemy out of their positions. ጠላትን ፡ የያዘውን ፡ ስፍራ ፡ አስለቀቁት

**drive out** (vi.)
1. በመኪና ፡ ሄደ. Let's drive out into the country! በመኪና ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ እንሂድ
2. ነድቶ ፡ ወጣ. He drove out of the compound in a hurry. ከግቢው ፡ በችኮላ ፡ ነድቶ ፡ ወጣ

**drive (through)** በመኪና ፡ አለፈ
We drove through the tunnel. በመኪና ፡ በመሿለኪያው ፡ ውስጥ ፡ አለፍን

**drive up close** ተጠጋ
The car drove up very close to the sidewalk. መኪናዋ ፡ ወደ ፡ እግረኛው ፡ መንገድ ፡ በጣም ፡ ተጠጋች
[See also 'bargain, crazy, home']

**drive** (n.)
1. በመኪና --- መንገድ. The station is an hour's drive from here. ጣቢያው ፡ በመኪና ፡ ከዚህ ፡ ያንድ ፡ ሰዓት ፡ መንገድ ፡ ነው
2. በመኪና ፡ መንሸራሸር. A Sunday drive in the country is very enjoyable. እሑድ ፡ እሑድ ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ በመኪና ፡ መንሸራሸር ፡ አስደሳች ፡ ነው
3. ትጋት ፤ የሥራ ፡ መንፈስ. The director is a person with great drive. ዲሬክተሩ ፡ ከፍተኛ ፡ ትጋት ፡ (የሥራ ፡ መንፈስ) ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው
4. መዋጮ. In the last drive, we raised five hundred dollars. ባለፈው ፡ መዋጮ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሰበሰብን

**strong drive** የሚገፋፋ ፡ ኀይል
The desire for praise is a strong drive in mankind. ምስጋና ፡ መፈለግ ፡ በሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ የሚገፋፋ ፡ ኀይል ፡ ነው

**take a drive** በመኪና ፡ ተንሸራሸረ
We took a nice drive. በመኪና ፡ ደኅና ፡ ተንሸራሸርን

**drivel** (v.) አፉን ፡ ምራቅ ፡ሞላው
The old man driveled when he saw that dinner was being served. ሽማግሌው ፡ እራት ፡ ቀርቦ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ አፉን ፡ ምራቅ ፡ ሞላው

**drivel** (n.) ለሀጭ
Wipe the drivel from the baby's chin! ከሕፃኑ ፡ አገጭ ፡ ላይ ፡ ለሀጩን ፡ ጥረገው

**driver**
1. ነጂ. He is a good driver and has never had an accident. ጥሩ ፡ ነጂ ፡ ስለሆነ ፡ አደጋ ፡ አጋጥሞት ፡ አያውቅም
2. ባለጋሪ. The driver cracked the whip over the horses. ባለጋሪው ፡ ፈረሶቹ ፡ ላይ ፡ አለንጋ ፡ አጮኸባቸው

**driver's license** የመንጃ ፡ ፈቃድ
You cannot drive without a driver's license. ያለ ፡ መንጃ ፡ ፈቃድ ፡ ልትነዳ ፡ አትችልም

**driveway** መግቢያ ፡ መንገድ
The driveway connects the house with the street. መግቢያው ፡ መንገድ ፡ ቤቱን ፡ ከጐዳናው ፡ ያገናኛል

**drizzle** (v.) አካፋ
It's been drizzling all day. ሲያካፋ ፡ ዋለ

**drizzle** (n.) ካፊያ
The drizzle has lasted all day long. ካፊያው ፡ ቀኑን ፡ሙሉ ፡ ዋለ

**drone** (v.)
1. አጕረመረመ. The planes droned overhead. አውሮፕላኖች ፡ በላያችን ፡ ላይ ፡ አጕረመረሙ
2. አነበነበ. Bees droned among the flowers. ንቦች ፡ በአበባው ፡ ዙሪያ ፡ አነበነቡ

**drone on** መነቸከ
A few people fell asleep as the speaker droned on. ተናጋሪው ፡ ሲመነቸክ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ እንቅልፍ ፡ ያዛቸው

**drone** (n.) ንብ
The drones make wax. ንብ ፡ ሰም ፡ ይሠራል

**drool** ለሀጩን ፡ አዝረከረከ
Babies often drool. ሕፃናት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ለሀጫቸውን ፡ ያዝረከርካሉ

**droop**
1. ጠወለገ. The flowers are beginning to droop. አበባዎቹ ፡ መጠውለግ ፡ ጀመሩ
2. ተንዘረፈፈ. The child's pants were so large that they drooped. የልጁ ፡ ሱሪ ፡ በዝቶበት ፡ ስለነበረ ፡ ተንዘረፈፈ
3. ደከመ. His spirits drooped. መንፈሱ ፡ ደከመ
4. ዘንጠፍ ፡ አለ. Flags droop when there is no breeze. ነፋስ ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ባንዲራው ፡ ዘንጠፍ ፡ ይላል

**drop** (dropped), vt.
1. ጣለ. She dropped the coffee pot on the floor. ጀበናውን ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ጣለችው
Please drop this card in the mail box! ይህን ፡ ካርድ ፡ ፖስታ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ጣለው
The plane dropped a bomb on us. አውሮፕላኑ ፡ ቦምብ ፡ ጣለብን
2. ጣል ፡ አደረገ. He dropped a remark which displeased me. አንድ ፡ ያስከፋኝ ፡ አስተያየት ፡ ጣል ፡ አደረገ
3. ከሥራ ፡ አሰናበተ. The boss dropped twenty-five men last week. አለቃው ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ሰዎች ፡ ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ከሥራ ፡ አሰናበተ
4. አወረደ. Please drop me at the corner! ከመጠምዘዣው ፡ አውርደኝ
5. ተወ. Let's drop the subject! ነገሩን ፡ እንተወው
She dropped her old friends when she married a rich man. ሀብታም ፡ አግብታ ፡ የድሮ ፡ ጓደኞቿን ፡ ተወች
6. ቀነሰ. Don't drop your voice at the end of a sentence! በዐረፍተ ፡ ነገር ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ድምፅህን ፡ አትቀንሰው

**drop** (vi.)
1. ወደቀ. The coffee pot dropped from her hand. ጀበናው ፡ ከእጇ ፡ ወደቀ
Some of them dropped from exhaustion. አንዳንዶቹ ፡ ደክሟቸው ፡ ወደቁ
The price of coffee will drop soon. የቡና ፡ ዋጋ ፡ በቅርቡ ፡ ይወድቃል
2. ዝቅ ፡ አለ. The student dropped to fifth place. ተማሪው ፡ ወደ ፡ አምስተኛነት ፡ ደረጃ ፡ ዝቅ ፡ አለ
3. ወረደ. The paratroopers dropped from the plane in parachutes. ያየር ፡ ወለድ ፡ ወታደሮች ፡ ከአውሮፕላኑ ፡ ላይ ፡ በጃንጥላ ፡ ወረዱ
4. ረገፈ. The oranges are dropping from the trees. ብርቱካኖቹ ፡ ከዛፎቹ ፡ ላይ ፡ በመርገፍ ፡ ላይ ፡ ናቸው
5. ቀነሰ. The temperature dropped very rapidly. ሙቀቱ ፡ ቶሎ ፡ ቀነሰ
6. ተንጠባጠበ. He was carrying so many books in his arms that they were dropping all over the place. እጅግ ፡ ብዙ ፡ መጽሐፎች ፡ ተሸክሞ ፡ ስለነበረ ፡ በየቦታው ፡ ተንጠባጠቡ
7. ጸጥ ፡ አለ. The wind has dropped. ነፋሱ ፡ ጸጥ ፡ ብሏል
8. ቆመ. There, the matter dropped. ጉዳዩ ፡ እዚሁ ፡ ላይ ፡ ቆመ

**be dropped** (= active) አስወጣ
+I will be dropped from the club because I did not pay my dues. ድርሻዬን ፡ ስላልከፈልኩ ፡ ከማኅበሩ ፡ ያስወጡኛል

**drop behind**
1. ተለይቶ ፡ ኋላ ፡ ቀረ. The two children dropped behind the group to chase butterflies. ቢራቢሮዎችን ፡ ለመያዝ ፡ ሁለቱ ፡ ሕፃናት ፡ ከሌሎቹ ፡ ተለይተው ፡ ኋላ ፡ ቀሩ
2. ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀረ. I dropped behind in my payments because of my illness. በሕመሜ ፡ ምክንያት ፡ ዕዳዬን ፡ ከመክፈል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀረሁ

**drop by** ብቅ ፡ አለ
Drop by when you are in town! ከተማ ፡ ስትመጣ ፡ ብቅ ፡ በል

**drop (one's) eyes** አንገቱን ፡ ደፋ
The students dropped their eyes when the teacher criticized them. መምህሩ ፡ ሲገሥጻቸው ፡ ተማሪዎቹ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፉ

**drop in** ብቅ ፡ አለ
Drop in to see me tomorrow! ነገ ፡ ብቅ ፡ ብለህ ፡ ጠይቀኝ

**drop off** (vt.) ሰጠ
Can you drop this off at the tailor's for me? ይህንን ፡ ለልብስ ፡ ሰፊው ፡ ልትሰጥልኝ ፡ ትችላለህ ?

**drop off** (vi.) ቀዘቀዘ
Business has dropped off since winter. ከክረምት ፡ ጀምሮ ፡ ንግድ ፡ ቀዝቅዟል

**drop out (of)**
1. ወጣ. Three students dropped out of school. ሦስት ፡ ተማሪዎች ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ወጡ

2. ወደቀ. The box dropped out of the window. ሣጥኑ ፡ በመስኮቱ ፡ ወደቀ
[See also 'cloak, fatigue, knee, line']

**drop** (n.)
1. ጠብታ. Take three drops in a glass of water! ሦስት ፡ ጠብታ ፡ በብርጭቆ ፡ ውስጥ ፡ አድርገህ ፡ ጠጣ
There are rain drops on the window. መስኮቱ ፡ ላይ ፡ የዝናም ፡ ጠብታዎች ፡ አሉ
2. ዝቅ ፡ ማለት. The sharp drop in prices disturbed the farmers. የእህል ፡ ዋጋ ፡ በድንገት ፡ ዝቅ ፡ ማለቱ ፡ ገበሬዎችን ፡ አሳሰባቸው
*This is a drop in the bucket. ጠብም ፡ አይል
**at the drop of a hat** ከመሬት ፡ ተነሥቶ
He will fight at the drop of a hat. ከመሬት ፡ ተነሥቶ ፡ ይደባደባል
**not a drop** ትንሽ ፡ እንኳን + negative verb
He hasn't a drop of courage. ትንሽ ፡ እንኳን ፡ ድፍረት ፡ የለውም
*There is not a drop of truth in what he says. በንግግሩ ፡ ውስጥ ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ያህል ፡ እውነት ፡ የለበትም

**drought** ድርቅ ፤ ድርቀት
Hararge is often afflicted by drought. ሐረርጌን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ድርቅ ፡ (ድርቀት) ፡ ይመታዋል

**drove,** see **drive**

**drove** (n.) መንጋ
A drove of cattle is passing by the house. የከብት ፡ መንጋ ፡ በቤቱ ፡ አጠገብ ፡ ያልፋል
**droves of people** ሰዎች ፡ በብዛት
Droves of people came to the exposition. ሰዎች ፡ በብዛት ፡ ወደ ፡ ኤክስፖዚሲዮኑ ፡ መጡ
**come in droves** ጎረፈ
People came in droves. ሰዎች ፡ ጎረፉ
**in droves** በብዛት
The soldiers deserted in droves. ወታደሮቹ ፡ በብዛት ፡ ከዱ

**drown** (vt.)
1. አሰጠመ. She had to drown the puppies. ቡችሎቹን ፡ ማስጠም ፡ ግድ ፡ ሆነባት
2. ተከላከለ. He drowned his sorrow in drink. ሐዘኑን ፡ በመጠጥ ፡ ተከላከለው
**drown** (vi.) ሰጥሞ ፡ ሞተ
He drowned in the river. ወንዙ ፡ ውስጥ ፡ ሰጥሞ ፡ ሞተ
**drown out** ዋጠ
The noise drowned out his remarks. ጫጫታው ፡ የተናገረውን ፡ ዋጠው

**drowning** (adj.) ሊሰጥም ፡ የነበረ
The drowning man snatched at the rope. ሊሰጥም ፡ የነበረው ፡ ሰውዬ ፡ ገመዱን ፡ ሊይዝ ፡ ይፍጨረጨር ፡ ነበር

**drowse** አንጎላጀ
She drowsed, but did not quite fall asleep. አንጎላጀች ፡ እንጂ ፡ እንቅልፍ ፡ አልወሰዳትም

**drowsy** የሚጫጫን
The drowsy summer weather prevented him from working. የሚጫጫነው ፡ የበጋ ፡ አየር ፡ እንዳይሠራ ፡ አገደው
**get drowsy** እንቅልፍ ፡ እንቅልፍ ፡ አለ(ው)
I get drowsy after a heavy meal. ብዙ ፡ ስበላ ፡ እንቅልፍ ፡ እንቅልፍ ፡ ይለኛል

**drudge, be a** ~ እንደ ፡ ባሪያ ፡ አገለገለ
She was a drudge in her stepmother's house. እንጀራ ፡ እናቷ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ ታገለግል ፡ ነበር

**drudgery** የማያስደስት ፡ ሥራ
Her life was spent in drudgery. የማያስደስት ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ዕድሜዋን ፡ አሳለፈች

**drug** (v.)
1. በመድኀኒት ፡ አደነዘዘ. The doctor drugged her so she wouldn't feel the pain. ሕመሙ ፡ እንዳይሰማት ፡ ሐኪሙ ፡ በመድኀኒት ፡ አደነዘዛት
2. የሚያፈዝ ፡ መድኀኒት ፡ ጨመረበት. The spy drugged the soldier's tea. ሰላዩ ፡ በወታደሩ ፡ ሻይ ፡ ላይ ፡ የሚያፈዝ ፡ መድኀኒት ፡ ጨመረበት
**be drugged** መድኀኒት ፡ ቀመሰ
His abnormal actions show that he has been drugged. ቅጥ ፡ ያጣው ፡ አኳኋኑ ፡ መድኀኒት ፡ መቅመሱን ፡ ያሳያል

**drug** (n.)
1. መድኀኒት. This drug is sold only by prescription. ይህ ፡ መድኀኒት ፡ የሚሸጠው ፡ በሐኪም ፡ ትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ሱስ ፡ የሚያሲዝ ፡ መድኀኒት. Opium is a dangerous drug.ኦፒየም ፡ አደገኛ ፡ የሆነ ፡ ሱስ ፡ የሚያሲዝ ፡ መድኀኒት ፡ ነው

**druggist** መድኀኒት ፡ ቀማሚ
The druggist makes up the prescriptions. መድኀኒት ፡ ቀማሚው ፡ የታዘዘውን ፡ መድኀኒት ፡ ይቀምማል

**drugstore** መድኀኒት ፡ ቤት
The drugstores have to be open at night. መድኀኒት ፡ ቤቶች ፡ ሌሊት ፡ ክፍት ፡ መሆን ፡ አለባቸው

**drum** (drummed), v.
1. ደበደበ. Please stop drumming on the table! ጠረጴዛውን ፡ መደብደቡን ፡ ተው
2. ታምቡር ፡ መታ. He drums when the soldiers march. ወታደሮቹ ፡ ተሰልፈው ፡ ሲጓዙ ፡ ታምቡር ፡ ይመታል

**(be) drummed into**
*His lessons had to be drummed into him because he did not like school. ትምህርት ፡ ስለማይወድ ፡ ትምህርቶችን ፡ በግድ ፡ መላልሰው ፡ ያስተምሩት ፡ ነበር

**drum up**
*He is trying to drum up votes. እሱን ፡ የሚደግፍ ፡ ድምፅ ፡ ለማግኘት ፡ ይሞክራል

**drum** (n.)
1. ከበሮ. Can you hear the drums? ከበሮውን ፡ ትሰማለህ ?
2. በርሜል. They unloaded six drums of gasoline. ስድስት ፡ በርሜል ፡ ቤንዚን ፡ አራገፉ

**drunk,** see **drink**

**drunk** (n.) ሰካራም
Was that drunk annoying you? ያ ፡ ሰካራም ፡ ያበሳጭህ ፡ ነበር ?

**(be) drunk**
1. ሰከረ. He is drunk with wine. በወይን ፡ ጠጅ ፡ ሰክሯል
2. (= tr.) አሰከረ. +He is drunk with power. ሥልጣን ፡ አሰክሮታል

**get drunk** ሰከረ
He got drunk at the birthday party. በልደቱ ፡ በዓል ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ሰከረ

**drunkard** ሰካራም
The drunkard was arrested by the police. ሰካራሙ ፡ በፖሊስ ፡ ተያዘ

**drunken** የሰከረ
A drunken man lay asleep in the doorway. የሰከረ ፡ ሰው ፡ ደጃፉ ፡ ላይ ፡ ተኛ

**drunkenness** ስካር ፤ ጠጭነት
He preached many sermons against drunkenness. ስካርን ፡ በማውገዝ ፡ ብዙ ፡ ስብከቶች ፡ አደረገ
Gluttony and drunkenness have been called carnal vices. ሆዳምነትና ፡ ጠጭነት ፡ የሥጋ ፡ መጥፎ ፡ ምግባሮች ፡ ይባላሉ

**dry** (dried), vt.
1. አደረቀ. Dry your hands on this towel! እጅህን ፡ በዚህ ፡ ፎጣ ፡ አድርቅ
Dry yourself well! ሰውነትህን ፡ በደምብ ፡ አድርቅ
2. ወለወለ. Who is going to dry the dishes? ሳሕኖቹን ፡ የሚወለውለው ፡ ማነው ?

**dry** (vi.) ደረቀ
The paint dries in five hours. ቀለሙ ፡ ባምስት ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ይደርቃል

**dry out** ደረቀ
He put the clothes in the sunshine to dry out. ልብሱ ፡ እንዲደርቅ ፡ ፀሐይ ፡ ላይ ፡ አሰጣው

**dry up** ደረቀ
Every summer this stream dries up. በየበጋው ፡ ይህ ፡ ምንጭ ፡ ይደርቃል

**dry** (adj.)
1. የደረቀ ፤ ደረቅ. Let's gather some dry wood! የደረቀ ፡ (ደረቅ) ፡ ዕንጨት ፡ እንልቀም
2. ድርቅ. This dry weather has done a lot of harm to the crops. ይህ ፡ ድርቅ ፡ ጊዜ ፡ ሰብሉን ፡ በጣም ፡ ጐዳው
3. የሚሰለች. A dry book, like one on economics, makes me fall asleep when I read it. እንደ ፡ ምጣኔ ፡ ሀብት ፡ ያለ ፡ የሚሰለች ፡ መጽሐፍ ፡ ሳነብ ፡ እንቅልፍ ፡ ይይዘኛል

**dry spell** ድርቀት
A dry spell accounted for the poor crop. አዝመራው ፡ የተበላሸው ፡ ከድርቀት ፡ የተነሣ ፡ ነው

**be dry**
1. ደረቀ. The wash is not dry yet. የታጠበው ፡ ልብስ ፡ ገና ፡ አልደረቀም
In the dry season, the wells are dry. በበጋ ፡ የውኃ ፡ ጉድጓዶች ፡ ይደርቃሉ
2. ነጠፈ. We have no milk because our cow is dry. ላማችን ፡ ስለነጠፈች ፡ ወተት ፡ የለንም

**run dry** ደረቀ
The well ran dry last summer. ጉድጓዱ ፡ ባለፈው ፡ በጋ ፡ ደረቀ
[See also 'high, stick']

**dry goods** ጨርቃ ፡ ጨርቆች
Dry goods are sold in my father's store. ጨርቃ ፡ ጨርቆች ፡ አባቴ ፡ሱቅ ፡ ውስጥ ፡ ይሸጣሉ

**dry land** የብስ
It is good to be on dry land again. እንደገና ፡ በየብስ ፡ ላይ ፡ መሆን ፡ ጥሩ ፡ ነው

**dry season** በጋ
It is quite out of the ordinary to have a heavy rain in the middle of the dry season. በበጋ ፡

ውስጥ ፡ ከባድ ፡ ዝናም ፡ መዝነቡ ፡ ፈጽሞ ፡ ያልተ ለመደ ፡ ነገር ፡ ነው

**dual** ሁለት
He has a dual purpose. ሁለት ፡ ዓላማ ፡ አለው
The learner's car has dual brakes. የለማጁ ፡ መኪና ፡ ሁለት ፡ ፍሬን ፡ አለው
*Can a half-caste have dual citizenship? ክልስ ፡ የሁለት ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ?

**dub** (dubbed) የቅጽል ፡ ስም ፡ አወጣ(ለት)
John's friends dubbed him "Slim". የዮሐንስ ፡ ጓደኞች ፡ « ቀጭኑ » ፡ ብለው ፡ የቅጽል ፡ ስም ፡ አወጡለት

**dubious**
1. ከልብ ፡ ያልሆነ. His dubious compliment offended me. ከልብ ፡ ያልሆነ ፡ ምስጋናው ፡ አስ ቀየመኝ
2. የማይታመን. A dubious friend is no friend at all in time of need. የማይታመን ፡ ጓደኛ ፡ ለችግር ፡ አይደርስም
3. የሚያስጠረጥር. He has a dubious scheme for getting rich. ሀብታም ፡ ለመሆን ፡ ያለው ፡ እቅድ ፡ የሚያስጠረጥር ፡ ነው
**feel dubious** አመነታ
I feel dubious about buying that used car. ያ ችን ፡ የሠራች ፡ መኪና ፡ ለመግዛት ፡ አመነታለሁ

**duck** (vt.)
1. ውኃ ፡ ነከረው. The winning team ducked their captain. አሸናፊው ፡ ቡድን ፡ አምባሉን ፡ ውኃ ፡ ነከሩት
2. አድበሰበሰ ፡ አለፈ. The cashier ducked the question about the embezzled money. ገንዘብ ፡ ቤቱ ፡ ገንዘብ ፡ ስለማጥፋቱ ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ አድበስብሶት ፡ አለፈ
**duck** (vi.) ለጥ ፡ አለ
When the shots were fired, everybody ducked. ጥይቶቹ ፡ ሲተኰሱ ፡ ሁሉም ፡ ለጥ ፡ አለ

**duck** (n.) ዳክዬ
There are many ducks in Lake Alemaya. በዓለማያ ፡ ሐይቅ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ዳክዬዎች ፡ አሉ

**due** (n.) የሚገባው
Pay the man his due! ለሰውዬው ፡ የሚገባውን ፡ ክፈለው
**dues** ድርሻ ፤ የማኅበርተኛነት ፡ ድርሻ ፤ መዋጮ
I will be dropped from the club because I did not pay my dues. ድርሻዬን ፡ ስላልከፈልኩ ፡ ከ ማኅበሩ ፡ ያስወጡኛል
I pay dues every month. የማኅበርተኛነት ፡ ድር ሻዬን ፡ በየወሩ ፡ እከፍላለሁ
Our treasurer reports that all dues are paid up. ገንዘብ ፡ ቤታችን ፡ መዋጮው ፡ ሁሉ ፡ መከፈሉን ፡ ይገልጻል
**due** (adj.)
1. ተገቢ. Use due care to be safe in crossing streets! ራስህን ፡ ከአደጋ ፡ ለመጠበቅ ፡ መንገዶች ን ፡ ስታቋርጥ ፡ ተገቢ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ አለብህ
2. የሚገባው. Good deeds deserve due reward. መልካም ፡ ተግባሮች ፡ የሚገባቸውን ፡ ዋጋ ፡ ማ ግኘት ፡ አለባቸው
*The wages due him will be paid tomorrow. የሠራበት ፡ ነገ ፡ ይከፈለዋል
**due** (adv.) በቀጥታ
The ship traveled due north. መርከቧ ፡ በቀጥ ታ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ አመራች
**be due**
1. ይከፈልበታል ፤ የሚደርሰው ፡ ነው. A fine is due on the library book. መጽሐፉ ፡ በጊ ዜው ፡ ስላልተመለሰ ፡ መቀጫ ፡ ይከፈልበታል
The rent is due next Monday. ኪራዩ ፡ የሚደር ሰው ፡ (የሚከፈለው) ፡ በሚመጣው ፡ ሰኞ ፡ ነው
2. ማስረከብ ፡ አለበት. My history paper is due tomorrow. ለታሪክ ፡ ትምህርት ፡ የጻፍኩትን ፡ ድር ሰት ፡ ነገ ፡ ማስረከብ ፡ አለብኝ
**is due one** ይገባዋል
Respect is due him. ክብር ፡ ይገባዋል
**is due to** (relative imperfect) + ነው
He is due to arrive at ten. የሚገባው ፡ በአራት ፡ ሰዓት ፡ ነው
**due to** ከ - - - የተነሣ ፤ በ ፤ በ - - - ምክንያት
The accident was due to careless driving. አደጋው ፡ የደረሰው ፡ ተጠንቅቆ ፡ ካለመንዳት ፡ የተነሣ ፡ ነው
Due to a mistake, she was not invited. በስሕተ ት ፡ ሳትጠራ ፡ ቀረች
She was in a state of agitation due to her recent bereavement. በቅርቡ ፡ በደረሰባት ፡ የዘመድ ፡ ሞ ት ፡ ምክንያት ፡ ተሸብራ ፡ ነበር
**fall due** የሚከፈል ፡ ነው
The bill falls due the first of each month. ሒሳቡ ፡ የሚከፈለው ፡ በየወሩ ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ነው
[See also 'course']

**duel** [በጐራዴ ፡ ወይም ፡ በጠር ፡ መሣሪያ ፡ በሁለ ት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ውጊያ]

**duet** [ሁለት ፡ ሰዎች ፡ በመዋሐድ ፡ የሚዘፍኑት ፡ ወ ይም ፡ የሚጫወቱት ፡ ሙዚቃ]

**dug**, see **dig**

**dugout** የሰው ፡ ሠራሽ ፡ ዋሻ
The refugees lived in dugouts. ስደተኞቹ ፡ በሰው ፡ ሠራሽ ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ኖሩ

**duke** መስፍን
They contributed money to the Duke of Harar Memorial Hospital. ለሐረር ፡ መስፍን ፡ መታሰቢያ ፡ ሆስፒታል ፡ መሥሪያ ፡ ገንዘብ ፡ አዋጡ

**dukedom** የመስፍን ፡ ግዛት
He was given a dukedom. የመስፍን ፡ ግዛት ፡ ተሰጠው

**dull**
1. ደነዝ. This dull knife cannot cut the meat. ይህ ፡ ደነዝ ፡ ቢላዋ ፡ ሥጋ ፡ አይቈርጥም
2. ደብዘዝ ፡ ያለ. She likes dull colors. ደብዘዝ ፡ ያለ ፡ ቀለም ፡ ትወዳለች
3. መጠነኛ. He felt a dull pain after the operation. ከቀዶ ፡ ጥገናው ፡ በኋላ ፡ መጠነኛ ፡ ሕመም ፡ ተሰማው
4. ደደብ. Mary seems dull beside her sister. ሜሪን ፡ ከእኅቷ ፡ ጋር ፡ ሲያወዳድሯት ፡ ደደብ ፡ ናት
5. የቸከ. I'd rather stay home than go to that dull play. እዚያ ፡ እቸከ ፡ ትያትር ፡ ከምሄድ ፡ እቤት ፡ ብቀር ፡ ይሻለኛል
6.ለዛ ፡ ቢስ. In spite of her dull husband, she is relatively happy. ምንም ፡ እንኳ ፡ ባሏ ፡ ለዛ ፡ ቢስ ፡ ቢሆን ፡ በመጠኑ ፡ ደስተኛ ፡ ናት
7. የሚያሰለች. Many people rate basketball as dull to watch. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የቅርጫት ፡ ኳስ ፡ ጨዋታን ፡ ለተመልካች ፡ የሚያሰለች ፡ አድርገው ፡ ይገምታሉ
*Most people find mathematics dull. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሒሳብ ፡ ትምህርት ፡ አይጥማቸውም

**be dull**
1. ዶለዶመ. The pencil is dull; please sharpen it for me! እርሳሱ ፡ ዶልዱሟል ፤ እስቲ ፡ ቅረጽልኝ
2. ቀዘቀዘ. The umbrella business is usually dull in the dry season. የጃንጥላ ፡ ንግድ ፡ በበጋ ፡ ወራት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ይቀዘቅዛል
3. ተሰለቸ. Life is dull in a small village. በትንሽ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ኑሮ ፡ ይሰለቻል
4. ጣዕም ፡ የለውም. This book on economic theory is a dull book. ይህ ፡ ስለ ፡ ምጣኔ ፡ ሀብት ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳብ ፡ የተጻፈ ፡ መጽሐፍ ፡ ጣዕም ፡ የለውም

**duly**
1. በሚገባ. The students were duly impressed by the fame of their teacher. ተማሪዎቹ ፡ በመምህራቸው ፡ ዝና ፡ በሚገባ ፡ ተደንቀው ፡ ነበር
2. በጊዜው. The debt was duly paid. ዕዳው ፡ በጊዜው ፡ ተከፍሏል

**dumb**
1. ድዳ. He was born deaf and dumb. ደንቆሮና ፡ ድዳ ፡ ሆኖ ፡ ነው ፡ የተወለደው
2. ደደብ. Boy, that guy is dumb! ያ ፡ ሰው ፡ ደደብ ፡ ነው

**remain dumb** ጭጭ ፡ አለ
The class remained dumb when the teacher asked a difficult question. መምህሩ ፡ አንድ ፡ አስቸጋሪ ፡ ጥያቄ ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ተማሪዎቹ ፡ ጭጭ ፡ አሉ

**(be) dumbfounded** አፉ ፡ ተያዘ
I was dumbfounded when I heard it. ነገሩን ፡ እንደሰማሁ ፡ አፌ ፡ ተያዘ

**dummy** ምስል
The dummy was dressed in the latest fashion. ምስሉን ፡ አዲሱን ፡ ዓይነት ፡ ልብስ ፡ አልብሰውታል

**dump** (v.)
1. ዘረገፈ. They dumped the coal in front of the basement. ከሰሉን ፡ ምድር ፡ ቤቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ዘረገፉት
2. ደፋ. He dumped the coffee dregs on the ground. የቡናውን ፡ አተላ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ደፋ
3. አፈሰሰ. They dumped the gravel in the street. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ጠጠር ፡ አፈሰሱ
4. ጣለ. Don't dump your troubles on me! ችግርህን ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ አትጣል
They dumped the waste from the factory into the stream. ከፋብሪካው ፡ የሚወጣውን ፡ ቆሻሻ ፡ ወንዙ ፡ ውስጥ ፡ ጣሉት

**dump** (n.)
1. ቆሻሻ ፡ መጣያ. That empty lot is used as a dump. ያ ፡ ባዶ ፡ ቦታ ፡ ለቆሻሻ ፡ መጣያ ፡ ያገለግላል
2. ማከማቻ. The ammunition dump blew up after it was hit by an enemy rocket. የጥይት ፡ ማከማቻው ፡ በጠላት ፡ ሮኬት ፡ ሲመታ ፡ ፈነዳ

**dumpy** አጭር ፡ ወፍራም
Who is that dumpy fellow near the door? ያ ፡ በሩ ፡ ጋ ፡ ያለው ፡ አጭር ፡ ወፍራም ፡ ልጅ ፡ ማነው ?

**dunce** ደደብ ፡ ተማሪ
The teacher had to give help to the dunce. ደደቡን ፡ ተማሪ ፡ መምህሩ ፡ መርዳት ፡ ነበረበት

**dune** የአሸዋ ፡ ክምር
The dunes extend for miles. የአሸዋው ፡ ክም ር ፡ ለብዙ ፡ ምዕራፍ ፡ ተዘርግቷል

**dung** ፍግ
Farmers sometimes use dung to fertilize their fields. ገበሬዎች ፡ ማሳቸውን ፡ ለማዳበር ፡ አንዳን ድ ፡ ጊዜ ፡ ፍግ ፡ ያፈሉበታል

**dungeon** ጭለማ ፡ ቤት
The dungeon was full of prisoners. ጭለማ ፡ ቤቱ ፡ በእስረኞች ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር

**dunk** ጠቀሰ
I like to dunk bread in the stew. ዳቦ ፡ በወ ጥ ፡ መጥቀስ ፡ እወዳለሁ

**dupe** (v.) አጭበረበረ
The dishonest peddler duped his customers. የማይታመነው ፡ አዟሪ ፡ ደምበኞቹን ፡ አጭበረበረ

**dupe** (n.) ተታላይ
It took the dupe a long time to understand the matter. ተታላዩ ፡ ነገሩ ፡ የገባው ፡ በጣም ፡ ቆይቶ ፡ ነው

**duplicate** (v.)
1. አባዛ. The secretary duplicated the president's letter. ጸሐፊዋ ፡ የፕሬዚዳንቱን ፡ ደብዳቤ ፡ አባዛች
2. ቀዳ. She duplicated the dress she had admired at the show. በትርኢይቱ ፡ ላይ ፡ ያደነቀች ውን ፡ ልብስ ፡ ሞድ ፡ ቀዳች
3. አስመስሎ ፡ ሠራ. It is not possible to duplicate this statue. ይህን ፡ ሐውልት ፡ አስመስ ሎ ፡ ለመሥራት ፡ አይቻልም
4. ደገመ. He duplicated his former record. የበፊት ፡ ሪከርዱን ፡ ደገመው

**duplicate** (n.)
1. ግልባጭ. Is that an original or a duplicate? ይህ ፡ ዋናው ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ግልባጩ ?
2. ሁለት ፡ ቅጂ. Send in this application in duplicate! ይህን ፡ ማመልከቻ ፡ በሁለት ፡ ቅጂ ፡ ላክ

**duplicate** (adj.) ተመሳሳይ
We have duplicate keys for the front door. ለፊተኛው ፡ በር ፡ ተመሳሳይ ፡ ቁልፎች ፡ አሉን

**duplicity** አታላይነት
It is often hard to see through the duplicity of a cunning man. የብልጣ ፡ ብልጥን ፡ አታ ላይነት ፡ ለመገንዘብ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ያዳግታል

**durable** ጽኑ
Their durable friendship withstood many a heated argument. ጽኑ ፡ የሆነ ፡ ጓደኝነታቸው ፡ ብዙ ፡ የተፋፋመ ፡ ክርክርን ፡ ተቋቁሟል

**be durable**
1. ብዙ ፡ ዕድሜ ፡ አለው. An iron griddle is more durable than a clay griddle. የብረት ፡ ምጣድ ፡ ከሸክላ ፡ ምጣድ ፡ ይልቅ ፡ ብዙ ፡ ዕድሜ ፡ አለው
2. በረከተ. This is a durable pair of shoes. ይህ ፡ ጫማ ፡ ይበረክታል

**duration**
*The duration of the war was more than four years. ጦርነቱ ፡ የፈጀው ፡ ጊዜ ፡ ከአራት ፡ ዓመት ፡ በ ላይ ፡ ነው

**for the duration of** እስከቆየበት ፡ ድረስ
For the duration of the war, gasoline was rationed. ጦርነቱ ፡ እስከቆየበት ፡ ድረስ ፡ ቤንዚ ን ፡ በቁጠባ ፡ ይታደል ፡ ነበር

**for the duration of his life** ዕድሜ ፡ ልኩን
He lived there for the duration of his life. ዕድሜ ፡ ልኩን ፡ እዚያ ፡ ኖረ

**duress, under** ~ የተገደደ ፡ እንደሆነ
He would enter the army only under duress. ወታደርነት ፡ የሚገባው ፡ የተገደደ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው

**during** በ - - - ጊዜ
I met him during the war. ከሱ ፡ ጋር ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ተዋወቅን
It was impossible to see during the dust storm. በዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ጊዜ ፡ አቧራ ፡ በብዛት ፡ ስለ ነበረ ፡ ማየቱ ፡ ያስቸግር ፡ ነበር

**dusk, in the** ~ ለዓይን ፡ ሲይዝ
It was hard to see the flag's colors in the dusk. ለዓይን ፡ ሲይዝ ፡ የሰንደቅ ፡ ዓላማውን ፡ ቀለማት ፡ መለየት ፡ ያስቸግር ፡ ነበር

**dust** (v.)
1. ወለወለ. Please dust my desk! ጠረጴዛዬን ፡ ወልውለው
2. ነሰነሰ. The cook dusted the cake with powdered sugar. የወጥ ፡ ቤቷ ፡ በኬኩ ፡ ላይ ፡ ደ ቃቅ ፡ ስኳር ፡ ነሰነሰች

**dust** (n.) አቧራ ፤ አዋራ
We could tell a car was coming by the dust rising in the air. ወደ ፡ ሰማይ ፡ ከሚነሣው ፡ አ ቧራ ፡ (አዋራ) ፡ መኪና ፡ መምጣቱን ፡ ለማወቅ ፡ ቻልን

**turn to dust** አመድ ፡ ሆነ
The old papers had turned to dust. አሮጌዎቹ ፡ ወ ረቀቶች ፡ አመድ ፡ ሆኑ

**dust storm** የአቧራ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ
The dust storm destroyed many houses. የአቧራ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ብዙ ፡ ቤት ፡ አፈረሰ

**dusty** አቧራማ ፤ አቧራ ፡ የሞላበት
The streets are very dusty. መንገዶቹ ፡ በጣም ፡ አቧራማ ፡ ናቸው
The maid shook out the dusty rug. ገረዲቱ ፡ አቧራ ፡ የሞላበትን ፡ ምንጣፍ ፡ አራገፈች

**duteous** ታዛዥ
A duteous child is the pride of his parents. ታዛዥ ፡ ልጅ ፡ ለወላጆቹ ፡ ኩራት ፡ ነው

**dutiful**
1. ቁም ፡ ነገረኛ. The dutiful son visits his mother often and gives her money. ቁም ፡ ነገረኛው ፡ ልጅ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እናቱን ፡ ለማየት ፡ ይሄዳል ፤ ገንዘብም ፡ ይሰጣታል
2. ቅን. The dutiful services of each citizen are required in wartime. በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የእያንዳንዱ ፡ ዜጋ ፡ ቅን ፡ አገልግሎት ፡ ይፈለጋል

**duty** (duties)
1. ተግባር. He performed his duty as a brave man should. ጐበዝ ፡ ሰው ፡ ሊያደርገው ፡ በሚገባው ፡ አኳኋን ፡ ተግባሩን ፡ ፈጸመ
2. ሥራ. The retired captain was recalled to duty. ጡረታ ፡ የወጣው ፡ ሻምበል ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ እንዲመለስ ፡ ተደረገ
3. ግዴታ ፤ ግዳጅ. It is the duty of every citizen to fight for his country. ላገር ፡ መሞት ፡ የማንኛውም ፡ ዜጋ ፡ ግዴታ ፡ (ግዳጅ) ፡ ነው
4. ቀረጥ. How much duty is there on this tobacco? ለዚህ ፡ ትምባሆ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ቀረጥ ፡ ይከፈላል ?

**answer the call of duty** ግዳጁን ፡ ፈጸመ
At the time of the Italian invasion, many Ethiopians answered the call of duty. በኢጣልያን ፡ ወረራ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ግዳጃቸውን ፡ ፈጸሙ

**be off duty** ከሥራ ፡ ውጭ ፡ ነው
I'm off duty after five-thirty. ከዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ በኋላ ፡ ከሥራ ፡ ውጭ ፡ ነኝ

**be on duty**
1. ተረኛ ፡ ነው. A lifeguard is on duty at the swimming pool. የሕይወት ፡ ጠባቂው ፡ በመዋኛው ፡ ስፍራ ፡ ተረኛ ፡ ነው
2. ሥራ ፡ ላይ ፡ ነው. I am on duty all night. ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ነኝ

**do duty** አገለገለ
This board does duty as a table. ይህ ፡ ሳንቃ ፡ እንደ ፡ ጠረጴዛም ፡ ያገለግላል

**path of duty** ግዳጅ
The soldier followed the path of duty. ወታደሩ ፡ ግዳጁን ፡ ፈጸመ
[See also 'breach, imperative, line, neglect, report']

**dwarf** (v.)
1. አቈረቈዘ. A poor diet dwarfed the children. በቂ ፡ አልሚነት ፡ የሌለው ፡ ምግብ ፡ ልጆቹን ፡ አቈረቈዘ
2. አቀጨጨ. The lack of rain dwarfed the flowers. የዝናብ ፡ መታጣት ፡ አበቦቹን ፡ አቀጨጫቸው

**dwarf** (n.) ድንክ
I have never in my life seen a dwarf. በሕይወቴ ፡ ድንክ ፡ አይቼ ፡ አላውቅም

**dwell** (dwelled, or dwelt) ኖረ.
The princess dwells in the palace. ልዕልቷ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ትኖራለች

**dwell (on)** ተነጋገረ
There is no point in dwelling on this subject any longer. በዚህ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ ይበልጥ ፡ መነጋገር ፡ ዋጋ ፡ የለውም

**dwelling** መኖሪያ ፡ ቤት
They found the remains of a large dwelling in Axum. በአክሱም ፡ አንድ ፡ የትልቅ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ፍራሽ ፡ አገኙ

**dwelt**, see **dwell**

**dwindle**
1. እየመነመነ ፡ ሄደ. The lost traveler watched his supply of food dwindle. የጠፋው ፡ መንገደኛ ፡ ሥንቁ ፡ እየመነመነ ፡ ሲሄድ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አየ
2. አጠጠ. The city's water supply dwindled from lack of rain. ከዝናብ ፡ መታጣት ፡ የተነሣ ፡ የከተማው ፡ ውኃ ፡ አጠጠ

**dye** (v.) ቀለም ፡ ነከረ
She dyed her blue dress black. ሰማያዊ ፡ ቀሚሷን ፡ ጥቁር ፡ ቀለም ፡ ነከረችው

**dye** (n.) መንከሪያ ፤ ማቅለሚያ
Please get me a package of blue dye! አንድ ፡ ባኮ ፡ ሰማያዊ ፡ መንከሪያ ፡ (ማቅለሚያ) ፡ አምጣልኝ

**dying** (adj.) የሚያጣጥር
The last wish of the dying man was to be buried near his parents. የሚያጣጥረው ፡ ሰውዬ ፡ የመጨረሻ ፡ ኑዛዜው ፡ ከወላጆቹ ፡ አጠገብ ፡ እንዲቀበር ፡ ነበር

**dynamic**
1. ታታሪ. The director is a dynamic person. ዲሬክተሩ ፡ ታታሪ ፡ ሰው ፡ ነው

2. ተወርዋሪ. The dynamic force of water is used to make electricity. ተወርዋሪ ፡ የውኃ ፡ ኀይል ፡ ኤሌክትሪክ ፡ ለማመንጨት ፡ ያገለግላል

**dynamite** ድማሚት
The rebels blew up the bridge with dynamite. ሽፍቶቹ ፡ ድልድዩን ፡ በድማሚት ፡ አፈረሱት

**dynamo** [የማሽከርከሪያን ፡ እንቅስቃሴ ፡ ወደ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ የሚለውጥ ፡ መሣሪያ]

**dynasty** ሥርወ ፡ መንግሥት
The Solomonid dynasty has been ruling for many centuries. የሰሎሞን ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ ሲገዛ ፡ ኖሯል

**dysentery** የተቅማጥ ፡ በሽታ
The impure water gave him dysentery. ቆሻሻው ፡ ውኃ ፡ የተቅማጥ ፡ በሽታ ፡ አስያዘው

# E

**each** (adj.)
1. እያንዳንድ. Give one to each child! ለእያንዳንዱ ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ስጥ
2. በየ. He comes here each week. በየሳምንቱ ፡ ወደዚህ ፡ ይመጣል

**each** (pr.) እያንዳንድ + suffix pronoun
These apples are a penny each. እነዚህ ፡ ቱፋዎች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ አንድ ፡ ሳንቲም ፡ ያወጣሉ
He gave them ten dollars each. ለእያንዳንዳቸው ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ ሰጣቸው
We each received a pack of cigarettes. እያንዳንዳችን ፡ ባኮ ፡ ሲጃራ ፡ ተቀበልን

**each and every one** እያንዳንድ + suffix pronoun
You can count on each and every one of us. በያንዳንዳችን ፡ ልትተማመንብን ፡ ትችላለህ

**each of** + (noun) እያንዳንዱ
Each of the boys bought a bicycle. እያንዳንዱ ፡ ልጅ ፡ ቢሲክሌት ፡ ገዛ

**each of** +(pronoun) እያንዳንድ+suffix pronoun
Each of us received a pack of cigarettes. እያንዳንዳችን ፡ አንዳንድ ፡ ባኮ ፡ ሲጃራ ፡ ተቀበልን

**each one** እያንዳንዱ
Each one has to contribute his full share. እያንዳንዱ ፡ ሙሉ ፡ ድርሻውን ፡ ማዋጣት ፡ አለበት

**each other** እርስ ፡ በርሳቸው+stem of reciprocity
We don't like each other. እርስ ፡ በርሳችን ፡ አንዋደድም

**eager**
1. የጓጓ. The eager children set up a clamor to get into the movie house. ሲኒማውን ፡ ለማየት ፡ የጓጉት ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ሲኒማ ፡ ቤቱ ፡ ለመግባት ፡ ይንጫጩ ፡ ነበር
2. ዝግጁ. He is always eager to forward his friends' plans. የጓደኞቹን ፡ እቅዶች ፡ እንዲሳኩ ፡ ለማድረግ ፡ ሁልጊዜ ፡ ዝግጁ ፡ ነው

**be eager** ጓጓ
I am eager to meet your friend. ጓደኛህን ፡ ለመገናኘት ፡ ጓጉቻለሁ

**eagerly** በጉጉት
She devoured the gossip eagerly. ወሬውን ፡ በጉጉት ፡ አደመጠችው

**eagle** ንስር
The eagle is used by many countries as a national symbol. ንስር ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ እንደ ፡ ብሔራዊ ፡ አርማ ፡ ሆኖ ፡ ይሠራበታል

**ear**
1. ጆሮ. A cat has pointed ears. ድመት ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ጆሮ ፡ አላት
It goes in one ear and out the other. ባንድ ፡ ጆሮው ፡ ሰምቶ ፡ በሌላው ፡ ያፈሳል
2. እጀታ. The ear of the pitcher was broken off by the maid. የማንቆርቆሪያውን ፡ እጀታ ፡ ገረዲ ፡ ገነጠለችው
*I have no ear for music. የሙዚቃ ፡ ስሜት ፡ የለኝም

**ear of corn** (እ)ራስ
I bought two roasted ears of corn at the market. ከገበያ ፡ ሁለት ፡ የተጠበሰ ፡ የበቆሎ ፡ እራስ ፡ ገዛሁ

**be all ears**
I am all ears. ልብ ፡ አድርጌ ፡ አደምጣለሁ

**be up to one's ears** ተዋጠ
I am up to my ears in work. በሥራ ፡ ተውጫለሁ

**gain the ear**
*Their complaints finally gained the ear of the prime minister. በመጨረሻ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አቤቱታቸውን ፡ ተቀበሏቸው
[See also 'grin, half, turn, strike']

**earlier** (adj.)
1. የበፊት. His book incorporates his earlier essay. መጽሐፉ ፡ የበፊት ፡ ድርሰቱን ፡ ጨምሮ ፡ ይዟል
2. የቀድሞ. In the light of his earlier behavior, it would be unwise to give him a job. የቀድሞውን ፡ ጠባዩን ፡ ስንመለከት ፡ ሥራውን ፡ ለርሱ ፡ መስጠት ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**earlier** (adv.) ቀደም ፡ ብሎ
He repudiated the statement he had made earlier. ቀደም ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ካደ

**be earlier** ቀደመ
The Christian era is 622 years earlier than the Muslim one. የክርስትና ፡ ዘመን ፡ ከእስላም ፡ ዘመን ፡ በስድስት ፡ መቶ ፡ ሀያ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ይቀድማል

**earliest** የሚቀድም
This is the earliest extant manuscript. ይህ ፡ ሊገኙ ፡ ከተቻሉት ፡ የሚቀድም ፡ የብራና ፡ ጽሑፍ ፡ ነው
[See also 'convenience']

**earlobe** [ሥጋ ፡ የበዛበት ፡ የታችኛው ፡ የጆሮ ፡ ክፍል]

**early** (adj.)
1. ፈጣን ፡ ያለ. We expect an early reply. ፈጣን ፡ ያለ ፡ መልስ ፡ እንጠባበቃለን
2. የጥንት. Tell me something about early life in Ethiopia. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የጥንት ፡ አኗኗር ፡ ንገረኝ
3. (= adv.) ቀደም ፡ ብሎ. We had an early dinner. ቀደም ፡ ብለን ፡ እራት ፡ በላን
4. (= adv.) በማለዳ. He is an early riser. በማለዳ ፡ ይነሣል

**early part** መጀመሪያ
Menelik ruled in the early part of this century. ምኒልክ ፡ በዚህኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ገዙ

**at a very early age** በልጅነቱ
He was struck down by illness at a very early age. በልጅነቱ ፡ በበሽታ ፡ ተቀጨ

**at an early age** ገና ፡ በወጣትነቱ
He has acquired a lot of knowledge at an early age. ገና ፡ በወጣትነቱ ፡ ብዙ ፡ ዕውቀት ፡ ቀሥሟል

**in one's early years** በወጣትነት ፡ ዘመን
In his early years he liked ships. በወጣትነት ፡ ዘመኑ ፡ መርከብ ፡ ይወድ ፡ ነበር

**early** (adv.)
1. ቶሎ. It gets dark early here. እዚህ ፡ ቶሎ ፡ ይመሻል
2. ጥንት. Men early learned the usefulness of weapons. ሰዎች ፡ የመሣሪያን ፡ ጥቅም ፡ ያወቁት ፡ ጥንት ፡ ነው
3. በ - - - መጀመሪያ ፡ ላይ. The settlers came to Kenya early in this century. ሰፋሪዎቹ ፡ ወደ ፡ ኬንያ ፡ የመጡት ፡ በዚህ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ነው
4. ማለዳ. He gets up early. ማለዳ ፡ ይነሣል
5. ከሰዓቱ ፡ ቀደም ፡ ብሎ. The guests came early and found us unprepared. እንግዶቹ ፡ ከሰዓቱ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ስለመጡ ፡ ሳንዘጋጅ ፡ ደረሱብን
6. ቀደም ፡ ብሎ. Call me early! ቀደም ፡ ብለህ ፡ ደውልልኝ
7. በጊዜ. The party was dead, so I went home early. ፓርቲው ፡ በጣም ፡ ቀዝቃዛ ፡ ስለ ነበር ፡ በጊዜ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ሄድኩ

**early in life** በልጅነት
Musical ability often shows itself early in life. የሙዚቃ ፡ ተሰጥዎ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በልጅነት ፡ ይታወቃል

**come early** ቀደም ፡ አለ
Easter comes early this year. ፋሲካ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ቀደም ፡ ይላል

**it's too early** ሰዓቱ ፡ ገና ፡ ነው
It's too early; the cinema does not open till 10 o'clock. ሰዓቱ ፡ ገና ፡ ነው ፤ ሲኒማ ፡ ቤቱ ፡ ከአራት ፡ ሰዓት ፡ በፊት ፡ አይከፈትም
[See also 'morning']

**earmark** (v.) ለይቶ ፡ አስቀመጠ
He earmarked the book for you. መጽሐፉን ፡ ለይቶ ፡ አስቀመጠልህ

**earmark** (n.) ምልክት
The owners recognize their cattle by means of earmarks. ባለቤቶች ፡ የቀንድ ፡ ከብቶቻቸውን ፡ በምልክታቸው ፡ ይለዩዋቸዋል

**earn**
1. አገኘ. How much do you earn a week? በሳምንት ፡ ስንት ፡ ታገኛለህ ?
2. አስገኘ(ለት). His conduct earned him universal respect. ጠባዩ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ክብርን ፡ አስገኘለት

**earn a living** ተዳደረ
She earns her living as a dressmaker. በልብስ ፡ ስፌት ፡ ሥራ ፡ ትተዳደራለች

**earn (one's) own living**
He will have to earn his own living. ራሱን ፡ ችሎ ፡ መኖር ፡ አለበት
[See also 'bread, livelihood']

**earnest** ቅን
He is an earnest worker. ቅን ፡ ሠራተኛ ፡ ነው

**be in dead earnest** የምሩን ፡ ነው
"No, it's no joke, I'm in dead earnest," I told him. የለም ፡ ቀልድ ፡ አይደለም ፤ የምሬን ፡ ነው ፡ አልኩት

**in earnest** በቅንነት
If you work in earnest you will succeed. በቅንነት ፡ ከሠራህ ፡ ይቃናልሃል

**earnings** የሚያገኝ
He spends all of his earnings on gambling. የሚያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ በቁማር ፡ ያባክናል

**earphone** የጆሮ ፡ ማድመጫ
Earphones are acoustic aids for deaf people. የጆሮ ፡ ማድመጫዎች ፡ ለደንቆሮዎች ፡ ለመስሚያ ፡ ረዳቶች ፡ ናቸው

**earring** ጉትቻ
She likes to wear earrings. ጉትቻ ፡ ማድረግ ፡ ትወዳለች

**earth**
1. መሬት. The moon goes around the earth. ጨረቃ ፡ መሬትን ፡ ትዞራለች
2. አፈር. He covered the roots with earth. ሥሩን ፡ አፈር ፡ አለበሰው
3. ምድር. Seas cover most of the surface of the earth. አብዛኛውን ፡ የምድር ፡ ገጽ ፡ ውኃ ፡ ሸፍኖታል

**how on earth** እረ ፡ ለመሆኑ
How on earth are you going to move that heavy rock? እረ ፡ ለመሆኑ ፤ ያንን ፡ ትልቅ ፡ ቋጥኝ ፡ እንዴት ፡ አድርገህ ፡ ታንቀሳቅሰው ፡ ይሆን ?
[See also 'bank']

**earthen** የሸክላ
The woman makes earthen jars for sale in the market. ሴትዮዋ ፡ ለገበያ ፡ የሸክላ ፡ እንስራዎች ፡ ትሠራለች

**earthenware** የሸክላ ፡ እቃ
Earthenware is sold in the market place. የሸክላ ፡ እቃ ፡ በገበያ ፡ ይሸጣል

**earthly** ምድራዊ
Earthly possessions are useless in heaven. ምድራዊ ፡ ንብረቶች ፡ በሰማይ ፡ ቤት ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ናቸው

**earthquake** የመሬት ፡ መንቀጥቀጥ
There was a bad earthquake in Japan. በጃፓን ፡ ኀይለኛ ፡ የመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ነበር
[See also 'shock']

**earthshaking** በጣም ፡ ከፍተኛ
The prime minister announced an earthshaking revision in the constitution. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ የሆነ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ መሻሻል ፡ አስታወቁ

**earwax** ኩክ
If earwax accumulates it may hurt the ear. ኩክ ፡ በጆሮ ፡ ሲጠራቀም ፡ ሊጎዳ ፡ ይችላል

**earthworm** ትል
The oral opening of the earthworm is small. የትል ፡ አፍ ፡ ትንሽ ፡ ነው

**ease** (v.)
1. አስታገሠ. This medicine will ease the pain. ይህ ፡ መድኀኒት ፡ ሕመሙን ፡ ያስታግሣል
2. አላላ. The belt is too tight; ease it a little! ቀበቶው ፡ በጣም ፡ ጠብቋል ፤ ትንሽ ፡ አላላው
3. አቃለለ. I'll help you if it will ease your job. ሥራህን ፡ የሚያቃልልህ ፡ ከሆነ ፡ እረዳሃለሁ
4. ቀስ ፡ ብሎ ፡ በጥንቃቄ ፡ አወጣ. He eased the big box through the narrow door. ትልቁን ፡ ሣጥን ፡ በጠባብ ፡ በር ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ በጥንቃቄ ፡ አወጣ

**ease out** ቀስ ፡ በቀስ ፡ አወረደ
He eased the minister out of his position. ሚኒስትሩን ፡ ከሥልጣናቸው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ አወረዳቸው

**ease up** ተቃለለ ፤ ቀነሰ
Now that all the exams are over, the pressure is beginning to ease up. አሁን ፡ ፈተናው ፡ ሁሉ ፡ ስላለቀ ፡ ጭንቀቱ ፡ እየተቃለለ ፡ (እየቀነሰ) ፡ ነው

**ease** (n.) ምቾት
He lives a life of ease. የምቾት ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል
*Did you notice the ease with which he does things? ሥራውን ፡ እንዴት ፡ በቀላሉ ፡ እንደሚያከናውን ፡ አየህ ?

**ease of his manner** ረጋ ፡ ያለው ፡ አኳኋን
The ease of his manner shows his self assurance. ረጋ ፡ ያለው ፡ አኳኋኑ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መተማመን ፡ ያሳያል

**feel at ease** እንደልቡ ፡ ሆነ ፤ ተዝናና
I never feel quite at ease when I'm with her. ከሷ ፡ ጋር ፡ ስሆን ፡ እንደልቤ ፡ አልሆንም
A genial host makes his guests feel at ease. ተጫዋች ፡ ጋባዥ ፡ እንግዶቹ ፡ እንዲዝናኑ ፡ ያደርጋቸዋል

**put at ease** እንዲዝናና ፡ አደረገ
He always puts his guests at ease. ሁልጊዜ ፡ እንግዶቹን ፡ እንዲዝናኑ ፡ ያደርጋቸዋል

**with ease** ያላንዳች ፡ ችግር
He translates Amharic with ease. አማርኛን ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ ይተረጉማል
[See also 'ill']

**(be) easier** ቀለለ
The job will be easier in daytime. ሥራው ፡ በቀን ፡ ይቀላል

**get easier and easier** ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየተቃለለ ፡ ሄደ
The burden of the tax gets easier and easier.

በግብሩ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ሸክም ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየተቃለለ ፡ ይሄዳል

**easily**

1. በቀላሉ. I can easily believe that. ያንን ፡ በቀላሉ ፡ ላምን ፡ እችላለሁ
He lightened the load and I could carry it easily. ሸክሙን ፡ ስለቀነሰልኝ ፡ በቀላሉ ፡ ልሸከመው ፡ ቻልኩ
2. ያለ ፡ ችግር. The traffic moves along easily. መኪናዎቹ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ይተላለፋሉ
3. ቶሎ. She blushes easily when she is in company. ከሰው ፡ ጋር ፡ ስትሆን ፡ ቶሎ ፡ ታፍራለች
4. ተመችቶት. The patient is resting easily. በሽተኛው ፡ ተመችቶት ፡ አረፍ ፡ ብሏል
5. በትንሹ. The train may easily be an hour late. ባቡሩ ፡ በትንሹ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ይዘገያል
6. ያለ ፡ ጥርጥር. She is easily the best student in class. ያለ ፡ ጥርጥር ፡ እሷ ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ምርጥ ፡ ተማሪ ፡ ናት
[See also 'handle']

**east** (n.) ምሥራቅ
The sun rises in the east. ፀሐይ ፡ በምሥራቅ ፡ ትወጣለች

**east** (adj.)
1. ምሥራቃዊ. The east side of the city was destroyed by the earthquake. የከተማው ፡ ምሥራቃዊ ፡ ክፍል ፡ በመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ምክንያት ፡ ፈረሰ
2. (= adv.) ከምሥራቅ. An east wind is blowing today. ዛሬ ፡ ነፋሱ ፡ ከምሥራቅ ፡ ይነፍሳል

**Easter** ፋሲካ
Easter comes early this year. ፋሲካ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ቀደም ፡ ይላል

**easterly** (= adv.) ከወደ ፡ ምሥራቅ
An easterly wind is blowing today. ዛሬ ፡ ነፋሱ ፡ ከወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይነፍሳል

**eastern** ምሥራቃዊ ፤ የምሥራቅ
I know the eastern part pretty well. ምሥራቃዊውን ፡ ክፍል ፡ በደንብ ፡ አውቃለሁ
Eastern countries are slowly improving themselves. የምሥራቅ ፡ አገሮች ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ በመሻሻል ፡ ላይ ፡ ናቸው

**eastward** ወደ ፡ ምሥራቅ
The plane disappeared flying eastward. አውሮፕላኑ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ በሮ ፡ ከዓይን ፡ ተሰወረ

**easy**
1. ቀላል. That was an easy question. ጥያቄው ፡ ቀላል ፡ ነበር
It is easy for you to talk, but it is I who will suffer the consequences. መናገሩ ፡ ላንተ ፡ ቀላል ፡ ነው ፡ ግን ፡ የምጐዳው ፡ እኔ ፡ ነኝ
2. (= adv.) በቀላሉ. He is a person who is easy to get on with. በቀላሉ ፡ የሚግባቡት ፡ ሰው ፡ ነው
3. ደኅና. He gave us easy terms on the loan. ለብድሩ ፡ ደኅና ፡ ድርድር ፡ አቀረበልን
4. ልል. Many students prefer easy teachers. ብዙ ፡ ተማሪዎች ፡ ልል ፡ መምህራንን ፡ ይመርጣሉ

**be easy** ቀለለ
English would be easy for you. እንግሊዝኛ ፡ ላንተ ፡ ይቀልሃል

**easy life**
He leads an easy life. ያለ ፡ ሐሳብ ፡ ይኖራል

**(at an) easy pace** በዝግታ
The mule ambled on at an easy pace along the road. በቅሎዋ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ በዝግታ ፡ ሄደች

**fairly easy** ቀለል ፡ ያለ
This is a fairly easy book. ይህ ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው

**take it easy**
I'm taking it easy today. ዛሬ ፡ እንደነገሩ ፡ ይገፍ ዋለሁ

**take it easy!** አትጨነቅ
Take it easy! You may hurt yourself working so hard. አትጨነቅ ፤ እንደዚህ ፡ በኀይል ፡ ስትሠራ ፡ ትጐዳ ፡ ይሆናል
[See also 'reach, stage']

**easy chair** ምቹ ፡ ወንበር
Easy chairs are sold here. ምቹ ፡ ወንበር ፡ እዚህ ፡ ይሸጣል

**easygoing** የማይነዛነዝ
An easygoing employer will have loyal workers. የማይነዛነዝ ፡ አሠሪ ፡ ታማኝ ፡ ሠራተኞች ፡ ይኖሩታል

**eat** በላ
The child did not eat the banana. ልጁ ፡ ሙዙን ፡ አልበላም
The acid ate into the iron. አሲዱ ፡ ብረቱን ፡ በላው

**eat away** ሸረሸረ
The river has eaten away the bank. ወንዙ ፡ ዳርቻውን ፡ ሸርሽሮታል

**eat out** ውጭ ፡ በላ
Let's eat out tonight! I am tired of cooking. እስቲ ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ ውጭ ፡ እንብላ ፤ ምግብ ፡ መሥራት ፡ ሰልችቶኛል

**eat up**
1. አሟጦ ፡ በላ. We were very hungry and ate everything up. በጣም ፡ እርቦን ፡ ስለነበረ ፡ አሟጠን ፡ በላን
2. አጠፋ ፤ ጨረሰ. The locusts ate up the grain. አንበጣ ፡ እህሉን ፡ አጠፋው ፡ (ጨረሰው)
3. ጨርሶ ፡ በላ. Eat up your dinner! እራትህን ፡ ጨርሰህ ፡ ብላ

**(be) eaten up** አረረ
He's eaten up with jealousy. በቅናት ፡ አረረ (or ቅናት ፡ አሰልስሎታል)
[See also 'fill, lightly, word']

**eater, big** ~ ሆዳም
He is a big eater. እሱ ፡ ሆዳም ፡ ነው

**be a great eater of** በብዛት ፡ በላ
They are great eaters of fish. ዓሣ ፡ በብዛት ፡ ይበላሉ

**be a small eater**
He is a small eater. ብዙ ፡ አይበላም

**eave** የቤት ፡ ክፈፍ
The gutter along the eaves is leaking. በቤቱ ፡ ክፈፍ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አሸንዳ ፡ ያፈሳል

**eavesdrop** (eavesdropped) በስውር ፡ አዳመጠ
He stood behind the door and eavesdropped on our conversation. ከመዝጊያው ፡ ሥር ፡ ተለጥፎ ፡ ንግግራችንን ፡ በስውር ፡ አዳመጠ

**ebb** (v.)
1. ሸሸ. As the tide ebbed, we picked up the pebbles. ሞገዱ ፡ ሲሸሽ ፡ ጠጠር ፡ ለቀምን
2. መነመነ. Our hopes for victory ebbed. ለማሸነፍ ፡ የነበረን ፡ ተስፋ ፡ መነመነ

**ebb** (n.)
*He likes to watch the ebb of the sea. የባሕር ፡ ማዕበል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሲመለስ ፡ ማየት ፡ ይወዳል

**ebony** [ጥንካሬው ፡ እንደ ፡ ቀረሮ ፡ የሆነ ፡ ጥቁር ፡ ዕንጨት]

**ebullient** ፍልቅልቅ
His ebullient manner makes people forget the problems he has. ፍልቅልቅ ፡ ጠባዩ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ችግር ፡ ያለበት ፡ እያስመስለውም

**be in ebullient mood** በደስታ ፡ ተፍለቀለቀ
The award winner was in an ebullient mood at the dinner in his honor. ሽልማቱን ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ ለክብሩ ፡ በተዘጋጀለት ፡ እራት ፡ ላይ ፡ በደስታ ፡ ተፍለቀለቀ

**eccentric** እንግዳ
It would be eccentric for you to turn around after every ten steps. ከእያንዳንዱ ፡ ዐሥር ፡ እርምጃ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መዞር ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ይሆንብሃል

**be eccentric** ከሰው ፡ አይገጥምም
His behavior is quite eccentric. ጠባዩ ፡ ከሰው ፡ አይገጥምም

**echo** (echoed), v.
1. አስተጋባ. The sound of the shot echoed through the hills. የተኰሱ ፡ ድምፅ ፡ በኮረብቶቹ ፡ መሃል ፡ አስተጋባ
2. እንደ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ደገመ. They echoed every word of their leader. የመሪያቸውን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ደገሙ

**echo** (echoes), n. የገደል ፡ ማሚቶ
If you listen you can hear the echo. ብታዳምጥ ፡ የገደል ፡ ማሚቶው ፡ ይሰማሃል

**eclipse** (v.) አስናቀ
She was so beautiful, she eclipsed every other woman at the party. በጣም ፡ ቆንጆ ፡ ከመሆኗ ፡ የተነሣ ፡ በግብዣው ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ሴቶች ፡ ሁሉ ፡ አስናቀቻቸው

**eclipse** (n.) የፀሐይ ፡ ግርዶሽ ፤ የፀሐይ ፡ ግርዶሽ
Darkness fell upon the town during the eclipse. በፀሐይ ፡ ግርዶሽ ፡ (ግርዶሽ) ፡ ጊዜ ፡ ከተማይቱ ፡ በጨለማ ፡ ተዋጠች

**lunar eclipse** የጨረቃ ፡ ግርዶሽ
The shadow of the earth on the moon causes the lunar eclipse. የመሬት ፡ ጥላ ፡ በጨረቃ ፡ ላይ ፡ ሲያርፍ ፡ የጨረቃ ፡ ግርዶሽ ፡ ይፈጠራል

**economic** የኤኮኖሚ
Ethiopia has received large amounts of economic aid. ኢትዮጵያ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የኤኮኖሚ ፡ እርዳታ ፡ ተቀብላለች

**economical** ቈጣቢ
She's a very economical housewife. እሷ ፡ በጣም ፡ ቈጣቢ ፡ የቤት ፡ እመቤት ፡ ነች

**be economical** ቈጠበ
This type of heating is very economical. የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ማሞቂያ ፡ በጣም ፡ ይቈጥባል

**economically** በቁጠባ
He has to offset his small salary by living economically. አነስተኛ ፡ ደሞዙን ፡ ለማብቃቃት ፡ በቁጠባ ፡ መኖር ፡ አለበት

**economics** የሀብት ፡ ምጣኔ ፤ ምጣኔ ፡ ሀብት ፤ ኤኮኖሚክስ
He attended a seminar in economics. በሀብት ፡ ምጣኔ ፡ (በኤኮኖሚክስ) ፡ ትምህርታዊ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ተካፍሏል

**economize** ቈጠበ
We have to economize now since we don't have much money left. ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ስላልተረፈን ፡ አሁን ፡ መቈጠብ ፡ አለብን

**economy** (economies) የሀብት ፡ ምጣኔ ፡ ይዞታ
The country's economy is in good shape. ያገሪቷ ፡ የሀብት ፡ ምጣኔ ፡ ይዞታ ፡ ጥሩ ፡ ነው
*By various little economies, she saved enough money for a vacation. ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ አጠረቃቅማ ፡ ለዕረፍት ፡ ጊዜዋ ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ አከማቸች

**it's an economy** ገንዘብ ፡ ይቈጥባል
It's an economy in the long run to buy good quality cloth. ጥሩ ፡ ጨርቅን ፡ መግዛት ፡ ለዘለቄታው ፡ ገንዘብን ፡ ይቈጥባል

**ecstasy** ፍንደቃ
His ecstasy knew no bounds. የሱ ፡ ፍንደቃ ፡ ወሰን ፡ አልነበረውም

**be in ecstasy** በደስታ ፡ ፈነደቀ
She was in ecstasy over the gift. ስጦታውን ፡ ስታገኝ ፡ በደስታ ፡ ፈነደቀች

**eczema** ችፌ
He suffered from eczema. ችፌ ፡ ይዞታል

**edge** (v.) ከፈፈ
He edged the table cloth with a red stripe. የጠረጴዛውን ፡ ልብስ ፡ በቀይ ፡ ጨርቅ ፡ ከፈፈው
The bookbinder edged the book in leather. መጽሐፍ ፡ ጠራዡ ፡ የመጽሐፉን ፡ ጠርዝ ፡ በቆዳ ፡ ከፈፈው

**edge along**
*The boy scouts edged along the cliff. በይ ፡ እስካውቶቹ ፡ በገደሉ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ በቀስታ ፡ ተጓዙ

**edge away** አፈገፈገ
He edged away from the mad dog. ከእብዱ ፡ ውሻ ፡ አፈገፈገ

**edge nearer** ጠጋ ፡ አደረገ
He edged his chair nearer to the fire. ወንበሩን ፡ ወደ ፡ እሳቱ ፡ ጠጋ ፡ አደረገ

**edge (through)** በጥንቃቄ ፡ አስገባ
They edged the huge box through the door. ትልቁን ፡ ሣጥን ፡ በበሩ ፡ በኩል ፡ በጥንቃቄ ፡ አስገቡት

**edge (one's way) through** ተሹሎክልኮ ፡ አለፈ
He edged his way through the crowd. በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መኻል ፡ ተሹሎክልኮ ፡ አለፈ

**edge** (n.)
1. ዳር ፤ ዳርቻ. He lives at the edge of the town. ከተማው ፡ ዳር ፡ ይኖራል
There is a shoe factory on the edge of the town. በከተማው ፡ ዳርቻ ፡ አንድ ፡ የጫማ ፡ ፋብሪካ ፡ አለ
2. ጠርዝ. The edge of this plate is chipped. የዚህ ፡ ሳሕን ፡ ጠርዝ ፡ ተሸርፏል
I cut myself on the edge of the paper. የወረቀቱ ፡ ጠርዝ ፡ ቈረጠኝ
3. አፋፍ. He stopped short at the edge of the cliff. ከገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ደርሶ ፡ ለጥቂት ፡ ዳነ
4. ስለት. The edge is dull. ስለቱ ፡ ደነዝ ፡ ነው
5. አፍ. This is a sword with a double edge. ይህ ፡ ሁለት ፡ አፍ ፡ ያለው ፡ ጎራዴ ፡ ነው

**be on edge** ሆድ ፡ ባሰ(ው)
She is on edge today because she had a quarrel with her husband. ከባሏ ፡ ጋር ፡ ተጣልታ ፡ ስለነበር ፡ ዛሬ ፡ ሆድ ፡ ብሷታል
[See also 'cutting, fine, heavy, keen, lose, tooth']

**edgewise, hold ~**
*Hold the knife edgewise when you sharpen it. ቢላዋውን ፡ ስትስል ፡ ስለቱን ፡ ወዳንተ ፡ አታድርግ

**edible** የሚበላ
Some fish are edible. አንዳንድ ፡ ዓሣዎች ፡ የሚበሉ ፡ ናቸው

**not be edible** አይበላም
This fruit is not edible. ይህ ፡ ፍሬ ፡ አይበላም

**edict** ዐዋጅ
An edict of amnesty is generally proclaimed on holidays. የምሕረት ፡ ዐዋጅ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በበዓል ፡ ቀኖች ፡ ይታወጃል

**edifice** ሕንጻ
The Jubilee Palace is an imposing edifice. የኢዮቤልዩ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ግሩም ፡ ሕንጻ ፡ ነው

**edify** (edified) አነቃቃ
His example edified us. መልካም ፡ ምሳሌነቱ ፡ አነቃቃን

**edit** አዘጋጀ
Two students were chosen to edit the school bulletin. ሁለት ፡ ተማሪዎች ፡ የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ መጽሔት ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ ተመረጡ

**edition** እትም
The book came out in two editions. መጽሐፉ ፡ በሁለት ፡ እትም ፡ ወጣ

**editor** አዘጋጅ
Who is the editor of this newspaper? የዚህ ፡ ጋዜጣ ፡ አዘጋጅ ፡ ማን ፡ ነው ?

**editorial** (n.) ርእሰ ፡ አንቀጽ
Did you read the editorial? ርእሰ ፡ አንቀጹን ፡ አነበብክ ?

**editorial** (adj.) የጽሑፍ ፡ አዘጋጅነት
Editorial work requires a broad education. የጽሑፍ ፡ አዘጋጅነት ፡ ሥራ ፡ ሰፊ ፡ ያለ ፡ ትምህርት ፡ ይጠይቃል

**educate** አስተማረ
We have to educate all of our children. ልጆቻችንን ፡ በሙሉ ፡ ማስተማር ፡ አለብን

**educate oneself** ራሱን ፡ በራሱ ፡ አስተማረ
The poor boy had to educate himself in the evenings after work. ችግረኛው ፡ ልጅ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ከሥራ ፡ ውጭ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ማስተማር ፡ ነበረበት

**educated** የተማረ
In common with educated people, he likes poetry. እንደተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ቅኔን ፡ ይወዳል

**education**
1. ትምህርት. Education is indispensable in our times. ትምህርት ፡ በጊዜያችን ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
2. መማሪያ. The money was put away for his education. ገንዘቡ ፡ የተቀመጠው ፡ ለሱ ፡ መማሪያ ፡ እንዲሆን ፡ ነበር

**higher education** ከፍተኛ ፡ ትምህርት
Where did he receive his higher education? ከፍተኛ ፡ ትምህርቱን ፡ የተማረው ፡ የት ፡ ነው?

**lack of education** አለመማር
His mistakes betrayed his lack of education. የፈጸማቸው ፡ ስሕተቶች ፡ አለመማሩን ፡ ገለጹበት

**receive an education** ተማረ
He received a good education abroad. በውጭ ፡ አገር ፡ በደንብ ፡ ተምሯል
[See also 'compulsory']

**educational** ትምህርት ፡ ነክ
Educational motion pictures have helped the students learn more. ትምህርት ፡ ነክ ፡ ፊልሞች ፡ ተማሪዎችን ፡ የበለጠ ፡ እንዲማሩ ፡ ረድተዋቸዋል

**educator** የትምህርት ፡ ሊቅ
The educators are considering school reform. የትምህርት ፡ ሊቃውንት ፡ ትምህርት ፡ ቤትን ፡ ለማሻሻል ፡ በማሰብ ፡ ላይ ፡ ናቸው

**efface** አጠፋ
He effaced the inscription on the wall. ግድግዳው ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ጽሑፍ ፡ አጠፋ

**efface oneself** ተሸሸገ
The shy boy effaced himself by staying in the background. ዓይናፋሩ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ በመሆን ፡ ተሸሸገ

**effect** (v.)
1. በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለ. He effected the change without difficulty. ለውጡን ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለው
2. አከናወነ. They effected the change from Maria Theresa dollars to the new currency without difficulty. ማርትሬዛን ፡ ባዲሱ ፡ ገንዘብ ፡ መተካቱን ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ችግር ፡ አከናወኑ
3. አስከተለ. His mother's death effected a change in his way of life. የእናቱ ፡ መሞት ፡ በኑሮው ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ለውጥ ፡ አስከተለ
*Studying this dictionary will effect an improvement in your language. ይህን ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ብታጠና ፡ በቋንቋ ፡ ረገድ ፡ መሻሻል ፡ ታገኛለህ

**effect** (n.)
1. ውጤት. His speech produced the desired effect. ንግግሩ ፡ የተፈለገውን ፡ ውጤት ፡ አስገኘ
2. ጥፋት. The country has recovered from the effects of the war. ሀገሪቱ ፡ ጦርነቱ ፡ ከደረሰባት ፡ ጥፋት ፡ አንሰራርታለች
3. ጉዳት. The effect of tobacco on health is a debatable question. ትምባሆ ፡ በጤንነት ፡ ላይ ፡ የሚያደርሰው ፡ ጉዳት ፡ የሚያከራክር ፡ ነው
4. ኀይል. The effect of heat on metals results in expansion. የሙቀት ፡ ኀይል ፡ ብረታ ፡ ብረትን ፡ ያስፋፋል

**effects** እቃ
The hotel seized his effects because he couldn't pay the bill. ያለበትን ፡ ሒሳብ ፡ ለመክፈል ፡ ስለማይችል ፡ ሆቴሉ ፡ እቃውን ፡ ያዘበት

**be in effect** ጸና
The rules are still in effect. ደንቦቹ ፡ አሁንም ፡ እንደጸኑ ፡ ናቸው

**be put into effect** በሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ
The new ruling was just put into effect. አዲሱ ፡ ሕግ ፡ ገና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉ ፡ ነው

**for effect** ለእዩልኝ
He wears a large gold ring with a large diamond on it for effect. ለእዩልኝ ፡ ትልቅ ፡ አልማዝ ፡ ጉብ ፡ ያለበት ፡ ትልቅ ፡ የወርቅ ፡ ቀለበት ፡ አድርጓል

**from the effects** ከ - - የተነሣ
The children were suffering from the effects of the hot weather. ልጆቹ ፡ ከሞቃቱ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ የተነሣ ፡ ይሠቃዩ ፡ ነበር

**give the effect of** መሰለ
The new plastic gives the effect of real leather. አዲሱ ፡ ፕላስቲክ ፡ ልክ ፡ እውነተኛ ፡ ቆዳ ፡ ይመስላል

**go into effect** በሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ
That law will go into effect next month. ሕጉ ፡ በሚመጣው ፡ ወር ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላል

**have an effect** ሠራ
The medicine had an immediate effect. መድኃኒቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ሠራ

**have great effect** አጥንት ፡ ሰበረ
The father's malediction has great effect. ያባት ፡ እርግማን ፡ አጥንት ፡ ይሰብራል

**have no effect** ግድ ፡ የለውም ፤ ምንም ፡ ውጤት ፡ አልነበረውም
+Scolding has no effect on him. ለስድብ ፡ ግድ ፡ የለውም
His protest had no effect. ተቃውሞው ፡ ምንም ፡ ውጤት ፡ አልነበረውም

**in effect**
*His silence was in effect a confirmation of the rumor. ዝም ፡ ማለቱ ፡ የወሬውን ፡ እርግጠኛነት ፡ እንደማመን ፡ የሚቈጠር ፡ ነው

**take effect** ሠራ
The injection is beginning to take effect. መርፌው ፡ ይሠራ ፡ ጀመር

**to that effect**
*He said he might agree to do it or words to that effect. ምናልባት ፡ ሊያደርገው ፡ እንደሚስማማ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አባባል ፡ ተናገረ

## effective
1. ጥሩ ፡ ውጤት ፡ የሚሰጥ ፤ ፍቱን. The government took effective measures against malaria. መንግሥቱ ፡ ወባን ፡ ለማጥፋት ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ የሚሰጥ ፡ (ፍቱን) ፡ እርምጃ ፡ ወሰደ
2. ተደማጭነት ፡ ያለው. An effective speaker is needed to present our case to the public. ለሕዝቡ ፡ ጉዳያችንን ፡ ለማቅረብ ፡ ተደማጭነት ፡ ያለው ፡ ተናጋሪ ፡ ያስፈልጋል

**be effective**
1. በሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ. A law is effective as soon as the President signs the act. ፕሬዚዳንቱ ፡ እንደፈረመበት ፡ ሕጉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላል
2. ቻለ. Our artillery was effective in destroying the city. ከባድ ፡ መሣሪያችን ፡ ከተማውን ፡ ለማጥፋት ፡ ቻለ

## effectuate አስገኘ
Only persistent effort will effectuate the desired results. ያለመሰልቸት ፡ የሚደረግ ፡ ጥረት ፡ ብቻ ፡ የተፈለገውን ፡ ውጤት ፡ ያስገኛል

## effeminate
1. የሴት. His way of dressing is effeminate. አለባበሱ ፡ የሴት ፡ ነው
2. ሴታ ፡ ሴት. His gait is effeminate. አረማመዱ ፡ ሴታ ፡ ሴት ፡ ነው

## effervescent ፍልቅልቅ ፤ ደማም
Her effervescent personality makes her a lovable companion. ፍልቅልቅ ፡ (ደማም) ፡ ጠባይዋ ፡ ተወዳጅ ፡ ያደርጋታል

**be effervescent** ፈላ
This mineral water is effervescent. ይህ ፡ ጠበል ፡ ይፈላል

## effete ኀይሉ ፡ የተሟጠጠበት
An effete civilization will soon lose influence. ኀይሉ ፡ የተሟጠጠበት ፡ ሥልጣኔ ፡ በቶሎ ፡ ተጽዕኖውን ፡ ያጣል

## efficacious
1. አጥጋቢ. An efficacious solution was found to the problem of the drought. ስለ ፡ ድርቀቱ ፡ አጥጋቢ ፡ የሆነ ፡ መፍትሔ ፡ ተገኘ
2. ጠቃሚ. Vaccination for smallpox is efficacious. ክትባት ፡ ለፈንጣጣ ፡ መከላከያ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው

## efficacy ፍቱንነት
He invented a drug of great efficacy. ታላቅ ፡ ፍቱንነት ፡ ያለው ፡ መድኃኒት ፡ ፈለሰፈ

## efficiency ቅልጥፍና
The mason worked with great efficiency. ግንበኛው ፡ በከፍተኛ ፡ ቅልጥፍና ፡ ሠራ

## efficient ቀልጣፋ
He is an efficient worker. ቀልጣፋ ፡ ሠራተኛ ፡ ነው

**be efficient** ጠቃሚነት ፡ አለው
Our new house is more efficient than our old one. ከድሮው ፡ ይልቅ ፡ አዲሱ ፡ ቤታችን ፡ የበለጠ ፡ ጠቃሚነት ፡ አለው

## effigy (effigies) ምስል
They made an effigy of the king. የንጉሡን ፡ ምስል ፡ ሠሩ

## effort
1. ድካም. All his efforts were in vain. ድካሙ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ነበር
2. ጥረት. He constantly belittles my efforts to write better. ጽሕፈቴን ፡ ለማሻሻል ፡ የማደርገውን ፡ ጥረት ፡ ሁልጊዜ ፡ ያንቋሽሻል

3. ትግል. The enemy may win yet if we relax our efforts. አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ትግላችንን ፡ ከ
ቀነስን ፡ ጠላት ፡ ድል ፡ ሊያደርገን ፡ ይችላል
4. (= make an effort) ለፋ. In spite of my efforts, the boy remained passive. ምንም ፡ ብለ
ፋ ፡ እንኳ ፡ ልጁ ፡ ተካፋይ ፡ ሳይሆን ፡ ቀረ

**bend every effort** የተቻለውን ፡ ሁሉ ፡ አደረገ
We must bend every effort to beat the enemy. ጠላትን ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ የተቻለንን ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ አለብን

**exert one's efforts** በጣም ፡ ተጣጣረ
He exerted his efforts to arrive early. ቀደም ፡ ብሎ ፡ ለመድረስ ፡ በጣም ፡ ተጣጣረ

**expend much effort** ብዙ ፡ ጥረት ፡ አደረገ
He expended much effort to learn Amharic. አማርኛ ፡ ለመማር ፡ ብዙ ፡ ጥረት ፡ አደረገ

**make an effort** ሞከረ
Please make an effort to come on time! በሰዓቱ ፡ ለመምጣት ፡ ሞክር

**make every effort** የተቻለውን ፡ ሁሉ ፡ አደረገ
I will make every effort to help you. አንተን ፡ ለመርዳት ፡ የተቻለኝን ፡ ሁሉ ፡ አደርጋለሁ
[See also 'combined, frantic, strain, stretch']

**effrontery** ብልግና ፤ ድፍረት
His effrontery offended the teacher. ብልግናው ፡ (ድፍረቱ) ፡ መምህሩን ፡ አስቀየመው

**have the effrontery** ደፈረ
She had the effrontery to ask for two free samples. ደፍራ ፡ ሁለት ፡ የነጻ ፡ ናሙና ፡ ጠየቀች

**effusive** በጣም ፡ የተሟሟቀ ፤ ስሜት ፡ የተሞላ
Her effusive greetings are embarrassing. በጣ
ም ፡ የተሟሟቀው ፡ (ስሜት ፡ የተሞላው) ፡ ሰላምታ
ዋ ፡ የሚያሳፍር ፡ ነው

**egg** እንቁላል
The chicken laid an egg. ዶሮዋ ፡ እንቁላል ፡ ጣ
ለች
[See also 'sit, white']

**eggplant** ማደርቻ ፤ መደርቻ

**eggshell** የእንቁላል ፡ ቅርፊት
The flimsy boat was crushed like an eggshell. ደቃቃዋ ፡ ጀልባ ፡ እንደ ፡ እንቁላል ፡ ቅርፊት ፡ ነካከተች

**egoism** ራስን ፡ ብቻ ፡ ወዳድነት
His biggest fault is his egoism. ትልቁ ፡ ጉድለቱ ፡ ራሱን ፡ ብቻ ፡ ወዳድነቱ ፡ ነው

**eight** ስምንት

**eight o'clock** ሁለት ፡ ሰዓት
I will be home at eight o'clock. በሁለት ፡ ሰዓት ፡ እቤት ፡ እገኛለሁ

**eighteen** ዐሥራ ፡ ስምንት

**eighth** ስምንተኛ

**eighty** ሰማንያ

**either** (adj. pron.)
1. አንደኛው ፤ አንዱም. Does either of these roads lead to Harar? ከነዚህ ፡ መንገዶች ፡ አንደኛው ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ይወስዳል ?
He looked at two cars, but did not buy either. ሁለት ፡ መኪናዎች ፡ አየ ፡ ግን ፡ አንዱንም ፡ አልገዛ
2. ሁለቱም. Either (one) is correct. ሁለቱም ፡ ልክ ፡ ነው
He can write with either hand. በሁለቱም ፡ እጁ ፡ ሊጽፍ ፡ ይችላል
3. ከሁለቱ ፡ የፈለገው. You may take either book. ከሁለቱ ፡ የፈለግኸውን ፡ መጽሐፍ ፡ ልት
ወስድ ፡ ትችላለህ
*There were trees on either side of the road. በመንገዱ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ዛፎች ፡ ነበሩ

**either** (adv.)
*He doesn't know it either. እሱም ፡ አያውቀ
ውም
*John has not been to Ethiopia and Bill has not been there either. ጆን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሄዶ ፡ አያውቅም ፤ ቢልም ፡ እንደዚሁ

**either ... or** ወይም
I leave either tonight or tomorrow morning. ዛሬ ፡ ማታ ፡ ወይም ፡ ነገ ፡ ጧት ፡ እሄዳለሁ
Either come or write. ና ፡ ወይም ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፍ
[See also 'hand']

**ejaculate, make ~** አጯደረ
The electric shock made him ejaculate with pain. ኮረንቲ ፡ ሲይዘው ፡ ሲል ፡ በሥቃይ ፡ አጯ
ደረ

**eject**
1. አስወጣ. The manager ejected them for not paying the rent. ኪራይ ፡ ስላልከፈሉ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ አስወጣቸው
2. ተፋ. The volcano ejected ashes. እሳተ ፡ ገ
ሞራው ፡ አመድ ፡ ተፋ

**eke, ~ out** አብቃቃ
The housewife eked out a dinner of leftovers by adding rice. የቤቷ ፡ እመቤት ፡ በተረፈው ፡ ም
ግብ ፡ ላይ ፡ ሩዝ ፡ ጨምራ ፡ ለእራት ፡ አብቃቃችው

*They managed to eke out a living by farming a small piece of land. ትንሽ ፡ መሬት ፡ በማረስ ፡ እየታገሉ ፡ ለመኖር ፡ቻሉ

**elaborate** (v.) በዝርዝር ፡ አዘጋጀ
The general elaborated his plan. ጄኔራሉ ፡ እቅዱን ፡ በዝርዝር ፡ አዘጋጀ

**elaborate upon** ትንሽ ፡ አብራራ
Can you elaborate upon your statement? የምትለውን ፡ ትንሽ ፡ ለማብራራት ፡ ትችላለህ ?

**elaborate** (adj.)
1. ረቂቅ. The Jubilee Palace is a very elaborate structure. የኢዮቤልዩ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሕንጸ ፡ ሥራው ፡ ረቂቅ ፡ ነው
2. ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ የሚደረግለት. Elaborate preparations are being made for the coronation ceremonies. ለዘውድ ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ የሚደረግለት ፡ ዝግጅት ፡ በመከናወን ፡ ላይ ፡ ነው

**elapse** አለፈ
Thirty minutes elapsed before the lecture began. ትምህርቱ ፡ ሳይጀመር ፡ ሠላሳ ፡ ደቂቃ ፡ አለፈ
*Many days elapsed before they returned. ሳይመለሱ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ሆናቸው

**elastic** (n.) ላስቲክ
Do you need any elastic for the blouse? ለሸሚዝሽ ፡ ላስቲክ ፡ ትፈልጊያለሽ ?

**elastic** (adj.) የሚለጠጥ
Rubber is elastic. ጎማ ፡ የሚለጠጥ ፡ ነገር ፡ ነው
*The government has an elastic foreign policy. መንግሥቱ ፡ እንደጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ ሊለዋወጥ ፡ የሚችል ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ መመሪያ ፡ አለው

**elate** አስፈነደቀ
Winning first prize elated her. የአንደኝነትን ፡ ሽልማት ፡ ማግኘቷ ፡ አስፈነደቃት

**be elated** ፈነደቀ
He was elated at the news. ወሬውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፈነደቀ

**elation** ፍንደቃ
His elation is due to his having received a scholarship. ፍንደቃው ፡ የነጻ ፡ ትምህርት ፡ ስላገኘ ፡ ነው

**elbow** (v.), ~ **aside** ገፋፍቶ ፡ አለፈ
He elbowed the other shoppers aside. ሌሎች ፡ ገበያተኞችን ፡ ገፋፍቶ ፡ አለፈ

**elbow one's way through** ተጋፍቶ ፡ አለፈ
She elbowed her way through the crowd. ሰው ፡ በተሰበሰበበት ፡ መኻል ፡ ተጋፍታ ፡ አለፈች

**elbow** (n.) ክርን
I banged my elbow. ክርኔን ፡ አጋጨኹት

**elder** (n.)
1. ሽማግሌ. The village elders held a council. የመንደሩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ስብሰባ ፡ አደረጉ
2. ታላቅ (pl. ታላላቅ). We must respect our elders. ታላላቆቻችንን ፡ ማክበር ፡ አለብን

**elder** (adj.) ታላቅ
My elder brother is in Ethiopia. ታላቅ ፡ ወንድሜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**elderly**
1. በዕድሜ ፡ የገፋ. I am living with an elderly couple. የምኖረው ፡ በዕድሜ ፡ ከገፉ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ጋር ፡ ነው
2. ጠና ፡ ያለ. I took lodging with an elderly lady. ካንዲት ፡ ጠና ፡ ካሉ ፡ ሴት ፡ ቤት ፡ ተከራየሁ

**eldest** የበኽር ፡ ልጅ
The eldest son becomes the head of the family when the father dies. አባት ፡ ሲሞት ፡ የበኽር ፡ ልጅ ፡ የቤተ ፡ ሰቡ ፡ አሳዳሪ ፡ ይሆናል

**elect** መረጠ
They elected him president. ለፕሬዚዳንትነት ፡ መረጡት
First-year students may elect French or German. የመጀመሪያ ፡ ዓመት ፡ ተማሪዎች ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ወይም ፡ ጀርመንኛ ፡ ለመምረጥ ፡ ይችላሉ

**election** ምርጫ
When were the last elections held? ያለፈው ፡ ምርጫ ፡ መቼ ፡ ተደረገ ?
His election took place last week. የሱ ፡ ምርጫ ፡ ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ተከናወነ

**elective** (n.) በምርጫ ፡ የሚወሰድ ፡ ትምህርት
French is an elective in our school. በትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ፈረንሳይኛ ፡ በምርጫ ፡ የሚወሰድ ፡ ትምህርት ፡ ነው

**elective** (adj.) በሕዝብ ፡ የሚመረጥ
In America senators hold elective office. በአሜሪካ ፡ አገር ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ አባሎች ፡ በሕዝብ ፡ የሚመረጡ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ናቸው

**electric** በኤሌክትሪክ ፡ የሚሠራ
The child received an electric train. ልጅ ፡ በኤሌክትሪክ ፡ የሚሠራ ፡ አሻንጉሊት ፡ ባቡር ፡ ተቀበለ

**electric bulb** አምፑል

**electric current** ኮረንቲ
The electric current has been turned off. ኮረንቲው ፡ ጠፍቷል

**electrician** የኤሌክትሪክ ፡ ሠራተኛ
Since there was no electrician around, we had no one to connect the electricity for us. የኤሌክትሪክ ፡ ሠራተኛ ፡ ባካባቢው ፡ ስላልነበረ ፡ መብራታችንን ፡ የሚቀጥልልን ፡ አጣን

**electricity** ኤሌክትሪክ ፤ ኮረንቲ
There is no electricity in our city. በከተማችን ፡ ኤሌክትሪክ ፡ (ኮረንቲ) ፡ የለም

**electrify** (electrified)
1. ኤሌክትሪክ ፡ አስገባ. The farmers of this village electrified their farms. በዚህ ፡ መንደር ፡ ያሉ ፡ ገበሬዎች ፡ ለእርሻቸው ፡ ኤሌክትሪክ ፡ አስገቡ
2. አስፈነጠዘ. The good news electrified the students. የምስራቹ ፡ ተማሪዎቹን ፡ አስፈነጠዛቸው

**be electrified** በኮረንቲ ፡ ኀይል ፡ ተገለገለ
Most farms have now been electrified. ባሁን ፡ ጊዜ ፡ አብዛኛዎች ፡ የእርሻ ፡ ቦታዎች ፡ በኮረንቲ ፡ ኀይል ፡ ይገለገላሉ

**(be) electrocuted** በኮረንቲ ፡ ተገደለ
The murderer was electrocuted. ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ በኮረንቲ ፡ ተገደለ

**elegant**
1. ያሸበረቀ. His elegant dress drew the eye of all onlookers. ያሸበረቀው ፡ ልብሱ ፡ የተመልካቾቹን ፡ ዓይን ፡ ሁሉ ፡ ማረከ
2. ያጊያጊጠ. The palace has elegant furnishings. ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ያጊያጊጡ ፡ እቃዎች ፡ አሉት
3. ድንቅ. He has elegant manners. ድንቅ ፡ ጠባይ ፡ አለው

**elegy** [ሟቹን ፡ የሚያሞግስ ፡ የልቅሶ ፡ ግጥም]

**element**
1. ባሕርይ. According to the ancients, the world consisted of four elements : earth, air, fire and water. ጥንታውያን ፡ እንደሚሉት ፡ ዓለም ፡ ካራት ፡ ባሕርያት ፡ የተሠራች ፡ ናት ፤ እነሱም ፡ እሳትና ፤ ውኃ ፤ ነፋስና ፡ መሬት ፡ ናቸው
2. ጥንተ ፡ ንጥር. Split up a compound into its elements. ውሑዱን ፡ በየጥንተ ፡ ንጥሩ ፡ ለየው
3. መሠረታዊ ፡ ነገር. Have you learned the elements of grammar? የሰዋስውን ፡ መሠረታዊ ፡ ነገሮች ፡ ተምረሃል ?
4. ነገር. Justice is an important element in good government. ለጥሩ ፡ መንግሥት ፡ ፍትሕ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው
Letters are the elements out of which the words are formed. ፊደላት ፡ ቃላት ፡ የሚመሠረቱባቸው ፡ ነገሮች ፡ ናቸው
5. መኖሪያ. Water is the natural element of a fish. ውኃ ፡ የዓሣ ፡ የተፈጥሮ ፡ መኖሪያ ፡ ነው

**elementary** የጀማሪዎች
He is still studying elementary mathematics. አሁንም ፡ ገና ፡ የጀማሪዎች ፡ ሒሳብ ፡ በማጥናት ፡ ላይ ፡ ነው

**elementary school** ያንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት
There are many elementary schools here. እዚህ ፡ ብዙ ፡ ያንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ አሉ

**elephant** ዝሆን
The elephant is a huge animal. ዝሆን ፡ ግዙፍ ፡ እንስሳ ፡ ነው

**elevate**
1. ከፍ ፡ አደረገ. The Emperor elevated him to the rank of Ras. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወደ ፡ ራስነት ፡ ማዕረግ ፡ ከፍ ፡ አደረጉት
2. አጐለመሰ. Great ideas elevate the mind. ታላላቅ ፡ ሐሳቦች ፡ አእምሮን ፡ ያጐለምሳሉ

**elevated** (adj.)
1. ከፍ ፡ ያለ. He spoke from an elevated platform. ከፍ ፡ ካለ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ተናገረ
2. ጥልቅ. The sermon was filled with elevated thoughts. ስብከቱ ፡ ጥልቅ ፡ የሆኑ ፡ ሐሳቦችን ፡ ያዘለ ፡ ነበር

**elevation**
1. ከፍታ. What is the elevation of Addis Ababa? አዲስ ፡ አበባ ፡ ከፍታው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?
2. ጉብታ. The house is built on a small elevation. ቤቱ ፡ በትንሽ ፡ ጉብታ ፡ ላይ ፡ ተሠርቷል
3. መውጣት. The elevation of Caesar to Emperor cost him his life. የቄሣር ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ደረጃ ፡ መውጣት ፡ ለሞቱ ፡ ምክንያት ፡ ሆነ

**elevator** አሳንሱር ፤ አሳንሰር ፤ ኤሌቬተር
Since the building is very tall, we went up in the elevator so as not to get tired. ሕንጻው ፡ ረዢም ፡ ስለሆነ ፡ እንዳይደክመን ፡ በአሳንሱር ፡ ወጣን

**eleven** ዐሥራ ፡ አንድ

**eleven o'clock** አምስት ፡ ሰዓት
On Sunday, they open the library at eleven o'clock. እሑድ ፡ እሑድ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቱን ፡ ባምስት ፡ ሰዓት ፡ ይከፍታሉ

**elicit**
1. እንዲገለጥ ፡ አደረገ. The purpose of the questioning was to elicit a full description of the accident. የምርመራው ፡ ዓላማ ፡ ያደጋው ፡ ሙሉ ፡ መግለጫ ፡ እንዲገለጥ ፡ ለማድረግ ፡ ነበር
2. አስከተለ. His jokes elicited laughter. ቀልዱ ፡ ሣቅ ፡ አስከተለ

**(be) eligible**
1. ይገባዋል. He is eligible for promotion. የማዕረግ ፡ እድገት ፡ ይገባዋል
2. ብቁ ፡ ሆነ. He had to pass several exams to be eligible for the scholarship. ለእስኮላርሽፑ ፡ ብቁ ፡ ለመሆን ፡ ብዙ ፡ ፈተናዎችን ፡ ማለፍ ፡ ነበረበት

**eliminate**
1. አስወጣ. During the race the judge eliminated him at the third lap. በሩጫው ፡ ጊዜ ፡ ዳኛው ፡ በሦስተኛው ፡ ዙር ፡ አስወጣው
2. አጠፋ. The municipality has a building program to eliminate slums. ደሳሳ ፡ ቤቶችን ፡ ለማጥፋት ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ የሕንጻ ፡ ሥራ ፡ ፕሮግራም ፡ አለው
3. ከግምት ፡ አላስገባም. The architect eliminated furniture in figuring the cost of the house. መሀንዲሱ ፡ ቤቱ ፡ የሚፈጅውን ፡ ሲገምት ፡ የቤት ፡ እቃዎችን ፡ ከግምት ፡ አላስገባም
4. አስወገደ. He eliminated the difficulties easily. ችግሮቹን ፡ በቀላሉ ፡ አስወገደ

**elite** ቁንጮ
The students are the elite of the society. ተማሪዎቹ ፡ የኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ቁንጮ ፡ ናቸው

**ellipse** [ሜፍና ፡ ሜፍ ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ የእንቁላል ፡ ቅርጽ ፡ ያለው ፡ ክብ ፡ ነገር]

**elocution**
1. የንግግር ፡ ትምህርት. Elocution used to be taught in high school. የንግግር ፡ ትምህርት ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይሰጥ ፡ ነበር
2. ንግግር. The actor's elocution is impeccable. የተዋናዩ ፡ ንግግር ፡ የተጣራ ፡ ነው

**elongate** (vt.) አስረዘመ
If you can elongate the string, it can cover the distance between the two poles. ገመዱን ፡ ብታስረዝመው ፡ ሁለቱም ፡ ምሰሶዎች ፡ ጋ ፡ ይደርሳል

**elongate** (vi.) ተሳበ
A rubber band will elongate easily. ላስቲክ ፡ በቀላሉ ፡ ይሳባል

**elope** ከእጮኛ ፡ ጋር ፡ ኮበለለ
His daughter eloped. የሱ ፡ ልጅ ፡ ከእጮኛዋ ፡ ጋር ፡ ኮበለለች

**eloquence** አንደበተ ፡ ርቱዕነት
The eloquence of the President moved the audience. የፕሬዚዳንቱ ፡ አንደበተ ፡ ርቱዕነት ፡ ያድማጮቹን ፡ ስሜት ፡ ቀሰቀሰ

**eloquent**
1. አንደበተ ፡ ርቱዕ. The prime minister is an eloquent speaker. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አንደበተ ፡ ርቱዕ ፡ ተናጋሪ ፡ ነው
2. የተሳካ. His eloquent speech moved the audience. የተሳካው ፡ ንግግሩ ፡ ያድማጮቹን ፡ ስሜት ፡ ነካ
3. ልብ ፡ የሚነካ. The lawyer made an eloquent plea to the judge. ጠበቃው ፡ ለዳኛው ፡ ልብ ፡ የሚነካ ፡ አቤቱታ ፡ አቀረበ

**else** ያለበለዚያ
Hurry, else you will be late. ፈጠን ፡ በል ፤ ያለበለዚያ ፡ ሰዓት ፡ ያልፍብሃል

**anybody else** ሌላ ፡ ሰው
Is anybody else here? እዚህ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አለ ?

**anywhere else** ሌላ ፡ ቦታ
Can't we meet anywhere else? ሌላ ፡ ቦታ ፡ ልንገናኝ ፡ አንችልም ?

**everybody else** ሁሉም ፤ ሌሎቹ ፤ የተቀሩት ፡ ሁሉ
Everybody else has gone. ሁሉም ፡ ሄዷል ፡ (ሌሎቹ ፡ ሄደዋል)
It is all right with me if it is all right with everybody else. ለተቀሩት ፡ ሁሉ ፡ ከተስማማ ፡ እኔ ፡ ግዴለኝም

**everything else** የተረፈው ፡ ሁሉ
I'll take everything else. የተረፈውን ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ እወስዳለሁ

**how else**
1. እንግዲያስ. Did you come to Lalibela by plane? How else? ላሊበላ ፡ የመጣሀው ፡ በአውሮፕላን ፡ ነው ? እንግዲያስ ?
2. እንዴት. How else would you get to Ethiopia if you didn't fly? ባውሮፕላን ፡ ካልሆነ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዴት ፡ መግባት ፡ ይቻላል ?

**nothing else** ሌላ ፤ ምንም ፡ ሌላ
I have nothing else to do today. ዛሬ ፡ ሌላ ፡ (ምንም ፡ ሌላ) ፡ የምሠራው ፡ ሥራ ፡ የለኝም

**or else** ያለዚያ
Run or else you will be late. ሩጥ ፤ ያለዚያ ፡ ሰዓት ፡ ያልፍብሃል
*Do it or else! ባትሠራው ፡ ወዮልህ

**someone else** ሌላ ፡ ሰው
Is someone else here? ሌላ ፡ ሰው ፡ እዚህ ፡ አለ ?
**what else** ሌላ ፡ ምን
What else do you want to take along? ሌላ ፡ ምን ፡ ይዘህ ፡ ልትሄድ ፡ ትፈልጋለህ ?
**where else** ሌላ ፡ ጋ ፡ የት
Where else did you go? ሌላ ፡ ጋ ፡ የት ፡ ሄድክ ?
[See also 'anything, nobody, somewhere']

**elsewhere**
1. ሌላ ፡ ቦታ. We'll have to look around elsewhere. ሌላ ፡ ቦታ ፡ መፈለግ ፡ ይኖርብናል
2. ሌላጋ. If you don't like it here, we'll go elsewhere. ይህንን ፡ ቦታ ፡ ካልወደድከው ፡ ሌላጋ ፡ እንሄዳለን
3. የትም ፡ አገር. There are more telephone users in the U.S. than elsewhere. ከየትም ፡ አገር ፡ ይልቅ ፡ በቴሌፎን ፡ የሚጠቀሙ ፡ ሰዎች ፡ በአሜሪካ ፡ ይበዛሉ

**elucidate** አብራራ
The scientist elucidated his theory by a few experiments. የሳይንሱ ፡ ሊቅ ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳቡን ፡ በጥቂት ፡ ሙከራዎች ፡ አብራራ

**elude**
1. አታለለ. The brigand eluded the police and escaped. ቀማኛው ፡ ፖሊሱን ፡ አታሎ ፡ አመለጠ
2. በዘዴ ፡ አመለጠ. The sly fox eluded the dogs. ብልጣ ፡ ብልጧ ፡ ቀበሮ ፡ ከውሾቹ ፡ በዘዴ ፡ አመለጠች
3. ጠፋ. His name eludes me. ስሙ ፡ ይጠፋኛል

**elusive** የማይጨበጥ
The elusive enemy got away. የማይጨበጠው ፡ ጠላት ፡ አመለጠ

**emaciate** አመነመነ
Hunger emaciated the survivors. ከሞት ፡ የተረፉትን ፡ ረኃብ ፡ አመንምኗቸዋል
**be emaciated** መነመነ
He was emaciated by a long illness. እርሱ ፡ በብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሕመም ፡ መንምኗል

**emanate**
1. ተፈነጠቀ. Light emanates from the sun. ብርሃን ፡ ከፀሐይ ፡ ይፈነጠቃል
2. መጣ. A faint smell emanated from the kitchen. አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሽታ ፡ ከማድቤቱ ፡ መጣ

**emancipate** ነጻ ፡ አወጣ ፤ አርነት ፡ አወጣ
Lincoln emancipated the American slaves in 1863. በ፲፰፻፶፮ ዓ.ም.ሊንኮልን ፡ የአሜሪካንን ፡ ባሮች ፡ ነጻ ፡ አወጣ ፡ (አርነት ፡ አወጣ)
**be emancipated** ነጻ ፡ ወጣ
Women have been emancipated from many old restrictions. ሴቶች ፡ ከብዙ ፡ የጥንት ፡ ልማዶች ፡ ነጻ ፡ ወጥተዋል

**emancipation**
1. ነጻ ፡ መውጣት. Emancipation of the slaves is no longer a live issue. የባሮች ፡ ነጻ ፡ መውጣት ፡ በሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ አይደለም
2. የእኩልነት ፡ መብት ፡ ማግኘት. Emancipation of women is necessary for progress. የሴቶች ፡ የእኩልነት ፡ መብት ፡ ማግኘት ፡ ለእድገት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**emasculate**
1. ሰለበ. In former days, they emasculated prisoners. ድሮ ፡ እስረኞችን ፡ ይሰልቡ ፡ ነበር
2. የወንድነት ፡ ወኔ ፡ ገደለ. A domineering mother can emasculate her sons. ኀይለኛ ፡ እናት ፡ የወንዶች ፡ ልጆቿን ፡ የወንድነት ፡ ወኔያቸውን ፡ ልትገድል ፡ ትችላለች

**embalm** እንዳይፈርስ ፡ መድኃኒት ፡ አደረገበት
The Egyptians embalmed their dead before burial. ግብጻውያን ፡ ሙታንን ፡ ከመቅበራቸው ፡ በፊት ፡ እንዳይፈርሱ ፡ መድኃኒት ፡ አደረጉባቸዋል

**embankment** ግድብ
The embankment protects the road from flooding. ግድቡ ፡ መንገዱን ፡ ጐርፍ ፡ እንዳያጥለቀልቀው ፡ ይከላከላል

**embargo** ማገጃ
The government put an embargo on all foreign vessels. መንግሥቱ ፡ በማናቸውም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ማገጃ ፡ አደረገ

**embark** መርከብ ፡ ተሳፈረ
The soldiers embarked at Massawa. ወታደሮቹ ፡ ምፅዋ ፡ ላይ ፡ መርከብ ፡ ተሳፈሩ
**embark on** ጀመረ
He embarked on a new business. አዲስ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ጀመረ

**embarrass**
1. አሳፈረ. The teacher's comments embarrassed the child. አስተማሪው ፡ የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ልጁን ፡ አሳፈረው
2. ቅር ፡ አሰኘ. You didn't embarrass me in the slightest. ምንም ፡ ቅር ፡ አላሰኘኸኝ
3. አሰናከለ. Lack of trucks embarrassed the army's movements. የመኪና ፡ እጦት ፡ የወታደሩን ፡ እንቅስቃሴ ፡ አሰናከለው
4. (= pass.) ተቸገረ. +Lack of money embarrassed him. በገንዘብ ፡ እጦት ፡ ተቸገረ

**be embarrassed** አፈረ
I was terribly embarrassed when my child insulted the teacher. ልጄ ፡ አስተማሪውን ፡ ሲሰድብ ፡ በጣም ፡ አፈርኩ

## embarrassing

1. አሳፋሪ. He persisted in asking embarrassing questions. አሳፋሪ ፡ ጥያቄዎች ፡ መጠየቁን ፡ ቀጠለ
2. የሚያስጨንቅ. It was an embarrassing situation. የሚያስጨንቅ ፡ ሁኔታ ፡ ነበር

## embarrassment እጥረት

His financial embarrassment kept him from buying a share of the company. የገንዘብ ፡ እጥረት ፡ የኩባንያውን ፡ አክሲዮን ፡ እንዳይገዛ ፡ አደረገው

**to one's embarrassment**
*To my embarrassment, I spilled my coffee. ቡናው ፡ ሲፈስብኝ ፡ አፈርኩ

## embassy ኤምባሲ

Where is the American embassy? የአሜሪካን ፡ ኤምባሲ ፡ የት ፡ ነው ?

## embattled የተመሸገ

The Suez Canal has become an embattled frontier. የስዌዝ ፡ ቦይ ፡ ወሰኑ ፡ የተመሸገ ፡ ሆኗል

## embed (embedded)

1. ገነባ. The mason embedded the tiles in cement. ግንበኛው ፡ ጡቡን ፡ በሲሚንቶ ፡ ገነባው
2. ተከለ. He embedded the spear in the ground. ጦሩን ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ተከለ

## embellish

1. አስጌጠ ፤ አሳመረ. She embellished her dress with a golden belt. ቀሚሷን ፡ ወርቅማ ፡ በሆነ ፡ ቀበቶ ፡ አስጌጠችው ፡ (አሳመረችው)
2. ቀባባ. He embellished the story with interesting details. ታሪኩን ፡ በሚያስደስቱ ፡ ዝርዝሮች ፡ ቀባባው

## embers ፍም

The fire has not completely gone out. Some embers are still left. እሳቱ ፡ ፈጽሞ ፡ አልጠፋም ፤ የቀረ ፡ ፍም ፡ አለ

## embezzle አጭበረበረ

The bank clerk embezzled ten thousand dollars from his bank. የባንኩ ፡ ጸሐፊ ፡ ከባንኩ ፡ ዐሥር ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ አጭበረበረ

## embezzler አደራ ፡ በሊታ ፤ አጭበርባሪ

His association with the embezzler blemished his reputation. ከአደራ ፡ በሊታው ፡ (ከአጭበርባሪው) ፡ ጋር ፡ መዋሉ ፡ ዝናውን ፡ አጉደፈው

## embitter

1. አመረረ. The expulsion from the club embittered him greatly. ከክበቡ ፡ መውጣቱ ፡ ብዙ ፡ አመረረው
2. አሳዘነ. The death of her only son embittered the woman. ያንድ ፡ ልጅዋ ፡ መሞት ፡ ሴትዮዋን ፡ አሳዘናት

**embitter against** አስጠላ
The divorce embittered him against all women. ፍቺው ፡ ሴቶችን ፡ ሁሉ ፡ አስጠላው

**be embittered** ተመረረ
The old man was embittered by the loss of all his money. ሽማግሌው ፡ በገንዘቡ ፡ መጥፋት ፡ ተመረረ

## emblem

1. ምሳሌ. The dove is an emblem of peace. እርግብ ፡ የሰላም ፡ ምሳሌ ፡ ነች
2. አርማ. The emblem of the school is a lion. የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አርማ ፡ አንበሳ ፡ ነው

## embodiment አርአያ

He is the embodiment of generosity. የለጋስነት ፡ አርአያ ፡ ነው

## embody (embodied)

1. ያዘ. This book embodies all the necessary information. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ተፈላጊ ፡ መረጃዎችን ፡ ሁሉ ፡ የያዘ ፡ ነው
2. አለ(ው). The latest cars embody many new features. በቅርቡ ፡ የወጡ ፡ መኪናዎች ፡ ብዙ ፡ አዳዲስ ፡ ነገሮች ፡ አሉዋቸው
3. ገለጸ. The sculptor embodies an idea in marble. ቅርጽ ፡ ሠሪው ፡ ሐሳቡን ፡ በእብነ ፡ በረድ ፡ አማካይነት ፡ ይገልጻል
*The Constitution embodies Jefferson's ideas on government. ጀፈርሰን ፡ ስለ ፡ መንግሥቱ ፡ የነበረው ፡ ሐሳብ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ሰፍሯል
*The Emperor embodies the nation in his person. ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ማለት ፡ ሀገር ፡ ነው

## embolden አደፋፈረ

The cheers emboldened the boxer. ጭብጨባው ፡ ቡጢኛውን ፡ አደፋፈረው

## embrace

1. አቀፈ. The father embraced his child before going to work. አባትዬው ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ ልጁን ፡ አቀፈ

2. ያዘ. Biology embraces botany and zoology. ባዮሎጂ ፣ የዕፀዋትና ፣ የእንስሳት ፣ ጥናትን ፣ ይይዛል
3. ተጠቀመ(በት). She embraced the chance to make a trip to Europe. ወደ ፣ አውሮፓ ፣ ለመጓዝ ፣ ያጋጠማትን ፣ ዕድል ፣ ተጠቀመችበት
4. ተቀበለ. Ethiopia embraced Christianity in the fourth century. ኢትዮጵያ ፣ ባራተኛው ፣ ክፍለ ፣ ዘመን ፣ የክርስትናን ፣ ሃይማኖት ፣ ተቀበለች
5. በደስታ ፣ ተቀበለ. The farmers embraced the idea of cooperative work. ገበሬዎቹ ፣ የኅብረትን ፣ ሥራ ፣ በደስታ ፣ ተቀበሉት

**embrace** (reciprocal) ተቃቀፉ
The two girls embraced. ሁለቱ ፣ ልጃገረዶች ፣ ተቃቀፉ

## embroider
1. ጠለፈ. She embroidered his name on a handkerchief. ስሙን ፣ በመሐረብ ፣ ላይ ፣ ጠለፈች
2. ቀባባ. He embroiders the story of his arrest every time he tells it. ስለ ፣ መያዙ ፣ ባወራ ፣ ቁጥር ፣ ይቀባባዋል

## embroidery ጥልፍ
Embroidery costs more than plain cloth. ጥልፍ ፣ ከልሙጥ ፣ ጨርቅ ፣ ይልቅ ፣ ይወደዳል

## embroil ጣለ ፤ አስገባ
The tax question embroiled the country in a civil war. የግብር ፣ ጉዳይ ፣ አገሪቷን ፣ እርስ ፣ በርስ ፣ ጦርነት ፣ ውስጥ ፣ ጣላት
His pride embroiled him in squabbles. ኩራቱ ፣ ከጥቃቅን ፣ ጭቅጭቅ ፣ አስገባው

## embryo ሽል
The embryo grows inside the uterus. ሽል ፣ የሚያድገው ፣ በማኅፀን ፣ ውስጥ ፣ ነው

## emend እንዲስማማ ፣ አድርጎ ፣ አሻሻለ
He emended the text for the students. ለተማሪዎቹ ፣ የመማሪያውን ፣ መጽሐፍ ፣ እንዲስማማ ፣ አድርጎ ፣ አሻሻለ

## emerald [ብሩህ ፣ አረንጓዴ ፣ በጣም ፣ ውድ ፣ የሆነ ፣ ድንጋይ]

## emerge
1. ብቅ ፣ አለ. The moon emerged from behind the clouds. ጨረቃዋ ፣ ከደመናው ፣ በስተኋላ ፣ ብቅ ፣ አለች
2. ተገለጸ. The facts emerged slowly. እውነቱ ፣ እያደር ፣ ተገለጸ
3. ቀረበ. No new ideas emerged during the talks. በንግግሩ ፣ ጊዜ ፣ ምንም ፣ አዲስ ፣ አሳብ ፣ አልቀረበም

## emergency (emergencies), n.
1. አስቸኳይ ፣ ጊዜ. Do you think he could act quickly in an emergency? ባስቸኳይ ፣ ጊዜ ፣ ፈጥኖ ፣ እርምጃ ፣ የሚወስድ ፣ ይመስልሃል ?
2. አስቸኳይ ፣ ሁኔታ. The present emergency overrides other matters. ያሁኑ ፣ አስቸኳይ ፣ ሁኔታ ፣ ከሌሎቹ ፣ ጉዳዮች ፣ ሁሉ ፣ ይበልጣል
3. ድንገተኛ ፣ ምክንያት. The doctor was called away on an emergency. ሐኪሙ ፣ በድንገተኛ ፣ ምክንያት ፣ ተጠርቶ ፣ ሄደ
4. ድንገተኛ ፣ አደጋ. I keep a first aid kit in my car for use in an emergency. ለድንገተኛ ፣ አደጋ ፣ እንዲሆን ፣ በማለት ፣ የመጀመሪያ ፣ እርዳታ ፣ መድኃኒት ፣ መኪናዬ ፣ ውስጥ ፣ አስቀምጣለሁ

**in case of emergency** ድንገተኛ ፣ አደጋ ፣ ቢደርስ
In case of emergency, call the doctor. ድንገተኛ ፣ አደጋ ፣ ቢደርስ ፣ ሐኪሙን ፣ ጥራ

**state of emergency** አስቸኳይ ፣ ጊዜ
The Emperor proclaimed a state of emergency. ንጉሠ ፣ ነገሥቱ ፣ ያስቸኳይ ፣ ጊዜ ፣ ዐዋጅ ፣ ዐወጁ

**emergency** (adj.)
1. ያደጋ. Pull the emergency brake! ያደጋ ፣ ፍሬን ፣ ሳብ
2. ላደጋ ፣ ጊዜ ፣ የሚሆን. The theater has no emergency exit. ቲያትር ፣ ቤቱ ፣ ላደጋ ፣ ጊዜ ፣ የሚሆን ፣ መውጫ ፣ የለውም
3. የሚያስቸኩል. He put the emergency plan into execution. የሚያስቸኩለውን ፣ እቅድ ፣ በሥራ ፣ ላይ ፣ አዋለው
4. ድንገተኛ. This fund is intended for emergency use only. ይህ ፣ ገንዘብ ፣ ለድንገተኛ ፣ ወጪ ፣ ብቻ ፣ የተመደበ ፣ ነው

## emigrant አገሩን ፣ ትቶ ፣ የሚሄድ ፣ ሰው
Each emigrant must obtain an exit permit. አገሩን ፣ ትቶ ፣ የሚሄድ ፣ ሰው ፣ የይለፍ ፣ ወረቀት ፣ ማግኘት ፣ አለበት

## emigrate ተሰደደ
In recent years many people have emigrated from Europe. በቅርብ ፣ ዓመታት ፣ ብዙ ፣ ሰዎች ፣ ከአውሮፓ ፣ ተሰደዋል
Many people emigrated recently to Australia. በቅርቡ ፣ ብዙ ፣ ሰዎች ፣ ወደ ፣ አውስትራሊያ ፣ ተሰደዱ

## eminence
1. (የ)ከፍታ ፣ ቦታ. We viewed the city from an

eminence across the river. ከወንዙ ፡ ባሻገር ፡ ባለ ፡ ከፍታ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሆነን ፡ ከተማውን ፡ ተመለከትን
2. ልቀት. He achieved eminence in the medical profession. በሕክምና ፡ ሙያ ፡ ልቀት ፡ አገኘ

**eminent**
1. ዝነኛ. Henry was an eminent writer. ሄንሪ ፡ ዝነኛ ፡ ደራሲ ፡ ነበር
2. የላቀ. Washington was eminent both as a general and as a President. ዋሽንግተን ፡ በጄኔራልነቱም ፡ ሆነ ፡ በፕሬዚዳንትነቱ ፡ የላቀ ፡ ነበር
3. ከፍ ፡ ያለ. The general rendered eminent services to his country. ጄኔራሉ ፡ ላገሩ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አገልግሎት ፡ ፈጸመ

**emissary** (emissaries) መልእክተኛ
The Emperor sent emissaries to various foreign countries. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የውጭ ፡ አገሮች ፡ መልእክተኞች ፡ ላኩ

**emit** (emitted)
1. አሰራጨ. The sun emits light and heat. ፀሐይ ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀት ፡ ታሰራጫለች
2. ለቀቀ. The child emitted a loud scream. ሕፃኑ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጩኸት ፡ ለቀቀ
3. ተፋ. A volcano emits smoke and ashes. እሳተ ፡ ገሞራ ፡ ጢስና ፡ አመድ ፡ ይተፋል

**emotion** ስሜት ፤ ትልቅ ፡ ስሜት
He couldn't hide his emotion. ስሜቱን ፡ ሊደብቅ ፡ አልቻለም
Her voice shook with emotion. ከትልቅ ፡ ስሜት ፡ የተነሣ ፡ ድምጿ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ ይል ፡ ነበር

**emotional**
1. ስሜትን ፡ የሚቀሰቅስ ፤ ስሜትን ፡ የሚነካ. The Emperor made an emotional appeal to his nation. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ስሜትን ፡ የሚቀሰቅስ ፡ (የሚነካ) ፡ ንግግር ፡ ለሕዝባቸው ፡ አደረጉ
2. በስሜት ፡ ተገፋፍቶ ፡ የተደረገ. An emotional decision is often a wrong decision. በስሜት ፡ ተገፋፍቶ ፡ የተደረገ ፡ ውሳኔ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የተሳሳተ ፡ ውሳኔ ፡ ነው
3. ርኅሩኅ. Emotional people are likely to cry if they hear sad stories. ርኅሩኅ ፡ ሰዎች ፡ የሚያሳዝን ፡ ወሬ ፡ ሲሰሙ ፡ ሳያለቅሱ ፡ አይቀሩም
4. ሆደ ፡ ባሻ. She is an emotional woman, easily upset by any disturbance. ሆደ ፡ ባሻ ፡ ሴት ፡ ናት ፤ በቀላሉ ፡ ትበሳጫለች

**empathy**
*He listened to his friend's worries with empathy. የጓደኛውን ፡ ችግር ፡ እንደራሱ ፡ አድርጎ ፡ አዳመጠ

**emperor** ንጉሠ ፡ ነገሥት
The emperor hands out degrees at every graduation. በተማሪዎች ፡ ምረቃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዲግሪ ፡ ይሰጣሉ
The emperor of Japan is a marine scientist. የጃፓን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የባሕር ፡ ሊቅ ፡ ናቸው

**emphasis** ሥረ ፡ ነገር
Morality was the emphasis of his speech. ግብረ ፡ ገብነት ፡ የንግግሩ ፡ ሥረ ፡ ነገር ፡ ነበር
**lay emphasis, put emphasis** አጠበቀ
Some schools lay special emphasis on language study. አንዳንድ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የቋንቋን ፡ ትምህርት ፡ ያጠብቃሉ
In reading, our teacher puts emphasis upon the important words. አስተማሪያችን ፡ ሲያነብ ፡ ዋና ፡ ዋናውን ፡ የሆኑት ፡ ቃላት ፡ ያጠብቃል

**emphasize**
1. አጥብቆ ፡ ተናገረ ፤ በጣም ፡ አሳሰበ. He emphasized the importance of careful driving. በጥንቃቄ ፡ ስለ ፡ መንዳት ፡ አስፈላጊነት ፡ አጥብቆ ፡ ተናገረ
The great number of accidents emphasizes the need for careful driving. ያደጋዎች ፡ በጣም ፡ መብዛት ፡ በጥንቃቄ ፡ የመንዳትን ፡ አስፈላጊነት ፡ በጣም ፡ ያሳስባል
2. አጐላ. His new tie emphasized the age of his shirt. አዲሱ ፡ ክራቫት ፡ የሸሚዙን ፡ አሮጌና ፡ አጐላ
3. አጋነነ. He emphasized the word by saying it very loudly. በጣም ፡ ጮኾ ፡ በመናገር ፡ ቃሉን ፡ አጋነነው

**emphatic**
1. የጐላ. Did you notice the emphatic contrast between black and white? በጥቁርና ፡ በነጭ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የጐላ ፡ ልዩነት ፡ አየህ ?
2. (= adv.) በማጋነን. His emphatic reply showed his determination. በማጋነን ፡ የሰጠው ፡ መልስ ፡ ቁራጥነቱን ፡ አሳየ

**emphatically** አጥብቆ
I will have to deny that emphatically. ያንን ፡ አጥብቄ ፡ መቃወም ፡ አለብኝ

**empire**
1. የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት. England is the center of an empire. የእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ያንድ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ እምብርት ፡ ነው
2. ግዛት. The Roman empire stretched over continents. የሮም ፡ ግዛት ፡ በአህጉራት ፡ ላይ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ነበር

3. ከፍ ፡ ያለ ፡ ሀብት. He built an oil empire for himself and his sons. ለራሱና ፡ ለልጆቹ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የዘይት ፡ ሀብት ፡ አከማቸ

**employ**
1. ቀጠረ. This factory employs a thousand workers. ይህ ፡ ፋብሪካ ፡ ሺህ ፡ ሠራተኞች ፡ ቀጥሯል
2. በ - - ተገለገለ. You employ a knife, fork and spoon in eating. ስትበላ ፡ በቢላዋ ፡ በሹካና ፡ በማንኪያ ፡ ትገለገላለህ

**be employed** ሠራ
Where are you employed? የት ፡ ትሠራለህ ?

**employee** ሠራተኛ
The employees object to long working hours. ሠራተኞቹ ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ መሥራትን ፡ ይቃወማሉ

**employer** አሠሪ ፤ ቀጣሪ
The employer refused to acknowledge the union. አሠሪው ፡ የሠራተኞቹን ፡ ማኅበር ፡ አላውቅም ፡ አለ
He takes great pains to please his employer. ቀጣሪውን ፡ ለማስደሰት ፡ ብዙ ፡ ይጨነቃል

**employment**
1. ሥራ. What kind of employment did you finally get? በመጨረሻ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ አገኘህ ?
2. መቅጠር. He was busy with the employment of new help. አዲስ ፡ ሠራተኞችን ፡ በመቅጠር ፡ ተጠምዶ ፡ ነበር
*Full employment keeps a country prosperous. ሁሉ ፡ ሰው ፡ ሲሠራ ፡ አገር ፡ ትበለጽጋለች

**employment agency** ያስቀጣሪ ፡ ድርጅት
Employment agencies help workers find jobs. ያስቀጣሪ ፡ ድርጅቶች ፡ ሠራተኞች ፡ ሥራ ፡ እንዲያገኙ ፡ ይረዳሉ

**out of employment** ሥራ ፡ ፈት
These men are out of employment. እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ናቸው

**empower** ሥልጣን ፡ ሰጠ
The boss empowered the secretary to sign certain papers. አለቃው ፡ አንዳንድ ፡ ሰነዶችን ፡ የመፈረም ፡ ሥልጣን ፡ ለጸሐፊው ፡ ሰጠ

**empress**
1. እቴጌ. Empress Menen visited the church. እቴጌ ፡ መነን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ጐበኙ
2. ንግሥተ ፡ ነገሥታት. Empress Zawditu preceded Haile Sellassie on the throne. ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ የነገሡት ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በፊት ፡ ነው

**empty** (emptied), vt.
1. አጋባ. Please empty this tank! ይህን ፡ በርሜል ፡ አጋባው
2. ገለበጠ. The maid emptied the water out of the bucket. ገረዲቱ ፡ ከባልዲው ፡ ውስጥ ፡ ውኃውን ፡ ገለበጠች
3. አፈሰሰ. Empty the coffee grounds in a garbage pail! ቆሻሻ ፡ ማጠራቀሚያው ፡ ባልዲ ፡ ውስጥ ፡ የቡናውን ፡ አተላ ፡ አፍሰው
4. ደፋ. The wastepaper basket is full; take it out and empty it! የቆሻሻ ፡ ወረቀት ፡ ማጠራቀሚያው ፡ ቅርጫት ፡ ስለሞላ ፡ አውጥተህ ፡ ድፋው
5. ጨለጠ. He emptied a glass of milk in one gulp. አንዱን ፡ ብርጭቆ ፡ ወተት ፡ ባንድ ፡ ትንፋሽ ፡ ጨለጠው

**empty** (vi.)
1. ባዶ ፡ ሆነ. The hall emptied in five minutes. አዳራሹ ፡ ባምስት ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ባዶ ፡ ሆነ
2. ፈሰሰ. This river empties into the ocean. ይህ ፡ ወንዝ ፡ ወደ ፡ ውቅያኖስ ፡ ይፈሳል

**be emptied** ባዶ ፡ ቀረ
The hall was emptied in ten minutes. አዳራሹ ፡ በዐሥር ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ባዶ ፡ ቀረ

**empty** (adj.)
1. ባዶ. Do you have an empty box? ባዶ ፡ ሣጥን ፡ አለህ ?
I wouldn't drink on an empty stomach. በባዶ ፡ ሆዴ ፡ አልጠጣም
2. ትርጉም ፡ የሌለው. These are empty words. እነዚህ ፡ ትርጉም ፡ የሌላቸው ፡ ቃላት ፡ ናቸው
3. ጭር ፡ ያለ. We walked along the empty streets of the city at night. ሌሊት ፡ ጭር ፡ ባሉት ፡ የከተማው ፡ መንገዶች ፡ ላይ ፡ ተዘዋወርን

**empty-handed**
1. ባዶ ፡ እጁን. I sent the servant to the market, but he came back empty-handed. አሽከሩን ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ብልከው ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ ተመለሰ
2. ሳይቀናው. The ambassador came back from his mission empty-handed. አምባሳደሩ ፡ ከተላከበት ፡ ሳይቀናው ፡ ተመለሰ

**emulate**
1. መሰለ. The proverb tells us to emulate the industry of the ant. ምሳሌው ፡ በትጋት ፡ ጉንዳንን ፡ እንድንመስል ፡ ይነግረናል
2. ተወዳደረ. The artists of New York now emulate those of Paris in achievement. የኒው ፡ ዮርክ ፡ አርቲስቶች ፡ ባሁን ፡ ጊዜ ፡ የፓሪሶቹን ፡ ይወዳደራሉ

**enable** አስቻለ

Resilience enabled him to leave the hospital in a week. በቶሎ ፡ መዳኑ ፡ ከሆስፒታል ፡ ባንድ ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ለመውጣት ፡ አስቻለው

**be enabled** ቻለ

When the workers came back, the company was enabled to resume bus service. ሠራተኞቹ ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ ኩባንያው ፡ የአውቶቡስ ፡ አገልግሎቱን ፡ ሊቀጥል ፡ ቻለ

**enable to get** አዋለ

This experience should enable you to get a good position. ይህ ፡ የሥራ ፡ ልምምድ ፡ ደኅና ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ያውልሃል

**enact**

1. አሳለፈ. Congress enacted a bill to lower tariffs. ምክር ፡ ቤቱ ፡ ቀረጥን ፡ ለመቀነስ ፡ የቀረበውን ፡ ሕግ ፡ አሳለፈ

2. በቲያትሩ ፡ ውስጥ ፡ ሠራ. He enacted the part of a judge. በቲያትሩ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ ሠራ

**(be) enamored** ተነደፈ

The prince was enamored of her beauty. ልዑሉ ፡ በውበቷ ፡ ተነደፈ

**become enamored** ወደደ

This is the young lady with whom he became enamored. የወደዳት ፡ ወጣት ፡ ይህች ፡ ናት

**encamp** ሰፈረ

The army encamped in the valley. ጦሩ ፡ ሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ሰፈረ

**enchant**

1. በጣም ፡ አስደሰተ. Her voice enchanted us. ድምጿ ፡ በጣም ፡ አስደሰተን

2. በአስማት ፡ ተበተበ. The witch enchanted the prince. ጠንቋይዋ ፡ ልዑሉን ፡ በአስማት ፡ ተበተበችው

**be enchanted** በደስታ ፡ ተዋጠ

She was enchanted with the flowers he sent her. በላከላት ፡ አበባ ፡ በደስታ ፡ ተዋጠች

**enchantment** የሚማርክ ፡ ውበት

The moon gave a certain enchantment to the place. ጨረቃዋ ፡ ለቦታው ፡ የሚማርክ ፡ ውበት ፡ ሰጠችው

**enchantress** አስማተኛ

The enchantress held the prince in thrall. አስማተኛዋ ፡ ልዑሉን ፡ አገልጋይዋ ፡ አደረገችው

**encircle**

1. ከበበ. The enemy encircled our troops. ጠላት ፡ ወታደሮቻችንን ፡ ከበበ

2. ዞረ. The earth encircles the sun. መሬት ፡ ፀሐይን ፡ ትዞራለች

**enclose**

1. አያይዞ ፡ ላከ. I enclosed the newspaper clipping you wanted. የፈለግኸውን ፡ ጽሑፍ ፡ ከጋዜጣ ፡ ቀድጄ ፡ አያይዤ ፡ ልኬልሃለሁ

2. ጨመረ. Don't seal the envelope yet. I have a letter to enclose. የምጨምረው ፡ ደብዳቤ ፡ ስላለኝ ፡ አምቦልኩን ፡ አታሽገው

3. ሸፈነ. We enclosed the baby's crib with mosquito netting. የሕፃኑን ፡ አልጋ ፡ በወባ ፡ ትንኝ ፡ መከላከያ ፡ መረብ ፡ ሸፈነው

4. አጠረ. He had to enclose his garden with a wall to keep goats out. ፍየሎች ፡ እንዳይገቡ ፡ ያትክልት ፡ ቦታውን ፡ በግምብ ፡ ማጠር ፡ ግድ ፡ ሆነበት

**enclosed** (adj.) ተያይዞ ፡ የሚገኝ

Enclosed is the sum still due you. ተያይዞ ፡ የሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያልተከፈለህ ፡ ነው

**be enclosed** ተከበበ

The valley is enclosed by high mountains. ሸለቆው ፡ በረጃጅም ፡ ተራራዎች ፡ ተከቧል

**enclosure**

1. ከልል. There are many sheep in the enclosure. በከልሉ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ በጎች ፡ አሉ

2. ማጐሪያ. Those cages are enclosures for the monkeys. የሽቦው ፡ ቤቶች ፡ ለዝንጀሮዎቹ ፡ ማጐሪያ ፡ ናቸው

3. ጉረኖ. Keep the ram in the enclosure! በጉን ፡ እጉረኖው ፡ አስገባው

4. (= to enclose) ማጠር. The enclosure of the yard with a high fence costs a lot of money. ግቢውን ፡ በረጅም ፡ አጥር ፡ ማጠር ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ይጠይቃል

5. አባሪ. The enclosure that was said to be in the letter was not there. ከደብዳቤው ፡ ጋር ፡ አለ ፡ የተባለው ፡ አባሪ ፡ አልተገኘም

**encompass**

1. ከበበ. The atmosphere encompasses the earth. ህዋው ፡ መሬትን ፡ ይከባታል

2. አጠቃለለ. His education encompasses many branches of knowledge. የሱ ፡ ትምህርት ፡ ብዙ ፡ የዕውቀት ፡ ቅርንጫፎችን ፡ ያጠቃልላል

**encounter** (v.)

1. አጋጠመ(ው). +On my trip, I encountered many difficulties. በጉዞዬ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ አጋጠመኝ

I encountered an old friend on the train. የድሮ ፡ ጓደኛዬን ፡ ባቡር ፡ ላይ ፡ አጋጠመኝ
2. ተጋጠመ. We will encounter the enemy at dawn. ጠላትን ፡ ጎሕ ፡ ሲቀድ ፡ እንጋጠመዋለን

**encounter each other** ተገጣጠመ
The two enemies encountered each other in the street. ሁለቱ ፡ ጥለኞች ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተገጣጠሙ

**encounter** (n.)
1. ግጭት. In the encounter at Gura, the Egyptians suffered heavy losses. በጉራ ፡ ግጭት ፡ ላይ ፡ ግብጾች ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ደረሰባቸው
2. መገናኘት. The encounter of the Emperor and the Egyptian president was cordial. የንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ የግብጽ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ መገናኘት ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ ነበር
3. በድንገት ፡ ማግኘት. Our encounter with the famous actor was exciting. የታወቀውን ፡ ተዋናይ ፡ በድንገት ፡ ማግኘታችን ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነበር

**encourage**
1. አደፋፈረ. She encouraged the child to take the bitter medicine. ልጁ ፡ መራራውን ፡ መድኃኒት ፡ እንዲጠጣ ፡ አደፋፈረችው
2. እንዲሆን ፡ አደረገው. His lenient attitude encourages the children to be disrespectful. የሚያሳየው ፡ ልልነት ፡ ልጆቹ ፡ ባለጌ ፡ እንዲሆኑ ፡ ያደርጋቸዋል

**encouragement**
1. ማበረታታት. He gave money for the encouragement of research. የምርምር ፡ ጥናትን ፡ ለማበረታታት ፡ ገንዘብ ፡ ሰጠ
2. ማደፋፈር. Constant encouragement helped the crippled child to walk again. ያልተቋጠበ ፡ ማደፋፈር ፡ ሽባው ፡ ልጅ ፡ እንደገና ፡ እንዲራመድ ፡ ረዳው

**encouraging** የሚያበረታታ
I have heard very encouraging news today. ዛሬ ፡ በጣም ፡ የሚያበረታታ ፡ ወሬ ፡ ሰማሁ

**encroach, ~ upon**
1. ጥሶ ፡ ገባ. The enemy encroached upon our border. ጠላት ፡ ወሰናችንን ፡ ጥሶ ፡ ገባ
2. ገፋ. The flooding river encroached on the land. የሞላው ፡ ወንዝ ፡ ወደ ፡ መሬቱ ፡ ገፋ

**encumber**
1. አስቸገረ. The girl's tight skirt encumbered her when she tried to run. ልጅቷ ፡ ለመሮጥ ፡ ስትሞክር ፡ ጠባብ ፡ ጉርደ ፡ አስቸገራት
2. ዕንቅፋት ፡ ሆነ. Rubbish and old boxes encumbered the stairway. ደረጃው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ቆሻሻና ፡ አሮጌ ፡ ሣጥን ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆነ

**be encumbered**
1. ተጫነ. She was encumbered with a valise and several packages. ሻንጣና ፡ ሌሎችም ፡ ብዙ ፡ ጥቅሎች ፡ ተጭና ፡ ነበር
2. ተያዘ. The estate is encumbered with mortgages. ርስቱ ፡ በመያዣነት ፡ ተይዟል

**encumbrance**
1. ችግር. I wish I were clear of that encumbrance. ከዚያ ፡ ችግር ፡ ብገላገል ፡ እወድ ፡ ነበር
2. ዕንቅፋት. Too much luggage is an encumbrance. በጣም ፡ ብዙ ፡ ጓዝ ፡ ዕንቅፋት ፡ ነው

**encyclopaedia** ዓውደ ፡ ጥበብ
The names of many great men are found in the encyclopaedia. የብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ በዐውደ ፡ ጥበብ ፡ ውስጥ ፡ ሰፍሯል

**end** (vt.)
1. ደመደመ ፤ መደምደሚያ ፡ ነው. He ended his story with a proverb. ታሪኩን ፡ በምሳሌ ፡ ደመደመው
This quotation ends the novel. ይህ ፡ ጥቅስ ፡ የመጽሐፉ ፡ መደምደሚያ ፡ ነው
2. ከፍጻሜ ፡ አደረሰ. This was the battle that ended the war. ጦርነቱን ፡ ከፍጻሜ ፡ ያደረሰው ፡ ውጊያ ፡ ይህ ፡ ነው
3. አቆመ. Let us end this fight! ይህን ፡ ጠብ ፡ እናቁም

**end** (vi.) አለቀ ፤ ተፈጸመ
Won't this gossip ever end? ይህ ፡ አሉባልታ ፡ ዘለዓለም ፡ አያልቅም ?
Their insecure partnership ended in a quarrel. የማያስተማምን ፡ ሽርክናቸው ፡ በጠብ ፡ ተፈጸመ
*That won't end well. ይህ ፡ መጨረሻው ፡ አያምርም
*The plan ended in failure. ውጥኑ ፡ ሳይሳካ ፡ ቀረ

**end up**
*If you continue to steal, you will end up in prison. መስረቅህን ፡ ከቀጠልክ ፡ መጨረሻህ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ይሆናል

**be ended**
1. ከተመ. The fledgling democratic movement was ended by the war. ያልጠናው ፡ የዴሞክራሲ ፡ ንቅናቄ ፡ በጦርነት ፡ ከተመ
2. ተደመሰሰ. Piracy was ended by the king's navy. የባሕር ፡ ላይ ፡ ዝርፊያ ፡ በንጉሡ ፡ የባሕር ፡ ኃይል ፡ ተደመሰሰ
[See also 'failure']

**end** (n.)
1. መጨረሻ. To whom does the house at the end of the street belong? ከመንገዱ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ቤት ፡ የማን ፡ ነው ?
I'll pay you the balance at the end of the month. በወሩ ፡ መጨረሻ ፡ ቀሪውን ፡ እከፍልሃለሁ
2. ማብቂያ. The demise of ancient Rome did not mean the end of the Latin language. የሮም ፡ መጥፋት ፡ የላቲን ፡ ቋንቋ ፡ ማብቂያ ፡ አልነበረም
3. ማለቂያ. The Olympic runner showed signs of distress toward the end of the race. እውድድሩ ፡ ማለቂያ ፡ ላይ ፡ የኦሊምፒክ ፡ ሯጭ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የድካም ፡ ምልክት ፡ ታየበት
4. ፍጻሜ. The robber was jailed for life and that was the end of him. ቀማኛው ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ተፈረደበትና ፡ ፍጻሜው ፡ ሆነ
5. መጥፊያ ፤ ፍጻሜ. Another war would be the end of civilization. ሌላ ፡ ጦርነት ፡ ቢመጣ ፡ የሥልጣኔ ፡ መጥፊያ ፡ (ፍጻሜ) ፡ ይሆናል
6. ጫፍ. Tie the two ends together! ሁለቱን ፡ ጫፍ ፡ አንድነት ፡ እሰር
Put the glass at the end of the table! ብርጭቆውን ፡ ጠረጴዛው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ አስቀምጥ
Place the tables end to end! ጠረጴዛዎቹን ፡ ጫፍ ፡ ለጫፍ ፡ አጋጥማቸው
7. የዘወትር ፡ ሐሳብ. He has this end in mind : to do his work without a mistake. ሥራውን ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ ለመሥራት ፡ የዘወትር ፡ ሐሳቡ ፡ ነው
8. ዋና ፡ ግብ. His family's happiness was the end for which he worked. የሥራው ፡ ዓላማ ፡ ዋና ፡ ግቡ ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ ማስደሰት ፡ ነበር
9. ተግባር. We should direct our efforts to useful ends. ጥረታችንን ፡ ሁሉ ፡ ለመልካም ፡ ተግባር ፡ ማዋል ፡ አለብን
*He scolded her a bit and that was the end of it. ትንሽ ፡ ወቀሳትና ፡ በዚሁ ፡ አበቃ

**ends** አጽናፍ
His fame spread to the ends of the earth. ዝናው ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ አጽናፍ ፡ ደረሰ

**come to an end**
1. ተፈጸመ. The meeting came to an end at last. ስብሰባው ፡ በመጨረሻ ፡ ተፈጸመ
2. አበቃ. The dynasty came to an end as a result of the war. ሥርወ ፡ መንግሥቱ ፡ በጦርነት ፡ ምክንያት ፡ አበቃ

**for hours on end** ለረጅም ፡ ጊዜ
We stood in line for hours on end. ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ በሰልፍ ፡ ቆምን

**in the end** በመጨረሻ
In the end, he agreed to go along with us. በመጨረሻ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ሊሄድ ፡ ተስማ

**meet one's end** የሕይወቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ
He met his end in battle. በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ የሕይወቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ

**no end** ብዙ
A year in America will cost you no end of money. በአሜሪካ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለመኖር ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ያስፈልጋል

**(have) no end of** ማለቂያ ፡ አልነበረውም
+We had no end of trouble on the trip. በጉዞው ፡ ላይ ፡ ችግራችን ፡ ማለቂያ ፡ አልነበረውም

**put an end (to)**
1. አቆመ. Can't you put an end to these squabbles? ይህንን ፡ ጭቅጭቅ ፡ ልታቆም ፡ አትችልም ?
2. አስወገደ. We must put an end to corruption. ብልሽትን ፡ ማስወገድ ፡ አለብን
3. አስቀረ. We must put an end to war. ጦርነት ፡ ማስቀረት ፡ አለብን
4. አወደመ. A major war will probably put an end to civilization. ትልቅ ፡ ጦርነት ፡ ሥልጣኔን ፡ ሳያወድም ፡ አይቀርም
[See also 'bitter, extreme, far, mean, meet, odds, rope, stand, tail, very']

**endanger** አደጋ ፡ ላይ ፡ ጣለ
He endangered his life by careless driving. በግድ ፡ የለሽ ፡ አነዳድ ፡ ሕይወቱን ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ጣለ

**endear** ተወዳጅ ፡ አደረገ
Her kindness endeared her to all of us. ደግነቷ ፡ በሁላችን ፡ ዘንድ ፡ ተወዳጅ ፡ አደረጋት

**endeavor** (v.) ተጣጣረ
He endeavored to please his wife. ሚስቱን ፡ ለማስደሰት ፡ ተጣጣረ

**endeavor** (n.) መድከም
His endeavor to be elected was successful. ለመመረጥ ፡ መድከሙ ፡ መልካም ፡ ፍሬን ፡ አስገኘ

**make every endeavor** ሞከረ
Please make every endeavor to be early! በተቻለህ ፡ መጠን ፡ ቀደም ፡ ለማለት ፡ ሞክር

**ending** ፍጻሜ
The story has a happy ending. የታሪኩ ፡ ፍጻሜ ፡ የሚያስደስት ፡ ነው

**endless**
1. ማለቂያ ፡ የሌለው. Her story was endless. ታሪኳ ፡ ማለቂያ ፡ የሌለው ፡ ነበር

2. መጀመሪያና ፡ መጨረሻ ፡ የሌለው. A bicycle chain is an endless chain. የቢስክሌት ፡ ካቴና ፡ መጀመሪያና ፡ መጨረሻ ፡ የሌለው ፡ ነው

**endorse**

1. አጸደቀ. Congress endorsed the President's plans. ምክር ፡ ቤቱ ፡ የፕሬዚዳንቱን ፡ እቅድ ፡ አጸደቀ
2. ፈረመ. Please endorse the check! ቼኩን ፡ ፈርም
3. መደገፉን ፡ ገለጸ. The newspaper endorsed the candidate. ጋዜጣው ፡ እጩ ፡ ተወዳዳሪውን ፡ መደገፉን ፡ ገለጸ

**endorsement**

1. ድጋፍ. The mayor's endorsement helped the candidate win the election. የከንቲባው ፡ ድጋፍ ፡ ተወዳዳሪው ፡ ምርጫውን ፡ እንዲያሸንፍ ፡ ረዳው
2. ፊርማ. I can't read the endorsement of this check. የዚህን ፡ ቼክ ፡ ፊርማ ፡ ማንበብ ፡ አልችልም

**endow**

1. ዐደለ. Nature endowed her with both beauty and brains. ተፈጥሮ ፡ ውበትና ፡ አእምሮ ፡ ዐድሏታል
2. ችሮታ ፡ አደረገ. The rich man endowed the church he used to attend. ሀብታሙ ፡ ሰው ፡ ይሳለመው ፡ ለነበረው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ችሮታ ፡ አደረገ

**endowment** ስጦታ

The college received a large endowment from Mr. Jones. ኮሌጁ ፡ ከሚስተር ፡ ጆንስ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስጦታ ፡ አገኘ

**endurance**

1. ብርታት. He showed great endurance while in the desert. በምድረበዳው ፡ ውስጥ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ብርታት ፡ አሳየ
2. መቻል. His endurance of the pain was remarkable. የሕመሙን ፡ ሥቃይ ፡ መቻሉ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነበር
3. ድካምን ፡ መቻል ፤ ጥንካሬ. A runner needs endurance. ሯጭ ፡ ድካምን ፡ መቻል ፡ (ጥንካሬ) ፡ ያስፈልገዋል

**have endurance** ዘለቀ

His friendships have little endurance. ጓደኝነቱ ፡ ብዙ ፡ አይዘልቅም

**endure** (vt.) ተቋቋመ

It takes character to endure calumny. ሐሜትን ፡ ለመቋቋም ፡ መንፈስ ፡ ጠንካራነትን ፡ ይጠይቃል

**can endure** ቻለ

He can't endure severe cold. ኀይለኛ ፡ ብርድ ፡ አይችልም

**endure** (vi.)

1. ታገለ. If help doesn't come, we must endure to the end. እርዳታ ፡ ካልመጣ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ መታገል ፡ አለብን
2. ኖረ. Lincoln's name will endure forever. የሊንከልን ፡ ስም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል

**enemy** (enemies)

1. ጠላት. Even his enemies respected him. ጠላቶቹ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀሩ ፡ ያከብሩት ፡ ነበር
We attacked the enemy at dawn. ጐሕ ፡ ሲቀድ ፡ ጠላትን ፡ ወጋነው
2. አጥፊ. Frost is an enemy of flowers. ውርጭ ፡ ያበቦች ፡ አጥፊ ፡ ነው

**energetic**

1. ታታሪ. We need an energetic leader. ታታሪ ፡ መሪ ፡ ያስፈልገናል
2. ጥብቅ. The parliament took energetic measures against crime. ምክር ፡ ቤቱ ፡ ወንጀልን ፡ ለመከላከል ፡ ጥብቅ ፡ እርምጃ ፡ ወሰደ

**energy**

1. ጉልበት. He has an excess of energy. ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ጉልበት ፡ አለው
2. ኀይል. Electricity and heat are forms of energy. ኮረንቲና ፡ ሙቀት ፡ የኀይል ፡ ዓይነቶች ፡ ናቸው
*He's full of energy. ሁልጊዜ ፡ መንፈሱ ፡ ኀይለኛ ፡ ነው

**drain one's energy** አደከመ

The operation drained the doctor's energy. ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ማድረጉ ፡ ዶክተሩን ፡ አደከመው
[See also 'inexhaustible']

**enervating** አድካሚ

A hot climate is enervating. ሞቃት ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ አድካሚ ፡ ነው

**enfeeble** አደከመ

Sickness enfeebled him. በሽታ ፡ አደከመው

**enfold** ጠቀለለ

She enfolded the vase in cloth to keep it from breaking. ያበባ ፡ ማስቀመጫው ፡ እንዳይሰበር ፡ በጨርቅ ፡ ጠቀለለችው

**enfold in one's arms** አቀፈ

The mother enfolded her baby in her arms. እናትየዋ ፡ ሕፃኑን ፡ አቀፈችው

**be enfolded** ተሸፈነ

What happened is enfolded in mystery. የሆነው ፡ ነገር ፡ በምስጢር ፡ ተሸፍኗል

## enforce

1. አስከበረ. Policemen and judges enforce the laws. ፖሊሶችና ፡ ዳኞች ፡ ሕግ ፡ ያስከብራሉ
The teacher enforced silence. መምህሩ ፡ ጸጥታ ፡ አስከበረ
2. አጠነከረ. The speaker enforced his argument by adding details. ተናጋሪው ፡ ዝርዝር ፡ ሁኔታዎችን ፡ በመጨመር ፡ ንግግሩን ፡ አጠነከረ
3. ሠራ(በት). The judge enforced the letter of the law. ዳኛው ፡ ሕጉን ፡ እንደተጻፈው ፡ ሠራበት

**be enforced** በሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ

This law has never been strictly enforced. ይህ ፡ ሕግ ፡ በደንብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ውሎ ፡ አያውቅም

## engage (vt.)

1. ቀጠረ. We have just engaged a new maid. ገና ፡ አሁን ፡ አዲስ ፡ ገረድ ፡ ቀጠርን
We engaged him for two concerts. ሁለት ፡ ኮንሰርት ፡ እንዲሠራ ፡ ቀጠርነው
2. ያዘ. She engaged him in conversation. በወሬ ፡ ያዘችው
3. ገጠመ. Our soldiers engaged the enemy. ወታደሮቻችን ፡ ጠላትን ፡ ገጠሙት
4. ለጦርነት ፡ አሰማራ. They engaged five divisions of troops. አምስት ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ለጦርነት ፡ አሰማሩ
5. ወሰደ(በት). Tennis engaged all his spare time. ቴኒስ ፡ ትርፍ ፡ ጊዜውን ፡ ሁሉ ፡ ወሰደበት
6. ማረከ. The book engaged his attention and interest. መጽሐፉ ፡ ሐሳቡንና ፡ ፍላጎቱን ፡ ማረከው
7. ሳበ. I tried to engage his attention. እንዲመለከተኝ ፡ ሐሳቡን ፡ ለመሳብ ፡ ሞከርኩ
8. ቃል ፡ ገባ. They engaged to meet again in ten years. ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ እንገናኛለን ፡ ብለው ፡ ቃል ፡ ገቡ

**engage (vi.)**

1. ነከሰ. The gears engaged. ማርሾ ፡ ነከሰ
2. ተሰማራ. He engages in constructive activity. ጠቃሚ ፡ በሆኑ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ይሰማራል
3. ገጠመ. The armies engaged at once. ሰራዊቱ ፡ ያኔውኑ ፡ ገጠመ
4. ገባ. I don't engage in politics. እኔ ፡ በፖለቲካ ፡ ውስጥ ፡ አልገባም

**engage in** ያዘ

The two friends engaged in a long discussion. ሁለቱ ፡ ጓደኞች ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ጭውውት ፡ ያዙ

**engage oneself** ቃል ፡ ገባ

He engaged himself to pay the debt. ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ ቃል ፡ ገባ

**be engaged**

1. ተያዘ. My time is completely engaged. ጊዜዬ ፡ በሙሉ ፡ ተይዟል
The telephone is engaged. ስልኩ ፡ ተይዟል
2. አጨ. John is engaged to Mary, and Mary's sister is engaged to me. ዮሐንስ ፡ ሜሪን ፡ አጭቷል ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ የሜሪን ፡ እኅት ፡ አጭቻለሁ
3. ታጨች. My sister is engaged to a doctor. እኅቴ ፡ ለሐኪም ፡ ታጭታለች
4. ተዋጋ. Ten divisions are engaged. ዐሥር ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ በመዋጋት ፡ ላይ ፡ ነው

**be engaged (to one another)** ተጫጩ

How long have they been engaged? ከተጫጩ ፡ ስንት ፡ ጊዜያቸው ፡ ነው ?

**be engaged in**

1. ያዘ. He is engaged in the development of his business. ንግዱን ፡ ማስፋፋት ፡ ይዟል
2. በ + verbal noun + ላይ ፡ ነው. He is engaged in the organization of a new club. አዲስ ፡ ክበብ ፡ በመቋቋም ፡ ላይ ፡ ነው

## engagement

1. ቀጠሮ. I'm sorry, but I have a previous engagement. አዝናለሁ ፤ አስቀድሜ ፡ ቀጠሮ ፡ አድርጌያለሁ
2. መታጨት ፤ መተጫጨት. She announced her engagement. መታጨቷን ፡ አስታወቀች
Their engagement is off. መተጫጨታቸው ፡ ፈረሰ
3. ግጥሚያ. We have had two engagements with the enemy this week alone. በዚህ ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ከጠላት ፡ ጋር ፡ ሁለት ፡ ግጥሚያ ፡ አደረግን
4. የተቀጠረ. Her engagement at the theater will last five weeks. ቲያትሩ ፡ ቤት ፡ የተቀጠረችው ፡ ላምስት ፡ ሳምንት ፡ ነው

**break (one's) engagement**

She broke her engagement. ቀለበቷን ፡ መለሰች

**have an engagement** ተቀጠረ

The actor had a three weeks' engagement in a theater. ተዋናዩ ፡ በትያትሩ ፡ ቤት ፡ ለሦስት ፡ ሳምንት ፡ ተቀጥሮ ፡ ነበር

## engaging (n.), by ~ in በ --- ሥራ

He sought wealth by engaging in smuggling. በኮንትሮባንድ ፡ ሥራ ፡ ሀብት ፡ ለማግኘት ፡ ፈለገ

## engaging (adj.) የሚማርክ

She has an engaging smile. የሚማርክ ፡ ፈገግታ ፡ አላት

**engender**
1. ወለደ. He engendered a male child. ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደ
2. አስገኘ. Truthfulness engenders confidence. እውነተኛነት ፡ እምነትን ፡ ያስገኛል

**engine** ሞተር
You left the engine running. ሞተሩን ፡ ሳታጠፉ ፡ ተውከው

**engineer** (v.)
1. ፕላን ፡ አወጣ. He engineered several big industrial projects. የብዙ ፡ ትላልቅ ፡ ፋብሪካዎችን ፡ ፕላን ፡ አወጣ
2. አቀደ. He engineered the election campaign from start to finish. የምርጫውን ፡ ውድድር ፡ ከመጀመሪያው ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ አቀደ

**engineer** (n.)
1. መሃንዲስ. The engineer designed a beautiful bridge. መሃንዲሱ ፡ ጥሩ ፡ ድልድይ ፡ ነደፈ
2. ባቡር ፡ ነጂ. The engineer stopped the train. ባቡር ፡ ነጂው ፡ ባቡሩን ፡ አቆመው

**England** የእንግሊዝ ፡ አገር
England was the center of an empire. የእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ያንድ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ እምብርት ፡ ነረበች

**English**
1. እንግሊዝኛ. English is hard for foreigners to learn well. እንግሊዝኛን ፡ በሚገባ ፡ ለማወቅ ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. የእንግሊዝ. I bought an English bicycle. የእንግሊዝ ፡ ብስክሌት ፡ ገዛሁ

**the English** እንግሊዞች
The English are mercantile people. እንግሊዞች ፡ የንግድ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው

**Englishman** እንግሊዝ
Two Englishmen hired a taxi. ሁለት ፡ እንግሊዞች ፡ አንድ ፡ ታክሲ ፡ ተከራዩ

**engrave** ቀረጸ (ተቀረጸ)
They engraved his name on the tombstone. በመቃብሩ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ስሙን ፡ ቀረጹ
His mother's face was engraved on his memory. የእናቱ ፡ መልክ ፡ በአእምሮው ፡ ውስጥ ፡ ተቀርጿል

**engraved** (adj.) በድንጋይ ፡ ላይ ፡ የተቀረጸ
Many engraved inscriptions have been found at Axum. ብዙ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ የተቀረጹ ፡ ጽሑፎች ፡ አክሱም ፡ ውስጥ ፡ ተገኝተዋል

**engraving** (n.)
1. ቅርጽ. The engraving shows long-ago London. ቅርጹ ፡ የጥንት ፡ ሎንዶንን ፡ ያሳያል
2. መቅረጽ. Engraving on steel is difficult. በዐረብ ፡ ብረት ፡ ላይ ፡ መቅረጽ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**engross**
1. ማረከ. Their discussion engrossed his attention. ጨዋታቸው ፡ ስሜቱን ፡ ማረከው
2. (= be engrossed) ተመሰጠ. +His study engrosses him. በትምህርቱ ፡ ተመስጧል

**be engrossed** ተመሰጠ
He is engrossed in his work. በሥራው ፡ ተመስጧል

**engulf** ዋጠ
A wave engulfed the small boat. ሞገዱ ፡ ትንሿን ፡ ጀልባ ፡ ዋጣት

**enhance** ጨመረ(ለት)
The necklace enhanced her beauty. ሐብሉ ፡ ውበት ፡ ጨመረላት

**enigma** ምስጢር
His intentions remained an enigma. ሐሳቡ ፡ ምስጢር ፡ ሆኖ ፡ ቀረ

**enigmatic** ምስጢራዊ
His enigmatic actions make it difficult to predict what he will do next. ምስጢራዊ ፡ የሆነው ፡ አድራጎቱ ፡ ወደፊት ፡ የሚያደርገውን ፡ ነገር ፡ ለማወቅ ፡ ያስቸግራል

**enjoin**
1. ትእዛዝ ፡ ሰጠ. The court enjoined the defendant to pay his taxes. ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከሳሹ ፡ ግብሩን ፡ እንዲከፍል ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ
2. መከረ. Parents enjoin good behavior on their children. ወላጆች ፡ ልጆቻቸው ፡ ጥሩ ፡ ጠባይ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ይመክራሉ
3. አዘዘ. The doctor enjoined a strict diet. ሐኪሙ ፡ የተወሰነ ፡ ምግብ ፡ አዘዘ

**enjoin from** እንድ + negative imperfect + አገደ
The court enjoined the union from striking. ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ እንዳያቆም ፡ አገደ

**enjoy**
1. ደስ ፡ አለ(ው). +I enjoy his company. ከሱ ፡ ጋር ፡ መሆን ፡ ደስ ፡ ይለኛል
2. ወደደ. How did you enjoy the picture? ሲኒማውን ፡ ወደድከው ?
3. (= give joy) አስደሰተ. +Did you enjoy the swim? ዋናው ፡ አስደሰተህ ?

4. አገኘ. The couple enjoyed celestial happiness. ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ሰማያዊ ፡ ደስታን ፡ አገኙ
5. ተካፈለ. Winston Churchill enjoyed a checkered career. ዊንስተን ፡ ቸርችል ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራ ፡ ዘርፍ ፡ ተካፍለዋል
*He's enjoying excellent health. ጤንነቱ ፡ የተሟላ ፡ ነው

**enjoy life** ዓለሙን ፡ አየ ፤ ዓለሙን ፡ ቀጨ
He is rich, and enjoys life. ሀብታም ፡ ነው ፤ ዓለሙን ፡ ያያል ፡ (ይቀጫል)

**enjoyable** ደስ ፡ የሚያሰኝ ፤ አስደሳች
I spent an enjoyable evening with my friend. ከጓደኛዬ ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ምሽት ፡ አሳለፍኩ
A Sunday drive in the country is very enjoyable. እሑድ ፡ እሑድ ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ በመኪና ፡ መንሸራሸር ፡ አስደሳች ፡ ነው

**find enjoyable** ደስ ፡ አለ(ው)
+I find history more enjoyable than mathematics. ከቁጥር ፡ ይልቅ ፡ ታሪክ ፡ የበለጠ ፡ ደስ ፡ ይለኛል

**enjoyment** ደስታ
He finds enjoyment in reading. ከማንበብ ፡ ደስታን ፡ ያገኛል

**get enjoyment** (= give joy) አስደሰተ
Do you get much enjoyment out of that? እሱ ፡ ነገር ፡ ብዙ ፡ ያስደስትሃል ?

**have the enjoyment (of)** ተጠቀመ
The son now has the enjoyment of his father's car. ልጁ ፡ አሁን ፡ ባባቱ ፡ መኪና ፡ ይጠቀማል

**enlarge** (vt.)
1. አሳደገ. Let's enlarge the photograph! It's so pretty. ፎቶግራፉ ፡ ስለሚያምር ፡ እናሳድገው
2. አሰፋ. They enlarged the house by adding a bedroom. መኝታ ፡ ቤት ፡ በመጨመር ፡ ቤታቸውን ፡ አሰፉት

**enlarge** (vi.) ተስፋፋ
The city gradually enlarges. ከተማው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ይስፋፋል

**enlarge (on)** አስፋፍቶ ፡ጻፈ
He enlarged on the matter in his book. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ አስፋፍቶ ፡ ጻፈ

**enlargement**
1. (= to enlarge) ማስፋት. The enlargement of the house took two years. ቤቱን ፡ ማስፋት ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ፈጀ
2. (= to enlarge) ማሳደግ. An enlargement of the photo will cost two dollars. ፎቶግራፉን ፡ ለማሳደግ ፡ ሁለት ፡ ብር ፡ ይፈጃል
3. የተቀጠለ. The bedroom is an enlargement to our house. የመኝታ ፡ ቤቱ ፡ በቤታችን ፡ ላይ ፡ የተቀጠለ ፡ ነው

**enlighten** አስረዳ
Can you enlighten me on this subject? ይህንን ፡ ነገር ፡ ልታስረዳኝ ፡ ትችላለህ ?

**enlightening** ከሣች
He found the lesson very enlightening. ትምህርቱን ፡ በጣም ፡ ከሣች ፡ ሆኖ ፡ አገኘው

**enlist** (vt.)
1. መለመለ. Today they enlisted 300 men for the army. ዛሬ ፡ ለወታደርነት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ መለመሉ
2. ሳበ. The Red Cross seeks to enlist the interest of all. ቀይ ፡ መስቀል ፡ የሁሉን ፡ ሐሳብ ፡ ለመሳብ ፡ ይፈልጋል

**enlist** (vi.)
1. ገባ. He enlisted in the army two days ago. ከሁለት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ወታደርነት ፡ ገባ
2. ተቀጠረ ፤ ተመዘገበ. He enlisted in the navy two days ago. ከሁለት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ባሕር ፡ ኀይል ፡ ውስጥ ፡ ተቀጠረ ፡ (ተመዘገበ)

**enlisted man** ባለ ፡ ሌላ ፡ ማዕረግ
He is just an enlisted man, not an officer. ባለ ፡ ሌላ ፡ ማዕረግ ፡ እንጂ ፡ መኰንን ፡ አይደለም

**enlistment**
*His enlistment was voluntary. ወታደርነት ፡ የገባው ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ ነበር

**enliven**
1. አደመቀ. He enlivened the party by telling funny stories. የሚያሥቁ ፡ ተረቶች ፡ በመናገር ፡ ፓርቲውን ፡ አደመቀ
2. አጌጠ. Flowers enliven the room. አበቦች ፡ ክፍሉን ፡ አጊጠውታል

**enmity** ጠላትነት
There is no enmity between these two countries. በነዚህ ፡ ሁለት ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ጠላትነት ፡ የለም

**ennoble** አስከበረ
A good deed ennobles the person who did it. ጥሩ ፡ ምግባር ፡ አድራጊውን ፡ ያስከብራል

**enormity** (enormities)
1. አሰቃቂነት. The enormity of his crime shocked everybody. የወንጀሉ ፡ አሰቃቂነት ፡ ሁሉን ፡ ሰው ፡ አስደነገጠ

2. ከፍተኛነት. The enormity of his learning surprised everyone. የዕዋቂነቱ ፡ ከፍተኛነት ፡ ሁሉን ፡ አስገረመ
3. ግፍና ፡ ጭካኔ. Hitler's many enormities shocked the world. የሂትለር ፡ ግፍና ፡ ጭካኔ ፡ ዓለ ምን ፡ አሸበረው

**enormous**
1. ከፍ ፡ ያለ. This project requires an enormous amount of work. ይህ ፡ እቅድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥ ራ ፡ ይጠይቃል
2. በጣም ፡ ትልቅ. An enormous stone blocked the road. በጣም ፡ ትልቅ ፡ ቋጥኝ ፡ መንገዱን ፡ ዘጋው
3. በጣም ፡ ግዙፍ. Long ago enormous animals lived on the earth. ከብዙ ፡ ዘመናት ፡ በፊት ፡ በ ምድር ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ ግዙፍ ፡ እንስሳዎች ፡ ይ ኖሩ ፡ ነበር

**enormously** እጅግ
The need for raw materials has grown enormously. ለጥሬ ፡ እቃ ፡ ያለው ፡ ፍላጎት ፡ እጅግ ፡ እየበዛ ፡ ሄዷል

**enough** (adj.) በቂ
Do you have enough money? በቂ ፡ ገንዘብ ፡ አለህ ?

**enough** (adv.)
1. (= adj.) የሚበቃ. Have you had enough to eat? የሚበቃ ፡ ምግብ ፡ አገኘህ ?
2. የሚፈለገውን ፡ ያህል. This room isn't large enough. ይህ ፡ ክፍል ፡ የሚፈለገውን ፡ ያህል ፡ ሰፊ ፡ አይደለም
3. የሚገባውን ፡ ያህል. The government curtailed the student's stipend because he wasn't studying enough. ተማሪው ፡ የሚገባውን ፡ ያ ህል ፡ ስላላጠና ፡ መንግሥቱ ፡ ቀለቡን ፡ ቈረጠበት
4. ይህን ፡ ያህል. Are you simple enough to believe everything your neighbors tell you? ጐረቤቶችህ ፡ የነገሩህን ፡ ሁሉ ፡ ለማመን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ቂል ፡ ነህ ?
5. በደንብ. The meat isn't cooked enough. ሥጋው ፡ በደንብ ፡ አልበሰለም
6. እንኳን. He is willing enough to work. ለመሥራት ፡ እንኳን ፡ ፈቃደኛ ፡ ነው
*You're old enough to know better. እንደ ፡ ዕድሜህ ፡ ከሆነ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ማወቅ ፡ ነበ ረብህ

**be enough** በቃ
Will that be enough? ይበቃል ?

**be enough for** አጠገበ
Your answer wasn't enough for me. መልስህ ፡ አ ላጠገበኝም

**have about enough of** በቃ(ው)
+I have had about enough of your impudence. ያንተ ፡ ብልግና ፡ በቅቶኛል

**well enough** ደኅና
She talks well enough for her age. በዚህ ፡ ዕ ድሜዋ ፡ ደኅና ፡ አፏን ፡ ፈታለች
[See also 'about, just, old, sure']

**enrage**
1. በጣም ፡ አናደደ. Teasing enraged the dog. መተንኳኰሱ ፡ ውሻውን ፡ በጣም ፡ አናደደው
2. አስቈጣ. His failure to observe the proprieties enraged everybody. ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ማ ጓደሉ ፡ ሁሉንም ፡ አስቈጣ

**enrapture** መሰጠ
Their music enraptured the audience. ሙዚቃቸ ው ፡ አድማጩን ፡ ሕዝብ ፡ መሰጠው

**enrich**
1. አበለጸገ. Grandfather's property enriched the whole family. ያያታቸው ፡ ንብረት ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ በሙሉ ፡ አበለጸገ
Education enriches your mind. ትምህርት ፡ አእ ምሮን ፡ ያበለጽጋል
2. አዳበረ. The rotting leaves enrich the soil. የበሰበሱት ፡ ቅጠሎች ፡ አፈሩን ፡ ያዳብሩታል
3. አሳመረ. Decorations enrich a room. ጌጣ ፡ ጌጥ ፡ ክፍል ፡ ያሳምራል

**enroll** (vt.) መዘገበ
The supervisor enrolled students for a special class. ተቈጣጣሪው ፡ ተማሪዎችን ፡ ለልዩ ፡ ትምህ ርት ፡ መዘገበ

**enroll** (vi.) ተመዘገበ ፤ ተቀጠረ
My brother enrolled in the university. ወንድሜ ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ውስጥ ፡ ተመዘገበ ፡ (ተቀጠረ)

**enrollment** የተማሪ ፡ ቁጥር
The enrollment at our school increased this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ በትምህርት ፡ ቤታችን ፡ የተማሪው ፡ ቁጥር ፡ ጨምሯል
*Enrollment in our school is not open to foreigners. ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ የውጭ ፡ አገ ር ፡ ተማሪዎችን ፡ አይቀበልም

**ensconce, ~ oneself**
1. ተደበቀ ፤ ተሸሸገ. The boys ensconced themselves in a cave. ልጆቹ ፡ እዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ተ ደበቁ ፡ (ተሸሸጉ)
2.ተደላድሎ ፡ ተቀመጠ. He ensconced himself in a comfortable seat. በምቹ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተደ ላድሎ ፡ ተቀመጠ

**enshrine**

1. በቅዱስ ፡ ስፍራ ፡ አስቀመጠ. They enshrined a fragment of the cross in the cathedral. ግማደ ፡ መስቀሉን ፡ በካቴድራሉ ፡ ውስጥ ፡ ቅዱስ ፡ ስፍራ ፡ አስቀመጡት
2. ቀረጸ. They enshrined his memory in their hearts. የሱን ፡ ትዝታ ፡ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ ቀረጹ

**enshroud** ሸፈነ
Fog enshrouded the city. ጉሙ ፡ ከተማውን ፡ ሸፈነ

**ensign** ሰንደቅ ፡ ዓላማ
The ensign of the United States has 50 stars. የአሜሪካ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ አምሳ ፡ ኮከቦች ፡ አሉበት

**enslave**

1. ባሪያ ፡ አደረገ. The Romans enslaved the conquered people. ሮማውያን ፡ የተሸነፉትን ፡ ሕዝቦች ፡ ባሪያ ፡ አደረጉ
2. ገዛ. Fear of poverty enslaves him. የድኽነት ፡ ፍርሃት ፡ ይገዛዋል

**be enslaved by**
*She was enslaved by her work. ሥራዋ ፡ አላላወሳትም

**ensnare** አጠመደ
The boy ensnared birds in a net. ልጁ ፡ ወፎችን ፡ በመረብ ፡ አጠመደ

**ensue** ተከተለ
A period of chaos ensued. የትርምስ ፡ ጊዜ ፡ ተከተለ
*When those two women meet, a battle of insults ensues. ሁለቱ ፡ ሴቶች ፡ ሲገናኙ ፡ የስድብ ፡ መዓት ፡ ይጐርፋል
*As the days ensued, he recovered his strength. እያደር ፡ እየበረታ ፡ ሄደ

**ensure**

1. አረጋገጠ. A letter of introduction will ensure your acceptance. የአደራ ፡ ደብዳቤው ፡ የሚቀበሉህ ፡ መሆኑን ፡ ያረጋግጥልሃል
This law ensures more freedom of speech. ሕጉ ፡ የንግግር ፡ ነጻነትን ፡ በበለጠ ፡ ያረጋግጣል
2. አደረገ. Careful planning ensured the success of the party. ጥንቃቄ ፡ የመላበት ፡ ዝግጅት ፡ ግብዣውን ፡ እንዲሳካ ፡ አደረገው
3. ረዳ. Proper clothing ensured us against suffering from the cold. ተገቢ ፡ ልብስ ፡ በብርድ ፡ እንዳንሠቃይ ፡ ረዳን
[See also 'arrival']

**entail** ጠየቀ
Your plans entail great expense. እቅዶችህ ፡ ትልቅ ፡ ወጪ ፡ ይጠይቃሉ

**entangle**

1. ሳይወድ ፡ አስገባ. They entangled me in the plot. በሴራው ፡ ውስጥ ፡ ሳልወድ ፡ አስገቡኝ
2. አባባሰ. His interference further entangled the dispute. የርሱ ፡ ጣልቃ ፡ መግባት ፡ ጠቡን ፡ አባባሰው
3. (= pass.) ተወሳሰበ(በት). +I entangled my fishing line in the reeds. ዓሣ ፡ ማጥመጃ ፡ ክሬ ፡ ቄጠማው ፡ ውስጥ ፡ ተወሳሰበብኝ

**be entangled** ተወሳሰበ ፤ ተያዘ
Your fishing line is entangled in the weeds. የዓሣ ፡ ማጥመጃ ፡ ክርህ ፡ በአረም ፡ ውስጥ ፡ ተወሳስቧል ፡ (ተይዟል)

**enter** (vt.)

1. አስገባ. Enter these names in the list! እነዚህን ፡ ስሞች ፡ ዝርዝሩ ፡ ውስጥ ፡ አስገባቸው
I entered my son in school today. ልጄን ፡ ዛሬ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አስገባሁ
2. (= intr.) ገባ. He just entered the theater. ቲያትር ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አሁን ፡ ገና ፡ ገባ
3. መዘገበ. Did you enter the last bill? ያለፈውን ፡ ሒሳብ ፡ መዝግበኸዋል ?
4. አቀረበ. The injured man entered a complaint in court. የተጐዳው ፡ ሰው ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ አቀረበ
5. ያዘ. A dictionary enters words in alphabetical order. መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ቃላትን ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ ይይዛል

**enter** (vi.) ገባ
Everyone rose when the professor entered. ፕሮፌሰሩ ፡ ሲገባ ፡ ሁሉም ፡ ተነሡ
I am not going to enter into details on this matter. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ አልገባም

**enter into** አነሣ
We will enter into the question of taxes at a future time. የታክሱን ፡ ጉዳይ ፡ ወደፊት ፡ እናነሣዋለን
[See also 'plea']

**enterprise**

1. የንግድ ፡ ድርጅት. In this country, there is not much private enterprise. በዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የግል ፡ ንግድ ፡ ድርጅት ፡ የለም
2. ሥራ. Catching crocodiles is a dangerous enterprise. አዞ ፡ ማጥመድ ፡ አደገኛ ፡ ሥራ ፡ ነው

*My brother has a spirit of enterprise. ወንድሜ ፡ ሥራ ፡ ለመፍጠር ፡ ንቁ ፡ ነው

**enterprising** ታታሪ
He is a very enterprising businessman. በጣም ፡ ታታሪ ፡ ነጋዴ ፡ ነው

**entertain**
1. አስተናገደ ፤ ጋበዘ. They entertained a large number of guests last night. ትናንትና ፡ ማታ ፡ ብዙ ፡ እንግዶች ፡ አስተናገዱ ፡ (ጋበዙ)
2. አስደሰተ. Television entertains children. ቴሌቪዥን ፡ ልጆችን ፡ ያስደስታል
3. አሰበ. We have never entertained any such proposal. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ አሳብ ፡ አስበን ፡ አናውቅም
*Even after failing twice, we still entertained a hope of success. ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ከወደቅን ፡ በኋላ ፡ እንኳ ፡ ይሳካልናል ፡ የማለት ፡ ተስፋ ፡ ነበረን

**entertainer** አጫዋች
Eddy Cantor was a famous entertainer. ኤዲ ፡ ካንቶር ፡ ዝነኛ ፡ አጫዋች ፡ ነበር

**(be) entertaining** አስደሰተ
Shows are very entertaining. ትርኢይቶች ፡ በጣም ፡ ያስደስታሉ

**entertainment**
1. ጨዋታ. Who's going to provide the entertainment? ጨዋታውን ፡ የሚያዘጋጀው ፡ ማነው ?
2. ማስተናገድ. The hostess devoted her time to the entertainment of her guests. ባለቤቷ ፡ ጊዜዋን ፡ በሙሉ ፡ እንግዶቿን ፡ ለማስተናገድ ፡ አዋለችው

**enthrall** መሰጠ
The speaker enthralled the audience with the story of his travels. ተናጋሪው ፡ ስለ ፡ ጉዞው ፡ በመናገር ፡ አድማጮቹን ፡ መሰጠ

**enthrone** ዙፋን ፡ ላይ ፡ አስቀመጠ
The Muslims sought to enthrone one who would protect their faith. እስላሞቹ ፡ እምነታቸውን ፡ የሚጠብቅላቸውን ፡ ሰው ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ለማስቀመጥ ፡ ፈለጉ

**enthuse** ደስ ፡ ተሰኘ
All the neighbors enthused over the new baby. ጐረቤቱ ፡ ሁሉ ፡ አዲስ ፡ ስለተወለደው ፡ ሕፃን ፡ ደስ ፡ ተሰኘ

**enthusiasm**
1. መንፈስ ፤ ስሜት. Continued failures dampened their enthusiasm. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሳይሳካላቸው ፡ መቅረቱ ፡ መንፈሳቸውን ፡ (ስሜታቸውን) ፡ አቀዘቀዘው
2. ጉጉት. He did not show enthusiasm for the trip. ለጉዞው ፡ ምንም ፡ ጉጉት ፡ አላሳየም
3. ትጋት. He did not show any enthusiasm for his studies. ለትምህርቱ ፡ ምንም ፡ ትጋት ፡ አላሳየም

**fan enthusiasm** አነሣሣ
He tried to fan enthusiasm for his proposal. ላቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ድጋፍ ፡ ለማግኘት ፡ ሰዎችን ፡ ለማነሣሣት ፡ ሞከረ

**show enthusiasm** ተደነቀ(በት) ፤ አድናቆት ፡ አሳየ
He did not show any enthusiasm for my plans. በእቅዴ ፡ ምንም ፡ አልተደነቀበትም ፡ ( or ለእቅዴ ፡ ምንም ፡ አድናቆት ፡ አላሳየም)

**(be) enthusiastic** ጓጓ
I am quite enthusiastic about the forthcoming trip. ወደፊት ፡ ለሚደረገው ፡ ጉዞ ፡ በጣም ፡ ጓጉቻለሁ

**enthusiastically** በጋለ ፡ ስሜት
He called out to her enthusiastically. በጋለ ፡ ስሜት ፡ ጠራት

**entice**
1. አባበለ. The crook enticed the children with candy. አታላዩ ፡ ሕፃናቱን ፡ በከረሜላ ፡ አባበላቸው
2. ሳበ. The smell of food enticed the hungry children into the house. የምግብ ፡ ሽታ ፡ የተራቡትን ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሳባቸው

**entire** (adj.)
1. ድፍን. The entire town came to see him off. ድፍን ፡ ከተማው ፡ ሊሸኘው ፡ መጣ
2. መላ. The accident bereaved him of his entire family. አደጋው ፡ መላ ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ አሳጣው
3. (= adv.) በሙሉ. He lost his entire fortune. ሀብቱን ፡ በሙሉ ፡ አጣ
He wrote the entire novel in only six weeks. መጽሐፉን ፡ በሙሉ ፡ በስድስት ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ጻፈው

**entire** (adv.) እንዳለ
The crown was recovered entire. ዘውዱን ፡ እንዳለ ፡ አስመለሱት

**entirely**
1. በፍጹም. The two are entirely different. ሁለቱ ፡ በፍጹም ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው
2. ፈጽሞ. The news came entirely unexpectedly. ወሬው ፡ ፈጽሞ ፡ ሳይታሰብ ፡ ደረሰ

3. ሙሉ ፡ በሙሉ. The committee is made up entirely of students. የደርጉ ፡ አባሎች ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ተማሪዎች ፡ ናቸው

**entirety** (= adv.) በሙሉ
He devoted the entirety of his life to medical research. ሕይወቱን ፡ በሙሉ ፡ ለሕክምና ፡ ጥናት ፡ አዋለ

**in its entirety** በሙሉ ፤ እንዳለ
The bill was rejected in its entirety. የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ በሙሉ ፡ (እንዳለ) ፡ ተቀባይነትን ፡ አጣ

**entitle**
1. መብት ፡ ሰጠ. The law entitles every criminal to a trial. ሕጉ ፡ ለማናቸውም ፡ ወንጀለኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመቅረብ ፡ መብት ፡ ይሰጠዋል
2. ብሎ ፡ ጠራ. How does one entitle a king when speaking directly to him? አንድ ፡ ሰው ፡ ከንጉሥ ፡ ጋር ፡ ሲነጋገር ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ ይጠራዋል ?
*Their age and experience entitles old people to the respect of young people. አዛውንትን ፡ በዕድሜያቸውና ፡ በልምምዳቸው ፡ ወጣቶች ፡ እንዲያከብሯቸው ፡ ይገባል

**be entitled**
1. ሥልጣን ፡ አለው. The nurse is entitled to administer drugs. ነርሷ ፡ መድኃኒት ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ አላት
2. ተባለ. A book that explains words is entitled a dictionary. የቃላትን ፡ ፍች ፡ የሚሰጥ ፡ መጽሐፍ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ይባላል

**entity** (entities)
1. አንድነት ፡ ያላት ፡ አገር. The United States is an entity rather than an association of states. አሜሪካ ፡ አንድነት ፡ ያላት ፡ አገር ፡ እንጂ ፡ የሀገሮች ፡ ኅብረት ፡ አይደለችም
2. አካል. Physical entities are perceived by the five senses. ግዙፍ ፡ አካሎችን ፡ ባምስቱ ፡ ሕዋሳት ፡ ለማወቅ ፡ እንችላለን

**entomb**
1. ቀበረ. The slide of rock entombed the miners. የተናደው ፡ አለት ፡ ማዕድን ፡ አውጪዎቹን ፡ ቀበራቸው
2. (= pass.) ተቀበረ. +This church entombs many great men. በዚህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ተቀብረዋል

**entrails** አንጀት
Only a dog eats entrails. አንጀት ፡ የሚበላ ፡ ውሻ ፡ ብቻ ፡ ነው

**entrance** (v.) መሰጠ
The music entranced him. ሙዚቃው ፡ መሰጠው

**entrance** (n.) መግቢያ
Where is the entrance to this hall? የዚህ ፡ አዳራሽ ፡ መግቢያው ፡ በየት ፡ ነው ?
*The actor's entrance was greeted with applause. ተዋናዩ ፡ ብቅ ፡ ሲል ፡ በጭብጨባ ፡ ተቀበሉት
*Entrance to the college is by examination only. ኮሌጁ ፡ የሚገባው ፡ በፈተና ፡ ብቻ ፡ ነው

**gain entrance** ለመግባት ፡ ፈቃድ ፡ አገኘ
He gained entrance to the palace. ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ለመግባት ፡ ፈቃድ ፡ አገኘ

**entrant** አዲስ ፡ ገቢ
A medical examination is required of all entrants. አዲስ ፡ ገቢዎች ፡ ሁሉ ፡ የጤና ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግላቸው ፡ ያስፈልጋል

**entrap** (entrapped)
1. አጠመደ. The hunters entrapped the jackals in nets. አዳኞቹ ፡ ቀበሮዎቹን ፡ በመረብ ፡ አጠመዱ
2. አግባባ. She sought to entrap him by telling him her parents were wealthy. ወላጆቿ ፡ ሀብታም ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ ልታግባባው ፡ ፈለገች

**entreat** ለመነ
The criminal entreated the judge to show mercy. ወንጀለኛው ፡ ርኅራኄ ፡ እንዲያደርግለት ፡ ዳኛውን ፡ ለመነ

**entreaty** (entreaties) ልመና
The warriors paid no attention to their captives' entreaties for mercy. ምርኮኞቻቸው ፡ ምሕረት ፡ እንዲያደርጉላቸው ፡ ያቀረቡትን ፡ ልመና ፡ አርበኞቹ ፡ ከምንም ፡ አልቈጠሩትም

**entrench, ~ oneself**
1. መሸገ. The soldiers entrenched themselves near the enemy lines. ወታደሮቹ ፡ ከጠላት ፡ ግንባር ፡ አጠገብ ፡ መሸጉ
2. ሥር ፡ ሰደደ. He strongly entrenched himself in the company. በኩባንያው ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ ሥር ፡ ሰደደ

**entrenched** (adj.) ሥር ፡ የሰደደ
It is difficult to change entrenched habits like smoking after meals. ከምግብ ፡ በኋላ ፡ ማጨስን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሥር ፡ የሰደዱ ፡ልማዶችን ፡ ለመለወጥ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**be entrenched** መሸገ
The enemy was strongly entrenched on the

other side of the barrier. ጠላት ፡ በገደቡ ፡ አሻገር ፡ በደምብ ፡ መሽጎ ፡ ነበር

**entrust**
1. እምነት ፡ ጣለ(በት). Can I entrust you with this task? ለዚህ ፡ ሥራ ፡ እምነቴን ፡ ልጥልብህ ፡ እችላለሁ ?
2. አደራ ፡ ሰጠ. While traveling, he entrusted the children to a nurse. በሚጓዝበት ፡ ጊዜ ፡ ልጆቹን ፡ ለሞግዚት ፡ አደራ ፡ ሰጠ
3. አስቀመጠ. We entrusted our money to a bank. ገንዘባችንን ፡ ባንክ ፡ አስቀመጥን

**entry** (entries)
1. አገባብ. Their entry into America was illegal. ወደ ፡ አሜሪካ ፡ አገባባቸው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ነበር
2. (= to enter) መግባት. Entry into the U.S. requires a visa. አሜሪካ ፡ ለመግባት ፡ ቪዛ ፡ ያስፈልጋል
3. የተመዘገበ ፡ ቃል. How many entries are there in this dictionary? በዚህ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ ስንት ፡ የተመዘገቡ ፡ ቃላት ፡ አሉ ?
4. የተመዘገበ. The last entry was five dollars. በመጨረሻ ፡ የተመዘገበው ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ነው
5. ተወዳዳሪ. The horse race had nine entries. የፈረሱ ፡ እሽቅድድም ፡ ዘጠኝ ፡ ተወዳዳሪዎች ፡ ነበሩት

**make its entry** ገባ
The army made its entry into the town unopposed. ጦሩ ፡ ካላንዳች ፡ ተቃውሞ ፡ ከተማው ፡ ውስጥ ፡ ገባ

**entwine, ~ around** ከበበ
Roses entwined around the little cottage. ትንሿን ፡ ጎጆ ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ ከቧታል

**be entwined** ተጠመጠመ
+The poles are entwined with ivy. ሐረጉ ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ ተጠምጥሟል

**entwine hands** እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተቈላለፉ
They entwined their hands as they walked. ሲራመዱ ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተቈላልፈው ፡ ነበር

**enumerate**
1. ቈጠረ. Can you enumerate the times the Emperor has gone abroad? ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሄዱባቸውን ፡ ጊዜዎች ፡ ልትቈጥር ፡ ትችላለህ ?
2. ዘረዘረ. He enumerated the capitals of the fifty states. የኀምሳዎቹን ፡ ግዛቶች ፡ ዋና ፡ ከተማዎች ፡ ዘረዘረ

**enunciate**
1. ተናገረ. The student enunciates his words clearly. ተማሪው ፡ ቃላቱን ፡ በግልጽ ፡ ይናገራል
2. ገለጸ. The scientist enunciated a new theory. የሳይንሱ ፡ ሊቅ ፡ አዲስ ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳብ ፡ ገለጸ

**envelop**
1. ጠቀለለ. The mother enveloped her baby in blankets. እናትዮዋ ፡ ሕፃኗን ፡ በብርድ ፡ ልብስ ፡ ጠቀለለችው
2. ሸፈነ. Mist enveloped the town. ከተማውን ፡ ጉም ፡ ሸፈነው
3. ከበበ. Our troops enveloped the enemy. ወታደሮቻችን ፡ ጠላትን ፡ ከበቡት

**envelope** አምቦልክ
I need an envelope for this letter. ለዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ አምቦልክ ፡ እፈልጋለሁ

**envenom** መረዘ
A deadly gas envenomed the air. መርዘኛ ፡ ጭስ ፡ አየሩን ፡ መረዘው

**enviable** የሚያስቀና
He has an enviable school record. የሚያስቀና ፡ የትምህርት ፡ ውጤት ፡ አለው

**(be) envious** ቀና
He is envious of my good fortune. በመልካም ፡ ዕድሌ ፡ ይቀናል

**environment** አካባቢ
The environment of the new school will make the students proud. የአዲሱ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አካባቢ ፡ ተማሪዎችን ፡ ያኮራል
Scholars investigate the social environments of different people. ዐዋቂዎች ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰዎችን ፡ የኑሮ ፡ አካባቢ ፡ ይመረምራሉ

**envisage**
1. ብሎ ፡ አሰበ. Do you envisage a raise in taxes? ግብር ፡ ይጨመራል ፡ ብለህ ፡ ታስባለህ ?
2. በዓይነ ፡ ኅሊና ፡ አሰበ. The scientist envisaged the happiness his invention would bring. የሳይንሱ ፡ ሊቅ ፡ ፍልሰፋው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ደስታ ፡ እንደሚያመጣ ፡ በዓይነ ፡ ኅሊናው ፡ አሰበ

**envoy** መልእክተኛ
The President sent a special envoy to the Emperor. ፕሬዚዳንቱ ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛ ፡ ላኩ

**envoy extraordinary** ልዩ ፡ መልእክተኛ
The envoy extraordinary was received by the king. ንጉሡ ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛን ፡ ተቀበሉ

**envy** (v.) ቀና(በት)
They envied him his success. ስለተቃናለት ፡ ቀኑበት

**envy** (n.) ቅናት
Envy devoured him. ቅናት ፡ ገደለው
*She was the envy of the younger girls in school. ወጣት ፡ ልጃገረዶችን ፡ ሁሉ ፡ በትምህር ት ፡ ቤት ፡ የምታስቀና ፡ ነበረች

**ephemeral** ኀላፊ
Man's life is ephemeral. የሰው ፡ ሕይወት ፡ ኀ ላፊ ፡ ነው

**epic** (n.) የጀግንነት ፡ ግጥም
The "Iliad" is an epic. ኢልያድ ፡ የጀግንነት ፡ ግ ጥም ፡ ነው

**epic deed** ጀብዱ
Flying over the Atlantic for the first time was an epic deed. በአትላንቲክ ፡ ላይ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ መብረር ፡ እንደ ፡ ጀብዱ ፡ የሚቈጠር ፡ ነበር

**epidemic** ተላላፊ ፡ በሽታ
An epidemic of malaria is reported from the southern provinces. የወባ ፡ ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ በደቡብ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ እንደተሰራጨ ፡ ተ ነገረ

**epilepsy** የሚጥል ፡ በሽታ
Epilepsy is a disease of the nervous system. የሚጥል ፡ በሽታ ፡ የነርቭ ፡ በሽታ ፡ ነው

**epilogue** ቅጣይ
He added an epilogue to his novel. በልብ ፡ ወለ ዱ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅጣይ ፡ ጨመረበት

**Epiphany** የጥምቀት ፡ በዓል
Epiphany is celebrated in Ethiopia. በኢትዮጵ ያ ፡ የጥምቀት ፡ በዓል ፡ ይከበራል

**episode**
1. ምዕራፍ. The year he spent in France was an important episode in the painter's life. በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ያሳለፈው ፡ ዓመት ፡ በሠዓሊ ው ፡ ሕይወት ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ምዕራፍን ፡ የያዘ ፡ ነው
2. ክፍል. The story was divided into different episodes. ታሪኩ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ የተከ ፈለ ፡ ነበር
3. ድርጊት. She remembered the episode of the drunken butcher vividly. የሰካራሙ ፡ ሥጋ ፡ ሻጭ ፡ ድርጊት ፡ በትዝታ ፡ ጕልቶ ፡ ታያት

**Epistle** መልእክት
Paul's Epistles were written in Greek. የጳውሎ ስ ፡ መልእክቶች ፡ የተጻፉት ፡ በጽርእ ፡ ነበር

**epistle** ደብዳቤ
The Emperor's epistle to the Pope was brought by the ambassador. ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ለጳጳ ሱ ፡ የተላከው ፡ ደብዳቤ ፡ በአምባሳደሩ ፡ አማካይ ነት ፡ ደረሰ

**epitaph** [ስለ ፡ ሟቹ ፡ የሚናገር ፡ በመቃብር ፡ ድንጊ ያ ፡ ላይ ፡ የሚቀረጽ ፡ አጭር ፡ መግለጫ]

**epithet** ቅጽል ፡ ስም
In "Richard the Lion-Hearted", the epithet is "the Lion-Hearted". « ሪቻርድ ፡ ልበ ፡ አንበ ሳ » ፡ በሚለው ፡ ውስጥ ፡ ቅጽል ፡ ስሙ ፡ « ል በ ፡ አንበሳ » ፡ የሚለው ፡ ነው

**epitome** ምሳሌ
Samson is the epitome of courage. ሳምሶን ፡ የ ጀግንነት ፡ ምሳሌ ፡ ነው

**epitomize** በ - - - ተመሰለ
Samson epitomizes courage. ሳምሶን ፡ በድፍረ ት ፡ ይመሰላል

**epoch**
1. ዘመን. The epoch begun by the atomic bomb has not yet ended. የአቶሚክ ፡ ቦምብ ፡ ዘመን ፡ አሁንም ፡ አላለቀም
2. ምዕራፍ. The first earth satellite marked a new epoch in the study of the universe. የመጀመሪያው ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጨረቃ ፡ በጠፈ ር ፡ ጥናት ፡ ውስጥ ፡ አዲስ ፡ ምዕራፍ ፡ ከፈተች

**Epsom salts** የእንግሊዝ ፡ ጨው
Soak your finger in a solution of Epsom salts! የሚሟ ፡ እንግሊዝ ፡ ጨው ፡ ውስጥ ፡ ጣትህን ፡ ንከ ረው

**equal** (equalled), v.
1. አከለ. The gains will never equal the losses. ትርፉ ፡ ኪሳራውን ፡ ከቶ ፡ አያክልም
2. እኩል ፡ ነው. Sixteen ounces equal one pound. ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ አውንስ ፡ ካንድ ፡ ፓ ውንድ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ነው
3. ሆነ ፤ ነው. Four times four equals sixteen. አራት ፡ ጊዜ ፡ አራት ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ይሆ ናል ፡ (ነው)
4. ደረሰ(በት). You can equal my score easily. የኔን ፡ ግብ ፡ በቀላሉ ፡ ልትደርስበት ፡ ትችላለህ

**equal** (n.)
1. እኩያ ፤ አቻ. He is my equal in every respect. በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ እኩያዬ ፡ (አቻዬ) ፡ ነው
2. ወደር. In reading, she has no equal. በንባብ ፡ ወደር ፡ የላትም

**equal** (adj.)
1. እኩል. The two nobles are equal in rank. ሁለቱ ፡ መኳንንት ፡ በማዕረግ ፡ እኩል ፡ ናቸው
2. የእኩልነት. They started out on an equal

footing. ሲጀምሩ ፡ በእኩልነት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ነበረ

3. አንድ ፡ ዓይነት. Equal pay for equal work. ላንድ ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ደሞዝ

4. ተመሳሳይ. The two students are of equal intelligence. ሁለቱ ፡ ተማሪዎች ፡ ተመሳሳይ ፡ የአእምሮ ፡ ችሎታ ፡ አላቸው

**be equal to** ዓቅም ፡ አለው

I am not equal to climbing that hill. ያንን ፡ ኮረብታ ፡ ለመውጣት ፡ ዓቅም ፡ የለኝም

[See also 'quality, term, turn']

**equality** እኩልነት

Equality between men and women is hard to bring about. በወንዶችና ፡ በሴቶች ፡ መካከል ፡ እኩልነትን ፡ ለመፍጠር ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**equalize** አስተካከለ

He equalized the pay of his workers. የሠራተኞቹን ፡ ደሞዝ ፡ አስተካከለ

**equally**

1. በትክክል. In a partnership, the partners share all liabilities equally. በሽርክና ፡ ተሻራኪዎች ፡ ማንኛውንም ፡ ወጪና ፡ ኪሳራ ፡ በትክክል ፡ ይካፈላሉ

2. እኩል. He divided the bread equally. እሱ ፡ ዳቦውን ፡ እኩል ፡ ከፈለው

*This dialect is equally removed from German and English. ይህ ፡ የቋንቋ ፡ ስልት ፡ ከጀርመንኛ ፡ የሚለየውን ፡ ያህል ፡ ከእንግሊዝኛም ፡ ይለያል

**equate** እኩል ፡ አድርጎ ፡ አየ

Many people equate wealth with happiness. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሀብትን ፡ ከደስታ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ አድርገው ፡ ያያሉ

**equator** የምድር ፡ መቀነት

The word equator connotes heat. የምድር ፡ መቀነት ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ሙቀትን ፡ ያሳስባል

**equestrian**

1. የፈረሰኛነት. His equestrian training helped him become the best cavalryman. በፈረሰኛነት ፡ መሠልጠኑ ፡ ምርጥ ፡ ፈረሰኛ ፡ ለመሆን ፡ ረዳው

2. በፈረስ ፡ ላይ ፡ ያለ. An equestrian statue of Menelik stands in the square. በፈረስ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የምኒልክ ፡ ሐውልት ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ ቆሟል

**equilibrium**

1. ሚዛን. The circus clown keeps his equilibrium with a pole. የሰርከሱ ፡ ተዋናይ ፡ ሚዛኑን ፡ በዘንግ ፡ አማካይነት ፡ ይጠብቃል

2. የመንፈስ ፡ እርጋታ. The extremities of the situation caused her to lose her equilibrium. የሁኔታው ፡ ከልክ ፡ ማለፍ ፡ የመንፈስ ፡ እርጋታዋን ፡ እንድታቃውስ ፡ አደረጋት

**be in equilibrium** ተመዛዘነ

Scales are in equilibrium when the weights on both sides are equal. ሚዛኖቹ ፡ በሁለቱም ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ ክብደት ፡ እኩል ፡ ሲሆን ፡ ይመዛዘናሉ

**equinox**

*The equinox occurs on March 21. እኩል ፡ ዕለት ፡ የሚሆንበት ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ መጋቢት ፡ ፳፭ ፡ ገደማ ፡ ይውላል

**equip** (equipped) አዘጋጀ.

They equipped the ship for a long voyage. መርከቡን ፡ ለረጅም ፡ ጉዞ ፡ አዘጋጁ

**be equipped**

1. ታጠቀ. The soldiers are equipped with modern arms. ወታደሮቹ ፡ ዘመናዊ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ታጥቀዋል

2. አለ(ው). Our planes are equipped with the latest instruments. አውሮፕላኖቻችን ፡ ዘመናዊ ፡ መሣሪያዎች ፡ አሏቸው

**equipment**

1. መሣሪያ. The factory has modern equipment. ፋብሪካው ፡ ዘመናዊ ፡ መሣሪያ ፡ አለው

Hunting equipment includes rifles and spears. ያደን ፡ መሣሪያዎች ፡ ጠመንጃንና ፡ ጦርን ፡ ይጨምራሉ

2. ትጥቅ. The equipment of the soldiers was carried in trucks. የወታደሮቹ ፡ ትጥቅ ፡ በመኪና ፡ ተጫነ

**equitable**

1. ትክክለኛ. They came to an equitable decision. ከትክክለኛ ፡ ውሳኔ ፡ ደረሱ

2. ተገቢ. The division of profits among the partners was equitable. የባለጥቅሞቹ ፡ የትርፍ ፡ አከፋፈል ፡ ተገቢ ፡ ነበር

**equity** ትክክለኛነት

No one questions the equity of this transaction. የዚህን ፡ ሽያጭ ፡ ትክክለኛነት ፡ የሚጠራጠር ፡ የለም

**equivalence** እኩልነት

The equivalence of the two currencies is threatened by inflation. የሁለቱን ፡ ገንዘቦች ፡ እኩልነት ፡ የገንዘብ ፡ መርከስ ፡ ያሰጋዋል

**equivalent** (n., adj.)
1. ተመዛዛኝ. These two objects are not equivalent in weight. እነዚህ ፡ ሁለት ፡ እቃዎች ፡ በክብደት ፡ ተመዛዛኝ ፡ አይደሉም
2. ተመጣጣኝ. He asked for 50 dollars or its equivalent in gold. አምሳ ፡ ብር ፡ ወይም ፡ በ ወርቅ ፡ ተመጣጣኙን ፡ ጠየቀ
3. ተመሳሳይ. Is there an equivalent for the English word "home" in French? « ሆም » ፡ የ ሚለው ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቃል ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ተ መሳሳይ ፡ አለው ?
*What is the equivalent of an American dollar in Ethiopian money? አንድ ፡ የአሜሪካ ፡ ብር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ገንዘብ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይሆናል ?

**be equivalent to** የ - - - ያህል ፡ ነው
Nodding your head is equivalent to saying "yes". ራስን ፡ ጐምበስ ፡ ቀና ፡ ማድረግ ፡ እሺ ፡ የ ማለት ፡ ያህል ፡ ነው

**equivocal** አጠራጣሪ
He gave an equivocal reply to my question. ለጥያቄዬ ፡ አጠራጣሪ ፡ መልስ ፡ ሰጠ

**equivocate** አዙሮ ፡ ተናገረ
He would rather equivocate than give a direct answer. ቀጥተኛ ፡ መልስ ፡ ከመስጠት ፡ ይልቅ ፡ አ ዙሮ ፡ ይናገራል

**era**
1. ዘመን. The Christian era is 622 years earlier than the Muslim one. የክርስትና ፡ ዘመን ፡ ከእ ስልምና ፡ ዘመን ፡ በስድስት ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ ሁለ ት ፡ ዓመት ፡ ይቀድማል
The use of electricity for power marked the beginning of a new era. በኤሌክትሪክ ፡ ኀይ ል ፡ መጠቀም ፡ ያዲስ ፡ ዘመን ፡ መክፈቻ ፡ ሆነ
2. የጌታችን ፡ ልደት. Julius Caesar died many years before our era. ዩልዩስ ፡ ቄሳር ፡ ከጌታችን ፡ ልደት ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ሞተ
[See also 'bygone']

**eradicate**
1. አጠፋ. Vaccination has nearly eradicated smallpox. ክትባት ፡ ፈንጣጣን ፡ ሊያጠፋው ፡ ምንም ፡ አልቀረው
2. አስወገደ. The gardener eradicated weeds from the garden. አትክልተኛው ፡ ካትክልቱ ፡ ቦታ ፡ አረሙን ፡ አስወገደ

**be eradicated** ጠፋ
Sickness can be eradicated by drugs. በሽታ ፡ በ መድኃኒት ፡ ሊጠፋ ፡ ይችላል

**erase** (vt.)
1. ፋቀ. He erased the signature. ፊርማውን ፡ ፋቀው
2. ጠረገ. Will you please erase the board? ጥቁር ፡ ሰሌዳውን ፡ ጥረገው

**erase** (vi.) ለቀቀ
This paper erases easily. ይህ ፡ ወረቀት ፡ በቀላ ሉ ፡ ይለቃል

**eraser** ላጲስ
I bought two pencils and an eraser. ሁለት ፡ እ ርሳስና ፡ አንድ ፡ ላጲስ ፡ ገዛሁ

**erect** (v.)
1. አቆመ. They erected a monument to Menelik II. ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ሐውልት ፡ አቆሙ
The workers erected a telephone pole. ሠራተኞ ቹ ፡ የስልክ ፡ ዕንጨት ፡ አቆሙ
2. አቋቋመ. The conqueror erected a new government. ድል ፡ አድራጊው ፡ አዲስ ፡ መንግ ሥት ፡ አቋቋመ
3. ሠራ. They will erect a new building. አዲስ ፡ ሕንጻ ፡ ይሠራሉ
4. ገጣጠመ. When the missing parts arrived, we erected the machine. የጐደሉት ፡ እቃዎች ፡ ሲመጡ ፡ መኪናውን ፡ ገጣጠምን

**be erected** ቆመ
A monument of Menilek was erected in the city. የአፄ ፡ ምኒልክ ፡ ሐውልት ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ቆሟል

**erect** (adj.)
1. (= gerundive) ቀጥ ፡ ብሎ. Please stand erect when talking to the Emperor! ከንጉሠ ፡ ነገሥ ቱ ፡ ጋር ፡ በምትነጋገርበት ፡ ጊዜ ፡ ቀጥ ፡ ብለ ህ ፡ ቁም
2. (= gerundive) አቁሞ. The cat faced the dog with fur erect. ድመቷ ፡ ጸጉሯን ፡ አቁማ ፡ ውሻው ፡ ፊት ፡ ቆመች

**hold erect** ቀና ፡ አደረገ
The child held her head erect. ሕፃኗ ፡ ራሷን ፡ ቀና ፡ አደረገች

**erode** ሸረሸረ
Rain and wind eroded the hillsides. ዝናብና ፡ ነ ፋስ ፡ ኮረብታውን ፡ ሸረሸረው

**erosion** መሸርሸር
Trees help prevent the erosion of soil. ዛፎች ፡ ያፈርን ፡ መሸርሸር ፡ ይከላከላሉ

**err**
1. አጠፋ. He erred in stating that I would come. ስለኔ ፡ መምጣት ፡ በመናገሩ ፡ አጠፋ
2. ተሳሳተ. He erred in his youth and later regretted it. በልጅነቱ ፡ ተሳስቶ ፡ በኋላ ፡ ተጸጸተ

**errand** መልእክት
I have a few errands to do. የማደርሰው ፡ ትንሽ ፡ መልእክት ፡ አለኝ

**run errands** ተላላክ
I've been running errands for my mother all morning. ጧቱን ፡ በሙሉ ፡ ለእናቴ ፡ ስላላክ ፡ ነበር

**errant**
1. ተዘዋዋሪ. The errant outlaws were caught by the police. ተዘዋዋሪዎቹ ፡ ሽፍታዎች ፡ በፖሊስ ፡ ተያዙ
2. ያልታረመ. His errant behavior was censured by the teacher. ስላልታረመው ፡ ጠባዩ ፡ መምህሩ ፡ ነቀፈው

**erratic**
1. ያልተስተካከለ. The erratic course of the plane showed that the pilot was inexperienced. ያውሮፕላኑ ፡ ያልተስተካከለ ፡ በረራ ፡ ነጂው ፡ ልምድ ፡ ያልነበረው ፡ መሆኑን ፡ አሳየ
2. የሚዋልል. An erratic mind jumps from one idea to another. የሚዋልል ፡ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ከንዱ ፡ ሐሳብ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ይዘላል
3. ልዩ ፡ ጠባይ ፡ ያለው. When I laughed loudly he was surprised, since I appeared to be erratic to him. ከት ፡ ብዬ ፡ በመሣቄ ፡ ልዩ ፡ ጠባይ ፡ ያለኝ ፡ መስዬ ፡ ስለታየሁት ፡ ተደነቀ

**erroneous** የተሳሳተ
He made an erroneous statement. የተሳሳተ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠ

**error**
1. ስሕተት. His speech contained several grammatical errors. ንግግሩ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ የሰዋስው ፡ ስሕተቶች ፡ ነበሩበት
2. ጉድለት. The controller checked the accounts and found no errors. ተቈጣጣሪው ፡ ሒሳቡን ፡ መርምሮ ፡ ምንም ፡ ጉድለት ፡ አላገኘም

**erudite**
1. ምሁር. My teacher is very erudite. አስተማሪዬ ፡ በጣም ፡ ምሁር ፡ ናቸው
2. የምሁር. He gave an erudite lecture. የምሁር ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**erudition** ዕውቀት
The teacher is a man of great erudition. መምህሩ ፡ የጠለቀ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**erupt**
1. ፈነዳ. The volcano erupted today. እሳተ ፡ ገሞራው ፡ ዛሬ ፡ ፈነዳ
2. ተቈጣ. Her skin erupted when she had measles. ኩፍኝ ፡ ሲይዛት ፡ ቆዳዋ ፡ ተቈጣ
3. ተነሣ. A serious battle erupted yesterday. ትናንትና ፡ ኀይለኛ ፡ ጦርነት ፡ ተነሣ
4. ወጣ. Burning debris erupted from the top of the volcano. የሚቃጠሉ ፡ ፍርስራሾች ፡ ከእሳተ ፡ ገሞራው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ይወጡ ፡ ነበር
5. (= active) አሰማ. His patience finally gave way, and words of anger erupted from him. በመጨረሻ ፡ ትዕግሥቱ ፡ አልቆ ፡ የቁጣ ፡ ቃላት ፡ ያሰማ ፡ ነበር

**eruption**
1. መፈንዳት. The eruptions of the volcano came about one hour apart. የእሳተ ፡ ገሞራው ፡ መፈንዳት ፡ በአንዳንድ ፡ ሰዓት ፡ ልዩነት ፡ ይደርስ ፡ ነበር
2. በድንገት ፡ መነሣት. The eruption of violence was due to religious rivalry. የብጥብጡ ፡ በድንገት ፡ መነሣት ፡ ከሃይማኖት ፡ ፉክክር ፡ የተነሣ ፡ ነበር
3. መቈጣት. He treated the eruption of her skin with an ointment. ለቆዳዋ ፡ መቈጣት ፡ የቅባት ፡ መድኃኒት ፡ አደረገላት

**escalate** (vt.)
1. ቆጠለ. Because of the strike, the stores escalated prices. በሥራ ፡ ማቆሙ ፡ አድማ ፡ ምክንያት ፡ መደብሮቹ ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ ቆጠሉ
2. አባባሰ. The raids only escalate the level of violence. ወረራው ፡ የጠቡን ፡ መጠን ፡ ያባብሰዋል

**escalate** (vi.) ተባባሰ ፡ ተለወጠ
The border clash escalated into a war. የድንበሩ ፡ ግጭት ፡ ተባብሶ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ተለወጠ

**escalator** ተንቀሳቃሽ ፡ ደረጃ
The office building had both an escalator and an elevator. የመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሕንጻ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ደረጃና ፡ አሳንሰር ፡ ነበረው

**escape** (vt.)
1. አመለጠ. He escaped the police. ከፖሊስ ፡ አመለጠ
Nothing escapes her. ምንም ፡ ነገር ፡ አያመልጣትም
2. ዳነ. He escaped defeat by a narrow margin. ለጥቂት ፡ ከመሸነፍ ፡ ዳነ
3. ትዝ ፡ አላለውም. Her face is familiar, but her name escapes me. መልኳን ፡ አስታውሳለሁ ፡ ግን ፡ ስሟ ፡ ትዝ ፡ አይለኝም
*A scream escaped her lips. ሳታስበው ፡ ጮኸች

**escape** (vi.)
1. **አመለጠ**. Two prisoners have escaped from the penitentiary. ሁለት ፡ እስረኞች ፡ ከወህኒ ፡ ቤት ፡ አምልጠዋል
2. **ቀስ ፡ በቀስ ፡ ወጣ**. Gas was escaping from the pipe. ቡታ ፡ ጋዝ ፡ ከቧንቧው ፡ ውስጥ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ይወጣ ፡ ነበር

**let escape ለቀቀ**
Make a hole and let the water escape! ቀዳዳ ፡ አብጅና ፡ ውኃውን ፡ ልቀቀው
[See also 'notice']

**escape** (n.)
1. **ማምለጥ**. The climax of the play was the prisoner's escape. የትርእይቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ክፍል ፡ የእስረኛው ፡ ማምለጥ ፡ ነበር
2. **የማምለጫ ፡ ዘዴ**. The prisoner designed an intricate escape. እስረኛው ፡ የተራቀቀ ፡ የማምለጫ ፡ ዘዴ ፡ አቀደ
3. **የችግር ፡ ማስረሻ**. Movies are her escape. ሲኒማ ፡ የችግር ፡ ማስረሻዋ ፡ ነው

**make good (one's) escape አመለጠ**
The thief threw off his pursuers and made good his escape. ሌባው ፡ የሚከታተሉትን ፡ ሰዎች ፡ አታሎ ፡ አመለጠ
[See also 'fire escape, narrow']

**escaped** (adj.) **ያመለጠ**
An escaped prisoner is likely to be a desperate man. ያመለጠ ፡ እስረኛ ፡ ተስፋ ፡ በመቍረጥ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ከማድረግ ፡ አይመለስም

**escarpment ቀጥ ፡ ያለው ፡ ገደል**
The escarpment runs along a desert valley. ቀጥ ፡ ያለው ፡ ገደል ፡ የምድረ ፡ በዳውን ፡ ሸለቆ ፡ ይዋሰናል

**eschew**
1. **ቀረ(በት)**. +You should eschew wine if you wish to stay healthy. ጤናማ ፡ ሆነህ ፡ ለመኖር ፡ ከፈለግህ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ይቅርብህ
2. **ከ - - - ራቀ**. A saint must eschew evil thoughts. ቅዱስ ፡ ከክፉ ፡ ሐሳብ ፡ መራቅ ፡ አለበት

**escort** (v.)
1. **ሸኘ**. Who will escort this young lady home? ልጂቱን ፡ ማን ፡ ይሸኛታል ?
2. **ዐጀበ**. Warships escorted the troopships. ወታደር ፡ የያዙትን ፡ መርከቦች ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ ዐጅበዋቸዋል

**escort** (n.) **አብሯት ፡ የሄደ ፡ ጓደኛ**
Her escort to the party was a tall, young man. ወደ ፡ ፓርቲው ፡ አብሯት ፡ የሄደው ፡ ጓደኛዋ ፡ ረዥም ፡ ያለ ፡ ወጣት ፡ ነበር

**escort of ዐጃቢዎች**
An escort of soldiers preceded the Emperor down the street. መንገዱ ፡ ላይ ፡ ዐጃቢዎቹ ፡ ወታደሮች ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊት ፡ ፊት ፡ ተጓዙ

**escutcheon** [አርማ ፡ የተሣለበት ፡ ጋሻ]

**especially በተለይ**
The poor especially suffered a lot. በተለይ ፡ ድኾች ፡ ብዙ ፡ ተሠቃዩ

**espionage ስለላ**
He was found guilty of espionage. በስለላ ፡ ወንጀል ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ተፈረደበት

**esplanade**
[በተለይ ፡ በጠረፉ ፡ ዳርቻ ፡ ያለ ፡ ዝርግ ፡ ደልዳላ ፡ ቦታ]

**espouse**
1. **ዳረ**. He espoused his daughter to a nobleman. ሴት ፡ ልጁን ፡ ላንድ ፡ መኳንንት ፡ ዳረ
2. **ተቀበለ**. Late in life he espoused a new religion. በዕድሜ ፡ ከገፋ ፡ በኋላ ፡ አዲስ ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀበለ
3. **ደገፈ**. The people espoused the freedom movement of the patriots. ሕዝቡ ፡ አርበኞች ፡ ያደረጉትን ፡ የነጻነት ፡ እንቅስቃሴ ፡ ደገፈ

**essay** (v.) **ሞከረ**
He essayed to cross the river on a log. ወንዙን ፡ በግንድ ፡ ለመሻገር ፡ ሞከረ

**essay** (n.)
1. **ድርሰት**. He likes to write essays on Ethiopia's literature. እርሱ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ድርሰት ፡ መጻፍ ፡ ይወዳል
2. **ፍላጎት**. His essays at friendliness were met with suspicion. ለመጐዳኘት ፡ ያለውን ፡ ፍላጎት ፡ በጥርጣሬ ፡ ተመለከቱት

**essence**
1. **መሠረት**. A friendly attitude is the essence of peace. የወዳጅነት ፡ መንፈስ ፡ ለሰላም ፡ መሠረት ፡ ነው
2. **ፍሬ ፡ ነገር**. The essence of his speech is contained in the last sentences. የንግግሩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በመጨረሻዎቹ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል
3. **ባሕርይ**. The two things are the same in outward appearance, but different in essence.

ሁለቱ ፡ ነገሮች ፡ በውጭ ፡ መልካቸው ፡ አንድ ፡
ሲሆኑ ፡ በባሕርይ ፡ ግን ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው

**be of the essence** በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
In chess, cool nerves are of the essence.
በሰንጠረዥ ፡ ጨዋታ ፡ ጊዜ ፡ ታጋሽነት ፡ በጣ
ም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**essential** (n.) ዋና ፡ ዋና፡ ነገር
You can learn the essentials in an hour.
ዋና ፡ ዋናውን ፡ ነገር ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ለመ
ማር ፡ ትችላለህ

**essential** (adj.)
1. ተፈላጊ. The body of the book contains all the essential facts. የመጽሐፉ ፡ ዋና ፡ ክፍል ፡
ተፈላጊዎቹን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ በሙሉ ፡ አዝሏል
2. ዋና ፡ ዋና. He changed the report in order to clear the essential points. ዋና ፡ ዋናዎ
ቹን ፡ ጉዳዮች ፡ በግልጽ ፡ ለማቅረብ ፡ ሪፖርቱን ፡
ለወጠው
3. በጣም ፡ አስፈላጊ. Fresh vegetables are essential to health. ትኩስ ፡ ቅጠላ ፡ ቅጠል ፡ ለጤና ፡
በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
4. የሚያስፈልግ ፡ ነገር. Limit your expenditures to what is essential! ወጪህን ፡ ለሚያስፈልግ ፡
ነገር ፡ ብቻ ፡ ወስን

**essentially** በመሠረቱ
Essentially he is right. በመሠረቱ ፡ እሱ ፡ ልክ ፡
ነው

**establish**
1. አቋቋመ ፤ መሠረተ. He established a new government. አዲስ ፡ መንግሥት ፡ አቋቋመ ፡ (መ
ሠረተ)
2. አቆመ. He established his son in business.
ልጁን ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ አቆመው
3. አመጣ. He established a new record.
አዲስ ፡ ክብረ ፡ ወሰን ፡ አመጣ
4. አወጣ. He established the rule that mathematics should be taught in the sixth grade. ሒሳ
ብ ፡ ስድስተኛ ፡ ክፍል ፡ እንዲሰጥ ፡ ሲል ፡ ደንብ ፡
አወጣ
5. አስከበረ. The Romans established order in the countries they subdued. ሮማውያን ፡ በያ
ዙት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ጸጥታን ፡ አስከበሩ

**established** (adj.) የታወቀ
Criminal jurisprudence is an established subject of study. የወንጀል ፡ ሕግ ፡ ፍልስፍና ፡ የታ
ወቀ ፡ ትምህርት ፡ ነው

**be established** ተደላደለ
We are now comfortably established in our new house. አሁን ፡ ባዲሱ ፡ ቤታችን ፡ ውስጥ ፡ በ
ሚገባ ፡ ተደላድለናል

**establish oneself** ራሱን ፡ አደረገ
He established himself as the leader of the party. ራሱን ፡ የፓርቲው ፡ መሪ ፡ አደረገ
*A new doctor has established himself on this street. አዲስ ፡ ሐኪም ፡ በዚህ ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡
የሕክምና ፡ ቤት ፡ ከፍቷል

**establishment**
1. (verbal noun) ማቋቋም. The establishment of the business took several years. የንግዱን ፡
ሥራ ፡ ለማቋቋም ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ፈጀ
2. መቆርቆር. The establishment of a new town will help to promote trade. ያዲስ ፡
ከተማ ፡ መቆርቆር ፡ ንግድን ፡ ለማስፋፋት ፡ ይረዳል
3. መደብር. That clothing establishment has been on this street for 60 years. ያ ፡ የልብስ ፡
መደብር ፡ ለስድሳ ፡ ዓመት ፡ በዚህ ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡ ቆ
ይቷል

**estate**
1. ርስትና ፡ ንብረት. His entire estate went to his oldest son. ርስትና ፡ ንብረቱ ፡ ሁሉ ፡ ለበኵር ፡
ልጁ ፡ ተሰጠ
2. ንብረት. He left his estate to one of the charities. ንብረቱን ፡ ላንድ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡
ድርጅት ፡ ትቶ ፡ ሞተ
3. ርስት. The minister lives on a large estate in the country. ሚኒስትሩ ፡ በገጠር ፡ ሰፊ ፡ ርስ
ት ፡ ላይ ፡ ይኖራል
4. የግል ፡ መሬት. He drives a car only within the bounds of his estate. በግል ፡ መሬቱ ፡ ክል
ል ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ መኪና ፡ ይነዳል

**man's estate** ዓቅመ ፡ አዳም
A boy attains man's estate at fifteen. ልጅ ፡ ዓ
ቅመ ፡ አዳም ፡ የሚደርሰው ፡ በዐሥራ ፡ አምስ
ት ፡ ዓመቱ ፡ ነው

**esteem** (v.)
1. አከበረ. I esteem his father for his wisdom.
ስለ ፡ ጥበቡ ፡ አባቱን ፡ አከብራለሁ
2. አደነቀ. We esteem courage. ጀግንነትን ፡ እ
ናደንቃለን
3. አድርጎ ፡ ቈጠረ. Men often esteem happiness the greatest good. ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡
ደስታን ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ነገር ፡ አድርገው ፡ ይቈ
ጥሩታል

**be esteemed** ተወደደ
Raw meat is greatly esteemed by Ethiopians.
ጥሬ ፡ ሥጋ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ የ
ተወደደ ፡ ነው

**esteem** (n.)
1. ከፍተኛ ፡ አስተያየት. He lowered himself in our esteem by his foolish behavior. የማይረባ ፡ ጠባዩ ፡ ስለሱ ፡ የነበረንን ፡ ከፍተኛ ፡ አስተያየት ፡ ዝቅ ፡ አደረገው
2. ግምት. She was greatly grieved because of the low esteem he had of her. በሷ ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ዝቅተኛ ፡ ግምት ፡ በጣም ፡ አዘነች
3. ክብር. Courage is held in esteem. ጀግንነት ፡ ክብር ፡ ነው

**hold in great esteem** ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ገመተ
He holds me in great esteem. እርሱ ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ይገምተኛል

**estimate** (v.) ገመተ
He estimated the flood damage at a million dollars. ጐርፉ ፡ ያደረሰውን ፡ ጉዳት ፡ ባንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ ገመተ

**estimate** (n.) ግምት
Is this a good book in your estimate? ባንተ ፡ ግምት ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ምርጥ ፡ ነው ?

**make an estimate** ግምት ፡ ነገረ
The painter made us an estimate. ቀለም ፡ ቀቢው ፡ ግምቱን ፡ ነገረን

**estimation** ግምት
In my estimation, this book is very well written. በኔ ፡ ግምት ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ጥሩ ፡ ተጽፏል
The high estimation in which he is held by his friends flatters him. ጓደኞቹ ፡ የሚሰጡት ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ያኩራዋል

**estrange**
1. አለያየ. Her peculiar behavior has estranged her from her friends. እንግዳ ፡ ጠባይዋ ፡ ከወዳጆቿ ፡ አለያያት
2. አራቀ. He has estranged his friends by gossiping. በሐሜታው ፡ ጓደኞቹን ፡ አራቃቸው

**estuary** [ወንዝ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ የሚፈስበት ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ መገናኛ]

**etc.** የመሳሰሉ ፤ ወዘተ
I hate to pay duties, fees, etc. ግብርና ፡ ቀረጥ ፡ የመሳሰሉትን ፡ ነገሮች ፡ (ወዘተ) ፡ መክፈል ፡ አልወድም

**etching**
[ከዝርግ ፡ ብረት ፡ የተቀረጸ ፡ ሥዕል ፡ ወይም ፡ ንድፍ]

**eternal**
1. ዘለዓለማዊ. The Christian religion promises eternal life. የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ የዘለዓለማዊ ፡ ሕይወት ፡ ተስፋ ፡ ይሰጣል
2. የማያልቅ. Stop this eternal chatter! ይህን ፡ የማያልቅ ፡ ወሬ ፡ አቁም
3. መሠረታዊ. This sect adheres to the eternal principles of the church. ይህ ፡ እምነት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማ ፡ ይከተላል

**eternity**
1. ዘለዓለማዊ ፡ ሕይወት. He will spend eternity in paradise. ዘለዓለማዊ ፡ ሕይወትን ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ያሳልፋል
2. ዘለዓለምነት. Eternity is timeless. ዘለዓለምነት ፡ የጊዜ ፡ ወሰን ፡ የለውም

**an eternity** ለብዙ ፡ ጊዜ
The injured man waited an eternity for the ambulance to arrive. የተጐዳው ፡ ሰውዬ ፡ አምቡላንሱ ፡ እስኪደርስ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጠበቀ
*It seemed an eternity to her before she learned of his safe arrival. ደኅና ፡ መግባቱን ፡ እስክትሰማ ፡ ጊዜው ፡ አልገፋ ፡ አላት

**ether**
[በሚተነፈስበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያደነዝዝ ፡ መድኃኒት]

**ethical**
1. የሐቀኝነት. Ethical behavior is required of lawyers. ከጠበቆች ፡ የሐቀኝነት ፡ ምግባር ፡ ይፈለጋል
2. (= noun) ሥነ ፡ ምግባር. It is not ethical for a lawyer to reveal secrets. ጠበቃ ፡ ሆኖ ፡ ምስጢርን ፡ ማውጣት ፡ ከሥነ ፡ ምግባር ፡ ውጭ ፡ ነው

**ethics** የሥነ ፡ ምግባር ፡ ትምህርት
He studied ethics in college. በኮሌጅ ፡ የሥነ ፡ ምግባር ፡ ትምህርት ፡ ተማረ

**Ethiopia** ኢትዮጵያ

**Ethiopian** (n.) ኢትዮጵያዊ (pl. ኢትዮጵያውያን)
Many Ethiopians study at the University of California. በካሊፎርኒያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ውስጥ ፡ የሚማሩ ፡ ብዙ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አሉ

**Ethiopian** (adj.) የኢትዮጵያ
He studies Ethiopian languages. የኢትዮጵያ ፡ ቋንቋዎች ፡ ያጠናል

**ethnic group** ጐሳ
Nigerians are a mixture of several different ethnic groups. ናይጀሪያውያን ፡ የብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጐሳዎች ፡ ድብልቅ ፡ ናቸው

**etiquette** ሥነ ፡ ሥርዓት
Etiquette requires a man to rise when a woman enters the room. ሴት ፡ ስትገባ ፡ ወንድ ፡ እንዲነሣ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ያስገድደዋል

**etymology** (etymologies) መሠረተ ፡ አመጣጥ ፤ ሥርው
The etymology of many Geez roots is not yet known. የብዙ ፡ የግዕዝ ፡ ቃላት ፡ መሠረተ ፡ አመጣጥ ፡ (ሥርው) ፡ ገና ፡ አይታወቅም

**eucalyptus** ባሕር ፡ ዛፍ
The eucalyptus tree was recently introduced to Ethiopia. ባሕር ፡ ዛፍ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጣው ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ነው

**eulogy** (eulogies) ለሞተ ፡ ሰው ፡ የቀረበ ፡ ውዳሴ
The priest's eulogy was written in Geez. ቄሱ ፡ ለሞተው ፡ ሰው ፡ ያቀረበው ፡ ውዳሴ ፡ የተጻፈው ፡ በግዕዝ ፡ ነበር

**deliver a eulogy** ሟቹን ፡ አመስግኖ ፡ ተናገረ
The director delivered the eulogy at the funeral of his employee. ዲሬክተሩ ፡ በሠራተኛው ፡ ሥርዓተ ፡ ቀብር ፡ ላይ ፡ ሟቹን ፡ አመስግኖ ፡ ተናገረ

**eunuch** ጃንደረባ
The messenger of the Queen of Sheba was a eunuch. የንግሥተ ፡ ሳባ ፡ መልእክተኛ ፡ ጃንደረባ ፡ ነበረ

**euphorbia** ቁልቋል
The euphorbia grows in many parts of Ethiopia. ቁልቋል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ይበቅላል

**Europe** አውሮፓ ፤ አውሮጳ

**evacuate**
1. ከ - - -ወጣ. Shoppers had to evacuate the burning building. ገበያተኞች ፡ ከሚቃጠለው ፡ ሕንጻ ፡ መውጣት ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው
2. ለቆ ፡ ወጣ. They evacuated the city. ከተማውን ፡ ለቀው ፡ ወጡ
3. አዛወረ. The government evacuated all foreign residents from the war zone. መንግሥቱ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎችን ፡ ከጦሩ ፡ ክልል ፡ አዛወረ
4. ሕዝብ ፡ አስለቀቀ. The government evacuated the area threatened by the fire. መንግሥት ፡ የእሳት ፡ አደጋ ፡ ያሰጋውን ፡ መንደር ፡ ሕዝብ ፡ አስለቀቀ
5. አስወጣ. If poison is swallowed, it will be necessary to evacuate the stomach. መርዝ ፡ ሲዋጥ ፡ ከሆድ ፡ ውስጥ ፡ ቶሎ ፡ ማስወጣት ፡ ያስፈልጋል

**be evacuated** ተወሰዱ
The women and children were evacuated to the country. ሴቶቹና ፡ ሕፃናቱ ፡ ወደ ፡ ባላገር ፡ ተወሰዱ

**evade**
1. አመለጠ. He tried to evade the law. ከሕግ ፡ ለማምለጥ ፡ ሞከረ
2. ሸሸ. He will evade the question about what he has done with the money. ገንዘቡን ፡ ምን ፡ እንዳደረገው ፡ የሚቀርብለትን ፡ ጥያቄ ፡ ሁሉ ፡ ይሸሻል
3. አድበሰበሰ. An equivocal answer is one that evades the question. አጠራጣሪ ፡ መልስ ፡ ነገር ፡ ያድበሰብሳል
*There are many words in the language that evade definition. በቋንቋው ፡ ውስጥ ፡ ፍች ፡ ሊሰጣቸው ፡ የማይችሉ ፡ ብዙ ፡ ቃላት ፡ አሉ

**evaluate**
1. አመዛዘነ. It is difficult to evaluate the importance of today's happenings. የዘመኑን ፡ ድርጊቶች ፡ አስፈላጊነት ፡ ለማመዛዘን ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. ገመገመ. Critics evaluate the new books as they are published. ተቺዎች ፡ አዳዲስ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ ታተሙ ፡ ይገመግማሉ

**evanescent**
*I have evanescent memories of early childhood. የልጅነት ፡ ጊዜዬ ፡ እየተረሳኝ ፡ ሄደ

**be evanescent** እንደ ፡ ዋለ ፡ ቀረ
His fame was evanescent. ዝናው ፡ እንደዋለ ፡ ቀረ

**evangelist** ወንጌላዊ
Evangelists accompanied the Spanish colonizers in South America. ወንጌላውያን ፡ የእስፓኝ ፡ ቅኝ ፡ ገዢዎችን ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ መጡ

**evangelize** ወንጌል ፡ ሰበከ
The missionaries evangelized the population of South America. ሚስዮናውያን ፡ የደቡብ ፡ አሜሪካን ፡ ሕዝብ ፡ ወንጌል ፡ ሰበኩት

**evaporate** (vt.) አተነነ
The sun evaporates water. ፀሐይ ፡ ውኃን ፡ ያተናል

**evaporate** (vi.) ተነነ
The fluid has evaporated. ፈሳሹ ፡ ተኗል

**(one's) courage evaporated** ውኃ ፡ ሆነ
His courage evaporated when he saw the lion. አንበሳውን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ውኃ ፡ ሆነ

**evaporation**
1. ተን. Evaporation reduces the quantity of water available to the farm. ተን ፡ እርሻ ፡ የሚያገኘውን ፡ የውኃ ፡ መጠን ፡ ይቀንሳል

2. (የ)ውኃ ፡ መትነን. Milk is condensed by evaporation. ወተት ፡ የሚረጋው ፡ ውኃው ፡ በመትነኑ ፡ ነው

**evasion**

1. ማድበስበስ. His evasion of the question is evidence of his guilt. ነገሩን ፡ ማድበስበሱ ፡ ጥፋተኛ ፡ ለመሆኑ ፡ መረጃ ፡ ነው

2. መዘንጋት. The employee was punished for his evasion of responsibility. ሠራተኛው ፡ ኀላፊነቱን ፡ በመዘንጋቱ ፡ ተቀጣ

**evasive** የማይጨበጥ

He gave me a very evasive answer. ፍጹም ፡ የማይጨበጥ ፡ መልስ ፡ ሰጠኝ

**eve** ዋዜማ

Where will you be New Year's Eve? ባዲሱ ፡ ዓመት ፡ ዋዜማ ፡ የት ፡ ትገኛለህ ?

The eve of their departure has arrived. የመሄጃቸው ፡ ዋዜማ ፡ ደርሷል

**even** (v.) አስተካከለ

She evened the edges by trimming them. ጠርዙን ፡ በመቍረጥ ፡ አስተካከለችው

**even out** አስተካከለ

We will have to even out these irregularities first. መጀመሪያ ፡ እነዚህን ፡ የተዛቡ ፡ ነገሮች ፡ ማስተካከል ፡ ይኖርብናል

**even** (adj.)

1. የተደላደለ. He has an even disposition. የተደላደለ ፡ ጠባይ ፡ አለው

2. ደልዳላ. Let's rest here where the ground is even! ደልዳላ ፡ ከሆነው ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ እንረፍ

3. ሙሉ. Two, four, and six are even numbers. ሁለት ፡ አራት ፣ ስድስት ፡ ሙሉ ፡ ቁጥር ፡ ናቸው

4. እኩል. The two horses were even in the race. ሁለቱ ፡ ፈረሶች ፡ በእሽቅድድሙ ፡ እኩል ፡ ነበሩ

We are even in rank, though not in age. በዕድሜ ፡ ብንለያይም ፡ በማዕረግ ፡ እኩል ፡ ነን

5. ትክክል. Check to see if the scales are even! ሚዛኑ ፡ ትክክል ፡ መሆኑን ፡ ተመልከት

*The car goes with an even motion. መኪናው ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ ይፈሳል

**be even** ደረሰ

The sand was even with the window. አሸዋው ፡ ከመስኮቱ ፡ ጠርዝ ፡ ደርሷል

*If I pay you 10 dollars, we are even. ዐሥር ፡ ብር ፡ ከከፈልኩህ ፡ ምንም ፡ አይኖርብኝም

**break even**

He is just breaking even. ትርፍም ፡ ኪሳራም ፡ የለበትም

**get even with** ብድር ፡ መለሰ

Just wait, I'll get even with you! ጠብቅ ፣ ብድሬን ፡ እመልሳለሁ

**even** (adv.)

1. እንኳን ፣ እንኳ ፣ ---ም ፡ እንኳ. Even a layman can understand that. ተራው ፡ ሰው ፡ እንኳን ፡ ይህንን ፡ ሊረዳው ፡ ይችላል

He was faithful even unto death. እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ እንኳን ፡ ታማኝ ፡ ነበር

He didn't even open the letter. ደብዳቤውን ፡ እንኳ ፡ አልከፈተም

Even now, I cannot convince her. አሁንም ፡ እንኳ ፡ ላሳምናት ፡ አልችልም

2. እንኳን ፡ ሳይቀር. They confiscated everything, even personal property. የግል ፡ ንብረት ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ውርስ ፡ አደረጉ

3. እንዲያውም. You can read even better if you try. ብትሞክር ፡ እንዲያውም ፡ የተሻለ ፡ ልታነብ ፡ ትችላለህ

He is ready, even eager, to fight. ለመጋጠም ፡ ዝግጁ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እንዲያውም ፡ ጓጉታል

**even as**

1. ልክ ፡ ስ + (imperfect). Even as I spoke the warning, he fell into the hole. ልክ ፡ ማስጠንቀቂያውን ፡ ስናገር ፡ ጉድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ገባ

2. እንደ + (perfect). He hurt himself even as I had said he would. ልክ ፡ እንዳልኩት ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ አደረሰ

3. እየ + (perfect). She answered even as I spoke. በመናገር ፡ ላይ ፡ እያለሁ ፡ መልስ ፡ ሰጠች

**even at that** ያም ፡ ቢሆን

Even at that, I would not pay more. ያም ፡ ቢሆን ፡ ከዚያ ፡ ይበልጥ ፡ አልከፍልም

**even if** ብ + imperfect + ም ፡ እንኳን ፣ ብ + imperfect + ም

I will go even if it rains. ቢዘንብም ፡ እንኳን ፡ እሄዳለሁ (or ቢዘንብም ፡ እሄዳለሁ)

**even more** የባሰ

You are even more stupid than your brother. ከወንድምህ ፡ የባሰክ ፡ ደደብ ፡ ነህ

**even so** ቢሆንም

Even so, I can't agree with you. ቢሆንም ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ አልስማማም

**even though**

1. ብ + imperfect + ም ፡ እንኳ. Even though he succeeds in everything, he is not satisfied. ሁሉም ፡ ነገር ፡ ቢሳካለትም ፡ እንኳ ፡ በቃኝ ፡ አይልም

2. ብ + imperfect + ም. He went there even

though I warned him against it. እንዳይሄድ ፡ ብስጠነቅቀውም ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ሄደ
[See also 'not, now']

**evening**
1. ምሽት. Let us spend the evening in the bar! ምሽቱን ፡ በቡና ፡ ቤት ፡ እናሳልፍ
2. ማታ. Let us meet in the evening! ማታ ፡ እንገናኝ

**evenings** ማታ ፡ ማታ
Is this restaurant open evenings? ይህ ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ክፍት ፡ ነው ?
The evenings here are cool. እዚህ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ቀዝቀዝ ፡ ይላል

**every evening** ማታ ፡ ማታ
We take a walk every evening. ማታ ፡ ማታ ፡ ሽርሽር ፡ እንሄዳለን

**get evening** መሸ
It gets evening early here. እዚህ ፡ ቶሎ ፡ ይመሻል

**good evening!** እንዴት ፡ አመሸህ? (for the sg. 2nd pers. masc.)
"Good evening!", they said as they entered the house. እነሱ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ እንደገቡ ፡ « እንዴት ፡ አመሻችሁ ? » ፡ አሉ

**late in the evening** በጣም ፡ አምሽቶ ፤ ሲመሽ
He comes home late in the evening. ወደ ፡ ቤት ፡ የሚመጣው ፡ በጣም ፡ አምሽቶ ፡ (ሲመሽ) ፡ ነው

**this evening** ዛሬ ፡ ማታ
Are they coming this evening? ዛሬ ፡ ማታ ፡ ይመጣሉ ?
[See also 'spend']

**evenly**
1. እኩል. Divide the apples evenly among you! ቱፋውን ፡ እኩል ፡ ተካፈሉ
2. ተስተካክሎ. The paint isn't spread evenly. ቀለሙ ፡ ተስተካክሎ ፡ አልተቀባም
[See also 'spin']

**event**
1. ድርጊት. It was the most important event of the year. ባመቱ ፡ ውስጥ ፡ ከተደረጉት ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ድርጊት ፡ ነበር
2. ጉዳይ. He has a lively interest in political events. ስለ ፡ ፖለቲካ ፡ ጉዳዮች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሜት ፡ አለው
3. የሚሆን ፡ ነገር. We made careful plans and awaited the event. እቅዶቹን ፡ በጥንቃቄ ፡ አውጥተን ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ ተጠባበቅን
4. ሁኔታ. The war has shaped the events of the future in many ways. ጦርነቱ ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ የወደፊት ፡ ሁኔታን ፡ መርቷል.

**at all events** የሆነው ፡ ቢሆን
At all events, she will take care of you until you are completely recovered. የሆነው ፡ ቢሆን ፡ ፈጽሞ ፡ እስክትድን ፡ ድረስ ፡ ታስታምምሃለች

**in any event** ምንም ፡ ቢሆን
I'll be there in any event. ምንም ፡ ቢሆን ፡ እዚያ ፡ እገኛለሁ

**in the event of**
1. ሲደርስ. In the event of an accident, notify the police. አደጋ ፡ ሲደርስ ፡ ለፖሊስ ፡ አስታውቅ
2. ከሆነ. In the event of rain, the party will be held indoors. ዝናም ፡ ከሆነ ፡ ፓርቲው ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ይደረጋል
[See also 'chain, course, march']

**eventful** ብዙ ፡ ድርጊት ፡ የተፈጸመበት
The eventful day left him exhausted. ብዙ ፡ ድርጊት ፡ የተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ መሆኑ ፡ በጣም ፡ አደከመው

**eventual** (= adv.) በመጨረሻ
His eventual success is certain. በመጨረሻ ፡ እንደሚቀናው ፡ እሙን ፡ ነው
*His mistakes led to his eventual dismissal. ስሕተቶቹ ፡ ከሥራ ፡ እስከ ፡ መውጣት ፡ አደረሱት

**eventually**
1. በመጨረሻ. We eventually became friends. በመጨረሻ ፡ ጓደኞች ፡ ሆንን
2. ውሎ ፡ አድሮ. Eventually we will have to agree on his proposal. ውለን ፡ አድረን ፡ በአሳቡ ፡ መስማማት ፡ አለብን
3. እያደር. He was certain that the political situation would eventually clarify. እሱ ፡ የፖለቲካው ፡ ሁኔታ ፡ እያደር ፡ ግልጽ ፡ እንደሚሆን ፡ እርግጠኛ ፡ ነበር
*He will eventually arrive. የኋላ ፡ ኋላ ፡ መምጣቱ ፡ አይቀርም

**ever**
1. gerundive of main verb + ያውቃል (or አያውቅም) occasionally reinforced by another word. Have you ever been in the United States? አሜሪካን ፡ አገር ፡ ሄደህ ፡ ታውቃለህ ?
Is he ever at home? ለመሆኑ ፡ እቤቱ ፡ ገብቶ ፡ ያውቃል ?
Haven't you ever been there? በፍጹም ፡ እዚያ ፡ ሄደህ ፡ አታውቅም ?
2. ምንጊዜም ፡ እንዴ. Won't this gossip ever end? ይህ ፡ አሉባልታ ፡ ምንጊዜም ፡ አያልቅ ፡ እንዴ ?

3. ምንጊዜም. This is the best work you have ever done. ምንጊዜም ፣ ከሠራኸው ፣ ሥራ ፣ ሁሉ ፣ ይኸኛው ፣ በጣም ፣ የበለጠ ፣ ነው
4. ሁልጊዜ. A mother is ever ready to help her children. እናት ፣ ልጆቿን ፣ ለመርዳት ፣ ሁልጊዜ ፣ ዝግጁ ፣ ናት
5. (zero). What did you ever do to make him so angry? ይህን ፣ ያህል ፣ የሚያናድድ ፣ ምን ፣ ነገር ፣ አደረግኸው ?
*If you had ever before gone abroad, you would think differently. ከሁን ፣ ቀደም ፣ ወደ ፣ ውጭ ፣ አገር፣ሄደህ ፣ ቢሆን ፣ ኖሮ ፣ አስተሳሰብህ ፣ የተለየ ፣ ይሆን ፣ ነበር

**ever after** ከዚያ ፣ በኋላ
They married and lived happily ever after. ተጋብተው ፣ ከዚያ ፣ በኋላ ፣ በደስታ ፣ ኖሩ

**ever so** በጣም
The ocean is ever so deep. ውቅያኖስ ፣ በጣም ፣ ጥልቅ ፣ ነው

**ever so much** እጅግ
Thank you ever so much! እጅግ ፣ አመሰግናለሁ

**if ever** አንድ ፣ ቀን
If you ever visit London, see the Tower. አንድ ፣ ቀን ፣ ሎንዶንን ፣ ስትጐበኝ ፣ ታወሩን ፣ እንድታየው
*She seldom, if ever, goes to the cinema. ሲኒማ ፣ ብትሄድም ፣ እንኳ ፣ አልፎ ፣ አልፎ ፣ ነው

**nothing ever** ምንም ፣ ድርጊት + negative verb
Nothing ever happens in this village. በዚህ ፣ መንደር ፣ ውስጥ ፣ ምንም ፣ ድርጊት ፣ አይፈጸምም

**than ever** ከመቼውም
It is raining harder than ever. ከመቼውም ፣ የባሰ ፣ በኀይል ፣ ይዘንባል

**than ever before** ከመቼውም
The study of science is more necessary than ever before. የሥነ ፣ ፍጥረት ፣ ጥናት ፣ ከመቼውም ፣ ይልቅ ፣ አሁን ፣ በይበልጥ ፣ ተፈላጊ ፣ ነው
[See also 'since, what, worse']

## evergreen ቅጠሉ ፣ የማይረግፍ
Evergreen trees grow in northern countries. ቅጠላቸው ፣ የማይረግፍ ፣ ዛፎች ፣ በሰሜናዊ ፣ ሀገሮች ፣ ይበቅላሉ

## everlasting
1. የዘለዓለም. God damned the Sodomites to everlasting punishment. እግዚአብሔር ፣ በሰዶማውያን ፣ ላይ ፣ የዘለዓለም ፣ ቅጣት ፣ ፈረደባቸው
2. ማለቂያ ፣ የሌለው. I am tired of your everlasting complaints. ማለቂያ ፣ የሌለው ፣ ንዝንዝህ ፣ አሰልችቶኛል

## evermore ሁልጊዜ
Promise that you will evermore be faithful! ሁልጊዜ ፣ ታማኝ ፣ እንደምትሆን ፣ ቃል ፣ ግባልኝ

## every
1. እያንዳንድ. Give every child one! ለያንዳንዱ ፣ ልጅ ፣ አንዳንድ ፣ ስጥ
2. ማንኛውም. In every way our plan is better than yours. በማንኛውም ፣ ረገድ ፣ የኛ ፣ እቅድ ፣ ከናንተ ፣ የተሻለ ፣ ነው
3. ሙሉ. I have every confidence in him. በሱ ፣ ላይ ፣ ሙሉ ፣ እምነት ፣ አለኝ
4. ሁሉ. I read every book on the list. በዝርዝሩ ፣ ላይ ፣ ያለውን ፣ መጽሐፍ ፣ ሁሉ ፣ አነበብኩ
5. በየ. He comes here every week. በየሳምንቱ ፣ እዚህ ፣ ይመጣል

**every bit** በማንኛውም ፣ በኩል
Our food is every bit as good as yours. ምግባችን ፣ በማንኛውም ፣ በኩል ፣ እንደናንተው ፣ ምግብ ፣ ጥሩ ፣ ነው

**every day** በየቀኑ
Such things do not happen every day. እንደዚህ ፣ ያሉ ፣ ነገሮች ፣ በየቀኑ ፣ አይሆኑም
I see him every day. በየቀኑ፣ አየዋለሁ

**every few days** አልፎ ፣ አልፎ
I go there every few days. አልፎ ፣ አልፎ ፣ እዚያ ፣ እሄዳለሁ

**every now and then** አልፎ ፣ አልፎ
He takes a drink every now and then. አልፎ ፣ አልፎ ፣ ይጠጣል

**every once in a while** አልፎ ፣ አልፎ
He takes a drink every once in a while. አልፎ ፣ አልፎ ፣ ይጠጣል

**every one of**
1. እያንዳንድ. Every one of us received a pack of cigarettes. እያንዳንዳችን ፣ አንዳንድ ፣ ፓኮ ፣ ሲጋራ ፣ ተቀበልን
2. በሙሉ. Every one of the children came. ልጆቹ ፣ በሙሉ ፣ መጡ

**every one of them** ሁሉም
Every one of them studies hard. ሁሉም ፣ በርትተው ፣ ያጠናሉ

**every other day** እያሠለሱ
They have meat every other day. እያሠለሱ ፣ ሥጋ ፣ ይበላሉ

**every time** (adv.) ሁልጊዜ
Our football team wins every time. የእግር ፣ ኳስ ፣ ቡድናችን ፣ ሁልጊዜ ፣ ያሸንፋል

**every time** (conj.) በ + perfect + ቁጥር
It rains every time we want to go out. ወደ ፡ ውጭ ፡ መሄድ ፡ በፈለግን ፡ ቁጥር ፡ ይዘንባል
[See also 'aspect, each, often, other']

**everybody** ሁሉ ፡ ሰው
Is everybody on board? ሁሉ ፡ ሰው ፡ ተሳፍሯል ?
Everybody laughed. ሁሉ ፡ ሰው ፡ ሣቀ
[See also 'else, most']

**everyday**
1. የዘወትር. A person wears everyday clothes to work. አንድ ፡ ሰው ፡ ለሥራ ፡ የዘወትር ፡ ልብስ ፡ ይለብሳል
2. የተራ. The diction of everyday talk is different from that of the essay. የተራ ፡ ንግግርና ፡ የድርሰት ፡ አጻጻፍ ፡ ስልት ፡ የተለዩ ፡ ናቸው
3. (= adv.) በየቀኑ. Accidents are everyday occurrences. አደጋ ፡ በየቀኑ ፡ የሚደርስ ፡ ነገር ፡ ነው

**everyone**
1. እያንዳንዱ ፡ ሰው. Everyone has to fulfill his duties toward his country. እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ለሀገሩ ፡ ያለውን ፡ ግዳጅ ፡ መፈጸም ፡ አለበት
2. ማንም. Everyone recognizes him to be an authority on Ethiopia. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዐዋቂ ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ ይቀበለዋል

**everything**
1. ማንኛውም ፡ ነገር. This shop sells everything needed for camping. ይህ ፡ መደብር ፡ ለካምፕ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ይሸጣል
2. ሁሉ ፡ ነገር ፤ ነገር ፡ ሁሉ. He has mixed up everything. ሁሉን ፡ ነገር ፡ አደበላልቆታል
I will do everything that is necessary. የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አደርጋለሁ
[See also 'else']

**everywhere**
1. በያለበት. Lamentations were heard everywhere when the king died. ንጉሡ ፡ ሲሞት ፡ በያለበት ፡ ለቅሶ ፡ ተሰማ
2. ሁሉም ፡ ቦታ. I have looked everywhere for that book. ያንን ፡ መጽሐፍ ፡ ሁሉም ፡ ቦታ ፡ ፈለግሁት
3. በየቦታው. People passed out leaflets everywhere. ሰዎች ፡ በየቦታው ፡ ጽሑፍ ፡ ዐደሉ

**evict** አስወጣ
The landlord evicted the tenants. የቤቱ ፡ ጌታ ፡ ተከራዮቹን ፡ አስወጣቸው

**evidence** (v.) ገለጸ
His smile evidences his pleasure. ፈገግታው ፡ ደስታውን ፡ ይገልጻል

**evidence** (n.) ማስረጃ ፤ መረጃ
He was convicted on false evidence. በሐሰት ፡ ማስረጃ ፡ ተፈረደበት
The case was thrown out of court for lack of evidence. መረጃ ፡ በመታጣቱ ፡ ክሱ ፡ ተሰረዘ
Her smile is clear evidence of her pleasure. ፈገግታዋ ፡ ለመደሰቷ ፡ ጉልህ ፡ ማስረጃ ፡ ነው

**be in evidence** ታየ
He is nowhere in evidence. የትም ፡ ቦታ ፡ አይታይም
*A crying baby is much in evidence. የሚያለቅስ ፡ ሕፃን ፡ ከሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ ተለይቶ ፡ በቀላሉ ፡ ይታያል ፡ (ይታወቃል)

**give evidence**
1. አመለከተ. The blood on the floor gave evidence of a fight. በወለሉ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ደም ፡ ጥል ፡ እንደነበረ ፡ አመለከተ
2. (= passive) ምልክት ፡ ታየ(በት). He gave no evidence of having understood. እንደገባው ፡ ምንም ፡ ምልክት ፡ አልታየበትም

**evident**
1. የተረጋገጠ. It is evident that he cannot come. ለመምጣት ፡ አለመቻሉ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው
2. ግልጽ. It was evident to all that the project was a failure. እቅዱ ፡ ውድቅ ፡ መሆኑ ፡ ለሁሉም ፡ ግልጽ ፡ ነበር
His good intentions are evident to all. መልካም ፡ አሳቢነቱ ፡ ለማንም ፡ ግልጽ ፡ ነው

**evidently** (= adj.) ግልጽ
He is evidently serious. ከምሩ ፡ እንደሆነ ፡ ግልጽ ፡ ነው
*It's ten o'clock. Evidently, he is not coming. ዐሥር ፡ ሰዓት ፡ ሆኗል ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሚመጣ ፡ አይመስለኝም

**evil** (n.)
1. መቅሠፍት. War is an evil. ጦርነት ፡ መቅሠፍት ፡ ነው
2. ኃጢአት. Sorcery is an evil. ጥንቆላ ፡ ኀጢአት ፡ ነው
3. ክፉ. He does not return good for evil. ክፉን ፡ በበጎ ፡ አይመልስም
4. መጥፎ ፡ ነገር. The evil must be extirpated. መጥፎው ፡ ነገር ፡ ተነቅሎ ፡ መጣል ፡ አለበት
5. ክፋት. Evil is the inverse of good. ክፋት ፡ የደግነት ፡ ተቃራኒ ፡ ነው

**evil** (adj.)
1. ክፉ. His evil character made him many enemies. ክፉ ፡ ጠባዩ ፡ ብዙ ፡ ጠላት ፡ አፈራበት
The old man fell on evil days. ሽማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ ክፉ ፡ ቀን ፡ አጋጠመው
2. መጥፎ. He was punished because of his evil deeds. በመጥፎ ፡ ምግባሩ ፡ ተቀጣ
3. የተንኰል. His evil plan to defraud the people was discovered. ሕዝቡን ፡ ለማታለል ፡ የነበረው ፡ የተንኰል ፡ እቅዱ ፡ ታወቀበት
4. ኀጢአተኛ. He prophesied cataclysm for the evil city. ኀጢአተኛ ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ መቅሠፍት ፡ ይወርዳል ፡ ብሎ ፡ ተነበየ

**evil spirit** እርኩስ ፡ መንፈስ ፤ ጋኔን (pl. አጋንንት)
The witch doctor exorcised the evil spirit from her. አስማተኛው ፡ እርኩስ ፡ መንፈስ ፡ አወጣላት
There are still people who believe in evil spirits. በአጋንንት ፡ የሚያምኑ ፡ ሰዎች ፡ አሁንም ፡ አሉ

**evildoer** አጥፊ
The evildoers were punished by public whippings. አጥፊዎቹ ፡ ባደባባይ ፡ በመገረፍ ፡ ተቀጡ

**evil eye** ቡዳ
Even now, many people believe in the evil eye. አሁንም ፡ በቡዳ ፡ የሚያምኑ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አሉ

**evince** ገለጸ
His smile evinced his pleasure. ፈገግታው ፡ ደስታውን ፡ ገለጸ

**evoke** አስከተለ
His letter evoked an angry answer. ደብዳቤው ፡ የቁጣ ፡ መልስ ፡ አስከተለ
[See also 'laugh, memory']

**evolution**
1. ሥነ ፡ ተፈጥሮ. In biology we study the evolution of animals. በባዮሎጂ ፡ የእንስሳትን ፡ ሥነ ፡ ተፈጥሮ ፡ እናጠናለን
2. እያደር ፡ የሚመጣ ፡ ለውጥ. In politics England has preferred evolution to revolution. በፖለቲካ ፡ ረገድ ፡ እንግሊዝ ፡ ከመሠረታዊ ፡ ለውጥ ፡ እያደር ፡ የሚመጣ ፡ ለውጥን ፡ መርጣለች
3. ቀስ ፡ በቀስ ፡ ማደግ. The evolution of the flower from the bud is explained in this book. ያበባው ፡ ከእንቡጥነት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ማደግ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጿል

**evolve** (vt.) ፈጠረ
He has evolved a new method. አዲስ ፡ ዘዴ ፡ ፈጥሯል

**evolve** (vi.)
1. ቀስ ፡ በቀስ ፡ አደገ. A sycamore tree evolves from a tiny acorn. የወርካ ፡ ዛፍ ፡ ከትንሽ ፡ ፍሬ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ያድጋል
2. ተባብሶ ፡ ተለወጠ. The dispute evolved into full-scale war. ጠቡ ፡ ተባብሶ ፡ ወደ ፡ እውነተኛ ፡ ጦርነት ፡ ተለወጠ
3. መጣ. Man has evolved from a lower stage of animal. ሰው ፡ የመጣው ፡ ከዝቅተኛ ፡ ደረጃ ፡ ከነበሩት ፡ እንስሳት ፡ ነው

**ewe** ሴት ፡ በግ

**ex —** ከዚህ ፡ ቀደም
She tried to hush up the fact that her husband was an ex-convict. ባሏ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተፈረደበት ፡ ወንጀለኛ ፡ መሆኑን ፡ ለማለባበስ ፡ ሞከረች

**exacerbate** አባሰ(በት)
His nagging only exacerbated her anger. ንዝንዙ ፡ ብስጭቷን ፡ አባሰባት

**exact** (v.)
1. አስገደደ. The creditor exacted full payment from his debtor. አበዳሪው ፡ ባለዕዳው ፡ ያለበትን ፡ በሙሉ ፡ እንዲከፍል ፡ አስገደደው
2. ጠየቀ. If he does the work well, he can exact payment for it. ሥራውን ፡ በሚገባ ፡ ከሠራ ፡ ዋጋ ፡ ሊጠይቅበት ፡ ይችላል
3. ፈለገ. The parents exacted obedience and respect from their children. ልጆቻቸው ፡ ፍጹም ፡ ታዛዥነትንና ፡ አክብሮትን ፡ እንዲያሳዩዋቸው ፡ ወላጆቹ ፡ ፈለጉ

**exact** (adj.)
1. ትክክለኛ. Is this an exact copy? ይህ ፡ ትክክለኛ ፡ ግልባጭ ፡ ነው ?
2 (= adv.) በትክክል. A scientist should be an exact thinker. የሳይንስ ፡ ሊቅ ፡ በትክክል ፡ የሚያስብ ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ አለበት
3. (= adv.) ቃል ፡ በቃል. Tell me his exact words! ያለውን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ንገረኝ

**exacting**
1. ጥንቃቄ ፡ የሚፈልግ. A doctor's work is very exacting. የዶክተር ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ ጥንቃቄ ፡ የሚፈልግ ፡ ነው
2. በቃኝ ፡ የማይል. An exacting employer will find it hard to keep his workers. በቃኝ ፡ የማይል ፡ አሠሪ ፡ ሠራተኞቹን ፡ ማቆየት ፡ ያስቸግረዋል

**exaction** ማስከፈል
The Treasury Department's hardest job is the

exaction of taxes. የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ከባዱ ፡ ሥራው ፡ ግብር ፡ ማስከፈል ፡ ነው
*The tenants protested the exactions their landlords imposed on them. ጭሰኞቹ ፡ ባለርስቶቹ ፡ ያላገባብ ፡ የጣሉባቸውን ፡ ግብር ፡ ተቃወሙ

**exactitude** ረቂቅነት
The exactitude of the work makes it more valuable. የሥራው ፡ ረቂቅነት ፡ ዋጋ ፡ ይጨምርለታል

**exactly**
1. ፍጹም. That's exactly the same. ያ ፡ ፍጹም ፡ አንድ ፡ ነው
2. ልክ. He came exactly at ten. ልክ ፡ ባራት ፡ ሰዓት ፡ መጣ
That's exactly what I expected. ልክ ፡ የጠበቅሁት ፡ ነገር ፡ ነው
3. በትክክል. Follow these instructions exactly! ይህንን ፡ መምሪያ ፡ በትክክል ፡ ተከተል

**exaggerate**
1. አዳነቀ. You are exaggerating as usual. እንደተለመደው ፡ ታዳንቃለህ
2. አጋነነ (ተጋነነ). Your admiration is exaggerated. አድናቆትህ ፡ የተጋነነ ፡ ነው
*Those shoes exaggerate the size of her feet. ጫማዋ ፡ እግሯን ፡ ትልቅ ፡ ያስመስለዋል

**exaggeration** መጋነን
His story is full of exaggerations. ታሪኩ ፡ መጋነን ፡ የበዛበት ፡ ነው

**exalt**
1. አወደሰ. They exalted God in their hymns. በመዝሙራቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አወደሱ
2. ከፍ ፡ አድርጎ ፡ መረጠ. The people exalted him to the office of President. ሕዝቡ ፡ ወደ ፡ ፕሬዚዳንትነት ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ መረጠው
3. ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሜት ፡ አሳደረበት. The lyrics of Shakespeare exalted the audience. የሼክስፒር ፡ ግጥም ፡ በአዳማጮቹ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሜት ፡ አሳደረባቸው

**exam** ፈተና
The exam was easy. ፈተናው ፡ ቀላል ፡ ነበር

**examination**
1. ፈተና. The examination was easy. ፈተናው ፡ ቀላል ፡ ነበር
2. ምርመራ. The examination of the witnesses lasted two hours. የምስክሮቹ ፡ ምርመራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ፈጀ

**put through an examination** መረመረ
The police put him through a severe examination. ፖሊሶቹ ፡ በጥብቅ ፡ መረመሩት
[See also 'medical']

**examine**
1. ፈተነ. We have to examine our students in Amharic. ተማሪዎቻችንን ፡ ባማርኛ ፡ መፈተን ፡ አለብን
2. መረመረ. The doctor examined me thoroughly. ሐኪሙ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ መረመረኝ
I'm here to examine the books. እዚህ ፡ የመጣሁት ፡ መጽሐፎቹን ፡ ለመመርመር ፡ ነው
3. ጠየቀ. The judge examined the witness. ዳኛው ፡ ምስክሩን ፡ ጠየቀው

**be examined** ታየ
The contents of your trunk have to be examined. እሣጥንህ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ እቃ ፡ መታየት ፡ አለበት

**example**
1. ምሳሌ. We all followed his example. ሁላችንም ፡ የሱን ፡ ምሳሌ ፡ ተከተልን
This is an example of the way they do things. በምን ፡ ዓይነት ፡ አኳኋን ፡ እንደሚሠሩ ፡ ይህ ፡ ምሳሌ ፡ ነው
Examples in arithmetic are explained in this book. የቁጥር ፡ ምሳሌ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጿል
This painting is an example of her best work. ይህ ፡ ሥዕል ፡ የሥራዋ ፡ ዓይነተኛው ፡ ምሳሌ ፡ ነው
2. አርአያ. We follow the examples of great men. የታላላቅ ፡ ሰዎችን ፡ አርአያ ፡ እንከተላለን
You should set a good example for the others. ለሌሎቹ ፡ ጥሩ ፡ አርአያ ፡ መሆን ፡ አለብህ
3. መቀጣጫ. The judge fined the speeder as an example to others. ዳኛው ፡ መኪና ፡ በፍጥነት ፡ የነዳውን ፡ ሰው ፡ ለሌሎች ፡ መቀጣጫ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ቀጣው

**for example** ለምሳሌ ፡ ያህል
Let's take Russia, for example. ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ሩሲያን ፡ እንውሰድ

**exasperate** በጣም ፡ አበሳጨ
Her folly exasperated him. ጅልነቷ ፡ በጣም ፡ አበሳጨው

**excavate**
1. ቁፍሮ ፡ አወጣ. They are excavating the ruins at Axum. የአክሱምን ፡ ፍራሾች ፡ ቁፍረው ፡ በማውጣት ፡ ላይ ፡ ናቸው
2. ቈፈረ. They excavated a cave in the hillside. ኮረብታው ፡ ጐን ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ዋሻ ፡ ቈፈሩ

**excavation**

1. ቁፈራ. Excavation was carried out by a modern machine. ቁፈራው ፡ በዘመናዊ ፡ መሣሪያ ፡ ተከናወነ

2. የተቈፈረ ፡ ጉድጓድ. The excavation filled with water. የተቈፈረውን ፡ ጉድጓድ ፡ ውኃ ፡ ሞላው

**exceed**

1. በለጠ. Addis Ababa exceeds Harar in size and population. አዲስ ፡ አበባ ፡ ሐረርን ፡ በስፋትና ፡ በሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ይበልጠዋል

2. አለፈ ፤ ከ - - - አለፈ. Do not exceed the speed limit! የተወሰነውን ፡ ፍጥነት ፡ አትለፍ
The director exceeded his powers and was dismissed. ዲሬክተሩ ፡ ከሥልጣኑ ፡ በማለፉ ፡ ከሥራ ፡ ተወገደ

3. ከ - - - በላይ ፡ ነው. To lift a heavy trunk exceeds a woman's strength. ትልቅ ፡ ሰንዱቅ ፡ ማንሣት ፡ ከሴት ፡ ዓቅም ፡ በላይ ፡ ነው

**exceeding**

*She is a girl of exceeding beauty. ለቁንጅናዋ ፡ ወደር ፡ የሌላት ፡ ልጃገረድ ፡ ነች

**exceedingly** እጅግ

She is an exceedingly beautiful woman. እሷ ፡ እጅግ ፡ የተዋበች ፡ ሴት ፡ ናት

**excel** (excelled) በለጠ

He excels all others in mathematics. ሌሎቹን ፡ ሁሉ ፡ በሒሳብ ፡ ይበልጣቸዋል

**excellence**

1. ከፍተኛ ፡ ችሎታ. He received a prize for excellence in Amharic. ለከፍተኛ ፡ ያማርኛ ፡ ችሎታው ፡ ሽልማት ፡ ተቀበለ

2. ምርጥነት. The restaurant is famous for the excellence of its food. ምግብ ፡ ቤቱ ፡ በምግቡ ፡ ምርጥነት ፡ የታወቀ ፡ ነው

**Excellency, His** ~ ክቡር

His Excellency the ambassador came to the party. ክቡር ፡ አምባሳደሩ ፡ ወደ ፡ ፓርቲው ፡ መጡ

**Your Excellency** ክቡርነትዎ

Your Excellency, may I have the week off? ክቡርነትዎ ፤ የሳምንት ፡ ፈቃድ ፡ ይሰጡኛል ?

**excellent** እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፤ ከፍተኛ

He is an excellent ball player. እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ኳስ ፡ ተጫዋች ፡ ነው
Having such an excellent teacher is to your profit. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ከፍተኛ ፡ መምህር ፡ ማግኘትህ ፡ ላንተ ፡ ጥቅም ፡ ነው

**except** (v.)

1. ውጭ ፡ አደረገ. I cannot except you from the provisions of the law. ሕጉ ፡ ከሚፈቅደው ፡ ውጭ ፡ ላደርግልህ ፡ አልችልም

2. አወጣ. He excepted their names from his list of guests. ከእንግዶቹ ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ የነሱን ፡ ስም ፡ አወጣ

**except** (prep.) ከ - - - በስተቀር

Everybody believed it except him. ከሱ ፡ በስተቀር ፡ ሁሉም ፡ አመኑት

**except for** ከ - - - በስተቀር

I like the book except for one chapter. ካንድ ፡ ምዕራፍ ፡ በስተቀር ፡ መጽሐፉን ፡ እወደዋለሁ

**excepted** ከ - - - በስተቀር

Present company excepted, I don't like visitors. እዚህ ፡ ካለው ፡ ሰው ፡ በስተቀር ፡ እንግዳ ፡ አልወድም

**excepting** ከ - - - በስተቀር

Everyone, excepting myself, applauded his speech. ከኔ ፡ በስተቀር ፡ ሁሉም ፡ ለንግግሩ ፡ አጨበጨቡ

**exception**

*This rule does not allow for any exception. ይህ ፡ ደንብ ፡ ለማንም ፡ የተለየ ፡ ይዞታ ፡ አይሰጥም

**be an exception to** አልተከተለም

This is an exception to the rules of grammar. ይህ ፡ የሰዋስውን ፡ ሕጎች ፡ አይከተልም
*I don't want to be an exception. ልዩ ፡ አስተያየት ፡ እንዲደረግልኝ ፡ አልፈልግም

**make an exception** ደንቡን ፡ አልተከተለም

He made an exception and allowed him to enter school without a certificate. ደንቡን ፡ ባለመከተል ፡ ያለ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲገባ ፡ ፈቀደለት

**make no exceptions**

*All of you must be here at eight; I can make no exceptions. ሁላችሁም ፡ በሁለት ፡ እዚህ ፡ መገኘት ፡ አለባችሁ ፤ እገሌ ፡ ከገሌ ፡ የምለው ፡ የለም

**take exception** ተቃወመ

He took exception to my description of Addis Ababa as a small town. አዲስ ፡ አበባ ፡ ትንሽ ፡ ከተማ ፡ ናት ፡ ብዬ ፡ ያልኩትን ፡ ተቃወመ

**with the exception of** ከ - - - በስተቀር

I like my studies, with the exception of German. ከጀርመንኛ ፡ በስተቀር ፡ ትምህርቶቼን ፡ እወዳለሁ

**without exception** አንድም ፡ ሳይቀር

Every student, without exception, must be there.

ተማሪ ፡ በሙሉ ፡ አንድም ፡ ሳይቀር ፡ እዚያ ፡ መ
ገኘት ፡ አለበት
[See also 'rule']

**exceptional**
1. ወደር ፡ የሌለው. She is an exceptional student. ወደር ፡ የሌላት ፡ ተማሪ ፡ ናት
2. የተለመደ ፡ አይደለም. This weather is exceptional for June. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ በሰኔ ፡ የተለመደ ፡ አይደለም

**excerpt** ምንባብ
He read an excerpt from the Bible to the class. ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተወሰደ ፡ ምንባብ ፡ ለክፍ ሉ ፡ አነበበ
Where did you take the excerpts from? ምንባቦቹን ፡ ከየት ፡ አገኘሻቸው ?
*An excerpt of his speech was printed in the paper. ንግግሩ ፡ በከፊል ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ታት ሞ ፡ ነበር

**excess** (n.)
1. ብልጫ. There was an excess of imports over exports last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ አ ገር ፡ ውስጥ ፡ የገቡት ፡ እቃዎች ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ከተላኩት ፡ ብልጫ ፡ ነበራቸው
2. ትርፍ. Pour off the excess! ትርፉን ፡ አፍስሰው
3. ብዛት. His teeth were harmed by an excess of candy. በከረሜላ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ጥርሱ ፡ ተ ጐድቶ ፡ ነበር
4. (= adj.) ከልክ ፡ ያለፈ. He has an excess of energy. ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ጉልበት ፡ አለው
5. (= adv.) ከመጠን ፡ በላይ. The doctor advised him to avoid excess in eating. ሐኪሙ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ እንዳይበላ ፡ ነገረው
*The excess of 7 over 5 is 2. ሰባት ፡ ካምስት ፡ የሚበልጠው ፡ በሁለት ፡ ነው
**in excess of** ከ - - - በላይ
The supply of cars was in excess of the demand. ለገበያ ፡ የሚቀርቡት ፡ መኪናዎች ፡ ከሚፈለገ ው ፡ በላይ ፡ ነበር
**to excess** ከመጠን ፡ በላይ
She is generous to excess. ከመጠን ፡ በላይ ፡ ለጋ ስ ፡ ናት
*I drink sometimes, but not to excess. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እጠጣለሁ ፤ ግን ፡ ከልኩ ፡ አላልፍም
**excesses, commit** ~ ግፍ ፡ ፈጸመ
The enemy army was charged with committing excesses. የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ግፍ ፡ በመፈጸማ ቸው ፡ ተከሰሱ
**excess** (adj.)
1. ትርፍ. Pour off the excess fat! ትርፉን ፡ ቅባ ት ፡ አፍስሰው
2. ከተወሰነው ፡ በላይ ፡ የሆነ. You have to pay 5 dollars a pound for excess baggage. ከተወሰነው ፡ በላይ ፡ ለሆነ ፡ ጓዝ ፡ በእያንዳንዱ ፡ ፓውንድ ፡ ፭ ፡ ብር ፡ መክፈል ፡ አለብህ

**excessive** ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሆነ
I won't pay these excessive charges. ይህንን ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ዋጋ ፡ አልከፍልም

**exchange** (v.)
1. ለወጠ. I want to exchange this book for another one. ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ በሌላ ፡ ለመለ ወጥ ፡ እፈልጋለሁ
2. ተለዋወጠ. John and Mary exchange books. ዮሐንስና ፡ ማርያም ፡ መጻሕፍት ፡ ይለዋወጣሉ
I have been exchanging ideas with your friend. ከጓደኛህ ፡ ጋር ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ እንለዋወጥ ፡ ነበር
[See also 'blow, word']

**exchange** (n.)
1. ልውውጥ. Is this a fair exchange? ይህ ፡ አግ ባብ ፡ ያለው ፡ ልውውጥ ፡ ነው ?
2. መለዋወጥ. Exchange of ideas is necessary for development. የሐሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ ለእድገ ት ፡ ተፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው
The Red Cross arranges for the exchange of prisoners. የቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፡ የእ ስረኞችን ፡ መለዋወጥ ፡ ያደራጃል
3. የገንዘብ ፡ ምንዛሪ. Control of foreign exchange is the duty of the National Bank. የውጭ ፡ አገ ር ፡ ገንዘብን ፡ ምንዛሪ ፡ መቈጣጠር ፡ የብሔራዊ ፡ ባ ንክ ፡ ተግባር ፡ ነው
4. የገንዘብ ፡ መመንዘሪያ ፡ ቦታ. The variations in the value of the world's currency are posted in the exchange. በዓለም ፡ ያሉ ፡ ገንዘቦች ፡ የዋጋ ፡ ልዩነት ፡ በገንዘብ ፡ መመንዘሪያ ፡ ቦታ ፡ ተለጥፏል
**in exchange for** በለውጡ
He's giving her French lessons in exchange for English ones. እሷ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ስታስተምረ ው ፡ በለውጡ ፡ እሱ ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ያስተምራታል
**rate of exchange** የምንዛሪ ፡ ዋጋ ፤ የምንዛሪ ፡ ሒሳብ
The rate of exchange is 2 1/2 Ethiopian dollars to 1 American dollar. የምንዛሪው ፡ ዋጋ ፡ (ሒሳ ብ) ፡ ላንድ ፡ የአሜሪካ ፡ ብር ፡ ሁለት ፡ ተኩል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ነው

**excise** ቈርጦ ፡ አወጣ
The surgeon excised the tumor with no difficulty. የቀዶ ፡ ጥገናው ፡ ሐኪም ፡ ኪንታሮቱን ፡ ያላ ንዳች ፡ ችግር ፡ ቈርጦ ፡ አወጣ
The censor excised two paragraphs on page

four. ሳንሱሩ ፡ ካራተኛው ፡ ገጽ ፡ ሁለት ፡ አንቀ
ጾች ፡ ቈርጦ ፡ አወጣ

**excitable** በቀላሉ ፡ የሚሸበር
My brother is an excitable person. ወንድሜ ፡ በ
ቀላሉ ፡ የሚሸበር ፡ ሰው ፡ ነው

**excite**
1. ስሜቱን ፡ ቀሰቀሰ. The President's speech
excited us. የፕሬዚዳንቱ ፡ ንግግር ፡ ስሜታችን
ን ፡ ቀሰቀሰ
2. ተተናኰሰ. Do not excite the dog! ውሻውን ፡
አትተናኰለው
3. አተረፈ(ለት). Her new dress excited envy.
አዲሱ ፡ ልብሷ ፡ ቅናት ፡ አተረፈላት

**be excited**
1.ስሜቱ ፡ ተቀሰቀሰ. I'm excited because I just
entered the competition. በውድድሩ ፡ ገና ፡ በመ
ግባቴ ፡ ስሜቴ ፡ ተቀስቅሷል
2. በጉጉት ፡ መንፈሱ ፡ ተቀሰቀሰ. The children
were excited by the Emperor's arrival. በንጉ
ሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መምጣት ፡ ልጆች ፡ በጉጉት ፡ መንፈሳ
ቸው ፡ ተቀሰቀሰ
3. ተደሰተ. Everyone was excited by the news
of the victory. በድሉ ፡ ዜና ፡ ሁሉም ፡ ተደስቶ ፡
ነበር
4. ጓጓ. Everyone is so happy about the picnic,
but I am not excited about it. ስለ ፡ ሽርሽሩ ፡ ሁ
ሉ ፡ ሰው ፡ ተደስቷል ፤ እኔ ፡ ግን ፡ አልጓጓሁለትም

**get excited** ተሸበረ
Don't get excited! I will find the books sooner
or later. አትሸበር ፤ አሁንም ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ ጊ
ዜ ፡ መጽሐፎቹን ፡ አገኝልሃለሁ

**excitement**
1. ስሜት. He tried to hide his excitement.
ስሜቱን ፡ ለመደበቅ ፡ ሞከረ
The incident created a lot of excitement.
ድርጊቱ ፡ የብዙውን ፡ ስሜት ፡ ቀሰቀሰ
2. ሽብር. The excitement will die down in a
few days. ሽብሩ ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ እየጠፋ ፡
ይሄዳል
3. ግርግር. Wait till the excitement settles
down! ግርግሩ ፡ እስኪረጋጋ ፡ ድረስ ፡ ቆይ
4. ድንጋጤ. His heart thumped with excite-
ment. ልቡ ፡ በድንጋጤ ፡ ከበሮ ፡ መታ
5. መደናገጥ. The declaration of a state of
emergency caused great excitement. የአስቸኳይ ፡
ጊዜ ፡ ዐዋጅ ፡ መታወጅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መደናገጥን ፡
ፈጠረ
6. የደስታ ፡ ብዛት. Her eyes sparkled with ex-
citement. ከደስታ ፡ ብዛት ፡ ዓይኗ ፡ ተብለጨለጨ

**exciting**
1. ደስ ፡ የሚያሰኝ ፤ ስሜትን ፡ የሚቀሰቅስ. That
was an exciting story. ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ (ስሜት
ን ፡ የሚቀሰቅስ) ፡ ታሪክ ፡ ነበር
2. የሚያስደስት. The discovery of gold is
exciting news. የወርቅ ፡ መገኘት ፡ የሚያስደስ
ት ፡ ወሬ ፡ ነው
3. የሚያስደንቅ. Our encounter with the famous
actor was exciting. የታወቀውን ፡ ተዋናይ ፡ በድ
ንገት ፡ ማግኘታችን ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነበር

**exclaim**
1. በደስታ ፡ ተናገረ. "I've passed the exam!" he
exclaimed. ፈተናውን ፡ አለፍኩ ! ፡ ብሎ ፡ በደ
ስታ ፡ ተናገረ
2. በመደነቅ ፡ ጠየቀ. "Haven't you done that
yet?" he exclaimed. እስካሁን ፡ ያንን ፡ አልሠ
ራኸውም ? ፡ ብሎ ፡ በመደነቅ ፡ ጠየቀ

**exclamation**
1. ቃለ ፡ አጋኖ. "Oh!" and "Help!" are exclama-
tions. « አ » ና ፡ « እሪ » ፡ ቃለ ፡ አጋኖ ፡ ናቸው
2. ድምፅ. His exclamation of surprise was
heard by the teacher. የመደነቅ ፡ ድምፁን ፡ አስ
ተማሪው ፡ ሰማው
3. ጩኸት. The speech was continually inter-
rupted by rude exclamations. ንግግሩ ፡ በብልግና ፡
ጩኸት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተቋርጦ ፡ ነበር

**exclude**
1. አስቀረ. The speaker excluded the unnecessa-
ry material from the report. ተናጋሪው ፡ ከራፖ
ሩ ፡ ውስጥ ፡ ተፈላጊ ፡ ያልሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ አስቀረ
2. ከግምት ፡ ውጭ ፡ አደረገ. He excluded the
possibility of an error in the date. በቀን ፡ አ
ቈጣጠር ፡ ምናልባት ፡ ሊኖር ፡ የሚችለውን ፡ ስሕ
ተት ፡ ከግምት ፡ ውጭ ፡ አደረገው
3. ከለከለ. They excluded him from member-
ship in our club. የክበባችን ፡ አባል ፡ እንዳይሆን ፡
ከለከሉት

**exclusion**
1. መከልከል. Her exclusion from the club
hurt her feelings. ከክበቡ ፡ መከልከሏ ፡ አስቀ
የማት
2. ከቁጥር ፡ አለማግባት. Exclusion of minors is
a good policy for us. ላካለ ፡ መጠን ፡ ያልደረ
ሱትን ፡ ገለል ፡ ማድረግ ፡ ለምንከተለው ፡ ዓላማ ፡
ጥሩ ፡ ነው

**to the exclusion of others** የሌሎችን ፡ ትቶ
He considers only his interests to the exclusion
of others. የሌሎችን ፡ ትቶ ፡ የራሱን ፡ ጥቅም ፡
ብቻ ፡ ያስባል

**exclusive**
1. የግል ፡ የሆነ. We have exclusive rights to this invention. ለዚህ ፡ ፍልሰፋ ፡ የግላችን ፡ የሆነ ፡ መብት ፡ አለን
2. (= adv.) ሙሉ ፡ በሙሉ. The director has exclusive control of the company. ዲሬክተሩ ፡ ኩባንያውን ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ይቈጣጠራል
3. (= adv.) በሙሉ ፡ ልብ. He manifested an exclusive devotion to his work. በሙሉ ፡ ልብ ፡ ሥራውን ፡ መውደዱን ፡ አሳየ
*This is quite an exclusive club. ይህ ፡ ለተወሰኑ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ የተፈቀደ ፡ ክበብ ፡ ነው

**exclusive of** ሳይቈጠር
There are twenty-six days in that month, exclusive of Sundays. እሑድ ፡ ሳይቈጠር ፡ በዚያ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ሃያ ፡ ስድስት ፡ ቀኖች ፡ አሉ

**exclusively** ብቻ
That selfish girl looks out for herself exclusively. ያቺ ፡ ራሷን ፡ ወዳድ ፡ ልጃገረድ ፡ ለራሷ ፡ ብቻ ፡ ታስባለች

**excommunicate** አወገዘ
The archbishop excommunicated his opponents. ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ተቃዋሚዎቻቸውን ፡ አወገዙ

**excommunication** ውግዘት
Excommunication was not widely practiced in Ethiopia. ውግዘት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ አይሠራበትም ፡ ነበር

**excrement** ኩስ
They make use of the excrement of bats for fertilizer. የሌሊት ፡ ወፎችን ፡ ኩስ ፡ ለመሬት ፡ ማዳበሪያ ፡ ይጠቀሙበታል

**human excrement** ዓይነ ፡ ምድር
The Japanese use human excrement as fertilizer. ጃፓኖች ፡ ዓይነ ፡ ምድርን ፡ ለመሬት ፡ ማዳበሪያ ፡ ያውሉታል

**excrete** ጣለ
The cow excretes dung. ላም ፡ እበት ፡ ትጥላለች

**excruciate** አሠቃየ
The headache excruciated him. ራስ ፡ ምታት ፡ አሠቃየው

**excruciating** የሚያሠቃይ
I had an excruciating toothache yesterday. ትናንት ፡ የሚያሠቃይ ፡ የጥርስ ፡ ሕመም ፡ ነበረብኝ

**exculpate**
*The judge exculpated him of the charge. ዳኛው ፡ ነጻ ፡ ለቀቀው

**excursion** ሽርሽር
Let's go on an excursion to Entotto! ወደ ፡ እንጦጦ ፡ ሽርሽር ፡ እንሂድ

**excusable** የሚታለፍ
The error is excusable. ስሕተቱ ፡ የሚታለፍ ፡ ነው

**excuse** (v.)
1. ይቅርታ ፡ አደረገ(ለት). Please excuse my bad Amharic! ስላልተጣራው ፡ አማርኛዬ ፡ ይቅርታ ፡ አድርግልኝ
2. (= pass.) ታለፈ. +Nothing can excuse such rudeness. እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ብልግና ፡ ጨርሶ ፡ ሊታለፍ ፡ አይችልም
3. ምክንያት ፡ ሆነው. Sickness excused his absence from school. መታመሙ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመቅረት ፡ ምክንያት ፡ ሆነው
4. ሸፈነ. She excused her own faults by blaming others. በሌሎች ፡ ላይ ፡ በመላከክ ፡ የራሷን ፡ ስሕተት ፡ ሸፈነች
5. አሳበበ. He tried to excuse his lateness by claiming that he had been ill. መዘግየቱን ፡ በሕመም ፡ ለማሳበብ ፡ ሞከረ

**excuse me!** ይቅርታ

**be excused** እንዲቀር ፡ ተፈቀደለት
He was excused for the afternoon because of a headache. ራሱን ፡ ስላመመው ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ እንዲቀር ፡ ተፈቀደለት
*You may be excused from the table. ከገበታው ፡ ላይ ፡ ለመነሣት ፡ ተፈቅዶልሃል

**excuse oneself** ይቅርታ ፡ ጠየቀ
She excused herself for being late. ዘግይታ ፡ ስለመጣች ፡ ይቅርታ ፡ ጠየቀች

**excuse** (n.)
1. በቂ ፡ ምክንያት. That's no excuse! በቂ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም
2. ምክንያት. His excuse was pure fiction. የሰጠው ፡ ምክንያት ፡ ፍጹም ፡ ፈጠራ ፡ ነበር
*Please give him my excuses for being absent! ስለቀረሁ ፡ ይቅርታ ፡ እንዲያደርግልኝ ፡ ንገረው

**ask for an excuse from**
*The child asked for an excuse from gym class. ልጁ ፡ ከሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ትምህርት ፡ ለመቅረት ፡ ፈቃድ ፡ ጠየቀ

**make excuses** ምክንያት ፡ ፈጠረ
He is always making excuses for being late. ለመዘግየቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ምክንያት ፡ ይፈጥራል
[See also 'lame']

**execrable**
1. አሰቃቂ. His execrable wickedness has gone

down in history. አስቃቂው ፡ ክፋቱ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ተመዝግቧል
2. ደስ ፡ የማይል. Wearing a purple tie with a green suit shows execrable taste in clothes. ባረንጓዴ ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ ሐምራዊ ፡ ክራቫት ፡ ማሰር ፡ ባለባበስ ፡ በኩል ፡ ደስ ፡ የማይል ፡ ምርጫ ፡ ያሳያል

**execrate** አወገዘ
He execrated all who opposed him. የተቃወሙትን ፡ ሁሉ ፡ አወገዘ

**execute**
1. ፈጸመ. It is your responsibility to execute all orders. ትእዛዞችን ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ ያንተ ፡ ኀላፊነት ፡ ነው
2. በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለ. We are going to execute our plan to dam the Awash. አዋሽን ፡ ለመገደብ ፡ ያለነን ፡ እቅድ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ልናውለው ፡ ነው

**be executed, ~ by hanging** ተሰቀለ
The murderer was executed by hanging. ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ ተሰቀለ
[See also 'shooting']

**execution**
1. አሠራር. His intention was good, but his execution of the plan was unsatisfactory. ሐሳቡ ፡ ጥሩ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አሠራሩ ፡ አጥጋቢ ፡ አልነበረም
2. የሚፈጸምበት ፡ የሞት ፡ ፍርድ. The plotters are in jail awaiting execution. ሴረኞቹ ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ሆነው ፡ የሚፈጸምባቸውን ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ በመጠባበቅ ፡ ላይ ፡ ናቸው
3. የሞት ፡ ቅጣት. At what time will the execution take place? የሞቱ ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ በስንት ፡ ሰዓት ፡ ነው ?

**put into execution** በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለ
He put the emergency plan into execution. የሚያስቸኩለውን ፡ እቅድ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለው
[See also 'stay']

**executive** (n.)
1. ባለሥልጣን. The delegation of duties to others is part of an executive's job. ኀላፊነትን ፡ ማከፋፈል ፡ ከባለሥልጣን ፡ ተግባር ፡ አንዱ ፡ ነው
2. አስተዳዳሪ. The executives met to discuss the company's policy. በኩባንያው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ለመነጋገር ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ ተሰበሰቡ

**executive** (adj.)
1. ትእዛዝ ፤ የመስጠት. The administrative assistant has executive powers also. ረዳት ፡ አስተዳዳሪው ፡ ትእዛዝ ፡ የመስጠትም ፡ ሥልጣን ፡ አለው
2. ያስተዳደር. He is highly appreciated because of his executive abilities. ባስተዳደር ፡ ችሎታው ፡ በጣም ፡ ይደነቃል

**executive head** ዋና ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚ
The President is the executive head of the nation. ፕሬዚዳንቱ ፡ ያገሩ ፡ ዋና ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚ ፡ ነው

**exemplary** አርአያነት ፡ ያለው
The boy's conduct was exemplary. የልጁ ፡ ጠባይ ፡ አርአያነት ፡ ያለው ፡ ነበር

**exemplary punishment** መቀጣጫ ፡ የሚሆን ፡ ቅጣት
The director administered an exemplary punishment. ዲሬክተሩ ፡ መቀጣጫ ፡ የሚሆን ፡ ቅጣት ፡ ሰጠ

**exemplify** (exemplified)
1. አርአያ ፡ ነው. These soldiers exemplify courage. እነዚህ ፡ ወታደሮች ፡ የጀግንነት ፡ አርአያዎች ፡ ናቸው
2. አመለከተ. This picture exemplifies the artist's style. ይህ ፡ ሥዕል ፡ የሠዓሊውን ፡ ስልት ፡ ያመለክታል

**exempt** (v.)
1. ነጻ ፡ አደረገ. They exempted him from military service. ከወታደራዊ ፡ አገልግሎት ፡ ነጻ ፡ አደረጉት
2. እንድ + negative imperfect + ፈቀደ(ለት). The teacher exempted the student from the test. መምህሩ ፡ ተማሪው ፡ ፈተናውን ፡ እንዳይወስድ ፡ ፈቀደለት

**exempt** (adj.) ነጻ
The school property is exempt from taxes. የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ንብረት ፡ ከግብር ፡ ነጻ ፡ ነው
[See also 'tax']

**exemption**
1. ነጻ ፡ ማድረግ. Tax exemptions have reduced the amount of revenue. ከግብር ፡ ነጻ ፡ ማድረግ ፡ የገቢውን ፡ መጠን ፡ ቀንሶታል
2. ውጪ ፡ መሆን. Military exemptions are granted only for deformities. ከወታደራዊ ፡ አገልግሎት ፡ ውጪ ፡ መሆን ፡ የሚፈቀድላቸው ፡ አካለ ፡ ጎደሎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**exercise** (vt.)
1. በልምምድ ፡ አጠነከረ. Exercise your weak ankle! ደካማውን ፡ ቁርጭምጭሚትህን ፡ በልምምድ ፡ አጠንክረው
2. አለማመደ. The cavalry troops exercise their

horses every day. ፈረሰኞቹ ፡ በየቀኑ ፡ ፈረሶቻቸ ውን ፡ ያለማምዳሉ

3. አሳየ. He exercised his patience while arguing with his wife. ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ሲከራ ከር ፡ ትዕግሥትን ፡ አሳየ

4. አለው. What others think exercises a great influence on most of us. ሌሎች ፡ የሚያስቡት ፡ በብዙዎቻችን ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተጽዕኖ ፡ አ ለው

**exercise** (vi.) ጅምናስቲክ ፡ ሠራ ፤ ልምምድ ፡ አደ ረገ ፤ ሰውነቱን ፡ አፍታታ

You have to exercise every morning. ሁልጊ ዜ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ጅምናስቲክ ፡ መሥራት ፡ አለብህ

The athlete exercised to keep himself in good shape. ስፖርተኛው ፡ ሰውነቱን ፡ በሚገባ ፡ ለመ ጠበቅ ፡ ልምምድ ፡ አደረገ

He spent all his energies exercising. ጉልበቱን ፡ ሰውነቱን ፡ በማፍታታት ፡ ብቻ ፡ ጨረሰው

**exercise power** በሥልጣን ፡ ገዛ ፤ በሥልጣን ፡ ተጠቀመ

The dictator exercised absolute power. አምባ ፡ ገነኑ ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ ሥልጣን ፡ ገዛ

The governor exercised his power to call out the militia. ገዢው ፡ በሥልጣኑ ፡ ተጠቅሞ ፡ ብ ሔራዊ ፡ ጦሩን ፡ አስከተተ

## exercise (n.)

1. መልመጃ. Exercise ten is difficult. ዐሥረኛ ው ፡ መልመጃ ፡ ከባድ ፡ ነው

2. ልምምድ. Military exercises are being held now. ወታደራዊ ፡ ልምምድ ፡ አሁን ፡ በመደረ ግ ፡ ላይ ፡ ነው

3. ሥነ ፡ ሥርዓት. Our graduation exercises opened with a song. የምረቃችን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓ ት ፡ በመዝሙር ፡ ተከፈተ

4. የሰውነት ፡ እንቅስቃሴ. He believes in a lot of exercise. ብዙ ፡ የሰውነት ፡ እንቅስቃሴ ፡ በማ ድረግ ፡ ያምናል

*The exercise of patience is essential in diplomacy. ታጋሽ ፡ መሆን ፡ ለዲፕሎማሲ ፡ ሥራ ፡ በ ጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**exercise of the body** የሰውነት ፡ እንቅስቃሴ

Exercise of the body is needed for health. የሰውነት ፡ እንቅስቃሴ ፡ ለጤንነት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**physical exercise** የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ልም ምድ

I need more physical exercise. ተጨማሪ ፡ የሰው ነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ልምምድ ፡ ያስፈልገኛል

## exert በ - - - ተጠቀመ

A ruler exerts authority. ገዥ ፡ በሥልጣን ፡ ይ ጠቀማል

A clever fighter exerts both strength and skill. ብልህ ፡ ቡጢኛ ፡ በጉልበቱም ፡ በዘዴውም ፡ ይ ጠቀማል

**exert oneself** ጥረት ፡ አደረገ

Exert yourself to finish the job on time! ሥራውን ፡ በጊዜ ፡ ለመጨረስ ፡ ጥረት ፡ አድርግ

[See also 'effort']

## exertion

1. ልፋት. He was panting from the exertion. ከልፋት ፡ የተነሣ ፡ ቁና ፡ ቁና ፡ ይተነፍስ ፡ ነበር

2. ድካም. His studies require little intellectual exertion on his part. ትምህርቱ ፡ እጅግም ፡ የ አእምሮ ፡ ድካም ፡ የለበትም

3. መጠቀም. Exertion of authority is not always appropriate; persuasion may be better. ሁልጊ ዜ ፡ በሥልጣን ፡ ብቻ ፡ መጠቀም ፡ ተገቢ ፡ አይደለ ም ፤ መግባባት ፡ ይሻል ፡ ይሆናል

## exhale

1. ወደ ፡ ውጭ ፡ ተነፈሰ. He exhaled the smoke. ጭሱን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ተነፈሰ

2. አመነጨ. Flowers exhale sweet odors. አበባዎች ፡ ጣፋጭ ፡ መዓዛ ፡ ያመነጫሉ

## exhaust (v.)

1. አሟልቶ ፡ አተተ. Her book about roses exhausted the subject. ስለ ፡ ጽጌረዳ ፡ የጻፈችው ፡ መጽሐፍ ፡ ጉዳዩን ፡ አሟልቶ ፡ አተተ

2. መታከት ፡ አደረገ. The climb up the hill exhausted us. ኮረብታውን ፡ መውጣት ፡ መታከት ፡ አደ ረገን

3. ሞከሮ ፡ አበቃ. I have exhausted all possibilities. የተቻለውን ፡ ሁሉ ፡ ሞክሬ ፡ አብቅቻለሁ

4. ባዶ ፡ አስቀረ. The leak exhausted the gas tank. ቀዳዳው ፡ የቤንዚኑን ፡ በርሜል ፡ ባዶ ፡ አስቀረው

5. ጨረሰ. I have exhausted all my money. ገንዘቤን ፡ ሁሉ ፡ ጨርሻለሁ

I have exhausted my patience. ትዕግሥቴን ፡ ጨ ርሻለሁ

**exhaust oneself** ራሱን ፡ አደከመ

I have exhausted myself working. ራሴን ፡ በሥ ራ ፡ አደከምኩ

## exhaust (n.) ጭስ

Exhaust from cars pollutes the air. የመኪና ፡ ጭ ስ ፡ አየርን ፡ ይመርዛል

## exhausted (adv.) ደክሞት

He came home exhausted after the long hike. ከረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሽርሽር ፡ በኋላ ፡ ደክሞት ፡ እቤ ት ፡ ገባ

**be exhausted**
1. በድካም ፡ ሙትት ፡ አለ. I was completely exhausted after that long trip. ከረጅሙ ፡ ጉዞ ፡ በኋላ ፡ በድካም ፡ ሙትት ፡ አልኩ
2. አከተመ. His longanimity was exhausted by her endless complaints. ታጋሽነቱ ፡ በማያቋርጥ ፡ ንትርኳ ፡ አከተመ

**leave one exhausted** ሰውነቱን ፡ አደቀቀው ፤ በጣም ፡ አደከመ
The grueling contest left him exhausted. በጣም ፡ አድካሚ ፡ የሆነው ፡ ትግል ፡ ሰውነቱን ፡ አደቀቀው
The eventful day left him exhausted. ብዙ ፡ ድርጊት ፡ የተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ በመሆኑ ፡ በጣም ፡ አደከመው

**exhaustion**
1. ድካም. Some of them dropped from exhaustion. እንዳንዶቹ ፡ ከድካም ፡ የተነሣ ፡ ወደቁ
2. ማነስ. The exhaustion of the water supply caused the municipality to ration water. የውኃው ፡ ማነስ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ያለውን ፡ ውኃ ፡ እየቈጠበ ፡ እንዲያድል ፡ አስገደደው

**drop from exhaustion** ደክም ፡ ወደቀ
Some of them dropped from exhaustion. እንዳንዶቹ ፡ ደክመው ፡ ወደቁ

**exhaustive** የተሟላ
He published an exhaustive study of Roman civilization. ስለ ፡ ሮማውያን ፡ የጥንት ፡ ሥልጣኔ ፡ የተሟላ ፡ ጽሑፍ ፡ አዘጋጅቶ ፡ አሳተመ

**exhibit** (v.) ለሕዝብ ፡ አሳየ
The artist exhibited his paintings. ሠዓሊው ፡ ሥዕሎቹን ፡ ለሕዝብ ፡ አሳየ
*The child exhibited a bad temper at an early age. ልጁ ፡ ገና ፡ በልጅነቱ ፡ የቍጡነት ፡ ጠባይ ፡ ይታይበታል

**exhibit** (n.) ትርኢይት
Have you seen the exhibit? ትርኢይቱን ፡ አይተሃል ?

**exhibition** የሥዕል ፡ ትርኢይት
The art school holds an exhibition every year. የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በያመቱ ፡ የሥዕል ፡ ትርኢይት ፡ ያሳያል
*His exhibition of strength impressed us. ያሳየው ፡ ጥንካሬ ፡ አስደነቀን

**exhilarate**
1. ደስ ፡ አሰኘ. The news that he was admitted to college exhilarated him. ኮሌጅ ፡ የተቀበሉት ፡ መሆኑን ፡ መስማቱ ፡ ደስ ፡ አሰኘው
2. አነቃቃ. The cold weather exhilarated the children. ቀዝቃዛው ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ ልጆቹን ፡ አነቃቃቸው

**exhort**
1. አጥብቆ ፡ አሳሰበ. He exhorted his listeners to give up smoking. አድማጮቹን ፡ ሲጋራ ፡ ማጨስ ፡ እንዲያቆሙ ፡ አጥብቆ ፡ አሳሰባቸው
2. አደፋፈረ. He exhorted his troops to attack the enemy. ጠላትን ፡ እንዲያጠቁ ፡ ወታደሮቹን ፡ አደፋፈረ

**exhume** ቈፍሮ ፡ አወጣ
They exhumed the body from a shallow grave. አስከሬኑን ፡ ጥልቅ ፡ ካልሆነ ፡ ጉድጓድ ፡ ቈፍረው ፡ አወጡት

**exigency** (exigencies) አስቸኳይነት
The exigencies of business kept him from leaving town. የሥራው ፡ አስቸኳይነት ፡ ከከተማ ፡ እንዳይወጣ ፡ አደረገው

**exile** (v.) አጋዘ
The governor exiled the disloyal official to the provinces. ታማኝነት ፡ የጐደለውን ፡ ሠራተኛ ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ወደ ፡ ገጠር ፡ አጋዙት

**exile** (n.)
1. ግዞት. The guilty governor went into exile for ten years. ጥፋተኛው ፡ ገዢ ፡ ለዐሥር ፡ ዓመት ፡ ግዞት ፡ ገባ
2. ስደት. During the war, many people were in exile. በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በስደት ፡ ላይ ፡ ነበሩ
3. ስደተኛ. He is an exile from the East. የምሥራቅ ፡ ስደተኛ ፡ ነው

**exist**
1. ነው. That exists only in your imagination. ነገሩ ፡ ያለው ፡ በሐሳብህ ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ኖረ. A man cannot exist without air. ሰው ፡ ያለ ፡ አየር ፡ ሊኖር ፡ አይችልም
3. አለ. War exists in many parts of the world. በብዙው ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ ጦርነት ፡ አለ
*Belief in magic still exists. በጥንቆላ ፡ ዛሬም ፡ ይታመናል

**existence**
1. ኑሮ. He leads a peaceful existence in the country. ባላገር ፡ ውስጥ ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል
2. መፈጠር. He is not even aware of my existence. መፈጠሬንም ፡ እንኳ ፡ አያውቅም
3. ሕይወት. There may be existence in the universe other than ours. ከኛ ፡ ዓለም ፡ ውጭ ፡

በሌላ ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ሕይወት ፡ ይኖር ፡ ይሆ
ናል
4. መኖር. The microscope reveals the existence of many tiny things. ማይክሮስኮፕ ፡ የብዙ ፡ ጥ
ቃቅን ፡ ነገሮችን ፡ መኖር ፡ ያሳያል
*This is the oldest Ethiopic manuscript in existence. ይህ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የብራና ፡ ጽሑፎ
ች ፡ ሁሉ ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ዕድሜ ፡ ያለው ፡ ነው

**be in existence** ሆነ
This company has been in existence for fifty years. ኩባንያው ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ ሆኖታል

**be no longer in existence** ቀረ
Capital punishment is no longer in existence in England. በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ወንጀለኛን ፡
በሞት ፡ መቅጣት ፡ ቀርቷል

**come into existence** ተፈጠረ
When did this world come into existence? ይህ ፡ ዓለም ፡ መቼ ፡ ተፈጠረ ?

**lead an existence** ኖረ
He led a miserable existence. በችግር ፡ ኖረ
[See also 'go out']

**existent** ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያለ
The existent traffic conditions have to be changed. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያሉት ፡ የትራፊክ ፡ ሁ
ኔታዎች ፡ መለወጥ ፡ አለባቸው

**be no longer existent** ጠፋ
Dinosaurs are no longer existent. ዳይኖሶር ፡ ጠ
ፍቷል

**exit** (v.) ወጣ
They exited through the backdoor. በጓሮ ፡ በ
ር ፡ ወጡ

**exit** (n.) መውጫ
Where is the exit in this building? የዚህ ፡ ሕን
ጻ ፡ መውጫው ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ?

**exit permit** የይለፍ ፡ ወረቀት
Each emigrant must have an exit permit. አገሩን ፡ ትቶ ፡ የሚሄድ ፡ ሰው ፡ የይለፍ ፡ ወረቀ
ት ፡ ማግኘት ፡ አለበት

**exodus**
*Every summer there is an exodus from the city. በየበጋው ፡ ሰዎች ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ይጐርፋሉ

**exonerate** ምንም ፡ ወንጀል ፡ እንዳልሠራ ፡ ፈ
ረደ
The judge exonerated the accused man. ዳኛው ፡ ተከሳሹ ፡ ምንም ፡ ወንጀል ፡ እንዳልሠራ ፡ ፈ
ረደ

**exorbitant**
1. በጣም ፡ ውድ. He asked an exorbitant price for his land. ለመሬቱ ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ የሆነ ፡ ዋ
ጋ ፡ ጠየቀ
2. ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሆነ. I could not accept his exorbitant demands. ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሆ
ነ ፡ ጥያቄውን ፡ ልቀበል ፡ አልቻልኩም

**exorcise** አወጣ(ለት)
The witch doctor exorcised the evil spirit from her. አስማተኛው ፡ እርኩስ ፡ መንፈስ ፡ አወጣላት

**exotic**
1. የባዕድ ፡ አገር. Eucalyptus is an exotic plant. ባሕር ፡ ዛፍ ፡ የባዕድ ፡ አገር ፡ ዕፅ ፡ ነው
2. እንግዳ ፡ የሆነ. We saw many exotic plants at the flower show. ባበባው ፡ ትርኢይት ፡ ላ
ይ ፡ ብዙ ፡ እንግዳ ፡ የሆኑ ፡ ዕፀዋት ፡ አየን
3. ትንግርት ፡ ያለው. She performed an exotic, Spanish dance. ትንግርት ፡ ያለው ፡ የስፓኝ ፡ ዳን
ስ ፡ አሳየች

**expand** (vt.) አስፋፋ
We are going to expand our business next year. ለሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ንግዳችንን ፡ እናስፋፋለን
He expanded the short story into a novel. አጭሩን ፡ ታሪክ ፡ ወደ ፡ ልበ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ አስፋፋው
Heat expands, cold contracts. ሙቀት ፡ ያ
ስፋፋል ፤ ቅዝቃዜ ፡ ያኰማትራል

**expand** (vi.)
1. ተለጠጠ. Tires expand when air is pumped into them. ጐማ ፡ ሲነፋት ፡ ይለጠጣል
2. ተስፋፋ. Metals expand when they are heated. ብረት ፡ ሲግል ፡ ይስፋፋል
3. ተወጠረ. A balloon expands when it is blown up. ፊኛ ፡ ሲነፋ ፡ ይወጠራል
4. ድንበሩን ፡ አስፋፋ. Our country has expanded many times. አገራችን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ድንበሯን ፡ አስፋፍታለች

**expand on** አብራራ
Please ask him to expand on that statement. የገለጸውን ፡ ሐሳብ ፡ እንዲያብራራው ፡ ጠይቀው

**expanse** አካል
The Pacific Ocean is a vast expanse of water. የፓሲፊክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ሰፊ ፡ የውኃ ፡ አካል ፡ ነው

**expanse of the field**
*The expanse of the racing field was completely covered with people. መላው ፡ የእሽቅድምድሙን ፡
ሜዳ ፡ ሰው ፡ አልብሶት ፡ ነበር

**expanse of the plain** ሜዳ
The broad expanse of the plain was dotted with trees. ለጥ ፡ ያለው ፡ ሜዳ ፡ አልፎ ፡ አልፎ
ዛፎች ፡ ይታይበታል

**expansion** ማስፋፋት
The expansion of France towards the south was one of Napoleon's policies. ፈረንሳይን ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ማስፋፋት ፡ ከናፖሊዮን ፡ ዓላማዎች ፡ አንዱ ፡ ነበር

**(be) expansive** የመስፋፋት ፡ ጠባይ ፡ አለው
Gases are expansive. ጋዞች ፡ የመስፋፋት ፡ ጠባይ ፡ አላቸው

**expansive stretch of** ለዓይን ፡ የሚታክት
An expansive stretch of desert can be seen from the mountaintop. ከተራራው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ሲቆሙ ፡ ለዓይን ፡ የሚታክት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይታያል

**expatriate** (vt.) ካገር ፡ ውጭ ፡ አወጣ
Foreign companies expatriate their profits thus impoverishing the country. የውጭ ፡ አገር ፡ ኩባንያዎች ፡ ትርፋቸውን ፡ ካገር ፡ ውጭ ፡ በማውጣት ፡ አገሪቱን ፡ ያደኸያሉ

**expatriate** (vi.) አገሩን ፡ ለቆ ፡ ወጣ
He expatriated before the war. ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ አገሩን ፡ ለቆ ፡ ወጣ

**expatriate** (n.) የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው
Many expatriates live in this country. ብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ

**become an expatriate** ካገሩ ፡ ወጣ
The writer became an expatriate before the war. ደራሲው ፡ ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ ካገሩ ፡ ወጣ

**expect** (vt.)
1. ጠበቀ. I expect him at three o'clock. በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ይመጣል ፡ ብዬ ፡ እጠብቀዋለሁ
2. ፈለገ. Does he expect a tip? ጉርሻ ፡ ይፈልጋል ?
3. ተስፋ ፡ አደረገ. I expect you to do a good job. ጥሩ ፡ ሥራ ፡ እንደምትሠራ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ

**expect** (vi.)
1. አሰበ. I expect to be back on Sunday. እሑድ ፡ ለመመለስ ፡ አስባለሁ
I am not surprised at his refusal. That's exactly what I expected. እምቢ ፡ በማለቱ ፡ አልደነቅም ፤ ልክ ፡ ያሰብኩት ፡ ነውና
2. ጠበቀ. You're expecting too much of her. ከሷ ፡ የምትጠብቀው ፡ ከሚገባ ፡ በላይ ፡ ነው
3. መሰለ(ው). Will he be late? I expect so. ይዘገይ ፡ ይሆን ? ይመስለኛል

**expectant mother** ነፍሰ ፡ ጡር ፡ ሴት
Expectant mothers should see a doctor regularly. ነፍሰ ፡ ጡር ፡ ሴቶች ፡ በየጊዜው ፡ ሐኪም ፡ ዘንድ ፡ መሄድ ፡ አለባቸው

**expectation** ግምት
Your work falls short of my expectations. ሥራህ ፡ ከግምቴ ፡ በታች ፡ ነው
*It doesn't come up to my expectations. ያሰብኩትን ፡ ያህል ፡ አይደለም

**contrary to my expectation** እንዳሰብኩት ፡ ሳይሆን
Contrary to my expectation, the experiment turned out well. እንዳሰብኩት ፡ ሳይሆን ፡ ሙከራው ፡ ተሳካ

**have expectations** ተስፋ ፡ አደረገ
He has expectations of money from a rich uncle. ከሀብታም ፡ አጐቱ ፡ ገንዘብ ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋል

**in expectation** አስቦ
He ate a light lunch in expectation of a big supper. በርካታ ፡ እራት ፡ ለመብላት ፡ አስቦ ፡ ቀላል ፡ ምሳ ፡ በላ
*He sat on the edge of his seat in expectation. ወምበሩ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ተጠባበቀ

**expectorate** ምራቅ ፡ ተፋ
You will expectorate when you chew tobacco. ሱረት ፡ ስትጐርስ ፡ ምራቅህን ፡ ትተፋለህ

**expedient**
1. ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ የታየው. In times of war, governments do things because they are expedient. በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ መንግሥታት ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ የታያቸውን ፡ ነገር ፡ ያደርጋሉ
2. ምቹ. The telephone is an expedient way to deliver messages. መልእክትን ፡ ለማስተላለፍ ፡ ስልክ ፡ ምቹ ፡ የሆነ ፡ መንገድ ፡ ነው
*In a crisis, much that we do is merely expedient. በችግር ፡ ጊዜ ፡ የምናደርገው ፡ ነገር ፡ ብዙው ፡ ለጊዜያዊ ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ ነው

**expedite** አፋጠነ
Let's work to expedite progress! እድገትን ፡ ለማፋጠን ፡ እንሥራ

**expedition**
1. ጓድ. There is a scientific expedition investigating the languages of Ethiopia. የኢትዮጵያን ፡ ቋንቋዎች ፡ የሚያጠና ፡ አንድ ፡ የሊቃውንት ፡ ጓድ ፡ አለ
2. ዘመቻ. Napier's expedition succeeded in releasing British prisoners. የናፒየር ፡ ዘመቻ ፡ የእንግሊዝን ፡ እስረኞች ፡ ለማስለቀቅ ፡ ቻለ

3. **መጓዝ**. An expedition to the North Pole is an adventurous undertaking. ወደ ፡ ሰሜናዊው ፡ ዋልታ ፡ መጓዝ ፡ ጀብዱ ፡ የበዛበት ፡ ድርጊት ፡ ነው
4. **ፍጥነት**. He has completed his work with expedition. በፍጥነት ፡ ሥራውን ፡ አጠናቀቀ

**expeditious**
1. **የተፋጠነ**. He performed the task in an expeditious manner. ሥራውን ፡ በተፋጠነ ፡ ሁኔታ ፡ አከናወነ
2. **ቀልጣፋ**. Our office has an expeditious filing system. ቢሮዋችን ፡ ቀልጣፋ ፡ የሆነ ፡ የመዝገብ ፡ አያያዝ ፡ ሥርዓት ፡ አለው

**expel** (expelled)
1. **አስወጣ**. The director expelled three students from school. ዲሬክተሩ ፡ ሦስት ፡ ተማሪዎች ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ አስወጣ
The army expelled the invader from our country. የጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ ጠላትን ፡ ካገራችን ፡ አስወጣ
2. **አስፈነጠረ**. This gun automatically expels the cartridges. ይህ ፡ ጠመንጃ ፡ እራሱ ፡ ቀለሁ ፡ ያስፈነጥራል

**be expelled ተባረረ**
The unruly student was expelled from school. በጥባጩ ፡ ተማሪ ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ ተባረረ

**expend ጨረሰ**
They expended all their ammunition firing in the dark. ጥይታቸውን ፡ ሁሉ ፡ በጨለማ ፡ በመተኰስ ፡ ጨረሱት
[See also 'effort']

**expenditure ወጪ**
Limit your expenditures to what is essential! ወጪህን ፡ ለሚያስፈልግ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ወስን

**expenditure of money ወጪ**
This job requires the expenditure of much money. ይህ ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ ወጪ ፡ ይጠይቃል

**expense**
1. **ወጪ**. Owning a car is a great expense. ባለመኪና ፡ መሆን ፡ ብዙ ፡ ወጪ ፡ ያስወጣል
He made the trip at his company's expense. የተጓዘው ፡ በኩባንያው ፡ ወጪ ፡ ነው
Don't go to any expense on my account! በኔ ፡ የተነሣ ፡ ምንም ፡ ወጪ ፡ አታድርግ
2. **ጉዳት**. This victory was won at terrible expense. ድሉ ፡ የተገኘው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ነው

**at the expense of**
1. **መሥዋዕት ፡ አድርጎ**. He became a brilliant scholar, but only at the expense of his health. ብልህ ፡ ምሁር ፡ ለመሆን ፡ የበቃው ፡ ጤንነቱን ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ነው
2. **በ - - - ትከሻ**. He aggrandized himself at the expense of others. በሌሎች ፡ ትከሻ ፡ ራሱን ፡ አሳደገ

**expensive ውድ**
This house is too expensive. ይህ ፡ ቤት ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ውድ ፡ ነው

**be expensive ብዙ ፡ ወጪ ፡ ጠየቀ**
Purification of water is expensive. ውኃን ፡ ማጣራት ፡ ብዙ ፡ ወጪ ፡ ይጠይቃል

**experience** (v.)
1. **አጋጠመ(ው)**. +I never experienced anything like it. እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አጋጥሞኝም ፡ አላውቅ
2. **ደረሰ(በት)**. He experienced great pain last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥቃይ ፡ ደረሰበት
3. **ቀመሰ**. Young as I am, I have experienced life. ወጣት ፡ ብሆንም ፡ ኑሮን ፡ ቀምሼዋለሁ

**experience** (n.)
1. **ልምድ**. I know from experience it won't work. ከልምድ ፡ እንዳገኘሁት ፡ ይህ ፡ እንደማይሠራ ፡ አውቃለሁ
2. **ልምምድ**. He had no previous experience in that field. ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በዚያ ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ልምምድ ፡ አልነበረውም
3. **የሥራ ፡ ልምምድ**. This experience should enable you to get a good position. ይህ ፡ የሥራ ፡ ልምምድ ፡ ደኅና ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ያውልሃል
4. **አጋጣሚ**. Being lost in the desert is an unpleasant experience. በረሃ ፡ ውስጥ ፡ መንገድ ፡ መሳት ፡ መጥፎ ፡ አጋጣሚ ፡ ነው
5. **ያጋጠመው ፡ ነገር**. They compared notes about their experiences in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ስላጋጠማቸው ፡ ነገር ፡ ያላቸውን ፡ ማስታወሻ ፡ አስተያዩ
6. **ዕውቀት**. The abstraction of philosophy contains the essence of human experience. የፍልስፍና ፡ ረቂቅነት ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ዕውቀት ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ይዟል
A trip around the world gives wide experience. ዓለምን ፡ መዞር ፡ ሰፊ ፡ ዕውቀት ፡ ይሰጣል

**have an experience ነገር ፡ አጋጠመ(ው)**
I had a strange experience last night. ትላንት ፡ ሌሊት ፡ አንድ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ አጋጠመኝ

**experienced** (adj.) **ልምድ ፡ ያለው**
He is an experienced driver. ልምድ ፡ ያለው ፡ ነጂ ፡ ነው

**experiment** (v.) ሞከረ
I experimented with the new colors. ባዲሶቹ ፡ ቀለሞች ፡ ሞከርኩ

**experiment** (n.) ሙከራ
The experiment was successful. ሙከራው ፡ የተሳካ ፡ ሆነ

**experimental**
1. ሙከራ ፡ የሚያስፈልገው. Chemistry is an experimental science. ኬሚስትሪ ፡ ሙከራ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሳይንስ ፡ ነው
2. ለሙከራ ፡ ያህል ፡ የተደረገ. This trip is only experimental. ይህ ፡ ጉዞ ፡ ለሙከራ ፡ ያህል ፡ የተደረገ ፡ ነው

**experimental stage** የሙከራ ፡ ደረጃ
It is still in an experimental stage. ገና ፡ በሙከራ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ነው

**expert** (n.)
1. ዐዋቂ. We will have to get the opinion of an expert. የዐዋቂ ፡ አስተያየት ፡ ማግኘት ፡ ይኖርብናል
2. ሊቅ. I have never laid claim to being an expert in geography. የጂኦግራፊ ፡ ሊቅ ፡ ነኝ ፡ ብዬ ፡ አላውቅም
3. የደረጃ ፡ ሰው. A game between an expert and a beginner is one-sided. በደረጃ ፡ ሰውና ፡ በጀማሪ ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ግጥሚያ ፡ የማይመጣጠን ፡ ነው
4. በሥራው ፡ የሠለጠነ ፡ ሰው. Only an expert knows how to deal with that problem. ለችግሩ ፡ መፍትሒ ፡ የሚያገኘው ፡ በሥራው ፡ የሠለጠነ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው

**expert** (adj.)
1. ጠለቅ ፡ ያለ. I need some expert advice. ጠለቅ ፡ ያለ ፡ ምክር ፡ እፈልጋለሁ
2. ጥልቅ. His expert knowledge is very useful for us. ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ዕውቀቱ ፡ ለኛ ፡ በጣም ፡ ጠቅሞናል
3. ባለሙያ. He is considered an expert mechanic for this job. በዚህ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ባለሙያ ፡ ሜካኒክ ፡ ይቈጠራል

**expiate**
1. አስወረደ. He tried to expiate his sin through penance. ኃጢአቱን ፡ በንስሐ ፡ ሊያስወርድ ፡ ሞከረ
2. (= pass.) ተሰረየ(ለት). +He expiated his sins by doing good works. መልካም ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ኀጢአቱ ፡ ተሰረየለት
3. ደመሰሰ. The thief expiated his theft by giving back the stolen amount. የሰረቀውን ፡ ገንዘብ ፡ በመመለስ ፡ ሌብነቱን ፡ ደመሰሰ

**expiation** ስርየት
Expiation can be granted only by a priest. ስርየት ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችለው ፡ በቄስ ፡ ብቻ ፡ ነው

**expiration** ፍጻሜ
The expiration of the UN session coincided with the arrival of the Indian President. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ስብሰባ ፡ ፍጻሜና ፡ የህንድ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ መምጣት ፡ ተገጣጠመ

**expiration of air** ወደ ፡ ውጭ ፡ መተንፈስ
Expiration of air is hindered by diphtheria. ወደ ፡ ውጭ ፡ መተንፈስ ፡ በጉሮሮ ፡ በሽታ ፡ ምክንያት ፡ ይታወካል

**expire**
1. ጊዜ ፡ አለቀ. When does your driver's license expire? የመንጃ ፡ ፈቃድህ ፡ ጊዜ ፡ የሚያልቀው ፡ መቼ ፡ ነው ?
2. አረፈ. He expired on the spot from a bullet wound. በጥይት ፡ ተመቶ ፡ ወዲያውኑ ፡ አረፈ
3. ተነፈሰ. At night, he appears to expire deeply. ሌሊቱን ፡ በኀይል ፡ የሚተነፍስ ፡ ይመስላል

**explain**
1. ምክንያት ፡ ሰጠ ፤ ምክንያት ፡ ነገረ. Please explain your actions of last night! ትናንት ፡ ማታ ፡ ለሠራኸው ፡ ነገር ፡ ምክንያትህን ፡ ስጥ
Can you explain your absence? የቀረህበትን ፡ ምክንያት ፡ ልትነግረን ፡ ትችላለህ ?
2. አስረዳ. I explained to him the obscure points of the contract. ከውለታው ፡ ውስጥ ፡ ለመረዳት ፡ የሚያስቸግሩትን ፡ ነጥቦች ፡ አስረዳሁት
3. አብራራ. Explain that again; I don't get the drift of your words. ያን ፡ እንደገና ፡ አብራራው ፤ የንግግርህን ፡ አዝማሚያ ፡ አልተረዳሁትም
4. አለ. How can you explain such a silly remark? እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ጅል ፡ አስተያየት ፡ ምን ፡ ትለዋለህ ?

**explanation**
1. ማብራሪያ. Not much explanation will be necessary. ብዙ ፡ ማብራሪያ ፡ አያሻም
2. አገላለጽ. His explanation was lucid. አገላለጹ ፡ ግልጽ ፡ ነበር
3. መግለጫ. The explanation of the theory covered many pages. የቲዎሪው ፡ መግለጫ ፡ በብዙ ፡ ገጽ ፡ የተጻፈ ፡ ነበር

**explanatory** (= noun) ማብራሪያ
This book has many explanatory footnotes. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ማብራሪያ ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻዎች ፡ አሉት

**explicate** አብራራ
The teacher asked the students to explicate the text. መምህሩ ፡ ጽሑፉን ፡ እንዲያብራሩ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ጠየቃቸው

**explicit** ግልጽ
He gave the servant explicit instructions not to let strangers into the house. እንግዶችን ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እንዳያስገባ ፡ ላሽከሩ ፡ ግልጽ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ

**be explicit** በግልጽ ፡ ነገረ
He was quite explicit on what he expected us to do for him. ምን ፡ ልንሠራለት ፡ እንደሚፈልግ ፡ በግልጽ ፡ ነገረን

**explode** (vt.) አፈነዳ
The French exploded an atomic bomb in the Pacific. ፈረንሳዮች ፡ በፓሲፊክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ውስጥ ፡ የአቶሚክ ፡ ቦምብ ፡ አፈነዱ

**explode** (vi.)
1. ፈነዳ. When the bomb exploded, many people were hurt. ቦምቡ ፡ ሲፈነዳ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተጐዱ
The speaker's mistake was so funny the audience exploded with laughter. የተናጋሪው ፡ ስሕተት ፡ የሚያሥቅ ፡ ስለነበረ ፡ አዳማጮቹ ፡ በሣቅ ፡ ፈነዱ
2. ቱግ ፡ አለ. He exploded with rage when contradicted. ሐሳቡን ፡ ቢቃወሙት ፡ በቁጣ ፡ ቱግ ፡ አለ
3. ከመቼውም ፡ ይበልጥ ፡ ጨመረ. World population has exploded in recent years. የዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ በቅርብ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ከመቼውም ፡ ይበልጥ ፡ ጨምሯል

**help to explode** ከንቱ ፡ ለማድረግ ፡ ረዳ
Columbus helped to explode the theory that the earth was flat. ኮለምበስ ፡ መሬት ፡ ዝርግ ፡ ነች ፡ የሚለውን ፡ ቲዎሪ ፡ ከንቱ ፡ ለማድረግ ፡ ረዳ

**exploit** (v.)
1. የ - - - ፡ ጉልበት ፡ ያላግባብ ፡ በላ. The colonialists exploited the natives in order to get rich. ቅኝ ፡ ገዢዎች ፡ ለመበልጸግ ፡ ሲሉ ፡ ያገሩን ፡ ተወላጆች ፡ ጉልበት ፡ ያላግባብ ፡ በሉ
2. ተገቢ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ተጠቀመበት. He exploited the child's ignorance in order to take money away from him. ገንዘቡን ፡ ከልጁ ፡ ለመንጠቅ ፡ ሲል ፡ የልጁን ፡ አለማወቅ ፡ ተገቢ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ተጠቀመበት
3. አገልግሎት ፡ ላይ ፡ አዋለ. The engineer exploited the water power of the river. መሃንዲሱ ፡ የወንዙን ፡ የውኃ ፡ ኀይል ፡ አገልግሎት ፡ ላይ ፡ አዋለው
4. በጥቅም ፡ ላይ ፡ አዋለ. We must exploit our natural resources. የተፈጥሮ ፡ ሀብታችንን ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ አለብን
5. ቈፈረ. They exploited the mine for its gold. ወርቅ ፡ ፍለጋ ፡ ማዕድኑን ፡ ቈፈሩ
*He exploits the workers. ሠራተኞቹን ፡ ደም ፡ እስኪተፉ ፡ ያሠራቸዋል

**exploit** (n.) ጀብዱ
He never stops talking about his exploits. ስለ ፡ ራሱ ፡ ጀብዱ ፡ ከማውራት ፡ አያቋርጥም

**exploitation**
*It is difficult to dissociate imperialism from exploitation. ኢምፔርያሊዝምን ፡ በሌሎች ፡ ሀብትና ፡ ጉልበት ፡ አላግባብ ፡ ከመጠቀም ፡ ለመለየት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**exploration** መፈለግ
The exploration for the bullet had to be done by X ray. ጥይቱ ፡ በራጅ ፡ መፈለግ ፡ ነበረበት
*The exploration of Sidamo province was not undertaken until recently. እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ተመርምሮ ፡ አልተጠናም ፡ ነበር

**explore**
1. እየተዘዋወረ ፡ ጥናት ፡ አደረገ. The expedition is exploring Ethiopia looking for gold. ጓዱ ፡ ወርቅ ፡ ለመፈለግ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ጥናት ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ነው
2. ፈለገ. The Ethiopian government gave the Sinclair Oil Company a concession to explore for oil. የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ለሲንክሌር ፡ ኩባንያ ፡ ነዳጅ ፡ ዘይት ፡ የሚገኝበትን ፡ ስፍራ ፡ እንዲፈልግ ፡ ፈቃድ ፡ ሰጠ
3. አውጥቶ ፡ አውርዶ ፡ ሞከረ. We explored all the possibilities. ሊሆን ፡ የሚችለውን ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ አውጥተን ፡ አውርደን ፡ ሞከርን
4. አየ. The children explored the new house from top to bottom. ልጆቹ ፡ አዲሱን ፡ ቤት ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ አዩት
5. መረመረ (ተመረመረ). The lunar landscape has only recently been explored. የጨረቃ ፡ ገጽ ፡ የተመረመረው ፡ በቅርቡ ፡ ነው

**explorer** አሳሽ
Amundsen was an intrepid explorer. አሙንድሰን ፡ ደፋር ፡ አሳሽ ፡ ነበር

**explosion**
1. ፍንዳታ. The explosion destroyed the building. ፍንዳታው ፡ ቤቱን ፡ አወደመው

2. የፈንጂ ፡ ድምፅ. The explosion was heard a mile away. የፈንጂው ፡ ድምፅ ፡ አንድ ፡ ማይል ፡ ርቆ ፡ ይሰማ ፡ ነበር

**explosive** (n.) ፈንጂ
The explosives are stored in an underground room. ፈንጂዎቹ ፡ እምድር ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ተከማችተዋል

**explosive** (adj.)
1. ፈንጂ ፡ የሚሠራበት. This chemical is an explosive substance. ይህ ፡ ኬሚካል ፡ ፈንጂ ፡ የሚሠራበት ፡ ነው
2. የማንፍልነት. The irritable old man has an explosive temper. በቀላሉ ፡ የሚናደድ ፡ ሽማግሌ ፡ የማንፍልነት ፡ ጠባይ ፡ አለው
3. አደገኛ. Riots caused an explosive situation. ብጥብጡ ፡ አደገኛ ፡ ሁኔታ ፡ አደረሰ

**exponent** ተንታኝ
He is an exponent of modern music. የዘመናዊ ፡ ሙዚቃ ፡ ተንታኝ ፡ ነው

**export** (v.) ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ላከ
Ethiopia exports hides. ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ቆዳ ፡ ትልካለች

**export** (n.)
1. ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ መላክ. The government has stopped the export of coal. መንግሥቱ ፡ የድንጋይ ፡ ከሰል ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ መላክ ፡ አቁሟል
2. ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚላክ ፡ ሸቀጥ. What are the chief exports of Ethiopia? ከኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚላኩ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ሸቀጦች ፡ ምንድ ፡ ናቸው ?

**be in export business** ላኪ ፡ ነው
He is in the import and export business. እሱ ፡ አስመጪና ፡ ላኪ ፡ ነው

**expose**
1. ገለጠ. The informer exposed the conspiracy to the police. ጆሮ ፡ ጠቢው ፡ አድማውን ፡ ለፖሊስ ፡ ገለጠ
2. አጋለጠ. The official bought off those who might expose him. ባለሥልጣኑ ፡ የሚያጋልጡትን ፡ ሰዎች ፡ በገንዘብ ፡ ደለላቸው
3. ገለበጠ. He exposed his chest and dared the enemy to shoot him. ደረቱን ፡ ገልብጦ ፡ ጠላቱን ፡ ተኩስብኝ ፡ እያለ ፡ በድፍረት ፡ ተናገረ
4. ጣለ. The general exposed the troops to unnecessary danger. ጄኔራሉ ፡ ወታደሮቹን ፡ አስፈላጊ ፡ ያልሆነ ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ጣላቸው
5. ዘረገፈ. The vendor exposed his wares. ሻጩ ፡ እቃውን ፡ ዘረገፈ
*Don't expose your skin to too much sunshine. ቆዳህን ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ፀሐይ ፡ አታስመታ

**be exposed**
1. ተጋለጠ. Soldiers in an open field are exposed to the enemy's fire. በአውላላ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ወታደሮች ፡ ለጠላት ፡ ጥይት ፡ ይጋለጣሉ
This chemical will fulminate if exposed to heat. ይህ ፡ ኬሚካል ፡ ለሙቀት ፡ የተጋለጠ ፡ እንደሆነ ፡ ይፈነዳል
2. ራሱን ፡ አጋለጠ. By playing with John, the children had all been exposed to the measles. ከዮሐንስ ፡ ጋር ፡ በመጫወት ፡ ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ ራሳቸውን ፡ ለኩፍኝ ፡ አጋለጡ

**exposition**
1. ኤክስፖዚሲዮን. The exposition contained exhibits from many countries. ኤክስፖዚሲዮኑ ፡ ላይ ፡ የብዙ ፡ አገር ፡ ትርኢይቶች ፡ ነበሩ
2. ማብራሪያ. His exposition of Hamlet was helpful. ስለ ፡ ሃምሌት ፡ የሰጠው ፡ ማብራሪያ ፡ ጠቃሚ ፡ ነበር

**expostulate** ሐሳቡን ፡ እንዲለውጥ ፡ ለመነው
I expostulated with my friend who intended to drop out of school. ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመውጣት ፡ ያሰበውን ፡ ጓደኛዬን ፡ ሐሳቡን ፡ እንዲለውጥ ፡ ለመንኩት

**exposure**
1. መታወቅ. The exposure of the real criminal cleared the innocent man. የእውነተኛው ፡ ወንጀለኛ ፡ መታወቅ ፡ ወንጀል ፡ ያልፈጸመውን ፡ ሰውዬ ፡ ነጻ ፡ አደረገው
2. አለመደበቅ. His exposure of his anger shocked the company. ቁጣውን ፡ አለመደበቁ ፡ አብረውት ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ አስደነገጣቸው
3. ሐሩርና ፡ ቍር. In ancient Greece, weaklings were left to die of exposure. በጥንታዊት ፡ ግሪክ ፡ ደካማ ፡ ሕፃናት ፡ ከሐሩርና ፡ ከቍር ፡ የተነሣ ፡ እንዲሞቱ ፡ ይጣሉ ፡ ነበር
*Exposure to the rain has spoiled this table. ይህ ፡ ጠረጴዛ ፡ ዝናም ፡ ስለመታው ፡ ተበላሸ
*This room has western exposure. ይህ ፡ ክፍል ፡ ፊቱ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ነው

**expound** አብራራ
He expounded the theory of evolution to the crowd. የሥነ ፡ ተፈጥሮን ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳብ ፡ ለተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ አብራራ

**express** (v.)
1. ተናገረ. He expressed his opinion freely. ሐሳቡን ፡ በግልጽ ፡ ተናገረ
Did he express any wish? ምን ፡ እንደሚፈልግ ፡ ተናገረ ?
2. ገለጸ. He expressed his dissent when asked if he agreed with the speaker. ከተናጋሪው ፡ ጋር ፡ ይስማማ ፡ እንደሆን ፡ ቢጠየቅ ፡ አለመስማማቱን ፡ ገለጸ
3. አመለከተ. A smile expresses joy. ፈገግታ ፡ ደስታን ፡ ያመለክታል
4. በፍጥነት ፡ ላከ. The company will express packages to any destination. ኩባንያው ፡ ወደ ፡ ተፈለገበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ጥቅሎችን ፡ በፍጥነት ፡ ይልካል
5. ጨመቀ. He expressed the juice from grapes to make wine. የወይን ፡ ጠጅ ፡ ለማዘጋጀት ፡ የወይኑን ፡ ፍሬ ፡ ጨመቀ

**express oneself** ሐሳቡን ፡ ገለጸ
He is able to express himself in Amharic. ሐሳቡን ፡ ባማርኛ ፡ መግለጽ ፡ ይችላል

**express** (n.) ፈጣን ፡ ባቡር ፤ በቀጥታ ፡ የሚሄድ ፡ ባቡር
The express is expected at five o'clock. ፈጣኑ ፡ ባቡር ፡ በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ይደርሳል
A local train takes twice as long as an express. በየጣቢያው ፡ የሚቆም ፡ ባቡር ፡ በቀጥታ ፡ ከሚሄደው ፡ ይልቅ ፡ ዕጥፍ ፡ ጊዜ ፡ ይወስዳል

**express** (adj.)
1. የተለየ. We have an express purpose in being here. እዚህ ፡ የመጣነው ፡ ለተለየ ፡ ጉዳይ ፡ ነው
2. በራሪ. An express bus passed the local bus. በራሪው ፡ አውቶቡስ ፡ የከተማውን ፡ አውቶቡስ ፡ ቀደመው
3. ግልጽ. His express wish was to go to Ethiopia. ግልጽ ፡ ፍላጎቱ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሄድ ፡ ነበር

**express** (adv.) በአስቸኳይ ፡ ፖስታ
Send this parcel express! ይህንን ፡ ጥቅል ፡ በአስቸኳይ ፡ ፖስታ ፡ ላክ

**expression**
1. አባባል. There is no better expression for it. ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ አባባል ፡ የለውም
2. አገላለጽ. His forceful expression of ideas was admired by the audience. የሐሳብ ፡ አገላለጹ ፡ ኀይለኛነት ፡ ባዳማጮቹ ፡ ተደነቀ
3. ምልክት. There was an expression of discontent on her face. በፊቷ ፡ ላይ ፡ የቅሬታ ፡ ምልክት ፡ ይታይ ፡ ነበር
4. ፊት ፤ አስተያየት. His expression showed that he was not happy. ፊቱ ፡ አለመደሰቱን ፡ ያሳይ ፡ ነበር
He construed from her expression that she was furious. ከአስተያየቷ ፡ የተቈጣች ፡ መሆኗን ፡ ገመተ
5. መግለጫ. This note is an expression of my gratitude. ይህ ፡ ማስታወሻ ፡ ለወሮታዬ ፡ መግለጫ ፡ የተጻፈ ፡ ነው
6. ስሜት. His face lacks expression. መልኩ ፡ ምንም ፡ ስሜት ፡ አይታይበትም
7. ስሜትን ፡ የሚነካ ፡ አኳኋን. She sang with such expression that the audience wept. ስሜትን ፡ በሚነካ ፡ አኳኋን ፡ ስለዘመረች ፡ አድማጮቹ ፡ አለቀሱ
8. ስሜት ፡ የሚሰጥ ፡ አኳኋን. Try to read with more expression! የበለጠ ፡ ስሜት ፡ በሚሰጥ ፡ አኳኋን ፡ ለማንበብ ፡ ሞክር
[See also 'placid, somber']

**expressive**
1. ትርጉም ፡ ያለው. Charlie Chaplin's gestures were very expressive. የቻርሊ ፡ ቻፕሊን ፡ እንቅስቃሴዎች ፡ በጣም ፡ ትርጉም ፡ ያላቸው ፡ ነበሩ
2. (= n.) መግለጫ. "Alas" is a word expressive of sadness. « ወዮ ! » ፡ የሐዘን ፡ መግለጫ ፡ ቃል ፡ ነው

**be expressive** ስሜት ፡ ገለጸ
His gestures are very expressive. የሰውነቱ ፡ እንቅስቃሴዎች ፡ ስሜትን ፡ በጣም ፡ ይገልጻሉ

**expressly**
1. በጥብቅ. You are expressly forbidden to touch it. እንዳትነካው ፡ በጥብቅ ፡ ተከልክለሃል
2. በግልጽ. She told us expressly to come home early. ቀደም ፡ ብለን ፡ እንድንመጣ ፡ በግልጽ ፡ ነገረችን
3. በተለይ. This is a dictionary expressly compiled for students of Amharic. ይህ ፡ በተለይ ፡ ላማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተማሪዎች ፡ የተዘጋጀ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ነው

**expropriate** በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ወረሰ
The mayor expropriated land to build a hospital. ከንቲባው ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ለማሠራት ፡ መሬቱን ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ወረሰ

**expulsion**
1. መባረር. The expulsion from the club embittered him greatly. ከክበቡ ፡ መባረሩ ፡ ብዙ ፡ አናደደው
2. ማስወጣት. Expulsion of water from the lungs of a drowning person will save him

from death. ከሰመጠ ፡ ሰው ፡ ሳምባ ፡ ውስጥ ፡ ውኃን ፡ ማስወጣት ፡ ከሞት ፡ ያድነዋል

**expurgate** የሚያስከፋውን ፡ ነገር ፡ ሰረዘ
The censor expurgated the latest novel. ሳንሱሩ ፡ ከዲሱ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚያስከፋውን ፡ ነገር ፡ ሰረዘ

**expurgated** (adj.) የታረመ
The expurgated edition of Shakespeare has no offensive passages in it. የታረመው ፡ የሼክስፒር ፡ ቴያትር ፡ በውስጡ ፡ የሚያስከፋ ፡ ክፍል ፡ የለበትም

**exquisite**
1. በጣም ፡ የሚደነቅ. She has exquisite manners. በጣም ፡ የሚደነቅ ፡ ጠባይ ፡ አላት
2. ውብ. This is an exquisite rose. ይህች ፡ ውብ ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ ናት

**extant**
1. ሊገኝ ፡ የተቻለ. This is the earliest extant manuscript. ይህ ፡ ሊገኙ ፡ ከተቻሉት ፡ የመጀመሪያው ፡ የብራና ፡ ጽሑፍ ፡ ነው
2. አሁን ፡ ያለ. He restored the original text by careful comparison of all extant copies. አሁን ፡ ያሉትን ፡ መጽሐፎች ፡ በጥንቃቄ ፡ በማወዳደር ፡ የመጀመሪያውን ፡ ጽሑፍ ፡ እንደነበረ ፡ አደረገ

**be extant** ኖረ
Some ancient fish are still extant. አንዳንድ ፡ የጥንት ፡ ዓሣዎች ፡ አሁንም ፡ ይኖራሉ

**extemporaneous** ያለ ፡ ዝግጅት
The director gave an extemporaneous speech. ዲሬክተሩ ፡ ያለ ፡ ዝግጅት ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**extend** (vt.)
1. ዘረጋ. He extended a rope between two posts. በሁለት ፡ ምሰሶዎች ፡ መካከል ፡ ገመድ ፡ ዘረጋ
He extended his arm to catch the rope. ገመዱን ፡ ለመያዝ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ
2. ቀጠለ. They are going to extend the railway to Arba Minch from Addis Ababa. የሐዲዱን ፡ መሥመር ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ እስከ ፡ አርባ ፡ ምንጭ ፡ ሊቀጥሉት ፡ ነው
3. አስፋፋ. The European powers extended their authority in Asia. የአውሮፓ ፡ ኀያላን ፡ ሥልጣናቸውን ፡ በእስያ ፡ አስፋፉት
4. ሰጠ. The bank extended credit to the farmers. ባንኩ ፡ ለገበሬዎች ፡ ብድር ፡ ሰጠ
5. አደረገ. This organization extends help to poor people. ይህ ፡ ድርጅት ፡ ለድኾች ፡ እርዳታ ፡ ያደርጋል
They extended a warm welcome to the director. ለዲሬክተሩ ፡ የጋለ ፡ አቀባበል ፡ አደረጉለት
6. አረዘመ. The ministry extended his visa. ሚኒስቴሩ ፡ ቪዛው ፡ የሚቆይበትን ፡ ጊዜ ፡ አረዘመለት
Can you extend your visit for a few days? ጉብኝትህን ፡ ለጥቂት ፡ ቀናት ፡ ልታረዝም ፡ አትችልም ?

**extend** (vi.)
1. ረዥም ፡ ነው ፤ ረዘመ. This road extends for miles and miles. ይህ ፡ ጐዳና ፡ በጣም ፡ ረዥም ፡ ነው
The beach extends for miles in both directions. ጠረፉ ፡ በሁለቱም ፡ አቅጣጫ ፡ ብዙ ፡ ማይል ፡ ይረዝማል
2. ተዘረጋ. The dunes extend for miles. ያሸዋ ፡ ክምር ፡ ለብዙ ፡ ምዕራፍ ፡ ተዘርግቷል
3. ቆየ. The conference extends from Wednesday to Saturday. ስብሰባው ፡ ከረቡዕ ፡ እስከ ፡ ቅዳሜ ፡ ይቆያል

**extension**
1. ቅጥያ. The extension to our house will soon be finished. የቤታችን ፡ ቅጥያ ፡ በቅርብ ፡ ያልቃል
2. (= to extend) ማስፋት. Extension of the road is needed to make it usable. አገልግሎቱ ፡ እንዲያምር ፡ መንገዱን ፡ ማስፋት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
3. መስፋፋት. He is studying the extension of foreign influence in Africa. በአፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ የባዕድን ፡ ተጽዕኖ ፡ መስፋፋት ፡ በማጥናት ፡ ላይ ፡ ነው
4. የውስጥ ፡ መሥመር. I am speaking to you from the extension. የማነጋግርህ ፡ በውስጥ ፡ መሥመሩ ፡ ነው

**ask for an extension** እንዲጨመርለት ፡ ጠየቀ
He has asked for an extension of his leave. የዓመት ፡ ፈቃዱ ፡ እንዲጨመርለት ፡ ጠየቀ

**give an extension** ጨመረ
He gave me another week's extension. አንድ ፡ ሳምንት ፡ ጨመረልኝ

**extension courses** የትርፍ ፡ ጊዜ ፡ ትምህርት
The college gives extension courses. ኮሌጁ ፡ የትርፍ ፡ ጊዜ ፡ ትምህርት ፡ ይሰጣል

**extensive**
1. ሰፊ. An extensive park is located in the western part of the country. በአገሪቷ ፡ ምዕራብ ፡ ክፍል ፡ ሰፊ ፡ የመናፈሻ ፡ ቦታ ፡ አለ
He has an extensive knowledge of Amharic. ሰፊ ፡ ያማርኛ ፡ ችሎታ ፡ አለው
He wants to have extensive political influence.

ሰፊ ፡ የፖለቲካ ፡ ተሰሚነት ፡ እንዲኖረው ፡ ይፈልጋል
2. ረጅም. This book has an extensive preface. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ረጅም ፡ መግቢያ ፡ አለው
The author describes in this book his extensive travels. ደራሲው ፡ ረጅም ፡ ጉዞውን ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያስረዳል

**extensively** በሰፊው
He spoke extensively on the subject. ስለ ፡ አርእስቱ ፡ በሰፊው ፡ ተናገረ
*He traveled extensively. ብዙ ፡ አገር ፡ አይቷል

**extent**
1. መጠን. The extent of the damage caused by the war is considerable. ጦርነቱ ፡ ያደረሰው ፡ ጉዳት ፡ መጠኑ ፡ ብዙ ፡ ነው
2. ከፍተኛነት. His mind couldn't compass the extent of the disaster. ያደጋውን ፡ ከፍተኛነት ፡ አእምሮው ፡ ሊገምት ፡ አልቻለም
3. ስፋት. From the roof we can see the full extent of the garden. ጣሪያው ፡ ላይ ፡ ሆነን ፡ የአትክልቱን ፡ ስፍራ ፡ ሙሉ ፡ ስፋት ፡ ለማየት ፡ እንችላለን
I was amazed at the extent of his knowledge. በዕውቀቱ ፡ ስፋት ፡ ተደነቅሁ

**to a certain extent**
1. በመጠኑ. I agree with him to a certain extent. ከሱ ፡ ጋር ፡ በመጠኑ ፡ እስማማለሁ
2. ባንድ ፡ በኩል ፡ ሲታሰብ ፤ በከፊል. To a certain extent he is responsible for the disaster. ባንድ ፡ በኩል ፡ ሲታሰብ ፡ (በከፊል) ፡ ለጥፋቱ ፡ ተጠያቂ ፡ ነው

**to some extent** በከፊል
To some extent, he feels it is his fault. የሱ ፡ ጥፋት ፡ መሆኑ ፡ በከፊል ፡ ይሰማዋል

**to what extent** የቱን ፡ ያህል
To what extent are you prepared to help us? የቱን ፡ ያህል ፡ ልትረዳን ፡ ተዘጋጅተሃል ?

**extenuate**
1. በከፊል ፡ ምክንያት ፡ ሆነ. His faulty education extenuates his faulty pronunciation. የተበላሸው ፡ ትምህርቱ ፡ ለተሳሳተ ፡ አነጋገሩ ፡ በከፊል ፡ ምክንያት ፡ ሆኗል
2. ጥፋተኛነት ፡ ቀነሰ. Nothing can extenuate his bad conduct. ምንም ፡ ነገር ፡ ለክፉ ፡ ተግባሩ ፡ ጥፋተኛነቱን ፡ ሊቀንስለት ፡ አይችልም

**exterior** (n.)
1. ውጪ. The exterior of the house is in bad shape. ቤቱ ፡ ውጪው ፡ ተበላሽቷል
2. (= adv.) ላይ ፡ ላዩን. She has a pleasant exterior, but inside she is tormented. ላይ ፡ ላዩን ፡ ደኅና ፡ ትመስላለች ፤ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ግን ፡ ተበሳጭታለች

**exterior** (adj.)
1. የውጭ. The exterior covering is made of iron. የውጪው ፡ ልባስ ፡ ከብረት ፡ የተሠራ ፡ ነው
2. ለውጭ ፡ የሚሆን. This store sells only exterior paint. ይህ ፡ መደብር ፡ ለውጭ ፡ የሚሆን ፡ ቀለም ፡ ብቻ ፡ ይሸጣል
3. ከውጭ ፡ የመጣ. Exterior forces destroyed the country. ከውጭ ፡ የመጡት ፡ ኀይሎች ፡ አገሪቱን ፡ አጠፏት

**exterminate**
1. ደመሰሰ. They exterminated their enemy by heavy bombardment. በከባድ ፡ የቦምብ ፡ ድብደባ ፡ ጠላታቸውን ፡ ደመሰሱ
2. አጠፋ. The workmen used poison to exterminate the ants. ሠራተኞቹ ፡ ጉንዳኖቹን ፡ በመርዝ ፡ አጠፏቸው

**external** የውጭ
War affects a nation's external trade. ጦርነት ፡ የሀገርን ፡ የውጭ ፡ ንግድ ፡ ይጐዳል

**external appearances** መልክ
External appearances are often a poor guide to character. መልክ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለጠባይ ፡ የተሳሳተ ፡ መመዘኛ ፡ ነው

**external sign** ምልክት
Red spots are an external sign of measles. ቀያይ ፡ ሽፍታዎች ፡ ቆዳ ፡ ላይ ፡ የሚታዩ ፡ የኩፍኝ ፡ ምልክቶች ፡ ናቸው

**for external use**
*This alcohol is for external use only. ይህ ፡ አልኮል ፡ ለመድኀኒትነት ፡ እንጂ ፡ ለመጠጥ ፡ የማይሆን ፡ ነው

**extinct**
1. የቀረ. Scratching one's face at the funeral is an extinct custom. ሰው ፡ ሲሞት ፡ ፊትን ፡ መንጨት ፡ የቀረ ፡ ልማድ ፡ ነው
2. ፈንድቶ ፡ ያለቀ(ለት). Zuqwala is an extinct volcano. ዝቋላ ፡ ፈንድቶ ፡ ያለቀለት ፡ እሳተ ፡ ገሞራ ፡ ነው

**be extinct** ጠፋ
This kind of animal is extinct. የዚህ ፡ የእንስሳ ፡ ዘር ፡ ጠፍቷል

**extinction**
1. መጥፋት. The extinction of the lights left us in total darkness. የመብራቱ ፡ መጥፋት ፡ ፍጹም ፡ ጨለማ ፡ ውስጥ ፡ አስቀረን

2. ማጥፋት. Physicians are working for the extinction of diseases. ሐኪሞች ፡ በሽታን ፡ ለማጥፋት ፡ ይታገላሉ

**extinguish**

1. አጠፋ. He tried to extinguish the fire with sand. እሳቱን ፡ በአሸዋ ፡ ለማጥፋት ፡ ሞከረ
2. (= intr.) ወደመ. Failure to succeed at all extinguished her hope. ምንም ፡ ስላልተሳካላት ፡ ያላት ፡ ተስፋ ፡ ወደመ

**extirpate** ፈጽሞ ፡ አስቀረ

The new laws will extirpate the use of certain drugs. አዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ ባንዳንድ ፡ መድኀኒቶች ፡ መጠቀምን ፡ ፈጽመው ፡ ያስቀራሉ

**be extirpated** ተነቅሎ ፡ ተጣለ

The evil must be extirpated. መጥፎው ፡ ነገር ፡ ተነቅሎ ፡ መጣል ፡ አለበት

**extol** (extolled) በማሞገስ ፡ ተናገረ

The priest extolled the virtues of the deceased. ቄሱ ፡ የሟቹን ፡ ደግነት ፡ እያነሡ ፡ በማሞገስ ፡ ተናገሩ

**extort (money)** አስከፈለ

They extorted money from him by threatening to burn down his house. ቤቱን ፡ ለማቃጠል ፡ በማስፈራራት ፡ ገንዘብ ፡ አስከፈሉት

**extort a confession** አሳመነ

The police used torture to extort a confession from him. ለማሳመን ፡ ፖሊሶቹ ፡ አሠቃዩት

**extra** (n.)

1. ተጨማሪ ፡ ሠራተኛ. The grocer hires extras to work on Saturday. ምግብ ፡ ሻጩ ፡ ቅዳሜ ፡ ቅዳሜ ፡ ተጨማሪ ፡ ሠራተኞች ፡ ይቀጥራል
2. ተጨማሪ ፡ ጋዜጣ. An extra was published when the war was declared. ጦርነቱ ፡ በታወጀ ፡ ጊዜ ፡ ተጨማሪ ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ ነበር
3. (= adv.) በተለይ. Her regular school fees are 500 dollars a semester; music and dancing are extras. መደበኛው ፡ የትምህርት ፡ ሒሳብ ፡ በሴመስተር ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ነው ፤ ሙዚቃና ፡ ዳንስ ፡ ግን ፡ በተለይ ፡ ይከፈልባቸዋል

**extra** (adj.)

1. ተጨማሪ ፤ ትርፍ. I want extra pay for extra work. ለትርፍ ፡ ሥራ ፡ ተጨማሪ ፡ ክፍያ ፡ እፈልጋለሁ

Because of the declaration of war they published an extra edition of the newspaper. የጦርነቱን ፡ መታወጅ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ተጨማሪ ፡ የጋዜጣ ፡ እትም ፡ አወጡ

Do you have a few extra pencils? ትርፍ ፡ እርሳሶች ፡ አሉህ ?

2. ልዩ. Extra services are charged for, of course. ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ ይከፈላል ፡ መቼም

**extra** (adv.) ከመጠን ፡ በላይ

He needs an extra strong box to pack it in. ለእቃው ፡ መያዣ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ጠንካራ ፡ የሆነ ፡ ሣጥን ፡ ያስፈልገዋል

**extract** (v.)

1. ነቀለ. The dentist extracted his tooth. ሐኪሙ ፡ ጥርሱን ፡ ነቀለለት
2. አወጣ. The doctor extracted a bullet from his leg. ሐኪሙ ፡ ከእግሩ ፡ ውስጥ ፡ ጥይት ፡ አወጣለት

He extracts oil from olives. እሱ ፡ ከወይራ ፡ ዘይት ፡ ያወጣል

3. መርጦ ፡ አወጣ. The student extracted from the book passages dealing with history. ተማሪው ፡ ከመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ታሪክ ፡ የሚናገሩትን ፡ ምንባቦች ፡ መርጦ ፡ አወጣ

**extract a confession**

He extracted a confession from the thief. ሌባውን ፡ በማስገደድ ፡ አሳመነ

**extract** (n.) የተውጣጣ ፡ ምንባብ

Read these extracts from my poem! እነዚህን ፡ ከግጥሜ ፡ የተውጣጡ ፡ ምንባቦች ፡ አንብብ

**extradite** ወደያገሩ ፡ መልሶ ፡ ላከ

In accordance with the treaty, our government will extradite all foreign criminals. በውሉ ፡ መሠረት ፡ መንግሥታችን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ወንጀለኞችን ፡ ወደያገራቸው ፡ መልሶ ፡ ይልካል

**extraneous**

*Sand or some other extraneous matter had gotten into the butter. ቅቤው ፡ ውስጥ ፡ አሸዋ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ጉድፍ ፡ ገብቶበታል

**be extraneous** ምንም ፡ ግንኙነት ፡ የለውም

His questions are extraneous to the discussion. ጥያቄው ፡ ከጉዳዩ ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ግንኙነት ፡ የለውም

**extraordinary**

1. ያልተለመደ. This rainy weather is extraordinary for this time of year. ያሁኑ ፡ ዝናም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያልተለመደ ፡ ነው
2. እጅግ ፡ ጐበዝ. Only an extraordinary woman could accomplish all that. ያንን ፡ ለመሥራት ፡ የምትችለው ፡ እጅግ ፡ ጐበዝ ፡ የሆነች ፡ ሴት ፡ ብቻ ፡ ነች
3. እጅግ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ያለው. Einstein was a man of extraordinary abilities. አይንስታይን ፡ እጅግ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነበር

4. ልዩ. Extraordinary powers are given to the President in wartime. በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ለፕሬዚ ዳንቱ ፡ ልዩ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል
[See also 'envoy']

**extravagance** ገንዘብ ፡ አባካኝነት
His extravagance kept him always in debt. ገንዘብ ፡ አባካኝነቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ከዕዳ ፡ እንዳይወ ጣ ፡ አደረገው

**extravagant** (= adv.) በማጋነን
People laughed at the inventor's extravagant claims for his invention. ፈልሳፊው ፡ ስለፈለሰ ፈው ፡ ነገር ፡ በማጋነን ፡ መናገር ፡ ሕዝቡ ፡ ማ ቀበት

**be extravagant**
*A dinner for four people costing 60 dollars is extravagant. ላራት ፡ ሰው ፡ እራት ፡ ስልሳ ፡ ብ ር ፡ ማውጣት ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ወጪ ፡ ነው
[See also 'spender, spending']

**extreme** (n.)
1. ተቃራኒ. Love and hate are extremes. ፍቅርና ፡ ጥላቻ ፡ ተቃራኒዎች ፡ ናቸው
2. የተራራቀ ፡ ሐሳብ. We must seek the mean between the two extremes. ከሁለቱ ፡ የተራራቁ ፡ ሐሳቦች ፡ አማካዩን ፡ ሐሳብ ፡ መፈለግ ፡ አለብን

**go to extremes**
*The director went to extremes to make his position clear. ዲሬክተሩ ፡ አቋሙን ፡ ለመግለ ጽ ፡ ከሚያስፈልግ ፡ በላይ ፡ ዝርዝር ፡ አቀረበ

**to an extreme** ከመጠን ፡ በላይ
The director is cautious to an extreme. ዲሬክተ ሩ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ጠንቃቃ ፡ ነው

**extreme** (adj.)
1. ከፍ ፡ ያለ ፤ ከፍተኛ. He shows extreme patience in dealing with pain. ሥቃይ ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትዕግሥት ፡ ያሳያል
He was rewarded for the extreme courage he manifested in battle. በጦርነቱ ፡ ውስጥ ፡ ስ ላሳየው ፡ ከፍተኛ ፡ ጀግንነት ፡ ተሸለመ
2. የመጨረሻ. Death is the extreme penalty of law. ሞት ፡ የመጨረሻው ፡ የፍርድ ፡ ቅጣት ፡ ነው
These are the extreme limits of the town. ይህ ፡ የከተማው ፡ መጨረሻ ፡ ድንበር ፡ ነው
3. የመጨረሻ ፡ ጥብቅ. We had to resort to extreme measures. የመጨረሻውን ፡ ጥብቅ ፡ እርም ጃ ፡ መውሰድ ፡ ግድ ፡ ሆነብን
4. ጽኑ. Extreme conformity often prevents original thought. ጽኑ ፡ የሆነ ፡ ባንድ ፡ አስተ ሳሰብ ፡ መመራት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ ሐሳ ብ ፡ ከማፍለቅ ፡ ያግዳል
5. ኀይለኛ. She lost consciousness due to extreme heat. ከኀይለኛው ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ነፍሷን ፡ ሳተች
6. ከልክ ፡ የሚያልፍ. He holds extreme political views. ከልክ ፡ የሚያልፉ ፡ የፖለቲካ ፡ ሐሳቦ ች ፡ አሉት

**(at the) extreme end** ወዲያኛው ፡ ጠርዝ ፡ ላይ
Their house is at the extreme end of the island. ቤታቸው ፡ ከደሴቱ ፡ ወዲያኛው ፡ ጠርዝ ፡ ላይ ፡ ነው

**extremely** እጅግ ፡ በጣም
This news is extremely sad. ይህ ፡ ዜና ፡ እጅ ግ ፡ በጣም ፡ አሳዛኝ ፡ ነው

**extremity** (extremities)
1. ጫፍ. The extremity of the flagpole is pointed. የሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ መስቀያ ፡ ጫፍ ፡ ሹል ፡ ነው
2. ጭንቅ. People on a sinking ship are in extremity. በሚሰጥም ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ የሚ ገኙ ፡ ሰዎች ፡ ጭንቅ ፡ ይበዛባቸዋል
3. የመጨረሻ ፡ ደረጃ. That poor family is living at the extremity of misery. ችግረኞቹ ፡ ቤተሰቦ ች ፡ የመጨረሻ ፡ ደረጃ ፡ በሆነ ፡ ድኽነት ፡ ው ስጥ ፡ ይኖራሉ
4. ከልክ ፡ ማለፍ. The extremities of the situation caused her to lose her equilibrium. የሁኔታ ው ፡ ከልክ ፡ ማለፍ ፡ የመንፈስ ፡ እርጋታዋን ፡ አቃወሰባት

**extremities** እጅና ፡ እግሮች
His extremities were numb from the cold. እጅና ፡ እግሮቹ ፡ ከብርዱ ፡ የተነሣ ፡ ደንዝዘዋል

**be forced to the extremity of** ግድ ፡ ሆነበት
The soldiers were forced to the extremity of firing to scatter the mob. ወታደሮቹ ፡ የሚረብ ሸውን ፡ ሕዝብ ፡ ለመበተን ፡ ተኵስ ፡ መክፈት ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው

**go to any extremity** የሚቻለውን ፡ ሁሉ ፡ አደረገ
Parents will go to any extremity to feed their children. ወላጆች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለመመገብ ፡ የሚቻላቸውን ፡ ሁሉ ፡ ያደርጋሉ

**in the extremity of**
*In the extremity of his misery, he sold his clothes. ችግር ፡ ቢጠናበት ፡ ልብሱን ፡ ሸጠ

**extricate** አላቀቀ
John extricated his brother from the barbed wire fence. ዮሐንስ ፡ ወንድሙን ፡ ከባለሾሁ ፡ የሽቦ ፡ አጥር ፡ አላቀቀ

**extricate oneself** ራሱን ፡ አወጣ
He extricated himself from the difficulty. ራሱን ፡ ከችግር ፡ አወጣ

**(be) extrinsic to** ከ - - - ውጭ ፡ ነው

His questions are extrinsic to the argument. ጥያቄዎቹ ፡ ከክርክሩ ፡ ውጭ ፡ ናቸው

**exuberance**

1. ብዛት. The exuberance of the area's plant life is remarkable. ባካባቢው ፡ ያለው ፡ የዕፀዋት ፡ ብዛት ፡ አስደናቂ ፡ ነው
2. የተነቃቃ ፡ መንፈስ. No amount of discipline could lessen his exuberance. የተነቃቃውን ፡ መንፈሱን ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ቁጥጥር ፡ አይቀንሰውም

**exuberant**

1. በጣም ፡ የጋለ. They gave the victorious team an exuberant welcome. ላሸናፊው ፡ ቡድን ፡ በጣም ፡ የጋለ ፡ አቀባበል ፡ አደረጉለት
2. በደስታ ፡ የተሞላ. The exuberant crowd cheered the Emperor. በደስታ ፡ የተሞላው ፡ ሕዝብ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ በጭብጨባ ፡ ተቀበላቸው

**exuberant vegetation** ልምላሜ

You will notice the exuberant vegetation of the jungle. የጫካውን ፡ ልምላሜ ፡ ታያለህ

**exude** ተንቆረቆረ

Sweat exuded from every pore. ከመላ ፡ ሰውነቱ ፡ ላብ ፡ ይንቆረቆር ፡ ነበር

**exult**

1. ፈነጠዘ. He exulted at the success of his experiment. ሙከራው ፡ ስለተቃናለት ፡ ፈነጠዘ
2. ፈነደቀ. The team exulted at winning the game. ቡድኑ ፡ ድልን ፡ በመቀዳጀቱ ፡ ፈነደቀ

**exultation** ፈንጠዚያ

There was exultation over the army's victory. ጦሩ ፡ ድል ፡ በመምታት ፡ ፈንጠዚያ ፡ ሆነ

**eye** (v.)

1. አየ. He eyed the food on the table with loathing. ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ምግብ ፡ በጥላቻ ፡ አየው
2. አትኩሮ ፡ ተመለከተ. The children eyed the stranger. ልጆቹ ፡ እንግዳውን ፡ ሰው ፡ አትኩረው ፡ ተመለከቱ

[See also 'longingly']

**eye** (n.)

1. ዓይን. He is blind in one eye. አንድ ፡ ዓይኑ ፡ ታውሯል
2. ቀዳዳ. The eye of this needle is too small. የዚህ ፡ መርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ በጣም ፡ ጠባብ ፡ ነው

**an eye for an eye** የገደለ ፡ ይሙት

An eye for an eye is required by the ancient law. የጥንት ፡ ሕግ ፡ የገደለ ፡ ይሙት ፡ ይላል

**cast one's eyes down** መልከት ፡ አደረገ

She cast her eyes down the page. ገጹን ፡ መልከት ፡ አደረገች

**have an eye for** መምረጥ ፡ ዐወቀ

She has an eye for antique furniture. የጥንት ፡ እቃዎችን ፡ መምረጥ ፡ ታውቃለች

**have an eye on** ዓይኑን ፡ ጣለ(በት)

I have had my eye on that for a long time. ያንን ፡ ነገር ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዓይኔን ፡ ጥዬበት ፡ ነበር

**in one's eyes** በሱ ፡ ዓይን

You are only a child in his eyes. በሱ ፡ ዓይን ፡ አንተ ፡ ገና ፡ ልጅ ፡ ነህ

**(be) in the public eye**

He's always in the public eye. ከሰው ፡ አፍ ፡ አይወጣም

**keep an eye on**

1. ጠበቀ. Keep an eye on the children while I'm out! ወደ ፡ ውጭ ፡ ስሄድ ፡ ልጆቹን ፡ ጠብቃቸው
2. በዓይነ ፡ ቁራኛ ፡ ተመለከተ. They kept an eye on the stranger who was acting suspiciously. አኳኋኑ ፡ አጠራጣሪ ፡ የሆነውን ፡ እንግዳ ፡ ሰው ፡ በዓይነ ፡ ቁራኛ ፡ ተመለከቱት

**keep one's eyes open** አየ

Keep your eyes open or we will miss the turn. እያየህ ፤ ያለበለዚያ ፡ መታጠፊያውን ፡ እንስታለን

**meet (one's) eye** አጋጠመ(ው)

A fearsome sight met the policemen's eyes. ፖሊሶቹን ፡ አሰቃቂ ፡ ትርእይት ፡ አጋጠማቸው

**see eye to eye** ተስማማ

We don't see eye to eye on the Vietnam problem. በቪየትናም ፡ ጉዳይ ፡ አንስማማም

**set eyes on** አየ

I hope I shall never set eyes on her again. ዳግመኛ ፡ እንደማላያት ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ

**with an eye to** በማለም

The Italians occupied Eritrea with an eye to the eventual conquest of Ethiopia. በመጨረሻ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመያዝ ፡ በማለም ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ኤርትራን ፡ ቅኝ ፡ አድርገው ፡ ነበር

[See also 'bat, blind, downcast, drop, open, run, shining, strike, wide']

**eyebrow** ሽፋሽፍት

His eyebrows are very black. ሽፋሽፍቱ ፡ በጣም ፡ ጥቁር ፡ ነው

**eyeglasses** መነጽር

He has worn eyeglasses since he was a young man. ከልጅነቱ ፡ ጀምሮ ፡ መነጽር ፡ ያደርጋል

**eyelash** ቅንድብ
She darkened her eyelashes. ቅንድቧን ፡ ኳለች

**eyelid** የዓይን ፡ ሽፋን ፤ የዓይን ፡ ቆብ
The doctor operated on the eyelid. ዶክተሩ ፡ የዓይኑን ፡ ሽፋን ፡ (ቆብ) ፡ ቀዶ ፡ ጠገነ

**eyesight**
1. ዓይን. His eyesight is very poor. ዓይኑ ፡ በጣም ፡ ደካማ ፡ ነው
2. የዓይን ፡ ብርሃን. His eyesight is getting dim. የዓይኑ ፡ ብርሃን ፡ እየደከመ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ነው

*The house is within eyesight. ቤቱ ፡ ዓይን ፡ ሊገመግመው ፡ በሚችል ፡ ርቀት ፡ ላይ ፡ ነው

**poor eyesight** የዓይን ፡ መታወክ.
His poor eyesight disqualified him from participating in the Olympic Games. የዓይኑ ፡ መታወክ ፡ በኦሊምፒክ ፡ ጨዋታ ፡ ከመካፈል ፡ አስቀረው

**eyewitness** የዓይን ፡ ምስክር
He was an eyewitness to the accident. ላደጋው ፡ የዓይን ፡ ምስክር ፡ ነበር

# F

**fable** የአፍ ፡ ታሪክ ፤ ተረት
There is a fable that a serpent once ruled in Eritrea. ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እባብ ፡ ኤርትራን ፡ ይገዛ ፡ እንደነበረ ፡ የሚነገር ፡ የአፍ ፡ ታሪክ ፡ አለ
He wrote a fable after the manner of Aesop. የኤዞፕን ፡ አጻጻፍ ፡ በመከተል ፡ አንድ ፡ ተረት ፡ ጻፈ

**fabric**
1. ጨርቅ. Wool makes a very warm fabric. የሱፍ ፡ ጨርቅ ፡ በጣም ፡ ይሞቃል
2. አቋም. The proposed reforms will affect the very fabric of society. የቀረበው ፡ መሻሻል ፡ የኅብረ ፡ ሰቡን ፡ መሠረታዊ ፡ አቋም ፡ ይነካል

**fabricate**
1. ሠራ. They fabricate airplane parts in California. በካሊፎርኒያ ፡ የአውሮፕላን ፡ መለዋወጫ ፡ እቃ ፡ ይሠራሉ
2. ፈጠረ. The child fabricated a story to explain his tardiness. ልጁ ፡ ለመዘግየቱ ፡ ምክንያት ፡ ፈጠረ

**fabulous**
1. እንደተረት ፤ እንደሕልም. The story of his finding the treasure is fabulous. የተደበቀውን ፡ ሀብት ፡ የማግኘቱ ፡ ወሬ ፡ እንደተረት ፡ (እንደሕልም) ፡ ነው
2. ይህ ፡ ነው ፡ የማይባል. He earned fabulous wealth in his business. ከንግዱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የማይባል ፡ ሀብት ፡ አገኘ

**facade** ፊት ፡ ለፊት
The facade of the building is made of white stone. የሕንጻው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በነጭ ፡ ድንጋይ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**face** (vt.)
1. ፊቱን ፡ አዞረ. Face the wall! ፊትህን ፡ ወደ ፡ ግድግዳው ፡ አዙር
2. አየ. Face me and tell the truth! ወደኔ ፡ እያየህ ፡ እውነተኛውን ፡ ንገረኝ
3. ገጠመ. They faced the enemy armed only with spears. ጦር ፡ ብቻ ፡ ይዘው ፡ ጠላትን ፡ ገጠሙ
4. ፊት ፡ ቆመ. The cat faced the dog with fur erect. ድመቷ ፡ ጸጉሯን ፡ አቁማ ፡ ውሻው ፡ ፊት ፡ ቆመች
5. ደረሰ(በት). The troops faced severe privation. ወታደሮቹ ፡ ከባድ ፡ ችግር ፡ ደረሰባቸው
6. ተቋቋመ. He faced the dilemma with courage. የሁለት ፡ ከፉ ፡ ምርጫውን ፡ በድፍረት ፡ ተቋቋመ
7. ፊት ፡ ለፊት ፡ ተገኘ. He lives in the house that faces the theater. በቲያትር ፡ ቤቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሚገኘው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል
8. ተመለከተ. Let's face the facts! እውነቱን ፡ ነገር ፡ እንመልከት

*They faced their house with red brick. የቤታቸውን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ጡብ ፡ አለበሱት

**face** (vi.)
1. ከ - - - ትይዩ ፡ ነው. Our room faces on the street. ክፍላችን ፡ ከመንገዱ ፡ ትይዩ ፡ ነው
2. በስተ - - - በኩል ፡ ነው ፤ በስተ - - - ነው. Our windows face south. መስኮታችን ፡ በስተ ደቡብ ፡ በኩል ፡ ነው
Their home faces west. የቤታቸው ፡ በራፍ ፡ በስተምዕራብ ፡ ነው

**be faced with** አጋጠመ(ው)
+He is faced with the necessity of giving up his job. ሥራውን ፡ እንዲለቅ ፡ የሚያስገድድ ፡ ሁኔታ ፡ አጋጥሞታል
*The building is faced with red brick. ሕንጻው ፡ ከፊት ፡ ለፊቱ ፡ በቀይ ፡ ጡብ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**face up to** ሊሸከም ፡ ቻለ
He couldn't face up to his responsibilities. ኀላፊነቱን ፡ ሊሸከም ፡ አልቻለም
[See also 'downwards, whirl']

**face** (n.)
1. ፊት. His face is sad. ፊቱ ፡ ላይ ፡ ሐዘን ፡ ይታያል
Tell him to his face that he's a liar. ውሸታም ፡ መሆኑን ፡ እፊቱ ፡ ንገረው
2. ገጽ. Many animals have disappeared from the face of the earth. ብዙ ፡ ዓይነት ፡ እንስሳዎች ፡ ከምድር ፡ ገጽ ፡ ጠፍተዋል

**face to face** ፊት ፡ ለፊት
He brought the enemies face to face. ጠበኞቹን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አገናኛቸው

**fall on (one's) face** ባፍ ፡ ጢሙ ፡ ተደፋ
He tripped and fell on his face. ተደናቅፎ ፡ ባፍ ፡ ጢሙ ፡ ተደፋ

**in the face of** ቢያጋጥመውም
She persevered in the face of many obstacles. ብዙ ፡ ችግር ፡ ቢያጋጥማትም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አላለችም

**on the face of it** ላይ ፡ ላዩን ፡ ሲያዩት
His evidence is false on the face of it. ላይ ፡ ላዩን ፡ ሲያዩት ፡ ማስረጃው ፡ ሐሰት ፡ ይመስላል

**keep a straight face**
*Try to keep a straight face when he talks to you. ሲያነጋግርህ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ስሜት ፡ አታሳየው

**lose face** ተዋረደ
He will lose face if he admits he was wrong and the child was right. ልጁ ፡ ልክ ፡ ሆኖ ፡ እሱ ፡ መሳሳቱን ፡ ካመነ ፡ ይዋረዳል

**make faces** አላገጠ
Children, stop making faces at strangers! ልጆች ፤ በእንግዶች ፡ ላይ ፡ አታላግጡ

**make (a) horrible face** አኰሳተረ
He drank the tapeworm medicine and made a horrible face. ኮሶውን ፡ ሲጠጣ ፡ ፊቱን ፡ አኰሳተረ

**show one's face** ታየ
He is ashamed to show his face at the club. በክበቡ ፡ ውስጥ ፡ ለመታየት ፡ ያፍራል
[See also 'bring, impassive, open, sad, save, scan, smooth, solemn, sour, straight, turn']

## facetious የፌዝ
A facetious remark about old men enraged the teacher. ስለ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የተሰጠው ፡ የፌዝ ፡ አስተያየት ፡ መምህሩን ፡ አናደደው

**be facetious** አሾፈ
Don't be facetious when you speak about God. ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስትናገር ፡ አታሹፍ

## facial የፊት
She uses facial cream every day. በየቀኑ ፡ የፊት ፡ ቅባት ፡ ትቀባለች
*He suffered facial wounds in the accident. ባደጋው ፡ ምክንያት ፡ ፊቱ ፡ ቈሰለ

**facial expression** ፊት
His facial expression shows disgust. ፊቱ ፡ አለመደሰቱን ፡ ያሳያል

## facile
1. ቀላል. Translation is a facile task for him. የትርጉም ፡ ሥራ ፡ ለሱ ፡ ቀላል ፡ ነው
2. ቀልጣፋ. A facile writer produces many books. ቀልጣፋ ፡ ደራሲ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ይደርሳል
A pianist must have facile fingers. ፒያኖ ፡ ተጫዋች ፡ ጣቱ ፡ ቀልጣፋ ፡ መሆን ፡ አለበት

## facilitate አቃለለ
Modern inventions have facilitated travel. ዘመናዊ ፡ ፍልሰፋዎች ፡ ጉዞን ፡ አቃለዋል
The customs official facilitated the visitors' entry. የጉምሩኩ ፡ ሹም ፡ ጐብኚዎቹ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የሚገቡበትን ፡ ዘዴ ፡ አቃለለላቸው

## facility (facilities)
1. ስጦታ. He has great facility in learning languages. እርሱ ፡ ትልቅ ፡ የቋንቋ ፡ መማር ፡ ስጦታ ፡ አለው
2. ቅልጥፍና. She dances with facility. በቅልጥፍና ፡ ትደንሳለች
3. ድርጅት. The facilities for study are very good here. ከዚህ ፡ የሚገኙት ፡ የመማሪያ ፡ ድርጅቶች ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ናቸው

## facing
*The facing of the house is red brick. ቤቱ ፡ ከፊት ፡ ለፊት ፡ ከጡብ ፡ የተሠራ ፡ ነው

## fact
1. ነገር. That's a well-known fact. ያ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነገር ፡ ነው
2. የደረሰ ፡ ነገር. The facts corroborate his account of the accident. የደረሰው ፡ ነገር ፡ እሱ ፡ ስላደጋው ፡ የተናገረውን ፡ ያረጋግጣል
3. እውነተኛ ፡ ነገር. That doesn't correspond to the facts. ያ ፡ ከእውነተኛው ፡ ነገር ፡ ጋር ፡ አይስማማም
4. እውነት. This story is based on facts. ይህ ፡ ታሪክ ፡ በእውነት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው
5. ፍሬ ፡ ነገር. The body of the book contains all the essential facts. የመጽሐፉ ፡ ዋና ፡ ክፍል ፡ ተፈላጊዎቹን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ በሙሉ ፡ አዝሏል
6. ማስረጃ ፤ መረጃ. Why don't you present the facts as they really are? ማስረጃዎቹን ፡ (መረጃዎቹን) ፡ እንዳሉ ፡ ለምን ፡ አታቀርባቸውም ?

**in fact** እንዲያውም
In fact, it was a wonder that anyone came at all. እንዲያውም ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ መምጣቱ ፡ የሚገርም ፡ ነው

**the fact of the matter is** እርግጡን ፡ ለመናገር
The fact of the matter is, I did not go. እርግጡን ፡ ለመናገር ፡ አልሄድኩም
[See also 'matter']

## faction ወገን
The party split into three factions. የፖለቲካው ፡ ፓርቲ ፡ በሦስት ፡ ወገን ፡ ተከፍሏል

**factitious** የለበጣ
We saw a factitious smile on his face. የለበጣ ፡ ሣቅ ፡ አየንበት

**factor**
1. ምክንያት. Lack of money is the main factor in the failure of his business. ለንግዱ ፡ መክሰር ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ የገንዘብ ፡ እጦት ፡ ነው
2. ነገር. Endurance is an important factor of success in sports. ጥንካሬ ፡ ለስፖርት ፡ መሳካት ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው

**factory** (factories) ፋብሪካ
There is a shoe factory on the edge of town. በከተማው ፡ ዳርቻ ፡ አንድ ፡ የጫማ ፡ ፋብሪካ ፡ አለ

**factual** እውነትን ፡ የያዘ
His reports are always factual. ሪፖርቶቹ ፡ ሁልጊዜ ፡ እውነትን ፡ የያዙ ፡ ናቸው

**faculty** (faculties)
1. ስጦታ. He has a faculty for learning languages. ቋንቋ ፡ የመማር ፡ ስጦታ ፡ አለው
2. አካል. The faculty of sight is God's most precious gift to us. የማየት ፡ አካል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጠን ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የላቀ ፡ ጸጋ ፡ ነው
3. አእምሮ. Though he is very old, he is in full possession of his faculties. በጣም ፡ ቢያረጅም ፡ አእምሮው ፡ የተሟላ ፡ ነው
4. ፋኩልቲ. There are four faculties at this university. በዚህ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ውስጥ ፡ አራት ፡ ፋኩልቲዎች ፡ አሉ

**fade** (vt.) አደበዘዘ
The bright sunlight faded the curtains. የፀሐዩ ፡ ኀይለኛ ፡ ሙቀት ፡ መጋረጃውን ፡ አደበዘዘው

**fade** (vi.)
1. ጠወለገ. These flowers faded very quickly. እነዚህ ፡ አበቦች ፡ ቶሎ ፡ ጠወለጉ
2. እየሞተ ፡ ሄደ. The music faded in the distance. እየራቁ ፡ ሲሄዱ ፡ የሙዚቃው ፡ ድምፅ ፡ እየሞተ ፡ ሄደ
3. ቀለም ፡ ለቀቀ. My socks faded in the wash. የእግር ፡ ሹራቤ ፡ ሲታጠብ ፡ ቀለሙ ፡ ለቀቀ

**fail** (vt.)
1. ወደቀ. Two students failed the exam. ሁለት ፡ ተማሪዎች ፡ ፈተናውን ፡ ወደቁ
2. ጉድ ፡ አደረገ. When we needed him, he failed us. በምንፈልገው ፡ ጊዜ ፡ ጉድ ፡ አደረገን
3. ከ --- አቃተ(ው). They failed to reach a conclusion on building a new bridge. አንድ ፡ አዲስ ፡ ድልድይ ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ ጉዳይ ፡ ከውሳኔ ፡ መድረስ ፡ አቃታቸው
4. ተወ. When his friend is away, he never fails to backbite him. የቅርብ ፡ ወዳጁ ፡ በሌለበት ፡ እሱን ፡ ማማቱን ፡ ፈጽሞ ፡ አይተውም
*I won't fail you. በኔ ፡ ይሁንብህ

**fail** (vi.)
1. ወደቀ. Five students failed in arithmetic. አምስት ፡ ተማሪዎች ፡ በቁጥር ፡ ወደቁ
2. ውድቅ ፡ ሆነ. His experiment failed. ሙከራው ፡ ውድቅ ፡ ሆነ
3. ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ ቀረ ፤ ከንቱ ፡ ሆነ. All our efforts failed. ጥረታችን ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ ቀረ
Mark well my words; his plans will fail. ምን ፡ አለ ፡ በለኝ ፤ የሱ ፡ እቅዶች ፡ ከንቱ ፡ ይሆናሉ
4. ከሸፈ. The intrigue to get him out of his job failed. ከሥራው ፡ ለማፈናቀል ፡ የተደረገው ፡ ተንኰል ፡ ከሸፈ
5. ሳይዋጣ ፡ ቀረ. The plan was unsound, so it failed. እቅዱ ፡ የተሟላ ፡ ስላልነበረ ፡ ሳይዋጣ ፡ ቀረ
6. አልተሳካለትም. I tried to pacify her with promises, but failed. ቃል ፡ ለመግባት ፡ ላባብላት ፡ ሞክሬ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ አልተሳካልኝም
7. ሳይሳካለት ፡ ቀረ. They failed in their attempt to climb the mountain. ተራራውን ፡ ለመውጣት ፡ ያደረጉት ፡ ሙከራ ፡ ሳይሳካላቸው ፡ ቀረ
8. ጠፋ. The crops failed because of drought. ሰብሉ ፡ በድርቀት ፡ ምክንያት ፡ ጠፋ
9. ተቀነሰ. His health failed after the operation. ከቀዶ ፡ ጥገና ፡ በኋላ ፡ ጤንነቱ ፡ ተቀነሰ
10. ተዳከመ. He is failing fast and may not survive the night. በጣም ፡ ስለተዳከመ ፡ ሌሊቱን ፡ አያድርም ፡ ይሆናል

**fail to**
1. ስ + negative imperfect + ቀረ. He failed to follow our advice. ምክራችንን ፡ ሳይቀበል ፡ ቀረ
2. (negative verb). The insult failed to ruffle his composure. ስድቡ ፡ እርጋታውን ፡ አላናወጸውም
*Don't fail to go there! እዚያ ፡ ሳትሄድ ፡ እንዳትቀር

**fail to come off** ሳይሳካ ፡ ቀረ
The conference failed to come off. ስብሰባው ፡ ሳይሳካ ፡ ቀረ

**fail to go off (gun)** ከሸፈ
He pulled the trigger, but the gun failed to go off. ምላጩን ፡ ቢስበው ፡ ጥይቱ ፡ ከሸፈ

**(his) courage failed** ሐሞቱ ፡ ፈሰሰ
His courage failed when he saw the policeman. ፖሊሱን ፡ ሲያይ ፡ ሐሞቱ ፡ ፈሰሰ

**words failed him**
1. መናገር ፡ አቃተው. He was so shocked at what he saw that words failed him. ባየው ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ስለደነገጠ ፡ መናገር ፡ አቃተው
2. ቃል ፡ አጠረው. Words fail me when I try to express my feelings toward him. ስለርሱ ፡ ያለኝን ፡ ስሜት ፡ ለመግለጽ ፡ ስሞክር ፡ ቃል ፡ ያጥረኛል
[See also 'doom']

**fail** (n.), **without ~**
*Be there at 6 o'clock without fail! ባሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ እንዳትቀር

**failing** (n.) ጉድለት
We all have our little failings. ሁላችንም ፡ የየራሳችን ፡ ጉድለት ፡ አለብን

**failing** (prep.)
*Failing good weather, the party will be held indoors. ያየሩ ፡ ጠባይ ፡ ከተበላሸ ፡ ፓርቲው ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ይደረጋል
*Failing payment, we shall sue. ካልተከፈለ ፡ እንከሳለን

**failing this** ይህ ፡ ካልተሳካ(ለት)
Failing this, we'll have to draw on our savings. ይህ ፡ ካልተሳካልን ፡ ያስቀመጥነውን ፡ ገንዘብ ፡ ማውጣት ፡ አለብን

**(be) failing**
1. ደከመ. His eyesight is failing. ዓይኑ ፡ እየደከመ ፡ ሄደ
2. ተቀነሰ. His health has been failing for the last two years. ባለፉት ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ጤንነቱ ፡ እየተቀነሰ ፡ ሄዷል
*The sick man's heart was failing. የበሽተኛው ፡ ልብ ፡ መምታቱን ፡ በየጊዜው ፡ ያቋርጥ ፡ ነበር

**failure**
1. ያለመሳካት. Success came after many failures. ግብ ፡ የተደረሰው ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያለመሳካት ፡ በኋላ ፡ ነው
2. ሰ + negative imperfect + መቅረት. Her failure to answer my letters worried me. ለደብዳቤዬ ፡ መልስ ፡ ሳትልክ ፡ መቅረቷ ፡ አሳሰበኝ
3. መጥፋት. The failure of his eyesight prevented him from reading. የዓይኑ ፡ መጥፋት ፡ ለማንበብ ፡ እንዳይችል ፡ አደረገው
4. መታወክ. The failure of his health made retirement necessary. የጤንነቱ ፡ መታወክ ፡ ጡረታ ፡ እንዲገባ ፡ አደረገው
5. መውደቅ. His failure in the history examination discouraged him. በታሪክ ፡ ፈተና ፡ መውደቁ ፡ ተስፋ ፡ አስቈረጠው
6. ፍሬ ፡ ቢስ I ውድቅ. It appears to me that the program was a failure. እንደኔ ፡ ፕሮግራሙ ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ (ውድቅ) ፡ የሆነ ፡ ይመስለኛል
7. መበላሸት. A mechanical failure caused the plane to crash. አውሮፕላኑ ፡ ወድቆ ፡ ሊሰባበር ፡ የቻለው ፡ ከሞተሩ ፡ መበላሸት ፡ የተነሣ ፡ ነው
8. ጉድለት. Because of a power failure, the station went off the air. በኤሌክትሪክ ፡ ጉድለት ፡ የተነሣ ፡ ጣቢያው ፡ ተቋረጠ

**be a failure** አልተሳካም I አልተሳካለትም
The campaign was a failure. ዘመቻው ፡ አልተሳካም ፡ ነበር
As a businessman, he was a complete failure. በንግድ ፡ በኩል ፡ በፍጹም ፡ አልተሳካለትም
*I'm a failure as a teacher. መምህርነት ፡ አይሆንልኝም

**end in failure** ከንቱ ፡ ሆነ
His effort ended in failure. ድካሙ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ሆነ
[See also 'power']

**faint** (v.) ነፍሱን ፡ ሳተ
She fainted from fright. ከድንጋጤ ፡ የተነሣ ፡ ነፍሷን ፡ ሳተች

**faint** (n.), **fall in a ~** ሕይወቱን ፡ ስቶ ፡ ወደቀ
On the receipt of the news, she fell in a faint. ወሬውን ፡ ስትሰማ ፡ ሕይወቷን ፡ ስታ ፡ ወደቀች

**in a dead faint**
She lay in a dead faint. ሕይወቷን ፡ ፍጹም ፡ ስታ ፡ ተኛች

**faint** (adj.)
1. የመነመነ. There is only a faint hope left. ያለው ፡ ተስፋ ፡ የመነመነ ፡ ነው
2. ቅስስ ፡ ያለ I መሳይ. I heard a faint noise in the dark. ጨለማው ፡ ውስጥ ፡ ቅስስ ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ (ድምፅ ፡ መሳይ) ፡ ሰማሁ
3. (= adv.) በጥቂት. I have a faint idea of what he wants. የሚፈልገውን ፡ ነገር ፡ በጥቂት ፡ አውቃለሁ
4. (= adv.) ላመል. There was a faint smell of incense in the church. በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ የዕጣን ፡ ሽታ ፡ ላመል ፡ ነበር
[See also 'spell']

**(the) faintest**
*I haven't the faintest idea. ምንም ፡ የማውቀው ፡ ነገር ፡ የለም

**faint-hearted** ፈሪ
The faint-hearted soldier was criticized by his superior. ፈሪው ፡ ወታደር ፡ ባለቃው ፡ ተገሠጸ

**fair** (n.) ትርኢይት
Let's go to the agricultural fair! ወደ ፡ እርሻ ው ፡ ትርኢይት ፡ እንሂድ

**fair** (adj.)
1. መጠነኛ. His knowledge of Amharic is fair. ያማርኛ ፡ ችሎታው ፡ መጠነኛ ፡ ነው
2. ትክክለኛ. A fair judge is greatly appreciated. ትክክለኛ ፡ ዳኛ ፡ በጣም ፡ ይመሰገናል
3. ደኅና. That's a fair price. ደኅና ፡ ዋጋ ፡ ነው
The weather will be fair today. አየሩ ፡ ዛሬ ፡ ደኅና ፡ ይሆናል
There is a fair crop of wheat this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ ደኅና ፡ የስንዴ ፡ ሰብል ፡ አለ
4. አግባብ. That wouldn't be fair. ይህ ፡ አግባ ብ ፡ አይደለም
5. ተገቢ. Make sure each boy gets a fair share of the food! እያንዳንዱ ፡ ልጅ ፡ ከምግቡ ፡ ተገ ቢ ፡ ድርሻውን ፡ ማግኘቱን ፡ አረጋግጥ
6. አግባብ ፡ ያለው. Is this a fair exchange? አግ ባብ ፡ ያለው ፡ ልውውጥ ፡ ነው?
7. ነጣ ፡ ያለ. The American girl has blue eyes and fair hair. አሜሪካዊቷ ፡ ልጃገረድ ፡ ሰማያ ዊ ፡ ዓይንና ፡ ነጣ ፡ ያለ ፡ ጠጉር ፡ አላት
[See also 'bid, play']

**fairly**
1. በትክክል. The money should be dealt out fairly to the needy. ገንዘቡ ፡ ለችግረኞቹ ፡ በት ክክል ፡ መታደል ፡ አለበት
2. በመጠኑ. He is fairly good in Amharic. ባማርኛ ፡ በመጠኑ ፡ ደኅና ፡ ነው
3. በተገቢ ፡ አኳኋን. He allocated the money fairly. ገንዘቡን ፡ በተገቢ ፡ አኳኋን ፡ ደለደለ

**deal fairly**
*He dealt fairly with the child. ለልጁ ፡ የሚገ ባ ፡ አያያዝ ፡ አደረገለት

**fair-minded** የማያዳላ ፡ ሰው
An arbitrator must be fair-minded. አስታራቂ ፡ የማያዳላ ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ አለበት

**fair play**
*We must uphold the principle of fair play. ጥሩ ፡ ጨዋታ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መሠረታዊ ፡ ደንብ ፡ መጠበቅ ፡ አለብን

**fairy** [በተረቶች ፡ ውስጥ ፡ ረቂቅ ፡ አስማተኛ ፡ የሆኑ ፡ ፍጡሮች]

**fairy tale** ተረት
That sounds like a fairy tale. ተረት ፡ ይመስ ላል

**faith**
1. ሃይማኖት. I don't know what his faith is. ሃይማኖቱ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ አላውቅም
He became a convert to the Christian faith. የክርስትናን ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀበለ
2. እምነት. I lost faith in him. በሱ ፡ ላይ ፡ የነበ ረኝ ፡ እምነት ፡ ጠፋ
Failure to appear would be breaking faith. በቀጠሮ ፡ አለመገኘት ፡ እምነትን ፡ ማጉደል ፡ ይ ሆናል
3. መንፈስ. He acted in bad faith. በተንኮል ፡ መንፈስ ፡ ሠራ
We acted in good faith. በቅን ፡ መንፈስ ፡ ሠ ራን

**have faith** አመነ
She has blind faith in his talent. የሱን ፡ ችሎታ ፡ በጭፍን ፡ ታምናለች
[See also 'profession']

**faithful** (n.) ምእመን (pl. ምእመናን)
The faithful meet outside the church every Sunday morning. ምእመናን ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ ጧት ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውጭ ፡ ይሰበሰባሉ

**faithful** (adj.)
1. ታማኝ. He is faithful to his wife. ለሚስቱ ፡ ታማኝ ፡ ነው
A faithful friend is more valuable than money. ታማኝ ፡ ጓደኛ ፡ ከገንዘብ ፡ ይበልጣል
2. ታማኝነት ፡ የመላበት. He was justly rewarded for his faithful service by being given a pension. ጡረታ ፡ በመገባት ፡ ታማኝነት ፡ ለመላበት ፡ አገል ግሎቱ ፡ በሚገባ ፡ ወረታ ፡ ተከፈለው
3. ትክክለኛ. The newspapers gave a faithful account of the accident. ጋዜጦቹ ፡ ስላደጋው ፡ ትክክለኛ ፡ ዜና ፡ አቀረቡ
This is a faithful copy of the original. ይህ ፡ የዋ ናው ፡ ትክክለኛ ፡ ግልባጭ ፡ ነው
4. (= adv.) ከልብ. They are faithful believers all. ሁሉም ፡ ከልብ ፡ አማኞች ፡ ናቸው
She's very faithful in her work. ሥራውን ፡ ከል ቧ ፡ ትሠራለች

**faithless** እምነተ ፡ ቢስ
The traitor was faithless to his country. ከሓዲው ፡ ለሀገሩ ፡ እምነተ ፡ ቢስ ፡ ነበር

**fake** (v.) መሰለ
Beggars often fake blindness. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ለማኞች ፡ ዕውር ፡ መስለው ፡ ይለምናሉ

*He faked a report showing non-existent profits. የሌለ፡ ትርፍ ፡ የሚያመለክት ፡ የውሸት ፡ ሪፖርት ፡ አቀረበ

**fake** (n.)
1. አባይ. He is not a real doctor; he is a fake. እሱ ፡ የእውነት ፡ ሳይሆን ፡ አባይ ፡ ሐኪም ፡ ነው
2. በማስመሰል ፡ የተሠራ. The dealer sold a fake as a genuine painting. ነጋዴው ፡ በማስመሰል ፡ የተሠራውን ፡ ሥዕል ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሸጠ

**fake** (adj.) የሐሰት
These documents are fake. እነዚህ ፡ ሰነዶች ፡ የሐሰት ፡ ናቸው

**falcon** ጭልፊት

**fall** (fell, fallen)
1. ወደቀ. Many trees fell during the storm. በኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ዛፎች ፡ ወደቁ
He fell from the ladder. ከመሰላሉ ፡ ላይ ፡ ወደቀ
The conservative government has fallen. ለውጥ ፡ የማይፈልገው ፡ መንግሥት ፡ ወደቀ
The city has fallen into the power of its enemies. ከተማው ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ወደቀ
The responsibility for the office fell on me. የሥራው ፡ ኀላፊነት ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ወደቀ
Their choice fell upon him. ምርጫቸው ፡ እሱ ፡ ላይ ፡ ወደቀ
2. ሞተ. Many soldiers fell in battle. ብዙ ፡ ወታደሮች ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞቱ
3. ረገፈ. Because of the drought, the leaves are falling from the tree. በድርቁ ፡ ምክንያት ፡ ቅጠሎቹ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ይረግፋሉ
The blossoms are falling off the tree. አበቦቹ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ይረግፋሉ
4. ጣለ. The rain was falling steadily. ዝናቡ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ይጥል ፡ ነበር
5. በረደ. The temperature fell rapidly. ሙቀቱ ፡ በፍጥነት ፡ በረደ
6. ዝቅ ፡ አለ. Prices are falling. የገበያ ፡ ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ሄደ
7. ደረሰ. His beard fell to his chest. ጢሙ ፡ እደረቱ ፡ ደርሷል
The estate fell to the eldest son. ርስቱ ፡ ለበኵር ፡ ልጁ ፡ ደረሰ
8. ከሰመ. His face fell at the bad news. መጥፎውን ፡ ወሬ ፡ ሲሰማ ፡ ፊቱ ፡ ከሰመ
9. ተለወጠ. Her voice fell to a whisper. ድምጿ ፡ ወደ ፡ ሹክሹክታ ፡ ተለወጠ
10. ተከፈለ. The subject falls into four divisions. ጉዳዩ ፡ በአራት ፡ ይከፈላል
His writings fall into two types : novels and plays. ጽሑፎቹ ፡ በሁለት ፡ ይከፈላሉ ፤ ልብ፡ ወለድ ፡ ታሪኮችና ፡ ቲያትሮች
11. ዋለ. Christmas falls on a Monday this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ ገና ፡ ሰኞ ፡ ለት ፡ ይውላል
*When night fell, it grew dark. ጀንበር ፡ ስትጠልቅ ፡ እየጨለመ ፡ ሄደ
*The President fell from the people's favor. ፕሬዚዳንቱ ፡ የሕዝቡን ፡ ፍቅር ፡ አጣ

**fall apart**
1. ፈረሰ. This monument has long since fallen apart. ይህ ፡ ሐውልት ፡ ከፈረሰ ፡ ዘመን ፡ የለውም
2. ወላለቀ. The stool is already falling apart. በርጩማው ፡ ወላልቋል
3. ተበጣጠሰ. The shoes he bought were so shoddy that they fell apart when he got them wet. ጫማው ፡ መናኛ ፡ ስለነበረ ፡ እርጥበት ፡ ሲነካው ፡ ተበጣጠሰ

**fall back** አፈገፈገ
Our attack was so strong the enemy fell back. ያደረግነው ፡ ማጥቃት ፡ በጣም ፡ ኀይለኛ ፡ ስለነበረ ፡ ጠላት ፡ አፈገፈገ

**fall back on** በ - - - ተጠቀመ
We can always fall back on our savings. ምንግዜም ፡ በተቀማጩ ፡ ገንዘባችን ፡ ልንጠቀም ፡ እንችላለን

**fall behind** ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀረ
He has fallen behind in his work. በሥራው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርቷል
*We fell behind in the rent. ውዝፍ ፡ ኪራይ ፡ አለብን

**fall (down)**
1. ወደቀ. He fell down the stairs. ከደረጃው ፡ ላይ ፡ ወደቀ
2. ወረደ. The cataract falling down the mountainside is quite attractive. ከተራራው ፡ ላይ ፡ የሚወርደው ፡ ፏፏቴ ፡ በጣም ፡ ያስደስታል
*I hope he won't fall down on the job. ሥራውን ፡ በደንብ ፡ እንደሚሠራ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ

**fall for** በፍቅር ፡ ተነደፈ
He fell for her as soon as he saw her. እንዳያት ፡ በፍቅር ፡ ተነደፈ

**fall in** ተደረመሰ
The roof fell in. ጣራው ፡ ተደረመሰ

**fall in (with)** ተስማማ
They fell in with our plans. በሐሳባችን ፡ ተስማሙ

**fall into**
Do not fall into bad habits! መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ አትልመድ

**fall off**
1. ወደቀ. The lid fell off. መክደኛው ፡ ወደቀ
2. ወልቆ ፡ ወደቀ. The ring fell off his finger. ቀለበቱ ፡ ከጣቱ ፡ ወልቆ ፡ ወደቀ
3. ቀነሰ. Receipts have been falling off lately. ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ገቢው ፡ እየቀነሰ ፡ ሄዷል

**fall on** አጠቃ
The enemy fell on them suddenly from the rear. ጠላት ፡ በድንገት ፡ ከኋላ ፡ አጠቃቸው

**fall on one** የሱ ፡ ኀላፊነት ፡ ነበር
It has fallen on me to support the family. ቤተሰቡን ፡ መደገፍ ፡ የኔ ፡ ኀላፊነት ፡ ነበር
*Our choice fell on him. ምርጫችን ፡ እሱ ፡ ሆነ

**fall out**
1. ረገፈ. His teeth fell out. ጥርሱ ፡ ረገፈ
2. ተጣላ ፤ ተጨቃጨቀ. The two men fell out. ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ ተጣሉ
They fell out over the placement of the fence. ስለ ፡ አጥሩ ፡ ድንበር ፡ ተጨቃጨቁ
3. ተነቅሎ ፡ አለቀ. All his hair fell out. ጠጉሩ ፡ ተነቅሎ ፡ አለቀ

**fall through**
1. አልተሳካም. The plans for the picnic fell through. የሽርሽሩ ፡ ፕላን ፡ አልተሳካም
2. ፈረሰ. The deal fell through, so we didn't sell the property after all. የሽያጩ ፡ ውል ፡ ስለፈረሰ ፡ ንብረቱን ፡ ገና ፡ አልሸጥነውም

**fall to** በ - - - እጅ ፡ ወደቀ
The entire province fell to the enemy at one blow. መላው ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ወደቀ

**fall under** በ - - - ሥር ፡ ነው
His case falls under my jurisdiction. የሱ ፡ ጉዳይ ፡ በኔ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ነው

**fall upon** በድንገት ፡ አጠቃ
The enemy fell upon the sleeping settlement. ተኝተው ፡ የነበሩትን ፡ መንደርተኞች ፡ ጠላት ፡ በድንገት ፡ አጠቃ
*Darkness fell upon the town during the eclipse. በጽላሎቱ ፡ ጊዜ ፡ ከተማይቱ ፡ በጨለማ ፡ ተዋጠች

**fall upon the idea** ሐሳቡ ፡ መጣ(ለት)
I fell upon the idea while looking through a magazine. መጽሔት ፡ ሳገላብጥ ፡ ሐሳቡ ፡ መጣልኝ

**fall upside down** ተደፋ
The box fell upside down. ሣጥኑ ፡ ተደፋ
[See also 'asleep, dead, disgrace, disuse, due, face, flat, knee, line, love, piece, prey, prostrate, short, star']

**fall** (n.)
1. አወዳደቅ. His fall was dangerous, but nothing was broken. አወዳደቁ ፡ አደገኛ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ አልተሰበረም
2. መውደቅ. The decadence of morals was one of the causes of the fall of Rome. የሮም ፡ መውደቅ ፡ ምክንያት ፡ ከሆኑት ፡ አንዱ ፡ የሞራል ፡ ውድቀት ፡ ነበር
3. በልግ. Fall is one of the four seasons of the year. በልግ ፡ ካራቱ ፡ ያመት ፡ ክፍሎች ፡ አንዱ ፡ ነው
*I'll be back next fall. መስከረም ፡ ሲጠባ ፡ እመለሳለሁ
*He hasn't recovered from his fall yet. ወድቆ ፡ እንደታመመ ፡ አልተሻለውም
*There has been a fall in the price of grain. የጥራጥሬ ፡ ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ ብሏል

**falls** ፏፏቴ
Have you seen Niagara Falls? የናያገራን ፡ ፏፏቴ ፡ አይተሃል ?

**fallacious** የተሳሳተ
It is fallacious reasoning to base a rule on only two instances. በሁለት ፡ ምሳሌዎች ፡ ብቻ ፡ መሥርቶ ፡ አንድን ፡ ነገር ፡ ማመን ፡ የተሳሳተ ፡ አስተሳሰብ ፡ ነው

**fallacy** (fallacies) የተሳሳተ ፡ ሐሳብ
This is a statement based on fallacy. ይህ ፡ ንግግር ፡ በተሳሳተ ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው

**(be) fallible**
All men are fallible. ሰው ፡ ሆኖ ፡ የማይሳሳት ፡ የለም

**falling star** ተወርዋሪ ፡ ኮከብ
There are many falling stars at this time of the year. በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ተወርዋሪ ፡ ከዋክብት ፡ አሉ

**fallow land** እዳሪ ፤ ያደረ ፡ መሬት
The farmer plowed the fallow land. ገበሬው ፡ እዳሪውን ፡ አረሰው
The fallow land is overgrown with grass. ያደረው ፡ መሬት ፡ በሣር ፡ ተውጧል

**false**
1. የውሸት. It was a false alarm. የማስጠንቀቂያው ፡ ድምፅ ፡ የውሸት ፡ ነበር
2. የተሳሳተ. He had a false idea of her character. ስለሷ ፡ ጠባይ ፡ የተሳሳተ ፡ አስተያየት ፡ ነበረው

3. (= noun) ሐሰት. Is this true or false? ይህ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ሐሰት ?
4. ትክክል ፡ ያልሆነ. He gave me a false picture of the situation in the country. ስለ ፡ አገሪቱ ፡ ሁኔታ ፡ ትክክል ፡ ያልሆነ ፡ መግለጫ ፡ ሰጠኝ
5. ሐሰተኛ. A false friend will tell your secrets to your enemies. ሐሰተኛ ፡ ጓደኛ ፡ ለጠላቶችህ ፡ ምስጢር ፡ ያወጣብሃል
6. ከንቱ. He deludes himself with false hopes. በከንቱ ፡ ተስፋ ፡ ራሱን ፡ ያታልላል
7. አጉል. False pride kept the poor man from accepting money from his rich brother. ድኻው ፡ ሰው ፡ ከሀብታም ፡ ወንድሙ ፡ ገንዘብ ፡ እንዳይቀበል ፡ አጉል ፡ ኩራት ፡ እስር ፡ ያዘው
8. ሰው ፡ ሠራሽ. Many people have false teeth. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጥርስ ፡ አላቸው
*He was false to his word. ቃል ፡ አባይ ፡ ነበር
[See also 'alarm']

**falsehood** ሐሰት
It is hard to disentangle truth from falsehood. እውነትን ፡ ከሐሰት ፡ መለየት ፡ ያዳግታል

**falsify** (falsified)
1. አማታ. The merchant falsified accounts, so he wouldn't have to pay taxes. ግብር ፡ እንዳይከፍል ፡ ሲል ፡ ነጋዴው ፡ የሒሳብ ፡ ሰነዱን ፡ አማታ
2. ዋሸ. He falsified the history of his family to conceal his humble origins. ከድኻ ፡ መወለዱን ፡ ለመደበቅ ፡ የቤተሰቡን ፡ ታሪክ ፡ ዋሸ

**falter**
1. ተደናቀፈ. The army advance faltered under enemy fire. የጦሩ ፡ ወደፊት ፡ መግፋት ፡ በጠላት ፡ ተኵስ ፡ ተደናቀፈ
He faltered for a moment, but continued speaking. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተደናቀፈና ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ
2. ተንተባተበ. He faltered as he tried to find the right word. ትክክለኛውን ፡ ቃል ፡ ለማግኘት ፡ ሲሞክር ፡ ተንተባተበ
3. አቅማማ. He faltered at the door wondering if he should go in. በሩ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ልግባ ፡ አልግባ ፡ በማለት ፡ አቅማማ

**fame** ዝና
His fame as a poet didn't come until after his death. የገጣሚነቱ ፡ ዝና ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ አልታወቀም ፡ ነበር

**famed** የታወቀ
This regiment is famed for its courage. ይህ ፡ የሻለቃ ፡ ጦር ፡ በጀግንነቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**familiar**
1. የተለመደ. Men in uniform are a familiar sight these days. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የደምብ ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ ሰዎች ፡ ማየት ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው
2. የሚያውቁት. It's good to see a familiar face. የሚያውቁትን ፡ ሰው ፡ ማግኘት ፡ ጥሩ ፡ ነው
3. የሚያውቀው. I recognized the familiar voice on the telephone. በስልኩ ፡ ውስጥ ፡ የማውቀውን ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ
4. የቅርብ. Familiar friends know each other very well. የቅርብ ፡ ጓደኞች ፡ በጣም ፡ ይተዋወቃሉ
*French was as familiar to him as English. ፈረንሳይኛ ፡ የእንግሊዝኛን ፡ ያህል ፡ ይችል ፡ ነበር

**be familiar**
Her face is familiar, but her name escapes me. መልኳን ፡ አስታውሳለሁ ፡ ግን ፡ ስሟ ፡ ትዝ ፡ አይለኝም

**be familiar with**
1. በደንብ ፡ ዐወቀ ፤ ዐወቀ. I am not familiar with that. ነገሩን ፡ በደንብ ፡ አላውቀውም
I am only familiar with electronics. እኔ ፡ የማውቀው ፡ ስለ ፡ ኤሌክትሮኒክስ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ተላመደ. He was not familiar with local conditions. ያገሩን ፡ ሁኔታ ፡ አልተላመደውም

**be on familiar terms**
Are you on familiar terms with your boss? ካለቃህ ፡ ጋር ፡ ቡና ፡ ትጣጣላችሁ ?

**get too familiar** ተዳፈረ
The nobility does not like their servants to get too familiar. መኳንንቱ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ እንዲዳፈሯቸው ፡ አይፈልጉም

**familiarity** ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ማወቅ
His familiarity with Ethiopia surprised me. ኢትዮጵያን ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ማወቁ ፡ አስደነቀኝ
*You shouldn't treat her with such familiarity. ይህን ፡ ያህል ፡ አታቅርባት

**familiarize** አስተዋወቀ
The radio has familiarized us with many foreign countries. ሬዲዮ ፡ ከብዙ ፡ የውጭ ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ አስተዋውቆናል

**familiarize oneself with** ተለማመደ
He familiarized himself with Amharic before going to Ethiopia. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ አማርኛ ፡ ተለማመደ

**family** (families)
1. ቤተሰብ. He has a large family. ብዙ ፡ ቤተሰብ ፡ አለው

He's a man of humble family. ከድኻ ፡ ቤተሰ
ብ ፡ የተወለደ ፡ ሰው ፡ ነው
2. ልጆች. She brought up a family. ልጆቿ
ን ፡ አሳደገች
3. ዘመድ. Has he any family in Addis Ababa?
አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ዘመድ ፡ አለው ?

**of good family**
1. ከመልካም ፡ ቤተሰብ ፡ የመጣ. Parents like
their daughters to marry men of good families.
ወላጆች ፡ ሴት ፡ ልጆቻቸው ፡ ከመልካም ፡ ቤተሰ
ብ ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡ እንዲያገቡ ፡ ይፈልጋሉ
2. ከጨዋ ፡ ቤተሰብ. He is of good family. ከጨ
ዋ ፡ ቤተሰብ ፡ ነው

**man of humble family** ከድኻ ፡ ቤተሰብ ፡ የመጣ
Though he was a man of humble family,
he became prime minister. ምንም ፡ እንኳ ፡ ከድ
ኻ ፡ ቤተሰብ ፡ የመጣ ፡ ቢሆን ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒ
ስትር ፡ ሆነ
[See also 'relationship, tree']

## famine
1. ረኃብ. Since there was a drought last year,
we were beset by famine. ባለፈው ፡ ዓመት ፡
ድርቅ ፡ ስለነበረ ፡ ረኃብ ፡ አጥቅቶናል
2. የረኃብ ፡ ዘመን. Many people died during the
famine. በረኃቡ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አለቁ

## famished የተራበ
The famished dogs were fighting over a scrap
of meat. የተራቡት ፡ ውሾች ፡ በቁራጭ ፡ ሥጋ ፡ ላ
ይ ፡ ይናከሱ ፡ ነበር

## famous
1. ዝነኛ. His book made him famous. የጻፈው ፡
መጽሐፍ ፡ ዝነኛ ፡ አደረገው
2. የታወቀ. The town is famous for its hot
springs. ከተማዋ ፡ በፍል ፡ ውኃዋ ፡ የታወቀ
ች ፡ ናት

## fan (fanned), v.
1. አራገበ. He fanned the fire with a piece of
cardboard. እሳቱን ፡ ባንድ ፡ የከርታስ ፡ ቁራ
ጭ ፡ አራገበው
2. አባባሰ. His attempts to conciliate the two
fanned the flames of the argument. ሁለቱን ፡
ለማስታረቅ ፡ ያደረገው ፡ ሙከራ ፡ ጭቅጭቁን ፡
አባባሰው

**fan oneself** ፊቱን ፡ አራገበ
She fanned herself with a sheet of paper.
ፊቷን ፡ በወረቀት ፡ አራገበች

**fan out** ተበታተነ
The hunters fanned out to cover the whole field.
አዳኞቹ ፡ ሜዳውን ፡ በሙሉ ፡ ለማዳረስ ፡ ተበታ
ተኑ
[See also 'enthusiasm']

## fan (n.)
1. ማራገቢያ. The fan was made from a palm
leaf. ማራገቢያው ፡ ከዘንባባ ፡ የተሠራ ፡ ነው
2. ነፋስ ፡ መስጫ. Turn on the fan! ነፋስ ፡
መስጫውን ፡ አስነሣው
3. ቀበኛ. My brother is a movie fan. ወንድሜ ፡
የሲኒማ ፡ ቀበኛ ፡ ነው

## fanatic (n.)
*The religious fanatics attacked the police post.
ዓይናቸውን ፡ ጨፍነው ፡ የሚያመልኩት ፡ የፖሊ
ሱን ፡ ጣቢያ ፡ አጠቁ

**fanatic** (adj.)
1. (= adv.) ዓይኑን ፡ ጨፍኖ. They have a
fanatic belief in witchcraft. ዓይናቸውን ፡ ጨፍ
ነው ፡ በጥንቈላ ፡ ያምናሉ
2. (= adv.) ከልክ ፡ ያለፈ. She is fanatic about
cleanliness. ለንጽሕና ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ትጠነቀ
ቃለች

## fanaticism, religious ~
*He was accused of stirring up religious
fanaticism. ዓይን ፡ ጨፍኖ ፡ የማምለክን ፡ እም
ነት ፡ በማነሣሣት ፡ ተከሰሰ

## fanciful ብልጭልጭ
His fanciful dress made everyone stare at him.
ብልጭልጭ ፡ ልብሱ ፡ ሁሉም ፡ ሰው ፡ እንዲመለ
ከተው ፡ አደረገ

**be fanciful** ከሕልም ፡ ሊቈጠር ፡ ቻለ
A story about a trip to the moon is no longer
fanciful. ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ወደ ፡ ጨረቃ ፡ የ
ሚደረገው ፡ ጉዞ ፡ ከሕልም ፡ ሊቈጠር ፡ አይችልም

## fancy (fancied),v.
1. መሰለ(ው). I fancy he'll want it. የሚፈልገው ፡
ይመስለኛል
2. ወደደ. Which dress do you fancy most?
የትኛውን ፡ ልብስ ፡ በይበልጥ ፡ ትወዳለህ ?
*Can you fancy yourself on the moon?
ጨረቃ ፡ ላይ ፡ እንዳለህ ፡ አድርገህ ፡ ልታስብ ፡ ት
ችላለህ ?

## fancy (fancies), n.
1. የፈጠራ ፡ ችሎታ. Such strange tales show
a lively fancy. እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ እንግዳ ፡ ተረቶ
ች ፡ አስደናቂ ፡ የፈጠራ ፡ ችሎታን ፡ ያሳያሉ
2. ሐሳብ. Is it my fancy, or do I hear a sound?
ድምፅ ፡ የምሰማው ፡ በሐሳብ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ በውን ?

3. **ሕልም**. His head was filled with fancies. በአንጐሉ ፣ ያለው ፣ ሐሳብ ፣ ሁሉ ፣ ሕልም ፣ ብቻ ፣ ነበር

**have a fancy for** ወደደ
He has a fancy for bright ties. ደመቅ ፣ ያሉ ፣ ክራቫቶች ፣ ይወዳል

**take a fancy to** ወደደ
He takes a fancy to walking barefoot in the streets. በባዶ ፣ እግሩ ፣ መንገድ ፣ ላይ ፣ መሄድ ፣ ይወዳል

**take a fancy to each other**
They took a fancy to each other. እንደመዋደድ ፣ ብለዋል

**fancy** (adj.)
1. **ብልጭልጭ**. She doesn't like fancy clothes. ብልጭልጭ ፣ ልብስ ፣ አትወድም
2. **ወደር ፣ የሌለው**. He charges fancy rates. ወደር ፣ የሌለው ፣ ዋጋ ፣ ይጠይቃል

**fang** ጥርስ
The tiger's fangs are strong. የነብር ፣ ጥርስ ፣ ኀይለኛ ፣ ነው

**fantastic**
1. **ጨርሶ ፣ የማይታመን**. He told me a fantastic story. ጨርሶ ፣ የማይታመን ፣ ታሪክ ፣ ነገረኝ
2. **የማይታመን**. We have made fantastic strides in the study of space. ስለ ፣ ጠፈር ፣ ጥናት ፣ የማይታመን ፣ እርምጃ ፣ አደረግን
3. **ሊታመን ፣ የማይቻል**. He spends fantastic sums of money. ሊታመን ፣ የማይቻል ፣ ገንዘብ ፣ ያጠፋል
4. **በጣም ፣ ልዩ ፣ የሆነ ፣ ቅርጽ ፣ ያለው**. The firelight cast fantastic shadows on the walls. የእሳቱ ፣ ብርሃን ፣ በግድግዳው ፣ ላይ ፣ በጣም ፣ ልዩ ፣ የሆነ ፣ ቅርጽ ፣ ያለው ፣ ጥላ ፣ ይፈጥራል

**fantasy** (fantasies) ቅዠት
He lives in a world of fantasy. በቅዠት ፣ ዓለም ፣ ውስጥ ፣ ይኖራል

**indulge in fantasy** ሲቃዥ ፣ ኖረ
He indulges in fantasy dreaming of the day he will become a prince. ልዑል ፣ የሚሆንበትን ፣ ጊዜ ፣ በማለም ፣ ሲቃዥ ፣ ይኖራል

**far** (adj.) ሩቅ
He came from a far country. ከሩቅ ፣ አገር ፣ መጣ

**far** (adv.)
1. **ርቆ**. Don't go too far from the house! ከቤቱ ፣ በጣም ፣ ርቀህ ፣ አትሂድ
2. **በጣም**. He is far taller than I am. ከኔ ፣ በጣም ፣ ይረዝማል
This idea is far better than your suggestion. ይህ ፣ ሐሳብ ፣ አንተ ፣ ካቀረብከው ፣ በጣም ፣ የተሻለ ፣ ነው

**be far** ራቀ
Nairobi is far from Addis Ababa. ናይሮቢ ፣ ከአዲስ ፣ አበባ ፣ ይርቃል

**be far away** በጣም ፣ ራቀ
Is Harar far away from Addis Ababa? ሐረር ፣ ከአዲስ ፣ አበባ ፣ በጣም ፣ ይርቃል ?

**be far from**
He is far from satisfied. ጨርሶ ፣ አልተደሰተም

**be far from each other** ተራራቀ
The farms are far from each other. ማሳዎቹ ፣ የተራራቁ ፣ ናቸው

**far above** በጣም ፣ ከፍ ፣ ብሎ
The bird flew far above the mountain. ወፏ ፣ ከተራራው ፣ በጣም ፣ ከፍ ፣ ብላ ፣ በረረች

**far and away the best** ከ - - - ሁሉ ፣ በጣም ፣ የላቀ
He is far and away the best student we've had. ከነበሩን ፣ ተማሪዎች ፣ ሁሉ ፣ በጣም ፣ የላቀ ፣ ነው

**far and wide**
1. **አገር ፣ አቋርጦ**. He traveled far and wide in search of his missing son. የጠፋውን ፣ ልጁን ፣ ፍለጋ ፣ አገር ፣ አቋርጦ ፣ ተጓዘ
2. **ካገር ፣ እስካገር**. The news spread far and wide. ወሬው ፣ ካገር ፣ እስካገር ፣ ተሰራጨ

**far away** ሩቅ
The mourners' dirge could be heard from far away. ያልቃሾች ፣ ሙሾ ፣ ከሩቅ ፣ ይሰማ ፣ ነበር

**far back** እጅግ ፣ ቀደም ፣ ብሎ
The coming of the South Arabians to Ethiopia took place far back in history. የደቡብ ፣ ዐረቦች ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ መምጣት ፣ በታሪክ ፣ ውስጥ ፣ እጅግ ፣ ቀደም ፣ ብሎ ፣ የሆነ ፣ ነገር ፣ ነው

**far be it**
*Far be it from me to criticize you! እንዴት ፣ እኔ ፣ አንተን ፣ እነቅፍሃለሁ

**far from** ቀርቶ
Far from admiring his paintings, I dislike them very much. ሥዕሎቹን ፣ ማድነቁ ፣ ቀርቶ ፣ በጣም ፣ እጠላቸዋለሁ

**far side** ጀርባ
We can see the near side of the moon, but not the far side. የጨረቃን ፣ ፊቷን ፣ እንጂ ፣ ጀርባዋን ፣ ማየት ፣ አንችልም

**(on the) far side of** ከ --- ማዶ
Our house is on the far side of the river. ቤታችን ፡ ከወንዙ ፡ ማዶ ፡ ነው

**as far as** (prep.) እስከ --- ድረስ
We walked together as far as the gate. እስከ ፡ በሩ ፡ ድረስ ፡ አብረን ፡ ሄድን

**as far as** (conj.)
1. እንደ + (relative imperfect). As far as I know, everything is all right. እኔ ፡ እንደማውቀው ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ደኅና ፡ ነው
2. እስከ + perfect + ድረስ. As far as I could see, everything was covered with sand. ዓይኔ ፡ እስከገመገመ ፡ ድረስ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ባሸዋ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር
*A dollar doesn't go as far today as it did 20 years ago. አንድ ፡ ብር ፡ ከሃያ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ይገዛ ፡ የነበረውን ፡ ያህል ፡ ዛሬ ፡ አይገዛም

**as far as he can** የተቻለውን ፡ ያህል
He will help you as far as he can. የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ይረዳሃል

**at the far end of** እ --- በወዲያኛው ፡ ጥግ
There was a picture at the far end of the room. እክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ በወዲያኛው ፡ ጥግ ፡ አንድ ፡ ሥዕል ፡ ነበር

**by far the best** ከሁሉም ፡ የተሻለ
This is by far the best hotel in town. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ከሁሉም ፡ የተሻለ ፡ ሆቴል ፡ ይህኛው ፡ ነው

**by far the most** በይበልጥ
He is by far the most famous man in town. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ በይበልጥ ፡ የታወቀው ፡ እሱ ፡ ነው

**from far and near** ከያለበት
They came from far and near to hear him. የሱን ፡ ንግግር ፡ ለመስማት ፡ ከያለበት ፡ መጡ

**go far** ራቀ
Don't go far! You'll lose your way. አትራቅ ፡ መንገዱ ፡ ይጠፋሃል
*The loan will go far in overcoming our financial troubles. ብድሩ ፡ የገንዘብ ፡ ችግራችንን ፡ ብዙ ፡ ያቃልልልናል

**go too far** ከልክ ፡ አለፈ
Don't go too far when joking with your boss! ከለቃህ ፡ ጋር ፡ ስትቃለድ ፡ ከልክ ፡ አትለፍ

**go very far**
*He won't go very far without an education. ያለ ፡ ትምህርት ፡ የትም ፡ ሊደርስ ፡ አይችልም

**not be far off** ተቃረበ
The holiday is not far off. ዓመት ፡ በዓሉ ፡ ተቃርቧል

**on the far side of** ከ --- ማዶ
Our house is on the far side of the river. ቤታችን ፡ ከወንዙ ፡ ማዶ ፡ ነው

**that far**
1. እስከዚህ. His memory does not go back that far. እስከዚህ ፡ ትዝ ፡ አይለውም
2. ያን ፡ ያህል. I can't walk that far. ያን ፡ ያህል ፡ በእግሬ ፡ ልሄድ ፡ አልችልም
[See also 'afield, ahead, concern, few, how, old, so, this, thus']

**faraway** ሩቅ
He went to a faraway place. እሱ ፡ ወደአንድ ፡ ሩቅ ፡ ቦታ ፡ ሄደ
*A faraway look in her eyes showed that she was daydreaming. ዝም ፡ ብላ ፡ አተኩራ ፡ ማየቷ ፡ በሐሳብ ፡ መናወዟን ፡ አመለከተ

**farce** ቀልድ
The last League of Nations meeting was a farce. የመጨረሻው ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ጉባኤ ፡ ስብሰባ ፡ ቀልድ ፡ ነበር

**fare** (v.) ግብር ፡ ገባ
They fared sumptuously. በሰፊው ፡ ግብር ፡ ገቡ
*How did you fare during your trip? መንገዱ ፡ እንዴት ፡ አደረገህ ?

**(it will) fare hard with** ወዮለት
It will fare hard with the thief if he is caught. ሌባው ፡ የተያዘ ፡ እንደሆነ ፡ ወዮለት

**fare well in** ተሳካለት
+He fared well in his profession. ሥራው ፡ ተሳካለት

**fare with**
How did it fare with him? እሱ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ?

**fare** (n.)
1. ዋጋ. What is the fare? ዋጋው ፡ ስንት ፡ ነው ?
2. የሚከፍለው ፡ ገንዘብ. Have your fares ready! የምትከፍሉትን ፡ ገንዘብ ፡ አዘጋጁ
3. መብልና ፡ መጠጥ. How is the fare in the hotel? የሆቴሉ ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ እንዴት ፡ ነው ?

**Far East** ሩቅ ፡ ምሥራቅ
Japan is in the Far East. ጃፓን ፡ የምትገኘው ፡ በሩቅ ፡ ምሥራቅ ፡ ነው

**farewell** (n.), **bid** ~ ተሰናበተ
He bade his friends farewell. ጓደኞቹን ፡ ተሰናበታቸው

**make one's farewell**
They made their farewell and left. ደኅና ፡ ሰንብቱ ፡ ብለው ፡ ሄዱ

**wish farewell** ተሰናበተ
They came to wish me farewell. ሊሰናበቱኝ ፡ መጡ

**farewell** (adj.)
He gave her a farewell kiss. ለመሰነባበቻ ፡ ሳማት

**farewell!**
Farewell, dear friends! ወዳጆቼ ፤ ደኅና ፡ ሰንብቱ

**far-fetched** የማይሆን ፡ ነገር ፡ መስሎ
The idea of bringing oil across the desert seems far-fetched. በረሃውን ፡ አቋርጦ ፡ ዘይት ፡ የማምጣቱ ፡ ሐሳብ ፡ የማይሆን ፡ ነገር ፡ መስሎ ፡ ይታያል

**farm** (v.) አረሰ
He is farming in our village. በመንደራችን ፡ ውስጥ ፡ ያርሳል

**farm out** አከፋፈለ
The contractor farmed out the construction of the buildings to different companies. ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የሕንጻውን ፡ ሥራ ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ኩባንያዎች ፡ አከፋፈለ

**farm** (n.)
1. ማሳ. The two farms are far from each other. ሁለቱ ፡ ማሳዎች ፡ የተራራቁ ፡ ናቸው
2. እርሻ. My brother has a large farm. ወንድሜ ፡ ሰፊ ፡ እርሻ ፡ አለው

**farm** (adj.) የእርሻ
Farm implements are sold in our store. የእርሻ ፡ መሣሪያዎች ፡ በመደብራችን ፡ ይሸጣሉ

**farmer** ገበሬ ፤ አራሽ
The farmers of this region are poor. የዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ገበሮች ፡ ድኾች ፡ ናቸው
Some farmers still use wooden plows. አንዳንድ ፡ አራሾች ፡ (ገበሬዎች) ፡ አሁንም ፡ በዕንጨት ፡ ማረሻ ፡ ያርሳሉ

**farm hand** ቅጥር ፡ አራሽ
Farm hands are needed at harvest time. ቅጥር ፡ አራሾች ፡ በመኸር ፡ ጊዜ ፡ ያስፈልጋሉ

**farming** (n.)
1. እርሻ. There is not much farming in this region. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ብዙ ፡ እርሻ ፡ የለም
2. የግብርና ፡ ሥራ. Do you find much pleasure in farming? በግብርና ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ ደስታ ፡ ታገኝበታለህ ?
3. ግብርና. He earns his livelihood by farming. የሚተዳደረው ፡ በግብርና ፡ ነው

**farming** (adj.) የእርሻ
A model farm was set up to spread new farming methods. አዲስ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴዎችን ፡ ለማስፋፋት ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ እርሻ ፡ ተቋቋመ

**farmyard** የገበሬ ፡ አጥር ፡ ግቢ
The farmyard was full of chickens. አገበሬው ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ዶሮዎች ፡ ሞልተዋል

**far-off** ሩቅ
He likes to visit far-off places. የሩቅ ፡ አገሮችን ፡ መጐብኘት ፡ ይወዳል

**far-reaching** በጣም ፡ ሰፊ ፤ ሰፋ ፡ ያለ
The invention of radio has had far-reaching effects. የራዲዮ ፡ መፈልሰፍ ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ ተጽዕኖ ፡ አለው
The students' manifesto demanded far-reaching reforms. የተማሪዎች ፡ መግለጫ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ መሻሻል ፡ እንዲደረግ ፡ ጠየቀ

**far-sighted** አርቆ ፡ አስተዋይ ፡ የሆነ
Far-sighted observers foresaw those difficulties. አርቆ ፡ አስተዋይ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ችግሩን ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ተገንዝበውታል
*My sister wears glasses since she is far-sighted. እኅቴ ፡ ከሩቅ ፡ እንጂ ፡ ከቅርብ ፡ ማየት ፡ ስለማትችል ፡ መነጽር ፡ ታደርጋለች

**fart** ፈሳ
Don't fart in public! በሰው ፡ መሃል ፡ አትፍሳ

**farther** (adj.) የወዲያኛ
The farther side of the mountain is rocky. የተራራው ፡ የወዲያኛው ፡ ክፍል ፡ ድንጋያማ ፡ ነው

**farther** (adv.) ራቅ ፡ ብሎ
You will have to walk a little farther. ጥቂት ፡ ራቅ ፡ ብለህ ፡ መሄድ ፡ አለብህ

**farther than** ከ - - - የበለጠ ፡ ርቆ
I can swim farther than you can. አንተ ፡ ከምትዋኘው ፡ የበለጠ ፡ ርቄ ፡ መዋኘት ፡ እችላለሁ

**be farther than** ከ - - - ራቀ
Three miles is farther than two. ከሁለት ፡ ማይል ፡ ሦስት ፡ ማይል ፡ ይርቃል

**on the farther bank** ከ - - - ማዶ
They saw an antelope on the farther bank of the river. ከወንዙ ፡ ማዶ ፡ አጋዘን ፡ አዩ

**farthest**
1. ከሁሉ ፡ የራቀ. Our house is the farthest down the road. ቤታችን ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ የራቀ ፡ ነው
2. ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ርቆ. Who can run farthest? ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ርቆ ፡ መሮጥ ፡ የሚችል ፡ ማነው ?

**be farthest** ራቀ
Which is farthest from Addis Ababa, Harar or Gondar? ከአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚርቀው ፡ የትኛው ፡ ነው ። ሐረር ፡ ወይስ ፡ ጐንደር ?

**the farthest** እርቆ
They wanted to see who could throw the farthest. እርቆ ፡ የሚወረውረው ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ለማየት ፡ ፈለጉ

## fascinate
1. ማረከ. The actress' beauty fascinated everyone. የተዋናይቱ ፡ ውበት ፡ ሁሉንም ፡ ማረከ
2. አፈዘዘ. Snakes are said to fascinate small birds. እባቦች ፡ ትናንሽ ፡ ወፎችን ፡ ያፈዛሉ ፡ ይባላል

**be fascinated** ተመሰጠ
The entire audience was fascinated by his story. አዳማጩ ፡ በሙሉ ፡ በታሪኩ ፡ ተመሰጠ

## fascinating አስደናቂ
This is a fascinating book. ይህ ፡ አስደናቂ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው

## fashion (v.) ሠራ
He fashioned a chair of bamboo. ከሸምበቆ ፡ ወንበር ፡ ሠራ

## fashion (n.)
1. ሞድ. Is that the latest fashion? አዲሱ ፡ ሞድ ፡ ይህ ፡ ነው ?
2. መልክ. Submitting reports in this fashion is not recommended. በዚህ ፡ መልክ ፡ ሪፖርት ፡ ማቅረብ ፡ የማይደገፍ ፡ ነው

**after a fashion** እንደምንም ፡ ብሎ
He can speak and write Amharic after a fashion. አማርኛን ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ ሊናገርና ፡ ሊጽፍ ፡ ይችላል

**go (be) out of fashion** ወረቱ ፡ አለፈ(በት)
Green clothes have gone out of fashion. አረንጓዴ ፡ ልብስ ፡ ወረቱ ፡ አልፎበታል

## fashionable
1. ያጌጠ. The fashionable woman attracted everyone's attention. ያጌጠችው ፡ ሴትዮ ፡ የሁሉን ፡ ዓይን ፡ ማረከች
2. ተወዳጅ. Long dresses are fashionable this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ ረጅም ፡ ቀሚስ ፡ ተወዳጅ ፡ ሆኗል

## fast (v.) ጾመ
The Ethiopians fast several times a year. ኢትዮጵያውያን ፡ በዓመት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይጾማሉ

## fast (n.) ጾም
The fast of Lent lasts fifty-five days in Ethiopia. የሁዳዴ ፡ ጾም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ኀምሳ ፡ አምስት ፡ ቀኖች ፡ ይቆያል

**keep the fast** ጾመ
Are you keeping the fast on Wednesday? ረቡዕን ፡ ትጾማለህ ?

## fast (adj.)
1. ፈጣን. The fast runner got the first prize. ፈጣኑ ፡ ሯጭ ፡ ያንደኛነትን ፡ ሽልማት ፡ አገኘ
He drives a fast car. ፈጣን ፡ መኪና ፡ ይነዳል
2. የልብ. They have been fast friends for years. ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ ጀምሮ ፡ የልብ ፡ ጓደኞች ፡ ናቸው
3. የማይለቅ. Good cloth is dyed with fast colors. ጥሩ ፡ ልብስ ፡ የማይለቅ ፡ ቀለም ፡ ይነከራል
4. (= adv.) በጥድፊያ. They ate a fast lunch. ምሳቸውን ፡ በጥድፊያ ፡ በሉ

**fast** (adv.)
1. ቶሎ ፡ ቶሎ. Don't talk so fast! እንዲህ ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ አትናገር
2. በፍጥነት. The train is going fast. ባቡሩ ፡ በፍጥነት ፡ ይጓዛል
3. በጥብቅ. The car stuck fast in the mud. መኪናው ፡ ጭቃው ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በጥብቅ ፡ ተያዘ

**be fast** ቀደመ
My watch is ten minutes fast. ሰዓቴ ፡ ዐሥር ፡ ደቂቃ ፡ ቀድማለች

**go fast** ፈጠነ
The train is going fast. ባቡሩ ፡ ይፈጥናል

**hard and fast** የማይሻር ፡ የማይለወጥ
In this case, you can't make hard and fast rules. እንደዚህ ፡ ላለ ፡ ነገር ፡ የማይሻር ፡ የማይለወጥ ፡ ሕግ ፡ ልታወጣ ፡ አትችልም

**make fast**
1. አጥብቆ ፡ አሰረ. He made the boat fast to the dock. ጀልባውን ፡ ከወደቡ ፡ ጋር ፡ አጥብቆ ፡ አሰረው
2. አጠበቀ. Make that rope fast before you leave the boat! ጀልባውን ፡ ትተህ ፡ ከመሄድህ ፡ በፊት ፡ ገመዱን ፡ አጥብቀው

**stand fast**
*He stood fast in the face of enemy attack. ለጠላት ፡ ውጊያ ፡ አልበገር ፡ አለ
[See also 'asleep, rate, thick']

## fasten
1. አሰረ. To what can I fasten the string? ሲባጎውን ፡ ምን ፡ ላይ ፡ ልሰረው ?

2. **አያያዘ**. He fastened the sheets of paper together with a clip. ወረቀቶቹን ፡ በአግራፍ ፡ አያያዛቸው
3. **ተከለ**. The dog fastened his eyes on the stranger. ውሻው ፡ እንግዳው ፡ ላይ ፡ ዓይኑን ፡ ተከለ

**faster** ፈጠን ፡ ብሎ ፤ ቶሎ
Can't you walk faster? ፈጠን ፡ ብለህ ፡ ልትራመድ ፡ አትችልም ?
You get older faster if you work too hard. ሥራ ፡ በጣም ፡ ካበዛህ ፡ ቶሎ ፡ ታረጃለህ

**(be) fastidious**
He is fastidious about his food. በምግቡ ፡ ረገድ ፡ እሱን ፡ ማስደሰት ፡ በጣም ፡ ያስቸግራል

**fat** (n.) ሞራ
The cook cut the fat off the meat. ወጥ ፡ ቤቷ ፡ ሞራውን ፡ ከሥጋው ፡ ላይ ፡ ቈረጠች

**fat** (adj.)
1. ወፍራም. A fat person cannot walk fast. ወፍራም ፡ ሰው ፡ በፍጥነት ፡ ሊራመድ ፡ አይችልም
2. ድልብ ፤ ደንዳና. The ox is fat. በሬው ፡ ድልብ ፡ (ደንዳና) ፡ ነው
3. ጮማ. Fat meat is served at banquets. ጮማ ፡ ሥጋ ፡ በግብር ፡ ጊዜ ፡ ይቀርባል

**get fat**
1. ወፈረ. He has gotten fat and cannot run. ወፍሯልና ፡ ሊሮጥ ፡ አይችልም
2. ደለበ. The ox has gotten fat. በሬው ፡ ደልቧል
[See also 'roll']

**fatal**
1. አደገኛ. That was a fatal mistake. ያ ፡ አደገኛ ፡ ስሕተት ፡ ነበር
2. ቁርጠኛ. At last the fatal day for the contest arrived. በመጨረሻ ፡ ቁርጠኛው ፡ የግጥሚያ ፡ ቀን ፡ ደረሰ
3. ሞት ፡ ያስከተለ. The fatal accident was due to the driver's carelessness. ሞት ፡ ያስከተለው ፡ ግጭት ፡ ሊደርስ ፡ የቻለው ፡ በነጂው ፡ ቸልተኝነት ፡ ነው

**be fatal**
1. ሞትን ፡ አስከተለ. The blow was fatal. ምቱ ፡ ሞትን ፡ አስከተለ
2. ቀጨ. The loss of our money was fatal to our plans. የገንዘባችን ፡ መጥፋት ፡ እቅዳችንን ፡ ቀጨው

**fatality** (fatalities)
1. መቅሠፍት. Earthquakes, floods, locust invasions, and other fatalities befell the country. የመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ጐርፍ ፡ አንበጣና ፡ ሌሎች ፡ መቅሠፍቶች ፡ ባገሪቱ ፡ ላይ ፡ ደረሱባት
2. ሞት. Doctors are trying to reduce the fatality of diseases. ሐኪሞች ፡ በሽታዎች ፡ የሚያደርሱትን ፡ ሞት ፡ ለመቀነስ ፡ ይጥራሉ
3. ለሕይወት ፡ አደገኛነት. The fatality of cancer has been reduced. የካንሰር ፡ ለሕይወት ፡ አደገኛነት ፡ ተቀንሷል
4. ዕድል. We struggle against fatality in vain. ከዕድል ፡ ጋር ፡ በከንቱ ፡ እንታገላለን
*The last earthquakes caused many fatalities. ያለፈው ፡ የመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ጨርሷል

**fatally**
*He was fatally injured in the accident. ባደጋው ፡ ምክንያት ፡ ሞተ

**fate**
1. የእግዜር ፡ ፍርጃ. Fate decreed that they should all die. ሁሉም ፡ እንዲሞቱ ፡ የእግዜር ፡ ፍርጃ ፡ ሆነ
2. ዕጣ. It was my fate to be sent to the country for the winter. በክረምት ፡ ወደ ፡ ባላገር ፡ መላክ ፡ ዕጣዬ ፡ ሆነ
3. የወደፊት ፡ ዕድል. A judicial decision will decide his fate. ፍርዱ ፡ የወደፊት ፡ ዕድሉን ፡ ይወስናል
*What was the fate of the ship in the storm? በማዕበሉ ፡ ጊዜ ፡ መርከቡ ፡ እንዴት ፡ ሆኖ ፡ ይሆን ?
[See also 'irony']

**fateful**
1. ወደፊት ፡ ዕድሉን ፡ የሚወስን. Mussolini's decision to ally himself with Germany was a fateful decision. የሙሶሊኒ ፡ ራሱን ፡ ከጀርመን ፡ ጋር ፡ ማጐዳኘት ፡ ወደፊት ፡ ዕድሉን ፡ የሚወስን ፡ ውሳኔ ፡ ነበር
2. ሕይወት ፡ የሚያጠፋ. The fateful explosion killed the inventor. ሕይወት ፡ የሚያጠፋው ፡ ፈንጂ ፡ ፈልሳፊውን ፡ ገደለ
*His fateful prophecy marked the end of peaceful times. ክፉ ፡ ቀን ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተነበየው ፡ የሰላም ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ

**father** (n.)
1. አባት. My father left for Harar. አባቴ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ሄደ
God is called Our Father. እግዚአብሔር ፡ አባታችን ፡ እየተባለ ፡ ይጠራል
2. አባ. I talked with Father Giyorgis about the church. ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ከአባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጋር ፡ ተነጋገርኩ

**father** (v.)
1. **ወለደ**. He fathered three sons. ሦስት ፡ ልጆች ፡ ወለደ
2. **አባት ፡ ነበረ**. Edison fathered many inventions. ኤዲሰን ፡ የብዙ ፡ ፍልሰፋዎች ፡ አባት ፡ ነበር

**father-in-law** **አማት ፤ አማች**
"He is my father-in-law," said the woman. አማቴ ፡ ናቸው ፡ አለች ፡ ሴትዮዋ
"He is my father-in-law," said the man. አማቼ ፡ ናቸው ፡ አለ ፡ ሰውዬው

**fatherland** **አገር**
The fatherland requires each man to sacrifice himself if need be. አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ አገር ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ መሥዋዕት ፡ እንዲያደርግ ፡ ትጠይቃለች

**fatherly** **አባታዊ**
He gave the young man fatherly advice. ለወጣቱ ፡ ሰውዬ ፡ አባታዊ ፡ ምክር ፡ ሰጠ

**fathom** (v.) **ተረዳ**
I cannot fathom the mystery. ምስጢሩን ፡ ልረዳው ፡ አልቻልኩም

**fathom** (n.) [ስድስት ፡ ጫማ ፡ ያለው ፡ የባሕር ፡ ጥልቀት ፡ መለኪያ]

**fatigue** (vt.) **አደከመ**
This work fatigues me. ይህ ፡ ሥራ ፡ ያደክመኛል

**fatigue** (vi.) **ደከመ**
He fatigues easily. በቶሎ ፡ ይደክማል

**fatigue** (n.) **ድካም**
He suffers from fatigue even after a short walk. ጥቂት ፡ እንኳ ፡ በእግሩ ፡ ሲሄድ ፡ ድካም ፡ ይሰማዋል

**drop from fatigue** **ደክሞ ፡ ወደቀ**
During the long march, seven men dropped from fatigue. በረጅሙ ፡ ጉዞ ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ፡ ሰዎች ፡ ደክመው ፡ ወደቁ

**fatness** **ውፍረ**
His fatness prevented him from running fast. ውፍሬው ፡ በፍጥነት ፡ እንዳይሮጥ ፡ አደረገው

**fatten**
1. **አወፈረ**. Eating all that candy will fatten you. ያንን ፡ ሁሉ ፡ ከረሜላ ፡ መብላት ፡ ያወፍርሃል
2. **አደለበ**. The farmer fattens the oxen by feeding them properly. ገበሬው ፡ ሰንጋዎቹን ፡ በደንብ ፡ ቀልቦ ፡ ያደልባል

**fatuous** **የጅል**
His fatuous remarks embarrassed me. የጅል ፡ አስተያየቱ ፡ አሳፈረኝ

**faucet** **ቧምቧ ፡ መክፈቻ**
The faucet controls the flow of water. ቧምቧ ፡ መክፈቻው ፡ የውኃውን ፡ መውረድ ፡ ይቈጣጠራል

**fault**
1. **ስሕተት**. There are many spelling faults in his essay. በድርሰቱ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የፊደል ፡ ስሕተት ፡ አለ
2. **ጥፋት**. It is not his fault. የሱ ፡ ጥፋት ፡ አይደለም
3. **ነውር**. Inhospitality is considered a fault by Ethiopians. እንግዳን ፡ አለመቀበል ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ነውር ፡ ይቈጠራል
4. **ጉድለት**. Forgetfulness is one of his faults. ከጉድለቱ ፡ አንዱ ፡ መርሳት ፡ ነው
His wife finds fault with everything he does. ሚስቱ ፡ በሚሠራው ፡ ሁሉ ፡ ጉድለት ፡ አታጣበትም

**be at fault**
1. **ተቃወሰ**. My memory was at fault. የማስታወስ ፡ ችሎታዬ ፡ ተቃውሶ ፡ ነበር
2. **የርሱ ፡ ጥፋት ፡ ነው**. As far as I am concerned, he is at fault. እንደኔ ፡ ከሆነ ፡ የርሱ ፡ ጥፋት ፡ ነው

**find fault with** **ጥፋት ፡ ፈለገበት ፤ ጉድለት ፡ አያጣበትም**
He is always finding fault with me. እርሱ ፡ ሁል ጊዜ ፡ ጥፋት ፡ ይፈልግብኛል

**have faults** **ተሳሳተ**
We all have our faults. ሁላችንም ፡ እንሳሳታለን

**faulty**
1. **የተበላሸ ፤ የተሳሳተ**. His faulty education extenuates his faulty pronunciation. የተበላሸው ፡ ትምህርቱ ፡ ለተሳሳተ ፡ አነጋገሩ ፡ በከፊል ፡ ምክንያት ፡ ሆኗል
2. **ስሕተተኛ**. His logic is faulty. አስተሳሰቡ ፡ ስሕተተኛ ፡ ነው
3. (= noun) **ብልሽት**. The car crashed because of a faulty steering wheel. ከመሪው ፡ ብልሽት ፡ የተነሣ ፡ መኪናው ፡ ተጋጨ

**be faulty** **ብልሽት ፡ አለበት**
The light is faulty and will not always turn on. መብራቱ ፡ ብልሽት ፡ ስላለበት ፡ ሁልጊዜ ፡ አይበራም

**fauna** **እንስሳት**
The fauna of Ethiopia is not well known. የኢትዮጵያ ፡ እንስሳት ፡ በደምብ ፡ አይታወቁም

**favor** (v.)
1. **አደላ**. When it comes to giving promotions,

he favors his relatives. የደረጃ ፡ እድገት ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ለዘመዶቹ ፡ ያደላል
2. ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ ወደደ. He favors the youngest child. የመጨረሻ ፡ ልጁን ፡ ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ ይወዳል
3. አበላለጠ. A father should not favor one child above the other. አባት ፡ አንዱን ፡ ልጅ ፡ ካንዱ ፡ ማበላለጥ ፡ የለበትም
4. አመቸ. The weather favored our trip. ያየሩ ፡ ሁኔታ ፡ ለሽርሽራችን ፡ አመቸ
5. ደገፈ. We favor his plan for lower taxes. ግብር ፡ እንዲቀነስ ፡ ያቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ እንደግፋለን
6. መረጠ. The Russians favored the use of heavy artillery. መስኮባውያን ፡ በከባድ ፡ መሣሪያ ፡ መጠቀምን ፡ መረጡ
*Favor us with a song! እባክህ ፡ ዝፈንልን

**favor** (n.)
1. ውለታ. I could not deny him such a small favor. ይችም ፡ ውለታ ፡ ሆና ፡ ልነፍገው ፡ አልፈልግም
2. አድልዎ. He obtained his position by favor and not by merit. ቦታውን ፡ ያገኘው ፡ በአድልዎ ፡ እንጂ ፡ በመልካም ፡ ሥራው ፡ አይደለም
3. ጥቅም. He feigned friendship to obtain favors. ለጥቅም ፡ ሲል ፡ ወዳጅ ፡ መሰለ
4. መውደድ. He insinuated himself into the minister's favor. ተለማምጦ ፡ የሚኒስትሩን ፡ መውደድ ፡ አገኘ
5. ስጦታ. Everyone at the party received a pen as a favor. በፓርቲው ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አንዳንድ ፡ የብዕር ፡ ስጦታ ፡ አገኘ

**be in favor** ተወደደ
A fashion in favor this year may be out of favor next year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ የተወደደው ፡ ሞድ ፡ በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ የማይወደድ ፡ ይሆናል

**be in favor of** ደገፈ
I am in favor of immediate action. አሁኑኑ ፡ እርምጃ ፡ ቢወሰድ ፡ እደግፋለሁ

**be in one's favor** ጠቀመ ፤ ደገፈ
The rate of exchange is now in our favor. የምንዛሪው ፡ ሒሳብ ፡ አሁን ፡ እኛን ፡ ይጠቅመናል
Several potent arguments were in his favor. የሚያስተማምኑ ፡ ብዙ ፡ ማስረጃዎች ፡ ደግፈውታል

**be in someone's favor** ተወዳጅ ፡ ነው
He is high in the Emperor's favor. በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ ተወዳጅ ፡ ነው

**be out of favor** ተቀያየመ
He is out of favor with his employer. ካሠሪው ፡ ጋር ፡ ተቀያይሟል

**do a favor** ውለታ ፡ ዋለ
He has done me many favors. ብዙ ፡ ውለታ ፡ ውሎልኛል

**look with favor on** ደስ ፡ ብሎት ፡ ተቀበለው
The bank looked on my plan with favor. ባንኩ ፡ ፕላኔን ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ተቀበለው

**show favor** አደላ
He shows favor to members of his own family. ለቤተሰቡ ፡ ያደላል

**speak in one's favor**
1. ደገፈ. That speaks in his favor. ይህ ፡ እሱን ፡ ይደግፋል
2. ጉብዝናውን ፡ መሰከረ(ለት). The fact that he tries hard to do the work speaks in his favor. ሥራውን ፡ በሚገባ ፡ ለመሥራት ፡ መጣሩ ፡ ጉብዝናውን ፡ ይመሰክርለታል

**view with favor** በደግ ፡ ተመለከተ
The teachers did not view with favor the plan for changing the teaching hours. የማስተማሪያ ፡ ጊዜዎችን ፡ ለመለወጥ ፡ የታቀደውን ፡ ሐሳብ ፡ አስተማሪዎቹ ፡ በደግ ፡ አልተመለከቱም

**win one's favor** መልካም ፡ አስተያየት ፡ አስገኘ
An able speech won the king's favor. የተደረገው ፡ ብቁ ፡ ንግግር ፡ የንጉሡን ፡ መልካም ፡ አስተያየት ፡ አስገኘ
[See also 'court, decide, prejudice, weigh']

**favorable**
1. የሚስማማ. He bought the house on very favorable terms. ቤቱን ፡ በሚስማማው ፡ ውል ፡ ገዛው
2. የሚያመች. I am only waiting for a favorable opportunity. የሚያመቸኝን ፡ ዕድል ፡ ነው ፡ የምጠብቀው
3. የሚደግፍ. He sent a favorable report of my work to the director. ሥራዬን ፡ የሚደግፍ ፡ ሪፖርት ፡ ለዲሬክተሩ ፡ ላከ
4. ጥሩ. A favorable wind soon brought us to the port. ጥሩ ፡ ነፋስ ፡ ወዲያውኑ ፡ ወደቡ ፡ እንድንደርስ ፡ አደረገን

**make a favorable impression** ደኅና ፡ መሰለ
The new secretary makes a favorable impression. አዲሷ ፡ ጸሐፊ ፡ ደኅና ፡ ትመስላለች

**favorably, be ~ received**
1. ተቀባይነትን ፡ አገኘ. The plan was favorably received. እቅዱ ፡ ተቀባይነትን ፡ አገኘ
2. አድናቆትን ፡ አገኘ. The play was favorably received. ቴያትሩ ፡ አድናቆትን ፡ አገኘ

**favored** (adj.) ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ የሚወደድ
Her beauty made her the favored child.

ቁንጅናዋ ፣ ከሁሉ ፣ የበለጠ ፣ የምትወደድ ፣ ልጅ ፣ አደረጋት

**favorite** (n.) ባለሟል
He is a favorite of the Emperor. የንጉሥ ፣ ነገሥቱ ፣ ባለሟል ፣ ነው

**favorite** (adj.) የሚወደው
This is my favorite pastime. ይህ ፣ የምወደው ፣ የጊዜ ፣ ማሳለፊያ ፣ ነው
*Dessert is my favorite part of a meal. ማጣጣሚያ ፣ ከምግብ ፣ ሁሉ ፣ አብልጬ ፣ እወዳለሁ

**be a favorite (with)**
1. ተወዳጅ ፣ ነው. He is a favorite with everybody. በሁሉም ፣ ዘንድ ፣ ተወዳጅ ፣ ነው
2. ተወዳጅነት ፣ አለው. This book is a great favorite with children. ይህ ፣ መጽሐፍ ፣ በልጆች ፣ ዘንድ ፣ በጣም ፣ ተወዳጅነት ፣ አለው

**favoritism** አድልዎ
Favoritism will harm the administration of an office. አድልዎ ፣ የመሥሪያ ፣ ቤትን ፣ አስተዳደር ፣ ይጐዳል

**fawn** [የአጋዘን ፣ ግልገል]

**fear** (v.)
1. ፈራ. You have nothing to fear. ምንም ፣ መፍራት ፣ የለብህም
2. ሰጋ. We feared for the baby's life. ለሕፃኑ ፣ ሕይወት ፣ ሰጋን
3. ተጠራጠረ. I fear he has failed. ወድቋል ፣ ብዬ ፣ እጠራጠራለሁ

**fear** (n.)
1. ፍርሃት. He does not know the meaning of fear. ፍርሃት ፣ ምን ፣ እንደሆነ ፣ አያውቅም
2. መፍራት. Did you notice the fear in her voice? መፍራቷን ፣ ከድምጿ ፣ ልብ ፣ አደረግህ ?

**for fear of** ፈርቶ
He took the taxi for fear of missing the train. ባቡሩ ፣ እንዳያመልጠው ፣ ፈርቶ ፣ በታክሲ ፣ ሄደ

**in fear of**
*The thief passed the day in fear of discovery. ሌባው ፣ ቀኑን ፣ ሙሉ ፣ አሁን ፣ ካሁን ፣ ተያዝኩ ፣ እያለ ፣ ሲበረግግ ፣ ዋለ

**fearful**
1. ፈሪ. He is a very fearful person; he is always worrying about something. እሱ ፣ በጣም ፣ ፈሪ ፣ ሰው ፣ ስለሆነ ፣ ሁልጊዜ ፣ ይጨነቃል
2. አስፈሪ, The fearful storm panicked the children. አስፈሪው ፣ ዝናብ ፣ ልጆችን ፣ አሸበራቸው

**be fearful**
1. ፈራ. The believer is fearful of the Lord. ምእመን ፣ ፈጣሪን ፣ ይፈራል
2. ተሸበረ. He is fearful of all sorts of minor dangers. በቀላል ፣ አደጋ ፣ ሁሉ ፣ ይሸበራል
3. በጣም ፣ ሰጋ. My mother is fearful about my health. እናቴ ፣ ስለ ፣ ጤንነቴ ፣ በጣም ፣ ትሰጋለች

**fearless** ደፋር
The fearless traveler crossed the desert. ደፋሩ ፣ መንገደኛ ፣ በረሃውን ፣ አቋረጠ

**fearsome** አሰቃቂ
A fearsome sight met the policemen's eyes. ፖሊሶቹን ፣ አሰቃቂ ፣ ትርእይት ፣ አጋጠማቸው

**feasible** ሊሳካ ፣ የሚችል
The committee selected the plan that seemed most feasible. ደርጉ ፣ ሊሳካ ፣ የሚችል ፣ መስሎ ፣ የታየውን ፣ እቅድ ፣ መረጠ
*Is it feasible that John is wrong? ጆን ፣ መሳሳቱ ፣ እውነት ፣ ነው ?

**feast** (vt.) ግብር ፣ አበላ
The king feasted his favorites. ንጉሡ ፣ ባለሟሎቹን ፣ ግብር ፣ አበላ
*We feasted our eyes on the sunset. ፀሐይ ፣ ስትጠልቅ ፣ እያየን ፣ በጣም ፣ ተደሰትን

**feast** (vi.) በላ
We feasted well at the Emperor's banquet. ንጉሠ ፣ ነገሥቱ ፣ ባደረጉት ፣ ግብር ፣ ላይ ፣ ደኅና ፣ አድርገን ፣ በላን

**feast** (n.)
1. ድግስ. The wedding feast was splendid. የሰርጉ ፣ ድግስ ፣ ግሩም ፣ ነበር
2. ግብዣ ፤ ግብር. They prepared a feast to honor the Emperor. ለንጉሠ ፣ ነገሥቱ ፣ ክብር ፣ ግብዣ ፣ አዘጋጁ
The king bade the nobles to a feast. ንጉሡ ፣ መኳንንቱን ፣ ግብር ፣ ጠሩዋቸው

**give a feast** ድግስ ፣ አበላ
He gave a feast to celebrate the wedding. ለሰርጉ ፣ ድግስ ፣ አበላ
[See also 'nuptial, wedding']

**feat**
1, ጀብዱ. To cross the desert by car was quite a feat. በረሃውን ፣ በመኪና ፣ ማቋረጥ ፣ ታላቅ ፣ ጀብዱ ፣ ነበር
2. ከፍተኛ ፣ ሙያ. Arranging the treaty was a diplomatic feat. ስምምነቱን ፣ ማዘጋጀቱ ፣ ከፍተኛ ፣ የዲፕሎማሲ ፣ ሙያ ፣ ነበር

**feather** ላባ
The crow has black feathers. ቁራ ፡ ጥቁር ፡ ላ ባ ፡ አለው
*Birds of a feather flock together. ዘመድ ፡ ከዘመዱ ፤ አህያ ፡ ካመዱ

**a feather in his cap** የሚያኮራ ፡ ነገር
Getting a scholarship is a feather in his cap. የነጻ ፡ ትምህርት ፡ ማግኘቱ ፡ የሚያኮራ ፡ ነገር ፡ ነው
[See also 'tuft']

**feathery** ላባ ፡ የሚመስል
The feathery leaves of this tree give it a strange look. ላባ ፡ የሚመስለው ፡ የዚህ ፡ ዛፍ ፡ ቅጠል ፡ ለዛፉ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ ሰጥቶታል

**feature** (v.) በተለይ ፡ ገለጸ
This book features a description of the schools. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በተለይ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ይገልጻል
*This film features a new French actress. እዚህ ፡ ፊልም ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ አዲስ ፡ ፈረንሳዊት ፡ ተዋናይት ፡ ዋና ፡ ሆና ፡ ትታያለች

**feature** (n.)
1. መልክ. Her features are feminine. የሴትነት ፡ መልክ ፡ አላት
2. የፊት ፡ ቅርጽ. Her features are regular. የፊቷ ፡ ቅርጽ ፡ የተስተካከለ ፡ ነው
3. ጐልቶ ፡ የሚታይ ፡ ክፍል. The Mercato is the dominant feature of Addis Ababa. አዲስ ፡ ከተማ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ጐልቶ ፡ የሚታየው ፡ ክፍል ፡ ነው
4. ነገር. Your plan for the picnic has many good features and some bad ones. የሽርሽሩ ፡ እቅድህ ፡ ብዙ ፡ ጥሩ ፡ ነገሮችና ፡ አንዳንድ ፡ መጥፎ ፡ ነገሮች ፡ አሉበት
The latest cars embody many new features. በቅርቡ ፡ የወጡ ፡ መኪናዎች ፡ ብዙ ፡ አዳዲስ ፡ ነገሮች ፡ አላቸው
5. ሁኔታ. Nationalism is one of the characteristic features of our age. ብሔራዊ ፡ ስሜት ፡ ጊዜያችን ፡ ከሚለይባቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ አንዱ ፡ ነው
6. ዋና ፡ መለያ. Veneration of saints is a feature of some religions. አንዳንድ ፡ ሃይማኖቶች ፡ ቅዱሳንን ፡ ማክበር ፡ ዋና ፡ መለያቸው ፡ ነው
7. ገጽ. The terrestrial features were obscured by clouds. የመሬቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ገጾች ፡ በደመና ፡ ተሸፍነው ፡ ነበር
8. ፊልም. They are showing a good feature this week. በዚህ ፡ ሳምንት ፡ ጥሩ ፡ ፊልም ፡ ያሳያሉ
[See also 'prominent']

**February** የካቲት

**fecund**
1. ወላድ. Rabbits are fecund; they can have several litters a year. ጥንቸሎች ፡ ወላዶች ፡ ሲሆኑ ፡ በዓመት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ግልገሎች ፡ ይወልዳሉ
2. ብሩህ. This scientist has a fecund mind. ይህ ፡ ሳይንቲስት ፡ ብሩህ ፡ አእምሮ ፡ አለው

**fed**, see **feed**

**federal** የኅብረት ፡ መንግሥት
In America, coining money is a federal power. በአሜሪካን ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ ማተም ፡ የኅብረቱ ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ነው

**federation**
1. ፌዴራሲዮን. The Federation of Ethiopia and Eritrea ended in 1962. የኤርትራና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፌዴራሲዮን ፡ በ፲፱፻፶፬ ዓ. ም. ቀረ
2. ፌዴሬሽን. The Ethiopian Sport Federation was founded many years ago. የኢትዮጵያ ፡ የስፖርት ፡ ፌዴሬሽን ፡ ከተመሠረተ ፡ ብዙ ፡ ዓመቱ ፡ ነው

**fee**
1. ዋጋ. That's a reasonable fee. መጠነኛ ፡ ዋጋ ፡ ነው
2. ገንዘብ. Did you pay the fees? ገንዘቡን ፡ ከፈልክ ?
3. የሚከፈል ፡ ዋጋ. A lawyer's fee is quite high. ጠበቃ ፡ ለመግዛት ፡ የሚከፈለው ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው

**feeble**
1. የደከመ. A feeble old man came to see me. አንድ ፡ የደከመ ፡ ሽማግሌ ፡ ሊጠይቀኝ ፡ መጣ
The old man spoke with a feeble voice. ሽማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ በደከመ ፡ አንደበት ፡ ተናገረ
2. (= adv.) የግድ. The sick man made a feeble attempt to smile. በሽተኛው ፡ የግድ ፡ ፈገግ ፡ ለማለት ፡ ሞከረ

**feeble-minded** አእምሮ ፡ ደካማ
Feeble-minded children are cared for in a special home. አእምሮ ፡ ደካማ ፡ ልጆች ፡ በልዩ ፡ ማሳደጊያ ፡ ቤት ፡ ጥንቃቄ ፡ ይደረግላቸዋል

**feed** (fed), vt.
1. ጋበዘ. She fed her guests the best food. እንግዶቿን ፡ ምርጥ ፡ ምግብ ፡ ጋበዘች
2. አበላ. The farmer feeds grass to his cattle. ገበሬው ፡ ከብቶቹን ፡ ሣር ፡ ያበላል
3. ቀለበ. The farmer fattens the oxen by

feeding them properly. ገበሬው ፡ ሰንጋዎቹን ፡ በደንብ ፡ ቀልቦ ፡ ያደልባል
4. መገበ. She is feeding the chickens. ዶሮቹን ፡ ትመግባለች
The mother feeds her child five times daily. እናትዮዋ ፡ ልጇን ፡ በቀን ፡ አምስት ፡ ጊዜ ፡ ትመግበዋለች
5. ጨመረ. We fed the stove with wood. ምድጃው ፡ ውስጥ ፡ ማገዶ ፡ ጨመርን
6. አቀበለ. This machine feeds paper into the printing press. ይህ ፡ መሣሪያ ፡ ለማተሚያው ፡ መሣሪያ ፡ ወረቀት ፡ ያቀብላል
*Praise fed his vanity. በማብዛናው ፡ ሙገሳ ፡ አረካው

**feed** (vi.) ጋጠ
We put cows to feed in the pasture. በመስኩ ፡ ላይ ፡ እንዲግጡ ፡ ላሞችን ፡ ለቀቅን

**feed on** በላ
Cattle feed only on grass. የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ ሣር ፡ ብቻ ፡ ይበላሉ

**be fed up** ፈጽሞ ፡ ሰለቸ(ው)
+I am fed up with this whole business. ይህ ፡ ነገር ፡ ፈጽሞ ፡ ሰልችቶኛል

## feed (n.) ምግብ
We can't get enough feed for our livestock. ለከብቶቻችን ፡ በቂ ፡ ምግብ ፡ አናገኝም

## feel (vt.)
1. ተሰማ(ው). +He felt the cool breeze. ቀዝቀዝ ፡ ያለው ፡ የነፋስ ፡ ሽውታ ፡ ተሰማው
2. ለካ. The doctor felt my pulse. ሐኪሙ ፡ ትርታዬን ፡ ለካ
3. ዳበሰ. The mother felt the child's forehead to see if it had a fever. ትኩሳት ፡ እንዳለበት ፡ ለማወቅ ፡ እናቲቱ ፡ የልጁን ፡ ግንባር ፡ ዳበሰች
4. ዳሰሰ. Feel this cloth! ይህን ፡ ጨርቅ ፡ ዳስሰው

**feel** (vi.)
1. አስተያየት ፡ አለው. How do you feel about the war? ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ ምን ፡ አስተያየት ፡ አለህ?
2. አየ. Feel how cold my hands are! እጆቼ ፡ እንዴት ፡ እንደሚቀዘቅዙ ፡ እይ
3. መሰለ(ው). I feel that we shall win. የምናሸንፍ ፡ ይመስለኛል
4. ገመተ. John felt that two years' seniority gave him the right to advise his brother. ጆን ፡ ከወንድሙ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ መብለጡ ፡ ወንድሙን ፡ ለመምከር ፡ የሚያስችለው ፡ መሆኑን ፡ ገመተ

**feel for**
1. አዘነ(ለት). I really feel for you. ከልብ ፡ አዝንልሃለሁ
2. ራራ. She feels for all who suffer. ለተቸገረ ፡ ሁሉ ፡ ትራራለች

**feel like** አሰኘ(ው)
+I don't feel like dancing. መደነስ ፡ አላሰኘኝም
*I feel like working this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ ሥራ ፡ ብሎኛል
*I felt like laughing. ሣቅ ፡ ሣቅ ፡ አለኝ
*I felt like running. ሩጥ ፡ ሩጥ ፡ አለኝ

**feel up to** አሰኘ(ው)
He didn't feel up to going to the theater so soon after his recent illness. በቅርቡ ፡ ታሞ ፡ መዳኑ ፡ ስለሆነ ፡ ወደ ፡ ቴያትር ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ አላሰኘውም

**feel (one's) way** በዳበሳ ፡ ሄደ
He felt his way to the bed when the lights went out. መብራቱ ፡ ሲጠፋ ፡ ወደ ፡ አልጋው ፡ በዳበሳ ፡ ሄደ

**not feel well**
He doesn't feel well. ደኅንነት ፡ አይሰማውም
[See also various adjectives and nouns, such as 'angry, cold, pain']

## feeling
1. ስሜት. He has no feeling for music. የሙዚቃ ፡ ስሜት ፡ የለውም
2. የስሜት ፡ ዓይነት. Joy, sorrow, and fear are feelings. ደስታ ፤ ሐዘንና ፡ ፍርሃት ፡ የስሜት ፡ ዓይነት ፡ ናቸው
3. መንፈስ. There was a brotherly feeling among the boys in the class. በክፍል ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ልጆች ፡ መሃከል ፡ የወንድማማችነት ፡ መንፈስ ፡ ነበረ
4. አስተያየት. What is your feeling about this idea? ስለዚህ ፡ ሐሳብ ፡ ምን ፡ አስተያየት ፡ አለህ?
5. ማሳዘን. He spoke with feeling about their suffering. ስለ ፡ ችግራቸው ፡ በማሳዘን ፡ ተናገረ
6. መዳሰስ. By feeling, we tell what is hard from what is soft. በመዳሰስ ፡ ጠንካራን ፡ ነገር ፡ ከለስላሳው ፡ እንለያለን

**have a feeling** መሰለ(ው)
I have a feeling (that) he won't come. የሚመጣ ፡ አይመስለኝም

**(not) have feeling in** ደነዘዘ
+He has no feeling in his fingers as a result of the accident. ከደጋው ፡ የተነሣ ፡ ጣቶቹ ፡ ደንዝዘዋል
[See also 'hurt, lacerate, prickly, strange']

## feet, see foot

## feign የ + verb + መሰለ
Some animals feign death when in danger

አንዳንድ ፡ እንስሳት ፡ ባደጋ ፡ ጊዜ ፡ የሞቱ ፡ ይመስላሉ
*He feigned friendship to obtain favors. ለጥቅም ፡ ሲል ፡ ወዳጅ ፡ መሰለ

**feint** ቃጣ
The fighter feinted at his opponent with his right hand and struck with his left. ቡጢኛው ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ቃጥቶ ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ተወዳዳሪውን ፡ መታው

**felicitate**
1. እንኳን ፡ ደስ ፡ ያለህ ፡ አለ. I felicitate you on passing the examination. ፈተናውን ፡ በማለፍህ ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ ያለህ ፡ እልሃለሁ
2. የምስራች ፡ አለው. I felicitated him on the birth of his child. ወንድ ፡ ልጅ ፡ ስለተወለደለት ፡ የምስራች ፡ አልኩት

**felicitous** ለጊዜው ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ
A felicitous phrase is Churchill's "blood, sweat and tears". የቸርቺል ፡ «ደም ። ላብና ፡ እንባ» ፡ የሚለው ፡ ሐረግ ፡ ለጊዜው ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ አባባል ፡ ነው

**felicity**
*His domestic felicity was increased by the birth of a son. ወንድ ፡ ልጅ ፡ በመወለዱ ፡ ትዳሩ ፡ እየሞቀ ፡ ደስታውም ፡ እየጨመረ ፡ ሄደ

**feline, with ~ movements** እንደ ፡ ድመት ፡ እየተሳበ
The hunter approached the deer with feline movements. አዳኙ ፡ እንደ ፡ ድመት ፡ እየተሳበ ፡ ወደ ፡ አጋዘኑ ፡ ተጠጋ

**fell**, see **fall**

**fell** ጣለ
The lumberman felled the tree. ዕንጨት ፡ ቈራጩ ፡ ዛፉን ፡ ጣለ
*One blow felled him. ባንድ ፡ ቡጢ ፡ ወደቀ

**fellow** ሰው
He is a nice fellow. ጥሩ ፡ ሰው ፡ ነው
Who is that dumpy fellow near the door? ያ ፡ በሩ ፡ ጋ ፡ ያለው ፡ አጭር ፡ወፍራም ፡ ሰው ፡ ማነው ?

**fellow** (modifier)
1. የሥራ ፡ ጓደኛ. He and his fellow teachers are meeting with the president of the university. እሱና ፡ መምህራን ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቹ ፡ ከዩኒቨርሲቲው ፡ፕሬዚዳንት ፡ ጋር ፡ ይገናኛሉ
2. መሰሉ ፡ የሆነ. My fellow guests and I like this hotel. እኔና ፡ መሰሎቼ ፡ የሆኑት ፡ እንግዶች ፡ ይህንን ፡ ሆቴል ፡ እንወደዋለን

**fellow countrymen!** ያገሬ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ!
Fellow countrymen, now is the time to unite! ያገሬ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ! አንድ ፡ የመሆናችን ፡ ጊዜ ፡ አሁን ፡ ነው

**fellow student** የትምህርት ፡ ጓደኛ
He forfeited the good will of his fellow students by reporting their activities. የትምህርት ፡ ጓደኞቹ ፡ የሚሠሩትን ፡ በማሳበቅ ፡ ፍቅራቸውን ፡ አጣ

**poor fellow!** ምስኪን
Poor fellow! He does not even have a penny to buy a notebook. ምስኪን ። ለደብተር ፡ መግዣ ፡ እንኳ ፡ ፍራንክ ፡ የለውም

**fellowship**
1. ጓደኝነት. The Boy Scouts promote good fellowship among boys. ቦይ ፡ እስካውቶች ፡ በልጆች ፡ መካከል ፡ ጥሩ ፡ ጓደኝነትን ፡ ያዳብራሉ
2. የመማሪያ ፡ እርዳታ. He received a fellowship from the government. ከመንግሥት ፡ የመማሪያ ፡ እርዳታ ፡ አገኘ

**felon** ወንጀለኛ
Murderers and thieves are felons. ነፍስ ፡ ገዳዮችና ፡ ሌቦች ፡ ወንጀለኞች ፡ ናቸው

**felony** (felonies) ከባድ ፡ ወንጀል
He is accused of a felony. በከባድ ፡ ወንጀል ፡ ተከሰሰ

**felt** [ከሱፍ ፡ ወይም ፡ ከጸጉር ፡ በመጣበቅ ፡ የሚሠራ ፡ ልብስ]

**felt** (v.), see **feel**

**female** (n.) ሴት ። እንስት
This basketball team consists of three males and two females. ይህ ፡ የቅርጫት ፡ ኳስ ፡ ቡድን ፡ ሦስት ፡ ወንዶችና ፡ ሁለት ፡ ሴቶች ፡ (or, ሦስት ፡ ተባዕቶችና ፡ ሁለት ፡ እንስቶች) ፡ አሉበት

**female** (adj.)
1. የሴት. Sewing is usually a female occupation. ልብስ ፡ ስፌት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሴት ፡ ተግባር ፡ ነው
2. ሴት. This is a female mouse. ይህች ፡ ሴት ፡ አይጥ ፡ ናት

**feminine** (n.) እንስታይ ፡ ጾታ
Geez has a special form for the feminine. የግዕዝ ፡ ሰዋስው ፡ ለእንስታይ ፡ ጾታ ፡ ልዩ ፡ ማመልከቻ ፡ አለው

**feminine** (adj.) የሴት
He has a feminine voice. የሴት ፡ ድምፅ ፡ አለው
Her features are feminine. የሴት ፡ መልክ ፡ አላት
**feminine gender,** see **feminine** (n.)

**fence** (v.) አጠረ
He fenced the pasture to keep people out.
ሰው ፡ እንዳይገባበት ፡ ግጦሹን ፡ አጠረው
**fence in** አጠረ (ታጠረ)
The pasture land is fenced in. የግጦሹ ፡ መሬ
ት ፡ ታጥሯል

**fence** (n.) አጥር
There is a hole in the fence. አጥሩ ፡ ቀዳዳ ፡ ነው
**put up a fence** አጠረ
We put up a fence around the house. ቤቱን ፡ ዙ
ሪያውን ፡ አጠርነው

**fencing** የሻቦላ ፡ ግጥሚያ
Fencing used to be a gentleman's sport.
የሻቦላ ፡ ግጥሚያ ፡ የጨዋ ፡ እስፖርት ፡ ነበር

**fend, ~ for oneself** ራሱን ፡ቻለ
When his parents died, the boy had to fend for
himself. ወላጆቹ ፡ ሲሞቱ ፡ ልጁ ፡ ራሱን ፡ መቻ
ል ፡ ነበረበት
**fend off** መከተ ፤ ተከላከለ
He fended off the blow which was aimed at
his head. ለጭንቅላቱ ፡ የተሰነዘረውን ፡ ምት ፡
መከተ ፡ (ተከላከለ)

**fender** ፈረፋንጎ
The fender on my car is dented. የመኪናዬ ፡
ፈረፋንጎ ፡ ተጨፍልቋል

**ferment** (v.)
1. ቦካ. When the dough has fermented, we
will bake it. ሊጡ ፡ ሲቦካ ፡ እንጋግረዋለን
2. ፈላ. The beer is fermenting now. ጠላው ፡
በመፍላት ፡ላይ ፡ ነው

**ferment** (n.) እርሾ
Ferment is added so that the dough will rise.
ሊጥ ፡ እንዲቦካ ፡ እርሾ ፡ ይጨመርበታል
**be in ferment**
*The whole nation was in ferment over the
election. ምርጫው ፡ የሕዝቡን ፡ ስሜት ፡ ቀሰቀ
ሰው

**ferocious** አስፈሪ
The lion is a ferocious animal when it is angry.
አንበሳ ፡ ሲቆጣ ፡ አስፈሪ ፡ ነው

**ferocity**
1. አውሬነት. The hyena's ferocity is well
known. የጅብ ፡ አውሬነት ፡ በሚገባ ፡ የታወቀ ፡
ነው
2. አስፈሪ ፡ ሁኔታ. The wolves attacked with
ferocity. ተኩሎቹ ፡ በአስፈሪ ፡ ሁኔታ ፡ ተተናኰ
ሉት

**ferret out** አድኖ ፡ ያዘ
The police ferreted out the criminal. ፖሊሱ ፡
ወንጀለኛውን ፡ አድኖ ፡ ያዘ

**ferry** የመመላለሻ ፡ ጀልባ
The ferry crosses the river twice a day. የመመ
ላለሻው ፡ ጀልባ ፡ በቀን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ወንዙን ፡
ያቋርጣል

**fertile**
1. ለም ፤ ለምለም. The soil here is very fertile.
እዚህ ፡ መሬቱ ፡ በጣም ፡ ለም ፡ ነው
The hill declines to a fertile valley. ኮረብታው ፡
ወደ ፡ ለምለም ፡ ሸለቆ ፡ ያቈለቍላል
2. ወላድ. Fertile cattle are needed to improve
the breed. ዘሩን ፡ ለማሻሻል ፡ ወላድ ፡ የቀንድ ፡
ከብት ፡ ያስፈልጋል
3. ያልገማ. Chicks hatch from fertile eggs.
ጫጩቶች ፡ ካልገማ ፡ እንቁላል ፡ ይፈለፈላሉ
4. አመንጪ. Thomas Edison had a fertile mind.
ቶማስ ፡ ኤዲሰን ፡ አመንጪ ፡ አእምሮ ፡ ነበረው

**fertility**
1. መራባት. The fertility of rabbits is amazing.
የጥንቸል ፡ መራባት ፡ ያስገርማል
2. ለምነት. The fertility of the soil is necessary
for good crops. ያፈር ፡ ለምነት ፡ ለጥሩ ፡ ሰብ
ል ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
3. ልምላሜ. The goddess of fertility was wor-
shipped in ancient times. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡
የልምላሜ ፡ አንስት ፡ ጣዖት ፡ ያመልኩ ፡ ነበር
**lose fertility** መውለድ ፡ አቆመ
Women lose their fertility after 40 or so.
ሴቶች ፡ በአርባ ፡ ወይም ፡ በአርባ ፡ ዓመት ፡ ገደ
ማ ፡ መውለድ ፡ ያቆማሉ

**fertilize** አዳበረ
Farmers fertilize the soil with dung. ገበሬዎቹ ፡
መሬቱን ፡ በፍግ ፡ ያዳብራሉ

**fertilizer** የመሬት ፡ ማዳበሪያ
They make use of the excrement of bats for
fertilizer. የሌሊት ፡ ወፎችን ፡ ኩስ ፡ ለመሬት ፡
ማዳበሪያ ፡ ይጠቀሙበታል

**fervent**
1. ከፍ ፡ ያለ. He displays fervent admiration
for me. ስለኔ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አድናቆት ፡ አለው

2. (= adv.) ልብ ፡ በሚነካ ፡ ሁኔታ. The mother made a fervent plea to the judge to spare her son. እናቲቱ ፡ ዳኛው ፡ ልጇን ፡ እንዲያተርፍላት ፡ ልብ ፡ በሚነካ ፡ ሁኔታ ፡ ለመነች

**fervid**
1. የጋለ. He manifests a fervid love for his friends. ለጓደኞቹ ፡ የጋለ ፡ ፍቅር ፡ ያሳያል
2. ጽኑ. He manifests a fervid hatred for his enemies. ለጠላቶቹ ፡ ጽኑ ፡ የሆነ ፡ ጥላቻን ፡ ያሳያል
3. ስሜት ፡ የሚነካ. His fervid oratory aroused the crowd. ስሜት ፡ የሚነካ ፡ ንግግሩ ፡ ሕዝቡን ፡ አነሣሣ

**fervor**
1. አድናቆት. She showed great fervor for his poetry. ስለ ፡ ግጥሙ ፡ ያላትን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አድናቆት ፡ አሳየች
2. (= adj.) የጋለ. The patriot's voice trembled from the fervor of his love for his country. ለሀገሩ ፡ ካለው ፡ የጋለ ፡ ፍቅር ፡ የተነሣ ፡ አርበኛው ፡ ሲቃ ፡ ያዘው

**fester** መግል ፡ ያዘ
If the wound gets dirty, it will fester. ቁስሉ ፡ ከቆሸሸ ፡ መግል ፡ ይይዛል

**festival**
1. በዓል. Every year the city has a music festival. በያመቱ ፡ በከተማው ፡ የሙዚቃ ፡ በዓል ፡ ይደረጋል
2. ሥርዓተ ፡ ቅዳሴ. The solemn festivals of the church were gratifying. የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሞገስ ፡ ያለው ፡ ሥርዓተ ፡ ቅዳሴ ፡ መንፈስ ፡ የሚያረካ ፡ ነበር

**festive** የደስታ
We were in a festive mood that Christmas Eve. በዚያ ፡ የልደት ፡ ዋዜማ ፡ በደስታ ፡ መንፈስ ፡ ነበርን

**festive meal** ድግስ
The champion was given a festive meal. አሸናፊው ፡ ድግስ ፡ ተደገሰለት

**festivity** (festivities)
1. ጨዋታ. For Coronation Day, many festivities were planned. ለዘውድ ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ ጨዋታዎች ፡ ታቅደው ፡ ነበር
2. ሥነ ፡ በዓል. Many guests came to participate in the school festivities. በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ ላይ ፡ ለመገኘት ፡ ብዙ ፡ እንግዶች ፡ መጡ

**festoon** [ለሰርግና ፡ ለሌሎችም ፡ በዓላት ፡ ጊዜ ፡ ለጌጥነት ፡ እንዲያገለግል ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ታስሮ ፡ እንደ ፡ ሰንሰለት ፡ የሚንጠለጠል ፡ ያበባ ፡ ጉንጉን]

**fetch**
1. ሄዶ ፡ ጠራ. Fetch the doctor at once! ሄደህ ፡ ሐኪሙን ፡ በፍጥነት ፡ ጥራው
2. ሄዶ ፡ አመጣ. The chair is in the garden; please fetch it! ወንበሩ ፡ በአትክልት ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፤ ሄደህ ፡ አምጣው
3. አወጣ. These eggs will fetch a good price. እነዚህ ፡ እንቁላሎች ፡ ብዙ ፡ ያወጣሉ

**fete** (v.) ጋበዘ (ተጋበዘ)
The engaged couple were feted by their friends. እጮኞቹ ፡ በወዳጆቻቸው ፡ ተጋበዙ

**fete** (n.) ግብዣ
She is holding a great fete for the benefit of the hospital. ለሐኪም ፡ ቤቱ ፡ እርዳታ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ታላቅ ፡ ግብዣ ፡ ታደርጋለች

**fetid** ግም
The dirt has a fetid smell. ቆሻሻው ፡ ግም ፡ ሽታ ፡ አለው

**fetish** [የአስማት ፡ ኀይል ፡ አለው ፡ የሚባል ፡ የዕንጨት ፡ ቅርጽ ፡ የመሳሰለ ፡ ነገር]

**fetter** (v.) በእግር ፡ ብረት ፡ አሰረ
The policeman fettered the criminal to a post. ፖሊሱ ፡ ወንጀለኛውን ፡ በእግር ፡ ብረት ፡ ከግንድ ፡ ጋር ፡ አሰረው

**fetter** (n.) የእግር ፡ ብረት
His fetters clank when he moves. ሲንቀሳቀስ ፡ የእግር ፡ ብረቱ ፡ ይቃጨላል

**fetus**, see **foetus**

**feud** ቂም ፡ በቀል ፤ ጠብ
There is a feud between these two families. በሁለቱ ፡ ቤተሰቦች ፡ መካከል ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ (ጠብ) ፡ አለ

**feudal** የባላባት
The feudal system was dominant in the Middle Ages. በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ የባላባት ፡ አገዛዝ ፡ ሰፍኖ ፡ ነበር

**fever** ትኩሳት
The fever nearly finished him. ትኩሳቱ ፡ ሊገድለው ፡ ምንም ፡ አልቀረ
*A fever of anxiety infected the candidate's family during the election night. በምርጫው ፡ ሌሊት ፡ የእጩ ፡ ተወዳዳሪው ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመንፈስ ፡ መሸበር ፡ ይዟቸው ፡ ነበር

**have a fever** **አተኰሰ(ው)**
+If you have a fever, don't go to school! አተኰሰህ ፡ እንደሆን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አትሂድ

**run a fever** **አተኰሰ(ው)**
+He's running a fever, and we called the doctor. ስላተኰሰው ፡ ሐኪም ፡ ጠራን
[See also 'hot, ill']

**feverish** **ትኩሳት ፡ የሚያመው**
Feverish patients are made to stay in bed. ትኩሳት ፡ የሚያማቸው ፡ ሰዎች ፡ እንዲተኙ ፡ ይደረጋል

**feverish activity** **ጥድፊያ**
Why all the feverish activity over there? ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጥድፊያ ፡ ምንድር ፡ ነው?

**feel feverish** **ትኩሳት ፡ ተሰማ(ው)**
+He feels feverish, and we called the doctor. ትኩሳት ፡ ስለተሰማው ፡ ሐኪም ፡ ጠራን

**in feverish haste** **እቻኰሎ**
He packed his bags in feverish haste. ሻንጣውን ፡ እቻኩሎ ፡ አሰረ

**feverishly, work ~ on** **አጣደፈ**
They are working feverishly on the new project. አዲሱን ፡ እቅድ ፡ ያጣድፉታል

**few** **ጥቂት**
Few people come to see us in the summer. በበጋ ፡ ሊጠይቁን ፡ የሚመጡት ፡ ሰዎች ፡ ጥቂት ፡ ናቸው

**few and far between** **ጥቂት**
Honest people are few and far between. ሐቀኛ ፡ ሰዎች ፡ ጥቂት ፡ ናቸው

**a few**
1. ትንሽ. There were a few clouds in the sky. ሰማዩ ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ ደመና ፡ ነበር
2. ጥቂት. May I ask a few questions? ጥቂት ፡ ጥያቄዎች ፡ ልጠይቅ?

**a few times** **አንዴ ፡ ሁለቴ**
I saw him only a few times. ያየሁት ፡ አንዴ ፡ ሁለቴ ፡ ነው

**be few in number** **በቁጥር ፡ ናቸው**
The days in which there is rain are few in number. ዝናብ ፡ የሚዘንብባቸው ፡ ቀኖች ፡ በቁጥር ፡ ናቸው

**every few days** **አልፎ ፡ አልፎ**
We go to see him every few days. አልፎ ፡ አልፎ ፡ እንጠይቀዋለን

**no fewer than** **ከ - - - የማያንሱ**
No fewer than twenty workers were absent from illness. ከሀያ ፡ የማያንሱ ፡ ሠራተኞች ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ቀርተው ፡ ነበር

**quite a few** **በርከት ፡ ያሉ**
Quite a few people were present. በርከት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ተገኝተው ፡ ነበር

**the few** **ጥቂቶች ፡ ብቻ**
That music appeals to the few. ይህ ፡ ሙዚቃ ፡ ጥቂቶችን ፡ ብቻ ፡ ይስባል
[See also 'moment']

**fewer** **አነስ ፡ ያሉ**
I see fewer stars now. አሁን ፡ የማያቸው ፡ ከዋክብት ፡ አነስ ፡ ያሉ ፡ ናቸው
Fewer of my friends have had colds this year than last. ዘንድሮ ፡ ጉንፋን ፡ የያዛቸው ፡ ጓደኞቼ ፡ ከዓምና ፡ አነስ ፡ ይላሉ

**(the) fewest** **ያነሰ**
Which of you made the fewest mistakes? ከሁላችሁም ፡ ያነሰ ፡ ስሕተት ፡ የሠራ ፡ ማን ፡ ነው?

**fiancé, fiancée** **እጮኛ**
John is Mary's fiancé, and Jane is my fiancée. ጆን ፡ የሜሪ ፡ እጮኛ ፡ ነው ፤ ጄን ፡ ደግሞ ፡ የኔ ፡ እጮኛ ፡ ናት

**fiasco** **ውድቅ**
The play was a fiasco and closed. ጨዋታው ፡ ውድቅ ፡ ስለሆነ ፡ ቆመ

**fib** (fibbed) **ዋሸ**
He fibbed about not taking my pencil. እርሳሱን ፡ አልወሰድኩም ፡ ብሎ ፡ ዋሸ

**fiber**
1. ቃጫ. Rope is made from fiber. ገመድ ፡ ከቃጫ ፡ ይሠራል
2. መንፈስ. He was a person of strong moral fiber and could resist temptation. ጠንካራ ፡ መንፈስ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ የሚፈታተነውን ፡ ነገር ፡ ይቋቋማል

**fickle** **እስስት**
He is too fickle to be relied upon. እስስት ፡ ስለሆነ ፡ በሱ ፡ መተማመን ፡ አይቻልም

**fiction**
1. ልብ ፡ ወለድ. He prefers history to fiction. ከልብ ፡ ወለድ ፡ ይልቅ ፡ እውነተኛ ፡ ታሪክን ፡ ይመርጣል
2. ፈጠራ. His excuse was pure fiction. የሰጠው ፡ ምክንያት ፡ ፍጹም ፡ ፈጠራ ፡ ነበር

**fictitious**
1. በሐሳብ ፡ የተፈጠረ. The students enjoy reading

about fictitious heroes. ተማሪዎቹ ፡ በሐሳብ ፡ ስለተፈጠሩ ፡ ባለታሪኮች ፡ ማንበብ ፡ ይወዳሉ
2. የፈጠራ. He took a fictitious name to hide his identity. ማንነቱን ፡ ለመደበቅ ፡ በፈጠራ ፡ ስም ፡ ተጠቀመ

**fiddle** (v.) ተጫወተ
He was fiddling with a piece of string. በብጣሽ ፡ ሲባጎ ፡ ይጫወት ፡ ነበር

**fiddle around** ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ
Stop fiddling around and get to work! ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ማለቱን ፡ ትተህ ፡ ሥራ ፡ ጀምር

**fiddle** (n.) የፈረንጅ ፡ ማሲንቆ
[See also 'second']

**fidelity** እምነት
He shows great fidelity to his principles. በሚያምንበት ፡ ነገር ፡ ጠንካራ ፡ እምነት ፡ አለው

**with fidelity** በትክክል
He reported the news with fidelity. ወሬውን ፡ በትክክል ፡ አቀረበ

**fidget** ተቍነጠነጠ
The boy was fidgeting in his chair. ልጁ ፡ በወንበሩ ፡ ላይ ፡ ይቍነጠነጥ ፡ ነበር

**fief** ጉልት
My grandfather was given a fief by Menelik. ወንድ ፡ አያቴ ፡ ከምኒልክ ፡ ጉልት ፡ ተሰጣቸው

**field**
1. ማሳ. Keep your cow out of my wheat fields! ላምህ ፡ ከስንዴ ፡ ማሳዬ ፡ እንዳትገባ
I saw many farmers working in their fields. ብዙ ፡ ገበሬዎች ፡ በማሳቸው ፡ ላይ ፡ ሲሠሩ ፡ አየሁ
2. ሜዳ. We walked across the fields. ሜዳውን ፡ በግራችን ፡ አቋረጥን
3. የጨዋታ ፡ ሜዳ. The teams are coming onto the field. ቡድኖቹ ፡ ወደ ፡ ጨዋታው ፡ ሜዳ ፡ ገቡ
4. ስፍራ. An oil field was discovered in the desert. በምድረ ፡ በዳው ፡ ውስጥ ፡ የዘይት ፡ ስፍራ ፡ ተገኘ
5. ዓለም. Einstein was a famous scholar in the field of physics. አይንስታይን ፡ በፊዚክስ ፡ ዓለም ፡ የገነነ ፡ ሊቅ ፡ ነበረ
6. ሙያ. Every scientist must learn the nomenclature of his field. ማንኛቸውም ፡ የሳይንስ ፡ ሊቅ ፡ የሙያውን ፡ መሪሐ፡ ቃላት ፡ ማጥናት ፡ አለበት
7. ትምህርት. He has published several studies in that field, ስለዚያ ፡ ትምህርት ፡ አያሌ ፡ ጽሑፎች ፡ አቅርቧል

**open field** አውላላ ፡ ሜዳ
Soldiers in an open field are exposed to the enemy's fire. በአውላላ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ወታደሮች ፡ ለጠላት ፡ ጥይት ፡ ይጋለጣሉ

**fiend** አረመኔ
The fiend stabbed the baby with a knife. አረመኔው ፡ ሕፃኑን ፡ በጩቤ ፡ ወጋው

**fierce**
1. ኀይለኛ. The heat is fierce today. ዛሬ ፡ ሙቀቱ ፡ ኀይለኛ ፡ ነው
2. የሚያስፈራ. He tried to panic the child by making fierce noises. የሚያስፈራ ፡ ድምፅ ፡ በማሰማት ፡ ሕፃኑን ፡ ሊያስደነግጥ ፡ ሞከረ
3. የጋለ ፤ አስፈሪ. The enemy's fierce attack finally breached our lines. የጋለው ፡ (አስፈሪው) ፡ የጠላት ፡ ማጥቃት ፡ በመጨረሻው ፡ ግንባራችንን ፡ ጣሰ
4. ከፍ ፡ ያለ. He made fierce efforts to get ahead. ለመሻሻል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥረት ፡ አደረገ
5. የከረረ. The deadly enemies have a fierce hatred for each other. በተማረሩ ፡ ባለጋራዎች ፡ መካከል ፡ የከረረ ፡ ጥላቻ ፡ አለ
6. ተናካሽ. Fierce dogs keep burglars away. ተናካሽ ፡ ውሾች ፡ ቤት ፡ ሰርሳሪዎችን ፡ አያስደርሱም

**fiery**
1. የጋለ. He made a fiery speech denouncing fascism. የፋሺስትን ፡ እምነት ፡ በመንቀፍ ፡ የጋለ ፡ ንግግር ፡ አደረገ
2. የቁጡነት. A fiery temper only causes trouble. የቁጡነት ፡ ጠባይ ፡ ከችግር ፡ ላይ ፡ ይጥላል
3. እሳት ፡ የሚያመነጭ. The fiery explosion was seen for miles. እሳት ፡ የሚያመነጨው ፡ ፈንጂ ፡ ከሩቅ ፡ ይታይ ፡ ነበር
*A fiery sunset was to be seen behind the sea. ከባሕሩ ፡ ማዶ ፡ ፀሐይቱ ፡ ስትጠልቅ ፡ ደም ፡ መስላ ፡ ትታይ ፡ ነበር

**fiery glowing** ፍም ፡ የመሰለ
In its primeval state, the earth was a fiery glowing ball. በመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ መሬት ፡ ፍም ፡ የመሰለች ፡ ድቡልቡል ፡ አካል ፡ ነበረች

**fifteen** ዐሥራ ፡ አምስት

**fifth** አምስተኛ
Payments are due on the fifth of the month. የሚከፈለው ፡ ወር ፡ በገባ ፡ ባምስተኛ ፡ ቀን ፡ ነው

**a fifth** ካምስት ፡ አንድ
He got only a fifth of the estate. ከርስቱ ፡ ካምስት ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ደረሰው

**fifty** አምሳ

**fig** በለስ
Figs grow in abundance in our country. በሀገራችን ፡ በለስ ፡ በብዛት ፡ ይበቅላል

**fight** (fought), vt.
1. ተዋጋ. We fought a difficult battle. ከባድ ፡ ውጊያ ፡ ተዋጋን
2. ተከላከለ. Fight disease by getting rid of flies! ዝንቦችን ፡ በማጥፋት ፡ በሽታን ፡ ተከላከል
3. አስወገደ. You have got to fight that habit. ይህን ፡ ልማድ ፡ ማስወገድ ፡ አለብህ
4. አጠፋ. The civilized world must fight ignorance. የሠለጠነው ፡ ዓለም ፡ ድንቁርናን ፡ ማጥፋት ፡ አለበት
5. ገፋ(በት). I'm going to fight this suit. ይህን ፡ ክስ ፡ እገፋበታለሁ

**fight** (vi.)
1. ተዋጋ. The rebels fought with government troops near our village. ዐመፀኞቹ ፡ ከመንግሥት ፡ ወታደሮች ፡ ጋር ፡ እመንደራችን ፡ አጠገብ ፡ ተዋጉ
The patriots fought for freedom. አርበኞቹ ፡ ለነጻነት ፡ ተዋጉ
2. ተጣላ. When dogs fight, they use their teeth. ውሾች ፡ ሲጣሉ ፡ ይናከሳሉ
3. ተጨቃጨቀ. The partners were always fighting over money. ሸሪኮቹ ፡ በገንዘብ ፡ ምክንያት ፡ ሁል ጊዜ ፡ ይጨቃጨቁ ፡ ነበር

**fight against**
1. ተቋቋመ. He fought bravely against despair. ተስፋ ፡ መቍረጥን ፡ በኀይል ፡ ተቋቋመው
2. ደመሰሰ. The orator promised to fight against poverty. ተናጋሪው ፡ ድኽነትን ፡ ለመደምሰስ ፡ ቃል ፡ ገባ
3. ለማስቀረት ፡ ታገለ. He fought against the innovations which had entered the church. በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ የመጣውን ፡ አዲስ ፡ አሠራር ፡ ለማስቀረት ፡ ታገለ

**fight it out** አጥብቆ ፡ ተጨቃጨቀ
He refuses to accept my plan, so I have to fight it out with him. ሐሳቤን ፡ ስላልተቀበለ ፡ አጥብቄ ፡ መጨቃጨቅ ፡ ግዴታ ፡ ሆነብኝ

**fight** (n.)
1. ጠብ. When the police arrived, the fight was already over. ፖሊሶቹ ፡ ሲደርሱ ፡ ጠቡ ፡ አብቅቶ ፡ ነበር
2. ግጥሚያ. The boxer was badly hurt in the last fight. በመጨረሻው ፡ ግጥሚያ ፡ ላይ ፡ ቡጢኛው ፡ ክፉኛ ፡ ተጐዳ
3. መጋጠም. The contestants shake hands before the fight begins. ተወዳዳሪዎቹ ፡ ከመጋጠማቸው ፡ በፊት ፡ የእጅ ፡ ሰላምታ ፡ ይለዋወጣሉ
4. ዘመቻ. The fight against malaria was successful. ወባን ፡ ለማጥፋት ፡ የተደረገው ፡ ዘመቻ ፡ ጥሩ ፡ ውጤትን ፡ አስገኘ
5. ጭቅጭቅ. She starts a fight every time she phones me. ስልክ ፡ በደወለችልኝ ፡ ቁጥር ፡ ጭቅጭቅ ፡ ትጀምራለች

**have a fight** ተጣላ
He had a fight with his wife. ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ተጣልቶ ፡ ነበር

**put up a good fight**
1. አጥብቆ ፡ ተቋቋመ. The enemy put up a good fight. ጠላት ፡ አጥብቆ ፡ ተቋቍሞን ፡ ነበር
2. ጥሩ ፡ ተጫወተ. The losing team put up a good fight. የተሸነፈው ፡ ቡድን ፡ ጥሩ ፡ ተጫውቶ ፡ ነበር
[See also 'lose, spoil']

**fighting** (n.) ውጊያ
The fighting destroyed many villages. ውጊያው ፡ ብዙ ፡ መንደሮችን ፡ አወደመ

**prone to fighting** ዱለኛ
Don't anger him; he is prone to fighting. አታናደው ፤ ዱለኛ ፡ ነው

**figurative** በዘይቤ ፡ የተሞላ
He has a figurative style of writing. አጻጻፉ ፡ በዘይቤ ፡ የተሞላ ፡ ነው

**figure** (v.)
1. በግምት ፡ መሰለ(ው). I figure it is about five-thirty. በግምት ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ተኩል ፡ ይመስለኛል
2. አሰላ. I don't just guess, I figure. አንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የምደርሰው ፡ በግምት ፡ ሳይሆን ፡ አስልቼ ፡ ነው
3. ተጠቀሰ. His name figures in the news. ስሙ ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ይጠቀሳል

**figure on** አሰበ
We did not figure on having company. እንግዳ ፡ ይመጣል ፡ ብለን ፡ አላሰብንም

**figure out**
1. አሰላ. Figure out how much it will cost! ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚያወጣ ፡ አስላ
2. ሠራ. Can you figure out this problem? ይህን ፡ ሒሳብ ፡ ልትሠራው ፡ ትችላለህ ?
*I need time to figure out a rebuttal. ክርክሩን ፡ ለማፍረስ ፡ የምዘጋጅበት ፡ ጊዜ ፡ ያስፈልገኛል

**figure up** ደመረ
Did you figure up the first column? የመጀመሪያውን ፣ ዓምድ ፣ ደመርከው ?

**be figured** ተሠራ
The idol is figured as part man, part beast. ጣዖቱ ፣ ግማሽ ፣ ሰው ፣ ግማሽ ፣ አውሬ ፣ ሆኖ ፣ ተሠርቷል

**figure** (n.)
1. ቁጥር. Add up these figures! እነዚህን ፣ ቁጥሮች ፣ ደምራቸው
2. ሒሳብ. Check the figures carefully! ሒሳቡን ፣ በጥንቃቄ ፣ አጣራ
3. የገንዘብ ፣ ልክ. The outside figure given for the cost of the new school was $1,000,000. አዲሱ ፣ ትምህርት ፣ ቤት ፣ የሚፈጀው ፣ ከፍተኛ ፣ የገንዘብ ፣ ልክ ፣ አንድ ፣ ሚሊዮን ፣ ብር ፣ ነበር
4. ቅርጽ. Circles and squares are geometrical figures. ክበቦችና ፣ አራት ፣ ማእዘኖች ፣ የጂኦሜትሪ ፣ ቅርጾች ፣ ናቸው
5. ምስል. The figures in the painting are well composed. በሥዕሉ ፣ ላይ ፣ ያሉት ፣ ምስሎች ፣ በሚገባ ፣ የተቀነባበሩ ፣ ናቸው
6. ሥዕል. This note refers to figure six. ይህ ፣ መግለጫ ፣ ሥዕል ፣ ስድስትን ፣ ይመለከታል
7. የሰውነት ፣ ቅርጽ. She has a nice figure. ጥሩ ፣ የሰውነት ፣ ቅርጽ ፣ አላት
8. አንድ ፣ ዓይነት ፣ ቅርጽ. I saw a figure approaching me in the darkness. በጨለማ ፣ ውስጥ ፣ አንድ ፣ ዓይነት ፣ ቅርጽ ፣ ሲቀርበኝ ፣ አየሁ
9. የጠየቀው ፣ ዋጋ. His figure for that house is very high. ለዚያ ፣ ቤት ፣ የጠየቀው ፣ ዋጋ ፣ በጣም ፣ ከፍተኛ ፣ ነው
10. ምሳሌ. She is the figure of distress. እርሷ ፣ የችግር ፣ ምሳሌ ፣ ነች
11. ሰው. He is a mighty important figure in this town. በዚህ ፣ ከተማ ፣ ውስጥ ፣ በጣም ፣ የታወቀ ፣ ሰው ፣ ነው
[See also 'round']

**figurehead** ለስም ፣ የተሾመ
The prime minister is only a figurehead in the government. በመንግሥቱ ፣ ውስጥ ፣ ጠቅላይ ፣ ሚኒስትሩ ፣ የተሾመው ፣ ለስም ፣ ብቻ ፣ ነው

**figure of speech** ዘይቤ
'As brave as a lion' is a figure of speech. « እንደ ፣ አንበሳ ፣ ደፋር » ፣ የሚለው ፣ ንግግር ፣ ዘይቤ ፣ ነው

**file** (v.)
1. ሞረደ. I have to file my nails. ጥፍሬን ፣ መሞረድ ፣ አለብኝ
2. አስገባ. I filed my application today. ማመልከቻዬን ፣ ዛሬ ፣ አስገባሁ
3. በደንብ ፣ አስቀመጠ. Did you file the letters? ደብዳቤዎቹን ፣ በደንብ ፣ አስቀመጥክ ?
4. አኖረ. He filed the document in the Foreign Ministry's archives. ሰነዱን ፣ ከውጭ ፣ ጉዳይ ፣ ሚኒስቴር ፣ መዝገብ ፣ ቤት ፣ አኖረው

**file out** በሰልፍ ፣ ወጣ
The students filed out. ተማሪዎቹ ፣ በሰልፍ ፣ ወጡ

**be filed** ፋይል ፣ ውስጥ ፣ ገባ
The letters have not yet been filed. ደብዳቤዎቹ ፣ ገና ፣ ፋይል ፣ ውስጥ ፣ አልገቡም

**be filed off** ተሞረደ
The rough edges were filed off. ሻካራው ፣ ጠርዝ ፣ ተሞረደ
[See also 'claim']

**file** (n.)
1. መሥመር. Line up in single file! ባንድ ፣ መሥመር ፣ ተሰለፉ
2. ፋይል. Do we have his application on file? የሱ ፣ ማመልከቻ ፣ በፋይል ፣ ውስጥ ፣ አለ ?
3. ሞረድ. You need a fine file for that silverwork. ለዚያ ፣ የብር ፣ እቃ ፣ አንድ ፣ ቀጭን ፣ ሞረድ ፣ ያስፈልግሃል
You need a finger file for it. ለዚህ ፣ የጥፍር ፣ ሞረድ ፣ ያስፈልግሃል

**have on file** መዘገበ
We have his report on file. እሱ ፣ የሰጠውን ፣ መግለጫ ፣ መዝግበናል

**filial**
*The children treat their parents with filial respect. ልጆቹ ፣ ልጅ ፣ ማድረግ ፣ እንደሚገባው ፣ ወላጆቻቸውን ፣ ያከብራሉ

**filing** (n.) ፋይል ፣ አያያዝ
Filing is a clerical task. ፋይል ፣ አያያዝ ፣ የጸሐፊዎች ፣ ሥራ ፣ ነው

**fill** (vt.)
1. ሞላ. Fill this bottle with water! ይህን ፣ ጠርሙስ ፣ ውኃ ፣ ሙላው
2. ቀለም ፣ አጠጣ. The students fill their pens before the exams. ከፈተና ፣ በፊት ፣ ተማሪዎቹ ፣ ብዕሮቻቸውን ፣ ቀለም ፣ ያጠጣሉ
3. ጻፈ. Fill your name in here! ስምህን ፣ እዚህ ፣ ላይ ፣ ጻፍ
4. ሰጠ. A druggist fills prescriptions. መድኃኒት ፣ ሻጩ ፣ በትእዛዙ ፣ መሠረት ፣ መድኃኒት ፣ ይሰጣል
5. በቃ. Can he fill the position of treasurer? ለገንዘብ ፣ ያዥነት ፣ ሊበቃ ፣ ይችላል ?

6. አሟላ. This history book fills a great need. ይህ ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የጊዜውን ፡ ፍላጎት ፡ ያሟላል

**fill** (vi.) ሞላ
The hall filled rapidly. አዳራሹ ፡ በፍጥነት ፡ ሞላ
*Her eyes filled with tears. ዓይኖቿ ፡ እንባ ፡ አቀረሩ

**be filled**
1. ሞላ. +The hall was filled only with women. አዳራሹን ፡ ሴቶች ፡ ብቻ ፡ ሞልተውት ፡ ነበር
This tooth has to be filled. ይህ ፡ ጥርስ ፡ መሞላ ት ፡ አለበት
2. ተያዘ. The position is filled. ቦታው ፡ ተይዟል
3. ተዘጋጀ. The order hasn't been filled yet. የታዘዘው ፡ እቃ ፡ ዝርዝር ፡ ገና ፡ አልተዘጋጀም

**be filled to capacity** ጢም ፡ ብሎ ፡ ሞላ
The hall was filled to capacity. አዳራሹ ፡ ጢም ፡ ብሎ ፡ ሞልቶ ፡ ነበር

**fill in**
*The assistant filled in for his sick chief at the meeting. ረዳቱ ፡ በታመመው ፡ አለቃው ፡ ምትክ ፡ በስብሰባው ፡ ላይ ፡ ተገኘ

**(be) filled in**
1. ተደፈነ. The seams of the boat must be filled in if they leak. የጀልባው ፡ መጋጠሚያ ፡ ከፈሰ ሰ ፡ መደፈን ፡ አለበት
2. ተሞላ. The ditch has been filled in. ጉድጓዱ ፡ ተሞልቷል

**fill out** ሞላ
Fill out this blank! ይህን ፡ ባዶ ፡ ቦታ ፡ ሙላ

**fill up**
1. ሞላ. He filled up the glasses. ብርጭቆቹን ፡ ሞላቸው
The theater was slowly filling up. ቲያትር ፡ ቤ ቱ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ይሞላ ፡ ነበር
2. (= intr.) ጠገበ. +The cookies filled them up. በብስኩት ፡ ጠገቡ

**fill (one) with** አሳደረ(በት)
The darkness of the room filled him with fear. የክፍሉ ፡ መጨለም ፡ ፍርሃት ፡ አሳደረበት
[See also 'capacity, disgust, repulsion, shoe']

**fill** (n.) መሙያ
The new building requires 3000 cubic yards of fill. አዲሱ ፡ ሕንጻ ፡ ሦስት ፡ ሺ ፡ ኩብ ፡ ያርዶ ች ፡ መሙያ ፡ ያስፈልገዋል

**eat (one's) fill** ሆዱን ፡ ሞላ
He ate his fill and left without saying thanks. ሆዱን ፡ ሞልቶ ፡ ሳያመሰግን ፡ ሄደ

**filling** (n.) ጥርስ ፡ ማስሞላት
How much do you pay for a filling? ጥርስህን ፡ ለማስሞላት ፡ ስንት ፡ ፈጀብህ ?

**filling station** የቤንዚን ፡ ማደያ
Where is the nearest filling station? ቅርቡ ፡ የቤንዚን ፡ ማደያ ፡ የት ፡ ነው?

**film** (v.) ፊልም ፡ አነሣ
They are filming rural life in Ethiopia. የኢትዮጵ ያን ፡ የገጠር ፡ ኑሮ ፡ የሚያሳይ ፡ ፊልም ፡ እያነ ሡ ፡ ነው

**film** (n.)
1. ፊልም. Put the film in the camera! ፎቶግራፍ ፡ ማንሻውን ፡ ፊልም ፡ ሙላበት
Did you see the latest film? በቅርቡ ፡ የወጣው ን ፡ ፊልም ፡ አይተሃል ?
2. ሰፈፍ. There is a film of oil on the water. በውኃው ፡ ላይ ፡ የዘይት ፡ ሰፈፍ ፡ አለበት

**filter** (vt.) አጣራ
We have to filter this water. ይህን ፡ ውኃ ፡ ማ ጣራት ፡ አለብን

**filter** (vi.) ተሰራጨ
The news filtered through town. ወሬው ፡ በከተ ማው ፡ ሁሉ ፡ ተሰራጨ

**filter** (n.) ማጣሪያ ፤ ማጥለያ
We need a filter for this muddy water. ለዚህ ፡ ድፍርስ ፡ ውኃ ፡ ማጣሪያ ፡ ያስፈልገናል
She clears the water by means of a filter. በማጥለያ ፡ ውኃውን ፡ ታጣራለች

**filth** ቆሻሻ
The poor dog was covered with filth. ምስኪኑ ፡ ውሻ ፡ በቆሻሻ ፡ ተበክሎ ፡ ነበር

**(be) filthy** ቆሸሸ
Your hands are filthy. Wash them at once! እጆችህ ፡ ቆሽሸዋል ፤ አሁን ፡ ታጠብ

**fin** ክንፍ
Remove the fins of the fish before you cook it! ዓሣን ፡ ከመጥበስህ ፡ በፊት ፡ ክንፎቹን ፡ ቁረጥ ና ፡ ጣል

**final**
1. የመጨረሻ. Is that your final decision? ይህ ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔህ ፡ ነው ?
2. ቁርጥ ፡ ያለ. A flat refusal was his final answer. ድርቅ ፡ ያለ ፡ እምቢታ ፡ ቁርጥ ፡ ያለ ፡ መልሱ ፡ ሆነ

**finalist** [በማጣሪያ ፡ ውድድር ፡ ገብቶ ፡ ለመጨረ ሻው ፡ ውድድር ፡ ለመቅረብ ፡ የተመረጠ]

**finality** (= adj.) የመጨረሻ
The finality of the court decision was accepted
by both parties. የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ የመጨረሻ ፡
ውሳኔ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ተቀበሉት

**finally** በመጨረሻ ፤ የኋላ ፡ ኋላ
What kind of employment did you finally get?
በመጨረሻ ፡ (የኋላ ፡ ኋላ) ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡
አገኘህ ?

**finals** የመጨረሻ ፡ ፈተና
I took my finals in algebra today. ዛሬ ፡ የአል
ጄብራ ፡ የመጨረሻ ፡ ፈተናዬን ፡ ተፈተንኩ

**finance** (v.) ወጪ ፡ ከፈለ
Municipal bonds will finance the new water-
works. የማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ቦንዶች ፡ አዲሱን ፡ የ
ውኃ ፡ ማስራጫ ፡ ወጪ ፡ ይከፍላሉ
*He financed the building with his own money.
ሕንጻውን ፡ በገዛ ፡ ገንዘቡ ፡ አሠራ

**be financed** በገንዘብ ፡ ተዳደረ
The school is privately financed. ትምህርት ፡ ቤ
ቱ ፡ በግል ፡ ገንዘብ ፡ የሚተዳደር ፡ ነው

**finance** (n.) የገንዘብ ፡ አያያዝ
He is an expert in finance. በገንዘብ ፡ አያያዝ ፡
በኩል ፡ ዐዋቂ ፡ ነው

**finances** የገንዘብ ፡ ይዞታ
The university's finances are in good shape.
የዩኒቨርሲቲው ፡ የገንዘብ ፡ ይዞታ ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡
ላይ ፡ ነው

**Finance Minister** የገንዘብ ፡ ሚኒስትር
The Finance Minister went abroad. የገንዘብ ፡
ሚኒስትሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሄዱ

**financial**
1. የገንዘብ. The financial affairs of his com-
pany are in good shape. የኩባንያው ፡ የገንዘብ ፡
ጉዳይ ፡ ጥሩ ፡ መልክ ፡ ይዟል
For financial reasons, I must say no. በገንዘብ ፡ ም
ክንያት ፡ እምቢ ፡ ማለት ፡ አለብኝ
2. የገንዘብ ፡ ነክ ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ. Addis Ababa
is the financial center of Ethiopia. አዲስ ፡ አ
በባ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የገንዘብ ፡ ነክ ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡
እምብርት ፡ ናት

**financially** በገንዘብ ፡ በኩል ፤ በገንዘብ
I'm financially dependent on him. በገንዘብ ፡ በ
ኩል ፡ የሱን ፡ እጅ ፡ እያየሁ ፡ እኖራለሁ
The government supports the national theater
financially. መንግሥቱ ፡ ብሔራዊውን ፡ ቲያትር ፡
በገንዘብ ፡ ይረዳል

**financier** የገንዘብ ፡ ሥራ ፡ ዐዋቂ
The financier formed a new bank. የገንዘብ ፡ ሥ
ራ ፡ ዐዋቂው ፡ አዲስ ፡ ባንክ ፡ አቋቋመ

**find** (found)
1. አገኘ. I found a coin in the street. መንገዱ ፡
ላይ ፡ ፍራንክ ፡ አገኘሁ
We found him to be dishonest. የማይታመን ፡ ሆ
ኖ ፡ አገኘነው
2. አመነ. Do you find that honesty pays?
ታማኝነት ፡ እንደሚጠቅም ፡ ታምናለህ ?
3. ተሰማ(ው). +He finds this music abominable.
ይህ ፡ ሙዚቃ ፡ አስከፊ ፡ ሆኖ ፡ ይሰማዋል
4. ዐወቀ. She was vexed to find the baby had
spilled the syrup. ሕፃኑ ፡ ሹሮፑን ፡ ማፍሰሱን ፡
ባወቀች ፡ ጊዜ ፡ ተናደደች

**find oneself** መሆኑን ፡ ተረዳ
When he came to, he found himself in the
hospital. ነፍሱን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ሆስፒታል ፡ ው
ስጥ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳ

**find out**
1. ዐወቀ. It is such a deep secret, I can't find
out anything about it. ጥብቅ ፡ ምስጢር ፡ ስለ
ሆነ ፡ ስለነገሩ ፡ ምንም ፡ ለማወቅ ፡ አልችልም
2. ለማወቅ ፡ ሞከረ. I will find out what is behind
it. መነሻውን ፡ ለማወቅ ፡ እሞክራለሁ
3. ደረሰ(በት). I found it out just yesterday.
የደረስኩበት ፡ ገና ፡ ትናንት ፡ ነው
4. ጠየቀ. Can you find that out for me?
ያንን ፡ ልትጠይቅልኝ ፡ ትችላለህ ?
5. አገኘ. I have a better system for finding out
information. መረጃ ፡ ለማግኘት ፡ የተሻለ ፡ ዘዴ ፡
አለኝ

**(be) found out** ታወቀበት
He tried to conceal his thefts, but was finally
found out. እርሱ ፡ ሌብነቱን ፡ ለመደበቅ ፡ ቢ
ሞክርም ፡ በመጨረሻ ፡ ታወቀበት
For fear of being found out, he fled the country.
ይታወቅብኛል ፡ ብሎ ፡ ፈርቶ ፡ ካገር ፡ ወጣ

**not find** አጣ
The child bawled because it could not find its
mother. ልጁ ፡ እናቱን ፡ ስላጣ ፡ ስቅቅ ፡ ብሎ ፡
አለቀሰ

**not find one's way** መንገድ ፡ ጠፋው
I never can find my way around here. የዚህ ፡
አካባቢ ፡ መንገድ ፡ ምንጊዜም ፡ ይጠፋኛል
[See also 'fault, guilt, hard, pleasure']

**findings** የምርመራ ፡ ውጤት
The committee reported its findings to the
governor. ደርጉ ፡ የምርመራውን ፡ ውጤት ፡ ለገ
ዢው ፡ አቀረበ

**fine** (v.) ቀጣ
The judge fined him five hundred dollars. ዳኛው ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ቀጣው

**be fined** መቀጫ ፡ ተወሰነበት ፤ ተቀጣ
He was fined for contempt of court. ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ በመጋፋቱ ፡ መቀጫ ፡ ተወሰነበት
The company was fined for adulterating canned meat. ኩባንያው ፡ እታሸገው ፡ ሥጋ ፡ ውስጥ ፡ የማይረባ ፡ ሥጋ ፡ በመቀላቀሉ ፡ ተቀጣ

**fine** (n.) መቀጫ ፤ ገንዘብ
He had to pay a fine. መቀጫ ፡ መክፈል ፡ ነበረበት
Perjury is punishable by a fine or imprisonment. በሐሰት ፡ መመስከር ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ በእስራት ፡ ያስቀጣል

**impose a fine on** ቀጣ
The judge imposed a fine of 500 dollars on the guilty man. ዳኛው ፡ ጥፋተኛውን ፡ ሰው ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ቀጣው

**fine** (adj.)
1. ደቃቅ. The sand on this beach is very fine. በዚህ ፡ ባሕር ፡ ዳርቻ ፡ ያለው ፡ አሸዋ ፡ በጣም ፡ ደቃቅ ፡ ነው
2. ቀጭን. The pen I bought has a fine point. የገዛሁት ፡ ብዕር ፡ ቀጭን ፡ ጫፍ ፡ አለው
3. ስል. Is the knife fine enough to carve well? ቢላዋው ፡ ለመፋቂያ ፡ በጣም ፡ ስል ፡ ነው ?
4. ስስ. Where did you get that fine cloth? ይህንን ፡ ስስ ፡ ጨርቅ ፡ ከየት ፡ አገኘኸው ?
5. የረቀቀ. That's too fine a distinction. ያ ፡ በጣም ፡ የረቀቀ ፡ ልዩነት ፡ ነው
Everybody praised her fine singing. የረቀቀ ፡ አዘፋፈኗን ፡ ሁሉም ፡ አደነቀ
6. ጥሩ. The weather in California is fine in July. በሐምሌ ፡ የካሊፎርኒያ ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፡ ጥሩ ፡ ነው
His son is a fine young man. ልጁ ፡ ጥሩ ፡ ወጣት ፡ ነው
This is a very fine painting. ይህ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ሥዕል ፡ ነው
7. አስደሳች. We rebelled at having to stay in on so fine a day. በእንደዚያ ፡ ያለ ፡ አስደሳች ፡ ቀን ፡ እቤት ፡ መዋሉን ፡ አልወደድነውም
8. የሚያማምር. Our town boasts many fine parks. ከተማችን ፡ ባሏት ፡ ብዙ ፡ የሚያማምሩ ፡ የመናፈሻ ፡ ስፍራዎች ፡ ትኰራለች
9. የታረመ. His fine manners show he is a gentleman. የታረመ ፡ ጠባዩ ፡ ጨዋ ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል

**fine edge** ስለት
The fine edge of the razor is protected by a piece of leather. የምላጩ ፡ ስለት ፡ በቆዳ ፡ ቁራጭ ፡ ተሸፍኗል

**one fine day** አንድ ፡ ቀን
One fine day, he popped up again. አንድ ፡ ቀን ፡ እንደገና ፡ በድንገት ፡ ብቅ ፡ አለ

**fine** (adv.)
1. በደንብ. That will suit me fine. ያ ፡ ለኔ ፡ በደንብ ፡ ይስማማኛል
2. በረቂቅ. He writes so fine, I can hardly read it. በረቂቅ ፡ ስለሚጽፍ ፡ ማንበብ ፡ ያዳግተኛል

**feel fine** ደኅና ፡ ነው
Thanks, I'm feeling fine. አመሰግናለሁ ፤ ደኅና ፡ ነኝ
[See also 'choice, print']

**fine arts** ሥነ ፡ ጥበብ
Do you prefer fine arts to sports? ከስፖርት ፡ ሥነ ፡ ጥበብን ፡ ትመርጣለህ ?

**finer** ጥቃቅን (pl.)
They dickered for hours about some of the finer points of the contract. ኮንትራቱን ፡ በሚመለከቱ ፡ ጥቃቅን ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ለብዙ ፡ ሰዓቶች ፡ ተከራከሩ

**finery** የክት ፡ ልብስና ፡ ጌጣጌጥ
She wears her finery only on Sunday. የክት ፡ ልብሷንና ፡ ጌጣጌጧን ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ ብቻ ፡ ታደርጋለች

**be dressed in (one's) best finery** ተሽቀረቀረ
The girls were dressed in their best finery. ልጃገረዶቹ ፡ ተሽቀርቅረው ፡ ነበር

**finesse**
1. ብልሃት. The shopkeeper shows finesse in dealing with customers. ባለሱቁ ፡ ደንበኞቹን ፡ በብልሃት ፡ ይይዛል
2. የረቀቀ ፡ ችሎታ. The artist shows finesse. ሠዓሊው ፡ የረቀቀ ፡ ችሎታ ፡ ያሳያል

**finest** ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ውብ
This is the finest house in Addis Ababa. ይህ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ውብ ፡ ነው

**finger** ጣት
The fingers are: thumb, index, middle finger, ring finger, and little finger. የጣቶች ፡ ስም ፡ አውራ ፡ ጣት ፤ ሌባ ፡ ጣት ፡ (ነፍጠኛ) ፤ የመኻል ፡ ጣት ፤ የቀለበት ፡ ጣትና ፡ ትንሽ ፡ ጣት ፡ ናቸው

**little finger** ትንሽ ፡ ጣት
The girl hurt her little finger. የልጅቷ ፡ ትንሽ ፡ ጣት ፡ ተጐዳ

**middle finger** የመኻል ፡ ጣት
I hurt my middle finger. የመኻል ፡ ጣቴን ፡ ጐዳሁት

**ring finger** የቀለበት ፡ ጣት
He cut his ring finger. የቀለበት ፡ ጣቱ ፡ ተቈረጠ
[See also 'burn, index finger, lift, sticky']

**fingernail** ጥፍር ፤ የጣት ፡ ጥፍር
Since my fingernails have grown, I need something to cut them with. ጥፍሬ ፡ (የጣት ፡ ጥፍሬ) ፡ ስላደገ ፡ የጥፍር ፡ መቍረጫ ፡ እፈልጋለሁ

**fingerprint** አሻራ ፤ የጣት ፡ አሻራ
His fingerprints on the window incriminate him. በመስኮቱ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አሻራ ፡ ጥፋተኛነቱን ፡ ያመለክታል
His fingerprints were visible on the glass. የጣቱ ፡ አሻራ ፡ በብርጭቆው ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**finish** (vt.)
1. ጨረሰ. Have you finished the job? ሥራውን ፡ ጨረስክ ?
When he finished speaking, the crowd applauded. ንግግሩን ፡ ሲጨርስ ፡ ሕዝቡ ፡ አጨበጨበ
The child finished a glass of milk. ልጁ ፡ አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ወተት ፡ ጨረሰ
2. ቀባ. The carpenter finished the desk in red varnish. አናጢው ፡ ጠረጴዛውን ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ቀባው

**finish** (vi.) አለቀ
The classes finish in July. ትምህርት ፡ በሐምሌ ፡ ያልቃል

**be finished, he'll be ~**
1. መጨረሻው ፡ ነው. If he gets drunk again, he'll be finished. እንደገና ፡ ከሰከረ ፡ መጨረሻው ፡ ነው
2. የሱ ፡ ነገር ፡ አከተመ ፤ የሱ ፡ ነገር ፡ አበቃ. If he does it once more, he is finished. ያንን ፡ ከደገመ ፡ የሱ ፡ ነገር ፡ አከተመ ፡ (አበቃ)

**finish off**
1. ጨረሰ. Finish off one job before you start another! ሌላ ፡ ሥራ ፡ ከመጀመርህ ፡ በፊት ፡ አንዱን ፡ ጨርስ
2. ፈጽሞ ፡ አጠፋ. This spray will finish off the bugs. ይህ ፡ መድኃኒት ፡ ትኋኖችን ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፋል
3. ገደለ. The fever nearly finished him off. ትኵሳቱ ፡ ሊገድለው ፡ ምንም ፡ አልቀረ

**finish up** ጨረሰ
Finish up before the bell rings! ደወሉ ፡ ከመደወሉ ፡ በፊት ፡ ጨርስ
The painter finished up a can of paint. ቀለም ፡ ቀቢው ፡ አንድ ፡ ቆርቆሮ ፡ ቀለም ፡ ጨረሰ

**finish with**
*I finished with that crowd last year. ከነዚያ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ የነበረኝን ፡ ግንኙነት ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ አቋረጥኩ
[See also 'halfway']

**finish** (n.)
1. መጨረሻ. The audience stayed to the finish. አድማጮቹ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ ቆዩ
2. ቅብ. Watch out! You will ruin the finish on my car. ተጠንቀቅ ፤ የመኪናዬን ፡ ቅብ ፡ ታበላሻለህ
[See also 'start']

**(be) finite** ወሰን ፡ አለው
Human understanding is finite. የሰው ፡ አእምሮ ፡ ወሰን ፡ አለው

**fiord** [በኖርዌይ ፡ አገር ፡ የሚገኘው ፡ በጣም ፡ ረጅምና ፡ ጠባብ ፡ የሆነው ፡ የባሕር ፡ ሰላጤ]

**fir** [ቅጠሉ ፡ ፈጽሞ ፡ የማይረግፍ ፡ ከዓመት ፡ ዓመት ፡ አረንጓዴ ፡ መስሎ ፡ የሚታይ ፡ የዛፍ ፡ ዓይነት]

**fire** (vt.)
1. ከሥራ ፡ አስወጣ. Why did the boss fire him? አለቃው ፡ ለምን ፡ ከሥራው ፡ አስወጣው ?
2. ቀሰቀሰ. Stories of adventures fire children's imagination. የጀብዱ ፡ ተረቶች ፡ የሕፃናትን ፡ ስሜት ፡ ይቀሰቅሳሉ

**fire** (vi.) ተኰሰ
The soldiers fired. ወታደሮቹ ፡ ተኰሱ

**be fired**
1. ተጠበሰ. Pots are fired to make them hard. ሸክላዎች ፡ እንዲጠነክሩ ፡ ይጠበሳሉ
2. ከሥራ ፡ ተወገደ ፤ ከሥራ ፡ ወጣ. On account of that, he was fired. በዚያ ፡ የተነሣ ፡ ከሥራ ፡ ተወገደ
It is beyond me how he manages to keep from being fired. ከሥራ ፡ እንዴት ፡ እንደማይወጣ ፡ ሊገባኝ ፡ አልቻለም

**get fired** ከሥራ ፡ አስወጡት
I will get fired if I am late. የዘገየሁ ፡ እንደሆነ ፡ ከሥራ ፡ ያስወጡኛል

**fire** (n.)
1. እሳት. Has the fire gone out? እሳቱ ፡ ጠፍቷል ?
2. ቃጠሎ. We had a big fire in town last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ትልቅ ፡ ቃጠሎ ፡ ነበረ

3. ተኩስ. They opened fire on the truck with rifles. በመኪናው ፡ ላይ ፡ የጠመንጃ ፡ ተኩስ ፡ ከፈቱ
4. ጥይት. Soldiers in an open field are exposed to the enemy fire. በአውላላ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ወታደሮች ፡ ለጠላት ፡ ጥይት ፡ ይጋለጣሉ
5. ስሜት. Their hearts and minds were full of patriotic fire. ልባቸውና ፡ አእምሮዋቸው ፡ በሀገር ፡ ፍቅር ፡ ስሜት ፡ ተውጦ ፡ ነበር
6. ውርጅብኝ. He resigned under the fire of criticism. ከንቀፌታ ፡ ውርጅብኝ ፡ የተነሣ ፡ ሥራውን ፡ በፈቃዱ ፡ ለቀቀ

**be on fire** ተቃጠለ
The house is on fire. ቤቱ ፡ እየተቃጠለ ፡ ነው

**catch fire** ተቀጣጠለ ፤ በእሳት ፡ ተያያዘ
The wood is so dry that it will catch fire easily. ዕንጨቱ ፡ በጣም ፡ ከመድረቁ ፡ የተነሣ ፡ በቀላሉ ፡ ይቀጣጠላል
The hay caught fire. ድርቆሹ ፡ በእሳት ፡ ተያያዘ

**light the fire** እሳት ፡ አነደደ
The room is cold; will you light the fire? ክፍሉ ፡ ይበርዳል ፤ እሳቱን ፡ ታነደው ?

**make a fire** እሳት ፡ አነደደ
If you are cold, I'll make a fire. ከበረደህ ፡ እሳት ፡ አነዳለሁ

**put on the fire** ጣደ
Put the kettle on the fire! ጀበናውን ፡ ጣደው

**put out the fire** እሳት ፡ አጠፋ
The fireman was injured putting out the fire. የእሳት ፡ አደጋ ፡ ሠራተኛው ፡ እሳቱን ፡ ሲያጠፋ ፡ ተጐዳ

**set fire to**
1. አቃጠለ. He set fire to his house. የራሱን ፡ ቤት ፡ አቃጠለው
2. እሳት ፡ ለቀቀ(በት). The children set fire to the haystack. ልጆቹ ፡ የሣሩን ፡ ክምር ፡ እሳት ፡ ለቀቁበት

**set on fire** አቃጠለ
He set the house on fire. ቤቱን ፡ አቃጠለ

**start a fire** እሳት ፡ አያያዘ
Will you start a fire in the fireplace? እምድጃው ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ ታያይዛለህ ?

**take fire** ስሜቱ ፡ ተቀሰቀሰ
Everyone who heard him speak, immediately took fire. ሲናገር ፡ ያዳመጠው ፡ ሁሉ ፡ ወዲያውኑ ፡ ስሜቱ ፡ ተቀሰቀሰ

**under fire** ተኩስ ፡ እየወረደበት
The soldiers advanced under the enemy's fire. ወታደሮቹ ፡ የጠላትን ፡ ተኩስ ፡ እየወረደባቸው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፉ

**(be) under fire** በኀይል ፡ ተነቀፈ
The school administration is under fire for its policies. የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አስተዳደር ፡ ስለ ፡ ፖሊሲው ፡ በኀይል ፡ በመነቀፍ ፡ ላይ ፡ ነው
[See also 'iron']

## firearm መሣሪያ ፤ ብረት
The troops had firearms. ወታደሮቹ ፡ መሣሪያ ፡ (ብረት) ፡ ነበራቸው

## fire brigade የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካይ ፡ ጓድ
The fire brigade puts out fires. የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካይ ፡ ጓድ ፡ ተግባሩ ፡ እሳት ፡ ማጥፋት ፡ ነው

## fire department የእሳት ፡ አደጋ ፡ መከላከያ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት
It is the fire department's responsibility to put out fires. ቃጠሎን ፡ ማጥፋት ፡ የእሳት ፡ አደጋ ፡ መከላከያ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ኀላፊነት ፡ ነው

## fire engine የእሳት ፡ አደጋ ፡ መኪና
The city bought two fire engines. ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ሁለት ፡ የእሳት ፡ አደጋ ፡ መኪናዎች ፡ ገዛ

## fire escape ከእሳት ፡ አደጋ ፡ ማምለጫ
A fire escape leads to the ground from the roof. ከእሳት ፡ አደጋ ፡ ማምለጫው ፡ ከጣራው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ቤት ፡ ይወርዳል

## fireman የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካይ
The fireman saved three lives. የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካይ ፡ የሦስት ፡ ሰዎች ፡ ሕይወት ፡ አዳነ

## fireplace ምድጃ
There is no fire in the fireplace. ምድጃው ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ የለም

## fireproof
They made the building fireproof. ሕንጻውን ፡ እሳት ፡ እንዳይበግረው ፡ አድርገው ፡ ሠሩት

## firewood ማገዶ
He broke up the boxes for firewood. ሣጥኖቹን ፡ ለማገዶ ፡ ሰባበራቸው

## fireworks ርችት
There was a fireworks display on Coronation Day. የዘውድ ፡ በዓል ፡ ዕለት ፡ ርችት ፡ ተተኰሶ ፡ ነበር

## firing (n.)
1. ተኩስ ፡ መክፈት. The soldiers were forced to the extremity of firing to scatter the mob. ወታደሮቹ ፡ የሚረብሸውን ፡ ሕዝብ ፡ ለመበተን ፡ ተኩስ ፡ መክፈት ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው
2. ከሥራ ፡ መባረር. The reason for the strike is

the firing of two laborers. ለሥራ ፡ ማቆም ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ የሁለት ፡ የቀን ፡ ሠራተኞች ፡ ከሥራ ፡ መባረር ፡ ነው

**firing** (adj.), ~ **squad** ተኳሽ ፡ ጓድ
A firing squad shot the deserter. ተኳሽ ፡ ጓድ ፡ ከሐዲውን ፡ በጥይት ፡ ገደለው

**firm** (n.) ኩባንያ ፤ የንግድ ፡ ድርጅት
What firm do you represent? የየትኛው ፡ ኩባንያ ፡ ወኪል ፡ ነህ ?
The firm went into bankruptcy. የንግዱ ፡ ድርጅት ፡ ከሰረ

**firm** (adj.)
1. ጥብቅ. The government took firm measures against the bandits. መንግሥቱ ፡ በሽፍቶቹ ፡ ላይ ፡ ጥብቅ ፡ እርምጃ ፡ ወሰደ
He is firm with his children. እርሱ ፡ በልጆቹ ፡ ላይ ፡ ጥብቅ ፡ ነው
Firm ground is needed to build the house on. ቤቱን ፡ ለመሥራት ፡ ጥብቅ ፡ መሬት ፡ ያስፈልጋል
2. የጠበቀ. They forged a firm bond of friendship between the two countries. በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ የጠበቀ ፡ ወዳጅነት ፡ መሠረቱ
3. ጽኑ. He is as firm as a rock when danger threatens. አደጋ ፡ በሚያሰጋበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ አለት ፡ ጽኑ ፡ ነው
4. የማያወላውል. We must maintain a firm attitude. በማያወላውል ፡ መንፈስ ፡ መቆየት ፡ አለብን
5. ቁርጥ ፡ ያለ. Their price is firm; it is useless to haggle. ዋጋቸው ፡ ቁርጥ ፡ ያለ ፡ ነው ። መከራከር ፡ ከንቱ ፡ ነው
His purpose is too firm for you to change easily. ዓላማው ፡ ቁርጥ ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ በቀላሉ ፡ ልትለውጠው ፡ አትችልም
6. በደንብ ፡ የተተከለ. The strong wind did not loosen the firm posts of the fence. ከባዱ ፡ ነፋስ ፡ በደንብ ፡ የተተከሉትን ፡ ያጥሩን ፡ ቋሚዎች ፡ አላነቃነቃቸውም
*I'm a firm believer in it. ነገሩን ፡ አጥብቄ ፡ አምንበታለሁ

**be firm** ጸና ፤ ጠና
The man is firm in his belief. ሰውዬው ፡ በሃይማኖቱ ፡ የጸና ፡ ነው
The baby is not very firm on its feet. ሕፃኑ ፡ ቆሞ ፡ ለመሄድ ፡ ወገቡ ፡ ገና ፡ አልጠናም

**become firm**
1. ደረቀ. Wait until the cement becomes firm before you walk on it. በላዩ ፡ ላይ ፡ ከመሄድህ ፡ በፊት ፡ ሲሚንቶ ፡ እስኪደርቅ ፡ ድረስ ፡ ቆይ
2. ጠጠረ. When you fry an egg, the white becomes firm. እንቁላል ፡ ስትጠብስ ፡ ዞፉ ፡ ይጠጥራል

**firmament** ሰማይ
The stars in the firmament were brilliant. ከዋክብት ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ብሩህ ፡ ሆነው ፡ ይታዩ ፡ ነበር

**(be) firmer** የበለጠ ፡ ጠበቅ ፡ አለ
The ground is firmer here. መሬቱ ፡ እዚህ ፡ የበለጠ ፡ ጠበቅ ፡ ይላል

**firmly**
1. በጥብቅ. The post is set firmly in the ground. ምሰሶው ፡ በጥብቅ ፡ ተተክሏል
2. በእርግጥ. I'm firmly convinced that she is innocent. ንጹሕ ፡ መሆኗን ፡ በእርግጥ ፡ አምናለሁ

**firmness** ጥብቅ ፡ መሆን
Parents' lack of firmness is the cause of much trouble today. ዛሬ ፡ የወላጆች ፡ ጥብቅ ፡ አለመሆን ፡ ብዙ ፡ ጠንቅ ፡ ያስከትላል

**first** (adj.)
1. የመጀመሪያ. It's the first house around the corner. ከመጠምዘዣው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የመጀመሪያው ፡ ቤት ፡ ነው
2. አንደኛ. He was the first in his class. ከክፍሉ ፡ አንደኛ ፡ ነበር
3. አንድ. What day is the first of June? ሰኔ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ መቼ ፡ ይውላል ?
4. ያንደኛነት. The fast runner got the first prize. ፈጣኑ ፡ ሯጭ ፡ ያንደኛነት ፡ ሽልማት ፡ አገኘ
5. ቀዳማዊ. The present Emperor is Haile Sellassie the First. ያሁኑ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ናቸው

**first** (adv.)
1. መጀመሪያ. First, let me ask you a question! መጀመሪያ ፡ አንድ ፡ ጥያቄ ፡ ልጠይቅህ
When did you first see him? መጀመሪያ ፡ ያየኸው ፡ መቼ ፡ ነው ?
2. ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ. I saw him when I first visited Italy. ጣልያንን ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ስጎበኝ ፡ አገኘሁት
*I would die first rather than give away a secret. ምስጢር ፡ ከማወጣ ፡ አስቀድሜ ፡ ብሞት ፡ ይሻለኛል

**be the first one** የሚቀድመው ፡ የለም
He's always the first one to complain. ለማማረር ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚቀድመው ፡ የለም

**first of all** መጀመሪያ ፡ ነገር
First of all, you misunderstood me. መጀመሪያ ፡ ነገር ፡ በደንብ ፡ አልተረዳኸኝም

**at first** በመጀመሪያ
I wouldn't believe it at first. በመጀመሪያ ፡ አላመንኩትም ፡ ነበር

**come in first** ቀድሞ ፡ ገባ
Which horse came in first? የትኛው ፡ ፈረስ ፡ ቀድሞ ፡ ገባ ?

**from the first** ከመጀመሪያውም
She was a nuisance from the first. ከመጀመሪያውም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበረች

**on the first** ለልደታ
I get paid on the first. ደሞዜን ፡ የማገኘው ፡ ለልደታ ፡ ነው
[See also 'hand, marriage, opening, place, sight, thing, very']

**first aid** የመጀመሪያ ፡ እርዳታ ፡ ሕክምና
I gave him first aid when he fell off his horse. ከፈረሱ ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ የመጀመሪያ ፡ እርዳታ ፡ ሕክምና ፡ አደረግሁለት

**first aid kit** የመጀመሪያ ፡ እርዳታ ፡ መድኃኒት
I keep a first aid kit in my car for use in an emergency. ለድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ እንዲሆን ፡ በማለት ፡ የመጀመሪያ ፡ እርዳታ ፡ መድኃኒት ፡ መኪናዬ ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጣለሁ

**first-born** የበኵር ፡ ልጅ ፤ አንጋፋ
He is the first-born child in that family. በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ውስጥ ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ (አንጋፋ) ፡ እሱ ፡ ነው

**first-class**
1. አንደኛ ፡ ማዕርግ. He travels first-class. የሚሄደው ፡ ባንደኛ ፡ ማዕርግ ፡ ነው
2. አንደኛ ፡ ደረጃ. The Hilton is a first-class hotel. ሂልተን ፡ አንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ሆቴል ፡ ነው

**first-hand** ከምንጩ ፡ የተገኘ
The information is first-hand. ወሬው ፡ ከምንጩ ፡ የተገኘ ፡ ነው

**first name** የመጀመሪያ ፡ ስም ፤ የመጠሪያ ፡ ስም
What is Mr. Smith's first name? ሚስተር ፡ እስሚዝ ፡ የመጀመሪያ ፡ (የመጠሪያ) ፡ ስሙ ፡ ማነው ?

**first-rate** አንደኛ ፡ ደረጃ
This is a first-rate hotel. ይህ ፡ አንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ሆቴል ፡ ነው

**fiscal** የገንዘብ ፡ አያያዝ
The fiscal policy of the country needs to be revised. የሀገሪቱ ፡ የገንዘብ ፡ አያያዝ ፡ ፖሊሲ ፡ መሻሻል ፡ አለበት

**fish** (v.) ዓሣ ፡ አጠመደ
Do you like to fish? ዓሣ ፡ ማጥመድ ፡ ትወዳለህ ?

**fish for**
1. ለመፈለግ ፡ በረበረ. He fished in his pocket for a quarter. ስሙኒ ፡ ለመፈለግ ፡ ኪሱን ፡ በረበረ
2. ጸር ፡ ጸር ፡ አለ. He is fishing for an invitation. ለመጋበዝ ፡ ጸር ፡ ጸር ፡ ይላል

**fish out** በርብሮ ፡ አወጣ
He fished a coin out of his pockets. ከኪሱ ፡ ፍራንክ ፡ በርብሮ ፡ አወጣ

**fish** (n.) ዓሣ
Do you like fish? ዓሣ ፡ ትወዳለህ ?

**fisherman** ዓሣ ፡ አጥማጅ
There are many fishermen in the village. በመንደሩ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ዓሣ ፡ አጥማጆች ፡ አሉ

**fishing** ዓሣ ፡ ማጥመድ
My father likes fishing. አባቴ ፡ ዓሣ ፡ ማጥመድ ፡ ይወዳል

**fishing line** የዓሣ ፡ ማጥመጃ ፡ ክር
Your fishing line is entangled in the weeds. የዓሣ ፡ ማጥመጃ ፡ ክርህን ፡ አረም ፡ ይዞታል

**fishy**
1. የዓሣ. The fishy smell of the store nauseates me. በሱቁ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የዓሣ ፡ ክርፋት ፡ ልቤን ፡ አጥወለወለኝ
2. (= noun) ተንኰል. There is something fishy about this proposal of his. ያቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ አንድ ፡ ተንኰል ፡ አለው

**fission** መከፋፈል
The fission of cells can be observed with a microscope. የሴል ፡ መከፋፈል ፡ በማይክሮስኮፕ ፡ ውስጥ ፡ ሊታይ ፡ ይቻላል

**fissure** ስንጥቅ
Water comes from a fissure in the rock. ውኃ ፡ ከቋጥኙ ፡ ስንጥቅ ፡ ይፈልቃል

**fist** ቡጢ ፤ ጡጫ
I hit him with my fist. በቡጢ ፡ (በጡጫ) ፡ መታሁት
*He shook his fist at me. እጁን ፡ ጨብጦ ፡ ዛተብኝ

**fit** (fitted), vt.
1. አስተካከለ. The tailor was fitting a suit for

a customer. ልብስ ፡ ሰፊው ፡ የደንበኛውን ፡ ልብስ ፡ ያስተካክል ፡ ነበር
2. አገባ(ለት). He fitted a new knob to the door. ለበሩ ፡ አዲስ ፡ እጀታ ፡ አገባለት
3. አስገባ. He fitted the picture into the frame. ሥዕሉን ፡ መስታወት ፡ ውስጥ ፡ አስገባ
4. ሆነ(ው). These shoes don't fit me. ይህ ፡ ጫማ ፡ አይሆነኝም
5. ገጠመ. Does this light bulb fit the socket? ይህ ፡ አምፑል ፡ ከመሰኪያው ፡ ይገጥማል ?
*The coat fits me perfectly. ኮቱ ፡ ልኬ ፡ ነው
*The dressmaker did not fit her dress properly. ልብስ ፡ ሰፊው ፡ ልብሷን ፡ በልኳ ፡ አልሰፋላትም

**fit** (vi.) ገጠመ
This door sticks because it doesn't fit well. ይህ ፡ በር ፡ በደንብ ፡ ስለማይገጥም ፡ ይነካሳል

**fit in** ገጠመ
My plans do not fit in with yours. ሐሳቤ ፡ ካንተ ፡ ሐሳብ ፡ ጋር ፡ አይገጥምም
*She does not fit in with that crowd. ከእነዚያ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ መዋል ፡ ቦታዋ ፡ አይደለም

**fit out** የሚያስፈልጉትን ፡ ነገሮች ፡ አዘጋጀ(ለት)
He fitted him out for a long stay in the desert. በበረሃው ፡ ውስጥ ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ለመቆየት ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ነገሮች ፡ አዘጋጀለት

**fit together** (vt.) አገጣጠመ
The carpenter fitted the bits of wood together skillfully. አናጢው ፡ በጥበቡ ፡ የዕንጨት ፡ ቁርጥራጮቹን ፡ አገጣጠመ

**fit together** (vi.) ተገጣጠመ
These parts do not fit together. እነዚህ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ አይገጣጠሙም

**be fitted**
*They cut back the stick until it could be fitted in the hole. ከቀዳዳው ፡ እንዲገባ ፡ ለማድረግ ፡ የብትሩን ፡ ጫፍ ፡ አስተካከሉት

**fit** (n.) የሚጥለው ፡ በሽታ
When he has a fit, he falls on the ground and foams at the mouth. የሚጥለው ፡ በሽታ ፡ ሲነሣበት ፡ ይወድቅና ፡ አረፋ ፡ ይደፍቃል

**have a fit** ከው ፡ አለ
She had a fit when she saw the bill. ሒሳቡን ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ከው ፡ አለች

**in a fit of**
*In a fit of anger, he hit his friend. በድንገተኛ ፡ ንዴት ፡ ጓደኛውን ፡ መታ
[See also 'coughing, depression']

**fit** (adj.)
1. ተስማሚ. We must decide on a fit time and place for the meeting. ለስብሰባው ፡ ተስማሚ ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ መወሰን ፡ አለብን
2. ተገቢ. It is not fit that you laugh when your brother is ill. ወንድምህ ፡ ታሞ ፡ ያንተ ፡ መሣቅ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**be fit for**
1. ተስማማ (with noun). What sort of work is he fit for? ለምን ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ይስማማል?
2. ቻለ (with verb). He is now well and fit for work. አሁን ፡ ተሽሎታል ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል
3. ሆነ. This permeable soil is not fit for plowing. ውኃ ፡ የሚመጥ ፡ መሬት ፡ ለእርሻ ፡ አይሆንም

**be fit to** ሆነ
This wine is not fit to drink. ይህ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ለመጠጥ ፡ አይሆንም

**keep fit** ሰውነቱን ፡ ጠበቀ
We have to keep fit to stay healthy. በጤንነት ፡ ለመቆየት ፡ ሰውነታችንን ፡ መጠበቅ ፡ አለብን

**look fit**
*He looks fit again after his illness. ታሞ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ሰውነቱ ፡ መለስ ፡ ብሏል

**see fit** ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ታየው
He did not see fit to accept my suggestion. ያቀረብኩትን ፡ ሐሳብ ፡ መቀበል ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ አልታየውም

**fitting** (n.) ፕሮባ
He went to the tailor's for a fitting. ለፕሮባ ፡ ወደ ፡ ልብስ ፡ ሰፊው ፡ ቤት ፡ ሄደ

**fitting** (adj.) ተገቢ
This is a fitting moment for prayer. ይህ ፡ ለጸሎት ፡ ተገቢ ፡ ጊዜ ፡ ነው

**five** አምስት

**five o'clock** ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት
We drink tea at five o'clock. በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሻይ ፡ እንጠጣለን

**fix**
1. ጠገነ. Can you fix the typewriter for me? የጽሕፈት ፡ መኪናውን ፡ ልትጠግንልኝ ፡ ትችላለህ ?
2. አስተካከለ. Fix your tie! ክራቫትህን ፡ አስተካክል
3. አሰናዳ. I have to fix supper now. አሁን ፡ እራት ፡ ማሰናዳት ፡ አለብኝ
4. ተከለ. He fixed his eyes on the beautiful girl. ዓይኖቹን ፡ በቆንጆዋ ፡ ልጃገረድ ፡ ላይ ፡ ተከለ
The sailor fixed a new mast on the boat.

መርከበኛው ፡ ጀልባው ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ የሸራ ፡ ምሰሶ ፡ ተከለ
5. ወሰነ. At each meeting, they fix the time of the next meeting. በእያንዳንዱ ፡ ስብሰባ ፡ የሚቀጥለውን ፡ የስብሰባ ፡ ጊዜ ፡ ይወስናሉ
He fixed the price at one dollar. ዋጋውን ፡ ባንድ ፡ ብር ፡ ወሰነ
6. አደረገ. She fixed the blame on the leader. ጥፋቱን ፡ በመሪው ፡ ላይ ፡ አደረገች
He fixed his attention on what he was doing. ሐሳቡን ፡ በሙላ ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ አደረገ

**be fixed up** ተስተካከለ
Everything is fixed up again. ሁሉም ፡ ነገር ፡ እንደገና ፡ ተስተካክሏል

**fixed** (adj.) የተወሰነ ፤ መደበኛ
He has a fixed salary. የተወሰነ ፡ ደሞዝ ፡ አለው
In addition to a fixed salary, he gets a commission. ከመደበኛ ፡ ደሞዙ ፡ ሌላ ፡ ከሚሲዮን ፡ ያገኛል

**fixing** ጥገና
My bicycle needs fixing. ቢሲክሌቴ ፡ ጥገና ፡ ያስፈልጋታል

**fixture** እቃዎች
The bathroom fixtures are made of gold. መታጠቢያው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ እቃዎች ፡ ከወርቅ ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው

**fizz** ፗ ፡ አለ
The soda fizzed when it was poured. ሶዳው ፡ ሲቀዳ ፡ ፗ ፡ አለ

**fizzle** ተንጣጣ
Wet fireworks fizzle. እርጥብ ፡ ርችት ፡ ይንጣጣል

**flabbergast** በጣም ፡ አስደነቀ
His ignorance will flabbergast you. ድንቁርናው ፡ በጣም ፡ ያስደንቅሃል

**flabby** ልፍስፍስ
He has flabby muscles. ጡንቻው ፡ ልፍስፍስ ፡ ነው

**flag** (flagged), v.
1. አነሰ. His strength was flagging. ኀይሉ ፡ እያነሰ ፡ ይሄድ ፡ ነበር
2. ተዳከመ. My horse was flagging, but I urged him on. ፈረሴ ፡ ተዳክሞ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቶሎ ፡ እንዲሄድ ፡ ኰረኰርኩት

**flag** (n.) ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፤ ባንዲራ
Flags were flying everywhere. ሰንደቅ ፡ ዓላማዎች ፡ (ባንዲራዎች) ፡ በየቦታው ፡ ይውለበለቡ ፡ ነበር
[See also 'salute']

**flagellate** ገረፈ
They flagellated the thief in public. ሌባውን ፡ ባደባባይ ፡ ገረፉት

**flagpole** የባንዲራ ፡ መስቀያ
The extremity of the flagpole is pointed. የባንዲራው ፡ መስቀያ ፡ ጫፍ ፡ ሹል ፡ ነው

**flagrant** ጉልህ
Flagrant spelling errors are unacceptable. ጉልህ ፡ የሆነ ፡ የቀለማት ፡ ስሕተት ፡ ተቀባይነት ፡ የለውም

**flagrant misconduct** አስከፊ ፡ ምግባር
His flagrant misconduct outraged the villagers. አስከፊ ፡ ምግባሩ ፡ መንደርተኞቹን ፡ አስቈጣቸው

**flagstaff** የባንዲራ ፡ መስቀያ
The flagstaff was bare. የባንዲራው ፡ መስቀያ ፡ ባዶ ፡ ነበር

**flail** መውቂያ
He broke his flail when he struck a stone. መውቂያውን ፡ ድንጊያ ፡ ሲመታበት ፡ ተሰበረ

**flair**
1. ተሰጥዎ. He has a flair for languages. የቋንቋ ፡ ተሰጥዎ ፡ አለው
2. ዘዴ. The trader has a flair for bargains. ነጋዴው ፡ በርካሽ ፡ የሚገዛበት ፡ ዘዴ ፡ አለው

**flake**
1. ቅርፍራፊ. The flakes of soap soon melt in the water. የሳሙና ፡ ቅርፍራፊ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ሲገባ ፡ ወዲያውኑ ፡ ይሟሟል
2. ቅርፊት. Flakes of paint lay on the ground. መሬቱ ፡ ላይ ፡ የቀለም ፡ ቅርፊት ፡ አለ

**flamboyant**
1. ብልጭልጭ. She wears flamboyant jewelry. ብልጭልጭ ፡ ጌጣጌጥ ፡ ታደርጋለች
2. (= noun) ድምቀት. A flamboyant sunset makes the sky look like fire. የምትጠልቀው ፡ ፀሐይ ፡ ድምቀት ፡ ሰማዩን ፡ ደም ፡ አስመስሎታል

**flame** (v.), ~ **quickly** ቦግ ፡ አለ
The match flamed quickly. ክብሪቱ ፡ ቦግ ፡ አለ

**make flame up** አንቦገቦገ
The gasoline made the fire flame up. ቤንዚኑ ፡ እሳቱን ፡ አንቦገቦገው

**flame** (n.)
1. ብርሃን. The flame of this candle is weak. የዚህ ፡ ሻማ ፡ ብርሃን ፡ ደካማ ፡ ነው
2. የእሳት ፡ ነበልባል. The flame left black marks on the wall. የእሳቱ ፡ ነበልባል ፡ ግድግዳውን ፡ አጠቈረው

3. ነበልባል. The flames consumed the wooden huts. ነበልባሉ ፡ ጎጆዎቹን ፡ አጋያቸው

**be in flames** በእሳት ፡ ተያያዘ
Soon the whole house was in flames. ወዲያው ፡ ቤቱ ፡ በሙሉ ፡ በእሳት ፡ ተያያዘ
[See also 'burst, quicken, spurt, tongue']

**flammable** በቀላሉ ፡ የሚያያዝ
Gas is flammable, so don't smoke cigarettes near it. ቤንዚን ፡ በቀላሉ ፡ የሚያያዝ ፡ ስለሆነ ፡ አጠገቡ ፡ ሲጃራ ፡ አታጭስ

**flank** vt. (= intr.) ግራና ፡ ቀኝ ፡ ተገኘ
High buildings flank the narrow alley. ትልልቅ ፡ ሕንጻዎች ፡ በጠባቡ ፡ መንገድ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ይገኛሉ

**be flanked** ከግራና ፡ ከቀኝ ፡ ታጀበ
The Emperor's car was flanked by guards. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መኪና ፡ ከግራና ፡ ከቀኝ ፡ በክብር ፡ ዘበኞች ፡ ታጅቦ ፡ ነበር

**flank** (n.)
1. ሽንጥ. The stirrup bruised the horse's flank. የፈረሱን ፡ ሽንጥ ፡ እርካብ ፡ ጉድቶታል
2. ወገን. They are attacking our army on the left flank. እነሱ ፡ ጦራችንን ፡ በግራ ፡ ወገን ፡ ያጠቃሉ

**flannel** [ለስላሳ ፡ ሙቀት ፡ ያለው ፡ ከሱፍ ፡ የተሠራ ፡ ጨርቅ]

**flap** (flapped), vt. አርገበገበ
The chicken flapped its wings. ዶሮዋ ፡ ክንፏን ፡ አርገበገበች

**flap** (vi.) ተውለበለበ
A shutter flapped outside the window. መጋረጃው ፡ ከመስኮቱ ፡ ውጭ ፡ ተውለበለበ

**flap away**
The large bird flapped away. ትልቋ ፡ ወፍ ፡ ክንፏን ፡ እያራገበች ፡ በረረች

**flap** (n.) ክዳን
The flap on my pocket is torn. የኪሴ ፡ ክዳን ፡ ተቀደደ
Glue the flap of the envelope! የእንቦልኩን ፡ ክዳን ፡ ማጣበቂያ ፡ አድርግበት

**flare** (v.) ቦግ ፡ አለ
The match flared and then went out. ክብሪቱ ፡ ቦግ ፡ ብሎ ፡ ወዲያው ፡ ጠፋ
*Anger flared in his eyes. በንዴት ፡ ዓይኑ ፡ ደም ፡ መሰለ

**flare up**
1. ቦግ ፡ አለ. The fire flared up when I poured some gasoline on it. ቤንዚን ፡ ብጨምርበት ፡ ጊዜ ፡ እሳቱ ፡ ቦግ ፡ አለ
2. ቱግ ፡ አለ. When he was accused of lying, he flared up. ውሸታም ፡ ነህ ፡ ሲባል ፡ ቱግ ፡ አለ

**flare** (n.)
1. ነበልባል. A red flare marked the spot of the accident. ቀይ ፡ ነበልባል ፡ ያደጋውን ፡ ቦታ ፡ አመለከተ
2. መብራት. They set up flares to guide the planes in landing. አውሮፕላኑ ፡ ሲያርፍ ፡ ለመምራት ፡ መብራት ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ አስቀመጡ

**flare-up** መቀስቀስ
A flare-up of violence brought police to the riot area again. የብጥብጡ ፡ መቀስቀስ ፡ ፖሊሶቹ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ሁከቱ ፡ ስፍራ ፡ እንዲሄዱ ፡ አደረገ

**flash** (vt.) አበራ
He flashed the light right in my face. መብራቱን ፡ በቀጥታ ፡ ፊቴ ፡ ላይ ፡ አበራብኝ

**flash** (vi.)
1. ብልጭ ፡ አለ. A light flashed on the dark shore. በጨለመው ፡ ጠረፍ ፡ ላይ ፡ ብርሃን ፡ ብልጭ ፡ አለ
2. ተተኰሰ. Meteors flash across the heavens every night. ተወርዋሪ ፡ ኮከቦች ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ ይተኰሳሉ
3. አበራ. Her eyes flashed with anger. ዓይኖቿ ፡ በንዴት ፡ አበሩ

**flash by** ሽው ፡ ብሎ ፡ አለፈ
A car flashed by. አንድ ፡ መኪና ፡ ሽው ፡ ብሎ ፡ አለፈ

**flash through one's mind** ብልጭ ፡ አለ(በት)
A good idea suddenly flashed through my mind. አንድ ፡ ጥሩ ፡ ሐሳብ ፡ በድንገት ፡ ብልጭ ፡ አለብኝ

**flash** (n.) ብልጭታ
Did you see the flash of lightning? የመብረቁን ፡ ብልጭታ ፡ አየህ ?

**flash of temper** ቁጣ
A flash of temper shows that he is still angry. ቁጣው ፡ አሁንም ፡ መናደዱን ፡ ያሳያል

**in a flash** ከመቅጽበት
It was all over in a flash. ከመቅጽበት ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ተፈጸመ

**flash flood** ደራሽ ፡ ውኃ
When driving in the desert, watch out for flash floods! ምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ ስትነዳ ፡ ከደራሽ ፡ ውኃ ፡ ተጠንቀቅ

**flashlight** ባትሪ
This flashlight gives strong light. ይህ ፡ ባትሪ ፡ ብዙ ፡ ብርሃን ፡ ይሰጣል

**flashy** ብልጭልጭ
He wears flashy clothes. ብልጭልጭ ፡ ልብስ ፡ ይለብሳል

**flask** ፋሽኮ
The flask was full of wine. ፋሽኮው ፡ በወይን ፡ ጠጅ ፡ ተሞልቷል

**flat** (n.) አፓርተማ
I just moved into a new flat. አሁን ፡ በቅርቡ ፡ አዲስ ፡ አፓርተማ ፡ ውስጥ ፡ ገባሁ

**have a flat** የመኪና ፡ ጎማ ፡ ተነፈሰ
On the way back, we had a flat. ስንመለስ ፡ የመኪናችን ፡ ጎማ ፡ ተነፈሰ

**hit (strike) with the flat of**
*He hit her with the flat of his hand. በቃሪያ ፡ ጥፊ ፡ መታት
*The officer struck the insubordinate soldier with the flat of the sword. መኰንኑ ፡ የማይታዘዘውን ፡ ወታደር ፡ በጎራዴ ፡ ጥፊ ፡ መታው

**flat** (adj.)
1. ለጥ ፡ ያለ. His house has a flat roof. ቤቱ ፡ ለጥ ፡ ያለ ፡ ጣሪያ ፡ አለው
2. ሜዳማ. The country is flat. አገሩ ፡ ሜዳማ ፡ ነው
3. ደልዳላ. They looked for a flat place on which to pitch their tent. ድንኳናቸውን ፡ ለመትከል ፡ ደልዳላ ፡ ቦታ ፡ ፈለጉ
4. ጠፍጣፋ. Some people still believe that the earth is flat. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ አሁንም ፡ መሬት ፡ ጠፍጣፋ ፡ ነች ፡ ብለው ፡ ያምናሉ
5. ዝርግ. A flat dish is used for serving fish. ዝርግ ፡ ሳሕን ፡ ለዓሣ ፡ ማቅረቢያ ፡ ያገለግላል
6. ደፍጣጣ. He has a flat nose. ደፍጣጣ ፡ አፍንጫ ፡ አለው
7. መደበኛ ፡ ብቻ. We paid a flat rate with no extra charges. ምንም ፡ ተጨማሪ ፡ ክፍያ ፡ ሳይሆን ፡ መደበኛውን ፡ ዋጋ ፡ ብቻ ፡ ከፈልን
8. ድርቅ ፡ ያለ. A flat refusal was his final answer. ድርቅ ፡ ያለ ፡ እምቢታ ፡ ቁርጥ ፡ ያለ ፡ መልሱ ፡ ሆነ
9. የማያንጸባርቅ. The wall is painted with flat paint. ግድግዳው ፡ የማያንጸባርቅ ፡ ቀለም ፡ ተቀብቷል

**be flat on one's back** ተኛ
He has been flat on his back for two weeks now with that cold. በጉንፋን ፡ ሕመም ፡ የተነሣ ፡ ካለፉት ፡ ሁለት ፡ ሳምንቶች ፡ ጀምሮ ፡ እንደተኛ ፡ ነው

**fall flat**
1. ተደፋ. He fell flat on his face. ባፍ ፡ ጢሙ ፡ ተደፋ
2. ተዘረረ. He fell flat on his back. በጀርባው ፡ ተዘረረ
3. ውድቅ ፡ ሆነ. His plan fell flat. እቅዱ ፡ ውድቅ ፡ ሆነ
4. ሊጠነዛ ፡ ይችላል. The best joke can fall flat if not told properly. በጣም ፡ አሥቂኝ ፡ የሆነ ፡ ወሬ ፡ ተጣጥሞ ፡ ካልተወራ ፡ ሊጠነዛ ፡ ይችላል

**get flat** ተኛ
Inflate the tire! It is getting flat. ጎማውን ፡ ንፋው ፤ ተኝቷል

**have a flat tire** ጎማ ፡ ተነፈሰ
I had a flat tire and couldn't come on time. ጎማዬ ፡ ስለተነፈሰ ፡ በጊዜው ፡ ልደርስ ፡ አልቻልኩም

**lay flat** ተዘረረ
He lay flat on the ground. መሬቱ ፡ ላይ ፡ ተዘረረ

**taste flat**
1. እህል ፡ ቅጠል ፡ አይልም. The food tastes flat. ምግቡ ፡ እህል ፡ ቅጠል ፡ አይልም
2. ውኃ ፡ ውኃ ፡ አለ. The beer tastes flat. ጠላው ፡ ውኃ ፡ ውኃ ፡ ይላል
[See also 'hammer, smash']

**flatly** በፍጹም
He flatly refused to go. በፍጹም ፡ አልሄድም ፡ አለ

**flatten**
1. ጠፈጠፈ. He flattened the iron with a hammer. ብረቱን ፡ በመዶሻ ፡ ጠፈጠፈው
2. ለሽ ፡ አደረገ. The hail has completely flattened the wheat. በረዶው ፡ ስንዴውን ፡ ለሽ ፡ አድርጎታል
3. አስተካከለ. The steamroller flattened the road surface. ዳምጠው ፡ መሬቱን ፡ አስተካከለው
4. ዘረረ. You are no match for him. He will flatten you with one blow. እኩያው ፡ አይደለህም ፤ ባንድ ፡ ምት ፡ ይዘርሃል

**flatten out** ተዘረጋጋ
The wrinkled silk will flatten out if you iron it. የተጨማደደው ፡ ሐር ፡ ሲተኮስ ፡ ይዘረጋጋል

**flatter**
1. በከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ደለለ ፤ በከንቱ ፡ አወደሰ ፤ ደለለ. He tried to flatter me. በከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ሊደልለኝ ፡ ሞከረ
He flattered his boss in the hope of getting a

promotion. እድገት ፡ ለማግኘት ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ አለቃውን ፡ በከንቱ ፡ አወደሰ
She angled for an invitation to his party by flattering him. እሱን ፡ በመደለል ፡ ወደ ፡ ግብዣ ፡ እንዲጠራት ፡ ልታግባባው ፡ ሞከረች
2. አኮራ. The high estimation in which he is held by his friends flatters him. ጓደኞቹ ፡ የሚሰጡት ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ያኮራዋል
3. በጣም ፡ አስደሰተ. Your invitation flatters me. ግብዣህ ፡ በጣም ፡ አስደስቶኛል
4. ያለመልኩ ፡ መልክ ፡ ሰጠው. This photo flatters her. ይህ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ያለመልኳ ፡ መልክ ፡ ሰጥቷታል

**flatter oneself** ራሱን ፡ አታለለ
He flatters himself he is a good judge of character. የሰውን ፡ ጠባይ ፡ አውቃለሁ ፡ እያለ ፡ ራሱን ፡ ያታልላል

**feel flattered** ተሸነገለ
She felt flattered by his remarks. እሷ ፡ በንግግሩ ፡ ተሸነገለች

**flattery**
1. ሽንገላ. I don't care for flattery from anyone. ከማንም ፡ ለሚሰነዘርብኝ ፡ ሽንገላ ፡ ግድ ፡ የለኝም
2. ድለላ. He makes use of the art of flattery. በድለላ ፡ ዘዴ ፡ ይጠቀማል
3. የከንቱ ፡ ውዳሴ. Don't let flattery turn your head! የከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ባሪያ ፡ አትሁን

**flaunt** ለይስሙላ ፡ አሳየ
She flaunts her riches before friends. በወዳጆቿ ፡ ፊት ፡ ሀብቷን ፡ ለይስሙላ ፡ ታሳያለች

**flavor** (v.) አጣፈጠ
Flavor the cake with lemon! ኬኩን ፡ በሎሚ ፡ አጣፍጠው

**flavor** (n.)
1. ጣዕም. The coffee has lost all its flavor. ቡናው ፡ ጣዕሙን ፡ አጥቷል
2. ነክነት. Stories about ships and sailors have a flavor of the sea. ስለ ፡ መርከብና ፡ መርከበኞች ፡ የሚነገሩት ፡ ታሪኮች ፡ ባሕር ፡ ነክነት ፡ አላቸው

**flavoring** ማጣፈጫ
Sugar is a common flavoring for soft drinks. ስኳር ፡ ለለስላሳ ፡ መጠጦች ፡ የተለመደ ፡ ማጣፈጫ ፡ ነው

**flaw**
1. ስንጥቅ. There is a flaw in the glass. ብርጭቆው ፡ ስንጥቅ ፡ አለበት
2. ጉድለት. There were several flaws in our plan. እቅዳችን ፡ ብዙ ፡ ጉድለት ፡ ነበረበት

**flawless** እንከን ፡ የሌለበት
His flawless English makes one think he is a native of England. እንከን ፡ የሌለበት ፡ እንግሊዝኛው ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ ያስመስለዋል

**flax** ተልባ
Flax must be steeped in water before it can be used. ተልባ ፡ ለምግብ ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ከመዋሉ ፡ በፊት ፡ መዘፍዘፍ ፡ አለበት

**flea** ቁንጫ
Fleas invaded the house. ቁንጫ ፡ ቤቱን ፡ ወርታል

**fleck**
1. ጠብታ. A fleck of sauce showed on his shirt. የወጥ ፡ ጠብታ ፡ ሸሚዙ ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ ነበር
2. ብናኝ. A fleck of dust is in my eye. የአቧራ ፡ ብናኝ ፡ ዓይኔ ፡ ውስጥ ፡ ገብቷል

**(be) flecked with** ጣል ፡ ጣል ፡ አለበት
The brown cloth is flecked with green. ቡና ፡ ዓይነት ፡ ልብሷ ፡ አረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ ብሎበታል

**fled,** see **flee**

**fledgling** (n.) የወፍ ፡ ጫጩት
The fledglings looked over the edge of the nest. የወፍ ፡ ጫጩቶች ፡ በጎጆው ፡ ጠርዝ ፡ ላይ ፡ አንገታቸውን ፡ ብቅ ፡ አድርገው ፡ ተመለከቱ

**fledgling** (adj.) ያልጠና
The fledgling democratic movement was ended by the war. ያልጠናው ፡ የዲሞክራሲ ፡ ንቅናቄ ፡ በጦርነት ፡ ከተመ

**flee** (fled) ሸሸ
The population fled to the country. ሕዝቡ ፡ ወደ ፡ ባላገር ፡ ሸሸ
You should always flee evil. ሁልጊዜ ፡ ከመጥፎ ፡ ነገር ፡ መሸሽ ፡ አለብህ

**fleece** የበግ ፡ ጸጉር
She wore a coat lined with fleece. በበግ ፡ ጸጉር ፡ የተከፈፈ ፡ ኮት ፡ ለብሳለች

**fleet** የጦር ፡ መርከቦች
The Ethiopian fleet is stationed in Massawa. የኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ ሰፈራቸው ፡ ምፅዋ ፡ ነው

**a fleet of** ብዙ
A fleet of fishing boats is off our coast. ብዙ ፡

ዓሣ ፡ ማጥመጃ ፡ ጀልባዎች ፡ በጠረፋችን ፡ አቅራቢያ ፡ አሉ

**fleeting** ብልጭ ፡ ያለ
The teacher's fleeting smile showed he thought the joke was funny. ያስተማሪው ፡ ብልጭ ፡ ያለ ፡ ፈገግታው ፡ ቀልዱ ፡ አሥቂኝ ፡ እንደመሰለው ፡ አመለከተ

**flesh**
1. ሥጋ. Tigers are fond of flesh. ነብሮች ፡ ሥጋ ፡ ይወዳሉ
The spirit is willing, but the flesh is weak. መንፈስ ፡ ብርቱ ፡ ሥጋ ፡ ግን ፡ ደካማ ፡ ነው
The flesh of the peach is white. የኮክ ፡ ሥጋ ፡ ነጭ ፡ ነው
2. ሰውነት. My flesh crawled when I saw a big snake. ትልቅ ፡ እባብ ፡ ባየሁ ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቴ ፡ ተሸመቀቀ
3. አካል. Mental patients must be treated like those who suffer from diseases of the flesh. የአእምሮ ፡ ሕመምተኞች ፡ እንደ ፡ አካል ፡ በሽተኞች ፡ መታከም ፡ አለባቸው

**flesh and blood**
He's my own flesh and blood. የሥጋዬ ፡ ቁራጭ ፡ ያጥንቴ ፡ ፍላጭ ፡ ነው
[See also 'creep']

**fleshy**
1. ደንዳና. The fleshy girl had to watch her weight. ደንዳናዋ ፡ ልጅ ፡ ክብደቷን ፡ መቈጣጠር ፡ ነበረባት
2. ያልቀጨጨ. We pick only the fleshy peaches. ያልቀጨጨውን ፡ ኮክ ፡ ብቻ ፡ እንለቅማለን

**flew**, see **fly**

**flexible**
1. ተለማጭ. The stick we need must be flexible. የምንፈልገው ፡ ዘንግ ፡ ተለማጭ ፡ መሆን ፡ አለበት
2. እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ የሚለዋወጥ. A flexible policy was adopted. እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ የሚለዋወጥ ፡ አመራር ፡ ለመከተል ፡ ተወሰነ

**flick** (v.)
1. አራገፈ. He flicked the dust from his shoes with a handkerchief. አቧራውን ፡ ከጫማዎቹ ፡ ላይ ፡ በመሐረብ ፡ አራገፈ
2. ሾጥ ፡ አደረገ. He flicked the horse with the whip. ፈረሱን ፡ ባለንጋ ፡ ሾጥ ፡ አደረገ

**flick** (n.)
*With a flick of his whip, he drove away the flies from the horse's head. ባለንጋ ፡ ዝንቦቹን ፡ ከፈረሱ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አባረረ

**give a flick** ሾጥ ፡ አደረገ
He gave the horse a flick of the whip. ፈረሱን ፡ ባለንጋ ፡ ሾጥ ፡ አደረገ

**flicker**
1. ብልጭ ፡ ድርግም ፡ አለ. The light is flickering. መብራቱ ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ ይላል
2. (= tr.) አውለበለበ. +The tongue of the snake flickered at us. እባቡ ፡ ምላሱን ፡ አውለበለበብን

**flier** አውሮፕላን ፡ ነጂ
He is a famous flier. የታወቀ ፡ አውሮፕላን ፡ ነጂ ፡ ነው

**flies**, see **fly** (n.)

**flight**
1. ደረጃ. How many more flights do we have to climb? ከሁን ፡ ወዲህ ፡ ስንት ፡ ደረጃዎች ፡ መውጣት ፡ ይኖርብናል ?
2. ፎቅ. He lives three flights up. ከዚህ ፡ ሦስተኛው ፡ ፎቅ ፡ ላይ ፡ ይኖራል
3. በረራ. All flights were canceled on account of the storm. ባውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ምክንያት ፡ በረራው ፡ ሁሉ ፡ ተሰርዞ ፡ ነበር
We watched the flight of the birds. የወፎቹን ፡ በረራ ፡ ተመለከትን
4. ሽሽት. They sought safety in flight. በሽሽት ፡ ካደጋ ፡ ለማምለጥ ፡ ፈለጉ

**downward flight** መሽቆልቆል
The downward flight of the bird was graceful. የወፊቱ ፡ መሽቆልቆል ፡ ደስ ፡ ይል ፡ ነበር

**make a flight** ሸሸ
After a warning from a neighbor, he made a precipitate flight. ጎረቤቱ ፡ ካስጠነቀቀው ፡ በኋላ ፡ በጥድፊያ ፡ ሸሸ

**put to flight** አሸሸ
We put the enemy soldiers to flight after a hard fight. ከከባድ ፡ ውጊያ ፡ በኋላ ፡ የጠላትን ፡ ወታደሮች ፡ አሸሸን

**take to flight** እግሬ ፡ አውጪኝ ፡ አለ
He took to flight when he saw the police coming. የፖሊሱን ፡ መምጣት ፡ ሲያይ ፡ እግሬ ፡ አውጪኝ ፡ አለ
[See also 'rough']

**flimsy**
1. ደቃቃ. The flimsy boat was crushed like an eggshell. ደቃቃዋ ፡ ጀልባ ፡ እንደ ፡ እንቁላል ፡ ቅርፊት ፡ ተፈረካከሰች

2. የማይመስል. This is a flimsy excuse. ይህ ፡ የማይመስል ፡ ምክንያት ፡ ነው

**flinch** ፍንክች ፡ አለ
He did not flinch when the doctor cut his arm. ሐኪሙ ፡ እጁን ፡ ሲቁርጠው ፡ ፍንክች ፡ አላለም

**fling** (flung) ወረወረ
He flung his hat in the air. ባርኔጣውን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወረወረ

**fling about** ተቊነጠነጠ
The excited horse flung about in his stall. የደነገጠው ፡ ፈረስ ፡ እጋጡ ፡ ውስጥ ፡ ተቊነጠነጠ

**fling oneself (into)** ተጠመደ
He flung himself into his work. በሥራው ፡ ተጠመደ

**fling open** በረገደ
He flung the door open. በሩን ፡ በረገደው

**fling out** በሮ ፡ ወጣ
She flung out of the room. ከክፍሉ ፡ በራ ፡ ወጣች

**flint** ባልጩት
In ancient times, they used to shave with flint. በድሮ ፡ ጊዜ ፡ በባልጩት ፡ ይላጩ ፡ ነበር

**flip** (flipped)
1. ወረወረ. He flipped a coin in the air. ሳንቲሙን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወረወረ
2. በፍጥነት ፡ ገላለጠ. The student flipped the pages of the book. ተማሪው ፡ የመጽሐፉን ፡ ገጾች ፡ በፍጥነት ፡ ገላለጠ

**flip back** ተፈናጠረ
The branch flipped back and scratched his face. ቅርንጫፉ ፡ ተፈናጥሮ ፡ ፊቱን ፡ ቧጨረው

**flip over** ገለበጠ
He flipped the book over to hide its title. አርእስቱ ፡ እንዳይታይ ፡ መጽሐፉን ፡ ገለበጠው

**flirt** (v.) ተጻራ
She flirts with every man she meets. ካገኘችው ፡ ሰው ፡ ትጻራለች

**flirt with the idea** አቅማማ
I have been flirting with the idea of going to Ethiopia for a long time. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እሄዳለሁ ፡ እያልኩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አቅማማ ፡ ነበር

**float** (v.)
1. ተንሳፈፈ. He swam for a while and then floated. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዋኝቶ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ተንሳፈፈ
A balloon floated in the air. አንድ ፡ ፊኛ ፡ አየር ፡ ላይ ፡ ተንሳፈፈ
2. ዋለለ. The silvery moon seemed to float through the sky. ብር ፡ የምትመስለው ፡ ጨረቃ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ የምትዋልል ፡ ትመስል ፡ ነበር
3. ነፈሰ. A nasty rumor about him is floating around town. እሱን ፡ የሚመለከት ፡ መጥፎ ፡ ወሬ ፡ በከተማው ፡ ይነፍሳል

**float down** በዝግታ ፡ ወረደ
She floated down the stairs. ደረጃውን ፡ በዝግታ ፡ ወረደች

**(be) floated down**
The logs were floated down the river. ግንዶቹ ፡ ወንዙ ፡ ላይ ፡ እየተንሳፈፉ ፡ እንዲወርዱ ፡ ተደረገ

**float** (n.) መንሳፈፊያ
The child was playing in a swimming pool with a float. ልጁ ፡ በመዋኛው ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ በመንሳፈፊያ ፡ ይጫወት ፡ ነበር

**flock** (v.) ጐረፈ
The children flocked into the circus. ልጆቹ ፡ ወደ ፡ ሰርከሱ ፡ ጐረፉ

**flock together** አንድ ፡ ላይ ፡ ተንጋጋ
Sheep usually flock together. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በጎች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ይንጋጋሉ

**flock** (n.)
1. መንጋ. They followed him like a flock of sheep. እንደ ፡ በግ ፡ መንጋ ፡ ተከተሉት
We saw a flock of birds flying south. የወፍ ፡ መንጋ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ሲበር ፡ አየን
2. ምእመናን. The priest and his flock attended the ceremony. ቄሱና ፡ ምእመናኑ ፡ በበዓሉ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ ተገኙ

**flog** (flogged) ገረፈ
He flogged the horse to make it pull the cart. ጋሪውን ፡ እንዲጐትት ፡ ለማድረግ ፡ ፈረሱን ፡ ገረፈው

**flood** (vt.)
1. አጥለቀለቀ. The river flooded our fields. ወንዙ ፡ ማሳችንን ፡ አጥለቀለቀው
2. ሞላ. A blaze of sunlight flooded the room. የጠራራ ፡ ፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ክፍሉን ፡ ሞላው

**flood** (vi.) ሞላ
The river floods every year. ወንዙ ፡ በያመቱ ፡ ይሞላል

**be flooded**
1. ተጥለቀለቀ. The whole street was flooded. መንገዱ ፡ በሙሉ ፡ ተጥለቅልቆ ፡ ነበር
2. (= tr.) ሞላ. +The room was flooded with light. ክፍሉን ፡ ብርሃን ፡ ሞልቶት ፡ ነበር

3. (= intr.) ጐረፈ(ለት). +We have been flooded with requests for help. የእርዳታ ፡ ጥያቄ ፡ ይጐርፍልን ፡ ነበር

**flood** (n.)

1. ጐርፍ. Many perished in the flood. በጐርፍ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አለቀ
2. የውኃ ፡ መጥለቅለቅ. A crook in the stream causes floods during heavy rains. በከባድ ፡ ዝናብ ፡ ጊዜ ፡ የወንዙ ፡ መጠምዘዝ ፡ የውኃ ፡ መጥለቅለቅን ፡ ያስከትላል
3. የውኃ ፡ ሙላት. A flood threatened the city. የውኃ ፡ ሙላት ፡ ከተማውን ፡ አስግቶታል

**Flood** የጥፋት ፡ ውኃ
Noah made an ark for the Flood. ኖኅ ፡ ለጥፋት ፡ ውኃ ፡ መርከብ ፡ ሠራ

**flood of** ቁጥር ፡ የሌለው
The candidate received a flood of letters. ተወዳዳሪው ፡ ቁጥር ፡ የሌለው ፡ ደብዳቤ ፡ ደረሰው

**flooded** (adj.) ጐርፍ ፡ ያጥለቀለቀው
The flooded fields were covered with silt. ጐርፍ ፡ ያጥለቀለቃቸው ፡ሜዳዎች ፡ ደለል ፡ ለብሰው ፡ ነበር

**flooding** (n.) ጐርፍ
The embankment protects the road from flooding. ግድብ ፡ መንገዱን ፡ ጐርፍ ፡ እንዳይወስደው ፡ ይከላከላል

**floor**

1. ወለል. Children like to sit on the floor. ሕፃናት ፡ በወለል ፡ ላይ ፡ መቀመጥ ፡ ይወዳሉ
In the Ethiopian countryside, the floor of the houses is not made of wood. በኢትዮጵያ ፡ ገጠር ፡ የቤቶች ፡ ወለል ፡ ጣውላ ፡ የለውም
They dropped their net to the floor of the ocean. መረባቸውን ፡ በውቅያኖስ ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ ዘረጉ
2. ፎቅ. Our house has three floors. ቤታችን ፡ ሦስት ፡ ፎቅ ፡ አለው

**have the floor** ተናገረ
May I have the floor? ለመናገር ፡ ይፈቀድልኝ ?

**take the floor** ተናገረ
The chairman asked the opponent of the proposal to take the floor. የእቅዱ ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነው ፡ ሰውዬ ፡ እንዲናገር ፡ ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ጠየቀው

**flop** (flopped), vt. እንዘጭ ፡ አደረገ
He flopped his books on a chair. መጽሐፎቹን ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ እንዘጭ ፡ አደረገ

**flop** (vi.) እንዘፍ ፡ አለ
She flopped into a chair. ወንበሩ ፡ ላይ ፡ እንዘፍ ፡ አለች

**flop around** ተንፈራፈረ
The fish that I caught were flopping around in the bottom of the boat. ያጠመድኳቸው ፡ ዓሣዎች ፡ ጀልባው ፡ ውስጥ ፡ ይንፈራፈሩ ፡ ነበር

**flop down** ዘፍ ፡ አለ
He flopped down on the bed and went to sleep. አልጋው ፡ ላይ ፡ ዘፍ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ እንቅልፍ ፡ ወሰደው

**flora** ዕፀዋት
A scientific group will study Ethiopia's fauna and flora. አንድ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ ጓድ ፡ የኢትዮጵያን ፡ እንስሳትና ፡ ዕፀዋት ፡ ይመረምራል

**florid** የተቀባባ
The teacher disapproved of the students' florid writing. መምህሩ ፡ የተማሪዎቹን ፡ የተቀባባ ፡ ጽሑፍ ፡ ነቀፈ
*Fever gave him a florid complexion. ትኩሳት ፡ ፊቱን ፡ ደም ፡ አስመሰለው

**florist** አበባ ፡ ሻጭ
The florist does good business on Saturday. አበባ ፡ ሻጩ ፡ ቅዳሜ ፡ ቅዳሜ ፡ ገበያ ፡ አለው

**flounce, ~ out** ተቈናጥሮ ፡ ወጣ
The girl flounced out of the room. ልጅቷ ፡ ከክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተቈናጥራ ፡ ወጣች

**flounder** (v.) ተፍጨረጨረ
He floundered in the deep mud for a while before getting out. ከማጥ ፡ ውስጥ ፡ ለመውጣት ፡ ተፍጨረጨረ

**flounder around** ቃበዘ
He floundered around trying to find the right answer. ትክክለኛውን ፡ መልስ ፡ ለማግኘት ፡ ቃበዘ

**flounder** (n.) [የዓሣ ፡ ዓይነት]

**flour** ዱቄት
I want a sack of flour. አንድ ፡ ጆንያ ፡ ዱቄት ፡ እፈልጋለሁ
[See also 'grind']

**flourish** (vt.) አውለበለበ
He flourished the handkerchief when he saw us. ሲያየን ፡ መሐረቡን ፡ አውለበለበ

**flourish** (vi.)
1. ጥሩ ፡ ሆኖ ፡ በቀለ. Oranges flourish in a warm climate. ብርቱካን ፡ በሞቃት ፡ ስፍራ ፡ ጥሩ ፡ ሆኖ ፡ ይበቅላል

2. በለጸገ. The kingdom of Aksum flourished in the fourth century. ያክሱም ፡ መንግሥት ፡ ባራተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በልጽጎ ፡ ነበር
3. ተስፋፋ. Business flourished this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ ንግድ ፡ ተስፋፍቷል

**flow** (v.)
1. ተትረፈረፈ. Wine flowed at the feast. በግብዣው ፡ ላይ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ተትረፍርፎ ፡ ነበር
2. ወረደ. Blood flows through a vein. ደም ፡ በደም ፡ ሥር ፡ ውስጥ ፡ ይወርዳል
The river flows through the desert. ወንዙ ፡ በረኸውን ፡ አቋርጦ ፡ ይወርዳል

**flow by** ጐረፈ
The crowds flowed by. ሕዝቡ ፡ ጐረፈ

**flow down** ተንዠረገገ
Her long, black hair flowed down her back. ረጅምና ፡ ጥቁር ፡ ጸጉሯ ፡ ጀርባዋ ፡ ላይ ፡ ተንዠርግጓል

**flow into**
1. ገባ. The Danube flows into the Black Sea. የዳንዩብ ፡ ወንዝ ፡ ጥቁር ፡ ባሕር ፡ ይገባል
2. ሞላ. Goods flowed into the store. ሸቀጣ ፡ ሸቀጥ ፡ መደብሩን ፡ ሞላው

**flow over its banks** ሞላ
The river flowed over its banks and flooded the surrounding area. ወንዙ ፡ ሞልቶ ፡ አካባቢውን ፡ አጥለቀለቀው

**flow** (n.)
1. መሙላትና ፡ መጉደል. They regulate the flow of water by a dam. የውኃውን ፡ መሙላትና ፡ መጉደል ፡ በግድብ ፡ ይቈጣጠሩታል
2. መውረድ. The faucet controls the flow of water. ቧምቧ ፡ መክፈቻው ፡ የውኃውን ፡ መውረድ ፡ ይቈጣጠራል
*The flow of supplies to our army has been cut. ለወታደሮቻችን ፡ የሚላክ ፡ ሥንቅና ፡ ትጥቅ ፡ ተቋርጧል

**flower** (v.) አበበ
This tree does not flower until October. ይህ ፡ ዛፍ ፡ እስከ ፡ ጥቅምት ፡ አያብብም

**flower** (n.)
1. አበባ. There are many flowers at the end of the rainy season. ክረምት ፡ ሲያበቃ ፡ ብዙ ፡ አበባዎች ፡ ይታያሉ
2. ምርጥ ፡ ምርጡ. The flower of the country's youth was killed by war. ካገሪቷ ፡ ወጣቶች ፡ ውስጥ ፡ ምርጥ ፡ ምርጡ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞቱ

**flower of life** አበባነት
He died in the flower of life. ገና ፡ በአበባነቱ ፡ ተቀጨ

**flower bed** አበባ ፡ መደብ
The dog buried a bone in the flower bed. ውሻው ፡ አበባው ፡ መደብ ፡ ውስጥ ፡ አጥንት ፡ ቀበረ

**flowery**
1. ባበባ ፡ ያሸበረቀ. The flowery meadow was pleasing to the eye. ባበባ ፡ ያሸበረቀው ፡ መስክ ፡ ለዓይን ፡ ያስደስት ፡ ነበር
2. አበባማ. He walked beneath a canopy of flowery trees. ባበባማ ፡ ዛፎች ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ተራመደ
3. ወርቃ ፡ ወርቅ. Flowery speech is preferred by Arab speakers. ዓረብኛ ፡ ተናጋሪዎች ፡ ወርቃ ፡ ወርቅ ፡ ንግግር ፡ ይመርጣሉ

**flowing** (adj.)
1. ዘርፋፋ. Nomads often wear flowing robes on account of the heat. ከሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ዘላኖች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ዘርፋፋ ፡ ልብስ ፡ ይለብሳሉ
2. የተንዠረገገ. The boys admired her flowing hair. ልጆቹ ፡ የተንዠረገገውን ፡ ጸጉሯን ፡ አደነቁ

**flowing water**
*Flowing water cools the machinery. የውኃው ፡ ሳያቋርጥ ፡ መውረድ ፡ መኪናውን ፡ ያቀዘቅዘዋል

**flu** ኢንፍሉዌንዛ
She had to go to bed because of the flu. ኢንፍሉዌንዛ ፡ ስለያዛት ፡ መተኛት ፡ ግድ ፡ ሆነባት

**fluctuate** ተለዋወጠ
Prices fluctuate. የገበያ ፡ ዋጋ ፡ ይለዋወጣል

**fluency**
*The orator had great fluency of speech. የተናጋሪው ፡ አንደበት ፡ ርቱዕ ፡ ነበር

**fluent** (= adv.) አቀላጥፎ
He speaks fluent Amharic. አማርኛ ፡ አቀላጥፎ ፡ ይናገራል

**fluent speaker**
The director is a fluent speaker. ዲሬክተሩ ፡ አንደበተ ፡ ርቱዕ ፡ ነው

**fluently** አቀላጥፎ
He has some acquaintance with Amharic, but does not speak it fluently. አማርኛ ፡ በመጠኑ ፡ ያውቃል ፡ እንጂ ፡ አቀላጥፎ ፡ አይናገረውም

**fluffy** ለስላሳ
He likes to sleep on a fluffy pillow. ለስላሳ ፡ ትራስ ፡ መንተራስ ፡ ይወዳል

**fluid** (n.) ፈሳሽ
The fluid has evaporated. ፈሳሹ ፡ ተኗል

**fluid** (adj.)
1. የቀለጠ. I watched them pour the fluid metal into a mold. የቀለጠውን ፡ ብረት ፡ ቅርጽ ፡ መስሚያው ፡ ውስጥ ፡ ሲጨምሩ ፡ ተመለከትኩ
2. የሚዋልል. The political situation in Nigeria was fluid. የናይጄርያ ፡ የፖለቲካ ፡ ሁኔታ ፡ የሚዋልል ፡ ነበር

**flung**, see **fling**

**flunk** ወደቀ
He flunked his chemistry examination. የኬሚስትሪ ፡ ፈተናውን ፡ ወደቀ

**fluorescent** ፍሎረሰንት
I don't like fluorescent lights. ፍሎረሰንት ፡ መብራት ፡ አልወድም

**flurry** (flurries) ብናኝ
Snow flurries began to whiten the fields. የበረዶ ፡ ብናኞች ፡ ሜዳውን ፡ ማንጣት ፡ ጀመሩ

**flurry of alarm** ድንጋጤ
A flurry of alarm spread through the crowd when the explosion was heard. ፈንጂው ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ድንጋጤ ፡ በሕዝቡ ፡ መኻል ፡ ተሰራጨ
*His flow of words was interrupted by a sob. ንግግሩን ፡ ሲያወርደው ፡ ሲቃ ፡ በድንገት ፡ አቋረጠው

**flush** (vt.)
1. አጠበ. The nurse flushed the wound with water. አስታማሚዋ ፡ ቁስሉን ፡ በውኃ ፡ አጠበች
2. ውኃ ፡ ለቀቀ. Don't forget to flush the toilet! ሽንት ፡ ቤት ፡ ገብተህ ፡ ስትወጣ ፡ ውኃውን ፡ መልቀቅ ፡ አትርሳ
3. አቀላ. Fever has flushed her cheeks. ትኩሳት ፡ ጉንጯን ፡ አቀላው

**flush** (vi.)
1. ፊቱ ፡ ደም ፡ መሰለ. The girl flushed when the man spoke to her. ሰውዬው ፡ ሲያነጋግራት ፡ ልጃገረዲቱ ፡ ፊቷ ፡ ደም ፡ መሰለ
2. ደሙ ፡ ፈላ. He flushed with anger. በንዴት ፡ ደሙ ፡ ፈላ

**flush into** አጥለቀለቀ
Water flushed into the room. ውኃ ፡ ክፍሉን ፡ አጥለቀለቀው

**flush** (adj.) ልክክ ፡ ብሎ ፡ የተሠራ
The door is flush with the wall. በሩ ፡ ከግድግዳው ፡ ጋር ፡ ልክክ ፡ ብሎ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**fluster** ግራ ፡ አጋባ
His constant criticism flustered her. የዘወትር ፡ ነቀፋው ፡ ግራ ፡ አጋባት

**flute** ዋሽንት
The melody of the flute is captivating. የዋሽንቱ ፡ ዜማ ፡ ይማርካል

**flutter** (vt.) አማታ
The bird was fluttering its wings in the cage. ወፏ ፡ በወፍ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሆና ፡ ክንፏን ፡ ታማታ ፡ ነበር

**flutter** (vi.)
1. ክንፉን ፡ አርገበገበ. The young birds fluttered to the ground. የወፍ ፡ ሚጪቶች ፡ ክንፋቸውን ፡ እያርገበገቡ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ወረዱ
2. ትር ፡ ትር ፡ አለ. Her heart fluttered when the car skidded. መኪናው ፡ ሲንሸራተት ፡ ልቧ ፡ ትር ፡ ትር ፡ አለ
3. ተርገበገበ. Her eyelids fluttered as she awoke. ስትነቃ ፡ ሽፋኗ ፡ ተርገበገበ
4. ተውለበለበ. Flags were fluttering in the breeze. ሰንደቅ ፡ ዓላማዎች ፡ በነፋሱ ፡ ሽውታ ፡ ውስጥ ፡ ይውለበለቡ ፡ ነበር

**flutter about** ጉድ ፡ ጉድ ፡ አለ
She fluttered about the room trying to get ready for the guests. እንግዶቹን ፡ ለመቀበል ፡ ጉድ ፡ ጉድ ፡ አለች

**flux, be in** ~ ተለዋወጠ
After a war, conditions are in flux. ከጦርነት ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ይለዋወጣል

**be in a state of flux** ጸጥታ ፡ አጣ
The country was in a state of flux after the revolution. ከሽብሩ ፡ በኋላ ፡ አገሪቱ ፡ ጸጥታ ፡ አጣች

**fly** (flew, flown), vt.
1. ነዳ. Can you fly a plane? አውሮፕላን ፡ መንዳት ፡ ትችላለህ ?
2. አውሮፕላን ፡ ነዳ. They have to study navigation before they are allowed to fly. አውሮፕላን ፡ እንዲነዱ ፡ ከመፈቀዱ ፡ በፊት ፡ አቅጣጫን ፡ የመለየት ፡ ትምህርት ፡ ማጥናት ፡ አለባቸው
3. አውለበለበ. They like to fly kites. ወላንዳ ፡ ማውለብለብ ፡ ይወዳሉ
4. በአውሮፕላን ፡ ወሰደ. They flew the merchandise to Addis Ababa. እቃውን ፡ በአውሮፕላን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ወሰዱት

**fly** (vi.)
1. በረረ. The birds are flying south. ወፎቹ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይበራሉ

We are flying to Paris tomorrow. ነገ ፡ ወደ ፡
ፓሪስ ፡ እንበራለን
2. ተሰቀለ. Our flag flies every day. ሰንደቅ ፡ ዓላ
ማችን ፡ በየቀኑ ፡ ይሰቀላል
3. ጥልቅ ፡ አለ. A moth flew into the flame of
the candle. የእሳት ፡ እራት ፡ ሻማው ፡ ነበልባል ፡
ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ አለች
4. ሮጠ. How time flies! ጊዜ ፡ እንዴት ፡ ይሮ
ጣል
*He flew to her aid. ከመቅጽበት ፡ ደረሰላት

**fly about**
1. ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ በረረ. The bats flew about
to catch insects. የሌሊት ፡ ወፎች ፡ ነፍሳት ፡ ለ
መያዝ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ በረሩ
2. በየስፍራው ፡ ተበታተነ. There are many bits
of paper flying about. ብዙ ፡ የወረቀት ፡ ቁራ
ጮች ፡ በየስፍራው ፡ ተበታትነዋል

**fly around** በአውሮፕላን ፡ ዞረ
He flew around the world in ten days. በአውሮፕ
ላን ፡ ዓለምን ፡ በዐሥር ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ዞረ

**fly in the breeze** ተውለበለበ
The flag flew in the breeze. ሰንደቅ ፡ ዓላማ
ው ፡ በነፋስ ፡ ውስጥ ፡ ተውለበለበ

**fly open** ተበረገደ
The wind blew, and the door flew open. ነፋሱ ፡
ሲነፍስ ፡ በሩ ፡ ተበረገደ

**fly overhead** በላዩ ፡ ላይ ፡ በሮ ፡ አለፈ
A squadron of planes flew overhead. አንድ ፡ እ
ስኳድሮን ፡ አውሮፕላን ፡ በላያችን ፡ ላይ ፡ በሮ ፡
አለፈ
[See also 'flurry, passion, rage, temper']

**fly** (flies), n. ዝንብ
There are many flies around here. እዚህ ፡ ገደ
ማ ፡ ብዙ ፡ ዝንቦች ፡ አሉ

**flying colors**
*The debating team came off with flying colors.
የክርክሩ ፡ ቡድን ፡ ድልን ፡ ተቀዳጀ

**fly swatter** ጭራ
The priest's fly swatter has a handle made of
horn. ቄሱ ፡ የሚይዙት ፡ ጭራ ፡ እጀታው ፡ ቀን
ድ ፡ ነው

**fly whisk** ጭራ
I need a fly whisk to chase away flies. ዝንቦቹ
ን ፡ ለማባረሪያ ፡ ጭራ ፡ ያስፈልገኛል

**foal** የፈረስ ፡ ውርንጭላ
The foal was still unsteady on its legs. የፈረሱ ፡
ውርንጭላ ፡ ገና ፡ እግሩ ፡ አልጠነከረም

**foam** (v.)
1. አረፋ ፡ ወጣ. She beat the milk until it foamed.
አረፋ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ ወተቱን ፡ ናጠችው
2. ደነፋ. He was foaming with anger. በንዴት ፡
ይደነፋ ፡ ነበር

**foam at the mouth** አረፋ ፡ ደፈቀ
When he has a fit, he falls on the ground and
foams at the mouth. የሚጥለው ፡ በሽታ ፡ ሲነ
ሣበት ፡ ይወድቅና ፡ አረፋ ፡ ይደፍቃል

**foam** (n.) አረፋ
There is more foam than beer. ከቢራው ፡ ይል
ቅ ፡ አረፋው ፡ ይበዛል

**focus** (v.)
1. በሙሉ ፡ አተኰረ. They focused their attention
on economic problems. ሐሳባቸውን ፡ በሙሉ ፡
በምጣኔ ፡ ሀብት ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ አተኰሩ
2. አሳረፈ. With a magnifying glass, he focused
the rays of the sun on a piece of paper. እርሱ ፡
ባንድ ፡ በሚያጐላ ፡ መስታወት ፡ የፀሐይን ፡ ጮ
ራ ፡ ባንድ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ አሳረፈ

**focus** (n.) [ከመስታወት ፡ ከነጠረ ፡ በኋላ ፡ የብርሃ
ን ፡ ጨረር ፡ የሚገናኝበት ፡ ቦታ]

**focus of attention**
*The speaker was the focus of attention.
ያድማጮቹ ፡ ሁሉ ፡ ሐሳብ ፡ በተናጋሪው ፡ ላ
ይ ፡ ነበር

**be out of focus** አልተስተካከለም
The camera is out of focus. ፎቶግራፍ ፡ ማንሻ
ው ፡ አልተስተካከለም

**fodder** ድርቆሽ
He gave fodder to the cows. ለላሞቹ ፡ ድርቆ
ሽ ፡ ሰጣቸው

**foe** ጠላት
He considers him his foe. እንደ ፡ ጠላቱ ፡ ያየዋል

**foetus** ሽል
The foetus grows inside the uterus. ሽል ፡ የሚያ
ድገው ፡ በማኅፀን ፡ ውስጥ ፡ ነው

**fog** ጭጋግ ፤ ጉም
A dense fog shut out the view of the mountain.
ጥቅጥቅ ፡ ያለው ፡ ጭጋግ ፡ ተራራውን ፡ ከለለው
Planes need radar to navigate through
thick fog. ጥቅጥቅ ፡ ባለው ፡ ጉም ፡ ውስጥ ፡ ለመ
ብረር ፡ እንዲችሉ ፡ አውሮፕላኖች ፡ ራዳር ፡ ያ
ስፈልጋቸዋል

**be in a fog** መንፈሱ ፡ ተሸበረ
The survivors were in a fog for days after

the catastrophe. ከደጋው ፡ የተረፉት ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ መንፈሳቸው ፡ ተሸብሮ ፡ ነበር

**foggy**

1. ጭጋግ፡የበዛበት. The foggy weather kept the airport closed. ጊዜው ፡ ጭጋግ ፡ ስለበዛበት ፡ ያውሮፕላን ፡ ጣቢያው ፡ ተዘግቶ ፡ ነበር
2. ድብዝዝ ፡ ያለ. He has foggy notions about the situation. ስለ ፡ ሁኔታው ፡ ድብዝዝ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ አለው

**be foggy** ጭጋግ ፡ በዛ
It is foggy here in winter. በክረምት ፡ እዚህ ፡ ጭጋግ ፡ ይበዛል

**foil**

1. አከሸፈ. The police foiled the students' attempt to demonstrate. ፖሊሶቹ ፡ ተማሪዎቹ ፡ ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ ለማድረግ ፡ የነበራቸውን ፡ ሐሳብ ፡ አከሸፉ
2. አጨናገፈ. The hero foiled the agent's plan. ጀግናው ፡ የሰላዩን ፡ እቅድ ፡ አጨናገፈ

**fold** (v.)

1. አጣመረ. He folded his arms. እጁን ፡ አጣመረ
2. ዐጠፈ. Shall I fold the letter? ደብዳቤውን ፡ ልጠፈው ?
3. ዐጣጠፈ. She folded the clothes and put them away. ልብሱን ፡ ዐጣጥፋ ፡ አስቀመጠች
4. ጠቀለለ. He folded the pills in a blue paper. ኪኒኖቹን ፡ በሰማያዊ ፡ ወረቀት ፡ ጠቀለለ

**fold in one's arms** ታቀፈ
She folded the child in her arms. ሕፃኑን ፡ ታቀፈችው

**fold up** (vt.) ዐጣጠፈ
He folded up the letter and put it in his pocket. ደብዳቤውን ፡ ዐጣጥፎ ፡ በኪሱ ፡ ከተተ

**fold up** (vi.)

1. መታተሙ ፡ ቆመ. The newspaper folded up last year. ካምና ፡ ጀምሮ ፡ ጋዜጣው ፡ መታተሙ ፡ ቆመ
2. ከስሮ ፡ ሥራውን ፡ አቆመ. The dress shop just folded up. የልብሱ ፡ ሱቅ ፡ በቅርቡ ፡ ከስሮ ፡ ሥራውን ፡ አቆመ

**fold** (n.) ዕጥፋት
Cut along the folds! ዕጥፋቱ ፡ ላይ ፡ ቊረጠው

**-fold** ዕጥፍ
He got a threefold return on his investment. ያወጣውን ፡ ወጪ ፡ ሦስት ፡ ዕጥፍ ፡ አድርጎ ፡ መለሰ

**folder** ማኅደር ፤ ክርታስ
The copies of the letter are in the folder. የደብዳቤው ፡ ግልባጮች ፡ ማኅደሩ ፡ (ክርታሱ) ፡ ውስጥ ፡ ናቸው

**folding chair** ታጣፊ ፡ ወምበር
He gave the new arrivals folding chairs to sit on. ላዲሶች ፡ እንግዶች ፡ ለመቀመጫ ፡ ታጣፊ ፡ ወምበር ፡ ሰጣቸው

**foliage** ቅጠል
This plant has abundant foliage. ይህ ፡ ተክል ፡ ብዙ ፡ ቅጠል ፡ አለው

**folk** ሰው
Is there more honesty among country folk than among city folk? ከከተማ ፡ ሰው ፡ ይልቅ ፡ በባላገር ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ የበለጠ ፡ ታማኝነት ፡ አለ ?

**folks** ዘመዶች ፤ ቤተሰቦች
How are your folks? ዘመዶችህ ፡ እንዴት ፡ ናቸው ?
Will your folks let you go? ቤተሰቦችህ ፡ እንድትሄድ ፡ ይፈቅዱልሃል ?

**folklore** ተረትና ፡ ምሳሌ
He is studying Ethiopian folklore. የኢትዮጵያን ፡ ተረትና ፡ ምሳሌ ፡ ያጠናል

**folk song** ባህላዊ ፡ ዘፈን
A group was singing folk songs. አንድ ፡ ጓድ ፡ ባህላዊ ፡ ዘፈኖች ፡ ይዘፍን ፡ ነበር

**folk tale** ተረት
The old man knows many folk tales. ሽማግሌው ፡ ብዙ ፡ ተረቶች ፡ ያውቃሉ

**follow**

1. ተከተለ. You can leave now, and we will follow later. አንተ ፡ አሁን ፡ ሂድ ፤ እኛ ፡ ጥቂት ፡ ቆይተን ፡ እንከተልሃለን
Follow these instructions exactly! ይህንን ፡ መምሪያ ፡ በትክክል ፡ ተከተል
Misery follows war. መከራ ፡ ጦርነትን ፡ ይከተላል
He is following in his father's footsteps. ያባቱን ፡ አርአያ ፡ ይከተላል
2. ተከታተለ. He spoke so fast that I couldn't follow him. በፍጥነት ፡ ይናገር ፡ ስለነበር ፡ ልከታተለው ፡ አልቻልኩም
3. በዓይን ፡ ተከተለ. I couldn't follow the bird's flight. ወፏ ፡ ስትበር ፡ በዓይኔ ፡ ልከተላት ፡ አልቻልኩም
4. የ - - - አክባሪ ፡ ነው. The people of Ethiopia follow ancient traditions. የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የጥንት ፡ ባህል ፡ አክባሪ ፡ ነው
5. ገባ(ው). +Do you follow my argument? ክርክሬ ፡ ገባህ ?

6. ያዘ. He expects to follow the profession of law. የጥብቅና ፡ ሙያ ፡ ለመያዝ ፡ ያስባል
*The speech follows the dinner. ከራት ፡ በኋላ ፡ ንግግር ፡ ይደረጋል

**follow (someone's) example**
I think I'll follow your example. እንዳንተ ፡ አደር ጋለሁ

**follow through on** ከፍጻሜ ፡ አደረሰ
He always follows through on his plans. እቅዱን ፡ ሁልጊዜ ፡ ከፍጻሜ ፡ ያደርሳል

**follow up** በጥንቃቄ ፡ ተከታተለ
We tried to follow up every complaint. እያንዳንዱን ፡ አቤቱታ ፡ በጥንቃቄ ፡ ለመከታተል ፡ ሞከርን

**be followed by**
*The hot weather was followed by rain. ሙቀቱ ፡ ሲያበቃ ፡ ዝናብ ፡ ጣለ

**it follows**
*From this, it follows that the contract could not be concluded. ይህ ፡ ከሆነ ፡ ዘንድ ፡ ውሉ ፡ ሊፈጸም ፡ እንደማይችል ፡ ግልጽ ፡ ነው

**it reads as follows** እንዲህ ፡ ይላል
The letter reads as follows. ደብዳቤው ፡ እንዲህ ፡ ይላል
[See also 'heel, lead, suit']

**follower** ተከታይ
He is one of his most faithful followers. እሱ ፡ እጅግ ፡ ታማኝ ፡ ከሆኑት ፡ ተከታዮቹ ፡ አንዱ ፡ ነው

**following** (n.) ተከታይ
He has a very large following. ብዙ ፡ ተከታይ ፡ አለው

**following** (adj.)
1. የሚከተሉ. I need the following items. የሚከተሉትን ፡ እቃዎች ፡ እፈልጋለሁ
2. የሚቀጥል. The following week, a show will be held in the theatre. በሚቀጥለው ፡ ሳምንት ፡ በቲያትር ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ጨዋታ ፡ ይታያል
[See also 'day, morning, nose']

**folly** (follies)
1. ጅልነት. Her folly exasperated him. ጅልነቷ ፡ በጣም ፡ አበሳጨው
2. ስሕተት. It is folly to build a factory far from the source of supply. ጥሬ ፡ እቃ ፡ ከሚገኝበት ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ፋብሪካ ፡ ማቋቋም ፡ ስሕተት ፡ ነው
3. ከንቱነት. She reasoned with me for hours about the folly of my plans. የሐሳቤን ፡ ከንቱነት ፡ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ አስረዳችኝ

**foment** አነሣሣ
Agents are fomenting rebellion in the outlying districts. አነሣሺዎች ፡ ራቅ ፡ ባሉት ፡ አውራጃዎች ፡ ውስጥ ፡ ብጥብጥ ፡ በማነሣሣት ፡ ላይ ፡ ናቸው

**fond** የፍቅር
A fond look appeared on her face. የፍቅር ፡ መልክ ፡ በፊቷ ፡ ላይ ፡ ታየ

**be (become) fond of** ወደደ
She is very fond of children. ልጆች ፡ በጣም ፡ ትወዳለች
We are fond of music. ሙዚቃ ፡ እንወዳለን

**fondest** የጓጓ(ለት)
Her fondest wish came true. በጣም ፡ የጓጓችለት ፡ ምኞቷ ፡ ተፈጸመላት

**fondle** ደባበሰ
The mother fondled the baby. እናትዮዋ ፡ ሕፃኑን ፡ ደባበሰችው

**font**
1. ጽዋ. He took some water from the font. ከጽዋው ፡ ውስጥ ፡ ጥቂት ፡ ውኃ ፡ ወሰደ
2. ምንጭ. He is a font of knowledge. የዕውቀት ፡ ምንጭ ፡ ነው

**food**
1. ምግብ. Our food got scarcer and scarcer. ምግባችን ፡ እየደር ፡ እያነሰ ፡ ሄደ
2. መብል. The food was plain, but substantial. መብሉ ፡ ተራ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ነበር

**food supplies** ቀለብ
Our food supplies are diminishing daily. ቀለባችን ፡ በየቀኑ ፡ እያለቀ ፡ ይሄዳል

**go without food** ተራበ
I had go to without food for nearly three days, I was so poor. ስለቸገረኝ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ተራብኩ

**supply food** አበላ
The father must supply food for his children. አባት ፡ ልጆቹን ፡ ማብላት ፡ አለበት
[See also 'mouthful']

**fool** (vt.) አሞኘ ፤ አታለለ
They tried to fool him. ሊያሞኙት ፡ ሞከሩ
His apparent sincerity fooled us. ታማኝ ፡ መምሰሉ ፡ አታለለን

**fool** (vi.) ተጫወተ
You will get hurt if you fool with a loaded gun. በጉረሰ ፡ ጠመንጃ ፡ ብትጫወት ፡ ልትጐዳ ፡ ትችላለህ
*I was only fooling. እንዲያው ፡ ቀልዴን ፡ ነበር

**fool around**
1. ነከከ. Don't fool around with that radio while I am gone. በሌለሁበት ፡ ራዲዮኑን ፡ አትነካካ
2. ተንቀዋለለ. This student is not serious; he just fools around. ይህ ፡ ተማሪ ፡ ትጉህ ፡ አይደለም ፡ እንዲያው ፡ ይንቀዋለላል

**fool away** በከንቱ ፡ አጠፋ
He fooled away the whole day. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ በከንቱ ፡ አጠፋ

**fool into thinking** አታለለ
He tried to fool me into thinking that he was a scholar. ምሁር ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ሊያታልለኝ ፡ ሞከረ

**fool** (n.) ቂል ፤ ጅል
He is a fool if he believes that story. ያንን ፡ ታሪክ ፡ ካመነ ፡ ቂል ፡ (ጅል) ፡ ነው
*He is nobody's fool. ማንም ፡ አያታልለውም

**feel like a fool** አፈረ
When I found out he was a Frenchman I felt like a fool for belittling his country. ፈረንሳዊ ፡ መሆኑን ፡ ካወቅሁ ፡ በኋላ ፡ አገሩን ፡ በማንኳሰሴ ፡ አፈርኩ

**make a fool of oneself** ራሱን ፡ አቀለለ
If you do that you will make a fool of yourself. እሱን ፡ ካደረግህ ፡ ራስህን ፡ ታቀልላለህ

**make a fool of someone** አሞኘ
He won't make a fool of me a second time. ሁለተኛ ፡ አያሞኘኝም

**foolhardy** አጉል
The man made a foolhardy attempt to go over Niagara Falls in a barrel. በበርሜል ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ በናያግራ ፡ ፏፏቴ ፡ ላይ ፡ ለመሄድ ፡ ሰውዬው ፡ አጉል ፡ ሙከራ ፡ አደረገ

**foolish**
1. ሞኝ. He is foolish and does what anyone tells him. ሞኝ ፡ ስለሆነ ፡ የነገሩትን ፡ ሁሉ ፡ ያደርጋል
2. የማይረባ. In the heat of the debate, many foolish things were said. ክርክሩ ፡ ተፋፍሞ ፡ ሳለ ፡ ብዙ ፡ የማይረቡ ፡ ነገሮች ፡ ተባሉ
3. የጅል. Stop that foolish chatter! ይህን ፡ የጅል ፡ ንግግርህን ፡ አቁም
4. (= noun) ጅልነት. It is foolish to court danger. አደጋን ፡ መጋፈጥ ፡ ጅልነት ፡ ነው
5. (= adv.) ከመሬት ፡ ተነሥቶ. He scoffs at her foolish fears. ከመሬት ፡ ተነሥታ ፡ ስለምትፈራ ፡ ያሾፍባታል

**be foolish** ቀለለ
Don't be foolish! አትቅለል

**make look foolish** መሳለቂያ ፡ አደረገ
When he spoke, his ignorance of the subject made him look foolish. ሲናገር ፡ ጉዳዩን ፡ አለማወቁ ፡ መሳለቂያ ፡ አደረገው

**foolproof**
*This plan is foolproof. እቅዱ ፡ እንከን ፡ የለውም

**foot** (v.), ~ **the bill** ቻለ ፤ ወጪውን ፡ ከፈለ
Who is going to foot the bill? ሒሳቡን ፡ ማን ፡ ሊችል ፡ ነው ? (or, ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ወጪውን ፡ የሚከፍል ፡ ማነው ?)

**foot** (feet), n.
1. እግር. My foot is all sore. እግሬ ፡ ቈስሏል
We had to cover the rest of the way on foot. የቀረውን ፡ መንገድ ፡ በእግራችን ፡ መሄድ ፡ ነበረብን
2. ጫማ. She's only five foot two. ቁመቷ ፡ አምስት ፡ ጫማ ፡ ከሁለት ፡ ኢንች ፡ ብቻ ፡ ነው

**at the foot of**
1. ግርጌ. The chest of drawers stands at the foot of the bed. ባለመሳቢያ ፡ ቁም ፡ ሣጥኑ ፡ አልጋው ፡ ግርጌ ፡ ነው
2. ከ - - በስተግርጌ. There was a note at the foot of the page. ከገጹ ፡ በስተግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ነበር
3. ሥር. The child crouched at the foot of the wall. ልጁ ፡ ግድግዳው ፡ ሥር ፡ ቁጢጥ ፡ ብሏል

**be on foot** በመዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ነው
A project is on foot to build a dam. አንድ ፡ ግድብ ፡ ለመሥራት ፡ እቅዱ ፡ በመዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ነው

**be on (one's) feet**
*In this kind of job he is always on his feet. ሥራው ፡ ሁልጊዜ ፡ እንዲቆም ፡ ያስገድደዋል

**be under foot**
*The child is constantly under foot. ልጁ ፡ ሁልጊዜ ፡ ከሰው ፡ እግር ፡ ሥር ፡ አይጠፋም

**put (one) back on his feet**
*A good rest will put him back on his feet. ደኅና ፡ ዕረፍት ፡ ቢያደርግ ፡ ሙሉ ፡ ጤንነቱ ፡ ይመለስለታል

**put one's foot down** ጥርሱን ፡ ነከሰ ፡ ሠራ
Discipline will not be restored unless you put your foot down. ጥርሳችሁን ፡ ነክሳችሁ ፡ ካልሠራችሁ ፡ የነበረው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አይመለስም

**rise to one's feet ተነሣ**
He rose to his feet and addressed the crowd. ተነሥቶ ፡ ለተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**set foot ገባ**
No woman may set foot in this monastery. እዚህ ፡ ገዳም ፡ ውስጥ ፡ ሴት ፡ ልትገባ ፡ አትችልም

**set foot on ረገጠ**
Never set foot on our property again! ሁለተኛ ፡ መሬታችንን ፡ እንዳትረግጥ

**stand on one's own feet ራሱን ፡ ቻለ**
He is old enough to stand on his own feet. ራሱን ፡ ለመቻል ፡ ዕድሜው ፡ ይፈቅድለታል
[See also 'cold, hard, leap, spring, stocking']

## football የእግር ፡ ኳስ
He likes to play football. የእግር ፡ ኳስ ፡ መጫወት ፡ ይወዳል

## foothold መረጋገጫ
He lost his foothold and fell. መረጋገጫውን ፡ ስቶ ፡ ወደቀ
*Assab was the Italians' first foothold on the Eritrean coast. በኤርትራ ፡ ጠረፍ ፡ ጣሊያኖች ፡ በመጀመሪያ ፡ የያዙት ፡ አሰብን ፡ ነበር

**have a foothold ሥር ፡ ሰደደ**
It is hard to break a habit after it has a foothold. ሥር ፡ ከሰደደ ፡ በኋላ ፡ ጠባይን ፡ ማስወገድ ፡ ከባድ ፡ ነው

## footing
1. መረጋገጫ. He lost his footing and fell. መረጋገጫውን ፡ ስቶ ፡ ወደቀ
2. ደረጃ. They started out on a equal footing. ሲጀምሩ ፡ በእኩልነት ፡ ደረጃ ፡ ነበሩ

**be on friendly footing ተወዳጀ**
He tries to be on friendly footing with his neighbors. ከጐረቤቶቹ ፡ ጋር ፡ ለመወዳጀት ፡ ይሞክራል

## footnote የግርጌ ፡ ማስታወሻ
This book has many explanatory footnotes. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ማብራሪያ ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻዎች ፡ አሉት

## footpath የእግር ፡ መንገድ
Only a footpath leads to my village. ወደኔ ፡ መንደር ፡ የሚወስደው ፡ አንድ ፡ የእግር ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ነው

## footprint ዱካ
I saw footprints in the mud by the side of the road. በመንገዱ ፡ ዳር ፡ ባለው ፡ ጭቃ ፡ ውስጥ ፡ ዱካ ፡ አየሁ

## footstep
1. የእግር ፡ ኮቴ. I heard footsteps outside. የእግር ፡ ኮቴ ፡ ከውጭ ፡ ሰማሁ
2. አርአያ. He is following in his father's footsteps. ያባቱን ፡ አርአያ ፡ ይከተላል

## for
1. (zero). He walked for a mile. አንድ ፡ ማይል ፡ በእግሩ ፡ ተጓዘ
2. ለ. He has to work for a living. ለኑሮው ፡ መሥራት ፡ አለበት
It is quite warm for January. ለጥር ፡ ወር ፡ ይህ ፡ በጣም ፡ ሞቃት ፡ ነው
Aspirin is good for headaches. ለራስ ፡ ምታት ፡ አስፕሪን ፡ ጥሩ ፡ ነው
What do you use for firewood? ለማገዶ ፡ ምን ፡ ታነዳለህ ?
There is not a house to be seen for miles and miles. ለብዙ ፡ ማይል ፡ ምንም ፡ የሚታይ ፡ ቤት ፡ የለም
I have not heard from him for a long time. ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሱን ፡ ወሬ ፡ አልሰማሁም
He is tall for his age. ለዚህ ፡ ዕድሜው ፡ ረጅም ፡ ነው
3. በ. He danced for joy when he got his check. ቼኩን ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ በደስታ ፡ ጨፈረ
These oranges are eight for a dollar. እነዚህ ፡ ብርቱካኖች ፡ በብር ፡ ስምንት ፡ ይገዛሉ
4. ከ - - - ጀምሮ. The treaty has been defunct for the last three years. ካለፈው ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ውሉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አልዋለም
5. ስለ. You may take my word for it. ስለሱ ፡ በኔ ፡ ይሁንብህ
6. ስለርሱ ፡ ክብር. A party was given for him. ስለርሱ ፡ ክብር ፡ ፓርቲ ፡ ተደረገ
7. ለብዙ. His decision agonized him for weeks. ያደረገው ፡ ውሳኔ ፡ ለብዙ ፡ ሳምንቶች ፡ አስጨነቀው
8. ስለ + (verb). He was punished for stealing. ስለሰረቀ ፡ ተቀጣ
9. ወደ - - - የሚሄድ. The train for Djibouti leaves in five minutes. ወደ ፡ ጂቡቲ ፡ የሚሄደው ፡ ባቡር ፡ ባምስት ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ይነሣል
10. ለ - - - ብሎ. He married her for love. ለፍቅር ፡ ብሎ ፡ አገባት
11. በ - - - ምክንያት. He was sent to prison for stealing. በስርቆት ፡ ምክንያት ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ገባ
12. ደጋፊ. There were 20 votes for, 60 against. በምርጫው ፡ ሀያ ፡ ደጋፊዎች ፡ ሥድሳ ፡ ተቃዋሚዎች ፡ ነበሩ

*It is warm for April. በሚያዚያ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሙቀት ፡ ያልተለመደ ፡ ነው

*For an American, he speaks Amharic well. አሜሪካዊ ፡ ቢሆንም ፡ አማርኛ ፡ ጥሩ ፡ ይናገራል

*They left him at the battlefield for dead. ሞቷል ፡ ብለው ፡ ከጦር ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ትተውት ፡ ሄዱ

**for all**

*For all his wealth, he is not happy. ያ ፡ ሁሉ ፡ ሀብት ፡ እያለው ፡ ደስተኛ ፡ አይደለም

**be all for** ደገፈ

I am all for an early start. ቀደም ፡ ብሎ ፡ መነሣቱን ፡ እደግፋለሁ

**be for** ደጋፊ ፡ ነው ፤ ደገፈ

Are you for or against the proposal? ለቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ደጋፊ ፡ ነህ ፡ ተቃዋሚ ?

I am for a change in the administration. ባስተዳደሩ ፡ ውስጥ ፡ ለውጥ ፡ ማድረግን ፡ እደግፋለሁ

[See also 'as, know, what']

**forage** ምግብ ፡ ፍለጋ ፡ በረበረ

The soldiers forage in our village. ወታደሮቹ ፡ ምግብ ፡ ፍለጋ ፡ መንደራችንን ፡ ይበረብራሉ

**foray, make ~** ወረረ

The soldiers made forays on the villages and took away cattle. ወታደሮቹ ፡ መንደሮቹን ፡ ወረው ፡ የቀንድ ፡ ከብቶችን ፡ ይዘው ፡ ሄዱ

**forbade, see forbid**

**forbear** (forebore)

1. ተወ. He forebore to press his claim. ይገባኛል ፡ ማለቱን ፡ ተወ

2. አሳልፎ ፡ ሰጠ. He forbore his claim. መብቱን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ

*I must ask you to forbear a while longer. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ታገሥ

*The boy forebore to hit back because the other boy was smaller. ሌላው ፡ ልጅ ፡ ትንሽ ፡ ስለነበረ ፡ ልጁ ፡ መልሶ ፡ ሳይመታው ፡ ቀረ

**forbid** (forbade) ከለከለ

He forbade his daughter to marry me. ልጁ ፡ እንዳታገባኝ ፡ ከለከላት

**God forbid!**

*God forbid that we have an earthquake! እግዚአብሔር ፡ ከመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ይሰውረን

**forbidden** ክልክል

Smoking is forbidden in the library. በቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ማጨስ ፡ ክልክል ፡ ነው

**(be) forbidding** አስፈራራ

Today's clouds are forbidding. የዛሬው ፡ ደመና ፡ ያስፈራራል

**forbore, see forbear**

**force** (v.)

1. አስገደደ. You cannot force me to eat the fish. ዓሣውን ፡ እንድበላ ፡ ልታስገድደኝ ፡ አትችልም

2. ሰብሮ ፡ ገባ. He forced the door. መዝጊያውን ፡ ሰብሮ ፡ ገባ

3. አስገባ. The doctor forced air into his lungs. ሐኪሙ ፡ ሳንባው ፡ ውስጥ ፡ አየር ፡ አስገባ

**force one's way through** ተጋፍቶ ፡ አለፈ

He forced his way through the crowd. በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መኻል ፡ ተጋፍቶ ፡ አለፈ

**force a smile** ሳይወድ ፡ ፈገግ ፡ አለ

Ruth forced a smile through her tears. ሩት ፡ ስታለቅስ ፡ ሳትወድ ፡ ፈገግ ፡ አለች

**be forced**

1. ግድ ፡ ሆነ(በት). The soldiers were forced to the extremity of firing to scatter the mob. ወታደሮቹ ፡ የሚረብሸውን ፡ ሕዝብ ፡ ለመበተን ፡ ተኵስ ፡ መክፈት ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው

2. በጉልበት ፡ ተከፈተ. The door has been forced. በሩ ፡ በጉልበት ፡ ተከፈተ

**be forced upon one**

*They said that the war had been forced upon them. ጠላት ፡ ገፍቶ ፡ ስለመጣ ፡ መዋጋት ፡ ግድ ፡ ሆነብን ፡ አሉ

*The food was forced upon him. ምግቡን ፡ በግድ ፡ አበሉት

[See also 'hand, passage']

**force** (n.)

1. ኀይል. We had to use force to get the children to leave the room. ልጆችን ፡ ከክፍል ፡ ውስጥ ፡ ለማስወጣት ፡ በኀይል ፡ መጠቀም ፡ ነበረብን

The enemy attacked in great force. ጠላት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ኀይል ፡ አጠቃ

The storm has not reached its full force yet. ዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ገና ፡ ከሙሉ ፡ ኀይሉ ፡ አልደረሰም

Force won't get you anywhere. ኀይል ፡ ብቻውን ፡ አያዋጣህም

2. ጕልበት. He used all his force in opening the window. ባለ ፡ ጕልበቱ ፡ መስኮቱን ፡ ከፈተ

*They felt the force of his argument. ኀይለኛ ፡ ክርክሩ ፡ ተሰማቸው

**be in force** ጸና

Is that law still in force? ሕጉ ፡ አሁንም ፡ እንደጸና ፡ ነው ?

**by force of will** በመንፈስ ፡ ብርታት
He overcame the desire to smoke by force of will. የማጨስን ፡ ፍላጎት ፡ በመንፈሱ ፡ ብርታት ፡ አሸነፈ

**from force of habit** ከልማድ ፡ የተነሣ
Though he has given up smoking, he still reaches for a cigarette from force of habit. ሲጃራ ፡ ማጤስ ፡ ቢያቆምም ፡ ከልማድ ፡ የተነሣ ፡ አሁንም ፡ ሲጃራ ፡ ሲያይ ፡ እጁን ፡ ይዘረጋል

**in full force** ያለ ፡ የሌለው
The police came out in full force. ያለ ፡ የሌለው ፡ ፖሊስ ፡ መጣ
[See also 'join, spend, vital']

**forced** (adj.)
1. ከአንገት ፡ በላይ ፡ የሆነ. He gave a forced smile. ከአንገት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ፈገግታ ፡ አሳየ
2. (= adv.) በድንገት. The airplane made a forced landing. አውሮፕላኑ ፡ በድንገት ፡ አረፈ
*The road was built by means of forced labor. መንገዱ ፡ የተሠራው ፡ ሠራተኞችን ፡ በማስገደድ ፡ ነበር

**forceful**
1. ጠንካራ. He is a very forceful person. በጣም ፡ ጠንካራ ፡ ሰው ፡ ነው
2. ኀይለኛ. The director gave a forceful speech. ሥራ ፡ መሪው ፡ ኀይለኛ ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**forceps, pair of ~** ጉጠት
The nurse handed the doctor a pair of forceps. አስታማሚዋ ፡ ለሐኪሙ ፡ ጉጠት ፡ አቀበለችው

**forcible**
1. የኀይል. The police took forcible measures to restore order. ፖሊስ ፡ ሕግን ፡ ለማስከበር ፡ የኀይል ፡ እርምጃ ፡ ወሰደ
2. (= adv.) በጉልበት. The police made a forcible entry into the room. ፖሊሶቹ ፡ በጉልበት ፡ እክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ገቡ

**ford** መልካ
If the river is full we will cross at the ford. ወንዙ ፡ ቢሞላም ፡ በመልካው ፡ እንሻገራለን

**fore** ፊተኛ
The second class passengers are not allowed on the fore part of the ship. የሁለተኛ ፡ ማዕረግ ፡ ተሳፋሪዎች ፡ በመርከቡ ፡ በፊተኛው ፡ ክፍል ፡ እንዲቀመጡ ፡ አይፈቀድላቸውም

**come to the fore** ቀዳሚነት ፡ ያዘ
Economic problems have come to the fore recently. የሀብት ፡ ምጣኔ ፡ ችግር ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ቀዳሚነትን ፡ ይዟል

**forearm** ክንድ
An ancient unit of measure was the forearm. ጥንት ፡ ክንድ ፡ መለኪያ ፡ ነበር

**forebears** አያት ፡ ቅድመ ፡ አያቶች
His forebears came to America in the 17th century. አያት ፡ ቅድመ ፡ አያቶቹ ፡ በዐሥራ ፡ ሰባተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ መጡ

**forebode** መምጣት ፡ አመለከተ
The black clouds forebode a storm. የጨለመው ፡ ደመና ፡ ኀይለኛ ፡ ዝናም ፡ መምጣቱን ፡ ያመለክታል

**foreboding**
*He has a foreboding of disaster. ክፉ ፡ ይመጣብኛል ፡ ብሎ ፡ ያስባል

**forecast** (v.) አስቀድሞ ፡ አስታወቀ
They forecast cooler weather. አየሩ ፡ የሚቀዘቅዝ ፡ መሆኑን ፡ አስቀድመው ፡ ያስታውቃሉ

**forecast** (n.) ትንቢት
His forecast turned out to be wrong. ትንቢቱ ፡ ሳይዝለት ፡ ቀረ

**foreclose** አቆመ
After an hour, the chairman foreclosed discussion on the matter. በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ የሚደረገውን ፡ ውይይት ፡ ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ከአንድ ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ አቆመው

**forefathers** አባቶች
Our forefathers came here to protect their freedom. አባቶቻችን ፡ ነጻነታቸውን ፡ ለመከላከል ፡ ሲሉ ፡ እዚህ ፡ መጡ

**forefinger** ሌባ ፡ ጣት
He pointed at me with his forefinger. ሌባ ፡ ጣቱን ፡ ቀሰረብኝ

**forefoot** የፊት ፡ እግር
The cow injured her forefoot. የላሟ ፡ የፊት ፡ እግር ፡ ተጐድቷል

**forefront** ግንባር
The forefront of the struggle is where the most danger lies. የትግሉ ፡ ግንባር ፡ አደጋ ፡ ይበዛበታል

**be in the forefront** ግንባር ፡ ቀደም ፡ ነው
He is in the forefront of the civil rights movement. ስለ ፡ ሰው ፡ ልጆች ፡ መብት ፡ በሚደረገው ፡ ንቅናቄ ፡ እሱ ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ነው

**foregoing** ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለ
The foregoing quotation is from the Bible.

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ጥቅስ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተወሰደ ፡ ነው

**foreground** (= adv.) ከፊት ፡ ለፊት
The foreground of the picture shows a procession. ሥዕሉ ፡ ከፊት ፡ ለፊት ፡ ሰልፍ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው
*He manages to keep himself in the foreground. እንደምንም ፡ ብሎ ፡ እራሱን ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ይሆንለታል

**forehead** ግንባር
He was hit with a stone on the forehead. ግንባሩ ፡ ላይ ፡ በድንጋይ ፡ ተመታ

**foreign**
1. የውጭ ፡ አገር. Do you speak any foreign language? የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ትናገራለህ ?
2. የባዕድ ፡ አገር. Foreign habits don't suit us. የባዕድ ፡ አገር ፡ ልማድ ፡ ለኛ ፡ አይስማማም
3. የውጭ. He visited many foreign countries in his youth. በልጅነቱ ፡ ብዙ ፡ የውጭ ፡ አገሮችን ፡ ጐበኘ
4. የባዕድ. The admixture of foreign words makes the language hard to understand. የባዕድ ፡ ቃላት ፡ መቀላቀሉ ፡ ቋንቋውን ፡ ለመረዳት ፡ ያስቸግራል
5. እንግዳ ፡ ነገር. Stealing is completely foreign to his nature. ስርቆት ፡ ለሱ ፡ ፍጹም ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ነው

**foreign body** ጉድፍ
There is a foreign body in his eye. በዓይኑ ፡ ውስጥ ፡ ጉድፍ ፡ አለ
[See also 'part']

**foreign affairs** የውጭ ፡ ጉዳይ
The President is in charge of foreign affairs. የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ኀላፊነቱን ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ይዘዋል

**Ministry of Foreign Affairs** የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር
The Ministry of Foreign Affairs is located in a new building. የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ አዲስ ፡ ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ ገብቷል

**foreign-born** የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ
A foreign-born citizen is ineligible for the presidency. የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ለመሆን ፡ መብት ፡ የለውም

**foreigner**
1. የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው. Before the war many foreigners came here. ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እዚህ ፡ መጥተዋል
2. የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ. Foreigners are ineligible to own land. የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ መሬት ፡ እንዲገዙ ፡ አይፈቀድላቸውም

**foreign minister** የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር
The foreign minister left for Paris. የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ሄዱ

**foreign office** የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር
He works in the foreign office. ውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ይሠራል

**foreleg** የፊት ፡ እግር
The dog put its dirty forelegs on my coat. ውሻው ፡ በቆሸሹ ፡ የፊት ፡ እግሮቹ ፡ ኮቴን ፡ ረገጠብኝ

**foreman** (foremen) የሠራተኞች ፡ አለቃ
The assignment of the various jobs in the factory is taken care of by the foreman. በፋብሪካው ፡ ውስጥ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራን ፡ የሚደለድል ፡ የሠራተኞቹ ፡ አለቃ ፡ ነው

**foremost** የላቀ
He was the foremost painter of his time. በዘመኑ ፡ የላቀ ፡ ሠዓሊ ፡ ነበር

**forenoon** ከሰዓት ፡ በፊት
This flower blooms in the forenoon. ይህ ፡ አበባ ፡ ከሰዓት ፡ በፊት ፡ ይፈነዳል

**forerunner, be a ~**
1. መምጣት ፡ አመለከተ. Black clouds are forerunners of a storm. ጥቁር ፡ ደመና ፡ ኀይለኛ ፡ ዝናም ፡ መምጣቱን ፡ ያመለክታል
2. ቀደምትነት ፡ አለው. The chariot was a forerunner of the automobile. ጋሪ ፡ ከአውቶሞቢል ፡ ቀደምትነት ፡ አለው

**foresee** (foresaw) ቀደም ፡ ብሎ ፡ ተገነዘበ
Far-sighted observers foresaw those difficulties long ago. አርቆ ፡ አስተዋይ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ችግሩን ፡ ከረጅም ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ተገንዝበውታል

**foresight** አርቆ ፡ አስተዋይነት
He showed great foresight when he got that insurance. ያንን ፡ ዋስትና ፡ በመግባቱ ፡ አርቆ ፡ አስተዋይነቱን ፡ አሳየ

**foreskin** የብልት ፡ ሸለፈት
In circumcision, only the foreskin is removed. በግርዘት ፡ ጊዜ ፡ የብልቱ ፡ ሸለፈት ፡ ብቻ ፡ ይቈረጣል

**forest**
1. ደን. This forest stretches for miles and

miles. ይህ ፡ ደን ፡ ለብዙ ፡ ማይል ፡ ይንጣለላል
2. ጫካ. The children gathered wood in the forest. ልጆቹ ፡ ከጫካ ፡ ዕንጨት ፡ ለቀሙ
[See also 'virgin']

**forestall** ከ --- አዳነ
His quick stop forestalled an accident. መኪናውን ፡ ቶሎ ፡ ማቆሙ ፡ ከአደጋ ፡ አዳነው
*He tried to forestall any questions about his policy. በቅድሚያ ፡ መልስ ፡ በማዘጋጀት ፡ ስለ ፡ አመራሩ ፡ የሚቀርቡትን ፡ ጥያቄዎች ፡ ለማከሽፍ ፡ ሞከረ

**foretell** (foretold) ተነበየ
The seer foretold a long war. ትንቢተኛው ፡ የረጅም ፡ ጊዜ ፡ ጦርነት ፡ እንደሚነሣ ፡ ተነበየ

**forever**
1. ሁልጊዜ. He is forever telling that same story. ሁልጊዜ ፡ ያንኑ ፡ ወሬ ፡ እየደጋገመ ፡ ይናገራል
2. ዕድሜውን ፡ሙሉ. I am afraid I will be stuck in this place forever. ዕድሜዬን ፡ ሙሉ ፡ እዚህ ፡ ቦታ ፡ ተወትፌ ፡ እንዳልቀር ፡ እፈራለሁ
3. ለዘለዓለም. The pyramids were built to last forever. ፒራሚዶች ፡ የተሠሩት ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዲኖሩ ፡ ነው

**forewarn** አስቀድሞ ፡ አስጠነቀቀ
I forewarned him of the danger on the road. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ስለሚያጋጥመው ፡ አደጋ ፡ አስቀድሜ ፡ አስጠንቅቄዋለሁ

**foreword** መቅድም
In the foreword of the book, he praised his teacher. በመጽሐፉ ፡ መቅድም ፡ ላይ ፡ አስተማሪውን ፡ አሞገሰ

**forfeit** አጣ
He forfeited the good will of his fellow students by reporting their activities. የትምህርት ፡ ጓደኞቹ ፡ የሚሠሩትን ፡ በማሳበቅ ፡ ፍቅራቸውን ፡ አጣ

**forfeit the game** እንደተሸናፊ ፡ ተቈጠረ
The team failed to show up and forfeited the game. ቡድኑ ፡ ሳይመጣ ፡ ስለቀረ ፡ እንደተሸናፊ ፡ ተቈጠረ

**forgave,** see **forgive**

**forge** (v.)
1. አስመስሎ ፡ ፈረመ. He forged my signature to his petition. ማመልከቻው ፡ ላይ ፡ የኔን ፡ ፊርማ ፡ አስመስሎ ፡ ፈረመ
2. መሠረተ. They forged a firm bond of friendship between the two countries. በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ የጠበቀ ፡ ወዳጅነት ፡ መሠረቱ
3. ቀጥቅጦ ፡ ሠራ. He forged a chain from several pieces of iron. ብዙ ፡ የተቈራረጡ ፡ ብረቶችን ፡ ቀጥቅጦ ፡ ሰንሰለት ፡ ሠራ

**forge ahead**
*One runner forged ahead of others and won the race. ከሯጮቹ ፡ አንዱ ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ ሌሎችን ፡ ቀድሟቸው ፡ አሸነፈ

**forge** (n.) ብረት ፡ ማቅለጫ
The blacksmith used a forge to heat iron. ብረት ፡ ቀጥቃጭ ፡ ብረቱን ፡ በብረት ፡ ማቅለጫ ፡ አጋለው

**forgery** በማስመሰል ፡ የተቀዳ
The signature on the check was a forgery. በቼኩ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ፊርማ ፡ በማስመሰል ፡ የተቀዳ ፡ ነበር

**forget** (forgot) ረሳ ፤ ዘነጋ
She has forgotten all her lessons. የተማረችውን ፡ ሁሉ ፡ ረስታለች
When he is playing football, he forgets his studies. ኳስ ፡ በሚጫወትበት ፡ ጊዜ ፡ ትምህርቱን ፡ ይዘነጋል

**forgetful** ዝንጉ
He is very forgetful of things. በጣም ፡ ዝንጉ ፡ ነው

**forgetfulness** ዝንጉነት
Forgetfulness is one of his faults. ከጉድለቶቹ ፡ አንዱ ፡ ዝንጉነት ፡ ነው

**forgive** (forgave) ይቅርታ ፡ አደረገ ፤ ይቅር ፡ አለ ፤ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነው
He will never forgive you for that. ለዚያ ፡ አድራጎትህ ፡ ፈጽሞ ፡ ይቅርታ ፡ አያደርግልህም
He forgave his enemies. ጠላቶቹን ፡ ይቅር ፡ አላቸው
Only God can forgive mortal sins. ከባድ ፡ ኀጢአትን ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነው

**forgiveness**
1. ምሕረት. He asks forgiveness. ምሕረት ፡ ይጠይቃል
2. ይቅር ፡ ማለት. He showed true greatness by his forgiveness of his enemies. ጠላቶቹን ፡ ይቅር ፡ በማለት ፡ እውነተኛ ፡ ታላቅነቱን ፡ አሳየ

**forgo** (forwent)
1. ለቀቀ. The prince had to forgo his privileges in order to marry a commoner. ተራ ፡ ሴት ፡ ለማ

ማባት ፡ ስለፈለገ ፡ ልዑሉ ፡ ክብሩን ፡ ሁሉ ፡ መል ቀቅ ፡ አለበት
2. ያለ - - - መኖር ፡ ለመደ. He will have to forgo good food while he is in the army. በጦር ፡ ሰራዊት ፡ ውስጥ ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ጥሩ ፡ ምግብ ፡ መኖር ፡ መልመድ ፡ አለበት

**forgot,** see **forget**

**fork** (v.) ተከፈለ
The road forks beyond the village. መንገዱ ፡ መንደሩን ፡ አልፎ ፡ ይከፈላል

**fork** (n.)
1. ሹካ. Could I have a knife and fork, please? ቢላዋና ፡ ሹካ ፡ ትሰጠኝ ?
2. ባላ. He laid his coat in the fork of a tree. ኮቱን ፡ ዛፉ ፡ ባላ ፡ ላይ ፡ አንጠለጠለው
3. መንታ. He came to a fork in the road and did not know where to go. መንታ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ የትኛውን ፡ እንደሚይዝ ፡ ቸገረው

**forked** (adj.) መንታ
Snakes have forked tongues. እባብ ፡ መንታ ፡ ምላስ ፡ አለው

**forlorn**
1. የተጣለ. The kitten, a forlorn little animal, was wet and dirty. ያች ፡ የተጣለች ፡ ግልገል ፡ ድመት ፡ ገላዋ ፡ ቆሽሾና ፡ ርሶ ፡ ነበር
2. ኦና. A forlorn old house stood in the middle of the fields. ያረጀ ፡ ኦና ፡ ቤት ፡ እሚዳው ፡ መካከል ፡ ይታይ ፡ ነበር

**feel forlorn** ብቸኝነት ፡ ተሰማ(ው)
He felt forlorn after leaving his friend. ከጓደኛው ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ ብቸኝነት ፡ ተሰማው

**form** (vt.)
1. ሰበሰበ. He formed a class of beginners in Amharic. አማርኛን ፡ በጀማሪነት ፡ ለመማር ፡ የሚፈልጉትን ፡ ተማሪዎች ፡ ሰበሰበ
2. መሠረተ. The clergy and the nobility formed a coalition. ካህናቱና ፡ መኳንንቱ ፡ ኅብረትን ፡ መሠረቱ
3. አቋቋመ. The financier formed a new bank. የገንዘብ ፡ ሥራ ፡ ዐዋቂው ፡ አዲስ ፡ ባንክ ፡ አቋቋመ
4. አነጸ. Discipline helps form a child's character. ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የልጅን ፡ ጠባይ ፡ ለማነጽ ፡ ይረዳል
5. አፈራ. Form good habits while you are young! በወጣትነትህ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ አፍራ
6. ሆነ. Parents and children form a family. ወላጆችና ፡ ልጆች ፡ አንድ ፡ ቤተሰብ ፡ ይሆናሉ
Water forms ice when it freezes. ውኃ ፡ ሲቀዘቅዝ ፡ በረዶ ፡ ይሆናል
7. ነው. Drill forms an important part of learning Amharic. ልምምድ ፡ ከማርኛ ፡ መመሪያ ፡ ዘዴ ፡ አንዱ ፡ ዋና ፡ ክፍል ፡ ነው
*How do you form the plural in Amharic? ባማርኛ ፡ ቃላት ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ ቁጥር ፡ የሚለወጡት ፡ እንዴት ፡ ነው ?

**form** (vi.) ተፈጠረ
Clouds form in the sky. ደመና ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ይፈጠራል

**be formed** ተሠራ
Some rocks are formed by accretion. አንዳንድ ፡ ቋጥኞች ፡ የሚሠሩት ፡ በጥቃቅን ፡ አካሎች ፡ መዋሐድ ፡ ነው
[See also 'opinion']

**form** (n.)
1. ቅርጽ. Circles and triangles are forms. ክብና ፡ ሦስት ፡ ማእዘን ፡ ያላቸው ፡ ነገሮች ፡ ቅርጾች ፡ ናቸው
2. ቅርጽ ፡ ማውጫ. You need a form for ice cream. ለአይስ ፡ ክሬም ፡ ቅርጽ ፡ ማውጫ ፡ ያስፈልግሃል
3. ነገር. A dark form could be seen in the distance. ከሩቅ ፡ ጥቁር ፡ ነገር ፡ ይታይ ፡ ነበር
4. አጻጻፍ. These words are different in form but the same in meaning. እነዚህ ፡ ቃላት ፡ በአጻጻፍ ፡ ቢለያዩም ፡ በትርጉም ፡ አንድ ፡ ናቸው
5. ዓይነት. Algebra is a form of mathematics. አልጀብራ ፡ የሒሳብ ፡ ዓይነት ፡ ነው
6. መልክ. The form of prayer used in our church has not changed since ancient times. በቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ውስጥ ፡ የሚሠራበት ፡ ጸሎት ፡ መልኩ ፡ ከጥንት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ አልተለወጠም
7. የሰውነት ፡ አቋም. Athletes exercise to keep in form. እስፖርተኞች ፡ የሰውነታቸውን ፡ አቋም ፡ ለመጠበቅ ፡ ልምምድ ፡ ያደርጋሉ
8. ወግና ፡ ልማድ. They observe ancient forms in the coronation ceremony. በዘውድ ፡ በዓሉ ፡ አከባበር ፡ ላይ ፡ የጥንት ፡ ወግና ፡ ልማድን ፡ ይጠብቃሉ
9. ፎርም. You will have to fill out this form. ይህንን ፡ ፎርም ፡ መሙላት ፡ አለብህ
*The devil appeared to him in the form of a snake. ሰይጣን ፡ እባብን ፡ ተመስሎ ፡ ታየው

**be in good form**
1. ነቃ ፡ ነቃ ፡ አለ. I am in good form today. ዛሬ ፡ ነቃ ፡ ነቃ ፡ ብያለሁ
2. ሰውነቱ ፡ በደንብ ፡ ተጠበቀ. If your horse is not in good form, he won't win the race. ፈረስህ ፡ ሰውነቱ ፡ በደንብ ፡ ካልተጠበቀ ፡ በእሽቅድድሙ ፡ አሸናፊ ፡ አይሆንም

**(a) matter of form ለደንቡ ፡ ያህል**
It is only a matter of form, but you have to hand in an application. ለደንቡ ፡ ያህል ፡ ቢሆንም ፡ ማመልከቻውን ፡ ማቅረብ ፡ አለብህ
[See also 'serial']

## formal

1. በደንብ ፡ የተጠበቀ. A written contract is a formal agreement to do something. በጽሑፉ ፡ ያለ ፡ ውል ፡ ማድረግ ፡ በደንብ ፡ የተጠበቀ ፡ ስምምነት ፡ ነው
2. የሥነ ፡ በዓል. Formal dress is required at the Emperor's banquet. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሚያደርጉት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ የሥነ ፡ በዓል ፡ ልብስ ፡ ያስፈልጋል
3. መደበኛ. He had little formal training in sociology. በሶሲዮሎጂ ፡ መደበኛ ፡ ትምህርት ፡ እምብዛም ፡ አልተማረም
4. (= adv.) በኦፊሴል. The ambassador paid the minister a formal visit. አምባሳደሩ ፡ ሚኒስትሩን ፡ በኦፊሴል ፡ ጐበኘው

**formal dinner የራት ፡ ግብዣ**
A formal dinner was held in honor of visiting heads of state. በጉብኝት ፡ ላይ ፡ ላሉት ፡ ያገር ፡ መሪዎች ፡ ክብር ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ተደረገ

**be formal ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተከተለ**
You must always be formal when addressing the Emperor. በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊት ፡ ንግግር ፡ ሲደረግ ፡ ሁልጊዜ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ መከተል ፡ ይገባል

## formality (formalities) ሥርዓት

You have to comply with all the necessary formalities before you can be admitted to Ethiopia. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንድትገባ ፡ ፈቃድ ፡ ከማግኘትህ ፡ በፊት ፡ አስፈላጊዎቹን ፡ ሥርዓቶች ፡ በሙሉ ፡ መፈጸም ፡ አለብህ
*You have to submit an application, but it is a mere formality. ማመልከቻ ፡ ማስገባት ፡ አለብህ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለደንቡ ፡ ያህል ፡ ነው

## format

1. አቀራረብ. The book was republished in a new format. መጽሐፉ ፡ ባዲስ ፡ አቀራረብ ፡ እንደገና ፡ ታተመ
2. ይዞታና ፡ አቀራረብ. The format of the newspaper was changed. የጋዜጣው ፡ ይዞታና ፡ አቀራረብ ፡ ተለውጧል

## formation

1. ሰልፍ. The planes flew overhead in formation. አውሮፕላኖቹ ፡ በሰልፍ ፡ ሆነው ፡ በረሩ
2. አፈጣጠር. We studied the formation of the tooth. ስለ ፡ ጥርስ ፡ አፈጣጠር ፡ ተማርን
3. (= verbal noun) ማነጽ. Formation of character requires much effort. ጠባይን ፡ ማነጽ ፡ ብዙ ፡ ጥረት ፡ ይጠይቃል

## formative, ~ years የማደጊያ ፡ ዓመታት

The formative years of youth are very important. የወጣት ፡ የማደጊያ ፡ ዓመታት ፡ በጣም ፡ ዋጋ ፡ አላቸው

## former

1. የፊተኛ. The former owner left the city. የፊተኛው ፡ ባለንብረት ፡ ከተማውን ፡ ለቋል
2. የድሮ. The house showed nothing of its former splendor. ቤቱ ፡ ምንም ፡ የድሮው ፡ ውበት ፡ አልታየበትም
3. የቀድሞ. His former friends assassinated him. የቀድሞ ፡ ጓደኞቹ ፡ ገደሉት
Who was the former President of the United States? የቀድሞው ፡ የዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ማን ፡ ነበር ?
*He raises horses and cows, the former for riding, the latter for milk. ፈረሶችና ፡ ላሞች ፡ ያረባል ፤ ፈረሶቹን ፡ ለግልቢያ ፡ ላሞቹን ፡ ለወተት

**former days ጥንት**
Ships of former days were built differently. የጥንት ፡ መርከቦች ፡ አሠራራቸው ፡ የተለየ ፡ ነበር

**in former times በቀድሞ ፡ ዘመን**
In former times, Ethiopia was much smaller than now. በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ካሁኑ ፡ በጣም ፡ ታንስ ፡ ነበር

## formerly ቀድሞ ፤ ድሮ ፤ ዱሮ

This was formerly the business section. ቀድሞ ፡ (ድሮ) ፡ ይህ ፡ የንግድ ፡ ሰፈር ፡ ነበር

## formidable

1. አዳጋች. To climb the mountain was a formidable task. ተራራውን ፡ መውጣት ፡ አዳጋች ፡ ነገር ፡ ነበር
2. ከፍ ፡ ያለ. There was a formidable opposition to the proposal. ለቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተቃውሞ ፡ ነበር
3. የማይገፋት. He is up against a formidable opponent. ከማይገፋት ፡ ባለጋራ ፡ ተጋፍጧል
4. የተመሰገነ. He has a formidable knowledge of history. የታሪክ ፡ ዕውቀቱ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው
*He is a man with a formidable appearance. ሰውዬው ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ያለው ፡ ነው

## formula

1. መምሪያ. He invented a formula for making

soap. ሳሙና ፡ ለመሥራት ፡ የሚያገለግለውን ፡ መምሪያ ፡ ፈጠረ
2. መሠረታዊ ፡ ደንብ. They tried to find a formula for peace. ሰላም ፡ ሊገኝ ፡ የሚችልበትን ፡ መሠረታዊ ፡ ደንብ ፡ ለመፍጠር ፡ ሞከሩ
3. አባባል. "How do you do?" is a polite formula. እንደምን ፡ አለህ ፡ ማለት ፡ የትሕትና ፡ አባባል ፡ ነው
4. ፎርሙላ. Algebra uses many formulas. አልጀብራ ፡ ብዙ ፡ ፎርሙላ ፡ አለው

**formulate**
1. ደነገገ. This country formulates laws according to its constitution. ይህች ፡ ሀገር ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ ሕጎችን ፡ ትደነግጋለች
2. አዘጋጀ. They formulated plans for their business. ለንግድ ፡ ሥራቸው ፡ እቅድ ፡ አዘጋጁ
3. በፎርሙላ ፡ አወጣ. The physicists formulated a new theory of gravitation. የፊዚክስ ፡ ሊቃውንት ፡ የስበትን ፡ አዲስ ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳብ ፡ በፎርሙላ ፡ አወጡ

**fornication** ዝሙት
Fornication is sinful. ዝሙት ፡ ኀጢአት ፡ ነው

**forsake** (forsook)
1. ጥሎ ፡ ጠፋ. He forsook his wife and children. ሚስቱንና ፡ ልጆቹን ፡ ጥሎ ፡ ጠፋ
2. ጥሎ ፡ ሄደ. He has forsaken his country for an uninhabited island. አገሩን ፡ ጥሎ ፡ ሰው ፡ ወደማይኖርበት ፡ ደሴት ፡ ሄደ

**forsook,** see **forsake**

**fort** ምሽግ
They decided to defend the fort. ምሽጉን ፡ ለመከላከል ፡ ቈረጡ

**forth** ጀምሮ
From this day forth I will be on time. ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ በሰዓቱ ፡ እገኛለሁ
[See also 'and, back']

**forthcoming**
1. በቅርቡ ፡ የሚወጣ. He sent me a list of forthcoming books. በቅርቡ ፡ የሚወጡትን ፡ መጻሕፍት ፡ የሚያሳይ ፡ ዝርዝር ፡ ላከልኝ
2. በቅርቡ ፡ የሚከናወን. We put notices of forthcoming activities on the bulletin board. በቅርቡ ፡ የሚከናወኑትን ፡ ድርጊቶችን ፡ የሚያሳይ ፡ ማስታወቂያ ፡ በማስታወቂያ ፡ ሰሌዳው ፡ ላይ ፡ ለጠፍን
3. ወደፊት ፡ የሚደረግ. I am quite enthusiastic about the forthcoming trip. ወደፊት ፡ ከሚደረገው ፡ ጉዞ ፡ በጣም ፡ ጓጕቻለሁ

**be forthcoming** በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ተገኘ
Money for the project will be forthcoming when needed. ለሥራው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ይገኛል

**forthright** (adj.) ፍርጥ ፡ ያለ
His forthright reply to my questions made me respect him. ለጥያቄዎቼ ፡ የሰጠው ፡ ፍርጥ ፡ ያለ ፡ መልስ ፡ እንዳከብረው ፡ አደረገኝ

**forthrightly** ወዲያው
He told us forthrightly just what his objections were. የማይስማማበት ፡ ምክንያት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ወዲያው ፡ ነገረን

**forthwith** ወዲያውኑ
Do what I told you forthwith! የነገርኩህን ፡ ወዲያውኑ ፡ አድርግ

**forties, in his ~**
*He is in his forties. ዕድሜው ፡ አርባ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**fortification**
1. ምሽግ. There were traces of an old fortification on the hilltop. በኮረብታው ፡ ጫፍ ፡ ያሮጌ ፡ ምሽግ ፡ ርዝራዥ ፡ ይታይ ፡ ነበር
2. ምሽግ ፡ መሥራት. The general was responsible for the fortification of the town. ከተማው ፡ ውስጥ ፡ ምሽግ ፡ ለመሥራት ፡ ኀላፊው ፡ ጀኔራሉ ፡ ነበር

**fortify** (fortified)
1. መሸገ. The soldiers fortified the island. ወታደሮቹ ፡ ደሴቱ ፡ ላይ ፡ መሸጉ
2. አጠነከረ. Vitamins help to fortify us against colds. ቪታሚን ፡ ሰውነታችንን ፡ አጠንክሮ ፡ ጉንፋን ፡ እንዳይዘን ፡ ይከላከልልናል

**fortitude** ጠንካራነት
Her fortitude enabled her to endure the pain of a broken leg. ጠንካራነቷ ፡ የተሰበረውን ፡ እግሯን ፡ ሕመም ፡ እንድትችል ፡ አደረጋት

**fortnight** ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን
He went away for a fortnight. ለዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ሄደ

**fortress** ትልቅ ፡ ምሽግ
There is a fortress near the mountain. በተራራው ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ምሽግ ፡ አለ

**fortuitous** አጋጣሚ
A series of fortuitous circumstances advanced her career. በልዩ ፡ ልዩ ፡ አጋጣሚ ፡ ዕድል ፡ ኑሮዋ ፡ ተቃናላት

**fortunate**
1. ዕድለኛ. He was very fortunate in his life. በኑሮው ፡ በጣም ፡ ዕድለኛ ፡ ነበር
You were fortunate to escape being injured in the accident. በአደጋው ፡ ሳትጐዳ ፡ በማምለጥህ ፡ ዕድለኛ ፡ ነህ
2. መልካም. That was a fortunate coincidence. መልካም ፡ አጋጣሚ ፡ ነበረ

**less fortunate** ዕድሉ ፡ ዝቅ ፡ ያለ
He has pity on people less fortunate than himself. ዕድላቸው ፡ ከሱ ፡ ዝቅ ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ ያዝናል

**fortunately** እንደ ፡ ዕድል ፡ ሆኖ
The lost battle was fortunately not an important one. ድል ፡ የሆነበት ፡ ጦርነት ፡ እንደ ፡ ዕድል ፡ ሆኖ ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ አልነበረውም

**fortune**
1. ሀብት. She inherited a large fortune. ብዙ ፡ ሀብት ፡ ወረሰች
2. ብዙ ፡ ሀብት. He made a fortune in his business. በንግድ ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ አተረፈ
3. ኮከብ. I had my fortune told the other day. ኮከብ ፡ ቈጣሪው ፡ ባለፈው ፡ ቀን ፡ ኮከቤን ፡ ቈጠረልኝ
4. ዕድል. Fortune was against us; we lost. ዕድል ፡ ከድቶን ፡ ተሸነፍን

**make (one's) fortune** ሀብታም ፡ ሆነ
He made his fortune in oil. በዘይት ፡ ንግድ ፡ ሀብታም ፡ ሆነ

**fortuneteller** ኮከብ ፡ ቈጣሪ
There are many fortunetellers in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ኮከብ ፡ ቈጣሪ ፡ አለ

**forty** አርባ

**forum** ሸንጎ
The United Nations is a forum of world opinion. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ የዓለም ፡ ሸንጎ ፡ ነው

**forward** (v.)
1. አደረሰ(ለት). Forward the message to the minister for me! ለሚኒስትሩ ፡ መልእክቱን ፡ አድርስልኝ
2. አስተላለፈ. Please forward the request to the proper authorities! ጥያቄውን ፡ አግባብ ፡ ላለው ፡ ባለሥልጣን ፡ አስተላልፍ
3. ላከ(ለት). Please forward my mail to my new address! ደብዳቤዎቼን ፡ ባዲሱ ፡ አድራሻዬ ፡ ላክልኝ
4. እንዲሳካ ፡ አደረገ. He is always ready to forward his friends' plans. የጓደኞቹን ፡ እቅዶች ፡ እንዲሳኩ ፡ ለማድረግ ፡ ሁልጊዜ ፡ ዝግጁ ፡ ነው

**be forwarded**
1. ተላለፈ. The letter has been forwarded to Ethiopia. ደብዳቤው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተላልፏል
2. ተላከ(ለት). Your mail will be forwarded to your new address. ደብዳቤህ ፡ ወደ ፡ አዲሱ ፡ አድራሻህ ፡ ይላክልሃል

**forward** (adj.)
1. ዓይን ፡ አውጣ. People criticize her because she is forward. ዓይን ፡ አውጣ ፡ ስለሆነች ፡ ሰዎች ፡ ይነቅፏታል
2. (= adv.) ወደ ፡ ፊት. Their forward march was blocked by a river. ወደ ፡ ፊት ፡ የሚያደርጉት ፡ ጉዞዋቸው ፡ ባንድ ፡ ወንዝ ፡ ታግዶ ፡ ነበር
*His speech took a forward look at the coming years. ንግግሩ ፡ ወደፊት ፡ የሚመጡትን ፡ ዓመታት ፡ ሁኔታ ፡ የሚመለከት ፡ ነበር

**forward** (adv.) ወደ ፡ ፊት
He moved slowly forward with his hands up. እጆቹን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሰቅሎ ፡ በዝግታ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሄደ

**forward part** ግንባር
The captain stood on the forward part of the ship. ካፒቴኑ ፡ በመርከቡ ፡ ግንባር ፡ በኩል ፡ ቆሟል

**from this time forward** ከእንግዲህ ፡ ወዲህ
From this time forward I will come regularly. ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሳላቋርጥ ፡ እመጣለሁ
[See also 'come, lean, look, march']

**forwards** ወደፊት
Go forwards and do not turn back! ወደፊት ፡ ሂድ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አትመለስ
[See also 'backwards']

**fossil** ቅሪተ ፡ አካል
Fossil plants were discovered in the rocks. በአለቶቹ ፡ ውስጥ ፡ የዕፀዋት ፡ ቅሪተ ፡ አካል ፡ ተገኘ

**foster**
1. አስፋፋ. Ignorance fosters superstitions. ድንቁርና ፡ አጉል ፡ እምነትን ፡ ያስፋፋል
His Majesty has fostered education in Ethiopia.

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ትምህርት ፡ አስፋፍተዋል

2. አነቃቃ. The children's concerts foster an appreciation of music. የሕፃናት ፡ ኮንሰርት ፡ የሙዚቃን ፡ ስሜት ፡ ያነቃቃል

3. አበረታታ. This plan fosters community development. ይህ ፡ እቅድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብ ፡ እ ድገትን ፡ ያበረታታል

4. አሳደገ. Not every person is able to foster a child properly. ልጅን ፡ በደንብ ፡ ለማሳደግ ፡ የሚችል ፡ ሁሉም ፡ አይደለም

**foster child** የማደጎ ፡ ልጅ

The foster child is well treated in this family. ይህ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የማደጎውን ፡ ልጅ ፡ በሚገባ ፡ ይዞ ታል

**foster father** አሳዳጊ

The man is his foster father, not his real one. ሰውዬው ፡ አሳዳጊው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ አባቱ ፡ አይደለም

**foster mother** አሳዳጊ ፡ እናት

My foster mother is very kind. አሳዳጊ ፡ እናቴ ፡ በጣም ፡ ደግ ፡ ናት

**foster parents** አሳዳጊዎች

Those are his foster parents, not his real ones. እነዚያ ፡ አሳዳጊዎቹ ፡ እንጂ ፡ ወላጆቹ ፡ አይደሉም

**fought,** see **fight**

**foul** (v.) በከለ

Mud fouls things. ጭቃ ፡ እቃን ፡ ይበክላል

*The sloppy sailor fouled the rope. ጥንቃቄ ፡ የጐደለው ፡ መርከበኛ ፡ የገመዱን ፡ ውል ፡ አጠ ፋው

**foul** (n.), **be declared a ~** ነጥቡ ፡ ፋርሽ ፡ ሆነ

Though the ball landed in the goal it was declared a foul. ኳሷ ፡ ግቡ ፡ ብትገባም ፡ ነጥቡ ፡ ፋርሽ ፡ ሆነ

**foul** (adj.)

1. የተበላሸ. We opened the windows to let out the foul air. የተበላሸውን ፡ አየር ፡ ለማስ ወጣት ፡ መስኮቶቹን ፡ ከፈትን

2. መጥፎ. Foul weather delayed the plane. መጥፎ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ አውሮፕላኑን ፡ አዘገየ

The meat left a foul taste in his mouth. ሥጋው ፡ አፉ ፡ ላይ ፡ መጥፎ ፡ ጣዕም ፡ አስቀረበት

*She uses foul language. አፏ ፡ ባለጌ ፡ ነው

**foul means** ተንኮል

He is going to succeed by fair means or foul. በቅንነትም ፡ ሆነ ፡ በተንኮል ፡ ሳይሳካለት ፡ አ ይቀርም

**foul play** ተንኮል ፤ የግፍ ፡ ሥራ

A man was found dead in the street, and foul play was suspected. አንድ ፡ ሰው ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ሞቶ ፡ ስለተገኘ ፡ በተንኮል ፡ (በግፍ ፡ ሥ ራ) ፡ የተደረገ ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ ጥርጣሬ ፡ ነበር

**found,** see **find**

**found**

1. ቈረቈረ. Menelik founded Addis Ababa in 1888. ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ በ፲፰፻፹ ዓ.ም. ቈረቈሩ

2. አቋቋመ. My uncle founded the bank in 1888. አጎቴ ፡ በ፲፰፻፹ ዓ.ም.ባንኩን ፡ አቋቋመ

3. መሠረተ. He founded his claim on facts. ይገባኛል ፡ ባይነቱን ፡ በእውነተኛ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ መሠረተ

**foundation**

1. መሠረት. His religious faith has a firm foundation. ሃይማኖቱ ፡ ጠንካራ ፡ መሠረት ፡ አለው

The foundation of a house is built first. ቤት ፡ ሲሠራ ፡ መሠረቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ይጣላል

The foundation of the United States began in 1776. የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ መሠረት ፡ የ ተጣለው ፡ በ፲፯፻፷፰ ዓ. ም. ነው

2. ድርጅት. The Haile Sellassie Charitable Foundation has done much good work. የቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ድ ርጅት ፡ ብዙ ፡ በጎ ፡ ተግባር ፡ አከናውኗል

**lay the foundation** መሠረት ፡ ጣለ ፤ መሠረት ፡ አኖረ

They laid the foundation for a new hospital last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ያዲሱን ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ መሠረት ፡ ጣሉ ፡ (አኖሩ)

**founder** (v.)

1. ሰጠመ. The ship foundered. መርከቧ ፡ ሰጠ መች

2. ሳይሳካ ፡ ቀረ. The project foundered because public support was lacking. የሕዝብ ፡ ድጋፍ ፡ ስላላገኘ ፡ እቅዱ ፡ ሳይሳካ ፡ ቀረ

**founder** (n.) መሥራች

Who is the founder of the Besse Company? የቤስ ፡ ኩባንያ ፡ መሥራች ፡ ማን ፡ ነው ?

**foundling** ተወልዶ ፡ የተጣለ ፡ ልጅ

The foundling was given to a nurse. ተወልዶ ፡ የተጣለው ፡ ልጅ ፡ ላስታማሚ ፡ ተሰጠ

**foundry** የብረት ፡ ማቅለጫ

The foundry makes parts for motors. የብረት ፡ ማቅለጫው ፡ የሞተሮች ፡ መለዋወጫ ፡ ይሠራል

**fountain** ምንጭ
The fountain stood in the middle of the garden. ምንጩ ፡ በአትክልቱ ፡ ስፍራ ፡ መካከል ፡ ነበር
A library is a fountain of knowledge. ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ የዕውቀት ፡ ምንጭ ፡ ነው

**fountain pen** ብዕር
I like to write with a fountain pen. በብዕር ፡ መጻፍ ፡ እወዳለሁ

**four** አራት
**four o'clock** ዐሥር ፡ ሰዓት
He left school at four o'clock. ከትምህርት ፡ ቤት ፡ በዐሥር ፡ ሰዓት ፡ ወጣ

**fourteen** ዐሥራ ፡ አራት

**fourth**
1. አራተኛ. Who is the fourth boy in the group over there? እዚያ ፡ ከቆሙት ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ አራተኛው ፡ ማነው ?
2. አራተኛ ፡ ቀን ፤ አራት ፡ ቀን. He died on the fourth of this month. ይህ ፡ ወር ፡ በገባ ፡ በአራተኛው ፡ ቀን ፡ ሞተ
I'll be there on the fourth of March. መጋቢት ፡ አራት ፡ ቀን ፡ እዚያ ፡ እገኛለሁ
3. አራተኛዎች. Only one fourth of the students came early. ከተማሪዎቹ ፡ አንድ ፡ አራተኛዎቹ ፡ ብቻ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ መጡ

**fowl** የአዕዋፍ ፡ ወገን
Ducks, chickens, geese, and turkeys are fowl. ዳክዬዎች ፡ ዶሮች ፡ ዝዬዎችና ፡ የቱርክ ፡ ዶሮዎች ፡ የአዕዋፍ ፡ ወገን ፡ ናቸው

**fox** ቀበሮ
He caught a fox in the trap. አንድ ፡ ቀበሮ ፡ በወጥመድ ፡ ያዘ

**fox hole** [ከጠላት ፡ ለመከላከል ፡ እንዲረዳ ፡ ወታደር ፡ የሚሸሸግበት ፡ ጉድጓድ]

**foxy** ተንኰለኛ
Don't deal with him! He is very foxy. በጣም ፡ ተንኰለኛ ፡ ስለሆነ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ አትግጠም

**foyer** የቲያትር ፡ መተላለፊያ
I was in the foyer during intermission. በዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ በቲያትሩ ፡ መተላለፊያው ፡ ላይ ፡ ነበርኩ

**fraction**
1. ክፍልፋይ. Leave out the fractions and give me the round number! ክፍልፋዮቹን ፡ ትተህ ፡ ሙሉ ፡ የተጠጋጋውን ፡ ቁጥር ፡ ንገረኝ
2. ጥቂት ፡ ክፍል. Only a fraction of the regiment came back. ከጦሩ ፡ ጥቂት ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ተመለሰ
3. (= adv.) በከፊል. He got only a fraction of his problems finished. ችግሩን ፡ የተወጣው ፡ በከፊል ፡ ነው

**fracture**, vt. (= intr.) ተሰበረ
He fell off the bicycle and fractured his arm. ከቢስክሌት ፡ ወድቆ ፡ እጁን ፡ ተሰበረ

**fracture** (n.) ስብራት
The fracture is healing slowly. ስብራቱ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየገጠመ ፡ ነው

**fragile** የሚሰበር
Be careful with that glass! It is very fragile. መስታወቱ ፡ በቀላሉ ፡ የሚሰበር ፡ ስለሆነ ፡ ጠንቀቅ ፡ በል
*He is of fragile health. ቀሰስተኛ ፡ ነው

**fragment**
1. ስብርባሪ. She dropped the pot and swept the fragments into the street. ማሰሮውን ፡ ጥላ ፡ ቢሰበርባት ፡ ስብርባሪውን ፡ ወደ ፡ መንገዱ ፡ ጠረገችው
2. ግማድ. They enshrined a fragment of the cross in the cathedral. ግማደ ፡ መስቀሉን ፡ በካቴድራሉ ፡ ውስጥ ፡ ቅዱስ ፡ ስፍራ ፡ አስቀመጡት
3. ክፍል. A fragment of his last novel was published after his death. ከመጽሐፉ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ እሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ታተመ
**fragments** (= adv.) ጫፍ ፡ ጫፉን
He could hear only fragments of their conversation. ወሬያቸውን ፡ ጫፍ ፡ ጫፉን ፡ ብቻ ፡ ለመስማት ፡ ቻለ

**fragmentary** ያልተሟላ
He gave a fragmentary report of the event. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ያልተሟላ ፡ ሪፖርት ፡ አቀረበ

**fragrance** መዓዛ
The fragrance of the flowers could be smelled from afar. ያበቦቹን ፡ መዓዛ ፡ ከሩቅ ፡ ለማሽተት ፡ ይቻል ፡ ነበር

**(be) fragrant**
1. ጣፋጭ ፡ መዓዛ ፡ አለው. This rose is very fragrant. ይህ ፡ ጽጌረዳ ፡ በጣም ፡ ጣፋጭ ፡ መዓዛ ፡ አለው
2. ጥሩ ፡ መዓዛ ፡ አለው. This herb is fragrant. ይህ ፡ ዕፅ ፡ ጥሩ ፡ መዓዛ ፡ አለው

**frail**

1. ደካማ. A frail old lady was trying to get on the bus. አንዲት ፡ ደካማ ፡ ባልቴት ፡ አውቶቡሱ ፡ ላይ ፡ ለመውጣት ፡ ይሞክሩ ፡ ነበር

The rope was too frail to lift such a heavy weight. ይህንን ፡ ከባድ ፡ እቃ ፡ ለማንሣት ፡ ገመዱ ፡ በጣም ፡ ደካማ ፡ ነበር

2. ተሰባሪ. This chair is too frail for a large fat man to sit on. ይህ ፡ ወምበር ፡ በቀላሉ ፡ ተሰባሪ ፡ ስለሆነ ፡ ወፍራም ፡ ሰው ፡ ሊቀመጥበት ፡ አይችልም

**frailty** (frailties) ደካማነት ፤ ጠባየ ፡ ደካማነት

Ignoring one's own faults is a human frailty. የራስን ፡ ጥፋት ፡ ችላ ፡ ማለት ፡ ሰብአዊ ፡ ደካማነት ፡ ነው

He is very tolerant of other people's frailties. የሌሎችን ፡ ጠባየ ፡ ደካማነት ፡ አይቶ ፡ እንዳላየ ፡ ያልፈዋል

**frame** (v.)

1. መስታወት ፡ ውስጥ ፡ አገባ. Please frame this picture! ይህንን ፡ ሥዕል ፡ መስታወት ፡ ውስጥ ፡ አግባው

2. አቀናበረ. John framed his reply carefully. ዮሐንስ ፡ መልሱን ፡ በጥንቃቄ ፡ አቀናበረ

3. አወጣ. The parliament framed a new constitution. ፓርለማ ፡ አዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አወጣ

**frame** (n.)

1. ክፈፍ. I would like to have a frame for the picture. ለሥዕሉ ፡ ክፈፍ ፡ እፈልግ ፡ ነበር

2. መያዣ. I have broken the frame of my glasses. የመነጽሬን ፡ መያዣ ፡ ሰበርኩት

3. መወጠሪያ. He distended the skin over the frame for drying. ቆዳው ፡ እንዲደርቅ ፡ በመወጠሪያው ፡ ላይ ፡ ወጠረው

4. ግድግዳና ፡ ጣሪያ. The frame of the house was finished in two days. የቤቱ ፡ ግድግዳና ፡ ጣሪያ ፡ በሁለት ፡ ቀን ፡ አለቀ

5. አውታር. The frame of the umbrella is covered with cloth. የጃንጥላው ፡ አውታር ፡ ጨርቅ ፡ ለብሷል

The skeleton is the frame of the body. ዐጽም ፡ ለሰውነት ፡ ቅርጽ ፡ የሚሰጥ ፡ አውታር ፡ ነው

6. አጥንት. The athlete has a large frame. እስፖርተኛው ፡ አጥንተ ፡ ሰፊ ፡ ነው

7. ሥርዓት. The constitution established our frame of government. ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የመንግሥታችንን ፡ ሥርዓት ፡ መሠረተ

**frame of mind** መንፈስ

He was in a cheerful frame of mind. በደስታ ፡ መንፈስ ፡ ነበር

**framework**

1. አውታር. The bridge has a steel framework. የድልድዩ ፡ አውታር ፡ ከዐረብ ፡ ብረት ፡ የተሠራ ፡ ነው

2. ጣሪያና ፡ ግድግዳ. The framework of the hut is made of sticks. የቤቱ ፡ ጣሪያና ፡ ግድግዳ ፡ ከዕንጨት ፡ የተሠራ ፡ ነው

**France** ፈረንሳይ ፤ ፈረንሳይ ፡ አገር

**franchise** ልዩ ፡ ፈቃድ

One must get a franchise from the government to operate a television station. የቴሌቪዥን ፡ ጣቢያ ፡ ለማቆም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ከመንግሥት ፡ ልዩ ፡ ፈቃድ ፡ ማግኘት ፡ አለበት

**frank**

1. ግልጽ. His criticism of my work was frank but absolutely fair. ስለ ፡ ሥራዬ ፡ የሰጠኝ ፡ አስተያየት ፡ ግልጽና ፡ ትክክለኛ ፡ ነበር

2. (= adv.) ከልብ. Is that your frank opinion? ይህ ፡ አስተያየት ፡ ከልብህ ፡ ነው ?

**to be frank** እውነቱን ፡ ለመናገር

To be frank, I don't know. እውነቱን ፡ ለመናገር ፡ አላውቅም

**frankly** ግልጥ ፡ አድርጎ

Why don't you tell me frankly what really happened? በርግጥ ፡ የተደረገውን ፡ ለምን ፡ ግልጥ ፡ አድርገህ ፡ አትነግረኝም ?

**frankness**

1. ፍርጥ ፡ አድርጎ ፡ እውነቱን ፡ መናገር. The speaker's frankness disarmed the angry mob. የተናጋሪው ፡ ፍርጥ ፡ አድርጎ ፡ እውነቱን ፡ መናገሩ ፡ የተናደደውን ፡ ሕዝብ ፡ አበረደው

2. የዋህ ፡ መሆን. His childlike frankness wins the heart of everybody. እንደ ፡ ሕፃን ፡ የዋህ ፡ መሆኑ ፡ የማንኛቸውንም ፡ ሰው ፡ ልብ ፡ ይማርካል

**frantic** የጭንቀት

We heard frantic cries for help. የጭንቀት ፡ ኡኡታ ፡ ሰማን

**make frantic efforts** ከፉኛ ፡ ተፍጨረጨረ

He made frantic efforts to free himself. ራሱን ፡ ነጻ ፡ ለማውጣት ፡ ክፉኛ ፡ ተፍጨረጨረ

**fraternal** የወንድምነት

Fraternal affection caused him to help us. የወንድምነት ፡ ፍቅሩ ፡ እንዲረዳን ፡ ገፋፋው

*He has a fraternal affection for Hailu. ኀይሉን ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ወንድሙ ፡ አድርጎ ፡ ይወደዋል

**fraternity** (fraternities)

1. ወንድማማችነት. The French creed is "Liberty, Equality, Fraternity". የፈረንሳይ ፡ እምነት ፡ « ነጻነት ፤ እኩልነት ፤ ወንድማማችነት » ፡ የሚል ፡ ነው

2. የወንድማማችነት ፡ ክበብ. He joined the best fraternity at his school. በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ምርጥ ፡ ከሆነው ፡ የወንድማማችነት ፡ ክበብ ፡ ገባ

**fraternize** ተወዳጀ

We did not fraternize with those who conquered us. ድል ፡ ካደረጉን ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ አልተወዳጀንም

**fraud**

1. ማጭበርበር. To tell country people that copper is gold is common fraud. መዳብን ፡ ወርቅ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ለባላገሮች ፡ መሸጥ ፡ የተለመደ ፡ ማጭበርበር ፡ ነው

2. የማጭበርበር ፡ ክስ. Do you plead guilty to this fraud? በማጭበርበሩ ፡ ክስ ፡ ጥፋተኛነትህን ፡ ታምናለህ ?

**perpetrate a fraud on** አታለለ

He perpetrated a fraud on his own people. የገዛ ፡ ወገኑን ፡ አታለለ

**fraudulent** የሐሰት

His fraudulent claim to be a nephew of the minister was soon disproved. የሚኒስትሩ ፡ የእኅት ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ የሚለው ፡ የሐሰት ፡ ወሬ ፡ ወዲያው ፡ ውሸት ፡ መሆኑ ፡ ተደረሰበት

**(be) fraught with**

*The expedition was fraught with danger. ጉዞው ፡ ብዙ ፡ አደጋ ፡ ብቻ ፡ ነበር

**fray** (= intr.) ነተበ

+Constant wear frayed his shirt cuffs. አዘውትሮ ፡ በመልበሱ ፡ የሸሚዙ ፡ እጅጌ ፡ ከፈፍ ፡ ነተበ

**get frayed** ተዘረዘረ

The border of this rug is getting frayed. የዚህ ፡ ምንጣፍ ፡ ጠርዝ ፡ ተዘረዘረ

**freak** ጉድ

A five-legged sheep is a freak. አምስት ፡ እግር ፡ ያለው ፡ በግ ፡ ጉድ ፡ ነው

**freckle** ጠቃጠቆ

She has freckles on her face. ፊቷ ፡ ላይ ፡ ጠቃጠቆ ፡ አለባት

**free** (v.)

1. አርነት ፡ አወጣ. He freed the slaves. ባሮችን ፡ አርነት ፡ አወጣቸው

2. ፈታ. The sailors worked to free the tangled ropes. መርከበኞቹ ፡ የተወሳሰበውን ፡ ገመድ ፡ ለመፍታት ፡ ታገሉ

3. ለቀቀ. The Americans freed the prisoners. አሜሪካኖቹ ፡ እስረኞቹን ፡ ለቀቁ

4. በነጻ ፡ ለቀቀ. The lawyer adduced a decision in which the judge freed a man charged with robbery. ጠበቃው ፡ በፊት ፡ ዳኛው ፡ በዘረፋ ፡ የተከሰሰውን ፡ ሰው ፡ በነጻ ፡ የለቀቀበትን ፡ ውሳኔ ፡ ጠቀሰ

5. አወጣ. His inheritance finally freed him from debt. ውርሱ ፡ በመጨረሻ ፡ ከዕዳው ፡ አወጣው

**free oneself** ራሱን ፡ ነጻ ፡ አወጣ

He made frantic efforts to free himself. ራሱን ፡ ነጻ ፡ ለማውጣት ፡ ክፉኛ ፡ ተፍጨረጨረ

**be freed** ነጻ ፡ ወጣ

The serfs were freed by the order of the king. ገባሮቹ ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ነጻ ፡ ወጡ

**free** (adj.)

1. ነጻ ፤ ከቀረጥ ፡ ነጻ ፡ የሆነ. Free trade between nations is hindered by regulations. በመንግሥታት ፡ መካከል ፡ ሊኖር ፡ የሚገባው ፡ ነጻ ፡ (ከቀረጥ ፡ ነጻ ፡ የሚሆን) ፡ ንግድ ፡ በደንቦች ፡ ምክንያት ፡ ተሰናክሏል

The countryside is now free from malaria. ባላገሩ ፡ አሁን ፡ ከወባ ፡ ነጻ ፡ ነው

This item is free of custom duties. እቃው ፡ ከጉምሩክ ፡ ቀረጥ ፡ ነጻ ፡ ነው

It's a free country, not a colony. ነጻ ፡ አገር ፡ እንጂ ፡ የቅኝ ፡ ግዛት ፡ አይደለችም

2. ነጻነት ፡ ያለበት. I can say what I please; it's a free country. የፈለግሁትን ፡ ልናገር ፡ እችላለሁ ፤ ነጻነት ፡ ያለበት ፡ አገር ፡ ነው

3. (= adv.) በነጻ. Admission free. መግቢያ ፡ በነጻ

4. ባዶ. There will be no rooms free in this hotel until after the holidays. በዓሉ ፡ እስኪያልፈ ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ሆቴል ፡ ባዶ ፡ ክፍል ፡ አይገኝም

5. (= adv.) እንደልቡ ፤ እንደልብ. We were appalled at his free behavior. እንደልቡ ፡ መሆኑ ፡ አስደንግጦን ፡ ነበር

Cut the snake bite so that there is a free flow of blood. ደሙ ፡ እንደልብ ፡ እንዲፈስ ፡ እባቡ ፡ የነከሰህን ፡ ቦታ ፡ ቍረጠው

*This is a free translation of the Amharic book. ይህ ፡ ካማርኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ የተተረጐመ ፡ አይደለም

**free** (adv.) በብላሽ ፤ በነጻ

I got it free. በብላሽ ፡ አገኘሁት

Smallpox inoculations will be given free. የፈንጣጣ ፡ ክትባት ፡ በነጻ ፡ ይሰጣል

**free speech** የንግግር ፡ ነጻነት
Without free speech, there is no real democracy. የንግግር ፡ ነጻነት ፡ ከሌለ ፡ እውነተኛ ፡ ዲሞክራሲ ፡ የለም

**be free**
1. ጊዜ ፡ አለው. Will you be free tomorrow? ነገ ፡ ጊዜ ፡ አለህ ?
2. ምንም ፡ ሥራ ፡ የለውም. I am free all afternoon. ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ የለኝም
3. አልተያዘም. The telephone line is free. የስልኩ ፡ መሥመር ፡ አልተያዘም
4. ተለቀቀ. Will the room be free tomorrow? ክፍሉ ፡ ነገ ፡ ይለቀቃል ?
As soon as the bird was free, it flew away. ወፏ ፡ እንደተለቀቀች ፡ ወዲያውኑ ፡ በረረች
5. ቻለ. You are free to go at any time. በፈለግኸው ፡ ጊዜ ፡ ለመሄድ ፡ ትችላለህ
6. መብት ፡ አለው. She's not free to marry anyone she wants. የፈቀደችውን ፡ የማግባት ፡ መብት ፡ የላትም

**be free from pain** ሕመሙ ፡ ለቀቀው
I am free from pain only after swallowing this pill. ይህንን ፡ ኪኒን ፡ ከዋጥኩ ፡ በኋላ ፡ ሕመሙ ፡ ለቀቀኝ

**be free of** የለበትም
The highway is now free of rocks. አውራ ፡ መንገዱ ፡ አሁን ፡ ድንጋይ ፡ የለበትም

**be free with one's money** ገንዘቡን ፡ ያለ ፡ ሐሳብ ፡ አወጣ
The reason he is always broke is that he is free with his money. ሁልጊዜ ፡ የሚቸግረው ፡ ገንዘቡን ፡ ያለ ፡ ሐሳብ ፡ ስለሚያወጣ ፡ ነው

**let free** በነጻ ፡ ለቀቀ
The police let him free. ፖሊሶች ፡ በነጻ ፡ ለቀቁት

**on one's own free will** በገዛ ፡ ፈቃዱ
He did it on his own free will. በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ አደረገው

**set free** በነጻ ፡ ለቀቀ
He set the prisoners free. እስረኞቹን ፡ በነጻ ፡ ለቀቃቸው
[See also 'charge, pretense, rein, tax']

**freeborn** ነጻ
He is a freeborn person, not a slave. ነጻ ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ ባሪያ ፡ አይደለም

**freedom**
1. ነጻነት. The fight for freedom is on. ለነጻነት ፡ የሚደረገው ፡ ትግል ፡ ተጀምሯል
He championed freedom of speech. ለንግግር ፡ ነጻነት ፡ ተጋደለ
2. መብት. Censorship impinges on our freedom. ሳንሱር ፡ መብታችንን ፡ ይነካል
*The tight coat hindered his freedom of movement. ጠባብ ፡ ኮቱ ፡ እንደልብ ፡ አላላውስ ፡ አለው
*The clerk was given a warning about the freedom of his manner with customers. ሻጩ ፡ ከደንበኞቹ ፡ ጋር ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ስላበዛ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ተሰጠው
*The guest has the freedom of our home. እንግዳው ፡ በቤታችን ፡ እንደልቡ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

**give freedom from** ተከላከለ
Screens give us comparative freedom from flies. መጋረጃዎች ፡ ዝንቦችን ፡ በመጠኑ ፡ ይከላከላሉ
[See also 'press, regain']

**free-for-all** አምባጓሮ
The dance ended in a free-for-all. ዳንሱ ፡ በአምባጓሮ ፡ ተፈጸመ

**freely**
1. በግልጽ. He admitted freely that he took it. እሱ ፡ መውሰዱን ፡ በግልጽ ፡ አመነ
2. ያለ ፡ ቁጥጥር. You can cross the border between the United States and Canada freely. በአሜሪካንና ፡ በካናዳ ፡ መሀከል ፡ ያለውን ፡ ወሰን ፡ ያለ ፡ ቁጥጥር ፡ ለማለፍ ፡ ትችላለህ
*You can speak freely. እንደፈለግህ ፡ ተናገር

**freeman** ነጻ ፡ ሰው
Freeman means a man who is not a slave. ነጻ ፡ ሰው ፡ ባሪያ ፡ ያልሆነ ፡ ማለት ፡ ነው።

**freethinker**
*There are many freethinkers in this country. በሃይማኖት ፡ ረገድ ፡ በራሳቸው ፡ አስተሳሰብ ፡ የሚመሩ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ አሉ

**freeze** (froze, frozen), vt.
1. አቀዘቀዘ. He froze vegetables to keep them from spoiling. ቅጠላ ፡ ቅጠሎቹ ፡ እንዳይበላሹ ፡ አቀዘቀዛቸው
2. አገደ. The government has frozen all foreign accounts. መንግሥቱ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሒሳቦችን ፡ ሁሉ ፡ አገደ
3. መታ. The cold froze the buds. እምቡጡን ፡ ውርጭ ፡ መታው

**freeze** (vi.)
1. ረጋ. The water in the pitcher froze during the night. ሌሊት ፡ ማሰሮው ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ ውኃ ፡ ረጋ

The pipe froze and then burst. ቧምቧው ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ውኃ ፡ ስለረጋ ፡ ቧምቧው ፡ ፈነዳ
2. በረዶ ፡ ሆነ. The plant froze during the night. ሌሊት ፡ ዕፁ ፡ በረዶ ፡ ሆነ
3. ብርድ ፡ አቈራመደ(ው). +We froze all winter long. ክረምቱን ፡ በሙሉ ፡ ብርድ ፡ አቈራመደን
4. በድን ፡ ሆነ. He froze with terror. በድንጋጤ ፡ በድን ፡ ሆነ

**freeze off** በረዶ ፡ ሆነ
My ears nearly froze off. ጆሮዬ ፡ በረዶ ፡ ሊሆን ፡ ምንም ፡ አልቀረው

**be frozen**
1. ቀዘቀዘ. The meat in the icebox is frozen. በረዶ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሥጋ ፡ ቀዝቅዟል
2. በረዶ ፡ ሆነ. The pond is frozen. ኩሬው ፡ በረዶ ፡ ሆነ

**be frozen hard** ድንጋይ ፡ በረዶ ፡ ሆነ
The lake was frozen hard. ሐይቁ ፡ ድንጋይ ፡ በረዶ ፡ ሆኖ ፡ ነበር

**be frozen to the spot** በድን ፡ ሆነ
He was frozen to the spot in horror. ከድንጋጤ ፡ የተነሣ ፡ በድን ፡ ሆነ

## freezer ማቀዝቀዣ
Take something out of the freezer for supper! ከማቀዝቀዣው ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለእራት ፡ አውጣ

## (be) freezing በጣም ፡ በረደ
It is freezing today. ዛሬ ፡ በጣም ፡ ይበርዳል

## freight (n.)
1. እቃ. The train conveys both passengers and freight. ባቡሩ ፡ ሰውም ፡ እቃም ፡ ይጭናል
2. እቃ ፡ ለመላክ ፡ ዋጋ. How much is the freight on the train? በባቡር ፡ እቃ ፡ ለመላክ ፡ ዋጋው ፡ ስንት ፡ ነው ?
3. ማጓጓዣ. The goods were sent by freight. ሸቀጦቹ ፡ በማጓጓዣ ፡ ተልከዋል
4. ጭነት. They trucked the freight to the warehouse. ጭነቱን ፡ ወደ ፡ መጋዘን ፡ በመኪና ፡ ወሰዱት

**freight** (adj.) የእቃ ፡ ማመላለሻ
The freight train was late again. የእቃ ፡ ማመላለሻው ፡ ባቡር ፡ አሁንም ፡ ዘገየ

**by air freight** ባየር
The box is so large, I had to send it by air freight. ሣጥኑ ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ስለሆነ ፡ ባየር ፡ መላክ ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ

## freighter የጭነት ፡ መርከብ
Freighters carry our products to foreign countries. የጭነት ፡ መርከቦች ፡ የንግድ ፡ እቃችንን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ያጓጉዛሉ

## French
1. ፈረንሳዊ. He looks French to me. ፈረንሳዊ ፡ ይመስለኛል
2. ፈረንሳይኛ. French is taught in many high schools. በብዙ ፡ ሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ይሰጣል

## Frenchman ፈረንሳዊ

## frenzy ኀይለኛ ፡ ስሜት
The speaker roused the audience to frenzy. ተናጋሪው ፡ ባድማጮቹ ፡ ላይ ፡ ኀይለኛ ፡ ስሜት ፡ ቀሰቀሰ

**be in a frenzy** እብድ ፡ ሆነ
The woman was in a frenzy because of the missing child. ሴትዮዋ ፡ ከልጅዋ ፡ መጥፋት ፡ የተነሣ ፡ እብድ ፡ ሆና ፡ ነበር

## frequency (frequencies) ድግግሞሽ
What is the frequency of the Addis Ababa radio station? የአዲስ ፡ አበባ ፡ ሬዲዮ ፡ ጣቢያ ፡ ድግግሞሹ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?
*We are alarmed by the frequency of fires in the neighborhood. ባካባቢያችን ፡ ደጋግሞ ፡ እሳት ፡ በመነሣቱ ፡ ደነገጥን
*The frequency of earthquakes in Addis Ababa is low. በአዲስ ፡ አበባ ፡ የመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይደርስም

## frequent (v.) አዘወተረ
He no longer frequents bars and coffeehouses. መጠጥ ፡ ቤትና ፡ ቡና ፡ ቤትን ፡ ማዘውተር ፡ ትቷል

## frequent (adj.)
1. አዘውትሮ ፡ የሚያደርግ. His frequent trips cost him a lot of money. አዘውትሮ ፡ የሚያደርገው ፡ ጉዞ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ፈጀበት
2. የተደጋገመ. The frequent mishaps boded disaster. የተደጋገሙት ፡ አደጋዎች ፡ የመዓት ፡ ምልክቶች ፡ ነበሩ

**be frequent** በዛ
Storms are frequent in the rainy season. በክረምት ፡ ወራት ፡ ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ይበዛል

## frequently ብዙ ፡ ጊዜ ፤ አዘውትሮ
I see him frequently. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አገኘዋለሁ
He drives frequently. አዘውትሮ ፡ ይነዳል

## fresh
1. ትኩስ. Are the eggs fresh? እንቁላሎቹ ፡ ትኩስ ፡ ናቸው ?

This newspaper prints only fresh news. ይህ ፡ ጋዜጣ ፡ ትኩስ ፡ ወሬዎችን ፡ ብቻ ፡ ያወጣል
Where can I buy fresh meat? ትኩስ ፡ ሥጋ ፡ ልገዛ ፡ የምችለው ፡ የት ፡ ነው ?
2. ያልዋለ ፡ ያላደረ. Please get me some fresh vegetables at the market! ከገበያ ፡ ያልዋለ ፡ ያላደረ ፡ አትክልት ፡ አምጣልኝ
3. አዲስ ፡ የተቀጠፈ. There is a big demand for fresh fruit. አዲስ ፡ የተቀጠፉ ፡ ፍሬፍሬዎች ፡ ብዙ ፡ ፈላጊ ፡ አላቸው
4. ተፈልቶ ፡ ያልቆየ. I drink only fresh coffee. ተፈልቶ ፡ ያልቆየ ፡ ቡና ፡ ብቻ ፡ እጠጣለሁ
5. አዲስ. Take a fresh sheet of paper and start again! አዲስ ፡ ወረቀት ፡ ውሰድና ፡ እንደገና ፡ ጀምር
He presented a fresh approach to the problem. ለችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ አዲስ ፡ ዘዴ ፡ ፈጠረ
6. ንጹሕ. Let's go out for some fresh air! እስቲ ፡ ወጣ ፡ ብለን ፡ ንጹሕ ፡ አየር ፡ እንቀበል
7. ፈሳሽ. The water of the pond will stagnate if no fresh water flows into it. የኩሬ ፡ ውኃ ፡ ከፈሳሽ ፡ ውኃ ፡ ካልተቀላቀለ ፡ ስለቆመ ፡ ይሸታል

**fresh complexion** የፊት ፡ ጥራት ፤ ወዝ
Her fresh complexion is due to her good health and her youth. የፊቷ ፡ ጥራት ፡ (ወዟ) ፡ ከወጣትነቷና ፡ ከጤንነቷ ፡ የተነሣ ፡ ነው

**fresh kid** ወጠጤ
I cannot stand that fresh kid. ያንን ፡ ወጠጤ ፡ ልታገሠው ፡ አልችልም

**(be) fresh water** ጨው ፡ የለበትም
Most lakes are fresh water. አብዛኞዎቹ ፡ ሐይቆች ፡ ጨው ፡ የለባቸውም

**be fresh** ጉልቶ ፡ ታየው
The memories of the war are still fresh in my mind. የጦርነቱ ፡ ትዝታ ፡ አሁንም ፡ በአእምሮዬ ፡ ውስጥ ፡ ጉልቶ ፡ ይታየኛል

**be fresh (from)** ገና ፡ ወጣ
He's just fresh from school and has no experience. ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ገና ፡ መውጣቱ ፡ ነው ፤ ምንም ፡ ልምምድ ፡ የለውም

**feel fresh** ነቃ ፡ አለ
The old man feels fresh after a nap. ሽማግሌው ፡ ከሸለብታ ፡ በኋላ ፡ ነቃ ፡ ብሏል

**get fresher**
*He gets fresher by the day. ብልግናው ፡ በየቀኑ ፡ እየጨመረ ፡ ይሄዳል

**freshen** (= intr.) አንሰራራ
+We need a good rain to freshen the flowers. አበባዎቹ ፡ እንዲያንሰራሩ ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ዝናብ ፡ እንፈልጋለን

**freshen up** ተጣጥቦ ፡ ልብሱን ፡ ለወጠ
After the long trip, we all freshened up. ከረጅሙ ፡ ጉዞ ፡ በኋላ ፡ ተጣጥበን ፡ ልብሳችንን ፡ ለወጥን

**freshman** የመጀመሪያ ፡ ዓመት ፡ ተማሪ
My brother is a freshman. ወንድሜ ፡ የመጀመሪያ ፡ ዓመት ፡ ተማሪ ፡ ነው

**fret** (fretted), vt. ቦርቡሮ ፡ አወጣ
The stream fretted a channel in the rock. ጅረቱ ፡ ድንጋዩን ፡ ቦርቡሮ ፡ ቦይ ፡ አወጣ

**fret** (vi.)
1. ተነጫነጨ. A baby frets in hot weather. ሕፃን ፡ በሙቀት ፡ ጊዜ ፡ ይነጫነጫል
2. ተበሳጨ. Don't fret about things you can't change! ልትለውጠው ፡ በማትችለው ፡ ነገር ፡ አትበሳጭ

**(be) fretful** ተጨነቀ
She is fretful about the coming examinations. ስለሚመጡት ፡ ፈተናዎች ፡ ተጨንቃለች

**friable** በቀላሉ ፡ የሚፈረከስ
There is a lot of friable rock in this region. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ብዙ ፡ በቀላሉ ፡ የሚፈረከስ ፡ ድንጋይ ፡ አለ

**friction**
1. ማፋጨት. Matches are lighted by friction. ክብሪት ፡ የሚጫረው ፡ በማፋጨት ፡ ነው
2. ግጭት. There is friction between the two. በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ግጭት ፡ አለ

**Friday** ዓርብ

**fried** (adj.), ~ **chicken** የዶሮ ፡ ጥብስ
I ate fried chicken at lunch. ለምሳ ፡ የዶሮ ፡ ጥብስ ፡ በላሁ

**fried eggs** ጥብስ ፡ እንቁላል
In the morning I eat fried eggs. ጧት ፡ ጧት ፡ ጥብስ ፡ እንቁላል ፡ እበላለሁ

**friend** ወዳጅ
He is a good friend of mine. ጥሩ ፡ ወዳጄ ፡ ነው
*They parted good friends. በፍቅር ፡ ተለያዩ

**close friend** የቅርብ ፡ ጓደኛ
The two are close friends. ሁለቱ ፡ የቅርብ ፡ ጓደኞች ፡ ናቸው

**become friends** ተወዳጁ ፤ ወዳጆች ፡ ሆኑ
The boy and the girl became friends. ልጁና ፡ ልጅቱ ፡ ተወዳጁ
Please settle your differences and become friends again! እባካችሁ ፡ ታረቁና ፡ እንደ ፡ ድሮዋችሁ ፡ ወዳጆች ፡ ሁኑ

**make friends** ወዳጅ ፡ አበጀ

Do you make friends easily? በቀላሉ ፡ ወዳጅ ፡ ማበጀት ፡ ትችላለህ ?

[See also 'bosom']

**friendliness** የወዳጅነት ፡ አቀራረብ ፤ ተጫዋችነት

His friendliness charmed the audience. የሱ ፡ የወዳጅነት ፡ አቀራረብ ፡ አድማጮቹን ፡ ማረከ

His only redeeming feature is his friendliness. መጥፎ ፡ ጠባዩን ፡ ችላ ፡ የሚያስኘለት ፡ ተጫዋችነት ፡ ብቻ ፡ ነው

**friendly**

1. ሰው ፡ ወዳድ. He is friendly by nature. እርሱ ፡ በተፈጥሮ ፡ ሰው ፡ ወዳድ ፡ ነው

The employees of this bank are friendly. የዚህ ፡ ባንክ ፡ ሠራተኞች ፡ ሰው ፡ ወዳዶች ፡ ናቸው

2. ወዳጅ. The defector sought refuge in a friendly embassy. ከዳተኛው ፡ በወዳጅ ፡ ኤምባሲ ፡ ውስጥ ፡ ጥገኝነት ፡ ፈለገ

3. የወዳጅነት. She has a friendly smile for everybody. ለሁሉም ፡ የወዳጅነት ፡ ፈገግታ ፡ ታሳያለች

There are friendly relations between these two countries. በነዚህ ፡ ሁለት ፡ አገሮች ፡ መሀከል ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ አለ

4. የወዳጅነት ፡ መልክ ፡ የሚያሳይ. He looked at the friendly stranger with distrust. የወዳጅነት ፡ መልክ ፡ የሚያሳየውን ፡ እንግዳ ፡ በጥርጣሬ ፡ ተመለከተ

5. ሰላማዊ. Don't be afraid! He is a friendly dog. አትፍራ ፤ ሰላማዊ ፡ ውሻ ፡ ነው

*Our dog is very friendly. ውሻችን ፡ ሰው ፡ አይተናከሉም

**friendly relations** ወዳጅነት

The government is trying to maintain friendly relations with all countries. መንግሥቱ ፡ ከሁሉም ፡ ሀገሮች ፡ ጋር ፡ ወዳጅነት ፡ ለማቆየት ፡ ይሞክራል

**act friendly**

He always acts friendly. ሁልጊዜ ፡ የወዳጅነት ፡ ጠባይ ፡ ያሳያል

**in a friendly way** በወዳጅነት

The argument was settled in a friendly way. ክርክሩ ፡ በወዳጅነት ፡ ተፈጸመ

[See also 'footing']

**friendship** ወዳጅነት

Friendship between people of different religions is not rare. በሃይማኖት ፡ በተለያዩ ፡ ሰዎች ፡ መኻል ፡ ወዳጅነት ፡ አይጠፋም

[See also 'tie']

**fright** ድንጋጤ ፤ ፍርሃት

Fright showed in her face. ፊቷ ፡ ላይ ፡ ድንጋጤ ፡ (ፍርሃት) ፡ ታየ

**take fright** በጣም ፡ ፈራ

He took fright when he saw the snake. እባቡን ፡ ሲያይ ፡ በጣም ፡ ፈራ

**frighten** (vt.)

1. አስፈራራ. You always frighten me. ሁልጊዜ ፡ ታስፈራራኛለህ

2. አስበረገገ. The battle cry of the patriots frightened the enemy. ያርበኞቹ ፡ ቀረርቶ ፡ ጠላትን ፡ አስበረገገው

3. አስደነገጠ. Don't let that frighten you! ያ ፡ አያስደንግጥህ

**frighten** (vi.) ደነገጠ

He frightens easily. በቀላሉ ፡ ይደነግጣል

**be frightened** ፈራ

Don't be frightened! Nothing will happen to you. አትፍራ ፤ ምንም ፡ አይነካህም

**frightful**

1. አሰቃቂ. I saw a frightful accident on the road. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ አሰቃቂ ፡ አደጋ ፡ አየሁ

2. ኀይለኛ. There was a frightful crush at the gate. በበሩ ፡ ላይ ፡ ኀይለኛ ፡ ግፊያ ፡ ነበር

**frigid**

1. በጣም ፡ ቀዝቃዛ. A frigid climate prevails in this region. በዚህ ፡ አካባቢ ፡ በጣም ፡ ቀዝቃዛ ፡ አየር ፡ አለ

We received a frigid welcome. ቀዝቃዛ ፡ አቀባበል ፡ ተደረገልን

2. የበረዶ. In the frigid zone, plants cannot grow. በዓለም ፡ የበረዶ ፡ ክበብ ፡ ዕፀዋት ፡ አይበቅሉም

**frill** ብልጭልጭ

The new cars have many frills. አዲሶቹ ፡ መኪናዎች ፡ ብልጭልጭ ፡ ይበዛቸዋል

**fringe** (vi.)

Bushes fringed the road. በመንገዱ ፡ ዳርና ፡ ዳር ፡ ቁጥቋጦ ፡ በቅሏል

**fringe** (n.)

1. ዘርፍ. There is a fringe on the curtain. መጋረጃው ፡ ዘርፍ ፡ አለው

2. ጥለት. She cheapened her dress by adding a fringe to it. ልብሷ ፡ ላይ ፡ ጥለት ፡ ቀጥላ ፡ አበላሸችው

3. ጠርዝ. The fringes of the leaves turned brown. የቅጠሉ ፡ ጠርዝ ፡ ወደ ፡ ቡናማ ፡ ተለወጠ

4. ዳር ፡ ዳር. One sees deer at the fringes of the forest. በጫካው ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ አጋዘን ፡ ይታያል
5. ወገን. In Latin America, the radical fringe is trying to take over the universities. በላቲን ፡ አሜሪካ ፡ ተራማጁ ፡ ወገን ፡ ዩኒቨርሲቲውን ፡ በ እጁ ፡ ለማድረግ ፡ ይሞክራል

**frisk** ቦረቀ
Our puppy frisks all over the house. ቡችላች ን ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይቧርቃል

**frisky** ተጫዋች
A frisky kitten was playing with the string. ተጫዋቿ ፡ የድመት ፡ ግልገል ፡ ከገመዱ ፡ ጋር ፡ ትጫወት ፡ ነበር

**fritter, ~ away** በተነ
He fritters away his money. ገንዘቡን ፡ ይበትናል

**frivolous**
1. አስተሳሰቡ ፡ ቀላል ፡ የሆነ. A thoughtful book will not be appreciated by a frivolous person. አስተሳሰቡ ፡ ቀላል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ጥልቅ ፡ መጽ ሐፍ ፡ አያደንቅም
2. (= adv.) በከንቱ. He likes to make frivolous remarks. በከንቱ ፡ መናገር ፡ ይወዳል

**fro,** see **to**

**frog** እንቁራሪት
There are many frogs in this pond. በዚህ ፡ ኩ ሬ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ እንቁራሪት ፡ አለ

**frolic** (frolicked) ቦረቀ
The children frolicked with the puppy. ልጆቹ ፡ ከቡችላው ፡ ጋር ፡ ቦረቁ

**from**
1. ከ. I received a letter from my brother. ከወንድሜ ፡ ደብዳቤ ፡ ደረሰኝ
He was tired from overwork. ከሥራ ፡ ብዛት ፡ ደክሞት ፡ ነበር
What prevented you from coming? ከመምጣት ፡ ምን ፡ አገደህ ?
2. በ. My brother is suffering from a cold. ወንድሜ ፡ በጉንፋን ፡ ይሠቃያል
3. በ - - - ምክንያት. No fewer than twenty workers were absent from illness. ከሀያ ፡ የማያንሱ ፡ ሠራተኞች ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ቀርተው ፡ ነበር
4. በ - - - በኩል. I saw it from the window. በመስኮት ፡ በኩል ፡ አየሁት
5. ከ - - - ርቆ. I live ten miles from the city. ከከተማ ፡ ዐሥር ፡ ማይል ፡ ርቄ ፡ እኖራለሁ
*He is from Harar. የሐረር ፡ ሰው ፡ ነው
*Where are you from? አገርህ ፡ የት ፡ ነው ?
**from what he says** እሱ ፡ እንደሚለው ፡ ከሆነ
From what he says, it must be very interesting. እሱ ፡ እንደሚለው ፡ ከሆነ ፡ ነገሩ ፡ በጣም ፡ አስ ደሳች ፡ መሆን ፡ አለበት
[See also 'aside, now, nowhere, then']

**front** (v.)
*They decided to front the building with bricks. የሕንጻውን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሸክላ ፡ ለማ ሠራት ፡ ወሰኑ
*Our house fronts the lake. ቤታችን ፡ ከሐይ ቁ ፡ ትይዩ ፡ ነው

**front** (n.)
1. ደጃፍ. The front of the house is painted white. የቤቱ ፡ ደጃፍ ፡ ነጭ ፡ ቀለም ፡ ተቀብቷል
2. ፊት. Sit down, you in front! አንተ ፡ እፊት ፡ ያለኸው ፤ ተቀመጥ
3. መጀመሪያ. The table of contents is in the front of the book. ማውጫው ፡ በመጽሐፉ ፡ መጀመሪያ ፡ ይገኛል
4. የጦር ፡ ግንባር ፤ የጦርነት ፡ ግንባር. The captain was at the front during the campaign. ሻምበሉ ፡ በዘመቻው ፡ ጊዜ ፡ በጦሩ ፡ (በጦርነቱ) ፡ ግንባር ፡ ላይ ፡ ነበር
**in front of**
1. ፊት ፡ ለፊት ፤ ከ - - - ፊት ፡ ለፊት. Let's meet in front of the post office! ፖስታ ፡ ቤቱ ፡ ፊ ት ፡ ለፊት ፡ እንገናኝ
He has a bed of flowers in front of his house. ከቤቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያበባ ፡ መደብ ፡ አለው
2. ፊት ፡ ፊት. He marched in front of me all the way. እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ፊት ፡ ፊቴ ፡ ተጓዘ
3. ደጃፍ. Mendicants are forbidden to sit in front of our hotel. ለማኞች ፡ ሆቴላችን ፡ ደጃፍ ፡ እንዳይቀመጡ ፡ ተከልክለዋል
**front** (adj.)
1. ፊተኛ. We had seats in the front row. በፊተ ኛው ፡ ረድፍ ፡ ተቀምጠን ፡ ነበር
2. የፊት. He bit his lips with his front teeth. ከንፈሩን ፡ በፊት ፡ ጥርሱ ፡ ነከሰው
3. የመጀመሪያ. Our teacher made the front page of the Amharic newspaper. መምህራችን ፡ ባማ ርኛው ፡ ጋዜጣ ፡ በመጀመሪያ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ወጣ
[See also 'pull up']

**frontage**
*The frontage of this property is 150 feet. መን ገዱ ፡ ዳር ፡ ያለው ፡ የመሬት ፡ ርዝመት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ጫማ ፡ ነው

**frontier** ወሰን
The frontier was closed. ወሰኑ ፡ ተዘግቶ ፡ ነበር

**front line** የጦር ፡ ግንባር
More soldiers were hurried to the front lines. ወደ ፡ ጦሩ ፡ ግንባር ፡ ተጨማሪ ፡ ወታደሮች ፡ በፍጥነት ፡ ተላኩ

**frost**
1. ውርጭ. We will have frost tomorrow. ነገ ፡ ውርጭ ፡ ይሆናል
2. አመዳይ. There was frost on the trees. ዛፎች ፡ ላይ ፡ አመዳይ ፡ ነበረ

**frosty, ~ weather** ውርጭ
The crops might be damaged by frosty weather. እህሉ ፡ በውርጭ ፡ ምክንያት ፡ ይጠፋ ፡ ይሆናል

**froth**
1. አረፋ. She beat the milk until it was covered with froth. አረፋ ፡ እስኪሞላው ፡ ድረስ ፡ ወተቱን ፡ ናጠችው
There was froth on the mouth of the child who had eaten poison. መርዝ ፡ የበላው ፡ ልጅ ፡ አፉ ፡ ላይ ፡ አረፋ ፡ ነበረ
2. ለሀጭ. If you see a dog with froth on its mouth, don't let it bite you. ለሀጩን ፡ የሚያዝረከርክ ፡ ውሻ ፡ እንዳይነክስህ ፡ ተጠንቀቅ

**frown** (v.) ግንባር ፡ ቋጠረ
Why are you frowning at me like that? ለምን ፡ እንደዚህ ፡ ግንባርህን ፡ ትቋጥርብኛለህ ?

**frown on** ጠላ
He frowns on gambling. ቁማርን ፡ ይጠላል

**frown upon** ናቀ
He frowned upon our scheme. እቅዳችንን ፡ ናቀብን

**frown** (n.) ፊትን ፡ መቋጠር ፤ ግንባርን ፡ መቋጥር
A frown marked her displeasure. አለመደሰቷ ፡ ፊቷን ፡ (ግንባሯን) ፡ ከመቋጠሯ ፡ ታወቀ

**froze,** see **freeze**

**frozen** (adj.)
1. የረጋ. They crossed the frozen lake easily. የረጋውን ፡ ሐይቅ ፡ በቀላሉ ፡ ተሻገሩት
2. በብርድ ፡ የደነዘዘ. His frozen fingers are insensible to pain. በብርድ ፡ የደነዘዙ ፡ ጣቶቹ ፡ ሕመም ፡ አይሰማቸውም
[See also 'freeze, solid']

**fructify** (fructified) ለማ
With careful tending, the soil will fructify. በጥንቃቄ ፡ ከተያዘ ፡ አፈሩ ፡ ይለማል

**frugal**
1. ቆጣቢ. She is a frugal housewife. ቆጣቢ ፡ የቤት ፡ እመቤት ፡ ናት
2. ቀላል. He ate a frugal supper. ቀላል ፡ እራት ፡ በላ

**fruit** (n.)
1. ፍሬ. Papaya is a fruit that is grown in the Awash valley. ፓፓያ ፡ በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ የሚበቅል ፡ ፍሬ ፡ ነው
His invention is the fruit of much effort. የሱ ፡ ፍልሰፋ ፡ የብዙ ፡ ጥረት ፡ ፍሬ ፡ ነው
2. ፍራፍሬ. Do you have any fresh fruit? ያልዋለ ፡ ያላደረ ፡ ፍራፍሬ ፡ አለህ ?

**bear fruit**
1. አፈራ. This tree bears no fruit. ይህ ፡ ዛፍ ፡ አያፈራም
2. ፍሬ ፡ ሰጠ. I hope your hard work will bear fruit. ብርቱ ፡ ሥራህ ፡ ፍሬ ፡ እንደሚሰጥ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ

**fruit** (adj.) የፍሬ
Fruit trees are cultivated by the farmers. ገበሬዎች ፡ የፍሬ ፡ አትክልት ፡ ያለማሉ

**fruitful** ፍሬያማ
His research into plant life proved fruitful. ስለ ፡ ዕፀዋት ፡ ሕይወት ፡ ያደረገው ፡ ምርምር ፡ ፍሬያማ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

**fruition**
*After much labor, he finally brought his idea to full fruition. ከብዙ ፡ ድካም ፡ በኋላ ፡ ሐሳቡ ፡ ፍሬ ፡ አስገኘለት

**fruitless** ፍሬ ፡ ቢስ
He made a fruitless search for the lost money. የጠፋውን ፡ ገንዘቡን ፡ ለማግኘት ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ፍለጋ ፡ አደረገ

**frustrate** አከሸፈ
Our army frustrated the enemy's plans. ጦራችን ፡ የጠላትን ፡ እቅድ ፡ አከሸፈ

**be frustrated** (= active) አበሳጨ
He is constantly frustrated by his lack of skill in sports. በስፖርት ፡ ቅልጥፍና ፡ ማጣቱ ፡ ዘወትር ፡ ያበሳጨዋል

**fry** (fried) ጠበሰ
Shall I fry the fish? ዓሣውን ፡ ልጥበሰው ?

**frying pan** መጥበሻ
Since I had no clean pot, I heated the sauce in the frying pan. ንጹሕ ፡ ብረት ፡ ድስት ፡ አጥቼ ፡ ወጡን ፡ በመጥበሻ ፡ አሞቅሁት

**fuel** ነዳጅ
Coal and wood are used as fuels. ከሰልና ፡ ዕንጨት ፡ እንደ ፡ ነዳጅ ፡ ይሠራባቸዋል

**be fuel to** አባሰ(በት)
His insults were fuel to her hatred. የሱ ፡ ስድብ ፡ ጥላቻዋን ፡ አባሰባት

**fueling** ነዳጅ ፡ መሙላት
Fueling of planes can be done in mid-air. በሰማይ ፡ ላይ ፡ ያውሮፕላን ፡ ነዳጅ ፡ ለመሙላት ፡ ይቻላል

**fueling station** የነዳጅ ፡ ማደያ ፡ ጣቢያ
There is now a fueling station for ships at Assab. አሁን ፡ አሰብ ፡ ውስጥ ፡ የመርከቦች ፡ የነዳጅ ፡ ማደያ ፡ ጣቢያ ፡ አለ

**fugitive**
1. የኰበለለ. They caught the fugitive convict. የኰበለለውን ፡ የተፈረደበት ፡ ወንጀለኛ ፡ ያዙት
2. የሚሸሽ ፡ ሰው. He is a fugitive from the law. እሱ ፡ ከሕግ ፡ የሚሸሽ ፡ ሰው ፡ ነው
3. ጊዜያዊ. His fugitive pleasures consisted of drinking beer whenever his wife was absent. ሚስቱ ፡ በሌለችበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ጊዜያዊ ፡ ደስታው ፡ ጠላ ፡ መጠጣት ፡ ነበር

**fulfill**
1. ፈጸመ. He fulfilled his promise. የገባውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ፈጸመ
2. ጠበቀ. An honest person fulfills his intention. ታማኝ ፡ ሰው ፡ ቃሉን ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቃል

**be fulfilled** ተከበረ
The specifications were not fulfilled, so the contract was voided. ዝርዝሮቹ ፡ ደንቦች ፡ ስላልተከበሩ ፡ ውሉ ፡ ፈረሰ

**fulfillment**
1. ቃልን ፡ መጠበቅ. There is always a lag between promise and fulfillment. ተስፋ ፡ መስጠትና ፡ ቃልን ፡ መጠበቅ ፡ አንድ ፡ አይደለም
2. ፍጻሜ. He finally witnessed the fulfillment of his dreams. በመጨረሻ ፡ የምኞቱን ፡ ፍጻሜ ፡ ተመለከተ

**full** (n.), **in** ~ በሙሉ
I paid the bill in full. ሒሳቡን ፡ በሙሉ ፡ ከፈልኩ

**to the full**
*She enjoyed life to the full. የልቧን ፡ ያህል ፡ ተደስታ ፡ ኖረች

**full** (adj.)
1. ሙሉ. The box is full; you cannot put anything in it. ሣጥኑ ፡ ሙሉ ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ልትከትበት ፡ አትችልም
Give me the full figure, and omit the fractions. ክፍልፋዩን ፡ ትተህ ፡ ሙሉውን ፡ ቁጥር ፡ ንገረኝ
2. የተሟላ. The papers carried a full account of the incident. ጋዜጣዎቹ ፡ ስለ ፡ ድርጊቱ ፡ የተሟላ ፡ ሐተታ ፡ አዝለው ፡ ነበር
3. ድብልብል. This girl has a full face. ይህች ፡ ልጅ ፡ ድብልብል ፡ ፊት ፡ አላት

**be full** ጠገበ
I cannot eat anymore. I am full. ስለጠገብኩ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ልበላ ፡ አልችልም

**be full of** ሞላ
The book is full of mistakes. መጽሐፉ ፡ ስሕተት ፡ ሞልቶበታል

**be completely full** ጢም ፡ ብሎ ፡ ሞላ
The confluent is completely full in the rainy months. ጅረቱ ፡ በክረምት ፡ ወራት ፡ ጢም ፡ ብሎ ፡ ይሞላል

**full** (adv.)
1. እስከ ፡ አፍ ፡ ገደፉ. Fill the pail full! ባልዲውን ፡ እስከ ፡ አፍ ፡ ገደፉ ፡ ሙላው
2. ሙሉ ፡ ለሙሉ. The ball hit him full in the face. ኳሱ ፡ ፊቱን ፡ ሙሉ ፡ ለሙሉ ፡ መታው

**full well** በደንብ
You know full well what I mean. ምን ፡ ማለቴ ፡ እንደሆነ ፡ በደንብ ፡ ታውቃለህ
[See also 'blast, force, growth, length, life, speed, stop, swing']

**full-grown**
1. ዐዋቂ. Only a full-grown man can lift this heavy stone. ይህንን ፡ ከባድ ፡ ደንጊያ ፡ ሊያነሣ ፡ የሚችል ፡ ዐዋቂ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ትልቅ. Full-grown elephants eat more than young elephants. ትልልቆቹ ፡ ዝሆኖች ፡ ከትንንሾቹ ፡ የበለጠ ፡ ይበላሉ

**be full-grown** አድጎ ፡ በቃው
The dog is full-grown. ውሻው ፡ አድጎ ፡ በቅቶታል

**full moon** ሙሉ ፡ ጨረቃ
Tomorrow is a full moon. ነገ ፡ ሙሉ ፡ ጨረቃ ፡ ይታያል

**fulltime** ሙሉ ፡ ቀን ፤ ሙሉ ፡ ጊዜ
Are you working fulltime now? አሁን ፡ ሙሉ ፡ ቀን ፡ (ጊዜ) ፡ ትሠራለህ ?

**fully**
1. በደንብ. He described it fully. በደንብ ፡ ገለጸው

2. በፍጹም. I am fully resolved to do it. ላደርገ ው ፡ በፍጹም ፡ ቈርጫለሁ

**be fully aware** ጠንቅቆ ፡ ዐወቀ
Are you fully aware of what is going on? ምን ፡ እንደሚደረግ ፡ ጠንቅቀህ ፡ ታውቃለህ ?

**fulminate** ፈነዳ
This chemical will fulminate if exposed to heat. ይህ ፡ ኬሚካል ፡ ለሙቀት ፡ የተጋለጠ ፡ እንደ ሆነ ፡ ይፈነዳል

**fulminate against** አወገዘ
The newspaper fulminated against taking bribes. ጋዜጣው ፡ ጉቦ ፡ መቀበልን ፡ አወገዘ

**fumble, ~ for**
1. በረበረ. He fumbled in his pockets for the key. ቁልፉን ፡ ፍለጋ ፡ ኪሱን ፡ በረበረ
2. ለማግኘት ፡ ተንገዛገዘ. He fumbled for the right expression. ተስማሚውን ፡ አባባል ፡ ለማግኘ ት ፡ ተንገዛገዘ

**fumble one's way** እየተሹለከለከ ፡ ሄደ
He fumbled his way through the crowded room. ሕዝብ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ባለበት ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ እየተሹለከለከ ፡ ሄደ

**fume** (v.)
1. ጨሰ. Something is fuming in the fireplace. ምድጃ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ይጨሳል
2. ደነፋ. He fumed because the bus was late. አውቶቡሱ ፡ ስለዘገየ ፡ ደነፋ

**fume** (n.) ጢስ
The fumes that escaped from the bottle were poisonous. ከጠርሙሱ ፡ የወጣው ፡ ጢስ ፡ መርዝ ፡ ነበር

**fumigate** ዐጠነ
They fumigated the room by burning sulphur. ድኝ ፡ በማጨስ ፡ ክፍሉን ፡ ዐጠኑት

**fun**
1. ጨዋታ. Let's try just for the fun of it! እስቲ ፡ ለጨዋታ ፡ ያህል ፡ እንሞክረው
2. ደስታ. She has spoiled all my fun. ደስ ታዬን ፡ ሁሉ ፡ አበላሸችብኝ
3. ቀልድ. I only said it in fun. ለቀልድ ፡ ነው ፡ ያልኩት

**be fun** ደስ ፡ አለ ፤ አስደሰተ
Fishing is a lot of fun. ዓሣ ፡ ማጥመድ ፡ በጣ ም ፡ ደስ ፡ ይላል
A picnic would be fun. ሽርሽር ፡ ያስደስታል

**for fun** ለቀልድ ፡ ብሎ
I just did it for fun. ያደረግሁት ፡ ለቀልድ ፡ ብ ዬ ፡ ነው

**make fun (of)** አላገጠ
The children made fun of the beggar. ሕፃናቱ ፡ በለማኙ ፡ አላገጡ
[See also 'poke']

**function** (v.) ሠራ
The radio doesn't function properly. ራዲዮኑ ፡ በደንብ ፡ አይሠራም
The editor functions as a reporter as well. የጋዜጣው ፡ አዘጋጅ ፡ እንደ ፡ ዜና ፡ አቀባይም ፡ ሆኖ ፡ ይሠራል

**function** (n.)
1. ሥራ. What is his function in the office? ቢሮ ፡ ውስጥ ፡ ሥራው ፡ ምንድን ፡ ነው ?
The function of the stomach is to digest food. የጨጓራ ፡ ሥራ ፡ ምግብን ፡ ማዋሐድ ፡ ነው
2. አሠራር. The teacher's comparison of the heart to a pump helped the student to understand its function. አስተማሪው ፡ ልቡን ፡ ከፖም ፕ ፡ ጋር ፡ ማነጻጸሩ ፡ ተማሪዎቹ ፡ አሠራሩን ፡ እን ዲረዱት ፡ ጠቀማቸው
3. ዓላማ. The function of education is to make people think. የትምህርት ፡ ዓላማ ፡ ሰዎችን ፡ እንዲያስቡ ፡ ለማድረግ ፡ ነው
4. ተግባር. It is the function of the newspaper to publish news. ወሬን ፡ ማተሙ ፡ የጋዜጣው ፡ ተግባር ፡ ነው
5. ሥነ ፡ ሥርዓት. The Emperor attends all official functions. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አፈሴላዊ ፡ በሆኑ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ይገኛሉ
[See also 'vital']

**functional**
*The functional design of this building shows its purpose clearly. አገልግሎቱን ፡ ከፕላኑ ፡ ለመ ረዳት ፡ የሚቻል ፡ ሕንጻ ፡ ዓላማውን ፡ በግልጽ ፡ ያሳያል

**functionary** (functionaries) ሠራተኛ
My brother is a functionary in the Foreign Ministry. ወንድሜ ፡ በውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ሠራተኛ ፡ ነው

**fund** (v.) ገንዘብ ፡ አገኘ
They will have to fund this project by selling bonds. ለዚህ ፡ ፕሮጀ ፡ ቦንድ ፡ በመሸጥ ፡ ገን ዘብ ፡ ማግኘት ፡ ይኖርባቸዋል

**fund** (n.)
1. መዋጮ. How much money did you contribute to the library fund? ለቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ መዋጮ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ አዋጥተሃል ?
2. የተመደበ. The school has a fund of $1,000 with which to buy books. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡

ለመጻሕፍት፡ መግዣ፡ የተመደበ፡ አንድ፡ ሺ፡ ብር፡ አለው

3. መጠን. His fund of knowledge is amazing. የዕውቀቱ ፡ መጠን ፡ አስደናቂ ፡ ነው

**fund of** ብዙ

There is a fund of knowledge in a dictionary. በመዝገበ፡ ቃላት፡ ውስጥ፡ ብዙ፡ ዕውቀት፡ ይገኛል

**funds**

1. ገንዘብ. We are short of funds and cannot buy anything for a while. ገንዘብ ፡ ስላጠረን ፡ ለጊዜው ፡ ምንም ፡ ልንገዛ ፡ አንችልም

2. እርዳታ. He is soliciting funds for a new building. ላዲስ ፡ ሕንጻ ፡ ማሠሪያ ፡ እርዳታ ፡ በመጠየቅ ፡ ላይ ፡ ነው

## fundamental መሠረታዊ

That's a fundamental difference. ያ ፡ መሠረታዊ ፡ ልዩነት ፡ ነው

## funeral ቀብር ፤ ሥርዓተ ፡ ቀብር ፤ የቀብር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት

I have to go to a funeral. ቀብር ፡ መሄድ ፡ አለብኝ

The question was whether to take the children to the funeral or leave them at home. ነገሩ ፡ ልጆቹን ፡ ወደ ፡ ሥርዓተ ፡ ቀብሩ ፡ (የቀብር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት) ፡ ይዞ ፡ መሄድ ፡ ወይም ፡ እቤት ፡ መተው ፡ ነበር

**funeral** (adj.)

1. የቀብር. A funeral march is very slow. የቀብር ፡ ማርሽ ፡ በጣም ፡ ዝግ ፡ ያለ ፡ ነው

2. በቀብሩ ፡ ላይ ፡ የተደረገ. We listened to the funeral oration in tears. በቀብሩ ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ ንግግር ፡ እንባ ፡ እያነቀን ፡ አዳመጥን

[See also 'cortege, oration, procession']

## funnel ማጥለያ

The funnel is too big for the bottle. ማጥለያው፡ ለጠርሙሱ ፡ ይበዛበታል

## funny

1. አሥቂኝ. That's a very funny story. ያ ፡ በጣም ፡ አሥቂኝ ፡ ታሪክ ፡ ነው

2. እንግዳ. I heard a funny noise during the night. ሌሊት ፡ እንግዳ ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ

You look so funny. Is something bothering you? ሁኔታህ ፡ እንግዳ ፡ ሆነብኝ ፤ የቸገረህ ፡ ነገር ፡ አለ ?

3. የሚያስገርም. I had a funny dream last night. ትናንትና ፡ ማታ ፡ አንድ ፡ የሚያስገርም ፡ ሕልም ፡ አየሁ

**sound funny** የማይመስል ፡ ሆኖ ፡ ታየ

His explanation sounds funny to me. የሰጠው ፡ ምክንያት ፡ የማይመስል ፡ ሆኖ ፡ ታየኝ

## fur

1. ጸጉር. Our cat has beautiful fur. ድመታችን ፡ ቆንጆ ፡ ጸጉር ፡ አላት

2. ያውሬ ፡ ጸጉር. Indians used to barter fur for rifles. ህንዶች ፡ ያውሬ ፡ ጸጉር ፡ በጠመንጃ ፡ ይለውጡ ፡ ነበር

3. ባለጸጉር ፡ ልብስ ፤ የጸጉር ፡ ልብስ. We put our furs in storage for the summer. ባለጸጉር ፡ (የጸጉር) ፡ ልብሳችንን ፡ ለበጋው ፡ ጊዜ ፡ ከተትነው

## furious

1. የተናደደ. The cashier tried to calm the furious woman. ገንዘብ ፡ ተቀባዩ ፡ የተናደደችውን ፡ ሴት ፡ ሊያበርድ ፡ ሞከረ

2. ኀይለኛ. A furious storm blew down many trees. ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ብዙ ፡ ዛፎች ፡ ገነዳደሰ

3. ከባድ. They smashed the enemy in a furious attack. ከባድ ፡ ማጥቃት ፡ አድርገው ፡ ጠላትን ፡ ድምጥማጡን ፡ አጠፉት

**be furious** በጣም ፡ ተናደደ

My boss will be furious if I don't come. ካልመጣሁ ፡ አለቃዬ ፡ በጣም ፡ ይናደዳል

## furiously

1. በኀይል. The wind was blowing furiously. ነፋሱ ፡ በኀይል ፡ ይነፍስ ፡ ነበር

2. እሳት ፡ ለብሶ. He entered the office furiously and began to shout at everyone. እሳት ፡ ለብሶ ፡ ወደ ፡ቢሮው ፡ ገባና ፡ በሁሉ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ መጮኽ ፡ ጀመረ

## furl ጠቀለለ

The boys broke camp and furled the tent. ልጆቹ ፡ ጓዛቸውን ፡ ለማንሣት ፡ ድንኳናቸውን ፡ ጠቀለሉ

## furlough ፈቃድ

He is on furlough, but will return to his battalion soon. በፈቃድ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ግን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሻለቃው ፡ ይመለሳል

## (be) furloughed ፈቃድ ፡ ተሰጠ

The troops were furloughed after their stay in the desert. ወታደሮቹ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ፈቃድ ፡ ተሰጣቸው

## furnace ምድጃ

There is no fire in the furnace. በምድጃው ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ የለም

## furnish

1. አቀረበ. Who furnishes supplies to the army? ለጦሩ ፡ ትጥቅና ፡ ሥንቅ ፡ የሚያቀርበው ፡ ማነው ?

Can you furnish proof? ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ትችላለህ ?

2. ሞላ. We will have to furnish the library with books. ቤተ ፡ መጻሕፍቱን ፡ መጻሕፍት ፡ መሙላት ፡ አለብን
3. እቃ ፡ አስገባ. I have not furnished my new apartment yet. ላዲሱ ፡ አፓርተማዬ ፡ ገና ፡ እቃ ፡ አላስገባሁም
4. ሰጠ. The sun furnishes heat. ፀሐይ ፡ ሙቀት ፡ ትሰጣለች

**furnished room** ክፍል ፡ ከነሙሉ ፡ እቃው
I want a furnished room. አንድ ፡ ክፍል ፡ ከነሙሉ ፡ እቃው ፡ እፈልጋለሁ

**furniture** የቤት ፡ እቃ
We still have to buy some furniture. ገና ፡ የቤት ፡ እቃ ፡ መግዛት ፡ አለብን

**furor**
1. ሽብር. The news caused a furor. ወሬው ፡ ሽብር ፡ ፈጠረ
2. ሁከት. Despite all the furor around him, John remained calm and collected. ብዙ ፡ ሁከት ፡ ቢከበውም ፡ ጆን ፡ ራሱን ፡ ገቶ ፡ ዝም ፡ አለ
*His new book caused quite a furor. አዲሱ ፡ መጽሐፉ ፡ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ስሜት ፡ ቀሰቀሰ

**raise a furor** አስቆጣ
His appointment raised a furor in our office. የሱ ፡ መሾም ፡ መሥሪያ ፡ ቤታችንን ፡ አስቆጣ

**furrow** (v.) አኰማተረ
Trouble had furrowed his brow. ችግር ፡ ግንባሩን ፡ አኰማትሮታል

**furrow** (n.)
1. ትልም. The farmer sows seed in the furrows of the field. ገበሬው ፡ በማሳው ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ትልም ፡ ላይ ፡ ዘር ፡ ይዘራል
2. መቋጠር. The furrow of his brow shows that he is deep in thought. የግንባሩ ፡ መቋጠር ፡ በሐሳብ ፡ መዋጡን ፡ ያመለክታል

**further** (v.)
1. እንዲስፋፋ ፡ አደረገ. The United Nations is trying to further the cause of peace. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሰላም ፡ እንዲስፋፋ ፡ ለማድረግ ፡ በመጣር ፡ ላይ ፡ ነው
2. አደራጀ. He only furthers his own interest. የገዛ ፡ ፍላጎቱን ፡ ብቻ ፡ ያደራጃል

**further** (adj.)
1. ሌላ. The bank refused further credit to the firm. ባንኩ ፡ ለንግዱ ፡ ድርጅት ፡ ሌላ ፡ ብድር ፡ ከለከለ
2. ተጨማሪ. Do you need further help? ተጨማሪ ፡ እርዳታ ፡ ትፈልጋለህ ?
3. (= adv.)በተጨማሪ. For further information, write to the director. በተጨማሪ ፡ ለመረዳት ፡ ለዲሬክተሩ ፡ ጻፍ
4. (= adv.) ከዚህ ፡ ወዲያ. Further meetings seem pointless. ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ መሰብሰብ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ አይመስልም
5. (= adv.) ከዚህም ፡ ይበልጥ. Does this mean a further delay? ከዚህም ፡ ይበልጥ ፡ ይዘገያል ፡ ማለት ፡ ነው ?
*This store will be closed until further notice. ሌላ ፡ መግለጫ ፡ እስኪተሰጠ ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ መደብር ፡ ዝግ ፡ ይሆናል

**further** (adv.)
1. ወደ ፡ ፊት. You'll have to walk a little further. ጥቂት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ መሄድ ፡ ያስፈልግሃል
2. ከዚህም ፡ በላይ. Further, I want you to leave at once. ከዚህም ፡ በላይ ፡ በፍጥነት ፡ እንድትሄድ ፡ እፈልጋለሁ
3. በይበልጥ. Inquire further into the matter! ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ በይበልጥ ፡ ጠይቅ
4. ይበልጥ. We need go no further into the matter. ወደ ፡ ነገሩ ፡ ይበልጥ ፡ ጠልቀን ፡ መግባት ፡ አያስፈልገንም
5. ከዚህ ፡ በበለጠ. Let's not discuss this matter further! ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ ከዚህ ፡ በበለጠ ፡ እንነጋገርበት
6. በሰፊው. He spoke further about his plans. ስለ ፡ እቅዱ ፡ በሰፊው ፡ ተናገረ

**further on** ወደፊት
The road gets narrow further on. መንገዱ ፡ ወደፊት ፡ እየጠበበ ፡ ይሄዳል

**any further** ከንግዲህ ፡ ወዲያ
I don't want to pursue the subject any further. ነገሩን ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ልከታተለው ፡ አልፈልግም

**furthermore** ከዚህ ፡ በላይ
Furthermore, I would like to add .... ከዚህ ፡ በላይ ፡ ልጨምርበት ፡ የምፈልገው

**furthermost** ከሁሉም ፡ ርቆ ፡ የሚገኝ
The furthermost house belongs to my uncle. ከሁሉም ፡ ርቆ ፡ የሚገኘው ፡ ቤት ፡ ያጎቴ ፡ ነው

**furtive**
1. ሹክክ ፡ ያለ ፤ የድብቅብቅ. His furtive manner aroused the policeman's suspicion. ሹክክ ፡ ያለ ፡ (የድብቅብቅ) ፡ ሁኔታው ፡ ፖሊሱን ፡ ጥርጣሬ ፡ አሳደረበት
2. (= adv.) ሰረቅ ፡ አድርጎ. She threw a furtive glance at him. ሰረቅ ፡ አድርጋ ፡ ተመለከተችው

**fury**

1. ንዴት. He tore his hair in a fury. በንዴት ፡ ጸጉሩን ፡ ነጨ

2. ኀይል. The fury of the hurricane frightened the townspeople. ያውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ኀይል ፡ የከተማውን ፡ ሰዎች ፡ አስደነገጠ

*In the fury of battle, many soldiers perished. በተፋፋመው ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ሞቱ

**fly into a fury** በንዴት ፡ ቱግ ፡ አለ
When he heard the news, he flew into a fury. ወሬውን ፡ ሲሰማ ፡ በንዴት ፡ ቱግ ፡ አለ

**fuse** (vt.) አቅልጦ ፡ አያያዘ
He fused two pieces of wire together. ሁለቱን ፡ የሽቦ ፡ ቁራጮች ፡ አቅልጦ ፡ አያያዛቸው

**fuse** (vi.)

1. ቀለጠ. At a relatively high temperature, the metal will fuse. ከፍ ፡ ባለ ፡ ሙቀት ፡ ኀይል ፡ ብረት ፡ ይቀልጣል

2. ተዋሐደ. My ideas fuse with his. ሐሳቤ ፡ ከሱ ፡ ሐሳብ ፡ ይዋሐዳል

**fuse** (n.) ባልቦላ
The fuse blew out. ባልቦላው ፡ ተቃጠለ

**fusion**

1. መዳቀል. The fusion of Hamites and Semites has produced the Ethiopian. የካምና ፡ የሴም ፡ ነገዶች ፡ መዳቀል ፡ ኢትዮጵያዊን ፡ አስገኘ

2. ማዋሐድ. High temperatures are needed to produce fusion of the two metals. ሁለቱን ፡ ብረቶች ፡ ለማዋሐድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሙቀት ፡ ያስፈልጋል

**fuss** (v.) ተነዛነዘ
She fusses about her work. በሥራዋ ፡ ላይ ፡ ትነዛነዛለች

**fuss around** ተንገላወደ
She has been fussing around in the kitchen all morning. ከጧት ፡ ጀምሮ ፡ ማድቤት ፡ ውስጥ ፡ ትንገላወዳለች

**fuss** (n.) ትርምስ
What a fuss! And it is such an unimportant thing. እንዲህ ፡ ላለ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ትርምስ ፡ ምንድነው ?

**make a fuss**

1. ተነዛነዘ. His wife is always making a fuss about the windows having cracks. ሚስቱ ፡ ስለ ፡ መስኮቶቹ ፡ መሰንጣጠቅ ፡ ሁልጊዜ ፡ ትነዛነዛለች

2. ተርበተበተ. When the Emperor paid a visit, the minister made a great fuss over him. በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጉብኝት ፡ ጊዜ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በጣም ፡ ተርበተበተ

3. እስከዚህ ፡ አጋነነ. It's not worth making a fuss over such a trifle. ይህንን ፡ የማይረባ ፡ ነገር ፡ እስከዚህ ፡ ማጋነን ፡ አይገባም

**fussing** (n.) መቸገር
All this fussing about such a small matter is hardly worthwile. ስለዚህ ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መቸገር ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ነው

**fussy** ዝብርቅርቅ
His writing is so fussy I lose the thread of the story. አጻጻፉ ፡ ዝብርቅርቅ ፡ ስለሆነ ፡ የታሪኩን ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ አልያዝኩትም

**be fussy**

1. ውኃ ፡ ቀጠነ ፡ የሚል. The waiter dislikes him because he is so fussy about his food. ስለ ፡ ምግቡ ፡ ውኃ ፡ ቀጠነ ፡ የሚል ፡ ስለሆነ ፡ አሳላፊው ፡ ይጠላዋል

2. ተነጫነጨ. That sick child is always fussy; nothing suits him. ያ ፡ በሽተኛ ፡ ልጅ ፡ ሁልጊዜ ፡ ይነጫነጫል ፤ ምንም ፡ ነገር ፡ አይስማማውም

3. ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ ጠየቀ. Watch repairing is a fussy job. ሰዓት ፡ የማደስ ፡ ሥራ ፡ ከፍተኛ ፡ ጥንቃቄን ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው

4. ከመጠን ፡ በላይ ፡ ተጠነቀቀ. The house is always neat because she is a fussy housekeeper. ከመጠን ፡ በላይ ፡ ስለምትጠነቀቅ ፡ ቤቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ንጹሕ ፡ ነው

**futile**

1. ከንቱ. He made a futile attempt to save the patient. በሽተኛውን ፡ ለማዳን ፡ ከንቱ ፡ ሙከራ ፡ አደረገ

2. ፍሬ ፡ ቢስ. His head is stuffed with silly, futile ideas. አእምሮው ፡ በማይረቡ ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ሐሳቦች ፡ ተሞልቷል

**future** (n.)

1. መጪ ፤ የወደፊት. You cannot look into the future. መጪውን ፡ (የወደፊቱን) ፡ ልታውቅ ፡ አትችልም

2. የወደፊት ፡ ኑሮ. He was contemplating his future. ስለ ፡ ወደፊቱ ፡ ኑሮው ፡ ያሰላስል ፡ ነበር

3. የወደፊት ፡ ዕድል. Don't build your future on dreams! የወደፊት ፡ ዕድልህን ፡ በከንቱ ፡ ምኞት ፡ ላይ ፡ አትመሥርት

4. ተስፋ. This job has no future. ይህ ፡ ሥራ ፡ ተስፋ ፡ የለውም

5. የትንቢት ፡ ጊዜ. The future in Amharic has the same form as that of the present. ባማርኛ ፡

የትንቢት ፡ ጊዜ ፡ ያሁን ፡ ጊዜ ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ አለው

**in the future** ለወደፊቱ ፤ ወደፊት
In the future, come on time! ለወደፊቱ ፡ በሰዓቱ ፡ ና
I'll buy it sometime in the future. ወደፊት ፡ እገዛዋለሁ

**future** (adj.) የወደፊት
He introduced his future son-in-law to me. የወደፊት ፡ አማቹን ፡ አስተዋወቀኝ
[See also 'immediate']

**future tense** የትንቢት ፡ ጊዜ ፤ ትንቢታዊ ፡ ጊዜ
The future tense in Amharic has the same form as that of the present. ባማርኛ ፡ የትንቢት ፡ (ትንቢታዊ) ፡ ጊዜ ፡ ያሁን ፡ ጊዜ ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ አለው

**fuzz** ለስላሳ ፡ የሆነ ፡ ስስ ፡ ጸጉር
Caterpillars are covered with fuzz. አባ ፡ ጨጓሬ ፡ ለስላሳ ፡ በሆነ ፡ ስስ ፡ ጸጉር ፡ የተሸፈነ ፡ ነው

## G

**gabble** አነበነበ
The little girl gabbled her prayers and jumped into bed. ትንሺ ፡ ልጅ ፡ ጸሎቷን ፡ አነብንባ ፡ አልጋዋ ፡ ውስጥ ፡ ገባች

**gadget** መሣሪያ
This is a new gadget for opening cans. ይሀ ፡ አዲስ ፡ የጣሳ ፡ መክፈቻ ፡ መሣሪያ ፡ ነው

**gag** (gagged)
1. አፈነ (ታፈነ). He was tied up and gagged. ታስሮም ፡ ታፍኖም ፡ ነበር
2. ቋቅ ፡ አሰኘ. The medicine gagged him. መድኀኒቱ ፡ ቋቅ ፡ አሰኘው

**gag** (vi.) ቋቅ ፡ አለ(ው)
He took a bite of food and gagged. የምግብ ፡ ቁራሽ ፡ ቁርሶ ፡ ቋቅ ፡ አለው

**gag** (n.) ማፈኛ
Take the gag out of his mouth! ማፈኛውን ፡ ከአፉ ፡ ውስጥ ፡ አውጣው

**gaiety**
1. ተደሳችነት. Her gaiety was noticed by all onlookers. ተደሳችነቷን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተመለከተ
2. ድምቀት. Flags added to the gaiety of the scene. ሰንደቅ ፡ ዓላማዎቹ ፡ ለትርኢቱ ፡ ድምቀት ፡ ጨመሩለት

**gaily**
*He walked in gaily as though nothing were wrong. ምንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንዳልደረሰ ፡ ሁሉ ፡ የደስታ ፡ መልክ ፡ እየታየበት ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ገባ
*The gaily painted walls do not go together with the furniture. የሚያብለጨልጨው ፡ የግድግዳ ፡ ቀለም ፡ ከቤት ፡ እቃው ፡ ጋር ፡ አይስማማም

**be gaily dressed** ደማቅ ፡ ልብስ ፡ ለበሰ
She was gaily dressed to receive her guests. እንግዶቿን ፡ ለመቀበል ፡ ደማቅ ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ ነበር

**gain** (vt.)
1. አገኘ. He gained much experience as a driver when he was in the army. ጦር ፡ ሰራዊት ፡ ውስጥ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ የሾፌርነት ፡ ልምምድ ፡ አገኘ
2. ጨመረ. He gained a lot of weight recently. በቅርቡ ፡ ብዙ ፡ ክብደት ፡ ጨምሯል
3. አተረፈ. He gained strength by arduous exercise. ብርቱ ፡ የሰውነት ፡ እንቅስቃሴ ፡ በማድረግ ፡ ጥንካሬን ፡ አተረፈ
4. አ - - ደረሰ. The swimmer gained the shore. ዋናተኛው ፡ እወንዙ ፡ ዳር ፡ ደረሰ
*How does he gain his living? በምን ፡ ይተዳደራል ?

**gain** (vi.)
1. ተሻለ(ው). The sick child is gaining and will soon be well. የታመመው ፡ ልጅ ፡ እየተሻለው ፡ ስለሄደ ፡ በቅርቡ ፡ ይድናል
2. ክብደት ፡ ጨመረ. When he found he had gained, he went on a diet. ክብደት ፡ መጨመሩን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ምግብ ፡ መቀነስ ፡ ጀመረ

**gain (in)** ጨመረ
With age, he gained in wisdom. እያረጀ ፡ ሲሄድ ፡ ዕውቀት ፡ ጨመረ

**gain (on)** ደረሰ(በት)
Can't you go faster? The car behind is gaining on us. ፈጠን ፡ ለማለት ፡ አትችልም ? ከኋላችን ፡ ያለው ፡ መኪና ፡ ሊደርስብን ፡ ነው

**gain over** ወደሱ ፡ ሳበ
He sought to gain over the church party. የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ፓርቲ ፡ ወደሱ ፡ ለመሳብ ፡ ሞከረ
[See also 'ascendancy, confidence, ear, entrance, ground, momentum, time']

**gain** (n.) ትርፍ
The love of gain caused him to buy that land. ትርፍ ፡ የማግኘት ፡ ፍቅር ፡ ያንን ፡ መሬት ፡ እንዲገዛ ፡ አደረገው

**gainful** ደኅና ፡ ገቢ ፡ የሚያስገኝ
He found a gainful occupation. ደኅና ፡ ገቢ ፡ የሚያስገኝ ፡ ሥራ ፡ ያዘ

**gainsay** ተቃወመ
I cannot gainsay what you have said. አንተ ፡ ያልከውን ፡ አልቃወምም

**gait** አረማመድ
He has an awkward gait. አረማመዱ ፡ ወልካፋ ፡ ነው

**gala** በዓል
The gala was attended by many dignitaries.

ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ በበዓሉ ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ ነበር

**be a gala affair** ቀለጠ
The party was a gala affair. ፓርቲው ፡ የቀለጠ ፡ ነበር

**galaxy** ከዋክብቶች
The retrograde motion of certain planets convinced Galileo that the sun was the center of our galaxy. ያንዳንድ ፡ ከዋክብት ፡ የኋልዮሽ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ፀሐይ ፡ የከዋክብቶቻችን ፡ እምብርት ፡ መሆኗን ፡ ጋሊሊዮን ፡ አሳመነው

**gale**
1. ዓውሎ ፡ ነፋስ. The gale blew the roofs off some of the huts. ዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ያን ዳንድ ፡ ቤቶችን ፡ ጣሪያ ፡ ገነጣጠለ
2. ማዕበል. The ship lost her masts in the gale. ከማዕበል ፡ የተነሣ ፡ የመርከቡ ፡ ምሰሶ ፡ ተሰበረ

**gale of laughter** ሣቅና ፡ ውካታ
When the man came home, he heard a gale of laughter. ሰውዬው ፡ እቤቱ ፡ ሲደርስ ፡ ሣቅና ፡ ውካታ ፡ ሰማ

**gall** (v.) አበሳጨ
Discourtesy galls me. ብልግና ፡ ያበሳጨኛል

**be galling** (= tr.) አበሳጨ
It's very galling to have a supervisor who is not adequately trained. በቂ ፡ ትምህርት ፡ የሌለው ፡ ተቈጣጣሪ ፡ በጣም ፡ ያበሳጫል

**gall** (n.) ሐሞት
Gall is used in digestion. ሐሞት ፡ ምግብን ፡ ለማዋሐድ ፡ ይጠቅማል

**gallant**
1. ጀግና. The gallant soldier was decorated. ጀግናው ፡ ወታደር ፡ ተሸለመ
2. ጨዋ. He is very gallant with women. ለሴቶች ፡ በጣም ፡ ጨዋ ፡ ነው

**gall bladder** የሐሞት ፡ ፊኛ
President Johnson had an operation on his gall bladder. ፕሬዚዳንት ፡ ጆንሰን ፡ የሐሞታቸውን ፡ ፊኛ ፡ ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ተደረገ

**gallery**
1. ሰገነት. Our seats are way up in the gallery. መቀመጫችን ፡ እላይ ፡ ከሰገነቱ ፡ ነው
2. የሥዕል ፡ አዳራሽ. Did you see the exhibit at the gallery? በሥዕሉ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ትርኢት ፡ ተመለከትክ ?

**galley** [መቅዘፊያና ፡ ሸራ ፡ ያለው ፡ ረዥም ፡ ቀጭን ፡ የጥንት ፡ መርከብ]

**gallon** ጋሎን
One American gallon is not quite four liters. አንድ ፡ የአሜሪካን ፡ ጋሎን ፡ ልክ ፡ አራት ፡ ሊትር ፡ አይደለም

**gallop** (vt.) ጋለበ
They galloped the horses. ፈረሶቹን ፡ ጋለቡ

**gallop** (vi.) ጋለበ
The horse galloped through the park. ፈረሱ ፡ በመናፈሻው ፡ ውስጥ ፡ ጋለበ

**gallop** (n.) ግልቢያ
The horse's gallop is very graceful. የፈረሱ ፡ ግልቢያ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው

**gallows** የሰው ፡ መስቀያ ፡ ዕንጨት
There are gallows in the prison. በእስር ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የሰው ፡ መስቀያ ፡ ዕንጨት ፡ አለ

**galore** በብዛት
There were pretty girls galore at the dance. በዳንሱ ፡ ላይ ፡ ቆንጆ ፡ ልጃገረዶች ፡ በብዛት ፡ ተገኝተው ፡ ነበር

**galoshes** ተደራቢ ፡ ቡት ፡ ጫማ
We wear galoshes in wet weather. በቀዝቃዛ ፡ ወራት ፡ ተደራቢ ፡ ቡት ፡ ጫማ ፡ እናደርጋለን

**gamble** (v.)
1. ቁማር ፡ ተጫወተ. They were gambling for high stakes. ከፍ ፡ ባለ ፡ ገንዘብ ፡ ቁማር ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር
2. ቁማርተኛ ፡ ነው. He doesn't gamble, but he drinks. ቁማርተኛ ፡ አይደለም ፡ ግን ፡ ጠጪ ፡ ነው
3. ተወራረደ. I am gambling that he will come tomorrow. ነገ ፡ ይመጣል ፡ ብዬ ፡ እወራረዳለሁ

**gamble away** በቁማር ፡ ጨረሰ
He gambled his whole salary away. ደሞዙን ፡ እንዳለ ፡ በቁማር ፡ ጨረሰ

**gamble** (n.) ባወጣ ፡ ያውጣ
Putting money into a new building is often a gamble. አዲስ ፡ ሕንጻ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ማፍሰስ ፡ ባወጣ ፡ ያውጣ ፡ ማለት ፡ ነው

**gambler** ቁማርተኛ
The gambler lost all his money. ቁማርተኛው ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ተበላ

**gambling** ቁማር
He spends all of his money on gambling. ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ በቁማር ፡ ይጨርሳል

**gambling den** የቁማር ፡ መጫወቻ ፡ ቦታ
The police raided the gambling den. ፖሊስ ፡ የቁማር ፡ መጫወቻውን ፡ ቦታ ፡ በድንገት ፡ ያዘው

**gambol** ቦረቀ
The sheep were gamboling in the field. በጎቹ ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ይቦርቁ ፡ ነበር

**game** (n.)
1. ጨዋታ. In the evening, children like to play games. ማታ ፡ ማታ ፡ ልጆች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጨዋታ ፡ መጫወት ፡ ይወዳሉ
We beat them in today's game. በዛሬው ፡ ጨዋታ ፡ አሸነፍናቸው
2. አጨዋወት. His game of chess was improving. ሰንጠረዥ ፡ አጨዋወቱ ፡ እየተሻሻለ ፡ ሄደ
3. ግጥሚያ. This newspaper gives a full story of the game. ይህ ፡ ጋዜጣ ፡ ስለ ፡ ግጥሚያው ፡ ሙሉ ፡ ሐተታ ፡ ይሰጣል
4. መጫዋቻ. Do you sell any children's games here? የልጆች ፡ መጫዋቻዎች ፡ እዚህ ፡ ትሸጣላችሁ ?
5. የአደን ፡ አውሬ. There's a lot of game in this region. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ብዙ ፡ የአደን ፡ አውሬ ፡ አለ
6. ተንኮል. He tried to trick us, but we saw through his game. ሊያታልለን ፡ ሞከረ ፡ ግን ፡ ተንኮሉን ፡ ደረስንበት

**game** (adj.) የአደን
The game laws are very strict. የአደን ፡ ሕግ ፡ በጣም ፡ ጥብቅ ፡ ነው
[See also 'forfeit']

**gamut**
*In one minute I ran the gamut of feeling from hope to despair. ባንድ ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ተስፋ ፡ ቁርጨ ፡ ብስጭት ፡ ገባሁ

**gander** ወንድ ፡ ዝይ
The gander rules all the geese. ወንዱ ፡ ዝይ ፡ ሴት ፡ ዝዮችን ፡ ሁሉ ፡ ይገዛል

**gang** (v.), **~ around** ዐጀበ
The boys ganged around their leader. ልጆቹ ፡ መሪያቸውን ፡ ዐጀቡት

**gang up on** ተባብሮ ፡ አጠቃ
The whole class ganged up on the new student. አዲሱን ፡ ተማሪ ፡ የክፍሉ ፡ ተማሪ ፡ ሁሉ ፡ ተባብሮ ፡ አጠቃው

**gang** (n.)
1. ጓድ. Two gangs of workmen were mending the road. የሁለት ፡ ጓዶች ፡ ሠራተኞች ፡ መንገዱን ፡ ይጠግኑ ፡ ነበር
A gang of ruffians attacked a policeman. የወንበዴዎች ፡ ጓድ ፡ ፖሊስ ፡ ደበደበ
2. ወንበዴዎች ፤ ዱሪዬዎች. The head of the gang was a notorious criminal. የወንበዴዎቹ ፡ መሪ ፡ የታወቀ ፡ ወንጀለኛ ፡ ነበር
Don't get mixed up with that gang! They spend too much time drinking and gambling. ከነዚህ ፡ ዱሪዬዎች ፡ ጋር ፡ አትግጠም ፤ ጊዜያቸውን ፡ በመጠጥና ፡ በቁማር ፡ ያባክናሉ

**gangplank** መሸጋገሪያ
There is a gangplank from the ship to the dock. መርከቡንና ፡ ወደቡን ፡ የሚያገናኝ ፡ መሸጋገሪያ ፡ አለ

**gangrene** [በሕመም ፡ ምክንያት ፡ የደም ፡ መዘዋወር ፡ ታግዶ ፡ በሰውነት ፡ ውስጥ ፡ የቁስል ፡ መበስበስ]

**gangster** ወሮበላ
The gangster escaped from the police. ወሮበላው ፡ ከፖሊሶቹ ፡ አመለጠ

**gap**
1. ባዶ ፡ ቦታ. The gap has to be filled. ባዶው ፡ ቦታ ፡ መሞላት ፡ አለበት
2. ቀዳዳ. The sheep got into the field through a gap in the hedge. በጎቹ ፡ ባጥሩ ፡ ቀዳዳ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ገቡ
3. ልዩነት. There is a wide gap between the views of the two statesmen. በሁለቱ ፡ መሪዎች ፡ አሳብ ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ ልዩነት ፡ አለ
*There are large gaps in his education. ትምህርቱ ፡ ያልተሟላ ፡ ነው
*There is a gap in my memory of the war years. ስለ ፡ ጦርነት ፡ ዘመናት ፡ የማላስታውሳቸው ፡ ነገሮች ፡ አሉ

**gape** አፉን ፡ ከፈተ
A deep hole in the earth gaped before us. ከፊት ፡ ለፊታችን ፡ አፉን ፡ የከፈተ ፡ ጉድጓድ ፡ አየን

**gape at** አፉን ፡ ከፈተ
The country boy gaped at the city sights. የባላገሩ ፡ ልጅ ፡ ከተማውን ፡ ሲያይ ፡ አፉን ፡ ከፈተ

**gape open** ተፈታ
The zipper gaped open. ዚፕሩ ፡ ተፈታ

**garage** ጋራዥ

**garb** (v.), **be garbed** ልብስ ፡ ለበሰ
The doctor was garbed in white. ሐኪሙ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሷል

**garb** (n.) የሥራ ፡ ልብስ
The garb of a nurse is white. የነርስ ፡ የሥራ ፡ ልብስ ፡ ነጭ ፡ ነው

**garbage** ቆሻሻ
Garbage is collected daily. ቆሻሻ ፡ በየቀኑ ፡ ይሰበሰባል

**garbage pail** ቆሻሻ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ባልዲ
Empty the coffee grounds in the garbage pail! ቆሻሻ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ባልዲ ፡ ውስጥ ፡ የቡናውን ፡ አተላ ፡ አፍስው

**garble** አዛባ
The newspapers garbled the quotation. ጋዜጣው ፡ ጥቅሱን ፡ አዛባው

**garden** (v.) አትክልት ፡ ተከለ
She likes to garden. አትክልት ፡ መትከል ፡ ትወዳለች

**garden** (n.) ያትክልት ፡ ቦታ
These flowers are from our garden. እነዚህ ፡ አበቦች ፡ ከኛ ፡ አትክልት ፡ ቦታ ፡ የተቀጠፉ ፡ ናቸው
[See also 'herb']

**gardener** አትክልተኛ
The gardener is the one who planted the flowers. አበቦቹን ፡ የተከለው ፡ አትክልተኛው ፡ ነው

**gargle** ጉሮሮውን ፡ አጠበ ፤ ተጉመጠመጠ
Gargle every three hours! በየሦስቱ ፡ ሰዓት ፡ ጉሮሮህን ፡ እጠብ
He has a sore throat, and gargles with salt water. ጉሮሮውን ፡ ስላመመው ፡ ጨው ፡ ባለበት ፡ ውኃ ፡ ይጉመጠመጣል

**garish** ብልጭልጭ
The mother disapproved of her daughter's garish earrings. ልጅቷ ፡ ያደረገችውን ፡ ብልጭልጭ ፡ ጉትቻ ፡ እናትየዋ ፡ አጥላላችባት

**garland** ያበባ ፡ ጉንጉን
They placed a garland on his grave. በመቃብሩ ፡ ላይ ፡ ያበባ ፡ ጉንጉን ፡ አኖሩ

**garlic** ነጭ ፡ ሽንኩርት
When one eats garlic it burns. ነጭ ፡ ሽንኩርት ፡ ሲበሉት ፡ ያቃጥላል

**garment** ልብስ
There was a tear in her garment. ልብሷ ፡ ቀዳዳ ፡ ነበረው

**garnish** አጋጌጠ
The cook garnished the potatoes with mint. ወጥ ፡ ቤቱ ፡ ድንቹን ፡ በናና ፡ አጋጌጠ

**garrison** (v.) መደበ
The Israelis have garrisoned two battalions in the Gaza Strip. እስራኤሎች ፡ በጋዛ ፡ ሰላጤ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ሻለቃ ፡ መድበዋል

**garrison** (n.) የወታደሮች ፡ የጦር ፡ ሰፈር
The girls went to see the garrison. ልጃገረዶቹ ፡ የወታደሮቹን ፡ የጦር ፡ ሰፈር ፡ ለማየት ፡ ሄዱ

**garrulous** ለፍላፊ
His garrulous wife annoys him very much. ለፍላፊ ፡ ሚስቱ ፡ በጣም ፡ ታበሳጨዋለች

**garter** ላስቲክ
The garter holds up the stocking. የእግር ፡ ሹራቧ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ እንዳይወርድ ፡ የሚይዝ ፡ ላስቲክ ፡ ነው

**gas**
1. ጋዝ. Turn off the gas! ጋዙን ፡ ዝጋው
2. የመርዝ ፡ ጢስ. Gas was used in the First World War. በመጀመሪያ ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የመርዝ ፡ ጢስ ፡ ለጦርነት ፡ አገልግሎት ፡ ውሎ ፡ ነበር

**deadly gas** መርዘኛ ፡ ጭስ
A deadly gas envenomed the air. መርዘኛ ፡ ጭስ ፡ አየሩን ፡ መረዘ
[See also 'attendant, poison gas']

**gash** (v.) ቈረጠ
The broken glass gashed his arm. ሰባራ ፡ ጠርሙስ ፡ ክንዱን ፡ ቈረጠው

**gash** (n.)
*There was a deep gash in his face. ፊቱ ፡ ላይ ፡ ከፋኛ ፡ ተቈርጦ ፡ ነበር

**gasoline** ቤንዚን
I would like fifteen gallons of gasoline. ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ጋሎን ፡ ቤንዚን ፡ እፈልጋለሁ

**gasp** (v.) አቃተተ
The sick man was gasping for air. በሽተኛው ፡ ለመተንፈስ ፡ ያቃትት ፡ ነበር

**gasp out** ትንፋሹን ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ አደረገ
He gasped out an urgent message. ትንፋሹን ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ እያደረገ ፡ አስቸኳይ ፡ መልእክት ፡ ተናገረ

**gasp** (n.), **come in gasps** ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ አለ
His breath came in gasps. ትንፋሹ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ አለ

**gas station** ቤንዚን ፡ ማደያ
He filled his tank at the gas station. መኪናውን ፡ ቤንዚን ፡ ማደያ ፡ ቤንዚን ፡ሞላ

**gate**
1. በር. Drive right through this gate! ቀጥታ ፡ በዚህ ፡ በር ፡ ንድተህ ፡ እለፍ
2. የውጭ ፡ በራፍ. The dog was smelling at the gate. ውሻው ፡ እውጭ ፡ በራፍ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ያነፈንፍ ፡ ነበር

**gatekeeper** በረኛ
The gatekeeper wouldn't let him in. በረኛው ፡ አላስገባም ፡ አለው

**gateway**
1. መግቢያ. The gateway is closed by a wooden gate. መግቢያው ፡ በዕንጨት ፡ መዝጊያ ፡ ይዘጋል
2. በር. A college education is one of the gateways to success. የኮሌጅ ፡ ትምህርት ፡ ለዕድል ፡ መሳካት ፡ አንደኛው ፡ በር ፡ ነው

**gather** (vt.)
1. ለቀመ. The children gathered wood in the forest. ልጆቹ ፡ ከጫካ ፡ ዕንጨት ፡ ለቀሙ
2. ሰበሰበ. He gathered information for his book. ለመጽሐፉ ፡ መረጃ ፡ ሰበሰበ
3. ጨመረ. The plane gathered speed, and took off. አውሮፕላኑ ፡ ፍጥነት ፡ እየጨመረ ፡ ተነሣ
4. ጠመጠመ. He gathered his scarf around his neck, and went out into the cold. አንገቱ ፡ ላይ ፡ ሻርፑን ፡ ጠምጥሞ ፡ በብርዱ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጣ
5. ተረዳ. I gather that he is rich. ሀብታም ፡ መሆኑን ፡ ተረዳሁ

**gather** (vi.)
1. ተሰበሰበ. A large crowd gathered in front of the City Hall. ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ አዳራሽ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተሰበሰበ

**gather around** (vi.) ተሰበሰበ
The crowd gathered around. ሕዝቡ ፡ ተሰበሰበ

**gather in** ሸነሸነ
The seamstress gathers the skirt in at the top. ልብስ ፡ ሰፊዋ ፡ ሴት ፡ ጉርዱን ፡ ቀሚስ ፡ ትሸነሽናለች

**gathering** ስብሰባ
There is a gathering of scientists in the next room. በሚቀጥለው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ ስብሰባ ፡ አለ

**gaudy** ብልጭልጭ
He has a gaudy necktie. ብልጭልጭ ፡ ክራቫት ፡ አለው

**gauge** (v.)
1. ገመተ. It is difficult to gauge his intentions by looking at him. ፊቱን ፡ በማየት ፡ ሐሳቡን ፡ መገመት ፡ ያስቸግራል
2. ለካ. Radar is now used to gauge the speed of automobiles. ራዳር ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የመኪናዎችን ፡ ፍጥነት ፡ ለመለካት ፡ ይጠቀማል

**gauge** (n.)
1. መለኪያ. The gauge that shows the speed is broken. የፍጥነቱ ፡ መለኪያ ፡ ተሰብሯል
2. መጠን. Wire is available in various gauges. ሽቦ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መጠን ፡ ይገኛል

**gaunt** የመነመነ
He is weak and gaunt after a long illness. ከረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሕመም ፡ በኋላ ፡ ደካማና ፡ የመነመነ ፡ ሆነ

**make gaunt** አመነመነ
Hunger and suffering make people gaunt. ረኀብና ፡ ችግር ፡ ሰዎችን ፡ ያመነምናሉ
*The disease left him with a gaunt appearance. በሽታው ፡ በጣም ፡ አከሳው

**gauze** ሻሽ
The nurse used gauze for the wound. ነርሷ ፡ ቊስሉን ፡ በሻሽ ፡ አሰረች

**gave**, see **give**

**gavel** የዕንጨት ፡ መዶሻ
The chairman rapped on the table twice with his gavel. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ በዕንጨት ፡ መዶሻው ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ጠረጴዛውን ፡ መታ

**gawk** አትኩሮ ፡ ተመለከተ
The onlookers gawked at the arriving film stars. ተመልካቾቹ ፡ የፊልም ፡ ተጫዋቾቹን ፡ አትኩረው ፡ ተመለከቱ

**gay**
1. የሚያስደስት. I like to hear the gay voices of young children. የሕፃናትን ፡ የሚያስደስት ፡ ድምፅ ፡ መስማት ፡ እወዳለሁ
2. ደስ ፡ ያለ(ው). The gay young people were singing as they decorated the hall. ደስ ፡ ያላቸው ፡ ወጣቶች ፡ አዳራሹን ፡ በሚያጌጡበት ፡ ጊዜ ፡ ይዘፍኑ ፡ ነበር
3. ደስ ፡ የሚያሰኝ. Gay music prompts happy thoughts. ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሙዚቃ ፡ የደስታ ፡ መንፈስ ፡ ያፈልቃል
4. ደማቅ. The room was painted in gay colors. ክፍሉ ፡ ደማቅ ፡ ቀለም ፡ ተቀባ

**gaze** (v.) አትኩሮ ፡ ተመለከተ
He gazed at the sea for a long time. እርሱ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ አትኩሮ ፡ ተመለከተ

**gaze** (n.) ዓይን
His gaze wandered about the room. ዓይኑ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተንከራተተ

**gazelle** የሜዳ ፡ ፍየል ፤ አጋዘን
There is only one gazelle in our zoo. በኛ ፡ የእንስሳት ፡ መታያ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ አጋዘን ፡ (የሜዳ ፡ ፍየል) ፡ ብቻ ፡ አለ

**gazette, official** ~ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ
The official gazette contains a list of the names of new appointees. ነጋሪት ፡ ጋዜጣው ፡ አዲስ ፡ የተሾሙትን ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ ይዟል

**gear** (v.) አስማማ
The factory geared its production to seasonal demands. ፋብሪካው ፡ የሚያወጣቸውን ፡ ነገሮች ፡ ከጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ አስማማ

**be geared** ታቀደ
Our training program is geared to produce trained people we need for the job. ፕሮግራማችን ፡ ለሥራው ፡ የሚያስፈልጉንን ፡ ሠራተኞች ፡ ለማሠልጠን ፡ የታቀደ ፡ ነው

**gear** (n.)
1. መሣሪያ. A fisherman's gear consists of rods, lines, etc. የዓሣ ፡ አጥማጅ ፡ መሣሪያ ፡ ዘንግ ፤ ሲባጎና ፡ የመሳሰሉትን ፡ ያጠቃልላል
2. ማርሽ. This car has four gears. ይህ ፡ መኪና ፡ አራት ፡ ማርሽ ፡ አለው

**get out of gear** ተሰናከለ
The pump got out of gear and would not run. የሞተሩ ፡ ቧንቧ ፡ ስለተሰናከለ ፡ አይሠራም

**put in gear** ማርሽ ፡ አገባ
He put the car in gear and drove slowly away. ማርሽ ፡ አግብቶ ፡ በዝግታ ፡ ሄደ

**geese**, see **goose**

**gem**
1. የከበረ ፡ ድንጋይ. The gems were valuable. የከበሩ ፡ ድንጋዮች ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ነበራቸው
2. በጣም ፡ ውድ ፡ የሆነ. The gem of his collection was a rare Ethiopian stamp. ከሰበሰበው ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ የሆነው ፡ ብርቅ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቴምብር ፡ ነበር

**(be) geminated** ተጠበቀ
In the Amharic verb, the second consonant is often geminated. ባማርኛ ፡ ግስ ፡ ውስጥ ፡ ሁለተኛው ፡ ተነባቢ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይጠበቃል

**gender** ጾታ
It is hard to tell the gender of chickens. የጫጩቶችን ፡ ጾታ ፡ መለየት ፡ ያስቸግራል
Many languages have a masculine and a feminine gender in the noun. ብዙ ፡ ቋንቋዎች ፡ የስሞች ፡ ተባዕታይና ፡ አንስታይ ፡ ጾታ ፡ አላቸው
[See also 'common, feminine, masculine, neuter']

**genealogy** የዘር ፡ አወራረድ ፤ የዘር ፡ ግንድ
He is well versed in the genealogy of his family. የቤተሰቡን ፡ የዘር ፡ አወራረድ ፡ በደንብ ፡ ጠንቅቆ ፡ ያውቃል
The appendix of this book deals with the genealogy of the kings. የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጨማሪ ፡ መግለጫ ፡ ስለ ፡ ነገሥታት ፡ የዘር ፡ ግንድ ፡ ይናገራል

**general** (n.) ጄኔራል
The general was wounded in the battle. ጄኔራሉ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ቆሰለ

**general** (adj.)
1. ጠቅላላ. A general election is held every year. በየዓመቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርጫ ፡ ይደረጋል
I have a general idea how planes work. አውሮፕላን ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠራ ፡ ጠቅላላ ፡ ሐሳብ ፡ አለኝ
2. የሕዝብ. A government takes care of the general welfare. መንግሥት ፡ ለሕዝቡ ፡ ደኅንነት ፡ ኀላፊ ፡ ነው
3. (= adv.) በሰፊው. Afternoon tea is a general custom in England. እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ሻይ ፡ መጠጣት ፡ በሰፊው ፡ የተለመደ ፡ ነው

**general term** የወል ፡ ስም
"Livestock" is a general term for cows, sheep, and goats. ከብት ፡ ለላሞች ፡ ለበጎችና ፡ ለፍየሎች ፡ የወል ፡ ስም ፡ ነው

**in general** በጠቅላላው
In general, things are all right. በጠቅላላው ፡ ነገሩ ፡ ደኅና ፡ ነው
[See also 'consent, secretary general, staff']

**generality, in generalities** በደፈናው
He talks in generalities. በደፈናው ፡ ይናገራል

**generality of** አብዛኛዎቹ
The generality of citizens of the United States eat well. አብዛኛዎቹ ፡ ያሜሪካን ፡ ነዋሪዎች ፡ ጥሩ ፡ ምግብ ፡ ያገኛሉ

**generalize**
1. ጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠ. Don't generalize on the basis of a few facts only! ጥቂት ፡ የተጨበጡ ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ መሠረት ፡ አድርገህ ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ አትስጥ
2. አስፋፋ. The doctors hope to generalize

the use of the new vaccine. ሐኪሞች ፡ ያዲሱን ፡ ክትባት ፡ ጥቅም ፡ ለማስፋፋት ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋሉ

**generally**

1. አብዛኛውን ፡ ጊዜ. He is generally on time. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በሰዓቱ ፡ ይደርሳል

2. በሰፊው. It was generally believed that the earth is flat. መሬት ፡ ዝርግ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በሰፊው ፡ ይታመን ፡ ነበር

[See also 'speaking']

**generate**

1. አስገኘ. Water power is often used to generate electricity. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የውኃ ፡ ኀይል ፡ ኤሌክትሪክ ፡ ለማስገኘት ፡ ይሠራበታል

2. አፈለቀ. He generates ideas that we all should consider. ሁላችንም ፡ ልንመለከተው ፡ የሚገባ ፡ ሐሳብ ፡ ያፈልቃል

3. አተረፈ. A friendly smile generates good will. የወዳጅነት ፡ ፈገግታ ፡ መልካም ፡ ስሜትን ፡ ያተርፋል

**generation**

1. ትውልድ. His family has been in America for four generations. ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ላራት ፡ ትውልድ ፡ ባሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ ኖሯል

2. (= to generate) ማስገኘት. Steam and water power are used for the generation of electricity. እንፋሎትና ፡ የውኃ ፡ ኀይል ፡ ኮሬንቲ ፡ ለማስገኘት ፡ ይጠቅማሉ

**generosity**

1. ለጋስነት. His generosity is well known. ለጋስነቱ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ነው

2. ጨዋነት. He showed generosity in praising his opponent. ተቃዋሚውን ፡ በማመስገን ፡ ጨዋነትን ፡ አሳየ

**generous**

1. ለጋስ ፤ ቸር. Don't be so generous with other people's money! በሰው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲህ ፡ ለጋስ ፡ (ቸር) ፡ አትሁን

2. የደግነት. To forgive your enemy is a generous act. ጠላትህን ፡ ይቅር ፡ ማለት ፡ የደግነት ፡ ተግባር ፡ ነው

**generous heart** ልበ ፡ ርኅርኅነት

His kind acts proclaim a generous heart. የደግነት ፡ ተግባሩ ፡ ልበ ፡ ርኅርኅነት ፡ ያሳያል

**generous supply of** በጣም ፡ ብዙ

The store has a generous supply of paper. መደብሩ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ የሚሸጥ ፡ ወረቀት ፡ አለው

**genesis** ምንጭ

We can see the genesis of this novel in an early short story of his. የዚህ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ ምንጩ ፡ እንደሚታየን ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ የተጻፈው ፡ አጭር ፡ ታሪክ ፡ ነው

**genial**

1. ተጫዋች. A genial host makes his guests feel at ease. ተጫዋች ፡ ጋባዥ ፡ እንግዶቹ ፡ እንዲዝናኑ ፡ ያደርጋቸዋል

2. የወዳጅነት. He gave him a genial greeting. የወዳጅነት ፡ ሰላምታ ፡ አቀረበለት

3. ለጤንነት ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ. Harar has a genial climate. ሐረር ፡ ለጤንነት ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ አየር ፡ አለው

**genitals**

1. ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፤ አባለ ፡ ዘር. The wild men's genitals were covered by a cloth strip. የጫካ ፡ ሰዎቹ ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ (አባለ ፡ ዘር) ፡ በጨርቅ ፡ ቁራጭ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር

2. ብልት. The animals had a disease of the genitals. እንስሳዎቹ ፡ የብልት ፡ ሕመም ፡ ይዟቸዋል

**genius**

1. በጣም ፡ ብልህ. Many people consider him a genius. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ እሱን ፡ በጣም ፡ ብልህ ፡ አድርገው ፡ ይመለከቱታል

2. ተሰጥኦ. He has a genius for arithmetic. የሒሳብ ፡ ተሰጥኦ ፡ አለው

**genteel** የጨዋነት

His genteel manners show he had good upbringing. የጨዋነት ፡ ጠባዩ ፡ ጥሩ ፡ አስተዳደግ ፡ እንደነበረው ፡ ያሳያል

**gentility** ጨዋነት

The gracious old lady had an air of gentility. ደርባባዋ ፡ አሮጊት ፡ የጨዋነት ፡ መልክ ፡ አላቸው

**gentle**

1. በጣም ፡ ገር ፤ ረጋ ፡ ያለ. He is a gentle person, particularly with children. በተለይ ፡ ለልጆች ፡ በጣም ፡ ገር ፡ ሰው ፡ ነው

She has a gentle nature. ረጋ ፡ ያለ ፡ ባሕሪይ ፡ አላት

2. ደግ. The doctor is gentle with his patients. ዶክተሩ ፡ ለሕመምተኞቹ ፡ ደግ ፡ ነው

3. የደግነት. The gentle manners of the nurse pleased all the patients. የነርሷ ፡ የደግነት ፡ ሁኔታ ፡ በሽተኞቹን ፡ ሁሉ ፡ አስደሰታቸው

4. ዘቅዘቅ ፡ ያለ. The house is built on a gentle slope. ቤቱ ፡ ዘቅዘቅ ፡ ባለ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ የተሠራ ፡ ነው

5. ገራም. This horse is very gentle. ይህ ፡ ፈረስ ፡ በጣም ፡ ገራም ፡ ነው
6. ለዘብ ፡ ያለ. There was a gentle breeze coming from the sea. ከባሕሩ ፡ ለዘብ ፡ ያለ ፡ ሽውታ ፡ ይነፍስ ፡ ነበር
7. ለስለስ ፡ ያለ. The gentle sound of music doesn't disturb me. ለስለስ ፡ ያለ ፡ የሙዚቃ ፡ ድምፅ ፡ አያስቸግረኝም

**have a gentle upbringing** በጨዋነት ፡ አደገ
This young man has had a gentle upbringing. ይህ ፡ ወጣት ፡ ሰው ፡ በጨዋነት ፡ ያደገ ፡ ነው

**gentleman** (gentlemen)
1. ሰው. Who is the gentleman in the corner? እዚያ ፡ ጥግ ፡ ያሉት ፡ ሰው ፡ ማናቸው ?
2. ጨዋ ፡ ሰው ፤ ጨዋ. He is a real gentleman. በእርግጥ ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ነው
Fencing used to be a gentleman's sport. የሻቦላ ፡ ግጥሚያ ፡ የጨዋ ፡ እስፖርት ፡ ነበር

**gentlemen**
1. ክቡራን. Ladies and gentlemen, please sit down! ክቡራትና ፡ ክቡራን ፡ እባካችሁ ፡ ቁጭ ፡ በሉ
2. ጌቶች. Gentlemen, please come this way! ጌቶቼ ፤ በዚህ ፡ በኩል ፡ ኑ

**old gentleman**
1. ሽማግሌ. The old gentleman reconciled the husband and wife who quarreled. ሽማግሌው ፡ የተጣሉትን ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አስታረቀ
2. አዛውንት. Ras Imru is a fine old gentleman. ራስ ፡ እምሩ ፡ ጥሩ ፡ አዛውንት ፡ ናቸው

**gently**
1. በርጋታ. He knocked gently on the door. መዝጊያውን ፡ በርጋታ ፡ አንኳኳ
You will have to treat him gently. በርጋታ ፡ ልትይዘው ፡ ይገባል
2. ቀስ ፡ በቀስ. The hill slopes gently down to the lake. ኮረብታው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ወደ ፡ ሐይቁ ፡ ያቈለቍላል

**gentry** መኳንንት
In certain countries, the gentry enjoys certain privileges. ባንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ መኳንንት ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ አላቸው

**genuflect** ተንበረከከ ፤ ሰገደ
Catholics often genuflect during the service. ካቶሊኮች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በቅዳሴ ፡ ላይ ፡ ይንበረከካሉ ፡ (ይሰግዳሉ)

**genuine**
1. እውነተኛ. Is this a genuine dollar bill? ይህ ፡ እውነተኛ ፡ ብር ፡ ነው ?
2. ሐሳበ ፡ ቀና. He is a genuine person, and everyone likes him. ሐሳበ ፡ ቀና ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ሁሉ ፡ ይወደዋል
3. ከልብ ፡ የመነጨ. Genuine sorrow left him unable to speak his grief. ከልብ ፡ የመነጨው ፡ ሐዘኑ ፡ ሐዘኑን ፡ ለመናገር ፡ አላስቻለውም
4. (= adv.) በርግጥ. This is a genuine picture by Rubens. ይህ ፡ በርግጥ ፡ ሩቤንስ ፡ የሠራው ፡ ሥዕል ፡ ነው
5. (= adv.) ከልብ. His welcome was genuine. አቀባበሉ ፡ ከልብ ፡ ነበር

**geography** ጂኦግራፊ ፤ ትምህርተ ፡ ምድር

**geology** ጂኦሎጂ ፤ ትምህርተ ፡ አለት

**geometry** ጂኦሜትሪ

**germ(s)** ረቂቅ ፡ ሕዋሳት
Germs can be seen only with a microscope. ረቂቅ ፡ ሕዋሳት ፡ ሊታዩ ፡ የሚችሉት ፡ በአጉሊ ፡ መነጽር ፡ ብቻ ፡ ነው

**German**
1. ጀርመን. There are not many Germans in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጀርመኖች ፡ የሉም
2. ጀርመንኛ. Do you know German? ጀርመንኛ ፡ ታውቃለህ ?

**Germany** የጀርመን ፡ አገር ፤ ጀርመን

**germinate** (vt.) እንዲበቅል ፡ አደረገ
Heat and moisture germinate seeds. ሙቀትና ፡ እርጥበት ፡ ዘር ፡ እንዲበቅል ፡ ያደርጋል

**germinate** (vi.) በቀለ
Seeds germinate in the spring. ዘር ፡ በጸደይ ፡ ይበቅላል

**gesticulate** እጁን ፡ ማንቃነቅ ፡ አበዛ
The Italians gesticulate when speaking. ኢጣልያኖች ፡ ሲናገሩ ፡ እጃቸውን ፡ ማንቃነቅ ፡ ያበዛሉ

**gesture**
1. ምልክት. Nodding the head from side to side is a gesture of refusal. ራስን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ መነቅነቅ ፡ የእምቢታ ፡ ምልክት ፡ ነው
2. ሲነጋገር ፡ የሚያደርገው ፡ እንቅስቃሴ. Her gestures are very expressive. ስትነጋገር ፡ የምታደርገው ፡ እንቅስቃሴ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ይገልጻል
3. የሰውነት ፡ እንቅስቃሴ. He makes many gestures when he talks. በሚናገርበት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ የሰውነት ፡ እንቅስቃሴ ፡ ያደርጋል
4. አኳኋን. With an imperious gesture, she ordered me to leave. እብሪት ፡ በተሞላበት ፡ አኳኋን ፡ ውጣ ፡ አለችኝ

5. ለይምሰል. His offer to give me a job was just a gesture. ሥራ ፡ ልስጥህ ፡ ማለቱ ፡ እንዲያው ፡ ለይምሰል ፡ ነበር

**get** (got), vt.
1. አገኘ. I could not get you on the phone. በስልክ ፡ ላገኝህ ፡ አልቻልኩም
After paying five dollars how much change did you get? አምስት ፡ ብር ፡ ከፍለህ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መልስ ፡ አገኘህ?
You can get the answer by Monday. መልሱን ፡ እስከ ፡ ሰኞ ፡ ልታገኝ ፡ ትችላለህ
Can you get me another copy? ሌላ ፡ ቅጂ ፡ ልታገኝልኝ ፡ ትችላለህ ?
2. አስገኘ. The insertion of an advertisement in a newspaper gets results. የንግድ ፡ ማስታወቂያን ፡ በጋዜጣ ፡ ማውጣት ፡ ውጤት ፡ ያስገኛል
3. ያዘ. Get him before he escapes! ሳያመልጥ ፡ ያዘው
4. አመጣ. Get me a ticket, please! ቲኬት ፡ አምጣልኝ
Get my shoes for me! ጫማዬን ፡ አምጣልኝ
5. አዘጋጀ. She is getting dinner. እራት ፡ እያዘጋጀች ፡ ናት
6. ወሰደ. He is drunk. Call a taxi and let's get him home! ሰክሯል ፤ ታክሲ ፡ ጥራና ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እንውሰደው
7. ገባ(ው) ፤ ተረዳ. +I don't get you. Please explain again! ያልከው ፡ አልገባኝም ፤ እንደገና ፡ ግለጽልኝ
+Did you get the idea? ሐሳቡ ፡ ገባህ ?
Explain that again; I don't get the drift of your words. ያን ፡ እንደገና ፡ አብራራው ፤ የንግግርህን ፡ አዝማሚያ ፡ አልተረዳሁትም
8. ሰማ. I didn't get your last name. ያባትህን ፡ ስም ፡ አልሰማሁም
9. ደረሰ(ው). +When did you get my letter? ደብዳቤዬ ፡ መቼ ፡ ደረሰህ ?
10. ተፈረደ(በት). The accused man got six years in jail. የተከሰሰው ፡ ሰው ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ተፈረደበት
11. መታ. The bullet got him in the leg. ጥይቱ ፡ እግሩን ፡ መታው

**get** (vi.)
1. ተሳፈረ. He got on the bus to go to the library. ወደ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ለመሄድ ፡ አውቶቡስ ፡ ላይ ፡ ተሳፈረ
2. ወጣ. He got on his horse and rode off. ፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ጋለበ
3. ደረሰ. I had to stretch in order to get at the top shelf. እላይኛው ፡ መደርደሪያ ፡ ለመድረስ ፡ መንጠራራት ፡ ነበረብኝ
I'll get there in an hour. እዚያ ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ እደርሳለሁ
4. ገባ. How did you get into the house? እቤቱ ፡ ውስጥ ፡ እንዴት ፡ ገባህ ?
Hold your temper in leash, or you'll get in trouble. ንዴትህን ፡ ግታ ፤ ያለዚያ ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ ትገባለህ
5. ሄደ. I will hunt up some old books when I get to Ethiopia. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስሄድ ፡ አንዳንድ ፡ አሮጌ ፡ መጻሕፍት ፡ ፈልጌ ፡ እገዛለሁ
6. ግንኙነት ፡ አደረገ. It was too late by the time he got to the authorities. ከባለሥልጣኖቹ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያደረገው ፡ ጊዜው ፡ ካለፈበት ፡ በኋላ ፡ ነበር

**get about**
1. ተዘዋወረ. He gets about a great deal. ብዙ ፡ ይዘዋወራል
2. ሄደ ፤ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ. The old man uses a walking stick to get about. ሽማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ የሚሄደው ፡ (ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ የሚለው) ፡ በምርኩዝ ፡ ነው
3. አደባባይ ፡ ወጣ. It was supposed to be a secret, but somehow it got about. ምስጢር ፡ መሆኑ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ባልታወቀ ፡ መንገድ ፡ አደባባይ ፡ ወጥቷል
4. ተሰራጨ. News gets about quickly. ወሬ ፡ ቶሎ ፡ ይሰራጫል

**get across** ተሻገረ
We could get across the river here. ወንዙን ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ልንሻገር ፡ እንችላለን

**get (a thing) across** አስረዳ
I was not able to get the idea across to him. ይህንን ፡ ሐሳብ ፡ ላስረዳው ፡ አልቻልኩም

**get ahead**
1. ዘለቀ. You will not get ahead without an education. ያለ ፡ ትምህርት ፡ ልትዘልቅ ፡ አትችልም
2. ተሳካ(ለት). +A faithful wife will help you get ahead in life. ታማኝ ፡ ሚስት ፡ ኑሮህ ፡ እንዲሳካልህ ፡ ትረዳሃለች

**get ahead of** በለጠ
Tom has gotten ahead of the other boys in class by studying hard. ጠንክሮ ፡ በማጥናት ፡ ቶም ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ በለጣቸው

**get along**
1. ቻለ. I will get along somehow. እንደምንም ፡ ብዬ ፡ እችለዋለሁ
2. ሊኖር ፡ ቻለ. He can't get along on his measly salary. በዚች ፡ ባነስተኛ ፡ ደሞዙ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም

3. ተዳደረ. Their family gets along on very little. የነሱ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ባነስተኛ ፡ ገቢ ፡ ይተዳደራል
4. መንገድ ፡ ጀመረ. I will have to be getting along now. አሁን ፡ መንገድ ፡ መጀመር ፡ አለብኝ
5. ተግባባ ፤ ተስማማ. We get along splendidly. በጣም ፡ ተግባብተናል ፡ (ተስማምተናል)

**get along in** ያዘ(ው)
+How is he getting along in France? የፈረንሳይ ፡ ሀገር ፡ እንዴት ፡ ይዞታል ?
+How are you getting along in your science course? የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ትምህርትህ ፡ እንዴት ፡ ይዞሃል ?

**get anywhere** አዋጣ(ው)
You won't get anywhere by writing such controversial reports. ይህንን ፡ የመሰለ ፡ አከራካሪ ፡ ጽሑፍ ፡ መጻፍ ፡ አያዋጣህም

**get around**
1. ዞረ. We got around a lot. ብዙ ፡ ዞርን
2. ተዘዋወረ. I get around by car. በመኪና ፡ እዘዋወራለሁ
3. ተነዛ ፤ ተዛመተ. Bad news gets around quickly. መጥፎ ፡ ወሬ ፡ በፍጥነት ፡ ይነዛል ፡ (ይዛመታል)
4. መውጫ ፡ አላጣም. A smart lawyer will find a way to get around the law. ብልህ ፡ ጠበቃ ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ መውጫ ፡ አያጣም
5. አለፈ. He got around your objections with clever arguments. ተቃውሞህን ፡ ጥሩ ፡ ክርክር ፡ በማቅረብ ፡ አለፈው

**get at**
What are you getting at? ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው?

**get away**
1. ወጣ. I am sorry, but I could not get away. አዝናለሁ ፤ ግን ፡ ለመውጣት ፡ አልቻልኩም ፡ ነበር
2. አመለጠ. He tried to get away, but the crowd was too dense. ለማምለጥ ፡ ሞክሮ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሕዝቡ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ ነበር
The thieves got away with the safe and one thousand dollars. ሌቦቹ ፡ ካዝናውን ፡ ካንድ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ጋር ፡ ይዘው ፡ አመለጡ
3. ተለየ. The idea of a vacation is to get away from work. የዕረፍት ፡ ዓላማው ፡ ከሥራ ፡ ለመለየት ፡ ነው

**get back,** vt. (= vi.) ተመለሰ(ለት)
+Did he get his money back? ገንዘቡ ፡ ተመልሶለታል ?

**get back** (vi.) ተመለሰ
When did you get back? መቼ ፡ ተመለስክ ?
I'll get back to the subject in a minute. ከትንሽ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሥረ ፡ ነገሩ ፡ እመለሳለሁ

**get back at** ተበቀለ
He will get back at me for the wrong I did him. ለፈጸምኩበት ፡ በደል ፡ ይበቀለኛል

**get by**
1. አለፈ ፤ ባጠገቡ ፡ አለፈ. How did you get by the guard? ዘበኛውን ፡ እንዴት ፡ አለፍከው ?
When I tried to get by him, he blocked my path. ባጠገቡ ፡ ለማለፍ ፡ ስሞክር ፡ መንገዱን ፡ ዘጋብኝ
2. ዘለቀ. I do not have much money, but I think I will get by somehow. ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም ፡ ግን ፡ እንደምንም ፡ እዘልቃ ፡ ይመስለኛል

**get down** (vt.) ዋጠ
The pill was so large that he couldn't get it down. ኪኒኑ ፡ ትልቅ ፡ ስለነበረ ፡ ሊውጠው ፡ አልቻለም

**get down** (vi.) ወረደ
She climbed the tree, but then couldn't get down again. ዛፉን ፡ ወጥታ ፡ መውረድ ፡ አቃታት

**get down to**
1. ጀመረ. We must get down to business and stop chatting. ወሬውን ፡ ትተን ፡ ሥራ ፡ መጀመር ፡ አለብን
2. ስለ - - - ተናገረ. Stop beating around the bush. Get down to the subject! ዳር ፡ ዳር ፡ አትበል ፤ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ተናገር

**get down to work** ሥራ ፡ ሠራ
After the holidays, it is hard to get down to work. ከባዕላት ፡ በኋላ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**get even,** see **even**

**get going** ጀመረ
They wanted to get going on the construction of the house. የቤቱን ፡ ሥራ ፡ ለመጀመር ፡ ፈለጉ

**get hold of** አገኘ
I would like to get hold of an Amharic dictionary. አንድ ፡ ያማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ማግኘት ፡ እፈልጋለሁ

**get home** ገባ
I got home early last night. ባለፈው ፡ ሌሊት ፡ በጊዜ ፡ እቤት ፡ ገባሁ

**get in** (vt.)
1. አገባ. Please get the clothes in before it rains! ከመዝነቡ ፡ በፊት ፡ ልብሱን ፡ አግባ
2. ሰበሰበ. We had better get in the crops before the rainy season. የዝናቡ ፡ ወራት ፡ ሳይመጣ ፡ እህሉን ፡ ብንሰበስብ ፡ ይሻላል

**get in** (vi.) ገባ
How did he manage to get in? እንዴት ፡ ሊገባ ፡ ቻለ ?

**get in one's way** መንገድ ፡ ዘጋ(በት)
He got in my way, so I shoved him aside. መንገድ ፡ ስለዘጋብኝ ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ገፋሁት

**get it over with**
*I'm going to the dentist, and I will be glad to get it over with. ወደ ፡ ጥርስ ፡ ሐኪም ፡ መሄዴ ፡ ነው ፤ እንደኛዬን ፡ ቢወጣልኝ ፡ ይሻለኛል

**get off** (vt.)
1. አወለቀ. I cannot get my shoes off. ጫማዬን ፡ ላወልቅ ፡ አልችልም
2. አነሣ. Can you get the wrapping off? ሽፋኑን ፡ ልታነሣው ፡ ትችላለህ ?
3. አስለቀቀ. How can I get the dirt off my shirt? እድፋን ፡ ከሸሚዜ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ላስለቅቀው ፡ እችላለሁ?
4. ጠረገ. How can I get the dirt off the wall? ቆሻሻውን ፡ ከግድግዳው ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ልጠርገው ፡ እችላለሁ ?
5. ሰደደ. Get the children off to school! ልጆቹን ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ስደዳቸው

**get off** (vi.)
1. ወረደ. You have to get off the bus in ten minutes. በዐሥር ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ከአውቶቡስ ፡ መውረድ ፡ አለባችሁ
2. ሄደ. Tomorrow I have to get off early to school. ነገ ፡ በጧት ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ አለብኝ
*We get two days off at Christmas. ለገና ፡ የሁለት ፡ ቀን ፡ ዕረፍት ፡ እናገኛለን

**get on** (vt.) አደረገ
Get your hat and coat on! We have to leave. ኮትህንና ፡ ባርኔጣህን ፡ አድርግ ፤ መሄድ ፡ አለብን

**get on** (vi.)
1. ገሰገሰ. Time is getting on. ጊዜው ፡ ይገሰግሳል
2. ተከሄደ. How's your work getting on? ሥራህ ፡ እንዴት ፡ ይከሄዳል ?
*How are you getting on in your work? ሥራህ ፡ እንዴት ፡ ይዞሃል ?

**get on in years** በዕድሜ ፡ ገፋ
I'm getting on in years, and I can't walk that much. በዕድሜ ፡ እየገፋሁ ፡ ስለሄድኩ ፡ ብዙ ፡ መንገድ ፡ ለመሄድ ፡ አልችልም

**get on well** ተስማማ ፤ ተግባባ
The three of us get on very well. ሦስታችን ፡ በጣም ፡ እንስማማለን ፡ (እንግባባለን)

**get on with** ቀጠለ
Now let's get on with the discussion! አሁን ፡ ውይይታችንን ፡ እንቀጥል

**get out** (vt.)
1. ነቀለ. I couldn't get the nail out. ምስማሩን ፡ ልነቅለው ፡ አልቻልኩም
2. አተረፈ. How much money did you get out of this deal? በዚህ ፡ ሥራ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ አተረፍክ ?
3. ተጠቀመ. You won't get much out of this course. ከዚህ ፡ ትምህርት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አትጠቀምም
4. አትሞ ፡ አወጣ. They are getting out a new book. አዲስ ፡ መጽሐፍ ፡ አትመው ፡ ሊያወጡ ፡ ነው
5. ቀዳ. If you tilt the bottle, you can get the milk out. ጠርሙሱን ፡ ብታዘነብለው ፡ ወተቱን ፡ ልትቀዳ ፡ ትችላለህ
6. ተነፈሰ. I was so frightened, I couldn't get a word out. ከመፍራቴ ፡ የተነሣ ፡ ቃልም ፡ ልተነፍስ ፡ አልቻልኩ

**get out** (vi.)
1. ወረደ. I will have to get out at the next stop. እሚቀጥለው ፡ መቆሚያ ፡ ላይ ፡ መውረድ ፡ አለብኝ
2. ወጣ. How do you get out of that room? ከክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ እንዴት ፡ ትወጣለህ ?
Her secret got out somehow. ምስጢሯ ፡ እንደ ምንም ፡ ወጣባት
3. ተሰማ. I don't know how the story got out. ወሬው ፡ እንዴት ፡ እንደተሰማ ፡ አላውቅም
4. ቀረ. I wish I could get out of going to that meeting. ወደዚያ ፡ ስብሰባ ፡ ከመሄድ ፡ መቅረት ፡ ብችል ፡ ጥሩ ፡ ነበር
5. ነጻ ፡ ሆነ. In the new year, we hope to get out of debt. ባዲሱ ፡ ዓመት ፡ ከዕዳ ፡ ነጻ ፡ ለመሆን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን

**get (oneself) out** ራሱን ፡ አወጣ
You got yourself out of the situation very skillfully. ከዚያ ፡ ውጥንቅጥ ፡ ራስህን ፡ በዘዴ ፡ አወጣህ

**(let) get out**
We mustn't let this story get out! ይህን ፡ ነገር ፡ እንዲታወቅ ፡ ማድረግ ፡ የለብንም

**get out of the way**
1. አስወገደ. We finally got that difficulty out of the way. በመጨረሻ ፡ ችግሩን ፡ አስወገድነው
2. ከ - - ተገላገለ. I finally got those boxes out of the way. በመጨረሻ ፡ ከነዚያ ፡ ሣጥኖች ፡ ተገላገልኩ

**get out of my way!** ዞር ፡ በል
Get out of my way! I am in a hurry. ዞር ፡ በል ። ቸኩያለሁ

**get (over)**
1. አለፈ. They caught him just before he could get over the border. ልክ ፡ ጠረፉን ፡ ሊያልፍ ፡ ሲል ፡ ያዙት
2. አሸነፈ. She cannot get over her shyness. ዓይናፋርነቷን ፡ ልታሸንፍ ፡ አትችልም
3. ዘለለ. I cannot get over this gate. It's too high. ይህንን ፡ በር ፡ ልዘለው ፡ አልችልም ። በጣም ፡ ረዥም ፡ ነው
4. አንሰራራ. He never got over his financial losses. ከደረሰበት ፡ የገንዘብ ፡ ኪሳራ ፡ ገና ፡ አላንሰራራም
5. ረሳ. She can't get over her sorrow. ሐዘኗን ፡ ልትረሳው ፡ አትችልም

**get over one's illness** ዳነ
He finally got over his illness and can go to work. በመጨረሻ ፡ ስለዳነ ፡ ሥራ ፡ ለመሄድ ፡ ይችላል

**get (through)**
1. አለፈ. You cannot get through here. በዚህ ፡ በኩል ፡ ልታልፍ ፡ አትችልም
2. ሆነ(ለት). I tried to call John, but I could not get through. ዮሐንስን ፡ በስልክ ፡ ላነጋግር ፡ ሞከርኩ ፡ ግን ፡ አልሆነልኝም
3. ዘለቀ. Only hard study helped him get through college. የኮሌጅ ፡ ትምህርቱን ፡ እንዲዘልቅ ፡ የረዳው ፡ ጠንክሮ ፡ ማጥናቱ ፡ ብቻ ፡ ነው
4. ጨረሰ. John is ambitious to get through high school in two years. ጆን ፡ ሁለተኛ ፡ ደረጃን ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ለመጨረስ ፡ በጣም ፡ ይመኛል

**get through with** ጨረሰ
As soon as I get through with my work, I will join you. ሥራዬን ፡ እንደጨረስኩ ፡ አንተ ፡ ዘንድ ፡ እመጣለሁ

**get to one**
1. አስረዳ. I couldn't get to him that his idea would not work. የሱ ፡ ሐሳብ ፡ የማይሳካ ፡ መሆኑን ፡ ላስረዳው ፡ አልቻልኩም
2. ደረሰ. The rebels are holed up in the mountains where the police cannot get to them. ዐመፀኞች ፡ ፖሊሶች ፡ ሊደርሱ ፡ በማይችሉበት ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ተሸሽገዋል

**get together** (vt.) ሰበሰበ
The leader could not get many people together. መሪው ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሊሰበስብ ፡ አልቻለም

**get together** (vi.)
1. ተሰበሰበ. We get together once a year. ባመት ፡ አንዴ ፡ እንሰበሰባለን
2. ተስማማ. They never seem to get together on anything. በምንም ፡ ነገር ፡ ፍጹም ፡ የሚስማሙ ፡ አይመስሉም

**get under way** መሥራት ፡ ያዘ
The project is slowly getting under way. እቅዱ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ መሥራት ፡ ይዟል

**get up** (vt.) ሰበሰበ
He asked for more time to get up the money. ገንዘቡን ፡ ለመሰብሰብ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጠው ፡ ጠየቀ

**get up** (vi.)
1. ተነሣ. I get up at six every morning. ጧት ፡ ጧት ፡ ባሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ እነሣለሁ
2. ደረሰ. We got up to the last chapter of this book. እመጽሐፉ ፡ መጨረሻ ፡ ምዕራፍ ፡ ደረስን
3. ብድግ ፡ አለ. He got up to ask a question. ጥያቄ ፡ ሊጠይቅ ፡ ብድግ ፡ አለ
[See also 'bed, best, better, credit, familiar, flat, fresh, gear, touch, well']

## get-together ስብሰባ
Our club had a get-together yesterday at my house. ትናንትና ፡ እኔ ፡ ቤት ፡ ክበባችን ፡ ስብሰባ ፡ አድርጎ ፡ ነበር

## ghastly አሰቃቂ
Murder is a ghastly crime. ነፍስ ፡ መግደል ፡ አሰቃቂ ፡ ወንጀል ፡ ነው

**look ghastly**
The sick man's face looks ghastly. በሽተኛው ፡ የጣረሞት ፡ መልክ ፡ ይታይበታል

## ghost ጣረሞት
You cannot make me believe in ghosts. በጣረሞት ፡ ልታሳምነኝ ፡ አትችልም
*He hasn't a ghost of a chance. ምንም ፡ ተስፋ ፡ የለውም

## giant
1. ግዙፍ. Compared to me, he is a giant. ከኔ ፡ ጋር ፡ ሲነጻጸር ፡ እሱ ፡ ግዙፍ ፡ ነው
2. ጭራቅ. Giants are said to have lived in ancient times. ጭራቆች ፡ በድሮ ፡ ዘመን ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ይባላል

## gibber ተንጫጫ
Monkeys gibber in the trees. ዝንጀሮዎች ፡ ዛፉ ፡ ላይ ፡ ይንጫጫሉ

## gibe አቃለለ ። አሾፈ
They gibed him for his mistakes. ስሕተት ፡ ስለሠራ ፡ አቃለሉት

My brother gibed at my efforts to paint a picture. ወንድሜ ፡ ሥዕል ፡ ለመሣል ፡ በማደርገው ፡ ጥረት ፡ አሾፈ

**giddy**
1. ወረተኛ. Nobody can tell what that giddy girl will do next. ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያቺ ፡ ወረተኛ ፡ ልጅ ፡ የምታደርገውን ፡ ለማወቅ ፡ አይቻልም
2. የሚያዞር. He looked down from a giddy height. የሚያዞር ፡ ከፍታ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ቁልቁል ፡ ተመለከተ

**make giddy** አዞረ
Climbing ladders makes me giddy. መሰላል ፡ መውጣት ፡ ያዞረኛል

**gift**
1. ስጦታ. Thank you for your beautiful gift! ስለ ፡ ጥሩ ፡ ስጦታህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ
2. ገጸ ፡ በረከት. The ambassador brought gifts from his country. አምባሳደሩ ፡ ከሀገሩ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ይዞ ፡ መጣ
3. ተሰጥዎ. He has a gift for drawing. የሥዕል ፡ ተሰጥዎ ፡ አለው

**give as a gift** አበረከተ
She gave her golden dishes as a wedding gift. ለሰርጓ ፡ የወርቅ ፡ ሳሕኖች ፡ አበረከተችላት

**gift certificate** የገጸ ፡ በረከት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት
We received a gift certificate instead of a present. በስጦታ ፡ ፈንታ ፡ የገጸ ፡ በረከት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ተሰጠን

**gifted** ተሰጥዎ ፡ ያለው
He is a gifted boy. He can do anything. ተሰጥዎ ፡ ያለው ፡ ልጅ ፡ ስለሆነ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል

**gigantic** ግዙፍ
The Empire State Building is a gigantic building. የኤምፓየር ፡ ስቴት ፡ ሕንጻ ፡ ግዙፍ ፡ ሕንጻ ፡ ነው
*He has a gigantic appetite. መሰብ ፡ አርግፍ ፡ ነው

**gigantic size** ግዙፍነት
He was impressed by the gigantic size of the houses. የቤቶቹ ፡ ግዙፍነት ፡ አስደነቀው

**giggle** ተንከተከተ
Girls like to giggle. ልጃገረዶች ፡ መንከትከት ፡ ይወዳሉ

**gild** ነከረ
Swindlers gild copper coins with gold and sell them to tourists. አጭበርባሪዎች ፡ የመዳብ ፡ ሳንቲሞችን ፡ ወርቅ ፡ እየነከሩ ፡ ላገር ፡ ጐብኝዎች ፡ ይሸጣሉ

**gilded** ወርቃማ
The architect glorified the building with a gilded dome. መሀንዲሱ ፡ በወርቃማ ፡ ቁብታ ፡ ሕንጻውን ፡ አስጌጠው

**ginger** ዝንጅብል
Some people like to flavor tea with ginger. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ሻያቸውን ፡ በዝንጅብል ፡ ማጣፈጥ ፡ ይወዳሉ

**gingerly** ሲፈራ ፡ ሲቸር
She lifted the trap gingerly. ወጥመዱን ፡ ስትፈራ ፡ ስትቸር ፡ አነሣች

**giraffe** ቀጭኔ
There are giraffes in Kenya. በኬንያ ፡ ውስጥ ፡ ቀጭኔዎች ፡ ይገኛሉ

**gird** (vt.) ከበበ
Mountains girded the valley. ሸለቆውን ፡ ተራራዎች ፡ ከበውታል

**gird** (vi.) ተዘጋጀ
The soldier girded for action. ወታደሩ ፡ ለተግባር ፡ ተዘጋጀ

**gird on** ታጠቀ
He girded on a sword, and left to fight the enemy. ጎራዴ ፡ ታጥቆ ፡ ጠላትን ፡ ለመውጋት ፡ ሄደ

**gird oneself** ታጠቀ
The soldiers girded themselves for battle. ወታደሮቹ ፡ ለጦርነት ፡ ታጠቁ
[See also 'loin']

**girdle** (v.) ከበበ
Clouds girdled the moon. ደመና ፡ ጨረቃዋን ፡ ከቧታል

**girdle** (n.) መቀነት
She is so fat, she has to wear a girdle. እርሷ ፡ በጣም ፡ ወፍራም ፡ ስለሆነች ፡ መቀነት ፡ መታጠቅ ፡ አለባት

**girl**
1. ልጃገረድ. They hired a girl to do their housework. የቤት ፡ ሥራ ፡ እንድትሠራላቸው ፡ ልጃገረድ ፡ ቀጠሩ
Isn't she a pretty girl! ውብ ፡ ልጃገረድ ፡ አይደለችም ?
2. ልጅ. Your little girl has grown a lot. ትንሿ ፡ ልጅህ ፡ በጣም ፡ አድጋለች
[See also 'office girl']

**girl friend** የከንፈር ፡ ወዳጅ
My girl friend and I went to the theater last

night. እኔና ፡ የከንፈር ፡ ወዳጄ ፡ ትላንትና ፡ ማታ ፡ ወደ ፡ ቲያትር ፡ ሄድን

**girlhood** የልጅነት ፡ ዘመን
The old woman recalled her girlhood with pleasure. አሮጊቷ ፡ የልጅነት ፡ ዘመኗን ፡ በደስታ ፡ አስታወሰች

**girth**
1. ስፋት. His girth at the waist is forty inches. የወገቡ ፡ ስፋት ፡ አርባ ፡ ኢንች ፡ ነው
2. ውፍረት. In our garden, there is a tree five feet in girth. ባትክልት ፡ ቦታችን ፡ ውስጥ ፡ ውፍረቱ ፡ አምስት ፡ ጫማ ፡ የሆነ ፡ ዛፍ ፡ አለ
3. ቅናት. The mule's girth broke and the saddle fell. የበቅሎዋ ፡ ቅናት ፡ ተበጥሶ ፡ ኮርቻው ፡ ወደቀ

**gist** ፍሬ ፡ ነገር
Tell me the gist of what he said! የተናገረውን ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ንገረኝ

**give** (gave, given), vt.
1. ሰጠ. Please give me my book! መጽሐፌን ፡ ስጠኝ
The government gave $10,000 to the Red Cross. መንግሥት ፡ ለቀይ ፡ መስቀል ፡ ዐሥር ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ሰጠ
This farm gives large crops. ይህ ፡ እርሻ ፡ ብዙ ፡ ሰብል ፡ ይሰጣል
2. አቀረበ. Please give her my love! ለሷ ፡ ሰላምታዬን ፡ አቅርብልኝ
3. ጣለ. The hen gave six eggs a week. ዶሮዋ ፡ በሳምንት ፡ ስድስት ፡ እንቁላል ፡ ጣለች
4. ፈረደ(በት). The judge gave him five years. ዳኛው ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ፈረደበት

**give** (vi.) ተከፈተ
The door gave under hard pushing. መዝጊያው ፡ በኀይል ፡ ሲገፋት ፡ ተከፈተ
*The window gives on the sea. መስኮቱ ፡ በባሕሩ ፡ አቅጣጫ ፡ ነው

**give (someone one's) arm** ክንዱን ፡ አስያዘው
He gave her his arm when they crossed the street. መንገዱን ፡ ሲሻገሩ ፡ ክንዱን ፡ አስያዛት

**give away**
1. አወጣ. Do not give away my secret! ምስጢሬን ፡ አታውጣብኝ
2. ለሰው ፡ ሰጠ. I gave my old clothes away. አሮጌ ፡ ልብሶቼን ፡ ለሰው ፡ ሰጠኋቸው

**give (one) away** አስነቃ(በት)
His foreign way of speaking gave him away. አነጋገሩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ አስነቃበት

**give back** መለሰ
Please give me back my pen! ብዕሬን ፡ መልስልኝ

**give in** (vt.) አስረከበ
Please give in your exam papers here! የፈተና ፡ ወረቀታችሁን ፡ እዚህ ፡ አስረክቡ

**give in** (vi.)
1. እጅ ፡ ሰጠ. The rebels were forced to give in. ዐመፀኞቹ ፡ እጃቸውን ፡ እንዲሰጡ ፡ ተገደዱ
2. ፊት ፡ ሰጠ. The principal gives in to the students too much. ዲሬክተሩ ፡ ለተማሪዎቹ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ፊት ፡ ይሰጣቸዋል
3. ለቀቀ. He is so bullheaded, he never gives in. በጣም ፡ ሐሳበ ፡ ግትር ፡ ስለሆነ ፡ ያለውን ፡ በፍጹም ፡ አይለቅም
4. (= tr.) አሞላቀቀ. You give in to the child too much. ልጁን ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ታሞላቅቀዋለህ
5. ተቀበለ. He gave in grudgingly. እያጕረመረመ ፡ ተቀበለው

**(refuse to) give in** አልበገር ፡ አለ
Though the enemy threatened him with torture, he refused to give in. ምንም ፡ እንኳን ፡ ጠላት ፡ ሊያሠቃየው ፡ ቢያስፈራራውም ፡ አልበገር ፡ አለ

**give off** ሰጠ
This flower gives off a strange odor. ይህ ፡ አበባ ፡ የተለየ ፡ ዓይነት ፡ ሽታ ፡ ይሰጣል

**give out** (vt.)
1. ዐደለ. Who is giving out the candy? ከረሜላውን ፡ የሚያድል ፡ ማን ፡ ነው ?
2. ገለጸ. They will not give out the names of those killed in the crash. በግጭቱ ፡ ጊዜ ፡ የሞቱትን ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ አይገልጹም

**give out** (vi.)
1. አለቀ. The candy gave out during the party. በግብዣው ፡ መካከል ፡ ከረሜላው ፡ አለቀ
2. ትይዩ ፡ ነው. The window gives out on the garden. መስኮቱ ፡ ባትክልቱ ፡ ስፍራ ፡ ትይዩ ፡ ነው

**give over**
1. አዛወረ. She gave over all property to her son. ንብረቷን ፡ ሁሉ ፡ ለልጅዋ ፡ አዛወረች
2. መደበ. The municipality gave over the park for a building. ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ የመናፈሻ ፡ ቦታውን ፡ ለሕንጻ ፡ መደበ

**(be) given over to**
*The day was given over to relaxing in the sun. ቀኑን ፡ ፀሐይ ፡ ላይ ፡ በመናፈስ ፡ አሳለፉት

**give rise to** አስከተለ
The raids only give rise to further retaliation. ዘመቻዎቹ ፡ ሌላ ፡ ዐጸፋ ፡ ያስከትላሉ

**(be) given to** ወደደ
He is much given to hunting and fishing. አደንና ፡ ዓሣ ፡ ማጥመድ ፡ በጣም ፡ ይወዳል
*He is given to bragging. ጉራ ፡ መንዛት ፡ ልማዱ ፡ ነው

**give up**
1. አቆመ. I am going to give up smoking. ሲጃራ ፡ ማጨስ ፡ ላቆም ፡ ነው
2. ለቀቀ. John gave up his job. ዮሐንስ ፡ ሥራውን ፡ ለቀቀ
The enemy gave up the fortress and withdrew. ጠላት ፡ ምሽጉን ፡ ለቆ ፡ አፈገፈገ
3. ተወ. Stick to it; don't give up now! በነገሩ ፡ ግፋበት ፡ አትተው
4. ተበፋ ፡ ቈረጠ. Make a stab at an answer before giving up! ተስፋ ፡ ከመቍረጥህ ፡ በፊት ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ሞክር
*They gave him up for lost. እንደጠፋ ፡ ቈጠሩት
*I give up! What is the answer? አቃተኝ ፤ መልሱ ፡ ምንድነው ?

**give (oneself) up** እጅ ፡ ሰጠ
He gave himself up to the police. እጁን ፡ ለፖሊስ ፡ ሰጠ

**give way** ፈረሰ
Because of the heavy truck traffic, the bridge gave way. ብዙ ፡ ከባድ ፡ መኪናዎች ፡ ስለሚመላለሱበት ፡ ድልድዩ ፡ ፈረሰ
[See also numerous nouns with 'give', such as 'air, notice, satisfaction']

## given (adj.)
1. የተወሰነ. You must finish the test in a given time. ፈተናውን ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መጨረስ ፡ አለብህ
2. የቀረበ. What can we judge from the given facts? ከቀረበልን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ውሳኔ ፡ ልንሰጥ ፡ እንችላለን ?

## gizzard መቋደሻ
He cut open the chicken and removed its gizzard. የዶሮውን ፡ ሆድ ፡ ቀዶ ፡ መቋደሻውን ፡ አወጣ

## glacial ብርዳማ
A glacial wind blew down from the mountain. ብርዳማ ፡ ነፋስ ፡ ከተራራው ፡ ነፈሰ

**glacial look** ግልምጫ
Her glacial look silenced him. ግልምጫዋ ፡ ዝም ፡ አሰኘው

## glacier [ግግር ፡ በረዶ ፤ የውርጭ ፡ ወንዝ]

## glad
1. የሚያስደስት. The glad news made her happy. የሚያስደስተው ፡ ወሬ ፡ አስፈነደቃት
2. የደስታ. The wedding was a glad occasion. ሰርጉ ፡ የደስታ ፡ ጊዜ ፡ ነበር

**be glad**
1. ተደሰተ. We are very glad about it. በነገሩ ፡ በጣም ፡ ተደስተናል
2. ፈቃደኛ ፡ ነው. I'm always glad to oblige you. ልታዘዝህ ፡ ምንጊዜም ፡ ፈቃደኛ ፡ ነኝ
3. ደስ ፡ አለ(ው). Glad to meet you! በመተዋወቃችን ፡ ደስ ፡ ብሎኛል
[See also 'tidings']

## gladden ደስ ፡ አሰኘ
The present will gladden her heart. ስጦታው ፡ ደስ ፡ ያሰኛታል

## gladly በደስታ
Would you do me a favor? Gladly. አንድ ፡ ነገር ፡ ልታደርግልኝ ፡ ትችላለህ ? በደስታ !

## glamor ውበት
The glamor of the East has always attracted me. የምሥራቅ ፡ ውበት ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ እንደማረከኝ ፡ ነው

## glance (v.), ~ about ቃኘ
The speaker glanced about the room before speaking. ተናጋሪው ፡ ከመናገሩ ፡ በፊት ፡ ክፍሉን ፡ ቃኘው

**glance at** ተመለከተ ፤ አየት ፡ አደረገ
He glanced at his watch. ሰዓቱን ፡ ተመለከተ ፡ (አየት ፡ አደረገ)

## glance (n.) መልከት ፡ ማድረግ
A glance at the newspaper is sufficient for reading the headlines. አርእስተ ፡ ዜናዎች ፡ ለማንበብ ፡ ጋዜጣውን ፡ መልከት ፡ ማድረግ ፡ ይበቃል

**at a glance** ባንዴ
I could tell at a glance that something was wrong. አንድ ፡ ጉድለት ፡ እንዳለው ፡ ባንዴ ፡ ዐወቅሁ

**cast a glance** ዓይኑን ፡ ወርወር ፡ አደረገ
He cast a glance at the pretty girl. ወደ ፡ ቆንጆዋ ፡ ልጅ ፡ ዓይኑን ፡ ወርወር ፡ አደረገ

**give a casual glance at** አየት ፡ አየት ፡ አደረገ
I gave a casual glance at the newspaper. ጋዜጣውን ፡ አየት ፡ አየት ፡ አደረግሁት

**give only a glance** አየት ፡ አደረገ
I gave the girl only a glance. ልጅቷን ፡ አየት ፡ አደረግኋት

**throw a glance** አየ ፤ ተመለከተ ፤ መልከት ፡ አደረገ
She threw a furtive glance at him. ሰረቅ ፡ አድ ርጋ ፡ አየችው ፡ (ተመለከተችው)
[See also 'covert, dart, oblique, passing, shoot, sneak, steal']

**gland** እጢ
Certain glands are in the throat. አንዳንድ ፡ እጢ ዎች ፡ ከጉሮሮ ፡ ሥር ፡ ይገኛሉ

**glare** (v.)
*Put on your sunglasses when the sun glares! የፀሐይ ፡ ጨረር ፡ ሲመታህ ፡ የፀሐይ ፡ መነጽርህን ፡ አድርግ

**glare at** አፈጠጠ(በት)
Why are you glaring at me like that? ለምን ፡ እንደዚህ ፡ ታፈጥብኛለህ ?

**glare** (n.)
1. ነጸብራቅ. The glare hurts my eyes. ነጸብራቁ ፡ ዓይኔን ፡ ይጐዳዋል
2. ብርሃን. The glare of the searchlight bedazzled him. የባውዛው ፡ ብርሃን ፡ ዓይኑን ፡ አጥበረበረው
3. ግልምጫ. His glare terrifies the secretary. ግልምጫው ፡ ጸሓፊዋን ፡ ያስደነግጣታል

**glaring** (adj.)
1. የሚያንጸባርቅ. How can you work in that glaring light? በዚህ ፡ በሚያንጸባርቅ ፡ ብርሃን ፡ እንዴት ፡ ለመሥራት ፡ ትችላለህ ?
2. በጣም ፡ ጉልህ. He made a glaring mistake in his report. በሪፖርቱ ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ ጉል ህ ፡ የሆነ ፡ ስሕተት ፡ አደረገ

**be glaring** አጥበረበረ
The light is too glaring. መብራቱ ፡ በጣም ፡ ያ ጥበረብራል

**glass** (n.)
1. መስታወት. The pitcher is made of glass. ማብረጃው ፡ የተሠራው ፡ ከመስታወት ፡ ነው
I cut myself on a piece of glass. የመስታወት ፡ ስባሪ ፡ ቈረጠኝ
2. ብርጭቆ. There is a crack in the glass. ብርጭቆው ፡ ስንጥቅ ፡ አለው
May I have a glass of water? አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ውኃ ፡ አገኛለሁ ?

**glass** (adj.) ከመስታወት ፡ የተሠራ
The glass dish broke. ከመስታወት ፡ የተሠራው ፡ ሳሕን ፡ ተሰበረ

**glasses** መነጽር
My glasses fell on the floor. መነጽሬ ፡ እወለሉ ፡ ላይ ፡ ወደቀ

**glassy** መስታወት ፡ የሚመስል
He likes to look at the glassy surface of the lake. መስታወት ፡ የሚመስለውን ፡ የሐይቁን ፡ ገጽ ፡ መመልከት ፡ ይወዳል

**be glassy** ፈዘዘ
The man's eyes were glassy. ሰውዬው ፡ ዐይኑ ፡ ፈዟል

**glaze**
1. መስታወት ፡ አስገባ. They finished glazing the windows in the new house. ላዲሱ ፡ ቤት ፡ መ ስኮት ፡ መስታወት ፡ አስገብተው ፡ ጨረሱ
2. አብረቅራቂ ፡ መልክ ፡ ሰጠ. These ovens are used to glaze the pottery. እነዚህ ፡ ምድጃዎ ች ፡ ለሸክላዎች ፡ አብረቅራቂ ፡ መልክ ፡ ለመስጠ ት ፡ ያገለግላሉ

**gleam** (v.)
1. አበራ. His eyes were gleaming. ዓይኖቹ ፡ ያበ ሩ ፡ ነበር
2. አንጸባረቀ. He polished the bucket until it gleamed. ባልዲውን ፡ እስኪያንጸባርቅ ፡ ወለ ወለው

**gleam** (n.) ጭላንጭል
A gleam of light could be seen in the distance. የብርሃን ፡ ጭላንጭል ፡ ከሩቅ ፡ ይታይ ፡ ነበር
There was a gleam of hope in his eyes. የተስ ፋ ፡ ጭላንጭል ፡ ይታይበት ፡ ነበር

**glean** ለቀመ
Ruth met Boaz while gleaning the grain. ሩት ፡ እህል ፡ ስትለቅም ፡ ቦአዝን ፡ አየችው

**glee** ደስታ
She expressed her glee in shouts. ደስታዋን ፡ በጩኸት ፡ ገለጸች

**be in glee** በደስታ ፡ ፈነደቀ
She was in glee when she learned the news. ወሬውን ፡ ስትሰማ ፡ በደስታ ፡ ፈነደቀች

**glee club** የሙዚቃ ፡ ክበብ
The glee club sings Ethiopian songs. የሙዚቃ ው ፡ ክበብ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዘፈኖች ፡ ይዘፍናል

**glib** አፈ ፡ ጮሌ
He is very glib, and can persuade anyone to do anything. በጣም ፡ አፈ ፡ ጮሌ ፡ ስለሆነ ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ እንዲሠራ ፡ ሊያግባባ ፡ ይ ችላል

**glide**
1. ተንሸራተተ. The children glided on the ice. ልጆቹ ፡ በረዶው ፡ ላይ ፡ ተንሸራተቱ

2. አሽርገመገመ. The kite glided downward. ወላንዳው ፡ ቁልቁል ፡ አሽርገመገመ

**glide by** ሮጠ
The years glide by. ጊዜው ፡ ይሮጣል

**glide in** አዘቀዘቀ
The plane glided in for a landing. አውሮፕላኑ ፡ ለማረፍ ፡ አዘቀዘቀ

**glide out** ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ወጣ
She glided out of the room. ከክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ሹልክ ፡ ብላ ፡ ወጣች

**glide past** ሮጠ
The years glided past. ጊዜው ፡ ሮጠ

**glimmer** (v.) ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ አለ
The candle glimmered and went out. ሻማው ፡ ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ ብሎ ፡ ጠፋ

**glimmer** (n.) ጭላንጭል.
The lost traveler saw a glimmer in the woods. መንገድ ፡ የጠፋው ፡ መንገደኛ ፡ በጫካው ፡ ውስ ጥ ፡ የመብራት ፡ ጭላንጭል ፡ ታየው
The doctor's report gave us only a glimmer of hope. የሐኪሙ ፡ መግለጫ ፡ የተስፋ ፡ ጭላንጭል ፡ ሰጠን

**glimpse** አየ
He glimpsed a man running quickly to the back of the building. ወደ ፡ ሕንጻው ፡ ጀርባ ፡ ሰው ፡ ውልብ ፡ ብሎ ፡ ሲያልፍ ፡ አየ

**glimpse at** አየት ፡ አየት ፡ አደረገ
The buyer glimpsed at the painting and left. ገዢው ፡ ሥዕሉን ፡ አየት ፡ አየት ፡ አድርጎ ፡ ሄደ

**glimpse** (n.)
*One glimpse of her was enough to make him fall in love. ለቅጽበት ፡ ቢያያት ፡ በፍቅር ፡ ተነደፈ

**catch a glimpse of** አየት ፡ አደረገ
He caught a glimpse of the girl. ልጅቷን ፡ አየት ፡ አደረጋት

**glisten** አንጸባረቀ
The streets glistened after the rain. መንገዶቹ ፡ ከዝናቡ ፡ በኋላ ፡ አንጸባረቁ

**glitter**
1. አንጸባረቀ. The snow glitters in the sun. በረዶው ፡ ከፀሐዩ ፡ ብርሃን ፡ የተነሣ ፡ ያንጸባር ቃል
2. ደመቀ. His speech glittered with wit. ንግግሩ ፡ በወግ ፡ የደመቀ ፡ ነበር

**gloat**
1. ፈነደቀ. He gloated over my misfortunes. መጥፎ ፡ ዕድል ፡ ስላጋጠመኝ ፡ ፈነደቀ
2. የሙጥኝ ፡ አለ. The miser gloats over his gold. ጩቁ ፡ ወርቁን ፡ የሙጥኝ ፡ ይላል

**global** ዓለም ፡ አቀፍ
This incident can create a global conflict. ይህ ፡ ግጭት ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ጥል ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል

**globe**
1. ሉል. A globe is useful for the study of geography. ሉል ፡ ለመልክአ ፡ ምድር ፡ ትምህርት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው
2. መሬት. The satellite circles the globe every 90 minutes. ሰው ፡ ሠራሿ ፡ ጨረቃ ፡ በየዘጠናው ፡ ደቂቃ ፡ መሬትን ፡ ትዞራለች

**gloom**
1. መተከዝ. His gloom made everyone feel uneasy. የሱ ፡ መተከዝ ፡ ሁሉንም ፡ እንዳይዝናኑ ፡ አደረጋቸው
2. ድብዛዛ ፡ ብርሃን. He could not see in the gloom without a flashlight. በድብዛዛው ፡ ብርሃን ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ባትሪ ፡ ሊያይ ፡ አልቻለም

**gloomy**
1. ቀፋፊ. Yesterday was a very gloomy day. ትናንትና ፡ በጣም ፡ ቀፋፊ ፡ ቀን ፡ ነበር
2. ጨለምለም ፡ ያለ. The child was afraid to walk down the gloomy corridor. ልጁ ፡ ጨለምለም ፡ ባለው ፡ መተላለፊያ ፡ ውስጥ ፡ መሄድ ፡ ፈራ
3. ተስፋ ፡ የሚያስቈርጥ. He gave a gloomy picture of the economic situation. ስለ ፡ ኢኮኖሚው ፡ ሁኔታ ፡ ተስፋ ፡ የሚያስቈርጥ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠ

**look gloomy**
He looks so gloomy. የከፋው ፡ ይመስላል

**glorify** (glorified)
1. አሞገሰ. He glorified the patriots in his book. በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ አርበኞቹን ፡ አሞገሳቸው
We sing hymns to glorify God. እግዚአብሔርን ፡ ለማሞገስ ፡ መዝሙር ፡ እንዘምራለን
2. አስጌጠ. The architect glorified the building with a gilded dome. መሀንዲሱ ፡ በወርቃማ ፡ ቁብታ ፡ ሕንጻውን ፡ አስጌጠው

**glorify one's name** ዝና ፡ አተረፈ(ለት)
His deeds have glorified his name. የሠራቸው ፡ ሥራዎች ፡ ዝና ፡ አተረፉለት

**glorious**
1. ያሸበረቀ. The wedding was a glorious event. ሰርጉ ፡ ያሸበረቀ ፡ ነበር

2. ታላቅ. They achieved a glorious victory over their enemies. እነርሱ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ድል ፡ ተቀዳጁ
3. የሚያኰራ. Ethiopia's heritage is a glorious one. የኢትዮጵያ ፡ ቅርስ ፡ የሚያኰራ ፡ ነው

**glory**
1. ክብር. There is no glory in being a thief. በሌብነት ፡ ክብር ፡ አይገኝም
Edison's inventions brought him glory. የኤዲሰን ፡ ፍልሰፋዎች ፡ ክብር ፡ አተረፉለት
2. ታላቅ ፡ ክብር. Greece was in her glory many centuries ago. ከብዙ ፡ ዘመናት ፡ በፊት ፡ ግሪክ ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ላይ ፡ ነበረች
3. ታላቅነት. The glory of heaven surpasses description. የሰማይን ፡ ታላቅነት ፡ ለመግለጽ ፡ ቃል ፡ አይገኝለትም
4. ምስጋና. Glory be to God! ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይድረሰው
5. መኩሪያ. The obelisks in Aksum are the glory of Ethiopia. የአክሱም ፡ ሐውልቶች ፡ የኢትዮጵያ ፡ መኩሪያ ፡ ናቸው
6. ውበት. The glory of the sunset filled his heart with a feeling of awe. የፀሐይ ፡ ጥልቀት ፡ ውበት ፡ ልቡን ፡ ባድናቆት ፡ ሞላው

**gloss** (v.), ~ **over** ሸፋፈነ
He tried to gloss over his mistakes. ስሕተቶቹን ፡ ለመሸፋፈን ፡ ሞከረ

**gloss** (n.) ወዝ
After a car has been left in the rain, it loses its gloss. መኪና ፡ ዝናም ፡ ውስጥ ፡ ሲቆይ ፡ ወዙን ፡ ያጣል

**glossary** (glossaries) አጭር ፡ መዝገበ ፡ ቃላት
Some schoolbooks have glossaries at the end. አንዳንድ ፡ የመማሪያ ፡ መጻሕፍት ፡ በስተመጨረሻቸው ፡ አጭር ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ አላቸው

**glossy** ልስልስና ፡ አንጸባራቂ
This paper is glossy. ይህ ፡ ወረቀት ፡ ልስልስና ፡ አንጸባራቂ ፡ ነው

**glove** የእጅ ፡ ሹራብ ፤ ጓንቲ
I lost a glove yesterday. ትላንት ፡ የእጅ ፡ ሹራብ ፡ (ጓንቴ) ፡ ጠፋብኝ
**pair of gloves** ጓንቴ ፤ የእጅ ፡ ሹራብ
I bought a pair of gloves yesterday. ትላንትና ፡ ጓንቴ ፡ (የእጅ ፡ ሹራብ) ፡ ገዛሁ
[See also 'hand']

**glow** (v.)
1. አበራ. The hot metal glows in the dark. የጋለው ፡ ብረት ፡ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ያበራል
2. ፈካ ፡ አበራ. She glowed with pride when she showed us the prize. ሽልማቱን ፡ ስታሳየን ፡ ፊቷ ፡ በኩራት ፡ ያበራ ፡ ነበር
3. ደምቆ ፡ ታየ. Embers glowed after the fire died. እሳት ፡ ከጠፋ ፡ በኋላ ፡ ፍሙ ፡ ደምቆ ፡ ታየ

**glow** (n.) ብርሃን
I can see the glow of a candle in the window. በመስኮቱ ፡ የሻማ ፡ ብርሃን ፡ ይታየኛል
**red glow** የደም ፡ መምሰል
The red glow at sunset is very beautiful. ፀሐይ ፡ ስትጠልቅ ፡ የሰማዩ ፡ ደም ፡ መምሰል ፡ በጣም ፡ ያምራል
**warm glow** ሙቀት
He drank the arrack and felt a warm glow inside him. አረቄውን ፡ ጠጥቶ ፡ ሰውነቱ ፡ ውስጥ ፡ ሙቀት ፡ ተሰማው

**glowing**
1. ብሩህ. This rainbow has glowing colors. ይህ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ ብሩህ ፡ ቀለማት ፡ አሉት
2. ስሜት ፡ የተሞላበት. He described his plan in glowing terms. እቅዱን ፡ ስሜት ፡ በተሞላባቸው ፡ ቃላት ፡ ገለጸ

**glue** (v.)
1. አጣበቀ. The cup broke and I had to glue it. ሲኒው ፡ ስለተሰበረ ፡ ማጣበቅ ፡ ነበረብኝ
2. ማጣበቂያ ፡ አደረገበት. Glue the flap of the envelope! ያንቦልኩን ፡ ክዳን ፡ ማጣበቂያ ፡ አድርግበት
3. በሙጫ ፡ አጣበቀ. He carefully glued each page. እያንዳንዱን ፡ ገጽ ፡ በጥንቃቄ ፡ በሙጫ ፡ አጣበቀ
4. ተከለ. He glued his eyes to the windows. ዓይኖቹን ፡ መስኮቱ ፡ ላይ ፡ ተከለ
**glue oneself to** ጥብቅ ፡ አለ
The child glues himself to his father's side. ልጁ ፡ አባቱ ፡ ላይ ፡ ጥብቅ ፡ ይላል

**glue** (n.) ሙጫ
Glue is one of many adhesives. ሙጫ ፡ ከብዙ ፡ ማጣበቂያ ፡ ዓይነቶች ፡ አንዱ ፡ ነው

**glum, look** ~ ቅፍፍ ፡ አለ(ው)
He looks glum. He must have failed the exam. ቅፍፍ ፡ ብሎታል ፤ በፈተና ፡ ሳይወድቅ ፡ አይቀርም

**glutton** ሆዳም
Don't be such a glutton! እንደዚህ ፡ ሆዳም ፡ አትሁን

**gluttony** ሆዳምነት
His gluttony is responsible for his obesity. ቦርጫም ፡ የሆነው ፡ ከሆዳምነቱ ፡ የተነሣ ፡ ነው

**gnarl** ዓይን
Wood with gnarls is hard to cut. ዓይን ፡ ያለውን ፡ ዕንጨት ፡ ለመቍረጥ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**gnash** አፋጨ
He gnashed his teeth. ጥርሱን ፡ አፋጨ

**gnat** ትንኝ
Gnats like to rest on dirty places. ትንኝ ፡ ቆሻሻ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ማረፍ ፡ ትወዳለች

**gnaw**
1. ቈረጣጠመ. The dog gnawed at the bone. ውሻው ፡ አጥንቱን ፡ ቈረጣጠመው
2. ከነከነ. The lie gnawed his conscience. የተናገረው ፡ ውሸት ፡ ኅሊናውን ፡ ከነከነው

**gnaw a hole** ሰርስሮ ፡ ቀዳዳ ፡ አበጀ
The rat gnawed a hole through the wall. አይጢ ፡ በግድግዳው ፡ ውስጥ ፡ ሰርስራ ፡ ቀዳዳ ፡ አበጀች

**go** (went)
1. ሄደ. How long has he been gone? ከሄደ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ሆነው ?
Let's go for a walk! እስቲ ፡ በእግራችን ፡ ሽር ሽር ፡ እንሂድ
The bus has already gone. አውቶቡሱ ፡ ሄዷል
2. ተነሣ. The train goes at five. ባቡሩ ፡ በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ይነሣል
3. ደረሰ. The wire goes to the basement. ሽቦው ፡ እምድር ፡ ቤት ፡ ይደርሳል
4. ተሰራጨ. The flu went through the whole school. ኢንፍሉዌንዛ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ ተሰራጨ
5. ጀመረ. Go when you hear the bell! ደወል ፡ ስትሰማ ፡ ጀምር
6. አለፈ. Winter has gone and spring is here. ክረምት ፡ አልፎ ፡ ጸደይ ፡ ተተካ
7. ነዳ. Go slow, or you'll damage your car. ቀስ ፡ ብለህ ፡ ንዳ ፤ አለዚያ ፡ መኪናህን ፡ ታበላሻለህ
Do not go beyond the speed limit! ከተወሰነው ፡ ፍጥነት ፡ በላይ ፡ አትንዳ
8. አለቀ. Everything is gone. ሁሉም ፡ ነገር ፡ አልቋል
My money goes for food and rent. ገንዘቤ ፡ የሚያልቀው ፡ በምግብና ፡ በቤት ፡ ኪራይ ፡ ነው
9. አዋለ. +All his spare money goes for books. ትርፍ ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ለመጻሕፍት ፡ ያውላል
10. ሟሟ. The snow is all gone. በረዶው ፡ በሙሉ ፡ ሟምቷል
11. ቀረበ. He went before the judge to explain his part in the accident. እርሱ ፡ ስለ ፡ አደጋው ፡ በበኩሉ ፡ ያለውን ፡ ለመግለጽ ፡ ዳኛው ፡ ፊት ፡ ቀረበ
12. ገባ. I do not want to go into details on this matter. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ዝርዝር ፡ ሐተታ ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ አልሻም
Let's go into the house! ወደ ፡ ቤት ፡ እንግባ
Go to the devil! ገደል ፡ ግባ
13. ተማረ. He goes to the University of California. ካሊፎርኒያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ውስጥ ፡ ይማራል
14. ተመራ. Do not go by what he says! እሱ ፡ ባለህ ፡ አትመራ
15. ተከተለ. I must go by what my lawyer says. ጠበቃዬ ፡ የሚለውን ፡ መከተል ፡ አለብኝ
16. ወሰደ. This road goes to Addis Ababa. ይህ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ይወስዳል
17. በሙሉ ፡ ተወገደ. Corrupt practices must go if the situation is to improve. ሁኔታው ፡ እንዲሻሻል ፡ ከተፈለገ ፡ ብልሹ ፡ ተግባሮች ፡ በሙሉ ፡ መወገድ ፡ አለባቸው
18. ሠራ. This clock won't go anymore. ሰዓቱ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ አይሠራም
19. ፈረሰ. This wall is so weak, it may go at any moment. ይህ ፡ ግድግዳ ፡ ልል ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል
20. ደከመ. His eyesight is beginning to go. የዓይኑ ፡ ብርሃን ፡ መድከም ፡ ጀምሯል
21. ተካሄደ. That's the way things go around here. እዚህ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ የሚካሄደው ፡ እንደዚህ ፡ ነው
How did the game go? ጨዋታው ፡ እንዴት ፡ ተካሄደ ?
22. ተፈጸመ. The meeting went without a hitch. ስብሰባው ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ ተፈጸመ
23. ነው. The song goes like this. ዘፈኑ ፡ እንዲህ ፡ ነው
24. ገዛ. A dollar does not go as far as it used to. አንድ ፡ ብር ፡ የድሮውን ፡ ያህል ፡ አይገዛም
25. (= tr.) አገኘ. +The first prize went to Hailu. ያንደኛነቱን ፡ ሽልማት ፡ ኀይሉ ፡ አገኘ
26. ተገናኘ. After their quarrel, he did not go with Mary anymore. ከተጣሉ ፡ ወዲህ ፡ ከሚሪ ፡ ጋር ፡ አይገናኝም
27. ጠፋ. The memory of the event was gone from his consciousness. ነገሩ ፡ ከሐሳቡ ፡ ጠፍቷል
*This book goes on the top shelf. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ቦታው ፡ ላይኛው ፡ መደርደሪያ ፡ ላይ ፡ ነው
*He goes by the name of John. ስሙ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው

**go about** ሥራ
Go about your business, and leave me alone! እኔን ፡ ተውና ፡ ሥራህን ፡ ሥራ
*You are not going about it in the right way. አሠራርህ ፡ በትክክለኛ ፡ መንገድ ፡ አይደለም
*How do you go about joining this association? የማኅበሩ ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ?
*If you want a job you have to know how to go about it in the right way. ሥራ ፡ ስትፈልግ ፡ ማድረግ ፡ ያለብህን ፡ ነገር ፡ በትክክል ፡ ማወቅ ፡ አለብህ

**go after** ተከታተለ
He is going after that pretty girl. ያችን ፡ ቆንጆ ፡ ልጃገረድ ፡ ይከታተላል

**go against** ተቃረነ
That goes against my principles. ይህ ፡ እምነቴን ፡ ይቃረናል

**go ahead**
1. ጀመረ. May I start now? Yes, go ahead. አሁን ፡ ልጀምር ? አዎን ፡ ጀምር
2. ቀደመ. You go ahead. I will follow later. ቅደም ፡ በኋላ ፡ እከተላለሁ
3. ዝም ፡ ብሎ ፡ ቀጠለ. He went ahead unmindful of the results. የሚያስከትለውን ፡ ነገር ፡ ሳያስተውል ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቀጠለ
4. ገፋ. Go ahead with this work! በዚህ ፡ ሥራ ፡ ግፋበት

**go along with**
1. ደገፈ. We are going along with his decision. የሱን ፡ ውሳኔ ፡ እንደግፋለን
2. ሄደ. I'll go along with you. ካንተ ፡ ጋር ፡ እሄዳለሁ
3. አብሮት ፡ ሄደ. He will go along with you as far as the church. ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ድረስ ፡ አብሮህ ፡ ይሄዳል

**go around**
1. ዞሮ ፡ ሄደ. The bridge between Addis Ababa and Harar is demolished, so we had to go around by way of Bale. በአዲስ ፡ አበባና ፡ በሐረር ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ ድልድይ ፡ ስለፈረሰ ፡ በባሌ ፡ በኩል ፡ ዞረን ፡ መሄድ ፡ ነበረብን
2. ተዳረሰ. There is not enough food to go around. ለሁሉም ፡ የሚዳረስ ፡ ምግብ ፡ የለም

**go as far as to say** እስከማለት ፡ ደረሰ
I will go as far as to say he deserves more money. እኔ ፡ እንዲያውም ፡ የበለጠ ፡ ገንዘብ ፡ ይገባዋል ፡ እስከማለት ፡ እደርሳለሁ

**go at** ጀመረ
He went at his work with a will. ሥራውን ፡ በሙሉ ፡ ልብ ፡ ጀመረ
2. ተተናኰለ. The dog went at the mailman. ውሻው ፡ ፖስታ ፡ አመላላሹን ፡ ተተናኰለው
3. ሰፈረ(በት). They went at the food like hungry wolves. እምግቡ ፡ ላይ ፡ እንደራበው ፡ ተኩላ ፡ ሰፈሩበት
*You are not going at it right. አያያዝህ ፡ ትክክል ፡ አይደለም

**go at each other** ተደባደበ
They went at each other furiously. በኀይል ፡ ተደባደቡ

**go away**
1. ሄደ. When did he go away? መቼ ፡ ነው ፡ የሄደው ?
2. ተወ. I wish this pain would go away. ይህ ፡ ሕመም ፡ በተወኝ

**go back** ተመለሰ
She went back into the house. ወደ ፡ ቤት ፡ ተመልሳ ፡ ገባች
*Their quarrel goes back to a dispute over land. የጠባቸው ፡ መነሻ ፡ የመሬት ፡ ክርክር ፡ ነው
*His memory does not go back that far. እስከ ፡ ዚህ ፡ ትዝ ፡ አይለውም

**go back on** ዐጠፈ
He went back on his promise. ቃሉን ፡ ዐጠፈ

**go behind** በ - - - ተከለለ
The sun went behind the clouds and the air grew cold. ፀሐይዋ ፡ በደመና ፡ ስትከለል ፡ አየሩ ፡ ቀዘቀዘ

**go behind one's back** በጐን ፡ ሄደ
After I refused, he went behind my back and got permission. እኔ ፡ እምቢ ፡ ካልኩኝ ፡ በኋላ ፡ በጐን ፡ ሄዶ ፡ ፈቃድ ፡ ተቀበለ

**go beyond**
*You have gone beyond your instructions. የሠራኸው ፡ ከተሰጠህ ፡ መምሪያ ፡ ውጭ ፡ ነው

**go by**
1. አለፈ. Time went by slowly. ጊዜው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ አለፈ
2. አመለጠ(ው). +I would not let that opportunity go by, if I were you. እኔ ፡ አንተን ፡ ብሆን ፡ ያ ፡ዕድል ፡ እንዲያመልጠኝ ፡ አላደርግም ፡ ነበር

**go down**
1. ወረደ. Prices for grain have gone down. የእህል ፡ ዋጋ ፡ ወርዷል
He went down the hill on a mule. በበቅሎ ፡ ቁልቁለቱን ፡ ወረደ
2. ወደ ፡ ታች ፡ ወረደ. The elevator is going down. አሳንሰሩ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ እየወረደ ፡ ነው

3. አዘቀዘቀ. The sun went down. ጀንበሯ ፡ አዘቀዘቀች
4. ዝቅ ፡ አለ. Infant mortality has been going down. የሚሞቱ ፡ ሕፃናት ፡ ቁጥር ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ሄዷል
5. ተዋጠ. Some foods go down more easily than others. አንዳንድ ፡ ምግብ ፡ ከሌላ ፡ ምግብ ፡ ይልቅ ፡ በቀላሉ ፡ ይዋጣል
6. ጐደለ. The water has gone down, so we can cross now. ውኃው ፡ ስለጐደለ ፡ አሁን ፡ ልንሻገር ፡ እንችላለን
7. ስሙ ፡ ተመዘገበ ፤ ተመዘገበ. Emperor Haile Sellassie will go down in history as a great statesman. ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ እንዳንድ ፡ ታላቅ ፡ መሪ ፡ ስማቸው ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ይመዘገባል
His execrable wickedness has gone down in history. አሰቃቂው ፡ ክፋቱ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ተመዝግቧል
8. አተተ. This history of Ethiopia only goes down to 1936. ይህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ከ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ጀምሮ ፡ ያለውን ፡ ብቻ ፡ ያትታል
*The army went down fighting. ወታደሮቹ ፡ ቢሸነፉም ፡ መዋጋታቸውን ፡ አላቋረጡም

**go faster** ፈጠን ፡ አለ
Can't you go any faster in your work? ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ፈጠን ፡ ብለህ ፡ ለመሥራት ፡ አትችልም ?

**go (for)**
1. ሄዶና ፡ ጠራ. Shall I go for a doctor? ልሂድና ፡ ሐኪም ፡ ልጥራ ?
2. ተመለከተ. What I said about him goes for you. ስለሱ ፡ የተናገርኩት ፡ አንተንም ፡ ይመለከታል
3. ደገፈ. He did not go for my idea at all. አሳቤን ፡ በፍጹም ፡ አልደገፈውም
4. ወደደ. It simply isn't the kind of life you would go for. አንተ ፡ የምትወደው ፡ ዓይነት ፡ ኑሮ ፡ አይደለም

**go for nothing** መና ፡ ቀረ
All his work went for nothing. ሥራው ፡ ሁሉ ፡ መና ፡ ቀረ

**go forward** ተገፋ
The work is not going forward very well. ሥራው ፡ እጅግም ፡ አልተገፋም

**go in**
1. ገባ. I didn't go in because it was late. ዘግይቶ ፡ ስለነበር ፡ ልገባ ፡ አልፈለግሁም
2. ተሻረከ. Would you like to go in with me on that deal? በንግዱ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ለመሻረክ ፡ ትፈልጋለህ ?

**go in for**
*Do you go in for sports? እስፖርት ፡ ትጫወታለህ ?

**go (into)** ጠልቆ ፡ ገባ
We need go no further into the matter. ወደ ፡ ነገሩ ፡ ይበልጥ ፡ ጠልቀን ፡ መግባት ፡ አያስፈልገንም
*My clothes won't go into such a small suitcase. ልብሶቼን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ትንሽ ፡ ሻንጣ ፡ አይችላቸውም
*He went into the clothing business. ልብስ ፡ ነጋዴ ፡ ሆነ
*Three goes into nine three times. ዘጠኝ ፡ ለሦስት ፡ ሲካፈል ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ይደርሳል

**go off**
1. ጠፋ. These goods have gone off the market. እነዚህ ፡ ሸቀጦች ፡ ከገበያ ፡ ጠፍተዋል
2. ነበረ. How did the performance go off? ቲያትሩ ፡ እንዴት ፡ ነበር ?
3. ባረቀ. Be careful! The gun might go off. ጠበንጃው ፡ እንዳይባርቅ ፡ ተጠንቀቅ
4. ፈነዳ. The bomb was timed to go off at nine. ቦምቡ ፡ የተጠመደው ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ እንዲፈነዳ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር
[See also 'air, fail']

**go off with**
1. ይዞ ፡ ሄደ. He has gone off with my razor. እርሱ ፡ ምላጬን ፡ ይዞ ፡ ሄዷል
2. ይዞበት ፡ ኰበለለ. Someone has gone off with his wife. አንድ ፡ ሰው ፡ ሚስቱን ፡ ይዞበት ፡ ኰበለለ

**go on**
1. ቀጠለ. If you go on like this, you will be expelled. በእንዲህ ፡ ዓይነት ፡ የቀጠልክ ፡ እንደሆነ ፡ ትባረራለህ
Go on until you get to page three! ሦስተኛው ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ እስክትደርስ ፡ ቀጥል
2. ሆነ. Don't go on like that! እንደዚህ ፡ አትሁን
He is going on twenty. ሀያ ፡ ዓመት ፡ ሊሆነው ፡ ነው
3. ሄደ. Go on until you get to the post office and then turn left! እስከ ፡ ፖስታ ፡ ቤቱ ፡ ድረስ ፡ ሄደህ ፡ ከዚያ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ታጠፍ
4. በራ. The lights are going on. መብራቱ ፡ በመብራት ፡ ላይ ፡ ነው
5. ገፋ. As the months went on, his illness got worse. ጊዜው ፡ እየገፋ ፡ ሲሄድ ፡ በሽታው ፡ እየጸናበት ፡ ሄደ
6. ተደረገ. He took no note of what was going on. ይደረግ ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ልብ ፡ አላለም
7. ተካሄደ. The debate went on for hours. ክርክሩ ፡ ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ተካሄደ
*What is going on here? ነገሩ ፡ ምንድን ፡ ነው ?

**go on! ተው !**
Go on, you're kidding me! ተው ፡ እባክህ ፤ ትቀልድብኛለህ

**go on and off ብልጭ ፡ ድርግም ፡ አለ**
The lights keep going on and off. መብራቶቹ ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ ይላሉ

**go on and on እየቀጠለ ፡ ሄደ**
The meeting went on and on, but nothing was decided. ስብሰባው ፡ እየቀጠለ ፡ ሄደ ፤ ግን ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አልተወሰነም

**go out**
1. ወጣ. Tesfaye went out of the office angry. ተስፋዬ ፡ ከቢሮው ፡ ውስጥ ፡ ተናዶ ፡ ወጣ
2. ወጣ ፡ አለ. Let's go out and visit some friends! እስቲ ፡ ወጣ ፡ ብለን ፡ ወዳጆቻችንን ፡ እንጠይቅ
3. ጠፋ. Suddenly the lights went out. መብራቱ ፡ በድንገት ፡ ጠፋ
4. አለቀ. The fashion for short skirts is going out. ያጭር ፡ ቀሚስ ፡ ወረት ፡ እያለቀ ፡ መሄዱ ፡ ነው
*The workers went out on strike for higher wages. ደሞዛቸው ፡ እንዲጨመር ፡ በመጠየቅ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ሥራ ፡ አቆሙ

**go out of existence ቀረ**
Slavery has gone out of existence. ባርነት ፡ ቀርቷል

**go out to one**
My heart went out to him. አዘንኩለት

**go out with ጋበዘ**
He went out with her only once. አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ጋበዛት

**go over**
1. ሄደ. I am going over to his house for an hour. ላንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ወደሱ ፡ ቤት ፡ እሄዳለሁ
2. ተመለሰ(በት). Let's go over the details once more! ዝርዝሩን ፡ እንደ ፡ እንመለስበት
3. መላልሶ ፡ አየ. I have gone over all the figures but I cannot find the mistakes. ድምሮቹን ፡ መላልሼ ፡ ባይም ፡ ስሕተቱን ፡ ለማግኘት ፡ አልቻልኩም
4. ዞረ. He has gone over to the other team. እርሱ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ቡድን ፡ ዞሯል
5. ገባ. He has gone over to the enemy, and is now broadcasting against us. ለጠላት ፡ ገብቶ ፡ እኛን ፡ በመቃወም ፡ በራዲዮ ፡ ይናገራል

**go (one's) own way**
*He went his own way, as usual. እንደተለመደው ፡ ለራሱ ፡ የመሰለውን ፡ ተከተለ

**go (through)**
1. መረመረ. Let's go through the arguments again! ክርክሩን ፡ እንደገና ፡ እንመርምረው
2. በሞላ ፡ ተመለከተ. We must go through the accounts. ሒሳቡን ፡ በሞላ ፡ መመልከት ፡ አለብን
3. በረበረ. His wife went through his pockets looking for money. ሚስቱ ፡ ገንዘብ ፡ ለመፈለግ ፡ ኪሱን ፡ በረበረች
4. ጨረሰ. How long will it take to go through the whole program? ፕሮግራሙን ፡ በሙሉ ፡ ለመጨረስ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይፈጃል ?
Did you go through college? የኮሌጅ ፡ ትምህርት ፡ ጨርሰሃል ?
5. ገፋ(በት). He is determined to go through with his plan. በሐሳቡ ፡ ሊገፋበት ፡ ቈርጧል
6. ተሳተፈ. He went through the whole ceremony without interruption. በሥርዓቱ ፡ ላይ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ተሳተፈ
7. ጸደቀ. The bill did not go through. የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ አልጸደቀም
8. ተቀባይ ፡ አገኘ. His plan of improving education will never go through. ትምህርትን ፡ ለማሻሻል ፡ ያለው ፡ እቅድ ፡ በፍጹም ፡ ተቀባይ ፡ አያገኝም
9. ጥሶ ፡ ሄደ. He went through the signal. የትራፊኩን ፡ ምልክት ፡ ጥሶ ፡ ሄደ
*Do you think my application will go through? ማመልከቻዬን ፡ የሚቀበሉት ፡ ይመስልሃል ?

**go through a lot ብዙ ፡ መከራ ፡ አየ**
The poor woman has gone through a lot. ምስኪኗ ፡ ሴትዮ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ አይታለች

**go through with**
*You must go through with the course since you have started it. ትምህርቱን ፡ አንዴ ፡ ጀምረሃልና ፡ ከግቡ ፡ ማድረስ ፡ አለብህ

**go to**
1. ገባ. Where did all the money go to? ገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ የት ፡ ገባ ?
2. ደረሰ(በት). He went to a lot of trouble to get you a job. ላንተ ፡ ሥራ ፡ በመፈለግ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ደረሰበት
3. ወሰደ. Where does this door go to? ይህ ፡ በር ፡ ወዴት ፡ ይወስዳል ?
*To whom did the property go when the old man died? ሽማግሌው ፡ ሲሞት ፡ ሀብቱን ፡ ማን ፡ ወረሰ ?

**go to and fro ወደኋላና ፡ ወደፊት ፡ አለ**
A rocking chair goes to and fro. የሚዋልል ፡ ወምበር ፡ ወደኋላና ፡ ወደፊት ፡ ይላል

**go to pieces**
1. እንክትክት ፡ አለ. The car went to pieces when it struck the wall. ከግድግዳው ፡ ጋር ፡ በተጋጨ ፡ ጊዜ ፡ መኪናው ፡ እንክትክት ፡ አለ
2. አእምሮው ፡ ተናወጠ. When he learned of his child's death, he went to pieces. እርሱ ፡ የልጁ ን ፡ ሞት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ አእምሮው ፡ ተናወጠ

**go together**
1. ተስማማ. Your tie and your suit don't go together. ክራቫትህና ፡ ልብስህ ፡ አይስማሙም
2. ተወዳጀ. They have gone together for two years. ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ተወዳጅተዋል

**go under**
1. ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ጠለቀ. His head went under, and he was never seen again. ውኃው ፡ ውስ ጥ ፡ እንደ ፡ ጠለቀ ፡ ቀረ
2. ሰጠመ. The ship went under, and all aboard were drowned. መርከቧ ፡ ስትሰጥም ፡ በውስጧ ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ ሰጠሙ
3. ከሰረ. Business was so bad the firm went under. ንግድ ፡ በጣም ፡ ስለተዳከመ ፡ ኩባንያ ው ፡ ከሰረ
*He goes under an assumed name. በሌላ ፡ ሰ ው ፡ ስም ፡ ይጠራል

**go up**
1. ወደ ፡ ላይ ፡ ወጣ. Did you see him go up? ወደ ፡ ላይ ፡ ሲወጣ ፡ አየኸው ?
2. ዋጋው ፡ ጨመረ. Everything went up except butter. ከቅቤ ፡ በቀር ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ዋጋ ው ፡ ጨመረ
3. በዛ. The patient's temperature went up and he became delirious. በሽተኛው ፡ ትኩሳቱ ፡ ስ ለበዛ ፡ ያቃዠዋል
4. ተሠራ. New buildings are going up everywhere. አዲስ ፡ ሕንጻዎች ፡ በያለበት ፡ በመሠራ ት ፡ ላይ ፡ ናቸው

**go (with)**
1. ተስማማ. This tie does not go with the suit. ይህ ፡ ክራቫት ፡ ከልብሱ ፡ ጋር ፡ አይስማማም
2. አብሮ ፡ ተሸጠ. Five acres of land go with the house. አምስት ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ ከቤቱ ፡ ጋር ፡ አ ብሮ ፡ ይሸጣል

**as far as it goes** እስካሁን
What he says is true, as far as it goes. እስካሁን ፡ የተናገረው ፡ እውነት ፡ ነው

**as far as that goes** በዚያ ፡ ረገድ
As far as that goes, he is right. በዚያ ፡ ረገድ ፡ እሱ ፡ ትክክል ፡ ነው

**as it goes along** እያደር
It may be hard at first, but it gets easier as it goes along. በመጀመሪያ ፡ የሚያስቸግር ፡ ቢሆን ም ፡ እያደር ፡ ይቀላል

**(it) is going on** መሆኑ ፡ ነው
It is going on five and we have to leave at six. ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ መሆኑ ፡ ነው ፤ እኛ ፡ በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ መሄድ ፡ አለብን
*How old is the child? He is four, going on five. ልጁ ፡ ስንት ፡ ዓመቱ ፡ ነው ? አራተኛ ፡ ዓመቱን ፡ ጨርሶ ፡ አምስተኛውን ፡ ይዟል

**it goes without saying** እሙን ፡ ነው
It goes without saying that they will fight on. መዋጋታቸውን ፡ እንደሚቀጥሉ ፡ እሙን ፡ ነው

**let go**
1. ለቀቀ. He let go the branch and fell. የዛፉን ፡ ቅርንጫፍ ፡ ለቀቀና ፡ ወደቀ
After questioning him, the police let him go. ፖሊሱ ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ ለቀቀው
I won't let you go too soon. ቶሎ ፡ አለቅህም
2. አሰናበተ. He had to let his maid go because he lost his job. ከሥራው ፡ ስለተሰናበተ ፡ ገረዱ ን ፡ ማሰናበት ፡ ግድ ፡ ሆነበት
3. ይቅርታ ፡ አለፈ. This time, we will let you go. ላሁኑ ፡ ይቅርታ ፡ እናልፍሃለን
4. ሸጠ. I cannot let this suit go for less than 30 dollars. ይህን ፡ ሙሉ ፡ ልብስ ፡ ከሠላሳ ፡ ብ ር ፡ በታች ፡ አልሸጥም

**let it go** አለፈ
I should punish you for this, but I will let it go just this once. ለዚህ ፡ ልቀጣህ ፡ ይገባኝ ፡ ነበ ር ፡ ግን ፡ ያሁኑን ፡ አልፌሃለሁ

**let oneself go** ነገረ ፡ ዓለሙን ፡ ተወ
Lately, she has let herself go terribly. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ነገረ ፡ ዓለሙን ፡ ትተዋለች
[See also various nouns with "go", such as 'bad, wrong']

**go** (n.), **be on the ~**
1. ሠራ. He is on the go day and night. ሌት ፡ ተቀን ፡ ይሠራል
2. ጉድ ፡ ጉድ ፡ አለ. She is on the go from morning till night. ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ጉድ ፡ ጉ ድ ፡ ትላለች

**make a go of** አስፋፋ
He made a go of his business. ንግዱን ፡ አስፋፋ

**goad** (v.) ገፋፋ
Hunger goaded him to steal a loaf of bread. ረኀብ ፡ ዳቦ ፡ እንዲሰርቅ ፡ ገፋፋው

**goad** (n.) ዘንግ
The goad is sharp. ዘንጉ ፡ ሹል ፡ ነው

**goal**
1. ዓላማ. Matrimony is the goal of many young women. የብዙ ፡ ልጃገረዶች ፡ ዓላማ ፡ ጋብቻ ፡ ነው
2. ግብ. Our team made three goals in the first half. ቡድናችን ፡ በመጀመሪያው ፡ ግማሽ ፡ ጨዋታ ፡ ሦስት ፡ ግብ ፡ አገባ
The plan failed to reach its goal. እቅዱ ፡ እግብ ፡ ሳይደርስ ፡ ቀረ
*His goal was Paris. ሊሄድ ፡ ያቀደው ፡ ፓሪስ ፡ ነበር

**goalkeeper** ግብ ፡ ጠባቂ
The goalkeeper kicked the ball. ግብ ፡ ጠባቂው ፡ ኳሷን ፡ ለጋት

**goat** ፍየል
My goat has a kid. ፍየሌ ፡ አንድ ፡ ግልገል ፡ አላት

**goatherd** እረኛ
The goatherd watches over the goats. እረኛው ፡ ፍየሎችን ፡ ያግዳል

**gobble** ዋጥ ፡ ዋጥ ፡ አደረገ
He gobbled his food. ምግቡን ፡ ዋጥ ፡ ዋጥ ፡ አደረገው

**go-between**
1. አስታራቂ. He served as a go-between, but was unable to reconcile the two parties. እንደ ፡ አስታራቂ ፡ ሆኖ ፡ ቢያገለግልም ፡ ሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ ለማስታረቅ ፡ አልቻለም
2. አማጭ. The parents sent an old man to act as go-between in arranging an appointment. ወላጆች ፡ ቀጠሮውን ፡ ለመወሰን ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ አማጭ ፡ ላኩ

**goblet** ዋንጫ
I drink beer in a goblet. ጠላ ፡ በዋንጫ ፡ እጠጣለሁ

**god**
1. አምላክ (pl. አማልክት). In ancient times people worshipped many gods. በጥንት ፡ ዘመን ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ አማልክት ፡ ያመልኩ ፡ ነበር
He swore by the God of Israel. በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ማለ
2. እግዚአብሔር. God is the creator of the world. እግዚአብሔር ፡ የዓለም ፡ ፈጣሪ ፡ ነው
[See also 'forbid']

**godchild** የክርስትና ፡ ልጅ
I bought a shirt for my godchild. ለክርስትና ፡ ልጄ ፡ ሸሚዝ ፡ ገዛሁ

**goddess** እንስት ፡ ጣዖት
The goddess of fertility was worshipped in ancient times. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ የልምላሜ ፡ እንስት ፡ ጣዖት ፡ ትመለክ ፡ ነበር

**godfather** የክርስትና ፡ አባት
He has no godfather. የክርስትና ፡ አባት ፡ የለውም

**godly** የእግዚአብሔር
He is a godly man. እሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ነው

**godmother** የክርስትና ፡ እናት
Her godmother died recently. የክርስትና ፡ እናቷ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ሞተች

**going**
1. ሞት. His going was sudden. ሞቱ ፡ ድንገተኛ ፡ ነበር
2. መሄድ. The going is hard on a muddy road. በጭቃ ፡ መንገድ ፡ መሄድ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
**(he is) going to** ል + imperfect + ነው
I'm going to bake a cake. ኬክ ፡ ልጋግር ፡ ነው
**get going**
*He tried hard to get the conversation going. ጨዋታው ፡ እንዲሞቅ ፡ ጣረ
**keep (one) going** አቆየ
This will keep you going until next payday. ይህ ፡ እስከሚቀጥለው ፡ ደሞዝ ፡ ድረስ ፡ ያቆይሃል

**goings-on** ድርጊት
There were all kinds of goings-on at his party. በሱ ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድርጊቶች ፡ ይፈጸሙ ፡ ነበር

**goiter** እንቅርት
Since she has a goiter, her lovely face is ruined. እንቅርት ፡ ስላወጣች ፡ እስደናቂ ፡ መልኳ ፡ ተበላሸ

**gold** (n.) ወርቅ
Is that real gold? እውነተኛ ፡ ወርቅ ፡ ነው ፡ እሱ ?
**gold** (adj.) የወርቅ
I bought my wife a gold watch. ለባለቤቴ ፡ የወርቅ ፡ ሰዓት ፡ ገዛሁላት

**golden**
1. የወርቅ. She gave her golden dishes as a wedding gift. ለሰርጓ ፡ የወርቅ ፡ ሳሕኖች ፡ አበረከተችላት
2. ከወርቅ ፡ የተሠራ. She wore a golden chain around her neck. ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ ሐብል ፡ አጥልቃ ፡ ነበር

3. ወርቅማ. She embellished her dress with a golden belt. ቀሚሷን ፡ ወርቅማ ፡ በሆነ ፡ ቀበቶ ፡ አስጌጠችው
4. ጥሩ. Going abroad will give you a golden opportunity to learn English well. ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ መሄድ ፡ እንግሊዝኛ ፡ በደንብ ፡ ለመማር ፡ ጥሩ ፡ አጋጣሚ ፡ ይሆንልሃል

**golden color** ወርቅማ
The paper has a golden color. ወረቀቱ ፡ ወርቅማ ፡ ነው

**goldsmith** ወርቅ ፡ ሠሪ
The goldsmith made me a beautiful ring. ወርቅ ፡ ሠሪው ፡ ውብ ፡ ቀለበት ፡ ሠራልኝ

**golf** [በትናንሽ ፡ ጠንካራ ፡ ኳስና ፡ በገና ፡ መሳይ ፡ ዘንጎች ፡ በደጅ ፡ የሚደረግ ፡ ጨዋታ]

**gondola** [በቬኒስ ፡ በይ ፡ ላይ ፡ የሚንሳፈፍ ፡ ረጅምና ፡ ቀጭን ፡ ጀልባ]

**gone,** see **go**

**be all gone** አለቀ
The bread is all gone. ዳቦው ፡ አለቀ

**gong** ደወል
The gong is struck to mark the hours. ሰዓቱን ፡ ለማስታወቅ ፡ ደወሉ ፡ ይደወላል

**gonorrhea** ጨብጥ
Gonorrhea is a common venereal disease. ጨብጥ ፡ የተዛመተ ፡ ያባለ ፡ ዘር ፡ በሽታ ፡ ነው

**good** (n.)
1. መልካም ፡ ባሕርይ. There is some good in everyone. ማንኛውም ፡ ሰው ፡ መልካም ፡ ባሕርይ ፡ አይታጣበትም
2. ጥቅም. I am only thinking of your good. ያሰብኩት ፡ ላንተ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ነው
He did it for the common good. ለጋራ ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ የሠራው ፡ ነገር ፡ ነው
3. ነገር. Men have often esteemed happiness as the greatest good. ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ደስታን ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ነገር ፡ አድርገው ፡ ይቈጥሩታል

**good** (adj.)
1. ጥሩ. He is a good man. እርሱ ፡ ጥሩ ፡ ሰው ፡ ነው
He has a good life. ጥሩ ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል
Is this meat good to eat? ይህ ፡ ሥጋ ፡ ለመብል ፡ ጥሩ ፡ ነው ?
His good name was ruined by one careless act. ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ዝንጋታ ፡ ጥሩ ፡ ስሙ ፡ ጐደፈ
2. ተስማሚ. It's a good day for swimming. ለዋና ፡ ተስማሚ ፡ ቀን ፡ ነው
3. ጐበዝ. He is very good at figures. በሒሳብ ፡ ጐበዝ ፡ ነው
4. እውነተኛ. It is hard to tell counterfeit money from good money. የሐሰት ፡ ገንዘብ ፡ ከእውነተኛ ፡ ገንዘብ ፡ ለመለየት ፡ ያስቸግራል
5. የቅርብ. He is a good friend of mine. የቅርብ ፡ ወዳጄ ፡ ነው
6. ሙሉ. I waited for him a good half hour. ግማሽ ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ጠበቅሁት
7. (= adv.) ደኅና ፡ አድርጎ. The teacher gave the lazy student a good scolding. መምህሩ ፡ ሰነፉን ፡ ተማሪ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ገሠጸው
*She has a good figure. መልክ ፡ ቀና ፡ ናት
*Have a good time! ጊዜው ፡ የደስታ ፡ ይሁንልህ !
*Put in a good word for me! ስሜን ፡ በመልካም ፡ አንሣልኝ

**a good**
1. ቢያንስ ፡ ቢያንስ. She lost a good three pounds. ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ ፓውንድ ፡ ያህል ፡ ከክብደቷ ፡ ቀንሳለች
2. በቀላሉ. It is a good three miles to the station. እስከ ፡ ጣቢያው ፡ በቀላሉ ፡ ሦስት ፡ ማይል ፡ ይሆናል

**a good deal** ብዙ
He spent a good deal of time on it. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አጥፍቶበታል

**a good hour** አንድ ፡ ሰዓት
I worked a good hour on your paper. ጽሑፍህን ፡ ስመለከት ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ አጠፋሁ

**a good many**
1. በርከት ፡ ያሉ. There are a good many foreigners in the hotel. በሆቴሉ ፡ ውስጥ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ አሉ
2. ብዙ. I have been there a good many times. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እዚያ ፡ ሄጃለሁ

**a good way** ብዙ
We have come a good way since morning. ከጧት ፡ ጀምረን ፡ ብዙ ፡ ተጕዘናል

**as good as** የ -- ያህል ፡ ደኅና
My car is as good as new, even though I have driven it 60,000 miles. ምንም ፡ እንኳን ፡ ስልሳ ፡ ሺ ፡ ማይል ፡ የነዳኋት ፡ ቢሆንም ፡ የኔ ፡ መኪና ፡ የአዲስ ፡ ያህል ፡ ደኅና ፡ ናት

**(is) as good as done**
The job is as good as done. ሥራው ፡ ተሠርቶ ፡ እንዳለቀ ፡ ያህል ፡ ይቈጠራል

**be good**
1. አገለገለ. The passport is good until the

fifteenth. ፓስፖርቱ ፡ እስከዚህ ፡ ወር ፡ ዐሥራ ፡ አ ምስተኛ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ያገለግላል
This suit will be good for many years. ይህ ፡ ልብስ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ያገለግላል
2. ተመቸ. This cloth is good for polishing. ይህ ፡ ጨርቅ ፡ ለመጥረግ ፡ ይመቻል
3. በጀ. Abstinence from liquor is good for health. ከሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ መጠበቅ ፡ ለጤ ንነት ፡ ይበጃል

**be good and mad** ጦፈ
He is good and mad at the bad thing you did yesterday. ትላንትና ፡ በሠራኸው ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ጦፏል

**be good at** ሆነው
Are you good at figures? ሒሳብ ፡ ይሆንሃል ?

**be too good (for)**
*These shoes are too good for such weather. ይህ ፡ ጫማ ፡ ጥሩ ፡ ስለሆነ ፡ ለዚህ ፡ አየር ፡ አ ይሆንም

**do good** ጠቀመ
The vacation has done him good. ያደረገው ፡ ዕ ረፍት ፡ ጠቅሞታል
Arguing won't do you any good. ንትርክ ፡ ም ንም ፡ አይጠቅምህም

**for good** እስከ ፡ መጨረሻው
I am through with him for good. ከርሱ ፡ ጋር ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ተቈራርጫለሁ
*He is leaving the country for good. እንደኛው ን ፡ ሀገሪቱን ፡ ለቆ ፡ መሄዱ ፡ ነው

**hold good** አዋጣ
The argument still holds good. ክርክሩ ፡ አሁ ንም ፡ ያዋጣል

**make good** (vt.)
1. አረጋገጠ. Can you make good your claims? የምትላቸውን ፡ ነገሮች ፡ ልታረጋግጥ ፡ ትችላለህ ?
2. ጠበቀ. He made good his promise. ቃሉን ፡ ጠበቀ
3. ተካ. The bank cashier made good the shortage and was given a light sentence. የባንኩ ፡ ገንዘብ ፡ ከፋይ ፡ የጐደለውን ፡ ስለተካ ፡ ቀላል ፡ ቅጣት ፡ ተወሰነበት

**make good** (vi.)
1. ከበረ. He went to the city and made good. ወደ ፡ ከተማ ፡ ሄዶ ፡ ከበረ
2. የተሳካ ፡ ውጤት ፡ አገኘ. Education is necessary to make good in politics. በፖለቲካ ፡ የተሳካ ፡ ው ጤት ፡ ለማግኘት ፡ ትምህርት ፡ ያስፈልጋል

**make good for** ተካ
I made good for the broken glasses. የሰበርኳቸ ውን ፡ ብርጭቆዎች ፡ ተካሁ

**make good on** ፈጸመ(ለት)
He made good on his promise to take her to the theater. ወደ ፡ ቴያትር ፡ ቤት ፡ ሊወስዳት ፡ የገ ባላትን ፡ ቃል ፡ ፈጸመላት

**(a) no-good** የማይረባ
He is a no-good liar. የማይረባ ፡ ውሸታም ፡ ነው

**will you be good enough**
Will you be good enough to come early? መልካም ፡ ፈቃድህ ፡ ሆኖ ፡ ቀደም ፡ ብለህ ፡ ትመጣ ?
[See also the many nouns, such as 'form, mood, taste' that occur with 'good']

**good afternoon!** እንደምን ፡ ዋልክ ? (2nd sg. masc.)

**goodbye!** ደኅና ፡ ሁን ! (2nd sg. masc.)
Goodbye! Have a good trip. ደኅና ፡ ሁን ፤ መን ገዱን ፡ ጨርቅ ፡ ያድርግልህ

**say goodbye** ተሰናበተ
John, did you say goodbye to him? ዮሐንስ ፤ ተሰናብተኸዋል ?

**good evening!** እንደምን ፡ አመሸህ ? (2nd sg. masc.)
Good evening! How are you? እንደምን ፡ አመ ሸህ ? ደኅና ፡ ነህ ?

**(be a) good-for-nothing** አይረባም
That student is a good-for-nothing. ያ ፡ ተማ ሪ ፡ አይረባም

**Good Friday** የስቅለት ፡ ዕለት
Many people go to church on Good Friday. የስቅለት ፡ ዕለት ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ ይሄዳል

**good-hearted** ደግ
The good-hearted woman gave the beggar a dollar. ደጓ ፡ ሴት ፡ ለለማኙ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ሰጠች

**good-looking**
1. መልከ ፡ ቀና. She is a very good-looking girl. በጣም ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ ልጅ ፡ ናት
2. መልከ ፡ መልካም. He is a good-looking man. መልከ ፡ መልካም ፡ ሰው ፡ ነው

**goodly**
1. መልከ ፡ መልካም. Only a goodly lad may hope to win her love. ልቧን ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችለ ው ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ የሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ከፍ ፡ ያለ ፤ ብዙ. He made a goodly sum of money on this deal. በዚህ ፡ መገበያየት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ (ብዙ) ፡ ገንዘብ ፡ አተረፈ

**good morning!** እንደምን ፡ አደርክ? (2nd sg. masc.)

**good-natured** ገር
He is very good-natured; he does not get mad easily. በጣም ፡ ገር ፡ ስለሆነ ፡ በቀላሉ ፡ አይናደድም

**goodness** ርኅራኄ
She is well known for her goodness to the needy. ለችግረኞች ፡ ያላት ፡ ርኅራኄ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ነው

**goodness me!** ይደንቃል
Goodness me! Isn't he big? ይደንቃል ፤ ትልቅ ፡ አይደለም ፡ እንዴ?

**for goodness' sake** በእግዚአብሔር
For goodness' sake, stop that noise! በእግዚአብሔር ፤ ያንን ፡ ጩኸት ፡ አቁም

**good night!** ደኅና ፡ እደር (2nd sg. masc.)

**goods**
1. ሸቀጦች. The goods were sent by freight. ሸቀጦቹ ፡ በማጓጓዣ ፡ ተልከዋል
2. ሸቀጣ ፡ ሸቀጥ. The goods were displayed in the shop. ሸቀጣ ፡ ሸቀጡ ፡ በሱቁ ፡ ውስጥ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲታይ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር

**goody** (goodies) ጣፋጭ
The boy finished the goodies on the table. በጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ጣፋጭ ፡ ልጁ ፡ ጨረሰው

**goose** (geese) ዝይ
Do you like goose or turkey for Christmas? ለልደት ፡ በዓል ፡ ዝይ ፡ ይሻልሃል ፡ ወይስ ፡ የቱርክ ፡ ዶሮ?

**gore** (v.) ወጋ
The bull gored him to death. ወይፈኑ ፡ ወግቶ ፡ ገደለው

**gore** (n.)
*Her hands were covered with gore from bandaging the wounded man. የቈሰለውን ፡ ሰው ፡ ቁስል ፡ ስታስር ፡ እጆቿ ፡ በደም ፡ ተበክለው ፡ ነበር

**gorge** (v.), ~ **oneself**
*The boy gorged himself with cake. ልጁ ፡ ቁንጣን ፡ እስኪይዘው ፡ ድረስ ፡ ኬክ ፡ በላ

**gorge** (n.) ገደልማ ፡ የወንዝ ፡ ሸለቆ
The river flows through a deep gorge. ወንዙ ፡ በጥልቅ ፡ ገደልማ ፡ የወንዝ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ይፈሳል

**gorgeous**
1. የወጣላት ፡ ቆንጆ. She is a gorgeous girl. የወጣላት ፡ ቆንጆ ፡ ናት
2. ዕጹብ ፡ ድንቅ. It was a gorgeous sunset. የጀንበሯ ፡ ጥልቀት ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ነበር

**gorilla** [ጎሪላ ፡ ከዝንጀሮ ፡ የሚዛመድ ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ የሆነ ፡ በአቋቋሙ ፡ ሰውን ፡ የሚመስል ፡ ከገመሬ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እንስሳ ፡ ነው]

**gory** የደም ፡ መፋሰስ ፡ የሞላበት
His gory stories are popular with everyone. የደም ፡ መፋሰስ ፡ የሞላባቸው ፡ ተረቶቹ ፡ በማንም ፡ ዘንድ ፡ የታወቁ ፡ ናቸው

**Gospel** ወንጌል
The priest read the Gospel during the sermon. ቄሱ ፡ በስብከቱ ፡ ጊዜ ፡ ወንጌል ፡ አነበበ

**gospel truth** የወንጌል ፡ ቃል
He accepts what I say as the gospel truth. እርሱ ፡ እኔ ፡ የምለውን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ወንጌል ፡ ቃል ፡ ይቀበላል

**gossip** (v.)
1. አወራ. They were gossiping about me when I walked in. ስገባ ፡ ስለኔ ፡ ያወሩ ፡ ነበር
2. አሉባልተኛ ፡ ነው. She is pious at church in the morning and gossips all afternoon. ጧት ፡ እቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጻድቅ ፤ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ አሉባልተኛ ፡ ናት

**gossip** (n.) ወሬ ፤ አሉባልታ
I wouldn't believe that gossip. ያንን ፡ ወሬ ፡ አላምንም
Won't this gossip ever end? ይህ ፡ አሉባልታ ፡ ዘለዓለም ፡ አያልቅም?

**an old gossip** የወሬ ፡ ቋት
His wife is an old gossip. ሚስቱ ፡ የወሬ ፡ ቋት ፡ ናት

**subject of neighborhood gossip** የቡና ፡ መጠጫ
His doings are the subject of neighborhood gossip. አድራጎቶቹ ፡ ሁሉ ፡ የቡና ፡ መጠጫ ፡ ሆነዋል
[See also 'invite']

**got,** see **get**

**gourd** ቅል
Gourds are used for making ladles. ቅል ፡ ጭልፋ ፡ ለመሥራት ፡ ያገለግላል

**gout** [የሰውነት ፡ መጋጠሚያዎችን ፡ የሚያሳብጥ ፡ የበሽታ ፡ ዓይነት]

**govern**

1. ገዛ. He governed his district with an iron hand. አውራጃውን ፡ ጸጥ ፡ ለጥ ፡ አድርጎ ፡ ገዛ
2. ወሰነ. A subject governs the number of its verb. በዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ባለቤቱ ፡ የግሱን ፡ ቁጥር ፡ ይወስናል
3. መሠረት ፡ ሆነ. The financial report governed their decision. ለውሳኔያቸው ፡ መሠረት ፡ የሆነ ው ፡ ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ጉዳይ ፡ የተሰጠው ፡ ሪፖርት ፡ ነው

**be governed**

1. ተዳደረ. The province was governed by a cruel administrator. ጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ በጨካ ኝ ፡ ገዥ ፡ ይተዳደር ፡ ነበር
2. ተመራ. Don't be governed by what others say! ሌሎች ፡ በሚሉት ፡ አትመራ

**government**

1. መንግሥት. The prime minister formed a new government. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አዲስ ፡ መንግሥት ፡ አቋቋሙ
2. አገዛዝ. Socialism is a kind of government. ሶሺያሊዝም ፡ የአገዛዝ ፡ ዓይነት ፡ ነው
3. አስተዳደር. The government of the city is the mayor's responsibility. የከተማው ፡ አስተዳደ ር ፡ የከንቲባው ፡ ኀላፊነት ፡ ነው

[See also 'puppet']

**government school** የመንግሥት ፡ ትምህርት ፡ ቤት

Students do not pay tuition in a government school. በመንግሥት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተማሪ ፡ ገንዘብ ፡ አይከፍልም

**governor**

1. አገረ ፡ ገዥ. The governor visited our school. አገረ ፡ ገዥው ፡ ትምህርት ፡ ቤታችንን ፡ ጐበኙ
2. ገዥ. He is the governor of the province. የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ገዥ ፡ ነው

**governor general** እንደራሴ

The governor general is in charge of the province. እንደራሴው ፡ ለጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ኀላ ፊ ፡ ነው

**gown** ቀሚስ ፤ ልብስ

She wore a pink gown to the reception. ለግብዣው ፡ ሐምራዊ ፡ ቀሚስ ፡ ለበሰች

Her bridal gown was red. የሙሽራ ፡ ልብሷ ፡ ቀ ይ ፡ ነበር

**grab** (grabbed)

1. መንተፈ. The dog grabbed the bone and ran away. ውሻው ፡ አጥንቱን ፡ መንትፎ ፡ ሮጠ
2. ያዘ. He grabbed the thief by the collar. ሌባውን ፡ አንቆ ፡ ያዘው
3. ወሰደ. In a moment of abstraction, he grabbed the wrong hat. በተመሰጠ ፡ ውስጥ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ባርኔጣ ፡ ወሰደ

**grab at**

1. ለመያዝ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ. He grabbed at the rope and missed. ገመዱን ፡ ለመያዝ ፡ እጁን ፡ ቢዘረጋ ፡ ሳተው
2. ሳያመነታ ፡ ተቀበለ. He grabbed at the chance to go abroad. ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ለመሄድ ፡ ያ ጋጠመውን ፡ ዕድል ፡ ሳያመነታ ፡ ተቀበለ

**grace** (v.)

1. ሞገስ ፡ ሰጠ. +The queen graced the party with her presence. የንግሥቲቱ ፡ መገኘት ፡ ለግብ ዣው ፡ ሞገስ ፡ ሰጠው
2. አሳመረ. Paintings graced the walls. ሥዕሎች ፡ ግድግዳውን ፡ አሳመሩት

*Will you grace our party with your presence? መልካም ፡ ፈቃድህ ፡ ሆኖ ፡ ፓርቲያችን ፡ ላይ ፡ ትገኛለህ ?

**grace** (n.)

1. ጸጋ. May God grant us His grace! እግዚአ ብሔር ፡ ጸጋውን ፡ ይስጠን
2. ደግነት. It was only through the principal's grace that he wasn't expelled from school. ከትምህርት ፡ ቤት ፡ አለመውጣቱ ፡ በዲሬክተሩ ፡ ደግነት ፡ ነው
3. ምሕረት. By an act of grace, he was freed from prison. ምሕረት ፡ ተደርጎለት ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ ወጣ
4. ለዛ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ. She danced with grace. እርሷ ፡ ለዛ ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ ደነሰች
5. ውበት. We admired the grace of the statue. የሐውልቱን ፡ ውበት ፡ አደነቅን
6. ባለሟልነት. He fell from grace and was exiled to a border post. ከባለሟልነቱ ፡ ወርዶ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ጠረፍ ፡ ተጋዘ

*Give us a week's grace, and we will pay in full. አንድ ፡ ሳምንት ፡ ጨምርልንና ፡ በሙሉ ፡ እንከፍላለን

**His Grace** ብፁዕነታቸው

His Grace is leaving for Europe. ብፁዕነታቸው ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ መሄዳቸው ፡ ነው

**be in good graces**

*I wonder whether I am in the teacher's good graces. አስተማሪው ፡ ይወደኝ ፡ እንደሆን ፡ አላውቅም

**have the grace** ትሕትና ፡ አሳየ

He had the grace to say he was sorry. ይቅርታ ፡ በመጠየቅ ፡ ትሕትና ፡ አሳየ

**say grace** ምስጋና ፡ አደረሰ
He said grace before the meal began. ምግብ ፡ መብላት ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ምስጋና ፡ አደረሰ

**with bad grace** ቅር ፡ እያለው
He did what I asked him to, but with bad grace. የጠየቅሁትን ፡ አደረገ ፡ ግን ፡ ቅር ፡ እያለው ፡ ነው

**with good grace** ቅር ፡ ሳይለው
She obeyed with good grace. ቅር ፡ ሳይላት ፡ ታዘዘች
[See also 'year']

## graceful

1. ለዛ ፡ ያለው. She is a graceful dancer. እርሷ ፡ ለዛ ፡ ያላት ፡ ዳንሰኛ ፡ ናት
She thanked them with a graceful speech. ለዛ ፡ ባለው ፡ ንግግር ፡ አመሰገነቻቸው
2. ደስ ፡ የሚያሰኝ. She sent me a graceful letter of thanks. ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ የምስጋና ፡ ደብዳቤ ፡ ላከችልኝ
The horse's gallop is very graceful. የፈረሱ ፡ ግልቢያ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው

**be graceful** ደስ ፡ አለ
The downward flight of the bird was graceful. የወፊቱ ፡ መሽቆልቆል ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ነበር

## gracious

1. ደግ. The gracious king declared amnesty. ደጉ ፡ ንጉሥ ፡ ምሕረት ፡ አደረጉ
2. የሞቀ. Their gracious home is admired by all. የሞቀ ፡ ቤታቸው ፡ በሁሉ ፡ ይደነቃል
3. ጥርብርብ. She is a very gracious hostess. በጣም ፡ ጥርብርብ ፡ እንግዳ ፡ ተቀባይ ፡ ናት
4. ደርባባ. The gracious old lady has an air of gentility. ደርባባዋ ፡ አሮጊት ፡ የጨዋነት ፡ መልክ ፡ አላቸው
5. ሞቅ ፡ ያለ. She received her guests in a gracious manner. እንግዶቹን ፡ ሞቅ ፡ ባለ ፡ ሁኔታ ፡ ተቀበለች

**be gracious** ምሕረት ፡ አደረገ
Be gracious, O king! ንጉሥ ፡ ሆይ ! ምሕረት ፡ አድርግልን

*It was very gracious of her to come. መምጣቷ ፡ በጣም ፡ የሚያስመሰግናት ፡ ነው

## gradation

*The rainbow shows gradations of color. የቀስተ ፡ ደመና ፡ ቀለማት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ካንዱ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ይሸጋገራሉ

## grade (vt.)

1. ውጤት ፡ ሰጠ. He graded them according to ability. እንደየችሎታቸው ፡ ውጤት ፡ ሰጣቸው
2. አረመ. When grading the papers, the teacher took the student's long illness into consideration. መምህሩ ፡ ወረቀቶቹን ፡ ሲያርም ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ለታመመው ፡ ተማሪ ፡ አስተያየት ፡ አደረገ
3. ለየ. He graded the papers according to size. ወረቀቶቹን ፡ እንደየመጠናቸው ፡ ለያቸው

**grade** (vi.) ቀስ ፡ በቀስ ፡ ተለወጠ
Red and yellow grade into orange. ቀይና ፡ ቢጫ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ወደ ፡ ብርቱካንማ ፡ ይለወጣሉ

**be graded** ተደለደለ
The road up the steep hill was graded. ቀጥ ፡ ያለውን ፡ ኮረብታ ፡ የሚወጣው ፡ መንገድ ፡ ተደልድሏል

## grade (n.)

1. ደረጃ. The rank of major is a grade higher than a captain. የሻለቅነት ፡ ማዕረግ ፡ ከሻምበልነት ፡ ባንድ ፡ ደረጃ ፡ ይበልጣል
2. ዓይነት. We buy the best grade of milk. ምርጡን ፡ ዓይነት ፡ ወተት ፡ እንገዛለን
3. ክፍል. In what grade is your boy? ልጅህ ፡ ስንተኛ ፡ ክፍል ፡ ነው ?
4. ውጤት. He received the highest grades in the class. ከክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛውን ፡ ውጤት ፡ አገኘ

**be on the downgrade** እየተቀነሰ ፡ ሄደ
His health has been on the downgrade since his illness. ከሕመሙ ፡ ወዲህ ፡ ጤንነቱ ፡ እየተቀነሰ ፡ ሄደ

**be on the upgrade** እየተሟሟቀ ፡ ነው
Business is on the upgrade on account of the opening of the new railroad. ባዲሱ ፡ የባቡር ፡ መሥመር ፡ መዘርጋት ፡ ምክንያት ፡ ንግዱ ፡ እየተሟሟቀ ፡ ነው

**not make the grade** አልተሳካለትም
It saddened him that his son couldn't make the grade in medical school. ልጁ ፡ ሕክምና ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ሳይሳካለት ፡ መቅረቱ ፡ አሳዘነው

**steep grade** ቀጥ ፡ ያለ ፡ ዳገት
The train went up a steep grade. ባቡሩ ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ዳገት ፡ ወጣ

## grade school አንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት

My little brother goes to grade school. ታናሽ ፡ ወንድሜ ፡ አንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይማራል

## gradual

1. ጋደል ፡ ያለ. The hill has a gradual slope. ኮረብታው ፡ ጋደል ፡ ያለ ፡ አግድመት ፡ አለው

2. (= adv.) ቀስ ፡ በቀስ. There is a gradual increase in the cost of living. የኑሮ ፡ ዋጋ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየጨመረ ፡ ነው

**gradually** ቀስ ፡ በቀስ
The economy is gradually improving. ኢኮኖሚው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየተሻሻለ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ነው

**graduate** (vt.) አስመረቀ
The university graduated three hundred students last year. ዩኒቨርሲቲው ፡ ዓምና ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ተማሪዎች ፡ አስመረቀ

**graduate** (vi.)
1. ተመረቀ. She graduated from high school. ከሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተመረቀች
2. ቀስ ፡ በቀስ ፡ ተላለፈ. These stripes graduate from light to dark. እነዚህ ፡ መሥመሮች ፡ ከነጭ ፡ ወደ ፡ ጥቁር ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ይተላለፋሉ

**graduate** (n.) ተመራቂ ፤ ምሩቅ
Most of our graduates have found good positions. ይበልጡዎቹ ፡ ተመራቂዎቻችን ፡ (ምሩቆቻችን) ፡ ጥሩ ፡ በታ ፡ አገኙ

**(be) graduated**
1. ተከፋፈለ. The ruler is graduated in inches. ማሥመሪያው ፡ በኢንች ፡ የተከፋፈለ ፡ ነው
2. ተደለደለ. Taxes are graduated according to income. ቀረጥ ፡ እንደየሰው ፡ ገቢ ፡ ይደለደላል

**graduate school**
He hopes to go to graduate school. ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ እሚሰጥበት ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ለመግባት ፡ ያስባል

**graduation**
1. የምረቃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት. His Majesty will attend the graduation. ግርማዊነታቸው ፡ በምረቃው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ
2. ቀስ ፡ እያለ ፡ መለወጥ. The graduation from light to dark cannot be noticed by the eye. የብርሃን ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ መለወጥ ፡ ለዓይን ፡ አይታይም

**graft** (v.)
*He grafted a lemon branch on to the orange tree. ሎሚውን ፡ ከብርቱካኑ ፡ ለማዳቀል ፡ የሎሚውን ፡ ቅርንጫፍ ፡ ቈርጦ ፡ ከብርቱካኑ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ አጣበቀው

**graft** (n.) ጉቦ
The minister was accused of taking graft from the contractors. ሚኒስትሩ ፡ ከሥራ ፡ ተቋራጮቹ ፡ ጉቦ ፡ በመውሰድ ፡ ተከሶ ፡ ነበር

*The graft failed to grow on the stump. እንዲዳቀል ፡ ተብሎ ፡ ከጉቶው ፡ ጋር ፡ የተጣበቀው ፡ ቅርንጫፍ ፡ ሳይዝ ፡ ቀረ

**grain**
1. ጥራ ፡ ጥሬ. Canada exports meat and grain. ካናዳ ፡ ሥጋና ፡ ጥራ ፡ ጥሬ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ትልካለች
2. እህል. Grain must be stored in a dry place. እህል ፡ ደረቅ ፡ ከሆነ ፡ ስፍራ ፡ መከማቸት ፡ አለበት
3. ፍሬ. There was only one grain of wheat left. የቀረች ፡ አንዲት ፡ የስንዴ ፡ ፍሬ ፡ ብቻ ፡ ነበረች
*Give the beggar a few grains of rice! ለለማኙ ፡ ጥቂት ፡ ሩዝ ፡ ስጠው
*There are some grains of sand in my food. በምግቤ ፡ ውስጥ ፡ አሸዋ ፡ አለ

**grain of truth**
*There is not a grain of truth in what he says. እሱ ፡ በሚለው ፡ ውስጥ ፡ ቅንጣት ፡ ታህል ፡ እውነት ፡ የለችበትም

**against one's grain**
*The thought of stealing goes against my grain. ስርቆት ፡ የሚሉት ፡ ነገር ፡ ሲያልፍም ፡ አይነካኝ

**with a grain of salt**
*You should take his promises with a grain of salt. እሱ ፡ የሚሰጠውን ፡ ተስፋ ፡ በሙሉ ፡ ልብ ፡ አትቀበለው
[See also 'parched, roasted, seed']

**gram** ግራም

**grammar** ሰዋስው
Amharic grammar is very difficult. አማርኛ ፡ ሰዋስው ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
*His grammar is poor. ሰዋስዋዊ ፡ ስሕተት ፡ ያደርጋል

**grammar school** አንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት
My little brother goes to grammar school. ታናሽ ፡ ወንድሜ ፡ አንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይማራል

**grammatical**
1. ትክክለኛ ፡ የሆነ. He speaks grammatical Amharic, but has an English accent. ትክክለኛ ፡ የሆነ ፡ አማርኛ ፡ ቢናገርም ፡ አነጋገሩ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ነው
2. ሰዋስዋዊ. His speech contained several grammatical errors. ንግግሩ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ሰዋስዋዊ ፡ ስሕተቶች ፡ ነበሩበት

**granary** ጐተራ
The granary in the villages is usually made of clay. ባገር ፡ ቤት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጐተራ ፡ የሚሠራው ፡ ከጭቃ ፡ ነው

**grand**
1. ትልቅ. It was a grand idea. ትልቅ ፡ ሐሳብ ፡ ነበር
2. ታላቅ (pl. ታላላቅ). The grand palace is built atop a hill. ታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የተሠራው ፡ በኮረብታ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ነው
The coronation will be a grand spectacle. የዘውድ ፡ በዓሉ ፡ ታላቅ ፡ ትርኢይት ፡ ይሆናል
He always entertains grand personages. ሁልጊዜ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ይጋብዛል
3. አስደናቂ. There is a grand view of the mountains from the windows. በመስኮቶቹ ፡ በኩል ፡ አስደናቂ ፡ የተራራዎች ፡ ትርኢይት ፡ ይታያል
4. የተከበረ. She is a grand lady. የተከበረች ፡ እመቤት ፡ ነች
5. ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ያለው. In front of an audience, her manner is grand. ባድማጮቹ ፡ መካከል ፡ ቁመናዋ ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ያለው ፡ ነው

**have a grand time**
*We had a grand time at your party. ፓርቲህ ፡ እጅግ ፡ አስደስቶን ፡ ነበር
[See also 'total']

**grandchild** የልጅ ፡ ልጅ
I have five grandchildren. አምስት ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ አሉኝ

**granddaughter** የልጅ ፡ ልጅ
His granddaughter came to visit him. የልጅ ፡ ልጁ ፡ ልትጠይቀው ፡ መጣች

**grandeur**
1. ውበት. He was impressed by the grandeur of the scenery. በትርኢይቱ ፡ ውበት ፡ ተደንቆ ፡ ነበር
2. ታላቅነት. The grandeur of the ceremony impressed everyone. የሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ታላቅነት ፡ ሁሉን ፡ ሰው ፡ አስደነቀ
3. ግርማ ፡ ሞገስ. He was insensitive to the sea's grandeur. የባሕሩ ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ስሜቱን ፡ አልነካውም
4. ትልቅነት. His delusions of grandeur led him to disappointments. ከንቱ ፡ የትልቅነት ፡ ስሜት ፡ ከብስጭት ፡ ላይ ፡ ጣለው

**grandfather** ወንድ ፡ አያት
My grandfather is ninety years old. ወንድ ፡ አያቴ ፡ ዘጠና ፡ ዓመታቸው ፡ ናቸው
[See also 'paternal']

**grandiose** ዓቢይ
His grandiose plan was too expensive to be practical. ዓቢይ ፡ እቅዱን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ወጪ ፡ ይጠይቃል

**be grandiose** ታላቅ ፡ ግርማ ፡ ነበረው
The coronation parade was grandiose. የዘውድ ፡ በዓሉ ፡ ሰልፍ ፡ ታላቅ ፡ ግርማ ፡ ነበረው

**grandmother** ሴት ፡ አያት
My grandmother died recently. ሴት ፡ አያቴ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ

**grandson** የልጅ ፡ ልጅ
When the king died, his grandson succeeded him. ንጉሡ ፡ ሲሞት ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ አልጋውን ፡ ወረሰ

**grandstand** ሰገነት
Grandstands are being built for the coronation. ለዘውድ ፡ በዓል ፡ ሰገነቶች ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ ናቸው

**granite** ጥቁር ፡ ድንጋይ
Granite is a very hard stone. ጥቁር ፡ ድንጋይ ፡ በጣም ፡ ጠንካራ ፡ ነው

**grant** (v.)
1. ሰጠ. The government granted the school 10,000 dollars for a new building. መንግሥት ፡ ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ተጨማሪ ፡ ሕንጻ ፡ ማሠሪያ ፡ ዐሥር ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ሰጠ
2. ተቀበለ ፤ ፈጸመ. He granted my request. ጥያቄዬን ፡ ተቀበለ
I question the propriety of granting his request. የጠየቀውን ፡ መፈጸም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ አልታየኝም
3. አመነ. I grant that I was wrong. መሳሳቴን ፡ አምናለሁ
*Please grant me a favor! አንድ ፡ ነገር ፡ አድርግልኝ
[See also 'audience, immunity, permission']

**grant** (n.) እርዳታ
He is studying medicine on a government grant. መንግሥት ፡ በሚያደርግለት ፡ እርዳታ ፡ ሕክምና ፡ ያጠናል

**granted** ከሆነ
Granted that your statement is correct .... ያልከው ፡ እውነት ፡ ከሆነ ...

**take for granted**
1. ምንም ፡ አልተጠራጠረም. We took it for granted that John would do well. ዮሐንስ ፡ እንደሚሳካለት ፡ ምንም ፡ አልተጠራጠርንም

2. አመነ. He took for granted that he was going with us. ከኛ ፡ ጋር ፡ የሚሄድ ፡ መሆኑን ፡ አምኖ ፡ ነበር

**granulated** ደቃቅ ፡ ሱኳር
The cook bought granulated sugar. ወጥ ፡ ቤቱ ፡ ደቃቅ ፡ ሱኳር ፡ ገዛ

**grape** ወይን
These grapes make good wine. ይህ ፡ ወይን ፡ ጥሩ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይወጣዋል

**graph** ግራፍ
The graph of exports shows a rise in prices. ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የተላኩትን ፡ እቃዎች ፡ የሚያሳየው ፡ ግራፍ ፡ ዋጋው ፡ ከፍ ፡ ማለቱን ፡ ያመለክታል

**graphic** ጉልህ
The soldier gave a graphic account of the battle. ወታደሩ ፡ ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ መግለጫ ፡ ሰጠ

**grapple** ተናነቀ
The wrestler grappled with his opponent. ታጋዩ ፡ ከተቃዋሚው ፡ ጋር ፡ ተናነቀ

**grasp** (v.)
1. ያዘ ፤ ጨበጠ. She grasped the rope with both hands. ገመዱን ፡ በሁለት ፡ እጅዋ ፡ ያዘች ፡ (ጨበጠች)
2. ገባ(ው). +I do not quite grasp what you mean by that. ምን ፡ ማለትህ ፡ እንደሆነ ፡ በደንብ ፡ አልገባኝም

**grasp** (n.) የጨበጠ ፤ አያያዝ
He let go his grasp and jumped to the ground. የጨበጠውን ፡ ለቆ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ዘለለ
He loosened his grasp. አያያዙን ፡ ላላ ፡ አደረገ
*Victory was almost in our grasp. ድል ፡ በእጃችን ፡ ልናደርግ ፡ ምንም ፡ አልቀረንም ፡ ነበር

**have a firm grasp on** በጥብቅ ፡ ጨበጠ
The mason had a firm grasp on the hammer. ግንበኛው ፡ መዶሻውን ፡ በጥብቅ ፡ ጨብጦት ፡ ነበር

**have a good grasp of** ጠልቆ ፡ ዐወቀ
He has a good grasp of the subject. ነገሩን ፡ ጠልቆ ፡ ያውቀዋል

**grass** ሣር
The Ethiopians cover their houses with grass. ኢትዮጵያውያን ፡ ቤታቸውን ፡ በሣር ፡ ይከድናሉ

**grasshopper** ፌንጣ
The grasshoppers ate up my flowers. ፌንጣዎቹ ፡ አበባዎቼን ፡ ጨርሰው ፡ በሉብኝ

**grate** (vt.) ፈረፈረ
Grate some cheese, please! ጥቂት ፡ ፎርማጆ ፡ ፈርፍርልኝ

**grate** (vi.) ሲጢጥ ፡ አለ
The chalk grated on the blackboard. ጠመኔው ፡ ጥቁር ፡ ሰሌዳው ፡ ላይ ፡ ሲጢጥ ፡ አለ

**grate** (n.)
1. የብረት ፡ መከደኛ. Somebody took the grate off the drain. የብረቱን ፡ መከደኛ ፡ ከጐርፉ ፡ መውረጃ ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ አንሥቶታል
2. ወንፊት. Since the grate is covered with ashes, the charcoal in the oven does not burn well. ወንፊቱን ፡ አመድ ፡ ስለደፈነው ፡ ማንደጃው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ከሰል ፡ በደንብ ፡ አይነድም

**grated** (adj.) የተፈረፈረ
He put some grated cheese on his spaghetti. ስፓጌቲው ፡ ላይ ፡ ጥቂት ፡ የተፈረፈረ ፡ ፎርማጆ ፡ አደረገበት

**grateful**
1. ውለታ ፡ የማይረሳ. A grateful person is not often encountered. ውለታውን ፡ የማይረሳ ፡ ሰው ፡ የሚገኘው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነው
2. የምስጋና. The children sent their uncle a grateful letter. ልጆቹ ፡ ላጎታቸው ፡ የምስጋና ፡ ደብዳቤ ፡ ላኩ
3. ታላቅ. The breeze is a grateful relief from the heat. የነፋሱ ፡ ሽውታ ፡ ለሙቀቱ ፡ ታላቅ ፡ እፎይታ ፡ ነው

**be grateful** አመሰገነ
I am grateful to you for your help. ስለረዳሽኝ ፡ አመሰግንሻለሁ

**feel grateful**
I feel truly grateful. ከልብ ፡ አመሰግናለሁ

**gratification**
1. ደስታ. His success was a great gratification to his parents. ስለቀናው ፡ ወላጆቹ ፡ ትልቅ ፡ ደስታ ፡ ተሰማቸው
2. ማርካት. The gratification of every wish is not possible. ምኞትን ፡ ሁሉ ፡ ለማርካት ፡ አይቻልም

**gratify** (gratified)
1. አረካ. He tried hard to gratify his child's thirst for knowledge. የልጁን ፡ የዕውቀት ፡ ጥም ፡ ለማርካት ፡ በጣም ፡ ሞከረ
2. ፈጸመ. He gratified her every wish. ምኞቷን ፡ ሁሉ ፡ ፈጸመላት
3. አስደሰተ. Flattery gratifies a vain person. ከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ግብዝ ፡ ሰውን ፡ ያስደስታል

**gratifying** የሚያስደስት ፤ መንፈስን ፡ የሚያረካ
The news is very gratifying. ዜናው ፡ በጣም ፡ የሚያስደስት ፡ ነው
The solemn festivities of the church were gratifying. የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሞገስ ፡ ያለው ፡ ሥርዓተ ፡ ቅዳሴ ፡ መንፈስን ፡ የሚያረካ ፡ ነበር

**gratis** በነጻ
I will give you this book gratis. ይህንን ፡ መጽሐፍ ፡ በነጻ ፡ እሰጥሃለሁ

**gratitude**
1. ምስጋና. His gratitude knows no bounds. ምስጋናው ፡ ወሰን ፡ የለውም
2. ውለታ. In his gratitude, he made me a present of his book. ውለታውን ፡ ለመግለጽ ፡ መጽሐፉን ፡ አበረከተልኝ

**gratuitous**
1. ነጻ. The lawyer gave gratuitous advice to his client. ጠበቃው ፡ ለደንበኛው ፡ ነጻ ፡ ምክር ፡ ሰጠ
2. (= adv.) ከመሬት ፡ ተነሥቶ. His gratuitous insult upset me greatly. ከመሬት ፡ ተነሥቶ ፡ ስለሰደበኝ ፡ በጣም ፡ ተናደድኩ

**gratuity** (gratuities) ጉርሻ
He received a salary plus gratuities. ደሞዙን ፡ ከጉርሻ ፡ ጋር ፡ ተቀበለ

**grave** (n.)
1. መቃብር. He visits the Empress' grave every Sunday. እሑድ ፡ እሑድ ፡ የእቴጌይቱን ፡ መቃብር ፡ ይጐበኛል
2. ሞት. They have insurance from the cradle to the grave. ከልደት ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ የሕይወት ፡ ዋስትና ፡ አላቸው

**grave** (adj.)
1. ከባድ. That's a grave mistake. ከባድ ፡ ስሕተት ፡ ነው
2. አስጊ. His condition is grave. ሁኔታው ፡ አስጊ ፡ ነው
3. ከፍ ፡ ያለ. I have grave doubts about the usefulness of his plan. ስለ ፡ እቅዱ ፡ ጠቃሚነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥርጣሬ ፡ አድሮብኛል
4. ኮስታራ. A grave person never laughs. ኮስታራ ፡ ሰው ፡ ፈጽሞ ፡ አይሥቅም
5. ጥልቅ. His grave thought is appreciated by those who know him. ጥልቅ ፡ አስተሳሰቡ ፡ በሚያውቁት ፡ ሁሉ ፡ ይደነቃል

**look grave** ኮስተር ፡ አለ
Everyone looked grave at the inauguration. በምረቃው ፡ ላይ ፡ ሁሉም ፡ ኮስተር ፡ ብሎ ፡ ነበር

**gravel** ጠጠር ፤ ኰረት
The path is covered with gravel. የእግር ፡ መንገዱ ፡ ጠጠር ፡ ፈሶበታል
A steamroller crushed the gravel on the road. ዳምጠው ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ኰረት ፡ አደቀቀው

**gravely**
1. ክፉኛ. He is gravely ill. ክፉኛ ፡ ታሟል
2. በሐዘን. When he read the announcement of the President's death, he spoke gravely. የፕሬዚዳንቱን ፡ ዕረፍት ፡ ሲገልጽ ፡ በሐዘን ፡ ተናገረ

**graven** የተቀረጸ
The Israelites were punished for worshipping graven images. እስራኤላውያን ፡ ለተቀረጹ ፡ ምስሎች ፡ በመስገዳቸው ፡ ተቀጥተው ፡ ነበር

**gravestone** የመቃብር ፡ ድንጋይ
The gravestone has his name on it. በመቃብሩ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ስሙ ፡ አለ

**graveyard** መካነ ፡ መቃብር
The graveyard is not far from the church. መካነ ፡ መቃብሩ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሩቅ ፡ አይደለም

**gravitate**
1. ቀስ ፡ በቀስ ፡ አመራ. The crowd gravitated toward the main tent of the exhibition. ሕዝቡ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ወደ ፡ ኤግዚቢሽኑ ፡ ዋና ፡ ድንኳን ፡ አመራ
2. ተሳበ. Comets gravitate toward the earth. ጅራታም ፡ ኮከቦች ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ይሳባሉ
3. ዘቀጠ. The sand gravitated to the bottom of the bottle. አሸዋው ፡ ጠርሙሱ ፡ ሥር ፡ ዘቀጠ

**gravitation** ስበት
Gravitation holds people to the surface of the earth. ስበት ፡ ሰዎችን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ይይዛል

**gravity**
1. አስጊነት. He quickly sensed the gravity of the situation. የሁኔታውን ፡ አስጊነት ፡ ወዲያው ፡ ተረዳው
2. ስበት. All objects fall to earth because of gravity. በስበት ፡ ምክንያት ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ይወድቃል

**gravy** መረቅ
He dipped the bread in the gravy. ዳቦውን ፡ መረቅ ፡ ውስጥ ፡ አጠቀሰ

**gray** (v.) ሸበተ
His hair is beginning to gray. ጸጉሩ ፡ መሸበት ፡ ጀምሯል

**gray** (adj.) ግራጫ
Gray and red go well together. ግራጫና ፡ ቀይ ፡ በደንብ ፡ ይስማማል

**gray hair** ሽበት
His gray hair looks very nice. ሽበቱ ፡ በጣም ፡ አምሮ ፡ ይታያል

**be gray, turn gray**
1. ሸበተ. My hair has turned gray. ጸጉሬ ፡ ሸብቷል
2. ከበደ. It is winter, and the day is gray. ክረምት ፡ ስለሆነ ፡ ቀኑ ፡ ይከብዳል

**gray-haired** ሽበቶ
The gray-haired old man sat warming himself in the sun. ሽበቶው ፡ ሽማግሌ ፡ ፀሐይ ፡ ይሞቃል

**graze** (vt.)
1. አጋጠ. He took the cattle to graze. ከብቶቹን ፡ ለማጋጥ ፡ ወሰደ
2. አሰማራ. The pastoral tribes of the mountains graze their sheep on the hillside. ተራራዎች ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ ከብት ፡ አርቢ ፡ ጐሳዎች ፡ በጎቻቸውን ፡ የሚያሰማሩት ፡ ጋራው ፡ ሥር ፡ ነው
3. ጫረ. The bullet grazed his shoulder. ጥይቱ ፡ ትከሻውን ፡ ጫረው
4. ጨረፈ. It was a close call; the heavy rock fell and grazed my elbow. ድንጋዩ ፡ ክንዴን ፡ ብቻ ፡ ጨርፎኝ ፡ በማለፉ ፡ ለጥቂት ፡ አመለጥኩ

**graze** (vi.) ጋጠ ፤ ተሰማራ
The cows are grazing in the fields. ላሞቹ ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ይግጣሉ ፡ (ይሰማራሉ)

**grazing** (adj.) የተሰማራ
The shepherd sat on a hillock and watched the grazing sheep. እረኛው ፡ ጉብታው ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ የተሰማሩትን ፡ በጎች ፡ ጠበቀ

**grazing land** የግጦሽ ፡ መሬት
Nomads must always hunt for good grazing land. ዘላኖች ፡ ሁልጊዜ ፡ ጥሩ ፡ የግጦሽ ፡ መሬት ፡ መፈለግ ፡ አለባቸው

**grease** (v.)
1. አሰሰ. She greased the griddle and then baked the bread. ብረት ፡ ምጣዱን ፡ ካሰሰች ፡ በኋላ ፡ ዳቦውን ፡ ጋገረች
2. ቅባት ፡ ቀባ. He forgot to grease my car before I left. ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ መኪናዬን ፡ ቅባት ፡ ሳይቀባት ፡ ቀረ

**grease** (n.) ቅባት
Don't leave the grease in the pan! ቅባቱን ፡ መጥበሻው ፡ ላይ ፡ አትተው

**(be) greasy** ቅባት ፡ ብቻ ፡ ነው
The dishes are still greasy. ሳሕኖቹ ፡ አሁንም ፡ ቅባት ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**great**
1. ትልቅ. The noble lives in a great house on the hill. መኰንኑ ፡ በኮረብታው ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል
The governor of this province is a great man. የዚህ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ገዢ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ነው
2. ታላቅ. The battle of Adowa was a great event in Ethiopian history. የዐድዋ ፡ ጦርነት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ምዕራፍ ፡ ይዟል
3. ሰፊ. The great forest which once covered the north was completely cut down. አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሰሜንን ፡ ሸፍኖ ፡ የነበረው ፡ ሰፊ ፡ ጫካ ፡ አሁን ፡ ተቈርጦ ፡ አልቋል
4. ጽኑ. He was in great pain. በጽኑ ፡ ሥቃይ ፡ ላይ ፡ ነበር
5. ከፍተኛ. The lively boys have a great appetite for amusement. ንቁ ፡ ልጆች ፡ ከፍተኛ ፡ የጨዋታ ፡ ፍላጎት ፡ አላቸው

**great big** በጣም ፡ ትልቅ
I need a great big box to put the things in. እቃውን ፡ የማስቀምጥበት ፡ አንድ ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ሰንዱቅ ፡ ያስፈልገኛል
[See also 'dimension, ideal, many, majority, occasion']

**(the) greatest** ከሉት ፡ ሁሉ ፡ ታላቅ
He is the greatest singer of our time. እሱ ፡ በጊዜያችን ፡ ካሉት ፡ ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ ዘፋኝ ፡ ነው

**great-grandchild** የልጅ ፡ ልጅ ፡ ልጅ
A great-grandchild was born to him recently. የልጅ ፡ ልጅ ፡ ልጅ ፡ በቅርቡ ፡ ተወለደለት

**great-grandfather** የወንድ ፡ ቅድመ ፡ አያት

**great-grandmother** የሴት ፡ ቅድመ ፡ አያት

**greatly**
1. በጣም. Raw meat is greatly esteemed by Ethiopians. ጥሬ ፡ ሥጋ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ ይወደዳል
2. ያለ ፡ ቅጥ. She exaggerates greatly. ያለ ፡ ቅጥ ፡ ታጋንናለች
3. በክብር. Solomon ruled greatly and wisely. ሰሎሞን ፡ በክብርና ፡ በጥበብ ፡ ገዛ

**greatness**
1. ትልቅነት. The greatness of the Grand Canyon excites admiration. የግራንድ ፡ ካንዮን ፡ ትልቅነት ፡ አስደናቂ ፡ ነው

2. ታላቅነት. He achieved greatness as an artist. በሥነ ፡ ጥበብ ፡ ታላቅነትን ፡ አተረፈ

**Greece** ግሪክ

**greed** ሥሥት
Greed made him keep his money to himself. ሥሥት ፡ ለራሱ ፡ ብቻ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያከማች ፡ አደረገው

**greedily** ተስገብግቦ
He ate the food greedily. ምግቡን ፡ ተስገብግቦ ፡ በላው

**greedy** ስግብግብ
That greedy fellow has eaten all the cake. ያ ፡ ስግብግብ ፡ ሰው ፡ ኬኩን ፡ ሁሉ ፡ በልቶታል

**be greedy** ተስገበገበ
Don't be so greedy! እንደዚህ ፡ አትስገብገብ

**Greek**
1. ግሪክ. There are many Greeks in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ግሪኮች ፡ አሉ
2. ጽርእ. Paul's epistles were written in Greek. የጳውሎስ ፡ መልእክቶች ፡ የተጻፉት ፡ በጽርእ ፡ ነበር
3. የግሪክ ፡ ቋንቋ. Greek is not taught at our university. የግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ በዩኒቨርሲቲያችን ፡ ውስጥ ፡ አይሰጥም

**green**
1. አረንጓዴ. The color of my car is green. የመኪናዬ ፡ ቀለም ፡ አረንጓዴ ፡ ነው
2. ለምለም. The leaves are still green. ቅጠሎቹ ፡ አሁንም ፡ ለምለም ፡ ናቸው
3. ጥሬ. Eating green bananas gave him diarrhea. ጥሬ ፡ ሙዝ ፡ መብላት ፡ ተቅማጥ ፡ ለቀቀበት
4. ያልበሰለ. Don't eat green fruit! It will make you ill. ያልበሰለ ፡ ፍሬ ፡ አትብላ ፤ ያሳምምሃል
5. ያልደረቀ. The lumber is still green and cannot be used for building. ዕንጨቱ ፡ ገና ፡ ስላልደረቀ ፡ ለሕንጻ ፡ መሥሪያ ፡ ሊውል ፡ አይችልም
6. አዲስ. Green recruits were sent into battle. አዲሶቹ ፡ ምልምሎች ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ተላኩ
7. እንግዳ. He is still green at his job. አሁንም ፡ ለሥራው ፡ እንግዳ ፡ ነው

**be green** ለመለመ
The vegetation is green after the rains. ከዝናቡ ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ ሣር ፡ ቅጠሉ ፡ ለምልሟል

**turn green (with envy)** አረረ
He turned green with envy when he heard I got the job. ሥራውን ፡ ማግኘቴን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በቅናት ፡ አረረ
[See also 'scum']

**greet**
1. ሰላምታ ፡ ሰጠ. She greeted me with a smile. በፈገግታ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠችኝ
2. ሰላምታ ፡ አቀረበ. We greet you on behalf of the class. በክፍሉ ፡ ስም ፡ ሰላምታ ፡ እናቀርብልሃለን
3. ተቀበለ. The crowd greeted the President with cheers. የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ፕሬዚዳንቱን ፡ በእልልታና ፡ በጭብጨባ ፡ ተቀበለው
4. ገጠመ(ው). A strange sight greeted her eyes. እንግዳ ፡ ትርእይት ፡ ዓይኖቿን ፡ ገጠማት
[See also 'nod']

**greeting**
1. ሰላምታ. He did not notice my greeting. ሰላምታዬን ፡ ልብ ፡ አላለም
2. አቀባበል. We never expected such a warm greeting. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ የጋለ ፡ አቀባበል ፡ ይደረግልናል ፡ ብለን ፡ በፍጹም ፡ አላሰብንም ፡ ነበር

**gregarious**
1. የመንጋ ፡ እንስሳ. Sheep are gregarious. በጎች ፡ የመንጋ ፡ እንስሶች ፡ ናቸው
2. ከሰው ፡ መቀላቀል ፡ የሚወድ. Gregarious people like to form clubs. ከሰው ፡ መቀላቀል ፡ የሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ክበቦችን ፡ ማቋቋም ፡ ይወዳሉ

**grenade** የእጅ ፡ ቦምብ
The rebel threw a grenade at the travelers and killed them. ሽፍታው ፡ የእጅ ፡ ቦምብ ፡ ወርውሮ ፡ መንገደኞቹን ፡ ገደላቸው

**griddle** ምጣድ
She poured the batter on the griddle. ሊጡን ፡ በምጣድ ፡ ላይ ፡ አሰፋችው

**grief** ሐዘን
She could not conceal her grief. ሐዘኗን ፡ ልትደብቅ ፡ አልቻለችም

**grievance** ቅሬታ
The workers presented their grievances. ሠራተኞቹ ፡ ቅሬታቸውን ፡ አሰሙ
[See also 'air']

**grieve** (vt.) አሳዘነ
His death grieved the whole nation. የሱ ፡ ሞት ፡ ሀገሪቷን ፡ በሙሉ ፡ አሳዘነ

**grieve** (vi.) አዘነ
She grieved for the loss of her son. በወንድ ፡ ልጇዋ ፡ ሞት ፡ አዘነች

**grieving** ሐዘንተኛ
He consoled the grieving widow for the loss

of her husband. ሐዘንተኛዋን ፡ ሴት ፡ ስለ ፡ ባሏ ፡ ሞት ፡ አጽናናት

**grievous**
1. ታላቅ. His death is a grievous loss to the country. የሱ ፡ ሞት ፡ ለሀገሪቷ ፡ ታላቅ ፡ ጉዳት ፡ ነው
Wasting food when people are starving is a grievous wrong. ሰዎች ፡ እየተራቡ ፡ ምግብ ፡ ማባከን ፡ ታላቅ ፡ በደል ፡ ነው
2. ጽኑ. He was suffering from a grievous wound. በጽኑ ፡ ቁስል ፡ ይሠቃይ ፡ ነበር
3. አሳዛኝ. The grievous news upset the whole family. አሳዛኙ ፡ ወሬ ፡ ቤተሰቡን ፡ ሁሉ ፡ አሸበረ

**grill** (v.)
1. ጠበሰ. They grilled the meat on a charcoal fire. በከሰል ፡ እሳት ፡ ሥጋውን ፡ ጠበሱ
2. በጥያቄ ፡ አዋከበ. The detectives grilled the prisoner until he finally confessed. መርማሪዎቹ ፡ እስረኛው ፡ ጥፋቱን ፡ እስኪያምን ፡ ድረስ ፡ በጥያቄ ፡ አዋከቡት

**grill** (n.) የብረት ፡ ምድጃ
The grill was red hot from the fire. የብረት ፡ ምድጃው ፡ ከእሳቱ ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ፍሟል

**grim**
1. ጭካኔ ፡ የተሞላ(በት). The grim struggle between the two men ended in the death of one of them. በሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ መሀከል ፡ በተደረገው ፡ ጭካኔ ፡ የተሞላበት ፡ ትግል ፡ አንደኛው ፡ ሞተ
2. የማይሆን. He made grim jokes about death and suffering. ስለ ፡ ሞትና ፡ ስለ ፡ መከራ ፡ የማይሆንን ፡ ቀልድ ፡ ቀለደ
3. አሰቃቂ ፤ የሚያሰቅቅ. He told a grim tale of the battle. ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ አሰቃቂ ፡ (የሚያሰቅቅ) ፡ ታሪክ ፡ ተናገረ
4. ፍጹም ፤ የማያወላውል. He took up the task with grim determination. ተግባሩን ፡ በፍጹም ፡ (በማያወላውል) ፡ ቈራጥነት ፡ ጀመረ

**be grim** ፊቱን ፡ አኰሰተረ
Father was grim when he heard about the broken windows. የመስኮቱን ፡ መሰበር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ አባቱ ፡ ፊቱን ፡ አኰሰተረ

**grimace**
*He made a hideous grimace. ፊቱን ፡ ኮሶ ፡ አስመሰለ

**grime** ላብና ፡ አቧራ
His face was covered with grime. ላብና ፡ አቧራ ፡ ፊቱ ፡ ላይ ፡ ተጋግሮበታል

**grin** (v.) ፈገግ ፡ አለ
The boys were grinning with delight. ልጆቹ ፡ በደስታ ፡ ፈገግ ፡ ብለው ፡ ነበር

**grin from ear to ear**
He grinned from ear to ear. አፉ ፡ ጆሮው ፡ እስኪደርስ ፡ ሣቀ

**grin** (n.) መገልፈጥ
His grin revealed all his teeth. መገልፈጡ ፡ ጥርሱን ፡ በሙሉ ፡ አሳየ

**grind** (ground)
1. ፈጨ. You have to grind this grain very fine. ይህንን ፡ እህል ፡ አልመሽ ፡ መፍጨት ፡ አለብሽ
2. አደቀቀ. His teeth ground the meat. በጥርሱ ፡ ሥጋውን ፡ አደቀቀ
3. ወቀጠ. Grind the coffee finely! ቡናውን ፡ አድቅቀህ ፡ ውቀጠው
She ground the spices in a mortar. ቅመሙን ፡ በሙቀጫ ፡ ወቀጠች
4. ሳለ. He ground his knife to a razor edge. ስንጢውን ፡ ምላጭ ፡ እስኪሆን ፡ ሳለው
5. አፋጨ. He ground his teeth. ጥርሱን ፡ አፋጨ
*Come here, I have an ax to grind with you. ወዲህ ፡ ና ፤ የምገልጽልህ ፡ ቅሬታ ፡ አለኝ

**grind to flour** ፈጨ
They ground the wheat to flour. ስንዴውን ፡ ፈጩት
[See also 'coarsely']

**grinding noise** ሕርጭርጭ ፡ የሚል ፡ ድምፅ
The grinding noise is made by friction. ሕርጭርጭ ፡ የሚለው ፡ ድምፅ ፡ የሚመጣው ፡ በማፋጨት ፡ ነው

**grindstone** መሳያ
He sharpened his ax on the grindstone. መጥረቢያውን ፡ በመሳያው ፡ ሳለ

**grip** (gripped), v.
1. አንቅ ፡ አድርጎ ፡ ያዘ. The frightened child gripped his mother's hand. የደነገጠው ፡ ልጅ ፡ የእናቱን ፡ እጅ ፡ አንቅ ፡ አድርጎ ፡ ያዘ
2. አጥብቆ ፡ ያዘ. If you grip the side of the cart, you will not fall out. ጐኑን ፡ አጥብቀህ ፡ ከያዝክ ፡ ከጋሪው ፡ ላይ ፡ አትወድቅም
3. ሐሳቡን ፡ ማረከ. An exciting story grips you. ስሜት ፡ የሚቀሰቅስ ፡ ታሪክ ፡ ሐሳብህን ፡ ይማርካል

**grip** (n.)
1. አያያዝ. His grip is tenacious and hard to shake loose. አያያዙ ፡ የጠበቀና ፡ ለማስለቀቅ ፡ የሚያስቸግር ፡ ነው

2. እጅ. The criminal broke loose from the policeman's grip and escaped. ወንጀለኛው ፡ ከፖሊስ ፡ እጅ ፡ ፈልቅቆ ፡ አመለጠ
3. አጨባበጥ. He has a strong grip. አጨባበጡ ፡ ኀይለኛ ፡ ነው

**come to grips** ጦርነት ፡ ገጠሙ
The two armies finally came to grips. ሁለቱ ፡ ጦሮች ፡ በመጨረሻ ፡ ጦርነት ፡ ገጠሙ

**come to grips with** ተቋቋመ
Failure to come to grips with the housing problem will only make matters worse. የመኖሪያ ፡ ቤትን ፡ ችግር ፡ ለመቋቋም ፡ አለመሞከር ፡ ችግሩን ፡ እያደር ፡ ያባብሰዋል

**have a grip on** ተረዳ(ው)
He has a good grip on the situation. ሁኔታውን ፡ በሚገባ ፡ ተረድቶታል

**hold in one's grip** እጅ ፡ አደረገ
The Roman empire held many small kingdoms in its grip. የሮማ ፡ መንግሥት ፡ ብዙ ፡ ታናናሽ ፡ መንግሥታትን ፡ እጅ ፡ አድርጎ ፡ ነበር

**take a good grip on** አጥብቆ ፡ ያዘ
Take a good grip on this rope! ይህን ፡ ገመድ ፡ አጥብቀህ ፡ ያዘው

**gripe**
1. አበሳጨ. Her criticism gripes me. ነቀፌታዋ ፡ ያበሳጨኛል
2. ሆዱን ፡ ቈረጠው. This green fruit will gripe you. ይህ ፡ ጥሬ ፡ ፍሬ ፡ ሆድህን ፡ ይቈርጥሃል

**grippe** ኢንፍሉዌንዛ
They say that green pepper is a good remedy for the grippe. ቃሪያ ፡ ለኢንፍሉዌንዛ ፡ ጥሩ ፡ መድኃኒት ፡ ነው ፡ ይባላል

**grisly** አስደንጋጭ
The child dreamed of grisly monsters. ልጁ ፡ አስደንጋጭ ፡ ስለሆኑ ፡ ጭራቆች ፡ አለመ

**grist** የሚፈጭ ፡ እህል
Farmers bring grist to the mill in large bags. ገበሬዎች ፡ በትልልቅ ፡ ስልቻዎች ፡ የሚፈጭ ፡ እህል ፡ ወፍጮ ፡ ቤት ፡ ያመጣሉ

**grit** (gritted) ነከሰ
She gritted her teeth until the ordeal was over. ሥቃዩ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ጥርሷን ፡ ነከሰች

**grit** (n.) የአሸዋ ፡ ብናኝ
Grit gets into the motor and damages it. የአሸዋ ፡ ብናኝ ፡ ሞተር ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ያበላሸዋል

**groan** (v.) አቃሰተ
The wounded men lay there groaning with no one to help them. ቁስለኞቹ ፡ የሚረዳቸው ፡ አጥተው ፡ ከወደቁበት ፡ ሆነው ፡ ያቃስቱ ፡ ነበር

**groan** (n.) ማቃሰት
We heard the groans of the wounded man. የቁስለኛውን ፡ ሰው ፡ ማቃሰት ፡ ሰማን

**grocer** ምግብ ፡ ነጋዴ ፤ ምግብ ፡ ሻጭ
The grocer sells only food and not drugs. ምግብ ፡ ነጋዴው ፡ (ሻጩ) ፡ ምግብ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ መድኃኒት ፡ አይሸጥም

**grocery** (groceries)
1. ለምግብ ፡ ሸቀጣ ፡ ሸቀጥ. I purchased my groceries in town. ለምግብ ፡ ሸቀጣ ፡ ሸቀጡን ፡ የገዛሁት ፡ ከከተማ ፡ ነው
2. የምግብ ፡ መደብር. You can find olive oil in any grocery. የወይራ ፡ ዘይት ፡ በማንኛውም ፡ የምግብ ፡ መደብር ፡ ይገኛል

**grocery store** የምግብ ፡ መደብር
The grocery store is closed on Sunday. የምግብ ፡ መደብር ፡ እሑድ ፡ ዝግ ፡ ነው

**groin** ብሽሽት
He was wounded in the groin. ከብሽሽቱ ፡ ላይ ፡ ቆስሎ ፡ ነበር

**groom** (v.) አበጣጠረ
He groomed his hair and went to the party. ጸጉሩን ፡ አበጣጥሮ ፡ ወደ ፡ ፓርቲው ፡ ሄደ

**be groomed** ልምምድ ፡ አደረገ
He was groomed to take over the manager's job. ያስተዳዳሪውን ፡ ቦታ ፡ ለመያዝ ፡ ልምምድ ፡ አድርጓል

**groom** (n.)
1. ሙሽራ. The groom was splendidly dressed in native attire. ሙሽራው ፡ በሀገር ፡ ልብስ ፡ አሸብርቆ ፡ ነበር
2. ባልደራስ. The groom made sure that the horses and mules were fed properly. ባልደራሱ ፡ ፈረሶቹና ፡ በቅሎዎቹ ፡ በሥርዓት ፡ መመገባቸውን ፡ አረጋገጠ

**groove**
1. ቡርቡር. The door does not swing out, but slides along grooves in the floor and ceiling. በሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አይከፈትም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በወለሉና ፡ በጣራው ፡ ባሉት ፡ ቡርቡሮች ፡ ውስጥ ፡ ይንሸራተታል
2. ጐድጓዳ ፡ ቦታ. My desk has a groove for pencils. የኔ ፡ ዴስክ ፡ ለእርሳስ ፡ ማስቀመጫ ፡ ጐድጓዳ ፡ ቦታ ፡ አለው

**cut a groove in** ቦረቦረ
He cut a groove in the wood. ዕንጨቱን ፡ ቦረ ቦረ

**grope**
1. ዳበሰ. He groped for the door in the dark. በጨለማ ፡ በሩን ፡ ፍለጋ ፡ ዳበሰ
2. ለማግኘት ፡ ጣረ. She groped for the right words. ትክክለኛውን ፡ ቃል ፡ ለማግኘት ፡ ጣረች
3. ለማግኘት ፡ ፍለጋ ፡ አደረገ. The detectives groped for some clues to the murder. ወንጀል ፡ መርማሪዎቹ ፡ ስለ ፡ ግድያው ፡ ፍንጭ ፡ ለማግኘት ፡ ፍለጋ ፡ አደረጉ

**grope one's way** በዳበሳ ፡ ደረሰ
He groped his way to the door. በዳበሳ ፡ ከበሩ ፡ ደረሰ

**gross**
1. ከባድ. That was a gross mistake. ያ ፡ ከባድ ፡ ስሕተት ፡ ነበር
2. ጉልህ. Only the gross errors are noticed by the machine. መኪናው ፡ ሊያውቅ ፡ የሚችለው ፡ ጉልህ ፡ የሆኑትን ፡ ስሕተቶች ፡ ብቻ ፡ ነው
3. ጠቅላላ. What was your gross income last year? ያምና ፡ ጠቅላላ ፡ ገቢህ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነበር ?
4. ጸያፍ. He uses gross language in the presence of women. በሴቶች ፡ ፊት ፡ ጸያፍ ፡ ንግግር ፡ ይናገራል
5. ያልታረመ. Her gross manners offended her companions. ያልታረመ ፡ ሁኔታዋ ፡ ጓደኞቿን ፡ አሳፈራቸው

**grossly** ያለቅጥ
That is grossly exaggerated. ያለቅጥ ፡ ተጋኗል

**grotesque**
1. አሥቂኝና ፡ አስደናቂ. His face had a grotesque look. መልኩ ፡ አሥቂኝና ፡ አስደናቂ ፡ ነበር
2. አስቀያሚ. The hunchback has a grotesque appearance. ጉባጣው ፡ አስቀያሚ ፡ ቁመና ፡ አለው

**grouch** ነጭናጫ
Don't be such a grouch! እንደዚህ ፡ ነጭናጫ ፡ አትሁን

**grouchy** ነጭናጫ
They tolerate the grouchy man because he is their employer. ነጭናጫውን ፡ ሰው ፡ ችላ ፡ ያሉት ፡ ቀጣሪያቸው ፡ ስለሆነ ፡ ነው

**be grouchy** ተነጫነጨ
He is grouchy right after he gets out of bed. ከአልጋው ፡ ላይ ፡ ሲነሣ ፡ ይነጫነጫል

**ground**, see **grind**

**ground** (vt.)
1. መሠረተ. The leaders tried to ground the government on democratic principles. መሪዎቹ ፡ መንግሥቱን ፡ በዲሞክራሲ ፡ መምሪያዎች ፡ ላይ ፡ ለመመሥረት ፡ ሞከሩ
2. መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ አስተማረ. He grounded the students in algebra. ተማሪዎቹን ፡ የአልጀብራን ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ አስተማራቸው
*On what do you ground your argument? ምን ፡ ይዘህ ፡ ነው ፡ የምትከራከረው ?

**ground** (vi.) መሬት ፡ ያዘ
The ship grounded in shallow water. መርከቢቱ ፡ ጥልቅ ፡ ባልሆነው ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ መሬት ፡ ያዘች

**be grounded**
1. ተመሠረተ. His arguments are grounded on facts. ክርክሩ ፡ በእውነተኛ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው
2. እንዳይበር ፡ ተከለከለ. The pilot was grounded. አውሮፕላን ፡ ነጂው ፡ እንዳይበር ፡ ተከለከለ
3. አልበረረም. The planes were grounded by thick fog yesterday. ጥቅጥቅ ፡ ካለ ፡ ጉም ፡ የተነሣ ፡ አውሮፕላኖች ፡ ትናንትና ፡ አልበረሩም

**ground** (n.)
1. መሬት. The ground is still wet. መሬቱ ፡ አሁንም ፡ እርጥብ ፡ ነው
How much ground goes with the house? ከቤቱ ፡ ጋር ፡ የሚሸጠው ፡ መሬት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?
The plane hit ground. አውሮፕላኑ ፡ መሬት ፡ ነካች
2. ምድር ፡ ቤት. A fire escape leads to the ground from the roof. ከእሳት ፡ አደጋ ፡ ማምለጫው ፡ ከጣራው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ቤት ፡ ይወርዳል
3. ቦታ. The forest was his favorite hunting ground. ጫካው ፡ በጣም ፡ የሚወደው ፡ የማደኛ ፡ ቦታ ፡ ነበር

**grounds**
1. ግቢ. The house is small, but the grounds are beautiful. ቤቱ ፡ ትንሽ ፡ ነው ፡ ግን ፡ ግቢው ፡ ያምራል
2. አተላ. Throw the coffee grounds into the sink! የቡናውን ፡ አተላ ፡ እቃ ፡ ማጠቢያ ፡ ውስጥ ፡ አፍስሰው
3. ምክንያት. On what grounds are you refusing? እምቢ ፡ የምትለው ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ?
4. በቂ ፡ ምክንያት. That is grounds for divorce. ይህ ፡ ለመፋታት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ነው

**break ground** የሕንጻ ፡ ሥራ ፡ ጀመረ
They will break ground for the factory next week. በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ የፋብሪካውን ፡ ሕንጻ ፡ ሥራ ፡ ይጀምራሉ

**(be on) common ground** ተስማማ
Here we are on common ground. እዚህ ፡ ላይ ፡ እንስማማለን

**cover ground**
1. ተጓዘ. He covers more ground in one day than most people do in two. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ የሚወስድባቸውን ፡ ጉዞ ፡ እሱ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ይጓዛል
2. ጉዳይ ፡ አጠቃለለ ፤ ነገር ፡ አጠቃለለ ፤ ነገር ፡ አቀረበ. He covered a great deal of ground in his lecture. በንግግሩ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጉዳዮችን ፡ አጠቃለለ
The report covers much new ground. ራፖሩ ፡ ብዙ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ያጠቃልላል
He talked for two hours without covering any new ground. ምንም ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሳያቀርብ ፡ ለሁለት ፡ ሰዓት ፡ ተናገረ

**from the ground up** ከሥር ፡ ጀምሮ
He changed everything from the ground up. ከሥር ፡ ጀምሮ ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ለወጠው

**gain ground**
1. ተለመደ. The new teaching method is gaining ground. አዲሱ ፡ የማስተማር ፡ ዘዴ ፡ እየተለመደ ፡ ሄዷል
2. ተቀባይነትን ፡ አገኘ. The case for tax reform is gaining ground throughout the country. ስለ ፡ ታክስ ፡ መሻሻል ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነትን ፡ እያገኘ ፡ ሄዷል

**give ground** አፈገፈገ
The army gave ground before the enemy attack. ጦሩ ፡ ከጠላት ፡ ጥቃት ፡ የተነሣ ፡ አፈገፈገ

**hold one's ground**
1. አልተንቃነቀም. The angry dog rushed at him, but he held his ground. የተቈጣው ፡ ውሻ ፡ ሮጦ ፡ ቢመጣበትም ፡ አልተንቃነቀም
2. ሐሳቡን ፡ አልለወጠም. Despite the arguments that were presented, he held his ground and refused to give in. ምንም ፡ እንኳን ፡ ብዙ ፡ መረጃዎች ፡ ቢቀርቡለት ፡ ሐሳቡን ፡ ሳይለውጥ ፡ አልበገርም ፡ አለ
3. ቦታውን ፡ ሳያስነካ ፡ ቆየ. Our troops held their ground bravely. ወታደሮቻችን ፡ በጀግንነት ፡ ቦታቸውን ፡ ሳያስነኩ ፡ ቆዩ

**(be) leveled to the ground** ወደመ
The village was leveled to the ground. መንደሩ ፡ ወደመ

**lose ground** ባሰ(በት)
The patient is losing ground despite the doctor's care. ሐኪሙ ፡ ቢረዳውም ፡ በሽተኛው ፡ እየባሰበት ፡ ሄደ
*Our candidate is losing ground in industrial areas. ተወዳዳሪያችን ፡ በኢንዱስትሪ ፡ አካባቢ ፡ የሚገኙ ፡ ነዋሪዎችን ፡ ድጋፍ ፡ እያጣ ፡ ሄዷል

**shift (one's) ground** ሐሳቡን ፡ ለወጠ
He shifted his ground whenever it seemed to his advantage to do so. ሁኔታው ፡ የሚጠቅመው ፡ በመሰለው ፡ ቁጥር ፡ ሐሳቡን ፡ ይለውጥ ፡ ነበር
[See also 'breeding, hunting, sink, stand, yield']

## ground floor ምድር ፡ ቤት
Our apartment is on the ground floor. አፓርተማችን ፡ እምድር ፡ ቤት ፡ ነው

## groundless መሠረተ ፡ ቢስ
This is a groundless accusation. ይህ ፡ መሠረተ ፡ ቢስ ፡ ክስ ፡ ነው

## group (vt.) መደበ
Group the men according to age! ሰዎቹን ፡ እንደየዕድሜያቸው ፡ መድባቸው

**group** (vi.) ተሰበሰበ
The people grouped slowly. ሰዎቹ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ተሰበሰቡ

**group oneself around** በ - - - ዙሪያ ፡ ተሰበሰበ
The children grouped themselves around the teacher. ልጆቹ ፡ ባስተማሪው ፡ ዙሪያ ፡ ተሰበሰቡ

## group (n.)
1. ወገን. The Italians are the strongest group in this city. በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ኀይለኞቹ ፡ ወገኖች ፡ ኢጣልያኖች ፡ ናቸው
Wheat and oats belong to the grain group. ስንዴና ፡ አጃ ፡ የእህል ፡ ወገኖች ፡ ናቸው
2. (zero). A group of children were playing ball. ልጆች ፡ ኳስ ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር

**in small groups** ስብስብ ፡ ስብስብ ፡ ብለው
People were standing about in small groups. ሰዎች ፡ ስብስብ ፡ ስብስብ ፡ ብለው ፡ ቆመው ፡ ነበር
[See also 'splinter'].

## grove ጫካ
The guardian spirit of this grove is worshipped by many people. የዚህን ፡ ጫካ ፡ አድባር ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያመልኩታል

**grove of trees** ዕጅብ ፡ ያሉ ፡ ዛፎች
There is a grove of trees around every Ethiopian church. በማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዙሪያ ፡ ዕጅብ ፡ ያሉ ፡ ዛፎች ፡ ይገኛሉ

**grow** (grew, grown), vt.
1. ተከለ. I grow roses. ጽጌረዳ ፡ እተክላለሁ
2. አበቀለ. Barren soil will not grow any wheat. ጭንጫ ፡ መሬት ፡ ምንም ፡ ስንዴ ፡ አያበቅልም
3. ዘራ. In Ethiopia, many farmers grow wheat. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ገበሬዎች ፡ ስንዴ ፡ ይዘራሉ
In Ethiopia, many farmers grow cotton. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ገበሬዎች ፡ ጥጥ ፡ ይዘራሉ
4. አሳደገ. My brother grew a beard. ወንድሜ ፡ ጢሙን ፡ አሳድጓል

**grow** (vi.)
1. አደገ. Your boy has certainly grown a lot. በእርግጥ ፡ ልጅህ ፡ በጣም ፡ አድጓል
This tree grows only in the lowland. ይህ ፡ ዛፍ ፡ በቆላ ፡ ብቻ ፡ ያድጋል
2. በቀለ. Much grain is grown in this region. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ብዙ ፡ እህል ፡ ይበቅላል
There are only a few hairs growing out of his chin. አገጩ ፡ ላይ ፡ ጥቂት ፡ ጸጉሮች ፡ ብቻ ፡ በቅለዋል
3. እየበረከተ ፡ ሄደ. The crowd grew rapidly. ሕዝቡ ፡ ቶሎ ፡ እየበረከተ ፡ ሄደ
4. እየበዛ ፡ ሄደ. The need for raw materials has grown enormously. ለጥሬ ፡ እቃ ፡ ያለው ፡ ፍላጎት ፡ እጅግ ፡ እየበዛ ፡ ሄዷል
5. ተስፋፋ. His business has grown fast. የሱ ፡ ንግድ ፡ በቶሎ ፡ ተስፋፍቷል
6. ገነነ. His fame grew. ዝናው ፡ ገነነ
7. ተጀመረ. Our friendship grew from a common interest in music. ጓደኝነታችን ፡ የተጀመረው ፡ ሁለታችንም ፡ ሙዚቃ ፡ በመውደዳችን ፡ ነው

**grow (into)** ሆነ
It started as something small, but grew into a big difficulty. ነገር ፡ እንደዋዛ ፡ ጀምሮ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ችግር ፡ ሆነ

**grow on one**
*I did not like the country at first, but it gradually grew on me. ሀገሪቷን ፡ በመጀመሪያ ፡ አልወደድኳትም ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየወደድኳት ፡ ሄድኩ

**grow (out) of** ተፈጠረ
Most prejudices grow out of ignorance. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጥላቻ ፡ የሚፈጠረው ፡ ከድንቁርና ፡ የተነሣ ፡ ነው
*His troubles grew out of his carelessness. ችግሩ ፡ የደረሰበት ፡ በግዴለሽነቱ ፡ ነው
*My son has grown out of his clothes. ልጄ ፡ ስላደገ ፡ ልብሶቹ ፡ አንሰውታል

**grow together** ተጋጠመ
The branches of this tree grew together. የዚህ ፡ ዛፍ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ተጋጥመዋል

**grow up**
1. አደገ. The children are growing up fast. ልጆቹ ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ያድጋሉ
2. ተሠራ. New cities grew up in the desert. በበረሃው ፡ ውስጥ ፡ አዳዲስ ፡ ከተማዎች ፡ ተሠሩ

**let grow** አሳደገ
She decided to let her hair grow. ጸጉሯን ፡ ለማሳደግ ፡ ወሰነች
[See also 'rampant']

**growl** (v.) አጕረመረመ
The dog growled when he heard the noise. ውሻው ፡ ድምፅ ፡ ሲሰማ ፡ አጕረመረመ
The students growled about the poor food. ተማሪዎቹ ፡ በምግቡ ፡ መጥፎነት ፡ አጕረመረሙ

**growl** (n.) ማጕረምረም
The growl of the dog frightened the child. የውሻው ፡ ማጕረምረም ፡ ልጁን ፡ አስደነገጠው

**grown** አካለ ፡ መጠን ፡ የደረሰ
A grown man is allowed to bear arms. አካለ ፡ መጠን ፡ የደረሰ ፡ ሰው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እንዲይዝ ፡ ይፈቀድለታል

**grown-up** (n.) ዐዋቂ
Children should keep quiet when grown-ups are talking. ዐዋቂ ፡ ሲያወራ ፡ ልጅ ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ አለበት

**grown-up** (adj.)
1. የደረሰ. She has a grown-up daughter. የደረሰች ፡ ልጅ ፡ አለቻት
2. (የ)ዐዋቂ ፡ ሰው. He has grown-up manners. ሁኔታው ፡ እንደ ፡ ዐዋቂ ፡ ሰው ፡ ነው

**be grown-up** ነፍስ ፡ ዐወቀ
Their children are already grown-up. ልጆቻቸው ፡ ነፍስ ፡ ያወቁ ፡ ናቸው

**growth**
1. እብጠት. The growth on his shoulder turned out to be malignant, so it was removed. በትከሻው ፡ ላይ ፡ ያደረበት ፡ እብጠት ፡ አደገኛ ፡ ስለሆነ ፡ በቀዶ ፡ ጥገና ፡ አስወጣው
2. እድገት. Sunshine hastens the growth of plants. የፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ የዕፀዋትን ፡ እድገት ፡ ያፋጥናል
*This plant has had a slow growth. ይህ ፡ ዛፍ ፡ ያደገው ፡ ዝግ ፡ ብሎ ፡ ነው
*Childhood is a period of rapid growth. ልጅነት ፡ ቶሎ ፡ የሚታደግበት ፡ ወቅት ፡ ነው

*There has been a large growth in population this past year. በዚህ ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ የሕዝብ ፡ ቁጥር ፡ በጣም ፡ ጨመረ

**arrest the growth of** አቀጨጨ
Poor food arrests the growth of the children. መጥፎ ፡ ምግብ ፡ ልጆችን ፡ ያቀጨጫል

**full growth** አካለ ፡ መጠን
He can marry now because he has reached his full growth. አሁን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ የደረሰ ፡ ስለሆነ ፡ ሊያገባ ፡ ይችላል

**thick growth of** ችፍግ ፡ ያለ
A thick growth of bushes covered the ground. ችፍግ ፡ ያለው ፡ ቁጥቋጦ ፡ መሬቱን ፡ ሸፍኖታል
[See also 'constrain, retard']

**grub** (grubbed) ቈፈረ
Pigs grub in the forest for food. አሳማዎች ፡ ምግብ ፡ ፍለጋ ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ ይቈፍራሉ

**grudge** (v.)
1. ቀና(በት). I do not grudge him his success. ሥራው ፡ ቢሳካለት ፡ አልቀናበትም
2. ቅር ፡ እያለው ፡ ጣለ(ለት). The evil man grudged his horse the food that it ate. ክፉው ፡ ሰው ፡ ቅር ፡ እያለው ፡ ለፈረሱ ፡ የሚበላውን ፡ ምግብ ፡ ጣለለት
3. ቅር ፡ አለ(ው). She grudged him even the small pleasure of a night out with his friends. ከጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ስላመሸ ፡ ቅር ፡ አላት

**grudge** (n.) ቂም
The grudge is a result of a dispute over land. ቂሙ ፡ በመሬት ፡ ክርክር ፡ የተነሣ ፡ ነው

**bear (have, hold) a grudge** ቂም ፡ ያዘ(በት)
He has a grudge against me because I voted against his plan. እቅዱን ፡ ተቃውሚ ፡ ድምፅ ፡ ስለሰጠሁ ፡ ቂም ፡ ይዞብኛል

**grudgingly** እያጕረመረመ
He gave in grudgingly. እያጕረመረመ ፡ ተቀበለው

**grueling** በጣም ፡ አድካሚ
The grueling contest left him exhausted. በጣም ፡ አድካሚ ፡ የሆነው ፡ ትግል ፡ ሰውነቱን ፡ አደቀቀው

**gruesome** አሰቃቂ
The Italians carried out a gruesome slaughter on February 12. ኢጣልያኖች ፡ የካቲት ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ አሰቃቂ ፡ እልቂት ፡ ፈጸሙ

**gruff** ጐርናና
He spoke in a gruff voice. በጐርናና ፡ ድምፅ ፡ ተናገረ

**have a gruff manner** ጠባዩ ፡ ቊጡ ፡ ነው
He has a good heart, but a gruff manner. ልቡ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ ጠባዩ ፡ ግን ፡ ቊጡ ፡ ነው

**grumble** አጕረመረመ
He grumbles each time he is asked to help. እርዳታ ፡ በተጠየቀ ፡ ቁጥር ፡ ያጕረመርማል
The thunder grumbled in the west. ነጐድጓድ ፡ ከበስተ ፡ ምዕራብ ፡ አጕረመረመ

**grumbling** ማማረር
His needless grumbling annoys people. ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ማማረሩ ፡ ሰው ፡ ያበሳጫል

**grunt** አጕረመረመ
He merely grunted when I asked him to come. እንዲመጣ ፡ ስጠይቀው ፡ አጕረመረመ

**guarantee** (v.)
1. ቃል ፡ ገባ. I guarantee to prove every statement I make. የተናገርኩትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ቃል ፡ እገባለሁ
He will guarantee us possession of the house by May. ቤቱን ፡ በግንቦት ፡ መጨረሻ ፡ ለኛ ፡ ሊያዛውርልን ፡ ቃል ፡ ገብቶልናል
2. ዋስትና ፡ ሰጠ. This company guarantees its clocks for a year. ይህ ፡ ኩባንያ ፡ ለሚሸጣቸው ፡ ሰዓቶች ፡ ሁሉ ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ ዋስትና ፡ ይሰጣል
3. ዋስትና ፡ አለው. Affluence does not guarantee happiness. ሀብት ፡ ደስታን ፡ ለማስገኘት ፡ ዋስትና ፡ የለውም
4. እርግጠኛ ፡ ነው. I guarantee that you will like that movie. ያንን ፡ ሲኒማ ፡ እንደምትወደው ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ

**be guaranteed** ተጠበቀ
Civil liberties are guaranteed by the constitution. ሕዝባዊ ፡ መብቶች ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው

**guarantee** (n.) ዋስትና
What guarantee do I have that he will pay? እሱ ፡ እንደሚከፍል ፡ ምን ፡ ዋስትና ፡ አለኝ ?
You get a five-year guarantee on the watch. ለሰዓት ፡ ያምስት ፡ ዓመት ፡ ዋስትና ፡ ይሰጥሃል
Wealth is no guarantee of happiness. ብልጽግና ፡ ለደስታ ፡ ዋስትና ፡ አይደለም

**guarantor**
1. ዋስ. Will you be a guarantor for Yohannes' loan? የሐንስ ፡ ገንዘብ ፡ ሲበደር ፡ ዋስ ፡ ትሆነዋለህ ?
2. ተያዥ. When I hired the servant, I asked him the name of his guarantor. አሽከር ፡ ስቀጥር ፡ የተያዠውን ፡ ስም ፡ ጠየቅሁት

**guard** (v.)

1. ጠበቀ. Two soldiers guarded the prisoners. ሁለት ፡ ወታደሮች ፡ እስረኞቹን ፡ ጠበቁ
2. ተጠንቀቀ. Lock the door to guard against thieves! ከሌባ ፡ ለመጠንቀቅ ፡ መዝጊያውን ፡ ቆልፍ

**guard against** ተከላከለ(ለት)
These pills are to guard you against malaria. እነዚህ ፡ ኪኒኖች ፡ ወባ ፡ ይከላከሉልሃል

**guard** (n.)

1. ዘብ. I will stand guard. እኔ ፡ ዘብ ፡ እቆማለሁ
2. ዘበኛ. The guard did not let me pass. ዘበኛው ፡ አላሳልፍ ፡ አለኝ
3. መከላከያ. Vaccination is our best guard against smallpox. ክትባት ፡ ዋና ፡ የፈንጣጣ ፡ መከላከያችን ፡ ነው

**guard duty** የዘብ ፡ ጥበቃ
He detailed two men for guard duty. ለዘብ ፡ ጥበቃ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ መደበ

**keep guard (over)** ጠበቀ
The parents kept guard over the small child. ወላጆቹ ፡ ትንሹን ፡ ልጅ ፡ ጠበቁት

**off guard** ሳያስበው
The teacher caught the student off guard with a question. አስተማሪው ፡ ተማሪውን ፡ ሳያስበው ፡ በጥያቄ ፡ አጣደፈው

**(be) on one's guard** ተጠንቀቀ
You have to be on your guard with her. ከሷ ፡ ጋር ፡ ስትሆን ፡ መጠንቀቅ ፡ አለብህ

**stand guard over** ተከላከለ
The dog stood guard over his wounded master. ውሻው ፡ ለቈሰለው ፡ ጌታው ፡ ተከላከለ
[See also 'honor']

**guarded** (adj.)

1. የተጠበቀ. The heavily guarded fort was not taken. በጥንቃቄ ፡ የተጠበቀው ፡ ምሽግ ፡ አልተወሰደም
2. በጥንቃቄ ፡ የሚሰጥ. "Maybe" is a guarded answer to a question. ምናልባት ፡ ማለት ፡ በጥንቃቄ ፡ የሚሰጥ ፡ መልስ ፡ ነው

**guardian**

1. ጠባቂ. The constitution is the guardian of our liberties. ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የመብታችን ፡ ጠባቂ ፡ ነው
2. ሞግዚት ፤ ያደራ ፡ አባት. The judge made my uncle my guardian until I am 18. ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ እስኪሆነኝ ፡ ዳኛው ፡ አጐቴን ፡ ሞግዚቴ ፡ (ያደራ ፡ አባቴ) ፡ አደረገው

**guardian angel** ታዳጊ ፡ መልአክ
Michael is a guardian angel. ሚካኤል ፡ ታዳጊ ፡ መልአክ ፡ ነው

**guardian spirit**

1. አድባር. The guardian spirit of this grove is worshipped by many people. የዚህን ፡ ጫካ ፡ አድባር ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያመልኩበታል
2. ውቃቢ ፡ አምላክ. He feels that he has a guardian spirit who brings him luck. ዕድሉን ፡ የሚያሳካለት ፡ ውቃቢ ፡ አምላክ ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ያምናል

**guerrilla** የደፈጣ ፡ ተዋጊ
The war in Vietnam is carried out by guerrillas. የቬየትናም ፡ ጦርነት ፡ የሚካሄደው ፡ በደፈጣ ፡ ተዋጊዎች ፡ ነው

**guess** (v.)

1. በመላ ፡ ዐወቀ. That is not hard to guess. ይህን ፡ በመላ ፡ ማወቅ ፡ አያስቸግርም
2. ገመተ. Can you guess my weight? ሚዛኔን ፡ ልትገምት ፡ ትችላለህ ?
3. ፈታ. He guessed the riddle. እንቆቅልሹን ፡ ፈታ
4. ዐወቀ. Guess what happened to me! ምን ፡ እንደደረሰብኝ ፡ ታውቃለህ ?
5. መሰለ(ው). I guess he is sick. ያመመው ፡ ይመስለኛል
I guess we should hurry. ፈጠን ፡ ማለት ፡ ያስፈልገናል ፡ መሰለኝ

**guess the answer to** ፈታ
Guess the answer to this riddle! ይህን ፡ እንቆቅልሽ ፡ ፍታ

**guess** (n.) ግምት
His guess is that the war will end in a year. በሱ ፡ ግምት ፡ ጦርነቱ ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ያበቃል

**make a guess** መላ ፡ መታ
Make a guess if you don't know exactly. ማወቅ ፡ ካቃተህ ፡ መላ ፡ ምታ

**only a guess**
It is only a guess. እንዲሁ ፡ በመላ ፡ ነው
[See also 'wild']

**guest** እንግዳ
He will be His Majesty's guest while he is in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ በሚቆይበት ፡ ጊዜ ፡ የግርማዊነታቸው ፡ እንግዳ ፡ ይሆናል
[See also 'wedding']

**guidance**

1. መሪነት. The country developed under his guidance. አገሪቱ ፡ በሱ ፡ መሪነት ፡ በለጸገች

2. አመራር. His guidance of foreign policy proved disastrous. የውጭ ፡ አገር ፡ ፖሊሲ ፡ አመራሩ ፡ አጥፊ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

**guide** (v.)
1. መራ. Can you guide us there? ወደዚያ ፡ ልትመራን ፡ ትችላለህ ?
2. አስጐበኘ. She guided a company of tourists. አንድ ፡ ያገር ፡ ጐብኚዎች ፡ ጓድ ፡ አስጐበኘች
3. መምሪያ ፡ ሆነ. The book guided us in the repair of the car. መጽሐፉ ፡ መኪናውን ፡ ለመጠገን ፡ መምሪያ ፡ ሆነን

**guide** (n.)
1. መንገድ ፡ መሪ. The guide told us to boil our water before drinking it. መንገድ ፡ መሪው ፡ ከመጠጣታችን ፡ በፊት ፡ ውኃ ፡ እንድናፈላ ፡ ነገረን
We took a guide. መንገድ ፡ መሪ ፡ ቀጠርን
2. መምሪያ. All the theaters are listed in the guide. ያሉት ፡ የቲያትር ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ በመምሪያው ፡ ውስጥ ፡ ተዘርዝረዋል
3. መመዘኛ. External appearances are often a poor guide to character. መልክ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለጠባይ ፡ የተሳሳተ ፡ መመዘኛ ፡ ነው

**guidebook** መግለጫ ፡ መጽሐፍ
The Ministry of Information published a guidebook of Ethiopia. የማስታወቂያ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መግለጫ ፡ መጽሐፍ ፡ አወጣ

**guideline** መምሪያ
We must have guidelines to keep from losing sight of the goal of our policy. ዓላማችን ፡ ግቡን ፡ እንዳይስት ፡ ለማድረግ ፡ መምሪያ ፡ እንዲኖረን ፡ ይገባል

**guild** ማኅበር
The porters formed a guild. ተሸካሚዎች ፡ ማኅበር ፡ አቋቋሙ

**guile** ብልሃት ፤ ተንኰል
By guile, the fox got the cheese from the crow. በብልሃት ፡ ቀበሮው ፡ ከቁራው ፡ አይብ ፡ ወሰደበት
A swindler uses guile; a robber uses force. አታላይ ፡ በተንኰል ፤ ቀማኛ ፡ ግን ፡ በኀይል ፡ ይጠቀማል

**guilt** ጥፋተኛነት
The guilt of the accused is in doubt. የተከሳሹ ፡ ጥፋተኛነት ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው

**guilty** ጥፋተኛ
The police arrested many suspects, but failed to find the guilty person. ፖሊሶች ፡ ብዙ ፡ የተጠረጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ያዙ ፤ ጥፋተኛውን ፡ ግን ፡ ሊያገኙ ፡ አልቻሉም

**find guilty** ፈረደ(በት)
The judge found the prisoner guilty. ዳኛው ፡ እስረኛውን ፡ ፈረደበት

**(be) found guilty** ተፈረደ(በት) ፤ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ
He was found guilty of espionage. በስላይነት ፡ ተፈረደበት
He was tried and found guilty. ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

**have a guilty conscience** የኅሊና ፡ ጸጸት ፡ አደረ(በት)
The one who committed the crime had a guilty conscience. ወንጀሉን ፡ የፈጸመው ፡ የኅሊና ፡ ጸጸት ፡ አደረበት
[See also 'plead']

**guinea fowl** ጅግራ
Guinea fowl are good to eat. ጅግራዎች ፡ ለመብል ፡ ጥሩ ፡ ናቸው

**guinea pig** [ደርፌጭ ፡ ያለች ፡ ትንሽ ፡ የአይጥ ፡ ዓይነት]

**guise**
1. ሌላ ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ መታየት. His guise was not easily penetrated. ሌላ ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ መታየቱ ፡ በቀላሉ ፡ አልታወቀበትም
2. መልክ. His theory was nothing but an old idea in a new guise. ፅንሰ ፡ ሐሳቡ ፡ የቆየ ፡ ሐሳብን ፡ ባዲስ ፡ መልክ ፡ ከማቅረብ ፡ የተለየ ፡ አልነበረም

**in the guise of** መስሎ
He traveled through Ethiopia in the guise of a monk. መነኵሴ ፡ መስሎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ተዘዋወረ

**under the guise of** መስሎ
Under the guise of friendship, he plotted treachery. ወዳጅ ፡ መስሎ ፡ ክሕደትን ፡ አሰበ

**guitar** [ስድስት ፡ ሽቦ ፡ ወይም ፡ ጅማት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ክራር ፡ ያለ ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ]

**gulf** የባሕር ፡ ሰላጤ
The Persian Gulf separates Arabia from Persia. የፋርስ ፡ የባሕር ፡ ሰላጤ ፡ ዓረብን ፡ ከፋርስ ፡ ይለያል

**leave a gulf between** አለያየ
The quarrel left a gulf between the old friends. ጠቡ ፡ የቆዩትን ፡ ወዳጆች ፡ አለያያቸው

**gull** የባሕር ፡ ጭላት
The gulls are flying over the waves. የባሕር ፡ ጭላቶች ፡ ከሞገዱ ፡ በላይ ፡ ይበራሉ

**gullible** ድልል
He is so gullible that he believes every word. በጣም ፡ ድልል ፡ ስለሆነ ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ ያምናል

**gully** ቦይ
The heavy rain made several gullies in the road. ከባዱ ፡ ዝናም ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ቦይ ፡ ቦረቦረ

**gulp** (v.) ጠጣ
The horse gulped the water. ፈረሱ ፡ ውኃውን ፡ ጠጣ

**gulp down**
1. ጭልጥ ፡ አድርጎ ፡ ጠጣ. He gulped down a cup of cold milk.. አንድ ፡ ሲኒ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ወተት ፡ ጭልጥ ፡ አድርጎ ፡ ጠጣ
2. ዋጥ ፡ አደረገ. The unhappy boy gulped down a sob. የከፋው ፡ ልጅ ፡ መንሰቅሰቁን ፡ ዋጥ ፡ አደረገ

**gulp** (n.), **in one ~** ባንድ ፡ ትንፋሽ
He emptied a glass of milk in one gulp. አንዱን ፡ ብርጭቆ ፡ ወተት ፡ ባንድ ፡ ትንፋሽ ፡ ጨለጠው

**take a gulp** ተጐነጨ
He took a gulp of tea and spat it out. ሻዩን ፡ ተጐንጭቶ ፡ ተፋው

**gum**
1. ማጣበቂያ. This stamp has no gum on it. ይህ ፡ ቴምብር ፡ ማጣበቂያ ፡ የለውም
2. ድድ. My gums are sore. ድዴ ፡ ቈስሏል
3. መስቲካ. The boy likes to chew gum. ልጁ ፡ መስቲካ ፡ ማኘክ ፡ ይወዳል

**gumption** የሚገፋፋ ፡ ኀይል
He hasn't the gumption to find a job. ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ የሚገፋፋ ፡ ኀይል ፡ የለውም

**gum tree** የሙጫ ፡ ዛፍ
Are there gum trees in Ethiopia? በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሙጫ ፡ ዛፍ ፡ አለ ?

**gun** (gunned), v. አስነሣ
He gunned the motor and roared away. ሞተሩን ፡ አስነሥቶ ፡ ተፈተለከ

**gun down** ረሸነ
He gunned the soldiers down as they came out of the house. ወታደሮቹ ፡ ከቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ሲወጡ ፡ ረሸናቸው

**gun** (n.)
1. ሽጉጥ. He pulled a gun on me. ሽጉጥ ፡ መዘዘብኝ
2. ጠመንጃ. He went hunting with a gun. ጠመንጃ ፡ ይዞ ፡ አደን ፡ ሄደ
3. መድፍ. They mounted a gun on the fortress wall. በትልቁ ፡ ምሽግ ፡ ግምብ ፡ ላይ ፡ መድፍ ፡ ጠመዱ

**stick to one's guns** አልበገርም ፡ አለ
There was enormous pressure on them to submit, but they stuck to their guns. ሐሳባቸውን ፡ እንዲለውጡ ፡ ገፋፍተዋቸው ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንበገርም ፡ አሉ

**gunfire** የጠመንጃ ፡ ተኩስ
When the soldiers heard gunfire, they took cover. ወታደሮቹ ፡ የጠመንጃ ፡ ተኩስ ፡ ሲሰሙ ፡ ጥግ ፡ ያዙ

**gunman** ባለመሣሪያ ፡ ወንበዴ
An unknown gunman killed the President. አንድ ፡ ያልታወቀ ፡ ባለመሣሪያ ፡ ወንበዴ ፡ ፕሬዚዳንቱን ፡ ገደለው

**gunner** መድፈኛ
The gunners fired the cannon at the enemy. መድፈኞቹ ፡ በጠላት ፡ ላይ ፡ ተኰሱ

**gunpowder** ባሩድ
The gunpowder is damp and won't ignite. ባሩዱ ፡ ስለረጠበ ፡ አይፈነዳም

**gunshot** የተኩስ ፡ ድምፅ
We heard gunshots. የተኩስ ፡ ድምፅ ፡ ሰማን

**gurgle** (v.)
1. ሣቅ ፡ ሣቅ ፡ አለ. The baby gurgled happily. ሕፃኑ ፡ በደስታ ፡ ሣቅ ፡ ሣቅ ፡ አለ
2. ተንዶቆዶቀ. Water gurgles when it is poured out of bottles. ውኃ ፡ ከጠርሙስ ፡ ሲገለበጥ ፡ ይንዶቆዶቃል

**gurgle** (n.) ማንቦጭቦጭ
I could tell by the gurgle that there was some water in the canteen. በኰዳው ፡ ውስጥ ፡ ውኃ ፡ እንዳለ ፡ በማንቦጭቦጭ ፡ ላውቅ ፡ ቻልኩ

**gush** (v.)
1. ፈለቀ. Oil gushed from the ground. ዘይት ፡ ከመሬት ፡ ፈለቀ
2. ጐረፈ. Tears gushed from her eyes. እንባ ፡ ከዓይኖቿ ፡ ጐረፈ

**gush out** ፈለቀ
Water gushed out of the side of the mountain. ውኃ ፡ ከተራራው ፡ ጐን ፡ ፈለቀ

**gush** (n.)
*If you get a deep cut, there usually is a gush of blood. ሥጋህ ፡ በጣም ፡ ሲቈረጥ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ይፈሳል

**gust** ኀይለኛ ፡ ነፋስ
A gust blew his hat off. ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ባርኔጣውን ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ ወሰደው

**in gusts** በኀይል
The wind was blowing in gusts. ነፋሱ ፡ በኀይል ፡ ይነፍስ ፡ ነበር

**gusty** በጣም ፡ ነፋሻ
It was a gusty day, so we held onto our hats. በጣም ፡ ነፋሻ ፡ ቀን ፡ ስለነበረ ፡ ባርኔጣችንን ፡ በእጃችን ፡ ያዝን

**gut** (v.) የሆድ ፡ እቃ ፡ አወጣ
You must gut the fish before you cook it. ዓሣውን ፡ ከመጥበስህ ፡ በፊት ፡ የሆድ ፡ እቃውን ፡ ማውጣት ፡ አለብህ

**gut** (n.) አንጀት
He cut the gut of the ox into strips. የበሬውን ፡ አንጀት ፡ ዘለዘለ

**guts** የሆድ ፡ እቃ
The guts of fish were on the floor. የዓሣው ፡ የሆድ ፡ እቃ ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ነበር

**gutter**
1. አሸንዳ. The gutter is leaking along the eaves. እቤቱ ፡ ከፈፍ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አሸንዳ ፡ ያፈሳል
2. ቦይ. He stumbled and fell in the gutter. አደናቅፎት ፡ እቦዩ ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ

**guttural** የጉሮሮ
Tigrinya has guttural sounds. ትግርኛ ፡ የጉሮሮ ፡ ድምፅ ፡ አለው

**guy** ሰው ፤ ልጅ
He is a nice guy. ጥሩ ፡ ሰው ፡ (ልጅ) ፡ ነው

**gym**
1. የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ. We have gym class three times a week. በሳምንት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ትምህርት ፡ እንማራለን
2. የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ክፍል ፤ የስፖርት ፡ አዳራሽ. Our school has a large gym. ተማሪ ፡ ቤታችን ፡ ትልቅ ፡ የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ክፍል ፡ (የስፖርት ፡ አዳራሽ) ፡ አለው

**gymnasium** የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ክፍል ፤ የስፖርት ፡ አዳራሽ
The gymnasium was built beside the swimming pool. የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ክፍል ፡ (የስፖርት ፡ አዳራሽ) ፡ የተሠራው ፡ ከመዋኛው ፡ ስፍራ ፡ አጠገብ ፡ ነበር

**gynecologist** የማሕፀን ፡ ሐኪም

## H

**habit** ልምድ ፤ ልማድ
Don't let yourself get into bad habits! መጥፎ ፡ ልምድ ፡ እንዲይዝህ ፡ አታድርግ
An ingrained habit is not soon forgotten. ሥር ፡ የሰደደ ፡ ልማድ ፡ ቶሎ ፡ አይረሳም

**habit-forming** ሱስ ፡ የሚያስይዝ
Habit-forming drugs demoralize people's characters. ሱስ ፡ የሚያስይዙ ፡ መድኀኒቶች ፡ የሰዎችን ፡ ጠባይ ፡ ያበላሻሉ

**adopt habits** ለመደ
He has adopted occidental food habits. የምዕራባውያንን ፡ ምግብ ፡ ለምዷል

**be in the habit of** ለመደ(በት)
I am in the habit of sleeping late. ተኝቶ ፡ ማርፈድ ፡ ለምዶብኛል

**get into the habit** ለመደ
I got into the habit of smoking at college. ማጨስ ፡ የለመድኩት ፡ ኮሌጅ ፡ ነው
[See also 'force, kick, miserly']

**habitable** ለመኖሪያ ፡ የሚሆን
There are no habitable houses in this neighborhood. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ለመኖሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ቤቶች ፡ የሉም

**habitat** መኖሪያ
The ocean is the habitat of the whale. ውቅያኖስ ፡ የዓሣ ፡ ነባሪ ፡ መኖሪያ ፡ ነው

**habitation** መኖሪያ
These houses are not fit for habitation. እነዚህ ፡ ቤቶች ፡ ለመኖሪያ ፡ ተስማሚ ፡ አይደሉም

**habitual**
1. የለመደበት. He is a habitual criminal. የለመደበት ፡ ወንጀለኛ ፡ ነው
2. የተለመደ. He took his habitual seat at the table. ገበታ ፡ ላይ ፡ እተለመደው ፡ ስፍራ ፡ ተቀመጠ
3. ልማድ ፡ ያለው. A habitual reader reads a great deal. የማንበብ ፡ ልማድ ፡ ያለው ፡ ብዙ ፡ ያነባል
4. (= adv.) በተለምዶ. His habitual kindness led him to be considered a saint. በተለምዶ ፡ የሚያደርገው ፡ ደግነት ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ አስቈጠረው

**habituate (to)** እንዲለምድ ፡ አደረገ
Wealth habituated him to luxury. ብልጽግና ፡ ድሎትን ፡ እንዲለምድ ፡ አደረገው

**be habituated** ለመደ
Truck drivers are habituated to hard work. የከባድ ፡ መኪና ፡ ሾፌሮች ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ለምደዋል

**hack** ተረከከ
He hacked the box apart with a dull ax. በደነዘ ፡ መጥረቢያ ፡ ሣጥኑን ፡ ተረከከው

**hack into chunks** ቈራረሰ
He hacked the loaf of bread into chunks. ዳቦውን ፡ ቈራረሰው

**had** ነበረ(ው)
He had a big house. ትልቅ ፡ ቤት ፡ ነበረው

**be had** ተታለለ
I have been had. ተታለልኩ

**haft**
1. እጀታ. The haft of the spear is broken. የጦሩ ፡ እጀታ ፡ ተሰብሯል
2. ዛቢያ. The haft of the ax is broken. የመጥረቢያው ፡ ዛቢያ ፡ ተሰብሯል

**hag** አስቀያሚ ፡ አሮጊት
The hag looked at him with suspicion. አስቀያሚዋ ፡ አሮጊት ፡ በጥርጣሬ ፡ ዓይን ፡ ተመለከተችው

**haggard, ~ appearance** ደከምከም ፡ ብሎ ፡ መታየት
His haggard appearance shows he has been working too hard. ደከምከም ፡ ብሎ ፡ መታየቱ ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንደነበር ፡ ያመለክታል

**haggle** ተከራከረ
They haggled over the price of the basket. በቅርጫቱ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ተከራከሩ

**haggling** ውጣ ፡ ውረድ
The price is $200 without haggling. ውጣ ፡ ውረድ ፡ የሌለበት ፡ ዋጋው ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ነው

**hail** (v.)
1. በረዶ ፡ ጣለ. It's hailing, so shut the window. በረዶ ፡ ይጥላልና ፡ መስኮቱን ፡ ዝጋ

2. ጠራ. The doorman hailed a passing cab. በረኛው ፡ አላፊውን ፡ ታክሲ ፡ ጠራ
3. አወረደ(በት). The angry crowd hailed blows on the thief. የተናደደው ፡ ሕዝብ ፡ በሌባው ፡ ላይ ፡ የዱላ ፡ መዓት ፡ አወረደበት
4. አመሰገነ. They hailed the recent advances in medicine. በመድኀኒት ፡ በኩል ፡ የተደረገውን ፡ የጊዜውን ፡ ዕውቀት ፡ አመሰገኑ
5. በጭብጨባ ፡ ተቀበለ. Crowds hail him everywhere. በየሄደበት ፡ ሕዝብ ፡ በጭብጨባ ፡ ይቀበለዋል
6. በማመስገን ፡ ተቀበለ. They hailed him as leader. እንዳለቃ ፡ በማመስገን ፡ ተቀበሉት

**hail from**
1. መጣ. Where does that ship hail from? ያ ፡ መርከብ ፡ የሚመጣው ፡ ከየት ፡ ነው ?
2. የ - - - ሰው ፡ ነው. His parents hail from California. ቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ የካሊፎርኒያ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው

**be hailed** ተባለ
It was hailed by the critics as the best movie of the year. በተቺዎቹ ፡ ያመቱ ፡ ታላቅ ፡ ፊልም ፡ ነው ፡ ተባለ

**hail** (n.)
1. በረዶ. That is not rain; that is hail. ይህ ፡ ዝናብ ፡ አይደለም ፤ በረዶ ፡ ነው
2. ውሽንፍር. A hail of bullets met the soldiers. የጥይት ፡ ውሽንፍር ፡ ወታደሮቹ ፡ ላይ ፡ ወረደባቸው
*Hail to the king! ንጉሡ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኑር

**hair** ጸጉር
I am going to have my hair cut. ጸጉሬን ፡ ልስተካከል ፡ ነው

**by a hair** ለጥቂት
The stone missed me by a hair. ድንጋዩ ፡ ለጥቂት ፡ ሳተኝ

**make one's hair stand on end** ፍርሃት ፡ አሳደረበት
The tales of the jungle made our hair stand on end. ስለ ፡ ጫካው ፡ የተነገረን ፡ ተረት ፡ ፍርሃት ፡ አሳደረብን

**tear one's hair** ከመጠን ፡ በላይ ፡ ተናደደ
He is tearing his hair over the way he was treated by them. እነሱ ፡ ባደረጉበት ፡ ነገር ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ተናዷል
[See also 'cut, gray, lose, split, white']

**hairbrush** የጸጉር ፡ ብሩሽ
I have a hairbrush whose handle is made of ivory. እጀታው ፡ ከዝሆን ፡ ጥርስ ፡ የተሠራ ፡ የጸጉር ፡ ብሩሽ ፡ አለኝ

**haircut** ጸጉር ፡ መቈረጥ
I have to get a haircut. ጸጉሬን ፡ መቈረጥ ፡ አለብኝ

**hairdo** የጸጉር ፡ አሠራር
What kind of hairdo does your wife prefer? ሚስትህ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ የጸጉር ፡ አሠራር ፡ ትመርጣለች ?

**hairdresser** ጸጉር ፡ አስተካካይ
The hairdresser is an Italian. ጸጉር ፡ አስተካካዩ ፡ ኢጣልያን ፡ ነው

**hairy** ጸጉራም
A hairy animal resembling a baboon was seen in the garden. ዝንጀሮ ፡ የሚመስል ፡ ጸጉራም ፡ እንስሳ ፡ ባትክልት ፡ ስፍራው ፡ ውስጥ ፡ ታየ

**hale** (v.) በግዴታ ፡ ወሰደ
The policeman haled the man into court. ፖሊሱ ፡ ሰውዬውን ፡ በግዴታ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወሰደው

**hale** (adj.) ጠንካራ
Grandfather is still hale. ወንድ ፡ አያታችን ፡ አሁንም ፡ ጠንካራ ፡ ነው

**hale and hearty** ጠንካራ
The old man is still hale and hearty. ሽማግሌው ፡ አሁንም ፡ ጠንካራ ፡ ነው

**half** (halves)
1. ግማሽ. Give me half a pound of butter! ግማሽ ፡ ፓውንድ ፡ ቅቤ ፡ ስጠኝ
This job is only half done. ይህ ፡ ሥራ ፡ ግማሹ ፡ ብቻ ፡ ተሠርቷል
I got it for half price at a sale. በማጣሪያ ፡ ሽያጭ ፡ ጊዜ ፡ በግማሽ ፡ ዋጋ ፡ ገዛሁት
2. እኩል ፤ ግማሽ. I will be back in half an hour. በኩል ፡ (በግማሽ) ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ እመለሳለሁ
It is half past nine. ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ነው
3. ገሚስ. I have achieved only half of what I hoped to do. ልሠራ ፡ ከምመኘው ፡ ገሚሱን ፡ ብቻ ፡ ሠርቻለሁ

**half bad**
That is not half bad. አይከፋም

**(be) half-cooked** በደምብ ፡ አልበሰለም
This meat is only half-cooked. ይህ ፡ ሥጋ ፡ በደምብ ፡ አልበሰለም

**(be) half-dead** ሙትት ፡ አለ
The beggar was half-dead from hunger. ለማኙ ፡ በረኀብ ፡ ሙትት ፡ ብሎ ፡ ነበር

**half-finished, leave ~** በግማሹ ፡ ወዘፈ
He left the task half-finished. ሥራውን ፡ በግማሹ ፡ ወዘፈ

**half-measure** በገሚስ ፡ የተወሰደ ፡ እርምጃ
Half-measures will not solve the problem. በገሚስ ፡ የተወሰዱ ፡ እርምጃዎች ፡ ለችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ አያስገኙም

**half (a) year** መንፈቅ
The course will be finished in half a year. ትምህርቱ ፡ በመንፈቅ ፡ ውስጥ ፡ ያልቃል

**cut in half** እሁለት ፡ ከፈለ
Shall I cut the orange in half? ብርቱካኑን ፡ እሁለት ፡ ልከፍለው ?

**with half an ear** በግማሽ ፡ ልብ
I have been listening with half an ear. በግማሽ ፡ ልቤ ፡ እሰማ ፡ ነበር
[See also 'cut, dead']

## half-breed ክልስ
He is a half-breed; his mother was Chinese, his father Kenyan. እርሱ ፡ ክልስ ፡ ነው ፤ እናቱ ፡ ቻይናዊት ፡ አባቱ ፡ ኬንያዊ ፡ ናቸው

## half brother የእናት ፡ ልጅ ፤ ያባት ፡ ልጅ
My half brother left for America. የእናቴ ፡ ልጅ ፡ (ያባቴ ፡ ልጅ) ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ ሄደ

## half-caste ክልስ
Can a half-caste have dual citizenship? ክልስ ፡ የሁለት ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ?

## half-hearted ከልብ ፡ ያልሆነ
He made a half-hearted attempt to leave the country. ከሀገሪቷ ፡ ለመውጣት ፡ ከልብ ፡ ያልሆነ ፡ ሙከራ ፡ አደረገ

## half-heartedly
1. በግማሽ ፡ ልብ. He does whatever I tell him to, but only half-heartedly. በግማሽ ፡ ልብ ፡ ቢሆንም ፡ የምነግረውን ፡ ሁሉ ፡ ይፈጽማል
2. ያለ ፡ ፍላጎት. He does his economics assignment half-heartedly because he does not really like the subject. የሀብት ፡ ምጣኔ ፡ ትምህርት ፡ ስለማይወድ ፡ ሥራውን ፡ ያለ ፡ ፍላጎቱ ፡ ይሠራል

## half hour ግማሽ ፡ ሰዓት
I waited for him a good half hour. ግማሽ ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ጠበቅሁት

## half sister የናት ፡ ልጅ ፤ ያባት ፡ ልጅ
My half sister will marry soon. የናቴ ፡ ልጅ ፡ (ያባቴ ፡ ልጅ) ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ታገባለች

## halfway (adj.) ያልተሟላ
Halfway measures will not suffice. ያልተሟላ ፡ ሥራ ፡ አያጠግብም

**halfway** (adv.)
1. ከንገት ፡ በላይ. They halfway consented to go. ለመሄድ ፡ ከንገት ፡ በላይ ፡ ተስማሙ
2. አማካይ ፡ በሆነ ፡ ቦታ. They met halfway between the two towns. በሁለቱ ፡ ከተሞች ፡ መካከል ፡ አማካይ ፡ በሆነ ፡ ቦታ ፡ ተገናኙ
*I'm willing to meet him halfway. እሱም ፡ ይተው ፡ እኔም ፡ ልተው

**halfway to**
We ran out of gas halfway to town. ከተማው ፡ ለመድረስ ፡ ግማሽ ፡ መንገድ ፡ ሲቀረን ፡ ቤንዚን ፡ አለቀብን

**be halfway finished** ተጋመሰ
The lesson is halfway finished. ትምህርቱ ፡ ተጋምሷል

## half-wit ቂል
A half-wit is harmless even though he does strange things. አንዳንድ ፡ እንግዳ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮችን ፡ ቢፈጽም ፡ ቂል ፡ ጉዳት ፡ አያደርስም

## hall
1. አዳራሽ. We stood at the back of the hall. አዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ በስተጀርባ ፡ ቆምን
2. መተላለፊያ. People were waiting in the hall for an audience with the governor. ከገዢው ፡ ጋር ፡ ለመገናኘት ፡ ሰዎች ፡ በመተላለፊያው ፡ ላይ ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበር
[See also 'city hall']

## hallmark መለዮ
Courtesy is a hallmark of a gentleman. ትሕትና ፡ የጨዋ ፡ መለዮ ፡ ነው

## hallow አወደሰ
Let us hallow God's name and keep His commandments! የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ እናወድስ ፡ ቃሉንም ፡ እንጠብቅ

## hallowed (adj.) የተቀደሰ
Parts of Jerusalem are hallowed ground. የኢየሩሳሌም ፡ አንዳንድ ፡ ክፍሎች ፡ የተቀደሱ ፡ ስፍራዎች ፡ ናቸው

**be hallowed** ተቀደሰ
Hallowed be Thy name! ስምህ ፡ ይቀደስ

## hallucination [እውነትነት ፡ ወይም ፡ መሠረት ፡ የሌላቸውን ፡ ነገሮች ፡ በሐሳብ ፡ የማየትና ፡ የመስማት ፡ ሁኔታ]

## hallway መተላለፊያ
The students gathered in the hallway. ተማሪዎቹ ፡ መተላለፊያው ፡ ላይ ፡ ተሰበሰቡ

**halo**

1. የቅዱሳን ፡ የብርሃን ፡ አክሊል. The halos of the saints are painted in gold. የቅዱሳኑ ፡ የብርሃን ፡ አክሊል ፡ ወርቃማ ፡ ቀለም ፡ ተቀብቷል
2. ዐውደ ፡ ብርሃን. A halo appeared around the moon last night. ትናንት ፡ ማታ ፡ በጨረቃ ፡ ዙሪያ ፡ ዐውደ ፡ ብርሃን ፡ ይታይ ፡ ነበር

**halt** (vt.)

1. አቆመ. The decision to halt the bombing was unilateral. የቦምብ ፡ ድብደባውን ፡ ለማቆም ፡ የተወሰነው ፡ ባንዱ ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ ነበር
2. አገደ. Our army halted the advance of the enemy. ጦራችን ፡ የጠላትን ፡ እርምጃ ፡ አገደው

**halt** (vi.)

1. ቆመ. "Halt or I'll fire"! cried the sentry. ቁም ፤ አለበለዚያ ፡ እተኵሳለሁ ፡ ብሎ ፡ ዘበኛው ፡ ጮኸ ፡ ተናገረ
2. ጕዞውን ፡ አቆመ. The soldiers halted and lay down to rest. ወታደሮቹ ፡ ጕዞዋቸውን ፡ አቁመው ፡ ለማረፍ ፡ ጋደም ፡ አሉ
3. አፋ ፡ ተያዘ. He began his speech briskly, but then soon halted. ንግግሩን ፡ ደኅና ፡ ከጀመረ ፡ በኋላ ፡ እያደር ፡ አፉ ፡ ተያዘ

**halt** (n.)

*After a short halt, the parade moved forward. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ቆም ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ሰልፉ ፡ ወደፊት ፡ ተጓዘ

**come to a halt** ቆመ

The train came to a halt. ባቡሩ ፡ ቆመ

**make halt** ንግግሩን ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ አደረገበት

Shyness made her halt as she talked. ስትናገር ፡ ዓይናፋርነቷ ፡ ንግግሯን ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ ያደርግባት ፡ ነበር

**halter** ለኮ

The mule's halter is made of rope. የበቅሎዋ ፡ ለኮ ፡ ከገመድ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**halting**

*His halting speech manifests his indecision. እልፎ ፡ እልፎ ፡ ንግግሩን ፡ ቆም ፡ ማድረጉ ፡ በሐሳቡ ፡ ያልቈረጠ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳል

**haltingly**

*He speaks Amharic haltingly. አማርኛ ፡ ሲናገር ፡ ይደዘዋል

**halve**

1. እኩል ፡ ከፈለ. Let's halve the oranges! ብርቱካኑን ፡ እኩል ፡ እንክፈለው
2. በግማሽ ፡ ቀነሰ. The new machine will easily halve the cost of doing the work. አዲሱ ፡ መሣሪያ ፡ የሥራውን ፡ ወጪ ፡ በቀላሉ ፡ በግማሽ ፡ ይቀንሰዋል

**halves** (n.), see **half**

**ham** [የታጠነ ፡ የአሳማ ፡ ውርች]

**hamlet** ትንሽ ፡ መንደር

You can see a hamlet on the top of the mountain. በተራራው ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ መንደር ፡ ይታያል

**hammer** (v.)

1. ምስማር ፡ ደበደበ. Our neighbor has been hammering all day long. ጐረቤታችን ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ምስማር ፡ ደበደበ
2. ቀጠቀጠ. He hammered the iron flat. ብረቱን ፡ ቀጥቅጦ ፡ ጠፍጣፋ ፡ አደረገው
3. ደበደበ. He hammered the table with his fist. ጠረጴዛውን ፡ በቡጢ ፡ ደበደበ

**hammer away** ደጋግሞ ፡ አስተማረ

The teacher hammered away at the multiplication table. መምህሩ ፡ የጊዜ ፡ ቤትን ፡ ደጋግሞ ፡ አስተማረ

**hammer in** መታ

He can't even hammer in a nail. ምስማር ፡ እንኳን ፡ መምታት ፡ አይችልም

**hammer into one's head** ሲያስቀጠቅጥ ፡ ዋለ

The teacher hammered arithmetic into the lazy boy's head. መምህሩ ፡ ሰነፉን ፡ ተማሪ ፡ ሒሳብ ፡ ሲያስቀጠቅጥ ፡ ዋለ

**hammer on** ደበደበ

He hammered on the door with his fists. መዝጊያውን ፡ በቡጢ ፡ ደበደበ

**hammer out** በስንት ፡ ጥረት ፡ አስወገደ

They hammered out their difficulties in a long meeting. ረዘም ፡ ባለ ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ ችግራቸውን ፡ በስንት ፡ ጥረት ፡ አስወገዱ

**hammer** (n.) መዶሻ

Please hand me the hammer! መዶሻውን ፡ አቀብለኝ

**hamper** አሰናከለ

His inability to speak English hampered him greatly. እንግሊዝኛ ፡ መናገር ፡ አለመቻሉ ፡ በጣም ፡ አሰናከለው

**hand** (v.) አቀበለ ፤ ሰጠ

Will you hand me that pencil? ያንን ፡ እርሳስ ፡ ታቀብለኛለህ? 

I handed her a sheaf of bills. አንድ ፡ ክምር ፡ የሒሳብ ፡ ደረሰኝ ፡ ሰጠኋት

**hand back** መለሰ
I gave him the book to read, but he handed it right back to me. መጽሐፉን ፡ እንዲያነበው ፡ ሰጥቼው ፡ ወዲያውኑ ፡ መለሰልኝ

**hand down**
1. አወረደ. Hand me down a pail! ባልዲ ፡ አውርድልኝ
2. ሰጠ. The judge handed down an unfavorable decision. ዳኛው ፡ የማይስማማ ፡ ፍርድ ፡ ሰጠ

**(be) handed down** ተላለፈ
The estate has been handed down from generation to generation. ርስቱ ፡ ከትውልድ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ ሲተላለፍ ፡ ቆይቷል

**hand in**
1. አገባ. I am going to hand in my application tomorrow. ማመልከቻዬን ፡ ነገ ፡ አገባለሁ
2. አስረከበ. It has come to my notice that students are not handing in their homework. ተማሪዎች ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ አለማስረከባቸውን ፡ ሰምቻለሁ

**hand out** ዐደለ
How many tickets did you hand out? ስንት ፡ ቲኬት ፡ ዐደልህ ?

**hand over**
1. አቀበለ. Would you hand over that book, please? እሱን ፡ መጽሐፍ ፡ ታቀብለኝ ?
2. አስረከበ. He handed the job over to his successor. ሥራውን ፡ ለተተኪው ፡ አስረከበ
[See also 'decision']

**hand** (n.)
1. እጅ. Where can I wash my hands? እጄን ፡ የት ፡ ልታጠብ ?
This job has to be done by hand. ይህ ፡ ሥራ ፡ በእጅ ፡ መሠራት ፡ አለበት
He has my fate in his hands. የወደፊት ፡ ዕድሌ ፡ በሱ ፡ እጅ ፡ ነው
2. ቈጣሪ. The hands of the clock say that it is four o'clock. የሰዓቱ ፡ ቈጣሪዎች ፡ ዐሥር ፡ ሰዓት ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታሉ
3. የእጅ ፡ ጽሕፈት. I recognized his hand on the envelope. ኤንቬሎፑ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የእጅ ፡ ጽሕፈቱን ፡ ዐወቅሁ
4. ሠራተኛ. He hired three new hands last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ሦስት ፡ አዲስ ፡ ሠራተኞች ፡ ቀጠረ

**hand and foot** እጅ ፡ ከወርች
They tied him hand and foot. እጅ ፡ ከወርች ፡ አሰሩት

**hand in glove** ሰምና ፡ ወርቅ
Several high-ranking diplomats were found to be hand in glove with enemy agents. ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ዲፕሎማቶች ፡ ከጠላት ፡ ሰላዮች ፡ ጋር ፡ ሰምና ፡ ወርቅ ፡ መሆናቸው ፡ ታወቀ

**hands down** ያላንዳች ፡ ድካም
He won the championship hands down. አሸናፊነትን ፡ ያላንዳች ፡ ድካም ፡ አገኘ

**hand-in-hand**
1. እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተያይዘው. The couple was walking hand-in-hand. ባልና ፡ ሚስቱ ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተያይዘው ፡ ይራመዱ ፡ ነበር
2. በኅብረት. Doctors and nurses work hand-in-hand to save lives. ሐኪሞችና ፡ ነርሶች ፡ ሕይወትን ፡ ለማዳን ፡ በኅብረት ፡ ይሠራሉ

**hands off!** አትንካ
Hands off! That cake is mine, ኬኩ ፡ የኔ ፡ ነው ። አትንካ !

**hand to hand** በጨበጣ
The soldiers fought hand to hand and drove off the enemy. ወታደሮቹ ፡ በጨበጣ ፡ ተዋግተው ፡ ጠላትን ፡ አባረሩ

**hands up!** እጅ ፡ ወደላይ
Hands up or I will shoot! እጅ ፡ ወደላይ ። አለበለዚያ ፡ እተኵሳለሁ

**ask for her hand** ለጋብቻ ፡ ጠየቀ
He asked for her hand and she said yes. ለጋብቻ ፡ ጠይቋት ፡ እሺ ፡ አለችው

**at hand**
1. በቅርቡ. There was a filling station at hand when we ran out of gas. ቤንዚን ፡ ባለቀብን ፡ ጊዜ ፡ የቤንዚን ፡ ማደያ ፡ በቅርቡ ፡ አገኘን
2. ሊደረግ ፡ ነው. A change of government is at hand in Brazil. ብራዚል ፡ ውስጥ ፡ የመንግሥት ፡ ለውጥ ፡ ሊደረግ ፡ ነው

**change hands**
*The business has changed hands. ሱቁን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ወስዶታል

**close at hand** በቅርብ
He lives close at hand. በቅርብ ፡ ይኖራል

**first hand** ከምንጩ
I got this information first hand. ይህን ፡ ወሬ ፡ የሰማሁት ፡ ከምንጩ ፡ ነው

**force one's hand** እርምጃ ፡ እንዲወስድ ፡ አደረገ
I am going to bring this up at the meeting in order to force his hand. እሱ ፡ እርምጃ ፡ እንዲወስድ ፡ ለማድረግ ፡ ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ ስብሰባው ፡ ላይ ፡ አነሣለሁ

**from hand to hand** ከንዱ ፡ ወደ ፡ እንዱ
This was passed from hand to hand till it came to me. እኔ ፡ ዘንድ ፡ ሳይደርስ ፡ ይህ ፡ ከንዱ ፡ ወደ ፡ እንዱ ፡ ሲተላለፍ ፡ ቆይቷል

**from hand to mouth**
He lives from hand to mouth. ኑሮው ፡ ከእጅ ፡ ወደ ፡ አፍ ፡ ነው

**get out of hand**
His students are getting out of hand. ተማሪዎቹን ፡ ለመቈጣጠር ፡ አልቻለም

**get the upper hand**
1. ቀኙ ፡ የርሱ ፡ ነበር. He got the upper hand in the dispute. በክርክሩ ፡ ጊዜ ፡ ቀኙ ፡ የርሱ ፡ ነበረ
2. አየለ. We have finally gotten the upper hand over the rebels. በመጨረሻ ፡ በዐመፀኞቹ ፡ ላይ ፡ አየልን
3. አሸነፈ. He got the upper hand in the struggle to control the ministry. ሚኒስቴሩን ፡ በቁጥጥር ፡ሥር ፡ ለማድረግ ፡ በተደረገው ፡ ትግል ፡ አሸነፈ

**give a big hand** የጋለ ፡ ጭብጨባ ፡ አደረገለት
They gave the performer a big hand. ለተጫዋቹ ፡ የጋለ ፡ ጭብጨባ ፡ አደረጉለት

**give (someone) a hand with** አገዘ
Can you give me a hand with this box? ይህን ፡ ሣጥን ፡ ታግዘኛለህ ?

**go hand in hand** አይለያዩም
War and disease go hand in hand. ጦርነትና ፡ በሽታ ፡ አይለያዩም

**have a hand in**
1. ገባ(በት). He must have had a hand in that. ከዚያ ፡ ሳይገባበት ፡ አልቀረም
2. ተካፈለ. He had a hand in making the decision. ውሳኔው ፡ ሲተላለፍ ፡ ተካፍሎ ፡ ነበር

**have in hand** በቁጥጥር ፡ ሥር ፡ አደረገ
He has the situation well in hand. ሁኔታውን ፡ በሚገባ ፡ በቁጥጥር ፡ ሥር ፡ አድርጓል

**have no hand in**
He had no hand in the matter. በነገሩ ፡ ውስጥ ፡ የለበትም

**have on (one's) hands** አለ(ው)
I have an empty house on my hands. ያልተያዘ ፡ ቤት ፡ አለኝ
*I've got a lot of work on my hands. ሥራ ፡ በዝቶብኛል

**have one's hands full** ሥራ ፡ በዛበት
I cannot accept this responsibility; I have my hands full. ሥራ ፡ ስለሚበዛብኝ ፡ ይህን ፡ ኀላፊነት ፡ ልቀበል ፡ አልችልም

**have the upper hand** አሸነፈ
My friend had the upper hand in the argument. በክርክሩ ፡ ጓደኛዬ ፡ አሸነፈ

**(with a) heavy hand** በኀይል
The law will punish offenders with a heavy hand. ሕግ ፡ አጥፊዎችን ፡ በኀይል ፡ ትቀጣለች

**hold hands** እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተያያዙ
They have been holding hands in public. ባደባባይ ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተያይዘው ፡ ነበር

**keep a hand in** አልፎ ፡ አልፎ ፡ ተቈጣጠረ
He turned the business over to his son, but they say he keeps a hand in it. የንግድ ፡ ሥራውን ፡ ለልጁ ፡ አስተላልፏል ፤ ሆኖም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይቈጣጠራል ፡ ይባላል

**keep on hand**
*We keep a supply of canned goods on hand. የቆርቆሮ ፡ ምግብ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አዘጋጅተን ፡ እናስቀምጣለን

**keep one's hand in** እንዳይረሳው
I read Arabic five hours a week just to keep my hand in. ዐረብኛ ፡ እንዳይረሳኝ ፡ ስል ፡ በሳምንት ፡ አምስት ፡ ሰዓት ፡ አነባለሁ

**keep one's hand in shape** እንዳይረሳው
I am practicing tennis once a week just to keep my hand in shape. እንዳይረሳኝ ፡ ብቻ ፡ በሳምንት ፡ አንዴ ፡ ቴኒስ ፡ እጫወታለሁ

**lay hands on**
1. አገኘ. I have the book, but I can't lay hands on it now. መጽሐፉ ፡ አለኝ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ላገኘው ፡ አልችልም
2. እጁ ፡ የገባው. He keeps anything he can lay his hands on. እጁ ፡ የገባውን ፡ ሁሉ ፡ ያስቀምጣል

**lay a hand on** ነካ
Don't lay a hand on me or I'll hit you. አትንካኝ ፤ ያለዚያ ፡ እመታሃለሁ

**lay one's hands on**
1. አገኘ. I cannot lay my hands on it right now. አሁን ፡ ላገኘው ፡ አልችልም
2. ያዘ. He wanted to lay his hands on the person who hit his car. መኪናውን ፡ የገጨበትን ፡ ሰው ፡ ለመያዝ ፡ ፈለገ

**left hand** ግራ
At his left hand were three boys. በግራው ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ ነበሩ

**lend a hand** ረዳ ፤ አገዘ
Lend me a hand; I cannot lift this box by myself. እርዳኝ ፡ (አግዘኝ) ፤ ይህን ፡ ሣጥን ፡ ብቻዬን ፡ ላነሣው ፡ አልችልም

**not lift a hand** ምንም ፡ አላደረገም
France did not lift a hand when Italy invaded Ethiopia. ኢጣሊያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረችበት ፡ ጊዜ ፡ ፈረንሳይ ፡ ምንም ፡ አላደረገችም

**(be) off one's hands** አለቀ
The lawyer planned a vacation as soon as the case was off his hands. ነገሩ ፡ እንዳለቀ ፡ ጠበቃው ፡ ዕረፍት ፡ ለማድረግ ፡ አቀደ
*Now, with her invalid mother off her hands, she will be free to marry. እንግዲህ ፡ አካለ ፡ ስንኩል ፡ እናቷን ፡ ከተገላገለች ፡ ለማግባት ፡ ነጻ ፡ ትሆናለች

**offer one's hand in marriage**
She offered him her hand in marriage. ሊታገባው ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆኗን ፡ ገለጸችለት

**on either hand** ግራና ፡ ቀኝ
Walking down the road, we saw trees on either hand. በመንገድ ፡ ስንሄድ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ዛፍ ፡ አየን

**on hand** በእጅ
I have some money on hand. በእጄ ፡ ጥቂት ፡ ገንዘብ ፡ አለኝ

**(be) on hand** ተገኘ
He is always on hand when I want him. እሱ ፡ በፈለግሁት ፡ ቁጥር ፡ ይገኛል

**on (one's) hands** በእጁ ፡ ላይ
He was left with a large surplus on his hands. ብዙ ፡ ትርፍ ፡ እቃ ፡ በእጁ ፡ ላይ ፡ ቀርቶ ፡ ነበር

**on the one hand ... on the other hand** ባንድ ፡ በኩል ... በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ
On the one hand, I need to study English; on the other hand, I cannot take time off from my job. ባንድ ፡ በኩል ፡ እንግሊዝኛ ፡ ማጥናት ፡ እፈልጋለሁ ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የሥራዬን ፡ ጊዜ ፡ ለመቀነስ ፡ አልችልም

**(but) on the other hand**
1. ይሁን ፡ እንጂ. The boy is skinny, but on the other hand, he plays football well. ልጁ ፡ ኮሳሳ ፡ ነው ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የግር ፡ ኳስ ፡ ጥሩ ፡ ይጫወታል
2. ባንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ. I don't want to vote for John, but on the other hand, I'd hate to hurt his feelings. ጆንን ፡ ለመምረጥ ፡ አልፈልግም ፤ ባንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ እንዳስቀይመው ፡ አልፈልግም

**out of one's hands** ከሱ ፡ ሥልጣን ፡ ውጪ
The matter is out of my hands. ነገሩ ፡ ከኔ ፡ ሥልጣን ፡ ውጪ ፡ ነው

**right hand** ቀኝ
At his right hand were three boys. በቀኙ ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ ነበሩ

**second-hand** የስሚ ፡ ስሚ
I heard the story second-hand. ታሪኩን ፡ የሰማሁት ፡ የስሚ ፡ ስሚ ፡ ነው

**show (one's) hand** ሐሳቡን ፡ ገለጸ
The vote forced him to show his hand. ድምፅ ፡ የመስጠቱ ፡ ጉዳይ ፡ ሐሳቡን ፡ እንዲገልጽ ፡ አስገደደው

**(by) show of hands** እጁን ፡ እያወጣ
Vote by show of hands! እጃችሁን ፡ እያወጣችሁ ፡ ድምፅ ፡ ስጡ

**take a hand in** ተካፋይ ፡ ሆነ
If the strike continues, the government will have to take a hand in the negotiations. ሥራ ፡ ማቆሙ ፡ ከቀጠለ ፡ መንግሥት ፡ በድርድሩ ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም

**take in hand**
1. ተነጋገረ(በት). We will take the matter in hand at the next meeting. ጉዳዩን ፡ በሚቀጥለው ፡ ስብሰባ ፡ እንነጋገርበታለን
2. ኀላፊ ፡ ሆኖ ፡ ወሰደ. When both parents died, an uncle took the youngster in hand. ሁለቱም ፡ ወላጆች ፡ ሲሞቱ ፡ አጐትዬው ፡ ልጁን ፡ ኀላፊ ፡ ሆኖ ፡ ወሰደው

**(be) taken in hand** (=active) ተቈጣጠረ
+Those children needed to be taken in hand. ልጆቹን ፡ መቈጣጠር ፡ አስፈለገ

**tie one's hands** እጁን ፡ አሰረው
The provisions of the will tied his hands. የኑዛዜው ፡ ቃል ፡ እጁን ፡ አሰረው

**try one's hand** ሞከረ
Why don't you try your hand at writing a book? መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ለምን ፡ አትሞክርም ?

**wash one's hands** ኀላፊነት ፡ የለበትም ፤ በጉዳዩ ፡ አልገባም
Now that he is in charge, I wash my hands of the whole thing. አሁን ፡ እሱ ፡ ኀላፊ ፡ ነው ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ኀላፊነት ፡ የለብኝም ፡ (በጉዳዩ ፡ አልገባም)
[See also 'back, clasp, entwine, iron, join, life, near, open, own, play, put, shake, shoulder, slip, thrust']

**handbag** የእጅ ፡ ቦርሳ
She put the car key in her handbag. የመኪናዋን ፡ ቁልፍ ፡ በእጅ ፡ ቦርሳዋ ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጠች

**handbook** የመምሪያ ፡ መጽሐፍ
This is a handbook for engineers. ይህ ፡ ለመሀንዲሶች ፡ የመምሪያ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው

**handcuff** (v.) በካቴና ፡ አሰረ
They handcuffed the prisoners. እስረኞቹን ፡ በካቴና ፡ አሰሩዋቸው

**handcuff** (n.) ካቴና
In some countries every policeman carries a pair of handcuffs with him. ባንዳንድ ፡ አገር ፡ እያንዳንዱ ፡ ፖሊስ ፡ ካቴና ፡ ይዞ ፡ ይዞራል

**handful** እፍኝ
He took a handful of nuts. አንድ ፡ እፍኝ ፡ ለውዝ ፡ ወሰደ

**handful of** ጥቂቶች
Only a handful of people came to the meeting. ጥቂቶች ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ስብሰባው ፡ መጡ

**handicap** (v.) ዕንቅፋት ፡ ሆነበት
Bad eyesight handicaps him. ደካማ ፡ ዓይኑ ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆኖበታል

**handicap** (n.) መሰናክል
His disease was a handicap to him. በሽታው ፡ መሰናክል ፡ ሆኖበት ፡ ነበር

**handicraft** የእጅ ፡ ሥራ ፡ ትምህርት ፤ ተግባረ ፡ እጅ ፡ ትምህርት
Handicrafts are being taught in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ (ተግባረ ፡ እጅ) ፡ ትምህርቶች ፡ ይሰጣሉ

**handily** በቅልጥፍና
He managed the boat handily. ጀልባዋን ፡ በቅልጥፍና ፡ ነዳት
*The books were handily at his side. መጽሐፎቹ ፡ እንደልቡ ፡ እሚደርስበት ፡ ቦታ ፡ ነበሩ

**handiwork** የእጅ ፡ ሥራ
His handiwork shows craftsmanship. የእጅ ፡ ሥራው ፡ ጥበበኛነቱን ፡ ያመለክታል
*This garden is Mary's handiwork. ይህ ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ በሜሪ ፡ ጥረት ፡ የተደራጀ ፡ ነው

**handkerchief** መሐረብ
I lost my handkerchief. መሐረቤን ፡ ጣልኩት

**handle** (v.)
1. ተቈጣጠረ. I cannot handle him anymore. ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ልቈጣጠረው ፡ አልችልም
2. ያዘ. He knows how to handle people. እሱ ፡ የሰውን ፡ አያያዝ ፡ ያውቃል
3. አካሄደ ፤ አየ. He handles his affairs with dexterity. ጉዳዩን ፡ በቅልጥፍና ፡ ያካሂዳል
Chiefs handle tribal affairs. የጎሳዎችን ፡ ጉዳዮች ፡ የሚያዩት ፡ ባላባቶች ፡ ናቸው
4. አስመጣ. We don't handle that brand. ያንን ፡ ዓይነት ፡ እቃ ፡ አናስመጣም
5. ሸጠ. That store handles meat and vegetables. ያ ፡ መደብር ፡ ሥጋና ፡ አትክልት ፡ ይሸጣል
6. ነካካ. Look at it all you want, but don't handle it. የምትፈልገውን ፡ ያህል ፡ ተመልከተው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አትነካካው
7. አስተናገደ. This restaurant can handle hundreds of customers during the lunch hour. ይህ ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ በምሳ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ደንበኞች ፡ ሊያስተናግድ ፡ ይችላል
8. አጠናቀቀ. This department handles the customers' checking accounts. ይህ ፡ ክፍል ፡ የደንበኞቹን ፡ የቼክ ፡ ሒሳብ ፡ ያጠናቅቃል

**handle easily** ታገሉኝ ፡ አይልም
The car handles easily. መኪናው ፡ ታገሉኝ ፡ አይልም

**handle roughly** አንገላታ
The bad boys handled the poor cat roughly. መጥፎዎቹ ፡ ልጆች ፡ ምስኪኗን ፡ ድመት ፡ አንገላቷት

**handle** (n.)
1. እጀታ. The handle of the knife came off. የቢላዋው ፡ እጀታ ፡ ወለቀ
2. ማንጠልጠያ. My suitcase needs a new handle. ሻንጣዬ ፡ አዲስ ፡ ማንጠልጠያ ፡ ያስፈልገዋል
3. ጆሮ. The handle of this cup is broken off. የዚህ ፡ ሲኒ ፡ ጆሮ ፡ ተሰብሯል

**handling** አያያዝ
Why don't you use common sense in handling your child? ስለ ፡ ልጅህ ፡ አያያዝ ፡ ለምን ፡ የተፈጥሮ ፡ ዕውቀትህን ፡ አትሠራበትም?

**handmade** በእጅ ፡ የተሠራ
These shoes are all handmade. እነዚህ ፡ ጫማዎች ፡ በእጅ ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው

**handouts** ምጽዋት
Beggars live on the handouts people give them. ለማኞች ፡ የሚኖሩት ፡ በምጽዋት ፡ ነው

**handshake** እጅ ፡ ለእጅ ፡ መጨባበጥ
They concluded the deal with a handshake. ውሉን ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ በመጨባበጥ ፡ ደመደሙ

**handsome**
1. መልከ ፡ ቀና ፤ መልከ ፡ መልካም. He is a handsome man. እሱ ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ (መልከ ፡ መልካም) ፡ ሰው ፡ ነው
2. የሚያምር. He lives in a handsome mansion. በሚያምር ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል

3. ደስ ፡ የሚያሰኝ. Each year he gives the servants a handsome gift of one hundred dollars. በያመቱ ፡ ላሽከሮቹ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ የመቶ ፡ ብር ፡ ስጦታ ፡ ያደርግላቸዋል
4. ብዙ. A thousand dollars is a handsome sum. አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ነው

**handsomely** በጥሩ ፡ አኳኋን
He treated me handsomely when I visited him. ልጠይቀው ፡ በሄድኩ ፡ ጊዜ ፡ በጥሩ ፡ አኳኋን ፡ አስተናገደኝ

**hand-to-hand** የጨበጣ
Many soldiers were killed in the hand-to-hand fight. ብዙ ፡ ወታደሮች ፡ በጨበጣ ፡ ውጊያ ፡ ሞቱ

**handwriting**
1. የእጅ ፡ ጽሕፈት. His handwriting is illegible. የእጅ ፡ ጽሕፈቱ ፡ አይነበብም
2. ጽሕፈት. He disguised his handwriting. ጽሕፈቱ ፡ እንዳይታወቅ ፡ አድርጎ ፡ ጻፈ
3. አጻጻፍ. The Ethiopian alphabet has no cursive handwriting. የኢትዮጵያ ፡ ፊደል ፡ የተቀጣጠለ ፡ አጻጻፍ ፡ የለውም

**handy**
1. ቀልጣፋ. He is handy with tools. በመሣሪያ ፡ አያያዝ ፡ ቀልጣፋ ፡ ነው
2. ባለሙያ. He is a very handy fellow. በጣም ፡ ባለሙያ ፡ ሰው ፡ ነው
3. ምቹ. There were handy shelves near the desk. በጠረጴዛው ፡ አጠገብ ፡ ምቹ ፡ የሆኑ ፡ መደርደሪያዎች ፡ ነበሩ
*A typewriter is a handy thing to have around. የጽሕፈት ፡ መኪና ፡ ጠቃሚ ፡ መገልገያ ፡ ነው

**come in handy** ጠቀመ ፤ አገለገለ
Typing will come in handy for you some day. የመኪና ፡ ጽሕፈት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ይጠቅምሃል ፡ (ያገለግልሃል)

**have (something) handy**
Have you got a pencil handy? እርሳስ ፡ በአቅራቢያህ ፡ አለ ?

**handyman** ባለሙያ
The handyman keeps the machines in repair. ባለሙያው ፡ መኪናዎችን ፡ ይጠግናል

**hang** (hung), vt.
1. ሰቀለ (ተሰቀለ). Where can I hang my coat? ኮቴን ፡ የት ፡ ልሰቀለው ?
Can't you hang the picture a little higher? ሥዕሉን ፡ ትንሽ ፡ ከፍ ፡ አድርገህ ፡ ልትሰቅለው ፡ አትችልም ?
He was hanged yesterday. ትላንትና ፡ ተሰቀለ
2. አጌጠ. She likes to hang the wall with pictures. ግድግዳውን ፡ በሥዕል ፡ ማጌጥ ፡ ትወዳለች

**hang** (vi.)
1. ተንጠለጠለ. A lamp hung from the ceiling. መብራት ፡ ከኮርኒሱ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሏል
Tell the children not to hang out the window! ልጆቹ ፡ መስኮቱ ፡ ላይ ፡ እንዳይንጠለጠሉ ፡ ንገራቸው
2. ተመሠረተ. My decision hangs on your answer. ውሳኔዬ ፡ የሚመሠረተው ፡ ባንተ ፡ መልስ ፡ ላይ ፡ ነው
3. ቆየ. Let that matter hang until our next meeting! ጉዳዩ ፡ እስከሚቀጥለው ፡ ስብሰባችን ፡ ይቆይ
4. አዘነበለ. The tree hung over the edge of the lake. ዛፉ ፡ ወደ ፡ ሐይቁ ፡ አዘንብሏል
5. በጥንቃቄ ፡ አዳመጠ. She was hanging on his every word. የተናገረውን ፡ ሁሉ ፡ በጥንቃቄ ፡ አዳመጠች
6. (= tr.) አለበሰ. Fog hung over the city. ጭጋግ ፡ ከተማውን ፡ አለበሰው

**hang about** ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ
A man is hanging about the house in a suspicious manner. አንድ ፡ ሰው ፡ በቤቱ ፡ አካባቢ ፡ በሚያጠራጥር ፡ ሁኔታ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይላል

**hang around**
1. አልጠፋም. He has been hanging around my house for a week now. አንድ ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ ከቤቴ ፡ አልጠፋም
2. ዋለ. He hangs around with an older crowd. ከታላላቆቹ ፡ ጋር ፡ ይውላል
3. ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ. They had stopped working and were just hanging around to talk. ሥራቸውን ፡ አቁመው ፡ ለወሬ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይሉ ፡ ነበር

**hang by (someone's) side** ከጐኑ ፡ ተጣበቀ
He hung by her side, unwilling to leave. ከጐኗ ፡ ተጣብቆ ፡ አልሄድ ፡ አለ

**hang down** ተንዠረገገ
A long plait was hanging down the girl's back. ረዥም ፡ የጸጉር ፡ ጉንጉን ፡ ልጂቷ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ተንዠርግጎ ፡ ነበር

**hang (one's) head** አንገቱን ፡ ደፋ ፤ አቀረቀረ
He hung his head in shame. በኀፍረቱ ፡ አንገቱን ፡ ደፋ
When he realized what he had done, he hung his head. የሠራውን ፡ በተገነዘበ ፡ ጊዜ ፡ አቀረቀረ

**hang in the balance** በሚያጠራጥር ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነበረ
The wounded man's life hung in the balance. የቈሰለው ፡ ሰውዬ ፡ ሕይወት ፡ በሚያጠራጥር ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነበር

**hang on**
1. ተስፋ ፡ አልቈረጠም. It is hard work, but if you hang on, you'll succeed in the end. ከባድ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ተስፋ ፡ ካል ቈረጥክ ፡ በመጨረሻ ፡ ይሳካልሃል
2. አጥብቆ ፡ ያዘ. I hung on as tight as I could. የምችለውን ፡ ያህል ፡ አጥብቄ ፡ ያዝኩ
3. ታገሠ. If you can hang on for a month longer, you will be free of hardship. ላንድ ፡ ወር ፡ ብትታገሥ ፡ ችግርህ ፡ ሁሉ ፡ ይወገድልሃል

**hang oneself** ራሱን ፡ ሰቀለ
He hanged himself from a beam. አግዳሚው ፡ ላይ ፡ ራሱን ፡ ሰቀለ

**hang out** (vt.)
1. አሰጣ. Did you hang the wash out? የታጠበውን ፡ ልብስ ፡ አሰጣህ ?
2. ሰቀለ. They were hanging out flags in honor of the Emperor's visit. ስለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጉብኝት ፡ ክብር ፡ ባንዴራዎች ፡ ይሰቅሉ ፡ ነበር

**hang (over)** አሰጋ
The danger of a flood hung over the village. የውኃ ፡ መጥለቅለቅ ፡ አደጋ ፡ መንደሩን ፡ አስግቶታል

**(let) hang over** እንዲቆይ ፡ አደረገ
They will probably let the decision hang over until next year. ውሳኔው ፡ እስከሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ እንዲቆይ ፡ ያደርጉ ፡ ይሆናል

**hang together** ሁላቸው ፡ ተባበሩ ፤ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆኑ
If we all hang together, our plan will succeed. ሁላችንም ፡ ከተባበርን ፡ (አንድ ፡ ላይ ፡ ከሆን) ፡ እቅዳችን ፡ ይቃናል

**hang up** (vt.)
1. ሰቀለ. Hang up your hat and coat! ኮትህንና ፡ ባርኔጣህን ፡ ስቀል
2. አወከ. The accident hung up the traffic for several hours. አደጋው ፡ የመኪናዎችን ፡ መዘዋወር ፡ ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ አውኮ ፡ ነበር

**hang up** (vi.) ስልክ ፡ ዘጋ(በት)
He got angry and hung up. ተናዶ ፡ ስልክ ፡ ዘጋብኝ

**hang upside down** ተዘቀዘቀ
Bats hang upside down when they sleep. የሌሊት ፡ ወፎች ፡ ተዘቅዝቀው ፡ ይተኛሉ
[See also 'lip, loose']

**hang** (n.), **get the ~ of**
*I cannot get the hang of driving a car. መኪና ፡ መንዳት ፡ አይሆንልኝም

**hangar** ጋራዥ
The plane was put in the hangar. አውሮፕላኑ ፡ ከጋራዡ ፡ ውስጥ ፡ ቆሟል

**hanger** መስቀያ
Put your coat on a hanger! ኮትህን ፡ መስቀያ ፡ ላይ ፡ ስቀለው

**hanging** (n.) ስቅለት
News of the hanging was not printed in the paper. የስቅለቱ ፡ ዜና ፡ በጋዜጣ ፡ አልወጣም
*Many people came to see the hanging. ሰውዬው ፡ ሲሰቀል ፡ ለማየት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ መጡ
*There were three hangings last month. ባለፈው ፡ ወር ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ተሰቀሉ

**hanging** (adj.) የተንጠለጠለ
The gardener watered the hanging baskets of flowers. አትክልተኛው ፡ የተንጠለጠሉትን ፡ ያበባ ፡ ማሳደጊያ ፡ ቅርጫቶች ፡ ውኃ ፡ አጠጣ

**public hanging** ባደባባይ ፡ ሰው ፡ መስቀል
They decided to outlaw public hanging. ባደባባይ ፡ ሰው ፡ መስቀልን ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ለማድረግ ፡ ወሰኑ
[See also 'execute']

**hanker** ጓጓ
He always hankers after money. ሁልጊዜ ፡ ለገንዘብ ፡ ይጓጓል

**haphazard**
1. አፍ ፡ እንዳመጣ ፡ የሚሰጥ. Haphazard answers are usually wrong. አፍ ፡ እንዳመጣ ፡ የሚሰጡ ፡ መልሶች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ስሕተት ፡ ይሆናሉ
2. ጊዜ ፡ የወለደው. Many haphazard things occurred last month. ባለፈው ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ የወለዳቸው ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ደረሱ
3. (= adv.) ሳይታሰብ. Their haphazard meeting led to love. ሳይታሰብ ፡ ተገናኝተው ፡ ለፍቅር ፡ በቁ

**haphazardly**
1. ያለ ፡ አቅድ. His failure is due to the fact that he does his work haphazardly. ሊወድቅ ፡ የቻለው ፡ ሥራውን ፡ ያለ ፡ አቅድ ፡ ስለሚሠራ ፡ ነው
2. በድንገት. They met haphazardly in the street. በድንገት ፡ አመንገድ ፡ ተገናኙ

**hapless** ምስኪን
He vented his wrath on the hapless child. ንዴቱን ፡ ምስኪኑ ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ተወጣ

**happen**
1. ሆነ. When did that happen? መቼ ፡ ነው ፡ የሆነው ?
What happened to the typewriter? Did someone use it? የጽሕፈት ፡ መኪናው ፡ ምን ፡ ሆነ ? የነካካው ፡ ሰው ፡ አለ ?
2. አይጠፋም. Something interesting is always happening in Addis Ababa. አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ሁልጊዜ ፡ አንዳንድ ፡ የሚያስደስት ፡ ነገር ፡ አይጠፋም
3. ነካ. What happened to me? ምን ፡ ነካኝ ?
4. ደረሰ. Accidents will happen. አደጋ ፡ ይደርሳል
Everything happens to me. የማይደርስብኝ ፡ ነገር ፡ የለም

**happen again** ተደገመ
This must never happen again. ይህ ፡ ነገር ፡ ፈጽሞ ፡ እንዳይደገም

**happen (on)** በድንገት ፡ አገኘ
She happened on a dollar while looking for the ball. ኳሷን ፡ ስትፈልግ ፡ በድንገት ፡ ብር ፡ አገኘች

**happen to** (= adv.) እንዳጋጣሚ
I happened to sit by Mary. እንዳጋጣሚ ፡ ሜሪ ፡ ጐን ፡ ተቀምጬ ፡ ነበር
He doesn't happen to be here. እንዳጋጣሚ ፡ እዚህ ፡ የለም

**as it happens** እንዳጋጣሚ
As it happens, I have my checkbook with me. እንዳጋጣሚ ፡ የቼክ ፡ ደብተሬን ፡ ይዣለሁ

**it so happens** እንዳጋጣሚ
It so happens that I know him. እንዳጋጣሚ ፡ የማውቀው ፡ ሰው ፡ ሆነ
[See also 'bound, whatever']

**happening** ድርጊት
There have been strange happenings here lately. በቅርብ ፡ ቀን ፡ እዚህ ፡ አንዳንድ ፡ እንግዳ ፡ ድርጊቶች ፡ ተፈጽመዋል

**happiest**
1. ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ደስተኛ. That was his happiest day. ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ደስተኛ ፡ የሆነበት ፡ ቀን ፡ ነበር
2. በጣም ፡ የተደሰተ(በት). Those were the happiest years of my life. እነዚያ ፡ በሕይወቴ ፡ በጣም ፡ የተደሰትኩባቸው ፡ ዓመቶች ፡ ነበሩ

**happily**
1. በደስታ. She lives happily. በደስታ ፡ ትኖራለች
2. በሚገባ. The two colors mix happily. ሁለቱ ፡ ቀለሞች ፡ በሚገባ ፡ ይስማማሉ
3. ደግነቱ. I had an exam Monday, but happily the date was changed. ሰኞ ፡ ፈተና ፡ ነበረብኝ ፤ ደግነቱ ፡ ቀኑ ፡ ተለወጠ
*They are happily married. ትዳራቸው ፡ የሞቀ ፡ ነው

**happiness** ደስታ
I wish you all the happiness in the world. ፍጹም ፡ ደስታ ፡ እመኝላችኋለሁ

**happy**
1. ደስተኛ. He is a happy fellow, always singing. ደስተኛ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ሁልጊዜ ፡ ይዘፍናል
2. የሚስማማ. This is a very happy selection of colors. ይህ ፡ በጣም ፡ የሚስማማ ፡ የቀለም ፡ ምርጫ ፡ ነው

**Happy Birthday!** መልካም ፡ ልደት !

**Happy New Year!** እንኳን ፡ ከዘመን ፡ ዘመን ፡ አሸጋገረህ (or, እንኳን ፡ ላዲስ ፡ ዘመን ፡ አደረሰህ)

**be happy** ደስ ፡ አለ(ው)
We shall be happy to accept your kind invitation. ጥሪዎን ፡ ስንቀበል ፡ ደስ ፡ ይለናል

**by a happy chance** በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ
By a happy chance, I found the lost money. በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የጠፋውን ፡ ገንዘብ ፡ አገኘሁት

**make happy**
1. አስፈነደቀ. The glad news made her happy. የሚያስደስተው ፡ ወሬ ፡ አስፈነደቃት
2. አስደሰተ. The recovery of the lost coat made him happy. ጠፍቶ ፡ የነበረው ፡ ካፖርቱ ፡ መገኘቱ ፡ አስደሰተው

**happy-go-lucky** ግድ ፡ የለሽ
He is a happy-go-lucky fellow. ግድ ፡ የለሽ ፡ ሰው ፡ ነው (or, ለምንም ፡ ነገር ፡ የማይጨነቅ ፡ ሰው ፡ ነው)

**harangue**
*The speaker harangued for hours on the Senate floor. በመወሰኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ተናጋሪው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተመላበት ፡ ረጅም ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**harass** ነዘነዘ
He harasses me with constant requests for money. አዘውትሮ ፡ ገንዘብ ፡ እየጠየቀ ፡ ይነዘንዘኛል

**harbinger** የሚያመለክት
The first rain is a harbinger of the rainy season.

መጀመሪያ ፡ የሚጥለው ፡ ዝናብ ፡ ክረምት ፡ መግባቱን ፡ የሚያመለክት ፡ ነው

**harbor** (v.)

1. አስጠጋ. He was arrested for harboring a criminal. ወንጀለኛ ፡ አስጠግተሃል ፡ ተብሎ ፡ ተይዞ ፡ ነበር
2. ያዘ. I harbor no ill toward those who have wronged me. በበደሉኝ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ቂም ፡ አልይዝም

**harbor** (n.) ወደብ

New York City has a good harbor. የኒው ፡ ዮርክ ፡ ከተማ ፡ ጥሩ ፡ ወደብ ፡ አለው

**hard** (adj.)

1. ጠንካራ. My brother is a hard worker. ወንድሜ ፡ ጠንካራ ፡ ሠራተኛ ፡ ነው
Is plastic soft or hard? ፕላስቲክ ፡ ለስላሳ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ጠንካራ?
2. አስቸጋሪ. This is a hard question to answer. ለመመለስ ፡ ይህ ፡ አስቸጋሪ ፡ ጥያቄ ፡ ነው
Amharic is a hard language for a foreigner. አማርኛ ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ አስቸጋሪ ፡ ቋንቋ ፡ ነው
3. ከባድ. Last winter was a hard winter. ያለፈው ፡ ክረምት ፡ ከባድ ፡ ክረምት ፡ ነበር
The student was able to solve all the hard problems. ተማሪው ፡ ከባዶቹን ፡ ፕሮብሌሞች ፡ ሁሉ ፡ መሥራት ፡ ቻለ
4. ከባድ ፤ ኀይለኛ. The hard rain prevented us from going to school. ከባዱ ፡ (ኀይለኛው) ፡ ዝናም ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ አስቀረን
5. ኀይለኛ. Vodka is hard liquor. ቮድካ ፡ ኀይለኛ ፡ መጠጥ ፡ ነው
A hard blow on the chin knocked him unconscious. አገጩ ፡ ላይ ፡ የተመታው ፡ ኀይለኛ ፡ ምት ፡ ነፍሱን ፡ እንዲስት ፡ አደረገው
6. አዳጋች. It is hard to carry this bulky package. ይህን ፡ መጠኑ ፡ ትልቅ ፡ የሆነ ፡ ጥቅል ፡ መሸከም ፡ አዳጋች ፡ ነው
+He is hard to please. እሱን ፡ ለማስደሰት ፡ አዳጋች ፡ ነው
7. ጨካኝ. A servant does not like a hard master. አሽከር ፡ ጨካኝ ፡ ጌታ ፡ አይወድም
8. መጥፎ. He has nothing but hard luck in his business. በሥራው ፡ ከመጥፎ ፡ ዕድል ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ አላጋጠመውም
9. ትልቅ. His losing his car was a hard blow. መኪናውን ፡ ማጣቱ ፡ ትልቅ ፡ ጉዳት ፡ ነበር
10. ክፉ. Those were hard times. ክፉ ፡ ቀን ፡ ነበር

*He has a hard look on his face. ፊቱ ፡ ቁጥር ፡ ብሏል
*The bread is as hard as a rock. ዳቦው ፡ ድንጋይ ፡ ሆኗል

**hard** (adv.)

1. ጠንክሮ ፤ በርትቶ. He works hard all day. እርሱ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ጠንክሮ ፡ (በርትቶ) ፡ ይሠራል
2. በኀይል. The wind is blowing hard outside. እውጭ ፡ ነፋሱ ፡ በኀይል ፡ ይነፍሳል
3. አጥብቆ. Hold my hand hard when the doctor gives you an injection. ሐኪሙ ፡ መርፌ ፡ ሲወጋህ ፡ እጄን ፡ አጥብቀህ ፡ ያዝ
4. በጣም. The town was hard hit by the storm. ከተማው ፡ በዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ በጣም ፡ ተጐዳ
He tried hard to do it right. በትክክል ፡ ለመሥራት ፡ በጣም ፡ ጣረ
5. ጨቋኝ. His brothers treat him hard. ወንድሞቹ ፡ ጨቍነው ፡ ይዘውታል

**hard and fast** የማይሻርና ፡ የማይለወጥ

In this case you cannot make hard and fast rules. እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ነገር ፡ የማይሻርና ፡ የማይለወጥ ፡ ሕግ ፡ ልታወጣ ፡ አትችልም

**hard (by)**

1. ጥግ. The house stood hard by the bridge. ቤቱ ፡ ድልድዩ ፡ ጥግ ፡ ነው
2. ዳር. The house is hard by the river. ቤቱ ፡ ወንዙ ፡ ዳር ፡ ነው

**hard words** ኀይለ ፡ ቃላት

Hard words were exchanged. ኀይለ ፡ ቃላት ፡ ተለዋወጡ

**be hard** አዳገተ

It is hard for me to climb stairs. ደረጃ ፡ መውጣት ፡ ያዳግተኛል

**be hard put** ተቸገረ

He was hard put to answer my questions. እርሱ ፡ ጥያቄዎቼን ፡ ለመመለስ ፡ ተቸግሮ ፡ ነበር

**be hard up for**

1. ቸገረ(ው). +I am hard up for money. ገንዘብ ፡ ቸግሮኛል
2. በጣም ፡ አነሰ(ው). +The country is hard up for doctors. አገሪቱ ፡ ሐኪሞች ፡ በጣም ፡ ያንሷታል

**be hit hard** በጣም ፡ ስሜቱ ፡ ተነካ

He was hit hard by her deceit. በሷ ፡ ክሕደት ፡ በጣም ፡ ስሜቱ ፡ ተነካ

**be too hard on someone**

You are being too hard on him. በጣም ፡ ትጫነዋለህ

**find it hard** አስቸገረ(ው) ፤ አቃተ(ው)

+A smoke addict finds it hard to stop smoking

cigarettes. የሲጃራ ፡ ሱሰኛ ፡ ሲጃራ ፡ ማቆም ፡ ያስቸግረዋል
+He was by nature a daydreamer and found it hard to buckle down. በተፈጥሮው ፡ ሐሳቡ ፡ የሚባክን ፡ ስለሆነ ፡ አእምሮውን ፡ ለሥራ ፡ መሰብሰብ ፡ አቃተው

**take (it) very hard** ከልቡ ፡ አዘነ
She took it very hard when they told her of his death. መሞቱን ፡ ሲነግሯት ፡ ከልቧ ፡ አዘነች
[See also 'breathe, cash, fare, frozen, hearing, labor, press, time']

**hard-boiled** ቅቅል
All we got was some hard-boiled eggs. ለማግኘት ፡ የቻልነው ፡ ቅቅል ፡ እንቁላል ፡ ብቻ ፡ ነበር

**hard-earned** በልፋት ፡ የተገኘ ፤ ለፍቶ ፡ ያገኘ
That was hard-earned money. በልፋት ፡ የተገኘ ፡ ገንዘብ ፡ ነበር
I won't spend my hard-earned money on trifles. ለፍቼ ፡ ያገኘሁትን ፡ ገንዘብ ፡ በማይረባ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ አላጠፋም

**harden** (vt.) አጠነከረ
He hardened his body by exercise. ሰውነቱን ፡ በጅምናስቲክ ፡ አጠነከረ
They hardened the earth by pounding on it. መሬቱን ፡ በመጠቅጠቅ ፡ አጠነከሩት

**harden one's heart** ጨከነ
He hardened his heart and rejected her request. ጨክኖ ፡ ልመናዋን ፡ አልቀበል ፡ አለ

**harden** (vi.)
1. ይበልጥ ፡ ጠጠረ. The cement hardened as it dried. ሲሚንቶው ፡ እየደረቀ ፡ ሲሄድ ፡ ይበልጥ ፡ ጠጠረ
2. ባሰ. Their courage hardened as the battle went against them. ጦርነቱ ፡ እየከዳቸው ፡ ሲሄድ ፡ ጉብዝናቸው ፡ እየባሰ ፡ ሄደ
*His personality hardened over the years. ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ ጠባዩ ፡ ግትር ፡ ሆነ

**hardened** (adj.) ልምደኛ ፤ የቆየ
The hardened criminal will not be pardoned. ልምደኛው ፡ (የቆየው) ፡ ወንጀለኛ ፡ ምሕረት ፡ አይደረግለትም
*The doctor's hardened attitude toward suffering surprised us. የዶክተሩ ፡ ሥቃዩን ፡ ከምንም ፡ አለመቊጠር ፡ አስገረመን

**hardheaded** ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ የማይል
My uncle is a hardheaded businessman. በንግድ ፡ ረገድ ፡ አጎቴ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ የማይል ፡ ሰው ፡ ነው

**hardly**
1. እምብዛም + (negative verb). I hardly know her. እምብዛም ፡ አላውቃትም
His story is hardly true. ታሪኩ ፡ እምብዛም ፡ እውነት ፡ አይደለም
2. ምንም + (negative verb). Under those circumstances, I could hardly blame her. በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ምንም ፡ ልወቅሳት ፡ አልችልም
3. ምንም ፡ ያህል + (negative verb). We hardly had time to eat breakfast. ቁርስ ፡ ለመብላት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ አልነበረንም
4. በልፋት. This is money hardly earned. በልፋት ፡ የተገኘ ፡ ገንዘብ ፡ ነው
*I am so tired I can hardly walk. በጣም ፡ ስለደከመኝ ፡ መራመድ ፡ እንኳ ፡ ተስኖኛል
*He had hardly begun to speak when there was warm applause. ንግግሩን ፡ ከመጀመሩ ፡ ጭብጨባው ፡ አስተጋባ
*You can hardly expect me to believe that. ያንን ፡ ያምናል ፡ ብለህ ፡ አታስብ
*That is hardly the case. ነገሩ ፡ እንዲህ ፡ አይደለም

**hardly any**
1. ምንም ፡ ያህል + negative verb. There is hardly any bread left. ምንም ፡ ያህል ፡ ዳቦ ፡ አልተረፈም
2. እምብዛም + (negative verb). The sea was quiet, with hardly any waves. እምብዛም ፡ ሞገድ ፡ ስላልነበረ ፡ ባሕሩ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ነበር

**hardly anybody** ምንም ፡ ያህል ፡ ሰው + negative verb
Hardly anybody came to the meeting. ምንም ፡ ያህል ፡ ሰው ፡ ለስብሰባው ፡ አልመጣም

**hardly any more** ምንም ፡ ያህል + negative verb
There are hardly any more eggs left. ምንም ፡ ያህል ፡ እንቁላል ፡ አልተረፈም

**hardly ever**
1. እምብዛም + (negative verb). I hardly ever go out. እምብዛም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አልወጣም
2. gerundive + አያውቅም. He hardly ever goes to bed before midnight. ከእኩለ ፡ ሌሊት ፡ በፊት ፡ ተኝቶ ፡ አያውቅም
[See also 'wait']

**hardship**
1. መከራ. He suffered many hardships when he was lost in the desert. ከምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ ጠፍቶ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ደረሰበት
2. ችግር. His boyhood conditioned him to hardship. በልጅነቱ ፡ ችግርን ፡ ለምዷል

**hardware** ከብረት ፡ የተሠሩ ፡ እቃዎች
Where can I buy hardware? ከብረት ፡ የተሠሩ ፡ እቃዎች ፡ ከየት ፡ ልገዛ ፡ እችላለሁ ?

**hard-working** ብርቱ ፡ ሠራተኛ
She is a hard-working woman. ብርቱ ፡ ሠራተኛ ፡ ናት
He is a hard-working man. ብርቱ ፡ ሠራተኛ ፡ ነው

**hardy**
1. ብርቱ. A hardy soldier can march all night. ብርቱ ፡ ወታደር ፡ ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ ሊጓዝ ፡ ይችላል
2. ችግር ፡ የሚችል. Only a hardy adventurer enjoys climbing tall mountains. ረጃጅም ፡ ተራራዎችን ፡ በመውጣት ፡ የሚደሰት ፡ ችግር ፡ የሚችል ፡ ጀብዱ ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው
3. ድርቅ ፡ የሚችል. This is a hardy plant and it can grow in a desert. ይህ ፡ ዕፅ ፡ ድርቅ ፡ የሚችል ፡ ስለሆነ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሊያድግ ፡ ይችላል

**hare** ጥንቸል
Hare breeding is expanding in America. በአሜሪካ ፡ ጥንቸል ፡ ማርባት ፡ እየተስፋፋ ፡ ነው

**harken** አዳመጠ
The congregation harkened to the words of the preacher. ምእመናኑ ፡ ሰባኪውን ፡ አዳመጡት

**harm** (v.)
1. ጐዳ. Smoking harms the lungs. ሲጋራ ፡ ማጤስ ፡ ሳንባን ፡ ይጐዳል
2. አደከመ. The paucity of native-born engineers harms our development. የሀገር ፡ ተወላጅ ፡ መሀንዲሶች ፡ ማነስ ፡ እድገታችንን ፡ ያደክመዋል

**harm** (n.)
1. ጉዳት. The bomb caused much harm to the building. ቦምቡ ፡ በሕንጻው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ አደረሰ
2. ጥፋት. How can I repair the harm done? ላጠፋሁት ፡ ጥፋት ፡ ምን ፡ ልካስ ?
*He means no harm by his remark. የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ለክፋት ፡ አይደለም

**do harm** ጐዳ
Will it do any harm if I leave it out? ባስቀረው ፡ ይጐዳል ?

**there is no harm** ግድ ፡ የለም
There is no harm if there are two. ሁለትም ፡ ከተገኙ ፡ ግድ ፡ የለም

**harmful** ጠንቅ
Smoking two packs of cigarettes a day is harmful to one's health. በቀን ፡ ሁለት ፡ ፓኬት ፡ ሲጃራ ፡ ማጬስ ፡ ለጤና ፡ ጠንቅ ፡ ነው

**be harmful (to)** ጐዳ
This custom is harmful to the country. ይህ ፡ ልማድ ፡ ሀገሪቷን ፡ ይጐዳል

**(be) harmless**
1. አልጐዳም. I tried to reassure her by showing her that the snake was harmless. እባቡ ፡ የማይጐዳ ፡ መሆኑን ፡ ላረጋግጥላት ፡ ሞከርኩ
2. ጉዳት ፡ አላደረሰም. A half-wit is harmless even though he does strange things. ቂል ፡ አንዳንድ ፡ እንግዳ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮችን ፡ ቢፈጽምም ፡ እንኳ ፡ ጉዳት ፡ አያደርስም

**harmonica** አርሞኒካ

**harmonious** በስምምነት ፡ የሚኖር
Their family is the most harmonious one I know. እንደነሱ ፡ ቤተሰብ ፡ በስምምነት ፡ የሚኖር ፡ ማንንም ፡ አላየሁም
*The children play together in a harmonious group. ልጆቹ ፡ ተስማምተው ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ይጫወታሉ
*A beautiful picture has harmonious colors. ውብ ፡ ሥዕል ፡ የቀለማት ፡ ኅብረት ፡ ይታይበታል

**harmonize** (vt.) አስማማ
He tried to harmonize the two factions. ሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ ለማስማማት ፡ ሞከረ

**harmonize** (vi.) ተስማማ
These colors harmonize well. እነዚህ ፡ ቀለማት ፡ በሚገባ ፡ ይስማማሉ

**harmony**
1. መዋሐድ. In a beautiful picture, there is harmony between the different colors. በውብ ፡ ሥዕል ፡ ውስጥ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ መዋሐድ ፡ ይታያል
2. ስምምነት. There was perfect harmony between the two. በሁለቱ ፡ መኻል ፡ ፍጹም ፡ ስምምነት ፡ ነበር

**be in harmony** ተስማማ
His plans are in complete harmony with mine. ሐሳቡ ፡ ከሐሳቤ ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ ይስማማል

**harness** (v.)
1. ጫነ. Don't forget to harness the horse! ፈረሱን ፡ መጫን ፡ አትርሳ
2. ገደበ. The engineers harnessed the waterfall. መሀንዲሶቹ ፡ ፏፏቴውን ፡ ገደቡ

**harness** (n.) የፈረስ ፡ እቃ
The newly bought harness broke. አዲስ ፡ የተገዛው ፡ የፈረስ ፡ እቃ ፡ ተበጠሰ

**take the harness off** ፈረሱን ፡ ፈታ
He took the harness off and let the horse run free in the field. ፈረሱን ፡ ፈቶ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ለቀቀው

**harp** (v.), ~ **on** አዘውትሮ ፡ አነሣ
She was always harping on how wonderful her daughter was. ልጇ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ግሩም ፡ እንደነበረች ፡ አዘውትራ ፡ ታነሣ ፡ ነበር

**harp** (n.) በገና
He can play an Ethiopian harp. የኢትዮጵያን ፡ በገና ፡ መደርደር ፡ ይችላል

**harp player** በገና ፡ ደርዳሪ
This man is the best harp player I know. ይህ ፡ ከማውቃቸው ፡ በገና ፡ ደርዳሪዎች ፡ ሁሉ ፡ የላቀ ፡ ነው

**(be) harried** ራሱ ፡ ዞረ
My father is harried by debts. አባቴ ፡ በዕዳ ፡ ራሱ ፡ ዞሯል

**harrowing** አስጨናቂ
The oral examination was harrowing. የቃል ፡ ፈተናው ፡ አስጨናቂ ፡ ነበር

**harrowing experience** በጣም ፡ አሰቃቂ
The plane crash was a harrowing experience. የአውሮፕላኑ ፡ አደጋ ፡ በጣም ፡ አሰቃቂ ፡ ነበር

**harry**
1. አስጨንቆ ፡ ዘረፈ. The pirates harried the towns along the coast. የባሕር ፡ ወንበዴዎች ፡ በጠረፉ ፡ ዳር ፡ የሚገኙትን ፡ ከተማዎች ፡ አስጨንቀው ፡ ዘረፉ
2. አዋከበ. He harried the speaker with many questions. ተናጋሪውን ፡ በብዙ ፡ ጥያቄ ፡ አዋከበው

**harsh**
1. ጥብቅ. He is a harsh judge. ጥብቅ ፡ ዳኛ ፡ ነው
2. መጥፎ. A harsh climate will shorten a person's life. መጥፎ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ የሰውን ፡ ዕድሜ ፡ ያሳጥራል
3. ጐርናና. A harsh voice is unpleasant to the ear. ጐርናና ፡ ድምፅ ፡ ለጆሮ ፡ ደስ ፡ አይልም
4. ኀይለኛ. His harsh words bruised her feelings. የተናገራት ፡ ኀይለኛ ፡ ቃል ፡ ስሜቷን ፡ ጐዳው
5. ሻካራ. Harsh soap irritates her skin. ሻካራ ፡ ሳሙና ፡ ቆዳዋን ፡ ያስቆጣል
6. አስቸጋሪ. The harsh life of the pioneers is described in this book. የቀደምት ፡ መጪዎቹ ፡ አስቸጋሪ ፡ ኑሮ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጿል
7. ከባድ. Those are harsh terms. የውሉ ፡ ግዴታዎች ፡ ከባድ ፡ ናቸው

**harsh treatment** መጕላላት
Harsh treatment commonly befalls servants. አሽከሮች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መጕላላት ፡ ይደርስባቸዋል

**harshly** በማመናጨቅ
He spoke to him harshly. በማመናጨቅ ፡ ተናገረው

**treat harshly** አጕሳቈለ
He treats his wife harshly. ሚስቱን ፡ ያጕሳቍላታል

**harvest** (v.)
1. አመረተ. He harvested more barley this year than last. ከዓምና ፡ ይልቅ ፡ ዘንድሮ ፡ ብዙ ፡ ገብስ ፡ አመረተ
2. ሰበሰበ. When do you harvest the wheat around here? እዚህ ፡ ስንዴ ፡ የምትሰበስቡት ፡ መቼ ፡ ነው ?

**harvest** (n.)
1. መኸር. Because of the drought, the harvest was bad this year. በድርቁ ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ መኸሩ ፡ መጥፎ ፡ ነበረ
2. አዝመራ. The farmer hired men for the wheat harvest. ገበሬው ፡ ለስንዴው ፡ አዝመራ ፡ ሰዎች ፡ ቀጠረ
3. ዋጋ. He is reaping the harvest of his mistakes. የጥፋቱን ፡ ዋጋ ፡ በመቀበል ፡ ላይ ፡ ነው

**hash** (v.) ከተፈ
He hashed the meat and roasted it in the pan. ሥጋውን ፡ ከትፎ ፡ በመጥበሻ ፡ ጠበሰው

**hash** (n.) ክትፎ
I ate hash for lunch today. ዛሬ ፡ ምሳ ፡ ክትፎ ፡ በላሁ

**hashish** ሀሺሽ
The government forbids the importation of hashish. መንግሥት ፡ ሀሺሽ ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ እንዳይገባ ፡ ይከለክላል

**hassle** የጋለ ፡ ጭቅጭቅ
My friend had a hassle with the taxi driver about the fare. ጓደኛዬ ፡ ከታክሲ ፡ ነጂው ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ዋጋው ፡ የጋለ ፡ ጭቅጭቅ ፡ አደረገ

**haste** ችኰላ ፤ ጥድፊያ
Why all this haste? ችኰላው ፡ (ጥድፊያው) ፡ ምንድን ፡ ነው ?
He left in haste. በችኰላ ፡ ሄደ

**be in haste** ተጣደፈ
He was in haste to get to the store before it closed. መደብሩ ፡ ከመዘጋቱ ፡ በፊት ፡ ለመድረስ ፡ ተጣደፈ

**make haste** ፈጠን ፡ አለ
Make haste or you will miss the plane. አውሮፕላኑ ፡ እንዳያመልጥህ ፡ ፈጠን ፡ በል
[See also 'feverish']

**hasten** (vt.)
1. አፋጠነ. Sunshine hastens the growth of plants. የፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ የዕፀዋትን ፡ እድገት ፡ ያፋጥናል
2. አቀረበ. Smoking will hasten the day of your demise. ማጨስ ፡ የመሞቻህን ፡ ቀን ፡ ያቀርበዋል
3. ቶሎ ፡ እንድ + imperfect + አደረገ. We hastened the children across the street. ልጆቹ ፡ መንገዱን ፡ ቶሎ ፡ እንዲሻገሩ ፡ አደረግን

**hasten** (vi.) ተጣደፈ
The children were hastening to get to school on time. ልጆቹ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በሰዓቱ ፡ ለመድረስ ፡ ይጣደፉ ፡ ነበር

**hastily** በችኰላ
They took leave hastily. በችኰላ ፡ ተሰናበቱ

**hastiness** ችኩልነት
I must reprehend your hastiness. በችኩልነትህ ፡ ልወቅስህ ፡ ይገባል

**hasty**
1. ችኩል. Don't be so hasty, give the matter more thought! እንደዚህ ፡ ችኩል ፡ አትሁን ፤ በጉዳዩ ፡ ትንሽ ፡ አስብበት
2. የችኰላ. His concession that he made a hasty decision was all we wanted to hear. ለመስማት ፡ የፈለግነው ፡ የችኰላ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠቱን ፡ ማመኑን ፡ ብቻ ፡ ነው
3. በችኰላ ፡ ያደረገ. His hasty decisions caused many mistakes. በችኰላ ፡ ያደረገው ፡ ውሳኔ ፡ ብዙ ፡ ስሕተቶችን ፡ አስከተለ
4. (= adv.) ጐራ ፡ ብሎ. He paid me a hasty visit while on his way to work. ወደ ፡ ሥራ ፡ ሲሄድ ፡ ጐራ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀኝ

**be hasty** አስቸኰለ
+I wouldn't be hasty about it. ምንም ፡ የሚያስቸኵል ፡ ነገር ፡ የለም
[See also 'retreat']

**hat** ባርኔጣ
Foreign hats were introduced only recently to Ethiopia. የውጭ ፡ አገር ፡ ባርኔጣዎች ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ነው
[See also 'drop, tip']

**hatch** (vt.) ፈለፈለ
The mother hen hatches her eggs by sitting on them. እናቲቱ ፡ ዶሮ ፡ እንቁላል ፡ የምትፈለፍለው ፡ በመታቀፍ ፡ ነው
A hen hatches chickens. ዶሮ ፡ ጫጩት ፡ ትፈለፍላለች

**hatch** (vi.) ተፈለፈለ
Three more chicks hatched today. ዛሬ ፡ ሌላ ፡ ሦስት ፡ ጫጩቶች ፡ ተፈለፈሉ
All the eggs hatched. እንቁላሎቹ ፡ በሙሉ ፡ ተፈለፈሉ

**hatch a scheme** በምስጢር ፡ ዘየደ
The rebels hatched a scheme to get arms. ሽፍቶቹ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ለማግኘት ፡ በምስጢር ፡ ዘየዱ

**hatchet** መጥረቢያ
He cut the branches off the tree with a hatchet. የዛፉን ፡ ቅርንጫፍ ፡ በመጥረቢያ ፡ ቈረጠ

**hatching** እንቁላል ፡ መቀፍቀፍ
This is the optimum temperature for hatching. እንቁላል ፡ ለመቀፍቀፍ ፡ ይህ ፡ እጅግ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ሙቀት ፡ ነው

**hate** (v.)
1. ጠላ. God! How I hate getting up in the morning! አቤት ! ጧት ፡ መነሣት ፡ እንደምጠላ !
2. አልወደደም. I hate to flatter anybody. ማንንም ፡ ቢሆን ፡ በከንቱ ፡ ማወደስ ፡ አልወድም
3. አዘነ. I hate to disoblige you, but I must leave now. ልረዳህ ፡ ስለማልችል ፡ አዝናለሁ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ መሄድ ፡ አለብኝ

**hate** (n.) ጥላቻ
He was consumed with hate for his tormentors. ባሠቃዩት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጥላቻ ፡ አደረበት

**hateful**
1. ጥላቻ ፡ የተመላበት. His hateful remarks reveal his bitterness towards his teacher. ጥላቻ ፡ የተመላበት ፡ አስተያየቱ ፡ ባስተማሪው ፡ መመረሩን ፡ ያሳያል
2. አስከፊ. Murder is a hateful crime. ነፍስ ፡ መግደል ፡ አስከፊ ፡ ወንጀል ፡ ነው

**hatemonger** ጥላቻ ፡ የሚነዛ
Don't listen to the hatemonger's speeches! ጥላቻ ፡ የሚነዛውን ፡ ሰውዬ ፡ ንግግር ፡ አታዳምጥ

**hatred**
1. ቂም. With passage of time, old hatreds are forgotten. ጊዜ ፡ እየገፋ ፡ ሲሄድ ፡ የጥንት ፡ ቂም ፡ ይረሳል
2. ጥላቻ. I feel no hatred for him. በሱ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ጥላቻ ፡ የለኝም

**haughtiness** እብሪት
His haughtiness offends everyone. እብሪቱ ፡ ሁ
ሉንም ፡ ያስቀይማል

**haughty**
1. የትዕቢት. His haughty words show he is infected with pride. የትዕቢት ፡ አነጋገሩ ፡ በኩ
ራት ፡ የተመረዘ ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል
2. ትዕቢተኛ. A haughty girl is unpopular in school. ትዕቢተኛ ፡ ልጃገረድ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተወዳጅ ፡ አይደለችም

**haul**
1. ጐተተ. They used several mules to haul the car out of the ditch. መኪናውን ፡ ከጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ለመጐተት ፡ በብዙ ፡ በቅሎዎች ፡ ተገለገሉ
2. አጓጓዘ. The company had to use extra buses to haul the crowd to the stadium. ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ ስታድዮሙ ፡ ለማጓጓዝ ፡ ኩባንያው ፡ በተጨማሪ ፡ አውቶቡሶች ፡ መገልገል ፡ ግድ ፡ ሆነበት

**haul away** ወሰደ
The truck hauled our furniture away. መኪና
ው ፡ እቃችንን ፡ ወሰደልን

**haul down** አወረደ
After their defeat, they hauled down their flag. ድል ፡ ከሆኑ ፡ በኋላ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማቸውን ፡ አወረዱ

**haunch** ወገብ
He hit him on the haunch with a stick. ከወገቡ ፡ ላይ ፡ በዱላ ፡ መታው

**haunt**
1. ሰፈረ(በት). They thought ghosts haunted the abandoned house. እናው ፡ ቤት ፡ ጣረሞቶች ፡ የሰፈሩበት ፡ መሰላቸው
2. አስበረገገ. The memory of the accident haunted him for many years. ያደጋው ፡ ትዝ
ታ ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ አስበረገገው
3. ከሐሳቡ ፡ አልጠፋ ፡ አለ. Memories of love haunted him. የፍቅር ፡ ትዝታ ፡ ከሐሳቡ ፡ አል
ጠፋ ፡ አለ
4. አልጠፋም. The specter of the murdered man still haunts the house. የተገደለው ፡ ሰውዬ ፡ መንፈስ ፡ አሁንም ፡ ከቤቱ ፡ አልጠፋም
5. አሸበረ. The specter of war haunts every sensible person. የጦርነቱ ፡ ስጋት ፡ አስተዋይ ፡ ሰ
ው ፡ ያሸብራል
6. አዘወተረ. He used to haunt bookstores. የመጻሕፍት ፡ መደብሮችን ፡ ያዘወትር ፡ ነበር

**have** (he has, he had)
1. አለ(ው). +I have a book. መጽሐፍ ፡ አለኝ
2. ያዘ(ው). +He had a bad cold last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ከፉ ፡ ጉንፋን ፡ ይዞት ፡ ነበር
3. በላ. He had some cake before going to bed. ከመተኛቱ ፡ በፊት ፡ ኬክ ፡ በልቶ ፡ ነበር
*Let him have it! (= keep it) እስቲ ፡ ተውለት
*Let him have it! (= hit him) በለው
*Rumor has it that the minister will resign. ሚኒስትሩ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ሥራቸውን ፡ ይለቃሉ ፡ የሚል ፡ ጭምጭምታ ፡ ይሰማል
*I will not have it. እንዲደረግ ፡ አልፈቅድም
*He wanted to marry her, but she wouldn't have him. ሊያገባት ፡ ፈልጎ ፡ ነበር ፤ እሷ ፡ ግን ፡ እ
ምቢ ፡ አለች

**had rather** ይወድ ፡ ነበር
I had much rather he go with you. አብሮህ ፡ ቢ
ሄድ ፡ እወድ ፡ ነበር

**have done**
*Pay the man off and have done with him! ከፈለውና ፡ ወዲያ ፡ ተገላገለው

**have it coming**
*When they lost their fortune, everyone said that they had it coming. ንብረታቸውን ፡ ሲያ
ጡ ፡ ሁሉም ፡ እንኳን ፡ አለ

**have it in for** ጠላ
She has it in for intelligent students who fail to use their abilities. በችሎታቸው ፡ የማይጠቀ
ሙ ፡ ጐበዝ ፡ ልጆችን ፡ ትጠላለች

**have it out**
*We've been in disagreement about this for a long time, and I think we should have it out, once and for all. በዚህ ፡ ነገር ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሳ
ንስማማ ፡ ቆይተናል ፤ ከእንግዲህ ፡ አንድ ፡ እል
ባት ፡ ብናበጅለት ፡ ይሻል ፡ ይመስለኛል

**have nothing on**
1. ራቁቱን ፡ ነው. The crazy person had nothing on and sat by the edge of the road. እብዱ ፡ ራቁቱን ፡ ሆኖ ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ተቀመጠ
2. ሥራ ፡ የለ(ውም). I have nothing on for tomorrow evening. ነገ ፡ ማታ ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ የለ
ኝም

**have on**
1. ለበሰ. He has his sweater on inside out. ሹራቡን ፡ ገልብጦ ፡ ለብሶታል
2. ለማድረግ ፡ አሰበ. What do you have on for Easter? ለፋሲካ ፡ ምን ፡ ለማድረግ ፡ አስበሃል ?

**have over** ጋበዘ
We are having the Smiths over for supper. ስሚዝንና ፡ ባለቤቱን ፡ ለራት ፡ ጋብዘናል

**have to**
1. አለ(በት). I have to go to the dentist tomorrow. ነገ ፡ ወደ ፡ ጥርስ ፡ ሐኪም ፡ መሄድ ፡ አለብኝ
2. ግድ ፡ ሆነ(በት). We didn't want to but we had to. አልፈለግንም ፡ ነበር ፤ ግድ ፡ ሆኖብን ፡ ነው

**have to do with**
1. በ - - - ገባ. I don't want to have anything to do with it. በጉዳዩ ፡ ለመግባት ፡ አልፈልግም
2. ግንኙነት ፡ አለ(ው). What does this proposal have to do with the irrigation project? ይህ ፡ ሐሳብ ፡ ከመስኖው ፡ ሥራ ፡ እቅድ ፡ ጋር ፡ ምን ፡ ግንኙነት ፡ አለው ?

**not have to** አይገባ(ውም)
You don't have to make fun of him. በሱ ፡ መቀለድ ፡ አይገባህም

## haven
1. ማረፊያ. The travelers found haven at the inn. መንገደኞቹ ፡ በሆቴሉ ፡ ማረፊያ ፡ አገኙ
2. መሸሸጊያ. These mountains are a haven for fugitives. እነዚህ ፡ ተራራዎች ፡ ወንጀል ፡ ፈጽመው ፡ ለሚደበቁ ፡ ሰዎች ፡ መሸሸጊያ ፡ ናቸው

## havoc ጥፋት
The floods caused terrible havoc. ጎርፉ ፡ ታላቅ ፡ ጥፋት ፡ አስከተለ

**play havoc with**
1. በታተነ. The wind played havoc with the papers on the desk. ነፋሱ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ወረቀት ፡ በታተነው
2. አበላሸ. The bad weather played havoc with our vacation plans. መጥፎው ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ እቅዳችንን ፡ አበላሸው

## hawk (v.)
*A peddler is hawking his wares outside. እዳጅ ፡ አንድ ፡ ሱቅ ፡ በደረቱ ፡ ይህን ፡ ፈላጊ ፡ እያለ ፡ ይጮኻል
*They hawked ice cream along the beach. ከባሕሩ ፡ ዳር ፡ አይስክሬም ፡ ፈላጊ ፡ እያሉ ፡ ላይ ፡ ታች ፡ አሉ

## hawk (n.) ጭልፊት
A hawk will kill your chicken. ጭልፊት ፡ ዶሮህን ፡ ትነጥቃለች

## hay ድርቆሽ
Cattle must have hay to eat. ከብቶች ፡ የሚበሉት ፡ ድርቆሽ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ያስፈልጋል

## haystack የድርቆሽ ፡ ክምር
Do farmers in Ethiopia have haystacks? በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ገበሬዎች ፡ የድርቆሽ ፡ ክምር ፡ ያስቀምጣሉ ?

## (be) haywire ትርምስምስ ፡ አለ
Everything is haywire. ሁሉ ፡ ነገር ፡ ትርምስምስ ፡ ብሏል

**go haywire** መላ ፡ ቅጡ ፡ ጠፋ
Everything went haywire in the house. እዚህ ፡ ቤት ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ መላ ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቷል

## hazard (v.)
*Thieves hazard arrest. ሌቦቹ ፡ ብንያዝም ፡ ብለው ፡ ይሰርቃሉ

**hazard one's life** ለሕይወቱ ፡ አሰጋ(ው) ፤ በሕይወቱ ፡ ተዋሰ
Pilots sometimes hazard their lives. አውሮፕላን ፡ ነጂዎች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ለሕይወታቸው ፡ ያሰጋቸዋል
I would hazard my life on his honesty. ለታማኝነቱ ፡ በሕይወቴ ፡ እዋሳለሁ

## hazard (n.) አደጋ
This dry hay is a fire hazard. ይህ ፡ ደረቅ ፡ ሣር ፡ የሳት ፡ አደጋ ፡ ያመጣል
The job was full of hazards. ሥራው ፡ አደጋ ፡ የበዛበት ፡ ነበር

**be a hazard**
1. አደጋ ፡ አስከተለ. Reckless drivers are hazards to other motorists. ግዴለሽ ፡ ነጂዎች ፡ ለሌሎች ፡ ባለመኪናዎች ፡ አደጋ ፡ ያስከትላሉ
2. አስነሣ. These oily rags are a fire hazard. እነዚህ ፡ ዘይት ፡ የጠጡ ፡ ጨርቆች ፡ እሳት ፡ ያስነሣሉ

## hazardous አደገኛ
It is hazardous to cross the desert during the daytime. ምድረ ፡ በዳውን ፡ በቀን ፡ ማቋረጥ ፡ አደገኛ ፡ ነው

## haze ጭጋግ
The haze kept us from seeing the mountains. ጭጋጉ ፡ ተራራዎችን ፡ ከማየት ፡ አገደን

## hazy ጭጋጋም
The air is hazy, and one cannot see the mountains. አየሩ ፡ ጭጋጋም ፡ ስለሆነ ፡ ተራራዎቹን ፡ ማየት ፡ አይቻልም

**be hazy** ግልጽ ፡ አይደለም
His ideas are hazy. ሐሳቡ ፡ ሁሉ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም

**he**

1. እርሱ ፤ እሱ. He is a student. እሱ ፡ (እርሱ) ፡ ተማሪ ፡ ነው
2. ወንድ. Is that lion a he or a she? ያ ፡ አንበሳ ፡ ወንድ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ሴት ?

**he is** ነው
He is lazy. ሰነፍ ፡ ነው

**he who**
1. የ + perfect. He who spoke just now is my brother. አሁን ፡ የተናገረው ፡ የኔ ፡ ወንድም ፡ ነው
2. የም ፡ (እም) + imperfect. He who leaves last should turn off the light. በመጨረሻ ፡ የሚወጣው ፡ መብራቱን ፡ ማጥፋት ፡ አለበት

**head** (vt.)

1. መራ. The honored guests headed the parade. የክብር ፡ እንግዶቹ ፡ ሰልፉን ፡ መሩ
The pilot headed his plane toward the sea. አውሮፕላን ፡ ነጂው ፡ አውሮፕላኑን ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ መራ
2. ሹም ፡ ሆነ ፤ ኀላፊ ፡ ነው. He hopes to head his department one day. ወደ ፡ ፊት ፡ የክፍሉ ፡ ሹም ፡ እንደሚሆን ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋል
Our teacher heads the history department. መምህራችን ፡ የታሪክ ፡ ክፍል ፡ ኀላፊ ፡ ነው
3. አንደኛ ፡ ሆነ. My boy heads his class at school. ልጄ ፡ ከክፍሉ ፡ አንደኛ ፡ ነው
*His name heads the list of candidates. በእጩዎቹ ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ የመጀመሪያው ፡ ስም ፡ የሱ ፡ ነው

**head** (vi.) አመራ
You are heading in the wrong direction. የምታመራው ፡ ወደ ፡ ተሳሳተ ፡ መንገድ ፡ ነው
It's getting late; we'd better head for home. እየመሸ ፡ ሄደ ፤ ወደ ፡ ቤት ፡ ብናመራ ፡ ይሻላል

**head off** ከ --- አዳነ
Quick thinking headed off a collision. ንቃት ፡ ከግጭት ፡ አዳነው

**head** (n.)

1. ራስ. My head hurts. ራሴን ፡ አሞኛል
2. ጭንቅላት. The head of a nail is designed for pounding. የምስማር ፡ ጭንቅላት ፡ ለመምታት ፡ እንዲመች ፡ ሆኖ ፡ የተሠራ ፡ ነው
The hand grenade blew off his head. የእጅ ፡ ቦምብ ፡ ጭንቅላቱን ፡ በታተነው
3. አውራ. He is the head of the family. የቤተ ፡ ሰቡ ፡ አውራ ፡ ነው
4. መሪ. Heads of government will meet in Cairo. የየመንግሥታት ፡ መሪዎች ፡ ካይሮ ፡ ላይ ፡ ይሰበሰባሉ
5. ኀላፊ. He is the head of the firm. የኩባንያው ፡ ኀላፊ ፡ ነው
6. ሊቀ ፡ መንበር. The head of a committee must serve for two years. የደርጉ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ማገልገል ፡ አለበት
7. አለቃ. He is the head of the gang. የዱሪዬዎቹ ፡ አለቃ ፡ ነው
8. ምንጭ. The head of the river is located in the mountains. የወንዙ ፡ ምንጭ ፡ የሚገኘው ፡ ተራራዎቹ ፡ ላይ ፡ ነው
9. አናት. He stood at the head of the staircase before descending. ከመውረዱ ፡ በፊት ፡ በደረጃው ፡ አናት ፡ ላይ ፡ ቆመ
Begin at the head of the page! ከገጹ ፡ አናት ፡ ጀምር
We were sitting at the head of the table. ከጠረጴዛው ፡ አናት ፡ ተቀምጠን ፡ ነበር
10. ርእስ (pl. አርእስት). He arranged his speech under four heads. ንግግሩን ፡ በአራት ፡ አርእስት ፡ አዘጋጀ
11. ጥቅል. Lettuce is ten cents a head. አንድ ፡ ጥቅል ፡ ሰላጣ ፡ ዐሥር ፡ ሳንቲም ፡ ነው
12. (zero). He sold five head of cattle. አምስት ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ ሸጠ
*He has a good head for arithmetic. ሒሳብ ፡ ይሆነዋል

**head** (adj.) ዋና
This is the head office. ይህ ፡ ዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ነው
The head nurse will give you instructions. ዋናዋ ፡ ነርስ ፡ መምሪያ ፡ ትሰጣችኋለች

**head and all** ልቅም ፡ አድርጎ
The dog ate the fish, head and all. ውሻው ፡ ዓሣውን ፡ ልቅም ፡ አድርጎ ፡ በላው

**head of the bed** (= adv.) አልጋው ፡ ራስጌ ፡ ላይ
The head of the bed has a lamp on it. አልጋው ፡ ራስጌ ፡ ላይ ፡ መብራት ፡ አለ

**heads or tails** ዘውድ ፡ ወይስ ፡ አንበሳ
Which is it? Heads or tails? Flip the coin again! ዘውድ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ አንበሳ ፤ ሳንቲሙን ፡ እንደገና ፡ ወርውረው

**head over heels** ከልክ ፡ በላይ
They were head over heels in love. ከልክ ፡ በላይ ፡ ተዋደው ፡ ነበር

**be head and shoulders above** በለጠ
In intelligence, he is head and shoulders above the children in his class. በችሎታው ፡ ከክፍል ፡ ጓደኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ይበልጣል

**be out of one's head** አበደ
The man is out of his head. ሰውዬው ፡ አብዷል

**be over one's head**
1. ከበደ. Arithmetic is over my head. ሒሳብ ፡ ይከብደኛል
2. ከችሎታው ፡ በላይ ፡ ሆነ(በት). The mathematical problems were over his head. የሒሳቡ ፡ ፕሮብሌሞች ፡ ከችሎታው ፡ በላይ ፡ ሆኑበት

**bring to a head** አፈረጠ
The committee's new position brought the entire matter to a head. ደርጉ ፡ የወሰደው ፡ አዲስ ፡ አቋም ፡ ነገሩን ፡ አፈረጠው

**come to a head**
1. ያበጠው ፡ መፈንዳቱ ፡ አይቀርም. The situation in the country is bad, and it will come to a head sooner or later. ሀገሪቷ ፡ ያለችበት ፡ ሁኔታ ፡ መጥፎ ፡ ነው ፤ ውሎ ፡ አድሮ ፡ ያበጠው ፡ መፈንዳቱ ፡ አይቀርም
2. ተካረረ. The quarrel between the two countries came to a head, and war broke out between them. በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ጠብ ፡ ተካሮ ፡ ጦርነት ፡ ተጀመረ
3. ተፋፋመ. The struggle for power came to a head. ሥልጣን ፡ ለመያዝ ፡ ያለው ፡ ትግል ፡ ተፋፋመ

**cry one's head off**
The child cried his head off. ልጁ ፡ እርር ፡ ብሎ ፡ አለቀሰ

**from head to toe**
He was wet from head to toe. ከራስ ፡ ጸጉሩ ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጥፍሩ ፡ ድረስ ፡ ርሶ ፡ ነበር

**go over one's head**
1. አለፈ. I don't want to go over the teacher's head and appeal to the principal. አስተማሪውን ፡ አልፌ ፡ ለሥራ ፡ መሪው ፡ አቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ አልፈልግም
2. ሥልጣኑን ፡ ተጋፋ. I don't want to go over his head. ሥልጣኑን ፡ ለመጋፋት ፡ አልፈልግም

**go to one's head**
1. ራሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ. The whiskey went to his head very quickly. ዊስኪው ፡ ቶሎ ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ
2. ትዕቢት ፡ አደረበት. Success has gone to his head. ስለተሳካለት ፡ ትዕቢት ፡ አድሮበታል

**have on one's head**
*Because of his reckless driving he now has the deaths of three persons on his head. በግዴለሽ ፡ አነዳዱ ፡ የሦስት ፡ ሰው ፡ ሕይወት ፡ አጥፍቷል

**hold (one's) head down** ጐንበስ ፡ አለ
He held his head down to show me that he was bald. መላጣውን ፡ ሊያሳየኝ ፡ ጐንበስ ፡ አለ

**keep one's head** ሳይሸበር ፡ ቆየ
He kept his head during the riot. በሁከቱ ፡ ጊዜ ፡ ሳይሸበር ፡ ቆየ

**lose one's head**
1. ናላው ፡ ዞረ. When the fire broke out he simply lost his head. ቃጠሎው ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ናላው ፡ ዞረ
2. ተቀላ. Many innocent persons lost their heads in the French Revolution. በፈረንሳይ ፡ ሽብር ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያለ ፡ ኀጢአታቸው ፡ ተቀሉ

**(not) lose one's head** ራሱን ፡ ተቈጣጠረ
The most important thing is not to lose your head. ዋናው ፡ ነገር ፡ ራስህን ፡ መቈጣጠር ፡ ነው

**make head or tail** በጭራሽ ፡ ተረዳ(ው) ፤ ገባ(ው)
I can't make head or tail of that poem. ያንን ፡ ግጥም ፡ በጭራሽ ፡ ለመረዳት ፡ አልችልም
Can you make head or tail of what he says? የሚለው ፡ ይገባሃል

**march at the head of** መራ
He marched at the head of the parade. ሰልፉን ፡ ይመራ ፡ ነበር

**put heads together** አንድ ፡ ላይ ፡ አሰቡ(በት) ፤ ተመካከሩ
I am sure that if you put your heads together, you will find a solution. አንድ ፡ ላይ ፡ ብታስቡበት ፡ (ብትመካከሩ) ፡ መፍትሔ ፡ እንደምታገኙለት ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ

**stand head and shoulders above** ልቆ ፡ ታየ
He stands head and shoulders above his rivals. ከተወዳዳሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ልቆ ፡ ይታያል

**turn one's head**
1. ኩራት ፡ አሳደረ. Praise will turn anyone's head. ምስጋና ፡ በማንኛውም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ኩራት ፡ ያሳድራል
2. የ - - - ተገዥ ፡ ሆነ. Don't let flattery turn your head! የከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ተገዥ ፡ አትሁን
[See also various nouns and verbs with 'head' such as 'bare, bow, roof']

## headache የራስ ፡ ምታት
I have a bad headache and cannot go to school. ኀይለኛ ፡ የራስ ፡ ምታት ፡ ስለያዘኝ ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ አልችልም

**give a headache** ራሱን ፡ አሳመመው
This noise gives me a headache. ይህ ፡ ጫጫታ ፡ ራሴን ፡ ያሳምመኛል

## headdress
1. የጸጉር ፡ አሠራር. She changes her headdress

every day. የጸጉር ፡ አሠራሯን ፡ በየቀኑ ፡ ትለዋውጠዋለች
2 ጉፈር. He wore a headdress made of a lion's mane. ከንበሳ ፡ ጋማ ፡ የተሠራ ፡ ጉፈር ፡ ለበሰ
3. ሻሽ. The women wore headdresses made of colorful cloth. ሴቶቹ ፡ ከዥጉርጉር ፡ ጨርቅ ፡ የተሠራ ፡ ሻሽ ፡ አስረው ፡ ነበር

**headfirst** ራሱን ፡ ቁልቁል ፡ አድርጎ
He dived into the water headfirst. ራሱን ፡ ቁልቁል ፡ አድርጎ ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ጠለቀ
**jump headfirst** በድንገት ፡ ጥልቅ ፡ አለ
He jumped headfirst into the argument. ከርክሩ ፡ ውስጥ ፡ በድንገት ፡ ጥልቅ ፡ አለ

**headgear** ቆብ
The miners' headgear is made of steel. የማዕድን ፡ ቆፋሪዎቹ ፡ ቆብ ፡ ከብረት ፡ የተሠራ ፡ ነው

**heading** ርእስ
Can we lump all these items together under one heading? እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ ባንድ ፡ ርእስ ፡ ሥር ፡ ልናጠቃልላቸው ፡ እንችላለን ?

**headlight** የፊት ፡ መብራት
Dim your headlights while driving in the city! ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ስትነዳ ፡ የፊት ፡ መብራትህን ፡ መቀነስ ፡ አለብህ

**headline** አርእስተ ፡ ዜና
The headline read, "War is declared". አርእስተ ፡ ዜናው ፡ « ጦርነት ፡ ታወጀ » ፡ የሚል ፡ ነበር

**headlong** ዓይኑን ፡ ጨፍኖ
He rushed headlong into a fight. ዓይኑን ፡ ጨፍኖ ፡ ጠቡ ፡ ውስጥ ፡ ዘሎ ፡ ገባ
**dash headlong** በድንገት ፡ ገባ
Chasing the ball he dashed headlong into the street. ኳሷን ፡ ሲያባርር ፡ በድንገት ፡ መንገድ ፡ ውስጥ ፡ ገባ
**plunge headlong** በራሱ ፡ ዘሎ ፡ ገባ
He plunged headlong into the river. ወንዙ ፡ ውስጥ ፡ በራሱ ፡ ዘሎ ፡ ገባ

**headman** ጭቃ ፡ ሹም
He is a village headman from Sidamo. በሲዳሞ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ጭቃ ፡ ሹም ፡ ነው

**headmaster** ዲሬክተር
He is a headmaster of a secondary school. የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዲሬክተር ፡ ነው

**head-on** (= adv.) ፊት ፡ ለፊት
Five died in a head-on collision yesterday. ትናንትና ፡ መኪኖች ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተጋጭተው ፡ አምስት ፡ ሰው ፡ ሞተ

**headquarters**
1. ጠቅላይ ፡ መምሪያ ፤ ዋና ፡ መምሪያ. This officer was attached to headquarters. መኰንኑ ፡ ጠቅላይ ፡ (ዋና) ፡ መምሪያው ፡ ተመደበ
2. ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት. The salesmen were always in touch with headquarters. አሻሻጮቹ ፡ ሁልጊዜ ፡ ከዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ነበራቸው

**headrest**
1. ትራስ. He rolled up his blanket and used it as a headrest. ብርድ ፡ ልብሱን ፡ ዐጣጥፎ ፡ ትራስ ፡ አደረገው
2. የዕንጨት ፡ ትራስ. Ethiopian women use headrests instead of pillows. ኢትዮጵያውያን ፡ ሴቶች ፡ በጨርቅ ፡ ትራስ ፡ ፈንታ ፡ የዕንጨት ፡ ትራስ ፡ ይንተራሳሉ

**headset** የጆሮ ፡ ማዳመጫ
Does this radio need a new headset? ይህ ፡ ሬዲዮ ፡ አዲስ ፡ የጆሮ ፡ ማዳመጫ ፡ ያስፈልገዋል ?

**headstall** ቶሎ
The straps of the headstall broke. የቶሎው ፡ ጠፍር ፡ ተበጠሰ

**headstrong** ሐሳበ ፡ ግትር
She is very headstrong and hard to control. እሷ ፡ በጣም ፡ ሐሳበ ፡ ግትርና ፡ ለመቈጣጠርም ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆነች ፡ ናት

**headwaters** ምንጭ
The headwaters of the Nile are in Ethiopia. የዓባይ ፡ ምንጩ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**headway, make ~** ወደፊት ፡ ገፋ
There have been many delays, but we are at last making headway. ብዙ ፡ መዘግየት ፡ ተደርጓል ፤ ሆኖም ፡ በመጨረሻው ፡ ወደፊት ፡ በመግፋት ፡ ላይ ፡ ነን
**make little headway** እምብዛም ፡ አልተሳካለትም
The club made little headway in raising funds. ክበቡ ፡ ገንዘብ ፡ በመሰብሰብ ፡ ረገድ ፡ እምብዛም ፡ አልተሳካለትም
**make no headway**
1. ምንም ፡ አላደረገም. They made no headway in solving their problems. ለችግራቸው ፡ መፍትሔ ፡ ለማግኘት ፡ ምንም ፡ አላደረጉም
2. ወደፊት ፡ ሊገፋ ፡ አልቻለም. They made no headway against the strong winds. በኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ምክንያት ፡ ወደፊት ፡ ሊገፉ ፡ አልቻሉም

**make slow headway** አዘገመ
We made only slow headway in the deep snow. በጥልቁ ፡ በረዶ ፡ ውስጥ ፡ አዘገምን

**heal** (vt.)
1. አዳነ. He healed the wound by putting medicine on it. ቁስሉን ፡ መድኃኒት ፡ አስሮ ፡ አዳነው
2. አስወገደ. He tried to heal the split between the two sides. እርሱ ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ አለመግባባት ፡ ለማስወገድ ፡ ሞከረ

**heal** (vi.) ጠገን ፤ ዳነ
The fracture is healing slowly. ስብራቱ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየጠገን ፡ ነው
The wound is not healing properly. ቁስሉ ፡ በደንብ ፡ አልድን ፡ አለ

**be healed** ዳነ
The wound is not healed yet. ቁስሉ ፡ ገና ፡ አልዳነም

**healer** መድኀኒተኛ
The healer resurrects the dead, so some people say. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ መድኀኒተኛው ፡ የሞቱትን ፡ ያድናል ፡ ይላሉ

**healing**
*The healing of the wound took several months. ቁስሉ ፡ ሳይድን ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ ቆየ

**health**
1. ጤንነት. Though he is very old he is still in good health. ምንም ፡ እንኳ ፡ በጣም ፡ ቢያረጅ ፡ ጤንነቱ ፡ አልታወከም
2. የጤና ፡ አጠባበቅ. Comprehension of the fundamental principles of health is essential. መሠረታዊ ፡ የጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ዘዴን ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**Ministry of Health** የጤና ፡ ጥበቃ ፡ ሚኒስቴር
The Ministry of Health distributed drugs against malaria to the people. የጤና ፡ ጥበቃ ፡ ሚኒስቴር ፡ የወባ ፡ መከላከያ ፡ መድኃኒት ፡ ለሕዝብ ፡ ዐደለ

**drink to one's health** ለ - - - ጤንነት ፡ ጽዋ ፡ አነሣ
We all drank to the bride's health. ሁላችንም ፡ ለሙሽሪቷ ፡ ጤንነት ፡ ጽዋችንን ፡ አነሣን

**public health** የጤና ፡ ጥበቃ
He published a pamphlet on public health. ስለ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ ትንሽ ፡ መጽሐፍ ፡ አወጣ
[See also 'bad, ill, low, poor']

**healthful** ጤና ፡ የሚሰጥ
Children must eat healthful food. ልጆች ፡ ጤና ፡ የሚሰጣቸውን ፡ ምግብ ፡ መብላት ፡ አለባቸው

**healthy**
1. ጤናማ. She looks healthy. ጤናማ ፡ ትመስላለች
2. ጤነኛ. A healthy body presupposes a proper diet. ጤነኛ ፡ አካል ፡ በተሟላ ፡ ምግብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው
3. ለጤና ፡ ተስማሚ. This is not a healthy climate. ይህ ፡ አየር ፡ ለጤና ፡ ተስማሚ ፡ አይደለም
4. ቅን. The minister's healthy attitude toward education was acclaimed. ሚኒስትሩ ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ያለው ፡ ቅን ፡ አስተያየት ፡ ተመሰገነ

**keep healthy** በሚገባ ፡ ያዘ
Farmers diversify crops to keep the soil healthy. አፈሩን ፡ በሚገባ ፡ ለመያዝ ፡ ገበሬዎች ፡ ሰብሉን ፡ ያለዋውጣሉ

**keep (one) healthy** በጤንነት ፡ አኖረ
His abstention from alcohol kept him healthy. ከአልኮል ፡ መጠበቁ ፡ በጤንነት ፡ አኖረው

**stay healthy** በጤንነት ፡ ቆየ
We have to keep fit to stay healthy. በጤንነት ፡ ለመቆየት ፡ ሰውነታችንን ፡ መጠበቅ ፡ አለብን

**heap** (v.)
1. ቈለለ(ተቈለለ). He heaped my plate with food. ሳሕኔ ፡ ላይ ፡ ምግብ ፡ ቈለለ
The table was heaped with all kinds of food. ጠረጴዛው ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ምግብ ፡ ተቈልሎበት ፡ ነበር
2. ከመረ. The farmer heaped grass in the corner of the shed. ገበሬው ፡ ሣሩን ፡ በጎጆ ፡ ሥር ፡ ከመረው
3. ጫነ(በት). The boss heaped work on the secretaries. አለቃው ፡ ጸሐፊዎቹ ፡ ላይ ፡ ሥራ ፡ ጫነባቸው

**heap on (upon)**
1. ብዙ ፡ አደረገ(ለት). He heaped gifts upon me. ብዙ ፡ ስጦታ ፡ አደረገልኝ
2. የ - - - መዓት ፡ አወረደ(በት). The man heaped insults on his enemy. ሰውዬው ፡ በጠላቱ ፡ ላይ ፡ የስድብ ፡ መዓት ፡ አወረደበት

**heap up** አከማቸ
He heaped up riches by dishonest dealings. በማጭበርበር ፡ ሀብት ፡ አከማቸ

**heap** (n.)
1. ክምር. There is a heap of books on the table. ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ የመጽሐፍ ፡ ክምር ፡ አለ
2. ቁልል. They put a heap of sand by my door. ደጃፌ ፡ ላይ ፡ ያሸዋ ፡ ቁልል ፡ አስቀመጡ

**heap of** መዓት
That's a heap of money. መዓት ፡ ገንዘብ ፡ ነው

**heaps of** ብዙ
We have heaps of books for sale. የሚሸጡ ፡ ብዙ ፡ መጽሐፎች ፡ አሉን
[See also 'pile']

**hear** (heard)
1. ሰማ. I didn't hear anything. ምንም ፡ አልሰማሁም
You must hear what he has to say. እሱ ፡ የሚለውን ፡ መስማት ፡ አለብህ
2. ተሰማ(ው). I hear someone coming. የሰው ፡ ኮቴ ፡ ይሰማኛል
3. ተቀበለ. They refused to hear our side of the argument. በበኩላችን ፡ ለንገሩ ፡ የነበረንን ፡ አስተያየት ፡ አንቀበልም ፡ አሉ
4. ወሬ ፡ ሰማ ፤ ወሬ ፡ ደረሰ(ው). Have you heard from your friend? ስለ ፡ ጓደኛህ ፡ ወሬ ፡ ሰማህ ?
I hear from her once in a blue moon. ወሬዋ ፡ የሚደርሰኝ ፡ በዓመት ፡ አንዴ ፡ ነው
5. አየ. The judge heard three cases today. ዛሬ ፡ ዳኛው ፡ ሦስት ፡ ጉዳዮች ፡ አዩ
*Well then, I will expect to hear from you. እንግዲህ ፡ መልእክትህ ፡ እንዲደርሰኝ ፡ እጠባበቃለሁ

**hear (one) out** አስጨርሶ ፡ አደመጠ
Hear me out before you do anything! ምንም ፡ ከማድረግህ ፡ በፊት ፡ አስጨርሰህ ፡ አድምጠኝ

**make oneself heard** ድምፁን ፡ አሰማ
He couldn't make himself heard above the noise. ከሚሚታው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ድምፁን ፡ ሊያሰማ ፡ አልቻለም

**(I) won't hear of** አልፈቅድም
I won't hear of anyone's tearing my books. ማንም ፡ ሰው ፡ መጻሕፍቴን ፡ እንዲቀድ ፡ አልፈቅድም

**hearer** አድማጭ
When he made the speech, his hearers did not agree with him. ንግግር ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ አድማጮቹ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ አልተስማሙም

**hearing** (n.)
1. መስማት. Hearing the good news made him happy. ጥሩ ፡ ዜና ፡ መስማቱ ፡ አስደሰተው
2. ጆሮ. The old man's hearing is poor. የሽማግሌው ፡ ጆሮ ፡ ደካማ ፡ ነው
3. የመስማት ፡ ችሎታ. One's hearing often becomes obtuse in old age. በሽምግልና ፡ ጊዜ ፡ የመስማት ፡ ችሎታ ፡ ይደክማል
4. የቀጠሮ ፡ ቀን. The company's attorney failed to show up at the hearing. የኩባንያው ፡ ጠበቃ ፡ በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ሳይቀርብ ፡ ቀረ
*The hearing was set for June sixth. ጉዳዩ ፡ ለሰኔ ፡ ስድስት ፡ ሊሰማ ፡ ተቀጠረ

**give a hearing** ክርክር ፡ አዳመጠ
The judge gave both sides a hearing. ዳኛው ፡ የሁለቱንም ፡ ወገን ፡ ክርክር ፡ አዳመጠ

**hard of hearing** የመስማት ፡ ችግር ፡ ያለበት ፡ ሰው
Modern aids are helpful for the hard of hearing. ዘመናዊ ፡ መሣሪያዎች ፡ የመስማት ፡ ችግር ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡ ሊረዱ ፡ ይችላሉ

**(be) hard of hearing**
My aunt is hard of hearing. አክስቴ ፡ ጆሮዋ ፡ አጥርቶ ፡ አይሰማላትም ፡ (እጅግም ፡ አትሰማም)

**within hearing**
*Mother stays within hearing of the baby. እናታችን ፡ ሕፃኑን ፡ ልትሰማ ፡ ከምትችልበት ፡ ቦታ ፡ ትቀመጣለች

**hearsay** (n.)
1. አሉባልታ. I do not believe it; it is merely hearsay. አሉባልታ ፡ ስለሆነ ፡ አልቀበለውም
2. በስሚ ፡ ስሚ ፡ የተገኘ ፡ ወሬ. Hearsay is not admissible evidence. በስሚ ፡ ስሚ ፡ የተገኘ ፡ ወሬ ፡ በመረጃነት ፡ ተቀባይነት ፡ አይኖረውም

**hearsay** (adj.) የስሚ ፡ ስሚ
Hearsay evidence is inadmissible in court because it cannot be substantiated. የስሚ ፡ ስሚ ፡ ምስክርነት ፡ ሊረጋገጥ ፡ ስለማይችል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አይቀበለውም

**hearse** የሬሳ ፡ መኪና
You can rent a hearse in Addis Ababa. ባዲስ ፡ አበባ ፡ የሚከራዩ ፡ የሬሳ ፡ መኪናዎች ፡ አሉ

**heart**
1. ልብ. He has a weak heart. ልቡ ፡ ደካማ ፡ ነው
2. መንፈስ. The losing team had plenty of heart. የተሸነፈው ፡ ቡድን ፡ ጥሩ ፡ መንፈስ ፡ ነበረው
3. መነሾ. I intend to get to the heart of the quarrel. የጠቡን ፡ መነሾ ፡ ለማወቅ ፡ እፈልጋለሁ
4. ውስጥ. The heart of the palm tree is very succulent. የዘንባባ ፡ ግንድ ፡ ውስጡ ፡ በጣም ፡ ውኃማ ፡ ነው
5. መካከል. The Saint George Church stands in the heart of Addis Ababa. የቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ መካከል ፡ ይገኛል
6. ፍሬ ፡ ነገር. A good essay gets right to the heart of the matter. ጥሩ ፡ ድርሰት ፡ የጉዳዩን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በጥልቅ ፡ ይመረምራል

**heart and soul** ከልቡ
She is in this work heart and soul. ሥራውን ፡ ከልቧ ፡ ትሠራለች

**(his) heart sank** ልቡ ፡ ፍስስ ፡ አለ
His heart sank when he heard about the accident. ስለ ፡ አደጋ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡ ፍስስ ፡ አለ

**after one's own heart**
*He is a man after my own heart. እሱ ፡ ከልቤ ፡ የማፈቅረው ፡ ሰው ፡ ነው

**at heart** በልቡ
At heart, he is really a good fellow. በልቡ ፡ በእርግጥ ፡ ጥሩ ፡ ሰው ፡ ነው

**break one's heart** ልቡን ፡ ነካው
The story of his misfortune broke my heart. የደረሰበት ፡ መጥፎ ፡ አጋጣሚ ፡ ልቤን ፡ ነክቶታል

**by heart** በቃል
She learned the poem by heart. ግጥሙን ፡ በቃል ፡ አጠናችው

**cry (one's) heart out** ስቅስቅ ፡ ብሎ ፡ አለቀሰ
When her husband died she cried her heart out. ባሏ ፡ የሞተ ፡ ጊዜ ፡ ስቅስቅ ፡ ብላ ፡ አለቀሰች

**do one's heart good** ደስ ፡ አለ(ው)
It does my heart good to see you again. እንደገና ፡ ሳይህ ፡ ደስ ፡ አለኝ

**have a change of heart** ሐሳቡን ፡ ለወጠ
He had a change of heart and decided not to punish the boy. ሐሳቡን ፡ ለውጦ ፡ ልጁን ፡ ሳይቀጣው ፡ ቀረ

**have a heart** ርኅሩኅ ፡ ነው
He has a heart and cannot stand to see others suffer. ርኅሩኅ ፡ ስለሆነ ፡ የሰውን ፡ መሠቃየት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ አይችልም

**have at heart**
*I have your best interests at heart. ላንተ ፡ ሁልጊዜ ፡ ደግ ፡ አስባለሁ

**have (one's) heart set on** በጣም ፡ ጓጓ
He had his heart set on buying a house. ቤት ፡ ለመግዛት ፡ በጣም ፡ ጓጉቶ ፡ ነበር

**have (a) kind heart**
He has a kind heart. ርኅሩኅ ፡ ነው

**in the heart of** ውስጥ
Robin Hood lived in the heart of the forest. ሮቢን ፡ ሁድ ፡ ጫካው ፡ ውስጥ ፡ ኖረ

**lose heart** ተስፋ ፡ ቈረጠ
He lost heart during the long struggle to achieve success. ዓላማውን ፡ ከግብ ፡ ለማድረስ ፡ ብዙ ፡ ከጣረ ፡ በኋላ ፡ ተስፋ ፡ ቈረጠ

**not have the heart** አልደፈረም
After he tried so hard, I haven't the heart to tell him he failed. ይህን ፡ ያህል ፡ ከጣረ ፡ በኋላ ፡ ያልተሳካለት ፡ መሆኑን ፡ ልነግረው ፡ አልደፍርም

**one's heart is in the right place** በልቡ ፡ ምንም ፡ አይል
The old gentleman may have a stern manner, but his heart is in the right place. ሽማግሌው ፡ ጨካኝ ፡ ይመስላሉ ፤ በልባቸው ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አይሉ

**put one's heart and soul into**
He puts his heart and soul into his work. ከልቡ ፡ ሥራውን ፡ ይሠራል

**put more heart to**
Put more heart to your work! ከልብህ ፡ ሥራህን ፡ ሥራ

**set one's heart against** አጥብቆ ፡ ተቃወመ
She had set her heart against selling the picture. ሥዕሉ ፡ እንዳይሸጥ ፡ አጥብቃ ፡ ተቃውማ ፡ ነበር

**set one's heart on** ጓጓ
He set his heart on a car. መኪና ፡ ለመግዛት ፡ ጓጉቷል

**take heart** ተጽናና
Her son's death was a great blow, but she eventually took heart. የልጇ ፡ መሞት ፡ ታላቅ ፡ አደጋ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ እያደር ፡ ተጽናናች

**take heart!** አይዞህ
Take heart! This trouble will soon pass. አይዞህ ፤ ይህ ፡ ችግር ፡ ቶሎ ፡ ያልፋል

**take to heart**
1. ለልቡ ፡ ተሰማ(ው). He took his father's advice to heart. ያባቱ ፡ ምክር ፡ ለልቡ ፡ ተሰማው
2. አስጨነቀ ፤ ተበሳጨ. +Don't take the defeat too much to heart! መሸነፉ ፡ በጣም ፡ እያስጨነቀህ ፡ (or, ስለተሸነፍክ ፡ በጣም ፡ አትበሳጭ)

**to (one's) heart's content**
Eat to your heart's content! እስክትጠግብ ፡ ድረስ ፡ ብላ

**with all his heart** ከንጀቱ
He loves her with all his heart. ከንጀቱ ፡ ይወዳታል
[See also 'depth, desire, harden, heavy, lighten, pure, soft, soften, sore, steal, story, talk, tear, tender, throb, wring']

**heart attack** የልብ ፡ ድካም
He died of a heart attack. ከልብ ፡ ድካም ፡ የተነሣ ፡ ሞተ

**heartbeat** የልብ ፡ ትርታ
He has a rapid heartbeat. የልቡ ፡ ትርታ ፡ ፈጣን ፡ ነው

**heartbreaking** እጅግ ፡ የሚያሳዝን
He told me a heartbreaking story. እጅግ ፡ የሚያሳዝን ፡ ታሪክ ፡ አጫወተኝ

**heartburn** ቃር
He suffers from heartburn. በቃር ፡ ይሠቃያል

**hearten** አበረታታ ፤ አደፋፈረ
This good news will hearten you. ይህ ፡ ጥሩ ፡ ዜና ፡ ያበረታታሃል
The officer's unflinching courage heartened his men. የመኰንኑ ፡ የማይበገር ፡ ጀግንነቱ ፡ ጦሩን ፡ አደፋፈረ

**heartfelt** ከልብ ፡ የመነጨ
You have my heartfelt sympathy in your loss. በደረሰብህ ፡ ጉዳት ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ የሐዘን ፡ ማጽናኛ ፡ ይድረስህ

**hearth** ምድጃ
There were bellows on the hearth. በምድጃው ፡ ላይ ፡ ወናፍ ፡ ነበረ

**heartily** ከልብ
We applauded heartily. ከልባችን ፡ አጨበጨብን
She set to work heartily. ከልቧ ፡ ሥራ ፡ ቀጠለች
We ate heartily. ከልባችን ፡ በላን

**heartless** ግፈኛ
The heartless ruler ordered women and children killed. ግፈኛው ፡ ገዥ ፡ ሴቶችና ፡ ሕፃናት ፡ እንዲገደሉ ፡ አዘዘ

**(be) heartsick** በጣም ፡ አዘነ
The children were heartsick about leaving their friends. ልጆቹ ፡ ከጓደኞቻቸው ፡ በመለየታቸው ፡ በጣም ፡ አዝነው ፡ ነበር

**heart-to-heart** (= adv.) ልብ ፡ ለልብ
I had a heart-to-heart talk with him. እኔና ፡ እሱ ፡ ልብ ፡ ለልብ ፡ ተጫወትን

**hearty**
1. ከልብ ፡ የመነጨ. They gave the minister a hearty welcome. ለሚኒስትሩ ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ አቀባበል ፡ አደረጉለት
2. አጥጋቢ. A hearty meal satisfied her hunger. አጥጋቢ ፡ ምግብ ፡ ረኀቧን ፡ አረካላት
3. (= adv.) ከልብ. He gave his hearty approval to our plan. ሐሳባችንን ፡ ከልብ ፡ ተቀበለው
*He is a hearty eater. ሆዱ ፡ ምግብ ፡ ይቀበላል

**have a hearty appetite** ብዙ ፡ መመገብ ፡ ቻለ
He is young and has a hearty appetite. ወጣት ፡ ስለሆነ ፡ ብዙ ፡ መመገብ ፡ ይችላል
[See also 'hale']

**heat** (vt.) አሞቀ
A stove heats the house. ምድጃ ፡ ቤቱን ፡ ያሞቃል

**heat** (vi.) ሞቀ
The soup is heating slowly. ሾርባው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየሞቀ ፡ ነው

**be heated** ሞቀ
The room is well heated. ክፍሉ ፡ በደንብ ፡ ይሞቃል

**heat up** (vt.) አሞቀ
I will have to heat up the water first. መጀመሪያ ፡ ውኃውን ፡ ማሞቅ ፡ አለብኝ

**heat up** (vi.) ጋለ
This engine heats up quickly. ይህ ፡ ሞተር ፡ ቶሎ ፡ ይግላል

**heat** (n.)
1. ሙቀት. I cannot stand the heat. ሙቀቱን ፡ አልቻልኩትም
2. የፀሐይ ፡ ሐሩር. He was overpowered by the heat. የፀሐዩን ፡ ሐሩር ፡ ሊቋቋም ፡ አልቻለም
3. ማሞቂያ. We include heat in the rent. የቤቱ ፡ ኪራይ ፡ የማሞቂያውንም ፡ ዋጋ ፡ ይጨምራል

**be in heat** ሻፈደ
Be careful! That mule is in heat. ያቺ ፡ በቅሎ ፡ ሻፍዳለችና ፡ ተጠንቀቅ

**in the heat of** ግሎ ፡ ሳለ ፤ ተፋፍሞ ፡ ሳለ
In the heat of the debate, many foolish things were said. ክርክሩ ፡ ግሎ ፡ (ተፋፍሞ) ፡ ሳለ ፡ ብዙ ፡ የማይረቡ ፡ ነገሮች ፡ ተነገሩ

**with (considerable) heat** በጋለ ፡ ስሜት
He spoke with considerable heat. በጋለ ፡ ስሜት ፡ ተናገረ
[See also 'wave']

**heated** (adj.) የጋለ ፤ የተፋፋመ
A heated argument developed about who should be the leader. ማን ፡ አለቃ ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ ለመወሰን ፡ የጋለ ፡ ክርክር ፡ ተደረገ
Their durable friendship withstood many a heated argument. ጽኑ ፡ የሆነው ፡ ጓደኝነታቸው ፡ ብዙ ፡ የተፋፋመ ፡ ክርክርን ፡ ተቋቁሟል

**heathen** አረመኔያዊ
There are heathen tribes in some parts of the

world. ባንዳንድ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ አረመኔያዊ ፡ ነገዶች ፡ ይገኛሉ

**heating** ማሞቂያ ፡ ነዳጅ
This type of heating is very economical. የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ማሞቂያ ፡ ነዳጅ ፡ ይቈጥባል

**heave** (vt.)
1. በስንት ፡ ችግር ፡ አወጣ. The mason heaved the stone to the top of the wall. ግንበኛው ፡ ደንጊያውን ፡ በስንት ፡ ችግር ፡ ከግድግዳው ፡ አናት ፡ ላይ ፡ አወጣው
2. በችግር ፡ ወረወረ. He heaved the rock into the water. ድንጋዩን ፡ በችግር ፡ ወደ ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ወረወረ

**heave** (vi.)
1. ጉብ ፡ አለ. The ground heaved during the blast. በፈንጂው ፡ ጊዜ ፡ መሬቱ ፡ ጉብ ፡ አለ
2. ከፍ ፡ ዝቅ ፡ አለ. The waves heaved during the storm. በማዕበሉ ፡ ጊዜ ፡ ሞገዱ ፡ ከፍ ፡ ዝቅ ፡ አለ
3. ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰ. He sat there heaving from the effort. ከድካሙ ፡ የተነሣ ፡ ቁና ፡ ቁና ፡ እየተነፈሰ ፡ ተቀመጠ
4. (= trans.) ነፋ. +His chest heaved with pride. ኩራት ፡ ልቡን ፡ ነፋው

**heave on** በጥረት ፡ ሳበ
They heaved on the rope. ገመዱን ፡ በጥረት ፡ ሳቡ

**heave a sigh** ቁና ፡ ተነፈሰ
He heaved a sigh and remained silent. ቁና ፡ ተነፈሰና ፡ ጸጥ ፡ አለ

**heaven** መንግሥተ ፡ ሰማያት
I am going to heaven when I die. ስሞት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እገባለሁ

**heavens** ሰማይ
Meteors flashed across the heavens every night. ተወርዋሪ ፡ ኮከቦች ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ ይተኰሳሉ

**heavens!** አቤት ፡ አቤት !
Heavens, what a cold room! አቤት ፡ አቤት ፤ ክፍሉ ፡ እንዴት ፡ ቀዝቃዛ ፡ ነው !

**for heaven's sake** ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ
For heaven's sake, stop that noise! ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ ያንን ፡ ጫጫታ ፡ ዝም ፡ አሰኝ

**good heavens!** ጉድ ፡ ሆኛለሁ !
Good heavens! I've lost my watch. ጉድ ፡ ሆኛለሁ ፤ ሰዓቴን ፡ ጣልኩት

**move heaven and earth** ሞትም ፡ ቢመጣ
She promised to move heaven and earth to be there for the wedding. ሞትም ፡ ቢመጣ ፡ ለሰርጉ ፡ እንደምትገኝ ፡ ገለጸች

**heavenly**
1. የሰማይ. The sun, moon and stars are heavenly bodies. ፀሐይ ፡ ጨረቃና ፡ ከዋክብት ፡ የሰማይ ፡ አካላት ፡ ናቸው
God is our heavenly Father. እግዚአብሔር ፡ የሰማይ ፡ አባታችን ፡ ነው
2. ብሩህ. It was a heavenly day. ብሩህ ፡ ቀን ፡ ነበር
3. በጣም ፡ አስደሳች. This garden is a heavenly spot for picnics. ይህ ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ ለሽርሽር ፡ በጣም ፡ አስደሳች ፡ ነው
[See also 'kingdom']

**(be) heavier** ከ - - - ከበደ
This table is heavier than that one. ይህ ፡ ጠረጴዛ ፡ ከዚያኛው ፡ ይከብዳል

**become heavier** ባሰ
Her troubles became heavier and heavier. ችግሯ ፡ እየባሰ ፡ ሄደ

**heavily** በኀይል
It rained heavily on Tuesday. ማክሰኞ ፡ ዕለት ፡ ዝናም ፡ በኀይል ፡ ጣለ

**heavily loaded** ብዙ ፡ ጭነት ፡ የተጫነ
The heavily loaded truck broke down. ብዙ ፡ ጭነት ፡ የተጫነው ፡ መኪና ፡ ተሰበረ

**weigh heavily upon** አቈራመደ
Cares weigh heavily upon him. ችግር ፡ አቈራምዶታል
[See also 'press']

**heaviness** ከባድነት
The heaviness of the air is due to moisture. ያየሩ ፡ ከባድነት ፡ ከተኑ ፡ የተነሣ ፡ ነው
*A great heaviness lay on her heart. ከባድ ፡ ሐዘን ፡ ተጭኗታል

**heavy**
1. ከባድ. A heavy box fell on my foot. ከባድ ፡ ሣጥን ፡ እግሬ ፡ ላይ ፡ ወደቀብኝ
Raising children is a heavy task. ልጆችን ፡ ማሳደግ ፡ ከባድ ፡ ተግባር ፡ ነው
The President's responsibilities are heavy. የፕሬዚዳንቱ ፡ ኀላፊነት ፡ ከባድ ፡ ነው
He ate a heavy meal before he went to bed. ከመተኛቱ ፡ በፊት ፡ ከባድ ፡ ምግብ ፡ በላ
2. ከፍ ፡ ያለ ፤ ከፍተኛ. He had to pay a heavy fine. ከፍ ፡ ያለ ፡ መቀጫ ፡ መክፈል ፡ ነበረበት
The expenses for the wedding were heavy. የሰርጉ ፡ ወጪ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነበር
The heavy taxes ruined the merchant. ከፍተኛ ፡ ታክስ ፡ ነጋዴውን ፡ ጐዳው

3. ሰፊ. His heavy bones make him look fat. ሰፊ ፡ አጥንቱ ፡ ወፍራም ፡ ያስመስለዋል
4. ወፍራም. He wore a shirt of some heavy cloth. ከወፍራም ፡ ጨርቅ ፡ የተሰፋ ፡ ሸሚዝ ፡ ለብሶ ፡ ነበር
5. ድብን ፡ ያለ. Heavy sleep is not easily disturbed. ድብን ፡ ያለ ፡ እንቅልፍ ፡ በቀላሉ ፡ አይታወክም
6. የጠቈረ. The heavy skies promise rain. የጠቈረው ፡ ሰማይ ፡ ዝናም ፡ መምጣቱን ፡ ያመለክታል
7. ጥቅጥቅ ፡ ያለ. We nearly smothered in the heavy smoke. ጥቅጥቅ ፡ ባለው ፡ ጭስ ፡ ውስጥ ፡ ልንታፈን ፡ ምንም ፡ አልቀረን ፡ ነበር
8. ኀይለኛ. He is a heavy drinker. ኀይለኛ ፡ ጠጪ ፡ ነው

**be heavy** ከበደ
Is that box too heavy for you? ሣጥኑ ፡ በጣም ፡ ይከብድሃል ?
+His eyes were heavy with sleep. እንቅልፍ ፡ ዓይኑን ፡ ከብዶታል

**be heavy with child** እርግዝናዋ ፡ ገፋ
She is heavy with child and can't travel. እርግዝናዋ ፡ የገፋ ፡ ስለሆነ ፡ ረዥም ፡ መንገድ ፡ ለመሄድ ፡ አትችልም

**one's heart was heavy** በጣም ፡ አዘነ
His heart was heavy at leaving home. ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ሲለይ ፡ በጣም ፡ አዝኖ ፡ ነበር
[See also 'blow, hand, odds, rain, traffic']

**heavy artillery** ከባድ ፡ መሣሪያ
Heavy artillery blasted the enemy off the hill. ከባድ ፡ መሣሪያ ፡ ጠላትን ፡ ከተራራው ፡ ላይ ፡ ድምጥማጡን ፡ አጠፋው

**heavy-handed** ችኮ
He is heavy-handed in his dealings with people. ከሰዎች ፡ ጋር ፡ መግባባት ፡ አያውቅበትም ፤ ችኮ ፡ ነው

**Hebrew** ዕብራይስጥ
You will have to learn Hebrew first. መጀመሪያ ፡ ዕብራይስጥ ፡ መማር ፡ አለብህ

**heckle** በጫጫታ ፡ ግራ ፡ አገባ
The audience heckled the speaker. አድማጮቹ ፡ ተናጋሪውን ፡ በጫጫታ ፡ ግራ ፡ አገቡት

**hectic** የግርግር
Registration day is always a hectic time at the university. በዩኒቨርሲቲው ፡ ውስጥ ፡ የምዝገባ ፡ ቀን ፡ ሁልጊዜ ፡ የግርግር ፡ ጊዜ ፡ ነው

**hedge** (vt.) አጠረ
He hedged the garden with flowering plants. ያትክልቱን ፡ ስፍራ ፡ በሚያብቡ ፡ ዕፀዋት ፡ አጠረ

**hedge** (vi.) አድበሰበሰ ፡ አለፈ
He hedged when asked about his policy. ስለ ፡ አመራሩ ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ አድበስብሶ ፡ አለፈ

**be hedged** ተከበበ
Switzerland is hedged by mountains. ስዊዘርላንድ ፡ በተራራዎች ፡ የተከበበች ፡ ናት

**feel hedged in** እንደሚያግደው ፡ ተሰማ(ው)
He felt hedged in by the rules of language. የቋንቋ ፡ ደንብ ፡ እንደሚያግደው ፡ ተሰማው

**hedge** (n.)
1. የተክል ፡ አጥር ፤ የቁጥቋጦ ፡ አጥር. There was a hedge around the house. በቤቱ ፡ ዙሪያ ፡ የተክል ፡ አጥር ፡ ነበር
The thick hedge breaks the force of the wind. ጥቅጥቅ ፡ ያለው ፡ የቁጥቋጦ ፡ አጥር ፡ የነፋሱን ፡ ኀይል ፡ ይቀንሰዋል
2. መጠባበቂያ. The savings were a hedge against unemployment. ያጠራቀመው ፡ ከሥራ ፡ ሲወጣ ፡ መጠባበቂያ ፡ ነበር

**heed** (v.)
1. ተቀበለ ፤ ሰማ. Heed my advice! ምክሬን ፡ ተቀበል ፡ (ስማ)
2. አከበረ. You must heed traffic regulations. የትራፊክን ፡ ሕጎች ፡ ማክበር ፡ አለበህ

**heed** (n.), **take ~**
1. ሰማ. Take no heed of what people say! ሰው ፡ የሚለውን ፡ አትስማ
2. ተጠነቀቀ. Take heed, or you may be hurt. ተጠንቀቅ ፤ ያለበለዚያ ፡ ትጐዳለህ

**pay heed** ተጠነቀቀ
She pays heed to her clothes. ለልብሷ ፡ ትጠነቀቃለች

**(be) heedful of** በጥንቃቄ ፡ ተመለከተ
A good driver is heedful of traffic signs. ጥሩ ፡ ነጂ ፡ የትራፊክ ፡ ምልክቶችን ፡ በጥንቃቄ ፡ ይመለከታል

**heedless** የማይጠብቅ
A driver who is heedless of traffic signs may have an accident. የትራፊክ ፡ ምልክት ፡ የማይጠብቅ ፡ ነጂ ፡ አደጋ ፡ ያጋጥመዋል

**heel** (vt.) ተረከዝ ፡ አገባ
The cobbler heeled my shoes. ጫማ ፡ ሰፊው ፡ ለጫማዎቼ ፡ ተረከዝ ፡ አገባ

**heel** (vi.)
1. ተከተለ. Did you teach the dog to heel? ውሻው ፡ እንዲከተልህ ፡ አሠልጥነኸዋል ?
2. አጋደለ. The ship heeled as it turned. መርከቧ ፡ ስትጠመዘዝ ፡ አጋደለች

## heel (n.) ተረከዝ
+I hit my heel on the stone. ድንጋይ ፡ ተረከዜን ፡ ገጨኝ

**be at one's heels**
The police are at his heels. ፖሊሶቹ ፡ ሊይዙት ፡ ተቃርበዋል

**come on the heels of**
*The rain came on the heels of the wind. ዝናሙ ፡ ነፋሱን ፡ ተከትሎ ፡ ወዲያውኑ ፡ ዘነበ

**follow on the heels of** ተከትሎ ፡ ገባ
Famine followed on the heels of the drought. ረኃብ ፡ ድርቀቱን ፡ ተከትሎ ፡ ገባ

**take to (one's) heels** እግሬ ፡ አውጪኝ ፡ አለ
The thief took to his heels when he saw the policeman. ፖሊሱን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ሌባው ፡ እግሬ ፡ አውጪኝ ፡ አለ

**turn on (one's) heel** በፍጥነት ፡ ዞር ፡ አለ
He turned on his heel and walked away. በፍጥነት ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ ሄደ
[See also 'click, head']

## hefty
1. ጡንቸኛ. The hefty fellow lifted the heavy trunk alone. ጡንቸኛው ፡ ሰውዬ ፡ ከባዱን ፡ ሣጥን ፡ ለብቻው ፡ አነሣው
2. በጣም ፡ ትልቅ. This dictionary is a hefty book. ይህ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ነው

## heifer ጊደር
They sold their heifer to the butcher. ጊደራቸውን ፡ ለሉካንዳ ፡ ነጋዴው ፡ ሸጡ

## height
1. ርዝመት. What is the height of that building? የዚያ ፡ ሕንጻ ፡ ርዝመት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?
2. ከፍታ . What is the height of that mountain? የዚያ ፡ ተራራ ፡ ከፍታ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?
3. ቁመት. He is a man of average height. መካከለኛ ፡ ቁመት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው
*He was then at the height of his power. ያን ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ከፍተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ደርሶ ፡ ነበር

**height of** ከፍተኛ
Fast driving on icy roads is the height of folly. በረዶ ፡ ባለበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በፍጥነት ፡ መንዳት ፡ ከፍተኛ ፡ እብደት ፡ ነው

**heights**
1. ከፍተኛ ፡ ጫፍ. In his dream, he reached the heights. በሕልሙ ፡ ከከፍተኛው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ደረሰ
2. አፋፍ. They stood on the heights and looked over the valley. ከአፋፍ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ ሸለቆውን ፡ ተመለከቱ
3. ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ. She is afraid of heights. ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ያስፈራታል
[See also 'order']

## heighten
1. አስረዘመ. They heightened the fence around the house. ከቤቱ ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ አጥር ፡ አስረዘሙት
2. አባሰ. His remarks only heightened her anger. የሱ ፡ አስተያየት ፡ ንዴቷን ፡ አባሰ
3. አስወደደ. Its age heightens the value of the painting. የቆየ ፡ መሆኑ ፡ የሥዕሉን ፡ ዋጋ ፡ ያስወድደዋል

## heinous አሰቃቂ
His heinous crimes are known to everyone. የፈጸማቸው ፡ አሰቃቂ ፡ ወንጀሎች ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ የታወቁ ፡ ናቸው

## heir ወራሽ
He died without having an heir. ያለ ፡ ወራሽ ፡ ሞተ

## heir apparent ሕጋዊ ፡ ወራሽ
He is the heir apparent to the throne. የዙፋኑ ፡ ሕጋዊ ፡ ወራሽ ፡ እሱ ፡ ነው

## heirloom ቅርስ
This old clock is a family heirloom. ይህ ፡ የድሮ ፡ የግድግዳ ፡ ሰዓት ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ቅርስ ፡ ነው

## held, see hold

## hell
1. ገሃነም. I hope he goes to hell. ገሃነም ፡ እንዲገባ ፡ እመኛለሁ
2. ሲኦል. In some religions, hell is the place of punishment after death. ባንዳንድ ፡ ሃይማኖት ፡ ሲኦል ፡ ከሞት ፡ በኋላ ፡ የቅጣት ፡ ስፍራ ፡ ነው

**make a hell** መራራ ፡ አደረገ
The boy made his mother's life a hell. ልጁ ፡ የናቱን ፡ ኑሮ ፡ መራራ ፡ አደረገው

**raise hell** ደነፋ
He raised hell when he found that his rival had been promoted. ተቀናቃኙ ፡ መሾሙን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ደነፋ
[See also 'condemn']

**hello** አሎ
Hello! Who is speaking? አሎ ! ማን ፡ ልበል ?

**helm** የመርከብ ፡ መሪ
Only a young sailor was at the helm. በመርከቡ ፡ መሪ ፡ ዘንድ ፡ የነበረው ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ መርከበኛ ፡ ብቻ ፡ ነበር

**take the helm** ሥልጣኑን ፡ ያዘ
Upon the President's death, the Vice-President took the helm. ፕሬዚዳንቱ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ሥልጣኑን ፡ ያዘ

**helmet** የራስ ፡ ቁር ፤ የብረት ፡ ባርኔጣ
He put on his helmet when the fighting started. ውጊያው ፡ ሲጀመር ፡ የራስ ፡ ቁሩን ፡ (የብረት ፡ ባርኔጣውን) ፡ ደፋ

**help** (v.)
1. ረዳ. I cannot lift this box; please help me. እኔ ፡ ይህን ፡ ሣጥን ፡ ማንሣት ፡ አልችልም ፤ እስቲ ፡ እርዳኝ
2. አሻለ. This medicine will help your cold. ይህ ፡ መድኃኒት ፡ ጉንፋንህን ፡ ያሽልልሃል
*Can I help you? ምን ፡ ላድርግልህ ?
*Don't tell him more than you can help. ልትነግረው ፡ ከሚገባህ ፡ በላይ ፡ አትንገረው

**help (one) off with**
He helped her off with her coat. ካፖርቷን ፡ ስታወልቅ ፡ አገዛት

**help (one) on with** አላበሰ
Shall I help you on with your coat? ካፖርትሽን ፡ ላላብስሽ ?

**help oneself**
1. ተጋበዘ. Help yourself to the meat! ሥጋውን ፡ ተጋበዝ
2. ራሱን ፡ ገታ. She burst out crying; she could not help herself. ተንሰቅስቃ ፡ አለቀሰች ፤ ራሷን ፡ ልትገታ ፡ አልቻለችም

**help oneself to** ወሰደ
He helped himself to the paper that he needed. ከወረቀቱ ፡ የሚፈልገውን ፡ ያህል ፡ ወሰደ

**help out** ረዳ
She helps us out on Sundays. እሑድ ፡ እሑድ ፡ ትረዳናለች

**help (one) to more** ጨመረ(ለት)
May I help you to some more meat? ከሥጋው ፡ ትንሽ ፡ ልጨምርልህ ?

**(he) cannot help (but)** ሳይወድ ፤ ያለውዴታው
He cannot help going to sleep. ሳይወድ ፡ እንቅልፍ ፡ ይወስደዋል
I couldn't help but see it. ያለውዴታዬ ፡ ማየት ፡ ነበረብኝ
*I cannot help thinking he is still alive. አሁንም ፡ በሕይወት ፡ አለ ፡ ብዬ ፡ ማሰቤን ፡ አልተውኩም
*I can't help laughing. መሣቅ ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ
*They spoke so loud, I couldn't help overhearing what they said. ጮኽ ፡ ብለው ፡ ይነጋገሩ ፡ ስለነበር ፡ የሚሉትን ፡ ላላዳምጥ ፡ አልቻልኩም

**I cannot help it** ምን ፡ ላድርግ
I cannot help it; that's my opinion. ምን ፡ ላድርግ ፤ አስተያየቴ ፡ ይኸው ፡ ነው

**so help me God** እግዚአብሔርን
So help me God! It is true. እግዚአብሔርን ! እውነት ፡ ነው

**help** (n.)
1. እርዳታ. Thank you for your kind help! ለመልካም ፡ እርዳታዎ ፡ አመሰግንዎታለሁ
2. ረዳቶች. The storekeeper treats his help well. ባለመደብሩ ፡ ረዳቶቹን ፡ በደንብ ፡ ይይዛቸዋል
3. መድኃኒት. There is no help for her illness. የሷ ፡ በሽታ ፡ መድኃኒት ፡ የለውም
*There is no help for it. ምንም ፡ ማድረግ ፡ አይቻልም

**extend help** ረዳ
He extends help to the poor. ድኻን ፡ ይረዳል

**render help** እርዳታ ፡ አደረገ
He renders help to those in need. ለችግረኞች ፡ እርዳታ ፡ ያደርጋል
[See also 'call, cry, shout, yell']

**helper**
1. ረዳት. I had two helpers. ሁለት ፡ ረዳቶች ፡ ነበሩኝ
2. ግብረ ፡ አበር. The thief implicated two helpers. ሌባው ፡ ሁለት ፡ ግብረ ፡ አበሮች ፡ እንዳሉት ፡ ተናገረ

**helpful**
1. ለመርዳት ፡ ዝግጁ. She is always helpful. ለመርዳት ፡ ዘወትር ፡ ዝግጁ ፡ ነች
2. ጠቃሚ. You have given me a helpful hint in applying for a job. ለሥራ ፡ ለማመልከት ፡ እንድችል ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ፍንጭ ፡ ሰጠሽኝ

**be helpful**
1. ረዳ. He was very helpful to me when I was sick. ታምሜ ፡ በነበርኩ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ረድቶኝ ፡ ነበር
2. ብዙ ፡ ተላላከ. My son is helpful around the house. ልጄ ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ይላላካል

**helping** (n.)
*I had two helpings of meat. ከሥጋው ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አነሣሁ

**helpless**

1. መከላከያ ፡ የሌለው. The army butchered the helpless civilians. ጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ መከላከያ ፡ የሌላቸውን ፡ ሲቪሎች ፡ ፈጀ

2. ራሱን ፡ የማይረዳ. The accident rendered him helpless. አደጋ ፡ ራሱን ፡ የማይረዳ ፡ አደረገው

**helpless invalid** አካለ ፡ ስንኩል

After the accident, he remained a helpless invalid. ከአደጋው ፡ በኋላ ፡ አካለ ፡ ስንኩል ፡ ሆኖ ፡ ቀረ

**be helpless**

1. ደከመ. She is completely helpless; she cannot move at all. በጭራሽ ፡ ደክማለች ፤ ለመንቀሳቀስ ፡ አትችልም

2. ሥልጣን ፡ የለውም. As far as granting scholarships is concerned, I am helpless. I can only recommend. የነጻ ፡ ትምህርት ፡ በመስጠት ፡ ረገድ ፡ እኔ ፡ ሥልጣን ፡ የለኝም ፤ የምችለው ፡ ሐሳብ ፡ ማቅረብ ፡ ብቻ ፡ ነው

**be rendered helpless** ስንኩል ፡ ሆኖ ፡ ቀረ

He was rendered helpless by an accident. ባደጋው ፡ ምክንያት ፡ ስንኩል ፡ ሆኖ ፡ ቀረ

**hem** (hemmed), v. ቀመቀመ

She will hem the skirt in an hour. ጉርድ ፡ ቀሚሷን ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ትቀመቅማለች

**be hemmed in** ተከበበ

The troops were hemmed in by the enemy. ወታደሮቹ ፡ በጠላት ፡ ተከበዋል

**hem** (n.) ቅምቅማት ፤ ጠርዝ

There is a hem on her skirt. ቀሚሷ ፡ ቅምቅማት ፡ አለው

The tailor basted the hem before he sewed it permanently. ልብስ ፡ ሰፊው ፡ ጠርዙን ፡ ከመስፋቱ ፡ በፊት ፡ ወሰወሰው

[See also 'stripe']

**hemisphere** ክፍለ ፡ ዓለም

The two Americas are in the Western hemisphere. ሁለቱ ፡ የአሜሪካ ፡ አህጉሮች ፡ በምዕራባዊ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ ይገኛሉ

**hemorrhage** የብዙ ፡ ደም ፡ መፍሰስ

He died of a hemorrhage. ከብዙ ፡ ደም ፡ መፍሰስ ፡ የተነሣ ፡ ሞተ

**hemorrhoids** የአህያ ፡ ኪንታሮት

The boy is suffering from hemorrhoids. ልጁ ፡ በአህያ ፡ ኪንታሮት ፡ ይሠቃያል

**hen** ዶሮ

The hen laid an egg. ዶሮዋ ፡ እንቁላል ፡ ጣለች

**hence**

1. ከ - - - በኋላ. A week hence, I will help you. ከሳምንት ፡ በኋላ ፡ እረዳሃለሁ

Come back a week hence! ከሳምንት ፡ በኋላ ፡ ና

2. ከዚህ. We shall be three miles hence by dusk. ለዓይን ፡ ሲይዝ ፡ ከዚህ ፡ ሦስት ፡ ማይል ፡ እንርቃለን

*The boy was tired and hence had to stay behind. ልጁ ፡ ስለደከመ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀረ

**henceforth** ከእንግዲህ ፡ ወዲህ

Henceforth, you will have to do your own work. ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የራስህን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ አለብህ

**her**

1. (possessive) የሷ, or suffix pronouns. This is her book. ይህ ፡ የሷ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው (or, ይህ ፡ መጽሐፏ ፡ ነው)

2. (direct object) expressed by object suffix pronoun, or by እሷን. I saw her yesterday. ትናንትና ፡ አይቻታለሁ ፡ (or, እሷን ፡ አይቻታለሁ)

**herald** (v.) አበሰረ

Trumpets heralded the coming of the festival. እምቢልታው ፡ የበዓሉን ፡ መድረስ ፡ አበሰረ

**herald** (n.) ዐዋጅ ፡ ነጋሪ

In olden days, the herald announced the coming of the governor. ድሮ ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ የገዢውን ፡ መምጣት ፡ ያስታውቅ ፡ ነበር

**herald** (adj.) አብሳሪ

The herald angel blew his horn three times. አብሳሪው ፡ መልአክ ፡ መለከቱን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ነፋ

**be the herald** አበሰረ

Dawn is the herald of day. ንጋት ፡ የቀንን ፡ መምጣት ፡ ያበስራል

**herb** ዕፅ

This herb is fragrant. ይህ ፡ ዕፅ ፡ ጥሩ ፡ መዓዛ ፡ አለው

**herbs** ቅጠላ ፡ ቅጠል

They used various herbs to flavor the stew. ወጡን ፡ ለማጣፈጥ ፡ ብዙ ፡ ቅጠላ ፡ ቅጠል ፡ ጨመሩበት

**herb garden** ያትክልት ፡ ቦታ

She has a small herb garden in the back of her house. ከቤቷ ፡ ጀርባ ፡ ትንሽ ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ አላት

**herbivorous** ዕፀ ፡ በል

Cattle and monkeys are herbivorous animals.

የቀንድ ፡ ከብቶችና ፡ ዝንጀሮች ፡ ዕፀ ፡ በል ፡ እን ስሳዎች ፡ ናቸው

**herd** (v.) አጐረ
They herded the prisoners into a room and locked them up. እስረኞቹን ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ አጐረው ፡ ቈለፉባቸው

**herd** (n.) መንጋ
I see a herd of sheep in the field. በሜዳው ፡ ላይ ፡ የበግ ፡ መንጋ ፡ አያለሁ

**herdsman** እረኛ
The herdsman stays in the field all day long. እረኛው ፡ ቀኑን ፡ሙሉ ፡ ሜዳ ፡ ይውላል

**here**
1. እዚህ. We cannot stay here. እዚህ ፡ መቆየት ፡ አንችልም
2. እዚህ ፡ ላይ. I disagree with you here. እዚህ ፡ ላይ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ አልስማማም
Here the speaker paused. እዚህ ፡ ላይ ፡ ተናጋሪ ው ፡ ቆም ፡ አለ
3. ይኸው. Here comes the bus! ይኸው ፤ አው ቶቡሱ ፡ መጣ !
*My friend here can help you. እሱ ፡ ወንድሜ ፡ ይረዳሃል
*Here, take it! እንካ
*Come here! ና

**here and now** አሁኑኑ
We must tend to the matter here and now. ጉዳዩን ፡ አሁኑኑ ፡ መፈጸም ፡ አለብን

**here and there**
1. አንዳንድ ፡ ቦታ. You can still find an old copy here and there. አሁንም ፡ አንዳንድ ፡ ቦታ ፡ አሮ ጌ ፡ መጽሐፍ ፡ ይገኛል
2. አልፎ ፡ አልፎ. Here and there you can still see mules in the city. አሁንም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ በቅሎች ፡ ይታያሉ

**here is** ይኸው
Here is the book. መጽሐፉ ፡ ይኸው

**here it is!** ይኸውልህ
Have you seen my book? Here it is! መጽሐፌ ን ፡ አየኸው ? ይኸውልህ !

**from here** ከዚህ ፡ በኋላ
Where do we go from here? ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ም ን ፡ እናደርጋለን ?
[See also 'around, near, neither, over']

**hereabouts** እዚህ ፡ ገደማ
I left my briefcase hereabouts. ቦርሳዬን ፡ እዚ ህ ፡ ገደማ ፡ ተውኩት

**hereafter** ከእንግዲህ
Hereafter, I will be more careful. ከእንግዲህ ፡ ይበልጥ ፡ እጠነቀቃለሁ

**the hereafter** ወዲያኛው ፡ ዓለም
In the hereafter, there is no death or sadness. በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ሞትም ፡ ሆነ ፡ ሐዘን ፡ የለም

**hereby** በዚህ ፡ ማዘዣ
You are hereby ordered to appear in court. በዚህ ፡ ማዘዣ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንድትቀርብ ፡ ታዘሃል
*The mayor declared, "I hereby declare Monday a holiday". ከንቲባው ፡ « ሰኞ ፡ በዓል ፡ ነው » ፡ ብለው ፡ አስታወቁ

**hereditary**
1. ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ. His hereditary estate is located in the mountains. ሲወርድ ፡ ሲ ዋረድ ፡ የመጣው ፡ ርስቱ ፡ በተራራዎች ፡ መካከ ል ፡ ይገኛል
2. ከዘር ፡ የተላለፈ (referring to abstract). The queen of England is a hereditary ruler. የእንግሊ ዝ ፡ ንግሥት ፡ ገዢነታቸው ፡ ከዘር ፡ የተላለፈ ፡ ነው

**be hereditary** በዘር ፡ ተላለፈ
Some diseases are hereditary. አንዳንድ ፡ በሽታ ዎች ፡ በዘር ፡ ይተላለፋሉ

**heredity** ዘር
Heredity determines what an individual can become. ሰው ፡ ወደፊት ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ ነገ ር ፡ በዘር ፡ ይወሰናል

**herein**
1. እዚህ ፡ ውስጥ. His name is listed herein. ስሙ ፡ እዚህ ፡ ውስጥ ፡ ተመዝግቧል
2. እዚህ ፡ ላይ. Herein you are wrong. እዚህ ፡ ላይ ፡ ተሳስተሃል

**heresy** (heresies) መናፍቅነት
The heresy was suppressed by force. መናፍቅነ ት ፡ በኀይል ፡ ተደመሰሰ

**heretic** መናፍቅ
The heretic was beaten to death by the religious leaders. መናፍቁ ፡ በሃይማኖት ፡ መሪዎች ፡ ተደ ብድቦ ፡ ሞተ

**heretofore** እስካሁን ፡ ድረስ
Heretofore, we have always paid for you. እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ስንከፍልልህ ፡ ቆይተናል

**hereupon** በዚህም ፡ ጊዜ
The speaker told a funny joke. Hereupon, the audience broke into laughter. ተናጋሪው ፡ የሚያ

ሥቅ ፡ ቀልድ ፡ ተናገረ ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ አድማጮ
ቹ ፡ በሣቅ ፡ ፈነዱ

**herewith** አባሪ ፡ አድርጎ
I am sending herewith a copy of his letter. የደብዳቤውን ፡ ግልባጭ ፡ አባሪ ፡ አድርጌ ፡ ልኬያለሁ

**heritage** ቅርስ
Ethiopia's heritage is a glorious one. የኢትዮጵያ ፡ ቅርስ ፡ የሚያኰራ ፡ ነው

**hermaphrodite** ፍናፍንት
A child which has both male and female organs is called a hermaphrodite. ልጅ ፡ የወንድና ፡ የሴት ፡ አካል ፡ ሲኖረው ፡ ፍናፍንት ፡ ይባላል

**hermit** ባሕታዊ
He lived in the desert as a hermit. በምድረ ፡ በዳው ፡ ባሕታዊ ፡ ሆኖ ፡ ኖረ

**hernia** ቡቃ
He has a hernia. ቡቃ ፡ ወርዶታል

**hero** (heroes)
1. ጀግና ፤ ባለጀብዱ. He was a hero in the last war. ባለፈው ፡ ጦርነት ፡ ጀግና ፡ (ባለጀብዱ) ፡ ነበር
2. ዋና ፡ ባለታሪክ. The hero of the story is of Italian origin. ዋናው ፡ ባለታሪክ ፡ ከጣልያን ፡ ዘር ፡ ነው

**heroic**
1. የጀግንነት ፤ የጀብዱ. They tell many heroic stories about him. ስለሱ ፡ ብዙ ፡ የጀግንነት ፡ (የጀብዱ) ፡ ታሪኮች ፡ ይናገራሉ
2. ጀግና. The heroic woman is credited with saving the lives of many children. የብዙ ፡ ልጆችን ፡ ሕይወት ፡ በማትረፏ ፡ ጀግናዋ ፡ ሴት ፡ ተመሰገነች
3. ስለ ፡ ጀግኖች ፡ የተገጠመ. The "Odyssey" is a heroic poem. « ኦዲሲይ » ፡ ስለ ፡ ጀግኖች ፡ የተገጠመ ፡ ግጥም ፡ ነው
4. የድፍረት. Only heroic measures could save the town from the flood. ከተማውን ፡ ከውኃ ፡ መጥለቅለቅ ፡ ሊያተርፉ ፡ የሚችሉ ፡ የድፍረት ፡ እርምጃዎች ፡ ናቸው

**heroism** የጀግንነት ፡ ሙያ
Heroism was often displayed by the patriots. አርበኞቹ ፡ በየጊዜው ፡ የጀግንነት ፡ ሙያ ፡ ይፈጽሙ ፡ ነበር

**herring** [በሰሜን ፡ አትላንቲክ ፡ የሚገኝ ፡ ትንሽ ፡ ዓሣ]

**hers** የርሷ ፤ የሷ
My hat is bigger than hers. የኔ ፡ ባርኔጣ ፡ ከርሷ ፡ (ከሷ) ፡ ባርኔጣ ፡ ይተልቃል

**of hers** የሷ
A friend of hers told it to me. አንድ ፡ የሷ ፡ ወዳጅ ፡ ነገረኝ

**herself, she ~**
1. ራሷ. She does not hire anyone to do the housework; she does it herself. የቤቱን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ማንንም ፡ አትቀጥርም ፤ ራሷ ፡ ትሠራዋለች
2. እርሷ ፡ ራሷ. She herself told me the news. ወሬውን ፡ እርሷ ፡ ራሷ ፡ ነገረችኝ

**be herself** እንደወትሮዋ ፡ ነች
Mary is not herself today. ሜሪ ፡ ዛሬ ፡ እንደወትሮዋ ፡ አይደለችም

**by herself**
1. ራሷ. She made the dress by herself. ልብሱን ፡ ራሷ ፡ ሰፋችው
2. ብቻዋን. She came by herself. ብቻዋን ፡ መጣች

**of herself** ራሷን
She is ashamed of herself. ራሷን ፡ ጠላች

**hesitant**
1. ወላዋይ. A hesitant person will not convince anyone. ወላዋይ ፡ ሰው ፡ ማንንም ፡ ሊያሳምን ፡ አይችልም
2. እያመነታ ፡ የሚያደርግ. His hesitant speech shows he has not studied the subject. እያመነታ ፡ የሚያደርገው ፡ ንግግሩ ፡ አርእስቱን ፡ በደንብ ፡ አለማጥናቱን ፡ ያሳያል

**hesitate** አመነታ
He hesitated a moment before he answered. ከመመለሱ ፡ በፊት ፡ ትንሽ ፡ አመነታ
She hesitated at the door before entering. ከመግባቷ ፡ በፊት ፡ አመነታች

**hesitation** ማመንታት
His talk was filled with hesitations. ንግግሩ ፡ ማመንታት ፡ የበዛበት ፡ ነበር
She agreed without the slightest hesitation. እርሷ ፡ ያለ ፡ ምንም ፡ ማመንታት ፡ ተስማማች
*After some hesitation, she bought the blue dress. ጥቂት ፡ ካመነታች ፡ በኋላ ፡ ሰማያዊውን ፡ ልብስ ፡ ገዛች

**without hesitation** ሳይጠራጠር
He answered without hesitation. ሳይጠራጠር ፡ መልስ ፡ ሰጠ

**heterogeneous** ቅይጥ
There is a heterogeneous population in the U.S.A. የአሜሪካን ፡ ሕዝብ ፡ ቅይጥ ፡ ነው

**hew**

1. ጠረበ. The masons hew stones for building. ግንበኞቹ ፡ ለሕንጻው ፡ ድንጋይ ፡ ይጠርባሉ
2. ቈረጠ. The soldiers hewed logs to build a bridge. ወታደሮቹ ፡ ድልድይ ፡ ለመሥራት ፡ ግንድ ፡ ቈረጡ
*The boy scout hewed a path through the forest. ቦይስካውቱ ፡ ጫካውን ፡ መንጥሮ ፡ መንገድ ፡ አወጣ

**hew down**
1. መለመለ. He hewed down the branch. ቅርንጫፉን ፡ መለመለ
2. ቈረጠ. He hewed down the tree. ዛፉን ፡ ቈረጠው

**heyday** የእፍላ ፡ ጊዜ
He was greatly admired in his heyday. በእፍላ ፡ ጊዜው ፡ በጣም ፡ ይደነቅ ፡ ነበር

**reach one's heyday** ልቆ ፡ ታወቀ
He reached his heyday as a boxer when he was only twenty-two. በቡጢኛነቱ ፡ ልቆ ፡ የታወቀው ፡ ገና ፡ በሃያ ፡ ሁለት ፡ ዓመቱ ፡ ነበር

**hiatus** ክፍት ፡ ቦታ
The hiatus in the old manuscript shows that something has been left out. ባረጀው ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ መጕደሉን ፡ ያሳያል

**hibernate**
*Bears and other animals hibernate. ተኵላዎችና ፡ ሌሎችም ፡ እንስሶች ፡ ክረምቱን ፡ በሙሉ ፡ በየጕሬያቸው ፡ ተኝተው ፡ ያሳልፉታል

**hiccups** ስርቅታ
How can I get rid of these hiccups? ይህን ፡ ስርቅታ ፡ እንዴት ፡ ላስወግደው ፡ እችላለሁ ?

**have the hiccups** ስርቅታ ፡ ያዘ(ው)
+I have the hiccups again. እንደገና ፡ ስርቅታ ፡ ይዞኛል

**hid**, see **hide.**

**hidden** የተሰወረ
His words have a hidden meaning. የሚናገራቸው ፡ ቃሎች ፡ የተሰወረ ፡ ትርጕም ፡ አላቸው

**hide** (hid), vt.
1. ደበቀ. He hid the money in a drawer. ገንዘቡን ፡ በመሳቢያ ፡ ውስጥ ፡ ደበቀ
She hid her anxiety. ስጋቷን ፡ ደበቀች
2. ከለለ. The trees hide the building. ዛፎቹ ፡ ሕንጻውን ፡ ከልለውታል
3. ሰወረ(ተሰወረ). The future is hidden from us. ወደፊት ፡ የሚሆነው ፡ ከኛ ፡ የተሰወረ ፡ ነው
4. ሸፈነ(ተሸፈነ). The sun was hidden by the clouds. ፀሐይዋ ፡ በደመና ፡ ተሸፍና ፡ ነበር

**hide** (vi.)
1. ተደበቀ. Let's hide in the garage! ጋራዡ ፡ ውስጥ ፡ እንደበቅ
2. ተሸሸገ. He hid behind the door when I came into the room. ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ስገባ ፡ ከመዝጊያው ፡ ሥር ፡ ተሸሸገ
[See also 'obscurity']

**hide** (n.) ቆዳ
Shoes are made of tanned hide. ጫማዎች ፡ የሚሠሩት ፡ ከለፋ ፡ ቆዳ ፡ ነው

**raw hide** ቆዳ
Ethiopia exports raw hides. ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ቆዳ ፡ ትልካለች

**hide-and-seek** ድብብቆሽ
Children like to play hide-and-seek. ልጆች ፡ ድብብቆሽ ፡ መጫወት ፡ ይወዳሉ

**hideaway** መደበቂያ
The robber's hideaway was in a large cave. የቀማኛው ፡ መደበቂያ ፡ ትልቁ ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ነበር

**hideous**
1. አሰቃቂ. A hideous crime was committed in Kafa. ከፋ ፡ ውስጥ ፡ አሰቃቂ ፡ ወንጀል ፡ ተፈጸመ
2. አስከፊ. The hideous face of the ape frightened us. የዝንጀሮው ፡ አስከፊ ፡ ፊት ፡ አስደነገጠን

**hideout** መደበቂያ ፤ ጐሬ
The police discovered the robbers' hideout. ፖሊሱ ፡ የቀማኞቹን ፡ መደበቂያ ፡ (ጐሬ) ፡ አገኘ

**hiding, go into ~** ተደበቀ
The robbers went into hiding after the robbery. ቀማኞቹ ፡ ከዘረፋ ፡ በኋላ ፡ ተደበቁ

**hiding place** የመደበቂያ ፡ ቦታ
The children have a secret hiding place. ልጆቹ ፡ ስውር ፡ የመደበቂያ ፡ ቦታ ፡ አላቸው

**hierarchy** (hierarchies)
1. ባለ ፡ ሥልጣናት. The hierarchy of the Ethiopian church is headed by the patriarch. የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለ ፡ ሥልጣናት ፡ አለቃ ፡ ጳጳስ ፡ ነው
2. ደረጃ . Zoologists have classified animal life in a hierarchy. ዞኦሎጂስቶች ፡ የእንስሳትን ፡ ዓይነት ፡ በደረጃ ፡ ከፋፍለውታል

**high**
1. ረጅም (pl. ረጃጅም). The Empire State

Building in New York is very high. የኒውዮርክ ፣ ኤምፓየር ፣ ስቴት ፣ ሕንጻ ፣ በጣም ፣ ረጅም ፣ ነው
There are many high buildings in New York. ኒውዮርክ ፣ ውስጥ ፣ ብዙ ፣ ረጃጅም ፣ ሕንጻዎች ፣ አሉ
2. ከፍተኛ. He is a high official in the government. ከፍተኛ ፣ የመንግሥት ፣ ባለሥልጣን ፣ ነው
High speed on a winding road is dangerous. በጠምዛዛ ፣ መንገድ ፣ ላይ ፣ በከፍተኛ ፣ ፍጥነት ፣ መንዳት ፣ አደገኛ ፣ ነው
His high ambitions were never realized. ከፍተኛ ፣ ምኞቱ ፣ ሳይፈጸምለት ፣ ቀረ
3. ከፍ ፣ ያለ. I have a high opinion of him. ስለሱ ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ ግምት ፣ አለኝ
4. ጥልቅ. He attained a high degree of skill in doctoring. ሰዎችን ፣ በማከም ፣ ጥልቅ ፣ ጥበብ ፣ ገበየ
5. የላቀ. My uncle is a man of high caliber. አጐቴ ፣ የላቀ ፣ ችሎታ ፣ ያለው ፣ ሰው ፣ ነው
6. ኀይለኛ. His high fever kept him out of school. ኀይለኛ ፣ ትኩሳት ፣ ከትምህርት ፣ ቤት ፣ አስቀረው
7. ቀጭን. I don't like his high voice. ቀጭኑን ፣ ድምፁን ፣ አልወድም
8. ውድ. Apples are high in winter. ቱፋ ፣ በክረምት ፣ ውድ ፣ ነው
9. ቀላል. He put the car in high gear. መኪናውን ፣ ቀላል ፣ ማርሽ ፣ አገባ
*How high is it? ርዝመቱ ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ነው ?
*That building is eight stories high. ሕንጻው ፣ ባለ ፣ ስምንት ፣ ፎቅ ፣ ነው

**high** (adv.)
1. ከፍ ፣ ብሎ. The eagle flies high. ንስሩ ፣ ከፍ ፣ ብሎ ፣ ይበራል
2. ከፍ ፣ አድርጎ. Aim high or you will miss the target. ከፍ ፣ አድርገህ ፣ አነጣጥር ፤ አለዚያ ፣ ዒላማውን ፣ ትስታለህ
*The plane was high in the clouds. አውሮፕላኑ ፣ ደመና ፣ ውስጥ ፣ ገብቶ ፣ ይበር ፣ ነበር

**be high** ከፍ ፣ አለ ፤ ተወደደ
Prices are very high this year. ዘንድሮ ፣ የእቃ ፣ ዋጋ ፣ በጣም ፣ ከፍ ፣ ብሏል
Apples are high in winter. ቱፋ ፣ በክረምት ፣ ይወደዳል

**high and dry** ብቻውን
He left her high and dry. ብቻዋን ፣ ጥሏት ፣ ጠፋ

**high and low** በየሥርቻው
They searched high and low but did not find him. በየሥርቻው ፣ እየገቡ ፣ ቢፈልጉት ፣ አላገኙትም

**high living** ሀብታም ፣ ደረጃ
They have indulged in high living for years. ለብዙ ፣ ዓመታት ፣ በሀብታም ፣ ደረጃ ፣ ኖረዋል

**on high** ተሰቅሎ
The flags waved on high. ሰንደቅ ፣ ዓላማዎቹ ፣ ተሰቅለው ፣ ይውለበለቡ ፣ ነበር
[See also 'altitude, cost, hand, jump, none, pitch, pride, tide']

**highborn** ከትልቅ ፣ የተወለደ
Only the highborn may enter the nobility. መኳንንት ፣ ሊሆን ፣ የሚችለው ፣ ከትልቅ ፣ የተወለደ ፣ ብቻ ፣ ነው

**highbrow** የተማረ
He comes from a highbrow family. ከተማረ ፣ ቤተሰብ ፣ ይወለዳል

**high chair** የሕፃን ፣ ወምበር
She put the baby in the high chair. ሕፃኑን ፣ በሕፃን ፣ ወምበር ፣ ላይ ፣ አስቀመጠች

**higher** ከ - - - ይልቅ ፣ ረዥም
That building is higher than this one. ከዚህኛው ፣ ይልቅ ፣ ያኛው ፣ ሕንጻ ፣ ረዥም ፣ ነው
[See also 'education']

**highhanded, in a ~ fashion** እንዳሻው
He ran the organization in a highhanded fashion. ድርጅቱን ፣ እንዳሻው ፣ ያስተዳድረው ፣ ነበር

**highhanded treatment** መጨቆን
I dislike his highhanded treatment of his workers. ሠራተኞቹን ፣ መጨቆኑን ፣ አልወድም

**highland** ደጋ
He lives in the Ethiopian highland. በኢትዮጵያ ፣ ደጋ ፣ ይኖራል

**highlight, be the ~** በጣም ፣ የደመቀ ፣ ነው
Our dance was the highlight of the season. በዓመቱ ፣ ውስጥ ፣ ከተደረጉት ፣ ነገሮች ፣ ሁሉ ፣ ያዘጋጀነው ፣ ዳንስ ፣ በጣም ፣ የደመቀ ፣ ነበር

**highly**
1. በጣም. She seemed highly pleased. በጣም ፣ ደስ ፣ ያላት ፣ ትመስል ፣ ነበር
That's highly interesting. በጣም ፣ የሚያስደንቅ ፣ ነው
2. በአድናቆት. He spoke highly of him. ስለሱ ፣ በአድናቆት ፣ ተናገረ
*He is highly paid for his job. ለሥራው ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ ደሞዝ ፣ ይከፈለዋል
*My brother is a highly placed official. ወንድሜ ፣ ከፍተኛ ፣ ሥልጣን ፣ ያለው ፣ ነው
[See also 'regard']

**high-minded** አርቆ ፡ አሳቢ
Everyone liked the high-minded ruler. ሁሉም ፡ ሰው ፡ አርቆ ፡ አሳቢውን ፡ ገዢ ፡ ወደደው

**Highness, His ~ the Prince** ልዑል
I am going to meet his Highness, Prince Philip. ልዑል ፡ ፊልፕ ፡ ዘንድ ፡ ልቀርብ ፡ ነው

**Her Highness the Duchess** ልዕልትነታቸው
Her Highness the Duchess is giving a tea. ልዕልትነታቸው ፡ የሻይ ፡ ግብዣ ፡ ያደርጋሉ

**Your Highness** ልዑል ፡ ሆይ
Your Highness, may I introduce Dr. Parker. ልዑል ፡ ሆይ ! ዶክተር ፡ ፓርከርን ፡ እንዳቀርብ ፡ ይፈቀድልኝ
[See also 'royal']

**high-pitched** ቀጭን
He has a high-pitched voice. ቀጭን ፡ ድምፅ ፡ አለው

**high priest** ሊቀ ፡ ካህናት
The high priest will perform the marriage ceremony. ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ የሰርጉን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይባርካሉ

**high-ranking** ከፍተኛ
The Emperor was accompanied by high-ranking officials. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ባለ ሥልጣኖች ፡ አስከትለው ፡ ነበር

**high school** ሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት
There are five hundred students in the high school. በሁለተኛው ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ተማሪዎች ፡ አሉ

**high seas** ባለቤት ፡ የሌላቸው ፡ ባሕሮች
The high seas must be open to all ships. ባለቤት ፡ የሌላቸው ፡ ባሕሮች ፡ ለመርከቦች ፡ ሁሉ ፡ ነጻ ፡ ይሆናሉ

**high spirits, be in ~** ደስ ፡ ደስ ፡ አለ(ው)
+He is in high spirits today because he got the first prize. ያንደኛነቱን ፡ ሽልማት ፡ ስላገኘ ፡ ዛሬ ፡ ደስ ፡ ደስ ፡ ብሎታል

**high-strung** ድንጉጥ
She is high-strung and is startled by the slightest noise. ድንጉጥ ፡ ስለሆነች ፡ ኳ ፡ ባለ ፡ ቁጥር ፡ ትበረግጋለች

**high time, it is ~**
*It is high time you started your homework. የቤት ፡ ሥራህን ፡ የመሥራት ፡ ጊዜው ፡ አሁን ፡ ነው

**highway** አውራ ፡ ጎዳና
The highway goes as far as the next turn. አውራ ፡ ጎዳናው ፡ እስከሚቀጥለው ፡ መጠምዘዣ ፡ ድረስ ፡ ይዘልቃል

**hijack** ጠለፈ
The guerrillas hijacked the plane. የደፈጣ ፡ ተዋጊዎቹ ፡ አውሮፕላኑን ፡ ጠለፉት

**hijacking** የአውሮፕላን ፡ መጠለፍ
The derangement of the schedule was caused by the hijacking. የፕሮግራሙ ፡ መቃወስ ፡ የደረሰው ፡ በአውሮፕላኑ ፡ መጠለፍ ፡ የተነሣ ፡ ነው

**hike** (v.)
1. ተጓዘ. He hiked five miles across the desert. በምድረ ፡ በዳው ፡ አቋርጦ ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ ተጓዘ
2. ከፍ ፡ አደረገ. The company hiked the wages of its workers. ኩባንያው ፡ የሠራተኞቹን ፡ አበል ፡ ከፍ ፡ አደረገ

**hike** (n.) ሽርሽር ፤ የእግር ፡ ሽርሽር
Let's go on a hike! ሽርሽር ፡ እንሂድ
On a long hike, he could always outlast me. በረጅም ፡ የእግር ፡ ሽርሽር ፡ ላይ ፡ ሁልጊዜ ፡ ከኔ ፡ ይበረታል

**hilarious** የሚያሥቅ
The most hilarious incidents happen to him. በጣም ፡ የሚያሥቅ ፡ ነገር ፡ ይደርስበታል

**hilarity** ውካታ
The hilarity of the neighbors bothered me greatly. የጐረቤት ፡ ውካታ ፡ በጣም ፡ አበሳጨኝ

**hill** ኰረብታ
What is on the other side of the hill? ከኰረብታው ፡ ጀርባ ፡ ምን ፡ አለ ?

**down the hill** ቁልቁለቱን
He went down the hill on a mule. በበቅሎ ፡ ቁልቁለቱን ፡ ወረደ

**line of hills** ሸንተረር
There is a line of hills along the border. በወሰኑ ፡ ላይ ፡ ሸንተረር ፡ አለ

**up the hill** ዳገቱን ፡ ሲወጣ
The cyclists had to push their machines up the hill. ቢስክሌተኞቹ ፡ ዳገቱን ፡ ሲወጡ ፡ ቢስክሌታቸውን ፡ መግፋት ፡ ነበረባቸው

**hillock** ጉብታ
The shepherd sat on a hillock and watched the grazing sheep. እረኛው ፡ ጉብታው ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ የተሰማሩትን ፡ በጎች ፡ ጠበቀ

**hillside** የኰረብታ ፡ ጎን ፤ የተራራ ፡ ጥግ
Rain and wind eroded the hillsides. ዝናብና ፡ ነፋስ ፡ የኰረብታውን ፡ ጎን ፡ ሸረሸረው

The rocky hillside had enough pasture for sheep. ድንጋያማው ፡ የተራራ ፡ ጥግ ፡ ለበጎች ፡ የሚበቃ ፡ ግጦሽ ፡ ነበረበት

**hilltop** የኰረብታ ፡ ጫፍ ፤ አፋፍ
After a fierce charge, our soldiers drove the enemy from the hilltop. ጠንክረው ፡ ካጠቁ ፡ በኋላ ፡ ወታደሮቻችን ፡ ጠላትን ፡ የኰረብታውን ፡ ጫፍ ፡ (አፋፉን) ፡ አስለቀቁት

**hilly** ኰረብታማ
Menz is a very hilly country. መንዝ ፡ በጣም ፡ ኰረብታማ ፡ አገር ፡ ነው

**him** እሱን, (or object suffix pronouns).
I saw him. አየሁት (or እሱን ፡ አየሁት).

**himself**
1. ራሱ. He himself told me the news. ወሬውን ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ነገረኝ
Did he do it himself? የሠራው ፡ ራሱ ፡ ነው ?
2. tä-stem. He fell down and hurt himself. ወድቆ ፡ ተጐዳ

**be himself** እንደወትሮው ፡ ነው
He is not himself today. ዛሬ ፡ እንደወትሮው ፡ አይደለም

**by himself** ብቻውን
He came by himself. ብቻውን ፡ መጣ
He built the shed by himself. ጎጆውን ፡ ብቻውን ፡ ሠራ

**hind** የኋላ
The hind leg of the table is broken. የጠረጴዛው ፡ የኋላ ፡ እግር ፡ ተሰብሯል

**hinder**
1. አደናቀፈ. Her long skirt hinders her in running. ረጅም ፡ ቀሚሷ ፡ ስትሮጥ ፡ ያደናቅፋታል
2. አስታጐለ. Deep mud hindered our travel. ማጥ ፡ ጉዞዋችንን ፡ አስታጐለ
3. ዕንቅፋት ፡ ሆነ. Lack of education will hinder you when you try to get a job. አለመማርህ ፡ ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ ዕንቅፋት ፡ ይሆንብሃል

**be hindered**
1. ተቃወሰ. Expiration of air from the lungs is hindered by diphtheria. ወደ ፡ ውጭ ፡ መተንፈስ ፡ በጉሮሮ ፡ በሽታ ፡ ምክንያት ፡ ይቃወሳል
2. ተሰናከለ. Free trade between nations is hindered by regulations. በመንግሥታት ፡ መካከል ፡ ሊኖር ፡ የሚገባው ፡ ነጻ ፡ ንግድ ፡ በደንቦች ፡ ምክንያት ፡ ተሰናክሏል

**hindrance** ዕንቅፋት
A poor education can be a hindrance to success. በቂ ፡ ያልሆነ ፡ ትምህርት ፡ ለሥራ ፡ መሳካት ፡ ዕንቅፋት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

**hindsight** ዞር ፡ ብሎ ፡ ማየት
Hindsight enables us to understand many things. ዞር ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ ብዙ ፡ ነገሮችን ፡ ለመረዳት ፡ ያስችለናል

**hinge** (v.), ~ **on** ተመሠረተ
Everything hinges on his decision. ማንኛውም ፡ ነገር ፡ በሱ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው

**hinge** (n.) ማጠፊያ
Take the door off its hinges! በሩን ፡ ከማጠፊያው ፡ ላይ ፡ ንቀለው

**hint** (v.)
1. አመለከተ. He hinted that something was up. አንድ ፡ ነገር ፡ መምጣቱን ፡ አመለከተ
2. አስገነዘበ. I hinted that Kathy ought to work harder. ካቲ ፡ ጠንከር ፡ ብላ ፡ መሥራት ፡ እንዳለባት ፡ አስገነዘብኩዋት

**hint at**
1. ለማለት ፡ ፈለገ. What are you hinting at? ምን ፡ ለማለት ፡ ፈለግህ ?
2. ጠቀስ ፡ አድርጎ ፡ አለፈ. He hinted at my failure in the exam. በፈተና ፡ መውደቄን ፡ ጠቀስ ፡ አድርጎ ፡ አለፈ

**hint** (n.)
1. ምክር. This book contains useful hints for housewives. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ለቤት ፡ እመቤቶች ፡ ጠቃሚ ፡ ምክሮችን ፡ ይዟል
2. ጥቅሻ. The boy was too obtuse to take the hint. ልጁ ፡ በጣም ፡ ድል ፡ ስለነበረ ፡ ጥቅሻው ፡ ሊገባው ፡ አልቻለም
3. የሚያስታውቅ ፡ ምልክት. The serene sea gave no hint of the approaching storm. ጸጥ ፡ ያለው ፡ ባሕር ፡ የመጣውን ፡ ማዕበል ፡ የሚያስታውቅ ፡ ምልክት ፡ አላሳየም

**give a hint**
1. በዘዴ ፡ አስታወቀ. She gave him a hint that she would like him to leave. እንዲሄድላት ፡ መፈለጓን ፡ በዘዴ ፡ አስታወቀችው
2. ጠቈመ. Give me a hint as to his identity! ማን ፡ እንደሆነ ፡ ጠቍመኝ

**hip** ወገብ ፤ ሽንጥ ፤ ዳሌ
He stood there with his hands on his hips. ወገቡን ፡ ይዞ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆመ
He broke his hip. ሽንጡን ፡ ሰበረው
This woman has large hips. ይህች ፡ ሴት ፡ ሰፊ ፡ ዳሌ ፡ አላት

**hippopotamus** ጉማሬ
This river abounds in hippopotamuses. ይህ ፡ ወንዝ ፡ ጉማሬ ፡ ሞልቶበታል

**hire** (v.)
1. ቀጠረ. We have to hire more people. ተጨማሪ ፡ ሰዎች ፡ መቅጠር ፡ አለብን
2. ተከራየ. We hired the boat for a whole day. ጀልባውን ፡ ለሙሉ ፡ ቀን ፡ ተከራየን
3. ገዛ. The fee for hiring a lawyer is quite high. ጠበቃ ፡ ለመግዛት ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው

**hire out** አከራየ
The farmer hires out his horses. ገበሬው ፡ ፈረሶቹን ፡ ያከራያል

**hire** (n.) ኪራይ
How much is the hire of this hall? የዚህ ፡ አዳራሽ ፡ ኪራይ ፡ ስንት ፡ ነው ?

**his** የሱ, (or suffix pronouns)
This is his book. ይህ ፡ የሱ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው (or, ይህ ፡ መጽሐፉ ፡ ነው).
This is his. ይህ ፡ የሱ ፡ ነው

**hiss**
1. አፏጨ. The snake raised its head and hissed. እባቡ ፡ ራሱን ፡ አቅንቶ ፡ አፏጨ
2. የጥላቻ ፡ ድምፅ ፡ አሰማ. Everytime he mentioned her name, the audience hissed. ስሟን ፡ ባነሣ ፡ ቁጥር ፡ የተሰበሰበው ፡ ሰው ፡ የጥላቻ ፡ ድምፅ ፡ አሰማ
3. ቱሽ ፡ አለ. Air hissed from the leak in the tire. አየር ፡ ከጐማው ፡ ቀዳዳ ፡ ቱሽ ፡ አለ

**hissing** (adj.) እስ ፡ የሚል
First I heard a hissing sound. መጀመሪያ ፡ እስ ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ

**historian** ታሪክ ፡ ጸሐፊ
Toynbee is a famous historian. ቶይንቢ ፡ የታወቀ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ ነው

**historic** ታሪካዊ
The return of the Emperor was an historic occasion. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መመለስ ፡ ታሪካዊ ፡ ድርጊት ፡ ነበር

**historical**
1. ታሪካዊ. Historical events used to be written down in chronicles. ታሪካዊ ፡ ድርጊቶች ፡ በዜና ፡ መዋዕል ፡ ይጻፉ ፡ ነበር
2. የጥንት. The actors wore historical costumes. ተዋንያን ፡ የጥንት ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ ነበር

**history** ታሪክ
Have you studied European history? የአውሮፓን ፡ ታሪክ ፡ አጥንተሃል ?
Ethiopia has a long history. ኢትዮጵያ ፡ የቆየ ፡ ታሪክ ፡ አላት
[See also 'dawn']

**hit** (hit)
1. መታ. The ball hit the fence. ኳሱ ፡ አጥሩን ፡ መታ
He hit the nail with the stone. ምስማሩን ፡ በድንጋይ ፡ መታ
I hit my knee. ጉልበቴን ፡ መታኹ
2. ለጋ. He hit the ball with a bat. ኳሷን ፡ በዱላ ፡ ለጋት
3. ከ -- ጋር ፡ ተጋጨ. The car hit the tree. መኪናው ፡ ከዛፉ ፡ ጋር ፡ ተጋጨ
4. አስደነገጠ. The news hit me very hard. ወሬው ፡ በጣም ፡ አስደነገጠኝ
5. ቀረበ. When will this report hit the papers? ሪፖርቱ ፡ ለጋዜጣ ፡ መቼ ፡ ይቀርባል ?

**hit against** ገጨ
+He hit his head against the wall. ራሱን ፡ ግድግዳ ፡ ገጨው

**hit back** መልሶ ፡ መታ
If I hit you, will you hit me back? ብመታህ ፡ መልሰህ ፡ ትመታኛለህ ?

**hit it off** ስምና ፡ ወርቅ ፡ ሆኑ
We hit it off immediately with the new neighbors. ከዲሶቹ ፡ ጐረቤቶቻችን ፡ ጋር ፡ ቶሎ ፡ ስምና ፡ ወርቅ ፡ ሆንን

**hit on**
1. ገጨ. +He hit his head on the door. ራሱን ፡ በሩ ፡ ገጨው
2. አገኘ. We hit on the right road in the dark. በጨለማ ፡ ትክክለኛውን ፡ መንገድ ፡ አገኘነው

**hit out at** ተደባደበ
The man hit out at the thieves who attacked him. ሰውዬው ፡ ሲያጠቁት ፡ ከነበሩት ፡ ሌቦች ፡ ጋር ፡ ተደባደበ

**hit upon** አገኘ
He hit upon a new idea for making beer. ስለ ፡ ቢራ ፡ አጠማመቅ ፡ አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ አገኘ

**be hit**
1. ተጐዳ. We were all hit by the deflation. በገንዘብ ፡ መርከስ ፡ ምክንያት ፡ ሁላችንም ፡ ተጐዳን
2. ስሜቱ ፡ ተነካ. He was hit hard by her deceit. በሷ ፡ ክሕደት ፡ ስሜቱ ፡ በጣም ፡ ተነካ
[See also 'hard, snag, spot']

**hit** (n.) ተወዳጅ
His song became a hit overnight. የሱ ፡ ዘፈን ፡ ባንዳፍታ ፡ ተወዳጅ ፡ ሆነ

**hit-or-miss** ባወጣ ፡ ያውጣው
This is a hit-or-miss method. ዘዴው ፡ ባወጣ ፡ ያውጣው ፡ ነው

**hit-and-run**
*A hit-and-run driver killed the child. ልጁን ፡ ገ
ጭቶ ፡ የገደለው ፡ ሰውዬ ፡ አመለጠ

**hitch** (v.)
1. አሰረ. He hitched his mule to a post and went into his house. በቅሎውን ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ አስሮ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ
2. አንፏቀቀ. He hitched the chair nearer to the fire. ወንበሩን ፡ ወደ ፡ እሳቱ ፡ አንፏቀቀ

**hitch along** እየተንገጫገጨ ፡ ሄደ
The old buggy hitched along. ያረጀው ፡ ጋሪ ፡ እ
የተንገጫገጨ ፡ ሄደ

**hitch on** ነከሰ
+He hitched his pants on a nail and tore them. ሱሪውን ፡ ምስማር ፡ ነክሶ ፡ ቀደደበት

**hitch** (n.)
1. መሰናክል. There was a sudden hitch in the program. ፕሮግራሙ ፡ ያልታሰበ ፡ መሰናክል ፡ ገጠመው
2. እንከን ፤ ችግር. The celebration went off without a hitch. በዓሉ ፡ ያላንዳች ፡ እንከን ፡ (ችግር) ፡ ተከናወነ

**hitchhike**
*He hitchhiked across the country. ባለመኪና ፡ እየለመነ ፡ አገሩን ፡ አቋረጠ

**hither** ወዲህ
Come hither! ወዲህ ፡ ና

**hitherto** እስካሁን ፡ ድረስ
Hitherto he was an unknown writer. እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ስሙ ፡ ያልታወቀ ፡ ደራሲ ፡ ነበር

**hive** ቀፎ
The hive was full of bees. ቀፎው ፡ በንብ ፡ ተ
ሞልቶ ፡ ነበር

**hives, be covered with ~** ተጉረበረበ
When he drinks mead, his body becomes covered with hives. ጠጅ ፡ ሲጠጣ ፡ ሰውነቱ ፡ ይጉረበረባል

**hoard** (v.) አከማቸ
They are hoarding sugar. ስኳር ፡ ያከማቻሉ

**hoard** (n.) ክምችት
His hoard of sugar was ruined by ants. የሱኳሩ ፡ ክምችት ፡ በጉንዳኖች ፡ ተበላሸ

**hoarfrost** አመዳይ
Hoarfrost covers the ground in the early morning. አመዳይ ፡ ማለዳ ፡ መሬቱን ፡ ይሸፍነዋል

**hoarse** ጉርናና
He has a hoarse voice. ጉርናና ፡ ድምፅ ፡ አለው
*Jim was hoarse from a cold. ጂም ፡ ጉሮሮውን ፡ ጉንፋን ፡ ዘግቶት ፡ ነበር
*He has shouted himself hoarse. ጉሮሮው ፡ እ
ስኪዘጋ ፡ ጮኸ
[See also 'shout, sound, talk']

**hoary, be ~ with frost** አመዳይ ፡ ለበሰ
The ground was hoary with frost. መሬቱ ፡ አመ
ዳይ ፡ ለብሶ ፡ ነበር

**hoax** ፈጠራ
It turned out that the news of the Emperor's visit was a hoax. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የጉብኝት ፡ ወሬ ፡ ፈጠራ ፡ መሆኑ ፡ ታወቀ

**hobble** ሰነከለ
At night we hobbled the horses. ማታ ፡ ፈረሶቹ
ን ፡ ሰነከልን

**hobble along** እየተውተረተረ ፡ ሄደ
The old man hobbled along with the aid of his stick. ሽማግሌው ፡ በምርኩዝ ፡ እየተውተረተ
ረ ፡ ሄደ

**hobby** (hobbies) የትርፍ ፡ ጊዜ ፡ ማሳለፊያ
His latest hobby is collecting stamps. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ የትርፍ ፡ ጊዜው ፡ ማሳለፊያ ፡ ቴ
ምብር ፡ መሰብሰብ ፡ ሆኗል

**hock** ቋንጃ
He who cuts the hock is punished by law. ቋንጃ ፡ የቈረጠ ፡ በሕግ ፡ ይቀጣል

**hockey** ገና
Hockey is a favorite game of the Ethiopians. ገና ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ጨዋታ ፡ ነው

**hodgepodge**
His report was a hodgepodge of lies and misinformation. ሪፖርቱ ፡ ውሸትና ፡ የተሳሳተ ፡ መረጃ ፡ የተቀላቀለበት ፡ ነበር

**hoe** (v.) ኰተኰተ
He hoed the garden to keep the weeds down.

አረሙን ፡ ለማጥፋት ፡ ያትክልቱን ፡ ቦታ ፡ ኰተኰተው

**hoe** (n.) መኰትኰቻ
Give me a hoe to dig a hole here! እዚህ ፡ ጉድጓድ ፡ የምቈፍርበት ፡ መኰትኰቻ ፡ ስጠኝ

**hog** አሳማ
The hog rooted around for waste. አሳማው ፡ ቆሻሻ ፡ ፍለጋ ፡ መሬቱን ፡ ጫረ

**hoist** (v.)
1. ሰቀለ. They hoisted the flag in the morning. ሰንደቅ ፡ ዓላማውን ፡ ጧት ፡ ሰቀሉ
2. አቆመ. This morning the workers hoisted the statue into its place. ዛሬ ፡ ጧት ፡ ሠራተኞቹ ፡ ሐውልቱን ፡ እስፍራው ፡ ላይ ፡ አቆሙት

**hoist** (n.) መሣሪያ
Is there a hoist for lifting heavy equipment to the top of the building? ከባድ ፡ እቃ ፡ ወደ ፡ ሕንጻው ፡ ጫፍ ፡ የሚያወጣ ፡ መሣሪያ ፡ አለ ?

**hold** (held), vt.
1. ያዘ. Since the chair is heavy, hold it with both your hands! ወንበሩ ፡ ከባድ ፡ ስለሆነ ፡ በሁለት ፡ እጅህ ፡ ያዘው
You must hold the rope tightly. ገመዱን ፡ አጥብቀህ ፡ መያዝ ፡ አለብህ
He held the post of prime minister in the last government. ባለፈው ፡ መንግሥት ፡ የጠቅላይ ፡ ሚኒስትርነትን ፡ ሥልጣን ፡ ይዞ ፡ ነበር
The room holds twenty people. ክፍሉ ፡ ሃያ ፡ ሰው ፡ ይይዛል
2. ለይቶ ፡ አስቀመጠ. Hold this coat for me until tomorrow! ይህን ፡ ኮት ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ለይተህ ፡ አስቀምጥልኝ
3. አቆየ. The police held him at the station house. ፖሊስ ፡ ጣቢያው ፡ ውስጥ ፡ አቆየው
4. ዋጥ ፡ አደረገ. Hold your breath! ትንፋሽህን ፡ ዋጥ ፡ አድርግ
5. ገታ. Hold your temper! ንዴትህን ፡ ግታ
6. ደገነ. The policeman held a gun on the prisoner. ፖሊሱ ፡ በእስረኛው ፡ ላይ ፡ ጠመንጃ ፡ ደገነ
7. አደረገ. Shall we hold a meeting tomorrow? ነገ ፡ ስብሰባ ፡ እናድርግ ?
8. አመነ. Early scholars held that the earth was flat. የጥንት ፡ ሊቃውንት ፡ መሬት ፡ ዝርግ ፡ ናት ፡ ብለው ፡ ያምኑ ፡ ነበር
*The soldiers held the fort. ወታደሮቹ ፡ ምሽጉን ፡ አናስደፍርም ፡ አሉ

**hold** (vi.)
1. ቆየ. How long will this fine weather hold? ይህ ፡ ጥሩ ፡ አየር ፡ ለምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይቆያል ?
2. ሠራ. This rule does not hold in every case. ይህ ፡ ሕግ ፡ ለሁሉም ፡ ሁኔታ ፡ አይሠራም
3. አመነ. I cannot hold it for certain that he returned. ተመለሰ ፡ ብዬ ፡ በእርግጥ ፡ አላምንም
4. እንዳለ ፡ ነው. My promise to you still holds. የገባሁልህ ፡ ተስፋ ፡ አሁንም ፡ እንዳለ ፡ ነው
5. አልተበገረም. The dike held during the flood. ግድቡ ፡ በውኃው ፡ መጥለቅለቅ ፡ አልተበገረም
6. አልተፈታም. That knot will hold. ያ ፡ ቋጥር ፡ አይፈታም
7. ጠብቆ ፡ ተሰፋ. Will this button hold? ይህ ፡ ቁልፍ ፡ ጠብቆ ፡ ተሰፍቷል?

**be held** ተደረገ
When were the last elections held? ያለፈው ፡ ምርጫ ፡ የተደረገው ፡ መቼ ፡ ነው ?

**hold back** (vt.)
1. አስቀረ. I wanted to go, but he held me back. መሄድ ፡ ፈልጌ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ እሱ ፡ አስቀረኝ
He held back ten dollars. ዐሥር ፡ ብር ፡ አስቀረ
2. አገደ. No scruples ever hold him back from prompt action. ከኅሊናው ፡ የሚመነጭ ፡ ጥርጣሬ ፡ ፈጣን ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠት ፡ አያግደውም
3. ወደፊት ፡ እንዳይሄድ ፡ አገደ. Police held back the crowd. ፖሊሶች ፡ ሕዝቡ ፡ ወደፊት ፡ እንዳይሄድ ፡ አገዱት
4. ሸሸገ. The judge warned the witness not to hold back material evidence. ዳኛው ፡ ምስክሩ ፡ የተጨበጡ ፡ ማስረጃዎችን ፡ እንዳይሸሽግ ፡ አስጠነቀቁት
5. ቈረጠ. The government holds back a part of his wages for a pension fund. መንግሥት ፡ ለጡረታ ፡ አበል ፡ ከደሞዙ ፡ ክፍሉን ፡ ይቈርጣል

**hold back** (vi.) አፈገፈገ
When volunteers were called for, they all held back. ፈቃደኞች ፡ እንዲሉ ፡ በተጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ አፈገፈጉ

**hold down**
1. ተጫነ. Hold the lid down! መክደኛውን ፡ ተጫነው
2. ጨቍና ፡ ያዘ. The South African Government holds down the natives by armed force. የደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ መንግሥት ፡ ያገሩን ፡ ተወላጆች ፡ በጦር ፡ ኀይል ፡ ጨቍና ፡ ይይዛቸዋል
3. አስታገሠ. Hold down that noise! ጫጫታውን ፡ አስታግሥ

**hold (oneself) in** ራሱን ፡ ገታ
He was raging inside, but held himself in. ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ተናዶ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ራሱን ፡ ገታ

**hold off** (vt.)
1. ዛሬ ፡ ነገ ፡ ብሎ ፡ አዘገየ. If you hold off applying for a passport, you may not be able to get one on time. ፓስፖርት ፡ ለማግኘት ፡ ማመልከትን ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ ብለህ ፡ ካዘገየህ ፡ በጊዜው ፡ ለማግኘት ፡ አትችል ፡ ይሆናል
2. ወደፊት ፡ እንዳይገፉ ፡ ተከላከለ. He held off the enemy for days. ጠላት ፡ ወደፊት ፡ እንዳይገፉ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ተከላከለ
*He held off calling me. እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ስልክ ፡ ሳይደውልልኝ ፡ ቀረ

**hold off** (vi.) አል + verb
The rain held off until evening. ዝናብ ፡ እስከ ፡ ምሽት ፡ አልጣለም

**hold on** (vi.) ታገሠ
Can you hold on for a minute? አንድ ፡ ደቂቃ ፡ መታገሥ ፡ ትችላለህ ?

**hold on to**
1. ያዘ. Hold on to this receipt for a few days! ይህን ፡ ደረሰኝ ፡ ለጥቂት ፡ ቀኖች ፡ ያዘው
Since it is very dark, hold on to me so that we don't get separated. በጣም ፡ ጨለማ ፡ ስለሆነ ፡ እንዳንጠፋፋ ፡ ያዘኝ
2. አጥብቆ ፡ ያዘ. He held on to the rope to keep from falling. እንዳይወድቅ ፡ ገመዱን ፡ አጥብቆ ፡ ያዘ
3. ቆየ. Can you hold on to that job just a little longer? በዚያ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ልትቆይ ፡ ትችላለህ ?
4. በእጁ ፡ ያዘ. It was a gusty day, so we held on to our hats. በጣም ፡ ነፋሻ ፡ ቀን ፡ ስለነበረ ፡ ባርኔጦቻችንን ፡ በእጃችን ፡ ያዝን

**hold out** (vt.) ዘረጋ
He held out his hand and showed me the cut. እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ የተቈረጠውን ፡ አሳየኝ

**hold out** (vi.)
1. ቆየ. How long can we hold out in this hot place without any water? በዚህ ፡ ሞቃት ፡ ቦታ ፡ ያለ ፡ ውኃ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ለመቆየት ፡ እንችላለን ?
2. በቃ. How long will our food supplies hold out? ቀለባችን ፡ ለምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይበቃናል ?
3. ችግሩን ፡ ተቋቋመ. We would have held out for months, if we had had enough food. በቂ ፡ ምግብ ፡ ቢኖረን ፡ ኖሮ ፡ ለብዙ ፡ ወራት ፡ ችግራችንን ፡ ልንቋቋም ፡ እንችል ፡ ነበር
4. ተቋቋመ. The defenders held out for weeks. ተከላካዮቹ ፡ ለብዙ ፡ ሳምንት ፡ ተቋቋሙ

**(be) held over** ተላለፈ
The matter was held over until the next meeting. ጉዳዩ ፡ ለሚቀጥለው ፡ ስብሰባ ፡ ተላለፈ

**hold (one's) own**
1. እንደ ፡ በፊቱ ፡ ነው. How is John? He is still holding his own. ጆን ፡ እንዴት ፡ ነው ? አሁንም ፡ እንደ ፡ በፊቱ ፡ ነው
2. ማንንም ፡ ቢሆን ፡ መከተ. He can hold his own in any fight. በማንኛውም ፡ ጠብ ፡ ማንንም ፡ ቢሆን ፡ መከተ
*The patient is barely holding his own. በሽተኛው ፡ ምንም ፡ አልተሻለውም

**hold to** ጸና
I hope you will hold to your convictions. በእምነትህ ፡ እንደምትጸና ፡ ተስፋ ፡ አለኝ

**hold together** አንድ ፡ አድርጎ ፡ ያዘ ፤ አጥብቆ ፡ ያዘ
The country needs a good leader who will hold it together. አገሪቱ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ የሚይዛት ፡ ጥሩ ፡ መሪ ፡ ያስፈልጋታል
Iron hoops hold the barrel together. ቦንዳ ፡ በርሜሉን ፡ አጥብቆ ፡ ይይዛል

**(be) held together** ተያያዘ
The dress was held together by pins. ቀሚሱ ፡ በስፒል ፡ ተያይዞ ፡ ነበር

**hold up** (vt.)
1. ቀና ፡ አደረገ. Hold your head up! ራስህን ፡ ቀና ፡ አድርግ
2. ወደ ፡ ላይ ፡ አነሣ. The prisoner held his hands up, so the guard wouldn't shoot him. ዘቡ ፡ እንዳይተኩስበት ፡ እስረኛው ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አነሣ
3. ታጠቀ. He held up his trousers with a belt. ሱሪውን ፡ በቀበቶ ፡ ታጠቀ
4. አዘገየ. Hurry! You are holding me up, and we will be late for the meeting. ቶሎ ፡ በል ፡ ታዘገየኛና ፡ ለስብሰባው ፡ በጊዜ ፡ አንደርስም
5. አስፈራርቶ ፡ ቀማ. The robber held me up with a gun. ሌባው ፡ በሽጉጥ ፡ አስፈራርቶ ፡ ቀማኝ
6. ጠቀሰ. She held up his father as an example to follow. አባቱን ፡ እንደ ፡ መልካም ፡ ምሳሌ ፡ ጠቀሰች
*He used suspenders to hold up his trousers. ሱሪው ፡ እንዳይወልቅበት ፡ በማንገቻ ፡ ይጠቀማል
*Mortar fire held up our advance. የአዳፍኔ ፡ ተኩስ ፡ ወደፊት ፡ እንዳንገፋ ፡ አደረገን

**hold up** (vi.)
1. ተቋቋመ. Our soldiers held up well under enemy fire. በጠላት ፡ ተኩስ ፡ ጊዜ ፡ ወታደሮቻችን ፡ በሚገባ ፡ ተቋቋሙ
2. (= trans.) ቻለ. How is he holding up under the strain? ጭንቀን ፡ እንዴት ፡ ቻለው ?

[See also numerous nouns with 'hold', such as 'arm, council, line']

**hold** (n.)

1. አያያዝ. His hold was tenuous, and he fell. አያያዙ ፡ ልል ፡ ስለነበረ ፡ ወደቀ
2. ተጽዕኖ. Religion had a great hold over the boy. ሃይማኖት ፡ በልጁ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተጽዕኖ ፡ ነበረው

**have a great hold over**
He has a great hold over his young brother. ታናሽ ፡ ወንድሙ ፡ ይገዛለታል

**lose (one's) hold** የያዘውን ፡ ለቀቀ
He lost his hold and fell. የያዘውን ፡ ለቆ ፡ ወደቀ

**maintain (one's) hold** ሥልጣን ፡ ያዘ
How long will the government maintain its hold over the district? መንግሥቱ ፡ በወረዳው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ሥልጣን ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ይይዛል ?

**take hold of** ያዘ
Take hold of the rope! ገመዱን ፡ ያዝ
[See also 'get']

**holdings** ንብረት
The company has large holdings in the West. ኩባንያው ፡ በምዕራብ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ንብረት ፡ አለው

**holdup**
He has nothing to do with the holdup. መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ በማስፈራራት ፡ በተደረገው ፡ ቅሚያ ፡ አልገባበትም

**hole** (v.) ቀደደ
They holed the mountain for a tunnel. ተራራውን ፡ ለመተላለፊያ ፡ ቀደዱ

**hole up** ተከተተ
Bears hole up in caves. ድቦች ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ይከተታሉ

**(be) holed up** ተሸሸገ
The rebels are holed up in the mountains where the police cannot get to them. ዐመፀኞች ፡ ፖሊሶች ፡ ሊደርሱ ፡ በማይችሉበት ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ተሸሽገዋል

**hole** (n.)

1. ቀዳዳ. Put the thread through the hole in the needle! ክሩን ፡ መርፌው ፡ ቀዳዳ ፡ ውስጥ ፡ አስገባው
2. ቦረቦር. The new road is already full of holes. አዲሱ ፡ መንገድ ፡ ካሁኑ ፡ ቦረቦር ፡ ብቻ ፡ ሆኗል
3. ጉድጓድ. The cat is waiting by the mouse-hole. ድመቷ ፡ አይጢ ፡ ጉድጓድ ፡ አጠገብ ፡ አድፍጣለች
4. ጉድለት. There is a hole in the senator's argument. የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ አባል ፡ ያቀረበው ፡ ክርክር ፡ ጉድለት ፡ አለው

**hole in the wall**
The first shop was a real hole in the wall. የመጀመሪያው ፡ ሱቅ ፡ ከቁጥርም ፡ የማይገባ ፡ ነበር

**be in the hole**
After Easter I am always in the hole. ከፋሲካ ፡ በኋላ ፡ ሁልጊዜ ፡ ገንዘብ ፡ ያጥረኛል

**make a hole in**

1. በሳ. He made a hole in the wall with a drill. ግድግዳውን ፡ በመሰርሰሪያ ፡ በሳ
2. አናጋ(በት). The hospital bill made a large hole in his salary. የሐኪም ፡ ቤት ፡ ሒሳብ ፡ ደሞዙን ፡ አናጋበት
3. አመነመነ(በት). A large bill from the doctor made a hole in my savings. ለዶክተሩ ፡ የከፈልኩት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘቤን ፡ አመነመነብኝ

**pick holes in** ሳንክ ፡ አወጣ(ለት)
As soon as I presented my argument, he began to pick holes in it. ሐሳቤን ፡ እንዳቀረብኩ ፡ ሳንክ ፡ ያወጣለት ፡ ጀመር
[See also 'bore, chew, drill, gnaw, peck, poke']

**holiday**

1. በዓል (pl. በዓላት). Sunday is a holiday in Christian countries. በክርስቲያን ፡ አገሮች ፡ እሑድ ፡ በዓል ፡ ነው
Will you go home during the holidays? በበዓላቱ ፡ ጊዜ ፡ ወዳገርህ ፡ ትሄዳለህ ?
2. ዓመት ፡ በዓል. Easter is an important holiday. ፋሲካ ፡ ትልቅ ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ ነው
3. ዕረፍት. He took a holiday last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ዕረፍት ፡ ወሰደ

**holiness** ቅድስትነት
Mary's holiness is revealed in the Gospel. የማርያም ፡ ቅድስትነት ፡ በቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ተገልጿል

**His Holiness** ብፁዕ
His Holiness, the patriarch, blessed the children. ብፁዕ ፡ ፓትሪያርኩ ፡ ልጆችን ፡ ባረኩ

**hollow** (v.), ~ **out** ቦረቦረ
She hollowed out the gourd to made a ladle. ጭልፋ ፡ ለመሥራት ፡ ቅሉን ፡ ቦረቦረችው

**hollow** (n.) ጉድጓድ
He made a little hollow in the ground. መሬቱ ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ ጉድጓድ ፡ ቈፈረ

**hollow** (adj.)
1. ክፍት. These walls seem to be hollow. እነዚህ ፡ ግድግዳዎች ፡ ክፍት ፡ ይመስላሉ
2. ጐድጓዳ. Take this hollow dish for the vegetables! ላትክልት ፡ ማውጫ ፡ ይህን ፡ ጐድጓዳ ፡ ሳሕን ፡ ውሰድ
3. ባዶ. The gourd must be hollow, it is so light. ቅሉ ፡ እንደዚህ ፡ የቀለለው ፡ ባዶ ፡ ስለሆነ ፡ ነው
4. የተቦረቦረ. The bees are making honey in a hollow tree. ንቦቹ ፡ በተቦረቦረው ፡ ዛፍ ፡ ውስጥ ፡ ማር ፡ ይሠራሉ
5. የተጣበቀ. His hollow cheeks are due to a disease. ጉንጮቹ ፡ የተጣበቁት ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ነው
6. የማይጨበጥ. He always makes hollow promises. ሁልጊዜ ፡ የማይጨበጥ ፡ ተስፋ ፡ ይሰጣል

**be hollow**
1. ቀፎ ፡ ነው. The trunk of the tree is completely hollow. የዛፉ ፡ ግንድ ፡ በሙሉ ፡ ቀፎ ፡ ነው
2. ለስሙ ፡ ብቻ ፡ ነበር. Since the enemy lost twice as many soldiers as we, his victory was hollow. ጠላት ፡ ከኛ ፡ ዕጥፍ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ስላለቀበት ፡ ያገኘው ፡ ድል ፡ ለስሙ ፡ ብቻ ፡ ነበር

**holocaust**
1. የእሳት ፡ መቅሠፍት. The bombs made a holocaust of the city. ቦምቦቹ ፡ በከተማው ፡ ላይ ፡ የእሳት ፡ መቅሠፍት ፡ አመጡ
2. እልቂት. The holocaust of the Jews is a stain on German history. የአይሁዶች ፡ እልቂት ፡ የጀርመንን ፡ ታሪክ ፡ የሚያጐድፍ ፡ ነው

**holy**
1. ቅዱስ. The head of the monastery is recognized by all as a holy man. የገዳሙ ፡ አለቃ ፡ በሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ይታያሉ
2. የተቀደሰ. This is a holy place, so behave properly. ይህ ፡ የተቀደሰ ፡ ቦታ ፡ ስለሆነ ፡ ተገቢውን ፡ ጥንቃቄ ፡ አድርግ
This monk leads a holy life. እኚህ ፡ መነኵሴ ፡ የተቀደሰ ፡ ኑሮ ፡ ይኖራሉ
The fight for freedom was a holy cause to him. ለነጻነት ፡ መጋደል ፡ ለርሱ ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባር ፡ ነበር

**Holy Bible** መጽሐፍ ፡ ቅዱስ
The Holy Bible should be in every home. መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ አለበት

**Holy Communion** ሥጋ ፡ ወደሙ
He is taking Holy Communion next Sunday. የሚመጣው ፡ እሑድ ፡ ሥጋ ፡ ወደሙ ፡ ይቀበላል

**Holy Ghost** መንፈስ ፡ ቅዱስ
In the name of the Father, Son and Holy Ghost, I bless you. በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ እባርክሃለሁ

**Holy Land** ቅድስት ፡ አገር
He is going to the Holy Land on a pilgrimage. ቅድስት ፡ አገርን ፡ ለመሳለም ፡ ይሄዳል

**holy of holies** ቅድስተ ፡ ቅዱሳን
You cannot enter the holy of holies unless you are a priest. ቄስ ፡ ካልሆኑ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ አይቻልም

**holy orders** ሥርዓተ ፡ ቅስና ፤ ተክህኖ ፤ ክህነት
He received holy orders and became a priest. ሥርዓተ ፡ ቅስና ፡ (ተክህኖ ፤ ክህነት) ፡ ተደርጎለት ፡ ቄስ ፡ ሆነ

**Holy Scripture** መጽሐፍ ፡ ቅዱስ
He reads the Holy Scripture before going to bed. ከመተኛቱ ፡ በፊት ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ያነባል

**holy water** ጠበል
The priest sprinkled the sick man with holy water. ቄሱ ፡ በሽተኛውን ፡ ጠበል ፡ አጠመቁት

**homage** አክብሮት
The speech began with homage to the king. ንግግሩን ፡ ለንጉሡ ፡ አክብሮቱን ፡ በመግለጽ ፡ ጀመረ

**pay homage (to)**
1. እጅ ፡ ነሣ. The nobles paid homage to the Emperor. መኳንንቱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ እጅ ፡ ነሡ
2. ምስጋና ፡ አቀረበ. In his speech, he paid homage to the leaders. በንግግሩ ፡ ውስጥ ፡ ለመሪዎቹ ፡ ምስጋና ፡ አቀረበ

**home**
1. መኖሪያ. Homes for old people are often charitable institutions. ያረጁ ፡ ሰዎች ፡ መኖሪያዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቶች ፡ ናቸው
2. ትዳር. Some homes are broken up by divorce. አንዳንድ ፡ ትዳር ፡ በፍች ፡ ይፈርሳል

He is longing for a home. ትጻር ፡ ለመያዝ ፡
ይጓጓል
3. ቤት. The lone traveler was glad to reach
home. ብቸኛው ፡ መንገደኛ ፡ ቤቱ ፡ በመድረሱ ፡
ደስ ፡ አለው
4. የትውልድ ፡ አገር. My home is Poland. የት
ውልድ ፡ አገሬ ፡ ፖላንድ ፡ ነው
5. አገር. Ethiopia was the home of the leop-
ard and the elephant. ኢትዮጵያ ፡ ብዙ ፡ ነብ
ርና ፡ ዝሆን ፡ የሚገኙባት ፡ አገር ፡ ነበረች

**home** (adj.)
1. የተወለደበት. His home town was destroyed
during the war. የተወለደባት ፡ ከተማ ፡ በጦር
ነት ፡ ጊዜ ፡ ጠፋች
2. ባገር ፡ ውስጥ ፡ የተሠራ. I only buy home
products. ባገር ፡ ውስጥ ፡ የተሠሩ ፡ እቃዎችን ፡
ብቻ ፡ እገዛለሁ

**home** (adv.) እቤት ፤ ወደ ፡ ቤት
I have to go home. እቤቴ ፡ መሄድ ፡ አለብኝ
He comes home late in the evening. ወደ ፡ ቤት ፡
የሚመጣው ፡ በጣም ፡ አምሽቶ ፡ ነው

**at home**
1. እቤት. I was at home all day yesterday.
ትላንት ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ እቤት ፡ ዋልኩኝ
2. በአገር ፡ ውስጥ. He is known at home and
abroad. በአገር ፡ ውስጥና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የታ
ወቀ ፡ ሰው ፡ ነው
*Make yourself at home! እንግዳ ፡ አትሁን

**be at home** ጠንቅቆ ፡ ዐወቀ
He is at home in Ethiopian literature. የኢትዮጵ
ያን ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ጠንቅቆ ፡ ያውቃል

**bring home to** አስገነዘበ
My illness brought the importance of insurance
home to me. መታመሚ ፡ የሕይወቴ ፡ ዋስትና
ን ፡ ጥቅም ፡ አስገነዘበኝ

**drive (an argument) home** በሚገባ ፡ አስረዳ
The speaker drove his argument home. ተናጋሪ
ው ፡ ክርክሩን ፡ በሚገባ ፡ አስረዳ

**feel at home**
1. እንደልቡ ፡ ሊሆን ፡ ቻለ. I cannot feel at home
in the Emperor's palace. እኔ ፡ በቤተ ፡ መንግሥ
ቱ ፡ ውስጥ ፡ እንደልቤ ፡ ልሆን ፡ አልችልም
2. እንደልብ ፡ ተናገረ. It is difficult to feel at
home in a foreign language. በውጭ ፡ አገር ፡ ቋ
ንቋ ፡ እንደልብ ፡ ለመናገር ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**make (one's) home** ኖረ
When I retire, I will make my home in the
country. ጡረታ ፡ ስወጣ ፡ እባላገር ፡ እኖራለሁ
[See also 'ancestral, get, show, welcome']

**homecoming** ወደ ፡ አገሩ ፡ መመለስ
His relatives are going to celebrate his home-
coming. ዘመዶቹ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ መመለሱን ፡ ም
ክንያት ፡ በማድረግ ፡ ሊደግሱለት ፡ ነው

**homeland** ትውልድ ፡ አገር
He is very anxious to see his homeland again.
ትውልድ ፡ አገሩን ፡ እንደገና ፡ ለማየት ፡ በጣ
ም ፡ ጓጉቷል

**homeless** ቤት ፡ የሌለው
The homeless refugees have settled by the
railroad station. ቤት ፡ የሌላቸው ፡ ስደተኞች ፡
ባቡር ፡ ጣቢያው ፡ አጠገብ ፡ ሰፍረዋል

**be made homeless** ቤቱን ፡ አጣ
Thousands were made homeless by the flood.
በጐርፉ ፡ የተነሣ ፡ በሺ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡
ቤታቸውን ፡ አጡ

**leave homeless** መጠጊያ ፡ አሳጣ
The upheaval left many people homeless.
ብጥብጡ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ መጠጊያ ፡ አሳጣ

**homely** ቤት ፡ ያፈራ
Homely food was served in the farmer's house.
በገበሬው ፡ ቤት ፡ የቀረበው ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ ያ
ፈራው ፡ ነበር
*She is a homely girl. ልጅቱ ፡ ለክፉ ፡ አትስ
ጥም

**homemade** ቤት ፡ የተሠራ
This is homemade marmalade. ቤት ፡ የተሠራ ፡
ማርማላታ ፡ ነው

**home office** ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት
The home office of our company is in Addis
Ababa. ኩባንያችን ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡
አዲስ ፡ አበባ ፡ ነው

**(be) homesick**
1. ናፈቀ(ው). +I am homesick, although I have
been away from home only a few weeks. ከገ
ሬ ፡ ከወጣሁ ፡ ጥቂት ፡ ሳምንታት ፡ ቢሆንም ፡
ናፈቀኝ
2. ዘመዶቹን ፡ ናፈቀ. She was homesick during
her first weeks at college. ኮሌጅ ፡ ገብታ ፡ አ
ንድ ፡ ሁለት ፡ ሳምንት ፡ እንደቆየች ፡ ዘመዶቿ
ን ፡ ናፈቀች

**homestead** መኖሪያ
Our homestead is located in a beautiful valley.
መኖሪያችን ፡ ውብ ፡ በሆነ ፡ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**home town** የተወለደበት ፡ ከተማ
Inquire after my friends when you go to my

home town. ወደ ፡ ተወለድኩበት ፡ ከተማ ፡ ስትሄድ ፡ ጓደኞቼን ፡ ጠይቅልኝ
*He is from my home town. ያገሬ ፡ ሰው ፡ ነው

**homeward** ወደ ፡ ቤቱ
He walked homeward after a day's work. የዕለቱን ፡ ሥራ ፡ ሲጨርስ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ

**homework** የቤት ፡ ሥራ
Have you done all your homework? የቤት ፡ ሥራህን ፡ በሙሉ ፡ ሠርተሃል ?

**homey**
*The little hotel has a homey atmosphere. ትንሿ ፡ ሆቴል ፡ እንደ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ያላት ፡ ናት

**homicide** ነፍስ ፡ መግደል
He was judged guilty of homicide. ነፍስ ፡ በመግደሉ ፡ ተፈረደበት

**homily** (homilies) ድርሳን
He composed a homily in honor of St. Michael. እርሱ ፡ አንድ ፡ ድርሳነ ፡ ሚካኤል ፡ ጻፈ

**homogeneous** አንድ ፡ ዓይነት
The country has a homogeneous population. አገሪቱ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሕዝብ ፡ አላት

**homonym** ተመሳሳይ
The Amharic words 'be wide' and 'sew' are homonyms. ያማርኛ ፡ ቃላት ፡ « ሰፋ » ፡ ና ፡ « ሰፋ » ፡ ተመሳሳይ ፡ ናቸው

**homosexual** የግብረ ፡ ሰዶም ፡ ሥራ ፡ የሚፈጽም ፡ ሰው
The police arrested the homosexual. የግብረ ፡ ሰዶም ፡ ሥራ ፡ የሚፈጽመውን ፡ ሰው ፡ ፖሊሶቹ ፡ ያዙት

**honest**
1. ሐቀኛ. Do you think he is honest? ሐቀኛ ፡ ይመስልሃል ?
2. ታማኝ. He has an honest face. መልኩን ፡ ሲያዩት ፡ ታማኝ ፡ ይመስላል
3. ሁነኛ. An honest judge cannot be servile to public opinion. ሁነኛ ፡ ዳኛ ፡ በሕዝብ ፡ አስተያየት ፡ አይመራም
4. እውነተኛ. Give me your honest opinion on this subject! በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ እውነተኛ ፡ አስተያየትህን ፡ ስጠኝ
Stores should sell honest goods. ባለሱቆች ፡ እውነተኛ ፡ የሆኑ ፡ እቃዎችን ፡ መሸጥ ፡ አለባቸው
5. ትክክለኛ. The laws require honest weights to be used. ሕጉ ፡ በትክክለኛ ፡ ሚዛን ፡ መጠቀምን ፡ ይጠይቃል
6. የሐቀኛነት. He lives an honest life. የሐቀኛነት ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል
7. ካለማወቅ ፡ የተሠራ. That was an honest mistake. ይህ ፡ ካለማወቅ ፡ የተሠራ ፡ ስሕተት ፡ ነበር
8. (= adv.) ትክክለኛ ፡ በሆነ ፡ መንገድ. He makes honest profits. ትክክለኛ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ትርፍ ፡ ያገኛል

**honestly**
1. በእውነቱ ፤ በእውነት. I was honestly surprised. በእውነቱ ፡ ተገረምኩ
Honestly, I do not know what to do with you. በእውነት ፡ አንተን ፡ ምን ፡ እንደማደርግ ፡ አላውቅም
2. (= n.) እውነቱን. To tell you honestly, I don't like it. እውነቱን ፡ ለመናገር ፡ ደስ ፡ አይለኝም

**honesty**
1. ታማኝነት. There is no question about his honesty. ስለ ፡ ታማኝነቱ ፡ ምንም ፡ የሚያጠራጥር ፡ ነገር ፡ የለም
2. ሐቀኝነት. The mother tried to inculcate honesty in her children. እናትዮዋ ፡ በልጆቿ ፡ ላይ ፡ ሐቀኝነትን ፡ ለማሳደር ፡ ሞከረች

**honey** ማር
The honey is sweet. ማር ፡ ጣፋጭ ፡ ነው

**honeycomb** የንብ ፡ እንጀራ
Wax is removed from the honeycomb and made into candles. ሰም ፡ ከንብ ፡ እንጀራ ፡ ተጣርቶ ፡ ሻማ ፡ ይሠራበታል

**honeymoon**
1. [ከጋብቻ ፡ በኋላ ፡ ሙሽሮች ፡ የሚያሳልፉት ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ].
2. የጫጉላ ፡ ጊዜ. She set up housekeeping right after their honeymoon. የጫጉላ ፡ ጊዜ ፡ ጨርሳ ፡ ጎጆ ፡ ወጣች

**honk** (vt.) ነፋ
Honk the horn three times, and I'll come down. የመኪናውን ፡ ጥሩምባ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ስትነፋ ፡ እመጣለሁ

**honk** (vi.) ጮኸ
We could hear the geese honking in their pen. ዝዪዎቹ ፡ ከመኖሪያቸው ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ሲጮኹ ፡ እንሰማ ፡ ነበር

**honor** (v.)
1. አከበረ. Children should honor their parents. ልጆች ፡ ወላጆቻቸውን ፡ ማክበር ፡ ይገባቸዋል
He honored the agreement to buy our house. ቤታችንን ፡ ለመግዛት ፡ ያደረግነውን ፡ ስምምነት ፡ አከበረ

2. አክብሮቱን ፡ ገለጸ(ለት). They honored him by making him captain of the team. የቡድኑ ፡ መሪ ፡ አድርገው ፡ በመምረጥ ፡ አክብሮታቸውን ፡ ገለጹለት

3. ተቀበለ. We cannot honor this check. ይህንን ፡ ቼክ ፡ አንቀበልም

*Will you honor me with a visit? ቤቴን ፡ መጥተው ፡ ቢያዩልኝ !

**feel highly honored** ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ተሰማ(ው)
I feel highly honored by the kind of things you say about me. ስለኔ ፡ በምትናገረው ፡ ነገር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል
[See also 'memory']

**honor** (n.)

1. ክብር. It is a great honor to be elected to the membership of the committee. ለደርጉ ፡ አባልነት ፡ መመረጥ ፡ ትልቅ ፡ ክብር ፡ ነው
We gave a banquet in his honor. ስለሱ ፡ ክብር ፡ ግብዣ ፡ አደረግን

2. ስም. You must uphold the honor of your family. የቤተሰብህን ፡ ስም ፡ መጠበቅ ፡ አለብህ

3. አክብሮት. He did her the honor of attending the party. በፓርቲው ፡ ላይ ፡ በመገኘት ፡ አክብሮቱን ፡ ገለጸላት
We pay honor to the leaders of science. ለሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ አክብሮት ፡ እንሰጣለን

4. ኩራት. Esther is an honor to her family. አስቴር ፡ ለቤተ ፡ ሰቧ ፡ ኩራት ፡ ናት

**honors**

1. ክብር. The soldier was buried with full military honors. ወታደሩ ፡ በሙሉ ፡ የወታደር ፡ ክብር ፡ ተቀበረ
The scientist received many honors for his work. የሳይንሱ ፡ ሊቅ ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ብዙ ፡ ክብር ፡ አገኘ

2. የክብር ፡ ማዕረግ. My brother graduated with honors. ወንድሜ ፡ የክብር ፡ ማዕረግ ፡ አግኝቶ ፡ ተመረቀ

**be honor bound** ኀሊናው ፡ አስገደደው
I'm honor bound to report your misconduct to the police. ጥፋትህን ፡ ለፖሊስ ፡ እንዳስታውቅ ፡ ኀሊናዬ ፡ አስገደደኝ

**be put on one's honor** እምነት ፡ ተጣለበት
He was put on his honor and left alone to finish the exam. ፈተናውን ፡ ያለ ፡ ተቈጣጣሪ ፡ እንዲጨርስ ፡ እምነት ፡ ተጣለበት

**be to one's honor** አስከበረው
It was greatly to his honor that he refused the award. ሽልማቱን ፡ አልቀበልም ፡ ማለቱ ፡ በጣም ፡ አስከበረው

**debt of honor**
*He considered it a debt of honor. እሱ ፡ ለስም ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የማይከፈል ፡ ዕዳ ፡ አድርጎ ፡ ቈጠረው

**do honor to** እጅ ፡ ነሣ
People came from near and far to do honor to the Emperor. ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ እጅ ፡ ለመንሣት ፡ ሰዎች ፡ ከያለበት ፡ መጡ

**do the honors** እንግዶቹን ፡ አስተናገደ
Do the honors while I am in the kitchen. ከወጥ ፡ ቤት ፡ እስክወጣ ፡ እንግዶቹን ፡ አስተናግድ

**guard of honor** የክብር ፡ ዘብ
A guard of honor preceded the Emperor. የክብር ፡ ዘብ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ነበር

**His Honor** ክቡር ፤ የተከበረ
His Honor, the judge, will now give his decision. ክቡር ፡ (የተከበሩ) ፡ ዳኛ ፡ አሁን ፡ ፍርዱን ፡ ይሰጣሉ

**may I have the honor of**
May I have the honor of your company? ከርስዎ ፡ ጋር ፡ እንድሆን ፡ ይፈቀድልኝ ?

**on my honor** ቃሌን ፡ እገባለሁ
On my honor, I will do my best to behave. በተቻለኝ ፡ መጠን ፡ ጠባዬን ፡ ለማሳመር ፡ ቃል ፡ እገባለሁ

**sense of honor** ክብር
He has no sense of honor. ክብር ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ አያውቅም

**will you do me the honor** ፈቃድዎ ፡ ይሁን
Will you do me the honor of dining with me this evening? ዛሬ ፡ ማታ ፡ እራት ፡ አብረን ፡ እንድንበላ ፡ ፈቃድዎ ፡ ይሁን ?

**Your Honor** ጌታዬ
"I'm not guilty, Your Honor," said the prisoner. እስረኛው ፤ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ጌታዬ ፡ አለ
[See also 'word']

**honorable**

1. ወግ ፡ ያለው. They concluded an honorable peace with their enemy. ወግ ፡ ያለው ፡ስምምነት ፡ ከጠላታቸው ፡ ጋር ፡ አደረጉ

2. ክብር ፡ የማይቀንስ. An honorable exchange of prisoners was arranged by the arbitrators. ክብር ፡ የማይቀንስ ፡ የእስረኞች ፡ መለዋወጥ ፡ ባስታራቂዎች ፡ ተዘጋጀ

3. የሚያኮራ. He has an honorable record of serving his country. ሀገሩን ፡ በማገልገል ፡ የሚያኮራ ፡ ታሪክ ፡ አለው

4. የሚያስከብር. His behavior is always honorable. ሁኔታው ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚያስከብረ ው ፡ ነው
5. ቅን ፡ የሆነ. His honorable intentions are doubted by no one. ቅን ፡ የሆነ ፡ ሐሳቡን ፡ ማንም ፡ አይጠራጠረውም
6. (= adv.) በክብር. He received an honorable discharge after the war. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ በክ ብር ፡ ተሰናበተ
[See also 'mention']

**honorarium** ገንዘብ
The mayor was given an honorarium for delivering a speech to our club. ከንቲባው ፡ ለ ክበባችን ፡ ንግግር ፡ ስላደረገ ፡ ገንዘብ ፡ ተከፈ ለው

**honorary** የክብር
He is the honorary president of my club. እርሱ ፡ የክበቤ ፡ የክብር ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ነው
The Emperor got an honorary degree from Harvard. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከሀርቫርድ ፡ ዩኒቨ ርሲቲ ፡ የክብር ፡ ዲግሪ ፡ ተቀበሉ

**honored** (adj.) የክብር
The honored guests headed the parade. የክብር ፡ እንግዶች ፡ ሰልፉን ፡ መሩ

**hood**
1. ቆብ. Usually a burnoose has a hood. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በርኖስ ፡ ቆብ ፡ አለው
2. ክዳን. He lifted the hood and put water into the radiator. ክዳኑን ፡ ከፍቶ ፡ ሞተሩ ፡ ማ ቀዝቀዣ ፡ ውስጥ ፡ ውኃ ፡ ጨመረበት

**hoodlum** ዱርዬ
A group of hoodlums were standing at the corner. ከመጠምዘዣው ፡ ላይ ፡ ዱርዬዎች ፡ ተ ሰብስበው ፡ ቆመው ፡ ነበር

**(be) hoodwinked** ተታለለ
Don't be hoodwinked by his promises! እርሱ ፡ በሚሰጥህ ፡ ቃል ፡ አትታለል

**hoof** (hoofs, or hooves) ኮቴ
Our horse got a nail in his hoof. ፈረሳችን ፡ ኮቴ ውን ፡ ምስማር ፡ ወግቶታል

**hook** (vt.)
1. ቈለፈ. Please hook my dress for me! ልብሴን ፡ ቈልፍልኝ
2. በመንጠቆ ፡ ያዘ. He hooked a fish. ዓሣ ፡ በ መንጠቆ ፡ ያዘ

**hook** (vi.)
1. ተቈለፈ. This dress hooks in the back. ይህ ፡ ልብስ ፡ ከኋላው ፡ ይቈለፋል
2. ታጠፈ. This road hooks to the left. ይህ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ይታጠፋል

**hook** (n.)
1. መንጠቆ. He suspended the lamp from a hook. ፋኖሱን ፡ በመንጠቆ ፡ ላይ ፡ አንጠለጠለው
2. ማንጠልጠያ. Hang your coat on the hook! ኮትህን ፡ ከማንጠልጠያው ፡ ላይ ፡ ስቀለው
3. መስቀያ. Take the receiver off the hook! የስልኩን ፡ መነጋገሪያ ፡ ከመስቀያው ፡ ላይ ፡ አ ንሣ

**by hook or by crook** በዚህም ፡ ሆነ ፡ በዚያም
He plans to get rich by hook or by crook. በዚህም ፡ ሆነ ፡ በዚያም ፡ ሀብታም ፡ መሆን ፡ ይ ፈልጋል

**on (one's) own hook** በገዛ ፡ ፍላጎቱ ፡ ተነሣሥቶ
He decided to go into business on his own hook. በገዛ ፡ ፍላጎቱ ፡ ተነሣሥቶ ፡ ንግድ ፡ ለመጀ መር ፡ ወሰነ

**hookworm** ወስፋት
He suffers from hookworm. ወስፋት ፡ ያጠቃዋል

**hooky, play ~** ያለ ፡ ፈቃድ ፡ ከትምህርት ፡ ቤ ት ፡ ቀረ
My friend played hooky yesterday. ጓደኛዬ ፡ ትናንትና ፡ ያለ ፡ ፈቃድ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀረ

**hooligan** ዱርዬ
He is just a hooligan and would not commit a serious crime. ጎይለኛ ፡ ወንጀል ፡ የማይፈጽ ም ፡ ዱርዬ ፡ ነው

**hoop, iron ~** ቦንዳ
Iron hoops hold the barrel together. ቦንዳ ፡ በ ርሜሉን ፡ አጥብቆ ፡ ይይዛል

**hoot** (v.)
1. ጮኸ. The owl hooted in the night. ጉጉቷ ፡ ሌሊት ፡ ጮኸች
2. በመናቅ ፡ ጮኸ(በት). The audience hooted the speaker's plan. አድማጮቹ ፡ የተናጋሪውን ፡ ሐሳብ ፡ በመናቅ ፡ ጮኹበት

**hoot** (n.) ጬኸት
The hoot of the owl woke me up. የጉጉት ፡ ጬ ኸት ፡ ቀሰቀሰኝ

**not give a hoot** ግድ ፡ የለውም
He does not give a hoot for anything. ለምንም ፡ ነገር ፡ ግድ ፡ የለውም

**hooves, see hoof**

**hop**
1. ዘለለ. Frogs hop. እንቁራሪቶች ፡ ይዘላሉ

2. እየዘለለ ፡ ሄደ. The child was hopping on the sidewalk. ልጁ ፡ በእግረኛው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ እየዘለለ ፡ ይሄድ ፡ ነበር
3. ጡብ ፡ ጡብ ፡ አለ. The children hop when they play hopscotch. ልጆች ፡ ሰኞ ፡ ማክሰኞን ፡ ሲጫወቱ ፡ ጡብ ፡ ጡብ ፡ ይላሉ

**hop about**
1. ጡብ ፡ ጡብ ፡ አለ. A few mornings ago, birds were hopping about in my garden. ከጥቂት ፡ ቀኖች ፡ በፊት ፡ ወፎች ፡ ባትክልቴ ፡ ቡታዬ ፡ ጡብ ፡ ጡብ ፡ ይሉ ፡ ነበር
2. ዘለል ፡ ዘለል ፡ አለ. He hurt his foot and hopped about in pain. እግሩን ፡ ስለተጎዳ ፡ በሥቃይ ፡ በሌላ ፡ እግሩ ፡ ዘለል ፡ ዘለል ፡ አለ
**hop around** ዘለል ፡ ዘለል ፡ አለ
He was hopping around on one leg. ባንድ ፡ እግሩ ፡ ዘለል ፡ ዘለል ፡ አለ

## hop(s) ጌሾ
Hops are used in making beer. ጌሾ ፡ ለጠላ ፡ መጥመቂያ ፡ ያገለግላል

## hope (v.) ተስፋ ፡ አደረገ
She had hoped to see you. ልታይህ ፡ ተስፋ ፡ አድርጋ ፡ ነበር
*Will it rain tomorrow? I hope not. ነገ ፡ ይዘንባል ? ባልዘነበ !
*I hope I haven't offended you. አላስቀየምኩህም ፡ መቸም

**hope against hope**
*We are hoping against hope for a change in her condition. ተስፋ ፡ ባይኖራትም ፡ ይሻላታል ፡ ብለን ፡ እንመኛለን
**hope for the best** የተሻለ ፡ ነገር ፡ ተመኘ
He hopes for the best; he is a real optimist. የተሻለ ፡ ነገር ፡ ይመኛል ፤ እርግጠኛ ፡ ባለ ፡ ተስፋ ፡ ነው

## hope (n.)
1. ተስፋ. It was a false hope that he would recover. ይድናል ፡ ማለት ፡ ከንቱ ፡ ተስፋ ፡ ነበር
2. አለኝታ. He is the hope of the family. የቤት ፡ ሰቡ ፡ አለኝታ ፡ ነው

**give up hope** ተስፋ ፡ ቈረጠ
Don't give up hope! Your husband will return. ተስፋ ፡ አትቍረጪ ፤ ባልሽ ፡ ይመለሳል
**hold out little hope** ምንም ፡ ያህል ፡ ተስፋ ፡ አልሰጠም
The doctors held out little hope for her recovery. ሐኪሞቹ ፡ ለመዳኗ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ተስፋ ፡ አልሰጡም
**lose hope** ተስፋ ፡ ቈረጠ
Don't lose hope! Everything will turn out all right. ተስፋ ፡ አትቍረጥ ፤ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ይሠምራል
[See also 'cherish, dash, kill, nourish, raise, surrender']

## hopeful
1. ተስፋ ፡ የሚጣልበት. The future does not seem very hopeful. መጪው ፡ ጊዜ ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልበት ፡ አይመስልም
2. ተስፋ ፡ የተመላበት. His hopeful words greatly encouraged me. ተስፋ ፡ የተመላባቸው ፡ ቃላቱ ፡ ብርታት ፡ ሰጡኝ

**be hopeful** ተስፋ ፡ አለ(ው)
He is hopeful of success. እንደሚቃናለት ፡ ተስፋ ፡ አለው

## hopeless ተስፋ ፡ የሚያስቈርጥ
The situation is completely hopeless. ሁኔታው ፡ በፍጹም ፡ ተስፋ ፡ የሚያስቈርጥ ፡ ነው

**be hopeless** አይሆንለትም
Balancing my budget is hopeless. ወጪና ፡ ገቢዬን ፡ ማቃናት ፡ አይሆንልኝም

## hopscotch ሰኞ ፡ ማክሰኞ
Children are playing hopscotch in the street. ልጆቹ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ሰኞ ፡ ማክሰኞ ፡ ይጫወታሉ

## horde
1. መንጋ. Hordes of locusts swarmed over the ground. ያንበጣ ፡ መንጋ ፡ መሬቱን ፡ አለበሰው
2. መዓት. +The baby bird was attacked by a horde of ants. የወፏን ፡ ጫጩት ፡ የጉንዳን ፡ መዓት ፡ ወረራት

**hordes of** በብዛት ፤ ብዙ
Hordes of Mongols invaded Europe in the Middle Ages. በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ሞንጎሎች ፡ አውሮፓን ፡ በብዛት ፡ ወረሩ
Hordes of tourists visited the museum. ብዙ ፡ ጎብኚዎች ፡ ቤተ ፡ መዘክሩን ፡ ጐበኙ

## horizon
1. አድማስ. There was a column of smoke on the horizon. ከአድማሱ ፡ ላይ ፡ ጭስ ፡ ይታይ ፡ ነበር
2. ዕውቀት. Travel widens our horizons. አገር ፡ ማየት ፡ ዕውቀትን ፡ ያስፋፋል

## horizontal አግዳሚ
A table top is horizontal. የጠረጴዛው ፡ ወለል ፡ አግዳሚ ፡ ነው

**horn**
1. ቀንድ. He grabbed the cow by the horn. ላሚን ፡ ቀንዷን ፡ ያዛት
The handle of this knife is made of horn. የዚህ ፡ ቢላዋ ፡ እጀታ ፡ የተሠራው ፡ ከቀንድ ፡ ነው
2. መለከት. The herald angel blew his horn three times. አብሳሪው ፡ መልአክ ፡ መለከቱን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ነፋ
3. ጥሩንባ. Don't blow the horn so much! ጥሩንባውን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ አትንፋ
4. ክላክስ ፡ ማድረጊያ. The horn is in the center of the steering wheel. ክላክስ ፡ ማድረጊያው ፡ መሪ ፡ መኻል ፡ ላይ ፡ ነው
**blow one's own horn** ጉራውን ፡ ነፋ
He is an agreeable fellow, but likes to blow his own horn. ደኅና ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ግን ፡ ጉራውን ፡ ይነፋል
**draw in (one's) horns** አደብ ፡ አለ
Since he lost so much at gambling, he has drawn in his horns a bit. በቁማር ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ስለተበላ ፡ ትንሽ ፡ አደብ ፡ ብሏል
**lock horns** ሳይስማሙ ፡ ቀሩ
The administration and the staff locked horns over the proposed measure. አስተዳደሩና ፡ ሠራተኞቹ ፡ በቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ ሳይስማሙ ፡ ቀሩ
[See also 'cup']

**hornet** ተርብ
The hornet stings. ተርብ ፡ ተናዳፊ ፡ ነው

**horny**
1. የቀንድ. A horny covering keeps the wood from wearing away. የቀንድ ፡ ሽፋን ፡ ዕንጨቱ ፡ እንዳይበላ ፡ ይከላከላል
2. ቆርፋዳ. A farmer's hands are horny from work. የገበሬ ፡ እጅ ፡ ከሥራ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ቆርፋዳ ፡ ነው

**horrible**
1. የሚያሰቅቅ. It was a horrible sight. ሲያዩት ፡ የሚያሰቅቅ ፡ ነበር
2. አስከፊ. The rainy weather is simply horrible. ክረምቱ ፡ ፍጹም ፡ አስከፊ ፡ ነው
*Why did you make such a horrible face? ፊትህን ፡ ኮሶ ፡ ያስመሰልከው ፡ ለምንድነው ?
[See also 'face']

**horrid**
1. በጣም ፡ አስከፊ. Her behavior is horrid. ጠባይዋ ፡ በጣም ፡ አስከፊ ፡ ነው
2. መጥፎ. Massawa has a horrid climate. ምፅዋ ፡ መጥፎ ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፡ አለው

**horrify** (horrified) አሰቀቀ
The sight of the dead soldiers horrified us. የሞቱትን ፡ ወታደሮች ፡ ማየቱ ፡ አሰቀቀን

**horror**
1. ሥቃይ. The horrors of war are indescribable. የጦርነት ፡ ሥቃይ ፡ ሊገለጽ ፡ አይችልም
2. ጥላቻ. She expressed her horror of cruelty. ለጭካኔ ፡ ያላትን ፡ ጥላቻ ፡ ገለጸች
3. ታላቅ ፡ ድንጋጤ. She shrank back from the corpse in horror. ሬሳውን ፡ አይታ ፡ በታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ ተሸማቀቀች
**horror** (adj.) የሚያስፈራ ፤ አሰቃቂ
A horror movie makes me shudder. የሚያስፈራ ፡ ፊልም ፡ ይዘገንነኛል
Horror stories make me jumpy. አሰቃቂ ፡ ታሪኮች ፡ ያስበረግጉኛል
**have a horror of** አልወደደም
A good housewife has a horror of dirt. ባለሙያ ፡ ሚስት ፡ ቆሻሻ ፡ አትወድም
**to (one's) horror**
*To her horror, she saw her husband fall off the cliff. ባሏ ፡ ገደል ፡ ሲገባ ፡ በዓይኗ ፡ ማየቷ ፡ አሰቃቂ ፡ ሆነባት

**horse** ፈረስ
He bought a horse yesterday. ትናንት ፡ አንድ ፡ ፈረስ ፡ ገዛ
**hold your horses!** ረጋ ፡ በል
Hold your horses! I'm almost ready. ረጋ ፡ በል ፤ ልዘጋጅ ፡ ምንም ፡ አልቀረኝ
[See also 'rider']

**horseback, on ~** በፈረስ
He rode all the way on horseback. እርሱ ፡ መንገዱን ፡ በሙሉ ፡ በፈረስ ፡ ተጓዘ

**horseback riding** ግልቢያ
Do you like swimming or horseback riding? የምትወደው ፡ ዋና ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ግልቢያ ?

**horsehair** የፈረስ ፡ ጭራ
Flywhisks are made of horsehair. ጭራ ፡ የሚሠራው ፡ ከፈረስ ፡ ጭራ ፡ ነው

**horseman** ፈረሰኛ
He is an excellent horseman. የወጣለት ፡ ፈረሰኛ ፡ ነው

**horsepower** የፈረስ ፡ ጉልበት
This car has 50 horsepower. ይህ ፡ መኪና ፡ አምሳ ፡ የፈረስ ፡ ጉልበት ፡ አለው

**horse race** የፈረስ ፡ እሽቅድምድም ፤ የፈረስ ፡ እሽቅድድም

**hostilities** ጦርነት
At the outbreak of hostilities, food became dearer. ጦርነቱ ፡ ሲነሣ ፡ ምግብ ፡ ውድ ፡ ሆነ

**hot**
1. ሙቅ. Do you have hot water? ሙቅ ፡ ውኃ ፡ አለ ?
2. የጋለ. Don't pick up that hot pan barehanded! ያን ፡ የጋለ ፡ መጥበሻ ፡ ባዶ ፡ እጅህን ፡ አታንሣው
3. ሞቃት. The weather is hot in the dry season. በበጋ ፡ አየሩ ፡ ሞቃት ፡ ነው

**be hot**
1. ሞቀ. The water is hot. ውኃው ፡ ይሞቃል
2. ተፋጀ. This pepper sure is hot. ይህ ፡ በርበሬ ፡ በጣም ፡ ይፋጃል
3. ሰነፈጠ. This mustard is hot. ይህ ፡ ሰናፍጭ ፡ ይሰነፍጣል
4. ጦፈ. He was hot with rage when he heard the news. ወሬውን ፡ ሲሰማ ፡ በንዴት ፡ ጦፎ ፡ ነበር

**be hot with fever** አተኰሰ(ው)
He was hot with fever and had to lie in bed. አተኵሶት ፡ ስለነበር ፡ መተኛት ፡ ነበረበት

**be red-hot** ፋመ
The grill was red-hot from the fire. የብረት ፡ ምድጃው ፡ ከእሳቱ ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ፍሟል

**feel hot**
1. ሞቀ. The air feels hot today. ዛሬ ፡ አየሩ ፡ ይሞቃል
2. አተኰሰ(ው). +His head feels hot. ራሱን ፡ ያተኵሰዋል

**have a hot temper**
He has a hot temper. ቁጡ ፡ ነው
[See also 'water']

**hotbed** ቋት
Our office is a hotbed of intrigue. መሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ የተንኰል ፡ ቋት ፡ ነው

**hot-blooded** ግልፍተኛ
Don't insult him! He is hot-blooded. አትስደበው ፤ ግልፍተኛ ፡ ነው

**hotel** ሆቴል
Where is the nearest hotel? ለዚህ ፡ አካባቢ ፡ ቀረብ ፡ ያለው ፡ ሆቴል ፡ የት ፡ ነው ?

**hothead** ግልፍተኛ
He is a hothead and is going to get into trouble. ግልፍተኛ ፡ ስለሆነ ፡ አምባጓሮ ፡ ውስጥ ፡ ይገባል

**hot-tempered** ግልፍተኛ
A judge should not be hot-tempered. ዳኛ ፡ ግልፍተኛ ፡ መሆን ፡ የለበትም

**hound** (v.) ነዘነዘ
She couldn't get her little brother to stop hounding her. ትንሹ ፡ ወንድሟ ፡ እንዳይነዘንዛት ፡ ልታስታግሠው ፡ አልቻለችም
*My creditors are hounding me for payment. አበዳሪዎቼ ፡ እናስቆም ፡ እናስቀምጥ ፡ ብለውኛል

**hound (one) out** አሳዶ ፡ አስወጣ
The mob hounded him out of town. ሕዝቡ ፡ ከከተማው ፡ አሳዶ ፡ አስወጣው

**hound** (n.) አዳኝ ፡ ውሻ
A hound has long ears. አዳኝ ፡ ውሻ ፡ ረጃጅም ፡ ጆሮዎች ፡ አሉት

**hour**
1. ሰዓት. I work eight hours a day. በቀን ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ እሠራለሁ
What are your working hours? የሥራ ፡ ሰዓቶችህ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ናቸው ?
2. ጊዜ (pl. ጊዜያት). In the hour of danger, he stayed with his friends. ባደጋ ፡ ጊዜ ፡ ከጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ኖረ
He works long hours to the detriment of his health. ጤንነቱን ፡ እስከሚጐዳው ፡ ድረስ ፡ ለረዥም ፡ ጊዜያት ፡ ይሠራል

**at all hours** በማንኛውም ፡ ሰዓት
I can be reached at all hours. በማንኛውም ፡ ሰዓት ፡ ልገኝ ፡ እችላለሁ

**every hour on the hour** በየሙሉ ፡ ሰዓቱ
The bus leaves every hour on the hour. አውቶቡሱ ፡ በየሙሉ ፡ ሰዓቱ ፡ ይሄዳል

**for hours** ለብዙ ፡ ሰዓት ፤ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ
She practices the piano for hours. ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ የፒያኖ ፡ ልምምድ ፡ ታደርጋለች
They debated the question for hours. ጉዳዩን ፡ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ ተከራከሩበት

**for hours at a time** ለብዙ ፡ ሰዓቶች ፡ ያለማቋረጥ
Monks meditate on holy things for hours at a time. መነኰሴዎች ፡ ለብዙ ፡ ሰዓቶች ፡ ያለማቋረጥ ፡ ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ነገሮች ፡ በአንክሮ ፡ ያስባሉ

**one's hour** የመሞቻ ፡ ሰዓት
The sick man knew that his hour had come. የታመመው ፡ ሰውዬ ፡ የመሞቻ ፡ ሰዓቱ ፡ መቃረቡን ፡ ዐውቆ ፡ ነበር
[See also 'best, end, good, late, morning, rush hour, scant, ungodly']

**hour hand** ሰዓት ፡ ቈጣሪ
The hour hand of my clock is broken. የሰዓቴ ፡ ሰዓት ፡ ቈጣሪው ፡ ተሰብሯል

**hourly** (adj.) በሰዓት ፡ የሚያገኘው
His hourly wage is $2.00. በሰዓት ፡ የሚያገኘው ፡ አበል ፡ ሁለት ፡ ብር ፡ ነው

**hourly** (adv.) በየሰዓቱ
The medicine is to be taken hourly. መድኃኒቱ ፡ በየሰዓቱ ፡ የሚዋጥ ፡ ነው

**house** (v.)
1. አኖረ. We housed the flood victims in schools. በጐርፍ ፡ የተጐዱትን ፡ ሰዎች ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አኖርናቸው
2. አለው. +The library houses 20,000 books. ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ሀያ ፡ ሺ ፡ መጻሕፍት ፡ አሉት
*We can house you and your friends if the hotels are full. ሆቴሎች ፡ ከተያዙ ፡ ላንተና ፡ ለጓደኞችህ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ ቦታ ፡ እንፈልግላችኋለን

**be housed**
1. ማረፊያ ፡ ተሰጠ ፤ አረፈ. Where are the visitors to be housed? ጎብኝዎቹ ፡ ማረፊያ ፡ የሚሰጣቸው ፡ የት ፡ ነው ?
The ambassador's retinue will be housed in our hotel. የአምባሳደሩ ፡ የክብር ፡ ተከታዮች ፡ ሆቴላችን ፡ ውስጥ ፡ ያርፋሉ
2. እንዲኖር ፡ ተደረገ. The refugees were housed in miserable shacks. ስደተኞቹ ፡ በደሳሳ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ እንዲኖሩ ፡ ተደረገ

**house** (n.)
1. ቤት. I want to rent a house. ቤት ፡ መከራየት ፡ እፈልጋለሁ
2. ዘር. He was a prince of the house of Solomon. ከሰሎሞን ፡ ዘር ፡ የሚወለድ ፡ ልዑል ፡ ነበር
3. ቤተሰብ. My eldest brother is the head of the house. ታላቅ ፡ ወንድሜ ፡ የቤተሰባችን ፡ ኀላፊ ፡ ነው
4. መደብር. He has a good position with a wholesale house. በጅምላ ፡ በሚሸጡበት ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ ጥሩ ፡ ሥራ ፡ አለው
5. አዳራሽ. The actor played to a full house. ተዋናዩ ፡ ጨዋታ ፡ ሲያሳይ ፡ አዳራሹ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ ነበር
6. ተመልካች. The play 'Othello' drew a full house. የኦቴሎ ፡ ድራማ ፡ ብዙ ፡ ተመልካች ፡ ሳበ
*The singer sang to a large house. ዘፋኙ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ በተሰበሰበበት ፡ ዘፈነ

**house of worship** ቤተ ፡ መቅደስ
Every religion has its own house of worship. ማንኛውም ፡ ሃይማኖት ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አለው

**around the house** ቤት ፡ ለቤት
I wear slippers around the house. ቤት ፡ ለቤት ፡ ነጠላ ፡ ጫማ ፡ አደርጋለሁ

**bring down the house**
*The children's performances brought down the house. ልጆቹ ፡ ላሳዩት ፡ ጨዋታ ፡ ቤቱ ፡ እስኪፈርስ ፡ ተጨበጨበ

**clean house**
*The union finally agreed it was time to clean house and regain its good reputation. የሥራ ፡ ማኅበሩ ፡ የማይገቡ ፡ አባሎችን ፡ አስወግዶ ፡ መልካም ፡ ስምን ፡ ማስመለስ ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ተስማማ

**keep house** ቤት ፡ አስተዳደረ
She keeps house for her uncle. ያጎቷን ፡ ቤት ፡ ታስተዳድራለች

**keep open house for**
*He keeps open house for all foreign students. ቤቱ ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ተማሪዎች ፡ እንደ ፡ ቤታቸው ፡ ነው

**(be) on the house** በነጻ ፡ ተሰጠ
At the exhibition, coffee and cookies were on the house. ኤግዚቢሽኑ ፡ ውስጥ ፡ ቡናና ፡ ኬክ ፡ በነጻ ፡ ይሰጥ ፡ ነበር

**put one's house in order**
*It is easy to criticize others, but it would be better to put one's own house in order first. ሌሎችን ፡ መንቀፍ ፡ ቀላል ፡ ነው ፤ ሆኖም ፡ የራስን ፡ ጉዳይ ፡ መጀመሪያ ፡ ማስተካከል ፡ ይሻላል
[See also 'back, behind, confine, lady, master']

**house arrest, be placed under ~**
The minister was placed under house arrest. ሚኒስትሩ ፡ በቁም ፡ እስር ፡ እንዲቆዩ ፡ ተደረጉ

**household**
*How many people are in your household? ምን ፡ ያህል ፡ ቤተሰብ ፡ አለህ ?

**housekeeper** የቤት ፡ ቀላቢት
He hired a housekeeper after his wife died. ሚስቱ ፡ ከሞተች ፡ በኋላ ፡ የቤት ፡ ቀላቢት ፡ ቀጠረ

**housekeeping** የቤት ፡ አያያዝ
Housekeeping involves cooking, washing dishes, and cleaning. የቤት ፡ አያያዝ ፡ ምግብ ፡ ማብሰል ፤ ሳሕን ፡ ማጠብንና ፡ ማጽዳትን ፡ ያጠቃልላል

**set up housekeeping** ጎጆ ፡ ወጣ
She set up housekeeping right after their honeymoon. የጫጉላ ፡ ጊዜዋን ፡ ጨርሳ ፡ ወዲያውኑ ፡ ጎጆ ፡ ወጣች

**housemaid** ገረድ
I am getting a housemaid for my wife. ለሚስቴ ፡ ገረድ ፡ ልቀጥር ፡ ነው

**housemother** ሞግዚት
The housemother maintains strict control over us. ሞግዚታችን ፡ በጣም ፡ ይቈጣጠሩናል

**housewife** የቤት ፡ እመቤት
She is a thrifty housewife. ቈጠብ ፡ የምታውቅ ፡ የቤት ፡ እመቤት ፡ ናት

**the good housewife** ባለሙያይቱ
The good housewife gets up in the morning and melts butter. ባለሙያይቱ ፡ ጧት ፡ ተነሥታ ፡ ቅቤ ፡ ታንጥራለች

**housework**
1. የቤት ፡ ውስጥ ፡ ሥራ. Housework is easy. የቤት ፡ ውስጥ ፡ ሥራ ፡ ቀላል ፡ ነው
2. ቤት ፡ ውስጥ ፡ መሥራት. Many girls prefer factory work to housework. ብዙ ፡ ልጃገረዶች ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ከመሥራት ፡ ይልቅ ፡ ፋብሪካ ፡ ውስጥ ፡ መሥራት ፡ ይመርጣሉ

**housing**
1. መኖሪያ ፤ መኖሪያ ፡ ቤት. The mayor has promised better housing for the needy. ከንቲባው ፡ ለችግረኞች ፡ የተሻለ ፡ መኖሪያ ፡ (መኖሪያ ፡ ቤት) ፡ ለማሠራት ፡ ቃል ፡ ገብቷል
2. ቤት ፡ ማግኘት. The housing of the laborers is his responsibility. ለቀን ፡ ሠራተኞቹ ፡ ቤት ፡ ማግኘት ፡ የርሱ ፡ ኀላፊነት ፡ ነው

**hovel** ደሳሳ ፡ ጎጆ
My hovel is my palace. ደሳሳ ፡ ጎጆዬ ፡ ለኔ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቴ ፡ ናት

**hover**
1. አንዣበበ. The hawk hovered for a moment above the chicken, then seized it. ጭልፊቷ ፡ ጥቂት ፡ አንዣብባ ፡ ዶሮዋን ፡ ያዘች
2. ዋለለ. The sick man hovered between life and death. በሽተኛው ፡ ሰው ፡ በሞትና ፡ በሕይወት ፡ መሀከል ፡ ይዋልል ፡ ነበር

**hover (around)**
1. ዞረ. The dogs hover around the meat truck. ውሾቹ ፡ የሥጋውን ፡ መኪና ፡ ይዞሩታል
2. ተዘዋወረ. The children hover around the place where toys are sold. ሕፃናቱ ፡ አሻንጉሊት ፡ በሚሸጥበት ፡ አካባቢ ፡ ይዘዋወራሉ

**hover overhead** አንዣበበ
The hawk is hovering overhead. ጭልፊቷ ፡ ታንዣብባለች

**how ?**
1. እንዴት. How shall I do it? እንዴት ፡ ልሥራው ?
How is it you did not come? እንዴት ፡ ነው ፡ ያልመጣኸው ?
2. እንደምን. How do you do? እንደምን ፡ ነህ ?
3. ምን ፡ ያህል. How damaged is the car? መኪናዋ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ተጐድታለች ?

**how**
1. ምን ፡ ያህል ፡ እንደ + (relative verb). You have no idea how worried we are. ምን ፡ ያህል ፡ እንደምንሰጋ ፡ አታውቅም
We do not know how serious his injuries are. ጉዳቱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ከባድ ፡ እንደሆነ ፡ አናውቅም
2. እንዴት ፡ እንደ + (relative verb). Tell her how to do it! እንዴት ፡ እንደምትሠራው ፡ ንገራት
Tell me how Mr. Parker is. ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ንገረኝ
3. ምንኛ ፡ እንደ + (verb). He looked back over his childhood and realized how lucky he had been. የልጅነቱን ፡ ጊዜ ፡ አስታውሶ ፡ ምንኛ ፡ ዕድለኛ ፡ እንደነበረ ፡ ተገነዘበ

**how!** እንዴት
How dirty the house is! ቤቱ ፡ እንዴት ፡ ቆሽሿል !
How beautiful she is! እንዴት ፡ ቆንጆ ፡ ልጅ ፡ ናት !

**how about** - ስ
How about going for a walk? ሽርሽር ፡ ብንሄድስ ?

**how come?** እንዴት
How come you are still here? እስከሁን ፡ እንዴት ፡ እዚህ ፡ ቆየህ ?

**how far?** እስከየት ፤ ምን ፡ ያህል ፤ ምን ፡ ያህል ፡ ሩቀ
How far does this road continue? ይህ ፡ መንገድ ፡ እስከየት ፡ ይዘልቃል ?
How far have you read in this book? ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ አንብበሃል ?
How far is it to his house? ቤቱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይርቃል ?

**how little**
*That shows how little you know. ይህ ፡ የዕውቀትህን ፡ ማነስ ፡ ያሳያል

**how long?**
1. ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፤ ስንት ፡ ጊዜ. How long have you been working together? ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ አብራችሁ ፡ ስትሠሩ ፡ ነበር ?
How long does it take by airplane? በአውሮፕላን ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ይፈጃል ?
2. ከ - - ስንት ፡ ጊዜ. How long have they been engaged? ከተጫጩ ፡ ስንት ፡ ጊዜያቸው ፡ ነው ?

**how long ago?** ከስንት ፡ ጊዜ ፡ በፊት
How long ago was that? ነገሩ ፡ የሆነው ፡ ከስን
ት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ነበር ?

**how many?** ስንት
How many oranges shall I take? ስንት ፡ ብር
ቱካን ፡ ልውሰድ ?

**how old?**
How old is he? ስንት ፡ ዓመቱ ፡ ነው ?

**how so?** ለምን
You haven't any desire to go. How so?
ለመሄድ ፡ ምንም ፡ ፍላጎት ፡ የለህም ፤ ለምን ?

**how tall?**
*How tall are you? ቁመትህ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?

**and how!** እንዴታ !
Are you happy? And how! ተደስተሃል ? እንዴታ !

**for how long?** ለምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፤ እስከ ፡ መ
ቼ ፡ ድረስ
For how long have you been deferred? ወታደር
ነት ፡ የምትመለመልበት ፡ ጊዜ ፡ የተላለፈልህ ፡
ለምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ነው ? (እስከ ፡ መቼ ፡ ድ
ረስ ፡ ነው?)
[See also 'earth, else, much, often, soon, well']

**however** (adv., conj.)
1. ነገር ፡ ግን. I would like to do it; however, I have no time. ብሠራው ፡ እወዳለሁ ፤ ነገር ፡ ግ
ን ፡ ጊዜ ፡ የለኝም
2. ምንም ፡ ያህል ፡ ብ + (imperfect). She won't succeed, however hard she tries. ምንም ፡ ያህ
ል ፡ ብትሞክር ፡ አይሳካላትም
3. በምንም ፡ ዓይነት ፡ ብ + (imperfect). However you do it, the boss will not be satisfied. በምንም ፡
ዓይነት ፡ ብትሠራው ፡ አለቅዬው ፡ አይደሰትም
*We will allow you to travel however you please. በፈለግኸው ፡ የመጓጓዣ ፡ ዓይነት ፡ ብት
ሄድ ፡ እንፈቅድልሃለን

**however?** እንዴት
However did you find the place? ቦታውን ፡ እን
ዴት ፡ ልታውቀው ፡ ቻልክ ?

**howl** (v.)
1. አላዘነ. The dog has been howling all night.
ውሻው ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ሲያላዝን ፡ አደረ
2. አፏጨ. The winds howled around our house.
ነፋሱ ፡ በቤታችን ፡ ዙሪያ ፡ አፏጨ

**howl with laughter** በሣቅ ፡ ተንከተከተ
The boys howled with laughter. ልጆቹ ፡ በሣ
ቅ ፡ ተንከተከቱ

**howl** (n.) ጩኸት
I thought I heard the howl of a wolf. የተኩላ ፡
ጩኸት ፡ የሰማሁ ፡ መሰለኝ

**hub** እምብርት
London is the hub of English life. ሎንዶን ፡ የእን
ግሊዝ ፡ እምብርት ፡ ነው

**hubbub** ግርግር
The hubbub was caused when a baby fell into a tub of water. ሕፃኑ ፡ ውኃ ፡ ገንዳ ፡ ውስ
ጥ ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ ግርግር ፡ ተፈጠረ

**huddle** (vt.)
1. አጎረ. We huddled the children into the car.
ልጆቹን ፡ መኪናው ፡ ውስጥ ፡ አጎርናቸው
2. እጁ ፡ እንዳመጣለት ፡ ቈለለ. He huddled his clothes in a heap. ልብሱን ፡ እጁ ፡ እንዳመጣለ
ት ፡ ቈለለ

**be huddled** ታፈገ
They were huddled in a corner. እጥግ ፡ ታፍገ
ው ፡ ነበር

**huddle together**
1. እፍግፍግ ፡ ብለው ፡ ተቀመጡ. They huddled together to keep warm. እንዲሞቃቸው ፡ እፍግፍ
ግ ፡ ብለው ፡ ተቀመጡ
2. ተጠጋግተው ፡ ቆሙ. The sheep huddled together in a corner. በጎቹ ፡ ተጠጋግተው ፡ ከጥግ ፡
ላይ ፡ ቆመዋል

**huddled up** ተኰርምቶ
He lay huddled up in bed. አልጋ ፡ ላይ ፡ ተኰ
ርምቶ ፡ ተኛ

**huddle** (n.), **go into a ~** በቆይታ ፡ ተመካከሩ
The ball players went into a huddle. ኳስ ፡ ተ
ጫዋቾቹ ፡ በቆይታ ፡ ተመካከሩ

**lay in a huddle** ተዘበራርቆ ፡ ተጣለ
His clothes lay in a huddle on the floor.
ልብሶቹ ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ተዘበራርቀው ፡ ተጥለው ፡
ነበር

**hue** ቀለም
The hues of the rainbow were clearly seen.
የቀስተ ፡ ደመናው ፡ ቀለሞች ፡ በግልጽ ፡ ይታዩ ፡
ነበር

**hug** (hugged), v.
1. እቅፍ ፡ አደረገ. She hugged her mother.
እናትዮዋን ፡ እቅፍ ፡ አደረገቻት
2. አቅፎ ፡ ያዘ. She soothed the frightened children by hugging them. የደነገጡትን ፡ ልጆ
ች ፡ አቅፋ ፡ በመያዝ ፡ አረጋጋቻቸው
3. ተጠግቶ ፡ ሄደ. The boat hugs the shore.
መርከቧ ፡ ጠረፉን ፡ ተጠግታ ፡ ትሄዳለች
4. ከ - - - ተለጠፈ. The fugitive hugged the wall to keep from being seen. ያመለጠው ፡ ሰው ፡ እ
ንዳይታይ ፡ ከግድግዳው ፡ ተለጠፈ

5. ሽጉጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ. The timorous boy hugged the corner. ፈሪው ፡ ልጅ ፡ ከጥግ ፡ ሽጉጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ

**hug closely** እንቆ ፡ ያዘ

A narrow-minded person hugs his opinions closely. ሐሳበ ፡ ጠባብ ፡ ሰው ፡ ሐሳቡን ፡ እንቆ ፡ ይይዛል

**hug** (n.), **give a ~** እቅፍ ፡ አደረገ

The mother gave her child a hug. እናቲቱ ፡ ልጅዋን ፡ እቅፍ ፡ አደረገችው

**huge**

1. ግዙፍ. The elephant is a huge animal. ዝሆን ፡ ግዙፍ ፡ እንስሳ ፡ ነው

2. ትልቅ. I need a huge box to put the dishes in. ሳሕኖችን ፡ የማስቀምጥበት ፡ ትልቅ ፡ ሣጥን ፡ ያስፈልገኛል

**hull** (v.) ፈለፈለ

The maid hulled the peas. ገረዲ ፡ አተሩን ፡ ፈለፈለች

**hull** (n.)

1. ገለባ. The floor was covered with peanut hulls. ወለሉ ፡ በኦቾሎኒ ፡ ገለባ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር

2. ቅርፊት. The hull must be removed before the almond can be eaten. ለውዝ ፡ ከመበላቱ ፡ በፊት ፡ ቅርፊቱ ፡ መውጣት ፡ አለበት

3. አካል. The hull of a ship is made of iron. የመርከቡ ፡ አካል ፡ ከብረት ፡ የተሠራ ፡ ነው

**remove the hulls of** ፈተገ

The women removed the hulls of the wheat. ሴቶቹ ፡ ስንዴውን ፡ ፈተጉ

**hum** (hummed)

1. አንጐራጐረ. The shepherd hums while guarding cattle. እረኛው ፡ ከብት ፡ ሲጠብቅ ፡ ያንጐራጕራል

2. እሹሩሩ ፡ አለ. The mother hums her baby to sleep. እናትዮዋ ፡ ሕፃኑን ፡ ለማስተኛት ፡ እሹሩሩ ፡ ትለዋለች

3. ጥዝ ፡ አለ. The bees were humming in the garden. ንቦቹ ፡ ባትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ጥዝ ፡ ይሉ ፡ ነበር

4. ተሯሯጠ. The household hummed in preparation for the reception. ቤተሰቡ ፡ ሁሉ ፡ ግብዣውን ፡ ለማሰናዳት ፡ ይሯሯጥ ፡ ነበር

5. አነበነበ. The electric fan hummed steadily. በኤሌክትሪክ ፡ የሚሠራው ፡ ነፋስ ፡ መስጫ ፡ ያለ ማቋረጥ ፡ አነበነበ

**human** (n.) ሰው

His cruelty suggests that he is not human. ጭካኔው ፡ ሰው ፡ ያለመሆኑን ፡ ያመለክታል

**human** (adj.)

1. የሰው. Arms and legs are integral parts of the human body. እጆችና ፡ እግሮች ፡ የሰውን ፡ አካል ፡ ሙሉ ፡ የሚያሰኙት ፡ ክፍሎች ፡ ናቸው

2. የሰው ፡ ልጅ. He is an ardent defender of human liberty. ጽኑ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ ተከራካሪ ፡ ነው

3. ሰብአዊ. Property rights should not take precedence over human rights. የንብረት ፡ መብቶች ፡ ከሰብአዊ ፡ መብቶች ፡ መቅደም ፡ የለባቸውም

4. የተፈጥሮ. Selfishness is a human weakness. ራስን ፡ መውደድ ፡ የተፈጥሮ ፡ ደካማነት ፡ ነው

**human being** ሰው

All human beings are equal. ሰው ፡ ሁሉ ፡ እኩል ፡ ነው

*He treats us like human beings. ደኅና ፡ ይዞናል

[See also 'race']

**humane**

1. በምሕረት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ. Laws ought to be humane. ሕግ ፡ በምሕረት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ መሆን ፡ አለበት

2. ሰብአዊ. The prisoner did not receive humane treatment. እስረኛው ፡ ሰብአዊ ፡ አያያዝ ፡ አል ተደረገለትም

3. ርኅሩኅ. He is more humane than his brother. ከወንድሙ ፡ የበለጠ ፡ ርኅሩኅ ፡ ነው

**humanitarian** (n.) በጎ ፡ አድራጊ

Humanitarians attempt to relieve human suffering. በጎ ፡ አድራጊዎች ፡ የሰውን ፡ መከራ ፡ ለማቃለል ፡ ይሞክራሉ

**humanitarian** (adj.) የበጎ ፡ አድራጎት

His humanitarian plans to eliminate famine are well known. ረኀብን ፡ ለማስወገድ ፡ የሚያደርገው ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ እቅድ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**humanity**

1. ሰው. God created humanity. እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ፈጠረ

2. የሰው ፡ ልጅ. Christ saved humanity. ክርስቶስ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ አዳነ

3. ርኅራኄ. Treat animals with humanity! እንስሳትን ፡ በርኅራኄ ፡ ያዝ

**humanly** እንደሰው

Animals cannot be expected to think humanly. እንስሳት ፡ እንደሰው ፡ እንዲያስቡ ፡ አይጠበቁም

*This is not humanly possible. ይህ ፡ ከሰው ፡ ዓቅም ፡ በላይ ፡ ነው

*We will do whatever is humanly possible. ሰው ፡ ሊያደርግ ፡ የሚችለውን ፡ ሁሉ ፡ እናደርጋለን

**humble**
1. ትሑት. I am your humble servant. ትሑት ፡ አገልጋይዎ ፡ ነኝ
2. ዝቅተኛ. Street cleaning is a humble occupation. መንገድ ፡ መጥረግ ፡ ዝቅተኛ ፡ ሥራ ፡ ነው
3. አልባሌ. His parents live in a humble home. ቤተሰቦቹ ፡ አልባሌ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ
4. ተራ. He cast away his humble habits when he became an officer. መኰንን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ተራ ፡ ጠባዩን ፡ ተወ
Will you partake of this humble meal? ይህንን ፡ ተራ ፡ ምግብ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ልትሳተፍ ፡ ትፈቅዳለህ ?

**humble circumstances** ድኽነት
Abraham Lincoln grew up in humble circumstances. አብርሃም ፡ ሊንኮልን ፡ ያደገው ፡ በድኽነት ፡ ነው

**act humble** ትሑት ፡ መስሎ ፡ ታየ
In the beginning, he acted very humble. በመጀመሪያ ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ ትሑት ፡ መስሎ ፡ ታየ

**of humble birth**
They are men of humble birth. ከድኻ ፡ ቤተሰብ ፡ ናቸው ፡ (ከዝቅተኛ ፡ ቤተሰብ ፡ የተወለዱ ፡ ናቸው)

**of humble condition** ተራ ፡ ኑሮ ፡ የሚኖር
Lincoln's parents were people of humble condition. የሊንኮልን ፡ ወላጆች ፡ ተራ ፡ ኑሮ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ
[See also 'family, origin, state']

**humid** እርጥበት ፡ የበዛበት ፤ እርጥበት ፡ ያለው
The air today seems to be humid. የዛሬው ፡ አየር ፡ እርጥበት ፡ የበዛበት ፡ ይመስላል
A humid climate debilitates one who is not used to it. እርጥበት ፡ ያለው ፡ ያየር ፡ ንብረት ፡ ላለመደው ፡ ሰው ፡ ያደክማል

**be humid**
1. ወበቀ. The air here is very humid. አየሩ ፡ እዚህ ፡ በጣም ፡ ይወብቃል
2. ረጠብ ፡ አለ. The air is humid before a rain. ሊዘንብ ፡ ሲል ፡ አየሩ ፡ ረጠብ ፡ ይላል

**humidify** (humidified) እንዲረጥብ ፡ አደረገ
This instrument humidifies the air. ይህ ፡ መሣሪያ ፡ አየር ፡ እንዲረጥብ ፡ ያደርጋል

**humidity** ወበቅ
Humidity makes my shirt stick to my back. ወበቁ ፡ ሸሚዜን ፡ ከጀርባዬ ፡ ላይ ፡ ያጣብቀዋል

**humiliate** አዋረደ
She humiliated me in front of my friends. በጓደኞቼ ፡ ፊት ፡ አዋረደችኝ

**humiliation**
1. ውርደት. Humiliation caused him to commit suicide. ከውርደቱ ፡ የተነሣ ፡ ራሱን ፡ ገደለ
2. እፍረት. In order to conceal her humiliation, she ran away. እፍረቷን ፡ ለመሸፈን ፡ ጠፋች

**humility** ትሕትና
He received the workers with humility. ሠራተኞቹን ፡ በትሕትና ፡ ተቀበላቸው

**humor** (v.) አጫወተ
You will have to humor him because he is ill. ስለታመመ ፡ ልታጫውተው ፡ ይገባሃል

**humor** (n.) ቀልድ ፤ የጨዋታ ፡ ለዛ
Mark Twain was famous for his humor. ማርክ ፡ ትዌይን ፡ በቀልዱ ፡ (በጨዋታው ፡ ለዛ) ፡ የታወቀ ፡ ነበር

**be in a bad humor** ከፋ(ው)
+Don't bother him when he is in a bad humor. በከፋው ፡ ጊዜ ፡ አትነዝንዘው

**be in a good humor** ደስ ፡ አለ(ው)
Are you in a good humor today? ዛሬ ፡ ደስ ፡ ብሎሃል ?

**be in an ill humor** ተነጫነጨ
Why are you in such an ill humor today? ዛሬ ፡ ምነው ፡ ትነጫነጫለህ ?

**full of humor** አሥቂኝ
This story is full of humor. ይህ ፡ ተረት ፡ አሥቂኝ ፡ ነው

**good humor** ተጨዋችነት
His good humor was particularly noticed. ተጨዋችነቱ ፡ በተለይ ፡ የታወቀለት ፡ ነው

**note of humor** ቀልድ ፡ መሳይ
There was a note of humor in his film. በሠራው ፡ ፊልም ፡ ውስጥ ፡ ቀልድ ፡ መሳይ ፡ ነበረበት

**put one in good humor** ደስ ፡ አሰኘ
Success puts you in good humor. አንድ ፡ ነገር ፡ ሲሳካ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል

**sense of humor** ቀልደኛነት
His only saving trait is his sense of humor. ከጠባዩ ፡ ሁሉ ፡ ጥሩው ፡ ነገር ፡ ቀልደኛነቱ ፡ ብቻ ፡ ነው

**(have) sense of humor** ቀልድ ፡ ዐወቀ
He has no sense of humor, so don't make jokes with him. ቀልድ ፡ አያውቅምና ፡ አትቀልደው

**humorous** አሥቂኝ
Mark Twain wrote humorous stories. ማርክ ፡ ትዌን ፡ አሥቂኝ ፡ ተረቶች ፡ ጻፈ

**hump** (v.), ~ **up** አበጥ ፡ አለ
The ground humps up in front of the door. መሬቱ ፡ ከመዝጊያው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አበጥ ፡ ይላል

**hump one's back** ጀርባውን ፡ ነፋ
The cat humped his back when he saw the dog. ድመቷ ፡ ውሻውን ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ጀርባዋን ፡ ነፋች

**hump** (n.)
1. ሻኛ. A camel has one or two humps. ግመል ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ሻኛ ፡ አለው
2. ጉብታ. There is a hump in the road. መንገዱ ፡ ላይ ፡ ጉብታ ፡ አለ

**humpback** ጐባጣ ፡ ሰው
The humpback works as a guard in the church. ጐባጣው ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘበኛ ፡ ሆኖ ፡ ያገለግላል

**humus** ዋልካ ፡ አፈር
Humus is needed to grow these plants in. ይህን ፡ ዕፀ ፡ ለማሳደግ ፡ ዋልካ ፡ አፈር ፡ ያስፈልጋል

**hunch** (v.) ጐብጦ ፡ ተቀመጠ
He hunched over his desk. ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ጐብጦ ፡ ተቀመጠ

**sit hunched up** ጐብጦ ፡ ተቀመጠ
Your back hurts because you are sitting hunched up. ጀርባህን ፡ የሚያምህ ፡ ጐብጠህ ፡ ስለምትቀመጥ ፡ ነው

**hunch** (n.)
1. የጀርባ ፡ መጕበጥ. His hunch is the result of a spinal injury. የጀርባው ፡ መጕበጥ ፡ ከአከርካሪው ፡ መጐዳት ፡ የተነሣ ፡ ነው
2. ግምት. His hunch proved correct, and we won $100. ግምቱ ፡ ትክክለኛ ፡ ሆኖ ፡ ስለተገኘ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ አገኘን

**have a hunch** ተሰማ(ው)
I have a hunch that something is wrong there. እንዳች ፡ የተሳሳተ ፡ ነገር ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መኖሩ ፡ ይሰማኛል

**hunchback** ጐባጣ
I mean the hunchback over there. ያንን ፡ ጐባጣ ፡ ነው ፡ የምልህ

**hunchbacked, get** ~ ጐበጠ
You will get hunchbacked sitting that way. እንደዚያ ፡ ብትቀመጥ ፡ ትጐብጣለህ

**hundred** መቶ

**a hundred** መቶ ፡ ዓመት
You won't be able to do this, even if you live to be a hundred. መቶ ፡ ዓመት ፡ እንኳን ፡ ብትኖር ፡ ይህንን ፡ ልትሠራው ፡ አትችልም

**hundreds of** በብዙ ፡ መቶ ፡ የሚቈጠሩ
Hundreds of people perished in the earthquake. በመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ በብዙ ፡ መቶ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ አለቁ

**hung**, see **hang**

**hunger** (v.), ~ **for**
1. ለማግኘት ፡ ጓጓ. He hungered for a good meal. ጥሩ ፡ ምግብ ፡ ለማግኘት ፡ ጓጓ
2. በጣም ፡ ጓጓ. She hungers for the love of her family. ለቤተ ፡ ሰብ ፡ ፍቅር ፡ በጣም ፡ ትጓጓለች

**hunger** (n.) ረኃብ ፤ ራብ
I nearly died of hunger. በረኃብ ፡ (በራብ) ፡ ልሞት ፡ ምንም ፡ አልቀረኝም ፡ ነበር
*He has a hunger for knowledge. ዕውቀት ፡ የጠማው ፡ ነው

**appease (one's) hunger** አጠገበ
A good dinner will appease your hunger. ጥሩ ፡ እራት ፡ ያጠግብሃል

**hungry** የተራበ
The hungry dog searched for food. የተራበው ፡ ውሻ ፡ ምግብ ፡ ፈለገ
*He went to bed hungry. ጦሙን ፡ አደረ

**be hungry** ራበ(ው)
+He is still hungry after that big meal. ያንን ፡ ሁሉ ፡ ምግብ ፡ በልቶ ፡ አሁንም ፡ እንደራበው ፡ ነው

**be hungry for** በጣም ፡ ጓጓ
The child was hungry for affection. ልጁ ፡ ለቤተ ፡ ሰብ ፡ ፍቅር ፡ በጣም ፡ ጓጓ

**go hungry** ተራበ
Even though they say there is no food, I have not yet gone hungry. እህል ፡ ጠፍቷል ፡ ቢባልም ፡ እስካሁን ፡ አልተራብሁም

**hunt**
1. አደነ. He is hunting deer. አጋዘን ፡ ያድናል
2. ፈለገ. They hunted the lost ball. የጠፋውን ፡ ኳስ ፡ ፈለጉ

**hunt down** አድኖ ፡ ያዘ
They hunted down the killers of the President. የፕሬዚዳንቱን ፡ ገዳዮች ፡ አድነው ፡ ያዙዋቸው

**hunt (for)** ፈለገ
We were hunting for an apartment. አፓርተማ ፡ስንፈልግ ፡ ነበር

Nomads must always hunt for good grazing land. ዘላኖቹ ፡ ሁልጊዜ ፡ ጥሩ ፡ የግጦሽ ፡ መሬት ፡ መፈለግ ፡ አለባቸው

**hunt up**

1. ፈለገ. I will hunt up some old books when I get to Ethiopia. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስሄድ ፡ አንዳንድ ፡ አሮጌ ፡ መጻሕፍት ፡ እፈልጋለሁ

He hunted up some old friends when he returned from abroad. ከውጭ ፡ አገር ፡ ሲመለስ ፡ አንዳንድ ፡ የቆዩ ፡ ወዳጆቹን ፡ ፈለገ

2. ፈልጎ ፡ አገኘ. How many books did you hunt up? ስንት ፡ መጻሕፍት ፡ ፈልገህ ፡ አገኘህ ?

**hunter** አዳኝ

Hunters are not allowed to hunt on my land. አዳኞች ፡ በመሬቴ ፡ ላይ ፡ እንዲያድኑ ፡ አይፈቀድላቸውም

**hunting** ማደን

Hunting is forbidden on these premises. በዚህ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ማደን ፡ ክልክል ፡ ነው

**hunting ground** የማደኛ ፡ ቦታ

The forest was his favorite hunting ground. ጫካው ፡ በጣም ፡ የሚወደው ፡ የማደኛ ፡ ቦታ ፡ ነበር

**go hunting** አደን ፡ ሄደ

We are going hunting tomorrow. ነገ ፡ አደን ፡ እንሄዳለን

**hurdle** (v.) ዘለለ

The horse hurdled both the fence and the ditch. ፈረሱ ፡ አጥሩንም ፡ ገደሉንም ፡ ዘለለ

**hurdle** (n.) መሰናክል

The runner's foot struck the hurdle and knocked it down. ሯጩ ፡ መሰናክሉን ፡ በእግሩ ፡ መቶ ፡ ጣለው

Passing the math exam is our last hurdle. የሒሳብ ፡ ፈተናችንን ፡ ማለፍ ፡ ያለብን ፡ የመጨረሻው ፡ መሰናክል ፡ ነው

**hurl**

1. ወረወረ. The rioters hurled rocks at the police. ረብሸኞቹ ፡ በፖሊሶች ፡ ላይ ፡ ድንጋይ ፡ ወረወሩ

2. አወረደ(በት). They hurled insults at the nightwatchman. ዘበኛውን ፡ ስድብ ፡ አወረዱበት

**hurl oneself at** ተጋፈጠ

They hurled themselves at the enemy. ጠላትን ፡ ተጋፈጡ

**hurrah** የምስራች

Hurrah! We are getting extra pay. የምስራች ። ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ልናገኝ ፡ ነው

*Hurrah for the king! ዕድሜ ፡ ለጃንሆይ !

**hurricane** ዓውሎ ፡ ነፋስ

A hurricane blew down my house. ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ቤቴን ፡ አፈራረሰው

**hurried** (adj.) የጥድፊያ

It was a hurried trip. የጥድፊያ ፡ ጉዞ ፡ ነበር

**be hurried** በፍጥነት ፡ ተላከ

More soldiers were hurried to the front lines. ተጨማሪ ፡ ወታደሮች ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ በፍጥነት ፡ ተላኩ

**hurriedly**

1. ወዲያውኑ ። በፍጥነት. The village was hurriedly deserted because bandits were in the area. ባካባቢው ፡ ሽፍቶች ፡ ስለነበሩ ፡ መንደሩ ፡ ወዲያውኑ ፡ (በፍጥነት) ፡ ተለቀቀ

2. በጥድፊያ. He spoke hurriedly. በጥድፊያ ፡ ተናገረ

**hurry** (hurried), vt.

1. አጣደፈ. Don't hurry me; I am not dressed yet. ገና ፡ ልብሴን ፡ እንኳ ፡ አልለበስኩም ። አታጣድፈኝ

2. በፍጥነት ፡ አደረሰ. A taxi hurried us home. ታክሲው ፡ በፍጥነት ፡ እቤት ፡ አደረሰን

3. በችኮላ ፡ ሠራ. If we hurry the work, it will be spoiled. ሥራውን ፡ በችኮላ ፡ ብንሠራ ፡ ይበላሻል

**hurry** (vi.)

1. ተጣደፈ. Don't hurry! I will wait for you. አትጣደፍ ፡ እጠብቅሃለሁ

2. ቶሎ ፡ አለ. Hurry, or we will be late. ቶሎ ፡ በል ። ያለዚያ ፡ እንዘገያለን

3. ተፋጠነ. As he is leaving tomorrow, we must hurry. ነገ ፡ ስለሚሄድ ፡ መፋጠን ፡ አለብን

**hurry up** ፈጠን ፡ አለ

Hurry up! The plane will leave without us. ፈጠን ፡ በል ። አውሮፕላኑ ፡ ጥሎን ፡ ይሄዳል

**hurry** (n.) ችኮላ

What's the hurry? We have fifteen more minutes before the train leaves. ችኮላው ፡ ምንድነው ? ባቡሩ ፡ የሚነሣው ፡ ገና ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ ነው

**be in a hurry** ቸኰለ

She was in a hurry to see her father. አባቷን ፡ ለማየት ፡ ቸኵላለች

**hurt** (hurt), vt.
1. ጐዳ. This will hurt business. ይህ ፡ ንግድን ፡ ይጐዳል
The stone hurt my foot badly. ድንጋይ ፡ እግሬን ፡ ክፉኛ ፡ ጐዳኝ
2. አሳመመ. The needle will hurt you. መርፌው ፡ ያሳምምሃል
3. ተጐዳ. He hurt his foot and hopped about in pain. እግሩን ፡ ስለተጐዳ ፡ በሥቃይ ፡ በሌላ ፡ እግሩ ፡ ዘለል ፡ ዘለል ፡ አለ
4. አስቀየመ. I did not mean to hurt you. ላስቀይምህ ፡ አላሰብኩም

**hurt** (vi.) አመመ(ው)
My arm hurts. እጄን ፡ ያመኛል

**be hurt**
She is easily hurt. በቀላሉ ፡ ትቀየማለች

**hurt (one's) feelings**
1. ቅር ፡ አሰኘ. His criticism hurt my feelings. ነቀፌታው ፡ ቅር ፡ አሰኘኝ
2. አስቀየመ. Her exclusion from the club hurt her feelings. ከክበቡ ፡ መከልከሏ ፡ አስቀየማት

**hurt oneself** ተጐዳ
She fell on the stairs and hurt herself. ደረጃ ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ ተጐዳች

**hurtle** እየተንጋጋ ፡ ወጣ
The boys hurtled out of the door. ልጆቹ ፡ እየተንጋጉ ፡ በበሩ ፡ ወጡ

**hurtle through** ሰንጥቆ ፡ በረረ
The jet hurtled through the air. ጄቱ ፡ አየሩን ፡ ሰንጥቆ ፡ በረረ

**husband** (v.) ቈጠበ
That man must husband his strength while he is ill. ያ ፡ ሰው ፡ በሕመሙ ፡ ጊዜ ፡ ጉልበቱን ፡ መቈጠብ ፡ አለበት

**husband** (n.) ባል ፤ ባለቤት
Where is her husband? ባሏ ፡ (ባለቤቷ) ፡ የት ፡ አለ ?

**husbandry**
1. አያያዝ. By good husbandry Mr. Parker amassed a considerable fortune. አያያዝ ፡ በማወቁ ፡ ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሀብት ፡ አከማቸ
2. እርባታ. Animal husbandry requires both training and money. የከብት ፡ እርባታ ፡ ዕውቀትንና ፡ ገንዘብን ፡ ይጠይቃል
3. እርሻ. Most of the people in that region are engaged in husbandry. የዚያ ፡ ቀበሌ ፡ ሰዎች ፡ ብዙዎቹ ፡ በእርሻ ፡ ይተዳደራሉ

**hush** (vt.) አባበለ
The mother hushed the crying child. እናትየዋ ፡ የሚያለቅሰውን ፡ ልጅ ፡ አባበለች

**hush** (vi.)
1. ጭጭ ፡ አለ. They hushed as the judge walked in. ዳኛው ፡ ሲገባ ፡ ጭጭ ፡ አሉ
2. ዝም ፡ አለ. We were asked to hush during the music, በሙዚቃው ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ እንድንል ፡ ተነገረን

**hush!** እሽ
Hush! I can't hear a word. እሽ ! ምንም ፡ አይሰማኝም

**hush up** አለባበሰ
She tried to hush up the fact that her husband was an ex-convict. ባሏ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተፈረደበት ፡ ወንጀለኛ ፡ መሆኑን ፡ ለማለባበስ ፡ ሞከረች

**hush up!** ዝም ፡ በል
Hush up! I am tired of your chatter. ዝም ፡ በል ! ልፍለፋህ ፡ ሰልችቶኛል

**(be) hushed up** ተደፋፈነ
The scandal was quickly hushed up. የሡሩት ፡ በደል ፡ ወዲያውኑ ፡ ተደፋፈነ

**hush** (n.) ጸጥታ
A hush settled over the room when the Emperor entered. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ጸጥታ ፡ ሰፈነ

**husk** (v.) ሸለቀቀ
They were husking the corn all day. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ በቆሎውን ፡ ሲሸለቅቁ ፡ ዋሉ

**husk** (n.) ላንፋ
Remove the husk from the corn before you cook it! በቆሎውን ፡ ከመቀቀልህ ፡ በፊት ፡ ላንፋውን ፡ ሸልቅቀው

**strip the husk** ሸለቀቀ
You must strip the husk from an ear of corn before you cook it. በቆሎ ፡ ከመቀቀሉ ፡ በፊት ፡ መሸልቀቅ ፡ አለበት

**husky**
1. ጐርናና. She has a husky voice. ጐርናና ፡ ድምፅ ፡ አላት
2. ጠብደል. He is a very husky man, and he can lift very heavy boxes. ጠብደል ፡ ስለሆነ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ሣጥኖችን ፡ ሊያነሣ ፡ ይችላል

**hustle** (vt.) እየገፈታተረ ፡ አስገባ
The police hustled the thief into the truck. ፖሊሶች ፡ ሌባውን ፡ ወደ ፡ መኪናው ፡ ውስጥ ፡ እየገፈታተሩት ፡ አስገቡት

**hustle** (vi.)
1. ፈጠን ፡ አለ. We have to hustle to get there. እዚያ ፡ ለመድረስ ፡ ፈጠን ፡ ማለት ፡ አለብን
2. ተጣደፈ. We had to hustle to get the dishes washed by six o'clock. ሳሕኖችን ፡ በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ አጥቦ ፡ ለማድረስ ፡ መጣደፍ ፡ ነበረብን

**hustle about** ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ተሯሯጠ
The maid hustled about putting the house in order. ገረዲቱ ፡ ቤቱን ፡ ለማዘጋጀት ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ተሯሯጠች

**hustle out** አቻኩሎ ፡ አስወጣ
They hustled him out of the bar. ከቡና ፡ ቤቱ ፡ አቻኩለው ፡ አስወጡት

**hustle to bed** ቶሎ ፡ አስተኛ
Mother hustled the baby to bed. እናቱ ፡ ሕፃኑን ፡ ቶሎ ፡ አስተኛችው

**hustle and bustle** ግርግር
The hustle and bustle of the big city tires me out. የትልቅ ፡ ከተማ ፡ ግርግር ፡ ያደክመኛል

**hut** ጎጆ
There is a little hut in the woods. ጫካው ፡ ውስጥ ፡ ትንሽ ፡ ጎጆ ፡ አለች

**hutch** [እንደ ፡ ጥንቸል ፡ ላሉ ፡ ትናንሽ ፡ እንስሳት ፡ መኖሪያ ፡ እንዲሆን ፡ የተሠራ ፡ ጎጆ]

**hybrid** ዲቃላ
The mule is a hybrid, being the offspring of a donkey and a horse. በቅሎ ፡ ከአህያና ፡ ከፈረስ ፡ የምትወለድ ፡ ዲቃላ ፡ ናት
A word formed of words from different languages is a hybrid. የልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋዎችን ፡ ቃላት ፡ በመቀያየጥ ፡ የተመሠረተ ፡ ቃል ፡ ዲቃላ ፡ ይባላል

**hydrant** [ከትልቁ ፡ የውኃ ፡ ማከማቻ ፡ ውኃ ፡ የሚስብ ፡ ቧምቧ]

**hydromel** ብርዝ
She washed her hands in preparation for clarifying the hydromel. ብርዙን ፡ ለማጣራት ፡ እጇን ፡ ታጠበች

**hyena** ጅብ
Hyenas abound in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ጅብ ፡ ሞልቷል

**hygiene** የጤና ፡ ጥበቃ ፡ ዘዴ
A team is teaching people about hygiene. አንድ ፡ ቡድን ፡ ሕዝቡን ፡ የጤና ፡ ጥበቃ ፡ ዘዴ ፡ በማስተማር ፡ ላይ ፡ ነው

**hymn** መዝሙር
They exalted God in their hymns. በመዝሙራቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አሞገሱ

**sing a hymn** ዘመረ
The priests sang a hymn during Mass. ቄሶች ፡ በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ ዘመሩ

**hyphen** ንኡስ ፡ ጭረት
Only recently have we started using the hyphen when we write Amharic. አማርኛ ፡ ስንጽፍ ፡ በንኡስ ፡ ጭረት ፡ መጠቀም ፡ የጀመርነው ፡ በቅርብ ፡ ነው

**hypocrisy** ግብዝነት
He is suspected of hypocrisy. እሱ ፡ በግብዝነት ፡ ይጠረጠራል

**hypocrite** ግብዝ
One cannot depend on a hypocrite's promises. የግብዝን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ለመተማመን ፡ አይቻልም

**hypothesis**
1. ግምት. Your hypothesis of weather changes has no foundation. ስለ ፡ አየር ፡ ሁኔታ ፡ መለዋወጥ ፡ ያለህ ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ የለውም
2. መላ ፡ ምት. A scientist cannot leap to conclusions, but must test every hypothesis. ሳይንቲስት ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ አይችኩልም ፤ ማንኛቸውንም ፡ መላ ፡ ምት ፡ ሁሉ ፡ ይመረምራል ፡ እንጂ

**hysteria** ብርክ
The soldier had an attack of hysteria in the middle of the battle. ወታደሩ ፡ በጦርነቱ ፡ መሀከል ፡ ብርክ ፡ ያዘው

# I

**I** እኔ
I am a student. እኔ ፡ ተማሪ ፡ ነኝ

**ice** በረዶ
There is ice on the ground. መሬቱ ፡ ላይ ፡ በረዶ ፡ አለ
Put some ice in my drink, please! መጠጤ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂት ፡ በረዶ ፡ አድርግበት
**cuts no ice** ምንም ፡ አይደል
Her father's position cuts no ice with me. ያባቷ ፡ ሥልጣን ፡ ለኔ ፡ ምንም ፡ አይደል
**on thin ice**
*Without some facts to support you, you are on thin ice with this argument. የሚደግፍህ ፡ አንዳንድ ፡ መረጃ ፡ ካላገኘህ ፡ ይህ ፡ ክርክር ፡ አያዋጣህም

**iceberg** የበረዶ ፡ አለት

**(be) icy** በበረዶ ፡ ተሸፈነ
Be careful driving; the streets are icy. ስትነዳ ፡ ተጠንቀቅ ፤ መንገዶቹ ፡ በበረዶ ፡ ተሸፍነዋል
**icy look**
*She gave him an icy look. ፊቷን ፡ አጠቁረች በት

**idea**
1. ትምህርት. This book will give you a good idea of life in ancient Greece. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ ጥንታዊ ፡ ግሪክ ፡ ኑሮ ፡ ጥሩ ፡ ትምህርት ፡ ይሰጥሃል
2. አስተሳሰብ. Their idea of beauty is quite different from ours. ስለ ፡ ውበት ፡ ያላቸው ፡ አስተሳሰብ ፡ ከኛ ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ ነው
His ideas on raising children are certainly strange. ልጆችን ፡ ስለ ፡ ማሳደግ ፡ ያለው ፡ አስተሳሰብ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ነው
3. አስተያየት. He had nebulous ideas on the subject. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ደብዛዛ ፡ አስተያየት ፡ ነበረው
4. ዓላማ. The idea of a vacation is to get away from work. የዕረፍት ፡ ዓላማው ፡ ከሥራ ፡ ለመለየት ፡ ነው
5. ሐሳብ. That is an excellent idea. እጅግ ፡ ጥሩ ፡ ሐሳብ ፡ ነው
**give the idea** ነገረ
What gave you the idea that I will lend you money? ገንዘብ ፡ ያበድርሃል ፡ ብሎ ፡ የነገረህ ፡ ማን ፡ ነው ?
**have an idea** መሰለ(ው)
I have an idea she will be late. የምትዘገይ ፡ ይመስለኛል
**have no idea**
1. አላወቀም. You have no idea how worried we were. ምን ፡ ያህል ፡ እንደሰጋን ፡ አታውቅም
2. አላሰበም. He had no idea that work at high school was so hard. የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ እስከዚህ ፡ ይከብዳል ፡ ብሎ ፡ አላሰበም ፡ ነበር
**not have the idea** ለማወቅ ፡ አልቻለም
I haven't the faintest idea what he wants. ምን ፡ እንደሚፈልግ ፡ ለማወቅ ፡ በፍጹም ፡ አልቻልኩም
[See also 'central, fall, flirt, impregnate, play, strike, toy']

**ideal**
1. ዓይነተኛ ፡ አርአያ. King Theodore has become the ideal of many young Ethiopians. አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ለብዙ ፡ ወጣት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ዓይነተኛ ፡ አርአያ ፡ ሆነዋል
2. ዓላማ. Love of money corrupted his ideals. የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ ዓላማውን ፡ አበላሸቶበታል
3. ደንብ. He tried to live up to the ideals of the Christian religion. በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ለመኖር ፡ ሞከረ
*He's my ideal. አመልክሃለሁ
**ideal** (adj.)
1. ተስማሚ. This is ideal weather for a holiday. አየሩ ፡ ለዕረፍት ፡ ተስማሚ ፡ ነው
2. የሰጠ. This is an ideal place for swimming. ይህ ፡ ለዋና ፡ የሰጠ ፡ ቦታ ፡ ነው
3. በጣም ፡ ጥሩ. It would be ideal if she could accompany us to care for the children. ልጆቹን ፡ ለመጠበቅ ፡ አብራን ፡ ብትሄድ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነበር
4. ዓይነተኛ. To many people Washington personifies the ideal American. ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ዋሽንግተን ፡ የዓይነተኛ ፡ አሜሪካዊ ፡ ምሳሌ ፡ ነው

**idealism** የኀልዮ ፡ ኑሮ
The young are influenced by idealism. ወጣቶች ፡ የኀልዮ ፡ ኑሮ ፡ ይማርካቸዋል

**idealize** ፍጹም ፡ አድርጎ ፡ አቀረበ
Some historians idealize their subjects. አንዳንድ ፡ የታሪክ ፡ ሊቃውንት ፡ ባለ ፡ ታሪኮችን ፡ ፍጹም ፡ አድርገው ፡ ያቀርቧቸዋል

**identical**
1. ልክ ፡ ይህን ፡ የመሰለ. This pen is identical with the one I lost. የጠፋብኝ ፡ ብዕር ፡ ልክ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነው
2. አንድ. Both events happened on the identical day. ሁለቱም ፡ ድርጊቶች ፡ ባንድ ፡ ዕለት ፡ የተደረጉ ፡ ናቸው

**be identical** ተመሳሰለ
These two books are identical. እነዚህ ፡ ሁለት ፡ መጽሐፎች ፡ ይመሳሰላሉ

**identification** መለያ ፡ ነገር
He carries identification with him all the time. ዘወትር ፡ መለያ ፡ ነገር ፡ ይዞ ፡ ይሄዳል

**identification card** መታወቂያ ፡ ወረቀት
Your identification card, please! እስኪ ፡ መታወቂያ ፡ ወረቀትህን ፡ አሳየን

**identification mark** ምልክት
Do you have any special identification marks? ሰውነትህ ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ አለህ ?

**identify** (identified)
1. ለየ. The police identified him by his fingerprints. ፖሊሱ ፡ በጣቱ ፡ አሻራ ፡ ለየው
2. አንድ ፡ አድርጎ ፡ አየ. One usually identifies wealth with success. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ሀብትንና ፡ የሥራ ፡ መቃናትን ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ የሚያዩ ፡ አሉ
3. መሆኑን ፡ አረጋገጠ. John identified the bag as his by telling what it contained. ዮሐንስ ፡ ሻንጣው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ እቃ ፡ ለይቶ ፡ በመናገር ፡ ሻንጣው ፡ የርሱ ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጠ

**identify oneself**
Can you identify yourself? ማን ፡ ትባላለህ ?
*He refused to identify himself with the scheme. እዚህ ፡ እቅድ ፡ ውስጥ ፡ አልገባበትም ፡ አለ

**be identified** ግንኙነት ፡ አለው
He is identified with the new party. ከዲሱ ፡ ፓርቲ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ አለው

**identity**
1. ተመሳሳይነት. She observed the identity of the dresses. የልብሶቹን ፡ ተመሳሳይነት ፡ ለየች
2. ማንነት. The writer concealed his identity under an assumed name. ጸሐፊው ፡ ማንነቱን ፡ በሌላ ፡ ስም ፡ ሸፈነው
3. መለያ. There was no proof of the identity of the thief. ሌባውን ፡ መለያ ፡ ምንም ፡ ማስረጃ ፡ አልነበረም

**ideology** የፖለቲካ ፡ ዘይቤ
Communism is an ideology. ኮሙኒዝም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የፖለቲካ ፡ ዘይቤ ፡ ነው

**idiom**
1. ፈሊጣዊ ፡ አነጋገር. Amharic is rich in idioms. አማርኛ ፡ በፈሊጣዊ ፡ አነጋገር ፡ የበለጸገ ፡ ነው
2. አነጋገር. He spoke in the idiom of the country people. እንደ ፡ ባላገሮች ፡ አነጋገር ፡ ተናገረ

**idiosyncrasy** (idiosyncrasies) መለዮ
Wearing only black ties is an idiosyncrasy of his. ጥቁር ፡ ከራቫቶች ፡ ብቻ ፡ ማሰር ፡ መለዮው ፡ ነው

**idiot** ደደብ
He looks like an idiot. ደደብ ፡ ይመስላል

**idiotic**
1. አይረባም. This film is idiotic. ይህ ፡ ፊልም ፡ አይረባም
2. (= noun) ጅልነት. His plan to spend the summer in this hot place is idiotic. በጋውን ፡ በዚህ ፡ ሞቃት ፡ ቦታ ፡ ለማሳለፍ ፡ ማቀዱ ፡ ጅልነት ፡ ነው

**idle** (vt.) ሥራ ፡ አስፈታ
The strike idled 300 workers. ሥራ ፡ የማቆም ፡ አድማው ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰዎችን ፡ ሥራ ፡ አስፈታ

**idle** (vi.) ሥራ ፡ ፈታ
Are you going to spend your whole vacation just idling? የዕረፍት ፡ ጊዜህን ፡ በሙሉ ፡ ሥራ ፡ ፈትህ ፡ ልታሳልፈው ፡ ነው ?
*Let the motor idle to warm it up! ሞተሩን ፡ አስነሥተህ ፡ እንዲሞቅ ፡ ተወው

**idle away** አባከነ ፤ አጠፋ
Don't idle away your time! ጊዜህን ፡ አታባክን ፡ (አታጥፋ)

**idle** (adj.)
1. ከንቱ. That's just idle talk. ከንቱ ፡ ወሬ ፡ ነው
2. የማይረባ. Idle rumors pop up every so often. የማይረባ ፡ ወሬ ፡ በየጊዜው ፡ ይነፍሳል
3. ሰነፍ. The reason he is so poor is because he is idle. የደኸየው ፡ ሰነፍ ፡ ስለሆነ ፡ ነው
4. መሠረተ ፡ ቢስ ፡ የሆነ. I tried to dispel his idle fears. መሠረተ ፡ ቢስ ፡ የሆነ ፡ ፍርሃቱን ፡ ላስወግድለት ፡ ሞከርኩ

5. ሥራ ፡ የፈታ. This factory has no idle machinery. ይህ ፡ ፋብሪካ ፡ ሥራ ፡ የፈታ ፡ መሣሪያ ፡ የለውም

**be idle** ሥራ ፡ ፈታ
Her fingers are never idle. እጇ ፡ ምንጊዜም ፡ ሥራ ፡ አይፈታም
Many people are idle at present. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ ፈተዋል

**idle workman** ሥራ ፡ ፈት ፡ ሰው
I see many idle workmen in the streets. በመንገድ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ሰዎች ፡ አያለሁ

**lay idle, stand idle** ሥራ ፡ ፈታ
The factory lay idle for years. ፋብሪካው ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ሥራ ፡ ፈታ
The factory has been standing idle for a year. ፋብሪካው ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ ሥራ ፡ ፈታ
[See also 'speculation']

**idleness**
1. ስንፍና. Idleness is not the only cause of poverty. የድኽነት ፡ መነሻ ፡ ስንፍና ፡ ብቻ ፡ አይደለም
2. ሥራ ፡ ፈትነት. Idleness begets crime. ሥራ ፡ ፈትነት ፡ ወንጀልን ፡ ያስከትላል

**idler** ሥራ ፡ ፈት
Laziness makes us all idlers. ስንፍና ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ያደርገናል

**idol** ጣዖት
People worshipped idols before Christianity came. ክርስትና ፡ ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ ሰዎች ፡ ጣዖት ፡ ያመልኩ ፡ ነበር

**idolatrous** ጣዖት ፡ አምላኪ
The idolatrous peoples were punished by God. ጣዖት ፡ አምላኪዎቹ ፡ ሕዝቦች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተቀጡ

**idolatry** የጣዖት ፡ አምልኮ
Christianity denounces idolatry. የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ የጣዖት ፡ አምልኮን ፡ ያወግዛል

**practice idolatry** ጣዖት ፡ አመለከ
Jews used to practice idolatry in ancient times. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ አይሁዶች ፡ ጣዖት ፡ ያመልኩ ፡ ነበር

**idolize** አመለከ
They say that the ancient Ethiopians idolized a serpent. የጥንት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በዘንዶ ፡ ያመልኩ ፡ ነበር ፡ ይባላል
Young people often idolize football players. ወጣቶች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ኳስ ፡ ተጫዋቾችን ፡ ያመልኳቸዋል

**idyll** [የባላገርን ፡ ኑሮ ፡ የሚገልጽ ፡ አጭር ፡ ታሪክ ፡ ወይም ፡ ግጥም]

**if**
1. የ + perfect + እንደሆነ. If anyone asks for me, say I'll be right back. ሰው ፡ የፈለገኝ ፡ እንደሆነ ፡ አሁን ፡ ይመለሳል ፡ በል
2. እንደ + (perfect). See if there is any mail for me. ደብዳቤ ፡ እንዳለኝ ፡ እይ
3. imperfect + እንደሆነ. He asked me if I knew Amharic. አማርኛ ፡ አውቅ ፡ እንደሆነ ፡ ጠየቀኝ
4. ከ + (perfect). If you like, we can go straight home. ከፈለግህ ፡ በቀጥታ ፡ እቤት ፡ ልንሄድ ፡ እንችላለን
I'll go if he goes. ከሄደ ፡ እሄዳለሁ
Sing if you want to. ከፈለግህ ፡ ዝፈን
5. ምንም ፡ እንኳ ፡ ብ + (imperfect). If he made a mistake, at least he meant well. ምንም ፡ እንኳ ፡ ስሕተት ፡ ቢሠራ ፡ ክፋት ፡ አላሰበም
*If I had known, I wouldn't have done it. ባውቅ ፡ ኖሮ ፡ አላደርገውም ፡ ነበር

**if only!**
*If I could only get there! እንደምንም ፡ ከዚያ ፡ ብደርስ !
[See also 'as, even, ever, what']

**ignite** (vt.)
1. አቀጣጠለ. They ignited the twigs to warm themselves. ለመሞቅ ፡ ጭራሮውን ፡ አቀጣጠሉ
2. እሳት ፡ አያያዘ. He ignited the paper with a lighted match. ከብሪት ፡ ጭሮ ፡ ወረቀቱን ፡ በእሳት ፡ አያያዘ

**ignite** (vi.)
1. ነደደ. Paper ignites easily. ወረቀት ፡ በቀላሉ ፡ ይነዳል
2. እሳት ፡ ተያያዘ. The dry twigs ignited from a spark. ጭራሮው ፡ በፍንጣሪ ፡ እሳት ፡ ተያያዘ
3. ፈነዳ. The gunpowder is damp and won't ignite. ባሩዱ ፡ ስለረጠበ ፡ አይፈነዳም

**ignition, turn on the ~** ቁልፍ ፡ ከፈተ
Turn on the ignition and start the car! ቁልፉን ፡ ከፈትና ፡ መኪናውን ፡ አስነሣው

**ignoble**
1. ወራዳ. A cheat is an ignoble man. አታላይ ፡ ሰው ፡ ወራዳ ፡ ነው
2. የሚያሳፍር. Their ignoble defeat will go down in history. የሚያሳፍር ፡ ድል ፡ መመታታቸው ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ይሰፍራል

**ignominious**
1. አሳፋሪ. Shooting an unarmed person in

the back is an ignominious act. መሣሪያ ፡ ያልያ
ዘን ፡ ሰው ፡ ተደብቆ ፡ በጥይት ፡ መምታት ፡ አሳ
ፋሪ ፡ ድርጊት ፡ ነው
2. አዋራጅ. His ignominious punishment only made him more rebellious. አዋራጅ ፡ ቅጣቱ ፡
የባሰ ፡ ዐመፀኛ ፡ አደረገው

**ignorance**
1. ድንቁርና. I have never seen such ignorance.
እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ድንቁርና ፡ አጋጥሞኝም ፡ አ
ላውቅ
2. አለማወቅ. Ignorance of the law is no excuse.
ሕግን ፡ አለማወቅ ፡ ከቅጣት ፡ አያድንም
3. አላዋቂነት. He showed abysmal ignorance of Ethiopian conditions. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሁኔ
ታ ፡ ወደር ፡ የሌለውን ፡ አላዋቂነት ፡ ታየበት

**ignorant**
1. ደንቆሮ. She is such an ignorant person!
እንዴት ፡ ያለች ፡ ደንቆሮ ፡ ናት
2. የጭፍን. The student gave an ignorant answer. ተማሪው ፡ የጭፍኑን ፡ መልስ ፡ ሰጠ

**be ignorant** አላወቀም
You are ignorant of the reasons for her behavior. እንዲህ ፡ የምትሆንበትን ፡ ምክንያት ፡
አታውቅም

**ignore** ችላ ፡ አለ
I ignored the rebuke. ግሣጼውን ፡ ችላ ፡ አል
ኩት

**be ignored** ታለፈ
Such vehement aspersions cannot be ignored.
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ከባድ ፡ ሐሜት ፡ የሚታለፍ ፡ አ
ይደለም

**ill** (n.)
1. በሽታ. She told us about the ills she had had. ስለነበረባት ፡ በሽታ ፡ ነገረችን
2. መቅሠፍት. War is one of the great ills.
ጦርነት ፡ ከታላላቅ ፡ መቅሠፍቶች ፡ አንዱ ፡ ነው
3. ክፉ. Don't do ill to those who won't agree with you! ካንተ ፡ ጋር ፡ የማይስማሙትን ፡
ክፉ ፡ አትሥራባቸው
4. ቂም. I harbor no ill toward those who have wronged me. በበደሉኝ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ምንም ፡
ቂም ፡ አልይዝም

**ill** (adv.)
*Work ill done will not be paid for. በደንብ ፡
ላልተሠራ ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ አይከፈልም

**ill effects** ጉጅነት
The doctor explained to him the ill effects of smoking. ሐኪሙ ፡ የሲጃራውን ፡ ጉጅነት ፡
አስረዳው

**ill feeling** ጥላቻ
He still has ill feelings toward his old enemies.
አሁንም ፡ ስለ ፡ ድሮ ፡ ጠላቶቹ ፡ ጥላቻ ፡ አለው

**ill luck**
1. መጥፎ ፡ አጋጣሚ. It was ill luck to meet my boss when I had reported that I was sick.
ታምሚያለሁ ፡ ብዬ ፡ ካስታወቅሁ ፡ በኋላ ፡ አለ
ቃዬን ፡ ማግኘቴ ፡ መጥፎ ፡ አጋጣሚ ፡ ነበር
2. ክፉ ፡ ነገር. He carries a charm to ward off ill luck. ከክፉ ፡ ነገር ፡ ለመጠበቅ ፡ ድግምት ፡ አድ
ርጓል

**ill manners** ብልግና
His ill manners make him unpopular with everyone. ብልግናው ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ የተጠ
ላ ፡ ያደርገዋል

**ill turn** ጉዳት
He did me an ill turn by telling the boss of my mistakes. ለአለቃዬ ፡ ስሕተቶቼን ፡ በመናገ
ር ፡ ጉዳት ፡ አደረሰብኝ

**ill will** ክፉ ፡ መንፈስ
His ill will showed clearly in his face. ክፉ ፡ መ
ንፈሱ ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**be ill** አመመ(ው)
+He was very ill and couldn't go to school.
ክፉኛ ፡ አሞት ፡ ስለነበረ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡
ሊሄድ ፡ አልቻለም

**be ill-advised** በመጥፎ ፡ ምክር ፡ ተመራ
He was ill-advised to take that trip. ያንን ፡ ጉዞ ፡
ያደረገው ፡ በመጥፎ ፡ ምክር ፡ ተመርቶ ፡ ነው

**be ill at ease** እንደልቡ ፡ መሆን ፡ አልቻለም
He is ill at ease in the company of rich people.
ከሀብታሞች ፡ ጋር ፡ ሲሆን ፡ እንደልቡ ፡ መሆን ፡ አ
ይችልም

**be ill-disposed toward** ጠላ
He is ill-disposed toward the workers' complaints. የሠራተኞቹን ፡ አቤቱታ ፡ ይጠላል

**be ill-provided**
They were ill-provided with rifles. በቂ ፡ ጠመን
ጃ ፡ አልተሰጣቸውም

**be ill with fever** አተኰሰ(ው)
+He is ill with fever and has to go to the hospital.
ስላተኰሰው ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ አለ
በት

**be in ill health** ጤና ፡ የለውም
He is in ill health now and cannot go to work.
እርሱ ፡ ጤና ፡ ስለሌለው ፡ ሥራ ፡ ሊሄድ ፡ አይችልም

**be in ill repute** ተረገመ
Fascism has always been in ill repute. ፋሺዝ
ም ፡ ምንጊዜም ፡ እንደተረገመ ፡ ነው

**(he) can ill afford** አያዋጣውም
He can ill afford to quit his job now. አሁን ፡ ሥራውን ፡ መተው ፡ አያዋጣውም

**fall ill** ታመመ
He has fallen ill and cannot come to the party. ስለታመመ ፡ ወደ ፡ ፓርቲው ፡ ሊመጣ ፡ አይችልም

**feel ill** ታመመ
She felt ill, so her teacher sent her to the nurse. ስለታመመች ፡ መምህሯ ፡ ወደ ፡ ነርሷ ፡ ላከቻት

**house of ill repute** የሴተኛ ፡ አዳሪ ፡ ቤት
There are many houses of ill repute in the city. ብዙ ፡ የሴተኛ ፡ አዳሪ ፡ ቤቶች ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ አሉ

**of ill repute**
She is a woman of ill repute. ሴትኛ ፡ አዳሪ ፡ ናት

**speak ill of** በክፉ ፡ አነሣ
He spoke ill of his neighbors. ጐረቤቶቹን ፡ በክፉ ፡ አነሣቸው

**take ill**
1. ታመመ. He took ill after eating fish. ዓሣ ፡ ከበላ ፡ በኋላ ፡ ታመመ
2. ቅር ፡ ተሰኘ. He took my promotion ill because he thought he deserved it. ለሱ ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ በማመን ፡ በማዕረግ ፡ እድገቴ ፡ ቅር ፡ ተሰኘ

**treat ill** በደለ
He treated his son ill. ልጁን ፡ በደለው
[See also 'humor']

## illegal ሕገ ፡ ወጥ ፤ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የሆነ
It is illegal to counterfeit money. አስመስሎ ፡ ገንዘብ ፡ መሥራት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ (ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የሆነ) ፡ ተግባር ፡ ነው

## illegible የማይነበብ
His illegible writing gave the secretary a lot of trouble. የማይነበብ ፡ ጽሕፈቱ ፡ ጸሐፊዋን ፡ በጣም ፡ አስቸገራት

**be illegible** አይነበብም
His writing is illegible. ጽሕፈቱ ፡ አይነበብም

## illegitimate
1. ሕገ ፡ ወጥ. This is an illegitimate claim. ይህ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ጥያቄ ፡ ነው
2. ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የሆነ. His illegitimate dealings were revealed in court. ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ አድራጎቱ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ተገለጸበት

**illegitimate child** ዲቃላ
Can illegitimate children inherit from the father? ዲቃላ ፡ ከአባት ፡ ሊወርስ ፡ ይችላልን ?

## ill-fated ገደ ፡ ቢስ
The bodies of the men on that ill-fated expedition were never found. በዚያ ፡ ገደ ፡ ቢስ ፡ ጉዞ ፡ ላይ ፡ የሞቱት ፡ ሰዎች ፡ ሬሳ ፡ በፍጹም ፡ አልተገኘም

## ill-founded መሠረት ፡ የሌለው
He presented an ill-founded plea for mercy. መሠረት ፡ የሌለው ፡ የምሕረት ፡ ልመና ፡ አቀረበ

## illicit የተከለከለ
He got into trouble selling illicit goods. የተከለከሉትን ፡ ሸቀጦች ፡ ሲሸጥ ፡ መከራ ፡ ላይ ፡ ወደቀ

## illiteracy መሃይምነት
They are trying to combat illiteracy. መሃይምነትን ፡ ለማውደም ፡ ይሞክራሉ

## illiterate መሃይም
The illiterates are being helped to learn to read. መሃይሞች ፡ ማንበብ ፡ በመማር ፡ ላይ ፡ ናቸው

## ill-mannered ባለጌ
He is an ill-mannered boy. ባለጌ ፡ ልጅ ፡ ነው

## illness ሕመም
Her illness lasted one week. ሕመሟ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ቆየባት

## illogical ከትክክለኛ ፡ አስተሳሰብ ፡ የወጣ
Her arguments are strictly illogical. ክርክሯ ፡ ከትክክለኛ ፡ አስተሳሰብ ፡ የወጣ ፡ ነው

## ill-omened ገደ ፡ ቢስ
Everybody on the ill-omened expedition perished. ሁሉም ፡ በገደ ፡ ቢሱ ፡ ጉዞ ፡ ላይ ፡ አለቁ

## ill-tempered ቁጡ
My boss is ill-tempered. አለቃዬ ፡ ቁጡ ፡ ነው

## ill-treat
1. አንገላታ ፤ አጕሳቈለ. Don't ill-treat the horse! ፈረሱን ፡ አታንገላታው ፡ (አታጕሳቍለው)
2. በደለ. Parents should not ill-treat their children. ወላጆች ፡ ልጆቻቸውን ፡ መበደል ፡ የለባቸውም

## ill-treatment በደል
Her ill-treatment of her children is well known. ልጆቿ ፡ ላይ ፡ የምታደርገው ፡ በደል ፡ የታወቀ ፡ ነው

## illuminate
1. ብርሃን ፡ ሰጠ. Street lights illuminate the street. የመንገድ ፡ መብራቶች ፡ ለመንገዱ ፡ ብርሃን ፡ ይሰጣሉ

2. አብራራ. He illuminated a difficult passage in the Bible. ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ አስቸጋሪ ፡ ምንባብ ፡ አብራራ
3. በሥዕል ፡ አስጌጠ. In former days Ethiopian scribes illuminated the manuscripts. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የብራና ፡ ጽሑፎችን ፡ በሥዕል ፡ ያስጌጡዋቸው ፡ ነበር
4. አበራ. A smile illuminated her face. ፈገግታ ፡ ፊቷን ፡ አበራው

**be illuminated**
1. በሥዕል ፡ አጌጠ. Some Ethiopian manuscripts are illuminated. አንዳንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የብራና ፡ ጽሑፎች ፡ በሥዕል ፡ ያጌጡ ፡ ናቸው
2. አሸበረቀ. The streets were illuminated for the celebration. ለክብረ ፡ በዓሉ ፡ መንገዶቹ ፡ አሸብርቀው ፡ ነበር

## illumination ማብራሪያ
The illumination of his theory was not convincing. ስለ ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳቡ ፡ የሰጠው ፡ ማብራሪያ ፡ አጥጋቢ ፡ አልነበረም
*Illumination in the hall is provided by large electric lights. ለአዳራሹ ፡ ብርሃን ፡ የሚሰጡት ፡ ትልልቅ ፡ የኮሬንቲ ፡ መብራቶች ፡ ናቸው

## illusion የተሳሳተ ፡ እምነት
He has the illusion that everyone likes him. ሁሉም ፡ ይወደኛል ፡ የሚል ፡ የተሳሳተ ፡ እምነት ፡ አለው

**give the illusion of** መሰለ
This wallpaper gives the illusion of a brick wall. ይህ ፡ የግድግዳ ፡ ወረቀት ፡ ጡብ ፡ ይመስላል

## illustrate
1. ለመግለጫ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሣለ. He illustrated the book with many beautiful drawings. ለመግለጫ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ውብ ፡ የሆኑ ፡ ሥዕሎች ፡ ሣለ
2. አብራራ. I can illustrate this best by an example. ይህን ፡ በምሳሌ ፡ የበለጠ ፡ ላብራራው ፡ እችላለሁ

**be illustrated** ሥዕሎች ፡ አሉ(በት)
The book is beautifully illustrated. መጽሐፉ ፡ የሚያማምሩ ፡ ሥዕሎች ፡ አሉበት

## illustration
1. ሥዕል. The catalogue has many illustrations. ካታሎጉ ፡ ብዙ ፡ ሥዕሎች ፡ አሉት
2. ማብራሪያ. He cited some examples in illustration of his theory. ለሐሳቡ ፡ ማብራሪያ ፡ አንዳንድ ፡ ምሳሌዎችን ፡ ጠቀሰ

## illustrative ማብራሪያ
A good teacher uses many illustrative examples to explain difficult ideas. መልካም ፡ መምህር ፡ ከባድ ፡ ሐሳብን ፡ ለማስረዳት ፡ በብዙ ፡ ማብራሪያ ፡ ምሳሌ ፡ ይጠቀማል

## illustrator ሠዓሊ
An illustrator can earn much money working for magazines. ሠዓሊ ፡ ለመጽሔቶች ፡ ሥዕል ፡ በመሣል ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል

## illustrious
1. ገናና. The Emperor came from an illustrious family. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከገናና ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የተወለዱ ፡ ናቸው
2. ስመ ፡ ጥር. Washington and Lincoln are illustrious Americans. ዋሽንግተንና ፡ ሊንኮልን ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ አሜሪካውያን ፡ ናቸው

## image
1. አምሳል. God created man in his image. እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ በአምሳሉ ፡ ፈጠረው
2. መልክ. She saw her image in the mirror. መልኳን ፡ በመስታወቱ ፡ አየች
3. ምስል. Do not worship graven images! ቅርጽ ፡ ምስሎችን ፡ አታምልክ
4. ሐሳብ. Images of what might happen frightened her. ምን ፡ ይመጣ ፡ ይሆን ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ አሸበራት
*She's the image of her mother. ቁርጥ ፡ እናቷን ፡ ናት

## imaginable
*He tried everything imaginable. እንኳል ፡ ማሰብ ፡ የሚችለውን ፡ ሁሉ ፡ ሞከሯል

**hardly imaginable**
*That's hardly imaginable! ያ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ የሚታሰብ ፡ አይደለም

## imaginary
1. ሐሳብ ፡ የወለደው ፤ በሐሳብ ፡ የወጣ. The story describes an imaginary hero. ታሪኩ ፡ የሚገልጸው ፡ ሐሳብ ፡ የወለደውን ፡ ጀግና ፡ ነው
Was the figure you saw last night real or imaginary? ትናንት ፡ ማታ ፡ ያየኸው ፡ ነገር ፡ እውነተኛ ፡ ነበር ፡ ወይስ ፡ በሐሳብ ፡ የወጣ ?
2. የሚያልም. The mental patient raved about his imaginary business. የአእምሮ ፡ ሕመምተኛው ፡ ስለሚያልመው ፡ ንግድ ፡ ቃዠ

## imagination
1. ዓይነ ፡ ኅሊና. He saw the whole world in his imagination. በዓይነ ፡ ኅሊናው ፡ ዓለምን ፡ በሙሉ ፡ አየ
2. ሐሳበ ፡ ሰፊነት. This job requires imagination. ይህ ፡ ሥራ ፡ ሐሳበ ፡ ሰፊነት ፡ ይጠይቃል

3. ስሜት. Stories of adventures fire children's imagination. የጀብዱ ፡ ተረቶች ፡ የሕፃናትን ፡ ስሜት ፡ ይቀሰቅሳሉ
4. ልብ ፡ ወለድ. That's pure imagination. ያ ፡ ፍጹም ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ነው
[See also 'stretch']

**imaginative** በሐሳቡ ፡ ፈጠራ ፡ የሚችል
The imaginative child made up horror tales. በሐሳቡ ፡ ፈጠራ ፡ የሚችል ፡ ልጅ ፡ አስፈሪ ፡ ታሪኮችን ፡ ፈጠረ

**imagine**
1. ራሱን ፡ አየ. Imagine that you are on a desert island! ምድረ ፡ በዳ ፡ በሆነች ፡ አንዲት ፡ ደሴት ፡ ላይ ፡ እንዳለህ ፡ ሆነህ ፡ ራስህን ፡ እየው
2. መሰለ(ው).+She imagined someone was watching her. ሰው ፡ የሚያያት ፡ መሰላት
3. አሰበ. Can you imagine him becoming famous? እሱ ፡ ዝነኛ ፡ ይሆናል ፡ ብለህ ፡ ታስባለህ?
4. ዐወቀ. I cannot imagine whom you mean. ማንን ፡ ማለትህ ፡ እንደሆነ ፡ አላወቅሁም
5. በሐሳቡ ፡ ፈጠረ. He is just imagining it. ዝም ፡ ብሎ ፡ በሐሳቡ ፡ እየፈጠረው ፡ ነው
6. ታየ. I cannot imagine what you mean. የምትለው ፡ አይታየኝም

**imbecile** ጅል
Only an imbecile would drink iodine to heal a cut. ቁስሉን ፡ ለማዳን ፡ አዮዲን ፡ የሚጠጣ ፡ ጅል ፡ ብቻ ፡ ነው

**imbibe**
1. መጠጠ. The roots of the plant imbibe moisture from the earth. የዕፅ ፡ ሥሮች ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡ እርጥበትን ፡ ይመጣሉ
2. ተቀረጸ(በት). +Children often imbibe superstitions that last all their lives. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሕፃናት ፡ በሕይወታቸው ፡ሙሉ ፡ የሚቆይ ፡ አጉል ፡ እምነት ፡ ይቀረጽባቸዋል

**imbue** ሞላ
He imbued his son's mind with the ambition to go to college. የልጁን ፡ አእምሮ ፡ ኮሌጅ ፡ በመግባት ፡ ፍላጎት ፡ ሞላው

**be imbued**
1. ተዋጠ. They are imbued with a warlike spirit. በጦር ፡ መንፈስ ፡ ተውጠዋል
2. ተመሰጠ. He is imbued with patriotism. በሀገር ፡ ፍቅር ፡ የተመሰጠ ፡ ነው

**imitate**
1. ቀዳ. He imitates the foreign way of dressing. የውጭ ፡ አገር ፡ አለባበስ ፡ ይቀዳል
2. በ - - - ወጣ. The little boy imitated his father. ልጁ ፡ ባባቱ ፡ ወጣ
3. አስመሰለ. The students amused themselves by imitating the teacher. ተማሪዎቹ ፡ መምህሩን ፡ እያስመሰሉ ፡ በመቀለድ ፡ ራሳቸውን ፡ አስደሰቱ
4. እንዲመስል ፡ ሆነ. Wood is sometimes painted to imitate stone. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ድንጋይ ፡ እንዲመስል ፡ ሆኖ ፡ ዕንጨት ፡ ቀለም ፡ ይቀባል
5. አስመስሎ ፡ ተናገረ. There are machines that imitate human speech. የሰውን ፡ ንግግር ፡ አስመስለው ፡ የሚናገሩ ፡ መኪናዎች ፡ አሉ

**be imitated by**
Their immoral conduct was imitated by others. ከግብረ ፡ ገብነት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ምግባራቸውን ፡ ሌሎችም ፡ ተከተሉት

**imitation** (n.)
1. ሰው ፡ ሠራሽ. These pearls are merely clever imitations. እነዚህ ፡ ዕንቁዎች ፡ በዘዴ ፡ የተፈጠሩ ፡ ሰው ፡ ሠራሾች ፡ ናቸው
2. ቅጅ. The carving is an imitation of an old Chinese piece. ቅርጹ ፡ የድሮ ፡ የቻይና ፡ ሥራ ፡ ቅጅ ፡ ነው
3. ከሌሎች ፡ መቅዳት. We learn things by imitation. አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ የምንማረው ፡ ከሌሎች ፡ በመቅዳት ፡ ነው

**imitation** (adj.)
1. የሚመስል. This is made of imitation leather. ይህ ፡ የተሠራው ፡ ቆዳ ፡ ከሚመስል ፡ ነገር ፡ ነው
2. ሰው ፡ ሠራሽ. He bought imitation pearls. ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ዕንቁ ፡ ገዛ

**do imitations of** እየመሰለ ፡ ታየ
The comedian did imitations of famous people. አጫዋቹ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎችን ፡ እየመሰለ ፡ ታየ

**immaculate**
1. ፍጹም ፡ ንጹሕ. Her clothes are immaculate. ልብሶቿ ፡ ፍጹም ፡ ንጹሕ ፡ ናቸው
2. እንከን ፡ የሌለው. His immaculate conduct won the teacher's praise. እንከን ፡ የሌለው ፡ ጠባዩ ፡ የመምህሩን ፡ ምስጋና ፡ አተረፈለት

**immaculate life** ብቃት
The book describes the immaculate life of the saint. መጽሐፉ ፡ ስለ ፡ ቅዱሱ ፡ ብቃት ፡ ይገልጻል

**Immaculate Conception** እመቤታችን ፡ በድንግልና ፡ መፀነስ
The Holy Scripture tells about the Immaculate Conception. እመቤታችን ፡ በድንግልና ፡ መፀነሷን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ያስረዳል

**(be) immaterial**
1. ግዙፍ ፡ አይደለም. Spirits are immaterial. መናፍስት ፡ ግዙፍ ፡ አይደሉም
2. ግድ ፡ የለውም. What you do is immaterial to me. አንተ ፡ ስለምታደርገው ፡ እኔ ፡ ግድ ፡ የለኝም
The cost is immaterial to him, if the quality is good. እቃው ፡ ጥሩ ፡ ከሆነ ፡ ለዋጋው ፡ ግድ ፡ የለውም

**immature**
1. ያልበሰለ. An immature ear of corn is not good to eat. ያልበሰለ ፡ በቆሎ ፡ መብላት ፡ ጥሩ ፡ አይደለም
2. በደንብ ፡ ያልታሰበበት. Immature plans will result in failure. በደንብ ፡ ያልታሰበባቸው ፡ እቅዶች ፡ ፍጻሜያቸው ፡ አያምርም
**be immature** አልበሰለም
She is very immature for twenty-three. ሃያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ቢሆናትም ፡ ገና ፡ አልበሰለችም

**immeasurable** ወሰን ፡ የሌለው
It is difficult to imagine the immeasurable space of the universe. ወሰን ፡ የሌለውን ፡ የዓለመ ፡ ዓለማትን ፡ ስፋት ፡ ለመገመት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**immediate**
1. የተፋጠነ ፤ ፈጣን ፡ ያለ. Take immediate action on my request! ለጥያቄዬ ፡ የተፋጠነ ፡ ውሳኔ ፡ ስጥልኝ
I am in favor of immediate action. ፈጣን ፡ ያለ ፡ እርምጃ ፡ እንዲወሰድ ፡ እደግፋለሁ
2. የቅርብ. My immediate neighbor is Mr. Parker. የቅርብ ፡ ጐረቤቴ ፡ ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ ነው
Only the immediate family will attend the funeral. የቅርብ ፡ ዘመዶቹ ፡ ብቻ ፡ በቀብሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ
I can't tell you our immediate plans. የቅርብ ፡ እቅዳችንን ፡ ልነግርህ ፡ አልችልም
3. አስቸኳይ. He is presumptuous; he demanded the minister grant him an immediate interview. ሚኒስትሩ ፡ አስቸኳይ ፡ መግለጫ ፡ እንዲሰጡት ፡ በመጠየቁ ፡ ደፋር ፡ ነው
4. (= adv.) ያኔውኑ. They pressed me for an immediate answer. ያኔውኑ ፡ መልስ ፡ እንድሰጥ ፡ ገፋፉኝ
5. (= adv.) ለጊዜው. This check will take care of your immediate needs. ለጊዜው ፡ ለሚያስፈልግህ ፡ ወጪ ፡ ይህ ፡ ቼክ ፡ ይበቃሃል

**immediate cause**
What was the immediate cause of their quarrel? ጠባቸውን ፡ የቀሰቀሰው ፡ ምንድነው ?
**immediate neighborhood** አቅራቢያ
There is no school in the immediate neighborhood. በዚህ ፡ አቅራቢያ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የለም
**be in immediate contact** ተነካካ
These two objects are in immediate contact. እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ ተነካክተዋል
**in the immediate future** በቅርቡ
We expect no big change in the immediate future. በቅርቡ ፡ ትልቅ ፡ ለውጥ ፡ እንደሚደረግ ፡ ተስፋ ፡ አናደርግም

**immediately**
1. አሁኑኑ. I will go there immediately. አሁኑኑ ፡ እዚያ ፡ እሄዳለሁ
2. ወዲያውኑ. Immediately afterwards I heard a scream. ወዲያውኑ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ጩኸት ፡ ሰማሁ
3. ልክ. The railroad station is immediately to the north of the post office. የባቡሩ ፡ ጣቢያ ፡ ልክ ፡ ከፖስታ ፡ ቤቱ ፡ በስተሰሜን ፡ ነው

**immemorial**
*These customs are handed down from time immemorial. እነዚህ ፡ ባህሎች ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲያያዙ ፡ የመጡ ፡ ናቸው
[See also 'time']

**immense**
1. በጣም ፡ ሰፊ. They have an immense living room. በጣም ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ ሳሎን ፡ አላቸው
2. በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ. His services to the state have been immense. ለመንግሥት ፡ ያደረገው ፡ አገልግሎት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነበር
3. ግዙፍ. The Empire State Building is an immense building. የኤምፓየር ፡ ስቴት ፡ ሕንጻ ፡ ግዙፍ ፡ ሕንጻ ፡ ነው

**immensely** እጅግ ፡ በጣም
They enjoyed themselves immensely. እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደሰቱ

**immerse** ነከረ
He immersed the package in water. ጥቅሉን ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ነከረው
The priest baptizes by immersing the child in water. ቄሱ ፡ ሕፃኑን ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ በመንከር ፡ ያጠምቃሉ
**be immersed** ተዋጠ
He was immersed in his work. በሥራው ፡ ተውጦ ፡ ነበር

**immigrant**
1. ስደተኛ. Immigrants are welcome here. ስደተኞቹ ፡ እዚህ ፡ እንዲኖሩ ፡ ይፈቀድላቸዋል
2. መጤ. He was an immigrant to the United States. ለዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ መጤ ፡ ነበር

**immigrate** ገባ
He hopes that no Chinese will immigrate to this country. አንዳችም ፡ የቻይና ፡ ተወላጅ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ እንዳይገባ ፡ ይመኛል

**immigration**
1. ስደት. There has been immigration to America from all countries of Europe. ከውሮፓ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ ስደት ፡ ተደርጓል
2. ስደተኞች. The immigration of 1918 included many Italians. በ፲፱፻፲፩ ፡ ዓ.ም.ከመጡት ፡ ስደተኞች ፡ መሀከል ፡ ብዙ ፡ ኢጣልያኖች ፡ ነበሩ
The government has reversed its policy on immigration. መንግሥቱ ፡ ስለ ፡ ስደተኞች ፡ ጉዳይ ፡ የነበረውን ፡ አመራር ፡ በተቃራኒው ፡ ለወጠ
3. ኢሚግሬሽን. The Immigration Office gives work permits. የኢሚግሬሽን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሥራ ፡ ፈቃድ ፡ ይሰጣል

**imminent**
*They ran home because of the imminent storm. ከመጣው ፡ ማዕበል ፡ ለመዳን ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሮጡ

**be imminent** የማይቀር ፡ ነው
Let us presume that economic collapse is imminent! የኤኮኖሚ ፡ ውድቀት ፡ የማይቀር ፡ ነው ፡ እንበል
*One who has optimism will not believe that war is imminent. ደግ ፡ አሳቢ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ጦርነት ፡ ይነሣል ፡ ብሎ ፡ አያስብም

**immobile, remain ~** ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ
The commander remained immobile while the Emperor was inspecting his troops. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወታደሮቹን ፡ ሲጐበኙ ፡ አዛዡ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ

**immobilize** አሰሮ ፡ አስቀመጠ
Illness immobilized him. ሕመም ፡ አስሮ ፡ አስቀመጠው

**immoderate,** adj. (= adv.) ከመጠን ፡ በላይ
The child has an immoderate appetite for sweets. ልጁ ፡ ጣፋጭ ፡ ነገር ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ይወዳል

**immodest**
1. አስነዋሪ. She had on an immodest dress. አስነዋሪ ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ ነበር
2. (= noun) ነውር. Interrupting her husband is considered immodest for an Ethiopian woman. ለኢትዮጵያዊት ፡ ሴት ፡ ባል ፡ ሲናገር ፡ ጣልቃ ፡ መግባት ፡ እንደ ፡ ነውር ፡ ይቈጠራል
3. ትሕትና ፡ የጐደለ(ው). Her behavior is immodest. ምግባሯ ፡ ትሕትና ፡ የጐደለው ፡ ነው

**immolate oneself** ራሱን ፡ ሠዋ ፤ ራሱን ፡ መሥዋዕት ፡ አደረገ
He immolated himself to protest the invasion of his country. ያገሩን ፡ መወረር ፡ በመቃወም ፡ ራሱን ፡ ሠዋ ፡ (ራሱን ፡ መሥዋዕት ፡ አደረገ)

**immoral**
1. ከግብረ ፡ ገብነት ፡ ውጭ ፡ የሆነ. Their immoral conduct was imitated by others. ከግብረ ፡ ገብነት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ምግባራቸውን ፡ ሌሎችም ፡ ተከተሉት
2. ግብረ ፡ ገብነት ፡ የጐደለው. He is immoral because he takes bribes. ጉቦ ፡ ስለሚበላ ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ የጐደለው ፡ ነው

**immortal** (n.) ሕያው ፡ ስም ፡ ያለው
Shakespeare is one of the immortals of English literature. ሼክስፒር ፡ ሕያው ፡ ስም ፡ ካላቸው ፡ የእንግሊዝ ፡ ጸሐፊዎች ፡ አንዱ ፡ ነው

**immortal** (adj.) ሕያው
Only God is immortal. ሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነው

**immortality** ሕያውነት
Immortality is one of God's attributes. ሕያውነት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ባሕሪያት ፡ አንዱ ፡ ነው

**immortalize** ለዘላለም ፡ እንዲታወስ ፡ አደረገ
The artist immortalized his mother in a painting. ሠዓሊው ፡ የእናቱን ፡ ሥዕል ፡ ሥሎ ፡ ለዘላለም ፡ እንድትታወስ ፡ አደረጋት

**immovable** የማይበገር
The child's immovable stubbornness could not be overcome by threats. የልጁ ፡ የማይበገር ፡ እልህ ፡ በማስፈራራት ፡ እንኳን ፡ ሊወገድ ፡ አልተቻለም

**be immovable** አልተንቀሳቀሰም
The ancient people thought that the earth was immovable. የጥንት ፡ ሰዎች ፡ መሬት ፡ አትንቀሳቀስም ፡ ብለው ፡ ያምኑ ፡ ነበር

**immovables** የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት
Immovables will be taxed at a lower rate than

movable property. በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሚከፈል ፡ ቀረጥ ፡ በሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ከሚከፈል ፡ ቀረጥ ፡ ያንሳል

**(be) immune** ሊያመልጥ ፡ አይችልም
Nobody is immune from criticism. ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከነቀፌታ ፡ ሊያመልጥ ፡ አይችልም

**be immune to**
1. ከ --- መድን ፡ ነው. I am immune to smallpox because of my vaccination. ስለተከተብኩ ፡ ከፈንጣጣ ፡ መድን ፡ ነኝ
2. ስሜት ፡ አልሰጠውም. He was immune to her charms. የሷ ፡ ውበት ፡ ስሜት ፡ አልሰጠውም

**immunity, give ~ to** መድን ፡ ወጣ
One attack of measles usually gives a person immunity to that disease. ሰው ፡ አንዴ ፡ ኩፍኝ ፡ ከያዘው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ መድን ፡ ይወጣል

**give immunity from** ከ --- ነጻ ፡ አደረገ
The law gives schools and churches immunity from taxation. ሕጉ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ከታክስ ፡ ነጻ ፡ ያደርጋል

**(be) granted immunity** ከ --- ነጻ ፡ ወጣ ፤ ከ --- ነጻ ፡ ነው
He was granted immunity from prosecution so he would testify. ለመመስከር ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ ከመከሰስ ፡ ነጻ ፡ ወጣ
Diplomats are granted immunity from taxation. ዲፕሎማቶች ፡ ከቀረጥ ፡ ነጻ ፡ ናቸው

**immutable** የማይለወጥ
Natural laws are immutable. የተፈጥሮ ፡ ሕጎች ፡ የማይለወጡ ፡ ናቸው

**impact**
1. ኀይል. The impact of the explosion was felt for miles. የፈንጂው ፡ ኀይል ፡ ብዙ ፡ ማይል ፡ ርቆ ፡ ተሰማ
The impact of the two colliding cars broke the windows. የሁለቱ ፡ መኪናዎች ፡ የግጭት ፡ ኀይል ፡ መስኮቱን ፡ ሰባበረው
2. መፋጨት. The impact of the two swords broke both of them. የሁለቱ ፡ ጐራዴዎች ፡ መፋጨት ፡ ከመሰበር ፡ አደረሳቸው
3. ግጭት. The impact dented the fender of the automobile. ግጭቱ ፡ የመኪናውን ፡ ፈረፋንጉን ፡ ጠረመሰው
4. ተጽዕኖ. Under the impact of new ideas, life in Ethiopia has begun to change. ባዲሱ ፡ ሥልጣን ፡ ተጽዕኖ ፡ ምክንያት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ መለዋወጥ ፡ ጀምሯል

**impair** ጐዳ
Poor food impaired his health. ያልተሟላ ፡ ምግብ ፡ ጤንነቱን ፡ ጐዳው

**be impaired** ደከመ
Her vision is impaired, so she must get glasses. ዓይኗ ፡ ስለደከመ ፡ መነጽር ፡ ማድረግ ፡ አለባት

**impart**
1. ሰጠ. Flowers impart beauty to the room. አበቦች ፡ ለክፍሉ ፡ ውበትን ፡ ይሰጣሉ
2. ነገረ. I have nothing of interest to impart to you today. ዛሬ ፡ የምነግራችሁ ፡ ምንም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ የለኝም

**impartial** አድሎ ፡ የሌለበት
That was an impartial act. አድሎ ፡ የሌለበት ፡ አድራጎት ፡ ነበር

**be impartial** አላደላም
I'll try to be impartial. ላለማድላት ፡ እሞክራለሁ

**(be, become) impassable**
1. አያሻግርም. This ford is impassable due to the rain. ከዝናብ ፡ የተነሣ ፡ መልካው ፡ አያሻግርም
2. አያስኬድም. These roads are impassable during the rains. በዝናብ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ መንገዶች ፡ አያስኬዱም
3. አያሳልፍም. As a result of the heavy rainfall, the roads become impassable. በኀይለኛ ፡ ዝናብ ፡ ምክንያት ፡ መንገዶች ፡ ሁሉ ፡ አያሳልፉም

**impasse, reach an ~**
*Negotiations have reached an impasse. ስምምነቱ ፡ ከምንም ፡ ሊደርስ ፡ አልቻለም

**impassive**
1. ረጋ ፡ ያለ. John's impassive face showed no sign of his anger. የጆን ፡ ረጋ ፡ ያለ ፡ ፊት ፡ መናደዱን ፡ አላስታወቀበትም
2. (= adv.) በድን ፡ ሆኖ. The wounded soldier lay impassive as though dead. ቁስለኛው ፡ ወታደር ፡ እንደሞተ ፡ ሁሉ ፡ በድን ፡ ሆኖ ፡ ተጋደመ

**impassively** ያለ ፡ ስሜት
He listened impassively. ያለ ፡ ስሜት ፡ አዳመጠ

**impatience** ትዕግሥት ፡ ማጣት
Her impatience showed in her tapping her feet. ትዕግሥት ፡ ማጣቷ ፡ ወለሉን ፡ በመቆርቆሯ ፡ ታወቀ

**(be) impatient**
1. ትዕግሥት ፡ አጣ. Don't be so impatient!

Letters will come soon. እንደዚሁ ፡ ትዕግሥት ፡ አትጣ ፤ ደብዳቤ ፡ አሁን ፡ ይመጣል
2. ቸኰለ. He is impatient to go swimming. ወደ ፡ ዋና ፡ ለመሄድ ፡ ቸኲሏል
3. ጓጓ. She is impatient to grow up. ለማደግ ፡ ትጓጓለች

**make impatient** ትዕግሥት ፡ አስጨረሰ
The tardy arrival of the train made us impatient. የባቡሩ ፡ ዘግይቶ ፡ መድረስ ፡ ትዕግሥታችንን ፡ አስጨረሰን

**impatiently**
1. በጉጉት. I have been impatiently waiting for your letter. ደብዳቤህን ፡ በጉጉት ፡ እጠባበቅ ፡ ነበር
2. ትዕግሥት ፡ በማጣት. She twitched impatiently in her chair. ትዕግሥት ፡ በማጣት ፡ ወንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቍነጠነጠች
[See also 'march']

**impeach** ወነጀለ
They impeached the judge for taking bribes. ዳኛውን ፡ ጉቦ ፡ በመቀበሉ ፡ ወነጀሉት

**impeccable** እንከን ፡ የሌለበት ፤ የመላእክት
The young man has impeccable manners. ወጣቱ ፡ ሰውዬ ፡ እንከን ፡ የሌለበት ፡ ጠባይ ፡ አለው ፡ (or, የመላእክት ፡ ጠባይ ፡ አለው)

**be impeccable** ተጣራ
The actor's elocution is impeccable. የተዋናዩ ፡ ንግግር ፡ የተጣራ ፡ ነው

**impede** አገደ
Fog impeded our making an early start. በማለዳ ፡ እንዳንሄድ ፡ ጭጋጉ ፡ አገደን

**impede one's progress** ወደኋላ ፡ አስቀረ ፤ ወደኋላ ፡ ጎተተ
The thick mud impeded his progress. ማጡ ፡ ወደኋላ ፡ አስቀረው ፡ (ጎተተው)

**impediment**
1. መሰናክል. Bad roads are an impediment to travel. መጥፎ ፡ መንገዶች ፡ ለጉዞ ፡ መሰናክል ፡ ናቸው
2. ዕንቅፋት. Stuttering is a speech impediment. መንተባተብ ፡ ለንግግር ፡ ዕንቅፋት ፡ ነው

**impel** (impelled)
1. ገፋ. The wind impelled the boat to shore. ነፋሱ ፡ ጀልባውን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ዳርቻ ፡ ገፋው
2. አስገደደ. Fear impelled him to lie. ፍርሃት ፡ እንዲዋሽ ፡ አስገደደው

**impend**
1. ሊነሣ ፡ አለ. When war impends, wise men try to prevent it. ጦርነት ፡ ሊነሣ ፡ ሲል ፡ ብልህ ፡ ሰዎች ፡ ለማስቀረት ፡ ይሞክራሉ
2. አይቀርም. Death impends. ሞት ፡ አይቀርም

**impending**
1. ሊደርስበት ፡ የሚችል. A consciousness of impending danger kept him awake. አደጋ ፡ ሊደርስበት ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ስላወቀ ፡ እንቅልፍ ፡ አጣ
2. (= adv.) በቅርብ. I just now heard of her impending arrival. በቅርብ ፡ እንደምትደርስ ፡ አሁን ፡ ሰማሁ
*Diplomats took the reports of an impending crisis with a grain of salt. ዲፕሎማቶች ፡ ይደርሳል ፡ ስለሚባለው ፡ ሽብር ፡ የቀረበውን ፡ ሪፖርት ፡ እንደነገሩ ፡ ተቀበሉት

**be impending** ሳይመጣ ፡ አይቀርም
Disaster seems to be impending. መዓት ፡ ሳይመጣ ፡ አይቀርም

**impenetrable** የማይደረስበት
Only religion provides comfort for the impenetrable mystery of death. ምስጢሩ ፡ ለማይደረስበት ፡ ሞት ፡ መጽናኛ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ነው

**be impenetrable**
1. የማይደፈር ፡ ነው. This forest is impenetrable. ይህ ፡ ጫካ ፡ የማይደፈር ፡ ነው
2. አያሳልፍም. This glass is impenetrable to light. ይህ ፡ መስታወት ፡ ብርሃን ፡ አያሳልፍም
3. አይበሳም. A thick sheet of metal is impenetrable by an ordinary bullet. ጠንካራ ፡ ብረት ፡ በተራ ፡ ጥይት ፡ አይበሳም

**imperative** (n.)
1. ትእዛዝ ፡ አንቀጽ. The imperative in Amharic is expressed by a special form. በአማርኛ ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ በልዩ ፡ መንገድ ፡ ይገለጻል
2. ትእዛዝ. The great imperative is "Love thy neighbor as thyself". ታላቁ ፡ ትእዛዝ ፡ « ጓደኛህን ፡ እንደራስህ ፡ ውደድ » ፡ የሚለው ፡ ነው

**imperative** (adj.) የትእዛዝ
"Go at once!", he said in an imperative manner. በትእዛዝ ፡ አነጋገር ፡ « በፍጥነት ፡ ሂድ » ፡ አለ

**imperative duty** መሠረታዊ ፡ ግዳጅ
The army's imperative duty is to defend the nation's borders. የጦር ፡ ኃይሎች ፡ መሠረታዊ ፡ ግዳጅ ፡ ያገርን ፡ ድንበር ፡ ማስከበር ፡ ነው

**be imperative** አስፈለገ
Is it imperative for them to have a large army? ብዙ ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ እንዲኖራቸው ፡ ያስፈልጋል ?

**(be) imperceptible** ጐልቶ ፡ አይታይም

The monthly growth of children is imperceptible. ልጆች ፡ በየወሩ ፡ የሚያደርጉት ፡ እድገት ፡ ጐልቶ ፡ አይታይም

**imperfect**

1. የተበላሸ. This stamp is imperfect. I don't want it. ይህ ፡ ቴምብር ፡ የተበላሸ ፡ ነው ። አልፈልገውም

2. ያልተሟላ. He has an imperfect knowledge of Amharic. ያልተሟላ ፡ ያማርኛ ፡ ዕውቀት ፡ አለው

**make imperfect** ጉድለት ፡ አሳደረበት

A crack in the pot makes it imperfect. ማሰሮው ፡ ያለው ፡ ስንጥቅ ፡ ጉድለት ፡ አሳድሮበታል

**Imperial** የንጉሠ ፡ ነገሥት

The Imperial Government demands you pay your tax. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግብር ፡ እንዲከፍሉ ፡ ያስገድዳል

**His Imperial Majesty** ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት

His Imperial Majesty will visit our school tomorrow. ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ትምህርት ፡ ቤታችንን ፡ ነገ ፡ ይጐበኙሉ

[See also 'bodyguard']

**imperialism** ኢምፔሪያሊዝም

Imperialism has been driven out of much of Africa. ኢምፔሪያሊዝም ፡ ከአብዛኛው ፡ የአፍሪካ ፡ ክፍል ፡ ተወግዷል

**imperialist** ኢምፔሪያሊስት

The imperialists are plotting against him. ኢምፔሪያሊስቶች ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ያሴራሉ

**imperil**

1. አደጋ ፡ ላይ ፡ ጣለ. His policy imperils the safety of the country. የሱ ፡ አመራር ፡ የሀገሪቷን ፡ ደኅንነት ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ይጥላል

2. አደጋ ፡ አደረሰ. Reckless drivers imperil people's lives. ግድ ፡ የለሽ ፡ የሆኑ ፡ መኪና ፡ ነጂዎች ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ያደርሳሉ

**imperious** እብሪት ፡ የተሞላበት

With an imperious gesture, he ordered me to leave. እብሪት ፡ በተሞላበት ፡ አኳኋን ፡ እንድወጣ ፡ አዘዘኝ

**imperishable**

1. የማይበላሽ. Only imperishable goods can be stored here. የማይበላሹ ፡ እቃዎች ፡ ብቻ ፡ እዚህ ፡ ሊቀመጡ ፡ ይችላሉ

2. የማይረሳ. The patriots' fame is imperishable. ያርበኞቹ ፡ ዝና ፡ የማይረሳ ፡ ነው

**impersonal**

1. ሰብአዊነት ፡ የሌለው. Electricity is an impersonal force. ኮሬንቲ ፡ ሰብአዊነት ፡ የሌለው ፡ ኀይል ፡ ነው

2. ማንንም ፡ የማይጠቅስ. An impersonal discussion of student problems may help to relieve their distress. ማንንም ፡ የማይጠቅስ ፡ የተማሪዎች ፡ ችግር ፡ ውይይት ፡ ቅሬታቸውን ፡ ለማስወገድ ፡ ሊረዳ ፡ ይችል ፡ ይሆናል

**impersonate**

1. እንደ - - - ሆኖ ፡ ሠራ. The student impersonated Hamlet on the stage. ተማሪው ፡ በመድረኩ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሀምሌት ፡ ሆኖ ፡ ሠራ

2. መስሎ ፡ ታየ. The spy impersonated an officer. ሰላዩ ፡ መኰንን ፡ መስሎ ፡ ታየ

3. ምሳሌ ፡ ነው. To many people Washington impersonates the ideal American. ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ዋሽንግተን ፡ የዓይነተኛ ፡ አሜሪካዊ ፡ ምሳሌ ፡ ነው

**impertinence** ብልግና

The teacher was shocked by the girl's impertinence. አስተማሪው ፡ በልጃገረዲቷ ፡ ብልግና ፡ ደነገጠ

**impertinent**

1. የማይገባ. He made some impertinent remarks while I was there. እዚያ ፡ በነበርኩበት ፡ ጊዜ ፡ የማይገባ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠ

2. ስድ ፡ አደግ. His children are impertinent. ልጆቹ ፡ ስድ ፡ አደጎች ፡ ናቸው

3. (= noun) ብልግና. Talking back to older people is impertinent. ለሽማግሌ ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ ብልግና ፡ ነው

**(be) impervious to**

1. አያስገባም. This tent is impervious to rain. ይህ ፡ ድንኳን ፡ ዝናብ ፡ አያስገባም

2. አልተሰማ(ውም). +She is impervious to criticism. ነቀፌታ ፡ አይሰማትም

**impetuous**

1. ችኩል. Children are more impetuous than grownups. ልጆች ፡ ካዋቂዎች ፡ ይልቅ ፡ ችኩል ፡ ናቸው

2. ኀይለኛ. The impetuous winds hindered our advance. ኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ ጉዟችንን ፡ እንዳንገፋ ፡ አደረገን

**impetus** ኀይል

The impetus of the falling rock shattered the concrete. የተናዳው ፡ ቋጥኝ ፡ ኀይል ፡ ሲሚንቶውን ፡ ብትንትኑን ፡ አወጣው

**give impetus** በር ፡ ከፈተ
The treaty will give a new impetus to trade.
የውሉ ፡ ስምምነት ፡ ለንግድ ፡ አዲስ ፡ በር ፡ ይ
ከፍታል

**impiety** ሃይማኖተ ፡ ቢስነት
His impiety caused the priests to excommuni-
cate him from the church. ሃይማኖተ ፡ ቢስነቱ ፡
ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲወገድ ፡ አደረገው

**impinge on**
1. ወጋ. Rays of light impinge on the eye.
የብርሃን ፡ ጨረሮች ፡ ዓይን ፡ ይወጋሉ
2. ነካ. Censorship impinges on our freedom.
ሳንሱር ፡ መብታችንን ፡ ይነካል

**implacable**
1. የማይበርድ. His implacable anger gave his
enemies reason to dread him. የማይበርደው ፡
ንዴቱ ፡ ጠላቶቹ ፡ እንዲፈሩት ፡ ምክንያት ፡ ሆና
ቸው
2. የምር. These two people are implacable
enemies. እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ የምር ፡ ጠላ
ቶች ፡ ናቸው

**implant** ቀረጸ
The teacher implanted new ideas in the minds
of the students. አስተማሪው ፡ በተማሮቹ ፡ አእ
ምሮ ፡ አዳዲስ ፡ ሐሳቦችን ፡ ቀረጸ

**implement** (v.)
1. ሠራ. Do not undertake a project unless you
can implement it. ልትሠራው ፡ ካልቻልክ ፡ አን
ድ ፡ እቅድ ፡ አትጀምር
2. ፈጸመ. Once in office, he failed to implement
his campaign promises. ከተመረጠ ፡ በኋላ ፡ እ
ሠራዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ የገባውን ፡ ሁሉ ፡ ሳይ
ፈጽም ፡ ቀረ

**be implemented** ሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ
The project for irrigating land will soon be
implemented. በመስኖ ፡ መሬት ፡ የማጠጣቱ ፡ እቅ
ድ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላል

**implement** (n.) መሣሪያ
He bought farming implements at the fair.
ከኤክስፖዚሲዮኑ ፡ የእርሻ ፡ መሣሪያዎችን ፡ ገዛ

**implicate** እንዳለው ፡ ተናገረ
The thief implicated two helpers. ሌባው ፡ ሁለ
ት ፡ ግብረ ፡ አበሮች ፡ እንዳሉት ፡ ተናገረ

**be implicated in** ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ ተከሰሰ
He was implicated in a plot to overthrow the
government. መንግሥቱን ፡ ለመገልበጥ ፡ በተደረገ
ው ፡ ሴራ ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ ተከሷል

**implication**
*There was no implication of dishonesty in
his failure in business. ንግዱ ፡ ሳይሳካለት ፡ የ
ቀረው ፡ ታማኝ ፡ ባለመሆኑ ፡ አይመስልም

**implicit**
1. ውስጣዊ. There was an implicit threat in
his words. በንግግሩ ፡ ውስጥ ፡ ውስጣዊ ፡ የማስ
ፈራራት ፡ ስሜት ፡ ነበረበት
2. ያልተገለጸ. Her silence gave implicit consent.
ዝምታዋ ፡ ያልተገለጸ ፡ መስማማቷን ፡ አመለከተ
3. (= adv.) ሳያወላውል. A soldier must give
implicit obedience to his officers. ወታደር ፡ ለአ
ለቆቹ ፡ ሳያወላውል ፡ መታዘዝ ፡ አለበት

**implore** ለመነ
He implored the judge for mercy. ዳኛውን ፡ ም
ሕረት ፡ ለመነ

**imply** (implied)
1. በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ ጠቀሰ. He implied
that I was dishonest. የማልታመን ፡ መሆኔን ፡
በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ ጠቀሰ
2. አመለከተ. Silence often implies consent.
አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ዝምታ ፡ መስማማትን ፡ ያመለ
ክታል

**impolite** (= noun) ብልግና
That was very impolite of him. ያደረገው ፡ ነገር ፡
ብልግና ፡ ነበር

**be impolite** አላከበረም
He is very impolite to old people. ሽማግሌ ፡
አያከብርም

**import** (v.)
1. አስመጣ. Many merchants import French
wines. ብዙ ፡ ነጋዴዎች ፡ የፈረንሳይ ፡ ወይን ፡ ጠ
ጅ ፡ ያስመጣሉ
2. ከውጭ ፡ አገር ፡ አስመጣ. They imported the
latest equipment. በቅርቡ ፡ የተሠራውን ፡ መሣ
ሪያ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ አስመጡ
3. አመለከተ. Some say a red sunset imports
a fair day on the morrow. ፀሐይ ፡ ስትጠልቅ ፡
ደም ፡ መምሰሉ ፡ በበነጋው ፡ የብራ ፡ ቀን ፡ እን
ደሚሆን ፡ ያመለክታል ፡ ይባላል

**be imported** ከውጭ ፡ መጣ
Farm implements are being imported. የእርሻ ፡
መሣሪያዎች ፡ ከውጭ ፡ ይመጣሉ

**import** (n.)
1. ፍሬ ፡ ነገር. What is the import of his state-
ment? የንግግሩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ምንድን ፡ ነው ?
2. ቁም ፡ ነገር. These are matters of great

import. እንዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያላቸው ፡ ናቸው

3. ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ማግባት. The government encouraged the import of raw materials. መንግሥት ፡ የጥሬ ፡ እቃን ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ማግባት ፡ አበረታታ

4. ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ እቃ. Last year exports exceeded imports in value. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ የተላኩ ፡ እቃዎች ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ከገቡት ፡ እቃዎች ፡ በዋጋ ፡ በለጡ

**be in the import business** አስመጪ ፡ ነው
He is in import and export business. እሱ ፡ አስመጪና ፡ ላኪ ፡ ነው

## importance

1. ጥቅም. My illness brought the importance of insurance home to me. መታመሜ ፡ የሕይወት ፡ ዋስትናን ፡ ጥቅም ፡ አስገነዘበኝ

2. ጠቃሚነት. The teacher impressed on them the importance of study. አስተማሪው ፡ የትምህርትን ፡ ጠቃሚነት ፡ በአእምሯቸው ፡ አሳደረባቸው

3. አስፈላጊ ፡ ነገር. Literacy is of primary importance. መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ መሠረታዊ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው

4. ዋጋ. You attach too much importance to it. ከሚገባው ፡ በላይ ፡ ዋጋ ፡ ትሰጠዋለህ

5. ትልቅነት. He maximizes the importance of what he had done. የሠራውን ፡ ትልቅነት ፡ ያጋንናል

**air of importance** ራሱን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ማሳየቱ
The deputy's air of importance is not in keeping with his real job. ምክትሉ ፡ ራሱን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ማሳየቱ ፡ ከኀላፊነቱ ፡ ጋር ፡ አይመጣጠንም

**of importance** በጣም ፡ አስፈላጊ
A birth certificate is a document of importance. የልደት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ሰነድ ፡ ነው
[See also 'attach, paramount, utmost, vast, vital']

## important

1. ብርቱ. I want to see you about an important matter. ለብርቱ ፡ ጉዳይ ፡ ላነጋግርህ ፡ እፈልጋለሁ

2. ከፍተኛ. Conformity of opinion is sometimes necessary in deciding important matters. ከፍተኛ ፡ ጉዳዮችን ፡ ለመወሰን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የሐሳብ ፡ መስማማት ፡ ያስፈልጋል

3. ጠቃሚ. The Emperor delivered an important address. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ንግግር ፡ አደረጉ

4. ታላቅ (pl. ታላላቅ). The important men of the town held a meeting. የከተማው ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ስብሰባ ፡ አደረጉ

5. (= noun) ፍሬ ፡ ነገር. Have you digested everything that is important in that book? በዚያ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ቀሥመሃል ?

**be important**
1. ተፈላጊነት ፡ አለው. The two books are equally important. ሁለቱም ፡ መጻሕፍት ፡ እኩል ፡ ተፈላጊነት ፡ አላቸው
2. ዋጋ ፡ አለው. The formative years of youth are very important. የወጣት ፡ የማደጊያ ፡ ዓመታት ፡ በጣም ፡ ዋጋ ፡ አላቸው

**important matter** ቁም ፡ ነገር
He likes to discuss important matters with his friends. ከጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ማውራት ፡ ይወዳል

**the most important**
1. ዋና ፡ ዋናዎቹ. The most important industries are concentrated in the north. ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ የተከማቹት ፡ በሰሜን ፡ ነው
2. እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ. He was the most important man in town. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነበር
3. ከሁሉ ፡ የላቀ. The opening of the Suez Canal was the most important event of the year. የስዌዝ ፡ ካናል ፡ መከፈት ፡ ባመቱ ፡ ውስጥ ፡ ከተደረጉት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ የላቀ ፡ ነበር

## importunate ሙጭጭ ፡ ያለ

He is an importunate beggar. ሙጭጭ ፡ ያለ ፡ ለማኝ ፡ ነው

## importune ወተወተ

She importuned her husband for more money. ባሏ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲጨምርላት ፡ ወተወተችው

## impose ጣለ ፤ አወጣ

The government imposed a tax on the farmers. መንግሥቱ ፡ በገበሬዎቹ ፡ ላይ ፡ ግብር ፡ ጣለ
The government imposed new sanitary laws. መንግሥቱ ፡ አዲስ ፡ የጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ሕግ ፡ አወጣ

**be imposed** ተጨመረ
New duties were imposed on cigarettes. በሲጃራ ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ ቀረጥ ፡ ተጨምሯል

**impose on**
1. አስቸገረ. Can I impose on you to drive me home? በመኪናህ ፡ እቤቴ ፡ እንድታደርሰኝ ፡ ላስቸግርህ ?
2. ሸክም ፡ ሆነበት. Do not impose on people who do not like you! በማይወዱህ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ሸክም ፡ አትሁንባቸው

3. እንዲቀበል ፡ አስገደደው. He did not impose his advice on me; I listened to him willingly. ምክሩን ፡ እንድቀበል ፡ አላስገደደኝም ፤ ግን ፡ በፈቃደኝነት ፡ አዳመጥኩት
[See also 'fine']

**imposing** ግርማ ፡ ያለው
The Jubilee Palace is an imposing edifice. የኢዮቤልዩ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ግርማ ፡ ያለው ፡ ሕንጻ ፡ ነው

**imposition**
1. መጣል. The imposition of a tax was decreed by the President. የግብር ፡ መጣሉ ፡ ሕግ ፡ በፕሬዚዳንቱ ፡ ተደነገገ
2. ሰውን ፡ ማስቸገር. Staying for a meal when you were not invited is an imposition. ሳትጋበዝ ፡ በምሳ ፡ ላይ ፡ መገኘት ፡ ሰውን ፡ ማስቸገር ፡ ነው
3. ማስቸገር. Would it be an imposition to ask you to mail this parcel? ይህን ፡ ጥቅል ፡ ፖስታ ፡ ቤት ፡ ብትወስድልኝ ፡ ማስቸገር ፡ ይሆንብኝ ፡ ይሆን ?

**impossibility** የማይቻል ፡ ነገር
To live long without food is an impossibility. ያለ ፡ ምግብ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መቆየት ፡ የማይቻል ፡ ነገር ፡ ነው

**impossible** የማይሆን
They dreamed up an impossible plan. የማይሆን ፡ እቅድ ፡ አወጡ

**be impossible**
1. አይቻልም. That plan is impossible to execute. እቅዱን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ አይቻልም
2. አስቸጋሪ. That man is absolutely impossible! ያ ፡ ሰው ፡ ፍጹም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**make impossible** አላስቻለም
The blare of the radio made conversation impossible. የሬዲዮው ፡ ጩኸት ፡ ለመጨዋወት ፡ አላስቻለም

**the most impossible** የማይቻል ፤ የማይሆን
They dreamed up the most impossible plan. የማይቻል ፡ (የማይሆን) ፡ እቅድ ፡ አወጡ

**impostor** አጭበርባሪ
The impostor was unmasked. አጭበርባሪው ፡ ተነቃበት

**(be) impotent** ጉልበት ፡ አልነበረውም ፤ ችሎታ ፡ አልነበረውም
We were impotent against the storm. ማዕበሉን ፡ ለመቋቋም ፡ ጉልበት ፡ አልነበረንም ፡ (ችሎታ ፡ አልነበረንም)

**impound**
1. በሕግ ፡ ያዘ. The police impounded his car. ፖሊሶቹ ፡ መኪናውን ፡ በሕግ ፡ ያዙ
2. አፈላማ ፡ ያዘ. The farmer impounded the stray cattle. ገበሬው ፡ ልቅ ፡ የሆኑትን ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ አፈላማ ፡ ያዘ

**impoverish** አደኸየ
Bad farming methods impoverish the soil. መጥፎ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ አፈርን ፡ ያደኸያል

**be impoverished** ደኸየ
The country was impoverished by wars. አገሪቷ ፡ በጦርነት ፡ ደኽይታለች

**(be) impracticable** ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ አይችልም
Most schemes to abolish poverty are impracticable. ብዙዎቹ ፡ ድኽነትን ፡ የማጥፋት ፡ እቅዶች ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውሉ ፡ አይችሉም

**impractical**
1. ሊሠራ ፡ አይቻልም. First it's expensive, second it's impractical, and third it's difficult to get. አንደኛ ፡ ውድ ፡ ነው ፤ ሁለተኛ ፡ ሊሠራ ፡ አይቻልም ፤ ሦስተኛ ፡ ደግሞ ፡ ለማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. ከንቱ. Buying things that you don't need just because they are on sale is impractical. የማያስፈልጉህን ፡ ነገሮች ፡ በቅናሽ ፡ ስለሚሸጡ ፡ ብቻ ፡ መግዛት ፡ ከንቱ ፡ ነው

**imprecation** እርግማን
The prophet rained imprecations on his enemies. ነቢዩ ፡ በጠላቶቹ ፡ ላይ ፡ እርግማን ፡ አወረደባቸው

**impregnable** የማይበገር
The fortress in the hills was impregnable. ኮረብታው ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ምሽግ ፡ የማይበገር ፡ ነበር

**impregnate** ጨመረ(በት)
The farmer impregnated the soil with insecticide. ገበሬው ፡ መሬቱን ፡ የተባይ ፡ ማጥፊያ ፡ ጨመረበት

**impregnate with ideas** አጐለመሰ
A great book impregnates the mind with new ideas. ጥሩ ፡ መጽሐፍ ፡ አእምሮን ፡ ያጐለምሳል

**be impregnated** ተነከረ
The wood is impregnated with a chemical that prevents it from burning. ዕንጨቱ ፡ ከመንደድ ፡ በሚያግደው ፡ ኬሚካል ፡ ተነክሯል
*Seawater is impregnated with salt. የባሕር ፡ ውኃ ፡ ጨው ፡ብቻ ፡ ነው

**impress** (v.)

1. አስደነቀ. His running fast did not impress me. በፍጥነት ፡ መሮጡ ፡ አላስደነቀኝም
His bombast impresses the boss, but not his colleagues. ጉራው ፡ አለቃውን ፡ እንጂ ፡ ጓደኞቹን ፡ አያስደንቅም
2. አስገረመ. The grandeur of the ceremony impressed everyone. የሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ታላቅነት ፡ ሁሉን ፡ ሰው ፡ አስገረመው
3. አነቃቃ. We have to invent a slogan to impress these students. እነዚህን ፡ ተማሪዎች ፡ ለማነቃቃት ፡ አንድ ፡ አርማ ፡ መፍጠር ፡ አለብን
4. እምነት ፡ አሳደረ(በት). He impressed us as a sincere young man. ታማኝ ፡ ወጣት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ እምነት ፡ አሳድሮብናል
5. ነካ. The speaker's assured manner impressed me greatly. የተናጋሪው ፡ በራሱ ፡ የመተማመን ፡ ሁኔታ ፡ በጣም ፡ ነካኝ
6. ስሜት ፡ ሰጠ. His perfunctory cordiality didn't impress me. ካንገት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ትሕትናው ፡ ስሜት ፡ አልሰጠኝም
7. ቀረጸ. He impressed his ring in the soft wax. ቀለበቱን ፡ ለስላሳው ፡ ሰም ፡ ላይ ፡ ቀረጸ

**be impressed**
1. ተቀረጸ. His words are impressed on my memory. ቃሉ ፡ ልቤ ፡ ውስጥ ፡ ተቀርጿል
2. ተገረመ. He was impressed by the grandeur of the scenery በትርኢይቱ ፡ ውበት ፡ ተገርሞ ፡ ነበር
3. ተደነቀ. The students were duly impressed by the fame of their teacher. ተማሪዎቹ ፡ በመምህራቸው ፡ ዝና ፡ በሚገባ ፡ ተደንቀው ፡ ነበር

**impress on** በአእምሮው ፡ አሳደረበት
The teacher impressed on them the importance of study. አስተማሪው ፡ የትምህርትን ፡ ጠቃሚነት ፡ በአእምሯቸው ፡ አሳደረባቸው

**impress** (n.) የሚገልጽ ፡ ምልክት
An author leaves the impress of his personality on what he writes. ጸሐፊ ፡ በሚጽፈው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ እሱነቱን ፡ የሚገልጽ ፡ ምልክት ፡ ይታይበታል

**impression**
1. ዱካ. There was an impression of his heel in the mud. የተረከዙ ፡ ዱካ ፡ ጭቃው ፡ ላይ ፡ ነበረ
2. መቅረጽ. The impression of a seal on wax serves as a signature on documents. ማኅተምን ፡ በሰም ፡ ላይ ፡ መቅረጽ ፡ በሰነዶች ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ፊርማ ፡ ያገለግላል
3. አሻራ. The police took an impression of his fingerprints. ፖሊሱ ፡ የጣቱን ፡ አሻራ ፡ አነሣ
4. ግምት. It is only an impression, but I think this is a very good car. እንዲያው ፡ በግምት ፡ ይህ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ መኪና ፡ ይመስለኛል
*It is my impression that he does not want to come. በኔ ፡ አስተያየት ፡ ለመምጣት ፡ የሚፈልግ ፡ አይመስለኝም

**be under the impression** መሰለ(ው)
I was under the impression that you were out of town. ወደ ፡ ውጭ ፡ የሄድክ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር

**give the impression** መስሎ ፡ ታየ
He gives the impression of being a decent fellow. ጨዋ ፡ ልጅ ፡ መስሎ ፡ ይታያል

**leave an impression on** ስሜት ፡ አሳደረበት
His trip to Europe left a great impression on him. ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ያደረገው ፡ ጉዞ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሜት ፡ አሳደረበት

**make an impression** ስሜት ፡ አሳደረ
She made a bad impression right off. ከመጀመሪያው ፡ መጥፎ ፡ ስሜት ፡ አሳደረች

**make little impression** ምንም ፡ ውጤት ፡ አልሰጠም
Punishment seems to make little impression on the child. ልጁን ፡ መቅጣት ፡ ምንም ፡ ውጤት ፡ የሚሰጥ ፡ አይመስልም
[See also 'favorable']

**impressive**
1. አስደናቂ. The inauguration was an impressive ceremony. የምረቃው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አስደናቂ ፡ ነበር
2. የሚደነቅ. The new government buildings are impressive. አዲሶቹ ፡ የመንግሥት ፡ ሕንጻዎች ፡ የሚደነቁ ፡ ናቸው

**imprint** (n.)
1. ዱካ. We saw the imprint of a foot in the sand. በአሸዋ ፡ ላይ ፡ የሰው ፡ ዱካ ፡ አየን
2. ምልክት. You can still see the imprint of a dirty hand on the wall. አሁንም ፡ በግድግዳው ፡ ላይ ፡ ያደፈ ፡ እጅ ፡ ምልክት ፡ ይታያል

**leave an imprint** ተነበበ
Suffering left its imprint on her face. መከራ ፡ ከፊቷ ፡ ይነበባል
*He left the imprint of his thought on all succeeding scholars. አስተሳሰቡ ፡ ከሱ ፡ በኋላ ፡ በመጡት ፡ ሊቃውንት ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**(be) imprinted**
1. ተቀረጸ. His face is imprinted in my memory. መልኩ ፡ በአእምሮዬ ፡ ውስጥ ፡ ተቀርጿል
2. ታተመ(በት). The paper was imprinted with

the state seal. ወረቀቱ ፡ የመንግሥት ፡ ማኅተም ፡ ታትሞበት ፡ ነበር

**imprison** አሰረ
The police imprisoned him several times. ፖሊሱ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አሰረው

**imprisonment** እስራት
The sentence of the court was three years' imprisonment. ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወሰነበት ፡ ቅጣት ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ነበር

**improbable** የማይመስል
It is improbable that Italy will again invade Ethiopia. ኢጣልያን ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንደገና ፡ ትወራለች ፡ ማለት ፡ የማይመስል ፡ ነገር ፡ ነው
*I consider the story improbable. ታሪኩ ፡ የሚሆን ፡ አይመስለኝም

**improper**
1. ትክክለኛ ፡ ያልሆነ. He gave me the improper address. ትክክለኛ ፡ ያልሆነ ፡ አድራሻ ፡ ሰጠኝ
2. የማይገባ. He increased his wealth by improper means. ሀብቱን ፡ በማይገባ ፡ መንገድ ፡ ከፍ ፡ አደረገ

**be improper** ተገቢ ፡ አይደለም
It is improper to eat peas with a knife. አተር ፡ በቢላዋ ፡ መብላት ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**impromptu**, adj. (= adv.) ሳይዘጋጅ
The governor gave an impromptu speech at the airport. አገረ ፡ ገዢው ፡ ሳይዘጋጁ ፡ በአውሮፕላን ፡ ጣቢያው ፡ ንግግር ፡ አደረጉ

**improve** (vt.)
1. አሻሻለ. They are going to improve the road to Addis Ababa. አዲስ ፡ አበባ ፡ የሚወስደውን ፡ መንገድ ፡ ሊያሻሽሉት ፡ ነው
2. ተጠቀመ(በት). He improved his spare time by reading. ትርፍ ፡ ጊዜውን ፡ በማንበብ ፡ ተጠቀመበት

**improve** (vi.) ተሻሻለ
Business has improved. ንግድ ፡ ተሻሽሏል
*His condition has improved. ሻል ፡ ብሎታል

**improvement** መሻሻል
I do not see any improvement in her condition. በሁኔታዋ ፡ ምንም ፡ መሻሻል ፡ አይታየኝም
I have noticed a number of improvements in town since I was there last. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ካየሁት ፡ ዛሬ ፡ ብዙ ፡ መሻሻል ፡ ተመልክቼያለሁ
*The improvements were made at the tenant's own expense. ቤቱ ፡ የታደሰው ፡ በተከራይው ፡ ኪሳራ ፡ ነው

**be an improvement** ተሻለ
The new teacher is a great improvement over his predecessor. አዲሱ ፡ መምህር ፡ ከዱሮው ፡ በጣም ፡ የተሻለ ፡ ነው
[See also 'room']

**improvise** ፈጠረ
As he sang he improvised words to fit the music. እየዘፈነ ፡ ለዜማው ፡ የሚስማማ ፡ ግጥም ፡ ፈጠረ
*The scouts improvised a shelter for the night. እስካውቶቹ ፡ ለሌሊቱ ፡ ጊዜያዊ ፡ መጠለያ ፡ ሠሩ

**imprudent**
1. የማይረባ. His imprudent behavior got him expelled from school. የማይረባ ፡ ጠባዩ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ አስወጣው
2. አስተዋይነት ፡ የጐደለ(ው). Isn't it imprudent of you to marry while you are still in school? በትምህርት ፡ ቤት ፡ እያለህ ፡ ማግባትህ ፡ አስተዋይነት ፡ የጐደለው ፡ አይመስልህም ?

**be imprudent** አለመጠንቀቅ ፡ ነው
It is imprudent to cross against the lights. ቀይ ፡ መብራት ፡ እየበራ ፡ መንገድ ፡ ማቋረጥ ፡ አለመጠንቀቅ ፡ ነው

**impudence** ብልግና
A child who talks backs to his parents shows his impudence. ለወላጆቹ ፡ መልስ ፡ የሚሰጥ ፡ ልጅ ፡ ብልግናውን ፡ ያሳያል

**impudent**
1. ባለጌ. The impudent boy insulted the guest. ባለጌው ፡ ልጅ ፡ እንግዳውን ፡ ሰደበው
2. ዓይን ፡ አውጣ. He is impudent because he is his mother's pet. ለናቱ ፡ ብርቅዬ ፡ ስለሆነ ፡ ዓይን ፡ አውጣ ፡ ነው

**be impudent** አላከበረም
He is impudent to his father. አባቱን ፡ አያከብርም

**impulse**
1. ግፊት. The impulse of the wind blew dust high in the air. የነፋሱ ፡ ግፊት ፡ አቧራውን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አበነነው
2. ስሜት. An angry mob is influenced more by impulse than by reason. የተናደደ ፡ ሕዝብ ፡ ነገርን ፡ በማመዛዘን ፡ ሳይሆን ፡ በስሜት ፡ የሚገፋፋ ፡ ነው

**feel an impulse to**
*I felt an impulse to run. ሩጥ ፡ ሩጥ ፡ አለኝ
*I feel an impulse to slap him. በጥፊ ፡ በለው ፡ በለው ፡ አለኝ

**impulsion**

1. ግፊት. This engine is moved by the impulsion of expanding steam. ይህ ፡ ሞተር ፡ በእንፋሎት ፡ ኀይል ፡ ግፊት ፡ ይንቀሳቀሳል
2. የገፋፋ. Duty was his main impulsion. ዋናው ፡ የገፋፋው ፡ ተግባሩ ፡ ነበር

**impulsive**

1. በስሜት ፡ የሚገፋፋ. The impulsive child gave all his money to the beggar. በስሜት ፡ የሚገፋፋው ፡ ልጅ ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ለለማኙ ፡ ሰጠ
2. ችኩል. He is impulsive and may say anything. ችኩል ፡ ስለሆነ ፡ አፉ ፡ ያመጣለትን ፡ ይናገር ፡ ይሆናል

**impunity, with ~** ሳይቀጣ ፡ ቀረ

Crooks robbed people with impunity during the war. ወንበዴዎቹ ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፡ ዘርፈው ፡ ሳይቀጡ ፡ ቀሩ
*You cannot ignore the rules of health with impunity. የጤናን ፡ ደንቦች ፡ ችላ ፡ ብሎ ፡ ከጉዳት ም ፡ አምልጦ ፡ አይቻልም

**impure**

1. የተበላሸ. Impure air is caused by smoke. የተበላሸ ፡ አየር ፡ የሚመጣው ፡ ከጢስ ፡ ነው
2. ቆሻሻ ፤ ያልተጣራ. They purified the impure water. ቆሻሻውን ፡ (ያልተጣራውን) ፡ ውኃ ፡ አጣሩት

**impute** የመጣ ፡ ነው ፡ አለ

They imputed the accident to speeding. አደጋው ፡ በፍጥነት ፡ ከመንዳት ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ አሉ

**in**

1. በ. Write in ink. በቀለም ፡ ጻፍ
Say it in English. በእንግሊዝኛ ፡ በለው
2. ወስጥ. They live in a big house. ትልቅ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ
3. በ - - - ውስጥ. I will be back in three days. በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ እመለሳለሁ
I can finish it in a week. ባንድ ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ልጨርሰው ፡ እችላለሁ
4. እ - - - ውስጥ. There is no table in my room. እክፍሌ ፡ ውስጥ ፡ ጠረጴዛ ፡ የለም
5. ከ. Cut the cake in half. ኬኩን ፡ ከሁለት ፡ ቍረጠው
Only one in a hundred can understand this mathematical problem. ከመቶ ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ይህንን ፡ የሒሳብ ፡ ፕሮብሌም ፡ ሊረዳ ፡ ይችላል
6. ወደ. Planes were introduced in Ethiopia in the early twenties. አውሮፕላን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገባው ፡ በሃያኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ነው
7. ለ. This parade was in honor of the returning heroes. ይህ ፡ ሰልፍ ፡ ክብር ፡ ለተመለሱት ፡ ጀግኖች ፡ ክብር ፡ የተደረገ ፡ ነው
8. (zero). My family is in the country. ቤተሰቦቼ ፡ አገር ፡ ቤት ፡ ናቸው
*You will always have a good friend in me. ምንግዜም ፡ ጥሩ ፡ ወዳጅህ ፡ ነኝ

**in and out**
He is always in and out of the hospital. እርሱ ፡ በየጊዜው ፡ ሆስፒታል ፡ እንደገባ ፡ ነው

**ins and outs** አንድ ፡ ባንድ
He knows the ins and outs of the business. የንግድ ፡ ሥራውን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ያውቀዋል

**in that**
*The income tax is harmful in that it discourages people from trying to earn more. ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ለማግኘት ፡ እንዳይጣጣሩ ፡ ስለሚያደርግ ፡ የገቢ ፡ ቀረጥ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ጐጂ ፡ ነው

**be in** ገባ
Is the train in yet? ባቡሩ ፡ ገብቷል ?
My husband won't be in until six o'clock. ባለቤቴ ፡ እስከሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ አይገባም
*She's not in to visitors. አሁን ፡ እንግዳ ፡ ለማነጋገር ፡ አትችልም

**be in for**
*I am afraid we are in for a storm. ኀይለኛ ፡ ዝናብ ፡ ሳይዘንብ ፡ አይቀርም

**be in for it** ወዮ(ለት)
When the boss finds out what we have done, we will be in for it. አለቃችን ፡ ያደረግነውን ፡ ያወቀ ፡ እንደሆን ፡ ወዮልን

**be in (with)** ስምም ፡ ናቸው
He is in with his boss, but he doubts that it will last. ካለቃው ፡ ጋር ፡ ስምም ፡ ናቸው ፣ ግን ፡ የሚዘልቅ ፡ መሆኑን ፡ ይጠራጠራል
[See also 'all']

**inability** ያለመቻል

His inability to speak English puts him at a disadvantage when he attends conferences. የርሱ ፡ እንግሊዝኛ ፡ መናገር ፡ ያለመቻል ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ሲገኝ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ይጥለዋል

**(be) inaccessible**

*This village is inaccessible by car. ይህ ፡ መንደር ፡ መኪና ፡ አያስገባም

**inaccuracy** (inaccuracies)

1. ጉድለት. This map has many inaccuracies. ይህ ፡ ካርታ ፡ ብዙ ፡ ጉድለቶች ፡ አሉት

2. አለመስተካከል. The inaccuracy of the time-table caused us to miss the train. የጊዜው ፡ መግለጫ ፡ አለመስተካከል ፡ ባቡሩ ፡ እንዲያመልጠን ፡ አደረገ

**(be) inaccurate** ትክክለኛ ፡ አይደለም
The statement was inaccurate. ንግግሩ ፡ ትክክለኛ ፡ አልነበረም

**inaction** ስንፍና
His inaction is his undoing. ለውድቀቱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ስንፍናው ፡ ነው

**inactive** ሙት
The inactive volcano now has a lake inside it. ሙቱ ፡ እሳተ ፡ ገሞራ ፡ አሁን ፡ ሐይቅ ፡ አለበት
*His inactive life is the cause of his boredom. ምንም ፡ የማይሠራ ፡ ስለሆነ ፡ ይሰለቸዋል

**be inactive** አልሠራም
The factory is inactive on Sundays. ፋብሪካው ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ አይሠራም

**make inactive** አላንቀሳቀሰው ፡ አለ
Sickness made the patient inactive. ሕመም ፡ በሽተኛውን ፡ አላንቀሳቀሰው ፡ አለ

**(be) inadequate** አይበቃም
The house is inadequate for such a large family. ቤቱ ፡ እንደዚህ ፡ ላለ ፡ ትልቅ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አይበቃም

**(be) inadmissible**
*Hearsay evidence is inadmissible in court because it cannot be substantiated. የሰሚ ፡ ሰሚ ፡ ምስክርነት ፡ ሊረጋገጥ ፡ ስለማይችል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አይቀበለውም

**inadvertent** ባለማወቅ ፡ የተደረገ
This was an inadvertent mistake. ይህ ፡ ባለማወቅ ፡ የተደረገ ፡ ስሕተት ፡ ነበር

**inadvertently** ተሳስቶ ፤ ሳያውቅ
When I inadvertently disclosed his secret, he gave me a sinister look. ተሳስቼ ፡ (ሳላውቅ) ፡ ምስጢሩን ፡ ባወጣ ፡ በክፉ ፡ ዓይን ፡ ተመለከተኝ

**(be) inadvisable** ተገቢ ፡ አይደለም
It is inadvisable to cross the river in the rainy season. በዝናብ ፡ ወራት ፡ ወንዙን ፡ መሻገር ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**inalienable** የማይገፈፍ
Freedom is an inalienable right of all citizens. ነጻነት ፡ የማይገፈፍ ፡ የማንም ፡ ዜጋ ፡ መብት ፡ ነው

**inane** ጅላጅል
He makes inane remarks. ጅላጅል ፡ አስተያየት ፡ ይሰጣል

**inanimate** ግዑዝ
Stones and minerals are inanimate. ድንጊያዎችና ፡ ማዕድኖች ፡ ግዑዝ ፡ ናቸው

**inanity** (= adj.) የጅል
The inanity of the remark angered the students. የሰጠው ፡ የጅል ፡ አስተያየት ፡ ተማሪዎቹን ፡ አበሳጫቸው

**(be) inapplicable** አግባብነት ፡ የለውም
This solution is inapplicable to the problem. ይህ ፡ መፍትሔ ፡ ለዚህ ፡ ችግር ፡ አግባብነት ፡ የለውም

**inappropriate** የማይገባ
He came to church in inappropriate attire. የማይገባ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጣ

**be inappropriate** አይሆንም
A party dress is inappropriate for a hike. የግብዣ ፡ ልብስ ፡ ለሽርሽር ፡ አይሆንም

**inapt** ተገቢ ፡ ያልሆነ
His inapt remark aroused everyone's anger. ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ አስተያየቱ ፡ ሁሉንም ፡ ሰው ፡ አስቆጣ

**inarticulate**
1. የማይለይ. I heard an inarticulate groan in the darkness. በጨለማው ፡ ውስጥ ፡ የማይለይ ፡ ማቃሰት ፡ ሰማሁ
2. የማይዋጣ(ለት). He is a brilliant writer but an inarticulate speaker. ግሩም ፡ ጸሐፊ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የማይዋጣለት ፡ ተናጋሪ ፡ ነው

**be inarticulate** አይናገርም
Cats and dogs are inarticulate. ድመቶችና ፡ ውሾች ፡ አይናገሩም

**inasmuch as, ~ as he is** እንደመሆኑ ፡ መጠን
Inasmuch as he is a member of the board, he knows the plans before anyone else does. የቦርዱ ፡ አባል ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ከማንም ፡ በፊት ፡ እቅዱን ፡ ያውቃል

**inattentive** የማይከታተል
The teacher punished the inattentive student. አስተማሪው ፡ የማይከታተለውን ፡ ተማሪ ፡ ቀጣ

**(be) inaudible** ሊሰማው ፡ አትችልም
The noise of the machinery is inaudible outside the factory. ከፋብሪካው ፡ ውጭ ፡ የመኪናውን ፡ ድምፅ ፡ ልትሰማው ፡ አትችልም

**inaugural** የምረቃ
The President gave an inaugural address when

he took office. ፕሬዚዳንቱ ፡ ሥልጣኑን ፡ ሲረከብ ፡ የምረቃ ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**inaugurate**
1. መረቀ. The President inaugurated the new hospital. ፕሬዚዳንቱ ፡ አዲሱን ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ መረቀ
2. ከፈተ. The invention of the airplane inaugurated a new era in transportation. የአውሮፕላን ፡ መፈልሰፍ ፡ በመጓጓዣ ፡ ረገድ ፡ አዲስ ፡ ምዕራፍ ፡ ከፈተ

**inauguration**
1. የምረቃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት. The inauguration of the new hospital took place yesterday. ያዲሱ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ የምረቃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ትናንትና ፡ ተደረገ
2. ቃለ ፡ ኪዳን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት. The Presidential inauguration took place in the White House. የፕሬዚዳንቱ ፡ ቃለ ፡ ኪዳን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በዋይት ፡ ሃውስ ፡ ውስጥ ፡ ተደረገ

**inauspicious** ገደ ፡ ቢስ
The inauspicious beginning of the crusade was followed by disaster after disaster. ገደ ፡ ቢሱ ፡ የመስቀል ፡ ጦርነት ፡ አጀማመር ፡ መቅሠፍት ፡ እየተከታተለ ፡ ደረሰበት

**inborn** የተፈጥሮ
He has an inborn talent for music. ለሙዚቃ ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታ ፡ አለው

**(be) inbred** እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተጋቡ
There are many tribes in which the families are inbred. ዘመዳሞች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚጋቡባቸው ፡ ብዙ ፡ ነገዶች ፡ አሉ

**inbreeding** የዘመዳሞች ፡ መጋባት
Inbreeding causes certain diseases. የዘመዳሞች ፡ መጋባት ፡ አንዳንድ ፡ በሽታዎች ፡ ያስከትላል

**incalculable** መጠን ፡ የሌለው
A flood in the valley caused incalculable losses. በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ የደረሰው ፡ የውኃ ፡ መጥለቅለቅ ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ ጉዳት ፡ አደረሰ

**be incalculable** ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የለውም
The grains of sand on the beach are incalculable. የባሕር ፡ ዳርቻ ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ አሸዋ ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የለውም

**incantation** ድግምት
The sorcerer recited an incantation in Geez. አስማተኛው ፡ በግዕዝ ፡ ድግምት ፡ ደገመ

**incapable** የሥራ ፡ ችሎታ ፡ የሌለው
An employer will not hire incapable workers. አሠሪ ፡ የሥራ ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸውን ፡ ሠራተኞች ፡ አይቀጥርም

**be incapable of**
1. አይገባውም. +He is incapable of learning. ትምህርት ፡ አይገባውም
2. አይሆንለትም. +He is incapable of telling a lie. ውሸት ፡ መናገር ፡ አይሆንለትም
3. አይችልም. His manner of speaking is incapable of improvement. አነጋገሩ ፡ ሊሻሻል ፡ አይችልም

**incapacitate** ከለከለ
His poor health incapacitated him from work. የጤንነቱ ፡ መታወክ ፡ እንዳይሠራ ፡ ከለከለው

**be incapacitated** ስንኩል ፡ ሆኖ ፡ ቀረ
He was incapacitated by a broken leg. እግሩ ፡ በመሰበሩ ፡ ስንኩል ፡ ሆኖ ፡ ቀረ

**incarcerate** አሰረ
They incarcerated the prisoners in small rooms. እስረኞቹን ፡ ትናንሽ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ አሰሯቸው

**incarnate**
1. መሰለ. Medieval belief incarnated the devil in many animal forms. የመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ እምነት ፡ ሰይጣንን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ እንስሳ ፡ መልክ ፡ ይመስል ፡ ነበር
2. አስመሰከረ. He incarnates the courage of the nation. የሃገሪቷን ፡ ጀግንነት ፡ ያስመሰክራል

**Incarnation** ሥጋ ፡ መልበስ
The Incarnation of Christ is a church holiday. የክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ መልበስ ፡ የሃይማኖት ፡ በዓል ፡ ነው

**be the incarnation of** ተመሰለ
He is the incarnation of honesty. በሐቅ ፡ ይመሰላል

**incendiary**
1. የእሳት. The town was set on fire with incendiary bombs. ከተማይቱ ፡ በእሳት ፡ ቦምብ ፡ በመደብደቧ ፡ ተቃጠለች
2. ሕዝብ ፡ የሚያነሣሣ. The editor wrote an incendiary article. የጋዜጣው ፡ አዘጋጅ ፡ ሕዝብ ፡ የሚያነሣሣ ፡ ጽሑፍ ፡ ጻፈ

**incense** (v.) አበሳጨ
Cruelty incenses kind people. ጭካኔ ፡ ደግ ፡ ሰዎችን ፡ ያበሳጫል

**be incensed** ጦፈ
He was incensed to find that his rival had taken away his place from him. ተቀናቃኙ ፡ ቦታውን ፡ እንደወሰደበት ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ጦፈ

**incense** (n.) ዕጣን
There was a faint smell of incense in the church. በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ ሳመል ፡ የዕጣን ፡ ሽታ ፡ ነበር

**incentive**
1. የሚገፋፋ ፡ ነገር. He does not have much incentive to work hard. ጠንክሮ ፡ እንዲሠራ ፡ የሚገፋፋው ፡ ነገር ፡ እምብዛም ፡ ነው
2. ማበረታቻ. The company gives bonuses as incentives. ኩባንያው ፡ ለማበረታቻ ፡ ብሎ ፡ ጉርሻ ፡ ይሰጣል

**inception** መጀመሪያ
The movement was successful from its inception. እንቅስቃሴው ፡ ከመጀመሪያው ፡ አንሥቶ ፡ የተሳካ ፡ ነበር

**incertitude** እርግጠኛ ፡ አለመሆን
The incertitude of a job caused him to avoid marriage. ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ እርግጠኛ ፡ አለመሆኑ ፡ ከጋብቻ ፡ እንዲሸሽ ፡ አደረገው

**incessant** (= adv.) ሳያቋርጥ
A week of incessant rain prevented us from traveling. ሳያቋርጥ ፡ ሳምንት ፡ሙሉ ፡ የዘነበው ፡ ዝናብ ፡ ጉዟችንን ፡ አገደ

**incessantly** ያለማቋረጥ
They chatter incessantly. ያለማቋረጥ ፡ ይለፈልፋሉ

**incest** በሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ መሀከል ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት
Incest is forbidden by church law. በሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ መሀከል ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ የተከለከለ ፡ ነው

**inch** ኢንች
The width of my table is thirty inches. የጠረጴዛዬ ፡ ስፋት ፡ ሠላሳ ፡ ኢንች ፡ ነው

**inch by inch** ቀስ ፡ በቀስ
I climbed the mountain inch by inch. ተራራውን ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ወጣሁት

**by inches** ለትንሽ
The car missed me by inches. መኪናው ፡ ለትንሽ ፡ ሳተኝ

**every inch** ሁለመናው
She is every inch a lady. ሁለመናዋ ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ነው

**every inch of** ስንዝር ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፤ እንዲት ፡ ቅንጣት ፡ እንኳ
Every inch of ground was stubbornly defended. ስንዝር ፡ መሬት ፡ እንኳ ፡ ሳትቀር ፡ አጥብቀው ፡ ተከላከሉ
The soldiers disputed every inch of ground when the enemy attacked. ወታደሮቹ ፡ ጠላት ፡ በገጠማቸው ፡ ጊዜ ፡ እንዲት ፡ ቅንጣት ፡ መሬት ፡ እንኳ ፡ አንለቅ ፡ አሉ

**within an inch of**
*He came within an inch of getting killed in the crash. በግጭቱ ፡ ምክንያት ፡ ከሞት ፡ አፋፍ ፡ ዳነ

**incidence**
*There is a high incidence of crime after wars. ከጦርነት ፡ በኋላ ፡ ወንጀል ፡ ይበረክታል

**incident**
1. ድርጊት. Who is responsible for the incident? ለዚህ ፡ ድርጊት ፡ ኀላፊው ፡ ማን ፡ ነው ?
2. አድራጎት. This incident can create a global conflict. ይህ ፡ አድራጎት ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ጠብ ፡ ሊፈጥር ፡ ይችላል
3. ችግር. Our trip passed without incident. ጉዟችን ፡ ያለ ፡ ምንም ፡ ችግር ፡ ተፈጸመ
4. ግጭት. The border incident precipitated a crisis in international relations. የድንበሩ ፡ ግጭት ፡ በዓለም ፡ አቀፍ ፡ ግንኙነት ፡ ላይ ፡ ጠንቅ ፡ አስከተለ
5. አጋጣሚ. The incident sidetracked him from pursuing the main matter. አጋጣሚው ፡ ዋናውን ፡ ነገር ፡ እንዳይከታተል ፡ አደረገው

**be incident (to)** የማይቀር ፡ ነው
Dangers are incident to a soldier's life. በወታደርነት ፡ ተግባር ፡ ውስጥ ፡ አደጋ ፡ የማይቀር ፡ ነው

**incidental(s)** ጥቃቅን ፡ ጉዳዮች
On our trip we spent $50 for meals and rooms, and $2.00 for incidentals. በጉዟችን ፡ ላይ ፡ ለምግብና ፡ ለመኝታ ፡ አምሳ ፡ ብር ፤ ለጥቃቅን ፡ ጉዳዮች ፡ ደግሞ ፡ ሁለት ፡ ብር ፡ አወጣን

**incidental** (adj.)
1. ልዩ. The government will pay your incidental expenses also. መንግሥት ፡ ልዩ ፡ ወጪህንም ፡ ይከፍልልሃል
2. ቀለል ፡ ያለ. He made an incidental remark about the director's speech. ዲሬክተሩ ፡ ስላደረገው ፡ ንግግር ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ ጣል ፡ አደረገ
3. (= adv.) እንዳጋጣሚ. The incidental meeting with an old friend made me very happy. የድሮ ፡ ጓደኛዬን ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ማግኘቴ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለኝ

**be incidental to** የማይቀር ፡ ነው
Discomfort is incidental to travel by mule. በበቅሎ ፡ ስትጓዝ ፡ መጒሳቈል ፡ የማይቀር ፡ ነው

**incidentally**
1. እንዳጋጣሚ. He just said it incidentally. ነገሩን ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ተናገረው
2. በነገራችን ፡ ላይ. Incidentally, I saw your friend Smith the other day. በነገራችን ፡ ላይ ፤ ጓደኛህን ፡ ስሚዝን ፡ በቀደም ፡ አየሁት

**incinerate** አቃጠለ
In our city we incinerate garbage. በከተማችን ፡ ቆሻሻ ፡ እናቃጥላለን

**incipient**
*The medicine stopped the boy's incipient cold. መድኃኒቱ ፡ ልጁ ፡ ጉንፋን ፡ ገና ፡ እንደያዘው ፡ አቆመለት

**incise** ቀረጸ
He incised his name in the bark of the tree. ስሙን ፡ በዛፉ ፡ ቅርፊት ፡ ላይ ፡ ቀረጸ

**incision** ቀዶ ፡ ጥገና
The incision healed rapidly. ቀዶ ፡ ጥገናው ፡ ቶሎ ፡ ጠገገ

**make an incision** በጥቶ ፡ አወጣ
The doctor made an incision to take out the splinters in my finger. ዶክተሩ ፡ ጣቴ ፡ ውስጥ ፡ የገባውን ፡ ስንጥር ፡ በጥቶ ፡ አወጣልኝ

**incisive** ጥልቅ
The committee made an incisive study of water pollution. ደርጉ ፡ ስለ ፡ ውኃ ፡ መበከል ፡ ጥልቅ ፡ ጥናት ፡ አደረገ

**incisor** የፊት ፡ ጥርስ
The incisors serve to bite off meat. የፊት ፡ ጥርስ ፡ ሥጋ ፡ ለመንጨት ፡ ይጠቅማል

**incite** አነሣሣ
The soldier was shot for inciting his companions to riot. ወታደሩ ፡ ጓደኞቹን ፡ እንዲያምፁ ፡ ስላነሣሣ ፡ በጥይት ፡ ተደበደበ

**incitement, be an ~** ገፋፋ
Selfishness is an incitement to crime. ራሱን ፡ መውደድ ፡ ወንጀልን ፡ ወደ ፡ መፈጸም ፡ ይገፋፋል

**inclemency** መጥፎነት
The inclemency of the weather kept us at home. ያየሩ ፡ መጥፎነት ፡ እቤት ፡ አዋለን

**inclement**
1. ጨቋኝ. An inclement ruler contributes to the backwardness of a country. ጨቋኝ ፡ ገዢ ፡ አገርን ፡ ወደኋላ ፡ ያስቀራል
2. መጥፎ. We had inclement weather throughout our vacation. በዕረፍት ፡ ጊዜያችን ፡ ወቅት ፡ ሁሉ ፡ አየሩ ፡ መጥፎ ፡ ነበር

**inclination**
1. ዝንባሌ. He showed no inclination to leave. ለመሄድ ፡ ምንም ፡ ዝንባሌ ፡ አላሳየም
2. ደፋ ፡ ቀና ፡ ማድረግ. He showed his agreement by an inclination of his head. ራሱን ፡ ደፋ ፡ ቀና ፡ በማድረግ ፡ መስማማቱን ፡ ገለጸ
*The inclination of the slope is ten degrees. ቁልቁለቱ ፡ ዐሥር ፡ ዲግሪ ፡ ያጋደለ ፡ ነው

**incline** (vt.)
1. አዘነበለ. The carpenter inclined the post to the right. አናጢው ፡ ዕንጨቱን ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ አዘነበለው
2. አደረገ. Your manner inclines me to believe what you say. ጠባይህ ፡ አንተ ፡ የምትለውን ፡ እንዳምን ፡ ያደርገኛል

**incline** (vi.) አጋደለ
The post inclines slightly to the left. ዕንጨቱ ፡ በትንሹ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ አጋድሏል

**be inclined**
1. ዝንባሌ ፡ አለው ፤ ሻ. Pacific people are not inclined to make war. ሰላምን ፡ የሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ የጦርነት ፡ ዝንባሌ ፡ የላቸውም ፡ (or ጦርነት ፡ ለማድረግ ፡ አይሹም)
2. ወደ - - - ደረሰ. I am inclined to believe him. እሱን ፡ ወደ ፡ ማመኑ ፡ ደርሻለሁ
*He's inclined to be lazy. ስንፍና ፡ ያጠቃዋል

**incline the head** ጐንበስ ፡ አለ
She inclined her head in prayer. ለጸሎት ፡ ጐንበስ ፡ አለች

**include**
1. ጨመረ. Your duties will include putting the children to bed. ሥራህ ፡ ልጆቹን ፡ ማስተኛትንም ፡ ይጨምራል
The dictionary does not include medical expressions. መዝገበ ፡ ቃላቱ ፡ የሕክምና ፡ ቃሎችን ፡ አይጨምርም
2. አጠቃለለ. His background includes courses in French and German. ትምህርቱ ፡ ፈረንሳይኛንና ፡ ጀርመንኛን ፡ ያጠቃልላል
3. ጨምሮ ፡ ያዘ. The package includes a book of instructions. ጥቅሉ ፡ መምሪያ ፡ መጽሐፍ ፡ ጨምሮ ፡ ይዟል

**included** (adj.) አብሮ ፡ የተያያዘ
The included summary was one page long. አብሮ ፡ የተያያዘው ፡ ባጭሩ ፡ የተውጣጣ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ ነበር

**service included** ሁሉንም ፡ ችሎ
The room is five dollars, service included. ሁሉንም ፡ ችሎ ፡ የክፍሉ ፡ ኪራይ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ነው

**including** ከ - - - ጋር ፤ ከነ
The record player, including three records, costs $100. ሸክላ ፡ መጫወቻው ፡ ከሦስት ፡ ሸክላ ፡ ጋር ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ያወጣል
He earns thirty dollars, including tips. ከጉርሻው ፡ ደሞዙ ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ ነው

**inclusive** አጠቃላይ
Make an inclusive list of your expenses! የወጪህን ፡ አጠቃላይ ፡ ዝርዝር ፡ አዘጋጅ
*I will be in Harar from June 1st to June 10th inclusive. ከሰኔ ፡ አንድ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሰኔ ፡ ዐሥር ፡ ድረስ ፡ ሐረር ፡ እቆያለሁ

**incognito** ማንነቱን ፡ ሳያሳውቅ
The prince traveled incognito. ልዑሉ ፡ ማንነቱን ፡ ሳያሳውቅ ፡ ተጓዘ

**incoherent** ተከታታይነት ፡ የሌለው
He told me an incoherent story. ተከታታይነት ፡ የሌለው ፡ ታሪክ ፡ ነገረኝ

**be incoherent**
He was so drunk as to be incoherent. ከመስከሩ ፡ የተነሣ ፡ የሚናገረው ፡ ሁሉ ፡ መላ ፡ ቅጥ ፡ አልነበረውም

**incombustible** የማይቃጠል
Incombustible materials are used in the interior of airplanes. የአውሮፕላን ፡ የውስጥ ፡ አካል ፡ የሚሠራው ፡ ከማይቃጠል ፡ ነገር ፡ ነው

**income** ገቢ
How much of an income does he have? ገቢው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?

**income tax** በገቢ ፡ ላይ ፡ የተጣለ ፡ ቀረጥ
The nobility opposed the income tax. መኳንንቶች ፡ በገቢ ፡ ላይ ፡ የተጣለውን ፡ ቀረጥ ፡ ተቃወሙ

**income tax return**
He made out his income tax return. የገቢ ፡ ቀረጥ ፡ ፎርም ፡ ሞላ

**incoming** አዲስ
The incoming mayor will appoint new department heads. አዲሱ ፡ ከንቲባ ፡ አዲስ ፡ የክፍል ፡ ኀላፊዎች ፡ ይሾማሉ
The incoming tenant will pay a higher rent. አዲሱ ፡ ተከራይ ፡ ተጨማሪ ፡ ኪራይ ፡ ይከፍላል

**(be) incommensurable** የሚወዳደሩበት ፡ መደብ ፡ የላቸውም
Love and money are incommensurable. ፍቅርና ፡ ገንዘብ ፡ የሚወዳደሩበት ፡ መደብ ፡ የላቸውም

**(be) incommensurate** ተመጣጣኝ ፡ አይደለም
His strength is incommensurate to his duties. ኀይሉ ፡ ከሚሠራው ፡ ጋር ፡ ተመጣጣኝ ፡ አይደለም

**incommunicado** ከማንም ፡ ጋር ፡ በማይገናኝበት ፡ ሁኔታ
The prisoner was being held incommunicado. እስረኛው ፡ ከማንም ፡ ጋር ፡ በማይገናኝበት ፡ ሁኔታ ፡ ታስሯል

**incomparable** ወደር ፡ የሌለው
Her incomparable beauty was admired by all. ወደር ፡ የሌለው ፡ ቁንጅናዋን ፡ ሁሉም ፡ አደነቀው

**(be) incompatible**
1. ተስማሚ ፡ አይደለም. Excessive drinking is incompatible with good health. ከመጠን ፡ በላይ ፡ መጠጣት ፡ ለጤንነት ፡ ተስማሚ ፡ አይደለም
2. ተቃረነ. Logic will show that the two ideas are incompatible. ትክክለኛ ፡ አስተሳሰብ ፡ ሁለቱ ፡ ሐሳቦች ፡ የሚቃረኑ ፡ መሆናቸውን ፡ ያሳያል

**incompetent** ችሎታ ፡ የሌለው
His predecessor was an incompetent man. ከሱ ፡ በፊት ፡ በቦታው ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ነበር

**be incompetent** ችሎታ ፡ የለውም
He is incompetent to teach science. ሳይንስ ፡ ለማስተማር ፡ ችሎታ ፡ የለውም

**(be) incomplete**
1. የተሟላ ፡ አይደለም. His training is incomplete; he needs to go to school much longer. የተሰጠው ፡ ትምህርት ፡ የተሟላ ፡ አይደለም ፤ ገና ፡ አድርጎ ፡ መማር ፡ ያስፈልገዋል
2. አላለቀም. This job is still incomplete. ይህ ፡ ሥራ ፡ ገና ፡ አላለቀም

**(be) incomprehensible** አይገባም
Your Amharic is incomprehensible. አማርኛህ ፡ አይገባም

**inconceivable** የማይታመን
Light travels at an inconceivable speed. ብርሃን ፡ በማይታመን ፡ ፍጥነት ፡ ይበራል

**be inconceivable** ሕልም ፡ ነው
It is inconceivable for her not to come to the party. ከግብዣው ፡ ትቀራለች ፡ ማለት ፡ ሕልም ፡ ነው

**(be) inconclusive**
*The results of the study were inconclusive.

የጥናቱ ፡ ውጤት ፡ ምንም ፡ ውሳኔ ፡ ሊሰጥ ፡ የሚ
ችል ፡ አልነበረም

**(be) incongruous** አይስማማም
Heavy shoes would be incongruous with a party dress. የሥራ ፡ ጫማ ፡ ከግብዣ ፡ ልብስ ፡ ጋ
ር ፡ አይስማማም

**(be) inconsiderate** አለማየቱ ፡ ነው
It is inconsiderate of him to keep us waiting so long. ይህን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ማስጠበቁ ፡ አዙሮ ፡
አለማየቱ ፡ ነው

**inconsistency** ሥርዓትን ፡ አለመከተል
The inconsistency of his work is puzzling. የሥራው ፡ ሥርዓትን ፡ አለመከተል ፡ ያስገርማል

**inconsistent**
1. ተለዋዋጭ. An inconsistent person is always changing opinions. ተለዋዋጭ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
ጊዜ ፡ ሐሳቡን ፡ ይቀያይራል
2. የሚፃረር ፤ የሚጋጭ. The defendant presented inconsistent arguments. ተከሳሹ ፡ የሚፃረሩ ፡ (የሚ
ጋጩ) ፡ ክርክሮች ፡ አቀረበ

**(be) inconsolable** በጣም ፡ ስላዘነ ፡ ሊጽናና ፡
አልቻለም
He was inconsolable over his friend's death. በጓደኛው ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ በጣም ፡ ስላዘነ ፡
ሊጽናና ፡ አልቻለም

**inconspicuous**
1. እንግሌ ፡ የማያስኝ. He played an inconspicuous part in the government. በመንግሥቱ ፡ ው
ስጥ ፡ እንግሌ ፡ የማያስኝ ፡ ሥራ ፡ ነበረው
2. ዓይን ፡ የማይማርክ. The woman wore an inconspicuous hat. ሴትዮዋ ፡ ዓይን ፡ የማይማር
ክ ፡ ባርኔጣ ፡ አድርጋለች
3. የማይታይበት ፡ ቦታ ፡ ያዘ. The mayor's wife tried to be inconspicuous. የከንቲባው ፡ ሚስት ፡
የማትታይበት ፡ ቦታ ፡ ለመያዝ ፡ ሞከረች

**inconvenience** (v.) አስቸገረ
I do not want to inconvenience you. ላስቸግርህ ፡
አልፈልግም

**inconvenience** (n.) ችግር
Getting up at 5:00 A.M. is a great inconvenience. ከሌሊቱ ፡ ባሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ መ
ነሣት ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡ ነው

**inconvenient** የማይመች
This is an inconvenient location for a school. ይህ ፡ ለትምህርት ፡ ቤት ፡ የማይመች ፡ ስፍራ ፡ ነው

**incorporate**
1. አስገባ. We will incorporate your suggestion in the new plan. ሐሳብህን ፡ ባዲሱ ፡ እቅድ ፡
ውስጥ ፡ እናስገባዋለን
2. የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ አደረገ. When Mr. Parker's business became large, he incorporated it. የሚስተር ፡ ፓርከር ፡ ንግድ ፡ እየተስፋፋ ፡ ሲሄድ ፡
የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ አደረገው
3. ጨምሮ ፡ ያዘ. His book incorporates his earlier essay. መጽሐፉ ፡ የፊተኛው ፡ ድርሰቱን ፡ ጨም
ሮ ፡ ይዟል

**be incorporated into one** ተዋሐደ
The two churches have been incorporated into one. ሁለቱ ፡ የሃይማኖት ፡ ወገኖች ፡ ተዋ
ሕደዋል

**incorrect**
1. ትክክለኛ ፡ ያልሆነ. The witness gave incorrect information about the accident. ምስክሩ ፡
ስለ ፡ አደጋው ፡ ትክክለኛ ፡ ያልሆነ ፡ መረጃ ፡ ሰጠ
2. መጥፎ. He was expelled from school because of his incorrect conduct. በመጥፎ ፡ ጠባዩ ፡ ከት
ምህርት ፡ ቤት ፡ ተባረረ

**be incorrect**
1. ስሕተት ፡ ነው. This answer is incorrect. ይህ ፡
መልስ ፡ ስሕተት ፡ ነው
2. ልክ ፡ አልሆነም. We have to redo his work as it was incorrect. ሥራው ፡ ልክ ፡ ስላልሆነ ፡ እ
ንደገና ፡ መሥራት ፡ አለብን

**incorrectly** በስሕተት
You have applied this rule incorrectly. ይህን ፡
ደንብ ፡ በስሕተት ፡ ተጠቅመህበታል

**incorrigible** የማይታረም
He has an incorrigible habit. የማይታረም ፡ ጠባ
ይ ፡ አለው

**incorruptible** የማይታለል
The incorruptible witness refused the bribe. የማይታለለው ፡ ምስክር ፡ ጉቦውን ፡ አልቀበልም ፡ አለ

**increase** (vt.)
1. ጨመረ. The driver increased the speed of the car. ነጂው ፡ የመኪናውን ፡ ፍጥነት ፡ ጨመረ
You have to increase your output. የሥራ ፡ ፍሬ
ህን ፡ መጨመር ፡ አለብህ
2. ከፍ ፡ አደረገ. Modern methods have increased agricultural productivity. ዘመናዊ ፡ ዘዴ
ዎች ፡ የእርሻን ፡ ሰብል ፡ ከፍ ፡ አድርገውታል
He increased his wealth by improper means. ሀብቱን ፡ በማይገባ ፡ መንገድ ፡ ከፍ ፡ አደረገ

**increase** (vi.)
1. ጨመረ. The population increased tremendously. የሕዝቡ ፡ ቁጥር ፡ ያለ ፡ ቅጥ ፡ ጨመረ
His weight has increased by ten pounds. ሚዛኑ ፡ በዐሥር ፡ ነጥር ፡ ጨምሯል
2. አደገ. The school was increased by the accession of ten new students. ዐሥር ፡ አዲስ ፡ ተማሪዎች ፡ በመጨመራቸው ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አደገ
[See also 'consistency']

**increase** (n.) መጨመር
Statistics show a considerable increase in population. ስታቲስቲኩ ፡ የሕዝቡ ፡ ቁጥር ፡ በጣም ፡ መጨመሩን ፡ ያመለክታል

**be on the increase**
1. በመጨመር ፡ ላይ ፡ ነው. The birthrate is on the increase. የሚወለዱት ፡ ሕፃናት ፡ ቁጥር ፡ በመጨመር ፡ ላይ ፡ ነው
2. እየበዛ ፡ ሄደ. He observed that crime was on the increase. ወንጀል ፡ እየበዛ ፡ መሄዱን ፡ ጠቀሰ

**increasingly** ይበልጥ
As we traveled south, the weather became increasingly warmer. ወደ ፡ ደቡብ ፡ ስንጓዝ ፡ ይበልጥ ፡ እየሞቀ ፡ ሄደ

**incredible** የማይመስል
No one believed his incredible story. የማይመስል ፡ ታሪኩን ፡ ማንም ፡ አላመነውም

**be incredible**
Your story is incredible. የነገርከን ፡ ታሪክ ፡ ታምር ፡ ነው (or, ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፤ or, የሚገርም ፡ ነው)

**(be) incredulous about** ተጠራጠረ
People nowadays are incredulous about sorcerers. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡ የአስማተኞችን ፡ መኖር ፡ ይጠራጠራሉ

**increment** ጭማሪ
He receives an increment of $50 a year. በያመቱ ፡ ያምሳ ፡ ብር ፡ ጭማሪ ፡ ያገኛል

**incriminate**
1. ጥፋተኛነቱን ፡ አመለከተ. His fingerprints on the window incriminate him. በመስኮቱ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የሱ ፡ አሻራ ፡ ጥፋተኛነቱን ፡ ያመለክታል
2. አወጣ. In his confession the thief incriminated two others. በሰጠው ፡ የእምነት ፡ ቃል ፡ ሌባው ፡ ሌላ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ አወጣ

**(be) incrusted (with)**
1. ነበረ(በት). The bracelet was incrusted with diamonds. አምባሩ ፡ ያልማዝ ፡ ፈርጦች ፡ ነበሩበት
2. ተለወሰ. His shoes were incrusted with mud. የሱ ፡ ጫማ ፡ በጭቃ ፡ ተለውሷል

**incubate** ተፈለፈለ
The eggs incubate in a warm, dark room. እንቁላሎቹ ፡ ሞቃት ፡ በሆነ ፡ ጨለማ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ይፈለፈላሉ

**inculcate** አሳደረ
The mother tried to inculcate honesty in her children. እናትዮዋ ፡ በልጆቿ ፡ ላይ ፡ ሐቀኝነትን ፡ ለማሳደር ፡ ሞከረች

**incumbent**
1. ሥልጣኑን ፡ ይዞ ፡ የነበረ. The incumbent mayor was defeated in the election. ሥልጣኑን ፡ ይዞ ፡ የነበረው ፡ ከንቲባ ፡ በምርጫው ፡ ተሸነፈ
2. የቀድሞ. He acceded to the chairmanship after the incumbent died. የቀድሞው ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ሲሞት ፡ እሱ ፡ ሊቀ ፡ መንበርነቱን ፡ ያዘ

**be incumbent on one** ግዴታው ፡ ነው
It is incumbent on all students to register. ተማሪዎች ፡ ሁሉ ፡ መመዝገብ ፡ ግዴታቸው ፡ ነው

**be incumbent upon one** ተግባሩ ፡ ነው
It is incumbent upon you to warn him against excessive smoking. ከመጠን ፡ በላይ ፡ እንዳያጨስ ፡ ማስጠንቀቅ ፡ ተግባርህ ፡ ነው

**incur** (incurred)
1. (ውስጥ) ፡ ገባ. He incurred debts because of illness. ስለታመመ ፡ ዕዳ ፡ ውስጥ ፡ ገባ
2. በራሱ ፡ ላይ ፡ አመጣ. The hunter incurred great danger in killing the tiger. ነብሩን ፡ በመግደሉ ፡ አዳኙ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ ሊያመጣ ፡ ነበር

**incurable** የማይፈወስ ፤ የማይድን ፤ የማይሽር
He had an incurable disease. የማይፈወስ ፡ (የማይድን ፤ የማይሽር) ፡ በሽታ ፡ ነበረበት

**incursion**
1. ወረራ. Their incursion on our territory lasted only a few hours. በግዛታችን ፡ ላይ ፡ ያደረጉት ፡ ወረራ ፡ የቆየው ፡ ለጥቂት ፡ ሰዓቶች ፡ ብቻ ፡ ነበር
2. ወደ ፡ ውጭ ፡ መግፋት. The incursion of sea water damaged the crops. የባሕሩ ፡ ውኃ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ መግፋት ፡ እህል ፡ አበላሸ

**make an incursion** በዘበዘ
The pirates made incursions along the coast. የባሕር ፡ ወንበዴዎች ፡ ጠረፉን ፡ በዘበዙት

**(be) indebted to**
1. ባለ ፡ ውለታው ፡ ነው. We are indebted to

you for your help. ስለ ፡ አደረግህልን ፡ እርዳታ ፡ ባለ ፡ ውለታህ ፡ ነን
2. የ - - - ገንዘብ ፡ ነበረበት. He was indebted to his friend for a large sum. የጓደኛው ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ነበረበት

**indecent** የብልግና
Her behavior was indecent. ጠባይዋ ፡ የብ ልግና ፡ ነበር
The student used indecent language and was expelled from school. ተማሪው ፡ የብልግና ፡ ቃ ል ፡ ስለተናገረ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ተባረረ

**indecent behavior** ብልግና
Because he took off his clothes in public, the police arrested him for indecent behavior. ልብሱን ፡ ባደባባይ ፡ ስላወለቀ ፡ ፖሊሱ ፡ ስ ለ ፡ ብልግናው ፡ ያዘው

**indecision** በሐሳቡ ፡ ያልቈረጠ ፡ መሆን
His halting speech manifests his indecision. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ንግግሩን ፡ ማቋረጡ ፡ በሐሳቡ ፡ ያልቈረጠ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳል

**indecisive** የማያጠግብ
The defendant gave indecisive evidence. ተከሳሹ ፡ የማያጠግብ ፡ ማስረጃ ፡ አቀረበ

**be indecisive** ውጤቱ ፡ አልለየም
The battle was severe but indecisive. ጦርነቱ ፡ ከ ባድ ፡ ቢሆንም ፡ ውጤቱ ፡ አልለየም

**indecorous** ተገቢ ፡ ያልሆነ
No one likes her because of her indecorous behavior. ጠባይዋ ፡ ተገቢ ፡ ስላልሆነ ፡ ማንም ፡ አይወዳትም

**indeed**
1. በእውነቱ. That's very good indeed! በእውነቱ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነው
2. በእርግጥ. Indeed, he is one of the nicest people I know. ከማውቃቸው ፡ ጥሩ ፡ ሰዎች ፡ በእርግጥ ፡ እሱ ፡ አንዱ ፡ ነው

**yes, indeed!** እንዴታ
Are you pleased with your son's success? Yes, indeed! ልጅህ ፡ ስለተቃናለት ፡ ተደስተሃል ? እንዴታ

**indefatigable** የማይታክት
My brother is an indefatigable worker. ወንድ ሜ ፡ የማይታክት ፡ ሠራተኛ ፡ ነው

**indefensible**
1. ተከላካይ ፡ ሊደረግለት ፡ የማይቻል. The indefensible bridge was soon captured by the enemy. ተከላካይ ፡ ሊደረግለት ፡ የማይቻለው ፡ ድልድይ ፡ በጠላት ፡ ተያዘ
2. በተገቢ ፡ ማስረጃ ፡ የማይደገፍ. Your point of view is indefensible. አስተያየትህ ፡ በተገቢ ፡ ማ ስረጃ ፡ የማይደገፍ ፡ ነው

**indefinite**
1. ግልጽ ፡ ያልሆነ. He has indefinite views on the question. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ግልጽ ፡ ያልሆነ ፡ አስ ተያየት ፡ አለው
2. ያልተወሰነ. We have an indefinite time to finish this work. ይህንን ፡ ሥራ ፡ ለመጨረስ ፡ ያልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ አለን

**indefinite article** ያልተወሰነ ፡ መስተአምር
The indefinite article is normally not expressed in Amharic. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ባማርኛ ፡ ያ ልተወሰነ ፡ መስተአምር ፡ አይገለጽም

**indelible** የማይለቅ
Indelible ink was put on the voters' fingers to prevent fraud. ማጭበርበርን ፡ ለማስቀረት ፡ በመ ራጮቹ ፡ ጣት ፡ ላይ ፡ የማይለቅ ፡ ቀለም ፡ ተደ ረገ

**indemnify** (indemnified) ገንዘብ ፡ ሰጠ
The government indemnified the farmer for the loss of the crops. የገበሬው ፡ ሰብል ፡ ስለተበላ ሸ ፡ መንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ሰጠው

**indemnity** (የጦር) ፡ ካሳ
The Italians paid an indemnity for the destruction they caused in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ስላደረሱት ፡ ጥፋት ፡ ኢጣልያኖች ፡ የጦር ፡ ካሳ ፡ ከፈሉ

**indent** ገባ ፡ ብሎ ፡ ጻፈ
Always indent each paragraph when you type! በጽሕፈት ፡ መኪና ፡ በምትጽፍበት ፡ ጊዜ ፡ አ ዲስ ፡ አንቀጽ ፡ ስትጀምር ፡ ሁልጊዜ ፡ ገባ ፡ ብለ ህ ፡ ጻፍ

**be indented** (= indent) ወጣ ፡ ገባ ፡ አለ
+The shoreline is indented with bays. በባሕሩ ፡ ዳ ርቻ ፡ ሰላጤዎች ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ ይላሉ

**independence** ነጻነት
Kenya obtained her independence recently. ኬንያ ፡ ነጻነቷን ፡ ያገኘችው ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ነው

**obtain independence** ራሱን ፡ ቻለ
His son obtained his independence by getting a good job. ጥሩ ፡ ሥራ ፡ ይዞ ፡ ልጁ ፡ ራሱን ፡ ቻለ

**independent**
1. ነጻ. Monaco is an independent state. ሞናኮ ፡ ነጻ ፡ አገር ፡ ናት

2. በራሱ ፡ ሐሳብ ፡ የሚመራ. His independent mind refuses to accept any philosophy. በራሱ ፡ ሐሳብ ፡ የሚመራው ፡ አእምሮው ፡ የማንንም ፡ አስተሳሰብ ፡ አይቀበልም

**independent of**
*Independent of monetary considerations, it was a promising position. የገንዘቡ ፡ ጉዳይ ፡ ቀርቶ ፡ ተስፋ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ነበር

**be independent** ራሱን ፡ ቻለ
He has been independent ever since he was sixteen. ከሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜው ፡ ጀምሮ ፡ ራሱን ፡ ችሏል

**be independent of**
1. ከ - - - ወጥቶ ፡ ራሱን ፡ ቻለ. This department is independent of the administration of the university. ይህ ፡ ክፍል ፡ ከዩኒቨርሲቲው ፡ አስተዳደር ፡ ወጥቶ ፡ ራሱን ፡ ችሏል
2. ከ - - - ተገላገለ. If you have a car, you are independent of buses. መኪና ፡ ካለህ ፡ ከውቶቡስ ፡ ትገላገላለህ
*Financially, she's completely independent of her husband. በገንዘብ ፡ በኩል ፡ ባለቤቷን ፡ ፈጽሞ ፡ አታሳስብም

**(be) indescribable** ሊገለጽ ፡ አይችልም
The horrors of war are indescribable. ጦርነት ፡ የሚያመጣው ፡ ሥቃይ ፡ ሊገለጽ ፡ አይችልም

**indestructible** የማይበላሽ
This new-style typewriter is indestructible. ይህ ፡ አዲስ ፡ ዓይነት ፡ የጽሕፈት ፡ መኪና ፡ የማይበላሽ ፡ ነው

**indeterminate** በትክክል ፡ ያልታወቀ
An indeterminate number of guests will attend the dinner. ቁጥራቸው ፡ በትክክል ፡ ያልታወቀ ፡ እንግዶች ፡ በእራት ፡ ግብዣው ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ

**index** (indexes, or indices)
1. መለኪያ. The sale of cars is an index of a country's prosperity. የመኪናዎች ፡ ሽያጭ ፡ ያንድ ፡ ሀገር ፡ ብልጽግና ፡ መለኪያ ፡ ነው
2. በፊደል ፡ ተራ ፡ የተጻፈ ፡ የቃላት ፡ ማውጫ. There is an index in back of the book. መጽሐፉ ፡ በመጨረሻ ፡ ላይ ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ የተጻፈ ፡ የቃላት ፡ ማውጫ ፡ አለው

**index finger** ሌባ ፡ ጣት
He pointed to it with his index finger. በሌባ ፡ ጣቱ ፡ አመለከተ

**India** ህንድ

**Indian** ህንዳዊ

**indicate**
1. አመለከተ. He indicated that the interview was over. የቃል ፡ ጥያቄው ፡ ማለቁን ፡ አመለከተ
The arrow indicates the way to go. ቀስቱ ፡ አቅጣጫን ፡ ያመለክታል
2. አሳየ. It indicates that he is serious about it. እሱ ፡ በጣም ፡ ያሰበበት ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል

**indication**
1. ፍንጭ. There was no indication that he intends to grant her request. ጥያቄዋን ፡ የሚቀበል ፡ ለመሆኑ ፡ ምንም ፡ ፍንጭ ፡ አልታየም
2. ምልክት. Fever is an indication of illness. ትኩሳት ፡ የሕመም ፡ ምልክት ፡ ነው

**give an indication** አመለከተ
Did he give any indication of his feelings? ምን ፡ ዓይነት ፡ ስሜት ፡ እንዳለው ፡ አመለከተ ?

**indicative** ምልክት
Is a high forehead indicative of great intelligence? ሰፊ ፡ ግንባር ፡ የብልህነት ፡ ምልክት ፡ ነው ?

**be indicative of** አስረዳ
Her questions are indicative of a keen mind. የምትጠይቃቸው ፡ ጥያቄዎች ፡ ንቁ ፡ አእምሮ ፡ እንዳላት ፡ ያስረዳሉ

**indicator, be an ~ of** ገለጸ
Facial expression is often an indicator of feelings. በፊት ፡ ላይ ፡ የሚታይ ፡ ሁኔታ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ስሜትን ፡ የሚገልጽ ፡ ነው

**indices,** see **index**

**indict** ከሰሰ
He indicted them on a charge of rioting. ጸጥታ ፡ በማደፍረስ ፡ ወንጀል ፡ ከሰሳቸው

**indifference**
1. ግዴለሽነት. She felt complete indifference toward her children. ለልጆቿ ፡ ፍጹም ፡ ግዴለሽነት ፡ ተሰማት
2. ችላ ፡ ማለት. He resented the crowd's indifference to his speech. አዳማጩ ፡ ንግግሩን ፡ ችላ ፡ ማለቱ ፡ ቅር ፡ አሰኘው

**be a matter of indifference** አስፈላጊ ፡ አይመስለውም
Attending the party is a matter of indifference to me. በግብዣው ፡ ላይ ፡ መገኘት ፡ ወይም ፡ አለመገኘት ፡ አስፈላጊ ፡ አይመስለኝም

**with indifference** እንደነገሩ
He treated my request with indifference. ልመናዬን ፡ እንደነገሩ ፡ ተቀበለው

**indifferent** የግዴለሽነት

They criticized his indifferent attitude toward the suffering of others. ስለ ፡ ሌሎች ፡ ችግር ፡ በሚያሳየው ፡ የግዴለሽነት ፡ ሁኔታ ፡ ወቀሱት

**be (remain) indifferent**

1. ዝም ፡ አለ. We cannot remain indifferent in this dispute. በዚህ ፡ ክርክር ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ አንችልም

2. ግድ ፡ የለሽ ፡ ሆነ. Don't be so indifferent! እንደዚህ ፡ ግድ ፡ የለሽ ፡ አትሁን

3. ምንም ፡ ግድ ፡ የለውም. I am indifferent to the time of starting. ስለ ፡ መነሻው ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ምንም ፡ ግድ ፡ የለኝም

**indigence** ድኽነት

Due to the indigence of the inhabitants, many children were undernourished. በነዋሪዎቹ ፡ ድኽነት ፡ ምክንያት ፡ ብዙዎቹ ፡ ሕፃናት ፡ በቂ ፡ ምግብ ፡ አላገኙም ፡ ነበር

**indigenous, ~ inhabitant** ተወላጅ

The indigenous inhabitants of the country have a culture of their own. ያገሪቷ ፡ ተወላጆች ፡ የራሳቸው ፡ ባህል ፡ አላቸው

*Eucalyptus is indigenous to Australia. አስትራልያ ፡ ለባሕር ፡ ዛፍ ፡ አገሩ ፡ ናት

**indigent** ምስኪን

An indigent widow needs to have some kind of income. ምስኪን ፡ የሆነች ፡ ባሏ ፡ የሞተባት ፡ ሴት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ገቢ ፡ ያስፈልጋታል

**be (become) indigent** ደኸየ

He became indigent when he lost his leg in an accident. ባደጋ ፡ ምክንያት ፡ እግሩን ፡ ከተቈረጠ ፡ በኋላ ፡ ደኸየ

**(be) indigestible** አይዋሐድም

This food is indigestible. ይህ ፡ ምግብ ፡ አይዋሐድም

**indigestion**

*Do you have any medicine for indigestion? ሆድ ፡ ሲጐረብጥ ፡ የሚያሽር ፡ መድኀኒት ፡ አለህ ?

**give indigestion** ሆዱን ፡ ጐረበጠው

Green apples give me indigestion. ጥሬ ፡ ቱፋ ፡ ሆዴን ፡ ይጐረብጠኛል

**(be) indignant** ተናደደ

He was indignant when he found the money was stolen. ገንዘቡ ፡ እንደ ፡ ተሰረቀ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ተናደደ

**indignation** ንዴት

His indignation knew no bounds. ንዴቱ ፡ ወሰን ፡ አልነበረውም

**indirect**

1. ዙሪያ. We walk to town by a road that is indirect, but very pleasant. ወደ ፡ ከተማ ፡ የምንሄድበት ፡ መንገድ ፡ ዙሪያ ፡ ቢሆንም ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ያለው ፡ ነው

2. ቀጥተኛ ፡ ያልሆነ. This is an indirect answer to my question. ይህ ፡ ለጥያቄዬ ፡ ቀጥተኛ ፡ ያልሆነ ፡ መልስ ፡ ነው

**indirect object,** see **object**

**indiscernible** በግልጽ ፡ የማይታይ

There is an indiscernible difference between these two houses. በነዚህ ፡ ሁለት ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ በግልጽ ፡ የማይታይ ፡ ልዩነት ፡ አለ

**indiscreet** ወሬ ፡ የማይቋጥር

The indiscreet girl talked with strangers about her problems. ወሬ ፡ የማትቋጥርዋ ፡ ልጃገረድ ፡ ችግሯን ፡ ለማታውቀው ፡ ሰው ፡ አዋየች

**be indiscreet** ወሬ ፡ አይቋጥርም

She is indiscreet, so don't tell her any secrets! ወሬ ፡ ስለማትቋጥር ፡ ምንም ፡ ምስጢር ፡ አትንገራት

**indiscretion**

*His indiscretion was punished by the government. ጥንቃቄ ፡ ስለጐደለው ፡ ባድራጎቱ ፡ መንግሥት ፡ ቀጣው

**indiscriminate** እጅ ፡ እንዳመጣ

Indiscriminate bombing results in many civilian casualties. እጅ ፡ እንዳመጣ ፡ በምብ ፡ መጣል ፡ ብዙ ፡ ሲቪሎችን ፡ ይገድላል

**be indiscriminate** አይመርጥም

He is indiscriminate in making friends. ጓደኛ ፡ ሲያበጅ ፡ አይመርጥም

**indiscriminate mixture** ውጥንቅጥ

This music is an indiscriminate mixture of various styles. ይህ ፡ሙዚቃ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ስልቶች ፡ ውጥንቅጥ ፡ ነው

**indispensable** አስፈላጊ

Air, food, and water are indispensable for life. አየር ፡ ምግብና ፡ ውኃ ፡ ለሕይወት ፡ አስፈላጊ ፡ ናቸው

**indispose** ደስ ፡ አላሰኘም

Hot weather indisposes a person to hard work. ሞቃት ፡ አየር ፡ ጠንክሮ ፡ ለመሥራት ፡ ደስ ፡ አያሰኝም

**be indisposed** ጤና ፡ አይደለም

I am indisposed because I have a headache. ራስ ፡ ምታት ፡ ስለያዘኝ ፡ ጤና ፡ አይደለሁም

**be indisposed to** ዝንባሌ ፡ የለውም
I am indisposed to take his request seriously. ጥያቄውን ፡ እንደ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ለመቍጠር ፡ ዝንባሌ ፡ የለኝም

## indistinct
1. የማይለይ. We hear an indistinct roar from the distant ocean. ሩቅ ፡ ከሆነው ፡ ውቅያኖስ ፡ የማይለይ ፡ ድምፅ ፡ ይሰማናል
2. የማይነበብ. I received a letter with an indistinct signature. የማይነበብ ፡ ፊርማ ፡ የሰፈረበት ፡ ደብዳቤ ፡ ደረሰኝ

## individual (n.)
1. አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻውን. The individual can do nothing. አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ ምንም ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም
2. ግለ ፡ ሰብ. This organization fights for the rights of the individual. ይህ ፡ ድርጅት ፡ ለግለ ፡ ሰብ ፡ መብት ፡ ይዋጋል
3. ሰው. He is a clever individual. ብልህ ፡ ሰው ፡ ነው

**individual** (adj.)
1. የግል. We each have our individual tastes. እያንዳንዳችን ፡ የግላችን ፡ የሆነ ፡ ፍላጎት ፡ አለን
2. እየግል. They slept in individual beds. በየግል ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ተኙ
3. የራሱ. Alice has an individual style of arranging her hair. አሊስ ፡ የራሷ ፡ የሆነ ፡ የጸጉር ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ አላት
4. (= adv.) ለየብቻ. The teacher cannot give individual help to all his pupils. አስተማሪው ፡ ተማሪዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ለየብቻ ፡ ሊረዳቸው ፡ አይችልም

**for each individual**
*They bought presents for each individual child. ለያንዳንዱ ፡ ልጅ ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ስጦታ ፡ ገዙ

## individualistic ግለኛ
Occidental society is individualistic in nature. የምዕራባውያን ፡ ኅብረ ፡ ሰብ ፡ በተፈጥሮው ፡ ግለኛ ፡ ነው

## individuality
1. ግላዊነት. The director is a person of marked individuality. ዲሬክተሩ ፡ የተለየ ፡ ግላዊነት ፡ ያለው ፡ ነው
2. Personal pronoun + ነት. He kept his individuality. እሱነትን ፡ ጠበቀ
Keep your individuality. አንተነትህን ፡ ጠብቅ

## individually
1. በየግል. The teacher helps us individually. አስተማሪው ፡ በየግላችን ፡ ይረዳናል
2. በግል. Each of us is individually responsible. እያንዳንዳችን ፡ በግል ፡ ኀላፊዎች ፡ ነን
3. አንድ ፡ ባንድ. The delegates were introduced individually. መልእክተኞቹ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ተዋወቁ

## indivisible ሊከፋፈል ፡ የማይችል
An atom was once indivisible. አቶም ፡ ሊከፋፈል ፡ የማይችል ፡ ነገር ፡ ነበር

## indoctrinate አሳመነ
He tried to indoctrinate me with his propaganda. በሐሰት ፡ ወሬው ፡ ሊያሳምነኝ ፡ ሞከረ

## indolence ስንፍና
His indolence is responsible for his poverty. ለድኽነቱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ስንፍናው ፡ ነው

## indolent ሰነፍ
He is very indolent and never works. በጣም ፡ ሰነፍ ፡ ስለሆነ ፡ ፈጽሞ ፡ አይሠራም

## indoor የቤት ፡ ውስጥ
In winter we play indoor games. በክረምት ፡ የቤት ፡ ውስጥ ፡ ጨዋታ ፡ እንጫወታለን

## indoors እቤት ፤ እቤት ፡ ውስጥ
You'd better stay indoors today. ዛሬ ፡ እቤት ፡ ብትውል ፡ ይሻልሃል
In the event of rain, the party will be held indoors. ዝናም ፡ ከሆነ ፡ ፓርቲው ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ይደረጋል
[See also 'keep']

## induce
1. አግባባ. We could not induce the old lady to sell us her land. አሮጊቷ ፡ መሬቷን ፡ እንድትሸጥልን ፡ ልናግባባት ፡ አልቻልንም
2. አስወሰደ ፤ አስመጣ. Some drugs induce sleep. አንዳንድ ፡ መድኃኒቶች ፡ እንቅልፍ ፡ ያስወስዳሉ ፡ (ያስመጣሉ)

**be induced** ተነሣ(በት)
His illness was induced by overwork. ሕመሙ ፡ የተነሣበት ፡ ከሥራ ፡ ብዛት ፡ ነው

## inducement የሚገፋፋ ፡ ነገር
He doesn't have much inducement to study. ለማጥናት ፡ የሚገፋፋው ፡ ነገር ፡ የለውም

## induct በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አደረገ
The committee inducted him as president. ደርጉ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ አደረገው

## (be) inducted (= act.) መለመለ
Men are inducted into the army once a month.

የጦር ፡ ሰራዊት ፡ ጉልማሳ ፡ ወንዶችን ፡ ለወታደርነት ፡ በወር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይመለምላል
*The mayor will be inducted in a ceremony at city hall. ለከንቲባው ፡ በከተማው ፡ አዳራሽ ፡ የምረቃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይደረግለታል

**indulge**
1. አንከባከበ. We often indulge a sick person. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በሽተኛን ፡ እናንከባከባለን
2. አሞላቀቀ. The mother indulges her children. እናትዮዋ ፡ ልጆቿን ፡ ታሞላቅቃለች
3. ለ - - - ተገዛ. We do not indulge all our desires. ለፍላጎታችን ፡ ሁሉ ፡ አንገዛም
**indulge in** ለ - - - ተበለጠ
The children indulge in candy. ሕፃናት ፡ ለከረሜላ ፡ ይበለጣሉ
[See also 'fantasy']

**indulgent** ልል
His parents are very indulgent. የሱ ፡ ወላጆች ፡ በጣም ፡ ልል ፡ ናቸው

**industrial** የኢንዱስትሪ
This country has a small industrial output. ይህች ፡ አገር ፡ ያላት ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሀብት ፡ ትንሽ ፡ ነው

**industrialize** በኢንዱስትሪ ፡ አበለጸገ
The government is trying to industrialize the country. መንግሥቱ ፡ ሀገሪቷን ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ለማበልጸግ ፡ ይጥራል

**industrious** ታታሪ
We need industrious farmers. ታታሪ ፡ ገበሬዎች ፡ ያስፈልጉናል

**industry** (industries) ኢንዱስትሪ
Many industries were developed after the war. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ ተቋቋሙ

**inebriate** አሰከረ
This liquor will inebriate a person very quickly. ይህ ፡ አልኮል ፡ ያለው ፡ መጠጥ ፡ ቶሎ ፡ ያሰክራል

**(be) inedible** አይበላም
Poisonous mushrooms are inedible. መርዝነት ፡ ያለው ፡ እንጉዳይ ፡ አይበላም

**ineffective** አጥጋቢ ፡ ያልሆነ
The lawyer presented an ineffective argument. ጠበቃው ፡ አጥጋቢ ፡ ያልሆነ ፡ ክርክር ፡ አደረገ
**be ineffective** ውጤት ፡ አይሰጥም
Circular arguments are ineffective. ዙሪያ ፡ ጥምጥም ፡ ክርክሮች ፡ ውጤት ፡ አይሰጡም

**inefficient**
1. አጥጋቢ ፡ ውጤት ፡ የማይሰጥ. Inefficient industries should be reformed. አጥጋቢ ፡ ውጤት ፡ የማይሰጡ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ መሻሻል ፡ አለባቸው
2. ቀልጣፋ ፡ ያልሆነ. He is very inefficient; he never does things right. ቀልጣፋ ፡ ስላልሆነ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ በትክክል ፡ አይሠራም
**be inefficient** ጠቃሚ ፡ አይደለም
A machine that uses too much electricity is inefficient. ከመጠን ፡ በላይ ፡ የኮሬንቲ ፡ ኀይል ፡ የሚስብ ፡ መኪና ፡ ጠቃሚ ፡ አይደለም

**(be) ineligible**
1. ተገቢ ፡ አይደለም. Due to his age, he is ineligible for the position. ከዕድሜው ፡ የተነሣ ፡ ለሥራው ፡ ተገቢ ፡ አይደለም
2. መብት ፡ የለውም. A foreign-born citizen is ineligible for the presidency. የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ለመሆን ፡ መብት ፡ የለውም
3. አይፈቀድለትም. Foreigners are ineligible to own land. የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ መሬት ፡ እንዲኖራቸው ፡ አይፈቀድላቸውም

**inept**
1. ሙያ ፡ የሌለው. An inept carpenter made these stairs crooked. ሙያ ፡ የሌለው ፡ አናጢ ፡ እነዚህን ፡ ደረጃዎች ፡ አዛንፎ ፡ ሠራቸው
2. ተገቢ ፡ ያልሆነ. His inept remark displeased the audience. ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ አስተያየቱ ፡ አዳማጮቹን ፡ አስከፋ
*Their inept diplomacy resulted in war. የዲፕሎማሲ ፡ ዘዴ ፡ አለማወቃቸው ፡ ጦርነትን ፡ አስከተለ

**inequality** (inequalities)
1. መበላለጥ. Great inequality in wealth caused social unrest. የሰዎች ፡ በሀብት ፡ በጣም ፡ መበላለጥ ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ ሁከትን ፡ ፈጠረ
2. (= adj.) ያልተስተካከለ. In some countries there is inequality of opportunity for education. ባንዳንድ ፡ አገሮች ፡ የትምህርት ፡ ዕድል ፡ ያልተስተካከለ ፡ ነው

**inequity** (inequities) ትክክለኛ ፡ አለመሆን
His students resented his inequities in grading papers. ተማሪዎቹ ፡ ማርክ ፡ ሲሰጥ ፡ ትክክለኛ ፡ ባለመሆኑ ፡ ቅር ፡ ተሰኙ

**inert** ግዑዝ
A stone is inert. ድንጋይ ፡ ግዑዝ ፡ ነው
**lay inert** በድን ፡ መስሎ ፡ ተኛ
He lay there completely inert until the enemy

passed. ጠላት ፣ እስኪያልፍ ፣ ድረስ ፣ ፈጽሞ ፣ በ
ድን ፣ መስሎ ፣ ተኛ

**inertia** ወዲያ ፣ ወዲህ ፣ ለማለት ፣ አለመቻል
His inertia is due to prolonged illness. ወዲያ ፣ ወዲህ ፣ ለማለት ፣ አለመቻሉ ፣ ለብዙ ፣ ጊዜ ፣ ስለታ
መመ ፣ ነው

**inevitable**
1. የማይጠረጠር. With this excellent team, victory seems inevitable. የዚህ ፣ በጣም ፣ ጥሩ ፣ ቡድን ፣ ድል ፣ ማድረግ ፣ የማይጠረጠር ፣ ነው
2. የማይቀር. Man's inevitable end is death. ሞት ፣ ለሰው ፣ የማይቀር ፣ ዕዳ ፣ ነው

**inexact** ትክክል ፣ ያልሆነ
He gave inexact answers on the test. በፈተና ፣ ላ
ይ ፣ ትክክል ፣ ያልሆነ ፣ መልስ ፣ ሰጠ

**inexcusable** የማይታለፍ
The boy's continuous carelessness is inexcusable. የልጁ ፣ የማያቋርጥ ፣ ቸልተኝነት ፣ የማይታለ
ፍ ፣ ነው

**inexhaustible** የማያልቅ
The wealth of our country seems inexhaustible to many people. ብዙ ፣ ሰዎች ፣ የሀገራችን ፣ ሀ
ብት ፣ የማያልቅ ፣ ይመስላቸዋል

**of inexhaustible energy** የማይታክት
The new president is a man of inexhaustible energy. አዲሱ ፣ ፕሬዚዳንት ፣ የማይታክት ፣ ሰው ፣ ነው

**(be) inexistent** የለም
Labor unions are completely inexistent in certain countries. ባንዳንድ ፣ አገሮች ፣ ውስጥ ፣ የሠራተኞች ፣ ማኅበሮች ፣ ፈጽሞ ፣ የሉም

**inexorable** የማይበገር
The forces of nature are inexorable. የተፈጥሮ ፣ ኀይሎች ፣ የማይበገሩ ፣ ናቸው

**inexpensive** ርካሽ
This dress is very inexpensive. ይህ ፣ ቀሚስ ፣ በ
ጣም ፣ ርካሽ ፣ ነው

**inexperience** ልምድ ፣ ማጣት ፤ የልምምድ ፣ እ
ጦት
His inexperience made him think the problem was easy to solve. ልምድ ፣ ከማጣቱ ፣ የተነሣ ፣ ችግሩ ፣ በቀላሉ ፣ መፍትሔ ፣ የሚገኝለት ፣ መሰ
ለው
We made allowance for Jack's inexperience. ለጃክ ፣ የልምምድ ፣ እጦት ፣ አስተያየት ፣ አደረግን

**inexperienced**
1. የሥራ ፣ ልምድ ፣ የሌለው. No inexperienced people will be given this job. የሥራ ፣ ልምድ ፣ የሌላቸው ፣ ሰዎች ፣ ይህ ፣ ሥራ ፣ አይሰጣቸውም
2. በቂ ፣ ልምድ ፣ የሌለው. The dissonance caused by an inexperienced harp player is unpleasant. በቂ ፣ ልምድ ፣ የሌለው ፣ በገና ፣ ተጫዋች ፣ ያቀረበ
ው ፣ ያልተቀናበረ ፣ ዜማ ፣ አያስደስትም

**be inexperienced** ልምድ ፣ አልነበረውም
The erratic course of the plane showed that the pilot was inexperienced. ያውሮፕላኑ ፣ ያልተ
ስተካከለ ፣ በረራ ፣ ነጂው ፣ ልምድ ፣ ያልነበረ
ው ፣ መሆኑን ፣ አሳየ

**(be) inexplicable** አይታወቅም
His behavior is inexplicable. ጠባዩ ፣ አይታወ
ቅም

**inextricable** መውጫ ፣ የሌለው
His embezzling the money involved him in inextricable difficulty. ገንዘብ ፣ ማጭበርበሩ ፣ መ
ውጫ ፣ ከሌለው ፣ ችግር ፣ ውስጥ ፣ ጣለው

**infallible** የማይሳሳት
Only the pope is said to be infallible. ጳጳሱ ፣ ብ
ቻ ፣ የማይሳሳት ፣ ነው ፣ ይባላል

**infamous** አስከፊ
His infamous conduct made him many enemies. አስከፊ ፣ ጠባዩ ፣ ብዙ ፣ ጠላት ፣ አፈራለት

**be infamous** ጠፋ
A traitor's name is infamous. የከሓዲው ፣ ስም ፣ ጠፍቷል

**infamy** (infamies) መጥፎ ፣ ስም
Traitors are held in infamy. ከሓዲዎች ፣ መጥ
ፎ ፣ ስም ፣ አላቸው

**infancy** የሕፃንነት ፣ ጊዜ
He spent his infancy in the palace. የሕፃንነት ፣ ጊዜውን ፣ ያሳለፈው ፣ በቤተ ፣ መንግሥት ፣ ነው

**be in its infancy** አልደረጀም
Fifty years ago the airplane was still in its infancy. ከኀምሳ ፣ ዓመታት ፣ በፊት ፣ አውሮፕላ
ን ፣ ገና ፣ አልደረጀም ፣ ነበር
*She's still in her infancy. ገና ፣ ሕፃን ፣ ናት

**infant** (n.) ሕፃን (pl. ሕፃናት)
The infant was playing on the floor. ሕፃኑ ፣ በ
ወለሉ ፣ ላይ ፣ ይጫወት ፣ ነበር
Infants' food must be soft. የሕፃናት ፣ ምግብ ፣ ለ
ስላሳ ፣ መሆን ፣ አለበት

**infant** (adj.) የልጅነት
He spent his infant years in Europe. የልጅነት ፡ ጊዜውን ፡ አውሮፓ ፡ ውስጥ ፡ አሳለፈ
[See also 'mortality']

**infantile**
1. የልጆች. This infantile disease kills many babies. ይህ ፡ የልጆች ፡ በሽታ ፡ ብዙ ፡ ሕፃናትን ፡ ይፈጃል
2. የሕፃንነት. Considering his age, his infantile behavior is strange. ዕድሜውን ፡ ሲመለከቱ ፡ የሕፃንነት ፡ ጠባዩ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ነው

**infantilism** ሕፃንነት
He retrogressed to infantilism. ወደ ፡ ሕፃንነት ፡ ተመለሰ

**infantry** የእግረኛ ፡ ጦር
The infantry attacked at dawn. የእግረኛው ፡ ጦር ፡ ጎሕ ፡ ሲቀድ ፡ አጠቃ
[See also 'light']

**infatuate** ማረከ ፤ አነሆለለ
Her beauty infatuates every man. ውበቷ ፡ ሁሉን ፡ ይማርካል ፡ (ያነሆልላል)

**be infatuated**
*He is infatuated with each pretty girl he meets. ለሚያገኛት ፡ ውብ ፡ ልጃገረድ ፡ ሁሉ ፡ ሞትኩልሽ ፡ ይላል

**infect**
1. መረዘ. Dirt infects an open cut. ቆሻሻ ፡ ገላጣ ፡ ቁስል ፡ ይመርዛል
2. አነሣሣ. The captain's courage infected his soldiers. የሻምበሉ ፡ ጀግንነት ፡ ወታደሮቹን ፡ አነሣሣ
3. አበላሸ. One bad boy may infect the whole class. አንድ ፡ መጥፎ ፡ ልጅ ፡ ክፍሉን ፡ በሙሉ ፡ ያበላሻል
4. ያዘ. A fever of anxiety infected the candidate's family during election night. በምርጫው ፡ ሌሊት ፡ የእጩ ፡ ተወዳዳሪው ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስጋት ፡ ይዟቸው ፡ ነበር

**be (become) infected**
1. ተመረዘ. The wound became infected. ቁስሉ ፡ ተመርዟል
His haughty words show he is infected with pride. የትዕቢት ፡ አነጋገሩ ፡ በኩራት ፡ የተመረዘ ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል
2. ተለከፈ. He became infected with the disease while in the South. ደቡብ ፡ ሳለ ፡ በበሽታ ፡ ተለከፈ

**infection** የቁስል ፡ ማመርቀዝ
Pus is a sign of infection. መግል ፡ የቁስል ፡ ማመርቀዝ ፡ ምልክት ፡ ነው
*Infection has set in. ቁስሉ ፡ መመረዝ ፡ ጀምሯል

**infectious** በጀርም ፡ የሚይዝ
Malaria is an infectious disease. ወባ ፡ በጀርም ፡ የሚይዝ ፡ በሽታ ፡ ነው

**be infectious** በሌሎቹም ፡ ላይ ፡ ተጋባ
Her laughter was infectious. ሣቋ ፡ በሌሎቹም ፡ ላይ ፡ ተጋባ

**infer** (inferred), vt. አመለከተ
Ragged clothing infers poverty. ቡትቶ ፡ ልብስ ፡ ድኽነትን ፡ ያመለክታል

**infer** (vt.) ተረዳ
I inferred from his remarks that he thinks I am a liar. በውሸተኛነት ፡ እንደገመተኝ ፡ በአነጋገሩ ፡ ተረዳሁ

**inferior** (n.) የበታች
A good leader gets on well with his inferiors. ጥሩ ፡ አለቃ ፡ ከበታቾቹ ፡ ጋር ፡ ይስማማል

**inferior** (adj.)
1. ዝቅተኛ. He occupies an inferior position in the office. በመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ዝቅተኛ ፡ ደረጃ ፡ የያዘ ፡ ነው
2. መናኛ. The goods produced in that country are inferior. እዚያ ፡ አገር ፡ የሚሠሩ ፡ እቃዎች ፡ መናኛ ፡ ናቸው
This cloth is inferior to real silk. ይህ ፡ ጨርቅ ፡ ከሐር ፡ ይልቅ ፡ መናኛ ፡ ነው

**be inferior** ዝቅ ፡ አለ
A lieutenant is inferior to a captain. የመቶ ፡ አለቃ ፡ ማዕርግ ፡ ከሻምበል ፡ ዝቅ ፡ ይላል

**feel inferior** ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ አየ
He feels inferior because of lack of education. ስላልተማረ ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ያያል

**inferiority**
*The inferiority of one race to another is no longer believed. አንዱ ፡ ዘር ፡ ከሌላው ፡ ዝቅተኛ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ እምነት ፡ ከእንግዲህ ፡ አይታመንበትም

**infernal** የገረረ
The infernal heat of the desert caused him much suffering. የገረረው ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ ሙቀት ፡ አሠቃየው

**infest** ወረረ
Mosquitoes infest swamps. የወባ ፡ ትንኞች ፡ ረግረግ ፡ ቦታ ፡ ይወራሉ

**infidel** አረመኔ
The infidels may not enter the church. አረመኔዎች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዳይገቡ ፡ ተከለከለ

**infidelity** ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ማፍረስ
His wife accused him of infidelity. ሚስቱ ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ በማፍረሱ ፡ ከሰሰችው

**infiltrate** ሰርጎ ፡ ገባ ፤ ተሾሽጎ ፡ ገባ
Agents have been infiltrating the countryside to stir up riots. አነሣሾች ፡ ሁከት ፡ ለማስነሣት ፡ በየባላገሩ ፡ ሁሉ ፡ ሰርገው ፡ (ተሾሽገው) ፡ ገብተዋል

**infiltrator** ሰርጎ ፡ ገብ
Infiltrators have crossed the border. ሰርጎ ፡ ገቦች ፡ ወሰኑን ፡ አቋርጠዋል

**infinite**
1. የማይወሰን. Trust in the infinite goodness of God! በማይወሰነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ እመን
2. መጠን ፡ የሌለው. The government spent infinite sums of money on war. መንግሥት ፡ ለጦርነት ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ ገንዘብ ፡ አወጣ
*She had infinite patience with him. በጣም ፡ ቻለችው

**be infinite** መነሻና ፡ መድረሻ ፡ የለውም
The universe is infinite. ዓለማት ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ የለውም

**of infinite importance** ተወዳዳሪ ፡ የሌለው
He made a discovery of infinite importance. ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ ፍልሰፋ ፡ አደረገ

**infinitely** አለቅጥ
Atoms are infinitely small. አቶም ፡ አለቅጥ ፡ ረቂቅ ፡ ነው

**infinity** (= adj.) ወሰን ፡ የሌለው
The preacher spoke about the infinity of God's mercy. ሰባኪው ፡ ወሰን ፡ ስለሌለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምሕረት ፡ ተናገሩ
*A line extends to infinity. መሥመር ፡ መጀመሪያና ፡ መጨረሻ ፡ የለውም

**infirm** ደካማ
He became infirm in his old age. በእርጅናው ፡ ጊዜ ፡ ደካማ ፡ ሆነ

**infirmary** (infirmaries) ክሊኒክ
Every school needs an infirmary. ማንኛውም ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ክሊኒክ ፡ ያስፈልገዋል

**infirmity** (infirmities)
1. ያካል ፡ ጉዶሎነት. He suffers from blindness or some other infirmity. ዓይነ ፡ ስውርነት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ያካል ፡ ጉደሎነት ፡ አለበት
2. ደካማነት. The old man's infirmity kept him from leaving the house. የሽማግሌው ፡ ደካማነት ፡ እቤት ፡ አዋለው

**inflame**
1. አቀላ. The smoke inflamed the fireman's eyes. ጢሱ ፡ የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካዩን ፡ ዓይን ፡ አቀላው
Salt inflames a cut. ጨው ፡ ቁስሉን ፡ ያቀላል
2. ደም ፡ አስመሰለ. The setting sun inflames the sky. የግባት ፡ ጀንበር ፡ ሰማዩን ፡ ደም ፡ ያስመስለዋል
3. አባሰ. Our remarks just inflamed his rage. የሰጠነው ፡ አስተያየት ፡ ንዴቱን ፡ አባሰበት
4. አስቈጣ. His speeches inflamed the public and caused riots. ንግግሩ ፡ ሕዝቡን ፡ በማስቈጣት ፡ ሁከት ፡ አስነሣ

**be inflamed**
1. ተመረዘ. My eye is inflamed. ዓይኔ ፡ ተመርዟል
2. አመመ(ው). His appendix is inflamed. ትርፍ ፡ አንጀቱ ፡ አሞታል

**inflammable** ነዳጅ
Caution! This liquid is inflammable. ተጠንቀቅ ! ይህ ፡ ፈሳሽ ፡ ነዳጅ ፡ ነው

**inflammation**
1. መመረዝ. The inflammation of his eye blinded him. የዓይኑ ፡ መመረዝ ፡ አሳወረው
2. የሰውነት ፡ ማጕረብረብ. Fever and inflammation are phenomena of diseases. ትኩሳትና ፡ የሰውነት ፡ ማጕረብረብ ፡ የበሽታ ፡ ምልክቶች ፡ ናቸው
*He died from an inflammation of the liver. ጉበቱ ፡ አብጦ ፡ ሞተ

**inflammatory** የሚያስቈጣ
His polemic writings are inflammatory. አከራካሪ ፡ ጽሑፎቹ ፡ የሚያስቈጡ ፡ ናቸው

**inflate**
1. ነፋ. Inflate the tire! It is getting flat. ጎማውን ፡ ንፋው ፤ ተኝቷል
2. አስወደደ. War inflates prices. ጦርነት ፡ የእቃን ፡ ዋጋ ፡ ያስወድዳል

**be inflated** ተወጠረ
He was inflated with pride. በኩራት ፡ ተወጥሮ ፡ ነበር

**inflation** የገንዘብ ፡ ዋጋ ፡ መውረድ
The country is suffering from inflation. አገሪቷ ፡ የገንዘቧ ፡ ዋጋ ፡ በመውረዱ ፡ ትቸገራለች

*Inflation of the balloon increases its size. ፊኛ ፡ ሲነፋ ፡ ትልቅ ፡ ይሆናል

**inflect** አረባ
The students inflected the pronoun. ተማሪዎቹ ፡ ተውላጠ ፡ ስሙን ፡ አረቡት

**inflection**
1. የድምፅ ፡ አሰባበር. His inflection showed that he was asking a question. የድምፁ ፡ አሰባበር ፡ ጥያቄ ፡ የሚጠይቅ ፡ መሆኑን ፡ አመለከተ
2. አረባብ. The inflection of the Amharic verb is difficult for foreigners. ያማርኛ ፡ ግሶች ፡ አረባብ ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ይከብዳል

**inflexible**
1. ንቅንቅ ፡ የማይል. The laws were inflexible, so he had to go to jail. ሕጉ ፡ ንቅንቅ ፡ የማይል ፡ ስለሆነ ፡ ሰውዬው ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ገባ
2. የማይናወጽ. His determination to go to school is inflexible. ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመግባት ፡ ያደረገው ፡ ቁርጥ ፡ ሐሳብ ፡ የማይናወጽ ፡ ነው

**inflict, ~ a blow** መታ
The police inflicted a blow on his head. ፖሊሱ ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ መታው

**inflict death penalty**
The judge inflicted the death penalty on him. ዳኛው ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረደበት

**inflict pain** ሰውን ፡ አሠቃየ
Only cruel people like to inflict pain. ሰውን ፡ ማሠቃየት ፡ የሚወዱ ፡ ጨካኝ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**inflict troubles** አስቸገረ
He inflicts his troubles on everyone. ተቸግሮ ፡ ያስቸግራል

**influence** (v.)
1. አግባባ. I am not trying to influence you. አንተን ፡ ላግባባህ ፡ አልሞከርም
2. አነሣሣ. His speeches influenced the public and caused riots. ንግግሩ ፡ ሕዝቡን ፡ አነሣሥቶ ፡ ሁከት ፡ አስከተለ
3. ተጽዕኖ ፡ አለው. The moon influences the tides. ጨረቃ ፡ በሞገድ ፡ ላይ ፡ ተጽዕኖ ፡ አላት
4. ተጽዕኖ ፡ አሳደረ. His advice influenced my decision. ምክሩ ፡ በውሳኔዬ ፡ ላይ ፡ ተጽዕኖ ፡ አሳደረ

**be influenced (by)**
1. ተማኸ. The young are influenced by idealism. ወጣቶች ፡ የኀልዮ ፡ ኑሮ ፡ ይማኻሉ
2. ተገፋፋ. An angry mob is influenced more by impulse than by reason. የተናደደ ፡ ሕዝብ ፡ ነገርን ፡ በማመዛዘን ፡ ሳይሆን ፡ በስሜት ፡ የሚገፋፋ ፡ ነው

**influence** (n.)
1. ምሳሌ. You have always been a good influence on him. ጥሩ ፡ ምሳሌ ፡ ሆነኸዋል
2. ተጽዕኖ. Her mother's influence made her stay. የእናቷ ፡ ተጽዕኖ ፡ እንድትቆይ ፡ አደረጋት
3. አማላጅ. He used influence to get the contract. ኮንትራቱን ፡ ለማግኘት ፡ በአማላጅ ፡ ተጠቀመ
4. ተሰሚነት. A person may have influence by his ability, position, or wealth. ሰው ፡ በችሎታው ፡ በሥልጣኑ ፡ ወይም ፡ በሀብቱ ፡ ምክንያት ፡ ተሰሚነት ፡ ይኖረው ፡ ይሆናል

**be under the influence of** ተማኸ
He was under the influence of drink. መጠጥ ፡ ተጭኖት ፡ ነበር

**have no influence**
*Don't go to him for help; he has no influence whatsoever. ለእርዳታ ፡ እሱ ፡ ዘንድ ፡ አትሂድ ። ከጤፍም ፡ የሚቆጥረው ፡ የለ

**influential** ተደማጭነት ፡ ያለው
He is an influential man. ተደማጭነት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**influenza** እንፍሉዌንዛ
Influenza broke out again this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ እንፍሉዌንዛ ፡ እንደገና ፡ ተነሥቷል

**influx** በብዛት ፡ መግባት
Due to the influx of tourists, all the hotel rooms are occupied. የቱሪስቶች ፡ በብዛት ፡ ወደ ፡ ገር ፡ መግባት ፡ ሆቴሎችን ፡ ሁሉ ፡ አጣበበ
*Last year there was an influx of immigrants. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ መጤዎች ፡ ጐረፉ

**inform**
1. ነገረ. Can you inform me where he lives? የት ፡ እንደሚኖር ፡ ልትነግረኝ ፡ ትችላለህ ?
2. አስታወቀ. The government informed the press that war had been declared. መንግሥቱ ፡ ጦርነት ፡ መታወጁን ፡ ለጋዜጠኞች ፡ አስታወቀ

**inform on** ጠቈመ
One thief informed on the others. አንዱ ፡ ሌባ ፡ ሌሎቹን ፡ ጠቈመ

**inform oneself of** ተረዳ
He informed himself of all the pertinent facts. አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መረጃዎች ፡ ሁሉ ፡ ተረዳ

**be informed**
1. ዐወቀ. He is unusually well informed. ከመጠን ፡ በላይ ፡ ያውቃል

2. ተነገረ(ው). I was not informed in time. በሰዓቱ ፡ አልተነገረኝም

**informal**

1. ኦፊሲዬል ፡ ያልሆነ. The statesmen held an informal discussion. መሪዎቹ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ያልሆነ ፡ ውይይት ፡ አደረጉ

2. መሳይ. We are having an informal party. ፓርቲ ፡ መሳይ ፡ ልናደርግ ፡ ነው

**informant** አስረጅ

The informant he has is not very reliable. የሱ ፡ አስረጅ ፡ የሚተማመኑበት ፡ ሰው ፡ አይደለም

**information**

1. መረጃ. Where can I get some information about that? ስለዚያ ፡ መረጃ ፡ ከየት ፡ አገኛለሁ ?
A dictionary gives information about words. መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ስለ ፡ ቃላት ፡ መረጃ ፡ ይሰጣል

2. መግለጫ. The information concerning applications for permits was published in the newspapers. ስለ ፡ ፈቃድ ፡ ወረቀት ፡ ማመልከቻ ፡ ጋዜጦቹ ፡ ላይ ፡ መግለጫ ፡ ወጣ

3. የዕውቀት ፡ መጠን. His wealth of general information is amazing. ያለው ፡ የጠቅላላ ፡ ዕውቀት ፡ መጠን ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው

4. ማዞሪያ. Dial information and ask for his phone number! ማዞሪያ ፡ ደውለህ ፡ የሱን ፡ ስልክ ፡ ቁጥር ፡ ጠይቅ

*This is for your information only. ይህ ፡ አንተ ፡ እንድታውቀው ፡ ብቻ ፡ ነው

**Ministry of Information** የማስታወቂያ ፡ ሚኒስቴር
The Ministry of Information publishes various daily newspapers. የማስታወቂያ ፡ ሚኒስቴር ፡ በየዕለቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጋዜጦች ፡ ያሳትማል
[See also 'piece, pump']

**information desk** መረጃ ፡ ክፍል

Ask at the information desk! መረጃ ፡ ክፍል ፡ ጠይቅ

**informative** መግለጫ ፡ የሚሰጥ

He gave an informative talk on Ethiopia. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መግለጫ ፡ የሚሰጥ ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**informer** ጆሮ ፡ ጠቢ ፤ ወሬ ፡ አቀባይ

An informer exposed the conspiracy to the police. ጆሮ ፡ ጠቢ ፡ (ወሬ ፡ አቀባይ) ፡ አድማውን ፡ ለፖሊስ ፡ ገለጠ

**infraction** መጣስ

Any infraction of these regulations will be severely punished. በምንም ፡ ዓይነት ፡ ይህን ፡ ሕግ ፡ መጣስ ፡ በጥብቅ ፡ ያስቀጣል

**infrequent** (= adv.) አልፎ ፡ አልፎ

He pays me infrequent visits. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይጠይቀኛል

**infrequently** አልፎ ፡ አልፎ

It rains infrequently in the desert. በምድረ ፡ በዳ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይዘንባል

**infringe** ጣሰ

Speeding on a busy street infringes the law. ተመላላሽ ፡ በሚበዛበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በፍጥነት ፡ መንዳት ፡ ሕግን ፡ መጣስ ፡ ነው

**infringe upon** ነካ
Do not infringe upon the rights of others! የሌሎችን ፡ መብት ፡ አትንካ

**infuriate** አናደደ

The students infuriate the teacher. ተማሪዎቹ ፡ አስተማሪውን ፡ ያናድዱታል

**infuriated** (adj.) የተቈጣ

The infuriated lion jumped upon her. የተቈጣው ፡ አንበሳ ፡ ዘሎ ፡ ጉብ ፡ አለባት

**infuse**

1. ዘፈዘፈ. The maid infused the tea leaves in hot water to make tea. ገረዷ ፡ ሻዩን ፡ ለማፍላት ፡ ቅጠሉን ፡ሙቅ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ዘፈዘፈች

2. አነቃቃ. He tried to infuse the soldiers with fresh courage. ወታደሮቹን ፡ ባዲስ ፡ የጀግንነት ፡ መንፈስ ፡ ሊያነቃቃ ፡ ሞከረ

**infuse courage into** አደፋፈረ
The captain infused courage into his soldiers. ሻምበሉ ፡ ወታደሮቹን ፡ አደፋፈራቸው

**infusion, make an ~** ጨመቀ

He made an infusion of herbs and drank it. ቅጠላ ፡ ቅጠል ፡ ጨምቆ ፡ ጠጣ

**ingenious**

1. አንደኛ. He is very ingenious when it comes to making up excuses. ምክንያት ፡ በመፍጠር ፡ አንደኛ ፡ ነው

2. ብልህ. Only an ingenious engineer could have built this bridge. ይህን ፡ ድልድይ ፡ ሊሠራ ፡ የሚችል ፡ ብልህ ፡ መሀንዲስ ፡ ብቻ ፡ ነው

3. በጣም ፡ የረቀቀ ፤ ዕጹብ ፡ ድንቅ. That's an ingenious device. በጣም ፡ የረቀቀ ፡ (ዕጹብ ፡ ድንቅ) ፡ መሣሪያ ፡ ነው

**ingenuity** ብልህነት

The boy showed ingenuity in making toys. ልጁ ፡ አሻንጉሊት ፡ ሲሠራ ፡ ብልህነት ፡ ይታይበታል

**ingenuous** የዋህ

The ingenuous girl believed that everyone

loved her. የዋኋ ፡ ልጃገረድ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የ
ሚወዳት ፡ መሰላት

**ingrained** ሥር ፡ የሰደደ
It is difficult to overcome ingrained super-
stitions. ሥር ፡ የሰደደ ፡ አጉል ፡ እምነት ፡ ማሸን
ፍ ፡ አዳጋች ፡ ነው

**ingratiate oneself** ተወደደ
He tried to ingratiate himself with his rich
uncle. በሀብታም ፡ አጐቱ ፡ ዘንድ ፡ ለመወደድ ፡
ጣረ

**ingratitude** ውለታ ፡ቢስነት ፤ ክፋት
He resented her ingratitude. ውለታ ፡ ቢስነቷ ፡
አስቀየመው
He requites kindness with ingratitude. ውለታን ፡
በክፋት ፡ (በውለታ ፡ ቢስነት) ፡ የሚመልስ ፡ ሰው ፡ ነው

**ingredient**
1. ቅመማ ፡ ቅመም. The ingredients for the stew
are pepper, onions, and salt. የወጥ ፡ ቅመማ ፡ ቅ
መም ፡ በርበሬ ፡ ሽንኩርትና ፡ ጨው ፡ ናቸው
2. ክፍል. Alcohol is the principal ingredient
for beer. አልኮል ፡ ዋናው ፡ የጠላ ፡ ክፍል ፡ ነው
*The ingredients of cement are sand, lime, and
water. ሲሚንቶ ፡ የአሸዋ ፡ የኖራና ፡ የውኃ ፡ ቅ
ይጥ ፡ ነው

**inhabit** ኖረ
Dinosaurs once inhabited the earth. ዳይኖሶሮች ፡
በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር

**be inhabited** ሰው ፡ ኖረበት
This island is inhabited. ይህ ፡ ደሴት ፡ ሰው ፡
ይኖርበታል

**inhabitant** ነዋሪ
All the inhabitants are farmers. ነዋሪዎቹ ፡ ሁ
ሉ ፡ ገበሬዎች ፡ ናቸው
[See also 'aboriginal']

**inhale**
1. ዋጠ. He inhaled the smoke of his cigarette.
የሲጋራውን ፡ ጭስ ፡ ዋጠ
2. አየር ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ሳበ. Inhale and smell
the fresh fragrance! አየሩን ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ስበ
ህ ፡ መዓዛን ፡ አሽትት

**inherent** የተፈጥሮ
In spite of flattery, she kept her inherent
modesty. ሰዎች ፡ በከንቱ ፡ ቢያወድሷትም ፡ እ
ሷ ፡ የተፈጥሮ ፡ ትሕትናዋን ፡ አልጣለችም

**be inherent in** የ - - - አንዱ ፡ ባሕርይ ፡ ነው
Lawlessness is inherent in rebellion. ሕገ ፡ ወጥ
ነት ፡ የዐመፅ ፡ አንዱ ፡ ባሕርይ ፡ ነው

**inherit** ወረሰ
She inherited a large fortune. ብዙ ፡ ሀብት ፡
ወረሰች
We inherited these traditions from our ances-
tors. እነዚህን ፡ ልማዶች ፡ የወረስነው ፡ ካባቶ
ቻችን ፡ ነው
*Mary inherits her father's blue eyes. ሜሪ ፡
ሰማያዊ ፡ ዓይን ፡ ካባቷ ፡ ያገኘችው ፡ ነው

**inheritance**
1. ውርስ. His inheritance was more than
$1 million. ያገኘው ፡ ውርስ ፡ ካንድ ፡ ሚሊዮን ፡
ብር ፡ በላይ ፡ ነበር
2. የወረሰው ፡ ሀብት. He was magnanimous with
his money and lost his inheritance. በጣም ፡ ለጋ
ስ ፡ ስለሆነ ፡ የወረሰውን ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ አጠፋ

**inhibit**
1. አጨናገፈ. Lack of rain inhibits plant
growth. የዝናብ ፡ እጦት ፡ የዕፀዋትን ፡ እድገት ፡
ያጨናግፋል
2. አገደ. The presence of the police inhibited
the crowd. የፖሊስ ፡ መኖር ፡ ሕዝቡን ፡ አገደው
*The presence of grownups inhibits the be-
havior of children. ጐልማሶች ፡ ባሉበት ፡ ቦታ ፡
ሕፃናት ፡ እንደልባቸው ፡ አይሆኑም

**inhospitable** እስተናጋጅነት ፡ የጐደለው
Her husband's inhospitable behavior offended
her guests. የባልየው ፡ እስተናጋጅነት ፡ የጐደ
ለው ፡ ጠባይ ፡ እንግዶቹን ፡ አስቀየመ

**be inhospitable** የሚስማማ ፡ አይደለም
The desert is an inhospitable place. በረሃው ፡
ለመኖሪያ ፡ የሚስማማ ፡ አይደለም

**inhospitality** እንግዳን ፡ አለመቀበል
Inhospitality is considered a fault by Ethi-
opians. እንግዳን ፡ አለመቀበል ፡ በኢትዮጵያውያን ፡
ዘንድ ፡ እንደ ፡ ነውር ፡ ይቈጠራል

**inhuman** ሰብአዊ ፡ ያልሆነ
We complained about the inhuman treatment
given prisoners. በእስረኞቹ ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡
ሰብአዊ ፡ ያልሆነ ፡ አያያዝ ፡ ተቃወምን

**inhumane** ሰብአዊ ፡ ያልሆነ
Inhumane punishment is forbidden by law.
ሰብአዊ ፡ ያልሆነ ፡ ቅጣት ፡ በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ ነው

**inimical**
1. ጐጂ. Narcotics are inimical to health.
ሱስ ፡ የሚሆን ፡ መድኃኒት ፡ ለጤና ፡ ጐጂ ፡ ነው
2. የጥላቻ. The inimical acts of the two
countries led to war. በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ የተደረ
ጉት ፡ የጥላቻ ፡ ተግባሮች ፡ ጦርነት ፡ አስከተሉ

**be inimical to** ጠላ
For some reason he is inimical to me. ባልታወቀ ፡ ምክንያት ፡ ይጠላኛል

**inimitable** መሰል ፡ የለሽ
Mark Twain's humor is inimitable. የማርክ ፡ ትዌን ፡ የጨዋታ ፡ ለዛ ፡ መሰል ፡ የለሽ ፡ ነው

**iniquitous** የግፍ
The judge's iniquitous deeds were punished by death. የዳኛው ፡ የግፍ ፡ አድራጎት ፡ በሞት ፡ አስቀጣው

**iniquity** (iniquities) ታማኝ ፡ አለመሆን
His iniquity became known when the bank went bankrupt. ታማኝ ፡ አለመሆኑ ፡ ባንኩ ፡ በከሰረ ፡ ጊዜ ፡ ተገለጸ

**initial** (n.) የስም ፡ መጀመሪያ ፡ ፊደሎች
His silverware has his initials on it. በገበታ ፡ እቃው ፡ ላይ ፡ የስሙ ፡ መጀመሪያ ፡ ፊደሎች ፡ ተቀርጸውበታል

**initial** (adj.)
1. የመነሻ. The initial salary is small. የመነሻ ፡ ደሞዙ ፡ ትንሽ ፡ ነው
2. የመጀመሪያ. Our initial visit to the new museum was brief. ያዲስ ፡ ቤተ ፡ መዘክር ፡ የመጀመሪያ ፡ ጉብኝታችን ፡ ላጭር ፡ ጊዜ ፡ ነበር

**initiate**
1. ጀመረ. They initiated the plan with the building of a road. እቅዱን ፡ መንገድ ፡ በመሥራት ፡ ጀመሩ
2., አስጨበጠ. The father initiated his son into business methods. አባቱ ፡ ለልጁ ፡ የንግድ ፡ ዘዴዎችን ፡ አስጨበጠው
*I initiated my friend into the study of Amharic. ጓደኛዬን ፡ ሰምቶ ፡ የማያውቀውን ፡ አማርኛ ፡ አስተማርኩት

**be initiated**
He was initiated into my fraternity. እኔ ፡ ባለሁበት ፡ የወንድማማች ፡ ክበብ ፡ ውስጥ ፡ አባል ፡ እንዲሆን ፡ አስፈላጊው ፡ ሥርዓት ፡ ተፈጸመለት

**initiative** ሐሳብ ፡ የማመንጨት ፡ ችሎታ
A leader must have initiative. አንድ ፡ መሪ ፡ ሐሳብ ፡ የማመንጨት ፡ ችሎታ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል
*You must tell him to do everything because he lacks initiative and does nothing on his own. ማድረግ ፡ ያለበትን ፡ ሁሉ ፡ ልትነግረው ፡ ይገባል ፤ ምክንያቱም ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አስቦ ፡ መሥራት ፡ አይሆንለትም

**take the initiative** ሐሳብ ፡ አመነጨ
He took the initiative in producing the play. ቲያትሩን ፡ ለማዘጋጀት ፡ ሐሳብ ፡ ያመነጨው ፡ እሱ ፡ ነው

**inject**
1. መርፌ ፡ ወጋ. The doctor injected medicine into his bloodstream. ዶክተሩ ፡ ደም ፡ ሥሩን ፡ መርፌ ፡ ወጋው
2. ጣልቃ ፡ አስገባ. He always injects politics into our discussion. በጨዋታችን ፡ ውስጥ ፡ ሁል ጊዜ ፡ የፖለቲካ ፡ ወሬ ፡ ጣልቃ ፡ ያስገባል

**injection** መርፌ
Are you getting injections? መርፌ ፡ ትወጋለህ ?

**injunction**
1. ትእዛዝ. He obeyed his father's injunction. ያባቱን ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀበለ
2. የፍርድ ፡ ቤት ፡ ማገጃ. An injunction directed the teachers' union not to strike. የመምህራን ፡ ኅብረት ፡ ሥራ ፡ እንዳያቆም ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ማገጃ ፡ መጣበት

**injure**
1. አበላሸ. Do not injure the bushes in the park! በመናፈሻው ፡ ቦታ ፡ ያሉትን ፡ ቁጥቋጦዎች ፡ አታበላሽ
2. ተጐዳ. She fell and injured her leg. ወድቃ ፡ እግሯን ፡ ተጐዳች
3. ጐዳ. Dishonesty injures a business. ታማኝነትን ፡ ማጉደል ፡ ሥራ ፡ ይጐዳል
4. አጐደፈ. The director injured his reputation. ዲሬክተሩ ፡ ዝናውን ፡ አጐደፈ
5. አዋረደ. He injured his pride by asking his parents for money. ወላጆቹን ፡ ገንዘብ ፡ በመጠየቅ ፡ ክብሩን ፡ አዋረደ

**injured** (n.) የተጐዳ ፤ የቈሰለ
After the fire, every available car was used to take the injured to the hospital. ከቃጠሎው ፡ በኋላ ፡ የተጐዱትን ፡ (የቈሰሉትን) ፡ ሰዎች ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ለማድረስ ፡ የተገኘው ፡ መኪና ፡ በሙሉ ፡ ተሠራበት

**be injured**
1. ቈሰለ. How many people were injured in the accident? በአደጋው ፡ ስንት ፡ ሰዎች ፡ ቈሰሉ ?
2. ተጐዳ. When a pregnant cow is injured, it will abort. ከብድ ፡ የሆነች ፡ ላም ፡ ስትጐዳ ፡ ትጨነግፋለች

**(be) injurious to** ጐዳ
Lack of sleep is injurious to health. እንቅልፍ ፡ ማጣት ፡ ጤናን ፡ ይጐዳል

**injury** (injuries)

1. ጉዳት. He received only a minor injury in the crash. ባደጋው ፡ የደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ትንሽ ፡ ነበር
2. ቁስል. His injury requires only slight treatment. ቁስሉ ፡ ቀላል ፡ ሕክምና ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚያስፈልገው
3. መጐዳት. The injury to his knee disabled him for many weeks. የጉልበቱ ፡ መጐዳት ፡ ለብዙ ፡ ሳምንታት ፡ ከሥራው ፡ ውጭ ፡ አደረገው
4. ማዋረድ. He considered it an injury to his pride to ask his parents for money. ወላጆቹን ፡ ገንዘብ ፡ መጠየቅን ፡ ክብሩን ፡ እንደ ፡ ማዋረድ ፡ ቈጠረው

**injustice**

1. በደል. He raged against the injustices inflicted on him. በደረሰበት ፡ በደል ፡ ጦፏል
2. የግፍ ፡ ሥራ. The troubles stem from injustices of long standing. ችግሩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከቆየ ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ የመነጨ ፡ ነው
3. ግፍ. Shooting cattle without any good reason is an injustice. የቀንድ ፡ ከብቶችን ፡ ያላንዳች ፡ ምክንያት ፡ መረሸን ፡ ግፍ ፡ ነው

**do an injustice** በደለ
You do him an injustice by not appointing him. ካልሾምከው ፡ በደልከው ፡ ማለት ፡ ነው

**ink** ቀለም
Write the test in ink! ፈተናውን ፡ በቀለም ፡ ጻፍ
[See also 'dip']

**inkling** ፍንጭ
Daniel had no inkling of their plans. ዳንኤል ፡ ስለ ፡ እቅዳቸው ፡ ምንም ፡ ፍንጭ ፡ አልነበረውም

**inkpad** የቀለም ፡ መርገጫ
He needs an inkpad for stamping documents. ሰነዶችን ፡ ለማተም ፡ የቀለም ፡ መርገጫ ፡ ያስፈልገዋል

**inkwell** የቀለም ፡ ማስቀመጫ
Each desk has an inkwell. እያንዳንዱ ፡ ዴስክ ፡ የቀለም ፡ ማስቀመጫ ፡ አለው

**inlaid** የተሰካበት
The desk had an inlaid design of ivory. ጠረጴዛው ፡ የዝሆን ፡ ጥርስ ፡ የተሰካበት ፡ ጌጥ ፡ ነበረው

**inland** (adj.) ገባ ፡ ያለ
Some inland areas do not yet have roads. አንዳንድ ፡ ገባ ፡ ያሉ ፡ ስፍራዎች ፡ ገና ፡ መንገድ ፡ አልተሠራላቸውም

**inland** (adv.) ወደ ፡ መኻል ፡ አገር
They left the ship and walked several miles inland on foot. ከመርከብ ፡ ወርደው ፡ ለብዙ ፡ ማይል ፡ ወደ ፡ መኻል ፡ አገር ፡ ገቡ

**in-laws** አማቶች
My in-laws are coming to visit me. አማቶቼ ፡ ሊጠይቁኝ ፡ ይመጣሉ

**inlay** (inlaid) ለበደ
He inlaid the chest with dark wood. ቁም ፡ ሣጥኑን ፡ በጥቁር ፡ ዕንጨት ፡ ለበደው

**inlet** ትንሽ ፡ ሰላጤ
His house is built beside an inlet of the lake. ቤቱ ፡ ከሐይቁ ፡ ዳር ፡ ትንሽ ፡ ሰላጤ ፡ አጠገብ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**inmate**

1. እስረኛ. The inmate refused to accept the food. እስረኛው ፡ ምግቡን ፡ አልቀበልም ፡ አለ
2. ነዋሪ ፡ በሽተኛ. One of the inmates of the mental institution escaped. የአእምሮ ፡ በሽተኞች ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ነዋሪ ፡ ከሆኑት ፡ በሽተኞች ፡ አንዱ ፡ አመለጠ

**inmost**

1. የልብ. His inmost desire was to be a writer. የልብ ፡ ምኞቱ ፡ ደራሲ ፡ ለመሆን ፡ ነበረ
2. የመጨረሻ. We went to the inmost depths of the mine. ማዕድኑ ፡ ውስጥ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ጥልቀት ፡ ገባን

**inn** ትንሽ ፡ ሆቴል
There is an inn on the road to Dessie. ወደ ፡ ደሴ ፡ በሚወስደው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ ሆቴል ፡ አለ

**innate** የተፈጥሮ
He has an innate talent for drawing. ለሥዕል ፡ ሥራ ፡ የተፈጥሮ ፡ ተሰጥኦ ፡ አለው

**inner**

1. የውስጠኛ. The inner door is locked. የውስጠኛው ፡ መዝጊያ ፡ ተቈልፏል
2. የልብ. She kept her inner thoughts to herself. የልብ ፡ ምስጢሯን ፡ በሆዷ ፡ ያዘች

**inner circle of** የቅርብ
Only the inner circle of his friends knows about his plans. ስለ ፡ እቅዱ ፡ የሚያውቁት ፡ የቅርብ ፡ ጓደኞቹ ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**innermost** የመካከለኛ
Only the innermost parts of the book have not been touched by the water. ውኃ ፡ ያልነካው ፡ የመጽሐፉን ፡ የመካከለኛው ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ነው

**innings**

*Our party will have its innings after the next election. የኛ ፡ ፓርቲ ፡ ከሚቀጥለው ፡ ምርጫ ፡ በኋላ ፡ እቅዱን ፡ ለማከናወን ፡ ዕድል ፡ ይኖረዋል

**innocence**

1. ንጹሕ ፡ መሆን ፤ ንጽሕና ፤ ጥፋተኛ ፡ አለመሆን. How did he prove his innocence of the crime? ከወንጀሉ ፡ ንጹሕ ፡ ለመሆኑ ፡ ምን ፡ ማረጋገጫ ፡ ሰጠ?

Even though his innocence was known, he died without receiving justice. ምንም ፡ እንኳ ፡ ንጽሕ ናው ፡ ቢታወቅም ፡ ፍትሕ ፡ ሳያገኝ ፡ ሞተ

His confession proved my innocence. የሱ ፡ ማመን ፡ የኔን ፡ ጥፋተኛ ፡ አለመሆን ፡ አረጋገጠ

2. አለማወቅ. She pleaded innocence of the law. ሕጉን ፡ ባለማወቅ ፡ ማጥፋቷን ፡ አመለከተች

3. የዋህነት. The innocence of little children is lost as they grow up. የትንንሽ ፡ ልጆች ፡ የዋህነት ፡ እያደጉ ፡ ሲሄዱ ፡ ይቀራል

**innocent**

1. የዋህ. Don't be so innocent as to believe everything the politicians say. የፖለቲካ ፡ ሰዎች ፡ የሚሉትን ፡ ሁሉ ፡ ለማመን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የዋህ ፡ አትሁን

2. (= noun) ወንጀለኛ ፡ አለመሆኑ. The investigation showed that he was innocent. ምርመራው ፡ ወንጀለኛ ፡ አለመሆኑን ፡ አረጋገጠ

3. ንጹሕ. The arrest of the innocent man disconcerted the policemen. የንጹሕ ፡ ሰው ፡ መያዝ ፡ ፖሊሶቹን ፡ አደናገራቸው

He was innocent of the crime. ከወንጀሉ ፡ ንጹሕ ፡ ነበር

4. (= adv.) ያለ ፡ ኀጢአት. Many innocent persons lost their heads in the French Revolution. በፈረንሳይ ፡ ሽብር ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያለ ፡ ኀጢአታቸው ፡ ተገደሉ

5. በቅን ፡ ልቡና ፡ የተሰጠ. It was just an innocent remark. በቅን ፡ ልቡና ፡ የተሰጠ ፡ አስተያየት ፡ ነበር

**be innocent** ጥፋተኛ ፡ አይደለም

The lawyer asserted that his client was innocent. ጠበቃው ፡ ነገርተኛው ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለም ፡ ሲል ፡ ተከራከረ

**stand innocent**

*He stands innocent of any wrong. ምንም ፡ ጥፋት ፡ የለበትም

**innocuous** የማያስከፋ

He made an innocuous remark. የማያስከፋ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠ

**be innocuous** መርዘኛ ፡ አይደለም

Some snakes are innocuous. አንዳንድ ፡ እባቦች ፡ መርዘኛ ፡ አይደሉም

**innovate**

1. አሁን ፡ አመጣ. They innovated the saying of prayers in Amharic. ባማርኛ ፡ ጸሎት ፡ ማድረስ ፡ አሁን ፡ ያመጡት ፡ ነገር ፡ ነው

2. አዲስ ፡ (ዘዴ) ፡ ፈጠረ. When the older methods no longer work, you must innovate. የቆዩ ፡ ዘዴዎች ፡ በማያገለግሉበት ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ መፍጠር ፡ አለብህ

**innovation**

1. የመጣ ፡ አዲስ ፡ አሠራር. He fought against the innovations which had entered the church. በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ የመጣውን ፡ አዲስ ፡ አሠራር ፡ ለማስቀረት ፡ ታገለ

2. አዲስ ፡ ነገር. Lighting by electricity was an innovation in 1890. በ፲፰፻፹፪ ዓ. ም. በኤሌክትሪክ ፡ ብርሃን ፡ መስጠት ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ነበር

**innuendo, make (innuendos)** በአሽሙር ፡ ተናገረ

He is making innuendos about my honesty. ስለኔ ፡ ታማኝነት ፡ በአሽሙር ፡ ይናገራል

**innumerable** ቁጥር ፡ስፍር ፡ የሌለው

There were innumerable ants on our food. በምግባችን ፡ ላይ ፡ ቁጥር ፡ ስፍር ፡ የሌለው ፡ ጉንዳን ፡ ነበር

**inoculate** ክትባት ፡ አደረገለት

The doctor will inoculate you against smallpox. ዶክተሩ ፡ የፈንጣጣ ፡ ክትባት ፡ ያደርግልሃል

**inoculation** ክትባት

Smallpox inoculations will be given free. የፈንጣጣ ፡ ክትባት ፡ በነጻ ፡ ይሰጣል

**inoffensive** የማያስቀይም

He has a very inoffensive manner, so no one gets mad at him. የማያስቀይም ፡ ጠባይ ፡ ስላለው ፡ ማንም ፡ አይናደድበትም

**(be) inoperative** ከገልግሎት ፡ ውጭ ፡ ሆነ

The law regulating slavery has been inoperative since slavery was abolished. ባርነትን ፡ የሚቈጣጠረው ፡ ሕግ ፡ ባርነት ፡ ከተወገደ ፡ ወዲህ ፡ ከገልግሎት ፡ ውጭ ፡ ሆኗል

**inopportune**

1. የማይመች. He came at an inopportune time. በማይመች ፡ ጊዜ ፡ መጣ

2. ያለጊዜው ፡ የመጣ. An inopportune call delayed us. ያለጊዜው ፡ የመጣ ፡ የቴሌፎን ፡ ጥሪ ፡ አዘገየን

**(be) inordinate ተገቢ ፡ አልነበረም**
His anger was inordinate. ቁጣው ፡ ተገቢ ፡ አልነበረም

**inordinate amount of መጠን ፡ የሌለው**
There was an inordinate amount of confusion on registration day. በምዝገባ ፡ ቀን ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ ትርምስምስ ፡ ነበረ

**inquest ምርመራ**
The inquest showed the woman died from drowning. ምርመራው ፡ ሴትዮዋ ፡ ሰጥማ ፡ መሞቷን ፡ አሳየ

**inquire ጠየቀ**
You'd better inquire first whether the job is still open. ሥራው ፡ አሁንም ፡ እንዳለ ፡ አስቀድመህ ፡ ብትጠይቅ ፡ ይሻላል

**inquire into መረመረ**
We must inquire into the matter of the missing money. ገንዘቡ ፡ ስለ ፡ መጥፋቱ ፡ ጉዳይ ፡ መመርመር ፡ አለብን

**inquire after one**
1. ጠየቀ. Inquire after my friends when you go to my hometown. ወደ ፡ ተወለድኩበት ፡ ከተማ ፡ ስትሄድ ፡ ጓደኞቼን ፡ ጠይቅልኝ
2. ስለ ፡ ጤንነት ፡ ዐወቀ. Friends have been calling all morning to inquire after you. ጓደኞችህ ፡ ስለ ፡ ጤንነትህ ፡ ለማወቅ ፡ ጧት ፡ ሲደውሉ ፡ አረፈዱ

**inquiry** (inquiries) **ምርመራ**
An inquiry into the crime is being held. ስለ ፡ ወንጀሉ ፡ ምርመራ ፡ በመደረግ ፡ ላይ ፡ ነው

**make inquiries አጠያየቀ**
He made inquiries about the suspect. ስለተጠረጠረው ፡ ሰው ፡ አጠያየቀ

**on inquiry በተጠየቀ ፡ ጊዜ**
Details will be given on inquiry. ዝርዝሩ ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ይሰጣል

**inquisition ምርመራ**
The inquisition uncovered many heresies. ምርመራው ፡ ብዙ ፡ መናፍቃንን ፡ አጋለጠ

**inquisitive ተመራማሪ**
He has an inquisitive mind, and had acquired a lot of knowledge at an early age. ተመራማሪ ፡ አእምሮ ፡ ስላለው ፡ ገና ፡ በወጣትነቱ ፡ ብዙ ፡ ዕውቀት ፡ ቀሥሟል

**be inquisitive ጥያቄ ፡ አበዛ**
Children are usually inquisitive. ልጆች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጥያቄ ፡ ያበዛሉ

**inroad, make an ~ into ጥሶ ፡ ገባ**
Our troops made an inroad into the enemy's line. ወታደሮቻችን ፡ ጠላትን ፡ ጥሰው ፡ ገቡ

**make inroads on**
1. አመነመነ. His expenses made great inroads on his savings. ወጪው ፡ ያጠራቀመውን ፡ ገንዘብ ፡ በጣም ፡ አመነመነው
2. አወከ. Eating too much makes inroads on your health. ብዙ ፡ መብላት ፡ ጤንነትህን ፡ ያውከዋል

**inrush ኀይለኛ ፡ አወራረድ**
The inrush of water quickly filled our tanks. የውኃው ፡ ኀይለኛ ፡ አወራረድ ፡ በርሜላችንን ፡ ቶሎ ፡ ሞላው

**insane** (n.)
1. እብድ. There are many of the insane in Emmanuel Hospital. አማኑኤል ፡ ሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ እብዶች ፡ አሉ
2. የአእምሮ ፡ ሕመምተኛ. A mental hospital treats the insane. የእብዶች ፡ ሆስፒታል ፡ የአእምሮ ፡ ሕመምተኞችን ፡ ያክማል

**insane** (adj.)
1. የእብዶች. There is an insane asylum in the city. በከተማ ፡ ውስጥ ፡ የእብዶች ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ አለ
2. አእምሮው ፡ የታወከ. Insane people are not responsible. አእምሮዋቸው ፡ የታወከ ፡ ሰዎች ፡ በኀላፊነት ፡ አይጠየቁም

**be insane አበደ**
You are insane if you think that he will give you any money. ገንዘብ ፡ ይሰጠኛል ፡ ብለህ ፡ አስበህ ፡ እንደሆን ፡ አብደሃል

**insanitary ለጤና ፡ ጠንቅ**
Letting flies walk on your food is insanitary. ዝንቦች ፡ በምግብህ ፡ ሲያርፉ ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ ለጤና ፡ ጠንቅ ፡ ነው

**insanitary conditions የንጽሕና ፡ ጉድለት**
The inspector criticized the insanitary conditions of the kitchen. ተቈጣጣሪው ፡ የማድቤቱን ፡ የንጽሕና ፡ ጉድለት ፡ ነቀፈ

**insanity**
1. እብደት. Due to his insanity, he had to be hospitalized. በእብደት ፡ ምክንያት ፡ ሆስፒታል ፡ መግባት ፡ ግድ ፡ ሆነበት
2. አንጐለ ፡ መታወክ. The criminal pleaded insanity. ወንጀለኛው ፡ አንጐለ ፡ መታወኩን ፡ እንደ ፡ ምክንያት ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረበ

**strain of insanity** ንክነት
There is a strain of insanity in the family. በቤተሰባቸው ፡ ንክነት ፡ አለ

**insatiable** የማይረካ
The child's insatiable curiosity often got him in trouble. የሕፃኑ ፡ የማይረካ ፡ የማወቅ ፡ ፍላጎ ት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ይጥለዋል

**be insatiable** አልጠገበም
He is insatiable, though he eats constantly. ያለማቋረጥ ፡ ቢበላም ፡ አይጠግብም

**inscribe**
1. ቀረጸ. I asked the jeweler to inscribe the ring with my name. በቀለበቱ ፡ ላይ ፡ ስሜን ፡ እ ንዲቀርጽ ፡ ላንጥረኛው ፡ ነገርኩት
2. አሰፈረ. The Emperor inscribed his name on the photograph. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ስማቸው ን ፡ በፎቶግራፉ ፡ ላይ ፡ አሰፈሩ

**be inscribed**
1. ተጻፈ. The words were inscribed over the door. ቃላቱ ፡ መዝጊያው ፡ ላይ ፡ ተጽፈው ፡ ነበር
2. ተቀረጸ. My father's words are inscribed on my memory. ያባቴ ፡ ንግግር ፡ በአእምሮዬ ፡ ውስጥ ፡ ተቀርጿል

**inscription**
1. ጽሑፍ. He cut an inscription into the wall of the castle. በግምቡ ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ ጽሑፍ ፡ ቀረጸ
2. የተቀረጸ ፡ ጽሑፍ. Can you read the inscription on the stone? በድንጊያው ፡ ላይ ፡ የተቀረጸው ን ፡ ጽሑፍ ፡ ልታነብ ፡ ትችላለህ?

**(be) inscrutable**
*The expression on his face was inscrutable. ፊቱን ፡ በማየት ፡ ብቻ ፡ የሚያስበውን ፡ ማወቅ ፡ አይቻልም

**insect** ነፍሳት
An insect is crawling down my back. አንድ ፡ ነ ፍሳት ፡ በጀርባዬ ፡ ላይ ፡ ትሄዳለች
[See also 'pest']

**insecticide** የተባይ ፡ ማጥፊያ ፤ የተባይ ፡ መከላከያ
The farmer impregnated the soil with insecticides. ገበሬው ፡ መሬቱን ፡ የተባይ ፡ ማጥፊያ ፡ (መ ከላከያ) ፡ ጨመረበት

**insecure** የማያስተማምን
Their insecure partnership ended in a quarrel. የማያስተማምን ፡ ሽርክናቸው ፡ በጠብ ፡ ተፈጸመ

**be insecure**
1. ጥብቅ ፡ አልሆነም. If the lock is insecure, the thief will be able to get in. ቁልፉ ፡ ጥብ ቅ ፡ ካልሆነ ፡ ሌባ ፡ ሊገባ ፡ ይችላል
2. አልተማመነም. She was insecure in her job. በሥራዋ ፡ አትማመንበትም ፡ ነበር

**feel insecure** ፍራቻ ፡ አደረ(በት)
The child feels insecure when his mother is away. እናቱ ፡ በሌለችበት ፡ ጊዜ ፡ ሕፃኑ ፡ ፍራ ቻ ፡ ያድርበታል

**insensible, by ~ degrees** በማይሰማ ፡ አኳኋን
The room grew cold by insensible degrees. ክፍሉ ፡ በማይሰማ ፡ አኳኋን ፡ እየቀዘቀዘ ፡ ሄደ

**be insensible** ነፍሱን ፡ ሳተ
The rock struck her on her head, and she was insensible for nearly an hour. በድንጋይ ፡ ራሷ ን ፡ ስለተመታች ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ነፍሷ ን ፡ ስታ ፡ ነበር

**be insensible of**
1. አልተገነዘበም. We are not insensible of your kindness. ደግነትህን ፡ ሳንገነዘብ ፡ አልቀረንም
2. አላወቀም. The boys in the boat were insensible of the danger. በመርከብ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ፡ ልጆች ፡ አደጋ ፡ መኖሩን ፡ አላወቁም ፡ ነበር

**be insensible to** አልተሰማ(ውም) ፤ ከጤፍም ፡ አልተሰማ(ውም)
⁺His frozen fingers are insensible to pain. በ ብርድ ፡ የደነዘዙ ፡ ጣቶቹ ፡ ሕመም ፡ አይሰማቸው ም ፡ ነበር
He was insensible to the needs of his children and did not give them any help. የልጆቹ ፡ ችግር ፡ ከጤፍም ፡ ስለማይሰማው ፡ ምንም ፡ እርዳ ታ ፡ አላደረገላቸውም

**(be) insensitive to** ስሜቱን ፡ አልነካውም
⁺He was insensitive to the sea's grandeur. የባሕሩ ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ስሜቱን ፡ አልነካውም

**make insensitive** አደነዘዘ
The dentist made Tom's tooth insensitive before he pulled it. ጥርሱን ፡ ከመንቀሉ ፡ በፊ ት ፡ ሐኪሙ ፡ የቶምን ፡ ጥርስ ፡ አደነዘዘው

**inseparable** የማይለያዩ
These two are inseparable friends. እነዚያ ፡ ሁለ ቱ ፡ የማይለያዩ ፡ ጓደኞች ፡ ናቸው

**insert**
1. አስገባ. Insert the screwdriver into the keyhole! ጠመንጃ ፡ መፍቻውን ፡ ቁልፉ ፡ ቀዳዳ ፡ ውስጥ ፡ አስገባ
2. ከተተ. He inserted the book into his pocket. መጽሐፉን ፡ ኪሱ ፡ ውስጥ ፡ ከተተው

3. **አከለ**. They inserted several maps into the history book. በታሪኩ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ካርታዎች ፡ አከሉ

**insertion** ማውጣት
The insertion of an advertisement in a newspaper often gets results. የንግድ ፡ ማስታወቂያን ፡ በጋዜጣ ፡ ማውጣት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ውጤት ፡ ያስገኛል
*The insertion of chemicals is done by machine. የኬሚካል ፡ ቅመም ፡ የሚጨመረው ፡ በመኪና ፡ ነው

**inside** (n.) ውስጥ
May I see the inside of the house? የቤቱን ፡ ውስጥ ፡ ማየት ፡ እችላለሁ ?

**inside** (adj.)
1. **የውስጥ**. The inside pages of the paper are missing. የጋዜጣው ፡ የውስጥ ፡ ገጾች ፡ ጠፍተዋል
2. **ምስጢራዊ**. Inside information shows that the government will seek a peaceful settlement. ምስጢራዊ ፡ ዜና ፡ መንግሥቱ ፡ ሰላማዊ ፡ ፍጻሜ ፡ የሚፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል

**inside** (prep.)
1. **ውስጥ ፤ እ - - - ውስጥ**. There is nothing inside this can. ጣሳው ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ የለም
They are inside the house now. አሁን ፡ እቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው
2. **በ - - - ውስጥ**. He promised to arrive inside an hour. ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ እደርሳለሁ ፡ ብሏል

**inside** (adv.)
1. **እውስጥ**. Don't take the chair out; leave it inside! ወንበሩን ፡ ከቤት ፡ አታውጣው ፤ እውስጥ ፡ ተወው
2. **በተፈጥሮው**. Inside, she is really very shy. በተፈጥሮዋ ፡ ዓይነ ፡ አፋር ፡ ናት
3. **ወደ ፡ ቤት**. Go inside! It is raining. ወደ ፡ ቤት ፡ ግባ ፤ ይዘንባል

**inside of በ - - - ውስጥ**
Inside of five minutes, the theater was empty. ባምስት ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ የቲያትር ፡ ቤቱ ፡ ባዶ ፡ ቀረ

**inside out**
1. **ጠንቅቆ**. He knows his business inside out. ሥራውን ፡ ጠንቅቆ ፡ ያውቃል
2. **መውጫ ፡ መግቢያውን**. I know that town inside out. ከተማውን ፡ መውጫ ፡ መግቢያውን ፡ አውቀዋለሁ
3. **ገልብጦ**. He has his sweater on inside out. ሹራቡን ፡ ገልብጦ ፡ ለብሶታል

**insider** ቤተኛ
Only the insiders know what's really going on. ነገሩን ፡ በእርግጥ ፡ የሚያውቁት ፡ ቤተኞች ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**insidious**
1. **የተንኰል**. His insidious plan to take control of the government nearly succeeded. መንግሥቱን ፡ ለመያዝ ፡ ያደረገው ፡ የተንኰል ፡ እቅድ ፡ ሊሳካ ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር
2. **ተንኰልን ፡ ያዘለ**. His insidious remark provoked a quarrel. ተንኰልን ፡ ያዘለ ፡ አስተያየቱ ፡ ጠብ ፡ ቀሰቀሰ
3. **ሳይታወቅ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ የሚበላ**. Cancer is an insidious disease. ካንሰር ፡ ሳይታወቅ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ የሚበላ ፡ በሽታ ፡ ነው

**insight**
*Because of his insight, many people come to ask his advice. አስተዋይ ፡ ስለሆነ ፡ ምክር ፡ ለማግኘት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደሱ ፡ ይመጣሉ

**get an insight ጠልቆ ፡ ዐወቀ**
That is how I got an insight into his character. ጠባዩን ፡ ጠልቄ ፡ ያወቅሁት ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ መንገድ ፡ ነው

**insignia** አርማ
The crown and the scepter are royal insignias. ዘውድና ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ የንጉሥ ፡ አርማ ፡ ናቸው

**insignificant**
1. **አነስተኛ**. Heavy industry plays an insignificant role here. ከባድ ፡ እንዱስትሪ ፡ እዚህ ፡ የሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ አነስተኛ ፡ ነው
2. **የማይረባ**. I am not interested in the insignificant details. ለማይረቡት ፡ ዝርዝር ፡ ጉዳዮች ፡ ግድ ፡ የለኝም

**insincere** ካንገት ፡ በላይ
Her smile is insincere. ፈገግታዋ ፡ ካንገት ፡ በላይ ፡ ነው

**insinuate**
1. **በአግቦ ፡ ተናገረ**. He insinuated that she is dishonest. ታማኝ ፡ ያለመሆኗን ፡ በአግቦ ፡ ተናገረ
2. **አሳደረ**. The enemy propaganda insinuated doubt into the minds of the people. የጠላት ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ጥርጣሬ ፡ አሳደረ

**insinuate oneself into**
1. **ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ገባ**. The stray cat insinuated himself into our kitchen. ባለቤት ፡ የሌለው ፡ ድመት ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ማድቤታችን ፡ ውስጥ ፡ ገባ

2. ተለማምጦ ፡ አገኘ. He insinuated himself into the minister's favor. ተለማምጦ ፡ የሚኒስትሩን ፡ መውደድ ፡ አገኘ

**(be) insipid** ጣዕም ፡ የለውም
The stew is insipid. ወጡ ፡ ጣዕም ፡ የለውም

**insist** ድርቅ ፡ አለ
He insisted that he was innocent. ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ብሎ ፡ ድርቅ ፡ አለ
*I insist that you go to see him. ልታየው ፡ ይገባል ፡ እላለሁ

**insist on** ታገለ
I insist on my rights. ለመብቴ ፡ እታገላለሁ
*The child insisted on having candy. ሕፃኑ ፡ ከረሜላ ፡ ካልሰጣችሁኝ ፡ ብሎ ፡ ችክ ፡ አለ
*Because this woman does not know how to manage money, her husband insists on doing it. ሴትዮዋ ፡ የገንዘብ ፡ አያያዝ ፡ ስለማታውቅ ፡ ባሏ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ ካልያዝኩት ፡ ይላል

**insistence** ችክ ፡ ማለት
His insistence that I go to school annoys me. ትምህርት ፡ ቤት ፡ ካልገባህ ፡ ብሎ ፡ ችክ ፡ ማለቱ ፡ ያበሳጨኛል

**insistent**
1. (= adv.) አጥብቆ. Despite his insistent urging, I didn't want to accept his proposal. ምንም ፡ እንኳ ፡ አጥብቆ ፡ ቢለምነኝ ፡ ያቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ ልቀበል ፡ አልፈለግሁም
2. (= adv.) አሁንም ፡ አሁንም. The insistent ringing of the telephone disturbed me in my work. የስልኩ ፡ አሁንም ፡ አሁንም ፡ መደወል ፡ ሥራ ፡ አላሠራ ፡ አለኝ

**be insistent**
1. ድርቅ ፡ አለ. In spite of the rain, he was insistent on going out. ምንም ፡ እንኳን ፡ ቢዘንብ ፡ ካልሄድኩ ፡ ብሎ ፡ ድርቅ ፡ አለ
2. በግድ ፡ ያዘ. I did not want to go but he was insistent. ለመሄድ ፡ አልፈለግሁም ፡ ነበር ፡ ግን ፡ በግድ ፡ ያዘኝ

**insofar as** እንደም + imperfect + ከሆነ
He is working insofar as I can tell. እኔ ፡ እንደማውቀው ፡ ከሆነ ፡ ይሠራል
*I shall do what I can insofar as I am able. በሚቻለኝ ፡ መጠን ፡ ዐቅሜ ፡ የሚፈቅድልኝን ፡ እሠራለሁ

**insolence** ብልግና ፤ ስድነት
How can you suffer such insolence? እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ብልግና ፡ (ስድነት) ፡ እንዴት ፡ ትታገሠዋለህ ?

**insolent** ባለጌ
Punish that insolent brat! ያንን ፡ ባለጌ ፡ ልጅ ፡ ቅጣው

**(be) insoluble**
1. አይቀልጥም. Grease is insoluble in cold water. ቅባት ፡ በቀዝቃዛ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ አይቀልጥም
2. ማወቅ ፡ አልተቻለም. The mystery of his death is insoluble. ያሟሟቱን ፡ ምስጢር ፡ ማወቅ ፡ አልተቻለም

**(be) insolvent** ዕዳውን ፡ ሊከፍል ፡ አልቻለም
Due to the crisis, the company was insolvent. በችግሩ ፡ ምክንያት ፡ ኩባንያው ፡ ዕዳውን ፡ ሊከፍል ፡ አልቻለም

**insomnia** የእንቅልፍ ፡ እጦት
He suffers from insomnia. በእንቅልፍ ፡ እጦት ፡ ይሠቃያል

**insomuch**
*He worked fast, insomuch that he finished first. በፍጥነት ፡ ከመሥራት ፡ የተነሣ ፡ ቀድሞ ፡ ጨረሰ

**inspect**
1. ጐበኘ. The general inspected the troops. ጀኔራሉ ፡ ወታደሮቹን ፡ ጐበኘ
2. ፈተሸ. The customs man inspected my baggage. የጉምሩክ ፡ ሠራተኛ ፡ እቃዬን ፡ ፈተሸ
3. መረመረ. A dentist inspects the children's teeth twice a year. የጥርስ ፡ ሐኪም ፡ የልጆችን ፡ ጥርስ ፡ በዓመት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ይመረምራል

**inspection** ፍተሻ
When do we pass the customs inspection? የጉምሩኩን ፡ ፍተሻ ፡ የምናልፈው ፡ መቼ ፡ ነው ?
The soldiers lined up for their daily inspection. ወታደሮቹ ፡ በየዕለቱ ፡ ለሚደረገው ፡ ፍተሻ ፡ ተሰለፉ
*An inspection of the roof showed no leaks. ጣሪያው ፡ ሲታይ ፡ የሚያፈስ ፡ ቀዳዳ ፡ ምንም ፡ አልተገኘም

**on inspection** ሲመረመር
On inspection, the coin proved to be counterfeit. ሲመረመር ፡ ፍራንኩ ፡ የውሸት ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

**inspector** ተቈጣጣሪ
An inspector visits the school every three months. ተቈጣጣሪ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ በየሦስት ፡ ወር ፡ ይጐበኛል

## inspiration

1. መኩሪያ. The captain was an inspiration to his men. ሻምበሉ ፡ ለወታደሮቹ ፡ መኩሪያ ፡ ነበር

2. የሚያነሣሣው ፡ መንፈስ. The poet's inspiration came from his everyday surroundings. ገጣሚውን ፡ የሚያነሣሣው ፡ መንፈስ ፡ ከሚኖርበት ፡ አካባቢ ፡ የመነጨ ፡ ነው

3. ድንቅ ፡ ሐሳብ. Your suggesting that we take an extra tire was an inspiration. ትርፍ ፡ ጎማ ፡ እንያዝ ፡ ብለህ ፡ ያቀረብከው ፡ ሐሳብ ፡ ድንቅ ፡ ሐሳብ ፡ ነበር

4. መተንፈስ. Inspiration through the nose was blocked by a clot of blood. ሰው ፡ አፍንጫው ፡ በረጋ ፡ ደም ፡ ሲደፈን ፡ መተንፈስ ፡ ያቅተዋል

**be an inspiration to** አነቃቃ

The music of the band was an inspiration to the marchers. የጓዱ ፡ ሙዚቃ ፡ ሰልፈኞቹን ፡ የሚያነቃቃ ፡ ነበር

**get inspiration** ስሜቱ ፡ ተቀሰቀሰ

Some people get inspiration from sermons, some from nature. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ስሜታቸው ፡ የሚቀሰቀሰው ፡ በስብከት ፡ ሲሆን ፡ ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ በተፈጥሮ ፡ ነው

**give inspiration** አነሣሣ

The Italian invasion gave inspiration to many Ethiopian writers. የጣሊያን ፡ ወረራ ፡ ብዙዎቹን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ደራሲዎች ፡ ድርሰት ፡ እንዲጽፉ ፡ አነሣሣ

**serve as an inspiration** መንፈስ ፡ አነቃቃ

His memory will serve as an inspiration to posterity. ትዝታው ፡ የተከታዩን ፡ ትውልድ ፡ መንፈስ ፡ ያነቃቃል

## inspire

1. ቀሰቀሰ. Patriotism inspires brave deeds. ጀግንነት ፡ የጀብዱ ፡ ሥራን ፡ ይቀሰቅሳል

2. እንዲጥልበት ፡ አደረገ. He has the quality of inspiring confidence. ሰዎች ፡ እምነት ፡ እንዲጥሉበት ፡ የማድረግ ፡ ችሎታ ፡ አለው

3. መንፈሱን ፡ አነሣሣ. The sunset inspired her to write a poem. የፀሐይ ፡ ጥልቀት ፡ ግጥም ፡ ልትገጥም ፡ መንፈሷን ፡ አነሣሣት

**be inspired**

1. ተገለጸ. He claims that his writings were inspired by God. የሚጽፋቸው ፡ ጽሑፎች ፡ በእግዜር ፡ የተገለጹልኝ ፡ ናቸው ፡ ይላል

2. (= active) ገፋፋ. They were inspired by a belief in a better future. የወደፊት ፡ መልካም ፡ ኑሮ ፡ ገፋፋቸው

## install

1. አቆመ. They installed the machinery in the factory. መኪናውን ፡ ፋብሪካው ፡ ውስጥ ፡ አቆሙ

2. ቀጠለ. The company installed my telephone yesterday. ኩባንያው ፡ ትናንትና ፡ ስልክ ፡ ቀጠለልኝ

3. አስገባ. The company installed a new gas stove. ኩባንያው ፡ አዲስ ፡ የጋዝ ፡ ምድጃ ፡ አስገባ

*The university installed a new president today. ዛሬ ፡ አዲሱ ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተደርጎለት ፡ ሥልጣኑን ፡ ተረከበ

**install oneself**

1. ጥቅልል ፡ ብሎ ፡ ተኛ. The cat installed itself near the fire. ድመቷ ፡ እሳቱ ፡ አጠገብ ፡ ጥቅልል ፡ ብላ ፡ ተኛች

2. ገባ. We installed ourselves yesterday in our new quarters. ትናንት ፡ አዲሱ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ገባን

## installation ድርጅት

In Algeria the underground movement succeded in capturing all important installations. አልጄሪያ ፡ ውስጥ ፡ ምስጢራዊው ፡ እንቅስቃሴ ፡ ዋናዋናዎቹን ፡ ድርጅቶች ፡ በቶሎ ፡ ለመያዝ ፡ ቻለ

## installment

1. ተከታታይ ፡ እትም. This story appeared in Life in five installments. ይህ ፡ ታሪክ ፡ በላይፍ ፡ መጽሔት ፡ ባምስት ፡ ተከታታይ ፡ እትም ፡ ወጣ

2. የጊዜ ፡ ክፍያ. You can pay it in five installments. ባምስት ፡ የጊዜ ፡ ክፍያ ፡ ልትጨርሰው ፡ ትችላለህ

**on installment**

*We bought the furniture on installment. የቤቱን ፡ እቃ ፡ ዋጋውን ፡ በየጊዜው ፡ ከፍለን ፡ ለመጨረስ ፡ ገዛን

## instance

1. ማስረጃ. This is another instance of his carelessness. የሱ ፡ ግድ ፡ የለሽነት ፡ ይህ ፡ ሌላው ፡ ማስረጃ ፡ ነው

2. ምሳሌ. Lincoln is an instance of a poor boy who became famous. ሊንኮልን ፡ ከድኽነት ፡ ተነሥቶ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ምሳሌ ፡ ነው

3. ጊዜ. The fine in the first instance is $10. ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ መቀጫው ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ ነው

**at the instance of** በ - - - መገፋፋት

The pupils entered the contest at the instance of their teacher. ባስተማሪው ፡ መገፋፋት ፡ ተማሪዎቹ ፡ ውድድሩ ፡ ውስጥ ፡ ገቡ

**for instance** ለምሳሌ

There are quite a few possibilities; for instance - - - ብዙ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ አለ ፤ ለምሳሌ - - -

**in the first instance** መጀመሪያ ፡ ነገር
In the first instance, this man is a thief. መጀመሪያ ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ሌባ ፡ ነው

**in this instance** በዚህ ፡ ረገድ
In this instance you are wrong. በዚህ ፡ ረገድ ፡ አንተ ፡ ተሳስተሃል

**instant** (n.), **at that ~** በዚያን ፡ ጊዜ
At that instant the bell rang. በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ደወሉ ፡ ተደወለ

**for an instant** ለጥቂት ፡ ጊዜ
He paused for an instant. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ቆም ፡ አለ

**in an instant** ባንድ ፡ አፍታ ፤ ባንዳፍታ
He was gone in an instant. ባንድ ፡ አፍታ ፡ እልም ፡ አለ

**just an instant** ጥቂት
Wait just an instant! ጥቂት ፡ ቆይ

**the instant** ወዲያው ፡ እንደ + perfect
I sent you the news the instant I heard it. ወሬውን ፡ ወዲያው ፡ እንደሰማሁት ፡ ላኩብህ

**this instant** አሁኑኑ
Come here this instant! አሁኑኑ ፡ ና

**instant** (adj.)
1. አስቸኳይ. When there is a fire, there is an instant need for action. የእሳት ፡ ቃጠሎ ፡ ሲነሣ ፡ አስቸኳይ ፡ እርምጃ ፡ መውሰድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
2. (= adv.) ወዲያውኑ. He felt instant relief when the medicine was put on. መድኃኒቱ ፡ ሲደረግለት ፡ ወዲያውኑ ፡ ከሥቃይ ፡ እፎይ ፡ አለ
3. (= adv.) ባንዳፍታ. The play was an instant success. ቲያትሩ ፡ ባንዳፍታ ፡ ተወዳጅነትን ፡ አገኘ
4. [አስቀድሞ ፡ የተዘጋጀ ፡ ለመጠጣትም ፡ ሆነ ፡ ለመብላት ፡ ሲፈለግ ፡ ውኃ ፡ ብቻ ፡ የሚያስጨምር ፡ መጠጥ ፡ ወይም ፡ ምግብ]

**instantly** ባንድ ፡ አፍታ ፤ ባንዳፍታ
I shall come instantly. ባንድ ፡ አፍታ ፡ እመጣለሁ

**instead** በሱ ፡ ፈንታ
If Henry is sick tomorrow take me on the trip instead. ሄንሪ ፡ ነገ ፡ ከታመመ ፡ በሱ ፡ ፈንታ ፡ ሽርሽር ፡ ውሰደኝ
What do you want instead? በሱ ፡ ፈንታ ፡ ምን ፡ ትፈልጋለህ ?

**instead of**
1. በ - - - ምትክ. Couldn't you go instead of me? በኔ ፡ ምትክ ፡ ልትሄድ ፡ አትችልም ?
2. በ - - - ፈንታ. He gave me tangerines instead of oranges. በብርቱካን ፡ ፈንታ ፡ መንደሪን ፡ ሰጠኝ
3. ከ + (verbal noun). Why don't you do something instead of complaining all the time? ዘወትር ፡ ከማማረር ፡ ለምን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አታደርግም ?

**instigate** አነሣሣ
The demonstration was not spontaneous; he instigated the whole thing. ሰላማዊ ፡ ሰልፉ ፡ ያልታቀደ ፡ አልነበረም ፤ ሁሉን ፡ ነገር ፡ ያነሣሣው ፡ እሱ ፡ ነው

**instigation** አነሣሽነት
His accusing me was done at the minister's instigation. ሊከሰኝ ፡ የቻለው ፡ በሚኒስትሩ ፡ አነሣሽነት ፡ ነበር

**instigator** አነሣሽ
The instigators of the plot were arrested. የአድማው ፡ አነሣሾች ፡ ተያዙ

**instill** አሳደረ
Reading good books instills a love for literature. ጥሩ ፡ መጻሕፍትን ፡ ማንበብ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍን ፡ ፍቅር ፡ ያሳድራል

**instinct**
1. የተፈጥሮ ፡ ስጦታ. He has an instinct for doing the right thing. ትክክለኛውን ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታ ፡ አለው
2. ተፈጥሮ. Birds learn to fly by instinct. ወፎች ፡ መብረር ፡ የሚለምዱት ፡ በተፈጥሯቸው ፡ ነው

**instinctive** የተፈጥሮ ፡ ችሎታ
Climbing is instinctive in monkeys. የዝንጀሮዎች ፡ ዛፍ ፡ መውጣት ፡ የተፈጥሮ ፡ ችሎታ ፡ ነው

**institute** (v.)
1. ደነገገ. The club instituted new laws. ክበቡ ፡ አዲስ ፡ ሕጎች ፡ ደነገገ
2. ያዘ. The police instituted a search. ፖሊሶቹ ፡ ፍለጋ ፡ ያዙ
3. ጀመረ. The college instituted a new course in Ethiopian literature. ኮሌጁ ፡ አዲስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ትምህርት ፡ ጀመረ

**Institute** (n.) ኢንስቲቱት
The Institute of African Studies deals with factors related to Africa. የአፍሪካ ፡ ጥናት ፡ ኢንስቲቱት ፡ የአፍሪካን ፡ ጉዳዮች ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ነገሮች ፡ ያጠናል

**institute** ድርጅት
We should have an institute that can grant

academic degrees. ለቀለም ፡ ትምህርት ፡ ዲግሪ ፡ የሚሰጥ ፡ ድርጅት ፡ እንዲኖረን ፡ ያሻል

**institution**
1. ልማድ. Marriage is an ancient institution. ጋብቻ ፡ ከጥንት ፡ የመጣ ፡ ልማድ ፡ ነው
2. ድርጅት. The government is an institution which regulates the welfare of the country. መንግሥት ፡ የሀገሪቷን ፡ ደኅንነት ፡ የሚጠብቅ ፡ ድርጅት ፡ ነው
3. መቋቋም. The institution of a new bank is regulated by law. ያዲሱ ፡ ባንክ ፡ መቋቋም ፡ በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ ነው
**institution of higher learning** ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት
He has never been in an institution of higher learning. ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ አያውቅም
[See also 'mental']

**instruct**
1. አዘዘ. She instructed the maid to sweep the house. ገረዲቷን ፡ ቤቱን ፡ እንድትጠርግ ፡ አዘዘቻት
2. አስታወቀ. My agent instructs me that you still owe me $200. የኔ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ እንዳለብህ ፡ ወኪሌ ፡ አስታወቀኝ
3. አስተማረ. He will instruct me in mathematics. ሒሳብ ፡ ያስተምረኛል

**instruction** ትምህርት
He received much instruction in history. የታሪክ ፡ ትምህርት ፡ በሰፊው ፡ ተምሯል
*Socrates spent his life in the instruction of others. ሶቅራጥስ ፡ ሌሎችን ፡ ሲያስተምር ፡ ሕይወቱን ፡ አሳለፈ
**instructions**
1. መምሪያ. The ambassador received his instructions before going to the conference. ወደ ፡ ጉባኤው ፡ ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ አምባሳደሩ ፡ መምሪያ ፡ ተቀበለ
The head nurse will give you instructions. ዋናዋ ፡ ነርስ ፡ መምሪያ ፡ ትሰጣችኋለች
2. ትእዛዝ. The messenger communicated the general's instructions to the men. ተላላኪው ፡ የጀኔራሉን ፡ ትእዛዝ ፡ ለወታደሮቹ ፡ አስተላለፈ

**(be) instructive**
1. ትምህርት ፡ ሰጠ. It is very instructive to see how country people live. የገጠር ፡ ሰዎች ፡ እንዴት ፡ እንደሚኖሩ ፡ ማየት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትምህርት ፡ ይሰጣል
2. ትምህርት ፡ ተገኘበት. The lecture was very instructive. ንግግሩ ፡ ትምህርት ፡ የሚገኝበት ፡ ነበር

**instructor** አስተማሪ
The arithmetic instructor is sick today. የሒሳብ ፡ አስተማሪው ፡ ዛሬ ፡ ታሟል

**instrument** መሣሪያ
A surgeon's instruments must be clean. የቀዶ ፡ ጠጋኝ ፡ ሐኪም ፡ መሣሪያዎች ፡ ንጹሕ ፡ መሆን ፡ አለባቸው
The army was the dictator's instrument for controlling the country. ጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ አምባገነኑ ፡ ሀገሪቱን ፡ የሚቈጣጠርበት ፡ መሣሪያ ፡ ነበር
The flute is a musical instrument. ዋሽንት ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ ፡ ነው

**(be) instrumental** ከረዱት ፡ ነገሮች ፡ ዋና ፡ ነበር ፤ ብዙ ፡ ረዳ
His tactics were instrumental in defeating the enemy. የተጠቀመባቸው ፡ ዘዴዎች ፡ ጠላትን ፡ ለማሸነፍ ፡ ከረዱት ፡ ነገሮች ፡ ዋናዎቹ ፡ ነበሩ
He was instrumental in finding a job for me. ሥራ ፡ እንዳገኝ ፡ ብዙ ፡ ረዳኝ

**insubordinate** የማይታዘዝ
The officer struck the insubordinate soldier with the flat of his sword. መኰንኑ ፡ የማይታዘዘውን ፡ ወታደር ፡ በጐራዴው ፡ ገጽ ፡ መታው
**be insubordinate** ትእዛዝ ፡ አላከበረም
The lieutenant was arrested because he was insubordinate. መቶ ፡ አለቃው ፡ ትእዛዝ ፡ ስላላከበረ ፡ ተያዘ

**insubordination** አለመታዘዝ
His insubordination was punished by the officer. ባለመታዘዙ ፡ መኰንኑ ፡ ቀጣው

**insubstantial** ብስክስክ
A cobweb is very insubstantial. የሸረሪት ፡ ድር ፡ ብስክስክ ፡ ነው
**be insubstantial** የኀልዮ ፡ ነው
Dreams and ghosts are insubstantial. ሕልምና ፡ ጣረሞት ፡ የኀልዮ ፡ ናቸው

**insufferable** ለመታገሥ ፡ የማይቻል
His insufferable rudeness offended everybody. ለመታገሥ ፡ የማይቻለው ፡ ብልግናው ፡ ሁሉንም ፡ አስቀየመ

**insufficient**
*The police had insufficient evidence to arrest the thief. ፖሊሶቹ ፡ ሌባውን ፡ ለመያዝ ፡ በቂ ፡ መረጃ ፡ አልነበራቸውም

*My funds are insufficient to allow me to buy a car. መኪና ፡ ለመግዛት ፡ ገቢዬ ፡ አይፈቅድል ኝም

**insular**
1. የደሴት. The insular climate is mild all year long. የደሴቱ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ ዓመቱን ፡ ሁሉ ፡ መሀከለኛ ፡ ነው
2. ጠባብ. Their insular attitudes were ridiculed by the French. በጠባብ ፡ አስተያየታቸው ፡ ፈረንሳዮች ፡ ተሳለቁባቸው

**(be) insulated**
*Telephone wires are often insulated by a covering of rubber. የስልክ ፡ ሽቦዎች ፡ ኮረንቲ ፡ እንዳያስተላልፉ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በላስቲክ ፡ ይሸፈናሉ

**insulation**
1. ኮረንቲ ፡ አገድ. He cut some insulation from the wire. ከሽቦው ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ ኮረንቲ ፡ አገድ ፡ ቈረጠ
2. የሙቀት ፡ መከላከያ. Putting insulation in the wall helps keep out the heat. በግድግዳ ፡ ላይ ፡ የሙቀት ፡ መከላከያ ፡ ማድረግ ፡ ሙቀትን ፡ ለመከላከል ፡ ይረዳል

**insult** (v.) ሰደበ ፤ ዘለፈ
Though he came to visit you, you insulted him. ሊጠይቅህ ፡ ቢመጣ ፡ ሰደብከው
The shamefaced boy asked the teacher's pardon for having insulted him. ዓይን ፡ አፋሩ ፡ ልጅ ፡ አስተማሪውን ፡ በመዝለፉ ፡ ይቅርታ ፡ ጠየቀ

**insult** (n.)
1. ዘለፋ. The ambassador complained about the insults to his country which were printed in the paper. አምባሳደሩ ፡ በጋዜጣው ፡ ላይ ፡ ስላገሩ ፡ ታትሞ ፡ ለወጣው ፡ ዘለፋ ፡ ተቃውሞውን ፡ አቀረበ
2. ስድብ. I consider that an insult. ያንን ፡ እንደ ፡ ስድብ ፡ እቈጥረዋለሁ

**make veiled insults about** በአግቦ ፡ ሰደበ
He made veiled insults about my mother. በአግቦ ፡ እናቴን ፡ ሰደባት

**insulting remark** ስድብ
Profound silence followed his insulting remark. ከርሱ ፡ ስድብ ፡ በኋላ ፡ ፍጹም ፡ ጸጥታ ፡ ሆነ

**insurance**
1. የሕይወት ፡ ዋስትና ፤ ዋስትና. She received much money from her husband's insurance. ከባሏ ፡ የሕይወት ፡ ዋስትና ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አገኘች
He showed great foresight when he got that insurance. ያንን ፡ ዋስትና ፡ በመግባቱ ፡ አርቆ ፡ አስተዋይነቱን ፡ አሳየ
2. የዋስትና ፡ ገንዘብ. The insurance was paid in a lump sum. የዋስትናው ፡ ገንዘብ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በሙሉ ፡ ተከፈለ

**be covered by insurance** ዋስትና ፡ አለው
Is your house covered by insurance? ቤትህ ፡ ዋስትና ፡ አለው ?

**insure**
1. አረጋገጠ. I am going to insure that you obey orders. ትእዛዝ ፡ መቀበልህን ፡ ለማረጋገጥ ፡ አደርጋለሁ
2. ዋስትና ፡ አስገባ. Insure my house for $20,000! ቤቴን ፡ በሃያ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ዋስትና ፡ አስገባልኝ
3. አዳነ. More care will insure you against making so many mistakes. ይበልጥ ፡ መጠንቀቅ ፡ ብዙ ፡ ስሕተቶችን ፡ ከመሥራት ፡ ያድንሃል

**be insured** ዋስትና ፡ አለው
Are you insured against all possible accidents? ሊደርስብህ ፡ ለሚችል ፡ አደጋ ፡ ሁሉ ፡ ዋስትና ፡ አለህ ?

**insurgency** ዐመፅ
The insurgency against the government in Nigeria was suppressed. ናይጄሪያ ፡ ውስጥ ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ዐመፅ ፡ ተደመሰሰ

**insurgent** ዐመፀኛ
The insurgents have finally been captured. ዐመፀኞቹ ፡ በመጨረሻ ፡ ተያዙ

**insurrection** ሁከት
An insurrection broke out in the Congo. ኮንጎ ፡ ውስጥ ፡ ሁከት ፡ ተነሣ

**intact** ሳይሰበር
I found my glasses intact along the roadway. መነጽሬን ፡ ሳይሰበር ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ አገኘሁት

**be intact** ምንም ፡ ጉድለት ፡ የለበትም
Even though it was not cared for properly, the machine was still intact. ምንም ፡ እንኳን ፡ ተገቢ ፡ ጥንቃቄ ፡ ባይደረግለትም ፡ መኪናው ፡ አሁንም ፡ ጉድለት ፡ የለበትም

**keep intact** አልነካም
He lived on the interest and kept his capital intact. ዋና ፡ ገንዘቡን ፡ ሳይነካ ፡ በወለዱ ፡ ብቻ ፡ ኖረ

**intake** ገቢ
The intake of money decreased after the manager was fired. ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ከሥራ ፡ ከተወገደ ፡ በኋላ ፡ የገንዘብ ፡ ገቢው ፡ ቀነሰ

*The intake of each boiler is 300 gallons an hour. የማፍያ ፡ ጋን ፡ በሰዓት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ጋሎን ፡ ሊያፈላ ፡ ይችላል

**intangible** የማይጨበጥ
Sound and light are intangible. ድምፅና ፡ ብርሃን ፡ የማይጨበጡ ፡ ናቸው
The child's intangible fear could not be removed by explanations. የልጁን ፡ የማይጨበጥ ፡ ፍርሃት ፡ በማስረዳት ፡ ለማስወገድ ፡ አይቻልም

**integral**
1. ዓይነተኛ. Freedom of the press is an integral part of democracy. የጽሑፍ ፡ ነጻነት ፡ ለዲሞክራሲ ፡ ዓይነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው
2. ሙሉ ፡ የሚያሰኙ. Arms and legs are integral parts of the human body. እጆችና ፡ እግሮች ፡ የሰውን ፡ አካል ፡ ሙሉ ፡ የሚያሰኙት ፡ ክፍሎች ፡ ናቸው
3. ጠቅላላ. The integral works of Hemingway were published recently. የሄሚንግዌይ ፡ ጠቅላላ ፡ ጽሑፍ ፡ በቅርቡ ፡ ታትሟል

**integrate** አዋሐደ
They are going to integrate the army and air force. ጦር ፡ ሰራዊቱንና ፡ ያየር ፡ ኀይሉን ፡ ሊያዋሕዷቸው ፡ ነው
*They are going to integrate the schools in our district. በኛ ፡ ቀበሌ ፡ ጥቁሮችና ፡ ነጮች ፡ ባንድ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ እንዲማሩ ፡ ሊያደርጉ ፡ ነው

**integrity**
1. ሐቀኛነት. Nobody questioned his integrity. ሐቀኛነቱን ፡ ማንም ፡ አልተጠራጠረም
2. አንድነት. Ethiopia will defend her territorial integrity. ኢትዮጵያ ፡ የግዛቶቿን ፡ አንድነት ፡ ታስከብራለች

**of integrity** ሐቀኛ
He is a man of integrity. ሐቀኛ ፡ ሰው ፡ ነው

**intellect**
1. የማሰብ ፡ ችሎታ. Intellect distinguishes men from the animals. ሰውን ፡ ከእንስሶች ፡ የሚለያቸው ፡ የማሰብ ፡ ችሎታቸው ፡ ነው
2. ሊቅ (pl. ሊቃውንት). Einstein was one of the greatest intellects of his time. አይንስታይን ፡ በጊዜው ፡ ከታወቁት ፡ ሊቃውንት ፡ አንዱ ፡ ነበር

**intellectual** (n.) ምሁር
That magazine is read by many intellectuals. መጽሔቱን ፡ ብዙ ፡ ምሁራን ፡ ያነቡታል

**intellectual** (adj.)
1. አእምሮ ፡ የሚጠይቅ. Teaching is an intellectual occupation. ማስተማር ፡ አእምሮ ፡ የሚጠይቅ ፡ ሙያ ፡ ነው
2. የአእምሮ. Winning a scholarship is an intellectual achievement. ስኮላርሺፕ ፡ ማግኘት ፡ በአእምሮ ፡ ችሎታ ፡ ነው
3. የማሰብና ፡ የመመራመር. He is a man of great intellectual powers. ከፍተኛ ፡ የማሰብና ፡ የመመራመር ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**intelligence**
1. የማሰብ ፡ ችሎታ. He shows little intelligence for one his age. ለዕድሜው ፡ ከሚገባው ፡ ያነሰ ፡ የማሰብ ፡ ችሎታ ፡ አለው
2. አእምሮ. He's below average in intelligence. አእምሮው ፡ ከመጠነኛ ፡ ሰው ፡ አእምሮ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ነው
3. ብልህነት. He is on a par with his brother in intelligence. በብልህነት ፡ ከወንድሙ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ነው
4. መረጃ. The general has secret intelligence of the plans of the enemy. ጄኔራሉ ፡ ስለ ፡ ጠላት ፡ እቅድ ፡ ምስጢራዊ ፡ መረጃ ፡ አለው

**intelligence department** የመረጃ ፡ ክፍል
He is an officer in the intelligence department. እሱ ፡ የመረጃ ፡ ክፍል ፡ መኰንን ፡ ነው

**intelligent** ብልህ
She has an intelligent child. ብልህ ፡ ልጅ ፡ አላት

**(be) intelligible** ጉልቶ ፡ ተሰማ
Because of the noise of the plane, your words are not intelligible. ከአውሮፕላኑ ፡ ጩኸት ፡ የተነሣ ፡ የምትናገረው ፡ ጉልቶ ፡ አይሰማም
*Your response was not very intelligible. መልስህን ፡ መረዳት ፡ ያስቸግር ፡ ነበር

**intemperate**
1. ያልተገታ. His intemperate language startled the audience. ያልተገታው ፡ ንግግሩ ፡ አድማጩን ፡ ሕዝብ ፡ አስደነገጠ
2. ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሚጠጣ. An intemperate person will soon lose his health. ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሚጠጣ ፡ ሰው ፡ በቶሎ ፡ ጤናውን ፡ ያጣል
3. ኀይለኛ. The intemperate winter ruined his health. ኀይለኛው ፡ ክረምት ፡ ጤንነቱን ፡ ጐዳው

**intend** አሰበ
What do you intend to do? ምን ፡ ልታደርግ ፡ ታስባለህ ?
*The author intended his book for adults.

ደራሲው ፡ መጽሐፉን ፡ የጻፈው ፡ ለዐዋቂ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው

**intended** (adj.) የታቀደ
We set off on our intended trip. የታቀደውን ፡ ጉዟችንን ፡ ጀመርን

**be intended (for)**
1. ተሰነዘረ. That remark was intended for him. ያ ፡ አስተያየት ፡ ለሱ ፡ የተሰነዘረ ፡ ነበር
2. ታሰበ. This book is intended for you. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ላንተ ፡ የታሰበ ፡ ነው
3. ተመደበ. This fund is intended for emergency use only. ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ለድንገተኛ ፡ ወጪ ፡ ብቻ ፡ የተመደበ ፡ ነው
4. ታጨ. His son is intended for the ministry. ልጁ ፡ ለቅስና ፡ ታጭቷል

**intense**
1. ኀይለኛ. I could not stand the intense heat. ኀይለኛውን ፡ ሙቀት ፡ አልቻልኩትም
2. የጋለ ፡ ስሜት ፡ ያለው. Those intense young men will make good soldiers. እነዚያ ፡ የጋለ ፡ ስሜት ፡ ያላቸው ፡ ወጣቶች ፡ ጥሩ ፡ ወታደሮች ፡ ይወጣቸዋል

**intensely** በርትቶ
He studies intensely. በርትቶ ፡ ያጠናል

**intensify** (intensified)
1. አጠነከረ. We will have to intensify our efforts if we are to finish on time. በጊዜ ፡ መጨረስ ፡ ከፈለግን ፡ ጥረታችንን ፡ ማጠንከር ፡ አለብን
2. ጠበቅ ፡ አደረገ. He intensified his studies before the examinations. ከፈተናው ፡ በፊት ፡ ጥናቱን ፡ ጠበቅ ፡ አደረገው
3. አበረታ. Blowing on a fire intensifies the heat. እሳቱን ፡ እፍ ፡ ማለት ፡ ሙቀቱን ፡ ያበረታዋል

**intensity**
1. ኀይል. The intensity of the heat melted the iron. የሙቀቱ ፡ ኀይል ፡ ብረቱን ፡ አቀለጠው
2. ግለት. The intensity of his anger showed that he would never forgive her. የንዴቱ ፡ ግለት ፡ ምንጊዜም ፡ ይቅርታ ፡ የማያደርግላት ፡ መሆኑን ፡ አሳየ

**intensive**
1. በጥንቃቄ ፡ የተደረገ. An intensive search turned up the missing key. በጥንቃቄ ፡ የተደረገው ፡ ፍለጋ ፡ የጠፋውን ፡ መክፈቻ ፡ አስገኘ
2. (= adv.) ጠንቅቆ. An intensive study of a few books is more valuable than much careless reading. ብዙዎችን ፡ በግዴለሽ ፡ ከማንበብ ፡ ይልቅ ፡ ጥቂቶች ፡ መጻሕፍትን ፡ ጠንቅቆ ፡ ማንበብ ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ አለው
*He is taking an intensive course in Amharic. አብዛኛውን ፡ ጊዜውን ፡ የሚያሳልፍበት ፡ ያማርኛ ፡ ትምህርት ፡ ይከታተላል

**intent** (n.)
1. ዓላማ. The intent of the committee was to raise funds. የደርጉ ፡ ዓላማ ፡ ገንዘብ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ነበር
2. ማለት. What was the intent of that remark? በሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ምን ፡ ማለቱ ፡ ነበር ?
*It was not my intent to harm you. ልጐዳህ ፡ አስቤ ፡ አልነበረም

**to all intents and purposes** በምንም ፡ ረገድ
To all intents and purposes, he is finished. በምንም ፡ ረገድ ፡ የሱ ፡ ነገር ፡ አበቃ

**with the intent to** አሰበ
I shot with the intent to kill. ለመግደል ፡ አስቤ ፡ ተኰስኩ

**intent** (adj.), **be ~ on** ሐሳቡ ፡ ሁሉ - - - ነበር
He was intent on my destruction. ሐሳቡ ፡ ሁሉ ፡ እኔን ፡ ለማጥፋት ፡ ነበር

**give an intent look** አትኵሮ ፡ ተመለከተ
He gave me an intent look when I said I had never cheated. አጭበርብሬ ፡ አላውቅም ፡ ስለው ፡ አትኵሮ ፡ ተመለከተኝ

**intention**
1. አሳቢነት. His good intentions are evident to all. መልካም ፡ አሳቢነቱ ፡ ለማንም ፡ ግልጽ ፡ ነው
2. ማሰብ. He intimated to me his intention of leaving early. ቀደም ፡ ብሎ ፡ ለመሄድ ፡ ማሰቡን ፡ ጠቈመኝ
3. ያሰበው ፡ ነገር. Was that really your intention? እውነት ፡ ያሰብከው ፡ ነገር ፡ ይኼ ፡ ነበር ?

**have intention** አሰበ
He has no intention of coming. ለመምጣት ፡ አያስብም

**with good intentions**
They acted with good intentions. በጥሩ ፡ መንፈስ ፡ (በቅን ፡ ልቡና) ፡ ነው ፡ የሠሩት

**intentional**
1. ታስቦ ፡ የተሰነዘረ. That blow was intentional. ዱላው ፡ ታስቦ ፡ የተሰነዘረ ፡ ነበር
2. (= adv.) ሆን ፡ ብሎ. His insult was intentional. ስድቡ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ያደረገው ፡ ነገር ፡ ነበር

**intentionally** ሆን ፡ ብሎ ፤ ዐውቆ
The child intentionally hit the dog. ልጁ ፡ ውሻውን ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ (ዐውቆ) ፡ መታው

**intently** በጥንቃቄ
They listened intently. በጥንቃቄ ፡ አዳመጡ

**interact** አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ተጽዕኖ ፡ አላቸው
These two chemicals interact. ሁለቱ ፡ የኬሚካል ፡ ቅመሞች ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ተጽዕኖ ፡ አላቸው

**intercalate** አስገባ
It is necessary to intercalate a five-day month to make a full year. ዓመቱን ፡ ሙሉ ፡ ለማድረግ ፡ ባለ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ወር ፡ ማስገባት ፡ ያስፈልጋል

**intercede** አማለደ
He interceded with the king to have my punishment reduced. ቅጣቴ ፡ እንዲቀነስልኝ ፡ ንጉሡን ፡ አማለደኝ

**intercept**
1. ወሰኑን ፡ ሳያልፍ ፡ ደርሶ ፡ ያዘ. The police intercepted a shipment of smuggled goods. የኮንትሮባንዱ ፡ እቃ ፡ ወሰኑን ፡ ሳያልፍ ፡ ፖሊሶቹ ፡ ደርሰው ፡ ያዙት
2. መንገድ ፡ ላይ ፡ ያዘ. The policemen intercepted a message she sent to her convict husband. ለወንጀለኛው ፡ ባሏ ፡ የላከችውን ፡ መልእክት ፡ ፖሊሶች ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ያዙት
3. ደረሰ(በት). I intercepted him before he reached his office. ቢሮ ፡ ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ ደረስኩበት

**intercession** አማላጅነት
His intercession on my behalf was very helpful. አማላጅነቱ ፡ በጣም ፡ ረዳኝ

**intercessor** አማላጅ
He acted as my intercessor with my father-in-law. አማቴ ፡ ዘንድ ፡ አማላጅ ፡ ሆኖ ፡ ሄደልኝ

**interchange** (v.)
1. አቀያየረ. You can interchange the parts of these machines. የመኪናዎቹን ፡ እቃ ፡ ልታቀያይረው ፡ ትችላለህ
2. ተለዋወጠ. The twins interchange clothes frequently. መንትዮቹ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ልብስ ፡ ይለዋወጣሉ

**interchange** (n.) መለዋወጥ
There was an interchange of views between the two parties. በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መሀከል ፡ የሐሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ ተደረገ

**(be) interchangeable** ሊለዋወጡ ፡ ቻሉ
Tires on an automobile are interchangeable. የመኪና ፡ ጎማዎች ፡ ሊለዋወጡ ፡ ይችላሉ

**intercommunicate** ተገናኘ
The dining room and kitchen intercommunicate. ምግብ ፡ ቤቱና ፡ ማድ ፡ ቤቱ ፡ ይገናኛሉ

**interconnect** ተገናኘ
The roads interconnect. መንገዶቹ ፡ ይገናኛሉ

**intercourse** ግንኙነት
Social intercourse is necessary for a proper life. ለደኅና ፡ ኑሮ ፡ የሕዝብ ፡ ግንኙነት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**interdict** ከለከለ
The government has interdicted all trade in narcotics. መንግሥቱ ፡ ማንኛውንም ፡ የናርኮቲክ ፡ ንግድ ፡ ከልክሏል

**interdiction** ማገጃ
The interdiction on selling arms was revoked after two years. መሣሪያ ፡ በመሸጥ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ማገጃ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ተነሣ

**interest** (v.)
1. ፍላጎት ፡ አሳደረ(በት). Can't you interest him in that? በዚያ ፡ ነገር ፡ ፍላጎት ፡ ልታሳድርበት ፡ አትችልም ?
2. ፍላጎትን ፡ አነሣሣ. An exciting story interests you. ስሜትን ፡ የሚቀሰቅስ ፡ ታሪክ ፡ ፍላጎትን ፡ ያነሣሣል
3. አስደሰተ. The book interests me, apart from the plot. ከታሪኩ ፡ በስተቀር ፡ መጽሐፉ ፡ በጠቅላላው ፡ አስደስቶኛል
4. ሳበ. Ethiopia's past interests historians. የኢትዮጵያ ፡ የጥንት ፡ ታሪክ ፡ የታሪክ ፡ ጸሐፊዎችን ፡ ይስባል
5. የ - - - ዓላማ ፡ ነው. The fight for peace interests all nations. ለሰላም ፡ መዋጋት ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ዓላማ ፡ ነው

**be interested in**
1. ወደደ. I am interested in sports. እስፖርት ፡ እወዳለሁ
2. ፈለገ. He is interested in her money. የሚፈልገው ፡ ገንዘቧን ፡ ነው
3. ፍላጎት ፡ አለ(ው). The Emperor has always been interested in developing education. ጃንሆይ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ትምህርትን ፡ የማስፋፋት ፡ ፍላጎት ፡ ነበራቸው
4. ዝንባሌ ፡ አለ(ው). He is deeply interested in Amharic. ላማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ከፍተኛ ፡ ዝንባሌ ፡ አለው
5. ስሜት ፡ አለው. I am interested in child welfare. ለሕፃናት ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ስሜት ፡ አለኝ
6. (= interest) አስደሰተ. +I am very much interested in ancient art. ጥንታዊ ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ በጣም ፡ ያስደስተኛል

7. ተካፈለ. He is actively interested in the project. በእቅዱ ፡ የሚካፈለው ፡ በሙሉ ፡ ልቡ ፡ ነው

**interest** (n.)

1. ስሜት. These events aroused great interest. እነዚህ ፡ ድርጊቶች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሜት ፡ ቀሰቀሱ
2. ፍላጎት. Interest lags in political matters. የፖለቲካ ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚመለከት ፡ ፍላጎት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ይቀነሳል
His purpose was to advance his own interests rather than the company's. ዓላማው ፡ የራሱን ፡ እንጂ ፡ የኩባንያውን ፡ ፍላጎት ፡ ለማዳበር ፡ አልነበረም
3. የሚወደው ፡ ነገር. He has many interests besides languages. ከቋንቋ ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ የሚወዳቸው ፡ ነገሮች ፡ አሉት
4. አድናቆት. The exciting life of the author gives the book additional interest. የደራሲው ፡ አስደሳች ፡ ኑሮ ፡ ለመጽሐፉ ፡ ተጨማሪ ፡ አድናቆት ፡ ይሰጠዋል
5. ጥቅም. He has an interest in the brewery. በቢራ ፡ ፋብሪካው ፡ ውስጥ ፡ ጥቅም ፡ አለው
6. ወለድ. How much interest does the bank pay? ባንኩ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ወለድ ፡ ይከፍላል ?

**the best interests** ጥቅም
The ambassador must protect the best interests of his country. አምባሳደሩ ፡ ያገሩን ፡ ጥቅም ፡ መጠበቅ ፡ አለበት

**have interests**
He has many interests. ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ይከታተላል

**lack interest** አልጣመም
A dull book lacks interest. የሚቸክ ፡ መጽሐፍ ፡ አይጥምም

**take an (active) interest in**
1. በሙሉ ፡ ልቡ ፡ ተካፈለ. He takes an active interest in the literacy campaign. በተምሮ ፡ ማስተማር ፡ ዘመቻ ፡ ውስጥ ፡ በሙሉ ፡ ልቡ ፡ ይካፈላል
2. በቅርብ ፡ ተከታተለ. He takes an interest in my work. የሥራዬን ፡ መከናውን ፡ በቅርብ ፡ ይከታተላል
[See also 'rate, secondary, vested, void']

**interesting**

1. የሚያስደስት. That's an interesting article. ያ ፡ የሚያስደስት ፡ ጽሑፍ ፡ ነው
2. አስደሳች. From what he says, it must be very interesting. እሱ ፡ እንደሚለው ፡ ከሆነ ፡ ነገሩ ፡ በጣም ፡ አስደሳች ፡ መሆን ፡ አለበት
People like him because he is an interesting person. አስደሳች ፡ ስለሆነ ፡ ሰው ፡ ይወደዋል
3. አስደናቂ. The film has an interesting plot. የፊልሙ ፡ ታሪክ ፡ አስደናቂ ፡ ነው

**interfere**

1. ጣልቃ ፡ ገባ. Don't interfere in other people's affairs! በሰው ፡ ነገር ፡ ጣልቃ ፡ አትግባ
2. አጋጠመ(ው). Come on Saturday if nothing interferes. ምንም ፡ ካላጋጠመህ ፡ ቅዳሜ ፡ ና

**interfere with**
1. አቃወሰ. Absences interfere with school work. ከትምህርት ፡ ቤት ፡ መቅረት ፡ ትምህርትን ፡ ያቃውሳል
2. አሰናከለ(በት). Do you allow pleasure to interfere with the performance of your duty? ደስታ ፡ ሥራህን ፡ እንዲያሰናክልብህ ፡ ትፈቅዳለህ ?
3. ዕንቅፋት ፡ ሆነበት. You are interfering with my work. በሥራዬ ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆንክብኝ
4. አወከ. A tight armband will interfere with circulation of the blood. የጠበቀ ፡ የክንድ ፡ ላይ ፡ እስር ፡ የደምን ፡ መዘዋወር ፡ ያውካል

**interference**

1. ጣልቃ ፡ መግባት. France's interference in Nigerian internal affairs is resented by that government. በናይጄሪያ ፡ የውስጥ ፡ ጉዳይ ፡ የፈረንሳይ ፡ ጣልቃ ፡ መግባት ፡ የናይጄሪያን ፡ መንግሥት ፡ ቅር ፡ አሰኝ
2. መሰናከል. The heavy rain was a serious interference to travel. ከባድ ፡ ዝናብ ፡ ለጉዞው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሰናከል ፡ ነበር
3. መንጫጫት. Because of the interference, we couldn't hear the radio broadcast. ከመንጫጫት ፡ የተነሣ ፡ በራዲዮ ፡ ወሬውን ፡ ልንሰማ ፡ አልቻልንም

**interim** ጊዜያዊ
The interim President turned over his office to the President-elect. ጊዜያዊው ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ለተመረጠው ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሥልጣኑን ፡ አስረከበ

**in the interim** በመካከሉ
In the interim, all order vanished. በመካከሉ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ ጠፋ

**interior** (n.) ውስጥ
The interior of the house was very beautiful. ቤቱ ፡ ውስጡ ፡ በጣም ፡ ያምር ፡ ነበር

**in the interior**
*The explorer is somewhere in the interior of Africa. አሳሹ ፡ አፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ ዘልቆ ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ ይገኛል

**Ministry of Interior** ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር
He is an employee of the Ministry of Interior. ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ሠራተኛ ፡ ነው

**interior** (adj.)
1. ያገር ፡ ውስጥ. Interior trade is regulated by the Ministry of Commerce. ያገር ፡ ውስጥ ፡ ንግድ ፡ በንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው
2. የመኻል. The interior rooms of the house are well heated. የቤቱ ፡ የመኻል ፡ ክፍሎች ፡ በደንብ ፡ የሞቁ ፡ ናቸው

**interject** ወርወር ፡ አደረገ
Every now and then the speaker interjected a question. ተናጋሪው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ጥያቄ ፡ ወርወር ፡ ያደርግ ፡ ነበር

**interjection** ቃለ ፡ አጋኖ
'Alas!' and 'Hurrah!' are interjections. ወይኔ! የምስራች! ቃለ ፡ አጋኖ ፡ ናቸው

**interlace** (vt.) አቈላለፈ
Baskets are made by interlacing bamboo strips. ቅርጫት ፡ የቀርቃሃ ፡ ስንጥሮችን ፡ በማቈላለፍ ፡ ይሠራል

**interlace** (vi.) ተጠላለፈ
The branches of the trees interlaced above the path. የዛፎቹ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ከመንገዱ ፡ በላይ ፡ ተጠላልፈዋል

**interline** በመሥመሩ ፡ መካከል ፡ ጻፈ
The editor interlined the manuscript with his corrections. አዘጋጁ ፡ እርማቱን ፡ በመሥመሩ ፡ መካከል ፡ ጻፈው

**interlock** ተጠላለፉ
The two deer interlocked horns. ሁለቱ ፡ አጋዘኖች ፡ ቀንድ ፡ ለቀንድ ፡ ተጠላለፉ

**interlocutor** በውይይቱ ፡ አብሮት ፡ ተካፋይ
Our interlocutors anticipate much of what we say. በውይይቱ ፡ አብረውን ፡ ተካፋዮች ፡ የነበሩት ፡ የምንለውን ፡ አስቀድመው ፡ ያውቁ ፡ ነበር

**interlude** የዕረፍት ፡ ጊዜ
There is an interlude between each act of the play. በያንዳንዱ ፡ የጨዋታ ፡ ትዕይንት ፡ መሀከል ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ አለ
*We appreciated the interlude of sunshine. በመካከሉ ፡ ፀሐይ ፡ ስናገኝ ፡ ደስ ፡ ብሎን ፡ ነበር

**intermarry** ተጋባ
Some governments do not want their employees to intermarry with foreigners. አንዳንድ ፡ መንግሥታት ፡ ሠራተኞቻቸው ፡ ከውጭ ፡ ዜጎች ፡ ጋር ፡ እንዲጋቡ ፡ አይፈልጉም

**intermediary** (n.)
1. አስታራቂ. The Swedish ambassador is the intermediary between Israel and Egypt. የስዊደን ፡ አምባሳደር ፡ በእስራኤልና ፡ በግብጽ ፡ መሀከል ፡ አስታራቂ ፡ ናቸው
2. ደላላ. When I bought the new house, my intermediary was Mr. Parker. አዲሱን ፡ ቤት ፡ ስገዛ ፡ ደላላዬ ፡ ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ ነበር

**intermediary** (adj.)
1. መካከለኛ. He is taking an intermediary course in mathematics. መካከለኛ ፡ የሒሳብ ፡ ትምህርት ፡ ይከታተላል
2. አስታራቂ. He suggested an intermediary proposal. አስታራቂ ፡ ሐሳብ ፡ አቀረበ

**intermediate** መካከል ፡ ያለ
This stage is intermediate between the advanced and primary stages. ይህ ፡ ደረጃ ፡ በከፍተኛውና ፡ በመጀመሪያው ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ነው

**interminable** ማለቂያ ፡ የሌለው
He gave an interminable speech. ማለቂያ ፡ የሌለው ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**intermingle** (vt.)
1. አደባለቀ ፤ ቀላቀለ. The farmer intermingled the goats with the cows. ገበሬው ፡ ፍየሎቹን ፡ ከላሞች ፡ ጋር ፡ አደባለቃቸው ፡ (ቀላቀላቸው)
2. ቀላቅሎ ፡ ጻፈ. The author intermingled history and fiction in his book. ደራሲው ፡ እውነተኛና ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክን ፡ ቀላቅሎ ፡ ጻፈ

**intermingle** (vi.)
1. ተደባለቀ. The goats intermingled with the cattle. ፍየሎቹ ፡ ከከብቶች ፡ ጋር ፡ ተደባለቁ
2. ተገናኘ. Many tribes intermingle in the marketplace. ገበያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጐሳዎች ፡ ይገናኛሉ

**intermission** የዕረፍት ፡ ጊዜ
Refreshments were served during the intermission. በዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ቀዝቃዛ ፡ መጠጥ ፡ ተሰጠ

**without intermission** ያለ ፡ ፋታ
He worked without intermission. ያለ ፡ ፋታ ፡ ሠራ

**intermittent** (= adv.) አልፎ ፡ አልፎ
Malaria causes intermittent fever. ወባ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ የሚነሣ ፡ ትኩሳት ፡ ያመጣል

**be intermittent**
*This stream is intermittent. የወንዙ ፡ ሙላትና ፡ ጉድለት ፡ ይፈራረቃል

**intermittently** አልፎ ፡ አልፎ
He does this work intermittently, since it doesn't always need to be done. ሥራው ፡ ሁል ጊዜ ፡ መሥራት ፡ ስለሌለበት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይሠራዋል

**intern** (v.) አስጠበቀ
The government interned the refugees in a military camp. መንግሥቱ ፡ ስደተኞቹን ፡ በወታደር ፡ ሰፈር ፡ ውስጥ ፡ አስጠበቃቸው

**be interned** በቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ቆየ
The prisoners were interned in the military camp. ምርኮኞቹ ፡ በወታደሩ ፡ ሰፈር ፡ ውስጥ ፡ በቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ቆዩ

**intern**, n. [ጥናቱን ፡ በሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ የሚያጠናቅቅ ፡ በቅርብ ፡ የተመረቀ ፡ ሐኪም]

**internal**
1. የውስጥ. A foreigner should not interfere in the internal affairs of a country. የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ጉዳይ ፡ መግባት ፡ የለበትም
The heart is an internal organ. ልብ ፡ የውስጥ ፡ አካል ፡ ነው
2. ውስጣዊ. He died of the internal injuries he received in the crash. በግጭቱ ፡ ከደረሰበት ፡ የውስጣዊ ፡ አካል ፡ ጉዳት ፡ የተነሣ ፡ ሞተ

**international** ዓለም ፡ አቀፍ
An international conference on postal matters will be held in Geneva. ስለ ፡ ፖስታ ፡ ጉዳዮች ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ጉባኤ ፡ በጄኔቫ ፡ ይደረጋል

**internist** የውስጥ ፡ አካል ፡ ሐኪም
My brother is an internist in Haile Sellassie I Hospital. ወንድሜ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሆስፒታል ፡ የውስጥ ፡ አካል ፡ ሐኪም ፡ ነው

**interpose** (vt.)
1. በ - - - መሀከል ፡ አደረገ. He interposed his body between his child and the falling rock. ሰውነቱን ፡ በልጁና ፡ በሚወድቀው ፡ ድንጋይ ፡ መሀከል ፡ አደረገ
2. በመሀከል ፡ አቀረበ. He interposed an objection at that point. በመሀከሉ ፡ ተቃውሞ ፡ አቀረበ

**interpose** (vi.) ጣልቃ ፡ ገባ
The teacher interposed in the dispute. አስተማሪዋ ፡ በክርክሩ ፡ መሀከል ፡ ጣልቃ ፡ ገባች

**interpret**
1. አስተረጐመ. He interpreted my statement for the Emperor. ንግግሬን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አስተረጐመ
2. ፈታ. He interpreted my dream of the night before. ያለፈውን ፡ ሌሊት ፡ ሕልሜን ፡ ፈታልኝ
3. ቈጠረ. We interpreted his silence as a refusal. ዝምታውን ፡ እንደ ፡ እምቢታ ፡ ቈጠርነው
4. መስሎ ፡ ሠራ. The actor interpreted the part of the soldier with skill. ተዋናዩ ፡ ወታደሩን ፡ መስሎ ፡ በጥሩ ፡ ችሎታ ፡ ሠራ
5. አብራርቶ ፡ አስረዳ. He interpreted the poem in his own words. የግጥሙን ፡ ፍቺ ፡ በራሱ ፡ አገላለጽ ፡ አብራርቶ ፡ አስረዳ

**interpretation**
1. ፍች. What is your interpretation of his strange behavior? ለዚህ ፡ እንግዳ ፡ ጠባዩ ፡ ምን ፡ ፍች ፡ ትሰጠዋለህ ?
2. ትርጉም. The obscurity of the paragraph makes several interpretations possible. ያንቀጹ ፡ ግልጽ ፡ አለመሆን ፡ ብዙ ፡ ትርጉም ፡ ሊያሰጥ ፡ ይችላል
3. አቀራረብ. The actor's interpretations were praised by most of the critics. የተዋናዩ ፡ አቀራረብ ፡ በአብዛኞቹ ፡ ተቺዎች ፡ ተመሰገነ
4. ማብራሪያ. This writer's work demands interpretation. የደራሲው ፡ ሥራ ፡ ማብራሪያ ፡ ያስፈልገዋል

**interpreter** አስተርጓሚ
The interpreter knows five languages. አስተርጓሚው ፡ አምስት ፡ ቋንቋዎች ፡ ያውቃል

**interrelate** አቀናበረ
The agencies must interrelate the dam building plan with the agricultural plan. ድርጅቱ ፡ የግድቡን ፡ ሥራ ፡ ከእርሻው ፡ እቅድ ፡ ጋር ፡ ማቀናበር ፡ አለበት

**interrogate** መረመረ
The police interrogated the prisoner for an hour. ፖሊሶቹ ፡ እስረኛውን ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ መረመሩት

**interrogation** ምርመራ
The interrogation is being held at police headquarters. ምርመራው ፡ በፖሊስ ፡ ጠቅላይ ፡ መምሪያ ፡ በመደረግ ፡ ላይ ፡ ነው

**interrogative** (n.) መጠይቅ
The interrogative is expressed by a special mark. መጠይቁ ፡ በልዩ ፡ ምልክት ፡ ይገለጻል

**interrogative** (adj.) ጥያቄ ፡ የሚገልጽ
His interrogative expression showed he did not understand what I said. ጥያቄ ፡ የሚገልጸው ፡ መልኩ ፡ የተናገርኩት ፡ ያልገባው ፡ መሆኑን ፡ አመለከተ

**interrogative pronoun** መጠይቅ ፡ ተውላጠ ፡ ስም
"Who?" and "what?" are interrogative pronouns. « ማን » ና ፡ « ምን » ፡ መጠይቅ ፡ ተውላጠ ፡ ስሞች ፡ ናቸው

**interrupt**
1. አቋረጠ. It is not polite to interrupt when someone is talking. አንድ ፡ ሰው ፡ ሲናገር ፡ ማቋረጥ ፡ ብልግና ፡ ነው
The floods interrupted traffic. ጐርፉ ፡ የተሽከርካሪዎችን ፡ መንቀሳቀስ ፡ አቋረጠ
2. በከፊል ፡ ከለከለ. A wall interrupts our view. ግድግዳ ፡ እንዳናይ ፡ በከፊል ፡ ይከለክለናል

**interruption** መቋረጥ
The interruption of electric service was caused by the storm. ለኮረንቲ ፡ መቋረጥ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ማዕበሉ ፡ ነው
*There was an interruption in the program for a special announcement. ለልዩ ፡ ማስታወቂያ ፡ ፕሮግራሙ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተቋርጦ ፡ ነበር
**without interruption** ሳያቋርጥ
He worked without interruption. ሳያቋርጥ ፡ ሠራ

**intersect** ተላለፈ
The roads intersect near Dessie. መንገዶቹ ፡ ደሴ ፡ አጠገብ ፡ ይተላለፋሉ

**intersection**
1. መገናኛ. The intersection of three main roads caused traffic jams. የሦስቱ ፡ አውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ መገናኛ ፡ የትራፊክ ፡ መተፋፈግ ፡ አስከተለ
2. የመንገዶች ፡ መገናኛ ፤ መስቀለኛ ፡ መንገድ. There is a light at the intersection. በመንገዶቹ ፡ መገናኛ ፡ ላይ ፡ መብራት ፡ አለ
Slow down when you come to an intersection! መስቀለኛ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ስትደርስ ፡ ዝግ ፡ በል

**intersperse** በተነ
The gardener interspersed leaves among the flowers. አትክልተኛው ፡ ባበቦቹ ፡ መሃከል ፡ ቅጠል ፡ በተነ
*The farmer interspersed the shrubs with flowers. ገበሬው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በቁጥቋጦው ፡ መካከል ፡ አበባ ፡ ተከለ

**interstice** ቀዳዳ
The interstices in the basket allow the air to circulate. የቅርጫቱ ፡ ቀዳዳዎች ፡ አየር ፡ እንዲዘዋወር ፡ ያደርጋሉ

**intertwine** ተጠላለፈ
The vines intertwined on the wall. የወይን ፡ ሐረጎች ፡ በግድግዳው ፡ ላይ ፡ ተጠላልፈዋል

**interval**
1. ዕረፍት. After a brief interval the play continued. ካጭር ፡ ዕረፍት ፡ በኋላ ፡ ቲያትሩ ፡ ቀጠለ
2. ጊዜ. An interval of twenty years between the two wars helped to build up the country. በሁለቱ ፡ ጦርነቶች ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ የሃያ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ሀገሪቱን ፡ ለማደርጀት ፡ ረዳ
3. ክፍት ፡ ቦታ. There is an interval of three feet between desks. በየጠረጴዛዎች ፡ መሃከል ፡ ሦስት ፡ ጫማ ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ አለ
*After an interval of a week, the mailman will come again. ፖስተኛው ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ካሳለፈ ፡ በኋላ ፡ ይመለሳል
**at intervals**
1. አልፎ ፡ አልፎ. At intervals, there were receptions at the governor's palace. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ባገረ ፡ ገዢው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ግብዣ ፡ ነበር
2. እኩል ፡ አራርቆ. The officer posted his men at intervals. መኰንኑ ፡ ወታደሮቹን ፡ እኩል ፡ አራርቆ ፡ አቆማቸው
**at intervals of**
1. በየ. The buses leave at intervals of 15 minutes. አውቶቡሶቹ ፡ በየዐሥራ ፡ አምስት ፡ ደቂቃው ፡ ይነሣሉ
2. በ - - - ልዩነት. The trucks travel at intervals of six or seven miles when crossing the desert. መኪናዎቹ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሲያቋርጡ ፡ በስድስት ፡ ወይም ፡ በሰባት ፡ ማይል ፡ ልዩነት ፡ ይጓዛሉ

**intervene**
*A week intervenes between these two holidays. በነዚህ ፡ ሁለት ፡ በዓሎች ፡ መሀከል ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ አለ
*We enjoyed the picnic until a thunderstorm intervened. መብረቅ ፡ እስከ ፡ ጣለበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ደስ ፡ ብሎን ፡ ተንሸራሽርን
**intervene in one's behalf** አማለደ(ለት)
His friends intervened in his behalf. ጓደኞቹ ፡ አማለዱለት
**if nothing intervenes** የሚያስቀረው ፡ ነገር ፡ ካልመጣ
I shall leave on Sunday if nothing intervenes. የሚያስቀረኝ ፡ ነገር ፡ ካልመጣ ፡ እሑድ ፡ እሄዳለሁ

**intervention**
1. ገላጋይነት. A friend's intervention pre-

vented a fight. የጓደኛ ፡ ገላጋይነት ፡ ጠቡን ፡ አስቀረ
2. አማላጅነት. The minister's intervention proved necessary to obtain his release. እሱን ፡ ለማስለቀቅ ፡ የሚኒስትሩ ፡ አማላጅነት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ
3. ማግለድ. Your intervention had an adverse effect. ያንተ ፡ ማግለድ ፡ ጉጂ ፡ ውጤት ፡ አስከተለ

**interview** (v.) የቃል ፡ ጥያቄ ፡ አቀረበ
The reporter interviewed the visiting diplomat. ዜና ፡ አቅራቢው ፡ ለእንግዳው ፡ ዲፕሎማት ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ አቀረበ

**interview** (n.) የቃል ፡ ጥያቄ ፤ ቃለ ፡ መጠይቅ
Will you favor me with an interview? ጥቂት ፡ የቃል ፡ ጥያቄዎችን ፡ (ቃለ ፡ መጠይቅ) ፡ ይመልሱልኛል ?

**give an interview** ለቃል ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ሰጠ
The ambassador refused to give an interview. አምባሳደሩ ፡ ለቃል ፡ ጥያቄው ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ እምቢ ፡ አለ

**have an interview with** አነጋገረ
Father had an interview with the teacher about my work. አባቴ ፡ አስተማሪውን ፡ ስለ ፡ ሥራዬ ፡ አነጋገረው

**intestinal** የአንጀት
Intestinal flu can be dangerous. የአንጀት ፡ ኢንፍሉዌንዛ ፡ አደገኛ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

**intestine** አንጀት
His intestine came out where he had been stabbed in the belly. ሆዱ ፡ ላይ ፡ በጩቤ ፡ በተወጋበት ፡ በኩል ፡ አንጀቱ ፡ ተዘረገፈ

**intimacy**
1. የቅርብ ፡ ግንኙነት. His intimacy with the king obtained a high office for him. ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ የቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደረጃ ፡ አሰጠው
2. ጥልቅ ፡ ዕውቀት. His intimacy with Ethiopia makes him a likely choice as ambassador to that country. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያለው ፡ ጥልቅ ፡ ዕውቀት ፡ ለሀገሪቱ ፡ አምባሳደርነት ፡ እጩ ፡ ሳያደርገው ፡ አይቀርም
*The teacher allowed his pupils the intimacy of calling him by his first name. መምህሩ ፡ ተማሪዎቹ ፡ በስሙ ፡ እስኪጠሩት ፡ ድረስ ፡ አቀረባቸው

**intimate** (v.) ጠቈመ
He intimated to me his intention of leaving early. ቀደም ፡ ብሎ ፡ ለመሄድ ፡ ማሰቡን ፡ ጠቈመኝ

**intimate** (n.) የቅርብ ፡ ወዳጅ
I have many acquaintances, but few intimates. ብዙ ፡ የማውቃቸው ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፤ የቅርብ ፡ ወዳጆቼ ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ናቸው

**intimate** (adj.)
1. የቅርብ. We are intimate friends. የቅርብ ፡ ጓደኞች ፡ ነን
2. የወዳጅነት. The intimate gathering was disrupted by outsiders. የወዳጅነት ፡ ስብሰባው ፡ በውጭ ፡ ሰዎች ፡ ተረበሸ
3. የጠለቀ. He has an intimate knowledge of the country. ስለ ፡ ሀገሪቷ ፡ የጠለቀ ፡ ዕውቀት ፡ አለው
4. የምስጢር. He told me the intimate details of his life. የኑሮውን ፡ ምስጢር ፡ ዝርዝር ፡ ነገረኝ

**be on intimate terms** የቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ አለው
He is on intimate terms with the Emperor. ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋር ፡ የቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ አለው

**intimately, be ~ acquainted**
1. በቅርብ ፡ ተዋወቀ. He is intimately acquainted with the minister. ከሚኒስትሩ ፡ ጋር ፡ በቅርብ ፡ ይተዋወቃል
2. የጠለቀ ፡ ዕውቀት ፡ አለው. He is intimately acquainted with Greek archaeology. ስለ ፡ ግሪክ ፡ አርኪዮሎጂ ፡ የጠለቀ ፡ ዕውቀት ፡ አለው

**intimation** ምልክት
A frown is often an intimation of disapproval. ፊትን ፡ መቋጠር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የተቃውሞ ፡ ምልክት ፡ ነው

**intimidate** አስፈራራ
The fascists tried to intimidate the people so they would not help the patriots. ፋሺስቶች ፡ ሕዝቡ ፡ አርበኞቹን ፡ እንዳይረዳ ፡ ለማስፈራራት ፡ ሞከሩ

**into**
1. ወደ. Can you translate this into English? ይህንን ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ልትተረጉመው ፡ ትችላለህ ?
2. ወደ - - - ውስጥ. He walked into the room. ወደ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ገባ
3. ውስጥ. The ball fell into a pond. ኳሷ ፡ ኩሬ ፡ ውስጥ ፡ ወደቀች
Put that book into the box! መጽሐፉን ፡ ሣጥኑ ፡ ውስጥ ፡ አድርገው

4. ላይ. He divided the land into ten parts. መሬቱን ፡ ዐሥር ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ከፈለው
*He worked all night and into the next day. ሥራውን ፡ ሲሠራ ፡ አድሮ ፡ አረፈደ

**intolerable** የማይቻል
The heat is intolerable. ሙቀቱ ፡ የማይቻል ፡ ነው

**intolerance** አለመቻቻል
Religious intolerance brought many settlers to America. በሃይማኖት ፡ አለመቻቻል ፡ ብዙ ፡ ሰፋሪዎችን ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ እንዲሰደዱ ፡ አደረገ

**intolerant** የሚቃወም ፤ የማይቀበል ፤ የማይደግፍ
There are religions that are intolerant of other religions. ሌሎች ፡ ሃይማኖቶችን ፡ የሚቃወሙ ፡ (የማይቀበሉ, or የማይደግፉ) ፡ ሃይማኖት ፡ አለ
**be intolerant** አልታገሠም
The government is intolerant of all opposition. መንግሥቱ ፡ ማንኛውንም ፡ ተቃውሞ ፡ አይታገሥም

**intonation**
1. ዝማሬ. The intonation of the prayer is accompanied by beating of drums. የጸሎት ፡ ዝማሬ ፡ በከበሮ ፡ ይታጀባል
2. የቃል ፡ አሰባበር. In a question, the intonation rises at the end of the sentence. ሲጠየቅ ፡ የቃል ፡ አሰባበር ፡ በዐረፍተ ፡ ነገር ፡ መጨረሻ ፡ ከፍ ፡ ይላል

**intone** አዜመ
The priest intones the church service. ቄሱ ፡ ቅዳሴ ፡ ያዜማል

**intoxicate**
1. አሰከረ. Whiskey intoxicates people. ዊስኪ ፡ ሰው ፡ ያሰክራል
2. አስፈነጠዘ. The warm spring air intoxicated the colt. ሞቃቱ ፡ የጸደይ ፡ አየር ፡ የፈረሱን ፡ ግልገል ፡ አስፈነጠዘው
**become intoxicated** ሰከረ
If a man drinks too much beer, he becomes intoxicated. አንድ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ቢራ ፡ ቢጠጣ ፡ ይሰክራል

**intoxicating** የሚያሰክር
The sale of intoxicating beverages to minors is prohibited. እካለ ፡ መጠን ፡ ላልደረሱ ፡ ሰዎች ፡ የሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ መሸጥ ፡ ክልክል ፡ ነው

**intransigent** ሐሳበ ፡ ግትር
The President is intransigent in political matters. ፕሬዚዳንቱ ፡ በፖለቲካ ፡ ነገር ፡ ሐሳበ ፡ ግትር ፡ ነው

**intransitive** የማይሻገር
The verbs 'go', and 'stand' are intransitives. «ሄደ» ና ፡ «ቆመ» ፡ የማይሻገሩ ፡ ግሶች ፡ ናቸው

**intrepid** ደፋር
Amundsen was an intrepid explorer. አሙንድሰን ፡ ደፋር ፡ አሳሽ ፡ ነበር

**intricacy** (intricacies) ውስብስብ
The story was full of intricacies. ታሪኩ ፡ ውስብስብ ፡ የበዛበት ፡ ነበር

**intricate**
1. የተወሳሰበ. His ideas are too intricate to be easily understood. ሐሳቡ ፡ በጣም ፡ የተወሳሰበ ፡ ስለሆነ ፡ በቀላሉ ፡ ለመረዳት ፡ አይቻልም
2. የረቀቀ ፤ የተራቀቀ. This cross has a very intricate design. ይህ ፡ መስቀል ፡ የረቀቀ ፡ (የተራቀቀ) ፡ አሠራር ፡ አለው

**intrigue** (vt.)
1. ከነከነ. The news of his unexpected dismissal intrigued all of us. ሳይታሰብ ፡ ከሥራ ፡ የመሰናበቱ ፡ ወሬ ፡ ሁላችንንም ፡ ከነከነን
2. ሳበ. The simplicity of your plan intrigues me, but I wonder if it would work. የእቅድህ ፡ ቀላልነት ፡ ስቦኛል ፤ ግን ፡ የሚሳካ ፡ መሆኑን ፡ እጠራጠራለሁ
3. ማረከ. The book's unusual title intrigues me. የመጽሐፉ ፡ እንግዳ ፡ የሆነ ፡ አርእስት ፡ ይማርከኛል
**intrigue** (vi.)
1. ተመሳጠረ. He was disgraced because he intrigued with the enemy. ከጠላት ፡ ጋር ፡ ስለ ተመሳጠረ ፡ ተዋረደ
2. አሴረ ፤ አደመ. They intrigued to get him out of his job. ከሥራው ፡ ለማስወጣት ፡ አሴሩበት ፡ (አደሙበት)

**intrigue** (n.)
1. ተንኰል. The intrigue to get him out of his job failed. ከሥራው ፡ ለማፈናቀል ፡ የተደረገው ፡ ተንኰል ፡ ከሸፈ
2. ነገር ፡ መተብተብ ፤ ተንኰል. She enjoys intrigue. ነገር ፡ መተብተብ ፡ (ተንኰል) ፡ ትወዳለች
3. ሴራ. Political intrigue threatens to disunite the country. የፖለቲካ ፡ ሴራ ፡ አገሪቷን ፡ እንዳይከፋፍላት ፡ ያሰፈራል

**intrinsic** እውነተኛ
The intrinsic worth of a man cannot be measured by his wealth. የሰው ፡ ልጅ ፡ እውነተኛ ፡ ዋጋው ፡ በሀብቱ ፡ መጠን ፡ ሊመዘን ፡ አይችልም

**introduce**

1. ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ አስመጣ. Menelik introduced the eucalyptus to Ethiopia. አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ባሕር ፡ ዛፍን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ አስመጡ

2. አቀረበ. He introduced an arms bill in the parliament. ስለ ፡ ጦር ፡ መሣሪያ ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ለምክር ፡ ቤቱ ፡ አቀረበ

3. አስገባ. The writer introduced many new words into the language. ደራሲው ፡ ብዙ ፡ አዳዲስ ፡ ቃላትን ፡ ቋንቋው ፡ ውስጥ ፡ አስገባ

4. አስተዋወቀ. The chairman introduced the lecturer to the audience. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ተናጋሪውን ፡ ከድማጩ ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ አስተዋወቀ
I'd like to introduce you to my father. ካባቴ ፡ ጋር ፡ ላስተዋውቅህ

5. ጀመረ. He introduced his speech by telling a joke. ንግግሩን ፡ በቀልድ ፡ ጀመረ

6. አስጀመረ. The teacher introduced the pupils to mathematics. መምህሩ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ሒሳብ ፡ አስጀመራቸው

7. ከተተ. The doctor introduced a long tube into the sick man's throat. ሐኪሙ ፡ እታመመው ፡ ሰው ፡ ጉሮሮ ፡ ውስጥ ፡ ረጂም ፡ ቱቦ ፡ ከተተ

**be introduced** መጣ
The eucalyptus tree was recently introduced to Ethiopia. ባሕር ፡ ዛፍ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጣው ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ነው

**introduction**

1. መግቢያ. It is mentioned in the introduction. መግቢያው ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሷል

2. አደራ. He brought me a letter of introduction. የአደራ ፡ ደብዳቤ ፡ አመጣልኝ

3. መምጣት. The introduction of steel made the construction of tall buildings possible. የዐረብ ፡ ብረት ፡ መምጣት ፡ ረጅም ፡ ሕንጻዎችን ፡ ለመሥራት ፡ አስቻለ

4. የመጣ ፡ ነገር. Radios are a later introduction than telephones. ሬዲዮ ፡ ከስልክ ፡ በኋላ ፡ የመጣ ፡ ነገር ፡ ነው
*She became shy because of her introduction to so many strangers at the same time. ከብዙ ፡ እንግዶች ፡ ጋር ፡ ባንዴ ፡ ስለተዋወቀች ፡ አፈረች

**introductory** የመግቢያ
The introductory paragraphs are very important. የመግቢያ ፡ አንቀጾቹ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ናቸው

**intrude** ጣልቃ ፡ ገባ ፤ ጥልቅ ፡ አለ
I intruded upon their conversation. በንግግራቸው ፡ ላይ ፡ ጣልቃ ፡ ገባሁ
He never fails to intrude into my private life. በግል ፡ ኑሮዬ ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ ማለትን ፡ ይወዳል

**intrusion**

1. መግባት. Intrusion into a private residence without a warrant is illegal. የግል ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማዘዣ ፡ መግባት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ተግባር ፡ ነው

2. ጣልቃ ፡ ገብነት. The card players resented his advice as an intrusion. ካርታ ፡ ተጫዋቾች ፡ ምክሩን ፡ እንደ ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ቈጥረው ፡ ተቀየሙ

**intrusive, ~ element** ጣልቃ ፡ ገብ
The authorities blamed intrusive elements for stirring up the riots. ጣልቃ ፡ ገቦቹ ፡ ረብሻውን ፡ በማነሣሣታቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ወቀሷቸው

**intuition** ስሜት
A woman's intuition often tells her that certain things are not good. አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ ጥሩ ፡ ያለመሆናቸውን ፡ የሴት ፡ ስሜቷ ፡ ይነግራታል

**(be) intuitive** የተፈጥሮ ፡ አስተዋይነት ፡ አለው
He is an intuitive judge of persons. ሰውን ፡ ለመገመት ፡ የተፈጥሮ ፡ አስተዋይነት ፡ አለው
*I have an intuitive dislike of him. ውቃቢዬ ፡ አይወደውም

**inundate**

1. አጥለቀለቀ. The flood inundated the plain. ጐርፉ ፡ ሜዳውን ፡ አጥለቀለቀው

2. አስጨነቀ. On holidays visitors inundate the museum. በበዓላት ፡ ቀን ፡ ጐብኚዎች ፡ ቤተ ፡ መዘክሩን ፡ ያስጨንቁታል

**be inundated** (= inundate) ጐረፈ(በት)
+We were inundated with requests for money. የገንዘብ ፡ ጥያቄ ፡ ጐረፈብን

**invade**

1. ወረረ. Didn't Napoleon try to invade England? ናፖሊዮን ፡ የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ ለመውረር ፡ አልሞከረም ?
Crowds invaded the new hotel. ሰዎች ፡ አዲሱን ፡ ሆቴል ፡ ወረሩት
Grasshoppers invade fields and eat the crops. ፌንጦች ፡ ማሳውን ፡ ወረው ፡ ሰብልን ፡ ይበላሉ

2. ነካ. The law punishes people who invade the rights of others. የሌሎችን ፡ መብት ፡ የሚነኩ ፡ ሰዎችን ፡ ሕጉ ፡ ይቀጣቸዋል

3. ጣልቃ ፡ ገባ(በት). Reporters invaded his privacy by asking personal questions. ጋዜጠኞች ፡ ስለ ፡ ግል ፡ ሁኔታ ፡ ጥያቄ ፡ እየጠየቁ ፡ በግል ፡ ኑሮው ፡ ጣልቃ ፡ ገቡበት

4. አፈነ. The smell of cooking invaded the house. የጥብስ ፡ ሽታ ፡ ቤቱን ፡ አፈነው

**invader** ወራሪ
The Ethiopians defended their land against the invader. ኢትዮጵያውያን ፡ አገራቸውን ፡ ከወራሪው ፡ ተከላከሉ

**invalid** (n.) አካለ ፡ ስንኩል ፡ ሰው ፤ ስንኩል ፤ አካለ ፡ ጐደሎ
The invalid finds solace in music. አካለ ፡ ስንኩሉ ፡ ሰው ፡ በሙዚቃ ፡ ይጽናናል
After the accident, he remained an invalid. ከደጋው ፡ በኋላ ፡ ስንኩል ፡ ሆኖ ፡ ቀረ
She poses as an invalid when really she is well and strong. ጠንካራና ፡ ደኅና ፡ ሆና ፡ ሳለች ፡ ለይምሰል ፡ እንደ ፡ አካለ ፡ ጐደሎ ፡ ትሆናለች
[See also 'helpless']

**(be) invalid** አልጸናም ፤ ውድቅ ፡ ሆነ
A will without a signature is invalid. ፊርማ ፡ የሌለበት ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ አይጸናም
His testimony was declared invalid. የምስክርነት ፡ ቃሉ ፡ ውድቅ ፡ ሆነ

**invalidate** ሻረ
The new will invalidates the old one. አዲሱ ፡ ኑዛዜ ፡ አሮጌውን ፡ ይሽረዋል

**be invalidated** ፈረሰ
The stipulations have not been met, so the contract has been invalidated. በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሱት ፡ ግዴታዎች ፡ ስላልተፈጸሙ ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል

**invaluable**
1. በገንዘብ ፡ የማይገኝ. This gold cup used by King Theodore is invaluable. ይህ ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ይጠቀሙበት ፡ የነበረው ፡ የወርቅ ፡ ዋንጫ ፡ በገንዘብ ፡ የማይገኝ ፡ ነው
2. ተወዳዳሪ ፡ የሌለው. He is an invaluable friend. ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ ጓደኛ ፡ ነው

**invariable** የማይለወጥ
He is a man of invariable habits. የማይለወጥ ፡ ልማድ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**invasion** ወረራ
The Italian invasion began in 1935. የኢጣልያን ፡ ወረራ ፡ በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. ተጀመረ

**invective** ውርጅብኝ
The angry woman's invective shocked him. የተናደደችው ፡ ሴት ፡ ውርጅብኝ ፡ አስደነገጠው

**invent**
1. ፈጠረ. Did you invent that story? ይህንን ፡ ታሪክ ፡ የፈጠርከው ፡ አንተ ፡ ነህ?
He invented a new approach to the study of language. ለቋንቋ ፡ ጥናት ፡ አዲስ ፡ ዘዴ ፡ ፈጠረ
2. ፈለሰፈ. He invented something new recently. በቅርቡ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ፈለሰፈ

**invention**
1. ፈጠራ. His story is a complete invention. ታሪኩ ፡ ፍጹም ፡ ፈጠራ ፡ ነው
2. የፈጠራ ፡ ችሎታ. The author shows much invention in telling the story. ደራሲው ፡ ታሪኩን ፡ ሲናገር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የፈጠራ ፡ ችሎታ ፡ ያሳያል
3. ፍልሰፋ. The invention of the telegraph helped to transmit news quickly. የቴሌግራም ፡ ፍልሰፋ ፡ ወሬን ፡ በፍጥነት ፡ ለማስተላለፍ ፡ ረዳ
4. አዲስ ፡ የተፈለሰፈ ፡ ነገር. The invention found widespread acceptance. አዲስ ፡ የተፈለሰፈው ፡ ነገር ፡ ሰፊ ፡ ተቀባይነት ፡ አገኘ
5. የፈለሰፈ ፡ ነገር. He coined a word for his invention. ለፈለሰፈው ፡ ነገር ፡ ቃል ፡ ፈጠረለት

**inventor** ፈልሳፊ
Benjamin Franklin was a great inventor. ቤንጃሚን ፡ ፍራንክሊን ፡ ታላቅ ፡ ፈልሳፊ ፡ ነበር

**inventory** ዝርዝር
The library made an inventory of its books. ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ የመጽሐፎቹን ፡ ዝርዝር ፡ አዘጋጀ

**inverse** ተቃራኒ
Your intervention to settle the quarrel had the inverse effect. ጠቡን ፡ ለማስታገሥ ፡ ያንተ ፡ ጣልቃ ፡ መግባት ፡ ተቃራኒ ፡ ውጤት ፡ ነበረው

**in inverse order**
Write the alphabet in inverse order! ፊደሉን ፡ ከኋላ ፡ ጀምረህ ፡ ወደፊት ፡ ጻፍ

**inversion** ግልብጥ
"Said he" is an inversion of "he said". « አለ ፡ እርሱ » ፡ የ « እርሱ ፡ አለ » ፡ ቃል ፡ ግልብጥ ፡ ነው

**invert**
1. ገለበጠ. If you invert 2/3 you get 3/2. 2/3 ገልብጠው ፡ ሲጽፉት ፡ 3/2 ይሆናል
2. አዙሮ ፡ ጻፈ. He inverted the order of the alphabet. የፊደሉን ፡ ተራ ፡ አዙሮ ፡ ጻፈ
3. ደፋ. He inverted the glass to show he did not want more water. ተጨማሪ ፡ ውኃ ፡ የማ

**introduce**

1. ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ አስመጣ. Menelik introduced the eucalyptus to Ethiopia. አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ባሕር ፡ ዛፍን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ አስመጡ

2. አቀረበ. He introduced an arms bill in the parliament. ስለ ፡ ጦር ፡ መሣሪያ ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ለምክር ፡ ቤቱ ፡ አቀረበ

3. አስገባ. The writer introduced many new words into the language. ደራሲው ፡ ብዙ ፡ አዳዲስ ፡ ቃላትን ፡ ቋንቋው ፡ ውስጥ ፡ አስገባ

4. አስተዋወቀ. The chairman introduced the lecturer to the audience. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ተናጋሪውን ፡ ከድማጩ ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ አስተዋወቀ
I'd like to introduce you to my father. ከባቴ ፡ ጋር ፡ ላስተዋውቅህ

5. ጀመረ. He introduced his speech by telling a joke. ንግግሩን ፡ በቀልድ ፡ ጀመረ

6. አስጀመረ. The teacher introduced the pupils to mathematics. መምህሩ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ሒሳብ ፡ አስጀመራቸው

7. ከተተ. The doctor introduced a long tube into the sick man's throat. ሐኪሙ ፡ እታመመው ፡ ሰው ፡ ጉሮሮ ፡ ውስጥ ፡ ረጂም ፡ ቱቦ ፡ ከተተ

**be introduced** መጣ
The eucalyptus tree was recently introduced to Ethiopia. ባሕር ፡ ዛፍ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጣው ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ነው

**introduction**

1. መግቢያ. It is mentioned in the introduction. መግቢያው ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሷል

2. አደራ. He brought me a letter of introduction. የአደራ ፡ ደብዳቤ ፡ አመጣልኝ

3. መምጣት. The introduction of steel made the construction of tall buildings possible. የዐረብ ፡ ብረት ፡ መምጣት ፡ ረጅም ፡ ሕንጻዎችን ፡ ለመሥራት ፡ አስቻለ

4. የመጣ ፡ ነገር. Radios are a later introduction than telephones. ሬዲዮ ፡ ከስልክ ፡ በኋላ ፡ የመጣ ፡ ነገር ፡ ነው
*She became shy because of her introduction to so many strangers at the same time. ከብዙ ፡ እንግዶች ፡ ጋር ፡ ባንዴ ፡ ስለተዋወቀች ፡ አፈረች

**introductory** የመግቢያ
The introductory paragraphs are very important. የመግቢያ ፡ አንቀጾቹ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ናቸው

**intrude** ጣልቃ ፡ ገባ ፤ ጥልቅ ፡ አለ
I intruded upon their conversation. በንግግራቸው ፡ ላይ ፡ ጣልቃ ፡ ገባሁ
He never fails to intrude into my private life. በግል ፡ ኑሮዬ ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ ማለትን ፡ ይወዳል

**intrusion**

1. መግባት. Intrusion into a private residence without a warrant is illegal. የግል ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማዘዣ ፡ መግባት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ተግባር ፡ ነው

2. ጣልቃ ፡ ገብነት. The card players resented his advice as an intrusion. ካርታ ፡ ተጫዋቾች ፡ ምክሩን ፡ እንደ ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ቈጥረው ፡ ተቀየሙ

**intrusive, ~ element** ጣልቃ ፡ ገብ
The authorities blamed intrusive elements for stirring up the riots. ጣልቃ ፡ ገቦቹ ፡ ረብሻውን ፡ በማነሣሣታቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ወቀሷቸው

**intuition** ስሜት
A woman's intuition often tells her that certain things are not good. አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ ጥሩ ፡ ያለመሆናቸውን ፡ የሴት ፡ ስሜቷ ፡ ይነግራታል

**(be) intuitive** የተፈጥሮ ፡ አስተዋይነት ፡ አለው
He is an intuitive judge of persons. ሰውን ፡ ለመገመት ፡ የተፈጥሮ ፡ አስተዋይነት ፡ አለው
*I have an intuitive dislike of him. ውቃቢዬ ፡ አይወደውም

**inundate**

1. አጥለቀለቀ. The flood inundated the plain. ጐርፉ ፡ ሜዳውን ፡ አጥለቀለቀው

2. አስጨነቀ. On holidays visitors inundate the museum. በበዓላት ፡ ቀን ፡ ጐብኚዎች ፡ ቤተ ፡ መዘክሩን ፡ ያስጨንቁታል

**be inundated** (= inundate) ጐረፈ(በት)
+We were inundated with requests for money. የገንዘብ ፡ ጥያቄ ፡ ጐረፈብን

**invade**

1. ወረረ. Didn't Napoleon try to invade England? ናፖሊዮን ፡ የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ ለመውረር ፡ አልሞከረም ?
Crowds invaded the new hotel. ሰዎች ፡ አዲሱን ፡ ሆቴል ፡ ወረሩት
Grasshoppers invade fields and eat the crops. ፌንጦች ፡ ማሳውን ፡ ወረው ፡ ሰብልን ፡ ይበላሉ

2. ነካ. The law punishes people who invade the rights of others. የሌሎችን ፡ መብት ፡ የሚነኩ ፡ ሰዎችን ፡ ሕጉ ፡ ይቀጣቸዋል

3. ጣልቃ ፡ ገባ(በት). Reporters invaded his privacy by asking personal questions. ጋዜጠኞች ፡ ስለ ፡ ግል ፡ ሁኔታ ፡ ጥያቄ ፡ እየጠየቁ ፡ በግል ፡ ኑሮው ፡ ጣልቃ ፡ ገቡበት

4. አፈነ. The smell of cooking invaded the house. የጥብስ ፡ ሽታ ፡ ቤቱን ፡ አፈነው

**invader** ወራሪ
The Ethiopians defended their land against the invader. ኢትዮጵያውያን ፡ አገራቸውን ፡ ከወራሪው ፡ ተከላከሉ

**invalid** (n.) አካለ ፡ ስንኩል ፡ ሰው ፤ ስንኩል ፤ አካለ ፡ ጎደሎ
The invalid finds solace in music. አካለ ፡ ስንኩሉ ፡ ሰው ፡ በሙዚቃ ፡ ይጽናናል
After the accident, he remained an invalid. ከደጋው ፡ በኋላ ፡ ስንኩል ፡ ሆኖ ፡ ቀረ
She poses as an invalid when really she is well and strong. ጠንካራና ፡ ደኅና ፡ ሆና ፡ ሳለች ፡ ለይምሰል ፡ እንደ ፡ አካለ ፡ ጎደሎ ፡ ትሆናለች
[See also 'helpless']

**(be) invalid** አልጸናም ፤ ውድቅ ፡ ሆነ
A will without a signature is invalid. ፊርማ ፡ የሌለበት ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ አይጸናም
His testimony was declared invalid. የምስክርነት ፡ ቃሉ ፡ ውድቅ ፡ ሆነ

**invalidate** ሻረ
The new will invalidates the old one. አዲሱ ፡ ኑዛዜ ፡ አሮጌውን ፡ ይሽረዋል

**be invalidated** ፈረሰ
The stipulations have not been met, so the contract has been invalidated. በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሱት ፡ ግዴታዎች ፡ ስላልተፈጸሙ ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል

**invaluable**
1. በገንዘብ ፡ የማይገኝ. This gold cup used by King Theodore is invaluable. ይህ ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ይጠቀሙበት ፡ የነበረው ፡ የወርቅ ፡ ዋንጫ ፡ በገንዘብ ፡ የማይገኝ ፡ ነው
2. ተወዳዳሪ ፡ የሌለው. He is an invaluable friend. ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ ጓደኛ ፡ ነው

**invariable** የማይለወጥ
He is a man of invariable habits. የማይለወጥ ፡ ልማድ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**invasion** ወረራ
The Italian invasion began in 1935. የኢጣልያን ፡ ወረራ ፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ተጀመረ

**invective** ውርጅብኝ
The angry woman's invective shocked him. የተናደደችው ፡ ሴት ፡ ውርጅብኝ ፡ አስደነገጠው

**invent**
1. ፈጠረ. Did you invent that story? ይህንን ፡ ታሪክ ፡ የፈጠርከው ፡ አንተ ፡ ነህ?
He invented a new approach to the study of language. ለቋንቋ ፡ ጥናት ፡ አዲስ ፡ ዘዴ ፡ ፈጠረ
2. ፈለሰፈ. He invented something new recently. በቅርቡ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ፈለሰፈ

**invention**
1. ፈጠራ. His story is a complete invention. ታሪኩ ፡ ፍጹም ፡ ፈጠራ ፡ ነው
2. የፈጠራ ፡ ችሎታ. The author shows much invention in telling the story. ደራሲው ፡ ታሪኩን ፡ ሲናገር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የፈጠራ ፡ ችሎታ ፡ ያሳያል
3. ፍልሰፋ. The invention of the telegraph helped to transmit news quickly. የቴሌግራም ፡ ፍልሰፋ ፡ ወሬን ፡ በፍጥነት ፡ ለማስተላለፍ ፡ ረዳ
4. አዲስ ፡ የተፈለሰፈ ፡ ነገር. The invention found widespread acceptance. አዲስ ፡ የተፈለሰፈው ፡ ነገር ፡ ሰፊ ፡ ተቀባይነት ፡ አገኘ
5. የፈለሰፈ ፡ ነገር. He coined a word for his invention. ለፈለሰፈው ፡ ነገር ፡ ቃል ፡ ፈጠረለት

**inventor** ፈልሳፊ
Benjamin Franklin was a great inventor. ቤንጃሚን ፡ ፍራንክሊን ፡ ታላቅ ፡ ፈልሳፊ ፡ ነበር

**inventory** ዝርዝር
The library made an inventory of its books. ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ የመጽሐፎቹን ፡ ዝርዝር ፡ አዘጋጀ

**inverse** ተቃራኒ
Your intervention to settle the quarrel had the inverse effect. ጠቡን ፡ ለማስታገሥ ፡ ያንተ ፡ ጣልቃ ፡ መግባት ፡ ተቃራኒ ፡ ውጤት ፡ ነበረው

**in inverse order**
Write the alphabet in inverse order! ፊደሉን ፡ ከኋላ ፡ ጀምረህ ፡ ወደፊት ፡ ጻፍ

**inversion** ግልብጥ
"Said he" is an inversion of "he said". « አለ ፡ እርሱ » ፡ የ « እርሱ ፡ አለ » ፡ ቃል ፡ ግልብጥ ፡ ነው

**invert**
1. ገለበጠ. If you invert 2/3 you get 3/2. 2/3 ገልብጠው ፡ ሲጽፉት ፡ 3/2 ይሆናል
2. አዙሮ ፡ ጻፈ. He inverted the order of the alphabet. የፊደሉን ፡ ተራ ፡ አዙሮ ፡ ጻፈ
3. ደፋ. He inverted the glass to show he did not want more water. ተጨማሪ ፡ ውኃ ፡ የማ

ይፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ለማሳየት ፡ ብርጭቆውን ፡ ደፋው

**invest**

1. ሰጠ. He invested his lawyer with complete power to act for him. እንደራሱ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሠራ ፡ ለጠበቃው ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጠው
2. አዋለ. He invested much time in the project. በእቅዱ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አዋለ
He invested his money in bonds and land. ገንዘቡን ፡ በቦንድና ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ አዋለ
3. ሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለ. They took counsel together before deciding to invest all their money. ያላቸውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ከመወሰናቸው ፡ በፊት ፡ ተመካከሩ
4. አወጣ. Why did you invest so much money in that ancient building? ለዚህ ፡ አሮጌ ፡ ሕንጻ ፡ ይህንን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ ለምን ፡ አወጣህ ?

**be invested**

1. ተሰጠ. The military governor has been invested with full authority. ወታደራዊው ፡ ገዢ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶት ፡ ነበር
2. ሹመት ፡ ተሰጠ. The new minister was invested by the king in a brief ceremony. አዲሱ ፡ ሚኒስትር ፡ ባጭር ፡ ሥርዓት ፡ በንጉሡ ፡ ሹመት ፡ ተሰጠው
3. ነገሠ. A king is invested by crowning him. ንጉሡ ፡ ዘውድ ፡ በመጫን ፡ ይነግሣል

**investigate**

1. መረመረ. The police investigated the conditions that caused the accident. ፖሊሱ ፡ አደጋ ፡ የደረሰበትን ፡ ሁኔታ ፡ መረመረ
2. አጠና. He is somewhere in the interior investigating the tribes. ጐሳዎቹን ፡ ለማጥናት ፡ በባላገር ፡ ውስጥ ፡ ነው

**investigation**

1. ምርመራ. An investigation has been ordered. ምርመራ ፡ እንዲደረግ ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጥቷል
2. ጥናት. His investigation of the tribes will be published. ስለ ፡ ጐሳው ፡ ያደረገው ፡ ጥናት ፡ ይታተማል

**investment**

1. ገንዘብ ፡ ማዋል. Investment in government bonds is a good thing. በመንግሥት ፡ ቦንዶች ፡ ላይ ፡ ገንዘብህን ፡ ማዋል ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ነው
2. ያወጣ ፡ ወጪ. He got a threefold return on his investment. ያወጣውን ፡ ወጪ ፡ ሦስት ፡ ዕጥፍ ፡ አድርጎ ፡ መለሰ
*The new house was a good investment. አዲሱ ፡ ቤት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ የወጣበት ፡ ነው

**inveterate**

1. የ - - ሱስ ፡ ያለበት ፡ ሰው. An inveterate smoker will damage his lungs. የሲጋራ ፡ ሱስ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ሳምባዎቹን ፡ ይጐዳል
2. የለመደበት. No one ever believes an inveterate liar. የለመደበትን ፡ ውሸታም ፡ ማንም ፡ አያምነውም
3. የተፈጥሮ. Cats have an inveterate dislike of dogs. ድመት ፡ ለውሻ ፡ የተፈጥሮ ፡ ጥላቻ ፡ አላት

**invidious** አስከፊ

The loser made an invidious remark. ተሸናፊው ፡ አስከፊ ፡ አስተያየት ፡ ሰነዘረ

**invigorate** አበረታ

Staying in a cold climate will invigorate you. በቀዝቃዛ ፡ አየር ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ ያበረታል

**invincible** የማይበገር

The champion wrestler seems invincible. ሻምፒዮኑ ፡ ትግለኛ ፡ የማይበገር ፡ ይመስላል

**inviolable** የማይጣስ

The law of gravity is an inviolable law. የስበት ፡ ሕግ ፡ የማይጣስ ፡ ሕግ ፡ ነው

**inviolate** የማይነካ

The inviolate privileges of diplomats have been recognized for centuries. የዲፕሎማቶች ፡ የማይነካ ፡ መብት ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ ጸንቶ ፡ ቆይቷል

**keep inviolate** አላፈረሰም

He kept his oath inviolate and died without possessions of any kind. መሐላውን ፡ ሳያፈርስ ፡ ምንም ፡ ንብረት ፡ ሳይጨብጥ ፡ ሞተ

**(be) invisible** አይታይም

Clean glass is invisible under certain conditions. ንጹሕ ፡ መስታወት ፡ ባንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ አይታይም

**invitation**

1. ግብዣ. I did not accept his invitation to go to the theater. ወደ ፡ ቲያትሩ ፡ ለመሄድ ፡ ያደረገልኝን ፡ ግብዣ ፡ አልተቀበልኩትም
2. የጥሪ ፡ ወረቀት. Admission is by invitation only. መግባት ፡ የሚቻለው ፡ በጥሪ ፡ ወረቀት ፡ ብቻ ፡ ነው
3. የሚያነሣሣ. The article was an invitation for public protest against the newspaper. ጽሑፉ ፡ ሕዝቡ ፡ በጋዜጣው ፡ ላይ ፡ ተቃውሞ ፡ እንዲያቀርብ ፡ የሚያነሣሣ ፡ ነበር

**invite**

1. ጠራ. He invited thirty people for the holiday. ለዓመት ፡ በዓሉ ፡ ሠላሳ ፡ ሰው ፡ ጠራ

He invites danger by driving fast. በፍጥነት ፡ በ መንዳት ፡ ሞትን ፡ ይጠራል
2. አጓጓ. The calm water invited us to swim. ጸጥ ፡ ያለው ፡ ውኃ ፡ እንድንዋኝ ፡ አጓጓን
3. ተቀበለ. The speaker invites your comments after his speech. ተናጋሪው ፡ ከንግግሩ ፡ በኋላ ፡ አስተያየታችሁን ፡ ይቀበላል
4. ተገባ(ው). +A good performance invites applause. ጥሩ ፡ ትርኢይት ፡ ጭብጨባ ፡ ይገባዋል

**invite gossip** መወያያ ፡ ሆነ
His sudden wealth invited gossip. በድንገት ፡ ሀ ብታም ፡ መሆኑ ፡ መወያያ ፡ ሆነ

**invite in** ግባ ፡ አለ
He did not invite me in. እርሱ ፡ ግባ ፡ አላለኝም

**invite to dinner** እራት ፡ ጋበዘ
I invited my friend to dinner tonight. ጓደኛዬን ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ እራት ፡ ጋብዤዋለሁ

## inviting የሚያጓጓ
He made me an inviting offer for a job. ስለ ፡ ሥ ራው ፡ የሚያጓጓ ፡ ድርድር ፡ አቀረበልኝ

## invocation ልመና ፡ ማቅረብ
A church mass often begins with an invocation to God. ቅዳሴ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልመና ፡ በማ ቅረብ ፡ ይጀመራል

## invoice ፋክቱር
Show me the invoice for that shipment of books! መጻሕፍቱ ፡ የተላኩበትን ፡ ፋክቱር ፡ አሳ የኝ

## invoke ለመነ
He invoked God's help in his struggle. በችግሩ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ እርዳታ ፡ ለመነ
The condemned criminal invoked the judge's mercy. የተፈረደበት ፡ ወንጀለኛ ፡ ዳኛውን ፡ ም ሕረት ፡ ለመነ

## involuntary
1. ባለማወቅ ፡ የደረሰ. An involuntary injury cannot be punished under the law. ባለማወቅ ፡ የደረሰ ፡ ጉዳት ፡ በሕግ ፡ ሊቀጣ ፡ አይችልም
2. (= adv.) ያለውዴታው. He was threatened until he gave involuntary consent to the plan. ያለውዴታው ፡ በሐሳቡ ፡ እስኪስማማ ፡ ድረስ ፡ አስፈራሩት

**be involuntary**
The beating of the heart is involuntary. የልብን ፡ ትርታ ፡ መቈጣጠር ፡ አይቻልም

## involve
1. አስከተለ. The trip involved a lot of expense. ጉዞው ፡ ብዙ ፡ ወጪ ፡ አስከተለ
2. ጠየቀ. Success always involves effort. ከግብ ፡ መድረስ ፡ ጥረትን ፡ ይጠይቃል
3. ከተተ. Repairing his house involved him in debt. ቤቱን ፡ ማሳደሱ ፡ ዕዳ ፡ ውስጥ ፡ ከተ ተው
4. ጣለ. His remark involved him in the argument. የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ ጣለው
5. አጠቃለለ. Housekeeping involves cooking, washing dishes, and cleaning. የቤት ፡ አያያዝ ፡ ምግብ ፡ ማብሰልን ፤ ሳሕን ፡ ማጠብንና ፡ ማጽዳ ትን ፡ ያጠቃልላል
6. ወሰደ(በት). Schoolwork involves most of my time. የትምህርት ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ አብዛኛ ውን ፡ ጊዜዬን ፡ ይወስድብኛል
7. ነካ. These changes in the company involve the interests of all the partners. ኩባንያው ፡ ው ስጥ ፡ የተደረገው ፡ ለውጥ ፡ የሸሪኮችን ፡ ፍላጎ ት ፡ ሁሉ ፡ ይነካል

## involved (adj.) የተወሳሰበ
Amharic likes to use very involved sentences. ባማርኛ ፡ የተወሳሰቡ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ይበዛሉ

**become involved** ተወሳሰበ
The more he spoke, the more involved his plan became. ይበልጥ ፡ በተናገረ ፡ ቁጥር ፡ እቅዱ ፡ እየተወሳሰበ ፡ ሄደ

**be involved in**
1. ተካፋይ ፡ ሆነ. He was involved in getting a scholarship for the student. ለተማሪው ፡ የነጻ ፡ ትምህርት ፡ በማስገኘት ፡ ረገድ ፡ ተካፋይ ፡ ሆነ
2. ገባ. He was involved in a plot to kill the merchant. ነጋዴውን ፡ ለመግደል ፡ በተደረገው ፡ አድማ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ነበር
3. አለ(በት). He does not realize how much work is involved in it. ምን ፡ ያህል ፡ ሥራ ፡ እንዳለበት ፡ አልተረዳውም

**be deeply involved** ተዋጠ
They were deeply involved in debt. በዕዳ ፡ ተውጠው ፡ ነበር

## invulnerable የማይበገር
The fortress was invulnerable. ምሽጉ ፡ የማይበ ገር ፡ ነበር
*No man is invulnerable to old age. ማንም ፡ ሰ ው ፡ ከእርጅና ፡ አያመልጥም
*Achilles was invulnerable except for his heel. አኪለስ ፡ ከተረከዙ ፡ በቀር ፡ ሌላውን ፡ ሰውነቱን ፡ ጉዳት ፡ አይበግረውም

## inward (adj.)
1. ውስጣዊ. A person's inward nature is not

easily revealed. የሰው ፡ ውስጣዊው ፡ ተፈጥሮ ው ፡ በቀላሉ ፡ ሊደረስበት ፡ አይቻልም

2. (= adv.) ወደ ፡ ውስጥ. An inward curve keeps cars from running off. ወደ ፡ ውስጥ ፡ የሚታጠፍ ፡ መጠምዘዣ ፡ መኪናዎች ፡ ከመንገድ ፡ እንዳይወጡ ፡ ይረዳል

**inward** (adv.) ወደ ፡ ውስጥ

This passage leads inward. ይህ ፡ መተላለፊያ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ያስገባል

*His thoughts turned inward. ሐሳቡን ፡ ውጦ ፡ አስቀረው

## inwardly

1. ውስጥ ፡ ውስጡን. Outwardly he was calm, but inwardly he was seething with rage. ላይ ፡ ላዩን ፡ የረጋ ፡ ነው ፤ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ግን ፡ በንዴት ፡ ጨሶ ፡ ነበር

2. ራሱን. Look inwardly and try to discover the truth. ራስህን ፡ መርምረህ ፡ እውነተኛውን ፡ ለማግኘት ፡ ሞክር

*She grieved inwardly. እንጀቷን ፡ በላት

## irascible ግልፍተኛ

The irascible old man frightened the children. ግልፍተኛው ፡ ሽማግሌ ፡ ልጆችን ፡ አስደነገጣቸው

## irate የተናደደ

The police dispersed the irate masses. ፖሊሶቹ ፡ የተናደደውን ፡ ሕዝብ ፡ በተኑት

## ire ቁጣ

His ire is easily provoked. ቁጣው ፡ አፍንጫው ፡ ላይ ፡ ነው

**arouse ire** አስቈጣ

The students' disobedience aroused the teacher's ire. የተማሪዎቹ ፡ አለመታዘዝ ፡ መምህሩን ፡ አስቈጣው

## irk ቅር ፡ አሰኘ

Your remarks irk me. የምትሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ቅር ፡ ያሰኘኛል

## irksome የሚያሰለች

Weeding is an irksome task. አረም ፡ ማረም ፡ የሚያሰለች ፡ ሥራ ፡ ነው

## iron (v.) ተኰሰ

She irons the sheets very well. አንሶላውን ፡ ጥሩ ፡ አድርጋ ፡ ትተኵሳለች

**be ironed out** ተጣራ

There are still a few things to be ironed out before they can sign the treaty. ውሉን ፡ ከመፈረማቸው ፡ በፊት ፡ ጥቂት ፡ የሚጣሩ ፡ ነገሮች ፡ አሉ

## iron (n.)

1. ብረት. This griddle is made of iron. ይህ ፡ ከብረት ፡ የተሠራ ፡ ምጣድ ፡ ነው

2. ካውያ. If the iron is hot I want to iron a shirt. ካውያው ፡ ግል ፡ እንደሆነ ፡ ሸሚዝ ፡ ልተኵስ ፡ እፈልጋለሁ

*Strike while the iron is hot. ፀሐይ ፡ ካለ ፡ ሩጥ

**irons** የእግር ፡ ብረት

Put the thief in irons! ሌባውን ፡ በእግር ፡ ብረት ፡ እሰረው

**irons in the fire**

He had other irons in the fire, so that one failure would not disappoint him. አንድ ፡ ነገር ፡ ባይሳካለት ፡ እንዳይወድቅ ፡ ሌሎች ፡ ሥራዎች ፡ ያካሂዳል

**iron** (adj.)

*He has an iron will. መንፈሰ ፡ ጠንካራ ፡ ነው

**with an iron hand** ጸጥ ፡ ለጥ ፡ አድርጎ

He governed his district with an iron hand. አውራጃውን ፡ ጸጥ ፡ ለጥ ፡ አድርጎ ፡ ገዛ

[See also 'band, strap']

## ironical

1. የምጸት. "Speedy" would be an ironical name for a snail. « ፈጣን » ፡ ለቀንድ ፡ አውጣ ፡ የምጸት ፡ ስም ፡ ነው

2. የዘበት. The speaker's ironical smile puzzled the audience. የተናጋሪው ፡ የዘበት ፡ ፈገግታ ፡ አዳማጮቹን ፡ አስገረማቸው

3. ዘበት. It's ironical that the student should know more than the teacher. ተማሪው ፡ ከአስተማሪው ፡ ይበልጥ ፡ ያውቃል ፡ ማለት ፡ ዘበት ፡ ነው

## ironing press ካውያ

The ironing press will take the wrinkles out of your suit. ካውያው ፡ የተጨማደደ ፡ ልብስህን ፡ ለመዘረጋጋት ፡ ይጠቅማል

## iron ore የብረት ፡ አፈር

Iron ore is smelted and made into iron. የብረት ፡ አፈር ፡ ቀልጦ ፡ ብረት ፡ ይሠራል

## irony ምጸት

The boys called the very thin boy "Fatty" in irony. ልጆቹ ፡ ቀጭኑን ፡ ልጅ ፡ በምጸት ፡ « ዱባ » ፡ አሉት

**irony of fate** የማይታመን

It was an irony of fate that the great cancer doctor died of cancer himself. ታላቁ ፡ የካንሰር ፡ ሐኪም ፡ ራሱ ፡ በካንሰር ፡ በሽታ ፡ መሞቱ ፡ የማይታመን ፡ ይመስላል

**irradiate** አደመቀ
Stars irradiate the night. ከዋክብት ፡ ሌትን ፡ ያደምቃሉ
*She seems to irradiate joy. የደስታ ፡ ምንጭ ፡ ነች

**irrational** መሠረተ ፡ ቢስ
He has an irrational fear of dogs. ስለ ፡ ውሻ ፡ መሠረተ ፡ ቢስ ፡ የሆነ ፡ ፍራቻ ፡ አለው

**irreconcilable** እርቅ ፡ የማይገባው
The two peoples are irreconcilable foes. ሁለቱ ፡ ሕዝቦች ፡ እርቅ ፡ የማይገባቸው ፡ ጠላቶች ፡ ናቸው

**irrefutable** የማይካድ
The omnipotence of God is irrefutable. የእግዚአብሔር ፡ ኀያልነት ፡ የማይካድ ፡ ነው

**irregular**
1. ሥርዓትን ፡ ያልተከተለ. Irregular court proceedings are invalid. ሥርዓትን ፡ ያልተከተለ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ አመራር ፡ አይጸናም
2. ሕግ ፡ ወጥ. This noun has an irregular plural. ይህ ፡ ስም ፡ ሕግ ፡ ወጥ ፡ የብዙ ፡ ቍጥር ፡ አለው
3. ከተለመደው ፡ የወጣ. Irregular breathing is a symptom of a disease. ከተለመደው ፡ የወጣ ፡ አተነፋፈስ ፡ የበሽታ ፡ ምልክት ፡ ነው
4. ወጣ ፡ ገባ. This coin has an irregular edge. ይህ ፡ ፍራንክ ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ ጠርዝ ፡ አለው
The surface of the ground is irregular. መሬቱ ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ ነው
5. ቁርጥ ፡ ቁርጥ. His respiration is irregular due to shock.ከድንጋጤ ፡ የተነሣ ፡ ትንፋሹ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ ይላል
*The student was irregular in class attendance. ተማሪው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ክፍል ፡ አይመጣም ፡ ነበር

**irregularity** (irregularities) የተዛባ ፡ ነገር
We will have to even out these irregularities first. መጀመሪያ ፡ እነዚህን ፡ የተዛቡ ፡ ነገሮችን ፡ ማስተካከል ፡ ይኖርብናል

**irrelevant** ከአርእስት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፤ የማይረባ
Don't confuse the issue with irrelevant questions! ከአርእስት ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ (ከማይረባ) ፡ ጥያቄ ፡ ጉዳዩን ፡ አታማታ

**be irrelevant**
1. ግንኙነት ፡ የለውም. Some people feel that European history is irrelevant to Ethiopian history. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የአውሮፓ ፡ ታሪክ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የለውም ፡ ይላሉ
2. አግባብነት ፡ የለውም. This provision is irrelevant. ይህ ፡ አንቀጽ ፡ አግባብነት ፡ የለውም

**irreligious** ሃይማኖተ ፡ ቢስ
His irreligious behavior was censured by all. ሃይማኖተ ፡ ቢስ ፡ ተግባሩ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ተነቀፈ

**irreplaceable** ምትክ ፡ የማይገኝለት
He thinks that he is irreplaceable. ምትክ ፡ የማይገኝለት ፡ ይመስለዋል

**irreproachable** እንከን ፡ የሌለው
His irreproachable conduct won him the admiration of the teachers. እንከን ፡ የሌለው ፡ ምግባሩ ፡ ያስተማሪዎችን ፡ አድናቆት ፡ አተረፈለት

**irresistible**
1. ለመቋቋም ፡ የማይቻል. The enemy's attack was irresistible. የጠላትን ፡ ጥቃት ፡ ለመቋቋም ፡ የማይቻል ፡ ነበር
2. የሚያጓጓ. Why do you put an irresistible dessert in front of me? ለምን ፡ የሚያጓጓ ፡ ማጣጣሚያ ፡ ፊት ፡ ለፊቴ ፡ ታስቀምጣለህ ?

**irresolute** ወላዋይ
Irresolute persons make poor leaders. ወላዋይ ፡ ሰዎች ፡ የማይረቡ ፡ መሪዎች ፡ ይሆናሉ

**irrespective of** ሳይለይ
Everyone was invited, irrespective of age. ዕድሜ ፡ ሳይለይ ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ተጋብዟል

**irresponsibility** ኀላፊነት ፡ መዘንጋት
His irresponsibility cost him his job. ኀላፊነቱን ፡ መዘንጋቱ ፡ ሥራውን ፡ አሳጣው

**irresponsible**
1. ግድ ፡ የለሽ. His irresponsible driving caused three deaths. ግድ ፡ የለሽ ፡ አነዳዱ ፡ የሦስት ፡ ሰው ፡ ሞት ፡ አስከተለ
2. እምነቱን ፡ የማይጠብቅ. He is an irresponsible businessman. እምነቱን ፡ የማይጠብቅ ፡ ነጋዴ ፡ ነው

**irretrievable**
1. የማይተካ. The books destroyed in the library fire are irretrievable. በቃጠሎው ፡ የጠፉት ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ መጽሐፎች ፡ የማይተኩ ፡ ናቸው
2. የማይመለስ. Soil washed out into the sea is irretrievable. ታጥቦ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ አፈር ፡ የማይመለስ ፡ ነው

**irreverent** አክብሮት ፡ የጐደለ(ው)
His irreverent attitude towards the Emperor enraged the courtiers. በንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊት ፡ አክብሮት ፡ የጐደለው ፡ ምግባር ፡ መፈጸም ፡ ባለሟሎቹን ፡ አናደደ

**(be) irreversible** ሊመለስ ፡ አይችልም
Once the combustion of gasoline begins, the process is irreversible. ቤንዚን ፡ እንዲ ፡ መቀጣ
ጠል ፡ ከጀመረ ፡ ሊመለስ ፡ አይችልም

**irrevocable** የማይሻር
The court's decision is irrevocable. የፍርድ ፡ ቤ
ቱ ፡ ውሳኔ ፡ የማይሻር ፡ ነው

**irrigate** በመስኖ ፡ አጠጣ
They are working out a new method for irrigating the land. መሬቱን ፡ በመስኖ ፡ ለማጠ
ጣት ፡ አዲስ ፡ ዘዴ ፡ በመፍጠር ፡ ላይ ፡ ናቸው

**irrigation** መስኖ
Irrigation enables us to raise three crops a year. መስኖ ፡ በዓመት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ለማምረት ፡ ያ
ስችለናል
The Egyptians have practiced irrigation for centuries. ግብጾች ፡ ከብዙ ፡ ዘመናት ፡ ጀምሮ ፡
በመስኖ ፡ ይጠቀሙ ፡ ነበር

**irritable** ግልፍተኛ
The driver is an irritable person ሹፌሩ ፡ ግል
ፍተኛ ፡ ሰው ፡ ነው

**be irritable**
1. ቁጣ ፡ ቁጣ ፡ አለ. He is very irritable this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ ቁጣ ፡ ቁጣ ፡ ብሎታል
2. ተቈጣ. My skin is easily irritable. ቆዳዬ ፡
በቀላሉ ፡ ይቈጣል

**irritably** በብስጭት
He blasted his horn irritably at every car in his way. በብስጭት ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ባጋጠሙ
ት ፡ መኪናዎች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ የመኪናውን ፡ ጥሩንባ ፡
በኀይል ፡ ነፋ

**irritate**
1. አበሳጨ ፤ አናደደ ፤ አስቈጣ. His remarks irritated me. የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ አበሳጨኝ ፡
(አናደደኝ ፤ አስቈጣኝ)
2. አጨናበሰ. The smoke irritated her eyes.
ጭሱ ፡ ዓይኗን ፡ አጨናበሳት
3. አስቈጣ. Harsh soap irritates her skin.
ሻካራ ፡ ሳሙና ፡ ቆዳዋን ፡ ያስቈጣዋል

**irritation** መቈጣት
The boss's irritation disturbed everyone.
የአለቃው ፡ መቈጣት ፡ ሁሉንም ፡ አስጨነቀ

**skin irritation** የተቈጣ ፡ ቆዳ
This medicine is not helping my skin irritation.
ለተቈጣው ፡ ቆዳዬ ፡ ይህ ፡ መድኃኒት ፡ አይረዳ
ኝም

**irrupt** ጥሶ ፡ ፈሰሰ
The water irrupted through the dike. ውኃው ፡
ግድቡን ፡ ጥሶ ፡ ፈሰሰ

**is**
1. ነው. He is a teacher. እርሱ ፡ አስተማሪ ፡ ነው
2. አለ. The girl is at the market. ልጅቱ ፡ እገበ
ያ ፡ አለች

**-ish,** expressed in Amharic by a composite verb
This coat is red, but that coat is reddish.
ይህ ፡ ኮት ፡ ቀይ ፡ ነው ፤ ግን ፡ ያኛው ፡ ኮት ፡ ቀ
ላ ፡ ያለ ፡ ነው

**Islam**
1. እስልምና. Islam spread in Africa. በአፍሪካ ፡
ውስጥ ፡ እስልምና ፡ ተስፋፍቷል
2. እስላም. Islam is the religion of Arabia.
የዐረቢያ ፡ ሃይማኖት ፡ እስላም ፡ ነው

**island** ደሴት
There are several islands in Lake Tana.
ጣና ፡ ሐይቅ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ደሴቶች ፡ አሉ

**isolate**
1. ከሌላ ፡ ሰፍራ ፡ ለየ. Lack of communications isolated the town. የመገናኛ ፡ እጦት ፡ ከተማው
ን ፡ ከሌላው ፡ ሰፍራ ፡ ለየው
2. ከሌሎች ፡ ለየ. The lack of a telephone isolated me. ስልክ ፡ ማጣቴ ፡ ከሌሎች ፡ ለየኝ
The scientist isolated the virus of the common cold. ሳይንቲስቱ ፡ የጉንፋኑን ፡ ቫይረስ ፡ ከሌሎቹ ፡
ለየው
3. ለይቶ ፡ አስተኛ. The hospital isolated contagious cases. ሆስፒታሉ ፡ ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ የያ
ዛቸውን ፡ ሰዎች ፡ ለይቶ ፡ አስተኛ

**isolated** (adj.) ገለልተኛ
The house is built on an isolated spot. ቤቱ ፡
ገለልተኛ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ተሠርቷል

**be isolated**
1. ከሌሎቹ ፡ ተገለለ. The sick children were isolated. የታመሙት ፡ ሕፃናት ፡ ከሌሎቹ ፡ ተገ
ለሉ
2. ከሌሎቹ ፡ ተነጠለ. Some of our units have been isolated by enemy forces. አንዳንድ ፡ የወታ
ደር ፡ ክፍሎቻችን ፡ በጠላት ፡ ኀይል ፡ ከሌሎቹ ፡
ተነጥለው ፡ ነበር

**isolation**
1. ለብቻ ፡ መሆን. He prefers isolation to being with other people. ከሌሎች ፡ ጋር ፡ ከመቀላቀል ፡
ይልቅ ፡ ለብቻ ፡ መሆንን ፡ ይመርጣል
2. የማግለል ፡ ዘዴ. Isolation is used in treating

contagious diseases. ተላላፊ ፡ በሽታዎችን ፡ ለማከም ፡ በማግለል ፡ ዘዴ ፡ ይጠቀማሉ

**issue** (vt.)
1. ዐደለ. They issued food and clothing to the refugees. ለስደተኞቹ ፡ ምግብና ፡ ልብስ ፡ ዐደሉ
2. አወጣ. The government issued a denial regarding the arrest of the ambassador. ስለ ፡ አምባሳደሩ ፡ መታሰር ፡ መንግሥት ፡ ማስተባበያ ፡ አወጣ
The government issued a new coin. መንግሥት ፡ አዲስ ፡ ገንዘብ ፡ አወጣ
The company issues an illustrated magazine. ኩባንያው ፡ ሥዕላዊ ፡ መጽሔት ፡ ያወጣል
3. ሰጠ. Only the government can issue passports. የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችል ፡ መንግሥት ፡ ብቻ ፡ ነው
4. ተፋ. The crater issues smoke. የእሳተ ፡ ገሞራው ፡ አፍ ፡ ጭስ ፡ ይተፋል

**issue** (vi.)
1. ወጣ. Pus issued from the wound. መግል ፡ ከቁስሉ ፡ ወጣ
2. መነጨ. Cold water issues from the mountain spring. ቀዝቃዛ ፡ ውኃ ፡ ከተራራው ፡ ሥር ፡ ይመነጫል
3. (= trans.) ተፋ. +Smoke issued from the crater. የእሳተ ፡ ገሞራው ፡ አፍ ፡ ጭስ ፡ ይተፋል
4. ተገኘ. Victory issued from our efforts. በጥረታችን ፡ ድል ፡ ተገኘ

**be issued** ወጣ
During the President's illness, a medical bulletin was issued daily. ፕሬዚዳንቱ ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ የጤንነታቸው ፡ መግለጫ ፡ በየቀኑ ፡ ይወጣ ፡ ነበር
[See also 'decree']

**issue** (n.)
1. እትም. I have not read the last issue. የመጨረሻውን ፡ እትም ፡ አላነበብኩትም
2. ጉዳይ. They debated the issue in parliament. ፓርላማ ፡ ውስጥ ፡ በጉዳዩ ፡ ተከራከሩበት
3. አከራካሪ ፡ ጉዳይ. New paving is an issue in our town. በከተማችን ፡ ውስጥ ፡ መንገድ ፡ ማሠራት ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ ነው
4. ውጤት. We will have to await the issue of the battle before we can do anything. አንዳች ፡ ነገር ፡ ከማድረጋችን ፡ በፊት ፡ የውጊያውን ፡ ውጤት ፡ መጠበቅ ፡ አለብን
5. መነታረኪያ. I do not want to make an issue of it. ይህንን ፡ መነታረኪያ ፡ ላደርገው ፡ አልፈልግም
6. ዘር. My uncle died without issue. አጎቴ ፡ ያለ ፡ ዘር ፡ አረፈ

**at issue** ንግግር ፡ የሚደረግበት ፡ ጉዳይ
At issue is the power of the state to control a person's life. ንግግር ፡ የሚደረግበት ፡ ጉዳይ ፡ መንግሥት ፡ የሰውን ፡ ኑሮ ፡ ሊቈጣጠር ፡ የሚችልበት ፡ ሥልጣን ፡ ነው

**the day of issue** የወጣበት ፡ ቀን
I bought many stamps on the day of issue. በወጡበት ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ ቴምብሮች ፡ ገዛሁ

**take issue with** ተቃወመ
The students took issue with the proposal. ተማሪዎቹ ፡ የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ ተቃወሙ

**isthmus** ልሳነ ፡ ምድር

**it** -ው, -ት
I cannot do it. እኔ ፡ ላደርገው ፡ አልችልም
They cannot do it. እነሱ ፡ ሊያደርጉት ፡ አይችሉም
*That's it! እንዲያ ፡ ነው

**it is** ነው
It is six o'clock. ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ነው

**it was** ነበር
Who was it? It was John. ማን ፡ ነበር ? ጆን ፡ ነበር

**Italian**
1. ኢጣሊያን. There are many Italians in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ አሉ
2. ኢጣሊያንኛ. I studied Italian last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ኢጣሊያንኛ ፡ ተማርኩ

**Italy** ኢጣልያ ፤ ኢጣሊያ

**itch** (vt.) ኰሰኰሰ
His wool shirt always itches him. ሱፍ ፡ ሸሚዙ ፡ ሁልጊዜ ፡ ይኰሰኵሰዋል

**itch** (vi.)
1. አሳከከ. The wound itches. ቁስሉ ፡ ያሳክካል
2. ኰሰኰሰ. The shirt itches. ሸሚዙ ፡ ይኰሰኵሳል
3. ጓጓ. He is itching to get his hands on her money. የሷን ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ይጓጓል

**itch** (n.) እከክ
Any itch can be cured by applying this powder. ማንኛውም ፡ እከክ ፡ በዚህ ፡ መድኃኒት ፡ ይድናል

**have an itch to** ጠንካራ ፡ ምኞት ፡ አለው
He has an itch to fly. አውሮፕላን ፡ ለመንዳት ፡ ጠንካራ ፡ ምኞት ፡ አለው

**item**
1. እቃ. We do not carry that item. ይህንን ፡ እቃ ፡ አናስመጣም
2. ክፍል. The first item on the program is a

native dance. በፕሮግራሙ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ብሔራዊ ፡ ጭፈራ ፡ ነው

3. ነገር. How many items are on that bill? ሒሳቡ ፡ ላይ ፡ ስንት ፡ ነገሮች ፡ ሰፍረዋል ?

4. ወሬ. Did you see the item in the paper? ወሬውን ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ አየኸው ?

5. ተራ ፡ ቁጥር. I don't understand the wording of item no. 3. በተራ ፡ ቁጥር ፡ ሦስት ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ አጻጻፍ ፡ አልገባኝም

**item by item** በውል ፡ በውሉ

He enumerated the merchandise item by item. የንግዱን ፡ እቃ ፡ በውል ፡ በውሉ ፡ ዘረዘረ

## itemize

1. ዘረዘረ. He itemized the changes he wants made. እንዲደረጉ ፡ የሚፈልጋቸውን ፡ ለውጦች ፡ ዘረዘረ

2. ዝርዝር ፡ ጻፈ. He itemized the bill for the books. የመጻሕፍትን ፡ ዋጋ ፡ ዝርዝር ፡ ጻፈ

## iterate

1. ደጋገመ. The teacher iterated his request that there be silence. መምህሩ ፡ ጸጥታ ፡ እንዲደረግ ፡ ደጋግሞ ፡ ጠየቀ

2. ደጋግሞ ፡ አስታወቀ. It is necessary to iterate the instructions. መምሪያዎችን ፡ ደጋግሞ ፡ ማስታወቅ ፡ ያስፈልጋል

## itinerant ተዘዋዋሪ

A troop of itinerant musicians came to town. ተዘዋዋሪ ፡ የሙዚቃ ፡ ጓድ ፡ ከተማ ፡ ገብቷል

## itinerary

1. ጉዞ. His itinerary was interrupted by a railway strike. በባቡር ፡ ጣቢያ ፡ ሠራተኞች ፡ አድማ ፡ ምክንያት ፡ ጉዞው ፡ ተቋርጧል

2. የጉዞ ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ. I do not know the Emperor's itinerary yet. የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ የጉዞ ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ፡ ገና ፡ አላወቅሁትም

## itself ብቻውን

The frame itself is worth more than the picture. ከሥዕሉ ፡ ይልቅ ፡ ክፈፉ ፡ ብቻውን ፡ የበለጠ ፡ ዋጋ ፡ አለው

**by itself**

1. ዐውቆ. The car won't stop by itself. መኪናው ፡ ዐውቆ ፡ አይቆምም

2. ራሱን ፡ ችሎ. This cannot stand by itself. ራሱን ፡ ችሎ ፡ አይቆምም

**in itself**

1. ራሱ. Card playing is not harmful in itself. ካርታ ፡ ጨዋታው ፡ ራሱ ፡ ጎጂ ፡ አይደለም

2. ብቻውን. That in itself is not important. ነገሩ ፡ ብቻውን ፡ ዋጋ ፡ የለውም

## ivory የዝሆን ፡ ጥርስ

This box is made of ivory. ይህ ፡ ሣጥን ፡ ከዝሆን ፡ ጥርስ ፡ የተሠራ ፡ ነው

## ivy ሐረግ

The walls were covered with ivy. ግድግዳው ፡ በሐረግ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር

# J

**jab**
1. ወጋ. He jabbed me with a fork. በሹካ፡ወጋኝ
2. ተከለ. The doctor jabbed the needle into his arm. ሐኪሙ ፡ መርፌውን ፡ ከክንዱ ፡ ላይ ፡ ተከለው
3. ጉሸመ. He jabbed his elbow into my ribs. ጐኔን ፡ በክርኑ ፡ ጉሸመኝ

**jack** ክሪክ
When you change the tire, use a jack to lift your car wheel off the ground. ጎማ ፡ ስትቀይር ፡ መኪናህን ፡ ለማንሣት ፡ በክሪክ ፡ ተጠቀም

**jackal** ቀበሮ
The jackal hunts kids. ቀበሮ ፡ የፍየል ፡ ግልገሎችን ፡ ያድናል

**jackass** (n.)
1. ወደል ፡ አህያ. The jackass brays very loudly. ወደል ፡ አህያ ፡ በጣም ፡ ያናፋል
2. ደደብ. Some jackass ran into my parked car. አንድ ፡ ደደብ ፡ የቆመች ፡ መኪናዬን ፡ ገጨት

**jacket** ጃኬት
He wears a jacket instead of a coat. በኮት ፡ ፈንታ ፡ ጃኬት ፡ ይለብሳል

**jade** [ለጌጣ ፡ ጌጥ ፡ የሚያገለግል ፡ ጠንካራ ፡ የከበረ ፡ ድንጋይ]

**jagged**
1. ወጣ ፡ ገባ. On the map, the coast has a jagged outline. በካርታ ፡ ሲታይ ፡ የባሕሩ ፡ ጠረፍ ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ ቅርጽ ፡ አለው
2. የሾለ. We cut our bare feet on the jagged rocks. የሾለው ፡ ድንጋይ ፡ ባዶውን ፡ እግራችንን ፡ ቈረጠ

**jaguar** [በመካከለኛው ፡ አሜሪካ ፡ የሚገኝ ፡ አስፈሪ ፡ የዱር ፡ ድመት]

**jail** (v.) አሰረ
The government jailed everyone who was suspected of theft. መንግሥቱ ፡ በሌብነት ፡ የተጠረጠሩትን ፡ ሁሉ ፡ አሰረ

**jail** (n.)
1. እስራት. He was sentenced to six months in jail. ስድስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ተፈረደበት
2. እስር ፡ ቤት. The police kept him in jail for three months. ፖሊስ ፡ ለሦስት ፡ ወር ፡ እስር ፡ ቤት ፡ አቆየው
3. ወህኒ ፡ ቤት. What is the name of the Addis Ababa jail? ያዲስ ፡ አበባው ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ስሙ ፡ ምንድነው ?

**land in jail** እስር ፡ ቤት ፡ ገባ
We nearly landed in jail. እስር ፡ ቤት ፡ ልንገባ ፡ ነበር

**jailer** የወህኒ ፡ አዛጋ
The jailer released the prisoners. የወህኒው ፡ አዛጋ ፡ እስረኞቹን ፡ ለቀቀ

**jam** (vt.)
1. ወሸቀ. He jammed a stick in the door to keep it from closing. በሩ ፡ እንዳይዘጋ ፡ ዕንጨት ፡ ወሸቀበት
2. አጨቀ. He jammed all his clothes into one suitcase. ልብሶቹን ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ሻንጣ ፡ ውስጥ ፡ አጨቀ
3. አጨናነቀ. Cars jammed the parking lot. መኪናዎቹ ፡ የመቆሚያውን ፡ ቦታ ፡ አጨናነቁት
4. ቀረጠፈ. +He jammed his finger in the door. በሩ ፡ ጣቱን ፡ ቀረጠፈው
5. ዘጋ. A pebble jammed the motor. ሞተሩን ፡ ጠጠር ፡ ዘጋው

**jam** (vi.) ነከሰ
The window has jammed; I cannot open it. መስኮቱ ፡ ነክሷል ፤ ልከፍተው ፡ አልችልም

**be jammed**
1. ተጣበበ. The corridors were jammed by crowds of schoolchildren. መተላለፊያው ፡ በተማሪዎች ፡ ብዛት ፡ ተጣበ ፡ ነበር
2. ተቀረቀረ. The ship was jammed between two rocks. መርከቧ ፡ በሁለት ፡ አለቶች ፡ መካከል ፡ ተቀረቀረች

**jam** (n.)
1. ማርመላታ. Waiter, please pass me the jam! አሳላፊ ፤ ማርመላታ ፡ አምጣልኝ
2. መተፋፈግ ፤ መጨናነቅ. The concurrence of three large highways causes traffic jams. የሦስት ፡ ታላላቅ ፡ አውራ ፡ መንገዶች ፡ መገናኘት ፡ የትራፊክ ፡ መተፋፈግ ፡ (መጨናነቅ) ፡ ይፈጥራል
*An accident caused a traffic jam. አደጋው ፡ ትራፊኩን ፡ ዘጋ

**janitor** ጠራጊ
Call the janitor and have him clean up this mess! ጠራጊውን ፡ ጠርተህ ፡ ይህንን ፡ ቆሻሻ ፡ አስጠርገው

**January** ጥር

**Japan** ጃፓን

**Japanese**
1. የጃፓን ፡ ሰው. My friend is Japanese. ጓደኛዬ ፡ የጃፓን ፡ ሰው ፡ ነው
2. የጃፓን ፡ ቋንቋ. Last year I studied Japanese. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ የጃፓን ፡ ቋንቋ ፡ ተማርኩ

**Japanese** (adj.) የጃፓን
The Japanese trade mission visited Ethiopia. የጃፓን ፡ የንግድ ፡ መልእክተኞች ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጐበኙ

**jar** (jarred), vt.
1. አንቃነቀ. Your heavy footsteps jarred my table. ኀይለኛው ፡ አረማመድህ ፡ ጠረጴዛዬን ፡ አንቃነቀው
2. ክው ፡ አደረገ. The news jarred him. ዜናው ፡ ክው ፡ አደረገው

**jar** (vi.)
1. ተጋጨ. We did not get on well together; our opinions always jarred. አልተግባባንም ፤ ሐሳባችን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተጋጨ
2. ሲጢጥ ፡ አለ. The brakes jarred as the car stopped. መኪናው ፡ ሲቆም ፡ ፍሬኑ ፡ ሲጢጥ ፡ አለ

**jar one's nerves** ሰቀጠጠ
The children's screams jar my nerves. የልጆች ፡ ጩኸት ፡ ይሰቀጥጠኛል

**jar** (n.)
1. ማሰሮ. We keep the potatoes in a jar. ድንቹን ፡ ማሰሮ ፡ ውስጥ ፡ እናኖራለን
2. ገንቦ. Put a label on the jar! ገንቦው ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ ለጥፍበት
3. ማስቀመጫ. He put the flowers in a glass jar. አበባዎቹን ፡ በብርጭቆው ፡ ማስቀመጫ ፡ ውስጥ ፡ አኖራቸው

**jargon** ልዩ ፡ ቋንቋ
The thieves have their own jargon. ሌቦቹ ፡ የራሳቸው ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ አላቸው

**jaundice** የወፍ ፡ በሽታ
He has a bad case of jaundice. መጥፎ ፡ የወፍ ፡ በሽታ ፡ ይዞታል

**jaunty** ቄንጠኛ
She wore a jaunty little hat. ትንሽ ፡ ቄንጠኛ ፡ ባርኔጣ ፡ አድርጋለች

**walk with jaunty steps** እየተረገረገ ፡ ተራመደ
The happy boy walked with jaunty steps. የተደሰተው ፡ ልጅ ፡ እየተረገረገ ፡ ተራመደ

**javelin** ጦር
He is the best javelin thrower. ከሁሉም ፡ የላቀ ፡ ጦር ፡ ወርዋሪ ፡ ነው

**jaw** ማንገጭላ
The punch broke his jaw. ቡጢው ፡ ማንገጭላውን ፡ አወለቀው

**jawbone** መንጋጋ
Samson killed many people with a donkey's jawbone. ሳምሶን ፡ በአህያ ፡ መንጋጋ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ገደለ

**jaywalk**
*You are not allowed to jaywalk. አውራ ፡ ጐዳናውን ፡ ያለማቋረጫው ፡ ማቋረጥ ፡ አይፈቀድልህም

**jealous**
1. ቀናተኛ. Be careful, her husband is jealous. ተጠንቀቅ ፤ ባሏ ፡ ቀናተኛ ፡ ነው
2. የማያስነካ. The dog was a jealous guardian of the child. ውሻው ፡ ልጁን ፡ የማያስነካ ፡ ጠባቂ ፡ ነበር

**be jealous**
1. ቀና ፤ ተመቀኘ. She's jealous because you have a new coat. አዲስ ፡ ኮት ፡ ስላለሽ ፡ ቀንታለች ፡ (ተመቅኝታለች)
2. ተጠነቀቀ. He is jealous of his good name. ስለ ፡ ስሙ ፡ በጣም ፡ ይጠነቀቃል

**jealousy** ቅናት
He is eaten up with jealousy. ቅናት ፡ አሰልስሎታል

**jeer** (v.)
1. ሣቀ(በት). The children jeered at the new student's mistake. ልጆቹ ፡ ባዲሱ ፡ ተማሪ ፡ ስሕተት ፡ ሣቁበት
2. ጮኸ(በት). The crowd jeered at the losing team. ተመልካቹ ፡ ሕዝብ ፡ በተሸናፊ ፡ ቡድን ፡ ጮኸበት

**jeer** (n.) የፌዝ ፡ ሣቅ
The children's jeers stabbed Tom to the heart. የልጆቹ ፡ የፌዝ ፡ ሣቅ ፡ የቶምን ፡ ስሜት ፡ ጐዳው

**jeopardize**
1. አጨናገፈ. I will not jeopardize my chances. ዕድሌን ፡ አላጨናግፍም
2. ባደጋ ፡ ላይ ፡ ጣለ. He jeopardized his life. ሕይወቱን ፡ ባደጋ ፡ ላይ ፡ ጣለ

**jeopardy** የሚያስጋ ፡ ሁኔታ
A fireman's life is often in jeopardy. የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካይ ፡ ሕይወት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በሚያስጋ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነው

**jerk** በፍጥነት ፡ ጎታ ፤ በፍጥነት ፡ ሳበ
He jerked the reins to make the horse stop. ፈረሱን ፡ ለማቆም ፡ ልጓሙን ፡ በፍጥነት ፡ ጎታ
He jerked a signal cord to make the train stop. ባቡሩ ፡ እንዲቆም ፡ የምልክት ፡ መስሚውን ፡ ሰንሰለት ፡ በፍጥነት ፡ ሳበ

**jerk along** እየተንገጫገጨ ፡ ሄደ
The bus jerked along. አውቶቡሱ ፡ እየተንገጫገጨ ፡ ሄደ

**jerk (out of)** መነጨቀ
She jerked the book out of his hands. መጽሐፉን ፡ ከእጁ ፡ መነጨቀችው

**jerk** (n.), **with a ~** ባኖ
The sleeping man awoke with a jerk. የተኛው ፡ ሰውዬ ፡ ባኖ ፡ ተነሣ
*The train started with a sudden jerk. ባቡሩ ፡ ሲነሣ ፡ ተንገጫገጨ

**jest** (v.) አፌዘ
It is not proper to jest about a serious matter. በቁም ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ማፌዝ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**jest** (n.) ቀልድ
His jests do not amuse me. ቀልዶቹ ፡ አያሥቁኝም
I said that only in jest. ለቀልድ ፡ ያልኩት ፡ ነው

**jester** አጫዋች
The jester entertained the court with his performance. አጫዋቹ ፡ ግቢውን ፡ በትርእይት ፡ አስደሰተ

**Jesuit** ኢየሱሳዊ
There are many Jesuits in Canada. ካናዳ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ኢየሱሳውያን ፡ ይገኛሉ

**jet**
1. ቡልቅታ. A jet of water spurted from the fountain. የውኃ ፡ ቡልቅታ ፡ ከምንጩ ፡ ውስጥ ፡ ተወረወረ
2. ጀት ፡ አውሮፕላን. Ethiopian Air Lines imported some jets recently. የኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ በቅርቡ ፡ ጥቂት ፡ ጀት ፡ አውሮፕላኖች ፡ አስመጣ

**Jew** አይሁዳዊ (pl. አይሁዳውያን)

**jewel**
1. የከበረ ፡ ድንጋይ ፡ ፈርጥ. There are many jewels on Theodore's crown. በቴዎድሮስ ፡ ዘውድ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የከበሩ ፡ ድንጋይ ፡ ፈርጦች ፡ አሉ
2. ዓይን. His new secretary is a jewel. አዲሷ ፡ ጸሐፊው ፡ ዓይን ፡ ናት

**jeweler** አንጥረኛ
The jeweler is fixing my ring. አንጥረኛው ፡ ቀለበት ፡ ይሠራልኛል

**jewelry** ጌጣጌጥ
His wife likes to exhibit her jewelry. ሚስቱ ፡ ጌጣጌጧን ፡ ማሳየት ፡ ትወዳለች

**Jewish** የአይሁዶች
The Jewish holiday is on Saturday. የአይሁዶች ፡ ሰንበት ፡ ቅዳሜ ፡ ነው

**jibe** ተጋጠመ ፤ ተገጣጠመ ፤ ተስማማ
Their stories do not jibe. የተናገሩት ፡ አይጋጠምም ፡ (አይገጣጠምም ፤ አይስማማም)

**jiffy, in a ~** በቶሎ
I will be there in a jiffy. በቶሎ ፡ እመጣለሁ

**jig, dance a ~** ጮቤ ፡ መታ
He danced a jig, he was so happy. ከደስታ ፡ የተነሣ ፡ ጮቤ ፡ መታ

**jiggle** አነቃነቀ
Don't jiggle my arm while I am holding a glass full of water. በብርጭቆ ፡ ሙሉ ፡ ውኃ ፡ ይዤ ፡ ሳለሁ ፡ እጄን ፡ አታነቃንቅ

**jilt** ከዳ
When he lost his job, she jilted him. ከሥራው ፡ ሲያስወጡት ፡ ከዳችው

**jingle** (vt.) አንቃጨለ
He jingled his keys. ቁልፎቹን ፡ አንቃጨለ

**jingle** (vi.) ተቅጨለጨለ
The bells jingled. ቃጭሎቹ ፡ ተቅጨለጨሉ

**jingle** (n.) መቃጨል
We heard the jingle of the bells. የደወሎቹን ፡ መቃጨል ፡ ሰማን

**jittery, feel ~** ተሸበረ
I feel jittery before every examination. ከፈተና ፡ በፊት ፡ ሁልጊዜ ፡ እሸበራለሁ

**job**
1. ሥራ. He is out of a job right now. አሁን ፡ ሥራ ፡ የለውም
It is quite a job to clean the cellar. ምድር ፡ ቤቱን ፡ ማጽዳት ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ ነው

It is not my job to tell him that. ያንን ፡ ለሱ ፡ መንገሩ ፡ የኔ ፡ ሥራ ፡ አይደለም
2. ተግባር. The regulation of trade is the job of the Ministry of Commerce. ንግድን ፡ መቈጣጠር ፡ የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ተግባር ፡ ነው
3. ነገር. It was an awful job to convince her. እርሷን ፡ ማግባባቱ ፡ እጅግ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ነበር
[See also 'pretty']

**jobless** ሥራ ፡ ፈት
There are large numbers of jobless people in the city. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ፈቶች ፡ አሉ

**jockey** [የመሽቀዳደሚያ ፡ ፈረሶችን ፡ የሚጋልብ ፡ ባለሙያ]

**jocose** የቀልድ
Jocose talk is not proper in church. በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ የቀልድ ፡ አነጋገር ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**jocular**
1. ቀልደኛ. A jocular person is needed to make the party lively. ፓርቲውን ፡ ለማድመቅ ፡ ቀልደኛ ፡ ሰው ፡ ያስፈልጋል
2. የፌዝ. I made a jocular reply to his question. ለጥያቄው ፡ የፌዝ ፡ መልስ ፡ ሰጠሁት

**jocund** ሣቂታ
Everyone likes the jocund old man. ሁሉም ፡ ሣቂታውን ፡ ሽማግሌ ፡ ይወዱታል

**jog** (jogged) ነካ ፡ አደረገ
She jogged his elbow to get his attention. ሐሳቡን ፡ ለመማረክ ፡ ክርኑን ፡ ነካ ፡ አደረገችው

**jog along** እያዘገመ ፡ ሄደ
The old horse jogged along. ያረጀው ፡ ፈረስ ፡ እያዘገመ ፡ ሄደ

**join** (vt.)
1. አገጣጠመ. How do you join these two parts? እነዚህን ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ እንዴት ፡ ታገጣጥማቸዋለህ ?
2. አስተሳሰረ. The priest joins the couple in marriage. ቄሱ ፡ ሙሽሮቹን ፡ በጋብቻ ፡ ያስተሳስራል
3. መጣ. Go now! I will join you later. አሁን ፡ ሂድ ፤ እኔ ፡ በኋላ ፡ እመጣለሁ
4. አብሮት ፡ ሄደ. He joined us when we went to the library. ወደ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ስንሄድ ፡ አብሮን ፡ ሄደ
5. ከ - - - ጋር ፡ ተቀላቀለ ፤ ከ - - - ገባ. The river Dedesa joins the Nile. የዴዴሳ ፡ ወንዝ ፡ ከዓባይ ፡ ጋር ፡ ይቀላቀላል
The brook joins the river. ጅረቱ ፡ ከወንዙ ፡ ይገባል
6. ከ - - - ጋር ፡ ተዋሰነ. His farm joins mine. ማሳው ፡ ከኔው ፡ ጋር ፡ ይዋሰናል
7. የ - - አባል ፡ ሆነ. He wants to join our club. የክበባችን ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ ይፈልጋል
*My wife joins me in thanking you for the gift. ባለቤቴም ፡ እኔም ፡ ስለ ፡ ስጦታው ፡ እናመሰግንሃለን

**join** (vi.)
1. ተገናኘ. The roads join outside the city. ከከተማው ፡ ወጣ ፡ ሲል ፡ መንገዶቹ ፡ ይገናኛሉ
2. ተባበረ. They joined in a plot to oust him. እርሱን ፡ ከሥልጣን ፡ ለማውረድ ፡ በአድማ ፡ ተባበሩ
3. ተካፋይ ፡ ሆነ. Why doesn't Tom join in the conversation? ቶም ፡ በውይይቱ ፡ ላይ ፡ ተካፋይ ፡ የማይሆነው ፡ ለምንድነው ?

**be joined** ተገናኘ
The two lakes are joined by a narrow channel. ሁለቱ ፡ ሐይቆች ፡ በጠባብ ፡ ሰላጤ ፡ ይገናኛሉ

**join (the) army** በጦር ፡ ሰራዊት ፡ ውስጥ ፡ ተቀጠረ ፤ ወታደርነት ፡ ገባ
A physical examination is a preliminary to joining the army. በጦር ፡ ሰራዊት ፡ ውስጥ ፡ ለመቀጠር ፡ (ወታደርነት ፡ ለመግባት) ፡ ያካል ፡ ምርመራ ፡ በቅድሚያ ፡ ይደረጋል

**join forces** ተባበረ
We joined forces to defeat the proposal. የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ ውድቅ ፡ ለማድረግ ፡ ተባበርን

**join hands**
1. እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተያያዘ. The children joined hands to form a large circle. ልጆቹ ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተያይዘው ፡ ትልቅ ፡ ክበብ ፡ ሠሩ
2. ተባበረ. The two companies joined hands to finish the work. ሁለቱ ፡ ኩባንያዎች ፡ ሥራውን ፡ ለመጨረስ ፡ ተባበሩ

**join together** ተረዳዳ
They joined together to pull the truck out of the mud. የጭነት ፡ መኪናውን ፡ ከጭቃው ፡ ውስጥ ፡ ለማውጣት ፡ ተረዳዱ

**joint** (n.)
1. ዓጽቅ. The finger joints are swollen by the disease. የጣቱ ፡ ዓጽቆች ፡ ከበሽታው ፡ የተነሣ ፡ አብጠዋል
2. አንጓ ፤ ዓጽቅ. He pierced the joints of the bamboo to make a pipe. ቱቦ ፡ ለመሥራት ፡ የቀርቀሃውን ፡ አንጓዎች ፡ (ዓጽቆች) ፡ በሳ

3. መገጣጠሚያ. All my joints ache. መገጣጠሚያዎቼን ፡ በሙሉ ፡ ይቈረጥመኛል
The joints in this chair are coming apart. የዚህ ፡ ወምበር ፡ መገጣጠሚያ ፡ ሊለያይ ፡ ነው

**be out of joint**
1. ወለቀ. My finger is out of joint. ጣቴ ፡ ወልቋል
2. ተቃወሰ. The times are out of joint. ጊዜው ፡ ተቃውሷል

**joint** (adj.) የጋራ
They came up with a joint communiqué. የጋራ ፡ መግለጫ ፡ አወጡ

**jointly** የጋራ(ቸው)
The two boys own the boat jointly. ለሁለቱ ፡ ልጆች ፡ ጀልባው ፡ የጋራቸው ፡ ነው

**joist** እርብራብ
The joists of the floor are hewn from logs. የወለሉ ፡ እርብራቦች ፡ ከግንድ ፡ የተጠረቡ ፡ ናቸው

**joke** (v.) አፌዘ
He joked about his misfortunes. ስለደረሰበት ፡ መከራ ፡ አፌዘ
*This time I'm not joking. አሁንስ ፡ ቀልዴን ፡ አይደለም

**joke** (n.) ቀልድ
I have heard that joke before. ቀልዱን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ሰምቼዋለሁ
He cannot take a joke. ቀልድ ፡ አይገባውም

**play a joke (jokes) on** ተጫወተ(በት) ፤ ቀለደ
I played a joke on him by putting a balloon full of water on his chair. በወምበሩ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ፊኛ ፡ ውኃ ፡ ሞልቼ ፡ በማስቀመጥ ፡ ተጫወትኩበት
He likes to play jokes on people. በሰው ፡ ላይ ፡ መቀለድ ፡ ይወዳል
[See also 'butt, target']

**joker** ቀልደኛ
That joker is always playing tricks on people. ያ ፡ ቀልደኛ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በሰዎች ፡ ይጫወታል

**joking** ቀልድ
All joking aside, I want my money. ቀልዱ ፡ ቀርቶ ፡ ገንዘቤን ፡ እፈልጋለሁ

**jolly**
1. ደስተኛ. A jolly person is always laughing. ደስተኛ ፡ ሰው ፡ ሁልጊዜ ፡ ይሥቃል
2. የደስታ. Christmas is a jolly season. ገና ፡ የደስታ ፡ ጊዜ ፡ ነው

**jolt**
1. አንገጫገጨ. The old bus jolted us as it went over the stony road. አሮጌው ፡ አውቶቡስ ፡ በኮረኮንች ፡ መንገድ ፡ ሲሄድ ፡ በጣም ፡ አንገጫገጨን
2. አስደነገጠ. His sudden death jolted us. ድንገተኛ ፡ አሟሟቱ ፡ አስደነገጠን

**jostle** ገፍቶ ፡ አስገባ
The crowd jostled him into the bus. ሕዝቡ ፡ ገፍቶ ፡ አውቶቡሱ ፡ ውስጥ ፡ አስገባው

**jostle each other** ተገፋፋ
The children were jostling each other in order to see the parade. ልጆቹ ፡ ሰልፉን ፡ ለማየት ፡ ይገፋፉ ፡ ነበር

**jot** (n.) ቅንጣት
There is not a jot of truth in it. አንዲትም ፡ የእውነት ፡ ቅንጣት ፡ የለችበትም

**jot down**
1. ጻፈ. Please jot down his address! አድራሻውን ፡ ጻፍ
2. በማስታወሻ ፡ ያዘ. The clerk jotted down the order. አሻሻጩ ፡ ትእዛዙን ፡ በማስታወሻ ፡ ያዘ

**journal**
1. መጽሔት. The archaeologists publish a journal. አርኪዎሎጂስቶች ፡ መጽሔት ፡ ያወጣሉ
2. ማስታወሻ. He keeps a journal of the day's happenings. የየቀኑን ፡ ድርጊቶች ፡ በማስታወሻ ፡ ይይዛል

**journalist** ጋዜጠኛ
He is a journalist in the Ministry of Information. በማስታወቂያ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ጋዜጠኛ ፡ ነው

**journey** (v.) ተጓዘ
We journeyed through the desert for miles. በበረሃው ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ማይል ፡ ተጓዝን

**journey** (n.)
1. መንገድ. They started their journey at dawn. ጎሕ ፡ ሲቀድ ፡ መንገድ ፡ ጀመሩ
2. ጉዞ. The journey from here to Gondar is now an easy one. ከዚህ ፡ እስከ ፡ ጎንደር ፡ የሚደረገው ፡ ጉዞ ፡ አሁን ፡ ቀላል ፡ ነው
*They set forth on a journey around the world. ዓለምን ፡ ለመዞር ፡ ተነሡ

**go on a journey** ተጓዘ
We are going on a journey to Addis Ababa. ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጓዛችን ፡ ነው

**make a journey** ሄደ ፤ ተጓዘ
They made a journey to the desert. ወደ ፡ በረሃ ፡ ሄዱ ፡ (ተጓዙ)

**jovial** ደስተኛ
His jovial attitude shows he has no worries. ደስተኛ ፡ መሆኑ ፡ ብስጭት ፡ እንደሌለበት ፡ ያሳያል

**joy** ደስታ
She was beaming with joy. በደስታ ፡ ብዛት ፡ ፊቷ ፡ ያበራ ፡ ነበር

**be a joy** ደስ ፡ አለ
This book is a joy to read. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ሲያነቡት ፡ ደስ ፡ ይላል

**joyful** አስደሳች ፤ የሚያስደስት
Have you heard the joyful news? The war is over! አስደሳቹን ፡ ዜና ፡ ሰምተሃል ? ጦርነቱ ፡ አበቃ
The advent of spring is a joyful occasion. የጸደይ ፡ መምጣት ፡ የሚያስደስት ፡ ወቅት ፡ ነው

**joyless** ደስታ ፡ የሌለበት
These unfortunate children have a joyless home. የእነዚህ ፡ ዕድለ ፡ ቢስ ፡ ልጆች ፡ ኑሮ ፡ ደስታ ፡ የሌለበት ፡ ነው

**joyous** የሚያስደስት
The Emperor's return was a joyous occasion. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መመለስ ፡ የሚያስደስት ፡ ወቅት ፡ ነበር

**jubilance** ፈንጠዝያ
The jubilance of the crowd was boundless. የሕዝቡ ፡ ፈንጠዝያ ፡ ወሰን ፡ አልነበረውም

**jubilant** በደስታ ፡ የተዋጠ
Jubilant crowds celebrated the victory. በደስታ ፡ የተዋጠው ፡ ሕዝብ ፡ የድሉን ፡ በዓል ፡ አከበረ

**be jubilant** ተደሰተ ፤ ፈነደቀ ፤ መሬት ፡ ጠበበው
He was jubilant when he found he had passed the exam. ፈተናውን ፡ ማለፉን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ተደሰተ ፡ (ፈነደቀ ፤ መሬት ፡ ጠበበው)

**jubilee** ኢዮቤልዩ
The jubilee of the coronation takes place next year. የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ የሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ይሆናል

**Jubilee Palace** ኢዮቤልዩ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት
The Emperor's residence is the Jubilee Palace. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መኖሪያ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ነው

**judge** (vt.)
1. ፍርድ ፡ ሰጠ. God judges all men. እግዚአብሔር ፡ በሁሉ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል
2. ግምት ፡ ጣለ. Don't judge him too harshly! ከባድ ፡ ግምት ፡ አትጣልበት
3. መሰለ(ው). I judge that you had forgotten the time. ጊዜውን ፡ የረሳህ ፡ ይመስለኛል
How tall do you judge him to be? ቁመቱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይመስልሃል ?

**judge** (vi.)
1. ፈረደ. After the judge heard the whole case, he judged against the plaintiff. ዳኛው ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ካዳመጠ ፡ በኋላ ፡ በከሳሹ ፡ ላይ ፡ ፈረደ
2. ውሳኔ ፡ ሰጠ. I have heard the evidence and will judge accordingly. መረጃውን ፡ ሰምቻለሁና ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ውሳኔውን ፡ እሰጣለሁ
3. ተረዳ. I judge from his manner that he doesn't like me. እንደማይወደኝ ፡ ከሁኔታው ፡ ተረዳሁ
4. አስተዋለ. He judges with great perspicacity. በብሩህ ፡ ልቦና ፡ ያስተውላል
5. ገመተ. I never judge by appearance. ፍጹም ፡ በመልክ ፡ አልገምትም
*To judge by his face, he is not very enthusiastic. ሲያዩት ፡ በጣም ፡ የጓጓ ፡ አይመስልም

**judge** (n.) ዳኛ
When is the judge going to pass sentence? ዳኛው ፡ ፍርድ ፡ የሚሰጠው ፡ መቼ ፡ ነው ?
The judges awarded his picture first prize. ዳኞቹ ፡ ለሱ ፡ ሥዕል ፡ ያንደኛነት ፡ ሽልማት ፡ ሰጡ
*He is a good judge of horses. ፈረስ ፡ መምረጥ ፡ ያውቃል

**Judges** መሳፍንት
The Era of the Judges follows the Solomonic Restoration. የመሳፍንት ፡ ዘመን ፡ ከሰሎሞን ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ዳግመኛ ፡ መነሣት ፡ በኋላ ፡ የመጣ ፡ ነው

**judg(e)ment**
1. ፍርድ. When a judgement has been made, it must be published in the newspaper. በነገሩ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ሲሰጥ ፡ በጋዜጣ ፡ መታወጅ ፡ አለበት
2. አስተያየት. His judgements are always without bias. አስተያየቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ያለ ፡ አድልዎ ፡ ነው
In my judgement, you are doing the wrong thing. በኔ ፡ አስተያየት ፡ የምትሠራው ፡ ሥራ ፡ ስሕተት ፡ ነው
3. የእግዚአብሔር ፡ ፍርጃ. The neighbors considered his broken leg a judgement on him. ጐረቤቶቹ ፡ የእግሩን ፡ መሰበር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍርጃ ፡ አደረጉት

4. አስተዋይነት. Don't accept his advice! His judgement is not good. ምክሩን ፡ አትቀበል ፤ አስተዋይነቱ ፡ የሚያስመካ ፡ አይደለም
*You can rely on his judgement. እርሱ ፡ በሚልህ ፡ መተማመን ፡ ትችላለህ

**get a judgement against** አስፈረደበት
When I refused to pay, he went to court and got a judgement against me. አልከፍልም ፡ ባልኩት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሶ ፡ አስፈረደብኝ

**make a judgement** ፍርድ ፡ ሰጠ
A judge must be circumspect when he makes a judgement. ዳኛ ፡ ፍርድ ፡ ሲሰጥ ፡ ጥንቁቅ ፡ መሆን ፡ አለበት
[See also 'soundness']

## judicial
1. የዳኝነት. A modern judicial system has been established in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ዘመናዊ ፡ የዳኝነት ፡ ሥርዓት ፡ ተቋቍሟል
2. የሕግ. Lend us your support in our fight for judicial reform! ለሕግ ፡ መሻሻል ፡ ለምናደርገው ፡ ትግል ፡ ድጋፍህን ፡ ስጠን
3. የሕግ ፡ ተርጓሚ. Executive power usually exceeds judicial power. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚው ፡ ሥልጣን ፡ ከሕግ ፡ ተርጓሚው ፡ ሥልጣን ፡ ይበልጣል
4. አመዛዛኝ. A judicial mind considers both sides of a dispute fairly before making a decision. አመዛዛኝ ፡ አእምሮ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ክርክር ፡ ያመዛዝናል

**judicial decision** ፍርድ
A judicial decision will decide his fate. ፍርዱ ፡ የወደፊት ፡ ዕድሉን ፡ ይወስናል

## judiciary ሕግ ፡ አውጪ
The judiciary is one of the branches of government. ሕግ ፡ አውጪ ፡ የመንግሥት ፡ አስተዳደር ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ነው
*He is a member of the judiciary. ዳኛ ፡ ነው

## judicious
1. ብልህ. That was a very judicious remark. በጣም ፡ ብልህ ፡ አስተያየት ፡ ነበር
2. አመዛዛኝ. A judicious historian considers facts carefully. አመዛዛኝ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ እውነተኛ ፡ ነገሮችን ፡ በጥንቃቄ ፡ ያመዛዝናል

## jug ደምበጃን
He put a jug of wine on the table. አንድ ፡ ደምበጃን ፡ ጠጅ ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠ

## juggle
1. ወደ ፡ ሰማይ ፡ በማፈራረቅ ፡ እየወረወረ ፡ ቀለበ. The clown juggled three oranges and a lemon. አሥቂኙ ፡ ተዋናይ ፡ ሦስት ፡ ብርቱካኖችና ፡ አንድ ፡ ሎሚ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በማፈራረቅ ፡ እየወረወረ ፡ ቀለበ
2. አዛብቶ ፡ ጻፈ. The manager juggled the figures to show a profit. ሥራ ፡ መሪው ፡ ትርፍ ፡ አለ ፡ ለማለት ፡ ቁጥሮችን ፡ አዛብቶ ፡ ጻፈ

## juice
1. ጭማቂ. These oranges give very little juice. እነዚህ ፡ ብርቱካኖች ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ጭማቂ ፡ ይወጣቸዋል
2. ውኃ. The juice of the euphorbia is slimy. የቁልቋል ፡ ውኃ ፡ ዝልግልግ ፡ ነው
[See also 'press']

## juicy ብዙ ፡ ውኃ ፡ ያለው
A juicy orange will drip on your shirt. ብዙ ፡ ውኃ ፡ ያለው ፡ ብርቱካን ፡ ሸሚዝህ ፡ ላይ ፡ ይንጠባጠባል

## July ሐምሌ

## jumble up አዘበራርቆ ፡ አስቀመጠ
He jumbled up his toys and books in the cupboard. አሻንጉሊቶቹንና ፡ መጻሕፍቱን ፡ በቁምሳጥን ፡ ውስጥ ፡ አዘበራርቆ ፡ አስቀመጠ

## jump (vt.)
1. አዘለለ. He jumped the horse over the fence. ፈረሱን ፡ በአጥሩ ፡ ላይ ፡ አዘለለ
2. (= intr.) ዘለለ. We jumped pages seven to twelve. ከሰባት ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ያሉትን ፡ ገጾች ፡ ዘለልን

**jump** (vi.)
1. ዘለለ. How high can you jump? ምን ፡ ያህል ፡ ከፍታ ፡ ትዘላለህ ?
2. ባንድ ፡ አፍታ ፡ ተለወጠ. The traffic light jumped from green to red. የትራፊክ ፡ መብራት ፡ ባንድ ፡ አፍታ ፡ ከረንጓዴ ፡ ወደ ፡ ቀይ ፡ ተለወጠ
3. ደነበረ. He jumped when he heard the noise. ድምፁን ፡ ሲሰማ ፡ ደነበረ
4. ተፍ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ. He jumped from his seat when the teacher entered. አስተማሪው ፡ ሲገባ ፡ ከመቀመጫው ፡ ተፍ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ
5. ከበሮ ፡ መታ. Her heart jumped when she heard the news. ወሬውን ፡ ስትሰማ ፡ ልቧ ፡ ከበሮ ፡ መታ
6. ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወጣ. Gold shares jumped on the stock exchange. በገበያ ፡ ምንዛሬ ፡ የወርቅ ፡ ዋጋ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወጣ
7. ቸኰለ. Don't jump to conclusions! ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ አትቸኵል

**jump across** (= pass.) በዝላይ ፡ ታለፈ
The chasm was too wide to jump across. ገደሉ ፡ ሰፊ ፡ ስለነበረ ፡ በዝላይ ፡ ሊታለፍ ፡ አል ተቻለም

**jump around** እንጣጥ ፡ እንጣጥ ፡ አለ
Stop jumping around! እንጣጥ ፡ እንጣጥ ፡ አትበል

**jump at** ወዲያውኑ ፡ ተቀበለ
He jumped at the offer. የቀረበለትን ፡ ሐሳብ ፡ ወዲያውኑ ፡ ተቀበለ

**jump in**
1. ዘሎ ፡ ገባ. He jumped in the water. ውኃ ፡ ው ስጥ ፡ ዘሎ ፡ ገባ
2. መኪናው ፡ ውስጥ ፡ ቶሎ ፡ ገባ. Jump in, and we will drive over to the movies. መኪናው ፡ ውስጥ ፡ ቶሎ ፡ ግባና ፡ ወደ ፡ ሲኒማ ፡ እንሄዳለን

**jump into** የ - - ተካፋይ ፡ ሆነ
He jumped into the discussion right away. ወዲያውኑ ፡ የንግግሩ ፡ ተካፋይ ፡ ሆነ

**jump off** ዘሎ ፡ ወረደ
He jumped off the cliff. ከአፋፉ ፡ ላይ ፡ ዘሎ ፡ ወረደ

**jump on**
1. ዘሎ ፡ ወጣ. The cat jumped on the table. ድመቱ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ዘሎ ፡ ወጣ
2. ዘሎ ፡ ረገጠ(ው). He jumped on the snake to kill it. እባቡን ፡ ለመግደል ፡ ዘሎ ፡ ረገጠው
3. ረገጠ. The donkey jumped on the grass. አህያው ፡ ሣሩን ፡ ረገጠ
4. ተቈጣ. The teacher jumped on the inattentive student. መምህሩ ፡ የማይከታተለውን ፡ ተ ማሪ ፡ ተቈጣው

**jump out**
1. ዘሎ ፡ ወጣ. He jumped out the window. በመስኮት ፡ ዘሎ ፡ ወጣ
2. ዘሎ ፡ ተነሣ. He jumped out of bed. ካልጋ ፡ ዘ ሎ ፡ ተነሣ

**jump over** ዘሎ ፡ ተሻገረ
He dared me to jump over the stream. ወንዙን ፡ ዘልዬ ፡ እንድሻገር ፡ አደፋፈረኝ

**jump up**
1. ዘለለ. He jumped up and touched the ceiling. ዘሎ ፡ ፕላፎኑን ፡ ነካ
2. ዘሎ ፡ ብድግ ፡ አለ. He jumped up when I came into the room. ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ስገባ ፡ ዘሎ ፡ ብድግ ፡ አለ

**jump upon** ዘሎ ፡ ጉብ ፡ አለ(በት)
The infuriated lion jumped upon her. የተቈጣ ው ፡ አንበሳ ፡ ዘሎ ፡ ጉብ ፡ አለባት
[See also 'headfirst']

**jump** (n.)
1. ዝላይ. His jump broke all records. የሱ ፡ ዝላይ ፡ የነበሩትን ፡ ክብረ ፡ ወሰኖች ፡ ሁሉ ፡ ሰበረ
2. በድንገት ፡ ከፍ ፡ ማለት. A jump in his temperature prevented him from going to work. ትኩሳቱ ፡ በድንገት ፡ ከፍ ፡ ማለቱ ፡ ከ ሥራ ፡ አስቀ ረው

**broad jump** የመሬት ፡ ዝላይ
He got first prize for the broad jump. በመሬት ፡ ዝላይ ፡ ውድድር ፡ ያንደኛነትን ፡ ሽልማት ፡ አ ገኘ

**high jump** የሰማይ ፡ ዝላይ ፤ የከፍታ ፡ ዝላይ
He got second prize for the high jump. በሰማይ ፡ (በከፍታ) ፡ ዝላይ ፡ ውድድር ፡ የሁለተኛነትን ፡ ሽል ማት ፡ አገኘ

**jumpy, make ~** አስበረገገ
Horror stories make me jumpy. አስቃቂ ፡ ታሪ ኮች ፡ ያስበረግጉኛል

**junction** መገናኛ
The junction of the two roads was blocked by a fallen tree. የሁለቱን ፡ መንገዶች ፡ መገናኛ ፡ የ ወደቀ ፡ ግንድ ፡ ዘግቶት ፡ ነበር

**juncture** መገናኘት
The juncture of the two armies marked the end of the war. የሁለቱ ፡ ጦሮች ፡ መገናኘት ፡ ጦርነቱን ፡ ከፍጻሜ ፡ አደረሰው

**at this juncture** እዚህ ፡ ላይ
At this juncture, it is best to recall our original purpose. እዚህ ፡ ላይ ፡ የተነሣንበትን ፡ ዓላማ ፡ ማስታወስ ፡ ያሻል

**June** ሰኔ

**jungle** ጫካ
There are many lions in the jungle. ጫካ ፡ ው ስጥ ፡ ብዙ ፡ አንበሶች ፡ አሉ

**junior**
1. የበታች. He is a junior clerk in the Ministry of Agriculture. በእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ የበ ታች ፡ ጸሐፊ ፡ ነው
When the commanding officer is absent a junior officer takes command. አዛዡ ፡ መኰንን ፡ በሌለበት ፡ የበታች ፡ መኰንን ፡ ያዛል
2. ታናሽ. He is his brother's junior by two years. ለወንድሙ ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ታናሹ ፡ ነው
*He's a junior in college. በኮሌጅ ፡ ውስጥ ፡ ሦ ስተኛ ፡ ዓመቱ ፡ ነው

**juniper** ጥድ

**junk** (v.) ጣለ
We finally junked our old car. በመጨረሻ ፡ አሮጌ ፡ መኪናችንን ፡ ጣልነው

**junk** (n.) እንቶ ፡ ፍንቶ ፤ ትርኪ ፡ ምርኪ
Junk is collected by very poor people who sell it. በጣም ፡ ድኻ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ እንቶ ፡ ፍንቶውን ፡ እየለቀሙ ፡ ይሸጣሉ
The storeroom is full of junk. እቃ ፡ ቤቱ ፡ ትርኪ ፡ ምርኪ ፡ ብቻ ፡ ነው

**juridical** ሕጋዊ
The juridical questions of the frontier were discussed by a commission. የድንበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ጉዳዮች ፡ በኮሚሲዮን ፡ ንግግር ፡ ተደረገባቸው

**jurisdiction** ሥልጣን
The student council has no jurisdiction over academic affairs. የተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ ትምህርትን ፡ በሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ የለውም
The case was not in his jurisdiction. ጉዳዩ ፡ በእርሱ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ አልነበረም

**jurisprudence** ሕገ ፡ ፍልስፍና
Criminal jurisprudence is an established subject of study. የወንጀል ፡ ሕገ ፡ ፍልስፍና ፡ የታወቀ ፡ ትምህርት ፡ ነው

**jurist** የሕግ ፡ ዐዋቂ
The jurists proposed the laws be revised. የሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ሕጉ ፡ እንዲሻሻል ፡ ሐሳብ ፡ አቀረቡ

**jury** [ከተራው ፡ ሕዝብ ፡ ተመርጠው ፡ ፍርድ ፡ የሚቀመጡ ፡ ፲፪ ሰዎች]

**just** (adj.)
1. ሐቀኛ. My father was a just man. አባቴ ፡ ሐቀኛ ፡ ሰው ፡ ነበር
2. ትክክለኛ. A just description should omit exaggerations. ትክክለኛ ፡ መግለጫ ፡ ማጋነንን ፡ ሁሉ ፡ ማስወገድ ፡ አለበት
Just weights are required by the law. የመገበያያ ፡ ሚዛኖች ፡ ትክክለኛ ፡ እንዲሆኑ ፡ ሕግ ፡ ያስገድዳል
3. የሚገባ. The criminal received his just deserts. ወንጀለኛው ፡ የሚገባውን ፡ ዋጋ ፡ አገኘ
4. ተገቢ. His anger is just. ቁጣው ፡ ተገቢ ፡ ነው

**just** (adv.)
1. ብቻ. I have come here just to see you. እዚህ ፡ የመጣሁት ፡ አንተን ፡ ለመጠየቅ ፡ ብቻ ፡ ነው
He had just enough money for himself. ለራሱ ፡ ብቻ ፡ የሚበቃ ፡ ገንዘብ ፡ ነበረው
2. ልክ. He is just like his father. ልክ ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ ነው
They caught him just before he could get over the border. ልክ ፡ ጠረፉን ፡ ሊያልፍ ፡ ሲል ፡ ያዙት
His house is just across the way. ቤቱ ፡ ልክ ፡ ከመንገዱ ፡ ማዶ ፡ ነው
3. ልክ ፡ በሰዓቱ. You just made it. ልክ ፡ በሰዓቱ ፡ ደረስክ
4. አሁን ፤ ልክ ፡ አሁን. Do you know the woman who just passed by? አሁን ፡ (ልክ ፡ አሁን) ፡ በዚህ ፡ ያለፈችውን ፡ ሴትዮ ፡ ታውቃታለህ ?
5. ገና ፡ አሁን. We've just received a new shipment of shoes. የተላከልን ፡ አዲስ ፡ ጫማ ፡ ገና ፡ አሁን ፡ ደረሰን
6. ገና. He is just a little boy. ገና ፡ ሕፃን ፡ ነው
Why are you leaving so soon? It's just two o'clock. ምን ፡ አስቸኰለህ ? ገና ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ነው
7. ለጥቂት. The bullet just missed us. ጥይቱ ፡ ለጥቂት ፡ ሳተን
8. ዝም ፡ ብሎ. They don't collect the garbage here; they just dump it in the streets. ቆሻሻ ፡ አይሰበስቡም ፤ ዝም ፡ ብለው ፡ መንገዶቹ ፡ ላይ ፡ ይዘረግፉታል
9. እስቲ. Just taste this! It's delicious. እስቲ ፡ ቅመሰው ፤ በጣም ፡ ይጣፍጣል
10. እንዲያው. Oh, that's just talk! እንዲያው ፡ ወሬ ፡ ነው
*There is just nothing you can do about it. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ምንም ፡ ልታደርግ ፡ አትችልም
*That's just what I wanted. የፈለግሁት ፡ ይህንን ፡ ነው
*Just don't worry! ምንም ፡ አታስብ

**just across** ሻገር ፡ ብሎ
His house is just across the way. ቤቱ ፡ መንገዱን ፡ ሻገር ፡ ብሎ ፡ ነው

**just as** ልክ ፡ ስ + imperfect
The siren blew just as we reached the hospital. ልክ ፡ ሆስፒታል ፡ ስንደርስ ፡ ሳይረን ፡ ጮኸ

**just as long** የዚህኑ ፡ ያህል ፡ ጊዜ
That takes just as long. እሱም ፡ የዚህኑ ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይፈጃል

**just as long as he is here** እዚህ ፡ ካለ ፡ ዘንድ
Just as long as you are here, we might as well discuss this matter too. እዚህ ፡ ካላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ይህንንም ፡ ጉዳይ ፡ ብንነጋገርበት ፡ መልካም ፡ ነው

**just as ... so also**
*Just as a child has corporeal parents, so also has he spiritual parents. ለልጅ ፡ የሥጋ ፡ ወላጆች ፡ እንዳሉት ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ የመንፈስ ፡ ወላጆች ፡ ደግሞ ፡ አሉት

**just as soon**
*I'd just as soon stay at home. እቤት ፡ መቆየት ፡ ይሻለኛል

**just at the right moment** በሰዓቱ
He came just at the right moment. በሰዓቱ ፡ ጠብ ፡ አለ

**just the same** ቢሆንም
Just the same, I am going to check the addition again. ቢሆንም ፡ ድምሩን ፡ አጣራለሁ

**have just about enough** በቃው
+I have had just about enough of your impudence. ብልግናህ ፡ በቅቶኛል
[See also 'instant, like, minute, moment, now, once, second, so, time']

**justice**
1. ትክክለኛ ፡ ፍርድ. Even though he took the matter to court, he could not obtain justice. ምንም ፡ እንኳን ፡ ጉዳዩን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቢያ ቀርበው ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ሊያገኝ ፡ አልቻለም
2. ተገቢነት. He upheld the justice of our cause by refusing to do anything illegal. ሕግን ፡ ያል ተከተለ ፡ ነገር ፡ አልሠራም ፡ በማለት ፡ የዓላማች ንን ፡ ተገቢነት ፡ ደገፈ
3. ዳኛ. His brother is a justice of the Supreme Court. ወንድሙ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ነው

**bring to justice** ሕግ ፡ ፊት ፡ አቀረበ
The police brought the criminal to justice. ፖሊሱ ፡ ወንጀለኛውን ፡ ሕግ ፡ ፊት ፡ አቀረበው

**dispense justice** ፈረደ
The judge dispenses justice without bias. ዳኛው ፡ ያለ ፡ አድልዎ ፡ ይፈርዳል

**do one justice**
*When you say that he is not very intelligent, you are not doing him justice. በጣም ፡ ብልህ ፡ አይደለም ፡ ማለትህ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**in justice to him**
*In justice to him, one must realize that Amharic is not his mother tongue. አማርኛ ፡ የእ ናት ፡ ቋንቋው ፡ አለመሆኑን ፡ ተገንዝቦ ፡ ለሱ ፡ እስ ተያየት ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ ነው

**Minister of Justice** የፍርድ ፡ ሚኒስትር
The Minister of Justice left for Paris. የፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ሄዱ

**with justice**
*He complained with justice of the bad treatment he had received. በደረሰበት ፡ በደል ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ስሞታ ፡ አቀረበ

**justifiable** ተገቢ ፡ ነው ፡ የሚባለው
An act is justifiable if it can be shown to be right. አንድ ፡ አድራጎት ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ የሚባ ለው ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኑ ፡ ሲረጋገጥ ፡ ነው

**justification** ምክንያት
What is your justification for being so late? ይህን ፡ ያህል ፡ ለመዘግየትህ ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ አለህ ?

**justify** (justified)
1. ተገቢ ፡ አስመሰለ. She tried to justify her actions. የሠራችውን ፡ ነገር ፡ ተገቢ ፡ ለማስመሰል ፡ ሞከረች
2. (= intr.) በቂ ፡ ምክንያት ፡ ነው. Your desire to go on a walk does not justify your leaving the baby alone. መንሸራሸር ፡ መፈለግሽ ፡ ሕፃኑን ፡ ብቻውን ፡ ጥለሽ ፡ ለመሄድ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አ ይደለም
3. ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ አቀረበ. He justified his shooting the criminal by saying that the man attacked him. ወንጀለኛውን ፡ በጥይት ፡ የገደለው ፡ ስለተናነቀው ፡ መሆኑን ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ አቀረበ
4. ምክንያት ፡ ሰጠ. How do you justify your absence? ለመቅረትህ ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ ትሰጣለህ ?
*He tries to justify himself before the court. ጥፋተኛ ፡ አለመሆኑን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ይሞክራል

**be justified** (= it is justified) ተገቢ ፡ ነው
You were perfectly justified in asking for more money. ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ መጠየቅህ ፡ ተገቢ ፡ ነበር

**justly** (= adj.) የሚገባ
He was justly rewarded for his faithful service by being given a pension. ጡረታ ፡ በማግኘት ፡ ታማኝነት ፡ ለመላበት ፡ አገልግሎቱ ፡ የሚገባ ፡ ወረታ ፡ ተከፈለው

**jute** ቃጫ
The lash of the whip is made of jute. ቁግ ፡ ከቃ ጫ ፡ ይገመዳል

**juvenile**
1. የወጣት ፡ ልጆች. Juvenile delinquency is widespread at present. በዛሬ ፡ ጊዜ ፡ የወጣት ፡ ልጆ ች ፡ ወንጀል ፡ ተስፋፍቷል
2. የወጣት. He is a juvenile offender. የወጣት ፡ አጥፊ ፡ ነው
3. የወጣት ፡ ጥፋተኞች. The boy's case was judged in juvenile court. የልጁ ፡ ጉዳይ ፡ በ ወጣት ፡ ጥፋተኞች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተወሰነ
4. ለወጣቶች ፡ የተጻፈ. This library has many juvenile books. ይህ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ለወጣቶ ች ፡ የተጻፉ ፡ ብዙ ፡ መጽሐፎች ፡ አሉት

**juxtapose** ጐን ፡ ለጐን ፡ አስቀመጠ
He juxtaposed dark and light paper. ጠቁር ፡ ያለና ፡ ነጣ ፡ ያለ ፡ ወረቀት ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ አስቀመጠ

## K

**keen**
1. ስል. A keen edge cuts better than a dull
edge. ስል ፡ የሆነ ፡ ወገን ፡ ከደነዘ ፡ ይልቅ ፡ የ
በለጠ ። ይቈርጣል
2. ከፍ ፡ ያለ. He has a keen interest in sports.
ለስፖርት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ፍላጎት ፡ አለው
3. ንቁ. Her questions are indicative of a
keen mind. የምትጠይቃቸው ፡ ጥያቄዎች ፡ ንቁ ፡
አእምሮ ፡ እንዳላት ፡ ያስረዳሉ

**keen edge** ስለት
The knife has a keen edge. ቢላዋው ፡ ስለት ፡ አለው

**have a keen mind** አንጐሉ ፡ ክፍት ፡ ሆነ
He has such a keen mind, he can figure out the
hardest problems quickly. አንጐሉ ፡ ክፍት ፡ ስለ
ሆነ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆኑትን ፡ ፕሮብሌሞች ፡
በፍጥነት ፡ ይሠራል

**keep** (kept), vt.
1. ያዘ. He keeps his things in good condition.
እቃውን ፡ በጥሩ ፡ አኳኋን ፡ ይይዛል
2. አስቀመጠ. Please keep this for me! እባክህን ፡
ይህንን ፡ አስቀምጥልኝ
3. ቋጠረ. Can you keep a secret? ምስጢር ፡ ትቋ
ጥራለህ ?
4. ጠበቀ ፤ አገደ. The shepherd keeps sheep. እ
ረኛው ፡ በግ ፡ ይጠብቃል ፡ (ያግዳል)
She keeps my dog when I travel. እኔ ፡ ወደ ፡
ሌላ ፡ አገር ፡ ስሄድ ፡ ውሻዬን ፡ ትጠብቅልኛለች
5. አስተዳደረ. She keeps house for her uncle.
ያጎቷን ፡ ቤት ፡ ታስተዳድራለች
He keeps the zoo for the government. የመንግሥ
ቱን ፡ የእንስሳት ፡ ቦታ ፡ ያስተዳድራል
6. ከ - - ዋለ. She keeps very rough company.
ካልታረሙ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ትውላለች
7. ወሰደ. May I keep this picture? ይህን ፡ ሥዕል ፡
ልውሰደው ?
8. አከበረ. The Jews keep the Sabbath.
አይሁዳውያን ፡ ቅዳሜን ፡ ያከብራሉ
9. አስመጣ. Do you sell postcards here?
I am sorry, we do not keep them anymore.
እዚህ ፡ ካርድ ፡ ትሸጣላችሁ ? አዝናለሁ ፤ ማስ
መጣት ፡ ትተናል
10. አቆየ. An exacting employer will find it
hard to keep his workers. በቃኝ ፡ የማይል ፡
አሠሪ ፡ ሠራተኞቹን ፡ ማቆየት ፡ ያስቸግረዋል
11. ገታ. In spite of these insults, she managed
to keep her temper. ይህን ፡ ያህል ፡ ተሰድባ ፡ እ
ንኳ ፡ ንዴቷን ፡ መግታት ፡ቻለች
12. አስ-stem. Sorry to have kept you wait-
ing. ስላስጠበቅሁህ ፡ ይቅርታ
*He kept belaboring the point after we had
agreed. ከተስማማንበትም ፡ በኋላ ፡ ጉዳዩን ፡ መላ
ልሶ ፡ ማንሣቱን ፡ አላቋረጠም

**keep** (vi.)
1. ሳይበላሽ ፡ ቆየ. This milk won't keep till
tomorrow. ይህ ፡ ወተት ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ድረስ ፡
ሳይበላሽ ፡ አይቆይም
2. ቀጠለ + noun. I told him to be quiet but
he kept shouting. ዝም ፡ እንዲል ፡ ነገርኩት ፡ ግ
ን ፡ ጩኸቱን ፡ ቀጠለ

**keep above** ከ - - በላይ ፡ አወጣ
He kept his head above water. ራሱን ፡ ከውኃ
ው ፡ በላይ ፡ አውጥቶ ፡ ነበር

**keep apart** (vt.) ገላገለ
Keep the two fighting boys apart! የሚጣሉትን ፡
ሁለት ፡ ልጆች ፡ ገላግላቸው

**keep apart** (vi.) ተገለለ ፤ ነጠል ፡ አለ
He kept apart from the unruly students out of
pride. ለክብሩ ፡ ሲል ፡ ከባለጌዎቹ ፡ ተማሪዎች ፡
ተገለለ ፡ (ነጠል ፡ አለ)

**keep at** ሳያቋርጥ ፡ ሠራ
He kept at it until he finished the job. ሥራው
ን ፡ እስኪጨርስ ፡ ድረስ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ሠራ

**keep away** (vt.)
1. አላስደረሰም. Fierce dogs keep burglars away.
ተናካሽ ፡ ውሾች ፡ ቤት ፡ ሰርሳሪዎችን ፡ አያስደርሱም
2. አስቀረ. What kept you away yesterday?
ትናንትና ፡ ምን ፡ አስቀረህ ?
3. አራቀ. Keep the baby away from the fire!
ሕፃኑን ፡ ከእሳቱ ፡ አርቂው

**keep away (from)**
*Keep away from the fire. እሳቱን ፡ አትጠጋ
*The doctor told him to keep away from
cigarettes. ሐኪሙ ፡ ሲጃራ ፡ ይቅርብህ ፡ አለው

**keep back** (vt.)
1. ቈረጠ. The government keeps back 5 percent
of one's pay for taxes. መንግሥት ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡
ደሞዝ ፡ ከመቶ ፡ አምስት ፡ ለግብር ፡ ይቈርጣል
2. ተከላከለ. They quickly made a barricade

to keep back the enemy. ጠላትን ፡ ለመከላከል ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ መከታ ፡ አበጁ

3. ወደ ፡ ኋላ ፡ መለሰ. The police had to keep the crowd back. ፖሊሶች ፡ ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መመለስ ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው

4. አልናገር ፡ አለ. The prisoner was keeping back vital information. እስረኛው ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ መረጃ ፡ አልናገር ፡ አለ

5. አገደ. The dikes keep back the flood waters. ግድቦቹ ፡ ጐርፉን ፡ ያግዳሉ

She struggled to keep back her tears. እንባዋን ፡ ለማገድ ፡ ታገለች

**keep back** (vi.) ወደ ፡ ኋላ ፡ መለስ ፡ አለ

Keep back! You are going too close to the edge of the cliff. ወደ ፡ ኋላ ፡ መለስ ፡ በል ፤ ገደሉ ፡ አፋፍ ፡ በጣም ፡ ተቃርበሃል

**keep doing something** እየደጋገመ + verb

The goat kept butting its head against the fence. ፍየሉ ፡ ራሱን ፡ ከጥሩ ፡ ጋር ፡ እየደጋገመ ፡ አጋጨ

**keep down** (vt.)

1. አቆመ. The government of the Congo is trying to keep down the rebellion. የኮንጎ ፡ መንግሥት ፡ የተነሣውን ፡ ዐመፅ ፡ ለማቆም ፡ ይሞክራል

2. ቀነሰ. We must keep down our expenses. ወጪያችንን ፡ መቀነስ ፡ አለብን

3. አጠፋ. He hoed the garden to keep the weeds down. አረሙን ፡ ለማጥፋት ፡ አትክልቱን ፡ ኰተኰተው

**keep down** (vi.) ጐንበስ ፡ አለ

Keep down or they will see you. ጐንበስ ፡ በል ፤ አለዚያ ፡ ያዩሃል

**keep from**

1. ከለከለ. Nobody can keep you from going there. እዚያ ፡ ከመሄድ ፡ ማንም ፡ አይከለክልህም

2. አገደ. Sectarian disputes keep Lebanon from being united. የሃይማኖት ፡ ልዩነት ፡ የሊባኖስን ፡ አንድነት ፡ አግዷል

3. እንድ + (negative imperfect) + አገደ. A constriction in the neck of the bottle kept the water from flowing out. የጠርሙሱ ፡ አንገት ፡ ጥበት ፡ ውኃው ፡ እንዳይፈስ ፡ አገደው

4. እንድ + (negative imperfect) + አደረገ. The absence of water keeps plants from growing. የውኃ ፡ አለመኖር ፡ ዕፀዋት ፡ እንዳያድጉ ፡ ያደርጋቸዋል

5. እንድ + (negative imperfect). He jammed a stick in the door to keep it from closing. በሩ ፡ እንዳይዘጋ ፡ ዕንጨት ፡ ወሸቀበት

6. ከ - - - አዳነ. He kept me from making a big mistake. ከታላቅ ፡ ስሕተት ፡ አዳነኝ

**keep hold of**

*Keep hold of it until I get back. እስክመለስ ፡ አንተ ፡ ጋ ፡ ይቆይ

**keep in** አቆየ

The teacher kept me in after school. አስተማሪው ፡ ከትምህርት ፡ በኋላ ፡ አቆየኝ

**keep (someone) indoors**

*The rainy weather kept us indoors. ዝናቡ ፡ ከቤት ፡ አላስወጣ ፡ አለን

**keep it to oneself** በምስጢር ፡ ያዘ

I'll tell you only if you promise to keep it to yourself. የምነግርህ ፡ በምስጢር ፡ የያዝከው ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው

**keep (someone) long** አቆየ

I won't keep you very long. ብዙ ፡ አላቆይህም

**keep off** (vt.)

1. አገደ. The engineers made a bank of earth across the road to keep off the cars. መኪናዎቹን ፡ ለማገድ ፡ መሀንዲሶቹ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ አፈር ፡ ቈለሉ

2. አባረረ. They made a smoky fire to keep off the bugs. ነፍሳቶቹን ፡ ለማባረር ፡ ብዙ ፡ ጭስ ፡ ያለው ፡ እሳት ፡ አነደዱ

**keep off** (vi.) ገለል ፡ አለ

When the policeman saw the children climbing on the automobile he told them to keep off. ፖሊሱ ፡ ልጆቹ ፡ መኪናው ፡ ላይ ፡ ሲንጠላጠሉ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ገለል ፡ እንዲሉ ፡ ነገራቸው

*Keep off the grass! ሣሩን ፡ አትርገጥ

**keep (someone) on** (vt.) አቆየ

The maid was very lazy, but we kept her on. ገረዲቱ ፡ በጣም ፡ ሰነፍ ፡ ነበረች ፤ ግን ፡ አቆየናት

**keep out** (vt.)

1. አስቀረ. Bad eyesight kept him out of the army. ዓይኑ ፡ በሽተኛ ፡ መሆኑ ፡ ከወታደርነት ፡ አስቀረው

2. ተከላከለ. Putting insulation in the wall helps keep out the heat. በግድግዳ ፡ ላይ ፡ የሙቀት ፡ መከላከያ ፡ ማድረጉ ፡ ሙቀትን ፡ ለመከላከል ፡ ይረዳል

*Keep him out of here! He only causes trouble. እንዳይገባ ፡ ከልክለው ፤ ያስቸግራል

*Shut the windows and keep the rain out! ዝናቡ ፡ እንዳይገባ ፡ መስኮቱን ፡ ዝጋው

**keep out!** መግባት ፡ ክልክል ፡ ነው

**keep out of** ከ - - - ራቀ ፤ ከ - - - ዳነ

Peaceable people keep out of quarrels. ሰላማዊ ፡ ሰዎች ፡ ከጠብ ፡ ይርቃሉ

My brother made a sound decision and so kept out of trouble. ወንድሜ ፡ አስቦ ፡ ውሳኔ ፡ ስላ ደረገ ፡ ከችግር ፡ ዳነ

**keep out of it**
*It's his affair; you'd better keep out of it. የራሱ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፤ አንተ ፡ ባትገባበት ፡ ይሻላል

**keep right on ቀጠለ**
Keep right on talking! ንግግርህን ፡ ቀጥል

**keep straight on ዝም ፡ ብሎ ፡ ሄደ**
Keep straight on until you get to the church! ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እስክትደርስ ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ሂድ

**keep to**
1. ያዘ. Keep to the right! ቀኝህን ፡ ያዝ
2. አከበረ. She keeps to the rules. ሕግ ፡ ታከብራለች
*I have to keep to a strict diet. የተወሰነ ፡ ምግብ ፡ መመገብ ፡ አለብኝ

**keep to oneself በሆዱ ፡ ያዘ**
She kept her inner thoughts to herself. የልብ ፡ ምስጢሯን ፡ በሆዷ ፡ ያዘች
*He always keeps to himself. ምንጊዜም ፡ ከሰው ፡ አይገናኝም ፡ (or, ብቻውን ፡ መሆን ፡ ይወዳል)

**keep together ሰብስቦ ፡ ያዘ**
During his imprisonment, his long-suffering wife kept the family together. በእስራቱ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ የታገሠችው ፡ ሚስቱ ፡ ቤተሰቡን ፡ ሰብስባ ፡ ያዘች

**keep up** (vt.)
1. ያዘ. Country people still keep up the custom of marrying their children young. የባላገር ፡ ሰዎች ፡ አሁንም ፡ ልጆቻቸውን ፡ በወጣትነት ፡ የመዳርን ፡ ልማድ ፡ እንደያዙ ፡ ናቸው
2. በሚገባ ፡ ያዘ. Can you keep up the house, now that you have lost your job? አሁን ፡ ሥራህን ፡ የለቀቅህ ፡ ስለሆነ ፡ ቤቱን ፡ በሚገባ ፡ ልትይዝ ፡ ትችላለህ ?
3. በደንብ ፡ ያዘ. How much does it cost to keep up your car? መኪናህን ፡ በደንብ ፡ ለመያዝ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ወጪ ፡ ያስፈልግሃል ?
4. ገፋ(በት). Keep it up, and see where it gets you! ግፋበትና ፡ የት ፡ እንደሚያደርስህ ፡ ተመልከት
Keep up the good work! ይህን ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ግፋበት

**keep up** (vi.)
*The rain kept up all day. ዝናቡ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሲዘንብ ፡ ዋለ

**keep up (with)**
1. ተወዳደረ. It is hard for me to keep up with the others. ከሌሎች ፡ ጋር ፡ ለመወዳደር ፡ ያዳግተኛል
2. ተከታተለ. I cannot keep up with you when you dictate so fast. እንደዚሀ ፡ ፈጥነህ ፡ ስታጽፈኝ ፡ ልከታተልህ ፡ አልችልም
I cannot keep up with my work. ሥራዬን ፡ ልከታተል ፡ አልችልም
3. ደረሰ(በት). Run to keep up with him! እንድትደርስበት ፡ ሩጥ
[See also 'alive, appearance, awake, background, balance, body, book, company, control, eye, face, fast, fit, go, hand, head, house, mind, posted, promise, temper, time, track, wind, word']

**keep** (n.)
1. ለኑሮው ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ነገሮች. The student earned his keep by doing odd jobs. ያገኘውን ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ተማሪው ፡ ለኑሮው ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ነገሮች ፡ ያገኛል
2. ጥበቃ. His son is in my keep. የሱ ፡ ልጅ ፡ በኔ ፡ ጥበቃ ፡ ሥር ፡ ነው
*That servant doesn't earn his keep. ያ ፡ አሽከር ፡ የሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ ከሚያገኘው ፡ ጥቅም ፡ ያነሰ ፡ ነው

**for keeps ለዘለቄታው**
They agreed to settle the controversy for keeps. አለመግባባታቸውን ፡ ለዘለቄታው ፡ ውሳኔ ፡ ሊሰጡት ፡ ተስማሙ

**keeper**
1. ዘበኛ. He is a keeper of the museum. የቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ዘበኛ ፡ ነው
2. ጠባቂ. Am I my brother's keeper? እኔ ፡ የወንድሜ ፡ ጠባቂ ፡ ነኝ ?

**keeping**
1. ማክበር. The keeping of Christmas is an old Christian custom. ልደትን ፡ ማክበር ፡ የቆየ ፡ የክርስቲያን ፡ ልማድ ፡ ነው
2. ማሳደጊያ. The keeping of the orphaned children was paid for by their uncle. ወላጆቻቸው ፡ ለሞቱባቸው ፡ ልጆች ፡ ማሳደጊያ ፡ የሚከፍለው ፡ አጐትዬው ፡ ነው

**be in keeping with ተስማማ ፤ ገጠመ ፤ ተመጣጠነ**
A good man's actions are in keeping with his principles. የጥሩ ፡ ሰው ፡ አድራጎት ፡ ከዓላማው ፡ ጋር ፡ ይስማማል ፡ (ይገጥማል)
The deputy's air of importance is not in keeping with his real job. ምክትሉ ፡ ራሱን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ማሳየቱ ፡ ከኀላፊነቱ ፡ ጋር ፡ አይመጣጠንም

**in (someone's) keeping** አደራ
She left the money in his keeping. ገንዘቧን ፡ አደራ ፡ ሰጠችው

**in keeping with** በ - - መሠረት
In keeping with our previous agreement, I am sending you a check. ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባደረግነው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ቼክ ፡ እልክልሃለሁ

**keepsake** ማስታወሻ
My friend gave me his picture as a keepsake before going away. ጓደኛዬ ፡ ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ ፎቶግራፉን ፡ ለማስታወሻ ፡ ሰጠኝ

**keg** ትንሽ ፡ በርሜል
The beer is stored in kegs. ጠላው ፡ ትንንሽ ፡ በርሜሎች ፡ ውስጥ ፡ ተደርጓል

**kennel** የውሻ ፡ ቤት
The kennel is painted red. የውሻው ፡ ቤት ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ተቀብቷል

**kept,** see **keep**

**kerchief** ሻሽ
She wore a colored kerchief on her head. ባለቀለም ፡ ሻሽ ፡ አስራለች

**kernel** ፍሬ
I put a kernel of corn in the ground. አንድ ፡ የበቆሎ ፡ ፍሬ ፡ ተከልሁ

**kerosene** ነጭ ፡ ጋዝ
Mary bought a liter of kerosene. ሜሪ ፡ አንድ ፡ ሊትር ፡ ነጭ ፡ ጋዝ ፡ ገዛች

**kerosene lamp** ኩራዝ
The country people light kerosene lamps. ባላገሮች ፡ ኩራዝ ፡ ያበራሉ

**kettle** ጀበና
Put the kettle on to boil! ጀበናውን ፡ ጣደው

**key** (v.) አስማማ
They try to key the radio program to the interests of the children. የሬዲዮኑን ፡ ፕሮግራም ፡ ከልጆቹ ፡ ፍላጎት ፡ ጋር ፡ ለማስማማት ፡ ይሞክራሉ

**be keyed to** እንዲስማሙ ፡ ተመረጡ
The colors of the curtains are keyed to the red and blue carpets. የመጋረጃዎቹ ፡ ቀለሞች ፡ ከቀይና ፡ ከሰማያዊ ፡ ስጋጃዎች ፡ ጋር ፡ እንዲስማሙ ፡ ሆነው ፡ ነው ፡ የተመረጡት

**be keyed up** በስሜት ፡ ተነሣሣ
The players were keyed up before the final championship game. ከመጨረሻው ፡ የሻምፒዮና ፡ ግጥሚያ ፡ በፊት ፡ ተጫዋቾቹ ፡ በስሜት ፡ ተነሣሥተው ፡ ነበር

**key** (n.)
1. ቁልፍ. I have lost the key to my room. የክፍሌ ፡ ቁልፍ ፡ ጠፋብኝ
2. ፍንጭ. This letter is the key to the whole mystery. ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ የምስጢሩ ፡ ሁሉ ፡ ፍንጭ ፡ ነው
3. ፍች. The key to this puzzle will be published next week. የዚህ ፡ እንቆቅልሽ ፡ ፍች ፡ በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ ይታተማል
4. ምሰሶ. The steel industry is the key to our nation's economy. የብረት ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ያገራችን ፡ ኢኮኖሚ ፡ ምሰሶ ፡ ነው
5. ዋና ፡ በር. Gibraltar is the key to the Mediterranean. ጅብራልታር ፡ ለሜዲተራኔያን ፡ ዋና ፡ በር ፡ ነው
6. አገላለጽ. He answered my letter in a mournful key. ደብዳቤዬን ፡ ሐዘን ፡ በተመላበት ፡ አገላለጽ ፡ መለሰለኝ

**key** (adj.)
1. ዋና ፡ ቦታ ፡ የሚይዝ. The Minister of Interior is often the key man in the government. ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትር ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ዋና ፡ ቦታ ፡ የሚይዝ ፡ ባለሥልጣን ፡ ነው
2. መሠረታዊ. Steel is a key industry. የብረት ፡ ኢንዱስትሪ ፡ መሠረታዊ ፡ ነው
[See also 'lock']

**keyhole** የቁልፍ ፡ ቀዳዳ
He could not find the keyhole in the dark. በጨለማ ፡ የቁልፉን ፡ ቀዳዳ ፡ ማግኘት ፡ አልቻለም

**keynote** ዋና ፡ መንፈስ
World peace was the keynote of his speech. የንግግሩ ፡ ዋና ፡ መንፈስ ፡ የዓለም ፡ ሰላም ፡ ነበር

**key ring** ዘለበት
I need a key ring for my keys. ለቁልፎቼ ፡ ዘለበት ፡ እፈልጋለሁ

**keystone** መሠረት
Freedom is the keystone of democracy. ነጻነት ፡ የዲሞክራሲ ፡ መሠረት ፡ ነው

**kick** (vt.)
1. ረገጠ. My brother kicked me. ወንድሜ ፡ ረገጠኝ
The horse kicked the boy. ፈረሱ ፡ ልጁን ፡ ረገጠው
2. ለጋ ፤ መታ. Kick the ball! ኳሱን ፡ ለጋ ፡ (ምታ)

**kick** (vi.) ተራገጠ
I hope this horse does not kick. ይህ ፡ ፈረስ ፡ እንደማይራገጥ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ
This shotgun kicks. ይህ ፡ ረሽ ፡ ይራገጣል

**kick about** ተዘዋወረ
He kicked about a good deal before settling down. የተደላደለ ፡ ኑሮ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ተዘዋወረ

**kick against**
1. በእግሩ ፡ ደበደበ. He kicked against the door so that someone would open it. ሰው ፡ መዝጊያ ውን ፡ እንዲከፍትለት ፡ በእግሩ ፡ ደበደበ
2. ቅሬታውን ፡ ገለጸ. He kicked against the treatment he was receiving. ስለተደረገበት ፡ ሁሉ ፡ ቅሬታውን ፡ ገለጸ

**kick around** ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ
He has been kicking around Europe since his discharge from the army. ከጦር ፡ ሰራዊት ፡ ከተሰናበተ ፡ ጀምሮ ፡ አውሮፓ ፡ ውስጥ ፡ ወዲ ያ ፡ ወዲህ ፡ ይል ፡ ነበር

**kick (the) habit** አመሉን ፡ ተወ
He tried in vain to kick the cigarette habit. የሲጋራ ፡ አመሉን ፡ ለመተው ፡ በከንቱ ፡ ጣረ

**kick off** አወላለቀ
He kicked off his shoes and climbed into bed. ጫማውን ፡ አወላልቆ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ወጣ

**kick out** ከቤት ፡ አስወጣ
I nearly kicked him out. ከቤት ፡ ላስወጣው ፡ ምንም ፡ አልቀረኝም ፡ ነበር

**kick** (n.), **give a ~** ረገጠ
The horse nearly gave me a kick. ፈረሱ ፡ ሊረግ ጠኝ ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር

**get a kick out of** ተደሰተ
The children got a kick out of going to the circus. ልጆቹ ፡ ወደ ፡ ሰርከስ ፡ በመሄዳቸው ፡ ተደሰቱ

**kid** (v.)
*I'm only kidding. ቀልዴን ፡ ነው

**kid** (n.)
1. ግልገል. The goat had two kids. ፍየሏ ፡ ሁለት ፡ ግልገሎች ፡ ነበሯት
2. ሕፃን. Don't act like a kid! ሕፃን ፡ አትሁን

**kid** (adj.) ትንሽ
She looks like her kid sister. ትንሽ ፡ እኅቷን ፡ ትመስላለች
[See also 'fresh']

**kidnap**
1. አፍኖ ፡ ወሰደ. He kidnapped the rich man's son. የሀብታሙን ፡ ሰውዬ ፡ ልጅ ፡ አፍኖ ፡ ወሰደ
2. ጠለፈ. After he kidnapped the girl to marry her, a search was made. ልጅቷን ፡ ሊያገባት ፡ ከጠ ለፈ ፡ በኋላ ፡ ፍለጋ ፡ ተደረገ

**kidney** ኩላሊት
He died of a kidney disease. በኩላሊት ፡ በሽታ ፡ ሞተ

**kill**
1. ገደለ. Thou shalt not kill. አትግደል
The long hike killed us. ረጅሙ ፡ ሽርሽር ፡ ገደለን
2. አጠፋ. The frost killed the sprouting grain. ውርጩ ፡ ቡቃያውን ፡ አጠፋው
We killed time by looking out the window. በመስኮት ፡ ስንመለከት ፡ ጊዜ ፡ አጠፋን
3. ፈጀ. This infantile disease kills many babies. ይህ ፡ የልጆች ፡ በሽታ ፡ ብዙ ፡ ሕፃናትን ፡ ይ ፈጃል
4. ውድቅ ፡ አደረገ. The senators killed the tax bill. አማካሪዎቹ ፡ የግብሩን ፡ ሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ውድቅ ፡ አደረጉት

**kill (one's) hope** ተስፋ ፡ አስቈረጠ
His defeat killed our hopes. የሱ ፡ መሸነ ፍ ፡ ተስፋችንን ፡ አስቈረጠን

**(to) kill time** ጊዜ ፡ ለማሳለፍ ፡ ያህል
We played cards to kill time. ጊዜ ፡ ለማሳለፍ ፡ ያህል ፡ ካርታ ፡ ተጫወትን

**be killed** ሞተ
The soldier was killed in action. ወታደሩ ፡ በጦ ር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ሞተ

**kilo** ኪሎ

**kilogram** ኪሎግራም

**kilometer** ኪሎሜትር

**kin**
1. ዘመዶች. We are near kin. የቅርብ ፡ ዘመዶ ች ፡ ነን
2. ዘመድ. Write down your next of kin! የቅርብ ፡ ዘመድህን ፡ ስም ፡ ጻፍ

**be kin (to)** ተዛመደ
This book is kin to that one in subject. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በያዘው ፡ ነገር ፡ ከዚያኛው ፡ የሚዛመድ ፡ ነው

**kind** (n.) ዓይነት
There were all kinds of books on the table. ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ መጻሕፍት ፡ ነበሩ
What kind of person is he? ምን ፡ ዓይነት ፡ ሰው ፡ ነው ?
*She's the kind of woman who likes to help people. ሰውን ፡ መርዳት ፡ የምትወድ ፡ ሴት ፡ ናት

**kind of** መሰል
They make a kind of wine from raisins.

ከዘቢብ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ መሰል ፡ መጠጥ ፡ ይሠራሉ
*I felt kind of sorry for him. እንደ ፡ ማዘን ፡ አልኩ ለት

**all kinds of** ብዙ ፡ ዓይነት
There were all kinds of goods on display. በትርኢይቱ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ እቃ ፡ ሊታይ ፡ ቀርቦ ፡ ነበር

**be kind of,** expressed by a composite verb
*The room was kind of dark. ክፍሉ ፡ ጨለም ፡ ብሎ ፡ ነበር

**have a kind of**
*I have a kind of suspicion that he was checking on my work. የምሠራውን ፡ እንደሚቈጣጠር ፡ ጥርጣሬ ፡ አድሮብኛል

**in kind** በሚያመርተው ፡ ዓይነት
The farmer pays taxes to the government in kind. ገበሬው ፡ በሚያመርተው ፡ ዓይነት ፡ ለመንግሥት ፡ ግብር ፡ ይከፍላል
*She will be repaid in kind for her rudeness. ለብልግናዋ ፡ ዋጋዋን ፡ ታገኛለች

**of a kind**
*The boxes and a plank make a table of a kind. ሣጥንና ፡ ሳንቃ ፡ እንደ ፡ ጠረጴዛ ፡ ሊያገለግሉ ፡ ይችላሉ

**of the kind** እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር
I did not say anything of the kind. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አልወጣኝም

**(be) two of a kind** አንድ ፡ ናቸው
The twins are two of a kind. መንትዮቹ ፡ አንድ ፡ ናቸው

**kind** (adj.)
1. ደግ. He is a kind person who is always nice to children. ሁልጊዜ ፡ ለልጆች ፡ ደግ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ነው
That's very kind of you. ደግ ፡ ሠርተሃል
2. የደግነት. His kind act balances his rough manner. የደግነት ፡ ሥራው ፡ ባለጌ ፡ ጠባዩን ፡ ይሸፍንለታል
3. መልካም. Her kind words assuaged my grief. የተናገረችኝ ፡ መልካም ፡ ቃል ፡ ከሐዘኔ ፡ አጽናናኝ
*How kind of you to help me! ስለረዳኸኝ ፡ አመሰግናለሁ
*Will you be kind enough to close the door? በሩን ፡ ብትዘጋው
[See also 'heart']

**kindhearted** ርኅሩኅ ፤ ደግ
He is very kindhearted; he does not like to see people suffer. በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ (ደግ) ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ሰዎች ፡ ሲሠቃዩ ፡ ማየት ፡ አይወድም

**kindle** (vt.)
1. አያያዘ. The sparks kindled the dry grass. የሳቱ ፡ ፍንጣሪ ፡ ደረቁን ፡ ሣር ፡ አያያዘው
2. አነደደ. He kindled a fire in the fireplace. እምድጃው ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ አነደደ
3. ቀሰቀሰ. His cruelty kindled our anger. የሱ ፡ ጭካኔ ፡ ንዴታችንን ፡ ቀሰቀሰው

**kindle** (vi.)
1. ነደደ. The damp wood would never kindle. እርጥብ ፡ ዕንጨት ፡ በፍጹም ፡ አይነድም
2. ቀላ. Her eyes kindled with anger. ዓይኖቿ ፡ በንዴት ፡ ቀሉ
3. አበራ. Her eyes kindled with joy. ዓይኖቿ ፡ በደስታ ፡ አበሩ

**kindly** (adj.) የደግነት
The kindly faces of the nurses reassured the frightened child. የአስታማሚዎቹ ፡ የደግነት ፡ አስተያየት ፡ የደነገጠውን ፡ ልጅ ፡ አጽናናው

**kindly** (adv.)
1. በርኅራኄ. He spoke kindly to the frightened child. ፈርቶ ፡ የነበረውን ፡ ሕፃን ፡ በርኅራኄ ፡ አነጋገረው
2. በቅን ፡ መንፈስ. He does not take kindly to criticism. ነቀፌታን ፡ በቅን ፡ መንፈስ ፡ አይቀበልም
3. በጣም. We thank you kindly. በጣም ፡ እናመሰግንሃለን
4. እባክህ. Kindly stop when your time is up! እባካችሁ ፡ ጊዜው ፡ ሲያልቅ ፡ አቁሙ

**most kindly** ተጨንቆ ፡ ተጠቦ
She received us most kindly. ተጨንቃ ፡ ተጠባ ፡ ተቀበለችን

**kindness**
1. ደግነት. I appreciate your kindness. ስለ ፡ ደግነትህ ፡ አመሰግንሃለሁ
2. ውለታ. She does not seem very appreciative of the kindness done to her. ለተደረገላት ፡ ውለታ ፡ አመስጋኝ ፡ አትመስልም

**kindred** (n.) ዘመዶች
Are they your kindred or your wife's? ያንተ ፡ ዘመዶች ፡ ናቸው ፡ ወይስ ፡ የሚስትህ ?

**kindred** (adj.)
1. በዝምድና ፡ የተቀራረበ. Kindred tribes live in the region. በዝምድና ፡ የተቀራረቡ ፡ ጐሳዎች ፡ በቀበሌው ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ
2. የተዛመደ. Writing and grammar are kindred studies. ጽሕፈትና ፡ ሰዋስው ፡ የተዛመዱ ፡ ትምህርቶች ፡ ናቸው
3. የመሳሰለ. We are studying about rain,

frost, and kindred elements of nature. ስለ ፡ ዝናም ፤ ውርጭና ፡ የመሳሰሉ ፡ ሁኔታዎች ፡ እናጠናለን

**king** ንጉሥ
George VI was king of England. ጆርጅ ፡ ስድስተኛ ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ነበሩ

**become king** ነገሠ
He became king before the Second World War. ከሁለተኛው ፡ ዓለም ፡ ጦርነት ፡ በፊት ፡ ነገሠ

**make (one) king** አነገሠ
They made him king after the old dynasty died out. ከቀድሞው ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ፍጻሜ ፡ በኋላ ፡ እሱን ፡ አነገሡት

**kingdom**
1. የንጉሥ ፡ ግዛት. He ruled a kingdom. በንጉሥ ፡ ግዛት ፡ ገዛ
2. ዘር. Does your question concern the animal kingdom? ጥያቄህ ፡ የእንስሳትን ፡ ዘር ፡ የሚመለከት ፡ ነው ?

**Heavenly Kingdom** መንግሥተ ፡ ሰማያት
Sinners will not enter the Heavenly Kingdom. ኀጢአተኞች ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አይገቡም
[See also 'divine']

**kingly**
1. ንጉሣዊ. His kingly pride made him choose death to surrender. ንጉሣዊ ፡ ኩራቱ ፡ እጁን ፡ ከመስጠት ፡ ሞትን ፡ እንዲመርጥ ፡ አደረገው
2. የንጉሥ. He wears a kingly crown. የንጉሥ ፡ ዘውድ ፡ ጭኗል

**kingly personages** ንጉሣውያን ፡ ቤተሰቦች
A large number of kingly personnages attended the funeral. ብዙ ፡ ንጉሣውያን ፡ ቤተሰቦች ፡ በቀብሩ ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ ነበር

**king of kings** ንጉሠ ፡ ነገሥት
The Ethiopian ruler is the king of kings. የኢትዮጵያ ፡ ገዢ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ናቸው

**kink**
*There is a kink in the rope. ገመዱ ፡ ታጥፏል

**kinky** ከርዳዳ
Some people have kinky hair. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከርዳዳ ፡ ጸጉር ፡ አላቸው

**kinship** ዝምድና
Kinship is based on a common ancestor. ለዝምድና ፡ መሠረት ፡ የሚሆነው ፡ አንድ ፡ አያት ፡ ቅድመ ፡ አያት ፡ ነው

**kiss** (v.) ሳመ
He tried to kiss me. ሊስመኝ ፡ ሞከረ

**kiss** (n.) መሳሳም
I heard the sound of a kiss in the next room. በሚቀጥለው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የመሳሳም ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ

**give a kiss** ሳመ
He gave his wife a kiss and went to work. ሚስቱን ፡ ስሞ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ ሄደ

**kit**
1. መሣሪያ. The nurse came with her first-aid kit. ነርሷ ፡ የመጀመሪያ ፡ እርዳታ ፡ መሣሪያዋን ፡ ይዛ ፡ መጣች
2. መገጣጠሚያ ፡ እቃዎች. He bought a radio kit for his son. ለልጁ ፡ የሬዲዮ ፡ መገጣጠሚያ ፡ እቃዎች ፡ ገዛለት
[See also 'first aid']

**kitchen** ማድቤት ፤ ወጥቤት
The cook is in the kitchen. ወጥቤቷ ፡ ማድቤት ፡ (ወጥቤት) ፡ ውስጥ ፡ ናት

**kite** ወላንዳ
They like to fly kites. ወላንዳ ፡ ማውለብለብ ፡ ይወዳሉ

**kitten**
1. የድመት ፡ ግልገል. A kitten grows up on milk. የድመት ፡ ግልገል ፡ በወተት ፡ ያድጋል
2. ግልገል. The cat is nursing her kittens. ድመቷ ፡ ግልገሎቿን ፡ ታጠባለች

**knack** ተሰጥኦ
He has a knack for carpentry. የአናጢነት ፡ ተሰጥኦ ፡ አለው

**not get the knack of it** ዘዴው ፡ አይሆንለትም
I want to dance well, but I cannot get the knack of it. በደንብ ፡ ለመደነስ ፡ እፈልጋለሁ ፡ ግን ፡ ዘዴው ፡ አይሆንልኝም

**knead** አቦካ
She washed her hands before kneading the dough. ሊጡን ፡ ከማቡካቷ ፡ በፊት ፡ እጇን ፡ ታጠበች

**knee** ጉልበት
I hurt my knee. ጉልበቴን ፡ ተጎዳሁ

**bring to (one's) knees** አንበረከከ
We brought the enemy to his knees. ጠላትን ፡ አንበረከክን

**drop on his knees** ተንበረከከ
He dropped on his knees to beg forgiveness. ይቅርታ ፡ ለመለመን ፡ ተንበረከከ

**fall on his knees** በጉልበቱ ፡ ወደቀ
He fell on his knees and begged for pardon. በጉልበቱ ፡ ወድቆ ፡ ምሕረት ፡ ለመነ

**go down on one's knees** በጉልበቱ ፡ ወደቀ
He went down on his knees to beg for pardon. ምሕረት ፡ ለመለመን ፡ በጉልበቱ ፡ ወደቀ
[See also 'bended']

**kneecap** የጉልበት ፡ ሎሚ
He fell and skinned his kneecap. ወድቆ ፡ የጉልበቱ ፡ ሎሚ ፡ ተላጠ

**kneel** (knelt) ተንበረከከ
He knelt before the statue of St. Mary. ከቅድስት ፡ ማርያም ፡ ሐውልት ፡ ፊት ፡ ተንበረከከ

**knell** (v.) ተደወለ
The church bells knelled all morning. የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ደወል ፡ ሲደወል ፡ አረፈደ

**knell** (n.), **sound the ~**
1. ተደወለ. A bell sounds the knell during each funeral. በየቀብሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ደወል ፡ ይደወላል
2. የ --- አገልግሎት ፡ ማብቂያ ፡ ሆነ. The invention of the automobile sounded the knell of the horse and buggy. የመኪና ፡ መፈልሰፍ ፡ የፈረስና ፡ የሰረገላ ፡ አገልግሎት ፡ ማብቂያ ፡ ሆነ

**knelt,** see **kneel**

**knew,** see **know**

**knife** (v.) በጩቤ ፡ ወጋ
He knifed his enemy in a fight. በጠቡ ፡ ላይ ፡ ጠላቱን ፡ በጩቤ ፡ ወጋ

**knife** (knives), n. ቢላዋ ፤ ቢላ
He cut his hand with a knife. እጁን ፡ ቢላዋ ፡ ቈረጠው
[See also 'back, pocket']

**knight** [በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጀብዱ ፡ ለፈጸመ ፡ የሚሰጥ ፡ የወታደር ፡ ክብር ፡ ማዕረግ]

**knit** ሠራ
She herself knit these gloves. እነዚህን ፡ የእጅ ፡ ሹራቦች ፡ የሠራቻቸው ፡ ራሷ ፡ ናት

**be knit together** ተሳሰረ
The two families are knit together by a common interest. ሁለቱ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ በጋራ ፡ ጥቅም ፡ ተሳስረዋል

**knives,** see **knife**

**knob**
1. እጀታ. The knob fell off the door. የበሩ ፡ እጀታ ፡ ወለቀ
2. ሉል. There is a knob on top of the flagpole. ከሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ መስቀያ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሉል ፡ አለ

**knock** (vt.) መታ
He knocked him on the head. እራሱ ፡ ላይ ፡ መታው

**knock** (vi.)
1. በሩን ፡ አንኳኳ. Please knock before you come in! ከመግባትህ ፡ በፊት ፡ በሩን ፡ አንኳኳ
2. አንኳኳ. Someone knocked at the door. ሰው ፡ በሩን ፡ አንኳኳ
3. ጮኸ. The engine is knocking. ሞተሩ ፡ ይጮኻል

**knock about** (vt.) አንገላታ
The waves knocked the boat about. ሞገዱ ፡ ጀልባውን ፡ አንገላታው

**knock about** (vi.) ተንከራተተ
He knocked about quite a lot in his youth. በልጅነቱ ፡ ብዙ ፡ ተንከራቷል

**knock against**
1. ከ --- ጋር ፡ አጋጨ. He knocked his head against the wall. ራሱን ፡ ከግድግዳ ፡ ጋር ፡ አጋጨ
2. ደበደበ. Don't knock against the table! ጠረጴዛውን ፡ አትደብድብ

**knock around**
*He has knocked around all over the world. በዓለም ፡ ላይ ፡ ያልረገጠው ፡ ስፍራ ፡ የለም

**knock down**
1. መቶ ፡ ጣለ. He overtook the running thief and knocked him down. ይሸሽ ፡ የነበረውን ፡ ሌባ ፡ ደረሰበትና ፡ መቶ ፡ ጣለው
2. ጣለ. Be careful not to knock down the flower vase! አበባ ፡ ማስቀመጫውን ፡ እንዳትጥል ፡ ተጠንቀቅ
3. ዋጋ ፡ ቀነሰ. The storekeeper knocked down his remaining winter clothes. ባለመደብሩ ፡ የተረፈውን ፡ የክረምት ፡ ልብስ ፡ ዋጋ ፡ ቀነሰ

**(be) knocked down**
1. ፈረሰ. These are the old houses that have to be knocked down. እነዚህ ፡ አሮጌ ፡ ቤቶች ፡ መፍረስ ፡ ያለባቸው ፡ ናቸው
2. ወደቀ. Reset the stakes that were knocked down! የወደቁትን ፡ ችካሎች ፡ መልሰህ ፡ ትከላቸው
3. (= tr.) ዳጠ. He was knocked down by a bus. አውቶቡስ ፡ ዳጠው
4. (= tr.) ገፍትሮ ፡ ጣለ. When crossing the river, he was knocked down by the onrush of water. ወንዙን ፡ ሲያቋርጥ ፡ ደራሽ ፡ ውኃ ፡ ገፍትሮ ፡ ጣለው

**knock (into)** ከ - - ጋር ፡ ተጋጨ
He knocked into many people as he ran. ሲሮጥ ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ተጋጨ

**knock off** (vt.)
1. ከራሱ ፡ ላይ ፡ ጣለ(በት). He nearly knocked my hat off. ባርኔጣዬን ፡ ከራሴ ፡ ላይ ፡ ሊጥልብኝ ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር
2. ነቀሰ. He knocked two dollars off the price. ከዋጋው ፡ ሁለት ፡ ብር ፡ ነቀሰ

**knock out**
1. አቋረጠ. The explosion knocked out the power for several hours. ፈንጂው ፡ ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ኮረንቲውን ፡ አቋረጠው
2. አስጣለ. He knocked the tray out of my hands. ዝርጉን ፡ ሳሕን ፡ ከእጄ ፡ አስጣለኝ

**knock (oneself) out**
*He really knocks himself out for football. ልቡ ፡ እስኪወልቅ ፡ ኳስ ፡ ይጫወታል

**(be) knocked out**
1. በጣም ፡ ደከመ. He was all knocked out after one game of tennis. ቴኒስ ፡ አንድ ፡ ዙር ፡ ከተጫወተ ፡ በኋላ ፡ በጣም ፡ ደከመው
2. ተሸነፈ. He was knocked out in the tenth round. ባሥረኛው ፡ ዙር ፡ ተሸነፈ
3. ወለቀ. A panel was knocked out of the door. ከመዝጊያው ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ወልቋል

**knock over** ደፋ
Who knocked the pail over? ባልዲውን ፡ ማን ፡ ደፋው ?

**(be) knocked over** ክው ፡ አለ
When the announcement came, we were completely knocked over. ማስታወቂያውን ፡ ስንሰማ ፡ ክው ፡ አልን

**knock together** (vt.) ውትፍትፍ ፡ አድርጎ ፡ ሠራ
The boys knocked together a sort of raft out of old boards. ልጆቹ ፡ ካረጀ ፡ ሳንቃ ፡ መንሳፈፊያ ፡ ቢጤ ፡ ውትፍትፍ ፡ አድርገው ፡ ሠሩ

**knock up** አበላሸ
The children knocked up the new table. ልጆቹ ፡ አዲሱን ፡ ጠረጴዛ ፡ አበላሹት

**(one's) knees knock together** ተብረከረከ
He was so scared, his knees knocked together. ከፍርሀቱ ፡ የተነሣ ፡ ተብረከረከ
[See also 'senseless, unconscious']

**knock** (n.) መንኳኳት
The knock on the door made us all jump with surprise. የመዝጊያው ፡ መንኳኳት ፡ አስበረገገን
*Did you hear the knock at the door? በሩ ፡ ሲንኳኳ ፡ ሰማህ ?

**knockout** መዘረር
The champion won by a knockout in the tenth round. የሁሉ ፡ ረቺ ፡ የሆነው ፡ ባሥረኛው ፡ ዙር ፡ ላይ ፡ በመዘረር ፡ አሸነፈ

**knoll** ጉብታ ፤ ሞላላ ፡ ኮረብታ
The shepherd sat on a knoll to watch his flock better. እረኛው ፡ ከብቶቹን ፡ በደንብ ፡ ለመመልከት ፡ እንዲችል ፡ ከጉብታው ፡ (ከሞላላው ፡ ኮረብታ) ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ

**knot** (v.) ቋጠረ
Shall I knot the string? ሲባጎውን ፡ ልቋጥረው ?

**knot** (n.)
1. ቋጠሮ. The string is full of knots. ገመዱ ፡ ብዙ ፡ ቋጠሮ ፡ አለበት
2. ዓይን. The board is full of knots. ሳንቃው ፡ ዓይን ፡ ብቻ ፡ ነው

**make a knot** ቋጠረ
Make a knot in this string, please! ይህንን ፡ ሲባጎ ፡ ቋጥረው

**tie a knot** ቋጠረ
Tie a knot in this string right here! ሲባጎውን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ቋጥረው

**knotty**
1. ዓይን ፡ የበዛበት. A knotty board is not good for making shelves. ዓይን ፡ የበዛበት ፡ ሳንቃ ፡ ለመደርደሪያ ፡ መሥሪያ ፡ አይረባም
2. በጣም ፡ አስቸጋሪ. That is a knotty problem. ጉዳዩ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**know** (knew)
1. ዐወቀ. Do you know him? No, I don't know him. ታውቀዋለህ ? የለም ፡ አላውቀውም
I do not know how to drive a car. መኪና ፡ መንዳት ፡ አላውቅም
2. ተረዳ. He suddenly knew that she would not stay. የማትቆይ ፡ መሆኗን ፡ በድንገት ፡ ተረዳ
3. ለየ. You will know his house by the red roof. ቤቱን ፡ በቀይ ፡ ጣሪያው ፡ ትለየዋለህ
4. አሳለፈ. He knew many days of adversity. ብዙ ፡ የመከራ ፡ ቀኖች ፡ አሳልፏል

**know of** ዐወቀ
Do you know of a good restaurant around here? በዚህ ፡ አካባቢ ፡ ጥሩ ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ ታውቃለህ ?

**for all I know** እንዲያውም
For all I know, he may be dead. እንዲያውም ፡ ሳይሞት ፡ አይቀርም

**let know** አስታወቀ
After this, please let me know in advance! ለወደፊቱ ፡ ቀደም ፡ ብለህ ፡ አስታውቀኝ
[See also 'place, rope']

**knowing** (adj.)
*She gave me a knowing wink. ያልኩት ፡ የገባት ፡ መሆኗን ፡ ገለጸችልኝ

**knowingly** ዐውቆ
He would never do anything knowingly to hurt you. በምንም ፡ ዓይነት ፡ ዐውቆ ፡ ሊጐዳህ ፡ አይፈልግም

**knowledge**
1. ዕውቀት. His knowledge of the area is remarkable. ስለ ፡ ቀበሌው ፡ ያለው ፡ ዕውቀት ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው
2. ችሎታ. His knowledge of Amharic is poor. ያማርኛ ፡ ችሎታው ፡ አነስተኛ ፡ ነው
3. መቻል. One of his recent requirements is a knowledge of French. በቅርቡ ፡ ከገበያቸው ፡ ነገሮች ፡ የፈረንሳይ ፡ ቋንቋ ፡ መቻሉ ፡ ነው

**come to one's knowledge** ሰማ
It has come to my knowledge that you are slandering us. እንደምታማን ፡ ሰምቻለሁ

**to one's knowledge** እሱ ፡ እንደሚያውቀው
To my knowledge, he hasn't been here. እኔ ፡ እንደማውቀው ፡ እሱ ፡ እዚህ ፡ አልነበረም

**to the best of one's knowledge** የሚያውቀውን ፡ ያህል
Answer to the best of your knowledge! የምታውቁትን ፡ ያህል ፡ መልሱ
[See also 'common']

**knowledgeable** ዐዋቂ
He is a knowledgeable young man. ዐዋቂ ፡ የሆነ ፡ ወጣት ፡ ነው

**knuckle** (v.), ~ **down**
*You'd better knuckle down to work! ኰስተር ፡ ብለህ ፡ ብትሠራ ፡ ይሻልሃል

**knuckle under to** ተቀበለ
Ethiopia did not knuckle under to Italy's demands. ኢትዮጵያ ፡ ኢጣልያ ፡ ያቀረበችውን ፡ ጥያቄ ፡ አልተቀበለችም

**knuckle** (n.) ዓጽቅ
I hurt the knuckles of my right hand. የቀኝ ፡ እጄን ፡ ዓጽቅ ፡ ጐዳሁት

## L

**label** (v.)

1. አለ. They labeled him a liar. ውሸታም ፡ አሉት
2. ስም ፡ ለጠፈ ፤ ምልክት ፡ ለጠፈ. The druggist labeled the jars. መድኃኒት ፡ ቀማሚው ፡ ጠርሙሶች ፡ ላይ ፡ የመድኃኒቱን ፡ ስም ፡ ለጠፈ

The clerk spent the day labeling the merchandise. አሻሻጩ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ እቃው ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ በመለጠፍ ፡ ዋለ

**label** (n.) ምልክት

Take the label off the bottle! ከጠርሙሱ ፡ ላይ ፡ ምልክቱን ፡ ላጠው

**labial** የከንፈር

The sound 'b' is labial. « በ » ፡ የከንፈር ፡ ድምፅ ፡ ነው

**labor** (v.)

1. ሠራ. He labored all day long in the factory. በፋብሪካው ፡ ውስጥ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሠራ
2. ብዙ ፡ ደከመ. He labored for the betterment of mankind. ለሰው ፡ ልጅ ፡ መሻሻል ፡ ብዙ ፡ ደከሟል
3. ጣረ. He labored to improve his farm. ማሳውን ፡ ለማሻሻል ፡ ጣረ
4. ተንገላታ. The ship labored in the high waves. መርከቧ ፡ በከፍተኛው ፡ ሞገድ ፡ ውስጥ ፡ ተንገላታች

**labor the point** ስለ ፡ ነገሩ ፡ ሐተታ ፡ አበዛ

The speaker labored the point so much that we lost interest. ተናጋሪው ፡ ስለ ፡ ነገሩ ፡ ሐተታ ፡ ስላበዛ ፡ ሰለቸን

**labor up** በጥረት ፡ ወጣ

The monk labored up the steep hill. መነኩሴው ፡ ዳገቱን ፡ በጥረት ፡ ወጣ

**labor** (n.)

1. የሙያተኛ ፡ ዋጋ. Labor alone will cost three hundred dollars. የሙያተኛ ፡ ዋጋ ፡ ብቻ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ይሆናል
2. የጉልበት ፡ ዋጋ. The farmer wants to be paid for his labor. ገበሬው ፡ የጉልበቱ ፡ ዋጋ ፡ እንዲከፈለው ፡ ይጠይቃል
3. ምጥ. His wife is in labor. ሚስቱ ፡ ምጥ ፡ ይዟታል
4. ጥረት. All our labor has been in vain. ጥረታችን ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ነው
5. ሠራተኞች. Ethiopia needs skilled labor. ኢትዮጵያ ፡ የሠለጠኑ ፡ ሠራተኞች ፡ ያስፈልጓታል

**hard labor** ጽኑ ፡ እስራት

He was sentenced to five years at hard labor. ያምስት ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ተፈረደበት

[See also 'communal']

**laboratory** ቤተ ፡ ሙከራ

A laboratory for testing bovine medicines has been established. ለላም ፡ የሚሆን ፡ መድኃኒቶች ፡ የሚፈትን ፡ ቤተ ፡ ሙከራ ፡ ተቋቁሟል

**laborer** የቀን ፡ ሠራተኛ

He is just a common laborer. ተራ ፡ የቀን ፡ ሠራተኛ ፡ ነው

**laborious**

1. ትጉህ. Bees and ants are laborious insects. ንቦችና ፡ ጉንዳኖች ፡ ትጉህ ፡ ነፍሳት ፡ ናቸው
2. አድካሚ. Looking through files is a laborious job. ዶሴ ፡ ማገላበጥ ፡ አድካሚ ፡ ሥራ ፡ ነው

**laboriously** በብዙ ፡ ድካም

The child traced his signature laboriously. ትንሹ ፡ ልጅ ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ ፈረመ

**labor pains** ምጥ

The labor pains made her cry out. ምጡ ፡ አስጮኻት

**labyrinth** [መውጫ ፡ መግቢያቸው ፡ በማይታወቅ ፡ አኳኋን ፡ የተሠሩ ፡ መተላለፊያዎች]

**lace** (v.) አሰረ

Wait till I lace my shoes! ጫማዬን ፡ እስካስር ፡ ቆይ

**lace together** አሰረ

He laced the sticks together with a strong vine. ዕንጨቶቹን ፡ በጥብቅ ፡ ሐረግ ፡ አሰረ

**lace** (n.)

1. ማሰሪያ. These shoes need new laces. ይህ ፡ ጫማ ፡ አዲስ ፡ ማሰሪያ ፡ ያስፈልገዋል
2. ዳንቴል. The girl's dress is trimmed with lace. የልጃገረዲቷ ፡ ቀሚስ ፡ በዳንቴል ፡ የተከፈፈ ፡ ነው

**lacerate**

1. ቧጠጠ. The thorns lacerated his flesh. እሾኩ ፡ ሥጋውን ፡ ቧጠጠው
2. ክፉኛ ፡ ቆረጠ. The shattered glass lacerated

his hand. የተሰበረው ፡ መስታወት ፡ እጁን ፡ ክፉኛ ፡ ቈረጠው
3. ነካ. Sharp criticism lacerated his pride. ከባድ ፡ ነቀፋ ፡ ክብሩን ፡ ነካው

**lacerate one's feelings** ስሜቱን ፡ ጐዳ
His cruel words lacerated his feelings. ክፉ ፡ አነጋገሩ ፡ ስሜቱን ፡ ጐዳው

**lack** (v.)
1. ጐደለ(ው). +I did not lack anything there. እዚህ ፡ ምንም ፡ የጐደለኝ ፡ ነገር ፡ አልነበረም
2. አነሰ(ው). +A coward lacks courage. ፈሪ ፡ ልብ ፡ ያንሰዋል
3. አጣ. Lacking butter, we put honey on our bread. ቅቤ ፡ ስላጣን ፡ ዳቦዎችንን ፡ ማር ፡ ቀባነው
[See also 'interest']

**lack** (n.)
1. እጥረት. There is a lack of trained personnel. የሠለጠኑ ፡ ሠራተኞች ፡ እጥረት ፡ አለ
2. እጦት. Lack of rest made him tired. የዕረፍት ፡ እጦት ፡ አደከመው
3. ማጣት. Lack of a telephone isolated me. ስልክ ፡ ማጣቴ ፡ ከሌሎች ፡ ለየኝ
4. አለ + (verbal noun). His mistakes betrayed his lack of education. የፈጸማቸው ፡ ስሕተቶች ፡ አለመማሩን ፡ ገለጹበት
*Our most serious lack was fresh water. በጣም ፡ የቸገረን ፡ ንጹሕ ፡ ውኃ ፡ ነበር

**for lack of**
1. ቢያጣ. For lack of something better to do, I went to the movies. ሌላ ፡ የተሻለ ፡ ነገር ፡ የማደርገው ፡ ባጣ ፡ ሲኒማ ፡ ገባሁ
2. ስለጠፋ. He was acquitted for lack of evidence. ማስረጃ ፡ ስለጠፋ ፡ በነጻ ፡ ተለቀቀ

**(be) lacking** አጣ
We have everything we need; only water is lacking. የምንፈልገው ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ አለን ፤ ውኃ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ያጣነው

**be lacking in**
1. ጐደለ(ው). +He is lacking in wisdom. ጥበብ ፡ ይጐድለዋል
2. አነሰ(ው). +A weak person is lacking in strength. ደካማ ፡ ሰው ፡ ጉልበት ፡ ያንሰዋል
*He is lacking in courage. ሐሞት ፡ የለውም

**laconic** አጥር ፡ ምጥን
He has a laconic style of writing. አጥር ፡ ምጥን ፡ ያለ ፡ ያጻጻፍ ፡ ዘዴ ፡ አለው

**lacuna** ግድፈት
There is a lacuna in the manuscript. በእጅ ፡ ጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ ግድፈት ፡ አለ

**lad** ልጅ
He is a handsome lad. መልክ ፡ ቀና ፡ ልጅ ፡ ነው

**ladder**
1. መሰላል. He climbed the ladder to the roof. በመሰላል ፡ ጣሪያው ፡ ላይ ፡ ወጣ
2. ደረጃ. He was high on the political and social ladder. በፖለቲካና ፡ በኅብረ ፡ ሰብ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ነበረው

**(be) laden** ተጫነ
The donkeys were laden with bundles of wood. አህያዎቹ ፡ ዕንጨት ፡ ተጭነው ፡ ነበር

**ladle** (v.), ~ **out** ጨለፈ
She ladled out the soup. ሾርባውን ፡ ጨለፈች

**ladle** (n.) ጭልፋ
The ladle is broken. ጭልፋው ፡ ተሰብሯል

**lady** (n.)
1. ሴት. Is that lady his mother? ያቺ ፡ ሴትዮ ፡ እናቱ ፡ ነች ?
2. ሴት ፡ ወይዘሮ. Mrs. Parker is a real lady. ወይዘሮ ፡ ፓርከር ፡ ጥሩ ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ናቸው
3. ወይዘሮ (pl. ወይዛዝርት). Ladies are requested to come at ten. ወይዛዝርት ፡ ባራት ፡ ሰዓት ፡ እንዲመጡ ፡ ይለመናሉ
4. ባለቤት. The ambassador and his lady arrived late. አምባሳደሩና ፡ ባለቤታቸው ፡ ዘግይተው ፡ ደረሱ

**ladies** ክቡራት
Ladies and Gentlemen! ክቡራትና ፡ ክቡራን !

**lady of the house** ባለቤት
The lady of the house is the one to hire the servants. አሽከሮች ፡ የሚቀጥሩት ፡ ባለቤቲቱ ፡ ናቸው

**Our Lady** እመቤታችን
He said a prayer to Our Lady. ለእመቤታችን ፡ ጸሎት ፡ አደረገ

**lady** (adj.) ሴት
She is a lady doctor. ሴት ፡ ሐኪም ፡ ናት
[See also 'old, refinement, waiting']

**ladylike** የወይዘሮነት
Her ladylike manners charmed everyone. የወይዘሮነት ፡ ሁኔታዋ ፡ ሁሉንም ፡ ማረከ

**lag** (lagged), v.
1. ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀረ. The plant often lags in making its quota. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፋብሪካው ፡ ሊሠራው ፡ ከሚገባው ፡ መጠን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ይቀራል

2. ቀዘቀዘ. Our interest lagged toward the end of the performance. ወደ ፡ ትርኢይቱ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ስሜታችን ፡ ቀዘቀዘ

**lag behind** ከ - - - ኋላ ፡ ቀረ
He is always lagging behind the others. ሁሌም ፡ ከሌሎች ፡ ኋላ ፡ ይቀራል

**lag** (n.) መራራቅ
There is always a lag between promise and fulfillment. ቃል ፡ በመስጠትና ፡ በመፈጸም ፡ መካከል ፡ ሁልጊዜ ፡ መራራቅ ፡ አለ

**lagoon** ሐይቀ ፡ ባሕር

**laid,** see **lay**

**lain,** see **lie**

**lair** ዋሻ
He found the robbers' lair. የዘራፊዎቹን ፡ ዋሻ ፡ አገኘ

**laissez passer** የይለፍ ፡ ወረቀት
The refugee has a laissez passer. ጥገኛው ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ አለው

**laity** ምእመናን
The laity and the clergy agreed to hold a council. ምእመናኑና ፡ ካህናቱ ፡ ስብሰባ ፡ ለማድረግ ፡ ተስማሙ

**lake** ሐይቅ
We went bathing in the lake. ሐይቁ ፡ ውስጥ ፡ ልንዋኝ ፡ ሄድን

**lamb** የበግ ፡ ጠቦት
When do you shear the lambs? የበግ ፡ ጠቦቶችን ፡ መቼ ፡ ትሸልታለህ ?

**boiled lamb** የበግ ፡ ቅቅል
We are having boiled lamb for supper. ለራት ፡ የበግ ፡ ቅቅል ፡ እንበላለን

**lame** (v.) አንካሳ ፡ አድርጎ ፡ አስቀረ
The accident lamed him for life. አደጋው ፡ ሕይወቱን ፡ ሙሉ ፡ አንካሳ ፡ አድርጎ ፡ አስቀረው

**lame** (adj.)
1. አንካሳ. He is lame as a result of an accident. ባደጋ ፡ ምክንያት ፡ አንካሳ ፡ ሆኗል
2. ሽባ. He has a lame leg. አንድ ፡ እግሩ ፡ ሽባ ፡ ነው
The lame man clumped along. ሽባው ፡ ሰውዬ ፡ እየተጎተተ ፡ ሄደ

**be lame** ተሳሰረ
His arm is lame from playing ball. ኳስ ፡ ከመጫወት ፡ የተነሣ ፡ ክንዱ ፡ ተሳስሯል

**be a lame excuse** በቂ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም
Sleeping too late is a lame excuse for being tardy. ተኝቶ ፡ ማርፈድ ፡ ዘግይቶ ፡ ለመነሣት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም

**lament** (v.)
1. አለቀሰ. They lament the death of their friend. ወዳጃቸው ፡ ስለሞተ ፡ ያለቅሳሉ
2. አዘነ. We lamented his absence. በመቅረቱ ፡ አዘንን

**lament** (n.) የሐዘን ፡ እንጉርጉሮ
The woman's lament moved the people to tears. የሴትዮዋ ፡ የሐዘን ፡ እንጉርጉሮ ፡ ሰውን ፡ አስለቀሰ

**lamentable**
1. በጣም ፡ የሚያሳዝን. It was a lamentable day when our dog was run over. ውሻችን ፡ የተዳጠበት ፡ ቀን ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ቀን ፡ ነበር
2. የማይረባ. The audience booed his lamentable violin playing. የማይረባውን ፡ የቫዮሊን ፡ ምቱን ፡ አድማጮቹ ፡ በጩኸት ፡ ተቃወሙት

**lamentation** ለቅሶ
Lamentations were heard everywhere when the king died. ንጉሡ ፡ ሲሞት ፡ በያለበት ፡ ለቅሶ ፡ ተሰማ

**lamp**
1. ፋኖስ. We need a new lamp for this room. ለዚህ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ ፋኖስ ፡ ያስፈልገናል
2. መብራት. The desk lamp is new. የጠረጴዛው ፡ መብራት ፡ አዲስ ፡ ነው
[See also 'kerosene lamp']

**lampshade** ሽፋን
We will buy a new lampshade for the desk lamp. ለጠረጴዛው ፡ መብራት ፡ አዲስ ፡ ሽፋን ፡ እንገዛለን

**lance** (v.) አፈረጠ
The doctor lanced the boil. ሐኪሙ ፡ ብጉንጁን ፡ አፈረጠው

**lance** (n.) ጦር
He can throw a lance twenty yards. ጦር ፡ ሃያ ፡ ያርድ ፡ አርቆ ፡ ሊወረውር ፡ ይችላል

**lancet** [ሁለት ፡ ስለት ፡ ያለው ፡ ሹል ፡ የሆነ ፡ ሐኪም ፡ የሚገለገልበት ፡ ትንሽ ፡ ቢላዋ]

**land** (vt.)
1. አሳረፈ. The captain managed to land the plane despite its broken wing. የአውሮፕላኑ ፡ ክንፍ ፡ ቢሰበርም ፡ ካፒቴኑ ፡ አውሮፕላኑን ፡ ለማሳረፍ ፡ ቻለ

2. አወረደ. The ship landed its passengers. መርከቧ ፡ ተሳፋሪዎችን ፡ አወረደች

3. አደረሰ. The train will land you in Addis Ababa on time. ባቡሩ ፡ በሰዓቱ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ያደርስሃል

**land** (vi.)

1. አረፈ. The plane landed smoothly. አውሮፕላኑ ፡ በርጋታ ፡ አረፈ

The cat jumped and landed on its feet. ድመቱ ፡ ዘሎ ፡ በእግሩ ፡ አረፈ

The ball landed in the middle of the court. ኳሷ ፡ ሜዳው ፡ መካከል ፡ አረፈች

2. ቆመ. The ship landed. መርከቧ ፡ ቆመች

3. ከመርከብ ፡ ወረደ. The passengers landed at noon. መንገደኞቹ ፡ ቀትር ፡ ላይ ፡ ከመርከብ ፡ ወረዱ

4. ገባ. Though the ball landed in the goal, it was declared a foul. ኳሷ ፡ ግብ ፡ ብትገባም ፡ ነጥቡ ፡ ፋርሽ ፡ ሆነ

[See also 'ground, jail']

**land** (n.)

1. ምድር. This is the land of Ethiopia. ይህ ፡ ምድረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነው

2. መሬት. The land here is very fertile. በዚህ ፡ አካባቢ ፡ መሬት ፡ በጣም ፡ ለም ፡ ነው

3. የብስ. After traveling by ship for a while, we were happy to see land. በመርከብ ፡ ስንሄድ ፡ ከርመን ፡ የብስ ፡ ስናይ ፡ ደስ ፡ አለን

4. አገር. He is visiting distant lands. ሩቅ ፡ አገሮችን ፡ ይጐበኛል

The whole land prayed for his health. አገር ፡ በሙሉ ፡ ለጤንነቱ ፡ ጸለየ

[See also 'pasture, piece, Promised Land, tongue, tract']

**land forces** የምድር ፡ ጦር

The land forces are 150,000 strong. የምድር ፡ ጦሩ ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሺ ፡ ነው

**landholder** ባለመሬት

The landholder must pay a tax. ባለመሬቱ ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ አለበት

**landholding** የመሬት ፡ ይዞታ

Landholdings vary in size in this province. በዚህ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ መጠኑ ፡ ይለያያል

**landing**

1. [በደረጃ ፡ መጨረሻ ፡ ወይም ፡ በደረጃና ፡ በደረጃ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ገላጣ ፡ ማረፊያ]

2. ማቆሚያ. They tied the boat up at the landing. ጀልባውን ፡ ከማቆሚያው ፡ አሰሩት

3. (= to land) ማረፍ. The pilot made an emergency landing. አውሮፕላን ፡ ነጂው ፡ በአደጋ ፡ ምክንያት ፡ ባስቸኳይ ፡ ማረፍ ፡ ነበረበት

*The landing of the American forces in France is known as D-Day. የአሜሪካ ፡ ወታደሮች ፡ የፈረንሳይን ፡ ምድር ፡ የረገጡበት ፡ ቀን ፡ « ዲ ፡ ዴይ » ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል

**landing field** የአውሮፕላን ፡ ማረፊያ

The landing field is not marked on the map. የአውሮፕላን ፡ ማረፊያው ፡ በካርታው ፡ ላይ ፡ አልተመለከተም

**landing strip** ማረፊያ ፡ የሚሆን ፡ ሜዳ

There is a landing strip for small planes. ለትናንሽ ፡ አውሮፕላኖች ፡ ማረፊያ ፡ የሚሆን ፡ ሜዳ ፡ አለ

**landlady** ባለቤት

The landlady demanded the rent. ባለቤቷ ፡ ኪራዩን ፡ ጠየቀች

**landlord** የቤቱ ፡ ጌታ

The landlord must fix my door. የቤቱ ፡ ጌታ ፡ መዝጊያዬን ፡ ማሠራት ፡ አለበት

**landmark**

1. ምልክት. Surveyors make landmarks after they have surveyed the land. ቀያሾች ፡ መሬቱን ፡ ከቀየሱ ፡ በኋላ ፡ ምልክት ፡ ያደርጋሉ

2. ጐልቶ ፡ የሚታየው. The City Hall is now a landmark of Addis Ababa. በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ አሁን ፡ ጐልቶ ፡ የሚታየው ፡ የከተማው ፡ አዳራሽ ፡ ነው

3. ትልቅ ፡ ምዕራፍ. The telephone and the radio are landmarks in the progress of communications. ስልክና ፡ ሬዲዮ ፡ በመገናኛ ፡ ረገድ ፡ ትልቅ ፡ ምዕራፍ ፡ ይዘዋል

4. የመሬት ፡ ድንበር ፡ የሚያመለክት ፡ ደንጊያ. The landmark was hard to find. የመሬቱን ፡ ድንበር ፡ የሚያመለክተውን ፡ ደንጊያ ፡ ማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር

**landowner** ባለርስት

The landowners have to pay new taxes. ባለርስቶች ፡ ተጨማሪ ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ አለባቸው

**land reform** የመሬት ፡ ይዞታ ፡ መሻሻል

Land reform is badly needed. የመሬት ፡ ይዞታ ፡ መሻሻል ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**landscape** የመሬት ፡ አቀማመጥ ፤ የመሬት ፡ መልክ ፤ ገጽ

The Ethiopian landscape in the north is bare. የሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመሬት ፡ አቀማመጥ ፡ የተራቆተ ፡ ነው

The landscape in the lowlands is monotonous. በቆላው ፡ አገር ፡ ያለው ፡ የመሬት ፡ መልክ ፡ ላይን ፡
ይሰለቻል
The lunar landscape has only recently been explored. የጨረቃ ፡ ገጽ ፡ የተመረመረው ፡ በቅር
ብ ፡ ብቻ ፡ ነው

**landslide** ናዳ
The road is blocked by a landslide. መንገዱ ፡ በ
ናዳ ፡ ተዘግቷል

**land tenure** የመሬት ፡ ይዞታ
Land tenure in the south is very complicated. በደቡብ ፡ ክፍል ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ የተወሳሰበ ፡
ነው

**lane**
1. የእግር ፡ መንገድ. A narrow lane leads from the road to his house. ጠባብ ፡ የእግር ፡ መንገድ ፡
ከመንገዱ ፡ እስከ ፡ እሱ ፡ ቤት ፡ ይወስዳል
2. ጠባብ ፡ መንገድ. A car drove down the muddy lane. መኪና ፡ በጨቀየው ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡
ተጓዘ

**language**
1. ቋንቋ. He speaks a foreign language. የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ይናገራል
2. ቃላት. It is difficult to understand the language of chemistry. የኬሚስትሪን ፡ ቃላት ፡
ለመረዳት ፡ ያስቸግራል

**bad language** የብልግና ፡ ቃላት
Don't use bad language with children around! ልጆች ፡ ባሉበት ፡ የብልግና ፡ ቃላት ፡ አትናገር

**languid** ልፍስፍስ
Hot weather makes people languid. ሞቃት ፡ አየ
ር ፡ ልፍስፍስ ፡ ያደርጋል

**languidly** እየተልፈሰፈሰ
The servant moved languidly toward me when I came in. አሽከሩ ፡ ስገባ ፡ እየተልፈሰፈሰ ፡ ወደ
ኔ ፡ መጣ
*He opened his eyes languidly and then fell back asleep. እንቅልፍ ፡ እያንገላጀጀው ፡ ዓይኑ
ን ፡ ከፍቶ ፡ ተመልሶ ፡ ተኛ

**languish**
1. ማቀቀ. He languished in prison. በእስር ፡ ቤት ፡
ማቀቀ
2. ጠወለገ. The roses languished in the summer heat. ጽጌሬዳዎቹ ፡ ከበጋው ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡
ጠወለጉ
3. ተቀነሰ. His vigilance never languished. ንቃቱ ፡ ምንጊዜም ፡ አልተቀነሰ

**languish for** ናፈቀ
The exiles languished for their native land. ስደተኞቹ ፡ የትውልድ ፡ አገራቸውን ፡ ናፈቁ

**languor, fill with ~, cause ~** አዝለፈለፈ
The intense heat filled the travelers with languor. ኃይለኛው ፡ ሙቀት ፡ መንገደኞቹን ፡ አዝ
ለፈለፋቸው
A long illness causes languor. ረጅም ፡ ሕመም ፡
ያዝለፈልፋል

**lank**
1. ቀጥ ፡ ያለ. Her lank hair does not make her look pretty. ቀጥ ፡ ያለው ፡ ጸጉሯ ፡ ቆንጆ ፡ አያ
ስመስላትም
2. ረጅም ፡ ቀጭን. A lank boy was leaning against the wall. ረጅም ፡ ቀጭን ፡ ልጅ ፡ ግ
ድግዳውን ፡ ተደግፎ ፡ ነበር

**lantern** ፋኖስ
Hang out a lantern so people won't fall in the hole. ሰዎች ፡ ከጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ እንዳይወ
ድቁ ፡ ፋኖስ ፡ አንጠልጥል

**lap** (lapped), v. ገረፈ
Waves lapped the shoreline. ሞገድ ፡ የባሕሩን ፡
ጠረፍ ፡ ገረፈው

**lap against** መታ ፡ አደረገ
The waves lapped against the side of the boat. ሞገዱ ፡ የጀልባውን ፡ ጐን ፡ መታ ፡ አደረገ

**lap over** ተደራረበ
One session lapped over into the next one. አንዱ ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፡ ከሚቀጥለው ፡ ጋር ፡ ተደራረበ

**lap up** ላስ ፡ አደረገ
The kitten lapped up the milk. የድመቷ ፡ ግልገ
ል ፡ ወተቱን ፡ ላስ ፡ አደረገችው

**lap** (n.)
1. ጭን. She held the baby in her lap. ልጁን ፡
እጭኗ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠች
2. ዙር. He was in the lead by five yards in the first lap. የመጀመሪያ ፡ ዙር ፡ ላይ ፡ ባምስት ፡ ያር
ድ ፡ እርቀት ፡ ይመራ ፡ ነበር

**in the lap of** በ - - - እጅ
His fate was in the lap of the gods. ዕድሉ ፡ በአ
ማልክት ፡ እጅ ፡ ነበር

**lapel** ኮሌታ
He is wearing a flower in his lapel. ኮሌታው ፡
ላይ ፡ አበባ ፡ አድርጓል

**lapse** (v.)
1. ተረሳ. Many local customs have lapsed in this century. በዚህ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ብ
ዙ ፡ ያገር ፡ ልማዶች ፡ ተረስተዋል

2. አለቀ. If I do not pay this premium my insurance policy will lapse. ክፍያዬን ፡ ካልከፈልኩ ፡ ኢንሹራንሴ ፡ ያልቃል
3. ጠፋ. The boy's interest soon lapsed. የልጁ ፡ ፍላጎት ፡ ያኔውኑ ፡ ጠፋ
*He lapsed into the bad habits he had before. ታጥቦ ፡ ጭቃ ፡ ሆነ

**lapse into ruin**
The house lapsed into ruin. ቤቱ ፡ እያደረ ፡ ፈረሰ

**let lapse** (= intr.) ተላለፈ(በት)
+Don't let your policy lapse! የሕይወት ፡ ዋስትና ፡ ኮንትራት ፡ ክፍያ ፡ እንዳይተላለፍብህ
[See also 'silence']

**lapse** (n.) መዛባት
Any lapse from true belief will be punished by the church. ከእውነተኛው ፡ እምነት ፡ መዛባት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያስቀጣል
*The lapse of local customs is due to contact with the city. ያገር ፡ ልማድ ፡ እየጠፋ ፡ የሚሄደው ፡ ከከተማ ፡ ጋር ፡ በሚደረገው ፡ ግንኙነት ፡ ነው

**lapse of memory** ያለማስታወስ ፡ ችግር
He suffers from an occasional lapse of memory. አንዳንዴ ፡ ያለማስታወስ ፡ ችግር ፡ አለበት

**lapse of time**
*A long lapse of time is necessary before they will forget. ነገሩን ፡ ከመርሳታቸው ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ማለፍ ፡ አለበት

**lapse of (the) tongue** ምላስ ፡ ሲያድጥ
A lapse of the tongue may easily be overlooked. ምላስ ፡ ሲያድጥ ፡ በቀላሉ ፡ ሊታለፍ ፡ ይችላል

**after a lapse of** ካለፈ ፡ በኋላ
After a lapse of five years, the committee met again. አምስት ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ደርጉ ፡ እንደገና ፡ ተሰበሰበ

**larceny** ሌብነት
He was accused of larceny. በሌብነት ፡ ተከሰሰ

**lard** የአሳማ ፡ ጮማ
Fry the potatoes in lard! ድንቹን ፡ በአሳማ ፡ ጮማ ፡ ጥበሰው

**large,** (n.) **at ~** በጠቅላላው
The country at large approved of his reforms. ሕዝቡ ፡ በጠቅላላው ፡ ለውጡን ፡ ተቀበለው
*Bandits roam at large in the countryside. በገጠር ፡ ሽፍቶች ፡ እንደልባቸው ፡ ይዘዋወራሉ

**be at large** አልተያዘም
The thief is still at large. ሌባው ፡ ገና ፡ አልተያዘም

**large** (adj.)
1. ሰፊ. He built a large house. ሰፊ ፡ ቤት ፡ ሠራ
2. ግዙፍ. He is a large man, nearly six and a half feet tall. ግዙፍ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ቁመቱ ፡ ስድስት ፡ ጫማ ፡ ተኩል ፡ ሊሆን ፡ ምንም ፡ አይቀረው
3. ብዙ. She inherited a large fortune. ብዙ ፡ ሀብት ፡ ወረሰች
A man with a large family needs a house. ብዙ ፡ ቤተሰብ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ያስፈልገዋል
*This room is not large enough. ይህ ፡ ክፍል ፡ በቂ ፡ ስፋት ፡ የለውም

**large** (adv.) በትልልቁ
Don't write so large! እንደዚህ ፡ በትልልቁ ፡ አትጻፍ

**by and large** በጠቅላላው
By and large, the results were satisfactory. በጠቅላላው ፡ ውጤቱ ፡ አጥጋቢ ፡ ነበር
[See also 'by, consignment, measure, multitude, number, proportion, quantity, scale']

**largely** በጠቅላላው
That is largely incorrect. በጠቅላላው ፡ ስሕተት ፡ ነው
*He is largely to be blamed for the fight. ለጠቡ ፡ ምክንያት ፡ ከፍተኛው ፡ ጥፋት ፡ የሱ ፡ ነው

**largess** ለጋስነት
The duke's largess was remembered by the people for years. የመስፍኑ ፡ ለጋስነት ፡ በሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ይታወስ ፡ ነበር

**larva** እጭ
After the larva hatches, it becomes a butterfly. እጭ ፡ ከተፈለፈለ ፡ በኋላ ፡ ቢራቢሮ ፡ ይሆናል

**larynx** ማንቁርት
He has cancer of the larynx. የማንቁርት ፡ ነቀርሳ ፡ ይዞታል

**lascivious** ዝሙት ፡ የሚቀሰቅስ
Her lascivious dance was finally forbidden by the police. ዝሙት ፡ የሚቀሰቅስ ፡ ዳንሷ ፡ በመጨረሻ ፡ በፖሊስ ፡ ተከለከለ

**lash** (v.)
1. ገረፈ. He lashed the horse across the back with a whip. ፈረሱን ፡ ባለንጋ ፡ ጀርባውን ፡ ገረፈው
2. ቈላ. The lion lashed his tail in fury. አንበሳው ፡ በንዴት ፡ ጅራቱን ፡ ቈላ

3. መታ. The wind lashed the trees. ነፋስ ፡ ዛፎቹን ፡ መታቸው

**lash against** ደበደበ
The rain lashed against the windows. ውሽንፍሩ ፡ መስኮቱን ፡ ደበደበ

**lash into a frenzy** በጋለ ፡ ስሜት ፡ አነሣሣ
The speaker lashed the crowd into a frenzy. ተናጋሪው ፡ አድማጮቹን ፡ በጋለ ፡ ስሜት ፡ አነሣሣቸው

**lash out against** አጥብቆ ፡ ነቀፈ
The speaker lashed out against his opponent. ተናጋሪው ፡ ተቃዋሚውን ፡ አጥብቆ ፡ ነቀፈ

**lash together** አሰረ
Lacking nails, they lashed the two poles together with a rope. ምስማር ፡ ስላጡ ፡ ሁለቱን ፡ ዕንጨቶች ፡ በገመድ ፡ አሰሯቸው

**lash** (n.) ጅራፍ
He was given two lashes. ሁለት ፡ ጅራፍ ፡ ተገረፈ

**last** (v.)
1. ቆየ. The war lasted six years. ጦርነቱ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ቆየ
I am afraid this good weather won't last long. ይህ ፡ ጥሩ ፡ አየር ፡ ብዙ ፡ የሚቆይ ፡ አይመስለኝም
2. ዘላቂነት ፡ አለው. Stone lasts longer than wood. ከዕንጨት ፡ ይልቅ ፡ ድንጋይ ፡ ይበልጥ ፡ ዘላቂነት ፡ አለው
3. ዘለቀ. He is in with his boss, but he doubts it will last. ከአለቃው ፡ ጋር ፡ ስምም ፡ ናቸው ፡ ግን ፡ የሚዘልቅ ፡ መሆኑን ፡ ይጠራጠራል
4. በረከተ. This suit did not last at all. ይህ ፡ ልብስ ፡ አልበረከተም
5. ፈጀ. The examination of the witness lasted two hours. የምስክሩ ፡ ምርመራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ፈጀ
6. (= tr.) አቆየ. I do not think my money will last. ገንዘቤ ፡ የሚያቆየኝ ፡ አይመስለኝም
*We will enjoy ourselves while our money lasts. ገንዘባችን ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ እንደሰታለን

**last one** በቃ
We have enough food to last us three days. ለሦስት ፡ ቀን ፡ የሚበቃ ፡ ምግብ ፡ አለን

**last** (adj.)
1. የመጨረሻ. Saturday is the last day of the week. ቅዳሜ ፡ የሳምንቱ ፡ የመጨረሻ ፡ ቀን ፡ ነው
2. ያለፈ. There was much rain last May. ባለፈው ፡ ግንቦት ፡ ብዙ ፡ ዘነበ
3. ያለው ፡ ሁሉ. She spent her last cent on that dress. ያላትን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ ልብስ ፡ ጨረሰች
*This book is the last word on politics. ስለ ፡ ፖለቲካ ፡ ከሚገለጹት ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ የሚያኸል ፡ የለም
*This is the last thing one would expect from him. ይህ ፡ ከርሱ ፡ ይመጣል ፡ ተብሎ ፡ ፈጽሞ ፡ የማይጠበቅ ፡ ነገር ፡ ነው

**last** (adv.)
1. ከሁሉም ፡ መጨረሻ. He arrived last. ከሁሉም ፡ መጨረሻ ፡ መጣ
2. በመጨረሻ. I cannot speak last at the meeting. በስብሰባው ፡ ላይ ፡ በመጨረሻ ፡ መናገር ፡ አልችልም
I last heard from him in May. በመጨረሻ ፡ ከሱ ፡ የሰማሁት ፡ ባለፈው ፡ ግንቦት ፡ ነው

**last but not least** በመጨረሻው
Last but not least, I would like to mention the weather. በመጨረሻ ፡ ስለ ፡ አየሩ ፡ ጠባይ ፡ ልናገር ፡ እፈልጋለሁ

**(the) last thing**
*Eating is the last thing I feel like doing. መብላት ፡ በፍጹም ፡ አላሰኘኝም

**at last** በመጨረሻ
At last we reached Addis Ababa. በመጨረሻ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገባን

**at long last** ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ
At long last they granted us a raise. ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ደሞዝ ፡ ጨመሩልን

**next to the last** ከመጨረሻው ፡ በፊት ፡ ያለ
You will find it on the next to the last page. ከመጨረሻው ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ታገኘዋለህ

**see the last of someone**
*I hope I've seen the last of her. ዳግመኛ ፡ እንዳላያት ፡ እመኛለሁ

**to the last** እስከ ፡ መጨረሻ
He remained faithful to the last. እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ታማኝ ፡ ሆኖ ፡ ቆየ
[See also 'leg, moment, night, recourse, straw, word, year']

**lasting**
1. ዘላቂ. Our goal is lasting peace. ዓላማችን ፡ ዘላቂ ፡ ሰላም ፡ መመሥረት ፡ ነው
2. የዘለዓለም. Nothing can assure lasting happiness. የዘለዓለም ፡ ደስታን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም
3. ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ. The border dispute caused lasting dissension. የወሰኑ ፡ ክርክር ፡ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ ንትርክ ፡ አስከተለ

**be lasting** ዘለቄታ ፡ ነበረው
The settlement was not a lasting one. ስምምነቱ ፡ ዘለቄታ ፡ አልነበረውም

**Last Judgment** ዕለተ ፡ ምጽአት
At the Last Judgment all mankind will be tried. በዕለተ ፡ ምጽአት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ለፍርድ ፡ ይቀርባል

**lastly** በመጨረሻ
And lastly, we shall sum up what we learned. በመጨረሻም ፡ የተማርነውን ፡ እናጠናቅቃለን

**latch** መወርወሪያ
The door is closed with a latch. መዝጊያው ፡ በመወርወሪያ ፡ ተዘግቷል

**late** (adj.)
1. የመጨረሻ. The late edition of this paper appears at 3 P.M. የዚህ ፡ ጋዜጣ ፡ የመጨረሻው ፡ እትም ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ይወጣል
2. ሟች. Your late brother was a friend of mine. ሟቹ ፡ ወንድምህ ፡ ወዳጄ ፡ ነበር
3. (= adv.) ዘግይቶ. We had a late dinner last night. ትላንትና ፡ ማታ ፡ ዘግይተን ፡ እራት ፡ በላን
The late arrival of the train messed up our plans. የባቡሩ ፡ ዘግይቶ ፡ መድረስ ፡ ሐሳባችንን ፡ ሁሉ ፡ አቃወሰብን
4. (= adv.) ቆይቶ. We had a late winter this year. የዘንድሮ ፡ ክረምት ፡ ቆይቶ ፡ ገባ
5. (= adv.) እስከ ፡ ምሽቱ. The committee had late meetings this week. በዚህ ፡ ሳምንት ፡ ደርጉ ፡ እስከ ፡ ምሽቱ ፡ ይሰበሰብ ፡ ነበር
6. (= adv.) ወደ - - - መጨረሻ ፡ ገደማ. The leaves began to fall in late autumn. ወደ ፡ በልግ ፡ መጨረሻ ፡ ገደማ ፡ ቅጠሎች ፡ መርገፍ ፡ ጀመሩ

**late** (adv.) ዘግይቶ
She arrived late. ዘግይታ ፡ ደረሰች
Roses bloomed late last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ጽጌረዳዎች ፡ ዘግይተው ፡ አበቡ

**be late**
1. ዘገየ. The teacher chided him for being late. ስለዘገየ ፡ አስተማሪው ፡ ገሠጸው
2. (morning) አርፍዶ ፡ መጣ. He was late for school this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አርፍዶ ፡ መጣ
3. (afternoon, evening) ዘግይቶ ፡ መጣ. He was late for school this afternoon. ዛሬ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዘግይቶ ፡ መጣ
He was late for school this evening. ዛሬ ፡ ማታ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዘግይቶ ፡ መጣ
4. (evening) አመሸ. She came late in the evening. አምሽታ ፡ መጣች

**late in life** በዕድሜው ፡ ከጠና ፡ በኋላ
He married late in life. በዕድሜው ፡ ከጠና ፡ በኋላ ፡ አገባ

**as late as yesterday** ትናንት ፡ እንኳን
I saw him as late as yesterday. ትናንት ፡ እንኳን ፡ አይቼው ፡ ነበር

**at a late hour** አምሽቶ
They arrived at a late hour. አምሽተው ፡ መጡ

**(it is) getting late** ሌሊቱ ፡ ገፍቷል
It is getting late and I am getting sleepy. ሌሊቱ ፡ ገፍቷል ። እንቅልፍም ፡ ይዞኛል

**(be) in one's late (years)**
*The man over there is in his late fifties. እዚያ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ስድሳው ፡ ተጠግቷል

**in the late**
Gordon was killed in the late 1880's. ጎርዶን ፡ ወደ ፡ ፲፰፻፹ ዓ. ም. ገደማ ፡ ተገደለ

**in the late afternoon** ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ሊመሽ ፡ ሲል
In the late afternoon, the game ended. ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ሊመሽ ፡ ሲል ፡ ጨዋታው ፡ አለቀ

**of late** ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ
Of late, I have been hearing about you. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ስላንተ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ እሰማለሁ

**stay up late** አመሸ
Staying up late is harmful to health. ማምሸት ፡ ለጤንነት ፡ ጥሩ ፡ አይደለም

**too late** ዘግይቶ
He discovered the deception too late. የማታለል ፡ ሥራ ፡ መሆኑን ፡ ዘግይቶ ፡ ደረሰበት
[See also 'evening, night']

**latecomer** ዘግይቶ ፡ የመጣ
The latecomers were seated in the back of the room. ዘግይተው ፡ የመጡት ፡ ከኋላ ፡ ተቀመጡ

**lately**
1. በቅርቡ. We have had much rain lately. በቅርቡ ፡ ብዙ ፡ ዝናብ ፡ ነበር
2. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ. I haven't been feeling so well lately. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ጤና ፡ አጥቻለሁ
3. (= adj.) የጊዜው. The prices lately are prohibitive. የጊዜው ፡ የገበያ ፡ ውድነት ፡ አይደፈርም

**lateness**
*He was punished for his lateness. ስለዘገየ ፡ ተቀጣ

**latent** የተዳፈነ
He has a latent talent for the theater. ለቲያት ር ፡ የተዳፈነ ፡ ችሎታ ፡ አለው
The city is calm now, but violence is latent. ከተማው ፡ አሁን ፡ ጸጥ ፡ ብሏል ፤ ብጥብጡ ፡ ግን ፡ እንደተዳፈነ ፡ ነው

**later**
1. ሌላ. The meeting was deferred to a later date. ስብሰባው ፡ ለሌላ ፡ ቀን ፡ ተላለፈ
2. (= adv.) ከጊዜ ፡ በኋላ. The last part of the legend is a later accretion. የታሪኩ ፡ የመጨረ ሻ ፡ ክፍል ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ የተጨመረ ፡ ነው

**later** (adv.)
1. ኋላ. You will find out later. ኋላ ፡ ትደርስበታለህ
2. ከ - - በኋላ. One day later the letter came. ካንድ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ደብዳቤው ፡ ደረሰ
3. ወደፊት. Don't destroy that box; it may be useful later. ያንን ፡ ሣጥን ፡ አታበላሸው ፤ ወደፊ ት ፡ ይጠቅምህ ፡ ይሆናል

**later on**
1. በኋላ. Later on, he told me the whole story. በኋላ ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ነገረኝ
2. ከዚያ ፡ በኋላ. Later on, they went to Harar. ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ሄዱ
3. ውሎ ፡ አድሮ. Prudence can spare a person much difficulty later on. መጠንቀቅ ፡ ውሎ ፡ አ ድሮ ፡ አንድን ፡ ሰው ፡ ከብዙ ፡ ችግር ፡ ያድናል

**no later than** ከ - - - ሰዓት ፡ በፊት
Please be at the game no later than 3 o'clock! በጨዋታው ፡ ላይ ፡ ከዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ በፊት ፡ ተገኝ
[See also 'sooner']

**lateral** የጐን
The fish has lateral fins as well as dorsal ones. ዓሣው ፡ የጐን ፡ ክንፍና ፡ የጀርባ ፡ ክንፍ ፡ አለው

**latest**
1. በቅርቡ ፡ የወጣ. The latest cars come in all kinds of shapes. በቅርቡ ፡ የወጡ ፡ መኪናዎች ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ቅርጽ ፡ አላቸው
2. በቅርቡ ፡ የተሠራ. They scrapped their old machinery and imported the latest equipment. ያረጀውን ፡ መሣሪያ ፡ ጥለው ፡ በቅርቡ ፡ የተሠ ራውን ፡ መሣሪያ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ አስመጡ
3. በቅርቡ ፡ የተፈጸመ. The newspapers condemned foreign agents for the latest disturbances. በቅርቡ ፡ በተፈጸመው ፡ ብጥብጥ ፡ የው ጭ ፡ አገር ፡ አነሣሾች ፡ ተካፋይ ፡ በመሆናቸው ፡ ጋ ዜጦቹ ፡ ነቀፉዋቸው
4. የመጨረሻ. He bought a car of the latest model. የመጨረሻውን ፡ ሞዴል ፡ መኪና ፡ ገዛ
5. በጣም ፡ ዘመናዊ. Our planes are equipped with the latest instruments. አውሮፕላኖቻችን ፡ በጣም ፡ ዘመናዊ ፡ መሣሪያ ፡ አላቸው
6. አዳዲስ. His shop was stocked with the latest goods. ሱቁ ፡ ባዳዲስ ፡ እቃዎች ፡ ተሞል ቷል

**latest news** ትኩስ ፡ ወሬ
The latest news is broadcast over the radio in a special bulletin. ትኩሱ ፡ ወሬ ፡ በልዩ ፡ ማ ስታወቂያ ፡ በራዲዮ ፡ ይነገራል

**at the latest** ቢዘገይ ፡ ቢዘገይ
I will be there at ten o'clock at the latest. ብዘገይ ፡ ብዘገይ ፡ ባራት ፡ ሰዓት ፡ እዚያ ፡ እደርሳ ለሁ

**the latest** በቅርቡ
Have you heard the latest about the director? ስለ ፡ ዲሬክተሩ ፡ በቅርቡ ፡ ሰምተሃል ?

**lather** (vt.)
1. ሳሙና ፡ ቀባ. He lathers his face before shaving. ከመላጨቱ ፡ በፊት ፡ ፊቱን ፡ ሳሙና ፡ ይቀባዋል

**lather** (vi.) አረፋ ፡ ወጣው
Soap does not lather well in salt water. ሳሙና ፡ በጨውማ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ አረፋ ፡ አይወጣ ውም

**lather** (n.) የሳሙና ፡ አረፋ
He smeared the lather on his face. ፊቱን ፡ የሳሙ ና ፡ አረፋ ፡ ቀባው

**latitude**
1. ኬትሮንስ. Ethiopia is located in the low latitudes. ኢትዮጵያ ፡ በዝቅተኛው ፡ ኬትሮንስ ፡ ላ ይ ፡ ትገኛለች
2. የሐሳብ ፡ ነጻነት. Does your government allow much latitude in political belief? መንግ ሥታችሁ ፡ በፖለቲካ ፡ ጉዳይ ፡ ብዙ ፡ የሐሳብ ፡ ነጻነት ፡ ይሰጣል ?
3. ሥልጣን. The diplomat was given wide latitude in negotiating the treaty. ዲፕሎማቱ ፡ የውሉን ፡ ድርድር ፡ ለመነጋገር ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ሥል ጣን ፡ ተሰጥቶት ፡ ነበር
4. መፈናፈኛ. In negotiating with the strikers, we do not have much latitude. ሥራ ፡ ካቆሙ ት ፡ ጋር ፡ በምንነጋገርበት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ መፈ ናፈኛ ፡ የለንም

**latrine** ሽንት ፡ ቤት
There is no latrine in the rented house. እተከራ የው ፡ ቤት ፡ ሽንት ፡ ቤት ፡ የለም

**latter**
1. የኋለኛ. Two matters were mentioned at the

meeting: the former concerned politics, and the latter concerned war. በስብሰባው ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮች ፡ ተነሥተው ፡ ነበር ፤ የመጀመሪያው ፡ ፖለቲካ ፡ ነክ ፡ ሲሆን ፡ የኋለኛው ፡ ጦር ፡ ነክ ፡ ነው
2. ሁለተኛ. I will come to Ethiopia in the latter half of the year. በዓመቱ ፡ ሁለተኛ ፡ አጋማሽ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እመጣለሁ

**lattice** ርብራብ
The lattice was intertwined with vines. ርብራቡ ፡ ላይ ፡ የወይን ፡ ሐረግ ፡ ተጠምጥሞበታል

**laud** አሞገሰ
We lauded the writer for his excellent book. ደራሲውን ፡ ስለ ፡ ምርጥ ፡ መጽሐፉ ፡ አሞገስነው

**laudable** የሚመሰገን
Generosity is laudable. ደግነት ፡ የሚመሰገን ፡ ነው

**laugh** (v.) ሣቀ
He laughed when I told him my story. ታሪኬን ፡ ስነግረው ፡ ሣቀ

**laugh at** ሣቀ(በት)
People laugh at him because of his deformity. ሰዎች ፡ በአካሉ ፡ ጉደሎነት ፡ ይሥቁበታል

**laugh off** ችላ ፡ አለ
You cannot laugh off this matter. ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ችላ ፡ ልትለው ፡ አትችልም

**laugh** (n.), **break into a ~**
He broke into a laugh. ከት ፡ ብሎ ፡ ሣቀ

**evoke a laugh** አሣቀ
A good joke evokes a laugh. ጥሩ ፡ ቀልድ ፡ ያሥቃል

**laughable** አሥቂኝ
Did you see her laughable costume? አሥቂኝ ፡ ልብሷን ፡ አየህ ?

**laughing** ቀላል
Cancer is no laughing matter. የነቀርሳ ፡ በሽታ ፡ ቀላል ፡ አይደለም

**laughing stock** መሳለቂያ
He is the laughing stock of the village. የመንደሩ ፡ መሳለቂያ ፡ ነው

**laughter** ሣቅ
We heard loud laughter behind us. ከኋላችን ፡ ጮክ ፡ ያለ ፡ ሣቅ ፡ ሰማን

**break into laughter** በሣቅ ፡ ፈነዳ
Hereupon, the audience broke into laughter. በዚህም ፡ ጊዜ ፡ አድማጮቹ ፡ በሣቅ ፡ ፈነዱ
[See also 'gale, howl, roar, shake, tempest']

**launch**
1. ከፈተ. He launched a new business. አዲስ ፡ ንግድ ፡ ከፈተ
2. ጀመረ. The enemy launched an attack at dawn. ጠላት ፡ ጐሕ ፡ ሲቀድ ፡ ማጥቃት ፡ ጀመረ
3. መርቆ ፡ አንሳፈፈ. The government launched a new boat at Massawa. መንግሥት ፡ በምፅዋ ፡ አዲስ ፡ መርከብ ፡ መርቆ ፡ አንሳፈፈ
4. ወረወረ. The hunter launched a spear at the gazelle. አዳኙ ፡ በሚዳ ፡ ፍየሏ ፡ ላይ ፡ ጦር ፡ ወረወረ
5. ተኰሰ. The ships launched missiles into the air. መርከቦቹ ፡ ሚሳይሎችን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተኰሱ
[See also 'blow, threat']

**laundry**
1. ልብስ. Put the dirty laundry in this basket! ያደፈውን ፡ ልብስ ፡ እዚህ ፡ ቅርጫት ፡ ውስጥ ፡ ክተት
2. የታጠበ ፡ ልብስ. My laundry just came back. የታጠበው ፡ ልብሴ ፡ አሁን ፡ መጣልኝ
3. የልብስ ፡ ንጽሕና ፡ መስጫ. Where is the nearest laundry? ቅርቡ ፡ የልብስ ፡ ንጽሕና ፡ መስጫ ፡ የት ፡ ነው ?

**laureate** [በኪነ ፡ ጥበብና ፡ በሳይንስ ፡ ችሎታው ፡ የተመሰከረለትና ፡ ሽልማት ፡ ወይም ፡ ክብር ፡ የተሰጠው ፡ ሰው]

**laurel** [ለስላሳ ፡ ብልጭልጭ ፡ ቅጠል ፡ ያለው ፡ ሁልጊዜ ፡ ለምለም ፡ ዛፍ]

**lava** የእሳተ ፡ ገሞራ ፡ ቅልጥ ፡ ድንጋይ
The lava spread over the plain. የእሳተ ፡ ገሞራ ፡ ቅልጥ ፡ ድንጋይ ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ፈሶ ፡ ነበር

**lavatory** (lavatories) የመጸዳጃ ፡ ክፍል
In Filoha hospital there are many lavatories. በፍል ፡ ውኃ ፡ ሆስፒታል ፡ ብዙ ፡ የመጸዳጃ ፡ ክፍሎች ፡ አሉ

**lavish** (v.) አፈሰሰ
The rich man lavishes money on his wife. ባለጸጋው ፡ ሚስቱ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ያፈሳል

**lavish** (adj.)
1. አባካኝ. His son is lavish with money. ልጁ ፡ ገንዘብ ፡ አባካኝ ፡ ነው
2. (= adv.) እንዳገኘ. His lavish spending ruined the family. እንዳገኘ ፡ ገንዘብ ፡ ማውጣቱ ፡ ቤተሰቡን ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ጣለ
3. (= adv.) ከመጠን ፡ በላይ. He was lavish in his praise of me. ከመጠን ፡ በላይ ፡ አሞገሰኝ

*Lavish gifts will not purchase true friendship. የስጦታ ፡ ብዛት ፡ እውነተኛ ፡ ጓደኝነትን ፡ አይገዛም

**be lavish with** አልቈጠበም
The teacher is lavish with his time, and helps every student. መምህሩ ፡ ማንኛውንም ፡ ተማሪ ፡ ጊዜውን ፡ ሳይቈጥብ ፡ ይረዳል

**law**
1. ሕግ. A man must be punished if he breaks the law. አንድ ፡ ሰው ፡ ሕግን ፡ ከጣሰ ፡ መቀጣት ፡ አለበት
His son chose law as a profession. ልጁ ፡ የሕግን ፡ ሙያ ፡ መረጠ
2. ደንብ. The law of motion was discovered by Kepler. የእንቅስቃሴ ፡ ደንብ ፡ የተገኘው ፡ በኬፕለር ፡ ነው

**in the name of the law** በሕግ ፡ አምላክ
Stop in the name of the law! በሕግ ፡ አምላክ ፡ ቁም !

**practice law** በሕግ ፡ ሥራ ፡ ተሰማራ ፤ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ሠራ
How long do you have to study before you can practice law? በሕግ ፡ ሥራ ፡ ከመሰማራት ፡ በፊት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ መማር ፡ አለብህ ?
My son is practicing law. ልጄ ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ ነው

**lay down the law** ደንቡን ፡ በሚገባ ፡ አስረዳ
Lay down the law to your students, or you will not be able to teach them. ደንቡን ፡ ለተማሪዎችህ ፡ በሚገባ ፡ አስረዳ ፤ ያለዚያ ፡ ልታስተምራቸው ፡ አትችልም
[See also 'civil law, criminal law, martial law']

**law-abiding** ሕግ ፡ አክባሪ
I am a law-abiding citizen. ሕግ ፡ አክባሪ ፡ ዜጋ ፡ ነኝ

**law court** ፍርድ ፡ ቤት
There is no law court in this small city. እዚች ፡ ትንሽ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የለም

**lawful** ሕጋዊ
Is it lawful to forbid people from eating in the theater? ሰዎች ፡ ቲያትር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እንዳይበሉ ፡ መከልከል ፡ ሕጋዊ ፡ ነው ?
Who is the lawful heir to the throne? ሕጋዊ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ማን ፡ ነው ?

**lawgiver** ሕግ ፡ አውጪ
Solon was a famous Greek lawgiver. ሶሎን ፡ የታወቀ ፡ የግሪክ ፡ ሕግ ፡ አውጪ ፡ ነበር

**lawless**
1. ሕግ ፡ የለሽ. A lawless country creates trouble for itself. ሕግ ፡ የለሽ ፡ አገር ፡ በራሷ ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ ታመጣለች
2. ሕግ ፡ የሚጥስ. A lawless person should be punished. ሕግ ፡ የሚጥስ ፡ ሰው ፡ መቀጣት ፡ አለበት

**lawlessness** ሕግ ፡ መጣስ ፤ ሕግ ፡ ወጥነት
Lawlessness is inherent in rebellion. ሕግ ፡ መጣስ ፡ (ሕግ ፡ ወጥነት) ፡ የዐመፅ ፡ አንዱ ፡ ባሕርይ ፡ ነው

**lawmaker** ሕግ ፡ አውጪ
The lawmakers were asked to legislate against prostitution. ሕግ ፡ አውጪዎቹ ፡ ሴተኛ ፡ አዳሪነትን ፡ የሚቃወም ፡ ሕግ ፡ እንዲያስተላልፉ ፡ ተጠየቁ

**lawn** የግቢ ፡ መስክ
The lawn still has to be sprinkled. የግቢው ፡ መስክ ፡ አሁንም ፡ ውኃ ፡ መጠጣት ፡ አለበት

**lawsuit** ሙግት
Did he win the lawsuit? ሙግቱን ፡ ረታ ?

**lawyer**
1. ጠበቃ. The fee for hiring a lawyer is quite high. ጠበቃ ፡ ለመግዛት ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው
2. የሕግ ፡ ዐዋቂ. Ethiopia has many good lawyers to administer justice. ኢትዮጵያ ፡ ፍትሕን ፡ የሚያስፈጽሙ ፡ ጥሩ ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ አሏት

**lax**
1. ግድ ፡ የለሽ. He is rather lax in his work. በሥራው ፡ ግድ ፡ የለሽ ፡ ቢጤ ፡ ነው
2. ልል. He is lax with his children. በልጆቹ ፡ አያያዝ ፡ ልል ፡ ነው

**be lax with** አሞላቀቀ
She has always been much too lax with her children. ልጆቿን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ታሞላቅቃለች

**laxative** የሚያስቀምጥ ፡ መድኃኒት
The doctor prescribed a laxative for her. ሐኪሙ ፡ የሚያስቀምጥ ፡ መድኃኒት ፡ አዘዘላት

**laxity**
1. ቸልተኝነት. Laxity in the performance of duty is a punishable offense. በሥራ ፡ ላይ ፡ ቸልተኝነት ፡ የሚያስቀጣ ፡ ጥፋት ፡ ነው
2. አለመጠበቅ. Laxity in discipline created chaos in the class. የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አለመጠበቅ ፡ በክፍል ፡ ውስጥ ፡ ረብሻ ፡ ፈጠረ

**lay** (laid), vt.
1. አስቀመጠ. Lay the book on the table! መጽሐፉን ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ አስቀምጥ

2. ጣለ. The government laid taxes on tea. መንግሥት ፡ በሻይ ፡ ቅጠል ፡ ላይ ፡ ቀረጥ ፡ ጣለ
Ants lay eggs. ጉንዳን ፡ እንቁላል ፡ ይጥላል
3. ጣል ፡ አደረገ. He laid his hand on my shoulder. እጁን ፡ ትከሻዬ ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አደረገ
4. አወጣ. He laid careful plans before starting his business. ንግዱን ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ እቅዱን ፡ በጥንቃቄ ፡ አወጣ
5. አሰረ. The doctor laid many bandages on his wounded arm. ሐኪሙ ፡ በቈሰለው ፡ ክንዱ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ፋሻ ፡ አሰረለት
6. አቀረበ. He laid his case before the commission. ጉዳዩን ፡ ለኮሚቴው ፡ አቀረበ
7. አጠመደ. He laid a trap for his adversary. በባለጋራው ፡ ላይ ፡ ወጥመድ ፡ አጠመደ
8. አስታገሠ. A shower has laid the dust. ካፊያው ፡ አቧራውን ፡ አስታገሠው
9. አነጠፈ. Who will lay the rug? ምንጣፉን ፡ ማን ፡ ያነጥፈዋል ?
10. (= passive) ተዘረረ. +One blow laid him on the floor. ባንድ ፡ ምት ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ተዘረረ
*She lays great stress on education. ለትምህርት ፡ ከፍተኛ ፡ አስተያየት ፡ አላት

**lay** (vi.) እንቁላል ፡ ጣለ
Our hens are laying well. ዶሮቻችን ፡ እንቁላል ፡ ደኅና ፡ ይጥላሉ

**lay ahead** ወደፊት ፡ ደረሰ
He little knew what lay ahead. ወደፊት ፡ የሚደርሰውን ፡ ምንም ፡ አያውቅም ፡ ነበር

**lay aside**
1. ቈጠበ. It is advisable to lay aside money for a rainy day. ለችግር ፡ ጊዜ ፡ ገንዘብ ፡ መቈጠብ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው
2. አስቀመጠ. He laid aside a pretty penny. ከፍ ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ አስቀመጠ
3. ተወ. They laid aside their childish pastimes and behaved as adults. ጊዜያቸውን ፡ እንደ ፡ ሕፃናት ፡ በከንቱ ፡ ማጥፋት ፡ ትተው ፡ እንደ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ሆኑ

**lay down**
1. አስተኛ. Lay the baby down gently! ሕፃኗን ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ አስተኛት
2. በቅድሚያ ፡ ከፈለ. He laid down $500 toward the purchase of a car. መኪና ፡ ለመግዛት ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ በቅድሚያ ፡ ከፈለ
3. አፈሰሰ. The workmen are laying down a coat of asphalt on the street. ሠራተኞቹ ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ አስፋልት ፡ ያፈሳሉ
4. አወጣ. The minister laid down rigid rules concerning demonstrators. ሚኒስትሩ ፡ ስለ ፡ ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ ጥብቅ ፡ ሕግ ፡ አወጡ
5. አስረከበ. The defeated army had to lay down arms. ድል ፡ የተመታው ፡ ጦር ፡ መሣሪያውን ፡ ማስረከብ ፡ ነበረበት

**(be) laid down** ተወሰነ
The prices are laid down by the government. ዋጋዎቹ ፡ በመንግሥት ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው

**lay for** አድፍጦ ፡ ጠበቀ
They laid for him at the corner. መታጠፊያው ፡ ላይ ፡ አድፍጠው ፡ ጠበቁት

**lay in** አከማቸ
Some animals lay in food for the winter. አንዳንድ ፡ እንስሳ ፡ ለክረምት ፡ የሚሆናቸውን ፡ ምግብ ፡ ያከማቻሉ

**lay off** ቀነሰ
He laid off his workers when he ran out of work for them to do. የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ ስለጠፋ ፡ ሠራተኞቹን ፡ ቀነሰ

**lay on**
1. ተደባደበ. When the mob became unruly, the police began to lay on. ሕዝቡ ፡ ሥርዓት ፡ አልጠብቅ ፡ ሲል ፡ ፖሊስ ፡ መደባደብ ፡ ጀመረ
2. ቀባ. The painter laid the paint on with a wide brush. ቀለም ፡ ቀቢው ፡ በሰፊ ፡ ብሩሽ ፡ ቀለም ፡ ቀባ

**lay open**
1. በግልጽ ፡ እንዲታይ ፡ አደረገ. The cut of the knife laid open his intestines. በጩቤ ፡ የተሸረከተው ፡ ሆዱ ፡ አንጀቱን ፡ በግልጽ ፡ እንዲታይ ፡ አደረገው
2. አጋለጠ. The arrest laid open a plot to kill the governor. የሰውዬው ፡ መያዝ ፡ ገዢውን ፡ ለመግደል ፡ የተደረገውን ፡ ሴራ ፡ አጋለጠ

**lay (oneself) open to** ራሱን ፡ አጋለጠ
He laid himself open to criticism. ለነቀፌታ ፡ ራሱን ፡ አጋለጠ
*He laid himself open to a charge of theft. በሌብነት ፡ ሊያስከስሰው ፡ የሚችል ፡ ሥራ ፡ ሠራ

**lay out**
1. አወጣ. How much did you lay out for me? ምን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ አወጣህልኝ ?
2. አዘጋጀ. She laid out the clothes I am to wear for my graduation. ለምረቃው ፡ በዓል ፡ የምለብሰውን ፡ ልብሴን ፡ አዘጋጀች

**(be) laid out** ተቀየሰ
These streets are well laid out. እነዚህ ፡ መንገዶች ፡ በደንብ ፡ የተቀየሱ ፡ ናቸው

**lay over** አደረ
We will have to lay over in Dire Dawa on our way to Djibouti. ወደ ፡ ጅቡቲ ፡ ስንሄድ ፡ ድሬ ፡ ዳዋ ፡ ማደር ፡ አለብን

**(be) laid over** ተላለፈ
The vote was laid over until next week. ድምፅ ፡ የመስጠቱ ፡ ጉዳይ ፡ እስከሚቀጥለው ፡ ሳምንት ፡ ተላለፈ

**lay to rest** ቀበረ
They laid him to rest last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ቀበሩት

**lay up** አከማቸ
He laid up a surplus of food for the winter. ለክረምት ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ምግብ ፡ አከማቸ
[See also various nouns and adjectives combined with 'lay', such as 'ambush, claim, low']

**lay, see lie**

**lay** (adj.) የተራ ፡ ሰው
In legal matters, it is better to have expert advice than lay opinion. በሕግ ፡ ጉዳዮች ፡ ከተራ ፡ ይልቅ ፡ የዐዋቂን ፡ ሰው ፡ ምክር ፡ መጠየቅ ፡ ይሻላል

**layer**
1. ደለል. Everything was covered with a heavy layer of sand. ሁሉም ፡ ነገር ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ያሸዋ ፡ ደለል ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር
2. ተደራቢ. Put another layer of paper over it! ከበላዩ ፡ ሌላ ፡ ተደራቢ ፡ ወረቀት ፡ አስቀምጥበት
*There is a heavy layer of dust on the table. ጠረጴዛው ፡ አቧራ ፡ ብቻ ፡ ነው

**form a (thick) layer** ተጋገረ
The ice formed a thick layer over the ground. በረዶው ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ ተጋገረ
[See also 'mud']

**layman**
1. ተራ ፡ ሰው. Even a layman can understand that. ተራ ፡ ሰው ፡ እንኳን ፡ ይህንን ፡ ሊረዳው ፡ ይችላል
2. መሃይምን. Laymen may not enter the sanctuary. መሃይምናን ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ አይገባቸውም

**layout**
1. አቀማመጥ. The layout of the factory makes the work easier. የፋብሪካው ፡ አቀማመጥ ፡ ሥራውን ፡ ቀላል ፡ ያደርገዋል
2. አቀያየስ. The layout of the streets is quite attractive. የመንገዱ ፡ አቀያየስ ፡ በጣም ፡ ያስደስታል

**layover** ማረፍ
A layover at Athens is necessary for travelers coming to Ethiopia from Europe. ከአውሮፓ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚመጡት ፡ መንገደኞች ፡ አቴን ፡ ላይ ፡ ማረፍ ፡ ያስፈልጋቸዋል

**laziness** ስንፍና
Laziness makes us all idlers. ስንፍና ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ያደርገናል

**lazy**
1. ሰነፍ. The teacher beat the lazy boy. መምህሩ ፡ ሰነፉን ፡ ልጅ ፡ መታው
2. ዝግተኛ. A lazy stream winds through the meadow. ዝግተኛ ፡ ምንጭ ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ይጠማዘዛል
3. የሚጫጫን. It was a hot, lazy day. ሞቃትና ፡ የሚጫጫን ፡ ቀን ፡ ነበር

**be lazy** ሰነፈ
Don't be so lazy! እንደዚህ ፡ አትስነፍ !

**leach** ለይቶ ፡ አጠበ
The rain has leached the salt from the soil. ዝናቡ ፡ ጨውን ፡ ካፈሩ ፡ ለይቶ ፡ አጥቦታል

**lead** (led), vt.
1. መራ. A general is leading the army. ጄኔራሉ ፡ ጦሩን ፡ ይመራል
2. አዛዥ ፡ ነበር. He led the Allied forces during the war. በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ጓዶች ፡ ኀይል ፡ አዛዥ ፡ ነበር
3. ሳበ. The boy led the horse by the reins. ልጁ ፡ ፈረሱን ፡ በልጓም ፡ ሳበው
4. ከፈተ. He led the dance. ዳንሱን ፡ ከፈተ

**lead** (vi.)
1. መራ. You lead; we'll follow. አንተ ፡ ምራ ፤ እኛ ፡ እንከተላለን
2. ቀደመ. This horse is leading in the race. ይህ ፡ ፈረስ ፡ ተወዳዳሪዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ቀድሟል
3. ወሰደ. This road leads to the city. ይህ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ይወስዳል
4. የ - - - ቁንጮ ፡ ነው. In arithmetic he is way down in the class, but in history he leads. በሒሳብ ፡ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ ሲሆን ፡ በታሪክ ፡ ግን ፡ የክፍሉ ፡ ቁንጮ ፡ ነው

**lead across** መርቶ ፡ አሻገረ
The dog led the blind man across the street. ውሻው ፡ ዓይነ ፡ ስውሩን ፡ ሰው ፡ መርቶ ፡ መንገዱን ፡ አሻገረው

**lead around to**
*You can lead him around to your point of view if you deal with him shrewdly. ካወቅህበት ፡ በሐሳብህ ፡ እንዲስማማ ፡ ልታደርገው ፡ ትችላለህ

**lead (a) life** ኖረ
He leads a lonely life in the country. ብቻውን ፡ በገጠር ፡ ይኖራል

**lead off** ንግግሩን ፡ ጀመረ

He led off by saying, "Gentlemen, we must unite". « ክቡራን ፤ መተባበር ፡ አለብን » ፡ በ ማለት ፡ ንግግሩን ፡ ጀመረ

**lead on**

*She led him on to think that she would eventually accept his proposal of marriage. በመጨረሻ ፡ ታገባኛለች ፡ የሚል ፡ እምነት ፡ አሳደረች በት

**lead (to)**

1. አስከተለ. Do not spit in public since it leads to the communication of disease. የበሽታ ፡ መተላለፍን ፡ ስለሚያስከትል ፡ ባደባባይ ፡ ምራቅህን ፡ አትትፋ

2. አስቻለ. The information you gave us led to his arrest. የሰጠኸን ፡ መረጃ ፡ እሱን ፡ ለመያዝ ፡ አስቻለን

3. አደረሰ. The clash between the workers and the factory owner led to a strike. በሠራተኞቹና ፡ በፋብሪካው ፡ ባለቤት ፡ መካከል ፡ የተነሣው ፡ ግጭት ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ማቆም ፡ አደረሰ

4. አስገኘ. Hard work leads to success. ጠንክሮ ፡ መሥራት ፡ ፍሬ ፡ ያስገኛል

5. እንድ + imperfect + አደረገ. Subsequent events led him to reconsider his position. ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ የመጡት ፡ ጉዳዮች ፡ ሐሳቡን ፡ እንደገና ፡ እንዲያስብበት ፡ አደረጉት

6. እንድ + imperfect + ገፋፋ. Her anxiety about succeeding led her to work hard. ካላማዋ ፡ ለመድረስ ፡ ያላት ፡ ጉጉት ፡ ጠንክራ ፡ እንድትሠራ ፡ ገፋፋት

*Where will all this arguing lead to? ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጭቅጭቅ ፡ መጨረሻው ፡ ምንድነው ?

**lead up**

1. አደረሰ. The latest events led up to the war. በቅርቡ ፡ የተደረጉት ፡ ነገሮች ፡ ከጦርነት ፡ አደረሱ

2. አወጣ. A circular stairway leads up to the balcony. የሚጠመዛዘዘው ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ሰገነት ፡ ያወጣል

**lead (the) way**

1. መራ. I will lead the way, and you follow. እኔ ፡ እመራለሁ ፤ አንተ ፡ ተከተል

2. ጥርጊያ ፡ ከፈተ. Ethiopia led the way to African independence. ኢትዮጵያ ፡ ለአፍሪካ ፡ ነጻነት ፡ ጥርጊያ ፡ ከፈተች

[See also 'astray, blow, command, dog, existence, nose']

**lead** (rhymes with 'bead'), n.

1. ቀዳሚነት. Russia is trying to reduce the American lead in the space race. ሩስያ ፡ በጠፈር ፡ እሽቅድምድም ፡ የአሜሪካንን ፡ ቀዳሚነት ፡ ለመቀነስ ፡ ትሞክራለች

2. ፍንጭ. The footprints were a lead in solving the crime. የእግር ፡ ዱካዎች ፡ የወንጀሉን ፡ ሁኔታ ፡ ለመረዳት ፡ ፍንጭ ፡ ሆኑ

**be in the lead** መራ

He was in the lead by five yards in the first lap. የመጀመሪያ ፡ ዙር ፡ ላይ ፡ ባምስት ፡ ያርድ ፡ እርቀት ፡ ይመራ ፡ ነበር

**follow the lead** ተመራ

He usually follows his sister's lead. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በእኅቱ ፡ ይመራል

**take the lead**

1. ቀደመ. He took the lead in the race. በሩጫ ፡ ቀደመ

2. ቀዳሚነት ፡ ያዘ. Take the lead, and keep it! ቀዳሚነቱን ፡ እንደ ፡ ያዝህ ፡ አትልቀቅ

**lead** (rhymes with 'dead'), n. እርሳስ.

Is this pipe made of lead? ይህ ፡ ቧምቧ ፡ ከእርሳስ ፡ የተሠራ ፡ ነው ?

**leaden** ከእርሳስ ፡ የተሠራ

The leaden coffin is very heavy. ከእርሳስ ፡ የተሠራው ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ነው

**leaden spirit** ከባድ ፡ ሐዘን

It was easy to understand the team's leaden spirit after the defeat. ከተሸነፈ ፡ በኋላ ፡ ቡድኑ ፡ የደረሰበትን ፡ ከባድ ፡ ሐዘን ፡ ለመረዳት ፡ ቀላል ፡ ነበር

**be leaden**

*His legs were leaden from fatigue. ከድካም ፡ የተነሣ ፡ እግሩን ፡ ማንሣት ፡ አቅቶታል

**leader**

1. መሪ. The leaders of all parties were present at the conference. የፓርቲው ፡ ሁሉ ፡ መሪዎች ፡ በስብሰባው ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ ነበር

Who is the leader of the group? የጓዱ ፡ መሪ ፡ ማነው ?

2. አለቃ. The police arrested the leader of the gang. ፖሊሶቹ ፡ የዱርዬዎቹን ፡ አለቃ ፡ ያዙት

**leadership**

1. መሪነት. Leadership is not a common virtue. መሪነት ፡ ሁሉ ፡ የሚያገኘው ፡ ጸጋ ፡ አይደለም

2. መሪዎች. The union leadership agreed to arbitrate. የማኅበሩ ፡ መሪዎች ፡ ድርድር ፡ ለማድረግ ፡ ተስማሙ

**leading**

1. ዓቢይ. The leading thought was .... ዓቢይ ፡ ሐሳቡ ፡ .... ነበር

2. የታወቀ. Many leading scientists live in California. ብዙ ፡ የታወቁ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቆች ፡ ካሊፎርንያ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ
3. (= adv.) ፊት ፡ ቀድሞ. He rode in the leading car. ፊት ፡ ቀድሞ ፡ እሚሄደው ፡ መኪና ፡ ውስጥ ፡ ነበር

**leading man** መሪ ፡ ተዋናይ
The leading man in the play was applauded. በቲያትሩ ፡ ውስጥ ፡ መሪው ፡ ተዋናይ ፡ ተጨበጨበለት
[See also 'light, spirit']

**leading article** ርእስ ፡ አንቀጽ ፤ ዓቢይ ፡ ጽሑፍ
The leading article in today's paper is good. የዛሬው ፡ ጋዜጣ ፡ ርእስ ፡ አንቀጽ ፡ (ዓቢይ ፡ ጽሑፍ) ፡ ጥሩ ፡ ነው

**leaf** (v.) ቅጠል ፡ አወጣ ፤ ለመለመ
The trees began to leaf in October. ዛፎቹ ፡ በጥቅምት ፡ ቅጠል ፡ ማውጣት ፡ (መለምለም) ፡ ጀመሩ

**leaf through** አገላበጠ
I am only leafing through the book. እንዲሁ ፡ መጽሐፉን ፡ አገላብጣለሁ

**leaf** (leaves), n. ቅጠል
There is not a leaf on that tree. በዛፉ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ቅጠል ፡ የለም
Someone tore a leaf from the book. አንድ ፡ ሰው ፡ ከመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ቅጠል ፡ ቀዶ ፡ አውጥቷል

**turn over a new leaf** ተሻሻለ
He promised to turn over a new leaf. እሻሻላለሁ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ ገባ
[See also 'put forth, send forth, shoot forth']

**leaflet** ጽሑፍ
People passed out leaflets everywhere. ሰዎች ፡ በየቦታው ፡ ጽሑፍ ፡ ዐደሉ

**league** ማኅበር
There is a league of war-haters here. ጦርነትን ፡ የሚቃወሙ ፡ ሰዎች ፡ ማኅበር ፡ እዚህ ፡ አለ

**League of Nations** የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር
The League of Nations died in 1935. የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ በ፲፱፻፳፯ ዓ. ም. አበቃ

**leak** (vt.) በድብቅ ፡ ነገረ
The minister leaked the secret to the press. ሚኒስትሩ ፡ ለጋዜጠኞች ፡ በድብቅ ፡ ምስጢር ፡ ነገራቸው

**leak** (vi.)
1. አፈሰሰ. This pot leaks. ይህ ፡ ማሰሮ ፡ ያፈሳል
2. ውኃ ፡ አስገባ. The ship was leaking badly. መርከቡ ፡ ውኃ ፡ በጣም ፡ ያስገባ ፡ ነበር
3. ተነፈሰ. I patched the tire, but it still leaks. ጎማውን ፡ ለጥፌው ፡ ነበር ፡ ግን ፡ አሁንም ፡ ይተነፍሳል
4. ሰርጎ ፡ ገባ. Water leaked into the boat. ውኃው ፡ ጀልባው ፡ ውስጥ ፡ ሰርጎ ፡ ገባ

**leak in**
*The rain is leaking in. ቤቱ ፡ ያፈሳል

**leak out**
1. ተንጠባጠበ ፤ እየፈሰሰ ፡ ወጣ. Water is leaking out because the pipe is broken. ቧምቧው ፡ ስለተሰበረ ፡ ውኃው ፡ ይንጠባጠባል
The drum gets lighter as the water leaks out. ውኃው ፡ እየፈሰሰ ፡ ሲወጣ ፡ በርሚሉ ፡ እየቀለለ ፡ ይሄዳል
2. ተሰራጨ. The story leaked out somehow. ወሬው ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ ተሰራጨ
[See also 'spring']

**leak** (n.) ቀዳዳ ፤ የሚያፈስ ፡ ቀዳዳ
There is a leak in the boat. ጀልባው ፡ ቀዳዳ ፡ አለው
He plugged the leak with a rag. የሚያፈሰውን ፡ ቀዳዳ ፡ ጨርቅ ፡ ወተፈው
[See also 'stop']

**leakage**
1. ፍሳሽ. The leakage results in a loss of several gallons a day. ፍሳሹ ፡ በቀን ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ጋሎን ፡ ይደርሳል
2. ሳይታወቅ ፡ መውጣት. The leakage of military information helps the enemy. የወታደራዊ ፡ ምስጢር ፡ ሳይታወቅ ፡ መውጣት ፡ ጠላትን ፡ ይረዳል

**lean** (vt.) አስደገፈ
Don't lean your chair against the wall! ወንበርህን ፡ ከግድግዳው ፡ ላይ ፡ አታስደግፈው

**lean** (vi.)
1. ዘመመ. There is a famous tower in Italy that leans. በኢጣልያ ፡ ውስጥ ፡ የታወቀ ፡ የዘመመ ፡ ግንብ ፡ አለ
2. ተደገፈ ፤ ተደግፎ ፡ ቆመ. The log was leaning against the wall. ግንዱ ፡ ግድግዳው ፡ ላይ ፡ ተደግፎ ፡ ነበር
The sailor was leaning against the mast. መርከበኛው ፡ የመርከቡን ፡ ምሰሶ ፡ ተደግፎ ፡ ቆሞ ፡ ነበር
3. ደገፍ ፡ አለ. The shepherd leaned on his staff to rest. እረኛው ፡ ለማረፍ ፡ ዘንጉ ፡ ላይ ፡ ደገፍ ፡ አለ
4. አዘነበለ. Her interests lean toward sports. ፍላጎቷ ፡ ወደ ፡ እስፖርት ፡ ያዘነብላል

**lean backwards** ወደ ፡ ኋላ ፡ ደገፍ ፡ አለ
He leaned backwards in his chair to make himself more comfortable. ወንበሩ ፡ ላይ ፡ ይበል ጥ ፡ ተመቻችቶ ፡ ለመቀመጥ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ደገፍ ፡ አለ

**lean forward** አንገቱን ፡ ብቅ ፡ አደረገ
If you lean forward you can see him. አንገትህን ፡ ብቅ ፡ ብታደርግ ፡ ታየዋለህ

**lean (the) head** ደገፍ ፡ አለ
Lean your head on my shoulder! ትከሻዬ ፡ ላይ ፡ ደገፍ ፡ በል

**lean on**
1. ተደገፈ. He was leaning on the table. ጠረጴዛ ውን ፡ ተደግፎ ፡ ነበር
2. ተመረኰዘ. He leaned on his walking stick. ዘንጉን ፡ ተመረኰዘ
3. በ -- ትከሻ ፡ ላይ ፡ ነው. John still leans on his parents. ዮሐንስ ፡ አሁንም ፡ በወላጆቹ ፡ ትከሻ ፡ ላ ይ ፡ ነው
*He leans on his friends for guidance. ለሚያደር ገው ፡ ሁሉ ፡ የጓደኞቹን ፡ ምክር ፡ ይጠይቃል

**lean out** ተንጠለጠለ
Don't lean out of the window! በመስኮቱ ፡ አት ንጠልጠል

**lean over** vi. (= vt.) አስጐነበሰ
+The trees leaned over in the wind. ነፋሱ ፡ ዛፎ ቹን ፡ አስጐንብሷቸዋል

**lean** (adj.) ቀጭን
He is very tall and lean. በጣም ፡ ረጅምና ፡ ቀጭ ን ፡ ነው

**lean meat** ብርንዶ
Do you want fat meat or lean? የምትፈልገው ፡ ጮማ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ብርንዶ ?

**lean year** የድርቅ ፡ ዓመት
It was a lean year for farmers. ይህ ፡ ዓመት ፡ ለ ገበሬዎች ፡ የድርቅ ፡ ዓመት ፡ ነበር

**leaning** (n.) ዝንባሌ
He has a leaning toward foreign languages. የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ለመማር ፡ ዝንባሌ ፡ አለው

**leap** (vt.) ዘለለ
The runner leaped the ditch. ሯጩ ፡ ጉድጓዱን ፡ ዘለለ

**leap** (vi.)
1. ዘለለ. Leap over the fence! በአጥሩ ፡ ላይ ፡ ዝ ለል
2. ወጣ. Tongues of flame were seen leaping into the air. የእሳት ፡ ነበልባል ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሲወጣ ፡ ይታይ ፡ ነበር
3. ዘሎ ፡ ወጣ. The cat leaped on the table. ድመቷ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ዘላ ፡ ወጣች
4. ቸኰለ. A scientist cannot leap to conclusions, but must test every hypothesis. ሳይንቲስ ት ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ አይቸኩልም ፤ ማንኛቸው ንም ፡ መላ ፡ ምት ፡ ሁሉ ፡ ይመረምራል ፡ እንጂ

**leap at** አፈፍ ፡ አደረገ
He leaped at the opportunity of going to Ethiopia. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመሄድ ፡ ያጋጠመ ውን ፡ ዕድል ፡ አፈፍ ፡ አደረገ

**leap to one's feet** ዘሎ ፡ ተነሣ
He leaped to his feet when the Emperor entered. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሲገቡ ፡ ዘሎ ፡ ተነሣ

**leap up** ወደላይ ፡ ዘለለ
The dog leaped up to catch the stick I threw. ውሻው ፡ የወረወርኩትን ፡ ዕንጨት ፡ ለመያዝ ፡ ወደላይ ፡ ዘለለ

**leap** (n.) ዝላይ
He cleared the ditch with one leap. ቦዩን ፡ በአን ድ ፡ ዝላይ ፡ ተሻገረው

**by leaps and bounds** በንዳፍታ
The lion covered the distance by leaps and bounds. አንበሳው ፡ በንዳፍታ ፡ መንገዱን ፡ ጨረሰ

**leap year** ዘመን ፡ ዮሐንስ
Last year was a leap year. ያለፈው ፡ ዓመት ፡ ዘመን ፡ ዮሐንስ ፡ ነበር
*When is the next leap year? ጳጉሜ ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ የሚኖረው ፡ መቼ ፡ ነው ?

**learn** (vt.)
1. ተማረ. He has not learned a thing. ምንም ፡ ነገር ፡ አልተማረም
I learned German in one year. ጀርመንኛ ፡ በ ንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ተማርኩ
2. ዐወቀ. He learned the truth too late. እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ያወቀው ፡ ዘግይቶ ፡ ነው
3. ለመደ. The baby has learned how to walk. ሕፃኑ ፡ መሬመድ ፡ ለምዷል
4. ደረሰ(በት). I accidentally learned the truth. እውነቱን ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ደረስኩበት

**learn** (vi.)
1. ሰማ. When did you learn of her illness? መታመሟን ፡ የሰማኸው ፡ መቼ ፡ ነው ?
2. ለመደ. She has never cooked, but she can learn. ምግብ ፡ ሠርታም ፡ አታውቅ ፤ ሆኖም ፡ ልትለምድ ፡ ትችላለች
3. ትምህርት ፡ ገባ(ው). +He learns quickly and gets good marks. ትምህርት ፡ ቶሎ ፡ ስለሚገባው ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ ያገኛል

**learn by heart** በቃል ፡ ያዘ
She learned the poem by heart. ግጥሙን ፡ በቃሏ ፡ ያዘችው

**come to learn** ዐወቀ
How did you come to learn where she is living? እሷ ፡ የምትኖርበትን ፡ ቦታ ፡ እንዴት ፡ ዐወቅህ ?

**learned** የተማረ
This professor is a very learned man. ይህ ፡ ፕሮፌሰር ፡ በጣም ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ ነው

**learner** ጀማሪ
This book is for learners. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ለጀማሪዎች ፡ ነው

**learning**
1. ትምህርት. Learning is very precious. ትምህርት ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው
2. ዐዋቂነት. The enormity of his learning surprised everyone. የዐዋቂነቱ ፡ ከፍተኛነት ፡ ሁሉን ፡ አስገረመ

**lease** (v.)
1. ተከራየ. The owner will not lease the apartment to noisy tenants. ባለቤቱ ፡ አፓርትማውን ፡ ጫጫታ ፡ ለሚያበዙ ፡ ሰዎች ፡ አያከራይም
2. ተኮናተረ. They have leased the hotel for five years. ሆቴሉን ፡ ላምስት ፡ ዓመት ፡ ተኮናተሩት

**lease** (n.) ኮንትራት
We had to sign a lease for one year. ቤቱን ፡ ስንከራየው ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ ኮንትራት ፡ መፈረም ፡ ነበረብን

**leash** (v.)
1. ማሰሪያ ፡ አደረገ. He leashed the dog before he went for a walk. ሽርሽር ፡ ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ ለውሻው ፡ ማሰሪያ ፡ አደረገ
2. ገታ. He leashed his anger and did not say a word. ንዴቱን ፡ ገቶ ፡ ምንም ፡ አልተናገረም
*They leashed the energy of the river with a dam. በውኃው ፡ ኀይል ፡ ለመጠቀም ፡ ወንዙን ፡ ገደቡት

**leash** (n) ማሰሪያ
He walks his dog without a leash. ውሻውን ፡ ያለ ፡ ማሰሪያ ፡ ይዞት ፡ ይዞራል

**be on a leash** ታሰረ
The dog was on a leash. ውሻው ፡ ታስሯል

**hold (keep) in leash** ገታ
Hold your temper in leash, or you'll get in trouble. ንዴትህን ፡ ግታ ፤ ያለዚያ ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ ትገባለህ

**least** ምንም ፡ ያህል + negative verb
I was least impressed by his poetry. በግጥሙ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልተደሰትኩም

**least of all**
1. በተለይም. None of you can complain, Charles least of all. ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ ማንም ፡ ሊያማርር ፡ አይገባም ፤ በተለይም ፡ ቻርልስ
2. በፍጹም + (negative verb). I would have expected that from you least of all. ይህንን ፡ ነገር ፡ አንተ ፡ ታደርገዋለህ ፡ ብዬ ፡ በፍጹም ፡ አላሰብኩም ፡ ነበር

**at least**
1. ቢያንስ ፡ ቢያንስ. He is at least as tall as you. ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ያንተን ፡ ያህል ፡ ይረዝማል
These shoes cost at least ten dollars. ይህ ፡ ጫማ ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ ያወጣል
2. ቢያንስ. At least make an attempt to pass your exam! ቢያንስ ፡ ፈተናውን ፡ ለማለፍ ፡ ሞክር
3. ያህል. There were at least a hundred people present. መቶ ፡ ያህል ፡ ሰው ፡ ነበር
4. የቀረው ፡ ቢቀር. He could at least have been courteous. የቀረው ፡ ቢቀር ፡ ትሕትና ፡ ማሳየት ፡ ይገባው ፡ ነበር
5. ሌላው ፡ ቢቀር. You may at least say 'thank you!' ሌላው ፡ ቢቀር ፡ እግዜር ፡ ይስጥልኝ ፡ ልትል ፡ ይገባል

**in the least** ትንሽም
It does not bother me in the least. ትንሽም ፡ አያስቸግረኝም

**not in the least** በፍጹም
Do you mind going with me? Not in the least. ከኔ ፡ ጋር ፡ ብትሄድ ፡ ቅር ፡ ይልሃል ? በፍጹም

**not the least**
1. ፈጽሞ. I haven't the least interest in the matter. ለነገሩ ፡ ፈጽሞ ፡ ፍላጎት ፡ የለኝም
2. ምንም. There is not the least wind today. ዛሬ ፡ ምንም ፡ ነፋስ ፡ የለም

**the least**
1. ቀላል. He argues over the least thing. በቀላል ፡ ነገር ፡ ይከራከራል
2. ከሁሉ ፡ አነስተኛ. Who did the least work? ከሁሉ ፡ አነስተኛ ፡ የሠራ ፡ ማነው ?
3. ትንሽ ፡ እንኳ. The least bit of dirt in a watch may make it stop. ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ትንሽ ፡ እንኳ ፡ የአቧራ ፡ ብናኝ ፡ ቢገባ ፡ ሊያቆመው ፡ ይችላል
4. አነስተኛ ፡ ነገር. That's the least you could do for him. ልታደርግለት ፡ የምትችለው ፡ አነስተኛው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው
5. ከሁሉ ፡ ያነሰ. All of us have little money,

but I have the least. ሁላችንም ፡ ያለን ፡ ገንዘብ ፡ ጥቂት ፡ ነው ፤ የኔ ፡ እንዲያውም ፡ ከሁሉ ፡ ያነሰ ፡ ነው

**the least of** የመጨረሻ ፡ አነስተኛ

The least of his crimes is robbery. እሱ ፡ ከፈጸማቸው ፡ ወንጀሎች ፡ ሁሉ ፡ የመጨረሻው ፡ አነስተኛ ፡ ዝርፊያ ፡ ነው

[See also 'last']

## leather ቆዳ

Shoes are made of leather. ጫማ ፡ ከቆዳ ፡ ይሠራል

**leather strap** ጠፍር

I tied it with a leather strap. በጠፍር ፡ አሰርኩት

**leather** (adj.) ከቆዳ ፡ የተሠራ

Leather gloves are expensive. ከቆዳ ፡ የተሠራ ፡ ጓንቲ ፡ ውድ ፡ ነው

## leathery

1. ቆዳማ. The elephant's trunk is long and leathery. የዝሆኑ ፡ ኩንቢ ፡ ረዥምና ፡ ቆዳማ ፡ ነው
2. ቆዳ ፡ ቢጤ. The covering of the chair is leathery. የመቀመጫው ፡ ሽፋን ፡ ቆዳ ፡ ቢጤ ፡ ነው

## leave (left), vt.

1. አስቀመጠ. Leave your hat and coat in the hall! ባርኔጣህንና ፡ ካፖርትህን ፡ መተላለፊያ ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጠው
2. ተወ. Did someone leave a message for me? መልእክት ፡ የተወልኝ ፡ ሰው ፡ አለ ?

Where did you leave your suitcase? ሻንጣህን ፡ የት ፡ ተውከው ?

He left his food on the plate. ምግቡን ፡ ሳይጨርስ ፡ ተወው

Leave the door open! በሩን ፡ ክፍት ፡ ተወው

Leave it to me! ለኔ ፡ ተወው

3. ለቀቀ. I am leaving the job. ሥራውን ፡ ልለቅ ፡ ነው
4. ተለየ. The boy left home when he was sixteen. ልጁ ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ሲሆነው ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ተለየ
5. አስቀረ. Leave some cake for me! ትንሽ ፡ ኬክ ፡ አስቀርልኝ

A long bout of illness left him weak and without money. የረዥም ፡ ጊዜ ፡ ሕመሙ ፡ ደካማና ፡ ድኻ ፡ አድርጎ ፡ አስቀረው

6. ሰጠ. This job does not leave me much leisure. ይህ ፡ ሥራ ፡ ምንም ፡ ትርፍ ፡ ጊዜ ፡ አይሰጠኝም
7. ወጣ. He left the room secretly. ከክፍሉ ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ወጣ

He left school before graduating. ሳይመረቅ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ወጣ

8. ጣለ. I left the matter in your hands. ጉዳዩን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ጥዬዋለሁ
9. ትቶ ፡ ሄደ. They left him for dead on the battlefield. ሞተ ፡ ብለው ፡ ከጦር ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ትተውት ፡ ሄዱ

He went away and left the child alone. ልጁን ፡ ብቻውን ፡ ትቶት ፡ ሄደ

The postman left a registered letter for you. ፖስተኛው ፡ በሬኮማንዴ ፡ የመጣ ፡ ደብዳቤ ፡ ትቶልሽ ፡ ሄደ

10. ጥሎ ፡ ሄደ. He is sad because his beloved left him. ወዳጁ ፡ ጥላው ፡ ስለሄደች ፡ አዝኗል
11. ተክቶ ፡ ሞተ. He left two sons and a daughter. ሁለት ፡ ወንድ ፡ ልጆችና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ተክቶ ፡ ሞተ
12. ትቶ ፡ ሞተ. He left his estate to one of the charities. ንብረቱን ፡ ላንድ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ትቶ ፡ ሞተ
13. አወረሰ. She left the house to her son. ቤቷን ፡ ለልጅዋ ፡ አወረሰች
14. አውርሶ ፡ ሞተ. He left a large legacy to his son. ለልጁ ፡ ብዙ ፡ ቅርስ ፡ አውርሶት ፡ ሞተ
15. (= be left) ቀረ. Three from seven leaves four. ከሰባት ፡ ሦስት ፡ ሲነሣ ፡ አራት ፡ ይቀራል

**leave** (vi.)

1. ሄደ. My father left yesterday for Europe. አባቴ ፡ ትናንት ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ሄደ
2. ተነሣ. The train leaves at two-thirty. ባቡሩ ፡ በስምንት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ይነሣል

**be left**

1. ተረፈ. Are there any tickets left for tonight? ለዛሬ ፡ ማታ ፡ የተረፈ ፡ ቲኬት ፡ አለ ?
2. ቀረ. When I pay all my debts, there will be nothing left. ዕዳዬን ፡ ሁሉ ፡ ስከፍል ፡ ምንም ፡ አይቀረኝም

**leave alone** ተወ

You'd better leave that alone! ጉዳዩን ፡ ብትተወው ፡ ይሻላል

**(be) left alone** ብቻውን ፡ ቀረ

I was left alone as before. እንደ ፡ በፊቱ ፡ ብቻዬን ፡ ቀረሁ

**(be) left back**

*He was left back in the third grade. ሦስተኛ ፡ ክፍል ፡ ደገመ

**leave behind** ትቶ ፡ ሄደ

We had to leave our trunk behind. ሣጥናችንን ፡ ትተን ፡ መሄድ ፡ ግድ ፡ ሆነብን

**leave lying around** አዝረከረከ

Don't leave your books lying around! መጽሐፎችህን ፡ አታዝረክርክ

**leave off** ተወ
Please leave off biting your nails! ጥፍርህን ፡ መብላት ፡ ተው
**leave on** አብርቶ ፡ ተወ
Someone left the lights on. አንዱ ፡ መብራቱን ፡ አብርቶ ፡ ትቶታል
**leave out**
1. ተወ. When you copy it, do not leave anything out. ጽሑፉን ፡ ስትገለብጥ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አትተው
2. ገደፈ. He left out two letters when he wrote the name. ስሙን ፡ ሲጽፍ ፡ ሁለት ፡ ፊደሎች ፡ ገደፈ
**leave out of** ከ --- ውስጥ ፡ አስቀረ
He always fights, so we left him out of the game. ሁልጊዜ ፡ ይጣላል ፤ ስለዚህ ፡ ከጨዋታው ፡ ውስጥ ፡ አስቀረነው
**(be) left out**
1. ተነጥሎ ፡ እንዲቀር ፡ ተደረገ. The children were left out of the group of students that was to go to Harar. ልጆቹ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ከሚሄደው ፡ የተማሪዎች ፡ ጓድ ፡ ተነጥለው ፡ እንዲቀሩ ፡ ተደረገ
2. ጐደለ. The hiatus in the old manuscript shows that something has been left out. ባረጀው ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ መጕደሉን ፡ ያሳያል
**(be) left over** ተረፈ
Nothing was left over after he finished eating. በልቶ ፡ ከበቃ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ አልተረፈውም ፡ ነበር
**(be) left to oneself** የሚቈጣጠር ፡ የለም
+The students were left to themselves during the holidays. በዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ተማሪዎችን ፡ የሚቈጣጠር ፡ የለም ፡ ነበር
*He wants to be left to himself. ሰው ፡ እንዳ ይደርስበት ፡ ይፈልጋል
[See also 'breathless, disorder, exhausted, gulf, impression, school, unmoved, unsaid, word']

**leave** (n.)
1. ፈቃድ. He has taken three months' leave. የሦስት ፡ ወር ፡ ፈቃድ ፡ ወስዷል
You have my leave to stay away from work tomorrow. ነገ ፡ ከሥራ ፡ ለመቅረት ፡ ፈቃድ ፡ ሰጥቼሃለሁ
2. ስንብት. After two years of work, I took a month's leave. ሁለት ፡ ዓመት ፡ ከሠራሁ ፡ በኋላ ፡ ላንድ ፡ ወር ፡ ስንብት ፡ ወሰድኩ
**leave of absence** ከሥራ ፡ የመቅረት ፡ ፈቃድ
He took a leave of absence for two months. ለሁለት ፡ ወር ፡ ከሥራ ፡ የመቅረት ፡ ፈቃድ ፡ ወሰደ
**leave-taking** የመሰነባበቻ ፡ ጊዜ
During the leave-taking, many tears were shed. በመሰነባበቻው ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተላቀሱ
**take leave** ተሰናበተ
He took his leave of the company. ከስብሰባው ፡ ተሰናበተ

**leaven** እርሾ
The leaven causes the bread to rise. እርሾው ፡ ዳቦውን ፡ ይነፋዋል

**leaves,** see **leaf**

**lectern** አትሮንስ
The speaker placed his notes on the lectern. ተናጋሪው ፡ ማስታወሻዎቹን ፡ አትሮንሱ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠ

**lecture** (v.) ትምህርት ፡ ሰጠ
He lectures on zoology at the university. በዩኒቨርሲቲው ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ እንስሳት ፡ ጥናት ፡ ትምህርት ፡ ይሰጣል
**lecture someone** ገሠጸ
The teacher lectured the boys for being lazy. አስተማሪው ፡ ተማሪዎቹ ፡ ስለሰነፉ ፡ ገሠጻቸው

**lecture** (n.) ንግግር
It was an interesting lecture. በጣም ፡ የሚያስደስት ፡ ንግግር ፡ ነበር
**give someone a lecture** ገሠጸ
He always gives us a lecture when we are late. በዘገየን ፡ ቍጥር ፡ ይገሥጸናል

**lecturer** ተናጋሪ
The audience hung on the lips of the lecturer. አዳማጮቹ ፡ ተናጋሪውን ፡ በተመስጦ ፡ አዳመጡት

**led,** see **lead**

**ledge** (የ)ገደል ፡ አፋፍ
The mountain climber obtained a precarious position on a narrow ledge. ተራራ ፡ ወጪው ፡ ቀጭን ፡ ገደል ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ አደገኛ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ይገኝ ፡ ነበር

**ledger** መዝገብ
He wrote the debts in a ledger. ያለበትን ፡ ዕዳ ፡ ሁሉ ፡ በመዝገብ ፡ ውስጥ ፡ አስፈረ

**leech** አልቅት
On the river banks of our country, there are many leeches. በገራችን ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ብዙ ፡ አልቅት ፡ አለ

**leer** ገረመመ

He stands on the corner and leers at the pretty girls passing by. ጥግ ፡ ቆሞ ፡ ውብ ፡ ልጃገረዶች ፡ ሲያልፉ ፡ ይገረምም ፡ ነበር

**(be) leery of** ተጠራጠረ

I am leery of anyone who promises me a prize without doing any work. ምንም ፡ ሳልሠራ ፡ ሽልማት ፡ ይሰጥሃል ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ የሚገባልኝን ፡ ሁሉ ፡ እጠራጠራለሁ

**lees** አተላ

Don't drink the lees of this beer! የዚህን ፡ ጠላ ፡ አተላ ፡ አትጠጣ

**leeway**

1. ክፍት ፡ ቦታ. There is little leeway between the table and the wall. በጠረጴዛውና ፡ በግድግዳው ፡ መሀከል ፡ ትንሽ ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ አለ

2. መፈናፈኛ. His instructions left him little leeway in the negotiations. የሰጠው ፡ መምሪያ ፡ በንግግር ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ መፈናፈኛ ፡ አልሰጠውም

**left,** see **leave**

**left** (n.) ግራ

You sit on the right, and I will sit on the left. አንተ ፡ በቀኝ ፡ ተቀመጥ ፡ እኔ ፡ በግራ ፡ እቀመጣለሁ

**at the left of** በ - - - በስተግራ

We had seats at the left of the stage. በመድረኩ ፡ በስተግራ ፡ ተቀምጠን ፡ ነበር

**left** (adj.) (የ)ግራ

Take the other bag in your left hand! ያኛውን ፡ ቦርሳ ፡ በግራ ፡ እጅህ ፡ ያዝ

**left** (adv.) ወደ ፡ ግራ

Turn left at the next corner! በሚቀጥለው ፡ መጠምዘዣ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ታጠፍ

[See also 'hand']

**left-hand**, adj. (= adv.) ወደ ፡ ግራ

Before you reach the hill, you make a left-hand turn. እኮረብታው ፡ ከመድረስህ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ተጠምዘዝ

**on the left-hand side** በስተግራ

His house is on the left-hand side of the street. ቤቱ ፡ የሚገኘው ፡ በመንገዱ ፡ በስተግራ ፡ ነው

**left-handed**

1. ግራኝ. Left-handed people have a difficult time learning to write. ግራኝ ፡ ሰዎች ፡ ጽሕፈት ፡ ሲማሩ ፡ ችግር ፡ አለባቸው

2. (= adv.) ከአንገት ፡ በላይ. He made me a left-handed compliment. ከአንገት ፡ በላይ ፡ አመሰገነኝ

**leftist** የግራ ፡ ክንፍ

All the leftist parties voted for him. የግራ ፡ ክንፉ ፡ የፖለቲካ ፡ ቡድኖች ፡ ሁሉ ፡ ለሱ ፡ ድምፅ ፡ ሰጡ

**leftover** ትራፊ

The servant ate the leftover meat. አሽከሩ ፡ ትራፊውን ፡ ሥጋ ፡ በላ

**leftovers** የተረፈ ፡ ምግብ

The housewife eked out a dinner of leftovers by adding rice. የቤቷ ፡ እመቤት ፡ በተረፈው ፡ ምግብ ፡ ላይ ፡ ሩዝ ፡ ጨምራ ፡ ለእራት ፡ አብቃቃችው

**leg** እግር

I have a pain in my right leg. ቀኝ ፡ እግሬን ፡ ያመኛል

The stool has three legs. በርጩማው ፡ ሦስት ፡ እግር ፡ አለው

*We are on the last leg of our trip. ይህ ፡ የጉዞዋችን ፡ መጨረሻ ፡ ነው

**be on one's (its) last legs** አጣጣረ

He was on his last legs when we saw him. እኛ ፡ ስናየው ፡ ያጣጥር ፡ ነበር

*Our car is on its last legs. መኪናችን ፡ አንድ ፡ ኀሙስ ፡ ቀርቷታል

**not have a leg to stand on** ምንም ፡ መሠረት ፡ የለውም

He claims he deserves the scholarship, but his claim does not have a leg to stand on. ስኮላርሺፕ ፡ ይገባኛል ፡ ብሎ ፡ ጠይቋል ፡ ግን ፡ ጥያቄው ፡ ምንም ፡ መሠረት ፡ የለውም

**pull (someone's) leg** አሾፈ(በት) ፤ አታለለ

He told me I had won the prize, but he was only pulling my leg. ሽልማቱ ፡ ደርሶሃል ፡ ብሎ ፡ ነገረኝ ፤ ግን ፡ ሲያሾፍብኝ ፡ ነበር

He loves to kid people, so be careful that he doesn't pull your leg. በሰው ፡ መቀለድ ፡ ስለሚወድ ፡ እንዳያታልልህ ፡ ተጠንቀቅ

**stretch one's legs** እግሩን ፡ አፍታታ

He got up during the intermission to stretch his legs. በዕረፍቱ ፡ ጊዜ ፡ እግሩን ፡ ለማፍታታት ፡ ተነሣ

**legacy** ቅርስ

He left a large legacy to his son. ለልጁ ፡ ብዙ ፡ ቅርስ ፡ አውርሶት ፡ ሞተ

*Our legacy of freedom was bequeathed to us by our warrior fathers. ነጻነታችንን ፡ ያቆዩልን ፡ አርበኞቹ ፡ አባቶቻችን ፡ ናቸው

**legal**

1. ሕግ ፡ የተከተለ. That's perfectly legal. ነገሩ ፡ ሕግ ፡ የተከተለ ፡ ነው

2. የሕግ. My legal advisor is away on business. የሕግ ፡ አማካሪዬ ፡ በሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሄዷል

**legal procedures** የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት
The committee used unfair legal procedures. ደርጉ ፡ ተገቢ ፡ ባልሆነ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተጠቀመ

**legal proceedings** ክስ
They instituted legal proceedings against him. በሱ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ አቀረቡበት

**legality** ሕጋዊነት
We discussed the legality of the case. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ሕጋዊነት ፡ ተነጋገርን

**legalize** ሕጋዊ ፡ አደረገ
Some states in the United States have legalized gambling. በአሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ ግዛቶች ፡ ቁማርን ፡ ሕጋዊ ፡ አድርገዋል

**legation** ሌጋሲዮን
The French legation has many buildings. የፈረንሳይ ፡ ሌጋሲዮን ፡ ብዙ ፡ ሕንጻዎች ፡ አሉት

**legend**
1. አፈ ፡ ታሪክ. There is a legend that a snake once ruled in Ethiopia. ኢትዮጵያን ፡ አንድ ፡ ዘንዶ ፡ ይገዛት ፡ ነበር ፡ የሚል ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፡ አለ
2. ጽሑፍ. Read the legend on the dollar bill! በብሩ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጽሑፍ ፡ አንብብ
3. መግለጫ. He couldn't decipher the legend of this picture. የዚህን ፡ ሥዕል ፡ መግለጫ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ አልቻለም

**legendary** ዝናን ፡ ያተረፈ
His deeds were legendary. የሱ ፡ ድርጊቶች ፡ ዝናን ፡ ያተረፉ ፡ ነበሩ
*Robin Hood is a legendary person. ሮቢን ፡ ሁድ ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፡ የሚነገርለት ፡ ሰው ፡ ነው

**(be) legible** ይነበባል
His handwriting is legible. የእጅ ፡ ጽሕፈቱ ፡ ይነበባል

**legion** ክፍለ ፡ ጦር
The army of ancient Rome consisted of several legions. የጥንታዊ ፡ ሮም ፡ ጦር ፡ ሰራዊት ፡ ብዙ ፡ ክፍለ ፡ ጦሮች ፡ ይገኙበት ፡ ነበር

**be legion** ቁጥር ፡ ስፍር ፡ የለውም
The number of sinners is legion. የኃጢአተኞች ፡ ብዛት ፡ ቁጥር ፡ ስፍር ፡ የለውም

**legislate**
1. ሕግ ፡ አወጣ. Parliament legislates for Ethiopia. ምክር ፡ ቤቱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ያወጣል
2. ሕግ ፡ አስተላለፈ. The lawmakers were asked to legislate against prostitution. ሕግ ፡ አውጪዎቹ ፡ ሴተኛ ፡ አዳሪነትን ፡ የሚቃወም ፡ ሕግ ፡ እንዲያስተላልፉ ፡ ተጠይቀው ፡ ነበር

**legislation**
1. ሕግ. There was not much legislation passed this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ ብዙ ፡ ሕግ ፡ አልወጣም
2. ሕግ ፡ ማውጣት. Parliament is responsible for legislation. ምክር ፡ ቤቱ ፡ ሕግ ፡ የማውጣት ፡ ኀላፊነት ፡ አለበት

**legislative** የሕግ
Legislative reforms are needed to end corruption. የባለ ፡ ሥልጣኖችን ፡ ምግባረ ፡ ቢስነት ፡ ለማቆም ፡ የሕግ ፡ መሻሻል ፡ ያስፈልጋል

**legislative body** ሕግ ፡ አውጪ ፡ ክፍል
The legislative body makes the laws for the country. ሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ ለሀገሪቷ ፡ ሕጎችን ፡ ይደነግጋል

**legislative decree** ድንጋጌ
The Emperor rules by legislative decree when parliament is not in session. ምክር ፡ ቤቱ ፡ በስብሰባ ፡ ላይ ፡ በማይገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በድንጋጌ ፡ ያስተዳድራል

**legislative powers** ሕግ ፡ የማውጣት ፡ ሥልጣን
The Senate has legislative powers. ሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ሕግ ፡ የማውጣት ፡ ሥልጣን ፡ አለው

**legislator** ሕግ ፡ አውጪ
The legislators must draft and submit bills. ሕግ ፡ አውጪዎች ፡ ሕግ ፡ አርቅቀው ፡ ማቅረብ ፡ አለባቸው

**legislature** የሕግ ፡ አውጪ ፡ ክፍል
The Senate and the House of Representatives form the legislature. ሕግ ፡ መወሰኛውና ፡ መምሪያው ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ የሕግ ፡ አውጪ ፡ ክፍል ፡ ናቸው

**legitimate**
1. ሕጋዊ. His claim to the throne was not legitimate. ዙፋኑ ፡ ይገባኛል ፡ ማለቱ ፡ ሕጋዊ ፡ አልነበረም
2. ሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ የተከተለ. His livelihood is not a legitimate one. መተዳደሪያው ፡ ሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ የተከተለ ፡ አይደለም
3. ተገቢ. The government used tax money for legitimate purposes. መንግሥቱ ፡ የተሰበሰበውን ፡ ግብር ፡ ለተገቢ ፡ ጉዳዮች ፡ አዋለው
4. ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ የተገኘ. A legitimate child will inherit his parents' property. ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ የተገኘ ፡ ልጅ ፡ የወላጆቹን ፡ ንብረት ፡ ይወርሳል

5. በቂ. Sickness is a legitimate reason for a child's being absent from school. ሕመም ፡ ለልጅ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመቅረያ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ነው

*If all the crops are poor, a legitimate conclusion is that the soil is poor. ሰብሉ ፡ በሙሉ ፡ ያነሰ ፡ ከሆነ ፡ መሬቱ ፡ መጥፎ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል

**leisure** (n.) ትርፍ ፡ ጊዜ

This job does not leave me much leisure. ይህ ፡ ሥራ ፡ ምንም ፡ ትርፍ ፡ ጊዜ ፡ አይሰጠኝም

**leisure time** ትርፍ ፡ ጊዜ

I can do it in my leisure time. በትርፍ ፡ ጊዜዬ ፡ ልሠራው ፡ እችላለሁ

**at one's leisure** ሲመችው

Take this book and read it at your leisure! ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ወስደህ ፡ ሲመችህ ፡ አንብበው

**be at leisure** ሥራ ፡ ፈታ

Call on him only when he is at leisure! ሥራ ፡ ሲፈታ ፡ ብቻ ፡ ጠይቀው

**leisurely** (adj.)

1. የማይጣደፍ. A leisurely person cannot be made to do things quickly. የማይጣደፍን ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ በችኰላ ፡ እንዲሠራ ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም

2. (= adv.) በረጋ ፡ መንፈስ. I had a leisurely conversation with my friend. ከጓደኛዬ ፡ ጋር ፡ በረጋ ፡ መንፈስ ፡ ተጫወትን

**leisurely** (adv.) በርጋታ

He was working leisurely at the task of folding papers. የወረቀት ፡ ማጠፍን ፡ ሥራ ፡ በርጋታ ፡ ያከያሄድ ፡ ነበር

**lemon** ሎሚ

Lemons are sour. ሎሚ ፡ ከምጣጣ ፡ ነው

**lemonade** ሎሚናት

Lemonade is a satisfying beverage. ሎሚናት ፡ የሚያረካ ፡ መጠጥ ፡ ነው

**lend** (lent)

1. (money) አበደረ. Can you lend me a dollar? አንድ ፡ ብር ፡ ልታበድረኝ ፡ ትችላለህ ?

2. (objects) አዋሰ. Lend me your book! መጽሐፍህን ፡ አውሰኝ

3. ሰጠ. The flowers lend brightness to the room. አበቦች ፡ ለክፍሉ ፡ ድምቀት ፡ ይሰጣሉ

Lend us your support in our fight for judicial reform! ለሕግ ፡ መሻሻል ፡ ለምናደርገው ፡ ትግል ፡ ድጋፍህን ፡ ስጠን

**lend oneself (itself) to**

1. ገባ. Don't lend yourself to such dishonest plans! እንደዚህ ፡ ባለ ፡ እምነተ ፡ ቢስ ፡ እቅድ ፡ ውስጥ ፡ አትግባ

2. አገለገለ. This tool lends itself to many uses. ይህ ፡ መሣሪያ ፡ ለብዙ ፡ ጥቅም ፡ ያገለግላል

*The pronouns lend themselves to ambiguity, so try to use nouns instead. ተውላጠ ፡ ስሞች ፡ አሻሚ ፡ ስለሚሆኑ ፡ በምትካቸው ፡ ስም ፡ አግባ

[See also 'hand']

**length**

1. ርዝመት. Let's measure the length of the room! የክፍሉን ፡ ርዝመት ፡ እንለካ

2. መርዘም. The length of a speech is no assurance that it will be good. የንግግሩ ፡ መርዘም ፡ ጥሩ ፡ ለመሆኑ ፡ ማረጋገጫ ፡ አይሆንም

3. አንድ ፡ ዓይነት ፡ ርዝማኔ ፡ ያለው. I bought three lengths of pipe. ሦስት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ርዝማኔ ፡ ያላቸው ፡ ቧምቧዎች ፡ ገዛሁ

*The length of a visit to a sick person should be only a few minutes. በሽተኛን ፡ ለመጠየቅ ፡ ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በላይ ፡ መቆየት ፡ አያስፈልግም

**length of time** ጊዜ

What is the length of time needed to do this job? ይህን ፡ ሥራ ፡ ለማከናወን ፡ የሚያስፈልገው ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?

**at full length** ተዘርሮ

He lay at full length on the bed. ተዘርሮ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ተኛ

**at length** በሰፊው

He spoke at length on the border problem. ስለ ፡ ወሰኑ ፡ ጉዳይ ፡ በሰፊው ፡ ተናገረ

**go to any length**

*He will go to any length to get what he wants. የሚያስፈልገውን ፡ ለማግኘት ፡ የማያደርገው ፡ ነገር ፡ የለም

**in length**

*The government report was 300 pages in length. የመንግሥቱ ፡ ሪፖርት ፡ ብዛት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ገጽ ፡ ነበር

**keep one at arm's length** አላቀርብ ፡ አለው

She kept me at arm's length though I met her every day. ምንም ፡ እንኳን ፡ በየቀኑ ፡ ባገኛትም ፡ አላቀርብ ፡ አለችኝ

**of some length** ብዙ ፡ ጊዜ

He made a stay of some length in Rome. ሮም ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆይቷል

**stretch full length** ተዘረረ
He stretched full length on the bed. አልጋው ፡ ላይ ፡ ተዘረረ

**lengthen** (vt.) አረዘመ
The tailor lengthened the trousers. ልብስ ፡ ሰፊው ፡ ሱሪውን ፡ አረዘመው

**lengthen** (vi.) ረዘመ
In March, the days begin to lengthen. በመጋቢት ፡ ወር ፡ ቀናት ፡ እየረዘሙ ፡ መሄድ ፡ ይጀምራሉ

**lengthwise** በቁመቱ
Cut the material lengthwise! ጨርቁን ፡ በቁመቱ ፡ ቊረጠው

**lengthy** ረጂም
The lengthy speech that he gave was boring. ያደረገው ፡ ረጂም ፡ ንግግር ፡ ያሰለች ፡ ነበር

**lenience** ልልነት
Lenience promotes disobedience. ልልነት ፡ አለመታዘዝን ፡ ያስከትላል

**lenient** ልል
You're too lenient with him. ለሱ ፡ በጣም ፡ ልል ፡ ሆነህለታል

**lenient attitude** ልልነት
His lenient attitude encourages the children to be disrespectful. የሚያሳየው ፡ ልልነት ፡ ልጆቹ ፡ ባለጌ ፡ እንዲሆኑ ፡ ያደርጋቸዋል

**lens** ሌንስ
The lens of this camera is broken. የዚህ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ማንሻ ፡ ሌንሱ ፡ ተሰብሯል

**lent**, see **lend**

**Lent** የሁዳዴ ፡ ጾም
When does Lent end? የሁዳዴ ፡ ጾም ፡ መቼ ፡ ያልቃል ?

**lentil** ምስር
Add some lentils to the soup! ሾርባው ፡ ውስጥ ፡ ምስር ፡ ጨምርበት

**leopard** ነብር
The leopard lives in the jungle. ነብር ፡ የሚኖረው ፡ በዱር ፡ ነው

**leper** ቆማጣ
Lepers stay in a place by themselves. ቆማጦች ፡ ለብቻቸው ፡ በተለየ ፡ ቦታ ፡ ይኖራሉ

**leprosy** ቁምጥና
He caught leprosy in his youth. ቁምጥና ፡ በልጅነቱ ፡ ያዘው

**lese majesty** ክብሩን ፡ ማቃለል
In Japan, printing pamphlets belittling the Emperor is lese majesty. በጃፓን ፡ ውስጥ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ የሚያንኳስስ ፡ መጽሔት ፡ ማውጣት ፡ ክብሩን ፡ ማቃለል ፡ ነው

**lesion** ቁስል
The lesion became infected because of the dirt. ቁስሉ ፡ ከቆሻሻው ፡ የተነሣ ፡ ተመረዘ

**less** (adj.)
1. ያነሰ. I have less money than he has. ከርሱ ፡ ያነሰ ፡ ገንዘብ ፡ አለኝ
2. አጠር ፡ ያለ. We will get home in less time if we fly. በአውሮፕላን ፡ ከሄድን ፡ አጠር ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ እቤት ፡ እንደርሳለን

**less** (adv.)
1. ያነሰ. I work less in the rainy season. በዝናብ ፡ ወራት ፡ ያነሰ ፡ እሠራለሁ
2. ትንሽ. I do less because I get no reward. ዋጋ ፡ ስለማላገኝበት ፡ ትንሽ ፡ እሠራለሁ

**less** (prep.)
*He spent a year less two days in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለዓመት ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ የቀረው ፡ ጊዜ ፡ አሳለፈ
*Five less two equals three. ከምስት ፡ ሁለት ፡ ሲቀነስ ፡ ሦስት ፡ ይቀራል

**be less** አነሰ
Tom is less clever than his brother. ቶም ፡ በብልህነት ፡ ከወንድሙ ፡ ያንሳል

**do something less** ቀነሰ
You must drink less if you want to stay healthy. ጤነኛ ፡ ሆነህ ፡ ለመቆየት ፡ ከፈለግህ ፡ መጠጥ ፡ መቀነስ ፡ አለብህ
Eat less, and you will get thin! ምግብ ፡ ብትቀንስ ፡ ትቀጥናለህ

**have less** (= intr.) ቀለል ፡ አለ
+I am having less difficulty with my work than I used to. በሥራዬ ፡ ከድሮ ፡ ይልቅ ፡ አሁን ፡ የሚያጋጥመኝ ፡ ችግር ፡ ቀለል ፡ ይላል

**in less than** ከ - - ባነሰ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ
In less than an hour, we will be home. ከንድ ፡ ሰዓት ፡ ባነሰ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ቤት ፡ እንደርሳለን

**no less (than)** ከ - - ያላነሰ
He won no less than five hundred dollars. በውድድሩ ፡ ከምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ያላነሰ ፡ አገኘ

**no less a person than**
*No less a person than the President came to see him. ፕሬዚዳንቱን ፡ የሚያህል ፡ ሰው ፡ ሊጠይቀው ፡ መጣ

**still less**
*He is not guilty of theft, still less of robbery by violence. እንኳን ፡ የቀማኝነት ፡ የሌብነትም ፡ ወንጀል ፡ አልፈጸመም

**the less ... the better**
*The less you worry about it, the better it will be. ብዙ ፡ ባትጨነቅበት ፡ የተሻለ ፡ ይሆናል
[See also 'more, much, nothing']

**lessee** ተከራይ
The lessee must keep the house in repair. ተከራዩ ፡ ቤቱን ፡ ማደስ ፡ አለበት

**lessen** (vt.)
1. ቀነሰ. In summer they lessen the working hours. በበጋው ፡ የሥራ ፡ ሰዓቶችን ፡ ይቀንሳሉ
2. አቃለለ. Don't lessen his service to the state! ላገሪቱ ፡ ያደረገውን ፡ አገልግሎት ፡ አታቃል

**lessen** (vi.) ቀለል ፡ አለ
The rain lessened. ዝናቡ ፡ ቀለል ፡ አለ

**lesser** አነስተኛ
He chose the lesser evil and remained in exile rather than return and go to jail. አነስተኛውን ፡ መከራ ፡ በመምረጥ ፡ አገሩ ፡ ተመልሶ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ከሚገባ ፡ ተሰዶ ፡ ቀረ

**lesson**
1. ትምህርት. Translate lesson eleven for next time! ለሚቀጥለው ፡ ጊዜ ፡ ዐሥራ ፡ አንደኛውን ፡ ትምህርት ፡ ተርጉም
The crash taught him a lesson. ግጭቱ ፡ ትምህርት ፡ ሆነው
2. ክፍል. My next lesson is at three o'clock. የሚቀጥለው ፡ ክፍሌ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ነው

**give lessons** አስተማረ
She gives Amharic lessons. አማርኛ ፡ ታስተምራለች
[See also 'review']

**lessor** አከራይ
Both lessor and lessee must sign the agreement. አከራዩም ፡ ተከራዩም ፡ ውሉን ፡ መፈረም ፡ አለባቸው

**lest** እንድ + (negative imperfect)
He hid lest he be discovered. እንዳይገኝ ፡ ብሎ ፡ ተደበቀ
*We watched all night lest the bandits should return. ሽፍቶቹ ፡ የተመለሱ ፡ እንደሆነ ፡ በማለት ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ስንጠብቅ ፡ አደርን

**let** (vt.)
1. አከራየ. The hotel lets rooms by the week. ሆቴሉ ፡ በሳምንት ፡ ሒሳብ ፡ ክፍሎች ፡ ያከራያል
2. ፈቀደ. Her father will not let her go to the party. አባቷ ፡ ወደ ፡ ፓርቲው ፡ እንድትሄድ ፡ አይፈቅድላትም
3. አስ-stem. He wouldn't let me do it. አላሠራም ፡ አለኝ

**let** (vi.) ተከራየ
The house lets for $80 a month. ቤቱ ፡ በወር ፡ ሰማንያ ፡ ብር ፡ ይከራያል

**let,** jussive
Let's start at once! አሁኑኑ ፡ እንጀምር

**let alone**
*He could not even understand Amharic, let alone speak it. አማርኛ ፡ መናገር ፡ ቀርቶ ፡ መስማትም ፡ አይችልም
*It would have been a hot day for summer, let alone for spring. እንኳን ፡ ለጸደይ ፡ ይቅርና ፡ ለበጋ ፡ እንኳን ፡ ሞቃት ፡ ቀን ፡ ይሆን ፡ ነበር

**let (someone, something) alone**
1. ታገሠ. Can't you let me alone for five minutes? ላምስት ፡ ደቂቃ ፡ ልትታገሠኝ ፡ ትችላለህ?
2. እንዳለ ፡ ተወ. If you approve of the plan, let it alone. በእቅዱ ፡ ከተስማማህ ፡ እንዳለ ፡ ተወው

**let by** አሳለፈ
Let him by since he is in a hurry to catch the bus. አውቶቡሱን ፡ ለመሳፈር ፡ ስለሚቸኩል ፡ አሳልፈው

**let down** (vt.)
1. አወረደ. The baby is not comfortable; let him down from your shoulder. ሕፃኑ ፡ አልተመቸውም ፤ ከትከሻህ ፡ ላይ ፡ አውርደው
2. ዘጋ. Please let down the blinds! መጋረጃውን ፡ ዝጋው
3. አሳፈረ. I was counting on him to help me, but he let me down. ይረዳኛል ፡ ብዬ ፡ ተማምኜበት ፡ ነበር ፤ ግን ፡ አሳፈረኝ

**let down** (vi.) ችላ ፡ አለ
He is beginning to let down in his work. ሥራውን ፡ ችላ ፡ ማለት ፡ ጀምሯል

**let have**
1. ሰጠ. Please let me have the menu! የምግቡን ፡ ዝርዝር ፡ ብትሰጠኝ
2. አበደረ. Can you let me have five dollars? አምስት ፡ ብር ፡ ልታበድረኝ ፡ ትችላለህ?

**let (him) have it** በለው
If he insults you once more, let him have it. ደግሞ ፡ እንደዚህ ፡ ከሰደበህ ፡ በለው

**let in** አስገባ
Don't let anybody in! ማንንም ፡ አታስገባ

**let (oneself) in for** ችግር ፡ ውስጥ ፡ ገባ
He did not know what he was letting himself in for when he took the job. ሥራውን ፡ ሲቀበል ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ እንደሚገባ ፡ አላወቀውም

**let (one) in on** አካፈለ
We let them in on the secret. ምስጢሩን ፡ አካፈልናቸው

**let into** አስገባ
The maid let us into the house. ገረዲቱ ፡ እቤት ፡ አስገባችን

**let off**
1. አወረደ. I asked the driver to let me off at the corner. ነጂው ፡ ከመታጠፊያው ፡ ላይ ፡ እንዲያወርደኝ ፡ ጠየቅሁት
2. አወጣ. This machine lets off a lot of steam. ይህ ፡ መኪና ፡ ብዙ ፡ እንፋሎት ፡ ያወጣል
3. ለቀቀ. The judge let him off with a warning. ዳኛው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሰጥቶ ፡ ለቀቀው
4. አሰናበተ. The manager let the clerks off at noon. ሥራ ፡ መሪው ፡ ቀትር ፡ ላይ ፡ ጸሐፊዎቹን ፡ አሰናበተ

**let on** ተናገረ
Don't let on that you see him! እሱን ፡ ማየትህን ፡ አትናገር

**let out**
1. ለቀቀ. At night we let the cat out. ማታ ፡ ማታ ፡ ድመቷን ፡ እንለቃታለን
The woman let out a scream when she was beaten. ሴትዮዋ ፡ ስትደበደብ ፡ ጩኸቷን ፡ ለቀቀች
Let the water out of the bathtub! ውኃውን ፡ ከገላ ፡ መታጠቢያው ፡ ውስጥ ፡ ልቀቀው
2. አወጣ. He lets out every secret you tell him. የነገርከውን ፡ ምስጢር ፡ ሁሉ ፡ ያወጣል
3. አስወጣ. We opened the windows to let out the foul air. የተበላሸውን ፡ አየር ፡ ለማስወጣት ፡ መስኮቶቹን ፡ ከፈትን
4. አሰፋ. The tailor let out my coat because I got fatter. ስለወፈርኩ ፡ ልብስ ፡ ሰፊው ፡ ኮቴን ፡ አሰፋልኝ

**(be) let out** ወጣ
Owing to a shortage of teachers, school will be let out early. በመምህራን ፡ እጥረት ፡ የተነሣ ፡ ተማሪዎች ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ይወጣሉ

**let through** አሳለፈ
The police wouldn't let us through. ፖሊሱ ፡ አላሳልፍ ፡ አለን

**let up**
1. በረድ ፡ አለ. The storm has let up. ዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ በረድ ፡ ብሏል
2. ጋብ ፡ አለ. Will the rain ever let up? መቼ ፡ ይሆን ፡ ዝናቡ ፡ ጋብ ፡ የሚለው?
3. ተወ. They refused to let up in the fight. ድብድቡን ፡ አንተውም ፡ ብለው ፡ እምቢ ፡ አሉ
[See also the various nouns and verbs combined with 'let', such as 'air, do, pass']

## letdown ዝቅ ፡ ማለት
The letdown in sales caused the closing of several stores. የሽያጭ ፡ ዝቅ ፡ ማለት ፡ ብዙዎች ፡ መደብሮች ፡ እንዲዘጉ ፡ አደረገ

**be a letdown (in, to)**
1. ትንሽ ፡ ቀዘቀዘ. There is a letdown in business this month. በዚህ ፡ ወር ፡ ንግድ ፡ ትንሽ ፡ ቀዝቅዟል
2. ቅሬታ ፡ አሳደረ(በት). The match was a letdown to the spectators. ግጥሚያው ፡ ተመልካቾቹን ፡ ቅሬታ ፡ አሳደረባቸው

## lethal ሊገድል ፡ የሚችል
A sharp fork can be a lethal weapon. ስለታም ፡ ሹካ ፡ ሊገድል ፡ የሚችል ፡ መሣሪያ ፡ ነው

## lethargic, ~ condition ልፍስፍስነት
His lethargic condition is due to ill health. ልፍስፍስነቱ ፡ በጤንነቱ ፡ መቃወስ ፡ ምክንያት ፡ ነው

**produce a lethargic condition** አልፈሰፈሰ
A hot, humid day produces a lethargic condition. ሞቃት ፡ እርጥብ ፡ ቀን ፡ ያልፈሰፍሳል

## lethargy መልፈስፈስ
The child's lethargy is the result of prolonged illness. የልጁ ፡ መልፈስፈስ ፡ ከረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሕመም ፡ የተነሣ ፡ ነው

## letter
1. ደብዳቤ. Are there any letters for me? ደብዳቤዎች ፡ አሉኝ ?
2. ፊደል. The word has five letters. ቃሉ ፡ አምስት ፡ ፊደሎች ፡ አሉት
*The judge enforced the letter of the law. ዳኛው ፡ ሕጉን ፡ እንደተጻፈው ፡ ሠራበት

**letters** ሥነ ፡ ጽሑፍ
The dean of the college is a man of letters. የኮሌጁ ፡ ዲን ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ሰው ፡ ናቸው

**to the letter** ቃል ፡ በቃል
He follows the rules to the letter. ሕጉን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ይከተላል
[See also 'capital letter, circular, dead, recommendation']

**letter box** የፖስታ ፡ ማጠራቀሚያ ፤ ፖስታ ፡ ሣጥን
The letter box is painted red. የፖስታው ፡ ማጠራቀሚያ ፡ (ፖስታው ፡ ሣጥን) ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ተቀብቷል

**letterhead** አርማ
Do you have paper with the letterhead of the Ministry of Education? የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ አርማ ፡ ያለበት ፡ ወረቀት ፡ አለህ?

**lettuce** ሰላጣ

**letup, be a ~** ቀዝቀዝ ፡ አለ
There was a brief letup in their work. ሥራቸው ፡ ላጭር ፡ ጊዜ ፡ ቀዝቀዝ ፡ ብሎ ፡ ነበር

**without a letup** ያለፋታ
I have been working ten hours without a letup. ዐሥር ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ያለፋታ ፡ እሠራ ፡ ነበር

**levee** ግድብ
There are levees in many places along this river. በዚህ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ግድቦች ፡ አሉ

**level** (v.)
1. **አስተካከለ**. Death levels us all. ሞት ፡ ሁላችንንም ፡ ያስተካክላል
2. **ደለደለ(ተደለደለ)**. The ground has to be leveled. መሬቱ ፡ መደልደል ፡ አለበት
3. **አወደመ**. The artillery fire leveled the town. የመድፉ ፡ ተኵስ ፡ ከተማውን ፡ አወደመው
4. **ገነደሰ**. The storm leveled the tree. ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ዛፉን ፡ ገነደሰው
5. **ቈረጠ**. They leveled the trees to make way for the new highway. ላዲሱ ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ ሲሉ ፡ ዛፎቹን ፡ ቈረጧቸው
6. **ሰነዘረ**. He leveled his criticism at the nation as a whole. ትችቱን ፡ በጠቅላላው ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ሰነዘረ

**level off** (vt.) **ደለደለ**
The machine levels off the mountaintops so that houses may be built. ቤት ፡ ይሠራባቸው ፡ ዘንድ ፡ መኪናው ፡ የተራራዎችን ፡ ጫፍ ፡ ይደለድላል

**level off** (vi.) **በመሬት ፡ አኳያ ፡ በረረ**
Airplanes level off just before landing. አውሮፕላኖች ፡ ከማረፋቸው ፡ በፊት ፡ በመሬት ፡ አኳያ ፡ ይበራሉ
[See also 'accusation']

**level** (n.)
1. **ደረጃ**. There are five salary levels in our office. በመሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ አምስት ፡ የደሞዝ ፡ ደረጃዎች ፡ አሉ
The civilization of mankind has taken thousands of years to reach its present level. የሰው ፡ ልጅ ፡ ሥልጣኔ ፡ አሁን ፡ ካለበት ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ ብዙ ፡ ሺ ፡ ዓመታት ፡ ፈጅቷል
There will be a conference at the ministerial level. በሚኒስትሮች ፡ ደረጃ ፡ ጉባኤ ፡ ይደረጋል
2. **ፎቅ**. You can buy tea or coffee on the upper level. እላይኛው ፡ ፎቅ ፡ ላይ ፡ ሻይ ፡ ወይም ፡ ቡና ፡ ልትገዛ ፡ ትችላለህ
3. **መጠን**. The raid only escalates the level of violence. ወረራው ፡ የጠቡን ፡ መጠን ፡ ያባብሰዋል
*The boy reached a high level of intelligence. ልጁ ፡ በጣም ፡ ብልህ ፡ ወጣው

**be on a level** ተመጣጠነ
His work is on a level with the best. ሥራው ፡ ምርጥ ፡ ከሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ የሚመጣጠን ፡ ነው

**rise to a level** ከፍ ፡ አለ
The flood rose to a level of fifty feet. የውኃው ፡ ሙላት ፡ አምሳ ፡ ጫማ ፡ ከፍ ፡ አለ

**level** (adj.)
1. **ደልዳላ**. We built our house on level ground. ቤታችንን ፡ በደልዳላ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሠራን
2. **በቁመት ፡ ትክክል**. The bookcase is level with the table. የመጽሐፍ ፡ መደርደሪያው ፡ ከጠረጴዛው ፡ ጋር ፡ በቁመት ፡ ትክክል ፡ ነው
3. **ያልተለዋወጠ**. He spoke in a calm and level tone. ረጋ ፡ ባለና ፡ ባልተለዋወጠ ፡ ድምፅ ፡ ተናገረ

**be level** ተስተካከለ
The ground was bumpy, but now it is level. መሬቱ ፡ አባጣ ፡ ጐባጣ ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ተስተካክሏል
*The water rose until it was level with the bank. ወንዙ ፡ እስከ ፡ አፍ ፡ ደገፉ ፡ ሞልቷል

**do (one's) level best** የተቻለውን ፡ አደረገ
He did his level best to stop the riot. ረብሻውን ፡ ለማቆም ፡ የተቻለውን ፡ አደረገ

**make level** አስተካከለ
Make this pile of sand level with the other! ይህን ፡ የአሸዋ ፡ ቁልል ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ አስተካክለው
[See also 'ground']

**level-headed** የማይሸበር
He is a level-headed person even in the worst situations. ከሁሉም ፡ የከፋ ፡ ጊዜ ፡ ሲመጣ ፡ እንኳን ፡ የማይሸበር ፡ ሰው ፡ ነው

**lever** [ከባድ ፡ እቃዎችን ፡ ወይም ፡ ደንጊያን ፡ ለመፈንቀል ፡ የሚረዳ ፡ እንደ ፡ ድጅኖ ፡ ያለ ፡ ረዥምም ፡ የብረት ፡ ዘንግ]

**levity** ቅብጠት
His levity makes him unfit to be a priest. ቅብጠቱ ፡ ለቄስነት ፡ ተገቢ ፡ አያደርገውም

**levy** (levied), v.
1. ጣለ. The government levies a tax on tobacco. መንግሥቱ ፡ በትምባሆ ፡ ላይ ፡ ቀረጥ ፡ ይጥላል
2. በግድ ፡ ለወታደርነት ፡ መለመለ. The government levies troops in time of war. መንግሥቱ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ሰዎችን ፡ በግድ ፡ ለወታደርነት ፡ ይመለምላል

**lexicon** መዝገበ ፡ ቃላት
We need an English-Amharic lexicon. እንግሊዝኛንና ፡ አማርኛን ፡ አጣምሮ ፡ የያዘ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ያስፈልገናል

**liability** (liabilities)
1. ወጪና ፡ ኪሳራ. In a partnership, the partners share all liabilities equally. በሽርክና ፡ ንግድ ፡ ውስጥ ፡ ሽርከኞች ፡ ማንኛውም ፡ ወጪና ፡ ኪሳራ ፡ እኩል ፡ ይደርስባቸዋል
2. መሰናክል. Poor eyesight is a liability. ደካማ ፡ ዓይን ፡ መሰናክል ፡ ነው
3. ኀላፊነት. The renter of the property has no liability for the owner's debts. የንብረቱ ፡ ተከራይ ፡ ለባለ ፡ ንብረቱ ፡ ዕዳ ፡ ኀላፊነት ፡ የለበትም
*He takes special precautions because of his liability to disease. በቀላሉ ፡ ሊታመም ፡ ስለሚችል ፡ የተለየ ፡ ጥንቃቄ ፡ ያደርጋል

**have liability** ተጠያቂ ፡ ሆነ
Minors have no liability for damages due to poor judgement. ዓቅመ ፡ አዳም ፡ ያልደረሱ ፡ ሰዎች ፡ ከተሳሳተ ፡ ግምት ፡ የተነሣ ፡ በሚያደርጉት ፡ ጉዳት ፡ ተጠያቂ ፡ አይሆኑም

**(be) liable** ካሳ ፡ መክፈል ፡ አለበት
You will be liable for any damages. ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ካሳ ፡ መክፈል ፡ አለብህ

**be liable to**
1. ስ + negative imperfect + አይቀርም. He is liable to forget. ሳይረሳ ፡ አይቀርም
The boxes are liable to fall. ሣጥኖቹ ፡ ሳይወድቁ ፡ አይቀሩም
2. ል + imperfect + ቻለ. Rioters are liable to arrest. ረብሸኞቹ ፡ ሊታሰሩ ፡ ይችላሉ

**consider (one) liable** በኀላፊነት ፡ ጠየቀ
If the car is damaged, I will consider you liable. መኪናው ፡ የተበላሸ ፡ እንደሆነ ፡ በኀላፊነት ፡ እጠይቅሃለሁ

**liaison** አገናኝ
He is the liaison officer for the Americans. ለአሜሪካኖች ፡ አገናኝ ፡ መኰንን ፡ ነው

**liar** ውሸታም
He is an awful liar. የባሰበት ፡ ውሸታም ፡ ነው

**libation** የመጠጥ ፡ መሥዋዕት
The Romans made libations to Jupiter. ሮማውያን ፡ ለጁፒተር ፡ የመጠጥ ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ

**libel**
1. የስም ፡ ማጥፋት ፡ ወንጀል. The government is suing the newspapers for libel. መንግሥት ፡ ጋዜጦችን ፡ በስም ፡ ማጥፋት ፡ ወንጀል ፡ ከሷቸዋል
2. ስም ፡ ማጥፋት. Libel must be proven by law. ስም ፡ ማጥፋት ፡ በሕግ ፡ መረጋገጥ ፡ አለበት

**libelous** ስም ፡ የሚያጠፋ
He is accused of having made a libelous statement. ስም ፡ የሚያጠፋ ፡ ጽሑፍ ፡ ጽፏል ፡ ተብሎ ፡ ተከሷል

**liberal**
1. ትልቅ. A liberal reward will be given to the person who finds my watch. ሰዓቴን ፡ ለሚያገኝልኝ ፡ ሰው ፡ ትልቅ ፡ ወሮታ ፡ ይከፈለዋል
2. ለጋስ. The contributions of some liberal donors assured the construction of the hospital. ያንዳንድ ፡ ለጋስ ፡ በጎ ፡ አድራጊዎች ፡ ስጦታ ፡ ሆስፒታሉ ፡ እንዲሠራ ፡ አስቻለ
She is liberal with her money. በገንዘቧ ፡ ረገድ ፡ ለጋስ ፡ ናት
3. በርከት ፡ ያለ. His liberal donations made the construction of the school possible. ችሮታዎቹ ፡ በርከት ፡ ስላሉ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሊሠራ ፡ ቻለ
4. የማይቃረን. The government has a liberal attitude toward religious worship. መንግሥቱ ፡ ማንኛውንም ፡ የሃይማኖት ፡ አምልኮ ፡ የማይቃረን ፡ አስተያየት ፡ አለው
5. ላላ ፡ ያለ. The government followed a liberal policy toward the country's artists and writers. መንግሥቱ ፡ ላገሪቱ ፡ ሠዓሊዎችና ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያለው ፡ ደንብ ፡ ላላ ፡ ያለ ፡ ነው
*There was a liberal supply of food and drink at the party. በፓርቲው ፡ ላይ ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ እንደልብ ፡ ነበር

**liberal views**
He has liberal views. ሰፊ ፡ አስተሳሰብ ፡ አለው

**liberality** (liberalities)
1. ለጋስነት. His liberality is remembered by the townspeople. ለጋስነቱ ፡ በከተማው ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ ይታወሳል

2. ስፋ ፡ አስተሳሰብ. His liberality offended the conservative members of the church. ስፋ ፡ አስተሳሰቡ ፡ ለውጥ ፡ የማይፈልጉትን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባሎች ፡ አስቀየመ

**liberate** ነጻ ፡ አወጣ
They liberated the country from its oppressors. አገሪቷን ፡ ከጨቋኞች ፡ ነጻ ፡ አወጧት

**liberty** (liberties)
1. ነጻነት. Everyone likes liberty. ሁሉም ፡ ሰው ፡ ነጻነት ፡ ይወዳል
Lincoln granted liberty to slaves. ሊንኮልን ፡ ለባሮች ፡ ነጻነት ፡ ሰጠ
2. መብት. The constitution is the guardian of our liberties. ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የመብታችን ፡ ጠባቂ ፡ ነው
*The prisoner pleaded for his liberty. እስረኛው ፡ በነጻ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ልመና ፡ አቀረበ

**be at liberty**
1. ቻለ. You are at liberty to go at any time. በፈለግኸው ፡ ጊዜ ፡ ለመሄድ ፡ ትችላለህ
I am not at liberty to tell you his secrets. ምስጢሩን ፡ ልነግርህ ፡ አልችልም
2. ጊዜ ፡ ሲያገኝ. The principal will see you as soon as he is at liberty. ሥራ ፡ መሪው ፡ ጊዜ ፡ ሲያገኝ ፡ ወዲያውኑ ፡ ይነግርሃል
3. እስር ፡ ቤት ፡ አይደለም. The burglar is at liberty right now. ሌባው ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ አይደለም

**be set at liberty** ነጻ ፡ ተለቀቀ
The prisoners were set at liberty by their guards. እስረኞቹ ፡ በጠባቂዎቻቸው ፡ ነጻ ፡ ተለቀቁ

**give the liberty**
*They gave us the liberty of the whole house. በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ እንደልባችን ፡ እንድንሆን ፡ ፈቀዱልን

**take liberties with** ተዳፈረ
He takes too many liberties with me. በጣም ፡ ይዳፈረኛል
*He takes liberties with his father's purse. ያባቱን ፡ ገንዘብ ፡ እንደልቡ ፡ ያወጣል

**take the liberty** ሳይጠይቀው
I took the liberty of borrowing your book. መጽሐፍህን ፡ ሳልጠይቅህ ፡ ተውሼዋለሁ

**librarian** ዐቃቤ ፡ መጻሕፍት
The librarian won't let me borrow any books. ዐቃቤ ፡ መጻሕፍቱ ፡ መጽሐፍ ፡ እንዳልዋስ ፡ ከለከለኝ

**library** (libraries)
1. ቤተ ፡ መጻሕፍት. The library has a large collection of Ethiopian books. ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ብዙ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጽሐፎች ፡ አሉት
2. መጻሕፍት. He has an extensive library on Ethiopia. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተጻፉ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ አሉት

**lice,** see **louse**

**license** (v.) የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ሰጠ
The ministry licenses teachers to teach. ሚኒስቴሩ ፡ ለመምህራን ፡ የማስተማር ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ይሰጣል

**license** (n.)
1. ፈቃድ. You have to have a license to open up a restaurant. ምግብ ፡ ቤት ፡ ለመክፈት ፡ ፈቃድ ፡ ያስፈልጋል
2. ጸያፍ ፡ ምግባር. The invaders showed unbelievable license. ወራሪዎች ፡ በጣም ፡ ጸያፍ ፡ የሆነ ፡ ምግባር ፡ ፈጸሙ
3. ብልግና. She showed license in calling her teacher by her first name. አስተማሪዋን ፡ በስሟ ፡ በመጥራት ፡ ብልግና ፡ አሳየች

**license plate** ሰሌዳ
The license plate was covered with mud. ሰሌዳው ፡ በጭቃ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር

**lick**
1. ላሰ. Just look at the cat licking her kittens! ድመቷ ፡ ግልገሎቿን ፡ ስትልስ ፡ ተመልከት
2. በምላስ ፡ አረጠበ. Lick a stamp before you put it on the evelope. ፖስታው ፡ ላይ ፡ ከመለጠፍህ ፡ በፊት ፡ ቴምብሩን ፡ በምላስህ ፡ አርጥበው
3. ገረፈ. Flames were licking the roof of the house. ነበልባሉ ፡ የቤቱን ፡ ጣሪያ ፡ ገረፈው
4. አሸነፈ. I bet I could still lick you. እንወራረድ ፤ አሁንም ፡ እሸንፍሃለሁ

**lick clean** ልሶ ፡ ባዶውን ፡ አስቀረ
The cat licked the plate clean. ድመቷ ፡ ሳሕኑን ፡ ልሳ ፡ ባዶውን ፡ አስቀረችው

**lick up** ጠጥቶ ፡ ጨረሰ
The cat licked up all the milk. ድመቷ ፡ ወተቱን ፡ ጠጥታ ፡ ጨረሰችው
[See also 'boot']

**lid**
1. መክደኛ. Take the lid off the pot when the water boils. ውኃው ፡ ሲፈላ ፡ መክደኛውን ፡ ከጀበናው ፡ ላይ ፡ አንሣ
2. ክዳን. Does this jar have a lid? ይህ ፡ ጠርሙስ ፡ ክዳን ፡ አለው ?

3. እሬያ. The wooden lid of the box is broken. የሣጥኑ ፡ ዕንጨት ፡ እሬያ ፡ ተሰብሯል

**lie** (lied, lying) ዋሸ
He lied when I asked him if he did it. አድርጎት ፡ እንደሆን ፡ ብጠይቀው ፡ ዋሸ

**lie** (n.) ውሸት
Everything he says is a lie. የሚለው ፡ ሁሉ ፡ ውሸት ፡ ነው

**give the lie to** ከንቱ ፡ አደረገ
His work gives the lie to his claims of experience. ሥራው ፡ ልምድ ፡ አለኝ ፡ ማለቱን ፡ ከንቱ ፡ ያደርገዋል
[See also 'tissue, web']

**lie** (lay, lain)
1. ተገኘ. Canada lies north of the United States. ካናዳ ፡ ከዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ በስተሰሜን ፡ ትገኛለች
The cure for ignorance lies in education. የድንቁርና ፡ መፍትሔ ፡ በትምህርት ፡ ይገኛል
2. ነው. The book lies on the table. መጽሐፉ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ነው
3. ተጋደመ. The child lies on the grass. ልጁ ፡ ሣሩ ፡ ላይ ፡ ተጋድሟል
4. ተንጋለለ. He was lying on his back. በጀርባው ፡ ተንጋሎ ፡ ነበር
5. ተዘርግቶ ፡ ታየ. When we got to the mountaintop, the plain lay before us. ተራራው ፡ ጫፍ ፡ ስንደርስ ፡ ሸለቆው ፡ ፊታችን ፡ ተዘርግቶ ፡ ታየን
6. ተቀመጠ. The book lay open on the table. መጽሐፉ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ተገልጦ ፡ ተቀምጧል
7. (body) ተቀበረ. His body lies in the churchyard. በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ቅጥር ፡ ውስጥ ፡ ተቀበረ

**lie about** በየቦታው ፡ ተበታተነ
Books were lying about the room. በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ መጻሕፍት ፡ በየቦታው ፡ ተበታትነው ፡ ነበር

**lie back** ተንጋለለ
He lay back in the armchair. ፎቴው ፡ ላይ ፡ ተንጋሏል

**lie down** ጋደም ፡ አለ
If you are tired, go lie down! ደክሞህ ፡ እንደሆነ ፡ ሂድና ፡ ጋደም ፡ በል

**lie over** ተላለፈ
The other business on the agenda had to lie over until the next meeting. በአጀንዳው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ሌላው ፡ ጉዳይ ፡ ለሚቀጥለው ፡ ስብሰባ ፡ መተላለፍ ፡ ነበረበት

**lie with one** የሱ ፡ ፈንታ ፡ ነው
The burden of proof lies with you. ማስረጃውን ፡ ማቅረብ ፡ ያንተ ፡ ፈንታ ፡ ነው

**take lying down**
*He did not take that insult lying down. ስድቡን ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አላለፈውም
[See also 'bed, idle, low, prone, ruin, wait']

**lien, have a ~ on** በወለድ ፡ አግድ ፡ ያዘ
The bank has a lien on my house until I pay back my loan. ዕዳዬን ፡ እስክከፍል ፡ ድረስ ፡ ባንኩ ፡ ቤቴን ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ይዞታል

**lieutenant** መቶ ፡ አለቃ
My brother is a lieutenant in the army. ወንድሜ ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ መቶ ፡ አለቃ ፡ ነው

**life** (lives)
1. ነፍስ. God gave Adam life. እግዚአብሔር ፡ አዳምን ፡ ነፍስ ፡ ዘራበት
2. ሕይወት. Is there any life on the moon? በጨረቃ ፡ ላይ ፡ ሕይወት ፡ አለ ?
I have lived here all my life. ሕይወቴን ፡ሙሉ ፡ እዚህ ፡ ኖሬያለሁ
3. ሰው ፤ የሰው ፡ ሕይወት. Five lives were lost in the accident. ባደጋው ፡ አምስት ፡ ሰዎች ፡ ሞቱ
How many lives were lost in the earthquake? በመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ምክንያት ፡ የስንት ፡ ሰዎች ፡ ሕይወት ፡ ጠፍቷል ?
4. የሕይወት ፡ ታሪክ. He is writing a life of the President. የፕሬዚዳንቱን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ይጽፋል
5. ዓይነት. Zoologists have classified animal life in a hierarchy. ዞኦሎጂስቶች ፡ የእንስሳትን ፡ ዓይነት ፡ በደረጃ ፡ ከፋፍለውታል
6. ንቃት. Put more life into your work! በሥራህ ፡ ላይ ፡ ንቃት ፡ ጨምርበት
7. እንቅስቃሴ. There is not much life in this small village. በዚች ፡ ትንሽ ፡ መንደር ፡ ብዙ ፡ እንቅስቃሴ ፡ የለም
8. ድምቀት. He was the life of the party. ለግብዣው ፡ ድምቀት ፡ ሰጥቶት ፡ ነበር
9. ዓለም. What we do in this life will determine what will be in the next life. በዚህ ፡ ዓለም ፡ የምናደርገው ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ የምንሆነውን ፡ ይወስናል
10. ኑሮ. Village life is different from life in the city. የባላገር ፡ ኑሮ ፡ ከከተማ ፡ ኑሮ ፡ የተለየ ፡ ነው
*What is the life of a battery? ባትሪው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይቆያል ?

**bring one to life** አነቃቃ
The music seemed to bring him to life. ሙዚቃው ፡ የሚያነቃቃው ፡ መሰለ

**come to life**
1. ነፍስ ፡ ዘራ. When Jesus touched him Lazarus came to life. ኢየሱስ ፡ በዳሰሰው ፡ ጊዜ ፡ አልአዛር ፡ ነፍስ ፡ ዘራ
He came to life when the pretty girl asked him a question. ቆንጆዋ ፡ ልጃገረድ ፡ ጥያቄ ፡ በጠየቀችው ፡ ጊዜ ፡ ነፍስ ፡ ዘራ
2. ድምቀት ፡ አገኘ. The evening passed, but somehow the party never came to life. እየመሸ ፡ ቢሄድም ፡ እንኳ ፡ ግብዣው ፡ ምንም ፡ ድምቀት ፡ አላገኘም

**for life** ዕድሜ ፡ ልኩን ፤ ዕድሜ ፡ ልክ
A leg wound maimed the soldier for life. እግሩ ፡ ላይ ፡ ቁስል ፡ ወታደሩን ፡ ዕድሜ ፡ ልኩን ፡ አካለ ፡ ጐደሎ ፡ አደረገው
The robber was jailed for life, and that was the end of him. ቀማኛው ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ተፈረደበትና ፡ ፍጻሜው ፡ ሆነ

**for the life of me**
*I can't remember for the life of me what happened. የሆነው ፡ ነገር ፡ በፍጹም ፡ ትዝ ፡ እንኳን ፡ አይለኝም

**full of life** ተጫዋች
People like to invite her to parties because she is so full of life. በጣም ፡ ተጫዋች ፡ ስለሆነች ፡ ሰዎች ፡ እሷን ፡ መጋበዝ ፡ ይወዳሉ
*His speech was full of life. ንግግሩ ፡ በጣም ፡ የሚያስደስት ፡ ነበር

**give (one's) life** ሕይወቱን ፡ አሳለፈ
He gave his life for his country. ላገሩ ፡ ሕይወቱን ፡ አሳለፈ

**lose (one's) life** ሞተ
He lost his life in an accident. አደጋ ፡ ስለደረሰበት ፡ ሞተ

**matter of life or death**
1. የሞት ፡ ወይም ፡ የመኖር ፡ ነገር. This trial is serious; it is a matter of life or death for the defendant. የዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ በጣም ፡ አሳሳቢ ፡ ነው ፤ ለተከሳሹ ፡ የሞት ፡ ወይም ፡ የመኖር ፡ ነገር ፡ ነው
2. የሞት ፡ ወይም ፡ የሽረት ፡ ጉዳይ. Let me in! It's a matter of life or death. አስገቡኝ ፤ ይህ ፡ የሞት ፡ ወይም ፡ የሽረት ፡ ጉዳይ ፡ ነው

**mode of life** አኗኗር
His mode of life is ascetic. አኗኗሩ ፡ የባሕታዊ ፡ ይመስላል

**take one's own life**
He took his own life. ራሱን ፡ ገደለ

**take one's life in one's hands** ሕይወቱን ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ጣለ
We were warned that we were taking our lives in our hands by going through that swampy area. በረግረጉ ፡ ውስጥ ፡ መሄዳችን ፡ ሕይወታችንን ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ መጣላችን ፡ መሆኑ ፡ ተነግሮን ፡ ነበር

**to the life**
*The portrait is my uncle to the life. ሥዕሉ ፡ አጐቴን ፡ በአምሳል ፡ እንዳለ ፡ አድርጎ ፡ ያሳያል

**way of life** አኗኗር
These stories are representative of the Ethiopian way of life. እነዚህ ፡ ታሪኮች ፡ የኢትዮጵያን ፡ አኗኗር ፡ የሚገልጹ ፡ ናቸው
[See also 'communal, duration, early, easy, flower, hazard, late, lead, loose, married, prime, real, retire, risk, run, sacrifice, sign, state, station, survivor, vagrant, walk']

**life belt** የመንሳፈፊያ ፡ ትጥቅ
Life belts are placed under the seats in the plane. የመንሳፈፊያ ፡ ትጥቅ ፡ ከአውሮፕላኑ ፡ መቀመጫ ፡ ሥር ፡ አለ

**lifeblood** የደም ፡ ሥር
Oil is the lifeblood of their economy. ዘይት ፡ ለኢኮኖሚያቸው ፡ የደም ፡ ሥር ፡ ነው

**lifeboat** የሕይወት ፡ ማዳኛ ፡ ጀልባ
The lifeboats are placed by the side of the ship. የሕይወት ፡ ማዳኛ ፡ ጀልባዎች ፡ ከመርከቧ ፡ ጐን ፡ ተቀምጠዋል

**lifeguard** ሕይወት ፡ አዳኝ
A lifeguard is on duty at the swimming pool. ሕይወት ፡ አዳኝ ፡ በመዋኛው ፡ ስፍራ ፡ ተረኛ ፡ ነው

**life imprisonment** ዕድሜ ፡ ይፍታህ ፤ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ እስራት
He was sentenced to life imprisonment. ዕድሜ ፡ ይፍታህ ፡ (የዕድሜ ፡ ልክ ፡ እስራት) ፡ ተፈረደበት

**life insurance**
1. የሕይወት ፡ዋስትና ፡ ዋጋ. I pay life insurance every three months. በየሦስት ፡ ወሩ ፡ የሕይወት ፡ ዋስትና ፡ ዋጋ ፡ እከፍላለሁ
2. የሕይወት ፡ ዋስትና. His wife is the beneficiary of his life insurance. ሚስቱ ፡ የሕይወት ፡ ዋስትናው ፡ ተጠቃሚ ፡ ናት

**lifeless** (adj.)
1. ፍጡር ፡ የሌለበት. The moon is a lifeless planet. ጨረቃ ፡ ፍጡር ፡ የሌለባት ፡ ዓለም ፡ ናት
2. ሕይወት ፡ የሌለው. Lifeless matter does not reproduce. ሕይወት ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ አይራባም

**lifeless** (adv.) በድን ፡ ሆኖ
He lay lifeless on the ground. በድን ፡ ሆኖ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ነበር

**lifeless body** ሬሳ
The lifeless body floated ashore. ሬሳው ፡ ተንሳፎ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ መጣ

**lifelong** የዕድሜ ፡ ልክ
These two old men have been lifelong friends. እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሽማግሌዎች ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ወዳጆች ፡ ናቸው

**lifelong imprisonment, to ~** ዕድሜ ፡ ይፍታህ
The judge doomed him to lifelong imprisonment. ዳኛው ፡ ዕድሜ ፡ ይፍታህ ፡ ፈረደበት

**lifetime**
1. ዕድሜ. Grandfather has seen many changes during his lifetime. አያቴ ፡ በዕድሜያቸው ፡ ብዙ ፡ ለውጦች ፡ አይተዋል
2. ያንድ ፡ ሰው ፡ ዕድሜ. A thing like that happens only once in a lifetime. እንደዚያ ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ዕድሜ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሚደርስ ፡ ነው

**life vest** የመንሳፈፊያ ፡ ትጥቅ
The life vest is under the seat. የመንሳፈፊያው ፡ ትጥቅ ፡ ከመቀመጫው ፡ ሥር ፡ ነው

**lift** (vt.)
1. አነሣ. He could not lift the heavy box. ከባዱን ፡ ሣጥን ፡ ማንሣት ፡ አቃተው
The box is too heavy to lift. ሣጥኑን ፡ ለማንሣት ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ነው
The court decision lifts the ban on the book. የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ የመጽሐፉን ፡ እገዳ ፡ ያነሣለታል
2. አነቃቃ. The good news lifted his spirits. ጥሩው ፡ ወሬ ፡ መንፈሱን ፡ አነቃቃው
3. ከፍ ፡ አደረገ. The children lifted their voices in song. ልጆቹ ፡ ድምፃቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ዘመሩ
*The window will not lift. መስኮቱ ፡ ወደላይ ፡ አልሳብ ፡ አለ

**lift** (vi.)
1. ገፈፈ. Toward noon, the fog lifted. ወደ ፡ እኩለ ፡ ቀን ፡ ገደማ ፡ ጭጋጉ ፡ ገፈፈ
2. ነቃ ፡ አለ. His spirits lifted when he heard the news. ወሬውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ መንፈሱ ፡ ነቃ ፡ አለ
3. ለቀቀ. The sky lightened as the clouds lifted. ደመና ፡ ሲለቅ ፡ ሰማዩ ፡ ጠራ

**be lifted**
1. አበቃ. The boycott was lifted. የንግዱ ፡ አድማ ፡ አበቃ
2. ተሰረዘ. The governor ordered that the restrictions be lifted. አገረ ፡ ገዢው ፡ ገደቦች ፡ እንዲሰረዙ ፡ አዘዘ

**lift (a) finger**
*I won't lift a finger for him. ምንም ፡ ቢሆን ፡ እርዳታ ፡ አላደርግለትም

**lift (one's) head** ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንጋጠጠ
The pupils lifted their heads to see the plane overhead. ተማሪዎቹ ፡ የሚበረውን ፡ አውሮፕላን ፡ ለማየት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንጋጠጡ

**lift oneself up** ራሱን ፡ አወጣ
He lifted himself up from poverty. ራሱን ፡ ከ ድህነት ፡ አወጣ

**lift up**
1. ቀና ፡ አደረገ. He lifted up his eyes and looked at me. ዓይኑን ፡ ቀና ፡ አድርጎ ፡ ተመለከተኝ
Lift your head up! ራስህን ፡ ቀና ፡ አድርገው
2. አነሣ. Lift your arms up! እጅህን ፡ አንሣ
[See also 'hand']

**lift** (n.), **give a ~**
1. ረዳ. Give me a lift with this job! ይህንን ፡ ሥራ ፡ እርዳኝ
2. አደረሰ. Will it put you out to give me a lift home? ቤቴ ፡ ብታደርሰኝ ፡ አስቸግርሃለሁ ?
3. መንፈሱን ፡ አነቃቃው. Praise always gives me a lift. ምስጋና ፡ ሁልጊዜ ፡ መንፈሴን ፡ ያነቃቃዋል

**lift** (n.) አሳንሰር ፤ አሳንሱር ፤ ኤሌቬተር
He got in the lift and went to the tenth floor. አሳንሰሩ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ዐሥረኛው ፡ ፎቅ ፡ ወጣ

**light** (lighted or lit), vt.
1. ለኰሰ. I want to light my pipe first. መጀመሪያ ፡ ፒፓዬን ፡ ልለኩሰ
2. አበራ. Lamps light the street. መብራቶች ፡ ጐዳናዎችን ፡ ያበራሉ
It is dark; light the lamp! ጨልሟል ፤ መብራቱን ፡ አብራው
3. አያያዘ. Wait till I light the fire. እሳቱን ፡ እስካያይዝ ፡ ድረስ ፡ ቆይ
4. ጫረ. Light a match so we can see. ለማየት ፡ እንድንችል ፡ ክብሪት ፡ ጫር

**light** (vi.)
1. ተቀጣጠለ. The dry wood lights easily. ደረቅ ፡ ዕንጨት ፡ በቀላሉ ፡ ይቀጣጠላል
2. አረፈ. The bird lighted on the tree. ወፏ ፡ በዛፉ ፡ ላይ ፡ አረፈች

3. በድንገት ፡ አረፈ. His eyes lighted upon a coin in the road. ዐይኖቹ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በወደቀው ፡ ሳንቲም ፡ ላይ ፡ በድንገት ፡ አረፉ
4. መታ. The blow lit on his head. ዱላው ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ መታው
5. ወረደ. He lighted from his horse. ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወረደ

**be lit** ተያያዘ
Is your cigarette still lit? ሲጃራህ ፡ አሁንም ፡ እንደተያያዘ ፡ ነው ?

**light up** (vt.)
1. ወለል ፡ አደረገ. The flashlight lit up the woods, and he could see the animal. ባትሪው ፡ ጫካውን ፡ ወለል ፡ ስላደረገው ፡ እንስሳውን ፡ ሊያየው ፡ ቻለ
2. አበራ. A smile lit up her face. ፈገግታ ፡ ፊቷን ፡ አበራው
3. ብርሃን ፡ ሰጠ. Hundreds of candles lighted up the cave. በብዙ ፡ መቶ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሻማዎች ፡ ለዋሻው ፡ ብርሃን ፡ ሰጡት

**light up** (vi.)
1. ቊልጭ ፡ ቊልጭ ፡ አለ. The children's eyes lit up. የልጆቹ ፡ ዓይን ፡ ቊልጭ ፡ ቊልጭ ፡ አለ
2. ፈካ. Her face lighted up with joy. ፊቷ ፡ በደስታ ፡ ፈካ
[See also 'fire, poorly']

## light (n.)
1. ብርሃን. God said, "Let there be light". እግዚአብሔርም ፡ አለ ፤ ብርሃን ፡ ይሁን
2. መብራት. On arriving home, I found the lights on. ቤት ፡ ስደርስ ፡ መብራቱ ፡ በርቶ ፡ አገኘሁት
3. ክብሪት. Do you have a light? I have run out of matches. ክብሪት ፡ አለህ ? ክብሪት ፡ አለቀብኝ
4. የትራፊክ ፡ መብራት. Don't cross till the light changes! የትራፊኩ ፡ መብራት ፡ እስኪለወጥ ፡ አትሻገር
5. መልክ. That throws quite a different light on the matter. ያ ፡ ለነገሩ ፡ ሌላ ፡ መልክ ፡ ይሰጠዋል
I never considered the matter in that light. ነገሩን ፡ ፈጽሞ ፡ በዚያ ፡ መልክ ፡ አልተመለከትኩም ፡ ነበር
6. ማብራሪያ. We need more light on the subject. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ተጨማሪ ፡ ማብራሪያ ፡ ያስፈልገናል
*Summer has more hours of light. በበጋ ፡ ቀኑ ፡ ረዘም ፡ ይላል

**bring to light** አስገኘ
The investigation brought many new facts to light. ምርመራው ፡ ብዙ ፡ አዳዲስ ፡ ነገሮች ፡ አስገኘ

**(be) brought to light** ተገኘ
New facts have been brought to light. አዲስ ፡ መረጃዎች ፡ ተገኝተዋል

**come to light** ተገኘ
Some previously unknown letters have come to light. ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያልታወቁ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ተገኝተዋል

**in the light of** ስንመለከት
In the light of his earlier behavior, it would be unwise to give him a job. የቀድሞውን ፡ ጠባዩን ፡ ስንመለከት ፡ ሥራውን ፡ ለርሱ ፡ መስጠት ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**leading light** ጉልቶ ፡ የሚታይ ፡ ሰው
George Washington is one of the leading lights in American history. ጆርጅ ፡ ዋሽንግተን ፡ በአሜሪካን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ጉልተው ፡ ከሚታዩት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ነው

**put on the light** መብራቱን ፡ አበራ
It is dark in the room; put on the light! ክፍሉ ፡ ስለጨለመ ፡ መብራቱን ፡ አብራው

**put out the light** መብራቱን ፡ አጠፋ
Put out the light before you leave! ከመሄድህ ፡ በፊት ፡ መብራቱን ፡ አጥፋው

**see the light** ነገሩ ፡ ገባ(ው)
He finally saw the light and accepted the idea. በመጨረሻ ፡ ነገሩ ፡ ስለገባው ፡ ሐሳቡን ፡ ተቀበለ

**shed light**
1. ብርሃን ፡ ሰጠ. The lamp shed a soft light. ፋኖሱ ፡ የሚሰጠው ፡ ብርሃን ፡ ደብዛዛ ፡ ነው
2. ማብራሪያ ፡ ሰጠ. This document sheds light on the financial problem. ይህ ፡ ሰነድ ፡ ስለ ፡ ገንዘቡ ፡ ችግር ፡ ማብራሪያ ፡ ይሰጣል

**(it's) staying light**
*It's staying light much longer. ጀምበሯ ፡ ቶሎ ፡ አትጠልቅም

**throw light on**
1. አብራራ. His confession threw light on a mystery of long standing. ኑዛዜው ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተሰውሮ ፡ የነበረውን ፡ ነገር ፡ አብራራ
2. ፍንጭ ፡ ሰጠ. The discovery throws light on conditions in early times. የተገኘው ፡ ነገር ፡ የጥንት ፡ ሁኔታ ፡ እንዴት ፡ እንደነበረ ፡ ፍንጭ ፡ ይሰጣል
[See also 'shine, traffic light']

## light (adj.)
1. ስስ. Why don't you take your light coat? ስሱን ፡ ኮትህን ፡ ለምን ፡ አትወስድም ?

2. ቀላል. The consequences of the accident were light. አደጋው ፡ ያስከተለው ፡ ቀላል ፡ ነበር
Light rain fell yesterday. ትናንት ፡ ቀላል ፡ ዝናብ ፡ ጣለ
She has been given some light duties. ቀላል ፡ ሥራ ፡ ተሰጥቷት ፡ ነበር
3. ቀለል ፡ ያለ. He eats only light food for breakfast. ለቁርስ ፡ የሚበላው ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ ምግብ ፡ ብቻ ፡ ነው
4. አነስ ፡ ያለ. The bank cashier made good the shortage and was given a light sentence. የባንኩ ፡ ገንዘብ ፡ ከፋይ ፡ የጐደለውን ፡ ስለሞላ ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ ተወሰነበት
5. ብሩህ. She prefers light colors. ብሩህ ፡ ቀለም ፡ ትወዳለች
6. ነጭ. The stripes graduate from light to dark. መሥመሮቹ ፡ ከነጭ ፡ ወደ ፡ ጥቁር ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ይተላለፋሉ
*He has a light manner of dealing with this problem. ነገሩን ፡ ሲይዝ ፡ እንደ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ አይቈጥርም
*She has a light complexion. ቀላ ፡ ያለች ፡ ናት

**lighten** (vt.)
1. ቀነሰ (ለት). He lightened the load, and I could carry it easily. ሸክሙን ፡ ስለቀነሰልኝ ፡ በቀላሉ ፡ ልሸከመው ፡ ቻልኩ
2. ጭነቱ ፡ እንዲቀለው. We threw some boxes overboard to lighten the boat. መርከቧ ፡ ጭነቱ ፡ እንዲቀላት ፡ በማለት ፡ ጥቂት ፡ ሣጥኖች ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ጣልን
3. አቃለለ. He was able to lighten the problem by working hard. ጠንክሮ ፡ በመሥራት ፡ ችግሩን ፡ ለማቃለል ፡ ቻለ
4. አነጣ. The sun lightened her hair. ፀሐዩ ፡ ጸጉሯን ፡ አነጣው
5. ለ - - - ብርሃን ፡ ሰጠ. A full moon lightened the road. ሙሉ ፡ ጨረቃ ፡ ለመንገዱ ፡ ብርሃን ፡ ሰጠ
6. አደመቀ. His jokes lighten any occasion. ጨዋታው ፡ ማንኛቸውንም ፡ ሁኔታ ፡ ያደምቃል

**lighten** (vi.)
1. ፈገግ ፡ አለ. His face lightened when he heard the good news. ጥሩ ፡ ወሬ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱ ፡ ፈገግ ፡ አለ
2. ጠራ. The sky lightened as the clouds lifted. ደመና ፡ ሲለቅ ፡ ሰማዩ ፡ ጠራ
3. ተብለጨለጨ. It lightened, and it thundered all night. ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ እየተብለጨለጨና ፡ ነጐድጓድ ፡ እያሰማ ፡ አደረ

**lighten one's heart** አስደሰተ
Such news lightens my heart. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ወሬ ፡ ያስደስተኛል

**lighter** (n.) ማቀጣጠያ
That cigarette lighter is expensive. ያ ፡ የሲጃራ ፡ ማቀጣጠያ ፡ ውድ ፡ ነው

**lighter, get ~** እየቀለለ ፡ ይሄዳል
The drum gets lighter as the water leaks out. ውኃው ፡ እየፈሰሰ ፡ ሲወጣ ፡ በርሜሉ ፡ እየቀለለ ፡ ይሄዳል

**light-footed** ቀልጣፋ
A light-footed dancer makes a pleasant dancing companion. ቀልጣፋ ፡ ደናሽ ፡ የምታስደስት ፡ የዳንስ ፡ ጓድ ፡ ይወጣታል

**light-headed** የማይረባ
That light-headed girl thinks of nothing but parties and clothes. ያች ፡ የማትረባ ፡ ልጅ ፡ ከፓርቲና ፡ ከልብስ ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ አታስብም

**be light-headed** ራሱን ፡ አዞረ
The sick man was light-headed from fever. በሽተኛው ፡ ከትኩሳት ፡ የተነሣ ፡ ራሱን ፡ ያዞረው ፡ ነበር

**lighthearted** ግድ ፡ የሌለው
Since he is lighthearted, he didn't mind even though he was passed by for an appointment to office. ግድ ፡ የሌለው ፡ ስለሆነ ፡ ሹመት ፡ ቢያልፈውም ፡ ቅር ፡ አላለው

**lighthouse** የፋና ፡ ቤት
The lighthouse is built on a high promontory. የፋናው ፡ ቤት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጉጥ ፡ ላይ ፡ ነው

**light infantry** ቀላል ፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ እግረኞች
Light infantry followed up the cavalry attack. ቀላል ፡ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ እግረኞች ፡ እያጠቁ ፡ የሚሄዱትን ፡ ፈረሰኞች ፡ ተከተሉ

**lighting** ብርሃን
The lighting in this room is bad. የዚህ ፡ ክፍል ፡ ብርሃን ፡ ደካማ ፡ ነው
[See also 'stroke']

**lightly**
1. ቀስ ፡ ብሎ. Please press lightly on the button! መጥሪያውን ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ ተጫነው
Walk lightly so you won't waken the child. ልጁን ፡ እንዳትቀሰቅስ ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ ተራመድ
2. እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር. You shouldn't treat that warning so lightly. ያንን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ መቍጠር ፡ የለብህም
3. አንኳሶ. He likes to speak lightly of other persons. ስለ ፡ ሌሎች ፡ አንኳሶ ፡ መናገር ፡ ይወዳል

**eat lightly** ቀላል ፡ ምግብ ፡ በላ
In the morning he eats lightly. ጧት ፡ ጧት ፡ የሚበላው ፡ ቀላል ፡ ምግብ ፡ ነው
[See also 'roast, think']

**lightning** መብረቅ
Lightning struck the church steeple. መብረቅ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ጉልላት ፡ መታው
**streak of lightning** መብረቅ
He moves like a streak of lightning. ልክ ፡ እን ደ ፡ መብረቅ ፡ ይተኰሳል
**stroke of lightning** መብረቅ
The house was hit by a stroke of lightning. ቤቱን ፡ መብረቅ ፡ መታው

**(be) likable** የሰው ፡ መውደድ ፡ አለው
He is a likable fellow; that's why he makes so many friends. የሰው ፡ መውደድ ፡ ስላለው ፡ ብዙ ፡ ጓደኞች ፡ ያፈራል

**like** (vt.)
1. ወደደ. I like this kind of cake. ይህን ፡ ዓይነት ፡ ኬክ ፡ እወዳለሁ
Do you like to dance? ዳንስ ፡ ትወዳለህ ?
I like him. እወደዋለሁ
2. ፈለገ. Would you like another cup of coffee? ቡና ፡ ለመድገም ፡ ትፈልጋለህ ?
I wouldn't like to disturb you now. አሁን ፡ ላስ ቸግርህ ፡ አልፈልግም
3. ተጋበዘ. "What would you like?", the host asked his guest. ምን ፡ ትጋበዛለህ ፡ ብሎ ፡ ባለቤቱ ፡ እንግዳውን ፡ ጠየቀ
**like** (vi.) አሰኘ
I will go when I like. ሲያሰኘኝ ፡ እሄዳለሁ

**like** (n.), **the ~ of**
1. እንዲህ. Did you ever see the like of this rain? እንዲህ ፡ ያለ ፡ ዝናብ ፡ አይተህ ፡ ታውቃለህ ?
2. ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር. Did you ever see the like of it? ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ አይተህ ፡ ታውቃለህ ?
**likes** የሚወደው ፡ ነገር
What are your likes and dislikes? የምትወደውና ፡ የምትጠላው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ምንድነው ?
**like** (adj.), **~ amount** ያንኑ ፡ ያህል
Bring me a cup of sugar, and a like amount of flour! አንድ ፡ ሲኒ ፡ ስኳርና ፡ ያንኑ ፡ ያህል ፡ ዱቄት ፡ አምጣልኝ
**like** (prep.) እንደ
The roar of a mill is like a lion's. የወፍጮ ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ነው
He ran like mad. እንደ ፡ እብድ ፡ ሮጠ
**and the like** የመሳሰሉት
Barley, oats, and the like are cereals. ገብስና ፡ አጃን ፡ የመሳሰሉት ፡ ጥራጥሬ ፡ ይባላሉ

**be like** መሰለ
What is he like? I have never met him. ምን ፡ ይመስላል ? አይቼውም ፡ አላውቅ
**just like** ቁርጥ
You are just like my sister. ቁርጥ ፡ እኅቴን ፡ ነሽ
**(it is) just like him** ልማዱ ፡ ነው
It is just like him to go away without telling us. ለኛ ፡ ሳይነግረን ፡ መሄድ ፡ ልማዱ ፡ ነው
**look like** (relative verb) + መሰለ
It looks like rain. የሚዘንብ ፡ ይመስላል
**something like** አንድ
The cost will be something like five dollars. ዋጋው ፡ አንድ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ነው
**there is nothing like**
*There is nothing like traveling. መንገድ ፡ መሄድን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ የለም
*There is nothing like leather for making shoes. ለጫማ ፡ መሥሪያ ፡ ቆዳን ፡ የሚያህል ፡ የለም
**what ... like?** እንዴት
What is the weather like today? ዛሬ ፡ አየሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
[See also 'such']

**likeliest, the ~**
*What do you think is the likeliest time to find him at home? እቤት ፡ የሚገኘው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ይመስልሃል ?

**likelihood**
*There is little likelihood that he will win. ለማሸነፍ ፡ ያለው ፡ ተስፋ ፡ ትንሽ ፡ ነው
*Is there any likelihood of rain this afternoon? ዛሬ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ይዘንብ ፡ ይሆን ?
*In all likelihood, he will get the job. በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ሥራውን ፡ የሚያገኝ ፡ ይመስላል

**likely** (adj.)
1. ሊሆን ፡ የሚችል. That's a likely story. ይህ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ታሪክ ፡ ነው
2. ምቹ. Is this a likely place to fish? ዓሣ ፡ ለማጥመድ ፡ ይህ ፡ ምቹ ፡ ቦታ ፡ ነው ?
*One likely result of this heavy rain is the rising of the river. ይህ ፡ ከባድ ፡ ዝናብ ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችለው ፡ አንዱ ፡ ነገር ፡ የወንዙ ፡ መሙላት ፡ ነው
**likely** (adv.)
*I shall very likely be here again. ወደዚህ ፡ ሳል መለስ ፡ አልቀርም
**be likely to**
1. (verbal noun) + የማይቀር ፡ ነው. Novices are likely to make some mistakes. ጀማሪዎች ፡ ስሕተት ፡ መሥራታቸው ፡ የማይቀር ፡ ነው

2. ስ + negative imperfect + አይቀርም. The fog is likely to persist in most areas. ጭጋጉ ፡ በ ብዙ ፡ ቦታዎች ፡ ሳይቆይ ፡ አይቀርም
3. ል + imperfect + ይችላል. A tense rope is likely to break. የተወጠረ ፡ ገመድ ፡ ሊበጠስ ፡ ይችላል

**be more likely**
That's more likely! እንዲያ ፡ በለኝ

**it is likely to** የም + imperfect + ይመስላል
Do you think it is likely to rain? የሚዘንብ ፡ ይ መስልሃል ?

**it is likely to be** ሊሆን ፡ ይችላል
It is likely to be hot in August. በነሐሴ ፡ ሞቃት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

**it is not likely** (relative imperfect) + አይመስልም
It is not likely that he will come any more. ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ለወደፊቱ ፡ የሚመጣ ፡ አይ መስልም

## liken መሰለ
The poet likened the clouds to a human face. ገጣሚው ፡ ደመናውን ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ መሰለው

## likeness መመሳሰል
The likeness between the two sisters is remarkable. የሁለቱ ፡ እኅትማማቾች ፡ መመሳሰል ፡ የ ሚያስገርም ፡ ነው
*That photograph is a good likeness of you. ያ ፡ ፎቶግራፍ ፡ አንተን ፡ ቁጭ ፡ ነው

**be in the likeness of** የ - - ቅርጽ ፡ አለው
The cloud is in the likeness of a camel. ደመናው ፡ የግመል ፡ ቅርጽ ፡ አለው

## likewise እንደዚሁ
Jim will sing, and Mary likewise. ጂም ፡ ይዘም ራል ፤ ሜሪም ፡ እንደዚሁ
*Watch him, and do likewise! ተመልከተውና ፡ እሱ ፡ እንደሚያደርገው ፡ አድርግ

**and likewise** - - - ም - - - ም
He is tall, and likewise strong. ረዥምም ፡ ጠንካ ራም ፡ ነው

## liking, have a ~ for ወደደ
I have a liking for Ethiopian food. የኢትዮጵያን ፡ ምግብ ፡ እወዳለሁ

**be to one's liking** ወደደ
+Is this food to your liking? ይህን ፡ ምግብ ፡ ትወደዋለህ ?

**not to one's liking** ደስ ፡ አይለውም
This is not to my liking. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ አይለኝም

**take a liking to**
*He took a liking to me right off. ገና ፡ ሲያየኝ ፡ ውቃቢው ፡ ወደደኝ

## lily [የአበባ ፡ ዓይነት]

## limb
1. እጅና ፡ እግር. He lost all his limbs in the war. በጦርነቱ ፡ እጅና ፡ እግሩን ፡ ሁሉ ፡ አጣ
2. አካል (pl. አካላት). The legs are articulate limbs. እግሮች ፡ ታጣፊ ፡ አካላት ፡ ናቸው
3. ቅርንጫፍ. He sawed the limb off the tree. የዛፉን ፡ ቅርንጫፍ ፡ በመጋዝ ፡ ቈረጠ

**move a limb** ተንቀሳቀሰ
I could not move a limb. ምንም ፡ ልንቀሳቀስ ፡ አልቻልኩም

## limber (v.) አፍታታ
Exercise limbers the body. ልምምድ ፡ ሰውነት ን ፡ ያፍታታል

**limber up** ሰውነቱን ፡ አፍታታ
The dancers limbered up. ዳንሰኞቹ ፡ ሰውነታቸ ውን ፡ አፍታቱ

## limber (adj.)
1. የሚለመጥ. The limber branches of the tree sway in the wind. የሚለመጡት ፡ የዛፍ ፡ ቅር ንጫፎች ፡ በነፋስ ፡ ይወዛወዛሉ
2. የቀለጠፈ. A piano player should have limber fingers. ፒያኖ ፡ የሚጫወት ፡ ሰው ፡ የ ቀለጠፉ ፡ ጣቶች ፡ እንዲኖሩት ፡ ያስፈልጋል

## lime (n.)
1. ሎሚ. Limes grow in Ethiopia. ሎሚ ፡ ኢትዮ ጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይበቅላል
2. ኖራ. The soil does not contain enough lime. አፈሩ ፡ ብዙ ፡ ኖራ ፡ የለበትም

**lime** (adj.) የሎሚ
Lime juice makes a nice drink. የሎሚ ፡ ጭማ ቂ ፡ ጥሩ ፡ መጠጥ ፡ ይወጣዋል

## limelight, be in the ~
*Film stars are often in the limelight. የፊልም ፡ ተጫዋቾች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ዓይን ፡ የሚያርፍባቸው ፡ ናቸው

## limestone በሃ ፡ ድንጋይ
Limestone is necessary for making cement. በሃ ፡ ድንጋይ ፡ ሲሚንቶ ፡ ለመሥራት ፡ አስፈላ ጊ ፡ ነው

## limit (v.) ወሰነ
Limit your essay to three paragraphs! ድርሰት ህን ፡ በሦስት ፡ አንቀጽ ፡ ወስነው

We must limit the expense to $10. ወጪው ፡ ከዐሥር ፡ ብር ፡ እንዳይበልጥ ፡ መወሰን ፡ አለብን
*Please limit your talk to three minutes! ንግግርህን ፡ ከሦስት ፡ ደቂቃ ፡ በላይ ፡ አታስረዝመው

**limit** (n.) **ልክ**
There is a limit to everything. ለሁሉም ፡ ነገር ፡ ልክ ፡ አለው
Speed limit: thirty-five miles an hour. የፍጥነት ፡ ልክ ፡ በሰዓት ፡ ሠላሳ ፡ አምስት ፡ ማይል

**limits**
1. **ክልል.** The limits of the town are some distance from the center. የከተማው ፡ ክልል ፡ ከመሀል ፡ ከተማ ፡ ራቅ ፡ ያለ ፡ ነው
2. **መጠን.** As we grow older, we learn the limits of our abilities. እያረጀን ፡ ስንሄድ ፡ የችሎታችንን ፡ መጠን ፡ እንገነዘባለን

**reach the limit of ጨረሰ**
I've reached the limit of my patience. ትዕግሥቴን ፡ ጨርሻለሁ

**that's the limit እንግዲህ ፡ በቃህ**
Now that you have insulted my father, that's the limit! አሁን ፡ አባቴን ፡ ከሰደብክ ፡ እንግዲህ ፡ በቃህ !

**within limit በመጠኑ**
I am willing to help you within limit. በመጠኑ ፡ ልረዳህ ፡ ፈቃደኛ ፡ ነኝ

**limitation**
1. **የተወሰነ ፡ መሆን.** He is unwilling to admit any limitations in his knowledge of Amharic. ያማርኛ ፡ ችሎታው ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑን ፡ ለማመን ፡ አይፈልግም
2. **ገደብ.** Anybody can take part in the contest with the following limitations. የሚከተሉትን ፡ ገደቦች ፡ አክብሮ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በውድድሩ ፡ ተካፋይ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል
3. **ዕንቅፋት.** His height is a limitation. ቁመቱ ፡ ዕንቅፋት ፡ ይሆነዋል

**limited** (adj.)
1. **የተወሰነ.** We have a limited amount of space available. ያለን ፡ ቦታ ፡ የተወሰነ ፡ ነው
He has limited intelligence. የአእምሮ ፡ ችሎታው ፡ የተወሰነ ፡ ነው
This discount is good for a limited time only. ቅናሹ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. **አጭር.** Our time is limited. ያለን ፡ ጊዜ ፡ አጭር ፡ ነው

**be limited to**
*His food was limited to bread and water. ምግቡ ፡ ዳቦና ፡ ውኃ ፡ ብቻ ፡ ነበር

**(be) limitless ወሰን ፡ የለውም**
Spatial distance is limitless. የጠፈር ፡ ስፋት ፡ ወሰን ፡ የለውም

**limp** (v.) **አነከሰ**
He limps noticeably. ሲያነክስ ፡ ይታወቅበታል

**limp** (n.) **ማንከስ**
His limp has gotten worse since his illness. ከታመመ ፡ ወዲህ ፡ ማንከሱ ፡ ብሶበታል

**(be) limp ተሻሸ**
My collar is too limp; I need a fresh one. ኮሌታዬ ፡ ተሻሽቷል ፤ አዲስ ፡ ያስፈልገኛል

**become limp ልፍስፍስ ፡ ሆነ**
The cardboard became limp when it got wet. ካርቶኑ ፡ በረጠበ ፡ ጊዜ ፡ ልፍስፍስ ፡ ሆነ

**go limp ተዝለፈለፈ**
She suddenly went limp and fell. በድንገት ፡ ተዝለፍልፋ ፡ ወደቀች

**look limp ጠወለገ**
The flowers look limp in the heat. አበቦቹ ፡ በፀሐዩ ፡ ምክንያት ፡ ጠውልገዋል

**limpid የጠራ**
Her blue eyes are like pools of limpid water. ሰማያዊ ፡ ዓይኖቿ ፡ የጠራ ፡ ውኃ ፡ ይመስላሉ

**line** (v.)
1. **አሠመረ.** Please line your paper with a pencil and ruler! ወረቀትህን ፡ በእርሳስና ፡ በማሥመሪያ ፡ አሥምር
2. (= intr.) **ተደረደረ.** Cars lined the road for many miles. መኪናዎች ፡ ለብዙ ፡ ማይል ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ተደርድረዋል

**be lined**
1. **ተጨማደደ.** His face was lined by age. ፊቱ ፡ ከእርጅና ፡ የተነሣ ፡ ተጨማዷል
2. **ተለበደ.** The trunk is lined with canvass. ሣጥኑ ፡ በሸራ ፡ ተለብዷል
*The jacket is lined with silk. የኮቱ ፡ ገበር ፡ ሐር ፡ ነው
*His pockets were lined with money. ኪሱ ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ነበር
*The road is lined with trees. ከመንገዱ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ዛፎች ፡ አሉ

**line out አወጣ**
We followed the plan he had lined out. እሱ ፡ ያወጣውን ፡ እቅድ ፡ ተከተልን

**line (the) streets በመንገዱ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ተሰለፈ**
Crowds lined the streets to watch the Emperor pass by. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሲያልፉ ፡ ለመመልከት ፡ ሕዝቡ ፡ በመንገዱ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ተሰለፈ

**line up** (vt.)
1. አገኘ. How many volunteers did you line up? ስንት ፡ ፈቃደኞች ፡ አግኝተሃል ?
2. አሰለፈ. The corporal lined up his men. ዐሥር ፡ አለቃው ፡ ሰዎቹን ፡ አሰለፈ

**line up** (vi.) ተሰለፈ
There are a lot of people lined up in front of the box office. ቲኬት ፡ መሸጫው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ተሰልፏል

**(be) lined up** ተቀጣጥለው ፡ ቆሙ
Cars were lined up along the road for miles. መኪናዎች ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ለብዙ ፡ ማይል ፡ ተቀጣጥለው ፡ ቆመው ፡ ነበር

**(have one) line up** አሰለፈ
Have the boys line up in the hall! ልጆቹን ፡ በአዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ አሰልፋቸው

**line** (n.)
1. መሥመር. I still have a few lines to write. ገና ፡ ጥቂት ፡ መሥመሮች ፡ መጻፍ ፡ አለብኝ
How many bus lines are there in this city? በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ስንት ፡ የአውቶቡስ ፡ መሥመሮች ፡ አሉ ?
The soldiers formed themselves into lines. ወታደሮቹ ፡ በመሥመር ፡ ገቡ
I shall proceed along these lines in my investigation. ምርመራዬን ፡ በዚሁ ፡ መሥመር ፡ እቀጥላለሁ
2. የስልክ ፡ መሥመር. The line is still busy. የስልኩ ፡ መሥመር ፡ እንደ ፡ ተያዘ ፡ ነው
3. ሰልፍ. People were standing in a long line. ሰዎች ፡ በረጅም ፡ ሰልፍ ፡ ቆመው ፡ ነበር
4. ዘር. Haile Sellassie is the descendant of a long line of kings. ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ የጥንት ፡ ነገሥታት ፡ ዘር ፡ አላቸው
5. ስልት. I cannot follow this line of argument. የዚህን ፡ ክርክር ፡ ስልት ፡ ልከተል ፡ አልችልም
6. ሐረግ. Short lines characterize his poetry. የሱ ፡ ግጥም ፡ ባጭር ፡ ሐረጉ ፡ ይታወቃል
7. ዓይነት. He carries the best line of shoes in town. በከተማው ፡ የሚገኙ ፡ ምርጥ ፡ ዓይነት ፡ ጫማዎችን ፡ ይሸጣል
Please proceed along these lines till further notice! ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪተሰጠ ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ቀጥሉ
This line of policy seeks security through military alliances. የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ፖሊሲ ፡ ጸጥታን ፡ በወታደራዊ ፡ ስምምነት ፡ ለማስገኘት ፡ የሚፈልግ ፡ ነው
8. ዓይነት ፡ እቃ. We do not carry that line. የዚህ ፡ ዓይነት ፡ እቃ ፡ አናስመጣም
9. ድንበር. This is the line between Texas and Mexico. ይህ ፡ የቴክሳስና ፡ የሜክሲኮ ፡ ድንበር ፡ ነው
10. የዓሣ ፡ ማጥመጃ. My line caught on a snag. የዓሣ ፡ ማጥመጃዬ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ተተበተበ
11. ሽቦ. The wash is still hanging on the line. የታጠበው ፡ ልብስ ፡ ሽቦው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተሰጣ ፡ ነው
12. ደብዳቤ. Yesterday I received a line from my friend. ትናንትና ፡ ከጓደኛዬ ፡ ደብዳቤ ፡ ደረሰኝ
13. ሥራ. What line is he in? ሥራው ፡ ምንድነው ?
*There is a long line of cars ahead of us. ከፊታችን ፡ ብዙ ፡ መኪና ፡ ተቀጣጥሎ ፡ ይሄዳል

**lines**
1. ቅርጽ. This car has good lines. ይህ ፡ መኪና ፡ ጥሩ ፡ ቅርጽ ፡ አለው
2. መልክ. Along what lines will the story be written? ታሪኩ ፡ በምን ፡ መልክ ፡ ይጻፋል ?
3. ግንባር. The army advanced toward the enemy lines. ጦሩ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ግንባር ፡ ገፋ
*There were deep lines in his face. ፊቱ ፡ ተጨማዷል

**all along the line**
1. ሁሉም ፡ ነገር. He had success all along the line. ሁሉም ፡ ነገር ፡ ሆነለት
2. ሙሉ ፡ በሙሉ. The report has proved inaccurate all along the line. ሪፖርቱ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ስሕተት ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

**(be) along the line** ከ - - ጋር ፡ ተያያዘ
It is along the line of what we discussed. ከተነጋገርንበት ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው

**bring into line**
1. በመሥመር ፡ አስገባ. The riders brought their mounts into line. ፈረሰኞቹ ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ በመሥመር ፡ አስገቡ
2. እንዲስማማ ፡ አደረገ. We must bring the dissidents into line. ተቃዋሚዎችን ፡ እንዲስማሙ ፡ ማድረግ ፡ አለብን

**draw the line** ወሰነ
You have to draw the line somewhere. አንዱ ጋ ፡ መወሰን ፡ አለብህ
*They would draw the line at murder. ሕይወት ፡ ከማጥፋት ፡ በስተቀር ፡ ማንኛውንም ፡ ወንጀል ፡ ይፈጽማሉ

**drop (someone) a line**
Drop me a line! ደብዳቤ ፡ ጻፍልኝ

**fall in line** ተሰለፈ
The soldiers fell in line at the officer's command. በመኰንኑ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ወታደሮቹ ፡ ተሰለፉ

**form a line** ተሰለፈ
The teacher told the students to form a line. መምህሩ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ተሰለፉ ፡ አላቸው

**get into line** ተሰለፈ
The members of the marching band got into line. ሙዚቀኞቹ ፡ ተሰለፉ

**hold the line against** ተከላከለ
We must hold the line against inflation. የገንዘብ ፡ መርከስ ፡ እንዳይደርስ ፡ መከላከል ፡ አለብን

**in (one's) line**
*That is not in my line; I am only familiar with electronics. ያ ፡ የሠለጠንኩበት ፡ ሥራ ፡ አይደለም ፤ እኔ ፡ የማውቀው ፡ ስለ ፡ ኤሌክትሮኒክስ ፡ ብቻ ፡ ነው
*This is not in my line! ይህ ፡ እኔን ፡ አይመለከትም

**(be) in line for**
*He is in line for the presidency. የሚቀጥለው ፡ ፕሬዚዳንት ፡ እሱ ፡ ይሆናል

**in line of duty** በተግባር ፡ ላይ ፡ እንዳለ
The policeman met his death in line of duty. ፖሊሱ ፡ በተግባር ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ሞተ

**in line with** በ - - - መሠረት
In line with our policy, we will refuse him a scholarship. በፖሊሲያችን ፡ መሠረት ፡ የነጻ ፡ ትምህርት ፡ አንሰጠውም

**keep in line** ገታ
He could never seem to keep his temper in line. ምን ፡ ጊዜም ፡ ንዴቱን ፡ ለመግታት ፡ የሚችል ፡ አይመስልም

**(be) out of line**
1. አልተስማማም. The conservatives are out of line with us. ለውጥ ፡ የማይፈልጉት ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ አይስማሙም
2. ከመሥመር ፡ ውጭ ፡ ነው. His answer is out of line. መልሱ ፡ ከመሥመር ፡ ውጭ ፡ ነው

**reading between the lines**
*Reading between the lines, he realized his wife wanted him to return. ከሚስቱ ፡ ደብዳቤ ፡ አጻጻፍ ፡ እንደ ፡ ገመተው ፡ ሚስቱ ፡ እንዲመለስ ፡ መፈለጓን ፡ ተረዳ

**single line** ተርታ
He disposed the cars in a single line. መኪናዎቹን ፡ በተርታ ፡ አቆማቸው
[See also 'hill, reform, strike']

**lineage** ዘር
The governor is a man of good lineage. ገዢው ፡ ዘረ ፡ መልካም ፡ ነው

**lineal, ~ descendant** በቀጥታ ፡ የወረደ
A grandson is a lineal descendant of his grandfather. የልጅ ፡ ልጅ ፡ ከወንድ ፡ አያት ፡ በቀጥታ ፡ የወረደ ፡ ነው

**linear** የርዝመት
An inch is a linear measure. ኢንች ፡ የርዝመት ፡ መለኪያ ፡ ነው

**linear drawing** ንድፍ
A linear drawing shows the plan of the palace. ንድፉ ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ፕላን ፡ ያሳያል

**lined** (adj.)
1. ባለ ፡ መሥመር. I want some lined paper. ባለ ፡ መሥመር ፡ ወረቀት ፡ እፈልጋለሁ
2. የተለበደ. She wore a coat lined with fleece. በበግ ፡ ጸጉር ፡ የተለበደ ፡ ኮት ፡ ለብሳለች

**linen**
1. ሊኖ. This tablecloth is made of linen. ይህ ፡ የጠረጴዛ ፡ ልብስ ፡ የተሠራው ፡ ከሊኖ ፡ ነው
2. የአልጋ ፡ ልብስ. The linen is changed every week. የአልጋ ፡ ልብስ ፡ በየሳምንቱ ፡ ይቀየራል

**liner** ትልቅ ፡ መርከብ
The liner carries more than 1,500 people. ትልቁ ፡ መርከብ ፡ ከሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ይበልጥ ፡ ይይዛል

**lineup**
*We could not identify the criminal in the police lineup. ፖሊስ ፡ ከደረደራቸው ፡ ሰዎች ፡ መሀከል ፡ ወንጀለኛውን ፡ ለመለየት ፡ አልቻልንም

**linger**
1. አሁንም ፡ አለ. A trace of smoke lingered in the air. አየሩ ፡ ውስጥ ፡ አሁንም ፡ ጥቂት ፡ ጢስ ፡ አለ
2. ቆየ. We lingered awhile after the party. ግብዣው ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ቆየን

**linger about** ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ
He lingered about after everybody had left so that he could be with her. ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ ከሷ ፡ ጋር ፡ እንዲቀር ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይል ፡ ነበር

**linger on** አሁንም ፡ ተገኘ
The custom of propitiating spirits lingers on in some country districts. ባድባር ፡ የመማጸን ፡ ባህል ፡ አሁንም ፡ ባንዳንድ ፡ ቀበሌዎች ፡ ይገኛል

**linger over** አዘገየ
He lingered over the decision. ውሳኔውን ፡ አዘገየ

**linguist** የቋንቋ ፡ ዐዋቂ
The linguist studies the structure of languages. የቋንቋ ፡ ዐዋቂ ፡ ስለ ፡ ቋንቋ ፡ ሁኔታ ፡ ያጠናል

**linguistics** የቋንቋ ፡ ጥበብ
He is interested in Ethiopian linguistics. የኢትዮጵያን ፡ ቋንቋ ፡ ጥበብ ፡ የማጥናት ፡ ፍላጎት ፡ አለው

**lining** ገበር
My coat needs a new lining. ኮቴ ፡ አዲስ ፡ ገበ ር ፡ ያስፈልገዋል

**link** (v.) አያያዘ
The new bridge will link the island to the mainland. አዲሱ ፡ ድልድይ ፡ ደሴቱን ፡ ከዋ ናው ፡ መሬት ፡ ጋር ፡ ያያይዛል

**be linked** ግንኙነት ፡ አለው
The police officer is linked with the criminal group. የፖሊሱ ፡ መኰንን ፡ ከወንጀለኞቹ ፡ ጓ ድ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ አለው

**link arms**
They linked arms. ከንድ ፡ ለክንድ ፡ ተያያዙ

**link up** ተያያዘ
Your story links up with what John told us. አንተ ፡ የነገርከንና ፡ ዮሐንስ ፡ የነገረን ፡ የተያያዘ ፡ ነው

**link** (n.)
1. ማያያዣ. One link of my watch chain is broken. የሰዓት ፡ ማሰሪያዬ ፡ አንዲ ፡ ማያያዣ ፡ ተበጥሳለች
2. የሚያያይዝ. Our generation is the link between the past and the future. የኛ ፡ ትውል ድ ፡ ያለፈውንና ፡ የሚመጣውን ፡ ትውልድ ፡ የ ሚያያይዝ ፡ ነው

**linseed** ተልባ
They make oil from linseed. ከተልባ ፡ ዘይት ፡ ያወጣሉ

**lint** የከርና ፡ የጨርቅ ፡ ብናኝ
Lint collects in the pockets of the suit. ኪስ ፡ ውስጥ ፡ የከርና ፡ የጨርቅ ፡ ብናኝ ፡ ይጠራቀማል

**lion** አንበሳ
The lion is called the king of beasts. አንበሳ ፡ ያራዊት ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ ይባላል

**lip**
1. ከንፈር. He cut his lip while shaving. ጢሙን ፡ ሲላጭ ፡ ከንፈሩን ፡ ቈረጠው
2. አፍ. The lip of the cup is chipped. የሲኒው ፡ አፍ ፡ ተሸርፏል

**bite one's lip** ታገሠ
He wanted to return the insult, but bit his lip in order to avoid a scene. መልሶ ፡ ሊሳደብ ፡ ፈልጎ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ የባሰ ፡ ጠብ ፡ እንዳይነሣ ፡ በማለት ፡ ታገሠ

**hang on the lips of** በተመስጦ ፡ አዳመጠ
The audience hung on the lips of the lecturer. አዳማጮቹ ፡ ተናጋሪውን ፡ በተመስጦ ፡ አዳመጡት

**lip service, give ~** በአፍ ፡ ብቻ ፡ ደለለ
The hypocrite gives lip service to the church. ግብዙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ በአፍ ፡ ብቻ ፡ ይ ደልላል

**lipstick** የከንፈር ፡ ቀለም
Almaz went to the Piazza to buy lipstick. አልማዝ ፡ የከንፈር ፡ ቀለም ፡ ለመግዛት ፡ ወደ ፡ ፒ ያሳ ፡ ሄደች

**liquefy** (liquefied), vt. አቀለጠ
The cook liquefied the butter in a pan. ወጥ ፡ ቤ ቱ ፡ ቅቤውን ፡ መጥበሻ ፡ ላይ ፡ አቀለጠው

**liquefy** (vi.) ቀለጠ
Let the butter liquefy in a warm pan! በትኩስ ፡ መጥበሻ ፡ ላይ ፡ ቅቤው ፡ ይቅለጥ

**be liquefied** ወደ ፡ ፈሳሽነት ፡ ተለወጠ
Gases can be liquefied. ጋዞች ፡ ወደ ፡ ፈሳሽነት ፡ ሊለወጡ ፡ ይችላሉ

**liquid** (n.)
1. ፈሳሽ ፡ ነገር. He is only allowed liquids. የተፈቀደለት ፡ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ፈሳሽ. Chemistry is the study of solids and liquids. ኬሚስትሪ ፡ የጥጥሮችንና ፡ የፈሳሾች ን ፡ ጠባይ ፡ ያጠናል

**liquid** (adj.)
1. ፈሳሽ. Do you have liquid soap? ፈሳሽ ፡ ሳሙ ና ፡ አለህ ?
2. በቀላሉ ፡ ወደ ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ሊለወጥ ፡ የሚችል. Bonds are liquid assets. ቦንድ ፡ በቀላሉ ፡ ወደ ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ሊለወጥ ፡ የሚችል ፡ ንብረት ፡ ነው
3. ልስልስ ፡ ያለ. The girl has a liquid voice. ልጅቷ ፡ ልስልስ ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ አላት

**liquidate**
1. ከፈለ. He very soon liquidated his debts. ወዲያውኑ ፡ ዕዳውን ፡ ሁሉ ፡ ከፈለ
2. ደመሰሰ. The dictator liquidated his enemies. አምባገነኑ ፡ ጠላቶቹን ፡ ደመሰሰ

**liquor** አልኮል
Drinking a lot of liquor is not good for the liver. አልኮል ፡ አብዝቶ ፡ መጠጣት ፡ ለጉበት ፡ ጥሩ ፡ አይደለም

**lisp** ተኰላተፈ
She lisps when she talks. ስትነጋገር ፡ ትኰላተፋ ለች

**lisping** ኮልታፋ ፡ አነጋገር
His lisping is annoying. የሱ ፡ ኮልታፋ ፡ አነጋገር ፡ ያበሳጫል

**list** (vt.)
1. በዝርዝር ፡ ጻፈ ፤ በዝርዝር ፡ አኖረ. He listed all the equipment that was lost. የጠፋውን ፡ መሣሪያ ፡ ሁሉ ፡ በዝርዝር ፡ ጻፈ ፡ (በዝርዝር ፡ አኖረ)
2. መዘገበ(ተመዘገበ). This item is not listed. ይህ ፡ እቃ ፡ አልተመዘገበም
3. አመለከተ. The bill of fare lists only Ethiopian food. ዝርዝሩ ፡ የሚያመለክተው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ምግብ ፡ ብቻ ፡ ነው

**list** (vi.) አዘነበለ
The boat is listing from a hole in the side. በጐኑ ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ ቀዳዳ ፡ የተነሣ ፡ ጀልባው ፡ አዘንብሏል

**list** (n.) ዝርዝር
Make a list of the things you must do! ማድረግ ፡ የሚገባህን ፡ ነገር ፡ ዝርዝር ፡ አውጣ
His name is not on the list. ስሙ ፡ ዝርዝሩ ፡ ውስጥ ፡ የለም

**listen**
1. አዳመጠ. We listened, but heard nothing. አዳመጥን ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አልሰማንም
I like to listen to good music. ጥሩ ፡ ሙዚቃ ፡ ማዳመጥ ፡ እወዳለሁ
2. ሰማ. I tried to tell him that what he was doing is stupid, but he just won't listen to me. የሚያደርገው ፡ ነገር ፡ የማይረባ ፡ መሆኑን ፡ ነገርኩት ፤ ግን ፡ አይሰማኝም

**listen for** ሰማ
Listen for the sound of the bell! የደወሉን ፡ ድምፅ ፡ ስማ
*The mother listens for her baby's cry. እናቲቱ ፡ ልጇ ፡ ሲያለቅስ ፡ እንድትሰማ ፡ ርቃ ፡ አትሄድም

**listen in** ተደብቆ ፡ አዳመጠ
I think our neighbor listens in on our telephone conversations. ጐረቤታችን ፡ በስልክ ፡ ስንነጋገር ፡ ተደብቆ ፡ የሚያዳምጥ ፡ ይመስለኛል
[See also 'reason']

**listless, make ~** ፍዝዝ ፡ አደረገ
Hot weather makes him listless. ሞቃት ፡ አየር ፡ ፍዝዝ ፡ ያደርገዋል

**list price** የተተመነ ፡ ዋጋ
He sold the car at 20 percent off the list price. መኪናውን ፡ ከተተመነው ፡ ዋጋ ፡ ሃያ ፡ በመቶ ፡ ቀንሶ ፡ ሸጠ

**lit**, see **light**

**litany** (litanies) ሊጦን
The priest recites the litany. ካህኑ ፡ ሊጦን ፡ ያደርሳል

**liter** ሊትር
Give me a liter of milk! አንድ ፡ ሊትር ፡ ወተት ፡ ስጠኝ

**literacy**
1. የጐልማሶች ፡ ትምህርት. He is a strenuous campaigner for literacy. ለጐልማሶች ፡ ትምህርት ፡ ብርቱ ፡ ተሟጓች ፡ ነው
2. መጻፍና ፡ ማንበብ. Literacy is of primary importance. መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ መሠረታዊ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው

**literacy campaign** ተምሮ ፡ ማስተማር ፤ ተምሮ ፡ ማስተማር ፡ ዘመቻ ፤ የፊደል ፡ ሰራዊት
Many young people engage in literacy campaigns in their spare time. ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ በትርፍ ፡ ጊዜያቸው ፡ በተምሮ ፡ ማስተማር ፡ (በተምሮ ፡ ማስተማር ፡ ዘመቻ) ፡ ይሰማራሉ
The literacy campaign helped many people to read. የፊደል ፡ ሰራዊት ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ እንዲያነቡ ፡ ረዳ

**literal**
1. (= adv.) አንድ ፡ ባንድ. The robbery victim gave a literal account of the robbery to the police. የተዘረፈው ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ዘረፋው ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ለፖሊሶች ፡ ነገረ
2. (= literally) ቃል ፡ በቃል. Please make a literal translation of that! ያንን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ተርጕመው

**literally** ቃል ፡ በቃል
You must not take him too literally. የሚናገረውን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ልትወስደው ፡ አይገባም
The teacher asked the students to translate the passage literally. መምህሩ ፡ ተማሪዎቹ ፡ ምንባቡን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ እንዲተረጕሙት ፡ ጠየቀ
*She is literally penniless. ቀዳዳ ፡ ፍራንክ ፡ የላትም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል

**literary** የሥነ ፡ ጽሑፍ
His latest novel is a literary masterpiece. በቅርቡ ፡ የወጣው ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፉ ፡ ግሩም ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ቅርስ ፡ ነው
Literary men gather at the club to discuss books. የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ መጻሕፍት ፡ ለመወያየት ፡ በክበቡ ፡ ይሰበሰባሉ

**literate** የተማረ
A literate person is needed for the job. ለሥራው ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ ያስፈልጋል

**literature**
1. ሥነ ፡ ጽሑፍ. Have you studied English literature? የእንግሊዝኛ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ተምረሃል ?
2. የተጻፈ. He has an enormous library on medical literature. ስለ ፡ ሕክምና ፡ የተጻፉ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ አሉት
3. መግለጫ. We wrote for literature on the electric typewriter. ስለ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ ታይፕ ፡ መግለጫ ፡ እንዲልኩልን ፡ ጻፍን

**litigant** ተሟጋች ፤ ነገረተኛ
One of the litigants asked me to write an application for him. ከተሟጋቾቹ ፡ (ከነገረተኞቹ) ፡ አንዱ ፡ ማመልከቻ ፡ እንድጽፍለት ፡ ጠየቀኝ

**litigate** ተሟገተ
They have litigated about the property for the last two years. ባለፈው ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ስለ ፡ ርስቱ ፡ ተሟገቱ

**litigation**ሙግት
Litigation ate up all his money. ሙግት ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ጨረሰበት

**litigious** ተሟጋች
Litigious persons spend several days a week in court. ተሟጋች ፡ ሰዎች ፡ በሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይውላሉ

**litter** (vt.)
1. አቆሸሸ. Don't litter your desk with paper! ጠረጴዛህን ፡ በወረቀት ፡ አታቆሽሽ
2. በታተነ. They littered their toys from one end of the room to the other. መጫወቻቸውን ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ በታተኑት

**litter** (vi.) ወለደ
The cat had littered in the closet. ድመቷ ፡ እቁም ፡ ሣጥኑ ፡ ውስጥ ፡ ወለደች

**be littered** ተረፈረፈ
The battlefield was littered with corpses. የጦር ፡ ሜዳው ፡ ሬሳ ፡ ተረፍርፎበት ፡ ነበር

**litter up** ተዝረከረከ
Dirty clothes littered up the room. የቆሸሸ ፡ ልብስ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተዝረክርኮ ፡ ነበር

**litter** (n.)
1. ቆሻሻ. Pick up your litter after the picnic! ከሽርሽሩ ፡ በኋላ ፡ ቆሻሻውን ፡ ልቀም
2. ቃሬዛ. The man was carried to the hospital on a litter. በሽተኛው ፡ በቃሬዛ ፡ ወደ ፡ ሆስፒታል ፡ ተወሰደ
3. ግልገሎች. Rabbits are fecund; they can have several litters a year. ጥንቸሎች ፡ ወላዶች ፡ ስለሆኑ ፡ በዓመት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ግልገሎች ፡ ይወልዳሉ

**little** (n.) ጥቂት
The little of his work that I have seen seems excellent. ጥቂትም ፡ ቢሆን ፡ ያየሁት ፡ ሥራው ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ይመስላል

**on so little** በዚህ ፡ አነስተኛ ፡ ገንዘብ
I earn only $20 a week, and I cannot live on so little. የማገኘው ፡ በሳምንት ፡ ሃያ ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ አነስተኛ ፡ ገንዘብ ፡ ልኖር ፡ አልችልም

**little** (adj.)
1. ትንሽ. She has a little girl. ትንሽ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ አለቻት
2. ጥቂት. Won't you stay with me for a little time? ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ አትቆይም ?
3. የማይረባ. She frets over little things. በማይረቡ ፡ ነገሮች ፡ ትበሳጫለች
4. ዝቅ ፡ ያለ. The girl has a little voice, and it is difficult to understand her. ልጅቷ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ ስላላት ፡ ለመስማት ፡ ያስቸግራል
5. አነስተኛ. This idea is of little matter. ይህ ፡ ሐሳብ ፡ አነስተኛ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነው
*It is only a little walk to the store. ወደ ፡ መደብሩ ፡ ብዙ ፡ አያስኬድም
*That is of little value to me. እምብዛም ፡ አይጠቅመኝም

**little one** ልጅ
How are the little ones? ልጆች ፡ ደኅና ፡ ናቸው ?

**little** (adv.)
1. ጥቂት. She gives little to charity. ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ የምትሰጠው ፡ ጥቂት ፡ ነው
It's a little warm here. እዚህ ፡ ጥቂት ፡ ሞቅ ፡ ይላል
2. ምንም + (negative). He little knew what lay ahead. ወደፊት ፡ ምን ፡ እንደሚደርስ ፡ ምንም ፡ አያውቅም ፡ ነበር
3. እንዲያው + (negative verb). He little knew that the police were about to arrest him. ፖሊስ ፡ ሊይዘው ፡ እንደነበረ ፡ እንዲያውም ፡ አላወቀ
4. እምብዛም + (negative). She is little known in the city. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ እምብዛም ፡ አትታወቅም

**little better than**
He is little better than a thief. ከሌባ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አይሻልም

**little by little**
1. እያደር. Little by little, he calmed down. እያደር ፥ ረጋ ፥ አለ
2. ቀስ ፡ በቀስ. The water level rose little by little. የውኃው ፡ መደብ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ከፍ ፡ አለ

**little-known** እምብዛም ፡ ያልታወቀ
They live in a little-known town. እምብዛም ፡ ባልታወቀች ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ

**a little**
1. ትንሽ ፡ ትንሽ. I can speak a little French. ፈረንሳይኛ ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ እናገራለሁ
2. ለጥቂት ፡ ጊዜ. Sit a little with me! ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ተቀመጥ

**a little way** ጥቂት
Come a little way with me! ጥቂት ፡ ሸኘኝ

**make little of** ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ተመለከተ
He makes little of my trouble. ችግሬን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ይመለከተዋል

**not a little** በጣም
He was not a little annoyed to find I had disobeyed him. ትእዛዙን ፡ አለመቀበሌን ፡ ሲያውቅ ፡ በጣም ፡ ጦፈ
*The problem gave us not a little trouble. በጉዳዩ ፡ ያጋጠመን ፡ ችግር ፡ ጥቂት ፡ አይደለም

**think little of**
1. ዝቅተኛ ፡ ግምት ፡ አለው. I think little of someone who destroys books. መጻሕፍትን ፡ ለሚያበላሹ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ዝቅተኛ ፡ ግምት ፡ አለኝ
2. ዋጋ ፡ እንዳለው ፡ ነገር ፡ አልቈጠረም. I think little of driving 50 miles to see a movie. ሲኒማ ፡ ለማየት ፡ አምሳ ፡ ማይል ፡ መሄድን ፡ ዋጋ ፡ እንዳለው ፡ ነገር ፡ አልቈጥርም

**very little**
1. ትንሽ. We slept very little last night. ትናንት ፡ ማታ ፡ የተኛነው ፡ ትንሽ ፡ ነው
2. አንዳንዴ. I see very little of him since he moved away. ከሄደ ፡ ጀምሮ ፡ የማየው ፡ አንዳንዴ ፡ ነው
[See also 'finger, how, mind, mischief, short, while']

**littler, the ~** አነስ ፡ ያለው
The littler of the two children is my son. ከሁለቱ ፡ ልጆች ፡ አነስ ፡ የሚለው ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ነው

**littlest, the ~** ከሁሉ ፡ የሚያንሰው
The littlest child got nothing. ከሁሉ ፡ የሚያንሰው ፡ ልጅ ፡ ምንም ፡ አላገኘም

**littoral region** የባሕር ፡ ዳርቻ ፡ አካባቢ
The people of the littoral region are mostly fishermen. በባሕር ፡ ዳርቻ ፡ አካባቢ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ አብዛኞቹ ፡ ዓሣ ፡ አጥማጆች ፡ ናቸው

**liturgy** (liturgies) የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት
The Ethiopian liturgy is much like the Egyptian Coptic liturgy. የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከግብጽ ፡ ኮፕቲክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ ይመሳሰላል

**(be) livable** ለመኖሪያ ፡ በቃ
The house is small but livable. ቤቱ ፡ ትንሽ ፡ ቢሆንም ፡ ለመኖሪያ ፡ ይበቃል

**quite livable** የሚያመች ፡ ሆኖ
He found life on the island quite livable. በደሴቱ ፡ ላይ ፡ ኑሮ ፡ የሚያመች ፡ ሆኖ ፡ አገኘው

**live** (v.)
1. ኖረ. Before the war, I lived in France. ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ እኖር ፡ ነበር
He lived a very happy life. በጣም ፡ ደስተኛ ፡ ኑሮ ፡ ኖረ
The Chinese live largely on rice. ቻይናዎች ፡ አብዛኛውን ፡ የሚኖሩት ፡ በሩዝ ፡ ነው
He lives well, even though he hasn't much money. ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ባይኖረውም ፡ ደኅና ፡ ይኖራል
I earn only $20 a week and I cannot live on so little. የማገኘው ፡ በሳምንት ፡ ሃያ ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ አነስተኛ ፡ ገንዘብ ፡ ልኖር ፡ አልችልም
2. ተዳደረ. He managed to live on $40 a week. በሳምንት ፡ አርባ ፡ ብር ፡ ሒሳብ ፡ ሊተዳደር ፡ ቻለ
*He knows how to live. የኑሮን ፡ ዘዴ ፡ ያውቃል
*His memory will always live in our hearts. ምን ፡ ጊዜም ፡ አንረሳው

**live in** እቤት ፡ ኖረ
Does your cook live in? ወጥ ፡ ቤት ፡ ሠራተኛህ ፡ የምትኖረው ፡ እቤትህ ፡ ነው ?

**live off**
1. በ - - - ትከሻ ፡ ኖረ. He lives off his parents. በወላጆቹ ፡ ትከሻ ፡ ይኖራል
2. ከ - - - በሚያገኘው ፡ ተዳደረ. The soldiers lived off the land. ወታደሮቹ ፡ ከአካባቢያቸው ፡ በሚያገኙት ፡ ተዳደሩ

**live (on)**
1. መኖሩን ፡ ቀጠለ. The old people died, but the young people lived on in the village. የመንደሩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ አለቁ ፤ ወጣቶቹ ፡ ግን ፡ ከዚያው ፡ መኖራቸውን ፡ ቀጠሉ
2. በላ. The people on this island live on

nothing but fish. የዚህ ፡ ደሴት ፡ ነዋሪዎች ፡ ያለ ፡
ዓሣ ፡ ምንም ፡ አይበሉም
3. ተቀርጾ ፡ ኖረ. His great words live on in our
hearts. የተናገራቸው ፡ ታላቅ ፡ ቃላት ፡ በልባችን ፡
ውስጥ ፡ ተቀርጸው ፡ ይኖራሉ

**live out** አለፈ
She won't live out the winter. ክረምትን ፡ አታ
ልፍም

**live through** አየ
He lived through two wars, and one revolution.
ሁለት ፡ ጦርነቶችና ፡ አንድ ፡ መሠረታዊ ፡ ለው
ጥ ፡ አይቷል

**live to**
*He lived to a ripe old age. በጣም ፡ አርጅቶ ፡ ሞተ

**live to be** እስኪሆነው ፡ ኖረ
He lived to be a hundred. መቶ ፡ ዓመት ፡ እስኪ
ሆነው ፡ ኖረ
*He did not live to be as old as his father.
እንዳባቱ ፡ አርጅቶ ፡ አልሞተም

**live up to** በ - - - መሠረት ፡ ኖረ
He tried to live up to the ideals of the Christian
religion. በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ደንብ ፡ መሠረ
ት ፡ ለመኖር ፡ ሞከረ
*He didn't live up to my expectations. እንዳሰብ
ኩት ፡ ሆኖ ፡ አላገኘሁትም
[See also 'affluence, camp, morally, seclusion, style']

**live** (adj.)
1. ነፍስ ፡ ያለው. It was a real, live lion. እውነ
ተኛ ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ አንበሳ ፡ ነበር
2. ከነነፍሱ ፡ ያለ. I bought some live fish. ከነነ
ፍሳቸው ፡ ያሉ ፡ ዓሣዎች ፡ ገዛሁ
3. አጨቃጫቂ. The border problem is a very
live question right now. የወሰኑ ፡ ችግር ፡ አ
ሁንም ፡ አጨቃጫቂ ፡ ጉዳይ ፡ ነው
4. ታታሪ. A live, young man may succeed in
making this store earn money. አንድ ፡ ታታሪ ፡
ወጣት ፡ ይህ ፡ መደብር ፡ ብዙ ፡ ትርፍ ፡ እንዲያገ
ኝ ፡ ማድረግ ፡ ይችል ፡ ይሆናል
5. ዋና. Emancipation of the slaves is no longer
a live issue. የባሮች ፡ ነጻ ፡ መውጣት ፡ ባሁኑ ፡ ጊ
ዜ ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ አይደለም
[See also 'coal, wire']

**livelihood** መተዳደሪያ
His livelihood is not a legitimate one. መተዳደሪ
ያው ፡ ሕጋዊ ፡ መንገድን ፡ የተከተለ ፡ አይደለም

**earn (one's) livelihood** ተዳደረ
He earns his livelihood by farming. የሚተዳደረ
ው ፡ በግብርና ፡ ነው

**livelier, be a little ~** ነቃ ፡ አለ
The patient seems a little livelier this evening.
በሽተኛው ፡ ዛሬ ፡ ከመሸ ፡ ነቃ ፡ ያለ ፡ ይመስላል

**livelong** ሙሉ
She is busy the livelong day. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሥ
ራ ፡ ላይ ፡ ነች

**lively**
1. ንቁ. He is a lively boy. ንቁ ፡ ልጅ ፡ ነው
2. የደመቀ. That was a lively party we had.
ፓርቲው ፡ በጣም ፡ የደመቀ ፡ ነበር
3. ደማቅ. She likes lively colors. ደማቅ ፡ ቀለሞ
ች ፡ ትወዳለች
4. ሞቅ ፡ ያለ. He played a lively tune. ሞቅ ፡
ያለ ፡ ዘፈን ፡ ተጫወተ
Their house is very lively. ቤታቸው ፡ ሞቅ ፡
ያለ ፡ ነው
5. ከፍ ፡ ያለ. He has a lively interest in political
events. ስለ ፡ ፖለቲካ ፡ ጉዳዮች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሜ
ት ፡ አለው
6. (= adv.) ስሜት ፡ በሚቀሰቅስ ፡ አኳኋን . He
gave a lively account of his adventures. ስለደረ
ሰበት ፡ ነገር ፡ ስሜት ፡ በሚቀሰቅስ ፡ አኳኋን ፡ ተ
ናገረ

**feel lively** ተደሰተ
Horses prance when they feel lively. ፈረሶቹ ፡
ሲደሰቱ ፡ ይፈነጫሉ

**make lively** አደመቀ
A jocular person is needed to make the party
lively. ፓርቲውን ፡ ለማድመቅ ፡ ቀልደኛ ፡ ሰው ፡
ያስፈልጋል

**liven** አደመቀ
Music livens a party. ሙዚቃ ፡ ግብዣን ፡ ያደም
ቃል

**liven up** ነቃ ፡ ነቃ ፡ አለ
She livened up after a nap. ጋደም ፡ ብላ ፡ ከተነ
ሣች ፡ በኋላ ፡ ነቃ ፡ ነቃ ፡ አለች

**liver** ጉበት
He has cancer of the liver. የጉበት ፡ ካንሰር ፡ አ
ለበት

**livery** (liveries) ልዩ ፡ ልብስ
The servants in the palace wear livery.
የቤተ ፡ መንግሥት ፡ አሽከሮች ፡ ልዩ ፡ ልብስ ፡
ይለብሳሉ

**lives,** see **life**

**livestock** ከብቶች
We cannot get enough feed for our livestock.
ለከብቶቻችን ፡ በቂ ፡ ምግብ ፡ አናገኝም

**(be) livid** አመድ ፡ ለበሰ
His face was livid with rage. ከንዴት ፡ የተነሣ ፡ ፊቱ ፡ አመድ ፡ ለበሰ

**living** (n.)
1. ኑሮ. Living is awfully expensive here. ኑሮ ፡ እዚህ ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ ነው
2. መኖር. The old man is tired of living. ሽማግሌው ፡ መኖር ፡ ሰልችቶታል
3. አኗኗር. The preacher urged the importance of right living. ሰባኪው ፡ የትክክለኛ ፡ አኗኗርን ፡ አስፈላጊነት ፡ በጥብቅ ፡ አሳሰበ

**do for a living**
What does he do for a living? ምን ፡ ሥርቶ ፡ ያድራል ?

**make a living** ተዳደረ
He makes a living by selling shoes. ጫማ ፡ በመሸጥ ፡ ይተዳደራል

**make one's living** እየሠራ ፡ ኖረ
How does he make his living? ምን ፡ እየሠራ ፡ ይኖራል ?
[See also 'cost, earn, high']

**living** (adj.)
1. ለዕለት ፡ የሚበቃ ፡ ብቻ. We pay our workers a living wage. ለሠራተኞቻችን ፡ ለዕለት ፡ የሚበቃ ፡ ደሞዝ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የምንከፍላቸው
2. (= while he is alive) በሕይወቱ ፡ ሳለ. A living author does not often find recognition. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ደራሲ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ስሙ ፡ አይጠራም
3. የሚሠራበት. Amharic is a living language. አማርኛ ፡ የሚሠራበት ፡ ቋንቋ ፡ ነው
4. ለምለም. The tree was struck by lightning while it was still living. ዛፉ ፡ ገና ፡ ለምለም ፡ ሳለ ፡ መብረቅ ፡ መታው
*He is the living image of his father. ቁርጥ ፡ አባቱን ፡ ነው

**be living** በሕይወት ፡ ኖረ
I don't know whether he is still living. በሕይወት ፡ መኖሩን ፡ አላውቅም

**living conditions** የኑሮ ፡ ሁኔታ
Living conditions here are very bad. እዚህ ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ በጣም ፡ መጥፎ ፡ ነው

**living costs** የኑሮ ፡ ውድነት
Our wages are pegged to living costs. ደሞዛችን ፡ ከኑሮ ፡ ውድነት ፡ ጋር ፡ ይለዋወጣል
[See also 'standard']

**living room** ሳሎን
The living room of this house is large. የዚህ ፡ ቤት ፡ ሳሎን ፡ ሰፊ ፡ ነው

**lizard** እንሽላሊት
The lizard walked on the wall. እንሽላሊት ፡ በግድግዳው ፡ ላይ ፡ ሄደች

**load** (vt.)
1. ጫነ. Load the cases on the truck! ሣጥኖቹን ፡ መኪናው ፡ ላይ ፡ ጫኗቸው
They loaded the car before the trip. ከጉዞው ፡ በፊት ፡ መኪናውን ፡ ጫኑ
Before going to market, they load the donkey. ገበያ ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ አህያ ፡ ይጭናሉ
The farmer loaded grain on the donkey. ገበሬው ፡ አህያውን ፡ እህል ፡ ጫነ
2. እቃ ፡ አሳፈረ ፤ ጫነ. Why don't you load the truck? እቃውን ፡ መኪናው ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ አታሳፍርም ፡ (አትጭንም) ?
3. ጐሰረ. He loaded his stomach with food. ሆዱን ፡ በምግብ ፡ ጐሰረ
4. አጐረሰ. The soldiers loaded the gun and fired. ወታደሮቹ ፡ ጠመንጃቸውን ፡ አጐርሰው ፡ ተኰሱ

**load** (vi.)
1. ተጫነ. The ship loaded at Massawa. መርከቡ ፡ ምፅዋ ፡ ላይ ፡ ተጫነ
2. (= active) እቃ ፡ አሳፈረ. The bus usually loads at the rear door. አውቶቡሱ ፡ እቃ ፡ የሚያሳፍረው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ በር ፡ ነው

**load with**
1. ጫነ. He loaded his workers with too much work. ሠራተኞቹን ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ጫናቸው
2. በገፍ ፡ አደረገ(ለት). He loaded his friends with gifts. ለጓደኞቹ ፡ ስጦታ ፡ በገፍ ፡ አደረገላቸው

**be loaded**
1. ተጫነ. The baggage is loaded on the plane. ጓዙ ፡ አውሮፕላኑ ፡ ላይ ፡ ተጭኗል
2. ጐረሰ. The gun was loaded. ጠመንጃው ፡ ጐርሷል

**be loaded down** ተሸከመ
She was loaded down with packages. ብዙ ፡ የተጠቀለሉ ፡ እቃዎች ፡ ተሸክማ ፡ ነበር

**be loaded with**
1. በዛ(በት). We are loaded with work. ሥራ ፡ በዝቶብናል
2. ወረደ(በት). She is loaded with troubles. ብዙ ፡ መከራ ፡ ወረደባት

**load** (n.)
1. ሸክም. The load is too heavy for him. ሸክሙ ፡ ለሱ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ከባድ ፡ ነው
2. ጭነት. I ordered a load of coal. አንድ ፡ ጭነት ፡ ከሰል ፡ አዘዝኩ

**loads of** መዓት
He has loads of money. መዓት ፡ ገንዘብ ፡ አለው
**(a) full load of** በሙሉ
He has a full load of classes this term. በዚህ ፡ ተርም ፡ የሚሰጠውን ፡ ትምህርት ፡ ዓይነት ፡ በሙሉ ፡ ይወስዳል
**have a load of** በዛ(በት)
+I have such a load of work that I must work on Sundays. ሥራ ፡ ስለሚበዛብኝ ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ መሥራት ፡ አለብኝ
**take a load off one's mind** ሐሳቡን ፡ አቃለ ለ(ለት)
Her safe arrival took a load off my mind. በደኅና ፡ መድረሷ ፡ ሐሳቤን ፡ አቃለለልኝ

**loaded** (adj.)
1. ጭነት ፡ የበዛበት. The loaded truck broke down. ጭነት ፡ የበዛበት ፡ መኪና ፡ ተሰበረ
2. አጨቃጫቂ. That is a loaded question. አጨቃጫቂ ፡ ጥያቄ ፡ ነው
3. የጐረሰ. You will get hurt if you fool with a loaded gun. በጐረሰ ፡ ጠመንጃ ፡ ብትጫወት ፡ ልትጐዳ ፡ ትችላለህ
[See also 'heavily']

**loaf** (loaves), ~ **of bread** ዳቦ
We need two loaves of bread. ሁለት ፡ ዳቦ ፡ ያስፈልገናል

**loaf** (v.) አላገጠ ፤ ቦዘነ
He was loafing on the job. በሥራው ፡ ያላግጥ ፡ (ይቦዝን) ፡ ነበር

**loafer** ሥራ ፡ ፈት
His wife divorced him because he was a loafer. ሥራ ፡ ፈት ፡ ስለሆነ ፡ ሚስቱ ፡ ፈታችው

**loam** ዋልካ ፡ መሬት
Cotton grows best on loam. ጥጥ ፡ በዋልካ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ይበቅላል

**loan** (v.)
1. (money) አበደረ. He loaned me five dollars. አምስት ፡ ብር ፡ አበደረኝ
2. (object) አዋሰ. He loaned me an interesting book. የሚያስደስት ፡ መጽሐፍ ፡ አዋሰኝ

**loan** (n.)
1. (money) ብድር ፤ የገንዘብ ፡ ብድር. I refused the loan he offered me. ውሰድ ፡ ያለኝን ፡ ብድር ፡ እምቢ ፡ አልኩ
Loans are decided by civil law. የገንዘብ ፡ ብድር ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ይወሰናል
2. (object) መዋስ. The loan of books is not allowed. መጽሐፍ ፡ መዋስ ፡ አይፈቀድም

**loanword** የትውስት ፡ ቃል
English has many French loanwords. እንግሊዝኛ ፡ ብዙ ፡ የፈረንሳይኛ ፡ የትውስት ፡ ቃላት ፡ አሉት

**(be) loath** ደስ ፡ አላለ(ውም)
I was loath to go to the party. ወደ ፡ ፓርቲው ፡ መሄድ ፡ ደስ ፡ አላለኝም

**loathe** በጣም ፡ ጠላ ፤ አንገሸገሸ(ው)
I loathe pork. የአሳማ ፡ ሥጋ ፡ በጣም ፡ እጠላለሁ ፡ (ያንገሸግሸኛል)

**loathing** ጥላቻ
He eyed the food on the table with loathing. ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ምግብ ፡ በጥላቻ ፡ ተመለከተው

**loaves**, see **loaf**

**lobby** (lobbies)
1. መተላለፊያ. They are waiting in the lobby. መተላለፊያው ፡ ላይ ፡ ይጠብቃሉ
2. [የምክር ፡ ቤት ፡ አባሎችን ፡ ለማግባባት ፡ የሚሞክሩ ፡ ሰዎች]

**lobe** ጆሮ
She pierced her lobes so she could wear earrings. ጉትቻ ፡ እንድታደርግ ፡ ጆሮዋን ፡ ተበሳች

**local**
1. የሀገር ፡ ውስጥ. Our papers carry local and international news. ጋዜጦቻችን ፡ የሀገር ፡ ውስጥና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜናዎችን ፡ ያወጣሉ
2. ያገር. He was not familiar with local conditions. ያገሩን ፡ ሁኔታ ፡ አልተላመደውም
3. የከተማ. The city administration abated local taxes. የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የከተማውን ፡ ግብር ፡ ቀነሰ
An express bus passed the local bus. በፈሪው ፡ አውቶቡስ ፡ የከተማውን ፡ አውቶቡስ ፡ ቀደመው
4. በየጣቢያው ፡ የሚቆም. A local train takes twice as long as an express. በየጣቢያው ፡ የሚቆም ፡ ባቡር ፡ በቀጥታ ፡ ከሚሄደው ፡ ይልቅ ፡ ዕጥፍ ፡ ጊዜ ፡ ይወስዳል
5. ባንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ የሆነ. The injury was local; so his leg was bandaged, and he went home. ጉዳቱ ፡ የደረሰው ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ እግሩ ፡ በፋሻ ፡ ታስሮ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ

**locality** (localities) ቀበሌ
There is no school in this locality. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የለም

**(be) localized**
*The infection is localized in the foot. የተጐዳው ፡ እግሩን ፡ ብቻ ፡ ነው

**locally** ባካባቢው ፡ ብቻ
The flood did much damage locally. ጐርፉ ፡ ባካባቢው ፡ ብቻ ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ አደረሰ

**locate** (vt.)
1. ፈልጎ ፡ አገኘ. I could not locate him. ፈልጌ ፡ ላገኘው ፡ አልቻልኩም
2. አመለከተ. Can you locate Addis Ababa on the map? በካርታው ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ ልታመለክት ፡ ትችላለህ ?
3. አቋቋመ. He located his store in the center of the city. ከተማው ፡ መካከል ፡ መደብር ፡ አቋቋመ
4. ደረሰ(በት). I couldn't locate the trouble. ችግሩን ፡ አልደረስኩበትም

**locate** (vi.) ሰፈረ
Early settlers located where there was water. የጥንት ፡ ሰፋሪዎች ፡ ውኃ ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ ይሰፍሩ ፡ ነበር

**be located**
1. ተገኘ. Where is your new store located? አዲሱ ፡ መደብርህ ፡ የሚገኘው ፡ የት ፡ ነው ?
2. ተሠራ. A new school is to be located in the town. አዲስ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከተማው ፡ ውስጥ ፡ ሊሠራ ፡ ነው

**location**
1. አቀማመጥ. The location of the hotel is ideal. የሆቴሉ ፡ አቀማመጥ ፡ የሰጠ ፡ ነው
2. ማግኘት. The location of missing persons is the duty of our office. የጠፉ ፡ ሰዎችን ፡ ማግኘት ፡ የመሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ ተግባር ፡ ነው

**lock** (vt.) ቈለፈ
Don't forget to lock the door when you leave! ስትሄድ ፡ በሩን ፡ መቈለፍ ፡ አትርሳ
I locked it in my desk. ጠረጴዛዬ ፡ ውስጥ ፡ ቈለፍኩበት

**lock** (vi.)
1. ተቈለፈ. The door locks easily. በሩ ፡ በቀላሉ ፡ ይቈለፋል
2. ነከሰ. The wheels locked, and the car skidded. ጎማው ፡ ስለነከሰ ፡ መኪናዋ ፡ ተንሸራተተች

**be locked**
1. ተጣበቀ. His jaws were locked, and he could not say a word. መንጋጋው ፡ ስለተጣበቀ ፡ ምንም ፡ መናገር ፡ አልቻለም
2. (= active) ቈለፈ. +The secret was locked in her heart. ምስጢሩን ፡ በልቧ ፡ ውስጥ ፡ ቈለፈችው

**lock arms** ክንድ ፡ ለክንድ ፡ ተያያዘ
The girls locked arms and walked down the street together. ልጃገረዶቹ ፡ ክንድ ፡ ለክንድ ፡ ተያይዘው ፡ አብረው ፡ በጐዳናው ፡ ላይ ፡ ተንሸራሸሩ

**lock in** አሰረ
The police locked in the criminal. ፖሊሱ ፡ ወንጀለኛውን ፡ አሰረ

**lock (oneself) out** መግቢያ ፡ አጣ
She closed the door and locked herself out because she forgot the key. ቁልፉን ፡ ውስጥ ፡ ረስታ ፡ በሩን ፡ ስለዘጋች ፡ መግቢያ ፡ አጣች

**(be) locked out**
1. ተዘጋ(በት). If you don't get in by midnight, you will be locked out. በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ ባትገባ ፡ ይዘጋብሃል
2. በሩ ፡ ተዘግቶበት ፡ ውጭ ፡ አደረ. I was locked out last night. ትናንት ፡ ማታ ፡ በሩ ፡ ተዘግቶብኝ ፡ ውጭ ፡ አደርኩ

**lock together** ተላተመ
The two cars locked together in passing. ሁለቱ ፡ መኪናዎች ፡ ሲተላለፉ ፡ ተላተሙ

**(be) locked together** ተቈላለፈ
The bumpers of the two cars were locked together. የሁለቱ ፡ መኪናዎች ፡ ፈረፋንጎች ፡ ተቈላለፉ

**lock up**
1. ቈለፈ(በት). They herded the prisoners into a room and locked them up. እስረኞቹን ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ አጉረው ፡ ቈለፉባቸው
2. ሁሉን ፡ ነገር ፡ ቈላለፈ. Be sure you lock up before you leave! ከመሄድህ ፡ በፊት ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ ቈላልፍ
3. ከሣጥን ፡ ቈለፈ. Lock up your jewelry before you go away! ከመሄድሽ ፡ በፊት ፡ ጌጣ ፡ ጌጥሽን ፡ ከሣጥን ፡ ቈልፊበት

**(be) locked up**
1. ተቈለፈ. The magician was locked up in a box. ጠንቋዩ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ተቈልፎበታል
2. እስር ፡ ቤት ፡ ገባ. He was arrested by the police and locked up. በፖሊስ ፡ ተይዞ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ገባ
[See also 'horn']

**lock** (n.)
1. የቁልፍ ፡ እናት. The lock needs oiling. የቁልፉ ፡ እናት ፡ ዘይት ፡ ያስፈልገዋል
2. (የቁልፍ) ፡ ቀዳዳ. He could not put the key in the lock. ቁልፉን ፡ ቀዳዳው ፡ ውስጥ ፡ መክተት ፡ አልቻለም
3. ዘለላ. A lock of her hair was found in his wallet. በቦርሳው ፡ ውስጥ ፡ የጸጉሯ ፡ ዘለላ ፡ ተገኘ

**lock, stock, and barrel** እንዳለ
I bought the store — lock, stock, and barrel. መደብሩን ፡ እንዳለ ፡ ገዛሁት

**be under lock and key** ተቈለፈ(በት)
The documents were under lock and key. ሰነዶቹ ፡ ተቈልፎባቸው ፡ ነበር

**locker** ሣጥን
He stowed his clothes in a locker. ልብሱን ፡ ጠቅልሎ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጠው

**lockout** ሥራ ፡ መዘጋት
The workers demonstrated against the lockout. ሠራተኞቹ ፡ ሥራ ፡ በመዘጋቱ ፡ ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ አደረጉ

**locksmith** ቁልፍ ፡ ሠራተኛ
The locksmith fixed the broken key for me. ቁልፍ ፡ ሠራተኛ ፡ የተሰበረውን ፡ ቁልፍ ፡ ሠራልኝ

**locomotion** መጓጓዣ
Trains and planes are means of locomotion. ባቡርና ፡ አውሮፕላን ፡ የመጓጓዣ ፡ ዘዴዎች ፡ ናቸው

**locomotive** ባቡር
Smoke comes from the locomotive. ባቡሩ ፡ ጭስ ፡ ይተፋል

**locust** አንበጣ
The locusts are bad this year. አንበጣ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ከፍቷል
[See also 'cloud']

**lodge** (vt.)
1. አኖረ. We will lodge the refugees in the schoolhouse. ስደተኞቹን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እናኖራቸዋለን
2. አቀረበ. I lodged a complaint against my opponent. በጠላቴ ፡ ላይ ፡ አቤቱታ ፡ አቀረብኩ
*The hunter lodged a bullet in the lion's heart. አዳኙ ፡ አንበሳውን ፡ ልቡን ፡ በጥይት ፡ መታው

**lodge** (vi.)
1. ሰነበተ. He lodged with his relatives. ከዘመዶቹ ፡ ጋር ፡ ሰነበተ
2. ገብቶ ፡ ቀረ. The bullet lodged in his shoulder. ጥይቱ ፡ ትከሻው ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ቀረ
3. ተይዞ ፡ ቀረ. The kite lodged in the top of a tree. ወላንዳዋ ፡ ዛፉ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ተይዛ ፡ ቀረች

**be lodged** ተቀረቀረ
His foot was lodged between two rocks, and he could not get loose. እግሩ ፡ ከሁለት ፡ ቋጥኝ ፡ መካከል ፡ ስለተቀረቀረ ፡ ለመውጣት ፡ አልቻለም

**lodge** (n.)
1. የማረፊያ ፡ ጎጆ. He owns a lodge in the mountains. በተራራው ፡ ላይ ፡ የማረፊያ ፡ ጎጆ ፡ አለው
2. የማኅበር ፡ ቅርንጫፍ. The lodge meets every Tuesday. ሁልጊዜ ፡ ማክሰኞ ፡ የማኅበሩ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ስብሰባ ፡ ያደርጋል

**lodger** ተከራዩ
How many lodgers does she have? ስንት ፡ ተከራዩዎች ፡ አሏት ?

**take in lodgers**
*The widow makes a living by taking in lodgers. ባሏ ፡ የሞተባት ፡ ሴትዮ ፡ የምትተዳደረው ፡ ቤቷ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ ክፍል ፡ እያከራየች ፡ ነው

**lodgings** መኖሪያ
His lodgings are on the second story. መኖሪያው ፡ በሁለተኛው ፡ ፎቅ ፡ ላይ ፡ ነው

**take lodging** ቤት ፡ ተከራየ
I took lodging with an elderly lady. ካንዲት ፡ ጠና ፡ ካሉ ፡ ሴት ፡ ቤት ፡ ተከራየሁ

**loft** ቆጥ
Store the hay in the loft! ድርቆሹን ፡ እቆጡ ፡ ላይ ፡ አድርገው

**lofty**
1. ከፍተኛ. His lofty aims proved impossible of realization. ከፍተኛ ፡ ዓላማዎቹ ፡ ለማከናወን ፡ የማይቻሉ ፡ ሆኑ
2. በጣም ፡ ከፍተኛ. The lofty mountain peaks can be seen from here. በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ የሆኑት ፡ የተራራዎቹ ፡ ጫፎች ፡ ከዚህ ፡ ሊታዩ ፡ ይችላሉ
3. ሞቅ ፡ ያለ. He treats his colleagues in a lofty manner. የሥራ ፡ ጓደኞቹን ፡ ሞቅ ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ ያነጋግራቸዋል

**log** (logged), v.
1. መነጠረ. They are still logging the forest. ጫካውን ፡ አሁንም ፡ በመመንጠር ፡ ላይ ፡ ናቸው

2. በማስታወሻ ፡ ደብተር ፡ ጻፈ. How many flight hours have you logged? ስንት ፡ የበረራ ፡ ሰዓት ፡ በማስታወሻ ፡ ደብተርህ ፡ ጽፈሃል ?

**log** (n.)
1. ግንድ. The log is still burning. ግንዱ ፡ አሁንም ፡ ይነዳል
2. ማስታወሻ ፡ ደብተር. The airline pilot keeps a log. ያየር ፡ መንገዱ ፡ አውሮፕላን ፡ ነጂ ፡ ማስታወሻ ፡ ደብተር ፡ ይይዛል
*I slept like a log. እንቅልፍ ፡ ድብን ፡ አድርጎ ፡ ወሰደኝ

**log** (adj.) ከግንድ ፡ የተሠራ ፤ የዕንጨት
He has a log house. ከግንድ ፡ የተሠራ ፡ ቤት ፡ አለው
They lived in a log cabin. የዕንጨት ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ ኖሩ

**logic**
1. ምርምር. He is guided by logic, not by feelings. የሚመራው ፡ በስሜት ፡ ሳይሆን ፡ በምርምር ፡ ነው
2. አስተሳሰብ. His logic is faulty. አስተሳሰቡ ፡ ስሕተተኛ ፡ ነው
3. ትክክለኛ ፡ አስተሳሰብ. Logic will show that the two ideas are incompatible. ትክክለኛ ፡ አስተሳሰብ ፡ ሁለቱ ፡ ሐሳቦች ፡ የሚቃረኑ ፡ መሆናቸውን ፡ ያሳያል
4. ቁም ፡ ነገር. There is much logic in what he says. የሚለው ፡ ብዙ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አለበት
5. ሎጂክ. He studies logic at the university. ዩኒቨርሲቲ ፡ ውስጥ ፡ ሎጂክ ፡ ያጠናል

**logical** ተገቢ ፡ አስተሳሰብ
It is logical to look for a fire if you see smoke. ጢስ ፡ ሲታይ ፡ እሳት ፡ ያለበትን ፡ ቦታ ፡ መፈለግ ፡ ተገቢ ፡ አስተሳሰብ ፡ ነው

**logical reasoning** ሎጂክን ፡ የተመረኮዘ ፡ ምርምር
Logical reasoning is required by science. በሳይንስ ፡ ሎጂክን ፡ የተመረኮዘ ፡ ምርምር ፡ ይፈለጋል

**loin** ወገብ
I have been sitting a lot, and my loins ache. ብዙ ፡ ስለተቀመጥኩ ፡ ወገቤን ፡ አሞኛል

**gird one's loins** ታጠቀ
Samson girded his loins and went into battle. ሳምሶን ፡ ታጥቆ ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ሄደ

**loincloth**
*He wore only a loincloth. ኀፍረቱን ፡ ለመሸፈን ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ ለብሷል

**loiter** ተንቀዋለለ
The police kept the young men from loitering on the corner. ፖሊሶች ፡ ወጣቶቹን ፡ ሰዎች ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ እንዳይንቀዋለሉ ፡ አደረጉ

**lone**
1. ብቸኛ. The lone traveler was glad to reach home. ብቸኛው ፡ መንገደኛ ፡ ቤቱ ፡ በመድረሱ ፡ ደስ ፡ አለው
2. (= adv.) ብቻ. He was the lone survivor of the accident. ከአደጋው ፡ የተረፈው ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ነው
3. ብቻውን ፡ የቆመ. A lone house was built on the summit of the hill. ብቻውን ፡ የቆመ ፡ ቤት ፡ በኮረብታው ፡ ላይ ፡ አለ

**loneliness** ብቸኝነት
The misery of loneliness was now compounded by his poverty. ድኽነት ፡ የብቸኝነት ፡ ሥቃዩን ፡ አባሰበት

**lonely**
1. የብቸኝነት. He lives a lonely life. የብቸኝነት ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል
2. ጭር ፡ ያለ. It may be dangerous to walk at night on a lonely road. ጭር ፡ ባለ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ሌሊት ፡ መሄድ ፡ አደገኛ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል
3. ብቻውን ፡ የቆመ. He sequestered himself in a lonely cabin. ብቻውን ፡ በቆመ ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ ተገልሎ ፡ ተቀመጠ

**be lonely**
1. ጭር ፡ አለ. This place is quite lonely in winter. በክረምት ፡ ይህ ፡ ቦታ ፡ ጭር ፡ ያለ ፡ ነው
2. ብቸኝነት ፡ ተሰማ(ው). She was lonely when among strangers. በእንግዶች ፡ መካከል ፡ በነበረችበት ፡ ጊዜ ፡ ብቸኝነት ፡ ተሰማት

**lonesome**
1. ብቸኛ. The lonesome widow sits for hours at the window. ባሏ ፡ የሞተባት ፡ ብቸኛ ፡ ሴት ፡ ለብዙ ፡ ሰዓቶች ፡ መስኮቱ ፡ አጠገብ ፡ ትቀመጣለች
2. (= adv.) ብቸኛ ፡ ሆኖ. He spent a lonesome evening at home. ብቸኛ ፡ ሆኖ ፡ ምሽቱን ፡ አቤት ፡ አሳለፈ

**be lonesome for** ናፈቀ
She is very lonesome for her family. ቤተሰቦቿን ፡ በጣም ፡ ናፍቃለች

**feel lonesome** ብቸኝነት ፡ ተሰማ(ው)
She has felt very lonesome since her husband went away on business. ባሏ ፡ በሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ስለሄደ ፡ ብቸኝነት ፡ በጣም ፡ ይሰማታል

**long** (v.) ጓጓ
I am longing to see my parents again. ወላጆቼን ፡ እንደገና ፡ ለማየት ፡ ጓጉቻለሁ

**long** (adj.)
1. ረጅም ፤ ረጂም ፤ ረዢም. The road is long. መንገዱ ፡ ረጅም ፡ ነው
He made a long speech after the dinner. ከራት ፡ በኋላ ፡ ረጅም ፡ ንግግር ፡ አደረገ
A year is a long time. አንድ ፡ ዓመት ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ነው
2. ረዘም ፡ ያለ. A long drought disheartens a farmer. ረዘም ፡ ያለ ፡ ድርቀት ፡ ገበሬን ፡ ተስፋ ፡ ያስቈርጣል
3. ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ የተደረገ. The long siege turned into a war of attrition. ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ የተደረገው ፡ መከበብ ፡ እንደ ፡ ማዳከም ፡ ጦርነት ፡ ሆነ
4. (= length) ርዝመት. The room is twenty feet long. የክፍሉ ፡ ርዝመት ፡ ሃያ ፡ ጫማ ፡ ነው
*He is late; he must have taken the long way home. የዘገየው ፡ አቋራጭ ፡ ባልሆነው ፡ መንገድ ፡ ቢመጣ ፡ ይሆናል

**long** (adv.)
1. ብዙ. I can't stay long. ብዙ ፡ ልቆይ ፡ አልችልም
2. ብዙ ፡ ጊዜ. He's awfully long getting here. እዚህ ፡ ለመድረስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይወስድበታል
3. ለረጅም ፡ ጊዜ. A reform long advocated by the younger generation was finally adopted. በወጣቱ ፡ ትውልድ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ የተጠየቀው ፡ መሻሻል ፡ በመጨረሻ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ
4. ለብዙ ፡ ጊዜ. War has long afflicted mankind. ጦርነት ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሰውን ፡ በጣም ፡ ጐድቶታል
5. ከ + perfect + ቆየ. I have long intended to call on you. ልጠይቅህ ፡ ካሰብኩ ፡ ቆይቻለሁ

**be (become) long**
1. ረዘመ. The trip became long. መንገዱ ፡ ረዘመ
2. ያህል ፡ ነው. The holidays are six weeks long. የዕረፍት ፡ ጊዜው ፡ ስድስት ፡ ሳምንት ፡ ያህል ፡ ነው

**long after** ከ + perfect + ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ
He got there long after we did. እኛ ፡ ከደረስን ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ደረሰ

**long ago**
1. ከብዙ ፡ (ከረጅም) ፡ ጊዜ ፡ በፊት. That happened long ago. ይህ ፡ የሆነው ፡ ከብዙ ፡ (ከረጅም) ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ነው
2. ከጥንት ፡ ጀምሮ. The medicinal value of this plant was discovered long ago. የዚህ ፡ ዕፅ ፡ ፈዋሽነት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የታወቀ ፡ ነው
3. ከ + perfect + ቆየ. I knew that long ago. ካወቅሁት ፡ ቆይቻለሁ

**long since**
This monument has long since fallen apart. ይህ ፡ ሐውልት ፡ ከፈረሰ ፡ ዘመን ፡ የለውም

**(a) long time** ብዙ ፡ ጊዜ
The trip took a long time. ጉዞው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፈጀ

**(a) long time ago**
1. ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት. Latin died out a long time ago. የላቲን ፡ ቋንቋ ፡ መነገሩ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ቀርቷል
2. ዱሮ. That was a long time ago. ያ ፡ ዱሮ ፡ ነበር

**(a) long way to** የ - - - በጣም ፡ ሩቅ
It is a long way to the top of the mountain. የተራራው ፡ ጫፍ ፡ በጣም ፡ ሩቅ ፡ ነው

**(be a) long way** በጣም ፡ ራቀ
The school is a long way from our house. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ከቤታችን ፡ በጣም ፡ የራቀ ፡ ነው

**(be a) long way off** አልተቃረበም
Christmas is still a long way off. የገና ፡ በዓል ፡ አሁንም ፡ አልተቃረበም

**all day long** ቀኑን ፡ ሙሉ ፤ ሙሉ ፡ ቀን
All day long, he sat there and cried. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ (ሙሉ ፡ ቀን) ፡ እዚያው ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ አለቀሰ

**(do something) all day long** ሲ + imperfect + ዋለ
The child cried all day long. ልጁ ፡ ሲያለቅስ ፡ ዋለ

**(do something) all night long** ሲ + imperfect + አደረ
The child cried all night long. ሕፃኑ ፡ ሲያለቅስ ፡ አደረ

**as long as**
1. እስከ + perfect + ድረስ. It does not bother me as long as the work gets done. ሥራው ፡ እስከ ፡ ተሠራ ፡ ድረስ ፡ ግድ ፡ የለኝም
2. ከ + perfect + ዘንድ. As long as you are here, have dinner with us. እዚህ ፡ ካለህ ፡ ዘንድ ፡ እራት ፡ አብረኸን ፡ ብላ

**as long as you wish** የፈለግኸውን ፡ ጊዜ ፡ ያህል
You can keep it as long as you wish. የፈለግኸውን ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ልታቆየው ፡ ትችላለህ

**(be) awfully long** ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወሰደ(በት)
He is awfully long getting here. እዚህ ፡ ለመድረስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይወስድበታል

**for so long** ለረጅም ፡ ጊዜ
I have not used mathematics for so long, I cannot do the problem. ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሒሳ
ብ ፡ ስላልሠራሁ ፡ ይህን ፡ ጥያቄ ፡ ልሠራ ፡ አ
ልችልም

**go a long way toward**
*This will go a long way toward meeting my needs. ይህ ፡ ችግሬን ፡ ብዙ ፡ ያቃልልልኛል

**the long and the short of it** ባጭሩ
The long and the short of it is that they will be forced to sell all their holdings. ባጭሩ ፡ ንብረታ
ቸውን ፡ እንዲሸጡ ፡ ይገደዳሉ
[See also 'before, how, just, keep, overdue, run, so, standing, that, too, trousers, twice, while, way']

**long-ago** የጥንት
The engraving shows long-ago London.
ቅርጹ ፡ የጥንት ፡ ሎንዶንን ፡ ያሳያል

**longanimity** ታጋሽነት
His longanimity was exhausted by her endless complaints. ታጋሽነቱ ፡ በማያቋርጥ ፡ ንትር
ኳ ፡ አከተመ

**long-distance** የሩቅ ፡ መሥመር
Long-distance phone calls are expensive.
የሩቅ ፡ መሥመር ፡ የስልክ ፡ ጥሪ ፡ ውድ ፡ ነው

**longer** ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ
I wish I could stay here longer. ረዘም ፡ ላ
ለ ፡ ጊዜ ፡ እዚህ ፡ ብቆይ ፡ ደስ ፡ ባለኝ ፡ ነበር

**any longer** እንግዲህስ ፤ ከንግዲህ ፡ ወዲያ
I cannot stand it any longer. እንግዲህስ ፡ ልታገ
ሥ ፡ አልችልም
I can't put off the matter any longer. ነገሩን ፡
ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ላስተላልፈው ፡ አልችልም

**make longer** አስረዘመ
You have to make the dress longer. ቀሚሱን ፡
ማስረዘም ፡ አለብሽ

**much longer** ገፋ ፡ አድርጎ
His training is incomplete; he needs to go to school much longer. የተሰጠው ፡ ትምህርት ፡
የተሟላ ፡ አይደለም ፤ ገፋ ፡ አድርጎ ፡ መማር ፡ ያስ
ፈልገዋል

**stay longer** ቆየ
He wanted to stay longer, but I was sleepy.
እሱ ፡ ሊቆይ ፡ ፈልጎ ፡ ነበር ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እንቅላፋኝ

**longest, at the** ~ ግፋ ፡ ቢል
I can stay only three days at the longest.
ግፋ ፡ ቢል ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ እቆያለሁ

**longevity** የዕድሜ ፡ መርዘም
Longevity is increasing because living standards are improving. የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ እየተሻሻለ ፡ በመ
ሄዱ ፡ የዕድሜ ፡ መርዘም ፡ እየጨመረ ፡ ይሄዳል

**longhand, in** ~ በእጅ
Write the letter in longhand! ደብዳቤውን ፡ በ
እጅ ፡ ጻፍ

**longing**
1. ጉጉት. His longing for fame caused him to die for his country. ለዝና ፡ የነበረው ፡ ጉጉት ፡
ለሀገሩ ፡ ከመሞት ፡ አደረሰው
2. ናፍቆት. He spoke to her in words charged with longing and love. ናፍቆትና ፡ ፍቅር ፡ ባዘ
ለ ፡ አኳኋን ፡ አነጋገራት

**longingly, eye** ~ በመጐምጀት ፡ ተመለከተ
He eyed the chocolate longingly. ቸኮላቱን ፡
በመጐምጀት ፡ ተመለከተ

**longitude** ኬክሮስ
Longitude is a line drawn from north to south.
ኬክሮስ ፡ ከሰሜን ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ የተሠመረ ፡
መሥመር ፡ ነው

**long-range** የረጅም ፡ ጊዜ
Our long-range plans aim at secondary education for all children. የረጅም ፡ ጊዜ ፡ እቅዶቻች
ን ፡ ለልጆች ፡ ሁሉ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህር
ት ፡ ለማድረስ ፡ ነው

**long-standing** የቆየ
The long-standing feud ended with the destruction of both families. የቆየው ፡ ጠብ ፡ በ
ሁለቱ ፡ ቤተሰቦች ፡ መጥፋት ፡ ተፈጸመ

**long-suffering** ብዙ ፡ የታገሠ
During his imprisonment, his long-suffering wife kept the family together. በእስራቱ ፡ ጊዜ ፡
ብዙ ፡ የታገሠችው ፡ ሚስቱ ፡ ቤተሰቡን ፡ ሰብስ
ባ ፡ ያዘች

**look** (v.)
1. ተመለከተ. He looked through the window and saw that the room was empty. በመስኮቱ ፡
ተመልክቶ ፡ ክፍሉ ፡ ባዶ ፡ መሆኑን ፡ አየ
He looked her up and down. ከእግር ፡ እስከ ፡ ራ
ሷ ፡ ተመለከታት
2. አትኩሮ ፡ ተመለከተ. We looked, but saw nothing. አትኩረን ፡ ብንመለከት ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አ
ላየንም
3. መሰለ. The picture's coloring looks fine.
የሥዕሉ ፡ ቀለም ፡ ደኅና ፡ ይመስላል

4. አዘነበለ. Conditions looked toward war. ሁኔታው ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ አዘነበለ
*He looks his age. መልኩ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ዕድሜው ፡ ነው

**look about** አየት ፡ አየት ፡ አደረገ
Look about and see whether you can find the book. መጽሐፉን ፡ ታገኝ ፡ እንደሆነ ፡ እስኪ ፡ አየት ፡ አየት ፡ አድርግ

**look about for** ፈለገ
Are you still looking about for a job? አሁንም ፡ ሥራ ፡ በመፈለግ ፡ ላይ ፡ ነህ ?

**look after**
1. ጠበቀ. Is there anyone to look after the children? ልጆቹን ፡ የሚጠብቅ ፡ ሰው ፡ አለ ?
2. አሰበ(ለት). He needs a wife to look after him. የምታስብለት ፡ ሚስት ፡ ታስፈልገዋለች
3. በዓይን ፡ ተከተለ. They looked after the train as it left the station. ባቡሩ ፡ ጣቢያውን ፡ ሲለቅ ፡ በዓይን ፡ ተከተሉት

**look ahead** መጪውን ፡ አሰበ
He's never in straits because he always looks ahead. መጪውን ፡ ስለሚያስብ ፡ ችግር ፡ ደርሶበት ፡ አያውቅም

**look alike** ተመሳሰለ
The two sisters look alike. ሁለቱ ፡ እኅትማማቾች ፡ ይመሳሰላሉ

**look around**
1. ዞሮ ፡ ፈለገ. Did you look around the bookstores? በየመጽሐፍ ፡ መደብሩ ፡ ዞረህ ፡ ፈለግህ?
2. ፈለገ. We'll have to look around elsewhere. ሌላ ፡ ቦታ ፡ መፈለግ ፡ ይኖርብናል
3. አመዛዘነ. Don't make a decision in a hurry; look around well first! በችኮላ ፡ ቁርጥ ፡ ሐሳብ ፡ አታድርግ ፤ አስቀድመህ ፡ አመዛዝን
4. በዓይኑ ፡ ቃኘ. He looked around the room. ክፍሉን ፡ በዓይኑ ፡ ቃኘ

**look around for** ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እያለ ፡ ፈለገ
When I looked around for her, she was leaving the hall. ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እያልኩ ፡ ስፈልጋት ፡ ከአዳራሹ ፡ ስትወጣ ፡ አየኋት

**look at**
1. አየ. I enjoy looking at pictures. ሥዕል ፡ ማየት ፡ እወዳለሁ
2. መረመረ. You must look at all the facts. መረጃዎቹን ፡ ሁሉ ፡ መመርመር ፡ አለብህ

**look away**
1. ፊቱን ፡ ዘወር ፡ አደረገ(በት). She looked away when I tried to catch her attention. እንድትመለከተኝ ፡ ምልክት ፡ ለመስጠት ፡ ስሞክር ፡ ፊቷን ፡ ዘወር ፡ አደረገችብኝ
2. ፊቱን ፡ ወዲያ ፡ አዞረ. Don't look away while I am taking your photograph. ፎቶግራፍ ፡ ሳነሣሽ ፡ ፊትሽን ፡ ወዲያ ፡ አታዙሪ

**look back** ዞር ፡ አለ
She looked back and saw her mother waving to her. ዞር ፡ ብትል ፡ እናቷ ፡ እጇን ፡ ስታርገበግብ ፡ ተመለከተች

**look back on**
1. መለስ ፡ ብሎ ፡ አሰበ. Looking back on my school days, it seems as if they were a century ago. የትምህርት ፡ ቤት ፡ ጊዜዬን ፡ መለስ ፡ ብዬ ፡ ሳስበው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የሆነው ፡ ይመስለኛል
2. አስታወሰ. He likes to look back on his youth. የልጅነት ፡ ጊዜውን ፡ ማስታወስ ፡ ይወዳል

**look back over** አስታወሰ
He looked back over his childhood and realized how lucky he had been. የልጅነቱን ፡ ጊዜ ፡ አስታውሶ ፡ ምንኛ ፡ ዕድለኛ ፡ እንደነበረ ፡ ተገነዘበ

**look down**
1. አዘቅዝቆ ፡ ተመለከተ. He looked down at the valley below him. ከበታቹ ፡ ያለውን ፡ ሸለቆ ፡ አዘቅዝቆ ፡ ተመለከተ
2. ናቀ. You must not look down on people just because they are poor. ሰውን ፡ ድኻ ፡ ስለሆነ ፡ ብቻ ፡ መናቅ ፡ አይገባህም

**look for**
1. ፈለገ. We are looking for a room. ክፍል ፡ እንፈልጋለን
Did you look in every drawer for the letter? ደብዳቤውን ፡ ሁሉም ፡ መሳቢያ ፡ ውስጥ ፡ ፈለግሽው?
2. ጠበቀ. I'll look for you about 3 o'clock. በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ እጠብቅሃለሁ

**look forward** ጓጓ ፤ በጉጉት ፡ ተጠባበቀ
I am looking forward to meeting you. እንተን ፡ ለማየት ፡ ጓጉቻለሁ
We are looking forward to our vacation. የዕረፍት ፡ ጊዜያችንን ፡ በጉጉት ፡ እንጠባበቃለን

**look good** አማረ
The house does not look so good from the inside. ቤቱ ፡ ከውስጥ ፡ እንደውጪው ፡ አያምርም

**look in on** ጐራ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ
Let's look in on our friends on the way home! ወደ ፡ ቤት ፡ ስንሄድ ፡ ወዳጆቻችንን ፡ ጐራ ፡ ብለን ፡ እንጠይቅ

**look into**
1. መረመረ. We will have to look into the matter. ነገሩን ፡ መመርመር ፡ አለብን
2. አጣራ. This may or may not be true, but we will look into it anyway. ይህ ፡ እውነት ፡ ሊ

ሆንም ፡ ላይሆንም ፡ ይችላል ፤ ያም ፡ ሆነ ፡ ይሁ ፡ ነገሩን ፡ እናጣራለን
3. *ዐወቀ*. You cannot look into the future. የወደፊቱን ፡ ልታውቅ ፡ አትችልም

**(they) look it too**
*These shoes are cheap, and they look it too. እነዚህ ፡ ጫማዎች ፡ ርካሽ ፡ ናቸው ፤ መልካቸውም ፡ ይመሰክራል

**look like** መሰለ
That pencil looks like mine. ያ ፡ እርሳስ ፡ የኔን ፡ እርሳስ ፡ ይመስላል
*After reading the news, I think it looks like war. ጋዜጣውን ፡ ካነበብኩ ፡ በኋላ ፡ ጦርነት ፡ እንደሚነሣ ፡ ተሰማኝ

**look on** ተመለከተ
The police did nothing to stop the rioters, but merely looked on. ፖሊሶቹ ፡ ረብሸኞቹን ፡ ለማቆም ፡ እርምጃ ፡ ሳይወስዱ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ይመለከቷቸው ፡ ነበር

**look on one as** እንደ --- ቈጠረ ፤ እንደ --- ተመለከተ
They looked on her as a stranger. እንደ ፡ እንግዳ ፡ ቈጠሯት
I look on him as my best friend. እንደ ፡ ልብ ፡ ጓደኛዬ ፡ እመለከተዋለሁ

**look oneself**
You don't look yourself. እንደ ፡ ወትሮህ ፡ አይደለህም

**look out**
1. ወደ ፡ ውጭ ፡ ተመለከተ. He looked out the window and saw a parade passing by. በመስኮት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ቢመለከት ፡ ሰልፈኞች ፡ ሲያልፉ ፡ አየ
2. ወደ ፡ ውጭ ፡ አየ. She parted the curtains to look out. ወደ ፡ ውጭ ፡ ለማየት ፡ መጋረጃዎቹን ፡ ገለጠች
3. አሰበ. The selfish girl looks out for herself exclusively. እራሷን ፡ ወዳድ ፡ ልጃገረድ ፡ ለራሷ ፡ ብቻ ፡ ታስባለች
4. ተጠነቀቀ. He has to look out for his health. ስለ ፡ ጤንነቱ ፡ መጠንቀቅ ፡ አለበት
Look out! There are things falling. ተጠንቀቅ ፡ የሚወድቅ ፡ ነገር ፡ አለ

**look out (at, on)**
1. አሻግሮ ፡ ተመለከተ. He leaned on the ship's rail and looked out at the ocean. በመርከቡ ፡ መደገፊያ ፡ ላይ ፡ ተደግፎ ፡ ወደ ፡ ውቅያኖስ ፡ አሻግሮ ፡ ተመለከተ
2. ከ --- ትይዩ ፡ ነው. Our windows look out on a large square. መስኮታችን ፡ ካንድ ፡ ሰፊ ፡ አደባባይ ፡ ትይዩ ፡ ነው

**look over**
1. በደንብ ፡ ተመለከተ. We must look over the house before we decide to buy it. ቤቱን ፡ ለመግዛት ፡ ከመወሰናችን ፡ በፊት ፡ በደንብ ፡ መመልከት ፡ አለብን
2. በጥንቃቄ ፡ ተመለከተ. Please look over your papers before you hand them in. ወረቀትህን ፡ ከመስጠትህ ፡ በፊት ፡ በጥንቃቄ ፡ ተመልከተው
3. አስተውሎ ፡ አየ. He looked him over from head to foot. ከእግር ፡ እስከ ፡ ራሱ ፡ አስተውሎ ፡ አየው
4. አንገቱን ፡ ብቅ ፡ አድርጎ ፡ ተመለከተ. The fledglings looked over the edge of the nest. የወፍ ፡ ጫጩቶች ፡ በጎጆው ፡ ጠርዝ ፡ ላይ ፡ አንገታቸውን ፡ ብቅ ፡ አድርገው ፡ ተመለከቱ

**look through**
1. ፈተሸ. Look through your clothes and see whether you have any of my shirts! ልብሶችህን ፡ ፈትሸና ፡ ሸሚዜ ፡ ተደባልቆ ፡ እንደሆነ ፡ እይልኝ
2. በውስጡ ፡ አየ. The glass is painted so that you cannot look through. በውስጡ ፡ ለማየት ፡ እንዳይቻል ፡ ተደርጎ ፡ መስታወቱ ፡ ቀለም ፡ ተቀብቷል
3. አገላበጠ ፡ ተመለከተ. Look through your notes before you take the exam. ፈተና ፡ ከመውሰድህ ፡ በፊት ፡ ደብተርህን ፡ አገላብጠህ ፡ ተመልከተው

**look to**
1. ተማመነ. The country must look to the army to defend it. ሀገሪቷ ፡ ለመከላከያ ፡ በጦር ፡ ሰራዊት ፡ መተማመን ፡ አለባት
2. በደንብ ፡ ያዘ. Look to your fences, or your cattle will get loose. አጥርህን ፡ በደንብ ፡ ያዝ ፤ ያለዚያ ፡ የቀንድ ፡ ከብቶችህ ፡ ይጠፋሉ
3. በተስፋ ፡ ተጠባበቀ ፤ በናፍቆት ተጠባበቀ. We look to the day when world peace will be a reality. የዓለም ፡ ሰላም ፡ የሚገኝበትን ፡ ጊዜ ፡ በተስፋ ፡ (በናፍቆት) ፡ እንጠባበቃለን

**look toward** በ --- ትይዩ ፡ ነው
The hotel looks toward the lake. ሆቴሉ ፡ በሐይቁ ፡ ትይዩ ፡ ነው

**look up** (vt.)
1. ተመለከተ. For my essay, I have to look up several books on the subject. ለድርሰቴ ፡ ስለ ፡ እርእሰቱ ፡ የሚገልጹ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ መመልከት ፡ አለብኝ
2. ፈለገ. I have to look up something. እምፈልገው ፡ ነገር ፡ አለ
When I came to Addis Ababa, I looked up an old friend. አዲስ ፡ አበባ ፡ ስመጣ ፡ የቆየ ፡ ጓደኛዬን ፡ ፈለግሁት

3. **መጥቶ ፡ ጠየቀ**. Look me up some time, won't you? አንድ ፡ ጊዜ ፡ መጥተህ ፡ ጠይቀኝ ፤ እሺ?

**look up** (vi.)

1. **ቀና ፡ አለ**. He did not even look up when I called him. ስጠራው ፡ ቀና ፡ እንኳን ፡ አላለም

2. **ተሻሻለ**. Things are beginning to look up, now that he is back. አሁን ፡ ስለተመለሰ ፡ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ መሻሻል ፡ ጀምሯል

**look up to**

1. **አመለከ**. She looks up to him because she thinks he is almost perfect. ፍጹም ፡ ስለሚመስላት ፡ ታመልከዋለች

2. **አከበረ**. He looks up to his older brother and follows his example. ታላቅ ፡ ወንድሙን ፡ ስለሚያከብረው ፡ አርአያውን ፡ ይከተላል

**look (one's) way ወደሱ ፡ ዞር ፡ አለ**

He did not look my way when he passed by. ሲያልፍ ፡ ወደኔ ፡ ዞርም ፡ አላለ

[See also 'bare, dejected, downcast, favor, fit, forward, grave, like, limp, nose, pensive, pleased, round, sharp, small, sullen, well']

**look** (n.)

1. **መልክ**. A look of pleasure came over her face. የደስታ ፡ መልክ ፡ እፊቷ ፡ ላይ ፡ ታየ

2. **አስተያየት**. He gazed at me with an abstracted look. በተመስጦ ፡ አስተያየት ፡ አትኩሮ ፡ ተመለከተኝ

**looks መልክ**

All we got was angry looks from the neighbors. ከጐረቤቶቻችን ፡ ያገኘነው ፡ የቁጣ ፡ መልክ ፡ ብቻ ፡ ነበር

**by his looks ከሁኔታው**

To judge by his looks, he is a warrior. ከሁኔታው ፡ ጦረኛ ፡ ይመስላል

**give (one) a look ተመለከተ**

He gave me an angry look. በቁጣ ፡ ተመለከተኝ

**have a look**

1. **መሰለ**. The town has a European look. ከተማው ፡ የአውሮፓን ፡ ከተሞች ፡ ይመስላል

2. **አየ**. Let's have a look at your hand! እስቲ ፡ እጅህን ፡ እንየው

**take a look at ተመለከተ**

Take a look at this painting, and tell me what it is supposed to be! ይህን ፡ ሥዕል ፡ ተመልከተህ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ንገረኝ

[See also 'desolate, foolish, glacial, icy, intent, sheepish']

**looking glass የፊት ፡ መስታወት**

She broke her looking glass. የፊት ፡ መስታወቷን ፡ ሰበረችው

**lookout ማማ**

A lookout was placed on every hill. በየኮረብታው ፡ ላይ ፡ ማማ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር

**be on the lookout for**

1. **ፈላለገ**. I will be on the lookout for you when you arrive at the station. ባቡር ፡ ጣቢያ ፡ ስትደርስ ፡ እፈላልግሃለሁ

Whenever he goes to the market, he is on the lookout for old books. ወደ ፡ ገበያ ፡ በወጣ ፡ ቁጥር ፡ አሮጌ ፡ መጽሐፍ ፡ ይፈላልጋል

2. **ተጠነቀቀ**. Be on the lookout for snakes while walking in the forest. በጫካው ፡ ውስጥ ፡ ስትሄድ ፡ እባብ ፡ ተጠንቀቅ

**keep a lookout ተጠባበቀ**

Keep a good lookout, and tell me when you see the train! በጥንቃቄ ፡ ተጠባበቅና ፡ ባቡሩን ፡ ስታይ ፡ ንገረኝ

**loom** (v.) **ታየ**

A tall shape loomed in the darkness. በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ረጅም ፡ ቅርጽ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ታየ

**loom** (n.) **የሸማኔ ፡ እቃ**

The weaver is weaving on a loom. ሸማኔው ፡ በሸማኔ ፡ እቃ ፡ ልብስ ፡ ይሠራል

**loop** (v.) **ወርውሮ ፡ አሳለፈ**

He looped a rope over the branch. ገመዱን ፡ በቅርንጫፉ ፡ ላይ ፡ ወርውሮ ፡ አሳለፈ

**loop** (n.)

1. **ቀለበት**. The letters d and q have loops. ደ ፡ እና ፡ ቀ ፡ ፊደሎች ፡ ቀለበት ፡ አላቸው

2. **ቋጠሮ**. The loop of the rope is wide. የገመዱ ፡ ቋጠሮ ፡ ሰፊ ፡ ነው

**loophole**

1. **ቀዳዳ**. The soldier made a loophole in the wall so that he could fire at the enemy. ወታደሩ ፡ በጠላት ፡ ላይ ፡ ለመተኰስ ፡ እንዲመቸው ፡ በግድግዳው ፡ ላይ ፡ ቀዳዳ ፡ አበጀ

2. **ማምለጫ ፡ መንገድ**. The lawyer found a loophole in the law. ጠበቃው ፡ ከሕጉ ፡ ትርጉም ፡ ማምለጫ ፡ መንገድ ፡ አገኘ

**loose** (v.)

1. **ለቀቀ**. The girl loosed her hair. ልጃገረዲቷ ፡ ጸጉሯን ፡ ለቀቀችው

We loosed the wild horse. ያልተገራውን ፡ ፈረስ ፡ ለቀቅነው

2. **ላላ ፡ አደረገ**. He loosed his grasp. አያያዙን ፡ ላላ ፡ አደረገ

**loose** (adj.)

1. **ልል**. It is easy to plow loose soil. ልል ፡ አፈርን ፡ ማረስ ፡ ቀላል ፡ ነው
2. **ያልታሰረ**. The loose ends of the rope became tangled. ያልታሰሩት ፡ የገመዱ ፡ ጫፎች ፡ ተወሳሰቡ
3. **ልክስክስ**. His loose conduct was ground for his dismissal. ልክስክስ ፡ ምግባሩ ፡ ከሥራ ፡ ለመሰናበቱ ፡ ምክንያት ፡ ነበር
4. **በደንብ ፡ ያልተደረገ**. A loose count showed there were more than fifty people. በደንብ ፡ ያልተደረገ ፡ ቈጠራ ፡ ከኀምሳ ፡ ሰዎች ፡ የበለጠ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ አሳየ
5. **በጣም ፡ የማይቃረብ**. This is a loose translation from Amharic. ካማርኛ ፡ በጣም ፡ የማይቃረብ ፡ ትርጉም ፡ ነው

*He is known for his loose business practices. በንግድ ፡ ሥራው ፡ ላይ ፡ እምነት ፡ አጕዳይነቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**loose life, lead a ~**
*He leads a loose life. ኑሮው ፡ የተልክሰከሰ ፡ ነው

**loose tongue, have a ~** ወሬኛ ፡ ነው
She has a loose tongue, so watch what you tell her. ወሬኛ ፡ ስለሆነች ፡ ስለምትነግራት ፡ ነገር ፡ ጠንቀቅ ፡ በል

**be loose**
1. **ላላ**. The button is loose. ቁልፉ ፡ ላልቷል
2. **ተፈታ**. The dog has been loose all night. ውሻው ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ተፈቶ ፡ ነበር

**break loose**
1. **ፈለቀቀ**. The criminal broke loose from the policeman's grip and escaped. ወንጀለኛው ፡ ከፖሊሱ ፡ እጅ ፡ ፈልቅቆ ፡ አመለጠ
2. **አመለጠ**. The man broke loose from prison. ሰውዬው ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ አመለጠ
3. **ተበጠሰ ፤ ተፈታ**. The box that was tied to the back of the car broke loose and fell on the road. ከመኪናው ፡ በስተጀርባ ፡ የነበረው ፡ ሣጥን ፡ ተበጥሶ ፡ (ተፈቶ) ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ወደቀ
4. **ከማሰሪያ ፡ አመለጠ**. The dog has broken loose. ውሻው ፡ ከማሰሪያው ፡ አመለጠ

**come loose** ለቀቀ
The seam on my coat is coming loose. የኮቴ ፡ ስፌት ፡ እየለቀቀ ፡ ነው

**cut loose** (vt.)
1. **ቈረጠ**. He cut loose the boat from the pier, and it sank. ጀልባው ፡ ከመቆሚያው ፡ ጋር ፡ የታሰረበትን ፡ ገመድ ፡ ስለቈረጠው ፡ ሰጠመ
2. **እስራቱን ፡ ቈርጦ ፡ ለቀቀው**. They found the owner of the store tied up, and they cut him loose. የሱቁን ፡ ባለቤት ፡ ታስሮ ፡ ስለ ፡ አገኙት ፡ እስራቱን ፡ ቈርጠው ፡ ለቀቁት
3. **ማሰሪያውን ፡ ቈረጠ**. The box was tied so tightly, they had to cut it loose. ሣጥኑ ፡ በጣም ፡ በጥብቅ ፡ ታስሮ ፡ ስለነበረ ፡ ማሰሪያውን ፡ መቍረጥ ፡ ነበረባቸው

**cut loose** (vi.) መረበሽ ፡ ጀመረ
They cut loose the minute the teacher leaves the room. አስተማሪው ፡ ገና ፡ ወጣ ፡ ሲል ፡ መረበሽ ፡ ይጀምራሉ

**get loose**
1. **አመለጠ**. One of the lions in the zoo has gotten loose. በአራዊት ፡ መሰብሰቢያ ፡ ስፍራ ፡ ካሉት ፡ አንበሶች ፡ አንዱ ፡ አምልጧል
2. **ወጣ**. His foot was lodged between two rocks, and he could not get loose. እግሩ ፡ ከሁለት ፡ ቋጥኝ ፡ መካከል ፡ ስለተቀረቀረ ፡ ለመውጣት ፡ አልቻለም
3. **ጠፋ**. Look to your fences, or your cattle will get loose. አጥርህን ፡ በደንብ ፡ ያዝ ፤ ያለዚያ ፡ የቀንድ ፡ ከብቶችህ ፡ ይጠፋሉ
4. **ማሰሪያውን ፡ ፈታ**. The dog got loose and ran away. ውሻው ፡ ማሰሪያውን ፡ ፈቶ ፡ አመለጠ

**hang loose** ተንዘረፈፈ
The coat hung loose. ኮቱ ፡ ተንዘረፈፈ

**let loose** ለቀቀ
He let loose the chained dog. የታሰረውን ፡ ውሻ ፡ ለቀቀው

**(be) on the loose** ከእስር ፡ ቤት ፡ አመለጠ
The criminal is on the loose. ወንጀለኛው ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ አምልጧል

**run around loose**
*Is the dog allowed to run around loose? ውሻው ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እንዲል ፡ ይለቀቃል ?

**set loose** ለቀቀ
He set loose the trapped animal. በወጥመድ ፡ የተያዘውን ፡ እንስሳ ፡ ለቀቀ

**shake loose** አስለቀቀ
His grip is tenacious and hard to shake loose. አያያዙ ፡ የጠበቀና ፡ ለማስለቀቅ ፡ የሚያስቸግር ፡ ነው

**turn loose** ፈቶ ፡ ለቀቀ ፤ ለቀቀ
He turned the dog loose and let it run. ውሻው ፡ እንዲሮጥ ፡ ፈቶ ፡ ለቀቀው
He turned the cat loose. ድመቷን ፡ ለቀቃት

**loosen** (vt.)

1. **አላላ**. Can you loosen this screw? ይህን ፡ ቅርንፉድ ፡ ልታላላው ፡ ትችላለህ ?

I want to loosen my shoe laces. የጫማዬን ፡ ማሰሪያ ፡ ለማላላት ፡ እፈልጋለሁ
2. አለሰለሰ. One should loosen the soil before planting. ከመዝራት ፡ በፊት ፡ መሬትን ፡ ማለስለስ ፡ ያስፈልጋል
3. አነቃነቀ. The strong wind did not loosen the posts of the fence. ከባዱ ፡ ነፋስ ፡ ያጥሩን ፡ ቋሚዎች ፡ አላነቃነቃቸውም

**loosen** (vi.) ላላ ፡ አለ
His hold on the children loosened as they got older. በልጆቹ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ቁጥጥር ፡ ልጆቹ ፡ እያደጉ ፡ ሲሄዱ ፡ ላላ ፡ አለ

**loot** (v.) ዘረፈ
The soldiers looted and massacred for three weeks. ወታደሮቹ ፡ ለሦስት ፡ ሳምንታት ፡ ያህል ፡ ሲዘርፉና ፡ ሲገድሉ ፡ ቆዩ

**loot** (n.)
1. ምርኮ. We raided the enemy's camp and got much loot. የጠላትን ፡ ሰፈር ፡ ወረን ፡ ብዙ ፡ ምርኮ ፡ አገኘን
2. የዘረፈው. The robbers divided their loot among themselves. ዘራፊዎቹ ፡ የዘረፉትን ፡ ተከፋፈሉት

**get loot** ዘረፈ
The robbers got much loot. ቀማኞቹ ፡ ብዙ ፡ ዘረፉ

**lopsided** ተጣሞ
The picture is hanging lopsided. ሥዕሉ ፡ ተጣሞ ፡ ተሰቅሏል

**be lopsided** አጋደለ
The load on the mule is lopsided and will soon fall. በቅሎው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጭነት ፡ አጋድሏልና ፡ በቅርቡ ፡ ይወድቃል

**loquacious** ለፍላፊ
His sister is very loquacious. እኅቱ ፡ በጣም ፡ ለፍላፊ ፡ ናት

**lord**
1. ፈላጭ ፡ ቈራጭ. He is the lord of that area. የዚያ ፡ ቀበሌ ፡ ፈላጭ ፡ ቈራጭ ፡ ነው
2. ሹም. They honored the lord of the town. የከተማውን ፡ ሹም ፡ አከበሩት

**Our Lord** ጌታችን
Our Lord died on the cross. ጌታችን ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ሞተ

**lore**
1. ወግ. Indian lore may be forgotten in another generation. የህንዶች ፡ ወግ ፡ ከአንድ ፡ ትውልድ ፡ በኋላ ፡ ይረሳ ፡ ይሆናል
2. ልማድ. The scouts learn Indian lore. እስካውቶቹ ፡ የህንዶችን ፡ ልማድ ፡ ይማራሉ

**lorry** የጭነት ፡ መኪና
Load the lorry with bricks! የጭነት ፡ መኪናውን ፡ ጡብ ፡ ጫነው

**lose** (lost), vt.
1. አጠፋ. We lost hours in the heavy traffic. ከመኪናው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ አጠፋን
2. አጣ. He lost his entire fortune during the war. በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ሃብቱን ፡ በሙሉ ፡ አጣ
They lost a son in the war. በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ልጃቸውን ፡ አጡ
3. ጣለ ፤ ጠፋ(በት). I lost my pencil again. እንደገና ፡ እርሳሴን ፡ ጣልኩ ፡ (ጠፋብኝ)
4. ሳተ. Don't lose your way! መንገድህን ፡ አትሳት
He lost his head in the crisis. በደረሰበት ፡ ችግር ፡ ራሱን ፡ ሳተ
5. አመለጠ(ው). +I did not lose a word of the lecture. ከንግግሩ ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ አላመለጠኝም
6. ተበላ. He lost $200 gambling. በቁማር ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ተበላ
7. ተሸነፈ. We lost the game. በግጥሚያው ፡ ተሸነፍን
8. ተረታ. I lost the lawsuit. ሙግቱን ፡ ተረታሁ
9. ተቈረጠ. He lost a leg in an auto accident. በመኪና ፡ አደጋ ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ እግሩ ፡ ተቈረጠ
10. ተጐዳ. You will lose nothing by waiting. ብትቆይ ፡ ምንም ፡ አትጐዳም
11. ከ - - - ወጣ ፤ ከ - - - ተሰናበተ ፤ ለቀቀ. He is morose because he lost his job. ከሥራው ፡ ስለወጣ ፡ (ስለተሰናበተ, or ሥራውን ፡ ስለለቀቀ) ፡ ከፍቶታል
12. ከሰረ. We lost on that deal. በዚያ ፡ ንግድ ፡ ከሰርን
13. ከ - - - አጣላ. His mean remarks lost him many friends. አስከፊ ፡ አስተያየቱ ፡ ከብዙ ፡ ጓደኞቹ ፡ አጣላው
14. ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀረ. My watch loses three minutes a day. ሰዓቱ ፡ በቀን ፡ ሦስት ፡ ደቂቃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ትቀራለች

**lose** (vi.) ተሸነፈ
We played well, but we lost. ጥሩ ፡ ተጫውተን ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ተሸነፍን

**be lost**
1. ጠፋ. My shirt was lost in the laundry. ሸሚዜ ፡ ልብስ ፡ አጣቢ ፡ ቤት ፡ ጠፋ
2. ተበላሸ. The harvest was lost because of too

much rain. ከዝናብ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ መኸሩ ፡ ተበላሸ

3. የሚያደርገውን ፡ አያውቅም. Since his wife's death, he is completely lost. ከሚስቱ ፡ ሞት ፡ ወዲህ ፡ የሚያደርገውን ፡ በፍጹም ፡ አያውቅም

4. መንገድ ፡ ሳተ. Being lost in the desert is an unpleasant experience. በረኻ ፡ ውስጥ ፡ መንገድ ፡ መሳት ፡ መጥፎ ፡ አጋጣሚ ፡ ነው

5. ተመሰጠ. He was lost in a book and failed to hear us come in. በመጽሐፉ ፡ ተመስጦ ፡ ስለነበር ፡ ስንገባ ፡ ሳይሰማን ፡ ቀረ

6. ተዋጠ. He is lost in thought. በሐሳብ ፡ ተውጧል

**lose (the) battle** ድል ፡ ተነሣ

The enemy lost the battle. ጠላት ፡ ድል ፡ ተነሣ

**lose (the) edge** ደነዘ

The plough must be tempered to keep it from losing its edge. ማረሻው ፡ እንዳይደንዝ ፡ በእሳት ፡ ግሎ ፡ መቀጥቀጥ ፡ አለበት

**lose (the) fight** ተሸነፈ

When I was losing the fight, he came to my aid. በድብድቡ ፡ ልሸነፍ ፡ ስል ፡ ሊያግዘኝ ፡ መጣ

**lose (one's) hair**

1. ጸጉሩ ፡ ተመለጠ. He is losing his hair because of a disease. ከበሽታ ፡ የተነሣ ፡ ጸጉሩ ፡ እየተመለጠ ፡ ነው

2. ተመለጠ. He's beginning to lose his hair. መመለጥ ፡ ጀምሯል

3. በራ ፡ ሆነ. I am losing my hair. በራ ፡ መሆኔ ፡ ነው

**lose (one's) memory** ማስታወስ ፡ አቃተው

He lost his memory because he was hit on the head. ራሱን ፡ ከተመታ ፡ ወዲህ ፡ ማስታወስ ፡ አቃተው

**lose money** ከሰረ

He lost a lot of money in business last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ በንግድ ፡ ብዙ ፡ ከሰረ

**lose oneself** ጠፋ

The boy lost himself in the crowd. ልጁ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ጠፋ

**lose sight of**

1. ዘነጋ. We must not lose sight of the fact that he is a thief. ሌባ ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ የለብንም

2. ጠፋ(በት). +I lost sight of him in the thick fog. ጥቅጥቅ ፡ ባለው ፡ ጭጋግ ፡ ውስጥ ፡ ጠፋብኝ

3. አላየም. I have lost sight of him lately. በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ አላየሁትም

*We must have guidelines to keep from losing sight of the goal. ዓላማችን ፡ ግቡን ፡ እንዳይስት ፡ ለማድረግ ፡ መምሪያ ፡ እንዲኖረን ፡ ይገባል

**lose (one's) strength** ደከመ

I've lost all my strength after this long trip. ከዚህ ፡ ከረጅም ፡ ጉዞ ፡ ወዲህ ፡ በፍጹም ፡ ደክሚያለሁ

[See also various nouns with 'lose', such as 'balance, life, weight']

**loss**

1. ማጣት. Loss of health is a serious matter. ጤና ፡ ማጣት ፡ አሳሳቢ ፡ ነገር ፡ ነው

2. ጥፋት. Losses in war are not soon made up. በጦርነት ፡ ምክንያት ፡ የሚደርሱ ፡ ጥፋቶች ፡ በቶሎ ፡ ሊተኩ ፡ አይችሉም

3. ጉዳት. They suffered heavy losses. ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ ደረሰባቸው

4. መጥፋት. The old man was embittered by the loss of his money. ሽማግሌው ፡ በገንዘቡ ፡ መጥፋት ፡ ተመረረ

5. ሞት. She grieved for the loss of her son. በወንድ ፡ ልጇ ፡ ሞት ፡ አዘነች

6. መሞት. He bewailed the loss of his son in battle. ልጁ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ በመሞቱ ፡ አለቀሰ

7. መመለጥ. Nothing can be done about loss of hair. ስለ ፡ ጸጉር ፡ መመለጥ ፡ ምንም ፡ ሊደረግ ፡ አይቻልም

8. ኪሳራ. I sold the house at a loss. ቤቱን ፡ በኪሳራ ፡ ሸጥኩት

*Can you come without any loss of time? ጊዜ ፡ ሳታባክን ፡ ልትመጣ ፡ ትችላለህ ?

*The loss of life increased each day. የሚሞተው ፡ ሰው ፡ ቁጥር ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ እየጨመረ ፡ ሄደ

**be at a loss** ግራ ፡ ገባ(ው)

+I am at a loss to understand your actions. አድራጎትህን ፡ ለመረዳት ፡ ግራ ፡ ገብቶኛል

*I am at a loss to explain his absence. የቀረበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ልል ፡ አልችልም

**be never at a loss for**

1. ምንጊዜም ፡ አያጣም. He is never at a loss for a excuse. ምንጊዜም ፡ ምክንያት ፡ አያጣም

2. አይቸግረውም. He has presence of mind and is never at a loss for an answer. አእምሮው ፡ ንቁ ፡ ስለሆነ ፡ ምንጊዜም ፡ መልስ ፡ አይቸግረውም

*He's never at a loss for something to do. እጁ ፡ ሥራ ፡ ፈቶ ፡ አያውቅም

**lost,** see **lose**

**lost** (adj.)
1. የባከነ. Lost time can never be made up. የባከነ ፡ ጊዜ ፡ አይመለስም
2. የጠፋ. The police found the lost boy. ፖሊሶች፡ የጠፋውን ፡ ልጅ ፡ አገኙት
3. መንገድ ፡ የጠፋ. The lost traveler saw a glimmer in the woods. መንገድ ፡ የጠፋው ፡ መንገደኛ ፡ በጫካው ፡ ውስጥ ፡ የመብራት ፡ ጭላንጭል ፡ ታየው
4. ወድቆ ፡ የተገኘ. Turn in lost articles to the principal! ወድቀው ፡ የተገኙ ፡ እቃዎችን ፡ ለሥራ ፡ መሪው ፡ አስረክብ
5. ድል ፡ የሆነበት. The lost battle was fortunately not an important one. ድል ፡ የሆነበት ፡ ጦርነት ፡ እንደ ፡ ዕድል ፡ ሆኖ ፡ ዋጋ ፡ አልነበረውም

**be lost** ከዓይን ፡ ተሰወረ
The hill is lost in the distance. ኮረብታው ፡ ከር ቀት ፡ የተነሣ ፡ ከዓይን ፡ ተሰውሯል

**get lost** ጠፋ
The dog wandered off and got lost. ውሻው ፡ ሲንከራተት ፡ ጠፋ

**lot**
1. መሬት. How big is your lot? መሬትህ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ስፋት ፡ አለው ?
2. መደብ. They measured off the ground into small lots. መሬቱን ፡ በትንንሽ ፡ መደብ ፡ ከፋፈ ሉት
3. ዕጣ. Let's draw lots to see who should go first. ማን ፡ መጀመሪያ ፡ እንደሚሄድ ፡ ዕጣ ፡ እ ናውጣ
4. ዕድል. His unhappy lot made him look old prematurely. መጥፎ ፡ ዕድሉ ፡ ያለ ፡ ጊዜው ፡ ያ ረጀ ፡ አስመሰለው
He cast in his lot with the gangsters. ዕድሉን ፡ ከወንበዴዎች ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አደረገ
5. ጥቅል. I will send you the books in three separate lots. መጽሐፎቹን ፡ በሦስት ፡ ጥቅል ፡ ከ ፍፍሎ ፡ እልክልሃለሁ
*He is the only one of the lot that you can trust. ከመሀከላቸው ፡ ልትተማመንበት ፡ የምትች ለው ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ነው

**lots of** ብዙ
She has lots of money. ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አላት

**a lot** በጣም
We like him a lot. በጣም ፡ እንወደዋለን
He is a lot better than people think. እሱ ፡ ሰዎ ች ፡ ከሚገምቱት ፡ በጣም ፡ የተሻለ ፡ ነው

**a lot of** ብዙ
I still have a lot of work. አሁንም ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ አለኝ

**quite a lot**
1. ብዙ ፡ ጊዜ. I saw quite a lot of her when I was in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በነበርኩ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አገኛት ፡ ነበር
2. ብዙ. For one day, he accomplished quite a lot. ባንድ ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ ፈጸመ

**quite a lot of** በርከት ፡ ያለ
I have quite a lot of money. በርከት ፡ ያለ ፡ ገ ንዘብ ፡ አለኝ

**(the) whole lot** ጠቅላላ
I will let you take the whole lot for only five dollars. ጠቅላላውን ፡ ባምስት ፡ ብር ፡ እሸጥ ልሃለሁ
[See also 'mean, think']

**lotion** ቅባት
She rubbed her skin with a soothing lotion. ሕመም ፡ በሚያስታግሥ ፡ ቅባት ፡ ቆዳዋን ፡ አሸች
[See also 'soothing']

**lottery** ሎተሪ
I bought a ticket in the national lottery. አንድ ፡ የብሔራዊ ፡ ሎተሪ ፡ ቲኬት ፡ ገዛሁ

**loud** (adj.)
1. ጉልህ ፤ ከፍ ፡ ያለ. She has a loud voice. ጉ ልህ ፡ (ከፍ ፡ ያለ) ፡ ድምፅ ፡ አላት
2. ጩኸት ፡ የበዛበት. The loud demonstration disturbed the quiet of the evening. ጩኸት ፡ የበ ዛበት ፡ ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ የምሽቱን ፡ ጸጥታ ፡ አ ወከው
3. ጮክ ፡ ያለ. We heard loud laughter behind us. ከኋላችን ፡ ጮክ ፡ ያለ ፡ ሣቅ ፡ ሰማን
4. የሚንጫጫ. The loud boys were told to go away. የሚንጫጩት ፡ ልጆች ፡ ዘወር ፡ እንዲሉ ፡ ተነገራቸው
5. ደማቅ. I do not like loud colors. ደማቅ ፡ ቀ ለም ፡ አልወድም

**loud** (adv.) ጮኾ
Don't talk so loud! እንደዚህ ፡ ጮኸህ ፡ አትና ገር
[See also 'crash, think']

**loudly**
1. በኀይል. Someone knocked loudly at the door. አንድ ፡ ሰው ፡ መዝጊያውን ፡ በኀይል ፡ አንኳኳ
2. ጮክ ፡ ብሎ. He spoke loudly. ጮክ ፡ ብሎ ፡ ተ ናገረ
3. ጮኾ. He emphasized the word by saying it very loudly. በጣም ፡ ጮኾ ፡ በመናገር ፡ ቃሉን ፡ አ ጋነነ

**loudspeaker** የድምፅ ፡ ማጒሊያ
I heard the announcement over the loudspeaker. ማስታወቂያውን ፡ በድምፅ ፡ ማጒሊያው ፡ ሰማሁ

**lounge** (v.) ተዝናና
Several young men were lounging around the counter when I came up. እኔ ፡ ስደርስ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ወጣቶች ፡ በባንኮው ፡ ዙሪያ ፡ ይዝናኑ ፡ ነበሩ

**lounge** (n.) የመዝናኛ ፡ ክፍል
Coffee is being served in the lounge. በመዝናኛ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ቡና ፡ እየታደለ ፡ ነው

**louse** (lice) ቅማል
Lice are carriers of disease. ቅማል ፡ በሽታ ፡ አስተላላፊ ፡ ነው

**lovable** የደስደስ ፡ ያለው ፤ ደስ ፡ የሚል
She is a lovable baby. የደስደስ ፡ ያላት ፡ (ደስ ፡ የምትል) ፡ ሕፃን ፡ ነች

**love** (v.)
1. ወደደ. I love apples. ቱፋ ፡ እወዳለሁ
He loves her very much. በጣም ፡ ይወዳታል
2. በጣም ፡ ደስ ፡ አለ(ው). Would you like a cup of coffee? I'd love one. አንድ ፡ ሲኒ ፡ ቡና ፡ ትፈልጋለህ ? በጣም ፡ ደስ ፡ ይለኛል

**love** (n.)
1. ፍቅር. Love is blind. ፍቅር ፡ ዓይን ፡ የለውም
2. መውደድ. His love of books led him to found a library. መጽሐፍ ፡ መውደዱ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍትን ፡ እንዲያቋቁም ፡ ገፋፋው
3. ፍላጎት. I study languages for love. ቋንቋ ፡ የማጠናው ፡ ለፍላጎት ፡ ብቻ ፡ ነው
*The theater is her great love. በጣም ፡ የምትወደው ፡ ነገር ፡ ቲያትር ፡ ነው

**be in love** ፍቅር ፡ ያዘው
He is acting so strange, he must be in love. ያለወትሮው ፡ እንዲህ ፡ የሚሆነው ፡ ፍቅር ፡ ይዞት ፡ ይሆናል

**fall in love** ፍቅር ፡ ያዘው
He has fallen in love with her. ከሷ ፡ ጋር ፡ ፍቅር ፡ ይዞታል

**for the love of God** ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ
For the love of God, don't do that! ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ ይህን ፡ አታድርግ

**no love lost**
*There was no love lost between the two brothers. በሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ መካከል ፡ ጥላቻ ፡ ነበረ
[See also 'philter']

**lovely** ደስ ፡ የሚል ፤ አስደሳች
They have a lovely home. ደስ ፡ የሚል ፡ ቤት ፡ አላቸው
Her complexion was a lovely dark brown. መልኳ ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ጠይም ፡ ነበር
The trees and the brook make a lovely picture. ዛፎቹና ፡ ምንጩ ፡ አስደሳች ፡ ትርእይት ፡ ናቸው
*We had a lovely time in your house. ቤትህ ፡ በቆየንበት ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎን ፡ ነበር

**lover**
1. ፍቅረኛ ፤ ፍቅርተኛ. Romeo and Juliet were famous lovers. ሮሚዎና ፡ ጁሊዬት ፡ የታወቁ ፡ ፍቅረኞች ፡ (ፍቅርተኞች) ፡ ነበሩ
2. ወዳጅ. He became her lover shortly after they met. በተገናኙ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ወዳጇ ፡ ሆነ

**be a lover of** ወደደ
He is a great lover of books. መጻሕፍት ፡ በጣም ፡ ይወዳል

**loving**
*She has a loving nature. ሰው ፡ ወዳድ ፡ ነች

**lovingly** በፍቅር
The child embraced its mother lovingly. ልጁ ፡ እናቱን ፡ በፍቅር ፡ አቀፋት

**low** (n.)
*He heard the low of a hungry cow. የተራበችው ፡ ላም ፡ እንቧ ፡ ስትል ፡ ሰማ

**low** (adj.)
1. ዝቅ ፡ ያለ ፤ ቀሰስተኛ. He asked the visitor in a low voice, "What do you wish"? ዝቅ ፡ ባለ ፡ (በቀሰስተኛ) ፡ ድምፅ ፡ ምን ፡ ይፈልጋሉ ፡ ሲል ፡ ጐብኚውን ፡ ጠየቀ
2. ዝቅተኛ. He always gets low marks. ሁልጊዜ ፡ ዝቅተኛ ፡ ማርክ ፡ ያገኛል
People of a low income bracket live in this neighborhood. ዝቅተኛ ፡ ገቢ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ አካባቢ ፡ ይኖራሉ
She had a low position as a kitchen maid. በወጥ ፡ ቤትነት ፡ ዝቅተኛ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ነበራት
I have a low opinion of him. ስለሱ ፡ ዝቅተኛ ፡ ግምት ፡ አለኝ
3. ዝቅተኛ ፡ ዋጋ. Twenty cents a gallon for gasoline is very low. ላንድ ፡ ጋሎን ፡ ቤንዚን ፡ ሃያ ፡ ሳንቲም ፡ በጣም ፡ ዝቅተኛ ፡ ዋጋ ፡ ነው
4. አነስ ፡ ያለ. Three is a low number. ሦስት ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ ቁጥር ፡ ነው
5. ርካሽ. Parcel post rates are low in this country. እዚህ ፡ አገር ፡ እቃ ፡ በፖስታ ፡ የሚላክበት ፡ ዋጋ ፡ ርካሽ ፡ ነው

6. አጭር. Do you want shoes with high or low heels? የምትፈልጊው ፡ ተረከዘ ፡ ረጅም ፡ ጫማ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ተረከዘ ፡ አጭር ?
7. ቦግ ፡ ያላለ. The low flame doesn't give much heat. ቦግ ፡ ያላለ ፡ ነበልባል ፡ ብዙ ፡ ሙቀት ፡ አይሰጥም
*Crossing at this place is possible only at low tide. በዚህ ፡ ቦታ ፡ መሻገር ፡ የሚቻለው ፡ ውኃው ፡ በጐደለ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው

**low** (adv.)
1. ዝቅ ፡ ብሎ. That plane is flying too low. ያ ፡ አውሮፕላን ፡ በጣም ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ይበራል
2. ዝቅ ፡ አድርጎ. Aim low, or you will miss the target. ዝቅ ፡ አድርገህ ፡ አነጣጥር ፡ ያለበለዚያ ፡ ዒላማውን ፡ ትስተዋለህ

**(of) low birth** ከዝቅተኛ ፡ ቤተሰብ ፡ የተወለደ
Men of low birth have occasionally attained high office. ከዝቅተኛ ፡ ቤተሰብ ፡ የተወለዱ ፡ ሰዎች ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ከፍተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ይዘዋል

**low grade (of)** መናኛ
A low grade of meat has a lot of fat. መናኛ ፡ ሥጋ ፡ ብዙ ፡ ሞሚ ፡ አለው

**low prices** ርካሽ
Buy at low prices, and sell at high prices! በርካሽ ፡ ገዝተህ ፡ በውድ ፡ ሽጥ

**be low**
1. ዝቅ ፡ አለ. Prices are low compared to what they were during the war. የእቃ ፡ ዋጋ ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ከነበረው ፡ ጋር ፡ ሲመዛዘን ፡ አሁን ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ነው
2. አዘቀዘቀ. The sun is quite low already. ጀምበሯ ፡ አሁኑኑ ፡ አዘቅዝቃለች
3. ደከመ. The sick man is very low today. በሽተኛው ፡ ሰው ፡ ዛሬ ፡ በጣም ፡ ደክሟል

**be low on** አጠረ(ው)
We are low on water. ውኃ ፡ አጥሮናል

**be in low spirits** አዘነ
I was in low spirits after I failed the test. ፈተናውን ፡ ከወደቅሁ ፡ በኋላ ፡ አዝኜ ፡ ነበር

**be in a low state of health** ጤንነቱ ፡ ታወከ
He is in a low state of health and cannot travel. ጤንነቱ ፡ ስለታወከ ፡ ሊጓዝ ፡ አይችልም

**feel low** ከፋ(ው)
I feel very low today, although I have nothing to complain about. ምንም ፡ እንኳ ፡ የማማረረው ፡ ነገር ፡ ባይኖርም ፡ ዛሬ ፡ ከፍቶኛል

**get low**
1. አነሰ. Our funds are getting low. ገንዘባችን ፡ እያነሰ ፡ ሄዷል
2. ጐደለ. The well is getting low. የጉድጓዱ ፡ ውኃ ፡ እየጐደለ ፡ ነው

**lay low**
1. አደቀቀ. Illness has laid me low. በሽታ ፡ አድቅቆኛል
2. ከመሬት ፡ ደባለቀ. One blow laid him low. አንድ ፡ ምት ፡ ከመሬት ፡ ደባለቀው

**lie low** ድምፁን ፡ አጥፍቶ ፡ ተደበቀ ፤ ተደብቆ ፡ ቆየ
The rebels lay low while the police were searching for them. ፖሊሶቹ ፡ ሲፈልጓቸው ፡ ዐመፀኞቹ ፡ ድምፃቸውን ፡ አጥፍተው ፡ ተደብቀው ፡ ነበር
The thief lay low until the police had gone. ፖሊሱ ፡ እስኪሄድ ፡ ድረስ ፡ ሌባው ፡ ተደብቆ ፡ ቆየ

**new low**
*Prices are expected to hit a new low. የእቃ ፡ ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ ይላል ፡ ተብሎ ፡ ይጠበቃል

**run low** ወደማለቁ ፡ ነው
Supplies are running low. የቤት ፡ ቀለብ ፡ ወደማለቁ ፡ ነው

**speak low** ድምፁን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ተናገረ
He speaks low; I can't understand him. ድምፁን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ስለሚናገር ፡ ልሰማው ፡ አልችልም
[See also 'crouch, high, tide']

**lowbred** አሳዳጊ ፡ የጐደለው
Lowbred children are disrespectful. አሳዳጊ ፡ የጐደላቸው ፡ ልጆች ፡ ባለጌዎች ፡ ናቸው

**low-cost, ~ housing** ባነስተኛ ፡ ገንዘብ ፡ የሚከራዩ ፡ ቤቶች
The city prepared a study on low-cost housing. ከተማዋ ፡ ባነስተኛ ፡ ገንዘብ ፡ ስለሚከራዩ ፡ ቤቶች ፡ ጥናት ፡ አዘጋጀች

**low country** ቆላ
They are going down to the low country to gather salt. ጨው ፡ ለመሰብሰብ ፡ ወደ ፡ ቆላው ፡ መውረዳቸው ፡ ነው

**lower** (vt.)
1. ዝቅ ፡ አደረገ. Please lower the blinds! መጋረጃዎቹን ፡ ዝቅ ፡ አድርጋቸው
His cowardly acts lowered him in our eyes. ፈሪነቱ ፡ ለሱ ፡ የነበረንን ፡ ግምት ፡ ዝቅ ፡ አደረገው
2. አወረደ. We lower the flag when darkness comes. ሲመሽ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማውን ፡ እናወርዳለን
3. ቀነሰ. Lower the rent, and you will have more tenants. ኪራዩን ፡ ብትቀንስ ፡ ብዙ ፡ ተከራይ ፡ ታገኛለህ

He lowered his voice when he saw her come in. ስትመጣ ፡ ባያት ፡ ጊዜ ፡ ድምፁን ፡ ቀነሰ

**lower** (vi.) **አቈለቈለ**
The sun lowered slowly. ፀሐይቱ ፡ በዝግታ ፡ አቈለቈለች

**be lowered**
1. **ወረደ**. The flags are lowered when darkness comes. ሲመሽ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ይወርዳል
2. **ተሰደደ**. Food was lowered to the workers in the mine by a rope. በማዕድን ፡ ውስጥ ፡ ላሉ ፡ ሠራተኞች ፡ ምግብ ፡ በገመድ ፡ ተሰደደላቸው

**lower oneself**
1. **ራሱን ፡ አዋረደ**. He would never lower himself by taking bribes. ጉቦ ፡ በመቀበል ፡ ፈጽሞ ፡ ራሱን ፡ አያዋርድም
2. **ወረደ**. He lowered himself to the ground by means of a rope. በገመድ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ወረደ

## lower (adj.)
1. **የበታች**. The higher court affirmed the lower court's decision. ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ አጸደቀ
2. **ያነሰ**. My competitor sells at lower prices than me. የንግድ ፡ ተወዳዳሪዬ ፡ እኔ ፡ ከምሸጠው ፡ ዋጋ ፡ ባነሰ ፡ ይሸጣል

**the lower part** **ሥር ፡ ሥሩ**
The lower part of the wall is painted blue. ግድግዳው ፡ ሥር ፡ ሥሩ ፡ ሰማያዊ ፡ ተቀብቷል

## lowermost, adj. (= adv.) ከሥር ፡ በኩል
The lowermost books were not damaged by water. ከሥር ፡ በኩል ፡ ያሉትን ፡ መጻሕፍት ፡ ውኃው ፡ አላበላሻቸውም

## lowland ቆላ
It is very hot in the lowlands. ቆላ ፡ በጣም ፡ ይሞቃል

## lowly
1. **ከተራ ፡ የተወለደ**. A lowly person may often be more polite than a well-born person. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከተራ ፡ የተወለደ ፡ ሰው ፡ ከጨዋ ፡ ልጅ ፡ ይልቅ ፡ ትሑት ፡ ይሆን ፡ ይሆናል
2. **ወራዳ**. Pottery making was considered a lowly occupation in olden days. የሸክላ ፡ ሥራ ፡ በጥንት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ወራዳ ፡ ሥራ ፡ ይቈጠር ፡ ነበር
3. **አነስተኛ**. His family lives in a lowly cottage. ቤተሰቦቹ ፡ ባነስተኛ ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ
4. (= adv.) **ዝቅ ፡ አድርጎ**. He had a lowly opinion of himself. ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ይገምት ፡ ነበር

## loyal ታማኝ
You could not have a more loyal friend. የተሻለ ፡ ታማኝ ፡ ጓደኛ ፡ ልታገኝ ፡ አትችልም
He has always been loyal to the government. ለመንግሥቱ ፡ ምንጊዜም ፡ ታማኝ ፡ ነው

## loyalty
1. **ታማኝነት**. You can depend on his loyalty. ታማኝነቱ ፡ አያጠራጥርም
2. **ታማኝ ፡ መሆን**. Nobody questions his loyalty to the government. ለመንግሥቱ ፡ ታማኝ ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ አይጠረጥርም

## lubricate ዘይት ፡ አጠጣ
I lubricate my car every month. መኪናዬን ፡ በየወሩ ፡ ዘይት ፡ አጠጣለሁ

## lucent የሚያንጸባርቅ
The lucent clouds seem made of silver. የሚያንጸባርቁት ፡ ደመናዎች ፡ ከብር ፡ የተሠሩ ፡ ይመስላሉ

## lucid
1. **የጠራ**. Fish can be seen swimming in the lucid lake. በጠራው ፡ ሐይቅ ፡ ውስጥ ፡ ዓሣ ፡ ሲዋኝ ፡ ይታያል
2. **ግልጽ**. His explanation was lucid. አገላለጹ ፡ ግልጽ ፡ ነበር

**lucid moment**
*Even the insane have their lucid moments. እብድ ፡ እንኳን ፡ የሚጨምትበት ፡ ጊዜ ፡ አለ

## luck
1. **ዕድል**. My luck has changed. ዕድሌ ፡ ተለወጠ
It was my good luck to find a $5 bill. አምስት ፡ ብር ፡ ወድቆ ፡ ማግኘቴ ፡ ጥሩ ፡ ዕድል ፡ ነበር
I wish you good luck. መልካም ፡ ዕድል ፡ እመኝልሃለሁ
2. **ገድ**. This man does not have good luck. ይህ ፡ ሰው ፡ ጥሩ ፡ ገድ ፡ የለውም
3. **አጋጣሚ**. It was his hard luck that the flood washed away his land. ጐርፉ ፡ የሱን ፡ መሬት ፡ ማጥለቅለቁ ፡ መጥፎ ፡ አጋጣሚ ፡ ነው
*I wish you all the luck in the world. ማንኛውም ፡ ነገር ፡ እንዲቀናህ ፡ እመኝልሃለሁ

**be in luck** **ታደለ**
We are in luck; our chance in the lottery won. ታድለናል ፤ የሎተሪ ፡ ዕጣችን ፡ ወጣልን

**be out of luck** **ዕድለ ፡ ቢስ ፡ ነው**
When it comes to getting theater tickets, we're usually out of luck. የቲያትር ፡ ቲኬት ፡ በማግኘት ፡ ረገድ ፡ ዕድለ ፡ ቢሶች ፡ ነን
*You are out of luck! We just sold the last

ticket. ልክ ፡ አሁን ፡ የመጨረሻውን ፡ ቲኬት ፡ ሸጥን ። ዕድልህ ፡ ነው

**good luck!** ይቅናህ!

**have bad luck** አልቀናውም
He had bad luck in that card game. በካርታ ፡ ጨዋታው ፡ አልቀናውም
[See also 'ill, pure, stroke']

**luckily** ደግነቱ
Luckily, she did not see me. ደግነቱ ፡ አላየችኝም

**lucky** ዕድለኛ
We were lucky to escape punishment. ከቅጣት ፡ ማምለጣችን ፡ ዕድለኞች ፡ ነን
*They recovered their losses when they made several lucky bets. ገድ ፡ ቀንቷቸው ፡ አንድ ፡ ሁለቴ ፡ ከተወራረዱ ፡ በኋላ ፡ የተበላባቸውን ፡ ገንዘብ ፡ አስመለሱ

**lucky charm**
1. የመልካም ፡ ገድ ፡ መድኀኒት. He always carries a lucky charm in his pocket. እሱ ፡ ሁልጊዜ ፡ የመልካም ፡ ገድ ፡ መድኀኒት ፡ በኪሱ ፡ ይይዛል
2. የመልካም ፡ ዕድል ፡ ክታብ. He wears a lucky charm around his neck. አንገቱ ፡ ላይ ፡ የመልካም ፡ ዕድል ፡ ክታብ ፡ አስሯል

**lucky coincidence** ጥሩ ፡ አጋጣሚ
It was a lucky coincidence that both of us came at the same time. ሁለታችንም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ መምጣታችን ፡ ጥሩ ፡ አጋጣሚ ፡ ነው

**be pretty lucky** ቀና(ው)
+So far you have been pretty lucky. እስካሁን ፡ ቀንቶሃል

**lucrative** ትርፍ ፡ ያለበት
This is a lucrative business. ይህ ፡ ትርፍ ፡ ያለበት ፡ ሥራ ፡ ነው

**ludicrous** የማላገጥ
His ludicrous attempt to speak Amharic made everyone smile. አማርኛን ፡ ለመናገር ፡ ያደረገው ፡ የማላገጥ ፡ ሙከራ ፡ ሁሉንም ፡ ሰው ፡ አሣቀ

**lug** (lugged)
1. በድካም ፡ ጐትቶ ፡ አወጣ. We lugged the rug into the yard to clean it. ምንጣፉን ፡ ለማጽዳት ፡ በድካም ፡ ጐትተን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አወጣነው
We lugged the heavy box upstairs. ከባዱን ፡ ሣጥን ፡ ወደ ፡ ፎቅ ፡ በድካም ፡ ጐትተን ፡ አወጣነው
2. በድካም ፡ ጐትቶ ፡ አስገባ. He lugged the television set into the room. ቴሌቪዥኑን ፡ በድካም ፡ ጐትቶ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አስገባው

**luggage** ጓዝ
Where can I put my luggage? ጓዜን ፡ የት ፡ ላስቀምጥ ?

**lugubrious** በጣም ፡ አሳዛኝ
The lugubrious tale of his misfortunes made her cry. ስለ ፡ መከራው ፡ ያወራው ፡ በጣም ፡ አሳዛኝ ፡ ታሪክ ፡ አስለቀሳት

**lukewarm**
1. ለብ ፡ ያለ. Take a lukewarm bath! ገላህን ፡ ለብ ፡ ባለ ፡ ውኃ ፡ ታጠብ
2. ቀዝቃዛ. The applause the speaker received was lukewarm. ለተናጋሪው ፡ የተደረገው ፡ ጭብጨባ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ነበር

**lull** (vt.)
1. አስታገሠ. I tried to lull her suspicions by pretending I was going to visit a sick friend. የታመመ ፡ ጓደኛዬን ፡ የምጠይቅ ፡ በማስመሰል ፡ ጥርጣሬዋን ፡ ለማስታገሥ ፡ ሞከርኩ
2. ቀነሰ(ላት). The good news lulled her fears. መልካሙ ፡ ዜና ፡ ፍርሃቷን ፡ ቀነሰላት

**lull** (vi.) ጸጥ ፡ አለ
The wind lulled. ነፋሱ ፡ ጸጥ ፡ አለ

**lull by singing softly** እሹሩሩ ፡ አለ
She lulled the baby to sleep by singing softly. እሹሩሩ ፡ እያለች ፡ ሕፃኑን ፡ አስተኛችው

**lullaby** (lullabies) እሹሩሩ
I know Amharic lullabies. ያማርኛ ፡ እሹሩሩ ፡ አውቃለሁ

**sing a lullaby** እሹሩሩ ፡ አለ
She sang a lullaby to put the baby to sleep. ሕፃኑን ፡ ለማስተኛት ፡ እሹሩሩ ፡ አለች

**lumber** ሳንቃ
How much lumber will be needed for the bookshelves? ለመጻሕፍት ፡ መደርደሪያዎቹ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ሳንቃ ፡ ያስፈልጋል ?

**lumberjack** ዕንጨት ፡ ፈላጭ
The lumberjacks cut down all the trees. ዕንጨት ፡ ፈላጮች ፡ ዛፎችን ፡ ሁሉ ፡ ቈረጡ

**lumberman** ዕንጨት ፡ ቈራጭ
The lumberman felled the tree. ዕንጨት ፡ ቈራጩ ፡ ዛፉን ፡ ጣለ

**lumberyard** የዕንጨት ፡ መሰንጠቂያ ፡ ቤት ፤ የዕንጨት ፡ ማከማቻ ፡ ክልል
The lumberyard makes boards from the logs. የዕንጨት ፡ መሰንጠቂያ ፡ ቤት ፡ ከግንድ ፡ ሳንቃ ፡ ይሠራል

The lumberyard is where the boards are stored. ሳንቃው ፡ የተከመረው ፡ በዕንጨት ፡ ማከማቻው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ነው

**luminary** (luminaries) የገነነ ፡ ሊቅ
Einstein was a luminary in the field of physics. አይንስታይን ፡ በፊዚክስ ፡ ዓለም ፡ የገነነ ፡ ሊቅ ፡ ነበረ

**luminary** (adj.) ብርሃን ፡ የሚሰጥ
He observes luminary bodies with a telescope. ብርሃን ፡ የሚሰጡ ፡ አካሎችን ፡ አጉልቶ ፡ በሚያሳይ ፡ መነጽር ፡ ይመለከታል

**luminous**
1. ብርሃን ፡ የበዛበት. The luminous room blinded him momentarily. ብርሃን ፡ የበዛበት ፡ ክፍል ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዓይኑን ፡ አሳወረው
2. ግልጽ. He gave a luminous report of his trip. ስለ ፡ ጉዞው ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ሪፖርት ፡ አቀረበ
3. ደም ፡ የመሰለ. The luminous sunset makes the mountain look on fire. ደም ፡ የመሰለው ፡ የፀሐይ ፡ ጥልቀት ፡ ተራራውን ፡ በእሳት ፡ የተያያዘ ፡ አስመሰለው
4. የሚያበራ ፡ ቀለም ፡ የተቀባ. A luminous plate is put on the telephone poles so you won't bump into them in the dark. በጨለማ ፡ ከስልክ ፡ ዕንጨቶች ፡ ጋር ፡ እንዳትጋጭ ፡ የሚያበራ ፡ ቀለም ፡ የተቀቡ ፡ ሰሌዳዎች ፡ በየዕንጨቱ ፡ ላይ ፡ ይደረጋሉ

**be luminous** አንጸባረቀ
The stars are luminous. ኮከቦቹ ፡ ያንጸባርቃሉ

**lump** (vt.) አጠቃለለ
Can we lump all these items under one heading? እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ ባንድ ፡ አርእስት ፡ሥር ፡ ልናጠቃልላቸው ፡ እንችላለን ?

**lump** (vi.) ጓጐለ
Porridge will lump unless well stirred. ገንፎ ፡ ካልተማሰለ ፡ ይጓጐላል

**lump** (n.)
1. ጓል. What are you going to do with that lump of clay? ይኸን ፡ የሸክላ ፡ ጓል ፡ ምን ፡ ልታደርግበት ፡ ነው ?
2. እንኳር. I take only one lump of sugar in my coffee. ለቡናዬ ፡ አንድ ፡ እንኳር ፡ ስኳር ፡ ብቻ ፡ ይበቃኛል
3. እብጠት. If you feel a lump under your skin, go to see the doctor. ቆዳህ ፡ ሥር ፡ እብጠት ፡ የተሰማህ ፡ እንደሆነ ፡ ሐኪም ፡ ዘንድ ፡ ሂድ

**lump sum** ባንዴ
The insurance gave the widow a lump sum of $10,000. የሕይወት ፡ ዋስትናው ፡ ባሏ ፡ ለሞተባት ፡ ሴት ፡ ዐሥር ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ባንዴ ፡ ከፈላት

**in a lump sum** በጠቅላላው
The insurance was paid in a lump sum. የዋስትናው ፡ ገንዘብ ፡ በጠቅላላው ፡ ተከፈለ

**lunacy** እብደት
It is sheer lunacy to walk in the desert without water. በበረሃ ፡ ውስጥ ፡ ውኃ ፡ ሳይዙ ፡ መጓዝ ፡ ፍጹም ፡ እብደት ፡ ነው

**lunar** የጨረቃ
The lunar landscape has only recently been explored. የጨረቃ ፡ ገጽ ፡ የተመረመረው ፡ በቅርቡ ፡ ነው
[See also 'eclipse']

**lunatic** እብድ
He is acting like a lunatic. አድራጎቱ ፡ እንደ ፡ እብድ ፡ ነው

**lunch** (v.) ምሳ ፡ በላ
Will you lunch with me? ምሳ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ትበላለህ ?

**lunch** (n.) ምሳ
It is almost time for lunch. የምሳ ፡ ሰዓት ፡ ሊደርስ ፡ ምንም ፡ አልቀረው

**lung** ሳምባ ፤ ሳንባ
His left lung was seriously infected. የግራ ፡ ሳምባው ፡ ክፉኛ ፡ ተጐድቶ ፡ ነበር
[See also 'congestion']

**lunge, ~ at** ዘሎ ፡ አፈፍ ፡ አደረገ
The dog lunged at the stranger. ውሻው ፡ ዘሎ ፡ እንግዳውን ፡ ሰው ፡ አፈፍ ፡ አደረገው

**lurch** (v.), **~ forward** እየተንገዳገደ ፡ ሄደ
The wounded man lurched forward. የቆሰለው ፡ ሰው ፡ እየተንገዳገደ ፡ ሄደ

**lurch** (n.), **leave in the ~** ትቶ ፡ ሄደ
His secretary left him in the lurch at the peak of the busy season. ጸሐፊው ፡ ሥራ ፡ በሚበዛበት ፡ ጊዜ ፡ ትታው ፡ ሄደች

**lure** (v.), **~ away**
1. አባብሎ ፡ ወሰደ. He lured away my maid by offering her more money. የበለጠ ፡ ገንዘብ ፡ በመስጠት ፡ ገረዴን ፡ አባብሎ ፡ ወሰደ
2. ሐሳቡን ፡ ከ - - - ላይ ፡ ወሰደ(በት). The sound of the parade lured the students away from their studies. የሰልፉ ፡ ድምፅ ፡ የተማሪዎቹን ፡ ሐሳብ ፡ ከትምህርታቸው ፡ ላይ ፡ ወሰደባቸው

**lure into**
1. አግባባ. He lured me into going with him. ከሱ ፡ ጋር ፡ እንድሄድ ፡ አግባባኝ

2. አታለ ፡ አስገባ. They lured the enemy into an ambush. ጠላትን ፡ አታለው ፡ ካደፈጡበት ፡ ቦታ ፡ አስገቡት

**lure** (n.)

1. ዘዴ. Women have many lures to attract men. ሴቶች ፡ ወንዶችን ፡ ለመማረክ ፡ ብዙ ፡ ዘዴ ፡ አላቸው

2. ማራኪነት. The lure of city life brings many young men to Addis Ababa. የከተማ ፡ ኑሮ ፡ ማራኪነት ፡ ብዙ ፡ ወጣቶችን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ይስባል

3. የሳበ. Gold was the lure that started a rush to California in 1849. በ፲፰፻፵፩ ዓ. ም. ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ወደ ፡ ካሊፎርኒያ ፡ የሳበ ፡ ወርቅ ፡ ነበር

**lurk**

1. አደፈጠ. There is some animal lurking in the bushes out there. እዚህ ፡ ቁጥቋጦ ፡ ውስጥ ፡ ያደፈጠ ፡ አውሬ ፡ አለ

2. እያደባ ፡ ሄደ. I saw a man lurking around the building. አንድ ፡ ሰው ፡ እያደባ ፡ በቤቱ ፡ ኋላ ፡ ሲሄድ ፡ አየሁ

**luscious** ጣፋጭ

He picked a luscious, ripe peach. የበሰለ ፡ ጣፋጭ ፡ ኮክ ፡ ለቀመ

**lush** ለምለም

Lush grass grows along the riverbanks. በወንዙ ፡ ዳርቻ ፡ ለምለም ፡ ሣር ፡ ይበቅላል

**lust** (v.), ~ **after** ተመኘ

He has lusted after my job for years. ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ሥራዬን ፡ ሲመኝ ፡ ነበር

**lust for** ለማግኘት ፡ ተስገበገበ

The tyrant lusted for more power. ጨቋኙ ፡ ገዢ ፡ የበለጠ ፡ ሥልጣን ፡ ለማግኘት ፡ ተስገበገበ

**lust** (n.)

1. ከፍተኛ ፡ ጉጉት. His lust for power was his downfall. ለሥልጣን ፡ የነበረው ፡ ከፍተኛ ፡ ጉጉት ፡ ለውድቀት ፡ አደረሰው

2. ዝሙት. Lust is considered a sin in some religions. ዝሙት ፡ ባንዳንድ ፡ ሃይማኖት ፡ እንደ ፡ ኃጢአት ፡ ይቈጠራል

**have a lust** ጓጓ

He has a lust for power. ለሥልጣን ፡ ይጓጓል

**luster**

1. ማንጸባረቅ. The luster of pearls makes them desirable. የሉሎች ፡ ማንጸባረቅ ፡ እንዲመኙዋቸው ፡ ያደርጋል

2. ድምቀት. Sickness has made her eyes lose their luster. ሕመም ፡ የዓይኖቿን ፡ ድምቀት ፡ ገፈፈ

**add luster to**

1. አጋነነ(ለት) ፤ የበለጠ ፡ አጋነነ(ለት). The runner's victory added new luster to his fame. የሯጩ ፡ ማሸነፍ ፡ ዝናውን ፡ አጋነነለት

The victory added luster to his name. ድሉ ፡ ስሙን ፡ የበለጠ ፡ አጋነነለት

**put a luster** እንዲያንጸባርቅ ፡ አደረገ

Polishing put a high luster on the silver bowl. መወልወል ፡ ጐድጓዳውን ፡ የብር ፡ ሳሕን ፡ በጣም ፡ እንዲያንጸባርቅ ፡ አደረገው

**lustre,** see **luster**

**lusty** የፋፋ

The lusty baby gave a loud yell as soon as he became hungry. የፋፋው ፡ ሕፃን ፡ ወዲያው ፡ እንደራበው ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ አለቀሰ

**lute** [በድሮ ፡ ጊዜ ፡ የሚሠራበት ፡ እስከ ፡ ሃያ ፡ አራት ፡ አውታሮች ፡ ያሉት ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ]

**luxuriant** ጥቅጥቅ ፡ ያለ

They cut their way through the luxuriant undergrowth. ጥቅጥቅ ፡ ያለውን ፡ ቁጥቋጦ ፡ እየጣሱት ፡ ሄዱ

**luxuriate**

1. ተደሰተ. He luxuriated in a hot bath. በሞቀ ፡ ውኃ ፡ ሰውነቱን ፡ በመታጠብ ፡ ተደሰተ

2. በብዛት ፡ በቀለ. The plants luxuriated in the new soil. ዕፀዋቱ ፡ ባዲሱ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በብዛት ፡ በቀሉ

**luxurious** ምቾትና ፡ ውበት ፡ ያለው

This hotel has luxurious furniture. ይህ ፡ ሆቴል ፡ ምቾትና ፡ ውበት ፡ ያላቸው ፡ እቃዎች ፡ አሉት

**luxury**

1. ድሎት. Most Americans live in luxury compared with people in very poor countries. በጣም ፡ ድኻ ፡ ከሆኑት ፡ አገሮች ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ ስናወዳድራቸው ፡ አብዛኛዎች ፡ አሜሪካኖች ፡ በድሎት ፡ ይኖራሉ

2. ምቾት. He likes the luxury of a soft easy chair. ከለስላሳ ፡ ወንበር ፡ የሚገኘውን ፡ ምቾት ፡ ይወዳል

**luxuries** የቅንጦት ፡ እቃዎች

Jewels and furs are luxuries. ዕንቁዎችና ፡ የጸጉር ፡ ልብሶች ፡ የቅንጦት ፡ እቃዎች ፡ ናቸው

**lying,** see **lie**

**lynch** ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ገደለ
The mob lynched an innocent man. ሕዝቡ ፡ ንጹሑን ፡ ሰው ፡ ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ገደለ

**lyre** ክራር
This man knows how to play the lyre. ሰውዬው ፡ ክራር ፡ መጫወት ፡ ይችላል

**lyric** [ግላዊ ፡ ስሜትን ፡ የሚገልጽ ፡ አጭር ፡ ግጥም]

**lyrics** ግጥም
He composed the lyrics for the school song. የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ የመዝሙር ፡ ግጥም ፡ ደረሰ

**lyrical** ስሜት ፡ የሚነካ
She gave a lyrical account of her trip. ስለ ፡ ጉዞዋ ፡ ስሜት ፡ የሚነካ ፡ መግለጫ ፡ ሰጠች

# M

**macabre** አስቃቂ
The battlefield was a macabre sight. የጦርነቱ ፡ ሜዳ ፡ አስቃቂ ፡ ትዕይንት ፡ ነበር

**macerate** (vt.) እንዲለሰልስ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ዘፈዘፈ
She macerated the meat for two days. ሥጋው ፡ እንዲለሰልስ ፡ ለሁለት ፡ ቀን ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ዘፈዘፈችው

**macerate** (vi.) መነመነ
The ascetic's body slowly macerated. የመናኙ ፡ ሰውነት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ መነመነ

**machine** መኪና
The machine is working again. መኪናው ፡ እንደገና ፡ ይሠራ ፡ ጀመር

**machine gun** መትረየስ
He sprayed the advancing troops with a machine gun. የሚገፋውን ፡ ጦር ፡ በመትረየስ ፡ ረፈረፈው

**machinery** ፋብሪካ
New machinery has just been installed. አዲስ ፡ ፋብሪካ ፡ ገና ፡ አሁን ፡ ተተከለ

**mad**
1. እብድ. He drove like mad. እንደ ፡ እብድ ፡ ነዳ
He was bitten by a mad dog. በእብድ ፡ ውሻ ፡ ተነከሰ
2. ከንቱ. The dog made a mad effort to catch up with the train. ውሻው ፡ በባቡሩ ፡ ላይ ፡ ለመድረስ ፡ ከንቱ ፡ ሙከራ ፡ አደረገ
3. ኀይለኛ. A mad gale swept across the channel. ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ በባሕር ፡ ሰላጤ ፡ ላይ ፡ አለፈ

**be mad** ጦፈ
He was so mad that his face was red. በጣም ፡ ጦፎ ፡ ስለነበረ ፡ ፊቱ ፡ ደም ፡ ለበሰ

**be mad about**
1. አበደ(ለት). She is mad about him because he is so pleasant. በጣም ፡ አስደሳች ፡ ስለሆነ ፡ አብዳለታለች
2. ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ወደደ. She is mad about hats. ባርኔጣ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ትወዳለች

**be mad at** ተናደደ
She is mad at me because I insulted her friend. ጓደኛዋን ፡ ስለሰደብኩባት ፡ ተናዳብኛለች

**be mad for**
*The dog was mad for water. ውሻውን ፡ በጣም ፡ ጠምቶት ፡ ነበር

**get mad** ተናደደ
He got mad and called me names. ተናዶ ፡ ሰደበኝ

**go mad** አበደ
He went mad during the bombardment. በቦምብ ፡ ድብደባው ፡ ጊዜ ፡ አበደ

**stark raving mad**
He was stark raving mad. ጨርቁን ፡ ጥሏል

**madam** ወይዘሮ
Madam Mammite came yesterday. ወይዘሮ ፡ ማሚቴ ፡ ትናንትና ፡ መጡ

**madame!** እሜቴ
Madame, your purse is open. እሜቴ ፤ ቦርሳዎ ፡ ክፍት ፡ ነው

**madden**
1. አሳበደ. The drug maddened him. መድኃኒቱ ፡ አሳበደው
2. አናደደ. His ignorance maddens me. የሱ ፡ ድንቁርና ፡ ያናድደኛል

**made**, see **make**

**mademoiselle** እቱ ፤ ወይዘሪት
Mademoiselle, please come here! እቱ ፤ ነይ ፡ እስቲ
Mademoiselle, how are you? ወይዘሪት ፤ እንደምን ፡ አለሽ ?

**made-up** የፈጠራ
This is a made-up tale. ይህ ፡ የፈጠራ ፡ ተረት ፡ ነው

**madhouse** የትርምስ ፡ ቦታ
The stores are madhouses during the Christmas rush. በገና ፡ በዓል ፡ ጊዜ ፡ መደብሮች ፡ የትርምስ ፡ ቦታዎች ፡ ናቸው

**madly** ሳይቋጠብ
They worked madly to fix the bridge. ድልድዩን ፡ ለመጠገን ፡ ሳይቋጠቡ ፡ ሠሩ

*He was madly in love with her. በፍቅሯ ፡ አብዷል

**run madly** እየከነፈ ፡ ሮጠ
He ran madly down the street. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ እየከነፈ ፡ ሮጠ

**madman** ያበደ ፡ ሰው
Madmen have to live in a sequestered place. ያበዱ ፡ ሰዎች ፡ በተከለለ ፡ ቦታ ፡ መኖር ፡ አለባቸው

**madness** እብደት
It would be madness to climb the mountain during a storm. በኀይለኛ ፡ ዝናብ ፡ ጊዜ ፡ ተራራውን ፡ መውጣት ፡ እብደት ፡ ነው

**magazine**
1. መጋዘን. The ammunition is stored in an underground magazine. ጥይቱ ፡ የተከማቸው ፡ ባንድ ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ባለ ፡ መጋዘን ፡ ውስጥ ፡ ነው
2. መጽሔት. This magazine appears twice monthly. ይህ ፡ መጽሔት ፡ በወር ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ይወጣል

**magic** (n.)
1. አስማት. They used magic to bewitch their enemies. ጠላቶቻቸውን ፡ በአስማት ፡ ያፈዙ ፡ ነበር
2. መተት. It suddenly appeared as if by magic. ልክ ፡ በመተት ፡ እንደሆነ ፡ ነገር ፡ በድንገት ፡ ታየ
3. ውበት. The magic of poetry captivates many people. የቅኔ ፡ ውበት ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ይማርካል

**magic** (adj.) በአስማት ፡ የተሠራ
A magic palace stood in place of their hut. በጎጆዋቸው ፡ ፈንታ ፡ በአስማት ፡ የተሠራ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ታየ

**black magic** አስማት
The witch doctor used black magic to injure his enemies. አስማተኛው ፡ ጠላቶቹን ፡ ለመጉዳት ፡ በአስማት ፡ ተጠቀመ

**magical, ~ spell** አስማት
A magical spell was cast on her. በአስማት ፡ ተይዛለች

**have a magical effect on** ነፍስ ፡ ዘራ(በት)
The sight of money had a magical effect on the tired man. ገንዘብ ፡ ማየቱ ፡ የደከመውን ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ ዘራበት

**magician**
1. አስማተኛ. The magician conjured a rabbit out of a hat. አስማተኛው ፡ በመተቱ ፡ ከባርኔጣው ፡ ውስጥ ፡ ጥንቸል ፡ አወጣ
2. ጠንቋይ. The magician foretold my future. ጠንቋዩ ፡ ስለ ፡ ወደፊት ፡ ዕድሌ ፡ ነገረኝ

**magisterial** ሥልጣኔ ፡ ያለው
The captain spoke with a magisterial voice. ሻምበሉ ፡ ሥልጣኔ ፡ ባለው ፡ ድምፅ ፡ ተናገረ

**magistrate** የሕግ ፡ ባለሥልጣን
The magistrate has the authority to perform marriages. የሕጉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ጋብቻን ፡ ለመፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ አለው

**magnanimity** ለጋስነት
His magnanimity prompts him to help everyone who is in trouble. ለጋስነቱ ፡ የተቸገረን ፡ ሁሉ ፡ ለመርዳት ፡ ይገፋፋዋል

**magnanimous**
1. ይቅር ፡ ባይ. He is magnanimous toward his enemies. ጠላቶቹን ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነው
2. ቸር. This magnanimous king is loved by his people. ይህ ፡ ቸር ፡ ንጉሥ ፡ በሕዝቡ ፡ የተወደደ ፡ ነው
*He showed a magnanimous attitude toward the conquered enemy. ድል ፡ የተመታውን ፡ ጠላት ፡ በፍቅር ፡ ዓይን ፡ ተመለከተ

**magnanimous with money** ለጋስ
He was magnanimous with his money and lost all his inheritance. በጣም ፡ ለጋስ ፡ ስለሆነ ፡ የወረሰውን ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ አጠፋ

**magnate** ሥልጣንና ፡ ሀብት ፡ ያለው
The magnates control all our industries. እንዱስትሪዎችን ፡ ሁሉ ፡ የያዙት ፡ ሥልጣንና ፡ ሀብት ፡ ያላቸው ፡ ናቸው

**magnet** ማግኔት
The magnet picks up nails. ማግኔት ፡ ምስማር ፡ ከመሬት ፡ ያነሣል

**magnetize**
1. ወደ ፡ ማግኔትነት ፡ ለወጠ. You can magnetize a needle by rubbing it with a magnet. መርፌን ፡ በማግኔት ፡ ላይ ፡ በመፈግፈግ ፡ ወደ ፡ ማግኔትነት ፡ ልትለውጥ ፡ ትችላለህ
2. ማረከ. Her beautiful voice magnetized the audience. የሚያምረው ፡ ድምጿ ፡ አድማጩን ፡ ማረከው

**magnificence** አስደናቂነት
The magnificence of mountain scenery attracts many visitors. የተራራው ፡ አስደናቂነት ፡ ብዙ ፡ ጐብኝዎችን ፡ ይስባል

**magnificent**
1. ዕጹብ ፡ ድንቅ. The Emperor's palace is magnificent. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ነው

2. በጣም ፡ ድንቅ. This is a magnificent idea. ይህ ፡ በጣም ፡ ድንቅ ፡ ሐሳብ ፡ ነው

**magnify** (magnified)
1. አጕልቶ ፡ አሳየ. This lens magnifies six times. ይህ ፡ መነጽር ፡ ስድስት ፡ እጅ ፡ አጕልቶ ፡ ያሳያል
2. አጋነነ. He magnifies the deeds that he has done. የሠራቸውን ፡ ተግባሮች ፡ ያጋንናል

**magnifying glass** የሚያጕላ ፡ መነጽር
You can see it only with a magnifying glass. ሊታየው ፡ የምትችለው ፡ በሚያጕላ ፡ መነጽር ፡ ብቻ ፡ ነው

**magnitude**
1. መጠን. The magnitude of the building makes it the largest in the world. የሕንጻው ፡ መጠን ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ ሁሉ ፡ ትልቅ ፡ ያደርገዋል
2. ከፍተኛነት. The magnitude of the loss ruined the business completely. የኪሳራው ፡ ከፍተኛነት ፡ ንግዱን ፡ ፈጽሞ ፡ አበላሸው

**of great magnitude** እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ
War brings problems of great magnitude to many nations. ጦርነት ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ችግሮችን ፡ ያስከትላል

**maid** ገረድ
We hired a maid last month. ባለፈው ፡ ወር ፡ ገረድ ፡ ቀጠርን

**maiden** (n.) ልጃገረድ
A maiden should not trust a young man's praises. ልጃገረድ ፡ የጕረምሳን ፡ ሙገሳ ፡ አምና ፡ መቀበል ፡ የለባትም

**maiden** (adj.)
1. ያልተዳረች. My maiden aunt is coming to see us today. ያልተዳረችው ፡ አክስቴ ፡ ዛሬ ፡ ልትጠይቀን ፡ ትመጣለች
2. የመጀመሪያ. This is the ship's maiden voyage. ይህ ፡ የመርከቧ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጕዞ ፡ ነው

**mail** (v.) በፖስታ ፡ ላከ
Please mail the letter for me! ደብዳቤውን ፡ በፖስታ ፡ ላክልኝ

**mail** (n.) ደብዳቤ
In some American cities, the mail is delivered twice a day. ባንዳንድ ፡ የአሜሪካ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ደብዳቤ ፡ በቀን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ይታደላል

**by mail** በፖስታ ፡ ቤት ፡ በኩል
The package will be sent to you by mail. ጥቅሉ ፡ በፖስታ ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ ይላክልሃል
[See also 'return']

**mailbox** የፖስታ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ሣጥን
Where is the nearest mailbox? ቀረብ ፡ ያለው ፡ የፖስታ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ሣጥን ፡ የት ፡ ነው ?

**mail carrier** ደብዳቤ ፡ አመላላሽ
A postman is sometimes called a mail carrier. ፖስተኛ ፡ አንዳንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ አመላላሽ ፡ ይባላል

**mailman** ፖስተኛ
I hope the mailman will bring me a letter. ፖስተኛው ፡ ደብዳቤ ፡ እንደሚያመጣልኝ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ

**maim** አካለ ፡ ጐደሎ ፡ አደረገ
A leg wound maimed the soldier for life. የግሩ ፡ ላይ ፡ ቁስል ፡ ወታደሩን ፡ ዕድሜ ፡ ልኩን ፡ አካለ ፡ ጐደሎ ፡ አደረገው

**main** (n.), **water ~** ቧምቧ
The water main broke and so we had no water. ቧምቧው ፡ ስለተሰበረ ፡ ውኃ ፡ አጣን

**in the main**
1. አብዛኛውን ፡ ጊዜ. The discussion revolved in the main around two questions. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ውይይቱ ፡ ስለ ፡ ሁለቱ ፡ ጥያቄዎች ፡ ነበር
2. በጠቅላላው. I agree with him in the main. በጠቅላላው ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ እስማማለሁ

**main** (adj.) ዋና
You have forgotten the main thing. ዋናውን ፡ ነገር ፡ ዘንግተሃል
Did you inquire at the main office? ዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጠይቀሃል ?
[See also 'point']

**mainland** የብስ
We crossed from the island to the mainland in a boat. ከደሴቱ ፡ ወደ ፡ የብስ ፡ በጀልባ ፡ አቋረጥን

**mainly** አብዛኛውን ፡ ጊዜ
He comes mainly on Tuesdays. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ማክሰኞ ፡ ይመጣል
*He is mainly interested in making money. ዋናው ፡ ፍላጎቱ ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ ነው

**mainstay**
1. መሠረት. The mainstay of Ethiopian economy is agriculture. የኢትዮጵያ ፡ የምጣኔ ፡ ሀብት ፡ መሠረት ፡ እርሻ ፡ ነው
2. ዋና ፡ ደጋፊ ፤ ምሰሶ. He is his parents' mainstay; without him, they would starve to death. የወላጆቹ ፡ ዋና ፡ ደጋፊ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ እሱ ፡ ባይኖር ፡ በረኃብ ፡ ይሞቱ ፡ ነበር

Through her work she was the mainstay of the family. በሥራዋ ፡ የቤቱ ፡ ምሰሶ ፡ እሷ ው ፡ ነበረች

**mainstream** ዋና ፡ ግንባር
The mainstream of American politics favors the center. ዋናው ፡ ያሜሪካን ፡ ፖለቲካ ፡ ግንባር ፡ የሚከተለው ፡ አማካዩን ፡ መንገድ ፡ ነው

**Main Street** ዋና ፡ ጐዳና
Main Street was full of cars. ዋናው ፡ ጐዳና ፡ በመኪና ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር

**maintain**
1. አስተዳደረ. He spends a hundred dollars a week just to maintain his family. ቤተሰቡን ፡ ለማስተዳደር ፡ ብቻ ፡ በሳምንት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ያወጣል
2. ያዘ. You must maintain your equipment in good condition. መሣሪያህን ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ መያዝ ፡ አለብህ
3. ጠበቀ. The church has a vested interest in maintaining its schools. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ ቤቶቿን ፡ ለመጠበቅ ፡ እሷን ፡ የሚነካ ፡ ጥቅም ፡ አላት
The government is trying to maintain friendly relations with all countries. መንግሥቱ ፡ ከሁሉም ፡ ሀገሮች ፡ ጋር ፡ ወዳጅነት ፡ ለመጠበቅ ፡ ይሞክራል
4. በሚገባ ፡ ጠበቀ. It costs a lot of money just to maintain the road. መንገዱን ፡ በሚገባ ፡ መጠበቁ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ይፈጃል
5. አለ. He maintains that he was there. እዚያ ፡ ነበርኩ ፡ ይላል
6. ተከራከረ. He maintains his innocence. ንጹሕ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ይከራከራል
7. አስከበረ. The police must maintain public security. ፖሊስ ፡ የሕዝብን ፡ ጸጥታ ፡ ማስከበር ፡ አለበት
8. አደረገ (ተደረገ). Contact with the main office is maintained by radio. ከዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የሚደረገው ፡ በሬዲዮ ፡ ነው
*Everyone wants to maintain a good reputation. ማንም ፡ ቢሆን ፡ መልካም ፡ ስም ፡ እንዲኖረው ፡ ይፈልጋል
[See also 'hold']

**maintenance**
1. መጠበቂያ. A thousand dollars have been granted for road maintenance. ለመንገድ ፡ መጠበቂያ ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ተሰጥቷል
2. መተዳደሪያ. Taxes pay for the maintenance of schools. ከግብር ፡ የሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ለትምህርት ፡ ቤቶች ፡ መተዳደሪያ ፡ ይውላል
3. ለኑሮ ፡ ያህል. His small farm provides a maintenance, but not much more. ትንሹ ፡ እርሻው ፡ ለኑሮው ፡ ያህል ፡ እንጂ ፡ የበለጠ ፡ አይሰጥም
4. ማክበር. Maintenance of quiet is necessary in a hospital. ሐኪም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ጸጥታን ፡ ማክበር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**maize** በቆሎ
Maize is seeded in May. በቆሎ ፡ የሚዘራው ፡ በግንቦት ፡ ነው

**majestic** ባለግርማ
The palace is a majestic building. ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ባለግርማ ፡ ሕንጻ ፡ ነው

**majestic appearance** ግርማ ፡ ሞገስ
He has a majestic appearance. ግርማ ፡ ሞገስ ፡ አለው

**majesty** (majesties)
1. ግርማ. The majesty of the night sky impressed him. የሌሊቱ ፡ ሰማይ ፡ ግርማ ፡ በጣም ፡ አስደነቀው
2. ሞገስ. The majesty of the mountains awed us. የተራራው ፡ ሞገስ ፡ አስደነቀን
3. ኀይል. Policemen and judges maintain the majesty of the law. ፖሊሶችና ፡ ዳኞች ፡ የሕግን ፡ ኀይል ፡ ያስከብራሉ

**majesties** ነገሥታት
The wedding was attended by the majesties of Europe. የአውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ በጋብቻው ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ ነበር

**His Majesty** ግርማዊነታቸው
His Majesty will see you now. አሁን ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ፊት ፡ ትቀርባለህ

**Your Majesty!** ግርማዊ ፡ ሆይ!
Your Majesty, may I present to you the Swedish ambassador. ግርማዊ ፡ ሆይ! የስዊድንን ፡ አምባሳደር ፡ እንዳቀርብ ፡ ይፈቀድልኝ

**major** (n.)
1. ሻለቃ. The major was promoted. ሻለቃው ፡ የማዕረግ ፡ እድገት ፡ አገኘ
2. ዋና ፡ ትምህርት. What was your major in college? ኮሌጅ ፡ ሆነህ ፡ ዋናው ፡ ትምህርትህ ፡ ምን ፡ ነበር ?

**major** (adj.)
1. ዋና. A major cause of accidents is driving while intoxicated. ያደጋዎች ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ በስካር ፡ መንፈስ ፡ መንዳት ፡ ነው
2. ትልቅ. A major war will probably put an end to civilization. ትልቅ ፡ ጦርነት ፡ ቢነሣ ፡ ሥልጣኔን ፡ ሳያወድም ፡ አይቀርም

3. ከፍ ፡ ያለ. Garbage disposal is a major problem for large cities. ለታላላቅ ፡ ከተማዎች ፡ ቆሻሻ ፡ ማንሣት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ነው

**major part** ይበልጡ
The major part of my income goes for rent. ከገቢዬ ፡ ይበልጡ ፡ የሚውለው ፡ ለቤት ፡ ኪራይ ፡ ነው

**majority** (majorities)
1. አብዛኞች. The majority was against it. አብዛኞቹ ፡ ተቃውመውት ፡ ነበር
2. በዛ ፡ ያለ ፡ ወገን. Ethiopia aligned herself with the majority on that vote. ኢትዮጵያ ፡ ድምፅ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ በዛ ፡ ካለው ፡ ወገን ፡ ተሰለፈች
3. የድምፅ ፡ ብልጫ. He was elected by a bare majority. የተመረጠው ፡ ባነስተኛ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ነው
4. ዓቅመ ፡ አዳም. When will he attain his majority? ለዓቅመ ፡ አዳም ፡ የሚደርሰው ፡ መቼ ፡ ነው ?
5. አካለ ፡ መጠን ፤ ዓቅመ ፡ ሔዋን. When will she attain her majority? እሷ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ (ለዓቅመ ፡ ሔዋን) ፡ የምትደርሰው ፡ መቼ ፡ ነው ?

**(the) majority of** አብዛኛዎቹ
The majority of the students were sick. አብዛኛዎቹ ፡ ተማሪዎች ፡ ታመው ፡ ነበር

**majority vote** የድምፅ ፡ ብልጫ
The farmers have the majority vote in all elections. በማንኛውም ፡ ምርጫ ፡ ገበሬዎቹ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ አላቸው

**(the) great majority of** እጅግ ፡ የሚበዛው
The great majority of people favor having elections. እጅግ ፡ የሚበዛው ፡ ሕዝብ ፡ ምርጫ ፡ እንዲደረግ ፡ ይደግፋል
[See also 'narrow, preponderate']

**make** (made)
1. አደረገ. They made him chairman. ሊቀ ፡ መንበር ፡ አደረጉት
2. አድርጎ ፡ ሾመ. The President made him his special envoy. ፕሬዚዳንቱ ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛ ፡ አድርገው ፡ ሾሙት
3. አዘጋጀ. Since the mother was at work, the daughter made the meal. እናትዮዋ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስለነበረች ፡ ምግቡን ፡ ልጅቷ ፡ አዘጋጀች
4. ሠራ. The man made a bed. ሰውዬው ፡ አልጋ ፡ ሠራ
5. አነጠፈ. The maid makes the bed every evening. ገረዲቱ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ አልጋ ፡ ታነጥፋለች
6. አገኘ. How much do you make a week? በሳምንት ፡ ስንት ፡ ታገኛለህ ?
7. ተጓዘ. We have made eighty miles since noon. ከእኩለ ፡ ቀን ፡ ወዲህ ፡ ሰማንያ ፡ ማይል ፡ ተጉዘናል
8. ወጣ. Our teacher made the front page of the Amharic newspaper. መምህራችን ፡ ባማርኛው ፡ ጋዜጣ ፡ በመጀመሪያ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ወጣ
9. ወጣ(ው). +If you study hard, you will make a good doctor. በርትተህ ፡ ካጠናህ ፡ ጥሩ ፡ ሐኪም ፡ ይወጣሃል
10. አፈራ. His disdainful attitude made him many enemies. ሰውን ፡ የመናቅ ፡ ጠባዩ ፡ ብዙ ፡ ጠላት ፡ አፈራለት
11. ደረሰ(በት) ፤ ደረሰ. Do you think we will make the train? ባቡሩን ፡ የምንደርስበት ፡ ይመስልሃል ?
You can make home by sundown. ፀሐይ ፡ ዘቅዘቅ ፡ ስትል ፡ እቤት ፡ ልትደርስ ፡ ትችላለህ
12. አስ-stem, or አ-stem. You make me laugh. ታሥቀኛለህ
13. ሆነ. Twelve inches make a foot. ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ኢንች ፡ አንድ ፡ ጫማ ፡ ይሆናል
Bread and milk will make a supper for us. ዳቦና ፡ ወተት ፡ እራት ፡ ይሆነናል
Two and two make four. ሁለትና ፡ ሁለት ፡ አራት ፡ ይሆናል
14. ነው. This makes the fifth time you failed an exam. ፈተና ፡ ስትወድቅ ፡ ይህ ፡ አምስተኛ ፡ ጊዜህ ፡ ነው
*He'll make his way in life all right. ኑሮው ፡ ይቃናለታል

**make after** አሳደደ
The men made after the thief, but could not catch him. ሰዎቹ ፡ ሌባውን ፡ አሳደዱት ፤ ግን ፡ ሊይዙት ፡ አልቻሉም

**make as if**
1. (relative verb) + መሰለ. We will make as if to leave, then come back and bring him a present. የምንሄድ ፡ መስለን ፡ ስጦታ ፡ ይዘንለት ፡ እንመለስ
2. ቃጣ. He made as if to strike me. ሊመታኝ ፡ ቃጣብኝ

**make away with**
1. ይዞ ፡ ጠፋ. The embezzler made away with thousands of dollars. አጭበርባሪው ፡ ብዙ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ይዞ ፡ ጠፋ
2. ጨረሰ. He made away with the whole loaf of bread. ዳቦውን ፡ በሙሉ ፡ ጨረሰው
3. አጠፋ. He made away with his enemies. ጠላቶቹን ፡ አጠፋቸው

**make do (with, without)**
1. በላ. You will have to make do with

roasted beans for dinner. ለእራት ፡ ቆሎ ፡ መብላት ፡ ይኖርብሃል
2. ኖረ. During the war, we had to make do without coffee or butter. በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ቡናና ፡ ያለ ፡ ቅቤ ፡ መኖር ፡ ነበረብን

**make (for)**
1. አመራ. They made for the hills. ወደ ፡ ኮረብታዎቹ ፡ አመሩ
2. ገሰገሰ. The soldiers made for the enemy camp by night. ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ሰፈር ፡ በሌሊት ፡ ገሰገሱ
3. ለማግኘት ፡ ረዳ. Respect for the rights of others makes for a happy life. የሌሎችን ፡ መብት ፡ ማክበር ፡ ደስተኛ ፡ ኑሮን ፡ ለማግኘት ፡ ይረዳል

**make (one's) fortune** ሀብታም ፡ ሆነ
He made his fortune in oil. በዘይት ፡ ንግድ ፡ ሀብታም ፡ ሆነ

**make it**
1. ደረሰ(በት). He just made it; the bus was leaving. አውቶቡሱ ፡ ሊነሣ ፡ ለጥቂት ፡ ደረሰበት
2. ሆነ(ለት). You don't have to worry; he will make it. አታስብ ፤ ይሆንለታል

**make of** አለ
What do you make of his strange behavior? ይህንን ፡ እንግዳ ፡ ጠባዩን ፡ ምን ፡ ትለዋለህ?

**make off** ሸሽቶ ፡ ሄደ
The witness to the accident made off before the police arrived. ባደጋው ፡ የነበረ ፡ ምስክር ፡ ፖሊስ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ሸሽቶ ፡ ሄደ

**make off with** ይዞ ፡ ጠፋ ፤ ዘረፈ
The thief made off with all my money. ሌባው ፡ ገንዘቤን ፡ ሁሉ ፡ ይዞ ፡ ጠፋ
Someone broke in and made off with all our money. አንድ ፡ ሰው ፡ ቤታችንን ፡ ሰብሮ ፡ ንብረታችንን ፡ ዘረፈን

**make out** (vt.)
1. ሞላ. Have you made out the application blank? የማመልከቻውን ፡ ፎርም ፡ ሞላህ?
2. ለየ. I can barely make out the ships in the distance. ከሩቅ ፡ መርከቡን ፡ እምብዛም ፡ አልለይም
3. ገባ(ው). +Can you make out what he means? የሚለው ፡ ይገባሃል?
4. ጻፈ. He made out a check for fifteen dollars. የዐሥራ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ቼክ ፡ ጻፈ
He made out his will. ኑዛዜውን ፡ ጻፈ
5. አሰበ(ለት). Please make out our bill! ሒሳባችንን ፡ አስብልን

**make out** (vi.)
1. ሆነ. How did you make out yesterday? ትላንትና ፡ እንዴት ፡ ሆንክ ?
2. ዘለቀ. He will make out all right. በደኅና ፡ ይዘልቃል
3. ያዘ(ው). +How are you making out in your new job? አዲሱ ፡ ሥራህ ፡ እንዴት ፡ ይዞሃል ?

**make (one) out**
*He is a strange person; I can't make him out at all. ጠባዩ ፡ የተለየ ፡ ስለሆነ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አልችልም

**make over**
1. አስተላለፈ. He made over the whole of his property to the national trust. ሀብቱን ፡ በሙሉ ፡ ለብሔራዊ ፡ ድርጅት ፡ አስተላለፈ
2. በሱ ፡ ስም ፡ አዛወረ(ለት). Her father made over the farm to her. አባቷ ፡ መሬቱን ፡ በሷ ፡ ስም ፡ አዛወረላት
3. ለወጠ. She tried to make over her husband after their marriage. ከተጋቡ ፡ በኋላ ፡ ባሏን ፡ ልትለውጠው ፡ ሞከረች

**make up** (vt.)
1. ፈጠረ. He is very ingenious when it comes to making up excuses. ምክንያት ፡ በመፍጠር ፡ አንደኛ ፡ ነው
2. አዘጋጀ. The druggist made up the prescription for me. መድኃኒት ፡ ቀማሚው ፡ መድኃኒቱን ፡ አዘጋጀልኝ
Did he make up the speech himself? ንግግሩን ፡ ያዘጋጀው ፡ ራሱ ፡ ነው ?
3. አሟላ. I still need five dollars to make up the sum you asked for. የጠየቅኸኝን ፡ ገንዘብ ፡ ለማሟላት ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ይቀረኛል
4. ሠራ. Make up a sentence with the word 'no'! « የለም » ፡ በሚለው ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ሥራ
*Water makes up most of the earth's surface. አብዛኛው ፡ የመሬት ፡ ገጽ ፡ በውኃ ፡ የተሸፈነ ፡ ነው

**(not) be made up**
1. ሊተካ ፡ አይችልም. Losses in war are not soon made up. በጦርነት ፡ ምክንያት ፡ የሚደርስ ፡ ጥፋት ፡ በቶሎ ፡ ሊተካ ፡ አይችልም
2. አልተመለሰም. Lost time can never be made up. የባከነ ፡ ጊዜ ፡ አይመለስም

**make up for**
1. አረመ. You cannot make up for past mistakes. ያለፈውን ፡ ስሕተት ፡ ለማረም ፡ አትችልም
2. ሸፈነ(ለት). His kind act made up for his rough manner. የደግነት ፡ ሥራው ፡ ባለጌ ፡ ጠባዩን ፡ ይሸፍንለታል

**make up with** ታረቀ
He made up with his wife after the quarrel. ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ከተጣላ ፡ በኋላ ፡ ታረቀ

[See also 'bed, believe, face, fortune, good, mind, nothing, time, way']

**make** (n.) ዓይነት
What make is your radio? ራዲዮንህ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ?

**make-believe** የማስመሰል
A make-believe battle was performed on the stage. በመድረኩ ፡ ላይ ፡ የማስመሰል ፡ ጦርነት ፡ ተሠራ

**makeshift**
1. ምትክ. When the electric lights went out, we used candles as a makeshift. ኮረንቲው ፡ በጠፋ ፡ ጊዜ ፡ በምትኩ ፡ ሻማ ፡ አበራን
2. በምትኩ ፡ ሌላ ፡ ነገር. We couldn't find any pliers, so we had to use a makeshift. መቆንጠጫ ፡ ስላልነበረን ፡ በምትኩ ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ መጠቀም ፡ ነበረብን
3. ቢጤ. He used a makeshift screwdriver to remove the screw. ቡሎኑን ፡ ለመፍታት ፡ በጠመንጃ ፡ መፍቻ ፡ ቢጤ ፡ ተጠቀመ

**makeup**
1. አቀማመጥ. The makeup of the front page is not clear. የመጀመሪያው ፡ ገጽ ፡ አቀማመጥ ፡ ጉልህ ፡ አይደለም
2. ፊቱን ፡ የተቀባባው. Her makeup was washed away by the rain. ፊቷን ፡ የተቀባባችው ፡ በዝናብ ፡ ሙልጭ ፡ ብሎ ፡ ታጠበ
3. የተፈጥሮ ፡ ጠባይ. Shyness is part of his makeup. ዓይነ ፡ አፋርነት ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባዩ ፡ ነው

**wear makeup** ተኳኳለ
She wears makeup all the time. ሁልጊዜ ፡ ትኳኳላለች

**making** መሥራት
The making of a violin requires great skill. ቫዮሊን ፡ መሥራት ፡ ትልቅ ፡ ጥበብ ፡ ይጠይቃል

**makings** ባሕርይ
I see in him the makings of a hero. የጀግና ፡ ባሕርይ ፡ አይቼበታለሁ

**maladjusted** ካካባቢው ፡ ጋር ፡ የማይስማማ
The maladjusted children show a tendency to be sick more often than the happy children. ካካባቢያቸው ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ልጆች ፡ ከደስተኞች ፡ ልጆች ፡ የበለጠ ፡ የመታመም ፡ ዝንባሌ ፡ ያሳያሉ

**malady** (maladies) በሽታ
Lying and cheating are social maladies. መዋሸትና ፡ ማጭበርበር ፡ የኅብረተ ፡ ሰብ ፡ በሽታዎች ፡ ናቸው

**malaria** ወባ
He got infected with malaria while in the swamp. ረግረጉ ፡ ውስጥ ፡ ሳለ ፡ ወባ ፡ ያዘው

**male** (n.) ወንድ ፤ ተባዕት
Is that dog a male or a female? ያ ፡ ውሻ ፡ ወንድ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ሴት ?
This basketball team consists of three males and two females. ይህ ፡ የቅርጫት ፡ ኳስ ፡ ቡድን ፡ ሦስት ፡ ተባዕቶችና ፡ ሁለት ፡ አንስቶች ፡ አሉበት

**male** (adj.) የወንዶች
Our school has a male choir only. ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ያለው ፡ የመዝሙር ፡ ጓድ ፡ የወንዶች ፡ ብቻ ፡ ነው

**male being** ወንድ
Only male beings are allowed in this monastery. እዚህ ፡ ገዳም ፡ ለመግባት ፡ የሚፈቀድላቸው ፡ ወንዶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**malediction** እርግማን
A father's malediction has great effect. ያባት ፡ እርግማን ፡ አጥንት ፡ ይሰብራል

**malevolent, ~ character** ተንኰለኛነት
His malevolent character shows in his constant efforts to belittle everyone. ተንኰለኛነቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ለማቃለል ፡ በሚያደርገው ፡ ጥረት ፡ ይታወቃል

**malformation** በትክክል ፡ አለመብቀል
A malformation of his teeth prevented him from chewing well. የጥርሱ ፡ በትክክል ፡ አለመብቀል ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ እንዳያኘክ ፡ አደረገው

**malice** ተንኰል
His malice was responsible for my losing my job. ሥራዬን ፡ ለማጣት ፡ ያደረሰኝ ፡ የሱ ፡ ተንኰል ፡ ነው

**malicious** ተንኰል ፡ ያዘለ
His malicious remarks irritated everybody. ተንኰል ፡ ያዘለ ፡ አስተያየቱ ፡ ሁሉንም ፡ ሰው ፡ አበሳጨ

**malign** (v.) አማ
He maligns me when I am not around. በሌለሁበት ፡ ያማኛል

**malign** (adj.) የጭካኔ
The malign rule of the tyrant caused revolts, massacres, and exile. የጨቋኙ ፡ የጭካኔ ፡ አገዛዝ ፡ ሁከት ፡ ፍጅትንና ፡ ከሀገር ፡ መሰደድን ፡ አስከተለ
*Gambling has a malign influence. ቁማር ፡ ጉዳትን ፡ ያስከትላል

**malignant**
1. አደገኛ. The growth on his shoulder turned out to be malignant, so it was removed. በትከሻው ፡ ላይ ፡ ያደረበት ፡ እብጠት ፡ አደገኛ ፡ ሆኖ ፡ ስለተገኘ ፡ በቀዶ ፡ ጥገና ፡ ወጣለት
2. በጣም ፡ አረመኔ. Hitler was a malignant person. ሂትለር ፡ በጣም ፡ አረመኔ ፡ ሰው ፡ ነበር
3. የተንኰል. The malignant plot to oust the director failed. ዲሬክተሩን ፡ ለመሻር ፡ የተደረገው ፡ የተንኰል ፡ አድማ ፡ ከሸፈ

**malleable** በመቀጥቀጥ ፡ ሊሠራ ፡ የሚችል
Gold is a malleable metal. ወርቅ ፡ በመቀጥቀጥ ፡ ሊሠራ ፡ የሚችል ፡ የብረታ ፡ ብረት ፡ ዓይነት ፡ ነው

**mallet** የዕንጨት ፡ መዶሻ

**malnutrition** የምግብ ፡ ጉድለት
Malnutrition can cripple children. የምግብ ፡ ጉድለት ፡ ሕፃናትን ፡ አካለ ፡ ጐደሎ ፡ ሊያደርጋቸው ፡ ይችላል

**malpractice** ከአግባብ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ሕክምና
The Medical Association hopes to prevent malpractice. የሕክምና ፡ ማኅበር ፡ ከአግባብ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ሕክምናን ፡ ለማስወገድ ፡ ያስባል

**malt** ብቅል
We make beer with malt. ከብቅል ፡ ጠላ ፡ ይጠመቃል

**maltreat** አንገላታ
He maltreated his horse. ፈረሱን ፡ አንገላታው

**mamma** እማማ
Mamma came to visit me yesterday. ትላንትና ፡ እማማ ፡ መጥታ ፡ ጠየቀችኝ

**mammal** ወተት ፡ የምትሰጥ ፡ እንስሳ
Mammals suckle their young. ወተት ፡ የሚሰጡ ፡ እንስሳት ፡ ግልገሎቻቸውን ፡ ያጠባሉ

**man** (v.)
*During the war, the women had to man the factories. በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ሴቶች ፡ በወንዶች ፡ ቦታ ፡ ተተክተው ፡ በየፋብሪካዎቹ ፡ መሥራት ፡ ነበረባቸው

**man oneself** ሐሞቱን ፡ ቋጠረ
The captive manned himself to endure torture. ምርኮኛው ፡ ሥቃዩን ፡ ለመቋቋም ፡ ሐሞቱን ፡ ቋጠረ

**man** (men), n.
1. ሰው. God created man in his image. እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ባምሳሉ ፡ ፈጠረ
He is not the man for it. እሱ ፡ የዚህ ፡ ሰው ፡ አይደለም
2. የሰው ፡ ልጅ. The two men engaged in a long dialogue concerning the rights of man. ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ ረጅም ፡ ውይይት ፡ አደረጉ
3. ባል. Man and wife are buried in the same grave. ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ባንድ ፡ መቃብር ፡ ተቀበሩ
4. ወንድ. The army will make a man of you. ውትድርና ፡ ወንድ ፡ ያደርግሃል
5. ወታደር. One officer and four men volunteered to capture the rebel. አንድ ፡ መኰንንና ፡ አራት ፡ ወታደሮች ፡ ሽፍታውን ፡ ለመያዝ ፡ ፈቃደኞች ፡ ሆኑ
*They were killed to the last man. አንድም ፡ ሰው ፡ ሳይቀር ፡ አለቁ

**any man** ማንም
Any man can do it. ማንም ፡ ሊሠራው ፡ ይችላል

**as one man** ባንድነት
They arose as one man to protest the verdict. ፍርዱን ፡ ለመቃወም ፡ ባንድነት ፡ ተነሡ

**to a man**
*To a man, the members of the team did their best. እያንዳንዱ ፡ የቡድኑ ፡ አባል ፡ የሚቻለውን ፡ ያህል ፡ ሠርቷል
[See also 'aged, estate, leading, mark, mean, note, old, room, white, young']

**manage** (vt.)
1. አካሄደ. He managed the store for six years. መደብሩን ፡ ለስድስት ፡ ዓመታት ፡ አካሄደ
The house is so big that I wouldn't be able to manage without help. ቤቱ ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ስለሆነ ፡ ያለረዳት ፡ ላካሂደው ፡ አልችልም
2. አስተዳደረ. Who manages the estate? ርስቱን ፡ ማን ፡ ያስተዳድራል ?
3. ተቈጣጠረ. I cannot manage the children. ልጆቹን ፡ ልቈጣጠራቸው ፡ አልችልም
4. ፈጸመ. He managed this difficult affair with admirable address. ይህን ፡ አስቸጋሪ ፡ ጉዳይ ፡ በሚያስደንቅ ፡ ችሎታ ፡ ፈጸመው
5. ቻለ. How did you manage to get the tickets? ቲኬቶቹን ፡ እንዴት ፡ ለማግኘት ፡ ቻልህ ?
He managed to see the governor. አገረ ፡ ገዢውን ፡ ለማነጋገር ፡ ቻለ
6. ተሳካ(ለት). He barely managed it. ለጥቂት ፡ ተሳካለት

**manage** (vi.)
1. ተዳደረ. We have to manage very carefully on our small salary. ባነስተኛ ፡ ደሞዛችን ፡ በጥንቃቄ ፡ መተዳደር ፡ አለብን

2. ሊኖር ፡ ቻለ. How can you manage on that salary? በዚያ ፡ ደሞዝ ፡ እንዴት ፡ ልትኖር ፡ ት ችላለህ ?

3. ኖረ. How will she manage with her husband gone? ባሏ ፡ ሄዶ ፡ እንዴት ፡ ትኖራለች ?

**manageable**

*We must begin while the task is still manageable. ሥራው ፡ ሊሠራ ፡ በሚችልበት ፡ ጊዜ ፡ አ ሁን ፡ መጀመር ፡ አለብን

**management**

1. አመራር. The management of the store is not very good. የመደብሩ ፡ አመራር ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ አይደለም

2. አስተዳዳሪዎች. Complain to the management! ላስተዳዳሪዎቹ ፡ አመልክት

**manager**

1. ሥራ ፡ አስኪያጅ. The manager left town. ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ሄደ

2. አስተዳዳሪ. His wife is a good manager. ሚስቱ ፡ ጥሩ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ናት

**mandate**

1. የተጣለበት ፡ አደራ. Our mandate allows us to do all we can to develop the country. የተጣ ለብን ፡ አደራ ፡ ሀገሪቷን ፡ ለማበልጸግ ፡ የተቻለ ንን ፡ ሁሉ ፡ እንድናደርግ ፡ ይፈቅድልናል

2. በሞግዚትንት ፡ የማስተዳደር ፡ ኀላፊነት. The mandate over Syria was given to France. ሶሪያን ፡ በሞግዚትነት ፡ የማስተዳደር ፡ ኀላፊነት ፡ የተሰጠው ፡ ለፈረንሳይ ፡ ነበር

**mandated** በሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ሥር ፡ የም ትገኝ ፤ በሞግዚትነት ፡ የምትተዳደር

Southwest Africa was a mandated territory. ደቡብ ፡ ምዕራብ ፡ አፍሪካ ፡ በሞግዚት ፡ አስተ ዳደር ፡ ሥር ፡ የምትገኝ ፡ ግዛት ፡ ነበረች

**mandatory** ግዴታ

Taxes have been mandatory. ግብር ፡ መክፈል ፡ ግዴታ ፡ ነው

**mandatory power** የሞግዚትነት ፡ አስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው

A mandatory power is in charge of the mandated territory. የሞግዚትነት ፡ አስተዳደር ፡ ሥል ጣን ፡ የተሰጠው ፡ በሞግዚትነት ፡ ለሚተዳደረው ፡ ግዛት ፡ ኀላፊ ፡ ነው

**mane** ጋማ

Comb out the horse's mane! የፈረሱን ፡ ጋማ ፡ አበጥረው

**maneuver** (v.)

1. በዘዴ ፡ ሊያስገባ ፡ ቻለ. He maneuvered his car into a small space. መኪናውን ፡ በዘዴ ፡ ከ ንዲት ፡ ጠባብ ፡ ቦታ ፡ ሊያስገባ ፡ ቻለ

2. አንቀሳቀሰ. The admiral maneuvered his fleet into an attack position. አድሚራሉ ፡ ለማጥቃ ት ፡ እንደሚመች ፡ አድርጎ ፡ መርከቦቹን ፡ አንቀሳ ቀሰ

3. በዘዴ ፡ መራ. The chairman maneuvered the discussion to his own advantage. ሊቀመንበሩ ፡ ውይይቱን ፡ ለሱ ፡ እንደሚመቸው ፡ አድርጎ ፡ በዘዴ ፡ መራው

4. ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ. Their maneuvering at the conference was a play for time. በስብሰባ ው ፡ ጊዜ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ማለታቸው ፡ ጊዜ ፡ ለማግኘት ፡ ነው

**maneuver oneself** እንደምንም ፡ ተሽሎክልኮ ፡ ደረሰ

He is trying to maneuver himself into a higher position. እንደምንም ፡ ተሽሎክልኮ ፡ ወደ ፡ ከፍተ ኛ ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ ይሞክራል

**maneuver** (n.)

1. ልምምድ. The troops are on maneuvers now. አሁን ፡ ወታደሮቹ ፡ በልምምድ ፡ ላይ ፡ ናቸው

2. የብልጠት ፡ ዘዴ. When we refused to use his idea, he tried to force it on us by a series of maneuvers. የሱን ፡ ሐሳብ ፡ ሥራ ፡ ለማዋል ፡ እምቢ ፡ ብንል ፡ እንድንቀበለው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የ ብልጠት ፡ ዘዴዎች ፡ ሊገፋፋን ፡ ሞከረ

**manger** ግርግም

They put oats in the manger. ግርግም ፡ ውስጥ ፡ አጃ ፡ አኖሩ

**mangle** ቀረጠፈ

A trap has mangled the rabbit's paw. ወጥመድ ፡ የጥንቸሏን ፡ መዳፍ ፡ ቀረጠፈው

**mango** ማንጎ

**manhandle** አንገላታ

The police manhandled the suspected murderer. በነፍስ ፡ ግዳይ ፡ የተጠረጠረውን ፡ ሰው ፡ ፖ ሊሶች ፡ አንገላቱት

**manhole** [ቆሻሻ ፡ መውረጃ ፡ ቦይ ፡ ውስጥ ፡ ለመ ግቢያ ፡ የሚያገለግል ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ባ ለ ፡ ክዳን ፡ ጉድጓድ]

**manhood**

1. አካለ ፡ መጠን. He has reached manhood. ላካለ ፡ መጠን ፡ ደርሷል

2. ወንድነት. Manhood is not acquired by

avoiding difficulty and hardship. ችግርና ፡ መከራን ፡ በመሸሽ ፡ ወንድነት ፡ አይገኝም
3. ወንዶች ፡ ሁሉ. The manhood of the nation answered the call to defend the country. አገሪቱን ፡ ከወራሪ ፡ ለመከላከል ፡ የተደረገውን ፡ ዐዋጅ ፡ ወንዶች ፡ ሁሉ ፡ ተቀበሉት

**mania, have a ~** ሻቀለ
She has a mania for new clothes. ላዲስ ፡ ልብስ ፡ ትሻቅላለች

**manifest** (v.)
1. ገለጸ. He manifested his joy by whistling. ደስታውን ፡ በፉጨት ፡ ገለጸ
2. ታየ(በት). +She does not manifest much of a desire to marry him. እሱን ፡ ለማግባት ፡ ብዙ ፡ ፍላጎት ፡ አይታይባትም

**manifest itself** ታወቀ
When did your illness manifest itself? በሽታህ ፡ የታወቀህ ፡ መቼ ፡ ነው ?

**manifest** (adj.) ግልጽ
This is something that should be manifest to all of you. ይህ ፡ ለሁላችሁም ፡ ግልጽ ፡ መሆን ፡ ያለበት ፡ ነገር ፡ ነው

**manifestation** መግለጫ
His whistling is a manifestation of joy. የሱ ፡ ፉጨት ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ ነው

**manifesto** መግለጫ
The students' manifesto demanded far-reaching reforms. የተማሪዎቹ ፡ መግለጫ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ መሻሻል ፡ እንዲደረግ ፡ ጠየቀ

**manifold**
1. ብዙ ፡ ዘርፍ ፡ ያለው. This manifold subject requires years of study to master. ብዙ ፡ ዘርፍ ፡ ያለውን ፡ ትምህርት ፡ አጠናቆ ፡ ለማወቅ ፡ የብዙ ፡ ዓመታት ፡ ጥናት ፡ ያስፈልጋል
2. ልዩ ፡ ልዩ. His manifold duties included editing a newspaper. ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ተግባሮቹ ፡ አንዱ ፡ ጋዜጣ ፡ ማዘጋጀት ፡ ነበር

**manipulate**
1. በእጅ ፡ አንቀሳቀሰ. He manipulated the controls of the car, but could not drive it. የመኪናውን ፡ መቈጣጠሪያዎች ፡ በእጅ ፡ ማንቀሳቀስ ፡ ችሏል ፡ ግን ፡ መንዳት ፡ አይችልም
2. አንቀሳቀሰ. Even though he is young, he manipulates the tractor well. ገና ፡ ወጣት ፡ ቢሆንም ፡ የእርሻ ፡ መኪናውን ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ ያንቀሳቅሰዋል
3. እንደፈለገው ፡ አግባባ. A clever politician manipulates people to get his own way. ብልህ ፡ የፖለቲካ ፡ ሰው ፡ የሚፈልገውን ፡ ለማግኘት ፡ ሰዎችን ፡ እንደፈለገው ፡ ያግባባቸዋል
4. አማታ. The bookkeeper manipulated the company's accounts to conceal his theft. ሒሳብ ፡ ያዡው ፡ ስርቆቱን ፡ ለመደበቅ ፡ የኩባንያውን ፡ ሒሳብ ፡ አማታ
5. እንደልቡ ፡ አደረገ. He manipulated the pliant twig. ተለማጩን ፡ ቅርንጫፍ ፡ እንደልቡ ፡ ያደርገው ፡ ነበር

**mankind**
1. ሰው. Mankind was created by God in his image. ሰውን ፡ እግዚአብሔር ፡ በአምሳሉ ፡ ፈጠረው
2. የሰው ፡ ልጅ. Mankind has committed crimes against nature. የሰው ፡ ልጅ ፡ ተፈጥሮን ፡ በድሏል
3. ሰብአዊ ፡ ፍጡር. The desire for praise is a strong drive in mankind. ምስጋና ፡ መፈለግ ፡ በሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ የሚገፋፋ ፡ ብርቱ ፡ ኀይል ፡ ነው

**manlike** ሰው ፡ የሚመስል
A manlike ape once lived in what is now Kenya. ሰው ፡ የሚመስል ፡ ዝንጀሮ ፡ አሁን ፡ ኬንያ ፡ በሚባለው ፡ አገር ፡ ይኖር ፡ ነበር

**manly**
1. ወንዳ ፡ ወንድ. He is a very manly boy for one so young. እንደሱ ፡ ያለ ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡ በጣም ፡ ወንዳ ፡ ወንድ ፡ ነው
2. የወንድ. Boxing is a manly sport. ቦክስ ፡ የወንድ ፡ ጨዋታ ፡ ነው
3. ጐበዝ. If you coddle your child, he won't grow up to be manly. ልጅህን ፡ ካሞላቀቅኸው ፡ ጐበዝ ፡ ሆኖ ፡ አያድግም

**man-made** ሰው ፡ ሠራሽ
Man-made objects were found in a cave. በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ እቃዎች ፡ ተገኙ

**manner**
1. ጠባይ. I do not like his manner. ጠባዩን ፡ አልወደውም
2. ዓይነት. What manner of man is he? ምን ፡ ዓይነት ፡ ሰው ፡ ነው ?
3. ሁኔታ. He sang in an amusing manner. በሚያሥቅ ፡ ሁኔታ ፡ ዘመረ
4. ዘዴ. What is the best manner of peeling onions? ሽንኩርትን ፡ ለመላጥ ፡ ጥሩው ፡ ዘዴ ፡ ምንድነው ?
5. (noun of manner). His manner of dressing shows much care. አለባበሱ ፡ ብዙ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረጉን ፡ ያሳያል

*These houses are built in the Mexican manner. እነዚህ ፡ ቤቶች ፡ የተሠሩት ፡ እንደ ፡ ሜክሲኮ ፡ ቤቶች ፡ ነው

**manners**
1. ልማድ. The manners of the ancient Romans are described in this book. የጥንት ፡ ሮማውያን ፡ ልማዶች ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጸዋል
2. ባህል. The literature of a nation reflects its manners. ያንድ ፡ አገር ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ያገሩን ፡ ባህል ፡ ይገልጻል
3. ጠባይ. He has good manners. ጥሩ ፡ ጠባይ ፡ አለው
4. ሥርዓት. After the guests left, the boy got a sermon on table manners from his father. እንግዶቹ ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ አባትዮው ፡ ለልጁ ፡ ስለ ፡ ገበታ ፡ ሥርዓት ፡ ምክር ፡ ሰጠው
*She has no manners. ስድ ፡ ናት

**bad manners** ብልግና ፤ መጥፎ ፡ ምግባር
It is bad manners to stare at people. ሰውን ፡ አፍጥጦ ፡ ማየት ፡ ብልግና ፡ ነው
You shouldn't correct your children for their bad manners in public. ስለ ፡ መጥፎ ፡ ምግባራቸው ፡ ልጆችህን ፡ ባደባባይ ፡ መቅጣት ፡ አይገባህም
[See also 'decisive, ease, ill, proper, smooth']

**mannered**, see **ill-mannered, well-mannered**

**mannerism** ጠባይ
Each of us has his own mannerisms. እያንዳንዳችን ፡ የየግል ፡ ጠባይ ፡ አለን

**mannerly** ጨዋ
A mannerly child is a source of pride to his parents. ጨዋ ፡ ልጅ ፡ ለወላጆቹ ፡ መኩሪያ ፡ ነው

**mannerly way** ጨዋነት
He spoke in a mannerly way. በጨዋነት ፡ ተናገረ

**mannish** የወንድ
She has a mannish voice. ድምጿ ፡ የወንድ ፡ ድምፅ ፡ ነው

**man-of-war** (pl. men-of-war) የጦር ፡ መርከብ
Portuguese men-of-war appeared in the Red Sea in 1520. በ፲፭፻፲፪ ዓ. ም. የፖርቱጋል ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ ቀይ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ታዩ

**manpower** ሰው
They need a lot of manpower to build new roads. አዲስ ፡ መንገድ ፡ ለመሥራት ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ያስፈልጋቸዋል
The army is short of manpower. ሰራዊቱ ፡ ሰው ፡ ያንሰዋል

**mansion** ትልቅ ፡ ቤት
He lives in a handsome mansion. በሚያምር ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል

**manslaughter**
1. ሳያውቅ ፡ ሰው ፡ መግደል. He was convicted of manslaughter. ሳያውቅ ፡ ሰው ፡ በመግደል ፡ ተፈርዶበታል
2. ነፍሰ ፡ ገዳይነት. The driver was proven innocent of manslaughter. ነጂው ፡ ከነፍሰ ፡ ገዳይነት ፡ ንጹሕ ፡ መሆኑ ፡ ተረጋገጠ

**mantel** [ከእሳት ፡ ማንደጃ ፡ በላይ ፡ የሚገኝ ፡ መደርደሪያ]

**mantle** ካባ
The nobles wore silk mantles. መኳንንቱ ፡ የሐር ፡ ካባ ፡ ለብሰው ፡ ነበር

**manual** (n.) መምሪያ
I am writing a teacher's manual. የመምህራን ፡ መምሪያ ፡ እጽፋለሁ

**manual** (adj.)
1. የጉልበት ፤ የሞያተኛነት. He looks down on manual labor. የጉልበት ፡ (የሞያተኛነት) ፡ ሥራን ፡ ይንቃል
2. የእጅ. Using a loom requires manual skill. የሸማኔ ፡ እቃ ፡ የእጅ ፡ ሙያን ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው

**manufacture** (v.)
1. ሠራ. They manufacture rifles and ammunition in this factory. በዚህ ፡ ፋብሪካ ፡ ውስጥ ፡ ጥይትና ፡ ጠመንጃ ፡ ይሠራሉ
2. ፈጠረ. The lazy boy manufactured excuses. ሰነፉ ፡ ልጅ ፡ ምክንያቶች ፡ ፈጠረ

**manufacture** (n.)
*The code on the label shows the date of manufacture. በንግድ ፡ እቃው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ልዩ ፡ ማስታወሻ ፡ እቃው ፡ የተሠራበትን ፡ ጊዜ ፡ ያመለክታል

**manufacturer** ባለፋብሪካ
Don't deal with middlemen; write directly to the manufacturer! ካትራፊ ፡ ጋር ፡ አትዋዋል ፤ ቀጥታ ፡ ለባለፋብሪካው ፡ ጻፍ

**manumission** አርነት ፡ ማውጣት
Manumission of slaves is an act of piety. ባሮችን ፡ አርነት ፡ ማውጣት ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባር ፡ ነው

**manure** ፍግ
Manure is used by farmers to fertilize their fields. ገበሬዎች ፡ መሬታቸውን ፡ ለማዳበር ፡ በፍግ ፡ ይጠቀማሉ

**manuscript**
1. የብራና ፡ መጽሐፍ. I want to buy an Ethiopian manuscript. የኢትዮጵያ ፡ የብራና ፡ መጽሐፍ ፡ ለመግዛት ፡ እፈልጋለሁ
2. የእጅ ፡ ጽሑፍ. This is the earliest extant manuscript. ይህ ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ ከጥንቶቹ ፡ ሁሉ ፡ የሚቀድም ፡ ነው

**many** ብዙ
I have many books. ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ አለኝ

**many a** ብዙ
Many a man owes his success to his wife. ብዙ ፡ ሰው ፡ በሚስቱ ፡ ምክንያት ፡ ሥራው ፡ ይቃናለታል
I have passed here many a time. በዚህ ፡ በኩል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልፌያለሁ

**many of** ብዙዎች + suffix pronouns
Many of us left early. ብዙዎቻችን ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ ሄድን

**a great many** ብዙ
A great many books have been written on that subject. በዚህ ፡ አርእስት ፡ ብዙ ፡ መጽሐፎች ፡ ተጽፈዋል

**in as many** የዚያኑ ፡ ያህል
You made ten spelling errors in as many lines. ዐሥር ፡ መሥመር ፡ ጽፈህ ፡ የዚያኑ ፡ ያህል ፡ የፊደል ፡ ስሕተት ፡ አድርገሃል

**one too many**
*I feel that I am one too many in this company. በዚህ ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ መገኘቴ ፡ የተፈለገ ፡ አይመስለኝም

**so many**
1. በጣም ፡ ብዙ. So many people have failed to pay attention to the warning! በጣም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ማስጠንቀቂያውን ፡ ከምንም ፡ ሳይቈጥሩት ፡ ቀሩ
2. ይህን ፡ ያህል. Do you need so many? ይህን ፡ ያህል ፡ ያስፈልግሃል ?

**too many**
1. አብልጦ. You gave me three too many. ሦስት ፡ አብልጠህ ፡ ሰጠኸኝ
2. ብዙ. A student who has too many activities does not have time to study. ብዙ ፡ ተግባሮች ፡ የሚያከናውን ፡ ተማሪ ፡ ለጥናት ፡ ጊዜ ፡ የለውም

**map** (mapped), v. ካርታ ፡ አነሣ
This scholar mapped Western America. ይህ ፡ ምሁር ፡ ምዕራብ ፡ አሜሪካን ፡ ካርታ ፡ አነሣ

**map out**
1. በንድፍ ፡ አወጣ. The general mapped out the campaign. ጄኔራሉ ፡ የዘመቻውን ፡ ስልት ፡ በንድፍ ፡ አወጣ
2. ወሰነ. Have you mapped out your route yet? የጉዞህን ፡ አቅጣጫ ፡ ወስነሃል ?
3. ደረጃ ፡ በደረጃ ፡ አወጣ. The students mapped out the week's tasks. ተማሪዎቹ ፡ የሳምንቱን ፡ ሥራ ፡ ደረጃ ፡ በደረጃ ፡ አወጡት

**map** (n.) ካርታ
He is making a map of Sidamo province. የሲዳሞን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ካርታ ፡ እየሠራ ፡ ነው

**put on the map** የታወቀ ፡ አደረገ
The discovery of gold put our town on the map. በከተማችን ፡ ውስጥ ፡ ወርቅ ፡ መገኘቱ ፡ የታወቀች ፡ አደረጋት

**mar** (marred) አወከ
Nothing marred the happiness of our outing. በሽርሽራችን ፡ ጊዜ ፡ የነበረንን ፡ ደስታ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አላወከውም

**be marred**
1. ተበላሸ. The painting was marred by cracks. ሥዕሉ ፡ በመቀዳደዱ ፡ ተበላሽቶ ፡ ነበር
2. ተሟጨረ ፤ ተቧጨረ. This table has been marred by knife marks. ይህ ፡ ጠረጴዛ ፡ በስንጢ ፡ ተሟጭሯል ፡ (ተቧጭሯል)

**maraud** ወረረ
The gang marauded over the countryside. ወንበዴዎቹ ፡ ገጠሩን ፡ ወረሩት
*A fox marauded the chicken coop. ቀበሮ ፡ ከዶሮው ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ዶሮዎች ፡ በላ

**marauder** ወንበዴ
The marauders pillaged the house and then set it on fire. ወንበዴዎቹ ፡ ቤቱን ፡ ከዘረፉ ፡ በኋላ ፡ እሳት ፡ ለኰሱበት

**marble** እብነ ፡ በረድ
The statue is made of marble. ሐውልቱ ፡ የተሠራው ፡ ከእብነ ፡ በረድ ፡ ነው

**marbles** ብይ
Boys like to play marbles. ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ብይ ፡ መጫወት ፡ ይወዳሉ

**march** (v.)
1. ተሰለፈ ፡ ተጓዘ. He drums when the soldiers march. ወታደሮቹ ፡ ተሰልፈው ፡ ሲጓዙ ፡ ታምቡር ፡ ይመታል
2. በሰልፍ ፡ ሄደ. Did you see the soldiers marching? ወታደሮቹ ፡ በሰልፍ ፡ ሲሄዱ ፡ አየህ ?

**march (someone) off** ወሰደ
The policeman marched the thief off to jail. ፖሊሱ ፡ ሌባውን ፡ ወደ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ወሰደው

**march on**
Time marches on. ጊዜው ፡ ይንጓጓል

**march through** አቋርጦ ፡ ሄደ
The soldiers marched through the desert to the front. ወታደሮቹ ፡ በረሃውን ፡ አቋርጠው ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ሄዱ

**march up and down** ላይና ፡ ታች ፡ አለ
He marched impatiently up and down outside the doctor's office. ከሐኪሙ ፡ ቢሮ ፡ ውጭ ፡ ያለ ፡ ትዕግሥት ፡ ላይና ፡ ታች ፡ ይል ፡ ነበር
[See also 'doom, head, step']

**march** (n.)
1. ጉዞ. We still have a long march ahead of us. ገና ፡ ረጅም ፡ ጉዞ ፡ ይቀረናል
2. ማርሽ. The band began with a march. የሙዚቀኞቹ ፡ ጓድ ፡ በማርሽ ፡ ጀመረ

**march of events** ከጊዜ ፡ ወደጊዜ ፡ የሚደረጉ ፡ ነገሮች
The march of events shows us that life is getting more complicated. ከጊዜ ፡ ወደጊዜ ፡ የሚደረጉት ፡ ነገሮች ፡ ኑሮ ፡ እየተወሳሰበ ፡ መሄዱን ፡ ያሳዩናል

**forward march** ግስጋሴ
Their forward march was blocked by a river. የነርሱ ፡ ግስጋሴ ፡ ባንድ ፡ ወንዝ ፡ ታግዶ ፡ ነበር

**March** መጋቢት
It rains in March. በመጋቢት ፡ ይዘንባል

**mare** ባዝራ
He kept two mares in the stall. ጋጣው ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ባዝራ ፡ አሰረ

**margin**
1. ኅዳግ. Leave a wider margin on the left side! በግራ ፡ በኩል ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ኅዳግ ፡ አስቀር
2. ዳርቻ. The margin of the lake is overgrown with reeds. የባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ በቄጠማ ፡ ተውጧል

**by a narrow margin** ለጥቂት
He escaped defeat by a narrow margin. ለጥቂት ፡ ከመሸነፍ ፡ ዳነ

**marginal**
1. በኅዳጉ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈ. A marginal note explains that the book was printed in 1910. በኅዳጉ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈው ፡ ማስታወሻ ፡ መጽሐፉ ፡ በ፲፱፻፪ ዓ. ም. መታተሙን ፡ ይገልጻል
2. (= adv.) እንደምንም ፡ ብሎ. The crops in that region are adequate for marginal subsistence. በዚያ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ያለው ፡ እህል ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ ለመኖሪያ ፡ ያህል ፡ ይበቃል

**be marginal** አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ አይደለም
This is marginal; we need not consider it in our plans. ይህ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ አይደለም ፤ በእቅዳችን ፡ ውስጥ ፡ ልናስገባው ፡ አያስፈልግም

**marinate** በቅመም ፡ ዘፈዘፈ
Marinate the meat to make it more tender! ሥጋውን ፡ ይበልጥ ፡ ለማለስለስ ፡ በቅመም ፡ ዘፍዝፈው

**marine** (n.) መርከቦች
Ethiopia has a small merchant marine. ኢትዮጵያ ፡ ጥቂት ፡ የንግድ ፡ መርከቦች ፡ አሏት

**marine** (adj.)
1. የባሕር. Whales are marine animals. ዓሣ ፡ ነባሪዎች ፡ የባሕር ፡ እንስሶች ፡ ናቸው
Marine insurance protects cargo ships. የባሕር ፡ ዋስትና ፡ ለጭነት ፡ መርከቦች ፡ ዋስትና ፡ ይሰጣል
2. ከባሕር ፡ የሚገኝ. Marine products are sold in Massawa. ምፅዋ ፡ ከባሕር ፡ የሚገኙ ፡ ሸቀጦች ፡ ይሸጣሉ

**marital**
1. የባል. Providing for one's wife is a marital obligation. ሚስት ፡ የሚያስፈልጋትን ፡ ሁሉ ፡ እንድታገኝ ፡ ማድረግ ፡ የባል ፡ ኀላፊነት ፡ ነው
2. የጋብቻ. A man and a woman take marital vows when they marry. ወንድና ፡ ሴት ፡ ሲጋቡ ፡ የጋብቻ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይፈጽማሉ

**maritime**
1. የባሕር ፡ ላይ. Maritime commerce was harmed when the Suez canal was closed. የሱዌዝ ፡ ቦይ ፡ በመዘጋቱ ፡ የባሕር ፡ ላይ ፡ ንግድ ፡ ተጐዳ
2. የባሕር ፡ አዋሳኝ. Eritrea is Ethiopia's maritime province. ኤርትራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የባሕር ፡ አዋሳኝ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ናት
3. የባሕር. He studies maritime law. የባሕር ፡ ሕግ ፡ ያጠናል

**mark** (vt.)
1. ምልክት ፡ አደረገ(በት). I have marked the important parts of the article. የጽሑፉን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ምልክት ፡ አድርጌበታለሁ
Have you marked your laundry? የሚታጠበውን ፡ ልብስህን ፡ ምልክት ፡ አድርገህበታል ?
2. አረመ. When will you mark our examination papers? የፈተና ፡ ወረቀታችንን ፡ መቼ ፡ ታርማለህ ?

3. አመለከተ. His answers mark him as a good student. የሚሰጣቸው ፡ መልሶች ፡ ጥሩ ፡ ተማሪ ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታሉ
He marked the enemy position on a chart. ጠላት ፡ ያለበትን ፡ ስፍራ ፡ በካርታ ፡ ላይ ፡ አመለከተ
4. ገለጸ. He marked his satisfaction with a smile. ደስታውን ፡ በፈገግታ ፡ ገለጸ
5. የተለየ ፡ አደረገ. Many important inventions mark the last hundred years. ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ፍልሰፋዎች ፡ ያለፉትን ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ የተለዩ ፡ ያደርጓቸዋል
6. ልብ ፡ አለ. You had better mark my warning! ማስጠንቀቂያዬን ፡ ልብ ፡ ብትል ፡ ይሻላል
7. ሞጫጨረ. Be careful not to mark the table! ጠረጴዛውን ፡ እንዳትሞጫጭር ፡ ተጠንቀቅ
8. (= pass.) ታወቀ. +A frown marked her displeasure. አለመደሰቷ ፡ ፊቷን ፡ ከመቋጠሯ ፡ ታወቀ

**mark** (vi.) አስተዋለ
Mark how carefully he moves! እንዴት ፡ በጥንቃቄ ፡ እንደሚራመድ ፡ አስተውል

**be marked**
1. ታወቀ. His face was marked by years of hard work. ጊዜውን ፡ በከባድ ፡ ሥራ ፡ ያሳለፈ ፡ መሆኑ ፡ በፊቱ ፡ ይታወቃል
2. ጠቃጠቀ. +His face is marked by smallpox. ፊቱን ፡ ፈንጣጣ ፡ ጠቅጥቆታል
3. ተመለከተ. The borderline is not marked on the map. ድንበሩ ፡ በካርታው ፡ ላይ ፡ አልተመለከተም

**mark down**
1. ጻፈ. I have marked down the things I want. የምፈልጋቸውን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ጽፌያቸዋለሁ
Mark down the address! አድራሻውን ፡ ጻፍ
2. ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ አደረገ. The store marked down the coats from seventy to fifty dollars. መደብሩ ፡ የኮቱን ፡ ዋጋ ፡ ከሰባ ፡ ወደ ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ዝቅ ፡ አደረገ

**(be) marked for** ተደገሰ(ለት)
+The informer is marked for death. ጆሮ ፡ ጠቢው ፡ ሞት ፡ ተደግሶለታል

**mark off** በምልክት ፡ ለየ
He marked off the distance on the map. ርቀቱን ፡ በካርታው ፡ ላይ ፡ በምልክት ፡ ለየ

**mark out** አሠመረ
We marked out a tennis court. የቴኒሱን ፡ ሜዳ ፡ አሠመርን

**mark up**
1. ጨመረ. The store marked up the prices ten per cent. መደብሩ ፡ ዋጋዎቹን ፡ በሥር ፡ በመቶ ፡ ጨመረ
2. ሞጫጨረ. Don't mark up the desk! ጠረጴዛውን ፡ አትሞጫጭር
[See also ' time, word']

**mark** (n.)
1. ምልክት. Make a mark after the names of those present! ባሉት ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ አንጻር ፡ ምልክት ፡ አድርግ
His face shows the marks of old age. ፊቱ ፡ ላይ ፡ የእርጅና ፡ ምልክት ፡ ይታይበታል
The wet glass left a mark on the table. እርጥቡ ፡ ብርጭቆ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ ተወ
2. ውጤት. He always got good marks in mathematics. እርሱ ፡ ሁልጊዜ ፡ በሒሳብ ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ ያገኝ ፡ ነበር
3. ዒላማ. He hit the mark with his first arrow. በመጀመሪያው ፡ ቀስት ፡ ዒላማውን ፡ መታ
4. ዘላቂ ፡ የሆነ ፡ መታሰቢያነት. Theodore left his mark on Ethiopia. ቴዎድሮስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ዘላቂ ፡ የሆነ ፡ መታሰቢያነትን ፡ ትተዋል
5. የተወሰነ ፡ ደረጃ. His dissertation was below the mark. ጽሑፉ ፡ ከተወሰነው ፡ ደረጃ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ነበር
6. መግለጫ. Remove the price mark from your new suit! ካዲሱ ፡ ልብስህ ፡ ላይ ፡ የዋጋውን ፡ መግለጫ ፡ ገንጥል
*Standing there, the lion was an easy mark. እዚያ ፡ እንደቆመ ፡ አንበሳው ፡ በቀላሉ ፡ ሊመታ ፡ ይችል ፡ ነበር

**as a mark of** የሚገልጽ
Accept this gift as a mark of my esteem! ይህን ፡ አክብሮቴን ፡ የሚገልጽ ፡ ስጦታ ፡ ተቀበለኝ

**(be) beside the mark** ከጉዳዩ ፡ ውጭ ፡ ነበር
The answers given by the witness were beside the mark. ምስክሩ ፡ የሰጣቸው ፡ መልሶች ፡ ከጉዳዩ ፡ ውጭ ፡ ነበሩ

**get black-and-blue marks**
Where did you get those black-and-blue marks? ሰውነትህን ፡ ምን ፡ አበለዘው ?

**make (one's) mark** ዝናን ፡ አተረፈ
He made his mark in the world. በዓለም ፡ ላይ ፡ ዝናን ፡ አተረፈ

**make dirty marks on** አቆሸሸ
Who made these dirty marks on my new book? አዲሱን ፡ መጽሐፌን ፡ ማን ፡ አቆሸሸው ?

**man of mark** ዝነኛ
His uncle is a man of mark. አጎቱ ፡ ዝነኛ ፡ ናቸው

**not feel up to the mark** እንደ ፡ ወትሮው ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም
A tired person does not feel up to the mark. የደከመው ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም

**(be) off the mark** ልክ ፡ አይደለም
His opinion is off the mark. አስተያየቱ ፡ ልክ ፡ አይደለም
[See also 'identification, passing, punctuation']

## marked
1. ጉልህ. There is a marked difference between the two brothers. በሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ መካከል ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ልዩነት ፡ አለ
2. ምልክት ፡ የተደረገበት. Did you read the marked passage? ምልክት ፡ የተደረገበትን ፡ ምንባብ ፡ አንብበሃል ?
3. ተጠርጣሪ. He was a marked man once his revolutionary past became known. ቀድሞ ፡ ደመ ፡ ነውጥ ፡ እንደነበረ ፡ ከታወቀ ፡ በኋላ ፡ ተጠርጣሪ ፡ ሰው ፡ ሆነ

## markedly በጣም
He has markedly improved. በጣም ፡ ተሻሽሏል

## marker ምልክት
The marker for the exact spot where Theodore died was made of bronze. ቴዎድሮስ ፡ የሞቱበትን ፡ ትክክለኛ ፡ ስፍራ ፡ የሚያሳየው ፡ ምልክት ፡ ከነሐስ ፡ የተሠራ ፡ ነው

## market (vt.)
1. ሸጠ. The farmers market their grain through cooperatives. ገበሬዎቹ ፡ እህላቸውን ፡ በኅብረት ፡ ድርጅት ፡ በኩል ፡ ይሸጣሉ
2. (= intr.) ለገበያ ፡ ቀረበ. My invention needs a few refinements before we market it. የፈለሰፍኩት ፡ ለገበያ ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ አንዳንድ ፡ መሻሻል ፡ ያስፈልገዋል

## market (n.) ገበያ
Everything is cheaper at the market. አገበያ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ረከስ ፡ ይላል
How is the coffee market today? ዛሬ ፡ የቡና ፡ ገበያ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
The market is under way. ገበያው ፡ ቆመ
The market is in full swing in the afternoon. ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ገበያው ፡ ይደራል
The market is over. ገበያው ፡ ተበተነ

**be in the market for** ለመግዛት ፡ ፈለገ
Are you in the market for a good car? ጥሩ ፡ መኪና ፡ ለመግዛት ፡ ትፈልጋለህ ?

**be off the market** ከገበያ ፡ ጠፋ
That item has been off the market for a year. ያ ፡ እቃ ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ ከገበያ ፡ ጠፍቷል

**be on the market** ገበያ ፡ ዋለ
Fresh vegetables will be on the market this week. ያልዋለ ፡ ያላደረ ፡ አትክልት ፡ በዚህ ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ገበያ ፡ ይውላል

**be put on the market** ገበያ ፡ ወጣ
This toothpaste has been put on the market only recently. ይህ ፡ የጥርስ ፡ ሳሙና ፡ ገበያ ፡ የወጣው ፡ ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ነው

**there is a market for**
*There is a big market for warm clothing during the winter. ገበያ ፡ ውስጥ ፡ በክረምት ፡ ሞቃት ፡ የሆኑ ፡ ልብሶች ፡ ይነግሉ

**there is no market for** ፈላጊ ፡ የለውም
There is no market here for these typewriters. እዚህ ፡ ለነዚህ ፡ የጽሕፈት ፡ መኪናዎች ፡ ፈላጊ ፡ የላቸውም

## (be) marketable ገገር ፡ አገኘ
His invention is marketable. እሱ ፡ የፈለሰፈው ፡ ነገር ፡ ገገር ፡ ያገኛል

## marketing, do ~ ገበየ
She does her marketing in the morning. ጧት ፡ ጧት ፡ ትገበያለች

## marketplace ገበያ
He went to the marketplace to see how the goods were selling. እቃዎቹ ፡ እንዴት ፡ እንደሚሸጡ ፡ ለማየት ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ሄደ

## marksman አነጣጣሪ
Since the hunter was a good marksman, the bullet did not hit the ground. አዳኙ ፡ ጥሩ ፡ አነጣጣሪ ፡ ስለሆነ ፡ ጥይቱ ፡ መሬት ፡ አልወደቀም

## marmalade ማርመላታ

## maroon (v.) ያለ ፡ መመለሻ ፡ አስቀረ ፤ ያለ ፡ መመለሻ ፡ ለቀቀ
The loss of our boat marooned us. የጀልባችን ፡ መጥፋት ፡ ያለ ፡ መመለሻ ፡ አስቀረን
Pirates used to maroon people on desert islands. የባሕር ፡ ሽፍቶች ፡ ሰዎችን ፡ በረሃማ ፡ በሆኑ ፡ ደሴቶች ፡ ላይ ፡ እየወሰዱ ፡ ያለ ፡ መመለሻ ፡ ይለቋቸው ፡ ነበር

## maroon (n.) [ሽክላ ፡ ዓይነት ፡ ቀለም]

## marriage
1. ጋብቻ. His marriage was considered a disgrace for the family. የሱ ፡ ጋብቻ ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ እንደ ፡ ኀፍረት ፡ ተቈጠረ

We wished the bride and groom a happy marriage. ለሙሽሪቷና ፡ ለሙሽራው ፡ የደስታ ፡ ጋብቻ ፡ እንዲሆንላቸው ፡ ተመኘንላቸው
2. ትዳር. Her career is more important to her than her marriage. ለርሷ ፡ ከትዳሯ ፡ ይልቅ ፡ ሥራዋ ፡ ይበልጥባታል
3. ማግባት. Before her marriage, she worked in an office. ከማግባቷ ፡ በፊት ፡ ቢሮ ፡ ውስጥ ፡ ትሠራ ፡ ነበር

**arrange marriages**
*Arranging marriages for one's children is outmoded. የወላጆች ፡ ለልጆች ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛ ፡ መምረጥ ፡ ድሮ ፡ ቀርቷል

**civil marriage** የብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ ሥርዓት
They had a civil marriage. የተጋቡት ፡ በብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ነው

**(from her) first marriage** ከመጀመሪያ ፡ ባሏ
She has a daughter from her first marriage. ከመጀመሪያ ፡ ባሏ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ወልዳለች

**give in marriage** ዳረ
He gave his daughter in marriage to a minister's son. ልጁን ፡ ለሚኒስትር ፡ ልጅ ፡ ዳረ
[See also 'propose, service']

**marriageable** ለትዳር ፡ የደረሰ
He has two marriageable daughters. ሁለት ፡ ለትዳር ፡ የደረሱ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ አሉት

**married** (adj.) ያገባ ፤ የተዳረች
He is a married man. እሱ ፡ ያገባ ፡ ሰው ፡ ነው
She is a married woman. እሷ ፡ ያገባች ፡ ሴት ፡ ናት
The adventurer looked for an unmarried girl whose father was rich. ሙሌው ፡ ያልተዳረች ፡ የባለጸጋ ፡ ልጅ ፡ ፈለገ

**married couple** ባለትዳር
This house is only for married couples. ይህ ፡ ቤት ፡ ለባለትዳር ፡ ብቻ ፡ ነው

**married life** ትዳር
Married life changed many of his previous habits. ትዳር ፡ ብዙውን ፡ የድሮ ፡ ልማዱን ፡ ለወጠው

**marrow** ቅልጥም
The marrow is taken from the bones and eaten. ቅልጥም ፡ ካጥንት ፡ ውስጥ ፡ ወጥቶ ፡ ይበላል

**marry** (married), vt.
1. አገባ. Is she going to marry him? ልታገባው ፡ ነው ?
Is he going to marry her? ሊያገባት ፡ ነው ?
2. ዳረ. He married his youngest daughter to a writer. ትንሿን ፡ ልጁን ፡ ለደራሲ ፡ ዳራት
3. አጋባ. The patriarch is going to marry them. ፓትሪያርኩ ፡ ሊያጋባቸው ፡ ነው

**marry** (vi.)
1. አገባ. He married late in life. በዕድሜው ፡ ከጠና ፡ በኋላ ፡ አገባ
2. ባል ፡ አገባች. She married late in life. ባል ፡ ያገባችው ፡ በዕድሜ ፡ ከጠናች ፡ በኋላ ፡ ነው

**marry off** ዳረ
He has married off all his daughters. ሴት ፡ ልጆቹን ፡ ሁሉ ፡ ድሯል

**be married**
1. አገባ. Were you married in church? ያገባኸው ፡ በተክሊል ፡ ነው ?
2. ተጋቡ. They've been married over a year. ከተጋቡ ፡ ዓመት ፡ አልፏቸዋል

**get married** አገባ
When is he getting married? መቼ ፡ ነው ፡ የሚያገባው ?
When is she getting married? እሷ ፡ የምታገባው ፡ መቼ ፡ ነው ?

**marsh** ረግረግ
They are draining the marsh to build houses on. ቤት ፡ ለመሥራት ፡ ረግረጉን ፡ እያደረቁ ፡ ናቸው

**marshal** (v.)
1. አዘጋጀ. He took great care in marshaling his facts for the court. ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርበውን ፡ በትልቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ አዘጋጀ
2. መራ. The host marshaled them into the room. ባለቤቱ ፡ ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ መራቸው

**be marshaled** በክብር ፡ ተወሰደ
The foreign visitor was marshaled into the presence of the Emperor. የውጭ ፡ አገሩ ፡ እንግዳ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወዳሉበት ፡ በክብር ፡ ተወሰደ

**marshal** (n.) [በጦር ፡ ሰራዊት ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ባለሥልጣን]

**marshland** ረግረግ ፡ ስፍራ
This marshland is a breeding ground for mosquitoes. ይህ ፡ ረግረግ ፡ ስፍራ ፡ የወባ ፡ ትንኝ ፡ መርቢያ ፡ ነው

**marshy** ረግረግ
Marshy land shelters many small animals. ረግረግ ፡ መሬት ፡ ብዙ ፡ ትንንሽ ፡ እንስሳትን ፡ ያኖራል

**martial**
1. የጀግንነት. The Ethiopian patriots showed

their martial spirit in battle. የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ የጀግንነት ፡ ስሜታቸውን ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ አሳዩ
2. ማርሽ. He likes martial music. ማርሽ ፡ ሙዚቃ ፡ ይወዳል

**martial law** ወታደራዊ ፡ ሕግ
The governor declared martial law. ገዢው ፡ ወታደራዊ ፡ ሕግ ፡ ዐወጀ

**martyr** ሰማዕት (pl. ሰማዕታት)
The church honors all martyrs. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰማዕታትን ፡ ሁሉ ፡ ታከብራለች

**martyrdom** ሰማዕትነት
The martyrdom of St. John the Baptist is the subject of a new play. የመጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ሰማዕትነት ፡ ያዲስ ፡ ቲያትር ፡ አርእስት ፡ ነው

**martyrize** አሠቃየ
The ancient Romans martyrized many Christians. የጥንት ፡ ሮማውያን ፡ ብዙ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ አሠቃዩ

**martyrize oneself**
He sought to martyrize himself. ሰማዕት ፡ ለመምሰል ፡ ሞከረ

**marvel** (v.) ተደነቀ
I marvel that you were able to succeed under these difficult conditions. በዚህ ፡ ከባድ ፡ ሁኔታ ፡ መካከል ፡ ስለተሳካልህ ፡ እደነቃለሁ

**marvel at** አደነቀ
He marveled at her skill in typing. የመኪና ፡ ጽሕፈት ፡ ቅልጥፍናዋን ፡ አደነቀ

**marvel** (n.)
1. ታምር. The marvels of modern science are amazing. የዘመናዊ ፡ ሳይንስ ፡ ታምር ፡ ያስገርማል
These pills work marvels. እነዚህ ፡ ኪኒኖች ፡ ታምር ፡ ይሠራሉ
2. ምሳሌ. Your room is a marvel of neatness and order. ክፍልህ ፡ የንጽሕናና ፡ የሥርዓት ፡ ምሳሌ ፡ ነው

**marvelous** ግሩም
This is a marvelous cake. ይህ ፡ ግሩም ፡ ኬክ ፡ ነው

**masculine** (n.) ተባዕታይ ፡ ጾታ
The masculine does not have a special marker in Amharic. ባማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተባዕታይ ፡ ጾታ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ የለውም

**masculine** (adj.)
1. የወንድ. Football is a masculine sport. የእግር ፡ ኳስ ፡ የወንድ ፡ ጨዋታ ፡ ነው
2. ተባዕታይ. "He" is a masculine pronoun. «እሱ» ፡ ተባዕታይ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ነው

**masculine gender,** see **gender**

**mash** (v.)
1. አደቀቀ. A rock fell on his foot and mashed it. ድንጋይ ፡ እግሩ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ አደቀቀው
The elephant's heavy feet mashed the grass. ዝሆኑ ፡ በከባድ ፡ እግሮቹ ፡ ሣሩን ፡ አደቀቀው
2. ፈጨ. I just have to mash the potatoes. ገና ፡ ድንቹን ፡ መፍጨት ፡ አለብኝ
3. ለነቀጠ. They mashed the chickpeas to make stew. ወጥ ፡ ለመሥራት ፡ ሽንብራውን ፡ ለነቀጡት

**mash** (n.) ቅልቅል
The baby ate a mash of bananas and water. ሕፃኑ ፡ የሙዝና ፡ የውኃ ፡ ቅልቅል ፡ በላ

**mask** (v.)
1. ደበቀ. He masked his anger behind a smile. ብስጭቱን ፡ በፈገግታ ፡ ደበቀው
2. እንዳይታወቅ ፡ ሸፈነ. The robber masked his face. ቀማኛው ፡ እንዳይታወቅ ፡ ፊቱን ፡ ሸፈነ

**mask** (n.) መደበቂያ
The robber wore a mask over his face. ቀማኛው ፡ ፊቱን ፡ በመደበቂያ ፡ ሸፍኖ ፡ ነበር
*His smile was a mask to hide his disappointment. ፈገግታው ፡ ቅሬታውን ፡ ለመደበቅ ፡ የተደረገ ፡ ነበር

**mason** ግንበኛ
The mason will build the wall. ግንበኛው ፡ ግድግዳውን ፡ ይገነባል

**masonry** የግንበኛነት ፡ ሥራ
He is an apprentice in masonry. እሱ ፡ በግንበኛነት ፡ ሥራ ፡ ተለማማጅ ፡ ነው

**mass** (vt.) አንድነት ፡ ሰበሰበ
The general massed his troops for an attack. ጄኔራሉ ፡ ወታደሮቹን ፡ ለውጊያ ፡ አንድነት ፡ ሰበሰበ

**mass** (vi.) ተሰበሰበ ፤ በብዛት ፡ ተሰበሰበ
Crowds were massing in the square. ባደባባዩ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተሰብስቦ ፡ ነበር
The troops massed for an attack. ወታደሮቹ ፡ ለማጥቃት ፡ በብዛት ፡ ተሰበሰቡ

**mass** (n.)
1. ክምር. A large mass of feathers will be light

in weight. ትልቅ ፡ የላባ ፡ ክምር ፡ ክብደቱ ፡ ቀላል ፡ ነው
2. ግዙፍነት. He couldn't move the piano because of its mass. ከግዙፍነቱ ፡ የተነሣ ፡ ፒያኖውን ፡ ሊያንቀሳቅሰው ፡ አልቻለም
3. (= adv.) በብዛት. Mass meetings are forbidden unless a permit is obtained from the police. ከፖሊስ ፡ ፈቃድ ፡ ካልተሰጠ ፡ በስተቀር ፡ በብዛት ፡ መሰብሰብ ፡ ክልክል ፡ ነው
Mass production results in lower costs. እቃን ፡ በብዛት ፡ መሥራት ፡ የመሥሪያ ፡ ዋጋውን ፡ ይቀንሳል
*The mass of opinion is against the plan. የአብዛኛው ፡ ሰው ፡ አስተሳሰብ ፡ እቅዱን ፡ የሚቃወም ፡ ነው
*The car is buried under a mass of mud. መኪናዋ ፡ ማጥ ፡ ውስጥ ፡ ተቀበረች

**masses** ተራ ፡ ሕዝብ
The masses are illiterate. ተራው ፡ ሕዝብ ፡ መሀይም ፡ ነው

**in the mass** በጠቅላላው
The valley, in the mass, is extremely fertile. ሸለቆው ፡ በጠቅላላው ፡ በጣም ፡ ለም ፡ ነው

**Mass** ቅዳሴ
Mass begins at 7 o'clock. ቅዳሴ ፡ የሚገባው ፡ ከጧት ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ነው

**celebrate Mass** ቅዳሴ ፡ ገባ
The priests are celebrating Mass now. ቄሶቹ ፡ ቅዳሴ ፡ ገብተዋል

**go to Mass**
She went to Mass. ልታስቀድስ ፡ ሄደች
[See also 'sing']

**massacre** (v.)
1. ገደለ. The soldiers looted and massacred for three weeks. ወታደሮቹ ፡ ለሦስት ፡ ሳምንታት ፡ ሲዘርፉና ፡ ሲገድሉ ፡ ቆዩ
2. ፈጀ. The enemy massacred the wounded. ጠላት ፡ ቁስለኞቹን ፡ ፈጃቸው

**massacre** (n.)
1. እልቂት. At Siddist Kilo there is a memorial to the Yekatit massacre. ስድስት ፡ ኪሎ ፡ ላይ ፡ ለየካቲት ፡ እልቂት ፡ የቆመ ፡ መታሰቢያ ፡ ሐውልት ፡ አለ
2. ፍጅት. The malign rule of the tyrant caused revolts and massacres. የጨቋኙ ፡ የጭካኔ ፡ አገዛዝ ፡ ሁከትና ፡ ፍጅት ፡ አስከተለ

**massage** (v.) አሸ
He massaged his cold fingers. ብርድ ፡ የመታቸውን ፡ ጣቶቹን ፡ አሸ

**massage** (n.) መታሸት
How much does a massage cost? ለመታሸት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይከፈላል ?

**get a massage** ታሸ
I'm going to get a massage to help my aching back. የሚያመኝን ፡ ጀርባዬን ፡ እንዲሽለኝ ፡ እታሻለሁ

**massive**
1. ግዙፍ. He was locked in by a massive door. ግዙፍ ፡ መዝጊያ ፡ ተዘጋበት
2. ብዙ. Massive evidence showed that the president was the embezzler. ፕሬዚዳንቱ ፡ የሕዝብ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያጭበረብር ፡ መሆኑ ፡ በብዙ ፡ መረጃ ፡ ታወቀ
3. ከፍ ፡ ያለ. His massive erudition impressed the audience. ከፍ ፡ ያለ ፡ ዕውቀቱ ፡ አዳማጮቹን ፡ ገረማቸው
4. መዓት. A massive swarm of locusts invaded the country. መዓት ፡ የአንበጣ ፡ መንጋ ፡ ሀገሪቷን ፡ ወረረ

**mast** የመርከብ ፡ ምሰሶ
The sailor was leaning against the mast. መርከበኛው ፡ የመርከቡን ፡ ምሰሶ ፡ ተደግፎ ፡ ቆሞ ፡ ነበር

**master** (v.)
1. ጠንቅቆ ፡ ዐወቀ ፤ በደንብ ፡ አጣርቶ ፡ ዐወቀ. It will take you five years to master Amharic. አማርኛን ፡ ጠንቅቆ ፡ ለማወቅ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ይፈጅብሃል
He was bent on mastering Amharic. አማርኛ ፡ በደንብ ፡ አጣርቶ ፡ ለማወቅ ፡ ጣረ
2. አጠናቆ ፡ ዐወቀ. The manifold subject requires years of study to master. ብዙ ፡ ዘርፍ ፡ ያለውን ፡ ትምህርት ፡ አጠናቆ ፡ ለማወቅ ፡ የብዙ ፡ ዓመታት ፡ ጥናት ፡ ያስፈልጋል
3. አጥርቶ ፡ ዐወቀ. He has mastered three foreign languages. ሦስት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋዎች ፡ አጥርቶ ፡ ያውቃል
4. ገታ. It took him quite a while to master his temper. ንዴቱን ፡ ለመግታት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወሰደበት

**master** (n.)
1. ጌታ. No man can serve two masters. አንድም ፡ ሰው ፡ ለሁለት ፡ ጌታ ፡ ሊገዛ ፡ አይችልም
The master beat the dog. ጌትየው ፡ ውሻውን ፡ መታው
2. መምህር. The master taught his pupils how to read. መምህሩ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ንባብ ፡ አስተማራቸው

*He is a master at story telling. ተረት ፡ ሲያወራ ፡ የሚያክለው ፡ የለም
*He is master of the situation. እንደ ፡ ሁኔታው ፡ የመሥራት ፡ ችሎታ ፡ አለው

**master of the house** ባለቤት
The master of the house is not in. ባለቤቱ ፡ እቤት ፡ የሉም

**master** (adj.) ዋና
The master bedroom has a large window. ዋናው ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ ትልቅ ፡ መስኮት ፡ አለው

**master musician** የሙዚቃ ፡ ሊቅ
He is a master musician, and everyone admires him. የሙዚቃ ፡ ሊቅ ፡ ስለሆነ ፡ ሁሉ ፡ ያደንቀዋል

**master plan** መሠረተ ፡ ፕላን
A master plan is needed for the city's development. ለከተማው ፡ እድገት ፡ መሠረተ ፡ ፕላን ፡ ያስፈልጋል

**masterful**
1. ሥልጣን ፡ የተመላበት. His masterful tone frightened all the clerks. ሥልጣን ፡ የተመላበት ፡ ድምፁ ፡ ሻጮቹን ፡ ሁሉ ፡ አስደነገጣቸው
2. ጥበብ ፡ የተሞላበት. His masterful ways gained her love. ጥበብ ፡ የተሞላበት ፡ ሥራው ፡ የሷን ፡ ፍቅር ፡ አስገኘለት
3. ረቂቅ ፡ የሆነ. The masterful performance of the pianist enchanted the audience. የፒያኒስቱ ፡ ረቂቅ ፡ የሆነ ፡ የፒያኖ ፡ አመታት ፡ አዳማጮቹን ፡ አስደሰታቸው

**master key** ዓይነተኛ ፡ ቁልፍ
This master key will unlock all the doors in this building. ይህ ፡ ዓይነተኛ ፡ ቁልፍ ፡ በሕንጻው ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ በሮች ፡ ሁሉ ፡ ይከፍታል

**masterly** የጠቢብ
He did a masterly job of repair work. በጥገና ፡ በኩል ፡ የጠቢብ ፡ ሥራ ፡ ሠራ

**mastermind** የወጠነ ፡ ሰው
The mastermind behind the revolt was caught. ሁከቱን ፡ ሁሉ ፡ የወጠነው ፡ ሰው ፡ ተያዘ

**Master of Arts** ማስተር ፡ ኦፍ ፡ አርትስ
He received his Master of Arts from the University of California. የማስተር ፡ ኦፍ ፡ አርትስ ፡ ዲግሪውን ፡ ከካሊፎርንያ ፡ ዩንቨርሲቲ ፡ አገኘ

**master of ceremonies** አስተዋዋቂ
He was master of ceremonies at the concert. በሙዚቃው ፡ በዓል ፡ ላይ ፡ አስተዋዋቂ ፡ ነበር

**masterpiece** ታላቅ ፡ ቅርስ
His latest novel is a literary masterpiece. በቅርቡ ፡ ያወጣው ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፉ ፡ ታላቅ ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ቅርስ ፡ ነው
*This painting is an artistic masterpiece. ይህ ፡ ሥዕል ፡ ታላቅ ፡ ርቀት ፡ ያለው ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ነው

**mastery**
1. በላይነት. The two teams vied for mastery. ሁለቱ ፡ ቡድኖች ፡ ለበላይነት ፡ ተወዳደሩ
2. ችሎታ. His mastery of arithmetic is noticed by all. በሒሳብ ፡ ረገድ ፡ ያለው ፡ ችሎታ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው
3. ለመቈጣጠር ፡ ያለው ፡ ችሎታ. His mastery over his temper helped him greatly in life. ንዴቱን ፡ ለመቈጣጠር ፡ ያለው ፡ ችሎታ ፡ በሕይወቱ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ረዳው

**masticate** አኘከ
He tried to masticate the tough leather. ጠንካራውን ፡ ጠፍር ፡ ለማኘክ ፡ ሞከረ

**mat** (v.) በታተነ
The sea breeze matted his hair. ከባሕር ፡ የሚመጣው ፡ ነፋስ ፡ ጸጉሩን ፡ በታተነው

**be matted**
1. ተቈጣጠረ. His hair is matted with blood. ጸጉሩ ፡ በደም ፡ ተቈጣጥሯል
2. ተደመደመ. The grass was matted because the animals trampled and rolled on it. እንስሳት ፡ ስለረጋገጡትና ፡ ስለተንደባለሉበት ፡ ሣሩ ፡ ተደመደመ

**mat** (n.) ሰሌን
Put a mat on the floor to sit on! ለመቀመጫ ፡ በወለሉ ፡ ላይ ፡ ሰሌን ፡ አንጥፍ

**match** (vt.)
1. ተመሳሳይ ፡ ነው. This color matches that one. ይህ ፡ ቀለም ፡ ከዚያኛው ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው
2. አከለ. My skills in typing do not match his. የመኪና ፡ ጽሕፈት ፡ ችሎታዬ ፡ የሱን ፡ አያክልም
*I'm ready to match my strength with yours. አንተን ፡ በጉልበት ፡ ለመቋቋም ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ

**match** (vi.) ተመሳሳይ ፡ ነው ፤ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ነው
The two candles match exactly. ሁለቱ ፡ ሻማዎች ፡ ፍጹም ፡ ተመሳሳዮች ፡ ናቸው
Your socks do not match. የእግር ፡ ሹራብህ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ አይደለም

**match** (n.)
1. ክብሪት. Give me a box of matches, please! አንድ ፡ ፓኮ ፡ ክብሪት ፡ ስጠኝ

Strike a match; I can't see in the dark. ክብሪት ፡ ጫር ፤ በጨለማ ፡ ለማየት ፡ አልችልም
2. ግጥሚያ. Who won the match? ግጥሚያውን ፡ ማን ፡ አሸነፈ ?
3. ተመሳሳይ. I am looking for a match for this paint. የዚህን ፡ ቀለም ፡ ተመሳሳይ ፡ እፈልጋለሁ
4. እኩያ. You're no match for him. He'll flatten you with one blow. እኩያው ፡ አይደለህም ፤ ባንድ ፡ ምት ፡ ይዘርርሃል
5. ጋብቻ. The parents did not approve of the match. ወላጆቹ ፡ ጋብቻውን ፡ አልፈቀዱም

**arrange a match** አጋባ
She tried to arrange a match between the bachelor and the widow. ወንደ ፡ ላጤውንና ፡ ባሏ ፡ የሞተባትን ፡ ሴት ፡ ለማጋባት ፡ ሞከረች

**be a good match**
1. ለጋብቻ ፡ ተስማማ. He is a good match. እሱ ፡ ለጋብቻ ፡ የሚስማማ ፡ ነው
2. ተስማማ. These colors aren't a good match. እነዚህ ፡ ቀለሞች ፡ አይስማሙም

**be a match** ተስተካከለ
She is not yet a match for her mother in cooking. በምግብ ፡ አሠራር ፡ እናቷን ፡ አትስተካከልም
[See also 'wrestling']

## matchmaker አማጭ
The matchmaker arranged a marriage between these two couples. አማጩ ፡ ሁለቱን ፡ ሰዎች ፡ ለጋብቻ ፡ አስማማ

## mate (v.)
1. ተጠቃ. The animals in the zoo haven't mated this year. በአራዊት ፡ መጠበቂያ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ እንስሶች ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ አልተጠቁም
2. ፈለፈለ. Birds mate in the spring and build their nests. ወፎች ፡ የሚፈለፍሉትና ፡ ጎጆ ፡ የሚሠሩት ፡ በጸደይ ፡ ነው

## mate (n.)
1. ጓደኛ. He and his mate left the school at 12 o'clock. እሱና ፡ ጓደኛው ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ወጡ
I lost the mate of this glove. የዚህ ፡ ጓንቲ ፡ ጓደኛው ፡ ጠፋብኝ
2. የትዳር ፡ ጓደኛ. One should treat one's mate with consideration. አንድ ፡ ሰው ፡ የትዳር ፡ ጓደኛውን ፡ በሚገባ ፡ መያዝ ፡ አለበት
3. ባል. The lioness and her mate were sunning themselves in the cage. አንበሳይቱና ፡ ባሏ ፡ እብረት ፡ ጎጆው ፡ ውስጥ ፡ ፀሐይ ፡ ይሞቁ ፡ ነበር
*The lion and his mate were sunning themselves in the cage. አንበሳውና ፡ አንበሳይቱ ፡ እብረት ፡ ጎጆው ፡ ውስጥ ፡ ፀሐይ ፡ ይሞቁ ፡ ነበር

## material (n.)
1. ጨርቅ. I have enough material to make a coat. ኮት ፡ ለመስፋት ፡ በቂ ፡ ጨርቅ ፡ አለኝ
2. እቃ. We use only the best materials. እኛ ፡ የምንሠራባቸው ፡ ምርጥ ፡ እቃዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው
The raw material is processed by the factory and turned into plastics. ጥሬው ፡ እቃ ፡ ፋብሪካው ፡ ውስጥ ፡ ከተሠራ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ፕላስቲክነት ፡ ይለወጣል
3. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማስረጃዎች. He is collecting material for a book. መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማስረጃዎችን ፡ በመሰብሰብ ፡ ላይ ፡ ነው

## material (adj.)
1. ዓለማዊ. She's only interested in material things. እሷ ፡ በዓለማዊ ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ ትደሰታለች
2. ጉልህ. There's no material difference between the two. በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ ጉልህ ፡ ልዩነት ፡ የለም
3. ጠቃሚ. The judge warned the witness not to hold back material evidence. ዳኛው ፡ ምስክሩ ፡ ጠቃሚ ፡ ማስረጃዎችን ፡ እንዳይደብቅ ፡ አስጠነቀቀው
4. ዋና. The baking is a material factor in making cake. ኬክ ፡ ሲሠራ ፡ ዋናው ፡ ሥራ ፡ መጋገሩ ፡ ነው
5. ለአካል ፡ የሚሰጥ. Food and shelter are material comforts. ምግብና ፡ መጠለያ ፡ ለአካል ፡ ምቾት ፡ የሚሰጡ ፡ ናቸው

**material needs** የሰውነት ፡ መሠረታዊ ፡ ፍላጎት
Every man needs to satisfy his material needs. ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሰውነት ፡ መሠረታዊ ፡ ፍላጎቱን ፡ ለማርካት ፡ ይፈልጋል

## materialize (vt.)
1. በመጀመሪያ ፡ አወጣ(ለት). An inventor materializes his ideas by building a model. ፈልሳፊው ፡ ሊሠራ ፡ ያሰበውን ፡ ነገር ፡ በመጀመሪያ ፡ ሞዴል ፡ ያወጣለታል
2. ከግብ ፡ አደረሰ. He materialized his ambition to become a doctor. ሐኪም ፡ ለመሆን ፡ የነበረውን ፡ ምኞት ፡ ከግብ ፡ አደረሰ

**materialize** (vi.) በሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ
Our plans did not materialize. እቅዶቻችን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አልዋሉም

## materially

1. በጣም. The teacher's ideas helped materially in planning the play. ቲያትሩን ፡ በማዘጋጀት ፡ ረገድ ፡ ያስተማሪው ፡ ሐሳቦች ፡ በጣም ፡ ረዱ
2. በመሣሪያ ፡ ረገድ. The enemy was strong materially, but weak in leadership. ጠላት ፡ በመሣሪያ ፡ ረገድ ፡ ጠንካራ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በመሪ ፡ በኩል ፡ ደካማ ፡ ነበር
3. በሀብት. The nation got better materially, but worse spiritually. አገሪቱ ፡ በሀብት ፡ ስትሻሻል ፡ በመንፈሳዊ ፡ ረገድ ፡ ግን ፡ እየተበላሸች ፡ ሄደች

## maternal

1. የእናት. A child needs maternal love. ልጅ ፡ የእናት ፡ ፍቅር ፡ ያስፈልገዋል
2. በእናቱ ፡ በኩል. His maternal grandparents are still alive. በእናቱ ፡ በኩል ፡ አያቶቹ ፡ አሁንም ፡ በሕይወት ፡ አሉ

**maternal care** የሕፃናት ፡ አስተዳደግ
Maternal care is being taught by health teams. የሕፃናት ፡ አስተዳደግ ፡ ትምህርት ፡ በጤና ፡ ጓዶች ፡ ይሰጣል

## maternity (n.) ወላድ ፡ መሆን

Maternity changes a woman in many ways. ወላድ ፡ መሆን ፡ ሴትን ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ይለውጣታል

**maternity** (adj.)
1. የማዋለጃ. This hospital has a maternity ward. ይህ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ የማዋለጃ ፡ ክፍል ፡ አለው
2. የእርጉዝ. She wears a maternity dress. የእርጉዝ ፡ ልብስ ፡ ትለብሳለች

## mathematician የሒሳብ ፡ ዐዋቂ

A mathematician is needed to solve this problem. ይህንን ፡ ፕሮብሌም ፡ ለመሥራት ፡ የሒሳብ ፡ ዐዋቂ ፡ ያስፈልጋል

## mathematics ሒሳብ

I study mathematics every day. ሁልቀን ፡ ሒሳብ ፡ አጠናለሁ

## matriarch [ቤተ ፡ ሰብን ፡ ወይም ፡ ጐሳን ፡ የምታስተዳድር ፡ እመቤት]

## matriculate ኮሌጅ ፡ ገባ

I matriculated last year. ዓምና ፡ ኮሌጅ ፡ ገባሁ

## matrimony ጋብቻ

Matrimony is the goal of many young women. የብዙ ፡ ልጃገረዶች ፡ ዓላማ ፡ ጋብቻ ፡ ነው

## matron [በዕድሜ ፡ ጠና ፡ ያሉ ፡ ያገቡ ፡ ወይም ፡ ባል ፡ የሞተባቸው ፡ ወይዘሮ]

## matter (v.) አስፈላጊ ፡ ነው

It hardly matters one way or the other. ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ እጅግም ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም

## matter (n.)

1. ጉዳይ. It's not a matter of price. የዋጋ ፡ ጉዳይ ፡ አይደለም
2. ነገር. I'll look into the matter. ነገሩን ፡ እመረምረዋለሁ
You're only making matters worse. ነገሩን ፡ ታባብሰዋለህ
3. ፍሬ ፡ ነገር. The matter of this book concerns everybody. የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ የሚመለከት ፡ ነው
4. ዋጋ. This idea is of little matter. ይህ ፡ አሳብ ፡ አነስተኛ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነው
5. ምክንያት. If a man is robbed, he has matter for complaint to the police. አንድ ፡ ሰው ፡ የተቀማ ፡ እንደሆነ ፡ ለፖሊስ ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ምክንያት ፡ ይኖረዋል
6. ግዘፍ ፡ ያለው ፡ ነገር. Solids and liquids are matter. ጥጥርና ፡ ፈሳሽ ፡ ነገሮች ፡ ግዘፍ ፡ ያላቸው ፡ ነገሮች ፡ ናቸው

**matter of fact, as a ~**
1. እንዲያውም. As a matter of fact, I'm leaving for that country myself. እንዲያውም ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ ወደዚያ ፡ አገር ፡ መሄዴ ፡ ነው
2. እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ. As a matter of fact, I wasn't even there. እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ ፡ እዚያም ፡ አልነበርኩ

**a matter of** ለብዙ
We waited a matter of hours. ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ጠበቅን

**be the matter** ነካ
What's the matter with this motor? ይህን ፡ ሞተር ፡ ምን ፡ ነካው ?
What's the matter? Why are you crying? ምን ፡ ነካህ ፡ (ምን ፡ ሆነሃል) ፤ ለምን ፡ ታለቅሳለህ ?

**for that matter** እንዲያውም
For that matter, he can stay where he is. እንዲያውም ፡ እዚያው ፡ ሊቆይ ፡ ይችላል

**in the matter of** በ - - - በኩል
He is strict in the matter of discipline. በሥርዓት ፡ በኩል ፡ ጥብቅ ፡ ነው

**it does not matter** ግድ ፡ የለም
It does not matter; I shall go myself. ግድ ፡ የለም ፤ እኔው ፡ ራሴ ፡ እሄዳለሁ

It did not matter to him whether he got paid or not. ቢከፈለው ፡ ባይከፈለው ፡ ግድ ፡ አልነበረውም

**it's of no matter** አያሳስብም
It's of no matter. The cut is a small one. የተቆረጠው ፡ ትንሽ ፡ ነው ፤ አያሳስብም

**no matter what** ምንም ፡ ብ + imperfect
No matter what I do, it doesn't please him. ምንም ፡ ብሠራ ፡ አያስደስተውም
Time moves on, no matter what we do. ምንም ፡ ብናደርግ ፡ ጊዜ ፡ ማለፍ ፡ አይቀርም
*We're going, no matter what you say. ያልከውን ፡ ብትል ፡ እንሄዳለን

**what does it matter** ምን ፡ ያደርጋል
What does it matter? I'm going anyway. ምን ፡ ያደርጋል ? ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ መሄዴ ፡ ነው
[See also 'course, dead, fact, form']

**matter-of-fact** (= adv.) ምንም ፡ እንዳልሆነ ፡ አድርጎ
His matter-of-fact explanation of the accident surprised everyone. ያደጋውን ፡ ሁኔታ ፡ ምንም ፡ እንዳልሆነ ፡ አድርጎ ፡ መናገሩ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አስገረመው

**mattress** ፍራሽ
I need a new mattress for my bed. ለአልጋዬ ፡ አዲስ ፡ ፍራሽ ፡ ያስፈልገኛል

**mature** (vt.) አጐለመሰ
This experience matured his character. ይህ ፡ በሕይወቱ ፡ የደረሰበት ፡ ነገር ፡ ጠባዩን ፡ አጐለመሰው

**mature** (vi.)
1. በሰለ. Wine matures in three months. ወይኑ ፡ ለመብሰል ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ይፈጅበታል
2. ጐለመሰ. He seems to have matured as a result of his experience in the war. ከጦርነት ፡ ባገኘው ፡ ልምምድ ፡ የጐለመሰ ፡ ይመስላል
3. ጠነከረ. Most animals mature faster than human beings. ብዙ ፡ እንስሳት ፡ ከሰው ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ይጠነክራሉ
4. የከፍያ ፡ ጊዜ ፡ ደረሰ. When your saving bonds mature, you can collect their full value. የቁጠባ ፡ ቦንድህ ፡ የከፍያ ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ሙሉ ፡ ዋጋውን ፡ ልትወስድ ፡ ትችላለህ

**mature** (adj.)
1. የበሰለ. A mature mind is capable of comparing things. የበሰለ ፡ አእምሮ ፡ ነገርን ፡ ማመዛዘን ፡ ይችላል
2. የጉልምስና. Fifty is a mature age. ኀምሳ ፡ የጉልምስና ፡ ዕድሜ ፡ ነው
3. ዐዋቂ. This job can be done only by a mature woman. ይህን ፡ ልትሠራ ፡ የምትችል ፡ ዐዋቂ ፡ ሴት ፡ ብቻ ፡ ናት

**be mature**
1. በሰለ. The boy is very mature for his age. ልጁ ፡ በዚህ ፡ ዕድሜው ፡ በጣም ፡ በስሏል
2. ተጠናቀቀ. His plans are not yet mature. የሱ ፡ እቅድ ፡ ገና ፡ አልተጠናቀቀም

**of mature years** የበሰለ
Persons of mature years are needed for this job. ለዚህ ፡ ሥራ ፡ የበሰሉ ፡ ሰዎች ፡ ያስፈልጋሉ

**maturity**
1. ዐቅመ ፡ አዳም. He had reached maturity by the time he was twenty. ሃያ ፡ ዓመት ፡ ሲሞላው ፡ ለዐቅመ ፡ አዳም ፡ ደርሶ ፡ ነበር
2. ዐቅመ ፡ ሔዋን. She had reached maturity by the time she was twenty. ሃያ ፡ ዓመት ፡ ሲሞላት ፡ ለዐቅመ ፡ ሔዋን ፡ ደርሳ ፡ ነበር

**be far from maturity** ገና ፡ አልበሰለም
Even though he is 30 he is far from maturity. ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ቢሆነውም ፡ ገና ፡ አልበሰለም

**bring to maturity** ከግብ ፡ አደረሰ
We brought our plan to maturity. እቅዳችንን ፡ ከግብ ፡ አደረስን

**reach maturity**
1. ተሟላ. When their plans reached maturity, they were able to begin. እቅዳቸው ፡ በተሟላ ፡ ጊዜ ፡ ለመጀመር ፡ ቻሉ
2. በሰለ. The oranges on the tree will reach maturity in two more weeks. በዚህ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ብርቱካኖች ፡ ከሁለት ፡ ሳምንት ፡ በኋላ ፡ ይበስላሉ

**(not) reach maturity** ዕድሜው ፡ ሳይደርስ ፡ ሞተ
Many fish and frogs never reach maturity. ብዙ ፡ ዓሣዎችና ፡ እንቁራሪቶች ፡ ዕድሜያቸው ፡ ሳይደርስ ፡ ይሞታሉ

**maul** በማንገላታት ፡ ጐዳ
The lion mauled his trainer. አንበሳው ፡ አሠልጣኙን ፡ በማንገላታት ፡ ጐዳው

**maxim** ምሳሌ
"Make hay while the sun shines" is a maxim. « አባት ፡ ሳለ ፡ አጊጥ ፤ ጀንበር ፡ ሳለ ፡ ሩጥ » ፡ የሚለው ፡ ምሳሌ ፡ ነው

**maximize**
1. አጋነነ. He maximized the importance of what he had done. የሠራውን ፡ ነገር ፡ ትልቅነት ፡ አጋነነ
2. አዳበረ. He will maximize profits by re-

ducing costs. ወጪን ፡ በመቀነስ ፡ ትርፍን ፡ ያዳብራል

**maximum** (n.)

1. መጨረሻ. I'm willing to pay twenty dollars, but that's the maximum. ሃያ ፡ ብር ፡ ለመክፈል ፡ እስማማለሁ ፤ ይህ ፡ ግን ፡ የመጨረሻው ፡ ነው

2. የመጨረሻ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍጥነት. The speed limit is 40 miles an hour; drivers must not exceed this maximum. የፍጥነቱ ፡ ወሰን ፡ በሰዓት ፡ አርባ ፡ ማይል ፡ ነው ፤ ነጂዎች ፡ ይህን ፡ የመጨረሻ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍጥነት ፡ ማለፍ ፡ የለባቸውም

**maximum** (adj.) ከፍተኛ

The maximum temperature ever recorded in the city is 100° F. እስካሁን ፡ በዚህ ፡ ከተማ ፡ የተመዘገበው ፡ ከፍተኛ ፡ ሙቀት ፡ 100° ፋረንሃይት ፡ ነው

He pays the maximum amount for old books. ላሮጌ ፡ መጻሕፍት ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ይከፍላል

*The maximum weight for baggage in air travel is 44 pounds. በአውሮፕላን ፡ ላይ ፡ የሚፈቀደው ፡ የእቃ ፡ ክብደት ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ነጥር ፡ ነው

**May** ግንቦት

**may** (might)

1. (jussive). May I offer you a cup of coffee? አንድ ፡ ሲኒ ፡ ቡና ፡ ልስጥህ ?

May I go now? ልሂድ ?

May you be very happy! ደስ ፡ ይበልህ

2. (verb) + ይሆናል. That may be so. እንዲያ ፡ ይሆን ፡ ይሆናል

I may be able to come. ልመጣ ፡ እችል ፡ ይሆናል

I may be too late already. አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ዘግይቼ ፡ ይሆናል

Be good, and I might let you have my bicycle tomorrow. ጠባይህን ፡ ካሳመርክ ፡ ነገ ፡ ብስክሌቴን ፡ እሰጥህ ፡ ይሆናል

3. ሊሆን ፡ ይችላል. It may be true. እውነት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

*If we had rushed, we might have caught the train. ብንሮጥ ፡ ኖሮ ፡ ባቡሩን ፡ ልንደርስበት ፡ እንችል ፡ ነበር

*You might at least say 'thank you'. ሌላው ፡ ቢቀር ፡ እግዜር ፡ ይስጥልኝ ፡ ልትል ፡ ይገባል

**may as well**

*We may as well stay where we are. ለዚህ ፡ ለዚህ ፡ ባለንበት ፡ እንቆይ

**(this) may or may not be** ሊሆንም ፡ ላይሆንም ፡ ይችላል

This may or may not be true, but we will look into it anyway. ይህ ፡ እውነት ፡ ሊሆንም ፡ ላይሆንም ፡ ይችላል ፤ ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ነገሩን ፡ እናጣራለን

**be that as it may** የሆነው ፡ ቢሆን ፤ ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፤ ግራም ፡ ነፈሰ ፡ ቀኝ

Be that as it may, I will go to New York anyway. የሆነው ፡ ቢሆን ፡ (ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፤ ግራም ፡ ነፈሰ ፡ ቀኝ) ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ኒውዮርክ ፡ መሄዴ ፡ ነው

**maybe**

1. ምናልባት. Will you come? Maybe. ትመጣለህ? ምናልባት

2. ምናልባት + gerundive + ይሆናል. Maybe he's lost. ምናልባት ፡ ጠፍቶ ፡ ይሆናል

**mayor**

1. ከንቲባ. Who is the mayor of Addis Ababa? የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከንቲባ ፡ ማን ፡ ነው ?

2. የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ሹም. Who is the mayor of Dessie? የደሴ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ማን ፡ ነው ?

**maze** መግቢያ ፡ መውጫው ፡ የሚያደናግር

Many ancient palaces were mazes. ብዙዎቹ ፡ የጥንት ፡ ቤተ ፡ መንግሥቶች ፡ መግቢያ ፡ መውጫቸው ፡ የሚያደናግር ፡ ነበር

*This maze of facts and figures is hard to understand. የተወሳሰቡትን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮችና ፡ ቁጥሮች ፡ መረዳት ፡ ያስቸግራል

**be in a maze** ተማታ

I was in such a maze, I couldn't answer. ተማቶብኝ ፡ ስለነበረ ፡ ልመልስ ፡ አልቻልኩም

**me,** expressed by the suffix pronoun -ኝ

Did you see me yesterday? ትናንት ፡ አይተኸኛል ?

Give me your book! መጽሐፍህን ፡ ስጠኝ

**mead** ጠጅ

Drink this mead! It's good. ይህንን ፡ ጠጅ ፡ ጠጣ ፤ ጥሩ ፡ ነው

**meadow** መስክ

The meadow is bordered by trees. በመስኩ ፡ ዙሪያ ፡ ዛፎች ፡ አሉ

**meager**

1. የማያጠግብ. He ate a meager meal of cold boiled potatoes. የማያጠግብ ፡ የበረደ ፡ ቅቅል ፡ ድንች ፡ በላ

2. የተጎሳቈለ. The meager face of the beggar aroused his compassion. የተጎሳቈለው ፡ የለማኙ ፡ ፊት ፡ አሳዘነው

3. እጅግም. The Central African Republic's resources are meager. የመሀከለኛ ፡ አፍሪካ ፡ ሪፑብሊክ ፡ ያላት ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ እጅግም ፡ ነው

**be meager** እምብዛም ፡ ጥሩ ፡ አልነበረም
The results were meager. ውጤቱ ፡ እምብዛም ፡ ጥሩ ፡ አልነበረም

**meal** ምግብ
Breakfast is the first meal of the day. ቁርስ ፡ የቀኑ ፡ የመጀመሪያው ፡ ምግብ ፡ ነው
I haven't eaten a decent meal in weeks. ለብዙ ፡ ሳምንት ፡ ጥሩ ፡ ምግብ ፡ አልበላሁም
*Three meals a day aren't enough for him. በቀን ፡ ሦስቴ ፡ መብላት ፡ አያጠግበውም

**humble meal** ተራ ፡ ምግብ
Will you partake of this humble meal? ይህችን ፡ ተራ ፡ ምግብ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ልትሳተፍ ፡ ትፈቅዳለህ ?
[See also 'festive, midday']

**mean** (v.)
1. ማለት ፡ ነው. Falling leaves mean winter is near. ቅጠሉ ፡ ቅጠል ፡ ሲረግፍ ፡ ክረምት ፡ ተቃርቧል ፡ ማለት ፡ ነው
What do you mean by that? እንዲህ ፡ ስትል ፡ ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ?
2. አሰበ. I meant to call, but I forgot. ልደውል ፡ አስቤ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ረሳሁት
I know he means well, but the way he does things annoys me. ቅን ፡ ማሰቡን ፡ አውቃለሁ ፤ ግን ፡ አሠራሩ ፡ ያናድደኛል
He says exactly what he means. የሚናገረው ፡ ልክ ፡ ያሰበውን ፡ ነው
3. ፈለገ. I didn't mean for you to see the letter. ደብዳቤውን ፡ አንተ ፡ እንድታየው ፡ አልፈለግሁም ፡ ነበር
4. የምሩን ፡ ነው. He certainly meant what he said. የምሩን ፡ ነው ፡ የተናገረው
5. ሰነዘረ. He meant those words for all of us. እስተያየቱን ፡ የሰነዘረው ፡ ለሁላችንም ፡ ነበር
6. አስከተለ. This frontier incident means war. ይህ ፡ የድንበር ፡ ግጭት ፡ ጦርነት ፡ ያስከትላል
7. የ---ምልክት ፡ ነው. Those black clouds mean rain. ያ ፡ ከባድ ፡ ደመና ፡ የዝናም ፡ ምልክት ፡ ነው
8. ትርጉም ፡ ሊኖረው ፡ ቻለ. One word often means several things. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ብዙ ፡ ትርጉም ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል
9. ትርጉም ፡ ነው. What do those signs mean? እነዚያ ፡ ምልክቶች ፡ ትርጉማቸው ፡ ምንድነው ?
10. ትርጉም ፡ ሰጠ. The dictionary tells you what words mean. መዝገበ ፡ ቃላት ፡ የቃላትን ፡ ትርጉም ፡ ይሰጣል

*I am sorry I offended her; I really did not mean any harm. ስላስቀየምኳት ፡ አዝናለሁ ፤ በእርግጥ ፡ ክፋት ፡ አስቤ ፡ አልነበረም

**mean a lot** ትልቅ ፡ ነገር ፡ ነው
His friendship means a lot to me. የርሱ ፡ ጓደኝነት ፡ ለኔ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ነው

**mean business** የምሩን ፡ ነው
When you say you'll fight, do you mean business? እጣላለሁ ፡ ስትል ፡ የምርህን ፡ ነው ?

**mean everything**
*Money means everything to him. ገንዘብ ፡ ነፍሱ ፡ ነው

**mean nothing** ከምንም ፡ አይቈጥረውም ፤ ምንም ፡ አይደለም
The high cost of living means nothing to some people. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የኑሮን ፡ መወደድ ፡ ከምንም ፡ አይቈጥሩትም
It means nothing to me. ለኔ ፡ ምንም ፡ አይደለም

**meant to be**
*Is this number meant to be a one or a seven? ይህ ፡ ቁጥር ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ሰባት ?

**mean to say** ማለቱ ፡ ነው
Do you mean to say you saw everything? ሁሉንም ፡ ነገር ፡ አይቻለሁ ፡ ማለትህ ፡ ነው ?

**mean well**
*When he punishes his child, I know he means well. ልጁን ፡ ሲቀጣ ፡ በጥሩ ፡ መንፈስ ፡ መሆኑን ፡ አውቃለሁ

**not mean much** ዋጋ ፡ የለውም
His promising to pay you back later doesn't mean much. ሌላ ፡ ጊዜ ፡ እከፍላለሁ ፡ ማለቱ ፡ ዋጋ ፡ የለውም

**mean** (n.)
1. አማካኝ ፡ ሐሳብ. We must seek the mean between the two extremes. ለሁለቱ ፡ የተራራቁ ፡ ሐሳቦች ፡ አማካኝን ፡ ሐሳብ ፡ መፈለግ ፡ አለብን
2. አማካይ. Gray is the mean between black and white. የጥቁርና ፡ የነጭ ፡ ቀለም ፡ አማካይ ፡ ግራጫ ፡ ነው

**means**
1. መንገድ. We won the game by fair means. ጨዋታውን ፡ ያሸነፍነው ፡ በትክክለኛ ፡ መንገድ ፡ ነው
2. ዐቅም. He doesn't have the means to do it. ያንን ፡ ለመሥራት ፡ ዐቅም ፡ የለውም
He lives beyond his means. ከቅሙ ፡ በላይ ፡ ይኖራል
*He uses paper as a means for sweeping up the dust. አቧራውን ፡ በወረቀት ፡ ይጠርጋል

**means to an end**
It was just a means to an end. ይህ ፡ ከግቡ ፡ ለመድረስ ፡ የሚረዳ ፡ ነገር ፡ ነው

**by all means** በምንም ፡ ዓይነት ፡ ቢሆን ፡ በምንም ፡ አኳኋን
By all means take the job! በምንም ፡ ዓይነት ፡ ቢሆን ፡ ሥራውን ፡ ተቀበል
Avoid that by all means! በምንም ፡ አኳኋን ፡ ያንን ፡ አስወግደው

**(not) by any means** ምንም + negative verb
He was not surprised at the news by any means. በወሬው ፡ ምንም ፡ አልተደነቀም

**by means of**
1. በ. You can regulate it by means of a screw. በቅርንፉድ ፡ ምስማር ፡ ልታስተካክለው ፡ ትችላለህ
2. በ - - አማካይነት. Among the deaf and dumb, communication is carried on by means of the sign alphabet. ደንቆሮና ፡ ድዳ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሐሳብ ፡ የሚለዋወጡት ፡ በጣት ፡ ምልክት ፡ አማካይነት ፡ ነው

**by no means**
1. በምንም ፡ ዓይነት + (negative verb). By no means will I allow you to do what you planned. ያቀድከውን ፡ እንድትሠራ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ አልፈቅድልህም
2. በፍጹም + (negative verb). He is by no means stupid. በፍጹም ፡ ደደብ ፡ አይደለም

**man of means** ባለጸጋ
He is a man of means; he can afford to pay more than other people. ባለጸጋ ፡ ስለሆነ ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ይበልጥ ፡ ሊከፍል ፡ ይችላል
[See also 'foul, ways']

## mean (adj.)

1. ወራዳ. His mean thoughts are unworthy of a person who is a priest. ወራዳ ፡ አስተሳሰቡ ፡ ቄስ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ተገቢ ፡ አይደለም
2. (= noun) ወራዳነት. It is mean of him to treat you like that. አንተን ፡ እንደዚህ ፡ ማድረጉ ፡ ወራዳነቱ ፡ ነው
3. አስከፊ. His mean remarks lost him many friends. አስከፊ ፡ አስተያየቱ ፡ ከብዙ ፡ ጓደኞች ፡ አጣላው
4. መሀከለኛ. What is the mean temperature of Addis Ababa? የአዲስ ፡ አበባ ፡ መሀከለኛ ፡ ሙቀት ፡ ስንት ፡ ነው ?
5. ማእከላይ. The mean number between 3 and 9 is 6. የሦስትና ፡ የዘጠኝ ፡ ማእከላይ ፡ ቁጥር ፡ ስድስት ፡ ነው
6. ስግብግብ. A miser is mean about money. ጨቅ ፡ ለገንዘብ ፡ ስግብግብ ፡ ነው
7. ደሳሳ. He lives in a mean, little house. በትንሽ ፡ ደሳሳ ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል

**no mean** በዕውቀቱ ፡ ከፍተኛ
He is no mean scholar, and everyone knows it. በዕውቀቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ምሁር ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ ያውቀዋል

**of mean birth** ከድኻ ፡ የተወለደ
This boy is of mean birth. ይህ ፡ ልጅ ፡ ከድኻ ፡ የተወለደ ፡ ነው

**of mean quality** መናኛ
He wears clothes of mean quality. መናኛ ፡ ልብስ ፡ ይለብሳል
[See also 'trick']

## meander

1. እየተጥመለመለ ፡ ፈሰሰ. The river meanders across the flat plain. ወንዙ ፡ ለጥ ፡ ባለው ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ እየተጥመለመለ ፡ ይፈሳል
2. ተንጐራደደ. We meandered through the park. በመናፈሻው ፡ ውስጥ ፡ ተንጐራደድን

## meaning

1. ፍች. This word has several meanings. ይህ ፡ ቃል ፡ ብዙ ፡ ፍች ፡ አለው
2. ትርጉም. What is the meaning of life? የመኖር ፡ ትርጉሙ ፡ ምንድነው ?
*He does not know the meaning of fear. ፍርሃት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ አያውቅም

## meaningful

1. ተገቢ. The choice of Amharic as the language of instruction was a meaningful decision. አማርኛን ፡ ለማስተማሪያ ፡ ቋንቋነት ፡ መምረጥ ፡ ተገቢ ፡ ውሳኔ ፡ ነበር
2. ሙሉ ፡ ስሜት ፡ የሚሰጥ. The teacher asked the students to make up meaningful sentences. መምህሩ ፡ ሙሉ ፡ ስሜት ፡ የሚሰጡ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮች ፡ እንዲሠሩ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ጠየቀ
3. (= adv.) በልዩ ፡ ስሜት. She gave me a meaningful look. በልዩ ፡ ስሜት ፡ ተመለከተችኝ

## meaningless

1. ትርጉም ፡ የሌለው. His meaningless gestures showed that he was dazed by the blow. ትርጉም ፡ የሌለው ፡ እንቅስቃሴው ፡ በምቱ ፡ የፈዘዘ ፡ መሆኑን ፡ አመለከተ
2. ዋጋ ፡ የሌለው. Most scientists never do meaningless research. ብዙ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ጥናት ፡ ፈጽሞ ፡ አያደርጉም

**be meaningless** ትርጉም ፡ አልሰጠም
The argot of thieves is meaningless to other people. የሌቦች ፡ ልዩ ፡ ንግግር ፡ ለሌሎች ፡ ትርጉም ፡ አይሰጥም

**meantime** (n.), **in the ~**

1. በመሀሉ. The police were busy fighting the fire. In the meantime, the criminal escaped from jail. ፖሊሶቹ ፡ እሳቱን ፡ በመከላከል ፡ ይጣደፉ ፡ ነበር ፤ በመሀሉ ፡ ወንጀለኛው ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ አመለጠ
2. እስከዚያ ፡ ድረስ. In the meantime, I'll just have to wait. እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ መጠበቅ ፡ አለብኝ

**for the meantime** ለጊዜው
I'll do as I've always done, for the meantime. ለጊዜው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳደረግሁት ፡ አደርጋለሁ

**meanwhile** እስከዚያ ፡ ድረስ ፤ እስከዚያ
Meanwhile, it had gotten too late. እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ በጣም ፡ ዘግይቶ ፡ ነበር
We must wait for him here. Meanwhile, we can play cards. እሱን ፡ እዚሁ ፡ መጠበቅ ፡ አለብን ፤ እስከዚያ ፡ ከርታ ፡ እንጫወት

**measles** ኩፍኝ
He got the measles while in Harar. ሐረር ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ኩፍኝ ፡ ያዘው

**measly** አነስተኛ
He can't get along on his measly salary. በዛች ፡ ባነስተኛ ፡ ደሞዙ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም

**measure** (vt.)

1. ለካ. We'll have to measure the room before we buy the rug. ምንጣፉን ፡ ከመግዛታችን ፡ በፊት ፡ ክፍሉን ፡ መለካት ፡ አለብን
2. ፈተነ. The novel measures the skill of an author in writing long stories. ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ ደራሲው ፡ ረጅም ፡ ታሪኮች ፡ ለመጻፍ ፡ ያለውን ፡ ችሎታ ፡ ይፈትናል
3. መዘነ. You have to measure the importance of the issue before you make a decision. ውሳኔ ፡ ከመስጠትህ ፡ በፊት ፡ የጉዳዩን ፡ ጠቃሚነት ፡ መመዘን ፡ አለብህ

**measure** (vi.)

1. የ - - ልክ ፡ ነው. How much does he measure around the waist? የወገቡ ፡ ልክ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?
2. ረዘመ. The front of the building measures 20 feet. ሕንጻው ፡ ከፊት ፡ ለፊቱ ፡ ሃያ ፡ ጫማ ፡ ይረዝማል

**measure off** ከፋፈለ
They measured off the ground into small lots. መሬቱን ፡ በትንንሽ ፡ መደብ ፡ ከፋፈሉት

**measure out** መዘነ
He measured out three kilos of sugar. ሦስት ፡ ኪሎ ፡ ስኳር ፡ መዘነ

**measure up** ብቁ ፡ ሆነ
As an administrator, he couldn't quite measure up. ለአስተዳዳሪነት ፡ ብቁ ፡ አልነበረም

**measure up to** እንደ - - ፡ ሆነ
The exhibition did not measure up to that of last year. ኤግዚቢሽኑ ፡ እንዳለፈው ፡ ዓመት ፡ አልሆነም
*The party did not measure up to her expectations. ድግሱ ፡ ያሰበችውን ፡ ያህል ፡ አላገኘችውም

**measure** (n.)

1. ልክ. The cloth is cut according to measure. ጨርቁ ፡ የተቀደደው ፡ በልክ ፡ ነው
2. መለኪያ. An inch is a measure of length. ኢንች ፡ የርዝመት ፡ መለኪያ ፡ ነው
3. መስፈሪያ. The measure I used for beer disappeared. ጠላ ፡ ለመቅዳት ፡ የተጠቀምኩበት ፡ መስፈሪያ ፡ ጠፋ
4. ሕግ. Congress passed a measure for flood control. ምክር ፡ ቤት ፡ የውኃን ፡ መጥለቅለቅ ፡ ለማገድ ፡ የተዘጋጀን ፡ ሕግ ፡ አሳለፈ
5. እርምጃ. All necessary measures have been taken. አስፈላጊው ፡ እርምጃ ፡ ሁሉ ፡ ተወስዷል
6. ሐሳብ. The administration and the staff locked horns over the proposed measure. አስተዳደሩና ፡ ሠራተኞቹ ፡ በቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ ሳይስማሙ ፡ ቀሩ

**beyond measure** ከመጠን ፡ በላይ
His joy was beyond measure. ደስታው ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ነበር

**in large measure** አብዛኛውን ፡ ጊዜ
His success is due in large measure to hard work. ሊሳካለት ፡ የቻለው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጠንክሮ ፡ በመሥራቱ ፡ ነው

**in some measure** በመጠኑ
Their success was in some measure the result of careful preparation. በመጠኑ ፡ ውጤታቸው ፡ ሊያምር ፡ የቻለው ፡ በጥንቃቄ ፡ ከመዘጋጀታቸው ፡ የተነሣ ፡ ነው

**some measure** (= adv.) በመጠኑ
The government had, at that time, some measure of power. በዚያን ፡ ጊዜ ፡ መንግሥቱ ፡ በመጠኑ ፡ ኀይል ፡ ነበረው

**take the measure** ለካ
Did you take the measure of the lot? መሬቱን ፡ ለክተሃል ?
[See also 'defense']

**measured** (adj.) የተወሰነ
Drive over a measured mile to test your car's

speed! የመኪናህን ፡ ፍጥነት ፡ ለማወቅ ፡ ለተወሰነ ፡ ማይል ፡ ንዳ

**measured words** መርጦ ፡ የተናገራቸው ፡ ቃላት
The speaker's measured words brought applause. ተናጋሪው ፡ መርጦ ፡ የተናገራቸው ፡ ቃላት ፡ አድናቆትን ፡ አተረፉ

**with measured steps** በተመጠነ ፡ የዝግታ ፡ እርምጃ
The funeral cortege walked with measured steps. ለቀስተኛው ፡ በተመጠነ ፡ የዝግታ ፡ እርምጃ ፡ ተጓዘ

**measurements** ልክ
Her measurements are 36 — 24 — 38. የደ ፡ ልክ ፡ ደረት ፡ ፴፮ ፣ ወገብ ፡ ፳፬ ፣ ዳሌ ፴፰ ፡ ነው

**meat**
1. ሥጋ. He won't eat raw meat. ጥሬ ፡ ሥጋ ፡ አይበላም
The meat of the nut is tasty. የለውዙ ፡ ሥጋ ፡ ጣፋጭ ፡ ነው
2. ፍሬ ፡ ነገር. The meat of the book is its description of 18th century Ethiopia. የመጽሐፉ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የነበረችበትን ፡ የሚገልጽ ፡ ነው
[See also 'lean']

**meaty**
1. ሥጋ ፡ የበዛበት. Meaty broth is given to sick people. ሥጋ ፡ የበዛበት ፡ መረቅ ፡ ለበሽተኞች ፡ ይሰጣል
2. ቁም ፡ ነገር ፡ የተሞላ. His meaty speeches are listened to with great attention. ቁም ፡ ነገር ፡ የተሞላ ፡ ንግግሩን ፡ በጸጥታ ፡ አዳመጡ

**mechanic** መካኒክ
I need a mechanic to fix my car. መኪናዬን ፡ የሚሠራልኝ ፡ መካኒክ ፡ እፈልጋለሁ

**mechanical**
1. አውቶማቲክ. Some mechanical device opens the door. በሩ ፡ የሚከፈተው ፡ ባንድ ፡ አውቶማቲክ ፡ መሣሪያ ፡ ነው
2. የሞተር. A mechanical failure caused the plane to crash. አውሮፕላኑ ፡ ወድቆ ፡ ሊሰባበር ፡ የቻለው ፡ ከሞተሩ ፡ መበላሸት ፡ የተነሣ ፡ ነው
3. ደረቅ. His reading is very mechanical. አነባበቡ ፡ ደረቅ ፡ ነው

**mechanics** [ስለ ፡ መሣሪያ ፡ እንቅስቃሴና ፡ ኀይል ፡ የሚገልጽ ፡ ሳይንስ]

**mechanism** መሣሪያ
A pulley is a simple mechanism. መዘውር ፡ ቀላል ፡ መሣሪያ ፡ ነው
*Sand in the mechanism will stop a watch. አሸዋ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ከገባ ፡ ሰዓቱን ፡ ያቆመዋል
*The bones and muscles are parts of the mechanism of the body. አጥንቶችና ፡ ጡንቻዎች ፡ ያካል ፡ ክፍሎች ፡ ናቸው

**mechanize** በዘመናዊ ፡ መሣሪያ ፡ አካሄደ
We need to mechanize the gold mines. የወርቁን ፡ ማዕድኖች ፡ በዘመናዊ ፡ መሣሪያ ፡ ማካሄድ ፡ አለብን

**medal** ሜዳይ ፣ ኒሻን
He received a medal for bravery. የጀግንነት ፡ ሜዳይ ፡ (ኒሻን) ፡ አገኘ

**meddle** ገባ ፣ ጣልቃ ፡ ገባ
He likes to meddle in other people's business. በሌላ ፡ ሰው ፡ ጉዳይ ፡ መግባት ፡ (ጣልቃ ፡ መግባት) ፡ ይወዳል

**meddlesome** የእርጎ ፡ ዝንብ
His meddlesome wife is into everything he does. የእርጎ ፡ ዝንብ ፡ የሆነችው ፡ ሚስቱ ፡ እሱ ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ሁሉ ፡ ጥልቅ ፡ ትላለች

**media** ዘዴዎች
Radio is one of the news media. ራዲዮ ፡ ከወሬ ፡ ማሰራጫ ፡ ዘዴዎች ፡ አንዱ ፡ ነው

**medial** መሀከለኛ
The medial section is 15 cm. wide. የመሀከለኛው ፡ ክፍል ፡ ስፋት ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ሳንቲሜትር ፡ ነው

**median** አማካይ ፡ ቁጥር
The median of 1, 3, 5, 8, 9 is 5. የ፩ ፣ ፫ ፣ ፭ ፣ ፰ ፣ ፱ ፡ አማካይ ፡ ቁጥር ፡ ፭ ፡ ነው

**mediate** በአስታራቂነት ፡ ገባ
Sweden will mediate in the dispute between the two countries. ስዊድን ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ በተፈጠረው ፡ ጭቅጭቅ ፡ በአስታራቂነት ፡ ትገባለች

**mediator** አስታራቂ
The mediator discussed the issue at length with both sides. አስታራቂው ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ከሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ጋር ፡ በሰፊው ፡ ተነጋገረ

**medical**

1. የሕክምና. He is attending medical school. በሕክምና ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በመማር ፡ ላይ ፡ ነው
2. የሐኪምነት. Family tradition destined him for the medical profession. የሐኪምነት ፡ ሥራ ፡ የዘራቸው ፡ በመሆኑ ፡ እሱም ፡ ሐኪም ፡ ሆነ
3. የጤንነት. During the President's illness, a medical bulletin was issued daily. ፕሬዚዳንቱ ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ የጤንነታቸው ፡ መግለጫ ፡ በየቀኑ ፡ ይወጣ ፡ ነበር
4. የጤና. A medical examination is required of all entrants. አዲስ ፡ ገቢዎች ፡ ሁሉ ፡ የጤና ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግላቸው ፡ ያስፈልጋል

**medical supplies** መድኃኒት
We need medical supplies because of the earthquake. በመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ምክንያት ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ መድኃኒት ፡ ያስፈልገናል

**be under medical treatment** ታከመ
I am under medical treatment because of the car wreck. በመኪና ፡ አደጋ ፡ ለደረሰብኝ ፡ ጉዳት ፡ በመታከም ፡ ላይ ፡ ነኝ

**medicament** መድኃኒት
In the old days, they had few medicaments. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡ ጥቂት ፡ መድኃኒቶች ፡ ነበሯቸው

**medicate** ቀባ
The doctor medicated the wound with iodine. ሐኪሙ ፡ ቁስሉን ፡ አዮዲን ፡ ቀባው

**medicate oneself** መድኃኒት ፡ ወሰደ
It is often dangerous to medicate oneself without a doctor's advice. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሐኪም ፡ ሳያዝ ፡ መድኃኒት ፡ መውሰድ ፡ አደገኛ ፡ ነው

**be medicated** መድኃኒትነት ፡ አለው
These candies are medicated. ይህ ፡ ከረሜላ ፡ መድኃኒትነት ፡ አለው

**medication** መድኃኒት
I need some medication for my chapped lips. ለተሰነጣጠቀው ፡ ከንፈሬ ፡ መድኃኒት ፡ ያስፈልገኛል

**medicinal, ~ value** ፈዋሽነት
The medicinal value of this plant was discovered long ago. የዚህ ፡ ዕፅ ፡ ፈዋሽነት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**have a medicinal taste** መድኃኒት ፡ መድኃኒት ፡ አለ
This liquor has a medicinal taste. ይህ ፡ የአልኮል ፡ መጠጥ ፡ መድኃኒት ፡ መድኃኒት ፡ ይላል

**medicine**

1. መድኃኒት. This medicine tastes bitter. ይህ ፡ መድኃኒት ፡ ይመራል
2. ሕክምና. My daughter is studying medicine. ልጄ ፡ ሕክምና ፡ ታጠናለች

**medieval** የመካከለኛ ፡ ዘመን
This country has medieval habits. ይህ ፡ አገር ፡ የመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ጠባይ ፡ አለበት

**mediocre** ተራ
Despite the considerable research involved, the study is mediocre. ብዙ ፡ ጥናት ፡ የተደረገበት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ጽሑፉ ፡ ተራ ፡ ነው

**be mediocre**
*He is not an excellent student, just a mediocre one. ጉበዝ ፡ ተማሪ ፡ አይደለም ፤ ሆኖም ፡ ምንም ፡ አይል

**remain mediocre** ከምንም ፡ አይቈጠር
Even if we discount the irrelevant material, the thesis remains mediocre. የማይረባውን ፡ ጉዳይ ፡ እንኳ ፡ ከቁጥር ፡ ባናገባ ፡ ጹሑፉ ፡ ከምንም ፡ አይቈጠር

**meditate**

1. አወጣ ፡ አወረደ. The general was meditating on an attack. ጀኔራሉ ፡ ለማጥቃት ፡ ያወጣ ፡ ያወርድ ፡ ነበር
He meditated upon his misfortunes. ስለ ፡ መጥፎ ፡ ዕድሉ ፡ አወጣ ፡ አወረደ
2. አሰበ. He meditated revenge. ሊበቀል ፡ አሰበ
3. በአንክሮ ፡ አሰበ. Monks meditate on holy things for hours at a time. መነኰሴዎች ፡ ለብዙ ፡ ሰዓቶች ፡ ያለማቋረጥ ፡ ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ነገሮች ፡ በአንክሮ ፡ ያስባሉ

**medium** (mediums, or media), n. ዘዴ
Radio is a medium of communication. ሬዲዮ ፡ የመገናኛ ፡ ዘዴ ፡ ነው
*A temperature of 70° is a happy medium. 70° ዲስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መሀከለኛ ፡ሙቀት ፡ ነው

**through the medium of** በ
Vacant positions are made known through the medium of the press. ክፍት ፡ የሥራ ፡ ቦታዎች ፡ በጋዜጣ ፡ ላይ ፡ በማስታወቂያ ፡ ይወጣሉ

**medium** (adj.) መካከለኛ
He is of medium height. ቁመቱ ፡ መካከለኛ ፡ ነው

**medium-sized** መጠነኛ
It is a medium-sized business. መጠነኛ ፡ ንግድ ፡ ነው

**medley** ውጥንቅጥ
There is a medley of races in Hawaii. ሀዋዪ ፡ ውስጥ ፡ የዘር ፡ ውጥንቅጥ ፡ አለ

**meek** የዋህ
She is as meek as a dove. እንደ ፡ ርግብ ፡ የዋህ ፡
ናት

**be meek** ጠባዩ ፡ ለስላሳ ፡ ነው
His wife mistreats him because he is so meek.
ጠባዩ ፡ ለስላሳ ፡ ስለሆነ ፡ ሚስቱ ፡ ታሠቃየዋለች

**meet** (met), vt.
1. አገኘ. Did you meet him on the street?
መንገድ ፡ ነው ፡ ያገኘኸው ?
2. ተቀበለ. He met us with a smile. በፈገግታ ፡ ተ
ቀበለን
I must go to the railway station and meet my
mother. ወደ ፡ ባቡር ፡ ጣቢያ ፡ ሄጄ ፡ እናቴን ፡
መቀበል ፡ አለብኝ
3. ተዋወቀ. Pleased to meet you! ስለ ፡ ተዋወቅሁ
ህ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል
4. ከ - - ተዋወቀ. Have you met my sister? ከእኅ
ቴ ፡ ጋር ፡ ተዋውቀሃል ?
5. ፈጸመ ፤ ፈጸመ(ለት). They couldn't meet
their obligations. ግዳጃቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ አ
ልቻሉም
He met all my demands. የጠየቅሁትን ፡ ሁሉ ፡
ፈጸመልኝ
6. ከፈለ. He did not have enough money to
meet his bills. ያለበትን ፡ ሒሳብ ፡ ለመክፈል ፡ የ
ሚበቃ ፡ ገንዘብ ፡ አልነበረውም
7. ሸፈነ. I can barely meet my expenses.
ወጪዬን ፡ የምሸፍነው ፡ በችግር ፡ ነው
8. ተቋቋመ. We must modify our requirements
for admission to the university to meet the
new situation. አዲሱን ፡ ሁኔታ ፡ ለመቋቋም ፡ ለዩ
ኒቨርሲቲ ፡ መግቢያ ፡ የተደነገገውን ፡ ደንብ ፡
ማሻሻል ፡ አለብን
Whatever befalls them, they are ready to
meet it. የሚያጋጥማቸውን ፡ ሁሉ ፡ ሊቋቋሙ ፡
ተዘጋጅተዋል
*We met the boat at 2 o'clock. በስምንት ፡ ሰዓ
ት ፡ መርከቡ ፡ ሲመጣ ፡ እዚያ ፡ ነበርን

**meet** (vi.)
1. ተገናኘ. We meet once a week. በሳምንት ፡ አ
ንድ ፡ ጊዜ ፡ እንገናኛለን
He met with the President and spoke with him
for an hour. ከፕሬዚዳንቱ ፡ ጋር ፡ ተገናኝቶ ፡ አን
ድ ፡ ሰዓት ፡ አነጋገረው
The two ends don't meet. ሁለቱ ፡ ጫፎች ፡ አ
ይገናኙም
2. ስብሰባ ፡ አደረገ. The Senate will meet next
month. የሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በሚ
መጣው ፡ ወር ፡ ስብሰባ ፡ ያደርጋል
3. ተሰበሰበ. The UN General Assembly meets
tomorrow. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጠቅላላ ፡
ጉባኤ ፡ ነገ ፡ ይሰበሰባል
4. ተጋጠመ. The two teams met to play for
the African Cup. ሁለቱ ፡ ቡድኖች ፡ ለአፍሪካ ፡
ዋንጫ ፡ ተጋጠሙ

**be met** ሊፈጸም ፡ ቻለ ፤ ተፈጸመ
My demands are easily met. የጠየቅሁት ፡ በቀላ
ሉ ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል
The stipulations have not been met, so the
contract has been invalidated. በውሉ ፡ ውስጥ ፡
የተጠቀሱት ፡ ግዴታዎች ፡ ስላልተፈጸሙ ፡ ውሉ ፡
ፈርሷል

**meet halfway**
*I am willing to meet him halfway. እሱም ፡ ይ
ተው ፡ እኔም ፡ ልተው

**meet (one's) needs** አስፈለገው
They starved because they did not take enough
food to meet their needs. የሚያስፈልጋቸውን ፡
ምግብ ፡ ባለ ፡ መያዛቸው ፡ ተራቡ

**meet with** አጋጠመ(ው)
On his trip in the desert, he met with mis-
fortune and never returned. በበረሃው ፡ ሲጓዝ ፡
ባጋጠመው ፡ መጥፎ ፡ ዕድል ፡ ምክንያት ፡ እንደ
ወጣ ፡ ቀረ
The proposal met with unexpected opposition.
የቀረበው ፡ አስተያየት ፡ ያልታሰበ ፡ ተቃውሞ ፡
አጋጠመው

**meet with one's approval** በ - - ተስማማ
+Does this explanation meet with your ap-
proval? በዚህ ፡ ማብራሪያ ፡ ትስማማለህ ?

**make both ends meet** አብቃቃ
I am having difficulty on my salary making
both ends meet. ደሞዜን ፡ ማብቃቃት ፡ አቅቶ
ኛል
[See also 'death, disapproval, doom, end,
obligation, refusal, response, reverse']

**meeting** ስብሰባ
There were five hundred people at the meeting.
በስብሰባው ፡ ላይ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡
ነበሩ
*I had a chance meeting with a friend. ጓደኛዬን ፡
የማግኘት ፡ ዕድል ፡ አጋጠመኝ

**meeting place** የሚገናኙበት ፡ ስፍራ
We chose a central meeting place. የምንገናኝበ
ትን ፡ ማእከላዊ ፡ ስፍራ ፡ መረጥን

**arrange for a meeting** እንዲገናኙ ፡ አደረገ
I arranged for a meeting of the two. ሁለቱ ፡ እ
ንዲገናኙ ፡ አደረግሁ
[See also 'order, summit']

**melancholy** (n.) ሐዘንና ፡ ትካዜ
He suffers from melancholy. በሐዘንና ፡ በትካዜ ፡ ተውጧል

**melancholy** (adj.) ሐዘንና ፡ ትካዜ ፡ ያጠቃው
Hamlet was a melancholy person. ሃምሌት ፡ ሐዘንና ፡ ትካዜ ፡ ያጠቃው ፡ ሰው ፡ ነበር

**mellow** (vt.) አለሰለሰ
Sorrow mellowed his nature. ሐዘን ፡ ጠባዩን ፡ አለሰለሰው

**mellow** (vi.) በሰለ
The mead has mellowed for two years. ጠጁ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በመከረመ ፡ በስሏል

**mellow** (adj.)
1. ረጋ ፡ ያለ. His father is a mellow old gentleman. አባቱ ፡ ረጋ ፡ ያሉ ፡ አዛውንት ፡ ናቸው
2. ለዛ ፡ ያለ. An expensive violin has a mellow tone. ውድ ፡ የሆነ ፡ ቫዮሊን ፡ ለዛ ፡ ያለው ፡ ድምፅ ፡ አለው
3. ጥዑም. This is a mellow wine. ይህ ፡ ጥዑም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ነው

**be mellow** በሰለ
If mangoes are not mellow, they have a sour taste. ማንጎ ፡ ካልበሰለ ፡ ይጎመዝዛል

**melodious** ለዛ ፡ ያለ
The priest's melodious voice makes the service beautiful. የቄሱ ፡ ለዛ ፡ ያለው ፡ ድምፅ ፡ ቅዳሴውን ፡ ያሳምራል

**melody** (melodies)
1. ዘፈን. We sang a familiar melody. አንድ ፡ የምናውቀውን ፡ ዘፈን ፡ ዘፈንን
2. ቃና ፡ ያለው ፡ ሙዚቃ. I heard him playing a wonderful melody. ግሩም ፡ ቃና ፡ ያለው ፡ ሙዚቃ ፡ ሲጫወት ፡ ሰማሁት

**melon** ሐብሐብ

**melt** (vt.)
1. አነጠረ. The good housewife gets up in the morning and melts butter. ባለሙያይቱ ፡ የቤት ፡ እመቤት ፡ ጧት ፡ ተነሥታ ፡ ቅቤ ፡ ታነጥራለች
He is melting gold in a melting pot. በማቅለጫው ፡ ውስጥ ፡ ወርቅ ፡ ያነጥራል
2. አሟሟ. He melted the sugar in hot water. ስኳሩን ፡ በሙቅ ፡ ውኃ ፡ አሟሟው
3. ውኃ ፡ አደረገ. Tears melt my heart. ለቅሶ ፡ ልቤን ፡ ውኃ ፡ ያደርገዋል

**melt** (vi.)
1. ሟሟ. Sugar melts in tea. ስኳር ፡ በሻይ ፡ ውስጥ ፡ ይሟሟል
The candy melted in his mouth. ከረሜላው ፡ አፉ ፡ ውስጥ ፡ ሟሟ
2. ቀለጠ. The butter melts easily on the fire. ቅቤ ፡ እሳት ፡ ሲነካው ፡ በቀላሉ ፡ ይቀልጣል
3. ልቡ ፡ ውኃ ፡ ሆነ. I melted at her smile. ፈገግ ፡ ስትል ፡ ልቤ ፡ ውኃ ፡ ሆነ

**melt away**
1. ተገፈፈ. The clouds melted away, and the sun came out. ደመናው ፡ ተገፈፈና ፡ ፀሐይ ፡ ወጣች
2. ጠፋ. His fear melted away. ፍርሃቱ ፡ ጠፋ

**melting pot** ማቅለጫ
He is melting gold in a melting pot. በማቅለጫው ፡ ውስጥ ፡ ወርቅ ፡ ያነጥራል

**member**
1. አባል. Are you a member of this club? የዚህ ፡ ክበብ ፡ አባል ፡ ነህ ?
He is a member of parliament. የፓርላማ ፡ አባል ፡ ነው
2. ከ - - አንዱ. A member of my family came to her wedding. ከቤተ ፡ ሰቦቼ ፡ አንዱ ፡ ለሰርጓ ፡ መጣ
3. ተከታይ. Christian practices have occasionally been adopted by members of other religions. አንዳንድ ፡ የክርስቲያን ፡ ምግባሮች ፡ በሌሎች ፡ እምነት ፡ ተከታዮች ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነት ፡ አግኝተዋል
4. ባልደረባ. The members of the company have to report to their superior officer. የጓዱ ፡ ባልደረቦች ፡ ከበላይ ፡ መኰንኑ ፡ ዘንድ ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው
5. እጅና ፡ እግር. All his members were covered by a plaster cast. እጅና ፡ እግሩ ፡ በጀሶ ፡ ተሸፍኗል

**membership** (n.)
1. አባልነት. Membership in the organization costs $3.00 a year. በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ላባልነት ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በዓመት ፡ ሦስት ፡ ብር ፡ ነው
2. የአባሎች ፡ ቁጥር. Our membership is down to less than one hundred. የአባሎቻችን ፡ ቁጥር ፡ ከመቶ ፡ በታች ፡ ሆኗል

**membership** (adj.) የአባልነት
I don't have my membership card on me. የአባልነት ፡ መታወቂያ ፡ ወረቀቴን ፡ አልያዝኩም

**memento**
1. መታሰቢያ. He gave me a ring as a memento of our friendship. ለጓደኝነታችን ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ቀለበት ፡ ሰጠኝ
2. ማስታወሻ. He has some mementos of the

Italian occupation. ስለ ፡ ኢጣልያን ፡ ወረራ ፡ አንዳንድ ፡ ማስታወሻ ፡ ይዟል
*He wrote a book dealing with mementos of the past. የጥንት ፡ ነገሮችን ፡ የሚያወሳ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፏል

**memoirs**
1. የሕይወት ፡ ታሪክ. Winston Churchil wrote his memoirs. ዊንስተን ፡ ቸርችል ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩን ፡ ጻፈ
2. ትዝታ. He wrote his father's memoirs. አባቱ ፡ ያላቸውን ፡ ትዝታ ፡ ጽፏል

**memorabilia** ትዝታ
His book is filled with memorabilia of the war years. መጽሐፉ ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ትዝታ ፡ የተሞላ ፡ ነው

**memorable** የማይረሳ
This was a memorable day. ይህ ፡ የማይረሳ ፡ ቀን ፡ ነበር

**memorandum** (memorandums, or memoranda) ማስታወሻ
Here is a memorandum from the Foreign Ministry. ከውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ የመጣ ፡ ማስታወሻ ፡ ይኸው

**memorial** (n.) መታሰቢያ ፡ ሐውልት
At Siddist Kilo, there is a memoral to the Yekatit massacre. ስድስት ፡ ኪሎ ፡ ላይ ፡ ለየካቲት ፡ እልቂት ፡ የቆመ ፡ መታሰቢያ ፡ ሐውልት ፡ አለ

**memorial service** የመታሰቢያ ፡ ጸሎት ፤ ተዝካር
They are holding a memorial service for my father. ላባቴ ፡ የመታሰቢያ ፡ ጸሎት ፡ ያደርጋሉ
Ethiopian Christians celebrate a memorial service on the fortieth day after burial. የኢትዮጵያ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሰው ፡ በሞተ ፡ ባርባኛው ፡ ቀን ፡ ተዝካር ፡ ያወጣሉ

**memorize** በቃል ፡ አጠና
I have to memorize my speech. ንግግሬን ፡ በቃል ፡ ማጥናት ፡ አለብኝ

**memory** (memories)
1. ትዝታ. I have pleasant memories of this town. ይህ ፡ ከተማ ፡ ጥሩ ፡ ትዝታ ፡ ቀርጾብኛል
His memory will serve as an inspiration to posterity. ትዝታው ፡ የትውልድን ፡ መንፈስ ፡ ያነቃቃል
2. ማስታወስ. He suffers from an occasional lapse of memory. አንዳንዴ ፡ የማስታወስ ፡ ችግር ፡ አለበት
3. የማስታወስ ፡ ችሎታ. My memory is not what it used to be. የማስታወስ ፡ ችሎታዬ ፡ እንደ ፡ ድሮው ፡ አይደለም

**from memory** በቃሉ
He recited the poem from memory. ግጥሙን ፡ በቃሉ ፡ ወጣው

**have a good memory**
*He has a good memory for names. ስም ፡ የማስታወስ ፡ ጥሩ ፡ ችሎታ ፡ አለው

**have a poor memory**
*I have a poor memory for names. ስም ፡ ማስታወስ ፡ አይሆንልኝም

**honor the memory**
*We honor the memory of our heroes. የጀግኖቻችንን ፡ መታሰቢያ ፡ እናከብራለን

**in memory of** ለ - - - መታሰቢያ
The inscription reads: "In memory of ...". የተቀረጸው ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ « ለ - - - መታሰቢያ »

**retain a memory of** አስታወሰ
She retains a clear memory of her childhood. የልጅነት ፡ ጊዜዋን ፡ በደንብ ፡ ታስታውሳለች

**within one's memory** እሱ ፡ እንደሚያውቀው ፡ ከሆነ
This has been the hottest summer within my memory. እኔ ፡ እንደማውቀው ፡ ከሆነ ፡ የዘንድሮ ፡ በጋ ፡ ከመቼውም ፡ ይበልጥ ፡ ሞቃት ፡ ነው
[See also 'lapse, lose, refresh, search']

**men,** see **man**

**menace** (v.) አሰጋ
War menaces the entire world. ጦርነት ፡ መላውን ፡ ዓለም ፡ ያሰጋዋል

**menace** (n.)
1. ዛቻ. The radio broadcast a speech filled with menace. ዛቻ ፡ የሞላበት ፡ ንግግር ፡ በራዲዮ ፡ ተላለፈ
2. ጠንቅ. He is a menace to society. ለኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ ጠንቅ ፡ ነው

**mend**
1. ጠቀመ. When will you mend my shirts? ሸሚዜን ፡ መቼ ፡ ትጠቅምልኛለህ ?
2. ጠገነ. The workers are mending the road. ሠራተኞቹ ፡ መንገዱን ፡ በመጠገን ፡ ላይ ፡ ናቸው
3. አሻሻለ. You'll have to mend your ways. ጠባይህን ፡ ማሻሻል ፡ አለብህ

**mendacious** ዋሾ
The mendacious old man cheated me again. ዋሾው ፡ ሽማግሌ ፡ እንደገና ፡ አታለለኝ

**mendacity** ዋሾነት
His mendacity is well known, so don't trust him. ዋሾነቱ ፡ የታወቀ ፡ ስለሆነ ፡ አትመነው

**mendicant** ለማኝ
Mendicants are forbidden to sit in front of our hotel. ለማኞች ፡ ሆቴላችን ፡ ደጃፍ ፡ እንዳይ ቀመጡ ፡ ተከልክለዋል

**mendicity** መለመን
Mendicity is not allowed in the streets. መንገድ ፡ ላይ ፡ መለመን ፡ አይፈቀድም

**menial** ዝቅተኛ
She spends a lot of time on menial tasks such as washing dishes. ሳሕን ፡ ማጠብን ፡ በመሳሰሉ ፡ ዝቅተኛ ፡ ሥራዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ታጠፋለች

**menses**
She is having her menses. ጽጌ ፡ ነች

**menstruate** አደፈች
Women menstruate from the time they become sexually mature. ሴቶች ፡ ለዐቅመ ፡ ሔዋን ፡ ከ ደረሱበት ፡ ጀምሮ ፡ ያድፋሉ

**menstruation** አደፍ
Menstruation occurs once a month. ሴት ፡ ልጅ ፡ አደፍ ፡ የሚታያት ፡ በወር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው

**mental**
1. የአእምሮ. Her illness is mental, not physical. በሽታዋ ፡ የአእምሮ ፡ እንጂ ፡ የሰውነት ፡ አይደለም
Mental patients must be treated like those who suffer from diseases of the flesh. የአእም ሮ ፡ ሕመምተኞች ፡ እንደ ፡ አካል ፡ በሽተኞ ች ፡ መታየት ፡ አለባቸው
2. የእብዶች. A mental hospital treats the insane. የእብዶች ፡ ሆስፒታል ፡ የአእምሮ ፡ ሕ መምተኞችን ፡ ያክማል

**mental institution** የአእምሮ ፡ በሽተኞች ፡ ሐኪ ም ፡ ቤት
One of the inmates of the mental institution escaped. የአእምሮ ፡ በሽተኞች ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ነዋሪ ፡ ከሆኑት ፡ በሽተኞች ፡ አንዱ ፡ አ መለጠ

**mentality** (mentalities)
1. አስተሳሰብ. His mentality is that of a five year old. አስተሳሰቡ ፡ እንደ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነው
2. የአእምሮ ፡ ችሎታ. He is a person of average mentality. መካከለኛ ፡ የአእምሮ ፡ ችሎታ ፡ ያለ ው ፡ ሰው ፡ ነው

**mentally**
*He is mentally ill. የአእምሮ ፡ በሽተኛ ፡ ነው
*He is strong mentally. አእምሮው ፡ ንቁ ፡ ነው
[See also 'deficient, disturbed, retard, unbalanced']

**mention** (v.)
1. ተናገረ. He didn't mention the price. ዋጋውን ፡ አልተናገረም
2. አነሣ ፣ ጠራ. I heard his name mentioned. ስሙን ፡ ሲያነሡ ፡ ሰማሁ
Mention my name, and you will be admitted. ስሜን ፡ ጥራ ፡ ያስገቡሃል
3. ጠቀሰ. I would also like to mention that … . በተጨማሪ ፡ ልጠቅሰው ፡ የምፈልገው

**don't mention it!** ምንም ፡ አይደል
Thank you, Mrs. Graham. Don't mention it! እግዜር ፡ ይስጥልኝ ፡ ሚሲስ ፡ ግራሃም ፣ ምንም ፡ አይደል !

**not to mention** -ማ ፡ ተወው
I enjoyed the meal, not to mention the conversation. ምግቡ ፡ በጣም ፡ አስደሰተኝ ፣ ጨዋታ ውንማ ፡ ተወው
*We are too busy to take a holiday, not to mention the fact that we can't afford it. ወጪው ን ፡ ከለመቻላችንም ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ስለሚበዛብን ፡ ለዕረፍት ፡ ለመሄድ ፡ አንችልም

**mention** (n.) ማንሣት
Mention of the incident caused surprise. ነገ ሩን ፡ ማንሣቱ ፡ አስገረመን

**mention is given** ተጠቀሰ
A brief mention of the flood was given in the newspaper. ስለ ፡ ውኃው ፡ መጥለቅለቅ ፡ ጋዜጣ ው ፡ ውስጥ ፡ ባጭሩ ፡ ተጠቅሷል

**make mention** ጠቀሰ
He made mention of his coming to Ethiopia. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መምጣቱን ፡ ጠቀሰ

**receive honorable mention** ስሙ ፡ በክብር ፡ ተጠራ
He didn't win a prize, but received honorable mention. ሽልማት ፡ ባያገኝም ፡ ስሙ ፡ በክብር ፡ ተጠርቷል

**mentioned, above ~** ከላይ ፡ የተጠቀሰ
The above-mentioned people will not be admitted to class. ከላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ሰዎች ፡ ክፍል ፡ እንዲገቡ ፡ አይፈቀድላቸውም

**menu** የምግብ ፡ ዝርዝር
The waiter brought me the menu. አሳላፊው ፡ የ ምግብ ፡ ዝርዝር ፡ አቀረበልኝ

**mercantile** የንግድ
Mercantile law specifies how contracts must be drawn up. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ውል ፡ እንዴት ፡ መዋዋል ፡ እንደሚገባ ፡ ይወስናል

**mercenary** (mercenaries), n. ቅጥር ፡ ወታደር
The mercenaries deserted when they were not paid. ቅጥር ፡ ወታደሮቹ ፡ ደሞዝ ፡ ሳይከፈላቸው ፡ በቀረ ፡ ጊዜ ፡ ከዱ

**mercenary,** adj. (= adv.) ለገንዘብ ፡ ሲል
His mercenary reasons for helping the rich man were soon discovered. ሀብታሙን ፡ ሰው ፡ የሚረዳው ፡ ለገንዘብ ፡ ሲል ፡ መሆኑ ፡ ወዲያው ፡ ታወቀ

**merchandise** (v.) ነገደ
My father merchandises office furniture. አባቴ ፡ የቢሮ ፡ እቃ ፡ ይነግዳል

**merchandise** (n.) ሸቀጣ ፡ ሸቀጥ
The merchandise arrived in good order. ሸቀጣ ፡ ሸቀጡ ፡ በደኅና ፡ ሁኔታ ፡ ደርሷል

**merchant** (n.) ነጋዴ
The merchants live in a special quarter. ነጋዴዎቹ ፡ በተለየ ፡ ሰፈር ፡ ይኖራሉ

**merchant** (adj.) የንግድ
Ethiopia's merchant marine is still small. የኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ መርከቦች ፡ አሁንም ፡ ጥቂት ፡ ናቸው
[See also 'retail']

**(be) merciful** ራራ
The judge was merciful to the offender. ዳኛው ፡ ለጥፋተኛው ፡ ራራለት

**merciless** ጨካኝ
The people did not like the merciless ruler. ሕዝቡ ፡ ጨካኙን ፡ ገዢ ፡ አልወደደውም

**mercilessly** ያለ ፡ ርኅራኄ
He whipped the horse mercilessly. ፈረሱን ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ ገረፈው

**mercury** ባዜቃ
If you swallow mercury, you will get sick. ባዜቃ ፡ ከዋጥክ ፡ ትታመማለህ

**mercy** ምሕረት
He pleaded for mercy, but the judge sentenced him to death. ምሕረት ፡ እንዲደረግለት ፡ ለመነ ፤ ግን ፡ ዳኛው ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረደበት
He has no mercy. ምሕረት ፡ የለውም

**at the mercy of**
*He is at the mercy of his employer. ቀጣሪው ፡ እንዳሻው ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል

**have mercy on** ይቅር ፡ አለ
Have mercy on the poor sinner! ምስኪኑን ፡ ኀጢአተኛ ፡ ይቅር ፡ በለው

**show mercy** ምሕረት ፡ አደረገ
They showed mercy to the defeated enemy. ለተሸነፈው ፡ ጠላት ፡ ምሕረት ፡ አደረጉ

**mere,** adj. (= adv.) ብቻ
The mere thought of it disturbs me. ማሰቡ ፡ ብቻ ፡ ይረብሸኛል
The mere sight of a dog makes him afraid. ውሻ ፡ ማየቱ ፡ ብቻ ፡ ያስፈራዋል

**merely**
1. እንዲያው. I was merely joking. እንዲያው ፡ ቀልዴን ፡ ነበር
2. ዝም ፡ ብሎ. The police did nothing to stop the rioters, but merely looked on. ፖሊሶቹ ፡ ረብሸኞቹን ፡ ለማቆም ፡ እርምጃ ፡ ሳይወስዱ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ይመለከቷቸው ፡ ነበር

**merest** በጣም ፡ አነስተኛ
The merest trifle upsets him. በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነገር ፡ ያበሳጨዋል

**merge** (vt.) አዋሐደ
The big company merged various small businesses. ትልቁ ፡ ኩባንያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አነስተኛ ፡ ንግዶችን ፡ አዋሐደ

**merge** (vi.)
1. ተዋሐደ. The two companies merged into one. ሁለቱ ፡ ኩባንያዎች ፡ ተዋሐዱ
2. ተቀላቀለ. The blue slowly merges into the green. ሰማያዊው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ከአረንጓዴው ፡ ጋር ፡ ይቀላቀላል
3. ተጋጠመ. Traffic merges here. መንገዱ ፡ እዚህ ፡ ይጋጠማል

**meridian** [ደቡባዊውንና ፡ ሰሜናዊውን ፡ ዋልታ ፡ ያገናኛል ፡ የሚባለው ፡ መሥመር ፡ « ሜሪዲየን » ፡ ይባላል]

**merit** (v.) ተገባ(ው)
+I think he merits a raise. የደሞዝ ፡ ጭማሪ ፡ የሚገባው ፡ ይመስለኛል

**merit** (n.), **merits**
1. መልካም ፡ ሥራ. His merits have been widely recognized. መልካም ፡ ሥራው ፡ በሰፊው ፡ ታውቆለታል
2. መልካም ፡ ተግባር. His vanity detracts from his merits. ግብዝነቱ ፡ መልካም ፡ ተግባሩን ፡ ይቀንስበታል
3. ችሎታ. His merits as a teacher have been

recognized. ያስተማሪነት ፡ ችሎታው ፡ ታውቆለታል
Promotion should be made on the basis of merit. የሥራ ፡ እድገት ፡ በችሎታ ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ አለበት
4. ሁኔታ. Judge the case on its merits, not on your feelings! ጉዳዩን ፡ እንደ ፡ ሁኔታው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ስሜትህ ፡ አትፍረድ
*There isn't much merit in giving away things you don't want. የማትፈልገውን ፡ ነገር ፡ መስጠት ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የሚያስመሰግን ፡ አይደለም

**meritorious** አስመስጋኝ ፤ ዝና ፡ የሚያተርፍ
He received a medal for meritorious conduct. ባስመስጋኝ ፡ ሥራው ፡ ሜዳይ ፡ ተሸለመ
The saving of lives is a meritorious action. የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ማዳን ፡ ዝና ፡ የሚያተርፍ ፡ ተግባር ፡ ነው

**merriment** ቡረቃ
The children's merriment annoyed the old man. የልጆቹ ፡ ቡረቃ ፡ ሽማግሌውን ፡ አበሳጨው

**merry** ደስተኛ
She is always merry. ሁልጊዜ ፡ ደስተኛ ፡ ናት
**Merry Christmas!** እንኳን ፡ ለብርሃነ ፡ ልደቱ ፡ አደረሳችሁ!
**make merry** ፈንጠዝያ ፡ አደረገ
They were making merry during the holidays. በበዓሉ ፡ ጊዜ ፡ ፈንጠዝያ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር
[See also 'vein']

**merry-go-round** [በሞተር ፡ የሚዞር ፡ ክብ ፡ የሆነ ፡ መድረክ ፤ በላዩ ፡ ላይ ፡ አግዳሚ ፡ ወንበርችና ፡ ከዕንጨት ፡ የተቀረጹ ፡ ፈረሶች ፡ ያሉበት]

**merrymaking** ፈንጠዝያ
Sounds of merrymaking came from the house. የፈንጠዝያ ፡ ድምፅ ፡ ከቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ይሰማል

**mesh** (v.) ተገጣጠመ
The teeth of a zipper mesh. የዚፐር ፡ ጥርስ ፡ ይገጣጠማል

**mesh** (n.) ቀዳዳ
The net has five-inch meshes. መረቡ ፡ አምስት ፡ ኢንች ፡ ስፋት ፡ ያላቸው ፡ ቀዳዳዎች ፡ አሉት

**mess** (v.), ~ **around** ተንጐዳጐደ
She likes to mess around at home. እቤት ፡ ውስጥ ፡ መንጐዳጐድ ፡ ትወዳለች

**mess up**
1. አዘበራረቀ. Who messed up the papers on my desk? ጠረጴዛዬ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ወረቀት ፡ ማን ፡ አዘበራረቀው?
2. አጨማለቀ. Don't mess up the floor with your wet feet! በርጥብ ፡ እግርህ ፡ ወለሉን ፡ አታጨማልቅ
3. አቃወሰ(በት). The late arrival of the train messed up our plans. የባቡሩ ፡ ዘግይቶ ፡ መድረስ ፡ ሐሳባችንን ፡ ሁሉ ፡ አቃወሰብን

**mess** (n.)
1. ምግብ ፡ ቤት. Common soldiers cannot eat at the officers' mess. ተራ ፡ ወታደሮች ፡ መኰንኖች ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እንዲበሉ ፡ አይፈቀድላቸውም
2. ጣጣ. Cheating got him into a mess. ቅጥፈት ፡ ጣጣ ፡ ውስጥ ፡ ከተተው
3. ቆሻሻ. Call the janitor and have him clean up the mess! ጠራጊውን ፡ ጥራና ፡ ቆሻሻ ፡ እንዲጠርግ ፡ ንገረው
4. ምስቅልቅል. The house is in an awful mess. ቤቱ ፡ ምስቅልቅሉ ፡ ወጥቷል
5. ውጥንቅጥ. I can't find anything in this mess. በዚህ ፡ ውጥንቅጥ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ላገኝ ፡ አልችልም
6. ዝብርቅርቅ. He burdened me with the responsibility of cleaning up the mess. ይህን ፡ ዝብርቅርቅ ፡ እንዳስተካክል ፡ ኀላፊነት ፡ ጫነብኝ
7. ዝርክርክ. She's a mess! ዝርክርክ ፡ ነች
**make an awful mess** አዝረከረከ
When the baby got into the flour, he made an awful mess. ልጁ ፡ ዱቄቱ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ አዝረከረከው

**message** መልእክት
Is there a message for me? ለኔ ፡ መልእክት ፡ አለ?
He found a message written in code. በምስጢር ፡ ጽሑፍ ፡ የተጻፈ ፡ መልእክት ፡ አገኘ

**messenger**
1. መልእክተኛ. The messenger is waiting for your reply. መልእክተኛው ፡ መልስህን ፡ ይጠብቃል
2. አብሳሪ. Dawn is the messenger of the day. ጎሕ ፡ የቀን ፡ አብሳሪ ፡ ነው

**Messiah** መሲሕ
Some religions wait for the arrival of the Messiah. አንዳንድ ፡ ሃይማኖቶች ፡ መሲሕ ፡ ይመጣልናል ፡ ብለው ፡ ይጠብቃሉ

**messy**
1. የተዝረከረከ. I have to put my messy room in order. የተዝረከረከውን ፡ ክፍሌን ፡ ማደራጀት ፡ አለብኝ

2. የተበላሸ. There was a messy political situation in the Congo. በኮንጎ ፡ ውስጥ ፡ የተበላሸ ፡ የፖለቲካ ፡ ሁኔታ ፡ ነበር

**be messy** ዝብርቅርቅ ፡ አለ
The kitchen was messy. ማድ ፡ ቤቱ ፡ ዝብርቅርቅ ፡ ብሎ ፡ ነበር

**met,** see **meet**

**metal** (n.)
1. ብረት. Gold is a precious metal. ወርቅ ፡ የከበረ ፡ ብረት ፡ ነው
Is it made of wood or metal? የተሠራው ፡ ከዕንጨት ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ከብረት ?
2. ብረታ ፡ ብረት. Cars are made of metal. መኪናዎች ፡ ከብረታ ፡ ብረት ፡ ይሠራሉ
Copper is a metal. መዳብ ፡ ከብረታ ፡ ብረቶች ፡ አንዱ ፡ ነው

**metal** (adj.) ከብረት ፡ የተሠራ
He washed his hands in a metal basin. እጆቹን ፡ ከብረት ፡ በተሠራ ፡ ጐድጓዳ ፡ ሳሕን ፡ ውስጥ ፡ ታጠበ
[See also 'sheet']

**mete, ~ out** ወሰነ
The judge meted out punishment to each criminal. ዳኛው ፡ ለያንዳንዱ ፡ ወንጀለኛ ፡ ቅጣት ፡ ወሰነ

**meteor** በራሪ ፡ ኮከብ
A meteor was seen in the sky last night. በራሪ ፡ ኮከብ ፡ ትናንት ፡ ማታ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ታየ

**meteorology** ያየር ፡ ጠባይ ፡ ትምህርት
Meteorology instructs us about atmospheric changes. ያየር ፡ ጠባይ ፡ ትምህርት ፡ ስለ ፡ አየር ፡ መለዋወጥ ፡ ያስረዳል

**meter**
1. ሜትር. A meter is about one yard long. አንድ ፡ ሜትር ፡ አንድ ፡ ያርድ ፡ ያህል ፡ ይረዝማል
2. ቈጣሪ. The water meter is not working. ውኃ ፡ ቈጣሪው ፡ አይሠራም
3. ምጣኔ. Poetry is written in various meters. ግጥም ፡ በተለያየ ፡ ምጣኔ ፡ ይጻፋል

**method** ዘዴ
Broiling is a common method of cooking meat. መጥበስ ፡ የተለመደ ፡ የሥጋ ፡ ማብሰያ ፡ ዘዴ ፡ ነው
This student worked with method. ይህ ፡ ተማሪ ፡ በዘዴ ፡ አጠና

**methodical**
1. ሥርዓት ፡ ያለው. His wife is a methodical housekeeper. ሚስቱ ፡ በቤት ፡ አያያዝ ፡ ሥርዓት ፡ ያላት ፡ ናት
2. (= adv.) በዘዴ. His methodical habits enable him to solve many problems. በዘዴ ፡ የመሥራት ፡ ልማዱ ፡ ለብዙ ፡ ችግሮች ፡ መፍትሔ ፡ እንዲያገኝ ፡ ያስችለዋል

**meticulous** ጥንቁቅ
He is very meticulous in his work. በሥራው ፡ በጣም ፡ ጥንቁቅ ፡ ነው

**metric**
*Ethiopia uses the metric system. ኢትዮጵያ ፡ በሜትር ፡ ላይ ፡ በተመሠረተ ፡ መለኪያ ፡ ዘዴ ፡ ትሠራለች

**metropolis** ትልቅ ፡ ከተማ
New York is a metropolis. ኒው ፡ ዮርክ ፡ ትልቅ ፡ ከተማ ፡ ነው

**mew** ጮኸ
The kittens mewed loudly. ድመቶቹ ፡ በኀይል ፡ ጮኹ

**mice,** see **mouse**

**microbe(s)** ረቂቅ ፡ ነፍሳት
Microbes can be seen only through the microscope. ረቂቅ ፡ ነፍሳትን ፡ ማየት ፡ የሚቻለው ፡ በማጉያ ፡ መነጽር ፡ ብቻ ፡ ነው

**microphone** ድምፅ ፡ ማጉያ
Please use the microphone so everybody can hear you. ሁሉ ፡ ሰው ፡ ሊሰማህ ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ በድምፅ ፡ ማጉያው ፡ ተናገር

**microscope** የማጉያ ፡ መነጽር
Our laboratory bought a new microscope. ቤተ ፡ ሙከራችን ፡ አዲስ ፡ የማጉያ ፡ መነጽር ፡ ገዛ

**mid** አጋማሽ
The term lasts from mid-June to mid-August. ተርሙ ፡ ከሰኔ ፡ አጋማሽ ፡ እስከ ፡ ነሐሴ ፡ አጋማሽ ፡ ይቆያል

**midair, in ~** ሰማይ ፡ ላይ
The bomb exploded in midair. ቦምቡ ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ ፈነዳ

**midday** (n.) ቀትር ፡ ጊዜ
The town is quiet at midday because of the heat. ከሙቀቱ ፡ የተነሣ ፡ ከተማው ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ ጭር ፡ ይላል

**midday** (adj.) በቀትር ፡ የሚደረግ
The midday rest period in hot countries is

called the siesta. በሞቃት ፡ አገሮች ፡ በቀትር ፡ የሚደረገው ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ሲዬስታ ፡ ይባላል

**midday meal** ምሳ
I take my midday meals in the hotel. ምሳዬን ፡ የምበላው ፡ ሆቴል ፡ ነው

**midday sun** የጠራራ ፡ ፀሐይ
Don't go out in the midday sun! በጠራራ ፡ ፀሐይ ፡ አትውጣ

**middle** (n.)
1. ወገብ. He seized her around the middle. ወገቧን ፡ አቅፎ ፡ ያዛት
2. አጋማሽ. I'm leaving the middle of next week. በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ አጋማሽ ፡ ላይ ፡ እሄዳለሁ
3. መኻል. The man collapsed in the middle of the street. ሰውዬው ፡ መንገዱ ፡ መኻል ፡ ተዝለፍልፎ ፡ ወደቀ
*They were in the middle of dinner when I called. ስደውልላቸው ፡ ራት ፡ ይበሉ ፡ ነበር
*He's put on weight around the middle. ቦርጭ ፡ አውጥቷል

**middle** (adj.) መካከለኛ ፤ መሀከለኛ
Open the middle window! መካከለኛውን ፡ መስኮት ፡ ክፈት
He is a man of middle height. መሀከለኛ ፡ ቁመት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው
*He is in his middle forties. ዕድሜው ፡ ወደ ፡ አርባ ፡ አምስቱ ፡ ነው
[See also 'finger']

**middle-aged** ጠና ፡ ያለ
He is a middle-aged man and is still strong. ጠና ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ቢሆንም ፡ ጠንካራ ፡ ነው

**Middle Ages** መካከለኛ ፡ ዘመን
The Middle Ages stretched from the fifth to the fifteenth century. መካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ከአምስተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ነበር

**middle class** መካከለኛ ፡ ገቢ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ
The middle class was hard hit because of the war. በጦርነቱ ፡ ምክንያት ፡ መካከለኛ ፡ ገቢ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ በጣም ፡ ተጐዳ

**Middle East** መካከለኛ ፡ ምሥራቅ
He is studying in the Middle East. መካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ውስጥ ፡ በመማር ፡ ላይ ፡ ይገኛል

**middleman** አትራፊ
Don't deal with middlemen; write directly to the manufacturer! ከአትራፊ ፡ ጋር ፡ አትዋዋል ፤ ቀጥታ ፡ ለባለፋብሪካው ፡ ጻፍ

**midget** ድንክ
In olden times, midgets used to be chosen as palace jesters. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ድንኮች ፡ ለቤተ ፡ መንግሥት ፡ አጫዋችነት ፡ ይመረጡ ፡ ነበር

**midnight** እኩለ ፡ ሌሊት
It was past midnight when we fell asleep. እንቅልፍ ፡ ሲወስደን ፡ እኩለ ፡ ሌሊት ፡ አልፎ ፡ ነበር

**midst, in the ~** በ - - መሃከል
In the midst of the crowd, we saw a policeman. በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መሃከል ፡ አንድ ፡ ፖሊስ ፡ አየን

**midway** አማካይ ፡ ስፍራ
Addis Ababa is approximately midway between Asmara and Nairobi. ከሞላ ፡ ጐደል ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለአሥመራና ፡ ለናይሮቢ ፡ አማካይ ፡ ስፍራ ፡ ናት

**midway through** በ - - - አጋማሽ ፡ ላይ
He caught cold midway through the campaign. በውድድሩ ፡ አጋማሽ ፡ ላይ ፡ ጉንፋን ፡ ያዘው

**midwife** አዋላጅ
Call the midwife when the labor pains begin. ምጥ ፡ ሲይዛት ፡ አዋላጇን ፡ ጥራ

**midyear** የዓመት ፡ አጋማሽ
He just passed his midyear examination. የዓመት ፡ አጋማሽ ፡ ፈተናውን ፡ ገና ፡ ማለፉ ፡ ነው
This store has a midyear sale. ይህ ፡ መደብር ፡ የዓመት ፡ አጋማሽ ፡ ሽያጭ ፡ አለው

**might** (n.)
1. ጉልበት. He works with all his might. ባለው ፡ ጉልበት ፡ ሁሉ ፡ ይሠራል
2. ኀይል. Might does not make right. ኀይል ፡ መብት ፡ አይደለም

**might**, see **may**

**mightily** በጣም
The workers tried mightily to finish before dark. ሠራተኞቹ ፡ ከመምሸቱ ፡ በፊት ፡ ለመጨረስ ፡ በጣም ፡ ጣሩ

**mighty** (adj.)
1. ታላቅ. He is a mighty man from a mighty nation. ከታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ የመጣ ፡ ታላቅ ፡ ሰው ፡ ነው
2. ኀይለኛ ፤ ጐበዝ. Theodore was a mighty warrior. ቴዎድሮስ ፡ ኀይለኛ ፡ (ጐበዝ) ፡ ጦረኛ ፡ ነበር

**mighty** (adv.) በጣም
I was mighty glad to see him again. እንደገና ፡ ሳየው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለኝ

He has done mighty little work today. ዛሬ ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ሥርቶ ፡ ዋለ

**migraine** ኀይለኛ ፡ የራስ ፡ ምታት
He has been suffering from migraines lately. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ኀይለኛ ፡ የራስ ፡ ምታት ፡ ያመዋል

**migrant** ተዘዋዋሪ
He hired migrant workers to harvest his fruit. ፍሬ ፡ ለማስለቀም ፡ ተዘዋዋሪ ፡ ሥራተኞች ፡ ቀጠረ

**migrate**
1. ፈለሰ. The Galla migrated from the South and settled in central Ethiopia. ጋሎች ፡ ከደቡብ ፡ ፈልሰው ፡ መሀል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰፈሩ
2. ተጓዘ. Ducks and geese migrate southward in the fall. ዳክዬና ፡ ዝዬ ፡ በመፀው ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይጓዛሉ

**migrate into** ወደ - - - ፡ ፈልሶ ፡ ገባ
The Arabs migrated across the Red Sea into Ethiopia. ዐረቦች ፡ ቀይ ፡ ባሕርን ፡ ተሻግረው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ፈልሰው ፡ ገቡ

**migration**
1. ከቦታ ፡ ወደ ፡ ቦታ ፡ መዘዋወር. The government is trying to prevent the migration of the nomads. መንግሥቱ ፡ የዘላኖችን ፡ ከቦታ ፡ ወደ ፡ ቦታ ፡ መዘዋወር ፡ ለመከልከል ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነው
2. (= verb) ፈለሰ. The migration of the Boers was from the coast into the interior. ቦሮች ፡ ከጠረፍ ፡ ፈልሰው ፡ ወደ ፡ መሀል ፡ ገቡ

**migratory** ተዘዋዋሪ
Migratory workers travel about from one job to another. ተዘዋዋሪ ፡ ሠራተኞች ፡ ካንዱ ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ይዘዋወራሉ

**mild**
1. ቀላል. He received only a mild punishment for his crime. ለወንጀሉ ፡ ቀላል ፡ ቅጣት ፡ ተቀበለ
2. ገር. He is a mild person who wouldn't harm a soul. ማንንም ፡ ለመጕዳት ፡ የማይፈልግ ፡ ገር ፡ ሰው ፡ ነው
3. ለስላሳ. They prefer mild tobacco for cigarettes. ሲጋራ ፡ ለመሥራት ፡ ለስላሳ ፡ ትምባሆ ፡ ይመርጣሉ
This sauce is mild. ይህ ፡ ወጥ ፡ ለስላሳ ፡ ነው
4. መካከለኛ. Because Addis Ababa is in the mountains, it has a mild climate. አዲስ ፡ አበባ ፡ በተራራዎች ፡ መሀከል ፡ በመሆኗ ፡ መካከለኛ ፡ አየር ፡ አላት

**mildew**
1. ሻጋታ. The bread is full of mildew. እንጀራው ፡ ሻጋታ ፡ በዝቶበታል
2. መሻገት. The moisture in the air causes mildew. ያየር ፡ ርጥበት ፡ መሻገትን ፡ ይፈጥራል

**be covered with mildew** ሻገተ
The bread is covered with mildew. ዳቦው ፡ ሻግቷል

**mile** ማይል
He ran a mile in 4 minutes. ባራት ፡ ባራት ፡ ደቂቃ ፡ አንድ ፡ ማይል ፡ ሮጠ
[See also 'stretch']

**mileage**
*His mileage on the trip to Asmara was close to five hundred. አሥመራ ፡ ሲሄድ ፡ ወደ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ማይል ፡ ርቀት ፡ ደርሶ ፡ ነበር
*He gets good mileage from a gallon of gasoline. ባንድ ፡ ጋሎን ፡ ቤንዚን ፡ ብዙ ፡ ማይል ፡ ይሄዳል

**milestone**
1. ርቀት ፡ የሚያመለክት ፡ ድንጋይ. The milestone shows the town is ten miles away. ርቀት ፡ የሚያመለክተው ፡ ድንጋይ ፡ ከተማው ፡ ዐሥር ፡ ማይል ፡ መራቁን ፡ ያሳያል
2. አዲስ ፡ ምዕራፍ. The coming of the Portuguese is a milestone in Ethiopian history. የፖርቱጊዞች ፡ መምጣት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ አዲስ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው

**militant**
1. ለመዋጋት ፡ የቈረጠ. A militant defender of freedom is prepared to fight in its defense. ለመዋጋት ፡ የቈረጠ ፡ ጀግና ፡ ለነጻነት ፡ ለመዋጋት ፡ ዝግጁ ፡ ነው
2. ነውጠኛ. The crowd was led by a militant leader. የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ በነውጠኛ ፡ መሪ ፡ ይመራ ፡ ነበር

**become militant** ለመዋጋት ፡ ቈረጠ
The Indians became very militant as settlers began to move west. መጤዎቹ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ሲገፉ ፡ ህንዶች ፡ ለመዋጋት ፡ ቈረጡ

**militarism** በጦር ፡ ኀይል ፡ መተማመን
The UN tries to combat militarism. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ በጦር ፡ ኀይል ፡ መተማመንን ፡ ለመቋቋም ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነው

**militarize** በጦር ፡ ኀይል ፡ አደረጀ
Hitler militarized Germany after 1933. ሂትለር ፡ ከ፲፱፻፳፭ ፡ ዓ. ም. በኋላ ፡ ጀርመንን ፡ በጦር ፡ ኀይል ፡ አደረጀ

**military** (n.) ሰራዊት
The military took charge of the village. ሰራዊቱ ፡ መንደሪቱን ፡ በእጁ ፡ አደረገ

**military** (adj.)
1. የወታደር. He was wearing a military uniform. የወታደር ፡ የደንብ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ነበር
2. የጦር ፡ ኀይል. The distribution of our troops is a military secret. የወታደሮቻችን ፡ ድልድል ፡ የጦር ፡ ኀይል ፡ ምስጢር ፡ ነው
3. የውትድርና. A soldier should have a military bearing. ወታደር ፡ የውትድርና ፡ አቋም ፡ እንዲኖረው ፡ ያሻል

**militate, ~ against** ጉዳት ፡ ላይ ፡ ጣለው
His rashness militated against him. ችኩልነቱ ፡ ጉዳት ፡ ላይ ፡ ጣለው

**militia** ብሔራዊ ፡ ጦር
The governor exercised his power to call out the militia. ገዢው ፡ በሥልጣኑ ፡ ተጠቅሞ ፡ ብሔራዊ ፡ ጦሩን ፡ አስከተተ

**milk** (v.)
1. አለበ. They milk their cows twice a day. ላሞቻቸውን ፡ በቀን ፡ ሁለቴ ፡ ያልቧታል
2. ገንዘብ ፡ ጠርጎ ፡ ወሰደ. He is milking his business as much as he can. ከንግዱ ፡ ያገኘውን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ ጠርጎ ፡ ይወስዳል

**milk** (n.) ወተት
Don't drink unboiled milk! ያልፈላ ፡ ወተት ፡ አትጠጣ
[See also 'powdered milk']

**milk tooth** የወፍ ፡ ጥርስ
The baby's milk teeth fell out one by one. የሕፃኑ ፡ የወፍ ፡ ጥርሶች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ረገፉ

**lose (one's) milk teeth** ጣግ ፡ ወጣ(ለት)
The baby has lost all his milk teeth. ሕፃኑ ፡ ጣግ ፡ ወጥቶለታል

**milky** ወተት ፡ ያለበት
The milky sauce tastes good. ወተት ፡ ያለበት ፡ ወጥ ፡ ይጣፍጣል

**Milky Way** የወተት ፡ ጐዳና
The Milky Way forms a band of light across the night sky. በሌሊት ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ የወተት ፡ ጐዳና ፡ ውጋጋን ፡ ይታያል

**mill** (v.) ፈጨ
The women mill a little grain for their household. ሴቶች ፡ ለቤት ፡ የሚሆን ፡ ጥቂት ፡ እህል ፡ ይፈጫሉ

**mill about** ተተረማመሰ
The frightened cattle began to mill about. የተደናገጡት ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ መተረማመስ ፡ ጀመሩ

**mill flour** ፈጨ
The stones mill flour from the wheat. ወፍጮዎቹ ፡ ስንዴ ፡ ይፈጫሉ

**mill** (n.)
1. ወፍጮ ፡ ቤት. When are you going to take the grain down to the mill? እህሉን ፡ ወፍጮ ፡ ቤት ፡ የምትወስደው ፡ መቼ ፡ ነው ?
2. ወፍጮ. A pepper mill is used to grind pepper. የበርበሬ ፡ ወፍጮ ፡ በርበሬ ፡ ለመፍጨት ፡ ያገለግላል
3. ፋብሪካ. We ordered the paper straight from the mill. ወረቀቱን ፡ በቀጥታ ፡ ከፋብሪካው ፡ አዘዝን

**millenium** አንድ ፡ ሺ ፡ ዓመታት
The Axumite Empire came to an end a millenium ago. የአክሱም ፡ መንግሥት ፡ የወደቀው ፡ ከአንድ ፡ ሺ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ነው

**millet** ማሽላ
Millet is widespread in Ethiopia. ማሽላ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በብዛት ፡ ይገኛል

**million** ሚሊዮን

**millionaire** ሀብታም
The charity was established in perpetuity by the millionaire. ሀብታሙ ፡ የበጎ ፡ አድራጎቱን ፡ ድርጅት ፡ ያቋቋመው ፡ ለምንጊዜም ፡ ነው

**millstone** የድንጋይ ፡ ወፍጮ
This millstone is too heavy to lift. ይህን ፡ የድንጋይ ፡ ወፍጮ ፡ ለማንሣት ፡ ከባድ ፡ ነው

**nether millstone** ወፍጮ ፤ እናት ፡ ወፍጮ
The nether millstone is made of a hard kind of stone. ወፍጮው ፡ (እናት ፡ ወፍጮው) ፡ ከጠንካራ ፡ ድንጋይ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**upper millstone** መጅ
So that the grain can be ground thoroughly, the upper and nether millstones have to be carved. እህል ፡ በደንብ ፡ መፍጨት ፡ እንዲቻል ፡ መጁና ፡ ወፍጮው ፡ መወቀር ፡ አለበት

**milt** ጣፊያ
When a sheep is killed, milt is given to the cat. በግ ፡ ሲታረድ ፡ ጣፊያው ፡ ለድመት ፡ ይሰጣል

**mimic** (v.)
1. መስሎ ፡ ቀለደ. We will get him to mimic

our old music teacher. ሽማግሌውን ፡ የሙዚቃ ፡ አስተማሪያችንን ፡ መስሎ ፡ እንዲቀልድ ፡ አናደርገዋለን

2\. ቀዳ. Parakeets mimic human voices. በቅበቃ ፡ የሰውን ፡ ድምፅ ፡ ይቀዳል

**mimic** (n.)

*Some comedians are skillful mimics. አንዳንድ ፡ የኮሜዲ ፡ ተጫዋቾች ፡ የመቅዳት ፡ ችሎታ ፡ አላቸው

**mimosa** የግራር ፡ ዓይነት ፡ ዛፍ

**minaret** የጸሎት ፡ መጥሪያ ፡ ግምብ

Each mosque has a minaret. እያንዳንዱ ፡ መስጊድ ፡ የጸሎት ፡ መጥሪያ ፡ ግምብ ፡ አለው

**mince** ከተፈ

The woman is mincing onions. ሴትዮዋ ፡ ሽንኩርት ፡ ትከትፋለች

Mince the meat finely and cook it! ሥጋውን ፡ አድቅቀሽ ፡ ከትፊና ፡ ሥሪው

**not mince words**

*I won't mince words with you. እቅጩን ፡ እነግርሃለሁ

**mind** (v.)

1\. ጠበቀ. Who is going to mind the baby? ሕፃኑን ፡ ማን ፡ ይጠብቃል ?

2\. ተቀበለ. If you don't mind my warning, you'll be hurt. ማስጠንቀቂያዬን ፡ ካልተቀበልክ ፡ ትጎዳለህ

3\. ተጠነቀቀ. Mind your step! The stair is loose here. ተጠንቀቀህ ፡ ተራመድ ፤ እዚያ ፡ ጋ ፡ ደረጃው ፡ ላልቷል

4\. ሰማ. My son doesn't mind me anymore. ልጄ ፡ እኔን ፡ መስማት ፡ ትቷል

5\. ታዘዘ. You must mind the policeman. ለፖሊስ ፡ መታዘዝ ፡ አለብህ

6\. ቅር ፡ አለ(ው). Do you mind if I smoke? ባጨስ ፡ ቅር ፡ ይልሃል ?

*If you don't mind, I would like to have another cup of coffee. ቡና ፡ ብትደግመኝ ፡ ደስ ፡ ይለኛል

**mind now!** ልብ ፡ አድርግ

Mind now, this is not a definite promise. ልብ ፡ አድርግ ፤ ይህ ፡ የተቈረጠ ፡ ቃል ፡ አይደለም

**mind you** ልብ ፡ በል

I have no objection, mind you, but I think it's unwise. ልብ ፡ በል ፤ የምቃወመው ፡ ነገር ፡ የለኝም ፤ ግን ፡ ተገቢ ፡ አይመስለኝም

**never mind!** ግድ ፡ የለም

Never mind! I am not hungry. ግድ ፡ የለም ፤ አልራበኝም

**not mind**

1\. ችላ ፡ አለ. Don't mind what he says! እሱ ፡ የሚለውን ፡ ችላ ፡ በለው

2\. ግድ ፡ የለውም. He doesn't mind the cold weather at all. ለብርዱ ፡ ፍጹም ፡ ግድ ፡ የለውም

**mind** (n.)

1\. ሐሳብ. I have changed my mind. ሐሳቤን ፡ ለውጫለሁ

Is he still of the same mind? አሁንም ፡ ሐሳቡ ፡ ያው ፡ ነው ?

On my way home, the thought flashed through my mind. ወደ ፡ ቤቴ ፡ ስሄድ ፡ ሐሳብ ፡ ብልጭ ፡ አለልኝ

2\. አንጎል. He has a very keen mind. በጣም ፡ ንቁ ፡ አንጎል ፡ አለው

3\. አእምሮ. You need an agile mind to solve the problem. ለችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ ለማስገኘት ፡ ንቁ ፡ አእምሮ ፡ ያስፈልግሃል

4\. ጠቢብ. Who are the great minds of our day? የዘመናችን ፡ ታላላቅ ፡ ጠቢባን ፡ እነማን ፡ ናቸው ?

**bear in mind** አስታወሰ

You must bear in mind that he is a foreign student. እሱ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተማሪ ፡ መሆኑን ፡ ማስታወስ ፡ አለብህ

**bring to mind** አስታወሰ

That brings to mind a funny story. አሥቂኝ ፡ ታሪክ ፡ ያስታውሰናል

**call to mind** አስታወሰ

That calls to mind a story I know. ያ ፡ አንድ ፡ የማውቀውን ፡ ታሪክ ፡ ያስታውሰኛል

**cross one's mind** በሐሳቡ ፡ መጣ

It never crossed my mind that he would object. ይቃወማል ፡ ብዬ ፡ በሐሳቤም ፡ አልመጣም

**give someone a piece of one's mind** ቅር ፡ እንደተሰኘ ፡ ገለጸለት

I will give him a piece of my mind for telling such a lie. ይህን ፡ መሳይ ፡ ውሸት ፡ ስለነገረኝ ፡ ቅር ፡ እንደተሰኘሁ ፡ እገልጽለታለሁ

**have a mind** አሰበ

I have a mind to punish him. እሱን ፡ ለመቅጣት ፡ አስባለሁ

**have (one's) mind set on** ቈርጦ ፡ ተነሣ

She has her mind set on going shopping today. ዛሬ ፡ ገበያ ፡ ለመውጣት ፡ ቈርጣ ፡ ተነሥታለች

**have in mind** አሰበ

Have you anyone definite in mind for the job? ለሥራው ፡ በተለይ ፡ ያሰብከው ፡ ሰው ፡ አለ ?

**keep in mind** አስታወሰ

We must keep in mind that foreign students

have different training. የውጭ ፡ አገር ፡ ተማሪ ዎች ፡ የተለያየ ፡ ትምህርት ፡ እንዳላቸው ፡ ማስ ታወስ ፡ አለብን

**keep one in mind** አስታወሰ
I expect that there will be a job open soon, so I will keep you in mind. በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ሥ ራ ፡ ይገኛል ፡ ብዬ ፡ ስለምገምት ፡ አስታውስሃለሁ

**keep one's mind on** ሐሳቡን - - - ላይ ፡ አሳረፈ
I can't keep my mind on my studies when the radio is playing. ራዲዮ ፡ ሲጫወት ፡ ሐሳቤን ፡ ጥ ናቴ ፡ ላይ ፡ ለማሳረፍ ፡ አልችልም

**know (one's) own mind**
*He's too young to know his own mind. የሚጠቅመውንና ፡ የሚጎዳውን ፡ ለመለየት ፡ ገና ፡ ልጅ ፡ ነው

**make up one's mind** ቈረጠ ፤ ሐሳቡን ፡ ቈረጠ ፤ ወጠነ
I cannot make up my mind which girl I like better. የትኛዋን ፡ ልጃገረድ ፡ የበለጠ ፡ እንደም ወድ ፡ ልቈርጥ ፡ አልቻልኩም
Sooner or later, we will have to make up our minds. ግራም ፡ ነፈሰ ፡ ቀኝ ፡ ሐሳባችንን ፡ መ ቍረጥ ፡ አለብን
A man of decision makes up his mind what to do and then does it. ቈርጠኛ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ እንደሚያደርግ ፡ ወጥኖ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያውለዋል

**(be) of one mind** ተስማማ
We are all of one mind on this matter. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሁላችንም ፡ ተስማምተናል

**(be) of two minds** አወላወለ
I am of two minds regarding the proposal. ስለቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ አወላውላለሁ

**(be) on (one's) mind** አሰበ
What's on your mind? ምን ፡ ታስባለህ ?

**(be) out of (one's) mind** አበደ
Are you out of your mind to go out in this heavy rain? በዚህ ፡ ከባድ ፡ ዝናብ ፡ ወደ ፡ ው ጭ ፡ የምትሄደው ፡ አብደሃል ?

**presence of mind** የአእምሮ ፡ እርጋታ
She had enough presence of mind to remember the license plate of the speeding car. በፍጥነት ፡ የሚበረውን ፡ የመኪና ፡ ሰሌዳ ፡ ለማስታወስ ፡ የሚ ያስችል ፡ የአእምሮ ፡ እርጋታ ፡ ነበራት

**(have) presence of mind** አእምሮው ፡ ንቁ ፡ ነው
He has presence of mind and is never at a loss for an answer. አእምሮው ፡ ንቁ ፡ ስለሆነ ፡ መል ስ ፡ አይቸግረውም

**(show) presence of mind** ሳይደነግጥ ፡ ረጋ ፡ አለ
When his clothes caught fire, he showed great presence of mind by extinguishing the fire. ልብሱ ፡ በእሳት ፡ ሲያያዝ ፡ ሳይደነግጥ ፡ ረጋ ፡ ብ ሎ ፡ አጠፋው

**set one's mind on** ቈረጠ
He has set his mind on learning English. እንግሊዝኛ ፡ ለመማር ፡ ቈርጧል

**(have a) small mind** ሐሳቡ ፡ ጠባብ ፡ ነው
He has a small mind and cannot be persuaded to accept new things. ሐሳቡ ፡ ጠባብ ፡ ስለሆነ ፡ አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ እንዲቀበል ፡ ልታግባባው ፡ አ ትችልም

**take one's mind off**
*Try to take his mind off his troubles! ስለ ፡ ች ግሮቹ ፡ እንዳያሰላስል ፡ አድርገው

**to my mind** እንደኔ
To my mind, she is the right person for the job. እንደኔ ፡ ለሥራው ፡ ተገቢ ፡ ሰው ፡ እሷ ፡ ናት

**would you mind**
*Would you mind opening the window? መስኮቱን ፡ ብትከፍተው ?
[See also 'flash, frame, keen, load, open, peace, piece, put, read, reel, rest, right, sink, speak, turn over, weigh']

## minded, be so ~ ፈለገ
He could do it if he were so-minded. ቢፈልግ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል

**be --- minded** ለ - - - ዝንባሌ ፡ አለው
He is mathematically minded and grasps every problem. ለሒሳብ ፡ ዝንባሌ ፡ ስላለው ፡ ማንኛቸው ም ፡ ዓይነት ፡ ፕሮብሌም ፡ ይገባዋል

## mindful, ~ of በመስማት
Mindful of your advice, I went slowly. ምክርህ ን ፡ በመስማት ፡ ዝግ ፡ ብዬ ፡ ሄድኩ

**be mindful**
1. ዐወቀ. Father was always mindful of the needs of the family. አባቴ ፡ የቤት ፡ ሰቡን ፡ ፍ ላጎት ፡ ሁልጊዜ ፡ ያውቅ ፡ ነበር
2. ልብ ፡ አለ. Be mindful of the many dangers you face! ስለሚገጥሙህ ፡ ብዙ ፡ ችግሮች ፡ ልብ ፡ በል

## mindless ግዴለሽ
He is mindless of all dangers. ለማንኛውም ፡ አደ ጋ ፡ ግዴለሽ ፡ ነው

**in a mindless sort of way** ሳያስብ
He does things in a mindless sort of way. አንድ ፡ ነገር ፡ ሲያደርግ ፡ ሳያስብ ፡ ነው

## mine (v.)
1. አወጣ. Do they mine gold in this region? እዚህ ፡ አካባቢ ፡ ወርቅ ፡ ያወጣሉ ?

2. ፈንጂ ፡ ቀበረ. The enemy mined the road to the harbor. ጠላት ፡ ወደ ፡ ወደቡ ፡ በሚያመራው ፡ መንገድ ፡ ፈንጂ ፡ ቀበረ

**mine** (n.)
1. ማዕድን. Are there coal mines in Ethiopia? በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የድንጋይ ፡ ከሰል ፡ ማዕድኖች ፡ አሉ ?
2. ፈንጂ. The rebels planted mines in the road. ዐመፀኞቹ ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ፈንጂ ፡ ቀበሩ
3. ምንጭ. A good dictionary is a mine of information. ጥሩ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ የዕውቀት ፡ ምንጭ ፡ ነው
*He is a mine of information about ships. ስለ ፡ መርከቦች ፡ ብዙ ፡ ያውቃል

**mine** (pron.) የኔ
It's not your hat, it's mine. ያንተ ፡ ባርኔጣ ፡ አይደለም ፤ የኔ ፡ ነው

**of mine** (suffix pronoun)
A friend of mine gave me this. አንድ ፡ ወዳጄ ፡ ይህንን ፡ ሰጠኝ

**miner** ማዕድን ፡ ቈፋሪ
Miners often endanger their lives. ማዕድን ፡ ቈፋሪዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሕይወታቸው ፡ በሚያሰጋ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነው

**mineral** ማዕድን
Coal and salt are minerals. የድንጋይ ፡ ከሰልና ፡ ጨው ፡ ማዕድኖች ፡ ናቸው

**mineral oil** የነዳጅ ፡ ዘይት
Mineral oil is used in cars. የነዳጅ ፡ ዘይት ፡ ለመኪና ፡ ያገለግላል

**mineral water** ጠበል
This mineral water is effervescent. ይህ ፡ ጠበል ፡ ይፈላል

**mingle** (vt.)
1. አዳበለ. One should not mingle sheep with tigers. በጎችን ፡ ከነብሮች ፡ ጋር ፡ ማዳበል ፡ አይገባም
2. (= vi.) ተቀላቀለ. The two rivers mingle their waters. የሁለቱ ፡ ወንዞች ፡ ውኃ ፡ ይቀላቀላል

**mingle** (vi.)
1. ተደባለቀ. The detectives mingled with the crowd. ጀሮ ፡ ጠቢዎቹ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ተደባለቁ
2. ገጠመ. He is very shy and does not mingle much with the children at school. በጣም ፡ ዓይን ፡ አፋር ፡ ስለሆነ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ከልጆች ፡ ጋር ፡ እምብዛም ፡ አይገጥምም

3. ተቀላቀለ. The waters of the Missouri and the Mississippi rivers mingle near St. Louis. የሚዙሪና ፡ የሚሲሲፒ ፡ ወንዞች ፡ ሴይንት ፡ ሉዊስ ፡ አጠገብ ፡ ይቀላቀላሉ

**miniature** (n.)
1. ሞዴል. In the museum, there is a miniature of the ship 'America'. ቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ውስጥ ፡ «አሜሪካ» ፡ የተሰኘችው ፡ መርከብ ፡ ሞዴል ፡ አለ
2. በጣም ፡ ትንሽ ፡ ሥዕል. There is only one miniature in this manuscript. በዚህ ፡ የብራና ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ሥዕል ፡ ብቻ ፡ ነው

**miniatures** ጥቃቅን ፡ ሥዕሎች
There are many miniatures in this manuscript. በዚህ ፡ የብራና ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጥቃቅን ፡ ሥዕሎች ፡ አሉ

**miniature** (adj.)
1. ጥቃቅን. There are miniature paintings in the old Geez manuscript. በጥንቱ ፡ የግዕዝ ፡ የብራና ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ጥቃቅን ፡ ሥዕሎች ፡ ይገኛሉ
2. አነስተኛ. There is a miniature train in the park. መናፈሻው ፡ ውስጥ ፡ አነስተኛ ፡ ባቡር ፡ አለ

**minimize**
1. ቀነሰ. Proper care will minimize the danger of fire. ተገቢ ፡ ጥንቃቄ ፡ የእሳትን ፡ አደጋ ፡ ሊቀንሰው ፡ ይችላል
2. አቃለለ. He minimized his act of bravery. የጀግንነት ፡ ሙያውን ፡ አቃለለው
An ungrateful person minimizes the help others have given him. ውለታ ፡ ቢስ ፡ ሰው ፡ ሌሎች ፡ ያደረጉለትን ፡ እርዳታ ፡ ያቃልላል

**minimum,** n. (= adv.) እጅግ ፡ ቢያንስ
Eight hours of sleep is the minimum that children should have. ሕፃናት ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ መተኛት ፡ አለባቸው

**a minimum of** ቢያንስ ፡ ቢያንስ
Study a minimum of three hours a day! ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በቀን ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ አጥና

**minimum** (adj.) አነስተኛ
The minimum salary is a hundred dollars a month. አነስተኛው ፡ ደሞዝ ፡ በወር ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ነው

**mining** (n.) ማውጣት
Coal mining is the chief industry of several states. የድንጋይ ፡ ከሰል ፡ ማውጣት ፡ የብዙ ፡ ግዛቶች ፡ ዋና ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ነው

**mining** (adj.) የማዕድን
A mining region produces gold and silver. የማዕድን ፡ ቀበሌ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ይወጣታል

**minister, ~ to**
1. አከመ. I need someone to minister to my wounds. ቁስሌን ፡ የሚያከምልኝ ፡ ሰው ፡ እፈልጋለሁ
2. አከናወነ. After his wife's death, his sister ministered to his needs. ሚስቱ ፡ ከሞተች ፡ በኋላ ፡ እኅቱ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ ታከናውንለት ፡ ነበር

**minister** (n.)
1. አለቃ. Our church has a new minister. ቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ አዲስ ፡ አለቃ ፡ አለው
2. ሚኒስትር. The Minister of Education visited our school today. የትምህርት ፡ ሚኒስትሩ ፡ ዛሬ ፡ ትምህርት ፡ ቤታችንን ፡ ጐበኙ
[See also 'deputy']

**ministry** (ministries)
1. ሚኒስቴር. He works at the Ministry of Education. ትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ይሠራል
2. ቅስና. His son is intended for the ministry. ልጁ ፡ ለቅስና ፡ ታጭቷል
*The ministry is sometimes chosen by parents for their children. ልጆች ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋዮች ፡ እንዲሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ሰቦቻቸው ፡ ያሳስቧቸዋል

**minor** (n.)
1. ለአካለ ፡ መጠን ፡ ያልደረሰ ፡ ሰው. No liquor will be served to minors. ለአካለ ፡ መጠን ፡ ላልደረሱ ፡ ሰዎች ፡ መጠጥ ፡ አይሸጥም
2. ለዐቅመ ፡ ሔዋን ፡ ያልደረሰች ፡ ሴት. Sexual relations with a minor is a criminal offense. ለዐቅመ ፡ ሔዋን ፡ ካልደረሰች ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ ፍትወተ ፡ ሥጋ ፡ መፈጸም ፡ በሕግ ፡ ያስቀጣል
3. (በትምህርት) ፡ ተጨማሪ ፡ ምርጫ. He has a major in history with a minor in sociology. ዋናው ፡ ትምህርቱ ፡ ታሪክ ፡ ሲሆን ፡ ተጨማሪ ፡ ምርጫው ፡ ደግሞ ፡ የኅብረ ፡ ሰብ ፡ ትምህርት ፡ ነው

**minor** (adj.)
1. ቀላል. He suffered minor injuries in his fall. በመውደቁ ፡ የደረሰበት ፡ ቁስል ፡ ቀላል ፡ ነው
2. አነስተኛ. I made only minor changes. ያደረግሁት ፡ ለውጥ ፡ አነስተኛ ፡ ነበር
3. ዝቅተኛ. He plays a minor part in the government. በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ኀላፊነት ፡ ዝቅተኛ ፡ ነው
His brother is a minor official. ወንድሙ ፡ ዝቅተኛ ፡ ባለሥልጣን ፡ ነው
4. ጥቃቅን. The office boy takes care of minor things. ተላላኪው ፡ ጥቃቅን ፡ ሥራዎችን ፡ ያከናውናል
5. ዝርዝር. Minor details are circumstantial compared with the main facts. ከዋናው ፡ ጉዳይ ፡ ጋር ፡ ሲመዛዘኑ ፡ ዝርዝሮቹ ፡ ነገሮች ፡ አጋጣሚዎች ፡ ናቸው

**minority** (minorities) .
1. በቁጥር ፡ አነስተኛ ፡ የሆነ ፡ ሕዝብ. The minority must often do what the majority decides to do. በቁጥር ፡ አነስተኛ ፡ የሆነው ፡ ሕዝብ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ ለማድረግ ፡ የሚወስነውን ፡ ማድረግ ፡ አለበት
2. በቁጥር ፡ አነስተኛ ፡ ወገን. We were in the minority. በቁጥር ፡ አነስተኛ ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ ነበርን

**minstrel** አዝማሪ
A minstrel will play songs at our wedding feast. ሰርጋችን ፡ ላይ ፡ አዝማሪ ፡ ይዘፍንልናል

**mint** ገንዘብ ፡ መሥሪያ
The mint is coining pennies. ገንዘብ ፡ መሥሪያው ፡ ሳንቲሞች ፡ በማተም ፡ ላይ ፡ ነው

**a mint of** እጅግ ፡ ብዙ
He made a mint of money. እጅግ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አተረፈ

**minus** (adj.)
1. የመቀነስ. The minus sign is — . የመቀነስ ፡ ምልክት ፡ — ነው
2. (= adv.) ከዜሮ ፡ በታች. Minus three is a negative quantity. ከዜሮ ፡ በታች ፡ ሦስት ፡ የአሉታ ፡ ጠባይ ፡ ነው

**minus** (prep.)
1. ሲቀነስ ፤ ሲነሣ. Three minus two equals one. ከሦስት ፡ ሁለት ፡ ሲቀነስ ፡ (ሲነሣ) ፡ አንድ ፡ ይቀራል
2. ያለ. I found the book minus its cover. መጽሐፉን ፡ ያለ ፡ ሽፋኑ ፡ አገኘሁት

**minus** (adv.) ከዜሮ ፡ በታች
The temperature is minus five degrees. ያየሩ ፡ ቅዝቃዜ ፡ ከዜሮ ፡ በታች ፡ አምስት ፡ ዲግሪ ፡ ወርዷል

**minute** (n.) ደቂቃ
I'll be back in five minutes. ባምስት ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ እመለሳለሁ

**minutes** ቃለ ፡ ጉባኤ
The secretary will read the minutes of the last meeting. ጸሓፊው ፡ ያለፈውን ፡ ስብሰባ ፡ ቃለ ፡ ጉባኤ ፡ ያነባል

**any minute** አሁን
The train will pull out any minute. ባቡሩ ፡ አሁን ፡ ይነሣል

**in a minute** በቶሎ ፤ በደቂቃ ፡ ውስጥ
He'll be done in a minute. በቶሎ ፡ ይጨርሳል ፡ (በደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ይጨርሳል)

**just a minute** እስቲ ፡ ቆይ
Just a minute, please; I have to answer the door. እስቲ ፡ ቆይ ፤ በሩን ፡ የሚያንኳኳው ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ልይ

**the minute** እንደ + perfect + ወዲያው
I'll call you the minute I know. እንደሰማሁ ፡ ወዲያው ፡ እደውልልሃለሁ

**this minute!** አሁኑኑ
Come here this minute! አሁኑኑ ፡ ና

**up to the minute** እጅግ ፡ ዘመናዊ
As far as fashion is concerned, she is up to the minute. በፋሽን ፡ ረገድ ፡ እጅግ ፡ ዘመናዊ ፡ ናት

**minute** (adj.)
1. ረቂቅ. It was so minute, you could hardly see it. ረቂቅ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ለማየት ፡ ያስቸግራል
2. ዝርዝር. He gave me minute instructions about how to do my work. ሥራዬን ፡ እንዴት ፡ እንደምሠራ ፡ ዝርዝር ፡ የሆነ ፡ መምሪያ ፡ ሰጠኝ
3. (= adv.) አንድ ፡ ባንድ. I have checked every minute detail. ጉዳዩን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ተመልክቼዋለሁ
*His story is of minute importance. የሱ ፡ ታሪክ ፡ ብዙም ፡ ጠቃሚነት ፡ የለው

**minutely** በዝርዝር
The plan of attack was minutely prepared. አደጋ ፡ የመጣሉ ፡ እቅድ ፡ በዝርዝር ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ነበር

**miracle** ተአምር (pl. ተአምራት)
It was a miracle that he escaped unharmed from the crash. በግጭቱ ፡ ሳይጐዳ ፡ መቅረቱ ፡ ተአምር ፡ ነው
Christ performed many miracles. ክርስቶስ ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ ሠርቷል

**miraculous**
1. ተአምር. Her recovery is miraculous. መዳኗ ፡ ተአምር ፡ ነው
2. ለተአምር ፡ የሚነገር. He had miraculous success in his business. በንግድ ፡ ሥራው ፡ ለተአምር ፡ የሚነገር ፡ ውጤት ፡ አገኘ
3. ተአምራዊ. Penicillin is a miraculous drug. ፔኒሲሊን ፡ ተአምራዊ ፡ መድኃኒት ፡ ነው

**mire,** vt. (= intr.) ማጥ ፡ ውስጥ ፡ ገባ
He mired his car and had to go for help. መኪናው ፡ ማጥ ፡ ውስጥ ፡ ስለገባ ፡ ሄዶ ፡ እርዳታ ፡ መፈለግ ፡ ግድ ፡ ሆነበት

**mire** (n.)
1. ማጥ. We waded through the mire to reach the road. ከመንገድ ፡ ለመድረስ ፡ በማጡ ፡ ውስጥ ፡ ተጓዝን
2. መጨቅየት. The mire of the road delayed the travelers. የመንገዱ ፡ መጨቅየት ፡ መንገደኞቹን ፡ አዘገያቸው

**turn into mire** አጨቀየ
The rain turned the dust of the road into mire. ዝናቡ ፡ መንገዱን ፡ አጨቀየው

**mirror** (v.)
1. ገለጸ. His face mirrored his feelings. ፊቱ ፡ ስሜቱን ፡ ገለጸ
2. ቁልጭ ፡ አድርጎ ፡ አሳየ. The book mirrors life in the countryside. መጽሐፉ ፡ የገጠርን ፡ ኑሮ ፡ ቁልጭ ፡ አድርጎ ፡ ያሳያል
3. ጥላ ፡ አሳየ. The water was so still that it mirrored the trees along the bank. ውኃው ፡ በጣም ፡ የረጋ ፡ ስለነበረ ፡ በዳርቻው ፡ ያሉትን ፡ የዛፎች ፡ ጥላ ፡ አሳየ

**mirror** (n.)
1. መስታወት. Her mirror is old. መስታወቷ ፡ አሮጌ ፡ ነው
This book is a mirror of life in Ethiopia. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያሳይ ፡ መስታወት ፡ ነው
2. ምሳሌ. That soldier was a mirror of bravery. ያ ፡ ወታደር ፡ የጀግንነት ፡ ምሳሌ ፡ ነበር

**mirth** ሣቅ
His sides shook with mirth. ልቡ ፡ በሣቅ ፡ ፈረሰ

**miry** ማጥ ፡ የበዛበት
He couldn't press forward because of the miry road. መንገዱ ፡ ማጥ ፡ የበዛበት ፡ ስለሆነ ፡ ሊገሰግስ ፡ አልቻለም

**misadventure** መጥፎ ፡ ዕድል ፤ መጥፎ ፡ ነገር ፤ የደረሰበት ፡ ችግር
They failed through misadventures, not from lack of skill. ችሎታ ፡ አጥተው ፡ ሳይሆን ፡ በመጥፎ ፡ ዕድል ፡ ምክንያት ፡ ወደቁ
We had several misadventures on the trip. በጉዞው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ መጥፎ ፡ ነገሮች ፡ አጋጥመውን ፡ ነበር
She spoke in a merry vein of her misadventure. ስለደረሰባት ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ እየቀለደች ፡ ተናገረች

**misalliance** ያላቻ ፡ ጋብቻ
A misalliance should not become a marriage. ያላቻ ፡ ጋብቻ ፡ ትዳር ፡ አይሆንም

**misapprehend** በደንብ ፡ አልገባ(ውም)
+The workers misapprehended the orders given by the boss. ሠራተኞቹ ፡ አለቅቆው ፡ የሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ በደንብ ፡ አልገባቸውም

**misapprehension** ሳይገባው ፡ መቅረት
Their misapprehension of the orders caused a delay in the work. ትእዛዙ ፡ ሳይገባቸው ፡ መቅረቱ ፡ ሥራው ፡ እንዲዘገይ ፡ አደረገ

**misappropriate** አጕደለ
The treasurer has misappropriated the club funds. ገንዘብ ፡ ያዢው ፡ የክበቡን ፡ ገንዘብ ፡ አጕደለ

**misbehave** ባለገ
The children misbehave when their father is away. ልጆቹ ፡ አባታቸው ፡ ሳይኖር ፡ ይባልጋሉ

**miscalculate** አጉል ፡ ገመተ
He miscalculated the distance he had to jump. መዝለል ፡ የነበረበትን ፡ ርቀት ፡ አጉል ፡ ገመተ

**miscarriage**
*She is in the hospital as a result of a miscarriage. ስላስወረዳት ፡ ሆስፒታል ፡ ገብታለች

**have a miscarriage** አስወረዳት
She had a miscarriage and had to go to the hospital. ስላስወረዳት ፡ ሆስፒታል ፡ መሄድ ፡ ነበረባት

**miscarry** (miscarried)
1. አስወረዳት. Our neighbor's wife miscarried, and had to go to the hospital. የጐረቤታችን ፡ ባለቤት ፡ ስላስወረዳት ፡ ሆስፒታል ፡ መሄድ ፡ ነበረባት
2. ተጨናገፈ. I am prepared to admit that my plan has miscarried. የሐሳቤን ፡ መጨናገፍ ፡ ለማመን ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ

**miscellaneous** (= adv.) በየዓይነቱ
He owns a miscellaneous collection of Ethiopian-made things. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የተሠሩ ፡ ነገሮች ፡ በየዓይነቱ ፡ ሰብስቧል

**mischief**
1. ተንኰል. A child's mischief may cause a serious fire. የልጅ ፡ ተንኰል ፡ ከባድ ፡ ቃጠሎ ፡ ሊያስነሣ ፡ ይችላል
2. ጉዳት. People who tell tales about others can do great mischief. አሳባቂዎች ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ሊያደርሱ ፡ ይችላሉ

**you little mischief!** አንተ ፡ ክይሲ
You little mischief! You tore my book. አንተ ፡ ክይሲ ! መጽሐፌን ፡ ቀደድክ

**mischievous**
1. ተጫዋች. The mischievous puppy amused us greatly. ተጫዋቿ ፡ ቡችላ ፡ በጣም ፡ አሣቀችን
2. የተንኰለኞች. Mischievous slander cost him his job. የተንኰለኞች ፡ አሉባልታ ፡ ሥራውን ፡ አሳጣው

**misconceive** በትክክል ፡ አልተረዳ(ውም)
He misconceived the problem. ችግሩን ፡ በትክክል ፡ አልተረዳውም

**misconception** አለማወቅ
Many mistakes result from misconceptions. ካለማወቅ ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ስሕተት ፡ ይደርሳል

**misconduct**
1. መጥፎ ፡ አመል. He was punished for his misconduct. በመጥፎ ፡ አመሉ ፡ ተቀጣ
2. ጥፋት. I'm honor bound to report your misconduct to the police. ጥፋትህን ፡ ለፖሊስ ፡ እንድገልጽ ፡ ኀሊናዬ ፡ ያስገድደኛል
[See also 'flagrant']

**misconstrue** በስሕተት ፡ ተረዳ(ው)
He misconstrued her silence as approval. ዝምታዋን ፡ እንደ ፡ መስማማት ፡ አድርጎ ፡ በስሕተት ፡ ተረዳው

**misdemeanor** አነስተኛ ፡ ወንጀል
It is a misdemeanor to throw litter in the streets. ቆሻሻ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ መጣል ፡ አነስተኛ ፡ ወንጀል ፡ ነው

**miser** ንፉግ
A miser does not spend money on his children. ንፉግ ፡ ለልጆቹ ፡ ገንዘብ ፡ አያወጣም

**miserable**
1. አሰቃቂ. He talked about the miserable life of the refugees after the war. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ስደተኞቹ ፡ ስለነበሩበት ፡ አሰቃቂ ፡ ኑሮ ፡ አወራ
2. መጥፎ. What a miserable meal that was! ምን ፡ ዓይነት ፡ መጥፎ ፡ ምግብ ፡ ነበር
3. ደሳሳ. They live in a miserable shack. ደሳሳ ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ
4. ብስጩ. A sick child is often miserable. የታመመ ፡ ልጅ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ብስጩ ፡ ነው

**feel miserable** ቀፈፈ(ው)
I feel miserable today; my stomach is upset. ዛሬ ፡ ሆዴን ፡ ስላመመኝ ፡ ቀፎኛል

**make miserable**
She makes life miserable for him. ኑሮውን ፡ መከራ ፡ ታደርግበታለች

**miserly** ጩቅ
This is a novel about a miserly man. ይህ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ጩቅ ፡ የሚናገር ፡ ነው
**miserly habits** ንፉግነት
His miserly habits are noticed by everybody. የሱ ፡ ንፉግነት ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ታውቋል
**in a miserly fashion** በሥሥት
He lives in a miserly fashion. በሥሥት ፡ ይኖራል

**misery** (miseries)
1. ችግር. The poor live in misery; they lack everything. ምንም ፡ ነገር ፡ ስለሌላቸው ፡ ድኾች ፡ በችግር ፡ ይኖራሉ
2. ችግረኛነት. Some people rose from misery to fortune. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከችግረኛነት ፡ ተነሥተው ፡ ሀብታሞች ፡ ሆኑ
3. መከራ. Misery follows war. መከራ ፡ ጦርነትን ፡ ይከተላል
4. ሥቃይ. The misery of loneliness was now compounded by his poverty. ድኽነት ፡ የብቸኝነት ፡ ሥቃይን ፡ አባሰበት
**be in misery** በጣም ፡ ተሠቃየ
He was in misery from a toothache. በጥርስ ፡ ሕመም ፡ በጣም ፡ ይሠቃይ ፡ ነበር

**misfire** ከሸፈ
The gun misfired, and the deer ran away. ጥይቱ ፡ በመክሸፉ ፡ አጋዘኑ ፡ አመለጠ
Our plans misfired, and the criminal got away. እቅዶቻችን ፡ ስለከሸፉ ፡ ወንጀለኛው ፡ አመለጠ

**misfit** ከሰው ፡ ጋር ፡ የማይግባባ ፡ ሰው
A misfit never finds friends. ከሰው ፡ ጋር ፡ ለማይግባባ ፡ ሰው ፡ ጓደኛ ፡ የለውም
**be a misfit** ልክ ፡ አልሆነውም
His coat was a misfit and his trousers baggy. ኮቱ ፡ ልክ ፡ አልሆነውም ፤ ሱሪውም ፡ ሰፍቶበታል

**misfortune**
1. መከራ. He commiserated with his friend on his misfortunes. ወዳጁ ፡ ለደረሰበት ፡ መከራ ፡ ሐዘኑን ፡ ገለጸ
2. መጥፎ ፡ ዕድል. He is brooding all day long over his misfortunes. በመጥፎ ፡ ዕድሉ ፡ ሙሉ ፡ ቀን ፡ በሐዘን ፡ ሲተክዝ ፡ ይውላል
3. ክፉ ፡ ቀን. Misfortune tests a person's character. ክፉ ፡ ቀን ፡ የሰውን ፡ ጠባይ ፡ ይፈትናል

**be a misfortune**
1. ጐዳ. It won't be a great misfortune if you don't get it. ባታገኘውም ፡ ብዙ ፡ አይጐዳ ህም
2. ዕጣ ፡ ከዳ(ው). It was his misfortune to be killed in the war. በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ የሞተው ፡ ዕጣ ፡ ከድቶት ፡ ነው
**suffer misfortune** መከራ ፡ ደረሰ(በት)
He suffered great misfortune when his wife died. ሚስቱ ፡ በሞተች ፡ ጊዜ ፡ ትልቅ ፡ መከራ ፡ ደረሰበት

**misgivings** ጥርጣሬ
He had no misgivings about his ability. ስለ ፡ ችሎታው ፡ ጥርጣሬ ፡ አልነበረውም
**have misgivings** ቅር ፡ አለ(ው)
We had some misgivings about hiring a servant who was suspected of theft. በሌብነት ፡ የተጠረጠረ ፡ አሽከር ፡ ለመቅጠር ፡ ጥቂት ፡ ቅር ፡ ብሎን ፡ ነበር

**misguide** አሳሳተ
The lawyer misguided his clients about the inheritance. ስለ ፡ ውርሱ ፡ ጉዳይ ፡ ጠበቃው ፡ ደንበኞቹን ፡ አሳሳታቸው

**mishandle**
1. አጕላላ. The night watchman mishandled the dog. ዘበኛው ፡ ውሻውን ፡ አጕላላው
2. በሚገባ ፡ አልጠበቀም. The heirs mishandled the estate. ወራሾቹ ፡ ርስቱን ፡ በሚገባ ፡ ሳይጠብቁት ፡ ቀሩ

**mishap**
1. አደጋ. The mishap was reported in the papers. አደጋው ፡ በጋዜጦች ፡ ተገልጾ ፡ ነበር
2. ጥፋት. The spilling of the sauce was his only mishap. ያደረሰው ፡ ጥፋት ፡ ወጥ ፡ መድፋት ፡ ብቻ ፡ ነው

**misinform** ውሸት ፡ ነገረ
He deliberately misinformed his employer about the situation. ለቀጣሪው ፡ ስለ ፡ ሁኔታው ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ውሸት ፡ ነገረው

**misinformation** የተሳሳተ ፡ መረጃ
His report is a hodgepodge of lies and misinformation. ሪፖርቱ ፡ ውሸትና ፡ የተሳሳተ ፡ መረጃ ፡ የተቀላቀለበት ፡ ነው

**misinterpret**
1. በስሕተት ፡ ተረጐመ. He misinterpreted his silence as giving consent. ዝምታውን ፡ ተስማምቷል ፡ በማለት ፡ በስሕተት ፡ ተረጐመው

2. በመጥፎ ፡ አየ. He misinterpreted my intentions and was offended. ሐሳቤን ፡ በመጥፎ ፡ ስላየው ፡ ቅር ፡ ተሰኘ

**misjudge**

1. በስሕተት ፡ ገመተ. He misjudged the distance and fell into the water. ርቀቱን ፡ በስሕተት ፡ በመገመቱ ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ

2. በተሳሳተ ፡ አስተያየት ፡ ገመተ. I have misjudged his character. ጠባዩን ፡ በተሳሳተ ፡ አስተያየት ፡ ገመትኩ

3. ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ገመተ. We mustn't misjudge the seriousness of the situation. የሁኔታውን ፡ አሳሳቢነት ፡ ዝቅ ፡ አድርገን ፡ መገመት ፡ የለብንም

4. (= intr.) ተሳሳተ. You misjudge him if you think he is trying to hurt you. ሊጐዳኝ ፡ ያስባል ፡ ብለህ ፡ እንደሆነ ፡ ተሳስተሃል

**mislaid**, see **mislay**

**mislay** (mislaid) የት ፡ እንዳስቀመጠው ፡ አላወቀም

I've mislaid my glasses. መነጽሬን ፡ የት ፡ እንዳስቀመጥኩ ፡ አላውቅም

**mislead** (misled)

1. በስሕተት ፡ መራ. Our guide misled us in the woods, and we got lost. መንገድ ፡ መሪያችን ፡ በስሕተት ፡ ስለመራን ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ ገብተን ፡ ጠፋን

2. አሳሳተ. He misled me into thinking that I could buy the house cheaply. ቤቱን ፡ በርካሽ ፡ ለመግዛት ፡ የምችል ፡ በማስመሰል ፡ አሳሳተኝ

3. አበላሸ. Bad companions often mislead young people. አጉል ፡ ጓደኞች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ወጣቶችን ፡ ያበላሻሉ

**misleading** አሳሳች

The description is misleading. መግለጫው ፡ አሳሳች ፡ ነው

**mismanage** በመጥፎ ፡ አመራር ፡ መራ

He mismanaged his father's store and soon became bankrupt. ያባቱን ፡ መደብር ፡ በመጥፎ ፡ አመራር ፡ ስለመራው ፡ ወዲያውኑ ፡ ከሰረ

**misplace** ያለቦታው ፡ አኖረ

He misplaced the book of poems in the science section. የግጥሙን ፡ መጽሐፍ ፡ ያለቦታው ፡ ከሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ክፍል ፡ አኖረው

**misprint** የኅትም ፡ ስሕተት

This word is not a real word; it is only a misprint. ይህ ፡ ቃል ፡ ትክክል ፡ አይደለም ፤ የኅትም ፡ ስሕተት ፡ ነው

**mispronounce** በተሳሳተ ፡ ሁኔታ ፡ አነበበ

Some foreigners mispronounce Amharic words. አንዳንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ያማርኛ ፡ ቃላትን ፡ በተሳሳተ ፡ ሁኔታ ፡ ያነቧቸዋል

**misquote** ያላለውን ፡ አለ

The student misquoted the teacher in reporting the accident. ተማሪው ፡ አደጋውን ፡ በሚያስረዳበት ፡ ጊዜ ፡ መምህሩ ፡ ያላለውን ፡ አለ

**misread** (misread)

1. ሲያነብ ፡ ተሳሳተ. She misread the recipe and spoiled the cake. የምግብ ፡ አሠራር ፡ መምሪያውን ፡ ስታነብ ፡ ስለተሳሳተች ፡ ኬኩን ፡ አበላሸችው

2. አልገባውም. She sometimes misreads my expression and thinks I am angry. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የፊቴ ፡ ሁኔታ ፡ ሳይገባት ፡ የተናደድኩ ፡ ይመስላታል

**misrepresent** በማይገባ ፡ ሁኔታ ፡ አቀረበ

The salesman misrepresented the product. አሻሻጩ ፡ እቃውን ፡ በማይገባ ፡ ሁኔታ ፡ አቀረበ

**miss** (v.)

1. አመለጠ(ው). +I missed the first part of his speech. የንግግሩ ፡ የመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ አመለጠኝ

+Do you think I'll miss my train? ባቡሩ ፡ የሚያመልጠኝ ፡ ይመስልሃል ?

+I missed the chance of a ride to town. ወደ ፡ ከተማ ፡ በመኪና ፡ የመሄድ ፡ ዕድል ፡ አመለጠኝ

2. ቀረ. He missed school for a week. ላንድ ፡ ሳምንት ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀረ

3. አላየም. I missed the beginning of the race. የውድድሩን ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ አላየሁትም

4. አልገባውም. +You missed the point of the story. የታሪኩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ አልገባህም

5. ሳተ. Our house is so easy to find, you can't miss it. ቤታችን ፡ በቀላሉ ፡ ስለሚገኝ ፡ ልትስተው ፡ አትችልም

He fired, but missed the target. ተኰሰ ፡ ዒላማውን ፡ ሳተ

6. ናፈቀ ፤ ናፈቀ(ው). I'll miss you terribly. በጣም ፡ እናፍቅሃለሁ

+He is a precious friend, and I shall miss him when he leaves. የሚወደድ ፡ ጓደኛ ፡ ስለሆነ ፡ ሲሄድ ፡ ይናፍቀኛል

7. መጥፋቱን ፡ ዐወቀ. When did you miss your briefcase? ቦርሳህ ፡ መጥፋቱን ፡ መቼ ፡ ዐወቅህ ?

**miss** (n.)

*His first shot was a miss. የመጀመሪያውን ፡ ተኰሰ ፡ ሳተ

[See also 'hit']

**Miss** ወይዘሪት
Did you see Miss Laqetch? ወይዘሪት ፡ ላቀችን ፡ አየሃት ?

**misshapen** የተበላሸ
His misshapen body results from an accident in his youth. የሰውነቱ ፡ ቅርጽ ፡ የተበላሸው ፡ በልጅነቱ ፡ በደረሰበት ፡ አደጋ ፡ ምክንያት ፡ ነው

**(be) missing**
1. ጠፋ. The child has been missing for three days. ልጁ ፡ ከጠፋ ፡ ሦስት ፡ ቀኑ ፡ ነው
2. ጐደለ. There are two pages missing in this book. ከዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ገጽ ፡ ጐድሏል
3. ቀረ. Four children were missing from class today. ዛሬ ፡ አራት ፡ ልጆች ፡ ከክፍል ፡ ቀር ተዋል
[See also 'action']

**mission**
1. መልእክት. He completed his mission successfully. መልእክቱን ፡ በሚገባ ፡ አከናወነ
2. መልእክተኞች. The Japanese trade mission visited Ethiopia. የጃፓን ፡ የንግድ ፡ መልእክተኞች ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጐበኙ
3. ተልእኮ. The mission of the troops is to catch a band of robbers. የወታደሮቹ ፡ ተልእኮ ፡ የቀማኞችን ፡ ጓድ ፡ መያዝ ፡ ነው
4. ዓላማ. His mission in life is to help the poor. የሕይወቱ ፡ ዓላማ ፡ ድኾችን ፡ መርዳት ፡ ነው
5. ሚስዮን. There is a Catholic mission near here. በዚህ ፡ አቅራቢያ ፡ አንድ ፡ የካቶሊክ ፡ ሚስዮን ፡ አለ

**go on a mission** ዘመተ
The chaplain who went on a mission with the soldiers gave the blessing. ከወታደሮቹ ፡ ጋር ፡ የዘመቱት ፡ ቄስ ፡ ቡራኬ ፡ ሰጡ

**missionary** (missionaries)
1. የወንጌል ፡ ሰባኪ. Missionaries disseminate the Christian belief all over the world. የወንጌል ፡ ሰባኪዎች ፡ የክርስቲያንን ፡ እምነት ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ያሰራጫሉ
2. ሚስዮናዊ. Missionaries are trying to convert the pagans. ሚስዮናውያን ፡ አረመኔዎችን ፡ ለማሳመን ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ናቸው

**misspell** ሲጽፍ ፡ ፊደሉን ፡ አሳሳተ
He misspelled the word "rhinoceros". አውራሪስ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ሲጽፍ ፡ ፊደሉን ፡ አሳሳተ

**misspent** የባከነ
He mourned his misspent youth. በባከነው ፡ የወጣትነት ፡ ዘመኑ ፡ ተጸጸተ

**mist** (v.)
*Tears misted her eyes. ዐይኖቿ ፡ እንባ ፡ አቀረሩ

**mist** (n.) ጭጋግ
The hills are hidden in the mist. ኮረብታዎቹ ፡ በጭጋግ ፡ ተሸፍነዋል

**mistake** (mistook), v. አልገባ(ውም)
+You mistake his real purpose. ትክክለኛው ፡ ዓላማው ፡ አልገባህም
*Please don't mistake me! የምለውን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አትተርጉመው
*Sorry, I mistook you for someone else. አዝናለሁ ፤ ሌላ ፡ ሰው ፡ መስለኸኝ ፡ ነው

**mistake** (n.)
1. ስሕተት. How could I make such a mistake? እንዴት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ ላደርግ ፡ እችላለሁ ?
Sorry, I took it by mistake. አዝናለሁ ፤ በስሕተት ፡ ነው ፡ የወሰድኩት
2. ጥፋት. I am sorry; it's my mistake. አዝናለሁ ፤ የኔ ፡ ጥፋት ፡ ነው

**make a mistake** ተሳሳተ
He made a mistake when he married her. እሷን ፡ ማግባቱ ፡ ተሳሳተ

**mistaken** (adj.) የተሳሳተ
That's a mistaken belief. የተሳሳተ ፡ እምነት ፡ ነው
A mistaken person should admit that he was wrong. የተሳሳተ ፡ ሰው ፡ መሳሳቱን ፡ ማመን ፡ አለበት

**be mistaken** ተሳሳተ
With regard to what you say about the French, there you are mistaken. ስለ ፡ ፈረንሳይ ፡ በተናገርከው ፡ ነገር ፡ ተሳስተሃል

**be mistaken for**
*He's often mistaken for his twin brother. እሱንና ፡ መንታ ፡ ወንድሙን ፡ ያሳስቷቸዋል
*He is often mistaken for an American. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡ አሜሪካዊ ፡ ይመስላቸዋል

**mistaking** ጥርጥር
There is no mistaking what we ought to do. መሥራት ፡ ስላለብን ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ ጥርጥር ፡ የለም
*There's no mistaking his intention. ዓላማው ፡ ስውር ፡ አይደለም

**Mister,** see **Mr.**

**mistook,** see **mistake**

**mistranslate** አሳስቶ ፡ ተረጐመ
He mistranslated the passage and got a bad grade. ምንባቡን ፡ አሳስቶ ፡ ስለተረጐመው ፡ መጥፎ ፡ ማርክ ፡ አገኘ

**mistreat**
1. በደለ. He mistreated the children. ልጆቹን ፡ በደላቸው
2. አሠቃየ. His wife mistreats him because he is so meek. ጠባዩ ፡ ለስላሳ ፡ ስለሆነ ፡ ሚስቱ ፡ ታሠቃየዋለች

**mistress**
1. እመቤት. Servants obey a kind mistress. አሽከሮች ፡ ለደግ ፡ እመቤት ፡ ይታዘዛሉ
2. ዕቁባት. He considered her his mistress. ዕቁባቱ ፡ አድርጎ ፡ ቈጠራት

**mistrust** (v.) ተጠራጠረ ፤ አላመነም
He mistrusts my intentions. ሐሳቤን ፡ ይጠራጠራል
I mistrust the story he told about his discovery. ስለ ፡ ፍልስፍናው ፡ የተናገረውን ፡ ታሪክ ፡ አላምንም ፡ (እጠራጠራለሁ)

**mistrust** (n.) አለመተማን
Mistrust prevents them from reaching an agreement. አለመተማመን ፡ ከስምምነት ፡ እንዳይደርሱ ፡ ያደርጋቸዋል

**feel mistrust of** ተጠራጠረ
He felt mistrust of the stranger. እንግዳውን ፡ ሰው ፡ ተጠራጠረው

**(be) misty**
1. ጭጋግ ፡ በዛ(በት) ፤ ጉም ፡ በዛ(በት). August is misty. ነሐሴ ፡ ጭጋግ ፡ (ጉም) ፡ ይበዛበታል
2. እንባ ፡ አዘለ. She didn't cry, but her eyes were misty. አላለቀሰችም ፤ ዓይኖቿ ፡ ግን ፡ እንባ ፡ አዝለው ፡ ነበር

**misunderstand** (misunderstood)
1. በደንብ ፡ አልተረዳም. First of all, you misunderstood me. መጀመሪያ ፡ ነገር ፡ በደንብ ፡ አልተረዳኸኝም
2. አልገባ(ውም). +You misunderstood when I said that I was coming on Tuesday. ማክሰኞ ፡ እመጣለሁ ፡ ያልኩህ ፡ አልገባህም
*Don't misunderstand me! የምለው ፡ ይግባህ

**misunderstanding**
1. አለመግባባት. They are trying to clear up the misunderstanding between Poland and Czechoslovakia. በፖላንድና ፡ በቼኮዝሎቫኪያ ፡ መካከል ፡ የተፈጠረውን ፡ አለመግባባት ፡ ለማስወገድ ፡ በመጣር ፡ ላይ ፡ ናቸው
2. በደንብ ፡ አለመረዳት. Her misunderstanding of the recipe caused her to make a mess of the cake. የምግብ ፡ አሠራሩን ፡ መምሪያ ፡ በደንብ ፡ ባለመረዳቷ ፡ ኬኩ ፡ ተበላሸ

**misuse**
1. አጕሳቈለ. He misuses his horses by giving them loads that are too heavy. ከመጠን ፡ በላይ ፡ ከባድ ፡ የሆኑ ፡ ጭነቶች ፡ በመጫን ፡ ፈረሶቹን ፡ ያጕሳቍላቸዋል
2. ያለ ፡ አግባብ ፡ አወጣ. He misused public funds to buy a car for himself. ለራሱ ፡ መኪና ፡ ለመግዛት ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ አወጣ
3. ያለ ፡ አግባብ ፡ ተጠቀመ(በት). He doesn't know Amharic well and misuses the words. አማርኛ ፡ በደንብ ፡ ስለማያውቅ ፡ ቃላቱን ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ ይጠቀምባቸዋል

**mitigate** አሻሻለ
He asked the judge to mitigate his sentence. ዳኛው ፡ ፍርዱን ፡ እንዲያሻሽሉለት ፡ ጠየቀ

**mitigating**
*There are no mitigating circumstances for your behavior. የሠራኸው ፡ ሥራ ፡ ሊታለፍ ፡ አይችልም

**mix** (vt.)
1. አቀላቀለ. I mixed yellow and red. ብጫና ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ አቀላቀልኩ
2. ደባለቀ. Don't mix business with pleasure! ሥራን ፡ ከጨዋታ ፡ አትደባልቅ
3. ጨመረ. The servant mixed a little oil into the dough. ገረዲቷ ፡ ሊጡ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂት ፡ ዘይት ፡ ጨመረች
4. ለወሰ. He mixed pepper with bile. በርበሬውን ፡ በአሞት ፡ ለወሰው

**mix** (vi.)
1. ተዋሐዳ. Water and oil don't mix. ውኃና ፡ ዘይት ፡ ሊዋሐዱ ፡ አይችሉም
2. ተስማማ. The two colors mix very well. እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ቀለሞች ፡ በሚገባ ፡ ይስማማሉ
3. ጥልቅ ፡ አለ. She likes to mix in other people's business. በሰው ፡ ነገር ፡ ጥልቅ ፡ ማለት ፡ ትወዳለች

**mix in** ጥልቅ ፡ አለ
Don't mix in. This is none of your business. ጥልቅ ፡ አትበል ፤ አያገባህም

**mix up**
1. አደበላለቀ. He has mixed up everything. ሁሉንም ፡ አደበላልቆታል
2. አመሳቀለ. Don't mix up the cards! ካርታውን ፡ አታመሳቅል

**mix (one) up**
1. አገባ. Don't mix me up in your argument! ጭቅጭቃችሁ ፡ ውስጥ ፡ አታግቡኝ
2. አደናገረ. His explanation mixed me up completely; I can't understand the problem at all. የሱ ፡ አገላለጽ ፡ ጭራሽ ፡ አደናገረኝ ፤ ፕሮብሌሙን ፡ በፍጹም ፡ ልረዳው ፡ አልችልም

**(be) mixed up** ተገኘ(በት)
The mayor is mixed up in the scandal. በመጥፎ ፡ ድርጊት ፡ ውስጥ ፡ ከንቲባውም ፡ ይገኝበታል

**(be all) mixed up**
1. ተማታ(በት). I'm all mixed up. Is he coming on Tuesday or Friday? ተማቶብኛል ፤ የሚመጣው ፡ ማክሰኞ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ዓርብ ?
2. ተመሰቃቀለ. The books are all mixed up, and it took me some time to sort them out. መጽሐፎቹ ፡ ተመሰቃቅለው ፡ ስለነበር ፡ በየመልኩ ፡ ለማስቀመጥ ፡ ጊዜ ፡ ወሰደብኝ

**(get) mixed up** ገጠመ
Don't get mixed up with that gang! ከነዚህ ፡ ዱሪዬዎች ፡ ጋር ፡ አትግጠም

**mix well** ተግባባ
He mixes well with all kinds of people. ከማንም ፡ ጋር ፡ ይግባባል

**mixed** (adj.)
1. የተደባለቀ. He bought three boxes of mixed nuts. ሦስት ፡ ሣጥን ፡ የተደባለቀ ፡ ገውዝ ፡ ገዛ
2. የተለያዩ ፡ ሰዎች ፡ የሚኖሩበት. He lives in a mixed neighborhood. የተለያዩ ፡ ሰዎች ፡ የሚኖሩበት ፡ አካባቢ ፡ ይኖራል
3. የመንግሥትና ፡ የግል ፡ አቋም ፡ ያለበት. The mixed economy of the country proved to be fairly successful. የመንግሥትና ፡ የግል ፡ አቋም ፡ ያለበት ፡ ያገሪቱ ፡ ኤኮኖሚ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ አሳየ

**mixture**
1. ቅልቅል. This drink is a mixture of fruit juices. ይህ ፡ መጠጥ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍሬዎች ፡ ጭማቂ ፡ ቅልቅል ፡ ነው
2. ድብልቅ. Nigerians are a mixture of several different ethnic groups. ናይጄሪያውያን ፡ የብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጐሳዎች ፡ ድብልቅ ፡ ናቸው
3. የተቀመመ ፡ መድኃኒት. He takes a special cough mixture for his cold. ለጉንፋኑ ፡ በተለይ ፡ የተቀመመ ፡ የሳል ፡ መድኃኒት ፡ ይወስዳል
[See also 'indiscriminate']

**mix-up** ምስቅልቅል
That was an awful mix-up. ያ ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ ምስቅልቅል ፡ ነበር

**moan** (v.) አቃሰተ
I could hear him moaning in the next room. እሚቀጥለው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ሲያቃስት ፡ እሰማው ፡ ነበር

**moan** (n.) ማቃሰት
His moans disturbed me all night long. የሱ ፡ ማቃሰት ፡ ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ አወከኝ

**moat** [በጥንት ፡ ዘመን ፡ ጠላት ፡ እንዳይገባ ፡ ለመከላከል ፡ በግምብ ፡ ዙሪያ ፡ የሚቈፈር ፡ ጥልቀትና ፡ ስፋት ፡ ያለው ፡ ጉድጓድ]

**mob** (mobbed), v. ወረረ
The crowd mobbed the consulate. ሕዝቡ ፡ ቆንስላውን ፡ ወረረው
Spectators mobbed the courtroom. ተመልካቾች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ወረሩት

**be mobbed**
*The stores are always mobbed right before Christmas. ገና ፡ ሲደርስ ፡ መደብሮች ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ይሆናሉ

**mob** (n.) ሕዝብ ፤ የሚረብሽ ፡ ሕዝብ ፤ ሲተራመስ ፡ የነበረ ፡ ሕዝብ
He barely escaped being beaten by the mob. ከሕዝቡ ፡ ድብደባ ፡ ለትንሽ ፡ አመለጠ
The soldiers were forced to the extremity of firing to scatter the mob. ወታደሮቹ ፡ የሚረብሸውን ፡ ሕዝብ ፡ ለመበተን ፡ ተኩስ ፡ መክፈት ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው
The mob almost lynched him. ሲተራመስ ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ሊገድለው ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር

**mobile** ተዘዋዋሪ
The Ministry of Education organized two mobile libraries. ትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ሁለት ፡ ተዘዋዋሪ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አዘጋጅቷል
*She has mobile features. ፊቷ ፡ ይለዋወጣል

**mobilization** የክተት ፡ ሰራዊት ፡ ትእዛዝ
Mobilization was decreed by the Emperor. የክተት ፡ ሰራዊት ፡ ትእዛዝ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ታወጀ

**mobilize**
1. አስከተተ. The President mobilized the armed forces. ፕሬዚዳንቱ ፡ የጦር ፡ ኀይሉን ፡ አስከተተ
2. ለመንግሥት ፡ ተግባር ፡ አዋለ. The President mobilizes industry in time of war. በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ኢንዱስትሪዎችን ፡ ለመንግሥት ፡ ተግባር ፡ ያውላቸዋል

**be mobilized** ተከተተ
The army was mobilized to meet the attack. ወራሪውን ፡ ለመቋቋም ፡ ሰራዊት ፡ ተከተተ

**mock** (v.)
1. አላገጠ(በት)፤ አፌዘ(በት)፤ አሾፈ(በት). The boys mocked the blind man. ልጆቹ ፡ ዕውሩን ፡ ሰውዬ ፡ አላገጡበት ፡ (አፌዙበት ፤ አሾፉበት)
2. አፌረሰ. His actions mock convention. አድራጎቱ ፡ ልማድን ፡ ያፈርሳል

**mock at** እንደ ፡ ቀልድ ፡ ቈጠረ
He mocked at the idea of a peaceful settlement. የሰላማዊ ፡ ውሳኔ ፡ ጉዳይን ፡ እንደ ፡ ቀልድ ፡ ቈጠረው

**mock** (adj.) የቀልድ
The dance represented a mock battle. ጭፈራው ፡ የቀልድ ፡ ጦርነት ፡ ይመስል ፡ ነበር

**mockery**
1. የመቀለድ ፡ ያህል. His trial was a mockery of justice. ፍርዱ ፡ በሕግ ፡ የመቀለድ ፡ ያህል ፡ ነበር
2. ፌዝ. Their mockery and insults made me cry. ፌዛቸውና ፡ ስድባቸው ፡ አስለቀሰኝ
3. መሳለቂያ. Through his foolishness, he became the mockery of the village. በጅልነቱ ፡ ምክንያት ፡ የመንደሩ ፡ መሳለቂያ ፡ ሆነ

**mode**
1. ሞድ. He dresses in the latest mode. አዲስ ፡ የወጣውን ፡ ሞድ ፡ ይለብሳል
2. ዘዴ. Riding on a donkey is a mode of travel. አህያ ፡ መቀመጥ ፡ የመጓጓዣ ፡ ዘዴ ፡ ነው

**model** (v.)
1. ምስል ፡ ሠራ. He modeled the minister's head in clay. የሚኒስትሩን ፡ ራስ ፡ ምስል ፡ በሸክላ ፡ ሠራ
2. በመከተል ፡ አደራጀ. He modeled his strategy on Napoleon's. የናፖሊዮንን ፡ የጦር ፡ ስልት ፡ በመከተል ፡ የጦር ፡ ዘዴውን ፡ አደራጀ
3. ሞዴል ፡ አሳየ. They model dresses in this shop. እዚህ ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ የልብስ ፡ ሞዴል ፡ ያሳያሉ

**model oneself** መንገድ ፡ ተከተለ
He modeled himself after his hero. የሚያደንቀውን ፡ ጀግና ፡ መንገድ ፡ ተከተለ

**model** (n.)
1. ሞዴል. He is working on the model of a bridge. የድልድይ ፡ ሞዴል ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ ነው
His sister works as a model. እኅቱ ፡ ሞዴል ፡ ሆና ፡ ትሠራለች
2. አርአያ. His behavior is a model for others. ምግባሩ ፡ ለሌሎች ፡ አርአያ ፡ ነው
3. ዓይነት. I want a dress like yours because the model is becoming to me. ዓይነቱ ፡ ስለሚስማማኝ ፡ ያንቺ ፡ ዓይነት ፡ ልብስ ፡ መልበስ ፡ እፈልጋለሁ

**model** (adj.) ምሳሌ ፡ የሆነ
A model farm was set up to spread new farming methods. አዲስ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴዎችን ፡ ለማስፋፋት ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆን ፡ እርሻ ፡ ተቋቋመ
*She is a model housewife. የቤት ፡ ቁንጮ ፡ ናት

**moderate** (v.)
1. በሊቀ ፡ መንበርነት ፡ መራ. We need someone to moderate our meeting. ስብሰባችንን ፡ በሊቀ ፡ መንበርነት ፡ የሚመራልን ፡ ሰው ፡ ያስፈልገናል
2. ለስለስ ፡ አደረገ. During the argument, he moderated his views. በክርክሩ ፡ ጊዜ ፡ ሐሳቡን ፡ ለስለስ ፡ አደረገ

**moderate** (n.) መሀከለኛ ፡ የሆነ
The radicals got many of the moderates to follow them. ተራማጆቹ ፡ በፖለቲካ ፡ አስተያየታቸው ፡ መሀከለኞች ፡ የሆኑት ፡ እንዲከተሏቸው ፡ አደረጉ

**moderate** (adj.)
1. መጠነኛ. He is a moderate drinker. መጠነኛ ፡ ጠጪ ፡ ነው
He has a moderate income and cannot afford to buy a house. ገቢው ፡ መጠነኛ ፡ ስለሆነ ፡ ቤት ፡ ለመግዛት ፡ አይችልም
2. መካከለኛ. His political views are moderate. የፖለቲካ ፡ አስተያየቱ ፡ መካከለኛ ፡ ነው
3. ለስለስ ፡ ያለ. He wrote a moderate reply to my angry letter. በንዴት ፡ ለጻፍኩት ፡ ደብዳቤ ፡ ለስለስ ፡ ያለ ፡ መልስ ፡ ጻፈ
4. ደኅና. Wheat is sold today at moderate prices. ዛሬ ፡ ስንዴ ፡ በደኅና ፡ ዋጋ ፡ ይሸጣል
He has moderate success as a painter. በሠዓሊነት ፡ ደኅና ፡ ስም ፡ አለው

**moderately**
1. ለስለስ ፡ አድርጎ. They expected him to give a fiery speech, but he spoke moderately. የጋለ ፡ ንግግር ፡ ያደርጋል ፡ ብለው ፡ አስበው ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ለስለስ ፡ አድርጎ ፡ ተናገረ
2. በመጠኑ. He drank moderately. በመጠኑ ፡ ጠጣ
*He acted moderately. ትሕትና ፡ አሳየ

**moderating**
*The UN exercises a moderating influence in world affairs. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ በዓለም ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሽማግሌ ፡ ሆኖ ፡ ይሠራል

**moderation** (= verbal noun) መመጠን
Moderation is necessary in eating. አበላልን ፡ መመጠን ፡ ያስፈልጋል

**practice moderation** መጠነ
People who are too fat must practice moderation in what they eat. በጣም ፡ ወፍራም ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የሚመገቡትን ፡ መመጠን ፡ አለባቸው

**with moderation** በመጠኑ
Eat and drink with moderation! በመጠኑ ፡ ብላ ፡ ጠጣ

**moderator** የውይይት ፡ መሪ
The moderator kept the two men from becoming very angry at each other. የውይይቱ ፡ መሪ ፡ ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ እንዳይጣረሩ ፡ አደረገ

**modern** ዘመናዊ ፤ የዘመን
The university gives courses in modern languages. ዩኒቨርሲቲው ፡ የዘመናዊ ፡ ቋንቋዎች ፡ ትምህርት ፡ ይሰጣል
Television is a modern invention. ቴሌቪዥን ፡ ዘመናዊ ፡ ፍልሰፋ ፡ ነው
Schools should adapt their curriculum to modern needs. ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርቱን ፡ ከዘመኑ ፡ ፍላጎት ፡ ጋር ፡ ማራመድ ፡ አለባቸው

**modernization** ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ
Ethiopia is making great strides in modernization. ኢትዮጵያ ፡ በዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ታላቅ ፡ እርምጃ ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ነች

**modernize**
1. ዘመናዊ ፡ አደረገ. We must modernize our house. ቤታችንን ፡ ዘመናዊ ፡ ማድረግ ፡ አለብን
2. አሻሻለ. We must modernize English spelling. የእንግሊዝኛን ፡ ጽሕፈት ፡ ማሻሻል ፡ አለብን

**modest**
1. ትሑት. She's a very modest person. በጣም ፡ ትሑት ፡ ሰው ፡ ናት
2. መጠነኛ. Though his income is modest, he dresses well. ገቢው ፡ መጠነኛ ፡ ቢሆንም ፡ አለባበሱ ፡ ጥሩ ፡ ነው
3. አነስ ፡ ያለ. He lives in a modest little house. አነስ ፡ ባለች ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል

**modesty** ትሕትና
Everyone likes her modesty. ሁሉም ፡ ትሕትናዋን ፡ ይወዳል

**modify** (modified)
1. ለወጠ. Having learned the facts, he modified his opinion. እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ካወቀ ፡ በኋላ ፡ አስተያየቱን ፡ ለወጠ
2. አሻሻለ. The judge modified the jail sentence. ዳኛው ፡ የእስራቱን ፡ ቅጣት ፡ አሻሻለ
We must modify our requirements for admission to the university to meet the new situation. አዲሱን ፡ ሁኔታ ፡ ለመቋቋም ፡ ለዩኒቨርሲቲ ፡ መግቢያ ፡ የተደነገገውን ፡ ደንብ ፡ ማሻሻል ፡ አለብን
3. ገለጸ. In the phrase 'old man', the adjective 'old' modifies the noun 'man'. ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ በሚለው ፡ ሐረግ ፡ ውስጥ ፡ « ሽማግሌ » ፡ የሚለው ፡ ቅጽል ፡ «ሰው» ፡ የሚለውን ፡ ስም ፡ ይገልጻል

**modulate**
1. አስተካከለ. The cantor wants to modulate the hymn. ሊቀ ፡ መዘምራኑ ፡ ዜማውን ፡ ለማስተካከል ፡ ይፈልጋል
2. አለሰለሰ. He modulated his tone considerably when he discovered that it was the minister, and not the secretary, who was on the phone. በስልክ ፡ የሚያነጋግረው ፡ ጸሐፊው ፡ ሳይሆን ፡ ሚኒስትሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ድምፁን ፡ በጣም ፡ አለሰለሰ

**moist** እርጥብ
The ground is moist. መሬቱ ፡ እርጥብ ፡ ነው

**moisten** አረጠበ
He moistened his lips and went on talking. ከንፈሩን ፡ አርጥቦ ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ

**moisture**
1. ርጥበት. The moisture in the air causes mildew. ያየር ፡ ርጥበት ፡ መሻገትን ፡ ይፈጥራል
2. ተን. The heaviness of the air is due to moisture. ያየሩ ፡ ከባድነት ፡ ከተኑ ፡ የተነሣ ፡ ነው

**molar, ~ tooth** መንጋጋ
My brother does not have his molar teeth yet. የኔ ፡ ወንድም ፡ ገና ፡ መንጋጋ ፡ አላወጣም

**mold** (v.)

1. **ምስል ፡ ሠራ**. He will mold the head in clay before he makes the statue. ሐውልቱን ፡ ከመሥራቱ ፡ በፊት ፡ የራስ ፡ ምስል ፡ ከሸክላ ፡ ይሠራል
2. **አረቀ**. His father's discipline molded his character. ያባቱ ፡ አያያዝ ፡ ጠባዩን ፡ አረቀው
3. **መራ**. His speeches were intended to mold public opinion. ንግግሮቹ ፡ የሕዝብን ፡ አስተያየት ፡ ለመምራት ፡ የታሰቡ ፡ ነበሩ

**mold** (n.)

1. **ቃሊብ**. When he poured the metal in the mold, it cracked. ብረቱን ፡ ቃሊብ ፡ ላይ ፡ ሲያፈሰው ፡ ተሰነጠቀ
2. **ቅርጽ ፡ ማውጫ**. You can use this mold for the cake. ይህን ፡ ለኬኩ ፡ ቅርጽ ፡ ማውጫ ፡ ተጠቀምበት

*There was a layer of mold on the cheese. አይቡ ፡ ሻገት ፡ ዙሮበታል

*The son is formed in his father's mold. ልጅዬው ፡ አባቱን ፡ ቁርጥ ፡ ነው

**molding ክፈፍ**

The moldings around the windows of this room are made of wood. የዚህ ፡ ክፍል ፡ መስኮት ፡ ክፈፎች ፡ ከዕንጨት ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው

**(be) moldy ሻገተ**

Since the bread is moldy, throw it away. ዳቦው ፡ ስለሻገተ ፡ ጣለው

**mole ፍልፈል**

The mole heaped up the dug-out earth. ፍልፈሉ ፡ አፈሩን ፡ ቈልሎታል

**have a mole ማርያም ፡ ሳመችው**

She has a mole on her cheek. ጉንጯ ፡ ላይ ፡ ማርያም ፡ ስማታለች

**molest**

1. **አበሳጨ**. The child molested her older sister. ልጅቷ ፡ ታላቅ ፡ እኅቷን ፡ አበሳጨቻት
2. **ነዘነዘ**. The beggars molested the tourists. ለማኞቹ ፡ አገር ፡ ጐብኚዎቹን ፡ ነዘነዙዋቸው

**mollify** (mollified)

1. **አባበለ**. She mollifed the crying child. የሚያለቅሰውን ፡ ልጅ ፡ አባበለችው
2. **ቀነሰ**. He mollified his demands after he understood the situation. ሁኔታውን ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፡ ያስፈልገኛል ፡ የሚለውን ፡ ነገር ፡ ቀነሰ

**molten**

1. **ከቀለጠ ፡ ብረት ፡ የሚሠራ**. A molten statue was worshipped by idol worshippers. ከቀለጠ ፡ ብረት ፡ የሚሠራ ፡ ሐውልት ፡ ጣዖት ፡ በሚያመልኩ ፡ ሰዎች ፡ ይሰገድለት ፡ ነበር
2. **የተቀለጠ**. The molten metal cracked the mold. የተቀለጠው ፡ ብረት ፡ ቃሊቡን ፡ ሰበረው

**moment**

1. **ጊዜ**. At that moment, there was no one around. በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በአካባቢው ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አልነበረም
2. **ዕለት**. The moment of her arrival was a happy one. እሷ ፡ የምትመጣበት ፡ ዕለት ፡ የደስታ ፡ ጊዜ ፡ ነበር

**a moment**

1. **ትንሽ**. Wait a moment! ትንሽ ፡ ቆይ
2. **ለጥቂት ፡ ጊዜ**. He stood on the doorsill a moment. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ደፉ ፡ ላይ ፡ ቆመ

**a moment ago ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት**

He was here a moment ago. ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ እዚህ ፡ ነበረ

**at a moment's notice ማስታወቂያ ፡ እንደተሰጠው ፡ ወዲያውኑ**

Be ready to leave at a moment's notice! ማስታወቂያ ፡ እንደተሰጠህ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለመነሣት ፡ ተዘጋጅ

**at any moment**

1. **አሁን ፡ ካሁን**. He was afraid he would be captured at any moment. አሁን ፡ ካሁን ፡ ተያዝኩ ፡ እያለ ፡ ይበረግግ ፡ ነበር
2. **አሁን**. He will come at any moment. አሁን ፡ ይመጣል
3. **ምን ፡ ጊዜም**. This wall is so weak that it may go at any moment. ግድግዳው ፡ ልል ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል

**at the last moment ጥቂት ፡ ሲቀረው**

He arrived at the last moment. ጥቂት ፡ ሲቀረው ፡ መጣ

**at the moment ለጊዜው ፤ አሁን**

At the moment, I can't give you any further information. ለጊዜው ፡ የምሰጥህ ፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ የለኝም

At the moment, our friendship is somewhat strained. አሁን ፡ ጓደኝነታችን ፡ ትንሽ ፡ ሻክሯል

**for a moment ለጥቂት ፡ ጊዜ**

A bright light blinded him for a moment. ብሩህ ፡ ብርሃን ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዓይኑን ፡ ከለለው

**great moment ታላቅ ፡ ምዕራፍ**

The Emperor's return was a great moment in Ethiopia's history. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መመለስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ምዕራፍ ፡ ነበር

**(be of) great moment** ታላቅነት ፡ አለው
This decision was of great moment. ይህ ፡ ውሳኔ ፡ ታላቅነት ፡ ያለው ፡ ነበር

**important moment, be an ~** ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ያዘ
His presentation at the court was an important moment of his life. ቤተ ፡ መንግሥት ፡ መቅረቡ ፡ በሕይወቱ ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ የያዘ ፡ ነው

**in a few moments** ባንድ ፡ አፍታ
It was all over in a few moments. ባንድ ፡ አፍታ ፡ አለቀ

**in a moment**
1. ከመቅጽበት. In a moment, all was changed. ከመቅጽበት ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ተለወጠ
2. አሁን. I'll give you your change in a moment. አሁን ፡ መልስህን ፡ እሰጥሃለሁ

**just a moment** እንዶ ፡ ቆይ
Just a moment, please; I am on the phone. እንዶ ፡ ቆይ ፤ ስልክ ፡ ይዤያለሁ

**just this moment** አሁን ፡ ገና
I have just this moment heard the news. ወሬውን ፡ አሁን ፡ ገና ፡ መስማቴ ፡ ነው

**not for a moment** ፈጽሞ
Have you thought of doing it yourself? Not for a moment! ራስህ ፡ ልትሠራው ፡ አስበህ ፡ ነበር ? ፈጽሞ !

**of moment** ከፍ ፡ ያለ
The President is busy on a matter of moment. ፕሬዚዳንቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ናቸው

**the moment** ልክ ፡ እንደ + perfect
I started the moment your letter arrived. ልክ ፡ ደብዳቤህ ፡ እንደደረሰኝ ፡ ተነሣሁ
[See also 'crucial, lucid, only, precise, spur, unguarded, very']

## momentarily
1. ለጥቂት ፡ ደቂቃ ፤ ለጥቂት ፡ ጊዜ. I saw him momentarily between two classes. በሁለት ፡ ክፍለ ፡ ጊዜያት ፡ መሃከል ፡ ለጥቂት ፡ ደቂቃ ፡ አየሁት
The luminous room blinded him momentarily. ብርሃን ፡ የበዛበት ፡ ክፍል ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዓይኑን ፡ አሳወረው
2. በየጊዜው. The danger of fire is increasing momentarily. የእሳት ፡ አደጋ ፡ በየጊዜው ፡ እየባሰ ፡ ይሄዳል
3. ለጊዜው. I am momentarily out of cash. ለጊዜው ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም
*We are expecting the doctor momentarily. ሐኪሙ ፡ መምጫው ፡ ነው

## momentary,
1. (= adv.) ለጥቂት ፡ ጊዜ. There was a momentary silence in the room. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ጸጥታ ፡ ነበር
2. (= adv.) በድንገት. They live in fear of momentary annihilation. በድንገት ፡ እናልቃለን ፡ በሚል ፡ ፍርሃት ፡ ይኖራሉ

## momentous ከፍ ፡ ያለ
The opening of the Koka dam was a momentous occasion. የቆቃ ፡ ግድብ ፡ መከፈት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በዓል ፡ ነበር

## momentum, gain ~
1. እያየለ ፡ ሄደ. The campaign to make him President gained momentum. እሱን ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ለማድረግ ፡ የሚደረገው ፡ ትግል ፡ እያየለ ፡ ሄደ
2. ፍጥነት ፡ እየጨመረ ፡ ሄደ. A falling object gains momentum as it falls. አንድ ፡ ነገር ፡ ሲወድቅ ፡ እስኪያርፍ ፡ ድረስ ፡ ፍጥነት ፡ እየጨመረ ፡ ይሄዳል

## monarch ንጉሠ ፡ ነገሥት
Haile Sellassie First is an Ethiopian monarch. ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ናቸው

## monarchy (monarchies) ንጉሣዊ ፡ አገዛዝ
Monarchy was established in Ethiopia centuries ago. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ንጉሣዊ ፡ አገዛዝ ፡ የተቋቋመው ፡ ከብዙ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ነው

## monastery (monasteries) ገዳም (pl. ገዳማት)
There are many monasteries in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ገዳማት ፡ አሉ

## monastic የገዳም ፤ የመነኰሳት
He lives a monastic life. የገዳም ፡ (የመነኰሳት) ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል

## Monday ሰኞ

## monetary የገንዘብ
The dollar is the monetary unit of the U.S.A. ብር ፡ የአሜሪካ ፡ የገንዘብ ፡ መቍጠሪያ ፡ ነው
*The old car has little monetary value. አሮጌው ፡ መኪና ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አያወጣም

## money ገንዘብ
I'm losing money on that deal. በዚያ ፡ ንግድ ፡ ገንዘብ ፡ እከስራለሁ

**make money** ገንዘብ ፡ አገኘ ፤ ገንዘብ ፡ አተረፈ
I have to make money on this job. በዚህ ፡ ሥራ ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ አለብኝ

He made a lot of money on the sale of the house. ቤቱን ፡ ሲሸጥ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አተረፈ

**put some money down** ቀብድ ፡ ከፈለ
You have to put some money down on this car. ለዚህ ፡ መኪና ፡ ቀብድ ፡ መክፈል ፡ አለብህ
[See also 'close, expenditures, free, lose, magnanimous, ready, roll, sum, tight, worth']

**moneylender** ገንዘብ ፡ አበዳሪ
I need money, so I'm going to the moneylender. ገንዘብ ፡ ስለሚያስፈልገኝ ፡ ወደ ፡ ገንዘብ ፡ አበዳሪው ፡ እሄዳለሁ

**money order** ሐዋላ
Can I buy a money order at the post office? ከፖስታ ፡ ቤቱ ፡ ሐዋላ ፡ ልገዛ ፡ እችላለሁ ?

**monitor** (v.) ጠለፈ ፡ አዳመጠ
The police are monitoring the telephone calls of all suspects. ፖሊሶች ፡ የተጠርጣሪዎችን ፡ ስልኮች ፡ ሁሉ ፡ ጠልፈው ፡ በማዳመጥ ፡ ላይ ፡ ናቸው

**monitor** (n.) አለቃ ፤ የክፍል ፡ አለቃ
The best student was appointed monitor of his class. ከሁሉ ፡ የተሻለው ፡ ተማሪ ፡ የክፍል ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ ተመረጠ
The monitor set the children against the newcomer. የክፍል ፡ አለቃው ፡ ልጆቹን ፡ አዲስ ፡ በመጣው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ አሳደመ

**monk** መነኩሴ
The monks always pray during a fast. መነኩሴ ፡ በጾም ፡ ጊዜ ፡ ጸሎት ፡ ያዘወትራል

**monkey** (v.), ~ **around with** ነካካ
Stop monkeying around with those tools! እነዚህን ፡ መሣሪያዎች ፡ አትነካካ

**monkey** (n.) ዝንጀሮ
The monkeys destroyed the wheat. ዝንጀሮዎቹ ፡ እህሉን ፡ አጠፉ

**monogamy**
*Most religions preach monogamy. አብዛኞቹ ፡ ሃይማኖቶች ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ካንድ ፡ ሴት ፡ የሚለውን ፡ ያስተምራሉ

**monolithic** ከቋጥኝ ፡ የተፈለፈለ
There are monolithic churches in Lalibela. በላሊበላ ፡ ውስጥ ፡ ከቋጥኝ ፡ የተፈለፈሉ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ አሉ

**monologue, deliver a** ~ ብቻውን ፡ ተናገረ
The actor delivered a monologue. ተዋናዩ ፡ ብቻውን ፡ ተናገረ

**monophysitism** የተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት
Monophysitism was accepted by Ethiopians in the fourth century. የተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባራተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ገባ

**monopolize**
1. አጠቃሎ ፡ ለብቻው ፡ ያዘ. The company seeks to monopolize the coffee market. ኩባንያው ፡ የቡናውን ፡ ገበያ ፡ አጠቃሎ ፡ ለብቻው ፡ ለመያዝ ፡ ይፈልጋል
2. ብቻውን ፡ ያዘ. He is always monopolizing the conversation. ሁልጊዜ ፡ ወሬውን ፡ ብቻውን ፡ ይይዘዋል

**monopoly** ሞኖፖል
In some countries, tobacco is a government monopoly. ባንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ትምባሆ ፡ የመንግሥት ፡ ሞኖፖል ፡ ነው

**monotheism** ባንድ ፡ አምላክ ፡ ማመን
Christians and Moslems prefer monotheism to polytheism. ክርስቲያኖችና ፡ እስላሞች ፡ ከብዙ ፡ አማልክት ፡ ይልቅ ፡ ባንድ ፡ አምላክ ፡ ማመንን ፡ ይመርጣሉ

**monotonous**
1. የሚያሰለች. Life in a small village is monotonous. ትንሽ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ የሚያሰለች ፡ ነው
2. የቸከ. His speech is monotonous. ንግግሩ ፡ የቸከ ፡ ነው

**be monotonous** ላይን ፡ ሰለቸ
The landscape in the lowlands is monotonous. በቆላው ፡ አገር ፡ ያለው ፡ የመሬት ፡ ገጽ ፡ ላይን ፡ ይሰለቻል

**monster**
1. ጉድ. A five-legged calf is a monster. አምስት ፡ እግር ፡ ያለው ፡ ጥጃ ፡ ጉድ ፡ ነው
2. ጭራቅ. He painted a picture of Satan in the form of a horrible monster. ሰይጣንን ፡ አስፈሪ ፡ ጭራቅ ፡ አስመስሎ ፡ ሣለው
3. ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ አረመኔ. He is a monster of cruelty. በጭካኔው ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ አረመኔ ፡ ነው

**monstrous**
1. በጣም ፡ አሰቃቂ. He committed a monstrous crime. በጣም ፡ አሰቃቂ ፡ የሆነ ፡ ወንጀል ፡ ፈጸመ
2. መዓት. The public debt is monstrous. የመንግሥቱ ፡ ዕዳ ፡ መዓት ፡ ነው

**month** (n.) ወር
I earn a hundred dollars a month. በወር ፡ መቶ ፡ ብር ፡ አገኛለሁ

**monthly** (n.) በየወሩ ፡ የሚወጣ ፡ ጋዜጣ
He writes for a monthly. በየወሩ ፡ ለሚወጣ ፡ ጋዜጣ ፡ ጽሑፍ ፡ ያዘጋጃል

**monthly** (adj.)
1. የወር. If you miss one monthly payment, they won't complain. ያንድ ፡ ወር ፡ ክፍያ ፡ ብትዘል ፡ አይጨቃጨቁህም
2. (= adv.) በየወሩ. You can pay the amount in monthly installments. ሒሳቡን ፡ በየወሩ ፡ እየከፈልክ ፡ ልትጨርስ ፡ ትችላለህ
3. (= adv.) በወር. His monthly salary is $500. ደሞዙ ፡ በወር ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ነው
[See also 'popular']

**monument**
1. ሐውልት. A monument to Menilek was erected in the city. የአፄ ፡ ምኒልክ ፡ ሐውልት ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ቆሟል
2. ታላቅ ፡ ቅርስ. Homer's works are monuments of Greek culture. የሆመር ፡ ጽሑፎች ፡ ለግሪኮች ፡ ባህል ፡ ታላቅ ፡ ቅርሶች ፡ ናቸው
3. ቅርስ. The Egyptian pyramids are prodigious monuments. የግብጽ ፡ ፒራሚዶች ፡ የሚያስደንቁ ፡ ቅርሶች ፡ ናቸው

**monumental** ታላቅ
Building a bridge is a monumental task. ድልድይ ፡ መሥራት ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ነው

**mood** ሁኔታ
In his present mood, you better not speak to him. አሁን ፡ ባለበት ፡ ሁኔታው ፡ ባታነጋግረው ፡ ይሻላል

**moods** ሁኔታ
His moods change from time to time. ሁኔታው ፡ በየጊዜው ፡ ይለዋወጣል

**be in a bad mood** ደስ ፡ አላለ(ውም)
Don't talk to him now; he is in a bad mood. አሁን ፡ አታነጋግረው ፤ ደስ ፡ አላለውም

**be in a good mood**
He is in a good mood. ደስ ፡ ደስ ፡ ብሎታል

**be in the mood for** አሰኘ(ው)
+I'm not in the mood for that. ያንን ፡ ማድረግ ፡ አላሰኘኝም
+I'm not in the mood for laughing. ሣቅ ፡ አላሰኘኝም
[See also 'ebullient, wayward']

**(be) moody**
1. ቀፈፈ. He is a very moody person. ሁልጊዜ ፡ እንደቀፈፈው ፡ ነው
2. ብስጩ ፡ ሆነ. She has been moody ever since she lost her job. ከሥራዋ ፡ ከተሰናበተች ፡ ወዲህ ፡ ብስጩ ፡ ሆናለች

**moon** (v.), ~ **about** በሐሳብ ፡ ዋለለ
She was mooning about all day. በሐሳብ ፡ ስትዋልል ፡ ዋለች

**moon** (n.) ጨረቃ
The moon appeared today. ዛሬ ፡ ጨረቃ ፡ ወጥታለች

**full moon** ሙሉ ፡ ጨረቃ
Is there a full moon tonight? ዛሬ ፡ ሙሉ ፡ ጨረቃ ፡ ትወጣለች ?

**new moon**
*We can see the stars better during the new moon. ጨረቃ ፡ በምትወለድበት ፡ ወቅት ፡ ከዋክብት ፡ በደንብ ፡ ይታዩናል

**once in a blue moon** ከስንት ፡ አንዴ
He visits me once in a blue moon. ከስንት ፡ አንዴ ፡ ሊጠይቀኝ ፡ ይመጣል

**moonless**
*It is a moonless night tonight. ጨረቃ ፡ ዛሬ ፡ አልወጣችም

**moonlight** የጨረቃ ፡ ብርሃን
The garden is beautiful in the moonlight. በጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ ያትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ደስ ፡ ይላል

**moonstruck**
He acts moonstruck. ወፈፍ ፡ ያደረገው ፡ ይመስላል

**moor** (v.) አሰሮ ፡ አቆመ
The sailor moored the ship to the shore with a thick rope. መርከበኛው ፡ መርከቧን ፡ በወፍራም ፡ ገመድ ፡ ባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ላይ ፡ አስሮ ፡ አቆማት

**moot** አከራካሪ ፤ መልስ ፡ የማይገኝለት
Which one of the two started the war is a moot point. ከሁለቱ ፡ ጦርነቱን ፡ የጀመረው ፡ ማን ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ አከራካሪ ፡ ነው
Whether the Germans would have surrendered had Hitler died in 1944 is a moot question. ሂትለር ፡ በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም. ቢሞት ፡ ኖሮ ፡ ጀርመኖች ፡ እጃቸውን ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ መልስ ፡ የማይገኝለት ፡ ጥያቄ ፡ ነው

**mop** (mopped), v.
1. ወለወለ. I have to mop the floor. ወለሉን ፡ መወልወል ፡ አለብኝ
2. ጠረገ. He mopped his forehead with a handkerchief. ግንባሩን ፡ በመሐረብ ፡ ጠረገ

**mop up** ለቃቀመ
The soldiers are mopping up the scattered enemy units. የተበታተኑትን ፡ የጠላት ፡ ጓዶች ፡ ወታደሮቹ ፡ በመለቃቀም ፡ ላይ ፡ ናቸው

**mop** (n.) መወልወያ
She swept the floor with the mop. ወለሉን ፡ በመወልወያ ፡ ወለወለችው

**mope** ቅር ፡ አለ(ው)
He moped indoors all day. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ቅር ፡ ብሎት ፡ እቤት ፡ ዋለ

**moral** (n.) ፍሬ ፡ ነገር
And the moral of the story is this.... የታሪኩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ይኸው ፡ ነው
**morals** ግብረ ፡ ገብ ፤ ግብረ ፡ ገብነት
He has no morals at all. ግብረ ፡ ገብ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ነው
The church condemns corrupt morals. ቤተ ፡ ክርስቲያኗ ፡ ውድቅ ፡ ግብረ ፡ ገብነትን ፡ ታወግዛለች
**moral** (adj.)
1. የመንፈስ. I need your moral support. ያንተን ፡ የመንፈስ ፡ ድጋፍ ፡ እፈልጋለሁ
Our country won a moral victory in the UN. ሀገራችን ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የመንፈስ ፡ ድል ፡ ተጐናጸፈች
2. የግብረ ፡ ገብ. Freely admitting one's guilt and accepting punishment is a moral act. ጥፋትን ፡ አምኖ ፡ ቅጣትን ፡ መቀበል ፡ የግብረ ፡ ገብ ፡ ተግባር ፡ ነው
3. ዐዋቂ. Man is a moral being. ሰው ፡ ዐዋቂ ፡ ፍጡር ፡ ነው
[See also 'value']

**morale** ሞራል
The morale of the troops was excellent. የወታደሮቹ ፡ ሞራል ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነበር

**morality** ግብረ ፡ ገብነት ፤ ግብረ ፡ ገብ ፡ መሆን
Critics complain that morality is declining in this country. ተቺዎች ፡ በዚህ ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ በመውደቅ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ያማርራሉ
They argued about the morality of dancing on Sunday. እሑድ ፡ እሑድ ፡ መደነስ ፡ ግብረ ፡ ገብ ፡ ስለመሆኑ ፡ ተከራከሩ

**morally** በግብረ ፡ ገብነት ፡ በኩል
What he did was morally wrong. እሱ ፡ ያደረገው ፡ በግብረ ፡ ገብነት ፡ በኩል ፡ ስሕተት ፡ ነበር
**live morally** ግብረ ፡ ገብነት ፡ ነበረው
Because he lived morally, he gained the respect of his neighbors. ግብረ ፡ ገብነት ፡ ስለነበረው ፡ የጐረቤቶችን ፡ አክብሮት ፡ አተረፈ

**morass, turn into a ~** አጨቀየ
Heavy rain turned the highway into a morass. ከባድ ፡ ዝናም ፡ አውራ ፡ ጐዳናውን ፡ አጨቀየው

**morbid** አስከፊ
He thinks morbid thoughts. ሐሳቡ ፡ ሁሉ ፡ አስከፊ ፡ ነው

**more** (adj.) ተጨማሪ
He is asking for more money. ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ይፈልጋል
I need more men to help me. የሚረዱኝ ፡ ተጨማሪ ፡ ሰዎች ፡ እፈልጋለሁ
**more** (adv.) በይበልጥ
Be more careful in the future! ለወደፊቱ ፡ በይበልጥ ፡ ተጠንቀቅ
**more or less**
1. ከሞላ ፡ ጐደል. I believe that report is more or less true. ያ ፡ ሪፖርት ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ትክክለኛ ፡ ይመስለኛል
2. ይብዛ ፡ ይነስ. All the offices on the first floor are more or less like this. በምድር ፡ ቤት ፡ የሚገኙት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቶች ፡ ይብዛ ፡ ይነስ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ናቸው
**more than**
1. ከ - - - በላይ. It's more than a month ago that I saw him. ካየሁት ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በላይ ፡ ሆኗል
There is more than enough. ከሚበቃ ፡ በላይ ፡ አለ
2. ከ - - - ይልቅ. She is more beautiful than my sister. እሷ ፡ ከእኅቴ ፡ ይልቅ ፡ ታምራለች
3. ከ --- የበለጠ. The elevator cannot carry more than ten persons. አሳንሰሩ ፡ ከዐሥር ፡ ሰው ፡ የበለጠ ፡ አይዝም
**more than once** ካንድ ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፤ ካንዴም ፡ ሁለቴ
King Theodore defeated Ras Ali more than once. አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ራስ ፡ ዓሊን ፡ ካንድ ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ (ካንዴም ፡ ሁለቴ) ፡ ድል ፡ አደረጓቸው
**as many more** በተጨማሪ ፡ ያንኑ ፡ ያህል
You gave me ten apples. I should like as many more. ዐሥር ፡ ቱፋ ፡ ሰጥተኸኛል ፤ በተጨማሪ ፡ ያንኑ ፡ ያህል ፡ እፈልጋለሁ
**get more and more** ይበልጥ ፡ (በይበልጥ) ፡ እየ + perfect + ሄደ
This disease is getting more and more complicated. ይህ ፡ በሽታ ፡ ይበልጥ ፡ እየባሰበት ፡ ይሄዳል
Everything is getting more and more expensive. ሁሉም ፡ ነገር ፡ ይበልጥ ፡ እየተወደደ ፡ ይሄዳል

He got more and more involved in the matter. በነገሩ ፡ በይበልጥ ፡ ተካፋይ ፡ እየሆነ ፡ ሄደ

**give more** ጨመረ
Give me two more bottles of wine! ሁለት ፡ ጠርሙስ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ጨምርልኝ

**have some more** ጨመረ
Won't you have some more soup? ሾርባ ፡ አትጨምርም ?

**in ... more** ከ --- በኋላ
The oranges on this tree will reach maturity in two more weeks. በዚህ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ብርቱካኖች ፡ ከሁለት ፡ ሳምንት ፡ በኋላ ፡ ይበስላሉ

**no more** ምንም + negative verb
I have no more money. ምንም ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም

**(be) no more** ፈረሰ
The house I lived in is no more. የኖርኩበት ፡ ቤት ፡ ፈረሰ

**no more of**
No more of that, please! እንግዲህ ፡ በቃ

**no more than**
*He's no more able to read Chinese than I am. እሱም ፡ ሆነ ፡ እኔ ፡ ቻይንኛ ፡ ማንበብ ፡ አንችልም

**not any more**
Don't do that any more! እንዳይለምድህ

**the more ... the**
*The more he spoke, the madder he got. በተናገረ ፡ ቁጥር ፡ ንዴቱ ፡ እየባሰበት ፡ ሄደ

**the more ... the more**
*The more I give him, the more he wants. በሰጠሁት ፡ ቁጥር ፡ ይበልጥ ፡ እንድሰጠው ፡ ይፈልጋል

**what more** ከዚህ ፡ በላይ ፡ ምን
What more do you want? ከዚህ ፡ በላይ ፡ ምን ፡ ትፈልጋለህ ?
[See also 'any, even, hardly, nothing, often, once, what']

**moreover** ከዚህም ፡ በላይ
Moreover, he talks a lot. ከዚህም ፡ በላይ ፡ ይለፈልፋል
*He is fat; moreover, he is short. ወፍራም ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ አጭር ፡ ነው

**moribund, be ~** እየቀረ ፡ ሄደ
Astrology is moribund as a science. የከዋክብት ፡ ቈጠራ ፡ ሳይንስነቱ ፡ እየቀረ ፡ ሄዷል

**morning**
1. ጧት. He slept all morning. ጧቱን ፡ ሙሉ ፡ ተኝቶ ፡ አረፈደ
Yesterday morning I came to see him. ትናንትና ፡ ጧት ፡ ልጠይቀው ፡ መጥቼ ፡ ነበር
2. ቀን. A few mornings ago, birds were hopping about in my garden. ከጥቂት ፡ ቀኖች ፡ በፊት ፡ ወፎች ፡ በአትክልት ፡ ቦታዬ ፡ ውስጥ ፡ ጡብ ፡ ጡብ ፡ ሲሉ ፡ ነበር

**early morning** ማለዳ
He gets up in the early morning. በማለዳ ፡ ይነሣል

**good morning!** እንደምን ፡ አደርክ ? (2nd masc. sg.)

**in the morning hours** ጧት ፡ ጧት
I like to work in the morning hours. ጧት ፡ ጧት ፡ መሥራት ፡ እወዳለሁ

**the following morning** በማግሥቱ ፡ ጧት
They made all the necessary arrangements to leave the following morning. በማግሥቱ ፡ ጧት ፡ ለመሄድ ፡ አስፈላጊውን ፡ ዝግጅት ፡ ሁሉ ፡ አደረጉ

**the next morning** በማግሥቱ
He came in the next morning with a smile on his face. በማግሥቱ ፡ ፊቱን ፡ ፈገግ ፡ አድርጎ ፡ ገባ

**this morning** ዛሬ ፡ ጧት
There was a lot to do this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ነበር
[See also 'thing']

**morning star** ያጥቢያ ፡ ኮከብ
Can you see the morning star? ያጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ ይታይሃል ?

**(be) morose** ከፋ(ው)
+He is morose because he lost his job. ከሥራው ፡ ስለወጣ ፡ ከፍቶታል

**morphology** እርባታ
The morphology of the Amharic verb is very difficult. ባማርኛ ፡ የግስ ፡ እርባታ ፡ በጣም ፡ ያስቸግራል

**morrow, on the ~** ነገ ፤ በበነጋው
I will see him on the morrow. ነገ ፡ አገኘዋለሁ
Some say a red sunset imports a fair day on the morrow. ፀሐይ ፡ ስትጠልቅ ፡ ደም ፡ መምሰሏ ፡ በበነጋው ፡ የብራ ፡ ቀን ፡ እንደሚሆን ፡ ያመለክታል ፡ ይባላል

**morsel, ~ of food** ቁራሽ
I haven't had a morsel of food since I left the house. ከቤት ፡ ከወጣሁ ፡ ቁራሽም ፡ አላገኘሁ

**mortal** (n.) ተራ ፡ ሰው
Entry into the holy of holies is not for

ordinary mortals. ቅድስት ፡ ቅዱሳን ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ የሚፈቀደው ፡ ለማንኛውም ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ አይደለም

**mortal** (adj.)
1. ሟች. Man is mortal. ሰው ፡ ሟች ፡ ነው
2. ከሞት ፡ የሚያደርስ. His injuries proved mortal. ጉዳቱ ፡ ከሞት ፡ የሚያደርስ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ
3. ከባድ. Only God can forgive mortal sins. ከባድ ፡ ኃጢአትን ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነው
4. ዕርቅ ፡ የማይገባው. They are mortal enemies. ዕርቅ ፡ የማይገባቸው ፡ ጠላቶች ፡ ናቸው
5. የሰው. We all have mortal weaknesses. ሁላችንም ፡ የሰው ፡ ደካማነት ፡ አለብን
6. (= adv.) የሞት ፡ ያህል. The people live in mortal fear of the nearby volcano. ሰዎቹ ፡ በአካባቢያቸው ፡ ያለውን ፡ እሳተ ፡ ገሞራ ፡ የሞት ፡ ያህል ፡ እየፈሩት ፡ ይኖራሉ

## mortality
1. ሟችነት. The mortality of man is a subject of many philosophers. የሰው ፡ ሟችነት ፡ የብዙ ፡ ፈላስፋዎች ፡ ርእስ ፡ ነገር ፡ ነው
2. የሚሞቱ ፡ ሰዎች. The high rate of mortality has been reduced by modern medicine. የሚሞቱት ፡ ሰዎች ፡ ቁጥር ፡ ዛሬ ፡ በዘመናዊ ፡ መድኃኒት ፡ ተቀንሷል
*The epidemic had a high rate of mortality. ወረርሽኙ ፡ በብዙ ፡ የሚቆጠር ፡ ሕዝብ ፡ ፈጀ

**infant mortality** የሚሞቱ ፡ ሕፃናት
The infant mortality rate has been going down. የሚሞቱ ፡ ሕፃናት ፡ ቁጥር ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ሄዷል

## mortally ከልብ
The soldiers were mortally grieved by the death of their general. ወታደሮቹ ፡ በጄኔራላቸው ፡ መሞት ፡ ከልብ ፡ አዘኑ
*He was mortally wounded. በጽኑ ፡ ስለቆሰለ ፡ አልተረፈም

**be mortally offended** እንጀቱ ፡ ተቈረጠ
He was mortally offended when she refused to speak to him. አላነጋግርህም ፡ ባለችው ፡ ጊዜ ፡ አንጀቱ ፡ ተቈረጠ

## mortar
1. ሙቀጫ. She ground the spices in a mortar. ቅመሙን ፡ በሙቀጫ ፡ ወቀጠች
2. ሲሚንቶ. The wall is made of stones held together by mortar. ግድግዳው ፡ በሲሚንቶ ፡ ከተያያዙ ፡ ድንጋዮች ፡ የተሠራ ፡ ነው

## mortar fire የአዳፍኔ ፡ ተኩስ
Mortar fire held up our advance. የአዳፍኔ ፡ ተኩስ ፡ ወደፊት ፡ እንዳንገፋ ፡ አደረገን

## mortgage (v.) አስያዘ
He mortgaged his property in order to get money for a car. ለመኪና ፡ መግዣ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ ንብረቱን ፡ አስያዘ

## mortgage (n.) መያዣ ፤ ወለድ ፡ አግድ
The estate is encumbered with mortgages. ርስቱ ፡ መያዣ ፡ ተሰጥቷል
I have a mortgage on his house. ቤቱን ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ይዤዋለሁ

## mortify (mortified) አጐሳቈለ
He mortified his body in order to find salvation. ሊጸድቅ ፡ አስቦ ፡ ሰውነቱን ፡ አጐሳቈለ

**be mortified** በጣም ፡ አፈረ
I was mortified by my son's rude behavior. በልጄ ፡ ብልግና ፡ በጣም ፡ አፈርኩ

## mosque መስጊድ
Muslims go to the mosque every Friday. እስላሞች ፡ ዓርብ ፡ ዓርብ ፡ ወደ ፡ መስጊድ ፡ ይሄዳሉ

## mosquito የወባ ፡ ትንኝ
We were all bitten up by the mosquitos. ሁላችንም ፡ በወባ ፡ ትንኝ ፡ ተነደፍን
[See also 'net']

## moss
1. የደንጊያ ፡ ሽበት. He scraped the moss from the rock. የደንጊያ ፡ ሽበት ፡ ከድንጊያው ፡ ላይ ፡ ፋቀ
2. አረንጓዴ. The stagnant water was covered with moss. የረጋውን ፡ ውኃ ፡ አረንጓዴ ፡ ሸፍኖ ታል

## most በጣም
The talk was most interesting. ንግግሩ ፡ በጣም ፡ አስደሳች ፡ ነበር
The music pleased me most. ሙዚቃው ፡ በጣም ፡ አስደሰተኝ
*She received us most kindly. መልክም ፡ አቀባበል ፡ አደረገችልን

**most certainly** በርግጥ
I will most certainly go. በርግጥ ፡ እሄዳለሁ

**most everybody** አብዛኞቹ
Most everybody has gone home. አብዛኞቹ ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄደዋል

**most of**
1. አብዛኛውን ፡ ጊዜ. He was ill most of the summer. ክበጋው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ታሞ ፡ ነበር

He is on the road most of the time. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይሄዳል
2. አብዛኞቹ. Most of those present were against it. ከተገኙት ፡ ሰዎች ፡ አብዛኞቹ ፡ ተቃውመውት ፡ ነበር
3. አብዛኛውን. He did most of the work. አብዛኛውን ፡ ሥራ ፡ የሠራው ፡ እሱ ፡ ነው

**at most** ቢበዛ
At most, the bill will come to twenty dollars. ቢበዛ ፡ ሒሳቡ ፡ ሃያ ፡ ብር ፡ ቢሆን ፡ ነው

**at the most** ግፋ ፡ ቢል
At the most, it's worth ten dollars. ግፋ ፡ ቢል ፡ ከዐሥር ፡ ብር ፡ በላይ ፡ አያወጣም

**make the most of** የሚቻለውን ፡ ያህል ፡ ተጠቀመበት
He did not have many opportunities, but he made the most of those that he had. ብዙ ፡ ዕድል ፡ አላገኘም ፤ ግን ፡ ያጋጠመውን ፡ ዕድል ፡ የሚቻለውን ፡ ያህል ፡ ተጠቀመበት
*She is not really beautiful, but she makes the most of her looks. በተፈጥሮ ፡ ቆንጆ ፡ አይደለችም ፡ ግን ፡ ባላት ፡ ውበት ፡ ሁሉ ፡ በሚቻላት ፡ ትጠቀማለች

**the most**
1. ከሁሉም. This is the most dangerous animal. ይህ ፡ ከሁሉም ፡ አደገኛ ፡ አውሬ ፡ ነው
2. ይበልጡን. Who did the most work? ይበልጡን ፡ ሥራ ፡ የሠራው ፡ ማን ፡ ነው ?
3. ከሁሉ ፡ ይበልጥ. This is the most beautiful church I've ever seen. ካየኋቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ ይበልጥ ፡ ያምራል
4. ብዙ. The pocketbook with the most money is hers. ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ያለበት ፡ ቦርሳ ፡ የሷ ፡ ነው
*That's the most I can pay. ልከፍል ፡ የምችለው ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ይህ ፡ ነው
*Do the most you can. የቻልከውን ፡ ያህል ፡ ሥራ
[See also 'far, kindly, part']

## mostly
1. ይበልጡ. The audience consisted mostly of women. በስብሰባው ፡ የነበሩት ፡ ይበልጡ ፡ ሴቶች ፡ ነበሩ
2. አብዛኛውን ፡ ጊዜ. He is mostly out on Sundays. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ እቤት ፡ አይውልም
3. በብዙ ፡ ረገድ. He's mostly right. በብዙ ፡ ረገድ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው

## moth የእሳት ፡ እራት
There are many moths flying around the lantern. ብዙ ፡ የእሳት ፡ እራቶች ፡ በፋኖሱ ፡ ዙሪያ ፡ ይበራሉ

## mother (v.) እንደ ፡ እናት ፡ አንከባከበ
She mothers him all the time. እንደ ፡ እናት ፡ ሁልጊዜ ፡ ታንከባክበዋለች

## mother (n.) እናት
My mother is forty years old. እናቴ ፡ አርባ ፡ ዓመቷ ፡ ነው

## mother-in-law አማት
My mother-in-law has much land. አማቴ ፡ ብዙ ፡ ርስት ፡ አላቸው

## motherhood እናትነት
She took the duties of motherhood seriously. የናትነቱን ፡ ኀላፊነት ፡ አጥብቃ ፡ ያዘች

## motherland የትውልድ ፡ አገር
They defended their motherland. ለትውልድ ፡ አገራቸው ፡ ተከላከሉ

## motherless እናቱ ፡ የሞተችበት
He is a motherless child. እናቱ ፡ የሞተችበት ፡ ልጅ ፡ ነው

## motherly የእናት
A young child needs motherly love. ሕፃን ፡ ልጅ ፡ የእናት ፡ ፍቅር ፡ ይፈልጋል

**motherly person** እናት
She's a motherly person. እሷ ፡ እናት ፡ ናት

## mother tongue የእናት ፡ ቋንቋ
His mother tongue is Amharic. የእናት ፡ ቋንቋው ፡ አማርኛ ፡ ነው

## motif ዓላማ
The motif of his book is that crime does not pay. የመጽሐፉ ፡ ዓላማ ፡ ወንጀል ፡ የማይጠቅም ፡ መሆኑን ፡ መግለጽ ፡ ነው

## motion (v.)
1. ምልክት ፡ ሰጠ. He motioned for the taxi to stop. ታክሲው ፡ እንዲቆም ፡ ምልክት ፡ ሰጠው
2. ጠቀሰ. He motioned me to be quiet. ዝም ፡ እንድል ፡ ጠቀሰኝ

## motion (n.)
1. መንቅነቅ. The motion of the car made him sick. የመኪናው ፡ መንቅነቅ ፡ አቅለሸለሸው
2. ንቅናቄ. Watch my motions carefully, and you will see how I do the trick. ልብ ፡ ብለህ ፡ የማደርገውን ፡ ንቅናቄ ፡ ተመልከትና ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ትንግርቱን ፡ እንደምሠራ ፡ ታያለህ
3. እንቅስቃሴ. If a thing is in motion, it is not at rest. አንድ ፡ ነገር ፡ በእንቅስቃሴ ፡ ላይ ፡ ከሆነ ፡ አልቆመም ፡ ማለት ፡ ነው

4. የቀረበ፡ሐሳብ. I second the motion to lower the taxes. ታክስ ፡ እንዲቀነስ ፡ የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ እደግፋለሁ

**be in motion** አልቆመም ፤ ተንቀሳቀሰ

The train was still in motion. ባቡሩ ፡ ገና ፡ አልቆመም

If a thing is in motion, it is not at rest. አንድ ፡ ነገር ፡ በሚንቀሳቀስበት ፡ ጊዜ ፡ ረግቶ ፡ አልቆመም ፡ ማለት ፡ ነው

**go through the motions** ለይምሰል ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ

He doesn't really do anything; he just goes through the motions. ለይምሰል ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ የሚሠራው ፡ ጠቃሚ ፡ ሥራ ፡ የለም

[See also 'circular']

**motionless** ዝም ፡ ብሎ

The lions stood motionless. አንበሶቹ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆሙ

**motion picture** ተንቀሳቃሽ ፡ ፊልም

Motion pictures are now being made in Ethiopia. ተንቀሳቃሽ ፡ ፊልሞች ፡ አሁን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይሠራሉ

**motivate** ገፋፋ

What motivates him to work so hard? እንደዚህ ፡ ጠንክሮ ፡ ለመሥራት ፡ የሚገፋፋው ፡ ምንድነው ?

**motive** (n.)

1. ምክንያት. What was his motive for killing her? እሷን ፡ የገደለበት ፡ ምክንያት ፡ ምን ፡ ነበር ?

2. የሚገፋፋው ፡ ሐሳብ. His motives are only too obvious. የሚገፋፋው ፡ ሐሳብ ፡ በግልጽ ፡ የሚታወቅ ፡ ነው

**motive** (adj.) የማንቀሳቀሻ

Engines supply motive power. ሞተር ፡ የማንቀሳቀሻ ፡ ኀይል ፡ ይሰጣል

**motley** (adj.)

1. ዥንጉርጉር. Her motley dress attracts attention. ዥንጉርጉር ፡ ልብሷ ፡ የሰው ፡ ዓይን ፡ ይስባል

2. ልዩ፡ልዩ. A motley crowd filled the streets. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕዝብ ፡ መንገዱን ፡ ሞላው

**motor** ሞተር

He put a motor in his boat. ለጀልባው ፡ ሞተር ፡ አስገባለት

**motorcycle** ሞተር ፡ ቢሲክሌት

Many traffic policemen ride motorcycles. ብዙ ፡ የትራፊክ ፡ ፖሊሶች ፡ በሞተር ፡ ቢሲክሌት ፡ ይሄዳሉ

**motorize** በመኪና ፡ አጓጓዘ

We have motorized the entire army since World War I. ከንደኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ ሰራዊት ፡ የምናጓጉዘው ፡ በመኪና ፡ ነው

**mottled** ዥንጉርጉር

The hyena has a mottled pelt. ጅብ ፡ ዥንጉርጉር ፡ ቆዳ ፡ አለው

**motto** መመሪያ

'Think before you speak!' is a good motto. « ከመናገርህ ፡ በፊት ፡ አስብ » ፡ የሚለው ፡ ጥሩ ፡ መመሪያ ፡ ነው

**mouldy,** see **moldy**

**mound**

1. ጉብታ. The mound that we see is undoubtedly a grave. የምናየው ፡ ጉብታ ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ መቃብር ፡ ነው

2. ቁልል. I found the book under a mound of papers. መጽሐፉን ፡ ከወረቀት ፡ ቁልል ፡ ሥር ፡ አገኘሁት

**mount** (vt.)

1. ተቀመጠ. He mounted his horse and rode off. ፈረሱን ፡ ተቀምጦ ፡ ጋለበ

2. ወጣ. He mounted the ladder. መሰላሉ ፡ ላይ ፡ ወጣ

Theodore mounted the throne in 1848. አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የወጡት ፡ በ፲፰፻፵ ዓ. ም. ነው

3. አስገባ. He is mounting photographs in an album. በአልቡም ፡ ውስጥ ፡ ፎቶግራፍ ፡ እያስገባ ፡ ነው

4. ጠመደ. They mounted a gun on the fortress wall. በትልቁ ፡ ምሽግ ፡ ግምብ ፡ ላይ ፡ መድፍ ፡ ጠመዱ

**mount** (vi.)

1. ፈረሱን ፡ ተቀመጠ. He mounted in haste and rode away. ፈረሱን ፡ በችኮላ ፡ ተቀምጦ ፡ ሸመጠጠ

2. ወጣ. The children mounted to the top of the steps. ልጆቹ ፡ ከደረጃው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ወጡ

3. ጨመረ. Our costs are mounting daily. ወጪያችን ፡ በየቀኑ ፡ እየጨመረ ፡ ይሄዳል

**mount** (n.)

1. ተራራ. Have you read the Sermon on the Mount? የተራራውን ፡ ስብከት ፡ አንብበሃል ?

2. ፈረስ ፤ የኮርቻ ፡ ፈረስ. The riders brought their mounts into line. ፈረሰኞቹ ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ በሰልፍ ፡ አቆሙ

The general had an excellent mount. ጄኔራሉ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ የሆነ ፡ የኮርቻ ፡ ፈረስ ፡ ነበረው

*His usual mount is a mule. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚቀመጠው ፡ በቅሎ ፡ ነው

**mountain** ተራራ
How high is that mountain? ያ ፡ ተራራ ፡ ከፍታው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?

**a mountain of** መዓት
He overcame a mountain of difficulties. መዓት ፡ ዕንቅፋቶችን ፡ ተወጣ

**mountain** (adj.)
1. የተራራ. The mountaintop was covered with snow. የተራራው ፡ እናት ፡ በበረዶ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር
2. በተራራ ፡ ላይ ፡ የሚኖር. Mountain people are used to a cold climate. በተራራ ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ቀዝቃዛ ፡ አየር ፡ ለምደዋል
[See also 'range']

**mountain chain** ሸንተረር
A mountain chain separates the two countries. ሸንተረር ፡ ሁለቱን ፡ አገሮች ፡ ያዋስናቸዋል

**mountaineer** [እንደ ፡ ስፖርት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ ቈጥሮት ፡ ተራራ ፡ የሚወጣ ፡ ሰው]

**mountain goat** የሚዳ ፡ ፍየል
The hunter brought down a mountain goat. አዳኙ ፡ የሚዳ ፡ ፍየሏን ፡ ተኩሶ ፡ ገደላት

**mountainous** ተራራማ
This region is mountainous. ይህ ፡ ቀበሌ ፡ ተራራማ ፡ ነው

**mountainside** የተራራ ፡ ጥጋት
The house stands on the mountainside almost all alone. ቤቱ ፡ ተነጥሎ ፡ በተራራው ፡ ጥጋት ፡ ላይ ፡ ይገኛል

**mounted** ፈረሰኛ
Mounted police accompanied the parade. ፈረሰኛ ፡ ፖሊሶች ፡ ሰልፉን ፡ ተከተሉት

**be mounted** በፈረስ ፡ ሄደ
Troops that are mounted are called cavalry. በፈረስ ፡ የሚሄዱ ፡ ወታደሮች ፡ ፈረሰኞች ፡ ይባላሉ

**mourn**
1. ሐዘን ፡ ላይ ፡ ነው. He mourns his father's death. ባባቱ ፡ ሞት ፡ ሐዘን ፡ ላይ ፡ ነው
2. አዘነ. The whole nation mourned his passing. በሱ ፡ ሞት ፡ አገሩ ፡ በሙሉ ፡ አዘነ
3. ተጸጸተ. He mourned his misspent youth. በባከነው ፡ የወጣትነት ፡ ዘመኑ ፡ ተጸጸተ

**mourner** ለቀስተኛ ፤ ሐዘንተኛ
There were many mourners at the funeral. በቀብሩ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ለቀስተኞች ፡ (ሐዘንተኞች) ፡ ነበሩ

**mournful**
1. የሐዘን. The priest read the prayer in a mournful voice. ቄሱ ፡ ጸሎቱን ፡ ያነበቡት ፡ በሐዘን ፡ ድምፅ ፡ ነበር
2. ሐዘን ፡ የተመላበት. He answered my letter in a mournful key. ደብዳቤዬን ፡ ሐዘን ፡ በተመላበት ፡ አገላለጽ ፡ መለሰልኝ

**mourning**
1. ልቅሶ ፤ ለቅሶ. The sound of mourning can be heard in the church. ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ግቢ ፡ ልቅሶ ፡ ይሰማል
2. ከል. She still wears mourning. አሁንም ፡ ከል ፡ ትለብሳለች

**be in mourning** ሐዘን ፡ ላይ ፡ ነው
I'm still in mourning. አሁንም ፡ ሐዘን ፡ ላይ ፡ ነኝ

**mouse** (mice) አይጥ
The cat caught a mouse. ድመቷ ፡ አይጡን ፡ ያዘች

**mousetrap** የአይጥ ፡ ወጥመድ
The mousetrap does not function. የአይጥ ፡ ወጥመዱ ፡ አይሠራም

**mouth**
1. አፍ. He opened his mouth and showed his teeth. አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ጥርሱን ፡ አሳየ
The dog stopped at the mouth of the cave. ውሻው ፡ ከዋሻው ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ ቆመ
2. መግቢያ. The river broadens at its mouth. ወንዙ ፡ በመግቢያው ፡ ላይ ፡ ይሰፋል
*He has four mouths to feed. አራት ፡ ተቀላቢዎች ፡ አሉት

**from mouth to mouth** ካንዱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡
The story passed from mouth to mouth. ታሪኩ ፡ ካንዱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ተላለፈ

**put words in one's mouth**
Don't put words in his mouth! ያላለውን ፡ አትናገር
[See also 'hand, roof, stuff, water, word']

**mouthful** ጕርሻ
The sick boy couldn't eat more than a mouthful. የታመመው ፡ ልጅ ፡ ካንድ ፡ ጕርሻ ፡ የበለጠ ፡ ሊበላ ፡ አልቻለም

**mouthful of food** ጕርሻ
He took a large mouthful of food. ትልቅ ፡ ጕርሻ ፡ ጐረሰ

**take a mouthful of**

*He took a mouthful of beer, but spat it on the ground. በጉንጩ ፡ ሙሉ ፡ ጠላ ፡ ተጉንጭቶ ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ ተፋው

## mouthpiece

1. አፍ. The mouthpiece of my flute is broken. የዋሽንቴ ፡ አፍ ፡ ተሰብሯል
2. አስተያየት ፡ የሚገልጽ. Al-Ahram is the mouthpiece of the government. አልአህራም ፡ የመንግሥቱን ፡ አስተያየት ፡ የሚገልጽ ፡ ጋዜጣ ፡ ነው

## movable ተንቀሳቃሽ

I sold all my movable property. ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቴን ፡ በሙሉ ፡ ሸጥኩት

Our fingers are movable. ጣቶቻችን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ናቸው

**be movable ተለዋወጠ**

Christmas is a fixed holiday, but Easter is a movable one. ገና ፡ የሚውልበት ፡ ቀን ፡ የተወሰነ ፡ ነው ፤ ፋሲካ ፡ ግን ፡ ይለዋወጣል

## move (vt.)

1. ዞር ፡ አደረገ. You'll have to move your car. መኪናህን ፡ ዞር ፡ ማድረግ ፡ አለብህ
2. አዘዋወረ. Let's move the table! ጠረጴዛውን ፡ እናዘዋውረው
3. አንቀሳቀሰ. She can't move her foot. እግሯን ፡ ልታንቀሳቅስ ፡ አትችልም
4. አጓጓዘ. Trucks were used to move troops to the front. ወታደሮቹን ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ለማጓጓዝ ፡ በከባድ ፡ መኪናዎች ፡ ተጠቀሙ
5. ወሰደ. A moving company moved our furniture. እቃ ፡ የሚያመላልሰው ፡ ኩባንያ ፡ የቤት ፡ እቃችንን ፡ ወሰደልን
6. አነሣ. Step aside while we are moving the table. ጠረጴዛውን ፡ ልናነሣው ፡ ነውና ፡ ዞር ፡ በል
7. ሐሳብ ፡ አቀረበ. I move that we adjourn. ስብሰባው ፡ እንዲያበቃ ፡ ሐሳብ ፡ አቀርባለሁ
8. ገፋፋ. Nothing I said moved him to offer his help. የተናገርኩት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እርዳታ ፡ እንዲያደርግ ፡ አልገፋፋውም
9. ስሜት ፡ ነካ. The eloquence of the President moved the audience. የፕሬዚዳንቱ ፡ አንደበተ ፡ ርቱዕነት ፡ ያድማጮቹን ፡ ስሜት ፡ ነካ

**move (vi.)**

1. ተንኰሻኰሸ. I hear something moving in the dark. በጨለማው ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሲንኰሻኰሽ ፡ ይሰማኛል
2. ቤት ፡ ለቀቀ ፤ ቤት ፡ ለወጠ ፤ ቤት ፡ ቀየረ. We're moving on October first. ይህን ፡ ቤት ፡ ጥቅምት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንለቃለን

We moved three times in the last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ቤት ፡ ለወጥን

This house is too small; we will be better off if we move. ይህ ፡ ቤት ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው ፤ ቤት ፡ ብንቀይር ፡ ይሻላል

3. ተሽከረከረ. When you press the button, the wheels of the machine begin to move. ቁልፉን ፡ ስትጫነው ፡ የመኪናው ፡ መንኰራኩሮች ፡ ይሽከረከራሉ
4. ተጓዘ. We are moving at a good speed now. አሁን ፡ የምንጓዝበት ፡ ፍጥነት ፡ ደኅና ፡ ነው
5. ተራመደ. Mark how carefully he moves! እንዴት ፡ በጥንቃቄ ፡ እንደሚራመድ ፡ አስተውል
6. ተነቃነቀ. His fetters clanked when he moved. ሲነቃነቅ ፡ የእግር ፡ ብረቱ ፡ ተቃጨለ
7. ተካሄደ. The work on the new gymnasium moved slowly. ያዲሱ ፡ ስፖርት ፡ አዳራሽ ፡ ሥራ ፡ በቀስታ ፡ ተካሄደ
8. ደረሰ. The police move quickly whenever a crime is committed. ወንጀል ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ፖሊሶች ፡ ፈጥነው ፡ ይደርሳሉ
9. ዋለ. He moves in the best society. ውሎው ፡ ከትልልቅ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ነው

**move along ወደፊት ፡ ሄደ**

The policeman ordered the crowd to move along. ፖሊሱ ፡ የተሰበሰቡትን ፡ ሰዎች ፡ ወደፊት ፡ እንዲሄዱ ፡ አዘዘ

*Things are finally moving along now. በመጨረሻ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ መልክ ፡ እያገኘ ፡ ሄዷል

**move around ተዘዋወረ**

Although the man was very old, he still moved around with alacrity. ምንም ፡ እንኳን ፡ ሰውዬው ፡ በጣም ፡ ያረጁ ፡ ቢሆኑም ፡ አሁንም ፡ ነቃ ፡ ብለው ፡ ይዘዋወራሉ

**move aside ፈቀቅ ፡ አደረገ**

Move the table aside! ጠረጴዛውን ፡ ፈቀቅ ፡ አድርገው

**move away** (vt.) ሌላ ፡ ጋ ፡ ወሰደ

Move the table away, please! ጠረጴዛውን ፡ ሌላ ፡ ጋ ፡ ውሰደው

**move away** (vi.) ቤት ፡ ለቀቀ

They moved away a long time ago. ቤቱን ፡ ከለቀቁ ፡ ብዙ ፡ ጊዜያቸው ፡ ነው

**move closer ጠጋ ፡ አደረገ**

Move the lamp closer! መብራቱን ፡ ጠጋ ፡ አድርገው

**move in ገባ(በት)**

The office is not occupied; you may move in. ቢሮው ፡ አልተያዘም ፤ ልትገባበት ፡ ትችላለህ

**move into** ገባ
We're already moved into our new house. አዲሱ ፡ ቤታችን ፡ ገብተናል

**move (a) little** ሳብ ፡ አደረገ
Please move your chair forward a little so I can get by. ለማለፍ ፡ እንድችል ፡ እስቲ ፡ ወንበርህን ፡ ወደፊት ፡ ሳብ ፡ አድርገው

**move on** አለፈ ፤ ሄደ
Time moves on, no matter what we do. ምንም ፡ ብናደርግ ፡ ጊዜ ፡ ማለፉ ፡ አይቀርም
Move on! ሂድ!

**move out**
*The train moves out slowly. ባቡሩ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ፍጥነት ፡ ይጨምራል

**move out to** ገባ
My parents have moved out to the country. ቤተ ፡ ሰቦቼ ፡ ገጠር ፡ ገብተዋል

**move slowly** ተጓተተ
The work on the building moves slowly. የሕንጻው ፡ ሥራ ፡ ይጓተታል

**move to** ገባ
We're moving to a new house on October first. ጥቅምት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አዲስ ፡ ቤት ፡ እንገባለን

**move up** አደገ
He moved up fast in his new job. ባዲሱ ፡ ሥራው ፡ ቶሎ ፡ አደገ

**move up and down** አርገበገበ
The bird moved its wing up and down. ወፏ ፡ ክንፏን ፡ አርገበገበች

**be deeply moved** ስሜቱ ፡ በጣም ፡ ተነካ ፤ ከባድ ፡ ሐዘን ፡ ተሰማ(ው)
I was deeply moved to hear about his tragic death. አሳዛኙን ፡ አሟሟቱን ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ስሜቴ ፡ በጣም ፡ ተነካ ፡ (ከባድ ፡ ሐዘን ፡ ተሰማኝ)

**make move** አስኬደ
The mule balked, and nothing could make it move. በቅሎዋ ፡ ለግማ ፡ ስለቆመች ፡ ምንም ፡ ሊያስኬዳት ፡ አልቻለም
[See also 'heaven, limb, tear']

**move** (n.)
1. ተራ. Whose move is it? የማን ፡ ተራ ፡ ነው ?
2. እርምጃ. This is a move in the right direction. ይህ ፡ ወደ ፡ ትክክለኛው ፡ አቅጣጫ ፡ የሚመራ ፡ እርምጃ ፡ ነው
*What will his next move be? ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ያደርግ ፡ ይሆን ?
*Do you know all the moves in chess? የሰንጠረዥን ፡ ጨዋታ ፡ ሕጉን ፡ ሁሉ ፡ ታውቃለህ ?

**be on the move** ተነሣ
Our planes reported that enemy forces were on the move. አውሮፕላኖቻችን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ መነሣቱን ፡ አስታወቁ
*They're forever on the move. ምንም ፡ ጊዜ ፡ አያርፉም

**make a move**
1. አደረገ. He can't make a move without asking his wife. ሚስቱን ፡ ሳይጠይቅ ፡ ምንም ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም
2. ተንቀሳቀሰ. Every move I make hurts. በተንቀሳቀስኩ ፡ ቁጥር ፡ ያመኛል
[See also 'strategic']

**movement**
1. እንቅስቃሴ. The enemy's movements were closely watched. የጠላትን ፡ እንቅስቃሴ ፡ በደንብ ፡ ይከታተሉ ፡ ነበር
By a series of rapid movements, our forces managed to halt the enemy's advance. በርከት ፡ ባሉ ፡ ፈጣን ፡ እንቅስቃሴዎች ፡ ወታደሮቻችን ፡ የጠላትን ፡ እርምጃ ፡ ሊገቱ ፡ ቻሉ
He never belonged to any political movement. ከምንም ፡ ዓይነት ፡ የፖለቲካ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ አልነበረውም
2. መግቢያ ፡ መውጫ. His movements were closely watched. መግቢያ ፡ መውጫውን ፡ በጥብቅ ፡ ይከታተሉ ፡ ነበር

**movie** ፊልም
They are showing a good movie today at the cinema. ዛሬ ፡ ሲኒማ ፡ ቤት ፡ ጥሩ ፡ ፊልም ፡ ይታያል

**movie camera** ሲኒማ ፡ ማንሻ
I bought a movie camera for my son. ለልጄ ፡ ሲኒማ ፡ ማንሻ ፡ ገዛሁለት

**movie theater** ሲኒማ ፡ ቤት
A new movie theater was built in the Mercato. መርካቶ ፡ አዲስ ፡ ሲኒማ ፡ ቤት ፡ ተሠርቷል

**moving**
1. የሚንቀሳቀስ. Any moving object attracts my attention. የሚንቀሳቀስ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሐሳቤን ፡ ይስበዋል
2. ስሜት ፡ የሚነካ. He told us a moving story. ስሜት ፡ የሚነካ ፡ ታሪክ ፡ ነገረን

**moving spirit**
1. ዋና ፡ አዘጋጅ. He was the moving spirit in planning for the party. የድግሱ ፡ ዋና ፡ አዘጋጁ ፡ እሱ ፡ ነበር
2. የታገለ. He was the moving spirit in getting the bill passed. የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ እንዲያልፍ ፡ የታገለው ፡ እሱ ፡ ነበር

**mow** ዐጨደ
I must mow the grass. ሣሩን ፡ ማጨድ ፡ አለብኝ
**mow down** ዐጨደ
He mowed the captives down with a gun. ምርኮኞቹን ፡ በጠመንጃ ፡ ዐጨዳቸው

**Mr.**
1. ሚስተር. Where is Mr. Smith? ሚስተር ፡ ስሚዝ ፡ የት ፡ ናቸው ?
2. አቶ. Where is Mr. Kebbede? አቶ ፡ ከበደ ፡ የት ፡ ናቸው ?

**Mrs.**
1. ሚስዝ. Where is Mrs. Smith? ሚስዝ ፡ ስሚዝ ፡ የት ፡ ናቸው ?
2. ወይዘሮ. Where is Mrs. Belaynesh? ወይዘሮ ፡ በላይነሽ ፡ የት ፡ ናቸው ?

**much**
1. ብዙ. There isn't much food in the house. እቤት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ምግብ ፡ የለም
2. በጣም. I feel much better. በጣም ፡ ተሽሎኛል
You should work much less; you are hurting your health. ጤንነትህን ፡ ስለምትጐዳ ፡ ሥራህን ፡ በጣም ፡ መቀነስ ፡ አለብህ
**much as** ምንም ፡ እንኳን
Much as I should like to go, I feel I must stay here. ምንም ፡ እንኳን ፡ ለመሄድ ፡ ብፈልግ ፡ እዚህ ፡ መቆየት ፡ አለብኝ
**much harder** የበለጠ ፡ ጠንክሮ
You must work much harder. የበለጠ ፡ ጠንክረህ ፡ መሥራት ፡ አለብህ
**much less**
*I didn't see him, much less speak to him. ማናገር ፡ ቀርቶ ፡ አላየሁትም
**much of** አብዛኛው
Much of what you say is true. የምትለው ፡ ነገር ፡ አብዛኛው ፡ እውነት ፡ ነው
**(be) much the same** ምንም ፡ ያህል ፡ አልተለወጠም
The patient's condition is pretty much the same. የበሽተኛው ፡ ሁኔታ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልተለወጠም
**as much as**
*This would be as much as saying 'I accept your idea'. ይህ ፡ አሳብህን ፡ እቀበላለሁ ፡ የማለት ፡ ያህል ፡ ነበር
**as much ... as** ---ም ፡ ---ም
It's as much your fault as mine. ስሕተቱ ፡ የኔም ፡ ያንተም ፡ ነው
**how much ?**
1. (ዋጋው) ፡ ስንት. How much is this? ይህ ፡ ዋጋው ፡ ስንት ፡ ነው ?
2. ምን ፡ ያህል. How much will this car cost me? ለዚህ ፡ መኪና ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ያስከፍሉኛል ?
**how much !**
1. እንዴት. How much I love that! ያንን ፡ እንዴት ፡ እወደዋለሁ ፡ መሰለህ !
2. ምንኛ. How much I love this country! ይህችን ፡ አገር ፡ ምንኛ ፡ እወዳታለሁ !
**make too much of** አጋነነ
We mustn't make too much of this incident. ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ ማጋነን ፡ የለብንም
**not much (of)** እምብዛም
He is not much of a scholar. የርሱ ፡ ምሁርነት ፡ እምብዛም ፡ ነው
**this much** ይህን ፡ ያህል
What's going to happen to you after you eat this much? ይህን ፡ ያህል ፡ በልተህ ፡ ምን ፡ ልትሆን ፡ ነው ?
*This much is certain: He won't play tricks on us again. ዳግመኛ ፡ እንደማይጫወትብን ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው
[See also 'ever, so, thank, that, too, twice, very']

**mucus** ንፍጥ
Wipe off the mucus! ንፍጥህን ፡ ጥረግ

**mud** ጭቃ
In the rainy season, it is difficult to go through the mud. በክረምት ፡ ጭቃው ፡ አያስኬድም
**be covered with mud** ጨቀየ
The doorstep was covered with mud where people had wiped their feet. ሰዎች ፡ እግራቸውን ፡ ስለጠረጉበት ፡ ደጃፉ ፡ ጨቅይቶ ፡ ነበር
**deposit of mud** ደለል
A deposit of mud covered the field after the flood had subsided. ጐርፉ ፡ ከጐደለ ፡ በኋላ ፡ ደለል ፡ ሜዳውን ፡ አለበሰው
**form into mud** አጨቀየ
The rain formed the dust into mud. ዝናቡ ፡ መሬቱን ፡ አጨቀየው
**layer of mud** ደለል
The flood deposited a layer of mud in the streets. ጐርፉ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ደለል ፡ አከማቸ

**muddle** (v.) አማታ
You have muddled the scheme completely. እቅዱን ፡ በፍጹም ፡ አማተሽዋል

**muddle up** አደናገረ
A financial crisis muddled up the British. እንግሊዞችን ፡ የገንዘብ ፡ ችግር ፡ አደናገራቸው

**be muddled** ተተራመሰ
Everything was muddled by the late arrival of the train. በባቡሩ ፡ ዘግይቶ ፡ መድረስ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ተተራመሰ

**muddle** (n.), **in a ~** ተመሰቃቅሎ
When mother came home, she found the house in a muddle. እናቴ ፡ እቤት ፡ ስትገባ ፡ ቤቱን ፡ ተመሰቃቅሎ ፡ አገኘችው

**muddy**
1. የጨቀየ. A car drove down the muddy lane. መኪናው ፡ በጨቀየ ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡ ተጓዘ
2. የጭቃ. Don't walk around with your muddy feet! በጭቃ ፡ እግርህ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አትሂድ
3. ድፍርስ. We need a filter for this muddy water. ለዚህ ፡ ድፍርስ ፡ ውኃ ፡ ማጣሪያ ፡ ያስፈልገናል
4. የተማታ. His muddy thinking is difficult to understand. የተማታውን ፡ አስተሳሰቡን ፡ ለመረዳት ፡ ያዳግታል

**be muddy**
1. ጨቀየ. The ground here is muddy. እዚህ ፡ ጋ ፡ መሬቱ ፡ ጨቅይቷል
2. ማጥ ፡ ብቻ ፡ ነው. The shore of the lake is muddy. የሐይቁ ፡ ዳርቻ ፡ ማጥ ፡ ብቻ ፡ ነው

**muffle**
1. ሸፈነ. She muffled her throat in a warm scarf. አንገቷን ፡ በወፍራም ፡ ያንገት ፡ ልብስ ፡ ሸፈነችው
2. አፈነ. You have to muffle this loud noise, it's disturbing everyone. ይህን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ ማፈን ፡ አለብህ ፤ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ያስቸግራል

**muffler** ጭስ ፡ ማውጫ
My car's muffler is broken. የመኪናዬ ፡ ጭስ ፡ ማውጫ ፡ ተሰብሯል

**muggy** ጭፍግግ ፡ ያለ
During the rainy season, the days are muggy. በክረምት ፡ ጊዜ ፡ ቀኑ ፡ ጭፍግግ ፡ ያለ ፡ ነው

**mulch** [ከገለባ ፡ ከቅጠሎችና ፡ ከለስላሳ ፡ አፈር ፡ የተደባለቀ ፡ ማዳበሪያ]

**mule** በቅሎ
You can find a good mule for two hundred dollars. ጥሩ ፡ በቅሎ ፡ በሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ትገኛለች

**muleteer** ለጓሚ
He hired a muleteer and four mules when he went on a trip to the mountains. ወደ ፡ ተራራው ፡ ለጉዞ ፡ ወጥቶ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ለጓሚና ፡ አራት ፡ በቅሎዎች ፡ ተከራየ

**mull (over)** ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ቆየ
He mulled over the decision for days. ውሳኔውን ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ቆየ

**multicolored** ብዙ ፡ ቀለማት ፡ ያለው
She put on the multicolored dress. ብዙ ፡ ቀለማት ፡ ያለው ፡ ልብስ ፡ ለበሰች

**multifarious** የተለያየ ፡ ዓይነት
He has multifarious interests. የተለያየ ፡ ዓይነት ፡ ፍላጎት ፡ አለው

**multilateral**
1. ብዙ ፡ ጐን ፡ ያለው. The hexagon is a multilateral geometrical figure. ሄክሳጎን ፡ ብዙ ፡ ጐን ፡ ያለው ፡ የጂዮሜትር ፡ ቅርጽ ፡ ነው
2. የጋራ. The NATO nations signed a multilateral defense agreement. የኔቶ ፡ ድርጅት ፡ አባል ፡ የሆኑ ፡ አገሮች ፡ ለመከላከያ ፡ የሚሆን ፡ የጋራ ፡ ስምምነት ፡ ተፈራረሙ

**multiple**
1. በርከት ፡ ያለ. He suffered multiple injuries. በርከት ፡ ያለ ፡ ያካል ፡ ጉዳት ፡ ደረሰበት
2. ልዩ ፡ ልዩ. He's a man of multiple interests. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ነው

**multiplication table** የጊዜ ፡ ቤት
Learn the multiplication table! የጊዜ ፡ ቤት ፡ አጥና !

**multiply** (multiplied), vt. አበዛ
If you multiply 10 by 4, you get 40. ዓሥርን ፡ በአራት ፡ ብታበዛ ፡ አርባ ፡ ይሆናል

**multiply** (vi.)
1. ተራባ. Rabbits multiply very quickly. ጥንቸሎች ፡ ቶሎ ፡ ይራባሉ
2. በዛ. His troubles multiplied. መከራው ፡ በዛ

**multitude, ~ of** በጣም ፡ ብዙ
A multitude of thoughts passed through my mind. በጣም ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ታሰቡኝ

**large mulitude** ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌለው ፡ ሕዝብ
A large multitude gathered in the street. መንገዱ ፡ ላይ ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌለው ፡ ሕዝብ ፡ ተሰበሰበ

**multitudinous** በጣም ፡ ብዙ
Multitudinous birds sang in the trees. በጣም ፡ ብዙ ፡ ወፎች ፡ በዛፉ ፡ ላይ ፡ ይንጫጩ ፡ ነበር

**mum, keep ~** ጸጥ ፡ አለ
Keep mum about this; tell no one! ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ጸጥ ፡ በል ፤ ለማንም ፡ አትንገር

**mumble** አጉመተመተ
We can't hear him because he always mumbles. ሁልጊዜ ፡ ስለሚያጉመተምት ፡ የሚለው ፡ አይሰማንም

**mummy** [እንዳይፈርስ ፡ በመድኃኒት ፡ አማካይነት ፡ የተጠበቀ ፡ የሰው ፡ ሬሳ]

**mumps** ጆሮ ፡ ደግፍ
I caught the mumps. ጆሮ ፡ ደግፍ ፡ ይዞኛል

**munch, ~ on**
1. አላመጠ. He is munching on a cookie. ብስኩት ፡ ያላምጣል
2. ቈረጠመ. He is munching on parched grain. ቆሎ ፡ ይቈረጥማል

**mundane** የዚህ ፡ ዓለም
Monks are uninterested in mundane affairs. መነኰሳት ፡ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ጉዳይ ፡ ግድ ፡ የላቸውም

**municipal** የማዘጋጃ ፡ ቤት
Municipal bonds will finance the new waterworks. የማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ቦንዶች ፡ ያዲሱን ፡ የውኃ ፡ ማሰራጫ ፡ ይከፍላሉ

**municipality** (municipalities)
1. ከተማ. There were mostly Moslems in this municipality. በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ እስላሞች ፡ ነበሩ
2. ማዘጋጃ ፡ ቤት. The municipality building of Addis Ababa is new. ያዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ሕንጻ ፡ አዲስ ፡ ነው

**munificent** ታላቅ
He made a munificent bequest to the university. ለዩኒቨርሲቲው ፡ ታላቅ ፡ ንብረት ፡ አወረሰ

**munition(s)** ትጥቅና ፡ ሥንቅ
The war was lost due to a shortage of munitions. በጦርነቱ ፡ የተሸነፍነው ፡ ትጥቅና ፡ ሥንቅ ፡ በማነሱ ፡ ነው

**mural** (n.) ግድግዳ ፡ ላይ ፡ የተሣለ ፡ ሥዕል
There is a large mural in Africa Hall. በአፍሪካ ፡ አዳራሽ ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ የተሣለ ፡ ትልቅ ፡ ሥዕል ፡ አለ

**murder** (v.)
1. ገደለ. He was accused of having murdered his wife. ሚስቱን ፡ በመግደል ፡ ተከሰሰ
2. አበላሸ. She murders the song everytime she tries to sing it. በዘፈነች ፡ ቁጥር ፡ ዘፈኑን ፡ ታበላሽዋለች

**murder** (n.)
1. ነፍስ ፡ ግዳይ. The murder was not discovered until a few days later. ነፍስ ፡ ግዳዩ ፡ እስከ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ አልታወቀም ፡ ነበር
2. ነፍስ ፡ ገዳይነት. The prisoner did not bat an eye when accused of murder. እስረኛው ፡ በነፍስ ፡ ገዳይነት ፡ ሲወነጀል ፡ ዓይኑን ፡ እንኳን ፡ አልሰበረም
3. ግድያ. The murder outraged the citizens. ግድያው ፡ ነዋሪዎቹን ፡ አስቈጣቸው
4. መጋደል. The antagonism between the two villages led to murders. በሁለቱ ፡ መንደሮች ፡ መሀከል ፡ ያለው ፡ ጥላቻ ፡ እስከ ፡ መጋደል ፡ አደረሳቸው
5. መግደል. The murder of the child was a beastly crime. የሕፃኑ ፡ መግደል ፡ የአውሬነት ፡ ተግባር ፡ ነበር
6. አሟሟት. The news of Kennedy's murder astounded everybody. የኬኔዲ ፡ አሟሟት ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አስደነገጠ

**commit murder** ሰው ፡ ገደለ
He committed murder, so the police arrested him. ሰው ፡ ስለገደለ ፡ ፖሊሶች ፡ ያዙት

**murderer** ነፍስ ፡ ገዳይ
The murderer escaped from the jail. ነፍስ ፡ ገዳዩ ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ አመለጠ

**murderous**
1. ሊገድል ፡ የሚችል. The villain aimed a murderous blow at the hero's back. ተንኰለኛው ፡ ጀግናው ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ሊገድል ፡ የሚችል ፡ ምት ፡ ሰነዘረ
2. ነፍስ ፡ ለማጥፋት ፡ የታቀደ. A murderous plot was uncovered by the police. ነፍስ ፡ ለማጥፋት ፡ የታቀደው ፡ አድማ ፡ በፖሊስ ፡ ተደረሰበት
3. ካፈር ፡ የሚደባልቅ. He gave me a murderous look. ካፈር ፡ በሚደባልቅ ፡ አስተያየት ፡ አየኝ

**murky** ጨለማ ፡ የሆነ
He could not see anything in the murky cave. ጨለማ ፡ በሆነው ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ሊያይ ፡ አይችልም

**murmur** (v.)
1. አጕረመረመ. They murmur about the work. ሥራው ፡ ስለበዛባቸው ፡ ያጕረመርማሉ
2. አፏጨ ፤ ጮኸ. The wind was murmuring. ነፋሱ ፡ ያፏጭ ፡ (ይጮኽ) ፡ ነበር

**murmur** (n.)
1. ጉሩምሩምታ. I hear a murmur of dissent.

ያለመስማማታቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ ጉሩምሩምታ ፡ ይሰማኛል
The brook's ceaseless murmur is enjoyable. የማያቋርጠው ፡ የምንጩ ፡ ጉሩምሩምታ ፡ አስደሳች ፡ ነው
2. ማጉረምረም. He paid the fine without a murmur. ቅጣቱን ፡ ያላንዳች ፡ ማጉረምረም ፡ ከፈለ

**muscle** ጡንቻ
Physical exercise develops muscles. ጅምናስቲክ ፡ ጡንቻዎቻችንን ፡ ያዳብራል
[See also 'strain']

**muscular**
1. የጡንቻ. He has a muscular ache. የጡንቻ ፡ ሕመም ፡ ይዞታል
2. ጡንቻማ. He has muscular legs. እግሩ ፡ ጡንቻማ ፡ ነው

**muse** አሰላሰለ
The boy spent the whole afternoon musing. ልጁ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ሲያሰላስል ፡ ጊዜውን ፡ አሳለፈ

**museum** ቤተ ፡ መዘክር
Let's visit the museum! ቤተ ፡ መዘክሩን ፡ እንጐብኘው

**mush**
1. ንፍሮ. He eats mush made of cornmeal. የበቆሎ ፡ ንፍሮ ፡ ይበላል
2. ማጥ. After the heavy rain, the old dirt road turned to mush. ከባዱ ፡ ዝናብ ፡ ከጣለ ፡ በኋላ ፡ አሮጌው ፡ የአፈሩ ፡ መንገድ ፡ ማጥ ፡ ሆነ

**mushroom** (v.) ብቅ ፡ ብቅ ፡ አለ
Stores mushroomed along the highway. በዋናው ፡ መንገድ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ሱቆች ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ አሉ
*The little town mushroomed into a city. ትንሿ ፡ ከተማ ፡ ቶሎ ፡ አደገች

**mushroom** (n.) እንጉዳይ
Mushrooms grow in the rainy season. እንጉዳይ ፡ በክረምት ፡ ይበቅላል

**music** ሙዚቃ
I like to listen to soft music. ለስላሳ ፡ ሙዚቃን ፡ መስማት ፡ እወዳለሁ

**musical** የሙዚቃ
Ethiopia has several kinds of musical instruments. ኢትዮጵያ ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያዎች ፡ አሏት

**musician** ሙዚቀኛ
The musicians took their seats in the hall. ሙዚቀኞቹ ፡ ባዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ስፍራቸውን ፡ ያዙ

**musk** ዝባድ
Musk is obtained from the civet cat. ዝባድ ፡ የሚገኘው ፡ ከጥርኝ ፡ ነው

**musket** ነፍጥ
I have a musket that my grandfather used. አያቴ ፡ ይይዙት ፡ የነበረ ፡ ነፍጥ ፡ አለኝ

**musketeer** ነፍጠኛ
The three musketeers are a famous trio in French literature. ሦስቱ ፡ ነፍጠኞች ፡ በፈረንሳይ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የታወቁ ፡ የሦስት ፡ ሰዎች ፡ ጓድ ፡ ነው

**musky** የዝባድ
This has a musky odor. ይህ ፡ የዝባድ ፡ ሽታ ፡ አለው

**Muslim** እስላም
There are many Muslims in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ እስላሞች ፡ አሉ

**muslin** ሻሽ
His head was wrapped in muslin to keep off the dirt. አቧራው ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ እንዳይበንበት ፡ ሻሽ ፡ አስሮ ፡ ነበር

**muss** በታተነ
The wind mussed her hair. ነፋሱ ፡ ጸጉሯን ፡ በታተነው

**must** (v.)
1. አለ(በት). This must be the book you want. የምትፈልገው ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ መሆን ፡ አለበት
We must see what can be done. ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚቻል ፡ ማሰብ ፡ አለብን
You must do as you are told. ያሉህን ፡ መሥራት ፡ አለብህ
2. gerundive + ይሆናል. He must have sneaked into the house. ሾልኮ ፡ ብሎ ፡ ገብቶ ፡ ይሆናል
I must have left my briefcase somewhere. ቦርሳዬን ፡ አንዱ ፡ ጋ ፡ ትቼው ፡ ይሆናል
*I must ask you not to do that again. እንዳይደግምህ ፡ አሳስብሃለሁ
*I must try to see him more often. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ላየው ፡ እሞክራለሁ
*You mustn't do that! እንዳታደርገው

**must have** ያስፈልገዋል
She said she must have a new hat for Easter. ለፋሲካ ፡ አዲስ ፡ ባርኔጣ ፡ ያስፈልገኛል ፡ አለች

**must have been** ሳይሆን ፡ አይቀርም
He must have been in Ethiopia at that time. በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም

**must** (n.), **be a ~** ግዴታ ፡ ነው ፤ የግድ ፡ ያስፈልጋል
To finish on time is a must. በጊዜ ፡ መጨረስ ፡ ግዴታ ፡ ነው
In winter warm clothes are a must. በክረምት ፡ ሞቃት ፡ ልብስ ፡ የግድ ፡ ያስፈልጋል

**mustache** ሪዝ
He is growing a mustache. ሪዙን ፡ ያሳድጋል

**mustard** ሰናፍጭ
Mustard is sold in the market. ሰናፍጭ ፡ ገበያ ፡ ውስጥ ፡ ይሸጣል

**muster** ሰበሰበ
The lieutenant is mustering the troops. የመቶ ፡ አለቃው ፡ ወታደሮቹን ፡ ይሰበስባል

**muster (one's) courage** ደረቱን ፡ ገለበጠ ፤ ደረቱን ፡ ገፋ
He mustered his courage and went to see the director. ደረቱን ፡ ገልብጦ ፡ (ገፍቶ) ፡ ሥራ ፡ መሪውን ፡ ለማነጋገር ፡ ሄደ

**muster in** ለወታደርነት ፡ ተመዘገበ
He mustered in last month. ባለፈው ፡ ወር ፡ ለወታደርነት ፡ ተመዘገበ

**be mustered out** ተሰናበተ
He was mustered out of service after the war. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ካገልግሎት ፡ ተሰናበተ

**musty** በስብሶ ፡ የሻገተ
The room was full of musty old clothes. ክፍሉ ፡ በስብሶ ፡ በሻገተ ፡ አሮጌ ፡ ልብስ ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር

**be musty** አና ፡ አና ፡ አለ
The room is musty from being closed so long. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተዘግቶ ፡ በመቆየቱ ፡ ክፍሉ ፡ አና ፡ አና ፡ ይላል

**(be) mutable** በየጊዜው ፡ የሚለዋወጥ
Tax and voting laws are mutable. የታክስና ፡ የምርጫ ፡ ሕጎች ፡ በየጊዜው ፡ የሚለዋወጡ ፡ ሕጎች ፡ ናቸው

**mutate** ተለወጠ
The vegetation of the earth mutated during the Ice Age. የመሬት ፡ ዕፀዋት ፡ የተለወጡት ፡ በበረዶ ፡ ዘመን ፡ ነው

**mutation** መለወጥ
A mutation of the earth's vegetation occurred during the Ice Age. የመሬት ፡ ዕፀዋት ፡ መለወጥ ፡ የሆነው ፡ በበረዶ ፡ ዘመን ፡ ነው

**mute** (v.) አለሰለሰ
He muted his voice. ድምፁን ፡ አለሰለሰ

**be muted** አነሰ
The sound was muted by the distance. ከርቀቱ ፡ የተነሣ ፡ ድምፁ ፡ አነሰ

**mute** (adj.) ዲዳ
He was born mute. ዲዳ ፡ ሆኖ ፡ ተወለደ

**remain mute** ተጋገረ
When the lawyer asked him a question, he remained mute. ጠበቃው ፡ በጠየቀው ፡ ጊዜ ፡ ተጋገረ
[See also 'deaf']

**mutilate**
1. ቈራረጠ. The robbers mutilated the body of the victim. ቀማኞቹ ፡ የገደሉትን ፡ ሰው ፡ ገላ ፡ ቈራረጡት
2. አበላሸ. He mutilated the page by drawing black lines on it. ጥቁር ፡ መሥመር ፡ እያሠመረ ፡ ገጹን ፡ አበላሸው

**mutinous** አድመኛ
The mutinous crew threatened the captain. አድመኞቹ ፡ መርከበኞች ፡ ካፒቴኑን ፡ አስፈራሩት

**mutiny** (mutinied), v. ዐመፀ
The Russian army mutinied before the revolution. የሩሲያ ፡ ወታደሮች ፡ ከሽብሩ ፡ በፊት ፡ ዐመፁ

**mutiny** (n.) ማመፅ
The mutiny of the troops was due to low pay. የወታደሮቹ ፡ ማመፅ ፡ በደሞዝ ፡ ማነስ ፡ ምክንያት ፡ ነበር

**mutter** (v.)
1. አጕረመረመ. Thunder muttered in the distance. ነጐድጓዱ ፡ ከሩቅ ፡ አጕረመረመ
2. ልቡ ፡ አጕረመረመ. He muttered in his sleep. በእንቅልፍ ፡ ልቡ ፡ አጕረመረመ

**mutter to oneself** ብቻውን ፡ አወራ
He was muttering to himself as he walked along. ብቻውን ፡ እያወራ ፡ ይሄዳል

**mutter under one's breath**
*He muttered a curse under his breath. በሆዱ ፡ ተሳደበ

**mutter** (n.)
1. ድምፅ. We could hear the mutter of distant thunder. የመብረቅ ፡ ድምፅ ፡ ከሩቅ ፡ ይሰማናል
2. ጕርምርምታ. There was a mutter of discontent in class. በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ የቅሬታ ፡ ጕርምርምታ ፡ ይሰማ ፡ ነበር

**mutton** የበግ ፡ ሥጋ
The Ethiopians like to eat mutton. ኢትዮጵያውያን ፡ የበግ ፡ ሥጋ ፡ ይወዳሉ

**mutual** የጋራ
The contract was extended by mutual agreement. ውሉ ፡ በጋራ ፡ ስምምነት ፡ ታደሰ
Mutual respect is essential for true friendship. ለእውነተኛ ፡ ጓደኝነት ፡ የጋራ ፡ አክብሮት ፡ ያስፈልጋል
It will be to our mutual advantage. ጥቅሙ ፡ የጋራችን ፡ ነው

**muzzle** (v.)
1. አፉን ፡ አሰረ. He muzzled the ox so that it would not eat the grain. በሬው ፡ እህል ፡ እንዳይበላ ፡ አፉን ፡ አሰረው
2. ነጻነት ፡ ከለከለ. The government muzzled the press. መንግሥቱ ፡ የጋዜጦችን ፡ ነጻነት ፡ ከለከለ

**muzzle** (n.) አፍ
There is blood on the dog's muzzle. ውሻው ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ደም ፡ አለ
*Oxen wear a muzzle so they won't eat the grain. በሬዎች ፡ እህል ፡ እንዳይበሉ ፡ አፋቸው ፡ ይታሰራል

**my**
1. የኔ. This is my book. ይህ ፡ የኔ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው
2. - e, - ዬ. He is my father. እሱ ፡ አባቴ ፡ ነው
This is my table. ይህ ፡ ጠረጴዛዬ ፡ ነው

**my! my!** አቤት ፡ አቤት!
My! my! What a pretty child she is! አቤት ፡ አቤት ፡ እንዴት ፡ ታምራለች !

**myriads of** ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌላቸው
There are myriads of stars on a June night. በሰኔ ፡ ምሽት ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌላቸው ፡ ከዋክብት ፡ ይታያሉ

**myriad** (adj.) ቁጥር ፡ የሌላቸው
They were admiring the myriad stars of the summer night. ቁጥር ፡ የሌላቸውን ፡ የበጋ ፡ ከዋክብት ፡ ያደንቁ ፡ ነበር

**myrrh** ከርቤ
Myrrh is found in the market. ከርቤ ፡ ከገበያ ፡ ይገኛል

**myself** ራሴ
I'll do it myself. ራሴ ፡ እሠራዋለሁ

**be myself**
I am not myself today. ዛሬ ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ አይደለሁም

**by myself**
1. ብቻዬን. I sat by myself in the garden. አትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ብቻዬን ፡ ተቀመጥኩ
2. ራሴ. I cooked the meal by myself. ምግቡን ፡ ራሴ ፡ አዘጋጀሁት

**mysterious**
1. እንግዳ ፡ የሆነ. His mysterious behavior made the police suspicious. እንግዳ ፡ የሆነው ፡ ሁኔታው ፡ ፖሊሶቹን ፡ ጥርጣሬ ፡ አሳደረባቸው
2. ልዩ ፡ ዓይነት. There was a mysterious light in the sky. በሰማይ ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ብርሃን ፡ ነበር

**mystery**
1. ምስጢር. The mystery of the minister's disappearance was never solved. የሚኒስትሩ ፡ መጥፋት ፡ ምስጢሩ ፡ አልተደረሰበትም
2. የተሰወረ ፡ ጉዳይ. The detective untangled the mystery after a few days. ወንጀል ፡ መርማሪው ፡ የተሰወረውን ፡ ጉዳይ ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ደረሰበት
3. ረቂቅ ፡ ነገር. One of the mysteries of life is love. ከሕይወት ፡ ረቂቅ ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ፍቅር ፡ ነው

**be a mystery** አልታወቀም
The name of the thief is a mystery. የሌባው ፡ ስም ፡ አልታወቀም

**mystic** (adj.) ረቂቅ
I am studying the mystic teachings of the ancients. የጥንታውያንን ፡ ረቂቅ ፡ ትምህርት ፡ አጠናለሁ

**mystify** (mystified) የሚለውን ፡ አሳጣው
The magician's tricks mystified the audience. የአስማተኛው ፡ ድርጊቶች ፡ ተመልካቾቹን ፡ የሚሉትን ፡ አሳጣቸው

**myth**
1. አፈ ፡ ታሪክ. There is a myth that serpents ruled the land in ancient times. በጥንት ፡ ዘመን ፡ ዘንዶዎች ፡ አገሩን ፡ ይገዙ ፡ ነበር ፡ የሚል ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፡ አለ
2. መሠረተ ፡ ቢስ ፡ እምነት. Racial superiority is a myth. አንዱ ፡ ነገድ ፡ ከሌላው ፡ ይበልጣል ፡ ማለት ፡ መሠረተ ፡ ቢስ ፡ እምነት ፡ ነው
3. ተረት. His large stamp collection was just a myth. ብዙ ፡ ቴምብር ፡ ሰብስቤያለሁ ፡ የሚለው ፡ ተረት ፡ ነው

**mythical** በአፈ ፡ ታሪክ ፡ የተፈጠረ
Hercules was a mythical hero. ሄርኩሊስ ፡ በአፈ ፡ ታሪክ ፡ የተፈጠረ ፡ ጀግና ፡ ነበር

**mythology** (mythologies) አፈ ፡ ታሪክ
We study Greek mythology in school. በትምህርት ፡ ቤት ፡ የግሪኮችን ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፡ እንማራለን

# N

**nag** (nagged)
1. **ጨቀጨቀ**. He nagged his father for a car. አባቱን ፡ መኪና ፡ ግዛልኝ ፡ እያለ ፡ ጨቀጨቀው
2. **አሠቃየ**. This headache has been nagging at me all day. ራስ ፡ ምታት ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሲያሠቃየኝ ፡ ዋለ

**nagging** ንዝንዝ
She drove me to drink by her constant nagging. በማያቋርጥ ፡ ንዝንዟ ፡ ከጠጭነት ፡ አደረሰችኝ

**nail** (v.) በምስማር ፡ መታ
Please nail the board to the wall! ሰሌዳውን ፡ ግድግዳው ፡ ላይ ፡ በምስማር ፡ ምታው

**nail down** ማሰሪያ ፡ አደረገ(ለት)
Signing the contract will finally nail down the agreement. ውሉን ፡ መፈረም ፡ ስምምነቱን ፡ ማሰሪያ ፡ ያደርግለታል

**nail together** በምስማር ፡ አያያዘ
Nail the boards together! ሳንቃዎቹን ፡ በምስማር ፡ አያይዛቸው

**nail** (n.)
1. **ምስማር**. Don't hammer the nail in too far! ምስማሩን ፡ በጣም ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ አትምታው
2. **ጥፍር**. I just broke a nail on my left hand. የግራ ፡ እጄ ፡ ጥፍር ፡ ተሰበረ

**hit the nail on the head** እቅጩን ፡ አመለከተ ፤ እቅጩን ፡ ተናገረ
Your analysis hit the nail on the head. ትንተናህ ፡ እቅጩን ፡ አመለከተ
When you told me he was a cheat, you hit the nail on the head. አታላይ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ስትነግረኝ ፡ እቅጩን ፡ ተናገርክ
[See also 'tooth']

**naive** ገራገር
She is a naive young woman. ገራገር ፡ የሆነች ፡ ወጣት ፡ ናት

**naked**
1. **ራቁት** + suffix pronouns + **ን**. He is naked. ራቁቱን ፡ ነው
The children run around naked. ሕፃናቱ ፡ ራቁታቸውን ፡ ይሯሯጣሉ
2. **ባዶ**. You can't see germs with the naked eye. ጀርሞችን ፡ በባዶ ፡ ዓይን ፡ ማየት ፡ አይቻልም
*The trees were left naked of leaves. የዛፎቹ ፡ ቅጠሎች ፡ በሙሉ ፡ ረግፈው ፡ ነበር

**(the) naked truth** እቅጩን
He told me the naked truth. እቅጩን ፡ ነገረኝ
[See also 'strip']

**name** (v.)
1. **ስም ፡ ጠራ**. Can you name all the stars? የከዋክብቶቹን ፡ ሁሉ ፡ ስም ፡ ትጠራለህ ?
2. **ስም ፡ ጠቀሰ**. Can you name the most important people of Asia? የእስያን ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ልትጠቅስ ፡ ትችላለህ ?
3. **ተናገረ**. Name your price! የምትሸጥበትን ፡ ተናገር
4. **ስም ፡ አወጣ(ለት)**. He named the baby May. ሕፃኗን ፡ ሜይ ፡ ብሎ ፡ ስም ፡ አወጣላት
5. **አቀረበ ፤ ሰጠ**. She named several reasons for her delay. ስለ ፡ መዘግየቷ ፡ ብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ አቀረበች ፡ (ሰጠች)
6. **ወሰነ**. The class named the day for the party. ተማሪዎቹ ፡ የፓርቲውን ፡ ቀን ፡ ወሰኑ

**name after** በ - - - ስም ፡ ጠራ
They named the baby after his father. ሕፃኑን ፡ በአባቱ ፡ ስም ፡ ጠሩት

**be named**
1. **ተሾመ**. Mr. Smith has been named acting director. ሚስተር ፡ስሚዝ ፡ ተጠባባቂ ፡ ዲሬክተር ፡ ሆኖ ፡ ተሾመ
2. **የ - - - ስም ፡ ተጠቀሰ**. Three persons were named in the report. ሪፖርቱ ፡ ውስጥ ፡ የሦስት ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ተጠቅሷል

**name** (n.) ስም
What's your name? ስምህ ፡ ማነው ?
He got a bad name. መጥፎ ፡ ስም ፡ አተረፈ
I know him only by name. የማውቀው ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ ነው

**call someone names** ሰደበ
He got mad and called me names. ተናዶ ፡ ሰደበኝ

**(a) good name** ዝና
He got a good name in the war. በጦርነቱ ፡ ዝናን ፡ አተረፈ

**in name only** በስም ፡ ብቻ
He is president in name only. ፕሬዚዳንትነቱ ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ ነው

**narrow-minded** ሐሳበ ፡ ጠባብ
A narrow-minded person hugs his opinions closely. ሐሳበ ፡ ጠባብ ፡ ሰው ፡ ሐሳቡን ፡ አንቆ ፡ ይይዛል

**nasal** የአፍንጫ
The nasal sounds are m, n. « መ » ፡ « ነ » ፡ የአፍንጫ ፡ ድምፆች ፡ ናቸው

**have a nasal (pronunciation, voice, tone)** ሲ + imperfect + ተነፋነፈ
French people have a nasal pronunciation of Amharic. ፈረንሳዮች ፡ አማርኛ ፡ ሲያነቡ ፡ ይነፋነፋሉ
He has a nasal voice. ሲናገር ፡ ይነፋነፋል
He sings in a nasal tone. ሲዘምር ፡ ይነፋነፋል

**nascent** በማደግ ፡ ላይ ፡ ያለው
The nascent republics of West Africa made mutual treaties with each other. በማደግ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ የምዕራብ ፡ አፍሪካ ፡ ግዛቶች ፡ የጋራ ፡ ስምምነት ፡ አደረጉ

**nasty**
1. አስጠያፊ. The nasty remark angered her. አስጠያፊው ፡ አስተያየት ፡ አናደዳት
2. መጥፎ. This medicine has a nasty taste. ይህ ፡ መድኃኒት ፡ መጥፎ ፡ ጣዕም ፡ አለው
A nasty rumor about him is floating around town. እሱን ፡ የሚመለከት ፡ መጥፎ ፡ ወሬ ፡ በከተማው ፡ ይነፍሳል
3. ቆሻሻ. The room was nasty and smelly. ክፍሉ ፡ ቆሻሻና ፡ ግም ፡ ነበር
4. የቀፈፈ. Do you always have such nasty weather? ያየሩ ፡ ሁኔታ ፡ ዘወትር ፡ እንደዚህ ፡ የቀፈፈ ፡ ነው ?

**be nasty** ጨከነ
Don't be so nasty to children! በልጆች ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ አትጨክን

**nation**
1. አገር. The whole nation mourned his death. በሱ ፡ ሞት ፡ አገሩ ፡ በሙሉ ፡ አዘነ
2. መንግሥት (pl. መንግሥታት). The nations of the world need to unite to stop war. ጦርነትን ፡ ለማቆም ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ መተባበር ፡ አለባቸው

**national** (n.) ዜጋ
He is a foreign national. የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ነው

**national** (adj.) ብሔራዊ
The government supports the national theater financially. መንግሥቱ ፡ ብሔራዊውን ፡ ቲያትር ፡ በገንዘብ ፡ ይረዳል
The national defense costs the government a lot of money. ብሔራዊ ፡ መከላከያ ፡ መንግሥቱን ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ያስወጣዋል
Next week there will be a national election. በሚቀጥለው ፡ ሳምንት ፡ ብሔራዊ ፡ ምርጫ ፡ ይደረጋል

**national anthem** የሕዝብ ፡ መዝሙር
The children sing the national anthem every morning. ተማሪዎቹ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ የሕዝብ ፡ መዝሙር ፡ ይዘምራሉ

**national holiday** ብሔራዊ ፡ በዓል
The 23rd of February is a national holiday. የካቲት ፡ ሀያ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ብሔራዊ ፡ በዓል ፡ ነው

**nationalism** ብሔራዊ ፡ ስሜት
Nationalism is one of the characteristic features of our age. ብሔራዊ ፡ ስሜት ፡ ጊዜያችን ፡ ከሚለይባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ አንዱ ፡ ነው

**nationalist** (n.) ብሔራዊ ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ ሰው
He is an ardent nationalist. ኀይለኛ ፡ ብሔራዊ ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**nationalist** (adj.) ብሔራዊ
The nationalist movement was repressed by the colonial government. ብሔራዊው ፡ ንቅናቄ ፡ በቅኝ ፡ ገዢው ፡ መንግሥት ፡ ተጨቍኖ ፡ ነበር

**nationality** (nationalities)
1. ዜግነት. What's his nationality? ዜግነቱ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
2. አገር. There were three men of different nationalities in charge. ሦስት ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ ኀላፊነቱን ፡ ወስደው ፡ ነበር
3. ነጻነት. The protectorate achieved nationality last year. በሞግዚትነት ፡ ሥር ፡ ትተዳደር ፡ የነበረችው ፡ አገር ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ነጻነቷን ፡ አገኘች

**nationalize** በመንግሥት ፡ ሥር ፡ አደረገ
There was a movement to nationalize the railroad. ባቡሩን ፡ በመንግሥት ፡ ሥር ፡ ለማድረግ ፡ ንቅናቄ ፡ ነበር

**nationally** ለሕዝቡ ፡ በሙሉ
The President's speech was broadcast nationally. የፕሬዚዳንቱ ፡ ንግግር ፡ ለሕዝቡ ፡ በሙሉ ፡ እንዲሰማ ፡ በሬዲዮ ፡ ተነገረ

**nationhood** መንግሥትነት
Israel obtained nationhood in 1948. እስራኤል ፡ በመንግሥትነት ፡ የታወቀችው ፡ በ፲፱፻፵ ዓ. ም. ነው

**native** (n.)

1. **ተወላጅ**. He is a native of Ethiopia. የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅ ፡ ነው

You speak French almost like a native. ፈረንሳይኛ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ተወላጆቹ ፡ ልትናገር ፡ ምንም ፡ አልቀረህም.

2. **አገሬ ፤ ያገር ፡ ተወላጅ**. The colonial government oppressed the natives. የቅኝ ፡ ገዢዎች ፡ መንግሥት ፡ አገሬውን ፡ (ያገሩን ፡ ተወላጅ) ፡ ጨቈነው

**native** (adj.)

1. **የትውልድ**. The United States is my native land. አሜሪካ ፡ የትውልድ ፡ አገሬ ፡ ናት

2. **የሀገር**. It is a native custom in America to go to church on Christmas Eve. በአሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ በገና ፡ ዋዜማ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሄድ ፡ የሀገር ፡ ልማድ ፡ ነው

The groom was splendidly dressed in native attire. ሙሽራው ፡ በሀገር ፡ ልብስ ፡ አሸብርቆ ፡ ነበር

3. (= noun) **የትውልድ ፡ ሀገር**. He returned to his native Harar. ወደ ፡ ትውልድ ፡ ሀገሩ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ተመለሰ

4. **የተፈጥሮ**. He has a native ability for languages. ለቋንቋ ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታ ፡ አለው

*Tobacco is native to America. አሜሪካ ፡ ለትምባሆ ፡ አገሩ ፡ ነው

**native-born** የሀገር ፡ ተወላጅ

The paucity of native-born engineers harms our development. የሀገር ፡ ተወላጅ ፡ መሀንዲሶች ፡ ማነስ ፡ እድገታችንን ፡ ያደክመዋል

*He is a native-born Ethiopian. በትውልድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ነው

**native country** የትውልድ ፡ አገር

He never returned to his native country. ወደ ፡ ትውልድ ፡ አገሩ ፡ በፍጹም ፡ አልተመለሰም

**native speech** የእናት ፡ ቋንቋ

The native speech of most Americans is English. ያብዛኞቹ ፡ አሜሪካኖች ፡ የእናት ፡ ቋንቋ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ነው

**native tongue** የእናት ፡ ቋንቋ

Amharic is his native tongue. የእናት ፡ ቋንቋው ፡ አማርኛ ፡ ነው

**Nativity** ልደት

The church celebrates the Nativity of Jesus. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የክርስቶስን ፡ ልደት ፡ ታከብራለች

**natural**

1. **የተፈጥሮ**. He has a natural talent for painting. ለሥዕል ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታ ፡ አለው

Ethiopia needs to protect her natural resources. ኢትዮጵያ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቷን ፡ መጠበቅ ፡ አለባት

Biology and chemistry are natural sciences. ባዮሎጂና ፡ ኬሚስትሪ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሳይንስ ፡ ናቸው

It is natural for a bird to fly. መብረር ፡ ለወፍ ፡ የተፈጥሮ ፡ ነው

2. **የሚገባ**. It was natural that he should hit back. መልሶ ፡ መምታቱ ፡ የሚገባ ፡ ነው

3. **የተለመደ**. It is natural for rivers to flood in the rainy season. በክረምት ፡ የወንዝ ፡ መሙላት ፡ የተለመደ ፡ ነው

Speak in your natural voice. Don't try to sound so educated! በዛው ፡ በተለመደው ፡ ድምፅህ ፡ ተናገር ፤ የተማረ ፡ ሰው ፡ ለመምሰል ፡ አትሞክር

4. **የእውነት**. The fruit in this picture looks very natural. እዚህ ፡ ሥዕል ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ፍሬ ፡ የእውነት ፡ ፍሬ ፡ ይመስላል

5. (= adverb) **በተፈጥሮው**. She is a natural painter. በተፈጥሮዋ ፡ ሠዓሊ ፡ ነች

*He died a natural death. እግዜር ፡ ገደለው

**natural state** ተፈጥሮ

In this zoo, animals can live in their natural state. በዚህ ፡ ያራዊት ፡ መጠበቂያ ፡ ቦታ ፡ አራዊት ፡ እንደ ፡ ተፈጥሯቸው ፡ ሊኖሩ ፡ ይችላሉ

[See also 'resource']

**naturalize** የዜግነት ፡ መብት ፡ ሰጠ

The new law naturalizes those born abroad who have one Ethiopian parent. አዲሱ ፡ ሕግ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የተወለዱ ፡ ባንድ ፡ ወገናቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሆኑትን ፡ የዜግነት ፡ መብት ፡ ይሰጣቸዋል

**naturalized** (adj.)

*He is a naturalized Ethiopian. ዜግነቱን ፡ ለውጦ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ነው

**naturalized citizen** በሕግ ፡ የዜግነት ፡ መብት ፡ ያገኘ ፡ ሰው

Naturalized citizens are permitted to vote. በሕግ ፡ የዜግነት ፡ መብት ፡ ያገኙት ፡ ሰዎች ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ ይፈቀድላቸዋል

**be naturalized** ዜጋ ፡ ሆነ

Aliens in the United States can be naturalized after living there a certain time. የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በአሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከኖሩ ፡ የአሜሪካ ፡ ዜጋ ፡ ለመሆን ፡ ይችላሉ

**naturally**

1. **በተፈጥሮው**. He is naturally shy. በተፈጥሮው ፡ ዓይን ፡ አፋር ፡ ነው

2. **እንደ ፡ ተፈጥሮ**. Speak naturally! Don't try to

imitate some actor! እንደ ፡ ተፈጥሮህ ፡ ተናገር ፤ እንዳንድ ፡ ተዋናይ ፡ ለመናገር ፡ አትሞክር
3. እንዴታ. Did you answer the letter? Naturally! ለደብዳቤው ፡ መልስ ፡ ሰጠህ ? እንዴታ !
Yes, naturally, we will go. እንዴታ ! እንሄዳለን
4. -ም. She offered me some candy. Naturally, I took it. ከረሜላ ፡ እንካ ፡ አለችኝ ፤ እኔም ፡ ተቀበልኩ
5. -ም ፡ እንዲሁ. Naturally we want you to come. አንተም ፡ እንዲሁ ፡ እንድትመጣ ፡ እንፈልጋለን

**behave naturally**
She behaves very naturally. ለመምሰል ፡ አትሞክርም ፡ (or, መስሎ ፡ ለመታየት ፡ አትሻም) ፡

**nature**
1. ተፈጥሮ. He enjoys the beauties of nature. በተፈጥሮ ፡ ውበት ፡ ይደሰታል
He is by nature a just man. በተፈጥሮው ፡ ቅን ፡ ሰው ፡ ነው
2. ዓይነት. I can't tell you anything about the nature of my job. ስለ ፡ ሥራዬ ፡ ዓይነት ፡ ምንም ፡ ልነግርህ ፡ አልችልም
3. ባሕርይ. It is human nature to be quarrelsome and suspicious. ጠበኛና ፡ ተጠራጣሪ ፡ መሆን ፡ የሰው ፡ ባሕርይ ፡ ነው
4. ጠባይ. Because of his evil nature, he doesn't make any friends. በክፉ ፡ ጠባዩ ፡ የተነሣ ፡ ጓደኞች ፡ አያገኝም
*She is of gentle nature. ረጋ ፡ ያለች ፡ ሰው ፡ ናት

**in a state of nature** በዱር
Wild animals live in a state of nature. አራዊት ፡ በዱር ፡ ይኖራሉ
[See also 'second']

**naught** ዜሮ
Five minus five equals naught. ከአምስት ፡ ላይ ፡ አምስት ፡ ሲቀነስ ፡ ዜሮ ፡ ይሆናል

**bring to naught** ከንቱ ፡ አደረገ
He brought my plans to naught by his intrigues. በተንኰሉ ፡ እቅዴን ፡ ከንቱ ፡ አደረገው

**come to naught** ከንቱ ፡ ሆነ
All his efforts came to naught. ጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ሆነ

**naughty**
1. ተንኰለኛ ፤ ባለጌ. You're a very naughty child. በጣም ፡ ተንኰለኛ ፡ ልጅ ፡ ነህ
The naughty girl was the despair of her parents. ባለጌዋ ፡ ልጅ ፡ ወላጆቿን ፡ አስመርራ ፡ ነበር
2. ተንኰል. It was naughty of you to pull the cat's tail. የድመቷን ፡ ጅራት ፡ መጐተትህ ፡ ተንኰል ፡ ነበር

**be naughty** ባለገ
She switched her child for being naughty. ልጇ ፡ ስለባለገ ፡ ገረፈችው

**nausea, be overcome by ~** አቅለሸለሸ(ው)
+I was overcome by nausea after having eaten too much. ብዙ ፡ ስለበላሁ ፡ አቅለሸለሸኝ

**nauseate**
1. አጥወለወለ. The fishy smell of the store nauseated me. በሱቅ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የዓሣ ፡ ክርፋት ፡ አጥወለወለኝ
2. አስጠላ. His behavior nauseates me. ሁኔታው ፡ ያስጠላኛል

**nauseous, make feel ~** አቅለሸለሸ
The motion of the plane made me feel nauseous. አውሮፕላኑ ፡ ሲሄድ ፡ ያቅለሸልሸኛል

**nautical** የመርከበኝነት
Nautical subjects are taught in this college. በዚህ ፡ ኮሌጅ ፡ ውስጥ ፡ የመርከበኝነት ፡ ትምህርት ፡ ይሰጣል

**naval**
1. የባሕር. England was a great naval power. እንግሊዝ ፡ በባሕር ፡ ኃይሏ ፡ ገናና ፡ ነበረች
2. የባሕር ፡ ኃይል. Naval officers are visiting us. የባሕር ፡ ኃይል ፡ መኰንኖች ፡ እኛን ፡ በመጐብኘት ፡ ላይ ፡ ናቸው

**navel** እምብርት
The donkey has no navel. አህያ ፡ እምብርት ፡ የለውም

**navigable** ለመርከብ ፡ ጉዞ ፡ የሚሆን
None of the Ethiopian rivers is navigable. ከኢትዮጵያ ፡ ወንዞች ፡ አንድም ፡ ለመርከብ ፡ ጉዞ ፡ የሚሆን ፡ የለም

**navigate** (vt.) መራ
It was difficult to navigate the ship during the storm. ማዕበል ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ መርከቡን ፡ መምራት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር

**navigate** (vi.) በረረ
Planes need radar to navigate through the thick fog. ጥቅጥቅ ፡ ባለው ፡ ጉም ፡ ውስጥ ፡ ለመብረር ፡ እንዲችሉ ፡ አውሮፕላኖች ፡ ራዳር ፡ ያስፈልጋቸዋል

**navigation**
1. በጀልባ ፡ መሄድ. A precipitous flow of water prevents navigation. በገደል ፡ ላይ ፡ የሚፈስ ፡ ውኃ ፡ በጀልባ ፡ ከመሄድ ፡ ያግዳል
2. አቅጣጫን ፡ የመለየት ፡ ትምህርት. They have to study navigation before they are allowed to

fly. አውሮፕላን ፡ እንዲነዱ ፡ ከመፈቀዱ ፡ በፊት ፡ አቅጣጫን ፡ የመለየት ፡ ትምህርት ፡ ማጥናት ፡ አለ ባቸው

**navy** የባሕር ፡ ኀይል
The Ethiopian navy is in Massawa. የኢትዮጵ ያ ፡ የባሕር ፡ ኀይል ፡ የሚገኘው ፡ ምፅዋ ፡ ላይ ፡ ነው

**near** (v.)
1. ተቃረበ. Slow down as you near the curve. ወደ ፡ መጠምዘዣው ፡ ስትቃረብ ፡ ዝግ ፡ በል
2. ተጠጋ. The ship was nearing land. መርከ ቧ ፡ ወደ ፡ የብስ ፡ በመጠጋት ፡ ላይ ፡ ነበረች

**near** (adj.) ቅርብ
The station is quite near. ጣቢያው ፡ በጣም ፡ ቅ ርብ ፡ ነው

**near** (prep.) በ - - - አቅራቢያ
A nun lives near the church. በቤተ ፡ ክርስቲያ ኑ ፡ አቅራቢያ ፡ አንዲት ፡ መነኵሲት ፡ ይኖራሉ

**near at hand**
*Always have a good dictionary near at hand! ሁልጊዜ ፡ ጥሩ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ አጠገብህ ፡ ይኑር

**near each other** አጠገብ ፡ ላጠገብ
They are standing near each other. አጠገብ ፡ ላ ጠገብ ፡ ቆመዋል

**near here** በዚህ ፡ አቅራቢያ
Is there a hotel near here? በዚህ ፡ አቅራቢያ ፡ ሆቴል ፡ አለ ?

**near relations** የቅርብ ፡ ዘመዶች
They are my near relations. እነሱ ፡ የቅርብ ፡ ዘ መዶቼ ፡ ናቸው

**near side** ፊት
We can see the near side of the moon, but not the far side. የጨረቃን ፡ ፊቷን ፡ እንጂ ፡ ጀርባዋ ን ፡ ማየት ፡ አንችልም

**as near as** እንደ
As near as I can guess, forty people came. እኔ ፡ እንደምገምተው ፡ የመጡት ፡ አርባ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው

**come near** ተቃረበ
We ran for cover when the storm came near. ኀይለኛው ፡ ዝናም ፡ ሲቃረብ ፡ ለመጠለል ፡ ሮ ጥን

**get near** ተጠጋ
Don't get near the fire! እሳቱን ፡ አትጠጋ

**nowhere near**
*The work was nowhere near completed. ሥራው ፡ ንቅንቅም ፡ አላለ
[See also 'draw, far']

**nearby** (adj.) በአቅራቢያ ፡ የሚገኝ
Ask at a nearby villlage! በአቅራቢያህ ፡ ወደሚ ገኘው ፡ መንደር ፡ ሄደህ ፡ ጠይቅ

**nearby** (adv.) በአካባቢው ፤ በዚህ ፡ አካባቢ
There is a park nearby. በአካባቢው ፡ የመናፈሻ ፡ ቦታ ፡ አለ
Is there a restaurant nearby? በዚህ ፡ አካባቢ ፡ የምግብ ፡ ቤት ፡ አለ ?

**(be) nearer**
*His house is nearer to mine than yours. ከንተው ፡ ይልቅ ፡ የሱ ፡ ቤት ፡ ለኔ ፡ ይቀርባል

**come nearer** ቀረብ ፡ አለ ፤ ተጠጋ
Come nearer! ቀረብ ፡ በል
If you come nearer, I'll hit you. ብትጠጋኝ ፡ እ መታሃለሁ

**nearest**
1. የሚቀርብ. Is this the nearest way home? ለቤት ፡ የሚቀርበው ፡ መንገድ ፡ ይህ ፡ ነው ?
2. የቅርብ. He is my nearest friend. የቅርብ ፡ ጓ ደኛዬ ፡ እሱ ፡ ነው

**nearly**
1. ል + imperfect + ምንም ፡ አልቀረው. It's nearly one o'clock. ሰባት ፡ ሰዓት ፡ ሊሆን ፡ ምንም ፡ አልቀረው
I nearly suffocated. ልታፈን ፡ ምንም ፡ አልቀረ ኝም
2. ያህል. There were nearly forty people at the wedding. በሰርጉ ፡ ላይ ፡ አርባ ፡ ሰዎች ፡ ያህ ል ፡ ነበሩ
The rock struck her on her head, and she was insensible for nearly an hour. ድንጋይ ፡ራሷን፡ ስለመታት ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ነፍሷን ፡ ስታ ፡ ነበር
3. ል + imperfect + ነበረ. He nearly lost his sight in the accident. ባደጋው ፡ ዓይኑ ፡ ሊ ጠፋ ፡ ነበር
[See also 'pretty']

**nearsighted** ሩቅ ፡ ለማየት ፡ የማይችል
Nearsighted people usually wear glasses. ሩቅ ፡ ለማየት ፡ የማይችሉ ፡ ሰዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ መነጽር ፡ ያደርጋሉ

**be nearsighted** ከፍንጫው ፡ አይርቅም
His policy on foreign affairs is nearsighted. ስለ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ጉዳይ ፡ ያለው ፡ አመራር ፡ ከፍንጫው ፡ አይርቅም

**neat**
1. ንጹሕ. His desk always looks neat. ጠረጴዛው ፡ ሁልጊዜ ፡ ንጹሕ ፡ ነው
2. ጥዱ. She always looks neat. ዘወትር ፡ ጥዱ ፡ ናት
3. ጥንቁቅ. A neat worker also works fast. ጥንቁቅ ፡ ሠራተኛ ፡ ፈጣን ፡ ሠራተኛ ፡ ነው
4. ደስ ፡ የሚል. He drew a neat design on the paper. በወረቀቱ ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ቅርጽ ፡ ሣለ

**neatly** በጥንቃቄ
Her gloves were neatly paired in a drawer. የእጅ ፡ ሹራቦቿ ፡ መሳቢያ ፡ ውስጥ ፡ በጥንቃቄ ፡ በጥንድ ፡ በጥንድ ፡ ተደርድረዋል

**be neatly dressed** ተሽቀረቀረ
He is always neatly dressed. ሁልጊዜ ፡ እንደተሽቀረቀረ ፡ ነው

**nebulous**
1. ደመናማ. In September the skies are nebulous. በመስከረም ፡ ሰማዩ ፡ ደመናማ ፡ ይሆናል
2. ድብዛዛ. He had nebulous ideas on the subject. ስለ፡ጉዳዩ፡ድብዛዛ፡አስተያየት፡ነበረው
3. ግልጽ ፡ ያልሆነ. He has nebulous plans concerning his future. ስለ፡ወደፊት፡ኑሮው፡ግልጽ፡ያልሆነ፡ዓላማ፡አለው

**necessaries** አስፈላጊ ፡ ነገሮች
Food, shelter, and clothing are necessaries of life. ምግብ ፤ ቤትና ፡ ልብስ ፡ ለሕይወት ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው

**necessarily**
*Big men are not necessarily strong. ግዙፍ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ጠንካራ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አይቻልም

**necessary** (adj.) አስፈላጊ ፤ ተፈላጊ
Can you raise the necessary funds? አስፈላጊውን ፡ (ተፈላጊውን) ፡ ገንዘብ ፡ ልትሰበስብ ፡ ትችላለህ ?
It is necessary that we get ready early. ቀደም ፡ ብሎ ፡ መዘጋጀቱ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**necessitate** አስፈለገ(ው)
Your proposal necessitates borrowing money. ያቀረብከው ፡ ሐሳብ ፡ የገንዘብ ፡ ብድር ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነው
The hard words in the article necessitate the use of a dictionary. በጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ከባድ ፡ ቃላት ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ያስፈልጋቸዋል

**necessity** (necessities)
1. አስፈላጊነት. We understand the necessity of eating. የመመገብን ፡ አስፈላጊነት ፡ እናውቃለን
2. አስፈላጊ. There is no necessity to do that more than once. ያንን ፡ ከአንድ ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ መሥራት ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም
3. የሚያስፈልገው. She did without necessities to be able to pay for her daughter's piano lessons. የሚያስፈልጋትን ፡ ሁሉ ፡ ችላ ፡ ብላ ፡ ለልጇ ፡ ፒያኖ ፡ ማስተማሪያ ፡ ከፈለች
4. አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ ነገር. We must bow to necessity. አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮችን ፡ መቀበል ፡ አለብን
5. ችግር. He was driven by necessity to steal food for his child. ለልጁ ፡ ምግብ ፡ እንዲሰርቅ ፡ ችግር ፡ አስገደደው

**necessities** አስፈላጊ ፡ ነገሮች
Food and water are necessities of life. ምግብና ፡ ውኃ ፡ ለኑሮ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው

**be a necessity** ያስፈልጋል
When abroad, a passport is a necessity. ከገር ፡ ውጭ ፡ ባሉበት ፡ ጊዜ ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ ያስፈልጋል

**in case of necessity** አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ
In case of necessity, call the hospital! አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሆስፒታል ፡ ደውሉ

**of necessity** የግድ
He did it of necessity, not because he wanted to. ወዶ ፡ ሳይሆን ፡ የግድ ፡ ስለሆነበት ፡ ነው ፡ የሠራው

**neck** አንገት
He fell down the stairs and broke his neck. ከደረጃው ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፡ አንገቱ ፡ ተቀጨ
The bottle has a very narrow neck. የጠርሙሱ ፡ አንገት ፡ በጣም ፡ ጠባብ ፡ ነው
[See also 'stiff, wear, yoke']

**necklace** ሐብል ፤ ያንገት ፡ ጌጥ ፤ ድሪ
She is wearing a beautiful necklace. በጣም ፡ የሚያምር ፡ ሐብል ፡ (ያንገት ፡ ጌጥ ፤ ድሪ) ፡ አድርጋለች

**necktie** ክራቫት
I bought a necktie for five dollars. ባምስት ፡ ብር ፡ ክራቫት ፡ ገዛሁ

**necrology** የሞት ፡ ዜና
The author's necrology appeared in the Sunday paper. የደራሲው ፡ የሞት ፡ ዜና ፡ በእሑድ ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ወጣ

**nectar** ያበባ ፡ ማር
Flowers secrete nectar. አበቦች ፡ ያበባ ፡ ማር ፡ ያወጣሉ

**need** (v.)

1. **አስፈለገ(ው)**. +Man needs air in order to live. **ሰው ፡ ለመኖር ፡ አየር ፡ ያስፈልገዋል**
+Plants need water in order to grow. **ዕፀዋት ፡ ለማደግ ፡ ውኃ ፡ ያስፈልጋቸዋል**
2. **ፈለገ**. Don't hesitate to call if you need me! **ከፈለግኸኝ ፡ ለመደወል ፡ አታመንታ**
We have all we need. **የምንፈልገው ፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ አለን**
3. **አለበት**. Does he need to know? **ማወቅ ፡ አለበት ?**
*You need not bother. **አትቸገር**

**need** (n.)

1. **ፍላጎት**. Father was always mindful of the needs of the family. **አባቴ ፡ የቤተ ፡ ሰቡን ፡ ፍላጎት ፡ ሁልጊዜ ፡ ያውቅ ፡ ነበር**
2. **ተፈላጊነት**. There's a great need for wool in winter. **በክረምት ፡ ሱፍ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተፈላጊነት ፡ አለው**
3. **አስፈላጊነት**. He emphasized the need for careful driving. **በጥንቃቄ ፡ ስለ ፡ መንዳት ፡ አስፈላጊነት ፡ አጥብቆ ፡ ተናገረ**
4. **የችግር ፡ ጊዜ**. He was a friend in need. **በችግር ፡ ጊዜ ፡ የሚደርስ ፡ ጓደኛ ፡ ነበር**
5. **ክፉ ፡ ቀን**. You are certainly a friend in need. **አንተ ፡ በእውነቱ ፡ የክፉ ፡ ቀን ፡ ወዳጅ ፡ ነህ**
*His needs are many. **ብዙ ፡ ነገር ፡ ይቸግረዋል**

**at need** **አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ**
You can call me at need. **አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ልትጠራኝ ፡ ትችላለህ**

**be in need of** **ያስፈልገዋል**
He is badly in need of a vacation. **የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ክፉኛ ፡ ያስፈልገዋል**

**have a need of** **ፈለገ**
He has no need of your charity. **ችሮታህን ፡ አይፈልግም**

**if need be** **ካስፈለገ**
I will go myself if need be. **ካስፈለገ ፡ ራሴ ፡ እሄዳለሁ**

**there is no need to** **አያስፈልግም**
There is no need to worry. **መጨነቅ ፡ አያስፈልግም**
[See also 'material, meet, sore']

**needful** **አስፈላጊ**
No needful service is to be looked on as base. **ማንኛቸውም ፡ ዓይነት ፡ አስፈላጊ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ወራዳ ፡ ነገር ፡ መቈጠር ፡ የለበትም**

**needle** (v.) **ቀለደ(በት)**
We needled him about his big ears. **ጆሮው ፡ ትልልቅ ፡ ስለሆነ ፡ ቀለድንበት**

**needle someone into** **ገፋፋ**
We needled her into going with us. **አብራን ፡ እንድትሄድ ፡ ገፋፋናት**

**needle** (n.) **መርፌ**
A needle serves for stitching clothes. **መርፌ ፡ ለልብስ ፡ መጥቀሚያ ፡ ያገለግላል**

**needless** **ተገቢ ፡ ያልሆነ ፤ የማይገባ**
His needless grumbling annoys people. **ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ (የማይገባ) ፡ ማማረሩ ፡ ሰው ፡ ያበሳጫል**

**needless to say** **ያም ፡ ሆነ ፡ ይ**
Needless to say, he kept his word. **ያም ፡ ሆነ ፡ ይ ፤ ቃሉን ፡ አከበረ**

**needlework** **ጥልፍ**
She does needlework for a living. **ጥልፍ ፡ በመሥራት ፡ ትተዳደራለች**

**needy** **ችግረኛ ፤ የተቸገረ**
The government is building houses for the needy. **መንግሥት ፡ ለችግረኞች ፡ ቤት ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ ነው**
They dispensed the clothing to needy refugees. **ለተቸገሩ ፡ ስደተኞች ፡ ልብስ ፡ ዐደሉ**

**nefarious** **አሰቃቂ**
The dictator's nefarious deeds shocked the world. **የአምባገነኑ ፡ አሰቃቂ ፡ ተግባር ፡ ዓለምን ፡ አሸበረ**

**negate**

1. **ዋጋ ፡ ቢስ ፡ አደረገ**. This negates all our work. **ይህ ፡ ሥራችንን ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ያደርገዋል**
2. **አፈረሰ**. The facts negate what he says. **የሆነው ፡ ነገር ፡ እሱ ፡ የሚለውን ፡ ያፈርሳል**

**negation**

1. **አሉታ**. Shaking the head is a sign of negation. **ራስን ፡ መነቅነቅ ፡ የአሉታ ፡ ምልክት ፡ ነው**
2. **ተቃራኒ**. Darkness is the negation of light. **ጭለማ ፡ የብርሃን ፡ ተቃራኒ ፡ ነው**
3. **የሚያስተባብል**. The statement he made today is a negation of his former beliefs. **ዛሬ ፡ የተናገረው ፡ የቀድሞ ፡ እምነቱን ፡ የሚያስተባብል ፡ ነው**

**negative** (n.)

1. **አሉታ**. 'I won't' is a negative. **እምቢ ፡ ማለት ፡ አሉታ ፡ ነው**
2. **ኔጋቲቭ**. Only the negatives of the films have been developed. **የታጠበው ፡ የፊልሙ ፡ ኔጋቲቭ ፡ ብቻ ፡ ነው**
*I asked him if he wanted to go, and he replied in the negative. **ለመሄድ ፡ ይፈልግ ፡ እንደሆን ፡ ብጠይቀው ፡ አልሄድም ፡ አለኝ**

**negative** (adj.)
1. የአሉታ. Minus three is a negative quantity. ከዜሮ ፡ በታች ፡ ሦስት ፡ የአሉታ ፡ ጠባይ ፡ ነው
2. ግራ. The teacher criticized the child's negative attitude. አስተማሪው ፡ የልጁን ፡ ግራ ፡ አስተሳሰብ ፡ ነቀፈ
3. የእምቢታ. His answer was negative. መልሱ ፡ የእምቢታ ፡ ነበር
He maintained a negative attitude toward cooperating. የነበረው ፡ የመግባባት ፡ ዝንባሌ ፡ የእምቢታ ፡ ነበር
4. ሌቱ. The negative charge should not by accident come in contact with the positive. የኮረንቲው ፡ ሌቴ ፡ ከወንዴው ፡ ጋር ፡ በድንገት ፡ መገናኘት ፡ የለበትም
5. ጉድለትን ፡ የሚያመለክት ፤ ጥፋትን ፡ የሚያመለክት. His criticisms are always negative. የሱ ፡ ትችት ፡ ሁልጊዜ ፡ ጉድለትን ፡ (ጥፋትን) ፡ የሚያመለክት ፡ ነው
*The results of the blood test were negative. የደም ፡ ምርመራው ፡ ውጤት ፡ ከበሽታ ፡ ንጹሕ ፡ መሆኑን ፡ አመለከተ

**negative results** ፍሬው ፡ አለማግር
The negative results of his work discouraged him. የሥራ ፡ ፍሬው ፡ አለማግር ፡ ተስፋ ፡ አስቈረጠው

**neglect** (v.)
1. ቸላ ፡ አለ. He went to dances and neglected his studies. በየዳንሱ ፡ ቤት ፡ ሲዞዞር ፡ ጥናቱን ፡ ቸላ ፡ ብሎታል
Lately, he neglected his family. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ቤተሰቦቹን ፡ ቸላ ፡ ብሏል
2. ቦዘነ. Don't neglect to water the plants! አታክልቱን ፡ ውኃ ፡ ከማጠጣት ፡ አትቦዝን
3. ስ + negative imperfect + ቀረ. He neglected to tell me that you were here. እዚህ ፡ መኖርህን ፡ ሳይነግረኝ ፡ ቀረ

**neglect** (n.)
1. ግዴለሽነት. The car has been ruined by neglect. መኪናዋ ፡ የተበላሸችው ፡ ከግዴለሽነት ፡ የተነሣ ፡ ነው
2. ቸላ ፡ ማለት. His neglect of the truth is astonishing. እውነቱን ፡ ነገር ፡ ቸላ ፡ ማለቱ ፡ የሚያስገርም ፡ ነው
3. ቸልታ. The house had gone to ruin from neglect. በቸልታ ፡ ምክንያት ፡ ቤቱ ፡ ፈራረሰ

**neglect of duty** ንዝህላልነት
He lost his job due to his neglect of duty. በንዝህላልነቱ ፡ ሥራውን ፡ አጣ

**(be) neglectful of** ቸላ ፡ አለ
He was neglectful of his health and fell seriously ill. ጤንነቱን ፡ ቸላ ፡ ስላለ ፡ በጣም ፡ ታመመ

**negligence** ቸልተኝነት
She was dismissed from the job on account of negligence. ከሥራው ፡ የተወገደችው ፡ በቸልተኝነቷ ፡ ነበር

**negligent** ቸልተኛ
He is negligent in his work. በሥራው ፡ ቸልተኛ ፡ ነው

**negligible** እምብዛም
The harvest this year is negligible. በዚህ ፡ ዓመት ፡ ሰብል ፡ እምብዛም ፡ ነው

**(be) negotiable**
*Their quarrel did not prove to be negotiable. ጥላቸው ፡ ሽማግሌ ፡ የሚገባው ፡ ሆኖ ፡ አልተገኘም

**negotiate**
1. ተነጋገረ. We are negotiating with our employers about our wage claims. ስለ ፡ ደሞዛችን ፡ ከአሠሪዎቻችን ፡ ጋር ፡ በመነጋገር ፡ ላይ ፡ ነን
They are negotiating the sale of our house. ቤታችን ፡ ስለሚሸጥበት ፡ ዋጋ ፡ በመነጋገር ፡ ላይ ፡ ናቸው
2. ተስማማ. They finally negotiated a peace treaty. በመጨረሻ ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ ለማድረግ ፡ ተስማሙ

**negotiation**
1. የስምምነት ፡ ንግግር. Negotiations were broken off after a week. ካንድ ፡ ሳምንት ፡ በኋላ ፡ የስምምነቱ ፡ ንግግር ፡ ተቋረጠ
2. ድርድር. If the strike continues, the government will have to take a hand in the negotiations. ሥራ ፡ ማቆም ፡ ከቀጠለ ፡ መንግሥት ፡ በድርድሩ ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ መሆን ፡ ይኖርበታል

**Negro** ጥቁር
The majority of Africans are Negroes. የአፍሪካ ፡ ሕዝብ ፡ ብዙው ፡ ጥቁር ፡ ነው
There are many Negroes in this city. በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጥቁሮች ፡ አሉ

**neigh** አሽካካ
I heard the horse neighing at night. ማታ ፡ ፈረሱ ፡ ሲያሽካካ ፡ ሰማሁ

**neighbor** (v.) አዋሰነ
My property neighbors his. መሬቱ ፡ የሱን ፡ መሬት ፡ ያዋስናል

**neighbor** (n.) ጐረቤት
He and I are neighbors. እኔና ፡ እሱ ፡ ጐረቤቶች ፡ ነን

**neighbor** (adj.) ጐረቤት
Sudan is a neighbor nation of Ethiopia. ሱዳን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጐረቤት ፡ አገር ፡ ናት

**neighborhood**
1. ጐረቤት. The whole neighborhood was there. ጐረቤቱ ፡ በሙሉ ፡ እዚያ ፡ ነበር
2. መንደር. Many artists and merchants live in our neighborhood. መንደራችን ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሠዓሊዎችና ፡ ነጋዴዎች ፡ ይኖራሉ
3. ሰፈር. Is Churchill Road a good neighborhood? የቸርችል ፡ ጐዳና ፡ ጥሩ ፡ ሰፈር ፡ ነው ?
4. አካባቢ. He wants to live in the neighborhood of London. በሎንዶን ፡ አካባቢ ፡ ለመኖር ፡ ይፈልጋል
5. አካባቢ ፡ መንደር. The potter makes pots for the entire neighborhood. ሸክላ ፡ ሠሪው ፡ ለአካባቢው ፡ መንደር ፡ በሙሉ ፡ የሸክላ ፡ እቃ ፡ ይሠራል
6. ቅርብነት. The neighborhood of the airport is a serious problem for us. የአውሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ቅርብነት ፡ ለኛ ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡ ነው

**in the neighborhood of** ገደማ
This house costs in the neighborhood of $30,000. ይህ ፡ ቤት ፡ ሠላሳ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ገደማ ፡ ያወጣል
[See also 'gossip, immediate']

**neighboring**
1. የሚቀጥል. A fire broke out in the neighboring village. በሚቀጥለው ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ ተነሣ
2. ጐረቤት. The neighboring country gave asylum to the rebel. ጐረቤት ፡ አገር ፡ ለዐመፀኛው ፡ ጥገኝነት ፡ ሰጠች

**neighboring country** ጐረቤት
The neighboring countries of Sudan and Kenya are plagued by locusts. ጐረቤቶቻችን ፡ ኬንያና ፡ ሱዳን ፡ በአንበጣ ፡ ተወረዋል

**neighborly, very ~** መልካም ፡ ጐረቤት
The people here are very neighborly. እዚህ ፡ ሕዝቡ ፡ መልካም ፡ ጐረቤቶች ፡ ናቸው

**neither** (adj.) ከሁለቱ ፡ አንዱም
Neither answer is correct. ከሁለቱ ፡ አንዱም ፡ መልስ ፡ ልክ ፡ አይደለም

**neither** (conj.) -ም ፡ -ም
He doesn't sing, neither does he dance. አይዘፍንምም ፡ አይደንስምም
*If you don't go, neither shall I. ካልሄድክ ፡ አልሄድም

**(be) neither here nor there** ከአርእስት ፡ ውጭ ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ ግባ ፡ የማይባል ፡ ነገር ፡ ነው
What you are saying about the accident is neither here nor there. ስለ ፡ አደጋው ፡ የምታወራው ፡ ከአርእስት ፡ ውጭ ፡ ነው
The fact that her family has no money is neither here nor there. ቤተሰቦቿ ፡ ገንዘብ ፡ የሌላቸው ፡ መሆናቸው ፡ ከዚህ ፡ ግባ ፡ የማይባል ፡ ነገር ፡ ነው

**neither ... nor**
1. -ም ፡ ሆነ + (negative verb). Neither he nor I will be there. እሱም ፡ ሆነ ፡ እኔ ፡ አንመጣም
I have neither time nor money. ጊዜም ፡ ሆነ ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም
2. -ም ፡ -ም + (verb). I could neither cry nor laugh. ማልቀስም ፡ መሣቅም ፡ አቃተኝ
I am neither for nor against it. ደጋፊም ፡ ተቃዋሚም ፡ አይደለሁም

**neither of**
1. አንድ + (suffix pronouns + negative verb). I like neither of them. አንዳቸውንም ፡ አልወድም
2. አንዱም + (negative verb). Neither of them will be satisfactory. አንዱም ፡ አጥጋቢ ፡ አይደለም

**in neither case** ከሁለቱ ፡ ባንዱም + negative verb
In neither case can I agree. ከሁለቱ ፡ ባንዱም ፡ ልስማማ ፡ አልችልም

**nephew** የወንድም ፡ ልጅ ፤ የእኅት ፡ ልጅ
The nephew is considered as a brother. የወንድም ፡ (የእኅት) ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ወንድም ፡ ይቈጠራል

**nerve**
1. የደም ፡ ሥር. He cut the nerve in his arm, and now he cannot move it. የክንዱ ፡ የደም ፡ ሥር ፡ ስለተቈረጠ ፡ እጁን ፡ ማንቀሳቀስ ፡ አይችልም
2. ጅማት. My foot is numb; I must have hurt the nerve. እግሬ ፡ ደንዝዟል ፤ ጅማቱ ፡ ተነክቶ ፡ ይሆናል

**get on one's nerves** አበሳጨ ፤ አስጨነቀ
The constant noise is getting on my nerves. የማያቋርጥ ፡ ጫጫታ ፡ ያበሳጨኛል ፡ (ያስጨንቀኛል)

**it takes nerve** ድፍረትን ፡ ይጠይቃል
It takes nerve to pilot an airplane. አውሮፕላን ፡ መንዳት ፡ ድፍረትን ፡ ይጠይቃል

**lose one's nerve** መቈጣጠር ፡ ተሳነ(ው)
The soldier lost his nerve and fled. ወታደሩ ፡ መቈጣጠር ፡ ተስኖት ፡ ሸሸ
[See also 'jar']

**nervous**
1. የተደናገጠ. His calm confidence steadied the nervous passengers. የረጋ ፡ እምነቱ ፡ የተደናገጡትን ፡ መንገደኞች ፡ አጽናናቸው
2. የስሜት ፡ ሕዋሳት. The nervous system is very complex. የስሜት ፡ ሕዋሳት ፡ አሠራር ፡ በጣም ፡ ረቂቅ ፡ ነው

**(be, get) nervous**
1. መንፈሱ ፡ ተጨነቀ. She takes tranquilizers because she is so nervous. መንፈሷ ፡ በጣም ፡ ስለሚጨነቅ ፡ ማስታገሻ ፡ መድኃኒት ፡ ትወጣለች
2. ተበሳጨ. The last few days I've been very nervous. ባለፉት ፡ ጥቂት ፡ ቀናት ፡ ተበሳጭቼ ፡ ነበር
3. ተርበደበደ. I get nervous when you watch me working. እኔ ፡ ስሠራ ፡ ትዞር ፡ ብለህ ፡ ስትመለከተኝ ፡ እርበደበዳለሁ
4. (= make nervous) አስፈራ. She is nervous about staying alone at night. ሌሊት ፡ ብቻዋን ፡ ማደሯ ፡ አስፈርቷታል

**make nervous** አቍነጠነጠ
Anticipation of the battle made the soldiers nervous. ጦርነቱን ፡ መጠባበቅ ፡ ወታደሮቹን ፡ አቍነጠነጣቸው
[See also 'jar, wreck']

**nervously** በመጨነቅ
He paced the room nervously. ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ በመጨነቅ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ

**nest** (v.) ጎጆ ፡ ሠራ
Birds nest in trees. ወፎች ፡ ጎጆዋቸውን ፡ የሚሠሩት ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ ነው

**nest** (n.) የወፍ ፡ ጎጆ
There were four tiny eggs in the nest. በወፍ ፡ ጎጆው ፡ ውስጥ ፡ አራት ፡ ትንንሽ ፡ እንቁላሎች ፡ ነበሩ

**nestle** ተመቻችቶ ፡ ተኛ
The baby nestled in his mother's arms. ሕፃኑ ፡ እናቱ ፡ ክንድ ፡ ላይ ፡ ተመቻችቶ ፡ ተኛ

**net** (netted), v.
1. አጠመደ. The fisherman nets fish. ዓሣ ፡ አጥማጁ ፡ ዓሣ ፡ ያጠምዳል
2. የተጣራ ፡ ገቢ ፡ አስገኘ(ለት). How much does this business net you a year? ይህ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ባመት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የተጣራ ፡ ገቢ ፡ ያስገኝልሃል ?
3. አስገኘ(ለት). The sale netted me a good profit. ሽያጩ ፡ ጥሩ ፡ ትርፍ ፡ አስገኝልኝ

**net** (n.)
1. መረብ. The nets were full of fish. መረቦቹ ፡ በዓሣ ፡ ተሞልተው ፡ ነበር
2. ቋት. He was caught in a net of lies. የውሸት ፡ ቋት ፡ መሆኑ ፡ ታወቀበት
**mosquito net** የወባ ፡ ትንኝ ፡ መከላከያ ፡ አጎበር
I need a mosquito net to put over my bed. አልጋዬን ፡ የምጋርድበት ፡ የወባ ፡ ትንኝ ፡ መከላከያ ፡ አጎበር ፡ እፈልጋለሁ

**net** (adj.)
1. የተጣራ. My weekly salary is fifty dollars net. በሳምንት ፡ የማገኘው ፡ የተጣራ ፡ ደሞዜ ፡ ኀምሳ ፡ ብር ፡ ነው
2. (= adv.) ብቻውን. The net weight of this truck is four thousand pounds. መኪናው ፡ ብቻውን ፡ አራት ፡ ሺ ፡ ፓውንድ ፡ ይመዝናል

**nethermost** የመጨረሻ
No light reaches the nethermost depths of the ocean. ብርሃን ፡ ከውቅያኖስ ፡ የመጨረሻ ፡ ጥልቀት ፡ አይደርስም

**neuter** ግዑዝ ፡ ጾታ
The Latin noun has a neuter. የላቲን ፡ ስም ፡ ግዑዝ ፡ ጾታ ፡ አለው

**neutral**
1. ገለልተኛ. Sweden was neutral during the First World War. በመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ስዊድን ፡ ገለልተኛ ፡ ነበረች
2. ደብዘዝ ፡ ያለ. Gray is a neutral color. ግራጫ ፡ ደብዘዝ ፡ ያለ ፡ ቀለም ፡ ነው

**neutrality** ገለልተኛነት
The big powers do not often observe the neutrality of small countries. ኀያላን ፡ መንግሥታት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የትናንሽ ፡ መንግሥታትን ፡ ገለልተኛነት ፡ አያከብሩም

**neutralize**
1. ፍሬ ፡ ቢስ ፡ አደረገ. His carelessness neutralized his efforts. ጠንቃቃ ፡ አለመሆኑ ፡ ጥረቱን ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ አደረገው
2. ዋጋ ፡ አሳጣ. Our artillery neutralized their cavalry. የኛ ፡ መድፈኞች ፡ የነሱን ፡ ፈረሰኞች ፡ ዋጋ ፡ አሳጧቸው

**never**
1. ፈጽሞ + (negative verb). She never eats fish. ዓሣ ፡ ፈጽሞ ፡ አትበላም
2. ፈጽሞ + (gerundive) + አያውቅም. Never in

my life have I seen such a fire. በሕይወቴ ፡ እን ደዚህ ፡ ያለ ፡ የእሳት ፡ ቃጠሎ ፡ ፈጽሞ ፡ አይ ቼ ፡ አላውቅም
3. ከቶ + (negative verb). We never travel without a spare tire. መቀየሪያ ፡ ጎማ ፡ ሳንይዝ ፡ ከቶ ፡ መንገድ ፡ አንሄድም
4. gerundive + አያውቅም. I never went to Ethiopia. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሄጄ ፡ አላውቅም
5. ምን ፡ ጊዜም + (negative verb). A carrier of bad news is never welcome. መጥፎ ፡ ወሬን ፡ የ ሚያመጣ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ በደስታ ፡ ተቀባይነት ፡ አያገኝም
*On his trip in the desert, he met with misfortune and never returned. በበረሃው ፡ ሲጓዝ ፡ ባጋጠመው ፡ መጥፎ ፡ ዕድል ፡ ምክንያት ፡ እንደ ወጣ ፡ ቀረ

**never again**
1. ሁለተኛ + (negative verb). I'll never go there again. ሁለተኛ ፡ እዚያ ፡ አልደርስም
2. ዳግመኛ ፡ ፈጽሞ + (gerundive) + አያውቅም. She never again came to visit me. ዳግመኛ ፡ ልት ጠይቀኝ ፡ ፈጽሞ ፡ መጥታ ፡ አታውቅም
[See also 'loss, mind']

**nevertheless** የሆነ ፡ ሆኖ
Nevertheless, I still can't believe it. የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ነገሩን ፡ ላምን ፡ አልችልም

**new**
1. አዲስ. I bought new clothes for my brother. ለወንድሜ ፡ አዲስ ፡ ልብስ ፡ ገዛሁለት
In the new year, we hope to get out of debt. ባዲሱ ፡ ዓመት ፡ ከዕዳ ፡ ነጻ ፡ ለመሆን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን
2. አዲስ ፡ ነገር. What's new? ምን ፡ አዲስ ፡ ነ ገር ፡ አለ ? (ምን ፡ ይወራል ?)
That's all new to me. ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለኔ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ነው
3. እንግዳ. I am new to this town. ለከተማው ፡ እ ንግዳ ፡ ነኝ
The idea is new to me. ሐሳቡ ፡ ለኔ ፡ እንግዳ ፡ ነው

**new arrival** እንግዳ
He is a new arrival here. Show him around! እንግዳ ፡ ስለሆነ ፡ አገሩን ፡ አሳየው

**be new from** ከ --- አዲስ ፡ መጣ
My servant is new from the country. አሽከሬ ፡ ከ ባላገር ፡ አዲስ ፡ የመጣ ፡ ነው
[See also 'high, moon']

**newborn baby** አራስ ፡ ልጅ
She held a newborn baby in her arms. አራስ ፡ ልጅ ፡ ታቅፋ ፡ ነበር

**newcomer**
1. አዲስ ፡ መጪ. All newcomers must register here. አዲስ ፡ መጪዎች ፡ ሁሉ ፡ እዚህ ፡ መመዝ ገብ ፡ አለባቸው
2. ገና ፡ የመጣ ፡ ሰው. He recapitulated the argument briefly for the benefit of the newcomers. ገና ፡ ለመጡት ፡ ሰዎች ፡ ሲል ፡ የተደረገውን ፡ ክ ርክር ፡ እንደገና ፡ ባጭሩ ፡ ገለጸ

**newfangled** ዘበናይ ፤ ዘመናዊ
The old man railed against newfangled ideas. ሽማግሌው ፡ ሰው ፡ ዘበናይ ፡ (ዘመናዊ) ፡ አስተ ሳሰባችንን ፡ አወገዘ

**newly** አዲስ ፤ ገና ፡ አዲስ
The newly bought harness broke. አዲስ ፡ የተ ገዛው ፡ የፈረስ ፡ እቃ ፡ ተበጣጠሰ
A newly married couple rented the next room. ገና ፡ አዲስ ፡ የተጋቡ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ የሚቀጥ ለውን ፡ ክፍል ፡ ተከራዩ

**newlyweds** በቅርቡ ፡ የተጋቡ ፡ ባልና ፡ ሚስቶች
The newlyweds are giving a party. በቅርቡ ፡ የ ተጋቡት ፡ ባልና ፡ ሚስቶች ፡ ግብዣ ፡ ያደርጋሉ

**news**
1. ወሬ. The news came entirely unexpectedly. ወሬው ፡ ፈጽሞ ፡ ሳይታሰብ ፡ ደረሰ
2. ትልቅ ፡ ዜና. His discovery made news. የፈ ለሰፈው ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ትልቅ ፡ ዜና ፡ አትርፏል
*That is news to me. ገና ፡ መስማቴ ፡ ነው

**be in the news** በሰፊው ፡ ይወራል
His efforts to invent a plane are in the news lately. አውሮፕላን ፡ ለመፈልሰፍ ፡ የሚያደርገው ፡ ጥረት ፡ በሰፊው ፡ ይወራል

**latest news** አዲስ ፡ ወሬ ፤ ትኩስ ፡ ወሬ
Tell me the latest news! አዲስ ፡ (ትኩስ) ፡ ወሬ ፡ ንገረኝ
[See also 'break']

**newscast** ወሬ
We listen to the newscast at five. በዐሥሩ ፡ አ ንድ ፡ ሰዓት ፡ ወሬ ፡ እናዳምጣለን

**newsman** ጋዜጠኛ
They shut all newsmen out of the meeting. ጋዜጠኞችን ፡ ሁሉ ፡ ከስብሰባው ፡ እንዳይገቡ ፡ ከ ለከሏቸው

**newspaper** ጋዜጣ
This newspaper appears twice a week. ይህ ፡ ጋ ዜጣ ፡ በሳምንት ፡ ሁለቴ ፡ ይወጣል

**New Testament** አዲስ ፡ ኪዳን
The deacon studies the New Testament. ዲያቆኑ ፡ አዲስ ፡ ኪዳን ፡ ያጠናል

**next** (adj.)

1. ተረኛ. "Who is next?" the nurse asked the patients. ተረኛ ፡ ማነው ? ብላ ፡ ነርሷ ፡ ሕመምተኞቹን ፡ ጠየቀች

2. የሚቀጥል. Next time do it right. በሚቀጥለው ፡ ጊዜ ፡ በትክክል ፡ ሥራው

The next bus will arrive in ten minutes. የሚቀጥለው ፡ አውቶቡስ ፡ ባሥር ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ይደርሳል

3. የሚመጣ. We are coming next month. በሚመጣው ፡ ወር ፡ እንመጣለን

By this time next week, we shall be in France. በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ነን

4. (= adv.) ቀጥሎ. Take the next turn to the right! ቀጥሎ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ የሚታጠፈውን ፡ መንገድ ፡ ያዝ

**next** (adv.)

1. ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቀጥሎ. What will you do next? ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቀጥሎ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ ?

2. ቀጥሎ. My name comes next on the list. በዝርዝሩ ፡ ውስጥ ፡ ስሜ ፡ ቀጥሎ ፡ ይመጣል

3. ሁለተኛ. When next we meet, smile! ሁለተኛ ፡ ስንገናኝ ፡ ፈገግ ፡ በል

**next day** በማግስቱ

He spent the day at the market, and the next day he got sick. ገበያ ፡ ውሎ ፡ በማግስቱ ፡ ታመመ

**next to**

1. ከ - - - ቀጥሎ. He was next to me in line. በሰልፉ ፡ ላይ ፡ ከኔ ፡ ቀጥሎ ፡ ነበር

Which town is next to London in size? በመጠን ፡ ከሎንዶን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ከተማ ፡ የቱ ፡ ነው ?

2. የ - - - ተከታይ. He is next to me in rank. በማዕርግ ፡ የኔ ፡ ተከታይ ፡ ነው

3. ጐን. Sit down next to me! ጐኔ ፡ ተቀመጥ

4. ከ - - - አጠገብ. They live next to the church. ቤታቸው ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አጠገብ ፡ ነው

**next to nothing** ምንም

No wonder she's so thin; she eats next to nothing. ቅጥነቷ ፡ አያስደንቅም ፤ ምንም ፡ አትበላ

**the next best thing** እንግዲህ ፡ የቀረው ፡ ሌላው ፡ ጥሩ ፡ ነገር

There are no tickets left for the circus. The next best thing is the zoo. ወደ ፡ ሰርከሱ ፡ እንዳንገባ ፡ ቲኬት ፡ አልቋል ፤ እንግዲህ ፡ የቀረን ፡ ሌላው ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ያራዊት ፡ መጠበቂያው ፡ ቅጥር ፡ ነው

[See also 'door, last, morning, time']

**next-door** (adj.) የቅርብ

We are next-door neighbors. የቅርብ ፡ ጐረቤት ፡ ነን

**next door** (adv.) በሚቀጥለው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፤ እሚቀጥለው ፡ ቤት

The tailor lives next door. ልብስ ፡ ሰፊው ፡ በሚቀጥለው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል

Please go next door! እሚቀጥለው ፡ ቤት ፡ ሂድ

**next of kin** የቅርብ ፡ ዘመድ

As soon as he died, they notified the next of kin. እንደሞተ ፡ ለቅርብ ፡ ዘመዱ ፡ ነገሩ

**nibble** ሸራረፈ

The mouse nibbled the bread. አይጧ ፡ ዳቦውን ፡ ሸራረፈችው

**nice**

1. ጥሩ. Let's go for a walk! It's a nice day today. ሽርሽር ፡ እንሂድ ፤ ዛሬ ፡ ጥሩ ፡ ቀን ፡ ነው

That wasn't a nice remark. ጥሩ ፡ አስተያየት ፡ አልነበረም

2. ደግ. It wasn't very nice of you to refuse that old lady a seat. አሮጊቷን ፡ ባልቴት ፡ ተነሥተህ ፡ አለማስቀመጥህ ፡ ደግ ፡ አላደረግህም

They are nice to strangers. ለእንግዶች ፡ ደጎች ፡ ናቸው

3. ረቂቅ. Artists must make nice distinctions between various colors. ሠዓሊዎች ፡ በቀለማት ፡ መካከል ፡ ረቂቅ ፡ ልዩነት ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው

**nice and ...**

1. ደኅና. It's nice and warm by the fire. እሳቱ ፡ ዳር ፡ ደኅና ፡ ይሞቃል

2. በደንብ. Be sure the beer is nice and cold! ቢራው ፡ በደንብ ፡ የቀዘቀዘ ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጥ

**nicely** በደንብ

The bench will fit nicely in that recess. አግዳሚው ፡ ወንበር ፡ በዚያ ፡ ግድግዳ ፡ ማስገቢያ ፡ ውስጥ ፡ ቢሆን ፡ በደንብ ፡ ይገጥማል

**do nicely, that will ~** ይኸማ ፡ ጥሩ

Would you like a sandwich? That will do nicely. ሳንድዊች ፡ ትፈልጋለህ ? ይኸማ ፡ ጥሩ

**quite nicely** ጥሩ ፡ አድርጎ

You did that quite nicely. ጥሩ ፡ አድርገህ ፡ ሠርተኸዋል

**nicety** (niceties)

1. ረቀቅ ፡ ያለው. He knows English well, but not the niceties of grammar. እንግሊዝኛ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ያውቃል ፡ ግን ፡ ረቀቅ ፡ ያለውን ፡ የሰዋስው ፡ ጥበብ ፡ አያውቅም

2. የሚመቹ ፡ ነገሮች. The niceties of life cannot be obtained in the desert. ለኑሮ ፡ የሚመቹ ፡ ነገሮችን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ ማግኘት ፡ አይቻልም

**niche** [ለልዩ ፡ ልዩ ፡ እቃ ፡ መደርደሪያ ፡ እንዲያ ገለግል ፡ በግድግዳ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ጕድጓ ዳ ፡ ስፍራ]

**nick, make a ~** ሸረፈ
She hit a cup and made a nick on the edge of it. ሲኒውን ፡ ገጭታ ፡ አፉ ፡ ላይ ፡ ሸረፈችው

**in the nick of time** በነፍስ ፡ እንዲደርስ
They summoned a doctor in the nick of time. ሐኪሙን ፡ በነፍስ ፡ እንዲደርስ ፡ ጠሩት

**nickname** የቅጽል ፡ ስም
Edward's nickname is Shorty. የኤድዋርድ ፡ የ ቅጽል ፡ ስም ፡ ኩሩሩ ፡ ነው

**niece** የእኅት ፡ ልጅ ፤ የወንድም ፡ ልጅ
My niece is going to be married tomorrow. የእኅቴ ፡ (የወንድሜ) ፡ ልጅ ፡ ነገ ፡ ልትዳር ፡ ነው

**niggard** ቈንቋና
His father is a niggard and will not buy shoes for him. አባቱ ፡ ቈንቋና ፡ ስለሆነ ፡ ጫማ ፡ እንኳ ፡ አይገዛለትም

**niggardly**
1. ቈንቋና. His father is a niggardly sort, and won't buy him shoes. አባትዬው ፡ ቈንቋና ፡ ቢ ጤ ፡ ስለሆነ ፡ ጫማ ፡ አይገዛለትም
2. አነስተኛ. This niggardly gift of a pair of socks does not repay me for the work I have done. የእግር ፡ ሹራቡ ፡ አነስተኛ ፡ ስጦታ ፡ ስለሆ ነ ፡ የሠራሁትን ፡ ሥራ ፡ አይመጥንም

**nigh, draw ~** ተቃረበ
The time draws nigh. ጊዜው ፡ ተቃረበ

**night** ሌሊት
He traveled day and night for a week. ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ተጓዘ

**nights** ሌሊት ፡ ሌሊት
He works during the day and writes at night. ቀን ፡ ቀን ፡ እየሠራ ፡ ሌሊት ፡ ሌሊት ፡ ይጽፋል

**night and day** ያለማቋረጥ
He worked night and day until the job was done. ሥራው ፡ እስኪለቀ ፡ ድረስ ፡ ያለማቋረ ጥ ፡ ሠራ

**(the) night before** ባለፈው ፡ ሌሊት
The night before, my father came by train from Addis Ababa. ባለፈው ፡ ሌሊት ፡ አባቴ ፡ በ ባቡር ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ መጡ

**good night!** ደኅና ፡ እደር (2nd masc. sg.)

**last night** ትላንትና ፡ ማታ
We had unexpected company last night. ትላንትና ፡ ማታ ፡ ያልታሰበ ፡ እንግዳ ፡ መጣብን

**late last night** ዛሬ ፡ ሌሊት
Late last night I heard a noise. ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ

**put up for the night** ዛሬ ፡ አሳደረ
Can you put us up for the night? ዛሬ ፡ ልታ ሳድረን ፡ ትችላለህ ?

**stay (two, etc.) nights** ቀን ፡ አደረ
He stayed at my house three nights. ከቤቴ ፡ ሦ ስት ፡ ቀን ፡ አደረ

**take in for the night** አሳደረ
She took him in for the night since there was no place else for him to go. መሄጃ ፡ ስላልነበረው ፡ አሳደረችው

**tomorrow night** ነገ ፡ ማታ
They are going to the movies tomorrow night. ነገ ፡ ማታ ፡ ወደ ፡ ሲኒማ ፡ ይሄዳሉ
[See also 'before, dead, retire, settle, spend, take in, young']

**nightfall, at ~** ሲመሽ
Children must come home at nightfall. ሲመሽ ፡ ልጆች ፡ ከቤት ፡ መከተት ፡ አለባቸው

**nightgown** የሌሊት ፡ ልብስ
Her nightgown is made of black silk. የሌሊት ፡ ልብሷ ፡ ከጥቁር ፡ ሐር ፡ የተሠራ ፡ ነው

**nightlong**, adj. (= adv.) ሌሊቱን ፡ ሙሉ
The nightlong rain caused a lot of damage. ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ የዘነመው ፡ ዝናም ፡ ብዙ ፡ ጉ ዳት ፡ አደረሰ

**all nightlong** ሌሊቱን ፡ ሙሉ
They typed all nightlong to finish the report. ሪፖርቱን ፡ ለመጨረስ ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ በመ ኪና ፡ ሲጽፉ ፡ አደሩ

**nightly**, adj. (= adv.) ማታ ፡ ማታ
His nightly bath takes 20 minutes. ማታ ፡ ማታ ፡ ገላውን ፡ ሲታጠብ ፡ ሀያ ፡ ደቂቃ ፡ ይፈጅል

**nightly** (adv.) ሌሊት ፡ ሌሊት
He wakes up nightly. ሌሊት ፡ ሌሊት ፡ ይባንናል

**nightmare** ቅዠት
The child woke up screaming because he had a nightmare. ልጁ ፡ በቅዠት ፡ ጮኾ ፡ ተነሣ

**be a nightmare** በጣም ፡ አስደንጋጭ ፡ ነበረ
The train crash was a nightmare I shall never forget. የባቡሩ ፡ ግጭት ፡ በጣም ፡ አስደንጋጭ ፡ ስለነበረ ፡ ምንጊዜም ፡ አልረሳውም

**have a nightmare** ቃዠ
He always has nightmares. ሁልጊዜ ፡ ይቃዣል

**night school** ማታ ፡ ትምህርት ፡ ቤት
He is attending night school. ማታ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይማራል

**nightstand** ኮመዲኖ
There is a nightstand by the bed. አልጋው ፡ አ ጠገብ ፡ ኮመዲኖ ፡ አለ

**nightwatchman** የሌሊት ፡ ዘበኛ
The nightwatchman keeps an eye on the house. የሌሊት ፡ ዘበኛ ፡ ቤቱን ፡ ይጠብቃል

**nimble**
1. ቀልጣፋ. The monkeys are nimble in climbing trees. ጦጣዎቹ ፡ ዛፍ ፡ በመውጣት ፡ ቀልጣፎች ፡ ናቸው
2. ንቁ. The boy had a nimble mind and could think up excuses for every occasion. ልጁ ፡ ንቁ ፡ አእምሮ ፡ ስለነበረው ፡ ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ ም ክንያት ፡ ይፈጥር ፡ ነበር

**nine** ዘጠኝ
**nine o'clock** ሦስት ፡ ሰዓት
I will come at nine o'clock በሦስት ፡ ሰዓት ፡ እ መጣለሁ

**nineteen** ዐሥራ ፡ ዘጠኝ

**ninety** ዘጠና

**ninth** ዘጠነኛ

**nip** (nipped), v.
1. ነከስ ፡ አደረገ. The puppy nipped me, and it hurt. ቡችላዋ ፡ ነከስ ፡ ስላደረገችኝ ፡ አመመኝ
2. አቃጠለ. The cold nipped our ears. ብርዱ ፡ ጆሮዎችንን ፡ አቃጠለን
3. ቀጨ. A late frost nipped the first flowers. ዘግይቶ ፡ የጣለ ፡ ውርጭ ፡ በመውጣት ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ አበቦች ፡ ቀጫቸው
4. ቀረጠፈ. +He nipped his finger in the door. መዝጊያው ፡ ጣቱን ፡ ቀረጠፈው
**nip off** ነጨ
The dog nipped off a piece of meat. ውሻው ፡ ሥጋውን ፡ ነጨ
**be nipped** (= active) መታ
The plants are wilting because they were nipped by the frost. ውርጭ ፡ ስለመታቸው ፡ ተ ክሎቹ ፡ ጠውልገዋል

**nip** (n.), **have a ~ of** ፉት ፡ አለ(ለት)
Have a nip of this whiskey! ከዚህ ፡ ውስኪ ፡ ፉ ት ፡ በልለት

**nipple** ጫፍ
The nipples of the breast of a woman who gives birth must be kept clean. የወላድ ፡ ጡት ፡ ጫፍ ፡ በንጽሕና ፡ መጠበቅ ፡ አለበት
**nipple of baby bottle** ጡጦ
She washed the nipples of the baby bottles. ጡጦውን ፡ አጠበችው

**no**
1. የለም. Is it Monday today? No, it isn't. ዛሬ ፡ ሰኞ ፡ ነው ? የለም ፡ አይደለም
2. አይደለም. Answer 'yes' or 'no'! ነው ፡ ወይም ፡ አይደለም ፡ ብለህ ፡ መልስ
3. (verb in the negative). He has no money. ገንዘብ ፡ የለውም
The desert is no place for a weak person to be. ምድረ ፡ በዳ ፡ ለደካማ ፡ ሰው ፡ አይስማማም
*No talking! መነጋገር ፡ ክልክል ፡ ነው
**no one**
1. ማንም + (negative verb). No one came to see me when I was sick. ታምሜ ፡ ሳለሁ ፡ ማን ም ፡ አልጠየቀኝም
2. ማንም ፡ ሰው ፡ + negative verb
It is an axiom that no one lives forever. ማንም ፡ ሰው ፡ ለዘላለም ፡ እንደማይኖር ፡ እሙን ፡ ነው
**no one of** አንድ + suffix pronouns + negative verb
No one of you can lift it. አንዳችሁም ፡ ልታ ነሡት ፡ አትችሉም
**no other man** ማንም + negative verb
No other man can do my work. ሥራዬን ፡ ማን ም ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም
[See also 'later, more, sooner, time, whatsoever']

**nobility**
1. መኳንንት. The nobility accompanied the Emperor to church. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ሲሄዱ ፡ መኳንንቱ ፡ ዐጀቧቸው
2. ትልቅነት. We did not agree with his method, but we admired the nobility of his aim. በዘዴው ፡ ባንስማማም ፡ የዓላማውን ፡ ትልቅነት ፡ አደነቅን

**noble** (n.) መኳንንት
Only a noble may receive the title of Ras. የራስነት ፡ ማዕርግ ፡ የሚያገኙ ፡ መኳንንት ፡ ብ ቻ ፡ ነው
**noble** (adj.)
1. ለጋስ. He is very noble when it comes to giving money. በገንዘብ ፡ ለጋስ ፡ ነው
2. የጨዋ. He is a man of noble character. የጨዋ ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

3. የላቀ. His noble thoughts manifest themselves in his actions. የላቀ ፡ አስተሳሰቡ ፡ በሥራው ፡ ይታወቃል
[See also 'countenance, presence']

**nobleman** (noblemen) መኳንንት
The nobleman has an obligation to support the church. መኳንንቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ የመደገፍ ፡ ግዴታ ፡ አለበት

**nobody**
1. ማንም + (negative verb). Nobody saw him. ማንም ፡ አላየውም
2. ማንም ፡ ሰው + (negative verb). Nobody may leave this room. ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ክፍል ፡ እንዲወጣ ፡ አይፈቀድለትም
3. አንድም + (negative verb). We saw nobody we knew. አንድም ፡ የምናውቀው ፡ ሰው ፡ አላየንም

**nobody else** ሌላ ፡ ማንም ፡ ሰው + negative verb
Nobody else offered to help me. ሌላ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አልረዳኝም

**nocturnal**
1. የሌሊት. The owl is a nocturnal bird. ጉጉት ፡ የሌሊት ፡ ወፍ ፡ ናት
2. (= adv.) ሌሊት ፡ ብቻ. Stars are a nocturnal sight. ኮከቦች ፡ ሌሊት ፡ ብቻ ፡ የሚታዩ ፡ አካሎች ፡ ናቸው

**nod** (nodded), v.
1. አንጐላጀ. He began to nod over his book. መጽሐፉን ፡ ሲያነብ ፡ ያንጐላጅ ፡ ነበር
2. ራሱን ፡ ነቀነቀ ፤ ጐምበስ ፡ ቀና ፡ አደረገ. She absently nodded in response to the question. በሌላ ፡ ሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ ተውጣ ፡ ሳለች ፡ ለጥያቄው ፡ መልስ ፡ ራሷን ፡ ነቀነቀች
Nodding your head is equivalent to saying yes. ራስን ፡ ጐምበስ ፡ ቀና ፡ ማድረግ ፡ እሺ ፡ የማለት ፡ ያህል ፡ ነው
3. ተወዛወዘ. Trees nod in the wind. ዛፎቹ ፡ በነፋሱ ፡ ይወዛወዛሉ
*He nodded to me as he passed. ሲያልፍ ፡ ራሱን ፡ ነቅንቆ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠኝ

**nod** (n.) ራሱን ፡ መነቅነቅ
He signified his consent with a nod. ራሱን ፡ በመነቅነቅ ፡ መስማማቱን ፡ ገለጸ

**give a nod**
*He gave us a nod as he passed. ሲያልፍ ፡ ራሱን ፡ በመነቅነቅ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠን

**greet with a nod**
He greeted us with a nod. እጅ ፡ ነሣን

**noise**
1. ጫጫታ. The noise in the street distracted me from reading. መንገዱ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጫጫታ ፡ ማንበብ ፡ ከለከለኝ
2. ውካታና ፡ ጫጫታ. His ears were attuned to the noise of the big city. ጆሮው ፡ የትልቁን ፡ ከተማ ፡ ውካታና ፡ ጫጫታ ፡ ለምዶታል
3. ድምፅ. I heard a faint noise in the dark. ጨለማው ፡ ውስጥ ፡ ድምፅ ፡ መሳይ ፡ ሰማሁ

**make noise** ተንጫጫ
Children, don't make so much noise! ልጆች ፤ ይህን ፡ ያህል ፡ አትንጫጩ

**noiseless** ድምፅ ፡ የሌለው
She owns a noiseless typewriter. ድምፅ ፡ የሌለው ፡ የጽሕፈት ፡ መኪና ፡ አላት

**noisy**
1. ጫጫታ ፡ የሚበዛበት. That's a noisy office. ይህ ፡ ጫጫታ ፡ የሚበዛበት ፡ ቢሮ ፡ ነው
2. ጫጫታ ፡ የሚያበዛ. The owner will not lease the apartment to noisy tenants. ባለቤቱ ፡ አፓርተማውን ፡ ጫጫታ ፡ ለሚያበዙ ፡ ሰዎች ፡ አያከራዩም
3. ጩኺ. The noisy boy did not let me finish my letter. ጩኺው ፡ ልጅ ፡ ደብዳቤዬን ፡ እንዳልጨርስ ፡ አደረገኝ

**be noisy**
1. ተንጫጫ. The children were noisy when the guests were trying to talk. እንግዶቹ ፡ ሲጫወቱ ፡ ልጆቹ ፡ ይንጫጩ ፡ ነበር
2. ጩኸት ፡ አበዛ. The patrons of this bar are asked not to be noisy. የዚህ ፡ ቡና ፡ ቤት ፡ ደንበኞች ፡ ጩኸት ፡ እንዳያበዙ ፡ ተጠይቀዋል
3. ጋጋታ ፡ በዛ(በት). The party is too noisy; let's slip away! ፓርቲው ፡ በጣም ፡ ጋጋታ ፡ በዝቶበታል ፤ ሹልክ ፡ ብለን ፡ እንውጣ

**nomad** ዘላን
Nomads take their cattle on a search for grass. ዘላኖቹ ፡ ግጦሽ ፡ ፍለጋ ፡ ከብቶቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ይዘዋወራሉ

**nomadic, ~ tribe** ዘላን
Nomadic tribes live in eastern Ethiopia. ዘላኖች ፡ በምሥራቅ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይኖራሉ

**nomenclature** መራሒ ፡ ቃላት
Every scientist must learn the nomenclature of his field. ማንኛቸውም ፡ የሳይንስ ፡ ሊቅ ፡ የሙያውን ፡ መራሒ ፡ ቃላት ፡ ማጥናት ፡ አለበት

**nominal**
1. በጣም ፡ ትንሽ. There is a nominal entrance fee. የመግቢያው ፡ ዋጋ ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው

2. (= adv.) በስም ፡ ብቻ ፤ ለስሙ. The queen is the nominal ruler of the country. ንግሥቲቱ ፡ ሀገሪቱን ፡ የምትገዛት ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ ነው
Though the king was the nominal ruler, his son governed the country. ንጉሡ ፡ ለስሙ ፡ ገዢ ፡ ቢሆንም ፡ አገሪቱን ፡ የሚያስተዳድረው ፡ ልጁ ፡ ነበር

**nominate**
1. ሾመ. The President nominates his ministers. ፕሬዚዳንቱ ፡ ሚኒስትሮቹን ፡ ይሾማል
2. አቀረበ. When do the parties nominate their candidates? ፓርቲዎቹ ፡ እጩዎቻቸውን ፡ የሚያቀርቡት ፡ መቼ ፡ ነው ?
**be nominated** በተወዳዳሪነት ፡ ቀረበ
He was nominated for the office of President, but not elected. ለፕሬዚዳንትነቱ ፡ በተወዳዳሪነት ፡ ቀርቦ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ አልተመረጠም

**nomination** መታጨት
The senate accepted the nomination of Mr. Parker as ambassador. የሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሚስተር ፡ ፓርከርን ፡ ላምባሳደርነት ፡ መታጨት ፡ ተቀበለ
*We will now hear the nomination for club secretary. ለክበቡ ፡ ጸሐፊነት ፡ ማን ፡ እንደታጨ ፡ አሁን ፡ እንሰማለን

**nonchalant** ግዴለሽ
He is nonchalant about his debts. ስላለበት ፡ ዕዳ ፡ ግዴለሽ ፡ ነው

**nondescript** ይህ ፡ ነው ፡ የማይባል
A small, nondescript dog came into our room. አንድ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የማይባል ፡ ትንሽ ፡ ውሻ ፡ ክፍላችን ፡ ገባ

**none**
1. ምንም + (negative verb). I needed some string, but there was none in the house. ሲባን ፡ ፈልጌ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ከቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ አልነበረም
None of the money is left. ከገንዘቡ ፡ ምንም ፡ አልተረፈም
2. አንዱም + (negative verb). None of my friends could help me. ከጓደኞቼ ፡ አንዱም ፡ ሊረዳኝ ፡ አልቻለም
**none but the best** ጥሩ ፡ ጥሩውን ፡ ነገር ፡ ብቻ
They choose none but the best. ሁልጊዜ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩውን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ይመርጣሉ
**none of**
1. ምኑም. None of this money is mine. ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ምኑም ፡ የኔ ፡ አይደለም
2. አንድ + (suffix pronouns). None of them has yet come back. እስካሁን ፡ አንዳቸውም ፡ አልተመለሱ
**none of your business**
That's none of your business. አንተን ፡ አያገባህም
**none other than** ራሱ
The one who called you is none other than the director. የጠሩህ ፡ ዲሬክተሩ ፡ ራሳቸው ፡ ናቸው
**none too good** ፈጽሞ ፡ ጥሩ + negative verb
The play was none too good. ቴያትሩ ፡ ፈጽሞ ፡ ጥሩ ፡ አልነበረም
**none too high** ብዙ ፡ አይደለም
The salary he pays is none too high. የሚከፍለው ፡ ደሞዝ ፡ ብዙ ፡ አይደለም
**none too soon** ልክ ፡ በሰዓቱ
We arrived none too soon since they were just beginning to eat. ገና ፡ መብል ፡ መጀመራቸው ፡ ስለነበረ ፡ ልክ ፡ በሰዓቱ ፡ ደረስን
[See also 'worse']

**nonentity** (nonentities)
My neighbor is a nonentity. ጐረቤቴ ፡ ከዚህ ፡ ግባ ፡ የማይባል ፡ ሰው ፡ ነው

**nonetheless** ዳሩ ፡ ግን
Though he cannot leave the house, he is busy nonetheless. ከቤቱ ፡ አይወጣም ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ሥራ ፡ በዝቶበታል

**nonexistent** የሌለ
He worries over nonexistent dangers. በሌለ ፡ አደጋ ፡ ይጨነቃል

**(be) nonplussed** ተደነጋገረ
The speaker was nonplussed by the sudden interruption. በድንገት ፡ ስላቋረጡት ፡ ተናጋሪው ፡ ተደነጋገረ

**nonsense**
1. የማይረባ ፡ ነገር. Don't talk such nonsense! እንዲህ ፡ ያለ ፡ የማይረባ ፡ ነገር ፡ አትናገር
Don't spend your money for such nonsense! ገንዘብህን ፡ ለዚህ ፡ ለማይረባ ፡ ነገር ፡ አታጥፋ
2. እርባን ፡ የለሽ. His conversation verges on nonsense. ጨዋታው ፡ እርባን ፡ የለሽ ፡ ሊባል ፡ ምንም ፡ አይቀረውም
3. መዘከር ፤ መጃጃል ፤ ዋጋ ፡ ቢስ. This is perfect nonsense. ያ ፡ ፍጹም ፡ መዘከር ፡ (መጃጃል ፤ ዋጋ ፡ ቢስ) ፡ ነው

**nonstop** ቀጥታ
He flew nonstop from New York to Paris. ከኒውዮርክ ፡ እስከ ፡ ፓሪስ ፡ ቀጥታ ፡ በረረ

**nook** [በክፍል ፡ ውስጥ ፡ ተከልሎ ፡ የሚገኝ ፡ አነስተኛ ፡ ቦታ]

**noon** እኩለ ፡ ቀን
Toward noon, the fog lifted. ወደ ፡ እኩለ ፡ ቀን ፡ ገደማ ፡ ጭጋጉ ፡ ገፈፈ.

**at noon**
1. በቀትር ፤ ቀትር ፡ ላይ. She is seldom home at noon. በቀትር ፡ እቤቷ ፡ የምትገኘው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነው
The manager let the clerks off at noon. ሥራ ፡ መሪው ፡ ቀትር ፡ ላይ ፡ ጸሐፊዎቹን ፡ አሰናበተ
2. በሰዓት. He comes home at noon for lunch. በሰዓት ፡ እቤቱ ፡ ለምሳ ፡ ይመጣል

**nor**
1. -ም + (negative verb). I have not gone there, nor will I ever go. እዚያ ፡ ሄጄ ፡ አላውቅም ፤ ወደፊትም ፡ ቢሆን ፡ አልሄድ
2. -ም ፡ -ም + (negative verb). He cannot do it, nor can I. እሱም ፡ እኔም ፡ ልንሠራው ፡ አንችልም

**nor ... nor**
Nor silver nor gold can buy it. ብርም ፡ ሆነ ፡ ወርቅ ፡ ሊገዛው ፡ አይችልም
[See also 'neither']

**norm**
1. መጠነኛ ፡ ቁጥር. The norm for daily production is about 10 cars. በቀን ፡ ተሠርተው ፡ የሚወጡት ፡ መኪናዎች ፡ መጠነኛው ፡ ቁጥር ፡ ዐሥር ፡ ነው
2. የተለመደ. Two cars per family is the norm in many American cities. በብዙ ፡ የአሜሪካን ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ መኪና ፡ ላንድ ፡ ቤተሰብ ፡ የተለመደ ፡ ነው

**normal** (n.) መጠን
During the rain, the river rose five feet above normal. በዝናቡ ፡ ጊዜ ፡ ወንዙ ፡ ከመጠኑ ፡ አምስት ፡ ጫማ ፡ አልፎ ፡ ሞልቶ ፡ ነበር

**normal** (adj.)
1. የተለመደ. The normal temperature of the human body is 98.6 Farenheit. የተለመደው ፡ የሰው ፡ አካል ፡ ሙቀት ፡ 98.6 ፋረንሃይት ፡ ነው
It is normal to make a mistake sometimes. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ መሳሳት ፡ የተለመደ ፡ ነው
2. እንከን ፡ የሌለው. He is a normal child. እንከን ፡ የሌለው ፡ ልጅ ፡ ነው
3. ሁኔታው ፡ የተለመደ. Some people are normal; insane people are not. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ሁኔታቸው ፡ የተለመደ ፡ ነው ፤ እብዶች ፡ ግን ፡ አይደሉም

**normally**
1. ብዙ ፡ ጊዜ. You will normally find him at the office at 10 o'clock. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ባራት ፡ ሰዓት ፡ ቢሮው ፡ ታገኘዋለህ
2. አብዛኛውን ፡ ጊዜ. Normally, I take a walk in the morning. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ በእግሬ ፡ እንሸራሸራለሁ

**behave normally** ሁኔታው ፡ ደኅና ፡ ሆነ
He has behaved normally since he finished his treatment. ሕክምናውን ፡ ከጨረሰ ፡ ወዲህ ፡ ሁኔታው ፡ ደኅና ፡ ሆኗል

**not act normally** አኳኋኑ ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ አይደለም
He is not acting normally; you think he is ill? አኳኋኑ ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ አይደለም ፤ የታመመ ፡ ይመስልሃል ?

**north** ሰሜን
Asmara is to the north of Addis Ababa. አሥመራ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ በስተሰሜን ፡ ነው

**northeast**
1. የሰሜናዊ ፡ ምሥራቅ. The northeast wind rarely blows. የሰሜናዊ ፡ ምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይነፍሳል
2. ከሰሜናዊ ፡ ምሥራቅ ፡ የሚነፍስ. The northeast wind brings rain. ከሰሜናዊ ፡ ምሥራቅ ፡ የሚነፍሰው ፡ ነፋስ ፡ ዝናም ፡ ያመጣል

**northern** ሰሜናዊ
The northern part of the island was flooded. የደሴቱ ፡ ሰሜናዊ ፡ ክፍል ፡ በጐርፍ ፡ ተጥለቀለቀ

**North Pole** የሰሜን ፡ ዋልታ
The North Pole was reached by man in 1907. የሰሜን ፡ ዋልታ ፡ የተደረሰበት ፡ ፲፱፻፯ ዓ. ም. ነው

**northwest**
1. የሰሜናዊ ፡ ምዕራብ. The northwest wind rarely blows. የሰሜናዊ ፡ ምዕራብ ፡ ነፋስ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይነፍሳል
2. ከሰሜናዊ ፡ ምዕራብ ፡ የሚነፍስ. The northwest wind brings rain. ከሰሜናዊ ፡ ምዕራብ ፡ የሚነፍሰው ፡ ነፋስ ፡ ዝናም ፡ ያመጣል

**nose** (vt.) አነፈነፈ
The dog nosed the grass in search of a trail. ውሻው ፡ መንገድ ፡ ፍለጋ ፡ ሣሩን ፡ አነፈነፈ

**nose** (vi.) አለፈ
The little boat nosed carefully between the rocks. ትንሿ ፡ ጀልባ ፡ በቋጥኞቹ ፡ መካከል ፡ በጥንቃቄ ፡ አለፈች

**nose** (n.)
1. አፍንጫ. Greek statues have straight noses. የግሪክ ፡ ሐውልቶች ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ አፍንጫ ፡ አላቸው

2. የማሽተት ፡ ችሎታ. Most dogs have a good nose. አብዛኛዎቹ ፡ ውሾች ፡ የማሽተት ፡ ችሎታቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው

**blow the nose** ተናፈጠ
I have to blow my nose. መናፈጥ ፡ አለብኝ

**count noses** ሰዎች ፡ ቈጠረ
Each time the troop left an exhibit the leader counted noses. ጓዱ ፡ ከኤግዚቢሽኑ ፡ በወጣ ፡ ቁጥር ፡ መሪው ፡ ሰዎቹን ፡ ይቈጥር ፡ ነበር

**following (one's) nose** በስሜት ፡ ብቻ
It had been many years since my last visit, but I found the house by following my nose. ከሄድኩ ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሆኖኝ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በስሜት ፡ ብቻ ፡ ቤቱን ፡ ለማግኘት ፡ ቻልኩ

**have a nose for**
*He has a nose for news. ወሬ ፡ አያመልጠውም ፡ (ወሬ ፡ የት ፡ እንደሚገኝ ፡ ያውቃል)

**lead by the nose**
*He let his wife lead him by the nose. ሚስቱ ፡ እንዳሻት ፡ እንድታደርገው ፡ ችላ ፡ አላት

**look down (one's) nose at** ናቀ
He always looks down his nose at foreigners. የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎችን ፡ ዘወትር ፡ እንደናቀ ፡ ነው

**turn up (one's) nose** ተጠየፈ ፤ ናቀ
He turned up his nose at the food he was given. የቀረበለትን ፡ ምግብ ፡ ተጠየፈ
She turned up her nose at the suggestion. የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ ናቀችው

**under one's nose** ከ - - - ዓይን ፡ ሥር
The theft took place right under the policeman's nose. ስርቆቱ ፡ የተፈጸመው ፡ ከፖሊሱ ፡ ዓይን ፡ ሥር ፡ ነው
[See also 'poke, running']

**nosebleed, have a ~** ነሰረ(ው)
He had a nosebleed from working too hard. ከሥራ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ነስሮት ፡ ነበረ

**nostalgia**
*His nostalgia causes him to constantly talk of the good old days. የጥንቱ ፡ ትዝ ፡ እያለው ፡ ስላለፉት ፡ ቀናት ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ ይናገራል

**nostalgic**
She was nostalgic for her youth. የልጅነት ፡ ጊዜዋ ፡ ትዝታ ፡ አልለቀቃትም

**nostril** አፍንጫ
The doctor inserted a tube in his right nostril. ሐኪሙ ፡ በቀኝ ፡ አፍንጫው ፡ ቱቦ ፡ ከተተበት

**nosy** ወሬ ፡ የሚወድ
He is so nosy that he always knows what's going on. ወሬ ፡ ስለሚወድ ፡ የሚሆነው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አያመልጠውም

**not,** expressed by the negative verb
Did you do that? Not I. አንተ ፡ ነህ ፡ ይህን ፡ ያደረግኸው ? እኔ ፡ አይደለሁም
He warned me not to be late. እንዳልዘገይ ፡ አስጠነቀቀኝ

**not at all**
1. ፈጽሞ ፤ ጭራሽ ፤ እንዲያውም. Are you tired? Not at all. ደክሞሃል ? ፈጽሞ ! (ጭራሽ ፤ እንዲያውም)
2. ፈጽሞ + (negative verb). I'm not at all sure. ፈጽሞ ፡ እርግጠኛ ፡ አይደለሁም
3. ምንም ፡ አይደል. Thank you very much! Not at all. በጣም ፡ አመሰግናለሁ ፤ ምንም ፡ አይደል

**not even** እንኳን + negative verb
Not even a dog would eat that. ውሻ ፡ እንኳን ፡ አይበላውም

**not only ... but also** ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ - - - ም
He was not only a good student but also an outstanding athlete. ጐበዝ ፡ ተማሪ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ዝነኛ ፡ ስፖርተኛም ፡ ነበር
[See also 'any, anybody, anything, bit, yet']

**notable** (n.) ታላቅ ፡ ሰው
Many notables came to the President's reception. ለፕሬዚዳንቱ ፡ ግብዣ ፡ ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ መጡ

**notable** (adj.) የሚታወስ
The restoration of independence was a notable event. የነጻነት ፡ መመለስ ፡ የሚታወስ ፡ ዕለት ፡ ነበር

**notary** [ውሎችንና ፡ ሰነዶችን ፡ የሚያጸድቅ ፡ መንግሥት ፡ ያወቀው ፡ አዋዋይ]

**notation(s)**
1. ማስታወሻ. The notations that he made on a bit of paper were illegible. በትንሽ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የጻፈው ፡ ማስታወሻ ፡ አይነበብም
2. ኖታ. Someone who is not a musician cannot understand musical notations. ሙዚቀኛ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ የሙዚቃን ፡ ኖታዎች ፡ ሊረዳ ፡ አይችልም

**notch, make a ~** ለምልክት ፡ ያህል ፡ ቈረጠ
He made a notch in the sheep's ear with a knife. የበጓን ፡ ጆሮ ፡ ለምልክት ፡ ያህል ፡ በቢላዋ ፡ ቈረጠ

**note** (v.)

1. **ተገነዘበ**. He noted that her hands were dirty. የእጇን ፡ መቆሸሽ ፡ ተገነዘበ
2. **አስተዋለ**. Note the difference between the two! በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ አስተውል
3. **ተመለከተ**. The groom noted that the horses and mules were fed properly. ባልደራሱ ፡ ፈረሶቹና ፡ በቅሎዎቹ ፡ በሥርዓት ፡ መመገባቸውን ፡ ተመለከተ
4. **ማስታወሻ ፡ አደረገ**. I have noted it on my calendar. በቀን ፡ መቍጠሪያው ፡ ላይ ፡ ማስታወሻ ፡ አድርጌያለሁ

**note down** መዘገበ
The policeman noted down every word I said. ፖሊሱ ፡ የተናገርኩትን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ መዘገበ

**note** (n.)

1. **ማስታወሻ**. See the note below! ከግርጌ ፡ ያለውን ፡ ማስታወሻ ፡ ተመልከት
2. **አጭር ፡ ደብዳቤ**. He sent me a note of thanks. አጭር ፡ የምስጋና ፡ ደብዳቤ ፡ ላከልኝ
3. **ወረቀት**. He cajoled me into signing the note. ደልሎ ፡ ወረቀቱን ፡ አስፈረመኝ
4. **ኖታ**. A skilled musician reads notes without any difficulty. ጥበበኛ ፡ ሙዚቀኛ ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ ኖታ ፡ ሊረዳ ፡ ይችላል
5. **ብር**. I have only five–dollar notes. ያለኝ ፡ ባለ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ ነው
6. **ድምፅ**. There was a note of doubt in her voice. ስትናገር ፡ የጥርጣሬ ፡ ድምፅ ፡ ነበራት
*There was a note of humor in his films. በሠራው ፡ ፊልም ፡ ውስጥ ፡ አነስተኛ ፡ የቀልድ ፡ ስሜት ፡ ነበረበት

**compare notes** ማስታወሻ ፡ አስተያየ
They compared notes about their experiences in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ስላጋጠማቸው ፡ ነገር ፡ ያላቸውን ፡ ማስታወሻ ፡ አስተያዩ

**keep notes on** በማስታወሻ ፡ ያዘ
The student kept notes on the lecture. ተማሪው ፡ ትምህርቱን ፡ በማስታወሻ ፡ ያዘ

**make a note of** በማስታወሻ ፡ ያዘ
Make a note of the time he left! የሄደበትን ፡ ጊዜ ፡ በማስታወሻ ፡ ያዝ

**man of note** የታወቀ ፡ ሰው
A man of note came to our town yesterday. ትናንት ፡ አንድ ፡ የታወቀ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ቀበሌያችን ፡ መጣ

**take no note** ከምንም ፡ አልቈጠረውም
He took no note of what was going on. ይደረግ ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ከምንም ፡ አልቈጠረውም

**take note** ልብ ፡ አደረገ ፤ ልብ ፡ አለ ፤ አስተዋለ
Have you taken note of the fact that he is always late in the morning? ጧት ፡ ጧት ፡ የሚዘገይ ፡ መሆኑን ፡ ልብ ፡ አድርገሃል ? (ልብ ፡ ብለሃል ?)
Take note of what he says. የሚናገረውን ፡ አስተውል

**take notes** ማስታወሻ ፡ ወሰደ
The students were told to take notes of the lecture. ተማሪዎቹ ፡ የመምህሩን ፡ ንግግር ፡ ማስታወሻ ፡ እንዲወስዱ ፡ ተነገሩ

**worthy of note** ደኅና ፡ የሚባል
There are few plays worthy of note this season. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ደኅና ፡ የሚባሉ ፡ ጥቂት ፡ ቲያትሮች ፡ አሉ

**notebook** የማስታወሻ ፡ ደብተር
I bought a notebook in the stationery shop. ከጽሕፈት ፡ መሣሪያ ፡ መደብር ፡ የማስታወሻ ፡ ደብተር ፡ ገዛሁ

**noted** (adj.) የታወቀ
This town is noted for its pottery. ይህ ፡ ከተማ ፡ በሸክላ ፡ እቃዎች ፡ የታወቀ ፡ ነው

**noteworthy** የሚደነቅ
The first flight across the Atlantic was a noteworthy achievement. አትላንቲክን ፡ በማቋረጥ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገው ፡ በረራ ፡ የሚደነቅ ፡ ነገር ፡ ነበር

**nothing**

1. **ምንም** + (negative verb). Can nothing be done? ምንም ፡ ማድረግ ፡ አይቻልም ?
Nothing came of our plans. እቅዳችን ፡ ከምንም ፡ አልደረሰ
The house shows nothing of its former splendor. ቤቱ ፡ ምንም ፡ የድሮው ፡ ውበት ፡ አይታይበትም
2. **ፈጽሞ** + (negative verb). It was nothing like that. ፈጽሞ ፡ እንደዚህ ፡ አልነበረም

**nothing but**
1. ከ - - - በስተቀር ፡ ምንም + (negative verb). They got nothing but bread and water. ከውኃና ፡ ከዳቦ ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ አላገኙም
2. **ብቻ**. For weeks our diet consisted of nothing but fish. ለብዙ ፡ ሳምንቶች ፡ ምግባችን ፡ ዓሣ ፡ ብቻ ፡ ነበር

**nothing doing** አይሆንም
How about lending me your pen? Nothing doing. ብዕርህን ፡ ብታውስኝስ ? አይሆንም

**nothing less than** ብቻ
She was used to nothing less than the best in

life. በሕይወቷ ፡ የለመደችው ፡ ጥሩውን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነበር

**nothing more**
*There is nothing more for me to do here. ከእንግዲህ ፡ እዚህ ፡ የምሠራው ፡ ነገር ፡ የለኝም

**all gone for nothing** መና ፡ ቀረ
"Six months of hard work, all gone for nothing," he cried. « የስድስት ፡ ወር ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ መና ፡ ቀረ »! ብሎ ፡ ጮኸ

**be nothing** ዋጋም ፡ የለው
Money is nothing when you are without health. ጤንነት ፡ ከሌለህ ፡ ገንዘብ ፡ ዋጋም ፡ የለው

**be nothing like**
1. በምንም ፡ አይመስልም. He is nothing like his brother. ወንድሙን ፡ በምንም ፡ አይመስልም
2. ፈጽሞ ፡ አያህልም. His new novel is nothing like his first one. አዲሱ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፉ ፡ ፈጽሞ ፡ የመጀመሪያውን ፡ አያህልም

**for almost nothing** በብላሽ --- ያህል
I got it for almost nothing. በብላሽ ፡ ያገኘሁት ፡ ያህል ፡ ነው

**for nothing**
1. በነጻ. He works for nothing. በነጻ ፡ ይሠራል
2. በከንቱ. It turns out I did all that work for nothing. ያንን ፡ ሁሉ ፡ የሠራሁት ፡ በከንቱ ፡ ነው

**have nothing on**
She has nothing on. ራቁቷን ፡ ናት ፡ (እርቃኗን ፡ ናት)

**have nothing to do with**
1. ምንም ፡ ግንኙነት ፡ የለውም. This had nothing to do with the matter we were discussing. ይህ ፡ ስንወያይ ፡ ከነበርነው ፡ ጉዳይ ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ግንኙነት ፡ የለውም
2. ምንም ፡ ጉዳይ ፡ አልነበረውም. He had nothing to do with him. ከሱ ፡ ምንም ፡ ጉዳይ ፡ አልነበረውም
3. በምንም ፡ ዓይነት ፡ አልገጠመም. I advise you to have nothing to do with that man. ከዚያ ፡ ሰውዬ ፡ ጋር ፡ ከቶ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ እንዳትገጥም ፡ እመክርሀለሁ

**make nothing of**
1. ከምንም ፡ አይቈጥረውም. He makes nothing of his children's disobedience. የልጆቹን ፡ አለመታዘዝ ፡ ከምንም ፡ አይቈጥረውም
2. ምንም ፡ አልገባው. He could make nothing of the complicated directions. የተሰጠው ፡ የተወሳሰበ ፡ መምሪያ ፡ ምንም ፡ አልገባው

**to nothing**
*The sound faded to nothing. ድምፁ ፡ ፈጽሞ ፡ ጠፋ

**to say nothing of**
*He had seven children in his car, to say nothing of two dogs and a rabbit. ስለ ፡ ሁለቱ ፡ ውሾችና ፡ አንድ ፡ ጥንቸል ፡ አናንሣና ፡ መኪናው ፡ ውስጥ ፡ ሰባት ፡ ልጆች ፡ አሳፍሯል
[See also 'else, ever, mean, next, think']

**notice** (v.)
1. አየ. I didn't notice the sign before. ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያንን ፡ ምልክት ፡ አላየሁትም
2. አየ(ለት). Everybody noticed his tie. ሰው ፡ ሁሉ ፡ ክራቫቱን ፡ አየለት
3. ልብ ፡ አለ. She scarcely noticed him. ልብም ፡ አላለችውም
I notice that he left early today. ዛሬ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ መሄዱን ፡ ልብ ፡ ብዬያለሁ
4. ልብ ፡ አደረገ. Did you notice the fear in her voice? መፍራቷን ፡ በድምጿ ፡ ልብ ፡ አደረግህ ?
5. ዐወቀ(ታወቀ). I noticed it right away. ወዲያው ፡ ዐወቅሁት
His good humor was particularly noticed. ተጫዋችነቱ ፡ በተለይ ፡ የታወቀለት ፡ ነው
6. ከቁም ፡ ነገር ፡ ጣፈ. It would be beneath my dignity to notice his insults. የሱን ፡ ስድብ ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ መጣፍ ፡ ክብሬን ፡ ይቀንሳል

**notice** (n.)
1. ማስታወቂያ. Did you read the notice on the bulletin board? በማስታወቂያው ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ ማስታወቂያ ፡ አነበብክ ?
2. ማስጠንቀቂያ. He was fired without notice. ያለ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከሥራ ፡ ተወገደ
3. ትችት. The new movie received good notices. አዲሱ ፡ ፊልም ፡ ጥሩ ፡ ትችት ፡ ተደረገለት

**attract notice** (= pass.) ጐልቶ ፡ ታየ
In a big city, peculiarity attracts less notice than in a small town. የእንግዳነት ፡ ጠባይ ፡ ከትላልቅ ፡ ከተማዎች ፡ ይልቅ ፡ በትናንሽ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ጐልቶ ፡ ይታያል

**come to one's notice** ሰማ ፤ ዐወቀ
It has come to my notice that students are not handing in their homework. ተማሪዎች ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ አለማስረከባቸውን ፡ ሰምቻለሁ ፡ (ዐውቂያለሁ)

**escape one's notice** አላስተዋለም
I don't know how it escaped my notice. እንዴት ፡ እንዳላስተዋልኩት ፡ አላውቅም

**give notice**
1. አስታወቀ. Did you give your landlord notice that you were moving? ቤቱን ፡ የምትለቅ ፡ መሆንህን ፡ ለባለቤቱ ፡ አስታውቀሃል ?

2. ሥራውን ፡ እንደሚለቅ ፡ አስታወቀ. Our maid gave us notice last week. ገረዳችን ፡ ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ሥራውን ፡ እንደምትለቅ ፡ አስታወቀችን
3. አስጠነቀቀ. The driver sounded his horn to give notice that he was going to turn the corner. መጠምዘዣው ፡ ላይ ፡ የሚጠመዘዝ ፡ መሆኑን ፡ ለማስጠንቀቅ ፡ ነጂው ፡ ጥሩንባውን ፡ ነፋ

**pay no notice**
She paid him no notice. ፊት ፡ አልሰጠችውም

**serve notice** አስታወቀ
The boss served notice that smoking is not allowed. አለቅዬው ፡ ማጨስ ፡ ክልክል ፡ መሆኑን ፡ አስታወቀ

**take no notice of** ችላ ፡ አለ
Take no notice of what he says! እሱ ፡ የሚለውን ፡ ችላ ፡ በለው

**take notice of** ልብ ፡ አለ
Take notice of what I say! የምናገረውን ፡ ልብ ፡ በል

**until further notice** ሌላ ፡ ማስታወቂያ ፡ እስከሚሰጥ ፡ ድረስ
This store will be closed until further notice. ሌላ ፡ ማስታወቂያ ፡ እስከሚሰጥ ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ሱቅ ፡ ይዘጋል

**(be) worthy of notice**
His last book is worthy of notice. የመጨረሻው ፡ መጽሐፉ ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጠው ፡ የሚገባ ፡ ነው
[See also 'moment']

## noticeable
1. ልዩ ፡ ዓይነት. There was a noticeable odor as we entered the hospital. ሆስፒታሉ ፡ ውስጥ ፡ ስንገባ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ሽታ ፡ ተሰማን
2. ጉልህ. There was a noticeable difference in his manner when he returned. ከውጭ ፡ አገር ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ በጠባዩ ፡ ላይ ፡ ጉልህ ፡ ለውጥ ፡ ታየ

**be noticeable**
1. ተለይቶ ፡ ታወቀ. Our kitten is very noticeable because its fur is yellow. ጸጉሯ ፡ ብጫ ፡ ስለሆነ ፡ ግልገል ፡ ድመታችን ፡ ተለይታ ፡ ትታወቃለች
2. በግልጽ ፡ ታየ. The prevalence of new methods over the old is noticeable. አዳዲስ ፡ ዘዴዎች ፡ በአሮጌው ፡ ላይ ፡ እያየሉ ፡ መሄዳቸው ፡ በግልጽ ፡ ይታያል

## notify (notified) አስታወቀ
You should have notified me in time. በጊዜው ፡ ልታስታውቀኝ ፡ ይገባህ ፡ ነበር

**be notified** ተነገረ
You will be notified as soon as the director arrives. ዲሬክተሩ ፡ እንደደረሰ ፡ ይነገርሃል

## notion
1. ሐሳብ. He had the mistaken notion that he could fly. አውሮፕላን ፡ እነዳለሁ ፡ የሚል ፡ የተሳሳተ ፡ ሐሳብ ፡ ነበረው
2. አስተያየት. He has foggy notions about the situation. ስለ ፡ ሁኔታው ፡ ድብዝዝ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ አለው
3. አስተሳሰብ. He has a preposterous notion about politics. ስለ ፡ ፖለቲካ ፡ ያለው ፡ አስተሳሰብ ፡ የማይረባ ፡ ነው
4. ምኞት. She had a notion to buy a new hat. አዲስ ፡ ባርኔጣ ፡ ለመግዛት ፡ ምኞት ፡ ነበራት
5. ከንቱ ፡ ሐሳብ. That silly girl has too many notions. ያች ፡ ሞኝ ፡ ልጃገረድ ፡ ብዙ ፡ ከንቱ ፡ ሐሳብ ፡ አላት

**notions** [መርፌ ፤ መርፌ ፡ ቁልፍ ፤ ክርና ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ አነስተኛ ፡ ሸቀጣ ፡ ሸቀጦች ፡ የሚሸጡበት ፡ ተራ]

**have a notion of** ገባ(ው) ፤ ዐወቀ
+Do you have any notion of what he meant? ምን ፡ ለማለት ፡ እንደፈለገ ፡ ገብቶሃል ?
I have no notion of what he means. ምን ፡ ማለቱ ፡ እንደሆነ ፡ በፍጹም ፡ አላውቅም

## notorious
1. የታወቀ. This metal is notorious for its resistance to rust. ይህ ፡ ብረት ፡ የማይዝግ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው
2. የወጣለት. He is a notorious liar, and no one believes him any more. የወጣለት ፡ ውሸታም ፡ ስለሆነ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አያምነውም
3. አገር ፡ ያሰለቸ. He is a notorious criminal. አገር ፡ ያሰለቸ ፡ ወንጀለኛ ፡ ነው

**make someone notorious** ክፉ ፡ ስም ፡ አተረፈ(ለት)
Laval's perfidy made him notorious. የላቫል ፡ ሸፍጥ ፡ ክፉ ፡ ስም ፡ አተረፈለት

## notwithstanding
1. ቢሆንም. It is raining, but I shall go notwithstanding. ይዘንባል ፤ ቢሆንም ፡ እሄዳለሁ
His deformity notwithstanding, he became a famous scientist. አካለ ፡ ጐደሎ ፡ ቢሆንም ፡ የታወቀ ፡ ሳይንቲስት ፡ ሆነ
2. ቢኖርም ፡ እንኳ. He drove on, notwithstanding the storm. ዓወሎ ፡ ነፋስ ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ መንዳቱን ፡ ቀጠለ

## nought, see naught

## noun ስም
Do nouns occur in the a plural? ስሞች ፡ የብዙ ፡ ቁጥር ፡ አላቸው ?
[See also 'common noun, proper noun']

**nourish**

1. መገበ. She nourished him and cared for him while he has ill. በታመመ ፡ ጊዜ ፡ በደንብ ፡ እየመገበች ፡ አስታመመችው

2. አፋፋ. Milk nourishes babies. ወተት ፡ ሕፃናትን ፡ ያፋፋል

Water and sunlight nourish plants. ውኃና ፡ የፀሐይ ፡ ሙቀት ፡ ዕፀዋትን ፡ ያፋፋሉ

**nourish the dream** አሰበ

He had long nourished the dream of living abroad. ውጭ ፡ አገር ፡ ለመኖር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያስብ ፡ ነበር

**nourish the hope** ተስፋ ፡ አደረገ

He nourished the hope that he would be promoted. እድገት ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ አደረገ

**(be) nourishing** መጋቢነት ፡ አለው

This food fills one's stomach, but is not nourishing. ይህ ፡ ምግብ ፡ ሆድ ፡ ይሞላል ፡ እንጂ ፡ መጋቢነት ፡ የለውም

**nourishment** ምግብ

He hasn't taken any nourishment in days. ለብዙ ፡ ቀናት ፡ ምንም ፡ ምግብ ፡ አልበላም

**novel** (n.) ልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፍ ፤ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ

Do you know of a good novel? ጥሩ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፍ ፡ (ታሪክ) ፡ ታውቃለህ ?

**novel** (adj.) አዲስ

That's rather a novel idea. ይህ ፡ አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ይመስላል

**novelist** የልብ ፡ ወለድ ፡ ደራሲ

The number of novelists is increasing in our country. የልብ ፡ ወለድ ፡ ደራሲያን ፡ ቁጥር ፡ በሀገራችን ፡ እየጨመረ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ነው

**novelty** (novelties)

1. አዲስ ፡ ነገር. The plane trip was a novelty for him. በአውሮፕላን ፡ መጓዝ ፡ ለሱ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ነበር

2. ወረት. The novelty will soon wear off. ወረቱ ፡ ቶሎ ፡ ያልፋል

**November** ኅዳር

November is a cold month. ኅዳር ፡ ብርዳማ ፡ ወር ፡ ነው

**novice** ጀማሪ

Novices are likely to make some mistakes. ጀማሪዎች ፡ ስሕተት ፡ መሥራታቸው ፡ የማይቀር ፡ ነው

**now**

1. አሁን. I have to leave now. አሁን ፡ መሄድ ፡ አለብኝ

Either do it now or not at all! አሁን ፡ ሥራው ፡ ወይም ፡ ተወው

Now that you mention it, I do remember. አሁን ፡ ብትጠቅሰው ፡ አስታወስኩት

2. ባሁኑ ፡ ወቅት. Most science books written twenty years ago are now antiquated. ከሀያ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የተጻፉት ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የሳይንስ ፡ መጻሕፍት ፡ ባሁኑ ፡ ወቅት ፡ ጊዜ ፡ ያለፈባቸው ፡ ናቸው

3. እንግዲህ. Now we'll never know what happened. እንግዲህ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ማወቅ ፡ አንችልም

We have finished this assignment; what shall we do now? ይህን ፡ ሥራ ፡ ጨርሰናል ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ እንሥራ ?

We missed the last bus, so now we must spend the night here. የመጨረሻው ፡ አውቶቡስ ፡ አመለጠን ፤ እንግዲህ ፡ እዚህ ፡ እንደር

*Now where could it be? የት ፡ ደርሶ ፡ ይሆን ?

*Now stop quarreling and listen! ጠቡን ፡ አቁሙና ፡ አዳምጡ

**now and again** አልፎ ፡ አልፎ

I write to him now and again. አልፎ ፡ አልፎ ፡ እጽፍለታለሁ

**now and then** አልፎ ፡ አልፎ

We go to the movies now and then. ወደ ፡ ሲኒማ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ እንሄዳለን

**now ... now** አንዳንዴም ... አንዳንዴም

They continued to argue, now in shouts, now in whispers. አንዳንዴ ፡ በመጮኽ ፤ አንዳንዴ ፡ በሹክሹክታ ፡ ሲጨቃጨቁ ፡ ቆዩ

**now that**

*Now that he is rich, he is constantly besieged by appeals for aid. ሀብታም ፡ ስለሆነ ፡ እርዳታ ፡ ጠያቂ ፡ በዛበት

**now then**

1. ታዲያ. Now then, what do you mean by that? ታዲያ ፤ ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ?

2. እንዴ ፤ እስቲ ፡ በል. Now then, what are you doing in my garden? እንዴ ፤ (እስቲ ፡ በል) ፤ የአትክልት ፡ ቦታዬ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ትሠራለህ ?

**by now** እስካሁን

He really ought to be here by now. እስካሁን ፡ እዚህ ፡ መድረስ ፡ ነበረበት

**even now** አሁንም

Even now many people believe in the evil eye. አሁንም ፡ በቡዳ ፡ የሚያምኑ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አሉ

**from now on** ከሁን ፡ ጀምሮ
From now on I'll be more careful. ከሁን ፡ ጀምሮ ፡ በጣም ፡ እጠነቀቃለሁ
**just now** አሁን ፡ ገና ፤ ገና ፡ አሁን
We just now received a report from him. አሁን ፡ ገና ፡ ከሱ ፡ ዘንድ ፡ መግለጫ ፡ ደረሰን
I talked to him just now. ገና ፡ አሁን ፡ አነጋገርኩት
[See also 'every, here, right, up, week']

**nowadays** በዛሬ ፡ ጊዜ ፤ ባሁን ፡ ጊዜ
Nowadays, young people do not respect their elders. በዛሬ ፡ ጊዜ ፡ (ባሁን ፡ ጊዜ) ፡ ወጣቶች ፡ ታላላቆቻቸውን ፡ አያከብሩም

**nowhere** የትም ፤ የትም ፡ ቦታ
The money was nowhere to be found. ገንዘቡ ፡ የትም ፡ (የትም ፡ ቦታ) ፡ ሊገኝ ፡ አልተቻለም
**from nowhere** ከየት ፡ መሆኑ ፡ ሳይታወቅ
A gang of thieves appeared from nowhere. ከየት ፡ መሆኑ ፡ ሳይታወቅ ፡ የሌባ ፡ ጓድ ፡ መጣ
[See also 'near']

**noxious**
1. ጤና ፡ የሚጎዳ. Noxious fumes filled the automobile. ጤና ፡ የሚጎዳ ፡ ጪስ ፡ መኪናውን ፡ ሞላው
2. መርዝ. This plant is noxious. ይህ ፡ ዕፅ ፡ መርዝ ፡ ነው

**nozzle** የቱቦ ፡ ጫፍ
He adjusted the nozzle so that the water came out in a fine spray. ውኃው ፡ በቀጭኑ ፡ እንዲረጭ ፡ የቱቦውን ፡ ጫፍ ፡ አስተካከለው

**nucleus**
1. ቆርቋሪ. A few faithful friends formed the nucleus of the club. ጥቂት ፡ የሚታመኑ ፡ ጓደኞች ፡ የክበቡ ፡ ቆርቋሪዎች ፡ ሆኑ
2. መነሻ. The few books which he gave as a present became the nucleus of a large library. ያበረከታቸው ፡ ጥቂት ፡ መጻሕፍት ፡ ለትልቅ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መነሻ ፡ ሆኑ

**nude** (n.) ራቁት + suffix pronouns
He swam in the nude ራቁቱን ፡ ይዋኝ ፡ ነበር
**nude** (adj.) እርቃን + suffix pronouns
They found a nude baby near the church. ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ እርቃኑን ፡ አገኙ

**nudge** (v.) ጐነተለ
I nudged him to wake him up. እንዲነቃ ፡ ጐነተልኩት

**nudge** (n.), **give a ~** ጐንተል ፡ አደረገ
He gave me a nudge when the girl passed by. ልጃገረዲቷ ፡ ስታልፍ ፡ ጐንተል ፡ አደረገኝ

**nudity** ራቁት ፡ መሆድ
Nudity is common in some hot countries. ባንዳንድ ፡ ሞቃት ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ራቁት ፡ መሄድ ፡ የተለመደ ፡ ነው

**nuisance**
1. ጣጣ. I have to go through the nuisance of registering again. እንደገና ፡ የመመዝገቡን ፡ ጣጣ ፡ መፈጸም ፡ አለብኝ
2. ጠንቅ. Cars splashing water on a rainy day are a nuisance to the pedestrians. በዝናም ፡ ቀን ፡ መኪና ፡ የሚረጨው ፡ ውኃ ፡ ለእግረኞች ፡ ጠንቅ ፡ ነው
**be a nuisance** አስቸገረ
The flies are a real nuisance this summer. በዚህ ፡ በጋ ፡ ዝምቡ ፡ በጣም ፡ ያስቸግራል

**(be) null** ዋጋ ፡ የለውም
A promise obtained by force is legally null. በማስገደድ ፡ የተገባ ፡ ቃል ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ የለውም
**be null and void** ዋጋ ፡ የለውም ፤ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ነው ፤ ፍርስና ፡ ውድቅ ፡ ነው
This passport is null and void. ይህ ፡ ፓስፖርት ፡ ዋጋ ፡ የለውም
The contract is null and void. ውሉ ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ (ፍርስና ፡ ውድቅ) ፡ ነው

**nullify** (nullified)
1. ሻረ. The governor tried to nullify the tax law. ገዢው ፡ የቀረጡን ፡ ሕግ ፡ ሊሽር ፡ ሞከረ
2. ዋጋም ፡ የለው. +The costs of the project were so great that they nullified its benefits. እቅዱ ፡ የሚፈጀው ፡ ገንዘብ ፡ ብዙ ፡ ስለሆነ ፡ ከሱ ፡ የሚገኘው ፡ ጥቅም ፡ ዋጋም ፡ የለው

**numb** የደነዘዘ
He rubbed his numb fingers to make them warm. የደነዘዙትን ፡ ጣቶቹን ፡ ለማሞቅ ፡ አሻሻቸው
**be numb** ደነዘዘ
My foot is numb; I must have hurt the nerve. እግሬ ፡ ደንዝዟል ፤ ጅማቴ ፡ ሳይነካ ፡ አይቀርም
My fingers are numb with cold. ጣቶቼ ፡ በብርድ ፡ ደንዝዘዋል
She was numb with grief. በሐዘን ፡ ደንዝዛ ፡ ነበር

**number** (vt.) ቁጥር ፡ ሰጠ
Let's number them from one to ten! ከአንድ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ቁጥር ፡ እንስጣቸው

*I numbered the people in the group at twenty. የተሰበሰበው ፡ ሰው ፡ ብዛት ፡ ሀያ ፡ የ ሚሆን ፡ ይመስለኛል

**number** (vi.)
*My books number about eighty. የመጻሕፍቴ ፡ ቁጥር ፡ እስከ ፡ ሰማንያ ፡ ይደርሳል

**be numbered**
1. ቁጥር ፡ ተጻፈበት. The seats aren't numbered. መቀመጫዎቹ ፡ ቁጥር ፡ አልተጻፈባቸውም
2. ከ - - - አንዱ. He is numbered among our friends. ከጓደኞቻችን ፡ አንዱ ፡ ነው
*His days are numbered. ቀኑ ፡ ደርሷል

**number oneself among** ከ - - - መካከል ፡ ነው
I number myself among his friends. እኔ ፡ ከጓደ ኞቹ ፡ መካከል ፡ ነኝ

## number (n.)
1. ቁጥር. Did you write down the number? ቁጥሩን ፡ ጻፍከው ?
The word 'we' shows plural number. « እኛ » ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የብዙ ፡ ቁጥርን ፡ ያመለክታል
2. ብዛት. The number of sinners is legion. የኀጢአተኞች ፡ ብዛት ፡ ቁጥር ፡ ስፍር ፡ የለውም
3. እትም. Do you have the current number of this magazine? የዚህ ፡ መጽሔት ፡ ያሁኑ ፡ እት ም ፡ አለህ ?
4. ክፍል. The program consisted of four musical numbers. ፕሮግራሙ ፡ አራት ፡ የሙዚቃ ፡ ክፍሎች ፡ ነበሩት

**numbers** ብዙ ፡ ሰዎች
Numbers were turned away. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተመለሱ

**a large number of** ብዙ
They entertained a large number of guests last night. ትናንትና ፡ ማታ ፡ ብዙ ፡ እንግዶች ፡ አስተናገዱ

**a number of** በርከት ፡ ያሉ
A number of men have been detached from my regiment to guard the railroad station. ከኔ ፡ ጦር ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ባቡር ፡ ጣቢ ያውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ተወስደዋል

**beyond number** ቁጥር ፡ ስፍር ፡ የሌላቸው
Stars beyond number appeared. ቁጥር ፡ ስፍር ፡ የሌላቸው ፡ ከዋክብት ፡ ወጡ

**in large numbers** በብዛት
People came to the fair in large numbers. ሕዝቡ ፡ በብዛት ፡ ወደ ፡ ኤግዚብሽኑ ፡ መጣ

**large numbers** ብዙ ፡ ሰዎች
Large numbers were turned away. ብዙ ፡ ሰዎ ች ፡ እንዲመለሱ ፡ ተደረገ

**quite a number of** በርከት ፡ ያሉ
Quite a number of people have come. በርከት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ መጥተዋል

## numberless ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌለው
There are numberless fish in the sea. ባሕር ፡ ው ስጥ ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌለው ፡ ዓሣ ፡ አለ

## numeral ቁጥር
The numeral "5" was written on it. አምስት ፡ ቁጥር ፡ ተጽፎበታል

## numerical የቁጥር
I cannot understand these numerical symbols. እነዚህን ፡ የቁጥር ፡ ምልክቶች ፡ መረዳት ፡ አልችልም

**numerical order** የተራ ፡ ቁጥር
He arranged them in numerical order. በተራ ፡ ቁጥር ፡ ደረደራቸው

## numerous ብዙ
His friends are numerous. ጓደኞቹ ፡ ብዙ ፡ ና ቸው

## numismatics [የታሪካዊ ፡ ገንዘቦች ፡ ጥናት]

## nun መነኩሲት
A nun lives near the church. ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አቅራቢያ ፡ አንዲት ፡ መነኩሲት ፡ ይኖራሉ

## nuptial(s) ሰርግ
Their nuptials were announced in the newspapers. ሰርጋቸው ፡ በጋዜጦች ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ ነበር

**nuptial** (adj.) የሰርግ
Their nuptial day will be in June. የሰርጉ ፡ ቀ ን ፡ በሰኔ ፡ ውስጥ ፡ ይሆናል

**nuptial feast** ሰርግ
The nuptial feast was attended by all the family. ቤተ ፡ ሰቡ ፡ በሙሉ ፡ የሰርጉ ፡ ተካፋይ ፡ ነበር

## nurse (v.)
1. አስታመመ. She nursed him back to health. ጨርሶ ፡ እስኪድን ፡ አስታመመችው
2. አጠባ. Does she nurse the baby herself? ሕፃኑን ፡ ታጠባዋለች ?
3. መድኃኒት ፡ አደረገ. You must nurse your cold or it will become worse. ለጉንፋንህ ፡ መድኃኒ ት ፡ ማድረግ ፡ አለብህ ፤ ያለዚያ ፡ ይብስብሃል
4. ያዘ(በት). He nursed a grudge against his boss. በአለቃው ፡ ላይ ፡ ቂም ፡ ይዞበታል

## nurse (n.)
1. ነርስ ፤ አስታማሚ. Some hospitals graduate many nurses every year. አንዳንድ ፡ ሆስፒታሎ ች ፡ በያመቱ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ነርሶች ፡ ያስመርቃሉ

He hired a nurse to take care of his invalid
mother. አካለ ፣ ስንኩል ፣ እናቱን ፣ እንድታስታም
ም ፣ አንድ ፣ አስታማሚ ፣ (ነርስ) ፣ ቀጠረላት
2. ሞግዚት. The children are out in the park
with the nurse. ልጆቹ ፣ ከሞግዚቷ ፣ ጋር ፣ በመ
ናፈሻው ፣ ቦታ ፣ ናቸው

**nursemaid** ሞግዚት
The nursemaid is taking care of the children.
ሞግዚቷ ፣ ልጆቹን ፣ ትጠብቃለች

**nursery** (nurseries)
1. የሕፃናት ፣ ማሳደጊያ. There is a nursery
attached to the school. ከትምህርት ፣ ቤቱ ፣ ጋ
ር ፣ የተያያዘ ፣ የሕፃናት ፣ ማሳደጊያ ፣ አለ
2. የችግኝ ፣ መሸጫ ፣ ቦታ. I bought these plants
at a nursery. እነዚህን ፣ አትክልቶች ፣ ከችግኝ ፣ መ
ሸጫው ፣ ቦታ ፣ ገዛሁ

**nursing mother** እመጫት
Nursing mothers need to eat good food.
እመጫቶች ፣ ጥሩ ፣ ምግብ ፣ መብላት ፣ አለባቸው

**nurture** አሳደገ
She nurtured the child as if he had been her
own. ሕፃኑን ፣ እንደራሷ ፣ ልጅ ፣ አድርጋ ፣ አሳ
ደገችው

**nut**
1. ለውዝ. He likes to put nuts in candy and
cakes. በከረሜላና ፣ በብስኩት ፣ ውስጥ ፣ ለውዝ ፣ መ
ጨመር ፣ ይወዳል
2. ቡሎን. This nut does not fit the bolt.
ቡሎኑ ፣ በመያዣው ፣ ውስጥ ፣ አይገባም

**nutrition** ያመጋገብ ፣ ዘዴ
The care and nutrition of children is an
important matter. የልጆች ፣ አያያዝና ፣ ያመጋገ
ብ ፣ ዘዴ ፣ በጣም ፣ አስፈላጊ ፣ ነው

**nutritious** መጋቢነት ፣ ያለው
A nutritious diet is important for health.
መጋቢነት ፣ ያለው ፣ ምግብ ፣ ለጤንነት ፣ አስፈ
ላጊ ፣ ነው

## O

**oak** [የዛፍ ፡ ዓይነት]

**oar** መቅዘፊያ
He broke the oar while rowing the boat. ጀልባውን ፡ ሲቀዝፍ ፡ መቅዘፊያውን ፡ ሰበረው

**oasis** የበረኻ ፡ ገነት
There are many palm trees in the oasis. እበረኻ ፡ ገነት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ዘምባባ ፡ አለ

**oat(s)** አጃ
They put oats in the manger. ግርግም ፡ ውስጥ ፡ አጃ ፡ አስቀመጡ

**oath** መሐላ
He took an oath to tell the truth. እውነቱን ፡ ለ
መናገር ፡ መሐላ ፡ ገባ

**be under oath** መሐላ ፡ ገባ
You are under oath when you testify in court. ፍርድ ፡ ቤት ፡ የምስክርነት ፡ ቃልህን ፡ ስትሰጥ ፡ መሐላ ፡ ገብተህ ፡ ነው

**take an oath** ማለ
He took an oath in court to tell the truth. እውነቱን ፡ እናገራለሁ ፡ ብሎ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ማለ

**utter an oath** እግዜርን ፡ አማረረ
He uttered an oath when he dropped a rock on his foot. እግሩ ፡ ላይ ፡ ድንጋይ ፡ ሲወድ
ቅ ፡ እግዜርን ፡ አማረረ
[See also 'allegiance']

**obdurate** ጋግርታም
The obdurate child would not answer. ጋግርታ
ሙ ፡ ልጅ ፡ መልስ ፡ አልሰጥ ፡ አለ

**obedience**
1. ታዛዥነት. Obedience is required in school. በትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ታዛዥነት ፡ ያስፈልጋል
2. መታዘዝ. The law requires obedience. ሕጉ ፡ መታዘዝን ፡ ይጠይቃል

**compel obedience** ትእዛዝ ፡ አስከበረ
The teacher compelled obedience by the threat of punishment. መምህሩ ፡ በቅጣት ፡ በማስ
ፈራራት ፡ ትእዛዝ ፡ አስከበረ

**obedient** ታዛዥ
Your child is not very obedient. ልጅህ ፡ ታዛ
ዥ ፡ አይደለም
The letter was signed, "Your obedient servant". ደብዳቤው ፡ ታዛዥ ፡ አገልጋይዎ ፡ ተብሎ ፡ ተ
ፈርሞበታል

**obelisk** ሐውልት
There are still obelisks in Axum. ዛሬም ፡ አክሱ
ም ፡ ውስጥ ፡ ሐውልቶች ፡ አሉ

**obese** ወፍራም
An obese child cannot wear ordinary clothes. ወፍራም ፡ ልጅ ፡ በልኩ ፡ ያልተሰፋ ፡ ልብስ ፡ ሊለ
ብስ ፡ አይችልም

**obesity**
*His gluttony is responsible for his obesity. ከሆዳምነቱ ፡ የተነሣ ፡ ቦርጫም ፡ ሆነ

**obey**
1· ታዘዘ. The lazy child doesn't obey his mother. ሰነፉ ፡ ልጅ ፡ ለእናቱ ፡ አይታዘዝም
2. ተቀበለ. I can't obey that order. ይህን ፡ ትእ
ዛዝ ፡ ልቀበል ፡ አልችልም
3. አከበረ. Obeying the law and paying taxes are civic duties. ሕግን ፡ ማክበርና ፡ ግብር ፡ መ
ክፈል ፡ ሕዝባዊ ፡ ግዴታዎች ፡ ናቸው
*A horse obeys the reins. ፈረስ ፡ በልጓሙ ፡ ይገ
ታል

**obituary** (obituaries) ዜና ፡ ዕረፍት
I read his obituary in the newspaper. ዜና ፡ ዕ
ረፍቱን ፡ ከጋዜጣ ፡ አነበብኩ

**object** (v.) ተቃወመ
Mother objected that the weather was too cold to play outdoors. አየሩ ፡ በጣም ፡ ቀዝቃዛ ፡ ስለ
ሆነ ፡ ደጅ ፡ መጫወት ፡ አይገባም ፡ ስትል ፡ እማ
ማ ፡ ተቃወመች

**object to** ተቃወመ
I hope you don't object to my smoking. ሲጃራ ፡ ማጨሴን ፡ እንደማትቃወም ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ

**object** (n.)
1. እቃ. Tell me the Amharic names of all the objects in this room. በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ያ
ሉትን ፡ እቃዎች ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ ባማርኛ ፡ ንገረኝ
2. ነገር. He was struck on the head with a heavy object. ራሱ ፡ በከባድ ፡ ነገር ፡ ተመቶ ፡ ነበር

3. ዓላማ. What's the object of your trip? የጉዞህ ፡ ዓላማ ፡ ምንድነው ?
4. ተሳቢ. The object in this sentence is expressed by a pronoun. የዚህ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ተሳቢ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ነው

**direct object** ርቱዕ ፡ ተሳቢ
The direct object in this sentence is expressed by a noun. የዚህ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ርቱዕ ፡ ተሳቢ ፡ ስም ፡ ነው

**indirect object** ኢርቱዕ ፡ ተሳቢ
This sentence has no indirect object. ይህ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ኢርቱዕ ፡ ተሳቢ ፡ የለውም

**objection** ተቃውሞ
He raised no objection when I told him what I was going to do. የማደርገውን ፡ በነገርኩት ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ ተቃውሞ ፡ አላቀረበም

**have objection** ተቃወመ
Do you have any objection? የምትቃወመው ፡ ነገር ፡ አለህ ?

**raise an objection** ተቃወመ
At this point, one of the members stood up and raised an objection. በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከአባሎቹ ፡ አንዱ ፡ ተነሥቶ ፡ ተቃወመ

**objectionable** የማይገባ
The censor removed the objectionable passages of the book. ሳንሱሩ ፡ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የማይገቡ ፡ ምንባቦች ፡ አወጣ
He uses objectionable language. የማይገባ ፡ አነጋገር ፡ ይናገራል
[See also 'smell']

**objective** (n.) ዓላማ
All our objectives were attained. ዓላማችንን ፡ ሁሉ ፡ ግብ ፡ አድርሰናል

**objective** (adj.)
1. የሚዳሰስና ፡ የሚታይ. Spirits have no objective existence. መናፍስት ፡ የማይዳሰሱና ፡ የማይታዩ ፡ ናቸው
2. ያልተዛባ. The policeman gave an objective report of the accident. ፖሊስ ፡ ስለደረሰው ፡ ግጭት ፡ ያልተዛባ ፡ መግለጫ ፡ አቀረበ

**be objective**
*I'll try to be as objective as possible in considering the conflict between the two people. በሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግጭት ፡ በተቻለኝ ፡ መጠን ፡ አንዳችም ፡ አድልዎ ፡ ሳላደርግ ፡ አመዛዝነዋለሁ

**objectively** በማመዛዘን
Now let's look at the problem objectively! አሁን ፡ ፕሮብሌሙን ፡ በማመዛዘን ፡ እንመልከት

**oblation** ቁርባን
I take the children to church for the oblation. ሕፃናቱን ፡ ለቁርባን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እወስዳቸዋለሁ

**obligate** አስገደደ
Accepting money from him obligates you to do him favors. ከሱ ፡ ገንዘብ ፡ መቀበልህ ፡ ባለውለታው ፡ አድርጎህ ፡ ዐጸፋውን ፡ እንድትመልስለት ፡ ያስገድድሃል

**be obligated** ግዴታ ፡ ገባ
He is obligated to spend a year teaching in the provinces. ላንድ ፡ ዓመት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ እንዲያስተምር ፡ ግዴታ ፡ ገብቷል

**be obligated to** ባለውለታው ፡ ነው
I am obligated to you for your help. ስለረዳኸኝ ፡ ባለውለታዬ ፡ ነህ

**obligation** ግዴታ
One must fulfill the obligations of citizenship. ማንም ፡ ሰው ፡ የዜግነቱን ፡ ግዴታ ፡ መፈጸም ፡ አለበት
A wife's first obligation is to her husband and children. ሚስት ፡ የመጀመሪያ ፡ ግዴታዋ ፡ ለባሏና ፡ ለልጆቿ ፡ ነው

**be under obligation to** ባለውለታው ፡ ነው
I am under obligation to him because of the many favors he has done me. ብዙ ፡ ነገር ፡ ስላደረገልኝ ፡ ባለውለታዬ ፡ ነው

**be under obligation** ግዴታ ፡ አለበት
The one who did the damage is under obligation to pay for it. ጉዳቱን ፡ ያደረሰው ፡ ሰው ፡ የመክፈል ፡ ግዴታ ፡ አለበት

**feel an obligation** ባለውለታ ፡ ነው
I feel an obligation to those who help me. ለሚረዱኝ ፡ ባለውለታ ፡ ነኝ

**meet one's obligation** የሚፈለግበትን ፡ ፈጸመ ፤ ግዳጅ ፡ ፈጸመ
He can't meet his obligations due to illness. በጤንነት ፡ ጉድለት ፡ ምክንያት ፡ የሚፈለግበትን ፡ (ግዳጁን) ፡ ሊፈጽም ፡ አይችልም

**obligatory** ግዴታ
Is attendance at school obligatory in this country? እዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መግባት ፡ ግዴታ ፡ ነው ?

**oblige**
1. አስገደደ. The law obliges parents to send their children to school. ሕጉ ፡ ወላጆች ፡ ልጆቻቸውን ፡ እንዲያስተምሩ ፡ ያስገድዳል
2. ታዘዘ. I am always glad to oblige you. ልታዘዝህ ፡ ምንጊዜም ፡ ፈቃደኛ ፡ ነኝ

*Mr. Jones will oblige us with a song. ሚስተር ፡ ጆንስ ፡ መልካም ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ ይዘፍንልናል
*Kindly oblige me by closing the door. በሩን ፡ ብትዘጋልኝ

**be much obliged** ባለውለታው ፡ ነው
I am much obliged for the ride. ስላደረስከኝ ፡ ባለውለታህ ፡ ነኝ

**be obliged** ግድ ፡ ሆነበት
He was obliged to walk on foot because he had no car. መኪና ፡ ስላልነበረው ፡ በእግር ፡ መሄድ ፡ ግድ ፡ ሆነበት

**be obliged to**
I'm much obliged to you. ብዙ ፡ ውለታ ፡ ውለሀልኛል

## (be) obliging ሰው ፡ ረዳ
He is always obliging. ሁልጊዜ ፡ ሰው ፡ እንደረዳ ፡ ነው

## oblique ገዳዳ
An oblique angle is any angle other than a right angle. ገዳዳ ፡ ማእዘን ፡ ማለት ፡ ትክክለኛ ፡ ማእዘን ፡ ያልሆነ ፡ አንዱ ፡ ነው

**give an oblique glance** የጐረጥ ፡ አየ
He gave me an oblique glance as I passed by. ሳልፍ ፡ የጐረጥ ፡ አየኝ

## obliterate
1. አጠፋ. The flood obliterated all trace of the boundaries. ጐርፉ ፡ የድንበሩን ፡ ምልክት ፡ ሁሉ ፡ አጠፋው
2. ጋረደ. A cloud obliterated the sun. ደመና ፡ ፀሐይዋን ፡ ጋረዳት

**be obliterated** ተደመሰሰ
The writing was obliterated by ink. ጽሕፈቱ ፡ በቀለም ፡ ተደምስሷል

## oblivion, fall into ~ ተረሳ
The memory of many great men has fallen into oblivion. የብዙ ፡ ትልልቅ ፡ ሰዎች ፡ ትዝታ ፡ ተረስቷል

**in complete oblivion** በተመስጦ
Grandfather sat by the fire in complete oblivion. ወንድ ፡ አያቴ ፡ በተመስጦ ፡ እሳቱ ፡ ዳር ፡ ተቀመጠ

## (be) oblivious
1.ረሳ. The book was so interesting that I was oblivious of my surroundings. መጽሐፉ ፡ በጣም ፡ አስደሳች ፡ ስለነበረ ፡ በዙሪያዬ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ረስቼ ፡ ነበር
2. ግዴለውም. He is oblivious to any danger. ስለ ፡ አደጋ ፡ ግዴለውም

## oblong ሞላላ
The shoes were in an oblong box. ጫማዎቹ ፡ ሞላላ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ

## obnoxious አስጠሊ
He is a very obnoxious person. በጣም ፡ አስጠሊ ፡ ሰው ፡ ነው

## obscene ጸያፍ
He uses obscene language. አነጋገሩ ፡ ጸያፍ ፡ ነው (or አፉ ፡ ያልታረመ ፡ ነው)

## obscure (v.) ጋረደ
Clouds obscure the sun. ደመናው ፡ ፀሐይዋን ፡ ይጋርዳል
*His arguments obscured the issue. የሱ ፡ ክርክር ፡ ጭብጡን ፡ አጠፋው

## obscure (adj.)
1. የማይታይ. The cat hid in an obscure corner of the room. ድመቷ ፡ ካንድ ፡ ከማይታይ ፡ ሥርቻ ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ ተደበቀች
2. ያልታወቀ. I am reading the poems of an obscure English poet. ያንድ ፡ ያልታወቀ ፡ የእንግሊዝ ፡ ገጣሚ ፡ ግጥም ፡ አነባለሁ
3. ግልጽ ፡ ያልሆነ. The obscure sound is made by termites which have burrowed into the wall. ግልጽ ፡ ያልሆነው ፡ ድምፅ ፡ ግድግዳውን ፡ ቈፍረው ፡ ከገቡት ፡ ምስጦች ፡ የሚመጣ ፡ ነው
4. ደብዛዛ. I noticed an obscure figure in the fog. ጭጋጉ ፡ ውስጥ ፡ ደብዛዛ ፡ ቅርጽ ፡ ታየኝ
5. ከቁጥር ፡ የማይገባ. He has an obscure position in a large company. በትልቅ ፡ ኩባንያ ፡ ውስጥ ፡ ከቁጥር ፡ የማይገባ ፡ ሥልጣን ፡ አለው
6. ለመረዳት ፡ የሚያስቸግር. I explained to him the obscure points of the contract. ከውለታው ፡ ውስጥ ፡ ለመረዳት ፡ የሚያስቸግሩትን ፡ አንቀጾች ፡ አስረዳሁት

**be obscure** ግልጽ ፡ አይደለም
The meaning of your words is obscure. Would you, please, clarify them for me? የተጠቀምክባቸው ፡ ቃላት ፡ ፍች ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ፤ ልታብራራው ፡ ትችላለህ ?

## obscurity
1. ጨለማ. The obscurity of the hall prevented me from finding the room. መተላለፊያው ፡ ጨለማ ፡ ስለሆነ ፡ ክፍሉን ፡ ላገኘው ፡ አልቻልኩም
2. ግልጽ ፡ አለመሆን. The obscurity of the paragraph makes several interpretations possible. የአንቀጹ ፡ ግልጽ ፡ አለመሆን ፡ ብዙ ፡ ትርጉም ፡ ሊያሰጥ ፡ ይችላል

**hide in the obscurity** ገብቶ ፡ ተደበቀ
The dog hid in the obscurity of the thick

bushes. ውሻው ፡ ጥቅጥቅ ፡ ካለው ፡ ቁጥቋጦ ፡
ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ተደበቀ

**pass into obscurity** ተረሳ
Many once famous names have now passed into obscurity. ድሮ ፡ ገናና ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡
አሁን ፡ ተረስተዋል

**rise from obscurity** ከትቢያ ፡ ተነሣ
Lincoln rose from obscurity to fame. ሊንኮል
ን ፡ ከትቢያ ፡ ተነሥቶ ፡ ዝናን ፡ አተረፈ

**obsequious** አድር ፡ ባይ
Obsequious courtiers greeted the king. አድር ፡
ባይ ፡ ባለሟሎች ፡ ንጉሡን ፡ እጅ ፡ ነሡ

**observance** የሚከበር ፡ በዓል
Epiphany and Easter are annual observances.
ጥምቀትና ፡ ፋሲካ ፡ ባመት ፡ አንዴ ፡ የሚከበሩ ፡
በዓላት ፡ ናቸው
*The observance of Independence Day was marked by parades. የነጻነት ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ በ
ሰልፍ ፡ ተከበረ
*The observance of the law is required by all citizens. የሀገሪቱ ፡ ነዋሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ሕግን ፡ እ
ንዲያከብሩ ፡ ይገደዳሉ

**religious observance** የሃይማኖት ፡ በዓል
There are few yearlong religious observances.
ከዓመት ፡ ዓመት ፡ የሚቆዩ ፡ ጥቂት ፡ የሃይማኖ
ት ፡ በዓላት ፡ አሉ

**observant** አስተዋይ
The child is very observant. ልጁ ፡ በጣም ፡
አስተዋይ ፡ ነው

**observant of** አክባሪ
He is observant of all religious prescriptions.
የሃይማኖት ፡ ሕጎችን ፡ ሁሉ ፡ አክባሪ ፡ ነው

**observation**
1. አስተያየት. He published his observations on the book recently. ስለ ፡ መጽሐፉ ፡ ያለውን ፡ አስተ
ያየት ፡ በቅርቡ ፡ አሳትሞ ፡ አወጣ
2. ማስተዋል. Try to develop your powers of observation! የማስተዋል ፡ ችሎታህን ፡ ለማዳበር ፡
ሞክር
3. መመልከት. A half-hour's observation taught me the game. ግማሽ ፡ ሰዓት ፡ መመልከቴ ፡ ጨ
ዋታውን ፡ አስተማረኝ
4. ምርመራ. He was taken to the hospital for observation. ለምርመራ ፡ ወደ ፡ ሆስፒታል ፡ ወሰ
ዱት

**keep under observation**
1. በዓይን ፡ ቁራኛ ፡ ተከታተለ. The police have kept him under observation for some time. ፖሊሶ
ች ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በዓይን ፡ ቁራኛ ፡ ይከታተ
ሉት ፡ ነበር
2. በቁጥጥር ፡ ሥር ፡ አዋለ. They kept the border under observation to discourage smuggling.
የኮንትሮባንድ ፡ እቃ ፡ እንዳይገባ ፡ ጠረፎቹን ፡ ሁሉ ፡
በቁጥጥር ፡ ሥር ፡ አዋሉ

**make an observation** ገለጸ
The President made an observation to reporters on the needs of the city. ፕሬዚዳንቱ ፡ ከተማ
ዋ ፡ ስለሚያስፈልጓት ፡ ነገሮች ፡ ለጋዜጠኞች ፡
ገለጹ

**my observation is** እንደኔ ፡ ከሆነ
My observation is that such clouds mean a storm. እንደኔ ፡ ከሆነ ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ደመና ፡
ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ያለበት ፡ ዝናብ ፡ ያስከትላል

**observatory** (observatories) ኦብዘርቫቶሪ
There is an observatory in Addis Ababa.
አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ኦብዘርቫቶሪ ፡ አለ

**observe**
1. ተመለከተ. The elders observed the doings of the young people with disapproval. ሽማግሌዎ
ች ፡ የወጣቶችን ፡ ድርጊት ፡ በትዝብት ፡ ተመለከቱ
2. ጠበቀ. We must observe silence in the classroom. ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ጸጥታን ፡ መጠበቅ ፡
አለብን
Pious people observe the church fasts. ሃይማኖ
ተኞች ፡ አጽዋማትን ፡ ይጠብቃሉ
3. ጠቀሰ. He observed that crime was on the increase. ወንጀል ፡ እየበዛ ፡ መሄዱን ፡ ጠቀሰ
4. አለ. "A good day for planting", the farmer observed as he went outside. « ጥሩ ፡ የዘር ፡ ቀን » ፡
አለ ፡ ገበሬው ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ እንደወጣ
5. ተከታተለ. He has been observing the political situation in Ethiopia for some time.
የኢትዮጵያን ፡ የፖለቲካ ፡ ይዞታ ፡ ለጥቂት ፡ ዓመ
ታት ፡ ይከታተል ፡ ነበር
6. መረመረ. An astronomer observes the stars.
የከዋክብት ፡ መርማሪ ፡ ከዋክብትን ፡ ይመረምራል
7. አከበረ. The Ethiopians observe Christmas in December. ኢትዮጵያውያን ፡ የገናን ፡ በዓ
ል ፡ በታኅሣሥ ፡ ያከብራሉ
The big powers do not always observe the neutrality of small countries. ኀያላን ፡ መንግሥ
ታት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የትናንሽ ፡ መንግሥ
ታትን ፡ ገለልተኛነት ፡ አያከብሩም

**observer**
1. ታዛቢ. United Nations observers are coming to check on arms smuggling. የተባበሩት ፡ መን
ግሥታት ፡ ታዛቢዎች ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ በኮ

ል ፣ የሚደረገውን ፣ የኮንትሮባንድ ፣ ንግድ ፣ ለመ መርመር ፣ ይመጣሉ
2. ተመልካች. The concurrent views of different observers show that the minister was in the wrong. የልዩ ፡ ልዩ ፡ ተመልካቾች ፡ አስተያየት ፡ መመሳሰል ፡ ሚኒስትሩ ፡ የተሳሳተ ፡ መሆኑን ፡ ያ መለክታል
3. የሚከታተል ፤ ተከታታይ. He was a close observer of the war situation. የጦርነቱን ፡ ሁኔታ ፡ በቅርቡ ፡ የሚከታተል ፡ እሱ ፡ ነበር
He is an acute observer of the political situation. በፖለቲካው ፡ ይዞታ ፡ ንቁ ፡ ተከታታይ ፡ ነው

**obsess** አስጨነቀ
Fear that someone might steal his money obsessed him. ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ይሰርቀኛል ፡ የ ሚል ፡ ፍርሃት ፡ አስጨነቀው

**be obsessed**
*He is obsessed with the idea of making money. ሐሳቡ ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ በማግኘት ፡ ላይ ፡ አተኰረል

**obsession**
*Tidiness is an obsession with her. ንጽሕና ፡ ከ ሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የምትወደው ፡ ነገር ፡ ነው

**obsidian** ባልጩት
Obsidian was used to make knives. ባልጩት ፡ ቢላዋ ፡ ለመሥራት ፡ ያገለግል ፡ ነበር

**obsolescence**
*Military weapons are subject to obsolescence. ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ ከገልግሎት ፡ ውጭ ፡ ይሆናል

**obsolescent** ጊዜ ፡ ያለፈ(በት)
These weapons are obsolescent. እነዚህ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ጊዜ ፡ ያለፈባቸው ፡ ናቸው

**(be) obsolete** ጊዜው ፡ አልፏል ፤ ዘመኑ ፡ አለ ፈ(በት)
This medicine is obsolete. ይህ ፡ መድኃኒት ፡ ጊ ዜው ፡ አልፏል
The firearms of this army are obsolete. የነዚህ ፡ ወታደሮች ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ዘመኑ ፡ ያለፈበት ፡ ነው

**obstacle**
1. ዕንቅፋት. His youth was an obstacle to his success. ልጅ ፡ መሆኑ ፡ ለዕድሉ ፡ መቃናት ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆነበት
2. መሰናክል. A tree fallen across the road was an obstacle to our car. መንገዱ ፡ ላይ ፡ የወደ ቀው ፡ ዛፍ ፡ ለመኪናችን ፡ መሰናክል ፡ ሆነ

**obstetrician** አዋላጅ ፡ ሐኪም
The obstetrician studied in California. አዋላጁ ፡ ሐኪም ፡ በካሊፎርንያ ፡ ነው ፡ የተማረው

**obstinacy** እልህ
He tried to cure the child's obstinacy by thrashing him. ልጁን ፡ በመግረፍ ፡ እልሁን ፡ ለማ ስተው ፡ ሞከረ

**obstinate**
1. ችኮ. She is so obstinate that nobody can argue with her. ችኮ ፡ ስለሆነች ፡ ማንም ፡ ሊከ ራከራት ፡ አይችልም
2. የማይበገር. His obstinate fever has defied the doctor's attempts to cure it. የማይበገረው ፡ ትኩሳቱ ፡ ሐኪሙ ፡ ለማዳን ፡ ያደረገውን ፡ሙ ከራ ፡ ሁሉ ፡ ተቋቋመ

**obstruct**
1. ዘጋ. Rock slides obstructed the road. የደ ንጊያ ፡ ናዳ ፡ መንገዱን ፡ ዘግቶታል
2. ጋረደ. The trees obstructed our view of the lake. ዛፎቹ ፡ ሐይቁን ፡ እንዳናይ ፡ ጋረዱን
3. አዛባ. He tried to obstruct justice by bribing the judge. ለዳኛው ፡ጉቦ ፡ በመስጠት ፡ ፍትሕን ፡ ለማዛባት ፡ ሞከረ

**obstruction**
1. የዘጋ ፡ ነገር. The obstruction in his throat was removed by the doctor. ጉሮሮው ፡ ውስጥ ፡ የዘጋውን ፡ ነገር ፡ ሐኪሙ ፡ አወጣለት
2. ማሰናከያ. The workers adopted a policy of obstruction due to their conflict with the boss. ካሠሪያቸው ፡ ጋር ፡ ባለመስማማታቸው ፡ የተነሣ ፡ ሠራተኞቹ ፡ በማሰናከያ ፡ ዘዴ ፡ ተጠ ቀሙ

**obtain**
1. አገኘ. He obtained what he wanted from his friend. ከጓደኛው ፡ የሚፈልገውን ፡ ነገር ፡ አገኘ
2. አወጣ. He compressed the beans to obtain the oil. ዘይት ፡ ለማውጣት ፡ የጉሎውን ፡ ዘይ ት ፡ ጨመቀ

**obtain for** አተረፈ(ለት)
This book obtained great fame for him. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ታላቅ ፡ ዝናን ፡ አተረፈለት

**obtrude** ሰደደ
He obtruded his hand through the opening. እጁን ፡ በቀዳዳ ፡ ውስጥ ፡ ሰደደ

**obtrude on** እንዲቀበለው ፡ አስገደደው
Don't obtrude your opinions on others! ያንተን ፡ አስተያየት ፡ ሌሎች ፡ እንዲቀበሉት ፡ አታ ስገድድ

**obtrude oneself upon** በ --- መሃል ፡ ጥልቅ ፡ አለ
While the nobles were talking, the servant obtruded himself upon their conversation. መኳንንቱ ፡ ሲጫወቱ ፡ አሽከሩ ፡ በወሬያቸው ፡ መሃል ፡ ጥልቅ ፡ አለ

**obtuse** ጅል
The boy was too obtuse to take the hint. ልጁ ፡ በጣም ፡ ጅል ፡ ስለነበረ ፡ ጥቅሻው ፡ ሊገባው ፡ አልቻለም

**become obtuse** ደከመ
One's hearing becomes obtuse in old age. በሽምግልና ፡ ጊዜ ፡ የመስማት ፡ ችሎታ ፡ ይደክማል

**form an obtuse angle** ጋደል ፡ አለ
The walls form an obtuse angle. ግድግዳው ፡ ጋደል ፡ ያለ ፡ ነው

**obverse** (n.)
1. መልክ. The obverse of the medal has an inscription. የሜዳዩ ፡ መልክ ፡ ጽሑፍ ፡ አለበት
2. (= adv.) በዘውድ ፡ በኩል. The obverse of an Ethiopian coin has the date on it. የኢትዮጵያ ፡ ፍራንክ ፡ በዘውዱ ፡ በኩል ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ተጽፎበታል

**obviate**
1. ከ --- አዳነ. Proper care of your car can obviate the need for much repair. ለመኪናህ ፡ በሚገባ ፡ መጠንቀቅ ፡ ከብዙ ፡ ጥገና ፡ ያድንሃል
2. ተከላከለ. These precautions obviate any chance of accident. እነዚህ ፡ ማስጠንቀቂያዎች ፡ ማንኛቸውንም ፡ ዓይነት ፡ አደጋ ፡ ይከላከላሉ

**obvious** ግልጽ
The answer is obvious. መልሱ ፡ ግልጽ ፡ ነው

**obviously** ፍጹም ፤ በእርግጥ
He was obviously right in asking to be admitted. ለመግባት ፡ እንዲፈቀድለት ፡ በመጠየቁ ፡ ፍጹም ፡ ትክክለኛ ፡ ነበር
The woman is obviously with child. ሴትዮዋ ፡ በእርግጥ ፡ አርግዛለች

**occasion** (v.) አስነሣ
His queer behavior occasioned a good deal of talk. እንግዳ ፡ ምግባሩ ፡ ብዙ ፡ ጨዋታ ፡ አስነሣ

**occasion** (n.)
1. ጊዜ. A dress like this can be worn for any occasion. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ልብስ ፡ ለማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሊለበስ ፡ ይችላል
On what occasion did he say it? ምንጊዜ ፡ ተናገረው ?
They met on three occasions. ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ተገናኙ
2. ወቅት. The advent of spring is a joyful occasion. የጸደይ ፡ መምጣት ፡ የሚያስደስት ፡ ወቅት ፡ ነው
3. በዓል. You must wear a dress to befit the occasion. ለበዓሉ ፡ የሚስማማ ፡ ልብስ ፡ መልበስ ፡ አለብሽ
4. ያጋጠመው ፡ ዕድል. He has had few occasions to speak Amharic. አማርኛ ፡ ለመናገር ፡ ያጋጠመው ፡ ዕድል ፡ ጥቂት ፡ ነው
5. ዕድል. Last year I had occasion to go to Addis Ababa. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለመሄድ ፡ ዕድል ፡ አጋጥሞኝ ፡ ነበር
6. ምክንያት. The dog that was the occasion of the quarrel had run away. የጥሉ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ውሻ ፡ ጠፍቷል
*Everybody is dressed up. What's the occasion? ሁሉም ፡ ሽክ ፡ ብሏል ፤ ምን ፡ አለ ?

**great occasion** ልዩ ፡ በዓል
The jewels are worn only on great occasions. ዕንቁ ፡ በልዩ ፡ በዓል ፡ ብቻ ፡ ይደረጋል

**on occasion** አልፎ ፡ አልፎ
He visits New York on occasion to see the new plays. አዲስ ፡ ቲያትር ፡ ለማየት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ኒው ፡ ዮርክ ፡ ይሄዳል

**on the occasion of** ምክንያት ፡ በማድረግ
On the occasion of Independence Day, the Emperor gave a speech. የነጻነትን ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ንግግር ፡ አደረጉ

**quite an occasion** ልዩ ፡ በዓል
His birthday will be quite an occasion. የልደት ፡ ቀኑ ፡ ልዩ ፡ በዓል ፡ ይሆናል
[See also 'sundry']

**occasional** (= adv.) አልፎ ፡ አልፎ ፤ አንዳንዴ
His occasional visits cheer me up. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ስለሚጠይቀኝ ፡ ደስ ፡ ይለኛል
He suffers from an occasional lapse of memory. አንዳንዴ ፡ የማስታወስ ፡ ችግር ፡ አለበት

**occasionally**
1. አልፎ ፡ አልፎ. I see him occasionally. አልፎ ፡ አልፎ ፡ አየዋለሁ
2. አንዳንድ ፡ ጊዜ. You have to discount occasionally what you read in the newspapers. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ የምታነበውን ፡ ችላ ፡ ማለት ፡ አለብህ

**Occident** ምዕራባዊ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም
The Occident succeeded in overpowering the Orient for a while. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ምዕራባዊ ው ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ በምሥራቃውያን ፡ ላይ ፡ አይሎ ፡ ነበር

**occidental** የምዕራባውያን
He has adopted occidental food habits. የምዕራባውያንን ፡ ምግብ ፡ ለምዷል

**occult** ስውር
Magic and astrology are occult arts. ጥንቆላና ፡ ኮከብ ፡ ቈጠራ ፡ ስውር ፡ ጥበቦች ፡ ናቸው

**occupancy** መያዝ
The occupancy of the land by farmers was opposed by the cattlemen. መሬቱ ፡ በአራሾች ፡ መያዙን ፡ ከብት ፡ አርቢዎች ፡ ተቃውመው ፡ ነበር

**occupant**
1. የሚኖር ፡ ሰው. The occupant of this house is very quiet. እዚህ ፡ ቤት ፡ የሚኖረው ፡ ሰው ፡ ድምፁም ፡ አይሰማ
2. የሚሠራ ፡ ሰው. The occupants of this office are out for lunch. እዚህ ፡ ቢሮ ፡ ውስጥ ፡ የሚ ሠሩት ፡ ሰዎች ፡ ለምሳ ፡ ወጣ ፡ ብለዋል

**occupation**
1. ሥራ. What's your occupation? ሥራህ ፡ ምንድ ን ፡ ነው ?
2. መያዝ. The occupation of the city by enemy troops was achieved in a few hours. የከተማይቱ ፡ በጠላት ፡ ወታደር ፡ መያዝ ፡ በጥቂት ፡ ሰዓቶች ፡ ተ ከናወነ

**Occupation** የጠላት ፡ ጊዜ
Where were you during the Occupation? በጠ ላት ፡ ጊዜ ፡ የት ፡ ነበርክ ?

**occupational** ከሥራው ፡ ጋር ፡ የተያያዘ
Crashes are an occupational hazard for truck drivers. ግጭት ፡ ለጭነት ፡ መኪና ፡ ሾፌሮች ፡ ከሥራቸው ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ አደጋ ፡ ነው

**occupied, not** ~ (house) ወና ፤ ኦና
The house hasn't been occupied for years. ቤቱ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ወና ፡ (ኦና) ፡ ነበር

**occupy** (occupied)
1. ያዘ. The enemy occupied the city at dawn. ጐሕ ፡ ሲቀድ ፡ ጠላት ፡ ከተማይቱን ፡ ያዘ
The store occupies the entire building. መደብ ሩ ፡ ሕንጻውን ፡ በሙሉ ፡ ይዞታል
He occupies an important position in the government. በመንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ከፍተ ኛ ፡ ሥራ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ነው
2. ኖረ. Who occupies this house? እዚህ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚኖረው ፡ ማን ፡ ነው ?
3. ገባ. My friend is waiting to occupy the new house he just bought. ጓደኛዬ ፡ በቅርቡ ፡ አገዛው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ በመጠባበቅ ፡ ላይ ፡ ነው
4. ፈጀ ፤ ፈጀ(በት). The dinner and speeches occupied three hours. እራቱና ፡ ንግግሩ ፡ ሦስ ት ፡ ሰዓት ፡ ፈጀ
School occupies all my time. ትምህርት ፡ ቤት ፡ ያለኝን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ይፈጅብኛል
*Many thoughts occupied my mind. በአንጎሌ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሐሳብ ፡ ነበረ

**be occupied**
1. ሥራ ፡ ያዘ(ው). The boss is occupied at the moment. ለጊዜው ፡ ሹሙ ፡ ሥራ ፡ ይዘዋል
2. ተያዘ. The office is not occupied; you may move in. ቢሮው ፡ አልተያዘም ፤ ልትገባበት ፡ ትችላለህ

**occupy oneself** ጊዜውን ፡ አሳለፈ
He occupied himself with solving algebra problems. የአልጀብራ ፡ ፕሮብሌሞችን ፡ በመሥ ራት ፡ ጊዜውን ፡ አሳለፈ

**keep someone occupied** አሠራ
That will keep him occupied for a little while. ይህ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ያሠራዋል

**occur** (occurred)
1. ተገኘ. Errors occur in his work. በሥራው ፡ ውስጥ ፡ ስሕተት ፡ ይገኛል
2. ደረሰ. The accident occurred while he was on his way to Harar. አደጋው ፡ የደረሰበት ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ሲሄድ ፡ ነው
3. ተጠቀሰ. The name occurs twice in the chapter. በምዕራፉ ፡ ውስጥ ፡ ስሙ ፡ ሁለት ፡ ጊ ዜ ፡ ተጠቅሷል

**occur to one**
1. አሰበ. It never occurred to him to close the door. መዝጊያውን ፡ ለመዝጋት ፡ አላሰበም ፡ ነበር
2. ሐሳብ ፡ መጣ(በት). It occurred to me that I should go to Ethiopia. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የ መሄድ ፡ ሐሳብ ፡ መጣብኝ

**occurrence**
1. የሚደርስ ፡ ነገር. Car accidents are an every-day occurrence. የመኪና ፡ አደጋ ፡ በየቀኑ ፡ የ ሚደርስ ፡ ነገር ፡ ነው
2. ጉዳይ. We were delayed by several unexpected occurrences. በብዙ ፡ ያልታሰቡ ፡ ጉዳ ዮች ፡ ምክንያት ፡ ዘገየን

**ocean** ውቅያኖስ
How far is it to the ocean from here? ከዚህ ፡ እስከ ፡ ውቅያኖሱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይርቃል ?

**ocean liner** ትልቅ ፡ መርከብ
The ocean liner anchored at Massawa at noon. ትልቁ ፡ መርከብ ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ ምፅዋ ፡ ገባች

**o'clock** ሰዓት
The shop is open evenings until eight o'clock. ሱቁ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ክፍት ፡ ነው

**octagon** [ስምንት ፡ ማእዝን ፡ ያለው ፡ ቅርጽ]

**October** ጥቅምት

**oculist** የዓይን ፡ ሐኪም
There is an oculist near the bank. ባንኩ ፡ አጠገብ ፡ የዓይን ፡ ሐኪም ፡ አለ

**odd**
1. እንግዳ ፡ ነገር. His absence at this time is very odd. በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሳይመጣ ፡ መቅረቱ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ነው
2. አንድ. It cost me thirty–odd dollars. አንድ ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ ፈጅቶብኛል
3. ጐዶሎ. Seven and eleven are odd numbers. ሰባትና ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ጐዶሎ ፡ ቁጥሮች ፡ ናቸው
4. ጓደኛ ፡ የሌለው. I have a couple of odd shoes. ጓደኛ ፡ የሌላቸው ፡ ሁለት ፡ ጫማዎች ፡ አሉኝ
5. የሆነ ፡ ያልሆነ. While he was in the city, he had odd jobs. ከተማው ፡ ውስጥ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ ያልሆነውን ፡ ሥራ ፡ ይሠራ ፡ ነበር
*He is a very odd person. ሁኔታው ፡ የማይታወቅ ፡ ሰው ፡ ነው

**at odd times** ባልተወሰነ ፡ ሰዓት
They pick up the garbage at odd times. ቆሻሻውን ፡ የሚያነሡት ፡ ባልተወሰነ ፡ ሰዓት ፡ ነው

**some odd** ጥቂት
I have five dollars and some odd change. አምስት ፡ ብርና ፡ ጥቂት ፡ ዝርዝር ፡ ፍራንክ ፡ አለኝ

**oddity** (oddities) እንግዳ ፡ ነገር
The oddity of wearing a fur coat over a bathing suit is indeed striking. የጸጉር ፡ ኮት ፡ በዋና ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ መደረብ ፡ በጣም ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ነው

**oddly** (= adj.) እንግዳ
He acts oddly. Do you think he may have been drinking? ሁኔታው ፡ እንግዳ ፡ ነው ፤ የጠጣ ፡ ይመስልሃል ?

**odds** ዕድል
The odds are against his being accepted by a university. ዩኒቨርሲቲው ፡ እሱን ፡ የመቀበሉ ፡ ዕድል ፡ አነስተኛ ፡ ነው
In a tug of war the odds are with the heavier team. በገመድ ፡ ጉተታ ፡ ውድድር ፡ ጊዜ ፡ ዕድሉ ፡ የወፍራሞቹ ፡ ወገን ፡ ነው
*The odds are in his favor. ሳይቀናው ፡ አይቀርም

**odds and ends**
1. ጥቃቅን ፡ ነገሮች. I still have some odds and ends to take care of. ገና ፡ የማጠናቅቃቸው ፡ ጥቃቅን ፡ ነገሮች ፡ አሉኝ
2. ቅራቅንቦ. The room is full of odds and ends. ክፍሉ ፡ በቅራቅንቦ ፡ የተሞላ ፡ ነው

**against heavy odds**
*Our troops fought against heavy odds. ወታደሮቻችን ፡ ተጋፍጠው ፡ ዕድል ፡ ሳይረዳቸው ፡ ቀረ

**be at odds**
He is at odds with everybody. ከማንም ፡ ስምምነት ፡ የለው

**the odds are**
*The odds are that it will rain today. ምናልባት ፡ ዛሬ ፡ ይዘንብ ፡ ይሆናል

**ode** [ስለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ነገር ፡ በተለይ ፡ የሚጻፍ ፡ ጥልቅ ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ ግጥም]

**odious** የሚያስጠላ
Torture is odious to civilized people. ለሠለጠነ ፡ ሕዝብ ፡ የማሠቃየት ፡ ቅጣት ፡ የሚያስጠላ ፡ ነው

**odium** ውርደትና ፡ ንቀት
He bears the odium of having betrayed his country. ሀገሩን ፡ ስለከዳ ፡ ውርደትና ፡ ንቀትን ፡ አተረፈ

**odor**
1. መዓዛ. The odor of this perfume is pleasant. የዚህ ፡ ሽቶ ፡ መዓዛ ፡ ጣፋጭ ፡ ነው
2. ሽታ. Rotten meat has an offensive odor. የገማ ፡ ሥጋ ፡ መጥፎ ፡ ሽታ ፡ አለው

**smell the odor** ሸተተ(ው)
+I smell the odor of onions cooking. የሽንኩርት ፡ ቁሌት ፡ ይሸተኛል
[See also 'detect']

**of**
1. ከ. Give me some of that cake! ከዚያ ፡ ኬክ ፡ ጥቂት ፡ ስጠኝ
The doctor cured him of syphilis. ሐኪሙ ፡ ከቂጥኝ ፡ አዳነው
The watch is made of gold. ሰዓቱ ፡ የተሠራው ፡ ከወርቅ ፡ ነው

He is one of us. እሱ ፡ ከኛ ፡ አንዱ ፡ ነው
2. የ. He is manager of a big department store. የትልቅ ፡ መደብር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ነው
The house of bricks belongs to me. ያ ፡ የሸክላ ፡ ቤት ፡ የኔ ፡ ነው
Have you read the works of Shakespeare? የሼክስፒርን ፡ ድርሰቶች ፡ አንብበሃል ?
Is he one of us? የኛ ፡ ሰው ፡ ነው ?
3. ስለ. He thinks well of me. ስለኔ ፡ ያለው ፡ አስተያየት ፡ ጥሩ ፡ ነው
I have been dreaming of this for a long time. ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሳልም ፡ ነበር
Are you sure of what you are saying? ስለምትለው ፡ ነገር ፡ እርግጠኛ ፡ ነህ ?
4. በ. He was accused of robbery. በቀማኛነት ፡ ተከሶ ፡ ነበር
His father died of a heart attack. አባቱ ፡ በልብ ፡ ድካም ፡ ሞቱ
*Where is that fool of a servant? ያ ፡ ጅል ፡ አሽከር ፡ የት ፡ አለ ?
*Give me a sheet of paper! አንድ ፡ ሉክ ፡ ወረቀት ፡ ስጠኝ
*He expected much of the new medicine. አዲሱ ፡ መድኃኒት ፡ በጣም ፡ ይጠቅማል ፡ ብሎ ፡ አስቦ ፡ ነበር
*He put the fear of God into him. ፍርሀተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሳደረበት

**off** ቀንሶ
He sold the car at 20 percent off list price. መኪናውን ፡ ከተተመነው ፡ ዋጋ ፡ ሀያ ፡ በመቶ ፡ ቀንሶ ፡ ሸጠ

**be off**
1. ተቋረጠ. The water is off. ውኃው ፡ ተቋርጧል
2. ፈረሰ. Their engagement is off. ቃለበታቸው ፡ ፈረሰ
3. ሄዴ. The children are off to school. ልጆቹ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሄደዋል
I'm off to Ethiopia on Monday. ሰኞ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሄዴ ፡ ነው
4. ቀረ. The conference is off. ስብሰባው ፡ ቀርቷል
The town is still 5 miles off. ከተማው ፡ ለመድረስ ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ ይቀራል
5. ከ --- ወጣ. The car is off the road. መኪናዋ ፡ ከመንገድ ፡ ወጣች
6. ጠፋ. The electricity is off. ኮረንቲው ፡ ጠፍቷል
7. ዕረፍት ፡ አለው. We are off Wednesdays during the summer. በበጋ ፡ ረቡዕ ፡ ረቡዕ ፡ ዕረፍት ፡ አለን

**off and on** አልፎ ፡ አልፎ
She works off and on. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ትሠራለች

**off with his head!** ራሱን ፡ ቍረጠው
The general cried, "Off with his head!". ጄኔራሉ ፡ ራሱን ፡ ቍረጠው ፡ ብሎ ፡ ጮኸ

**have off**
*Your Excellency, may I have a week off? ክቡርነትዎ ፡ የአንድ ፡ ሳምንት ፡ ፈቃድ ፡ ቢሰጡኝ

**with his (shirt) off** (ሸሚዙን) ፡ አውልቆ
He works with his shirt off. ሸሚዙን ፡ አውልቆ ፡ ይሠራል
[See also 'cry, day, duty, guard, mark, record']

**offend** (vt.)
1. አስቀየመ. I hope I haven't offended you. አላስቀየምኩህም ፡ መቼም
2. አናደደ. He wittingly offended the judge. ዳኛውን ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ አናደደው
3. ደስ ፡ አላለም. Colors that don't match offend the eye. የማይስማሙ ፡ ቀለማት ፡ ላይን ፡ ደስ ፡ አይሉም

**offend** (vi.) አጠፋ
Those who offend are often punished. ያጠፉ ፡ በሕግ ፡ ይቀጣል
[See also 'mortally']

**offender** ጥፋተኛ ፤ አጥፊ
The offender was sentenced to a year in jail, but he escaped from police custody. ጥፋተኛው ፡ የዓመት ፡ እስራት ፡ ተፈርዶበት ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ከፖሊስ ፡ እጅ ፡ አመለጠ
The law will punish offenders with a heavy hand. ሕግ ፡ አጥፊዎችን ፡ በኀይል ፡ ትቀጣለች

**offense**
1. ጥፋት. The punishment for that offense is two years in prison. ለጥፋቱ ፡ የሚሰጠው ፡ ቅጣት ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ነው
2. ማጥቂያ. The rocket is a weapon of offense. ሮኬት ፡ የማጥቂያ ፡ መሣሪያ ፡ ነው
3. ማጥቃት. The most effective defense is offense. ከሁሉ ፡ የሚበልጠው ፡ መከላከያ ፡ ማጥቃት ፡ ነው

**be an offense to** አስቀየመ
Your garbage pile is an offense to the neighborhood. የከመርከው ፡ ቆሻሻ ፡ ጐረቤት ፡ ያስቀይማል

**cause offense** ሰው ፡ አስቀየመ
He tried not to cause offense. ሰው ፡ ላለማስቀየም ፡ ሞከረ

**penal offense** ወንጀል
Stealing is a penal offense. ስርቆት ፡ ወንጀል ፡ ነው

**take offense** ተቀየመ
I don't know why she took offense. ለምን ፡ እንደተቀየመች ፡ አላውቅም

**offensive** (n.) ማጥቃት
The enemy offensive was halted by our troops. የጠላት ፡ ማጥቃት ፡ በወታደሮቻችን ፡ ታገደ

**offensive** (adj.)
1. መጥፎ. Rotten meat has an offensive odor. የገማ ፡ ሥጋ ፡ መጥፎ ፡ ሽታ ፡ አለው
2. የሚያስከፋ. His behavior was offensive. አኳኋኑ ፡ የሚያስከፋ ፡ ነበር
3. አስከፊ. They removed the offensive passages, and reissued the statement. አስከፊ ፡ የሆነውን ፡ ካስቀሩ ፡ በኋላ ፡ ንግግሩን ፡ እንደገና ፡ አትመው ፡ አወጡ
4. አጸያፊ. His uncivil letter was offensive. ብልግና ፡ የተመላበት ፡ ደብዳቤው ፡ አጸያፊ ፡ ነበር
5. የማጥቂያ. Their offensive weapons are not effective. የማጥቂያ ፡ መሣሪያዎቻቸው ፡ ኀይለኛ ፡ አይደሉም

**offer** (vt.)
1. ሰጠ(ተሰጠ). May I offer you a cup of coffee? ቡና ፡ ልስጥህ ?
This will offer you the opportunity to visit Ethiopia. ይህ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመጐብኘት ፡ ዕድል ፡ ይሰጥሃል
I was offered a job in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሥራ ፡ ተሰጥቶኝ ፡ ነበር
2. አቀረበ. He offers only French books for sale. ለሽያጭ ፡ የሚያቀርበው ፡ የፈረንሳይ ፡ መጻሕፍት ፡ ብቻ ፡ ነው
3. ጋበዘ. He offered me a bottle of beer. አንድ ፡ ቢራ ፡ ጋበዘኝ
He offered me a cigarette. ሲጋራ ፡ ጋበዘኝ
4. ሊሸጥ ፡ አሰበ. We offered the house at a fair price. ቤቱን ፡ በደኅና ፡ ዋጋ ፡ ልንሸጠው ፡ አስበናል
5. አበረከተ(ለት). I would like to offer you a few words of advice. ጥቂት ፡ የምክር ፡ ቃላት ፡ ላበረክትላችሁ ፡ እወዳለሁ
6. መፍቀዱን ፡ገለጸ. She offered her services as a housekeeper. በቤት ፡ ጠባቂነት ፡ ለማገልገል ፡ መፍቀዷን ፡ ገለጸች
*He offered to help me. ልርዳህ ፡ አለኝ

**offer** (vi.) አጋጠመ
I will come if opportunity offers. ዕድል ፡ ሲያጋጥም ፡ እመጣለሁ
[See also 'hand, prayer, resistance']

**offer** (n.)
1. ድርድር. The employer made me a good offer for the job. አሠሪው ፡ ለሥራው ፡ ጥሩ ፡ ድርድር ፡ አቅርቦልኝ ፡ ነበር
2. ያቀረበው ፡ ውል. His offer included a high salary and three weeks' paid vacation. ያቀረበው ፡ ውል ፡ ከፍተኛ ፡ ደሞዝና ፡ ከደሞዝ ፡ ጋር ፡ የሦስት ፡ ሳምንት ፡ ዕረፍት ፡ እንደሚሰጥ ፡ ይገልጻል
3. ያቀረበ(ለት) ፡ ሐሳብ. Will you accept my offer to work with me? ከኔ ፡ ጋራ ፡ እንድትሠራ ፡ ያቀረብኩልህን ፡ ሐሳብ ፡ ትቀበላለህ ?
4. የሰጠው. His offer of $30,000 for the house was accepted by the seller. ለቤቱ ፡ የሰጠውን ፡ ሠላሳ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ሻጩ ፡ ተቀበለው
5. ስጦታ. The child distrusted the stranger's offer. ልጁ ፡ የእንግዳውን ፡ ስጦታ ፡ ተጠራጠረ
*I refused his offer of help. የሱን ፡ እርዳታ ፡ እምቢ ፡ አልኩ

**make an offer** ዋጋ ፡ ነገረ
Did he make you an offer for your house? ቤትህን ፡ የሚገዛበትን ፡ ዋጋ ፡ ነገረህ ?

**offering** የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለት
The deacon collected the offering. ዲያቆኑ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ስለት ፡ ተቀበለ

**offhand**
1. እንደሚመስለው. Offhand, I would say that he had paid 1,000 dollars for it. እንደሚመስለኝ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ሳይከፍልበት ፡ አልቀረም
2. ሳያስብበት. I can't tell you offhand how much a month I can pay you. በወር ፡ ስንት ፡ እንደምከፍልህ ፡ ሳላስብበት ፡ ልነግርህ ፡ አልችልም

**off-hours** የዕረፍት ፡ ጊዜ
I spent my off-hours reading. የዕረፍት ፡ ጊዜዬን ፡ በንባብ ፡ አሳለፍኩ

**office**
1. መሥሪያ ፡ ቤት. The offices close at five o'clock. መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የሚዘጋው ፡ በዐሥሩ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ነው
2. ቢሮ. You can see me in my office. እቢሮዬ ፡ ልትመጣ ፡ ትችላለህ
3. የመሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሰው. The whole office was at her wedding. የመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሰው ፡ በሙሉ ፡ በሰርጓ ፡ ላይ ፡ ነበር
4. ተግባር. He performs the office of priest. የቅስና ፡ ተግባር ፡ ይፈጽማል
5. ሥልጣን. He was elected to a high office. ለከፍተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ተመረጠ
6. የጸሎት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት. There are seven daily offices in the Catholic Church. በካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በቀን ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ የጸሎት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይደረጋል

**offices, through the good** ~ በ --- አማካይነት
I obtained the post through the good offices

of a friend. ሥራውን ፡ በጓደኛዬ ፡ አማካይነት ፡ አገኘሁ

**office of ...** - - - ነት
He is running for the office of mayor. ለከንቲባነት ፡ ይወዳደራል

**be in office**
1. በሥልጣን ፡ ላይ ፡ ቆየ. How long has the mayor been in office? ከንቲባው ፡ በሥልጣኑ ፡ ላይ ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ ቆይቷል ?
2. በስፍራው ፡ ተተካ. Which man will be in office if the prime minister dies? ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ቢሞቱ ፡ በስፍራቸው ፡ የሚተካ ፡ ማነው ?

**office boy** ተላላኪ
The office boy takes care of minor things. ተላላኪው ፡ ጥቃቅን ፡ ሥራዎችን ፡ ያከናውናል

**office girl** ቢሮ ፡ የምትሠራ ፡ ልጃገረድ
The office girls are giving a party. ቢሮ ፡ የሚሠሩት ፡ ልጃገረዶች ፡ ግብዣ ፡ ያደርጋሉ

**officer**
1. መኰንን. He was an officer during the last war. ባለፈው ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ መኰንን ፡ ነበር
2. ሹም. Are you an officer of this club? በዚህ ፡ ክበብ ፡ ውስጥ ፡ ከሹማምንቱ ፡ አንዱ ፡ ነህ ?

**official** (n.)
1. ባለሥልጣን. He is a State Department official. በውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ባለሥልጣን ፡ ነው
2. ሠራተኛ. The customs officials searched us. የጉምሩክ ፡ ሠራተኞች ፡ ፈተሹን

**official** (adj.)
1. የይፋ. He paid me an official visit. የይፋ ፡ ጉብኝት ፡ አደረገልኝ
2. የመንግሥት. The papers bear the official seal. ወረቀቶቹ ፡ የመንግሥት ፡ ማኅተም ፡ አለባቸው
*I received an official letter informing me of my appointment. የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡ ደረሰኝ

**official opening**
*The official opening of the store will be on Monday. ሱቁ ፡ የሚመረቀው ፡ ሰኞ ፡ ነው

**official status** በይፋ ፡ የታወቀ ፡ ሥልጣን
He has no official status with the government. በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ በይፋ ፡ የታወቀ ፡ ሥልጣን ፡ የለውም

**official uniform** የደንብ ፡ ልብስ
Policeman wear an official uniform. ፖሊሶች ፡ የደንብ ፡ ልብስ ፡ ይለብሳሉ

**Official Gazette** ነጋሪት ፡ ጋዜጣ
My brother's appointment was announced in the Official Gazette. የወንድሜ ፡ መሾም ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ተገለጸ

**officially** በይፋ
It was announced officially. በይፋ ፡ ተነግሯል

**officiate**
1. ሠራ. He officiated as chairman during the debate. በክርክሩ ፡ ጊዜ ፡ በሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ሠራ
2. ቡራኬ ፡ ሰጠ. The minister who officiates at the wedding is a friend of ours. በሰርጉ ፡ ላይ ፡ ቡራኬ ፡ የሰጡት ፡ ቄስ ፡ ወዳጃችን ፡ ናቸው

**offing, in the ~**
*There seems to be some trouble in the offing. ወደፊት ፡ አንድ ፡ ችግር ፡ ሳይፈጠር ፡ አይቀርም

**off-season** (n.)
*Fares are lower when one travels in the off-season. ሕዝቡ ፡ ብዙ ፡ በማይጓጓዝበት ፡ ጊዜ ፡ የቲኬት ፡ ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ ይላል

**offset**
1. አብቃቃ. He has to offset his small salary by living economically. ትንሹን ፡ ደሞዙን ፡ ለማብቃቃት ፡ በቁጠባ ፡ መኖር ፡ አለበት
2. ሸፈነ. The gains offset the losses. ትርፉ ፡ ኪሳራውን ፡ ይሸፍናል
The better roads offset the greater distance. ጥሩው ፡ መንገድ ፡ ርቀቱን ፡ ይሸፍነዋል
3. አሟላ. Good training of soldiers offsets numbers. ወታደሮችን ፡ በሚገባ ፡ ማሠልጠን ፡ የቁጥርን ፡ ማነስ ፡ ያሟላል

**offshoot**
1. ዝርያዎች. An offshoot of this tribe settled in the mountains. የዚህ ፡ ጐሳ ፡ ዝርያዎች ፡ በተራራዎቹ ፡ ላይ ፡ ሰፍረዋል
2. ተቀጥያ. The offshoots of this plant grow several feet in all directions. የዚህ ፡ ዛፍ ፡ ተቀጥያዎች ፡ በሁሉም ፡ አቅጣጫ ፡ ለብዙ ፡ ጫማዎች ፡ ያድጋሉ
3. ዘርፍ. French is an offshoot of Latin. ፈረንሳይኛ ፡ የላቲን ፡ ዘርፍ ፡ ነው
4. ውጤት. As an offshoot of their discussion, a contract resulted. የንግግራቸው ፡ አንድ ፡ ውጤት ፡ ውለታ ፡ መፈራረም ፡ ነበር

**offshore,** adj. (= adv.) ከጠረፍ ፡ ራቅ ፡ ብሎ
Offshore drilling for oil is going on in the Red Sea. በቀይ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ከጠረፍ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ የዘይት ፡ ጉድጓድ ፡ በመቈፈር ፡ ላይ ፡ ነው

**offspring** ዘር
The couple didn't leave any offspring. ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ዘር ፡ አልተውም

**be an offspring** ተወለደ
The mule is a hybrid, being the offspring of a donkey and a horse. በቅሎ ፡ ከአህያና ፡ ከፈረስ ፡ የምትወለድ ፡ ዲቃላ ፡ ናት

**offstage, go ~** ከመድረኩ ፡ ተገለለ
The actor went offstage. ተዋናዩ ፡ ከመድረኩ ፡ ተገለለ

**often** ብዙ ፡ ጊዜ
We often go to Ethiopia in the summer. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በበጋ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንሄዳለን

**as often as** በ - - -ቁጥር
As often as I try to get an answer from him, he makes some excuse. ከሱ ፡ መልስ ፡ በጠየቅሁ ፡ ቁጥር ፡ ምክንያት ፡ ይፈጥራል

**be once too often** (= active) አበዛ
He was late once too often and was fired. መዘግየት ፡ ስላበዛ ፡ ከሥራ ፡ ተባረረ

**every so often** አልፎ ፡ አልፎ ፤ በየጊዜው
Every so often, I get a letter from him. አልፎ ፡ አልፎ ፡ (በየጊዜው) ፡ ከሱ ፡ ደብዳቤ ፡ ይደርሰኛል

**how often?** ስንት ፡ ጊዜ ፤ ስንቴ
How often do you go to the movies in a week? በሳምንት ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ (ስንቴ) ፡ ሲኒማ ፡ ትሄዳለህ ?

**more often** ይበልጡን ፡ ጊዜ
In English, the definite article is used more often than in Amharic. ካማርኛ ፡ ይልቅ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ የተወሰነ ፡ መስተአምር ፡ ይበልጡን ፡ ጊዜ ፡ ይሠራበታል

**more often than not** አብዛኛውን ፡ ጊዜ
The child comes late more often than not. ልጁ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ዘግይቶ ፡ ይመጣል

**oftentimes** ብዙ ፡ ጊዜ
I saw him oftentimes during my stay in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ስኖር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አገኘው ፡ ነበር

**oil** (v.) ዘይት ፡ አደረገ(በት)
Oil the typewriter or it will rust. የጽሕፈት ፡ መኪናውን ፡ ዘይት ፡ አድርግበት ፤ አለበለዚያ ፡ ይዝጋል

**oil** (n.) ዘይት
What kind of oil does she cook with? ምግብ ፡ የምትሠራው ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ ዘይት ፡ ነው ?
Put some oil in my car, please! እመኪናዬ ፡ ውስጥ ፡ ዘይት ፡ አድርግበት
After several years of trial, they finally struck oil. ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ ሙከራ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ዘይት ፡ አገኙ
[See also 'mineral oil, vegetable oil']

**oil lamp** ፋኖስ
I need an oil lamp to read by. ለማንበብ ፡ ፋኖስ ፡ ያስፈልገኛል

**oil tanker** ዘይት ፡ ጫኝ ፡ መርከብ
Oil tankers bring oil to Assab. ዘይት ፡ ጫኝ ፡ መርከቦች ፡ ወደ ፡ አሰብ ፡ ዘይት ፡ ይጭናሉ

**oily**
1. ዘይት ፡ የጠጣ. These oily rags are a fire hazard. እነዚህ ፡ ዘይት ፡ የጠጡ ፡ ጨርቆች ፡ እሳት ፡ ያስነሣሉ
2. በዘይት ፡ የተበከለ. He washed his oily hands in the sink. በዘይት ፡ የተበከለውን ፡ እጁን ፡ በመታጠቢያው ፡ ውስጥ ፡ ታጠበ

**ointment** ቅባት
Put some ointment on my burn! ከተቃጠለው ፡ እጄ ፡ ላይ ፡ ቅባት ፡ አድርግልኝ

**old**
1. አሮጌ. Have you any old clothes for sale? የሚሸጡ ፡ አሮጌ ፡ ልብሶች ፡ አሉህ ?
2. የቆየ. This food is too old to eat. ይህ ፡ ምግብ ፡ በጣም ፡ የቆየ ፡ ስለሆነ ፡ አይበላም
Is this an old model? ይህ ፡ የቆየ ፡ ሞዴል ፡ ነው ?
I broke with my old friend. ከቆየ ፡ ጓደኛዬ ፡ ተቈራረጥኩ
3. የብዙ ፡ ጊዜ ፤ የዱሮ ፤ የጥንት. The man is an old friend of mine, but is not akin to me. ሰውዬው ፡ የብዙ ፡ ጊዜ ፡ (የጥንት ፤ የድሮ) ፡ ወዳጄ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አይዛመደኝም
4. የቀድሞ. We were directed to follow the old regulations. የቀድሞዎቹን ፡ ደንቦች ፡ እንድንከተል ፡ ታዘዝን
*How old are you? ስንት ፡ ዓመትህ ፡ ነው ?
*He is thirty years old. እሱ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመቱ ፡ ነው

**old age** እርጅና ፤ የሽምግልና ፡ ጊዜ ፤ የእርጅና ፡ ጊዜ
Old age brings many diseases with it. እርጅና ፡ ብዙ ፡ ሕመም ፡ ያስከትላል
One's hearing becomes obtuse in old age. በሽምግልና ፡ (በእርጅና) ፡ ጊዜ ፡ የመስማት ፡ ችሎታ ፡ ይደክማል

**old lady** ባልቴት
It is courteous to help an old lady. ባልቴት ፡ መርዳት ፡ የትሕትና ፡ ተግባር ፡ ነው

**old man** ሽማግሌ
Old men should be respected. ሽማግሌዎች ፡ መከበር ፡ አለባቸው

**old people** ሽማግሌዎች
Old people are wiser than the young. ከወጣቶቹ ፡ ይልቅ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ብልሆች ፡ ናቸው

**old woman** አሮጊት
We have a special club for old women. ላሮጊቶች ፡ ልዩ ፡ ክበብ ፡ አለን

**a bit too old** ትንሽ ፡ ቆየት ፡ ያለ
The bread is a bit too old to eat. ለመብላ ፡ ዳቦው ፡ ትንሽ ፡ ቆየት ፡ ያለ ፡ ነው

**be old (man, woman)** አረጀ
He is an old man now. አሁን ፡ አርጅቷል
She is an old woman now. አሁን ፡ አርጅታለች

**be far too old** ሸመገለ
He is far too old for a young girl like you to marry. እንዳንቺ ፡ ያለች ፡ ወጣት ፡ ልጃገረድ ፡ ለማግባት ፡ ሸምግሏል

**be old enough** ዕድሜው ፡ ብቁ ፡ ነው
He is old enough to know better. ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ለማወቅ ፡ ዕድሜው ፡ ብቁ ፡ ነው

**get old** አረጀ
What will he do when he gets old and cannot work? አርጅቶ ፡ መሥራት ፡ ሲያቅተው ፡ ምን ፡ ያደርጋል ?

**grow old** በዕድሜ ፡ ገፋ
Our grandmother did not lose her charm for us as she grew old. አያታችን ፡ በዕድሜ ፡ እየገፉ ፡ ቢሄዱም ፡ ለዛቸውን ፡ አላጡም
[See also 'gentleman, gossip, how, stuff']

**olden** የድሮ ፤ የዱሮ
In olden days, each family educated its own children. በድሮ ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ ቤተሰብ ፡ ልጆቹን ፡ በየቤቱ ፡ ያስተምር ፡ ነበር
[See also 'time']

**older** ታላቅ
He is my older brother. ታላቅ ፡ ወንድሜ ፡ ነው

**be older than**
1. በዕድሜ ፡ በለጠ. I'm older than she by five years. በዕድሜ ፡ እሷን ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ እበልጣታለሁ
2. ከ - - - አረጀ. This building is older than ours. ይህ ፡ ሕንጻ ፡ ከኛ ፡ ሕንጻ ፡ ያረጃል
3. የ - - - ታላቅ ፡ ነው. He is older than his brother. የወንድሙ ፡ ታላቅ ፡ ነው

**get older** አረጀ
You get older faster if you work too hard. ሥራ ፡ በጣም ፡ ካበዛህ ፡ ቶሎ ፡ ታረጃለህ

**grow older** አረጀ
As we grow older, we learn the limits of our abilities. እያረጀን ፡ ስንሄድ ፡ የችሎታችንን ፡ መጠን ፡ እንገነዘባለን

**old-fashioned**
1. የነፈሰበት. She has such old-fashioned ideas. አስተያየቷ ፡ ሁሉ ፡ የነፈሰበት ፡ ነው
2. የድሮ. Old-fashioned weapons were cumbersome. የድሮ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ለመያዝ ፡ የማይመቹና ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበሩ

**old hand, be an ~ at** ልምድ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው
He is an old hand at playing cards. በካርታ ፡ ጨዋታ ፡ ልምድ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**old maid, be an ~** ቆማ ፡ ቀረች
She refused to marry and is now an old maid. አላገባም ፡ ብላ ፡ ቆማ ፡ ቀረች

**Old Testament** ብሉይ ፡ ኪዳን
The Old Testament was originally written in Hebrew. ብሉይ ፡ ኪዳን ፡ መጀመሪያ ፡ የተጻፈው ፡ በዕብራይስጥ ፡ ነው

**old-time** የድሮ
Old-time dances are performed by our group. ቡድናችን ፡ የድሮ ፡ ጭፈራዎችን ፡ ያሳያል

**old-timer** ሽማግሌ
Listen to the old-timers talk about the battles they've been in. ስለተዋጉት ፡ ጦርነት ፡ ሲያወሩ ፡ ሽማግሌዎችን ፡ አዳምጡ

**olive** የወይራ ፡ ፍሬ
They kept the olives in a jar. የወይራውን ፡ ፍሬ ፡ በማሰሮ ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጡ

**olive oil** የወይራ ፡ ዘይት
You can find olive oil in any grocery. የወይራ ፡ ዘይት ፡ በማንኛውም ፡ የምግብ ፡ መደብር ፡ ይገኛል

**olive tree** ወይራ
Many olive trees grow in the highland. ደጋው ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ወይራ ፡ ይበቅላል

**omen**
1. ገድ. The cry of some birds is considered a good omen. ያንዳንድ ፡ ወፎች ፡ ጩኸት ፡ ጥሩ ፡ ገድ ፡ ነው ፡ ይባላል
2. የገድ ፡ ምልክት. A black cat is considered a bad omen. ጥቁር ፡ ድመት ፡ የመጥፎ ፡ ገድ ፡ ምልክት ፡ ናት ፡ ይባላል

**omen of good fortune** ገድ
The ancients considered the flight of birds

an omen of good fortune. የድሮ ፡ ሰዎች ፡ ወፎች ፡ ሲበሩ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ገድ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያምኑ ፡ ነበር

**be an omen of** መምጣቱን ፡ አመለከተ
The dark sky is an omen of rain. የጨለመው ፡ ሰማይ ፡ ዝናም ፡ መምጣቱን ፡ ያመለክታል

**ominous, ~ sign** መጥፎ ፡ ገድ
Some people consider the cry of an owl as an ominous sign. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የጉጉትን ፡ ጩኸት ፡ እንደ ፡ መጥፎ ፡ ገድ ፡ ይቈጥሩታል

**omission** መገደፍ
The omission of certain letters made this sentence hard to read. ያንዳንድ ፡ ፊደል ፡ መገደፍ ፡ ይህን ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ለማንበብ ፡ አስቸጋሪ ፡ አደረገው

**omit** (omitted)
1. ገደፈ. He omitted the last letter of the word 'brother'. ወንድም ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ የመጨረሻ ፡ ፊደል ፡ ገደፈው
2. አስቀረ. Tell me the whole story. Do not omit a single detail! አንዳችም ፡ ነገር ፡ ሳታስቀር ፡ ታሪኩን ፡ በሙሉ ፡ ንገረኝ
3. ሰ + (negative imperfect) + ቀረ. She omitted making her bed. አልጋዋን ፡ ሳታነጥፍ ፡ ቀረች

**be omitted** ተዘለለ
Your name was omitted by oversight. ስምህ ፡ የተዘለለው ፡ በስሕተት ፡ ነበር

**omnipotence** ኀያልነት
The omnipotence of God is irrefutable. የእግዚአብሔር ፡ ኀያልነት ፡ የማይካድ ፡ ነው

**omnipotent** ኀያል
God is omnipotent. እግዚአብሔር ፡ ኀያል ፡ ነው

**omnipresent** የትም ፡ የሚገኝ
The belief in an omnipresent God is found in many religions. እግዚአብሔር ፡ የትም ፡ የሚገኝ ፡ መሆኑ ፡ በብዙ ፡ ሃይማኖት ፡ ይታመናል

**omniscient** ሁሉን ፡ ዐዋቂ
According to certain religions, God is omniscient. ባንዳንድ ፡ ሃይማኖት ፡ መሠረት ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁሉን ፡ ዐዋቂ ፡ ነው

**on**
1. በ. Is the train on time? ባቡሩ ፡ በጊዜ ፡ ይደርሳል ?
He swore on the Bible to tell the truth. እውነቱን ፡ ለመናገር ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ማለ
He was arrested on a charge of theft. በስርቆት ፡ ወንጀል ፡ ተይዞ ፡ ነበር
Do you sell on credit? በዱቤ ፡ ትሸጣለህ ?
You can depend on him. በሱ ፡ ልትተማመን ፡ ትችላለህ
2. በ - - - ላይ. Books are on sale now. መጽሐፎች ፡ አሁን ፡ በመሸጥ ፡ ላይ ፡ ናቸው
There is only one town on the border. በጠረፉ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ከተማ ፡ ብቻ ፡ ነው
I live on King George Street. ቤቴ ፡ በኪንግ ፡ ጆርጅ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ነው
He is on vacation just now. አሁን ፡ በዕረፍት ፡ ላይ ፡ ነው
This is based on facts. ይህ ፡ በእውነት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው
3. ላይ. Put it on the table! ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ አስቀምጠው
We had lunch on the plane. ምሳ ፡ የበላነው ፡ አውሮፕላን ፡ ላይ ፡ ነው
He carried his coat on his arm. ኮቱን ፡ ክንዱ ፡ ላይ ፡ አደረገ
Continue on page five! ገጽ ፡ አምስት ፡ ላይ ፡ ቀጥል
He hung his coat on a nail. ኮቱን ፡ ምስማር ፡ ላይ ፡ ሰቀለ
4. እ - - - ላይ. What was it standing on? እምን ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ?
5. ከ. Is there anything interesting on the radio? ከራዲዮ ፡ የሰማኸው ፡ የሚያስደስት ፡ ነገር ፡ አለ ?
6. ከ - - - በስተ. He sat on the speaker's left. ከተናጋሪው ፡ በስተግራ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር
7. በ - - - በኩል. A highway bounds the farm on the west. እርሻውን ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ያዋስነዋል
8. ውስጥ. Who's on the team? ቡድኑ ፡ ውስጥ ፡ ማን ፡ አለ ?
9. ስለ. What are your ideas on that subject? ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አስተያየትህ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
It's a book on animals. ስለ ፡ እንስሳት ፡ የተጻፈ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው
10. ለ. The boss is out on business. አለቃው ፡ ለሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ወጥቷል
11. ወደ. They marched on the enemy's capital. ወደ ፡ ጠላት ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ዘመቱ
12. የ. The interest on your money is three percent. የገንዘብህ ፡ ወለድ ፡ በመቶ ፡ ሦስት ፡ ነው
13. (= when) ሲ + imperfect. On the death of his father, he became king. አባቱ ፡ ሲሞት ፡ ነገሠ
14. (zero). Are you open on Saturday? ቅዳሜ ፡ ትከፍታላችሁ ?
*He hit him on the head. ራሱን ፡ መታው

**on and on** ያለማቋረጥ
She chattered on and on about her children. ስለ ፡ ልጆቿ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ለፈለፈች
*She talks on and on. ወሬዋ ፡ አያቋርጥም

**on with** ይቀጥል
On with the show! ጨዋታው ፡ ይቀጥል

**be on**
1. ተጀመረ. The race is on. የሩጫው ፡ ውድድር ፡ ተጀምሯል
2. በመደረግ ፡ ላይ ፡ ነው. Don't you know there's a war on? ጦርነት ፡ በመደረግ ፡ ላይ ፡ መሆኑን ፡ አታውቅም ?
3. አልመጣም. Is the water on yet? ውኃው ፡ አልመጣም ?

**be on someone**
This dinner is on me. የራቱን ፡ ሒሳብ ፡ የምከፍለው ፡ እኔ ፡ ነኝ

**have nothing on** ራቁቱን ፡ ነበር
The woman was shocked to see he had nothing on. ራቁቱን ፡ ሆኖ ፡ ባየችው ፡ ጊዜ ፡ ሴትዮዋ ፡ በጣም ፡ ደነገጠች

**what's on ?** ምን ፡ አለ
What's on at the cinema today? ዛሬ ፡ ምን ፡ ፊልም ፡ አለ ?
[See also 'off']

**once**
1. አንዴ. He read the book not once but twice. መጽሐፉን ፡ ያነበበው ፡ አንዴ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሁለቴ ፡ ነው
2. አንድ. He did it once or twice. አንድ ፡ ሁለቴ ፡ አድርጎታል
3. አንድ ፡ ጊዜ. I've seen him only once. አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ያየሁት
4. አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ. Once doesn't count. አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ አይበቃም
5. እንደ + (perfect). Once you understand Amharic, you can go to the market. አማርኛን ፡ መናገር ፡ እንደቻልክ ፡ ገበያ ፡ ልትወጣ ፡ ትችላለህ
6. ድሮ. This was once the railway station. ይህ ፡ ስፍራ ፡ ድሮ ፡ ባቡር ፡ ጣቢያ ፡ ነበር
7. ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን. There is a fable that a serpent once ruled in Eritrea. ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እባብ ፡ ኤርትራን ፡ ይገዛ ፡ እንደነበረ ፡ የሚነገር ፡ የአፍ ፡ ታሪክ ፡ አለ
8. በቀድሞ ፡ ዘመን. Dinosaurs once inhabited the earth. ዳይኖሶሮች ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር
9. ከ + perfect. If she once starts talking, she is hard to stop. መናገር ፡ ከጀመረች ፡ ለማቆም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
10. ብ + imperfect + ወዲያው. He will succeed once given a chance. ዕድል ፡ ቢሰጠው ፡ ወዲያው ፡ ይሳካለታል

**once and again** ተደጋግሞ
He has been told once and again not to slam the door. በሩን ፡ በኀይል ፡ እንዳይዘጋ ፡ ተደጋግሞ ፡ ተነግሮት ፡ ነበር

**once and for all** የመጨረሻውን ፡ ነው
I am telling you once and for all, stop it! የምነግርህ ፡ የመጨረሻውን ፡ ነው ። ተው
*Once and for all, no! ቁርጥ ፡ ያለውን ፡ ነው ። አይሆንም

**once in a great while** ከስንት ፡ አንዴ
He visits me once in a great while. ከስንት ፡ አንዴ ፡ ሊጠይቀኝ ፡ ይመጣል

**once in a while** አልፎ ፡ አልፎ ። ከስንት ፡ አንዴ
Once in a while I like a good glass of wine. አልፎ ፡ አልፎ ፡ (ከስንት ፡ አንዴ) ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ መጠጣት ፡ እወዳለሁ

**once more** አንዴ ፡ ደግሞ ። እንደገና
Let's try it once more! አንዴ ፡ ደግሞ ፡ እንሞክር
Say it once more, please! እንደገና ፡ በለው ፡ እስቲ

**once upon a time** ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን
Once upon a time there was a giant with two heads. ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሁለት ፡ ራስ ፡ ያለው ፡ ጭራቅ ፡ ነበረ

**at once**
1. ባንዴ. Everything came at once. ሁሉም ፡ ባንዴ ፡ ሆነ
2. በፍጥነት ። አሁን. Come here at once! በፍጥነት ፡ (አሁን) ፡ ወዲህ ፡ ና
3. አሁኑኑ. I am leaving for Rome at once. አሁኑኑ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ መሄዴ ፡ ነው
4. ቶሎ. Do it at once! ቶሎ ፡ አድርገው
*This book is at once interesting and instructive. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የሚያስደስትና ፡ ትምህርትም ፡ የሚሰጥ ፡ ነው

**just this once**
1. ላሁኑ. I should punish you for this, but I'll let it go just this once. ስለዚህ ፡ ልቀጣህ ፡ ይገባኝ ፡ ነበር ። ግን ፡ ላሁኑ ፡ አልፌሃለሁ
2. ያሁኑን ፡ ብቻ. Come with us just this once! ያሁኑን ፡ ብቻ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ሂድ

**not once** አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንኳን + negative verb
He didn't once offer to help. አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ ልርዳ ፡ አላለም

**this once** ያሁኑን ፡ ብቻ
Forgive me this once! ያሁኑን ፡ ብቻ ፡ ይቅርታ ፡ አድርግልኝ
[See also 'all, every, moon, more, often, while']

**one** (adj.)
1. አንድ. I've only one question to ask. አንድ ፡ ጥያቄ ፡ ብቻ ፡ አለኝ
One day he will be sorry. አንድ ፡ ቀን ፡ ይጸጸታል
I'll call you one day next week. በሚቀጥለው ፡ ሳምንት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እደውልልሃለሁ
A short speech was made by one Mr. John. አንድ ፡ ሚስተር ፡ ጆን ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ አጭር ፡ ንግግር ፡ አደረገ
2. አንደኛ. Start with book one, chapter one and read twenty pages! አንደኛውን ፡ መጽሐፍ ፡ ከምዕራፍ ፡ አንድ ፡ ጀምረህ ፡ ሃያ ፡ ገጽ ፡ አንብብ
3. (hour) ሰባት ፡ ሰዓት. It's almost one. ሰባት ፡ ሰዓት ፡ ሊሆን ፡ ነው

**one** (pron.)
1. ሰው. He is not one to worry about money. ለገንዘብ ፡ የሚጨነቅ ፡ ሰው ፡ አይደለም
2. ከሰዎች ፡ መካከል ፡ አንዱ. He is one who never worries about money. ለገንዘብ ፡ ከማይጨነቁ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ነው
3. ማንም ፡ ሰው. One tries not to hurt oneself. ማንም ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ለመጕዳት ፡ አይፈልግም
4. አንድ ፡ ሰው. One cannot think only of oneself. አንድ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ ማሰብ ፡ የለበትም
5. (zero). Your plan is a good one. ሐሳብህ ፡ ጥሩ ፡ ነው
Do you want a black one or a red one? የምትፈልገው ፡ ጥቁር ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ቀይ ?
I have no pen. Can you lend me one? ብዕር ፡ የለኝም ፤ ልታውሰኝ ፡ ትችላለህ ?

**one after another** ተከታትለው
His family died one after another. ቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ ተከታትለው ፡ ሞቱ

**one after the other** ተከታትለው ፡ አንድ ፡ ባንድ
They left, one after the other. ተከታትለው ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ወጡ

**one and all** ማንም ፡ ሳይቀር
One and all came to the wedding banquet. ማንም ፡ ሳይቀር ፡ በሰርጉ ፡ ላይ ፡ ተገኘ

**one and the same** አንድ ፡ ዓይነት
One and the same idea occurred to each of them. ሁሉም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሐሳብ ፡ መጣላቸው

**one at a time** አንድ ፡ ባንድ
One at a time, please! እባካችሁ ፡ አንድ ፡ ባንድ

**one by one** አንድ ፡ ባንድ
They came one by one. አንድ ፡ ባንድ ፡ መጡ

**one fine day** አንድ ፡ ቀን ፡ ሲመቸው
One fine day I will be back. አንድ ፡ ቀን ፡ ሲመቸኝ ፡ ደግሞ ፡ ብቅ ፡ እላለሁ

**one from the other** አንዱን ፡ ካንዱ ፤ አንዱን ፡ ከሌላው
They are so much alike it's hard to tell one from the other. በጣም ፡ ስለሚመሳሰሉ ፡ አንዱን ፡ ካንዱ ፡ (አንዱን ፡ ከሌላው) ፡ መለየት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**one o'clock** ሰባት
It's almost one o'clock. ሰባት ፡ ሰዓት ፡ ሊሆን ፡ ነው

**one of**
1. ከ - - - አንዱ. One of my friends arrived late. ከጓደኞቼ ፡ አንዱ ፡ ዘግይቶ ፡ ደረሰ
2. አንድ + (suffix pronoun). One of us can buy the tickets. አንዳችን ፡ ቲኬቶቹን ፡ ልንገዛ ፡ እንችላለን

**one of these days** በዚህ ፡ ሰሞን ፡ አንዱን ፡ ቀን
I'll see him one of these days. በዚህ ፡ ሰሞን ፡ አንዱን ፡ ቀን ፡ እጠይቀዋለሁ

**(be) all one in** ሁሉም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ነው
We are all one in wishing you great success. ታላቅ ፡ ዕድል ፡ ስንመኝልህ ፡ ሁላችንም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ነው

**(be) at one**
1. ባንድ ፡ ድምፅ ፡ ተስማሙ. The judges were at one about the winner. ዳኞቹ ፡ ስለ ፡ አሸናፊው ፡ ባንድ ፡ ድምፅ ፡ ተስማሙ
2. ተስማሙ. We are at one about the plan for the exhibit. ስለ ፡ ኤግዚቢሽን ፡ ፕላን ፡ ተስማምተናል

**by ones and twos** አንድ ፡ ሁለት ፡ እያሉ
People began leaving the meeting by ones and twos. ሰዎች ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ እያሉ ፡ ስብሰባውን ፡ ጥለው ፡ መሄድ ፡ ጀመሩ

**(I) for one** እኔ ፡ በበኩሌ
I for one don't like this fashion. እኔ ፡ በበኩሌ ፡ ይህንን ፡ ሞድ ፡ አልወድም

**in one** አጣምሮ
He is president, chairman, and secretary in one. ፕሬዚዳንትነቱን ፡ ሊቀ ፡ መንበርነቱንና ፡ ጸሐፊነቱን ፡ አጣምሮ ፡ ይዟል

**no one** ማንም + negative verb
No one came to see me when I was sick. ታምሜ ፡ሳለሁ ፡ ማንም ፡ አልጠየቀኝ

**the one**
*The black puppy is the one I want. የምፈልገው ፡ ጥቁሯን ፡ ቡችላ ፡ ነው
[See also 'another, no, only, that, this']

**onerous** ከባድ
Overtime work is well paid, but it is sometimes

onerous. ለትርፍ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ ይከፈላል ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ከባድ ፡ ነው

**oneself** ራሱ
One cannot think only of oneself. አንድ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ ማሰብ ፡ የለበትም
At the age of five, one ought to dress oneself. ልጅ ፡ በአምስት ፡ ዓመቱ ፡ ልብሱን ፡ ራሱ ፡ መልበስ ፡ መቻል ፡ አለበት

**be oneself**
*One makes more friends by being oneself than by putting on airs. አንድ ፡ ሰው ፡ ሌላውን ፡ ልምሰል ፡ ብሎ ፡ ሳይሆን ፡ እውነተኛ ፡ ራሱን ፡ በመሆን ፡ ይበልጥ ፡ ጓደኞች ፡ ሊያበጅ ፡ ይችላል

**by oneself** ያለ ፡ ረዳት
It's hard to become very rich by oneself. ያለ ፡ ረዳት ፡ በጣም ፡ ሀብታም ፡ መሆን ፡ ከባድ ፡ ነው

**(be) one-sided**
1. አደላ. The judge seems one-sided in his decision. ዳኛው ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ያደላ ፡ ይመስላል
2. የማይመጣጠን ፡ ነው. A game between an expert and a beginner is one-sided. በዐዋቂ ፡ ሰውና ፡ በጀማሪ ፡ መሀከል ፡ የሚደረግ ፡ ግጥሚያ ፡ የማይመጣጠን ፡ ነው

**one-track, have a ~ mind** አስተሳሰበ ፡ ጠባብ ፡ ሆነ
He has a one-track mind, and you cannot discuss politics with him. አስተሳሰበ ፡ ጠባብ ፡ ስለሆነ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ፖለቲካ ፡ ልትነጋገር ፡ አትችልም

**one-track railroad** አንድ ፡ የባቡር ፡ መሥመር
Many countries have only a one-track railroad. ብዙ ፡ አገሮች ፡ አንድ ፡ የባቡር ፡ መሥመር ፡ ብቻ ፡ አላቸው

**one-way, ~ street** አንድ ፡ አቅጣጫ ፡ መንገድ
You can't drive in here; it's a one-way street. አንድ ፡ አቅጣጫ ፡ መንገድ ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ መንዳት ፡ አይቻልም

**one-way ticket** የመሄጃ ፡ ቲኬት ፤ መሄጃ ፡ ቲኬት ፡ ብቻ
I bought a one-way ticket to Chicago. ወደ ፡ ቺካጎ ፡ ለመሄድ ፡ የመሄጃ ፡ ቲኬት ፡ (መሄጃ ፡ ቲኬት ፡ ብቻ) ፡ ገዛሁ

**onion** ሽንኩርት
The woman is mincing onions. ሴትዮዋ ፡ ሽንኩርት ፡ ትከትፋለች

**onlooker** ተመልካች
The resplendent uniform dazzled the eyes of the onlookers. የሚያንጸባርቀው ፡ የደንብ ፡ ልብስ ፡ የተመልካቾቹን ፡ ዓይን ፡ አጭበረበረ

**only** (adj.) ብቻ
Am I the only woman here? እዚህ ፡ ያለሁት ፡ ሴት ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ ነኝ ?
This is the only soap to use on a baby's skin. ለሕፃን ፡ ቆዳ ፡ የሚሆን ፡ ምርጥ ፡ ሳሙና ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው
Mary and John are their only children. የነሱ ፡ ልጆች ፡ ሜሪና ፡ ጆን ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**only** (adv.) ብቻ
I'm only doing it to please you. ይህንን ፡ የማደርገው ፡ አንተን ፡ ለማስደሰት ፡ ብቻ ፡ ነው
This is only for you. ይህ ፡ ላንተ ፡ ብቻ ፡ ነው

**only** (conj.)
*I was going to buy it, only he told me not to. እሱ ፡ ከለከለኝ ፡ እንጂ ፡ ልገዛው ፡ ነበር
*I would have gone, only you objected. አንተ ፡ ተቃወምክ ፡ እንጂ ፡ እሄድ ፡ ነበር

**only a moment ago** ገና ፡ አሁን
I got here only a moment ago. ገና ፡ አሁን ፡ ደረስኩ

**only one** አንዱ
You are only one among the many who need help. እርዳታ ፡ ከሚያስፈልጋቸው ፡ ከብዙዎቹ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ነህ

**only too** በጣም
I shall be only too pleased to get home to Ethiopia. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሀገሬ ፡ ለመመለስ ፡ በቻልኩ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ባለኝ

**an only child**
He is an only child. ለእናቱ ፡ አንድ ፡ ነው

**the only one** ብቻ
You are the only one who is able to do it. ልትሠራው ፡ የምትችል ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህ

**the only person** ብቻ
Smith is the only person able to do it. ሊሠራው ፡ የሚችል ፡ ስሚዝ ፡ ብቻ ፡ ነው
[See also 'if, not']

**onrush, ~ of water** ወራጅ ፡ ውኃ
When crossing the river, he was knocked down by the onrush of water. ወንዙን ፡ ሲያቋርጥ ፡ ወራጅ ፡ ውኃ ፡ ገፍትሮ ፡ ጣለው

**onset**
*The onset of the enemy attack took us by surprise. የጠላት ፡ ማጥቃት ፡ አስደነበረን

*The onset of this disease is gradual. ይህ ፡ በሽታ ፡ የሚጀምረው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ነው

**onslaught** ኀይለኛ ፡ ማጥቃት
They had to bear the onslaught of the enemy troops. የጠላት ፡ ወታደሮችን ፡ ኀይለኛ ፡ ማጥቃት ፡ መታገሥ ፡ ነበረባቸው

**onto** ላይ
Let's get onto the boat! ጀልባው ፡ ላይ ፡ እንውጣ

**onward** ወደፊት
We must push onward, because we can't stay here. እዚህ ፡ ለመቆየት ፡ ስለማንችል ፡ ወደፊት ፡ መግፋት ፡ አለብን

**ooze** (vt.) ቀስ ፡ በቀስ ፡ አፈሰሰ
The cracked bottle was oozing oil. የተሰነጠቀው ፡ ጠርሙስ ፡ ዘይት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ያፈስ ፡ ነበር

**ooze** (vi.) ተንጠባጠበ
The mud oozed between the child's squeezing fingers. ልጁ ፡ ሲጨብጠው ፡ ጭቃው ፡ በጣቶቹ ፡ መሀከል ፡ ተንጠባጠበ

**ooze away** እየበረደ ፡ ሄደ
His courage oozed away as he waited. እያደር ፡ ድፍረቱ ፡ እየበረደ ፡ ሄደ

**ooze** (n.) ማጥ
He was stuck in the ooze. ማጥ ፡ ውስጥ ፡ ገባ

**opaque** ብርሃን ፡ የማያስተላልፍ
An opaque window glass hides the trees. ብርሃን ፡ የማያስተላልፈው ፡ የመስኮት ፡ መስተዋት ፡ ዛፎቹን ፡ ይጋርዳል

**open** (vt.)
1. ከፈተ. Open the door, please! በሩን ፡ ትከፍተው
My uncle opened a new store. አጐቴ ፡ አዲስ ፡ መደብር ፡ ከፈተ
They opened an account at the National Bank. በብሔራዊ ፡ ባንክ ፡ ሒሳብ ፡ ከፍተዋል
The chairman opened the debate with a short speech. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ውይይቱን ፡ ባጭር ፡ ንግግር ፡ ከፈተ
2. ገለጠ. He opened his shirt to show him his wound. ቁስሉን ፡ ለሱ ፡ ለማሳየት ፡ ሸሚዙን ፡ ገለጠ

**open** (vi.)
1. ተከፈተ. The door opens easily now. በሩ ፡ አሁን ፡ በቀላሉ ፡ ይከፈታል
2. ጀመረ. The story opens with a wedding. ታሪኩ ፡ በሰርግ ፡ ይጀምራል
3. ተመረቀ. The bridge opened last Saturday. ድልድዩ ፡ ባለፈው ፡ ቅዳሜ ፡ ተመረቀ

**be opened** ተከፈተ
The new store will be opened next Friday. አዲሱ ፡ መደብር ፡ የሚመጣው ፡ ዓርብ ፡ ይከፈታል
The new road will soon be opened to traffic. አዲሱ ፡ መንገድ ፡ በቅርቡ ፡ ላገልግሎት ፡ ይከፈታል

**open (into)** አስገባ
This door opens into the dining room. ይህ ፡ በር ፡ ወደ ፡ ምግብ ፡ ቤቱ ፡ ያስገባል

**open one's eyes** አስደነቀ
The new buildings in town will really open your eyes. በከተማው ፡ ያሉት ፡ አዳዲስ ፡ ሕንጻዎች ፡ ያስደንቁሃል

**open one's eyes to** ለማወቅ ፡ አስቻለ
His angry outbursts really opened my eyes to his true personality. የቁጣ ፡ ንግግሩ ፡ ትክክለኛ ፡ ማንነቱን ፡ ለማወቅ ፡ አስቻለኝ

**open out** የሚያወጣ ፡ በር ፡ አለው
Our bedroom opens out onto the garden. መኝታ ፡ ቤታችን ፡ ወደ ፡ አትክልቱ ፡ ስፍራ ፡ የሚያወጣ ፡ በር ፡ አለው

**open wide**
1. ወለል ፡ አድርጎ ፡ ከፈተ. Open all the windows wide! መስኮቶቹን ፡ ሁሉ ፡ ወለል ፡ አድርገህ ፡ ክፈታቸው
2. በጣም ፡ ከፈተ. Open your mouth wide! አፍህን ፡ በጣም ፡ ክፈት

**open up** ከፈተ
The pioneers opened up the West to settlement. አገር ፡ አቅኚዎቹ ፡ ምዕራባዊውን ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ለሰፋሪዎች ፡ ከፈቱ

**help to open**
1. አሰፋ(ለት). Traveling to foreign places helps to open your mind. ወደ ፡ አዲስ ፡ ስፍራዎች ፡ መሄድ ፡ ዕውቀትህን ፡ ያሰፋልሃል
2. ወደ --- ለመድረስ ፡ አስቻለ. Railroads helped open the West. የባቡር ፡ ሐዲድ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ለመድረስ ፡ አስቻለ

**open** (adj.)
1. ክፍት. The door is open. በሩ ፡ ክፍት ፡ ነው
Is the job still open? ሥራው ፡ አሁንም ፡ ክፍት ፡ ነው ?
2. የተከፈተ. He must have come in through the open window. በተከፈተው ፡ መስኮት ፡ በኩል ፡ ገብቶ ፡ ይሆናል
3. ገላጣ. Dirt infects an open cut. ቆሻሻ ፡ ገላጣ ፡ ቁስል ፡ ይመርዛል

4. ግልጽ. An open letter to the President was printed in the newspaper. ለፕሬዚዳንቱ ፡ የተጻፈ ፡ ግልጽ ፡ ደብዳቤ ፡ በጋዜጣ ፡ ወጣ
They held an open meeting to decide on the taxes. ስለ ፡ ግብሩ ፡ ለመነጋገር ፡ ግልጽ ፡ ስብሰባ ፡ አደረጉ
The car picked up speed once it was on the open road. ግልጽ ፡ መንገድ ፡ ብታገኝ ፡ መኪናዋ ፡ ፍጥነቷን ፡ ጨመረች
Please be open with me! እባክህ ፡ ግልጽ ፡ ሁንልኝ
5. አከራካሪ. Tax reform is still an open question. የግብር ፡ መሻሻል ፡ አሁንም ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ ነው
6. የቀረ. The only course still open to us was to go to court. የቀረን ፡ መንገድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከት ፡ ብቻ ፡ ነበር

**open air, in the ~** ከቤት ፡ ውጭ
Children like to play in the open air. ልጆች ፡ ከቤት ፡ ውጭ ፡ መጫወት ፡ ይወዳሉ

**open country** ገጠር
We were riding in a jeep through the open country. በገጠር ፡ ውስጥ ፡ በጂፕ ፡ እንጓዝ ፡ ነበር

**(have an) open face** ቅን ፡ አስተያየት ፡ ያለው
People trust him because he has an open face. ቅን ፡ አስተያየት ፡ ስላለው ፡ ሰዎች ፡ ያምኑታል

**open hand**
*He gives with an open hand. ለጋስ ፡ ነው

**(have an) open mind**
He has an open mind to suggestions. የሰው ፡ ሐሳብ ፡ ይቀበላል

**open time**
*Have you any open time on Monday? ሰኞ ፡ ጊዜ ፡ አለህ ?

**be open**
1. ተከፈተ. The dining room isn't open yet. ምግብ ፡ ቤቱ ፡ ገና ፡ አልተከፈተም
2. ፈነዳ. The flowers are all open now. አሁን ፡ አበባዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ፈንድተዋል
3. አልተወሰነም. That murder case is still open. የግድያው ፡ ወንጀል ፡ ገና ፡ አልተወሰነም

**be open (to)**
1. ተቀበለ. His mind is open to new ideas. አእምሮው ፡ አዲስ ፡ ሐሳቦች ፡ ይቀበላል
I am open to any reasonable offer. የሚቀርብልኝ ፡ ነገር ፡ ደኅና ፡ መስሎ ፡ ከታየኝ ፡ እቀበለዋለሁ
2. ተጋለጠ. The city is open to attack. ከተማዋ ፡ ለጥቃት ፡ ተጋልጣለች

*The race is open to boys under 15. ዕድሜያቸው ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ የሆነ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ በእሽቅድምድሙ ፡ ተካፋይ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ

**come out into the open** ብቅ ፡ አለ
Come out into the open where I can see you. ብቅ ፡ በል ፤ እስቲ ፡ ልይህ

**in the open** ከቤት ፡ ውጭ
You should spend more time in the open. ይበልጡን ፡ ጊዜ ፡ ከቤት ፡ ውጭ ፡ መሆን ፡ አለብህ

**keep open** አልያዘም
Keep the telephone line open for an important call. አስፈላጊ ፡ ጥሪ ፡ ስለሚመጣ ፡ ስልኩን ፡ አትያዥው
[See also 'arm, blow, break, burst, cut, field, fling, fly, gape, house, lay, pop, pry, rip, slit, smash, swing, tear']

**open-ended** ገደብ ፡ የሌለበት
The two countries made an open-ended agreement to assist each other. ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ገደብ ፡ የሌለበት ፡ የእርዳታ ፡ ስምምነት ፡ አደረጉ

**open house, keep ~**
We're keeping open house for foreign students. ለውጭ ፡ አገር ፡ ተማሪዎች ፡ ቤቱ ፡ ምንጊዜም ፡ ክፍት ፡ ነው

**opening** (n.)
1. መክፈቻ. We missed the opening of his speech. የንግግሩን ፡ መክፈቻ ፡ ሳንሰማው ፡ ቀረን
2. መከፈት. The opening of the Koka dam was a momentous occasion. የቆቃ ፡ ግድብ ፡ መከፈት ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ በዓል ፡ ነበር
3. ቀዳዳ. The opening isn't big enough. ቀዳዳው ፡ በቂ ፡ አይደለም
4. ክፍት ፡ ቦታ. There are no openings for clerks today. አሁን ፡ ለጸሐፊዎች ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ የለንም
5. ገላጣ ፡ ሜዳ. Deer were grazing in an opening in the forest. በጫካው ፡ ውስጥ ፡ ባለ ፡ ገላጣ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ አጋዘን ፡ ይግጥ ፡ ነበር
6. ምቹ ፡ ጊዜ. He waited for an opening in the discussion to offer his plan. በውይይቱ ፡ ወቅት ፡ እቅዱን ፡ ለማቅረብ ፡ ምቹውን ፡ ጊዜ ፡ ተጠባበቀ

**at the opening of** ሲከፈት
Were you at the opening of the exhibition? ኤክስፖዚሲዮኑ ፡ ሲከፈት ፡ ነበርክ ?

**opening** (adj.) የመክፈቻ ፤ የመግቢያ
The opening words of his speech dealt with the war. የንግግሩ ፡ የመክፈቻ ፡ (የመግቢያ) ፡ ቃላት ፡ ጦርነቱን ፡ የሚመለከቱ ፡ ነበሩ
[See also 'official, oral']

**openly** በግልጽ
He spoke openly of his disappointment. ስለተሰማው ፡ ቅሬታ ፡ በግልጽ ፡ ተናገረ

**open-minded** ሐሳበ ፡ ሰፊ ፡ የሆነ
An open-minded person is accessible to reason. ሐሳበ ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የሌሎችን ፡ አስተሳሰብ ፡ ይቀበላል

**operate** (vt.)
1. አንቀሳቀሰ. How do you operate this machine? ይህንን ፡ መኪና ፡ እንዴት ፡ ታንቀሳቅሰዋለህ ?
2. አካሄደ. The company operates these factories. እነዚህን ፡ ፋብሪካዎች ፡ የሚያካሂደው ፡ ኩባንያው ፡ ነው

**operate** (vi.)
1. ሠራ. He operates in a peculiar manner, but he always gets what he wants. እንግዳ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ይሠራል ፤ ሆኖም ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚፈልገውን ፡ ያገኛል
This drug operates on the heart. ይህ ፡ መድኀኒት ፡ የሚሠራው ፡ በልብ ፡ ላይ ፡ ነው
The machinery operates night and day. መኪናው ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ይሠራል
2. ቀዶ ፡ ጥገና ፡ አደረገ. The doctor says he'll have to operate. ሐኪሙ ፡ ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ማድረግ ፡ እንዳለበት ፡ ተናገረ

**operate to one's advantage** ጠቀመ(ው)
The new law operates to our advantage. አዲሱ ፡ ሕግ ፡ ይጠቅመናል

**operation**
1. ማንቀሳቀስ. The operation of this machine is simple. ይህን ፡ መኪና ፡ ማንቀሳቀስ ፡ ቀላል ፡ ነው
2. አፈጻጸም. His negligence is harmful to the operation of our plan. የሱ ፡ ግድ ፡ የለሽነት ፡ ለእቅዳችን ፡ አፈጻጸም ፡ ዕንቅፋት ፡ ነው
3. ቀዶ ፡ ጥገና. His spleen was removed in an operation. ጣፊያው ፡ ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ተደርጎ ፡ ወጣ
*One machine does the whole process in a single operation. አንድ ፡ መኪና ፡ ሁሉንም ፡ አጠቃሎ ፡ ይሠራል

**be in operation** በሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ
Is this rule in operation yet? ይህ ፡ ደንብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ውሏል ?

**(be) operative** ሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ
The new contract will be operative in May. አዲሱ ፡ ውል ፡ ከግንቦት ፡ ጀምሮ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላል

**operator**
1. ማዞሪያ. Operator, please give me the telephone number of Mr. Parker! ማዞሪያ ፤ የሚስተር ፡ ፓርከርን ፡ ቁጥር ፡ ስጪኝ
2. የሚያስነሣ ፡ ሰው. Where is the operator of this machine? ይህን ፡ መኪና ፡ የሚያስነሣው ፡ ሰው ፡ የት ፡ ነው ?
[See also 'telephone']

**opinion**
1. ሐሳብ. I gave him my frank opinion. ግልጥ ፡ ያለውን ፡ ሐሳቤን ፡ ነገርኩት
2. አስተያየት. We will have to get the opinion of an expert. የዐዋቂ ፡ አስተያየት ፡ ብናገኝ ፡ ይሻላል
What is your opinion of the doctor? ስለ ፡ ሐኪሙ ፡ ያለህ ፡ አስተያየት ፡ ምንድን ፡ ነው ?
3. ግምት. I have a very high opinion of him. ስለሱ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ አለኝ

**form an opinion** አስተያየት ፡ ወሰነ
I have not formed an opinion yet. ገና ፡ አስተያየቴን ፡ አልወሰንኩም

**hold an opinion** አስተያየት ፡ አለው
He holds a different opinion than mine on this matter. በጉዳዩ ፡ ከኔ ፡ የተለየ ፡ አስተያየት ፡ አለው

**in my opinion** እንደኔ ፡ አስተያየት
In my opinion, it is a waste of time. እንደኔ ፡ አስተያየት ፡ ጊዜ ፡ ማባከን ፡ ነው

**public opinion** የጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ አስተያየት
Public opinion is against changing this law. የጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ አስተያየት ፡ የዚህን ፡ ሕግ ፡ መለወጥ ፡ ይቃወማል
[See also 'climate, conflict, critical, private, venture']

**opinionated** ሐሳበ ፡ ግትር
It's useless to argue with an opinionated person. ከሐሳበ ፡ ግትር ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ መከራከር ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ነው

**opium** አፒዩም
Opium is an addiction-causing drug. አፒዩም ፡ ሱስ ፡ የሚያሲዝ ፡ መድኃኒት ፡ ነው

**opponent**
1. ባላጋራ. He suspected his opponent of giving the judge a bribe. ባላጋራው ፡ ለዳኛው ፡ ጉቦ ፡ ሰጥቷል ፡ ብሎ ፡ ጠረጠረ
2. ተወዳዳሪ. My opponent won in the last election. ባለፈው ፡ ምርጫ ፡ ላይ ፡ ተወዳዳሪዬ ፡ አሸነፈ
3. ተቃዋሚ. The wrestler grappled with his opponent. ታጋዩ ፡ ከተቃዋሚው ፡ ጋር ፡ ተናነቀ

**opportune** ምቹ
He arrived at an opportune moment. ምቹ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ደረሰ

**opportunist** አድር ፡ ባይ
The opportunist obtained his present position through his activities. አድር ፡ ባዩ ፡ በአድራጎቱ ፡ አሁን ፡ ያለበትን ፡ ደረጃ ፡ ያዘ

**opportunity** (opportunities)
1. ዕድል. I'm only waiting for a favorable opportunity. የምጠብቀው ፡ የሚያመቸኝን ፡ ዕድል ፡ ነው
I've had no opportunity to discuss the matter with you. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ለመወያየት ፡ ምንም ፡ ዕድል ፡ አላገኘሁም
This job offers many opportunities for an ambitious man. ይህ ፡ ሥራ ፡ ታታሪ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ዕድል ፡ ይሰጣል
2. አጋጣሚ. Take this opportunity to learn English! እንግሊዝኛ ፡ ለመማር ፡ ይህን ፡ አጋጣሚ ፡ ተጠቀምበት
3. የሚያጋጥም ፡ ዕድል. He takes advantage of every opportunity. የሚያጋጥመውን ፡ ዕድል ፡ ሁሉ ፡ ይጠቀምበታል
*When will you have an opportunity to see him? እሱን ፡ ለማየት ፡ የሚመችህ ፡ መቼ ፡ ነው ?
[See also 'seize']

**oppose**
1. ተቃወመ. The people of the town opposed the tax. የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ የግብሩን ፡ መጣል ፡ ተቃወመ
2. አገደ. A swamp opposed the advance of the army. የወታደሩን ፡ ወደፊት ፡ መግፋት ፡ ረግረግ ፡ አገደው

**opposed** ተቃራኒ
Black is opposed to white. ጥቁር ፡ የነጭ ፡ ተቃራኒ ፡ ነው

**be opposed to** ተቃወመ
I am very much opposed to your going abroad. ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ መሄድህን ፡ በጣም ፡ እቃወማለሁ

**opposing** ተቃዋሚ
The newspaper published a smear against the opposing candidate. ጋዜጣው ፡ የተቃዋሚውን ፡ እጩ ፡ ስም ፡ የሚያጠፋ ፡ ወሬ ፡ ጻፈ

**opposite** (n.) ተቃራኒ
Black and white are opposites. ጥቁርና ፡ ነጭ ፡ ተቃራኒዎች ፡ ናቸው

**opposite** (adj.) ተቃራኒ
He feels that taxes should be lower, but he took the opposite view. ግብር ፡ መቀነስ ፡ እንዳለበት ፡ ይስማማል ፡ ግን ፡ ተቃራኒውን ፡ ሐሳብ ፡ ደገፈ
They fought on opposite sides in the war. ጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ ወገን ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ተዋጉ
*I expected him to come from the east, but he came from the opposite direction. ከምሥራቅ ፡ ይመጣል ፡ ብዬ ፡ ስጠባበቅ ፡ ከምዕራብ ፡ መጣ

**opposite** (prep.)
1. ከ - - - አንጻር. We live opposite the library. ቤታችን ፡ ከመጻሕፍት ፡ ቤቱ ፡ አንጻር ፡ ነው
2. ከ - - - ፊት ፡ ለፊት. I sat opposite the President at the banquet. በግብዣው ፡ ላይ ፡ ከፕሬዚዳንቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተቀመጥኩ

**directly opposite** ከ - - - ፊት ፡ ለፊት
Our house is directly opposite the store. ቤታችን ፡ ከሱቁ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ነው

**on opposite sides** ፊት ፡ ለፊት
They sat on opposite sides of the table at dinner. ማእድ ፡ ሲቀርቡ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተቀመጡ

**opposition**
1. ተቃውሞ. The proposal met with unexpected opposition. የቀረበው ፡ አስተያየት ፡ ያልታሰበ ፡ ተቃውሞ ፡ አጋጠመው
The campaign was a great success, considering the strong opposition. የተቃውሞውን ፡ ብርታት ፡ ሲመለከቱት ፡ ዘመቻው ፡ ታላቅ ፡ ድል ፡ ነበር
2. የተቃዋሚ ፡ ወገን. The opposition tried to break up the meeting. የተቃዋሚው ፡ ወገን ፡ ስብሰባውን ፡ ለመበተን ፡ ሞከረ
3. ተቃዋሚ ፡ ጦር. Our troops encountered strong opposition on the front. በጦር ፡ ግንባሩ ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ ወታደሮቻችን ፡ ኀይለኛ ፡ ተቃዋሚ ፡ ጦር ፡ አጋጠማቸው

**oppress**
1. ጨቈነ. The South African government oppresses Blacks. የደቡብ ፡ አፍሪካ ፡ መንግሥት ፡ ጥቁሮችን ፡ ይጨቍናል
2. ተጫጫነ. This dismal weather oppresses me. ይህ ፡ ቀፋፊ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ ይጫጫነኛል
3. አስጨነቀ. A sense of trouble ahead oppressed my spirits. ወደ ፡ ፊት ፡ ስለሚመጣ ፡ ችግር ፡ ማሰብ ፡ መንፈሴን ፡ አስጨነቀው

**oppression** የጭቆና ፡ ቀንበር
They are victims of oppression. የጭቆና ፡ ቀንበር ፡ የወደቀባቸው ፡ ሰዎች ፡ ናቸው

**oppressive**
1. የሚጨቁን. We must abolish all oppressive laws. የሚጨቁኑ ፡ ሕጎችን ፡ ሁሉ ፡ መሻር ፡ አለብን
2. በጣም ፡ ከባድ. The heat is oppressive today. ዛሬ ፡ ሙቀቱ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ነው

**oppressor** ጨቋኝ
The oppressor will be defeated and driven out. ጨቋኙ ፡ ተሸንፎ ፡ ይባረራል

**opprobrious** አስከፊ
His opprobrious conduct disappointed everyone. አስከፊ ፡ ጠባዩ ፡ ሁሉን ፡ አበሳጨ

**opprobrious name** ስድብ
Coward, liar, and thief are opprobrious names. « ፈሪ » ፤ « ዋሾ »ና ፡ « ሌባ » ፡ ስድብ ፡ ናቸው

**opt** መረጠ
He opted to remain in America another year. አሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ በተጨማሪ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ መቆየት ፡ መረጠ

**optician** ያይን ፡ መነጽር ፡ ሻጭ
Past the Ras Makonnen bridge, there is an optician. ከራስ ፡ መኮንን ፡ ድልድይ ፡ አለፍ ፡ ብሎ ፡ ያይን ፡ መነጽር ፡ ሻጭ ፡ ይገኛል

**optimal** እጅግ ፡ ምቹ
This plant will grow only under optimal conditions. ይህ ፡ ዕፅ ፡ የሚያድገው ፡ እጅግ ፡ ምቹ ፡ የሆኑ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲያገኝ ፡ ብቻ ፡ ነው

**optimism** ባለ ፡ ተስፋነት
Optimism helps one to overcome the difficulties of life. ባለ ፡ ተስፋነት ፡ ችግር ፡ ለመቋቋም ፡ ይረዳል

**optimist** ባለ ፡ ተስፋ
He always hopes for the best; he is a real optimist. የተሻለ ፡ ነገር ፡ ይመኛል ፤ እውነተኛ ፡ ባለ ፡ ተስፋ ፡ ነው

**optimum** እጅግ ፡ ተስማሚ
This is the optimum temperature for hatching. እንቁላል ፡ ለመቀፍቀፍ ፡ ይህ ፡ እጅግ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ሙቀት ፡ ነው

**option** ምርጫ
I have no option in the matter; I must do it. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ምርጫ ፡ የለኝም ፤ በግድ ፡ መሥራት ፡ አለብኝ

**optional** በምርጫ ፡ የሚወሰድ
This course is optional. ይህ ፡ ትምህርት ፡ በምርጫ ፡ የሚወሰድ ፡ ነው

**opulence** ድሎት
He lives in opulence. በድሎት ፡ ይኖራል

**opulent**
1. እጅግ ፡ ሀብታም. America is an opulent country. አሜሪካ ፡ እጅግ ፡ ሀብታም ፡ አገር ፡ ነው
2. ጥቅጥቅ ፡ ያለ. The opulent forests were soon destroyed. ጥቅጥቅ ፡ ያለው ፡ ጫካ ፡ ወዲያውኑ ፡ ወደመ

**or**
1. ወይም. He is coming today or tomorrow. ዛሬ ፡ ወይም ፡ ነገ ፡ ይመጣል
It is either on the table or in the drawer. ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ መሳቢያው ፡ ውስጥ ፡ ነው
2. ወይስ (in a question). Is he coming today or tomorrow? የሚመጣው ፡ ዛሬ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ነገ ?
3. ያለበለዚያ ፤ አለዚያ. Oil the typewriter or it will rust. የጽሕፈት ፡ መኪናውን ፡ ዘይት ፡ አድርግበት ፤ ያለበለዚያ ፡ ይዝጋል
Go slow or you will damage your car. ቀስ ፡ ብለህ ፡ ንዳ ፤ አለዚያ ፡ መኪናህን ፡ ታበላሻለህ

**or rather** ማለት
His autobiography, or rather memoirs, is ready for publication. የሕይወት ፡ ታሪኩ ፤ ማለት ፡ ትዝታው ፡ ለእትም ፡ ተዘጋጅቷል

**or so**
1. ያህል. I would like twenty or so. ሃያ ፡ ያህል ፡ እፈልጋለሁ
2. አንድ. I need five dollars or so. አንድ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ያስፈልገኛል
*It will be ready in a month or so. ከወር ፡ በማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይደርሳል
[See also 'either, else, whether']

**oracle** [በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ቄሶች ፡ ከማልከት ፡ ጋር ፡ ይወያያሉ ፡ ተብሎ ፡ የሚታመንበት ፡ ስፍራ]

**oral**
1. የቃል. I passed my oral examination in French. በፈረንሳይኛ ፡ የቃል ፡ ፈተና ፡ አለፍኩ
2. የሚዋጥ. The doctor prescribed an oral medicine. ሐኪሙ ፡ የሚዋጥ ፡ መድኃኒት ፡ አዘዘ

**oral opening** አፍ
The oral opening of the earthworm is small. የትል ፡ አፍ ፡ ትንሽ ፡ ነው

**orally** በቃል
He told me orally that I had been appointed. መሾሜን ፡ በቃል ፡ ነገረኝ

**orange** (n.) ብርቱካን
Oranges grow in the region of Harar. የሐረር ፡ አካባቢ ፡ ብርቱካን ፡ ያበቅላል

**orange** (adj.) ብርቱካንማ
There was an orange ribbon on her dress. በቀሚሷ ፡ ላይ ፡ ብርቱካንማ ፡ ሪበን ፡ ነበረ

**orange juice** የብርቱካን ፡ ጭማቂ
In the morning, I usually drink orange juice. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ የብርቱካን ፡ ጭማቂ ፡ እጠጣለሁ

**oration** ንግግር
At the end of the oration everybody applauded the speaker. ከንግግሩ ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለተናጋሪው ፡ አጨበጨበ

**funeral oration** በቀብሩ ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ ንግግር
We listened in tears to the funeral oration. በቀብሩ ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ ንግግር ፡ እንባ ፡ እያነቀን ፡ አዳመጥን

**orator** ተናጋሪ
The orator promised to fight against poverty. ተናጋሪው ፡ ድኽነትን ፡ ለመዋጋት ፡ ቃል ፡ ገባ

**oratory** ንግግር
His fervid oratory aroused the crowd. ስሜት ፡ የሚነካ ፡ ንግግሩ ፡ ሕዝቡን ፡ አነሣሣ

**orbit** ምሕዋር
The orbit of the moon is around the earth. የጨረቃ ፡ ምሕዋር ፡ በመሬት ፡ ዙሪያ ፡ ነው

**orchard** ተክል
Our neighbor has an apple orchard. ጐረቤታችን ፡ የቱፋ ፡ ተክል ፡ አለው

**orchestra** የሙዚቃ ፡ ጓድ
The orchestra is giving a concert tonight. የሙዚቃው ፡ ጓድ ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ ሙዚቃ ፡ ያሰማል

**ordain**
1. ወሰነ. God has ordained that all men shall die. እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲሞት ፡ ወስኗል
2. አዘዘ. The governor ordained that the restrictions be lifted. አገረ ፡ ገዢው ፡ ገደቦቹ ፡ እንዲነሡ ፡ አዘዘ

**be ordained** (expressed by an abstract noun + ተቀበለ)
He was ordained deacon at the age of twelve. በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ዲቁናን ፡ ተቀበለ
He was ordained a priest yesterday. ትናንት ፡ ቅስና ፡ ተቀበለ

**ordeal**
1. የመከራ ፡ ጊዜ. For many, the second World War was a terrible ordeal. ለብዙዎች ፡ ሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ አሰቃቂ ፡ የመከራ ፡ ጊዜ ፡ ነበረ
2. ሥቃይ. He dreaded the ordeal of a visit to the dentist. ጥርስ ፡ ሐኪም ፡ ዘንድ ፡ ሄዶ ፡ ጥርሱን ፡ የመነቀሉን ፡ ሥቃይ ፡ ፈራ

**order** (v.)
1. አዘዘ. He ordered their arrest. እንዲያዙ ፡ አዘዘ
We have ordered lunch, but it isn't here yet. ምሳ ፡ አዘናል ፤ ግን ፡ ገና ፡ አልቀረበልንም
The doctor ordered rest for his patient. ሐኪሙ ፡ ለበሽተኛው ፡ ዕረፍት ፡ አዘዘለት
2. እንዲመጣ ፡ ነገረው. Order the taxi for six o'clock! ታክሲው ፡ በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ እንዲመጣ ፡ ንገረው
3. አጠናቀቀ. I must order my affairs before I leave. ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ ያሉኝን ፡ ጉዳዮች ፡ ማጠናቀቅ ፡ አለብኝ
*The gods ordered it otherwise. አማልክት ፡ እንደማይሆን ፡ አደረጉት

**order around**
*Stop ordering me around! ይህን ፡ አድርግ ፡ ያን ፡ አታድርግ ፡ አትበለኝ

**order** (n.)
1. ትእዛዝ. We have no orders to do that. ያንን ፡ ለማድረግ ፡ ምንም ፡ ትእዛዝ ፡ አልተሰጠንም
2. ተራ. Put the names in alphabetical order! ስሞቹን ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ አስገባቸው
3. ሥርዓት. Put the books in order on the shelf! መጽሐፎቹን ፡ በሥርዓት ፡ መደርደሪያው ፡ ላይ ፡ አስቀምጣቸው
Be sure your notebook is in order! ማስታወሻ ፡ ደብተርህ ፡ በሥርዓት ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጥ
4. ደንብ. He set his affairs in order before he died. ከመሞቱ ፡ በፊት ፡ ጉዳዩን ፡ በደንብ ፡ አከናውኖ ፡ ነበር
5. እንዲላኩለት ፡ ያቀረበው ፡ ጥያቄ. He canceled his order for the books. መጽሐፎቹ ፡ እንዲላኩለት ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ሰረዘ
6. ደረጃ. His ability is of a high order. የሱ ፡ ችሎታ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያለው ፡ ነው
7. የሃይማኖት ፡ ማኅበር. To what order does this priest belong? ይህ ፡ ቄስ ፡ የየትኛው ፡ የሃይማኖት ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ ነው ?
8. ጸጥታ. Some teachers have trouble keeping order in their classes. አንዳንድ ፡ መምህራን ፡ የክፍላቸውን ፡ ጸጥታ ፡ መጠበቅ ፡ ያስቸግራቸዋል

*The chef prepared four orders of fried chicken. ዋናው ፡ ወጥ ፡ ቤት ፡ ሰራት ፡ ሰው ፡ የዶሮ ፡ ጥብስ ፡ አዘጋጀ

**order of the day** ዕለታዊ ፡ ትእዛዝ
The order of the day was to be alert for air attack. ዕለታዊው ፡ ትእዛዝ ፡ ላየር ፡ ጥቃት ፡ ዝግጁ ፡ ሁኑ ፡ የሚል ፡ ነበር

**bring to order** ጸጥ ፡ አደረገ
The police brought the riotous crowd to order. ፖሊሶች ፡ ረብሸኛውን ፡ ሕዝብ ፡ ጸጥ ፡ አደረጉት

**call the meeting to order**
*He called the meeting to order by rapping on the table. ጠረጴዛውን ፡ በመምታት ፡ ስብሰባው ፡ በሥርዓት ፡ እንዲመራ ፡ ጠየቀ
*I now call the meeting to order. አሁን ፡ ስብሰባው ፡ ተጀምሯል

**(be) called to order**
*He was called to order by the chairman. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲከተል ፡ ነገረው
*The assembly was called to order. የስብሰባው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲከበር ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጠ

**give an order for** እንዲያቀርብ ፡ ጠየቀው
They gave me an order for twelve dozen eggs. ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ደርዘን ፡ እንቁላል ፡ እንዳቀርብ ፡ ጠየቁኝ

**in good order** በደኅና
The merchandise arrived in good order. ሸቀጡ ፡ በደኅና ፡ ደርሷል

**(be) in order**
1. በሥርዓት ፡ ነው. Is your passport in order? ፓስፖርትህ ፡ በሥርዓት ፡ ነው ?
2. ተገቢ ፡ ነው. His remark is quite in order. የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ተገቢ ፡ ነው
3. ተዘጋጀ. Everything is in order for the departure. ለመሄድ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ተዘጋጅቷል

**(not be) in order** ቅደም ፡ ተከተል ፡ ትክክል ፡ አይደለም
The pagination of this book is not in order. የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የገጽ ፡ ቁጥር ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ትክክል ፡ አይደለም

**in order of** በ
Line up in order of height! በቁመት ፡ ተሰለፉ

**in order that** እንድ + imperfect
We ought to leave early in order that we not miss the train. ባቡሩ ፡ እንዳያመልጠን ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ መነሣት ፡ አለብን

**in order to**
1. ለ + (verbal noun). I've come from Chicago in order to see you. አንተን ፡ ለማየት ፡ ከቺካጎ ፡ መጣሁ
2. እንድ + (imperfect). In order not to fail, you have to work harder. እንዳትወድቅ ፡ ጠንክረህ ፡ መሥራት ፡ አለብህ

**in short order** ቶሎ
The merchandise arrived in short order. ሸቀጣ ፡ ሸቀጡ ፡ ቶሎ ፡ ደረሰ

**make to order**
*He has his suits made to order. ልብሱን ፡ በልኩ ፡ ያሰፋል

**(be) on order** እንዲመጣ ፡ አዘዘ
We don't have that item right now, but it is on order. ይህ ፡ እቃ ፡ ለጊዜው ፡ የለንም ፡ ግን ፡ እንዲመጣ ፡ አዘናል

**on the order**
*I would like a dress on the order of the one I saw in the display window. በመስታወት ፡ ውስጥ ፡ ያየሁትን ፡ ዓይነት ፡ የሚመስል ፡ ቀሚስ ፡ እፈልጋለሁ

**(be) out of order**
1. ተበላሸ ፤ አልሠራም. The elevator is out of order. አሳንሰሩ ፡ ተበላሽቷል ፡ (አይሠራም)
2. አግባብ ፡ የለውም. His question is out of order. ጥያቄው ፡ አግባብ ፡ የለውም

**pay to the order of** ለ --- ይከፈላቸው
He wrote on the check, "Pay to the order of Mrs. Smith". በቼኩ ፡ ላይ ፡ «ለሚስዝ ፡ ስሚዝ ፡ ይከፈላቸው » ፡ ብሎ ፡ ጻፈ

**place an order** እንዲያስመጣለት ፡ አዘዘ
We placed an order for hats in this store. ይህ ፡ መደብር ፡ ባርኔጣ ፡ እንዲያስመጣልን ፡ አዘዝን

**place in order** በቅደም ፡ ተከተል ፡ ደረደረ
Place the books in the right order! መጽሐፎቹን ፡ በትክክለኛው ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ደርድር

**(in) proper order** በቅደም ፡ ተከተል
Please put these cards back in their proper order! እነዚህን ፡ ካርታዎች ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ አስቀምጣቸው

**put in battle order** ለጦርነት ፡ አሰለፈ
We have put our troops in battle order. ወታደሮቻችንን ፡ ለጦርነት ፡ አሰልፈናቸዋል

**put in order**
1. በጥንቃቄ ፡ አከናወነ. He is putting his affairs in order. ጉዳዩን ፡ ሁሉ ፡ በጥንቃቄ ፡ ያከናውናል
2. አዘጋጀ. The maid hustled about putting the house in order. ገረዲቱ ፡ ቤቱን ፡ ለማዘጋጀት ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ተሯሯጠች

**(be) quite in order** ትክክለኛ ፡ መሥመር ፡ ያዘ
Your remark is quite in order. አስተያየትህ ፡ ትክክለኛ ፡ መሥመር ፡ የያዘ ፡ ነው

**restore order**
1. ሁከትን ፡ መልሶ ፡ አረጋጋ. Only a potent ruler could restore order. ሁከትን ፡ መልሶ ፡ ማረጋጋት ፡ የሚችል ፡ ኀይለኛ ፡ መሪ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ሕግን ፡ አስከበረ ፤ ጸጥታ ፡ አስከበረ. The police took forcible measures to restore order. ፖሊስ ፡ ሕግን ፡ (ጸጥታ) ፡ ለማስከበር ፡ ጥብቅ ፡ እርምጃ ፡ ወሰደ

**take one's order** ጠየቀ
Waiter, will you take my order? ስማ ! እስቲ ፡ ና ፡ ጠይቀኝ
[See also 'inverse, numerical, procedure, reverse, rule, serial, working order']

## orderly (n.)
1. ረዳት. He is an orderly in the hospital and not a doctor. በሆስፒታሉ ፡ ውስጥ ፡ ረዳት ፡ እንጂ ፡ ሐኪም ፡ አይደለም
2. ተላላኪ. The general's orderly has fallen ill. የጄኔራሉ ፡ ተላላኪ ፡ ታሟል

**orderly** (adj.)
1. ሥርዓትን ፡ የጠበቀ. The orderly class was praised by the principal. ሥርዓትን ፡ የጠበቀው ፡ ክፍል ፡ በሥራ ፡ መሪው ፡ ተመሰገነ
2. በሥርዓት ፡ የሚጓዝ. An orderly crowd thronged the street. በሥርዓት ፡ የሚጓዘው ፡ ሕዝብ ፡ መንገዱን ፡ አጥለቀለቀው
3. በሥርዓት ፡ የሆነ. He has an orderly desk and always finds whatever he wants. የቢሮ ፡ ጠረጴዛው ፡ በሥርዓት ፡ ስለሆነ ፡ የሚፈልገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያገኛል

## ordinal መደበኛ
How do you form the ordinal number in Amharic? ባማርኛ ፡ መደበኛ ፡ ቁጥሮችን ፡ እንዴት ፡ ታመለክታለህ ?

## ordinance
1. ድንጋጌ. An ordinance was passed against doing business without a license. ያለፈቃድ ፡ መነገድን ፡ የሚከለክል ፡ ድንጋጌ ፡ ተላልፏል
2. ደንብ. Please observe the No Smoking ordinance. ማጤስ ፡ ክልክል ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ደንብ ፡ ጠብቅ

## ordinarily እንደተለመደው
Ordinarily, I am at work Wednesdays. እንደተለመደው ፡ ሮብ ፡ ሮብ ፡ እሠራለሁ

**quite ordinarily** እንደነገሩ
She was dressed quite ordinarily. አለባበሷ ፡ እንደነገሩ ፡ ነበር
*He behaves quite ordinarily. ሁኔታው ፡ የተለመደ ፡ ዓይነት ፡ ነው

## ordinary
1. ተራ. He is just an ordinary mechanic. እሱ ፡ ተራ ፡ መካኒክ ፡ ነው
She has a pretty face, but her clothes are ordinary. መልኳ ፡ ጥሩ ፡ ልብሷ ፡ ግን ፡ ተራ ፡ ነው
2. በልኩ ፡ ያልተሰፋ. The obese child cannot wear ordinary clothes. ይህ ፡ ወፍራም ፡ ልጅ ፡ በልኩ ፡ ያልተሰፋ ፡ ልብስ ፡ ሊለብስ ፡ አይችልም
3. የተለመደ. The ordinary price is $10. የተለመደው ፡ ዋጋ ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ ነው

**out of the ordinary** ያልተለመደ ፡ ነገር
It's quite out of the ordinary to have a heavy rain in the middle of the dry season. በበጋ ፡ መሀከል ፡ ከባድ ፡ ዝናም ፡ መዝነቡ ፡ ፈጽሞ ፡ ያልተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው

## ordination, ~ of priests የቅስና ፡ ማዕረግ
The ordination of priests can be performed only by a bishop. የቅስና ፡ ማዕረግ ፡ ለመስጠት ፡ የሚችል ፡ ጳጳስ ፡ ብቻ ፡ ነው

## ore የብረት ፡ አፈር
The ore is carried in trucks to the foundry. የብረቱ ፡ አፈር ፡ በጭነት ፡ መኪና ፡ ወደ ፡ ማቅለጫው ፡ ይወሰዳል

## organ
1. አካል. The eye is a visual organ. ዓይን ፡ የማያ ፡ አካል ፡ ነው
Parliament is the chief organ of government. ምክር ፡ ቤት ፡ የመንግሥት ፡ ዋናው ፡ አካል ፡ ነው
2. አባል. The tongue is one of the organs of speech. ምላስ ፡ ከአባላተ ፡ ልሳን ፡ አንዱ ፡ ነው
3. ኦርጋኖን. Our teacher plays the organ in our church. አስተማሪያችን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ኦርጋኖን ፡ ይጫወታል

## organic
1. የውስጥ ፡ አካል. Organic diseases can rarely be cured by surgery. የውስጥ ፡ አካል ፡ በሽታዎች ፡ በመቀደድ ፡ የሚድኑት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነው
2. ሕይወት ፡ ያለው. Coal is organic rather than mineral in origin. የድንጋይ ፡ ከሰል ፡ ምንጩ ፡ ከማዕድን ፡ ሳይሆን ፡ ሕይወት ፡ ከነበራቸው ፡ ነገሮች ፡ ነው

**organism** ሕይወት ፡ ያለው ፡ ነገር
Plants and animals are organisms. ዕፀዋትና ፡ እንስሳት ፡ ሕይወት ፡ ያላቸው ፡ ነገሮች ፡ ናቸው

**organization**
1. ማኅበር. What organization do you belong to? የየትኛው ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ ነህ ?
2. ድርጅት. The secretariat of the Organization of African Unity is in Addis Ababa. የአፍሪካ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ነው
3. ማቋቋም. He is engaged in the organization of a new club. አዲስ ፡ ክበብ ፡ በማቋቋም ፡ ላይ ፡ ነው
4. አሠራር. The organization of this painting is quite remarkable. የሥዕሉ ፡ አሠራር ፡ የሚደነቅ ፡ ነው

**organize**
1. አዘጋጀ. He didn't organize the party well. ፓርቲውን ፡ በደንብ ፡ አላዘጋጀውም
2. አቋቋመ. He organized three committees. ሦስት ፡ ደርጎች ፡ አቋቋመ
3. አቀናበረ. He organized his work very well. ሥራውን ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ አቀናበረው

**organize** (vi.) ማኅበር ፡ አቋቋመ
The workers organized for higher wages. ሠራተኞቹ ፡ ደሞዝ ፡ ለማስጨመር ፡ ማኅበር ፡ አቋቋሙ
*I'll have to get my work better organized. ሥራዬ ፡ የተሻለ ፡ መሥመር ፡ እንዲይዝ ፡ ማድረግ ፡ አለብኝ

**Orient** ምሥራቅ
Buddhism is widespread in the Orient. በምሥራቅ ፡ አገሮች ፡ የቡድሃ ፡ ሃይማኖት ፡ ተስፋፍቷል

**orient** (v.) አዘነበለ
He oriented his ideas to new conditions. ሐሳቡን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ ሁኔታዎች ፡ አዘነበለ

**orient oneself** አቅጣጫውን ፡ ለየ
In ancient times, sailors used to orient themselves by the position of the stars. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ መርከበኞች ፡ አቅጣጫቸውን ፡ የሚለዩት ፡ በከዋክብት ፡ አቀማመጥ ፡ ነበር
*He found it difficult to orient himself because of the heavy fog. ጥቅጥቅ ፡ ካለው ፡ ጭጋግ ፡ የተነሣ ፡ የት ፡ እንዳለ ፡ ለማወቅ ፡ ተቸገረ

**be oriented**
*The building is oriented north. የሕንጻው ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ የዞረ ፡ ነው

**Oriental** (n.) የሩቅ ፡ ምሥራቅ ፡ ሰው
Many Orientals live in Tanzania. ታንዛንያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የሩቅ ፡ ምሥራቅ ፡ ሰዎች ፡ ይኖራሉ

**oriental** (adj.) የምሥራቅ
I like to listen to oriental music. የምሥራቅ ፡ ሙዚቃ ፡ መስማት ፡ እወዳለሁ

**orientate** መግለጫ ፡ ሰጠ
We must orientate the new members so they will know what to do. ላዲሶቹ ፡ አባሎች ፡ ተግባራቸውን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ መግለጫ ፡ ልንሰጣቸው ፡ ይገባናል

**orientation** (n.)
1. አቅጣጫ. The ship's orientation was changed from north to northeast. የመርከቡ ፡ አቅጣጫ ፡ ከሰሜን ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ምሥራቅ ፡ ተለወጠ
2. ዝንባሌ. John shows a strong orientation toward literature. ጆን ፡ ለሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ከፍተኛ ፡ ዝንባሌ ፡ አለው

**orientation** (adj.) የመተዋወቂያ
The new students attended an orientation meeting. አዲሶቹ ፡ ተማሪዎች ፡ በመተዋወቂያ ፡ ስብሰባ ፡ ተገኙ

**origin**
1. መነሾ. The origin of the quarrel is a woman. የጥሉ ፡ መነሾ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ናት
The origin of the war is still a matter of argument. የጦርነቱ ፡ መነሾ ፡ አሁንም ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ ነው
2. መሠረት. There are many Amharic words of Geez origin. መሠረታቸው ፡ ግዕዝ ፡ የሆነ ፡ ብዙ ፡ ያማርኛ ፡ ቃላት ፡ አሉ
*The origin of the Blue Nile is near Lake Tana. ጥቁር ፡ ዐባይ ፡ የሚነሣው ፡ ከጣና ፡ ሐይቅ ፡ ነው

**of humble origin** የድኻ ፡ ዘር
He is a man of humble origin, and yet he became prime minister. የድኻ ፡ ዘር ፡ ቢሆንም ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነ

**original** (n.)
1. ዋና. Is this picture an original, or is it copy? ይህ ፡ ሥዕል ፡ ዋናው ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ቅጂው ?
2. ዋና ፡ ጽሑፍ. The translation does not correspond to the original. ትርጉሙ ፡ ከዋናው ፡ ጽሑፍ ፡ ጋር ፡ አይስማማም
3. መጀመሪያ ፡ የተጻፈበት ፡ ቋንቋ. Did you read "The Glory of the Kings" in the original? ክብረ ፡ ነገሥትን ፡ መጀመሪያ ፡ በተጻፈበት ፡ ቋንቋ ፡ አንብበኸዋል ?

**original** (adj.)

1. የመጀመሪያ. My original idea was to go on a picnic. የመጀመሪያው ፡ ሐሳቤ ፡ ሽርሽር ፡ ለመሄድ ፡ ነበር

The original inhabitants of Ethiopia were Cushites. የመጀመሪያዎቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነዋሪዎች ፡ የኩሽ ፡ ዘር ፡ ነበሩ

2. አዲስ (pl. አዳዲስ). He has very original ideas. አዳዲስ ፡ የሆኑ ፡ ሐሳቦች ፡ አሉት

3. የቀድሞ. I have returned to my original idea. ወደ ፡ ቀድሞ ፡ ሐሳቤ ፡ ተመልሻለሁ

4. ዋና. I have only a copy, but the original letter is with the minister. እኔ ፡ ያለኝ ፡ ግልባጩ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ዋናው ፡ ደብዳቤ ፡ እሚኒስትሩ ፡ ዘንድ ፡ ነው

5. ራሱ ፡ ያመነጨው. She wrote an original poem. ራሷ ፡ ያመነጨችውን ፡ ግጥም ፡ ጻፈች

6. የተነሣበት. At this juncture, it is best to recall our original purpose. እዚህ ፡ ላይ ፡ የተነሣንበትን ፡ ዓላማ ፡ ማስታወስ ፡ ያሻል

*Edison had an original mind. ኤዲሰን ፡ አዳዲስ ፡ ነገሮችን ፡ የሚያመነጭ ፡ አንጐል ፡ ነበረው

**originally**

1. በመጀመሪያ. He wanted to be a doctor originally. በመጀመሪያ ፡ ሐኪም ፡ ለመሆን ፡ አስቦ ፡ ነበር

2. በመሠረቱ. Originally nomads, they learned agriculture at a later period. በመሠረቱ ፡ ዘላኖች ፡ ነበሩ ። በኋላ ፡ ግን ፡ የእርሻን ፡ ሥራ ፡ ተማሩ

3. ልዩ ፡ ዓይነት. The stage decorations were designed very originally. የመድረኩ ፡ ጌጥ ፡ የተዘጋጀው ፡ በልዩ ፡ ዓይነት ፡ ነበር

*Originally, he is from California. ትውልዱ ፡ ካሊፎርንያ ፡ ነው

**originate** (vt.) ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ፈጠረ

The Chinese originated fireworks. ርችትን ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የፈጠሩ ፡ ቻይናውያን ፡ ናቸው

**originate** (vi.) ተነሣ

The fight originated in a dispute over land. ጠቡ ፡ የተነሣው ፡ በመሬት ፡ ክርክር ፡ ነው

**ornament** (v.) አስጌጠ

She ornamented the room with flags. ክፍሉን ፡ በሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ አስጌጠችው

**ornament** (n.)

1. ጌጣ ፡ ጌጥ. We put ornaments on trees at Christmas time. በገና ፡ ጊዜ ፡ በዛፎች ፡ ላይ ፡ ጌጣ ፡ ጌጥ ፡ እናደርጋለን

2. ኩራት. She is so charming that she would be an ornament to any society. በጣም ፡ ውብ ፡ ስለሆነች ፡ ለማንኛውም ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ኩራት ፡ ልትሆን ፡ ትችላለች

**ornamental**

1. የማጌጫ. Ornamental plants decorate the entrance of the hotel. የሆቴሉ ፡ መግቢያ ፡ በማጌጫ ፡ ዕፀዋት ፡ አምሯል

2. የጌጣ ፡ ጌጥ. The chest was covered with ornamental designs. ሣጥኑ ፡ በጌጣ ፡ ጌጥ ፡ ሥዕሎች ፡ ተሸፍኗል

**ornate**

1. እጅግ ፡ ያጌጠ. I bought an ornate vase yesterday. ትላንትና ፡ እጅግ ፡ ያጌጠ ፡ ያበባ ፡ ማስቀመጫ ፡ ገዛሁ

2. የተራቀቀ. He writes in a very ornate style. እጅግ ፡ የተራቀቀ ፡ ያጻጻፍ ፡ ስልት ፡ አለው

**orphan** የሙት ፡ ልጅ

He is an orphan and cannot continue school. የሙት ፡ ልጅ ፡ ስለሆነ ፡ ትምህርቱን ፡ ሊቀጥል ፡ አይችልም

**orthodox**

1. የኦርቶዶክስ. There are several orthodox religions in the Orient. በምሥራቅ ፡ አገሮች ፡ ብዙ ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖቶች ፡ አሉ

2. ተቀባይነት ፡ ያገኘ. He holds orthodox political views. ተቀባይነት ፡ ያገኘ ፡ የፖለቲካ ፡ አስተሳሰብ ፡ አለው

**orthography** የቃላት ፡ አጻጻፍ

English orthography is very difficult. የእንግሊዝኛ ፡ ቃላት ፡ አጻጻፍ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**oscillate** አወላወለ

He oscillates between the two possibilities. በሁለት ፡ ምርጫዎች ፡ ላይ ፡ ያወላውላል

**ossify** (ossified) ጠነከረ

The soft spots in a baby's skull ossify as he grows. ትምቡክ ፡ ትምቡክ ፡ የሚለው ፡ የሕፃን ፡ አናት ፡ ሕፃኑ ፡ እያደገ ፡ ሲሄድ ፡ ይጠነክራል

**ostensible** ግልጽ

He has no ostensible reason for staying away from school. ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመቅረቱ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ የለውም

**ostensibly** ላይ ፡ ላዩን

He is ostensibly friendly, but I doubt his sincerity. ላይ ፡ ላዩን ፡ ወዳጅ ፡ ይመስላል ፡ ቅንነቱን ፡ ግን ፡ እጠራጠራለሁ

**ostentatious**

*He lives in an ostentatious manner. በኑሮ ፡ ልታይ ፡ ልታይ ፡ ይላል

**ostrich** ሰጐን
Ostrich eggs are decorations for the church. የሰጐን ፣ እንቁላል ፣ ለቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ጉልላት ፣ ጌጥ ፣ ይሆናል

**other** (adj., pron.) ሌላ
I have no other place to go. ሌላ ፣ የምሄድበት ፣ ቦታ ፣ የለኝም
I don't like these: have you others? እነዚህን ፣ አልፈልጋቸውም ፤ ሌሎች ፣ አለህ ?
His other friends are still in school. ሌሎቹ ፣ ጓደኞቹ ፣ ገና ፣ ትምህርት ፣ ቤት ፣ ናቸው
*He has no consideration for other people. ለሰው ፣ አያስብም

**other than** ከ - - - ሌላ
I see no reason for staying indoors other than the chance of rain. ዝናብ ፣ ይዘንብ ፣ ይሆናል ፣ ከማለት ፣ ሌላ ፣ እቤት ፣ ውስጥ ፣ የምቆይበት ፣ ምክንያት ፣ አይታየኝም
*We can't collect the rent other than by suing the tenant. ተከራዩን ፣ ካልከሰስን ፣ ኪራዩን ፣ ልንቀበል ፣ አንችልም

**among other things** ከተናገራቸው ፣ መሀከል
Among other things, he mentioned that his brother was a director general. ከተናገራቸው ፣ መሀከል ፣ ወንድሙ ፣ ዋና ፣ ዲሬክተር ፣ መሆኑን ፣ ገለጸ

**each other**
1. እርስ ፣ በርሳቸው. You have to help each other. እርስ ፣ በርሳችሁ ፣ መረዳዳት ፣ አለባችሁ
2. (reciprocal stem). Do you see each other every day? በየቀኑ ፣ ትገናኛላችሁ ?

**every other** ሌሎች ፣ (ግን)
John is stupid. Every other boy in the class knows the answer. ጆን ፣ ደደብ ፣ ነው ፤ በክፍሉ ፣ ውስጥ ፣ ያሉ ፣ ሌሎች ፣ ልጆች ፣ ግን ፣ በሙሉ ፣ መልሱን ፣ ያውቃሉ
*Take out every other book from the shelf! ከመጽሐፍ ፣ መደርደሪያው ፣ ላይ ፣ ያሉትን ፣ መጻሕፍት ፣ አንዳንድ ፣ እያለፍክ ፣ አንሣ

**every other (Sunday)** በየሁለት ፣ ሳምንት ፣ እሑድ ፣ እሑድ
The meetings are held every other Sunday. በየሁለት ፣ ሳምንት ፣ እሑድ ፣ እሑድ ፣ ስብሰባ ፣ ይደረጋል

**on the other side of** ከ - - - ማዶ
I saw him standing on the other side of the street. ከመንገዱ ፣ ማዶ ፣ ቆሞ ፣ አየሁት
*How do I get to the other side of the river? ወንዙን ፣ እንዴት ፣ ልሻገር ፣ እችላለሁ ?

**one after the other** አንድ ፣ ባንድ ፣ ተከታትለው
They came one after the other. አንድ ፣ ባንድ ፣ ተከታትለው ፣ መጡ

**some day or other** አንድ ፣ ቀን
I'll be coming again some day or other. አንድ ፣ ቀን ፣ ተመልሼ ፣ እመጣለሁ

**somehow or other**
1. እንደምንም ፣ ብሎ. Somehow or other, he managed to climb the mountain. እንደምንም ፣ ብሎ ፣ ተራራውን ፣ ሊወጣ ፣ ቻለ
2. ባንድ ፣ ምክንያት. He must have forgotten it somehow or other. ባንድ ፣ ምክንያት ፣ ሳይረሳው ፣ አልቀረም

**someone or other** ሰው
Are you sure that someone or other will be there to meet you? ሰው ፣ እዚያ ፣ እንደሚቀበልህ ፣ እርግጠኛ ፣ ነህ ?

**the other** ሌላው
This one is mine; the other is my sister's. ይህ ፣ የኔ ፣ ነው ፤ ሌላው ፣ ግን ፣ የእኅቴ ፣ ነው

**the other day** በቀደም ፣ ዕለት
I saw your friend the other day. ወዳጅህን ፣ በቀደም ፣ ዕለት ፣ አገኘሁት
[See also 'any, hand, no, none, one, something']

**otherwise**
1. ያለበለዚያ. Do as you are told; otherwise, you will be punished. እንደታዘዝከው ፣ ሥራ ፤ ያለበለዚያ ፣ ትቀጣለህ
What would you do otherwise? ያለበለዚያ ፣ ምን ፣ ታደርግ ፣ ነበር ?
2. በተረፈ. Otherwise, I'm satisfied with his work. በተረፈ ፣ በሱ ፣ ሥራ ፣ ተደስቻለሁ
*You obviously think otherwise. እንደሚታየው ፣ ሐሳብህ ፣ ሌላ ፣ ነው

**ought**
1. ይገባዋል. At your age, you ought to know better. በዚህ ፣ ዕድሜህ ፣ ከዚህ ፣ የበለጠ ፣ ማወቅ ፣ ይገባሃል
2. አለበት. Ought we to visit her? እሷን ፣ መጠየቅ ፣ አለብን ?
Coffee ought to be drunk while it is hot. ቡና ፣ በትኩሱ ፣ መጠጣት ፣ አለበት
3. ይኖርበታል. You ought to start at once. ባንዴ ፣ መጀመር ፣ ይኖርብሃል
*I ought to go before it rains. ከመዝነቡ ፣ በፊት ፣ ብሄድ ፣ ይሻለኛል
*He does not act as he ought. ሁኔታው ፣ የሚገባ ፣ አይደለም

**it ought to be ሳይሆን ፡ አይቀርም**
It ought to be a fine day tomorrow. ነገ ፡ ጥሩ ፡ ቀን ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም

**there ought to be እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል**
There ought to be more buses in the evening. ሲመሽ ፡ ተጨማሪ ፡ አውቶቡሶች ፡ እንዲኖሩ ፡ ያስፈልጋል

**ounce** ወቄት
We will buy an ounce of gold. አንድ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ እንገዛለን

**our**
1. የኛ. Is this our house? ይህ ፡ የኛ ፡ ቤት ፡ ነው ?
2. suffix pronoun a-ችን. Our cat is growing fast. ድመታችን ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ታድጋለች

**ours** የኛ
Ours is larger than theirs. የኛ ፡ ከነርሱ ፡ ይተልቃል
Those books are ours. እነዚያ ፡ መጻሕፍት ፡ የኛ ፡ ናቸው

**ourselves**
1. ራሳችን. Let us not fool ourselves! ራሳችንን ፡ አናታል
We ourselves would never say such a thing. እኛ ፡ ራሳችን ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አንልም
2. እኛ. Nobody likes it but ourselves. ከኛ ፡ በስተቀር ፡ ማንም ፡ አይወደውም

**be ourselves እንደ ፡ ወትሮዋችን**
We weren't quite ourselves yesterday. ትናንት ፡ እንደ ፡ ወትሮዋችን ፡ አልነበርንም

**oust**
1. አስወጣ. The umpire ousted him from the game. ዳኛው ፡ ከጨዋታው ፡ አስወጣው
2. ከሥልጣን ፡ አወረደ. They joined in a plot to oust him. እርሱን ፡ ከሥልጣን ፡ ለማውረድ ፡ በአድማ ፡ ተባበሩ

**ouster** ከሥልጣን ፡ ማውረድ
The ouster of the President was the first sign of trouble. ፕሬዚዳንቱን ፡ ከሥልጣን ፡ ማውረዱ ፡ የረብሻው ፡ መጀመሪያ ፡ ነበር

**out**
1. ከ. Choose one out of these ten! ከነዚህ ፡ ከሥሩ ፡ አንዱን ፡ ምረጥ
2. ከ - - - ውጭ. Fish cannot live out of water. ዓሣ ፡ ከውኃ ፡ ውጭ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም
My wife kept Mrs. Belaynesh company while her husband was out of town. የወይዘሮ ፡ በላይነሽ ፡ ባል ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ የኔ ፡ ሚስት ፡ አብራት ፡ ቆየች
3. በ. Drink tea out of a cup. ሻይ ፡ በኩባያ ፡ ጠጣ
The cat and dog eat out of the same dish. ድመቷና ፡ ውሻው ፡ ባንድ ፡ ሳሕን ፡ ይበላሉ

**out of ለ - - - ብሎ ፤ ለ - - - ሲል**
He did it out of spite. ለመጉዳት ፡ ብሎ ፡ አደረገው
I have to go out of courtesy. ለትሕትና ፡ ስል ፡ መሄድ ፡ አለብኝ
2. ከ - - - የተነሣ. I did it out of pity. ከሐዘኔታ ፡ የተነሣ ፡ አደረግሁት

**out there እዚያ**
What are you doing out there? እዚያ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ ?

**out with it! ተናገር**
Out with it! I want to hear what you have to say. ተናገር ፤ የምትለውን ፡ ለመስማት ፡ እፈልጋለሁ

**be at outs with each other ተጣሉ**
They are at outs with each other over the most trivial matter. ፈጽሞ ፡ በማይረባ ፡ ነገር ፡ ይጣላሉ

**be out**
1. ቀረ. He is out because of illness. በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ቀርቷል
She has been out of work ever since her illness. ከታመመች ፡ ወዲህ ፡ ከሥራ ፡ ቀርታለች
2. ቤት ፡ አልነበረም. They were out when we called them. ስንደውልላቸው ፡ ቤት ፡ አልነበሩም
3. ቤት ፡ አልዋለም. He is mostly out on Sunday. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ ቤት ፡ አይውልም
4. ወደ ፡ ውጭ ፡ ሄደ. Keep an eye on the children while I am out. ወደ ፡ ውጭ ፡ ስሄድ ፡ ልጆቹን ፡ ጠብቃቸው
5. ወጣ. The book I wanted is out. የፈለግሁት ፡ መጽሐፍ ፡ ወጥቷል
Would you please air the room while I am out. እኔ ፡ ስወጣ ፡ ክፍሉን ፡ አናፍሰው
The sun is out now. አሁን ፡ ፀሐይ ፡ ወጥታለች
The secret is out. ምስጢሩ ፡ ወጥቷል
The new edition isn't out yet. አዲሱ ፡ እትም ፡ ገና ፡ አልወጣም
6. ታትሞ ፡ ወጣ. His new book is out. አዲሱ ፡ የሱ ፡ መጽሐፍ ፡ ታትሞ ፡ ወጥቷል
7. ጠፋ. The lights are out. መብራቶቹ ፡ ጠፍተዋል

8. አለቀ. He'll be here before the week is out. ሳምንቱ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ ይመጣል
9. ተለቀቀ. Since the trial will not be held until next month, he is out on bail. ጉዳዩ ፡ እስከ ሚመጣው ፡ ወር ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለማይታይ ፡ በ ገንዘብ ፡ ዋስ ፡ ተለቋል

**be out after** ተከታተለ
He is out after you. አንተን ፡ ይከታተልሃል

**be out for** ፈለገ ፤ ፍላጎት ፡ አለው
She is only out for a good time. የምትፈልገው ፡ መደሰትን ፡ ብቻ ፡ ነው
That country is out for conquest. ያች ፡ አገር ፡ ለመውረር ፡ ፍላጎት ፡ አላት

**be out of** አለቀ(በት)
We are out of toothbrushes; we hope to get some tomorrow. የጥርስ ፡ ብሩሽ ፡ አልቆብናል ፤ ነገ ፡ ይመጣልናል ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን
*That's out of the question. ይህ ፡ በፍጹም ፡ አ ይታሰብም
*It's a dishonest scheme; I'm glad to be out of it. እቅዱ ፡ የማታለል ፡ ነበር ፤ ስለሌለሁበት ፡ ደስ ፡ ብሎኛል

**not be out to** ሐሳብ ፡ የለውም
I'm not out to reform the world. ዓለምን ፡ የ ማሻሻል ፡ ሐሳብ ፡ የለኝም
[See also 'blue, breath, door, fashion, order, power, print, town, way, work']

**out-and-out** እልም ፡ ያለ ፤ ዓይን ፡ የሌለው
He is an out-and-out scoundrel. እልም ፡ ያለ ፡ ወሮበላ ፡ ነው
That is an out-and-out lie. ያ ፡ ዓይን ፡ የሌለው ፡ ውሸት ፡ ነው

**outbid** አሸነፈ
He outbid me at the auction. በሐራጁ ፡ አሸነፈኝ

**outbound for** ወደ - - - የሚበር
He caught the outbound plane for London. ወደ ፡ ለንደን ፡ በሚበረው ፡ አውሮፕላን ፡ ተሳፈረ

**be outbound for** ወደ - - - አመራ
The plane is outbound for London. አውሮፕላኑ ፡ ወደ ፡ ለንደን ፡ ያመራል

**outbreak** መነሣት
The doctors are fighting an outbreak of malaria. ሐኪሞች ፡ የወባን ፡ መነሣት ፡ እየተከላከሉ ፡ ናቸው

**at the outbreak of** ሲጀመር
At the outbreak of the war, there were many Italians in Ethiopia. ጦርነቱ ፡ ሲጀመር ፡ ብዙ ፡ ኢጣልያኖች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነበሩ

**outburst**
*His outburst was quickly silenced by the chairman. በድንፋታ ፡ ሲናገር ፡ ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ወዲያውኑ ፡ ጸጥ ፡ እንዲል ፡ አደረገው

**outcast** ከኅብረ ፡ ሰብእ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ሰው
In the beginning, the area was settled by outcasts. በመጀመሪያ ፡ በስፍራው ፡ የሚኖሩት ፡ ከ ኅብረ ፡ ሰብእ ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ

**outclass** አስናቀ
This model outclasses all the other cars. ይህ ፡ ሞዴል ፡ ሌሎቹን ፡ መኪናዎች ፡ ሁሉ ፡ ያስንቃል

**outcome** ውጤት
The outcome of the election was known early in the evening. የምርጫው ፡ ውጤት ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ታወቀ

**outcry** ጩኸት
The outcry of the crowd shows the opposition. የተመልካቹ ፡ ሕዝብ ፡ ጩኸት ፡ ተቃውሞን ፡ የሚገልጽ ፡ ነው

**raise an outcry** ጮኸ(በት)
The crowd raised an outcry at the umpire's decision. በውሳኔው ፡ ባለመስማማት ፡ ተመልካቹ ፡ በዳኛው ፡ ላይ ፡ ጮኸበት

**(be) outdated** ዘመኑ ፡ አልፏል
This way of doing things is outdated. የዚህ ፡ ዓይነት ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፡ ዘመኑ ፡ አልፏል

**outdistance** ጥሎት ፡ በረረ
The rabbit outdistanced the hunting dog. ጥንቸሏ ፡ አዳኙን ፡ ውሻ ፡ ጥላው ፡ በረረች

**outdo** (outdid) በለጠ
He can outdo me in every subject except science. ከሳይንስ ፡ በስተቀር ፡ በሁሉም ፡ ትምህርት ፡ ሊበልጠኝ ፡ ይችላል

**outdoor** (adj.) የውጭ
He prefers an outdoor job to an office job. ከቢሮ ፡ ሥራ ፡ ይልቅ ፡ የውጭ ፡ ሥራን ፡ ይመርጣል
*Football is an outdoor game. የእግር ፡ ኳስ ፡ ከ ቤት ፡ ውጭ ፡ የሚጫወቱት ፡ ጨዋታ ፡ ነው

**outdoors** ውጭ
It's too cold to sit outdoors. ውጭ ፡ ለመቀመጥ ፡ በጣም ፡ ይበርዳል

**outer**
1. የውጭ. The outer wall of the city fell into ruin. የከተማው ፡ የውጭ ፡ ግንብ ፡ ፈረሰ

2. (= adv.) ከላይ. The outer garment is made of silk. ከላይ ፡ የለበሰችው ፡ ልብስ ፡ ከሐር ፡ የተሠራ ፡ ነው

**outfit** (v.) አደራጀ
It costs a lot of money to outfit an expedition properly. ላንድ ፡ ጉዞ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ በሚገባ ፡ ለማደራጀት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ይጠይቃል

**outfit** (n.)
1. እቃዎች. He bought his wife an expensive cooking outfit. ለሚስቱ ፡ ውድ ፡ የሆኑ ፡ የማብሰያ ፡ እቃዎች ፡ ገዛላት
2. ትጥቅ. Space travelers will need a very complicated outfit. የጠፈር ፡ ተጓዦች ፡ በጣም ፡ የተራቀቀ ፡ ትጥቅ ፡ ያስፈልጋቸዋል
3. ልብስ. She wore a silk outfit. የሐር ፡ ልብስ ፡ ለብሳለች

**outflow** የሚወጣ
We need to measure the outflow. የሚወጣውን ፡ መለካት ፡ አለብን

**outgoing**
1. የሥራ ፡ ጊዜውን ፡ የጨረሰ. The outgoing president gave his last speech today. የሥራ ፡ ጊዜያቸውን ፡ የጨረሱት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ዛሬ ፡ የመጨረሻ ፡ ንግግራቸውን ፡ አደረጉ
2. ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚላክ. The outgoing mail will be picked up at 4 o'clock. ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚላከው ፡ ደብዳቤ ፡ ባሥር ፡ ሰዓት ፡ ይሰበሰባል
*He is a very outgoing person. ከሰው ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ ይግባባል

**outgrow** (outgrew)
1. በቁመት ፡ በለጠ. By the time he was ten, he had outgrown his older brother. በዐሥር ፡ ዓመት ፡ ዕድሜው ፡ ከታላቅ ፡ ወንድሙ ፡ በቁመት ፡ በለጠ
2. (ስላደገ) ፡ ተወ. He outgrew his babyish habits. ስላደገ ፡ የሕፃንነት ፡ ጠባዩን ፡ ትቷል
3. ተለቀ(በት). Those fish will outgrow the small tank. እነዚያ ፡ ዓሣዎች ፡ ለመያዣው ፡ ይተልቁበታል
*The children have outgrown their clothes. ልጆቹ ፡ ከማደጋቸው ፡ የተነሣ ፡ ልብሳቸው ፡ አንሷቸዋል
*Our business has grown so much, we have outgrown our office. ንግዳችን ፡ በጣም ፡ ስለተስፋፋ ፡ ካንድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ዐቅም ፡ በላይ ፡ ሆኗል

**outgrowth** የሚበቅል
A callus is an outgrowth of the skin. መጅ ፡ በቆዳ ፡ ላይ ፡ የሚበቅል ፡ ነው

**be an outgrowth of**
1. በ --- ላይ ፡ ተመሥርቶ ፡ ተስፋፋ. This dictionary is an outgrowth of a small pocket dictionary. ይህ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ባንድ ፡ ትንሽ ፡ የኪስ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ላይ ፡ ተመሥርቶ ፡ የተስፋፋ ፡ ነው
2. ከመስፋፋት ፡ የተነሣ ፡ ነው. This big store is an outgrowth of a little shop. ይህ ፡ ትልቅ ፡ መደብር ፡ ከዚህ ፡ የደረሰው ፡ ትንሿ ፡ መደብር ፡ ከመስፋፋቷ ፡ የተነሣ ፡ ነው

**outhouse** የውጭ ፡ ሽንት ፡ ቤት ፤ የሰገራ ፡ ቤት
Every house should have at least an outhouse. እያንዳንዱ ፡ ቤት ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ የውጭ ፡ ሽንት ፡ ቤት ፡ (የሰገራ ፡ ቤት) ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል

**outing** ሽርሽር
They went for an outing in the mountains. ለሽርሽር ፡ ወደ ፡ ተራራዎች ፡ ሄዱ

**outlandish** ከሰው ፡ የተለየ
She wears the most outlandish clothes. በጣም ፡ ከሰው ፡ የተለየ ፡ ልብስ ፡ ትለብሳለች

**outlast**
1. ከ --- የበለጠ ፡ ቆየ. This memorial will outlast all the others. ይህ ፡ መታሰቢያ ፡ ከሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ይቆያል
2. ከ --- በረታ. On a long hike, he could always outlast me. በረጅም ፡ የእግር ፡ ሽርሽር ፡ ላይ ፡ ሁልጊዜ ፡ ከኔ ፡ ይበረታል
3. ከ --- ይልቅ ፡ በረከተ. Leather shoes usually outlast those made of cloth. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የቆዳ ፡ ጫማ ፡ ከሸራ ፡ ጫማ ፡ ይልቅ ፡ ይበረክታል

**outlaw** (v.) ከሕግ ፡ ውጭ ፡ አደረገ
They decided to outlaw public hanging. ባደባባይ ፡ ሰው ፡ መስቀልን ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ለማድረግ ፡ ወሰኑ

**outlaw** (n.) ሕገ ፡ ወጥ ፤ ሽፍታ
The outlaw was caught by the police. ሕገ ፡ ወጡ ፡ (ሽፍታው) ፡ በፖሊስ ፡ ተያዘ

**outlet**
1. መፍሰሻ. The outlet of Lake Tana is the Abbai. የጣና ፡ ሐይቅ ፡ መፍሰሻ ፡ ዐባይ ፡ ነው
2. የኮረንቲ ፡ መሰኪያ. Where is an outlet so I can plug in the radio? ሬዲዮኑን ፡ እንድሰካው ፡ የኮረንቲ ፡ መሰኪያው ፡ የት ፡ ነው ?

*Boys need an outlet for their energy. ልጆች ፡ ኀይላቸውን ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውሉበት ፡ ነገር ፡ ማግኘት ፡ አለባቸው

**outline** (v.)
1. **ዘረዘረ**. He outlined the course he was going to take. የሚጠቀምበትን ፡ ዘዴ ፡ ዘረዘረ
2. **እቅድ ፡ ገለጸ**. She outlined their trip abroad. ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሚያደርጉትን ፡ ጉዞ ፡ እቅድ ፡ ገለጸች
3. **ነደፈ**. The painter outlined two figures in his picture. ሠዓሊው ፡ በሥዕሉ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ቅርጾች ፡ ነደፈ
4. **አወጣ**. We will follow the plan he had outlined. እሱ ፡ ያወጣውን ፡ እቅድ ፡ እንከተላለን

**outline** (n.)
1. **ቅርጽ**. We could see the outlines of the mountains in spite of the mist. ምንም ፡ እንኳ ፡ ጭጋግ ፡ ቢሆን ፡ የተራራዎቹን ፡ ቅርጽ ፡ ለማየት ፡ ቻልን
2. **ረቂቅ**. Have you made an outline of what you are going to say? ስለምታደርገው ፡ ንግግር ፡ ረቂቅ ፡ አውጥተሃል ?
3. **አርእስተ ፡ ጉዳይ**. I read just the outline of the lecture. ያነበብኩት ፡ የትምህርቱን ፡ አርእስተ ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ ነው
4. **ንድፍ**. The outline of this drawing is broken. የዚህ ፡ ሥዕል ፡ ንድፍ ፡ የተያያዘ ፡ አይደለም

*The coast has a jagged outline. የባሕሩ ፡ ጠረፍ ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ ነው
[See also 'broad']

**outlive**
*He outlived all his children. ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ ሲሞቱ ፡ እሱ ፡ ቀረ

**outlive its usefulness** አሁን ፡ አይጠቅምም
The idea was good once, but it has outlived its usefulness. ድሮ ፡ ይህ ፡ ሐሳብ ፡ ጥሩ ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ግን ፡ አይጠቅምም

**outlook**
1. **የወደ ፡ ፊት ፡ ሁኔታ**. The outlook for trade is very promising. የንግዱ ፡ የወደ ፡ ፊት ፡ ሁኔታ ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልበት ፡ ነው
2. **አስተያየት**. He has a very narrow outlook on education. ስለ ፡ ትምህርት ፡ ያለው ፡ አስተያየት ፡ በጣም ፡ ጠባብ ፡ ነው

*The outlook for our picnic is not very good; it looks as if it will rain. የሽርሽራችን ፡ ነገር ፡ የሚሳካ ፡ አይመስልም ፤ ሳይዘንብ ፡ አይቀርም

*The outlook from the room includes the lake and the mountains. በመስኮቱ ፡ ከሚታዩት ፡ ነገሮች ፡ መሀከል ፡ ሐይቁና ፡ ተራራዎቹ ፡ ይገኛሉ

**outlying** ራቅ ፡ ብሎ ፡ የሚገኝ ፤ ራቅ ፡ ያለ
There are still some farms in the outlying districts of the city. ከከተማው ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ በሚገኙት ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ አሁንም ፡ የእርሻ ፡ ቦታዎች ፡ አሉ
Agitators are fomenting rebellion in outlying districts. አነሣሺዎቹ ፡ ራቅ ፡ ባሉት ፡ አውራጃዎች ፡ ውስጥ ፡ ብጥብጥ ፡ በማነሣሣት ፡ ላይ ፡ ናቸው

**outmoded** ጊዜው ፡ ያለፈበት
Her living room has outmoded furniture. የእንግዳ ፡ መቀበያ ፡ ክፍሏ ፡ ጊዜው ፡ ያለፈበት ፡ እቃ ፡ አለው

**be outmoded** ድሮ ፡ ቀረ ፤ ጊዜው ፡ አለፈ
Arranging marriages for one's children is outmoded. የወላጆች ፡ ለልጃቸውን ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛ ፡ መምረጥ ፡ ድሮ ፡ ቀርቷል ፡ (ጊዜው ፡ አልፏል)

**outnumber**
*Boys outnumber girls in the university. በዩኒቨርሲቲው ፡ ውስጥ ፡ ከሴቶች ፡ ይልቅ ፡ የወንዶች ፡ ቁጥር ፡ ይበልጣል

**(be) out-of-date** ዘመኑ ፡ አለፈ
This machine is out-of-date. ይህ ፡ መኪና ፡ ዘመኑ ፡ አልፏል

**out-of-the-way**
1. **ከመንገድ ፡ ውጭ**. This place is somewhat out-of-the-way. ይህ ፡ ቦታ ፡ ከመንገድ ፡ ውጭ ፡ ነው
2. (= adv.) **ከመንገድ ፡ ወጣ ፡ ብሎ**. He lives in an out-of-the-way place in the industrial area. ቤቱ ፡ ፋብሪካ ፡ ባለበት ፡ አካባቢ ፡ ከመንገድ ፡ ወጣ ፡ ብሎ ፡ ነው

**outpatient** ተመላላሽ ፡ በሽተኛ
Outpatients should report to the hospital at least once a week. ተመላላሽ ፡ በሽተኞች ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሆስፒታል ፡ መምጣት ፡ አለባቸው

**outplay** ከ - - - የበለጠ ፡ ተጫወተ
The other team outplayed us. ሌላው ፡ ቡድን ፡ ከኛ ፡ የበለጠ ፡ ተጫወተ

**outpost** በገጠር ፡ የሚገኝ ፡ የጠላት ፡ ሰፈር
The outpost was attacked by the natives. በገጠር ፡ የሚገኘው ፡ የጠላት ፡ ሰፈር ፡ በሀገሩ ፡ ተወላጆች ፡ ተጠቃ

**outpour** ነጐድጓድ
There was a great outpour of applause. የጭብጨባ ፡ ነጐድጓድ ፡ ነበር

**output**
1. የሥራ ፡ ምርት ፤ ውጤት. You have to increase your output. የሥራ ፡ ምርትህን ፡ (ውጤትህን) ፡ መጨመር ፡ አለብህ
2. ሥርቶ ፡ የሚያወጣ. The output of our factory is 3,000 pairs of shoes a week. ፋብሪካችን ፡ በሳምንት ፡ ሥርቶ ፡ የሚያወጣው ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ ጥንድ ፡ ጫማዎች ፡ ነው

**outrage** (v.)
1. በጣም ፡ አናደደ. His rude behavior outraged her. የብልግና ፡ ጠባዩ ፡ በጣም ፡ አናደዳት
2. አስቈጣ. The murder outraged the citizens. ግድያው ፡ ነዋሪዎቹን ፡ አስቈጣቸው

**outrage** (n.) የጭካኔ ፡ ሥራ
Killing women and children is an outrage. ሴቶችንና ፡ ሕፃናትን ፡ መግደል ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ነው

**outrageous** አሰቃቂ
This is an outrageous crime. ይህ ፡ አሰቃቂ ፡ ወንጀል ፡ ነው

**outrank** በማዕረግ ፡ በለጠ
He outranks everybody because he is the only officer. ያለው ፡ መኰንን ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ሁሉንም ፡ በማዕረግ ፡ ይበልጣል

**outright** (adj.) ፍጹም
He told an outright lie. ፍጹም ፡ ውሸት ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ተናገረ

**outright** (adv.)
1. ግልጥ ፡ አድርጎ. Tell him outright what you think of his behavior. ስለ ፡ ሁኔታው ፡ የሚሰማህን ፡ ግልጥ ፡ አድርገህ ፡ ንገረው
2. ወዲያውኑ. He was hired outright. ወዲያውኑ ፡ ተቀጠረ
3. ያኔውኑ. I paid for the car outright in cash. ለመኪናው ፡ ያኔውኑ ፡ እጅ ፡ በእጅ ፡ ከፈልኩ
4. እንዳለ. The farm was sold outright. የእርሻ ፡ ቦታው ፡ እንዳለ ፡ ተሸጠ

**outrun** (outran)
1. በሩጫ ፡ ቀደመ. He can outrun his older brother. በሩጫ ፡ ታላቅ ፡ ወንድሙን ፡ ሊቀድመው ፡ ይችላል
2. በለጠ. His expenses outran his income. ወጪው ፡ ከገቢው ፡ በለጠ

**outset, at the ~ of** በ --- መጀመሪያ ፡ ላይ
It began to rain at the outset of our trip. በጉዞዋችን ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ዝናቡ ፡ መጣል ፡ ጀመረ

**outshine** (outshone) አስናቀ
My brother outshines the other players. ወንድሜ ፡ ሌሎቹን ፡ ተጨዋቾች ፡ ያስንቃል

**outside** (n.)
1. ውጭ. The house looks very pretty from the outside. ከውጭ ፡ ሲመለከቱት ፡ ቤቱ ፡ በጣም ፡ ያምራል
2. (= adv.) ከውጭ ፡ በኩል. The outside of the house is painted green. ቤቱ ፡ ከውጭ ፡ በኩል ፡ አረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ ተቀብቷል

**outside** (adj.)
1. የውጭ. We shall need outside help for this job. ለዚህ ፡ ሥራ ፡ የውጭ ፡ እርዳታ ፡ ያስፈልገናል
2. ከፍተኛ. The outside figure given for the cost of the new school was $10,000. አዲሱ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚፈጀው ፡ ከፍተኛ ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ ዐሥር ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ነበር
3. (= adv.) ከውጭ ፡ በኩል. The outside measurements of the house are 50 ft. ከውጭ ፡ በኩል ፡ የቤቱ ፡ ልክ ፡ ኀምሳ ፡ ጫማ ፡ ነው

**outside** (prep.) ከ --- ውጭ
There was a noise outside the school. ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ውጭ ፡ ጩኸት ፡ ነበር
His trip took him outside the country. ጉዞው ፡ ከገር ፡ ውጭ ፡ ወሰደው
This is outside my plans. ይህ ፡ ከቀድኩት ፡ ውጭ ፡ ነው

**outside** (adv.)
1. ውጪው. It's cold outside. ውጪው ፡ ብርድ ፡ ነው
2. እደጅ. A peddler is hawking his wares outside. እደጅ ፡ አንድ ፡ ሱቅ ፡ በደረቱ ፡ ይህን ፡ ፈላጊ ፡ እያለ ፡ ይጮኻል

**outside of** ከ --- ሌላ
I wouldn't trust anyone here outside of you. ካንተ ፡ ሌላ ፡ እዚህ ፡ ማንንም ፡ አላምንም

**outside of this** ከዚህ ፡ ሌላ
Outside of this, there's no other possibility. ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ምርጫ ፡ የለም

**at the outside** ቢበዛ
I can do it in a week, at the outside. ቢበዛ ፡ በሳምንት ፡ ልሠራው ፡ እችላለሁ
[See also 'pale']

**outsider** የውጭ ፡ ሰው
He is an outsider and does not know what's going on. የውጭ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ የሚደረገውን ፡ ነገር ፡ አያውቅም
The intimate gathering was interrupted by outsiders. የወዳጅነት ፡ ስብሰባው ፡ በውጭ ፡ ሰዎች ፡ ተረበሸ

**outskirts**
1. አካባቢ. The outskirts of Addis Ababa consist of small buildings. የአዲስ ፡ አበባ ፡ አካባቢ ፡ ትናንሽ ፡ ሕንጻዎች ፡ አሉት
2. ዳር. Hyenas occasionally come into the outskirts of the town. ጅቦች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ዳር ፡ ይመጣሉ

**outspoken**
*He's very outspoken in his remarks. አስተያየቱን ፡ መግለጽ ፡ አይፈራም

**outspread** (= ger.) ዘርግቶ
He rushed at her with arms outspread. እጆቹን ፡ ዘርግቶ ፡ ወደ ፡ እሷ ፡ ሮጠ
*I saw an eagle with outspread wings. ክንፉን ፡ የዘረጋ ፡ ንስር ፡ አየሁ

**outstanding**
1. የታወቀ. He is an outstanding scholar. የታወቀ ፡ ሊቅ ፡ ነው
2. ጐልቶ ፡ የሚታይ. An outstanding feature of Paris is the Eiffel Tower. በፓሪስ ፡ ውስጥ ፡ ጐልቶ ፡ የሚታየው ፡ የአይፈል ፡ ታወር ፡ ነው
3. እጁ ፡ ያልገባ. I have a lot of money outstanding. እጄ ፡ ያልገባ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አለኝ

**be outstanding** ተወዳዳሪ ፡ የለውም
The performance of his work was outstanding. የሥራው ፡ ቅልጥፍና ፡ ተወዳዳሪ ፡ የለውም
[See also 'credit']

**outstretched** (= adv.) ዘርግቶ
*He received me with outstretched arms. ክንፉን ፡ ዘርግቶ ፡ ተቀበለኝ

**lie outstretched** ተዘረረ ፤ ለጥ ፡ ብሎ ፡ ተኛ
He lay outstretched on the grass. ሣሩ ፡ ላይ ፡ ተዘረረ ፡ (ለጥ ፡ ብሎ ፡ ተኛ)

**outstrip** (outstripped) አስከነዳ
He can outstrip most boys in sports and in studies. በስፖርትና ፡ በትምህርት ፡ አብዛኞቹን ፡ ልጆች ፡ ሊያስከነዳ ፡ ይችላል

**outstrip in running** ከ --- ፈጠነ
A horse can outstrip a man in running. ፈረስ ፡ ከሰው ፡ ይፈጥናል

**outward** (adj.) የውጭ
The two things are the same in outward appearance, but different in essence. ሁለቱ ፡ ነገሮች ፡ በውጭ ፡ መልካቸው ፡ አንድ ፡ ሲሆኑ ፡ በባሕሪይ ፡ ግን ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው
*The outward appearance of things can be deceptive. መልክ ፡ አይቶ ፡ መፍረድ ፡ በጣም ፡ አሳሳች ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

**outward** (adv.) ወደ ፡ ውጭ
The door opens outward. በሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይከፈታል

**outward-bound** ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚሄድ
The outward-bound traffic is quite heavy today. ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚሄደው ፡ መኪና ፡ ዛሬ ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ነው

**turn outward** ገለበጠ
He turned his coat with the lining outward. የኮቱን ፡ ገበር ፡ ገለበጠው

**outwardly** ሲያዩት ፤ ላይ ፡ ላዩን
Outwardly she looks gentle. ሲያይዋት ፡ ጨዋ ፡ ትመስላለች
Outwardly, he was calm, but inwardly he was seething with rage. ላይ ፡ ላዩን ፡ የረጋ ፡ ነበር ፤ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ግን ፡ በንዴት ፡ ጨሶ ፡ ነበር

**outwear** (outwore) ከ --- ይልቅ ፡ በረከተ
This suit will outwear any other. ይህ ፡ ልብስ ፡ ከማንኛውም ፡ ልብስ ፡ ይልቅ ፡ ይበረከታል

**outweigh** ከ --- በላይ ፡ መዘነ ፤ ከ --- አመዘነ
This outweighs the forty pounds allowed us. ይህ ፡ ከተፈቀደልን ፡ አርባ ፡ ፓውንድ ፡ በላይ ፡ ይመዝናል
The advantages outweigh the disadvantages. ጥቅሙ ፡ ከጉዳቱ ፡ ያመዝናል

**outwit** (outwitted) አሞኘ
The prisoner outwitted his guards and escaped. እስረኛው ፡ ዘበኞቹን ፡ አሞኝቶ ፡ አመለጠ

**oval** ሞላላ
An egg has an oval shape. እንቁላል ፡ ሞላላ ፡ ቅርጽ ፡ አለው

**ovation** ከፍ ፡ ያለ ፡ ጭብጨባ
When he finished his speech, he received an ovation. ንግግሩን ፡ ሲጨርስ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጭብጨባ ፡ ተደረገለት

**oven**
1. ምድጃ. She heated the oven. ምድጃውን ፡ እሳት ፡ አነደደችበት
2. የዳቦ ፡ መጋገሪያ. My aunt bakes bread in an

oven. አክስቴ ፡ ዳቦ ፡ በዳቦ ፡ መጋገሪያው ፡ ት ጋግራለች

**over** (prep.)

1. በ -- ላይ. Telegraph wires over the streets are ugly. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ የቴሌግራም ፡ ገመዶች ፡ ያስቀይማሉ

He jumped over the fence. ባጥሩ ፡ ላይ ፡ ዘ ለለ

Don't fight over it! በሱ ፡ ላይ ፡ አትጣሉ

Put your jacket over the sweater! በሹራብህ ፡ ላ ይ ፡ ኮትህን ፡ ደርብ

We drove over the new road yesterday. ትናንት ፡ ባዲሱ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ነዳን

2. ከ -- በላይ. My room is over the kitchen. ክፍሌ ፡ ከወጥቤቱ ፡ በላይ ፡ ነው

A general is over a colonel. ጄኔራል ፡ ከኮሎኔ ል ፡ በላይ ፡ ነው

There is a lamp over my bed. ከአልጋዬ ፡ በላይ ፡ መብራት ፡ አለ

The water was over his shoulders. ውኃው ፡ ከ ትከሻው ፡ በላይ ፡ ነበር

3. (noun) + ላይ. Your coat is hanging over the chair. ኮትህ ፡ ወንበሩ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሏል

The weeds grew over the road. መንገዱ ፡ ላይ ፡ አረም ፡ በቀለበት

He fell over the dog sleeping in the doorway. ደጃፉ ፡ ላይ ፡ የተኛው ፡ ውሻ ፡ አደናቅፎት ፡ ወ ደቀ

4. በ -- ላይ ፡ አሻግር. He batted the ball over the fence. ኳሱን ፡ ባጥሩ ፡ ላይ ፡ አሻግሮ ፡ ለጋት

I can't see over his head, he is so tall. ረጅም ፡ ስ ለሆነ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አሻግሬ ፡ ለማየት ፡ አልችልም

5. ከ -- ይልቅ. They chose him over me. ከኔ ፡ ይ ልቅ ፡ እሱን ፡ መረጡት

6. ከ --- የበለጠ. We spent over twenty dollars yesterday. ትናንት ፡ ከሃያ ፡ ብር ፡ የበለጠ ፡ አጠፋን

7. ከ --- ኋላ. She lives over the hill. ከኮረብ ታው ፡ ኋላ ፡ ትኖራለች

8. በ --- ሁሉ. The news spread over the country. ወሬው ፡ ባገሩ ፡ ሁሉ ፡ ተነዛ

9. ስለ. He is troubled over his health. ስለ ፡ ጤንነቱ ፡ ተቸግሯል

10. (= adv.) በሙሉ. Next year we shall travel over Europe. በሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ አውሮፓን ፡ በሙሉ ፡ እንዞራለን

*The committee adjourned over the holidays. የደርጉ ፡ ስብሰባ ፡ በዓሉ ፡ እስከሚያልቅበት ፡ ጊ ዜ ፡ ድረስ ፡ ተላለፈ

**over** (adv.)

1. እንደገና. Write the letter over! ደብዳቤውን ፡ እ ንደገና ፡ጻፈው

The work was so badly done, I had to do it over. ሥራው ፡ በደንብ ፡ ባለመሠራቱ ፡ እንደገ ና ፡ መሥራት ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ

2. ከዚያ ፡ በላይ. Children of 14 and over have to pay more. ዐሥራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ የሆናቸው ና ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ልጆች ፡ ይበልጥ ፡ መክፈል ፡ አለባቸው

**over and above** ከ --- በላይ

The waiters get tips over and above their wages. አሳላፊዎች ፡ ከደሞዛቸው ፡ በላይ ፡ጉ ርሻ ፡ ያገኛሉ

**over and over again** ደጋግሞ

He asked the same question over and over again. ያንኑ ፡ ጥያቄ ፡ ደጋግሞ ፡ ጠየቀ

**over by** ከ --- ላይ

He lives over by the hill. ከዚያ ፡ ጉብታ ፡ ላይ ፡ ይኖራል

**over here** እዚህ ፤ እዚህ ፡ ጋ

Right over here is where I want the table. ጠረጴዛው ፡ ልክ ፡ እዚህ ፡ እንዲሆን ፡ ነው ፡ የም ፈልገው

Over here the room is cooler. እዚህ ፡ ጋ ፡ ክ ፍሉ ፡ ቀዝቀዝ ፡ ያለ ፡ ነው

**over there** እዚያ ፡ ጋ ፤ እዚያ

What's over there? እዚያ ፡ ጋ ፡ ምን ፡ አለ ?

Who is the fourth boy in the group over there? እዚያ ፡ ከቆሙት ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ አራተኛ ው ፡ ማነው ?

**over (the) years** ከጊዜ ፡ በኋላ

His personality hardened over the years. ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ ጠባዩ ፡ ግትር ፡ ሆነ

**be over**

1. አለቀ. When is the show over? ቲያትሩ ፡ መ ቼ ፡ ያልቃል ?

2. አበቃ. It's all over with him. የሱ ፡ ነገር ፡ አ በቃ

3. ከ -- በለጠ. Is it over three miles? ከሦስት ፡ ማይል ፡ ይበልጣል ?

**for over** ከ -- በላይ

He spoke for over an hour. ካንድ ፡ ሰዓት ፡ በላይ ፡ ተናገረ

**from over** ከ -- ባሻገር

We heard voices from over the fence. ከጥሩ ፡ ባሻገር ፡ ድምፅ ፡ ሰማን

[See also 'all, well, yonder']

**overage** በዕድሜ ፡ ገፉ ፡ ያለ

The government pensioned off the overage officers. በዕድሜ ፡ ገፉ ፡ ያሉትን ፡ መኰንኖች ፡ መንግሥት ፡ ጡረታ ፡ መደባቸው

**overall** ጠቅላላ
The overall cost is $50. ጠቅላላ ፡ ዋጋው ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ነው
The overall length of the boat was 40 feet. የጀልባው ፡ ጠቅላላ ፡ እርዝማኔ ፡ አርባ ፡ ጫማ ፡ ነበር

**overboard** ከመርከቡ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፤ ከመርከብ ፤ ወደ ፡ ባሕር
Throw that heavy box overboard! ያንን ፡ ከባድ ፡ ማጥን ፡ ከመርከቡ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ጣለው
He jumped overboard and swam ashore. ከመርከብ ፡ ዘሎ ፡ ወደ ፡ ዳርቻ ፡ ዋኘ
We threw some boxes overboard to lighten the boat. መርከቢ ፡ ጭነቱ ፡ እንዲቀላት ፡ በማለት ፡ ጥቂት ፡ ማጥኖች ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ጣልን

**go overboard**
*The critics went overboard in praising the last film. ተቾቹ ፡ ያለፈውን ፡ ፊልም ፡ ከሚገባው ፡ በላይ ፡ አወደሱት

**throw overboard** ዋጋ ፡ አሳጣ
They threw the plan overboard. እቅዱን ፡ ዋጋ ፡ አሳጡት

**overcast** ደመናማ
We stayed home because the sky was overcast. ሰማዩ ፡ ደመናማ ፡ ስለሆነ ፡ እቤት ፡ ዋልን

**overcharge** ከዋጋው ፡ በላይ ፡ አስከፈለ
He overcharged me by $50. ከዋጋው ፡ በላይ ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ አስከፈለኝ

**overcoat** ካፖርት
Put on your overcoat! ካፖርትህን ፡ ደርብ

**overcome** (overcame)
1. አሸነፈ ፤ ተወጣ. She had many difficulties to overcome. ብዙ ፡ ችግሮችን ፡ ማሸነፍ ፡ ነበረባት
He overcame a mountain of difficulties. መዓት ፡ ዕንቅፋቶችን ፡ ተወጣ
2. ተጫነ. Sadness has overcome him since his mother's death. እናቱ ፡ ከሞቱ ፡ ጀምሮ ፡ ሐዘን ፡ ተጭኖታል
3. ራሱን ፡ እንዲስት ፡ አደረገ. The heavy smoke overcame two firemen. ከባዱ ፡ ጪስ ፡ ሁለት ፡ የእሳት ፡ አደጋ ፡ ሠራተኞችን ፡ ራሳቸውን ፡ እንዲስቱ ፡ አደረጋቸው
4. አቃለለ. The loan will go far in overcoming our financial troubles. ብድሩ ፡ የገንዘብ ፡ ችግራችንን ፡ ብዙ ፡ ያቃልልልናል
5. አስወገደ. The close communion between friends helps in overcoming difficulties. የወዳጆች ፡ መተሳሰር ፡ ችግሮችን ፡ ለማስወገድ ፡ ይረዳል

**be overcome**
1. ተዋጠ. She was overcome with fright when she saw the hyena. ጅቡን ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ በድንጋጤ ፡ ተዋጠች
She was overcome with joy when she won the prize. ሽልማቱን ፡ ባገኘች ፡ ጊዜ ፡ በደስታ ፡ ተዋጠች
2. ተወገደ. The child's stubborness could not be overcome by threats. የልጁ ፡ እልህ ፡ በማስፈራራት ፡ ሊወገድ ፡ አልተቻለም

**(be) overcrowded** ሰው ፡ ጥቅጥቅ ፡ አለ
The bus was so overcrowded it broke down. አውቶቡሱ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ሰው ፡ ጥቅጥቅ ፡ በማለቱ ፡ ተሰበረ

**overdo** (overdid)
1. ከመጠን ፡ አለፈ. I am allowed to play tennis as long as I don't overdo it. ከመጠን ፡ እስካላለፍኩ ፡ ድረስ ፡ ቴኒስ ፡ እንድጫወት ፡ ተፈቅዶልኛል
2. ከልክ ፡ በላይ ፡ አበሰለ. Don't overdo the meat! ሥጋውን ፡ ከልክ ፡ በላይ ፡ አታብስለው

**be overdone** ተጋነነ
The funny scenes in the play were overdone. በቲያትሩ ፡ ውስጥ ፡ አሥቂኝ ፡ የሆኑት ፡ ክፍሎች ፡ ተጋነዋል

**overdose**
*His death was traced to an overdose of medicine. የሞተው ፡ መድኃኒት ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ በመውሰዱ ፡ መሆኑ ፡ ታወቀ

**overdraw** (overdrew) ከ - - በላይ ፡ አወጣ
I have overdrawn my account. ካለኝ ፡ በላይ ፡ ከሒሳቤ ፡ አውጥቻለሁ

**(be) overdue**
1. ሳይከፈል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆነው. These bills are overdue. ሒሳቡ ፡ ሳይከፈል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖታል
2. ዘገየ. Everyone is worried because the plane is five hours overdue. አውሮፕላኑ ፡ አምስት ፡ ሰዓት ፡ ስለዘገየ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተጨንቋል

**be long overdue**
*The reform in the school system was long overdue. የትምህርት ፡ ሥርዓት ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ መሻሻል ፡ ነበረበት

**overeating** አብዝቶ ፡ መብላት
Overeating is a detriment to health. አብዝቶ ፡ መብላት ፡ ለጤንነት ፡ ጉጂ ፡ ነው

**overestimate**
He overestimated his strength. ጉልበቱን ፡ ከሚገባው ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ገመተው

**overflow** (vt.)
1. ሞልቶ ፡ ፈሰሰ. The milk is overflowing the cup. ወተቱ ፡ ሲኒውን ፡ ሞልቶ ፡ ፈሰሰ
2. ከ - - - ተረፈ. The crowd overflowed the hall and filled the corridor. ሕዝቡ ፡ ከዳራሹ ፡ ተርፎ ፡ መተላለፊያውን ፡ ሞላው
*The river overflowed its banks. ወንዙ ፡ አፍ ፡ እስከአፉ ፡ ሞልቶ ፡ ተትረፍርፏል

**overflow** (vi.)
1. ሞልቶ ፡ ፈሰሰ. Stop pouring, or your glass will overflow. አትቅዳ ፡ ያለበለዚያ ፡ ብርጭቆህ ፡ ሞልቶ ፡ ይፈሳል
2. ሞላ. In the rainy season, the river overflows causing great damage. በክረምቱ ፡ ጊዜ ፡ ወንዙ ፡ ሞልቶ ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ያደርሳል
*The river overflowed its banks. ወንዙ ፡ ሞልቶ ፡ ዳርቻውን ፡ አልፎ ፡ ፈሰሰ

**overflow into** እስጨነቀ
The crowd overflowed into the hall. ሕዝቡ ፡ መተላለፊያውን ፡ አስጨነቀ

**overgrow** ሸፈነ
Every year we kill the weeds that overgrow the path. የእግር ፡ መንገዱን ፡ የሚሸፍነውን ፡ አረም ፡ በያመቱ ፡ እናርማለን

**be overgrown**
1. ለበሰ. The clearing is now overgrown with bushes. የተመነጠረው ፡ መሬት ፡ አሁን ፡ ቁጥቋጦ ፡ ለብሷል
2. ተዋጠ. The shore of the lake is overgrown with reeds. የባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ በቄጠማ ፡ ተውጧል
3. በጣም ፡ ትልቅ ፡ ነው. He is overgrown for his age. ለዚህ ፡ ዕድሜው ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ነው

**overhang** (overhung)
1. ከ - - - አልፎ ፡ ወጣ. The roof overhangs the house. ጣሪያው ፡ ከቤቱ ፡ አልፎ ፡ ወጥቷል
2. ተንዠረገገ. Trees overhang the brook. የዛፍ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ጅረቱ ፡ ላይ ፡ ተንዠርግጓል

**overhaul**
1. መረመረ. The mechanics overhaul the plane after every flight. ከያንዳንዱ ፡ በረራ ፡ በኋላ ፡ ሜካኒኮቹ ፡ አውሮፕላኑን ፡ ይመረምራሉ
2. ቀደመ. An automobile can overhaul any horse. መኪና ፡ ፈረስን ፡ ይቀድማል
3. ደረሰ(በት). The police car overhauled the speeding truck. የፖሊስ ፡ መኪና ፡ በፍጥነት ፡ የሚሄደውን ፡ መኪና ፡ ደረሰበት

**overhead** (n.) የሥራ ፡ ማስኬጃ ፡ ወጪ
A good businessman tries to keep his overhead down. ጥሩ ፡ ነጋዴ ፡ የሥራ ፡ ማስኬጃ ፡ ወጪውን ፡ ለመቀነስ ፡ ይሞክራል

**overhead** (adv.)
1. እላይኛው ፡ ፎቅ ፡ ላይ. The people overhead are too noisy. እላይኛው ፡ ፎቅ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ጫጫታ ፡ ያበዛሉ
2. ከበላዩ. The bird settled on a branch overhead. ወፏ ፡ ከበላዩ ፡ ካለው ፡ ቅርንጫፍ ፡ አረፈች
3. አናት ፡ ላይ. The sun is overhead. ፀሐይ ፡ አናት ፡ ላይ ፡ ነች
*The stars twinkled overhead. የሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ ይላሉ

**overhear**
1. ጆሮው ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ አለ. I overheard him saying he didn't like me. አልወደውም ፡ ሲል ፡ ጆሮዬ ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ አለ
2. አዳመጠ. They spoke so loud that I could not help overhearing what they said. ጮክ ፡ ብለው ፡ ይነጋገሩ ፡ ስለነበር ፡ የሚሉትን ፡ ላላዳምጥ ፡ አልቻልኩም

**(be) overlaid** ተለበጠ
The box is overlaid with ivory. ሣጥኑ ፡ በዝሆን ፡ ጥርስ ፡ የተለበጠ ፡ ነው

**overlap** (overlapped) ተደራረበ
The functions of the two departments overlap. የሁለቱ ፡ ክፍሎች ፡ ሥራ ፡ ይደራረባል

**overload** ከመጠን ፡ በላይ ፡ ሞላ
She overloaded the washing machine. የልብስ ፡ ማጠቢያውን ፡ መኪና ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ልብስ ፡ ሞላችበት

**be overloaded**
1. በዛ(በት). I am overloaded with work. ሥራ ፡ በዝቶብኛል
2. ጭነት ፡ በዛ(በት). The truck was overloaded and broke down. ካሚዮኑ ፡ ጭነት ፡ ስለበዛበት ፡ ተሰበረ

**overlook**
1. አለፈ. Shall I overlook his mistake? ስሕተቱን ፡ ልለፈው ?
2. ሳያስተውለው ፡ ቀረ. He must have overlooked it. ሳያስተውለው ፡ ቀርቶ ፡ ይሆናል
3. ተቈጣጠረ. She had to overlook a large number of employees. ብዙ ፡ ሠራተኞች ፡ መቈጣጠር ፡ ነበረባት
4. በ - - ጉልቶ ፡ ታየ. The municipality building overlooks the city. የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ሕንጻ ፡ በከተማው ፡ ጉልቶ ፡ ይታያል
*My room overlooks the Piazza. ክፍሌ ፡ ውስጥ ፡ ሆኜ ፡ ፒያሳን ፡ ማየት ፡ ይቻላል

**overlord** ጌታ
The overlord was accompanied by many people on his way to the market. ጌትዬው ፡ ገበ ያ ፡ ሲወጡ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ዐጀባቸው

**overly** ከልክ ፡ ያለፈ
He is overly polite. ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ትሑት ፡ ነው

**overnight** (adj.) ያንድ ፡ ምሽት
The corporal got an overnight pass. ያሥር ፡ አለቃው ፡ ያንድ ፡ ምሽት ፡ ፈቃድ ፡ ተሰጠው

**overnight** (adv.)
1. በንዳፍታ. He got rich overnight. በንዳፍታ ፡ ባለጸጋ ፡ ሆነ
2. በንዴ. Fear aged him overnight. በንዴ ፡ ፍርሃት ፡ አሸመገለው
3. በንድ ፡ ቀን. Preparations for the party were made overnight. ለግብዣው ፡ መሰናዶ ፡ በንድ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ የተደረገው
4. ባንድ ፡ ሌሊት. The cement set overnight. ሲሚንቶው ፡ ባንድ ፡ ሌሊት ፡ ደረቀ

**overnight stay** ያሳለፈው ፡ ሌሊት
My overnight stay at my friend's was very pleasant. ጓደኛዬ ፡ ዘንድ ፡ ያሳለፍኩት ፡ ሌሊት ፡ በጣም ፡ አስደሳች ፡ ነበር

**stay overnight** አደረ
I intend to stay there overnight. እዚያ ፡ ላድር ፡ እስቢያለሁ
[See also 'stop']

**overpass** (v.) አለፈ
We had overpassed the frontier during the night. ሌሊቱን ፡ በድንበሩ ፡ አልፈን ፡ ነበር

**overpass** (n.) ተደራራቢ ፡ ድልድይ
This highway has several overpasses. በዚህ ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ተደራራቢ ፡ ድልድዮች ፡ አሉ

**overpay** (overpaid) ትርፍ ፡ ከፈለ
He overpaid fifty cents for his lunch. ለምሳው ፡ ኀምሳ ፡ ሳንቲም ፡ ትርፍ ፡ ከፈለ

**be overpaid**
*He was overpaid for the work he did. ለሥራው ፡ ከሚገባ ፡ በላይ ፡ ተከፈለው

**overpayment, receive an** ~ ከሚገባው ፡ በላይ ፡ ተከፈለው
I received an overpayment for my services. ላገልግሎቴ ፡ ከሚገባኝ ፡ በላይ ፡ ተከፈለኝ

**overpower**
1. አሸነፈ. He overpowered the robber and tied him up. ቀማኛውን ፡ አሸንፎ ፡ አሰረው
Grief overpowered her. ኀዘን ፡ አሸነፋት
2. አየለ. The Occident succeeded in overpowering the Orient for a while. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ምዕራባዊው ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ በምሥራቃውያን ፡ ላይ ፡ አይሎ ፡ ነበር

**be overpowered** ሊቋቋም ፡ አልቻለም
He was overpowered by the heat. የፀሐዩን ፡ ሐሩር ፡ ሊቋቋም ፡ አልቻለም

**(be) overpowering**
The stench is overpowering. ግማቱ ፡ አፍንጫ ፡ ይበጥሳል
The heat is overpowering. ሙቀቱ ፡ በቆሎ ፡ ይጠብሳል

**overproduction** ከተፈላጊው ፡ በላይ ፡ እቃ ፡ መሥራት
Because of overproduction, they had to close the factory for two weeks. ከተፈላጊው ፡ በላይ ፡ እቃ ፡ ከመሥራቱ ፡ የተነሣ ፡ ፋብሪካው ፡ ለሁለት ፡ ሳምንት ፡ መዘጋት ፡ ነበረበት

**overrate** ከመጠን ፡ በላይ ፡ አድርጎ ፡ ገመተ
He overrated his abilities. ችሎታውን ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ አድርጎ ፡ ገመተ

**override** (overrode)
1. ሻረ. The new rule overrides all previous ones. አዲሱ ፡ ደንብ ፡ የቀድሞዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ይሽራቸዋል
2. ችላ ፡ አለ. He overrode my objections and went to the party. ተቃውሞዬን ፡ ችላ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ፓርቲው ፡ ሄደ
3. ከ--- በለጠ. The present emergency overrides other matters. ያሁኑ ፡ አስቸኳይ ፡ ሁኔታ ፡ ከሌሎቹ ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ይበልጣል

**overrule** ገለበጠ
The judge overruled the previous decision. ዳኛው ፡ የፊተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ገለበጠው

**be overruled** ሐሳቡ ፡ ወደቀ
He was overruled by the majority. ሐሳቡ ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ወደቀ

**overrun** (overran)
1. ወረረ. The looting hordes overran the province. ዘራፊዎች ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቱን ፡ ወረሩት
2. ከ --- ወጥቶ ፡ አረፈ. The new jet had overrun the landing field. አዲሱ ፡ ጄት ፡ ከሚዳው ፡ ወጥቶ ፡ አረፈ
3. በላ. Weeds had overrun the old garden. የድሮውን ፡ ያትክልት ፡ቦታ ፡ አረም ፡ በልቶታል
*The speaker overran the time set for him. ተናጋሪው ፡ ከተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ ተናገረ

**be overrun** ተወረረ
The house was overrun by rats. ቤቱ ፡ በአይጥ ፡ ተወርሮ ፡ ነበር

**overseas** ውጭ ፡ አገር ፤ ባሕር ፡ ማዶ
Have you ever been overseas? ውጭ ፡ አገር ፡ (ባሕር ፡ ማዶ) ፡ ሄደህ ፡ ታውቃለህ ?

**overseas** (adj.) የባሕር ፡ ማዶ
Great Britain has granted independence to most of her overseas possessions. ታላቋ ፡ ብሪታንያ ፡ ለብዙዎቹ ፡ የባሕር ፡ ማዶ ፡ ይዞታዎቿ ፡ ነጻነት ፡ ሰጥታለች

**oversee** (oversaw)
1. ተቈጣጠረ. I have to oversee everything he does. የሚሠራውን ፡ ሁሉ ፡ መቈጣጠር ፡ አለብኝ
2. ተመለከተ. He happened to oversee the burglar leaving the premises. ሌባው ፡ ከግቢው ፡ ሲወጣ ፡ ተመለከተው

**overseer** ተቈጣጣሪ
The overseer reported the theft to me. ተቈጣጣሪው ፡ የተደረገውን ፡ ስርቆት ፡ ለኔ ፡ አመለከተ

**overshadow**
1. አስናቀ. The older boy overshadowed his brother in school. ትልቁ ፡ ልጅ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ወንድሙን ፡ አስናቀ
2. አጨለመ(በት). Troubles overshadowed his life. ችግር ፡ ሕይወቱን ፡ አጨለመበት
3. ሸፈነ. His quick temper overshadows his real kindness. ግልፍተኛነቱ ፡ እውነተኛ ፡ ደግነቱን ፡ ይሸፍነዋል

**oversight** ቁጥጥር
While children are at school, they are under their teacher's oversight and direction. ልጆች ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ሳሉ ፡ ባስተማሪው ፡ ቁጥጥርና ፡ መሪነት ፡ሥር ፡ ናቸው

**by oversight** በስሕተት
Your name was omitted by oversight. ስምህ ፡ የተዘለለው ፡ በስሕተት ፡ ነበር

**oversize** ትልቅ
This is an oversize tire, and I cannot use it. ይህ ፡ ጎማ ፡ ትልቅ ፡ ስለሆነ ፡ ልገለገልበት ፡ አልችልም

**oversleep** በጣም ፡ አርፍዶ ፡ ነቃ ፤ ተኝቶ ፡ አረፈደ
I overslept this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ በጣም ፡ አርፍጄ ፡ ነቃሁ
He overslept and missed the train. ተኝቶ ፡ ስላረፈደ ፡ ባቡር ፡ አመለጠው

**overstate** አጋነነ
He always overstates his case. እሱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ጉዳዩን ፡ ያጋንነዋል

**overstay** ከ - - ጊዜ ፡ በላይ ፡ ቆየ ፤ የ - - - ጊዜ ፡ አሳለፈ
He overstayed his leave. ከፈቃድ ፡ ጊዜው ፡ በላይ ፡ ቆየ ፡ (የፈቃድ ፡ ጊዜ ፡ አሳለፈ)

**overt** ግልጽ
Violation of a peaceful country's frontier is an overt act of aggression. ያንድ ፡ ሰላማዊ ፡ ሀገርን ፡ ድንበር ፡ መጣስ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ የወረራ ፡ ተግባር ፡ ነው

**overtake** (overtook)
1. ደረሰ(በት). He overtook the running thief and knocked him down. ይሸሽ ፡ የነበረውን ፡ ሌባ ፡ ደረሰበትና ፡ መቶ ፡ ጣለው
A sudden storm overtook us. ድንገተኛ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ደረሰብን
2. ቀደመ. Japan overtook many countries in steel production. በብረት ፡ ሥራ ፡ ጃፓን ፡ ብዙዎቹን ፡ አገሮች ፡ ቀደመቻቸው

**overthrow** (overthrew) ገለበጠ
Mussolini overthrew the elected government in Italy. ሙሶሊኒ ፡ በሕዝብ ፡ የተመረጠውን ፡ የኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ ገልብጦ ፡ ነበር

**overtime** ሰዓት ፡ እላፊ ፤ የትርፍ ፡ ጊዜ
I had to work overtime. ሰዓት ፡ እላፊ ፡ መሥራት ፡ ነበረብኝ
Overtime work is well paid, but it is sometimes onerous. ለትርፍ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ ይከፈላል ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ከባድ ፡ ነው

**overturn** (vt.) ገለበጠ ፤ ደፋ
The maid overturned the flower vase. ገረዲቱ ፡ ያበባ ፡ ማስቀመጫውን ፡ ገለበጠችው
Whether by accident or design, he overturned the lamp. ሳያውቅ ፡ ይሁን ፡ ዐውቆ ፡ ኩራዙን ፡ ደፋው
The rebels overturned the government. ዐመፀኞቹ ፡ መንግሥቱን ፡ ገለበጡ

**overturn** (intr.) ተገለበጠ
If the boat should overturn, don't panic. ድንገት ፡ ጀልባው ፡ ቢገለበጥ ፡ አትሸበር

**overture, make (overtures)** ፍንጭ ፡ አሳየ
The enemy is making overtures for peace. ጠላት ፡ ሰላም ፡ ለማድረግ ፡ ፍንጭ ፡ በማሳየት ፡ ላይ ፡ ነው

**(be) overweight** ከሚገባው ፡ በላይ ፡ ክብደት ፡ አለው
He is fifty pounds overweight. ከሚገባው ፡ በላ ይ ፡ አምሳ ፡ ፓውንድ ፡ ክብደት ፡ አለው

**overwhelm**
1. በዛ(በት). Your kindness overwhelms me. ደግነትህ ፡ በዛብኝ
2. ኀይል ፡ ሰበረ. Our army overwhelmed the enemy. ጦራችን ፡ የጠላትን ፡ ኀይል ፡ ሰበረ

**be overwhelmed** ተዋጠ
He was overwhelmed by grief. በሐዘን ፡ ተውጦ ፡ ነበር

**overwork** (v.) ከሚገባው ፡ በላይ ፡ አለፋ
The supervisor overworked the laborers. ከበ ላው ፡ ሠራተኞቹን ፡ ከሚገባው ፡ በላይ ፡ አለፋቸው

**overwork oneself** እስኪደክመው ፡ ሠራ
He doesn't overwork himself. እስኪደክመው ፡ አይሠራም

**overwork** (n.) የሥራ ፡ ብዛት
His illness was induced by overwork. ሕመሙ ፡ የተነሣበት ፡ ከሥራ ፡ ብዛት ፡ ነው

**from overwork** ከመጠን ፡ በላይ ፡ ስለሠራ
He was tired from overwork. ከመጠን ፡ በላይ ፡ ስለሠራ ፡ ደክሞት ፡ ነበር

**owe**
1. የሱ + noun + አለበት. He owes me fifty dollars. የኔ ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ አለበት
I still owe him a small sum. አሁንም ፡ ጥቂት ፡ የ ሱ ፡ ገንዘብ ፡ አለብኝ
How much do I owe you? ያንተ ፡ ገንዘብ ፡ ስን ት ፡ አለብኝ ?
2. ተገባ(ው). +We owe respect to our parents. ወላጆቻችንን ፡ ማክበር ፡ ይገባናል
+I owe you an explanation for my absence. የቀረሁበትን ፡ ምክንያት ፡ ልገልጽልህ ፡ ይገባኛል
3. የ + noun + ውለታ ፡ አለበት. We owe a great deal to our parents and teachers. የወላጆቻችን ና ፡ ያስተማሪዎቻችን ፡ ብዙ ፡ ውለታ ፡ አለብን
*She owes everything to him. እዚህ ፡ የደረሰችው ፡ በሱ ፡ ትከሻ ፡ ነው

**owing to** በ --- ምክንያት
Owing to the rain, they were unable to come. በዝናቡ ፡ ምክንያት ፡ሊመጡ ፡ አልቻሉም

**owl** ጉጉት
The owl flies at night. ጉጉት ፡ ሌሊት ፡ ትበራለች

**own** (vt.)
1. አለ(ው). He owns a house. የራሱ ፡ ቤት ፡ አለው
2. የሱ ፡ ነው. We used to rent this house, but now own it. ይህን ፡ ቤት ፡ ተከራይተነው ፡ ነበ ር ፤ አሁን ፡ ግን ፡ የኛ ፡ ነው

**own** (vi.) አመነ
He owned that he was wrong. መሳሳቱን ፡ አመነ

**own** (adj.)
1. የራሱ. He has his own horse. የራሱ ፡ ፈረስ ፡ አለው
I'm my own boss. የራሴ ፡ አዛዥ ፡ እኔው ፡ ነኝ
2. የግል. His preoccupation with his own affairs prevented him from organizing the meeting. በግል ፡ ጉዳዩ ፡ መጠመዱ ፡ ስብሰባው ን ፡ እንዳያዘጋጅ ፡ አደረገው

**be on one's own** ራሱን ፡ ችሎ ፡ ኖረ
He has been on his own ever since he was sixteen. ከዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመቱ ፡ ጀምሮ ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ ይኖራል

**by one's own hand**
He died by his own hand. ራሱን ፡ ገደለ ፡ (or, የገዛ ፡ ሕይወቱን ፡ አጠፋ)

**come into one's own** የሚገባውን ፡ ደረጃ ፡ አገኘ
In the latest exhibition, he came into his own as a painter of the first magnitude. በቅርቡ ፡ በተ ደረገው ፡ ኤግዚቢሽን ፡ በተደናቂ ፡ ሠዓሊነቱ ፡ የሚ ገባውን ፡ ደረጃ ፡ አገኘ

**for one's very own** ለራሱ
May I have this for my very own? ይህንን ፡ ለራ ሴ ፡ ልውሰደው ?

**for reasons of his own**
For reasons of his own, he refused to join the club. ክበቡ ፡ አልገባም ፡ ለማለቱ ፡ የራሱ ፡ ምክንያት ፡ አለው

**of its own** የተለየ ፡ የራሱ
Mead has a flavor of its own. ጠጅ ፡ የተለየ ፡ የራሱ ፡ ጣዕም ፡ አለው

**of one's own**
1. ለብቻው. Can I have a room of my own? ለብቻዬ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ላገኝ ፡ እችላለሁ ?
2. የራሱ. She needed a dress, and I gave her one of my own. ልብስ ፡ ስላስፈለጋት ፤ የራሴን ፡ አንዱን ፡ ሰጠኋት

**on one's own** ራሱን ፡ ችሎ
He is working on his own. ራሱን ፡ ችሎ ፡ ይሠራል

**one's own**
1. የራሱ. This room is his own. ይህ ፡ ክፍል ፡ የራሱ ፡ ነው
2. የገዛ. He only furthers his own interest. የገዛ ፡ ፍላጎቱን ፡ ብቻ ፡ ያሟላል
[See also 'hold']

**owner** ባለቤት

Who is the owner of the store? የመደብሩ ፡ ባለቤት ፡ ማን ፡ ነው ?

**ownership**

1. ባለቤትነት. The dispute is about the ownership of this land. ክርክሩ ፡ በዚህ ፡ መሬት ፡ ባለቤትነት ፡ ላይ ፡ ነው

2. ባለንብረት. The company came under new ownership. ኩባንያውን ፡ አዲስ ፡ ባለንብረት ፡ ተረከበው

**ox** በሬ

He uses an ox to plough the field. ማሳውን ፡ የሚያርሰው ፡ በበሬ ፡ ነው

[See also 'pair, yoke']

## P

**pace** (v.) ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ
He paced the room nervously. ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ በመጨነቅ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ

**pace off** በእርምጃ ፡ ለካ
He paced off on the ground the area he wanted plowed. እንዲታረስ ፡ የሚፈልገውን ፡ መሬት ፡ በእርምጃ ፡ ለካ

**pace** (n.) እርምጃ
Walk ten paces to the north! ዐሥር ፡ እርምጃ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ተራመድ
*He hikes at a pace of three miles an hour. በሰዓት ፡ ሦስት ፡ ማይል ፡ ይሄዳል

**keep pace with someone** ከሱ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ተራመደ
I can't keep pace with him; he walks too fast. ከሱ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ልራመድ ፡ አልችልም ። በጣም ፡ በፍጥነት ፡ ይራመዳል

**set a fast pace**
*He sets a fast pace for walking. ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ስለሚራመድ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ መሄድ ፡ አዳጋች ፡ ነው

**set the pace** ምሳሌ ፡ ነው
He sets the pace for everybody else in our class. በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ ተማሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ምሳሌ ፡ ነው
[See also 'easy, slack, smart']

**pacific**
1. ሰላምን ፡ የሚወድ. Those pacific people are not inclined to make war. እነዚያ ፡ ሰላምን ፡ የሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ጦርነት ፡ ለማድረግ ፡ አይሹም
2. የሰላም. The last century was a pacific era in history. ያለፈው ፡ ዘመን ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የሰላም ፡ ዘመን ፡ ነበር

**make pacific advances** በሰላም ፡ ቀረበ
The traders made pacific advances toward the Indians. ነጋዴዎቹ ፡ ህንዶችን ፡ በሰላም ፡ ቀረቧቸው

**pacification** (= verbal noun) ማረጋጋት
The pacification of the occupied city did not succeed. የተያዘውን ፡ ከተማ ፡ ለማረጋጋት ፡ የተደረገው ፡ ሙከራ ፡ አልተሳካም

**pacify** (pacified)
1. አባበለ. I tried to pacify her with promises but failed. ቃል ፡ በመግባት ፡ ላባብላት ፡ ሞክሬ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ አልተሳካልኝም
2. አረጋጋ. The troops are trying to pacify the city. ወታደሮቹ ፡ ከተማውን ፡ ለማረጋጋት ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ናቸው

**pack** (vt.)
1. እቃ ፡ ከተተ. Have you packed your trunk yet? እቃህን ፡ በሻንጣህ ፡ ውስጥ ፡ ከተሃል ?
2. ከተተ. I packed two shirts and some socks in my valise. ሁለት ፡ ሸሚዞችና ፡ ጥቂት ፡ የእግር ፡ ሹራቦች ፡ ሻንጣዬ ፡ ውስጥ ፡ ከተትኩ
3. አደራጅቶ ፡ አስቀመጠ. Pack your books in this box! መጻሕፍትህን ፡ እዚህ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አደራጅተህ ፡ አስቀምጥ
4. ሞላ. He packed his suitcase with clothes. ሻንጣውን ፡ ልብስ ፡ ሞላው
5. አሰረ. He packed his bags in feverish haste. ሻንጣውን ፡ አቻኩሎ ፡ አሰረ
6. ጫነ. We packed the mules and then set off for the lake. በቅሎዎቹን ፡ ጭነን ፡ ወደ ፡ ሐይቁ ፡ ለመሄድ ፡ ተነሣን
7. ግጥም ፡ አለ(በት). +People packed the theatre. ቲያትር ፡ ቤቱ ፡ ሰው ፡ ግጥም ፡ ብሎበታል
8. አጨቀ(ታጨቀ). They shouldn't pack us into the train this way. ባቡር ፡ ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ ሊያጭቁን ፡ አይገባም
The farmer shook down the sack of grain until it was firmly packed. እህሉ ፡ በደንብ ፡ እስኪታጨቅ ፡ ገበሬው ፡ ጆንያውን ፡ ጠቀጠቀው

**pack** (vi.) እቃውን ፡ አዘጋጀ
We packed last night and are ready to go. እቃችንን ፡ ባለፈው ፡ ሌሊት ፡ ስላዘጋጀን ፡ ለመሄድ ፡ ተዘጋጅተናል

**pack away** አስቀመጠ
Pack these clothes away in a large trunk! እነዚህን ፡ ልብሶች ፡ በትልቅ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጥ

**pack off** መልሶ ፡ ላከ
We packed her off to her mother because she could not follow the rules. ትእዛዝ ፡ ለመጠበቅ ፡ ስላልቻለች ፡ ወደ ፡ እናቷ ፡ መልሰን ፡ ላክናት

**pack up** (vt.) ጠቀለለ
He packed up his things and left. ጓዙን ፡ ጠቅልሎ ፡ ሄደ

**pack up** (vi.) እቃ ፡ ጠቀለለ
It's time to pack up and leave this place. እቃችንን ፡ ጠቅልለን ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ መሄድ ፡ አለብን

**pack** (n.)
1. ጭነት. The donkeys were loaded down with heavy packs. አህዮቹ ፡ ከባድ ፡ ጭነት ፡ ተጭነው ፡ ነበር
2. ፓኬት. Give me a pack of cigarettes! አንድ ፡ ፓኬት ፡ ሲጃራ ፡ ስጠኝ

**pack of thieves** የሌባ ፡ ዋሻ
This company is nothing but a pack of thieves. ይህ ፡ ኩባንያ ፡ የሌባ ፡ ዋሻ ፡ ነው

**in packs** በብዛት
Hyenas hunt in packs; lions hunt alone. ጅቦች ፡ የሚያድኑት ፡ በብዛት ፡ ሲሆን ፡ አንበሳ ፡ ግን ፡ ብቻውን ፡ ነው

**package**
1. ጥቅል. The mailman brought a package for you. ፖስተኛው ፡ አንድ ፡ ጥቅል ፡ አመጣልህ
2. መጠቅለያ. Use thick cardboard for the package! ለመጠቅለያው ፡ በወፍራም ፡ ካርቶን ፡ ተጠቀም

**pack animal** የጭነት ፡ ከብት
Renting pack animals will cost a lot of money. የጭነት ፡ ከብት ፡ መከራየት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ይጠይቃል

**packhorse** አጋሰስ
I have hired three packhorses to carry my stuff. እቃዬን ፡ የምጭንባቸው ፡ ሦስት ፡ አጋሰሶች ፡ ተከራይቻለሁ

**pact** ውል
They made a pact to permit free trade. ከቀረጥ ፡ ነጻ ፡ የሆነ ፡ ንግድ ፡ ለመፍቀድ ፡ ውል ፡ አደረጉ

**pad** (padded)
1. አስደረተ. I padded my coat so it would be warmer. ይበልጥ ፡ እንዲሞቀኝ ፡ ኮቴን ፡ አስደረትኩት
2. ሞላ. He padded his story with unnecessary details. በማያስፈልጉ ፡ ዝርዝሮች ፡ ታሪኩን ፡ ሞላው

**pad** (n.)
1. ፍራሽ. The baby's carriage has a pad made to fit it. የሕፃኑ ፡ አልጋ ፡ በልኩ ፡ የተሠራ ፡ ፍራሽ ፡ አለው
2. ድብዳብ ፡ መሳይ. He put a pad on the horse's back to keep it from being chafed. የፈረሱ ፡ ጀርባ ፡ እንዳይላጥ ፡ ድብዳብ ፡ መሳይ ፡ ጣለበት

**pad of paper**
I need a pad of paper. ጥቂት ፡ የማስታወሻ ፡ ደብተር ፡ ያስፈልገኛል

**paddle** (v.) ቀዘፈ
He paddled the canoe across the lake. ታንኳውን ፡ እየቀዘፈ ፡ ሐይቁን ፡ አቋረጠ

**paddle** (n.) መቅዘፊያ
He lost one of the two paddles. ከሁለቱ ፡ መቅዘፊያ ፡ አንዱ ፡ ጠፋበት

**pagan** (n.) አረማዊ
Pagans are still found in certain parts of the world. አሁንም ፡ ባንዳንድ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ አረማውያን ፡ ይገኛሉ

**pagan** (adj.) የአረማውያን
There are still pagan ceremonies in some regions. ባንዳንድ ፡ በታዎች ፡ ዛሬም ፡ የአረማውያን ፡ ሥርዓቶች ፡ ይገኛሉ

**paganism** ጣዖት ፡ ማምለክ
The tribe relapsed into paganism. ነገዱ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ ማምለክ ፡ ተመለሰ

**page** (v.) አስጠራ
I asked him to page my brother in the hotel lobby. በሆቴል ፡ ሳሎን ፡ ውስጥ ፡ ወንድሜን ፡ እንዲያስጠራው ፡ ጠየቅሁት

**page** (n.)
1. ገጽ. The book is two hundred pages long. መጽሐፉ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ገጽ ፡ አለው
2. ምዕራፍ. The settling of the West is an exciting page in our history. የሕዝብ ፡ በምዕራብ ፡ መስፈር ፡ በታሪካችን ፡ ውስጥ ፡ ትልቅ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው
3. ተላላኪ. I sent the page for the newspaper. ጋዜጣ ፡ እንዲያመጣልኝ ፡ ተላላኪውን ፡ ላክሁት

**pageant** ሥነ ፡ ሥርዓት
The coronation of the king was a splendid pageant. የንጉሡ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በጣም ፡ የደመቀ ፡ ነበር

**pagination** የገጽ ፡ ቁጥር
The pagination of this book is not in order. የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የገጽ ፡ ቁጥር ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ትክክል ፡ አይደለም

**pail** ባልዲ
Fill the pail with water! ባልዲውን ፡ ውኃ ፡ ሙላው
[See also 'garbage']

**pain** (v.) አመመ(ው)
Does your tooth pain you? ጥርስህን ፡ ያምሃል ?

**pain** (n.)
1. ውጋት. I feel a sharp pain in my back. ጀርባዬን ፡ ኀይለኛ ፡ ውጋት ፡ ይሰማኛል
2. ሥቃይ. A toothache is a pain. የጥርስ ፡ ሕመም ፡ ሥቃይ ፡ ነው

**pains** ድካም
Great pains have been taken to finish the project. እቅዱን ፡ ለመጨረስ ፡ ታላቅ ፡ ድካም ፡ አድርጓል

**feel a dull pain in** ተወጋጋ(ው)
+I feel a dull pain in my side. ጐኔን ፡ ይወጋጋኛል

**feel (a) pain in**
1. አመመ(ው). +Do you feel pain in the tooth? ጥርስህን ፡ ያምሃል ?
2. ውጋት ፡ ተሰማ(ው). +All of a sudden, I felt a sharp pain in my back. በድንገት ፡ ጀርባዬ ፡ ላይ ፡ ኀይለኛ ፡ ውጋት ፡ ተሰማኝ

**have a pain in** አመመ(ው)
+I have a pain in my knee. ጉልበቴን ፡ ያመኛል

**take pains**
1. ብዙ ፡ ደከመ. He took pains to have the place neat and clean. ቦታውን ፡ ለማጽዳት ፡ ብዙ ፡ ደከመ
2. ተጨነቀ. He takes great pains to please his employer. ቀጣሪውን ፡ ለማስደሰት ፡ ብዙ ፡ ይጨነቃል
[See also 'free, inflict, stab, throb']

**(be) painful**
1. አመመ. Was the operation very painful? ቀዶ ፡ ጥገናው ፡ በጣም ፡ ያም ፡ ነበር ?
2. አስቀጠጠ. It is painful to see him suffer. ሲሠቃይ ፡ ማየቱ ፡ ያስቀጥጣል
3. ሥቃይ ፡ ነው. Childbirth is painful for women. ልጅ ፡ መውለድ ፡ ለሴቶች ፡ ሥቃይ ፡ ነው

**painless** ያለምንም ፡ ሥቃይ
This treatment is a painless cure for cancer. ይህ ፡ ሕክምና ፡ ከካንሰር ፡ በሽታ ፡ ያለምንም ፡ ሥቃይ ፡ የሚፈውስ ፡ ነው

**painstaking** ታላቅ
He repaired the damaged car with painstaking care. የተበላሸውን ፡ መኪና ፡ በታላቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ ጠገነው

**paint** (vt.)
1. ቀባ. He painted the house light blue. ቤቱን ፡ ውኃ ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ ቀባ
2. ሣለ. Who painted this portrait? ይህን ፡ የሰው ፡ ሥዕል ፡ ማን ፡ ሣለው ?
3. ገለጸ. He painted an exciting story of his travels. የጉዞውን ፡ ታሪክ ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ ገለጸው

**paint** (vi.) ሣለ
She paints in oils. በዘይት ፡ ቀለም ፡ ትሥላለች

**paint** (n.) ቀለም
The paint is still wet. ቀለሙ ፡ አሁንም ፡ እርጥብ ፡ ነው

**paintbrush** የቀለም ፡ ብሩሽ
The paintbrush is dry. የቀለሙ ፡ ብሩሽ ፡ ደርቋል

**painter**
1. ሠዓሊ. A famous painter is going to visit our country. ዝነኛ ፡ ሠዓሊ ፡ አገራችንን ፡ ሊጐበኝ ፡ ነው
2. ቀለም ፡ ቀቢ. The painter distributed the paint evenly over the wall. ቀለም ፡ ቀቢው ፡ ግድግዳውን ፡ አስተካክሎ ፡ ቀባው

**painting** ሥዕል
That's a beautiful painting. ያ ፡ ውብ ፡ ሥዕል ፡ ነው

**pair** (v.), ~ **off** ሁለት ፡ ሁለት ፡ ሆነው ፡ ሄዱ
The boys and girls paired off. ወንዶቹና ፡ ልጃገረዶቹ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ሆነው ፡ ሄዱ

**be paired** በጥንድ ፡ በጥንድ ፡ ተደረደረ
Her gloves were neatly paired in a drawer. የእጅ ፡ ሹራቦቿ ፡ መሳቢያው ፡ ውስጥ ፡ በጥንቃቄ ፡ በጥንድ ፡ በጥንድ ፡ ተደርድረዋል

**pair** (n.)
1. ጥምድ ፤ ጥንድ. Many articles like shoes are sold in pairs. እንደጫማ ፡ ያሉ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ የሚሸጡት ፡ በጥንድ ፡ ነው
A pair of oxen pulls the plow. አንድ ፡ ጥንድ ፡ በሬ ፡ ሞፈር ፡ ይጐትታል
2. ሁለት. The pair danced alone on the dance floor. ሁለቱ ፡ በዳንሱ ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ ብቻቸውን ፡ ደነሱ

**pairs** ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ጥንድ ፡ ጥንድ ፡ እየሆኑ
Many happy pairs were waltzing on the dance floor. በዳንስ ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የተደሰቱ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ጥንድ ፡ ጥንድ ፡ እየሆኑ ፡ ይደንሱ ፡ ነበር
[See also 'glove, trousers']

**pajamas** ፒጃማ
Pajamas are worn during bedtime hours. ፒጃማ ፡ የሚለበሰው ፡ በመኝታ ፡ ጊዜ ፡ ነው

**palace** ቤተ ፡ መንግሥት
The palace was built last year. ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ የተሠራው ፡ ዓምና ፡ ነው
[See also 'jubilee']

**(be) palatable** ጣዕም ፡ አለው
This food is not palatable. ይህ ፡ ምግብ ፡ ጣዕም ፡ የለውም

**palate** ላንቃ
I have a sore on my palate. ላንቃዬ ፡ ቆስሏል

**palatial** ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የመሰለ
His palatial house was destroyed by the rebels. ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የመሰለ ፡ ቤቱን ፡ ዐመፀኞቹ ፡ አፈረሱበት

**pale** (v.) አመድ ፡ መሰለ
His face paled at the bad news. መጥፎ ፡ ወሬ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱ ፡ አመድ ፡ መሰለ

**pale** (n.) ዕንጨት
Some pales of the fence are broken. ያጥሩ ፡ አንዳንድ ፡ ዕንጨቶች ፡ ተሰብረዋል

**outside the pale**
*Murderers are outside the pale of civilized society. ነፍስ ፡ ገዳይ ፡ እንደሠለጠነ ፡ ሰው ፡ አይቈጠርም

**pale** (adj.)
1. የገረጣ. Sick people often have pale faces. የታመሙ ፡ ሰዎች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የገረጣ ፡ መልክ ፡ አላቸው
2. ደብዘዝ ፡ ያለ. The bright stars are surrounded by pale ones. በብሩሆች ፡ ኮከቦች ፡ ዙሪያ ፡ ደብዘዝ ፡ ያሉ ፡ ኮከቦች ፡ አሉ

**be pale** ገረጣ
When you have been ill, your face is sometimes pale. ሰው ፡ ሲታመም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱ ፡ ይገረጣል

**turn pale** ፊቱ ፡ አመዱ ፡ ቡን ፡ አለ
When he heard that, he turned pale. ይህን ፡ ሲሰማ ፡ ፊቱ ፡ አመዱ ፡ ቡን ፡ አለ

**palisade** አጥር
The bull broke through the palisades of the cattle pen. ወይፈኑ ፡ ከጋጣ ፡ ውስጥ ፡ አጥሩን ፡ ሰብሮ ፡ ወጣ

**palliate**
1. አስታገሠ. The medicine palliates a fever. መድኃኒቱ ፡ ትኩሳትን ፡ ያስታግሣል
2. አድበሰበሰ. He attempted to palliate the crime by paying back the stolen money. የሰረቀውን ፡ ገንዘብ ፡ በመመለስ ፡ ወንጀሉን ፡ ሊያድበሰብስ ፡ ሞከረ

**pallid** የገረጣ
His pallid face shows the severity of the fever. የገረጣው ፡ ፊቱ ፡ የትኩሳትን ፡ ኀይለኛነት ፡ ያመለክታል

**pallor** መገርጣት
The pallor showed that he was ill. መገርጣቱ ፡ ታሞ ፡ እንደነበረ ፡ ያሳያል

**palm**
1. ዘምባባ. These palms are thirty feet high. እነዚህ ፡ ዘምባባዎች ፡ ሠላሳ ፡ ጫማ ፡ ይረዝማሉ
2. መዳፍ. His palm is callused from digging a lot. ብዙ ፡ በመቈፈሩ ፡ የተነሣ ፡ መዳፉ ፡ ሻክሯል

**Palm Sunday** የሆሣዕና ፡ ዕለት
Our Lord Jesus Christ went to Jerusalem on Palm Sunday. የሆሣዕና ፡ ዕለት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገባ

**palpable**
1. ሊዳሰስ ፡ የሚችል. There was a palpable bump on his head. በራሱ ፡ ላይ ፡ ሊዳሰስ ፡ የሚችል ፡ እብጠት ፡ ነበር
2. ጉልህ. His writing his name on the check was a palpable error. በቼኩ ፡ ላይ ፡ ስሙን ፡ መጻፉ ፡ ጉልህ ፡ ስሕተት ፡ ነበር

**palpate** ደባበሰ
The doctor palpated my abdomen to see if I had an appendicitis. ሐኪሙ ፡ የትርፍ ፡ አንጀት ፡ በሽታ ፡ እንዳለብኝ ፡ ለማወቅ ፡ ሆዴን ፡ ደባበሰ

**palpitate**
1. ከበሮ ፡ መታ. The boy's heart palpitated with fear. ከፍርሀት ፡ የተነሣ ፡ የልጁ ፡ ልብ ፡ ከበሮ ፡ መታ
2. ተንዘፈዘፈ. His body palpitated with terror. በፍርሀት ፡ ሰውነቱ ፡ ተንዘፈዘፈ

**pamper** አሞላቀቀ
She pampered her child by giving him everything he wanted. ለልጇ ፡ የፈለገውን ፡ እየሰጠች ፡ አሞላቀቀችው

**pamphlet** አነስተኛ ፡ መጽሔት
He published a pamphlet on public health. ስለ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ አነስተኛ ፡ መጽሔት ፡ አወጣ

**pan** መጥበሻ
Give me a pan to cook this meat in! ይህን ፡ ሥጋ ፡ የምጠብስበት ፡ መጥበሻ ፡ ስጠኝ

**pancake** [ከቂጣ ፡ ሳሳ ፡ ያለ ፡ ከእንጀራ ፡ ወፈር ፡ ያለ ፡ ከስንዴ ፡ ዱቄት ፡ የሚሠራ ፡ ዳቤ ፡ የመሰለ ፡ ኬክ]

**pane** መስታወት
The boy threw a stone at the windowpane. ልጁ ፡ መስኮቱ ፡ መስታወት ፡ ላይ ፡ ድንጋይ ፡ ወረወረ

**panel**
1. ክፍል. A panel was knocked out of the door. ከመዝጊያው ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ወልቋል
2. ጓድ. He is a member of a special panel for studying crime. ወንጀል ፡ የሚያጠና ፡ ያንድ ፡ ልዩ ፡ ጓድ ፡ አባል ፡ ነው

**(be) paneled** ተለበደ
The room is paneled in cedar. ግድግዳው ፡ በጥድ ፡ ተለብዷል

**pang**
*Pangs of hunger did not let him study. ረኃብ ፡ እየሞረሞረ ፡ አላስጠና ፡ አለው
[See also 'sorrow']

**panic** (panicked), vt.
1. አስፈራራ ፤ አስደነገጠ. He tried to panic the child by making fierce noises. የሚያስፈራ ፡ ድምፅ ፡ በማሰማት ፡ ሕፃኑን ፡ ሊያስፈራራ ፡ (ሊያስደነግጥ) ፡ ሞከረ
2. አሸበረ. The fearful storm panicked the children. አስፈሪው ፡ ዝናብ ፡ ልጆቹን ፡ አሸበራቸው

**panic** (vi.) ተሸበረ
The soldiers panicked because of the bombing. ከቦምቡ ፡ ድብደባ ፡ የተነሣ ፡ ወታደሮቹ ፡ ተሸበሩ

**panic** (n.) ሽብር
There was a panic when fire started in the movie. በሲኒማ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ሽብር ፡ ሆነ
*Panic seized the crowd. ሕዝቡ ፡ ተደናገጠ

**panicked,** see **panic**

**(be) panic-stricken** በፍርሃት ፡ ተርበደበደ ፤ ተሸበረ
The children were panic-stricken when the fire broke out. ቃጠሎ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ልጆቹ ፡ በፍርሃት ፡ ተርበደበዱ ፡ (ተሸበሩ)

**panorama**
*The panorama of the city can be seen from the top of the mountain. ከተራራው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ከተማው ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ይታያል

**pant**
1. ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰ. The load was heavy, and he came panting up the stairs. ሸክሙ ፡ ስለከበደው ፡ ቁና ፡ ቁና ፡ እየተነፈሰ ፡ ደረጃውን ፡ ወጣ
2. ትንፋሹ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ አለ. "Come quick, come quick!" panted John. ጆን ፡ ትንፋሹ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ እያለ ፡ « ቶሎ ፡ ና ፤ ቶሎ ፡ ና » ፡ አለ
3. በጣም ፡ ተጣጣረ. The director panted after fame and fortune. ሥራ ፡ መሪው ፡ ለዝናና ፡ ለሀብት ፡ በጣም ፡ ተጣጣረ

**panther** አነር
Are there panthers in Ethiopia? በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አነሮች ፡ አሉ ?

**pantomime** እንቅስቃሴ ፡ ብቻ
He acted out the play in pantomime. በንቅስቃሴ ፡ ብቻ ፡ ቲያትሩን ፡ ሠራ

**pantry** (pantries) ጓዳ
The dishes are kept in a pantry. ሳሕኖቹ ፡ ጓዳ ፡ ናቸው

**pants** ሱሪ
His pants are dark. ሱሪው ፡ ጥቁር ፡ ነው

**pair of pants** ሱሪ
I bought a suit with two pairs of pants. አንድ ፡ ሙሉ ፡ ልብስ ፡ ከሁለት ፡ ሱሪ ፡ ጋር ፡ ገዛሁ

**papa!** አባባ
She saw her father and cried out, "Papa!". አባቷን ፡ አይታ ፡ « አባባ » ፡ ብላ ፡ ተጣራች

**papaya** ፓፓያ
Papaya is a fruit that is grown in the Awash Valley. ፓፓያ ፡ በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ የሚበቅል ፡ ፍሬ ፡ ነው

**paper** (v.) የግድግዳ ፡ ወረቀት ፡ ለጠፈ(በት)
He has not papered the room for five years. አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ቤቱን ፡ የግድግዳ ፡ ወረቀት ፡ አልለጠፈበትም

**paper** (n .)
1. ወረቀት. The paper in this notebook is dirty. የዚህ ፡ ደብተር ፡ ወረቀት ፡ ቆሻሻ ፡ ነው
2. ጋዜጣ. I read the story in today's paper. ወሬውን ፡ ያነበብኩት ፡ ከዛሬው ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ነው
3. ሰነድ. Some important papers are missing. አንዳንድ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ሰነዶች ፡ ጠፍተዋል
4. ጽሑፍ. He read a paper on the Amharic verb at the meeting. በስብሰባው ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ አማርኛ ፡ ግስ ፡ የተጻፈ ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ አነበበ

Let's have this contract on paper! ይህንን ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ እናድርገው
5. ድርሰት. My history paper is due tomorrow. ለታሪክ ፡ ትምህርት ፡ የጻፍኩትን ፡ ድርሰት ፡ የማስረክቢያው ፡ ቀን ፡ ነገ ፡ ነው

**sheet of paper** ወረቀት I ቅጠል ፡ ወረቀት
The envelope contained only a blank sheet of paper. ኤንቬሎፑ ፡ ባዶ ፡ ወረቀት ፡ ብቻ ፡ ይዟል
Give me two sheets of paper. ሁለት ፡ ቅጠል ፡ ወረቀት ፡ ስጠኝ

**paperback** የወረቀት ፡ ጥራዝ
This book has come out in paperback. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በወረቀት ፡ ጥራዝ ፡ ታትሞ ፡ ወጣ

**paper boy** ጋዜጣ ፡ ሻጭ
The paper boy wants his money. ጋዜጣ ፡ ሻጩ ፡ ገንዘቡን ፡ ይፈልጋል

**paperwork** የጽሑፍ ፡ ሥራ
My job requires a lot of paperwork. ሥራዬ ፡ ብዙ ፡ የጽሑፍ ፡ ሥራ ፡ ይጠይቃል

**par, be on a ~** እኩል ፡ ነው
He is on a par with his brother in intelligence. በብልህነት ፡ ከወንድሙ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ነው

**up to par** እንደወትሮ
With his injured knee, Abraham's running is not up to par. ጉልበቱን ፡ ስለታመመ ፡ የአብርሃም ፡ሩጫ ፡ እንደወትሮው ፡ አይደለም

**parable** ምሳሌ
Jesus spoke in parables. ኢየሱስ ፡ በምሳሌ ፡ ይናገር ፡ ነበር

**parachute** ጃንጥላ
The paratroopers dropped from the plane in parachutes. ያየር ፡ ወለድ ፡ ወታደሮች ፡ ከአውሮፕላኑ ፡ ላይ ፡ በጃንጥላ ፡ ወረዱ

**parade** (v.) በሰልፍ ፡ ተዘዋወረ
The army paraded through the town. ሰራዊቱ ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ በሰልፍ ፡ ተዘዋወረ

**parade** (n.)
1. ሰልፍ. He marched at the head of the parade. ሰልፉን ፡ መራ
2. ሰልፈኞች. When he looked out of the window, he saw a parade passing by. በመስኮት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ቢመለከት ፡ ሰልፈኞቹ ፡ ሲያልፉ ፡ አየ

**make a parade of** እዩልኝ ፡ አለ
A modest man does not make a parade of his wealth. ትሑት ፡ ሰው ፡ ሀብቱን ፡ እዩልኝ ፡ አይልም

**paradigm** እርባታ
These students can recite Amharic nouns and verb paradigms. እነዚህ ፡ ተማሪዎች ፡ ያማርኛን ፡ ስምና ፡ ግስ ፡ እርባታ ፡ ሊሰጡ ፡ ይችላሉ

**paradise** ገነት
His garden is a veritable paradise. ያትክልቱ ፡ ቦታ ፡ በእውነት ፡ ገነት ፡ ነው

**paradox** ተፃራሪ ፡ አባባል
'Make haste slowly' is a paradox. በዝግታ ፡ ተፋጠን ፡ ማለት ፡ ተፃራሪ ፡ አባባል ፡ ይመስላል

**paragraph** አንቀጽ
This is the beginning of a new paragraph. ይህ ፡ ያዲስ ፡ አንቀጽ ፡ መጀመሪያ ፡ ነው
The student condensed the long speech to a paragraph. ተማሪው ፡ ረጅሙን ፡ ንግግር ፡ ባንድ ፡ አንቀጽ ፡ አሳጠረው

**parakeet** በቀቀን
Parakeets mimic human voices. በቀቀን ፡ የሰውን ፡ ድምፅ ፡ ይቀዳል

**parallel** (v.)
1. ተከትሎ ፡ ሄደ. The roads parallel the river. መንገዶቹ ፡ ወንዙን ፡ ተከትለው ፡ ይሄዳሉ
2. ተመሳሰለ. Your experience parallels mine. ያጋጠመህ ፡ ነገር ፡ እኔን ፡ ካጋጠመኝ ፡ ይመሳሰላል

**parallel** (n.)
1. አግዳሚ ፡ መሥመር. Draw a parallel to this line! ለዚህ ፡ መሥመር ፡ አግዳሚ ፡ መሥመር ፡ አሥምር
2. ተመሳሳይ. This story is without a known parallel. ታሪኩ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሌለው ፡ ነው

**be a parallel** ተመሳሰለ
Her experience was an interesting parallel to ours. ያጋጠማት ፡ ነገር ፡ እኛን ፡ ካጋጠመን ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ የሚመሳሰል ፡ ነበር

**draw a parallel** አነጻጸረ
He drew a parallel between this rainy season and last rainy season. የዘንድሮውንና ፡ ያምናውን ፡ ክረምት ፡ አነጻጸረ

**parallel** (adj.)
1. አግዳሚ. Rails of a railway track are parallel. የባቡሩ ፡ ሐዲድ ፡ መሥመሮች ፡ አግዳሚ ፡ ናቸው
2. የሚመሳሰል. The scholar found parallel customs in different countries. ምሁሩ ፡ በተለያዩ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ የሚመሳሰሉ ፡ ልማዶች ፡ እንዳሉ ፡ ተመለከተ

**be parallel** ተመሳሰለ
Your training is parallel to mine. የኔና ፡ ያንተ ፡ ትምህርት ፡ ይመሳሰላል

**parallelism** ተመሳሳይነት
There is little parallelism between human and animal language. በሰውና ፡ በእንስሳት ፡ ቋንቋ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ተመሳሳይነት ፡ እምብዛም ፡ ነው

**paralysis** መስለል ፤ የሰውነት ፡ መስለል
Paralysis of the arm resulted in the atrophy of the muscles. የክንዱ ፡ መስለል ፡ የጡንቻዎችን ፡ መመንመን ፡ አስከተለ
His paralysis forces him to rest several hours a day. የሰውነቱ ፡ መስለል ፡ በቀን ፡ ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ እንዲያርፍ ፡ ያደርገዋል

**cause a paralysis of** (= intr.) ቆመ
*The war caused a paralysis of trade. ከጦርነቱ ፡ የተነሣ ፡ ንግድ ፡ ቆሟል

**paralyze**
1. ሽባ ፡ አደረገ. Polio may paralyze people. ፖሊዮ ፡ ሰዎችን ፡ ሽባ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል
2. ዘጋ. The flood paralyzed transportation. ጐርፉ ፡ መመላለሻውን ፡ ዘጋው

**be paralyzed**
1. ሽባ ፡ ሆነ. She has been paralyzed ever since she has had that disease. ያ ፡ ሕመም ፡ ካደረባት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሽባ ፡ ሆናለች
His hand was paralyzed, and he could not move it. እጁ ፡ ሽባ ፡ ስለሆነ ፡ ሊያንቀሳቅሰው ፡ አልቻለም
2. ተዘጋ. The traffic was completely paralyzed. በመኪና ፡ ብዛት ፡ ትራፊክ ፡ በፍጹም ፡ ተዘግቶ ፡ ነበር
3. በድን ፡ ሆነ. I was paralyzed with fear. በፍርሀት ፡ በድን ፡ ሆንኩ

**leave paralyzed** አሰለለ
The stroke left the governor paralyzed on one side of his body. የደም ፡ መርጋት ፡ በሽታ ፡ የእንደራሴውን ፡ ግማሽ ፡ ጐን ፡ አሰለለው

**paramount** ዋና
Her family was her paramount concern. ዋና ፡ ሐሳቧ ፡ ለቤተሰቦቿ ፡ ነበር

**be of paramount importance** ከሁሉም ፡ ነገር ፡ ቀዳሚነት ፡ አለው
The country's welfare is of paramount importance. የሀገሪቱ ፡ ደኅንነት ፡ ከሁሉም ፡ ነገር ፡ ቀዳሚነት ፡ ያለው ፡ ነው

**paraphrase** [ያንድ ፡ ምንባብን ፡ ይዞታ ፡ በራስ ፡ አገላለጽ ፡ አስረዳ]

**parasite**
1. ጥገኛ ፡ ነፍሳት. Ticks are parasites that carry various diseases. መዥገር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሽታዎችን ፡ የሚያመጣ ፡ ጥገኛ ፡ ነፍሳት ፡ ነው
2. በሰው ፡ ትከሻ ፡ የሚኖር. He is a parasite; he gets everything he needs from his relatives and friends. በሰው ፡ ትከሻ ፡ የሚኖር ፡ ስለሆነ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ ከዘመዶቹና ፡ ከወዳጆቹ ፡ ያገኛል

**parasol** ጃንጥላ
Men and women carry parasols. ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ጃንጥላ ፡ ይይዛሉ

**paratrooper** ያየር ፡ ወለድ ፡ ወታደር
The paratrooper receives special training. ያየር ፡ ወለድ ፡ ወታደሩ ፡ ልዩ ፡ ትምህርት ፡ ይሰጠዋል

**parcel** (v.), ~ **out** ሸንሽኖ ፡ አከፋፈለ
The government parceled out land to settlers. መንግሥቱ ፡ አዲስ ፡ ለሰፈሩት ፡ ሰዎች ፡ መሬት ፡ ሸንሽኖ ፡ አከፋፈለ

**parcel** (n.)
1. የተጠቀለለ ፡ እቃ. You forgot your parcels. የተጠቀለሉትን ፡ እቃዎችህን ፡ ረስተሃል
2. ጥቅል. This parcel was not properly tied for mailing. ይህ ፡ ጥቅል ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ለመላክ ፡ በሚገባ ፡ አልታሰረም ፡ ነበር
3. ቁራጭ. I bought a parcel of land in the mountains. በተራራዎቹ ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ ቁራጭ ፡ መሬት ፡ ገዛሁ
[See also 'part']

**parcel post** በፖስታ ፡ የሚላክ
Parcel post rates are very low in this country. እዚህ ፡ አገር ፡ እቃ ፡ በፖስታ ፡ የሚላክበት ፡ ዋጋ ፡ ርካሽ ፡ ነው

**by parcel post** በፖስታ ፡ ቤት ፡ በኩል
We sent the coat by parcel post. ኮቱን ፡ በፖስታ ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ ላክን

**parch** (vt.)
1. ቆላ. We parch wheat and eat it. ስንዴ ፡ ቆልተን ፡ እንበላለን
2. አደረቀ. The hot sun parched the soil. የገረረው ፡ ፀሐይ ፡ መሬቱን ፡ አደረቀው

**parch** (vi.) ደረቀ
The land parched under the hot sun. መሬቱ ፡ በፀሐይ ፡ ሙቀት ፡ ምክንያት ፡ ደረቀ

**parched** (adj.) ደርቆ ፡ የተሰነጣጠቀ
Nothing could grow in the parched ground. ደርቆ ፡ በተሰነጣጠቀው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ አይበቅልም

**parched corn** የተቆላ ፡ በቆሎ
Have you any parched corn left? የተቆላ ፡ በቆሎ ፡ ተርፎሃል ?

**parched grain** ቆሎ
He is munching on parched grain. ቆሎ ፡ ይቈረጥማል

**parchment** ብራና
Old books are written on parchment. የጥንት ፡ መጽሐፎች ፡ የተጻፉት ፡ በብራና ፡ ነው

**pardon** (v.)
1. ምሕረት ፡ አደረገ(ለት) ፤ ማረ. The President pardoned him at the last moment. ፕሬዚዳንቱ ፡ በመጨረሻው ፡ ላይ ፡ ምሕረት ፡ አደረገለት
Most governors have the prerogative of pardoning prisoners. ብዙ ፡ ገዢዎች ፡ እስረኞችን ፡ የመማር ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው
2. ይቅር ፡ አለ. Please pardon my mistake! ስሕተቴን ፡ ይቅር ፡ በለኝ

**pardon** (n.) ምሕረት
He was refused a pardon. ምሕረት ፡ ተከለከለ
*I beg your pardon. Where is Churchill Avenue? እባክዎ ፤ የቸርቺል ፡ ጐዳና ፡ ወዴት ፡ ነው ?

**ask (someone's) pardon** ይቅርታ ፡ ጠየቀ
The shamefaced boy asked the teacher's pardon for having insulted him. ዓይን ፡ አፋሩ ፡ ልጅ ፡ አስተማሪውን ፡ በመዝለፉ ፡ ይቅርታ ፡ ጠየቀ

**pare**
1. ላጠ. The mother pared the apple for the child. እናትዮዋ ፡ ቱፋውን ፡ ለልጁ ፡ ላጠችለት
2. ቀነሰ. We must pare our expenses until we pay off our debt. ዕዳችንን ፡ እስክንከፍል ፡ ድረስ ፡ ወጪያችንን ፡ መቀነስ ፡ አለብን

**parent**
1. ወላጅ. A parent should teach his children. ወላጅ ፡ ልጁን ፡ ማስተማር ፡ አለበት
2. ምንጭ. Latin is the parent of various languages. ላቲን ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋዎች ፡ ምንጭ ፡ ነው

**parents**
1. ወላጆች. We must honor our parents. ወላጆቻችንን ፡ ማክበር ፡ አለብን
2. ቤቶች. She can always move back with her parents. ከፈለገች ፡ ቤቶቿ ፡ ዘንድ ፡ ለመመለስ ፡ ትችላለች

**parentage** ቤተሰብ
Even though he is of humble parentage, he reached a high position. ከድኻ ፡ ቤተሰብ ፡ የመጣ ፡ ቢሆንም ፡ ከታላቅ ፡ ማዕረግ ፡ ላይ ፡ ደርሷል

**parental** የወላጅ
The boy listens to parental advice. ልጁ ፡ የወላጅን ፡ ምክር ፡ ይቀበላል

**parenthesis** ቅንፍ
He wrote the translation in parenthesis. ትርጉሙን ፡ በቅንፍ ፡ ውስጥ ፡ ጻፈው

**parenthood**
1. ወላጅ ፡ መሆን. Parenthood requires patience and understanding. ወላጅ ፡ መሆን ፡ ታጋሽነትንና ፡ አድማጭነትን ፡ ይጠይቃል
2. ወላጅ. Poor parenthood results in unruly children. መጥፎ ፡ ወላጅ ፡ የማይታዘዙ ፡ ልጆች ፡ ያወጣል

**parings** ልጣጭ
He threw away the parings of the apple. የቱፋውን ፡ ልጣጭ ፡ ጣለው

**parish**
1. ደብር. This parish is very small in comparison with others. ይህ ፡ ደብር ፡ ከሌሎች ፡ ጋር ፡ ሲመዛዘን ፡ አነስተኛ ፡ ነው
2. የደብር ፡ ሕዝብ. The parish voted to repair the church. የደብሩ ፡ ሕዝብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ መታደስ ፡ ደገፈ

**parishoners** የደብር ፡ ሕዝብ
The parishoners celebrate the festival of St. Mary every month. የደብሩ ፡ ሕዝብ ፡ የቅድስት ፡ ማርያምን ፡ በዓል ፡ በየወሩ ፡ ያከብራሉ

**parity** በሰው ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ እኩልነት
Parity is difficult to achieve. በሰው ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ እኩልነት ፡ ማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**reach parity** በዋጋ ፡ ተመጣጠነ
The two currencies have now reached parity. የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ገንዘብ ፡ አሁን ፡ በዋጋ ፡ ተመጣጥኗል

**park** (vt.) አቆመ
Where can I park my car? መኪናዬን ፡ የት ፡ ላቆም ፡ እችላለሁ ?

**park** (vi.) አቆመ
He parked in a busy street. ትራፊክ ፡ አበዛበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ አቆመ

**park** (n.) መናፈሻ ፡ ቦታ
There is a beautiful park in the center of the city. በከተማው ፡ መሀከል ፡ አንድ ፡ ጥሩ ፡ መናፈሻ ፡ ቦታ ፡ አለ

**parking place** መኪና ፡ ማቆሚያ ፡ ስፍራ
This is a public parking place. ይህ ፡ ለሕዝቡ ፡ የተሠራ ፡ መኪና ፡ ማቆሚያ ፡ ስፍራ ፡ ነው

**parkway** አውራ ፡ ጐዳና
A parkway is safe and enjoyable to drive along.

አውራ ፡ ጐዳና ፡ ሰላምና ፡ ለመንዳትም ፡ የሚያስ ደስት ፡ ነው

**parley** ስብሰባ
The opposing generals met in a parley to discuss the exchange of prisoners. እስረኞችን ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ፡ ጉዳይ ፡ ለመነጋገር ፡ የሁለቱም ፡ ጦር ፡ ጄኔራሎች ፡ ስብሰባ ፡ አደረጉ

**parliament** ምክር ፡ ቤት ፤ ፓርላማ
The Ethiopian parliament has two houses. የኢትዮጵያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ (ፓርላማ) ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ አሉት

**parliamentarian** የሕጉን ፡ ሥርዓት ፡ ዐዋቂ
The parliamentarian interprets the rules of order. የሕጉን ፡ ሥርዓት ፡ ዐዋቂው ፡ ደንቡን ፡ ያስረዳል

**parliamentary** የፓርላሜንት
The meeting was conducted strictly by parliamentary procedure. ስብሰባው ፡ የፓርላሜንትን ፡ ሥርዓት ፡ ተከትሎ ፡ ተካሄደ

**parlor** ማረፊያ ፡ ክፍል
The servant let me in to the parlor. አሽከሩ ፡ ወደ ፡ ማረፊያው ፡ ክፍል ፡ አስገባኝ
[See also 'beauty parlor']

**parochial**
1. የቤተ ፡ ክህነት. Both parochial and public education receive government support. የቤተ ፡ ክህነትና ፡ የመንግሥት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ከመ ንግሥት ፡ እርዳታ ፡ ያገኛሉ
2. በጣም ፡ የተወሰነ. He has lived in one place so long that his ideas are parochial. ባንድ ፡ ቦታ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስለኖረ ፡ አስተሳሰቡ ፡ በጣ ም ፡ የተወሰነ ፡ ነው

**parody** [ቁም ፡ ነገር ፡ ጽሑፍ ፡ አሥቂኝ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ጽፎ ፡ ማቅረብ]

**parole**
*The convict is now free on parole. እስረኛው ፡ በየጊዜው ፡ ባለሥልጣን ፡ ፊት ፡ መቅረብ ፡ ቢኖር በትም ፡ በነጻ ፡ ተለቋል

**parrot** (v.) አስተጋባ
He parrots his employer's words. የቀጣሪውን ፡ ቃል ፡ ያስተጋባል

**parrot** (n.) በቀቀን
The parrot repeats what anybody says. በቀቀን ፡ ሰው ፡ የሚናገረውን ፡ መልሳ ፡ ትናገራለች

**parry** (parried)
1. መከተ. He parried the sword with his staff. ጐራዴውን ፡ በዘንግ ፡ መከተ
2. ለመመለስ ፡ ሞከረ. She parried our question by asking us one. ጥያቄያችንን ፡ በጥያቄ ፡ ለመ መለስ ፡ ሞከረች

**parse** ተነተነ
The advanced students parse the most complex sentences. የገፉት ፡ ተማሪዎች ፡ በጣም ፡ የተወሳሰ ቡ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮችን ፡ ይተነትናሉ

**parsimonious** ቆጥቋጣ
He is so parsimonious, he won't spend money on good food. በጣም ፡ ቆጥቋጣ ፡ ስለሆነ ፡ ለጥሩ ፡ ምግብ ፡ ገንዘብ ፡ አያወጣም

**parsimony** ሥሥታምነት
His parsimony is well known to everybody. ሥሥታምነቱ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ ታውቋል

**parson** የደብር ፡ አለቃ
The parson was educated in Gondar. የደብሩ ፡ አለቃ ፡ ጐንደር ፡ ነው ፡ የተማሩት

**part** (vt.)
1. መንገድ ፡ አስለቀቀ. The police parted the crowd to let the dignitaries pass. ታላላቆቹ ፡ ሰዎች ፡ እን ዲያልፉ ፡ ፖሊሶች ፡ ሕዝቡን ፡ መንገድ ፡ አስለቀቁት
2. አለያየ. A misunderstanding parted them. አለመግባባት ፡ አለያያቸው
3. ከፈለ. On which side do you part your hair? ጸጉርህን ፡ የምትከፍለው ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ?
4. ገለጠ. She parted the curtains to look out. ወደ ፡ ውጭ ፡ ለማየት ፡ መጋረጃዎቹን ፡ ገለጠች

**part** (vi.)
1. መንገድ ፡ ለቀቀ(ለት). The crowd parted to let us through. እንድናልፍ ፡ ሕዝቡ ፡ መንገድ ፡ ለቀ ቀልን
2. ተለያየ. She parted from her friends in tears. ከጓደኞቿ ፡ በእንባ ፡ ተለያየች
We parted at the corner. መታጠፊያው ፡ ላይ ፡ ተለያየን
3. ተበጠሰ. The rope parted in the middle. ገመዱ ፡ መሀሉ ፡ ላይ ፡ ተበጠሰ
4. ገለጠ. The clouds parted, revealing the sun. ደመናው ፡ ስለገለጠ ፡ ፀሐይዋ ፡ ታየች

**part with**
1. አወጣ. He hates to part with his money. ገንዘብ ፡ ማውጣት ፡ አይወድም
2. ከእጅ ፡ አወጣ. I wouldn't part with that book for any price. ያንን ፡ መጽሐፍ ፡ በምን ም ፡ ዓይነት ፡ ከእጄ ፡ አላወጣውም
[See also 'company']

**part** (n.)

1. ክፍል. That part of the work isn't finished yet. ከሥራው ፡ ያኛው ፡ ክፍል ፡ ገና ፡ አላለቀም
The western part of Ethiopia is very hot. የኢትዮጵያ ፡ ምዕራባዊ ፡ ክፍል ፡ በጣም ፡ ሞቃት ፡ ነው
2. ድርሻ. Everyone must do his part. ሁሉም ፡ ሰው ፡ ድርሻውን ፡ መሥራት ፡ አለበት
3. ግማሽ. The fence is part wood and part stone. አጥሩ ፡ ግማሹ ፡ ዕንጨት ፡ ግማሹ ፡ ግምብ ፡ ነው
4. ቦታ. I have a good part in the play. ቲያትሩ ፡ ውስጥ ፡ ጥሩ ፡ ቦታ ፡ ተሰጥቶኛል
5. ኀላፊነት. He plays a minor part in the government. በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ኀላፊነት ፡ ዝቅተኛ ፡ ነው
6. ፈንታ. The detective's part was to find the criminal. የወንጀል ፡ መርማሪ ፡ ፈንታ ፡ ወንጀለኛውን ፡ ማግኘት ፡ ነበር
7. አባል. He felt himself to be a part of the gang. የጓዱ ፡ አባል ፡ እንደሆነ ፡ ተሰማው
*He's part Indian. የህንድ ፡ ክልስ ፡ ነው

**parts**
1. አገር. Are you from these parts? የዚህ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ነህ ?
2. ግድም. I haven't traveled much in these parts. በዚህ ፡ ግድም ፡ ብዙ ፡ አልተዘዋወርኩም

**part and parcel** መሠረታዊ ፡ ክፍል
The guarantee was part and parcel of the bargain. ዋስትናው ፡ የግገርው ፡ መሠረታዊ ፡ ክፍል ፡ ነበር
*Her love for her child was part and parcel of her life. ሕይወቷ ፡ የተመሠረተው ፡ በልጇ ፡ ፍቅር ፡ ላይ ፡ ነው

**for my part** በኔ ፡ በኩል ፤ በበኩሌ
For my part, I can let you have the book. በኔ ፡ በኩል ፡ መጽሐፉን ፡ ላውስህ ፡ እችላለሁ
For my part, I feel that it is advisable to do so. በበኩሌ ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ የሚያዋጣ ፡ ይመስለኛል

**for the most part**
1. አብዛኞቹ. His company is made up for the most part of volunteers. የሱ ፡ ሰዎች ፡ አብዛኞቹ ፡ ወዶ ፡ ዘማቾች ፡ ናቸው
2. አብዛኛውን ፡ ጊዜ. For the most part, the weather has been nice this summer. በዚህ ፡ በጋ ፡ አየሩ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጥሩ ፡ ነው
3. በብዙ ፡ በኩል. For the most part, I agree with him. በብዙ ፡ በኩል ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ እስማማለሁ

**foreign parts** ውጭ ፡ አገር
He has traveled much in foreign parts. ውጭ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ዞሯል

**have part in** ነበረ(በት)
He had no part in the robbery. በዝርፊያው ፡ ውስጥ ፡ አልነበረበትም

**in good part**
1. በወዳጅነት ፡ መልክ. He took the joke in good part. ቀልዱን ፡ በወዳጅነት ፡ መልክ ፡ ተቀበለው
2. አብዛኛው. His success is in good part ascribable to dogged determination. ከሰበው ፡ መድረሱ ፡ አብዛኛው ፡ ከጠንካራ ፡ መንፈሱ ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል

**in part** በከፊል
I agree with you in part. በከፊል ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ እስማማለሁ

**on my part** በበኩሌ
On my part, I cannot understand his English. በበኩሌ ፡ የሱ ፡ እንግሊዝኛ ፡ አይገባኝም

**play a part** ቦታ ፡ ያዘ
Private enterprise plays a small part in Ethiopia's development. በኢትዮጵያ ፡ ልማት ፡ ውስጥ ፡ የግል ፡ ንግድ ፡ የያዘው ፡ ቦታ ፡ አነስተኛ ፡ ነው

**take part**
1. ተካፈለ. He took part in the African campaign. በአፍሪካ ፡ ዘመቻ ፡ ተካፍሏል
2. ተካፋይ ፡ ሆነ. Are you going to take part in the discussion? በውይይቱ ፡ ተካፋይ ፡ ትሆናለህ ?

**take someone's part** ደገፈ
He always takes his brother's part. ሁልጊዜ ፡ ወንድሙን ፡ ይደግፋል
[See also 'early, spare']

**partake**
1. ከሱ ፡ ጋር ፡ ተሳተፈ. Will you partake of this humble meal? ይችን ፡ ተራ ፡ ምግብ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ልትሳተፍ ፡ ትፈቅዳለህ ?
2. ተካፈለ. He is still convalescent and cannot partake in sports. አሁንም ፡ ገመምተኛ ፡ ስለ ሆነ ፡ በእስፖርት ፡ ሊካፈል ፡ አይችልም

**partial** ከፊል
That is only partial payment of what you owe. ላለብህ ፡ ዕዳ ፡ ይህ ፡ ከፊል ፡ ክፍያ ፡ ነው

**be partial to**
1. አደላ. He has always been partial to his youngest daughter. ለትንሿ ፡ ልጁ ፡ ዘወትር ፡ ያደላል
2. ወደደ. He is partial to French cooking. የፈረንሳይን ፡ ምግብ ፡ ይወዳል

**partiality** ዝንባሌ
His son shows a strong partiality for history

books. ልጁ ፡ ለታሪክ ፡ መጻሕፍት ፡ የተለየ ፡ ዝንባሌ ፡ አለው

**partially** በከፊል
You are partially right. በከፊል ፡ ልክ ፡ ነህ

**participant** ተካፋይ
I was a participant in the Olympic Games once. በኦሊምፒክ ፡ ውድድር ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተካፋይ ፡ ነበርኩ

**participate** ተካፋይ ፡ ሆነ
How many will participate in the meeting? በስብሰባው ፡ ላይ ፡ስንት ፡ ሰዎች ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናሉ ?

**participation** ተካፋይ ፡ መሆን
Participation of student groups in running the university is a new idea. በዩኒቨርሲቲው ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ ተማሪዎችም ፡ ተካፋይ ፡ መሆናቸው ፡ አዲስ ፡ የመጣ ፡ ሐሳብ ፡ ነው

**participle** ቦዝ ፡ አንቀጽ
The Amharic participle has a special form. በአማርኛ ፡ ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ የተለየ ፡ መልክ ፡ አለው

**particle** ቅንጣት
There is not a particle of truth in that story. በዚያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የእውነት ፡ ቅንጣት ፡ የለበትም
*I got a particle of dust in my eye. ዓይኔ ፡ ውስጥ ፡ አቧራ ፡ ገባ

**particular** (n.) ረገድ
The work is complete in every particular. ሥራው ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ተጠናቋል

**particulars** ዝርዝር
For further particulars, write to the publishers. ተጨማሪውን ፡ ዝርዝር ፡ አታሚውን ፡ በጽሑፍ ፡ ጠይቅ

**particular** (adj.)
1. የተለየ. Is he a particular friend of yours? የተለየ ፡ ጓደኛህ ፡ ነው ?
I went on a walk for no particular reason. ምንም ፡ የተለየ ፡ ዓላማ ፡ ሳይኖረኝ ፡ ልንሸራሸር ፡ ወጣሁ
2. ልዩ. His particular task is to care for the dog. ልዩ ፡ ሥራው ፡ ውሻውን ፡ ማንከባከብ ፡ ነው
3. ራሱ. The table I want is this particular one. የምፈልገው ፡ ጠረጴዛ ፡ ይህ ፡ ራሱ ፡ ነው
4. (= adv.) በተለይ. Pay particular attention to what the teacher says. አስተማሪው ፡ የሚለውን ፡ በተለይ ፡ ልብ ፡ ብለህ ፡ አድምጥ

**be particular** ተጠነቀቀ
My husband is very particular about his food. ባለቤቴ ፡ ስለ ፡ ምግቡ ፡ እጅግ ፡ ይጠነቀቃል

**in particular** በተለይ
I remember one of them in particular. አንደኛውን ፡ በተለይ ፡ አስታውሰዋለሁ

**this particular** ይህኛው
This particular dress costs more. ይህኛው ፡ ልብስ ፡ ይበልጥ ፡ ያወጣል

**particularity** (particularities) የተለየ ፡ ጠባይ
A particularity of his is great attention to detail. ዝርዝር ፡ ጉዳዮችን ፡ አጥብቆ ፡ መመርመር ፡ የተለየ ፡ ጠባዩ ፡ ነው

**particularly**
1. በተለይ. He is particularly interested in science. በተለይ ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ዝንባሌ ፡ አለው
2. በጥንቃቄ. The inspector examined the machine particularly. ተቈጣጣሪው ፡ መኪናውን ፡ በጥንቃቄ ፡ መረመረ

**parting** (n.) መለየየት
The parting of friends is sad. የወዳጆች ፡ መለያየት ፡ አሳዛኝ ፡ ነው

**parting** (adj.)
*The thieves fired a parting shot at us. ሌቦቹ ፡ ሲሸሹ ፡ ተኰሱብን

**partisan**
1. የደፈጣ ፡ ተዋጊ. The partisans attacked the village. የደፈጣ ፡ ተዋጊዎች ፡ መንደሩን ፡ አጠቁ
2. ደጋፊ. Party partisans voted against the passage of the bill. የፓርቲው ፡ ደጋፊዎች ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ እንዳያልፍ ፡ ድምፃቸውን ፡ ሰጡ

**partition** (v.) ከፋፈለ
They partitioned the room and made several small rooms out of it. ክፍሉን ፡ ከፋፍለው ፡ ብዙ ፡ ትናንሽ ፡ ክፍሎች ፡ ሠሩ

**partition** (n.)
1. መከፋፈል. The partition of India resulted in two new countries. የህንድ ፡ መከፋፈል ፡ ለሁለት ፡ አዲስ ፡ አገሮች ፡ መፈጠር ፡ ምክንያት ፡ ሆነ
2. የቤት ፡ አካፋይ. I made a hole in the partition. በቤቱ ፡ አካፋይ ፡ ውስጥ ፡ ቀዳዳ ፡ አበጀሁ
3. የሚከፋፍል ፡ አነስተኛ ፡ ግድግዳ. The desks in the office were separated by partitions. ቢሮው ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ጠረጴዛዎች ፡ በሚከፋፍል ፡ አነስተኛ ፡ ግድግዳ ፡ ተለያይተዋል

**partly** ግማሹ
The house is only partly rented. ቤቱ ፡ ግማሹ ፡ ብቻ ፡ ተከራይቷል

**partner**
1. ሽርካ ፤ ሽሪክ. My partner is coming back tomorrow. ሽርካዬ ፡ (ሽሪኬ) ፡ ነገ ፡ ይመለሳል
2. ባለጥቅም ፤ ማኅበርተኛ. The division of profits among the partners was equitable. የባለጥቅሞቹ ፡ የትርፍ ፡ አከፋፈል ፡ ተገቢ ፡ ነበር
He apportioned the profits among the partners. ትርፉን ፡ ለማኅበርተኞቹ ፡ አከፋፈለ
*I was his tennis partner once a week. በሳምንት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ ቡድን ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ቴኒስ ፡ እንጫወት ፡ ነበር

**partner in crime** ግብረ ፡ አበር
His partner in crime was later arrested by the police. ግብረ ፡ አበሩ ፡ ቆይቶ ፡ በፖሊስ ፡ ተያዘ
[See also 'silent']

**partnership** ሽርክና
The partnership was broken up by the death of the younger one. በታናሽዬው ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ ሽርክናው ፡ ፈረሰ

**partook,** see **partake**

**partridge** ቆቅ
Some of my friends hunt partridge. አንዳንድ ፡ ጓደኞቼ ፡ ቆቅ ፡ ያድናሉ

**part-time** የትርፍ ፡ ሰዓት
I am looking for a part-time job. የትርፍ ፡ ሰዓት ፡ ሥራ ፡ በመፈለግ ፡ ላይ ፡ ነኝ

**party** (parties)
1. ግብዣ. She likes to give big parties. ትልቅ ፡ ግብዣ ፡ ማድረግ ፡ ትወዳለች
2. የፖለቲካ ፡ ቡድን. What party do you belong to? የየትኛው ፡ የፖለቲካ ፡ ቡድን ፡ አባል ፡ ነህ ?
3. ሰው. The party you were calling is on the telephone now. በስልክ ፡ የምትፈልገው ፡ ሰው ፡ ቀርቧል
4. ነገረተኛ. Neither of the two parties appeared at the trial. ከነገረተኞቹ ፡ አንዱም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አልቀረበም
5. ጓድ. A search party set out to find the missing boy. የጠፋውን ፡ ልጅ ፡ ለመፈለግ ፡ የፈላጊዎች ፡ ጓድ ፡ ተሰማራ
6. ወገን. He served as a go-between, but was unable to reconcile the two parties. እንደ ፡ አስታራቂ ፡ ሆኖ ፡ ቢያገላግልም ፡ ሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ ለማስታረቅ ፡ አልቻለም

**be a party to** ተካፋይ ፡ ሆነ
I don't want to be a party to any conspiracy. በማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ አድማ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ አልፈልግም

**throw a party** ፓርቲ ፡ አደረገ
He threw a party to welcome the returning students. ከውጭ ፡ አገር ፡ የተመለሱትን ፡ ተማሪዎች ፡ ለመቀበል ፡ ፓርቲ ፡ አደረገ

**paschal** የፋሲካ
The paschal lamb is expensive. የፋሲካ ፡ በግ ፡ ውድ ፡ ነው

**pass** (vt.)
1. አለፈ. I pass this bank building every day. ሁል ፡ ቀን ፡ በዚህ ፡ ባንክ ፡ በኩል ፡ አልፋለሁ
Did you pass your examination? ፈተናህን ፡ አለፍክ ?
2. አሳለፈ. He passed most of the time reading. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በማንበብ ፡ አሳለፈ
After much deliberation, they passed the bill. ብዙ ፡ ከተነጋገሩበት ፡ በኋላ ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ አሳለፉ
The teacher passed the whole class this term. በዚህ ፡ ተርም ፡ አስተማሪው ፡ ተማሪዎቹን ፡ ሁሉ ፡ አሳለፈ
3. ቀደመ. An express bus passed the local bus. በራሪ ፡ አውቶቡስ ፡ የከተማውን ፡ አውቶቡስ ፡ ቀደመው
4. አቀበለ. Will you please pass the bread? እስቲ ፡ ዳቦውን ፡ አቀብለኝ
Will you pass me the sugar, please! ስኳሩን ፡ ታቀብለኝ
5. አስገባ. The sentry passed the returning soldiers. ዘቡ ፡ ተመላሾቹን ፡ ወታደሮች ፡ አስገባቸው
6. ለሰው ፡ ሰጠ. He was in prison for passing bad checks. የሐሰት ፡ ቼክ ፡ ለሰው ፡ በመስጠቱ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ነበር
7. ሰጠ. I can't pass an opinion on your work before seeing it. ሥራህን ፡ ሳላይ ፡ ስለ ፡ ሥራህ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ አስተያየት ፡ ልሰጥ ፡ አልችልም
The judge will pass sentence today. ዳኛው ፡ ዛሬ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል
8. ጣሰ. You passed the red light. ቀይ ፡ መብራት ፡ ጣስክ

**pass** (vi.)
1. አለፈ. The days pass quickly when you are busy. ሥራ ፡ ሲይዙ ፡ ቀኑ ፡ ቶሎ ፡ ያልፋል
2. ተላለፈ. The land passes from father to son. ርስቱ ፡ ከአባት ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ ይተላለፋል
3. ሆነ. Tell me everything that passed be-

tween you. በሁለታችሁ ፡ መካከል ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ንገረኝ

4. ተለወጠ. Water passes to a solid state when it freezes. ውኃ ፡ ሲረጋ ፡ ወደ ፡ በረዶነት ፡ ይለወጣል

5. ጸደቀ ፤ አለፈ. The new tax bill quickly passed. አዲሱ ፡ የግብር ፡ ሕግ ፡ በቶሎ ፡ ጸደቀ ፡ (አለፈ)

**pass across each other** ተላለፈ

The two lines pass across each other. ሁለቱ ፡ መሥመሮች ፡ ይተላለፋሉ

**pass around**

1. አስተላለፈ. Pass the bottle around! ጠርሙሱን ፡ አስተላልፍ

2. አሰረ. He passed a rope around the barrel. በርሜሉ ፡ ዙሪያ ፡ ገመድ ፡ አሰረ

**pass away**

1. አረፈ. Her mother passed away last week. እናቷ ፡ ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ አረፉ

2. አለፈ. All this trouble will pass away. ይህ ፡ ሁሉ ፡ ችግር ፡ ያልፋል

**pass for**

1. ተቈጠረ ፤ ታየ. He passes for a learned man in this small village. በዚህ ፡ ትንሽ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ እንደተማረ ፡ ሰው ፡ ይቈጠራል ፡ (ይታያል)

2. መስሎ ፡ አሳሳተ. They look so much alike that they could pass for brothers. በመልክ ፡ አንድ ፡ ስለሆኑ ፡ ወንድማማቾች ፡ መስለው ፡ ያሳስታሉ

**pass in review** (tr.) ሰልፍ ፡ ጐበኘ

The general passed the troops in review. ጄኔራሉ ፡ የወታደሩን ፡ ሰልፍ ፡ ጐበኘ

**pass in review** (intr.) በሰልፍ ፡ አለፈ

The troops passed in review before the Emperor. ወታደሮቹ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊት ፡ በሰልፍ ፡ አለፉ

**pass off** (vi.)

1. ተከናወነ. The strike meeting passed off quietly. ሥራ ፡ ለማቆም ፡ የተደረገው ፡ ስብሰባ ፡ በጸጥታ ፡ ተከናወነ

2. (= tr.) ተወ. The headache passed off in the late afternoon. ራስ ፡ ምታቱ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ቆየት ፡ ብሎ ፡ ተወኝ

**pass oneself off as**

He passed himself off as a doctor. በሐሰት ፡ ሐኪም ፡ ነኝ ፡ አለ

**pass out** (vt.) ዐደለ

They passed out pamphlets at the meeting. በስብሰባው ፡ ላይ ፡ አነስተኛ ፡ መጽሔት ፡ ዐደሉ

**pass out** (vi.) ነፍሱን ፡ ሳተ

Several people passed out from the heat. ከሙቀቱ ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ነፍሳቸውን ፡ ሳቱ

**pass over**

1. ዳሰሰ. Pass your hand over the silk and feel how soft it is! ሐሩን ፡ ዳስሀ ፡ እንዴት ፡ እንደሚለሰልስ ፡ ተመልከት

2. ችላ ፡ አለ ፤ አለፈ. Just pass over the first part of the letter! የደብዳቤውን ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ ችላ ፡ በለው ፡ (እለፈው)

**pass up** ሳይቀበለው ፡ ቀረ

He passed up the chance to go to America. አሜሪካ ፡ ለመሄድ ፡ የነበረውን ፡ ዕድል ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀረ

**come to pass** ተደረገ

Strange things came to pass. እንግዳ ፡ ነገሮች ፡ ተደረጉ

**it will pass** ምንም ፡ አይል

This copy isn't very good, but it will pass. ይህ ፡ ግልባጭ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ አይደለም ፤ ሆኖም ፡ ምንም ፡ አይል

**let pass**

1. አሳለፈ. The guard didn't let me pass. ዘበኛው ፡ አላሳልፍ ፡ አለኝ

2. እንዲያልፍ ፡ ፈቀደ. The censor let the letter pass. ሳንሱሩ ፡ ደብዳቤው ፡ እንዲያልፍ ፡ ፈቀደ

3. ችላ ፡ አለ. He decided to let the insult pass. ስድቡን ፡ ችላ ፡ ለማለት ፡ ወሰነ

4. አመለጠ(ው). +Don't let the opportunity to go to Ethiopia pass. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመሄድ ፡ ያጋጠመህ ፡ ዕድል ፡ እንዳያመልጥህ

[See also 'obscurity']

**pass** (n.)

1. የፈቃድ ፡ ወረቀት ፤ ፈቃድ. You will need a pass to get by the gate. በሩን ፡ ለማለፍ ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀት ፡ (ፈቃድ) ፡ ያስፈልግሃል

2. ጊዜያዊ ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት. Stateless persons may be granted passes, but not passports. ዜግነት ፡ የሌላቸው ፡ ጊዜያዊ ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ እንጂ ፡ ፓስፖርት ፡ አይሰጣቸውም

3. በተራራዎች ፡ መሀል ፡ ያለ ፡ መተላለፊያ. The pass was held by the government troops. በተራራዎች ፡ መሀል ፡ ያለው ፡ መተላለፊያ ፡ በመንግሥት ፡ ወታደሮች ፡ ተይዞ ፡ ነበር

**passable** መጠነኛ

He has a passable knowledge of Amharic. መጠነኛ ፡ ያማርኛ ፡ ችሎታ ፡ አለው

**be passable** ያስኬዳል

This road is passable only in the dry season. ይህ ፡ መንገድ ፡ የሚያስኬደው ፡ በበጋ ፡ ብቻ ፡ ነው

**passage**

1. መተላለፊያ. We had to go through a dark

passage. ጭልም ፡ ባለ ፡ መተላለፊያ ፡ ማለፍ ፡ ነበረብን
2. የማለፍ ፡ ፈቃድ. He was given passage through the enemy lines. በጠላት ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የማለፍ ፡ ፈቃድ ፡ ተሰጠው
3. ጉዞ. We had a calm passage across the Atlantic. አትላንቲክን ፡ ስናቋርጥ ፡ ደኅና ፡ ጉዞ ፡ አጋጠመን
4. ምንባብ. He read us an interesting passage from his book. ከመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ የሚያስደስት ፡ ምንባብ ፡ አነበበልን
5. ክፍል. The expurgated edition of Shakespeare has no offensive passages in it. የታረመው ፡ የሼክስፒር ፡ ቲያትር ፡ በውስጡ ፡ የሚያስከፋ ፡ ክፍል ፡ የለበትም
6. ማለፍ. The passage of the bill was very well received. የረቂቁን ፡ ማለፍ ፡ በደስታ ፡ ተቀበሉት

**book passage** በታ ፡ ያዘ
He booked passage to New York. ወደ ፡ ኒው ፡ ዮርክ ፡ ለመሄድ ፡ በታ ፡ ያዘ

**force passage** ተጋፍቶ ፡ አለፈ
He had to force passage through the crowd. በሕዝቡ ፡ መሀከል ፡ ተጋፍቶ ፡ ማለፍ ፡ ነበረበት

**with the passage of time** በቀን ፡ ብዛት
With the passage of time, old hatreds are forgotten. በቀን ፡ ብዛት ፡ የቆየ ፡ ቂም ፡ ይረሳል

**passenger** መንገደኛ ፤ ተሳፋሪ
The bus holds only thirty passengers. አውቶቡሱ ፡ ሠላሳ ፡ መንገደኞች ፡ ብቻ ፡ ይይዛል
Boats ply among the islands of Lake Tana carrying food and passengers. ጀልባዎች ፡ ምግብና ፡ ተሳፋሪዎች ፡ ይዘው ፡ በጣና ፡ ደሴቶች ፡ መካከል ፡ ይመላለሳሉ

**passer-by** መንገደኛ ፤ አላፊ ፡ አግዳሚ
A passer-by must have picked it up. መንገደኛ ፡ (አላፊ ፡ አግዳሚ) ፡ አንሥቶት ፡ ይሆናል

**passing** (n.) ሞት
The whole nation mourned his passing. በሱ ፡ ሞት ፡ አገሩ ፡ በሙሉ ፡ አዘነ

**passing** (adj.)
1. ተላላፊ. The passing crowd paid no attention to the sick child. ተላላፊው ፡ ሕዝብ ፡ በሽተኛውን ፡ ልጅ ፡ ዞር ፡ ብሎም ፡ አላየው
2. ዘላቂነት ፡ የሌለው. This is only a passing fashion. ይህ ፡ ሞድ ፡ ዘላቂነት ፡ የሌለው ፡ ነው

**give a passing glance** መልከት ፡ አደረገ
I gave the girl a passing glance. ልጅቷን ፡ መልከት ፡ አደረግኳት

**give a passing mark** አሳለፈ
The teacher gave the student a passing mark. አስተማሪው ፡ ተማሪውን ፡ አሳለፈው

**in passing** በነገሬ ፡ ላይ
In passing, I'd like to say that ... በነገሬ ፡ ላይ ፡ ለማለት ፡ የምፈልገው

**passion**
1. ስሜት. He is guided by passion rather than by reason. በምርምር ፡ ሳይሆን ፡ በስሜት ፡ ይመራል
2. ፍቅር. The sight of her filled him with passion. ሲያያት ፡ በፍቅር ፡ ተነሸጠ
*Music is her passion. ሙዚቃ ፡ በጣም ፡ ትወዳለች

**fly into a passion** በንዴት ፡ ጦፈ
He flew into a passion when he heard his speech. ንግግሩን ፡ ሲሰማ ፡ በንዴት ፡ ጦፈ

**have a passion for** በጣም ፡ ወደደ
She has a passion for American food. የአሜሪካንን ፡ ምግብ ፡ በጣም ፡ ትወዳለች

**passionate**
1. የጋለ ፡ ስሜት ፡ ያለው. Passionate believers in religion are willing to fight to the death. ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ለሃይማኖቱ ፡ የጋለ ፡ ስሜት ፡ ካለው ፡ ሕይወቱን ፡ ለመሠዋት ፡ እንኳ ፡ አይመለስም
2. (= adv.) በጋለ ፡ ስሜት. He made a passionate speech. በጋለ ፡ ስሜት ፡ ንግግር ፡ አደረገ
*He's a very passionate man. ሲወድ ፡ ከልቡ ፤ ሲጠላም ፡ እንዲሁ ፡ ነው

**passionately** በጥልቅ ፡ ስሜት
He spoke passionately of Ethiopia's sufferings in the war. በጦርነቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ስለደረሰው ፡ ሥቃይ ፡ ሲያወራ ፡ በጥልቅ ፡ ስሜት ፡ ነው

**passive**
1. ተከፋይ ፡ ያልሆነ. In spite of my efforts, the boy remained passive. ምንም ፡ ብለፋ ፡ እንኳ ፡ ልጁ ፡ ተከፋይ ፡ ሳይሆን ፡ ቀረ
2. የታዛዥነት. His son has a passive disposition. ልጁ ፡ የታዛዥነት ፡ ጠባይ ፡ አለው
*The child listened to the scolding in passive silence. ልጁ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ቁጣውን ፡ ተቀበለ

**passive resistance** ሰላማዊ ፡ ተቃውሞ
Gandhi was a strong believer in passive resistance. ጋንዲ ፡ የሰላማዊ ፡ ተቃውሞ ፡ ተከራካሪ ፡ ነበር

**passport** የይለፍ ፡ ወረቀት ፤ ፓስፖርት
When passing through customs, you have to

show your passport. ጉምሩክ ፡ ተቈጣጣሪዎች ፡ ዘንድ ፡ ሲደርሱ ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ (ፓስፖርት) ፡ ማሳየት ፡ አለብዎ

**password** የመለያ ፡ ቃል ፤ የማለፊያ ፡ ቃል
In order to be allowed to enter the soldiers' camp, you have to know the password. ከወታደሮቹ ፡ ሰፈር ፡ ለመግባት ፡ የመለያውን ፡ ቃል ፡ (የማለፊያውን ፡ ቃል) ፡ ማወቅ ፡ አለብህ

**past** (n.)
1. የጥንት ፡ ታሪክ. Ethiopia's past interests historians. የኢትዮጵያ ፡ የጥንት ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎችን ፡ ይስባል
2. (= adj.) የቀረ. Slavery is a thing of the past. ባርነት ፡ የቀረ ፡ ነገር ፡ ነው
3. ያለፈ ፡ ነገር ፤ ያለፈ. History deals with the past. ታሪክ ፡ ስላለፈ ፡ ነገር ፡ ይናገራል
Try to forget the past now that your troubles are over. አሁን ፡ ችግርህ ፡ ስላለፈ ፡ ያለፈውን ፡ እርሳው
4. ጥንት. The old man talked of the past. ሽማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ ስለ ፡ ጥንቱ ፡ ተናገረ
5. ያሳለፈው ፡ ጊዜ. The explorer had a colorful past. አሳሹ ፡ ያሳለፈው ፡ ጊዜ ፡ የሚያስደስት ፡ ነው

**past** (adj.)
1. ያለፈ. Where were you this past week? ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ የት ፡ ነበርክ ?
2. የቀድሞ. Three past presidents of the club came to the meeting. ሦስት ፡ የክበቡ ፡ የቀድሞ ፡ ፕሬዚዳንቶች ፡ ለስብሰባው ፡ መጡ
3. የድሮ. The book describes the past glories of Greece. መጽሐፉ ፡ የግሪክን ፡ የድሮ ፡ ዝና ፡ ይገልጻል

**past** (prep.) ከ --- አለፍ ፡ ብሎ
Past the Ras Makonnen bridge, there is an optician. ከራስ ፡ መኰንን ፡ ድልድይ ፡ አለፍ ፡ ብሎ ፡ ያይን ፡ መነጽር ፡ ሻጭ ፡ ይገኛል
*It's five minutes past twelve. ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ከምስት ፡ ደቂቃ ፡ ነው

**be past** ታለፈ
The most dangerous part of the trip is past. የጉዞው ፡ አደገኛ ፡ ክፍል ፡ ታልፏል

**go past** በ --- በኩል ፡ አለፈ
Does this bus go past Arat Kilo? ይህ ፡ አውቶቡስ ፡ በአራት ፡ ኪሎ ፡ በኩል ፡ ያልፋል ?

**in the past** ከዚህም ፡ በፊት
That has often happened in the past. ያ ፡ ከዚህም ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተደርጓል

**run past** በ --- በኩል ፡ ሮጦ ፡ አለፈ
The boy ran past the house. ልጁ ፡ በቤቱ ፡ በኩል ፡ ሮጦ ፡ አለፈ

**walk right past** ባጠገብ ፡ አለፈ
He walked right past me without seeing me. ሳያየኝ ፡ ባጠገቤ ፡ አለፈ
[See also 'distant, remote']

**paste** (v.) ለጠፈ
Paste these labels on the jars! እነዚህን ፡ ምልክቶች ፡ በማሰሮዎቹ ፡ ላይ ፡ ለጥፋቸው

**paste** (n.) ሙቅ
Do you have any paste to put on this paper? ይህንን ፡ ወረቀት ፡ ማጣበቂያ ፡ ሙቅ ፡ አለህ ?

**pastime** የጊዜ ፡ ማሳለፊያ
Children need some kind of pastime on rainy days. በዝናብ ፡ ጊዜያት ፡ ሕፃናት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የጊዜ ፡ ማሳለፊያ ፡ ያስፈልጋቸዋል

**pastor** ካህን
The pastor of the Lutheran church will give a speech. የሉተራን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካህን ፡ ንግግር ፡ ያደርጋሉ

**pastoral**
1. ከብት ፡ አርቢ. The pastoral tribes of the mountains graze their sheep on the hillside. ተራራዎች ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ ከብት ፡ አርቢ ፡ ጐሳዎች ፡ በጎቻቸውን ፡ የሚያሰማሩት ፡ ጋራው ፡ ጥጋት ፡ ላይ ፡ ነው
2. ያገር ፡ ቤት. Pastoral life is depicted in these paintings. ያገር ፡ ቤት ፡ ኑሮ ፡ በነዚህ ፡ ሥዕሎች ፡ ላይ ፡ ተገልጿል
3. መንፈሳዊ. The priest read the bishop's pastoral letter to the church members. ቄሱ ፡ የጳጳሱን ፡ መንፈሳዊ ፡ መልእክት ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አባሎች ፡ አነበቡ
4. የቅስና. Pastoral duties include visiting the sick. የቅስና ፡ ተግባር ፡ የታመሙ ፡ ሰዎችን ፡ መጐብኘት ፡ ይጨምራል

**pastry** (pastries) ብስኩት ፡ መሳይ
I like to have pastry with my coffee. ቡና ፡ ስጠጣ ፡ ብስኩት ፡ መሳይ ፡ መብላት ፡ ደስ ፡ ይለኛል

**past tense** ኀላፊ ፡ ጊዜ
The past tense of 'walk' is 'walked'. የ« መሄድ » ፡ ኀላፊ ፡ ጊዜ ፡ « ሄደ » ፡ ነው

**pasture** (v.) በላ
The sheep pastured on the hillside. በተራራው ፡ ጥጋት ፡ ላይ ፡ በጎች ፡ ይበሉ ፡ ነበር

**pasture** (n.) ግጦሽ
He takes the cattle to pasture early every

morning. ሁልቀን ፡ ማለዳ ፡ ከብቶቹን ፡ ወደ ፡ ግጦሽ ፡ ይወስዳል
The rocky hillside had enough pasture for sheep. ድንጋያማው ፡ የተራራ ፡ ጥግ ፡ ለበጎች ፡ የሚበቃ ፡ ግጦሽ ፡ ነበረበት

**pasture land** የግጦሽ ፡ መሬት
The pasture land is fenced in. የግጦሹ ፡ መሬት ፡ ታጥሯል

**pat** (patted)
1. አሻሸ. He patted the dog. ውሻውን ፡ አሻሸው
2. መታ ፡ መታ ፡ አደረገ. He patted me on the back to comfort me. ሊያጽናናኝ ፡ ጀርባዬን ፡ መታ ፡ መታ ፡ አደረገ
3. ጠፈጠፈ. She patted the dough into a flat cake. ቂጣውን ፡ ስስ ፡ እንዲሆን ፡ ጠፈጠፈችው

**pat oneself on the back** ራሱን ፡ በራሱ ፡ አሞገሰ
He has been patting himself on the back for the deal he made yesterday. ትላንት ፡ ስለፈጸመው ፡ ጉዳይ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ አሞገሰ

**pat** (adj.) ተገቢ
A pat solution is to work hard. ተገቢው ፡ መፍትሔ ፡ ተግቶ ፡ መሥራት ፡ ነው

**stand pat** አጥብቆ ፡ ተከተለ
The government must stand pat in its policy. መንግሥቱ ፡ መመሪያውን ፡ አጥብቆ ፡ መከተል ፡ አለበት

**patch** (v.)
1. ለጠፈ. I patched the tire, but it still leaks. ጎማውን ፡ ለጥፌው ፡ ነበር ፡ ግን ፡ አሁንም ፡ ይተነፍሳል
2. ጣፈ. Mother has to patch my trousers. እናቴ ፡ ሱሪዬን ፡ መጣፍ ፡ አለባት

**patch together**
He patched together a speech. በችኮላ ፡ ንግግር ፡ አጠናቀረ

**patch up**
1. ታረቀ. They haven't patched up their quarrel yet. በተጣሉበት ፡ ነገር ፡ አሁንም ፡ አልታረቁም
2. ጠገን ፡ አደረገ. I have patched up the leak. የሚያፈሰውን ፡ ጠገን ፡ አድርጌዋለሁ

**patch** (n.)
1. ልጥፍ. He put a new patch on the tire. ጎማው ፡ ቡት ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ ልጥፍ ፡ አደረገበት
2. እራፊ. I will have to put a new patch on the trousers. ሱሪዬ ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ እራፊ ፡ መጣፍ ፡ አለብኝ
3. ጨርቅ. He covered the perforation with a patch. ቀዳዳውን ፡ በጨርቅ ፡ ለጠፈ
4. ፋሻ. He wore a patch over his eye for days. ለብዙ ፡ ቀኖች ፡ ዓይኑ ፡ ላይ ፡ ፋሻ ፡ አስሮ ፡ ነበር
5. መደብ. Her garden patch has only tomato plants in it. አትክልት ፡ መደቧ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የቲማቲም ፡ ተክል ፡ ብቻ ፡ ነው

**patent** (n.) የመብት ፡ ማስከበሪያ ፡ ሰነድ
He took out a patent to protect his invention. እሱ ፡ ላደረገው ፡ ፍልሰፋ ፡ የመብት ፡ ማስከበሪያ ፡ ሰነድ ፡ አወጣ

**patent** (adj.) እልም ፡ ያለ
That's a patent lie. ይህ ፡ እልም ፡ ያለ ፡ ውሸት ፡ ነው

**paternal**
1. አባታዊ. He gave me some paternal advice. አባታዊ ፡ ምክር ፡ ሰጠኝ
2. (= adv.) እንደ ፡ አባት ፡ ሆኖ. Some governors want to appear paternal. አንዳንድ ፡ ገዢዎች ፡ እንደ ፡ አባት ፡ ሆነው ፡ ለመታየት ፡ ይፈልጋሉ

**paternal grandfather** ያባት ፡ አባት
My paternal grandfather is still alive. ያባቴ ፡ አባት ፡ አሁንም ፡ በሕይወት ፡ አለ

**paternalism** አባታዊ ፡ አስተዳደር
The employees appreciate the paternalism of the old president. ሠራተኞቹ ፡ የቀድሞውን ፡ ፕሬዚዳንት ፡ አባታዊ ፡ አስተዳደር ፡ ይወዳሉ

**paternity** አባት ፡ መሆን
He refused to acknowledge the paternity of the child. የልጁ ፡ አባት ፡ መሆኑን ፡ ካደ
*They couldn't trace the paternity of the child. የልጁ ፡ አባት ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ አልቻሉም

**path**
1. የእግር ፡ መንገድ. Keep to the path, or you will lose your way! የእግር ፡ መንገዱን ፡ ተከተል ፤ ያለበለዚያ ፡ ትጠፋለህ
2. መንገድ. A narrow path leads to the river. አንድ ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ወንዙ ፡ ይወስዳል
He followed the path of righteousness all his life. ሕይወቱን ፡ በሙሉ ፡ የቅድስናን ፡ መንገድ ፡ ተከተለ

**beat a path**
*We beat a path through the tall grass. ደገላውን ፡ በዱላ ፡ እየጣስን ፡ሄድን
[See also 'cleave, duty']

**pathetic** አሳዛኝ
The cries of the wounded were pathetic. የቁስለኞቹ ፡ ጩኸት ፡ አሳዛኝ ፡ ነበር

**patience** ትዕግሥት ፤ ታጋሽነት
He lacks the patience to endure the noise of children. የልጆችን ፡ ጫጫታ ፡ ለመቻል ፡ ትዕግሥት ፡ የለውም
Parenthood requires patience and understanding. ወላጅ ፡ መሆን ፡ ታጋሽነትንና ፡ አድማጭነትን ፡ ይጠይቃል

**patient** (n.) በሽተኛ
There are two more patients waiting outside. ሌሎች ፡ ሁለት ፡ በሽተኞች ፡ ውጭ ፡ ይጠብቃሉ

**patient** (adj.)
1. ትዕግሥተኛ. The patient boy let his comrade's insult go by as though he did not hear it. ትዕግሥተኛው ፡ ልጅ ፡ የጓደኛውን ፡ ስድብ ፡ እንዳልሰማ ፡ ሰምቶ ፡ አለፈው
2. ቻይ. His wife nags him because he is very patient. በጣም ፡ ቻይ ፡ ስለሆነ ፡ ሚስቱ ፡ ትነዘንዘዋለች
*It took five years of patient labor to perfect his invention. ፍልሰፋውን ፡ ከፍጹምነት ፡ ለማድረስ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በትዕግሥት ፡ ሠራ

**patiently** ጥርሱን ፡ ነክሶ
He endured his disease patiently. በሽታውን ፡ ጥርሱን ፡ ነክሶ ፡ ቻለ

**patriarch**
1. ባለቤት. The patriarch of the family rules with an iron hand. ባለቤቱ ፡ ቤተሰቡን ፡ በጥብቅ ፡ ያስተዳድራል
2. ባላባት. Abraham was one of the Jewish patriarchs. አብርሃም ፡ ከአይሁድ ፡ ባላባቶች ፡ አንዱ ፡ ነበር
3. ፓትሪያርክ. The Patriarch will dedicate the new church. ፓትሪያርኩ ፡ አዲሱን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይመርቃሉ

**patrimony** (patrimonies) የወረሰው ፡ ሀብት
His patrimony was worth millions of dollars. የወረሰው ፡ ሀብት ፡ ብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ የሚያወጣ ፡ ነበር

**patriot** አገሩን ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፤ አርበኛ
Patriots will always serve their country. አገራቸውን ፡ የሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ሀገራቸውን ፡ ያገለግላሉ
The patriot was a pattern of bravery. አርበኛው ፡ የጀግንነት ፡ ምሳሌ ፡ ነበር

**patriotic**
1. ያገር ፡ ፍቅር. We wrote patriotic songs for the schools. ለትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ያገር ፡ ፍቅር ፡ መዝሙሮች ፡ ጻፍን
2. ያገር ፡ ፍቅር ፡ ያለበት. The patriotic soldier fights hard. ያገር ፡ ፍቅር ፡ ያለበት ፡ ወታደር ፡ ጠንክሮ ፡ ይዋጋል

**patriotism** የሀገር ፡ ፍቅር ፤ ያገር ፡ ፍቅር
He is imbued with patriotism. በሀገር ፡ ፍቅር ፡ የተመሰጠ ፡ ነው

**patrol** (patrolled), v. እየተዘዋወረ ፡ ጠበቀ
A policeman patrols these streets all night long. ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ ፖሊስ ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ይጠብቃል

**patrol** (n.) ቅኝት ፤ ቃኚ ፡ ጓድ
The patrol was surrounded and captured by the enemy. ቅኝቱ ፡ (ቃኚው ፡ ጓድ) ፡ በጠላት ፡ ከተከበበ ፡ በኋላ ፡ ተማረከ

**patron**
1. ደንበኛ. The patrons of this bar are asked not to be too noisy. የዚህ ፡ ቡና ፡ ቤት ፡ ደንበኞች ፡ ጩኸት ፡ እንዳያበዙ ፡ ተጠይቀዋል
2. በጎ ፡ አድራጊ. Most of the museum's expenses are paid by patrons. የቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ወጪ ፡ አብዛኛው ፡ የሚከፈለው ፡ በበጎ ፡ አድራጊዎች ፡ ነው
[See also 'saint']

**patronage**
*Thank you for your patronage of our restaurant! እምግብ ፡ ቤታችን ፡ መጥተህ ፡ ስለተመገብህ ፡ እናመሰግንሃለን
**under the patronage of** በ --- ፡ ደጋፊነት ፡ ሥር
The exhibit was under the patronage of the Patriotic Association. ኤግዚቢሽኑ ፡ ባገር ፡ ፍቅር ፡ ማኅበር ፡ ደጋፊነት ፡ ሥር ፡ ነበር

**patronize**
1. ደንበኛ ፡ ነው. She patronizes the same dressmaker. እሷና ፡ እኔ ፡ ያንድ ፡ ልብስ ፡ ሰፊ ፡ ደንበኞች ፡ ነን
2. ረዳ. My uncle patronizes the museum. አጐቴ ፡ ቤተ ፡ መዘክሩን ፡ ይረዳል
3. ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ገመተ. Don't patronize me! I'm every bit as good as you are. በምንም ፡ ካንተ ፡ ስለማላንስ ፡ ዝቅ ፡ አድርገህ ፡ አትገምተኝ

**patron saint** ታዳጊ
Our patron saint is St. George. ታዳጊያችን ፡ ጊዮርጊስ ፡ ነው

**patronymics** ያባቱ ፡ ስም
Ethiopians are not called by their patronymics. ኢትዮጵያውያን ፡ ባባታቸው ፡ ስም ፡ አይጠሩም

**patter** ገረፈ
The rain pattered on the windowpane. ዝናቡ ፡ የመስኮቱን ፡ መስታወት ፡ ገረፈ

**patter about** ተሯሯጠ
The child pattered about the room. ልጁ ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተሯሯጠ

**patter on** ቀባጠረ
The salesman pattered on while displaying his wares. አሻሻጩ ፡ የሚሸጡትን ፡ እቃዎች ፡ እያሳየ ፡ ቀባጠረ

**pattern** (v.) አመሳሰለ
He patterned his life after his father's. ኑሮውን ፡ ከባቱ ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ አመሳሰለው

**pattern oneself after** የ - - - ፡ አርአያ ፡ ተከተለ
He patterns himself after Napoleon. የናፖሊዮንን ፡ አርአያ ፡ ይከተላል

**pattern** (n.)
1. ሐረግ. This rug has a pretty pattern. ይሀ ፡ ምንጣፍ ፡ ጥሩ ፡ ሐረግ ፡ አለው
2. ንድፍ. Where did you get the pattern for your new dress? ላዲሱ ፡ ልብስሽ ፡ ንድፍ ፡ ከየት ፡ አገኘሽ ?
3. ምሳሌ. The patriot was a pattern of bravery. አርበኛው ፡ የጀግንነት ፡ ምሳሌ ፡ ነበር
4. ሁኔታ. The behavior pattern of the young generation is different from that of the old. የወጣቶች ፡ የጠባይ ፡ ሁኔታ ፡ ከዐዋቂዎች ፡ የተለየ ፡ ነው

**paucity** ማነስ
The paucity of native-born engineers harms our development. የሀገር ፡ ተወላጅ ፡ መሀንዲሶች ፡ ማነስ ፡ እድገታችንን ፡ ያደክመዋል

**pauper** የኔ ፡ ቢጤ
A pauper was out begging this morning. አንድ ፡ የኔ ፡ ቢጤ ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ ሲለምን ፡ ነበር

**pause** (v.)
1. ቆም ፡ አለ. He paused each time he could not think of the proper word. ትክክለኛውን ፡ ቃል ፡ ባጣ ፡ ቁጥር ፡ ቆም ፡ ይል ፡ ነበር
2. ሰፊ ፡ ሐተታ ፡ ሰጠ. The speaker paused upon a particular point of his speech. ተናጋሪው ፡ በተለይ ፡ ባንድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሰፊ ፡ ሐተታ ፡ ሰጠ

**pause** (n.)
1. እረፍት. There was a pause of several seconds between each ringing of the bell. ባንዳንዱ ፡ በተከታዩ ፡ የደወል ፡ ድምፅ ፡ መካከል ፡ የብዙ ፡ ሰከንድ ፡ እረፍት ፡ ነበር
2. ዕረፍት. Everyone welcomed the pause after the long test. ከረጅሙ ፡ ፈተና ፡ በኋላ ፡ በመጣው ፡ ዕረፍት ፡ ሁሉም ፡ ደስ ፡ አለው
*There was a pause in the fighting which lasted only a short time. ጦርነቱ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ቆም ፡ ብሎ ፡ ነበር

**after a short pause** ትንሽ ፡ ቆም ፡ ካለ ፡ በኋላ
After a short pause, the speaker continued. ትንሽ ፡ ቆም ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ተናጋሪው ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ

**pave**
1. አነጠፈ. The highway authorities are paving the street in front of our house. የአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ከቤታችን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያለውን ፡ መንገድ ፡ በማንጠፍ ፡ ላይ ፡ ነው
2. ጠረገ. Technology paves the way to better living. ቴክኖሎጂ ፡ ለተሻለ ፡ ኑሮ ፡ መንገድ ፡ ይጠርጋል

**be paved** ባስፋልት ፡ ተነጠፈ
Our street has finally been paved. መንገዳችን ፡ በመጨረሻው ፡ ባስፋልት ፡ ተነጠፈ
[See also 'way']

**pavement** የተነጠፈ ፡ መንገድ
The pavement is very bumpy. የተነጠፈው ፡ መንገድ ፡ በጣም ፡ አባጣ ፡ ጎባጣ ፡ ይበዛዋል

**pavilion** [ለኤግዚቢሽን ፡ የሚያገለግል ፡ ጊዜያዊ ፡ ዳስ ፡ መሳይ ፡ ቤት]

**paving** አስፋልት
To repair the leak, the paving had to be ripped up. የሚመነጨውን ፡ ለመድፈን ፡ አስፋልቱ ፡ መቆፈር ፡ ነበረበት

**paw** (v.)
1. ፎገረ. The angry bull pawed the ground. የተናደደው ፡ ወይፈን ፡ መሬቱን ፡ ፎገረ
2. በፊት ፡ እግሩ ፡ ነካ ፡ ነካ ፡ አደረገ. The cat pawed the mouse she had caught. ድመቷ ፡ የያዘቻትን ፡ አይጥ ፡ በፊት ፡ እግሯ ፡ ነካ ፡ ነካ ፡ አደረገቻት

**paw** (n.) መዳፍ
The dog has hurt his paw. ውሻው ፡ መዳፉን ፡ ተጎዳ

**pawn** (v.) አስያዘ
I have to pawn my watch to get some money. ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ሰዓቴን ፡ ማስያዝ ፡ አለብኝ

**pawn** (n.) መያዣ
He left his watch in pawn. ሰዓቱን ፡ መያዣ ፡ ሰጠ

**pay** (paid), vt.
1. ከፈለ. We will pay all your expenses. ወጪህን ፡ በሙሉ ፡ እንከፍላለን
2. ጠቀመ. It will pay you to follow my advice. ምክሬን ፡ ብትከተል ፡ ይጠቅምሃል
3. አስገኘ. The job pays $100 a week. ሥራው ፡ በሳምንት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ያስገኛል

**pay** (vi.) ከፈለ
If you paid, let's go! ከከፈልክ ፡ እንሂድ

**pay back**
1. ብድር ፡ መለሰ. I'll pay you back for all those insults. እንደዚያ ፡ ስለሰደብከኝ ፡ ብድሬን ፡ እመልሳለሁ
2. መለሰ. I'll pay you back the dollar on Monday. ብሩን ፡ ሰኞ ፡ እመልስልሃለሁ
3. ከፈለ. He paid me back the favor that I did him. የዋልኩለትን ፡ ውለታ ፡ ከፈለኝ

**pay down** በቅድሚያ ፡ ከፈለ
He agreed to pay $40 down and $10 a month. አርባ ፡ ብር ፡ በቅድሚያ ፡ ከፍሎ ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ ደግሞ ፡ በየወሩ ፡ ሊከፍል ፡ ተስማማ

**pay (for)**
1. ዋጋውን ፡ አገኘ. The thief paid for his crime with a term in jail. ሌባው ፡ እስር ፡ ቤት ፡ በመግባት ፡ ለሠራው ፡ ወንጀል ፡ ዋጋውን ፡ አገኘ
2. ተካ. Money will not pay for the loss of his home. የጠፋውን ፡ ቤቱን ፡ ገንዘብ ፡ አይተካውም

**pay for itself** ዋጋውን ፡ መለሰ
This machine will pay for itself in five months. ይህ ፡ መሣሪያ ፡ ዋጋውን ፡ ባምስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ይመልሳል

**pay off** ከፍሎ ፡ ጨረሰ
He paid off all his debts. ዕዳውን ፡ ሁሉ ፡ ከፍሎ ፡ ጨረሰ

**pay out** ከፈለ (ተከፈለ)
The money is paid out on Fridays. ገንዘቡ ፡ የሚከፈለው ፡ ዓርብ ፡ ዓርብ ፡ ነው

**pay up** ከፍሏል
I'm all paid up. ዕዳዬን ፡ ሁሉ ፡ ከፍያለሁ

**pay (one's) way through**
*He paid his way through college by selling magazines. መጽሔት ፡ እየሸጠ ፡ ለትምህርቱ ፡ በመክፈል ፡ ኮሌጅን ፡ ጨረሰ

[See also 'attention, call, compliment, heed, homage, notice, order, sum, tribute, visit']

**pay** (n.)
1. ደሞዝ. How much is your monthly pay? የወር ፡ ደሞዝህ ፡ ስንት ፡ ነው ?
2. ክፍያ. Equal pay for equal work. ለተመጣጣኝ ፡ ሥራ ፡ እኩል ፡ ክፍያ

**(be) payable** መከፈል ፡ አለበት
This bill is payable today. ይህ ፡ ሒሳብ ፡ ዛሬ፡ መከፈል ፡ አለበት

**payday** ልደታ
I am penniless until payday. እስከ ፡ ልደታ ፡ ባዶ ፡ እጄን ፡ ነኝ

**payment**
1. መከፈል. Prompt payment is requested. በጊዜው ፡ መከፈል ፡ አለበት
2. ክፍያ. I still have three more payments to make on my car. ለመኪናዬ ፡ ሦስት ፡ ክፍያ ፡ ቀርቶኛል
*Her thanks was payment enough for my work. ለሥራዬ ፡ ምስጋናዋ ፡ ብቻ ፡ የዋጋ ፡ ያህል ፡ ነበር

**payroll**
*How many men are on our payroll? ደሞዝ ፡ የሚከፈላቸው ፡ ስንት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ?
*The payroll of this company is more than twenty thousand dollars a week. ይህ ፡ ኩባንያ ፡ ለሠራተኞች ፡ ደሞዝ ፡ የሚያወጣው ፡ በሳምንት ፡ ከሃያ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ ነው

**pea** አተር
Children eat peas. ልጆች ፡ አተር ፡ ይበላሉ

**peace**
1. ሰላም. Our goal is lasting peace. ዓላማችን ፡ ዘላቂ ፡ ሰላም ፡ ነው
He doesn't give me any peace. ሰላም ፡ ይነሣኛል
2. የሰላም ፡ ውል. Peace was signed between the two countries. በሁለቱ ፡ ሀገሮች ፡ መሀከል ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ ተፈረመ

**peace of mind** የመንፈስ ፡ ዕረፍት
Insurance gives one peace of mind. ኢንሹራንስ ፡ የመንፈስ ፡ ዕረፍት ፡ ይሰጣል

**be at peace** ሰላም ፡ ነው
The country has been at peace for the last twenty years. ከሀያ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ አገሩ ፡ ሰላም ፡ ነው

**break the peace** ጸጥታ ፡ አደፈረሰ
He broke the peace by firing a gun. ጠመንጃውን ፡ በመተኰስ ፡ ጸጥታውን ፡ አደፈረሰ

**keep the peace** ጸጥታ ፡ አስከበረ
Three policemen were on hand to keep the peace. ጸጥታውን ፡ ለማስከበር ፡ ሦስት ፡ ፖሊሶች ፡ ተገኝተው ፡ ነበር

**make peace**
1. አስታረቀ. He tried to make peace between the quarreling parties. የተጣሉትን ፡ ወገኖች ፡ ለማስታረቅ ፡ ሞከረ
2. ታረቀ. They made peace after their bitter quarrel. የከረረ ፡ ጥል ፡ ከተጣሉ ፡ በኋላ ፡ ታረቁ

**peaceable** ሰላማዊ
Peaceable people keep out of quarrels. ሰላማዊ ፡ ሰዎች ፡ ከጠብ ፡ ይርቃሉ

**Peace Corps** የሰላም ፡ ጓድ
Peace Corps volunteers taught English in Ethiopia. የሰላም ፡ ጓድ ፡ አባሎች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ያስተምሩ ፡ ነበር

**peaceful**
1. ጸጥ ፡ ያለ. Everything is peaceful around here. በዚህ ፡ አካባቢ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ነው
2. ሰላማዊ. This peaceful tribe tries to avoid war. ይህ ፡ ሰላማዊ ፡ ነገድ ፡ ከጦርነት ፡ ለመራቅ ፡ ይሞክራል

**peach** ኮክ

**peacock** ጣውስ

**peak**
1. ጫፍ. We climbed to the peak of the mountain. ወደ ፡ ተራራው ፡ ጫፍ ፡ ወጣን
2. ጽንፍ. He was then at the peak of his power. ያኔ ፡ ከሥልጣኑ ፡ ጽንፍ ፡ ላይ ፡ ነበር
*Traffic reaches its peak on this road about five o'clock. በዚህ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛው ፡ የትራፊክ ፡ መጨናነቅ ፡ የሚደርሰው ፡ በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ነው

**peal** (v.) ተደወለ
The bells pealed. ደወሎቹ ፡ ተደወሉ

**peal** (n.)
*A peal of laughter interrupted his speech. ክት ፡ ክት ፡ ብሎ ፡ ሲሥቅ ፡ ንግግሩ ፡ ተቋረጠ

**peanut** ኦቾሎኒ
They sell peanuts in the streets. መንገድ ፡ ላይ ፡ ኦቾሎኒ ፡ ይሸጣሉ

**pear** [የፍሬ ፡ ዓይነት]

**pearl** ሉል
The necklace is made of beautiful pearls. ድሪው ፡ ከውብ ፡ ሉል ፡ የተሠራ ፡ ነው

**peasant** ገበሬ
The peasants would like to use modern agricultural methods. ገበሬዎቹ ፡ በዘመናዊ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ መጠቀም ፡ ይፈልጋሉ

**pebble** ጠጠር
The path is covered with pebbles. ጠባቡ ፡ መንገድ ፡ ጠጠር ፡ ፈሶበታል

**peck** (v.)
1. ለቀመ. The chicken pecked at the grain on the ground. ዶሮዋ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጥራጥሬ ፡ ለቀመች
2. ጠቈመ. The parrot pecked my arm. በቀቀኑ ፡ ክንዴን ፡ ጠቈመኝ

**peck a hole in** እየጠቈመ ፡ በሳ
An unhatched chick pecks a hole in the shell. ያልተቀፈቀፈች ፡ ጫጩት ፡ የእንቁላሉን ፡ ቅርፊት ፡ እየጠቈመች ፡ ትበሳለች

**peck** (n.) መስፈሪያ
Give me a peck of barley! አንድ ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ ስጠኝ

**give a peck** ጠቈመ
The hen gave me a peck. ዶሮዋ ፡ ጠቈመችኝ

**peculiar**
1. የተለየ ፤ እንግዳ. Her peculiar behavior has estranged her from her friends. የተለየ ፡ (እንግዳ) ፡ ጠባይዋ ፡ ከወዳጆቿ ፡ አለያያት
2. ልዩ. He is a peculiar fellow. ልዩ ፡ ሰው ፡ ነው
3. (= adv.) ብቻ. These markings are peculiar to this bird. እንዲህ ፡ ዓይነት ፡ ቀለም ፡ ያላት ፡ ይህች ፡ ወፍ ፡ ብቻ ፡ ናት

**be peculiar** ይገርማል
It is peculiar that he has not come, for he promised he would. እመጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ ገብቶ ፡ መቅረቱ ፡ የሚገርም ፡ ነው

**peculiarity** (peculiarities)
1. ልዩ ፡ ጠባይ. One of his peculiarities is his interest in birds. ከልዩ ፡ ጠባዮቹ ፡ አንዱ ፡ ለወፍ ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፡ ነው
2. የእንግዳነት ፡ ጠባይ. In a big city, peculiarity attracts less notice than in a small town. የእንግዳነት ፡ ጠባይ ፡ ከትላልቅ ፡ ከተማዎች ፡ ይልቅ ፡ በትናንሽ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ጐልቶ ፡ ይታያል

**pecuniary** የገንዘብ
Because of his present pecuniary difficulties, he cannot afford to buy the house. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ስላለበት ፡ የገንዘብ ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ ቤቱን ፡ ሊገዛ ፡ አይችልም

**pedal** (v.), ~ **a bike** ቢስኪሌት ፡ ነድቶ ፡ ወጣ
It is hard to pedal a bike uphill. ቢስኪሌት ፡ ዳገት ፡ ነድቶ ፡ መውጣት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**pedal** (n.) መርገጫ
The pedal came off my bicycle. የቢስኪሌቱ ፡ መርገጫ ፡ ወለቀ

**step on the pedal** ቤንዚን ፡ መስጫውን ፡ ረገጠ
The driver accelerated the motor by stepping on the pedal. ነጂው ፡ ቤንዚን ፡ መስጫውን ፡ በመርገጥ ፡ የሞተሩን ፡ ፍጥነት ፡ ጨመረ

**pedantic** ጥራዝ ፡ ነጠቅ
He is a pedantic scholar. እሱ ፡ ጥራዝ ፡ ነጠቅ ፡ ምሁር ፡ ነው

**peddle** እየዞረ ፡ ሸጠ
He peddles small items like pins. እንደ ፡ ወረቀት ፡ መርፌ ፡ ያሉ ፡ ትናንሽ ፡ ነገሮች ፡ እየዞረ ፡ ይሸጣል

**peddler** ሱቅ ፡ በደረቴ ፤ አዟሪ
A peddler is hawking his wares outside. እውጭ ፡ አንድ ፡ ሱቅ ፡ በደረቴ ፡ ይሁን ፡ ፈላጊ ! እያለ ፡ ይጮኻል
The dishonest peddler duped his customers. አታላዩ ፡ አዟሪ ፡ ደንበኞቹን ፡ አጭበረበረ

**pedestal** መቆሚያ
Only the pedestal of the statue remains. የቀረው ፡ የሐውልቱ ፡ መቆሚያ ፡ ብቻ ፡ ነው

**pedestrian** እግረኛ
For pedestrians only! ለእግረኞች ፡ ብቻ

**pedestrian** (adj.)
1. የእግረኞች. A pedestrian bridge crosses the highway. የእግረኞች ፡ ድልድይ ፡ አውራ ፡ ጎዳናውን ፡ ያቋርጣል
2. የማይማርክ. He gave a pedestrian lecture suitable for a general audience. ለማንም ፡ አዳማጭ ፡ የሚስማማ ፡ የማይማርክ ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**pedigree** የዘር ፡ ግንድ
The Emperor's pedigree appears in several books. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የዘር ፡ ግንድ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል

**have a pedigree**
Does this dog have a pedigree? ይህ ፡ ውሻ ፡ ዘሩ ፡ ጥሩ ፡ ነው ?

**peek**
1. አሾልቆ ፡ አየ. A child peeked through the door. ሕፃን ፡ በበሩ ፡ አሾልቆ ፡ አየ
2. ተመለከተ. We crept up and peeked over the wall. ቀስ ፡ ብለን ፡ ባጥሩ ፡ ላይ ፡ አጮልቀን ፡ ተመለከትን

**peel** (vt.) ላጠ
I have to peel the potatoes. ድንቹን ፡ መላጥ ፡ አለብኝ

**peel** (vi.)
1. ተቀረፈ. The paint is beginning to peel. ቀለሙ ፡ መቀረፍ ፡ ጀምሯል
2. እየተቀረፈ ፡ ወደቀ. My skin is peeling. ቆዳዬ ፡ እየተቀረፈ ፡ ይወድቃል
3. ተላጠ. My back is peeling from my sunburn. ከፀሐይ ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ጀርባዬ ፡ ሊላጥ ፡ ነው

**peel** (n.) ቆዳ ፤ ልጣጭ
These oranges have a thick peel. እነዚህ ፡ ብርቱካኖች ፡ ወፍራም ፡ ቆዳ ፡ አላቸው
Throw away the orange peel! የብርቱካኑን ፡ ልጣጭ ፡ ጣል

**peep** (v.)
1. አሾልቆ ፡ አየ. I peeped through the window to see what she was doing. ምን ፡ ታደርግ ፡ እንደ ነበረ ፡ ለማየት ፡ በመስኮቱ ፡ አሾልቄ ፡ አየሁ
2. ብቅ ፡ ብቅ ፡ አለ. Stars peeped through the clouds. ከከቦች ፡ በደመናው ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ አሉ
3. ጮኸ. The little bird peeped in its nest. ትንሺ ፡ ወፍ ፡ ጎጆዋ ፡ ውስጥ ፡ ሆና ፡ ጮኸች

**peep** (n.), **let out a** ~ ትንፍሽ ፡ አለ
Quiet! Don't let out a peep! ጭጭ ፡ በል ፤ ትንፍሽ ፡ እንዳትል

**take a peep** ሰርቆ ፡ አየ
He took a peep into the room. ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ሰርቆ ፡ አየ

**peer** (v.)
1. አትኩሮ ፡ ተመለከተ. He peered into the darkness, but could see nothing. በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ አትኩሮ ፡ ተመለከተ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ሊያይ ፡ አልቻለም
2. ብቅ ፡ አለ. The sun was peering from behind a cloud. ፀሐይዋ ፡ በደመና ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ ብላ ፡ ነበር

**peer** (n.)
1. የሚስተካከል. It will not be easy to find his

peer. እሱን ፡ የሚስተካከል ፡ ለማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. እኩያ. His work can only be judged by his peers. ሥራው ፡ ሊገመት ፡ የሚችለው ፡ በእኩዮቹ ፡ ብቻ ፡ ነው

**peerless** ተወዳዳሪ ፡ የሌለው
The peerless beauty of the girl was admired by all. ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ ቁንጅናዋ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ተደነቀ

**(be) peeved** ተበሳጨ
Mother will be peeved if we are late. የዘገየን ፡ እንደሆነ ፡ እናታችን ፡ ትበሳጫለች

**peevish** ብስጩ
Illness made her peevish. ሕመሙ ፡ ብስጩ ፡ አደረጋት

**peg** (v.), ~ **down** ቸከለ
We must peg down our tent. ድንኳናችንን ፡ መቸከል ፡ አለብን

**be pegged to** ከ - - - ጋር ፡ ተለዋወጠ
Our wages are pegged to living costs. ደሞዛችን ፡ ከኑሮው ፡ ውድነት ፡ ጋር ፡ ይለዋወጣል

**peg** (n.) ዕንጨት ፤ ችካል
The boards are joined by pegs. ሳንቃዎቹ ፡ የተጋጠሙት ፡ በዕንጨት ፡ ነው
This tent requires ten pegs. ይህ ፡ ድንኳን ፡ ዐሥር ፡ ችካሎች ፡ ያስፈልጉታል

**pellet** ጥይት
The pellets of a shotgun are made of lead. የረሽ ፡ ጠመንጃ ፡ ጥይቶች ፡ ከእርሳስ ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው

**pell-mell**
1. ሳያጣጥፍ. He tossed his clothes pell-mell into the suitcase. ልብሱን ፡ ሳያጣጥፍ ፡ ሻንጣው ፡ ውስጥ ፡ ወረወረው
2. ተንጋግተው. The children rushed out onto the playground pell-mell. ልጆቹ ፡ ተንጋግተው ፡ ወደ ፡ መጫወቻ ፡ ሜዳው ፡ ሮጡ

**pelt** (v.)
1. ደበደበ. Rain pelted the roof. ዝናብ ፡ ጣሪያውን ፡ ደበደበ
2. ወረወረ. The boys pelted the windows with pebbles. ልጆቹ ፡ መስኮቶቹ ፡ ላይ ፡ ጠጠር ፡ ወረወሩ

**pelt** (n.) ቆዳ
I bought a tiger's pelt at the market. ከገበያ ፡ የነብር ፡ ቆዳ ፡ ገዛሁ

**pelvis** የወገብ ፡ አጥንት
The doctor examined the man's pelvis with an X ray. ሐኪሙ ፡ የሰውዬውን ፡ የወገብ ፡ አጥንት ፡ በራጂ ፡ መረመረ

**pen** (penned), v. አጐረ
He penned the sheep in a small enclosure. በጎቹን ፡ በትንሽ ፡ አጥር ፡ ውስጥ ፡ አጐራቸው

**pen in a corner** ወስዶ ፡ ዘጋ(በት)
He had me penned in a corner where I could not escape. ማምለጥ ፡ ከማልችልበት ፡ ወስዶ ፡ ዘጋብኝ

**be penned up** ታሰረ
His wife complained that she is penned up in the house all day. ሚስቱ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ታሰርኩ ፡ ብላ ፡ ተነጫነጨች

**pen** (n.)
1. ብዕር. This pen scratches. ይህ ፡ ብዕር ፡ ይጭራል
2. በረት ፤ ጋጣ. The cattle got out of the pen somehow. ከብቶቹ ፡ ከበረታቸው ፡ (ከጋጣቸው) ፡ እንደምንም ፡ ወጡ

**penal** የወንጀለኞች
The only settlement in the wilderness was a penal colony. በበረሃው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ መኖሪያ ፡ የወንጀለኞች ፡ ብቻ ፡ ነበር
Penal labor is used in constructing some highways. አንዳንድ ፡ አውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ በወንጀለኞች ፡ ጉልበት ፡ ይሠራሉ
[See also 'offense']

**penal code** የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ
The new penal code is harsh. አዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጥብቅ ፡ ነው

**penalize** ቀጣ
The judge penalized him for speeding. ከፍጥነት ፡ በላይ ፡ በመንዳቱ ፡ ዳኛው ፡ ቀጣው

**penalty** (penalties)
1. ቅጣት. The penalty is ten years' imprisonment. ቅጣቱ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ነው
2. መቀጮ. If you do wrong, you have to pay the penalty. ካጠፋህ ፡ መቀጮ ፡ መክፈል ፡ አለብህ
3. ሥቃይ. Indigestion is often the penalty for eating fast. የሆድ ፡ ቁርጠት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በችኰላ ፡ ከመብላት ፡ የሚመጣ ፡ ሥቃይ ፡ ነው
[See also 'death, inflict']

**penance** ንስሐ
He tried to expiate his sin through penance. ኀጢአቱን ፡ በንስሐ ፡ ሊያስወርድ ፡ ሞከረ

**do penance** ንስሐ ፡ ገባ
He must do penance for his sins. ስለሥራው ፡ ኀጢአት ፡ ንስሐ ፡ መግባት ፡ አለበት

**pencil** እርሳስ
The point of my pencil is broken. የእርሳሴ ፡ ጫፍ ፡ ተሰብሯል

**pendant, a diamond ~** የተንጠለጠለ ፡ አልማዝ
She wore a diamond pendant as her necklace. የተንጠለጠለ ፡ አልማዝ ፡ እንደ ፡ ሐብል ፡ አድርጋ ፡ አጥልቃለች

**pending** (adj.)
1. በይደር ፡ ላይ ፡ ያለ. Tax reform is the pending business of parliament. የግብር ፡ መሻሻል ፡ በይደር ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ የፓርላማ ፡ ተግባር ፡ ነው
2. (= adv.) በቀጠሮ. The matter is still pending. ነገሩ ፡ ገና ፡ በቀጠሮ ፡ ነው

**pending**, prep. (= adv.) እስከሚደረግ ፡ ድረስ
The police sealed all the drawers of the desk pending an investigation. ፖሊሱ ፡ ምርመራ ፡ እስከሚደረግ ፡ ድረስ ፡ የጠረጴዛውን ፡ መሳቢያዎች ፡ ሁሉ ፡ አሸጋቸው
*We sat in the garden pending father's return. አባባን ፡ አትክልት ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠን ፡ ጠበቅነው
*The equipment is kept in a storehouse pending future use. ለወደፊት ፡ አገልግሎት ፡ እንዲውል ፡ መሣሪያው ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጧል

**pendulum** የግድግዳ ፡ ሰዓት ፡ ዘንግ
The pendulum swings back and forth. የግድግዳው ፡ ሰዓት ፡ ዘንግ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይወዛወዛል

**pendulum clock** የግድግዳ ፡ ሰዓት
The pendulum clock strikes every hour. የግድግዳው ፡ ሰዓት ፡ በየሰዓቱ ፡ ይደውላል

**penetrate** (vt.)
1. ገባ. New ideas have penetrated the countries of Asia. አዳዲስ ፡ ሐሳቦች ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ አገሮች ፡ ገብተዋል
Smoke penetrated the living room. ጭስ ፡ ሳሎኑ ፡ ውስጥ ፡ ገብቷል
2. ደረሰ(በት). I could not penetrate the mystery. ምስጢሩን ፡ ልደርስበት ፡ አልቻልኩም
3. ሰብሮ ፡ ገባ. The bullet penetrated his skull. ጥይቱ ፡ ራስ ፡ ቅሉን ፡ ሰብሮ ፡ ገባ
4. ዘለቀ. Gradually, the sound of the bell penetrated the sleeping man's consciousness. የደወሉ ፡ ድምፅ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ የተኛውን ፡ ሰው ፡ አንጐል ፡ ዘለቀው
5. ጣሰ. The troops penetrated the enemy lines. ወታደሮቹ ፡ የጠላትን ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ጣሱት
6. ሊያይ ፡ ቻለ. Our eyes couldn't penetrate the darkness. ዓይኖቻችን ፡ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ሊያዩ ፡ አልቻሉም

**penetrate** (vi.) ገባ
The water penetrates slowly into the ground. ውኃው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ ይገባል

**penetrating** ጥልቅ
He made a penetrating remark. ጥልቅ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠ

**peninsula** ባሕረ ፡ ገብ ፡ መሬት
The peninsula of Italy was reunited in 1871. የኢጣልያን ፡ ባሕረ ፡ ገብ ፡ መሬት ፡ እንደገና ፡ አንድ ፡ የሆነው ፡ በ፲፰፻፸፩ ዓ. ም. ነው

**penitence** ንስሐ
He was given three Hail Marys as penitence. ለንስሐው ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በሰላመ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ መልአክን ፡ እንዲደግም ፡ ታዘዘ

**penitent** የጸጸት
He had a penitent expression on his face. በፊቱ ፡ ላይ ፡ የጸጸት ፡ መልክ ፡ ይታይበት ፡ ነበር

**penitential** የንስሐ
Lent is a penitential season. ሁዳዴ ፡ የንስሐ ፡ ጊዜ ፡ ነው

**penitentiary** (penitentiaries) ወህኒ ፡ ቤት
Two prisoners have escaped from the penitentiary. ሁለት ፡ እስረኞች ፡ ከወህኒ ፡ ቤት ፡ አምልጠዋል

**penknife** ሰንጢ
He cut the meat with a penknife. ሥጋውን ፡ በሰንጢ ፡ ቈረጠ

**penmanship** የእጅ ፡ ጽሕፈት
His penmanship is bad. የእጅ ፡ ጽሕፈቱ ፡ መጥፎ ፡ ነው

**penniless** ባዶ ፡ እጁን
The thief snatched my purse and left me penniless. ሌባው ፡ በርሳዬን ፡ ነጥቆ ፡ ባዶ ፡ እጄን ፡ አስቀረኝ

**be penniless**
She is literally penniless. ቀዳዳ ፡ ፍራንክ ፡ የላትም

**penny** (pennies) ቤሳ
Let alone a dollar, I will not give you even a penny. እንኳን ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ቤሳ ፡ አልሰጥህም
[See also 'pinch']

**penny-pinching, by ~** እየሠሠተ
He saves money by penny-pinching. እየሠሠተ ፡ ገንዘብ ፡ ያጠራቅማል

**(be) penny-wise** ገንዘብ ፡ በጣም ፡ ቈጠበ
He is penny-wise and never pays the regular price. ገንዘብ ፡ በጣም ፡ ስለሚቈጥብ ፡ የተወሰነውን ፡ ዋጋ ፡ አይከፍልም

**pension off** ጡረታ ፡ አስገባ ፤ ጡረታ ፡ መደበ
The government pensioned off the overage officers. በዕድሜ ፡ የገፉትን ፡ መኰንኖች ፡ መንግሥት ፡ ጡረታ ፡ አስገባቸው ፡ (መደባቸው)
**be pensioned** ጡረታ ፡ ገባ
He was pensioned at sixty-five. በስልሳ ፡ አምስት ፡ ዓመቱ ፡ ጡረታ ፡ ገባ

**pension** (n.) የጡረታ ፡ አበል
He received a small pension from the government. ከመንግሥት ፡ ጥቂት ፡ የጡረታ ፡ አበል ፡ አገኘ

**pensive, ~ mood** መተከዝ
His pensive mood was noticed by everyone. መተከዙን ፡ ሁሉም ፡ ዐውቆ ፡ ነበር
**be pensive** ተከዘ
Why are you so pensive today? ዛሬ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ተክዘሃል ?
**look pensive** ተከዘ
He looks pensive today. ዛሬ ፡ ተክዟል

**pensively**
*She was pensively tapping the ground with her foot. በትካዜ ፡ መሬቱን ፡ በእግሯ ፡ ትቆረቆር ፡ ነበር

**Pentecost** የቆንጠጰስጤ ፡ በዓል
Pentecost is celebrated in our country. የቆንጠጰስጤ ፡ በዓል ፡ ባገራችን ፡ ይከበራል

**pent-up** ታፍኖ ፡ የነበረ
With the latest insult, his pent-up rage burst forth. በቅርቡ ፡ በደረሰበት ፡ ስድብ ፡ ታፍኖ ፡ የነበረ ፡ ቁጣው ፡ ገነፈለ
**be pent up** ተጨበጠ
Children love the spring after being pent up all winter. ክረምቱን ፡ ሙሉ ፡ ከተጨበጡ ፡ በኋላ ፡ ሕፃናት ፡ በልግን ፡ ይወዳሉ

**penultimate** ከመጨረሻው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለ
The penultimate consonant in this verb is geminated. የዚህ ፡ ግስ ፡ ከመጨረሻው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተናባቢ ፡ ይጠብቃል

**penury** ድኽነት
His penury is due to the fact that he is ill and unable to work. ድኽነቱ ፡ በመታመሙ ፡ ምክንያት ፡ ለመሥራት ፡ ካለመቻሉ ፡ የተነሣ ፡ ነው
**of penury** (= adv.) ተቈራምዶ
He hopes to save a lot of money by living a life of penury. ተቈራምዶ ፡ ኖሮ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ለማስቀመጥ ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋል

**people** (v.) ሰፈረ
The pioneers peopled the West. የቀድሞ ፡ ሰፋሪዎች ፡ በምዕራብ ፡ ሰፈሩ

**people** (n.)
1. ሰው. Were there many people at the meeting? ስብሰባው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ነበር ?
2. ሰዎች. Can you name the most important people of Asia? የእስያን ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ልትጠቅስ ፡ ትችላለህ ?
3. ቤቶች. You must come home with me and meet my people. እቤቴ ፡ መጥተህ ፡ ከቤቶቼ ፡ መተዋወቅ ፡ አለብህ
4. ዘሮች. My people came to America from Italy. ዘሮቼ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ የመጡት ፡ ከኢጣሊያ ፡ ነው
5. ሕዝብ. The French nobles oppressed the people. የፈረንሳይ ፡ መኳንንት ፡ ሕዝቡን ፡ ጨቈኑት
The people of Ethiopia follow ancient traditions. የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የጥንት ፡ ባህል ፡ አክባሪ ፡ ነው
Many peoples of Africa have only recently obtained their independence. ብዙ ፡ የአፍሪካ ፡ ሕዝቦች ፡ ነጻነታቸውን ፡ የተቀዳጁት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ነው
*He does not fear what people will say. ይሉኝታ ፡ አይፈራም
**people of the village** መንደርተኞች
The people of the village like the new doctor. መንደርተኞቹ ፡ አዲሱን ፡ ሐኪም ፡ ይወዱታል
[See also 'colored, old, simple, young']

**(be) peopled** (= act.) ሰፈረ
+The area is thickly peopled by various small tribes. በቀበሌው ፡ ብዙ ፡ ትናንሽ ፡ ጐሳዎች ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብለው ፡ ሰፍረውበታል

**pep** (v.), **~ up** አነቃቃ
A brisk walk after dinner will pep you up.

ከእራት ፡ በኋላ ፡ ፈጠን ፡ ባለ ፡ እርምጃ ፡ ብትንሸራሸር ፡ ያነቃቃሃል

**pep** (n.) ንቃት
He is full of pep. ንቃት ፡ አለው

**pepper** በርበሬ
Pepper is hot. በርበሬ ፡ ያቃጥላል

**peppery** በርበሬ ፡ የበዛበት
A peppery meal makes me thirsty. በርበሬ ፡ የበዛበት ፡ ምግብ ፡ ውኃ ፡ ያስጠማኛል

**per**
1. በ -- እጅ. I sent the letter per my son. ደብዳቤውን ፡ በልጄ ፡ እጅ ፡ ላክሁት
2. በ. How much do you earn per day? በቀን ፡ ስንት ፡ ታገኛለህ ?
3. ለ. Two cars per family is the norm in many American cities. በብዙ ፡ የአሜሪካን ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ መኪና ፡ ላንድ ፡ ቤተሰብ ፡ የተለመደ ፡ ነው
*How much is this sugar per kilo? ይህ ፡ ስኳር ፡ ኪሎው ፡ ስንት ፡ ነው ?

**perambulate** ተንሸራሸረ
The lovers perambulate through the park. ፍቅረኞቹ ፡ መናፈሻው ፡ ውስጥ ፡ ይንሸራሸራሉ

**per capita** የነፍስ ፡ ወከፍ
The per capita income in this country is $150. የዚህ ፡ አገር ፡ የነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ገቢ ፡ በዓመት ፡ መቶ ፡ ኀምሳ ፡ ብር ፡ ነው

**perceive**
1. ታየ(ው). +I perceived an object looming through the mist. በጭጋጉ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ታየኝ
2. ገባ(ው). +On entering his house, he at once perceived that something was amiss. ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ሲገባ ፡ አንድ ፡ ያልሆነ ፡ ነገር ፡ መኖሩ ፡ ወዲያውኑ ፡ ገባው
I perceive that you are unwilling to do it. ልትሠራው ፡ ፈቃደኛ ፡ እንዳልሆንክ ፡ ይገባኛል
3. መሰለ(ው). +This is a nice idea, but I perceive difficulties in putting it into practice. ይህ ፡ ጥሩ ፡ ሐሳብ ፡ ነው ፤ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ግን ፡ ችግር ፡ የሚያመጣ ፡ ይመስለኛል
4. ተገነዘበ. I soon perceived that the air was cold. አየሩ ፡ ቀዝቃዛ ፡ መሆኑን ፡ ወዲያውኑ ፡ ተገነዘብኩ

**percent** በመቶ
The cost of living has risen ten percent. የኑሮ ፡ ዋጋ ፡ በመቶ ፡ ዐሥር ፡ ከፍ ፡ ብሏል

**percentage**
1. ከመቶ. What percentage of Ethiopians live in towns? ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከመቶው ፡ ስንቱ ፡ ነው ፡ ከተማ ፡ የሚኖረው ?
2. ከመቶ ፡ እጅ. The tenant farmers get a fixed percentage of the crop. ጭሰኞቹ ፡ ከምርቱ ፡ ከመቶ ፡ የተወሰነ ፡ እጅ ፡ ይደርሳቸዋል
3. ድርሻ. The agent receives a large percentage of the painter's income. ወኪሉ ፡ ከሠዓሊው ፡ ገቢ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድርሻ ፡ ያገኛል
*A large percentage of these books deal with Ethiopia. ከነዚህ ፡ መጽሐፎች ፡ በርከት ፡ ያሉት ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይናገራሉ

**perceptible** ጉልህ
There is a perceptible difference between these two brothers. በነዚህ ፡ ሁለት ፡ ወንድማማቾች ፡ መካከል ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ልዩነት ፡ አለ

**be perceptible**
1. ታየ. The ship was barely perceptible in the fog. በጭጋጉ ፡ ውስጥ ፡ መርከቡ ፡ እምብዛም ፡ አይታይም ፡ ነበር
2. ተሰማ. The sound was very perceptible. ድምፁ ፡ በጣም ፡ ይሰማ ፡ ነበር

**perception**
1. የጠለቀ ፡ አስተሳሰብ. He lacks perception into foreign affairs. ስለ ፡ ውጭ ፡ አገሮች ፡ ጉዳይ ፡ የጠለቀ ፡ አስተሳሰብ ፡ የለውም
2. የመለየት ፡ ችሎታ. His perception of color is poor. ቀለም ፡ የመለየት ፡ ችሎታው ፡ አነስተኛ ፡ ነው

**have a clear perception** በግልጽ ፡ ተረዳ
He had a clear perception of what was wrong and soon fixed it. ስሕተቱን ፡ በግልጽ ፡ ተረድቶ ፡ ስለነበር ፡ ወዲያውኑ ፡ አስተካከለው

**perceptive**
1. የተጣራ. He gave a perceptive analysis of the political situation. ስለ ፡ ፖለቲካው ፡ ሁኔታ ፡ የተጣራ ፡ ሐተታ ፡ ሰጠ
2. አስተዋይ. A perceptive writer can express the spirit of the time. አስተዋይ ፡ ደራሲ ፡ የጊዜውን ፡ መንፈስ ፡ ሊገልጽ ፡ ይችላል

**perch** (v.) አረፈ
The bird perched on a branch of the tree. ወፏ ፡ በዛፉ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ላይ ፡ አረፈች

**be perched** ጉብ ፡ ብሎ ፡ ታየ
The fort is perched on a high hill. ምሽጉ ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ጋራ ፡ ላይ ፡ ጉብ ፡ ብሎ ፡ ይታያል

**perch** (n.)
1. ቆጥ. The parrot fell off his perch and

squawked. በቀቀኑ ፡ ከቆጡ ፡ ላይ ፡ በመውደቁ ፡ ጮኸ
2. ማረፊያ. The bird sat on a perch. ወፏ ፡ ማረፊያው ፡ ላይ ፡ ተቀምጣለች

**perchance** ምናልባት + imperfect + ይሆናል
Perchance, I shall return to Ethiopia some day. ምናልባት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ኢትዮጵያ ፡ እመለስ ፡ ይሆናል

**percolate** ዘለቀ
Water percolates through sand. ውኃው ፡ አሸዋውን ፡ ይዘልቃል

**percussion** ድምፅ
The loud percussion of a drum was heard. ኀይለኛ ፡ የከበሮ ፡ ድምፅ ፡ ይሰማ ፡ ነበር

**percussion instrument** [በዕንጨት ፤ በእጅና ፡ በመሳሰሉት ፡ ነገር ፡ የሚመታ ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ]

**per diem** የቀን ፡ አበል
He gets ten dollars per diem. ዐሥር ፡ ብር ፡ የቀን ፡ አበል ፡ ያገኛል

**perdition** ሲኦል
The angry priest told him to go to perdition. የተናደደው ፡ ቄስ ፡ ሲኦል ፡ እንዲገባ ፡ ረገመው

**peregrination** ጉዞ
His peregrination made him an authority on several countries. ጉዞው ፡ ስለ ፡ ብዙ ፡ አገሮች ፡ ዐዋቂ ፡ አደረገው

**peremptory** ድርቅ ፡ ያለ
The officer's peremptory commands were uttered in a loud voice. መኰንኑ ፡ ድርቅ ፡ ያለ ፡ ትእዛዙን ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ተናገረ

**perennial**
1. ዘላቂነት ፡ ያለው. The perennial beauty of the lakes attracts many visitors. ዘላቂነት ፡ ያለው ፡ የሐይቆች ፡ ውበት ፡ ብዙ ፡ ጐብኚዎችን ፡ ይማርካል
2. ከዓመት ፡ እስከ ፡ ዓመት ፡ የማይደርቅ. The perennial stream never freezes. ከዓመት ፡ እስከ ፡ ዓመት ፡ የማይደርቀው ፡ ወንዝ ፡ ፈጽሞ ፡ አይረጋም
3. ከዓመት ፡ ዓመት ፡ የሚያብብ. My garden has perennial flowers. ያትክልት ፡ ቦታዬ ፡ ከዓመት ፡ ዓመት ፡ የሚያብቡ ፡ አበባዎች ፡ አሉት
*He is a perennial candidate for public office. ምርጫ ፡ በተደረገ ፡ ቁጥር ፡ ይወዳደራል

**perfect** (v.)
1. እንከን ፡ የሌለበት ፡ ሥራ. They have perfected a new engine. እንከን ፡ የሌለበት ፡ አዲስ ፡ ሞተር ፡ ሠርተዋል
2. ከፍጹምነት ፡ አደረሰ. It took five years of patient labor to perfect his invention. ፍልሰፋውን ፡ ከፍጹምነት ፡ ለማድረስ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በትዕግሥት ፡ ሠራ

**perfect** (adj.)
1. ፍጹም. The method is not yet perfect. ዘዴው ፡ ገና ፡ ፍጹም ፡ አልሆነም
They have perfect control over the territory. ግዛቱ ፡ በነሱ ፡ ፍጹም ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው
2. ትክክል. He drew a perfect circle with a compass. በኮምፓስ ፡ ትክክል ፡ የሆነ ፡ ክብ ፡ ሠራ
3. ጥሩ. The car is in perfect condition. መኪናው ፡ በጥሩ ፡ አኳኋን ፡ ይገኛል
4. ሙሉ. He is in perfect health. ሙሉ ፡ ጤንነት ፡ አለው
5. እንከን ፡ የማይወጣለት. He speaks perfect French. እንከን ፡ የማይወጣለት ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ይናገራል
6. (= adv.) ጨርሶ. He is a perfect stranger to me. እሱ ፡ ለኔ ፡ ጨርሶ ፡ እንግዳ ፡ ነው
**be perfect** እንከን ፡ የለውም
Her beauty is perfect. ቁንጅናዋ ፡ እንከን ፡ የለውም

**perfection**
1. እንከን ፡ የማይወጣለት ፡ መሆን. His perfection made everyone jealous. እሱ ፡ እንከን ፡ የማይወጣለት ፡ መሆኑ ፡ ሁሉን ፡ ሰው ፡ አስቀና
2. (= verbal noun) የተሟላ ፡ ማድረግ. Perfection of our plans will take another week. ሥራችንን ፡[የተሟላ]፡ ለማድረግ ፡ በተጨማሪ ፡ ሳምንት ፡ ይወስድብናል
**bring to perfection** ከፍጹምነት ፡ አደረሰ
He brought the method of painting to perfection. የሥዕል ፡ አቀባብን ፡ ዘዴ ፡ ከፍጹምነት ፡ አደረሰው
**to perfection** ፍጹም ፡ አድርጎ
He did his job to perfection. ሥራውን ፡ ፍጹም ፡ አድርጎ ፡ ሠራው

**perfectly**
1. በደንብ. He was perfectly satisfied. በደንብ ፡ ተደስቶ ፡ ነበር
2. በትክክል. He did it perfectly the first time. በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በትክክል ፡ ሠራው
3. በሚገባ. The music and the action synchronized perfectly. ሙዚቃውና ፡ ድርጊቱ ፡ በሚገባ ፡ ተስማሙ
**perfectly well** በደንብ ፡ አድርጎ
I know him perfectly well. በደንብ ፡ አድርጌ ፡ አውቀዋለሁ

**be perfectly willing** ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ፈቃደኛ ፡ ነው
He is perfectly willing to work in the evening. ማታ ፡ ማታ ፡ ለመሥራት ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ፈቃደኛ ፡ ነው

**perfidious** ሸፍጠኛ
His perfidious behavior earned him the contempt of all. ሸፍጠኛ ፡ መሆኑ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ አስጠላው

**perfidy** ሸፍጥ
Laval's perfidy made him notorious. የላቫል ፡ ሸፍጥ ፡ ክፉ ፡ ስም ፡ አተረፈለት

**perforate** በሳ
A nail perforated the tire. ጎማውን ፡ ምስማር ፡ በሳው
The ticket seller perforates each ticket sold. ቲኬት ፡ ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ ቲኬት ፡ ሁሉ ፡ ይበሳል

**perforation** ቀዳዳ
He covered the perforation with a patch. ቀዳዳውን ፡ በጨርቅ ፡ ለጠፈ

**perforce** የግድ
I must perforce consult with my lawyer in this matter. ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ከጠበቃዬ ፡ ጋር ፡ የግድ ፡ መነጋገር ፡ አለብኝ

**perform** (vt.)
1. ፈጸመ ፤ አከናወነ. He performed the task assigned him with diligence. የተሰጠውን ፡ ሥራ ፡ በትጋት ፡ ፈጸመ ፡ (አከናወነ)
2. አደረገ. Who performed the operation? ቀዶ ፡ ጥገናውን ፡ ያደረገ ፡ ማነው ?

**perform** (vi.)
1. ተጫወተ. He is performing as Hamlet tonight. ዛሬ ፡ ማታ ፡ ሃምሌትን ፡ ሆኖ ፡ ይጫወታል
2. ተግባሩን ፡ አከናወነ. He performs well on that committee. በዚያ ፡ ደርግ ፡ ውስጥ ፡ ተግባሩን ፡ ደኅና ፡ ያከናውናል

**performance**
1. አፈጻጸም. His performance of his duties leaves much to be desired. የሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ብዙ ፡ እንከን ፡ አለበት
2. ቅልጥፍና. The performance of his work is outstanding. የሥራው ፡ ቅልጥፍና ፡ ተወዳዳሪ ፡ የለውም
3. ትርኢይት. Our interest lagged toward the end of the performance. ወደ ፡ ትርኢይቱ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ያለን ፡ ስሜታችን ፡ ቀዘቀዘ
4. ጨዋታ. The actor's performance was brilliant. ተዋናዩ ፡ ያሳየው ፡ ጨዋታ ፡ ድንቅ ፡ ነበር
5. ጨዋታ ፡ ማሳየት. The young actor was tremulous before the performance. ወጣቱ ፡ ተዋናይ ፡ ጨዋታውን ፡ ከማሳየቱ ፡ በፊት ፡ ተርበደበደ
6. ዘፈን. The singer's performance was brilliant. ዘማሪው ፡ ያሰማው ፡ ዘፈን ፡ ድንቅ ፡ ነበር
*There are two performances of the play on Saturday. ቅዳሜ ፡ ቲያትሩ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ይታያል
[See also 'skillful']

**performer** ተጫዋች ፤ ተዋናይ
They gave the performer a big hand. ለተጫዋቹ ፡ (ለተዋናዩ) ፡ የጋለ ፡ ጭብጨባ ፡ አደረጉለት

**perfume** (v.)
1. አወደ. Roses perfumed the air. የጽጌ ፡ ረዳ ፡ መዐዛ ፡ አየሩን ፡ አወደው
2. ሽቶ ፡ ረጨ. He perfumed the air to hide the smell of roasted meat. የተጠበሰውን ፡ ሥጋ ፡ ሽታ ፡ ለማጥፋት ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ሽቶ ፡ ረጨ

**perfume** (n.) ሽቶ
I smell perfume in the air. ሽቶ ፡ ይሸተኛል
She bought the perfume in Paris. ሽቶውን ፡ ከፓሪስ ፡ ገዛች

**perfunctory**
1. ግዴለሽ. Her perfunctory performance caused her boss to fire her. ግዴለሽ ፡ አሠራሯ ፡ አለቃዋ ፡ እንዲያባርራት ፡ ምክንያት ፡ ሆነ
2. ከንገት ፡ በላይ ፡ የሆነ. His perfunctory cordiality didn't impress me. ካንገት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ትሕትናው ፡ ስሜት ፡ አልሰጠኝም

**perhaps** ምናልባት
Perhaps I'll come along with you. ምናልባት ፡ አብሬህ ፡ እመጣለሁ

**peril** አደጋ
Travelers in the desert are in peril if they cannot find water. የምድረ ፡ በዳ ፡ መንገደኞች ፡ ውኃ ፡ ካላገኙ ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ

**perilous** አደገኛ
They went on a perilous journey. አደገኛ ፡ ጉዞ ፡ አደረጉ

**period**
1. ዘመን. The last century was an interesting period in American history. ያለፈው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በአሜሪካ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ዘመን ፡ ነበረ

2. ጊዜ. He worked here for a short period.
ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እዚህ ፡ ይሠራ ፡ ነበር
3. ክፍለ ፡ ጊዜ. I have a third period free.
በሦስተኛው ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፡ ነጻ ፡ ነኝ
4. አራት ፡ ነጥብ. You forgot to put a period here.
እዚህ ፡ አራት ፡ ነጥብ ፡ ማድረግ ፡ ረሳህ

**periodic** (= periodically) አልፎ ፡ አልፎ
He has periodic attacks of malaria. አልፎ ፡ አ
ልፎ ፡ ወባ ፡ ትነሣባታለች
His periodic visits cheered up the ill. አልፎ ፡
አልፎ ፡ ሊጠይቃቸው ፡ መሄዱ ፡ ሕመምተኞቹን ፡
አበረታታ

**periodical** (n.) መጽሔት
I subscribe to several periodicals. በርከት ፡ ያ
ሉ ፡ መጽሔቶች ፡ በደንበኝነት ፡ እገዛለሁ

**periodically** በየወቅቱ
Eclipses occur periodically. የፀሐይ ፡ ግርዶሽ ፡ በየ
ወቅቱ ፡ ይደርሳል
*This stream flows periodically in the rainy
season. ይህ ፡ ወንዝ ፡ ክረምት ፡ ክረምት ፡ ይሞላል

**periphery**
1. ጠረፎች. The periphery of Ethiopia is settled
largely by nomads. በኢትዮጵያ ፡ ጠረፎች ፡ የሚ
ኖሩት ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ዘላኖች ፡ ናቸው
2. ዳር. The airport is located at the periphery
of the city. አውሮፕላን ፡ ማረፊያው ፡ የሚገኘው ፡
ከተማው ፡ ዳር ፡ ነው

**perish**
1. አለቀ. Hundreds of people perished in the
earthquake. በመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ በብዙ ፡ መ
ቶ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ አለቁ
2. ሞተ. In the fury of the battle, many
soldiers perished. በተፋፋመው ፡ ጦርነት ፡ ውስ
ጥ ፡ ብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ሞቱ
3. ተበላሸ. Some fruits perish quickly if not
properly packed. አንዳንድ ፡ ፍራፍሬዎች ፡ በ
ደንብ ፡ ካልታሸጉ ፡ ቶሎ ፡ ይበላሻሉ

**perishable** የሚበላሽ
These vegetables are perishable, so keep them
in the refrigerator. እነዚህ ፡ አትክልቶች ፡ የሚ
በላሹ ፡ ስለሆኑ ፡ በማቀዝቀዣው ፡ ውስጥ ፡ አ
ስቀምጧቸው

**perjure, ~ oneself** በሐሰት ፡ መሰከረ
He perjured himself at the trial. በሙግቱ ፡ ጊዜ ፡
በሐሰት ፡ መሰከረ

**perjuror** በሐሰት ፡ የመሰከረ
The perjuror was jailed by the judge. በሐሰት ፡
የመሰከረው ፡ በዳኛው ፡ ትእዛዝ ፡ ታሰረ

**perjury** በሐሰት ፡ መመስከር
Perjury is punishable by a fine or imprison-
ment. በሐሰት ፡ መመስከር ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ በ
እስራት ፡ ያስቀጣል

**perk** አቆመ
The dog perked his ears when he heard his
master's voice. ውሻው ፡ የጌታውን ፡ ድምፅ ፡ ሲ
ሰማ ፡ ጆሮውን ፡ አቆመ

**perk up** (vt.) አነቃቃ
His compliment perked her up. የሱ ፡ ምስጋና ፡
አነቃቃት

**perk up** (vi.) ነቃ ፡ ነቃ ፡ አለ
The sick girl perked up when she received the
flowers. የታመመችው ፡ ልጅ ፡ አበባውን ፡ ስታገ
ኝ ፡ ነቃ ፡ ነቃ ፡ አለች

**permanency** ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ መቆየት
The permanency of the financial crisis nearly
ruined the country. የገንዘብ ፡ ችግር ፡ ረዘም ፡ ላ
ለ ፡ ጊዜ ፡ መቆየቱ ፡ አገሪቱን ፡ ሊያጠፋት ፡ ምን
ም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር

**permanent** ቋሚ
At the moment, I have no permanent address.
ለጊዜው ፡ ቋሚ ፡ አድራሻ ፡ የለኝም

**permanently** ለሁል ፡ ጊዜ ፤ ለዘለቄታው
The road is closed temporarily, not permanent-
ly. መንገዱ ፡ የተዘጋው ፡ ለጊዜው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
ለሁል ፡ ጊዜ ፡ (ለዘለቄታው) ፡ አይደለም

**permeable** ውኃ ፡ የሚመጥ
This permeable soil is not fit for plowing.
ይህ ፡ ውኃ ፡ የሚመጥ ፡ መሬት ፡ ለእርሻ ፡ አይ
ሆንም

**be permeable** ፈሳሽ ፡ ነገርን ፡ መጠጠ
Blotting paper is a permeable material.
የማምጠጫ ፡ ወረቀት ፡ ፈሳሽ ፡ ነገርን ፡ ይመጣል

**permeate**
1. ዘለቀ ፤ በሙሉ ፡ ዘለቀ. The rain permeated
the roof. ዝናቡ ፡ ጣሪያውን ፡ ዘለቀ
The water has permeated the soil. ውኃው ፡ አፈ
ሩን ፡ በሙሉ ፡ ዘልቆታል
2. ዘለቀ ፤ ገባ. New ideas have permeated even
the uneducated class. አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ያልተማ
ረውን ፡ ሕዝብ ፡ እንኳን ፡ ዘልቆታል ፡ (ገብቶታል)
3. አወደ. The smells of cooking permeated
the house. የምግብ ፡ ሽታ ፡ ቤቱን ፡ አወደው

**(be) permissible** ተፈቀደ
Playing in the park is permissible only during
the daytime. መናፈሻው ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ መ
ጫወት ፡ የሚፈቀደው ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ነው

**permission** ፈቃድ ፤ ፍቃድ
He asked for permission to visit his parents. ወላጆቹን ፡ ለመጠየቅ ፡ ፈቃድ ፡ ጠየቀ

**grant permission** ፈቀደ(ለት)
He granted us permission to leave early. ቀደም ፡ ብለን ፡ እንድንሄድ ፡ ፈቀደለን

**permissive** ልል
She is very permissive, and so her children often do bad things. በጣም ፡ ልል ፡ ስለሆነች ፡ ልጆቿ ፡ በየጊዜው ፡ መጥፎ ፡ ነገሮች ፡ ያደርጋሉ

**permit** (permitted), vt. ፈቀደ
I can't permit smoking in my house. ቤቴ ፡ ውስጥ ፡ ሲጃራ ፡ እንዲጨስ ፡ አልፈቅድም
Permit me to explain my case! ጉዳዬን ፡ እንዳቀርብ ፡ ይፍቀዱልኝ

**permit** (vi.) አመቸ
We will fly if weather permits. ያየሩ ፡ ሁኔታ ፡ ካመቸ ፡ ባውሮፕላን ፡ እንሄዳለን
*Write when time permits. ሲመችህ ፡ ጻፍ

**be permitted** ተፈቀደ
No one is permitted to enter this building. እዚህ ፡ ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ ማንም ፡ እንዲገባ ፡ አይፈቀድለትም
Is smoking permitted? ሲጃራ ፡ ማጨስ ፡ ይፈቀዳል ?

**permit** (n.) የፈቃድ ፡ ወረቀት
Have you a permit to hunt on this land? እዚህ ፡ ቦታ ፡ እንድታድን ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀት ፡ አለህ ?

**permitting**
*Weather permitting, we sail on Monday. አየሩ ፡ ከተስማማን ፡ ሰኞ ፡ በመርከብ ፡ እንነሣለን

**permutation** እያለዋወጡ ፡ ማስቀመጥ
The permutation of numbers is an important part of math. ቁጥሮችን ፡ እያለዋወጡ ፡ ማስቀመጥ ፡ የሒሳብ ፡ ዋናው ፡ ክፍል ፡ ነው

**permute** ለወጠ
Time permutes all customs. ጊዜ ፡ ልማዶቹን ፡ ሁሉ ፡ ይለውጣል

**pernicious** ጠንቅ
This pollution of the air is pernicious to our health. ይህ ፡ ያየር ፡ መበላሸት ፡ ለጤናችን ፡ ጠንቅ ፡ ነው

**perpendicular**
1. ቀጥ ፡ ብሎ ፡ የሚወርድ. He drew a perpendicular line on the board. በሰሌዳው ፡ ላይ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ የሚወርድ ፡ መሥመር ፡ ሣለ
2. ቀጥ ፡ ያለ. The wall should be perpendicular to the floor. ግድግዳው ፡ ከወለሉ ፡ ጋር ፡ ሲተያይ ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ መሆን ፡ አለበት

**perpetrate** ፈጸመ
He perpetrated a crime on the ignorant farmer. በደንቆሮው ፡ ገበሬ ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ ፈጸመ
[See also 'fraud']

**perpetual**
1. የማያቋርጥ. She is tired of their perpetual chatter. የማያቋርጠው ፡ ወሬያቸው ፡ ሰልችቷታል
2. ዘላቂ. This insurance will provide your children with a perpetual income. ይህ ፡ የሕይወት ፡ ዋስትና ፡ ለልጆችህ ፡ ዘላቂ ፡ ገቢ ፡ ይሆናቸዋል

**perpetually**
1. ሁልጊዜ. He is perpetually late. ሁልጊዜ ፡ ዘግይቶ ፡ ይመጣል
2. ያለማቋረጥ. The earth turns perpetually on its axis. መሬት ፡ ያለማቋረጥ ፡ በዘንጓ ፡ ላይ ፡ ትሽከረከራለች

**perpetuate** ጠብቆ ፡ አቆየ
This statue will perpetuate the memory of our heroes. ይህ ፡ ሐውልት ፡ የጀግኖቻችንን ፡ ትዝታ ፡ ጠብቆ ፡ ያቆያል

**perpetuity, in ~**
1. እስከነጭራሹ. This land has been given to the church in perpetuity. ይህ ፡ መሬት ፡ እስከነጭራሹ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሰጥቷል
2. ለዘለቄታው. The charity was established in perpetuity by the millionaire. ሀብታሙ ፡ የበጎ ፡ አድራጎቱን ፡ ድርጅት ፡ ያቋቋመው ፡ ለዘለቄታው ፡ ነው

**perplex** ግራ ፡ አጋባ ፤ አደናገረ
The problems perplexed him greatly. ፕሮብሌሙ ፡ በጣም ፡ ግራ ፡ አጋባው
His talk perplexed me. ንግግሩ ፡ አደናገረኝ

**perplexed** (adv.) ግራ ፡ ገብቶት
He stood perplexed at the crossroads, not knowing which way to go. የት ፡ እንደሚሄድ ፡ ግራ ፡ ገብቶት ፡ በመንገዶቹ ፡ መገናኛ ፡ ላይ ፡ ቆመ

**perplexity** (perplexities)
1. መደናገር. His perplexity was so great that he had to ask several people for advice. በጣም ፡ ከመደናገሩ ፡ የተነሣ ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ምክር ፡ መጠየቅ ፡ ነበረበት
2. የሚያደናግር ፡ ነገር. There are many perplexities in such a complicated job. እንዲህ ፡ በተወሳሰበ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የሚያደናግሩ ፡ ነገሮች ፡ አሉ

**perquisite, as a ~** ከደሞዙ ፡ ሌላ
The maid had the old dresses of her mistress given her as a perquisite. ገረዲቱ ፡ ከደሞዟ ፡ ሌላ ፡ የሚሰጣትን ፡ የእመቤቷን ፡ አሮጌ ፡ ልብስ ፡ ታስቀምጥ ፡ ነበር

**persecute**
1. አሠቃየ. The Romans persecuted the Christians in the early days. በጥንት ፡ ዘመን ፡ ሮማውያን ፡ ክርስቲያኖችን ፡ አሠቃይተዋቸዋል
2. አስቸገረ. The older boys in school persecuted the younger ones. በትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ትልልቆቹ ፡ ትንንሾቹን ፡ ልጆች ፡ አስቸገሯቸው
3. ሊያጠቃው ፡ ፈለገ. He is possessed by the idea that someone is persecuting him. አንድ ፡ ሰው ፡ ሊያጠቃኝ ፡ ይፈልጋል ፡ በሚል ፡ ሐሳብ ፡ ተውጧል

**persecution** ማሠቃየት
The boy's persecution of the kitten was cruel. የልጁ ፡ ድመቲቷን ፡ ማሠቃየት ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ነበር
*The persecution of the Christians by the Romans is described in this book. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ሮማውያን ፡ ክርስቲያኖችን ፡ እንዳሠቃዩዋቸው ፡ ይገልጻል
*He remained secure in his faith despite persecution. ቢያሳድዱት ፡ እንኳ ፡ በእምነቱ ፡ ጸንቶ ፡ ቆየ

**perseverance** የመጣጣር ፡ ብዛት
By perseverance, the lame boy learned to swim. ከመጣጣር ፡ ብዛት ፡ አንካሳው ፡ ልጅ ፡ መዋኘት ፡ ለመደ

**persevere**
1. ያለመሰልቸት ፡ ጣረ. He persevered until he learned how to do it perfectly. በደንብ ፡ መሥራት ፡ እስኪቻለ ፡ ድረስ ፡ ያለመሰልቸት ፡ ጣረ
2. ወደ ፡ ኋላ ፡ አላለም. She persevered in the face of many obstacles. ብዙ ፡ ችግር ፡ ቢያጋጥማትም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አላለችም

**Persian**
1. ፋርስ. Persians used to rule Yemen. ፋርሶች ፡ የመንን ፡ ይገዙ ፡ ነበር
2. የፋርስ ፡ ቋንቋ. Can you speak Persian? የፋርስ ፡ ቋንቋ ፡ መናገር ፡ ትችላለህ ?

**persist**
1. ቀጠለ. He persisted in asking embarrassing questions. አሳፋሪ ፡ ጥያቄዎች ፡ መጠየቁን ፡ ቀጠለ
2. ቆየ. The fog is likely to persist in most areas. ጭጋጉ ፡ በብዙ ፡ ቦታዎች ፡ ሳይቆይ ፡ አይቀርም
*He persists in reading in bed. አልጋ ፡ ላይ ፡ ተጋድሚ ፡ ካላነበብኩ ፡ ይላል
*The child persists in playing in the living room. ልጁ ፡ አሻፈረኝ ፡ ብሎ ፡ እንግዳ ፡ ማረፊያው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ይጫወታል

**persistence** መንፈስ ፡ ጠንካራነት
By persistence, many people won religious freedom. በመንፈስ ፡ ጠንካራነት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሃይማኖት ፡ ነጻነት ፡ አገኙ

**persistent**
1. ያልተቈጠበ. Only persistent effort will effectuate the desired results. ያልተቈጠበ ፡ ጥረት ፡ ብቻ ፡ የተፈለገውን ፡ ውጤት ፡ ያስገኛል
2. የማያቋርጥ. Last August was a month of persistent rain. ያለፈው ፡ ነሐሴ ፡ የማያቋርጥ ፡ ዝናም ፡ የዘነበበት ፡ ወር ፡ ነበር
3. ቶሎ ፡ የማይጠፋ. Walking through the house, I became aware of the persistent odor of pepper. እቤት ፡ ውስጥ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ስል ፡ ቶሎ ፡ የማይጠፋ ፡ የበርበሬ ፡ ሽታ ፡ ሸተተኝ
4. (= adv.) ነጋጠባ. He gave in to her persistent demands and bought her a fur coat. እሷ ፡ ነጋጠባ ፡ በምታደርገው ፡ ጉትጐታ ፡ ተሸንፎ ፡ አንድ ፡ ጸጉራማ ፡ ኮት ፡ ገዛላት
*He suffers persistent attacks of malaria. ወባው ፡ ይመላለስበታል

**person**
1. ሰው. She is a nice person. ጥሩ ፡ ሰው ፡ ነች
2. ሰውነት. We should keep our persons clean. ሰውነታችንን ፡ በንጽሕና ፡ መጠበቅ ፡ አለብን
3. መደብ. The verb agrees with the subject in person and gender. ግስ ፡ በመደብና ፡ በጾታ ፡ ከባለቤት ፡ ጋር ፡ ይስማማል

**in person**
1. ራሱ. I shall be present at the meeting in person. ስብሰባው ፡ ላይ ፡ ራሴ ፡ እገኛለሁ
2. በጁ. Please deliver this to him in person! እደራሁን ፡ ይህንን ፡ በጁ ፡ ስጠው

**per person** እያንዳንዳቸው
They paid fifty cents per person to see the show. ትርእይቱን ፡ ለማየት ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ኀምሳ ፡ ሳንቲም ፡ ከፈሉ

**this person** ይህ ፡ ሰውዬ
This person is the only one here who knows Amharic. እዚህ ፡ አማርኛ ፡ የሚያውቅ ፡ ይህ ፡ ሰውዬ ፡ ብቻ ፡ ነው

**personable** መልክ ፡ መልካም
He is a personable young man. መልክ ፡ መልካም ፡ ወጣት ፡ ነው

**personage** ሰው
Important personages will attend the ceremonies. ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ
[See also 'kingly']

**personal**
1. የግል. He would like to discuss a personal matter with you. ካንተ ፡ ጋር ፡ የግል ፡ ጉዳይ ፡ ለመወያየት ፡ ይፈልጋል
They confiscated everything, even personal property. የግል ፡ ንብረት ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ወረሱ
2. የግል ፡ ሁኔታ. Reporters invaded his privacy by asking personal questions. ጋዜጠኞች ፡ ስለግል ፡ ሁኔታ ፡ እየጠየቁ ፡ በግል ፡ ኑሮው ፡ ጣልቃ ፡ ገቡበት
3. እሱን ፡ የሚነካ ፡ ነገር. I meant nothing personal, so do not take my remarks to heart. አንተን ፡ የሚነካ ፡ ነገር ፡ ስላላሰብኩ ፡ የሰጠሁትን ፡ አስተያየት ፡ ከክፋት ፡ አትቍጠረው
*The Emperor paid the soldier a personal visit while he was in a hospital. ወታደሩ ፡ ሆስፒታል ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሄደው ፡ ጠየቁት
*Do you have personal knowledge of this matter? ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ራስህ ፡ የምታውቀው ፡ ነገር ፡ አለ ?

**be personal** ሰው ፡ ነካ
He always becomes personal in a dispute. በክርክር ፡ ጊዜ ፡ ዘወትር ፡ ሰው ፡ ይነካል

**personal beauty** መልክ
Personal beauty is not as important as intelligence. መልክ ፡ የብልህነትን ፡ ያህል ፡ አይጠቅምም
[See also 'personal pronoun']

**personality** (personalities)
1. ባሕርይ. The two brothers have different personalities. ሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ የተለያየ ፡ ባሕርይ ፡ አላቸው
2. ጠባይ. The boy is developing a fine personality. ልጁ ፡ ጥሩ ፡ ጠባይ ፡ ይዟል
3. ማንነት. You have to respect a child's personality. የልጅን ፡ ማንነት ፡ ልታከብርለት ፡ ይገባል
4. እሱነት. An author leaves an imprint of his personality on what he writes. ጸሐፊ ፡ በሚጽፈው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ እሱነቱን ፡ የሚገልጽ ፡ ይታይበታል
5. ሰው. He is a leading personality of the theater. እሱ ፡ በቲያትር ፡ ቤቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ሰው ፡ ነው

**personally**
1. በበኩሉ. Personally, I have no objection to your joining us. በበኩሌ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ብትሆን ፡ አልቃወምም
2. እሱን ፡ ራሱን. I would like to speak to him personally. እሱን ፡ ራሱን ፡ ለማነጋገር ፡ እፈልጋለሁ
3. ራሱ. The hostess personally saw to the comfort of her guests. ባለቤቲቷ ፡ ራሳቸው ፡ እንግዶቹን ፡ ተከባከቡ
*I dislike the painter personally, but I respect his talent. ለሠዓሊው ፡ የግል ፡ ጥላቻ ፡ ቢኖረኝም ፡ ችሎታውን ፡ አደንቃለሁ

**take personally**
She took his remark personally. የሰጠውን ፡ አስተያየት ፡ በሷ ፡ ላይ ፡ የተሰነዘረ ፡ አድርጋ ፡ ቈጠረችው

**personal pronoun** ምድብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም
"I", "you", and "he" are personal pronouns. « እኔ » ፤ « አንተ » ና ፡ « እሱ » ፡ ምድብ ፡ ተውላጠ ፡ ስሞች ፡ ናቸው

**personification** መልካም ፡ ምሳሌ
She is the personification of neatness. ለንጽሕና ፡ መልካም ፡ ምሳሌ ፡ ናት

**personify** (personified)
1. መሰለ. The poet personified truth as a beautiful maiden. ገጣሚው ፡ እውነትን ፡ በውብ ፡ ወይዘሮ ፡ መሰላት
2. የ - - - ምሳሌ ፡ ነው ፤ የ - - - መጨረሻ ፡ ነው.
A snake personifies the devil. እባብ ፡ የሰይጣን ፡ ምሳሌ ፡ ነው
This man personifies avarice. ይህ ፡ ሰው ፡ የንፉግ ፡ መጨረሻ ፡ ነው

**personnel** ሠራተኞች
There is a lack of trained personnel. የሠለጠኑ ፡ ሠራተኞች ፡ እጥረት ፡ አለ
[See also 'authorized']

**perspective**
1. አስተያየት. You must view foreign affairs in the proper perspective. የውጭ ፡ ሀገርን ፡ ጉዳይ ፡ በተገቢው ፡ አስተያየት ፡ መመልከት ፡ አለብህ
2. ሐሳብ. Working in a factory gave him a new perspective in labor problems. በፋብሪካው ፡ ውስጥ ፡ መሥራት ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ችግር ፡ አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ጨመረለት

**in perspective** ርቀትንና ፡ ቅርበትን ፡ ጠብቆ
It is difficult to learn how to draw in perspective. ርቀትንና ፡ ቅርበትን ፡ ጠብቆ ፡ ሥዕል ፡ መሣልን ፡ መማር ፡ ከባድ ፡ ነው

**perspicacious**
1. አስተዋይ. He is a perspicacious person, so you can rely on whatever he tells you. አስተዋይ ፡ ስለሆነ ፡ በሚነግርህ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ልትተማመን ፡ ትችላለህ
2. ጮሌ. The perspicacious trader made a large profit selling grain. ጮሌው ፡ ነጋዴ ፡ እህል ፡ በመሸጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ትርፍ ፡ አገኘ

**perspicacity** ልቡና
He judges with great perspicacity. በብሩህ ፡ ልቡና ፡ ያስተውላል

**perspiration** ላብ
His shirt was wet with perspiration. ሸሚዙ ፡ በላብ ፡ በስብሶ ፡ ነበር

**perspire** አላበ(ው)
He perspired so profusely that his shirt was wet. በጣም ፡ ስላላበው ፡ ሸሚዙ ፡ ርሷል

**persuade** አግባባ
He persuaded me to accept the money. ገንዘቡን ፡ እንድቀበል ፡ አግባባኝ

**persuasion**
1. (= being persuaded) መግባባት. Exertion of authority is not always appıopriate; persuasion may be better. በሥልጣን ፡ ኀይል ፡ ብቻ ፡ መሥራት ፡ ሁልጊዜ ፡ ጥሩ ፡ አይደለም ፤ መግባባት ፡ ይሻል ፡ ይሆናል
2. እምነት. The two brothers had different political persuasions. ሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ የተለያየ ፡ የፖለቲካ ፡ እምነት ፡ ነበራቸው
*I am open to persuasion. የሰው ፡ ሐሳብ ፡ ለመስማት ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ

**persuasive** የማግባባት
The salesman had a very persuasive way of talking. አሻሻጩ ፡ ሰው ፡ የማግባባት ፡ ችሎታው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው

**pert** ደፋር
The pert girl was scolded by the teacher. አስተማሪው ፡ ደፋሯን ፡ ልጃገረድ ፡ ገሠጻት

**pertain**
1. ተመለከተ. This does not pertain to you. ይህ ፡ አንተን ፡ አይመለከትም
These are the duties that pertain to your new job. አዲሱን ፡ ሥራህን ፡ የሚመለከቱት ፡ ተግባሮች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው
2. አስፈላጊ ፡ ሆነ ፤ ተገቢ ፡ ሆነ. We had goose and everything else that pertains to a holiday dinner. ዝዪና ፡ ሌሎችም ፡ ለበዓል ፡ ቀን ፡ እራት ፡ አስፈላጊ ፡ (ተገቢ) ፡ የሆኑ ፡ የምግብ ፡ ዓይነቶች ፡ ሁሉ ፡ ነበሩን

**pertaining** ከነ - -
He bought the house and the land pertaining to it. መሬቱን ፡ ከነቤቱ ፡ ገዛው

**pertinacious**
1. የማያቋርጥ. His pertinacious efforts finally resulted in his getting the job. የማያቋርጥ ፡ ጥረቱ ፡ በመጨረሻ ፡ ሥራውን ፡ አስገኘለት
2. ሞዛዛ. A pertinacious salesman offends many of his customers. ሞዛዛ ፡ አሻሻጭ ፡ ብዙ ፡ ደንበኞቹን ፡ ያበሳጫል

**pertinence** ተገቢነት
The pertinence of the boy's replies shows that he is not stupid. የልጁ ፡ መልስ ፡ ተገቢነት ፡ ደደብ ፡ አለመሆኑን ፡ ያመለክታል

**pertinent**
1. ተገቢ. He made a pertinent comment on the international situation. ስለ ፡ ዓለም ፡ ሁኔታ ፡ ተገቢ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠ
2. አግባብነት ፡ ያለው. His observations are not always pertinent. የሚሰጣቸው ፡ አስተያየቶች ፡ ሁልጊዜ ፡ አግባብነት ፡ ያላቸው ፡ አይደሉም
3. አስፈላጊ. He informed himself of all the pertinent facts. አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መረጃዎች ፡ ሁሉ ፡ ተረዳ

**perturb** አሳሰበ
The rise in crime perturbs many people. የወንጀል ፡ መብዛት ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያሳስባል

**perusal** በጥንቃቄ ፡ ማንበብ
His daily perusal of the newspaper takes him an hour. በየቀኑ ፡ በጥንቃቄ ፡ ጋዜጣ ፡ ማንበቡ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ይፈጅበታል

**peruse** በጥንቃቄ ፡ አነበበ
He perused the book. መጽሐፉን ፡ በጥንቃቄ ፡ አነበበ

**pervade**
1. አወደ. The odor of roses pervades the air. የጽጌ ፡ ረዳ ፡ መዓዛ ፡ አየሩን ፡ ያውዳል
2. ዐጠነ ፤ በከለ ፤ አወደ. The stink of rotting meat pervaded the air. የገማው ፡ ሥጋ ፡ ሽታ ፡ አየሩን ፡ ዐጠነው ፡ (በከለው ፤ አወደው)
3. ሞላ. A sickening odor of burned flesh pervaded the room. የሚያቅለሸልሽ ፡ ያረረ ፡ ሥጋ ፡ ሽታ ፡ ክፍሉን ፡ ሞላው

4. ሰፈነ(በት). Joy pervades his poems. ግጥሙ ፡ ሁሉ ፡ ደስታ ፡ ሰፍኖበታል

**perverse**

1. እልኸኛ. The perverse child did just what we told him not to do. እልኸኛው ፡ ልጅ ፡ ል ከ ፡ እንዳያደርግ ፡ የነገርነውን ፡ ነገር ፡ አደረገ
2. የሰው ፡ ምክር ፡ የማይቀበል ፤ ድርቅ ፡ ብዬ. The perverse man continued to smoke, against his doctor's orders. የሰው ፡ ምክር ፡ የማይቀበ ለው ፡ (ድርቅ ፡ ብዬ) ፡ ሰው ፡ የሐኪሙን ፡ ት እዛዝ ፡ ጥሶ ፡ ሲጋራ ፡ ማጨሱን ፡ ቀጠለ
3. ብልሹ. He has a perverse mind which delights in causing trouble. ብልሹ ፡ አእም ሮ ፡ ስላለው ፡ ችግር ፡ ማምጣት ፡ ያስደስተዋል
4. የተሳሳተ. His perverse reasoning leads him to believe that riots are beneficial. የተሳሳተ ፡ አ ስተሳሰቡ ፡ ሁከት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ እ ምነት ፡ አሳድሮበታል

**perverse act** ኀጢአት
Cruelty to animals is a perverse act. በእን ስሳት ፡ መጨከን ፡ ኀጢአት ፡ ነው

**perversion** ማዛባት
Perversion of the facts is harmful to true understanding. እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ማዛባት ፡ በደንብ ፡ ለመግባባት ፡ ዕንቅፋት ፡ ይሆናል

**pervert** (v.)

1. አዞረ. His enemies perverted his friendly remark and made it into an insult. ጠላቶቹ ፡ እሱ ፡ የሰጠውን ፡ የወዳጅነት ፡ አስተያየት ፡ አዙረ ው ፡ ስድብ ፡ አስመለሱት
2. አበላሸ. He perverted the minds of the young people. የወጣቶቹን ፡ አእምሮ ፡ አበላሸ
Reading silly stories perverts our taste for good books. የማይረባ ፡ ታሪኮችን ፡ ማንበብ ፡ ጥ ሩ ፡ መጽሐፍ ፡ ለማንበብ ፡ ያለንን ፡ ስሜት ፡ ያ በላሽብናል

**pessimism**
*An air of pessimism prevails regarding the efforts to end the war. ጦርነቱን ፡ ለማቆም ፡ የሚደረገው ፡ ጥረት ፡ ውጤት ፡ አያምርም ፡ የሚ ል ፡ እምነት ፡ አለ

**pessimist** ክፉ ፡ አሳቢ
The pessimist always looks at the dark side of things. ክፉ ፡ አሳቢ ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚደረጉት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ መጥፎ ፡ መስለው ፡ ይታዩታል

**(be) pessimistic about** ጥሩ ፡ መስሎ ፡ አይታየ ውም
I am pessimistic about his chances of passing the examination. ፈተናውን ፡ ለማለፍ ፡ ያለው ፡ ዕ ድል ፡ ጥሩ ፡ መስሎ ፡ አይታየኝም

**pest**

1. ወረርሽኝ ፡ በሽታ. The pest known as the Black Death depopulated Europe in the Middle Ages. በመሀከለኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ጥቁር ፡ ሞት ፡ የተባለው ፡ ወረርሽኝ ፡ በሽታ ፡ የ አውሮፓን ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ቀነሰው
2. መርዘኛ ፡ ነፍሳት. Mosquitoes are pests. የወባ ፡ ትንኞች ፡ መርዘኛ ፡ ነፍሳት ፡ ናቸው
3. መኸገር. He is a pest; he always wants some favor to be given him. መኸገር ፡ ነው ፤ ዘወት ር ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንድታደርግለት ፡ ይፈልጋል

**insect pest** ተባይ
We must destroy insect pests or we'll lose our crops. ተባዮችን ፡ ማጥፋት ፡ አለብን ፤ አለበለዚ ያ ፡ ሰብላችን ፡ ይበላሻል

**pester** ጨቀጨቀ
Don't pester me to go with you to the store! ወደ ፡ ሱቅ ፡ አብረኸኝ ፡ ክልሄድክ ፡ ብለሽ ፡ አት ጨቅጭቂኝ

**pestilence** ቸነፈር
A pestilence has broken out in the South. በደቡብ ፡ ቸነፈር ፡ ተነሥቷል

**pestilent**

1. መርዘኛ. A pestilent disease like typhus will cause many deaths. ተስቦን ፡ የመሰለ ፡ መርዘኛ ፡ በሽታ ፡ ሰው ፡ ይጨርሳል
2. አስከፊ. The pestilent barking of the dog keeps me awake. የውሻው ፡ አስከፊ ፡ ጩኸት ፡ እንቅልፍ ፡ አላስወስድ ፡ አለኝ

**pestle** ዘነዘና
The pestle is used in grinding coffee. ዘነዘና ፡ ቡና ፡ ለመውቀጫ ፡ ያገለግላል

**pet** (petted)

1. ደባበሰ. She petted the child to make it stop crying. ሕፃኑ ፡ ማልቀሱን ፡ እንዲያቆም ፡ ደባበሰችው
2. አንከባከበ. A mother often pets her sick child. እናት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የታመመ ፡ ልጇ ን ፡ ታንከባክባለች

**pet** (n.)

1. ለማዳ ፡ እንስሳ. We are not allowed to keep pets in our apartment. አፓርተማችን ፡ ውስጥ ፡ ለማዳ ፡ እንስሳ ፡ እንድናኖር ፡ አይፈቀድልንም
2. ብርቅዬ. She is her mother's pet. ለናቷ ፡ ብርቅ ዬ ፡ ናት

**pet** (adj.) ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የሚያስበው
Building a school for the blind is his pet project. ለዕውራን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ማቋቋም ፡ ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የሚያስበው ፡ ነገር ፡ ነው

**petal** (ያበባ) ፡ ቅጠል
This flower has waxy petals. ይህ ፡ አበባ ፡ ሰም ፡ መሳይ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ቅጠል ፡ አለው

**petition** (v.) አቤቱታ ፡ አቀረበ
We petitioned the mayor for a new school. አዲስ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲሠራ ፡ ለከንቲባው ፡ አቤቱታ ፡ አቀረብን

**petition** (n.)
1. አቤቱታ. He sent a petition to the mayor asking for a new traffic light. አዲስ ፡ የትራፊክ ፡ መብራት ፡ እንዲገባ ፡ ለከንቲባው ፡ አቤቱታ ፡ አቀረበ
2. ማመልከቻ. He forged my signature to his petition. ማመልከቻው ፡ ላይ ፡ የኔን ፡ ፊርማ ፡ አስመስሎ ፡ ፈረመ

**petrify** (petrified)
1. እንደ ፡ ድንጋይ ፡ አደረገ. Heat and the passage of time petrifies wood. ሙቀትና ፡ የጊዜ ፡ ብዛት ፡ ዕንጨቱን ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ያደርጋል
2. በድን ፡ አደረገ. The sight of the fire petrified him. ቃጠሎውን ፡ ማየት ፡ በድን ፡ አደረገው

**be petrified** እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ጠጠረ
The wood became petrified after being many years in the ground. ዕንጨቱ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ ወድቆ ፡ ስለቆየ ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ጠጠረ

**be petrified with fear** በድን ፡ ሆነ
He was petrified with fear when he saw the lion. አንበሳውን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በድን ፡ ሆነ

**petrol** ቤንዚን
Fill my gas tank with petrol! የነዳጅ ፡ ጋኔን ፡ በቤንዚን ፡ ሙላው

**petroleum** ዘይት
Does Ethiopia import all its petroleum? ኢትዮጵያ ፡ ዘይቷን ፡ በሙሉ ፡ የምታስመጣው ፡ ከውጭ ፡ ነው ?

**petty**
1. ዝቅተኛ. My uncle is a petty official in the Ministry of Education. አጐቴ ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ዝቅተኛ ፡ ባለሥልጣን ፡ ነው
2. የማይረባ ፡ ጥቃቅን. They argued over petty details. በማይረባ ፡ ጥቃቅን ፡ ዝርዝሮች ፡ ላይ ፡ ተከራከሩ

**petty cash** ለጥቃቅን ፡ ወጪ ፡ የተመደበ ፡ ገንዘብ
The thief stole the petty cash that was in the drawer. ሌባው ፡ መሳቢያ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ ለጥቃቅን ፡ ወጪ ፡ የተመደበውን ፡ ገንዘብ ፡ ሰረቀው

**petulant**
*The child's petulant behavior is due to his parents' refusal to buy him candy. ልጁ ፡ የሚነጫነጨው ፡ ወላጆቹ ፡ ከረሜላ ፡ አንገዛልህም ፡ ስላሉት ፡ ነው

**pew** [የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አግዳሚ ፡ መቀመጫ]

**phantom** ጣረ ፡ ሞት ፡ የሚመስል ፡ ነገር
He thought he saw a phantom in the graveyard. በመካነ ፡ መቃብሩ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጣረ ፡ ሞት ፡ የሚመስል ፡ ነገር ፡ ያየ ፡ መሰለው

**pharmacist** መድኃኒት ፡ ቀማሚ
The pharmacist compounds medicine. መድኃኒት ፡ ቀማሚው ፡ መድኃኒት ፡ ይቀምማል

**pharmacy** (pharmacies) መድኃኒት ፡ ቤት
The pharmacy that remains open this evening is near our house. የዛሬ ፡ መድኃኒት ፡ ቤት ፡ ተረኛ ፡ በቤታችን ፡ አጠገብ ፡ ነው

**phase** (v.), ~ **out** ቀስ ፡ በቀስ ፡ አስቀረ
The factory has plans to phase out the obsolescent machinery. ፋብሪካው ፡ ጊዜ ፡ ያለፈባቸውን ፡ መሣሪያዎች ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ለማስቀረት ፡ ያስባል

**phase** (n.)
1. ምዕራፍ. This is a critical phase in world history. ይህ ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የሚያሳስብ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው
2. የእድገት ፡ ደረጃ. Adolescence is a phase we all go through. ጕርምስና ፡ ሁላችንም ፡ የምናልፍበት ፡ የእድገት ፡ ደረጃ ፡ ነው
3. ክፍል. What phase of arithmetic are you studying now? አሁን ፡ የምታጠናው ፡ የሒሳብ ፡ ክፍል ፡ የትኛው ፡ ነው ?
*The admiral wrote about the naval phase of the invasion. አድሚራሉ ፡ የባሕሩን ፡ ጦርነት ፡ ስለሚመለከተው ፡ ወረራ ፡ ጻፈ
*In the final phase of his illness, his skin became entirely yellow. ሕመሙ ፡ ሲለቀው ፡ ሲል ፡ ቆዳው ፡ ፍጹም ፡ ቢጫ ፡ ሆነ

**pheasant** ጣዎስ

**phenomenon** (phenomena)
1. ምልክት. Fever and inflammation are phenomena of diseases. ትኩሳትና ፡ የሰውነት ፡ ማጉረብረብ ፡ የበሽታ ፡ ምልክቶች ፡ ናቸው

2. ያልተለመደ ፡ ሁኔታ. The moon turned red last night. No one can explain this phenomenon. ትላንትና ፡ ማታ ፡ ጨረቃ ፡ ደም ፡ መሰለች ! ይህንን ፡ ያልተለመደ ፡ ሁኔታ ፡ ማንም ፡ ሊገልጸው ፡ አይችልም

3. ሁኔታ. We studied gravitation and relative phenomena. ስለ ፡ ስበትና ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሁኔታዎች ፡ አጠናን

*Lightning is an electrical phenomenon. መብረቅ ፡ ከኤሌክትሪክ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው

**philanthropic** የችሮታ

His philanthropic bequests have created museums and libraries. በሱ ፡ የችሮታ ፡ ኑዛዜዎች ፡ ቤተ ፡ መዘክሮችና ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ተሠርተዋል

**philanthropy** (philanthropies)

1. ችሮታ. A home for orphans was one of his philanthropies. እናት ፡ አባት ፡ ለሌላቸው ፡ ልጆች ፡ ቤት ፡ መስጠቱ ፡ ከችሮታው ፡ አንዱ ፡ ነው

2. የበጎ ፡ አድራጊዎች ፡ እርዳታ. The Red Cross appeals to philanthropy. ቀይ ፡ መስቀል ፡ የበጎ ፡ አድራጊዎችን ፡ እርዳታ ፡ ይለምናል

**philosopher** ፈላስፋ

There were many philosophers in ancient Greece. በጥንታዊት ፡ ግሪክ ፡ ብዙ ፡ ፈላስፋዎች ፡ ነበሩ

**philosophy** (philosophies) ፍልስፍና

We study philosophy in college. ኮሌጅ ፡ ውስጥ ፡ ፍልስፍና ፡ እናጠናለን

**philter** መድኃኒት

The witch gave the man a philter which turned him into a frog. አስማተኛዋ ፡ ወደ ፡ እንቁራሪትነት ፡ የሚለውጥ ፡ አስማት ፡ ለሰውዬው ፡ ሰጠችው

**love philter** መስተፋቅር

He went to a medicine man to have a love philter made for him. መስተፋቅር ፡ እንዲያደርግለት ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ ሄደ

**phlegm** አክታ

He has a lot of phlegm due to his cold. ከጉንፋኑ ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ አክታ ፡ አለው

**phlegmatic** ግድየለሽ

The phlegmatic fellow showed no concern about the coming hurricane. ግድየለሹ ፡ ሰው ፡ ስለሚመጣው ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ምንም ፡ አልተጨነቀም

**phone** (v.) ስልክ ፡ ደወለ

Did anyone phone? ስልክ ፡ የደወለ ፡ ሰው ፡ ነበር ?

**be on the phone** ስልክ ፡ ያዘ

Just a moment; I am on the phone. አንዴ ፡ ቆይ ፤ ስልክ ፡ ይዤያለሁ

**phone** (n.) ስልክ

The phone is ringing. ስልኩ ፡ ይደውላል

**phonetic** የድምፅ

The marks used in a dictionary to show pronunciation are called phonetic symbols. በመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ የቃላትን ፡ አነባበብ ፡ ለማመልከት ፡ የምንጠቀምባቸው ፡ የድምፅ ፡ ምልክቶች ፡ ይባላሉ

**phonetics** የድምፅ ፡ ልሳን ፡ ጥናት

Phonetics teaches how the sounds are pronounced. የድምፅ ፡ ልሳን ፡ ጥናት ፡ የንግግር ፡ ድምፆችን ፡ አጠራር ፡ ያስተምረናል

**phonograph** ሸክላ ፡ ማጫወቻ

The phonograph is playing too loudly. ሸክላ ፡ ማጫወቻው ፡ አለመጠን ፡ ይጮኻል

**phony** የውሸት

He is a sucker for phony oil stocks. ተላላ ፡ ስለሆነ ፡ የውሸት ፡ የዘይት ፡ አክሲዮኖች ፡ ያግበስብሳል

**photo** ፎቶግራፍ

This is my sister's photo. ይህ ፡ የእኅቴ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ነው

**photograph** (v.) ፎቶግራፍ ፡ አነሣ

They photographed the coronation. የዘውድ ፡ በዓሉን ፡ ሥርዓት ፡ ፎቶግራፍ ፡ አነሡ

**photographer** ፎቶግራፍ ፡ አንሺ

The photographer photographed the ceremony. ፎቶግራፍ ፡ አንሺው ፡ በዓሉን ፡ ፎቶግራፍ ፡ አነሣ

**phrase** (v.) ገለጸ

He phrased his excuse in polite words. ምክንያቱን ፡ በትሕትና ፡ ገለጸ

**phrase** (n.) ሐረግ

How do you translate the phrase "to be or not to be" into Amharic? « ቱ ፡ ቢ ፡ ኦር ፡ ኖት ፡ ቱ ፡ ቢ » ፡ የሚለውን ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ሐረግ ፡ እንዴት ፡ አድርገህ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ትተረጉመዋለህ ?

**phraseology** አነጋገር
Legal phraseology is hard to understand. የሕግን ፡ አነጋገር ፡ መረዳት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**physical**
1. ግዙፍ. Physical entities are perceived by the five senses, the spiritual ones are not. ግዙፍ ፡ አካሎችን ፡ ባምስቱ ፡ ሕዋሳት ፡ ለማወቅ ፡ ስንችል ፡ ረቂቁን ፡ ግን ፡ አንችልም
2. ግዘፍ. The change from water to ice is a physical change. የውኃ ፡ ወደ ፡ በረዶነት ፡ መለወጥ ፡ ግዘፍ ፡ ለውጥ ፡ ነው
3. አካላዊ. He has to give up all physical activity for a while. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውንም ፡ አካላዊ ፡ እንቅስቃሴ ፡ መተው ፡ አለበት
4. የሰውነት. His illness is mental, not physical. በሽታው ፡ የአእምሮ ፡ እንጂ ፡ የሰውነት ፡ አይደለም
5. የተፈጥሮ. The physical laws determine the structure of a building. የተፈጥሮ ፡ ሕጎች ፡ የንድን ፡ ሕንጻ ፡ አሠራር ፡ ይወስናሉ
[See also 'exercise']

**physically** ባካል
It is physically impossible to be in two places at once. ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ቦታ ፡ ባካል ፡ ለመገኘት ፡ አይቻልም

**physician** ሐኪም
The physician prescribes a medicine to the patient. ሐኪም ፡ ለበሽተኛ ፡ መድኃኒት ፡ ያዛል

**physics** ፊዚክስ
He is taking a course in physics. ፊዚክስ ፡ ይማራል

**physiology** የሰው ፡ አካል ፡ ጥናት

**piano** ፒያኖ

**pick** (v.)
1. ቀጠፈ. I will pick some roses for the table. ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ለማኖር ፡ ጥቂት ፡ ጽጌረዳዎች ፡ እቀጥፋለሁ
2. ለቀመ (ተለቀመ). The farmer picked coffee from the tree. ገበሬው ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ቡና ፡ ለቀመ
Is the fruit ripe enough to pick? ፍሬው ፡ ለመለቀም ፡ ደርሷል ?
3. ገፈፈ. She picked the meat from the bones. ሥጋውን ፡ ካጥንቱ ፡ ላይ ፡ ገፈፈች
4. ያዘ. Pick an odd number! ጐዶሎ ፡ ቁጥር ፡ ያዝ
5. መረጠ. The judges picked the winner. ዳኞቹ ፡ አሸናፊውን ፡ መረጡ
6. ጐረጐረ. The boy picks his teeth with a toothpick. ልጁ ፡ በስንጥር ፡ ጥርሱን ፡ ይጐረጕራል

**pick about** ለቃቀመ
The hens were busily picking about in their coop. ዶሮዎቹ ፡ በዶሮ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ይለቃቅማሉ

**pick at** ቀመስ ፡ አድርጎ ፡ ተወ
She only picked at her food. ምግቡን ፡ ቀመስ ፡ አድርጋ ፡ ተወችው

**pick (off)** ላጠ
Don't pick the scab off your wound! የቁስልህን ፡ ቅርፊት ፡ አትላጠው

**pick on**
1. ተነኰሰ. Don't always pick on the child! ሕፃኑን ፡ ሁልጊዜ ፡ አትተንኰሰው
2. መረጠ. The teacher always picks on me to translate long passages. ረዥም ፡ ምንባቦችን ፡ ለመተርጐም ፡ መምህሩ ፡ ዘወትር ፡ እኔን ፡ ይመርጡኛል

**pick out**
1. መረጠ. He picked out a very nice gift for his wife. ለሚስቱ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ የሆነ ፡ ስጦታ ፡ መረጠ
2. ለየ. Can you pick me out in this picture? እዚህ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ውስጥ ፡ ልትለየኝ ፡ ትችላለህ ?

**pick (one's) pocket** ከኪሱ ፡ ሰረቀው ፤ ኪስ ፡ ገባ
Someone picked my pocket. አንድ ፡ ሰው ፡ ከኪሴ ፡ ሰረቀኝ
A thief picked my pocket. ሌባ ፡ ኪሴ ፡ ገባ

**pick up** (vt.)
1. ለቃቀመ ፤ ቃረመ. He is out picking up bits of information. ከዚያም ፡ ከዚህም ፡ ወሬ ፡ ለመለቃቀም ፡ (ለመቃረም) ፡ ወጥቷል
2. አሳፈረ. The bus stops here to pick up passengers. መንገደኞችን ፡ ለማሳፈር ፡ አውቶቡሱ ፡ እዚህ ፡ ይቆማል
3. ወሰደ. He picks up his letters from the post office box. ደብዳቤዎቹን ፡ ከፖስታው ፡ ሣጥን ፡ ይወስዳል
4. አነሣ. Pick up the paper from the floor! ወረቀቱን ፡ ከወለሉ ፡ ላይ ፡ አንሣው
5. ያዘ. The police picked up several suspects. ፖሊስ ፡ ብዙ ፡ ተጠርጣሪዎችን ፡ ያዘ
6. አገኘ. The woman picked up a bargain at the dress sale. በልብስ ፡ መሸጫው ፡ መደብር ፡ ሴትዮዋ ፡ ጥሩ ፡ ግዢ ፡ አገኘች
7. ቃረመ ፤ ተማረ. I picked up a lot of Italian on my trip. በጉዞዬ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ጣሊያንኛ ፡ ቃረምኩ ፡ (ተማርኩ)

**pick up** (vi.)
1. ሞቀ. Business picks up after the rainy

season is over. ከረምቱ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ንግድ ፡ ይሞቃል
2. ጀምሮ ፡ ቀጠለ. Tom picked up where he stopped the day before. ቶም ፡ ባለፈው ፡ ቀን ፡ ካቆመበት ፡ ጀምሮ ፡ ቀጠለ
3. ፍጥነት ፡ ጨመረ. The car picked up once it was on the open road. ግልጽ ፡ መንገድ ፡ ስ ታገኝ ፡ መኪናዋ ፡ ፍጥነቷን ፡ ጨመረች

**pick (oneself) up** ብድግ ፡ አለ
She slipped and fell, but quickly picked herself up. አድጧት ፡ ወድቃ ፡ ወዲያውኑ ፡ ብድግ ፡ አ ለች
[See also 'bone, hole, quarrel, tab']

**pick** (n.)
1. ዶማ. The men were carrying picks and shovels. ሰዎች ፡ ዶማ ፡ አካፋ ፡ ተሸክመው ፡ ነበር
2. ምርጫ. He is our pick for president. ለፕሬዚ ዳንትነት ፡ ምርጫችን ፡ እሱ ፡ ነው
3. አዝመራ. The pick is poor this season. በዚህ ፡ ወቅት ፡ አዝመራው ፡ መጥፎ ፡ ነው

**take one's pick** የሚመርጠውን ፡ ወሰደ
Take your pick of these books! ከነዚህ ፡ መጻሕ ፍት ፡ የምትመርጠውን ፡ ውሰድ

**the pick of** ምርጥ ፡ የሆኑት
We got a high price for the pick of the roses. ምርጥ ፡ ለሆኑት ፡ ጽጌረዳዎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ አገኘን

**pickaxe** ዶማ
A pickaxe is used to break hard ground. ዶማ ፡ ጠንካራ ፡ መሬትን ፡ ለመቆፈር ፡ ያገለግላል

**picket** (v.) ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ አደረገ
The employees picketed the store for better wages. ሠራተኞቹ ፡ ደሞዝ ፡ እንዲጨመርላቸው ፡ ከመደብሩ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ አደረጉ

**picket** (n.), **wooden ~** የሾላ ፡ አጠና
The fence is made of wooden pickets. አጥሩ ፡ የተሠራው ፡ ከሾላ ፡ አጠና ፡ ነው

**pickle** [በኮምጣጤና ፡ በጨው ፡ የተዘፈዘፈ ፡ ዱባ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ፍሬ]

**pickpocket** ኪስ ፡ አውላቂ
The pickpocket was caught and beaten. ኪስ ፡ አውላቂው ፡ ተይዞ ፡ ተደበደበ

**pickup**
*The mailman makes three pickups a day. ፖስተኛው ፡ በቀን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ደብዳቤ ፡ ይሰ በስባል
*There was a pickup in retail sales last month. ባለፈው ፡ ወር ፡ የችርቻሮ ፡ ሽያጭ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ነበር

**have a good pickup** የፍጥነት ፡ ኀይል ፡ አለው
Our old car still has a good pickup. አሮጌዋ ፡ መኪናችን ፡ አሁንም ፡ የፍጥነት ፡ ኀይል ፡ አላት

**picnic** (picnicked)
*Our family often picnics at the beach. ቤተ ፡ ሰባችን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ዳር ቻ ፡ ለሽርሽር ፡ ሄደው ፡ እዚያው ፡ በልተው ፡ ይውላሉ

**picnic** (n.) ሽርሽር
Let's go on a picnic! ሽርሽር ፡ እንሂድ

**pictorial** ሥዕላዊ
A pictorial magazine will be published for the tourists. ላገር ፡ ጐብኚዎች ፡ ሥዕላዊ ፡ መ ጽሔት ፡ ይታተማል
A photograph album is a pictorial record of the family. የፎቶግራፍ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ የቤተሰ ቡ ፡ ሥዕላዊ ፡ መዝገብ ፡ ነው

**picture** (v.)
1. ገለጸ. This novel pictures life a thousand years ago. ይህ ፡ የልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ ከሺ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ኑሮ ፡ ይገልጻል
2. ሣለ. The artist pictured the saints. ሠዓሊው ፡ ቅዱሳኑን ፡ ሣለ
3. አሳየ. The scenery pictures a garden in the moonlight. የቲያትሩ ፡ ትርእይት ፡ ጨረቃ ፡ የፈነጠቀችበት ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ ያሳያል
4. አስተያየት ፡ ሰጠ. He pictured the situation in America differently. የአሜሪካንን ፡ ሁኔታ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠው
5. አሰበ. It is hard to picture life a hundred years ago. ከመቶ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የነበረው ን ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ ማሰብ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**be pictured** ተነበበ
Joy is pictured in his face. ደስታ ፡ በፊቱ ፡ ላ ይ ፡ ይነበባል

**picture oneself** ራሱን ፡ ቈጠረ
He likes to picture himself as an explorer. ራሱን ፡ እንደ ፡ አሳሽ ፡ መቍጠር ፡ ይወዳል

**picture someone as** መሰለ(ው)
+I can't picture you as a politician. የፖለቲካ ፡ ሰው ፡ አትመስለኝም

**picture** (n.)
1. ሥዕል. They have some beautiful pictures for sale. የሚሸጡ ፡ አንዳንድ ፡ ጥሩ ፡ ሥዕሎች ፡ አሉዋቸው

2. መግለጫ. He gave me a false picture of the situation in the country. ስለ ፡ አገሪቱ ፡ ሁኔታ ፡ ትክክል ፡ ያልሆነ ፡ መግለጫ ፡ ሰጠኝ
3. ትርእይት. The trees and the brook make a lovely picture. ዛፎቹና ፡ ምንጩ ፡ አስደሳች ፡ ትርእይት ፡ ናቸው
4. ፊልም. Yesterday we saw a picture with Greta Garbo. ግሬታ ፡ ጋርቦ ፡ ያለችበትን ፡ ፊልም ፡ ትላንትና ፡ አየን
5. ፎቶግራፍ. That is a picture of my fiancée. ያ ፡ የእጮኛዬ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ነው
*She's the picture of health. ጤነኛ ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ እሷ ፡ ናት
*She is the pict.re of her mother. ቁርጥ ፡ እናቷን ፡ ናት

**have a picture of** ታየ(ው)
I have a clear picture of how he looked that day. ያን ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ይመስል ፡ እንደነበረ ፡ በግልጽ ፡ ይታየኛል

**take a picture** ፎቶግራፍ ፡ አነሣ
Take a picture of me and send it to your friends! ፎቶግራፍ ፡ አንሣኝና ፡ ለጓደኞችህ ፡ ላክላቸው

**picture** (adj.) ሥዕላዊ
There is little reading in this picture magazine. በዚህ ፡ ሥዕላዊ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ የሚነበብ ፡ ጥቂት ፡ ነው

**picturesque** ውብና ፡ ማራኪ
Gondar is a picturesque city. ጐንደር ፡ ውብና ፡ ማራኪ ፡ ከተማ ፡ ናት
*This is a picturesque description of life in the city. ይህ ፡ የከተማን ፡ ኑሮ ፡ በዓይን ፡ ጎሊና ፡ እንደሚታይ ፡ አድርጎ ፡ ይገልጻል

**piece** (v.), ~ **together**
1. አጠናቀረ. They pieced together bits of information to discover the cause of the explosion. የፈንጅውን ፡ ምክንያት ፡ ለማግኘት ፡ የተገኙትን ፡ ጥቃቅን ፡ ማስረጃዎች ፡ አጠናቀሩ
2. ገጣጠመ. I pieced the broken jug together. የተሰበረውን ፡ ገንቦ ፡ ገጣጠምኩት

**piece** (n.)
1. ቁራሽ. May I have a piece of cake? ቁራሽ ፡ ኬክ ፡ ልትሰጠኝ ፡ ትችላለህ ?
2. ቁራጭ. Sew the two pieces together! ሁለቱን ፡ ቁራጮች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ስፋቸው
May I have another piece of meat? ከሥጋው ፡ አንዲት ፡ ቁራጭ ፡ ትጨምርልኝ ?
3. ስብርባሪ. I swept up the pieces of glass. የብርጭቆውን ፡ ስብርባሪ ፡ ጠረግሁት
*This table is a fine piece of workmanship. ይህ ፡ ጠረጴዛ ፡ በልዩ ፡ ጥበብ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**piece of information** ወሬ
He gave me a useful piece of information. አንዲት ፡ ጠቃሚ ፡ ወሬ ፡ ነገረኝ

**piece of land** ትንሽ ፡ መሬት
I bought a piece of land yesterday. ትናንት ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ መሬት ፡ ገዛሁ

**break to pieces** እንክትክቱ ፡ ወጣ
The teapot fell and was broken to pieces. የሻዩ ፡ ጀበና ፡ ወድቆ ፡ እንክትክቱ ፡ ወጣ

**by the piece**
1. በሥራው ፡ መጠን. These workers are paid by the piece and not by the hour. እነዚህ ፡ ሠራተኞች ፡ በሠሩት ፡ መጠን ፡ እንጂ ፡ በሰዓት ፡ አይከፈሉም
2. እየቸረቸረ. He sells cloth by the piece. ጨርቅ ፡ የሚሸጠው ፡ እየቸረቸረ ፡ ነው

**fall to pieces**
1. ተገነጣጠለ. This book is falling to pieces. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ሊገነጣጠል ፡ ነው
2. ፈራረሰ. That old house is falling to pieces. ያ ፡ አሮጌ ፡ ቤት ፡ ሊፈራርስ ፡ ነው
3. ውልቅልቁ ፡ ወጣ. This car is so old, it's falling to pieces. ይህ ፡ መኪና ፡ በጣም ፡ ከማርጀቱ ፡ የተነሣ ፡ ውልቅልቁ ፡ ሊወጣ ፡ ነው

**give one a piece of his mind**
1. ክፉኛ ፡ ነቀፈው. He gave his employee a piece of his mind when he saw that he did not do his job well. ሥራውን ፡ በደንብ ፡ ባለመሥራቱ ፡ ባለቤቱ ፡ ሠራተኛውን ፡ ክፉኛ ፡ ነቀፈው
2. ቅር ፡ እንደተሰኘ ፡ ገለጸ(ለት). I will give him a piece of my mind for telling such a lie. ይህን ፡ መሳይ ፡ ውሸት ፡ ስለነገረኝ ፡ ቅር ፡ እንደተሰኘሁ ፡ እገልጽለታለሁ
[See also 'go, pull, rend']

**piecemeal** ጥቂት ፡ በጥቂት
He did the work piecemeal. ሥራውን ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ሠራው

**pier** የወደብ ፡ መድረክ
He was standing on the pier waiting for the boat. የወደቡ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ጀልባውን ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር

**pierce**
1. በሳ. The bullet pierced his skull. ጥይቱ ፡ ራስ ፡ ቅሉን ፡ በሳው
2. ጥሶ ፡ ገባ. Our forces have pierced the enemy lines. የኛ ፡ የጦር ፡ ኀይሎች ፡ የጠላትን ፡ ይዞታ ፡ ጥሰው ፡ ገቡ

3. ጥሶ ፡ ወጣ. The sun pierced the clouds. ፀሐይ ፡ ደመናውን ፡ ጥሳ ፡ ወጣች
4. ወጋ. The needle pierced her finger. መርፌው ፡ ጣቷን ፡ ወጋው
5. ዘልቆ ፡ ገባ. The cold wind pierced our clothes. ቀዝቃዛው ፡ ነፋስ ፡ ልብሳችንን ፡ ዘልቆ ፡ ገባ
6. ነካ. The loss of her kitten pierced the little girl's heart. የድመቷ ፡ መጥፋት ፡ የትንሺቱን ፡ ልጅ ፡ ልብ ፡ ነካው
7. ደረሰ(በት). She couldn't pierce his thoughts. ሐሳቡ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ልትደርስበት ፡ አልቻለችም

**piercing**
1. በጣም ፡ ቀጭን. She has a piercing voice. በጣም ፡ ቀጭን ፡ ድምፅ ፡ አላት
2. ጆሮ ፡ የሚበጥስ. The child let out a piercing scream. ልጁ ፡ ጆሮ ፡ የሚበጥስ ፡ ጩኸት ፡ ለቀቀ
3. አጥንት ፡ የሚሰብር. A piercing wind chilled us to the bone. አጥንት ፡ የሚሰብር ፡ ነፋስ ፡ አኰራመተን

**piety**
1. ሃይማኖተኛነት. He is famous for his piety. በሃይማኖተኛነቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው
2. ቅድስና. Because of his piety, people came from far to receive his blessing. ስለ ፡ ቅድስናው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ቡራኬ ፡ ለማግኘት ፡ ከሩቅ ፡ መጡ
**act of piety** የተቀደሰ ፡ ተግባር
Manumission of slaves is an act of piety. ባሮችን ፡ አርነት ፡ ማውጣት ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባር ፡ ነው

**pig** አሳማ
There are not many pigs in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ አሳማዎች ፡ የሉም

**pigeon** እርግብ
The pigeon alighted on a tree. እርግቢ ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ አረፈች

**pigeonhole** (v.) በጉን ፡ አኑሮ ፡ ረሳው
British officials pigeonholed Emperor Theodore's letter to Queen Victoria. የእንግሊዝ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ከአፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ለንግሥት ፡ ቪክቶርያ ፡ የተላከውን ፡ ደብዳቤ ፡ በጉን ፡ አኑረው ፡ ረሱት

**pigeonhole,** n. [ደብዳቤዎችና ፡ ወረቀቶች ፡ የሚቀመጡባቸው ፡ እንደ ፡ ሣጥን ፡ ያሉ ፡ ትናንሽ ፡ የጠረጴዛ ፡ ክፍሎች]

**piggy** ግልገል ፡ አሳማ ፤ ትንሽ ፡ አሳማ

**piggyback, carry ~** አዘለ
The father carried the baby piggyback. አባትዬው ፡ ልጁን ፡ አዘለ

**pigheaded** ሐሳበ ፡ ግትር
Don't argue with him! He is pigheaded. ከሱ ፡ ጋር ፡ አትከራከር ፤ ሐሳበ ፡ ግትር ፡ ነው

**pigment** ማቅለሚያ
Pigment is added to oil to make paint. ቀለም ፡ ለመሥራት ፡ ማቅለሚያው ፡ ከዘይት ፡ ጋር ፡ ይቀላቀላል

**pike** ጦር
This pike was captured in a battle centuries ago. ይህ ፡ ጦር ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ የተገኘ ፡ ምርኮ ፡ ነው

**pile** (vt.)
1. ቆለለ. He piled the books on the table. መጻሕፍቱን ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ቆለለ
2. ጫነ. The farmer piled the wagon with hay. ገበሬው ፡ ጋሪውን ፡ ድርቆሽ ፡ ጫነው
**pile** (vi.)
1. ተቆለለ. Snow piled against the fences. በረዶው ፡ አጥሩ ፡ ላይ ፡ ተቆለለ
2. ታጐረ. We piled into the bus. አውቶቡሱ ፡ ውስጥ ፡ ታጐርን
**pile in a heap** ከመረ
He piled the sand in a heap. አሸዋውን ፡ ከመረው
**pile up** (vt.) ከመረ
The gardener piled up the leaves. አትክልተኛው ፡ ቅጠሉን ፡ ከመረ
**pile up** (vi.) ተከመረ
My debts are piling up. ዕዳዬ ፡ እየተከመረ ፡ ሄደ

**pile** (n.)
1. ቁልል. The green book is on the bottom of the pile. አረንጓዴው ፡ መጽሐፍ ፡ ከመጽሐፉ ፡ ቁልል ፡ ሥር ፡ ነው
2. ክምር. What am I to do with that pile of books? ያን ፡ የመጽሐፍ ፡ ክምር ፡ ምን ፡ ላድርገው ?
3. የዕንጨት ፡ ምሰሶ. The building rests on wooden piles. ሕንጻው ፡ የቆመው ፡ ዕንጨት ፡ ምሰሶዎች ፡ ላይ ፡ ነው
**a pile of** ብዙ
I have a pile of work to do. ብዙ ፡ የምሠራው ፡ ሥራ ፡ አለኝ
*Here's a pile of letters to answer. መልስ ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ደብዳቤዎች ፡ ተከምረዋል

**make a pile of stones** ድንጋይ ፡ ከበ
Make a pile of stones to show the boundary of your field! የመሬታችሁን ፡ ድንበር ፡ ለማሳየት ፡ ድንጋይ ፡ ከቡ

**pilfer** ሰረቀ
The thief pilfered coins. ሌባው ፡ ገንዘብ ፡ ሰረቀ

**pilgrim** ተሳላሚ
The pilgrims are going to Mecca by ship. ተሳላሚዎቹ ፡ ወደ ፡ መካ ፡ በመርከብ ፡ ይሄዳሉ

**pilgrimage** ወደ ፡ ቅዱሳን ፡ ስፈር ፡ ያደረገው ፡ ጉዞ ፤ መሳለም
His pilgrimage lasted four weeks. ወደ ፡ ቅዱሳን ፡ ስፍራዎች ፡ ያደረገው ፡ ጉዞ ፡ አራት ፡ ሳምንት ፡ ወሰደበት
He is going to the Holy Land on a pilgrimage. ቅድስት ፡ አገርን ፡ ለመሳለም ፡ ይሄዳል
**make a pilgrimage** ሊሳለም ፡ ሄደ
He made a pilgrimage to the Holy Land. ቅድስት ፡ አገርን ፡ ሊሳለም ፡ ሄደ

**pill** ኪኒን
He takes several different kinds of pills for his illness. ለበሽታው ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኪኒን ፡ ይውጣል

**pillage** (v.) ዘረፈ
The bandits pillaged the village and fled. ሽፍቶቹ ፡ መንደሩን ፡ ዘርፈው ፡ ሸሹ

**pillage** (n.) የተዘረፈ ፡ ንብረት
A lot of pillage was recovered from the outlaws. ብዙ ፡ የተዘረፈ ፡ ንብረት ፡ በሽፍቶቹ ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ተያዘ

**pillar**
1. ዓምድ. A large pillar blocked my view of the stage. አንድ ፡ ትልቅ ፡ ዓምድ ፡ መድረኩን ፡ እንዳላይ ፡ ከለለኝ
2. ምሰሶ. These three men are the pillars of the community. እነዚህ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ የኅብረ ፡ ሰቡ ፡ ምሰሶ ፡ ናቸው

**pillory** [ለእጅና ፡ ላንገት ፡ ማስገቢያ ፡ ያለው ፡ ከዕንጨት ፡ የተሠራ ፡ ወንጀለኛ ፡ ባደባባይ ፡ የሚቀጣበት ፡ ነገር]

**pillow**
1. ትራስ. I bought a pillow for three dollars. በሦስት ፡ ብር ፡ ትራስ ፡ ገዛሁ
2. መከዳ. Give me a pillow for a chair! ለወንበሩ ፡ የሚሆን ፡ መከዳ ፡ ስጠኝ

**sleep on a pillow** ትራስ ፡ ተንተራሰ
I like to sleep on two pillows. ሁለት ፡ ትራስ ፡ መንተራስ ፡ እወዳለሁ

**pillowcase** የትራስ ፡ ልብስ
The pillowcase is dirty. የትራስ ፡ ልብሱ ፡ ቆሽሿል

**pilot** (v.)
1. መራ. The captain piloted the ship through the storm. ካፒቴኑ ፡ መርከቧን ፡ በማዕበሉ ፡ ውስጥ ፡ መራ
2. ነዳ. The captain piloted the plane through the storm. ካፒቴኑ ፡ አውሮፕላኑን ፡ በዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ውስጥ ፡ ነዳ
**pilot to a landing** አሳረፈ
He piloted the aircraft to a safe landing. አውሮፕላኑን ፡ ያላንዳች ፡ አደጋ ፡ አሳረፈው

**pilot** (n.)
1. የመርከብ ፡ ነጂ. The pilot brought the ship into harbor. የመርከቡ ፡ ነጂ ፡ መርከቧን ፡ ወደ ፡ ወደብ ፡ አስገባ
2. አውሮፕላን ፡ ነጂ. The pilot of the plane prevented a serious accident. አውሮፕላን ፡ ነጂው ፡ አውሮፕላኑን ፡ ከሚያሰጋ ፡ አደጋ ፡ አዳነው

**pilot** (adj.) የሙከራ
A small pilot study was done first. በመጀመሪያ ፡ አነስተኛ ፡ የሙከራ ፡ ጥናት ፡ ተደረገ

**pimple** ብጉር
His face is covered with pimples. ፊቱን ፡ ብጉር ፡ ወርሶታል

**pin** (pinned), v.
1. ላከከ. They pinned the crime on him. ወንጀሉን ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ላከኩ
2. አጣበቀ. When the tree fell, it pinned him to the ground. ዛፉ ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ ከመሬት ፡ ጋር ፡ አጣበቀው
3. ሰካ. She pinned a flower on her dress. ቀሚሷ ፡ ላይ ፡ አበባ ፡ ሰካች
**be pinned** ተቀረቀረ
He was pinned under the wreckage of his car. ባደጋው ፡ ከተጨራመተው ፡ መኪና ፡ ሥር ፡ ተቀርቅሮ ፡ ነበር
**pin down**
1. እንዲወስን ፡ አደረገ. We couldn't pin him down to a definite date. ቁርጥ ፡ ያለ ፡ ቀን ፡ እንዲወስን ፡ ለማድረግ ፡ አልቻልንም
2. ቃል ፡ አስገባ. He couldn't pin his boss down to a raise in pay. አለቃው ፡ የደሞዝ ፡ ጭማ

ሬ ፡ የሚያደርግለት ፡ ለመሆኑ ፡ ቃል ፡ ሊያስገ ባው ፡ አልቻለም

**pin on** በእስፒል ፡ አስያዘ
I'll pin the flower on for you. አበባውን ፡ በእስ ፒል ፡ እኔ ፡ እሲዝልሃለሁ

**pin** (n.)
1. እስፒል ፤ የወረቀት ፡ መርፌ. She stuck her finger with a pin. ጣቷን ፡ በስፒል ፡ (በወረ ቀት ፡ መርፌ) ፡ ወጋች
2. አርማ. She wore her class pin. የክፍሏን ፡ አ ርማ ፡ ሰከታለች

**pincers** ወረንጦ
I need a pair of pincers to remove this thorn. ይህንን ፡ እሾህ ፡ ለማውጣት ፡ ወረንጦ ፡ ያስፈ ልገኛል

**pinch** (vt.)
1. ቁነጠጠ. Her brother pinched her arm. ወንድሟ ፡ ክንዷን ፡ ቁነጠጣት
2. ያዘ. Her shoe pinches her toes. ጫማዋ ፡ ጣ ቷን ፡ ይዟታል
3. ቀረጠፈ. +He pinched his finger in the door. መዝጊያው ፡ ጣቱን ፡ ቀረጠፈው
4. አሠቃየ. Poverty pinched the family for many years. ድኽነት ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ቤ ተሰቡን ፡ አሠቃይቶት ፡ ነበር

**pinch** (vi.)
1. ጥርሱን ፡ ነክሶ ፡ ገንዘብ ፡ ቈጠበ. He pinched for years to buy a car. መኪና ፡ ለመግዛት ፡ ለ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ጥርሱን ፡ ነክሶ ፡ ገንዘብ ፡ ቈጠበ
2. ያዘ. Where does the shoe pinch? ጫማው ፡ የ ሚይዘው ፡ የት ፡ ላይ ፡ ነው ?

**pinch pennies**
*They didn't pinch pennies on the new municipality building. ላዲሱ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ማሠ ሪያ ፡ ገንዘብ ፡ ሲያወጡ ፡ ወደኋላ ፡ አላሉም

**be pinched** ተቸገረ
The builders were pinched by the shortage of good lumber. በጥሩ ፡ ዕንጨት ፡ እጥረት ፡ ምክን ያት ፡ ገንቢዎቹ ፡ ተቸገሩ

**get pinched** (= active) ቀረጠፈ
+I got my finger pinched in the door. በሩ ፡ ጣ ቴን ፡ ቀረጠፈኝ

**pinch** (n.) ቁንጥጫ
The pinch really hurts. ቁንጥጫው ፡ በጣም ፡ ያ ማል
*Add a pinch of salt to the soup. ሾርባው ፡ ላ ይ ፡ ጨው ፡ ቈንጥረህ ፡ ጨምርበት

**do in a pinch** ለድንገተኛ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ አይል
This string is not very strong, but it will do in a pinch. ይህ ፡ ሲባጎ ፡ በጣም ፡ ጠንካራ ፡ አ ይደለም ፤ ቢሆንም ፡ ለድንገተኛ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ አይል

**pine** (v.) ጓጓ
She is pining to see him again. እንደገና ፡ ልታየ ው ፡ ጓጉታለች

**pine away** መነመነ
The prisoner pined away. እስረኛው ፡ መነመነ

**pine** (n.) የፈረንጅ ፡ ጥድ

**pinion , ~ one's arms** (v.) የፊጥኝ ፡ አሰረው
The thieves pinioned the man's arms. ሌቦቹ ፡ ሰውየውን ፡ የፊጥኝ ፡ አሰሩት

**pink** (v.) በጨረፍታ ፡ መታ
The bullet only pinked him. ጥይቱ ፡ የመታው ፡ በጨረፍታ ፡ ብቻ ፡ ነው

**pink** (adj.) ቀላ ፡ ያለ ፤ ሐምራዊ
She wears a pink blouse. ቀላ ፡ ያለ ፡ (ሐምራዊ) ፡ ብሉዝ ፡ ትለብሳለች

**pinnacle**
1. የተራራ ፡ ጫፍ. They reached the pinnacle after several days of climbing. ከብዙ ፡ ቀናት ፡ በኋላ ፡ ተራራው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ደረሱ
2. ከፍተኛ ፡ ደረጃ. Still in his youth, he reached the pinnacle of his profession. ገና ፡ በወጣትነቱ ፡ በሥራው ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ደረሰ

**pinpoint** ለይቶ ፡ አመለከተ
The detectives pinpointed the criminals' hideout. ሰላዮቹ ፡ የወንጀለኞቹን ፡ ጉሬ ፡ ለይተው ፡ አ መለከቱ

**pint** [የፈሳሽ ፡ መለኪያ]

**pioneer** (v.) ቀዳሚነት ፡ ያዘ
Walter Reed pioneered in finding the cause of yellow fever. ዋልተር ፡ ሪድ ፡ የወባን ፡ መነሾ ፡ በ ማወቅ ፡ ረገድ ፡ ቀዳሚነትን ፡ ይዟል

**pioneer** (n.)
1. አቅኚ ፤ ሰፋሪ. The pioneers opened up the land to cultivation. አቅኚዎቹ ፡ (ሰፋሪዎቹ) ፡ መ ሬቱን ፡ ለእርሻ ፡ መነጠሩት
2. ቀዳሚነት ፡ የያዘ. Benjamin Franklin was a pioneer in the study of electricity. ቤንጃሚን ፡ ፍራንክሊን ፡ በኮሬንቲ ፡ ምርመራ ፡ ረገድ ፡ ቀ ዳሚነትን ፡ የያዘ ፡ ነው

**pious**
1. ሃይማኖተኛ. Pious people always observe the church fasts. ሃይማኖተኞች ፡ ሁልጊዜ ፡ አጽዋማትን ፡ ይጠብቃሉ
2. ጻድቅ. She is pious at church in the morning and gossips all afternoon. ጧት ፡ እቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጻድቅ ፡ ትመስላለች ፤ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ አሉባልተኛ ፡ ናት

**pipe** (v.) አሰማ
The little boy piped a tune in a high voice. ትንሹ ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ዜማ ፡ በቀጭን ፡ ድምፅ ፡ አሰማ

**pipe in** በቧምቧ ፡ አመጣ
The municipality is piping water in from the hills. ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ውኃ ፡ ከተራራው ፡ ላይ ፡ በቧምቧ ፡ ያመጣል

**pipe** (n.)
1. ዋሽንት. He plays the pipe well. ዋሽንት ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ ይጫወታል
2. ፒፓ. He smokes a pipe. ፒፓ ፡ ያጨሳል
3. ቧምቧ. The pipe has burst. ቧምቧው ፡ ፈንድቷል

**piracy** የባሕር ፡ ላይ ፡ ዝርፊያ
Piracy was ended by the king's navy. የባሕር ፡ ላይ ፡ ዝርፊያ ፡ በንጉሡ ፡ የባሕር ፡ ኀይል ፡ ተደመሰሰ

**pirate** የባሕር ፡ ላይ ፡ ዘራፊ ፤ የባሕር ፡ ወንበዴ
There are no more pirates today. በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ የባሕር ፡ ላይ ፡ ዘራፎች ፡ (የባሕር ፡ ወንበዴዎች) ፡ የሉም

**pistol** ሽጉጥ
He carried a pistol in his pocket. በኪሱ ፡ ሽጉጥ ፡ ይዞ ፡ ነበር

**pit**
1. ጉድጓድ. Joseph's brothers threw him in a pit. ዮሴፍን ፡ ወንድሞቹ ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ጣሉት
2. ፍሬ. Here's a peach, but don't swallow the pit! ኮክ ፡ ይኸውልህ ፤ ፍሬውን ፡ ግን ፡ አትዋጠው

**in the pit of** ውስጥ
He felt a strange feeling in the pit of his stomach. ሆዱ ፡ ውስጥ ፡ ልዩ ፡ ስሜት ፡ ተሰማው

**pitch** (vt.)
1. ወረወረ. Pitch the ball to me! ኳሱን ፡ ወርውርልኝ
2. ተከለ. Where shall we pitch the tent? ድንኳኑን ፡ የት ፡ እንትከለው ?

*He pitched his hopes too high. ሁሉን ፡ ነገር ፡ አገኛለሁ ፡ የሚል ፡ ተስፋ ፡ አደረበት

**pitch** (vi.) ኮራ
The roof pitches sharply. ጣሪያው ፡ በጣም ፡ ኮርቷል

**pitch (down)** ተደፋ
The man lost his balance and pitched down the cliff. ሰውዬው ፡ ሚዛኑን ፡ ስለሳተ ፡ ከዳገቱ ፡ ላይ ፡ ተደፋ

**pitch forward** ተደፋ
The man pitched forward on his face. ሰውየው ፡ ባፍ ፡ ጢሙ ፡ ተደፋ

**pitch in**
1. ረዳ. Pitch in and help us finish the work on time! ሥራውን ፡ በጊዜ ፡ እንድንጨርስ ፡ እርዳን
2. በረታ. If I really pitch in, I may be able to finish my book by tomorrow. ከበረታሁ ፡ መጽሐፌን ፡ ነገ ፡ እጨርስ ፡ ይሆናል
3. አዋጣ. When they took up a collection for the dinner party, he promised to pitch in. ለእራት ፡ ግብዣው ፡ መዋጮ ፡ ሲሰበስቡ ፡ ለማዋጣት ፡ ቃል ፡ ገባ

**pitch into** ጠመደ
The hungry boy pitched into the food piled on the table. የተራበው ፡ ልጅ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ የተቆለለውን ፡ ምግብ ፡ ጠመደው

**pitch** (n.)
1. ሙጫ. The farmers smear hides with pitch to make them waterproof. ገበሬዎች ፡ ቆዳው ፡ ውኃ ፡ እንዳይዘልቀው ፡ ሙጫ ፡ ይቀቡታል
2. ድምፅ. She sings in a high pitch. በቀጭን ፡ ድምፅ ፡ ታዜማለች

**be at high pitch** በጣም ፡ ከፍ ፡ አለ
Our excitement was at high pitch. ስሜታችን ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ነበር

**have a steep pitch** ዳገትነቱ ፡ ቀጥ ፡ አለ
Some roads in the mountains have a very steep pitch. በተራራው ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ አንዳንድ ፡ መንገዶች ፡ ዳገትነታቸው ፡ በጣም ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ነው

**pitch-black** በጣም ፡ ጨለማ
Since the road was pitch-black, he fell into a hole. መንገዱ ፡ በጣም ፡ ጨለማ ፡ ስለነበረ ፡ እጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ

**pitch-dark** ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ጨለማ
It was pitch-dark when we came home. ወደ ፡ ቤት ፡ ስንመጣ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ጨለማ ፡ ነበር

**pitcher**
1. ማንቆርቆሪያ. Please get me a pitcher of water! አንድ ፡ ማንቆርቆሪያ ፡ ውኃ ፡ አምጣልኝ
2. ኳስ ፡ አቀባይ. The pitcher hit him with the ball. ኳስ ፡ አቀባዩ ፡ ሰውየውን ፡ በኳስ ፡ መታው

**pitchfork** መንሽ
The pitchfork is one of the farmer's tools. መንሽ ፡ ከገበሬ ፡ መሣሪያዎች ፡ አንዱ ፡ ነው

**piteous** የሚያሳዝን
In the middle of the night, I heard piteous cries for help. እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ላይ ፡ የሚያሳዝን ፡ የ ድረሱልኝ ፡ ጩኸት ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ
*Starving children are a piteous sight. የተ ራቡት ፡ ልጆች ፡ ለሚያያቸው ፡ ያሳዝናሉ

**piteously** በሚያሳዝን ፡ ሁኔታ
The sheep bleated piteously. በጎቹ ፡ በሚያሳዝን ፡ ሁኔታ ፡ ባ ፡ አሉ

**pitfall** ዕንቅፋት
A person will encounter many pitfalls before reaching the desired goal. አንድ ፡ ሰው ፡ ከፈ ለገው ፡ ግብ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ዕን ቅፋት ፡ ያጋጥመዋል

**pitiful**
1. አሳዛኝ. When they found the lost child, he was in a pitiful condition. የጠፋው ፡ ልጅ ፡ ሲገኝ ፡ በአሳዛኝ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነበር
2. የማይረባ. He repaired my car in a pitiful way. መኪናዬን ፡ የጠገናት ፡ በማይረባ ፡ አኳኋን ፡ ነው

**(be) pitiless** ርኅራኄ ፡ የለውም
He is pitiless towards all lawbreakers. ሕግ ፡ ለሚያፈርሱ ፡ ሁሉ ፡ ርኅራኄ ፡ የለውም

**pity** (v.) አዘነ(ለት) ፤ ለ --- አዘነ
I pity you if you think you deserve to be helped. እርዳታ ፡ የሚያስፈልግህ ፡ መስሎ ፡ ከ ታየህ ፡ አዝንልሃለሁ
She pities any child who is hurt. ለተጐዳ ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ታዝናለች

**be pitied** ታዘነ(ለት)
She doesn't want to be pitied. እንዲታዘንላት ፡ አትፈልግም

**pity** (n.) ሐዘኔታ ፤ ርኅራኄ
He gave the beggar a few coins out of pity. ከሐዘኔታ ፡ የተነሣ ፡ ለለማኙ ፡ ጥቂት ፡ ፍራንክ ፡ ሰ ጠው
Pity is often akin to love. ርኅራኄ ፡ ብዙ ፡ ጊ ዜ ፡ ከመውደድ ፡ ጋር ፡ የተዛመደ ፡ ነው

**have pity on** አዘነ
He has pity on people less fortunate than himself. የሱን ፡ ያህል ፡ ላልታደሉ ፡ ሰዎች ፡ ያዝናል

**it's a pity** ያሳዝናል
It's a pity you can't come. ለመምጣት ፡ አለመ ቻልህ ፡ ያሳዝናል

**take pity on** አዘነ(ለት)
She took pity on him because he was so ill. በጣም ፡ ታሞ ፡ ስለነበር ፡ አዘነችለት

**what a pity** እንዴት ፡ ያሳዝናል
What a pity you could not go! ለመሄድ ፡ አለመ ቻልህ ፡ እንዴት ፡ ያሳዝናል

**pivot** (v.)
1. ተሽከረከረ. The earth pivots on its axis. መሬት ፡ በእንዝርቷ ፡ ላይ ፡ ትሽከረከራለች
2. ተመሠረተ. The arguments pivot on that point. ጉዳዩ ፡ እዚያ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ይመሠረታል
*John pivoted on his toe and faced me. ጆን ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ ፊቱን ፡ ወደኔ ፡ መለሰ

**pivot** (n.)
1. ማሽከርከሪያ. A swinging door turns on a pivot. ተወዛዋዥ ፡ መዝጊያ ፡ በማሽከርከሪያ ፡ ላ ይ ፡ ይዞራል
2. መሠረት. This point is the pivot of his argument. ይህ ፡ የክርክሩ ፡ መሠረት ፡ ነው

**placate** አባበለ
I tried to placate the angry woman with sweet words. የተናደደችውን ፡ ሴትዮ ፡ በለስላሳ ፡ አንደበ ት ፡ ለማባበል ፡ ሞከርኩ

**place** (v.)
1. አኖረ ፤ አስቀመጠ. He placed the book on the table. መጽሐፉን ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ አኖረ ፡ (አስ ቀመጠ)
2. መደበ. The President placed him in the Ministry of Education. ፕሬዚዳንቱ ፡ በትምህ ርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ መደበው
3. ቦታ ፡ አስያዘ. We have placed all of our graduates. ምሩቆቻችንን ፡ ሁሉ ፡ ቦታ ፡ አስይዘ ናል
4. ጣለ. The people placed confidence in their leader. ሕዝቡ ፡ እምነቱን ፡ በመሪው ፡ ላይ ፡ ጣለ
He placed the entire organization in my hands. ድርጅቱን ፡ በሙሉ ፡ እኔ ፡ ላይ ፡ ጣለ
5. ቦታው ፡ ትዝ ፡ አለ(ው). *I've met him before, but I can't place him. ከዚህ ፡ በፊት ፡ አግኝቼ ው ፡ ነበር ፤ ቦታው ፡ ግን ፡ ትዝ ፡ አይለኝም

6. ሆነ. He placed sixth in the race. በውድድሩ ፡ ስድስተኛ ፡ ሆነ

**be placed** ተደረገ
The table can be placed over there. ጠረጴዛው ፡ እዚያ ፡ ጋ ፡ ሊደረግ ፡ ይችላል
[See also 'ambush, command, credit, order']

**place** (n.)
1. ቦታ. Please put it back in the same place! ከነበረበት ፡ ቦታ ፡ መልሰው
Put yourself in my place! በኔ ፡ ቦታ ፡ ሆነህ ፡ እየው
Please take your places when the bell rings. ደወሉ ፡ ሲደውል ፡ በየቦታችሁ ፡ ተቀመጡ
2. ቤት. Please come and have dinner at my place! እቤቴ ፡ መጥተህ ፡ እራት ፡ ብላ
3. ተገቢ ፡ ቦታ. A café is not the place for an argument. ቡና ፡ ቤት ፡ ለክርክር ፡ ተገቢ ፡ ቦታ ፡ አይደለም
4. ሥራ. He lost his place at the bank. የባንክ ፡ ቤት ፡ ሥራውን ፡ ተነጠቀ
5. ሥልጣን. Who will take the place of the President when he dies? ፕሬዚዳንቱ ፡ ሲሞት ፡ ሥልጣኑን ፡ ማን ፡ ይይዛል ?
6. ተግባር. It is not my place to find fault. ስሕተት ፡ መልቀም ፡ የኔ ፡ ተግባር ፡ አይደለም
7. መኖሪያ. The Parkers have a beautiful place in the country. የሚስተር ፡ ፓርከር ፡ ቤተሰቦች ፡ ገጠር ፡ ውስጥ ፡ ጥሩ ፡ መኖሪያ ፡ አላቸው

**(be) in place**
1. ተገቢ ፡ ነው. Laughter is not in place in church. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ መሣቅ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም
2. ተዘጋጀ. Dinner is ready, and everything is in place. እራት ፡ ደርሷል ፤ እንዲሁም ፡ ማንኛቸውም ፡ ነገር ፡ ተዘጋጅቷል

**in (one's) place**
1. በሱ ፡ ምትክ. He couldn't go, so I went in his place. ሊሄድ ፡ ስላልቻለ ፡ በሱ ፡ ምትክ ፡ ሄድኩ
2. እሱን ፡ ቢሆን. I wouldn't have done it in his place. እሱን ፡ ብሆን ፡ አላደርገውም ፡ ነበር

**in place of** በ --- ፈንታ
May I have another book in place of this one? በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ሌላ ፡ መጽሐፍ ፡ ልወስድ ፡ እችላለሁ ?

**in the first place** አንደኛ ፡ ነገር
In the first place, we can't leave until tomorrow. አንደኛ ፡ ነገር ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ልንሄድ ፡ አንችልም

**know one's place** ደረጃውን ፡ ጠበቀ
They treated their servants well, but expected them always to know their place. አሽከሮቻቸውን ፡ በደንብ ፡ ይይዟቸዋል ፤ ሆኖም ፡ ደረጃቸውን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር

**(be) out of place**
1. አግባብ ፡ የለውም. Your remark is out of place. አስተያየትህ ፡ አግባብ ፡ የለውም
2. ተበታተነ. The chairs are out of place. ወንበሮቹ ፡ ተበታትነዋል

**put one in one's place** ልክ ፡ አገባ
Someone ought to put him in his place. አንድ ፡ ሰው ፡ ልክ ፡ ሊያገባው ፡ ያስፈልጋል

**take place**
1. ተደረገ. A great change has taken place in this country in the last twenty years. ባለፉት ፡ ሃያ ፡ ዓመታት ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ለውጥ ፡ ተደርጓል
2. ተፈጸመ ፤ ነው. The celebration took place yesterday. የበዓሉ ፡ አከባበር ፡ ትላንትና ፡ ተፈጸመ
When will the wedding take place? ሰርጉ ፡ መቼ ፡ ነው ?

**take the place of**
1. ተካ. Who will take the place of our boss when he is on vacation? አለቃችን ፡ ዕረፍት ፡ ሲሄድ ፡ ማን ፡ ይተካዋል ?
2. ዙፋኑን ፡ ወረሰ. The Crown Prince will take the place of the Emperor when he dies. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሲያርፉ ፡ ዙፋኑን ፡ አልጋ ፡ ወራሹ ፡ ይወርሳሉ
[See also 'any, first, second, setting']

**placement** አቀማመጥ
The placement of the furniture in the room has to be changed. የዚህ ፡ ክፍል ፡ የቤት ፡ እቃ ፡ አቀማመጥ ፡ መለወጥ ፡ አለበት

**placement office** መቅጠሪያ ፡ ቢሮ
The school has a placement office for students. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የተማሮች ፡ መቅጠሪያ ፡ ቢሮ ፡ አለው

**placenta** የእንግዴ ፡ ልጅ
In the villages, the placenta is buried in a certain spot. በገጠር ፡ ውስጥ ፡ የእንግዴ ፡ ልጅ ፡ በተወሰነ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ይቀበራል

**placid** ጸጥ ፡ ያለ
The lake is placid this afternoon. ዛሬ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ሐይቁ ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ነው

**have a placid expression** ረጋ
She has a placid expression, much like a cow's. እንደ ፡ ወተት ፡ የረጋች ፡ ናት

**plagiarize** የራሱ ፡ አስመሰሎ ፡ ቀዳ
He deliberately plagiarized from earlier books.

ሆነ ፡ ብሎ ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ ከተጻፉት ፡ መጻሕፍት ፡ የ ራሱ ፡ አስመስሎ ፡ ቀዳ

**plague** (v.)
1. አስጨነቀ. The child plagued his uncle with questions. ልጁ ፡ አጐቱን ፡ በጥያቄ ፡ አስጨነቀው
2. ወረሰ. Severe unemployment plagued the nation. ኀይለኛ ፡ የሥራ ፡ መታጣት ፡ አገሪቱን ፡ ወርሷታል

**be plagued**
1. ተሠቃየ. As a child, he was plagued with illness. ልጅ ፡ ሆኖ ፡ በሕመም ፡ ይሠቃይ ፡ ነበር
2. ተወረረ. The neighboring countries of Sudan and Kenya are plagued by locusts. ጐረቤቶቻችን ፡ ኬንያና ፡ ሱዳን ፡ በአንበጣ ፡ ተወረዋል

**plague** (n.) ወረርሽኝ ፤ መዓት
A plague almost depopulated Europe in the Middle Ages. በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ወረርሽኝ ፡ ያውሮፓን ፡ ሕዝብ ፡ ሊጨርሰው ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር
A plague of locusts devoured the crops. የአንበጣ ፡ መዓት ፡ እህሉን ፡ አወደመው

**plain** (n.) ሜዳ
Many people prefer the mountains to the plains. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከሜዳ ፡ ይልቅ ፡ ተራራ ፡ ይመርጣሉ

**plain** (adj.)
1. ተራ. We have a plain home in the country. በገጠር ፡ አንድ ፡ ተራ ፡ ቤት ፡ አለን
Poetic speech is harder to understand than plain speech. ከተራ ፡ ንግግር ፡ ይልቅ ፡ የረቀቀ ፡ ንግግር ፡ መረዳት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
They are plain people. ተራ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው
The food was plain but substantial. መብሉ ፡ ተራ ፡ ቢሆንም ፡ ምግብነት ፡ ያለው ፡ ነበር
2. ግልጽ. It's quite plain that he is after her money. ገንዘቧን ፡ መፈለጉ ፡ ግልጽ ፡ ነው
3. ፍጹም. It is plain stupidity to try to cross the desert without water. ውኃ ፡ ሳይዙ ፡ በረኻን ፡ ለማቋረጥ ፡ መሞከር ፡ ፍጹም ፡ ጅልነት ፡ ነው
4. ጉልህ. The printed numbers are very plain. የታተሙት ፡ ቁጥሮች ፡ በጣም ፡ ጉልህ ፡ ናቸው
5. ፍርጥ ፡ ያለው. I told him the plain truth. ፍርጥ ፡ ያለውን ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነገርኩት
6. ልሙጥ. Embroidery costs more than plain cloth. ጥልፍ ፡ ከልሙጥ ፡ ጨርቅ ፡ ይወደዳል
7. ጌጥ ፡ የሌለበት. He bought a plain necktie for two dollars. ጌጥ ፡ የሌለበት ፡ ክራቫት ፡ በሁለት ፡ ብር ፡ ገዛ
8. የማያምር. Girls who were plain in their childhood become pretty as they grow up. በልጅነታቸው ፡ የማያምሩ ፡ የነበሩት ፡ ልጃገረዶች ፡ እያደር ፡ ሲያድጉ ፡ መልክ ፡ ይገዛሉ
9. (= plainly) በጉልህ. That's in plain view. ይህ ፡ በጉልህ ፡ የሚታይ ፡ ነው
*To put it in plain language: you are a thief. እቅጩን ፡ ለመናገር ፤ ሌባ ፡ ነህ

**plain** (adv.) ፈጽሞ
He is just plain stupid. እሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ደደብ ፡ ነው

**make plain** በግልጽ ፡ አስረዳ
He made his meaning quite plain. ምን ፡ ማለቱ ፡ መሆኑን ፡ በግልጽ ፡ አስረዳ

**to be plain with you** እውነቱን ፡ ልንገርህ
To be plain with you, I cannot hire you for any job. እውነቱን ፡ ልንገርህ ፤ ለምንም ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ልቀጥርህ ፡ አልችልም

**plainclothesman** ነጭ ፡ ለባሽ
A plainclothesman caught the shoplifter. ነጭ ፡ ለባሽ ፡ የሱቁን ፡ ሌባ ፡ ያዘው

**plainest** ግልጽ
The warning was conceived in the plainest language. ማስጠንቀቂያው ፡ የተነገረው ፡ በግልጽ ፡ አነጋገር ፡ ነበር

**plainly**
1. በጉልህ. All the goods are plainly priced. የእቃው ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ በጉልህ ፡ ተጽፏል
2. በግልጽ. I thought they stated it plainly. በግልጽ ፡ የተናገሩ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር
Speak plainly; the people have difficulty understanding your words. በግልጽ ፡ ተናገር ፤ ሰዎች ፡ የምትለውን ፡ ለማዳመጥ ፡ ይቸገራሉ

**plain-spoken** የልቡን ፡ የሚናገር
A plain-spoken person has few friends. የልቡን ፡ የሚናገር ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ወዳጆች ፡ አይኖሩትም

**plaintiff** ከሳሽ
The plaintiff lost his case. ከሳሹ ፡ ተረታ

**plaintive, ~ song** የሐዘን ፡ እንጉርጉሮ
He sang a plaintive song. የሐዘን ፡ እንጉርጉሮ ፡ አዜመ

**plait** (v.) ጐነጐነ
The mother plaited the girl's hair. እናትዮዋ ፡ የልጂን ፡ ጸጉር ፡ ጐነጐነችላት

**plait** (n.) የጸጉር ፡ ጉንጉን
A long plait was hanging down the girl's back.

ረዥም ፡ የጸጉር ፡ ጉንጉን ፡ ልጅቷ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ተንዠርግጎ ፡ ነበር

**plan** (planned), v.
1. አቀደ. We planned our trip carefully. ጉዞዋችንን ፡ በጥንቃቄ ፡ አቀድን
2. መደበ. He doesn't know how to plan his time. ጊዜውን ፡ መመደብ ፡ አይችልም
3. አሰበ. Where do you plan to spend the summer? በጋውን ፡ የት ፡ ለማሳለፍ ፡ ታስባለህ ?
4. ንድፍ ፡ አወጣ ፤ ነደፈ. An architect is planning their new house. መሀንዲስ ፡ ያዲሱን ፡ ቤታቸውን ፡ ንድፍ ፡ በማውጣት ፡ ላይ ፡ ነው
The architect planned the building in a new style. መሀንዲሱ ፡ ሕንጻውን ፡ የነደፈው ፡ ባዲስ ፡ መልክ ፡ ነው

**plan** (n.)
1. ፕላን. The plans for the new house are ready. ያዲሱ ፡ ቤት ፡ ፕላን ፡ ተዘጋጅቷል
The third five-year development plan was approved by parliament. ሦስተኛውን ፡ ያምስት ፡ ዓመት ፡ የልማት ፡ ፕላን ፡ ፓርላማው ፡ ተቀበለው
2. እቅድ. Our plans were discovered by the enemy. እቅዳችንን ፡ ጠላት ፡ ደረሰበት
3. ምኞት ፤ ሐሳብ. She has ambitious plans for her husband. ባሏ ፡ ከትልቅ ፡ ቦታ ፡ እንዲደርስ ፡ ከፍተኛ ፡ ምኞት ፡ አላት
She has very ambitious plans; she wants to become the supervisor of the department. ሐሳቧ ፡ ትልቅ ፡ ነው ፤ የክፍሉ ፡ ተቈጣጣሪ ፡ መሆን ፡ ትፈልጋለች

**according to plan** እንደታቀደ
Everything went according to plan. ሁሉም ፡ ነገር ፡ እንደታቀደው ፡ ሆነ

**make plans** አቀደ
Have you made any plans yet for the future? ለወደፊቱ ፡ ያቀድከው ፡ ነገር ፡ አለ ?
[See also 'devise, master']

**plane** (v.) ላገ
The carpenter planed the board. አናጢው ፡ ሳንቃውን ፡ ላገ

**plane** (n.)
1. አውሮፕላን. This plane flies to Athens. ይህ ፡ አውሮፕላን ፡ ወደ ፡ አቴን ፡ ይበራል
2. ደረጃ. The discussion was not on a very high plane. ውይይቱ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ደረጃ ፡ አልነበረም
3. መላጊያ. I need a plane to fix the door. በሩን ፡ ለመግጠም ፡ መላጊያ ፡ ያስፈልገኛል

**plane** (adj.) ዝርግ
The lines intersect on a plane surface. መሥመሮቹ ፡ በዝርግ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ይተላለፋሉ

**planet** ዓለም
The sun has nine planets in its system. ፀሐይ ፡ በዙሪያዋ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓለማት ፡ አሏት

**plank** ሳንቃ
The floor is made of rough planks. ወለሉ ፡ ከሸካራ ፡ ሳንቃ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**plant** (v.)
1. ተከለ. We planted flowers in our garden. አትክልት ፡ ስፍራችን ፡ ውስጥ ፡ አበባ ፡ ተከልን
2. ዘራ. They planted wheat. ስንዴ ፡ ዘሩ
3. ቸከለ. The workers planted posts along the road. ሠራተኞቹ ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ችካል ፡ ቸከሉ
4. አቆመ. During the demonstration, they planted policeman on every street. በሰላማዊ ፡ ሰልፉ ፡ ጊዜ ፡ በየመንገዱ ፡ ፖሊስ ፡ አቆሙ
5. አሳደረ(በት). His answer planted a doubt in my mind. መልሱ ፡ አእምሮዬ ፡ ውስጥ ፡ ጥርጣሬ ፡ አሳደረብኝ
The leader planted new ideas among his people. መሪው ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ አዳዲስ ፡ ሐሳቦችን ፡ አሳደረባቸው
*He planted his feet firmly on the ground and refused to move. ተንፈራጦ ፡ ቆሞ ፡ አልንቀሳቀስም ፡ አለ

**plant** (n.)
1. ዕፅ (pl. ዕፀዋት). Various kinds of plants have been imported to Ethiopia. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕፀዋት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲመጡ ፡ ተደርጓል
2. ፋብሪካ. The manager showed me around the plant. አስተዳዳሪው ፡ ፋብሪካውን ፡ አዞሮ ፡ አስጐበኘኝ
3. ድርጅት. The school has a fine plant, but not enough teachers. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ጥሩ ፡ ድርጅት ፡ አለው ፤ ግን ፡ በቂ ፡ አስተማሪዎች ፡ የሉትም

**plantation** እርሻ
There are many false banana plantations in the South. በደቡብ ፡ ክፍል ፡ የእንሰት ፡ እርሻ ፡ በብዛት ፡ አለ

**planter** ባለመሬት
George Washington was a wealthy planter. ጆርጅ ፡ ዋሽንግቶን ፡ ሀብታም ፡ ባለመሬት ፡ ነበር

**plaster** (v.) ለሰነ
Have they finished plastering the walls yet? ግድግዳውን ፡ መለሰን ፡ ገና ፡ አልጨረሱም ?

**plaster** (n). ልስን
The plaster on the wall is all cracked. የግድግዳው ፡ ልስን ፡ በሙሉ ፡ ተሰነጣጥቋል

**lay on a coat of plaster**
The man laid on a coat of plaster. ሰውዬው ፡ ግድግዳውን ፡ ለሰነው
[See also 'cast']

**plastic** ፕላስቲክ
Many household articles are made of plastic. ብዙ ፡ የቤት ፡ እቃዎች ፡ ከፕላስቲክ ፡ ይሠራሉ

**plate** (v.) ነከረ
The goldsmith plated the cross with gold. ወርቅ ፡ አንጣሪው ፡ መስቀሉን ፡ ወርቅ ፡ ነከረው

**plate** (n.)
1. ሥዕል. The book has four hundred pages and twelve plates. መጽሐፉ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ገጾችና ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሥዕሎች ፡ አሉት
2. ሳሕን. She bought three soup plates. ሦስት ፡ የሾርባ ፡ ሳሕን ፡ ገዛች
3. ምሳ. You can get lunch in this restaurant at a dollar a plate. እዚህ ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ምሳ ፡ ባንድ ፡ ብር ፡ ታገኛለህ
4. ቆርቆሮ. The warship was covered with steel plates. የጦሩ ፡ መርከብ ፡ ከዐረብ ፡ ብረት ፡ በተሠሩ ፡ ቆርቆሮዎች ፡ የተለበደ ፡ ነው
*The banquet costs $25 a plate. ግብዣው ፡ በነፍስ ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ይከፈልበታል

**plateau** አምባ
A plateau covers the northern part of Ethiopia. ሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ አምባ ፡ የበዛበት ፡ ነው

**plated** ቅብ
This watch is plated with gold. ይህ ፡ ሰዓት ፡ የወርቅ ፡ ቅብ ፡ ነው
[See also 'silver']

**platform**
1. መድረክ. The speakers were seated on the platform. ተናጋሪዎቹ ፡ ከመድረኩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር
2. መምሪያ. The platform of the new political party demands lower taxes. ያዲሱ ፡ የፖለቲካ ፡ ቡድን ፡ መምሪያ ፡ ግብር ፡ እንዲቀነስ ፡ ነው

**platoon** የመቶ
The platoon was attacked by enemy soldiers. የመቶው ፡ በጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ተጠቃ

**platter** ዝርግ ፡ ሳሕን
The roast lamb was served on a platter. አንድ ፡ የተጠበሰ ፡ በግ ፡ በዝርግ ፡ ሳሕን ፡ ቀረበ

**(be) plausible** እውነት ፡ ይመስላል
His excuse is plausible, but I don't really believe it. ምክንያቱ ፡ እውነት ፡ ይመስላል ፡ ግን ፡ አላመንኩትም

**play** (vt.)
1. ተጫወተ. The children played store. ልጆቹ ፡ ገበርና ፡ ነጋዴ ፡ ሆነው ፡ ተጫወቱ
We played cards for money. በገንዘብ ፡ ካርታ ፡ ተጫወትን
He plays the piano. ፒያኖ ፡ ይጫወታል
He played the title role in Hamlet. በሃምሌት ፡ ውስጥ ፡ መሪውን ፡ ቦታ ፡ ይዞ ፡ ተጫወተ
2. መታ. He plays the drum. ከበሮ ፡ ይመታል
He plays the violin very well. ማሲንቆ ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ ይመታል
3. ነፋ. He plays the trumpet. ጥሩምባ ፡ ይነፋል
He plays the flute. ዋሽንት ፡ ይነፋል
4. ደረደረ. He plays the harp. በገና ፡ ይደረድራል
5. ሠራ. He played Othello last night. ትላንትና ፡ ማታ ፡ ኦቴሎን ፡ ሆኖ ፡ ሠራ
You shouldn't play tricks. ተንኰል ፡ አትሥራ

**play** (vi.)
1. ተጫወተ. The children are playing in the garden. ልጆቹ ፡ ባትክልት ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ ይጫወታሉ
The orchestra played brilliantly. የሙዚቃ ፡ ጓዱ ፡ አሳምሮ ፡ ተጫወተ
2. ታየ. What is playing at the movies tonight? ዛሬ ፡ ሲኒማ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚታየው ፡ ምንድነው ?
A smile played across her face. በፊቷ ፡ ላይ ፡ ፈገግታ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**play around** ማገጠ
You have been playing around long enough. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስትማግጥ ፡ ነበር

**play at** ቀለደ
She is merely playing at being a student. ተማሪ ፡ ሆና ፡ ትቀልዳለች

**play down** አነስተኛ ፡ ግምት ፡ ሰጠ
The newspaper played down the clash. ጋዜጣው ፡ ለግጭቱ ፡ አነስተኛ ፡ ግምት ፡ ሰጠው

**play fair** እንደሚገባው ፡ አየ
He doesn't play fair with anyone. ማንንም ፡ ሰው ፡ እንደሚገባው ፡ አያይም

**play for time** ጊዜ ፡ ለማግኘት
Their maneuvering at the conference was a play for time. በስብሰባው ፡ ጊዜ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ማለታቸው ፡ ጊዜ ፡ ለማግኘት ፡ ነው

**play (a) great role** ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥረት ፡ አደረገ
The director played a great role in improving education. ትምህርትን ፡ ለማሻሻል ፡ ሥራ ፡ መሪው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥረት ፡ አድርገዋል

**play into (one's) hands**
*The candidate play into his opponent's hands. እጩው ፡ በተወዳዳሪው ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ የሚጥለውን ፡ ተግባር ፡ ፈጸመ

**play off** አጋጨ
The director plays off his secretaries against each other. ሥራ ፡ መሪው ፡ ጸሐፊዎቹን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ያጋጫቸዋል

**play out** ጨረሰ
Let's play out this game! ይህንን ፡ ጨዋታ ፡ እንጨርስ

**play up** በማጋነን + verb
The newspapers played up the incident as something serious. ጋዜጦች ፡ የተደረገውን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ በማጋነን ፡ ጻፉት

**play with the idea** አወጣ ፡ አወረደ
He was playing with the idea of going to Ethiopia. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመሄድ ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ነበር
[See also 'havoc, joke, part, trick']

**play** (n.)
1. ጨዋታ. The children are completely absorbed in their play. ልጆቹ ፡ በጨዋታቸው ፡ በፍጹም ፡ ተመስጠዋል
2. ቲያትር. Are there any good plays in town? ከተማው ፡ ውስጥ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ቲያትሮች ፡ አሉ ?
3. ቀልድ. He just said it in play. ያለው ፡ እንዲያው ፡ ለቀልድ ፡ ነው
*It's your play next. ያንተ ፡ ተራ ፡ ነው

**play on words** ሰምና ፡ ወርቅ ፤ ባማርኛ ፡ መናገር
This poem is mostly a play on words. ይህ ፡ ግጥም ፡ የተጻፈው ፡ በይበልጥ ፡ በሰምና ፡ ወርቅ ፡ ነው
Some people are fond of plays on words. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ባማርኛ ፡ መናገር ፡ ይወዳሉ

**be brought into play** ቀረበ
New evidence has been brought into play in this trial. በዚህ ፡ ነገር ፡ አዲስ ፡ ማስረጃ ፡ ቀርቧል

**come into play** በየጊዜው ፡ ተነሣ
Certain forces come into play to complicate the situation even more. ሁኔታውን ፡ የባሰ ፡ እስቸጋሪ ፡ ለማድረግ ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ በየጊዜው ፡ ይነሣሉ

**put on a play** ቲያትር ፡ አሳየ
The students are putting on a play. ተማሪዎቹ ፡ ቲያትር ፡ ያሳያሉ
[See also 'dirty, foul, word']

**player** ተጫዋች
One of the players got hurt during the game. ከተጫዋቾቹ ፡ አንዱ ፡ በጨዋታው ፡ ጊዜ ፡ ተጐዳ
[See also 'harp']

**playful** ተጫዋች
The children laughed at the playful puppy. ልጆቹ ፡ በተጫዋቹ ፡ ቡችላ ፡ ሣቁ

**playground** የመጫወቻ ፡ ስፍራ
There are no playgrounds in this city. በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ የመጫወቻ ፡ ስፍራዎች ፡ የሉም

**playing card** የመጫወቻ ፡ ካርታ
I don't have any playing cards. ምንም ፡ የመጫወቻ ፡ ካርታ ፡ የለኝም

**playmate** ጓደኛ
My child and his are playmates. ልጄና ፡ ልጁ ፡ ጓደኞች ፡ ናቸው

**plaything** መጫወቻ
The child left its playthings scattered about. ልጁ ፡ መጫወቻዎቹን ፡ እንደ ፡ ተበታተኑ ፡ ተዋቸው

**playwright** የቲያትር ፡ ደራሲ
The playwright received no money for his play. የቲያትሩ ፡ ደራሲ ፡ ለቲያትሩ ፡ ገንዘብ ፡ አልተቀበለም

**plea**
1. ልመና. He ignored my plea. ልመናዬን ፡ ችላ ፡ አለ
2. ጥያቄ. The judge rejected his plea for a stay. ቀጠሮው ፡ እንዲራዘምለት ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ዳኛው ፡ አልተቀበሉትም
3. ምክንያት. Illness was his plea for being absent. ለመቅረቱ ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ የሰጠው ፡ መታመሙን ፡ ነበር

**enter a plea**
*He entered a plea of guilty. ጥፋተኛ ፡ ነኝ ፡ አለ

*He entered a plea of bankruptcy. መክሰሩን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስታወቀ

**make a plea** ለመነ
The mother made a fervent plea to the judge to spare her son. እናቲቱ ፡ ዳኛው ፡ ልጇን ፡ እንዲያተርፍላት ፡ ልብ ፡ በሚነካ ፡ ሁኔታ ፡ ለመነች

**plead**
1. ተሟገተ. He pleaded his case without a lawyer. ጠበቃ ፡ ሳያቆም ፡ ተሟገተ
2. ለመነ. When the rent was due, the poor man pleaded for more time. ኪራይ ፡ መክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ድኻው ፡ ሰው ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመነ
3. ልመና ፡ አቀረበ ፤ አቤቱታ ፡ አቀረበ. The prisoner pleaded for his liberty. እስረኛው ፡ በነጻ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ልመና ፡ (አቤቱታ) ፡ አቀረበ
4. እንደ ፡ ምክንያት ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረበ. The criminal pleaded insanity. ወንጀለኛው ፡ አንጐሉ ፡ መታወኩን ፡ እንደ ፡ ምክንያት ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረበ
5. ምክንያት ፡ ሰጠ. He pleaded poverty when caught stealing. ሲሰርቅ ፡ ቢያዝ ፡ በድኽነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ምክንያት ፡ ሰጠ

**plead guilty** ጥፋተኛነትን ፡ አመነ
Do you plead guilty to the charge of murder? በነፍስ ፡ ገዳይነት ፡ ለቀረበብህ ፡ ክስ ፡ ጥፋተኛ ነትህን ፡ ታምናለህ ?

**plead with** ለመነ
She pleaded with him not to go. እንዳይሄድ ፡ ለመነችው

**pleasant**
1. ደስ ፡ የሚል. She is a pleasant person. ደስ ፡ የምትል ፡ ሰው ፡ ነች
2. የሚያስደስት. After a long march, soaking one's foot in warm water is a very pleasant sensation. ከረዥም ፡ ጉዞ ፡ በኋላ ፡ እግርን ፡ ሙቅ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ መዘፍዘፍ ፡ በጣም ፡ የሚያስደስት ፡ ስሜት ፡ ይሰጣል
*Goodbye, have a pleasant trip! ደኅና ፡ ግባ ፡ (or, መንገዱን ፡ ጨርቅ ፡ ያድርግልህ)

**be pleasant for** ደስ ፡ አለው
It will be pleasant for her to have news of her family. ስለ ፡ ቤተሰቦቿ ፡ ወሬ ፡ ብትሰማ ፡ ደስ ፡ ይላታል

**pleasantry** (pleasantries) የቀልድ ፡ አነጋገር
The workers smiled at the minister's pleasantries. በሚኒስትሩ ፡ የቀልድ ፡ አነጋገር ፡ ሠራተኞቹ ፡ ፈገግ ፡ አሉ

**please** (vt.)
1. አስደሰተ ፤ ደስ ፡ አሰኘ. You can't please everybody. ሁሉንም ፡ ማስደሰት ፡ (ደስ ፡ ማሰኘት) ፡ አይቻልም
2. የ - - መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ነበር. It pleased the king to go. መሄድ ፡ የንጉሡ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ነበር
*Go where you please! እፈለግህበት ፡ ሂድ
*Take as many cookies as you please! የፈለግኸውን ፡ ያህል ፡ ብስኩት ፡ ውሰድ

**please!**
1. እባክህ. Please shut the door! እባክህ ፡ መዝጊያውን ፡ ዝጋ
2. (jussive). Come in, please! ይግቡ

**be pleased** ደስ ፡ አለ(ው)
+I am pleased to see he is working again. እንደገና ፡ ሥራ ፡ በመግባቱ ፡ ደስ ፡ አለኝ

**as I (you, he) please**
1. የፈለግሁትን. I shall do as I please with my money. በገንዘቤ ፡ የፈለግሁትን ፡ አደርጋለሁ
2. እንደልቡ. You may come in and go out as you please. እንደልብህ ፡ ልትገባና ፡ ልትወጣ ፡ ትችላለህ

**do as you please** እንዳሰኘህ ፤ እንደተመቸህ
Should I come tomorrow or the day after tomorrow? Do as you please. ነገ ፡ ልምጣ ፡ ተነገ ፡ ወዲያ ? እንዳሰኘህ ፡ (እንደተመቸህ)

**if you please** ፈቃድህ ፡ ቢሆን
And now, if you please, I will read you the contract. አሁን ፡ ፈቃድህ ፡ ቢሆን ፡ ውሉን ፡ አነብልሃለሁ

**look pleased** ደስ ፡ የተሰኘ ፡ መስሎ ፡ ታየ
He looked very pleased with himself when he got the award. ሽልማቱን ፡ ሲያገኝ ፡ በራሱ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የተሰኘ ፡ መስሎ ፡ ታየ

**pleasing** የሚያስደስት
She has a very pleasing voice. በጣም ፡ የሚያስደስት ፡ ድምፅ ፡ አላት

**be pleasing** አስደሰተ
The flowery meadow was pleasing to the eye. በአበባ ፡ ያሸበረቀው ፡ መስክ ፡ ለዓይን ፡ ያስደስት ፡ ነበር

**pleasure** (v.) ደስ ፡ አለ(ው)
+I pleasure in your company. ካንተ ፡ ጋር ፡ መሆን ፡ ደስ ፡ ይለኛል

**pleasure** (n.)
1. ደስታ. He never combines business with pleasure. እሱ ፡ ከቶ ፡ ሥራን ፡ ከደስታ ፡ ጋር ፡ አያጣምርም

2. መደሰት. He alternates work with pleasure. መሥራትና ፡ መደሰትን ፡ ያፈራርቃል
3. የሚያስደስት ፡ ነገር. It is a pleasure to hear her sing. ስትዘፍን ፡ መስማት ፡ የሚያስደስት ፡ ነገር ፡ ነው
4. መልካም ፡ ፈቃድ. Is it your pleasure to go now? አሁን ፡ ለመሄድ ፡ መልካም ፡ ፈቃድዎ ፡ ነው ?
*For dessert, what is your pleasure? ለማጣጣሚያ ፡ ምን ፡ ትፈቅዳለህ ?

**afford pleasure** ደስ ፡ አሰኘ
The movie afforded pleasure to all who saw it. ፊልሙ ፡ ያየውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አሰኘ

**find pleasure** ደስ ፡ አለ(ው)
Do you find much pleasure in farming? በማብርና ፡ ብዙ ፡ ደስ ፡ ይልሃል ?

**take pleasure** ተደሰተ
Some boys take pleasure in teasing their sisters. አንዳንድ ፡ ልጆች ፡ በእኅቶቻቸው ፡ በማሾፍ ፡ ይደሰታሉ

**pleat** (v.) ሸነሸነ
It takes a lot of effort to pleat a skirt properly. ጉርድ ፡ ቀሚስን ፡ በሚገባ ፡ ለመሸንሸን ፡ ብዙ ፡ ጥረት ፡ ይጠይቃል

**pleat** (n.) ሽንሽን
Her skirt has many pleats in it. ቀሚሷ ፡ ብዙ ፡ ሽንሽን ፡ አለው

**pledge** (v.)
1. ቃል ፡ ገባ. He pledged $100 in the campaign to raise money for the new church. ላዲሱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገንዘብ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ለሚደረገው ፡ ጥረት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመስጠት ፡ ቃል ፡ ገባ
We pledge loyalty to our country. ለሀገራችን ፡ ታማኝ ፡ ለመሆን ፡ ቃል ፡ ገብተናል
2. ቃል ፡ አስገባ. The speaker pledged the hearers to secrecy. ተናጋሪው ፡ አዳማጮቹ ፡ ንግግሩን ፡ በምስጢር ፡ እንዲይዙ ፡ ቃል ፡ አስገባቸው

**pledge allegiance** የመሐላ ፡ ቃል ፡ ገባ ፤ ታማኝነትን ፡ ገለጸ
In America, students pledge allegiance to the flag every morning. የአሜሪካ ፡ ተማሪዎች ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ለሰንደቅ ፡ ዓላማቸው ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ ይገባሉ ፡ (ያላቸውን ፡ ታማኝነት ፡ ይገልጻሉ)

**pledge as a security** መያዣ ፡ አደረገ
He pledged his house as a security for the loan. ቤቱን ፡ ለብድሩ ፡ መያዣ ፡ አደረገው

**pledge** (n.)
1. ቃል ፡ መግባት. Their pledge not to wage war was not believed by anyone. ጦር ፡ አናነሣም ፡ ሲሉ ፡ ቃል ፡ መግባታቸውን ፡ ማንም ፡ አላመነም
2. ማስታወሻ. He gave her a ring as a pledge of his love. ለፍቅሩ ፡ ማስታወሻ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ቀለበት ፡ ሰጣት
3. ማረጋገጫ. We shook hands as a pledge of friendship. ለጓደኝነታችን ፡ ማረጋገጫ ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተጨባበጥን
4. መያዣ. He left his mule as pledge for the borrowed horse. ለተዋሰው ፡ ፈረስ ፡ መያዣ ፡ እንድትሆን ፡ በቅሎውን ፡ ሰጠ

**pledge of allegiance** ቃለ ፡ መሐላ
The new recruits recited the pledge of allegiance. አዲስ ፡ ቅጥሮቹ ፡ ቃለ ፡ መሐላ ፡ ገቡ

**be under the pledge** ቃል ፡ ገባ ፤ ግዴታ ፡ አለበት
He is under the pledge of secrecy as long as he works for the government. በመንግሥት ፡ አገልግሎት ፡ ውስጥ ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ ምስጢር ፡ ላያወጣ ፡ ቃል ፡ ገብቷል ፡ (ግዴታ ፡ አለበት)

**take the pledge** ቃል ፡ ገባ
The President takes a pledge to defend the constitution. ፕሬዚዳንቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ለመጠበቅ ፡ ቃል ፡ ይገባል

**sign a pledge** በፊርማ ፡ ቃል ፡ ገባ
Mr. Parker signed a pledge to give $50 to charity. ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ችሮታ ፡ ለመስጠት ፡ በፊርማ ፡ ቃል ፡ ገባ

**plenary** ሙሉ
In America, the parliament has plenary power. በአሜሪካ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አለው

**plenary session**
*The parliament is in plenary session. የምክር ፡ ቤቱ ፡ ሙሉ ፡ ስብሰባ ፡ ሁሉም ፡ እንደራሴዎች ፡ በተገኙበት ፡ ተደረገ

**plenipotentiary** (plenipotentiaries) ባለሙሉ ፡ ሥልጣን
He was minister and envoy plenipotentiary to Sweden in 1908. በ፲፱፻፩ ፡ ዓ. ም. በስዊድን ፡ ሀገር ፡ ሚኒስትርና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ መልእክተኛ ፡ ነበሩ

**plenitude** መዓት
There is a plenitude of flies in the market. ገበያው ፡ ውስጥ ፡ የዝምብ ፡ መዓት ፡ አለ

**plenteous** (= n.) መብዛት
A plenteous crop means happiness for the farmers. የሰብል ፡ መብዛት ፡ ለገበሬዎች ፡ ደስታ ፡ ነው

**plenteous supply of** በብዛት
There is usually a plenteous supply of raw materials. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጥሬ ፡ እቃ ፡ በብዛት ፡ ይገኛል

**plentiful, ~ supply of** ብዙ
We have a plentiful supply of grain. ብዙ ፡ እህል ፡ አለን

**be plentiful** ሞላ
Deer are plentiful in this area. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ አጋዘን ፡ ሞልቷል

**plenty** ጥጋብ
These are years of peace and plenty. እነዚህ ፡ የሰላምና ፡ የጥጋብ ፡ ዓመታት ፡ ናቸው

**plenty of** ብዙ ፤ በብዛት
There was plenty of food and drink at the party. በግብዣው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ ነበር
We have plenty of time before the plane leaves. አውሮፕላኑ ፡ ከመነሣቱ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አለን
She has plenty of dresses. ልብስ ፡ በብዛት ፡ አላት

**be plenty** በቃ
Six potatoes will be plenty. ስድስት ፡ ድንች ፡ ይበቃል

**have plenty** ሞላ(ው)
+We had plenty to eat. የሚበላ ፡ ሞልቶን ፡ ነበር

**in plenty of time** ቀደም ፡ ብሎ
We must get to the station in plenty of time. ጣቢያው ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ መድረስ ፡ አለብን

**pleurisy** የሳምባ ፡ በሽታ
He has pleurisy and doesn't leave the house. የሳምባ ፡ በሽታ ፡ ስለያዘው ፡ ከቤት ፡ አይወጣም

**pliable** ሊተጣጠፍ ፡ የሚችል
This wire is pliable. ይህ ፡ ሽቦ ፡ ሊተጣጠፍ ፡ የሚችል ፡ ነው

**pliant**
1. የሚተጣጠፍ. Pliant vines are woven into mats. የሚተጣጠፈው ፡ ሐረግ ፡ ሰሌን ፡ ይሠራበታል
2. ተወዛዋዥ. Children were swinging on the tree's pliant branches. ልጆች ፡ በዛፉ ፡ ተወዛዋዥ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ላይ ፡ ይንጠላጠሉ ፡ ነበር
3. ተለማጭ. He manipulated the pliant twig. ተለማጭ ፡ ቅርንጫፍ ፡ እንደልቡ ፡ ያደርገው ፡ ነበር
4. የመስሎ ፡ አደር. His pliant behavior saved him from the soldiers' arrogance. የመስሎ ፡ አደር ፡ ጠባዩ ፡ ከወታደሮች ፡ ትዕቢተኛነት ፡ አዳነው
*He has a pliant nature and does what others tell him. በሰው ፡ ሐሳብ ፡ ስለሚመራ ፡ የነገሩትን ፡ ያደርጋል

**pliers** ጉጠት
I need pliers to take off the bolt. መቀርቀሪያውን ፡ ለመንቀል ፡ ጉጠት ፡ ያስፈልገኛል

**plight** መከራ
The plight of the refugees was sad to see. የስደተኞቹን ፡ መከራ ፡ ማየት ፡ አሳዛኝ ፡ ነበር

**plod** (plodded), **~ along**
1. አዘገመ. The weary soldier was plodding along the side of the road. የደከመው ፡ ወታደር ፡ የመንገዱን ፡ ዳር ፡ ይዞ ፡ ያዘግም ፡ ነበር
2. ለገመ. He just plods along at his job. በሥራው ፡ ላይ ፡ ይለግማል

**plod away** መላልሶ ፡ አጠና
He plods away at his lessons until he learns them. ትምህርቱ ፡ እስኪገባው ፡ ድረስ ፡ መላልሶ ፡ ያጠናል

**plod past** እያዘገመ ፡ አለፈ
The prisoners plodded past. እስረኞቹ ፡ እያዘገሙ ፡ አለፉ

**plot** (plotted), v. አደመ ፤ አሴረ
They plotted against the director of the prison. በእስር ፡ ቤት ፡ አለቃው ፡ ላይ ፡ አደሙ
The imperialists are plotting against him. ኢምፔሪያሊስቶች ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ያሴራሉ

**plot** (n.)
1. አድማ. He was involved in a plot to kill the director. ዲሬክተሩን ፡ ለመግደል ፡ በተደረገው ፡ አድማ ፡ ገብቶ ፡ ነበር
2. ቁራጭ. He bought a plot of land in the city. ከከተማው ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ቁራጭ ፡ መሬት ፡ ገዛ
3. ታሪክ. The film has an interesting plot. የፊልሙ ፡ ታሪክ ፡ አስደናቂ ፡ ነው

**plotter** ሴረኛ ፤ አድመኛ
The plotter was executed by the soldiers. ሴረኛው ፡ (አድመኛው) ፡ በወታደሮች ፡ ተገደለ

**plow** (vt.) አረሰ
I will need all day to plow this field. ይህን ፡ ማሳ ፡ ለማረስ ፡ሙሉ ፡ ቀን ፡ ይፈጅብኛል

**plow through** ሰንጥቆ ፡ ተጓዘ
The ship plowed through the rough seas. መርከቡ ፡ ማዕበሉን ፡ ሰንጥቆ ፡ ተጓዘ

**plow (one's) way** እየተጋፋ ፡ አለፈ
He plowed his way through the crowd. በሕዝብ ፡ መካከል ፡ እየተጋፋ ፡ አለፈ

**plow** (n.) ማረሻ
The farmer's plow broke on a stone. የገበሬውን ፡ ማረሻ ፡ ድንጋይ ፡ ሰበረበት

**pluck**
1. ነጨ. Did you pluck the chickens yet? ዶሮዎቹን ፡ ነጭተሻቸዋል ?
2. ቀጠፈ. He plucked an apple from a tree. ከዛፍ ፡ ላይ ፡ ቱፋ ፡ ቀጠፈ
3. ነቀለ. She spent the day plucking weeds. ቀኑን ፡ ያሳለፈችው ፡ አረም ፡ በመንቀል ፡ ነው
4. መታ. He plucked the strings of the harp to test the sound. ድምፁን ፡ ለመፈተን ፡ የበገናውን ፡ አውታር ፡ መታ

**pluck at** ሳብ ፡ ሳብ ፡ አደረገ
He plucked at my sleeve to get my attention. ወደ ፡ እሱ ፡ ዞር ፡ እንድል ፡ የኮቴን ፡ እጅጌ ፡ ሳብ ፡ ሳብ ፡ አደረገው
[See also 'string']

**plug** (plugged), v.
1. ወተፈ. He plugged the leak with a rag. የሚያፈሰውን ፡ ቀዳዳ ፡ ጨርቅ ፡ ወተፈው
2. ሰካ. Plug the lamp into the socket! መብራቱን ፡ መሰኪያው ፡ ውስጥ ፡ ሰካው

**plug in** ሰካ
Where is an outlet so I can plug in the radio? ሬዲዮኑን ፡ እንድሰካው ፡ የኮረንቲ ፡ መሰኪያው ፡ የት ፡ ነው ?

**plug up** ደፈነ
Give me some plaster to plug up this crevice! ይህን ፡ የግድግዳውን ፡ ስንጥቅ ፡ የምደፍንበት ፡ ጭቃ ፡ ስጠኝ

**plug** (n.)
1. ውታፍ. He took the plug out of the tub. ከመታጠቢያው ፡ ገንዳ ፡ ውስጥ ፡ ውታፉን ፡ ነቀለው
2. የኮረንቲ ፡ መሰኪያ. The radio went off because you pulled the plug out. የኮረንቲውን ፡ መሰኪያ ፡ ስለነቀልከው ፡ ሬዲዮኑ ፡ ጠፋ

**plumb** (v.) ገመድ ፡ ሰደደ
They plumbed the depths of the lake to find out how deep it was. የሐይቁን ፡ ጥልቀት ፡ ለመለካት ፡ ገመድ ፡ ሰደዱ

**plumb** (n.), ~ **line** ቱንቢ
The mason used a plumb line to keep the wall straight. ግንበኛው ፡ ግድግዳውን ፡ ቀጥ ፡ አድርጎ ፡ ለመሥራት ፡ በቱንቢ ፡ ተጠቀመ

**be out of plumb** ዘመመ
The wall is out of plumb. ግድግዳው ፡ ዘሟል

**plumber** ቧምቧ ፡ ሠራተኛ
Call the plumber; the water is leaking from the pipe. ቧምቧው ፡ ውኃ ፡ ስለሚያፈስ ፡ ቧምቧ ፡ ሠራተኛውን ፡ ጥራ

**plumbing** የቧምቧ ፡ ሥራ
The plumbing of the new house is up-to-date. ያዲሱ ፡ ቤት ፡ የቧምቧ ፡ ሥራ ፡ ዘመናዊ ፡ ነው

**plummet**
1. [ገመድ ፡ ወይም ፡ ሽቦ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ታስሮ ፡ የባሕር ፡ ርቀት ፡ የሚለካበት ፡ የብረት ፡ አሎሎ]
2. ቱንቢ. The mason measured the right angle of the wall with a plummet. ግንበኛው ፡ የግድግዳውን ፡ ቀጥተኛ ፡ ማእዘን ፡ በቱንቢ ፡ ለካ

**plump down** እንዘፍ ፡ አደረገ
She plumped down the heavy bag on the table. ከባዱን ፡ ከረጢት ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ እንዘፍ ፡ አደረገች

**plump oneself down** ረብ ፡ አለ
He plumped himself down on the bed. አልጋው ፡ ላይ ፡ ረብ ፡ አለ

**plump** (adj.) የፋፋ
Your baby is very plump. ሕፃኗ ፡ ልጅሽ ፡ በጣም ፡ የፋፋች ፡ ናት

**plunder** (v.) ዘረፈ
The bandits plundered the village. ሽፍቶቹ ፡ መንደሩን ፡ ዘረፉት

**plunder** (n.) የዘረፈው ፤ ዘረፋ
The army fled leaving its plunder behind. ጦሩ ፡ የዘረፈውን ፡ ጥሎ ፡ ሸሸ
The plunder consisted of livestock and goods. ዘረፋው ፡ የተፈጸመው ፡ በከብቶችና ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ነበር

**plunge** (vt.)
1. ጣለ. His policies plunged the country into war. አመራሩ ፡ አገሪቷን ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ጣላት
2. ሰካ. He plunged the dagger into his enemy's heart. ጠላቱን ፡ ደረቱ ፡ ላይ ፡ ጩቤ ፡ ሰካበት
3. ነከረ. He plunged his burnt arm into the water. የተቃጠለውን ፡ ክንዱን ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ነከረው

**plunge** (vi.)
1. ጥልቅ ፡ አለ. He plunged into the midst of the crowd and separated the fighting boys. ሕዝቡ ፡ መሀል ፡ ጥልቅ ፡ ብሎ ፡ የሚጣሉትን ፡ ልጆች ፡ ገላገለ
2. ዘሎ ፡ ገባ. He plunged into the water. ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ዘሎ ፡ ገባ

**plunge into** ተያያዘ
We plunged into our work. ሥራችንን ፡ ተያያዝነው

**plunge through** ሰንጥቆ ፡ አለፈ
The ship plunged through the waves. መርከብ ፡ ሞገዱን ፡ ሰንጥቆ ፡ አለፈ
[See also 'headlong']

**plunk** (vt.) መታ
He plunked his guitar. ጊታሩን ፡ መታ

**plunk** (vi.) ቦርጫቅ ፡ አለ
The stone plunked into the water. ድንጋዩ ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ቦርጫቅ ፡ አለ

**plunk down** በኀይል ፡ ጣለ
He plunked his book down on the desk. መጽሐፋን ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ በኀይል ፡ ጣለ

**plural** የብዙ ፡ ቁጥር
The Amharic plural has a special ending. ባማርኛ ፡ የብዙ ፡ ቁጥር ፡ የተለየ ፡ ቅጥያ ፡ አለው

**plurality** ብልጫ
He received a plurality of all votes cast. በተደረገው ፡ ውድድር ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ አገኘ

**plus** (adj.) የመደመር
The plus sign resembles a cross. የመደመር ፡ ምልክት ፡ መስቀል ፡ ይመስላል

**plus** (prep.)
1. ሲደመር. Five plus seven is twelve. አምስትና ፡ ሰባት ፡ ሲደመር ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ይሆናል
2. ከ - - - ሌላ. It costs $10 plus tax. ከታክስ ፡ ሌላ ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ ያወጣል
3. ከ - - - ጋር. He received a salary plus gratuities. ደሞዙን ፡ ከጉርሻ ፡ ጋር ፡ ተቀበለ

**ply** (plied), vt.
1. ሠራ. He plied the trade of carpenter for many years. ባናጢነት ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሠራ
2. ቀዘፈ. We plied the water with our oars. ባሕሩን ፡ በመቅዘፊያ ፡ ቀዘፍን
3. በ - - - ተጠቀመ. The dressmaker plies her needle. ልብስ ፡ ሰፊዋ ፡ በመርፌ ፡ ትጠቀማለች

**ply** (vi.) ተመላለሰ
Boats ply among the islands of Lake Tana carrying food and passengers. ጀልባዎች ፡ ምግብና ፡ ተሳፋሪዎች ፡ ይዘው ፡ በጣና ፡ ደሴቶች ፡ መካከል ፡ ይመላለሳሉ

**ply with** አትረፈረፈ(ለት)
Our host plied us with food. ጋባዣችን ፡ ምግብ ፡ አትረፈረፈልን

**ply with questions** አዋከበ
The enemy plied our messenger with questions to make him divulge his mission. ጠላት ፡ መልእክተኛችንን ፡ መልእክቱን ፡ እንዲነግር ፡ አዋከበው

**ply** (plies), n. **two-ply** ዕጥፍ ፡ ውፍረት ፡ ያለው
A two-ply tire is safer than an ordinary tire. ዕጥፍ ፡ ውፍረት ፡ ያለው ፡ ጎማ ፡ ከተራው ፡ ጎማ ፡ ይልቅ ፡ ካደጋ ፡ ይጠብቃል

**pneumonia** የሳምባ ፡ ምች
He caught pneumonia last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ የሳምባ ፡ ምች ፡ መታው

**poach** ያለ ፡ ፈቃድ ፡ አደነ
He poached on his neighbor's land. በጐረቤቱ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያለፈቃድ ፡ አደነ

**pocket** (v.)
1. እኪሱ ፡ አደረገ. He pocketed the money without saying a word. አንዲት ፡ ቃል ፡ ሳይናገር ፡ ገንዘቡን ፡ እኪሱ ፡ አደረገ
2. ሰርቆ ፡ ወሰደ. His partner pocketed all the profits. ሸሪኩ ፡ ትርፉን ፡ በሙሉ ፡ ሰርቆ ፡ ወሰደ
3. ዋጥ ፡ አደረገ. He pocketed his pride and begged for help. ኩራቱን ፡ ዋጥ ፡ አድርጎ ፡ እርዳታ ፡ ለመነ

**pocket** (n.) ኪስ
Put this in your pocket! ይህንን ፡ ኪስህ ፡ ውስጥ ፡ ክተት

**pocket** (adj.) የኪስ
I bought a pocket radio. የኪስ ፡ ሬዲዮ ፡ ገዛሁ
[See also 'pickpocket']

**pocketbook** ቦርሳ
She lost her pocketbook. ቦርሳዋ ፡ ጠፋባት

**pocketknife** ሰንጢ
May I borrow your pocketknife? ሰንጢህን ፡ ታውሰኝ ?

**pod** ፍልፋይ
She threw out the pods with the garbage. ፍልፋዩን ፡ ከቆሻሻ ፡ ጋር ፡ ጣለችው

**podium** መድረክ
The podium was too high for the audience to see the speaker. መድረኩ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለነበረ ፡ አድማጮቹ ፡ ተናጋሪውን ፡ ለማየት ፡ አልቻሉም

**poem** ግጥም
This book contains all his poems. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የሱን ፡ ግጥሞች ፡ በሙሉ ፡ ይይዛል

**poet** ባለቅኔ
He is the chief poet of our time. በጊዜያችን ፡ ታላቁ ፡ ባለቅኔ ፡ እሱ ፡ ነው

**poetic**

1. የግጥም. Advanced students eagerly read poetic literature. በትምህርታቸው ፡ የገፉ ፡ ተማሪዎች ፡ የግጥም ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍን ፡ በደስታ ፡ ያነባሉ

2. ቅኔያዊ. She gave a poetic description of nature. ስለ ፡ ተፈጥሮ ፡ ቅኔያዊ ፡ መግለጫ ፡ ሰጠች

3. በግጥም ፡ የተጻፈ. There are a few poetic dramas in Amharic. ባማርኛ ፡ ጥቂት ፡ በግጥም ፡ የተጻፉ ፡ ድራማዎች ፡ አሉ

**poetic speech** የረቀቀ ፡ ንግግር

Poetic speech is harder to understand than plain speech. ከተራ ፡ ንግግር ፡ ይልቅ ፡ የረቀቀ ፡ ንግግር ፡ መረዳት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**poetry**

1. ግጥም. She writes beautiful poetry. ጥሩ ፡ ግጥም ፡ ትገጥማለች

2. ቅኔ. He writes religious poetry in Geez. መንፈሳዊ ፡ ቅኔዎችን ፡ በግዕዝ ፡ ይጽፋል

3. ስሜት. There is poetry in her dancing. ዳንሷ ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ ነው

**point** (vt.)

1. ደገነ. The fireman pointed his hose at the flames. እሳት ፡ ተከላካዩ ፡ የውኃውን ፡ ቧምቧ ፡ ወደ ፡ ነበልባሉ ፡ ደገነ

He pointed a gun at me. ጠበንጃ ፡ ደገነብኝ

2. አመለከተ. The arrow points north. ቀስቱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ያመለክታል

**point at** አሳየ

He pointed his finger at the thief. ሌባውን ፡ በጣቱ ፡ አሳየ

**point out**

1. አሳየ. Point out the place you told me about! የነገርከኝን ፡ ስፍራ ፡ አሳየኝ

2. አመለከተ. The guide pointed out where the bandits were hiding. ሽፍቶቹ ፡ የተደበቁበትን ፡ መሪው ፡ አመለከተ

3. አስገነዘበ. The minister pointed out that his policy will bring about peace. ሚኒስትሩ ፡ የሱ ፡ አመራር ፡ ሰላም ፡ እንደሚያመጣ ፡ አስገነዘበ

**point to**

1. አመለከተ. Everything points to his guilt. ማንኛውም ፡ ነገር ፡ የሱን ፡ ጥፋት ፡ ያመለክታል

2. ጠቈመ. Point to the man you mean! የምትለውን ፡ ሰው ፡ ጠቍም

**point toward** አመለከተ

All signs point toward a cold winter. ሁሉም ፡ ነገር ፡ ክረምቱ ፡ ቀዝቃዛ ፡ እንደሚሆን ፡ ያመለክታል

**point** (n.)

1. ጫፍ. The point of my knife broke. የሰንጢዬ ፡ ጫፍ ፡ ተሰበረ

2. ፍሬ ፡ ነገር. You missed the point of the story. የታሪኩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ አልገባህም

3. ዋና ፡ ነገር. The speaker listed each point of his plan. ተናጋሪው ፡ የፕላኑን ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ በዝርዝር ፡ አኖረ

4. ሁኔታ. He reached the point where he could no longer pay his debts. ዕዳውን ፡ ሊከፍል ፡ ከማይችልበት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ደረሰ

5. ቦታ. Here is the point where two lines intersect. ሁለት ፡ መሥመሮች ፡ የሚተላለፉበት ፡ ቦታ ፡ ይህ ፡ ነው

6. ጠባይ. He has his good points and his bad ones too. ጥሩም ፡ መጥፎም ፡ ጠባይ ፡ አለው

7. ደረጃ ፤ መጠን. The freezing point of water is 32° F. ውኃ ፡ በረዶ ፡ የሚሆንበት ፡ ደረጃ ፡ 32° F. ነው

What is the boiling point of water? ውኃ ፡ ለመፍላት ፡ የሚችልበት ፡ የሙቀት ፡ መጠን ፡ ስንት ፡ ነው ?

8. ነጥብ. Our team won by five points. ቡድናችን ፡ ባምስት ፡ ነጥብ ፡ ብልጫ ፡ አሸነፈ

His argument can be divided into several points. የሱ ፡ ክርክር ፡ በብዙ ፡ ነጥቦች ፡ ሊከፋፈል ፡ ይችላል

*The turning point of the Second World War was the battle of Stalingrad. የስታሊንግራድ ፡ ጦርነት ፡ ሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ መልኩ ፡ የተቀየረበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር

**point by point** አንድ ፡ ባንድ

We have gone over the contract point by point. ውሉን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ መርምረነዋል

**at that point** ልክ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ

At that point, the telephone rang. ልክ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ስልኩ ፡ ተደወለ

**(be) at the point of** ሊ + imperfect + ነው.

He is at the point of death. ሊሞት ፡ ነው

**at this point**

1. አሁን ፡ ባለበት ፡ ሁኔታው. At this point, I can't tell if it is working or not. አሁን ፡ ባለበት ፡ ሁኔታው ፡ መሥራት ፡ አለመሥራቱን ፡ ላውቅ ፡ አልችልም

2. በዚህን ፡ ጊዜ. At this point, one of the members stood up and raised an objection. በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከአባሎቹ ፡ አንዱ ፡ ተነሥቶ ፡ ተቃወመ

**beside the point**

That's beside the point. ይህ ፡ ከነገሩ ፡ ውጭ ፡ ነው

**(a) case in point**
Let me give you a case in point! ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከት ፡ ምሳሌ ፡ ልስጥህ

**come to the point** ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ተናገረ
Why don't you stop beating around the bush and come to the point? ዳር ፡ ዳር ፡ ማለትህን ፡ ትተህ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ለምን ፡ አትናገርም ?

**come to the point of** ል + imperfect + ምንም ፡ አልቀረውም
They almost came to the point of exchanging blows. ሊደባደቡ ፡ ምንም ፡ አልቀራቸውም ፡ ነበር

**main point** ፍሬ ፡ ነገር
The main point of his speech was that the danger of war must be avoided. የንግግሩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ የጦርነት ፡ አደጋ ፡ መወገድ ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ ነው

**make a point of**
1. (= adv.) በይፋ. He made a point of mentioning his opponent's illness. የተቃዋሚውን ፡ መታመም ፡ በይፋ ፡ ተናገረ
2. እንደ ፡ ተገቢ ፡ ነገር ፡ ቈጠረው. In that country, one makes a point of bringing flowers if invited for dinner. እዚያ ፡ አገር ፡ ለራት ፡ የተጋበዘ ፡ ሰው ፡ አበባ ፡ ይዞ ፡ መሄድን ፡ እንደ ፡ ተገቢ ፡ ነገር ፡ ይቈጥረዋል

**make it a point**
Make it a point to be on time! በሰዓቱ ፡ መድረስ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ አስተውል

**(be) on the point of** ል + imperfect + ሲል
We were on the point of leaving when company arrived. ልንሄድ ፡ ስንል ፡ እንግዶች ፡ መጡ

**rise several points** በጣም ፡ ጨመረ
The cost of living rose several points last month. ባለፈው ፡ ወር ፡ የኑሮ ፡ ዋጋ ፡ በጣም ፡ ጨመረ

**strong point**
1. ምሽግ. The enemy's strong point was bombarded before we attacked. ከማጥቃታችን ፡ በፊት ፡ የጠላት ፡ ምሽግ ፡ በቦምብ ፡ ተደበደበ
2. ተሰጥኦ. Learning languages is not my strong point. ቋንቋ ፡ መማር ፡ ተሰጥኦዬ ፡ አይደለም

**there is no point in** ምንም ፡ ዋጋ ፡ የለውም
There is no point in continuing the discussion. ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ክርክሩን ፡ መቀጠሉ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ የለውም

**to the point**
Let's stick to the point! ከነገሩ ፡ አንውጣ

**to the ... point** እስከ + imperfect + ድረስ
The balloon was distended to the bursting point. ፊኛው ፡ እስኪፈነዳ ፡ ድረስ ፡ ተነፍቶ ፡ ነበር

**(be) to the point**
1. ጉዳዩን ፡ ተመለከተ. His comments are always to the point. ትችቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ጉዳዩን ፡ የሚመለከት ፡ ነው
2. ቁም ፡ ነገር ፡ አዘለ. His speech was brief, but to the point. ንግግሩ ፡ አጭር ፡ ቢሆንም ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያዘለ ፡ ነበር

**to the point of** እስከ + imperfect + ድረስ
He was provoked to the point of losing his temper. ትዕግሥቱን ፡ እስኪጨርስ ፡ ድረስ ፡ ገፋፋት

**up to a certain point** በከፊል
I can understand it up to a certain point. በከፊል ፡ ይገባኛል

**what's the point**
What's the point in crying? ማልቀስ ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ? (or, ምን ፡ ያደርጋል ?)
[See also 'cardinal, labor, return, salient, score, terminal, turn, vantage']

**point-blank** (= adv.) በቀጥታ
With no hesitation, he gave a point-blank refusal. ሳያቅማማ ፡ በቀጥታ ፡ እንቢ ፡ አለ
*He fired at the thief point-blank. ሌባውን ፡ ከነመረቁ ፡ አጠማው

**pointed**
1. ሹል ፤ የሾለ. Be careful with that pointed stick! ያንን ፡ ሹል ፡ ብትር ፡ ተጠንቀቅ
She has a pointed nose. የሾለ ፡ አፍንጫ ፡ አላት
2. ቀጥ ፡ ያለ. A cat has pointed ears. ድመት ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ጆሮ ፡ አላት
3. የተደገነ. His pointed gun frightened the thief. የተደገነው ፡ ጠመንጃው ፡ ሌባውን ፡ አስደነገጠው
4. ሰው ፡ የሚነካ. His pointed sayings offended many people. ሰው ፡ የሚነካ ፡ ንግግሩ ፡ ብዙውን ፡ ሰው ፡ አስቀየመ

**pointer**
1. መጠቆሚያ. The teacher uses a pointer in the geography class. አስተማሪው ፡ ጂኦግራፊ ፡ ሲያስተምር ፡ በመጠቆሚያ ፡ ይገለገላል
2. ምክር. The food expert gave some good pointers on making better cakes. የምግብ ፡ ሊቁ ፡ የተሻለ ፡ ኬክ ፡ ስለሚሠራበት ፡ ዘዴ ፡ አንዳንድ ፡ ምክሮችን ፡ ሰጠ

**pointless**
1. የዶለዶመ. He gave me a pointless pencil. የዶለዶመ ፡ እርሳስ ፡ ሰጠኝ

2. ፍሬ ፡ ቢስ ፡ የሆነ. He told me a pointless anecdote. ፍሬ ፡ ቢስ ፡ የሆነ ፡ ተረት ፡ አወራልኝ

**seem pointless** ዋጋ ፡ ያለው ፡ አይመስልም
Further meetings seem pointless. ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ መሰብሰብ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ አይመስልም

**point of order** ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይጠበቅ
Point of order, Mr. Chairman! ሊቀ ፡ መንበር ፤ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይጠበቅ !

**point of view** አስተያየት ፤ ሐሳብ
What is your point of view on the matter? በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ያንተ ፡ አስተያየት ፡ (ሐሳብ) ፡ ምንድን ፡ ነው ?

**poise** (v.), ~ **itself** ቆመ
The bird poised itself on one leg. ወፏ ፡ ባንድ ፡ እግሯ ፡ ቆመች

**poise** (n.) የረጋ ፡ መንፈስ ፤ የርጋታ ፡ መንፈስ
He kept his poise throughout the crisis. በሁከት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የረጋ ፡ መንፈሱ ፡ አልተናወጸም
He shows poise in company. በሰው ፡ መካከል ፡ ሲሆን ፡ የርጋታ ፡ መንፈስ ፡ አለው

**poison** (v.)
1. መርዝ ፡ አደረገ(በት). He poisoned the food of his enemy. የጠላቱን ፡ ምግብ ፡ መርዝ ፡ አደረገበት
2. መርዝ ፡ አበላ. The thief poisoned the dog. ሌባው ፡ ውሻውን ፡ መርዝ ፡ አበላው
3. አበላሸ. Fear poisoned his happiness. ፍርሃት ፡ ደስታውን ፡ አበላሸበት
4. ጥላቻ ፡ አሳደረ(በት). His wife poisoned the child's mind against his father. ሚስትየዋ ፡ ልጁ ፡ ባባቱ ፡ ላይ ፡ ጥላቻ ፡ አሳደረችበት

**poison** (n.) መርዝ
Opium is poison. ኦፒዩም ፡ መርዝ ፡ ነው

**poison gas** የመርዝ ፡ ጢስ
The enemy used poison gas in the war. በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ጠላት ፡ በመርዝ ፡ ጢስ ፡ ተጠቀመ

**poisonous**
1. መርዘኛ. He was bitten by a poisonous snake. መርዘኛ ፡ እባብ ፡ ነደፈው
2. መርዝነት ፡ ያለው. Poisonous mushrooms are inedible. መርዝነት ፡ ያለው ፡ እንጉዳይ ፡ አይበላም
3. መርዝ ፡ ያለበት. The analysis of the water proved that it was poisonous. ምርመራው ፡ ውኃው ፡ መርዝ ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጠ

**poke**
1. ወጋጋ. He poked me in the ribs with his fingers. በጣቶቹ ፡ ጐኔን ፡ ወጋጋኝ
2. ጐሸመ. He poked me in the ribs with his elbow. በክርኑ ፡ ጐኔን ፡ ጐሸመኝ
3. ቈሰቈሰ. Poke the fire to keep it going! እሳቱ ፡ እንዲነድ ፡ ቈስቍሰው

**poke around in** በረበረ
He poked around in the cellar. ምድር ፡ ቤቱን ፡ በረበረ

**poke at** ነካካ
He was poking at the rubbish with his cane. ቆሻሻውን ፡ በከዘራው ፡ ይነካካ ፡ ነበር

**poke fun** አሾፈ
He pokes fun at his wife. በሚስቱ ፡ ያሾፍባታል

**poke (a) hole in** ነደለ
He poked a hole in the sack. ኬሻውን ፡ ነደለው

**poke one's nose into** ጥልቅ ፡ አለ
Don't poke your nose into my affairs! በጉዳዬ ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ አትበል

**poke (out)**
1. ጓጐጠ. He poked his eye out with a stick. ዓይኑን ፡ በዕንጨት ፡ ጓጐጠው
2. ብቅ ፡ አደረገ. He poked his head out the window. በመስኮቱ ፡ አንገቱን ፡ ብቅ ፡ አደረገ

**Poland** ፖሎኝ ፤ ፖላንድ

**polar** የምድር ፡ ዋልታ
It is very cold in the polar regions. የምድር ፡ ዋልታ ፡ አካባቢ ፡ በጣም ፡ ቀዝቃዛ ፡ ነው

**Pole** የፖላንድ ፡ ሰው
This store is owned by a Pole. የዚህ ፡ ሱቅ ፡ ባለቤት ፡ የፖላንድ ፡ ሰው ፡ ነው

**pole**
1. ምሰሶ. Will the pole be long enough? የምሰሶው ፡ ቁመት ፡ በቂ ፡ ነው ?
2. አጠና. The fence is made of poles lashed together with rope. አጥሩ ፡ የተሠራው ፡ በገመድ ፡ በተሳሰሩ ፡ አጠናዎች ፡ ነው
3. ዕንጨት. He hung his wet clothes on a pole to dry. እርጥብ ፡ ልብሶቹን ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ አሰጣ
The child climbed up the streetlight pole. ልጁ ፡ ኮረንቲው ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ ወጣ
4. የምድር ፡ ዋልታ. Admiral Byrd reached the pole after a difficult voyage. አድሚራል ፡ ቢርድ ፡ ከከባድ ፡ ጉዞ ፡ በኋላ ፡ ከምድር ፡ ዋልታ ፡ ደረሰ

5. ወገን. His attitude represents one pole of opinion. አቋሙ ፡ ያንዱን ፡ ወገን ፡ አስተሳሰብ ፡ ያመለክታል

**be poles apart** በጣም ፡ ተለያዩ
In education, they are poles apart. በትምህርት ፡ በጣም ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው

**North Pole** የሰሜን ፡ ዋልታ
How cold does it get at the North Pole? የሰሜኑ ፡ ዋልታ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይቀዘቅዛል ?

**South Pole** የደቡብ ፡ ዋልታ
The South Pole is located in the middle of a continent. የደቡብ ፡ ዋልታ ፡ አንድ ፡ አህጉር ፡ እምብርት ፡ ላይ ፡ ይገኛል

**polemic** (n.) የሚቃረን
This book is a polemic against previously advanced ideas. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የቀረቡትን ፡ ሐሳቦች ፡ የሚቃረን ፡ ነው

**polemic** (adj.) ተቃራኒ ፡ ክርክር ፡ ያዘለ
His writings are polemic. ጽሑፎቹ ፡ ተቃራኒ ፡ ክርክሮች ፡ ያዘሉ ፡ ናቸው

**polemics** ክርክር
This politician is a master of polemics. ይህ ፡ የፖለቲካ ፡ ሰው ፡ የክርክር ፡ ሊቅ ፡ ነው

**police** (v.) ተቈጣጠረ
They policed the streets to reduce crime. ወንጀልን ፡ ለመቀነስ ፡ መንገዶችን ፡ ተቈጣጠሩ

**be well policed** በቂ ፡ ፖሊሶች ፡ አለው
The streets are well policed. መንገዶቹ ፡ በቂ ፡ ፖሊሶች ፡ አሉዋቸው

**police** (n.) ፖሊስ ፤ ፖሊሶች
Call the police! I've been robbed. ፖሊስ ፡ ጥሩልኝ ፤ ተዘርፌያለሁ
Extra police were on duty today. ተጨማሪ ፡ ፖሊሶች ፡ ዛሬ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ተሰማርተው ፡ ነበር

**police force** የፖሊስ ፡ ሰራዊት
The police force protects the people from criminals. የፖሊስ ፡ ሰራዊት ፡ ሕዝቡን ፡ ከወንጀለኞች ፡ ይከላከላል

**police headquarters** ፖሊስ ፡ ጠቅላይ ፡ መምሪያ
The interrogation is being held at police headquarters. ምርመራው ፡ በፖሊስ ፡ ጠቅላይ ፡ መምሪያ ፡ በመደረግ ፡ ላይ ፡ ነው

**policeman** (policemen) ፖሊስ
A policeman stopped me for speeding. ከተወሰነው ፡ ፍጥነት ፡ በላይ ፡ በመንዳቴ ፡ ፖሊስ ፡ አቆመኝ

**police station** ፖሊስ ፡ ጣቢያ
The policeman took the thief to the police station. ፖሊሱ ፡ ሌባውን ፡ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ወሰደው

**policy** (policies)
1. ዓላማ. The policy of the government is to keep peace with the neighboring countries. የመንግሥቱ ፡ ዓላማ ፡ ከጐረቤት ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ በሰላም ፡ ለመኖር ፡ ነው
2. አመራር. Cuba's government policy is leftist oriented. የኩባ ፡ መንግሥት ፡ አመራር ፡ የኮሙኒስት ፡ መንፈስ ፡ አለበት
3. ቋሚ ፡ መምሪያ. It is my policy to talk to every applicant myself. እያንዳንዱን ፡ አመልካች ፡ ራሴ ፡ ማነጋገር ፡ ቋሚ ፡ መምሪያዬ ፡ ነው
4. የሕይወት ፡ ዋስትና ፡ ውል. Don't let your policy lapse! የሕይወት ፡ ዋስትና ፡ ውልህ ፡ ጊዜው ፡ እንዳያልፍ ፡ ተጠንቀቅ
[See also 'scorch']

**polish** (v.)
1. ጠረገ. I don't have time to polish my shoes. ጫማዬን ፡ የምጠርግበት ፡ ጊዜ ፡ የለኝም
2. ወለወለ. The maid polished all the door knobs. ገረድዋ ፡ የመዝጊያዎቹን ፡ እጀታዎች ፡ ሁሉ ፡ ወለወለች
3. አሻሻለ. You need to polish your manners if you are going to associate with them. ከነሱ ፡ ጋር ፡ ለመጐዳኘት ፡ ብትፈልግ ፡ ጠባይህን ፡ ማሻሻል ፡ ያስፈልግሃል
He polished his French by taking private lessons. የግል ፡ ትምህርት ፡ በመከታተል ፡ ፈረንሳይኛውን ፡ አሻሻለ

**polish** (n.) ቀለም
Give me a can of shoe polish! አንድ ፡ ቆርቆሮ ፡ የጫማ ፡ ቀለም ፡ ስጠኝ

**acquire polish** አእምሮው ፡ በሰለ
He has acquired polish by years of study and travel. ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ ትምህርትና ፡ ጉዞ ፡ የተነሣ ፡ አእምሮው ፡ በስሏል
*After years of practice, he acquired the polish of a professional singer. ከብዙ ፡ ዓመት ፡ ልምምድ ፡ በኋላ ፡ የዘፋኝነትን ፡ ሙያ ፡ ተቀዳጀ

**have a (nice) polish** አንጸባረቀ
Your car has a nice polish. መኪናህ ፡ ታንጸባርቃለች

**Polish** የፖላንድ ፡ ቋንቋ
We don't learn Polish in our school. ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ውስጥ ፡ የፖላንድ ፡ ቋንቋ ፡ አንማርም

**polite**
1. ትሑት. A lowly person may often be more polite than a well-born person. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከተራ ፡ የተወለደ ፡ ሰው ፡ ከጨዋ ፡ ከተወለደ ፡ ሰው ፡ ይልቅ ፡ ትሑት ፡ ይሆን ፡ ይሆናል
2. የጨዋ. She wished to learn all the customs of polite society. የጨዋ ፡ ኅብረት ፡ ሰብን ፡ ልማዶች ፡ ሁሉ ፡ ለመማር ፡ ተመኘች

**polite words** ትሕትና
He phrased his excuse in polite words. ምክንያቱን ፡ በትሕትና ፡ ገለጸ

**politely** በትሕትና
I answered him as politely as I could. በተቻለኝ ፡ መጠን ፡ በትሕትና ፡ መለስኩለት

**politeness** ትሕትና
Politeness is a mark of good upbringing. ትሕትና ፡ የመልካም ፡ አስተዳደግ ፡ ምልክት ፡ ነው

**political** የፖለቲካ
There are two political parties in America. በአሜሪካ ፡ ሁለት ፡ የፖለቲካ ፡ ቡድኖች ፡ አሉ

**politician** የፖለቲካ ፡ ሰው
My uncle is a politician. አጎቴ ፡ የፖለቲካ ፡ ሰው ፡ ነው ፡

**politics**
1. የፖለቲካ ፡ አስተሳሰብ. My father's politics favor the welfare of the farmer. ያባቴ ፡ የፖለቲካ ፡ አስተሳሰብ ፡ የገበሬዎችን ፡ ደኅንነት ፡ ይደግፋል
2. ፖለቲካ. I'm not interested in politics. ፖለቲካ ፡ ውስጥ ፡ የመግባት ፡ ስሜት ፡ የለኝም

**poll** (v.)
1. አስተያየት ፡ ጠየቀ. They polled the city concerning the new school building. ስለ ፡ አዲሱ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሕንጻ ፡ ጉዳይ ፡ የከተማውን ፡ ሕዝብ ፡ አስተያየት ፡ ጠየቁ
2. አገኘ. My friend polled a majority of the votes cast. ጓደኛዬ ፡ ከተሰጠው ፡ ድምፅ ፡ ውስጥ ፡ አብዛኛውን ፡ አገኘ

**poll** (n.)
1. የምርጫ ፡ ጣቢያ. The people are going to the polls to choose a new parliament. ሕዝቡ ፡ አዲስ ፡ የፓርላማ ፡ መማክርት ፡ ለመምረጥ ፡ ወደ ፡ ምርጫው ፡ ጣቢያ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ነው
2. ያስተያየት ፡ ትመና. They are taking a poll to find out how people like the new policy. ሕዝቡ ፡ አዲሱን ፡ የአመራር ፡ ዓላማ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚወድ ፡ ለማወቅ ፡ ያስተያየት ፡ ትመና ፡ በመቀበል ፡ ላይ ፡ ናቸው
3. የድምፅ ፡ አሰጣጥ. A poll of our class shows that most of us want a picnic. የክፍላችን ፡ የድምፅ ፡ አሰጣጥ ፡ አብዛኞቻችን ፡ ሽርሽር ፡ ለመሄድ ፡ እንደምንፈልግ ፡ ያሳያል

**pollen** ያበባ ፡ ዱቄት
The pollen makes me sneeze. ያበባው ፡ ዱቄት ፡ ያስነጥሰኛል

**polling booth** የድምፅ ፡ መስጫ ፡ ጣቢያ
The polling booths were crowded with people. የድምፅ ፡ መስጫዎቹ ፡ ጣቢያዎች ፡ በሕዝብ ፡ ተጨናንቀው ፡ ነበር

**pollute**
1. በከለ. Sewage has polluted our drinking water. የቆሻሻው ፡ እጣቢ ፡ የመጠጥ ፡ ውኃችንን ፡ በክሎታል
The smokers pollute the air with smoke. ሲጋራ ፡ አጫሾች ፡ አየርን ፡ በጢስ ፡ ይበክላሉ
2. አረከሰ. The mischievous boys polluted the houses of worship. ባለጌዎቹ ፡ ልጆች ፡ ቤተ ፡ መቅደሱን ፡ አረከሱት

**pollution**
1. መበላሸት. The pollution of the air is pernicious to our health. ያየሩ ፡ መበላሸት ፡ ለጤናችን ፡ ጠንቅ ፡ ነው
2. መበከል. The committee made an incisive study of water pollution. ደርጉ ፡ ስለ ፡ ውኃ ፡ መበከል ፡ ጥልቅ ፡ ጥናት ፡ አደረገ

**polygamy** ካንድ ፡ ሚስት ፡ በላይ ፡ ማግባት
The Christian faith forbids polygamy. በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ካንድ ፡ ሚስት ፡ በላይ ፡ ማግባት ፡ ክልክል ፡ ነው

**polyglot** ብዙ ፡ ቋንቋ ፡ ለመናገር ፡ የሚችል ፡ ሰው
This office employs only polyglots. ይህ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚቀጥረው ፡ ብዙ ፡ ቋንቋ ፡ ለመናገር ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎችን ፡ ብቻ ፡ ነው

**polytheism** በብዙ ፡ አማልክት ፡ ማመን
Christians and Muslims prefer monotheism to polytheism. ክርስቲያኖችና ፡ እስላሞች ፡ ከብዙ ፡ አማልክት ፡ ይልቅ ፡ ባንድ ፡ አምላክ ፡ ማመን ፡ ይመርጣሉ

**pomegranate** ሮማን
The pomegranate has a sour taste. ሮማን ፡ ጎምዛዛ ፡ ነው

**pommel** (v.) በቡጢ ፡ መታ
He pommeled him and threw him to the ground. በቡጢ ፡ መቶ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ዘረረው

**pommel** (n.) ቀዳማ
The pommel of the saddle is made of wood. የኮርቻው ፡ ቀዳማ ፡ ከዕንጨት ፡ የተሠራ ፡ ነው

**pomp** ድምቀትና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት
The Parliament was opened with great pomp. ምክር ፡ ቤቱ ፡ በታላቅ ፡ ድምቀትና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተከፈተ

**pompous** ጉረኛ
The minister is a pompous person. ሚኒስትሩ ፡ ጉረኛ ፡ ሰው ፡ ነው

**pond** ኩሬ
The cows get their water from a pond. ላሞቹ ፡ ውኃ ፡ የሚጠጡት ፡ ከኩሬ ፡ ነው

**ponder** አወጣ ፡ አወረደ
He pondered the effects of his policies on the situation. የሱ ፡ አመራር ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ውጤት ፡ እንደሚሰጥ ፡ ያወጣ ፡ ያወርድ ፡ ነበር

**ponder over** አሰላሰለ
He pondered over the problems. ችግሩን ፡ አሰላሰለ

**ponderous**
1. ግዙፍ. The ponderous elephant plodded along. ግዙፉ ፡ ዝሆን ፡ አዘገመ
2. የሚያሰለች. The speaker talked in a ponderous way. ተናጋሪው ፡ በሚያሰለች ፡ ሁኔታ ፡ ተናገረ

**pontificate** እየተጐላመሰ ፡ ተናገረ
He likes to pontificate about the responsibilities of a good citizen. ስለ ፡ መልካም ፡ ዜጋ ፡ ኀላፊነት ፡ እየተጐላመሰ ፡ መናገር ፡ ይወዳል

**pony** (ponies) ድንክ ፡ ፈረስ
He breeds ponies. ድንክ ፡ ፈረሶች ፡ ያረባል

**pool** (v.)
1. ባንድ ፡ አዋሐደ. African nations must pool their resources to develop faster. የአፍሪካ ፡ አገሮች ፡ በፍጥነት ፡ ለመበልጸግ ፡ ሀብቶቻቸውን ፡ ባንድ ፡ ማዋሐድ ፡ አለባቸው
2. አዋጣ. We pooled our money and rented a cottage. ገንዘብ ፡ አዋጥተን ፡ አንድ ፡ ጎጆ ፡ ተከራየን

**pool** (n.) ኩሬ
There are no fish in this pool. እዚች ፡ ኩሬ ፡ ውስጥ ፡ ዓሣ ፡ የለም

**pool of cars**
*The company owns a pool of cars for its employees. ኩባንያው ፡ ለሠራተኞቹ ፡ አገልግሎት ፡ የሚውሉ ፡ የተወሰኑ ፡ መኪናዎች ፡ አሉት
[See also 'swimming pool']

**poor**
1. ድኻ. Many poor people live in this neighborhood. በዚህ ፡ ሰፈር ፡ ብዙ ፡ ድኾች ፡ ይኖራሉ
Sudan is poor in oil resources. ሱዳን ፡ በዘይት ፡ ሀብት ፡ ድኻ ፡ ነች
2. ችግር ፡ የበዛበት. This is a very poor district. ይህ ፡ በጣም ፡ ችግር ፡ የበዛበት ፡ ቀበሌ ፡ ነው
3. የማይረባ. This is a poor excuse. ይህ ፡ የማይረባ ፡ ምክንያት ፡ ነው
4. አሸር ፡ ባሸር ፤ መጥፎ ፤ ያልተሟላ. Poor food stunted the child's growth. አሸር ፡ ባሸር ፡ ምግብ ፡ ሕፃኑን ፡ አቀጨጨው
Poor food contributed to the child's illness. ለልጁ ፡ ሕመም ፡ መጥፎው ፡ ምግብ ፡ አንደኛው ፡ ምክንያት ፡ ነው
Poor food impaired his health. ያልተሟላ ፡ ምግብ ፡ ጤንነቱን ፡ ጐዳው
5. ደካማ. He is very poor in arithmetic. በሒሳብ ፡ በጣም ፡ ደካማ ፡ ነው
6. በቂ ፡ ያልሆነ. A poor education can be a hindrance to success. በቂ ፡ ያልሆነ ፡ ትምህርት ፡ ለኑሮ ፡ መሳካት ፡ ዕንቅፋት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል
7. ምስኪን. The poor little dog has been abandoned. ምስኪኑ ፡ ቡችላ ፡ ተጥሏል
8. አነስተኛ. The attendance at the last three meetings was very poor. ባለፉት ፡ ሦስት ፡ ስብሰባዎች ፡ ላይ ፡ የተገኘው ፡ ሕዝብ ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነበር
9. የተሳሳተ. External appearances are often a poor guide to character. ከውጭ ፡ የሚታዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ጠባይ ፡ የተሳሳተ ፡ ግምት ፡ ይሰጣሉ
10. የተጓደለ. Bus service here is very poor. የአውቶቡስ ፡ አገልግሎት ፡ እዚህ ፡ በጣም ፡ የተጓደለ ፡ ነው
*This is a poor representation of a village scene. ይህ ፡ ሥዕል ፡ የመንደርን ፡ ሁኔታ ፡ በሚገባ ፡ አያመለክትም

**be poor**
1. ጥሩ ፡ አይደለም. The connections with that town are very poor. ከዚያ ፡ ከተማ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ መገናኛ ፡ ጥሩ ፡ አይደለም
2. አይሆንም. This is poor soil for wheat. ይህ ፡ አፈር ፡ ለስንዴ ፡ አይሆንም

**poor health**
1. (የ)ጤና ፡ ማጣት. He was despondent over

his wife's poor health. ስለ ፡ ሚስቱ ፡ ጤና ፡ ማጣት ፡ አዝኖ ፡ ተክዞ ፡ ነበር
2. የጤንነት ፡ መታወክ. His poor health incapacitated him for work. የጤንነቱ ፡ መታወክ ፡ እንዳይሠራ ፡ ከለከለው

**(be in) poor health** ጤና ፡ አጣ
He has been in poor health for years. ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ ጀምሮ ፡ ጤና ፡ አጥቷል

**(of) poor quality** መናኛ
Goods of poor quality will not sell easily. መናኛ ፡ እቃዎች ፡ በቀላሉ ፡ ሊሸጡ ፡ አይችሉም
[See also 'creature, devil, fellow, memory, sport']

**poorly**
1. እንደነገሩ. The whole thing was poorly organized. ሁሉም ፡ ነገር ፡ የተዘጋጀው ፡ እንደነገሩ ፡ ነበር
2. መጥፎ. The team played poorly. ቡድኑ ፡ መጥፎ ፡ ተጫወተ
*A desert is poorly supplied with water. በምድረ ፡ በዳ ፡ የሚገኘው ፡ ውኃ ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ነው
*He did poorly on the test. የፈተናው ፡ ውጤት ፡ መጥፎ ፡ ነበር

**be poorly dressed** አልባሌ ፡ ልብስ ፡ ለበሰ
She is poorly dressed though her family is well-to-do. ቤተሰቦቿ ፡ ሀብታም ፡ ቢሆኑም ፡ አልባሌ ፡ ልብስ ፡ ትለብሳለች

**be poorly lighted** በቂ ፡ መብራት ፡ የለውም
The streets are poorly lighted. መንገዶች ፡ በቂ ፡ መብራት ፡ የላቸውም (or, የመንገድ ፡ መብራት ፡ ደካማ ፡ ነው)

**feel poorly** ጤንነት ፡ አይሰማውም
She has been feeling poorly for several days. ከጥቂት ፡ ቀናት ፡ ወዲህ ፡ ጤንነት ፡ አይሰማትም

**pop** (popped), vt. ብቅ ፡ አደረገ
She popped her head through the doorway. እንገቷን ፡ በበሩ ፡ ብቅ ፡ አደረገች

**pop** (vi.)
1. ብው ፡ ብሎ ፡ ፈነዳ. The balloon popped. ፊኛው ፡ ብው ፡ ብሎ ፡ ፈነዳ
2. ፈነዳ. The cork popped. ቡሹ ፡ ፈነዳ
3. ፈጠጠ. His eyes were popping with curiosity. ዓይኖቹ ፡ በጉጉት ፡ ፈጠው ፡ ነበር

**pop in**
1. ብቅ ፡ አለ. Our neighbors popped in for a while. ጎረቤቶቻችን ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ብቅ ፡ አሉ
2. ገባ ፡ አደረገ. He popped his head in at the door. እንገቱን ፡ በበሩ ፡ ገባ ፡ አደረገ

**pop open** ፈነዳ
The castor beans popped open. የጉሎው ፡ ፍሬ ፡ ፈነዳ

**pop out**
1. ፍጥጥ ፡ አለ. His eyes almost popped out with surprise. በድንጋጤ ፡ ዓይኑ ፡ ፍጥጥ ፡ አለ
2. ፈትለክ ፡ ብሎ ፡ ወጣ. The rabbit popped out of its hole. ጥንቸሏ ፡ ከጉድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ፈትለክ ፡ ብላ ፡ ወጣች
3. ተፍ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ. He popped out of bed. ከአልጋው ፡ ተፍ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ

**pop up**
1. በድንገት ፡ ተፈጠረ. An urgent matter popped up. አስቸኳይ ፡ ነገር ፡ በድንገት ፡ ተፈጠረ
2. በድንገት ፡ ብቅ ፡ አለ. One fine day he popped up again. አንድ ፡ ቀን ፡ እንደገና ፡ በድንገት ፡ ብቅ ፡ አለ
3. ነፈሰ. Idle rumors pop up every so often. የማይረባ ፡ ወሬ ፡ በየጊዜው ፡ ይነፍሳል

**pop** (n.), **with a ~** ጧ ፡ ብሎ
The balloon burst with a pop. የላስቲክ ፡ ፊኛው ፡ ጧ ፡ ብሎ ፡ ፈነዳ

**popcorn** የበቆሎ ፡ ቆሎ
Popcorn is sold like candy. የበቆሎ ፡ ቆሎ ፡ እንደ ፡ ከረሜላ ፡ ይሸጣል

**pope** ሊቀ ፡ ጳጳስ
The pope blessed the people. ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ሕዝቡን ፡ ባረኩ

**poplar** [የዛፍ ፡ ዓይነት]

**populace** ሕዝብ
The populace is in favor of the law. ሕዝቡ ፡ ሕጉን ፡ ይደግፋል

**popular**
1. የተዛመተ. It is a popular belief that black cats bring bad luck. ጥቁር ፡ ድመቶች ፡ መጥፎ ፡ ዕድል ፡ ያመጣሉ ፡ የሚል ፡ የተዛመተ ፡ እምነት ፡ አለ
2. ሕዝቡን ፡ የሚወክል. Some countries have popular governments. አንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ሕዝቡን ፡ የሚወክል ፡ መንግሥት ፡ አላቸው
3. የሕዝብ. Popular discontent has grown lately. በቅርቡ ፡ የሕዝብ ፡ ቅሬታ ፡ እያደገ ፡ ሄዷል
4. ለተራ ፡ ሰው ፡ ሊገባ ፡ የሚችል. He gives popular lectures on science. ለተራ ፡ ሰው ፡ ሊገባ ፡ የሚችል ፡ የሳይንስ ፡ ትምህርት ፡ ይሰጣል

5. መጠነኛ. These meals are at popular prices. የዚህ ፡ ምግብ ፡ ዋጋ ፡ መጠነኛ ፡ ነው
6. ተወዳጅ. His good nature makes him popular. መልካም ፡ ጠባዩ ፡ ተወዳጅ ፡ ያደርገዋል
7. የተወደደ. Singing is very popular in America. ባሜሪካን ፡ አገር ፡ ዘፈን ፡ በጣም ፡ የተወደደ ፡ ነው
8. ዘመናዊ. They play only popular songs. ዘመናዊ ፡ ዘፈኖች ፡ ብቻ ፡ ይዘፍናሉ

**popular monthly** በየወሩ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚወጣ ፡ ጋዜጣ
He writes for a popular monthly. በየወሩ ፡ ለሕዝብ ፡ ለሚወጣ ፡ ጋዜጣ ፡ ጽሑፍ ፡ ያዘጋጃል

**popularity** ተወዳጅነት
His confident manner gained him popularity. ልበ ፡ ሙሉነቱ ፡ ተወዳጅነትን ፡ አተረፈለት

**popularize** በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ አደረገ
We need books to popularize sciences. ሳይንስን ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ለማድረግ ፡ መጽሐፎች ፡ ያስፈልጉናል

**populate** በብዛት ፡ ሰፈረ
Europeans populated America. አውሮፓውያን ፡ አሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ በብዛት ፡ ሰፍረዋል

**be populated** ሕዝብ ፡ ሰፈረበት
+The lowland areas are not densely populated. የቆላዎቹን ፡ ክፍሎች ፡ ሕዝብ ፡ በብዛት ፡ አልሰፈረባቸውም

**be thickly (densely) populated**
1. ሕዝብ ፡ ጥቅጥቅ ፡ አለበት. The industrial area is thickly populated. የኢንዱስትሪው ፡ ቀበሌ ፡ ሕዝብ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎበታል
2. ከፍ ፡ ያለ ፡ የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ አለው. The Gurage country is densely populated. የጉራጌ ፡ ክፍለ ፡ አገር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ አለው

**population**
1. ሕዝብ. The population of the city will be increased by the construction of the new highway. የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ ባዲሱ ፡ መንገድ ፡ መሠራት ፡ ይጨምራል
2. የሕዝብ ፡ ቁጥር. The population has almost doubled in the last twenty years. ባለፉት ፡ ሀያ ፡ ዓመታት ፡ የሕዝቡ ፡ ቁጥር ፡ ዕጥፍ ፡ ሊሆን ፡ ምንም ፡ አልቀረውም
3. የሕዝብ ፡ ብዛት. Addis Ababa exceeds Harar in size and population. አዲስ ፡ አበባ ፡ ሐረርን ፡ በስፋትና ፡ በሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ይበልጠዋል
4. በሕዝብ ፡ መሞላት. The gold rush speeded the population of California. ለወርቅ ፡ የተደረገው ፡ ሽሚያ ፡ የካሊፎርኒያን ፡ በሕዝብ ፡ መሞላት ፡ አፋጠነው
*The government is encouraging the population of forest areas. ሕዝቡ ፡ ጫካማ ፡ በሆኑ ፡ ስፍራዎች ፡ እንዲሰፍር ፡ መንግሥት ፡ ያበረታታል

**populous** የተጨናነቀ
It is unpleasant to live in a populous city. በተጨናነቀ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ አያስደስትም

**porcelain** የሸክላ
He poured his coffee into a porcelain cup. ቡናውን ፡ በሸክላ ፡ ሲኒ ፡ ቀዳ

**porch** ታዛ ፤ በረንዳ
I like to sit on the porch in hot weather. በሞቃት ፡ ጊዜ ፡ ከታዛ ፡ (ከበረንዳ) ፡ መቀመጥ ፡ እወዳለሁ

**porcupine** ጃርት
A porcupine dug up the ground. ጃርት ፡ መሬቱን ፡ ቈፈረች

**pore (over)**
1. አሰላሰለ. He pored over the strange events of the preceding evening. ባለፈው ፡ ምሽት ፡ ስለደረሱት ፡ አንዳንድ ፡ እንግዳ ፡ ነገሮች ፡ አሰላሰለ
2. ተደፋ. He would rather pore over a book than play. ከመጫወት ፡ ይልቅ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ መደፋት ፡ ይወዳል

**pore** (n.) የቆዳ ፡ ቀዳዳ
Perspiration goes through the pores. ላብ ፡ በቆዳ ፡ ቀዳዳ ፡ ውስጥ ፡ ይወጣል
*He was sweating from every pore. ላብ ፡ አስምጦት ፡ ነበር

**pork** ያሳማ ፡ ሥጋ
The Ethiopians do not eat pork. ኢትዮጵያውያን ፡ ያሳማ ፡ ሥጋ ፡ አይበሉም

**porous** ውኃ ፡ የሚያሳልፍ
There is a stratum of porous rock beneath the soil. ካፈሩ ፡ ሥር ፡ ውኃ ፡ የሚያሳልፍ ፡ የድንጋይ ፡ ድርብርብ ፡ አለ

**be porous** ጥቃቅን ፡ ቀዳዳዎች ፡ አለው
Cloth and blotting paper are porous. ጨርቅና ፡ ማምጠጫ ፡ ወረቀት ፡ ጥቃቅን ፡ ቀዳዳዎች ፡ አሏቸው

**porridge** ገንፎ
They prepared the porridge for the guests. ለእንግዶች ፡ ገንፎ ፡ አገነፉ

**port** ወደብ
The ship was at anchor in the port. መርከቡ ፡ መልሕቁን ፡ ጥሎ ፡ ወደቡ ፡ ላይ ፡ ቆሟል

**portable**
1. የእጅ. I want to buy a portable radio. የእጅ ፡ ሬድዮ ፡ ልገዛ ፡ እፈልጋለሁ
2. ቀላል ፤ ትንሽ. A portable typewriter can be moved from place to place. ቀላል ፡ (ትንሽ) ፡ የጽሕፈት ፡ መኪና ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ ሊዘዋወር ፡ ይችላል

**portal** ትልቅ ፡ በር
The portal in front of the palace is built of stone. ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያለው ፡ ትልቁ ፡ በር ፡ ከድንጋይ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**portend**
1. መምጣት ፡ አመለከተ. Black clouds portend a storm. የጨለመው ፡ ደመና ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ መምጣቱን ፡ ያመለክታል
2. የሚመጣ ፡ መሆኑን ፡ አሳየ. The street disturbances may portend a general uprising. በመንገድ ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ሁከት ፡ ጠቅላላ ፡ ሽብር ፡ የሚመጣ ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል

**portent, be a ~** የሚከተል ፡ መሆኑን ፡ አመለከተ
The black clouds were a portent of bad weather. የጨለመው ፡ ደመና ፡ መጥፎ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ የሚከተል ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል

**porter**
1. ተሸካሚ ፤ ኩሊ. Shall I call a porter? ተሸካሚ ፡ (ኩሊ) ፡ ልጥራ ?
2. በረኛ. When he arrived at the hotel, the porter carried his baggage. ሆቴሉ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በረኛው ፡ እቃውን ፡ ተሸከመለት

**portfolio** ቦርሳ
I got a leather portfolio for my birthday. ለልደቴ ፡ የቆዳ ፡ ቦርሳ ፡ ተሰጠኝ

**without portfolio**
*He was appointed minister without portfolio in the reshuffle. ባዲሱ ፡ የሚኒስትሮች ፡ መለዋወጥ ፡ ውስጥ ፡ የሚኒስትርነት ፡ ሹመት ፡ ካልተወሰነ ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ ተሰጠው

**portion** (v.) አከፋፈለ
The mother portioned the candy evenly among the children. እናቲቱ ፡ ከረሜላውን ፡ ለልጆቹ ፡ በትክክል ፡ አከፋፈለች

**portion out** አከፋፈለ
She portioned out the food. ምግቡን ፡ አከፋፈለች

**portion** (n.)
1. ክፋል. He ceded a portion of his land to the government. ከመሬቱ ፡ ክፋሉን ፡ ለመንግሥት ፡ ለቀቀ
2. ድርሻ. My portion is larger than his. የኔ ፡ ድርሻ ፡ ከሱ ፡ ይበልጣል
*Do they always serve such small portions? ዘወትር ፡ የሚያቀርቡት ፡ ምግብ ፡ እንደዚህ ፡ ትንሽ ፡ ነው ?

**tear off a portion** ቈረሰ
Tear off a portion of the bread and dip it in the sauce! ከእንጀራው ፡ ቈርሰህ ፡ ወጡን ፡ አጥቅስ

**portly** ወፍራም
The portly gentleman was out of breath from climbing the steps. ወፍራሙ ፡ ሰውዬ ፡ ደረጃውን ፡ ሲወጣ ፡ ትንፋሹ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ አለ

**be portly** ባለግርማ ፡ ሆነ
A judge's bearing should be portly. የዳኛ ፡ ቁመና ፡ ባለግርማ ፡ መሆን ፡ አለበት

**portrait**
1. ሥዕል. I have a portrait of my father. ያባቴ ፡ ሥዕል ፡ አለኝ
2. የሰው ፡ ሥዕል. Who painted the portrait? ይህን ፡ የሰው ፡ ሥዕል ፡ ማን ፡ ሣለ ?

**portray**
1. ገለጸ. This book portrays life in medieval Europe. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የአውሮፓውያንን ፡ የመካከለኛ ፡ ዘመን ፡ አኗኗር ፡ ይገልጻል
2. ሣለ. The artist portrayed the sunny field in brilliant colors. የፀሐዩ ፡ ብርሃን ፡ ያረፈበትን ፡ ሜዳ ፡ ሠዓሊው ፡ በብሩህ ፡ ቀለማት ፡ ሣለው
3. እንደ --- ሆኖ ፡ ሠራ. The actor portrays a doctor. ተዋናዩ ፡ እንደ ፡ ሐኪም ፡ ሆኖ ፡ ይሠራል

**portrayal** ማሳየት
She is weak in the portrayal of tragic roles. አሳዛኝ ፡ ድርጊቶችን ፡ በማሳየት ፡ ረገድ ፡ ደካማ ፡ ናት

**give a portrayal** አስረዳ
The book gives an accurate portrayal of eighteenth-century life. መጽሐፉ ፡ የዐሥራ ፡ ስምንተኛውን ፡ መቶኛ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ኑሮ ፡ በትክክል ፡ ያስረዳል

**pose** (vt.)
1. አስቀመጠ. The artist posed the children around their mother. ሠዓሊው ፡ ልጆቹን ፡ በእናታቸው ፡ ዙሪያ ፡ አስቀመጣቸው

2. ፈጠረ. The slums pose a problem for the city. የቆሸሹ ፡ መኖሪያ ፡ ቤቶች ፡ ለከተማው ፡ ንጽሕና ፡ ችግር ፡ ይፈጥራሉ

**pose** (vi.) ተቀመጠ
Who posed for the painting? ለሥዕሉ ፡ ማን ፡ ተቀመጠለት ?

**pose as** ባደባባይ ፡ መስሎ ፡ ታየ ፤ መስሎ ፡ ታየ ፤ ለይምሰል ፡ እንደ --- ፡ ሆነ
He poses as a war hero though he had never been in battle. ጦር ፡ ሜዳ ፡ ሳይውል ፡ ባደባባይ ፡ ጀግና ፡ መስሎ ፡ ይታያል
He posed as an expert on African affairs. ስለ ፡ አፍሪካ ፡ ጉዳዮች ፡ ዐዋቂ ፡ መስሎ ፡ ታየ
She poses as an invalid when really she is well and strong. ጠንካራና ፡ ደኅና ፡ ሆና ፡ ሳለች ፡ ለይምሰል ፡ እንደ ፡ አካለ ፡ ጐደሎ ፡ ትሆናለች

**pose** (n.)
1. መዋሸት. His pose was discovered when they gave him a test and he failed to pass it. ፈተና ፡ ሰጥተውት ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ መዋሸቱ ፡ ታወቀበት
2. ለይስሙላ. His kindness is a pose. የሱ ፡ ደግነት ፡ ለይስሙላ ፡ ነው
3. ሁኔታ. Her pose was aristocratic. ሁኔታዋ ፡ የእመቤትነት ፡ ነበር
**take the pose of** ለይምሰል ፡ እንደ ፡ --- ሆነ
She takes the pose of being an invalid when really she is well and strong. ጠንካራና ፡ ደኅና ፡ ሆና ፡ ሳለች ፡ ለይምሰል ፡ እንደ ፡ አካለ ፡ ጐደሎ ፡ ትሆናለች

**position**
1. ሥራ. He has a good position with a wholesale house. በጅምላ ፡ ከሚሸጡበት ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ ጥሩ ፡ ሥራ ፡ አለው
2. ቦታ ፤ ደረጃ. He has a good position in the government. በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ደኅና ፡ ቦታ ፡ አለው
He has attained a high position in the government. በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ደርሷል
3. ሁኔታ. A man in your position has to be careful of his appearance. ባንተ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ለሰውነቱ ፡ መጠንቀቅ ፡ አለበት
This places me in a very difficult position. ይህ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ይጥለኛል
4. ሥልጣን. My uncle is a person of wealth and position. አጐቴ ፡ ሀብትና ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው
He was my precursor in this position. በዚህ ፡ ሥልጣን ፡ እሱ ፡ የኔ ፡ ተቀዳሚ ፡ ነበር
5. አኳኋን. I had to sit in an uncomfortable position on the bus. በአውቶቡሱ ፡ ላይ ፡ በማይመች ፡ አኳኋን ፡ መቀመጥ ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ
6. ይዞታ ፤ ስፍራ. The enemy counterattacked our position last night. ጠላት ፡ ትላንት ፡ ማታ ፡ ይዞታችንን ፡ ዐጸፋውን ፡ መለሰ
He marked the enemy positions on a chart. ጠላት ፡ ያለበትን ፡ ስፍራ ፡ በካርታ ፡ አመለከተ
7. አቋም. What is your position on this problem? በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ያንተ ፡ አቋም ፡ ምንድን ፡ ነው ?
8. የሚያምንበት ፡ ሐሳብ. The director declared his position in the controversy. ዲሬክተሩ ፡ በንትርኩ ፡ ጊዜ ፡ የሚያምንበትን ፡ ሐሳብ ፡ ገለጸ
*Put the baby in a comfortable position. ሕፃኑን ፡ አመቻችተህ ፡ አስቀምጠው

**be in a position** ቻለ
I am not in a position to pay right away. አሁኑኑ ፡ ልከፍል ፡ አልችልም

**positive**
1. እርግጠኛ. I am positive it's not mine. እርግጠኛ ፡ ነኝ ፤ የኔ ፡ አይደለም
2. ቁርጥ ፡ ያለ. "No, I will not do it" was his positive refusal. የለም ፤ አላደርገውም ፡ ሲል ፡ ቁርጥ ፡ ያለውን ፡ እምቢታውን ፡ ገለጸ
3. የእሺታ. I expect a positive answer. የእሺታ ፡ መልስ ፡ እጠባበቃለሁ
4. መልካም. Do you have positive things to say about the painting? ስለ ፡ ሥዕሉ ፡ የምታቀርበው ፡ መልካም ፡ አስተያየት ፡ አለ ?
5. ጠቃሚ. He gave us positive help. ጠቃሚ ፡ እርዳታ ፡ አደረገልን
6. ወንዴ. A positive charge should not come in contact with a negative charge by accident. ወንዴና ፡ ሴቴ ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ኀይል ፡ ባጋጣሚ ፡ እንዳይገናኙ ፡ ያስፈልጋል
*He never has any positive suggestions for our problems. ለችግራችን ፡ ማቃለያ ፡ የሚረዱ ፡ ሐሳቦች ፡ አቅርቦልንም ፡ አያውቅም

**be positive** በሽታው ፡ እንዳለበት ፡ አመለከተ
The tuberculosis test was positive. የሳምባ ፡ ነቀርሳው ፡ ምርመራ ፡ በሽታው ፡ እንዳለበት ፡ አመለከተ

**positive manner** ዐዋቂ ፡ ነኝ ፡ ባይነት
Her positive manner annoys people. ዐዋቂ ፡ ነኝ ፡ ባይነቷ ፡ ሰዎችን ፡ ያበሳጫል

**positively** በእርግጥ
Do you know it positively? በእርግጥ ፡ ታውቀዋለህ ?

**possess**

1. አለ(ው). +He possesses a house and a car. ቤትና ፡ መኪና ፡ አለው
He possesses great wisdom. ታላቅ ፡ ጥበብ ፡ አለው
2. ያዘ. At one time, the Spanish possessed Florida. ድሮ ፡ እስፓኞች ፡ ፍሎሪዳን ፡ ይዘው ፡ ነበር
3. ወረረ. Fear suddenly possessed her. ፍርሃት ፡ ሰውነቷን ፡ ወረረው
4. ገፋፋ. I don't know what possesses him to act like that. እንደዚህ ፡ እንዲያደርግ ፡ የሚገፋፋው ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ አላውቅም
5. አደረ(በት). She thought that a spirit possessed her. ዛር ፡ ያደረባት ፡ መሰላት

**possessed** የተለከፈ
He cried like one possessed. እንደተለከፈ ፡ ሰው ፡ ጮኸ

**be possessed** ተዋጠ
He is possessed by the idea that someone is persecuting him. አንድ ፡ ሰው ፡ ሊያጠቃኝ ፡ ይፈልጋል ፡ በሚል ፡ ሐሳብ ፡ ተውጧል
[See also 'spirit']

**possession**

1. ንብረት. They lost all their possessions. መላው ፡ ንብረታቸው ፡ ጠፋ
2. በእጅ ፡ ማድረግ. The soldiers fought hard for the possession of the hilltop. ወታደሮቹ ፡ የኮረብታቸውን ፡ ጫፍ ፡ በእጃቸው ፡ ለማድረግ ፡ በኀይል ፡ ተዋጉ
3. ግዛት. Great Britain has granted independence to most of her overseas possessions. ታላቋ ፡ ብሪታንያ ፡ ለብዙዎች ፡ የባሕር ፡ ማዶ ፡ ግዛቶቿ ፡ ነጻነት ፡ ሰጥታለች
*Is the woman in full possession of her senses? ሴትዮዋ ፡ ጤና ፡ የላትም ?

**be in one's possession** በሱ ፡ እጅ ፡ ገባ
How long has that been in your possession? ያ ፡ ባንተ ፡ እጅ ፡ ከገባ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜው ፡ ነው ?

**come into possession**
1. ባለቤት ፡ ሆነ. He came into possession of a large estate. የትልቅ ፡ ርስት ፡ ባለቤት ፡ ሆነ
2. እጁ ፡ ውስጥ ፡ ገባ. When did this medal come into your possession? ይህ ፡ ሜዳይ ፡ እጅህ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ መቼ ፡ ነው ?

**get possession of** ወሰደ
The pirate tried to get possession of the treasure. ወንበዴው ፡ ሀብቱን ፡ ለመውሰድ ፡ ሞከረ

**take full possession** በቁጥጥር ፡ ሥር ፡ አደረገ
The new cook took full possession of our kitchen. አዲሱ ፡ ወጥ ፡ ቤት ፡ ማእድ ፡ ቤታችንን ፡ በቁጥጥር ፡ ሥር ፡ አደረገው

**take possession** ተረከበ
The new owner hasn't taken possession of the house yet. አዲሱ ፡ ባለቤት ፡ ገና ፡ ቤቱን ፡ አልተረከበም

**possessive** ሁሉ ፡ የሚቈጣጠር
He has a very possessive mother and has to consult with her before he goes anywhere or does anything. ሁሉ ፡ የምትቈጣጠረው ፡ እናት ፡ ስላለችው ፡ ሲወጣ ፡ ሲገባ ፡ እሷን ፡ ማማከር ፡ አለበት

**be possessive** የራሱ ፡ የማድረግ ፡ መንፈስ ፡ አለው
A young child is so possessive that he will not allow another to play with his toys. ሕፃን ፡ እቃን ፡ የራሱ ፡ የማድረግ ፡ መንፈስ ፡ ስላለው ፡ መጫወቻውን ፡ ሌላ ፡ እንዲነካበት ፡ ፈጽሞ ፡ አይፈቅድም

**possessive pronoun** አገናዛቢ ፡ ተውላጠ ፡ ስም
"Mine" is a possessive pronoun. « የኔ » ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ አገናዛቢ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ነው

**possessor** ባለቤት
The possessor of movable property must pay a certain tax. የተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ባለቤት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ አለበት
The house remained in the hands of the same possessor for many years. ቤቱ ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ ባንድ ፡ ባለቤት ፡ እጅ ፡ ቆየ

**possibility** (possibilities)

1. መንገድ. I see no other possibility. ሌላ ፡ መንገድ ፡ አይታየኝም
2. ምርጫ. Outside of this, there's no other possibility. ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ምርጫ ፡ የለም
3. የሚቻል. Let's not confuse possibility with probability! የሚቻልን ፡ ከይሆናል ፡ ጋር ፡ አናማታ
4. ለወደፊት ፡ ውጤት. I see great possibilities in this plan. በዚህ ፡ እቅድ ፡ ውስጥ ፡ ለወደፊቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ውጤት ፡ ይታየኛል
*There is no possibility of his coming now. አሁን ፡ ለመምጣት ፡ የሚችልበት ፡ መንገድ ፡ የለም
*Is there any possibility that you will go to Ethiopia this year? በዚህ ፡ ዓመት ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምትሄድ ፡ ይመስልሃል ?

**be a possibility** ስ + negative imperfect + አይቀርም
A whole week of rain is a possibility. ሳምንቱን ፡ በሙሉ ፡ ሳይዘንብ ፡ አይቀርም

**possible**
1. ሊደርስበት ፡ የሚችል. Are you insured against all possible accidents? ሊደርስብህ ፡ ለሚችል ፡ አደጋ ፡ ሁሉ ፡ ዋስትና ፡ አለህ ?
2. ሊስማማ ፡ የሚችል. He is the only possible man for the position. ለሥራው ፡ ሊስማማ ፡ የሚችል ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ነው
*There are two possible routes to Harar. ወደ ፡ ሐረር ፡ የሚወስድ ፡ ሁለት ፡ መንገድ ፡ አለ

**be possible**
1. ሊሆን ፡ ቻለ. That's quite possible. ያ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ነው
2. gerundive + ይሆናል. It is possible that he went. ሄዶ ፡ ይሆናል

**make possible** አስቻለ
Canning makes the preservation of food possible. በጣሳ ፡ ማሸግ ፡ ምግብን ፡ በደኅና ፡ ሁኔታ ፡ ለመጠበቅ ፡ ያስችላል

**possibly** ምናልባት
Are you going to get a raise? Possibly. የደሞዝ ፡ ጭማሪ ፡ ልታገኝ ፡ ነው ? ምናልባት
Could you possibly call me? ምናልባት ፡ ልትደውልልኝ ፡ ትችላለህ ?
*They cannot possibly arrive before midnight. ከእኩለ ፡ ሌሊት ፡ በፊት ፡ ሊገቡ ፡ አይችሉም
*I can't possibly go. የምሄድ ፡ አይመስለኝም
*He works as fast as he possibly can. በሚቻለው ፡ ፍጥነት ፡ ይሠራል

**post** (v.)
1. መደበ (ተመደበ). There were soldiers posted at the bridge. ድልድዩ ፡ አጠገብ ፡ የተመደቡ ፡ ወታደሮች ፡ ነበሩ
2. አቆመ. The captain posted guards at the door. ሻምበሉ ፡ በሩ ፡ ላይ ፡ ዘብ ፡ አቆመ
3. ለጠፈ. Post no bills! ማስታወቂያ ፡ አትለጥፍ
4. ፖስታ ፡ ቤት ፡ አስገባ. I posted the letter yesterday. ደብዳቤውን ፡ ትናንት ፡ ፖስታ ፡ ቤት ፡ አስገባሁ

**keep one posted** ጻፈ(ለት)
Keep me posted on what happens while I am gone. በሌለሁበት ፡ ጊዜ ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጻፍልኝ
*Informers keep him posted. ወሬ ፡ አቀባዮች ፡ የሚደረገው ፡ ሁሉ ፡ እንዳያመልጠው ፡ ወሬ ፡ ያቀብሉታል

**post** (n.)
1. እጠና ፤ ምሰሶ. We need posts for our fence. ላጥራችን ፡ እጠና ፡ ያስፈልገናል
The post is fast in the ground. ምሰሶው ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ ጠብቆ ፡ ተተክሏል
2. ችካል. The workers planted posts along the road. ሠራተኞቹ ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ችካል ፡ ቸከሉ
3. የተመደበበት ፡ ቦታ. A good soldier never deserts his post. ጥሩ ፡ ወታደር ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የተመደበበትን ፡ ቦታ ፡ አይለቅም
4. ስፍራ. He was given the post of school director. የትምህርት ፡ ቤት ፡ ዲሬክተርነት ፡ ስፍራ ፡ ተሰጠው
5. ፖስታ. I shall send the package by post. ጥቅሉን ፡ በፖስታ ፡ እልካለሁ
[See also 'border']

**postage** (n.) ቴምብር
Postage due: twenty cents. የቴምብር ፡ ቀረጥ ፡ ሃያ ፡ ሳንቲም ፡ ነው

**postage** (adj.) የፖስታ
Postage stamps are printed in every country. የፖስታ ፡ ቴምብሮች ፡ በያገሩ ፡ ይታተማሉ

**postal** የፖስታ
The postal service is very good in the country. ያገሪቱ ፡ የፖስታ ፡ አገልግሎት ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነው

**postbox** የደብዳቤ ፡ ማጠራቀሚያ
The postboxes are painted red. የደብዳቤ ፡ ማጠራቀሚያዎቹ ፡ ቀይ ፡ ተቀብተዋል

**postcard** ካርድ
Postcards showing the palace are sold here. የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሥዕል ፡ ያለባቸው ፡ ካርዶች ፡ እዚህ ፡ ይሸጣሉ

**poster** ሥዕላዊ ፡ መግለጫ
The Tourist Office has several posters showing Ethiopia's antiquities. የቱሪስት ፡ ድርጅት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥንታዊነት ፡ የሚገልጹ ፡ ብዙ ፡ ሥዕላዊ ፡ መግለጫዎች ፡ አሉት

**posterior** የኋለኛ
The posterior part of the building was damaged by an earthquake. የሕንጻው ፡ የኋለኛ ፡ ክፍል ፡ በመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ምክንያት ፡ ተጐድቷል

**be posterior** በኋላ ፡ ነው
The Time of the Judges is posterior to the Solomonic restoration. የመሳፍንት ፡ ዘመን ፡ ከሰሎሞን ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ዳግመኛ ፡ መነሣት ፡ በኋላ ፡ ነው

**posterity** ወደፊት ፡ የሚመጣው ፡ ትውልድ
His poetry will be admired by posterity. የርሱ ፡ ግጥም ፡ ወደፊት ፡ በሚመጣው ፡ ትውልድ ፡ የሚደነቅ ፡ ይሆናል

**posthumously**
1. ከሞተ ፡ በኋላ. The book was published posthumously. መጽሐፉ ፡ የታተመው ፡ ደራሲው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ነው
2. ካባቱ ፡ ሞት ፡ በኋላ. The child was born posthumously. ሕፃኑ ፡ ካባቱ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ተወለደ

**postman** ፖስታ ፡ አመላላሽ ፤ ፖስተኛ
Has the postman come yet? ፖስታ ፡ አመላላሹ ፡ (ፖስተኛው) ፡ ገና ፡ አልመጣም ?

**postmark** (n.) የፖስታ ፡ ቤት ፡ ማኅተም
The postmark on this letter shows it was mailed last week. በዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የፖስታ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ እንደተላከ ፡ ያሳያል

**(be) postmarked** የፖስታ ፡ ቤት ፡ ማኅተም ፡ አለበት
This letter is postmarked May 15. ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ ግንቦት ፡ ዐሥራ ፡ እምስት ፡ የሚል ፡ የፖስታ ፡ ቤት ፡ ማኅተም ፡ አለበት

**post office** ፖስታ ፡ ቤት
The post office is closed on Sunday. ፖስታ ፡ ቤቱ ፡ እሑድ ፡ ዝግ ፡ ነው

**post office box**
1. የፖስታ ፡ ሣጥን. He picks up his letters from the post office box. ደብዳቤዎቹን ፡ ከፖስታው ፡ ሣጥን ፡ ይወስዳል
2. የፖስታ ፡ ሣጥን ፡ ቁጥር. My post office box is 229. የኔ ፡ ፖስታ ፡ ሣጥን ፡ ቁጥር ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ ዘጠኝ ፡ ነው

**postpone** አስተላለፈ
I can't postpone the appointment. ቀጠሮውን ፡ ላስተላልፈው ፡ አልችልም

**be postponed** ተላለፈ
The game was postponed on account of the rain. ጨዋታው ፡ በዝናቡ ፡ ምክንያት ፡ ተላለፈ

**postscript** ከደብዳቤ ፡ ግርጌ ፡ ያለ ፡ ተጨማሪ
The postscript was written in pencil, but the letter is typed. ከደብዳቤው ፡ ግርጌ ፡ ያለው ፡ ተጨማሪ ፡ የተጻፈው ፡ በእርሳስ ፡ ሲሆን ፡ ደብዳቤው ፡ ግን ፡ በመኪና ፡ ነው

**postulate** (v.) አመለከተ
To tell someone to do a thing postulates that it can be done. አንድ ፡ ሰው ፡ አንድን ፡ ነገር ፡ እንዲያደርግ ፡ መንገር ፡ ሊደረግ ፡ መቻሉን ፡ ያመለክታል

**postulate** (n.) መሠረተ ፡ ነገር
One postulate of geometry is that a straight line may be drawn between any two points. ከጂዎሜትሪ ፡ መሠረተ ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ በሁለት ፡ ነጥቦች ፡ መካከል ፡ ቀጥተኛ ፡ መሥመር ፡ ይሠመራል ፡ የሚል ፡ ነው

**posture**
1. የሰውነት ፡ አቋም. Good posture is important for health. ጥሩ ፡ የሰውነት ፡ አቋም ፡ ለጤንነት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው
2. ሁኔታ. In the present posture of public affairs, it is difficult to invest money safely. ባሁኑ ፡ የሕዝብ ፡ ሁኔታ ፡ ገንዘብን ፡ ያለፍርሃት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ከባድ ፡ ነው

**pot**
1. ሸክላ. I bought many different kinds of pots while I was in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ በነበርኩበት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ሸክላዎች ፡ ገዛሁ
2. ማሰሮ. Put the pot on the fire! I need some hot water. ማሰሮውን ፡ ጣደው ፤ ሙቅ ፡ ውኃ ፡ እፈልጋለሁ

**go to pot**
1. ወደቀ. The store went to pot. መደብሩ ፡ ወድቋል
2. ከሸፈ. Our plans went to pot. እቅዳችን ፡ ከሸፈ
[See also 'coffeepot']

**potable** ለመጠጥ ፡ የሚሆን
This water is potable. ይህ ፡ ውኃ ፡ ለመጠጥ ፡ የሚሆን ፡ ነው

**potash** ፖታሽ
Potash is obtained from deposits in the desert. ፖታሽ ፡ ከበረኻ ፡ ውስጥ ፡ ተከማችቶ ፡ ይገኛል

**potato** (potatoes) ድንች
He eats boiled potatoes. የተቀቀለ ፡ ድንች ፡ ይበላል

**potent**
1. ኀይለኛ. The doctor prescribed a potent medicine. ሐኪሙ ፡ ኀይለኛ ፡ መድኃኒት ፡ አዘዘ
Only a potent ruler could restore order. ሁከትን ፡ መልሶ ፡ ማረጋጋት ፡ የሚችል ፡ ኀይለኛ ፡ መሪ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. የሚያስተማምን. Several potent arguments were in his favor. የሚያስተማምኑ ፡ ብዙ ፡ ማስረጃዎች ፡ ደግፈውታል

**potentate** ገዥ
A Middle Eastern potentate is going to visit Washington. አንድ ፡ የመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ገዥ ፡ ዋሽንግተንን ፡ ሊጐበኝ ፡ ነው

**potential** (n.)
*The child shows great potential. ሕፃኑ ፡ ሊበለጽግ ፡ የሚችል ፡ ችሎታ ፡ አለው

**potential,** adj. (= adv.) ወደፊት
The potential sales of this book are great. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ወደፊት ፡ ብዙ ፡ ገበያ ፡ ይኖረዋል
He has the character of a potential leader. ወደፊት ፡ መሪ ፡ ለመሆን ፡ የሚያስችል ፡ ባሕሪይ ፡ ይታይበታል
*There is a potential danger of being bitten when playing with a dog. ከውሻ ፡ ጋር ፡ ሲጫወቱ ፡ መነከስም ፡ አለ

**potentiality** (potentialities)
1. ወደፊት ፡ ለማልማት ፡ የሚቻልበት ፡ ሁኔታ. The conference is discussing the potentialities of the Awash valley. ጉባኤው ፡ የአዋሽን ፡ሸለቆ ፡ ወደፊት ፡ ለማልማት ፡ የሚቻልበትን ፡ ሁኔታ ፡ ይነጋገራል
2. ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ ነገር. Atomic destruction is a grim potentiality. የአቶሚክ ፡ እጥፋነት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችል ፡ አሰቃቂ ፡ ነገር ፡ ነው

**potion** መድኃኒት
The sorcerer put a sleeping potion in the man's drink. ጠንቋዩ ፡ በሰውዬው ፡ መጠጥ ፡ ውስጥ ፡ የሚያስተኛ ፡ መድኃኒት ፡ ጨመረበት

**potsherd** የሸክላ ፡ ስብርባሪ
The archeologist made a collection of potsherds found at Axum. አርኪዎሎጂስቱ ፡ አክሱም ፡ የተገኙትን ፡ የሸክላ ፡ ስብርባሪዎች ፡ ሰበሰበ

**potter** (v.) ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ
He pottered around the house all day. እቤት ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲል ፡ ዋለ

**potter** (n.) ሸክላ ፡ ሠሪ
The potter makes pots for the entire neighborhood. ሸክላ ፡ ሠሪው ፡ ለአካባቢው ፡ መንደር ፡ በሙሉ ፡ የሸክላ ፡ እቃ ፡ ይሠራል

**pottery** (potteries)
1. ሸክላ. In this village, women make pottery. በዚህ ፡ መንደር ፡ ያሉ ፡ ሴቶች ፡ ሸክላ ፡ ይሠራሉ
2. የሸክላ ፡ ሥራ. Is this clay good for pottery? ይህ ፡ አፈር ፡ ለሸክላ ፡ ሥራ ፡ ጥሩ ፡ ነው ?

**pouch** ከረጢት
The traveler carried his provisions in a large pouch. መንገደኛው ፡ ሥንቁን ፡ በትልቅ ፡ ከረጢት ፡ ተሸከመ
The old man has pouches under his eyes. የሽማግሌው ፡ ሰው ፡ ዓይኑ ፡ ከረጢት ፡ ያበጃል ፡ (or, ዓይኑ ፡ ተንቋርዟል)

**poultry** ዶሮ
The raising of poultry is being encouraged by the government. መንግሥቱ ፡ የዶሮ ፡ ርቢን ፡ ያበረታታል

**pounce** ድንገት ፡ ወርዶ ፡ ያዘ
The hawk pounced on the pigeon. ጭልፊቷ ፡ ርግቧን ፡ ድንገት ፡ ወርዳ ፡ ያዘቻት

**pound** (vt.)
1. ሸከሸከ. The women pounded the grain to remove the hulls. ሴቶች ፡ እህሉን ፡ ለመፈተግ ፡ ሸከሸኩት
2. ወቀጠ. The woman pounded wheat in a mortar. ሴትዮዋ ፡ ስንዴውን ፡ በሙቀጫ ፡ ወቀጠች
3. ደበደበ. He pounded the door with his fists. በሩን ፡ በጡጫ ፡ ደበደበ
4. መታ. He pounded nails into the wall. ግድግዳው ፡ ላይ ፡ ምስማር ፡ መታ

**pound** (vi.)
1. ተመታ. We could hear drums pounding in the distance. ከሩቅ ፡ ከበሮ ፡ ሲመታ ፡ ይሰማን ፡ ነበር
2. በኀይል ፡ መታ. His heart was pounding with excitement. ልቡ ፡ በድንጋጤ ፡ በኀይል ፡ ይመታ ፡ ነበር

**pound against** ገረፈ
Waves pounded against the seashore. ማዕበሉ ፡ የባሕሩን ፡ ዳርቻ ፡ ገረፈው

**pound on**
1. ደበደበ. We pounded on the door for five minutes before they heard us. እነሱ ፡ ከመስማታቸው ፡ በፊት ፡ አምስት ፡ ደቂቃ ፡ ሙሉ ፡ መዝጊያውን ፡ ስንደበድብ ፡ ነበር
2. ደለደለ. They hardened the earth by pounding on it. መሬቱን ፡ ደልድለው ፡ አጠነከሩት

**pound** (n.)
1. ነጥር. She bought two pounds of sugar. ሁለት ፡ ነጥር ፡ ስኳር ፡ ገዛች
2. ፓውንድ. This book cost five English pounds. የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ዋጋ ፡ አምስት ፡ የእንግሊዝ ፡ ፓውንድ ፡ ነው

**pour** (vt.)

1. ቀዳ. Please pour me a cup of coffee! እስቲ ፡ አንድ ፡ ሲኒ ፡ ቡና ፡ ቅዳልኝ
2. አጠጣ. The plants drank up the water I poured on them. ተክሎቹ ፡ ያጠጣኋቸውን ፡ ውኃ ፡ መጠጡት
3. ገለበጠ. He poured the coffee from the coffeepot into a jug. ቡናውን ፡ ከጀበናው ፡ ማንቆርቆሪያው ፡ ውስጥ ፡ ገለበጠ
4. አፈሰሰ. He poured a lot of money into this business. ንግዱ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አፈሰሰ
John had a rude shock when the other boys poured a pail of water on him. ጆን ፡ ልጆቹ ፡ አንድ ፡ ባልዲ ፡ ውኃ ፡ ባፈሰሱበት ፡ ጊዜ ፡ ደነገጠ
5. ጨመረ. The fire flared up when I poured some gasoline on it. ቤንዚን ፡ ብጨምርበት ፡ ጊዜ ፡ እሳት ፡ ቦግ ፡ አለ
6. አወረደ. They poured scorn on their rivals. በተወዳዳሪዎቻቸው ፡ ላይ ፡ የስድብ ፡ መዓት ፡ አወረዱባቸው

**pour** (vi.)

1. ፈሰሰ. Water pours from the broken pipe. ከተሰበረው ፡ ቧንቧ ፡ ውኃ ፡ ይፈሳል
2. ዶፍ ፡ ወረደ. It's pouring outside. እውጭ ፡ ዶፍ ፡ ይወርዳል
3. ወረደ. Wet salt will not pour from the shaker. እርጥብ ፡ ጨው ፡ ከብልቃጡ ፡ ውስጥ ፡ አይወርድም

**pour down**

1. ተንቆረቆረ. The sweat was pouring down his face. ላቡ ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ይንቆረቆር ፡ ነበር
2. ወረደ. The rain poured down. ዶፍ ፡ ወረደ

**pour out**

1. ፈሰሰ. The grain poured out of a hole in the sack. እህሉ ፡ በጆኒያው ፡ ቀዳዳ ፡ ፈሰሰ
2. ጐረፈ. The crowd was just then pouring out of the theater. ያኔ ፡ ሕዝቡ ፡ ገና ፡ ከቲያትሩ ፡ ይጐርፍ ፡ ነበር
3. የ --- መዓት ፡ አወረደ(በት). He poured out his insults on him. የስድብ ፡ መዓት ፡ አወረደበት

**pour over** አልፎ ፡ ፈሰሰ
The water poured over the dam after the heavy rain. ከባድ ፡ ዝናም ፡ ከጣለ ፡ በኋላ ፡ ውኃው ፡ ግድቡን ፡ አልፎ ፡ ፈሰሰ

**pout** ለምቦጩን ፡ ጣለ
The child pouted because his mother would not buy any candy for him. ልጁ ፡ እናቱ ፡ ከረሜላ ፡ ስላልገዛችለት ፡ ለምቦጩን ፡ ጣለ

**poverty**

1. ድኽነት. He is living in great poverty. በከባድ ፡ ድኽነት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል
2. (= adj.) ለም ፡ ያልሆነ. The poverty of the soil makes the crops small. ለም ፡ ያልሆነ ፡ አፈር ፡ እህል ፡ ያጫጫል
*A dull person's talk shows a poverty of ideas. ለዛ ፡ ቢስ ፡ ሰው ፡ የሚናገረው ፡ ነገር ፡ ጥሩ ፡ ሐሳብ ፡ ይጐድለዋል
[See also 'sordid']

**powder** (v.)

1. ፈጨ. The housewife powdered the sugar. የቤቷ ፡ እመቤት ፡ ስኳሩን ፡ ፈጨችው
2. ነሰነሰ. She powdered the cookies with sugar. ኬኩ ፡ ላይ ፡ ስኳር ፡ ነሰነሰች

**be powdered** በነነ(በት)
+The ground was lightly powdered with snow. መሬቱ ፡ በመጠኑ ፡ በረዶ ፡ በኖበታል

**powder** (n.)

1. ድማሚት. There is enough powder here to blow up the whole town. እዚህ ፡ ከተማውን ፡ በሙሉ ፡ ለማውደም ፡ በቂ ፡ ድማሚት ፡ አለ
2. ባሩድ. The powder is contained in a capsule. ባሩዱ ፡ በካምሱር ፡ ውስጥ ፡ ነው
3. ፑዱር. She uses face powder. ፊቷን ፡ ፑዱር ፡ ትቀባለች
4. ዱቄት. A powder made of sugar is sprinkled over the cake. በኬኩ ፡ ላይ ፡ የስኳር ፡ ዱቄት ፡ ተነስንሶ ፡ ነበር

**crush to a fine powder** ደቈሰ
She crushed the pepper to a fine powder. በርበሬውን ፡ ደቈሰችው

**(be) reduced to powder** ዱቄት ፡ ሆነ.
The chalk was reduced to powder. ጠመኔው ፡ ዱቄት ፡ ሆነ

**powdered** (adj.) ደቃቅ
The cook dusted the cake with powdered sugar. የወጥ ፡ ቤቲቱ ፡ በኬኩ ፡ ላይ ፡ ደቃቅ ፡ ስኳር ፡ ነሰነሰች

**powdered milk** ዱቄት ፡ ወተት
He likes to put powdered milk in his coffee. እቡናው ፡ ውስጥ ፡ ዱቄት ፡ ወተት ፡ መጨመር ፡ ይወዳል

**power**

1. ኀይል. The power of his blow split the wooden door. የምቱ ፡ ኀይል ፡ የዕንጨቱን ፡ መዝጊያ ፡ ተረተረው

Running water can be used to produce electric power. ወራጅ ፡ ውኃ ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ኀይል ፡ ለማስገኘት ፡ ያገለግላል

Water power is needed to bring electricity to houses in the country. ለባላገር ፡ ቤቶች ፡ ኮረንቲ ፡ ለማግባት ፡ የውኃ ፡ ኀይል ፡ ያስፈልጋል

Is the press a great power in your country? ባገርህ ፡ ጋዜጦች ፡ ኀይል ፡ አላቸው ?

2. ኮረንቲ. The explosion knocked out the power for several hours. ፈንጂው ፡ ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ኮረንቲውን ፡ አቋረጠው

3. ሥልጣን. The American Congress has the power to declare war. የአሜሪካ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጦርነት ፡ ለማወጅ ፡ ሥልጣን ፡ አለው

That's beyond my power. ያ ፡ ከሥልጣኔ ፡ በላይ ፡ ነው

How long were the Socialists in power? ሶሺያሊስቶቹ ፡ በሥልጣን ፡ ላይ ፡ ለስንት ፡ ጊዜ ፡ ቆዩ ?

4. ችሎታ. He is a man of great intellectual powers. ከፍተኛ ፡ የማሰብና ፡ የመመራመር ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

The chameleon has the power to change its color. እስስት ፡ መልኳን ፡ የመለዋወጥ ፡ ችሎታ ፡ አላት

5. ብርቱነት. The power of his argument won many to his side. የክርክሩ ፡ ብርቱነት ፡ ብዙዎቹን ፡ የሱ ፡ ወገን ፡ አደረጋቸው

**power failure** የኤሌክትሪክ ፡ ጉድለት

Because of a power failure, the station went off the air. በኤሌክትሪክ ፡ ጉድለት ፡ የተነሣ ፡ የሬዲዮው ፡ ፕሮግራም ፡ ተቋረጠ

**come into power** ሥልጣን ፡ ጨበጠ ፤ ሥልጣን ፡ ያዘ

When did the Republicans come into power? ሬፓብሊካኖች ፡ ሥልጣን ፡ የጨበጡት ፡ (የያዙት) ፡ መቼ ፡ ነው ?

**Great Powers** ኀያላን ፡ መንግሥታት

The Great Powers are going to hold a disarmament conference. ኀያላን ፡ መንግሥታት ፡ ስለ ፡ ጦር ፡ መሣሪያ ፡ ቅነሳ ፡ ስብሰባ ፡ ሊያደርጉ ፡ ነው

**in one's power** የሚችል ፤ የሚቻለው

I'll do everything in my power. የምችለውን ፡ (የሚቻለኝን) ፡ ሁሉ ፡ አደርጋለሁ

**(be) out of power** ከሥልጣን ፡ ወረደ

The Socialist Party is out of power. የሶሺያሊስቶቹ ፡ ፓርቲ ፡ ከሥልጣን ፡ ወርዷል

[See also 'legislative, mandatory, reasoning, will power']

## (be) powered by የ - - - ኀይል ፡ አለው

The machine is powered by an engine. መሣሪያው ፡ የሞተር ፡ ኀይል ፡ አለው

## powerful

1. ኀይለኛ. The powerful nation could not be defeated. ኀይለኛው ፡ መንግሥት ፡ ሊሸነፍ ፡ አልቻለም

They invented a powerful drug against malaria. የወባ ፡ ትንኝ ፡ ለመከላከያ ፡ ኀይለኛ ፡ መድኃኒት ፡ ፈጠሩ

My father is a large, powerful man. አባቴ ፡ በጣም ፡ ግዙፍና ፡ ኀይለኛ ፡ ናቸው

2. ጉልህ. He has a powerful voice. ጉልህ ፡ ድምፅ ፡ አለው

## (be) powerless ዓቅም ፡ አጣ

He was powerless to resist the temptation. ፈተናውን ፡ ለመቋቋም ፡ ዓቅም ፡ አጣ

## practicable ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የሚችል

He presented a practicable plan to combat the disease. በሽታውን ፡ ለመቋቋም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የሚችል ፡ እቅድ ፡ አቀረበ

## practical

1. ተገቢ. It's not very practical to take one's vacation in the rainy season. በዝናቡ ፡ ወራት ፡ ዕረፍት ፡ መውሰድ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

2. ሁኔታውን ፡ አይቶ ፡ የሚሠራ. He is a practical businessman and is therefore very successful. ሁኔታውን ፡ አይቶ ፡ የሚሠራ ፡ ነጋዴ ፡ ስለሆነ ፡ በጣም ፡ ተሳክቶለታል

3. በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የሚችል. Theoretically the plan is fine, but it is not very practical. በኀልዮ ፡ እቅዱ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ ግን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የሚችል ፡ አይደለም

4. (= adv.) በመሠረቱ. So many of our soldiers were killed that our victory was a practical defeat. ብዙዎቹ ፡ ወታደሮቻችን ፡ ስለሞቱ ፡ ማሸነፋችን ፡ በመሠረቱ ፡ የመሸነፍ ፡ ያህል ፡ ነው

**be practical**

1. የገንዘብ ፡ አያያዝ ፡ ዐወቀ. Her husband insists on handling the money because she is not very practical. ሴትዮዋ ፡ የገንዘብ ፡ አያያዝ ፡ ስለማታውቅ ፡ ባሏ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ ካልያዝኩት ፡ ይላል

2. (= trans.) ሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለ. His grandiose plan is too expensive to be practical. ከፍተኛ ፡ የሆነው ፡ እቅዱን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ወጪ ፡ ይጠይቃል

## practically

1. እንደሚበጅ ፡ አድርጎ. You have to look at things practically. ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ እንደሚበጅ ፡ አድርገህ ፡ መመልከት ፡ አለብህ

2. በተግባር. He knows machinery both practically and theoretically. መሣሪያዎችን ፡ በተግባርም ፡ በኀልዮም ፡ ያውቃል

3. በመሠረቱ. It is practically useless to protest. በመሠረቱ ፤ መቃወም ፡ ዋጋ ፡ የለውም
4. ለማለት ፡ ይቻላል. Their provisions were practically gone. ሥንቃቸው ፡ አልቋል ፡ ለማለት ፡ ይቻላል
*The movie is practically over. ሲኒማው ፡ ወደ ፡ ማለቂያው ፡ ተዳርሷል

**be practically out of** ምንም ፡ ያህል ፡ አልቀረው
I am practically out of cigarettes. ምንም ፡ ያህል ፡ ሲጋራ ፡ አልቀረኝ

**be practically the same** እጅግም ፡ አይለያዩ
Portuguese and Spanish are practically the same. የፖርቱጋልና ፡ የስፓኝ ፡ ቋንቋዎች ፡ እጅግም ፡ አይለያዩ

**practice** (v.)
1. ተለማመደ. He is practicing the piano. ፒያኖ ፡ ይለማመዳል
2. ፈጸመ. Do you practice what you preach? ለሰው ፡ የምትመክረውን ፡ ትፈጽማለህ ?
3. ሠራ. He has practiced medicine for twenty years. ሀያ ፡ ዓመት ፡ሙሉ ፡ በሕክምና ፡ ሠርቷል

**be practiced** ተሠራ(በት)
Circumcision has been practiced in Ethiopia since ancient times. ግርዘት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ይሠራበታል
[See also 'idolatry, law, moderation']

**practice** (n.)
1. ልማድ. We'll have to put a stop to the practice of working at night. ማታ ፡ ማታ ፡ የመሥራትን ፡ ልማድ ፡ ማቆም ፡ አለብን
I have made it a practice to get to work on time. ለሥራ ፡ በሰዓቱ ፡ መድረስን ፡ ልማድ ፡ አድርጌዋለሁ
2. ልምምድ. They did better after a little practice. ከጥቂት ፡ ልምምድ ፡ በኋላ ፡ የተሻለ ፡ አድርገው ፡ ሠሩት
3. ገቢር. Naval officers must understand both the theory and the practice of navigation. የባሕር ፡ መኰንኖች ፡ የመርከብ ፡ መንዳትን ፡ ሥራ ፡ በኀልዮም ፡ በገቢርም ፡ ማወቅ ፡ አለባቸው
4. ምግባር. Christian practices have occasionally been adopted by members of other religions. አንዳንድ ፡ የክርስቲያን ፡ ምግባሮች ፡ በሌሎች ፡ እምነት ፡ ተከታዮች ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነት ፡ አግኝተዋል
5. ሥራ. The doctor wanted his son to take over his practice when he got old. ዶክተሩ ፡ እሱ ፡ በሚያረጅበት ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ በሥራው ፡ እንዲተካ ፡ ፈለገ
*The practice of closing stores on Sunday is a good one. እሑድ ፡ እሑድ ፡ ሱቅ ፡ ዝግ ፡ መሆኑ ፡ ጥሩ ፡ ነው
*The doctor has a large practice. ሐኪሙ ፡ ብዙ ፡ በሽተኞች ፡ አሉት
*The lawyer has a large practice. ጠበቃው ፡ ብዙ ፡ ነገረተኞች ፡ አሉት

**practices** ሥራ
He is known for his loose business practices. በንግድ ፡ ሥራው ፡ ላይ ፡ እምነት ፡ አጕዳይነቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**be in practice** በሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ
The law is in practice now. ሕጉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ውሏል

**put into practice** በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለ
They decided to put the scheme into practice. እቅዱን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ወሰኑ

**practiced** (adj.) ሥልጡን
Years of study have made him a practiced musician. የብዙ ፡ ዓመታት ፡ ጥናት ፡ ሥልጡን ፡ሙዚቀኛ ፡ አድርጎታል

**prairie** የሣር ፡ ሜዳ
There are large prairies in North America. በሰሜን ፡ አሜሪካ ፡ ሰፋፊ ፡ የሣር ፡ ሜዳዎች ፡ አሉ

**praise** (v.)
1. አመሰገነ. Praise God for all His blessings! እግዜርን ፡ ስለ ፡ ቸርነቱ ፡ አመስግን
The coach praised the team for its fine playing. አሠልጣኙ ፡ ቡድኑ ፡ ጥሩ ፡ ስለተጫወተ ፡ አመሰገነ
2. አደነቀ(ለት). Everybody praises his work. ሁሉም ፡ ሥራውን ፡ ያደንቅለታል
**praise oneself** ራሱን ፡ አሞገሰ
I don't want to praise myself, but I can speak Amharic better than anybody. ራሴን ፡ ማሞገስ ፡ አይሁንብኝ ፡ እንጂ ፡ አማርኛ ፡ ከማንም ፡ ይበልጥ ፡ እናገራለሁ

**praise** (n.) ምስጋና
Praise be to God! ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው

**be beyond all praise**
His bravery is beyond all praise. ለጐብዝናው ፡ በሰው ፡ አፍ ፡ የሚነገር ፡ ምስጋና ፡ አይበቃውም

**speak in praise of** በማሞገስ ፡ ተናገረ
The Emperor spoke in praise of the soldiers who died for Ethiopia. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መሥዋዕት ፡ የሆኑትን ፡ ወታደሮች ፡ በማሞገስ ፡ ተናገሩ
[See also 'sing']

**praiseworthy** ምስጋና ፡ የሚገባው
His intentions were praiseworthy, but unsuccessful. አልተሳካለትም ፡ እንጂ ፡ ሐሳቡ ፡ ምስጋና ፡ የሚገባው ፡ ነው

**prance** ፈነጨ
Horses prance when they feel lively. ፈረሶቹ ፡ ሲደሰቱ ፡ ይፈነጫሉ

**prance about** ቦረቀ
The children pranced about in their new costumes. ሕፃናቶቹ ፡ አዲሱን ፡ ልብሳቸውን ፡ ለብሰው ፡ ቦረቁ

**prank** ቀልድ
He left a balloon full of water on the chair as a prank. ለቀልድ ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ ፊኛ ፡ ውኃ ፡ ሞልቶ ፡ ወንበሩ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠ

**prattle** (v.) ለፈለፈ
The child prattled all day long. ሕፃኑ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሲለፈልፍ ፡ ዋለ

**prattle** (n.) ልፍለፋ
The child's prattle disturbed me. የልጁ ፡ ልፍለፋ ፡ አስቸገረኝ

**pray** (vt.) ለመነ
I pray you to think again. እንደገና ፡ እንድታስብበት ፡ እለምንሃለሁ

**pray** (vi.) ጸለየ
He got up at night and prayed. ሌሊት ፡ ተነሥቶ ፡ ጸለየ

**pray!** እባክህ!
Pray come with me! እባክህ ፡ አብረኸኝ ፡ ሂድ

**prayer**
1. ጸሎት. These prayers are written in Geez. ይህ ፡ ጸሎት ፡ የተጻፈው ፡ በግዕዝ ፡ ነው
2. መጸለይ. Ablution must be performed by Muslims before prayer. እስላሞች ፡ ከመጸለያቸው ፡ በፊት ፡ መታጠብ ፡ አለባቸው
*His entire speech was a prayer for justice. ንግግሩ ፡ በሞላ ፡ ሕግ ፡ እንዲኖር ፡ የሚጠይቅ ፡ ነበር

**(The) Lord's Prayer** አቡነ ፡ ዘበሰማያት
Recite the Lord's Prayer before you go to bed! ከመተኛትህ ፡ በፊት ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያትን ፡ ድገም

**offer prayers** ጸሎት ፡ አደረገ
He offered prayers that the plane would not crash. አውሮፕላኑ ፡ እንዳይጋጭ ፡ ጸሎት ፡ አደረገ

**say prayers**
Did you say your prayers? ጸሎት ፡ አደረስክ?

**preach** (v.)
1. ሰበከ. The priest preaches every Sunday. ቄሱ ፡ በየሳምንቱ ፡ እሑድ ፡ ይሰብካል
2. አሳሰበ. He preaches the need for new fire trucks. ያዲስ ፡ የእሳት ፡ አደጋ ፡ መኪናዎችን ፡ አስፈላጊነት ፡ ያሳስባል

**preacher** ሰባኪ
This preacher is new to our church. ይህ ፡ ሰባኪ ፡ ለደብራችን ፡ እንግዳ ፡ ነው

**preamble** መግቢያ
The preamble to the constitution states that all men are created equal. የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መግቢያ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በተፈጥሮ ፡ እኩል ፡ መሆናቸውን ፡ ይናገራል

**(be) prearranged** በቅድሚያ ፡ ታቀደ
Our meeting was prearranged. የኛ ፡ መገናኘት ፡ በቅድሚያ ፡ የታቀደ ፡ ነበር

**precarious**
1. አደገኛ. A soldier leads a precarious life. የወታደር ፡ ኑሮ ፡ አደገኛ ፡ ነው
2. የማያስተማምን. A gambler leads a precarious life. ቁማርተኛ ፡ የማያስተማምን ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል

**precaution**
1. ጥንቃቄ. His precaution is due to his bad experiences in the past. ጥንቃቄው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባጋጠመው ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ የመጣ ፡ ነው
2. ማስጠንቀቂያ. These precautions obviate any chance of accident. እነዚህ ፡ ማስጠንቀቂያዎች ፡ ማንኛቸውንም ፡ ዓይነት ፡ አደጋ ፡ ይከላከላሉ
*One of the precautions against fire is a good supply of water. በርከት ፡ ያለ ፡ ውኃ ፡ ማስቀመጥ ፡ ከእሳት ፡ አደጋ ፡ ለመከላከል ፡ ይረዳል

**as a precaution** ለምናልባቱ
Take an umbrella as a precaution! ለምናልባቱ ፡ ጃንጥላ ፡ ያዝ

**take precautions** ተጠነቀቀ
Take precautions against fire! ከእሳት ፡ አደጋ ፡ ተጠንቀቁ

**precede**
1. ቀደመ. General Eisenhower preceded Kennedy as President. በፕሬዚዳንትነት ፡ ጄኔራል ፡ አይዘናወር ፡ ኬኔዲን ፡ ቀደሙ
2. በለጠ. A major precedes a captain in rank. በደረጃ ፡ ሻለቃ ፡ ከሻምበል ፡ ይበልጣል
3. በፊት ፡ አለ. The calm that precedes the storm often deceives many people. ዝናም ፡ ከ

መጣሉ ፡ በፊት ፡ ያለው ፡ ጸጥታ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ሰውን ፡ ያታልላል

4. ቀድሞ ፡ ተሰለፈ. The officers precede the soldiers. መኰንኖች ፡ ከወታደሮች ፡ ቀድመው ፡ ይሰለፋሉ

5. ፊት ፡ ፊት ፡ ነበረ. A guard of honor preceded the Emperor. የክብር ፡ ዘብ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊት ፡ ፊት ፡ ነበር

6. አስቀድሞ ፡ አለ. The chairman preceded his statement with a welcome to the audience. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ከንግግሩ ፡ አስቀድሞ ፡ አዳማጮቹን ፡ እንኳን ፡ ደኅና ፡ መጣችሁ ፡ አለ

**precedence** ቅድሚያ

The minister gave precedence to consideration of our financial needs. ሚኒስትሩ ፡ የገንዘብ ፡ ችግራችንን ፡ ለማጥናት ፡ ቅድሚያ ፡ ሰጥቶታል

**in order of precedence** በማዕረግ ፡ ቅደም ፡ ተከተል

Seating at the banquet table was done in order of precedence. በራት ፡ ግብዣው ፡ ላይ ፡ ያቀማመጡ ፡ ሥርዓት ፡ በማዕረግ ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ነበር

**take precedence** ቀደምትነት ፡ አለው ፤ ቀደመ

This question takes precedence over all others. ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ከሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ ቀደምትነት ፡ የሚኖረው ፡ ነው

Proprietary rights should not take precedence over human rights. የንብረት ፡ መብቶች ፡ ከሰብአዊ ፡ መብቶች ፡ መቅደም ፡ የለባቸውም

**precedent** (n.) የሚያሳይ ፡ ምሳሌ

There are precedents for a common soldier becoming a general. ተራ ፡ ወታደር ፡ ጄኔራል ፡ ለመሆን ፡ እንደሚችል ፡ የሚያሳዩ ፡ ምሳሌዎች ፡ አሉ

*Is there a precedent for this ruling? የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ውሳኔ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተደርጓል ?

**preceding**

1. ቀዳሚ. In the preceding paragraph, we discussed economic problems. በቀዳሚው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ የምጣኔ ፡ ሀብት ፡ ችግሮችን ፡ ተወያየን

2. ያለፈ. He pored over the strange events of the preceding evening. ባለፈው ፡ ምሽት ፡ ስለደረሱት ፡ እንግዳ ፡ ነገሮች ፡ አሰላሰለ

**on the preceding day** በቀደም ፡ ለት

There had been a heavy rain on the preceding day. በቀደም ፡ ለት ፡ ኀይለኛ ፡ ዝናብ ፡ ጥሎ ፡ ነበር

**precept**

1. ምክር. Example is better than precept. ከምክር ፡ ይልቅ ፡ ምሳሌ ፡ መሆን ፡ ይበልጣል

2. መመሪያ. "Look before you leap" is a well-known precept. ከመዝለልህ ፡ በፊት ፡ ተመልከት ፡ የሚለው ፡ የታወቀ ፡ መመሪያ ፡ ነው

**precinct** ቀበሌ

The precinct is patrolled by policemen. ፖሊሶቹ ፡ ቀበሌውን ፡ ይጠብቃሉ

**precincts**

1. ቅጽር ፡ ግቢ. Do not leave the school precincts during school hours! በትምህርት ፡ ሰዓቶች ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ቅጽር ፡ ግቢ ፡ አትውጡ

2. ክልል. The parade will be held within the precincts of the town. ሰልፉ ፡ በከተማው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ይደረጋል

**precious** (adj.)

1. የከበረ. Gold is precious, but lead is not. ወርቅ ፡ የከበረ ፡ ነው ፤ እርሳስ ፡ ግን ፡ አይደለም

2. ጠቃሚ. Learning is very precious. መማር ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው

3. ብርቅ. This girl is precious to her parents. ልጅቱ ፡ ለወላጆቿ ፡ ብርቅ ፡ ናት

4. የሚወደድ. He is a precious friend, and I shall miss him when he leaves. የሚወደድ ፡ ጓደኛ ፡ ስለሆነ ፡ ሲሄድ ፡ ይናፍቀኛል

5. የላቀ. The faculty of eyesight is God's most precious gift to us. የማየት ፡ አካል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጠን ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የላቀ ፡ ጸጋ ፡ ነው

6. ረቂቅ. This author has a precious style of writing. ይህ ፡ ደራሲ ፡ ረቂቅ ፡ ያጻጻፍ ፡ ዘዴ ፡ አለው

**precious** (adv.) በጣም

He had precious little to say for himself. ራሱ ፡ ሊገልጸው ፡ የፈለገው ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ነበር

**my precious one** የኔ ፡ ሸጋ

My precious one, what happened to you? የኔ ፡ ሸጋ ፤ ምን ፡ ነካሽ ?

**precipice** ገደል

He felt dizzy when he stood on the edge of the precipice. ከገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ሲቆም ፡ ጭው ፡ አለበት

**precipitate** (v.)

1. አስከተለ. The border incident precipitated a crisis in international relations. የድንበሩ ፡ ግጭት ፡ በዓለም ፡ አቀፍ ፡ ግንኙነት ፡ ላይ ፡ ጠንቅ ፡ አስከተለ

2. አንከባለለ. The workers precipitated a rock down the cliff. ሠራተኞቹ ፡ ቋጥኙን ፡ ወደ ፡ ገደል ፡ አንከባለሉት

**precipitate** (adj.)
1. (= adv.) ባንድ ፡ አፍታ. The cold wind caused a precipitate drop in temperature. ቀዝቃዛው ፡ ነፋስ ፡ ሙቀቱን ፡ ባንድ ፡ አፍታ ፡ አቀዘቀዘው
2. (= adv.) በጥድፊያ. After a warning from a neighbor, he made a precipitate flight. ጐረቤቱ ፡ ካስጠነቀቀው ፡ በኋላ ፡ በጥድፊያ ፡ ሸሸ

**precipitately** በፍጥነት
At the sight of the hunters, the birds flew away precipitately. አዳኞቹን ፡ ሲያዩ ፡ ወፎች ፡ በፍጥነት ፡ በረሩ

**precipitation**
1. ችኰላ. She made the decision with precipitation. ውሳኔውን ፡ ያደረገችው ፡ በችኰላ ፡ ነው
2. የዝናብ ፡ መጠን. There were four inches of precipitation yesterday. ትላንት ፡ የዝናቡ ፡ መጠን ፡ አራት ፡ ኢንች ፡ ነበር

**precipitous** ቀጥ ፡ ያለ
The precipitous hillside makes climbing very dangerous. ቀጥ ፡ ያለውን ፡ የተራራ ፡ ወገን ፡ መውጣት ፡ አደገኛ ፡ ነው
*A precipitous flow of water prevents navigation. በገደል ፡ ላይ ፡ የሚፈስ ፡ ውኃ ፡ በጀልባ ፡ ከመሄድ ፡ ያግዳል

**précis** አኅጽሮተ ፡ ጽሑፍ
It is difficult to write an accurate précis. ትክክለኛ ፡ የሆነ ፡ አኅጽሮተ ፡ ጽሑፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ከባድ ፡ ነው

**precise**
1. ጠንቃቃ. She is precise in her manners. በሁኔታዋ ፡ ጠንቃቃ ፡ ነች
2. ጥብቅ. She had precise orders to come home by nine o'clock. ልክ ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እንድትመጣ ፡ ጥብቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጥቶዋታል
3. ትክክለኛ. He gave me precise directions how to get to his house. እቤቱ ፡ እንዴት ፡ እንደምደርስ ፡ ትክክለኛ ፡ የሆነ ፡ መምሪያ ፡ ሰጠኝ
Please have the precise amount ready! ትክክለኛውን ፡ ሒሳብ ፡ አዘጋጁ
4. ይኸው ፡ ራሱ. This is the precise dress that she wanted. የፈለገችው ፡ ልብስ ፡ ይኸው ፡ ራሱ ፡ ነው

**at the precise moment** ልክ
At the precise moment that the doorbell sounded, the telephone rang. ልክ ፡ የበሩ ፡ ደወል ፡ ሲደወል ፡ ስልኩም ፡ ጮኸ

**precisely**
1. ልክ. Precisely at two o'clock, it began to rain. ልክ ፡ በስምንት ፡ ሰዓት ፡ መዝነብ ፡ ጀመረ
2. በትክክል. State the facts precisely! ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ በትክክል ፡ ግለጽ
3. ነውና. Do you mean you cannot come? Precisely. መምጣት ፡ አትችልም ፡ ማለት ፡ ነው ? ነውና!

**precision** (n.) ትክክለኛነት
The precision of this instrument allows us to measure very small things. የዚህ ፡ መሣሪያ ፡ ትክክለኛነት ፡ በጣም ፡ ጥቃቅን ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ለመለካት ፡ ያስችለናል

**precision** (adj). ከፍተኛ ፡ ትክክለኛነትን ፡ የሚያስገኝ
Japan produces many precision instruments. ጃፓን ፡ ብዙ ፡ ከፍተኛ ፡ ትክክለኛነትን ፡ የሚያስገኝ ፡ መሣሪያዎች ፡ ትሠራለች

**preclude** እንድ + negative verb + አደረገ
The heavy thunderstorm precluded our going to the beach. ኀይለኛው ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ እንዳንሄድ ፡ አደረገን

**precocious** ከዕድሜው ፡ የቀደመ ፡ ብልህ
The child is very precocious and can read, even though he has not yet been to school. ሕፃኑ ፡ ገና ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ያልገባ ፡ ቢሆንም ፡ ከዕድሜው ፡ የቀደመ ፡ ብልህ ፡ በመሆኑ ፡ ማንበብ ፡ ይችላል

**preconceived** መሠረት ፡ የሌለው
He has preconceived ideas about almost everything. ስለ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ አስተያየት ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ነው

**precursor**
1. ቀዳሚ. He was my precursor in this position. በዚህ ፡ ሥልጣን ፡ እሱ ፡ የኔ ፡ ቀዳሚ ፡ ነበር
2. መግባት ፡ የሚያበስር. These flowers are a precursor of spring. እነዚህ ፡ አበባዎች ፡ የጸደይን ፡ መግባት ፡ የሚያበስሩ ፡ ናቸው

**predate**
1. በፊት ፡ ነበረ. The Civil War predated World War I. የአሜሪካን ፡ የእርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ከመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በፊት ፡ ነበረ
2. አስቀድሞ ፡ ጻፈ. He predated the check by three days. ቼኩን ፡ ከቀኑ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ ጻፈው

**predatory** ሌሎችን ፡ እንስሳት ፡ በማደን ፡ የሚኖር
Predatory animals have caused serious damage to farmers who raise a lot of chickens. ሌሎችን ፡ እንስሳት ፡ በማደን ፡ የሚኖሩ ፡ እንስሳት ፡ ብዙ ፡ ዶሮ ፡ በሚያረቡት ፡ ገበሬዎች ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ አድርሰዋል

**predecessor**
1. በፊት ፡ በቦታው ፡ የነበረ. His predecessor was an incompetent man. ከሱ ፡ በፊት ፡ በቦታው ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ነበር
2. የድሮ. The new teacher is a great improvement over his predecessor. አዲሱ ፡ መምህር ፡ ከድሮው ፡ በጣም ፡ የተሻለ ፡ ነው

**be the predecessor** ቀደመ
Taft was the predecessor of Wilson as President. በፕሬዚዳንትነት ፡ ከዊልሰን ፡ ቀድመው ፡ የነበሩት ፡ ታፍት ፡ ናቸው

**predestination** ያርባ ፡ ቀን ፡ ዕድል
Many religions believe in predestination. ብዙ ፡ ሃይማኖቶች ፡ ባርባ ፡ ቀን ፡ ዕድል ፡ ያምናሉ

**predestined**
1. የታጨ. He seems predestined to achieve high office. ለከፍተኛ ፡ ሥልጣን ፡ የታጨ ፡ ይመስላል
2. ከመጀመሪያው ፡ የታደለ. He seems predestined to be a poet. ገጣሚ ፡ ለመሆን ፡ ከመጀመሪያው ፡ የታደለ ፡ ይመስላል

**predetermine** አስቀድሞ ፡ ወሰነ
It is difficult to predetermine our requirements for next year. ለሚመጣው ፡ ዓመት ፡ የሚያስፈልጉንን ፡ አስቀድሞ ፡ መወሰን ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**predicament** አስቸጋሪ ፡ ሁኔታ
He is in a predicament because he made two different appointments for the same time. ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ቀጠሮ ፡ በመስጠቱ ፡ ባስቸጋሪ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነው

**predicate** (v.)
1. ብሎ ፡ አመነ. Most religions predicate life after death. ብዙ ፡ ሃይማኖቶች ፡ ከሞት ፡ በኋላ ፡ ሕይወት ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ያምናሉ
2. አመለከተ. His retraction predicates a change in attitude. ሐሳቡን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ማለቱ ፡ የሁኔታውን ፡ መለወጥ ፡ ያመለክታል

**be predicated upon** ተመረኰዘ
The decisions of the court are predicated upon the constitution. የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔዎች ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ የተመረኰዙ ፡ ናቸው

**predicate** (n.) አንቀጽ
A sentence can be divided into subject and predicate. ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ በባለቤትና ፡ በአንቀጽ ፡ ይከፈላል

**predict** ተነበየ
It's difficult to predict the weather. ያየሩን ፡ ሁኔታ ፡ መተንበይ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**prediction** ትንቢት
Do you believe the prediction that the world will end in 1976? ዓለም ፡ በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ታልፋለች ፡ የሚለውን ፡ ትንቢት ፡ ታምናለህ ?

**predilection** መውደድ
His predilection for sweets is well known. የሚጣፍጥ ፡ ነገር ፡ መውደዱ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**have a predilection** ወደደ
He has a predilection for sweets. ጣፋጭ ፡ ምግቦችን ፡ ይወዳል

**predispose** በቀላሉ ፡ ጣለ
Being tired predisposes a person to illness. ድካም ፡ ሰውን ፡ በቀላሉ ፡ ሕመም ፡ ላይ ፡ ይጥላል
*The evidence predisposes him to public censure. ማስረጃው ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ እስከ ፡ መነቀፍ ፡ ያደርሰዋል

**be predisposed** በቅድሚያ ፡ ወሰነ
The director is predisposed to grant all his requests. ሥራ ፡ መሪው ፡ እሱ ፡ የጠየቀውን ፡ ሁሉ ፡ ሊፈጽም ፡ በቅድሚያ ፡ ወስኗል

**predominant**
1. በይበልጥ ፡ የሚታይ. Green is the predominant color in the forest. በጫካው ፡ ውስጥ ፡ በይበልጥ ፡ የሚታየው ፡ ቀለም ፡ አረንጓዴ ፡ ነው
2. የበለጠ. The mayor had the predominant voice in the discussion. በውይይቱ ፡ ወቅት ፡ ከንቲባው ፡ የበለጠ ፡ ተደማጭነት ፡ ነበረው

**predominantly** (= adj.) አብዛኛዎቹ
In this region the inhabitants are predominantly Christians. በዚህ ፡ አካባቢ ፡ የሚኖሩት ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ክርስቲያኖች ፡ ናቸው

**predominate** በይበልጥ ፡ ታየ
Yellow predominates in this picture. በዚህ ፡ ሥዕል ፡ ውስጥ ፡ ቢጫው ፡ በይበልጥ ፡ ይታያል

**predominate over**
1. ከ --- በዛ. Sunny days predominate over rainy days in desert regions. በበረሃማ ፡ ቀበሌዎች ፡ ፀሐያማ ፡ ቀናት ፡ ከዝናብ ፡ ቀናት ፡ ይበዛሉ
2. ተሟኘ. He predominated over his weaker comrades. አነስተኛ ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቹን ፡ ተሟኘናቸው

**preeminence** ልቀት
The world admired him for his preeminence in medicine. በሕክምና ፡ ልቀት ፡ ዓለም ፡ አድንቆታል

**(be) preeminent** ላቀ
He is preeminent above all his rivals. ከተወዳዳሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ይልቃል

**preempt**
1. ከሁሉ ፡ ቀድሞ ፡ ወሰደ. Our neighbor preempted the choicest cut of meat. ጐረቤታችን ፡ ምርጥ ፡ የሆነውን ፡ የሥጋ ፡ ብልት ፡ ከሁሉ ፡ ቀድሞ ፡ ወሰደ
2. አስቀድሞ ፡ ያዘ. The cat has preempted the comfortable chair. ድመቷ ፡ አስቀድማ ፡ ምቹውን ፡ ወንበር ፡ ያዘች

**preface** (v.) ከ --- በፊት ፡ ተሰጠ
A lecture prefaced the movie. ከሲኒማው ፡ በፊት ፡ ንግግር ፡ ተሰጠ
*He prefaced his speech with some cutting remarks about the principal. በንግግሩ ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ ዲሬክተሩን ፡ የሚነካ ፡ አስተያየት ፡ ሰነዘረ

**preface** (n.) መቅድም
The author explains his intention in the preface. ደራሲው ፡ ዓላማውን ፡ በመቅድሙ ፡ ውስጥ ፡ ይገልጻል

**prefer** (preferred)
1. መረጠ. I prefer to wait until the weather is cooler. ጥላ ፡ በረድ ፡ እስኪል ፡ መቆየትን ፡ እመርጣለሁ
2. ወደደ. I should prefer that you not go there alone. እዚያ ፡ ብቻህን ፡ ባትሄድ ፡ እወዳለሁ
3. ፈለገ. I will come later, if you prefer. ከፈለግህ ፡ በኋላ ፡ እመጣለሁ
4. ተሻለ(ው). +I prefer to go by train. በባቡር ፡ መሄድ ፡ ይሻለኛል

**prefer to someone** አብልጦ ፡ ወደደ
He prefers my sister to me. ከኔ ፡ እኅቴን ፡ አብልጦ ፡ ይወዳል
[See also 'charge']

**(be) preferable** ተሻለ
Which is preferable– to wait here till the rain stops, or to run home as fast as you can? ዝናቡ ፡ እስኪያባራ ፡ እዚህ ፡ ከመቆየትና ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ በተቻለው ፡ ፍጥነት ፡ በሩጫ ፡ መሄድ ፡ የትኛው ፡ ይሻላል ?

**find preferable** መረጠ
I find summer preferable to winter. ከክረምት ፡ ይልቅ ፡ በጋን ፡ እመርጣለሁ

**preference** ምርጫ
My preference is for beef rather than lamb. ምርጫዬ ፡ ከበግ ፡ ሥጋ ፡ ይልቅ ፡ የበሬ ፡ ሥጋ ፡ ነው
*What are your preferences? ምን ፡ ትመርጣለህ ?
*I would like this in preference to any other. ከሌላው ፡ ሁሉ ፡ ይህንን ፡ እመርጣለሁ

**give preference** አደላ
He gives preference to his relatives when any new jobs are open. አዲስ ፡ ሥራ ፡ በተገኘ ፡ ቁጥር ፡ ለዘመዶቹ ፡ ያደላል

**have preferences for** መረጠ
He has a preference for modern music. ዘመናዊ ፡ ሙዚቃ ፡ ይመርጣል

**have preference in** ቅድሚያ ፡ ተሰጠው
Veterans have preference in getting government jobs. በጦርነት ፡ ያገለገሉ ፡ ሰዎች ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ ቅድሚያ ፡ ይሰጣቸዋል

**preferential** ያድላዊነት
His preferential policies prevented him from dealing with some companies. ያድላዊነት ፡ ተግባሩ ፡ ከንዳንድ ፡ ኩባንያዎች ፡ ጋር ፡ ከመግባባት ፡ አገደው

**prefix** ባዕድ ፡ መነሻ
The future tense is expressed in Amharic with prefixes and suffixes. ባማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ትንቢታዊ ፡ ጊዜ ፡ ባዕድ ፡ መነሻና ፡ ባዕድ ፡ መድረሻ ፡ አሉዋቸው

**pregnancy** የነፍሰ ፡ ጡርነት ፡ ጊዜ
She often got sick during her pregnancy. በነፍሰ ፡ ጡርነት ፡ ጊዜዋ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያማት ፡ ነበር

**pregnant**
1. ነፍሰ ፡ ጡር. That woman is pregnant and has to go to the hospital. ያቺ ፡ ሴት ፡ ነፍሰ ፡ ጡር ፡ ስለሆነች ፡ ሆስፒታል ፡ መሄድ ፡ አለባት
2. ከባድ. The cow is pregnant and will calve soon. ላሟ ፡ ከባድ ፡ ስለሆነች ፡ በቅርቡ ፡ ትወልዳለች

**be pregnant with**
1. አስከተለ. The political events are pregnant with consequences. የፖለቲካ ፡ ጉዳዮች ፡ ብዙ ፡ ነገሮችን ፡ ያስከትላሉ
2. አዘለ. This is a book pregnant with ideas. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ብዙ ፡ ሐሳብ ፡ ያዘለ ፡ ነው

**become pregnant** ፀነሰ
She became pregnant while abroad. እውጭ ፡ አገር ፡ በነበረችበት ፡ ጊዜ ፡ ፀነሰች

**prejudge** አስቀድሞ ፡ ፈረደ
Do not prejudge the case, but wait until you have heard all the evidence. ማስረጃውን ፡ ሁሉ ፡ እስክትሰማ ፡ ድረስ ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ አስቀድመሀ ፡ አትፍረድ

**prejudice** (v.)
*One low grade prejudiced his chances for a scholarship. ነጻ ፡ ትምህርት ፡ በማግኘት ፡ የነበረው ፡ ዕድል ፡ ባንድ ፡ ዝቅተኛ ፡ ማርክ ፡ ተቀጨ

**prejudice against** ጥላቻ ፡ አሳደረበት
He prejudiced his child against foreigners. በልጁ ፡ ላይ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ጥላቻ ፡ አሳደረበት

**prejudice in one's favor** እንዲያደላ(ለት) ፡ ገፋፋው
His honesty and sincerity prejudiced us in his favor. ታማኝነቱና ፡ እውነተኛነቱ ፡ እንድናደላለት ፡ ገፋፋን

**prejudice** (n.) አግባብ ፡ የሌለው ፡ ጥላቻ
Prejudice has caused much trouble in the world. አግባብ ፡ የሌለው ፡ ጥላቻ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ አስከትሏል

**have prejudice against** የ --- ጥላቻ ፡ አለበት
I have no prejudice against Indians. የሀንድ ፡ ጥላቻ ፡ የለብኝም

*I have no prejudice against him. ከመሬት ፡ ተነሥቼ ፡ አልጠላውም

**preliminary** የመጀመሪያ ፡ ደረጃ
Preliminary discussions on trade will be held in the capital. በመናገሻው ፡ ከተማ ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ውይይት ፡ ይደረጋል

**be a preliminary to** በቅድሚያ ፡ ተደረገ
A physical examination is a preliminary to joining the army. በጦር ፡ ሰራዊትነት ፡ ለመቀጠር ፡ የአካል ፡ ምርመራ ፡ በቅድሚያ ፡ ይደረጋል

**prelude**
1. መግቢያ. The prelude to the Second World War was the invasion of Ethiopia. የኢትዮጵያ ፡ መወረር ፡ ለሁለተኛው ፡ ዓለም ፡ ጦርነት ፡ መግቢያ ፡ ነበር
2. ዋዜማ. The thunder was a prelude to the storm. መብረቁ ፡ የኀይለኛው ፡ ዝናም ፡ ዋዜማ ፡ ነበር

**(be) premature** ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ ነው
The suggestion is premature. ሐሳቡ ፡ የቀረበው ፡ ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ ነው

**prematurely**
1. ያለ ፡ ቀኑ ፡ ቀድሞ. The child was born two months prematurely. ሕፃኑ ፡ ያለ ፡ ቀኑ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ቀድሞ ፡ ተወለደ
2. ያለ ፡ ጊዜው. His unhappy lot made him look old prematurely. መጥፎ ፡ ዕድሉ ፡ ያለ ፡ ጊዜው ፡ ያረጀ ፡ ያስመስለዋል

**(be) premeditated**
The crime was premeditated. ወንጀሉ ፡ በቅድሚያ ፡ ታስቦበት ፡ የተፈጸመ ፡ ነው

**Premier** ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር
The French Premier will pay a visit to Ethiopia. የፈረንሳይ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ይጎበኛሉ

**premise** መሠረት
The premise of his policy was that war would soon come. የአመራሩ ፡ መሠረት ፡ ጦርነቱ ፡ በቅርቡ ፡ ይነሣል ፡ የሚል ፡ ነበር

**premises** ግቢ
Keep off the premises! ከግቢው ፡ አትድረስ

**on the premise that** በሚል ፡ አስተሳሰብ
He did it on the premise that quick action is better than delay. ከመዘግየት ፡ መፍጠን ፡ ይሻላል ፡ በሚል ፡ አስተሳሰብ ፡ ፈጸመው

**premium**
1. ጉርሻ. The company offered a premium to the man with the highest sales. ኩባንያው ፡ ብዙ ፡ ሸቀጥ ፡ ለሸጠው ፡ ሰው ፡ ጉርሻ ፡ ሰጠ
2. ከፍተኛ ፡ ግምት. She puts a premium on neatness. ለጽዳት ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ አላት
3. ክፍያ. If I don't pay the premium, my insurance policy will lapse. ክፍያዬን ፡ ካልከፈልኩ ፡ ዋስትናዬ ፡ ያበቃል

**at a premium**
*Theater tickets are sold at a premium. የቲያትሩ ፡ ቲኬቶች ፡ በጣም ፡ ስለሚፈለጉ ፡ በውድ ፡ ዋጋ ፡ ይሸጣሉ

**be at a premium** እጥረት ፡ አለ ፤ አይገኝም
Housing in that area is at a premium. በዚያ ፡ አካባቢ ፡ የመኖሪያ ፡ ቤት ፡ እጥረት ፡ አለ ፡ (አይገኝም)

**premium** (adj.) ከፍተኛ
Ethiopian coffee gets premium prices. የኢትዮጵያ ፡ ቡና ፡ በከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ይሸጣል

**premonition, have a ~** ተሰማ(ው)
+I have a premonition of disaster. መዓት ፡ እንደሚመጣ ፡ ይሰማኛል

**preoccupation**
1. ያሳሰበው ፡ ነገር. His greatest preoccupation

was how to find money for a holiday in Europe. በጣም ፡ ያሳሰበው ፡ ነገር ፡ ለዕረፍት ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ የሚሄድበት ፡ ገንዘብ ፡ የማግኘት ፡ ዘዴ ፡ ነበር
2. መጠመድ. His preoccupation with his own affairs prevented him from organizing the meeting. በግል ፡ ጉዳዩ ፡ መጠመዱ ፡ ስብሰባውን ፡ እንዳይዘጋጅ ፡ አደረገው

**preoccupy** (preoccupied) በኀይል ፡ አሳሰበ
His financial situation preoccupies him. የገንዘብ ፡ ችግር ፡ በኀይል ፡ ያሳስበዋል

**(be) prepaid** በቅድሚያ ፡ ተከፈለበት
We will not send any books unless they are prepaid. ማንኛውንም ፡ መጽሐፍ ፡ በቅድሚያ ፡ ካልተከፈለበት ፡ አንልክም

**preparation**
1. ዝግጅት. I have made all the necessary preparations for the trip. ለጉዞው ፡ አስፈላጊውን ፡ ዝግጅት ፡ ሁሉ ፡ አድርጌያለሁ
2. (= to prepare) ማዘጋጀት. How long did the preparation of the dinner take you? እራት ፡ ማዘጋጀቱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ወሰደብሽ ?
3. ቅይጥ. The preparation included sulphur. በቅይጡ ፡ ውስጥ ፡ ድኝም ፡ ይገኝበታል

**be in preparation** በመዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ነው
Plans are in preparation. እቅዱ ፡ በመዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ነው

**preparatory** ቀዳሚ
He made preparatory plans for his trip to Europe. ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ስለሚያደርገው ፡ ጉዞ ፡ ቀዳሚ ፡ እቅድ ፡ አዘጋጀ

**preparatory school** [ተማሪዎችን ፡ ለዩኒቨርሲቲ ፡ የሚያዘጋጅ ፡ የግል ፡ የሆነ ፡ ሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት]

**prepare** (vt.)
1. አዘጋጀ ፤ አሰናዳ. They prepared the expedition very carefully. ጉዞውን ፡ በጥንቃቄ ፡ አዘጋጁት ፡ (አሰናዱት)
2. ሠራ. Who is going to prepare the meal? ምግቡን ፡ የሚሠራው ፡ ማን ፡ ነው ?
3. ቀመመ. The pharmacist prepared the medicine. መድኃኒት ፡ ቀማሚው ፡ መድኃኒቱን ፡ ቀመመ

**prepare** (vi.) ተዘጋጀ
Did you prepare for tomorrow's exam? ለነገ ፡ ፈተና ፡ ተዘጋጅተሃል ?

**prepared** (adj.) ዝግጁ
We are prepared to supply the goods you asked for. የጠየቃችኋቸውን ፡ እቃዎች ፡ ለማቅረብ ፡ ዝግጁ ፡ ነን

**be prepared** ተዘጋጀ
I'm prepared for the worst. ከዚህ ፡ ለባሰው ፡ ተዘጋጅቻለሁ

**preponderant** ከሁሉ ፡ የበለጠ
The preponderant consideration seems to be money. ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ አሳሳቢ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ይመስላል

**preponderant majority** ከሰዎች ፡ በጣም ፡ ብዙዎች
The preponderant majority is in favor of peace. ከሰዎቹ ፡ በጣም ፡ ብዙዎቹ ፡ ሰላምን ፡ ይደግፋሉ

**preponderate**
1. ከሁሉም ፡ በዛ. Italians preponderate in this district. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ጣሊያኖች ፡ ከሁሉም ፡ ይበዛሉ
2. አመዘነ. These are the reasons that preponderate over all others. ከሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ የሚያመዝኑት ፡ ምክንያቶች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው

**preposition** መስተዋድድ
English makes widespread use of verbs and prepositions. በእንግሊዝኛ ፡ ግስና ፡ መስተዋድድ ፡ ያላቸው ፡ አገልግሎት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው

**preposterous** የማይረባ
He has a preposterous notion about politics. ስለ ፡ ፖለቲካ ፡ ያለው ፡ አስተሳሰብ ፡ የማይረባ ፡ ነው

**prerequisite, be a ~** ያስፈልጋል
A high school education is a prerequisite for this job. ለዚህ ፡ ሥራ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ያስፈልጋል

**prerogative**
1. ሥልጣን. Most governors have the prerogative of pardoning prisoners. አብዛኛዎቹ ፡ ገዢዎች ፡ እስረኞችን ፡ የመማር ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው
2. መብት. Choosing the children's school is the parents' prerogative. የልጆችን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መምረጥ ፡ የወላጆች ፡ መብት ፡ ነው

**presage** እንደሚመጣ ፡ አመለከተ
Dark clouds presage a storm. የጨለመ ፡ ደመና ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ እንደሚመጣ ፡ ያመለክታል

**presbyter** ቀሲስ
In former days, the presbyter was the leader of

the people. በጥንት ፡ ዘመን ፡ ቀሲስ ፡ የሕዝብ ፡ መሪ ፡ ነበር

**prescribe** አዘዘ

The doctor prescribed these pills for me. ሐኪሙ ፡ እነዚህን ፡ ኪኒኖች ፡ አዘዘልኝ

Good citizens do what the laws prescribe. መልካም ፡ ዜጋዎች ፡ ሕግ ፡ የሚያዘውን ፡ ይፈጽማሉ

**be prescribed**

1. ተወሰነ. The definition of the mayor's duties is prescribed by law. የከንቲባው ፡ ሥልጣን ፡ በሕግ ፡ ተወስኗል

2. ተመደበ. These textbooks are prescribed for secondary schools. እነዚህ ፡ የመማሪያ ፡ መጽሐፎች ፡ ለሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተመደቡ ፡ ናቸው

**prescription** የመድኃኒት ፡ ማዘዣ ፤ የሐኪም ፡ ትእዛዝ

I lost the prescription that the doctor gave me. ሐኪሙ ፡ የሰጠኝ ፡ የመድኃኒት ፡ ማዘዣ ፡ ጠፋብኝ

This drug is sold only by prescription. ይህ ፡ መድኃኒት ፡ የሚሸጠው ፡ በሐኪም ፡ ትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ ነው

**presence** መኖር

The presence of gas was revealed by a foul smell. ጋዝ ፡ መኖሩ ፡ በመጥፎ ፡ ሽታው ፡ ታወቀ

*We were admitted to the king's presence. ንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ እንድንቀርብ ፡ ተፈቅዶልን ፡ ነበር

*Your presence is requested at the meeting. በስብሰባው ፡ ላይ ፡ እንዲገኙ ፡ ይጠየቃሉ

**in one's presence, in the presence (of)**

1. ባለበት. The document has to be signed in your presence. ሰነዱ ፡ አንተ ፡ ባለህበት ፡ መፈረም ፡ አለበት

He signed his name in the presence of two witnesses. ስሙን ፡ የፈረመው ፡ ሁለት ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ ነው

2. በ --- ፊት. He uses gross language in the presence of women. በሴቶች ፡ ፊት ፡ ጸያፍ ፡ ንግግር ፡ ይናገራል

*He is calm in the presence of danger. አደጋ ፡ ባጋጠመው ፡ ጊዜ ፡ መንፈሰ ፡ ርጉ ፡ ነው

**noble presence** ግርማ ፡ ሞገስ

The young prince had a noble presence. ወጣቱ ፡ መስፍን ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ አላቸው

[See also 'mind']

**present** (v.)

1. አቀረበ. Why don't you present the evidence as it really is? ማስረጃውን ፡ ለምን ፡ እንዳለ ፡ አታቀርበውም ?

2. ሸለመ. The teacher presented a book to the student. መምህሩ ፡ ለተማሪው ፡ መጽሐፍ ፡ ሸለመ

3. አሳየ. The company will present Hamlet next week. የቲያትሩ ፡ ጓድ ፡ በሚቀጥለው ፡ ሳምንት ፡ ሀምሌትን ፡ ያሳያል

4. አመጣ. Each separate case presents new difficulties. እያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ አዳዲስ ፡ ችግር ፡ ያመጣል

5. አስተዋወቀ. John presented his friend to me. ጆን ፡ ከጓደኛው ፡ ጋር ፡ አስተዋወቀኝ

6. አለ(ው). The new post office presents a fine appearance. አዲሱ ፡ ፖስታ ፡ ቤት ፡ ጥሩ ፡ መልክ ፡ አለው

**present itself** ተገኘ

A good opportunity has presented itself for doing what you suggest. ያቀረብከውን ፡ ሐሳብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ጥሩ ፡ አጋጣሚ ፡ ተገኝቷል

**present oneself** መጣ

He presented himself at my office. ቢሮዬ ፡ መጣ

**present with** አበረከተ

He presented the school with a new blackboard. ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አዲስ ፡ ጥቁር ፡ ሰሌዳ ፡ አበረከተ

**be presented to** ቀረበ

The new ambassador is going to be presented to the Emperor tomorrow. አዲሱ ፡ አምባሳደር ፡ ነገ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዘንድ ፡ ይቀርባሉ

**be presented with** ተሸለመ

He was presented with a gold watch. የወርቅ ፡ ሰዓት ፡ ተሸለመ

**present** (n.)

1. ስጦታ. Did you give him a present for his birthday? ለልደቱ ፡ ስጦታ ፡ አደረግህለት ?

2. ገጸ ፡ በረከት. The ambassador brought presents to the Emperor. አምባሳደሩ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ አምጥቷል

3. ያሁን ፡ ጊዜ. In grammar, the present is expressed differently from the past. በሰዋስው ፡ ያሁን ፡ ጊዜ ፡ ከኅላፊ ፡ ጊዜ ፡ በተለየ ፡ አነጋገር ፡ ይገለጻል

**make a present of** አበረከተ(ለት)

He made me a present of this sword. ይህን ፡ ጐራዴ ፡ አበረከተልኝ

**at present** አሁን

At present, he is in Chicago. አሁን ፡ ያለው ፡ ቺካጎ ፡ ነው

**for the present** ላሁኑ

The food will be enough for the present. ያለው ፡ ምግብ ፡ ላሁኑ ፡ ይበቃል

**in the present** ባሁኑ ፡ ዘመን
We live in the present, not in the past. የምንኖረው ፡ ባሁኑ ፡ እንጂ ፡ ባለፈው ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ አይደለም

**present** (adj.)
1. አቤት. When the teacher called the roll, he answered "Present". አስተማሪው ፡ ስም ፡ ሲጠራ ፡ አቤት ፡ አለ
2. ያሁኑ. Are you content with your present salary? ባሁኑ ፡ ደሞዝህ ፡ ተደስተሃል ?
Old books are hard to get at the present time. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አሮጌ ፡ መጻሕፍትን ፡ ማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
3. አሁን ፡ ያለበት. The opportunist obtained his present position through his activities. አድር ፡ ባዩ ፡ ባድራጎቱ ፡ አሁን ፡ ያለበትን ፡ ደረጃ ፡ ያዘ
*In my present position, I can't do anything else. አሁን ፡ ባለሁበት ፡ ሁኔታ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ማድረግ ፡ አልችልም

**be present**
1. ነበረ (past), አለ (present). All his friends were present. ጓደኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ነበሩ
The whole class is present. የክፍሉ ፡ ተማሪዎች ፡ በሙሉ ፡ አሉ
2. እዚያው ፡ ነበረ. He was present when the building came down. ሕንጻው ፡ ሲደረመስ ፡ እዚያው ፡ ነበረ

**presentable**
*He rewrote his composition in a presentable form. ድርሰቱን ፡ እንደሚስማማ ፡ አድርጎ ፡ እንደገና ፡ ጻፈው

**be presentable** ሰው ፡ ፊት ፡ ሊቀርብ ፡ ቻለ
Unlike yesterday, he is presentable today. እንደ ፡ ትላንትናው ፡ ሳይሆን ፡ ዛሬ ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችል ፡ ነው

**presentation**
1. አቀራረብ. His presentation of the plan was favorably received. የእቅዱ ፡ አቀራረብ ፡ ተቀባይ ፡ አግኝቷል
2. መቅረብ. His presentation at the court was an important moment of his life. ቤተ ፡ መንግሥት ፡ መቅረቡ ፡ በሕይወቱ ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ የያዘ ፡ ነው

**presentation of award** የሽልማት ፡ ስጦታ
There will be a presentation of the award at the end of the year. ባመቱ ፡ መጨረሻ ፡ የሽልማት ፡ ስጦታ ፡ ይደረጋል

**present-day** ያሁኑ ፡ ጊዜ ፤ የዘመኑ
Present-day styles in clothing are different from those of ten years ago. ያሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያለባበስ ፡ ሁኔታ ፡ ከዐሥር ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ከነበረው ፡ የተለየ ፡ ነው
Present-day students must know a lot of science. የዘመኑ ፡ ተማሪዎች ፡ ስለ ፡ ሳይንስ ፡ ብዙ ፡ ማወቅ ፡ አለባቸው

**presentiment, have a ~ of** ጥርጣሬ ፡ አደረበት
He has presentiments of disaster. መጥፎ ፡ ነገር ፡ ይመጣል ፡ የሚል ፡ ጥርጣሬ ፡ አድሮበታል

**presently**
1. አሁን. The Secretary of State is presently in Africa. የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አሁን ፡ አፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው
I will be with you presently. አሁን ፡ መጣሁ
2. በቅርቡ. He will be home presently. በቅርቡ ፡ እቤት ፡ ይደርሳል

**present tense** ያሁን ፡ ጊዜ
In grammar, the present tense is expressed differently from the past. በሰዋስው ፡ ያሁን ፡ ጊዜ ፡ ከኀላፊ ፡ ጊዜ ፡ በተለየ ፡ አነጋገር ፡ ይገለጻል

**preservation**
1. መጠበቅ. Doctors work for the preservation of our health. ሐኪሞች ፡ ጤናችንን ፡ ለመጠበቅ ፡ ይጥራሉ
2. በደኅና ፡ ሁኔታ ፡ መጠበቅ. Canning makes the preservation of food possible. በጣሳ ፡ ማሸጉ ፡ ምግብን ፡ በደኅና ፡ ሁኔታ ፡ ለመጠበቅ ፡ ያስችላል
3. ጥበቃ. Preservation of forests is very necessary for Ethiopia. የደን ፡ ጥበቃ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**preserve** (v.)
1. [ምግብ ፡ ፍራፍሬ ፡ ወይም ፡ ቅጠል ፡ እንዳይበላሹ ፡ በቅመም ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዘዴ ፡ መከላከል]
2. ጠበቀ. He tried to preserve his dignity. ክብሩን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሞከረ
3. በደንብ ፡ ጠበቀ. They preserved his grave by surrounding it with a high wall. በከፍተኛ ፡ ግንብ ፡ በመከበብ ፡ መቃብሩን ፡ በደንብ ፡ ጠበቁ

**be preserved** በሥርዓት ፡ ተጠበቀ
Few early manuscripts have been preserved. ጥቂት ፡ የጥንት ፡ የብራና ፡ ጽሑፎች ፡ በሥርዓት ፡ ተጠብቀዋል

**preserve** (n.) የዱር ፡ አራዊት ፡ ክልል
People are not allowed to hunt on the preserve.

በዱር ፡ አራዊት ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ማደን ፡ አይፈቀድም

**preserves** የቆርቆሮ ፡ ምግብ
Preserves are made from raspberries and peaches. ከእንጆሪና ፡ ከኮክ ፡ የቆርቆሮ ፡ ምግብ ፡ ይዘጋጃል

## preside (over)

1. በሊቀ ፡ መንበርነት ፡ መራ. The prime minister presides over most cabinet meetings. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አብዛኛውን ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ በሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ይመራሉ
2. ተቈጣጠረ. The manager presides over the business of our store. ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ የመደብራችንን ፡ ሥራ ፡ ይቈጣጠራል

## presidency

1. ፕሬዚዳንትነት. There are several candidates for the presidency. ለፕሬዚዳንትነት ፡ ብዙ ፡ እጩዎች ፡ አሉ
2. የፕሬዚዳንትነት ፡ ዘመን. His presidency was marked by important events. የፕሬዚዳንትነቱ ፡ ዘመን ፡ ታላላቅ ፡ ድርጊቶች ፡ የተፈጸሙበት ፡ ነበር

## president ፕሬዚዳንት

The President gave another speech yesterday. ፕሬዚዳንቱ ፡ ትናንት ፡ ሌላ ፡ ንግግር ፡ አደረጉ
He is the president of our company. የኩባንያችን ፡ ፕሬዚዳት ፡ ናቸው

## presidential የፕሬዚዳንትነት

American presidential campaigns last several months. የአሜሪካ ፡ የፕሬዚዳንትነት ፡ ውድድር ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ ይወስዳል

## press (vt.)

1. ተኰሰ. She pressed my trousers for me. ሱሪዬን ፡ ተኰሰችልኝ
2. ጨበጠ. He pressed my hand warmly. እጄን ፡ በጋለ ፡ ስሜት ፡ ጨበጠው
3. ጫን ፡ አለ. Press the button to ring the bell! ደወሉን ፡ ለመደወል ፡ ቁልፉን ፡ ጫን ፡ በል
4. ጨምቆ ፡ አወጣ. They pressed the oil out of the seeds. ዘይቱን ፡ ከፍሬዎቹ ፡ ጨምቀው ፡ አወጡ
5. ሳበ. He pressed the trigger of the gun. የጠበንጃውን ፡ ምላጭ ፡ ሳበ
6. እቅፍ ፡ አደረገ. The mother pressed the baby to her. እናትዮዋ ፡ ሕፃኑን ፡ እቅፍ ፡ አደረገችው
7. አስጨነቀ. His creditors are pressing him. አበዳሪዎቹ ፡ ያስጨንቁታል
8. አጥብቆ ፡ ጠየቀ. Because of the rain, we pressed our guest to stay all night. በዝናቡ ፡ ምክንያት ፡ እንግዳውን ፡ ሰው ፡ እንዲያድሩ ፡ አጥብቀን ፡ ጠየቅናቸው
9. ገፋ. The crowd pressed him into a corner. ሕዝቡ ፡ ወደ ፡ ጥግ ፡ ገፋው
10. ገፋፋ. They pressed me for an immediate answer. ያኔውኑ ፡ እንድመልስ ፡ ገፋፉኝ
She pressed the gift on her friend. ስጦታውን ፡ እንዲቀበላት ፡ ገፋፋችው

**press** (vi.)
1. ተጣደፈ. Tom is pressing for an affirmative answer. ቶም ፡ የአዎንታ ፡ መልስ ፡ ለማግኘት ፡ ተጣድፏል
2. እየተጋፋ ፡ ገባ. Hundreds pressed into the stadium. በብዙ ፡ መቶ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ እስታዲዮም ፡ እየተጋፉ ፡ ገቡ
3. ገፋ. They pressed forward through the heavy rain and mud. በከባድ ፡ ዝናብና ፡ በጭቃ ፡ ውስጥ ፡ ወደፊት ፡ ገፉ
4. ተጋፋ. The crowd pressed against the gate. ሕዝቡ ፡ ለመግባት ፡ በሩ ፡ ላይ ፡ ተጋፋ

**press down** ጫን ፡ አለ
Press down before you open the lid! ክዳኑን ፡ ከመክፈትህ ፡ በፊት ፡ ጫን ፡ በለው

**press for** እንዲደረግ ፡ ጐተጐተ
The newspapers are pressing for an investigation concerning the murder. ጋዜጦች ፡ ስለ ፡ ነፍስ ፡ ግዳዩ ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግ ፡ ይጐተጕታሉ

**(be) pressed for** አጠረ(ው)
+I am pressed for time. ጊዜ ፡ አጥሮኛል

**press hard** ፋታ ፡ አሳጣ
They pressed the enemy hard. ጠላትን ፡ ፋታ ፡ አሳጡት

**press heavily on** ከበደ(ው)
His responsibilities press heavily on him. ያለበት ፡ ኀላፊነት ፡ ከብዶታል

**press (the) juice** ጨመቀ
Press all the juice from the oranges! ብርቱካኖቹን ፡ በደንብ ፡ ጭመቃቸው

**press on** ጉዞውን ፡ ቀጠለ
Though it was getting dark, the travelers pressed on. ቢመሽም ፡ መንገደኞች ፡ ጉዞዋቸውን ፡ ቀጠሉ

**press (one's) way through** እየተጋፋ ፡ አለፈ
He pressed his way through the crowd. በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ እየተጋፋ ፡ አለፈ

**be hard pressed** በጣም ፡ ቸገረ(ው)
+He was hard pressed for an answer. መልስ ፡ ለመስጠት ፡ በጣም ፡ ቸግሮት ፡ ነበር
[See also 'heavily']

## press (n.)

1. የማተሚያ ፡ መኪና. The newspaper bought a

new press. የጋዜጣው ፡ ድርጅት ፡ አዲስ ፡ የማተሚያ ፡ መኪና ፡ ገዛ

2. መጭመቂያ ፡ መኪና. The oil seeds are crushed in a large press. የዘይት ፡ ፍሬዎቹ ፡ ባንድ ፡ ትልቅ ፡ መጭመቂያ ፡ መኪና ፡ ይጨመቃሉ

3. ጋዜጦች. The book was favorably received by the press. መጽሐፉ ፡ በጋዜጦች ፡ ተመስግኖ ፡ ነበር

4. ጋዜጠኞች. Will the press be admitted to the conference? ጋዜጠኞቹ ፡ ወደ ፡ ስብሰባው ፡ እንዲገቡ ፡ ይፈቀድላቸዋል ?

*The little boy was lost in the press of the crowd. ትንሹ ፡ ልጅ ፡ በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ጠፋ

**freedom of the press** የጋዜጣ ፡ ነጻነት

Freedom of the press is necessary for democracy. ለዲሞክራሲ ፡ የጋዜጣ ፡ ነጻነት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**go to press** ታተመ

The manuscript is ready to go to press. ጽሑፉ ፡ ለመታተም ፡ ተዘጋጅቷል

[See also 'ironing press']

## pressing

1. አስቸኳይ. The matter is pressing and must be settled now. ጉዳዩ ፡ አስቸኳይ ፡ ስለሆነ ፡ አሁኑኑ ፡ ማለቅ ፡ አለበት

2. ብርቱ. I came to see you on a pressing matter. ለብርቱ ፡ ጉዳይ ፡ ላነጋግርህ ፡ መጣሁ

3. የሚያስቸኩል. I have a pressing engagement. የሚያስቸኩል ፡ ቀጠሮ ፡ አለኝ

## pressure

1. ጭንቀት. Now that all the exams are over, the pressure is beginning to ease up. አሁን ፡ ፈተናው ፡ ሁሉ ፡ ስላለቀ ፡ ጭንቀት ፡ እየተቃለለ ፡ ነው

2. ብዛት. Now that I have an assistant, the pressure of work is beginning to ease up. ረዳት ፡ በማግኘቴ ፡ የሥራው ፡ ብዛት ፡ እየተቃለለ ፡ መሄድ ፡ ጀምሯል

3. ያየር ፡ ግፊት. The pressure in the plane has to be the same as the pressure at sea level. በአውሮፕላን ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ያየር ፡ ግፊት ፡ ከባሕር ፡ ወለል ፡ ያየር ፡ ግፊት ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ አለበት

4. መገፋፋት. The pressure for school reform is continuing. ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ለማሻሻል ፡ የሚደረገው ፡ መገፋፋት ፡ ቀጥሏል

5. መነፋት. See that the pressure in the tire is right! ጎማው ፡ በደንብ ፡ መነፋቱን ፡ እይ

*He works well under pressure. ሲገፋፉት ፡ ደኅና ፡ ይሠራል

**bring pressure on** አስገደደ

He brought considerable pressure on him to change his mind. ሐሳቡን ፡ እንዲለውጥ ፡ በጣም ፡ አስገደደው

**bring pressure to bear**

1. አማላጅ ፡ላከ. He brought pressure to bear on the police to get his son released. ልጁን ፡ ለማስፈታት ፡ ወደ ፡ ፖሊሶች ፡ አማላጅ ፡ ላከ

2. ገፋፋ. John's parents brought pressure to bear on him to return to college. የጆን ፡ ወላጆች ፡ ኮሌጅ ፡ ተመልሶ ፡ እንዲማር ፡ ገፋፉት

**put pressure on** ገፋፋ

We'll have to put pressure on him to accept our proposal. ያቀረብነውን ፡ ሐሳብ ፡ እንዲቀበለን ፡ እሱን ፡ መገፋፋት ፡ አለብን

[See also 'blood']

## prestige ክብር

A Ph.D. holder has more prestige than an M.A. holder. የፍልስፍና ፡ ዶክተር ፡ ያለው ፡ ኤም ፡ ኤ ፡ ዲግሪ ፡ ካለው ፡ ይልቅ ፡ የበለጠ ፡ ክብር ፡ አለው

## prestigious ስመ ፡ ጥር

He is one of the most prestigious authors of our time. በጊዜያችን ፡ ካሉት ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ደራሲዎች ፡ አንዱ ፡ እሱ ፡ ነው

## presumable

*Unless they lose their way, noon is the presumable time of their arrival. መንገዳቸውን ፡ ካልሳቱ ፡ በስተቀር ፡ እኩለ ፡ ቀን ፡ ላይ ፡ ይደርሳሉ ፡ ተብሎ ፡ ይጠበቃል

## presumably ምናልባት

He will presumably come at four o'clock. ምናልባት ፡ ባሥር ፡ ሰዓት ፡ ይመጣል

## presume መሰለ(ው)

+I presume you are tired after your hike. ከሽርሽሩ ፡ በኋላ ፡ የደከምክ ፡ ይመስለኛል

*May I presume to tell you that you are wrong? ደፈረኝ ፡ አትበለኝና ፡ መሳሳትህን ፡ ልንገርህ

**let us presume** እንበል

Let us presume that economic collapse is imminent. የኤኮኖሚ ፡ ውድቀት ፡ የማይቀር ፡ ነው ፡ እንበል

## presumed (adj.) የሚባል

The child's presumed father was waiting outside. የልጁ ፡ አባት ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ እውጭ ፡ ቆሞ ፡ ነበር

**be presumed** ተብሎ ፡ ይገመታል
He is missing in action and presumed dead. በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ስለጠፋ ፡ ሞቷል ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል

**it is presumed** ይባላል
It is presumed that early Ethiopians emigrated from Yemen. የጥንቶቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የፈለሱት ፡ ከየመን ፡ ነው ፡ ይባላል

## presumption መድፈር
His presumption in ordering us to leave is astonishing. ሂዱ ፡ ብሎ ፡ ለማዘዝ ፡ መድፈሩ ፡ በጣም ፡ የሚገርም ፡ ነው

**the presumption is** ተብሎ ፡ ይገመታል
Because of the dark clouds, the presumption is that it will rain. ደመናው ፡ ስለጠቈረ ፡ ሳይዘንብ ፡ አይቀርም ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል

## presumptuous ልበ ፡ ሙሉ
He is presumptuous; he demanded the minister grant him an immediate interview. ልበ ፡ ሙሉ ፡ ስለሆነ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ወዲያውኑ ፡ ቃለ ፡ መጠይቅ ፡ እንዲሰጡት ፡ ጠየቀ

**presumptuous behavior** አጉል ፡ በራሱ ፡ መተማመን
His presumptuous behavior annoys me. የሱ ፡ አጉል ፡ በራሱ ፡ መተማመን ፡ ያናድደኛል

**be presumptuous** ዓይን ፡ አውጣነት ፡ ነው
It is presumptuous to go to a party when one has not been invited. ወደ ፡ አልተጠራበት ፡ ግብዣ ፡ መሄድ ፡ ዓይን ፡ አውጣነት ፡ ነው

## presuppose
1. ቀደም ፡ ሲል ፡ መኖሩን ፡ አመለከተ. The existence of a university presupposes a secondary school system. ዩኒቨርሲቲ ፡ መኖሩ ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ ሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መኖሩን ፡ ያመለክታል
2. በ - - - ተመሠረተ. A healthy body presupposes a proper diet. ጤነኛ ፡ አካል ፡ በተሟላ ፡ ምግብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው
*Our plans presuppose our having the same vacation time. ለእቅዳችን ፡ መፈጸም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ያስፈልገናል

## pretend
1. በሐሰት ፡ አለ. He pretended that he was a doctor. በሐሰት ፡ ሐኪም ፡ ነኝ ፡ አለ
2. መሰለ. She pretends to like you, but talks about you behind your back. የምትወድህ ፡ ትመስላለች ፡ እንጂ ፡ ዞር ፡ ስትል ፡ ታማሃለች
He pretended ignorance in order to avoid being fined for breaking the law. ሕግ ፡ በመጣሱ ፡ እንዳይቀጣ ፡ ደንቡን ፡ የማያውቅ ፡ መሰለ
3. ራሱን፡አስመሰለ. The children pretended to be grownups. ልጆቹ ፡ እራሳቸውን ፡ ትልቅ ፡ አስመሰሉ

**pretend (to)** ይገባኛል ፡ አለ
James Stuart pretended to the English throne. ጄምስ ፡ እስቱዋርት ፡ የእንግሊዝ ፡ ዙፋን ፡ ይገባኛል ፡ ብሎ ፡ ነበር

## pretender (to the throne) በሐሰት ፡ ዙፋኑ ፡ ይገባኛል ፡ የሚል ፡ ሰው
In the England of former days, a pretender to the throne was often beheaded. ድሮ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ በሐሰት ፡ ዙፋኑ ፡ ይገባኛል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ አንገቱን ፡ ይቈረጥ ፡ ነበር

## pretense
1. ሰበብ. He uses any pretense to avoid work. ሥራ ፡ ለመፍታት ፡ ሰበብ ፡ ያበዛል
2. ለይምሰል. His anger was all pretense. ንዴቱ ፡ ሁሉ ፡ ለይምሰል ፡ ነበር
*He made no pretense to being rich. ባለጸጋ ፡ መስሎ ፡ ለመታየት ፡ አልሞከረም

**(be) free from pretense** ልታይ ፡ ልታይ ፡ አላለም
Her manner is modest and free from pretense. ትሑትና ፡ ልታይ ፡ ልታይ ፡ የማትል ፡ ነች

**on the pretense** መስሎ
He called on the pretense of asking my advice. ምክሬን ፡ የሚፈልግ ፡ መስሎ ፡ ደወለ

**under pretense** መስሎ
Under pretense of picking up the handkerchief, she took the money. መሐረቡን ፡ ያነሣች ፡ መስላ ፡ ገንዘቡን ፡ ወሰደች

## pretension አለሁ ፡ አለሁ ፡ ማለት
The other girls were annoyed by her pretension. በርሷ ፡ አለሁ ፡ አለሁ ፡ ማለት ፡ የቀሩት ፡ ልጃገረዶች ፡ ተበሳጭተው ፡ ነበር

**have pretensions to** ይገበኛል ፡ ባይ ፡ ነው
The younger son has pretensions to the estate. የመጨረሻው ፡ ልጅ ፡ መሬቱ ፡ ይገባኛል ፡ ባይ ፡ ነው

**make no pretensions** አያወራም
He makes no pretensions to being an expert on the subject. ነገሩን ፡ በደንብ ፡ አውቃለሁ ፡ ብሎ ፡ አያወራም

## pretentious
1. (= adv.) ለጉራ. He makes a pretentious display of his wealth. ለጉራ ፡ ሀብቱን ፡ ያሳያል
2. የእዩልኝ. Her dress is pretentious. አለባበሷ ፡ የእዩልኝ ፡ ነው

**pretext** ሰበብ

He is just looking for a pretext. ሰበብ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚፈልገው

**under the pretext of** በ --- አሳበ

She was bored, but left under the pretext of being ill. በጣም ፡ ቢሰለቻት ፡ በሕመም ፡ አሳባ ፡ ሄደች

**pretty** (v.), ~ **oneself** ተጊያጊያጠ

The girl prettied herself for the party. ልጅቷ ፡ ለድግሱ ፡ ተጊያጊያጠች

**pretty up** አሳመረ

The maid prettied up the room. ገረዲቱ ፡ ክፍሉን ፡ አሳመረች

**pretty** (adj.)

1. ቆንጆ. She is a very pretty girl. በጣም ፡ ቆንጆ ፡ ልጅ ፡ ናት

2. በርከት ፡ ያለ. The accident will cost him a pretty sum. አደጋው ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ ያስወጣዋል

*This is a pretty mess. በጣም ፡ የተበላሸ ፡ ሆኗል

**pretty** (adv.) በጣም

I'm pretty tired. በጣም ፡ ደክሞኛል

**pretty well** በደንብ

I know the eastern part pretty well. ምሥራቃዊውን ፡ ክፍል ፡ በደንብ ፡ አውቃለሁ

*We're pretty well finished with the job. ሥራውን ፡ ወደ ፡ መጨረሱ ፡ ገደማ ፡ ነው

**a pretty good job** ጥሩ ፡ አድርጎ

He did a pretty good job of painting the house. ቤቱን ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ ቀለም ፡ ቀባው

**or pretty nearly so** ለማለት ፡ ይቻላል

The car is new or pretty nearly so. መኪናው ፡ አዲስ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል

**prevail**

1. ተሳካ. +With all our efforts, we did not prevail. ጥረታችን ፡ ሁሉ ፡ አልተሳካም

2. ተሟላ. Calm prevails in the country. ያገሪቱ ፡ ጸጥታ ፡ የተሟላ ፡ ነው

3. አሁንም ፡ አለ. Superstition prevailed in the countryside. ባገር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አጉል ፡ እምነት ፡ አሁንም ፡ አለ

4. አየለ. Westerly winds prevail in that region. ከምዕራብ ፡ የሚነፍስ ፡ ነፋስ ፡ በዚያ ፡ ቀበሌ ፡ አይሏል

*Quiet prevailed when the teacher entered the room. መምህሩ ፡ ሲገባ ፡ ክፍሉ ፡ ጸጥ ፡ አለ

**prevail against** አጠቃ

We must stand shoulder to shoulder, or else the enemy will prevail against us. መተባበር ፡ አለብን ፤ አለበለዚያ ፡ ጠላት ፡ ያጠቃናል

**prevail on** አግባባ

We tried to prevail on him to come along. ከኛ ፡ ጋር ፡ እንዲመጣ ፡ ልናግባባው ፡ ሞከርን

**prevail over** አሸነፈ

Truth will prevail over falsehood. እውነት ፡ ሐሰትን ፡ ታሸንፋለች

**prevailing**

1. የሚበዛ. Red is the prevailing color in her house. በቤቷ ፡ ውስጥ ፡ የሚበዛው ፡ ቀይ ፡ ነገር ፡ ነው

2. (= adv.) ብዙ ፡ ጊዜ. The islands have prevailing winds from the west. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የምዕራብ ፡ ነፋስ ፡ በደሴቶች ፡ ላይ ፡ ይነፍሳል

**prevalence** ብዛት

The prevalence of automobiles has created many problems. የመኪና ፡ ብዛት ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ፈጥሯል

*The prevalence of new methods over the old is noticeable. አዳዲስ ፡ ዘዴዎች ፡ ባሮጌው ፡ ላይ ፡ እያየሉ ፡ መሄዳቸው ፡ በግልጽ ፡ ይታያል

**prevalent** ያብዛኛው ፡ ሕዝብ

The prevalent opinion favors school reforms. ያብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ ሐሳብ ፡ የትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ይዘታ ፡ መሻሻል ፡ የሚደግፍ ፡ ነው

**be prevalent**

1. በብዛት ፡ ተገኘ. Malaria is prevalent in swampy areas. በረግረግ ፡ ቦታዎች ፡ ወባ ፡ በብዛት ፡ ይገኛል

2. አየለ. Colds are prevalent in winter. በክረምት ፡ ወራት ፡ ጉንፋን ፡ ያያል

**prevent** አስቀረ

The pilot of the plane prevented a serious accident. አውሮፕላን ፡ ነጂው ፡ ትልቅ ፡ አደጋ ፡ አስቀረ

**prevent from**

1. እንድ + negative imperfect + ከለከለ. What prevented you from coming? እንዳትመጣ ፡ ምን ፡ ከለከለህ ?

2. ከ --- አገደ. The bulk of the elephant does not prevent him from walking fast. ዝሆንን ፡ ግዙፍነቱ ፡ በፍጥነት ፡ ከመሄድ ፡ አያግደውም

3. ከ --- አስቀረ. His bellyache prevented him from going to school. የቁርጠት ፡ ሕመም ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከመሄድ ፡ አስቀረው

4. እንድ + imperfect + አልፈቀደ(ለትም). His commitment to his job prevents him from taking leave. ለሥራው ፡ ያለው ፡ አሳቢነት ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ እንዲወስድ ፡ አይፈቅድለትም
5. እንድ + negative imperfect + አደረገ. His deformity prevented him from playing games. አካለ ፡ ጐደሎነቱ ፡ ስፖርት ፡ እንዳይጫወት ፡ አደረገው

**prevention**
1. አስቀድሞ ፡ መከላከል. Prevention of sickness is better than curing it. በሽታን ፡ ከማዳን ፡ ይልቅ ፡ አስቀድሞ ፡ መከላከሉ ፡ የተሻለ ፡ ነው
2. መከላከያ. Take this remedy as a prevention against cold! ለጉንፋን ፡ መከላከያ ፡ ይህንን ፡ መድኃኒት ፡ ውሰድ

**preventive** (n.) መከላከያ
Vaccination is a preventive against smallpox. ክትባት ፡ የፈንጣጣ ፡ መከላከያ ፡ ነው

**preventive** (adj.)
*The city must take preventive measures against crime. ከተማው ፡ ወንጀልን ፡ ለመከላከል ፡ እርምጃ ፡ መውሰድ ፡ አለበት

**previous**
1. የፊተኛ. The judge overruled the previous decision. ዳኛው ፡ የፊተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ገለበጠው
2. ቀደም ፡ ያለ. I've made a previous engagement. ቀደም ፡ ያለ ፡ ቀጠሮ ፡ አድርጌያለሁ
3. ከዚህ ፡ በፊት ፡ የቀረበ. This book is a polemic against previous ideas. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የቀረቡትን ፡ ሐሳቦች ፡ የሚቃረን ፡ ነው
4. የድሮ. Married life changed many of his previous habits. ትዳር ፡ ብዙውን ፡ የድሮ ፡ ልማዱን ፡ ለወጠው
5. (= adv.) ከዚህ ፡ ቀደም. He had no previous experience in that field. ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በዚያ ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ልምምድ ፡ አልነበረውም
6. (= adv.) ባለፈው ፡ ጊዜ. I met him on a previous visit to England. ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሄጄ ፡ በነበርኩበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ያገኘሁት

**previous to** ከ --- በፊት
Previous to coming here, he was ambassador to Russia. እዚህ ፡ ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ በሩሲያ ፡ አምባሳደር ፡ ነበር

**previously** ከዚህ ፡ በፊት
Had you been to Africa previously? ከዚህ ፡ በፊት ፡ አፍሪካ ፡ ሄደህ ፡ ነበር ?

**prey, ~ on** ወረረ
The Vikings preyed on coastal settlements. ቫይኪንጎች ፡ የጠረፍ ፡ ቀበሌዎችን ፡ ወረሩ

**prey upon**
1. በማጭበርበር ፡ ኖረ. Swindlers prey upon the ignorant. አታላዮች ፡ ደንቆሮውን ፡ ሕዝብ ፡ በማጭበርበር ፡ ይኖራሉ
2. እያደኑ ፡ በላ. Cats prey upon mice. ድመቶች ፡ አይጥ ፡ እያደኑ ፡ ይበላሉ
*Worry about her debts preys upon her mind. ያለባትን ፡ ዕዳ ፡ ማሰቡ ፡ የመንፈስ ፡ ጭንቀት ፡ አሳድሮባታል

**prey** (n.) የገደለውን ፡ እንስሳ
The tiger devoured its prey. ነብሩ ፡ የገደለውን ፡ እንስሳ ፡ በላ

**of prey** አድኖ ፡ የሚበላ
The tiger is an animal of prey. ነብር ፡ አድኖ ፡ የሚበላ ፡ አውሬ ፡ ነው

**fall prey to** በእጅ ፡ ወደቀ
The gazelle fell prey to the hunters. ድኩላው ፡ በአዳኞቹ ፡ እጅ ፡ ወደቀ

**price** (v.) ዋጋ ፡ አየ
I priced the radio in several stores. በየመደብሩ ፡ የሬዲዮኑን ፡ ዋጋ ፡ አየሁ

**be priced**
1. ተተመነ. The hat was priced at $10. ባርኔጣው ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ ተተምኗል
2. ዋጋ ፡ ተጻፈ. All the goods are plainly priced. የእቃው ፡ ዋጋ ፡ ሁሉ ፡ በጉልህ ፡ ተጽፏል

**price** (n.)
1. ዋጋ. The price of food is very high here. የምግብ ፡ ዋጋ ፡ እዚህ ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ ነው
2. መሥዋዕት. We paid a heavy price for the victory. ድሉን ፡ ለማግኘት ፡ ከፍተኛ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገናል
*A price has been put on the bandit's head. ሽፍታውን ፡ ለያዘ ፡ ወይም ፡ ለገደለ ፡ መንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ይከፍላል

**price range** ዋጋ
That's all I have in this price range. በዚህ ፡ ዋጋ ፡ የሚሸጥ ፡ ያለኝ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው

**at any price** በምንም ፡ ዋጋ
There were no bananas to be had at any price. ሙዝ ፡ በምንም ፡ ዋጋ ፡ ሊገኝ ፡ አልተቻለም

**for any price** በምንም ፡ ዓይነት
I wouldn't part with that book for any price. ያንን ፡ መጽሐፍ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ከእጄ ፡ አላወጣውም

**(at) high prices** በውድ
Buy at low prices and sell at high prices! በርካሽ ፡ ገዝተህ ፡ በውድ ፡ ሽጥ
[See also 'low, retail, rock bottom']

**priceless** እጅግ ፡ ውድ
The monastery owns several priceless manuscripts. ገዳሙ ፡ እጅግ ፡ ውድ ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ ጥንታዊ ፡ የጅ ፡ ጽሑፎች ፡ አሉት

**be priceless** እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ አለው
This statue is priceless; it cannot be duplicated. ይህ ፡ ሐውልት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ስላለው ፡ የሚመስለው ፡ በጭራሽ ፡ አይገኝም

**prick**
1. ወጋ. She pricked her finger with a needle. ጣቷን ፡ በመርፌ ፡ ወጋችው
2. ቧጠጠ. The cat pricked me with its claws. ድመቷ ፡ በጥፍሮቿ ፡ ቧጠጠችኝ
3. ነካ. Guilt pricked his conscience. ጥፋቱ ፡ ኅሊናውን ፡ ነካው

**prick up** አቆመ
The dog pricked up its ears. ውሻው ፡ ጆሮውን ፡ አቆመ
He pricked up his ears at the mention of the job. የሥራው ፡ ወሬ ፡ ሲነሣ ፡ ጆሮውን ፡ አቆመ

**prickle** (v.), **~ one's skin** ቧጨረ
The bush prickled her skin. ቁጥቋጦው ፡ ቧጨራት

**prickle** (n.) ጥቃቅን ፡ እሾህ
The bush is covered with prickles. ቁጥቋጦው ፡ ጥቃቅን ፡ እሾህ ፡ ሞልቶበታል

**feel a prickle** ወረረ(ው)
I feel a prickle when I use this lotion on my face. ይህን ፡ ቅባት ፡ ስቀባ ፡ ፊቴን ፡ ይወረኛል

**prickly** እሾህማ
Euphorbia is a prickly plant. ቁልቋል ፡ እሾህማ ፡ ዕፅ ፡ ነው

**have a prickly feeling**
*I have a prickly feeling from the wool scarf. የሱፉ ፡ አንገት ፡ ልብስ ፡ ሲኰሰኵሰኝ ፡ ይሰማኛል

**pride** (v.), **~ oneself on** ኰራ
She prides herself on her good housekeeping. በጥሩ ፡ ቤት ፡ አያያዝ ፡ ትኰራለች

**pride** (n.)
1. ኩራት. Pride was considered a sin by churchmen. በካህናት ፡ ዘንድ ፡ ኩራት ፡ እንደ ፡ ኀጢአት ፡ ይቈጠር ፡ ነበር
2. ኩሩነት. His pride kept him from asking for money. ኩሩነቱ ፡ ገንዘብ ፡ ከመጠየቅ ፡ አገደው
3. ክብር. Don't you have any pride? ክብርህን ፡ አትጠብቅም ?
4. ትምክሕት. False pride in his abilities has caused him much harm. በችሎታው ፡ ያለው ፡ የተሳሳተ ፡ ትምክሕት ፡ ብዙ ፡ጉዳት ፡ አድርሶበታል
5. መኩሪያ. The girl is her mother's pride. ልጅቷ ፡ ለእናቷ ፡ መኩሪያ ፡ ነች

**take pride in** ኰራ(በት)
He takes great pride in his work. በሥራው ፡ በጣም ፡ ይኰራበታል

**priest** ቄስ
The priest blessed the new church. ቄሱ ፡ አዲሱን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባረኩ

**become a priest** ቀሰሰ
The deacon became a priest after ten years. ዲያቆኑ ፡ ካሥር ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ቀሰሰ

**priesthood** ካህናት
Priesthood plays an important role in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ካህናት ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ አላቸው

**priestly** የቅስና
He performs his priestly duties well. የቅስና ፡ ተግባሩን ፡ በሚገባ ፡ ያከናውናል

**priestly class** ካህናት
The priestly class is well represented at this convention. በዚህ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ካህናት ፡ ተገኝተዋል

**primacy** ቀደምትነት
The primacy of the Patriarch of Alexandria is recognized by the Ethiopian church. የእስክንድርያው ፡ ፓትሪያርክ ፡ ቀደምትነት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታውቋል

**primarily**
1. በይበልጥ. He is primarily interested in tennis. በይበልጥ ፡ የሚወደው ፡ ቴኒስ ፡ ነው
2. በመሠረቱ. The idea was primarily yours. አሳቡ ፡ በመሠረቱ ፡ ያንተ ፡ ነበረ

**primary**
1. መሠረታዊ. The primary meaning of the word is the same in all the related languages. የቃሉ ፡ መሠረታዊ ፡ ትርጉም ፡ በሚዛመዱ ፡ ቋንቋዎች ፡ ሁሉ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ነው
Literacy is of primary importance. መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ መሠረታዊ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው
2. ዋና. Our primary concern is the transport of troops. ዋናው ፡ ዓላማችን ፡ ወታደሮችን ፡ ማጓጓዝ ፡ ነው
3. ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ አስፈላጊ. Good health and character are primary. ጥሩ ፡ ጤንነትና ፡ መልካ

ም ፡ ጠባይ ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ አስፈላጊዎች ፡ ናቸው

**primary school** አንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት
My sister goes to primary school. እኅቴ ፡ አንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ትማራለች

**prime** (v.)
1. ለማንቀሳቀስ ፡ አዘጋጀ. He primed the pump by pouring a little water into the top of it. ፖምፑ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂት ፡ ውኃ ፡ በመጨመር ፡ ለማንቀሳቀስ ፡ አዘጋጀው
2. አስቀድሞ ፡ አዘጋጀ. The teacher primed the students for the test. መምህሩ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ለፈተና ፡ አስቀድሞ ፡ አዘጋጃቸው

**prime** (n.) አፍላ
The athlete is in his prime. ስፖርተኛው ፡ በአፍላው ፡ ላይ ፡ ነው

**prime of life** የዕድሜ ፡ አፍላ ፤ የሕይወት ፡ አፍላ
A man of forty is in the prime of life. የአርባ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ በዕድሜው ፡ (በሕይወቱ) ፡ አፍላ ፡ ላይ ፡ ነው

**prime** (adj.) ዋና
His prime motive is love of money. ዋና ፡ ዓላማው ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ ነው

**prime minister** ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር
The prime minister went abroad. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሄደዋል

**primer** ዐውደ ፡ ንባብ
Primers have been given free to all schoolchildren. ዐውደ ፡ ንባቦች ፡ ለትምህርት ፡ ቤት ፡ በነጻ ፡ ታድለዋል

**primeval** የመጀመሪያ
In its primeval state, the earth was a fiery glowing ball. በመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ መሬት ፡ ፍም ፡ የመሰለች ፡ ድቡልቡል ፡ አካል ፡ ነበረች

**primitive**
1. የጥንት. Primitive man did not know how to cook food. የጥንት ፡ ሰው ፡ ምግብ ፡ ማብሰል ፡ አያውቅም ፡ ነበር
A primitive way of making fire was by rubbing two sticks together. የጥንት ፡ የእሳት ፡ ማውጫ ፡ ዘዴ ፡ ሁለት ፡ ዕንጨቶችን ፡ በማፋጨት ፡ ነበር
2. ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረ. Conditions are very primitive in some parts of Brazil. በብራዚል ፡ ውስጥ ፡ ያንዳንዱ ፡ ቀበሌ ፡ ሁኔታ ፡ በጣም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረ ፡ ነው
3. ያልሠለጠነ. Some primitive peoples still go naked. አንዳንድ ፡ ያልሠለጠኑ ፡ ሕዝቦች ፡ አሁንም ፡ እራቁታቸውን ፡ ይሄዳሉ
4. ባልሠለጠነ ፡ አሠራር ፡ የተሠራ. They still wear primitive straw hats in this village. በዚህ ፡ መንደር ፡ አሁንም ፡ ባልሠለጠነ ፡ አሠራር ፡ የተሠራ ፡ የሣር ፡ ባርኔጣ ፡ ያደርጋሉ

**primogeniture**
1. ብኵርና. Esau traded his primogeniture for a trifle. ኤሳው ፡ ብኵርናውን ፡ በማይረባ ፡ ነገር ፡ ለወጠው
2. የበኵር ፡ ልጅ ፡ ይውረስ ፡ የሚለው ፡ ደንብ. Primogeniture assures that the eldest son will inherit the estate. የበኵር ፡ ልጅ ፡ ይውረስ ፡ የሚለው ፡ ደንብ ፡ ታላቅ ፡ ልጅ ፡ ንብረቱን ፡ እንዲወርስ ፡ ያደርጋል

**prince** ልዑል
An Ethiopian prince visited England. የኢትዮጵያ ፡ ልዑል ፡ የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ ጐበኘ

**Crown Prince** አልጋ ፡ ወራሽ
The Crown Prince will visit our office soon. አልጋ ፡ ወራሽ ፡ መሥሪያ ፡ ቤታችንን ፡ በቅርቡ ፡ ይጐበኛሉ

**princely**
1. የልዑልነት. His princely powers are described in the constitution. የልዑልነት ፡ ሥልጣኑ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጿል
2. ከፍተኛ ፤ ከፍ ፡ ያለ. Last year he earned a princely salary. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ከፍተኛ ፡ ደሞዝ ፡ አገኘ
He gave me a princely gift. ከፍ ፡ ያለ ፡ ስጦታ ፡ አደረገልኝ

**princess** ልዕልት
The princess is in charge of the women's association. ልዕልቲቱ ፡ የሴቶች ፡ ማኅበር ፡ ኀላፊ ፡ ናቸው

**principal** (n.)
1. ሥራ ፡ መሪ ፤ ዲሬክተር. The principal called the teachers into his office. ሥራ ፡ መሪው ፡ (ዲሬክተሩ) ፡ መምህራኑን ፡ እቢሮው ፡ ጠራቸው
2. ዋና ፡ ገንዘብ. Have you paid interest on the principal? የዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ ወለድ ፡ ከፍለሃል ?

**principal** (adj.) ዋና
Chicago is the principal city of Illinois. ቺካጎ ፡ የኢሊኖይ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ነች

**principle**
1. መሠረታዊ ፡ ደንብ. Do you know the principle by which a machine works? መኪና ፡ የሚሠራበትን ፡ መሠረታዊ ፡ ደንብ ፡ ታውቃለህን ?

2. መሠረት. It works in principle, but not in practice. በመሠረቱ ፡ የሚሆን ፡ ይመስላል ። በሥራ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ሊውል ፡ አይችልም
3. መሠረተ ፡ ሐሳብ. Do you know the principles of arithmetic? የሒሳብን ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ፡ ታውቃለህ ?
4. ደንብ. I make it a principle to save some money every month. በየወሩ ፡ ጥቂት ፡ ገንዘብ ፡ ማጠራቀምን ፡ እንደ ፡ ደንብ ፡ አድርጌ ፡ ይዤዋለሁ
5. እምነት. His actions are consonant with his principles. አድራጎቱ ፡ ከእምነቱ ፡ ጋር ፡ የተስማማ ፡ ነው
6. ሥርዓት. An eye for an eye is a crude principle of justice. ዓይን ፡ ያጠፋ ፡ ዓይኑ ፡ ይጥፋ ፡ የሚለው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረ ፡ የፍትሕ ፡ ሥርዓት ፡ ነው
7. ይሉኝታ. He will do anything for money because he has no principles whatever. ይሉኝታ ፡ ስለሌለው ፡ ለገንዘብ ፡ ሲል ፡ የማያደርገው ፡ ነገር ፡ የለም
8. የሚያምንበት ፡ ነገር. He shows great fidelity to his principles. ለሚያምንበት ፡ ነገር ፡ ይሞታል
9. መምሪያ. The leaders tried to ground the government on democratic principles. መሪዎቹ ፡ መንግሥቱን ፡ በዲሞክራሲ ፡ መምሪያዎች ፡ ላይ ፡ ለመመሥረት ፡ ሞከሩ

**as a matter of principle** በሕጉ ፡ መሠረት
A judge should not take a bribe as a matter of principle. በሕጉ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ዳኛ ፡ ጉቦ ፡ መቀበል ፡ የለበትም
*I don't do such things as a matter of principle. ከማምንበት ፡ ነገር ፡ውጭ ፡ ስለሆነ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ አላደርገውም

**man of principles**
He is a man of principles. ጽኑ ፡ ዓላማ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**on principle** ባስተሳሰቡ ፡ እምነት ፡ ምክንያት
He refused on principle to cheat on his income tax. ባስተሳሰቡ ፡ እምነት ፡ ምክንያት ፡ የገቢ ፡ ቀረጡን ፡ ማጭበርበር ፡ እምቢ ፡ አለ

## print (v.)

1. አተመ. The printing press printed many books this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ ማተሚያ ፡ ቤቱ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ አተመ
The magazine printed his story. መጽሔቱ ፡ እሱ ፡ የጻፈውን ፡ ታሪክ ፡ አተመው
2. በጉልህ ፡ ጻፈ. Please print your name! ስምህን ፡ በጉልህ ፡ ጻፍ

## print (n.)

1. [በእጅ ፡ ከተሣለ ፡ ሥዕል ፡ ላይ ፡ በመኪና ፡ ታትሞ ፡ የተባዛ ፡ ሥዕል]
2. ፊደሎች. The print in this book is very small. የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ፊደሎቹ ፡ በጣም ፡ ረቂቅ ፡ ናቸው
3. ቅጂ. How many prints shall I make of each picture? ከያንዳንዱ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ስንት ፡ ቅጂ ፡ ላውጣልህ ?
4. አሻራ. The prints of his fingers could be seen on the glass. ብርጭቆው ፡ ላይ ፡ የጣቶቹ ፡ አሻራ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**(of) colored print** ባለ ፡ አበባ
She has a dress of colored print. ባለ ፡ አበባ ፡ ቀሚስ ፡ አላት

**fine print** በረቂቅ ፡ የተጻፉ
Read the fine print before you sign any contract. ማንኛውንም ፡ ውል ፡ ከመፈረምህ ፡ በፊት ፡ በረቂቅ ፡ የተጻፉትን ፡ ሁሉ ፡ ልብ ፡ አድርገህ ፡ አንብብ

**in print** ታትሞ
He finally saw his story in print. በመጨረሻ ፡ የጻፈውን ፡ ታሪክ ፡ ታትሞ ፡ አየው

**(be) in print** ይገኛል
This book is still in print. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ አሁንም ፡ ይገኛል

**(be) out of print** አለቀ
The book is out of print. የታተመው ፡ መጽሐፍ ፡ አልቋል

## printer አታሚ

Who is the printer of this book? የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ አታሚ ፡ ማነው ?

## printing እትም

The printing in this book is very clear. የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ እትሙ ፡ ቁልጭ ፡ ያለ ፡ ነው

## printing press ማተሚያ ፡ መኪና

The printing press broke down. ማተሚያው ፡ መኪና ፡ ተሰበረ

## prior ቀደም ፡ ያለ

Due to a prior invitation, I couldn't come to your party. ቀደም ፡ ያለ ፡ ጥሪ ፡ ስላለብኝ ፡ ግብዣህ ፡ ልመጣ ፡ አልቻልኩም
*He has a prior claim to the land. መሬቱ ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ ቀደምትነት ፡ አለው

**prior to** ከ --- በፊት
Prior to my departure, I consulted with the minister. ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ ከሚኒስትሩ ፡ ጋር ፡ ተማከርኩ

## priority ቀደምትነት

The plan was given priority over all others. እቅዱ ፡ ከሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ ቀደምትነት ፡ ተሰጥቶታል

**have priority** ቅድሚያ ፡ ተሰጠው
Fire engines have priority over other traffic. የእሳት ፡ አደጋ ፡ መኪናዎች ፡ ከሌሎቹ ፡ ቅድሚያ ፡ ይሰጣቸዋል

## prison እስር ፡ ቤት
The prison is heavily guarded. እስር ፡ ቤቱ ፡ በጥብቅ ፡ ይጠበቃል
[See also 'confine, confinement']

## prisoner እስረኛ
A prisoner has just escaped. እስረኛ ፡ አሁን ፡ አመለጠ

**prisoner of war** ምርኮኛ
The prisoners of war were badly treated. ምርኮኞቹ ፡ በጣም ፡ ተጐሳሉ

**keep a prisoner** እስሮ ፡ አስቀመጠ
He kept his dog a prisoner in the garage. ውሻውን ፡ መኪና ፡ ማቆሚያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አስሮ ፡ አስቀመጠው

**take prisoner** ማረከ
We took three hundred prisoners. ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ማረክን

## pristine
*The bodies of the first kings were found in pristine condition. የቀድሞዎቹ ፡ ነገሥታት ፡ አስከሬን ፡ እንዳለ ፡ ተገኘ

## privacy
1. ለብቻ ፡ መሆን. Hard study requires privacy. በደንብ ፡ ለማጥናት ፡ ለብቻ ፡ መሆን ፡ ያስፈልጋል
2. ቆይታ. They discussed personal affairs in privacy. የግል ፡ ጉዳያቸውን ፡ በቆይታ ፡ ተወያዩ
3. የግል ፡ ኑሮ. Reporters invaded his privacy by asking personal questions. ጋዜጠኞች ፡ ስለ ፡ ግል ፡ ሁኔታ ፡ ጥያቄ ፡ እየጠየቁ ፡ በግል ፡ ኑሮው ፡ ጣልቃ ፡ ገቡበት

## private (n.) ተራ ፡ ወታደር
He was a private in the First World War. በመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ተራ ፡ ወታደር ፡ ነበር

**private** (adj.)
1. የግል. This is my private property. ይህ ፡ የግል ፡ ሀብቴ ፡ ነው
He attends private school. በግል ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይማራል
Private enterprise plays a small part in Ethiopia's development. በኢትዮጵያ ፡ ልማት ፡ ውስጥ ፡ የግል ፡ ንግድ ፡ የሚያበረክተው ፡ ድርሻ ፡ አነስተኛ ፡ ነው
2. ልዩ. They held their meeting in a private room. ስብሰባቸውን ፡ በልዩ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ አደረጉ
3. ተራ. A private citizen should take an interest in what the government does. ተራው ፡ ዜጋ ፡ የመንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ ተከፋይ ፡ መሆን ፡ አለበት

**(my) private opinion is** እንደኔ ፡ ከሆነ
My private opinion is that he should not go abroad. እንደኔ ፡ ከሆነ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ መሄድ ፡ የለበትም

**in private**
1. ለብቻ. I'd like to talk to you in private. ለብቻህ ፡ ላነጋግርህ ፡ እፈልጋለሁ
2. በዝግ. The session will be conducted in private. ስብሰባው ፡ በዝግ ፡ ይካሄዳል

## private secretary ልዩ ፡ ጸሐፊ
The Emperor's private secretary will attend the meeting. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ልዩ ፡ ጸሐፊ ፡ ስብሰባው ፡ ላይ ፡ ይገኛል

## privation
1. በምግብና ፡ በልብስ ፡ ችግር. Our family suffered privation during the war. ቤተሰባችን ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ በምግብና ፡ በልብስ ፡ ችግር ፡ ተሠቃይቶ ፡ ነበር
2. ችግር. The troops faced severe privation. ወታደሮቹ ፡ ከባድ ፡ ችግር ፡ ደረሰባቸው

## privilege ልዩ ፡ መብት
He was denied all the privileges. ልዩ ፡ መብቶቹን ፡ ሁሉ ፡ ተነፈገ

## privileged የታደለ
The students are a privileged class in this country. በዚህ ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ ተማሪዎች ፡ ከታደለው ፡ ወገን ፡ የሚቈጠሩ ፡ ናቸው

**be privileged** ተፈቀደ(ለት)
He is privileged to use the library whenever he wishes. ቤተ ፡ መጻሕፍቱን ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ እንዲጠቀምበት ፡ ተፈቅዶለታል

## privy, be ~ to ውስጡን ፡ ዐወቀ
The minister was privy to the details of the conspiracy. ሚኒስትሩ ፡ አድማውን ፡ ውስጡን ፡ ያውቁት ፡ ነበር

## prize (v.) አብልጦ ፡ ወደደ
He prizes the book that he received from his teacher more than anything else. ከስተማሪው ፡ የተሰጠውን ፡ መጽሐፍ ፡ ከማናቸውም ፡ ነገር ፡ አብልጦ ፡ ይወደዋል

**prize** (n.)
1. ሽልማት. Who won the first prize in poetry? በግጥም ፡ አንደኛውን ፡ ሽልማት ፡ ማን ፡ አገኘ ?
2. የሚበልጥ. This puppy is the prize of the litter. ይህ ፡ ቡችላ ፡ ከሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ የሚበል
ጥ ፡ ነው
*His friendship would be a great prize. ጓደኝነ
ቱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አይባልም

**prize** (adj.) ዋጋ ፡ ያለው
This is a prize house. ይህ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ቤት ፡
ነው

**Prize Trust** የሽልማት ፡ ድርጅት
The Haile Sellassie Prize Trust was created to promote Ethiopian studies. የቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡
ሥላሴ ፡ የሽልማት ፡ ድርጅት ፡ የተቋቋመው ፡
የኢትዮጵያን ፡ ጥናት ፡ ለማበረታታት ፡ ነው

**prized, highly** ~ ውድ
Thoroughbred horses from Arabia are highly prized. ከዐረብ ፡ አገር ፡ የሚመጡ ፡ ዘረ ፡ መልካ
ም ፡ ፈረሶች ፡ ውድ ፡ ናቸው

**pro(s)** ጥቅም
He wants to consider the pros and cons before he makes up his mind. ሐሳቡን ፡ ከመቍረጡ ፡
በፊት ፡ ጥቅሙንና ፡ ጉዳቱን ፡ ሊያመዛዝን ፡ ይ
ፈልጋል

**pro-** የሚደግፍ
He has a pro-British point of view. እንግሊዝን ፡
የሚደግፍ ፡ አስተያየት ፡ አለው

**probability** (probabilities)
1. ይሆናል. Let's not confuse possibility with probability! የሚቻልን ፡ ከይሆናል ፡ ጋር ፡ አናማታ
2. ዕድል. The probability of his coming in this rain is very small. በዚህ ፡ በዝናም ፡ ለመምጣ
ት ፡ ያለው ፡ ዕድል ፡ አነስተኛ ፡ ነው
*The probability of rain forced me to stay home. ዝናም ፡ ይመጣል ፡ የሚል ፡ ፍራቻ ፡ ከቤት ፡
አዋለኝ
*There is a probability that school will close a week earlier than usual. ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከተ
ለመደው ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ይ
ዘጋ ፡ ይሆናል

**in all probability**
*In all probability, you will have to make a down payment first. እንደምገምተው ፡ የመጀመሪ
ያ ፡ ክፍያ ፡ መክፈል ፡ ሳይኖርብህ ፡ አይቀርም

**probable**
*Something he ate is the probable cause of his pain. የሕመሙ ፡ ምክንያት ፡ የበላው ፡ ነገር ፡
ሳይሆን ፡ አይቀርም
*The probable result of any war is that everybody will lose and nobody will win. ማንኛው
ም ፡ ጦርነት ፡ ውጤቱ ፡ ሁሉም ፡ ተሸንፎ ፡
ማንም ፡ አለማሸነፍን ፡ የሚያስከትል ፡ ይመስላል

**be probable, seem probable** ሰ + negative imperfect + አልቀረም ፡ (አይቀርም)
It is probable that he is the guilty one. ጥፋተ
ኛው ፡ እርሱ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም
It seems probable that the letter was lost. ደብዳቤው ፡ ሳይጠፋ ፡ አልቀረም

**probably** ምናልባት
You'll probably meet him on the train. ምናልባት ፡ ባቡር ፡ ላይ ፡ ታገኘዋለህ

**probation** የሙከራ ፡ ደረጃ
The student has been placed on probation until his grades improve. ውጤቱን ፡ እስኪያሻ
ሽል ፡ ተማሪው ፡ በሙከራ ፡ ደረጃ ፡ ይማራል
*The judge placed the young boy on probation for two years. ዳኛው ፡ ልጁ ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡
ጊዜ ፡ በአመክሮ ፡ እንዲቆይ ፡ አደረገው

**probe** (v.) መረመረ
The committee is probing into his financial activities. ደርጉ ፡ ገንዘቡን ፡ ከምን ፡ ሥራ ፡ እን
ዳዋለው ፡ ይመረምራል

**probe** (n.) ምርመራ
The mayor demanded a probe of gambling in the city. ከንቲባው ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ የቁ
ማር ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግ ፡ አዘዋል

**probity** ሐቀኝነት
He is a man of unquestioned probity. እርሱ ፡ የ
ማያጠራጥር ፡ ሐቀኝነት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**problem**
1. ጉዳይ. The border problem will be discussed by the U.N. የድንበሩ ፡ ጉዳይ ፡ በተባበሩት ፡
መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ውይይት ፡ ይደረግበ
ታል
That's your problem. ያ ፡ ያንተ ፡ ጉዳይ ፡ ነው
2. ችግር. Social problems must be studied by experts. የኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ ችግሮች ፡ በዐዋቂዎች ፡
መጠናት ፡ አለባቸው
3. ጣጣ. He has many domestic problems. ብዙ ፡ የቤት ፡ ጣጣ ፡ አለበት
4. ጥያቄ. I couldn't solve the second problem. ሁለተኛውን ፡ ጥያቄ ፡ ልሠራው ፡ አልቻልኩም

**problem child**
His son is a problem child. ልጁ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
[See also 'deal, racial']

**problematic** አጠራጣሪ
What the weather will be is problematic. ያየሩ ፡ ሁኔታ ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው

**procedure** ሥርዓት
The procedures to follow in applying for a visa are complicated. ቪዛ ፡ ለማውጣት ፡ የምንከተለው ፡ ሥርዓት ፡ ውስብስብ ፡ ነው
[See also 'legal']

**proceed**
1. ጀመረ. He proceeded to inform me about conditions there. እዚያ ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ ይነግረኝ ፡ ጀመር
2. ጕዞ ፡ ቀጠለ. They proceeded to Harar on foot after their car broke down. መኪናቸው ፡ ከተበላሸ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ በእግር ፡ ጕዞ ፡ ቀጠሉ
3. ገፋ. The fallen tree across the road did not let us proceed any further. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ የተጋደመው ፡ ዛፍ ፡ ወደፊት ፡ እንዳንገፋ ፡ ከለከለን
4. ተራመደ. The path is slippery; you had better proceed with caution. መንገዱ ፡ ስለሚያዳልጥ ፡ በጥንቃቄ ፡ ብትራመድ ፡ ይሻላል

**proceed from** አስከተለ
+Famine and disease proceed from war. ጦርነት ፡ ረኀብን ፡ በሽታን ፡ ያስከትላል

**proceed to, proceed with** ቀጠለ
Let us proceed to business! ሥራችንን ፡ እንቀጥል
Please proceed with your story! ታሪክህን ፡ ቀጥል

**proceeding** ነገር
It was a strange proceeding when the Senate adjourned without any decision. ሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ያለ ፡ ውሳኔ ፡ ሲለያይ ፡ ያልተለመደ ፡ ነገር ፡ ነበር

**way of proceeding** የአሠራር ፡ ዘዴ
What's the best way of proceeding? የተሻለው ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፡ የትኛው ፡ ነው ?

**proceedings** የሥራ ፡ ውጤት
The proceedings of the meeting are printed once a month. የስብሰባው ፡ የሥራ ፡ ውጤት ፡ በየወሩ ፡ ይታተማል
*The proceedings of the meeting were disorderly. ስብሰባው ፡ የተተራመሰ ፡ ነበር

**start proceedings against** ከሰሰ
He started proceedings against his neighbor. ጐረቤቱን ፡ ከሰሰ

**proceeds** ያገኘው ፡ ገንዘብ
He invested the proceeds from the sale of his farm. የእርሻ ፡ ቦታውን ፡ በመሸጥ ፡ ያገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለው

**process** (v.)
1. አዘጋጀ. This plant processes 150 tons of fish a day. ይህ ፡ ፋብሪካ ፡ በቀን ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ቶን ፡ ዓሣ ፡ ያዘጋጃል
2. በየክፍላቸው ፡ ደለደለ. They processed the students on registration day. በመመዝገቢያው ፡ ቀን ፡ ተማሪዎቹን ፡ በየክፍላቸው ፡ ደለደሉ
3. ደለደለ. They processed all the recruits in one day. ምልምሎቹን ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ደለደሏቸው

**process** (n.)
1. ጕዳይ. That will be a long drawn-out process. ያ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጅ ፡ ጕዳይ ፡ ይሆናል
2. ዘዴ. By what process is cloth made from wool? ሱፍ ፡ ልብስ ፡ የሚሆነው ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ዘዴ ፡ ነው ?
That process was worked out in our school laboratory. ዘዴው ፡ የተፈጠረው ፡ በትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ቤተ ፡ሙከራ ፡ ውስጥ ፡ ነው
*Training to become a doctor is a lengthy process. የሕክምና ፡ ትምህርት ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው

**have in process** በ --- ላይ ፡ ነው
*The author has just finished one book and has another in process. ደራሲው ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ በቅርቡ ፡ ጨርሶ ፡ ሌላ ፡ በመጻፍ ፡ ላይ ፡ ነው

**in process of time** በጊዜ ፡ ብዛት
In process of time, racial harmony will be achieved. በጊዜ ፡ ብዛት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘሮች ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ ይፈጠራል

**(be) in the process of** በ --- ላይ ፡ ነው
The building is still in the process of construction. ሕንጻው ፡ ገና ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ ነው

**(be a) slow process**
Unloading the ship was a slow process. መርከቡን ፡ ማራገፍ ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ፈጀ

**procession**
1. ሰልፍ. The students walked in procession through the streets. ተማሪዎቹ ፡ በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ በሰልፍ ፡ አለፉ
2. ጕዞ. The procession was accompanied by a hymn. ጕዞው ፡ በዝማሬ ፡ ይመራ ፡ ነበር

**funeral procession** ሬሳ
The funeral procession passed by my house. ሬሳው ፡ በቤቴ ፡ አጠገብ ፡ አለፈ

**proclaim**
1. ዐወጀ. The governor proclaimed a state of emergency. አገረ ፡ ገዢው ፡ የአስቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ ዐዋጅ ፡ ዐወጁ

2. አስታወቀ ፤ ገለጸ. He proclaimed his ideas to anyone who listened. ላዳመጠ ፡ ሁሉ ፡ ሐሳቡን ፡ አስታወቀ ፡ (ገለጸ)

3. አሳየ. His kind acts proclaim a generous heart. የደግነት ፡ ተግባሩ ፡ ልበ ፡ ርኅሩኅነቱን ፡ ያሳያል

**proclamation**

1. ዐዋጅ. The proclamation was written in English and Amharic. ዐዋጁ ፡ የተጻፈው ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ነው

2. መታወጅ. The proclamation of a holiday was greeted with cheers. የበዓልን ፡ መታወጅ ፡ በጭብጨባ ፡ ተቀበሉት

**proclivity** ዝንባሌ

He has a proclivity to gossip. የወሬ ፡ ዝንባሌ ፡ አለው

**procrastinate** አቆየ ፤ ዛሬ ፡ ነገ ፡ አለ

Don't procrastinate any longer! ከሁን ፡ ወዲያ ፡ ነገሩን ፡ አታቆየው

While John procrastinated, Mary prepared for the exam. ጆን ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ ሲል ፡ ሜሪ ፡ ለፈተናው ፡ ተዘጋጀች

**procure**

1. አገኘ. Can you procure some specimens for me? ለዓይነት ፡ አንዳንድ ፡ ልታገኝልኝ ፡ ትችላለህ ?

2. አደረገ. The secret service procured the arrest of the criminal. የጸጥታ ፡ ክፍል ፡ ወንጀለኛው ፡ እንዲያዝ ፡ አደረገ

*He procured his rival's removal by stirring up an intrigue against him. ተቃዋሚውን ፡ ሰው ፡ ከሥራው ፡ ሊያስለቅቅ ፡ የቻለው ፡ ተንኰል ፡ ፈጥሮ ፡ ነው

**prod** (prodded), v.

1. ወጋ ፡ ወጋ ፡ አደረገ. The farmer prodded the ox to make it move on. በሬው ፡ እንዲሄድለት ፡ ገበሬው ፡ ወጋ ፡ ወጋ ፡ አደረገው

2. ገፋፋ. He prodded the students to do their best. ተማሪዎቹ ፡ የተቻላቸውን ፡ እንዲያደርጉ ፡ ገፋፋቸው

**prod** (n.) ሹል ፡ ዘንግ

Prods are used to make recalcitrant cattle move. ሹል ፡ ዘንግ ፡ ልግመኛ ፡ ከብቶችን ፡ ለመንዳት ፡ ይረዳል

**(be) prodigal**

1. አባከነ. The son is prodigal with his father's money. ልጁ ፡ ያባቱን ፡ ገንዘብ ፡ ያባክናል

2. ያላግባብ ፡ አጠፋ. America has been prodigal of its forests. አሜሪካ ፡ ጫካዎቿን ፡ ያላግባብ ፡ ታጠፋ ፡ ነበር

**Prodigal Son** የጠፋው ፡ ልጅ

Have you read the story of The Prodigal Son? የጠፋውን ፡ ልጅ ፡ ታሪክ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ አንብበሃል ?

**prodigious**

1. የሚያስደንቅ. The Egyptian pyramids are prodigious monuments. የግብጽ ፡ ፒራሚዶች ፡ የሚያስደንቁ ፡ ቅርሶች ፡ ናቸው

2. እጅግ ፡ በጣም ፡ ብዙ. Prodigious sums of money were spent on arms. እጅግ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ለጦር ፡ መሣሪያ ፡ ወጣ

**prodigy** (prodigies) ተሰጥዎ ፡ ያለው ፡ ልጅ

The violin prodigy will give a concert. የቫዮሊን ፡ ተሰጥዎ ፡ ያለው ፡ ልጅ ፡ የሙዚቃ ፡ ትርእይት ፡ ያሳያል

**prodigies of** ተወዳዳሪ ፡ የሌለው

The warriors performed prodigies of valor. ጦረኞቹ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ ጀብዱ ፡ ሠሩ

**produce** (v.)

1. ሠራ(ተሠራ). The cars are produced by a factory near here. መኪናዎቹ ፡ በዚህ ፡ አቅራቢያ ፡ በሚገኝ ፡ ፋብሪካ ፡ ይሠራሉ

2. አመረተ. We must produce more of our own food and import less. የራሳችንን ፡ ምግብ ፡ ይበልጡን ፡ አምርተን ፡ ከውጭ ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ ማምጣት ፡ አለብን

3. ሠርቶ ፡ አወጣ. We have produced a hundred tons of cement this week. በዚህ ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ቶን ፡ ሲሚንቶ ፡ ሠርተን ፡ አወጣን

4. አበቀለ. Our fruit farm produces many different kinds of fruit. የፍራፍሬ ፡ እርሻችን ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ፍራፍሬዎች ፡ ያበቅላል

5. ወጣ(በት). A mining region produces gold and silver. የማዕድኑ ፡ ቀበሌ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ይወጣበታል

6. አቀረበ. Can you produce any written proof? የጽሑፍ ፡ መረጃ ፡ ልታቀርብ ፡ ትችላለህ ?

7. አፈለቀ. A static mind produces no new ideas. የላሸቀ ፡ አእምሮ ፡ አዲስ ፡ ሐሳቦችን ፡ አያፈልቅም

8. አሳየ. Please produce your tickets at the gate! ቲኬታችሁን ፡ እመግቢያው ፡ ላይ ፡ አሳዩ

9. አስገኘ. Hard work produces success. ጠንክሮ ፡ መሥራት ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ ያስገኛል

10. አስከተለ. His book produced great controversy. መጽሐፉ ፡ ትልቅ ፡ ክርክር ፡ አስከተለ

**produce** (n.) የእርሻ ፡ ሀብት
They sell their produce on the market. የእርሻ ፡ ሀ
ብታቸውን ፡ ገበያ ፡ አውጥተው ፡ ይሸጣሉ

**product**
1. ሀብት. The chief products of Ethiopia are coffee and hides. የኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሀብቷ ፡ ቡናና ፡
ቆዳ ፡ ነው
2. ምርት. The farm products are very good in this province. በዚህ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡
የእርሻ ፡ ምርት ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነው
3. እቃ. At present, most factory products are imported. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አብዛኞቹ ፡ የፋ
ብሪካ ፡ እቃዎች ፡ ከውጭ ፡ የሚመጡ ፡ ናቸው
4. ፍሬ. This child is a product of an excellent school. ይህ ፡ ልጅ ፡ የምርጥ ፡ ትምህርት ፡ ቤ
ት ፡ ፍሬ ፡ ነው
*His failure was a product of laziness. ሳይሳካ
ለት ፡ የቀረው ፡ ከስንፍና ፡ የተነሣ ፡ ነው

**production**
1. የፋብሪካ ፡ ውጤት. Production was reduced by the strike. በሠራተኞቹ ፡ ሥራ ፡ ማቆም ፡ ም
ክንያት ፡ የፋብሪካው ፡ ውጤት ፡ ተቀንሶ ፡ ነበር
2. መሥራት. Production of automobiles has not yet begun in Ethiopia. መኪና ፡ መሥራት ፡ ገና ፡
በኢትዮጵያ ፡ አልተጀመረም
3. ሥራ. Japan overtook many countries in steel production. በብረት ፡ ሥራ ፡ ጃፓን ፡ ብዙ
ዎቹን ፡ አገሮች ፡ ቀደመቻቸው

**productive**
1. ጠቃሚ. We must encourage our students to engage in productive activity. ተማሪዎቻችን ፡
ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ እንዲሰማሩ ፡
ማበረታታት ፡ አለብን
2. ትርፍ ፡ ያለበት. He has a very productive business. ብዙ ፡ ትርፍ ፡ ያለበት ፡ ንግድ ፡ አለው
3. ለም. This productive soil yields large crops.
ይህ ፡ ለም ፡ መሬት ፡ ብዙ ፡ እህል ፡ ያፈራል
4. ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚጽፍ. He is a very productive writer. ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚጽፍ ፡ ደ
ራሲ ፡ ነው

**be productive** ማምረት ፡ ቻለ
The land is very productive because the soil is rich. አፈሩ ፡ ለም ፡ ስለሆነ ፡ ብዙ ፡ ማምረት ፡
ይችላል

**productivity**
1. ምርት ፤ ሰብል. Modern methods have increased agricultural productivity. ዘመናዊ ፡ ዘ
ዴዎች ፡ የእርሻን ፡ ምርት ፡ (ሰብል) ፡ ከፍ ፡ አ
ድርገውታል
2. የሥራ ፡ ውጤት. Improvement in health services will increase productivity. የጤና ፡ አገ
ልግሎት ፡ መሻሻል ፡ የሥራ ፡ ውጤትን ፡ ያሳድጋል

**profane** (v.) አረከሰ
Vandals profaned the church by smashing the altar. መንበሩን ፡ በመስበር ፡ ወራሪዎች ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያኑን ፡ አረከሱት

**profane** (adj.)
1. ዓለማዊ. Profane literature is now written in Amharic. ዓለማዊ ፡ ጽሑፍ ፡ ባማርኛ ፡ መጻ
ፍ ፡ ጀምሯል
2. የብልግና. Don't use profane language around me! አጠገቤ ፡ የብልግና ፡ ቃል ፡ አትናገር
3. (= adv.) በከንቱ. To use God's name for profane things is a sacrilege. የእግዚአብሔርን ፡
ስም ፡ በከንቱ ፡ ማንሣት ፡ ማራከስ ፡ ነው

**profanity** (profanities) ጸያፍ ፡ ነገር
He uttered a stream of profanities. ብዙ ፡ ጸያ
ፍ ፡ ነገሮች ፡ ተናገረ

**profess**
1. ገለጸ. He professed a great interest in my welfare. ስለኔ ፡ ደኅንነት ፡ በጣም ፡ የሚቆረቆር ፡
መሆኑን ፡ ገለጸ
2. አመነ. Christians profess the Christian religion. ክርስቲያኖች ፡ በክርስትና ፡ ያምናሉ
3. ባይ ፡ ነው. He professed respect for the law.
ሕግ ፡ ይከበር ፡ ባይ ፡ ነው
4. አለ. I don't profess to be an expert. ሊቅ ፡ ነ
ኝ ፡ አልልም

**profession**
1. ሙያ. The profession of the dentist is a good one. የጥርስ ፡ ሕክምና ፡ ሙያ ፡ ጥሩ ፡ ነው
2. ዓለም. He is respected by the medical profession. በሕክምና ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ የተከበ
ረ ፡ ነው

**profession of faith** የሃይማኖትን ፡ ወገንነት ፡ መ
ግለጽ
Profession of faith should not be compulsory.
የሃይማኖትን ፡ ወገንነት ፡ መግለጽ ፡ ግዴታ ፡ መሆ
ን ፡ የለበትም

**professional** (n.) የጨዋታ ፡ ባለሙያ
She took her tennis lessons from a professional.
የቴኒስ ፡ ጨዋታ ፡ ያጠናችው ፡ ከጨዋታው ፡
ባለሙያ ፡ ነው

**professional** (adj.)
1. የሙያ. The professional ethics of a lawyer should be respected. የጠበቃ ፡ የሙያ ፡ መምሪያ ፡
መከበር ፡ አለበት

2. ፕሮፌሽናል. He is a professional basketball player. ፕሮፌሽናል ፡ የቅርጫት ፡ ኳስ ፡ ተጫዋች ፡ ነው
3. የሠለጠነ. He is not a professional builder. የሠለጠነ ፡ ገንቢ ፡ አይደለም

**professional duties** ሙያ
The professional duties of a lawyer are quite heavy. የጥብቅና ፡ ሙያ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ነው

**professor** መምህር ፤ ፕሮፌሰር
He is a professor of Amharic. እሱ ፡ ያማርኛ ፡ መምህር ፡ (ፕሮፌሰር) ፡ ነው

**proffer** ገለጸ
They proffered friendship to their new neighbor. ላዲሱ ፡ ጐረቤታቸው ፡ ወዳጅነታቸውን ፡ ገለጹ

**proficiency** ችሎታ
She was praised for her proficiency at teaching. በማስተማር ፡ ችሎታዋ ፡ ተመሰገነች

**proficient** በቂ ፡ ችሎታ ፡ ያለው
It's not easy to find proficient translators. በቂ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ተርጓሚዎችን ፡ ለማግኘት ፡ ቀላል ፡ አይደለም

**be proficient in**
1. ሠለጠነ. She was very proficient in music. በሙዚቃ ፡ በጣም ፡ ሠልጥና ፡ ነበር
2. በደንብ ፡ ተናገረ. He is proficient in three languages. ሦስት ፡ ቋንቋዎች ፡ በደንብ ፡ ይናገራል

**profile**
1. ጐን. He asked me to take his picture in profile. ከጐን ፡ ፎቶግራፍ ፡ እንዳነሣው ፡ ጠየቀኝ
2. ቅርጽ. You can see from afar the profile of a mountain range. የተራራውን ፡ ሰንተረር ፡ ቅርጽ ፡ ከሩቅ ፡ ለማየት ፡ ትችላለህ
*She has a very attractive profile. በጐን ፡ ስትታይ ፡ በጣም ፡ የሚማርክ ፡ ገጽ ፡ አላት

**write a profile** ባጭሩ ፡ ገለጸ
When you apply for a job, you have to write a profile listing your abilities and experience. ሥራ ፡ ለመግባት ፡ ስታመለክት ፡ ችሎታህንና ፡ የሥራ ፡ ልምድህን ፡ ባጭሩ ፡ መግለጽ ፡ ይኖርብሃል

**profit** (v.)
1. ጠቀመ. What can it profit him? ምን ፡ ይጠቅመዋል ?
2. ጥቅም ፡ አገኘ. I didn't profit much by the lecture. ከንግግሩ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ጥቅም ፡ አላገኘሁበትም
3. ትርፍ ፡ አገኘ. He profited by the sale of his house. ቤቱን ፡ ሲሸጥ ፡ ትርፍ ፡ አገኘ
4. ተማረ. A wise person profits by his mistakes. ዐዋቂ ፡ ሰው ፡ ከስሕተቱ ፡ ይማራል

**profit** (n.)
1. ትርፍ. Does the business show any profit? ንግዱ ፡ ትርፍ ፡ ያስገኛል ?
2. ጥቅም. There is no profit in arguing about this. ስለሱ ፡ መከራከር ፡ ጥቅም ፡ የለውም
Having such an excellent teacher is to your profit. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ከፍተኛ ፡ መምህር ፡ ማግኘትህ ፡ ላንተ ፡ ጥቅም ፡ ነው
*What profit is there in worrying? መጨነቅ ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ?

**at a profit** አትርፎ
I sold it at a profit. አትርፌ ፡ ሸጥኩት

**make a profit** አተረፈ
He made a large profit selling land. መሬት ፡ በመሸጥ ፡ ብዙ ፡ አተረፈ

**profitable**
1. ትርፍ ፡ የሚያስገኝ. Is it a profitable business? ትርፍ ፡ የሚያስገኝ ፡ ንግድ ፡ ነው ?
2. የሚያዋጣ. Salvage is a profitable business. ውራጅን ፡ መሰብሰብ ፡ የሚያዋጣ ፡ ንግድ ፡ ነው
3. ጠቃሚ. We spent a profitable afternoon in the library. ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ጠቃሚ ፡ ጊዜ ፡ አሳለፍን

**profound**
1. ጥልቅ. He is a man of profound learning. ጥልቅ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው
2. ጥልቅ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው. He is a profound scholar and is respected by all. ጥልቅ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ሊቅ ፡ ስለሆነ ፡ ሁሉም ፡ ያከብረዋል
3. ፍጹም. Profound silence followed his insulting remark. ከርሱ ፡ ስድብ ፡ በኋላ ፡ ፍጹም ፡ ጸጥታ ፡ ሆነ
4. ከባድ. His profound grief was noticed by all present. ከባድ ፡ ሐዘን ፡ እንዳደረበት ፡ አጠገቡ ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ዐወቁ

**profuse** በጣም ፡ ብዙ
There was a profuse display of flowers in her room. በክፍሏ ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ያበባ ፡ ድርድር ፡ ነበር
*He showered me with profuse thanks. ምስጋናውን ፡ አዥጐደጐደልኝ
*He was extremely weak from a profuse loss of blood. ብዙ ፡ ደም ፡ ስለፈሰሰው ፡ በጣም ፡ ደክሞ ፡ ነበር

**be profuse** ለጋስ ፡ ሆነ
He was so profuse with his contributions that he is now poor. መዋጮ ፡ ሲሰጥ ፡ በጣም ፡ ለጋስ ፡ ስለሆነ ፡ አሁን ፡ ደኸየ

## profusely ከመጠን ፡ በላይ
He apologized profusely. ይቅርታ ፡ በመጠየቅ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ለመነ
*He spent his money profusely. ገንዘቡን ፡ ረጨ ፡ (በተነ)

## profusion
*She spends money in great profusion. ገንዘብ ፡ ትረጫለች ፡ (ታባክናለች)

**a profusion of** ብዙ
There was a profusion of flowers in their garden. ባትክልት ፡ ቦታቸው ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ አበባዎች ፡ ነበሩ

## progenitor
1. ቅድመ ፡ አያት. The progenitors of the Ethiopians came to this region thousands of years ago. የኢትዮጵያውያን ፡ ቅድመ ፡ አያቶች ፡ ወደዚህ ፡ ቀበሌ ፡ የመጡት ፡ ከብዙ ፡ ሺህ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ነው
2. አመንጪ. Einstein is the progenitor of the theory of relativity. አይንስታይን ፡ የሬላቲቪቲ ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳብ ፡ አመንጪ ፡ ነው

## progeny ተወላጆች
He left a large estate to his progeny. ለተወላጆቹ ፡ ብዙ ፡ ንብረት ፡ አወረሰ

## prognosis ግምት ፤ አስተያየት
According to the weather prognosis, there will be rain tomorrow. እንደ ፡ አየሩ ፡ ሁኔታ ፡ ግምት ፡ ነገ ፡ ይዘንባል
According to the prognosis of the doctors, his heart will always be weak. እንደ ፡ ሐኪሙ ፡ ግምት ፡ (አስተያየት) ፡ ልቡ ፡ ዘወትር ፡ ደካማ ፡ ይሆናል

## prognosticate ይመጣል ፡ አለ
The fortune-teller prognosticated doom. ኮከብ ፡ ቈጣሪው ፡ ክፉ ፡ ቀን ፡ ይመጣል ፡ አለ

## prognostication, give a ~ of መምጣት ፡ አመለከተ
The clouds in the sky give a prognostication of rain. በሰማይ ፡ ላይ ፡ የሚታዩት ፡ ደመናዎች ፡ የዝናብን ፡ መምጣት ፡ ያመለክታሉ

## program ፕሮግራም
The city has a program for road construction. ከተማው ፡ የመንገድ ፡ ሥራ ፡ ፕሮግራም ፡ አለው
What's the program for tomorrow? የነገው ፡ ፕሮግራም ፡ ምንድን ፡ ነው ?

## progress (v.)
1. ገፋ. You've progressed a lot in the six weeks I've been away. እኔ ፡ ቀርቼ ፡ በነበርኩበት ፡ ስድስት ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ገፍተሃል
2. ተፋጠነ ፤ ተኪያሄደ. The building of the new library progressed quickly during the summer. ያዲሱ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ሕንጻ ፡ ሥራ ፡ በበጋው ፡ ወራት ፡ ተፋጥኗል
The new building is progressing rapidly. አዲሱ ፡ ሕንጻ ፡ በፍጥነት ፡ እየተኪያሄደ ፡ ነው
3. እየተሻለ(ው) ፡ ሄደ. He has progressed under the doctor's care. በሐኪሙ ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ እየተሻለው ፡ ሄዷል
4. ተሻሻለ. Science has helped man progress. ሳይንስ ፡ ሰዎች ፡ እንዲሻሻሉ ፡ ረድቷል

**progress slowly** አዘገመ
They progressed slowly through the mud. በጭቃው ፡ ውስጥ ፡ አዘገሙ

## progress (n.)
1. መሻሻል. Ethiopia is making much progress lately. ኢትዮጵያ ፡ በቅርቡ ፡ ብዙ ፡ መሻሻል ፡ አድርጋለች
The students are making good progress. ተማሪዎቹ ፡ ብዙ ፡ መሻሻል ፡ ያደርጋሉ
2. እርምጃ. The progress of science is constantly increasing. የሳይንስ ፡ እርምጃ ፡ እየጨመረ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ነው

**be in progress** ተጀመረ
The meeting was already in progress when I arrived. ስደርስ ፡ ስብሰባው ፡ ተጀምሮ ፡ ነበር

**make no progress** ምንም ፡ ያህል ፡ አልሄደም
We made no progress through the heavy traffic. በመኪናው ፡ ብዛት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልሄድንም

**make progress** ገፋ
Are you making any progress with your book? በመጽሐፍህ ፡ ገፍተሃል ?

## progressive
1. ታዳጊ. A progressive country's revenue will increase as the number of taxpayers increases. የግብር ፡ ከፋዩ ፡ ቁጥር ፡ እየጨመረ ፡ ሲሄድ ፡ ታዳጊ ፡ የሆነው ፡ አገር ፡ ገቢው ፡ ከፍ ፡ ይላል
2. አርቆ ፡ አሳቢ. The progressive municipality built a new stadium. አርቆ ፡ አሳቢው ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ እስታዲዮም ፡ ሠራ
3. ተራማጅ. The progressive group wants rapid changes in politics. ተራማጁ ፡ ወገን ፡ የፖለቲካ ፡ አቋም ፡ ቶሎ ፡ እንዲለወጥ ፡ ይፈልጋል

4. (= adv.) በየጊዜው. We could observe the progressive improvement of the patient. በሽተኛው ፡ በየጊዜው ፡ እየተሻለው ፡ መሄዱን ፡ ልናይ ፡ ችለናል

**progressive stage** (= adv.) በየደረጃ
He described in his book the progressive stages in growing up. በየደረጃ ፡ የሚደረገውን ፡ እድገት ፡ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ገልጿል

**progressive tax**
*A progressive tax is needed to improve the development of land tenure. የመሬት ፡ ይዞታን ፡ ለማሻሻል ፡ በገቢ ፡ መጠን ፡ ቀረጥ ፡ ማስከፈል ፡ ያስፈልጋል

**prohibit**
1. ከለከለ. He prohibited the book from being printed. መጽሐፉ ፡ እንዳይታተም ፡ ከለከለ
2. አስቀረ. The expenses of the new house prohibit a vacation this year. ላዲሱ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ማውጣታችን ፡ ለዕረፍት ፡ ከመሄድ ፡ አስቀረን

**(be) prohibited** ተከለከለ
Smoking is strictly prohibited. ሲጋራ ፡ ማጨስ ፡ በጥብቅ ፡ ተከልክሏል

**prohibition** መከልከል
Prohibition of the sale of narcotics is necessary. የናርኮቲክን ፡ ሽያጭ ፡ መከልከል ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**prohibitive**
*Lately prices have been prohibitive. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ የገበያ ፡ ውድነት ፡ አይደፈርም
*Thirty dollars for a shirt is prohibitive. ላንድ ፡ ሸሚዝ ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ መጠየቅ ፡ ገገርን ፡ ማባረር ፡ ነው

**project** (vt.)
1. ፈነጠቀ. The flashlight projected a beam of light into the darkness. ባትሪው ፡ በጨለማው ፡ ውስጥ ፡ የብርሃን ፡ ጮራ ፡ ፈነጠቀ
2. አስፈነጠረ. A cannon projects shells. መድፍ ፡ ሲተኰስ ፡ ጥይት ፡ ያስፈነጥራል
3. አቀደ. The municipality projects a new school building. ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ አዲስ ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ሕንጻ ፡ ለመሥራት ፡ አቅዷል
4. ገመተ. They projected the building costs for the next five years. በሚቀጥሉት ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ለሕንጻ ፡ የሚወጣውን ፡ ገመቱ

**project** (vi.) ዘልቆ ፡ ገባ
The hill projects far into the sea. ኮረብታው ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ዘልቆ ፡ ገብቷል

**be projected** ታየ
The film was projected on the wall. ሲኒማው ፡ ግድግዳው ፡ ላይ ፡ ታየ

**project** (n.)
1. እቅድ. The project for irrigating land will soon be implemented. በመስኖ ፡ መሬትን ፡ የማጠጣቱ ፡ እቅድ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላል
2. የታቀደ ፡ ሥራ. She began work on the project right away. የታቀደውን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ወዲያው ፡ ጀመረች
3. ውጥን. A project is underway to build a dam. አንድ ፡ ግድብ ፡ ለመሥራት ፡ አንድ ፡ ውጥን ፡ በመዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ነው

**projection** ወጣ ፡ ያለ ፡ ጉጥ ፡ ነገር
He caught his coat on a projection on the wall and tore it. ኮቱን ፡ ከግድግዳው ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ ያለ ፡ ጉጥ ፡ ነገር ፡ ይዞ ፡ ቀደደበት

**projector** (የሲኒማ) ፡ ማሳያ
He bought the movie projector in France. የሲኒማውን ፡ ማሳያ ፡ የገዛው ፡ ከፈረንሳይ ፡ ነው

**proliferate**
1. ቁጥራቸው ፡ ከመጠን ፡ አለፈ. Government agencies tend to proliferate unless strict control is exercised. የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ጥብቅ ፡ ቁጥጥር ፡ ካልተደረገባቸው ፡ ቁጥራቸው ፡ ከመጠን ፡ ያልፋል
2. እየተባዛ ፡ ሄደ. Cells proliferate in cancerous tissue. የካንሰር ፡ በሽታ ፡ ሲይዝ ፡ ሴል ፡ እየተባዛ ፡ ይሄዳል

**prolific** ወላድ
She is very prolific; she has 14 children. በጣም ፡ ወላድ ፡ ነች ፤ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ልጆች ፡ አሏት

**be prolific** በብዛት ፡ ተራባ
Rabbits are prolific. ጥንቸሎች ፡ በብዛት ፡ ይራባሉ
*He is a prolific writer. እሱ ፡ ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ ይጽፋል

**prologue** መቅድም
The prologue explains the reasons for writing the book. መቅድሙ ፡ መጽሐፉ ፡ የተጻፈበትን ፡ ምክንያት ፡ ይገልጻል

**prolong** አራዘመ
You are prolonging the agony. ሥቃዩን ፡ ታራዝመዋለህ

**prolonged** (adj.) የረጅም ፡ ጊዜ
The child's lethargy is the result of prolonged illness. የልጁ ፡ መልፈስፈስ ፡ ከረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሕመም ፡ የተነሣ ፡ ነው

**promenade** (v.) ተንሸራሸረ
The girls promenade in the streets every evening. ሁልጊዜ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ልጃገረዶቹ ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ይንሸራሸራሉ

**promenade** (n.) የሕዝብ ፡ መንሸራሸሪያ
They built a promenade along the lake shore. በሐይቁ ፡ ዙሪያ ፡ የሕዝብ ፡ መንሸራሸሪያ ፡ ሠርተዋል
*The Easter promenade takes place every year in New York. ኒውዮርክ ፡ ውስጥ ፡ በየዓመቱ ፡ የፋሲካ ፡ ዕለት ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ በየመንገዱ ፡ የክት ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ይንሸራሸራል

**prominence** መታወቅ
The school's prominence in science brings in many students. የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በሳይንስ ፡ መታወቅ ፡ ብዙ ፡ ተማሪዎችን ፡ ይስባል

**prominent**
1. ስመ ፡ ጥር. He is a prominent artist. ስመ ፡ ጥር ፡ አርቲስት ፡ ነው
2. የፈጠጠ. Some insects have prominent eyes. አንዳንድ ፡ ነፍሳት ፡ የፈጠጠ ፡ ዓይን ፡ አላቸው
3. ጐላ ፡ ያለ. The camel has a prominent hump. ግመል ፡ ጐላ ፡ ያለ ፡ ሻኛ ፡ አለው
4. ዋነኛ. The editorial has a prominent place in the newspaper. በጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ ርእሰ ፡ አንቀጽ ፡ ዋነኛውን ፡ ስፍራ ፡ ይይዛል

**prominent feature** መለዮ
The eucalyptus is a prominent feature of the Addis Ababa landscape. ባሕር ፡ ዛፍ ፡ ለአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ የመለዮ ፡ ያህል ፡ ነው

**be prominent** ዓይን ፡ ሳበ
A single tree in a field is prominent. በሜዳ ፡ ውስጥ ፡ ብቻውን ፡ ያለ ፡ ዛፍ ፡ ዓይን ፡ ይስባል

**promiscuous** ልክስክስ ፡ ሴት
She is promiscuous, so don't form any attachment with her. ልክስክስ ፡ ሴት ፡ ስለሆነች ፡ ከሷ ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ግንኙነት ፡ አታድርግ
*There is a promiscuous heap of clothing on the bed. ባልጋው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ልብሶች ፡ ተከምረዋል

**promise** (v.)
1. ቃል ፡ ገባ ፤ ቃል ፡ ገባ(ለት). We promised him a present. ስጦታ ፡ ልናደርግለት ፡ ቃል ፡ ገብተን ፡ ነበር
He promised that he would write to me every week. በየሳምንቱ ፡ ሊጽፍልኝ ፡ ቃል ፡ ገብቶልኛል
2. ተስፋ ፡ ሰጠ. Many religions promise eternal life. ብዙ ፡ ሃይማኖቶች ፡ የዘለዓለማዊ ፡ ሕይወትን ፡ ተስፋ ፡ ይሰጣሉ
3. አበሰረ ፤ አመለከተ. Clear skies promise good weather. የጠራ ፡ ሰማይ ፡ መልካም ፡ አየርን ፡ ያበስራል ፡ (ያመለክታል)
*It promises to be warm this afternoon. ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ሞቅ ፡ ሳይል ፡ አይቀርም

**promise** (n.)
1. ቃል ፤ የገባው ፡ ቃል. You didn't keep your promise. ቃልህን ፡ አልጠበቅህም
You must abide by your promise. የገባኸውን ፡ ቃል ፡ ማክበር ፡ አለብህ
2. ቃል ፡ መስጠት. There is always a lag between promise and fulfillment. ቃል ፡ በመስጠትና ፡ በመፈጸም ፡ መካከል ፡ ሁልጊዜ ፡ መራራቅ ፡ አለ
3. ተስፋ. One cannot depend on a hypocrite's promises. የግብዝን ፡ ተስፋ ፡ ለመተማመን ፡ አይቻልም

**hold out the promise** አጓጓ
He held out the promise that he will be promoted soon. በቅርቡ ፡ የደረጃ ፡ እድገት ፡ ታገኛለህ ፡ በማለት ፡ አጓጓው

**keep (one's) promise** ቃሉን ፡ ጠበቀ
He said that he would come tomorrow, and he kept his promise. ነገ ፡ እመጣለሁ ፡ እንዳለ ፡ ቃሉን ፡ ጠበቀ

**make a promise** ቃል ፡ ገባ
He absolved him from the promise he made. ገብቶለት ፡ የነበረውን ፡ ቃል ፡ ሰረዘለት

**show promise**
*The young man showed promise that he would become a great man some day. ወጣቱ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ትልቅ ፡ ለመሆን ፡ ተስፋ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው
[See also 'sacred, solemn']

**Promised Land** ምድረ ፡ ተስፋ
Moses led his people to the Promised Land. ሙሴ ፡ ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ተስፋ ፡ መራቸው

**promising** ተስፋ ፡ ያለው ፤ ተስፋ ፡ የሚጣልበት
Independent of monetary considerations, it was a promising position. የገንዘቡ ፡ ጉዳይ ፡ ቀርቶ ፡ ተስፋ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ነበር
The outlook for trade is very promising. የንግዱ ፡ የወደፊት ፡ ሁኔታ ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልበት ፡ ነው
He is a promising poet. ተስፋ ፡ ያለው ፡ ገጣሚ ፡ ነው

**promontory** ጉጥ
The lighthouse is built on a high promontory. የፋናው ፡ ቤት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጉጥ ፡ ላይ ፡ ነው

**promote**

1. አስፋፋ. Most countries promote their foreign trade. ብዙ ፡ አገሮች ፡ የውጭ ፡ ንግዳቸውን ፡ ያስፋፋሉ
2. አበረታታ. The state is promoting collective ownership of coffee-cleaning facilities. መንግሥቱ ፡ የቡና ፡ ማጣሪያ ፡ እቃዎች ፡ የጋርዮሽ ፡ እንዲሠራባቸው ፡ ያበረታታል
3. አዳበረ. The tourist office is promoting tours to Lalibela. የቱሪስት ፡ ድርጅት ፡ የላሊበላን ፡ ጉብኝት ፡ በማዳበር ፡ ላይ ፡ ነው
4. ለማቋቋም ፡ ረዳ. Several bankers promoted the new company. ብዙ ፡ የባንክ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ አዲሱን ፡ ኩባንያ ፡ ለማቋቋም ፡ ረዱት
5. አደረጀ. A kindly feeling toward other countries will promote peace. ሌሎች ፡ አገሮችን ፡ በመልካም ፡ መመልከት ፡ ሰላምን ፡ ያደረጃል
6. አስከተለ. Lenience promotes disobedience. ልልነት ፡ አለመታዘዝን ፡ ያስከትላል
7. አስከበረ. Our school segregates the sexes in order to promote discipline. ሥርዓትን ፡ ለማስከበር ፡ ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ለየብቻ ፡ ይመድባል

**be promoted** የደረጃ ፡ (የማዕረግ) ፡ እድገት ፡ አገኘ
He felt aggrieved when I was promoted. እኔ ፡ የደረጃ ፡ እድገት ፡ ባገኘሁ ፡ ጊዜ ፡ ቅር ፡ ተሰኘ
In the course of the conversation, he learned that he was to be promoted. በጨዋታው ፡ ላይ ፡ የማዕረግ ፡ እድገት ፡ የሚያገኝ ፡ መሆኑን ፡ ሰማ

**promotion**

1. ሹመት. His promotion was announced in the newspapers. ሹመቱ ፡ በጋዜጣ ፡ ወጣ
2. እድገት. The boss dashed my hopes for promotion. አለቃዬ ፡ ለእድገት ፡ ያለኝን ፡ ተስፋ ፡ አስቈረጠኝ
3. የደረጃ ፡ እድገት ፤ የሥራ ፡ እድገት. When it comes to giving promotions, he favors his relatives. የደረጃ ፡ እድገት ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ለዘመዶቹ ፡ ያድላል
Promotion should be made on the basis of merit. የሥራ ፡ እድገት ፡ በችሎታ ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ አለበት
4. ማስፋፋት. The doctors were busy in the promotion of a health campaign. ሐኪሞቹ ፡ የጤና ፡ ጥበቃን ፡ ዘመቻ ፡ ለማስፋፋት ፡ በሥራ ፡ ተጠምደው ፡ ነበር

**prompt** (v.)

1. ገፋፋ. His good nature prompted him to offer his help. ቅንነቱ ፡ የሚችለውን ፡ እርዳታ ፡ እንዲያደርግ ፡ ገፋፋው
2. አፈለቀ. Gay music prompts happy thoughts. ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሙዚቃ ፡ የደስታ ፡ መንፈስ ፡ ያፈልቃል
3. ፍንጭ ፡ ሰጠ. Please prompt me if I forget my lines in the play. ቲያትሩን ፡ ስሠራ ፡ የምናገረው ፡ ከተረሳኝ ፡ ፍንጭ ፡ ስጠኝ

**prompt** (adj.)

1. (= adv.) ወዲያውኑ. Prompt payment is requested upon receipt of the bill. ሒሳቡ ፡ ሲደርስ ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዲከፈል ፡ ያስፈልጋል
2. (= adv.) በጊዜው. He's prompt in paying his debts. ዕዳውን ፡ በጊዜው ፡ ይከፍላል
3. (= adv.) በአስቸኳይ. I expect a prompt reply. መልስ ፡ በአስቸኳይ ፡ እጠባበቃለሁ

**be prompt** ፈጠነ
Be prompt to obey! ለመታዘዝ ፡ የፈጠንክ ፡ ሁን

**promptitude**

*The promptitude with which the army acted saved the country. ሰራዊቱ ፡ በፍጥነት ፡ እርምጃ ፡ መውሰዱ ፡ አገሪቱን ፡ አዳናት

**promptly**

1. ልክ. We start promptly at five. ልክ ፡ በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ እንጀምራለን
2. ወዲያውኑ. He paid promptly. ወዲያውኑ ፡ ከፈለ

**promulgate**

1. ዐወጀ. The Emperor promulgated a proclamation abolishing capital punishment. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሞት ፡ ፍርድን ፡ የሚያስቀር ፡ ዐዋጅ ፡ ዐወጁ
2. አወጣ. He promulgated laws to ameliorate living conditions. የኑሮን ፡ ሁኔታ ፡ ለማሻሻል ፡ ሕግ ፡ አወጣ
3. አስፋፋ. Schools try to promulgate knowledge and good habits. ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ዕውቀትንና ፡ መልካም ፡ ጠባዮችን ፡ ለማስፋፋት ፡ ይጣጣራሉ

**prone, be ~ to** ዝንባሌ ፡ አለ(ው)
We are prone to think evil of people we dislike. ለማንወዳቸው ፡ ሰዎች ፡ ክፉ ፡ የማሰብ ፡ ዝንባሌ ፡ አለን
*He seems prone to serious accidents. ከባድ ፡ አደጋ ፡ ይፈልገዋል
*He is prone to forget people's names. የሰው ፡ ስም ፡ መያዝ ፡ አይሆንለትም

**lie prone** ተደፍቶ ፡ ተኛ ፤ በደረቱ ፡ ተኛ ፤ በሆዱ ፡ ተኛ
He lay prone on the floor. ወለሉ ፡ ላይ ፡ ተደፍቶ ፡ ተኛ ፡ (በደረቱ ፡ ተኛ ፤ በሆዱ ፡ ተኛ)

**prong** ጣት
This fork has three prongs. ይህ ፡ ሹካ ፡ ሦስት ፡ ጣት ፡ አለው

**pronoun** ተውላጠ ፡ ስም
The Amharic pronoun has a singular and a plural. ያማርኛ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ነጠላና ፡ ብዙ ፡ ቁጥር ፡ አለው

**pronounce**
1. አስታወቀ. The doctors pronounced him out of danger. ሐኪሞቹ ፡ እንደማያሰጋው ፡ አስታወቁ
He pronounced himself in favor of the plan. እቅዱን ፡ የሚደግፍ ፡ መሆኑን ፡ አስታወቀ
2. ተናገረ. Pronounce the words clearly! ቃላቱን ፡ በግልጽ ፡ ተናገራቸው
*The minister pronounced them man and wife. ቄሱ ፡ አጋቧቸው
[See also 'sentence']

**pronounced** (adj.)
1. የተጨበጠ. She held pronounced opinions on gambling. ስለ ፡ ቁማር ፡ የተጨበጠ ፡ አስተያየት ፡ አላት
2. (= adv.) አጥብቆ. She has very pronounced likes and dislikes. አጥብቃ ፡ የምትወዳቸውና ፡ የምትጠላቸው ፡ ነገሮች ፡ አሏት

**pronunciation**
1. አባባል. That's not the correct pronunciation. ያ ፡ ደንበኛው ፡ አባባል ፡ አይደለም
2. የቃላት ፡ አነባበብ. Amharic pronunciation is difficult. ያማርኛ ፡ የቃላት ፡ አነባበብ ፡ ያስቸግራል

**proof**
1. ማስረጃ ፤ መረጃ. Can you furnish any written proof? የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ (መረጃ) ፡ ልታቀርብ ፡ ትችላለህ ?
2. የመፈተኛ ፡ እትም. The printer sent me the proofs of my book today. አታሚው ፡ የመጽሐፌን ፡ የመፈተኛ ፡ እትም ፡ ዛሬ ፡ ላከልኝ

**burden of proof** ማስረጃውን ፡ ማቅረብ
The burden of proof lies with you. ማስረጃውን ፡ ማቅረብ ፡ ያንተ ፡ ፈንታ ፡ ነው

**put to the proof** ፈተነ
He tried to put my friendship to the proof. ለሱ ፡ ያለኝን ፡ የጓደኝነት ፡ ፍቅር ፡ ለመፈተን ፡ ሞከረ

**prop** (propped) ደገፈ
They propped the roof with steel columns. ጣራውን ፡ በብረት ፡ ምሰሶዎች ፡ ደገፉት

**prop oneself against** ተደገፈ
He propped himself against a pillow. ትራሱን ፡ ተደገፈ

**prop up**
1. ደገፈ. He propped up the roof with logs. ጣሪያውን ፡ በምሰሶ ፡ ደገፈ
2. አነቃቃ. We propped up his low spirits with a bit of good news. ትካዜ ፡ የገባውን ፡ መንፈሱን ፡ በሚያስደስት ፡ ወሬ ፡ አነቃቃንለት

**propaganda**
1. የሐሰት ፡ ወሬ. He tried to indoctrinate me with his propaganda. በሐሰት ፡ ወሬው ፡ ሊያሳምነኝ ፡ ሞከረ
2. ፕሮፓጋንዳ ፤ ስብከት. I am fed up with the enemy's propaganda. የጠላት ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ (ስብከት) ፡ ሰለቸኝ

**propagate** አሰራጨ
We need to propagate news favorable to us. እኛን ፡ የሚደግፍ ፡ ወሬ ፡ ማሰራጨት ፡ አለብን

**propagate the species** ተራባ
Animals and plants propagate their species. እንስሳትና ፡ ዕፀዋት ፡ ይራባሉ

**propagate themselves** ተባዛ
Trees propagate themselves by seeds. ዛፎች ፡ በዘር ፡ አማካይነት ፡ ይባዛሉ

**propel** (propelled)
1. አመጠቀ. The motor propelled the rocket into space. ሞተሩ ፡ ሮኬቱን ፡ ወደ ፡ ጠፈር ፡ አመጠቀው
2. አስኬደ. We propel a boat by oars. ጀልባ ፡ የምናስኬደው ፡ በመቅዘፊያ ፡ ነው

**be propelled** (= active) ገፋፋ
+He was propelled by good will to help the orphan. ወላጅ ፡ የሌለውን ፡ ልጅ ፡ ለመርዳት ፡ ቅንነት ፡ ገፋፋው

**propeller** ውልብልቢት
The plane's propeller fell off. የአውሮፕላኑ ፡ ውልብልቢት ፡ ወልቆ ፡ ወደቀ

**propensity** ዝንባሌ
He has a propensity for saving things. አንዳንድ ፡ ነገሮችን ፡ የማጠራቀም ፡ ዝንባሌ ፡ አለው

**proper**
1. ተገቢ. Is this the proper tool for the job? ይህ ፡ ለሥራው ፡ ተገቢ ፡ መሣሪያ ፡ ነው ?
This isn't the proper time to ask questions. ጥያቄ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይህ ፡ ተገቢ ፡ ጊዜ ፡ አይደለም
It was only proper to wear a hat. ባርኔጣ ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ ነበር

2. ትክክለኛ. During his speech, he paused each time he could not think of the proper word. ንግግር ፡ ሲያደርግ ፡ ትክክለኛው ፡ ቃል ፡ በጠፋው ፡ ቁጥር ፡ ቆም ፡ ይል ፡ ነበር
3. የተሟላ. A healthy body presupposes a proper diet. ጤነኛ ፡ አካል ፡ በተሟላ ፡ ምግብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው
4. አግባብ ፡ ያለው. Please forward the request to the proper authorities! ጥያቄውን ፡ አግባብ ፡ ላለው ፡ ባለሥልጣን ፡ አስተላልፍ
5. ዋና. Footnotes are clearly set off from the text proper. የግርጌ ፡ ማስታወሻዎች ፡ ከዋናው ፡ ጽሑፍ ፡ ተለይተው ፡ ይጻፋሉ
6. ደኅና. Social intercourse is necessary for a proper life. ለደኅና ፡ ኑሮ ፡ የሕዝብ ፡ ግንኙነት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
*Puerto Rico is not part of the United States proper. ፖርቶ ፡ ሪኮ ፡ የተባበረው ፡ አሜሪካ ፡ የራሱ ፡ ክፍል ፡ አይደለችም

**be proper to** በተለይ ፡ ተገኘ
This climate is proper to Ethiopia. ይህ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ በተለይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚገኝ፡ነው

**have proper manners** ምግባረ ፡ ጨዋ ፡ ነው
She has proper manners, and everyone likes her. ምግባረ ፡ ጨዋ ፡ ስለሆነች ፡ ሁሉም ፡ ይወዳታል
[See also 'order, sequence']

**properly**
1. በደንብ. Do it properly! በደንብ ፡ ሥራው
2. (= adj.) ተስማሚ. She was properly dressed for the occasion. ለበዓሉ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ልብስ ፡ ለብሳለች
*The judge was properly indignant when he was offered a bribe. ዳኛው ፡ ጉቦ ፡ ውሰድ ፡ ሲሉት ፡ መቆጣቱ ፡ ተገቢ ፡ ቁጣ ፡ ነበር

**properly speaking** እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ
Properly speaking, you were in the wrong. እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ ፡ ጥፋተኛው ፡ አንተ ፡ ነበርክ

**proper noun** የተጸውዖ ፡ ስም
John is a proper noun. ዮሐንስ ፡ የተጸውዖ ፡ ስም ፡ ነው

**property** (properties)
1. ንብረት. I own some property in Harar. በሐረር ፡ ውስጥ ፡ ንብረት ፡ አለኝ
There is a fence around our property. ንብረታችን ፡ ዙሪያውን ፡ ታጥሯል
2. ሀብት. All the furniture is my property. የቤት ፡ እቃው ፡ በሙሉ ፡ ሀብቴ ፡ ነው
3. ርስት. They are litigating about the property now. በርስቱ ፡ በመሟገት ፡ ላይ ፡ ናቸው
4. መሬት. Never set foot on our property again! ሁለተኛ ፡ መሬታችንን ፡ እንዳትረግጥ
5. ጠባይ. What are the properties of iron? የብረት ፡ ጠባዮች ፡ ምን ፡ ምን ፡ ናቸው ?

**property owner** ባለ ፡ ንብረት
The mayor debated the property owners' demands. ከንቲባው ፡ የባለ ፡ ንብረቶችን ፡ ጥያቄ ፡ መረመረ

**prophecy** (prophecies) ትንቢት
The prophecy that the world would come to an end in 1965 was not fulfilled. ዓለም ፡ በ፲፱፻፷፭ ዓ. ም. ያልፋል ፡ የሚለው ፡ ትንቢት ፡ አልተፈጸመም

**prophesy** (prophesied) ተነበየ
It is difficult to prophesy what will happen twenty years from now. የዛሬ ፡ ሃያ ፡ ዓመት ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ ለመተንበይ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**prophet** ነቢይ
Isaiah was a prophet in ancient Israel. ኢሳይያስ ፡ በጥንታዊት ፡ እስራኤል ፡ የኖረ ፡ ነቢይ ፡ ነው

**prophetic**
1. የነቢይነት. We admired his prophetic wisdom. የነቢይነት ፡ ጥበቡን ፡ አደነቅንለት
2. ትንቢታዊ. His prophetic remark was proved true when the war broke out. ትንቢታዊ ፡ አስተያየቱ ፡ ጦርነቱ ፡ ሲነሣ ፡ ተረጋገጠ

**prophylactic** ለመከላከል ፡ የሚረዳ
This is a prophylactic measure against malaria. ይህ ፡ የወባን ፡ በሽታ ፡ ለመከላከል ፡ የሚረዳ ፡ እርምጃ ፡ ነው

**propinquity** ጉርብትና
The propinquity of the two tribes is the source of constant friction. የሁለቱ ፡ ጐሳዎች ፡ ጉርብትና ፡ ለማያቋርጥ ፡ ጠብ ፡ መንሻ ፡ ነው

**propitiate**
1. ተማጸነ. They sacrificed an ox to propitiate the rain god. የዝናምን ፡ አምላክ ፡ ለመማጸን ፡ በሬ ፡ ሠዉለት
2. አበረደ. He tried to propitiate the boss by offering to work on Saturday without pay. ቅዳሜ ፡ በነጻ ፡ የሚሠራ ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ አለቃውን ፡ ለማብረድ ፡ ሞከረ

**propitious**
1. ተስማሚ. The weather is propitious for our outing. አየሩ ፡ ለሽርሽራችን ፡ ተስማሚ ፡ ነው
2. ቸር. They believed that the gods were propitious. አማልክት ፡ ቸር ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ያምኑ ፡ ነበረ

**proponent, be a ~** ደገፈ
The minister is a proponent of lower taxes. ሚኒስትሩ ፡ ቀረጥ ፡ እንዲቀነስ ፡ ይደግፋሉ

**proportion** (v.)
*The judge proportioned the punishment to the crime. ዳኛው ፡ ለወንጀሉ ፡ ተመጣጣኝ ፡ ቅጣት ፡ ወሰነ

**proportion** (n.) ክፍል
A large proportion of Nevada is desert. አብዛኛው ፡ የኔቫዳ ፡ ክፍል ፡ በረኻ ፡ ነው
*The proportion of girls to boys in our class is three to two. ክፍላችን ፡ ውስጥ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሦስት ፡ ልጃገረዶች ፡ ሁለት ፡ ወንድ ፡ ተማሪዎች ፡ አሉ

**proportions**
1. አመጣጠን. The proportions in that picture are all wrong. የዚህ ፡ ሥዕል ፡ አመጣጠን ፡ በሙሉ ፡ ስሕተት ፡ ነው
2. መጠን. It's a house of large proportions. መጠኑ ፡ ትልቅ ፡ የሆነ ፡ ቤት ፡ ነው

**in proportion to**
1. እንደየ-. Each man's pay will be in proportion to his work. የእያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ክፍያ ፡ እንደየሥራው ፡ ነው
2. ከ --- ጋር ፡ ሲታይ. This desk is too wide in proportion to its height. ይህ ፡ ጠረጴዛ ፡ ከቁመቱ ፡ ጋር ፡ ሲታይ ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ ነው

**large proportion of** አብዛኛው
A large proportion of the earth is covered with water. አብዛኛው ፡ የመሬት ፡ ክፍል ፡ በውኃ ፡ የተሸፈነ ፡ ነው

**(be) out of proportion** አይመጣጠንም
His expenses are entirely out of proportion to his income. ወጪው ፡ ከገቢው ፡ ጋር ፡ በፍጹም ፡ አይመጣጠንም

**(be) proportional to** እንደየ — ፡ ነው
The number of Congressmen from a state is proportional to its population. ከየግዛቱ ፡ የሚላኩት ፡ አማካሪዎች ፡ ብዛት ፡ እንደየግዛቱ ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ነው

**(be) proportionate** ተመጣጠነ
The money obtained from the fair was really not proportionate to the effort we put into it. ከትርኢይቱ ፡ የተገኘው ፡ ገቢ ፡ ከድካማችን ፡ ጋር ፡ አልተመጣጠነም

**proportioned, well ~** የተደላደለ
Her figure is well proportioned. የሰውነቷ ፡ ቅርጽ ፡ የተደላደለ ፡ ነው

**proposal**
1. ሐሳብ. A proposal for increasing trade between these two countries was refused. በነዚህ ፡ ሁለት ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ንግድን ፡ ለማሳደግ ፡ የቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ተቀባይነት ፡ አጣ
2. ለጋብቻ ፡ ያቀረበው ፡ ጥያቄ. His proposal was accepted by the girl with alacrity. ለጋብቻ ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ልጃገረዲቱ ፡ ያላንዳች ፡ ማመንታት ፡ ተቀበለችው

**propose**
1. አሰበ. We propose to leave at noon. በእኩለ ፡ ቀን ፡ ለመነሣት ፡ እናስባለን
2. ሐሳብ ፡ አቀረበ. I propose Mr. Smith for chairman. ሚስተር ፡ ስሚዝ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ እንዲሆኑ ፡ ሐሳብ ፡ አቀርባለሁ
*I propose that we go to the movies. ወደ ፡ ሲኒማ ፡ እንሂድ
*He proposed to her, and she accepted. ለጋብቻ ፡ ጠይቋት ፡ እሺ ፡ አለች

**proposition** ሐሳብ
He made me an excellent proposition. ጥሩ ፡ ሐሳብ ፡ አቀረበልኝ
Let us examine the mayor's first proposition! ከንቲባው ፡ በመጀመሪያ ፡ ያቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ እንመርምረው

**propound** አቀረበ
He propounded a new theory. አዲስ ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳብ ፡ አቅርቧል

**proprietary**
1. የንብረት. Proprietary rights should not take precedence over human rights. የንብረት ፡ መብቶች ፡ ከሰብአዊ ፡ መብቶች ፡ መቅደም ፡ የለባቸውም
2. ባለንብረት. The proprietary class had special privileges in the past. ድሮ ፡ ባለንብረቱ ፡ ወገን ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ነበረው

**proprietor** ባለቤት
The proprietor of this store lives on the second floor. የዚህ ፡ መደብር ፡ ባለቤት ፡ የሚኖረው ፡ ሁለተኛው ፡ ፎቅ ፡ ላይ ፡ ነው

**propriety** (proprieties)
1. ሥነ ፡ ሥርዓት. Propriety requires that one address the Emperor as "Your Majesty". ማንም ፡ ሰው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ « ግርማዊነትዎ » ፡ እንዲል ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ያስገድዳል
2. ተገቢነት. Her actions stayed within the compass of propriety. ሁኔታዋ ፡ ሁሉ ፡ ከተገቢነት ፡ ያልወጣ ፡ ነበር

**question the propriety** ተገቢ ፡ መስሎ ፡ አልታየውም
I question the propriety of granting his request. የጠየቀውን ፡ መፈጸም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ አልታየኝም

**prorate** ከፈለ
We will prorate the expense among the five of us. ወጪውን ፡ ባምስታችን ፡ መካከል ፡ እንከፍለዋለን

**proscribe**
1. አወገዘ. In earlier days, the church proscribed dancing and card playing. በድሮ ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዳንስንና ፡ ካርታ ፡ ጨዋታን ፡ ታወግዝ ፡ ነበር
2. ለሕዝብ ፡ እንዳይሸጥ ፡ አገደ. The government proscribed the author's works. መንግሥቱ ፡ የደራሲቸው ፡ ድርሰቶች ፡ ለሕዝብ ፡ እንዳይሸጡ ፡ አገደ
3. እንዳይታይ ፡ አገደ. The government proscribed the new film. መንግሥቱ ፡ አዲሱ ፡ ፊልም ፡ እንዳይታይ ፡ አገደ
**be proscribed** (= active) ከለከለ
Candy is proscribed for children by most dentists. ልጆች ፡ ከረሜላ ፡ እንዳይበሉ ፡ ብዙ ፡ የጥርስ ፡ ሐኪሞች ፡ ይከለክላሉ

**proscription** እገዳ
Proscription of books is common practice in many countries. የመጻሕፍት ፡ እገዳ ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ የተለመደ ፡ አድራጎት ፡ ነው

**prose** ስድ ፡ ንባብ
I prefer prose to poetry. ከግጥም ፡ ስድ ፡ ንባብን ፡ እመርጣለሁ

**prosecute**
1. ሕግ ፡ ፊት ፡ አቀረበ. The government will prosecute the swindlers. መንግሥት ፡ አጭበርባሪዎችን ፡ ሕግ ፡ ፊት ፡ ያቀርባል
2. ቀጠለ. He prosecuted his studies. ጥናቱን ፡ ቀጠለ
The detective prosecuted the investigation in spite of the difficulties. ብዙ ፡ ችግር ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ መረጃ ፡ ሰብሳቢው ፡ ምርመራውን ፡ ቀጠለ

**prosecution**
1. አያያዝ. The prosecution of the war was criticized. የጦርነቱ ፡ አያያዝ ፡ ተነቅፎ ፡ ነበር
2. ማከናወን. In prosecution of his plan, he stored away a supply of food. እቅዱን ፡ ለማከናወን ፡ ምግብ ፡ በተለይ ፡ አከማቸ
3. ክስ. The prosecution will be abandoned if the stolen money is returned. የተሰረቀው ፡ ገንዘብ ፡ ከተመለሰ ፡ ክሱ ፡ ይቀራል
4. መከሰስ. He was granted immunity from prosecution so he would testify. ለመመስከር ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ ከመከሰስ ፡ ነጻ ፡ ወጣ
[See also 'attorney']

**prosecutor** ሕግ ፡ አስከባሪ
The prosecutor tried to have the accused man hanged. ሕግ ፡ አስከባሪው ፡ የተከሰሰው ፡ ሰው ፡ እንዲሰቀል ፡ አመለከተ

**proselyte** ተከታይ
The proselytes of this religious sect are increasing in number. የዚህ ፡ ሃይማኖት ፡ ተከታዮች ፡ ቁጥር ፡ እየጨመረ ፡ ሄዷል

**proselytize** ሰበከ
Protestant missionaries proselytize in various parts of Africa. ፕሮቴስታንት ፡ ሚስዮናውያን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የአፍሪካ ፡ ክፍሎች ፡ ይሰብካሉ

**prospect** (v.) ፈለገ
The old man has been prospecting for gold for forty years. ሽማግሌው ፡ ወርቅ ፡ በመፈለግ ፡ አርባ ፡ ዓመቱ ፡ ነው

**prospect** (n.)
1. ተስፋ. Is there no prospect of his recovering? ለመዳን ፡ ተስፋ ፡ የለውም ?
2. ዕድል. What are his prospects of getting a job? ሥራውን ፡ ለማግኘት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ዕድል ፡ አለው ?
3. ትዕይንት. The prospect from the mountains is grand. ከተራራዎቹ ፡ ላይ ፡ ሲታይ ፡ ትዕይንቱ ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ነው
*The manager held out bright prospects to me if I would take the job. ሥራውን ፡ ብቀበል ፡ ለወደፊት ፡ ጥሩ ፡ ተስፋ ፡ ያለኝ ፡ መሆኑን ፡ አስተዳዳሪው ፡ ነገረኝ

**prospective** የወደፊት
He is my prospective son-in-law. የወደፊት ፡ አማቼ ፡ ነው
*We discussed prospective changes. ይደረጋሉ ፡ በምንላቸው ፡ ለውጦች ፡ ላይ ፡ ተነጋገርን

**prosper** በለጸገ
The country prospered during peacetime. አገሪቷ ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ በለጸገች

**prosperity** ብልጽግና
The prosperity of the country is based on free trade. የአገሪቷ ፡ ብልጽግና ፡ የተመሠረተው ፡ በነጻ ፡ ንግድ ፡ ላይ ፡ ነው

**prosperous**
1. የበለጸገ. The wretched tyrant reduced the

prosperous city to a poor village. ጨቋኙ ፡ ገዢ ፡ የበለጸገችውን ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ድኽነት ፡ አወረዳት
2.የሚያበላ. This is a prosperous business. የሚያበላ ፡ ሥራ ፡ ነው

**prostitute** ሴትኛ ፡ አዳሪ ፤ ሸርሙጣ
In our country, it is shameful to be a prostitute. ሴትኛ ፡ አዳሪ ፡ (ሸርሙጣ) ፡ መሆን ፡ ባገራችን ፡ ነውር ፡ ነው

**prostitution** ሴትኛ ፡ አዳሪነት
The lawmakers were asked to legislate against prostitution. ሕግ ፡ አውጪዎች ፡ ሴትኛ ፡ አዳሪነትን ፡ የሚቃወም ፡ ሕግ ፡ እንዲያወጡ ፡ ተጠየቁ

**prostrate**
1. ገነዳደሰ. The storm prostrated the trees. ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ዛፎቹን ፡ ገነዳደሳቸው
2. አደከመ. An attack of fever completely prostrated me. ትኩሳት ፡ ፈጽሞ ፡ አደከመኝ

**prostrate oneself**
1. ሰገደ. The pagan prostrated himself before his god. አረመኔው ፡ በጣዖቱ ፡ ፊት ፡ ሰገደ
2. በግንባሩ ፡ ወደቀ. The captives prostrated themselves before the conqueror. ምርኮኞቹ ፡ ከገዢው ፡ ፊት ፡ በግንባራቸው ፡ ወደቁ

**prostrate** (adj.), **be ~** ከሰውነት ፡ ውጭ ፡ ሆነ
She is prostrate with her great grief. በደረሰባት ፡ ሐዘን ፡ ከሰውነት ፡ ውጭ ፡ ሆናለች

**fall prostrate** ተዘረረ
He fell prostrate on the floor. በወለሉ ፡ ላይ ፡ ተዘረረ

**(be) laid prostrate** ተዘረረ
The boxer was laid prostrate by the blow. ቡጢኛው ፡ በቡጢ ፡ ተዘረረ

**protect**
1. ጠበቀ. The government protects industry by taxing imports. መንግሥቱ ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ እንዱስትሪን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲል ፡ ከውጭ ፡ በሚገባው ፡ እቃ ፡ ላይ ፡ ቀረጥ ፡ ይጥላል
2. ተከላከለ. The casing protects the wires from the rain. ሽፋኑ ፡ ሽቦውን ፡ ከዝናብ ፡ ይከላከለዋል
Our forefathers came here to protect their freedom. አባቶቻችን ፡ ነጻነታቸውን ፡ ለመከላከል ፡ ሲሉ ፡ እዚህ ፡ መጡ

**protection** መከላከያ
There is no protection against old age. እርጅና ፡ መከላከያ ፡ የለውም
The night watchman carried a gun for protection. የሌሊት ፡ ዘበኛው ፡ ለመከላከያ ፡ ጠመንጃ ፡ ይዞ ፡ ነበር
*We have policemen for our protection. የሚጠብቀን ፡ ፖሊስ ፡ አለን

**under the protection** በ - - - ጥበቃ ፡ ሥር
They were under the protection of the police while they were in town. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ሲኖሩ ፡ በፖሊስ ፡ ጥበቃ ፡ ሥር ፡ ነበሩ

**protective**
1. የመከላከያ. The protective tariff helps the country's sugar industry. የመከላከያ ፡ ቀረጥ ፡ ያገሪቱን ፡ የስኳር ፡ እንዱስትሪ ፡ ይረዳል
2. ተከላካይ. We must put a protective coating over the drawing. በሥዕሉ ፡ ላይ ፡ ተከላካይ ፡ ቅባት ፡ ማድረግ ፡ አለብን

**protector** የሚከላከል
Your big brother is my protector. ታላቅ ፡ ወንድምህ ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ የሚከላከልልኝ ፡ ነው

**protectorate** በሞግዚትነት ፡ ሥር ፡ የምትተዳደር ፡ አገር
The protectorate achieved independence last year. በሞግዚትነት ፡ ሥር ፡ ትተዳደር ፡ የነበረችው ፡ አገር ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ነጻነቷን ፡ አገኘች

**protégé**
*He is the minister's protégé and cannot be dismissed. ሚኒስትሩ ፡ ቤት ፡ ወጪ ፡ ገቢ ፡ ስለሆነ ፡ ከሥራ ፡ የሚያስወጣው ፡ የለም

**protest** (v.)
1. ተከራከረ. He protested that he was innocent. ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ሲል ፡ ተከራከረ
2. ተቃወመ. He was deluged with letters protesting his decision to close the school. ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ለመዝጋት ፡ ያደረገውን ፡ ቁርጥ ፡ ሐሳብ ፡ የሚቃወሙ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ጐረፉበት

**protest** (n.)
1. ተቃውሞ. They ignored his protest and continued hammering on the wall. የሱን ፡ ተቃውሞ ፡ ቸል ፡ ብለው ፡ ግድግዳውን ፡ መምታታቸውን ፡ ቀጠሉ
They returned to work only after protest. ተቃውሟቸውን ፡ ከገለጹ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ ተመለሱ
2. የተቃውሞ ፡ መልእክት. The President sent a protest to the Brazilian ambassador. ፕሬዚዳንቱ ፡ ለብራዚል ፡ አምባሳደር ፡ የተቃውሞ ፡ መልእክት ፡ ላኩ

*The accused man was judged guilty in spite of his protest of innocence. ምንም ፡ እንኳ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ቢል ፡ ተከሳሹ ፡ ተፈረደበት

**under protest** እየተነጫነጨ
The farmer paid the tax under protest. ገበሬው ፡ እየተነጫነጨ ፡ ግብሩን ፡ ከፈለ

**Protestant** ፕሮቴስታንት
There are many Protestants in America. በአሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ፕሮቴስታንቶች ፡ አሉ

**protocol** ፕሮቶኮል
Protocol requires that dignitaries be addressed by their titles. ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ በማዕርግ ፡ ስማቸው ፡ እንዲጠሩ ፡ ፕሮቶኮል ፡ ያስገድዳል

**according to protocol** በማዕርግ ፡ የተወሰነ
Seating at the banquet is according to protocol. በታላቁ ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ አቀማመጡ ፡ በማዕረግ ፡ የተወሰነ ፡ ነው

**prototype**
*A modern ship has its prototype in the hollowed logs used in olden days. ዘመናዊ ፡ መርከብ ፡ ጥንት ፡ ግንድ ፡ እየተቦረቦረ ፡ ከሚሠራው ፡ ጀልባ ፡ የመጣ ፡ ነው

**protract** አራዘመ
My uncle unexpectedly protracted his visit. አጐቴ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ የሚቆይበትን ፡ ጊዜ ፡ ሳይታሰብ ፡ አራዘመው

**protracted** (adj.) ረጅም
After protracted debate, the bill was passed. የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ከረጅም ፡ ክርክር ፡ በኋላ ፡ አለፈ

**protrude** (vt.) አወጣ
The naughty child protruded his tongue. ባለጌው ፡ ልጅ ፡ ምላሱን ፡ አወጣ

**protrude** (vi.) ገጠጠ
His teeth protrude too far. ጥርሱ ፡ በጣም ፡ የገጠጠ ፡ ነው

**protruding** ያፈነገጠ
I caught my coat on a nail protruding from the wall. አንድ ፡ ከግድግዳው ፡ ላይ ፡ ያፈነገጠ ፡ ምስማር ፡ ኮቴን ፡ ያዘብኝ

**proud** ኩሩ
He is a very proud man and will not accept charity. በጣም ፡ ኩሩ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ችሮታ ፡ አይቀበልም
*It was a proud moment for him when he shook hands with the President. ከፕሬዚዳንቱ ፡ ጋር ፡ ሲጨባበጥ ፡ ኩራት ፡ ተሰምቶት ፡ ነበር

**be proud** ኰራ
I am proud to be an Ethiopian. ኢትዮጵያዊ ፡ በመሆኔ ፡ እኰራለሁ

**be proud of** ኰራ(በት)
You are a good student, and I am proud of you. ጐበዝ ፡ ተማሪ ፡ ስለሆንክ ፡ እኰራብሃለሁ

**prove**
1. አረጋገጠ. I can prove I didn't do it. እንዳላደረግሁት ፡ ለማረጋገጥ ፡ እችላለሁ
The goldsmith proved the purity of the gold. ወርቅ ፡ ሠሪው ፡ የወርቁን ፡ ጥራት ፡ አረጋገጠ
2. አስረዳ. That doesn't prove much. ያ ፡ እምብዛም ፡ አያስረዳም
3. መሰከረ. Your grades prove that you study. ማጥናትህን ፡ ውጤትህ ፡ ይመሰክራል

**prove to be**
1. መሆኑ ፡ ታወቀ. The rumor proved to be false. ወሬው ፡ ሐሰት ፡ መሆኑ ፡ ታወቀ
2. ሆኖ ፡ ተገኘ. The new secretary proved to be useless. አዲሱ ፡ ጸሐፊ ፡ የማይረባ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

**proverb** ምሳሌ
I cannot understand Amharic proverbs. ያማርኛ ፡ ምሳሌ ፡ አይገባኝም

**proverbial** ለምሳሌነት ፡ የሚበቃ
His reputation for hard work is proverbial. በጠንካራ ፡ ሠራተኛነቱ ፡ ያገኘው ፡ ስም ፡ ለምሳሌነት ፡ የሚበቃ ፡ ነው

**provide** (vt.)
1. አዘዘ. Our club's rules provide that dues must be paid monthly. የክበባችን ፡ ደንቦች ፡ መዋጮው ፡ በየወሩ ፡ እንዲከፈል ፡ ያዛሉ
2. ሰጠ. The school provides free books. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ መጻሕፍት ፡ በነጻ ፡ ይሰጣል
3. አዘጋጀ. Who is going to provide the entertainment? ጨዋታውን ፡ የሚያዘጋጀው ፡ ማነው ?
4. ሆነ. The land was bare and provided no cover for the troops. መሬቱ ፡ ገላጣ ፡ ስለነበረ ፡ ለወታደሮቹ ፡ ተገን ፡ አልሆነም
5. አስገኘ(ለት). Sheep provide us with wool. በጎቹ ፡ የሱፍ ፡ ጸጉር ፡ ያስገኙልናል

**provide** (vi.) አንቀጽ ፡ አለው
The constitution provides for such special cases. እንዲህ ፡ ላሉ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ አለው

**provide (for)**
1. አስተዳደረ. He had a large family to provide for. የሚያስተዳድረው ፡ ብዙ ፡ ቤተሰብ ፡ ነበረው

2. የሚያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ አደረገ. A father provides for his children. አባት ፡ ለልጆቹ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ ያደርጋል
*Providing for one's wife is a marital obligation. ሚስት ፡ የሚያስፈልጋትን ፡ ሁሉ ፡ እንድታገኝ ፡ ማድረግ ፡ የባል ፡ ኀላፊነት ፡ ነው

**provide for oneself** ራሱን ፡ ደገፈ
Since his parents' death, he has had to provide for himself. ወላጆቹ ፡ ከሞቱ ፡ ወዲህ ፡ ራሱን ፡ መደገፍ ፡ ግዴታ ፡ ሆነበት

**be provided with**
1. አገኘ. I'm already provided with all I need. የሚያስፈልገኝን ፡ ሁሉ ፡ አግኝቼያለሁ
2. ተሰጠ. We were provided with supplies these last two weeks. ላለፉት ፡ ሁለት ፡ ሳምንቶች ፡ የሚበቃ ፡ ሥንቅ ፡ ተሰጥቶን ፡ ነበር

**without providing** ምንም ፡ ሳይተው
He died without providing for his family. ለቤተሰቡ ፡ ምንም ፡ ሳይተው ፡ ሞተ
[See also 'ill']

**provided** ከ + perfect.
I will subscribe ten dollars provided that you do too. አንተ ፡ ካወጣህ ፡ እኔም ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ አወጣለሁ
I'll go provided you come with me. ከኔ ፡ ጋር ፡ የምትሄድ ፡ ከሆነ ፡ እሄዳለሁ

**providence** አርቆ ፡ አስተዋይነት
Because of our father's providence, we were all able to go to college. ባባታችን ፡ አርቆ ፡ አስተዋይነት ፡ ሁላችንም ፡ ኮሌጅ ፡ መማር ፡ ቻልን

**Providence** እግዚአብሔር
May Providence watch over you! እግዚአብሔር ፡ ይጠብቅህ

**provident** አርቆ ፡ አሳቢ
Provident men lay aside money for their families. አርቆ ፡ አሳቢዎች ፡ ለቤተ ፡ ሰቦቻቸው ፡ ገንዘብ ፡ ያስቀምጣሉ

**providing**
*Providing he should come, we must have some supplies ready. ምናልባት ፡ ቢመጣ ፡ ምግብ ፡ ማዘጋጀት ፡ አለብን

**province**
1. ጠቅላይ ፡ ግዛት. Ethiopia is divided into fourteen provinces. ኢትዮጵያ ፡ በዐሥራ ፡ አራት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ትከፈላለች
2. ሥልጣን. Granting jobs is outside my province. ሥራ ፡ መስጠት ፡ ከኔ ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ ነው
3. ተግባር. Teaching spelling is not within the province of a college. ሥርዓተ ፡ ሆህያትን ፡ ማስተማር ፡ የኮሌጅ ፡ ተግባር ፡ አይደለም
*Greek is outside my province. የግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ አልችልም ፡ (አላውቅም)

**provincial**
1. የጠቅላይ ፡ ግዛት. The provincial government does not have charge of building all the roads. የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ አስተዳደር ፡ መንገዶችን ፡ ሁሉ ፡ የመሥራት ፡ ኀላፊነት ፡ የለበትም
2. የባላገርነት. His provincial manners do not make him many friends in the city. የባላገርነት ፡ ሁኔታው ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጓደኞች ፡ እንዳያፈራ ፡ አደረገው

**provision**
1. አንቀጽ. The provisions of the law do not take this matter into account. የሕጉ ፡ አንቀጾች ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ አይመለከቱም
2. ደንብ. Our library has a provision that hands must be clean before books are taken out. ቤተ ፡ መጻሕፍታችን ፡ መጻሕፍትን ፡ ከመንካት ፡ በፊት ፡ እጆችን ፡ ማጽዳት ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚል ፡ ደንብ ፡ አለው
3. ቃል. The provisions of the will tied his hands. የኑዛዜው ፡ ቃል ፡ እጁን ፡ አሰረው
4. ወደፊት ፡ እቅድ. There is a provision for making the building larger if necessary. ወደፊት ፡ ሕንጻው ፡ ላይ ፡ ለመጨመር ፡ የሚቻልበት ፡ እቅድ ፡ አለ
5. (= to provide) ማቅረብ. The provision of hay for the cattle is his responsibility. ለከብቶቹ ፡ ድርቆሽ ፡ ማቅረብ ፡ የሱ ፡ ኀላፊነት ፡ ነው
6. የሚረዳ. His savings are a provision for his old age. ያስቀመጠው ፡ ገንዘብ ፡ በእርጅና ፡ ጊዜው ፡ የሚረዳው ፡ ነው
*There is a large provision of hay for the cattle. ለከብቶቹ ፡ ምግብ ፡ የሚሆን ፡ ብዙ ፡ ድርቆሽ ፡ አለ
*The boy was left the money with the provision that it be for his education. ልጁ ፡ ለትምህርት ፡ ብቻ ፡ የሚያውለው ፡ ገንዘብ ፡ ወረሰ

**provisions** ሥንቅ
Our provisions are running low. ሥንቃችን ፡ እያለቀ ፡ ሄደ

**make provision for** ካሁኑ ፡ አሰበ(በት)
Make provision for your old age now! ለመጦሪያህ ፡ ካሁኑ ፡ አስብበት

**provisional** ጊዜያዊ
This is only a provisional government. ይህ ፡ ጊዜያዊ ፡ መንግሥት ፡ ነው

**proviso**
*Tom was admitted to the eighth grade with the proviso that he was to be put back if he failed any subject. ምንም ፡ ዓይነት ፡ ትምህርት ፡ ቢወድቅ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ሊከለስ ፡ ቶም ፡ ስምንተኛ ፡ ክፍል ፡ ገባ

**provocation** ማነሣሣት
Deliberate provocation of a quarrel is a serious matter. ሆን ፡ ብሎ ፡ ጠብን ፡ ማነሣሣት ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ ነው
*The border attacks are a provocation likely to start war. የድንበሩ ፡ ማጥቃት ፡ ጦርነት ፡ ሊቀሰቅስ ፡ ይችላል

**be a provocation to** አናደደ
His noisy parties are a provocation to the neighbors. ጫጫታ ፡ የበዛበት ፡ ግብዣው ፡ ጎረቤቶቹን ፡ የሚያናድድ ፡ ነው

**without any provocation** ከመሬት ፡ ተነሥቶ
He hit me without any provocation. ከመሬት ፡ ተነሥቶ ፡ መታኝ

**provoke**
1. አስከተለ. The President's speech provoked much controversy. የፕሬዚዳንቱ ፡ ንግግር ፡ ብዙ ፡ ክርክር ፡ አስከተለ
2. ቀሰቀሰ. His insidious remark provoked a quarrel. ተንኰልን ፡ ያዘለ ፡ አስተያየቱ ፡ ጠብ ፡ ቀሰቀሰ
3. አስቈጣ. The child's rudeness provoked the old man. የልጁ ፡ ብልግና ፡ ሽማግሌውን ፡ አስቈጣቸው

**provoke to anger** ከንዴት ፡ አደረሰ
An insult provokes a person to anger. ስድብ ፡ ሰውን ፡ ከንዴት ፡ ያደርሳል

**be provoked**
1. አበሳጩት. He was provoked to the point of losing his temper. ትዕግሥቱን ፡ እስኪጨርስ ፡ ድረስ ፡ አበሳጩት
2. ሁኔታው ፡ አስገደደው. He was provoked to answer rudely. በኀይለ ፡ ቃል ፡ እንዲመልስ ፡ ሁኔታው ፡ አስገደደው

**be provoking** አበሳጨ
His behavior is provoking. ጠባዩ ፡ ያበሳጫል

**prowl** አደባ
I hear someone prowling around my house during the night. በቤቴ ፡ ዙሪያ ፡ ሰው ፡ ሌሊት ፡ ሌሊት ፡ ሲያደባ ፡ እሰማለሁ
Many wild animals prowl at night. ብዙ ፡ አራዊት ፡ ሌሊት ፡ ያደባሉ

**prowler** ሹልክ ፡ ብሎ ፡ የሚሄድ ፡ ሰው
The police arrested the prowler on suspicion of theft. ፖሊሶቹ ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ የሚሄደውን ፡ ሰውዬ ፡ በሌብነት ፡ ጥርጣሬ ፡ ያዙት

**proximity** ቅርበት ፡ መሆን
The proximity of the airport makes us very nervous. የአውሮፕላን ፡ ማረፊያው ፡ ቅርበት ፡ መሆኑ ፡ በጣም ፡ አበሳጭቶናል

**in close proximity to** አቅራቢያ
Our house is in close proximity to the church. ቤታችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አቅራቢያ ፡ ነው

**proxy** ወኪል
The proxy voted to support the proposal. ወኪሉ ፡ የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ በመደገፍ ፡ ድምፅ ፡ ሰጠ

**prude**
*He is a prude in his way of dressing. ባለባበሱ ፡ እንከን ፡ እንዲወጣለት ፡ አይፈልግም

**prudence**
1. መጠንቀቅ. Prudence can spare a person much difficulty later on. መጠንቀቅ ፡ ውሎ ፡ አድሮ ፡ አንድን ፡ ሰው ፡ ከብዙ ፡ ችግር ፡ ያድናል
2. አስተዋይነት. The child lacks prudence. ሕፃኑ ፡ አስተዋይነት ፡ ይጐድለዋል

**prudent** አርቆ ፡ የሚያስብ
A prudent man saves part of his wages. አርቆ ፡ የሚያስብ ፡ ሰው ፡ ከደሞዙ ፡ ቀንሶ ፡ ያስቀምጣል

**be prudent** ተጠነቀቀ
If you are not prudent, you will get into trouble. ካልተጠነቀቅህ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ትወድቃለህ

**prune** ከረከመ ፤ ገረዘ
The gardener prunes the fruit trees very carefully. አትክልተኛው ፡ ያትክልቱን ፡ ዛፎች ፡ በጥንቃቄ ፡ ይከረክማል ፡ (ይገርዛል)
*The author pruned his novel. ደራሲው ፡ ከልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ያልሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ አወጣ

**pry** (pried) ጣልቃ ፡ ገባ
He tried to pry into my affairs. በጉዳዬ ፡ ውስጥ ፡ ጣልቃ ፡ ሊገባ ፡ ሞከረ

**pry off** አነሣ
Pry the lid off with a knife! ክዳኑን ፡ በቢላዋ ፡ አንሣው

**pry open** ሰብሮ ፡ ከፈተ
I had to pry open the box with a crowbar. ሣጥኑን ፡ በብረት ፡ መፈልቀቂያ ፡ ሰብሬ ፡ መክፈት ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ

**pry out** አዋጣ
We finally pried the secret out of him. በመጨ
ረሻ ፡ ምስጢሩን ፡ አዋጣነው

**Psalms** የዳዊት ፡ መዝሙር
Recite the Psalms to me! የዳዊትን ፡ መዝሙር ፡
በቃልህ ፡ ውጣልኝ

**pseudonym** የብዕር ፡ ስም
He wrote the book under a pseudonym. መጽሐ
ፉን ፡ በብዕር ፡ ስም ፡ ጻፈ

**psychiatrist** የአእምሮ ፡ ሐኪም
Do you see a psychiatrist? የአእምሮ ፡ ሐኪም ፡
ዘንድ ፡ ትሄዳለህ ?

**psychiatry** የአእምሮ ፡ ሕክምና
I'm studying psychiatry. የአእምሮ ፡ ሕክምና ፡
አጠናለሁ

**psychic** ከሕገ ፡ ተፈጥሮ ፡ ውጭ
People used to think that an eclipse was due to psychic forces. ሰዎች ፡ የፀሐይ ፡ ግርዶሽ ፡
የሚሆነው ፡ ከሕገ ፡ ተፈጥሮ ፡ ውጭ ፡ ነው ፡
ብለው ፡ ያምኑ ፡ ነበር

**psychology**
1. የሥነ ፡ ልቡና ፡ ትምህርት. Psychology is taught in the third year of college. የሥነ ፡ ልቡና ፡ ት
ምህርት ፡ ሦስተኛ ፡ ዓመት ፡ ኮሌጅ ፡ ላይ ፡ ይ
ሰጣል
2. አስተሳሰብ. He doesn't understand the psychology of an American. የአሜሪካዊ ፡ አስተ
ሳሰብ ፡ አይገባውም

**puberty**
1. ዐቅመ ፡ አዳም. He has not yet attained puberty. ገና ፡ ለዐቅመ ፡ አዳም ፡ አልደረሰም
2. ዐቅመ ፡ ሔዋን. She has not yet attained puberty. ገና ፡ ለዐቅመ ፡ ሔዋን ፡ አልደረሰችም

**public** (n.) ሕዝብ
Is this park open to the public? ይህ ፡ መናፈሻ ፡
ቦታ ፡ ለሕዝብ ፡ ክፍት ፡ ነው ?

**in public** ባደባባይ
That's no way to behave in public. ባደባባይ ፡
እንዲህ ፡ አይኮንም

**public** (adj.)
1. የሕዝብ. A public park for old people was built by the city. ከተማው ፡ የአዛውንት ፡ የሕ
ዝብ ፡ መናፈሻ ፡ ቦታ ፡ አሠራ
Public affairs are the concern of the government. የሕዝብ ፡ ጉዳዮች ፡ መንግሥትን ፡ ይመለ
ከታሉ
The public library bought many new books.
የሕዝብ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ብዙ ፡ አዳዲስ ፡
መጽሐፎችን ፡ አስመጥቷል
2. ለሕዝብ ፡ የሚሆን. New public works are being planned. አዲስ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚሆኑ ፡ ሥ
ራዎች ፡ ታቅደዋል

**become public** በይፋ ፡ ታወቀ
The fact became public. ነገሩ ፡ በይፋ ፡ ታወቀ

**make public** ለሕዝብ ፡ አስታወቀ
He made his opinion public. ሐሳቡን ፡ ለሕዝብ ፡
አስታወቀ
[See also 'eye, opinion']

**publication** የታተመ ፡ ጽሑፍ
Do you have any Amharic publications?
ባማርኛ ፡ የታተመ ፡ ጽሑፍ ፡ አለህ ?
*The publication of his book is scheduled for next month. በሚመጣው ፡ ወር ፡ መጽሐፉ ፡ ሊ
ታተም ፡ ታቅዷል
*He is in the publication business and makes a lot of money. መጽሐፍ ፡ በማሳተም ፡ ሥራ ፡ ብ
ዙ ፡ ገንዘብ ፡ ያገኛል

**for publication** ለሕዝብ ፡ የሚገለጽ
This report is not for publication. ይህ ፡ ሪፖርት ፡
ለሕዝብ ፡ የሚገለጽ ፡ አይደለም

**publicity**
1. በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ መታወቅ. Actors always like publicity. ተዋንያን ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በሕ
ዝብ ፡ ዘንድ ፡ መታወቅን ፡ ይወዳሉ
2. የንግድ ፡ ማስታወቂያ. He hired an agent to handle his publicity. የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ የ
ሚያዘጋጅለት ፡ ወኪል ፡ ቀጠረ

**public life** የመንግሥት ፡ ሥራ
He entered public life at an early age. ገና ፡ በ
ወጣትነቱ ፡ በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ተቀጠረ

**publicly**
1. ባደባባይ. The rebel was hanged publicly.
ዐመፀኛው ፡ ባደባባይ ፡ ተሰቀለ
2. በሕዝብ ፡ ዘንድ. His disgrace became publicly known. ውርደቱ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ታወቀ

**public opinion** የሕዝቡ ፡ አስተያየት
The public opinion is against war. የሕዝቡ ፡
አስተያየት ፡ ጦርነቱን ፡ የሚቃወም ፡ ነው

**public relations** የሕዝብ ፡ ግንኙነት
We must promote public relations. የሕዝብ ፡ ግን
ኙነትን ፡ ማበረታታት ፡ አለብን

**public school** መንግሥት ፡ ትምህርት ፡ ቤት
In America, most children go to public school.

አሜሪካን ፡ አገር ፡ አብዛኞች ፡ ተማሮች ፡ መንግሥ ት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይማራሉ

**public servant** የመንግሥት ፡ ሠራተኛ
All public servants must buy government bonds. የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ሁሉ ፡ የመን ግሥት ፡ ቦንድ ፡ መግዛት ፡ አለባቸው

**public speaker** ለሕዝብ ፡ ንግግር ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው
A thin voice is a handicap to a public speaker. ለሕዝብ ፡ ንግግር ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው ፡ ቀጭን ፡ ድምፅ ፡ ዕንቅፋት ፡ ነው

**public view** አደባባይ
She secluded herself from public view. እርሷ ፡ ከአደባባይ ፡ ራሷን ፡ አገለለች

**publish**
1. አሳተመ. He hopes to publish his new book very soon. በቅርቡ ፡ አዲሱን ፡ መጽሐፉን ፡ ለማ ሳተም ፡ ያስባል
2. አቀረበ. It is the function of a newspaper to publish the news. ወሬ ፡ ማቅረብ ፡ የጋዜጣ ፡ ተ ግባር ፡ ነው
3. ገለጸ(ተገለጸ). His acquittal was published in the newspaper. በነጻ ፡ መለቀቁ ፡ በጋዜጣ ፡ ተገለጸ
4. አዛመተ. Don't publish the faults of your friends! የጓደኞህን ፡ ጉድለት ፡ አታዛምት

**publisher** አሳታሚ
The publisher, not the author of the book, becomes rich. የሚከብረው ፡ የመጽሐፉ ፡ ደራ ሲ ፡ ሳይሆን ፡ አሳታሚው ፡ ነው

**pucker** አሞጠሞጠ
He puckered his lips and tried to whistle. ከንፈሮቹን ፡ አሞጥምጦ ፡ ለማፏጨት ፡ ሞከረ

**puddle** የተቋጠረ ፡ ውኃ
I stepped in a puddle and got wet. መንገዱ ፡ ላ ይ ፡ የተቋጠረው ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ገብቼ ፡ በሰበሰኩ

**pudgy** ድምቡጭ ፡ ያለ
The baby has a pudgy face. ሕፃኑ ፡ ድምቡጭ ፡ ያለ ፡ ፊት ፡ አለው

**puerile** የሕፃን
He asks puerile questions. የሕፃን ፡ ጥያቄ ፡ ይ ጠይቃል

**puff** (v.)
1. ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰ. After running so hard, he was puffing. በኀይል ፡ ከሮጠ ፡ በኋላ ፡ ቁና ፡ ቁና ፡ ይተነፍስ ፡ ነበር
2. ቡልቅ ፡ ቡልቅ ፡ አደረገ. He was puffing on his pipe when I came in. ስገባ ፡ ፒፓውን ፡ ቡ ልቅ ፡ ቡልቅ ፡ ያደርግ ፡ ነበር
*The engine puffed uphill. የእንፋሎት ፡ መኪ ና ፡ ዳገቱን ፡ ሲወጣ ፡ እንፋሎት ፡ ይተፋ ፡ ነበር

**puff out**
1. ነፋ. He puffed out his chest when the teacher praised his work. አስተማሪው ፡ ሥራው ን ፡ ሲያመሰግንለት ፡ ጊዜ ፡ ደረቱን ፡ ነፋ
2. አጠፋ. The wind puffed out the flame. ነፋሱ ፡ እሳቱን ፡ አጠፋ

**(be) puffed up** ተወጠረ
The film star was puffed up with conceit. የፊልሙ ፡ ኮከብ ፡ በእብሪት ፡ ተወጥራለች

**puff** (n.) ትንፋሽ
He tried to blow out the candles with one puff. ሻማዎቹን ፡ ባንድ ፡ ትንፋሽ ፡ ለማጥፋት ፡ ሞከረ

**pugnacious** ጠበኛ
The new student is very pugnacious. አዲሱ ፡ ተማሪ ፡ በጣም ፡ ጠበኛ ፡ ነው

**pull** (vt.)
1. ጐተተ. Don't pull so hard! እንዲህ ፡ በኀይ ል ፡ አትጐትት
2. ጐትቶ ፡ አወጣ. They pulled a heavy rock up the mountainside. አንድ ፡ ትልቅ ፡ ቋጥኝ ፡ ጐትተው ፡ ተራራው ፡ ላይ ፡ አወጡ
3. ነቀለ. The dentist pulled his teeth yesterday. የጥርስ ፡ ሐኪሙ ፡ ትላንት ፡ ጥርሱን ፡ ነቀለለት
4. መዘዘ(በት). He pulled a gun on me. ሽጉጥ ፡ መዘዘብኝ
5. (= passive) ተሸመቀቀ. +The football player pulled a tendon. ኳስ ፡ ተጫዋቹ ፡ ሥሩ ፡ ተሸመቀቀ

**pull** (vi.)
1. ሲሳብ ፡ ቻለ. This wagon pulls easily. ይህ ፡ ጋሪ ፡ በቀላሉ ፡ ሲሳብ ፡ ይችላል
2. ገባ. The car pulled into the garage. መኪናዋ ፡ ወደ ፡ ጋራዥ ፡ ገባች

**pull ahead** ቀደመ
He was behind me, but he soon pulled ahead. ከኋላዬ ፡ ነበረ ፤ ግን ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ቀደመኝ

**pull at** ጐተተ
He pulled at the rope. ገመዱን ፡ ጐተተው

**pull back** መንጨቀ
I tried to grab her by the hand, but she pulled back. እጇን ፡ ለመያዝ ፡ ስሞክር ፡ መንጨቀችኝ

**pull down**
1. አፈረሰ. They're going to pull down all the old houses. አሮጌዎቹን ፡ ቤቶች ፡ በሙሉ ፡ ሊያፈርሱ ፡ ነው

2. አወረደ. Shall I pull down the shades? የሸራ ፡ መጋረጃውን ፡ ላውርድ ?

**pull each other's hair** ጸጉር ፡ ተነጫጩ
The fighting boys pulled each other's hair. ልጆቹ ፡ ሲጣሉ ፡ ጸጉር ፡ ተነጫጩ

**pull in** (vt.) ወደ ፡ ውስጥ ፡ አስገባ
Pull in your stomach! ሆድህን ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ አስገባ

**pull in** (vi.) ገባ
When did the train pull in? ባቡር ፡ መቼ ፡ ገባ ?

**pull on** አጠለቀ
He pulled on a sweater. ሹራቡን ፡ አጠለቀ

**pull oneself together** ራሱን ፡ ተቈጣጠረ ፤ በርታ ፡ አለ
Pull yourself together! People are watching you. ራስህን ፡ ተቈጣጠረው ፡ (በርታ ፡ በል) ፤ ሰው ፡ እያየህ ፡ ነው

**pull out** (vt.)
1. ነቀለ. The children pulled out all the weeds. ልጆቹ ፡ አረሙን ፡ በሙሉ ፡ ነቀሉት
2. አወጣ. He pulled a gem out of his pocket. ከኪሱ ፡ ውስጥ ፡ የከበረ ፡ ደንጊያ ፡ አወጣ

**pull out** (vi.)
1. ተነሣ. The train will pull out any minute. ባቡሩ ፡ አሁን ፡ ይነሣል
2. ለቆ ፡ ወጣ. The troops pulled out of the occupied territory. ወታደሮቹ ፡ የያዙትን ፡ ግዛት ፡ ለቀው ፡ ወጡ

**pull out from behind** ከ - - - ኋላ ፡ ወጥቶ ፡ ቀድሞ ፡ አለፈ
A car pulled out from behind the truck. አንድ ፡ መኪና ፡ ከጭነት ፡ መኪናው ፡ ኋላ ፡ ወጥታ ፡ ቀድማ ፡ አለፈች

**pull over** ወጥቶ ፡ አቆመ
Pull over to the side of the road! ወደ ፡ ዳር ፡ ወጥተህ ፡ አቁም

**pull over one's head**
1. ተከናነበ. Don't pull the blanket over your head! ብርድ ፡ ልብሱን ፡ አትከናነብ
2. አጠለቀ. He pulled the sweater over his head. ሹራቡን ፡ አጠለቀ

**(not) pull through** አይድንም
We were afraid she might not pull through, she was so sick. በጣም ፡ ስላመማት ፡ አትድንም ፡ ብለን ፡ ሰግተን ፡ ነበር

**pull up**
1. ነቃቀለ. Someone pulled up all my flowers. አንድ ፡ ሰው ፡ አበባዎቼን ፡ በሙሉ ፡ ነቃቀለብኝ
2. ከፍ ፡ አደረገ. Pull up your socks! የእግር ፡ ሹራብህን ፡ ከፍ ፡ አድርግ
*Pull up a chair! ወንበር ፡ ሳብ ፡ አድርገህ ፡ ተቀመጥ

**pull up in front** ፊት ፡ ለፊት ፡ አቆመ
He pulled up his car in front of the house. መኪናውን ፡ እቤቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አቆመው

**pull (sumething) up to**
1. አስጠግቶ ፡ አቆመ. The driver pulled the car up to the curve. ሾፌሩ ፡ መኪናውን ፡ መጠምዘዣው ፡ ላይ ፡ አስጠግቶ ፡ አቆመ
2. ጠጋ ፡ አደረገ. Pull your chair up to the table! ወንበርህን ፡ ወደ ፡ ጠረጴዛው ፡ ጠጋ ፡ አድርገው
[See also 'leg, string, wire']

**pull** (n.)
*His pull got him the job. ሥራውን ፡ ያገኘው ፡ በዘመድ ፡ ነው

**give a pull** ሳብ ፡ አደረገ
He gave my sleeve a pull. እጅጌዬን ፡ ሳብ ፡ አደረገ

**pulley** መዘውር
The rope passed through a pulley. ገመዱ ፡ ባንድ ፡ መዘውር ፡ ላይ ፡ አለፈ

**pulmonary** የሳምባ
He has a pulmonary infection. የሳምባ ፡ በሽታ ፡ ይዞታል

**pulp** ሥጋ
The pulp of the orange is full of juice. የብርቱካን ፡ ሥጋ ፡ ውኃ ፡ ሞልቶታል

**beat to a pulp**
*He beat him to a pulp. አፈር ፡ አስጋጠው ፡ (or, እንዳይሞት ፡ እንዳይሽር ፡ አደረገው)

**wood pulp** የተፈጨ ፡ ዕንጨት
Paper is made from wood pulp. ወረቀት ፡ የሚሠራው ፡ ከተፈጨ ፡ ዕንጨት ፡ ነው

**pulpit** መስበኪያ ፡ ሰገነት
The preacher stood in the pulpit to give a sermon. ቄሱ ፡ ለመስበክ ፡ መስበኪያው ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ ቆሙ

**pulsate** ትር ፡ ትር ፡ አለ
I could feel his heart pulsate. ልቡ ፡ ትር ፡ ትር ፡ ሲል ፡ ይሰማኝ ፡ ነበር

**pulse** (v.) ታምቡር ፡ መታ
His heart pulsed with excitement. ከደስታ ፡ ብዛት ፡ ልቡ ፡ ታምቡር ፡ መታ

**pulse** (n.) የልብ ፡ ትርታ
The patient has a weak pulse. የበሽተኛው ፡ የልቡ ፡ ትርታ ፡ ደክሟል

**pulverize**
1. አደቀቀ. The boulder pulverized all the stones it fell on. ትልቁ ፡ ቋጥኝ ፡ የወደቀባቸ
ውን ፡ ድንጋዮች ፡ ሁሉ ፡ አደቀቃቸው
2. አወደመ. The air raid pulverized the enemy's fortifications. ያየር ፡ ወረራው ፡ የጠላትን ፡ ምሽግ ፡ አወደመው

**pump** (v.) በፖምፕ ፡ አወጣ
Shall I pump some water? ውኃ ፡ በፖምፕ ፡ ላ
ውጣ ?

**pump for information** ጥያቄዎች ፡ አበዛበት
He pumped me for information about my plans. እቅዴን ፡ ለመረዳት ፡ ጥያቄዎች ፡ አበዛብኝ

**be pumped out** በፖምፕ ፡ ተቀዳ
The water was pumped out of the hole. ውኃው ፡ ከጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ በፖምፕ ፡ ተቀዳ

**be pumped up** በፖምፕ ፡ መጣ
Our water is pumped up from the spring. የኛ ፡ ውኃ ፡ ከምንጩ ፡ በፖምፕ ፡ ይመጣል

**pump** (n.) ፖምፓ
The pump in our house broke down. የቤታችን ፡ ፖምፓ ፡ ተሰብሯል

**pumpkin** ዱባ
Pumpkin is the poor man's food. ዱባ ፡ የድኻ ፡ ምግብ ፡ ነው

**pun** የኅብር ፡ አነጋገር
I don't enjoy making puns. የኅብር ፡ አነጋገ
ር ፡ አልወድም

**punch** (v.)
1. በሳ. Did the conductor punch your ticket? ቲኬት ፡ ቈራጩ ፡ ቲኬትህን ፡ በስቶልሃል ?
2. በቡጢ ፡ መታ. He punched him in the nose. በቡጢ ፡ አፍንጫው ፡ ላይ ፡ መታው

**punch** (n.)
1. [ልዩ ፡ ልዩ ፡ የፍራፍሬ ፡ ጭማቂዎችና ፡ የአል
ኮል ፡ መጠጦች ፡ ተደባልቀው ፡ የሚገኙበት ፡ መ
ጠጥ]
2. ቡጢ. The punch broke his jaw. ቡጢው ፡ ማ
ንገጭላውን ፡ አወለቀው
He knocked him down with a punch. በቡጢ ፡ አ
ንዴ ፡ መቶ ፡ ጣለው

**give a punch** በቡጢ ፡ መታ
I gave him a punch on the jaw. መንጋጋው ፡ ላ
ይ ፡ በቡጢ ፡ መታሁት

**punctilious** በጣም ፡ ጥንቁቅ
A nurse should be punctilious in obeying the doctor's orders. ነርስ ፡ የሐኪሙን ፡ ትእዛዝ ፡ በምትፈጽምበት ፡ ወቅት ፡ በጣም ፡ ጥንቁቅ ፡ መሆ
ን ፡ አለባት

**punctual** ሰዓት ፡ አክባሪ
He is so punctual you could set your watch by him. በጣም ፡ ሰዓት ፡ አክባሪ ፡ ከመሆኑ ፡ የ
ተነሣ ፡ ሰዓትህን ፡ በሱ ፡ ልታስተካክል ፡ ትችላለህ

**punctuate**
1. ነጥብ ፡ አደረገ. Punctuate the end of the sentence, so it will be easier to read. ለማንበብ ፡ እንዲቀልህ ፡ በዐረፍተ ፡ ነገሩ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ነጥብ ፡ አድርግ
2. አቋረጠ. Cheers punctuated the speaker's words. የተናጋሪውን ፡ ንግግር ፡ ጭብጨባና ፡ ጩኸት ፡ ያቋርጡት ፡ ነበር
3. አገነነ. He punctuated his remarks with gestures. የንግግሩን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ በጁ ፡ እ
ንቅስቃሴ ፡ አገነነ

**punctuation** ሥርዓተ ፡ ነጥብ
Ethiopian punctuation is not like that of English. የኢትዮጵያ ፡ ሥርዓተ ፡ ነጥብ ፡ እንደ ፡ እንግ
ሊዝኛ ፡ አይደለም

**punctuation mark** ነጥብ
Please put punctuation marks in your sentences! ዐረፍተ ፡ ነገሮችህን ፡ ነጥብ ፡ አድርግባቸው

**puncture** (v.) በሳ
A nail punctured my tire. ጎማዬን ፡ ምስማር ፡ በ
ሳብኝ

**puncture (one's) skin** ወጋ
A needle punctured his skin. መርፌ ፡ ወጋው

**puncture** (n.) ቡኮ
The puncture in the tire was caused by a nail. ቡኮው ፡ የደረሰው ፡ በምስማር ፡ ምክንያት ፡ ነው

**pungent**
1. የሚሰነፍጥ. This fruit has a pungent odor. ይህ ፡ ፍሬ ፡ የሚሰነፍጥ ፡ ሽታ ፡ አለው
2. ሰው ፡ የሚነካ. He likes to make pungent remarks. ሰው ፡ የሚነካ ፡ አስተያየት ፡ መስጠት ፡ ይወዳል

**punish** ቀጣ
He punished his child for breaking the window. መስኮቱን ፡ ስለሰበረ ፡ ልጁን ፡ ቀጣው

**punishable** የሚያስቀጣ
In wartime, treason is punishable by death. በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ አገርን ፡ መክዳት ፡ በሞት ፡ የሚ
ያስቀጣ ፡ ነው

**punishment** ቅጣት
The punishment was too severe. ቅጣቱ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ነበር

**receive punishment** ተቀጣ
The boy received punishment for coming late to school. ልጁ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዘግይቶ ፡ በመምጣቱ ፡ ተቀጣ
[See 'exemplary, remit']

**punitive**
1. የሚያስቀጣ. Punitive laws helped put an end to the slave trade. የሚያስቀጣው ፡ ሕግ ፡ የባርነትን ፡ ንግድ ፡ አቆመ
2. ለመቀጣጫ ፡ የሚሆን. A punitive raid was made by the rebels. ሽፍቶቹ ፡ ለመቀጣጫ ፡ የሚሆን ፡ ወረራ ፡ አደረጉ

**pupil**
1. ተማሪ. The pupils came late to class today. ዛሬ ፡ ተማሪዎቹ ፡ ዘግይተው ፡ ወደ ፡ ክፍል ፡ መጡ
2. (የዓይን) ፡ ብሌን ፤ (የዓይን) ፡ ብረት. The pupils of the cat's eyes dilate in the dark. የድመት ፡ የዓይን ፡ ብሌን ፡ (ብረት) ፡ በጨለማ ፡ ይሰፋል

**puppet** አሻንጉሊት
Have you read the story of Pinocchio who was a little wooden puppet? አፍንጮ ፡ የሚባለውን ፡ የትንሹን ፡ የዕንጨት ፡ አሻንጉሊት ፡ ታሪክ ፡ አንብበሃል ?
*The king was the puppet of his ministers. ንጉሡ ፡ በሚኒስትሮቹ ፡ እጅ ፡ ውስጥ ፡ ነበር

**puppet government** የሌላ ፡ መሣሪያ ፡ የሆነ ፡ መንግሥት
During Second World War, various puppet governments were set up. በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የሌሎች ፡ መሣሪያዎች ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ መንግሥታት ፡ ተቋቁመው ፡ ነበር

**puppy** (puppies) ቡችላ
I bought a puppy for my boy. ለልጄ ፡ ቡችላ ፡ ገዛሁለት

**purchase** (v.) ገዛ
I purchased the shoes in the market. ከገበያ ፡ ጫማ ፡ ገዛሁ

**purchase** (n.)
1. የገዛው ፡ እቃ. He filled his car with his purchases. መኪናውን ፡ በገዛው ፡ እቃ ፡ ሞላው
I have purchases to make. የምገዛው ፡ እቃ ፡ አለኝ
2. መግዛት. The prime minister announced the purchase of defensive weapons. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የመከላከያ ፡ መሣሪያዎች ፡ መግዛታቸውን ፡ አስታወቁ
3. ሸቀጥ. There is a tax on all purchases. በማንኛውም ፡ ሸቀጥ ፡ ላይ ፡ ቀረጥ ፡ ይጣላል

**pure**
1. ንጹሕ. Make sure that the water is pure before you drink it! ውኃውን ፡ ከመጠጣትህ ፡ በፊት ፡ ንጹሕ ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጥ
The necktie is pure silk. ክራቫቱ ፡ ንጹሕ ፡ ሐር ፡ ነው
2. የጠራ. He speaks pure Amharic. የጠራ ፡ አማርኛ ፡ ይናገራል
3. ፍጹም. That's pure nonsense. ያ ፡ ፍጹም ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ነገር ፡ ነው

**by pure luck** በእቦ ፡ ሰጡኝ
He won the race by pure luck. ውድድሩን ፡ በእቦ ፡ ሰጡኝ ፡ አሸነፈ

**(one's) heart is pure** ቅን ፡ ልቡና ፡ አለው
Everybody likes him because his heart is pure. ቅን ፡ ልቡና ፡ ስላለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይወደዋል

**purely**
1. በሞላ. This is purely an administrative job. ይህ ፡ በሞላ ፡ ያስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ነው
2. ያህል. I am doing this work purely to please you. ይህንን ፡ ሥራ ፡ የምሠራው ፡ አንተን ፡ ለማስደሰት ፡ ያህል ፡ ነው
3. እንዲያው. He came purely by accident. እንዲያው ፡ በድንገት ፡ መጣ

**purgative** የሚያስቀምጥ ፡ መድኃኒት
The doctor gave the child a purgative. ሐኪሙ ፡ ለልጁ ፡ የሚያስቀምጥ ፡ መድኃኒት ፡ ሰጠው

**be a purgative** ያስቀምጣል
This plant is supposed to be a purgative. ይህ ፡ ቅጠል ፡ ያስቀምጣል ፡ ይባላል

**purgatory** የንስሐ ፡ ቦታ
A soul must spend some time in purgatory. ነፍስ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በንስሐ ፡ ቦታ ፡ መቆየት ፡ አለባት

**purge**
1. አስቀመጠ. Did this medicine purge you? ይህ ፡ መድኃኒት ፡ አስቀመጠህ ?
2. በሙሉ ፡ አስወገደ. The mayor purged the city of slums. ከንቲባው ፡ ደሳሳዎቹን ፡ ቤቶቹ ፡ በሙሉ ፡ አስወገደ
He purged his cabinet of dissidents. ከካቢኔው ፡ ተቃዋሚዎቹን ፡ ሁሉ ፡ አስወገደ

**be purged** ነጻ
I feel purged of sin. ከኃጢአት ፡ የነጻሁ ፡ ይመስለኛል

**purge** (n.) የሚያስቀምጥ ፡ መድኃኒት
He took a purge to loosen his bowels. እንዲያስ ቀምጠው ፡ የሚያስቀምጥ ፡ መድኃኒት ፡ ወሰደ

**purification** ማጣራት
Purification of water is expensive. ውኃን ፡ ማ ጣራት ፡ ብዙ ፡ ወጪ ፡ ይጠይቃል

**purified** (adj.) የተጣራ
We drink purified water. የተጣራ ፡ ውኃ ፡ እ ንጠጣለን

**purify** (purified) አጠራ
We need something to purify the air. አየሩን ፡ ለ ማጥራት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ያስፈልገናል

**purist** የቋንቋ ፡ ጥራት ፡ ደጋፊ
Purists reject foreign words. የቋንቋ ፡ ጥራት ፡ ደ ጋፊዎች ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቃላትን ፡ አይቀበሉም

**purity**
1. ንጹሕ ፡ መሆን. The purity of this water is doubtful. ይህ ፡ ውኃ ፡ ንጹሕ ፡ መሆኑ ፡ ያጠራ ጥራል
2. ንጽሕና. The dove is the symbol of purity. ርግብ ፡ የንጽሕና ፡ ምልክት ፡ ናት

**purple** የወይን ፡ ጠጅ
My sister likes purple sweaters. እኅቴ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ሹራብ ፡ ትወዳለች

**purport** (v.) ተባለ
This book purports to be written by an Ethiopian. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ የተ ጻፈ ፡ ነው ፡ ይባላል
This is a book that purports to give the true facts. እውነተኛውን ፡ ጉዳይ ፡ ይዟል ፡ የሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው

**purport** (n.) ፍሬ ፡ ነገር
The purport of her letter was that she could not come. የደብዳቤው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ አለመም ጣቷን ፡ የሚገልጽ ፡ ነበር

**purpose**
1. ጉዳይ. This machine can be used for various purposes. ይህ ፡ መሣሪያ ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉ ዳዮች ፡ ያገለግላል
2. ፍላጎት. Will this answer your purpose? ይህ ፡ ፍላጎትህን ፡ ያረካልሃል ?
3. ያሰበው ፤ ዓላማ. He has achieved his purpose. ያሰበውን ፡ (ዓላማውን) ፡ ከግቡ ፡ አደረሰ
*What's the purpose of all these plans? ይህ ፡ ሁሉ ፡ እቅድ ፡ ለምንድን ፡ ነው ?

**for the purpose of** ሲል
I won't go to London just for the purpose of buying clothes. ልብስ ፡ ለመግዛት ፡ ስል ፡ ብቻ ፡ ለንደን ፡ አልሄድም

**on purpose**
1. ሆን ፡ ብሎ. I left my coat home on purpose. ኮቴን ፡ እቤቴ ፡ የተውኩት ፡ ሆን ፡ ብዬ ፡ ነው
2. ዐውቆ. Did you do that on purpose? ያንን ፡ ያደረግኸው ፡ ዐውቀህ ፡ ነው ?
3. ለ + (imperfect). He came here on purpose to borrow money from you. የመጣው ፡ ገንዘብ ፡ ካንተ ፡ ሊበደር ፡ ነው

**serve the purpose** ለጉዳዩ ፡ ተስማማ
The solution was not according to the book, but it served the purpose. የችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ ደንቡን ፡ ባይከተልም ፡ ለጉዳዩ ፡ ተስማምቷል

**to no purpose** እንዲያው
It is to no purpose to hold class the day before Christmas. ለልደት ፡ ዋዜማ ፡ ለማስተማር ፡ መሞከር ፡ እንዲያው ፡ ነው
[See also 'intent, sole']

**purposely** ሆን ፡ ብሎ
He purposely opened the door. ሆን ፡ ብሎ ፡ በሩን ፡ ከፈተ

**purr** አንኳራፋ
The cat purred contentedly on my lap. ድመ ቷ ፡ ተደስታ ፡ በጭኔ ፡ ላይ ፡ ተኝታ ፡ ታንኳራ ፋ ፡ ነበር

**purse** (v.) አሞጠሞጠ
I pursed my lips to whistle. ለማፏጨት ፡ ከንፈ ሬን ፡ አሞጠሞጥኩ

**purse** (n.) ቦርሳ
She lost her purse. ቦርሳዋ ፡ ጠፋባት

**purser** [የመርከብ ፡ ወይም ፡ ያውሮፕላን ፡ ገንዘብ ፡ ያዥ]

**pursuance, in ~**
*In pursuance of my goal, I intend to go to school. ካሰብኩት ፡ ለመድረስ ፡ እንድችል ፡ ትምህር ት ፡ ቤት ፡ ለመግባት ፡ አስባለሁ ፡

**pursuant to** በ --- መሠረት
He will leave now, pursuant to our plans. በእቅዳችን ፡ መሠረት ፡ እሱ ፡ አሁን ፡ ይነሣል
Pursuant to his studies, he took a job in our office. በትምህርቱ ፡ መሠረት ፡ እመሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ ተቀጠረ

**pursue**

1. ተከታተለ. The police pursued the robber. ፖሊሶቹ ፡ ቀማኛውን ፡ ተከታተሉት
I don't want to pursue the subject any further. ነገሩን ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ልከታተለው ፡ አልፈልግም
His reputation as a thief pursued him wherever he went. በሌብነት ፡ ያገኘው ፡ ስም ፡ በየሄደበት ፡ ተከታተለው
2. አሳደደ. The hunters pursued their quarry to no avail. አዳኞቹ ፡ የሚያድኑትን ፡ እንስሳ ፡ በከንቱ ፡ አሳደዱ
3. አስቸገረ. The boy pursued his father with questions. ልጁ ፡ አባቱን ፡ በጥያቄ ፡ አስቸገረው
4. ሞከረ. She pursues pleasure, but does not seem to be happy. ለመደሰት ፡ ብትሞክርም ፡ የምትደሰት ፡ አትመስልም

**pursuer** አባራሪ
His pursuers closed rapidly. አባራሪዎቹ ፡ በፍጥነት ፡ ተቃረቡት

**pursuit** መከታተል
Pursuit of study requires money. ትምህርትን ፡ መከታተል ፡ ገንዘብ ፡ ይጠይቃል
The pursuit of the robbers was exhausting. ቀማኞቹን ፡ መከታተል ፡ አድካሚ ፡ ነበር

**(be) purulent** መግል ፡ ቋጠረ
The boil is purulent. ቡጉንጁ ፡ መግል ፡ ቋጠረ

**purvey** አቀረበ
This canning factory purveys meat for the army. ይህ ፡ የሥጋ ፡ ፋብሪካ ፡ ለጦር ፡ ሰራዊት ፡ ሥጋ ፡ ያቀርባል

**pus** መግል
The wound has pus. ቁስሉ ፡ መግል ፡ ይዟል
**discharge pus** መገለ
The wound discharges pus. ቁስሉ ፡ ይመግላል
**squeeze the pus from** አፈረጠ
Squeeze the pus from this pimple! ይህን ፡ ብጉር ፡ አፍርጠው

**push** (vt.)

1. ገፋ. Push the table over by the window! ጠረጴዛውን ፡ ወደ ፡ መስኮቱ ፡ ግፋው
2. ገፋ(በት). He pushed his plans strongly. ሐሳቡን ፡ በርትቶ ፡ ገፋበት
3. ተጫነ. Did you push the button? ቁልፉን ፡ ተጭነኸዋል ?
4. ሰደደ. Trees push their roots down into the ground. ዛፎች ፡ ሥራቸውን ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ ይሰዳሉ
5. ገፋፋ. He pushed the men to work harder. ሰዎቹን ፡ በኀይል ፡ እንዲሠሩ ፡ ገፋፋቸው

**push** (vi.) ተጨናንቆ ፡ ገባ
The crowd pushed into the elevator. የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ አሳንሰሩ ፡ ውስጥ ፡ ተጨናንቆ ፡ ገባ
**push around** እንዳሰኘ(ው) ፡ አደረገ
His wife pushes him around. ሚስቱ ፡ እንዳሰኛት ፡ ታደርገዋለች
**push for** አጣደፈ
He pushed me for payment. እንድከፍል ፡ አጣደፈኝ
**push off**
*It's time we pushed off. የመሄጃችን ፡ ጊዜ ፡ ደርሷል
**push on** ገሰገሰ
It's getting dark, but we must push on to our destination. እየጨለመ ፡ ስለሄደ ፡ ወደፊት ፡ መገስገስ ፡ አለብን
**push oneself forward**
He never pushes himself forward. ዕወቁኝ ፡ ባይ ፡ አይደለም
**push out** ነቅሎ ፡ ጣለ
The blast pushed out the window. የፈንጂው ፡ ኀይል ፡ መስኮቱን ፡ ነቅሎ ፡ ጣለው
**push over** ገፍቶ ፡ ጣለ
Don't push me over! ገፍተህ ፡ እንዳትጥለኝ
**push through** በ --- ገፋ
We must push the matter through. በጉዳዩ ፡ መግፋት ፡ አለብን
**push (one's) way through** እየተጋፋ ፡ ሄደ
He pushed his way through the crowd. በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መሀከል ፡ እየተጋፋ ፡ ሄደ

**push**, n. (= verbal noun) መግፋት
A hard push is needed to open the door. በሩን ፡ ለመክፈት ፡ በጣም ፡ መግፋት ፡ ያስፈልጋል
**have push**
*He hasn't enough push to succeed. ትጋት ፡ ስለሚጐድለው ፡ አይቃናለትም
**make a push** ገፋ
The enemy made a push on the western front. በምዕራቡ ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ በኩል ፡ ጠላት ፡ ገፍቷል

**pusillanimous** ፈሪ
He is so pusillanimous that he will not react to any insult. በጣም ፡ ፈሪ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ሲሰድቡት ፡ ዝም ፡ ይላል

**put** (put)

1. አስቀመጠ. Where shall I put the trunks? ሣጥኖቹን ፡ የት ፡ ላስቀምጣቸው ?

Put the bottle on the shelf! ጠርሙሱን ፡ በመደርደሪያው ፡ ላይ ፡ አስቀምጠው
2. አደረገ. Put the table over there! ጠረጴዛውን ፡ እዚያ ፡ ጋ ፡ አድርገው
3. አስደገፈ. They put the log against the wall. ግንዱን ፡ አግድግዳው ፡ ላይ ፡ አስደገፉት
4. አስገባ. He put a new handle on the knife. ለቢላዋው ፡ አዲስ ፡ እጀታ ፡ አስገባለት
After the farmer put the cattle in the pen, he bolted the gate. ገበሬው ፡ ከብቶቹን ፡ በረት ፡ ውስጥ ፡ ካስገባቸው ፡ በኋላ ፡ በሩን ፡ ቀረቀረው
5. ጨመረ. Did you put milk in my coffee? ቡናዬ ፡ ውስጥ ፡ ወተት ፡ ጨመርክ ?
6. ከተተ. Put the dagger in its sheath! ሳንጃውን ፡ አፎቱ ፡ ውስጥ ፡ ከተተው
7. አቀረበ. You have put the case very clearly. ጉዳዩን ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ አቅርበኸዋል
8. አስረዳ. The teacher puts things clearly. አስተማሪው ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ በግልጽ ፡ ያስረዳል
9. አለ. How would you put this in Amharic? ይህን ፡ ባማርኛ ፡ እንዴት ፡ ትለዋለህ ?
*Let me put it to you this way : either you work harder or you will be fired. እንግዲህ ፡ ልንገርህ ፡ በደንብ ፡ ሥራ ፤ ያለበለዚያ ፡ ትባረራለህ

**put across** አስረዳ
I don't know how to put it across to him, that .... ምን ፡ ብዬ ፡ እንደማስረዳው ፡ አላውቅም

**put against** ጥግ ፡ አደረገ
Put the chair against the wall! ወንበሩን ፡ ግድግዳው ፡ ጥግ ፡ አድርገው

**put around**
She put her arms around him. ተጠመጠመችበት

**put around the waist** ታጠቀ
He put the cartridge belt around his waist. ዝናሩን ፡ ታጠቀ

**put aside**
1. አስቀመጠ. Can you put the tie aside for me until tomorrow? ክራቫቱን ፡ እስከነገ ፡ ድረስ ፡ ልታስቀምጥልኝ ፡ ትችላለህ ?
She has been putting aside a little money each month. በየወሩ ፡ ትንሽ ፡ ገንዘብ ፡ ታስቀምጥ ፡ ነበር
2. ወዲያ ፡ አስቀመጠ. Put the book aside! መጽሐፉን ፡ ወዲያ ፡ አስቀምጠው

**put at**
*I would put her age at not more than sixty. ዕድሜዋ ፡ ከስልሳ ፡ የሚበልጥ ፡ አይመስለኝም

**put away** አስቀመጠ
Put my Sunday clothes away in a large box! የክት ፡ ልብሶቼን ፡ ትልቅ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጣቸው

**(be) put away** ተቀመጠ
The money was put away for his education. ገንዘቡ ፡ የተቀመጠው ፡ ለሱ ፡ መማሪያ ፡ እንዲሆን ፡ ነበር

**put back**
1. መለሰ. Put the book back where you got it! መጽሐፉን ፡ አነሣህበት ፡ ቦታ ፡ መልሰው
2. ወደኋላ ፡ መለሰ. She put back the clock one hour. ሰዓቱን ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ወደኋላ ፡ መለሰችው
3. ቀነሰ. The strike at the factory put back production. የሠራተኞቹ ፡ ማደም ፡ ፋብሪካው ፡ የሚያወጣውን ፡ እቃ ፡ ብዛት ፡ ቀነሰ

**put down**
1. አወረደ. Do you want to put the box down here? ሣጥኑን ፡ እዚህ ፡ ልታወርደው ፡ ትፈልጋለህ ?
2. ጻፈ. Put down your name and address! ስምህን ፡ ከነአድራሻህ ፡ ጻፍ
3. መዘገበ. Put me down for five dollars! ላምስት ፡ ብር ፡ መዝግበኝ
4. ደመሰሰ. They put down the rebellion by force. ዐመፁን ፡ በኀይል ፡ ደመሰሱት

**(be) put down to**
*His disease was put down to drinking. የበሽታው ፡ ምክንያት ፡ መጠጥ ፡ ነው ፡ ተባለ

**put (an) end to** አቆመ
I will have to put an end to that nonsense. ያን ፡ የማይረባ ፡ ነገር ፡ ማቆም ፡ አለብኝ
*He put an end to his life. ሕይወቱን ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ አጠፋ

**put forth** አወጣ
The plants put forth new shoots. ዕፀዋት ፡ እምቡጥ ፡ አወጡ

**put forth new leaves** አቈጠቈጠ
The trees put forth new leaves. ዛፎቹ ፡ አቈጠቈጡ

**put forward**
1. አቀረበ. He put forward a new theory. አዲስ ፡ ዕንሰ ፡ ሐሳብ ፡ አቀረበ
2. አስቀደመ. Put the clock forward one hour! ሰዓቱን ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ አስቀድመው

**put in**
1. አስገባ. They put in a new windowpane today. ዛሬ ፡ ለመስኮቱ ፡ አዲስ ፡ መስታወት ፡ አስገቡለት
2. አስቀመጠ(በት). I need a huge box to put the dishes in. ሳሕኖችን ፡ የማስቀምጥበት ፡ ትልቅ ፡ ሣጥን ፡ ያስፈልገኛል
3. ገባ ፡ አደረገ. He put his head in at the window. ራሱን ፡ በመስኮቱ ፡ ገባ ፡ አደረገ

4. አጠፋ. They put in a lot of time on that job. በዚያ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አጥፍተዋል
5. ማመልከቻ ፡ አቀረበ. I'm putting in for a transfer. ለዝውውር ፡ ማመልከቻ ፡ አቅርቤያለሁ
6. ጠየቀ. He put in a claim for damages. ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ካሳ ፡ ጠየቀ

**put in mind of** አስታወሰ
This place puts me in mind of Addis Ababa. ይህ ፡ ቦታ ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ ያስታውሰኛል

**put into one's hand** በሙሉ ፡ ለሱ ፡ ተወ(ለት)
I put my affairs into his hands. ጉዳዬን ፡ በሙሉ ፡ ለሱ ፡ ተውኩለት

**put off**
1. አስተላለፈ. I can't put the matter off any longer. ነገሩን ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ላስተላልፈው ፡ አልችልም
2. አዘገየ. He hoped to gain time by putting off signing the papers for a few days more. ወረቀቶቹን ፡ መፈረሙን ፡ ለጥቂት ፡ ቀናት ፡ በማዘግየት ፡ ጊዜ ፡ ለማግኘት ፡ ተስፋ ፡ አደረገ
3. ወዘፈ. Putting things off is her weakness. የሷ ፡ ጉድለት ፡ ሥራ ፡ መወዘፏ ፡ ነው
*When I ask her for payment, she puts me off with promises. እንድትከፍለኝ ፡ ስጠይቃት ፡ እሺ ፡ ነገ ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ታልፈኛለች

**put off (for)** ተነሣ
The Mayflower put off for America from England in 1620.ሜይፍላወር ፡ የተባለችው ፡ መርከብ ፡ በ፲፮፻፳ ዓ.ም. ወደ ፡ አሜሪካ ፡ ለመምጣት ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ተነሣች

**put on**
1. ክብደት ፡ ጨመረ. I have put on three kilos. ሦስት ፡ ኪሎ ፡ ክብደት ፡ ጨምሬያለሁ
2. ለበሰ. Which dress shall I put on? የትኛውን ፡ ልብስ ፡ ልልበስ ?
3. አለበሰ. Put on a clean tablecloth! ንጹሕ ፡ የጠረጴዛ ፡ ልብስ ፡ አልብስ
4. አደረገ. He put on his glasses. መነጽሩን ፡ አደረገ
Put your hat on! ባርኔጣህን ፡ አድርግ
Put your shoes on! ጫማህን ፡ አድርግ
Put on another record! ሌላ ፡ ሸክላ ፡ አድርግ
5. አጠለቀ. The mother asked the child to put on his trousers. እናቲቱ ፡ ልጁን ፡ ሱሪሀን ፡ እጥልቅ ፡ አለችው
6. አሳየ. The students put on a play. ተማሪዎቹ ፡ ቲያትር ፡ አሳዩ
7. ጣደ. Put the kettle on! ጀበናውን ፡ ጣደው

**(be) put on** ለይምሰል ፡ ነው
The girl's crying is put on. ልጂቱ ፡ የምታለቅሰው ፡ ለይምሰል ፡ ነው

**put out**
1. አወጣ. They put out a series of new books. አዳዲስ ፡ ተከታታይ ፡ መጻሕፍትን ፡ ያወጣሉ
The rude girl put her tongue out at a friend. ባለጌዋ ፡ ልጅ ፡ በጓደኛዋ ፡ ላይ ፡ ምላሷን ፡ አወጣች
2. አስወጣ. Don't make noise, or they'll put you out. አትጩህ ፤ ያለዚያ ፡ ያስወጡሃል
3. ዘረጋ. The hungry man put out his hand begging for money. የተራበው ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ለመና ፡ እጁን ፡ ዘረጋ
4. አጠፋ. Put out the light before you leave! ከመሄድህ ፡ በፊት ፡ መብራቱን ፡ አጥፋው
Put your cigarette out! ሲጃራህን ፡ አጥፋ

**put (one) out** አስቸገረ
Will it put you out to give me a lift home? በመኪና ፡ እቤቴ ፡ ብታደርሰኝ ፡ ያስቸግርሃል ?

**(be) put out**
1. ጠፋ. The fire was put out quickly. እሳቱ ፡ ቶሎ ፡ ጠፋ
2. ቅር ፡ ተሰኘ. He was put out to find that no one was listening to him. ማንም ፡ ስላላዳመጠው ፡ ቅር ፡ ተሰኘ

**put over the top** ከደነ
Put something over the top of the jar to keep out the flies! ማሰሮው ፡ ውስጥ ፡ ዝንቦች ፡ እንዳይገቡ ፡ ምናምን ፡ ክደነው

**put through** አጣራ
It took him six weeks to put his application through. ማመልከቻውን ፡ ለማጣራት ፡ ስድስት ፡ ሳምንት ፡ ፈጀበት

**(be) put to** ዋለ
The money will be put to good use. ገንዘቡ ፡ ለደኅና ፡ ነገር ፡ ይውላል

**(be hard) put to** ፈጽሞ ፡ አልቻለም
I'm hard put to pay my bills. ዕዳዬን ፡ መክፈል ፡ ፈጽሞ ፡ አልችልም

**put together**
1. አገጣጠመ. Can you put the pieces together? ቁርጥራጮቹን ፡ ልታገጣጥም ፡ ትችላለህ ?
2. ጐን ፡ ለጐን ፡ አደረገ. Put them together and see which is larger! ጐን ፡ ለጐን ፡ አድርጋቸውና ፡ የቱ ፡ እንደሚበልጥ ፡ ተመልከት

**put up**
1. አወጣ. I'll supply the material if you put up ten thousand dollars. ዐሥር ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ካወጣህ ፡ እኔ ፡ እቃውን ፡ አቀርባለሁ
2. አነሣ. Put up your hands! እጅህን ፡ አንሣ
3. ለጠፈ. They put up a notice that the house

was sold. ቤቱ ፡ መሸጡን ፡ የሚገልጽ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለጠፉ

*We can put you up for a week. ላንድ ፡ ሳምንት ፡ እኛ ፡ ጋ ፡ ልታርፍ ፡ ትችላለህ

**(be) put up**

1. ተሠርቶ ፡ አለቀ. The building was put up in six months. ሕንጻው ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ተሠርቶ ፡ አለቀ

2. ተተከለ. New telephone poles are being put up. አዲስ ፡ የስልክ ፡ ምሰሶች ፡ በመተከል ፡ ላይ ፡ ናቸው

3. ቀረበ. The oxen will be put up for sale this week. በሬዎቹ ፡ በዚህ ፡ ሳምንት ፡ ለገበያ ፡ ይቀርባሉ

**put (one) up to** አነሣሣ

His friends put him up to asking the boss for a raise. አለቃውን ፡ የደሞዝ ፡ ጭማሪ ፡ እንዲጠይቅ ፡ ጓደኞቹ ፡ አነሣሡት

**put up with**

*I can't put up with his impudence any longer. ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ስድቡን ፡ ችዬ ፡ ለመኖር ፡ አልችልም

[See also numerous nouns combined with 'put']

**putrefy** (putrefied) ሸተተ

Meat will putrefy if not put into the icebox. በረዶ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ካልተቀመጠ ፡ ሥጋ ፡ ይሸታል

**putrescent** የገማ

It is not wise to eat putrescent meat. የገማ ፡ ሥጋ ፡ መብላት ፡ ጥሩ ፡ አይደለም

**(be) putrid** ገማ

This meat is putrid, so don't eat it! ይህ ፡ ሥጋ ፡ ስለገማ ፡ አትብላው

**puzzle** (v.)

1. አደናገረ. The speaker's ambiguous words puzzled the audience. የተናጋሪው ፡ አሻሚ ፡ ቃላት ፡ አዳማጮቹን ፡ አደናገሯቸው

2. አስገረመ. The speaker's ironical smile puzzled the audience. የተናጋሪው ፡ የዘበት ፡ ፈገግታ ፡ አዳማጮቹን ፡ አስገረማቸው

3. ግራ ፡ አጋባ. The technicality of the book puzzled me. የመጽሐፉ ፡ የረቀቀ ፡ አገላለጽ ፡ ግራ ፡ አጋባኝ

**be puzzled** ግራ ፡ ገባ(ው)

He was puzzled as to what to do next. ቀጥሎ ፡ ምን ፡ እንደሚያደርግ ፡ ግራ ፡ ገብቶት ፡ ነበር

**puzzle** (n.) እንቆቅልሽ

That is a puzzle for me. ይህ ፡ ለኔ ፡ እንቆቅልሽ ፡ ነው

*It's a puzzle to me how he got there so quickly. እዚያ ፡ እንዴት ፡ ቶሎ ፡ እንደደረሰ ፡ ገርሞኛል

**pyjamas**, see **pajamas**

**pyramid** ፒራሚድ

The pyramids of Egypt are ancient. የግብጽ ፡ ፒራሚዶች ፡ የጥንት ፡ ናቸው

**python** ዘንዶ

Are there pythons in Ethiopia? ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ዘንዶ ፡ አለ ?

# Q

**quack** (v.) አስካካ
The ducks quacked loudly. ዳክዬዎች ፡ ጮክ ፡ ብለው ፡ አስካኩ

**quack** (n.) አጭበርባሪ
That doctor is not a real one but a quack. አጭበርባሪ ፡ እንጂ ፡ እርግጠኛ ፡ ሐኪም ፡ አይደለም

**quadrangle** አራት ፡ ማእዘን
The breakfast table has the form of a quadrangle. የቁርስ ፡ ጠረጴዛችን ፡ ቅርጹ ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ ነው
*The room is in the form of a quadrangle. ቤቱ ፡ ስቀላ ፡ ነው

**quadrant** የክበብ ፡ ሩብ

**quadrilateral** [አራት ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ ቅርጽ]

**quadruped** አራት ፡ እግር ፡ ያለው ፡ እንስሳ
Quadrupeds can move faster than animals having only two feet. አራት ፡ እግር ፡ ያላቸው ፡ እንስሳት ፡ ሁለት ፡ እግር ፡ ካላቸው ፡ እንስሳት ፡ ይፈጥናሉ

**quadruple** (v.) በአራት ፡ ዕጥፍ ፡ ከፍ ፡ አለ
The population of the city has quadrupled. የከተማው ፡ ነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ በአራት ፡ ዕጥፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏል

**quadruple** (adj.) ባለአራት
A quadruple wire enables us to have four telephones. ባለአራት ፡ ሽቦ ፡ መሥመር ፡ አራት ፡ ስልክ ፡ ለማግባት ፡ ያስችለናል

**quadruplet** [ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተወለዱ ፡ አራት ፡ ሕፃናት ፡ መካከል ፡ አንዱ]

**quaint**
Americans like to visit quaint English villages. አሜሪካኖች ፡ ጥንታዊነት ፡ ያለባቸውን ፡ ደስ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንደሮችን ፡ መጐብኘት ፡ ይወዳሉ

**quake** (v.) ተንቀጠቀጠ
The ground quaked. መሬቱ ፡ ተንቀጠቀጠ

**quake** (n.) የመሬት ፡ መንቀጥቀጥ
They reconstructed the town after the quake. ከመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ በኋላ ፡ ከተማውን ፡ እንደገና ፡ ሠሩት

**qualification**
1. ጉድለት. His pleasure had one qualification : his friends could not enjoy it. ደስታው ፡ አንድ ፡ ጉድለት ፡ አለበት ፤ ይኸውም ፡ ጓደኞቹ ፡ የማይካፈሉበት ፡ ነው
2. ገደብ. You can accept his statement without qualification. እሱ ፡ የሚለውን ፡ ያላንዳች ፡ ገደብ ፡ ልትቀበለው ፡ ትችላለህ

**qualifications**
1. ብቁነት. He has the qualifications to become a doctor. ሐኪም ፡ ለመሆን ፡ ብቁነት ፡ አለው
2. ችሎታ. Do you think she has the necessary qualifications for the job? ለሥራው ፡ የሚያስፈልገው ፡ ችሎታ ፡ ሁሉ ፡ ያላት ፡ ይመስልሃል ?

**qualified** (adj.)
1. ብቁ. He is not qualified for this job. ለዚህ ፡ ሥራ ፡ ብቁ ፡ አይደለም
2. ገደብ ፡ ያለው. His qualified answer was "I will go, but only if you will come with me". ገደብ ፡ ያለው ፡ መልሱ ፤ « እሄዳለሁ ፤ ግን ፡ አንተ ፡ አብረኸኝ ፡ የምትመጣ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው » ፡ የሚል ፡ ነበር

**qualify** (qualified)
1. አበቃ. His work qualifies him for promotion. ሥራው ፡ ለደረጃ ፡ እድገት ፡ ያበቃዋል
2. ፈቀደ(ለት). His license qualifies him to drive a car. የመንጃ ፡ ፈቃዱ ፡ መኪና ፡ እንዲነዳ ፡ ይፈቅድለታል
3. ገደብ ፡ አበጀ(ለት). He qualified his statement that boys are lazy by saying that some of them are not. ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ሰነፎች ፡ ናቸው ፡ ያለውን ፡ አንዳንዶቹ ፡ አይደሉም ፡ በማለት ፡ ገደብ ፡ አበጀለት

**qualify oneself** ራሱን ፡ አበቃ
He qualified himself to become a teacher by going to night school. ማታ ፡ ማታ ፡ እየተማረ ፡ ራሱን ፡ ለመምህርነት ፡ ሥራ ፡ አበቃ

**quality** (qualities)
1. ዓይነት. Don't you have any better quality? ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ዓይነት ፡ የለህም ?

2. ችሎታ. He has the quality of inspiring confidence. ሰዎች ፡ እምነት ፡ እንዲጥሉበት ፡ የማድረግ ፡ ችሎታ ፡ አለው
3. ጥሩነት ፤ ተመራጭነት. We guarantee the quality of our product. ለምንሠራቸው ፡ እቃዎች ፡ ጥሩነት ፡ (ተመራጭነት) ፡ ኀላፊ ፡ ነን
4. ነገር. She has many good qualities. ብዙ ፡ የሚወደድ ፡ ነገር ፡ አላት
[See also 'mean, poor']

**qualm** ጸጸት
The thief had no qualms about taking the money. ሌባው ፡ ገንዘቡን ፡ በመውሰዱ ፡ ጸጸት ፡ አልተሰማውም

**with some qualms** ደንገጥ ፡ ብሎ
I took the test with some qualms. ፈተናውን ፡ ስሠራ ፡ ደንገጥ ፡ ብዬ ፡ ነበር

**quandary, be in a ~** አወላወለ
I was in a quandary whether to marry her or to finish my education first. እሷን ፡ ከማግባትና ፡ ትምህርቴን ፡ ከመጨረስ ፡ የትኛውን ፡ እንደምመርጥ ፡ አወላውል ፡ ነበር

**quantity** (quantities)
1. ብዛት. It's not the quantity, but the quality that counts. የሚታየው ፡ ብዛቱ ፡ ሳይሆን ፡ ዓይነቱ ፡ ነው
2. መጠን. Evaporation reduces the quantity of water available to the farm. ተን ፡ እርሻ ፡ የሚያገኘውን ፡ የውኃ ፡ መጠን ፡ ይቀንሳል

**quantities of** ብዙ
She owns quantities of books. ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ አላት

**equal quantities of** እኩል
Use equal quantities of nuts and raisins in the cake! ብስኩቱ ፡ ውስጥ ፡ እኩል ፡ ለውዝና ፡ ዘቢብ ፡ ጨምርበት

**in large quantities** በብዛት
Radios are now produced in large quantities. ራዲዮን ፡ አሁን ፡ በብዛት ፡ ይሠራል

**(a) small quantity** ጥቂት
There is only a small quantity left. ጥቂት ፡ ቀርቷል

**what quantity** ምን ፡ ያህል
What quantity do you want? ምን ፡ ያህል ፡ ትፈልጋለህ ?

**quarantine** (n.) የተገለለ ፡ ቦታ
The cows were kept in quarantine for three months. ላሞቹ ፡ በተገለለ ፡ ቦታ ፡ ለሦስት ፡ ወር ፡ እንዲቆዩ ፡ ተደረገ
*A quarantine was imposed on the passengers of the ship. የመርከቡ ፡ መንገደኞች ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከመርከብ ፡ እንዳይወርዱ ፡ ታግደው ፡ ነበር

**quarrel** (v.) ተጣላ
The thieves quarreled about how to divide the loot. ሌቦቹ ፡ የሰረቁትን ፡ እንዴት ፡ እንደሚከፋፈሉ ፡ ተጣሉ

**quarrel** (n.)
1. ጥል ፤ ጠብ. The quarrel ended in bloodshed. ጥሉ ፡ (ጠቡ) ፡ ከደም ፡ መፋሰስ ፡ አደረሰ
I have no quarrel with you. ካንተ ፡ ጋር ፡ ጠብ ፡ የለኝም
2. አለመግባባት. Instead of fighting, the two nations settled their quarrels in an amicable way. ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ በመካከላቸው ፡ ስለነበረው ፡ አለመግባባት ፡ ከመዋጋት ፡ ይልቅ ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ ከስምምነት ፡ ደረሱ

**pick a quarrel** ጠብ ፡ ጫረ
With whom does he pick a quarrel? ከማን ፡ ጋር ፡ ጠብ ፡ ይጭራል ?

**quarrelsome**
1. ጠበኛ. Is it human nature to be quarrelsome and suspicious? ጠበኛና ፡ ተጠራጣሪ ፡ መሆን ፡ የሰው ፡ ተፈጥሮ ፡ ነው ?
2. ነጭናጫ. She squelched the quarrelsome child. ነጭናጫውን ፡ ልጅ ፡ ወዲያውኑ ፡ ዝም ፡ አሰኘችው

**quarry** (v.) ፈለጠ
They quarry marble for monuments. ለሐውልቱ ፡ መሥሪያ ፡ እብነ ፡ በረድ ፡ ይፈልጣሉ

**quarry** (quarries), n.
1. (የድንጋይ) ፡ መፍለጫ ፡ ቦታ. The stone quarry is five miles from here. የድንጋይ ፡ መፍለጫው ፡ ቦታ ፡ ከዚህ ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ ይርቃል
2. የሚያድነው ፡ እንስሳ. The hunters pursued their quarry to no avail. አዳኞቹ ፡ የሚያድኑትን ፡ እንስሳ ፡ በከንቱ ፡ ሲያሳድዱ ፡ ዋሉ

**quart**
[አንድ ፡ ሊትር ፡ ያህል ፡ የሚይዝ ፡ የፈሳሽ ፡ መለኪያ]

**quarter** (v.) ለአራት ፡ ከፈለ
Mother quartered the apple. እናትዮዋ ፡ ቱፋውን ፡ ለአራት ፡ ከፈለችው

**be quartered** ተመራ
The troops are quartered in the town. ወታደሮቹ ፡ ከተማው ፡ ውስጥ ፡ ተመሩ

**quarter** (n.)
1. ሩብ. He traveled a mile and a quarter before sun-up. ፀሐይ ፡ ከመውጣቷ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ማይል ፡ ከሩብ ፡ ተጓዘ
The store is a quarter of a mile from here. ሱቁ ፡ ከዚህ ፡ ሩብ ፡ ማይል ፡ ይርቃል
Each partner received a quarter of the profits. እያንዳንዱ ፡ ሽርካ ፡ ከትርፉ ፡ ሩቡን ፡ ወሰደ
2. የተለየ ፡ ሰፈር. San Francisco has a Chinese quarter. ሳን ፡ ፍራንሲስኮ ፡ የተለየ ፡ የቻይኖች ፡ ሰፈር ፡ አለው
3. ስሙኒ. I need four quarters. አራት ፡ ስሙኒ ፡ እፈልጋለሁ
4. ርኅራኄ. They showed the enemy no quarter. ለጠላት ፡ ምንም ፡ ርኅራኄ ፡ አላሳዩም

**quarters**
1. ሰፈር. All soldiers are to return to quarters at once. ወታደሮች ፡ ሁሉ ፡ አሁኑኑ ፡ ወደየሰፈራቸው ፡ እንዲመለሱ
2. ማረፊያ. Our quarters are in a small hotel. ማረፊያችን ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ሆቴል ፡ ውስጥ ፡ ነው
3. ቤት. He showed me the servants' quarters. ያሽከር ፡ ቤቱን ፡ አሳየኝ

**quarter after three** ዘጠኝ ፡ ተሩብ
It's a quarter after three already. ዘጠኝ ፡ ተሩብ ፡ ሆኗል

**quarter to three** ለዘጠኝ ፡ ሩብ ፡ ጉዳይ
The train leaves at a quarter to three. ባቡሩ ፡ ለዘጠኝ ፡ ሩብ ፡ ጉዳይ ፡ ይነሣል

**from all quarters of the world** ከመላው ፡ ዓለም
When President Kennedy died, men came from all quarters of the world to attend his funeral. ፕሬዚዳንት ፡ ኬኔዲ ፡ ሲሞቱ ፡ በቀብር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓታቸው ፡ ላይ ፡ ለመገኘት ፡ ከመላው ፡ ዓለም ፡ ሰዎች ፡ መጡ
[See also 'close quarters']

**quarterly** (n.) የየሦስት ፡ ወር ፡ መጽሔት
Our university publishes a quarterly. ዩኒቨርሲቲያችን ፡ በየሦስት ፡ ወር ፡ መጽሔት ፡ ያወጣል

**quarterly** (adv.) በየሦስት ፡ ወር
I pay my insurance quarterly. የሕይወት ፡ ዋስትናዬን ፡ በየሦስት ፡ ወር ፡ እከፍላለሁ

**quartermaster** መጋቢ
He is a quartermaster sergeant. መጋቢ ፡ የጎምሳ ፡ አለቃ ፡ ነው

**quartet** [አራት ፡ መዘምራን ፡ ወይም ፡ ተጫዋቾች ፡ የሚገኙበት ፡ የሙዚቃ ፡ ጓድ]

**quartz** [በጣም ፡ ጠንካራ ፡ የሆነ ፡ እብነ ፡ በረድ ፡ የሚመስል ፡ ብልጭልጭ ፡ ድንጋይ]

**quash**
1. ደመሰሰ. The troops quashed the revolt. የተደረገውን ፡ ዐመፅ ፡ ወታደሮቹ ፡ ደመሰሱት
2. ሰረዘ. The judge quashed the charges against the prisoner. ዳኛው ፡ በእስረኛው ፡ ላይ ፡ የቀረበውን ፡ ክስ ፡ ሰረዘ

**quasi-** ቢጤ
He has a quasi-ministerial position. የሚኒስትርነት ፡ ደረጃ ፡ ቢጤ ፡ አለው

**quaver** ተርገበገበ
The old man's voice quavered when he spoke. ሽማግሌው ፡ ሲናገር ፡ ድምፁ ፡ ተርገበገበ

**queen** ንግሥት
The queen died recently. ንግሥቲቷ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ
[See also 'bee']

**queenly** የንግሥት
She has a queenly carriage. የንግሥት ፡ ዛላ ፡ አላት

**queer**
1. የሚገርም. It's queer that he did not come to class today. ዛሬ ፡ ወደ ፡ ክፍል ፡ አለመምጣቱ ፡ የሚገርም ፡ ነው
2. እንግዳ. His queer behavior occasioned a good deal of talk. የሱ ፡ እንግዳ ፡ ጠባይ ፡ ብዙ ፡ ጨዋታ ፡ አስነሣ
3. ጠባዩ ፡ የማይታወቅ. He is a queer person. ጠባዩ ፡ የማይታወቅ ፡ ሰው ፡ ነው

**feel queer** ተጫጫነ(ው)
I sat down for a moment because I felt queer. ስለተጫጫነኝ ፡ ጥቂት ፡ ዐረፍ ፡ አልኩ

**quell** ደመሰሰ
The government of Argentina quelled the riot. የአርጀንቲና ፡ መንግሥት ፡ ብጥብጡን ፡ ደመሰሰ

**quench**
1. አረካ. I simply couldn't quench my thirst. ፈጽሞ ፡ ጥሜን ፡ ላረካ ፡ አልቻልኩም
2. አጠፋ. Water will quench the fire. ውኃ ፡ እሳት ፡ ያጠፋል

**querulous** ነዝናዛ
He is a querulous old man. ነዝናዛ ፡ ሽማግሌ ፡ ነው

**query** (queried), v.
1. ጠየቀ. He queried my reasons for leaving. ለምን ፡ እንደምሄድ ፡ ጠየቀኝ
2. ትክክለኛ ፡ መሆኑን ፡ ተጠራጠረ. I query the date that he gives in his article. በጽሑፉ ፡ ላይ ፡

የጠቀሰው ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኑን ፡ እጠራጠራለሁ

**query** (queries), n. ጥያቄ
The minister received a query regarding expenditures. ሚኒስትሩ ፡ ስለ ፡ ገንዘቡ ፡ ወጪ ፡ ጥያቄ ፡ ቀረበላቸው

**quest** ፍለጋ
He read many books in quest of knowledge. ጥበብን ፡ ፍለጋ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ አነበበ

**question** (v.)
1. መረመረ. The police questioned him all night long. ፖሊሱ ፡ ሌሊቱን ፡ሙሉ ፡ ሲመረምረው ፡ አደረ
2. ጠየቀ. The students questioned the teacher. ተማሪዎቹ ፡ አስተማሪውን ፡ ጠየቁት
3. ተጠራጠረ. I question his sincerity. እውነተኛ ፡ መሆኑን ፡ እጠራጠራለሁ

**question** (n.)
1. ጥያቄ. They asked a lot of questions. ብዙ ፡ ጥያቄ ፡ ጠየቁ
Who raised the question about school finances? ስለ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገንዘብ ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረበው ፡ ማን ፡ ነው ?
2. ጉዳይ. The border question is not yet settled. የድንበሩ ፡ ጉዳይ ፡ እሁንም ፡ ውሳኔ ፡ አላገኘም
It's a question of money, not of time. የገንዘብ ፡ እንጂ ፡ የጊዜ ፡ ጉዳይ ፡ አይደለም
3. ጥርጣሬ. There was no question of my being made chairman. እኔ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ እንደምመረጥ ፡ ጥርጣሬ ፡ አልነበረም
4. ክርክር. A question arose about the ownership of the property. ስለ ፡ ንብረቱ ፡ ባለ ፡ ሀብትነት ፡ ክርክር ፡ ተነሣ

**beg the question** አጥጋቢ ፡ አይደለም
Your answer begs the question I asked about the government's policy. ስለ ፡ መንግሥቱ ፡ አመራር ፡ ለጠየቅሁት ፡ ጥያቄ ፡ የሰጠኸኝ ፡ መልስ ፡ አጥጋቢ ፡ አይደለም

**beside the question** ከአርእስቱ ፡ ውጭ
That's beside the question. We are discussing economics, not politics. ይህ ፡ ከአርእስቱ ፡ ውጭ ፡ ነው ፤ እኛ ፡ የምንወያየው ፡ ስለ ፡ ምጣኔ ፡ ሀብት ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ፖለቲካ ፡ አይደለም

**(be) beyond question** አያጠራጥርም
His honesty is beyond question. ታማኝነቱ ፡ አያጠራጥርም

**(be) called in question** (= active) ተጠራጠረ
+His ability was called in question during the debate. በክርክሩ ፡ ጊዜ ፡ ችሎታውን ፡ ተጠራጠሩ

**come into question** በነገሩ ፡ ላይ ፡ ቢነሣ
If my being sent to Australia comes into question, I shall protest. የኔ ፡ ወደ ፡ አውስትራሊያ ፡ መላክ ፡ በነገሩ ፡ ላይ ፡ ቢነሣ ፡ እቃወማለሁ

**in question** የተጠቀሰው
The gentleman in question was not there. የተጠቀሰው ፡ ሰው ፡ እዚያ ፡ አልነበረም

**(be) out of the question**
That's certainly out of the question. ይህ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ የማይሆን ፡ ነው

**(be clearly) out of the question** የማይታሰብ ፡ ነው
It is clearly out of the question to stop teaching. ማስተማርን ፡ ማቆም ፡ የማይታሰብ ፡ ነው

**(be) ready for the question**
*The chairman asked if the members were ready for the question. አባሎቹ ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ ተዘጋጅተው ፡ እንደሆነ ፡ ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ጠየቀ

**without question** ያለጥርጥር
He is without question the best student we have. ካሉን ፡ ተማሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ጐበዙ ፡ ያለጥርጥር ፡ እርሱ ፡ ነው
[See also 'ply, propriety']

**questionable** አጠራጣሪ ፤ የሚያጠራጥር
The utility of this machine is questionable. የዚህ ፡ መኪና ፡ ጠቃሚነት ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው
His actions are highly questionable. ሥራው ፡ ሁሉ ፡ የሚያጠራጥር ፡ ነው

**be questionable**
1. ለመቀበል ፡ ያዳግታል. His assertion is questionable. የተናገረውን ፡ ለመቀበል ፡ ያዳግታል
2. አልተረጋገጠም. It is questionable whether the child in the womb has a soul. በማሕፀን ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ፅንስ ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ አልተረጋገጠም

**questioning**
1. ጥያቄ. The police detained him for questioning. ፖሊሶቹ ፡ ለጥያቄ ፡ አቆዩት
2. አጠያየቅ. We admired the lawyer's adroit questioning of the witness. ጠበቃው ፡ ለምስክሩ ፡ ያቀረበውን ፡ ዘዴኛ ፡ አጠያየቅ ፡ አደነቅን

**question mark** የጥያቄ ፡ ምልክት
Write a question mark at the end of the sentence! በዐረፍተ ፡ ነገሩ ፡ መጨረሻ ፡ የጥያቄ ፡ ምልክት ፡ አድርግ

**questionnaire** መጠይቅ
I received a questionnaire to fill out. የሚሞላ ፡ መጠይቅ ፡ ደረሰኝ

**queue** ሰልፍ
The queue was too long, and I couldn't get into the theater. ሰልፉ ፡ ስለበዛብኝ ፡ ቲያትር ፡ ሳልገባ ፡ ቀረሁ
**form a queue** ተሰለፈ
The people formed a queue in front of the theater. ሰዎች ፡ በቲያትሩ ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተሰለፉ

**quibble** ተከራከረ
They quibbled over the price. በዋጋው ፡ ተከራከሩ

**quick**
1. የተፋጠነ ፤ በፍጥነት ፡ የተደረገ. This situation confronts me with the need to make a quick decision. ይህ ፡ ሁኔታ ፡ የተፋጠነ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ እንድደርስ ፡ ያስገድደኛል
That was a quick decision. በፍጥነት ፡ የተደረገ ፡ ውሳኔ ፡ ነበር
2. ፈጣን. The boss rewarded the quick workers. አለቃው ፡ ለፈጣኖቹ ፡ ሠራተኞች ፡ ስጦታ ፡ አደረገላቸው
3. ንቁ. His quick mind enables him to solve almost any problem. ንቁ ፡ አእምሮው ፡ ለማንኛውም ፡ ችግር ፡ መፍትሔ ፡ ለማግኘት ፡ ይረዳዋል
4. ቁጡ. His quick temper causes many arguments. ቁጡ ፡ ጠባዩ ፡ ብዙ ፡ ክርክር ፡ ያስነሣል
5. (= adv.) ቶሎ. He's quick to understand. ቶሎ ፡ ይገባዋል
**to the quick** እስከ ፡ ሥጋው ፡ ድረስ
He cut his nail to the quick. ጥፍሩን ፡ እስከ ፡ ሥጋው ፡ ድረስ ፡ ቈረጠው

**quicken** (vt.)
1. አፋጠነ. He quickened his steps. እርምጃውን ፡ አፋጠነ
2. አለማ. The spring rains quickened the earth. የበልግ ፡ ዝናም ፡ መሬቱን ፡ አለማው
**quicken** (vi.) ተቀሰቀሰ
When I realized that they were talking about my sister, my interest quickened. የሚያወሩት ፡ ስለ ፡ እኅቴ ፡ መሆኑን ፡ በተገነዘብኩ ፡ ጊዜ ፡ ንግግሩን ፡ ለማዳመጥ ፡ ፍላጎቴ ፡ ተቀሰቀሰ
*Our pace quickened. ፈጠን ፡ ፈጠን ፡ ብለን ፡ ተራመድን
**quicken into flames** አቀጣጠለ
He quickened the hot ashes into flames. የተዳፈነውን ፡ እሳት ፡ አቀጣጠለ

**quickly** ቶሎ ፤ ቶሎ ፡ ብሎ ፤ ባንዴ ፤ በፍጥነት
The wind will dry it quickly. ነፋሱ ፡ ቶሎ ፡ ያደርቀዋል
They quickly made a barricade to keep back the enemy. ጠላትን ፡ ለመከላከል ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ (በፍጥነት) ፡ መከታ ፡ አበጁ
The mole quickly burrowed out of sight. ፍልፈሏ ፡ ባንዴ ፡ መሬቱን ፡ ምሳ ፡ ገባች

**quicksand** የሚከዳ ፡ አሸዋ
Watch out for quicksand when you are in the desert! ምድረ ፡ በዳን ፡ ስታቋርጥ ፡ ከሚከዳ ፡ አሸዋ ፡ ተጠንቀቅ

**quicksilver** ባዜቃ
Quicksilver is a heavy metal. ባዜቃ ፡ ከባድ ፡ የብረት ፡ ዓይነት ፡ ነው

**quick-tempered** ቁጠኛ
His quick-tempered wife is always shouting at him. ቁጠኛ ፡ ሚስቱ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ትጮኽበታለች

**quiescent** የበረደ
The quiescent volcano shows no signs of resuming activity. የበረደው ፡ እሳተ ፡ ጐሞራ ፡ እንደገና ፡ የሚቀሰቀስ ፡ ለመሆኑ ፡ ምንም ፡ ምልክት ፡ አያሳይም
**be quiescent** ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አይንቀሳቀስም
The bear is quiescent during his winter hibernation. ድብ ፡ የክረምት ፡ ወራቶችን ፡ በሚያሳልፍበት ፡ ጊዜ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አይንቀሳቀስም

**quiet** (vt.) ዝም ፡ አሰኘ
See if you can quiet that talkative woman. ያችን ፡ ለፍላፊ ፡ ሴት ፡ ዝም ፡ ማሰኘት ፡ ትችል ፡ እንደሆን ፡ ሞክር
**quiet down**
1. በረደ. Let's wait till the excitement quiets down! ግርግሩ ፡ እስኪበርድ ፡ እንጠብቅ
2. ጸጥ ፡ አለ. The wind quieted down. ነፋሱ ፡ ጸጥ ፡ አለ
3. ዝም ፡ አለ. Quiet down and go to sleep! ዝም ፡ ብለህ ፡ ተኛ
**be quieted** (= act.) ጸጥ ፡ አደረገ
The noisy children were quieted by the teacher. የሚንጫጩትን ፡ ተማሪዎች ፡ አስተማሪው ፡ ጸጥ ፡ አደረጋቸው

**quiet** (n.) ጸጥታ
I demand absolute quiet. ፍጹም ፡ ጸጥታ ፡ እፈልጋለሁ
**quiet** (adj.)
1. ጸጥ ፡ ያለ. I live in a quiet neighborhood. ጸጥ ፡ ባለ ፡ አካባቢ ፡ እኖራለሁ

2. ጸጥተኛ. The quiet audience pleased the speaker. ጸጥተኛው ፡ አዳማጭ ፡ ተናጋሪውን ፡ አስደሰተው
3. ግርግር ፡ ያልበዛበት. He leads a quiet life. ግርግር ፡ ያልበዛበት ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል
4. ደብዘዝ ፡ ያለ. His tie has quiet colors. ክራቫቱ ፡ ደብዘዝ ፡ ያለ ፡ ቀለም ፡ አለው
*He spent a quiet evening at home. እቤቱ ፡ አርፎ ፡ አመሸ

**be quiet**
1. ዝም ፡ አለ. Be quiet! The teacher is coming. ዝም ፡ በል ! መምህሩ ፡ በመምጣት ፡ ላይ ፡ ነው
2. ጭር ፡ አለ. The town is quiet at midday because of the heat. ከሙቀቱ ፡ የተነሣ ፡ ከተማው ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ ጭር ፡ ይላል
3. ጸጥ ፡ አለ. The sea was quiet, with hardly any waves. እምብዛም ፡ ሞገድ ፡ ስላልነበረ ፡ ባሕሩ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ነበር
4. ድምፁም ፡ አልተሰማ. The baby was quiet last night. ባለፈው ፡ ሌሊት ፡ ሕፃኑ ፡ ድምፁም ፡ አልተሰማ

**keep quiet**
1. ዝም ፡ አለ. Can't you keep quiet? ዝም ፡ ልትሉ ፡ አትችሉም ?
2. አልተናገረም. They kept quiet about what they were up to. ምን ፡ እንደሚያደርጉ ፡ አልተናገሩም

**quietly** ዝም ፡ ብሎ ፤ በጸጥታ
I do my work quietly. ሥራዬን ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ እሠራለሁ
The strike meeting passed off quietly. ሥራ ፡ ለማቆም ፡ የተደረገው ፡ ስብሰባ ፡ በጸጥታ ፡ ተከናወነ

**quill** የመቃ ፡ ብዕር
They used to write with quills in the old days. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ በመቃ ፡ ብዕር ፡ ይጽፉ ፡ ነበር

**quilt** ድሪቶ
It is good to cover oneself with a quilt at night. ሌሊት ፡ ድሪቶ ፡ መልበስ ፡ ጥሩ ፡ ነው

**quintal** ኩንታል

**quintessence** ጥሩ ፡ አርአያ
He is the quintessence of politeness. እሱ ፡ ለትሕትና ፡ ጥሩ ፡ አርአያ ፡ ነው

**quintet** [አምስት ፡ መዘምራን ፡ ወይም ፡ ተጫዋቾች ፡ ያሉበት ፡ የሙዚቃ ፡ ጓድ]

**quintuplet** [ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ከሚወለዱት ፡ ከአምስት ፡ መንትዮች ፡ አንዱ]

**quip** (quipped), v. ቀለደ
He quipped about his difficulties. ስለ ፡ ችግሩ ፡ እንኳ ፡ ሲቀልድ ፡ ነበር

**quip** (n.) ቀልድ
His quip was misunderstood. ቀልዱን ፡ በሌላ ፡ ተረጐሙበት

**quit** (quit), v.
1. ለቀቀ. He quit his job yesterday. ሥራውን ፡ ትላንትና ፡ ለቀቀ
If he does not pay his rent, he will receive notice to quit the apartment. ኪራዩን ፡ ካልከፈለ ፡ እንዲለቅ ፡ ማስታወቂያ ፡ ይሰጠዋል
2. ወጣ. He quit the army. ከጦር ፡ ሰራዊት ፡ ወጥቷል
3. አቆመ. The child quit crying. ልጁ ፡ ማልቀሱን ፡ አቆመ
4. ተወ. He quit old beliefs. የጥንት ፡ ልማድን ፡ ተወ

**quit** (adj.), **be ~ of**
1. ተላቀቀ. He gave him money to be quit of him. ለመላቀቅ ፡ ሲል ፡ ገንዘብ ፡ ሰጠው
2. ተገላገለ. I am quit of that debt. ከነበረብኝ ፡ ዕዳ ፡ ተገላገልኩ

**quite**
1. ፍጹም. The two things look alike, but they are not quite the same. ሁለቱ ፡ ነገሮች ፡ ይመሳሰላሉ ፡ ግን ፡ ፍጹም ፡ አንድ ፡ አይደሉም
2. በፍጹም. What he said is quite another story. እሱ ፡ የተናገረው ፡ በፍጹም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ነው
3. ሙሉ ፡ በሙሉ. I quite agree. ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ እስማማለሁ
4. በጣም. He is quite polite, but not ready to help me. በጣም ፡ ትሑት ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ግን ፡ ሊረዳኝ ፡ ፍላጎት ፡ የለውም
5. በእውነት. The remark is quite appropriate. አስተያየቱ ፡ በእውነት ፡ ተገቢ ፡ ነው
*That's quite possible. ሊሆን ፡ ይችላል

**for quite some time** ለብዙ ፡ ጊዜ
He has been courting her for quite some time. ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲያሽኮረምማት ፡ ቆይቷል
[See also 'bit, few, lot, occasion, order, ordinarily, right']

**(be) quits** ተቻቻለ
Pay me a dollar and we will be quits. አንድ ፡ ብር ፡ ስጠኝና ፡ እንቻቻላለን

**quiver** (vi.)
1. ተንቀጠቀጠ. He quivered with fear. በፍርሃት ፡ ተንቀጠቀጠ

2. (= active) አወዛወዘ. +The leaves quivered in the breeze. ቅጠሎቹን ፡ ነፋስ ፡ አወዛወዛቸው

**quiver** (n.) [ከቆዳ ፡ የሚሠራ ፡ እንደ ፡ ድርቆ ፡ ያለ ፡ የቀስት ፡ መያዣ]

**quiz** (quizzed), v. ጠያየቀ
She quizzed him on his activities. ስላሚያደርገው ፡ ነገር ፡ ጠያየቀችው

**quiz** (quizzes), n. አጭር ፡ ፈተና
I have a quiz tomorrow. ነገ ፡ አጭር ፡ ፈተና ፡ አለብኝ

**quorum** ምልአተ ፡ ጉባኤ
The parliament needs a quorum to pass the bill. የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ ለማሳለፍ ፡ በፓርላማው ፡ ውስጥ ፡ ምልአተ ፡ ጉባኤ ፡ ያስፈልጋል

**quota**
1. (= adj.) የተወሰነ. He met the daily quota of work. ለዕለቱ ፡ የተወሰነውን ፡ ሥራ ፡ አከናወነ
2. ለገበያ ፡ የሚቀርብ ፡ መጠን. The coffee quota has been reduced. ለገበያ ፡ የሚቀርበው ፡ የቡና ፡ መጠን ፡ ተቀነሰ

**quotation**
1. ጥቅስ. This quotation is taken from the Bible. ይህ ፡ ጥቅስ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተወሰደ ፡ ነው
2. የተጠየቀ ፡ ዋጋ. The quotation for building the garage is too high. ጋራዡን ፡ ለመሥራት ፡ የተጠየቀው ፡ ዋጋ ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ ነው

**quotation marks** ትእምርተ ፡ ጥቅስ
Put quotation marks after your sentence! ከዐረፍተ ፡ ነገርህ ፡ በኋላ ፡ ትእምርተ ፡ ጥቅስ ፡ አድርግ

**quote**
1. ጠቀሰ. Can you quote a recent instance? በቅርቡ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ልትጠቅስ ፡ ትችላለህ ?
He likes to quote from the Bible. ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ መጥቀስ ፡ ይወዳል
2. አለ. What price did he quote you? ዋጋውን ፡ ስንት ፡ አለህ ?

# R

**rabbit** ጥንቸል
My son bought a rabbit instead of a monkey.
ልጄ ፡ በዝንጀሮ ፡ ፈንታ ፡ ጥንቸል ፡ ገዛ

**rabble** ተራ ፡ ሕዝብ
In ancient Rome, the rabble screamed for bread.
በጥንታዊት ፡ ሮም ፡ ተራው ፡ ሕዝብ ፡ እህል ፡ ለማግኘት ፡ አቤት ፡ ይል ፡ ነበረ

**rabid**
1. እብድ. The rabid dog was shot by a policeman. እብዱን ፡ ውሻ ፡ ፖሊስ ፡ በጥይት ፡ ገደለው
2. (= adv.) ከልክ ፡ በላይ. He is a rabid lover of antiquities. የጥንት ፡ እቃዎችን ፡ ከልክ ፡ በላይ ፡ ይወዳል

**rabies** [የውሻ ፡ በሽታ]

**race** (vt.)
1. በሩጫ ፡ ተወዳደረ. I'll race you to the fence. እስከ ፡ አጥሩ ፡ ድረስ ፡ በሩጫ ፡ እወዳደርሃለሁ
2. ለእሽቅድምድም ፡ አቀረበ. Three people raced their horses. ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ለእሽቅድምድም ፡ አቀረቡ

**race** (vi.)
1. ጋለበ. This horse can race much faster than any other. ይህ ፡ ከሌሎች ፡ ፈረሶች ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ይጋልባል
2. ከነፈ. The car raced through the streets. መኪናዋ ፡ በየመንገዱ ፡ ከነፈች
3. ተሽቀዳደመ. The children said, "Let's race"! ልጆቹ ፡ እንሽቀዳደም ፡ አሉ
4. ሮጠ. I saw the boys racing home from school. ልጆቹ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሲሮጡ ፡ አየሁ
5. ቧረቀ. The lion cubs were racing across the steppe. ያንበሳዎቹ ፡ ግልገሎች ፡ ባውላላው ፡ ሜዳ ፡ ይቧርቁ ፡ ነበር

**race** (n.)
1. ዘር. There is no such thing as a pure race. ንጹሕ ፡ ዘር ፡ ብሎ ፡ ነገር ፡ የለም
2. የፈረስ ፡ እሽቅድምድም. When does the race start? የፈረሱ ፡ እሽቅድምድም ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ይጀመራል ?
3. ዙር. He was eliminated in the third race. በሦተስኛው ፡ ዙር ፡ ወጣ

**human race** የሰው ፡ ልጅ
The human race has spread all over the world. የሰው ፡ ልጅ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ተሰራጭቷል
[See also 'relay']

**race course** የሩጫ ፡ መወዳደሪያ ፡ ሜዳ
There is a big race course in this city. በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ትልቅ ፡ የሩጫ ፡ መወዳደሪያ ፡ ሜዳ ፡ አለ

**race problem** የቀለም ፡ ልዩነት ፡ ጉዳይ
The race problem is a touchy subject in America. በአሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ የቀለም ፡ ልዩነት ፡ ጉዳይ ፡ በጣም ፡ የሚያስቆጣ ፡ ነው

**race track**, see **track**

**racial** የዘር
There is racial discrimination in several parts of the world. በብዙ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ የዘር ፡ ልዩነት ፡ አለ

**racial problem** የዘር ፡ ልዩነት ፡ ጉዳይ
The racial problem is rending the nation. የዘር ፡ ልዩነት ፡ ጉዳይ ፡ አገሪቱን ፡ በመከፋፈል ፡ ላይ ፡ ነው
[See also 'superiority']

**racing** እሽቅድድም
The Romans used chariots for fighting and racing. ሮማውያን ፡ ለጦርነትና ፡ ለእሽቅድድም ፡ በሰረገላ ፡ ይጠቀሙ ፡ ነበር

**rack** (v.), ~ **with pain** በጣም ፡ አሠቃየ
The disease racked the man with pain. በሽታው ፡ ሰውዬውን ፡ በጣም ፡ አሠቃየው

**rack (one's) brains** ተጠበበ
He racked his brains for an answer. መልስ ፡ ለማግኘት ፡ ተጠበበ

**rack** (n.) ማስጫ
Put these wet clothes on a rack to dry! ልብሱ ፡ እንዲደርቅ ፡ ማስጫው ፡ ላይ ፡ ዘርጋው

**racket**
1. ሁካታ. The racket gave him a headache. ሁካታው ፡ የራስ ፡ ምታት ፡ አሳደረበት
2. ማጭበርበር. This whole business is nothing but a racket. ጠቅላላውን ፡ ነገሩ ፡ ማጭበርበር ፡ ያለበት ፡ ነው

3. ራኬት. He broke his tennis racket. የቴኒስ ፡ ራኬቱን ፡ ሰበረ

**make a racket** ተንጫጫ
The children are making an awful racket. ልጆቹ ፡ ክፉኛ ፡ ይንጫጫሉ

**radiance** ደስታ
Her face was full of radiance. ፊቷ ፡ በደስታ ፡ ያበራ ፡ ነበር

**radiant**
1. ደማቅ. He likes to paint in radiant colors. በደማቅ ፡ ቀለም ፡ መሣል ፡ ይወዳል
2. ብሩህ. Her radiant smile won her many friends. ብሩህ ፡ ፈገግታዋ ፡ ብዙ ፡ ወዳጆች ፡ አተረፈላት
3. ብርሃን ፡ የሚሰጥ. The sun is a radiant body. ፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ የምትሰጥ ፡ አካል ፡ ናት

**radiant sun** የፀሐይ ፡ ጮራ
The radiant sun made the world seem new. የፀሐይዋ ፡ ጮራ ፡ ዓለምን ፡ አዲስ ፡ አስመሰለ

**radiate** (vt.) ሰጠ
The stove radiates warmth. ምድጃው ፡ ሙቀትን ፡ ይሰጣል
The sun radiates light and heat. ፀሐይ ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀት ፡ ትሰጣለች
*She radiates happiness. የደስታ ፡ ምንጭ ፡ ናት
*He radiates confidence. ሁኔታው ፡ ያበረታታል

**radiate** (vi.)
1. በየቅጣጫው ፡ ተከፋፈለ. The streets radiate from a central square. መንገዶቹ ፡ ካንድ ፡ ማእከላዊ ፡ አደባባይ ፡ ተነሥተው ፡ በየቅጣጫው ፡ ይከፋፈላሉ
2. ተፈነጠቀ. Light radiates from the sun. ብርሃን ፡ ከፀሐይ ፡ ይፈነጠቃል

**radiation** ራዲዮሽን
Radiation presents a danger to all life. ራዲዮሽን ፡ ለጠቅላላው ፡ ሕይወት ፡ ጠንቅ ፡ ነው

**radiator**
1. የቤት ፡ ማሞቂያ. The house was warmed by radiators. የቤት ፡ ማሞቂያው ፡ ቤቱን ፡ አሞቀው
2. የሞተር ፡ ማቀዝቀዣ. He lifted the hood and put water into the radiator. ክዳኑን ፡ ከፍቶ ፡ ሞተሩ ፡ ማቀዝቀዣ ፡ ውስጥ ፡ ውኃ ፡ ጨመረበት

**radical** (n.) ፊደል
In this verb, the last two radicals are repeated. በዚህ ፡ ግስ ፡ ውስጥ ፡ የመጨረሻዎቹ ፡ ሁለት ፡ ፊደሎች ፡ ተደጋግመዋል

**radical** (adj.)
1. ለውጥ ፡ ፈላጊ ፤ ተራማጅ. He is a member of a radical party. የለውጥ ፡ ፈላጊ ፡ (የተራማጅ) ፡ ፓርቲ ፡ አባል ፡ ነው
2. መሠረታዊ. He wants to make some radical changes. መሠረታዊ ፡ ለውጥ ፡ ለማድረግ ፡ ይፈልጋል

**radio** ሬዲዮ ፤ ራዲዮ
You can hear world news over the radio. የዓለም ፡ ወሬዎች ፡ በሬዲዮ ፡ (በራዲዮ) ፡ ይሰማሉ

**radio station** ሬዲዮ ፡ ጣቢያ
Have you seen the new radio station? አዲሱን ፡ ሬዲዮ ፡ ጣቢያ ፡ አይተኸዋል ?

**radish** ቀይ ፡ ሥር
I like radishes in my salad. ሰላጣዬ ፡ ውስጥ ፡ ቀይ ፡ ሥር ፡ ቢጨመርበት ፡ እወዳለሁ

**radius** ከመሃል ፡ እስከ ፡ ዳሩ ፡ ያለው ፡ ርቀት
The radius of this circle is five inches. የዚህ ፡ ክብ ፡ ከመሃል ፡ እስከ ፡ ዳሩ ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ አምስት ፡ ኢንች ፡ ይሆናል

**within a radius** በ - - - ርቀት
The bomb damaged every house within a radius of two miles. በምቡ ፡ በሁለት ፡ ማይል ፡ ርቀት ፡ ባሉ ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ አደረሰ

**raft** መንሳፈፊያ ፤ ታንኳ
They crossed the river on a raft. ወንዙን ፡ በመንሳፈፊያ ፡ (በታንኳ) ፡ ተሻገሩ

**rafter** ወራጅ
The covering of the roof must be firmly fastened to the rafters. የጣሪያው ፡ ክዳን ፡ ከወራጁ ፡ ጋር ፡ አጥብቆ ፡ መታሰር ፡ አለበት

**rag** ጨርቅ
Do you have a rag to dust the table? ለጠረጴዛው ፡ መወልወያ ፡ ጨርቅ ፡ አለህ ?

**rags** ቡትቶ
The starving beggar wore nothing but rags. የተራበው ፡ ለማኝ ፡ ቡትቶ ፡ ብቻ ፡ ለብሷል

**rage** (v.)
1. ባሰ(በት). A storm is raging. ኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ እየባሰበት ፡ ሄደ
2. በጣም ፡ ተናደደ ፤ ጦፈ. He raged against the injustices inflicted on him. በተደረገበት ፡ በደል ፡ በጣም ፡ ተናደደ ፡ (ጦፈ)
*He raged like a bull. ነብር ፡ ሆነ

**rage on** ነፈሰ
The storm raged on unabated. ኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ነፈሰ

**rage** (n.)

1. ንዴት. His face turned red with rage. ፊቱ ፡ በንዴት ፡ ደም ፡ መሰለ

2. ኀይለኛነት. The rage of the storm frightened the children. የነፋሱ ፡ ኀይለኛነት ፡ ልጆቹን ፡ አስፈራቸው

3. ተወዳጅ. Short skirts are the rage this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ አጭር ፡ ቀሚስ ፡ ተወዳጅ ፡ ሆኗል

**fly into a rage** በጣም ፡ ተቈጣ ፤ ጦፈ

My father flew into a rage when I told him what I did last night. አባቴ ፡ ትናንትና ፡ ሌሊት ፡ ያደረግሁትን ፡ ስነግራቸው ፡ በጣም ፡ ተቈጡ ፡ (ጦፉ)

**work oneself into a rage** በንዴት ፡ አረረ

He worked himself into a rage by thinking about the bad treatment he received. የደረሰበትን ፡ በደል ፡ በማሰብ ፡ በንዴት ፡ አረረ

**ragged** ቡትቶ ፡ የለበሰ

The ragged little boy was begging in the street. ቡትቶ ፡ የለበሰው ፡ ትንሽ ፡ ልጅ ፡ በመንገዱ ፡ ይለምን ፡ ነበር

**ragged clothes** ቡትቶ

We wore ragged clothes. ቡትቶ ፡ ለብሰን ፡ ነበር

**be ragged** ነተበ

The sleeve of his coat was ragged. የኮቱ ፡ እጅጌ ፡ ነትቦ ፡ ነበር

**raid** (v.)

1. ወረረ. We raided the enemy's camp and got much loot. የጠላትን ፡ ሰፈር ፡ ወረን ፡ ብዙ ፡ ምርኮ ፡ አገኘን

2. ዘረፈ(ተዘረፈ). The armory was raided by the rebels. የጦር ፡ መሣሪያው ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ በአጋሚዶዎች ፡ ተዘረፈ

3. በድንገት ፡ ያዘ. The police raided the gambling den. ፖሊስ ፡ የቁማር ፡ መጫወቻውን ፡ ቦታ ፡ በድንገት ፡ ያዘው

**raid** (n.)

1. ወረራ. Our raid is in reprisal for an enemy attack. የኛ ፡ ወረራ ፡ ጠላት ፡ ላደረገው ፡ ማጥቃት ፡ ዐጸፋውን ፡ ለመመለስ ፡ ነው

2. ድንገተኛ ፡ ጥቃት. The enemy's raid was beaten off. የጠላትን ፡ ድንገተኛ ፡ ጥቃት ፡ መለሱት

**make a raid on** በዘበዘ

The hungry boys made a raid on the icebox. የተራቡት ፡ ልጆች ፡ ማቀዝቀዣውን ፡ በዘበዙት

**rail** (v.) በጣም ፡ ተማረረ

He railed at his fate. በዕድሉ ፡ በጣም ፡ ተማረረ

**rail against** አወገዘ

The old man railed against newfangled ideas. ሽማግሌው ፡ ሰው ፡ ዘበናይ ፡ አስተሳሰብን ፡ አወገዘ

**rail** (n.)

1. ሐዲድ. The rebels took the rails from the railway track. ዐመፀኞቹ ፡ የባቡሩን ፡ ሐዲድ ፡ ነቀሉት

2. መደገፊያ. He leaned on the ship's rail and looked out on the ocean. በመርከቡ ፡ መደገፊያ ፡ ላይ ፡ ተደግፎ ፡ ወደ ፡ ውቅያኖሱ ፡ አሻግሮ ፡ ተመለከተ

**railhead** የሐዲድ ፡ መሥመር ፡ መጨረሻ

The railhead is now ten miles outside the capital. የሐዲዱ ፡ መሥመር ፡ መጨረሻ ፡ ከከተማው ፡ ከዚህ ፡ ዐሥር ፡ ማይል ፡ ርቆ ፡ ነው

**railing** መደገፊያ

Hold on to the railing! መደገፊያውን ፡ ያዝ

**railroad**

1. ባቡር. I prefer to go by railroad. በባቡር ፡ መሄድ ፡ ይሻለኛል

2. የባቡር ፡ ሐዲድ. They built a new railroad. አዲስ ፡ የባቡር ፡ ሐዲድ ፡ ዘረጉ

**railroad station** ባቡር ፡ ጣቢያ ፤ ላጋር

I am going to the railroad station. ወደ ፡ ባቡር ፡ ጣቢያ ፡ መሄዴ ፡ ነው

The Addis Ababa railroad station was built many years ago. ያዲስ ፡ አበባ ፡ ላጋር ፡ የተሠራው ፡ ከብዙ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ነበር

**railroad tracks** የባቡር ፡ ሐዲድ

The railroad tracks were blown up by the rebels. የባቡሩን ፡ ሐዲድ ፡ ዐመፀኞች ፡ በፈንጂ ፡ አፈራረሱት

**railway** የባቡር ፡ ሐዲድ

The railway is government controlled. የባቡሩ ፡ ሐዲድ ፡ በመንግሥት ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው

**railway track** መሥመር

The rebels took the rails from the railway track. ዐመፀኞቹ ፡ ሐዲዱን ፡ ከመሥመሩ ፡ ነቅለው ፡ ወሰዱ

**rain** (vt.) አጕረፈ(ለት)

Friends rained presents on them. ወዳጆቻቸው ፡ ስጦታ ፡ አጕረፉላቸው

**rain** (vi.) ዝናብ ፡ ጣለ ፤ ዘነበ ፤ ዘነመ

It rained all morning. ዝናብ ፡ ሲጥል ፡ አረፈደ

It rains every afternoon in the rainy season. በክረምት ፡ ሁልጊዜ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ይዘንባል

*Bullets rained about them. የጥይት ፡ መዓት ፡ ወረደባቸው

**rain** (n.) ዝናብ ፤ ዝናም
We stayed home because of the rain. በዝናቡ ፡ ምክንያት ፡ እቤት ፡ ዋልን

**rains** ክረምት
The rains begin in June. ክረምት ፡ በሰኔ ፡ ይገባል

**heavy rain** ዶፍ
We can't leave in that heavy rain. በዛ ፡ ዶፍ ፡ ውስጥ ፡ ልንሄድ ፡ አንችልም

**rainbow** ቀስተ ፡ ደመና
We saw a rainbow in the sky. ሰማዩ ፡ ላይ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ አየን

**raincoat** የዝናብ ፡ ልብስ
Lend me your raincoat! የዝናብ ፡ ልብስህን ፡ አውሰኝ

**rainfall** ዝናብ
As a result of the heavy rainfall, the roads became impassable. በኀይለኛው ፡ ዝናብ ፡ ምክንያት ፡ መንገዶቹ ፡ ሁሉ ፡ አላሳልፍ ፡ አሉ
The rainfall averages 30 inches a year. ዝናቡ ፡ ባመት ፡ ሠላሳ ፡ ኢንች ፡ ያህል ፡ ነው

**rain gauge** የዝናብ ፡ መለኪያ
The rain gauge was broken by a storm. የዝናቡን ፡ መለኪያ ፡ ኀይለኛ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ሰበረው

**rainy** ዝናብ ፡ የሚበዛበት
July is a rainy month. ሐምሌ ፡ ዝናብ ፡ የሚበዛበት ፡ ወር ፡ ነው

**rainy day** ክፉ ፡ ቀን
Save your money for a rainy day! ገንዘብህን ፡ ለክፉ ፡ ቀን ፡ አስቀምጥ

**rainy season** ክረምት
The rainy season has started. ክረምት ፡ ገብቷል

**rainy weather** ዝናብ
I like rainy weather. ዝናብ ፡ እወዳለሁ

**raise** (v.)
1. አቆመ. They raised a monument to the martyrs. ለሰማዕታቱ ፡ ሐውልት ፡ አቆሙ
2. ወልዳ ፡ አሳደገች. She has raised nine children. ዘጠኝ ፡ ልጆች ፡ ወልዳ ፡ አሳድጋለች
3. አረባ. Many farmers in America raise pigs. አሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ገበሬዎች ፡ አሳማ ፡ ያረባሉ
4. አመረተ. They raise a lot of wheat here. እዚህ ፡ ብዙ ፡ ስንዴ ፡ ያመርታሉ
5. አስነሣ. Jesus raised Lazarus from the dead. ኢየሱስ ፡ አልአዛርን ፡ ከሞት ፡ አስነሣው
The truck raised a cloud of dust as it sped along. የጭነት ፡ መኪናው ፡ በፍጥነት ፡ ሲሄድ ፡ ብዙ ፡ አቧራ ፡ አስነሣ
6. ከፍ ፡ አደረገ. They raised him from a corporal to a sergeant. ከዐሥር ፡ አለቅነት ፡ ወደ ፡ ኀምሳ ፡ አለቅነት ፡ ከፍ ፡ አደረጉት
7. አነሣ. He raised his hand in the air to show how high the water would reach. የውኃውን ፡ ከፍታ ፡ ለማሳየት ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አነሣ
Who raised the question about school finances? ስለ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የገንዘብ ፡ ሁኔታ ፡ ያነሣው ፡ ማነው ?
8. አወጣ. All in favor, raise your hands! ደጋፊዎች ፡ የሆናችሁ ፡ ሁሉ ፡ እጃችሁን ፡ አውጡ
9. አቀና. The snake raised its head and hissed. እባቡ ፡ ራሱን ፡ አቅንቶ ፡ አፏጨ
Raise the overturned lamp! የተደፋውን ፡ መብራት ፡ አቅናው
10. አስጠጋ. He raised his glass to his lips, but did not drink. ብርጭቆውን ፡ ወደ ፡ አፉ ፡ አስጠጋ ፡ እንጂ ፡ አልጠጣም
11. ጨመረ. I raised my servant's salary because he was so reliable. አሽከሬ ፡ በጣም ፡ ታማኝ ፡ ስለ ሆነ ፡ ደሞዝ ፡ ጨመርኩለት
12. አቀረበ. The members raised objections to the proposal. አባሎቹ ፡ በእቅዱ ፡ ላይ ፡ ተቃውሞ ፡ አቀረቡ
13. ለቀቀ. The boys raised a shout. ልጆቹ ፡ ጩኸታቸውን ፡ ለቀቁ
14. ሰበሰበ. They are raising money for a new school. አዲስ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለማሠራት ፡ ገንዘብ ፡ ይሰበስባሉ
The leader raised an army. መሪው ፡ ወታደር ፡ ሰበሰበ

**raise (one's) head** ቀና ፡ አለ
He raised his head and looked at me. ቀና ፡ ብሎ ፡ ተመለከተኝ

**raise (one's) hopes** ብዙ ፡ ተስፋ ፡ አሳደረበት
Don't raise his hopes! He may not be chosen. ብዙ ፡ ተስፋ ፡ አታሳድርበት ፤ ላይመረጥ ፡ ይችላል

**raise oneself** አበቃ
The boy raised himself by hard study to be a great lawyer. ልጁ ፡ ተግቶ ፡ በመማሩ ፡ ራሱን ፡ ለትልቅ ፡ ጠበቃነት ፡ አበቃ

**raise the roof** ተናዶ ፡ ያዙኝ ፡ ልቀቁኝ ፡ አለ
He raised the roof when he heard the news. ወሬውን ፡ ሲሰማ ፡ ተናዶ ፡ ያዙኝ ፡ ልቀቁኝ ፡ አለ

**raise (one's) voice** ጮክ ፡ አለ
He raised his voice to make himself heard. እንዲሰማ ፡ ጮክ ፡ አለ

**be raised**
1. አደገ. He was raised from a sergeant to first lieutenant. ከነምሳ ፡ አለቅነት ፡ ወደ ፡ መቶ ፡ አለቅነት ፡ አደገ
2. ጨመረ. The rent will be raised on October 1st. ጥቅምት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የቤቱ ፡ ኪራይ ፡ ይጨምራል
[See also 'furor, hell, objection, outcry']

**raise** (n.)
1. የደሞዝ ፡ ጭማሪ. Civil servants got a raise. የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የደሞዝ ፡ ጭማሪ ፡ አገኙ
2. የሹመት ፡ እድገት. The private refused to lick the lieutenant's boots to get a raise. ወታደሩ ፡ ለሹመት ፡ እድገት ፡ ሲል ፡ መቶ ፡ አለቃውን ፡ መለማመጥ ፡ አሻፈረኝ ፡ አለ
**grant a raise** ደሞዝ ፡ ጨመረ
At long last they granted us a raise. ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ደሞዝ ፡ ጨመሩልን

**raisin** ዘቢብ
They make a kind of wine from raisins. ከዘቢብ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ መሰል ፡ መጠጥ ፡ ይሠራሉ

**rake** (v.)
1. ጫረ. He raked the ashes looking for live coals. ፍም ፡ ፍለጋ ፡ አመዱን ፡ ጫረ
2. ሰበሰበ. He rakes the leaves every morning. ሁልጊዜ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ቅጠሎችን ፡ ይሰበስባል
3. በረበረ. They raked the apartment looking for the missing jewels. የጠፋውን ፡ ጌጣጌጥ ፡ ለመፈለግ ፡ ቤቱን ፡ በረበሩ
**rake through** በዘበዘ
He raked through the old papers looking for a letter. ደብዳቤ ፡ ለመፈለግ ፡ አሮጌዎቹን ፡ ወረቀቶች ፡ ሁሉ ፡ በዘበዘ

**rake** (n.) ቅጠል ፡ መጥረጊያ
We need a new rake for the garden. ላትክልት ፡ በታችን ፡ አዲስ ፡ ቅጠል ፡ መጥረጊያ ፡ ያስፈልገናል

**rally** (rallied), vt. መልሶ ፡ ሰበሰበ
The commander was able to rally the fleeing troops. አዛዡ ፡ የሚሸሹትን ፡ ወታደሮች ፡ መልሶ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ቻለ
**rally** (vi.)
1. ተሰበሰበ. The troops rallied around the general. ወታደሮቹ ፡ በጄኔራሉ ፡ ዙሪያ ፡ ተሰበሰቡ
2. አገገመ. He rallied from his illness. ከበሽታው ፡ አገገመ
**rally to**
1. ደገፈ. Men from all walks of life rallied to the cause. አገሌ ፡ ከአገሌ ፡ ሳይባል ፡ ሁሉም ፡ ዓላማውን ፡ ደገፈው
2. ደረሰ(ለት). They rallied to the side of their friend in trouble. በችግር ፡ ላይ ፡ ለወደቀው ፡ ጓደኛቸው ፡ ደረሱለት

**rally** (rallies), n. ስብሰባ
Come with me to the rally! ስብሰባው ፡ አብረን ፡ እንሂድ

**ram** (rammed), v. ገጨ
+I rammed my head against the door in the dark. በጭለማው ፡ በሩ ፡ ራሴን ፡ በኀይል ፡ ገጨኝ
**ram through**
1. በጠረቀ. He rammed his fist through the thin boards. ስሱን ፡ ሳንቃ ፡ በቡጢ ፡ በጠረቀው
2. በመገፋፋት ፡ በጥድፊያ ፡ አሳለፈ. The government rammed the bill through the Parliament. መንግሥቱ ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ ፓርላማን ፡ በመገፋፋት ፡ በጥድፊያ ፡ አሳለፈው

**ram** (n.)
1. በግ. Keep the ram in the enclosure! በጉን ፡ እጉረኖው ፡ አስገባው
2. መስበሪያ. They used a log as a ram to smash down the door. በሩን ፡ ለመስበር ፡ በግንድ ፡ መስበሪያ ፡ ተጠቀሙ

**ramble**
1. ዘባረቀ ፤ ቀባጀረ. The speaker rambled, and everybody was bored. ተናጋሪው ፡ በመዘባረቁ ፡ (በመቀባጀሩ) ፡ ሁሉም ፡ ሰው ፡ ተሰለቸ
2. ዞረ ፤ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ. He loves to ramble through the countryside. በየገጠሩ ፡ መዞር ፡ ይወዳል
They rambled through the shop until closing time. የመዘጊያው ፡ ጊዜ ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ በሱቁ ፡ ውስጥ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አሉ

**ramifications** ከ - - - ጋር ፡ የተያያዙ ፡ ነገሮች
He understands all the ramifications of this problem. ከጉዳዩ ፡ ጋር ፡ የተያያዙትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል

**ramify** (ramified) ዘርፍ ፡ አወጣ
This system has ramified over the years. ይህ ፡ ድርጅት ፡ ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ዘርፍ ፡ አውጥቷል

**ramp** የተጋደመ ፡ መወጣጫ
A ramp enables cars to be driven from the road onto the railroad car. የተጋደመው ፡ መወጣጫ ፡ መኪናዎችን ፡ ወደ ፡ ፉርጎ ፡ ውስጥ ፡ ለማስገባት ፡ ያስችላል

**rampage** (v.) ተራወጠ
A bull elephant rampages through the jungle. አንድ ፡ ወንድ ፡ ዝሆን ፡ በጫካው ፡ ውስጥ ፡ ይራወጣል

**rampage** (n.), **go on a ~**
1. ምስቅልቅሉን ፡ አወጣ. The children went on a rampage when the teacher was out of the room. መምህሩ ፡ ከክፍል ፡ እንደወጣ ፡ ልጆቹ ፡ ክፍሉን ፡ ምስቅልቅሉን ፡ አወጡ
2. በዘበዘ ፤ ሕዝቡን ፡ ፈጀ. When the enemy went on a rampage in the city, no one was spared. ጠላት ፡ ከተማውን ፡ በበዘበዘበት ፡ ጊዜ ፡ ማንንም ፡ አላስቀረም
On February 12, the enemy went on a rampage in Addis Ababa. የካቲት ፡ ዓሥራ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ጠላት ፡ ሕዝቡን ፡ ፈጀ
3. ተቈጣ. The elephant went on a rampage and killed its keeper. ዝሆኑ ፡ ተቈጥቶ ፡ ጠባቂውን ፡ ገደለው

**(be) rampant** ተዛመተ
Disease is rampant in the South. በደቡብ ፡ ክፍል ፡ በሽታ ፡ ይዛመታል

**grow rampant in** አለበሰ
The weeds grew rampant in the garden. አረሙ ፡ ያትክልቱን ፡ ስፍራ ፡ አለበሰው

**run rampant** ተዛመተ
Economic difficulties run rampant in this region. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ችግር ፡ ተዛመተ

**rampart** ግምቡ ፡ ጫፍ ፡ ያለ ፡ መተኳኰሻ
The soldiers manned the ramparts to ward off attacks. ወታደሮቹ ፡ ወረራውን ፡ ለመከላከል ፡ ግምቡ ፡ ጫፍ ፡ ካለው ፡ መተኳኰሻ ፡ ላይ ፡ ወጡ

**ranch**
1. ከብት ፡ ማርቢያ ፡ መሬት. We have ten thousand head of cattle on our ranch. ከብት ፡ ማርቢያ ፡ መሬታችን ፡ ላይ ፡ ዐሥር ፡ ሺ ፡ ከብቶች ፡ አሉን
2. እርሻ. Our fruit ranch produces many different kinds of fruit. የፍራፍሬ ፡ እርሻችን ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ፍራፍሬዎች ፡ ያበቅላል

**rancid** የቦካ
Certain tribes put rancid butter in their hair. አንዳንድ ፡ ጐሳዎች ፡ የቦካ ፡ ቅቤ ፡ እራሳቸውን ፡ ይቀባሉ

**be rancid** ቦካ
The butter is rancid. ቅቤው ፡ ቦክቷል

**rancor** ክፍ ፡ ያለ ፡ ጥላቻ
His soul was filled with rancor. ክፍ ፡ ያለ ፡ ጥላቻ ፡ አድሮበታል

**random** በአፉ ፡ የመጣ
He was not listening, and made a random answer to the teacher's question. ጠንቅቆ ፡ ስላላዳመጠ ፡ አስተማሪው ፡ላቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ በአፉ ፡ የመጣ ፡ መልስ ፡ ሰጠ

**at random** እንዳገኘ
The soldiers fired their guns at random. ወታደሮቹ ፡ ጠመንጃውን ፡ እንዳገኙ ፡ ተኰሱ

**rang**, see **ring**

**range** (vt.) ደረደረ
The librarian ranged the books by size. ዐቃቤ ፡ መጻሕፍቱ ፡ መጻሕፍቱን ፡ በየመጠናቸው ፡ ደረደረ

**range** (vi.)
1. ደረሰ. The temperature ranges from 50 to 80 degrees. የሙቀቱ ፡ መጠን ፡ ካምሳ ፡ እስከ ፡ ሰማንያ ፡ ዲግሪ ፡ ይደርሳል
2. ተዘዋወረ. Bears ranged in the forests. ድቦች ፡ ጫካው ፡ ውስጥ ፡ ተዘዋወሩ
3. ተገኘ. Rocky cliffs range along the seashore. ቋጥኝ ፡ የበዛባቸው ፡ ገደሎች ፡ በባሕሩ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ ይገኛሉ

**range oneself with** ከ --- ጐን ፡ ተሰለፈ
Loyal citizens ranged themselves with the king. ታማኝ ፡ ዜጎች ፡ ከንጉሡ ፡ ጐን ፡ ተሰለፉ

**range over** አጠቃለለ
Our talk ranged over all that had happened on our vacation. ንግግራችን ፡ በዕረፍት ፡ ጊዜያችን ፡ ያደረግነውን ፡ ሁሉ ፡ ያጠቃልል ፡ ነበር

**range** (n.)
1. መጠን. The annual range of temperature is from 70° to 100°. ዓመታዊው ፡ ያየር ፡ ሙቀት ፡ መጠን ፡ ከሰባ ፡ ዲግሪ ፡ እስከ ፡ መቶ ፡ ይደርሳል
2. ዓይነት. These shirts come in a wide range of colors. እነዚህ ፡ ሸሚዞች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ቀለም ፡ ይገኛሉ
3. ምድጃ. Gas and electric ranges have replaced the coal range. የጋዝና ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ምድጃዎች ፡ የከሰል ፡ ምድጃውን ፡ ተክተዋል
*This store has a range of prices from $70 to $100. ይህ ፡ መደብር ፡ ከሰባ ፡ እስከ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ የሚደርስ ፡ የእቃ ፡ ዋጋ ፡ አለው
*Try to stay within range of my voice! ስጠራህ ፡ ልትሰማኝ ፡ በምትችልበት ፡ ርቀት ፡ ሁን

**at close range** ቅርብ ፡ ሆኖ
He fired at close range. ቅርብ ፡ ሆኖ ፡ ተኰሰ

**cattle range** ከብት ፡ ማሰማሪያ
Our land is used for a cattle range. መሬታችን ፡
ለከብት ፡ ማሰማሪያ ፡ ውሏል

**mountain range** ሸንተረር
Can you see the mountain ranges from here?
ሸንተረሮቹን ፡ ከዚህ ፡ ልታይ ፡ ትችላለህ ?
[See also 'price']

**rank** (vt.)
1. ቈጠረ. Would you rank him among the
world's great men? ካለም ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ እ
ንዳንዱ ፡ ትቈጥረዋለህ ?
2. መደበ. He ranked the soldiers according
to height. ወታደሮቹን ፡ በቁመት ፡ መደባቸው

**rank** (vi.)
*New York State ranks first in wealth. የኒውዮ
ርክ ፡ ግዛት ፡ በሀብት ፡ አንደኛ ፡ ነው
*A captain ranks below a major. በማዕረግ ፡ ሻ
ምበል ፡ ከሻለቃ ፡ በታች ፡ ነው
*John ranks low in the test. የዮሐንስ ፡ ፈተ
ና ፡ ውጤት ፡ ዝቅተኛ ፡ ነው

**rank above** በማዕረግ ፡ በለጠ ፤ በለጠ
A captain in the navy ranks above a captain
in the army. በማዕረግ ፡ የባሕር ፡ ኀይል ፡ ሻምበ
ል ፡ ከጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሻምበል ፡ ይበልጣል
A major ranks above a captain. ሻለቃ ፡ ከሻም
በል ፡ ይበልጣል

**rank among** ቈጠረ
I would rank this school among the best.
ይህን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ከሚባሉ
ት ፡ እንዳንዱ ፡ እቈጥረዋለሁ

**rank** (n.)
1. ማዕረግ. What's that officer's rank? ያ ፡ መ
ኰንን ፡ ማዕረጉ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
2. ትልቅ ፡ ማዕረግ. A duke is a man of rank.
መስፍን ፡ ትልቅ ፡ ማዕረግ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው
*People from all ranks of life voted for him.
እገሌ ፡ ከእገሌ ፡ ሳይባሉ ፡ ለሱ ፡ ድምፃቸው
ን ፡ ሰጡ

**rank of** የተሰለፉ
There was a rank of soldiers in front of the
station. ከጣቢያው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የተሰለፉ ፡
ወታደሮች ፡ ነበሩ

**rise from the ranks** ከባለሌላ ፡ ማዕረግ ፡ ተነሣ
He rose from the ranks to become general.
ከባለሌላ ፡ ማዕረግ ፡ ተነሥቶ ፡ ጀኔራል ፡ ሆነ

**(be) rank**
1. መጥፎ ፡ ሽታ ፡ አለው. This meat is rank. ይ
ህ ፡ ሥጋ ፡ መጥፎ ፡ ሽታ ፡ አለው
2. ጋሸበ. Vegetation is rank in the tropics.
በሞቃት ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ተክሉ ፡ ይጋሸባል

**rank and file** አባሎች
The rank and file of the party approved the
decision of the leaders. የፓርቲው ፡ አባሎች ፡
የመሪዎችን ፡ ውሳኔ ፡ አጸደቁ

**rankle** (vt.) ሆዱን ፡ በላው
This slight rankled her. ችላ ፡ መባሏ ፡ ሆዷን ፡ በ
ላት

**ransack**
1. ዘረፈ. Bandits ransacked the town. ሽፍቶች ፡
ከተማውን ፡ ዘረፉት
2. ምስቅልቅሉን ፡ አወጣ. Thieves ransacked our
apartment. ሌቦች ፡ አፓርተማችንን ፡ ምስቅልቅሉ
ን ፡ አወጡት

**ransom** (v.) ማስለቀቂያ ፡ ቤዛ ፡ ከፈለ
He refused to ransom his son. ለልጁ ፡ ማስለቀ
ቂያ ፡ ቤዛ ፡ አልከፍልም ፡ አለ

**ransom** (n.)
1. ቤዛ. The captive was released after the
delivery of his ransom. ምርኮኛው ፡ ቤዛው ፡ ከ
ተከፈለለት ፡ በኋላ ፡ ተለቀቀ
2. ማስለቀቂያ ፡ ገንዘብ. They kidnapped the
girl, and held her for ransom. ልጅቷን ፡ ጠልፈ
ው ፡ ማስለቀቂያ ፡ ገንዘብ ፡ ካልተሰጠን ፡ አንመ
ልስም ፡ አሉ

**rap** (rapped) ደበደበ
He rapped the table to get my attention.
ሐሳቤን ፡ ወደሱ ፡ ለመመለስ ፡ ጠረጴዛውን ፡ ደ
በደበ

**rap on** መታ
He called the meeting to order by rapping on
the table. ጠረጴዛውን ፡ በመምታት ፡ ስብሰባው ፡
በሥርዓት ፡ እንዲመራ ፡ ጠየቀ

**rap out**
*The captain rapped out an order. ሻምበሉ ፡ ጮ
ክ ፡ ብሎ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ

**rap** (n.)
*I heard a rap at the door. በሩ ፡ በኀይል ፡ ሲንኳ
ኳ ፡ ሰማሁ

**rapacious**
1. አድኖ ፡ የሚኖር. Hawks are rapacious birds.
ጭልፊቶች ፡ አድነው ፡ የሚኖሩ ፡ ወፎች ፡ ናቸው
2. ቆንቋና. A rapacious landlord will raise the
rent, but refuse to make any repairs. ቆንቋና ፡ ባ
ለቤት ፡ ኪራይ ፡ ከመጨመር ፡ በቀር ፡ ቤቱን ፡ አ
ያሳድስም

3. በቃኝን ፡ የማያውቅ. The people fled in fear of the rapacious invader. በቃኝን ፡ የማያውቀውን ፡ ዘራፊ ፡ በመፍራት ፡ ሕዝቡ ፡ ሸሸ

**rapacity** ዘራፊነት
Some landlords are notorious for their rapacity. አንዳንድ ፡ ቤት ፡ አከራዮች ፡ በዘራፊነታቸው ፡ የታወቁ ፡ ናቸው

**rapid(s)**, n. ፈረሰኛ ፡ ውኃ
Rapids are found where the river is shallow. ወንዙ ፡ ጥልቅ ፡ ያልሆነበት ፡ ቦታ ፡ ፈረሰኛ ፡ ውኃ ፡ ይገኛል

**rapid** (adj.) ፈጣን
Our progress was rapid. ያደረግነው ፡ እርምጃ ፡ ፈጣን ፡ ነበር
*We walked at a rapid pace. በፍጥነት ፡ ተራመድን

**rapidity** መፍጠን
The rapidity of her speech amazes everyone. ስትናገር ፡ መፍጠኗ ፡ ማንንም ፡ ያስደንቃል

**rapidly**
1. ቶሎ ፡ ቶሎ. He works rapidly. ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ይሠራል
2. በፍጥነት. He drove as rapidly as he could. የሚችለውን ፡ ያህል ፡ በፍጥነት ፡ ነዳ

**rapport** መግባባት
There is rapport between the various offices. በልዩ ፡ ልዩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ መግባባት ፡ አለ

**(be) rapt** ተመሰጠ
Rapt in his work, he did not hear his wife coming in. በሥራው ፡ ከመመሰጡ ፡ የተነሣ ፡ ሚስቱ ፡ ስትገባ ፡ አልሰማትም

**rapture** የደስታ ፡ መንፈስ
The music filled him with rapture. ሙዚቃው ፡ የደስታ ፡ መንፈስ ፡ አሳደረበት

**with rapture** በተመስጦ
He gazed with rapture at the face of the girl he adored. የወደዳትን ፡ ልጅ ፡ ፊት ፡ በተመስጦ ፡ አተኩሮ ፡ ተመለከተ

**rare**
1. ብርቅ. Rain is rare in the desert. በምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ ዝናብ ፡ ብርቅ ፡ ነው
The gem of his collection was a rare Ethiopian stamp. ከሰበሰበው ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ የሆነው ፡ ብርቅ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቴምብር ፡ ነበር
2. እንግዳ. This is a rare disease, and there is no cure for it. ይህ ፡ እንግዳ ፡ በሽታ ፡ ስለሆነ ፡ መድኃኒት ፡ የለውም
3. ልዩ. She chanced on a rare kind of mushroom on her walk through the woods. በጫካው ፡ ውስጥ ፡ ስትሄድ ፡ በድንገት ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ እንጉዳይ ፡ አየች
Edison had rare powers as an inventor. ኤዲሰን ፡ የፈልሳፊነት ፡ ልዩ ፡ ችሎታ ፡ ነበረው
4. እንደልብ ፡ የማይገኝ. That's a rare flower. እንደልብ ፡ የማይገኝ ፡ አበባ ፡ ነው
5. በደንብ ፡ ያልበሰለ. He likes rare meat. በደንብ ፡ ያልበሰለ ፡ ሥጋ ፡ ይወዳል
*The rare air of high mountains causes him difficulties in breathing. በከፍተኛ ፡ ተራራዎች ፡ ያለው ፡ ያየር ፡ ማነስ ፡ ለመተንፈስ ፡ ያስቸግራል

**be rare**
1. አይገኝም. Old manuscripts are now quite rare. የጥንት ፡ የእጅ ፡ጽሑፎች ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አይገኙም
2. በብዛት ፡ የለም. Houses are rare on that part of the coast. በዚያ ፡ ጠረፍ ፡ አካባቢ ፡ ቤቶች ፡ በብዛት ፡ የሉም

**(not) be rare** አይጠፋም
Friendship between people of different religions is not rare. ወዳጅነት ፡ በሁለት ፡ በሃይማኖት ፡ በተለያዩ ፡ ሰዎች ፡ መኻል ፡ አይጠፋም

**rarely**
1. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብቻ. The child rarely goes to school. ልጁ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚሄደው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. እምብዛም + (negative verb). He is rarely late for appointments. ለቀጠሮ ፡ እምብዛም ፡ ዘግይቶ ፡ አይመጣም

**rarity**
1. ብርቅ ፡ መሆን. The rarity of diamonds makes them valuable. የአልማዞች ፡ ብርቅ ፡ መሆን ፡ ውድ ፡ ያደርጋቸዋል
2. ብርቅ. This old coin is a rarity. ይህ ፡ የጥንት ፡ ገንዘብ ፡ ብርቅ ፡ ነው
3. ማነስ. The rarity of the air on high mountains is bad for some people. በከፍተኛ ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ያየር ፡ ማነስ ፡ ላንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ መጥፎ ፡ ነው

**rascal** ወስላታ ፤ ቀጣፊ
He is a rascal and cannot be trusted. ወስላታ ፡ (ቀጣፊ) ፡ ስለሆነ ፡ ሊታመን ፡ አይችልም

**rash** (n.) ሽፍታ ፤ ችፍታ
The first sign of measles is a rash. የኩፍኝ ፡ የመጀመሪያ ፡ ምልክት ፡ ሽፍታ ፡ (ችፍታ) ፡ ነው

**rash** (adj.)
1. ችኩል. He is too rash to be given any

responsibility. ችኩል ፡ ስለሆነ ፡ ለሱ ፡ ኀላፊነት ፡ መስጠት ፡ አይገባም
2. አደገኛ. It is rash to cross the street without looking both ways. ግራና ፡ ቀኝ ፡ ሳያዩ ፡ መንገድ ፡ ማቋረጥ ፡ አደገኛ ፡ ነው

**rashness** ችኩልነት
His rashness militates against him. ችኩልነቱ ፡ ጉዳት ፡ ላይ ፡ ይጥለዋል

**rasp** (vt.) ሞረደ
The blacksmith rasped the horse's hoof. ባለ ፡ እጁ ፡ የፈረሱን ፡ ኮቴ ፡ ሞረደው

**rasp** (vi.) ተፋጨ
The file rasped as he worked. እርሱ ፡ ሲሠራ ፡ ሞረዱ ፡ ተፋጨ

**rasp (one's) nerves** አስቀጠጠ
The squeaky door rasps my nerves. ሲጢጥ ፡ የሚለው ፡ በር ፡ ያስቀጥጠኛል

**rasp** (n.) ሞረድ
He smoothed the wood with a rasp. በሞረድ ፡ ዕንጨቱን ፡ አለሰለሰ

**rasping** ጐርናና
He speaks in a rasping voice. ድምፁ ፡ ጐርናና ፡ ነው

**rat** አይጥ
Rats invaded the house. አይጥ ፡ ቤቱን ፡ ወረረው

**rate** (v.)
1. ደረጃ ፡ ሰጠ. How do you rate this hotel? ለዚህ ፡ ሆቴል ፡ ምን ፡ ደረጃ ፡ ትሰጠዋለህ ?
2. ገመተ. He rated him low in reading ability. በማንበብ ፡ ችሎታ ፡ ዝቅተኛ ፡ አድርጎ ፡ ገመተው
Many people rate basketball as dull to watch. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የቅርጫት ፡ ኳስ ፡ ጨዋታን ፡ ለተመልካች ፡ የሚያሰለች ፡ አድርገው ፡ ይገምታሉ

**rate** (n.) ዋጋ
What are the rates for airmail? ያየር ፡ መልእክት ፡ ዋጋው ፡ ስንት ፡ ነው ?
*What are the rates for single rooms? አንድ ፡ ሰው ፡ መኝታ ፡ ክፍል ፡ የሚከፍለው ፡ ስንት ፡ ነው ?
*This salary is figured on an hourly rate. ይህ ፡ ደሞዝ ፡ የሚታሰበው ፡ በሰዓት ፡ ላይ ፡ ነው

**rate of interest** ወለድ
The rate of interest is 6 cents on the dollar. ወለዱ ፡ በመቶ ፡ ስድስት ፡ ነው

**rate of speed** ፍጥነት
In America, the rate of speed is measured in miles per hour. በአሜሪካ ፡ ፍጥነት ፡ የሚለካው ፡ በሰዓትና ፡ በማይል ፡ ነው

**at a fast rate** በፍጥነት
He works at a fast rate. በፍጥነት ፡ ይሠራል

**at a very fast rate** ቶሎ ፡ ቶሎ
She can make dresses at a very fast rate. ቀሚስ ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ መስፋት ፡ ትችላለች

**at any rate** ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ
At any rate, I'd like to see you. ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ላነጋግርህ ፡ እፈልጋለሁ

**at the rate of**
*He walked at the rate of three miles an hour. በሰዓት ፡ ሦስት ፡ ማይል ፡ ሒሳብ ፡ ተራመደ

**at this rate** በዚህ ፡ አያያዝ
At this rate, we will never get done. በዚህ ፡ አያያዝ ፡ መቼም ፡ አንጨርስ

**birth rate** የሚወለዱት ፡ ሕፃናት ፡ ቁጥር
The birth rate is on the increase. የሚወለዱት ፡ ሕፃናት ፡ ቁጥር ፡ በመጨመር ፡ ላይ ፡ ነው
[See also 'exchange']

**rather**
1. እንዲያውም. We won't go; rather, we will stay. አንሄድም ፤ እንዲያውም ፡ እንቆያለን
2. (expressed by composite verbs). The play was rather long. ቲያትሩ ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ነበር
Fifty dollars is rather a lot to pay for a dress. ላንድ ፡ ቀሚስ ፡ ኀምሳ ፡ ብር ፡ መክፈል ፡ ወደድ ፡ ይላል
3. መሳይ. He is a rather crude person. ባለጌ ፡ መሳይ ፡ ሰው ፡ ነው

**rather not**
*Will you come with us? I'd rather not. ከኛ ፡ ጋር ፡ ትሄዳለህ ? ባልሄድ ፡ ይሻለኛል

**rather than**
*This book is based on conjecture rather than research. መጽሐፉ ፡ የተመሠረተው ፡ በይሆናል ፡ እንጂ ፡ በምርምር ፡ ላይ ፡ አይደለም
*This is for your father to decide rather than for you. ይህን ፡ የሚወስኑ ፡ አባትህ ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ አይደለህም

**rather—than**
*I'd rather wait than leave now. አሁን ፡ ከምሄድ ፡ ይልቅ ፡ ብቆይ ፡ ይሻላል
*I'd rather die than give in. ከምተወው ፡ ብሞት ፡ ይሻለኛል
*I would rather go today than tomorrow. ከነገ ፡ ይልቅ ፡ ዛሬ ፡ ብሄድ ፡ እወዳለሁ

**or rather** እንዲያውም
He arrived late last night, or rather, very early this morning. ትናንት ፡ በጣም ፡ አምሽቶ ፡ ገባ ፤ እንዲያውም ፡ ሊነጋጋ ፡ ሲል ፡ ነው

**ratify** (ratified) አጸደቀ
The Senate has to ratify the treaty before it can go into force. ውሉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋሉ ፡
በፊት ፡ የመወሰኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ማጽደቅ ፡
አለበት

**be ratified** ጸደቀ
The treaty was ratified today. ስምምነቱ ፡ ዛሬ ፡
ጸደቀ

**rating**
1. የደረጃ ፡ ድልድል. The rating of the year's best books was published today. ያመቱ ፡ ምር
ጥ ፡ መጽሐፎች ፡ የደረጃ ፡ ድልድል ፡ ዛሬ ፡ ተጽ
ፎ ፡ ወጣ
2. ደረጃ. The rating of this hotel has declined.
የዚህ ፡ ሆቴል ፡ ደረጃ ፡ ዝቅ ፡ ብሏል

**ratio** ተመዛዛኝነት
The ratios of 1 to 5 and 20 to 100 are the same.
አንድ ፡ ላምስትና ፡ ሃያ ፡ ለመቶ ፡ ተመዛዛኝ
ነታቸው ፡ አንድ ፡ ነው

**ration** (v.) እየመጠነ ፡ አከፋፈለ ፤ እየቈጠበ ፡
ዐደለ
Because there were so many, they had to ration food to the refugees. ስደተኞቹ ፡ ብዙ ፡ በመሆናቸ
ው ፡ ምግቡን ፡ እየመጠኑ ፡ ማከፋፈል ፡ (እየቈጠ
በ ፡ ማደል) ፡ ነበረባቸው

**be rationed** በቊጠባ ፡ ታደለ
For the duration of the war, gasoline was rationed. ጦርነቱ ፡ እስከቆየበት ፡ ድረስ ፡ ቤን
ዚን ፡ በቊጠባ ፡ ይታደል ፡ ነበር

**ration** (n.)
1. ራሽን. Rations of sugar were given to the prisoners. ለእስረኞች ፡ የስኳር ፡ ራሽን ፡ ተሰጥ
ቷቸዋል
2. የተወሰነ. The daily ration of meat and bread was absolutely insufficient. ለቀን ፡ የተወ
ሰነው ፡ ሥጋና ፡ ዳቦ ፡ ፈጽሞ ፡ የማይበቃ ፡ ነበር
*Rations of coal were allotted to people who were suffering from the cold. በብርድ ፡ የሚሠ
ቃዩት ፡ ሰዎች ፡ ከሰል ፡ ታደሉ

**rations** ቀለብ
Our rations were bread and soup. ቀለባችን ፡ ሾ
ርባና ፡ ዳቦ ፡ ነበር

**rational**
1. አእምሮ ፡ ያለው. Man is a rational being.
ሰው ፡ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ፍጡር ፡ ነው
2. አስተዋይ. As children grow older, they become more rational. ሕፃናት ፡ እያደጉ ፡ ሲሄዱ ፡
ይበልጥ ፡ አስተዋይ ፡ ይሆናሉ
3. በምርምር ፡ የተደረሰበት. There is a rational explanation for thunder and lightning. ነጐድጓድ
ና ፡ መብረቅ ፡ በምርምር ፡ የተደረሰበት ፡ ምክንያ
ት ፡ አላቸው

**act in a rational way** አመዛዘነ
When very angry, people seldom act in a rational way. ሰዎች ፡ በጣም ፡ ሲናደዱ ፡ እምብዛ
ም ፡ አያመዛዝኑም

**rationalize**
1. አሳበበ. We rationalized the team's defeat by blaming it on the weather. የቡድኑ ፡ መሸነ
ፍ ፡ ካየር ፡ አለመስማማት ፡ ነው ፡ ብለን ፡ አሳበብን
2. በተፈጥሮ ፡ አሠራር ፡ አስረዳ. The teacher likes to rationalize miracles. አስተማሪው ፡ ተ
አምራትን ፡ በተፈጥሮ ፡ አሠራር ፡ ማስረዳት ፡
ይወዳል

**rattle** (vt.)
1. አንገጫገጨ. The wind rattled the windows.
ነፋሱ ፡ መስኮቶቹን ፡ አንገጫገጫቸው
2. አንኰሻኰሸ. The child rattles his toy. ል
ጁ ፡ መጫወቻውን ፡ ያንኰሻኵሻል
3. አደናገረ. A sudden noise rattled the speaker. ድንገተኛ ፡ ድምፅ ፡ ተናጋሪውን ፡ አደ
ናገረው

**rattle** (vi.)
1. ተንገጫገጨ. The window rattled during the storm. በኀይለኛው ፡ ዝናብ ፡ ጊዜ ፡ መስኮቱ ፡ ተንገ
ጫገጨ
2. (= vt.) አንኳኳ. Hail rattled on the roof.
በረዶ ፡ ጣሪያውን ፡ አንኳኳው

**rattle down** እየተንገጫገጨ ፡ ሄደ
The bus rattled down the rocky road. አውቶቡ
ሱ ፡ በኰረኰንቹ ፡ መንገድ ፡ እየተንገጫገጨ ፡ ሄደ

**rattle off** በቃሉ ፡ አንበለበለ
The boy rattled off the poem he had learned.
ልጁ ፡ ያጠናውን ፡ ግጥም ፡ በቃሉ ፡ አንበለበለው

**rattle on** ማውራት ፡ አበዛ
Mary rattles on about her new clothes.
ሜሪ ፡ ስለገዛቻቸው ፡ ልብሶች ፡ ማውራት ፡ ታበዛለች

**rattle** (n.)
1. የሚቅጨለጨል ፡ መጫወቻ. Let the baby have his rattle! ለልጁ ፡ የሚቅጨለጨለውን ፡ መ
ጫወቻ ፡ ስጡት
2. መንቀጫቀጭ. We heard the rattle of the milk bottles in the early morning. የወተት ፡ ጠርሙሶቹ
ን ፡ መንቀጫቀጭ ፡ ማለዳ ፡ ሰማን
3. ድምፅ. The rattle in the car is caused by a defective motor. መኪናው ፡ የሚያሰማው ፡ ድ
ምፅ ፡ ከሞተሩ ፡ መበላሸት ፡ የመጣ ፡ ነው

**raucous** ጉርናና
The man has a raucous voice. ሰውዬው ፡ ጉርና ና ፡ ድምፅ ፡ አለው

**ravage** (v.)
1. አወደመ. The locusts ravaged the fields. አንበጣው ፡ ማሳውን ፡ አወደመው
2. አጠፋ. The forest fire ravaged the country. ጫካው ፡ ውስጥ ፡ የተነሣው ፡ እሳት ፡ አገር ፡ አጠፋ

**ravage** (n.) ጥፋት
The ravages of the wars are indescribable. ጦርነቱ ፡ ያደረሰው ፡ ጥፋት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አይባልም

**rave**
1. ቃዠ. The mental patient raved about his imaginary business. የአእምሮ ፡ ሕመምተኛው ፡ ስ ለሚያልመው ፡ ንግድ ፡ ቃዠ
2. አድንቆ ፡ ተናገረ ፤ በአድናቆት ፡ ተናገረ. Everyone raves about his new book. ስለ ፡ አዲሱ ፡ መጽሐፉ ፡ ሁሉም ፡ አድንቀው ፡ ይናገራሉ
She raved about the food she had in France. ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ስለበላችው ፡ ምግብ ፡ በአድ ናቆት ፡ ተናገረች

**make rave** አቃዠ
The fever made him rave. ትኩሳቱ ፡ አቃዠው

**ravel** ነተበ
The shirt began to ravel at the sleeves. የሸሚዙ ፡ እጅጌ ፡ ነትቧል

**raven** ቁራ
The raven feeds on worms. ቁራ ፡ ትላትል ፡ ይበላል

**ravenous** በቃኝን ፡ የማያውቅ ፤ ስግብግብ
The ravenous boy has eaten everything in the house. በቃኝን ፡ የማያውቀው ፡ (ስግብግቡ) ፡ ል ጅ ፡ የቀረበለትን ፡ ሁሉ ፡ ጨረሰ
*He has a ravenous appetite ብዙ ፡ ይበላል

**ravine** ገደል
The truck fell into the ravine. ካሚዮኑ ፡ ገደል ፡ ውስጥ ፡ ገባ

**raving,** adj. (= adv.) እየቃዠ
Because of his high fever, he made a raving speech. ከንደለኛው ፡ ትኩሳቱ ፡ የተነሣ ፡ እየ ቃዠ ፡ ይናገር ፡ ነበር
*His sister is a raving beauty. እኅቱ ፡ በውበ ቷ ፡ ወደር ፡ የላትም

**(be) ravished** ተመሰጠ
He was ravished by the music. በሙዚቃው ፡ ተ መሰጠ

**ravishing** የሚማርክ
We have a ravishing view of the mountains. የሚማርከውን ፡ የተራራውን ፡ ትርኢይት ፡ ለማየ ት ፡ እንችላለን

**raw**
1. ጥሬ. The meat is raw. ሥጋው ፡ ጥሬ ፡ ነው
Don't eat those potatoes raw! ድንቹን ፡ ጥሬው ን ፡ አትብላው
2. ያልተፈላ. Avoid drinking raw milk! ያልተፈ ላ ፡ ወተት ፡ አትጠጣ
3. ያልተቀቀለ. He eats raw vegetables. ያልተቀ ቀለ ፡ አታክልት ፡ ይበላል
4. ያልሠለጠነ. He sent the raw recruits to the front. ያልሠለጠኑትን ፡ ወታደሮች ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ላካቸው
5. የተላጠ. The raw wound was very painful. የተላጠው ፡ ቁስል ፡ በጣም ፡ ያም ፡ ነበር
6. ቀዝቃዛና ፡ እርጥበት ፡ ያለው. A raw wind blew yesterday. ቀዝቃዛና ፡ እርጥበት ፡ ያለው ፡ ነፋስ ፡ ትናንት ፡ ነፈሰ
*His manners are raw. ባለጌ ፡ ነው

**be raw** ተሰነጣጠቀ
My throat is raw. ጉሮሮዬ ፡ ተሰነጣጥቋል
[See also 'hide, rub']

**rawhide strap** ጠፍር
He tied the poles together with rawhide straps. አጣናዎቹን ፡ በጠፍር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አሰራቸው

**raw materials** ጥሬ ፡ እቃ
Most of Ethiopia's exports are raw materials. አብዛኛዎቹ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ የምት ልካቸው ፡ ጥሬ ፡ እቃዎች ፡ ናቸው

**ray**
1. ጮራ. Ordinary glass keeps out the rays. ተራ ፡ መስታወት ፡ ጮራ ፡ አያስገባም
2. ጨረር. Close the blinds because the sunrays are too hot. የፀሐይዋ ፡ ጨረር ፡ በጣም ፡ ስለሚ ሞቅ ፡ መጋረጃውን ፡ ዝጋው
3. ጭላንጭል. There is still a ray of hope. አሁንም ፡ የተስፋ ፡ ጭላንጭል ፡ አለ

**raze** ድምጥምጡን ፡ አጠፋ
The Romans razed Carthage. ሮማውያን ፡ ካር ታጅን ፡ ድምጥምጧን ፡ አጠፉት

**be razed** ጨርሶ ፡ ተደመሰሰ
The city was razed by the earthquake. ከተማ ው ፡ በመሬቱ ፡ መናወጥ ፡ ጨርሶ ፡ ተደመሰሰ

**razor** ምላጭ
I have to buy a new razor. አዲስ ፡ ምላጭ ፡ መግዛት ፡ አለብኝ

**razor blade** ምላጭ
Please buy me a dozen razor blades! አንድ ፡ ደርዘን ፡ ምላጭ ፡ ግዛልኝ

**to a razor edge** ምላጭ ፡ እስኪሆን
He ground his knife to a razor edge. ቢንጢውን ፡ ምላጭ ፡ እስኪሆን ፡ ሳለው

**reach** (vt.)
1. ደረሰ. We reached the city at daybreak. ጎሕ ፡ ሲቀድ ፡ ከከተማው ፡ ደረስን
The news reached me this morning. ወሬው ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ ደረሰኝ
2. ደረሰ(በት). The child cannot reach the things that are on the shelf. ሕፃኑ ፡ በመደርደሪያው ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ነገሮች ፡ ሊደርስባቸው ፡ አይችልም
3. አቀበለ. Please reach me the salt! ጨውን ፡ ብታቀብለኝ
4. አገኘ. You can reach me at this address. በዚህ ፡ አድራሻ ፡ ታገኘኛለህ
5. ነካ. I cannot reach the top of the wall. የግድግዳውን ፡ ጫፍ ፡ መንካት ፡ አልችልም
The speaker reached the hearts of his hearers. ተናጋሪው ፡ ያድማጮቹን ፡ ስሜት ፡ ነካ
*It took him years to reach my height. በቁመት ፡ እኔን ፡ ለማከል ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ ፈጀበት
*The radio reaches millions. ሬዲዮኑን ፡ በብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ያደምጣሉ

**reach** (vi.) ደረሰ
The damages reached into thousands of dollars. የደረሰው ፡ ጥፋት ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ደረሰ
*The United States reaches from ocean to ocean. አሜሪካ ፡ ከውቅያኖስ ፡ እስከ ፡ ውቅያኖስ ፡ የተዘረጋ ፡ አገር ፡ ነው

**reach for**
1. ሊወስድ ፡ ፈለገ. The little fellow reaches for everything he sees. ትንሹ ፡ ልጅ ፡ ያየውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሊወስድ ፡ ይፈልጋል
2. እጁን ፡ ዘረጋ. Though he has given up smoking, he still reaches for a cigarette from force of habit. ሲጃራ ፡ ማጨስ ፡ ቢያቆምም ፡ ከልማድ ፡ የተነሣ ፡ አሁንም ፡ ሲጃራ ፡ ሲያይ ፡ እጁን ፡ ይዘረጋል
3. ለመውሰድ ፡ እጁን ፡ ሰደደ. The man reached for his gun. ሰውዬው ፡ ሽጉጡን ፡ ለመውሰድ ፡ እጁን ፡ ሰደደ

**reach into**
*He reached into the bag, and took out a book. ከቦርሳው ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ አወጣ

**reach out** እጁን ፡ ዘረጋ
He reached out to grab the knife. ቢላዋውን ፡ ለመውሰድ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ
He reached out to greet us. ሊጨብጠን ፡ እጁን ፡ ዘረጋ

**reach up** ተንጠራራ
He reached up, and shook the branch. ተንጠራርቶ ፡ ቅርንጫፉን ፡ አወዛወዘው

**as far as the eye can reach** ዓይን ፡ እስኪታክት ፡ ድረስ
There was nothing but sand as far as the eye could reach. ዓይን ፡ እስኪታክት ፡ ድረስ ፡ ከሸዋ ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ አልነበረም
[See also 'heyday, limit, maturity, understanding']

**reach** (n.)
*Philosophy is beyond a child's reach. ፍልስፍና ፡ የሕፃን ፡ አእምሮ ፡ የማይደርስበት ፡ ነገር ፡ ነው
*The ball was out of his reach. ኳሷን ፡ ሊይዛት ፡ አልቻለም ፡ ነበር

**within easy reach** ቅርብ
The hotel is within easy reach of the station. ሆቴሉ ፡ ለባቡያው ፡ ቅርብ ፡ ነው

**within (one's) reach**
*I like to have the dictionary within my reach. መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ካጠገቤ ፡ እንዲኖር ፡ እፈልጋለሁ

**(be) within (one's) reach**
1. ለማግኘት ፡ ዕድል ፡ አለው. The office of premier is within his reach. የጠቅላይ ፡ ሚኒስትርነትን ፡ ሥልጣን ፡ ለማግኘት ፡ ዕድል ፡ አለው
2. ሊደርስበት ፡ የሚችል. The city is within reach of the enemy's airforce. ከተማይቱ ፡ የጠላት ፡ አየር ፡ ኀይል ፡ ሊደርስበት ፡ ከሚችል ፡ ስፍራ ፡ ናት

**react**
1. ተቃወመ. The people reacted against the system. ሕዝቡ ፡ ሥርዓቱን ፡ ተቃወመ
2. ዐጸፋውን ፡ ገለጸ. Do children react to kind treatment by becoming friendly? ልጆች ፡ በጥሩ ፡ አኳኋን ፡ ሲያዙ ፡ ዐጸፋውን ፡ በፍቅር ፡ ይገልጻሉ ?
3. አለ. How did the audience react to his remarks? የሱን ፡ አስተያየት ፡ ሲሰሙ ፡ አዳማጮቹ ፡ ምን ፡ አሉ ?
*He reacted against penicillin by getting a high fever. ሰውነቱ ፡ ፔኒሲሊን ፡ አልቀበል ፡ ብሎ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትኩሳት ፡ አመጣበት
*The patient reacts favorably to the treatment. በሽተኛው ፡ ሕክምናው ፡ የተስማማው ፡ ይመስላል

*Do wages and prices react on each other in rising and falling? አበልና ፡ የኑሮ ፡ ውድነት ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ በማለት ፡ የሚገናኙበት ፡ ነገር ፡ አለ ?

**react upon** ደሰ ፡ አሰኘ

Applause reacts upon the speaker. ጭብጨባ ፡ ተናጋሪውን ፡ ደስ ፡ ያሰኘዋል

**not react to** ዝም ፡ አለ

He is so pusillanimous that he will not react to any insult. በጣም ፡ ፈሪ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ሲሰድቡት ፡ ዝም ፡ ይላል

**reaction** አስተያየት

What was his reaction to your suggestion? ስላቀረብከው ፡ አሳብ ፡ አስተያየቱ ፡ እንዴት ፡ ነበር ?

*What was the patient's reaction to the new medicine? አዲሱ ፡ መድኃኒት ፡ በሽተኛውን ፡ እንዴት ፡ አደረገው ?

**reaction against** ተቃውሞ

There was a strong reaction against the new ideas. ስለ ፡ አዲሱ ፡ አስተሳሰብ ፡ ብርቱ ፡ ተቃውሞ ፡ ነበር

**forces of reaction** ለውጥ ፡ የማይፈልጉ ፡ ወገኖች

The forces of reaction in South America made reform difficult. በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ ለውጥ ፡ የማይፈልጉት ፡ ወገኖች ፡ ለመሻሻል ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆኑ

**reactionary** (reactionaries) ለውጥ ፡ የማይፈልግ

In many countries, reactionary classes oppose any reform. በብዙ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ለውጥ ፡ የማይፈልጉ ፡ ወገኖች ፡ ማንኛውንም ፡ መሻሻል ፡ ይቃወማሉ

**read** (read), vt.

1. አነበበ. You should read this book. ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ማንበብ ፡ አለብህ

Can you read music? ኖታ ፡ ማንበብ ፡ ትችላለህ ?

2. አየ(ለት). He read her future in the pebbles. ዕድሏን ፡ በጠጠር ፡ አየላት

3. አሳየ. The thermometer reads thirty-five degrees. የሙቀቱ ፡ መለኪያ ፡ ሠላሳ ፡ አምስት ፡ ዲግሪ ፡ ያሳያል

4. ዐወቀ. God reads man's heart. እግዚአብሔር ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ ያውቃል

5. ተረዳ. I read the answer in his face. መልሱን ፡ ከፊቱ ፡ ተረዳሁ

6. ሊተረጐም ፡ ተቻለ. This rule reads two different ways. ይህ ፡ ሕግ ፡ በሁለት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገዶች ፡ ሊተረጐም ፡ ይቻላል

**read** (vi.)

1. አነበበ. Half the population cannot read. ከሕዝቡ ፡ ግማሹ ፡ ማንበብ ፡ አይችልም

2. አለ. The text reads different from what you told us. ጽሑፉ ፡ የሚለው ፡ አንተ ፡ ከነገርከን ፡ የተለየ ፡ ነገር ፡ ነው

**read like** መሰለ

This does not read like a child's composition. ይህ ፡ የልጅ ፡ ድርሰት ፡ አይመስልም

**read (one's) mind** የ - - - ፍላጎት ፡ ዐወቀ

A good servant can read his master's mind. መልካም ፡ አገልጋይ ፡ የጌታውን ፡ ፍላጎት ፡ ያውቃል

**read out** ጮኽ ፡ ብሎ ፡ አነበበ

He read out the law to us. ሕጉን ፡ ጮኽ ፡ ብሎ ፡ አነበበልን

[See also 'follow, line']

**(be) readable** ይነበባል

This book is easily readable by beginners. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ለጀማሪዎች ፡ በቀላሉ ፡ ይነበባል

His writing is readable. የእጅ ፡ ጽሕፈቱ ፡ ይነበባል

**reader**

1. አንባቢ. Our newspaper has more than a million readers. ጋዜጣችን ፡ ከሚሊዮን ፡ በላይ ፡ አንባቢዎች ፡ አሉት

2. የንባብ ፡ መጽሐፍ. We need third-grade readers. የሦስተኛ ፡ ክፍል ፡ የንባብ ፡ መጻሕፍት ፡ ያስፈልጉናል

**readership** አንባቢዎች

This periodical has a small readership. ይህ ፡ መጽሔት ፡ ያሉት ፡ አንባቢዎች ፡ ጥቂት ፡ ናቸው

**readily**

1. ወዲያው ፤ በፍጥነት. He admitted his guilt readily. ጥፋቱን ፡ ወዲያው ፡ አመነ

Tom acclimated himself readily to the new town. ቶም ፡ አዲሱ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ በፍጥነት ፡ ለመደ

2. ጉልቶ. Beneath the veneer of Western civilization, the spirit of Islam is readily apparent. ከምዕራባዊ ፡ ሥልጣን ፡ ሽፋን ፡ ሥር ፡ የእስላም ፡ መንፈስ ፡ ጉልቶ ፡ ይታያል

**readiness** ዝግጁ ፡ መሆን

His readiness to help made him many friends. ለመርዳት ፡ ዝግጁ ፡ መሆኑ ፡ ብዙ ፡ ወዳጆች ፡ አተረፈለት

**in readiness** ተዘጋጅቶ

Wait in readiness for the announcement of the plane departure! አውሮፕላኑ ፡ ስለሚነሣበት ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠውን ፡ መግለጫ ፡ ተዘጋጅተህ ፡ ጠብቅ

**reading**

1. ንባብ. He got seventy in reading. በንባብ ፡ ሰባ ፡ አገኘ

2. አነባበብ. I like his poetry reading. የግጥም ፡ አነባበቡ ፡ ደስ ፡ ይለኛል

3. የሚነበብ. There is little reading in this picture magazine. በዚህ ፡ ሥዕላዊ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ የሚነበብ ፡ ጥቂት ፡ ነው

4. (= to read) ማንበብ. This novel is good reading. ይህን ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፍ ፡ ማንበብ ፡ ያስደስታል

*I have written down the readings of my thermometer. የሙቀት ፡ መለኪያው ፡ በየጊዜው ፡ የሚያሳየውን ፡ የሙቀት ፡ ልክ ፡ መዝግቤያለሁ

**give a reading** ለሕዝብ ፡ አሰማ

Our class gave a reading of Dickens' story. ክፍላችን ፡ ዲከንስ ፡ የጻፈውን ፡ ታሪክ ፡ ለሕዝብ ፡ አሰማ

**make good reading** ሲያነቡት ፡ ደስ ፡ ይላል

The story of his life makes good reading. የሕይወት ፡ ታሪኩ ፡ ሲያነቡት ፡ ደስ ፡ ይላል

**reading room** የንባብ ፡ ክፍል

This library has a large reading room. ይህ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ሰፊ ፡ የንባብ ፡ ክፍል ፡ አለው

**readjust** አስተካከለ

The jeweler readjusted my watch. ሰዓት ፡ ሠሪው ፡ ሰዓቴን ፡ አስተካከለልኝ

**ready** (v.) አዘጋጀ

Did you ready the house for company? ለእንግዶች ፡ ቤቱን ፡ አዘጋጀሽ ?

**ready oneself** የሚያስፈልገውን ፡ ዝግጅት ፡ አደረገ

He readied himself for a long trip. ለረጅም ፡ ጉዞ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ዝግጅት ፡ አደረገ

**ready** (adj.)

1. ዝግጁ. The soldiers are ready to die for their country. ወታደሮቹ ፡ ላገራቸው ፡ ለመሞት ፡ ዝግጁ ፡ ናቸው

I am always ready to help. ምንጊዜም ፡ ለመርዳት ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ

2. (= adv.) በፍጥነተ. The students gave ready answers. ተማሪዎቹ ፡ በፍጥነት ፡ መልስ ፡ ሰጡ

*He always has a ready answer. ምን ፡ ጊዜም ፡ መልስ ፡ አያጣም

**ready money** ገንዘብ

I have no ready money. ምንም ፡ ገንዘብ ፡ አልያዝኩ

**be ready**

1. ተዘጋጀ. Are you ready? The bus is going to leave. ተዘጋጅታችኋል? አውቶቡሱ ፡ ሊነሣ ፡ ነው

2. ደረሰ. Dinner is ready. ራት ፡ ደርሷል

**be ready to** ል + imperfect + ምንም ፡ አልቀረው

She is so upset, she is ready to cry. በጣም ፡ ተበሳጭታለች ፤ ልታለቅስ ፡ ምንም ፡ አልቀራት

**get ready** (vt.)

1. አዘጋጀ. Since I am going to Harar tomorrow, get my clothes ready. ነገ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ስለምሄድ ፡ ልብስ ፡ አዘጋጂልኝ

2. ሠራ. I have to get breakfast ready. ቁርስ ፡ መሥራት ፡ አለብኝ

**get ready** (vi.) ተዘጋጀ

How long will it take you to get ready? ለመዘጋጀት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይፈጅብሃል ?

**keep ready** አዘጋጅቶ ፡ ተጠባበቀ

Keep pen and pencil ready for the exam! ፈተና ፡ ስለደረሰ ፡ ብዕርና ፡ እርሳስ ፡ አዘጋጅተህ ፡ ተጠባበቅ

**make ready** አዘጋጀ

The municipality made the stadium ready for the Olympic Games. ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ እስታዲዮሙን ፡ ለኦሎምፒክ ፡ ጨዋታዎች ፡ አዘጋጀ

**ready-made**

1. ተዘጋጅቶ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚሸጥ. Ready-made meals are popular in the United States. በአሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ ተዘጋጅተው ፡ ለሕዝብ ፡ የሚሸጡ ፡ ምግቦች ፡ በጣም ፡ ተወዳጆች ፡ ናቸው

2. እንደተሰፋ. Do you buy your clothes ready-made? ልብስህን ፡ የምትገዛው ፡ እንደተሰፋ ፡ ነው ?

**reaffirm** ደግሞ ፡ አረጋገጠ

He reaffirmed his intention to leave. ለመሄድ ፡ ያለውን ፡ ሐሳብ ፡ ደግሞ ፡ አረጋገጠ

**real**

1. እውነተኛ. That's what I call a real friend. እውነተኛ ፡ ጓደኛ ፡ የምለው ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ነው

Was the thing you saw last night real or imaginary? ትናንት ፡ ማታ ፡ ያየኸው ፡ ነገር ፡ እውነተኛ ፡ ነበር ፡ ወይስ ፡ በሐሳብ ፡ የመጣ ?

2 የእውነት. He is not a real doctor; he is a fake. እሱ ፡ የእውነት ፡ ሳይሆን ፡ አባይ ፡ ሐኪም ፡ ነው

3. ትክክል. This word is not a real word; it is only a misprint. ይህ ፡ ቃል ፡ ትክክል ፡ አይደለም ፤ የእትም ፡ ስሕተት ፡ ነው

4. ዋና. What was the real reason for his leaving the country? አገሩን ፡ ትቶ ፡ የሄደበት ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ምንድን ፡ ነው ?
5. ደንበኛ. Is this real silk? ይህ ፡ ደንበኛ ፡ ሐር ፡ ነው ?
6. (= adv.) በጣም. It was a real pleasure to listen to him deliver his speech. ንግግሩን ፡ ሲያደርግ ፡ ማዳመጥ ፡ በጣም ፡ ያስደስት ፡ ነበር

**in real life** በውን
That never happens in real life. እንዲህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ በውን ፡ አይደርስም
[See also 'thing']

**real estate** የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት
They have imposed a new tax on all real estate. በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ አዲስ ፡ ቀረጥ ፡ ጥለዋል

**realistic** ትክክለኛ
She gave a realistic description of the town. ስለ ፡ ከተማው ፡ ትክክለኛውን ፡ መግለጫ ፡ ሰጠች
*He is a realistic man, not a dreamer. በተጨበጠ ፡ ነገር ፡ የሚያምን ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ በሐሳብ ፡ ብቻ ፡ የሚኖር ፡ አይደለም
*He is very realistic about his chances of getting that job. ለመቀጠርና ፡ ላለመቀጠር ፡ ያለውን ፡ ዕድል ፡ አመዛዝኖ ፡ ተመልክቶታል

**reality** (realities)
1. እውነት. He confuses dreams with reality. ሕልምንና ፡ እውነትን ፡ አይለይም
2. ሥጋዌ. He believes in the reality of Christ. በክርስቶስ ፡ ሥጋዌ ፡ ያምናል
*Slaughter and destruction are the realities of war. መግደልና ፡ ንብረት ፡ ማጥፋት ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ መድረሳቸው ፡ የማይቀር ፡ ነው

**in reality** በእውነቱ
In reality, he is only a poor student. በእውነቱ ፡ በጣም ፡ ችግረኛ ፡ ተማሪ ፡ ነው

**realization**
1. ከግብ ፡ መድረስ. The realization of her hope to become a singer made her happy. ዘማሪ ፡ ለመሆን ፡ ያላት ፡ ተስፋ ፡ ከግብ ፡ መድረሱ ፡ አስደስቷታል
2. ማከናወን. His lofty aims proved impossible of realization. ከፍተኛ ፡ ዓላማዎቹ ፡ ለማከናወን ፡ የማይቻሉ ፡ ነው
*He spent ten years in the realization of his hope for a new hospital. አዲስ ፡ ሆስፒታል ፡ ለመሥራት ፡ የነበረው ፡ ሐሳቡ ፡ በዐሥር ፡ ዓመቱ ፡ ተፈጸመለት
*Full realization of what had happened came years later. ምን ፡ ሆኖ ፡ እንደነበረ ፡ ለማወቅ ፡ የተቻለው ፡ ከብዙ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ነው

**have a realization of** ተረዳ
The travelers had a full realization of the dangers they would face. መንገደኞቹ ፡ የሚገጥሟቸውን ፡ አደጋዎች ፡ በሙሉ ፡ ተረድተው ፡ ነበር

**realize**
1. ከፍጻሜ ፡ አደረሰ. Her uncle's present made it possible for her to realize her dream of going to college. ያጐቷ ፡ ስጦታ ፡ ኮሌጅ ፡ ለመግባት ፡ የነበራትን ፡ ሐሳብ ፡ ከፍጻሜ ፡ አደረሰላት
2. ፈጸመ(ተፈጸመ). His high ambitions were never realized. ከፍተኛ ፡ ምኞቱ ፡ ሳይፈጸምለት ፡ ቀረ
3. አመነ. I simply can't realize he is dead. መሞቱን ፡ ማመን ፡ አልችልም
4. ተገነዘበ. When he realized what he had done, he hung his head. የሠራውን ፡ በተገነዘበ ፡ ጊዜ ፡ አቀረቀረ
5. ተረዳ(ው). He doesn't realize how much work is involved. ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚያደክም ፡ አልተረዳውም
6. ዐወቀ. Does he realize how sick he is ? ምን ፡ ያህል ፡ እንደታመመ ፡ ያውቀዋል ?
7. አገኘ. He realized quite a profit on that business. በዚያ ፡ ንግድ ፡ ጠቀም ፡ ያለ ፡ ትርፍ ፡ አገኘ
8. ሸጠ. Before going to England, he realized all his American property. ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ በአሜሪካ ፡ የነበረውን ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ ሸጠ

**really**
1. በእውነቱ. Really, you shouldn't do that. በእውነቱ ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ አይገባህም
He is really the best teacher we have. በእውነቱ ፡ ካሉን ፡ አስተማሪዎች ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ እርሱ ፡ ነው
2. በእርግጥ. The alleged theft never really happened. የተባለው ፡ ስርቆት ፡ በእርግጥ ፡ አልደረሰም
3. በጣም. The pinch really hurts. ቁንጥጫው ፡ በጣም ፡ ያማል
*He is really older than he looks. እንደፊቱ ፡ ሳይሆን ፡ በዕድሜው ፡ ጠና ፡ ያለ ፡ ነው
*Do you really mean it? የምርህን ፡ ነው ?

**realm** ግዛት
The realm of Ethiopia stretches from the Red Sea to the Sudan. የኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ከቀይ ፡ ባሕር ፡ እስከ ፡ ሱዳን ፡ ይደርሳል

*The realm of poetry is closed to some people. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ግጥም ፡ አይሆንላቸውም

**realty** የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት
Realty is expensive in Los Angeles. ሎስ ፡ አንጀለስ ፡ ውስጥ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ውድ ፡ ነው

**reanimate** አዲስ ፡ ኀይል ፡ ሰጠ
The cheers of the crowd reanimate the losing team. የተመልካቾቹ ፡ ማበረታታት ፡ ለተሸናፊው ፡ ቡድን ፡ አዲስ ፡ ኀይል ፡ ይሰጠዋል

**reap**
1. *አመረተ*. He is reaping ten times as much as he sowed. *የዘራውን ፡ ዐሥር ፡ ዕጥፍ ፡ ያመርታል*
2. አገኘ. He reaped his just reward. የሚገባውን ፡ ዋጋ ፡ አገኘ

**reappear**
1. እንደገና ፡ ብቅ ፡ አለ. He reappeared after an absence of twenty years. ሃያ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ጠፍቶ ፡ እንደገና ፡ ብቅ ፡ አለ
2. እንደገና ፡ ወጣ. The river reappears on the other side of the mountain. ወንዙ ፡ እንደገና ፡ በተራራው ፡ በስተጀርባ ፡ ይወጣል

**reappraisal**
*Our relations require reappraisal. ግንኙነታችን ፡ እንደገና ፡ እንዲታሰብበት ፡ ያስፈልጋል

**rear** (vt.)
1. አሳደገ. She reared her family on milk and bread. ልጆቿን ፡ በወተትና ፡ በዳቦ ፡ አሳደገች
2. አረባ. His main income is from rearing horses. ዋና ፡ ገቢው ፡ ፈረስ ፡ በማርባት ፡ ነው
3. ቀና ፡ አደረገ. The snake reared his head. እባቡ ፡ ጭንቅላቱን ፡ ቀና ፡ አደረገ
4. አቆመ. The men of old reared altars to their gods. የጥንት ፡ ሰዎች ፡ ለጣዖቶቻቸው ፡ መሠዊያዎች ፡ አቆሙ

**rear** (vi.) በኋላ ፡ እግሮቹ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ
The horse reared, and threw his rider. ፈረሱ ፡ በኋላ ፡ እግሮቹ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ በመቆም ፡ ጋላቢውን ፡ ጣለው

**rear** (n.)
1. መቀመጫ. I gave him a kick in the rear. መቀመጫው ፡ ላይ ፡ ረገጥኩት
2. ጀርባ. We attacked the enemy in the rear. ጠላትን ፡ ከጀርባ ፡ ወጋነው
3. ኋላ. He was attacked from the rear. ከኋላው ፡ ተመታ
4. (= adv.) ከኋላ ፡ በኩል. The rear of the bus was full of passengers. አውቶቡሱ ፡ ከኋላ ፡ በኩል ፡ ሞልቶ ፡ ነበር

**in the rear of** ከ - - - በስተጀርባ
The kitchen is in the rear of the hotel. ወጥ ፡ ቤቱ ፡ ከሆቴሉ ፡ በስተጀርባ ፡ ነው

**rear** (adj.) ኋለኛ
The rear wheels are stuck in the mud. ኋለኛውን ፡ ጎማ ፡ ጭቃ ፡ ይዞታል
Leave by the rear door of the bus! በኋለኛው ፡ የአውቶቡሱ ፡ በር ፡ ውጡ

**rear guard** የደጀን ፡ ዘብ
An attack on the rear guard demoralized the army. የደጀኑ ፡ ዘብ ፡ መጠቃት ፡ የጦሩን ፡ ሞራል ፡ ሰበረው

**rearm** እንደገና ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ራሱን ፡ አደረጀ
Our country needs to rearm now. አገራችን ፡ እንደገና ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ራሷን ፡ ማደርጀት ፡ አለባት

**rearmost** ከ - - - ኋላ ፡ የነበረ
The rearmost man slipped away from the parade and hid. ከሰልፉ ፡ ኋላ ፡ የነበረው ፡ ሰውዬ ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ወጥቶ ፡ ተደበቀ

**reason** (vt.)
1. ገመተ. He reasoned that if we started at dawn, we could arrive home by noon. ጐሕ ፡ ሲቀድ ፡ ብንነሣ ፡ ቀትር ፡ ላይ ፡ ቤታችን ፡ እንደምንደርስ ፡ ገመተ
2. አመዛዝኖ ፡ ደረሰበት. The detective reasoned that the murderer was a man. ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ ወንድ ፡ መሆኑን ፡ ወንጀል ፡ መርማሪው ፡ አመዛዝኖ ፡ ደረሰበት

**reason** (vi.)
1. *ተመራመረ*. A child cannot reason. ሕፃን ፡ ሊመራመር ፡ አይችልም
2. አስረዳ. The teacher reasoned so clearly that anyone could follow him. አስተማሪው ፡ ማንም ፡ ሊከተለው ፡ በሚችል ፡ መንገድ ፡ በግልጽ ፡ ያስረዳ ፡ ነበር
3. በሚገባ ፡ አስረዳ. He reasoned with her and made her change her mind. በሚገባ ፡ አስረድቶ ፡ ሐሳቧን ፡ እንድትለውጥ ፡ አደረጋት

**reason with** አግባባ
It is hard to reason with a stubborn child. ድርቅ ፡ የሚልን ፡ ሕፃን ፡ ማግባባት ፡ ያስቸግራል

**reason** (n.)
1. ምክንያት. Is that the reason you didn't go? ያልሄድክበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ?

I have reasons for believing that he is still in Ethiopia. እስካሁን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ መሆኑን ፡ የሚያሳምኑኝ ፡ ምክንያቶች ፡ አሉኝ
2. አእምሮ. The poor fellow lost his reason when his wife died. ምስኪኑ ፡ ሚስቱ ፡ በሞተችበት ፡ ጊዜ ፡ አእምሮውን ፡ ሳተ
3. የማሰብ ፡ ኀይል. Only man has reason. የማሰብ ፡ ኀይል ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው
4. ምርምር. Should sentiment be controlled by reason? ስሜት ፡ በምርምር ፡ ይገታ ?
*He gave me no reason for complaint. ላማርርበት ፡ የሚያስችለኝ ፡ ምንም ፡ አላደረገም

**bring (someone) to reason** አግባባ
The mother tried to bring her stubborn daughter to reason. እናቲቱ ፡ እልኸኛ ፡ ልጇን ፡ ለማግባባት ፡ ሞከረች

**by reason of** (= conj.) ስለ
He was consulted regarding such problems by reason of his long experience. የረጅም ፡ ጊዜ ፡ ልምድ ፡ ስላለው ፡ እንዚህን ፡ ስለመሳሰሉ ፡ ጉዳዮች ፡ ምክር ፡ ይጠየቃል

**listen to reason** ሰው ፡ የሚለውን ፡ ሰማ ፤ የሰው ፡ ሐሳብ ፡ ተቀበለ
Please listen to reason, and don't go out at night! ሰው ፡ የሚልህን ፡ ስማና ፡ ማምሸት ፡ ይቅርብህ
I tried to remonstrate with her, but she wouldn't listen to reason. በመቃወም ፡ ልከራከራት ፡ ሞከርኩ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ሐሳብ ፡ አትቀበልም

**with reason** በቂ ፡ ማስረጃ ፡ በመስጠት
He complains, with reason, that he has been unfairly punished. በቂ ፡ ማስረጃ ፡ በመስጠት ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ መቀጣቱን ፡ አማረረ

**within reason**
Her demands are within reason. ጥያቄዋ ፡ ከተገቢው ፡ ውጭ ፡ አይደለም
[See also 'own, rhyme, sentimental, stand']

## reasonable
1. አስተዋይ. I like to work with him since he is a very reasonable person. በጣም ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ መሥራት ፡ እወዳለሁ
2. መጠነኛ. Ninety dollars is a reasonable amount to pay for a coat. ላንድ ፡ ኮት ፡ ዘጠና ፡ ብር ፡ መክፈል ፡ መጠነኛ ፡ ዋጋ ፡ ነው
3. ተገቢ. He is a reasonable choice for chairman. ለሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ቢመረጥ ፡ ተገቢ ፡ ነው
4. ደኅና. He gave me reasonable terms for paying back the debt. ዕዳውን ፡ የምከፍልበት ፡ ደኅና ፡ ውል ፡ አደረገልኝ
5. ደኅና ፡ መስሎ ፡ የታየ. I am open to any reasonable offer. የሚቀርብልኝ ፡ ነገር ፡ ደኅና ፡ መስሎ ፡ ከታየኝ ፡ እቀበለዋለሁ

**be reasonable** ረከሰ ፡ አለ
Chicken is reasonable this week. በዚህ ፡ ሳምንት ፡ ዶሮ ፡ ረከስ ፡ ብሏል

## reasoning አስተሳሰብ
I can't understand your reasoning. አስተሳሰብህ ፡ አይገባኝም
*He solved the problem after long reasoning. ብዙ ፡ ካወጣና ፡ ካወረደ ፡ በኋላ ፡ ለጉዳዩ ፡ መፍትሔ ፡ አገኘ
*There is no reasoning with that woman. ከዚያች ፡ ሴትዮ ፡ ጋር ፡ መከራከር ፡ ለመድረቅ ፡ ነው

**powers of reasoning** ተመራማሪነት
He surpasses us in powers of reasoning. በተመራማሪነት ፡ ይበልጠናል
[See also 'logical']

## reassemble (vt.) ገጣጠመ
The watchmaker took my watch apart, and reassembled it. ሰዓት ፡ ሠሪው ፡ ሰዓቴን ፡ ፈታቶ ፡ ገጣጠመው

**reassemble** (vi.) እንደገና ፡ ተሰበሰበ
The class reassembled after recess. ተማሪዎቹ ፡ ከዕረፍት ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ተሰበሰቡ

## reassure
1. አረጋገጠ. He reassured her that he was no bandit. ሽፍታ ፡ አለመሆኑን ፡ አረጋገጠላት
2. አጽናና. The captain's confidence during the storm reassured the passengers. ማዕበሉ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ የመርከቡ ፡ አዛዥ ፡ ያሳየው ፡ በራስ ፡ የመተማመን ፡ መንፈስ ፡ መንገደኞችን ፡ አጽናናቸው

**feel reassured** ተጽናና
She felt reassured when she saw there were policemen nearby. በአቅራቢያው ፡ ፖሊሶች ፡ መኖራቸውን ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ተጽናናች

## rebate ቅናሽ
You can get a rebate on goods produced in this country. ባገር ፡ ውስጥ ፡ ከተሠሩ ፡ እቃዎች ፡ ላይ ፡ ቅናሽ ፡ ታገኛለህ

## rebel (rebelled), v.
1. በመቃወም ፡ ዐመፀ. The workers rebelled against the tax. ሠራተኞቹ ፡ ግብሩን ፡ በመቃወም ፡ ዐመፁ
2. አልወደደም. We rebelled at having to stay in on so fine a day. በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አስደሳች ፡ ቀን ፡ እቤት ፡ መዋሉን ፡ አልወደድነውም

**rebel** (n.) ዐመፀኛ ፤ አግዳሚ
The rebel was hanged publicly. ዐመፀኛው ፡ (አግዳሚው) ፡ ባደባባይ ፡ ተሰቀለ

**rebellion** ዐመፅ
The rebellion was put down with bloodshed. ዐመፁ ፡ በደም ፡ መፋሰስ ፡ ተደመሰሰ
The slaves rose in rebellion against their masters. ባርያዎቹ ፡ በጌቶቻቸው ፡ ላይ ፡ በዐመፅ ፡ ተነሡ

**rebellious**
1. ያመፀ. The rebellious colonies achieved independence. ያመፁት ፡ ቅኝ ፡ ግዛቶች ፡ ነጻነታቸውን ፡ አገኙ
2. ዐመፀኛ. The child has become rebellious since her father's death. ልጅቷ ፡ አባቷ ፡ ከሞቱ ፡ ወዲህ ፡ ዐመፀኛ ፡ ሆናለች

**rebirth** ማንሰራራት
The rebirth of learning in the West was brought about by Italians. በምዕራብ ፡ የጥበብ ፡ ማንሰራራት ፡ ሊገኝ ፡ የቻለው ፡ በጣሊያኖች ፡ ነው

**(be) reborn** እንደገና ፡ ተወለደ
Mussolini claimed that the Roman Empire was reborn when he took power. ሙሶሊኒ ፡ ሥልጣን ፡ ሲይዝ ፡ የጥንት ፡ ሮማውያን ፡ መንግሥት ፡ እንደገና ፡ መወለዱን ፡ ገለጸ

**rebound** (v.) ነጥሮ ፡ ተመለሰ
The ball rebounded off the wall. ኳሱ ፡ ግድግዳው ፡ ላይ ፡ ነጥሮ ፡ ተመለሰ

**rebound** (n.), **on the ~** ነጥሮ ፡ ሲመለስ
I caught the ball on the rebound. ኳሱን ፡ ነጥሮ ፡ ሲመለስ ፡ ቀለብኩት

**rebuff** (v.) በንቀት ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀረ ፤ አልቀበልም ፡ አለ
He rebuffed our friendship. የኛን ፡ ጓደኝነት ፡ በንቀት ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀረ
She rebuffed all his efforts to make peace. ለመታረቅ ፡ ያደረገውን ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ አልቀበልም ፡ አለች

**rebuff** (n.), **meet with a ~** እምቢ ፡ ተባለ
I met with a rebuff when I asked for the car. መኪና ፡ ብለምን ፡ እምቢ ፡ ተባልኩ

**rebuild** (rebuilt) እንደገና ፡ አሠራ
The government rebuilt the bridge which had been destroyed in the flood. በጐርፉ ፡ የተበላሸውን ፡ ድልድይ ፡ መንግሥት ፡ እንደገና ፡ አሠራው

**rebuilt** (adj.) የታደሰ ፤ እጅ ፡ ሥራ ፡ የገባበት
I bought a rebuilt typewriter. የታደሰ ፡ የጽሕፈት ፡ መኪና ፡ ገዛሁ
I bought a rebuilt gun. እጅ ፡ ሥራ ፡ የገባበት ፡ ጠመንጃ ፡ ገዛሁ

**rebuke** (v.) ገሠጸ
She rebuked him for his rudeness. ስለ ፡ ብልግናው ፡ ገሠጸችው

**rebuke** (n.) ነቀፌታ ፤ ግሣጼ
The rebuke abashed him. ነቀፌታው ፡ አሳፈረው
He listened to the rebuke in silence. ግሣጼውን ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አዳመጠ

**rebut** (rebutted) አፈረሰ(በት)
I tried to rebut his argument. ክርክሩን ፡ ላፈርስበት ፡ ሞከርኩ

**rebuttal** ክርክሩን ፡ ማፍረስ
I need time to figure out a rebuttal. ክርክሩን ፡ ለማፍረስ ፡ የማዘጋጅበት ፡ ጊዜ ፡ ያስፈልገኛል

**recalcitrant**
1. እምቢተኛ. The teacher punished the recalcitrant student. አስተማሪው ፡ እምቢተኛውን ፡ ተማሪ ፡ ቀጣው
2. ልግመኛ. Prods are used to make recalcitrant cattle move. ሾል ፡ ዘንግ ፡ ልግመኛን ፡ ከብቶች ፡ ለመንዳት ፡ ይረዳል

**recall**
1. አስታወሰ. Do you recall whether he was there? እዚያ ፡ መኖሩን ፡ ታስታውሳለህ ?
2. ነጠቀ. The municipality recalled his driver's license. ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ የመንጃ ፡ ፈቃዱን ፡ ነጠቀው

**be recalled**
1. ወደ ፡ አገሩ ፡ ተጠራ. The ambassador has been recalled. አምባሳደሩ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተጠራ
2. እንዲመለስ ፡ ተደረገ. The retired captain was recalled to duty. ጡረታ ፡ የወጣው ፡ ሻምበል ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ እንዲመለስ ፡ ተደረገ
3. ተመለሰ. The order has been given, and cannot be recalled. ትእዛዙ ፡ ስለተላለፈ ፡ ሊመለስ ፡ አይችልም

**recant**
1. ዐጠፈ. The witness recanted his testimony during the trial. ምስክሩ ፡ በፍርድ ፡ በቀረበበት ፡ ጊዜ ፡ ቃሉን ፡ ዐጠፈ
2. ካደ. He publicly recanted his views. የቀድሞ ፡ አስተያየቱን ፡ በይፋ ፡ ካደ

**make recant** ሐሳብ ፡ አስለወጠ
The police could not make the man recant. ፖሊሶቹ ፡ የሰውዬውን ፡ ሐሳብ ፡ ሊያስለውጡት ፡ አልቻሉም

**recapitulate** እንደገና ፡ ገለጸ
He recapitulated the argument briefly for the benefit of the newcomers. ገና ፡ ለመጡት ፡ ሰዎች ፡ ሲል ፡ የተደረገውን ፡ ክርክር ፡ እንደገና ፡ ባጭሩ ፡ ገለጸ

**recapture** መልሶ ፡ ያዘ
The soldiers recaptured the city. ወታደሮቹ ፡ ከተማውን ፡ መልሰው ፡ ያዙ

**recede** ሸሸ ፤ ወደኋላ ፡ ሸሸ
When the water receded, it left the streets covered with mud. ውኃው ፡ ከሸሸ ፡ በኋላ ፡ መንገዱ ፡ ሁሉ ፡ ደለል ፡ ብቻ ፡ ነበር
The waves recede from the rocks. ሞገዱ ፡ ከአለቱ ፡ ይሸሻል
Due to the action of the waves, the shoreline is gradually receding. ከሞገዱ ፡ የተነሣ ፡ የባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ወደኋላ ፡ ሸሽቷል
*The airplane receded in the distance. አውሮፕላኑ ፡ እየራቀ ፡ ሄደ

**receding**
He has a receding chin. አገጩ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፡ ያለ ፡ ነው
**be receding** እያለቀ ፡ ነው
His hair is receding. ጸጉሩ ፡ እያለቀ ፡ ነው

**receipt**
1. ደረሰኝ. Please give me a receipt for my payment! የከፈልኩበትን ፡ ደረሰኝ ፡ ስጠኝ
2. መድረስ. Please acknowledge receipt! መድረሱን ፡ ግለጽልኝ
*I am in receipt of your letter of 10 May. ግንቦት ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ የተጻፈው ፡ ደብዳቤህ ፡ ደርሶኛል
**receipts** ገቢ
The receipts were low today. ዛሬ ፡ ገቢው ፡ ዝቅተኛ ፡ ነበር
**on (upon) the receipt of**
1. ሲሰማ. On the receipt of the news, she fell in a faint. ወሬውን ፡ ስትሰማ ፡ ሕይወቷን ፡ ስታ ፡ ወደቀች
2. ሲደርሰው. Upon the receipt of the telegram, she fainted. ቴሌግራሙ ፡ ሲደርሳት ፡ ነፍሷን ፡ ሳተች

**receive**
1. ተቀበለ. He received us at the door when we arrived. ስንደርስ ፡ ከበር ፡ ተቀበለን
2. ተቀብሎ ፡ አነጋገረ. The President received the new ambassador. ፕሬዚዳንቱ ፡ አዲሱን ፡ አምባሳደር ፡ ተቀብለው ፡ አነጋገሩ
3. ደረሰ(ው). +Did you receive my telegram? ቴሌግራሜ ፡ ደረሰህ ?
4. ሳበ. Our radio receives poorly. ሬዲዮናችን ፡ በደንብ ፡ አይስብም
*The audience received the speech with wild applause. አዳማጮቹ ፡ ለንግግሩ ፡ ታላቅ ፡ ጭብጨባ ፡ አደረጉ
*The hotel is now open to receive guests. ሆቴሉ ፡ አሁን ፡ ለሕዝብ ፡ ክፍት ፡ ነው
**be received** አቀባበል ፡ ተደረገ(ለት)
We were cordially received. ከልብ ፡ የሆነ ፡ አቀባበል ፡ ተደረገልን
**be well received** ተቀባይነት ፡ አገኘ ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተቀባይነት ፡ አገኘ
His commentary on Ethiopia was well received. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሰጠው ፡ ሐተታ ፡ ተቀባይነት ፡ (ከፍ ፡ ያለ ፡ ተቀባይነት) ፡ አገኘ
[See also 'education, state, weight']

**receiver**
1. ተቀባይ. John was the receiver of the football award. ጆን ፡ የእግር ፡ ኳሱ ፡ ሽልማት ፡ ተቀባይ ፡ ነበር
2. የስልክ ፡ መነጋገሪያ. Take the receiver off the hook! የስልኩን ፡ መነጋገሪያ ፡ ከመስቀያው ፡ ላይ ፡ አንሣ

**recent**
1. የቅርብ. Telephones with dials are a recent invention. በቁጥር ፡ የሚደወሉ ፡ ስልኮች ፡ የቅርብ ፡ ፍልሰፋ ፡ ናቸው
2. በቅርብ ፡ የወጣ. Don't you have any recent newspapers? በቅርብ ፡ የወጡ ፡ ጋዜጦች ፡ የሉህም ?
3. በቅርቡ ፡ የሆነ. Can you quote a recent instance? በቅርቡ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ልትጠቅስ ፡ ትችላለህ ?
4. (= adv.) በቅርብ. Radio is a recent invention. ራዲዮን ፡ በቅርብ ፡ የተፈለሰፈ ፡ ነገር ፡ ነው
*What is the recent news? ምን ፡ ይወራል ?

**recently** በቅርብ ፡ ጊዜ ፤ በቅርቡ
The eucalyptus tree was recently introduced to Ethiopia. ባሕር ፡ ዛፍ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጣው ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ነው
I heard it only recently. የሰማሁት ፡ በቅርቡ ፡ ነው

**receptacle**
1. ቆሻሻ ፡ ማከማቻ. Throw all the rags in the

receptacle! ቡትቶውን ፡ ሁሉ ፡ ቆሻሻው ፡ ማከማ
ቻ ፡ ውስጥ ፡ ጣለው
2. የሚከትበት ፡ እቃ. I need a receptacle to put these things in. እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ የምከትበ
ት ፡ እቃ ፡ እፈልጋለሁ

**reception**
1. አቀባበል. He gave us a warm reception. የጋለ ፡ አቀባበል ፡ አደረገልን
2. መቀበያ. The rooms were prepared for the reception of guests. ክፍሎቹ ፡ ለእንግዶች ፡ መ
ቀበያ ፡ ተዘጋጅተው ፡ ነበር
3. መቀበል. Everything is ready for the reception of the shipment. እቃውን ፡ ለመቀበል ፡ ማንኛ
ቸውም ፡ ነገር ፡ ተዘጋጅቷል
4. ግብዣ. He held a reception for the American ambassador. ለአሜሪካን ፡ አምባሳደር ፡ ግብዣ ፡
አደረገ
5. (ራዲዮ) ፡ ለማስተላለፍ. The mountains make radio reception difficult. ተራራዎቹ ፡ ራዲዮ ፡
ለማስተላለፍ ፡ ችግር ፡ ይፈጥራሉ

**reception desk** የእንግዶች ፡ መቀበያ ፡ ቦታ ፤ እ
ንግዳ ፡ መቀበያ ፡ ጠረጴዛ
The reception desk at the hotel has a phone. የሆቴሉ ፡ የእንግዶች ፡ መቀበያ ፡ ቦታ ፡ (እንግ
ዳ ፡ መቀበያ ፡ ጠረጴዛ) ፡ ስልክ ፡ አለው

**receptionist** አስተናጋጅ
The receptionist is a very friendly person. አስተናጋጇ ፡ በጣም ፡ ሰው ፡ ወዳድ ፡ ናት

**(be) receptive** ተቀበለ
He is receptive to new ideas. አዳዲስ ፡ ሐሳብ ፡
ይቀበላል

**recess** (v.)
1. ለማረፍ ፡ ተበታተነ. Congress recessed until January. የምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ እስከ ፡ ጥር ፡
ለማረፍ ፡ ተበታተኑ
2. ወጣ. The ministers recessed for lunch. ሚኒስትሮቹ ፡ ለምሳ ፡ ወጥተዋል

**be recessed**
*The table was recessed into the wall. ጠረጴዛው ፡ በግድግዳው ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፡ ብሎ ፡ በ
ተሠራ ፡ ስፍራ ፡ ተደረገ

**recess** (n.)
1. ዕረፍት. We have a short recess at ten in the morning. ጧት ፡ ባራት ፡ ሰዓት ፡ አጭር ፡ ዕረፍ
ት ፡ አለን
2. ግድግዳ ፡ ገባ ፡ ያለበት ፡ ስፍራ. The bench will fit nicely in that recess. አግዳሚው ፡ ወንበር ፡ በ
ዚያ ፡ ግድግዳው ፡ ገባ ፡ ባለበት ፡ ስፍራ ፡ ቢሆን ፡
በደንብ ፡ ይገጥማል

**recession** ሥራ ፡ መጥፋት
The recession caused a lot of unemployment. ሥራ ፡ በመጥፋቱ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ሆኑ

**recipe**
1. ያሠራር ፡ መምሪያ. Do you have a simple recipe for a cake? ለኬኩ ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ ያሠራር ፡ መምሪ
ያ ፡ አለህ ?
2. የምግብ ፡ መምሪያ. The cook concocted a new recipe. ወጥ ፡ ቤቷ ፡ አዲስ ፡ የምግብ ፡ መምሪ
ያ ፡ አዘጋጀች
3. ሐሳብ. He offered a recipe for world peace. የዓለም ፡ ሰላም ፡ ሊገኝበት ፡ የሚችል ፡ አንድ ፡
ሐሳብ ፡ አቀረበ

**recipient** ተቀባይ
The recipient of the award gave a speech. የሽልማቱ ፡ ተቀባይ ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**reciprocal**
1. የጋራ. The reciprocal agreement was signed yesterday. የጋራው ፡ ስምምነት ፡ ትናንት ፡ ተፈረመ
2. (expressed by the reciprocal stem). Their affection is reciprocal. ሁለቱም ፡ ይዋደዳሉ

**reciprocate**
1. ዐጸፋ ፡ መለሰ. I reciprocate your good wishes. ለመልካም ፡ ምኞትህ ፡ ዐጸፋ ፡ እመልሳለሁ
2. ውለታውን ፡ መለሰ. She reciprocated with a gift. ውለታዬን ፡ በስጦታ ፡ መለሰች

**reciprocity** ለጋራ ፡ ጥቅም ፡ ስምምነት
Reciprocity in trade is necessary. በንግድ ፡ በኩ
ል ፡ ለጋራ ፡ ጥቅም ፡ ስምምነት ፡ ያስፈልጋል

**recital**
*They were interested in the recital of the events of the day. በዕለቱ ፡ የተደረጉትን ፡ ንግ
ግሮች ፡ ወሬ ፡ ለመስማት ፡ ፍላጎት ፡ ነበራቸው
*During the recital, the audience applauded the violinist several times. ቫዮሊን ፡ ተጫዋቹ ፡
ሙዚቃ ፡ ባሰማ ፡ ጊዜ ፡ አድማጩ ፡ ሕዝብ ፡ ደጋ
ግሞ ፡ አጨበጨበለት
*During the recital, the audience applauded the poet several times. ግጥሙ ፡ ሲነበብ ፡ አድማ
ጩ ፡ ሕዝብ ፡ ለገጣሚው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አጨበ
ጨበለት

**recite**
1. ደገመ ፤ አደረሰ. He recited the prayer by heart. ጸሎቱን ፡ በቃሉ ፡ ደገመው
He recites the prayers early in the morning. ጸሎቱን ፡ ጧት ፡ በማለዳ ፡ ያደርሳል
2. ጠራ. Recite the names of all the provinces! የጠቅላይ ፡ ግዛቶቹን ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ ጥራ

3. አሰማ. He recited his poetry to a large audience. የደረሰውን ፡ ግጥም ፡ ለብዙ ፡ አድማጮች ፡ አሰማ

4. በቃሉ ፡ ወጣ. Mary recited the lesson with great ease. ሜሪ ፡ ትምህርቱን ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ በቃሏ ፡ ወጣችው

**reckless**

1. ግድየለሽ. Reckless drivers imperil our lives. ግድየለሽ ፡ ነጂዎች ፡ ለሕይወታችን ፡ አደገኞች ፡ ናቸው

2. (= adv.) በግዴለሽነት. He was sent to prison for reckless driving. በግዴለሽነት ፡ ስለነዳ ፡ ታሰረ

**reckon**

1. አሰበ. Reckon the cost before you decide! ውሳኔ ፡ ከመስጠትህ ፡ በፊት ፡ የሚያስከትለውን ፡ ወጪ ፡ አስብ

The cashier reckoned my bill. ገንዘብ ፡ ተቀባዩ ፡ ሒሳቤን ፡ አሰበው

2. አድርጎ ፡ ቈጠረ. I reckon him a real friend. እውነተኛ ፡ ጓደኛዬ ፡ አድርጌ ፡ እቈጥረዋለሁ

3. ተማመነ. Can we reckon on your help? በርዳታህ ፡ ልንተማመን ፡ እንችላለን ?

4. መሰለ(ው). +I reckon that it will rain. የሚዘንብ ፡ ይመስለኛል

**reckon on** ገመተ

He didn't reckon on our strength. ኀይላችንን ፡ አልገመተም

**reckon with** አሰበ

The U.N. will have to reckon with China. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ የቻይናን ፡ ጉዳይ ፡ ማሰብ ፡ አለበት

**be reckoned**

1. ታሰበ. Interest is reckoned from the date of deposit. ወለዱ ፡ የሚታሰበው ፡ ገንዘቡ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ጊዜ ፡ እንሥቶ ፡ ነው

2. ተቈጠረ. The epoch is reckoned in cycles of fifty-two years. በየአምሳ ፡ ሁለት ፡ ዓመቱ ፡ ዐውድ ፡ ይቈጠራል

**reckoning** ግምት

By my reckoning, we are five miles from home. በኔ ፡ ግምት ፡ ቤታችን ፡ ለመድረስ ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ ይቀረናል

**day of reckoning** የመጨረሻይቱ ፡ ቀን

The day of reckoning will come, and you'll be sorry. የመጨረሻይቱ ፡ ቀን ፡ ስትመጣ ፡ ታዝናለህ

**reclaim**

1. የጠፋውን ፡ ጠይቆ ፡ አገኘ. He reclaimed his pen at the office. የጠፋውን ፡ ብዕሩን ፡ ከቢሮ ፡ ጠይቆ ፡ አገኘ

2. አለማ. The government is trying to reclaim swamp land. መንግሥት ፡ ረግረጉን ፡ መሬት ፡ ለማልማት ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነው

3. ሰላማዊ ፡ ዜጋ ፡ አደረገው. Society reclaims criminals by teaching them skills. ኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ ወንጀለኞችን ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ አስተምሮ ፡ ሰላማዊ ፡ ዜጎች ፡ ያደርጋቸዋል

4. ለይቶ ፡ አወጣ. The company reclaims tin from old tin cans. ኩባንያው ፡ ከሮጌ ፡ ጣሳዎች ፡ የቆርቆሮ ፡ ማዕድን ፡ ለይቶ ፡ ያወጣል

**recline** ጋደም ፡ አለ

She reclined on the sofa. ሶፋው ፡ ላይ ፡ ጋደም ፡ አለች

**recluse** ብቸኛ

He is a recluse, and rarely is seen in town. ብቸኛ ፡ ስለሆነ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ እምብዛም ፡ አይታይም

**reclusion** የብቸኝነት ፡ ኑሮ

His reclusion continued until his death. የብቸኝነት ፡ ኑሮው ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ቀጠለ

**recognition** መታወቅ

Recognition of Israel angered the Arab countries. የእስራኤል ፡ መታወቅ ፡ የዐረብ ፡ አገሮችን ፡ አስቈጣ

*He passed me without a sign of recognition. እኔ ፡ መሆኔን ፡ ሳያውቅ ፡ ዝም ፡ ብሎኝ ፡ አለፈ

**beyond recognition** ለዓይን ፡ እስኪያሳስት ፡ ድረስ

The town has changed beyond recognition since I saw it last. ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ካየሁት ፡ ወዲህ ፡ ከተማው ፡ ለዓይን ፡ እስኪያሳስት ፡ ድረስ ፡ ተለውጧል

**in recognition (of)** ለ--- መታወቂያ

He received a prize in recognition of his services. ላገልግሎቱ ፡ መታወቂያ ፡ ሽልማት ፡ ተቀበለ

**find recognition** ስሙ ፡ ተጠራ

A living author does not often find recognition. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ደራሲ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ስሙ ፡ አይጠራም

**win recognition** ታዋቂ ፡ ሆነ

The actor won recognition from the public. ተዋናዩ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ታዋቂ ፡ ሆነ

**recognize**

1. ለየ. I recognize him by his voice. በድምፁ ፡ አለየዋለሁ

2. ዐወቀ. You have grown so much, I wouldn't recognize you. በጣም ፡ ከማደግህ ፡ የተነሣ ፡ ላውቅህ ፡ አልቻልኩም
Ethiopia recognized Kenya recently. ኢትዮጵያ ፡ ኬንያን ፡ ያወቀችው ፡ በቅርብ ፡ ነው
3. ዐወቀ(ለት). He recognized my right to argue against his point of view. ልከራከረው ፡ ያለኝን ፡ መብት ፡ ዐወቀልኝ
4. እንዲናገር ፡ ፈቀደ(ለት). The chair recognized Mr. Parker. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ እንዲናገሩ ፡ ፈቀደላቸው
*Everyone recognizes him to be an authority on Ethiopia. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በደንብ ፡ የሚያውቅ ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ ያምናል

**recognize each other**
*When we met in the street, we recognized each other right away. መንገድ ፡ ላይ ፡ ስንገናኝ ፡ ወዲያውኑ ፡ እሱም ፡ ዐወቀኝ ፡ እኔም ፡ ዐወቅሁት

**recoil** (v.)
1. አፈገፈገ. The woman recoiled in horror from the snake. ሴትዮዋ ፡ በድንጋጤ ፡ ከእባቡ ፡ አፈገፈገች
2. ወደ ፡ ኋላ ፡ ተራገጠ. The rifle recoils in firing. ጠመንጃው ፡ ከተተኰሰ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ይራገጣል

**recoil** (n.) እርግጫ
The gun's recoil bruised his shoulder. የጠመንጃው ፡ እርግጫ ፡ ትከሻውን ፡ ጐዳው

**recollect** አስታወሰ
I don't recollect having heard that before. ከዚህ ፡ በፊት ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ መስማቴን ፡ አላስታውስም

**recollection**
1. ትዝታ. I have a dreary recollection of my childhood. የልጅነት ፡ ትዝታዬ ፡ የማያስደስት ፡ ነው
2. የሚያወሳው ፡ ነገር. His recollection of past events is not very reliable. ስላለፉት ፡ ድርጊቶች ፡ የሚያወሳው ፡ ነገር ፡ እጅግም ፡ ሊታመን ፡ አይችልም
*To the best of my recollection, he was born in 1896. እንደማስታውሰው ፡ የተወለደው ፡ በ፲፰፻፹፰ ዓ. ም. ነበር

**recommend**
1. ብቁ ፡ መሆኑን ፡ መሰከረ(ለት). The teacher recommended his student for the job. መምህሩ ፡ ተማሪው ፡ ለሥራው ፡ ብቁ ፡ መሆኑን ፡ መሰከረለት
2. አዘዘ. The doctor recommended that she stay in bed. ሐኪሙ ፡ ተኝታ ፡ እንድትሰነብት ፡ አዘዘ
3. አሳሰበ. The teachers' council recommended a raise. ያስተማሪዎቹ ፡ ደርግ ፡ የደሞዝ ፡ ጭማሪ ፡ እንዲደረግ ፡ አሳሰበ
4. ሐሳብ ፡ አቀረበ. As far as granting scholarships is concerned, I am helpless; I can only recommend. የነጻ ፡ ትምህርት ፡ በመስጠት ፡ ረገድ ፡ እኔ ፡ ሥልጣን ፡ የለኝም ፤ ሐሳብ ፡ ማቅረብ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የምችለው
5. ነገረ. Can you recommend a good mechanic? ጥሩ ፡ ሜካኒክ ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ልትነግረኝ ፡ ትችላለህ ?
6. ተስማሚ ፡ አደረገው. The location of the camp recommends it as a summer home. የሰፈሩ ፡ አቀማመጥ ፡ ለበጋው ፡ ወራት ፡ ማረፊያ ፡ ተስማሚ ፡ ያደርገዋል
7. ደገፈ. The delegates recommended the constitution of a peace commission. መልእክተኞቹ ፡ የሰላም ፡ ኮሚስዮንን ፡ መቋቋም ፡ ደገፉ
8. አጨ(ታጨ). He has been recommended to a high position. ለከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ታጭቷል

**recommend to one's care** አደራ ፡ ሰጠ
He recommended his son to my care. ልጁን ፡ ለኔ ፡ አደራ ፡ ሰጠ

**recommendation**
1. አስተያየት. He was hired on the strength of your recommendation. በሰጠህለት ፡ አስተያየት ፡ ደጋፊነት ፡ ተቀጠረ
2. የሚመከር. My recommendation is that you return. እኔ ፡ የምመክርህ ፡ እንድትመለስ ፡ ነው
*I did it on your recommendation. አንተ ፡ በነገርከኝ ፡ መሠረት ፡ አደረግሁት
*It was the doctor's recommendation that I should stay in the hospital. ሆስፒታል ፡ እንድተኛ ፡ ሐኪሙ ፡ አዘዘኝ

**letter of recommendation** ብቁ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ ደብዳቤ
You will need letters of recommendation when you apply for that job. ያንን ፡ ሥራ ፡ ስትጠይቅ ፡ ብቁ ፡ መሆንህን ፡ የሚገልጽ ፡ ደብዳቤ ፡ ያስፈልግሃል

**recompense** (v.)
1. ወሮታውን ፡ ከፈለ. She recompensed him for his work. ለሠራላት ፡ ሥራ ፡ ወሮታውን ፡ ከፈለች
2. ተካ. We will recompense your loss. የጠፋብህን ፡ እንተካልሃለን

**recompense** (n.) ካሳ
He received $1,000 in recompense for the

damages to his car. በመኪናው ፡ ላይ ፡ ስለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ካሳ ፡ ተቀበለ

**reconcile**
1. አስታረቀ. He reconciled the angry couple. የተጣሉትን ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አስታረቀ
2. አስማማ. It is hard to reconcile the two accounts. ሁለቱን ፡ ታሪኮች ፡ ማስማማት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
It is difficult to reconcile his promises with what he actually did. የሚሠራውንና ፡ የሚለውን ፡ ለማስማማት ፡ ያስቸግራል

**reconcile oneself**
*It is hard to reconcile oneself to being sick a long time. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መታመምን ፡ እንደ ማይቀር ፡ ዕድል ፡ አድርጎ ፡ ለመቀበል ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**reconcile to** እንዲቀበል ፡ አደረገው
Time has reconciled him to his fate. የጊዜ ፡ ብዛት ፡ ዕድሉን ፡ እንዲቀበል ፡ አደረገው

**be reconciled** ታረቀ
The couple was reconciled. ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ታረቁ

**be reconciled to**
*We were reconciled to the loss of our money. በጠፋው ፡ ገንዘባችን ፡ ራሳችንን ፡ አጽናናን

**reconciliation** ዕርቅ
Reconciliation was achieved by getting both sides to make concessions. ዕርቅ ፡ የተገኘው ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ለመተው ፡ በመስማማታቸው ፡ ነው

**recondite** ረቂቅ
He couldn't find a publisher for his recondite studies on mathematics. ያዘጋጀውን ፡ ረቂቅ ፡ የሒሳብ ፡ ጥናት ፡ የሚያሳትምለት ፡ አላገኘም

**reconnaissance** መቃኘት
Reconnaissance of enemy movements was hampered by bad weather. የጠላትን ፡ ንቅናቄ ፡ መቃኘቱ ፡ በመጥፎ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ ተሰናከለ

**reconnoiter** ቃኘ ፤ ሰለለ
The patrol will reconnoiter the area tomorrow. ቃኚው ፡ ጓድ ፡ ነገ ፡ አካባቢውን ፡ ይቃኛል ፡ (ይሰልላል)

**reconsider** እንደገና ፡ መረመረ
They reconsidered their decision. ውሳኔያቸውን ፡ እንደገና ፡ መረመሩት

**reconstitute** መልሶ ፡ አቋቋመ
He was asked to reconstitute the political party. የፖለቲካ ፡ ማኅበሩን ፡ መልሶ ፡ እንዲያቋቁም ፡ ተጠየቀ

**reconstruct**
1. እንደገና ፡ ሠራ. They reconstructed the town after the quake. ከመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ በኋላ ፡ ከተማውን ፡ እንደገና ፡ ሠሩት
2. እንዴት ፡ እንደተፈጸመ ፡ ዐወቀ. The detective tried to reconstruct the crime from the information he had obtained. ወንጀል ፡ መርማሪው ፡ ካገኘው ፡ መረጃ ፡ ወንጀሉ ፡ እንዴት ፡ እንደተፈጸመ ፡ ለማወቅ ፡ ሞከረ

**record** (v.)
1. አሰፈረ. We record history in books. ታሪክን ፡ በመጽሐፍ ፡ እናሰፍራለን
2. ጻፈ. Listen to the speaker, and record what he says! ተናጋሪው ፡ የሚለውን ፡ እያዳመጥክ ፡ ጻፍ
3. ለካ. A thermometer records temperatures. የሙቀት ፡ መለኪያ ፡ ሙቀትን ፡ ይለካል
4. ቀዳ. He recorded the song on tape. ዘፈኑን ፡ በቴፕ ፡ ቀዳው

**record** (n.)
1. የስም ፡ መጥሪያ. The record of school attendance was given to the principal. የስም ፡ መጥሪያው ፡ ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ኀላፊ ፡ ተሰጥቷል
2. መዝገብ. All the records were destroyed. መዝገቦቹ ፡ ሁሉ ፡ ወድመዋል
3. ፋይል. There was no birth certificate on record to reveal her age. ዕድሜዋን ፡ የሚገልጽ ፡ የልደት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ፋይል ፡ ውስጥ ፡ አልነበረም
4. ማስታወሻ. I can't find any record of that bill. ከዚያ ፡ ሒሳብ ፡ ምንም ፡ ማስታወሻ ፡ ማግኘት ፡ አልቻልም
5. ታሪክ. He has an honorable record of serving his country. ሀገሩን ፡ በማገልገል ፡ የሚያኮራ ፡ ታሪክ ፡ አለው
6. የሕይወት ፡ ታሪክ. In view of his record, I don't think he should be hired. የሕይወት ፡ ታሪኩ ፡ ሲታይ ፡ መቀጠር ፡ የሚገባው ፡ አይመስለኝም
7. ሪኮርድ. The student has an excellent record. ተማሪው ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ሪኮርድ ፡ አለው
They discovered that the suspect had a record. ተጠርጣሪው ፡ ሪኮርድ ፡ እንዳለበት ፡ ዐወቁ
8. የሙዚቃ ፡ ሸክላ. The store has a good selection of records. መደብሩ ፡ ምርጥ ፡ የሆኑ ፡ የሙዚቃ ፡ ሸክላዎች ፡ አሉት

9. ክብረ ፡ ወሰን. The runner broke the old
record. ሯጩ ፡ የዱሮውን ፡ ክብረ ፡ ወሰን ፡ ሰበረ

**go on record**
*I don't want to go on record as saying war
is inevitable. ጦርነት ፡ አይቀርም ፡ ያልኩት ፡ እ
ንዲጠቀስ ፡ አልፈልግም

**keep a record of** መዘገበ
Keep a careful record of all expenses! ወጪህን ፡
ሁሉ ፡ በጥንቃቄ ፡ መዝግብ

**make a record of** መዘገበ
The secretary made a record of everything.
ጸሐፊው ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መዝግቧል

**(be) off the record** መታተም ፡ የለበትም ፤ ኦፊ
ሲየል ፡ አይደለም
The President's remarks are off the record.
ፕሬዚዳንቱ ፡ የተናገሩት ፡ መታተም ፡ የለበትም ፡
(ኦፊሲየል ፡ አይደለም)

**(be) put on the record** ሊታተም ፡ ተቻለ
His statement regarding the future of the
country can now be put on the record. ስለ ፡ አ
ገሪቱ ፡ የወደፊት ፡ ዕድል ፡ የሰጠው ፡ መግለጫ ፡
አሁን ፡ ሊታተም ፡ ይቻላል

**record** (adj.) ከምን ፡ ጊዜም ፡ የበለጠ
We have a record wheat crop this year. በዚህ ፡
ዓመት ፡ ከምን ፡ ጊዜም ፡ የበለጠ ፡ የስንዴ ፡ ምር
ት ፡ አለን
[See also 'time']

**recording** የተቀዳ ፡ ሙዚቃ
This is a recording of Ethiopian folk music.
ይህ ፡ የተቀዳው ፡ ሙዚቃ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሀገር ፡
ባህል ፡ ዘፈን ፡ ነው

**record player** የሸክላ ፡ ማጫወቻ
I bought a new record player yesterday.
ትናንት ፡ አዲስ ፡ የሸክላ ፡ ማጫወቻ ፡ ገዛሁ

**recount**
1. ዘርዝሮ ፡ አወራ. He recounted the story of his
adventures in Africa. በአፍሪካ ፡ ያጋጠመውን ፡
ሁሉ ፡ ዘርዝሮ ፡ አወራ
2. እንደገና ፡ ቈጠረ (ተቈጠረ). The votes must be
recounted. የተሰጠው ፡ ድምፅ ፡ እንደገና ፡ መቈ
ጠር ፡ አለበት

**recoup** (vt.) መለሰ
He recouped his losses by investing in stocks.
ገንዘቡን ፡ በአክሲዮን ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ ኪሳራ
ውን ፡ መለሰ

**recoup** (vi.) አንሰራራ
How will he recoup after such a disaster?
ከእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ በኋላ ፡ እንዴት ፡ ያን
ሰራራል ?

**recourse** እርዳታ ፡ የሚጠይቀው
Our recourse in illness is to a doctor. በታመምን ፡
ጊዜ ፡ እርዳታ ፡ የምንጠይቀው ፡ ከሐኪም ፡ ነው
*Bankruptcy is my only recourse. መፍትሔ ፡
የማገኘ ፡ ዘዴዬ ፡ መክሰሬን ፡ ማመልከት ፡ ብቻ ፡ ነው

**as a last recourse** የሚያደርገው ፡ ቢያጣ
As a last recourse, he called the police. የሚያደ
ርገው ፡ ቢያጣ ፡ ፖሊስ ፡ ጠራ

**recover** (vt.)
1. መልሶ ፡ ለመጠበቅ ፡ ቻለ. He recovered his
balance immediately. ሚዛኑን ፡ በፍጥነት ፡ መ
ልሶ ፡ ለመጠበቅ ፡ ቻለ
2. አስመለሰ. Did you finally recover your
watch? ሰዓትህን ፡ የኋላ ፡ ኋላ ፡ አስመለስክ ?
3. ካሳ ፡ አገኘ. He filed a claim in order to
recover damages to his car. በመኪናው ፡ ላይ ፡ ለ
ደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ካሳ ፡ ለማግኘት ፡ ክስ ፡ አቀረበ
4. አዲስ ፡ ልብስ ፡ አለበሰ. We recovered our
couch recently. በቅርቡ ፡ ሶፋችንን ፡ አዲስ ፡
ልብስ ፡ አለበስነው
*He recovered his health. ጤንነቱ ፡ ተመለሰለት

**recover** (vi.)
1. አንሰራራ. The country has recovered from
the effects of the war. ሀገሪቱ ፡ ጦርነቱ ፡ ከደ
ረሰባት ፡ ጥፋት ፡ አንሰራርታለች
2. ዳነ. He recovered quickly from his illness.
ከበሽታው ፡ ቶሎ ፡ ዳነ
3. ለቀቀ(ው). +The thief escaped before they
recovered from their surprise. ድንጋጤው ፡ ሳይ
ለቃቸው ፡ ሌባው ፡ አመለጠ

**recover oneself** ዳነ
He started to fall, but recovered himself.
ሊወድቅ ፡ ነበር ፡ ዳነ

**recover (one's) sight** ዓይኑ ፡ በራ(ለት)
He recovered his sight after twenty years
of blindness. ሃያ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ታውሮ ፡ ዓይ
ኑ ፡ በራለት

**be recovered**
1. ዳነ. At all events, she will take care of you
until you are completely recovered. የሆነው ፡ ቢ
ሆን ፡ ፈጽሞ ፡ እስክትድን ፡ ድረስ ፡ ታስታምምሃለች
2. ተያዘ. A lot of pillage was recovered from
the outlaws. ብዙ ፡ የተዘረፈ ፡ ንብረት ፡ በሽፍ
ቶች ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ተያዘ

**recovery**
1. ማገገም. He is on the road to recovery.
ወደ ፡ ማገገሙ ፡ ነው

2. መዳን. Her recovery was miraculous. መዳኗ ፡ ተአምር ፡ ነው

3. መገኘት. The recovery of the lost coat made him happy. ጠፍቶ ፡ የነበረው ፡ ኮት ፡ መገኘቱ ፡ አስደሰተው

*I wish you a speedy recovery. ቶሎ ፡ እንድትድን ፡ እመኝልሃለሁ

**recreate**

*The criminal recreated the crime. ወንጀለኛው ፡ ወንጀሉን ፡ እንዴት ፡ እንደፈጸመው ፡ አሳየ

**recreation** የሚዝናናው

His only recreation is playing tennis. የሚዝናናው ፡ ቴኒስ ፡ በመጫወት ፡ ብቻ ፡ ነው

**recrimination, engage in ~** በእንካ ፡ ስላንቲያ ፡ ተያያዙ

Both parties engaged in recrimination. ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በእንካ ፡ ስላንቲያ ፡ ተያያዙ

**recruit** (v.)

1. መለመለ. They are recruiting young men for military training. ለወታደርነት ፡ ትምህርት ፡ ወጣቶችን ፡ ይመለምላሉ

2. አስገባ. Our club recruited six new members. ክበባችን ፡ ስድስት ፡ አዲስ ፡ አባሎች ፡ አስገባ

**recruit** (n.) ምልምል ፡ ወታደር

The battalion is made up of new recruits. የሻለቃው ፡ ጦር ፡ ምልምል ፡ ወታደሮች ፡ ይበዙበታል

**rectangle** አራት ፡ ማእዘን

It is not difficult to trace a rectangle. አራት ፡ ማእዘን ፡ መሣል ፡ ከባድ ፡ አይደለም

**rectangular** አራት ፡ ማእዘን

This field is rectangular. ይህ ፡ ሜዳ ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ ነው

**rectify** (rectified) አስተካከለ

We will have to rectify our error. ስሕተታችንን ፡ ማስተካከል ፡ አለብን

**rectitude** ታማኝነት

His rectitude made him worthy to be a judge. ታማኝነቱ ፡ ለዳኝነት ፡ ብቁ ፡ አደረገው

**recuperate** አገገመ

He went to a mineral spring to recuperate. ለማገገም ፡ ወደ ፡ ጠበል ፡ ሄደ

**recuperation** (= verbal noun) ማገገም

His recuperation lasted several years. ለማገገም ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ፈጀበት

**recur** (recurred)

1. ተቀሰቀሰ(በት). Malaria may recur if one fails to continue taking medicine. ወባ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ መድኃኒት ፡ መዋጡን ፡ ካልቀጠለ ፡ ወባዋ ፡ ትቀሰቀስበታለች

2. ሆነ. Leap year recurs every four years. ባራት ፡ ዓመት ፡ አንዴ ፡ ጳጕሜ ፡ ስድስት ፡ ትሆናለች

**recur to** ደገመ

The speaker recurred to his first point. ተናጋሪው ፡ መጀመሪያ ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ ደገመ

**recurrence**

*More care in the future will prevent recurrence of the mistake. ሰፋ ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ስሕተቱ ፡ እንዳይደገም ፡ (ዳግመኛ ፡ እንዳይደርስ) ፡ ይረዳል

**recurrent**

He suffers from recurrent chills and fever. ብርድና ፡ ትኩሳት ፡ እያገረሸ ፡ ያስቸግረዋል

**red** ቀይ

She put on a red dress. ቀይ ፡ ቀሚስ ፡ ለብሳለች

**be in the red** እየከሰረ ፡ ሄደ

The business is in the red. ንግዱ ፡ እየከሰረ ፡ ሄዷል

**be red** ደም ፡ መሰለ

He was so mad that his face was red. በጣም ፡ ጦፎ ፡ ስለነበረ ፡ ፊቱ ፡ ደም ፡ መሰለ

**see red** ተናደደ

When the workers went on strike, the boss saw red. ሠራተኞቹ ፡ ሥራ ፡ ቢያቆሙ ፡ አለቅየው ፡ ተናደደ

**turn red**

1. ፊቱ ፡ ሳምባ ፡ መሰለ. She turned red with embarrassment. በእፍረት ፡ ፊቷ ፡ ሳምባ ፡ መሰለ

2. ደም ፡ መሰለ. His face turned red with rage. ፊቱ ፡ በንዴት ፡ ደም ፡ መሰለ

[See also 'glow, hot']

**red carpet treatment** ታላቅ ፡ አቀባበል

They gave the ambassador the red carpet treatment. ለአምባሳደሩ ፡ ታላቅ ፡ አቀባበል ፡ አደረጉላቸው

**Red Cross** ቀይ ፡ መስቀል

The Red Cross helps the wounded and sick. ቀይ ፡ መስቀል ፡ ቁስለኞችንና ፡ በሽተኞችን ፡ ይረዳል

**reddish** ቀላ ፡ ያለ

Her new reddish coat is attractive. ቀላ ፡ ያለው ፡ አዲስ ፡ ካፖርቷ ፡ ደስ ፡ ይላል

**redeem**

1. አዳነ. Jesus redeemed the world. ኢየሱስ ፡ ዓለምን ፡ አዳነ

2. አስመለሰ. I will redeem my watch from the moneylender. ከገንዘብ ፡ አበዳሪው ፡ ሰዓቴን ፡ አስመልሳለሁ

3. ሰረዘ(ለት). His brave act redeemed his faults. የፈጸመው ፡ ጀብዱ ፡ ጥፋቱን ፡ ሰረዘለት

4. ከፈለ. He redeemed the debt. ዕዳውን ፡ ከፈለ

5. ለወጠ. She redeemed the coupon for a free box of soap. ኩፖኗን ፡ ባንድ ፡ ፓኮ ፡ ሳሙና ፡ ለወጠች

6. ፈጸመ. He redeemed his promise. የገባውን ፡ ቃል ፡ ፈጸመ

7. ገንዘብ ፡ ከፍሎ ፡ ነጻ ፡ አወጣ. He redeemed his friend from captivity. ገንዘብ ፡ ከፍሎ ፡ ጓደኛውን ፡ ከምርኮ ፡ ነጻ ፡ አወጣው

**redeemer** መድኃኒት

Jesus is the redeemer of the world. ኢየሱስ ፡ የዓለም ፡ መድኃኒት ፡ ነው

**redeeming, ~ feature**

*His only redeeming feature is his friendliness. መጥፎ ፡ ጠባዩን ፡ የሚያስረሳለት ፡ ተጫዋችነቱ ፡ ብቻ ፡ ነው

**redemption**

*Redemption of the world was achieved through Jesus' death. ዓለም ፡ ከኀጢአቷ ፡ የነጻችው ፡ በኢየሱስ ፡ ሞት ፡ ነው

*Redemption of articles is done through cash payments. እቃዎች ፡ የሚመለሱት ፡ እጅ ፡ በጅ ፡ በመክፈል ፡ ነው

**red-handed** እጅ ፡ ከፍንጅ

The thief was caught red-handed. ሌባው ፡ እጅ ፡ ከፍንጅ ፡ ተያዘ

**(be) red-hot** ጋለ

The griddle is red-hot, so don't touch it. ምጣዱ ፡ ስለጋለ ፡ አትንካው

**redirect** በሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ አደረገ

We must redirect our efforts, as nothing we have yet done has succeeded. እስከ ፡ አሁን ፡ የሠራነው ፡ ፍሬ ፡ ስላልሰጠ ፡ ጥረታችንን ፡ በሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ ማድረግ ፡ አለብን

**redo** (redid) እንደገና ፡ ሠራ

We have to redo his work, as it was incorrect. ሥራው ፡ ልክ ፡ ስላልሆነ ፡ እንደገና ፡ መሥራት ፡ አለብን

**redouble** ዕጥፍ ፡ አደረገ

He redoubled his efforts to win the race. በሩጫው ፡ ለማሸነፍ ፡ ጥረቱን ፡ ዕጥፍ ፡ አደረገ

**redoubt** ምሽግ

The redoubt was captured by our soldiers. ምሽጉ ፡ በወታደሮቻችን ፡ ተያዘ

**redress** አረመ

You should confess and redress your errors. ጥፋትህን ፡ ማመንና ፡ ማረም ፡ ይገባሃል

**red tape**

*This application requires a lot of red tape. ይህ ፡ ማመልከቻ ፡ ብዙ ፡ ዝርዝር ፡ የመሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ አሉበት

**reduce** (vt.)

1. ቀነሰ. We have to reduce our expenses. ወጭያችንን ፡ መቀነስ ፡ አለብን

We have reduced the prices ten percent. ዋጋውን ፡ በመቶ ፡ ዐሥር ፡ ቀንሰናል

He reduced his speed while passing through the town. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ሲያልፍ ፡ ፍጥነቱን ፡ ቀነሰ

2. ዝቅ ፡ አደረገ. They reduced the major to the rank of captain. ሻለቃውን ፡ ወደ ፡ ሻምበልነት ፡ ዝቅ ፡ አደረጉት

3. ድል ፡ አድርጎ ፡ ያዘ. The army reduced the enemy fort. ጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ የጠላትን ፡ ምሽግ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ያዘ

4. አደረሰ. Misfortune reduced that poor woman to begging. ያችን ፡ ድኻ ፡ ሴት ፡ ችግር ፡ ከልመና ፡ አደረሳት

**reduce** (vi.) ክብደት ፡ ቀነሰ

The doctor advised him to reduce. ሐኪሙ ፡ ክብደቱን ፡ እንዲቀንስ ፡ መከረው

[See also 'chaos, powder, silence']

**reduction** መቀነስ

The reductions in price were announced in the paper. የዋጋው ፡ መቀነስ ፡ በጋዜጣ ፡ ተገለጸ

**redundant**

*If you use two negatives in English, one is often redundant. በእንግሊዝኛ ፡ በሁለት ፡ አሉታ ፡ መጠቀም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የማያስፈልግ ፡ መደጋገም ፡ ይሆናል

**reduplicate** አባዛ

They tried to reduplicate the manuscript, but were unable to do so. የእጅ ፡ ጽሑፉን ፡ እንዳለ ፡ ለማባዛት ፡ ሞከረው ፡ ሳይሆንላቸው ፡ ቀረ

**reed** መቃ
The reeds grow by the lake shore. መቃ ፡ በሐይቅ ፡ ዳር ፡ ይበቅላል

**reef** አለታዊ ፡ ባሕረ ፡ ጠረፍ
A reef keeps ships from entering the harbor. መርከቦች ፡ ወደ ፡ ወደቡ ፡ እንዳይገቡ ፡ አለታዊ ፡ ባሕረ ፡ ጠረፍ ፡ ያግዳቸዋል

**reek** (v.), ~ **of** (repeated noun) + ሸተተ
This sauce reeks of garlic. ይህ ፡ ወጥ ፡ ነጭ ፡ ሽንኩርት ፡ ነጭ ፡ ሽንኩርት ፡ ይሸታል

**reek** (n.) ደስ ፡ የማይል ፡ ሽታ
We noticed the reek of cabbage as we entered the hall. ከመተላለፊያው ፡ እንደገባን ፡ ደስ ፡ የማይል ፡ የጎመን ፡ ሽታ ፡ ሸተተን

**reel** (v.)
1. ዞረ. The room seemed to reel before his eyes. ክፍሉ ፡ የሚዞር ፡ መሰለው
2. ተግተረተረ. The boxer reeled and fell. ቡጢኛው ፡ ተግተርትሮ ፡ ወደቀ

**reel in** ጠመጠመ
He reeled in the string, and brought the kite down. ገመዱን ፡ በመጠምጠም ፡ ወላንዶውን ፡ አወረደው

**reel out** ከመጠቅለያ ፡ ላይ ፡ ተረተረ
The firemen reeled out the hose. የእሳት ፡ አደጋ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ቱቦውን ፡ ከመጠቅለያ ፡ ላይ ፡ ተረተሩት

**his mind reeled** ራሱ ፡ ዞረ
His mind reeled when he heard the news. ወሬውን ፡ ሲሰማ ፡ ራሱ ፡ ዞረ

**reel** (n.) ጥቅል
I bought a reel of twine. አንድ ፡ ጥቅል ፡ ሲባጎ ፡ ገዛሁ
I have one reel of film taken in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያነሣሁት ፡ አንድ ፡ ጥቅል ፡ ፊልም ፡ አለኝ

**reeling, send one** ~ አምዘግዝጎ ፡ ጣለው
The blow sent him reeling into the street. ምቱ ፡ አምዘግዝጎ ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ጣለው

**refectory** [በገዳም ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ምግብ ፡ ቤት]

**refer** (referred)
1. አቀረበ. We referred our argument to the teacher. ክርክራችንን ፡ ለመምህሩ ፡ አቀረብን
2. እንዲመለከት ፡ መራ. Our teacher is referring us to many good books. መምህራችን ፡ ብዙ ፡ ጠቃሚ ፡ መጻሕፍት ፡ እንድንመለከት ፡ ይመራናል
3. አማረረ. Many people refer their failures to bad luck instead of to poor work. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሳይሳካላቸው ፡ ሲቀር ፡ በመጥፎ ፡ ሥራቸው ፡ ሳይሆን ፡ በዕድላቸው ፡ ያማርራሉ

**refer to**
1. ተመለከተ. What he said refers to all of you. እሱ ፡ ያለው ፡ ሁላችሁንም ፡ ይመለከታል
The speaker often referred to his notes. ተናጋሪው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ማስታወሻውን ፡ ይመለከት ፡ ነበር
2. ጠቀሰ. She referred to it in her book. በመጽሐፏ ፡ ውስጥ ፡ ጠቅሳዋለች
3. አስታወሰ. We refer to your letter of the fifth of June. ሰኔ ፡ አምስት ፡ የጻፍከውን ፡ ደብዳቤ ፡ እናስታውሳለን
4. ነካ. When I said some people are stupid, I was not referring to you. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ደደቦች ፡ ናቸው ፡ ማለቴ ፡ አንተን ፡ መንካቴ ፡ አልነበረም
5. አነሣ. He seldom refers to his brother. ወንድሙን ፡ ብዙም ፡ አያነሣ

**(be) referred to**
1. እንዲያነጋግር ፡ መሩት. I was referred to the manager. ሥራ ፡ አስኪያጁን ፡ እንዳነጋግር ፡ መሩኝ
2. እንዲቀርብ ፡ ተደረገ. The dispute was referred to the U.N. ክርክሩ ፡ ለተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ እንዲቀርብ ፡ ተደረገ

**referee**
1. አጫዋች. The game came to an end when the referee blew the whistle. አጫዋቹ ፡ ፊሽካውን ፡ ሲነፋ ፡ የጨዋታው ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ
2. ዳኛ. My father was the referee in this affair. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ዳኛ ፡ የነበረው ፡ አባቴ ፡ ነው

**reference** (n.)
1. መግለጫ. You will find that reference on page twenty. መግለጫውን ፡ በገጽ ፡ ሃያ ፡ ላይ ፡ ታገኘዋለህ
2. የምስክር ፡ ወረቀት. The boy had excellent references from men for whom he had worked. ልጁ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ከሠራላቸው ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ነበረው
3. ተጠያቂ. You may give me as a reference if you need one in your application. ማመልከቻው ፡ ላይ ፡ ተጠያቂ ፡ ቢያስፈልግ ፡ የኔን ፡ ስም ፡ ጥቀስ
*The book is full of references to Ethiopia. መጽሐፉ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብዙ ፡ ይጠቅሳል

**reference** (adj.) የቃላትን ፡ ፍች ፡ የሚያመለክት
A dictionary is a reference book. መዝገበ ፡ ቃላት ፡ የቃላትን ፡ ፍች ፡ የሚያመለክት ፡ መጽሐፍ ፡ ነው

**in reference to**
*In reference to your ad in the paper ....
በጋዜጣው ፡ ላይ ፡ ያወጡትን ፡ ማስታወቂያ ፡ መ
ሠረት ፡ በማድረግ

**make reference** አነሣ
Do not make any reference to his blindness!
ስለ ፡ ዕውርነቱ ፡ ምንም ፡ አታንሣ

**without reference to** ሳይወሰን
The test has to be taken by all students without
reference to age or grade. ዕድሜ ፡ ወይም ፡ የ
ክፍል ፡ ደረጃ ፡ ሳይወሰን ፡ ተማሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ፈ
ተናውን ፡ መውሰድ ፡ አለባቸው

## referendum
*A referendum is being held to find out which
country they prefer. የትኛውን ፡ አገር ፡ እንደሚ
መርጡ ፡ ለማወቅ ፡ ጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ ድም
ፅ ፡ በመስጠት ፡ ላይ ፡ ነው

## refill (v.)
1. አጠጣ. I need to refill my pen with ink.
ብዕሬን ፡ ቀለም ፡ ማጠጣት ፡ አለብኝ
2. (ቤንዚን) ፡ ሞላ. Make sure you refill the tank
when you bring my car. መኪናዬን ፡ ስትመልስ ፡
ቤንዚን ፡ መሙላትህን ፡ አረጋግጥ

## refill (n.) መለወጫ ፡ ቀለም
I will buy a refill for my pen. ለብዕሬ ፡ መለወ
ጫ ፡ ቀለም ፡ እገዛለሁ

## refined የጠራ
He used very refined language. በጣም ፡ የጠ
ራ ፡ ንግግር ፡ ተናገረ

**be refined** ተጣራ
Sugar is refined here in Ethiopia. ስኳር ፡ ኢት
ዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይጣራል

## refinement
1. የታረመ ፡ ጠባይ. His lack of refinement is due
to poor upbringing. የታረመ ፡ ጠባይ ፡ አለማ
ሳየቱ ፡ ከስተዳደጉ ፡ ጉድለት ፡ ነው
2. መሻሻል. My invention needs a few refine-
ments before we market it. አዲስ ፡ የሠራሁት ፡
ነገር ፡ ለገበያ ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ አንዳንድ ፡
መሻሻል ፡ ያስፈልገዋል
*Gasoline is produced by the refinement of
petroleum. ቤንዚን ፡ ከፔትሮል ፡ ተጣርቶ ፡ የ
ሚገኝ ፡ ነዳጅ ፡ ነው

**lady of refinement** ጨዋ ፡ ሴት
A lady of refinement does not use coarse
language. ጨዋ ፡ ሴት ፡ ያልታረመ ፡ ቃል ፡ አይወ
ጣትም

## refinery, oil ~ የነዳጅ ፡ ማጣሪያ ፡ ፋብሪካ
There is an oil refinery in Assab. በአሰብ ፡ የነዳ
ጅ ፡ ማጣሪያ ፡ ፋብሪካ ፡ አለ

## reflect (vt.)
1. ገለጸ. The literature of a nation reflects its
culture. ያንድ ፡ አገር ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ያገሩን ፡
ባህል ፡ ይገልጻል
2. አሳየ. The mirror reflects my face. መስታወ
ቱ ፡ ፊቴን ፡ ያሳያል
3. አንጸባረቀ. This glass reflects light. ይህ ፡
መስታወት ፡ ብርሃን ፡ ያንጸባርቃል

**reflect** (vi.) አሰበ
He reflected a moment before replying. ከመመ
ለሱ ፡ በፊት ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አሰበ

**be reflected** ታየ
The trees are reflected in the lake. የዛፎቹ ፡ ጥ
ላ ፡ በሐይቁ ፡ ውስጥ ፡ ይታያል

**reflect on**
1. አሰደበ. The child's bad behavior reflects
on his home training. የልጁ ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡
አሳዳጊውን ፡ ያሰድባል
2. አስመሰገነ. The child's good behavior reflects
on his home training. የልጁ ፡ ጥሩ ፡ ጠባይ ፡ አ
ሳዳጊውን ፡ ያስመሰግናል
[See also 'credit']

## reflection
*After much reflection, he began to write.
ብዙ ፡ ካወጣ ፡ ካወረደ ፡ በኋላ ፡ መጻፍ ፡ ጀመረ
*The reflection of the trees in the water makes
a pleasant scene. የዛፎቹ ፡ ጥላ ፡ በውኃው ፡ ው
ስጥ ፡ ሲታይ ፡ ደስ ፡ ይላል
*I intended no reflection on your character.
በተናገርኩት ፡ ውስጥ ፡ አንተን ፡ የሚነካ ፡ ነገር ፡
አላሰብኩም

**on reflection** መለስ ፡ ብዬ ፡ ሳየው
On reflection, I'd rather not do it. መለስ ፡ ብ
ዬ ፡ ሳየው ፡ አለማድረጌን ፡ እመርጣለሁ

**without reflection** ሳያስብ
He did it without reflection. ሳያስብ ፡ አደረገው

## reflex, be a ~ አሳየ
A law should be a reflex of the will of the
people. ሕግ ፡ የሕዝቡን ፡ ፍላጎት ፡ የሚያሳይ ፡
መሆን ፡ አለበት

**reflex action** ሳይታሰብ ፡ የሚሆን ፡ ድርጊት
Blinking your eye when someone threatens to
hit you in the face is a reflex action. ሰው ፡ እፊ
ትህ ፡ ላይ ፡ ሊመታህ ፡ ሲቃጣ ፡ ዓይንን ፡ ማርገብ
ገብ ፡ ሳይታሰብ ፡ የሚሆን ፡ ድርጊት ፡ ነው

**in reflex** ሳያስብ
He blinked his eye in reflex. ሳያስብ ፡ ዓይኑን ፡ አርገበገበ

**reforest** እንደገና ፡ ደን ፡ አደረገ
The government has decided to reforest the region. መንግሥቱ ፡ አካባቢውን ፡ እንደገና ፡ ደን ፡ ለማድረግ ፡ ወስኗል

**reform** (vt.) አሻሻለ
He tries to reform the working conditions in the factory. በፋብሪካው ፡ ውስጥ ፡ የሥራውን ፡ አካሄድ ፡ ለማሻሻል ፡ ይሞክራል
**reform** (vi.) ጠባዩን ፡ አሻሻለ
She spoke without sincerity of her desire to reform. ጠባይዋን ፡ ለማሻሻል ፡ የተናገረችው ፡ ከልቧ ፡ አልነበረም
**reform the line** እንደገና ፡ ተዘጋጀ
The soldiers reformed their lines, and attacked again. ወታደሮቹ ፡ እንደገና ፡ ተዘጋጅተው ፡ አጠቁ

**reform** (n.)
1. ለውጥ. He introduced many reforms. ብዙ ፡ ለውጥ ፡ አደረገ
2. መሻሻል. The reform in the school system was long overdue. የትምህርቱ ፡ ሥርዓት ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ መሻሻል ፡ ነበረበት

**reformation**
*The ministry is urging the reformation of the school administration. የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ እንዲሻሻል ፡ ይገፋፋል
**Reformation** የሃይማኖት ፡ ማሻሻል ፡ ንቅናቄ
The Reformation in Europe began a new period in history. በአውሮፓ ፡ የተደረገው ፡ የሃይማኖት ፡ ማሻሻል ፡ ንቅናቄ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ያዲስ ፡ ዘመን ፡ መክፈቻ ፡ ሆነ

**refract**
*Glass refracts light. መስታወት ፡ የብርሃንን ፡ ጨረር ፡ አቅጣጫውን ፡ ያስለውጠዋል

**refractory**
1. ግትር. This child is as refractory as a mule. ይህ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ በቅሎ ፡ ግትር ፡ ነው
2. ልግመኛ. The refractory ox could not be made to move. ልግመኛውን ፡ በሬ ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ አልተቻለም
3. የማይድን. After repeated stays in the hospital, he found that the refractory disease still bothered him. ደጋግሞ ፡ ሆስፒታል ፡ ቢገባም ፡ የማይድን ፡ በሽታው ፡ አሁንም ፡ ያስቸግረዋል

**refrain** (v.) ተቈጠበ
Please refrain from spitting in the street! በመንገድ ፡ ላይ ፡ ከመትፋት ፡ ተቈጠብ

**refrain** (n.) አዝማች
The teacher sang the song, and the pupils sang the refrain. መምህሩ ፡ መዝሙሩን ፡ ተማሪዎቹ ፡ ደግሞ ፡ አዝማቹን ፡ ዘመሩ

**refresh**
1. አነቃቃ. His bath refreshed him. ገላውን ፡ መታጠቡ ፡ አነቃቃው
2. አረጠበ. The rain refreshed the scorched ground. ዝናም ፡ የደረቀውን ፡ መሬት ፡ አረጠበው
**refresh (one's) memory**
*He refreshed my memory with photographs. በፎቶግራፍ ፡ አማካይነት ፡ እንዳስታውስ ፡ ረዳኝ
**refresh oneself** ተነቃቃ
He refreshed himself with a cup of tea. አንድ ፡ ሲኒ ፡ ሻይ ፡ በመጠጣት ፡ ተነቃቃ

**(be) refreshing**
1. አእምሮን ፡ አደሰ. It is refreshing to meet a person with new ideas. አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ካለው ፡ ጋር ፡ ማውራት ፡ አእምሮን ፡ ያድሳል
2. መንፈስን ፡ አነቃቃ. This cool breeze is refreshing. ይህ ፡ ቀዝቀዝ ፡ ያለ ፡ ሽውታ ፡ መንፈስን ፡ ያነቃቃል

**refreshments** ቀዝቃዛ ፡ መጠጥና ፡ ልዩ ፡ ቀላል ፡ ምግቦች
Refreshments were served during the intermission. በዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ቀዝቃዛ ፡ መጠጥና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀላል ፡ ምግቦች ፡ ቀረቡ

**refrigerate** ማቀዝቀዣ ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጠ
In hot countries, they refrigerate meat. በሞቃት ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ሥጋ ፡ ማቀዝቀዣ ፡ ውስጥ ፡ ያስቀምጣሉ

**refrigerator** ማቀዝቀዣ
These vegetables are perishable, so keep them in the refrigerator. እነዚህ ፡ አትክልቶች ፡ የሚበላሹ ፡ ስለሆኑ ፡ ማቀዝቀዣው ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጧቸው

**refuge**
1. ጐሬ. He claimed that the forest has become a refuge for bandits. ጫካው ፡ የሽፍቶች ፡ ጐሬ ፡ ሆኗል ፡ አለ
2. ጥገኝነት. The defector sought refuge in an embassy. ከዳተኛው ፡ባንዱ ፡ ኤምባሲ ፡ ውስጥ ፡ ጥገኝነት ፡ ጠየቀ

3. መጠጊያ. Wild land affords refuge for game. ሰው ፡ ያልሰፈረበት ፡ መሬት ፡ ላውሬዎች ፡ መጠጊያ ፡ ይሆናል
*Music was his refuge from his many cares. ከብዙ ፡ ጭንቀቱ ፡ የሚላቀቀው ፡ በሙዚቃ ፡ ነው

**seek refuge** ተጠለለ
He sought refuge from the storm under a large rock. አንድ ፡ ትልቅ ፡ ቋጥኝ ፡ ሥር ፡ ገብቶ ፡ ከኀይለኛ ፡ ዝናም ፡ ተጠለለ

**take refuge** ተደብቆ ፡ ቆየ
Take refuge in the cave! ዋሻው ፡ ውስጥ ፡ ተደብቀህ ፡ ቆይ

**refugee**
1. ስደተኛ. Many refugees poured over the border. ብዙ ፡ ስደተኞች ፡ ወሰኑን ፡ ተሻግረው ፡ መጡ
2. ጥገኛ. The refugee has a laissez passer. ጥገኛው ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ አለው

**refund** (v.)
1. ተካ. I'll refund your expenses. ያወጣኸውን ፡ እተካልሃለሁ
2. መለሰ. Please refund my payment on the books! መጽሐፎቹን ፡ የገዛሁበትን ፡ መልስልኝ

**refund** (n.) ተመላሽ ፡ ገንዘብ
I received a refund in the mail. ተመላሹ ፡ ገንዘብ ፡ በፖስታ ፡ ደረሰኝ
*No refunds. የተሸጠ ፡ አይመለስም

**refusal**
1. እምቢታ. Nodding the head from side to side is a gesture of refusal. ራስን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ መነቅነቅ ፡ የእምቢታ ፡ ምልክት ፡ ነው
2. እምቢ ፡ ማለት. Our hopes were demolished by his refusal. እምቢ ፡ በማለቱ ፡ ተስፋችን ፡ ወደመ

**give a refusal** እምቢ ፡ አለ
With no hesitation, he gave a point-blank refusal. ሳያቅማማ ፡ በቀጥታ ፡ እምቢ ፡ አለ

**meet with refusal** ተቀባይ ፡ አጣ
His plans met with refusal. እቅዱ ፡ ተቀባይ ፡ አጣ

**refuse** (v.)
1. እምቢ ፡ አለ. She refused him when he begged her to marry him. እንዲያገባት ፡ ቢለምናት ፡ እምቢ ፡ አለችው
2. (negative verb) + አለ. She refused to help me. አልረዳሁም ፡ አለችኝ
He refuses to accept my resignation. የሥራ ፡ መልቀቂያ ፡ ደብዳቤዬን ፡ አልቀበልም ፡ አለኝ
3. (negative verb). I refuse to sign the contract. ውሉን ፡ አልፈርምም

**refuse** (n.) ቆሻሻ
Place refuse in a container! ቆሻሻውን ፡ መጣያ ፡ ውስጥ ፡ ጣለው

**refute**
1. አስተባበለ. I can refute what he said. ያለውን ፡ ላስተባብል ፡ እችላለሁ
2. አፈረሰ· I tried to refute his argument. ክርክሩን ፡ ላፈርስበት ፡ ሞከርኩ

**regain**
1. አስመለሰ. Many African countries have regained their independence lately. ብዙ ፡ የአፍሪካ ፡ አገሮች ፡ ነጻነታቸውን ፡ ያስመለሱት ፡ በቅርቡ ፡ ነው
2. አገኘ. You regain the main road by turning right. ወደ ፡ ቀኝ ፡ ታጥፈህ ፡ ዋናውን ፡ መንገድ ፡ ታገኘለህ
He regained his freedom by jumping over the fence. ባጥሩ ፡ ላይ ፡ ዘሎ ፡ በማምለጥ ፡ ነጻነቱን ፡ አገኘ
3. ተመለሰ(ለት). +He regained his health slowly. ቀስ ፡ በቀስ ፡ ጤናው ፡ ተመለሰለት
[See also 'consciousness']

**regal**
1. ንጉሣዊ. The regal power descends from father to son. ንጉሣዊ ፡ ሥልጣን ፡ ከባት ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ ይተላለፋል
His regal bearing impressed everybody. ንጉሣዊ ፡ ግርማው ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አስደነቀ
2. የክብር. The regal robes are worn on occasions of state. የክብር ፡ ልብሶቹ ፡ የሚለበሱት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የበዓል ፡ ቀናት ፡ ነው

**regale** አስደሰተ
He regaled me with stories of his adventures. ያጋጠሙትን ፡ ነገሮች ፡ በማጫወት ፡ አስደሰተኝ

**regale oneself with** በመብላት ፡ ተደሰተ
The children regaled themselves with candy. ሕፃናቶቹ ፡ ከረሜላ ፡ በመብላት ፡ ተደሰቱ

**regalia** የክብር ፡ ልብስ
The royal regalia is made of velvet and gold brocade. የንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ የክብር ፡ ልብስ ፡ ከከፈይና ፡ ከረቀቀ ፡ የወርቅ ፡ ጉንጉን ፡ የተሠራ ፡ ነው

**regard** (v.)
1. ተመለከተ. I regard his activities with suspicion. የሚያደርገውን ፡ ሁሉ ፡ በጥርጣሬ ፡ እመለከታለሁ

This does not regard me at all. ይህ ፡ በፍጹም ፡ አይመለከተኝም
2. ቈጠረ (ተቈጠረ). I regard him as a friend. እንደ ፡ ጓደኛዬ ፡ እቈጥረዋለሁ
He is regarded as an authority on American history. የአሜሪካን ፡ ታሪክ ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ እንደ ፡ ሊቅ ፡ ይቈጠራል
3. ጠበቀ. He never regards the feelings of others. የሌሎችን ፡ ስሜት ፡ ፈጽሞ ፡ አይጠብቅም
4. ሞላ. She always regards her parents' wishes. የወላጆቿን ፡ ፈቃድ ፡ ሁልጊዜ ፡ ትሞላለች
5. አከበረ. I regard him highly. በጣም ፡ አከብረዋለሁ
6. ተቀበለ. He seldom regards my advice. ምክሬን ፡ እምብዛም ፡ አይቀበልም
*My decision regards your happiness. የሰጠሁት ፡ ውሳኔ ፡ አንተ ፡ የምትደሰትበት ፡ ነው

**regard** (n.) ዓይን
The boy's regard seemed fixed upon some distant object. የልጁ ፡ ዓይን ፡ ባንድ ፡ ሩቅ ፡ ባለ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የተተከለ ፡ ይመስል ፡ ነበር

**regards** ሰላምታ
Give my regards to your wife! ለባለቤትዎ ፡ ሰላምታዬን ፡ ያቅርቡልኝ

**as regards** በ - - - በኩል
As regards money, I have enough. በገንዘብ ፡ በኩል ፡ በቂ ፡ አለኝ
*As regards his education, it does not seem to have been adequate. የሱ ፡ ትምህርት ፡ እንኳ ፡ የተሟላ ፡ አይመስለኝም

**have regard** አሰበ
He has no regard at all for others. ፈጽሞ ፡ ለሰው ፡ አያስብም

**hold in high regard** በጣም ፡ አከበረ
He holds his father in high regard. አባቱን ፡ በጣም ፡ ያከብራቸዋል

**in regard to** ስለ
John spoke in regard to the meeting. ጆን ፡ ስለ ፡ ስብሰባው ፡ ተናገረ

**in that regard** እሱ ፡ ላይ
In that regard, I agree with you. እሱ ፡ ላይ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ እስማማለሁ

**with regard to**
1. ስለ. The students were split into two camps with regard to their school's rules. ተማሪዎቹ ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ቤታቸው ፡ ሕግ ፡ ሁኔታ ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ተከፍለዋል
2. በማስታወስ. With regard to your letter of January first . . . . ጥር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የጻፍከውን ፡ ደብዳቤ ፡ በማስታወስ

**without regard to**
*You'll get in trouble if you act without regard to good behavior. ጠባይህን ፡ ካላሳመርክ ፡ ጣጣ ፡ ያገኝሃል

**(be) regardful** ተጠነቀቀ
He is regardful of the feelings of others. ለሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ስሜት ፡ ይጠነቀቃል

**regarding**
1. ስለ. A letter regarding the boy's conduct was sent to his father. ስለ ፡ ልጁ ፡ ጠባይ ፡ ለአባትዬው ፡ ደብዳቤ ፡ ተላከ
2. በማስታወስ. Regarding your inquiry of January 10th . . . . ጥር ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ የጠየቅኸውን ፡ በማስታወስ - - -
3. የሚመለከት. The church canon regarding marriage is often violated. ጋብቻን ፡ የሚመለከተው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይጣሳል

**regardless**
*We objected, but he went regardless. እኛ ፡ ብንቃወምም ፡ እሱ ፡ ሄደ

**regardless of** ምንም ፡ ያህል ፡ ቢሆን
Regardless of the cost, I will buy it. ዋጋው ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ቢሆን ፡ እገዛዋለሁ
*I will do it regardless of what you told me. ያልከውን ፡ ብል ፡ እንጂ ፡ አደርገዋለሁ

**regency** እንደራሴነት
The regency will terminate when the king comes of age. ንጉሡ ፡ ለአካለ ፡ መጠን ፡ ሲደርሱ ፡ እንደራሴነቱ ፡ ያበቃል
[See also 'council']

**regenerate**
1. እንደገና ፡ አበቀለ. A tadpole can regenerate a leg which has been cut off. የጓጉንቸር ፡ ትል ፡ እግር ፡ ቢቈረጥ ፡ እንደገና ፡ አዲስ ፡ ታበቅላለች
2. ከፈተ. His discovery regenerated a whole field of study. እርሱ ፡ ያገኘው ፡ ነገር ፡ ብዙ ፡ የትምህርት ፡ መስክ ፡ ከፈተ

**regent** እንደራሴ
The king's uncle is now regent. የንጉሡ ፡ አጐት ፡ አሁን ፡ እንደራሴ ፡ ናቸው

**regime**
1. መንግሥት. South Africa has a very authoritarian regime. ደቡብ ፡ አፍሪካ ፡ በጣም ፡ ፈላጭ ፡ ቈራጭ ፡ መንግሥት ፡ አለው

2. ዘመን. During the regime of the Judges, there was much strife. በመሳፍንት ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ብጥብጥ ፡ ነበር
*The baby's regime includes two naps a day. ሕፃኑ ፡ በደንብ ፡ እንዲያድግ ፡ በቀን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ እንቅልፍ ፡ ማግኘት ፡ አለበት
[See also 'austerity']

**regiment** (v.) ወታደራዊ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲከተል ፡ አደረገ
The dictator regimented even the children. አምባገነኑ ፡ ሕፃናት ፡ እንኳ ፡ ሳይቀሩ ፡ ወታደራዊ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲከተሉ ፡ አደረገ

**regiment** (n.) ሬጂሜንት
The regiment is made up of new recruits. ሬጂሜንቱ ፡ የምልምል ፡ ወታደሮች ፡ ነው

**regimentation** ሥርዓት
The regimentation of military life is well described in his book. የወታደር ፡ ሥርዓት ፡ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ በደንብ ፡ ተገልጿል

**region**
1. ቀበሌ. A mountainous region separates the desert from the highlands. ተራራማ ፡ የሆነ ፡ ቀበሌ ፡ በረኻውን ፡ ከደጋው ፡ ይለያል
A mining region produces gold and silver. የማዕድኑ ፡ ቀበሌ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ይወጣበታል
2. ክፍለ ፡ ሀገር. There is much rain in the region in which we live. ያለንበት ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ዝናም ፡ ይበዛዋል
3. አካባቢ. The people of this region live in abysmal poverty. የዚህ ፡ አካባቢ ፡ ሰዎች ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ
4. ክፍል. They began the investigation of the upper region of the atmosphere. የህዋውን ፡ ከፍተኛ ፡ ክፍል ፡ መመርመር ፡ ጀመሩ

**(in) the region of** አካባቢ
He has pains in the region of the liver. ጉበቱ ፡ አካባቢ ፡ ሕመም ፡ ይሰማዋል

**regional**
1. የቀበሌ. This is a regional meeting of the Boy Scouts. ይህ ፡ የቀበሌ ፡ እስካውቶች ፡ ስብሰባ ፡ ነው
2. በቀበሌ ፡ የተሠራ. Regional products are favored by our customers. ደንበኞቻችን ፡ በቀበሌ ያችን ፡ የተሠሩትን ፡ እቃዎች ፡ ይመርጣሉ

**register** (vt.)
1. መዘገበ. He registered twenty students today. ዛሬ ፡ ሃያ ፡ ተማሪዎች ፡ መዘገበ
How many degrees does the thermometer register? ቴርሞሜትሩ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ሙቀት ፡ ይመዘግባል ?
2. አረፈ. He is not registered at this hotel. እዚህ ፡ ሆቴል ፡ አያርፍም
*His face registered surprise. ፊቱ ፡ ላይ ፡ የመደነቅ ፡ ስሜት ፡ ይነበብ ፡ ነበር

**register** (vi.)
1. ታየ. A broad smile registered on his face. ከፍ ፡ ያለ ፡ ፈገግታ ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ታየ
2. ተመዘገበ. A person must register before he can vote. አንድ ፡ ሰው ፡ ድምፅ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ መመዝገብ ፡ አለበት

**register letters**
Where do you register letters? ያደራ ፡ ደብዳቤ ፡ መላኪያው ፡ የት ፡ ነው ?

**register** (n.) መዝገብ
Did you sign the register? መዝገቡ ፡ ላይ ፡ ፈረምክ ?

**registered letter** ሬኮማንዴ
I got a registered letter today. ዛሬ ፡ ሬኮማንዴ ፡ ደረሰኝ

**registrar** ሬጂስትራር
The registrar registered many students today. ሬጂስትራሩ ፡ ዛሬ ፡ ብዙ ፡ ተማሪዎችን ፡ መዘገበ

**registration**
1. መመዝገቢያ. The registration period ends today. የመመዝገቢያው ፡ ጊዜ ፡ ዛሬ ፡ ያልቃል
2. የባለቤትነት ፡ መታወቂያ. Show me your automobile registration! የመኪና ፡ የባለቤትነት ፡ መታወቂያህን ፡ አሳየኝ
*This year registration for school is higher than last year. ዘንድሮ ፡ የተመዘገቡት ፡ ተማሪዎች ፡ ብዛት ፡ ካለፈው ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ ነው

**registration day** የምዝገባ ፡ ቀን
There was an inordinate amount of confusion on registration day. በምዝገባ ፡ ቀን ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ ትርምስምስ ፡ ነበር

**registry** (registries) መዝገብ ፡ ቤት
The registry is out of application forms. መዝገብ ፡ ቤቱ ፡ የማመልከቻ ፡ ፎርም ፡ አልቆበታል

**regress** ዝቅ ፡ አለ
The project regressed to the level of six months ago. የፕሮጀክቱ ፡ ሥራ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ደረጃ ፡ ዝቅ ፡ አለ

**regression** አእምሮው ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ መሄዱ
The child's regression worries the parents.

የሕፃኑ ፡ አእምሮ ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ መሄዱ ፡ ወላጆቹን ፡ አሳስቧል

**regret** (regretted), v.
1. ተጸጸተ. I don't regret having said it. በመናገሬ ፡ አልጸጸትም
2. ቈጨ(ው). +I've always regretted not having traveled much. ብዙ ፡ አገር ፡ አለማየቴ ፡ ሁልጊዜ ፡ ይቈጨኛል

**(be) regretted** አዘኑ
+He died regretted by all who knew him. የሚያውቁት ፡ ሁሉ ፡ በመሞቱ ፡ አዘኑ

**regret** (n.)
1. ጸጸት. He expressed his regret by asking pardon. ይቅርታ ፡ በመጠየቅ ፡ ጸጸቱን ፡ ገለጸ
2. ይቅርታ ፡ መጠየቅ. He invited me to the party, but I had to send my regrets. ፓርቲው ፡ ጋብዞኝ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ይቅርታ ፡ በመጠየቅ ፡ መልእክት ፡ መላክ ፡ ነበርብኝ
*I decline with regret. ለመቀበል ፡ ባለመቻሌ ፡ አዝናለሁ

**have regrets** አዘነ
I'd rather study than have regrets later. በኋላ ፡ ከማዘን ፡ አሁን ፡ ማጥናት ፡ ይሻለኛል

**much to my regret** በጣም ፡ ቅር ፡ ያሰኘኛል
Much to my regret, I am unable to accept their invitation. ጥሪያቸውን ፡ ለመቀበል ፡ አለመቻሌ ፡ በጣም ፡ ቅር ፡ ያሰኘኛል

**regrettable** የሚያሳዝን
This is a regrettable mistake. ይህ ፡ የሚያሳዝን ፡ ስሕተት ፡ ነው

**regular** (n.) ደንበኛ
He is one of the regulars here. ከደንበኞቻችን ፡ አንዱ ፡ ነው

**regular** (adj.)
1. ደንበኛ. The regular price is five dollars. ደንበኛው ፡ ዋጋ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ነው
2. የተወሰነ. He is a man with regular habits. የተወሰነ ፡ ልምድ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው
3. የተለመደ. He sat in his regular place. በተለመደ ፡ ስፍራው ፡ ተቀመጠ
4. መደበኛ. Her regular school fees are 500 dollars a semester. መደበኛው ፡ የትምህርት ፡ ሒሳብ ፡ በሴመስተር ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ነው
5. የዘወትር. Regular care of the teeth is important. ለጥርስ ፡ የዘወትር ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
6. ቀዋሚ ፤ ቋሚ. He has no regular work. ቀዋሚ ፡ ሥራ ፡ የለውም
This country has no regular army. ይህች ፡ አገር ፡ ቋሚ ፡ የጦር ፡ ኀይል ፡ የላትም
7. የተስተካከለ. Her features are regular. የፊቷ ፡ ቅርጽ ፡ የተስተካከለ ፡ ነው
8. ፍጹም. The game was a regular battle. ግጥሚያው ፡ ፍጹም ፡ ጦርነት ፡ ነበር

**regularity**
*Regularity of attendance in school is necessary for good grades. ጥሩ ፡ ውጤት ፡ ለማግኘት ፡ ዘወትር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መገኘት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**regularly**
1. ሳያቋርጥ ፤ ያለማቋረጥ. He pays regularly. ሳያቋርጥ ፡ ይከፍላል
She goes to confession regularly. ያለማቋረጥ ፡ ንስሓ ፡ ትገባለች
2. በየጊዜው. She regularly confides her troubles to her friend. ችግሯን ፡ በየጊዜው ፡ ለጓደኛዋ ፡ ታካፍላለች

**regulate**
1. ወሰነ. The law regulates the speed at which vehicles may be driven. ተሽከርካሪዎች ፡ የሚነዱበትን ፡ ፍጥነት ፡ ሕጉ ፡ ይወስናል
2. ተቈጣጠረ. The two countries signed a pact to regulate trade between them. ሁለቱ ፡ ሀገሮች ፡ በመሀከላቸው ፡ ንግድን ፡ ለመቈጣጠር ፡ ውል ፡ ተፈራረሙ
There is a special device to regulate the heat. ሙቀቱን ፡ የሚቈጣጠር ፡ ልዩ ፡ መሣሪያ ፡ አለ
3. ጠበቀ. The government is an institution which regulates the welfare of the country. መንግሥት ፡ የሀገሪቷን ፡ ደኅንነት ፡ የሚጠብቅ ፡ ድርጅት ፡ ነው

**be regulated** በ - - - ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው
The price of coffee is regulated by the government. የቡና ፡ ዋጋ ፡ በመንግሥት ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው

**regulation** (n.)
1. ደምብ ፤ ደንብ ፤ ሥርዓት. That's against police regulations. ያ ፡ ከፖሊስ ፡ ደንብ ፡ (ሥርዓት) ፡ ውጭ ፡ ነው
2. መቈጣጠር. The regulation of trade is the job of the Ministry of Commerce. ንግድን ፡ መቈጣጠር ፡ የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ተግባር ፡ ነው

**regulation** (adj.) የደንብ
Soldiers wear a regulation uniform. ወታደሮች ፡ የደንብ ፡ ልብስ ፡ ይለብሳሉ

**regurgitate** አቀረሸ(ው)
+The baby regurgitated food from his stomach. ሕፃኑ ፡ አቀረሸው

**rehabilitate**
*Society must rehabilitate criminals. ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ወንጀለኞችን ፡ ወደ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እንዲመለሱ ፡ መርዳት ፡ አለበት

**rehabilitate oneself** ራሱን ፡ አረመ
The former criminal rehabilitated himself and was respected by all. የቀድሞው ፡ ወንጀለኛ ፡ ራሱን ፡ አርሞ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ የተከበረ ፡ ሆኗል

**be rehabilitated** እንደገና ፡ መልካም ፡ ስም ፡ አገኘ
He has been rehabilitated in public esteem. በሕዝቡ ፡ በኩል ፡ እንደገና ፡ መልካም ፡ ስም ፡ አግኝቷል

**(be) rehashed**
The question had been rehashed again and again. ጉዳዩ ፡ ተደጋግሞ ፡ ውይይት ፡ የተደረገበት ፡ ነው

**rehearsal** የቲያትር ፡ ልምምድ
The rehearsal was interrupted by fights among the actors. የቲያትሩ ፡ ልምምድ ፡ በተጫዋቾች ፡ ድብድብ ፡ ምክንያት ፡ ተቋረጠ

**rehearse**
1. ተለማመደ. We are rehearsing this play. ይህን ፡ ቲያትር ፡ በመለማመድ ፡ ላይ ፡ ነን
2. መልሶ ፡ አጫወተ ፤ በድጋሚ ፡ አጫወተ. He rehearsed all his troubles to me. ችግሮቹን ፡ ሁሉ ፡ መልሶ ፡ (በድጋሚ) ፡ አጫወተኝ

**reign** (v.)
1. ነገሠ. King Theodore reigned from 1855 to 1868. አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የነገሡት ፡ ከ፲፰፻፵፯ ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፷ ዓ. ም. ድረስ ፡ ነበር
2. ሰፈነ. On a still night, silence reigns. ጭር ፡ ባለ ፡ ሌሊት ፡ ጸጥታ ፡ ይሰፍናል

**reign** (n.)
1. ዘመነ ፡ መንግሥት. His reign was marked by prosperity. ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ የብልጽግና ፡ ዘመን ፡ ነበር
2. አገዛዝ. The reign of a wise man benefits the country. የብልህ ፡ ሰው ፡ አገዛዝ ፡ አገርን ፡ ይጠቅማል
3. የግዛት ፡ ዘመን. The apex of Mussolini's reign was the conquest of Ethiopia. የሙሶሊኒ ፡ የግዛት ፡ ዘመን ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የደረሰው ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረ ፡ ጊዜ ፡ ነበር

**reimburse** ተካ(ለት) ፤ ያወጣውን ፡ መለሰ(ለት)
The company reimbursed him for his expenses on the trip. ኩባንያው ፡ ለጉዞው ፡ ያደረገውን ፡ ወጪ ፡ ተካለት
We must have a voucher before we will reimburse you. ያወጣኸውን ፡ እንድንመልስልህ ፡ ደረሰኝ ፡ አቅርብ

**rein** (v.) ልጓሙን ፡ አጥብቆ ፡ ያዘ
He reined the horse to keep it from bolting. ፈረሱ ፡ እንዳይሸመጥጥ ፡ ልጓሙን ፡ አጥብቆ ፡ ያዘ

**rein** (n.)
1. ልጓም. He pulled at the reins to make the horse stop. ፈረሱን ፡ ለማቆም ፡ ልጓሙን ፡ ሳበ
2. ሥልጣን. When the President was ill, the Vice-President took the reins of government. ፕሬዚዳንቱ ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ያዘ

**give free rein** ሳይገታ ፡ ቀረ
He gave his imagination free rein. ዓይነ ፡ ኅሊናውን ፡ ሳይገታ ፡ ቀረ

**hold the reins**
*He holds the reins of government. መንግሥቱ ፡ በእጁ ፡ ነው

**keep tight rein on** በጥብቅ ፡ ተቈጣጠረ
She keeps tight rein on her son. ልጇን ፡ በጥብቅ ፡ ትቈጣጠራለች

**(be) reincarnated** እንደገና ፡ ተፈጠረ
According to the legend, the man was reincarnated as a crow. በአፈ ፡ ታሪኩ ፡ መሠረት ፡ ሰውዬው ፡ ቁራ ፡ ሆኖ ፡ እንደገና ፡ ተፈጠረ

**reincarnation**
1. [ከሞት ፡ በኋላ ፡ የነፍስ ፡ በሌላ ፡ መልክ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ መመለስ ፡ ያንዳንድ ፡ ሃይማኖት ፡ እምነት]
2. ትንሣኤ. The reincarnation of Christ is celebrated as a church holiday. የክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ፡ እንደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዓል ፡ ይከበራል

**reinforce** አጠነከረ
Fresh troops are to reinforce the front lines. አዲስ ፡ ወታደሮች ፡ የግንባሩን ፡ ጦር ፡ ሊያጠነክሩ ፡ ነው

**reinforcements** ተጨማሪ ፡ ጦር
Reinforcements are being flown to the front. የግንባሩን ፡ ጦር ፡ ለማጠንከር ፡ ተጨማሪ ፡ ጦር ፡ በአውሮፕላን ፡ በመላክ ፡ ላይ ፡ ነው

**reinstate** ወደ - - - መለሰ
They reinstated him as chairman. ወደ ፡ ሊቀ ፡ መንበርነቱ ፡ መለሱት

**reissue** እንደገና ፡ አትሞ ፡ አወጣ
They removed the offensive passages, and reissued the statement. አስከፊ ፡ የሆነውን ፡ አንቀጽ ፡ ካስቀሩ ፡ በኋላ ፡ ንግግሩን ፡ እንደገና ፡ አትመው ፡ አወጡ

**reiterate** ደጋገመ
The boy did not move though the teacher reiterated his command. መምህሩ ፡ ትእዛዙን ፡ ቢደጋግምም ፡ ተማሪው ፡ አልንቀሳቀስ ፡ አለ

**reject**
1. አልተቀበለም. The judge rejected his plea for a stay. ቀጠሮ ፡ እንዲደረግ ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ዳኛው ፡ አልተቀበሉትም
2. ሳይቀበል ፡ ቀረ. He rejected the advice I gave him. ምክሬን ፡ ሳይቀበለኝ ፡ ቀረ
3. አልቀበልም ፡ አለ. He hardened his heart, and rejected her request. ጨክኖ ፡ ልመናዋን ፡ አልቀበልም ፡ አለ
4. ጣለ. He rejected the rotten apples. የበሰበሱትን ፡ ቱፋሆች ፡ ጣላቸው

**be rejected**
1. አልቀበልህም ፡ ተባለ. He tried to join the army, but was rejected. ወታደርነት ፡ ለመግባት ፡ ሞክሮ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንቀበልህም ፡ ተባለ
2. ተቀባይነትን ፡ አጣ. The bill was rejected in its entirety. የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ በሙሉ ፡ ተቀባይነትን ፡ አጣ

**rejection** ተቀባይነት ፡ ማጣት
The rejection of his proposal chagrined him deeply. ያቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ተቀባይነት ፡ ማጣቱ ፡ ቅር ፡ አሰኘው

**rejoice** (vt.) አስደሰተ
The sight of her gifts rejoiced Mary greatly. የተሰጡትን ፡ ስጦታዎች ፡ ማየቱ ፡ ሜሪን ፡ አስደሰታት

**rejoice** (vi.) ተደሰተ
He rejoiced when he was told he had a son. ወንድ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ተወለደለት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ተደሰተ

**rejoicing** ሣቅና ፡ ጨዋታ
The sounds of rejoicing could be heard all night long. ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ ሣቅና ፡ ጨዋታ ፡ ይሰማ ፡ ነበር

**rejoin**
1. እንደገና ፡ ከ - - - ተቀላቀለ. The members of our family will rejoin us next month. ቤተሰቦቻችን ፡ በሚቀጥለው ፡ ወር ፡ እንደገና ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ይቀላቀላሉ
2. ከ - - - ጋር ፡ እንደገና ፡ ተደባለቀ. He rejoined his unit after a short absence. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ ከጦሩ ፡ ጋር ፡ እንደገና ፡ ተደባለቀ
3. ተጋጠመ. The side road rejoins the main road five miles further on. ተገንጣዩ ፡ መንገድ ፡ ከምስት ፡ ማይል ፡ በኋላ ፡ ከዋናው ፡ መንገድ ፡ ጋር ፡ ይጋጠማል

**rejuvenate**
1. ወደ ፡ ልጅነት ፡ መለሰ. This potion is supposed to rejuvenate old men. ይህ ፡ መድኃኒት ፡ ሽማግሌዎችን ፡ ወደ ፡ ልጅነት ፡ ይመልሳል ፡ ይባላል
2. ሰውነቱን ፡ አደሰ(ለት). The rest rejuvenated us. ዕረፍቱ ፡ ሰውነታችንን ፡ አደሰልን

**relapse** (v.)
1. ተመለሰ. The tribe relapsed into paganism. ነገዱ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ ማምለክ ፡ ተመለሰ
2. አገረሸ(በት). After a few weeks of recovery, he relapsed. ለጥቂት ፡ ሳምንታት ፡ ከተሻለው ፡ በኋላ ፡ አገረሸበት
[See also 'unconsciousness']

**relapse** (n.)
*His relapse worried his family. በሽታው ፡ ስላገረሸበት ፡ ቤተሰቡ ፡ ተጨነቀ

**suffer a relapse** ሕመሙ ፡ አገረሸ(በት)
He suffered a relapse after leaving the hospital. ከሐኪም ፡ ቤት ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ሕመሙ ፡ አገረሸበት

**relate** (vt.)
1. አወራ. He related his adventures to the eager children. ያጋጠመውን ፡ ነገር ፡ ለጓጉት ፡ ልጆች ፡ አወራላቸው
2. አዛመደ. It is difficult to relate this result to any specific cause. የተገኘውን ፡ ውጤት ፡ ካንድ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ ጋር ፡ ማዛመድ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**relate** (vi.) ነካ
She notices only that which related to herself. ልብ ፡ የምትለው ፡ በግል ፡ እሷን ፡ የሚነካትን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው

**related** (adj.) የሚዛመድ
Mathematics and astronomy are related disciplines. ሒሳብና ፡ አስትሮኖሚ ፡ የሚዛመዱ ፡ ትምህርቶች ፡ ናቸው
The primary meaning of the word is the same in all the related languages. የቃሉ ፡ መሠረታዊ ፡ ትርጉም ፡ በሚዛመዱ ፡ ቋንቋዎች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ነው

**be related**
1. ተዛመደ. We're related on my mother's side. በናቴ ፡ በኩል ፡ እንዛመዳለን
2. የተያያዘ. Is the rise of living costs related to the closing of the Suez Canal? የኑሮ ፡ መወደድ ፡ ከስዌዝ ፡ ቦይ ፡ መዘጋት ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው ?
[See also 'remotely']

**relation**

1. የነገረው ፡ ነገር. We were interested by the soldier's relation of his adventures. ወታደሩ ፡ ስለሠራው ፡ ጀብዱ ፡ የነገረን ፡ ነገር ፡ አስደስተን

2. ዘመድ. I have a lot of relations there. እዚያ ፡ ብዙ ፡ ዘመዶች ፡ አሉኝ

She is no relation of mine. ዘመዴ ፡ አይደለችም

3. ግንኙነት. His remark has no relation to the discussion. አስተያየቱ ፡ ከውይይቱ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የለውም

Keep in mind the relation of poverty to crime! የድኽነትንና ፡ የወንጀልን ፡ ግንኙነት ፡ አስታውስ

The relations between our two countries are good. በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ጥሩ ፡ ነው

**bear relation to** ተመጣጠነ

The results of the project bear no relation to the expenses involved. የፕሮጄክቱ ፡ ውጤት ፡ ከተደረገው ፡ ወጪ ፡ ጋር ፡ አይመጣጠንም

**in relation to** ስለ

The foreman will ask questions in relation to your education and experience. የክፍሉ ፡ አለቃ ፡ ስለ ፡ ትምህርትህና ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ልምድህ ፡ ጥያቄዎች ፡ ያቀርብልሃል

**with relation to** በማሰብ

We must plan with relation to the future. የወደፊቱን ፡ በማሰብ ፡ ማቀድ ፡ አለብን

*With relation to the preceding, I would like to add a few remarks. በፊት ፡ በተባለው ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ለመጨመር ፡ እፈልጋለሁ

[See also 'near']

**relationship** ግንኙነት

The relationship between the two people is friendly. በሁለቱ ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ አለ

**family relationship** ዝምድና

What is the family relationship between those two girls? የነዚያ ፡ የሁለት ፡ ልጃገረዶች ፡ ዝምድና ፡ እንዴት ፡ ነው ?

**relative** (n.) ዘመድ

They are close relatives of ours. የቅርብ ፡ ዘመዶቻችን ፡ ናቸው

**relative** (adj.)

1. የተያያዘ. We studied gravitation and relative phenomena. ስለ ፡ ስበትና ፡ የተያያዙ ፡ ሁኔታዎች ፡ አጠናን

2. (= adv.) ከሌላው ፡ ጋር ፡ ሲነጻጸር. They are living in relative comfort. ከሌላው ፡ ጋር ፡ ሲነጻጸር ፡ እነሱ ፡ የሚኖሩት ፡ በምቾት ፡ ነው

*Before ordering our dinner, we considered the relative merits of chicken and veal. እራታችንን ፡ ከማዘዛችን ፡ በፊት ፡ ከዶሮና ፡ ከጥጃ ፡ ሥጋ ፡ የትኛው ፡ እንደሚሻል ፡ አመዛዘን

**relative (to)**

1. እንደ. Value is relative to demand. ዋጋው ፡ እንደ ፡ እቃው ፡ ተፈላጊነት ፡ ነው

2. (= adv.) ሲመዛዘን. He is strong relative to his size. ከሰውነቱ ፡ ጋር ፡ ሲመዛዘን ፡ ጠንካራ ፡ ነው

3. ግንኙነት ፡ ያለው. Give me the papers relative to our discussion. ከውይይታችን ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸውን ፡ ጽሑፎች ፡ ስጠኝ

**(be) relative (to)** ተዛመደ ፣ ተያያዘ

Is your question relative to the subject? ጥያቄህ ፡ ከጉዳዩ ፡ ጋር ፡ የተዛመደ ፡ (የተያያዘ) ፡ ነው?

**relatively**

1. በመጠኑ. In spite of her dull husband, she is relatively happy. ባሏ ፡ ለዛ ፡ ቢስ ፡ ቢሆንም ፡ በመጠኑ ፡ ደስተኛ ፡ ናት

2. ከሌሎች ፡ ጋር ፡ ሲወዳደር. In this town, Mr. Parker is considered relatively rich. ከሌሎች ፡ ጋር ፡ ሲወዳደር ፡ በዚህ ፡ ከተማ ፡ ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ ሀብታም ፡ ነው

**relative pronoun** አዛማጅ ፡ ተውላጠ ፡ ስም

Amharic uses a special relative pronoun for the past tense. አማርኛ ፡ ለኀላፊ ፡ ጊዜ ፡ የተለየ ፡ አዛማጅ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ አለው

**relax** (vt.)

1. ቀነሰ. The enemy may win yet if we relax our efforts. አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ትግላችንን ፡ ከቀነስን ፡ ጠላት ፡ ድል ፡ ሊያደርገን ፡ ይችላል

2. መንፈሱን ፡ አረካ ፣ መንፈሱን ፡ አደሰ. Playing folk songs relaxes me. ያገር ፡ ቤት ፡ ዘፈን ፡ መዝፈን ፡ መንፈሴን ፡ ያረካዋል ፡ (ያድሰዋል)

3. አላላ. They relaxed the requirements for a driver's license. ለመንጃ ፡ ፈቃድ ፡ የሚጠይቋቸውን ፡ ነገሮች ፡ አላሉ

**relax** (vi.)

1. ዕረፍት ፡ አገኘ. I can't relax until it's finished. እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ዕረፍት ፡ አላገኝም

2. ተዝናና. He relaxes by taking a walk in his garden. ባትክልት ፡ ስፍራው ፡ ውስጥ ፡ በመንሸራሸር ፡ ይዝናናል

3. (= active) ዕረፍት ፡ ሰጠ. +The body relaxes in sleep. መኝታ ፡ ለሰውነት ፡ ዕረፍት ፡ ይሰጣል

**be relaxed** ላላ ፡ አለ

Discipline in our school has been relaxed since the new principal took over. አዲሱ ፡ ዲረክ

ተሩ ፡ ከመጡ ፡ ወዲህ ፡ የትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላላ ፡ ብሏል

**relaxation**
What do you do for relaxation? የምትዝናናው ፡ እንዴት ፡ ነው ?

**relay** (v.) አስተላለፈ
Messengers will relay your message. ተላላኪዎች ፡ መልእክትህን ፡ ያስተላልፉልሃል

**be relayed** ተላለፈ
The news was relayed to headquarters by radio and by messengers. ዜናው ፡ ለዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተላለፈው ፡ በሬዲዮና ፡ በተላላኪዎች ፡ አማካይነት ፡ ነው

**relay** (n.) መፈራረቅ
They finished the job by working in relays. ሥራውን ፡ በመፈራረቅ ፡ እየሠሩ ፡ ጨረሱት

**relay race** የዱላ ፡ ቅብብል ፡ እሽቅድድም
They ran a relay race. የዱላ ፡ ቅብብል ፡ እሽቅድድም ፡ አደረጉ

**release** (v.)
1. ለቀቀ. The police released him right away. ፖሊሱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለቀቀው
2. ፈታ. The archbishop released the priest from his vows. ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ቄሱን ፡ ከቃለ ፡ መሐላው ፡ ፈቱት
They acted in complete accord with him in releasing the prisoner. እስረኛውን ፡ ሲፈቱ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ በሙሉ ፡ መግባባት ፡ ነበር
3. ባለ ፡ ንብረትነት ፡ አዛወረ. Mr. Parker released his house to the bank. ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ የቤቱን ፡ ባለንብረትነት ፡ ለባንክ ፡ አዛወረ
4. ማረ. She released him from the promise. የገባላትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ማረችው
5. እንዲጣል ፡ ለቀቀ. This trigger releases the bombs. ይህ ፡ ምላጭ ፡ ቦምቡ ፡ እንዲጣል ፡ ይለቀቃል
6. እንዲታይ ፡ ፈቀደ. The censor released the film for distribution. ሳንሱሩ ፡ ፊልሙ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲታይ ፡ ፈቀደ

**release from** ማረ
He released me from the debt. ዕዳውን ፡ ማረኝ

**release** (n.) መለቀቅ
The release of the prisoners was announced over the radio. የእስረኞቹ ፡ መለቀቅ ፡ በሬዲዮ ፡ ተነገረ
*The release from pain was due to the medicine. መድኃኒቱ ፡ ሕመሙን ፡ አስታገሠ

**relegate**
1. አስተላለፈ. He relegated the task to the assistant. ሥራውን ፡ ለረዳቱ ፡ አስተላለፈ
2. አስቀመጠ. We relegated the old furniture to the garage. አሮጌውን ፡ የቤት ፡ እቃ ፡ ጋራዥ ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጥን
*He relegated his wife to the position of a slave. ሚስቱን ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ ተመለከታት

**relent** ላላ ፡ አለ
The judge relented, and gave him twenty years instead of life. ዳኛው ፡ ላላ ፡ በማለት ፡ ከዕድሜ ፡ ይፍታህ ፡ ወደ ፡ ሃያ ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ አሻሻሉለት

**relentless**
1. ምሕረት ፡ የማያውቅ. His relentless foe captured him after a pursuit lasting twenty years. ምሕረት ፡ የማያውቀው ፡ ጠላቱ ፡ ሃያ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ከተከታተለው ፡ በኋላ ፡ ያዘው
2. (= adv.) ባለማቋረጥ. The relentless pounding of the waves on the beach did not let me sleep. ማዕበሉ ፡ ባለማቋረጥ ፡ የሚያደርገው ፡ ጩኸት ፡ አላስተኛ ፡ አለኝ

**(be) relevant** አግባብ ፡ አለው
Is your argument relevant to what I have been saying? ያንተ ፡ ክርክር ፡ እኔ ፡ ካልኩት ፡ ጋር ፡ አግባብ ፡ አለው ?

**reliable**
1. የታመነ. I got it from a reliable source. ያገኘሁት ፡ ከታመነ ፡ ምንጭ ፡ ነው
2. ታማኝ. I raised my servant's salary because he was so reliable. አሽከሬ ፡ በጣም ፡ ታማኝ ፡ ስለሆነ ፡ ደሞዝ ፡ ጨመርኩለት
3. ሊተማመኑበት ፡ የሚችል. He is a very reliable person. በጣም ፡ ሊተማመኑበት ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ ነው
4. እምነት ፡ የሚጣልበት. That is a reliable firm. እምነት ፡ የሚጣልበት ፡ ኩባንያ ፡ ነው

**be reliable** ሊታመን ፡ ቻለ
His recollection of past events is not very reliable. ስላለፈው ፡ ጊዜ ፡ የሚያወሳው ፡ ሊታመን ፡ አይችልም

**reliance**
1. እምነት. Airplane travelers put complete reliance in the pilot. ያየር ፡ መንገደኞች ፡ ሙሉ ፡ እምነታቸውን ፡ በነጂው ፡ ላይ ፡ ይጥላሉ
2. መመካት. As she grew older, she had less reliance on her family. እያደገች ፡ ስትሄድ ፡ በቤተ ፡ ሰቦቿ ፡ ላይ ፡ መመካቷ ፡ እየተቀነሰ ፡ ሄደ

3. መመኪያ. The widow's son was her chief reliance. ባሏ ፡ ለሞተባት ፡ ሴትዮ ፡ ዋና ፡ መመኪያዋ ፡ ልጇ ፡ ነበር

**relic** ቅርስ

This ruined bridge is a relic of the Roman period. ይህ ፡ የፈረሰ ፡ ድልድይ ፡ የሮማውያን ፡ ዘመን ፡ ቅርስ ፡ ነው

**relief**

1. እርዳታ. Ethiopia sent relief to the flood victims. ኢትዮጵያ ፡ የጐርፍ ፡ አደጋ ፡ ለደረሰባቸው ፡ እርዳታ ፡ ላከች

2. (= to relieve) መርዳት. Our soldiers are hurrying to the relief of the troops surrounded by the enemy. በጠላት ፡ የተከበበውን ፡ ጦር ፡ ለመርዳት ፡ ወታደሮቻችን ፡ በመገስገስ ፡ ላይ ፡ ናቸው

3. ፋታ. Did the medicine give you any relief? መድኃኒቱ ፡ ትንሽ ፡ ፋታ ፡ ሰጠህ ?

4. ግልግል. It's a relief to get out of this stuffy hall. ከዚህ ፡ ከታፈነ ፡ አዳራሽ ፡ መውጣት ፡ ግልግል ፡ ነው

5. ዕረፍት. Workers get a ten-minute relief every morning. ሁልጊዜ ፡ ከሰዓት ፡ በፊት ፡ ሠራተኞች ፡ ያሥር ፡ ደቂቃ ፡ ዕረፍት ፡ ይሰጣቸዋል

6. ተቀያሪ. The nurse's relief arrives at seven. የነርሷ ፡ ተቀያሪ ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ይገባል

*The tall building was in relief against the sky. የረጅም ፡ ፎቅ ፡ ቅርጽ ፡ በሰማይ ፡ ጐልቶ ፡ ታየ

**be on relief** ከመንግሥት ፡ እርዳታ ፡ አገኘ

The unemployed are on relief. ሥራ ፡ ፈቶች ፡ ከመንግሥት ፡ እርዳታ ፡ ያገኛሉ

**feel relief** ከሕመሙ ፡ እፎይ ፡ አለ

He felt instant relief when the medicine was put on. መድኃኒቱ ፡ ሲደረግለት ፡ ወዲያውኑ ፡ ከሕመሙ ፡ እፎይ ፡ አለ

**to (one's) great relief**

*The difficulties have been removed to my great relief. ችግሩ ፡ በመወገዱ ፡ እፎይ ፡ ብያለሁ

**relief map** የመሬት ፡ ቅጥ ፡ ካርታ

There is a relief map in our classroom. የመሬት ፡ ቅጥ ፡ ካርታ ፡ እክፍላችን ፡ ውስጥ ፡ አለ

**relieve**

1. አሻለ ፤ አስታገሠ. This will relieve your headache. ይህ ፡ የራስ ፡ ምታትህን ፡ ያሽልሃል

This medicine relieves all aches. ይህ ፡ መድኃኒት ፡ ሁሉንም ፡ ሕመም ፡ ያስታግሣል

2. ተከላከለ. Soldiers were sent to relieve the fort. ምሽጉን ፡ እንዲከላከሉ ፡ ወታደሮች ፡ ተልከው ፡ ነበር

3. ረዳ. His beneficence relieved the poor. ችሮታው ፡ ችግረኞችን ፡ ረዳቸው

4. አቃለለ. The Red Cross did everything to relieve the distress. ቀይ ፡ መስቀል ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ የገባውን ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ ሞከረ

5. አስወገደ. An impersonal discussion of student problems may help to relieve their distress. ማንንም ፡ የማይጠቅስ ፡ የተማሪዎች ፡ ችግር ፡ ውይይት ፡ ቅሬታቸውን ፡ ለማስወገድ ፡ ሊረዳ ፡ ይችል ፡ ይሆናል

6. ቀየረ. They relieve the guard promptly at noon. ዘቡን ፡ ልክ ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ ይቀይራሉ

**relieve of**

1. አገዘ. Let me relieve you of that heavy suitcase! ከባዱን ፡ ሻንጣህን ፡ ላግዝህ

2. አዳነ. Your coming relieved me of writing a long letter. መምጣትህ ፡ ረጅም ፡ ደብዳቤ ፡ ከመጻፍ ፡ አዳነኝ

**relieve one another** ተራ ፡ በተራ ፡ ተቀያየረ

The nurses relieve one another during the night. ነርሶቹ ፡ ሌሊት ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ ይቀያየራሉ

**be relieved**

1. ሐሳብ ፡ ቀለል ፡ አለ(ለት). We were relieved to hear that you arrived safely. በደኅና ፡ መድረስህን ፡ ስንሰማ ፡ ሐሳብ ፡ ቀለል ፡ አለልን

2. እፎይ ፡ አለ. We were relieved when the danger passed. አደጋው ፡ ሲያልፍ ፡ እፎይ ፡ አልን

**be relieved of** ተገላገለ

I am glad I have been relieved of that responsibility. ከዚያ ፡ ኀላፊነት ፡ በመገላገሌ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል

*I am glad I have been relieved of that worry. ሐሳቡ ፡ ስለወረደልኝ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል

**religion** ሃይማኖት

There are several religions in America. በአሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሃይማኖቶች ፡ አሉ

**religious**

1. ሃይማኖተኛ. He is very religious, and observes the fasts. ጽኑ ፡ ሃይማኖተኛ ፡ ስለሆነ ፡ አጽዋማትን ፡ ያከብራል

2. የሃይማኖት. Religious differences have caused many wars. የሃይማኖት ፡ ልዩነት ፡ ብዙ ፡ ጦርነት ፡ አስነሥቷል

There are various religious orders in the Catholic Church. የካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሃይማኖት ፡ ወገኖች ፡ አሉት

3. ሃይማኖት ፡ ነክ. The missionaries hand out religious tracts to passers-by. ሚስዮናውያን ፡ ላላፊ ፡ አግዳሚው ፡ ትንሽ ፡ ሃይማኖት ፡ ነክ ፡ ጽሑፎች ፡ ያድላሉ

4. ክፍ ፡ ያለ. He manifests a religious attention to work. ለሥራ ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ያደርጋል

**religious services** የጸሎት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት
Religious services will be held on Sunday for Christmas. እሑድ ፡ የልደት ፡ የጸሎት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይደረጋል

**religiously**
*He follows the doctor's orders religiously. የሐኪሙን ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ያከብራል

**relinquish**
1. ለቀቀ. Because of poor health, he relinquished his position. በጤና ፡ መታወክ ፡ ምክንያት ፡ ሥራውን ፡ ለቀቀ
He relinquished his grasp and fell. የያዘውን ፡ ለቀቀና ፡ ወደቀ
2. ተወ. The small dog relinquished his bone to the big dog. ትንሹ ፡ ውሻ ፡ አጥንቱን ፡ ለትልቁ ፡ ውሻ ፡ ተወ
3. ቈረጠ. She has relinquished all hope of going to Europe this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ አውሮፓ ፡ የመሄድ ፡ ተስፋዋን ፡ ሁሉ ፡ ቈረጠች

**relish** (v.) ወደደ
I don't relish the idea of camping in the desert. በበረኻው ፡ ውስጥ ፡ የመስፈሩን ፡ አሳብ ፡ አልወደድኩትም

**relish** (n.)
1. [ስኳርና ፡ ቅመማ ፡ ቅመም ፡ የተጨመረበት ፡ የተከተፈ ፡ ለጋ ፡ ዱባ].
2. ጣዕም. Salt adds relish to a stew. ጨው ፡ ለወጥ ፡ ጣዕም ፡ ይጨምርለታል

**give relish** ተወዳጅ ፡ አደረገ
Hunger gives relish to simple food. ረኀብ ፡ መናኛ ፡ ምግብን ፡ ተወዳጅ ፡ ያደርገዋል

**have relish for** (= act.) አስደሰተ
+The teacher has no relish for John's jokes. መምህሩ ፡ የጆን ፡ ቀልዶች ፡ አያስደስቱትም

**with great relish** ደስ ፡ ብሎት
The hungry boy ate with great relish. የተራበው ፡ ልጅ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ በላ

**relocate** እንደገና ፡ አሰፈረ
The commander relocated the army camp in a better position. አዛዡ ፡ ጦር ፡ ሰራዊቱን ፡ በተሻለ ፡ ስፍራ ፡ እንደገና ፡ አሰፈረ

**be relocated** ተዛወረ
The factory was relocated to the south of the country. ፋብሪካው ፡ ወደ ፡ ሀገሪቱ ፡ ደቡብ ፡ ክፍል ፡ ተዛወረ

**relocation** ሌላ ፡ ቦታ ፡ ማስፈር
There are no plans for the relocation of the people whose homes were destroyed by the flood. ቤታቸው ፡ በጐርፍ ፡ የፈረሰባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ለማስፈር ፡ የታቀደ ፡ ነገር ፡ የለም

**reluctance** የማይፈልግ ፡ መሆን
His reluctance to speak is known by everybody. ለመናገር ፡ የማይፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ ያውቀዋል

**with reluctance** ቅር ፡ እያለው
She took part in the game with reluctance. በጨዋታው ፡ የተካፈለችው ፡ ቅር ፡ እያላት ፡ ነው

**(be) reluctant** ፈቃደኛ ፡ አልነበረም
I was reluctant to spend more money. ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ለማውጣት ፡ ፈቃደኛ ፡ አልነበርኩም

**rely** (relied), ~ **on**
1. አመነ. You can rely on it that he will be late. እንደሚዘገይ ፡ እመን
2. ተማመነ(በት). You can't rely on him. ልትተማመንበት ፡ አትችልም
3.እምነት ፡ ጣለ(በት). He has become senile, and you can't rely on him. ስለጃጀ ፡ እምነት ፡ ልትጥልበት ፡ አትችልም
4. በ - - - ሥር ፡ ነው. Grandmother relies on our care. ሴት ፡ አያታችን ፡ በኛ ፡ ጥገኝነት ፡ ሥር ፡ ነች

**remain**
1. ቀረ. Only five students remained. አምስት ፡ ተማሪዎች ፡ ብቻ ፡ ቀሩ
2. ቆየ. We shall remain in the country until August. እስከ ፡ ነሐሴ ፡ በገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ እንቆያለን
Let things remain as they have been in the past! ሁሉም ፡ ነገር ፡ ድሮ ፡ እንደነበረው ፡ ይቆይ
3. እስከ ፡ ዘለቄታው ፡ ሆነ. He remained loyal to his friends. ለጓደኞቹ ፡ እስከ ፡ ዘለቄታው ፡ ታማኝ ፡ ሆነ
*There remains nothing else for us to do but to wait. ከመጠበቅ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የምናደርገው ፡ ነገር ፡ የለም
*That remains to be seen. ወደፊት ፡ ይታያል

**remain away** እሄደበት ፡ ቆየ
How many weeks will you remain away? እሄድክበት ፡ ስንት ፡ ሳምንት ፡ ትቆያለህ ?

**remainder**
1. የቀረ. Twenty people came in, and the remainder stayed outside. ሃያ ፡ ሰዎች ፡ ገብተው ፡ የቀሩት ፡ ውጭ ፡ ቆዩ

2. ቀረ. When 3 is subtracted from 10, the remainder is 7. ከዐሥር ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ሲነሣ ፡ ቀሪው ፡ ሰባት ፡ ነው

**remaining** የተረፈ
What did you do with the remaining books? የተረፉትን ፡ መጻሕፍት ፡ የት ፡ አደረስካቸው ?

**remains**
1. ፍራሽ. They found the remains of a large dwelling in Axum. በአክሱም ፡ ትልቅ ፡ የመኖሪያ ፡ ፍራሽ ፡ አገኙ
2. የተረፈ. Give the remains of our supper to the poor! ከራት ፡ የተረፈንን ፡ ለድኻ ፡ ስጠው
3. አስከሬን ፤ ዐጽም. His remains are buried in the church. አስከሬኑ ፡ የተቀበረው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ነው
The remains of the general still rest where they were buried. የጄኔራሉ ፡ ዐጽም ፡ ቀድሞ ፡ ከተቀበረበት ፡ ቦታ ፡ እንዳረፈ ፡ ነው

**remark** (vt.)
1. ተናገረ. He remarked that he would be absent the next day. በሚቀጥለው ፡ ቀን ፡ እንደሚቀር ፡ ተናገረ
2. አየ. Did you remark the similarity between them? በመካከላቸው ፡ ያለውን ፡ መመሳሰል ፡ አየህልኝ ?
3. ተረዳ. We remarked his worried look. መጨነቁን ፡ በፊቱ ፡ ተረዳን

**remark** (vi.) አስተያየት ፡ ሰጠ
It would be rude to remark on her appearance. ስለ ፡ መልኳ ፡ አስተያየት ፡ መስጠት ፡ ብልግና ፡ ይሆናል

**remark** (n.) አስተያየት
His remarks met with general disapproval. አስተያየቱን ፡ ሁሉም ፡ ነቀፈበት
[See also 'derogatory']

**remarkable** የሚያስደንቅ ፡ ነገር ፤ የሚደነቅ
What is so remarkable about a man landing on the moon? ሰው ፡ ጨረቃ ፡ ላይ ፡ በማረፉ ፡ ምን ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነገር ፡ አለ ?
The austere life of the first pioneers was remarkable. የቀደምቶቹ ፡ ሰፋሪዎች ፡ ምቾት ፡ ያጣ ፡ ኑሮ ፡ የሚደነቅ ፡ ነበር

**remarry** (remarried) እንደገና ፡ አገባ
His brother remarried yesterday. ወንድሙ ፡ ትናንትና ፡ እንደገና ፡ አገባ

**remedy** (remedied), v.
1. አቃና. We don't know how to remedy the defects in his pronunciation. ያነጋገሩን ፡ ጉድለት ፡ እንዴት ፡ እንደምናቃናው ፡ አናውቅም
2. አሻሻለ. The government is trying to remedy the deficiencies in the collection of taxes. በግብር ፡ አሰባሰብ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ጉድለት ፡ መንግሥት ፡ ለማሻሻል ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነው

**remedy** (remedies), n.
1. መድኃኒት. That's a good remedy for colds. ይህ ፡ ለጉንፋን ፡ ጥሩ ፡ መድኃኒት ፡ ነው
2. መፍትሔ. The government needs to find a remedy for the teacher shortage. የመምህራንን ፡ እጥረት ፡ ችግር ፡ ለማስወገድ ፡ መንግሥት ፡ መፍትሔ ፡ ማግኘት ፡ ይኖርበታል
3. የሚያዋጣህ. Your only remedy is to go to court. የሚያዋጣህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ ብቻ ፡ ነው

**remember** (vt.)
1. አስታወሰ. He remembered with pleasure his days as a student in Paris. በፓሪስ ፡ ያሳለፈውን ፡ የተማሪነቱን ፡ ጊዜ ፡ በደስታ ፡ አስታወሰ
2. አልረሳም ፤ አልዘነጋም. Remember to turn out the light! መብራቱን ፡ ማጥፋት ፡ አትርሳ
Remember to look both ways before crossing! መንገድ ፡ ከማቋረጥህ ፡ በፊት ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ መመልከትን ፡ አትዘንጋ
3. አንድ ፡ ነገር ፡ ላከ(ለት). He always remembers me at Christmas. ለገና ፡ ሁልጊዜ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ይልክልኛል

**remember** (vi.) የማስታወስ ፡ ችሎታ ፡ አለው
Dogs remember. ውሾች ፡ የማስታወስ ፡ ችሎታ ፡ አላቸው

**remember someone to** ሰላምታውን ፡ አቀረበለት
Remember me to your mother! ለናትህ ፡ ሰላምታዬን ፡ አቅርብልኝ

**remembrance**
1. ማስታወሻ. He gave her a ring in remembrance of his affection for her. ለፍቅራቸው ፡ ማስታወሻ ፡ እንዲሆን ፡ ቀለበት ፡ ሰጣት
2. መታሰቢያ. They held a service in remembrance of those killed in the war. በጦርነቱ ፡ ለሞቱት ፡ ሁሉ ፡ የመታሰቢያ ፡ ጸሎት ፡ አደረጉላቸው
3. ትዝታ. The remembrances of the old days were written down in a book. የጥንቱ ፡ ትዝታ ፡ ሁሉ ፡ በመጽሐፍ ፡ ሰፍሮ ፡ ይገኛል

**remind**
1. አስታወሰ. Please remind me to return the book tomorrow! መጽሐፉን ፡ ነገ ፡ እንድመልስ ፡ አስታውሰኝ

2. (ሲያየው) ፡ ትዝ ፡ አለው. +He reminded me of his brother. ሳየው ፡ ወንድሙ ፡ ትዝ ፡ አለኝ

**reminder** ማስታወሻ
Send him a reminder about the letter! ስለ ፡ ደብዳቤው ፡ ማስታወሻ ፡ ላክበት

**reminisce** በማስታወስ ፡ ተናገረ
The old warrior reminisced about his campaigns with Menelik. ሽማግሌው ፡ ጦረኛ ፡ ከዳ ፡ ምኒልክ ፡ ጋር ፡ ስላደረጉት ፡ ዘመቻ ፡ በማስታወስ ፡ ተናገሩ

**reminiscence** ትዝታ
His reminiscences of the war are being written down. የጦርነቱን ፡ ትዝታ ፡ በመጻፍ ፡ ላይ ፡ ነው

**(be) remiss** ግዴለሽ ፡ ሆነ
You have been remiss in your duties. በሥራህ ፡ ግዴለሽ ፡ ሆነሃል

**remission** ምሕረት
Remission of taxes will be granted all those who lost property in the flood. በጐርፉ ፡ ንብረታቸውን ፡ ላጡ ፡ ሁሉ ፡ የግብር ፡ ምሕረት ፡ ይደረግላቸዋል

**be granted remission**
1. ተማረ. Remission of debts was granted those who had lost everything in the fire. በእሳቱ ፡ አደጋ ፡ ንብረታቸውን ፡ ያጡት ፡ ሁሉ ፡ ከዕዳቸው ፡ ተማሩ
2. (= act.) ይቅር ፡ አለ. Remission of sins may be granted by God. ኀጢአትን ፡ ይቅር ፡ የሚል ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው

**remit** (remitted), vt.
1. ላከ. He remits half his pay to his family back home. ግማሽ ፡ ደሞዙን ፡ ለቤተሰቡ ፡ ይልካል
2. ከፈለ. Please remit the money you owe! ያለብህን ፡ ገንዘብ ፡ ክፈል
3. ከ --- ነጻ ፡ አደረገ. Christ gave His disciples power to remit sins. ክርስቶስ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙሩ ፡ ኃጢአተኞችን ፡ ከኃጢአት ፡ ነጻ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጠ
4. ቈጠበ. He kept working without remitting his efforts. ጥረቱን ፡ ሳይቈጥብ ፡ መሥራቱን ፡ ቀጠለ

**remit** (vi.) ተቀነሰ
Her fever remitted. ትኩሳቷ ፡ ተቀንሷል

**remit the punishment** ምሕረት ፡ አደረገ(ለት)
The governor is remitting the prisoners' punishment. ገዢው ፡ ለእስረኞቹ ፡ ምሕረት ፡ እያደረጉ ፡ ናቸው

**be remitted**
1. ተላለፈ. The matter was remitted to a higher court. ጉዳዩ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተላለፈ
2. የ --- ምሕረት ፡ ተደረገ. Taxes have been remitted. የግብር ፡ ምሕረት ፡ ተደርጓል

**remittance** የተላከ ፡ ገንዘብ
I received a remittance from my parents in the mail. ከወላጆቼ ፡ የተላከ ፡ ገንዘብ ፡ በፖስታ ፡ ደረሰኝ

**remnant**
1. ትራፊ. The remnants of the banquet were given to the poor. የድግሱ ፡ ትራፊ ፡ ለድኾች ፡ ተሰጠ
2. የቀረ. The remnants of the British Empire are scattered around the globe. ከእንግሊዝ ፡ ግዛት ፡ የቀሩት ፡ በዓለም ፡ በያለበት ፡ ይገኛሉ
3. ጥቂቶች. This town has only a remnant of its former population. ይህች ፡ ከተማ ፡ ቀድሞ ፡ ከሚኖሩባት ፡ ሰዎች ፡ ጥቂቶች ፡ ብቻ ፡ ይገኙባታል
4. ቅርስ. These ruins are remnants of former greatness. እነዚህ ፡ ፍርስራሾች ፡ የጥንት ፡ ጊዜ ፡ ታላቅነት ፡ ቅርሶች ፡ ናቸው

**remodel**
1. ቅድ ፡ ለወጠ. The tailor remodeled the suit. ልብስ ፡ ሰፊው ፡ የልብሱን ፡ ቅድ ፡ ለወጠ
2. አፍርሶ ፡ ባዲስ ፡ ቅርስ ፡ ሠራ. They remodeled the house from top to bottom. ቤቱን ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ አፍርሰው ፡ ባዲስ ፡ ቅርስ ፡ ሠሩት

**remonstrate** በመቃወም ፡ ተከራከረ ፤ ነገሩ ፡ እንዲገባው ፡ ተከራከረ
I tried to remonstrate with her, but she wouldn't listen to reason. በመቃወም ፡ ልከራከራት ፡ (ነገሩ ፡ እንዲገባት ፡ ልከራከራት) ፡ ሞከርኩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ሐሳብ ፡ አትቀበልም

**remorse** ጸጸት
I felt remorse at having run over the dog. ውሻውን ፡ ስለዳጥኩት ፡ ጸጸት ፡ ተሰማኝ

**remote**
1. ሩቅ. The village is so remote that they never heard about the President. መንደሩ ፡ በጣም ፡ ሩቅ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ስለ ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ምንም ፡ አልሰሙም
2. የሩቅ. You can't expect help from a remote relative. የሩቅ ፡ ዘመድ ፡ እርዳታ ፡ ያደርግልኛል ፡ ብለህ ፡ መጠበቅ ፡ አይቻልም

**be remote** በጣም ፡ ራቀ
This question is remote from the subject. ይህ ፡ ጥያቄ ፡ ከጉዳዩ ፡ በጣም ፡ የራቀ ፡ ነው

**remote district** (የ)ዳር ፡ አገር
He has been sent to a remote district as punishment. በቅጣት ፡ ወደ ፡ ዳር ፡ አገር ፡ ተላከ

**in the remote past** ጥንት
The Habashat entered Ethiopia in the remote past. አበሻ ፡ የሚባለው ፡ ነገድ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገባው ፡ ጥንት ፡ ነው

**remotely, be ~ related** የሩቅ፤ ዘመዶች ፡ ናቸው
Smith and I are remotely related. እኔና ፡ ስሚዝ ፡ የሩቅ ፡ ዘመዶች ፡ ነን

**remotest** (=adv.) ፈጽሞ
I haven't the remotest idea what he means. ምን ፡ ማለቱ ፡ እንደሆነ ፡ ፈጽሞ ፡ አልገባኝም

**removal**
1. ማንሣት. Rubbish removal is necessary for sanitation. ቆሻሻን ፡ ማንሣት ፡ ለንጽሕና ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
2. መነሣት. His removal from the office was announced over the radio. የርሱ ፡ ከሥራ ፡ መነሣት ፡ በሬዲዮ ፡ ተነገረ
3. መዛወር. The store announced its removal to other quarters. መደብሩ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ መዛወሩን ፡ አስታወቀ

**remove**
1. አስለቀቀ. Will this remove ink stains from cloth? ይህ ፡ ነገር ፡ የቀለም ፡ ጠብታን ፡ ከልብስ ፡ ላይ ፡ ያስለቅቃል ?
2. አወጣ. The doctors removed a bullet from his lung. ሐኪሞቹ ፡ ከሳምባው ፡ ውስጥ ፡ ጥይት ፡ አወጡለት
3. አስወጣ. The father removed his child from school because of ill health. ልጁ ፡ ጤንነቱ ፡ ስለታወከ ፡ አባቱ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ አስወጣው
They removed him from office for taking bribes. ጉቦ ፡ በመቀበሉ ፡ ከሥራ ፡ አስወጡት
4. ነቀለ. The dentist removed the boy's tooth. የጥርስ ፡ ሐኪሙ ፡ የልጁን ፡ ጥርስ ፡ ነቀለለት
Some intrigue is afoot to remove him from the post. እሱን ፡ ከሥራው ፡ ለመንቀል ፡ አንድ ፡ ሴራ ፡ በመደረግ ፡ ላይ ፡ ነው
5. አወለቀ. Please remove your hat! ባርኔጣህን ፡ አውልቅ
6. ቈረጠና ፡ ጣለ. Remove the fins of the fish before you cook it! ዓሣን ፡ ከመጥበስህ ፡ በፊት ፡ ክንፎቹን ፡ ቈርጠህ ፡ ጣል
7. ቀነሰ. You can concentrate orange juice by removing water. ውኃውን ፡ በመቀነስ ፡ የብርቱካኑን ፡ ጭማቂ ፡ ልታወፍረው ፡ ትችላለህ
8. አስወገደ. This should remove all doubt. ይህ ፡ ማንኛውንም ፡ ጥርጣሬ ፡ ማስወገድ ፡ አለበት
9. አነሣ. Remove everything from the desks! ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ አንሣ

**be removed**
1. ተለየ. This dialect is equally removed from German and English. ይህ ፡ የቋንቋ ፡ ስልት ፡ ከጀርመንኛ ፡ የሚለየውን ፡ ያህል ፡ ከእንግሊዝኛም ፡ ይለያል
2. ተሻረ. The priest's anathema was removed when the governor promised to obey. አገረ ፡ ገዢው ፡ ለመታዘዝ ፡ ቃል ፡ ስለገባ ፡ የቄሱ ፡ ውግዘት ፡ ተሻረ

**be far removed** በጣም ፡ ራቀ
Their house was far removed from the village. ቤታቸው ፡ ከመንደሩ ፡ በጣም ፡ የራቀ ፡ ነበር
[See also 'hull']

**remunerate** ዋጋ ፡ ከፈለ
They remunerated him for his trouble. ለድካሙ ፡ ዋጋውን ፡ ከፈሉት

**remuneration** ዋጋ
He received thirty dollars in remuneration for his services. ላገልግሎቱ ፡ ዋጋ ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ ተከፈለው

**remunerative** ትርፍ ፡ የሚያስገኝ
This is a remunerative job. ይህ ፡ ትርፍ ፡ የሚያስገኝ ፡ ሥራ ፡ ነው

**renaissance**
*There is a renaissance of interest in old-time dramas. የድሮ ፡ ጊዜ ፡ ቲያትር ፡ በማንሰራራት ፡ ላይ ፡ ነው

**(be) renamed**
*Bishoftu was renamed Debre Zeit. የቢሾፍቱ ፡ ስም ፡ ተለውጦ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ተባለ

**renascence** ማንሰራራት
The renascence in literature, that took place after the war, is well described in this book. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ የተደረገው ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ማንሰራራት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በሚገባ ፡ ተገልጿል

**renascent**
*There is a renascent interest in Shakespeare. የሼክስፒር ፡ ጽሑፎች ፡ በይበልጥ ፡ እየተወደዱ ፡ ሄዱ

**rend** (rent, or rended)
1. ቀደደ. The boy rent the curtain. ልጁ ፡ መጋረጃውን ፡ ቀደደ

2. ከፋፈለ. The racial problem is rending the nation. የዘር ፡ ልዩነት ፡ ጉዳይ ፡ አገሪቱን ፡ በመ ከፋፈል ፡ ላይ ፡ ነው

**rend to pieces**
1. ቦጫጨቀ. The dogs rent the poor rabbit to pieces. ውሾቹ ፡ ምስኪኗን ፡ ጥንቸል ፡ ቦጫጨቋት
2. ሰባበረ. The storm rent the ship to pieces. ማዕበሉ ፡ መርከቧን ፡ ሰባበራት

**render**
1. በሥዕል ፡ ገለጸ. The painter knows how to render life in Ethiopia. ሠዓሊው ፡ የኢትዮጵያን ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ በሥዕል ፡ መግለጽ ፡ ያውቃል
2. መለሰ. A good man must render good for evil. ጥሩ ፡ ሰው ፡ ክፉን ፡ በደግ ፡ መመለስ ፡ አለ በት
3. አቀረበ. The treasurer rendered an account of all the money spent. ገንዘብ ፡ ያዢው ፡ ስ ላወጣው ፡ ገንዘብ ፡ የሒሳብ ፡ መግለጫ ፡ አቀረበ
4. ተረጐመ. We rendered the French poem into Amharic. የፈረንሳይኛን ፡ ግጥም ፡ ወደ ፡ አማር ኛ ፡ ተረጐምነው
5. ሠራ. The actor rendered the part of Hamlet well. ተዋናዩ ፡ ሀምሌትን ፡ ሆኖ ፡ በሚገ ባ ፡ ሠራ
6. አደረገ. An accident has rendered him helpless. የደረሰበት ፡ አደጋ ፡ አቅጉል ፡ አደረገው
[See also 'help, service']

**rendezvous** መገናኛ
Their rendezvous was discovered by the police. መገናኛቸው ፡ በፖሊሱ ፡ ተደረሰበት

**have a rendezvous** ተገናኘ
Let's have a rendezvous at the municipality! ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ እንገናኝ

**renegade** ከዳተኛ
The renegade was captured and shot. ከዳተኛ ው ፡ ተይዞ ፡ በጥይት ፡ ተደበደበ

**renege** አፈረሰ
He reneged on his promise to help me. እረዳሃለ ሁ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አፈረሰ

**renew**
1. አሳደሰ. I have to renew my lease. ውሉን ፡ ማሳደስ ፡ አለብኝ
2. አደሰ. The Embassy renewed my passport. ኤምባሲው ፡ የይለፍ ፡ ወረቀቴን ፡ አደሰልኝ
3. እንደገና ፡ ጀመረ. The enemy renewed his attack on our fortress. ጠላት ፡ በምሽጋችን ፡ ላ ይ ፡ ተኵሱን ፡ እንደገና ፡ ጀመረ
4. ቀጠለ. They renewed their friendship. የቀድሞ ፡ ጓደኝነታቸውን ፡ ቀጠሉ

**(be) renewable** መታደስ ፡ ቻለ
This license is not renewable. ይህ ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀት ፡ መታደስ ፡ አይችልም

**renounce**
1. ካደ. The father renounced his wicked son. አባቱ ፡ እርጉሙን ፡ ልጁን ፡ ካደው
He renounced his faith. ሃይማኖቱን ፡ ካደ
2. በፈቃዱ ፡ ተወ. The Duke of Windsor renounced his right to the throne. የዊንድሶር ፡ መስፍ ን ፡ ለዙፋኑ ፡ የነበራቸውን ፡ መብት ፡ በፈቃዳቸ ው ፡ ተዉ
*He renounced the world. ዓለም ፡ በቃኝ ፡ አለ

**renovate** አሳደሰ
We must renovate the building; it is beginning to fall apart. ሕንጻውን ፡ ማሳደስ ፡ አለብን ፤ መ ፈራረስ ፡ ጀምሯል

**renown** ዝና
His renown as a warrior spread through the land. ያርበኝነቱ ፡ ዝና ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ተሰራጨ

**renowned** የታወቀ
He is renowned as a Hebrew scholar. የታወ ቀ ፡ የዕብራይስጥ ፡ ሊቅ ፡ ነው

**rent,** see **rend**

**rent** (vt.)
1. አከራየ. She rents three rooms, and thus supplements her income. ሦስት ፡ ክፍል ፡ እያ ከራየች ፡ ገቢዋን ፡ ታሟላለች
2. ተከራየ. I rented a room for three months. አንድ ፡ ክፍል ፡ ለሦስት ፡ ወር ፡ ተከራየሁ

**rent** (vi.) ተከራየ
This house rents for $200 a month. ይህ ፡ ቤት ፡ በወር ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ይከራያል

**be rented** ተከራየ
All rooms are rented. ሁሉም ፡ ክፍል ፡ ተከራ ይቷል

**rent** (n.)
1. ኪራይ ፤ የቤት ፡ ኪራይ. How much rent do you pay for your apartment? ለአፓርተማህ ፡ ም ን ፡ ያህል ፡ ኪራይ ፡ ትከፍላለህ ?
Rents have shot up in the last few months. ባለፉት ፡ ጥቂት ፡ ወራት ፡ ውስጥ ፡ የቤት ፡ ኪራ ይ ፡ ሰማይ ፡ ደርሷል
2. ቀዳዳ. The gas escaped through a rent in the balloon. ፊኛው ፡ ቀዳዳ ፡ ስለነበረበት ፡ ተነፈሰ

**be for rent** ተከራየ
That vacant house is for rent. ባዶው ፡ ቤት ፡ ይ ከራያል

**rental** የቤት ፡ ኪራይ
She gets her income from rentals. ገቢዋ ፡ ከቤት ፡ ኪራይ ፡ ነው

**rentor** ተከራይ
The rentor of the property has no liability for the owner's debt. የንብረቱ ፡ ተከራይ ፡ ለባለ ፡ ንብረቱ ፡ ዕዳ ፡ ኀላፊነት ፡ የለበትም

**reopen** እንደገና ፡ ከፈተ
We will reopen the shop after the holiday. ሱቁን ፡ ከዓመት ፡ በዓሉ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ እንከፍታለን

**reorganize** እንደገና ፡ አደራጀ
The director reorganized the work in the office. ሥራ ፡ መሪው ፡ የቢሮውን ፡ አካሄድ ፡ እንደገና ፡ አደራጀ

**repair** (vt.)
1. ጠገነ. They will repair the road tomorrow. መንገዱን ፡ ነገ ፡ ይጠግናሉ
He repaired my typewriter. የጽሕፈት ፡ መኪናዬን ፡ ጠገነልኝ
2. ካሰ. How can I repair the harm done? ላጠፋሁት ፡ ጥፋት ፡ ምን ፡ ልካስ ?
3. አሟላ. The father repaired the wrong done by his son. አባትዬው ፡ ልጁ ፡ ያጠፋውን ፡ አሟላ

**repair** (vi.) ሄደ
After class, they repaired to the library. ከክፍል ፡ ሲወጡ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ሄዱ

**repair** (n.)
1. ጥገና. The car needs only minor repairs. መኪናው ፡ የሚያስፈልገው ፡ ጥገና ፡ ትንሽ ፡ ነው
2. መታደስ. The shop will be closed for repair. ሱቁ ፡ ለመታደስ ፡ ይዘጋል
3. የሚገናኙበት ፡ ቦታ. This café is a favorite repair for students. ይህ ፡ ቡና ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ የሚወዱት ፡ የሚገናኙበት ፡ ቦታ ፡ ነው

**be in bad repair** ተበላሸ
My car is in bad repair. መኪናዬ ፡ ተበላሽቷል

**be in good repair** በደንብ ፡ ታደሰ
The typewriter is in good repair. የጽሕፈት ፡ መኪናው ፡ በደንብ ፡ ታድሷል

**keep in repair** ጠገነ ፤ አደሰ
The handyman keeps the machines in repair. ባለሙያው ፡ መኪናዎችን ፡ ይጠግናል
The lessee must keep the house in repair. ተከራዩ ፡ ቤቱን ፡ ራሱ ፡ ማደስ ፡ አለበት

**make repairs** አደሰ
He made repairs recently on his house. በቅርቡ ፡ ቤቱን ፡ አደሰ

**reparation**
*They sent a check in reparation for the damage they caused. ላደረሱት ፡ጉዳት ፡ ክፍያ ፡ የሚሆን ፡ ቼክ ፡ ላኩ

**reparations** የጦር ፡ ካሳ
Italy paid Ethiopia reparations. ጣሊያን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ካሳ ፡ ከፈለች

**repast**
1. ምግብ. The guest partook of a pleasant repast in the palace. እንግዳው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ አስደሳች ፡ ምግብ ፡ ተመገበ
2. ግብር. The Emperor provided a sumptuous repast. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ታላቅ ፡ ግብር ፡ አገቡ

**repatriate** ወደመጣበት ፡ እንዲመለስ ፡ አደረገ
The government wants to repatriate all the refugees. መንግሥቱ ፡ ስደተኞቹን ፡ ሁሉ ፡ ወደመጡበት ፡ እንዲመለሱ ፡ ለማድረግ ፡ ይፈልጋል

**repay** (repaid)
1. ከፈለ. If you lend me five dollars, I will repay you next week. አምስት ፡ ብር ፡ ብታበድረኝ ፡ በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ እከፍልሃለሁ
2. መለሰ. I must repay him a favor. ውለታውን ፡ መመለስ ፡ አለብኝ
*The boy's success repaid the teacher for his efforts. ልጁ ፡ ስለተሳካለት ፡ የመምህሩ ፡ ድካም ፡ ዋጋ ፡ አገኘ

**repay for** መጠነ
This niggardly gift of a pair of socks does not repay me for the work I have done. የእግር ፡ ሹራቡ ፡ አነስተኛ ፡ ስጦታ ፡ ስለሆነ ፡ የሠራሁትን ፡ ሥራ ፡ አይመጥንም

**repeal** ሻረ
Parliament repealed the laws on the sale of cigarettes. ፓርላማ ፡ የሲጋራ ፡ ሽያጭ ፡ ሕጎችን ፡ ሻረ

**repeat**
1. ደገመ. Repeat what I just said! አሁን ፡ ያልኩትን ፡ ድገመው
2. አለ. Repeat these words after me! እነዚህን ፡ ቃላት ፡ ከኔ ፡ በኋላ ፡ በል
3. መልሶ ፡ ተናገረ. The parrot repeats what anybody says. በቀቀን ፡ ሰው ፡ የሚናገረውን ፡ መልሳ ፡ ትናገራለች
4. በድጋሚ ፡ ገለጸ. I repeat that I cannot come out now. አሁን ፡ ለመውጣት ፡ አለመቻሌን ፡ በድጋሚ ፡ እገልጻለሁ
5. አወራ. They like to repeat everything they hear. የሰሙትን ፡ ሁሉ ፡ ማውራት ፡ ይወዳሉ

6. አወጣ. He promised not to repeat the secret. ምስጢር ፡ እንዳያወጣ ፡ ቃል ፡ ገባ

**repeat oneself** ነገር ፡ ደጋገመ
Don't repeat yourself! ነገር ፡ አትደጋግም

**repeated** (adj.) ደግሞ ፡ ደጋግሞ ፡ ያደረገ
His repeated efforts at last won success. ደግሞ ፡ ደጋግሞ ፡ ያደረገው ፡ ጥረት ፡ በመጨረሻው ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ አተረፈለት

**be repeated** ተደጋገመ
In this verb, the last two radicals are repeated. በዚህ ፡ ግስ ፡ ውስጥ ፡ የመጨረሻዎቹ ፡ ሁለት ፡ ፊደሎች ፡ ተደጋግመዋል

**repeatedly** ደጋግሞ
He struck her repeatedly. ደጋግሞ ፡ መታት

**repel** (repelled)
1. መለሰ. We repelled the enemy troops. የጠላትን ፡ ጦር ፡ መለስነው
2. አስከፋ. Her bad breath repelled him. መጥፎ ፡ ትንፋሿ ፡ አስከፋው
3. እንዲሸሽ ፡ አደረገ. Her vanity repels all those who know her. እብሪቷ ፡ የሚያውቃትን ፡ ሁሉ ፡ ከሷ ፡ እንዲሸሽ ፡ ያደርገዋል
4. አላስገባም. This raincoat repels water. ይህ ፡ የዝናብ ፡ ልብስ ፡ ውኃ ፡ አያስገባም
5. አልቀበልም ፡ አለ. He repelled the offer of a bribe. ጉቦ ፡ ቢሰጠው ፡ አልቀበልም ፡ አለ

**repel each other** አልተቀላቀሉም
Water and oil repel each other. ውኃና ፡ ዘይት ፡ አይቀላቀሉም

**repellent** (n.) መከላከያ
Give me some mosquito repellent! የወባ ፡ ትንኝ ፡ መከላከያ ፡ ስጠኝ

**repellent** (adj.) መጥፎ
A repellent smell drove us from the room. አንድ ፡ መጥፎ ፡ ሽታ ፡ ከክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ አባረረን

**be water repellent** ውኃ ፡ አይዘልቀውም
This fabric is water repellent. ይህ ፡ ጨርቅ ፡ ውኃ ፡ አይዘልቀውም

**repent**
1. ተጸጸተ. She repented her rudeness. በብልግናዋ ፡ ተጸጸተች
2. ቈጨ(ው). +Don't you repent having wasted your money? ገንዘብህን ፡ ማባከንህ ፡ አይቈጭህም ?
*I repented of my sins. ንስሓ ፡ ገባሁ

**repentance** ጸጸት
He showed no repentance for the crime. ለሠራው ፡ ወንጀል ፡ ምንም ፡ ጸጸት ፡ አልተሰማውም

**(be) repentant** ተጸጸተ
She was repentant for her rudeness. በብልግናዋ ፡ ተጸጸተች

**repercussion** ማስተጋባት
The repercussion of gunfire could be heard for miles. የጠመንጃው ፡ ማስተጋባት ፡ ብዙ ፡ ማይል ፡ ርቆ ፡ ሊሰማ ፡ ይችላል

**have repercussions**
1. መዘዝ ፡ አስከተለ. The discovery of a foreign agent had serious repercussions in the government. የውጭ ፡ አገር ፡ ሰላይ ፡ መገኘት ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ መዘዝ ፡ አስከተለ
2. ለውጥ ፡ አስከተለ. Kennedy's assassination had repercussions in the United States. የኬኔዲ ፡ መገደል ፡ በአሜሪካን ፡ ውስጥ ፡ በፖለቲካ ፡ ረገድ ፡ ለውጥ ፡ አስከተለ

**repertoire** የሚያውቀው
She sang all the songs in her repertoire. የምታውቀውን ፡ ዘፈን ፡ ሁሉ ፡ ዘፈነች

**repertory** (repertories)
*He has many folk songs in his repertory. ብዙ ፡ የሀገር ፡ ባህል ፡ ዘፈኖች ፡ ያውቃል

**repetition**
1. መላልሶ ፡ ማጥናት. One learns a language by repetition. አንድ ፡ ሰው ፡ ቋንቋ ፡ የሚማረው ፡ መላልሶ ፡ በማጥናት ፡ ነው
2. ድጋሚ. This lesson is a repetition of one we did earlier. ይህ ፡ ትምህርት ፡ በፊት ፡ የተማርነው ፡ ድጋሚ ፡ ነው
*A repetition of the offense will be punished. ጥፋቱ ፡ ሲደጋገም ፡ ያስቀጣል

**repetitious** (= adv.) ደጋግሞ
The repetitious account of their trip bores me. ደጋግሞ ፡ ስለ ፡ ጉዟቸው ፡ የሚያወሩት ፡ ያሰለቸኛል

**replace**
1. መልሶ ፡ አስቀመጠ. He replaced the dictionary on the shelf. መዝገበ ፡ ቃላቱን ፡ መጽሐፍ ፡ መደርደሪያው ፡ ላይ ፡ መልሶ ፡ አስቀመጠው
2. በሱ ፡ ቦታ ፡ ተተካ. We haven't been able to get anyone to replace her. በሷ ፡ ቦታ ፡ የሚተካ ፡ ሰው ፡ ለማግኘት ፡ አልቻልንም

**be replaced** ተገኘ
These glasses can't be replaced. እነዚህ ፡ ብርጭቆዎች ፡ አይገኙም

**replacement** ምትክ
His replacement is a young college man. የሱ ፡ ምትክ ፡ ከኮሌጅ ፡ የተመረቀ ፡ ወጣት ፡ ነው

**replenish** እንደገና ፡ ሞላ
We replenished our supplies at a small country store. ያለቀውን ፡ ሥንቃችንን ፡ ባንድ ፡ ትንሽ ፡ የገጠር ፡ ሱቅ ፡ እንደገና ፡ ሞላን

**(be) replete**
*The book was replete with errors. መጽሐፉ ፡ ስሕተት ፡ ብቻ ፡ ነበር

**replica** ቅጂ
This is a replica of Theodore's crown; the real one is still in Axum. ይህ ፡ የአፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘውድ ፡ ቅጂ ፡ ነው ፤ ደንበኛው ፡ ያለው ፡ አክሱም ፡ ነው

**reply** (replied). v.
1. መለሰ. He didn't reply to my question. ጥያቄዬን ፡ አልመለሰልኝም
2. መልስ ፡ ገለጸ. He replied that they would be glad to come. ለመምጣት ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚላቸው ፡ መሆናቸውን ፡ በሰጠው ፡ መልስ ፡ ገለጸ
3. መልሶ ፡ ተኰሰ(በት). The enemy replied quickly to our fire. ጠላት ፡ ላደረግንበት ፡ ተኩስ ፡ ያኔውኑ ፡ መልሶ ፡ ተኰሰብን

**reply** (replies), n. መልስ
I never received a reply to my letter. ለደብዳቤዬ ፡ መልስ ፡ ደርሶኝም ፡ አያውቅ

**report** (vt.)
1. አተተ. The newspaper reported news about the depraved criminal. ጋዜጣው ፡ ስለ ፡ ነውረኛው ፡ ወንጀለኛ ፡ አተተ
2. ገለጸ(ተገለጸ). Our treasurer reports that all dues are paid up. ገንዘብ ፡ ቤታችን ፡ መዋጮው ፡ ሁሉ ፡ መከፈሉን ፡ ይገልጻል
The names of the deceased have not yet been reported. የሟቾቹ ፡ ስም ፡ እስካሁን ፡ አልተገለጸም
3. መግለጫ ፡ ሰጠ. We will report on our trip today. ስለ ፡ ጉዞችን ፡ ዛሬ ፡ መግለጫ ፡ እንሰጣለን.
4. አስረዳ. The student misquoted the teacher in reporting the accident. ተማሪው ፡ አደጋውን ፡ በሚያስረዳበት ፡ ጊዜ ፡ መምህሩ ፡ ያላለውን ፡ አለ
5. አስታወቀ. Our planes reported that the enemy forces were on the move. አውሮፕላኖቻችን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ በመንቀሳቀስ ፡ ላይ ፡ መሆኑን ፡ አስታወቁ
6. ነገረ(በት) ፤ አሳበቀ. Somebody must have reported him to the police. አንዱ ፡ ለፖሊስ ፡ ነግሮበት ፡ ይሆናል
He forfeited the good will of his fellow students by reporting their activities. የትምህርት ፡ ጓደኞቹ ፡ የሚሠሩትን ፡ በማሳበቅ ፡ ፍቅራቸውን ፡ አጣ
7. አመለከተ. The overseer reported the theft to me. ተቈጣጣሪው ፡ የተደረገውን ፡ ስርቆት ፡ ለኔ ፡ አመለከተ

**report** (vi.) አነጋገረ
When I arrive at the university, to whom do I report? ከዩኒቨርሲቲው ፡ ስደርስ ፡ የማነጋግረው ፡ ማንን ፡ ነው ?

**report for duty** ሥራ ፡ ገባ ፤ ለሥራ ፡ መጣ
He reported for duty just yesterday. ገና ፡ ትላንት ፡ ሥራ ፡ ገባ ፡ (ለሥራ ፡ መጣ)

**report** (n.)
1. መግለጫ. Newspaper reports indicate fighting is still going on. የጋዜጣ ፡ መግለጫዎች ፡ ጦርነቱ ፡ አሁንም ፡ እንደቀጠለ ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታሉ
2. ወሬ. Don't listen to false reports! የውሸት ፡ ወሬ ፡ አትስማ
3. ሪፖርር. When will you make your report? ሪፖርቱን ፡ መቼ ፡ ታቀርባለህ ?

**report card** የተማሪ ፡ ማመልከቻ
She always brought home good report cards. ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ሁልጊዜ ፡ ጥሩ ፡ የተማሪ ፡ ማመልከቻ ፡ ታመጣለች

**reporter** ጋዜጠኛ ፤ ዜና ፡ አቀባይ ፤ ዜና ፡ አጠናቃሪ
The reporter was jailed for revealing state secrets. ጋዜጠኛው ፡ (ዜና ፡ አቀባዩ ፤ ዜና ፡ አጠናቃሪው) ፡ የመንግሥት ፡ ምስጢር ፡ ስላወጣ ፡ ታሰረ

**repose** (vt.) ጣለ(በት)
He reposed great trust in his son. በልጁ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ እምነት ፡ ጣለበት

**repose** (vi.)
1. ጋደም ፡ አለ. She reposed on a soft mattress. በለስላሳ ፡ ፍራሽ ፡ ላይ ፡ ጋደም ፡ አለች
2. ተተከለ. The statue reposes on a pedestal. ሐውልቱ ፡ መቆሚያ ፡ ላይ ፡ ተተክሏል

**repose** (n.)
1. ዕረፍት. Don't disturb the minister's repose! ሚኒስትሩን ፡ ዕረፍት ፡ አትንሣ
2. ሰላምና ፡ ጸጥታ. The repose of the countryside is beneficial for health. የገጠር ፡ ሰላምና ፡ ጸጥታ ፡ ለጤንነት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው
*Her manner was one of repose. ሁኔታዋ ፡ የረጋ ፡ ነበር

**repository** ማስቀመጫ
The box was the repository for old magazines. ሣጥኑ ፡ የቆዩ ፡ መጽሔቶች ፡ ማስቀመጫ ፡ ነበር

**reprehend** ወቀሰ
I must reprehend your hastiness. በችኩልነትህ ፡ ልወቅስህ ፡ ይገባል

**reprehensible** አስከፊ
The enemy's treatment of war prisoners was reprehensible. ጠላት ፡ ለጦር ፡ ምርኮኞች ፡ ያደረገው ፡ አያያዝ ፡ አስከፊ ፡ ነበር

**represent**
1. ገለጸ. This painting represents the story of Solomon and the Queen of Sheba. ይህ ፡ ሥዕል ፡ የሰሎሞንና ፡ የሳባን ፡ ንግሥት ፡ ታሪክ ፡ ይገልጻል
2. አሳየ. The statue represents Lincoln as a young man. ሐውልቱ ፡ ሊንኮልንን ፡ በወጣትነቱ ፡ ጊዜ ፡ ያሳያል
3. አመለከተ. Each mark on the map represents ten thousand people. በካርታው ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ እያንዳንዱ ፡ ነጥብ ፡ ዐሥር ፡ ሺ ፡ ሰው ፡ ያመለክታል
The letters of the alphabet represent sounds. የፊደል ፡ ሆሄያት ፡ ድምፅን ፡ የሚያመለክቱ ፡ ናቸው
4. ወከለ. He delegated his son to represent him at the conference. በስብሰባው ፡ ላይ ፡ እንዲወክለው ፡ ልጁን ፡ ላከ
5. ጠበቃ ፡ ነው. Who is representing the defendant? የተከሳሹ ፡ ጠበቃ ፡ ማነው ?
6. ተመስሎ ፡ ሠራ. Each child will represent an animal at the party. በግብዣው ፡ ላይ ፡ እያንዳንዱ ፡ ልጅ ፡ በእንስሳ ፡ ተመስሎ ፡ ይሠራል
7. ምሳሌ ፡ ነው. He represents the youth of America. እሱ ፡ የአሜሪካ ፡ ወጣቶች ፡ ምሳሌ ፡ ነው

**represent oneself as**
*He represents himself as an authority on Ethiopian education. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ትምህርት ፡ ዐዋቂ ፡ ነኝ ፡ ባይ ፡ ነው

**be represented** እንደራሴ ፡ አለው
People in all stations of life are represented in the parliament. ትንሽ ፡ ትልቁ ፡ በፓርላማ ፡ ውስጥ ፡ እንደራሴ ፡ አለው

**representation** መግለጫ
His representation of her part in the accident was untrue. እሷ ፡ ባደጋው ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆኗ ፡ የሰጠው ፡ መግለጫ ፡ እውነት ፡ አልነበረም
*The students demanded representation on the committee. ተማሪዎቹ ፡ በደርጉ ፡ ውስጥ ፡ እንዲወከሉ ፡ ጠየቁ

**be a representation of** አመለከተ
The statue is a representation of a sleeping lion. ሐውልቱ ፡ የተኛ ፡ አንበሳን ፡ የሚያመለክት ፡ ነው

**representative** (n.)
1. መልእክተኛ. Who is the Ethiopian permanent representative to the United Nations? በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቋሚ ፡ መልእክተኛ ፡ ማነው ?
2. ወኪል. He is the European representative of a big company. በአውሮፓ ፡ ያንድ ፡ ትልቅ ፡ ኩባንያ ፡ ወኪል ፡ ነው

**representative** (adj.)
1. ጥሩ ፤ ዓይነተኛ. That was a representative example of his wit. የቀልደኛነቱ ፡ ጥሩ ፡ (ዓይነተኛ) ፡ ምሳሌ ፡ ይህ ፡ ነበር
2. የሚያሳይ. These stories are representative of the Ethiopian way of life. እነዚህ ፡ ታሪኮች ፡ የኢትዮጵያን ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያሳዩ ፡ ናቸው
3. የሕዝብ. Is representative government more effective than government by party? የሕዝብ ፡ መንግሥት ፡ በፓርቲ ፡ ከሚመራ ፡ መንግሥት ፡ የተሻለ ፡ ውጤት ፡ አለው ?
*Images representative of animals were made out of clay by the children. ልጆቹ ፡ የእንስሳትን ፡ ምስሎች ፡ ከሸክላ ፡ ሠሩ

**repress**
1. ደመሰሰ. The ship's captain swiftly repressed the mutiny. የመርከቡ ፡ አዛዥ ፡ መርከቡ ፡ ላይ ፡ የተነሣውን ፡ ዐመፅ ፡ በፍጥነት ፡ ደመሰሰው
2. ገታ. He tried to repress his laughter, because he was in church. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ስለነበረ ፡ ሣቁን ፡ ለመግታት ፡ ሞከረ
3. ቀጨ. He might have been a good actor, but his family repressed his talent. ቤተሰቦቹ ፡ ችሎታውን ፡ ባይቀጩት ፡ ኖሮ ፡ ጥሩ ፡ ተዋናይ ፡ ይሆን ፡ ነበር

**be repressed** ተጨቈነ
The nationalist movement was repressed by the colonial government. ብሔራዊው ፡ ንቅናቄ ፡ በቅኝ ፡ ገዢው ፡ መንግሥት ፡ ተጨቍኖ ፡ ነበር

**repression** ጭቈና
Repression often causes rebellion later on. ጭቈና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆይቶ ፡ ዐመፅን ፡ ያስከትላል

**repressive** የጭቈና
The South African government passed repressive laws against the indigenous people. የደቡብ ፡

አፍሪካ ፣ መንግሥት ፣ በአገሬዎች ፣ ላይ ፣ የጭ
ቈና ፣ ሕግ ፣ አወጣ

**reprieve** (v.)
*The court reprieved the condemned prisoner. ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ የተፈረደበትን ፣ እስረኛ ፣ ቅጣቱ ፣ ሳይፈጸምበት ፣ እንዲቆይ ፣ አደረገ

**reprieve** (n.)
*He was granted a reprieve minutes before his execution was to take place. ሊገደል ፣ ጥቂት ፣ ደቂቃዎች ፣ ሲቀሩት ፣ ቅጣቱ ፣ ለሌላ ፣ ጊዜ ፣ እንዲተላለፍ ፣ ተደረገ

**reprimand** ገሠጸ ፤ ወቀሰ ፤ ዘለፈ
The teacher reprimanded the lazy student. አስተማሪው ፣ ሰነፉን ፣ ተማሪ ፣ ገሠጸው ፣ (ወቀሰው ፤ ዘለፈው)

**reprint** (v.) እንደገና ፣ አተመ
The university reprinted Shakespeare's works. የሼክስፒርን ፣ ጽሑፎች ፣ ዩኒቨርሲቲው ፣ እንደገና ፣ አተመ

**reprint** (n.) ድጋሚ ፣ እትም
This book is a reprint of an earlier edition. ይህ ፣ መጽሐፍ ፣ ከዚህ ፣ በፊት ፣ የወጣው ፣ መጽሐፍ ፣ ድጋሚ ፣ እትም ፣ ነው

**reprisal, in ~** ዐጸፋውን ፣ ለመመለስ
Our raid is in reprisal for an enemy attack. እኛ ፣ ያደረግነው ፣ ወረራ ፣ ጠላት ፣ ላደረገው ፣ ማጥቃት ፣ ዐጸፋውን ፣ ለመመለስ ፣ ነው

**reproach** (v.) ወቀሰ
He reproached his wife for her carelessness. ግዴለሽ ፣ በመሆኗ ፣ ሚስቱን ፣ ወቀሳት

**reproach** (n.)
1. ወቀሳ. I didn't mean that as a reproach. ይህን ፣ ማለቴ ፣ ለወቀሳ ፣ አይደለም
2. አሳፋሪ. Slums are a reproach to a city. ደሳሳ ፣ መኖሪያዎች ፣ ለከተማ ፣ አሳፋሪዎች ፣ ናቸው

**reproachful** የቅሬታ
He gave me a reproachful look. በቅሬታ ፣ ዓይን ፣ ተመለከተኝ

**reprobate** ውዳቂ
He is an old reprobate. እሱ ፣ ውዳቂ ፣ ሽማግሌ ፣ ነው

**reprobation** ወቀሳ
He is afraid of his father's reprobation. ያባቱን ፣ ወቀሳ ፣ ይፈራል

**reproduce** (vt.)
1. ቀዳ. Tape recorders reproduce sound. ቴፕ ፣ ሪኮርደር ፣ ድምፅ ፣ ይቀዳል
2. ሣለ. The artist has reproduced your face well in this portrait. በዚህ ፣ ሥዕል ፣ ላይ ፣ ሠዓሊው ፣ መልክህን ፣ ጥሩ ፣ አድርጎ ፣ ሥሎታል
3. አሳየ. This photo reproduces her expression exactly. ይህ ፣ ፎቶግራፍ ፣ ፊቷን ፣ በትክክል ፣ ያሳያል

**reproduce** (vi.) ተራባ
Plants reproduce just like animals. ዕፀዋትም ፣ እንደ ፣ እንስሳት ፣ ሁሉ ፣ ይራባሉ

**reproduce oneself** ተራባ
Animals reproduce themselves in various ways. እንስሳት ፣ በብዙ ፣ ዓይነት ፣ መንገዶች ፣ ይራባሉ

**reproduction**
1. ቅጂ. This is a reproduction of an ancient statue. ይህ ፣ የቀድሞ ፣ ሐውልት ፣ ቅጂ ፣ ነው
2. መራባት. The book describes the reproduction of animals. መጽሐፉ ፣ የእንስሳትን ፣ መራባት ፣ ያስረዳል

**reproof** ወቀሳ
She deserves reproof for her rudeness. ለብልግናዋ ፣ ወቀሳ ፣ ይገባታል

**reprove** ገሠጸ
Fathers reprove their sons for their misconduct. አባቶች ፣ ልጆችን ፣ በብልግናቸው ፣ የተነሣ ፣ ይገሥጹቸዋል

**reptile** [እባብንና ፣ እንሽላሊትን ፣ የመሳሰሉ ፣ በልብ ፣ የሚሳቡ ፣ እንስሳት]

**republic** ሬፑብሊክ
Some countries are monarchies, others are republics. አንዳንድ ፣ አገሮች ፣ በንጉሥ ፣ የሚተዳደሩ ፣ ሲሆኑ ፣ አንዳንዶቹ ፣ ደግሞ ፣ ሬፑብሊክ ፣ ናቸው

**repudiate**
1. ካደ. He repudiated the statement he had made earlier. ቀደም ፣ ብሎ ፣ የተናገረውን ፣ ካደ
2. ፈታ. He repudiated his wife, and married another woman. ሚስቱን ፣ ፈቶ ፣ ሌላ ፣ አገባ
3. ጣለ. He repudiated his family. ቤተሰቦቹን ፣ ጣለ
4. አልከፍልም ፣ አለ. He repudiated the debt. ዕዳውን ፣ አልከፍልም ፣ አለ

**repugnance** መጥላት
His repugnance for my proposal shows in his face. ያቀረብኩትን ፣ ሐሳብ ፣ መጥላቱ ፣ በፊቱ ፣ ላይ ፣ ይታያል

**repugnant**

1. ግም. The repugnant odor of rotting fish kept us from swimming in the pool. የበሰበሰው ፡ ዓሣ ፡ ግም ፡ ሽታ ፡ በኩሬው ፡ ውስጥ ፡ እንዳንዋኝ ፡ ከለከለን

2. አስከፊ. Killing is repugnant to a true believer. ሃይማኖተኛ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ ማጥፋት ፡ አስከፊ ፡ ነው

**be repugnant (to)** አይስማማም

This conduct is repugnant to his character. ይህ ፡ ዓይነት ፡ ጠባይ ፡ ከሁኔታው ፡ ጋር ፡ አይስማማም

**repulse**

1. መለሰ. We repulsed the enemy troops. የጠላትን ፡ ጦር ፡ መለስነው

2. ራቀ. He repulsed his former friends. የቀድሞ ፡ ጓደኞቹን ፡ ራቃቸው

**be repulsed** ሊመለስ ፡ ቻለ

The assault was repulsed with heavy losses. ጥቃቱ ፡ ሊመለስ ፡ የቻለው ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ነው

**repulsion, feel ~ for** (= active) ቀፈፈ(ው)

+I feel repulsion for slimy creatures. ዝልግልግ ፡ እንስሳት ፡ ይቀፉኛል

**fill with repulsion** አስጠላ

The idea filled her with repulsion. ሐሳቡ ፡ አስጠላት

**repulsive** ቀፋፊ

The girl is repulsive. ልጅቷ ፡ ቀፋፊ ፡ ናት

Snakes are repulsive to some people. ላንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ እባብ ፡ ቀፋፊ ፡ ነው

**reputable**

1. ስመ ፡ ጥር. He is a reputable businessman. ስመ ፡ ጥር ፡ ነጋዴ ፡ ነው

2. ደኅና ፡ ስም ፡ ያለው. It pays to buy from a reputable firm. ደኅና ፡ ስም ፡ ካለው ፡ ድርጅት ፡ መገብየት ፡ ይጠቅማል

**reputation**

1. ዝና. He has a reputation for being a good worker. በጥሩ ፡ ሠራተኛነቱ ፡ ዝና ፡ ያተረፈ ፡ ሰው ፡ ነው

2. ስም. The newspaper besmirched his reputation. ጋዜጣው ፡ ስሙን ፡ አጕደፈው

He has a poor reputation as a lawyer. በጥብቅና ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ስም ፡ አለው

**repute** ዝና

I know him by repute only. የማውቀው ፡ በዝና ፡ ብቻ ፡ ነው

**of good repute** መልካም ፡ ስም ፡ ያለው

He is a man of good repute. መልካም ፡ ስም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

[See also 'ill']

**reputed** የሚባል

The reputed owner of the house sold his property. የቤቱ ፡ ባለቤት ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ ንብረቱን ፡ ሸጠ

**be reputed** ተባለ

He is reputed to be wealthy. ሀብታም ፡ ነው ፡ ይባላል

**request** (v.) ጠየቀ

I must request you to leave this place. ይህንን ፡ ቦታ ፡ ለቀህ ፡ እንድትሄድ ፡ እጠይቅሃለሁ

**request** (n.)

1. የጠየቀ. In accordance with your request, we are sending you three books. በጠየቅኸው ፡ መሠረት ፡ ሦስት ፡ መጽሐፍ ፡ ልከንልሃል

2. የተጠየቀ. Request granted. የተጠየቀው ፡ ተፈቅዷል

3. ልመና. He treated my request with indifference. ልመናዬን ፡ እንደማንም ፡ ተመለከተው

**at the request of** ስላሳሰበው

I am writing to you at the request of a friend. የምጽፍልህ ፡ ወዳጅ ፡ ስላሳሰበኝ ፡ ነው

**be in request**

1. ተጋበዘ. He's very much in request as a speaker. በንግግር ፡ ዐዋቂነቱ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይጋበዛል

2. ጠያቂዎች ፡ አሉት. Is this book much in request? ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ብዙ ፡ ጠያቂዎች ፡ አሉት ?

**by request** ተጠይቆ

He sang by request. ተጠይቆ ፡ ዘፈነ

**make a request for** ጠየቀ

He made a request for more money. ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ጠየቀ

**on request** ሲጠይቅ

I will give it to you on request. ስትጠይቀኝ ፡ እሰጥሃለሁ

**require**

1. ጠየቀ. That will require some time. በርከት ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ይጠይቃል

How much money does that require? ምን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ ይጠይቃል ?

2. ፈጀ. How much time will that require? ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይፈጃል ?

3. አዘዘ. I have done everything that the law requires. ሕጉ ፡ የሚያዘውን ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ፈጽሜያለሁ
4. ፈለገ(ተፈለገ). Ethical behavior is required of lawyers. ከጠበቆች ፡ የሐቀኝነት ፡ ምግባር ፡ ይፈለጋል
5. አስፈለገ(ው). +I require seven hours' sleep a night. ሌሊት ፡ የሰባት ፡ ሰዓት ፡ እንቅልፍ ፡ ያስፈልገኛል
*A thing like that requires careful study. እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ በጥንቃቄ ፡ መጠናት ፡ አለበት

**require of**
*What do you require of me? ምን ፡ እንዳደርግ ፡ ትፈልጋለህ ?

**requirement**
1. የተደነገገ ፡ ደንብ. We must modify our requirements to meet the new situation. አዲሱን ፡ ሁኔታ ፡ ለመቋቋም ፡ የተደነገገውን ፡ ደንብ ፡ ማሻሻል ፡ አለብን
2. ብቁ ፡ የሚያደርገው ፡ ነገር. He couldn't fulfill the requirements for the job. ለሥራው ፡ ብቁ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ነገሮች ፡ ሊያሟላ ፡ አልቻለም
3. አስፈላጊ ፡ የሚባል ፡ ነገር. They plan to do away with most of the requirements. አስፈላጊ ፡ ከሚባሉት ፡ ነገሮች ፡ ብዙዎቹን ፡ ለማስወገድ ፡ ያቅዳሉ
4. አስፈላጊ ፡ ነገር ፤ ዋና ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር. Patience is a requirement in teaching. ለማስተማር ፡ ትዕግሥት ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው
Vitamins are a requirement of the diet. በምግብ ፡ ውስጥ ፡ ቪታሚኖች ፡ ዋና ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው

**requisite** (n.) አስፈላጊ ፡ ነገር
Food and air are requisites for life. ምግብና ፡ አየር ፡ ለሕይወት ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው

**requisite** (adj.) አስፈላጊ
We lack the requisite capital for setting up a business. ንግድ ፡ ለማቋቋም ፡ አስፈላጊው ፡ ገንዘብ ፡ የለንም

**requisition** (v.) ጠይቆ ፡ ወሰደ
The army requisitioned all the vehicles to transport troops. የጦር ፡ ሰራዊት ፡ ወታደሮቹን ፡ ለማጓጓዝ ፡ መኪናዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ጠይቆ ፡ ወሰደ

**requisition** (n.) መጠየቂያ
The officer signed the requisition for the vehicles. መኰንኑ ፡ የመኪናዎቹን ፡ መጠየቂያ ፡ ፈረመ

**requite**
1. መለሰ. He requites kindness with ingratitude. ደግነትን ፡ በውለታ ፡ ቢስነት ፡ ይመልሳል
2. ብድሩን ፡ ከፈለ. How can I requite him for his help? ስለ ፡ እርዳታው ፡ እንዴት ፡ ብድሩን ፡ ልከፍል ፡ እችላለሁ ?

**rerout** በሌላ ፡ መንገድ ፡ ላከ
The general rerouted the troops. ጄኔራሉ ፡ ወታደሮቹን ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ላካቸው

**rescind** ሻረ
The parliament rescinded the tax law last year. ፓርላማው ፡ የግብሩን ፡ ሕግ ፡ ዓምና ፡ ሻረው

**rescue** (v.) አዳነ ፤ አተረፈ
I rescued the child from drowning. ሕፃኑን ፡ ከመስጠም ፡ አዳንኩት
The courageous boy rushed into the burning building to rescue the child. ደፋሩ ፡ ልጅ ፡ ሕፃኑን ፡ ለማትረፍ ፡ የተቀጣጠለው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሮጦ ፡ ገባ

**rescue** (n.) የማዳን ፡ ተግባር
The rescue was hampered by the storm. የማዳኑ ፡ ተግባር ፡ በኀይለኛው ፡ ዝናብ ፡ ምክንያት ፡ ተሰናከለ

**come to the rescue** ለማዳን ፡ መጣ
The cavalry came to the rescue of the besieged settlers. ፈረሰኛው ፡ የተከበቡትን ፡ ሰፋሪዎች ፡ ለማዳን ፡ መጣ
*He came to her rescue just in time. በነፍሷ ፡ ደረሰ

**research** (v.) መረመረ
He researches genealogies for a living. የዘር ፡ ግንዶች ፡ በመመርመር ፡ ይተዳደራል

**research** (n.)
1. ምርመራ. He is doing research on the causes of cancer. ስለ ፡ ካንሰር ፡ መነሻ ፡ ምርመራ ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ነው
2. ጥናት. Research on language problems is necessary. የቋንቋ ፡ ችግሮች ፡ ጥናት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
He is doing research for his report. ለሪፖርቱ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ጥናት ፡ ያደርጋል

**researcher** ተመራማሪ
Pasteur blazed a trail which other researchers followed. ፓስተር ፡ የተለመውን ፡ የጥበብ ፡ ፋና ፡ ሌሎች ፡ ተመራማሪዎች ፡ ተከተሉት

**resemblance** መመሳሰል
There is very little resemblance between father and son. ባባትና ፡ በልጅ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ መመሳሰል ፡ ትንሽ ፡ ነው

**resemble** መሰለ
Don't you think he resembles his mother? እናቱን ፡ አይመስልም ?

**resent**
1. ቅር ፡ አሰኘ. He resents any favor being shown to his brother. ለወንድሙ ፡ የሚደረግለት ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ቅር ፡ ያሰኘዋል
2. ተቀየመ. The card players resented his advice as an intrusion. ካርታ ፡ ተጫዋቾች ፡ ምክሩን ፡ እንደ ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ቈጥረው ፡ ተቀየሙ
3. ጠላ. He resents all restrictions. ማንኛቸውንም ፡ ዓይነት ፡ ቍጥጥር ፡ ይጠላል

**(be) resentful** ቅር ፡ ተሰኘ
He is resentful of the insults he received. ስለደረሰበት ፡ ስድብ ፡ ቅር ፡ ተሰኝቷል

**resentment** ቅሬታ
He bears no resentment for the bad treatment he received in school. በትምህርት ፡ ቤት ፡ ስለተደረገበት ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ቅሬታ ፡ አልገባውም

**reservation**
1. (verbal noun =) ቦታ ፡ መያዝ. I couldn't get a reservation on that train. በዚያ ፡ ባቡር ፡ ላይ ፡ ቦታ ፡ ለመያዝ ፡ አልቻልኩም
2. የያዘው ፡ ቦታ. Our reservations are in the fifth row. የያዝናቸው ፡ ቦታዎች ፡ አምስተኛው ፡ ረድፍ ፡ ላይ ፡ ነው
3. ገደብ. The United States accepted the plan with reservations. አሜሪካ ፡ ስምምነቱን ፡ ካንዳንድ ፡ ገደቦች ፡ ጋር ፡ ተቀበለች
4. የተወሰነ ፡ ክልል. Indians live on reservations in the United States. ህንዶች ፡ በአሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ በተወሰነ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ

**without reservations** እንዳለ
You can't accept everything he says without reservations. የሚለውን ፡ ሁሉ ፡ እንዳለ ፡ ለመቀበል ፡ አትችልም

**reserve** (v.)
1. ያዘ. I reserved two seats at the theater. ቲያትር ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ መቀመጫዎች ፡ ያዝኩ
2. ቈጠበ. Reserve your strength for the race! ጉልበትህን ፡ ለውድድሩ ፡ ቈጥብ
3. ከ --- ተቈጠበ. Mother reserved her complaint about my messy room until my friend left. ጓደኛዬ ፡ እስኪሄድ ፡ ድረስ ፡ እናቴ ፡ ስለተዝረከረከው ፡ ክፍሌ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ወቀሳ ፡ ከመሰንዘር ፡ ተቈጠበች
4. አስቀመጠ. Reserve enough money for your fare home! ወደ ፡ ቤትህ ፡ ለመመለሻ ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ አስቀምጥ
5. መደበ. He reserves his Saturday evenings for entertaining friends. ቅዳሜ ፡ ቅዳሜ ፡ ማታን ፡ ጓደኞቹን ፡ ለማስተናገጃ ፡ መድቧል
6. ለሌላ ፡ ጊዜ ፡ አስተላለፈ. The judge reserved his decision. ዳኛው ፡ ውሳኔውን ፡ ለሌላ ፡ ጊዜ ፡ አስተላለፈ
7. የራሴ ፡ ነው ፡ ይላል. He reserves all rights to his invention. በፈለሰፈው ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ መብቱ ፡ የራሴ ፡ ነው ፡ ይላል

**reserve the right** መብት ፡ አለው
I reserve the right to refuse. እምቢ ፡ ለማለት ፡ መብት ፡ አለኝ

**reserve** (n.)
1. ተቀማጭ. I'm afraid we'll have to dig into our reserves. ከተቀማጫችን ፡ ማውጣት ፡ ያለብን ፡ ይመስለኛል
2. መጠባበቂያ. He has little food in reserve. ትንሽ ፡ መጠባበቂያ ፡ ምግብ ፡ ይዟል
Banks must keep a reserve of money. ባንኮች ፡ የመጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ ማስቀመጥ ፡ አለባቸው
3. ክልል. Do you have permission to hunt on the game reserve? በአደን ፡ ክልሉ ፡ ውስጥ ፡ ለማደን ፡ ፈቃድ ፡ አለህ ?
4. ገለልተኛነት. His reserve makes people think that he is standoffish. ገለልተኛነቱ ፡ ሰው ፡ የማይወድ ፡ ያስመስለዋል

**reserves** ተጠባባቂ ፡ ወታደሮች
Reserves will be sent to help the men fighting at the front. ከጦሩ ፡ ግንባር ፡ የሚዋጉትን ፡ ወታደሮች ፡ ለመርዳት ፡ ተጠባባቂ ፡ ወታደሮች ፡ ይላካሉ

**without reserve** በሙሉ ፡ ልብ ፤ ምንም ፡ ሳያስቀር
We accept your statement without reserve. ያልከውን ፡ በሙሉ ፡ ልብ ፡ ተቀብለነዋል
He told us the plain facts without reserve. እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ ሳያስቀር ፡ ነገረን

**reserved** (adj.) ጭምት
He is a very reserved person. በጣም ፡ ጭምት ፡ ሰው ፡ ነው

**be reserved** ተያዘ
Is this seat reserved? ይህ ፡ መቀመጫ ፡ ተይዟል ?

**reservoir**
1. ማጠራቀሚያ ፤ የውኃ ፡ ማጠራቀሚያ. The volume of water which the reservoir holds is more than 3 million gallons. ማጠራቀሚያው ፡ የሚይዘው ፡ ውኃ ፡ ከሦስት ፡ ሚሊዮን ፡ ጋሎን ፡ ይበልጣል
The reservoir is nearly dry. የውኃው ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ወደ ፡ መድረቁ ፡ ነው
2. መያዣ. A fountain pen has an ink reservoir. ብዕር ፡ የቀለም ፡ መያዣ ፡ አለው
3. ምንጭ. His mind is a reservoir of wisdom. አእምሮው ፡ የጥበብ ፡ ምንጭ ፡ ነው

**reset** (reset)
1. መልሶ ፡ ተከለ. Reset the stakes that were knocked down! የወደቁትን ፡ ችካሎች ፡ መልሰህ ፡ ትከላቸው
2. ጠገነ(ተጠገነ). John's broken arm had to be reset. የጆን ፡ የተሰበረ ፡ ክንዱ ፡ መጠገን ፡ ነበረበት

**resettle** አሰፈረ
The government resettled the refugees near the border. መንግሥቱ ፡ ስደተኞቹን ፡ ጠረፍ ፡ አጠገብ ፡ አሰፈረ

**reshuffle** (v.) በወዘ
He reshuffled the cards. ካርታውን ፡ በወዘው

**reshuffle** (n.) መለዋወጥ ፤ ሹም ፡ ሽር
One of these days, there will undoubtedly be a cabinet reshuffle. ሰሞኑን ፡ የሚኒስትሮች ፡ መለዋወጥ ፡ (ሹም ፡ ሽር) ፡ እንደሚደረግ ፡ አይጠረጠርም

**reside**
1. ኖረ. He resides in a town near here. ቅርብ ፡ በሚገኝ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል
2. ነው. Her charm resides in her happy smile. መልኳ ፡ ፈገግታዋ ፡ ላይ ፡ ነው

**reside with** በ --- እጅ ፡ ነው
Supreme authority resides in the Emperor. ከፍተኛው ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እጅ ፡ ነው

**residence**
1. መኖሪያ. The palace is the residence of the Emperor. ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መኖሪያ ፡ ነው
2. መቀመጥ. Her two years' residence in Italy was profitable. ሁለት ፡ ዓመት ፡ ኢጣልያን ፡ አገር ፡ መቀመጧ ፡ ጠቃሚ ፡ ነበር
3. አድራሻ. Any change of residence must be brought to the attention of the police. አድራሻ ፡ በተለወጠ ፡ ጊዜ ፡ ለፖሊስ ፡ ማስታወቅ ፡ ያስፈልጋል

**resident** (n.)
She is a resident of California. ተቀማጪነቷ ፡ ካሊፎርኒያ ፡ ነው

**resident** (adj.) ሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር
Dr. Parker is a resident physician at the hospital. ዶክተር ፡ ፓርከር ፡ ሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር ፡ ሐኪም ፡ ነው

**be resident** ኖረ
These birds are resident here the year round. እነዚህ ፡ ወፎች ፡ ከዓመት ፡ ዓመት ፡ እዚህ ፡ ይኖራሉ

**residential** የመኖሪያ
This is a residential area. ይህ ፡ የመኖሪያ ፡ ሰፈር ፡ ነው

**residual** ቀሪ
Any residual funds revert to the government. ማንኛውም ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ይሆናል

**residue**
1. የተረፈ. Mr. Smith's will directed that after payment of all debts, the residue of his property should go to his son. የሚስተር ፡ ስሚዝ ፡ ኑዛዜ ፡ ዕዳው ፡ ሁሉ ፡ ከተከፈለ ፡ በኋላ ፡ የተረፈው ፡ ገንዘብ ፡ ለልጁ ፡ እንዲሰጥ ፡ ያዛል
2. ዝቃጭ. There is an oily residue in the bottle. ጠርሙሱ ፡ ውስጥ ፡ የዘይት ፡ ዝቃጭ ፡ አለ

**resign**
1. ሥራውን ፡ በፈቃዱ ፡ ለቀቀ. There was a spate of reports that he will resign. ሥራውን ፡ በፈቃዱ ፡ ይለቃል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ይነፍስ ፡ ነበር
2. ወጣ. I have resigned from the club. ከክበቡ ፡ ወጥቻለሁ
*He resigned as chairman. ሊቀ ፡ መንበርነቱን ፡ ለቀቀ

**resign oneself to** ግድ ፡ ሆነበት
He had to resign himself to a week in bed when he hurt his back. ወገቡን ፡ ስላመመው ፡ ላንድ ፡ ሳምንት ፡ መተኛት ፡ ግድ ፡ ሆነበት
*He resigned himself to his fate. ተስፋውን ፡ ሁሉ ፡ በዕድሉ ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ ቁጭ ፡ አለ

**be resigned to** ግድ ፡ ሆነበት
He is resigned to doing without servants. ያለ ፡ አሽከር ፡ መኖሩ ፡ ግድ ፡ ሆነበት

**resignation**
1. ከሥራ ፡ ለመሰናበት ፡ ያቀረበው ፡ ጥያቄ. His resignation was not accepted. ከሥራ ፡ ለመሰናበት ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ አልተቀበሉትም
2. የሥራ ፡ መልቀቂያ ፡ ደብዳቤ. He refused to accept my resignation. የሥራ ፡ መልቀቂያ ፡ ደብዳቤዬን ፡ አልቀበልም ፡ አለኝ

3. ትዕግሥት. She bore the pain with resignation. ሕመሙን ፡ በትዕግሥት ፡ ቻለች
*We demand his resignation. ሥራውን ፡ እንዲለቅ ፡ እንጠይቃለን

**resilience** ቶሎ ፡ መዳን
His resilience enabled him to leave the hospital in a week. ቶሎ ፡ በመዳኑ ፡ ከሆስፒታል ፡ ባንድ ፡ ሳምንት ፡ ወጣ
*Rubber has resilience. ላስቲክ ፡ ሲሳብ ፡ ወደ ፡ ጥንተ ፡ ቅርጹ ፡ የመመለስ ፡ ጠባይ ፡ አለው

**resin** ሙጫ
Stop up the hole in the jar with resin! የእንስራውን ፡ ቀዳዳ ፡ በሙጫ ፡ ድፈነው

**resist**
1. ተቋቋመ. Our troops resisted the enemy's attack. ወታደሮቻችን ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ ተቋቋሙ
I couldn't resist the temptation. ፈተናውን ፡ ልቋቋመው ፡ አልቻልኩም
2. ገታ. I could not resist laughing. ሣቄን ፡ ለመግታት ፡ አልቻልኩም
3. ቻለ. This glass resists heat. ይህ ፡ ብርጭቆ ፡ ሙቀት ፡ ይችላል
*The window resisted his efforts to open it. መስኮቱ ፡ አልከፈት ፡ አለ
*He was fired at and wounded while resisting arrest. አልያዝም ፡ ብሎ ፡ ሲታገል ፡ ተተኩሶበት ፡ ቈሰለ

**resistance**
1. የመቋቋም ፡ ኀይል. Fatigue lowered his resistance, and he caught a cold. ድካም ፡ የመቋቋም ፡ ኀይሉን ፡ ስለቀነሰበት ፡ ጉንፋን ፡ ያዘው
2. ቅስም. Bombing broke the enemy's resistance. የቦምቡ ፡ ድብደባ ፡ የጠላትን ፡ ቅስም ፡ ሰበረው
3. መከላከያ. We need more troops to stiffen our resistance. መከላከያችንን ፡ ለማጠንከር ፡ ተጨማሪ ፡ ወታደሮች ፡ ያስፈልጉናል
4. መከላከል. Their sturdy resistance blocked the enemy's advance. በቈራጥነት ፡ መከላከላቸው ፡ ጠላትን ፡ ወደፊት ፡ ከመግፋት ፡ አገደው
5. ተጋድሎ. Gandhi preached passive resistance. ጋንዲ ፡ ሰላማዊ ፡ ተጋድሎን ፡ አስተማረ
6. ተቃውሞ. His resistance spoiled our plans. ተቃውሞው ፡ እቅዳችንን ፡ አበላሸብን
*The fabric's resistance to wear is tested in the laboratory. የጨርቁ ፡ ጥንካሬ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ በቤተ ፡ ሙከራው ፡ ተጠንቷል
*She took the line of least resistance. የሚያዋጣትን ፡ ቀላሉን ፡ መንገድ ፡ መረጠች

**break the back of one's resistance** ቅስም ፡ ሰበረ
Bombing broke the back of the enemy's resistance. የቦምቡ ፡ ድብደባ ፡ የጠላትን ፡ ቅስም ፡ ሰበረ

**not put up resistance** ያለ ፡ ማስቸገር ፡ እጁን ፡ ሰጠ
The robber didn't put up any resistance when the police caught him. ሌባው ፡ ፖሊሶች ፡ ሊይዙት ፡ ሲመጡ ፡ ያለ ፡ ማስቸገር ፡ እጁን ፡ ሰጠ

**offer resistance** ተቋቋመ
The enemy offered no resistance to our troops. ጠላት ፡ ወታደሮቻችንን ፡ አልተቋቋመም ፡ ነበር
[See also 'passive']

**resistant** የእምቢተኛነት
He has a resistant nature. የእምቢተኛነት ፡ ጠባይ ፡ አለው

**be water resistant** ውኃ ፡ የማይዘልቀው ፡ ነው
Is this cloth water resistant? ይህ ፡ ልብስ ፡ ውኃ ፡ የማይዘልቀው ፡ ነው ?

**resolute** ቈራጥ
He is very resolute, and does not waver in a difficult situation. በጣም ፡ ቈራጥ ፡ ስለሆነ ፡ በችግር ፡ ጊዜ ፡ አያመነታም
A soldier must be resolute in battle. ወታደር ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ቈራጥ ፡ መሆን ፡ አለበት

**resolution**
1. ውሳኔ. The club passed a resolution thanking the president. ክበቡ ፡ ፕሬዚዳንቱን ፡ በማመስገን ፡ ውሳኔ ፡ አስተላለፈ
2. ቁርጥ ፡ ሐሳብ. He kept his resolution to get up early. ማልዶ ፡ ለመነሣት ፡ ያደረገውን ፡ ቁርጥ ፡ ሐሳብ ፡ አከበረ
3. ቈራጥነት. Lincoln's resolution overcame his poverty. የሊንኮልን ፡ ቈራጥነት ፡ ድኽነቱን ፡ እንዲያሸንፍ ፡ ረዳው
4. መፍትሔ. The resolution of the problem presents many difficulties. የችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ ብዙ ፡ ችግሮች ፡ አሉበት

**make a resolution** ቈረጠ
He made a resolution to get up early. ማለዳ ፡ ለመነሣት ፡ ቈረጠ

**resolve** (v.)
1. ቈረጠ. He resolved to join the army. ወታደርነት ፡ ለመግባት ፡ ቈረጠ
2. ወሰነ. Parliament has resolved that a new tax should be imposed on business. በንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ ቀረጥ ፡ እንዲጣል ፡ ፓርላማው ፡ ወሰነ
3. ውሳኔ ፡ አስተላለፈ. The club resolved that a letter of thanks be sent to the chairman. ክበ

ቡ ፡ ለሊቀ ፡ መንበሩ ፡ የምስጋና ፡ ደብዳቤ ፡ እንዲላክ ፡ ውሳኔ ፡ አስተላለፈ
4. መፍትሔ ፡ አስገኘ. The United Nations resolved the conflict between the two nations. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ላለው ፡ ጠብ ፡ መፍትሔ ፡ አስገኘ
5. አስወገደ. His letter resolved all our doubts. ደብዳቤው ፡ ጥርጣሬያችንን ፡ ሁሉ ፡ አስወገደልን
6. ከፈለ. He resolved the main subject into four topics. ዋናውን ፡ አርእስት ፡ በአራት ፡ ከፈለው

**resolve itself** ተለወጠ
The conversation resolved itself into an argument. ወሬው ፡ ወደ ፡ ክርክር ፡ ተለወጠ

**be resolved**
1. ውሳኔ ፡ ተላለፈ. It was resolved that our school have a lunchroom. ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ የምሳ ፡ መብያ ፡ ክፍል ፡ እንዲኖረው ፡ ውሳኔ ፡ ተላለፈ
2. ተለያየ. Some chemical compounds can be resolved by heat. አንዳንድ ፡ የኬሚካል ፡ ውሑዶች ፡ በሙቀት ፡ ይለያያሉ
3. መፍትሔ ፡ ተገኘ(ለት). The quarrel was resolved by an arbitrator. ጥሉ ፡ ባስታራቂ ፡ መፍትሔ ፡ ተገኘለት

**resolve** (n.) ቈራጥነት ፤ ቁርጠኛነት
The circumstances of her childhood called forth her courage and resolve. የልጅነት ፡ ሁኔታዋ ፡ ጉብዝናዋንና ፡ ቈራጥነትን ፡ (ቁርጠኛነትን) ፡ ሰጣት

**of great resolve** እጅግ ፡ ቈራጥ
George Washington was a man of great resolve. ጆርጅ ፡ ዋሽንግተን ፡ እጅግ ፡ ቈራጥ ፡ ሰው ፡ ነበር

**resonant** የሚያስተጋባ
The resonant walls make the music sound better. የሚያስተጋቡ ፡ ግድግዳዎች ፡ ለሙዚቃ ፡ የተሻለ ፡ ድምፅ ፡ ይሰጡታል

**resort** (v.)
1. ለዕረፍት ፡ ሄደ. Many people resort to the mountains in hot weather. በሞቃት ፡ ወራት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ለዕረፍት ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ይሄዳሉ
2. ተጠቀመ. I don't want to resort to force. በጉልበት ፡ ለመጠቀም ፡ አልፈልግም
3. ጠየቀ. Who will I resort to in my need? ለሚያስፈልገኝ ፡ ነገር ፡ ማንን ፡ ልጠይቅ ?

**resort** (n.)
1. የመዝናኛ ፡ ቦታ. A new resort is being built in the mountains. በተራራው ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ የመዝናኛ ፡ ቦታ ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ ነው
2. ረዳት. Your best resort in this case is a lawyer. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ዋና ፡ ረዳትህ ፡ ጠበቃ ፡ ነው
3. ምርጫ. Selling his watch was his last resort. ሰዓቱን ፡ መሸጥ ፡ የመጨረሻ ፡ ምርጫው ፡ ነበር

**resound**
1. አስተጋባ. The room resounded with the children's shouts. ክፍሉ ፡ በልጆቹ ፡ ጩኸት ፡ አስተጋባ
Her shout resounded throughout the cave. ጩኸቷ ፡ በዋሻው ፡ ውስጥ ፡ አስተጋባ
2. የ - - - ድምፅ ፡ ተሰማ. Radios resound from every house. ከየቤቱ ፡ የሬዲዮ ፡ ድምፅ ፡ ይሰማል

**resource**
1. የገቢ ፡ ምንጭ. His main resource during illness was his savings. በሕመሙ ፡ ጊዜ ፡ ዋናው ፡ የገቢ ፡ ምንጩ ፡ ያጠራቀመው ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ነበር
2. መጠጊያ. God is our only resource in time of distress. በችግር ፡ ጊዜ ፡ ያለን ፡ መጠጊያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነው
3. የመጨረሻ ፡ ማምለጫ ፡ ዘዴ. Climbing a tree is a cat's resource when chased by a dog. ውሻ ፡ ሲያባርራት ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ መውጣት ፡ ለድመት ፡ የመጨረሻ ፡ ማምለጫዋ ፡ ዘዴ ፡ ነው
4. ነገር. Electric power is a necessary resource for industry. ለኢንዱስትሪ ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ኀይል ፡ ዋና ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው

**resources**
1. ሀብት ፤ ሀብቶች. Sudan is poor in oil resources. ሱዳን ፡ በዘይት ፡ ሀብት ፡ ድኻ ፡ ነች
African nations must pool their resources to develop faster. የአፍሪካ ፡ አገሮች ፡ በፍጥነት ፡ ለመበልጸግ ፡ ሀብቶቻቸውን ፡ ባንድ ፡ ማዋሐድ ፡ አለባቸው
2. የሚቻል ፡ መንገድ. I have exhausted all resources. የሚቻለውን ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ ሞከሬያለሁ

**natural resources** የተፈጥሮ ፡ ሀብት
We must exploit our natural resources. የተፈጥሮ ፡ ሀብታችንን ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ አለብን

**resourceful** ዘዴኛ
He is very resourceful in emergencies. ባደጋ ፡ ጊዜያት ፡ በጣም ፡ ዘዴኛ ፡ ነው

**respect** (v.)
1. አከበረ. You must respect your elders. ታላቆችህን ፡ ማክበር ፡ አለብህ
2. ተቀበለ. I respect your opinion. አስተያየትህን ፡ እቀበላለሁ

3. ጠበቀ. I respect your rights. መብትህን ፡ እጠብቃለሁ
4. አደነቀ. I dislike the painter personally, but I respect his talent. ለሠዓሊው ፡ የግል ፡ ጥላቻ ፡ ቢኖረኝም ፡ ችሎታውን ፡ አደንቃለሁ
5. ተመለከተ. The matter respects our welfare. ጉዳዩ ፡ ደኅንነታችንን ፡ ይመለከታል

**respect** (n.)
1. ሰውን ፡ ማክበር. Respect is the foundation of politeness. ሰውን ፡ ማክበር ፡ የትሕትና ፡ መሠረት ፡ ነው
2. አክብሮት. Mutual respect is essential for true friendship. ለእውነተኛ ፡ ጓደኝነት ፡ የጋራ ፡ አክብሮት ፡ ያስፈልጋል
3. ክብር. He commands much respect for his attitude. ለሁኔታው ፡ ብዙ ፡ ክብር ፡ ይሰጠዋል

**respects** ሰላምታ ፤ አክብሮት
My father sends you his respects. አባቴ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቦውልሃል
He paid his respects to the host. አክብሮቱን ፡ ለባለቤቶቹ ፡ ገለጠ

**command respect** ተከበረ
The general commands respect. ጄኔራሉ ፡ የተከበረ ፡ ነው

**have respect for**
She had respect for our feelings. ለስሜታችን ፡ ትጠነቀቃለች

**hold (someone) in respect** አከበረ
The community held him in respect. ኅብረ ፡ ሰቡ ፡ አከበረው

**in every respect** በማንኛውም ፡ ረገድ
He is my equal in every respect. በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ እኩያዬ ፡ ነው

**in many respects** በብዙ ፡ መንገድ
In many respects, I agree with you. በብዙ ፡ መንገድ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ እስማማለሁ

**in some respects** ባንዳንድ ፡ ነገሮች
They resemble each other in some respects. ባንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ ይመሳሰላሉ

**in this respect** እዚያ ፡ ላይ
In this respect, he is wrong. እዚያ ፡ ላይ ፡ ተሳስቷል

**show respect to**
1. አከበረ. Children should show respect to those who are older. ልጆች ፡ ታላቆቻቸውን ፡ ማክበር ፡ አለባቸው
2. በጥንቃቄ ፡ ያዘ. We should show respect to school buildings and public libraries. የትምህርት ፡ ቤት ፡ ሕንጻዎችንና ፡ የሕዝብ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቶችን ፡ በጥንቃቄ ፡ መያዝ ፡ አለብን

**win the respect of** ፍቅር ፡ አገኘ
He won the respect of the community. የኅብረ ፡ ሰቡን ፡ ፍቅር ፡ አገኘ

**with respect to** በ --- ላይ ፤ ለ
With respect to this problem, may I suggest further discussion. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በተጨማሪ ፡ እንድንወያይበት ፡ ሐሳብ ፡ አቀርባለሁ
We must plan with respect to the future. ለወደፊቱ ፡ ማሰብ ፡ አለብን

**respectability** መልካም ፡ ስም
His respectability was most important to him. ለሱ ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ ስሙ ፡ ነበር

**respectable**
1. የተከበረ. These are respectable people. እነዚህ ፡ የተከበሩ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው
2. መልካም. Respectable citizens obey the law. መልካም ፡ ዜጎች ፡ ሕግን ፡ ያከብራሉ
3. ተስማሚ. Are these clothes respectable enough for the dinner party? ለራት ፡ ግብዣው ፡ ይህ ፡ ልብስ ፡ ተስማሚ ፡ ነው ?
4. ከፍ ፡ ያለ. He earns a respectable amount of money. ከፍ ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ ያገኛል
5. በቂ. His grades are respectable. የፈተናው ፡ ውጤት ፡ በቂ ፡ ነው
6. ደኅና. This is a respectable score for an amateur player. ለአማተር ፡ ተጫዋች ፡ ውጤቱ ፡ ደኅና ፡ ነው

**respected** (adj.) የተከበረ
He is a respected statesman. የተከበረ ፡ ባለሥልጣን ፡ ነው

**respectful** ትሕትና ፡ የተመላበት
He gave a respectful reply. ትሕትና ፡ የተመላበት ፡ መልስ ፡ ሰጠ

**be respectful toward** አከበረ
The child is not very respectful toward his elders. ልጁ ፡ ታላቆቹን ፡ እምብዛም ፡ አያከብርም

**respectfully** በአክብሮት
You are respectfully requested to attend the celebration. በሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ እንዲገኙ ፡ በአክብሮት ፡ ተጋብዘዋል

**respectfully yours**
I remain respectfully yours. ምንጊዜም ፡ አክባሪዎ

**respecting** ስለ
I know little respecting this plan. ስለዚህ ፡ እቅድ ፡ የማውቀው ፡ ጥቂት ፡ ነው

**respective**
1. እየ. The party ended, and we went to our

respective rooms. ፓርቲው ፡ ሲያልቅ ፡ ወደየ ክፍላችን ፡ ሄድን
The men were given work according to their respective abilities. ሰዎቹ ፡ እንደየችሎታቸው ፡ ሥራ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ነበር
2. (= adv.) በየተራ. I will discuss the respective merits of each candidate. የእያንዳንዱን ፡ ተወዳዳሪ ፡ ችሎታ ፡ በየተራ ፡ እገልጻለሁ

**respectively** እንደ ፡ ቅደም ፡ ተከተላቸው
John, Mary, and Tom are respectively 7, 9, and 10 years old. ጆን ፡ ሜሪና ፡ ቶም ፡ እንደ ፡ ቅደም ፡ ተከተላቸው ፡ ሰባት ፤ ዘጠኝና ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ አላቸው

**respiration** ትንፋሽ
His respiration is irregular due to shock. ከድንጋጤ ፡ የተነሣ ፡ ትንፋሹ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ ይላል

**respiratory** የመተንፈሻ
The lungs are one of the respiratory organs. ሳምባ ፡ ከመተንፈሻ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ ነው

**respite** ፋታ
He worked without respite until the job was done. ሥራውን ፡ እስኪጨርስ ፡ ያለ ፡ ፋታ ፡ ሠራ
**bring a respite from** መለስ ፡ አደረገ
A thick cloud brought a respite from the glare of the sun. ጥቅጥቅ ፡ ያለው ፡ ደመና ፡ የፀሐይዋን ፡ ሐሩር ፡ መለስ ፡ አደረገ

**resplendent** የሚያንጸባርቅ
The resplendent uniform dazzled the eyes of the onlookers. የሚያንጸባርቀው ፡ የደንብ ፡ ልብስ ፡ የተመልካቾቹን ፡ ዓይን ፡ አጭበረበረ
**be resplendent** አሸበረቀ
The queen was resplendent with jewels. ንግሥቲቱ ፡ በዕንቁ ፡ አሸብርቃ ፡ ነበር

**respond** መለሰ
When I greeted him, he responded with a nod. ሰላምታ ፡ ስሰጠው ፡ አንገቱን ፡ በመቀለስ ፡ መለሰልኝ
A child responds to kind treatment by loving his parents. ልጅ ፡ የወላጆቹን ፡ ውለታ ፡ የሚመልሰው ፡ በፍቅር ፡ ነው
**respond to**
*He failed to respond to treatment. ሕክምናው ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ መሻሻልን ፡ አላደረገለትም

**response** መልስ
My letter of application brought no response. ማመልከቻዬ ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ አላገኘም
**in response to** ስለ + verb
I came in response to your call. ስለጠራኸኝ ፡ መጣሁ
**meet with no response** ተሰሚነት ፡ አጣ ፤ ምንም ፡ ፍሬ ፡ አልሰጠም
My appeal to her pity met with no response. እንድታዝንልኝ ፡ መጠየቄ ፡ ተሰሚነት ፡ አጣ ፡ (ምንም ፡ ፍሬ ፡ አልሰጠም)

**responsibility** (responsibilities) ኀላፊነት
Her education is my responsibility. የትምህርቷ ፡ ጉዳይ ፡ የኔ ፡ ኀላፊነት ፡ ነው
**be a responsibility** ኀላፊነትን ፡ ይጠይቃል
A family is a great responsibility. ቤተ ፡ ሰብ ፡ ብዙ ፡ ኀላፊነትን ፡ ይጠይቃል

**responsible**
1. ኀላፊ. He is no longer responsible, because he is so old. በጣም ፡ ስላሸመገለ ፡ ለሚያደርገው ፡ ነገር ፡ ካሁን ፡ ወዲያ ፡ ኀላፊ ፡ አይደለም
2. ተጠያቂ. To a certain extent, he is responsible for the disaster. ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ በከፊል ፡ ተጠያቂ ፡ ነው
3. ታላቅ ፡ ኀላፊነት ፡ ያለበት. Supervising an office is a responsible job. ቢሮ ፡ መቈጣጠር ፡ ታላቅ ፡ ኀላፊነት ፡ ያለበት ፡ ሥራ ፡ ነው
4. ታማኝ. The class chose a responsible pupil to take care of its money. ተማሪዎቹ ፡ ገንዘብ ፡ የሚይዝላቸው ፡ ታማኝ ፡ ልጅ ፡ መረጡ
**be responsible**
1. በኀላፊነት ፡ ተጠየቀ. Insane people are not responsible. እእምሮዋቸው ፡ የታወከ ፡ ሰዎች ፡ በኀላፊነት ፡ አይጠየቁም
2. ምክንያት ፡ ሆነ. His indolence is responsible for his poverty. ለድኽነቱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ስንፍናው ፡ ነው
**hold responsible** በኀላፊነት ፡ ጠየቀ
He holds me responsible for what my wife did. ሚስቴ ፡ ላደረገችው ፡ ነገር ፡ በኀላፊነት ፡ ይጠይቀኛል
**(be) held responsible** ኀላፊ ፡ ነው ፡ ተባለ
He was held responsible for the damage. ለጥፋቱ ፡ ኀላፊ ፡ ነው ፡ ተባለ

**responsive** አድናቂ ፡ የሆነ
Actors appreciate a responsive audience. ተዋንያን ፡ አድናቂ ፡ የሆነ ፡ ተመልካች ፡ ይወዳሉ
*He showed his support by a responsive wink. ደጋፊነቱን ፡ በጥቅሻ ፡ ገለጸ
*He is responsive to kind treatment. ውለታ ፡ መላሽ ፡ ነው

**rest** (vt.)
1. አሳረፈ. He stopped to rest his horse. ፈረሱን ፡ ለማሳረፍ ፡ ቆመ
2. አስደገፈ. He rested the ladder against the wall. መሰላሉን ፡ ግድግዳው ፡ ላይ ፡ አስደገፈው
3. (= passive) ተደገፈ. She rested her elbows on the table. በክርኗ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ተደገፈች
4. ማረ. May God rest his soul! እግዚአብሔር ፡ ነፍሱን ፡ ይማረው
5. መሠረተ. I rest my conclusion on three facts. ውሳኔዬን ፡ በሦስት ፡ መረጃዎች ፡ ላይ ፡ እመሠርታለሁ

**rest** (vi.)
1. አረፈ. Rest awhile! ትንሽ ፡ እረፍ
The remains of the general still rest where they were buried. የጀኔራሉ ፡ ዐጽም ፡ ቀድሞ ፡ ከተቀበረበት ፡ ቦታ ፡ እንዳረፈ ፡ ነው
2. በሰላም ፡ አረፈ. The old man now rests with his forefathers. ሽማግሌው ፡ ሰው ፡ ባባቶቻቸው ፡ ጐን ፡ በሰላም ፡ አርፈዋል
3. ጋደም ፡ አለ. He went upstairs to rest. ጋደም ፡ ለማለት ፡ ወደ ፡ ፎቅ ፡ ወጣ
4. እፎይ ፡ አለ. The shepherd leaned on his staff to rest. እረኛው ፡ ዘንጉ ፡ ላይ ፡ ደገፍ ፡ ብሎ ፡ እፎይ ፡ አለ
5. ቆመ. The matter cannot rest here. ጉዳዩ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ሊቆም ፡ አይችልም
6. ተመሠረተ. His theory rested on new facts. ፅንሰ ፡ ሐሳቡ ፡ ባዲስ ፡ መረጃዎች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው
7. በ - - ላይ ፡ ነው. The whole responsibility rests on him. ኀላፊነቱ ፡ ሁሉ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ነው
8. ተደገፈ. The roof rests on steel beams. ጣሪያው ፡ የተደገፈው ፡ በብረት ፡ አውራጅ ፡ ነው
9. (= tr.) ጣለ. +His eyes rested on me for a moment. ዓይኖቹን ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ጣለ
*A smile rested on the girl's lips. ልጅቷ ፡ ፈገግ ፡ አለች

**rest against** ተደገፈ
The ladder was resting against the wall. መሰላሉ ፡ ግድግዳውን ፡ ተደግፎ ፡ ነበር

**rest with** የ - - - ፈንታ ፡ ነው
It rests with you to decide. መወሰኑ ፡ ያንተ ፡ ፈንታ ፡ ነው

**let rest**
1. እንዲቆይ ፡ አደረገ. Since some of the members got angry, they let the matter rest for the time being. አንዳንዶቹ ፡ አባሎች ፡ ስለተናደዱ ፡ ጉዳዩ ፡ ለጊዜው ፡ እንዲቆይ ፡ አደረጉ
2. አከረመ. We shall let this field rest for a year. ይህንን ፡ መሬት ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ እናከርመዋለን
[See also 'assured']

**rest** (n.)
1. ዕረፍት. I went to the mountains for a rest. ለዕረፍት ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጣሁ
It's amazing what an hour's rest can do for you. ያንድ ፡ ሰዓት ፡ ዕረፍት ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እንደሚጠቅም ፡ ያስደንቃል
2. የቀረ. Eat some now and save the rest! አሁን ፡ ትንሽ ፡ ብላና ፡ የቀረውን ፡ አስቀምጥ
Where are the rest of the boys? የቀሩት ፡ ልጆች ፡ የት ፡ ናቸው ?

**be at rest** ሕመሙ ፡ ታገሠ(ለት)
The injured man is now at rest. የቈሰለው ፡ ሰውዬ ፡ አሁን ፡ ሕመሙ ፡ ታግሦለታል

**be laid to rest** ተቀበረ
He was laid to rest in the church yard. በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ተቀበረ

**bring to rest** አቆመ
The driver brought the car to rest. ነጂው ፡ መኪናውን ፡ አቆመ

**come to rest**
1. አረፈ. The falling rock came to rest near my tent. የወደቀው ፡ ድንጋይ ፡ ድንኳኔ ፡ አጠገብ ፡ አረፈ
2. ቆመ. After the deluge, Noah's ark came to rest on Mt. Ararat. ከጥፋት ፡ ውኃ ፡ በኋላ ፡ የኖኅ ፡ መርከብ ፡ በአራራት ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ቆመች

**not be at rest** ረግቶ ፡ አልቆመም
If a thing is in motion, it is not at rest. አንድ ፡ ነገር ፡ በሚንቀሳቀስበት ፡ ጊዜ ፡ ረግቶ ፡ አልቆመም ፡ ማለት ፡ ነው

**set (someone's) mind at rest** ከሐሳብ ፡ አሳረፈ
He set my mind at rest by telling me he would pay my expenses. ወጪህን ፡ እከፍልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ከሐሳብ ፡ አሳረፈኝ

**take a rest** ዕረፍት ፡ አደረገ
We worked a lot today; let's take a short rest! ዛሬ ፡ ብዙ ፡ ስለሠራን ፡ ትንሽ ፡ ዕረፍት ፡ እናድርግ

**restaurant** ምግብ ፡ ቤት
He ate lunch in the big restaurant. ምሳውን ፡ ከትልቁ ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ በላ

**(be) restful**
1. ዕረፍት ፡ ሰጠ. Sleep is restful. እንቅልፍ ፡ ዕረፍት ፡ ይሰጣል
2. የኅሊና ፡ ዕረፍት ፡ ሰጠ. This music is very

restful. ይህ ፡ ሙዚቃ ፡ የጎሊና ፡ ዕረፍት ፡ የሚሰጥ ፡ ነው

**not be restful** ዕረፍት ፡ ነሣ

Dreamy sleep is not restful. ሕልም ፡ የበዛበት ፡ ሌሊት ፡ ዕረፍት ፡ ይነሣል

**restitution**

1. መመለስ. The restitution of the statue was reported in the press. የሐውልቱ ፡ መመለስ ፡ በጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ተገልጿል

2. ካሳ. As restitution, the aggressor government gave 10 million dollars. አጥቂው ፡ መንግሥት ፡ ዐሥር ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ ካሳ ፡ ከፈለ

3. ምትክ. It is only fair that those who do the damage should make restitution. ብልሽት ፡ ያደረሱ ፡ ምትክ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ያስፈልጋል

**(be) restive** ተቍነጠነጠ

He became restive during the long ceremony. በረጅሙ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጊዜ ፡ ተቍነጠነጠ

**restless** ቁንጥንጥ

The restless child was kicking his feet against the chair. ቁንጥንጡ ፡ ልጅ ፡ ወንበሩን ፡ በእግሩ ፡ ይመታ ፡ ነበር

*The sick child passed a restless night. የታመመው ፡ ልጅ ፡ ሌሊቱን ፡ እንዲሁ ፡ አደረ

**get restless** ተቍነጠነጠ

The audience was getting restless when the actor failed to appear. ተዋናዩ ፡ ብቅ ፡ ባለማለቱ ፡ ተመልካቹ ፡ ሕዝብ ፡ ተቍነጠነጠ

**restoration**

1. እድሳት. The parliament building is closed for restoration. የምክር ፡ ቤቱ ፡ ሕንጻ ፡ ለእድሳት ፡ ተዘግቷል

2. መመለስ. The restoration of independence was a notable event. የነጻነት ፡ መመለስ ፡ የሚታወስ ፡ ዕለት ፡ ነበር

*This antique chair is a good restoration. ይህ ፡ የጥንት ፡ ወንበር ፡ ጥሩ ፡ ሆኖ ፡ እንደነበር ፡ ታድሷል

*His restoration to health was followed by his taking up his old habits again. ጤናው ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ የጥንት ፡ ልማዱን ፡ ጀመረ

*The restoration of stolen property is required by law. የተሰረቁ ፡ ሀብቶች ፡ እንዲመለሱ ፡ ሕግ ፡ ያስገድዳል

[See also 'anniversary']

**restore**

1. መለሰ. He restored the books to the shelf. መጽሐፎቹን ፡ ወደ ፡ መደርደሪያው ፡ መለሰ

2. መለሰ(ለት). A rest soon restored him to health. ዕረፍት ፡ ማድረጉ ፡ ጤንነቱን ፡ ወዲያውኑ ፡ መለሰለት

3. መልሰ ፡ ሰጠ. The honest boy restored the money to its owner. ታማኙ ፡ ልጅ ፡ ገንዘቡን ፡ ለባለቤቱ ፡ መልሶ ፡ ሰጠ

4. እንደነበረ ፡ አደረገ. He restored the original text by careful comparison of all extant copies. አሁን ፡ ያሉትን ፡ መጽሐፎች ፡ በጥንቃቄ ፡ በማወዳደር ፡ የመጀመሪያውን ፡ ጽሑፍ ፡ እንደነበረ ፡ አደረገ

**be restored**

1. ታደሰ. The building was restored to its original condition. ሕንጻው ፡ ታድሶ ፡ እንደነበረ ፡ ሆነ

2. ወደ ፡ ድሮው ፡ ሁኔታ ፡ ተመለሰ. Law and order have been restored in the riot–torn city of Chicago. በብጥብጥ ፡ በተሸበረው ፡ ቺካጎ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ ወደ ፡ ድሮው ፡ ሁኔታ ፡ ተመለሰ

3. የነበረ --- ተመለሰ. Discipline will not be restored unless you put your foot down. ጥርሳችሁን ፡ ነክሳችሁ ፡ ካልሠራችሁ ፡ የነበረው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አይመለስም

[See also 'order']

**restrain**

1. ገታ. He restrained his anger with difficulty. ንዴቱን ፡ በግድ ፡ ገታው

2. ያዘ. He restrained the dog when guests came. እንግዶቹ ፡ ሲመጡ ፡ ውሻውን ፡ ያዘ

**restraint** ጥብቅ ፡ ቁጥጥር

The child was kept under restraint as long as he was in our house. ልጁ ፡ እቤታችን ፡ ውስጥ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በጥብቅ ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነበር

**with restraint** ተቈጥቦ

He was very angry, but he spoke with restraint. በጣም ፡ ተናዶ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ተቈጥቦ ፡ ነው ፡ የተናገረው

**without restraint**

He acts without restraint. ያሰኘውን ፡ ያደርጋል

**restrict** ወሰነ (ተወሰነ)

The law restricts our freedom to do as we please. ደስ ፡ ያለንን ፡ ሁሉ ፡ እንዳናደርግ ፡ ሕጉ ፡ የነጻነታችንን ፡ ልክ ፡ ይወስናል

This area is restricted to authorized personnel. ይህ ፡ ቦታ ፡ ለተፈቀደላቸው ፡ ሠራተኞች ፡ ብቻ ፡ ተወስኗል

*The trees restrict our view of the city. ዛፎቹ ፡ ከተማውን ፡ ሙሉ ፡ ለሙሉ ፡ እንዳናይ ፡ ጋርደውናል

**restriction**
1. ገደብ. The governor ordained that the restrictions be lifted. አገረ ፡ ገገርው ፡ ገደቦቹ ፡ እንዲነሡ ፡ አዘዘ
2. ቁጥጥር. He resents all restrictions. ማንኛቸውንም ፡ ዓይነት ፡ ቁጥጥር ፡ ይጠላል
*The restriction on smoking applies to you. ማጨስ ፡ ክልክል ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ሕግ ፡ አንተንም ፡ ይመለከታል

**without restriction** እንደልብ
We are permitted to use the library without restriction. ቤተ ፡ መጻሕፍቱን ፡ እንደልባችን ፡ እንድንገለገልበት ፡ ተፈቅዶልናል

**restroom** ሽንት ፡ ቤት
Where is the men's restroom? የወንዶች ፡ ሽንት ፡ ቤት ፡ የት ፡ ነው ?

**result** (v.)
1. ምክንያት ፡ ሆነ. The partition of India resulted in two countries. የህንድ ፡ መከፋፈል ፡ ለሁለት ፡ አዲስ ፡ አገሮች ፡ መፈጠር ፡ ምክንያት ፡ ሆነ
2. መጣ. Floods may result from heavy rains. የውኃ ፡ መጥለቅለቅ ፡ ከኀይለኛ ፡ ዝናብ ፡ ሊመጣ ፡ ይችላል
Any damage resulting from negligence will be paid for by you. ከቸልተኝነት ፡ የሚመጣውን ፡ ማንኛውንም ፡ ጥፋት ፡ የምትከፍል ፡ አንተ ፡ ነህ

**result in**
1. አስከተለ. Their inept diplomacy resulted in war. የዲፕሎማሲ ፡ ዘዴ ፡ አለማወቃቸው ፡ ጦርነትን ፡ አስከተለ
2. ከ - - አደረሰ. The chasm between England and the American colonies resulted in the Revolutionary War. በእንግሊዝና ፡ በአሜሪካን ፡ ቅኝ ፡ ግዛቶች ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ የሐሳብ ፡ ልዩነት ፡ ከጦርነት ፡ አደረሳቸው
3. አስገኘ. Your efforts will result in success. ጥረትህ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ያስገኝልሃል

**result** (n.) ውጤት
The results were very satisfactory. ውጤቱ ፡ በጣም ፡ አጥጋቢ ፡ ነበር
*The immediate result of the rain was a drop in temperature. ዝናብ ፡ ወዲያውኑ ፡ ያስከተለው ፡ ያየሩ ፡ መቀዝቀዝ ፡ ነበረ

**as a result of** በ - - - ምክንያት
The dynasty came to an end as a result of the war. ሥርወ ፡ መንግሥቱ ፡ በጦርነቱ ፡ ምክንያት ፡ አበቃ

**give good results** ውጤቱ ፡ አማረ
Conscientious work gives good results. በጥንቃቄ ፡ የተሠራ ፡ ሥራ ፡ ውጤቱ ፡ ያምራል
[See also 'negative']

**resume** (vt.)
1. ቀጠለ. They resumed their journey the next day. ጉዟቸውን ፡ በማግሥቱ ፡ ቀጠሉ
Resume reading where we left off! ካቆምንበት ፡ ጀምረህ ፡ ንባቡን ፡ ቀጥል
2. እንደገና ፡ ያዘ. After the lunch period, the delegates resumed their places. ከምሳ ፡ በኋላ ፡ መልእክተኞቹ ፡ እንደገና ፡ ስፍራ ፡ ስፍራቸውን ፡ ያዙ

**resume** (vi.) እንደገና ፡ ተጀመረ
Talks will resume next Wednesday. የሚመጣው ፡ ረቡዕ ፡ ንግግሩ ፡ እንደገና ፡ ይጀመራል

**resumé, give a ~** ባጭሩ ፡ ነገረ
Give me a resumé of this book! የዚህን ፡ መጽሐፍ ፡ ታሪክ ፡ ባጭሩ ፡ ንገረኝ

**resumption**
*The resumption of flights to Africa was announced. ተቋርጦ ፡ የነበረው ፡ ወደ ፡ አፍሪካ ፡ የሚደረገው ፡ በረራ ፡ እንደገና ፡ መጀመሩ ፡ ተነገረ

**resurgence, be a ~** አንሰራራ
After the war, there was a resurgence of business activity. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ የንግድ ፡ እንቅስቃሴ ፡ አንሰራራ

**resurgent**
*Resurgent nationalism is causing problems in several countries. አዲስ ፡ የብሔራዊ ፡ ስሜት ፡ እንቅስቃሴ ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ ፈጥሯል

**resurrect**
1. አዳነ. The healer resurrects the dead, some people say. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ መድኀኒተኛው ፡ የሞተ ፡ ያድናል ፡ ይላሉ
2. እንደገና ፡ ሠራ(በት). They resurrected an old plan in dealing with this problem. ለዚህ ፡ ችግር ፡ መፍትሔ ፡ ለማግኘት ፡ የቆየውን ፡ እቅድ ፡ እንደገና ፡ ሠሩበት

**be resurrected** ተነሣ
Jesus was resurrected from the tomb. ኢየሱስ ፡ ከመቃብር ፡ ተነሣ

**Resurrection** የትንሣኤ ፡ በዓል
We shall celebrate the Resurrection at home. የትንሣኤን ፡ በዓል ፡ እቤት ፡ እናከብራለን

**resuscitate** ትንፋሽ ፡ መለሰ
He tried to resuscitate the drowned child. ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ሰጥሞ ፡ ለነበረው ፡ ልጅ ፡ ትንፋሽ ፡ ለመመለስ ፡ ሞከረ

**retail** (vt.)
1. ቸረቸረ. The woman retails coffee. ሴትዮዋ ፡ ቡና ፡ ትቸረችራለች

2. በችርቻሮ ፡ ሸጠ. My father retails shoes. አባቴ ፡ ጫማ ፡ በችርቻሮ ፡ ይሸጣል

**retail** (vi.)

*This article retails at $1.50. ይህ ፡ እቃ ፡ ሱቅ ፡ ባንድ ፡ ብር ፡ ከኀምሳ ፡ ይሸጣል

**retail** (n.) ችርቻሮ

He sells wholesale and retail. በጅምላም ፡ በችርቻሮም ፡ ይሸጣል

**retail dealer** ቸርቻሪ

Retail dealers have to pay a tax. ቸርቻሪዎች ፡ ቀረጥ ፡ መክፈል ፡ አለባቸው

**retail merchant** ቸርቻሪ

Small retail merchants must buy a license. አነስተኛ ፡ ቸርቻሪዎች ፡ የንግድ ፡ ፈቃድ ፡ ማውጣት ፡ አለባቸው

**retail price**

*What's the retail price of this article? ይህ ፡ እቃ ፡ ሱቅ ፡ ስንት ፡ ያወጣል ?

**retailer** ቸርቻሪ

The retailer of such merchandise must have a license. የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሸቀጣ ፡ ሸቀጥ ፡ ቸርቻሪ ፡ የንግድ ፡ ፈቃድ ፡ እንዲኖረው ፡ ያሻል

**retain**

1. ያዘ. This pot won't retain water. ይህ ፡ ማሰሮ ፡ ውኃ ፡ አይዝም

2. ገዛ. He retained a good lawyer to defend him. እንዲከራከርለት ፡ ጥሩ ፡ ጠበቃ ፡ ገዛ

3. ከመናድ ፡ ተከላከለ. We built a wall to retain the earth behind our house. ከቤታችን ፡ ኋላ ፡ ያለውን ፡ አፈር ፡ ከመናድ ፡ ለመከላከል ፡ ግንብ ፡ ገነባን

4. አስታወሰ. She retained the tune but not the words of the song. ግጥሙን ፡ አልያዘችውም ፤ የምታስታውሰው ፡ ዜማውን ፡ ብቻ ፡ ነው

*Some stones retain heat for a long time. አንዳንድ ፡ ድንጋዮች ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደጋሉ ፡ ይቆያሉ

*The old lady has retained her interest in reading. አሮጊቷ ፡ አሁንም ፡ ማንበብ ፡ ትወዳለች [See also 'memory']

**retainer**

1. አገልጋይ. The king's faithful retainer has been with him for 30 years. የንጉሡ ፡ ታማኝ ፡ አገልጋይ ፡ ለሠላሳ ፡ ዓመታት ፡ አብሮት ፡ ኖሯል

2. የቅድሚያ ፡ ክፍያ. The lawyer receives a retainer before he begins work on a case. ነገሩን ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ጠበቃ ፡ የቅድሚያ ፡ ክፍያ ፡ ይቀበላል

**retaining** ደጋፊ

The retaining wall collapsed. ደጋፊው ፡ ግድግዳ ፡ ተደረመሰ

**retaliate**

1. ዐጸፋ ፡ እርምጃ ፡ ወሰደ(በት). If we raise our duties, the neighboring countries may retaliate against us. ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ በሚገቡ ፡ እቃዎች ፡ ላይ ፡ ቀረጥ ፡ ብንጨምር ፡ ጎረቤት ፡ አገሮቹ ፡ ዐጸፋ ፡ እርምጃ ፡ ይወስዱብን ፡ ይሆናል

2. ዐጸፋውን ፡ መለሰ. We will retaliate for any attack made on us. ለሚደረግብን ፡ ጥቃት ፡ ሁሉ ፡ ዐጸፋውን ፡ እንመልሳለን

3. ብድሩን ፡ መለሰ. She is vindictive, and will retaliate if you offend her in any way. ቂመኛ ፡ ስለሆነች ፡ ከነካሃት ፡ ብድሯን ፡ ትመልሳለች

**retaliation** ዐጸፋ

The raid was in retaliation for the bombing. ወረራው ፡ ለተደረገው ፡ የቦምብ ፡ ድብደባ ፡ ዐጸፋ ፡ ነበር

**retard**

1. ወደ ፡ ኋላ ፡ ጎተተ. Quarrels retarded the progress of the job. ጭቅጭቅ ፡ የሥራውን ፡ እርምጃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ጎተተው

2. አዘገየ. Heavy rain retarded our progress in the trip. ከባድ ፡ ዝናም ፡ የጉዟችንን ፡ እርምጃ ፡ አዘገየ

**retard growth** አቀጨጨ

Poor food retards growth. አጉል ፡ ምግብ ፡ ያቀጨጫል

**retarded, be mentally ~**

This child is mentally retarded. ይህ ፡ ልጅ ፡ አእምሮው ፡ ከዕድሜው ፡ ጋር ፡ ያልበሰለ ፡ ነው

**retch** አስመለሰ(ው)

⁺The child drank soapy water and retched on the floor. ሕፃኑ ፡ ሳሙና ፡ ያለው ፡ ውኃ ፡ ስለጠጣ ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ አስመለሰው

**retell** (retold) መልሶ ፡ አወራ

He retells the same story every time we see him. ባገኘነው ፡ ቁጥር ፡ ያንኑ ፡ ታሪክ ፡ መልሶ ፡ ያወራል

**retentive, ~ memory** የማስታወስ ፡ ችሎታ

He has a very retentive memory. የማስታወስ ፡ ችሎታው ፡ ግሩም ፡ ነው

**reticent** ዝምተኛ

He is so reticent that you cannot find out anything from him. ዝምተኛ ፡ ስለሆነ ፡ ሐሳቡን ፡ ፈጽሞ ፡ ለማወቅ ፡ አይቻልም

**retinue** የክብር ፡ ተከታዮች
The ambassador's retinue will be housed in our hotel. የአምባሳደሩ ፡ የክብር ፡ ተከታዮች ፡ ሆቴላችን ፡ ውስጥ ፡ ያርፋሉ

**retire** (vt.)
1. ጡረታ ፡ አስገባ. The army retired all overage officers. የጦር ፡ ሰራዊት ፡ በዕድሜያቸው ፡ የገፉትን ፡ መኰንኖች ፡ ሁሉ ፡ ጡረታ ፡ አስገባ
2. አስወገደ. The government retires torn bills from use. መንግሥት ፡ የተቀዳደደ ፡ ብር ፡ እንዳይሠራበት ፡ ያስወግዳል

**retire** (vi.)
1. ጡረታ ፡ ገባ. Civil servants retire at sixty-five. የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በስድሳ ፡ አምስት ፡ ዓመታቸው ፡ ጡረታ ፡ ይገባሉ
2. ሥራውን ፡ አቆመ. He sold out his share and retired. ድርሻውን ፡ ከሸጠ ፡ በኋላ ፡ ሥራውን ፡ አቆመ
3. ተኛ. In winter, we retire early. በክረምት ፡ የምንተኛው ፡ በጊዜ ፡ ነው
4. ገባ. He retired to the library after dinner. እራቱን ፡ ከበላ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ማንበቢያ ፡ ክፍሉ ፡ ገባ
She retired to a convent. ገዳም ፡ ገባች
5. ተመለሰ. Our forces have retired to previously prepared positions. ወታደሮቻችን ፡ አስቀድመው ፡ ወደ ፡ አዘጋጁት ፡ ምሽጋቸው ፡ ተመለሱ
6. ሄደ. He has retired to the country for a rest. ለዕረፍት ፡ ወደ ፡ ገጠር ፡ ሄደ
*These goods have been retired from the market. እነዚህ ፡ እቃዎች ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ከመውጣት ፡ ቀርተዋል

**retire for the night** ተኛ
He retired to his bedroom for the night. መኝታ ፡ ክፍሉ ፡ ገብቶ ፡ ተኛ

**retire from**
1. ተወ. He has retired from government office. የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ትቷል
2. ናቀ. She retired from the world to enter a convent. ዓለምን ፡ ንቃ ፡ ገዳም ፡ ገባች

**retired** (adj.)
1. ጡረታ ፡ የወጣ. He is a retired civil servant. ጡረታ ፡ የወጣ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ነው
2. ሥራውን ፡ ያቆመ. He is a retired doctor. ሥራውን ፡ ያቆመ ፡ ዶክተር ፡ ነው

**retired life** ገለልተኝነት
He lives a retired life in a small village. በትንሽ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ በገለልተኝነት ፡ ይኖራል

**retirement**
1. ጡረታ. He reached the age of retirement. ዕድሜው ፡ ለጡረታ ፡ ደረሰ
2. ገለለ ፡ ያለ ፡ ስፍራ. He lives in retirement. ገለል ፡ ባለ ፡ ስፍራ ፡ ይኖራል
*There have been several retirements in my office. ከመሥሪያ ፡ ቤቴ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ለጡረታ ፡ ተመድበዋል

**retiring** ዓይን ፡ አፋር ፤ ዝምተኛ
She is very retiring; it's hard to talk to her. ዓይን ፡ አፋር ፡ (ዝምተኛ) ፡ ስለሆነች ፡ እሷን ፡ ማነጋገር ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**retold**, see **retell**

**retort**
1. መለሰ. He retorts insult for insult. ለስድብ ፡ ስድብ ፡ ይመልሳል
2. በንዴት ፡ መለሰ. She retorted that it was entirely his fault. ያንተ ፡ ጥፋት ፡ ነው ፡ ስትል ፡ በንዴት ፡ መለሰችለት

**retrace**
1. እንደገና ፡ ነደፈ. He carefully retraced the map. ካርታውን ፡ በጥንቃቄ ፡ እንደገና ፡ ነደፈ
2. ቈጠረ. I was able to retrace my family line. የቤተሰቤን ፡ የዘር ፡ አወራረድ ፡ ለመቍጠር ፡ ቻልኩ

**retrace one's steps** በመጣበት ፡ መንገድ ፡ ተመለሰ
He retraced his steps, but did not find his wallet. በመጣበት ፡ መንገድ ፡ ተመልሶ ፡ ቢፈልግም ፡ ቦርሳውን ፡ አላገኘም

**retract**
1. ዐጠፈ. He retracted the statement that he made yesterday. ትናንትና ፡ የተናገረውን ፡ ዐጠፈ
2. ሰበሰበ. The plane retracted its wheels after take-off. አውሮፕላኑ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ጎማውን ፡ ሰበሰበ

**retraction** ሐሳቡን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ማለት
His retraction indicates a change in attitude. ሐሳቡን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ማለቱ ፡ የሁኔታውን ፡ መለወጥ ፡ ያመለክታል

**retread** አሳደሰ
Is it worthwhile retreading the tire? ጎማውን ፡ ማሳደስ ፡ ይጠቅማል ?

**retreat** (v.)
1. ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈገ. The troops retreated. ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈጉ
2. ለዕረፍት ፡ ሄደ. He retreats to the country every year. በያመቱ ፡ ለዕረፍት ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ቤት ፡ ይሄዳል

**retreat** (n.)
1. የወታደሮች ፡ ማፈግፈግ ፤ ማፈግፈግ. The retreat was disorderly. የወታደሮቹ ፡ ማፈግፈግ ፡ ቅጥ ፡ ያጣ ፡ ነበር
The enemy's retreat turned into a rout. የጠላት ፡ ማፈግፈግ ፡ ቅጥ ፡ የሌለው ፡ ሽሽት ፡ ሆነ
2. የማምለጫ ፡ ቦታ. The library was his retreat from the noise of the children. ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ከልጆች ፡ ጫጫታ ፡ የማምለጫ ፡ ቦታው ፡ ነበር

**be in retreat** ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈገ
The enemy was in retreat. ጠላት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈገ

**beat a hasty retreat** ተፈተለከ
He beat a hasty retreat when he saw the police coming. ፖሊስ ፡ ሲመጣ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ተፈተለከ

**beat a retreat** አፈገፈገ
The army beat a retreat after the battle. ከውጊያው ፡ በኋላ ፡ ጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ አፈገፈገ

**go into retreat** ሱባዔ ፡ ገባ
Pious people like to go into retreat for at least a week once a year. ሃይማኖተኛ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ሱባዔ ፡ ይገባሉ

**sound retreat**
The trumpets sounded retreat. ጡሩምባው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈግፍጉ ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ አሰማ

**retrench** (vt.) ወሰደ(በት)
The government may retrench rights granted to a company if it violates a contract. ኩባንያው ፡ ውሉን ፡ ከጣሰ ፡ መንግሥት ፡ የሰጠውን ፡ መብት ፡ ይወስድበታል

**retrench** (vi.) ወጪ ፡ ቀነሰ
We must retrench this year if we are to have enough money for a vacation next year. በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲኖረን ፡ ከፈለግን ፡ ዘንድሮ ፡ ወጪያችንን ፡ መቀነስ ፡ አለብን

**retribution**
*Retribution for wrongs done to one is not a good policy. ክፉን ፡ በክፉ ፡ መበቀል ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**in retribution** ዐጸፋውን
He insulted her in retribution for her rudeness. ለብልግናዋ ፡ ዐጸፋውን ፡ ሰደባት

**retrieve**
1. ፈልጎ ፡ አመጣ. A hunter can train a dog to retrieve birds that he has killed. አንድ ፡ አዳኝ ፡ የገደላቸውን ፡ አዕዋፍ ፡ ፈልጎ ፡ ለማምጣት ፡ የሚችል ፡ ውሻ ፡ ማሠልጠን ፡ ይችላል
2. አገኘ. I retrieved the lost pocketbook. የጠፋብኝን ፡ የኪስ ፡ ደብተሬን ፡ አገኘሁት
3. አረመ. A person can retrieve a mistake. ማንም ፡ ሰው ፡ ስሕተቱን ፡ ሊያርም ፡ ይችላል

**(be) retroactive** ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ሠራ
The new law is not retroactive. አዲሱ ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ አይሠራም
*Your new salary will be retroactive to last month. አዲሱ ፡ ደሞዝህ ፡ ካለፈው ፡ ወር ፡ ጀምሮ ፡ ይታሰባል

**retrograde** የኋሊዮሽ
The retrograde motion of certain planets convinced Galileo that the sun was the center of our galaxy. ያንዳንድ ፡ ከዋክብት ፡ የኋሊዮሽ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ፀሐይ ፡ የከዋክብቶቻችን ፡ እምብርት ፡ መሆኗን ፡ ጋሊሊዮን ፡ አሳመነው

**retrogress**
1. ተመለሰ. He retrogressed to infantilism. ወደ ፡ ሕፃንነት ፡ ተመለሰ
2. እየባሰ ፡ ሄደ. His condition has retrogressed these last three days. ሁኔታው ፡ ባለፉት ፡ ሦስት ፡ ቀኖች ፡ እየባሰ ፡ ሄደ

**retrospect, in ~** መለስ ፡ ብሎ ፡ ሲያስበው
In retrospect, I realize I was wrong at that time. መለስ ፡ ብዬ ፡ ሳስበው ፡ ያኔ ፡ መሳሳቴን ፡ ተረድቻለሁ

**return** (vt.)
1. መለሰ. Don't forget to return the book! መጽሐፉን ፡ መመለስ ፡ እንዳትረሳ
"Never mind", he returned, "I will do it myself". ግድ ፡ የለም ፤ እኔ ፡ ራሴ ፡ እሠራዋለሁ ፡ ሲል ፡ መለሰ
He never returns a favor. ፈጽሞ ፡ ውለታ ፡ አይመልስም
2. ዐጸፋውን ፡ መለሰ. They returned the enemy's fire. ለጠላት ፡ ተኩስ ፡ ዐጸፋውን ፡ መለሱ
*I returned his call. መልሼ ፡ ደወልኩለት

**return** (vi.) ተመለሰ
When did you return? መቼ ፡ ተመለስክ ?
I have returned to my original idea. ወደ ፡ ቀድሞው ፡ ሐሳቤ ፡ ተመልሻለሁ

**return a verdict** ፈረደ
The judges returned a verdict of guilty. ዳኞች ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ፈረዱ

**never return** እንደወጣ ፡ ቀረ
On his trip in the desert, he met with misfortune and never returned. በበረሃው ፡ ሲጓ

ዝ ፡ ባጋጠመው ፡ መጥፎ ፡ ዕድል ፡ ምክንያት ፡ እ
ንደወጣ ፡ ቀረ

**return** (n.)

1. መመለስ. The Emperor's return was announced in the papers. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መ
መለስ ፡ በጋዜጦች ፡ ተገለጸ
2. ትርፍ. He gets a good return on the money he invested in stocks. በአክሲዮን ፡ ላይ ፡ ካዋለ
ው ፡ ገንዘብ ፡ ጥሩ ፡ ትርፍ ፡ ያገኛል

**returns** ውጤት ፤ የምርጫ ፡ ውጤት
The election returns will be published tomorrow. የምርጫው ፡ ውጤት ፡ ነገ ፡ ይታተማል
Despite the unfavorable returns, the candidate clung to the belief that he would be elected. ምንም ፡ እንኳ ፡ የገባው ፡ የምርጫ ፡ ውጤት ፡ የማ
ይደግፈው ፡ ቢሆንም ፡ ተወዳዳሪው ፡ እመረጣለሁ ፡
በሚል ፡ እምነት ፡ ጸና

**in return**
1. ልዋጭ. In return for this book, I will give you a camera. ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ልዋጭ ፡ አንድ ፡ ፎ
ቶግራፍ ፡ ማንሻ ፡ እሰጥሃለሁ
2. በዐጸፋው. I bowed my head to her, and she bowed hers in return. እጅ ፡ ስነሣት ፡ እሷም ፡
በዐጸፋው ፡ መለሰችልኝ

**on his return** ሲመለስ
I found many things changed on my return. ስመለስ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ተለውጦ ፡ አገኘሁ

**the point of no return** ወደ ፡ ኋላ ፡ መመለስ ፡
የማይችልበት ፡ ቦታ
The plane has reached the point of no return. አውሮፕላኑ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መመለስ ፡ የማይችልበ
ት ፡ ቦታ ፡ ደረሰ

**return** (adj.), ~ **ticket** የመመለሻ ፡ ቲኬት
I did not use my return ticket. የመመለሻ ፡ ቲኬ
ቴን ፡ አልሠራሁበትም

**by return mail**
Please answer by return mail! እንደደረሰህ ፡ ወዲ
ያው ፡ መልሱን ፡ጻፍልኝ

**reunify** (reunified) መልሶ ፡ አዋሐደ
The President reunified the country after the civil war. ከእርስ ፡ በእርስ ፡ ጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ፕሬ
ዚዳንቱ ፡ አገሪቱን ፡ መልሶ ፡ አዋሐደ

**reunion**

1. አንድ ፡ ላይ ፡ መገኘት. The family reunion was a happy occasion. የቤተ ፡ ሰቡ ፡ ሁሉ ፡
አንድ ፡ ላይ ፡ መገኘት ፡ የሚያስደስት ፡ ጊዜ ፡ ነበር
2. አንድ ፡ ላይ ፡ የተመረቁ ፡ ተማሪዎች ፡ ስብሰባ. The school reunion was attended by 150 people. አንድ ፡ ላይ ፡ በተመረቁት ፡ ተማሪዎች ፡ ስብሰ
ባ ፡ ላይ ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ተገኝ
ተው ፡ ነበር

**reunite** (vt.)

1. አንድ ፡ አደረገ. The Nigerian government reunited Nigeria and Biafra. የናይጄሪያ ፡ መ
ንግሥት ፡ ናይጄሪያንና ፡ ቢያፍራን ፡ አንድ ፡ አደረገ
2. አገናኘ. The wedding reunited all the members of the family. ሰርጉ ፡ ቤተ ፡ ዘመዱን ፡
ሁሉ ፡ አገናኘ

**be reunited**
1. ተዋሐደ. Eritrea was reunited with Ethiopia in 1952. ኤርትራ ፡ በ፲፱፻፵፭ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡
ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ ተዋሐደች
2. እንደገና ፡ ተዋሐዱ. The former enemies were reunited by a treaty. የቀድሞዎቹ ፡ ጠላቶች ፡ በስ
ምምነት ፡ ውል ፡ እንደገና ፡ ተዋሐዱ
3. እንደገና ፡ ተገናኙ. Mother and child were reunited after years of separation. እናትና ፡ ልጁ ፡
ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ከተለያዩ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡
ተገናኙ

**revalue** አዲስ ፡ ዋጋ ፡ ሰጠ
De Gaulle revalued the old French currency. ደጎል ፡ የፈረንሳይን ፡ የጥንት ፡ ገንዘብ ፡ አዲስ ፡
ዋጋ ፡ ሰጠው

**reveal**

1. ገለጸ. He revealed that he is going to write a book. መጽሐፍ ፡ እንደሚጽፍ ፡ ገለጸ
2. አወጣ. The reporter was jailed for revealing state secrets. የመንግሥት ፡ ምስጢር ፡ በማውጣ
ቱ ፡ ጋዜጠኛው ፡ ታሰረ
3. አሳየ. She took off her hat revealing her golden hair. ባርኔጣዋን ፡ አንሥታ ፡ ወርቃማ ፡
ጸጉሯን ፡ አሳየች
4. (= passive) ታየ. +The clouds parted revealing the sun. ደመናው ፡ ገፎ ፡ ፀሐይዋ ፡ ታየች

**be revealed** ሊደረስበት ፡ ተቻለ
A person's inward nature is not easily revealed. የሰው ፡ ውስጣዊ ፡ ባሕሪይ ፡ በቀላሉ ፡ ሊደረስ
በት ፡ አይቻልም

**revel** ፈነጠዘ
The students reveled until dawn. ተማሪዎቹ ፡ እ
ስከ ፡ ንጋቱ ፡ ድረስ ፡ ፈነጠዙ

**revel in** ወደደ
He revels in gossip of all kinds. ወሬ ፡ ሲባል ፡
ይወዳል

**revelation**

1. ራእይ. Saint Paul received a revelation on his way to Damascus. ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወደ ፡
ደማስቆስ ፡ ሲሄድ ፡ ራእይ ፡ ታየው

2. ያልታሰበ ፡ ነገር. It was a revelation to John when Mary told him she had only married him for his money. ሜሪ ፡ ዮሐንስን ፡ ያገባችው ፡ ለገንዘቡ ፡ ስትል ፡ መሆኑን ፡ ስትነግረው ፡ ያልታሰበ ፡ ነገር ፡ ሆነበት
3. (= to reveal) ማውጣት. His revelation of the secret was quite a surprise. ምስጢሩን ፡ ማውጣቱ ፡ የሚያስገርም ፡ ነበር
*The revelation of the thieves' hiding place was due to the treachery of one of their members. የሌቦቹ ፡ መደበቂያ ፡ የታወቀው ፡ አንዱ ፡ ባልደረባቸው ፡ ባደረገው ፡ ስብቀት ፡ ነው

**be a revelation** አስደነቀ
Her skill as a cook is a revelation to me. የምግብ ፡ ሥራ ፡ ሙያዋ ፡ ያስደንቀኛል

**revelry** ፈንጠዝያ
The students' revelry made so much noise that no one could sleep. የተማሪዎቹ ፡ ፈንጠዝያ ፡ ብዙ ፡ ጫጫታ ፡ ስለፈጠረ ፡ ማንም ፡ ሊተኛ ፡ አልቻለም

**revenge** (v.) ተበቀለ
He revenged his friend's death. የጓደኛውን ፡ ሞት ፡ ተበቀለ

**revenge** (n.) በቀል
Revenge does not restore things to what they were. በቀል ፡ የሆነውን ፡ እንደነበረ ፡ አይመልሰውም

**take revenge on** ተበቀለ
He took revenge on his sister's murderer. የእኅቱን ፡ ገዳይ ፡ ተበቀለ

**revengeful** የበቀል
His revengeful actions kept the quarrel alive for years. የበቀል ፡ ተግባሩ ፡ ጠባቸውን ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ አቆይቷል

**revenue** ገቢ
The revenue from the cigarette tax is very high. ከሲጃራ ፡ ቀረጥ ፡ የሚገኘው ፡ ገቢ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው

**reverberate** አስተጋባ
The roar of the cannon reverberated among the hills. የመድፉ ፡ ጩኸት ፡ በኰረብታዎቹ ፡ መካከል ፡ አስተጋባ

**revere** በጣም ፡ አከበረ
He reveres his parents. ወላጆቹን ፡ በጣም ፡ ያከብራል

**reverence** (v.) አከበረ
He reverences his country's tradition. ያገሩን ፡ ባህል ፡ ያከብራል

**reverence,** n. (= to revere) ማክበር
Reverence for elders is an Ethiopian tradition. ሽማግሌዎችን ፡ ማክበር ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ባህል ፡ ነው

**hold in reverence** አከበረ
He holds the clergy in reverence. ካህናትን ፡ ያከብራል

**show reverence for** አከበረ
He shows no reverence for holy relics. ቅዱሳን ፡ ቅርሶችን ፡ አያከብርም

**reverend** አባ
I will speak to the reverend about it. ስለሱ ፡ ከአባ ፡ ጋር ፡ እነጋገራለሁ

**Reverend** የተከበሩ ፡ ቄስ
The Reverend Thomas Johnson will visit us today. የተከበሩ ፡ ቄስ ፡ ቶማስ ፡ ጆንሰን ፡ ዛሬ ፡ ይጐበኙናል

**reverent** ሰው ፡ አክባሪ
He is very reverent and never fails to bow to people. እጅግ ፡ ሰው ፡ አክባሪ ፡ ስለሆነ ፡ ማንንም ፡ እጅ ፡ ሳይነሣ ፡ አያልፍም

**reverie** ሐሳብ
She was so lost in reverie that she did not hear the bell. እጅግ ፡ በሐሳብ ፡ ተውጣ ፡ ስለነበር ፡ ደወሉን ፡ አልሰማችም

**indulge in reveries** አለመ
He loves to indulge in reveries about the future. ስለ ፡ መጪው ፡ ማለም ፡ ይወዳል

**reverse** (v.)
1. በተቃራኒው ፡ ለወጠ. The government has reversed its policy on immigration. መንግሥቱ ፡ ስለ ፡ ስደተኞች ፡ የነበረውን ፡ አመራር ፡ በተቃራኒው ፡ ለወጠ
2. ሻረ. The Supreme Court reversed the lower court's decision. ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የበታቹን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ሻረ
3. ወደዚያ ፡ አዞረ. Reverse that gun; don't point it at me. ያን ፡ ጠመንጃ ፡ ወደዚያ ፡ አዙረው ፤ ወደኔ ፡ አትደግን

**reverse** (n.)
1. ተቃራኒ. He said "yes", but meant just the reverse. አዎን ፡ ቢልም ፡ ያሰበው ፡ ተቃራኒውን ፡ ነበር
2. ጀርባ. On the reverse of the coin, the denomination is stamped. በፍራንኩ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ዋጋው ፡ ታትሟል
3. ጉዳት. Our forces have suffered a slight reverse. ወታደሮቻችን ፡ ጥቂት ፡ ጉዳት ፡ ደረሰባቸው

4. ችግር. Financial reverses ruined him. በገንዘብ ፡ በኩል ፡ የደረሰበት ፡ ችግር ፡ ከኪሳራ ፡ ላይ ፡ ጣለው

**reverse, ~ side** (= adv.) ከጀርባው
Don't forget to fill in the reverse side of the card! ካርዱን ፡ ከጀርባው ፡ መሙላት ፡ አትርሳ
*Play the reverse side of the record! ሸክላውን ፡ ገልብጠህ ፡ አጫውት

**in reverse** ወደ ፡ ኋላ
Drive the car in reverse until you are out of the garage. ከጋራዥ ፡ እስክትወጣ ፡ መኪናውን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ንዳ

**in reverse order** ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በተራ
Write the alphabet in reverse order! ፊደሎቹን ፡ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በተራ ፡ ጻፍ

**meet with reverses** አዱኛ ፡ ከዳው
He used to be rich, but he met with reverses in his business. ሀብታም ፡ ነበር ፤ ሆኖም ፡ በንግዱ ፡ አዱኛ ፡ ከዳው

**reversible** በመልኩም ፡ በፈርሱም ፡ የሚለበስ
A reversible coat is useful in rainy and dry weather. በመልኩም ፡ በፈርሱም ፡ የሚለበስ ፡ ካፖርት ፡ በዝናብም ፡ በሞቃትም ፡ ጊዜ ፡ ይጠቅማል

**be reversible** ሊሻር ፡ ቻለ
The judgments of the lower courts are reversible. የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ፍርዶች ፡ ሊሻሩ ፡ ይችላሉ

**revert**
1. ተመለሰ. Many tamed animals revert to a wild state when set free. ብዙ ፡ ለማዳ ፡ እንስሳዎች ፡ በተለቀቁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አውሬነት ፡ ይመለሳሉ
2. ገባ. If a man dies without heirs, his property reverts to the state. ሰው ፡ ያለ ፡ ወራሽ ፡ ከሞተ ፡ ንብረቱ ፡ ለመንግሥት ፡ ይገባል

**review** (v.)
1. ጐበኘ. The general reviewed his troops. ጄኔራሉ ፡ ወታደሮቹን ፡ ጐበኘ
2. መረመረ. The superior court reviewed the decision of the lower court. ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የበታቹን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ መረመረ
He reviewed the events that led to their quarrel. የተጣሉበትን ፡ ምክንያት ፡ መረመረ
3. ከለሰ. He reviewed the lesson given last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ የተሰጠውን ፡ ትምህርት ፡ ከለሰው
4. አቃቂር ፡ ጻፈ. He reviewed a book on Ethiopia recently. በቅርቡ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተጻፈ ፡ መጽሐፍ ፡ አቃቂር ፡ ጻፈ

**review** (n.)
1. ሰልፍ. The army passed by in review. የጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ በሰልፍ ፡ አለፈ
2. አቃቂር. This magazine publishes reviews. ይህ ፡ መጽሔት ፡ አቃቂር ፡ ያትማል
3. ምርመራ. A review of the events shows that the situation is serious. የድርጊቱ ፡ ምርመራ ፡ ሁኔታው ፡ አስጊ ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል
4. ክለሳ. The term's work ended with a comprehensive review. የተርሙ ፡ ሥራ ፡ ባጠቃላይ ፡ ክለሳ ፡ ተፈጸመ

**review lesson** ክለሳ
The next lesson is a review lesson. የሚቀጥለው ፡ ትምህርት ፡ ክለሳ ፡ ነው

**come under review** ተመረመረ
Our finances come under review next month. የገንዘብ ፡ ይዞታችን ፡ በሚመጣው ፡ ወር ፡ ይመረመራል

**have a review** ከለሰ
Before the examinations, we had a review of everything we had studied. ከፈተናው ፡ በፊት ፡ የተማርነውን ፡ ሁሉ ፡ ከለስን
[See also 'pass']

**revile** ሙልጭ ፡ አድርጎ ፡ ሰደበ
He reviled me in the coarsest language. ባልታረመ ፡ ቃላት ፡ ሙልጭ ፡ አድርጎ ፡ ሰደበኝ

**revise**
1. ለወጠ. He revised the estimate to include the cost of paint. የቀለሙን ፡ ዋጋ ፡ ለመጨመር ፡ የፊተኛውን ፡ ሒሳብ ፡ ለወጠው
He revised his opinion of her after meeting her. ካገኛት ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ እርሷ ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ ለወጠ
2. አሻሻለ. She has revised the long story she wrote to make it shorter. የጻፈችውን ፡ ረዥም ፡ ታሪክ ፡ በማሻሻል ፡ አሳጠረችው

**be revised** እንደገና ፡ ተሻሻለ
The fiscal policy of the country needs to be revised. የሀገሪቱ ፡ የገንዘብ ፡ አያያዝ ፡ መምሪያ ፡ እንደገና ፡ መሻሻል ፡ አለበት

**revision** መሻሻል
Revision of the constitution can only be done by parliament. ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ለማሻሻል ፡ የሚችለው ፡ የምክር ፡ ቤቱ ፡ ብቻ ፡ ነው

**revival** ማንሰራራት
The revival of tribalism is being combatted by the Nigerian government. የጐሳን ፡ ልዩነት ፡ ማንሰራራት ፡ የናይጄሪያ ፡ መንግሥት ፡ በመከላከል ፡ ላይ ፡ ነው

The revival of Ethiopian literature in the 16th century opened a new chapter in the spread of Amharic. በ፲፮ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ማንሰራራት ፡ ላማርኛ ፡ መስፋፋት ፡ አዲስ ፡ ምዕራፍ ፡ ከፈተ

**experience a revival** አንሰራራ

Ethiopia experienced a revival of literature in the 16th century. ኢትዮጵያ ፡ በሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ረገድ ፡ ያንሰራራችው ፡ በ፲፮ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ነበር

**revive** (vt.)

1. አነቃቃ. Hot coffee revives a tired man. ትኩስ ፡ ቡና ፡ የደከመን ፡ ሰው ፡ ያነቃቃል

2. (= intr.) ነፍስ ፡ ዘራ(በት). The rain revived the wilting plants. ዝናቡ ፡ የጠወለጉትን ፡ ዕፀዋት ፡ ነፍስ ፡ ዘራባቸው

3. ነፍስ ፡ እንዲዘራ ፡ አደረገው. He was nearly drowned, but we revived him. ሰጥሞ ፡ ሊሞት ፡ ነበር ፣ ግን ፡ ነፍስ ፡ እንዲዘራ ፡ አደረግነው

4. ሕይወት ፡ ሰጠ. Recently they revived old customs. በቅርቡ ፡ ለቆዩ ፡ ልማዶች ፡ ሕይወት ፡ ሰጧቸው

5. አስታወሰ. He likes to revive memories of childhood. የልጅነት ፡ ጊዜ ፡ ትዝታውን ፡ ማስታወስ ፡ ይወዳል

**revive** (vi.)

1. ተነቃቃ. His spirits revived after having heard the good news. ጥሩ ፡ ወሬ ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ መንፈሱ ፡ ተነቃቃ

2. ታደሰ. Our hopes revived when we heard the minister's speech. የሚኒስትሩን ፡ ንግግር ፡ በሰማን ፡ ጊዜ ፡ ተስፋችን ፡ ታደሰ

3. እንደገና ፡ ለመለመ. The wilted flower revived in water. የጠወለገው ፡ አበባ ፡ ውኃ ፡ ሲያገኝ ፡ እንደገና ፡ ለመለመ

**(be) revocable** ሊሻር ፡ ተቻለ

The privileges given to the nobility are revocable. ለመኳንንት ፡ የተሰጠው ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ሊሻር ፡ ይቻላል

**revoke**

1. ነጠቀ. The government revoked his driver's license. መንግሥቱ ፡ የመንጃ ፡ ፈቃዱን ፡ ነጠቀው

2. ሰረዘ. The government revoked the company's concessions. መንግሥቱ ፡ ከኩባንያው ፡ ጋር ፡ ያደረገውን ፡ ስምምነት ፡ ሰረዘ

**be revoked**

1. ተሻረ. His death penalty was revoked by the Emperor. የሞት ፡ ፍርዱ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ተሻረ

2. ተነሣ. The interdiction of selling arms was revoked after two years. መሣሪያ ፡ በመሸጥ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ማገጃ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ተነሣ

**revolt** (vt.) ዘገነነ

The sight of blood revolted her. ደም ፡ ስታይ ፡ ይዘገንናታል

**revolt** (vi.)

1. ዐመፀ. The American colonies revolted against England. በእንግሊዝ ፡ ሥር ፡ የነበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ ቅኝ ፡ ግዛቶች ፡ ዐመፁ

2. አልተቀበለም. Human nature revolts at such a crime. ሰው ፡ በተፈጥሮው ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ ወንጀል ፡ አይቀበለውም

3. አሻፈረኝ ፡ አለ. The girl revolted against her family's discipline. ልጅቱ ፡ የቤተ ፡ ሰቧን ፡ ቁጥጥር ፡ አሻፈረኝ ፡ አለች

**revolting** (n.) በገዢ ፡ ላይ ፡ መነሣት

By revolting, the colonies asserted their right to govern themselves. በገዢዎቻቸው ፡ ላይ ፡ በመነሣት ፡ ቅኝ ፡ ግዛቶች ፡ ራሳቸውን ፡ ለማስተዳደር ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ አረጋገጡ

**revolting** (adj.) ጨርሶ ፡ መጥፎ

His behavior is revolting. ጠባዩ ፡ ጨርሶ ፡ መጥፎ ፡ ነው

**revolution**

1. ሽብር ፣ መሠረታዊ ፡ ለውጥ. The French Revolution occurred in 1789. የፈረሳንይ ፡ ሽብር ፡ (መሠረታዊ ፡ ለውጥ) ፡ የተደረገው ፡ በ፲፯፻፹፱ ዓ. ም. ነው

2. ከፍተኛ ፡ ለውጥ. The automobile caused a revolution in ways of traveling. በጉዞ ፡ ረገድ ፡ መኪና ፡ ከፍተኛ ፡ ለውጥ ፡ አምጥቷል

3. መሽከርከር. The revolution of the earth around the sun was proven by Gallileo. የመሬትን ፡ በፀሐይ ፡ ዙሪያ ፡ መሽከርከር ፡ ጋሊሌዮ ፡ አረጋገጠ

**make revolutions** (turns) ተሽከረከረ

This wheel makes 350 revolutions a minute. ይህ ፡ መንኰራኵር ፡ በደቂቃ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ጊዜ ፡ ይሽከረከራል

**revolutionary** (n.) ደመ ፡ ነውጠኛ

The revolutionaries were put to death. ደመ ፡ ነውጠኞቹ ፡ ተገደሉ

**revolutionary** (adj.)

1. ሞገደኛ. The revolutionary leaders were executed. ሞገደኞቹ ፡ መሪዎች ፡ ተገደሉ

2. ከፍተኛ ፡ ለውጥ ፡ ያመጣ. Radio and television were two revolutionary inventions of the

20th century. ሬዲዮና ፡ ቴሌቪዥን ፡ በሀያኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ከተፈለሰፉት ፡ ነገሮች ፡ ከፍተኛ ፡ ለውጥ ፡ ያመጡ ፡ መሣሪያዎች ፡ ናቸው

**revolutionize** ከፍተኛ ፡ ለውጥ ፡ አስከተለ
Electricity revolutionized all kinds of industries. ኤሌክትሪክ ፡ በሁሉም ፡ ዓይነት ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ለውጥ ፡ አስከተለ

**revolve** (vt.) አብላላ
He wishes to revolve the problem before giving an answer. መልስ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ነገሩን ፡ ሊያብላላው ፡ ይፈልጋል

**revolve** (vi.)
1. ዞረ. The earth revolves around the sun. መሬት ፡ በፀሐይ ፡ ዙሪያ ፡ ትዞራለች
2. ተመሠረተ. The discussion revolved around two questions. ውይይቱ ፡ በሁለት ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነበር
3. ተፈራረቀ. The seasons revolve. ወራት ፡ ይፈራረቃሉ

**revolver** ሽጉጥ
My uncle bought a revolver, and gave it to me as a present. አጐቴ ፡ ሽጉጥ ፡ ገዝተው ፡ ሸለሙኝ

**revulsion** ጥላቻ
When I saw that, I could not hide my revulsion. ያን ፡ ባየሁ ፡ ጊዜ ፡ ጥላቻዬን ፡ ልደብቅ ፡ አልቻልኩም

**reward** (v.)
1. ወሮታ ፡ ከፈለ. She rewarded my loyalty. ለታማኝነቴ ፡ ወሮታ ፡ ከፈለችኝ
2. ዋጋው ፡ ከፈለው. The boss rewarded the quick workers. አለቃው ፡ ትጉሆችን ፡ ሠራተኞች ፡ ዋጋቸውን ፡ ከፈላቸው

**be rewarded** (= act.) ዋጋ ፡ አስገኘ
Righteousness will be rewarded by God. ጻድቅነት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ ያስገኛል
*I was richly rewarded. የድካሜን ፡ ዋጋ ፡ በገፍ ፡ አገኘሁ

**be well rewarded** ተገቢ ፡ ዋጋ ፡ ተሰጠው
His diligence was well rewarded. ትጋቱ ፡ ተገቢ ፡ ዋጋ ፡ ተሰጥቶታል

**reward** (n.)
1. ሽልማት. There is a $1,000 reward for the capture of the bank robber. ባንኩን ፡ የዘረፈውን ፡ ሌባ ፡ ለያዘ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ሽልማት ፡ ይሰጣል
2. ዋጋ. He reaped his just reward. የሚገባውን ፡ ዋጋ ፡ አገኘ

**rewarding**
*He finds his work very rewarding. ሥራው ፡ ፍላጎቱን ፡ ያረካለታል

**reword**
1. ለወጥ ፡ አድርጎ ፡ አቀረበ. The speaker reworded his statement. ተናጋሪው ፡ ንግግሩን ፡ ለወጥ ፡ አድርጎ ፡ አቀረበው
2. አሳጥሮ ፡ ጻፈ. If we reword the telegram, we can save money. ቴሌግራሙን ፡ አሳጥረን ፡ ብንጽፍ ፡ ትንሽ ፡ ገንዘብ ፡ ልንቈጥብ ፡ እንችላለን
3. አቀራረቡን ፡ ለወጠ. He reworded his request to make it more polite. ጥያቄው ፡ የትሕትና ፡ መንፈስ ፡ እንዲይዝ ፡ አቀራረቡን ፡ ለወጠ

**rewrite** (rewrote) አሻሽሎ ፡ እንደገና ፡ ጻፈ
I rewrote the entire report. ራፖሩን ፡ አሻሽዬ ፡ እንደገና ፡ ጻፍኩት

**rewrote,** see **rewrite**

**rhetoric** ንግግርን ፡ ማሳመር
Rhetoric is popular with the Arabs. በዐረቦች ፡ ዘንድ ፡ ንግግርን ፡ ማሳመር ፡ ይወደዳል

**rhetorical** መልስ ፡ የማይሰጥበት
He asked his audience a rhetorical question. አዳማጮቹን ፡ መልስ ፡ የማይሰጥበት ፡ ጥያቄ ፡ ጠየቀ

**rheumatism** ቍርጥማት
I suffer from rheumatism. ቍርጥማት ፡ አለብኝ

**rhinoceros** አውራሪስ
I saw a rhinoceros in the field. እሜዳው ፡ ላይ ፡ አውራሪስ ፡ አየሁ

**rhyme** (v.) ቤት ፡ መታ
This poetry does not rhyme. ይህ ፡ ግጥም ፡ ቤት ፡ አይመታም

**rhyme** (n.) የቤት ፡ መምቻ
The rhyme of this poem is in every third line. የዚህ ፡ ግጥም ፡ ቤት ፡ መምቻው ፡ በየሦስተኛው ፡ መሥመር ፡ ላይ ፡ ነው

**without rhyme or reason** ያለ ፡ ምክንያት ፤ ከመሬት ፡ ተነሥቶ
He did it without rhyme or reason. ያለ ፡ ምክንያት ፡ አደረገው (or, ከመሬት ፡ ተነሥቶ ፡ አደረገው)

**rhythm** ውዝዋዜ
The rhythm of the dance was accentuated by drumbeats. የጭፈራውን ፡ ውዝዋዜ ፡ የሚመራው ፡ በከበሮ ፡ ምት ፡ ነው

**rhythmic** የተስተካከለ
Rhythmic clapping accompanied the dance. ጭፈራው ፡ በተስተካከለ ፡ ጭብጨባ ፡ ታጅቦ ፡ ነበር

**rib**

1. ጐድን. He is so thin that you can see his ribs.
ከመከሳቱ ፡ የተነሣ ፡ ጐድኑ ፡ ይቈጠራል
2. ሽቦ. The wind broke one of the ribs of my umbrella. ነፋሱ ፡ ከዣንጥላዬ ፡ ሽቦ ፡ አንዱን ፡ ሰ
በረው

**ribbon**

1. ሪበን. She tied her hair with a ribbon.
ጸጉሯን ፡ በሪበን ፡ አሰራ ፡ ነበር
2. ጥብጣብ. She embellished her dress with ribbons. ቀሚሷን ፡ በጥብጣብ ፡ አሳመረችው
3. ክር. I need a new typewriter ribbon.
አዲስ ፡ የጽሕፈት ፡ መኪና ፡ ክር ፡ ያስፈልገኛል

**be in ribbons, be torn to ribbons** ተበጫጨቀ
Her dress was in ribbons. ልብሷ ፡ የተበጫጨ
ቀ ፡ ነበር

**rice** ሩዝ
Rice grows in India. ሩዝ ፡ በህንድ ፡ አገር ፡
ይበቅላል

**rich**

1. ሀብታም ፤ ባለጸጋ ፤ ቱጃር. He is a rich man. ሀ
ብታም ፡ (ባለጸጋ ፤ ቱጃር) ፡ ሰው ፡ ነው
The United States is rich in oil and coal.
አሜሪካ ፡ በነዳጅ ፡ ዘይትና ፡ በድንጋይ ፡ ከሰል ፡
ሀብታም ፡ ናት
2. ለም. It's rich soil. መሬቱ ፡ ለም ፡ ነው
3. ውድ. He sells only rich fabrics. ውድ ፡ የሆ
ነ ፡ ጨርቅ ፡ ብቻ ፡ ይሸጣል
4. ጥሩ. This singer has a rich voice. ይህ ፡ ዘፋ
ኝ ፡ ጥሩ ፡ ድምፅ ፡ አለው
5. መልካም. The rich harvest made the farmer happy. መልካሙ ፡ አዝመራ ፡ ገበሬውን ፡ አስደሰተው
6. ደማቅ. The color of her dress is a rich red.
የልብሷ ፡ ቀለም ፡ ደማቅ ፡ ቀይ ፡ ነው

**rich family** ሀብታም
He comes from a rich family. የሀብታም ፡ ል
ጅ ፡ ነው

**be rich in** ብዙ ፡ አለው
Oranges are rich in vitamins. ብርቱካን ፡ ብዙ ፡
ቪታሚን ፡ አለው

**get rich** ከበረ
He got rich by selling bread. ዳቦ ፡ ሸጦ ፡ ከበረ

**riches** ሀብት
He lost all his riches in the war. ሀብቱን ፡ ሁሉ ፡
በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ አጣ

**richly**
I was richly rewarded. የድካሜን ፡ ዋጋ ፡ በገፍ ፡
አገኘሁ

**rickets** [የአጥንት ፡ መለስለስ ፡ በሽታ]

**rickety** ሊፈርስ ፡ የደረሰ
I wouldn't drive my car across that rickety old bridge. እኔ ፡ ብሆን ፡ በዚያ ፡ ሊፈርስ ፡ በደረሰ ፡
አሮጌ ፡ ድልድይ ፡ ላይ ፡ መኪናዬን ፡ አልነዳም ፡
ነበር

**ricochet** ተፈናጠረ
The bullet ricocheted and hit the child. ጥይቱ ፡
ተፈናጥሮ ፡ ልጁን ፡ መታው

**rid** (rid) አጠፋ
Theodore tried to rid the country of bandits.
አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ካገሪቷ ፡ ላይ ፡ ሽፍቶችን ፡ ሊያ
ጠፉ ፡ ሞከሩ

**rid oneself of** ራሱን ፡ ነጻ ፡ አደረገ
He wants to rid himself of debt. ከዕዳ ፡ ራሱን ፡
ነጻ ፡ ለማድረግ ፡ ይፈልጋል

**get rid (of)**
1. ተገላገለ. I got rid of her at last. በመጨረሻ ፡
ከሷ ፡ ተገላገልኩ
2. አጠፋ. I got rid of the rats by using poison.
አይጦቹን ፡ በመርዝ ፡ አጠፋኋቸው
3. ተላቀቀ. Bad habits are easy to contract and hard to get rid of. መጥፎ ፡ ጠባዮችን ፡ መል
መድ ፡ ቀላል ፡ ሲሆን ፡ መላቀቁ ፡ ግን ፡ ያስቸ
ግራል
4. አስወገደ. How can I get rid of these hiccups? ይህን ፡ ስርቅታ ፡ እንዴት ፡ ላስወግደው ፡
እችላለሁ ?

**riddance, good** ~ ግልግል ፤ ዕረፍት
Their departure is good riddance. መሄዳቸው ፡
ግልግል ፡ (ዕረፍት) ፡ ነው

**riddle** (v.) በሳሳ
Worms riddled our apples. ትሎች ፡ ቱፋዎቻች
ን ፡ በሳሷቸው

**riddle** (n.) እንቆቅልሽ
Some parents play riddles with their children every evening. አንዳንድ ፡ ወላጆች ፡ ማታ ፡ ማ
ታ ፡ ከልጆቻቸው ፡ ጋር ፡ እንቆቅልሽ ፡ ይጫወ
ታሉ

**ride** (vt.)
1. ነዳ. Do you know how to ride a motorcycle? ሞተር ፡ ብስክሌት ፡ መንዳት ፡ ትችላለህ ?
2. ጋለበ. Do you know how to ride a horse?
ፈረስ ፡ መጋለብ ፡ ታውቃለህ ?
3. ተቀመጠ. Do you know how to ride a mule?
በቅሎ ፡ መቀመጥ ፡ ታውቃለህ ?

**ride** (vi.)
1. ተጓዘ. He rode all the way in a bus. መንገዱን ፡ ሁሉ ፡ በአውቶቡስ ፡ ተጓዘ
2. ሄደ. The train rides on rails. ባቡር ፡ ሐዲድ ፡ ላይ ፡ ይሄዳል
We rode in the car as John drove. ጆን ፡ እየነዳ ፡ በመኪና ፡ ሄድን

**ride away** በግልቢያ ፡ ሄደ
He mounted his horse and rode away. ፈረሱን ፡ ተቀምጦ ፡ በግልቢያ ፡ ሄደ

**ride before** በፈረስ ፡ ሆኖ ፡ መራ
The officer rode before his troops. መኰንኑ ፡ በፈረስ ፡ ሆኖ ፡ ሰራዊቱን ፡ መራ

**ride off** ጋለበ
He mounted his horse and rode off. ፈረሱን ፡ ተቀምጦ ፡ ጋለበ

**ride on (one's) shoulders** (= active) እሽኮኮ ፡ አለ ፤ እንኮኮ ፡ አለ
+The little boy was riding on his father's shoulders. አባትዬው ፡ ትንሹን ፡ ልጅ ፡ እሽኮኮ ፡ (እንኮኮ) ፡ ብሎት ፡ ነበር

**ride smoothly** አልነቀነቀም
This car rides smoothly. ይህ ፡ መኪና ፡ አይነቀንቅም

**ride** (n.) ጉዞ
He enjoyed his first airplane ride. የመጀመሪያው ፡ የአውሮፕላን ፡ ጉዞው ፡ አስደሰተው

**give a ride** በመኪና ፡ አደረሰ
Can you give me a ride to town? በመኪናህ ፡ ከተማ ፡ ልታደርሰኝ ፡ ትችላለህ ?

**go for a ride** በመኪና ፡ ተንሸረሸረ
We went for a ride before breakfast. ቁርስ ፡ ከመብላታችን ፡ በፊት ፡ በመኪና ፡ ተንሸረሸርን

**rider** ማሟያ
The committee added a rider to the bill. ደርጉ ፡ በሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ማሟያ ፡ አከለበት
*I cannot take riders with me in my car. በመኪናዬ ፡ ሰው ፡ ልጭን ፡ አልችልም

**rider of horses**
*She is not a good rider of horses. ፈረስ ፡ በደንብ ፡ መጋለብ ፡ አትችልም

**ridge**
1. ተረተር. The ridge was occupied by soldiers. ተረተሩ ፡ በወታደሮች ፡ ተይዞ ፡ ነበር
2. ትልም. The ridges in the ground were made by car wheels. የመኪናው ፡ ጎማ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ትልም ፡ አብጅቷል
3. ቁልል. The wind made a ridge of sand beside the road. ነፋሱ ፡ በመንገዱ ፡ ዳር ፡ ያሸዋ ፡ ቁልል ፡ አበጀ

**ridge of roof** ማዋቀሪያ
The ridge of the roof has an antenna fastened to it. ማዋቀሪያው ፡ ላይ ፡ አንቴና ፡ አለ

**ridicule** (v.) አሾፈ(በት)
They ridiculed the old crippled man. ሽባውን ፡ ሽማግሌ ፡ አሾፉበት

**ridicule** (n.), **expose to ~** መሣቂያ ፡ አደረገው
Foolish actions expose a person to ridicule. የቂልነት ፡ ተግባር ፡ ሰውን ፡ መሣቂያ ፡ ያደርገዋል

**ridiculous**
1. የሚያሥቅ. She wears a ridiculous hat. የሚያሥቅ ፡ ባርኔጣ ፡ አድርጋለች
2. የማይታመን. He wants a ridiculous price for his property. ለንብረቱ ፡ የጠየቀው ፡ ዋጋ ፡ የማይታመን ፡ ነው
3. ሞኝ. Don't be ridiculous; the moon will not break in half. ሞኝ ፡ አትሁን ፤ ጨረቃ ፡ አትገመስም

**(be) rife** በዛ
Superstition is rife in certain parts of the country. ባገሪቱ ፡ ባንዳንድ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ አጉል ፡ እምነት ፡ ይበዛል

**rifle** (v.) በዘበዘ
Soldiers rifled the city. ወታደሮች ፡ ከተማይቱን ፡ በዘበዟት

**rifle** (n.) ጠበንጃ ፤ ጠመንጃ
It is not known when the rifle was introduced to Ethiopia. ጠበንጃ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገባበት ፡ ዘመን ፡ አይታወቅም
[See also 'shell']

**rift** ስንጥቅ
There is a rift in the rock. ባለቱ ፡ ላይ ፡ ስንጥቅ ፡ አለ
*There is a rift in their friendship. ወዳጅነታቸው ፡ ሻክሯል

**rig** (rigged)
1. አጭበረበረ. They rigged the prices. ዋጋዎቹን ፡ አጭበረበሩ
2. አበጀ. The sailor rigged a toy boat for the little boy. መርከበኛው ፡ ለትንሹ ፡ ልጅ ፡ የጀልባ ፡ አሻንጉሊት ፡ አበጀለት

**be rigged** በዘዴ ፡ ታቀደ
The election was rigged in favor of the Socialist Party. ምርጫው ፡ የሶሺያሊስት ፡ ፓርቲ ፡ እንዲያሸንፍ ፡ በዘዴ ፡ የታቀደ ፡ ነበር

**rig oneself up in ለበሰ**
The children rigged themselves up in queer clothes. ልጆቹ ፡ እንግዳ ፡ የሆነ ፡ ልብስ ፡ ለበሱ

**rig up ሠራ**
The boys rigged up a tent with a rope and blanket. ልጆቹ ፡ ብርድ ፡ ልብሱን ፡ በገመድ ፡ ወጥረው ፡ ድንኳን ፡ ሠሩ

**right** (v.)
1. መልሶ ፡ አቆመ. The driver righted the overturned car. ነጂው ፡ የተገለበጠችውን ፡ መኪና ፡ መልሶ ፡ አቆማት
2. መልሶ ፡ አቀና. The boys righted the boat. ልጆቹ ፡ ጀልባውን ፡ መልሰው ፡ አቀኑ
3. አቀና. They righted the flagpole. የሰንደቅ ፡ ዓላማውን ፡ መስቀያ ፡ አቀኑት
4. አስተካከለ. It is difficult to right injustices of long standing. የቆየን ፡ በደል ፡ ማስተካከል ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**right** (n.)
1. መብት. Women's rights were not recognized until recently. የሴቶች ፡ መብት ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ አልታወቀም ፡ ነበር
I have as much a right to it as you do. ለነገሩ ፡ አንተ ፡ ያለህን ፡ ያህል ፡ መብት ፡ እኔም ፡ አለኝ
2. ደግ. He can't tell right from wrong. ደግና ፡ ክፉ ፡ አይለይም
3. ቀኝ. Take the road on the right! ወደ ፡ ቀኝ ፡ የሚሄደውን ፡ መንገድ ፡ ያዝ
The car on the right has the right of way. ቀኙን ፡ የያዘ ፡ መኪና ፡ ቅድሚያ ፡ አለው
4. ቀኝ ፡ ክፍል. Parties of the right advocate free trade. የቀኝ ፡ ክፍል ፡ ፓርቲዎች ፡ ለነጻ ፡ ንግድ ፡ ይከራከራሉ

**right** (adj.)
1. ተስማሚ. She has the right dress for the dance. ለዳንሱ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ልብስ ፡ አላት
It is important to find the right calling. ተስማሚውን ፡ ሙያ ፡ ማግኘት ፡ ያስፈልጋል
2. ትክክለኛ. Are we going the right way? ትክክለኛውን ፡ መንገድ ፡ ይዘናል ?
3. ልክ. Only part of what you say is right. ከተናገርከው ፡ ውስጥ ፡ ልክ ፡ የሆነው ፡ ግማሹ ፡ ብቻ ፡ ነው
4. የቀኝ ፡ እጅ. I've lost my right glove. የቀኝ ፡ እጄን ፡ ጓንቲ ፡ ጣልኩት
5. ተገቢ. To my mind, she is the right person to do the job. እንደኔ ፡ ለሥራው ፡ ተገቢ ፡ ሰው ፡ እሷ ፡ ናት

**right** (adv.)
1. ወደ ፡ ቀኝ. Turn right at the corner! መታጠፊያው ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ታጠፍ
2. ልክ ፤ ትክክል. I guessed right. ልክ ፡ (ትክክል) ፡ ገምቻለሁ
3. ልክ. The house is right next to the church. ቤቱ ፡ ልክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አጠገብ ፡ ነው
That's right. ልክ ፡ ነው
He stood right behind me. ልክ ፡ ከኋላዬ ፡ ቆመ
4. በትክክል. Do it right! በትክክል ፡ ሥራው
5. በቀጥታ. I'm coming right home from the office. ከመሥሪያ ፡ ቤት ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መምጣቴ ፡ ነው
Go right to the end of this road and turn left! በቀጥታ ፡ እስከ ፡ መንገዱ ፡ መጨረሻ ፡ ሂድና ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ታጠፍ
*We're going right after dinner. እራት ፡ በልተን ፡ እንደጨረስን ፡ እንሄዳለን

**right away**
1. አሁኑኑ. Let's go right away, or we'll be late. አሁኑኑ ፡ እንሂድ ፤ አለበለዚያ ፡ እንዘገያለን
2. ወዲያውኑ. That's what I thought right away. ወዲያውኑ ፡ ያሰብኩት ፡ እሱኑ ፡ ነበር

**(be in one's) right mind ጤነኛ ፡ ሆነ**
If you were in your right mind, you wouldn't think of doing that. ጤነኛ ፡ ብትሆን ፡ ኖሮ ፡ እንዲህ ፡ አታደርገውም ፡ ነበር

**right now አሁን**
I'm busy right now. አሁን ፡ ሥራ ፡ ይዣለሁ

**right off ከመጀመሪያው**
She made a bad impression right off. ከመጀመሪያው ፡ መጥፎ ፡ ስሜት ፡ አሳደረች

**right side (of coat, cloth) መልክ**
This is the right side of the coat. ኮቱ ፡ መልኩ ፡ ይህ ፡ ነው
Which is the right side of the cloth? የጨርቁ ፡ መልክ ፡ የትኛው ፡ ነው ?

**right thing ደግ**
You didn't do the right thing. ደግ ፡ አልሠራህም

**all right**
1. ደኅና. Everything will turn out all right. ሁሉም ፡ ነገር ፡ ደኅና ፡ ይሆናል
He'll be all right again in a few days. ከጥቂት ፡ ቀናት ፡ በኋላ ፡ ደኅና ፡ ይሆናል
2. እሺ. All right, I'll do it if you want me to. እሺ ፤ ከፈለግህ ፡ እሠራዋለሁ

**be in the right ትክክል ፡ ነው**
I am in the right this time. አሁን ፡ እኔ ፡ ትክክል ፡ ነኝ

**be right along**
I will be right along. መጣሁ

**be right down** መጣ
I'll be right down in a minute. በደቂቃ ፡ ው
ስጥ ፡ እመጣለሁ

**be right over** መጣ
I'll be right over in a minute. ባንድ ፡ ደቂቃ ፡
ውስጥ ፡ እመጣለሁ

**by right of** በመመርኰዝ
The dictator ruled the country by right of force.
አምባ ፡ ገነኑ ፡ ኀይልን ፡ በመመርኰዝ ፡ አገሪቱን ፡ ገዛ

**by rights** በሕጉ ፡ መሠረት
The professors should by rights have been given a voice in administering the university.
በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ አስተዳደር ፡
ተካፋዮች ፡ እንዲሆኑ ፡ ለመምህራኑ ፡ መብት ፡
መሰጠት ፡ ነበረበት

**get (something) right** ዐወቀ
Let's get the directions right before we start.
ከመነሣታችን ፡ በፊት ፡ የምንሄድበትን ፡ አቅ
ጣጫ ፡ እንወቅ

**in (one's) own right** በበኩሉ
She is a scholar in her own right. እሷም ፡ በበ
ኩሏ ፡ ምሁር ፡ ናት

**just at the right time**
You came just at the right time. ደኅና ፡ አግር ፡
ጣለህ

**put someone right** አረመ
It is not your business to put me right. እኔን ፡ ማ
ረም ፡ ያንተ ፡ ሥራ ፡ አይደለም

**put something right** አስተካከለ
A short note put the matter right. ነገሩን ፡ አጭ
ር ፡ ማስታወሻ ፡ አስተካከለው

**quite all right** ደኅና
I think it's quite all right if you come at three.
በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ብትመጣ ፡ ደኅና ፡ ይመስለኛል

**(it) serves him right** ይገባዋል
It serves him right, so don't feel sorry for him.
ይገባዋል ፤ አትዘንለት

**set right** አቃለለ
Will this payment set things right? ይህ ፡ ክፍያ ፡
ነገሩን ፡ ያቃልለዋል ?

[See also 'bear, civil, divine, dot, hand, reserve, sense']

## righteous መልካም

His righteous act of returning the stolen money impressed everyone. የሰረቀውን ፡ ገንዘብ ፡ በመ
መለስ ፡ ያደረገው ፡ መልካም ፡ ምግባር ፡ ሰውን ፡
አስደነቀ

*He has a reputation for being righteous.
በደግ ፡ ሥራው ፡ ዝና ፡ አትርፏል

## righteousness

1. ጻድቅነት. Righteousness will be rewarded by God. ጻድቅነት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
ዋጋ ፡ ያስገኛል
2. ቅድስና. He followed the path of righteousness all his life. ሕይወቱን ፡ በሙሉ ፡ የቅድስና
ን ፡ መንገድ ፡ ተከተለ

## rightful

1. ሕጋዊ ፤ እውነተኛ. He is the rightful heir to the property. የንብረቱ ፡ ሕጋዊ ፡ (እውነተኛ) ፡ ወ
ራሽ ፡ እሱ ፡ ነው
2. በሕግ ፡ የሚገባው. His rightful property was stolen by his mother-in-law. በሕግ ፡ የሚገባው ፡
ንብረቱ ፡ በአማቱ ፡ ተወሰደበት

## rightfully በሕግ

This property is rightfully mine. ይህ ፡ ንብረ
ት ፡ በሕግ ፡ ይገባኛል

## right-hand (= adv.) ወደ ፡ ቀኝ

Make a right-hand turn! ወደ ፡ ቀኝ ፡ ተጠምዘዝ

**right-hand man** ቀኝ ፡ እጅ
He is the President's right-hand man. የፕሬዚዳ
ንቱ ፡ ቀኝ ፡ እጅ ፡ ነው

**in the right-hand** በቀኝ ፡ በኩል
Write your name in the right-hand column!
ስምህን ፡ በቀኝ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡
ጻፈው

**on the right-hand side of** ከ - - - በስተቀኝ
The school is on the right-hand side of the street. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ከመንገዱ ፡ በስተቀኝ ፡
ነው

## (be) right-handed

Johnny is right-handed. ጆን ፡ የሚሠራው ፡ በ
ቀኝ ፡ እጁ ፡ ነው

## rightly

1. በሚገባ. He is rightly called our benefactor.
ረዳታችን ፡ ተብሎ ፡ የተጠራው ፡ በሚገባ ፡ ነው
2. (= adj.) ትክክል. Am I rightly informed?
የሰማሁት ፡ ነገር ፡ ትክክል ፡ ነው ?
*If I remember rightly, he died last year.
ትዝ ፡ እንደሚለኝ ፡ የሞተው ፡ ዓምና ፡ ነው

**rightly or wrongly** ልክ ፡ ይሁንም ፡ አይሁን
Rightly or wrongly, I don't think he should be punished. ልክ ፡ ይሁንም ፡ አይሁን ፡ መቀጣ
ት ፡ ያለበት ፡ አይመስለኝም

**and rightly so** (= adj.) የሚገባ
He criticized her behavior and rightly so.
እሷን ፡ መንቀፉ ፡ የሚገባ ፡ ነው

**right-of-way** የመንገድ ፡ ቅድሚያ
The right-of-way rules are published in the traffic guide. የመንገድ ፡ ቅድሚያ ፡ የትራፊክ ፡ ደንቦች ፡ በትራፊክ ፡ መምሪያው ፡ ውስጥ ፡ ታትሟል
*Does the car on the right have the right-of-way? በቀኝ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ መኪና ፡ ቀድሞ ፡ ለማለፍ ፡ መብት ፡ አለው ?
*Fire engines have the right-of-way. የእሳት ፡ አደጋ ፡ መኪናዎች ፡ ሲመጡ ፡ መንገድ ፡ መለቀቅ ፡ አለበት

**rigid**
1. ጥብቅ. The rules of this organization are very rigid. የዚህ ፡ ድርጅት ፡ ደንቦች ፡ በጣም ፡ ጥብቅ ፡ ናቸው
2. ደረቅ. The stick was rigid and would not bend. በትሩ ፡ ደረቅ ፡ ስለነበረ ፡ አልጐበጥ ፡ አለ

**be rigid** በድን ፡ ሆኖ ፡ ቀረ
He was rigid with fear. በፍርሀት ፡ በድን ፡ ሆኖ ፡ ቀረ

**rigor**
1. መከራ. The rigors of war reduced him to skin and bone. የጦርነቱ ፡ መከራ ፡ ባጥንቱ ፡ አስቀረው
2. ብርታት. The rigor of the heat exhausted us. የሙቀቱ ፡ ብርታት ፡ አደከመን

**with rigor** በጥብቅ
The traffic laws were enforced with rigor. የትራፊክ ፡ ሕጎች ፡ በጥብቅ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ዋሉ

**rigorous**
1. ጥብቅ. The rigorous discipline of a prison is supposed to improve the character of the prisoners. በእስር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ጥብቅ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የእስረኞቹን ፡ ጠባይ ፡ ያሻሽላል ፡ ይባላል
2. በጣም ፡ ትክክል. He uses rigorous methods in his teaching. ሲያስተምር ፡ በጣም ፡ ትክክል ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፡ ይጠቀማል
3. መጥፎ. I don't like the rigorous climate of this country. የዚህን ፡ አገር ፡ መጥፎ ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፡ አልወደውም

**rim**
1. አፍ. The rim of the glass is broken. የብርጭቆው ፡ አፍ ፡ ተሸርፏል
2. ክፈፍ. The horn rims of his glasses are broken. ከቀንድ ፡ የተሠሩት ፡ የመነጽሩ ፡ ክፈፎች ፡ ተሰብረዋል
3. ቸርኬ. I took the tire off the rim. ጎማውን ፡ ከቸርኬው ፡ ላይ ፡ አወለቅሁት

**(be) rimmed** ተከፈፈ
The glasses are rimmed with gold. መነጽሩ ፡ በወርቅ ፡ ተከፏል

**rind** ልጣጭ
The rind of the papaya is green. የፓፓያው ፡ ልጣጭ ፡ አረንጓዴ ፡ ነው

**ring** (rang, rung), vt. ደወለ
Have you rung the bell? ደወሉን ፡ ደወልክ ?
*The bell rang the hour. ሰዓቱ ፡ ደወለ

**ring** (vi.)
1. ደወለ. Did you ring? ደወልክ ?
2. ተደወለ. The doorbell just rang. የበሩ ፡ ደወል ፡ ልክ ፡ አሁን ፡ ተደወለ
3. ጮኸ. The phone rang. ስልኩ ፡ ጮኸ
4. ጭው ፡ አለ(በት). My ears are ringing. ጆሮዬ ፡ ጭው ፡ ብሎብኛል
5. አስተጋባ. The room rang with shouts and laughter. ክፍሉ ፡ በጩኸትና ፡ በሳቅ ፡ አስተጋባ
6. መሰለ. His excuse rings false. ምክንያቱ ፡ ውሸት ፡ ይመስላል
*The noise is still ringing in my ears. ጩኸቱ ፡ አሁንም ፡ ይሰማኛል
*Her voice rang with anger. ቁጣን ፡ ባዘለ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸች

**ring for** በመጥሪያ ፡ ደወል ፡ ጠራ
She rang for the maid. ገረዲቱን ፡ በመጥሪያ ፡ ደወል ፡ ጠራቻት

**ring up** ደወለ(ለት)
I will ring you up tomorrow. ነገ ፡ እደውልልሃለሁ
[See also 'bell, true']

**ring** (n.)
1. ቀለበት. She wears a ring on her right middle finger. እቀኝ ፡ እጇ ፡ መሀል ፡ ጣት ፡ ላይ ፡ ቀለበት ፡ ታደርጋለች
2. ዘለበት. I lost the key ring. የቁልፉን ፡ ዘለበት ፡ ጣልኩት
3. ድምፅ. That bell has a peculiar ring. ያ ፡ ደወል ፡ ልዩ ፡ ድምፅ ፡ አለው
I can still hear the ring of applause. የጭብጨባውን ፡ ድምፅ ፡ አሁንም ፡ እሰማለሁ
4. ክበብ. There was a ring of light around the moon. በጨረቃ ፡ ዙሪያ ፡ የብርሃን ፡ ክበብ ፡ ነበር
5. ክብ ፡ መሥመር. He dated the tree by counting the rings in its trunk. የዛፉን ፡ ክብ ፡ መሥመር ፡ በመቍጠር ፡ የዛፉን ፡ ዕድሜ ፡ ዐወቀ
6. ክብ ፡ ቅርጽ. The wet glass left a ring on the table. እርጥቡ ፡ ብርጭቆ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ክብ ፡ ቅርጽ ፡ አበጀ

7. ሰፈር. The tourists visited the circus ring. ሀገር ፡ ጐብኚዎቹ ፡ የሰርከሱን ፡ ሰፈር ፡ ጐበኙ
8. ቡድን. The Ministry of Interior discovered a spy ring. ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የሰላይ ፡ ቡድኑን ፡ ደረሰበት
*The general's voice had the ring of authority. የጀኔራሉ ፡ ድምፅ ፡ አዛዥነትን ፡ የሚገልጽ ፡ ነበር
*There was a ring at the door. የበሩ ፡ ደወል ፡ ተደውሎ ፡ ነበር

**ring of truth** እውነት
There was a ring of truth in his voice. በንግግሩ ፡ ውስጥ ፡ እውነት ፡ ያለበት ፡ ይመስላል

**give a ring** ደወለ
Give me a ring tomorrow! ነገ ፡ ደውልልኝ
[See also 'key']

**ring finger** የቀለበት ፡ ጣት
He cut off his ring finger by accident. ሳያስበው ፡ የቀለበት ፡ ጣቱን ፡ ቈረጠ ፡ ጣለው

**ringing** መደወል
The insistent ringing of the telephone disturbed me in my work. የስልክ ፡ አሁንም ፡ አሁንም ፡ መደወል ፡ ሥራ ፡ አላሠራ ፡ አለኝ

**ringleader** የተንኰል ፡ መሪ ፤ የተንኰል ፡ ቀንደኛ
The ringleaders escaped, and only the small fry were caught. የተንኰል ፡ መሪዎች ፡ (ቀንደኞች) ፡ አምልጠው ፡ የተያዙት ፡ አጫፋሪዎቻቸው ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**rinse**
1. አለቀለቀ. Rinse the teapot after using it. ሻይ ፡ አፍልተህ ፡ ስታበቃ ፡ ጀበናውን ፡ አለቅልቀው
I rinse my wash twice. ልብሴን ፡ ከመጠምዘዜ ፡ በፊት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አለቀልቀዋለሁ
2. ተጕመጠመጠ. Rinse your mouth with a little salt and water! አፍህን ፡ በትንሽ ፡ ውኃና ፡ ጨው ፡ ተጕመጥመጥ

**riot** (v.) በጠበጠ
The students rioted against the school administration. የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ አስተዳደር ፡ በመቃወም ፡ ተማሪዎቹ ፡ በጠበጡ

**riot** (n.) ረብሻ ፤ ሽብር
Two people were killed in the Chicago riot. በቺካጎው ፡ ረብሻ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ሞቱ
Law and order have been restored in the riot-torn city. በሽብር ፡ ታውከ ፡ በነበረችው ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ ወደ ፡ ዱሮው ፡ ሁኔታ ፡ ተመልሷል
*The fields were a riot of color. ሜዳው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ አሸብርቆ ፡ ነበር

**rioter** ረብሸኛ
The rioters hurled rocks at the police. ረብሸኞቹ ፡ በፖሊሶቹ ፡ ላይ ፡ ድንጋይ ፡ ወረወሩ

**rioting** (n.) ጸጥታ ፡ ማደፍረስ
He indicted them on a charge of rioting. ጸጥታ ፡ በማደፍረስ ፡ ወንጀል ፡ ከሰሳቸው

**riotous**
1. የተራበሸ. The police brought the riotous crowd to order. ፖሊስ ፡ የተራበሸውን ፡ ሕዝብ ፡ ጸጥ ፡ አደረገው
2. ረብሸኛ. He was expelled from school for riotous conduct. በረብሸኛ ፡ ጠባይ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ተባረረ

**rip** (ripped)
1. ተረተረ. I have to rip the seams and resew them. ስፌቱን ፡ ተርትሬ ፡ እንደገና ፡ መስፋት ፡ አለብኝ
2. ቀደደ. He ripped the cloth in two. ጨርቁን ፡ ከሁለት ፡ ቀደደው
3. ገነጠለ. Rip the cover off this box! የዚህን ፡ ሣጥን ፡ ሽፋን ፡ ገንጥለው
4. (= passive) ተቀደደ. I ripped my pants climbing the fence. አጥሩን ፡ ስዘል ፡ ሱሪዬ ፡ ተቀደደ

**rip off** አነሣ
The wind ripped the cover off. ነፋሱ ፡ ሽፋኑን ፡ አነሣው

**rip open** ቀዶ ፡ ከፈተ
He ripped open the letter. ደብዳቤውን ፡ ቀዶ ፡ ከፈተው

**rip out** ቈረጠ
She ripped out the seams of the dress. የልብሱን ፡ ዘርፍ ፡ ቈረጠችው

**rip**, n. (= adj.) የተቀደደ
Please sew up this rip in my sleeve! የተቀደደውን ፡ እጅጌ ፡ ስፋልኝ

**ripe** የበሰለ
Ripe fruit is good to eat. የበሰለ ፡ ፍሬ ፡ ለመብላ ፡ ጥሩ ፡ ነው
My uncle has ripe experience in these matters. አጐቴ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ የበሰለ ፡ ልምድ ፡ አለው
*He lived to a ripe old age. ዕድሜ ፡ ጠግቦ ፡ ሞተ

**be ripe** በሰለ
Is this fruit ripe? ይህ ፡ ፍሬ ፡ በስሏል ?

**be ripe for** ተዘጋጀ
The infantry company was ripe for the assault. እግረኛው ፡ ጓድ ፡ ለማጥቃት ፡ ተዘጋጅቷል

This land is ripe for development. ይህን ፡ መሬት ፡ ለማልማት ፡ ጊዜው ፡ ነው
The time is ripe for us to make our attempt. ሙከራ ፡ ለማድረግ ፡ ጊዜው ፡ አሁን ፡ ነው
*He was ripe for college. ዕድሜው ፡ ለኮሌጅ ፡ ደርሶ ፡ ነበር

**ripen** (vt.) አበሰለ
The sun ripens the fruit. ፀሐይ ፡ ፍሬ ፡ ፍሬን ፡ ታበስላለች

**ripen** (vi.) በሰለ
The grapes ripened in the sun. ወይኑ ፡ በፀሐይ ፡ በሰለ

**ripple** (vt.) አንቀጠቀጠ
A breeze rippled the quiet waters. የነፋሱ ፡ ሽውታ ፡ የረጋውን ፡ ውኃ ፡ አንቀጠቀጠው

**ripple** (vi.) እየተንፏፏ ፡ ወረደ
The brook rippled over the stones. ምንጩ ፡ በድንጋዮች ፡ ላይ ፡ እየተንፏፏ ፡ ወረደ

**ripple** (n.) ትንሽ ፡ ሞገድ
The wind makes ripples on the lake. ነፋሱ ፡ በሐይቁ ፡ ላይ ፡ ትንንሽ ፡ ሞገዶች ፡ ይሠራል
*I heard a ripple of laughter in the crowd. የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ሲሣሣቅ ፡ ሰማሁ

**rise** (rose)
1. ተነሣ. He rises very early. በማለዳ ፡ ይነሣል
The river rises from a spring. ወንዙ ፡ ከምንጭ ፡ ይነሣል
In ancient Rome, slaves rose against their masters. በጥንታዊት ፡ ሮማ ፡ ባሮች ፡ በጌቶቻቸው ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፡ ነበር
Jesus rose from the dead. ኢየሱስ ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ተነሣ
All the students rose from their seats when the teacher entered. መምህሩ ፡ ሲገቡ ፡ ተማሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ከመቀመጫቸው ፡ ተነሡ
Quarrels often rise from trifles. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጠብ ፡ የሚነሣው ፡ በማይረባ ፡ ነገር ፡ ነው
2. ወጣ. The sun rises early. ፀሐይዋ ፡ በማለዳ ፡ ትወጣለች
3. ጨመረ. The price of wheat is still rising. የስንዴ ፡ ዋጋ ፡ አሁንም ፡ በመጨመር ፡ ላይ ፡ ነው
4. ተመነጠቀ. The kite rises in the air. ወላንዳው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይመነጠቃል
5. ሞላ. The river is rising fast. ወንዙ ፡ በፍጥነት ፡ እየሞላ ፡ ሄደ
6. ኩፍ ፡ አለ. The dough won't rise. ቡኮው ፡ ኩፍ ፡ አይልም
7. አደገ. He rose from the ranks to a first lieutenant. ከባለ ፡ ሌላ ፡ ማዕርግ ፡ ወደ ፡ መቶ ፡ አለቅነት ፡ አደገ
8. ታየ. A range of hills rose on our left. በስተግራችን ፡ ሸንተረር ፡ ታየ
9. ዳገት ፡ ሆነ. Over there the road rises again. እዚያ ፡ ጋ ፡ ሲደርስ ፡ መንገዱ ፡ እንደገና ፡ ዳገት ፡ ይሆናል
10. (= active) ቀሰቀሰ. +His anger rose at that remark. ትችቱ ፡ ንዴቱን ፡ ቀሰቀሰበት
11. (= active) አነቃቃ. +Our spirits rose at the good news. ጥሩ ፡ ወሬ ፡ ስንሰማ ፡ መንፈሳችንን ፡ አነቃቃው
*At the edge of the desert, the hills begin to rise. ከምድረ ፡ በዳው ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ የተራራዎቹ ፡ ከፍታ ፡ እየጨመረ ፡ ይሄዳል

**rise to** ረዘመ
The building rises to a height of 80 feet. ሕንጻው ፡ ሰማንያ ፡ ጫማዎች ፡ ይረዝማል

**rise up** እንደ ፡ ምሰሶ ፡ ቆመ
A huge column of smoke rose up over the town. ከከተማው ፡ በላይ ፡ ጢስ ፡ እንደ ፡ ምሰሶ ፡ ቆሞ ፡ ነበር

**cause to rise** ነፋ
The leaven causes the bread to rise. እርሾው ፡ ዳቦውን ፡ ይነፋዋል
[See also 'foot, level, obscurity, point, rank']

**rise** (n.)
1. ጉብታ. His house is built on a slight rise. ቤቱ ፡ የተሠራው ፡ ትንሽ ፡ ጉብታ ፡ ላይ ፡ ነው
2. ከፍተኛ ፡ ቦታ. The fort was built on a rise for safety against attack. ከአጥቂ ፡ ለመከላከያ ፡ እንዲሆን ፡ ምሽጉ ፡ የተሠራው ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው
3. መሙላት. The river's rise threatens the people who live in the lowlands. የወንዙ ፡ መሙላት ፡ በረባዳ ፡ ቦታዎች ፡ የሚኖሩትን ፡ ሰዎች ፡ ያሰጋል
4. መጨመር. A rise in prices hurts the poor. የዋጋ ፡ መጨመር ፡ ድኾችን ፡ ይጐዳል
5. መብዛት. The rise in crime perturbs many people. የወንጀል ፡ መብዛት ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያሳስባል

**give rise to**
1. አስነሣ. Undefined borders give rise to quarrels. ያልተከለሉ ፡ ወሰኖች ፡ ጠብ ፡ ያስነሣሉ
2. አስከተለ. The new law gave rise to discontent. አዲሱ ፡ ሕግ ፡ ቅሬታን ፡ አስከተለ
3. ፈጠረ. Such conduct might give rise to misunderstanding. ይህ ፡ ዓይነት ፡ ተግባር ፡ አለመግባባትን ፡ ይፈጥር ፡ ይሆናል

**rising** (n.) መሙላት
One likely result of this heavy rain is the rising of the river. ይህ ፡ ከባድ ፡ ዝናብ ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችለው ፡ አንዱ ፡ ነገር ፡ የወንዙን ፡ መሙላት ፡ ነው

**rising** (adj.)
*The rising water submerged the town. የውኃው ፡ሙላት ፡ ከተማውን ፡ አለበሰው

**risk** (v.) አባከነ
He risked his entire fortune gambling. ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ በቁማር ፡ አባከነው
*They risked defeat in fighting the larger army. ብንሸነፍም ፡ እንሸነፍ ፡ ብለው ፡ ከኀይለኛ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ገጠሙ
*They risked getting wet. ቢዘንብም ፡ ባወጣ ፡ ያውጣው ፡ ብለው ፡ ሄዱ

**risk (one's) life**
He risked his life to save her. እሷን ፡ ለማዳን ፡ የገዛ ፡ ሕይወቱን ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ጣለ

**risk** (n.)
*There is no risk of your catching cold if you are warmly dressed. ሙቀት ፡ የሚሰጥ ፡ ልብስ ፡ ከለበስክ ፡ ጉንፋን ፡ አይዝህም

**at the risk of his life** በነፍሱ ፡ ቈርጦ
We escaped at the risk of our lives. በነፍሳችን ፡ ቈርጠን ፡ አመለጥን

**run the risk of** ሰ + negative imperfect + አይቀርም
If you go out in this weather, you run the risk of catching cold. በዚህ ፡ ብርድ ፡ ብትወጣ ፡ ጉንፋን ፡ ሳይዝህ ፡ አይቀርም
*He ran the risk of losing all his money. በገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ ቈርጦ ፡ ገባበት

**risky** አስጊ
This action looks risky. ይህ ፡ አድራጎት ፡ አስጊ ፡ ይመስላል

**rite** ሥነ ፡ ሥርዓት
The burial rites were performed last Tuesday. የቀብሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተፈጸመው ፡ ባለፈው ፡ ማክሰኞ ፡ ነው

**last rites of the church**
He received the last rites of the church. ሊሞት ፡ ሲል ፡ ሥጋ ፡ ወደሙን ፡ ቀመሰ

**ritual** (n.)
1. ሥነ ፡ ሥርዓት. The ritual of the Coptic Church is different from the ritual of the Roman Catholic Church. የተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከሮማ ፡ ካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተለየ ፡ ነው
2. የጸሎት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት. There is a certain ritual to be performed on every holiday. በየመቱ ፡ በዓሉ ፡ የጸሎት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይደረጋል

**rival** (v.)
1. ተወዳደረ. No other Ethiopian city rivals Addis Ababa in size. ማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ከተማ ፡ በስፋት ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ አይወዳደርም
2. ተመሳሰለ. The sunset rivaled the sunrise in beauty. በውበት ፡ የፀሐይ ፡ መግባት ፡ ከፀሐይ ፡ መውጣት ፡ ጋር ፡ ተመሳሰለ
3. (ደንበኛ ፡ ለመሳብ) ፡ ተፎካከረ. The two stores rivaled one another in selling at lower prices. ሁለቱ ፡ መደብሮች ፡ በቅናሽ ፡ በመሸጥ ፡ ደንበኛ ፡ ለመሳብ ፡ ተፎካከሩ

**rival** (n.)
1. ተወዳዳሪ. They have always been rivals in racing. ሁልጊዜ ፡ በሩጫ ፡ ተወዳዳሪዎች ፡ ነበሩ
2. ተቀናቃኝ. It seems, by all accounts, that Ras Ali was a rival of King Theodore. እንደሚባለው ፡ ራስ ፡ ዓሊ ፡ የንጉሥ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ተቀናቃኝ ፡ የነበሩ ፡ ይመስላል

**rivalry**
1. ተፎካካሪነት. Their rivalry is well known to all. ተፎካካሪነታቸው ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው
2. ፉክክር. The eruption of violence was due to religious rivalry. የብጥብጡ ፡ በድንገት ፡ መነሣት ፡ ከሃይማኖት ፡ ፉክክር ፡ የተነሣ ፡ ነበር

**river** ወንዝ
The river is full during the rainy season. በክረምት ፡ ወንዙ ፡ ይሞላል

**river basin** የወንዝ ፡ ሸለቆ
The Awash river basin is going to be developed for farming. የአዋሽ ፡ ወንዝ ፡ ሸለቆ ፡ ለእርሻ ፡ ልማት ፡ ሊውል ፡ ነው

**riverbed** የወንዝ ፡ መውረጃ
The riverbed is completely dry in summer. በበጋ ፡ የወንዙ ፡ መውረጃ ፡ ጨርሶ ፡ ይደርቃል

**rivet** (n.) ሪቬት
A rivet is pounded flat on one end when it is hot. ሪቬት ፡ ሲሞቅ ፡ አንደኛው ፡ ጫፍ ፡ ጠፍጣፋ ፡ እንዲሆን ፡ ይመታል

**(be) riveted on** በ --- ላይ ፡ ተተከለ
His attention was riveted on the speaker. ሐሳቡ ፡ በተናጋሪው ፡ ላይ ፡ ተተክሎ ፡ ነበር

**be riveted together** በሪቬት ፡ ተያያዘ
The steel beams are riveted together. የብረቱ ፡ ወራጆች ፡ በሪቬት ፡ ተያይዘዋል

**road** መንገድ
Where does this road go to? ይህ ፡ መንገድ ፡ የሚሄደው ፡ ወዴት ፡ ነው ?

**be on the road** ወደ ፡ ውጭ ፡ ሄደ
He is on the road most of the time. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይሄዳል

**be on the road to** ወደ --- ነው
He is on the road to recovery. ወደ ፡ ማገገሙ ፡ ነው

**be the road to** ወደ --- መራ
Drinking is the road to ruin. መጠጥ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ይመራል
[See also 'uphill']

**roadblock** መሰናከል
Our progress has overcome all roadblocks. እርምጃችን ፡ ማንኛውንም ፡ መሰናከል ፡ አሸንፏል

**set up a roadblock** መንገዱን ፡ ዘጋ
The police set up a roadblock to catch the criminal. ፖሊሶች ፡ ወንጀለኛውን ፡ ለመያዝ ፡ መንገዱን ፡ ዘጉ

**roadway** መንገድ
I found my glasses intact along the roadway. መነጽሬን ፡ ሳይሰበር ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ አገኘሁት

**roam**
1. ተንቀዋለለ. I found him roaming the streets of the city. ከተማ ፡ ውስጥ ፡ በየመንገዱ ፡ ሲንቀዋለል ፡ አየሁት
2. ተዘዋወረ. The gazelles roam over the plains of Ethiopia. አጋዘኖች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሜዳዎች ፡ ላይ ፡ ይዘዋወራሉ

**roar** (v.)
1. ጮኸ. The crowd roared its disapproval of the umpire's decision. ሕዝቡ ፡ ያጫዋቹን ፡ ውሳኔ ፡ በመቃወም ፡ ጮኸ
The train roared past us. ባቡሩ ፡ እየጮኸ ፡ አልፎን ፡ ሄደ
2. አገሣ. The lion roared. አንበሳው ፡ አገሣ
3. ከት ፡ ብሎ ፡ ሣቀ. Everyone roared when Henry acted out the episode with the teacher. ሄንሪ ፡ ከመምህሩ ፡ ጋር ፡ ድርጊቱን ፡ ያለ ፡ ንግግር ፡ በምልክት ፡ ብቻ ፡ ሲያሳይ ፡ ሁሉም ፡ ከት ፡ ብለው ፡ ሣቁ

**roar away** ተፈተለከ
He gunned the motor and roared away. ሞተሩን ፡ አስነሥቶ ፡ ተፈተለከ

**roar out**
*The officer roared out an order. መኰንኑ ፡ ጮክ ፡ ብሎ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ

**roar past** ሽው ፡ ብሎ ፡ አለፈ
The car roared past in a cloud of dust. መኪናው ፡ በአቧራው ፡ ውስጥ ፡ ሽው ፡ ብሎ ፡ አለፈ

**roar with laughter**
They roared with laughter. በሣቅ ፡ ተንከተከቱ

**roar** (n.)
1. ድምፅ. We can hear the roar of the waterfall from here. የፏፏቴውን ፡ ድምፅ ፡ ከዚህ ፡ ልንሰማ ፡ እንችላለን
2. ጩኸት. The cannon's roar could be clearly heard in the capital. የመድፉ ፡ ጩኸት ፡ ከተማ ፡ ሆኖ ፡ በግልጽ ፡ ይሰማ ፡ ነበር
3. ግሣት. The sound I heard sounded more like the roar of a lion. የሰማሁት ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ አንበሳ ፡ ግሣት ፡ ያደላል

**roast** (vt.)
1. ጠበሰ. He didn't roast the meat long enough. ሥጋውን ፡ እስኪበቃው ፡ አልጠበሰውም
2. ቈላ. The servant roasted the coffee lightly. ልጅቱ ፡ ቡናውን ፡ በቀዩ ፡ ቈላችው

**roast** (vi.)
1. ተጠበሰ. The meat roasted in the oven. ሥጋው ፡ ምድጃ ፡ ውስጥ ፡ ተጠበሰ
2. ተቃጠለ. We roasted in the summer heat. በበጋ ፡ ፀሐይ ፡ ተቃጠልን

**roast** (n.) ጥብስ ፡ ሥጋ
The roast is tough today. ጥብሱ ፡ ሥጋ ፡ ዛሬ ፡ አኞ ፡ ሆኗል

**roast** (adj.) ጥብስ
Roast meat is better than boiled meat. ከቅቅል ፡ ይልቅ ፡ ጥብስ ፡ ሥጋ ፡ ይሻላል

**roasted grain** ቆሎ
Children like to eat roasted grain. ልጆች ፡ ቆሎ ፡ መብላት ፡ ይወዳሉ

**roasting pan** መጥበሻ
They used the roasting pan to cook the chicken. ዶሮዋን ፡ በመጥበሻ ፡ ጠበሷት

**rob** (robbed)
1. ዘረፈ ፤ ቀማ. The bandit robbed me of my money. ቀማኛው ፡ ገንዘቤን ፡ ዘረፈኝ ፡ (ቀማኝ)
They robbed and pillaged. ዘረፉም ፡ ገፈፉም
2. አስነጠቀ. Slander robbed him of his honor. ሐሜታ ፡ ክብሩን ፡ አስነጠቀው

**be robbed of** ተቀማ
He was robbed of the rewards of his labor. በላቡ ፡ ያገኘውን ፡ ተቀማ

**robber** ቀማኛ
The robber was caught and imprisoned. ቀማኛው ፡ ተይዞ ፡ ታሰረ

**robbery**
1. ዘራፊነት ፤ ቀማኛነት. He was convicted of robbery. በዘራፊነት ፡ ተፈረደበት
He was accused of robbery. በቀማኛነት ፡ ተከሶ ፡ ነበር
2. ዘረፋ. The witness told of an event antecedent to the robbery. ምስክሩ ፡ ከዘረፋው ፡ በፊት ፡ ስለተደረገው ፡ ነገር ፡ ተናገረ
3. መስረቅ. The young man confessed to a robbery. ወጣቱ ፡ ሰውዬ ፡ መስረቁን ፡ አመነ
4. ስርቆት. He served six years for the robbery. በስርቆት ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ታሰረ
[See also 'victim']

**robe** (v.) አለበሰ
Fog robed the city in white. ጉም ፡ ከተማውን ፡ ነጭ ፡ አለበሰው
**be robed** ለበሰ
The priest was robed in white. ቄሱ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሷል

**robe** (n.)
1. ልብስ. The priestly robes were white. የቄሱ ፡ ልብስ ፡ ነጭ ፡ ነበር
2. ካባ. The imperial robe is colored purple. የንጉሡ ፡ ካባ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ነው
[See also 'clerical']

**robust**
1. ጠንካራ. Only a robust man should undertake to cross the desert on foot. በረኻውን ፡ በእግር ፡ ለማቋረጥ ፡ መሞከር ፡ ያለበት ፡ ጠንካራ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ሙሉ. Her good color indicates robust health. የደም ፡ ግባቷ ፡ ሙሉ ፡ ጤንነቷን ፡ ያሳያል

**rock** (vt.)
1. አወዛወዘ. She rocked the cradle until the baby fell asleep. ሕፃኑ ፡ እስኪተኛ ፡ ድረስ ፡ አልጋውን ፡ አወዛወዘችለት
She rocked the baby in her arms. ሕፃኑን ፡ በእጆቿ ፡ አወዛወዘች
2. አናጋ ፤ አንቀጠቀጠ. The explosion rocked the town. ፈንጂው ፡ ከተማውን ፡ አናጋው ፡ (አንቀጠቀጠው)

**rock** (vi.)
1. ተዋለለ. The boat is rocking in the sea. ጀልባው ፡ በባሕሩ ፡ ላይ ፡ ይዋልላል
2. ተወዛወዘ. He sat in his chair and rocked. ወንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ተወዛወዘ

**rock** (n.)
1. ቋጥኝ. They dragged a heavy rock up the mountainside. አንድ ፡ ትልቅ ፡ ቋጥኝ ፡ ጐትተው ፡ ተራራው ፡ ላይ ፡ አወጡ
2. ድንጋይ. He was throwing rocks. ድንጋይ ፡ ይወረውር ፡ ነበር
3. አለት ፤ ቋጥኝ. She spread her wet dress on a flat rock to dry. ልብሷን ፡ ለማድረቅ ፡ ጠፍጣፋ ፡ አለት ፡ (ቋጥኝ) ፡ ላይ ፡ አሰጣችው

**rock bottom, hit ~** ጥንቡን ፡ ጣለ
Coffee prices hit rock bottom last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ቡና ፡ ጥንቡን ፡ ጣለ
**rock-bottom prices** ርካሽ
Rather than selling at rock-bottom prices, we should wait until the market improves. በርካሽ ፡ ከምንሸጥ ፡ የገበያውን ፡ መሻሻል ፡ ብንጠብቅ ፡ ይሻላል

**rocker** የሚወዛወዝ ፡ ወንበር ፤ ተወዛዋዥ ፡ ወንበር ፤ የሚዋልል ፡ ወንበር
The sick person sits in a rocker, and bathes in the sun. በሽተኛው ፡ በሚወዛወዝ ፡ (በተወዛዋዥ ፤ በሚዋልል) ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ፀሐይ ፡ ይሞቃል

**rocket** መንኰራኲር
The rocket traveled through space to the moon. መንኰራኲሩ ፡ ጠፈርን ፡ አቋርጦ ፡ ወደ ፡ ጨረቃ ፡ ተጓዘ

**rocking chair**, see **rocker**

**rocky**
1. ቋጥኝ ፡ የበዛበት. Rocky cliffs range along the seashore. ቋጥኝ ፡ የበዛባቸው ፡ ገደሎች ፡ በባሕሩ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ ይገኛሉ
2. ድንጋያማ. The road is too rocky for anything but lorries. መንገዱ ፡ ድንጋያማ ፡ ስለሆነ ፡ ከከባድ ፡ መኪናዎች ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ መኪና ፡ ሊሄድበት ፡ አይችልም
3. ኰረኰንች. The mule ambled along the rocky path. በቅሎዋ ፡ በኰረኰንቹ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ አዘገመች
4. የሚነቃነቅ. That table seems a bit rocky to me. ያ ፡ ጠረጴዛ ፡ ትንሽ ፡ የሚነቃነቅ ፡ ይመስለኛል

**rod**
1. ዘንግ. He hangs the clothes on an iron rod. ልብሱን ፡ እብረት ፡ ዘንግ ፡ ላይ ፡ ይሰቅለዋል
2. ማንጠልጠያ ፡ ብረት. These curtain rods are of variable length. የዚህ ፡ መጋረጃ ፡ ማንጠልጠያ ፡ ብረቶች ፡ ርዝመታቸው ፡ ሊለዋወጥ ፡ ይችላል

**rode**, see **ride**

**rodent** የአይጥ ፡ ዝርያ
Rodents destroy grain. የአይጥ ፡ ዝርያዎች ፡ እህል ፡ ይጨርሳሉ

**rogue** ወስላታ
Some rogues broke the store window and stole the goods. ወስላቶች ፡ የመደብሩን ፡ መስኮት ፡ ሰብረው ፡ እቃዎቹን ፡ ሰረቁ

**the little rogue** ተንኰለኛ ፡ ሕፃን
The little rogue has his grandpa's glasses on. ተንኰለኛው ፡ ሕፃን ፡ ያያቱን ፡ መነጽር ፡ አድርጓል

**role**
1. ስፍራ. The clergy plays an important role in Spain. ካህናት ፡ በእስፓኝ ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ አላቸው
2. ቦታ ፤ ክፍል ፤ ስፍራ. He played the title role in Hamlet. በሀምሌት ፡ ውስጥ ፡ መሪውን ፡ ቦታ ፡ (ስፍራ ፤ ክፍል) ፡ ይዞ ፡ ተጫወተ
[See also 'play, sinister']

**roll** (vt.)
1. ጠቀለለ. The movers rolled the rug. ተሸካሚዎች ፡ ምንጣፉን ፡ ጠቀለሉት
2. አንከባለለ. He was rolling a marble in his hand. እጁ ፡ ላይ ፡ ብይ ፡ ያንከባልል ፡ ነበር
Men rolled logs to the river. ሰዎች ፡ ግንድ ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ አንከባለሉ
She rolled her eyes. ዓይኖቿን ፡ አንከባለለች
3. አድቦለቦለ. She rolled the dough into little balls. ሊጡን ፡ በትንንሽ ፡ በትንሹ ፡ አድቦለቦለችው
4. ገፋ. The nurse rolls the baby carriage. ነርሷ ፡ የሕፃኑን ፡ ጋሪ ፡ ትገፋለች
5. አንገላታ. The giant waves rolled the ship. ኀይለኛው ፡ ሞገድ ፡ መርከቡን ፡ አንገላታው

**roll** (vi.)
1. ተንደባለለ. The donkey rolled in the dust. አህያው ፡ አቧራው ፡ ላይ ፡ ተንደባለለ
2. ዋለለ. The ship was rolling heavily. መርከቡ ፡ በኀይል ፡ ይዋልል ፡ ነበር
3. እየተወዛወዘ ፡ ዘለቀ. The ship rolled through the waves. መርከቧ ፡ በማዕበሉ ፡ ውስጥ ፡ እየተወዛወዘች ፡ ዘለቀች
4. ተንከባለለ. The ball rolled under the table. ኳሱ ፡ ወደ ፡ ጠረጴዛው ፡ ሥር ፡ ተንከባለለ
He rolled down the hill. ከዳገቱ ፡ ላይ ፡ ተንከባለለ
5. አጕረመረመ. The thunder rolled through the distance. ነጐድጓዱ ፡ ከሩቅ ፡ አጕረመረመ
6. ተመታ. The drums rolled. ታምቡሩ ፡ ተመታ
7. ተጠቀለለ. The cloth rolls easily. ጨርቁ ፡ በቀላሉ ፡ ይጠቀለላል

**roll along** ተሽከረከረ
The automobile rolls along. አውቶሞቢሉ ፡ ይሽከረከራል

**roll by** ተሽከረከረ
The wagon rolls by. ሰረገላው ፡ ይሽከረከራል

**roll down**
1. አዘቀዘቀ. The hills roll down to the sea. ኰረብታዎቹ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ያዘቀዝቃሉ
2. ኮለል ፡ አለ. The tears rolled down her cheeks. እንባዋ ፡ በጉንጯ ፡ ላይ ፡ ኮለል ፡ አለ

**roll in** ገፋ
The waves rolls in to the beach. ሞገዱ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ገፋ

**roll in money**
He is rolling in money. በሀብት ፡ ተጨማልቋል

**roll into a ball** አድቦለቦለ
He rolled the string into a ball. ክሩን ፡ አድቦለቦለ

**roll on** ሳይታወቅ ፡ አለፈ
The seasons roll on. ወራቶቹ ፡ ሳይታወቅ ፡ ያልፋሉ

**roll oneself up** ጥቅልል ፡ አለ
He rolled himself up in a blanket. በብርድ ፡ ልብስ ፡ ጥቅልል ፡ አለ

**roll up**
1. ጠቀለለ. We rolled up the rug. ስጋጃውን ፡ ጠቀለልነው
He rolled up his blanket, and used it as a headrest. ብርድ ፡ ልብሱን ፡ ጠቅሎ ፡ ትራስ ፡ አደረገው
2. ዐጠፈ. He rolled up his umbrella. ጃንጥላውን ፡ ዐጠፈ

**roll** (n.)
1. ጥቅል. He used up a whole roll of wrapping paper. አንዱን ፡ ጥቅል ፡ የመጠቅለያ ፡ ወረቀት ፡ በሙሉ ፡ ተጠቀመበት
2. ድምፅ. You can still hear the roll of thunder. አሁንም ፡ የነጐድጓዱን ፡ ድምፅ ፡ ልትሰማ ፡ ትችላለህ
3. ድቡልቡል ፡ ዳቦ. He cut the roll in half, and spread butter on it. ድቡልቡሉን ፡ ዳቦ ፡ ሁለት ፡ ላይ ፡ ቈርጦ ፡ ቅቤ ፡ ቀባው

**rolls** መዝገብ
His name was taken off the rolls. ስሙ ፡ ከመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ተፋቀ

**roll of fat**
*He had a thick roll of fat under his chin. አንገቱ ፡ ኩልኩልት ፡ አውጥቷል

**call the roll** ስም ፡ ጠራ
When the teacher called the roll, he answered "present". አስተማሪው ፡ ስም ፡ ሲጠራ ፡ አቤት ፡ አለ

**roll call**
*The roll call showed that six students were absent. ስም ፡ ሲጠራ ፡ ስድስት ፡ ተማሪዎች ፡ ቀሪ ፡ መሆናቸው ፡ ታወቀ

**roller** ተሽከርካሪ ፡ ነገር
Heavy objects can be moved on rollers. ከባድ ፡ እቃዎችን ፡ በተሽከርካሪ ፡ ነገር ፡ ማጓዝ ፡ ይቻላል

**roller skate** መንሸራተቻ ፡ ጫማ
Buy me some roller skates! መንሸራተቻ ፡ ጫማ ፡ ግዛልኝ

**Roman** ሮማዊ

**romance**
1. ማሽኮርመም. His romance with the President's daughter is well known. የፕሬዚዳንቱን ፡ ልጅ ፡ ማሽኮርመሙ ፡ የታወቀ ፡ ነው
2. ስለ ፡ ፍቅር ፡ የተጻፈ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ. She reads romances in French and German. በጀርመንኛና ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ስለ ፡ ፍቅር ፡ የተጻፉ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪኮች ፡ ታነባለች
3. [የጅብዱ ፡ ታሪክ].

**romantic**
*She loves him because he is so romantic. እሱን ፡ የምትወደው ፡ ስለ ፡ ፍቅረኛነት ፡ ስሜቱ ፡ ነው
*She likes romantic tales of love. ስለ ፡ ፍቅር ፡ የሚያወሩ ፡ አስደናቂ ፡ ተረቶች ፡ ትወዳለች

**romp, ~ all over** ቦረቀ
The children romped all over the house. ልጆቹ ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ቦረቁ

**roof** ጣራ ፤ ጣሪያ
The rain leaked through the thatched roof. ዝናቡ ፡ የሣር ፡ ክዳኑን ፡ ጣሪያ ፡ ዘለቀው

**roof of the mouth** ላንቃ
The hot soup burned the roof of my mouth. ትኩሱ ፡ ሾርባ ፡ ላንቃዬን ፡ አቃጠለኝ

**have a roof over one's head**
He doesn't have a roof over his head. ራሱን ፡ ማስገቢያ ፡ ጎጆ ፡ የለውም

**under the same roof** አንድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ
How can you live under the same roof with that woman? ከዚያች ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ እንዴት ፡ አንድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ለመኖር ፡ ትችላለህ ?
[See also 'raise, ridge']

**roofing** የጣሪያ ፡ ክዳን
In America, wood is a common roofing for houses. አሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ ዕንጨት ፡ የተለመደ ፡ የጣሪያ ፡ ክዳን ፡ ነው

**room** (v.) ኖረ
Mr. Parker rooms in the red house. ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ ቀዩ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል
They roomed together while in college. ኮሌጅ ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ ተዳብለው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር

**room** (n.)
1. ክፍል. Where can I get a furnished room? ሙሉ ፡ እቃ ፡ ያለው ፡ ክፍል ፡ የት ፡ አገኛለሁ ?
2. ቦታ. Is there any room left for my baggage? ለጓዜ ፡ ትርፍ ፡ ቦታ ፡ አለ ?
3. ቤት. The whole room laughed. ቤቱ ፡ በሙሉ ፡ ሣቀ

**room and board** ምግብና ፡ መኝታ
How much do you pay for room and board? ለምግብና ፡ ለመኝታ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ትከፍላለህ ?

**room for doubt**
*There is no room for doubt. ጥርጥር ፡ የለውም

**room for improvement**
*There is room for improvement in your work. ሥራህን ፡ ማሻሻል ፡ አለብህ

**ladies' room** የሴቶች ፡ ሽንት ፡ ቤት
Where's the ladies' room? የሴቶች ፡ ሽንት ፡ ቤት ፡ የት ፡ ነው ?

**men's room** የወንዶች ፡ ሽንት ፡ ቤት
Where is the men's room? የወንዶች ፡ ሽንት ፡ ቤት ፡ የት ፡ ነው ?
[See also 'board, seating, suite, underground']

**roomer** ተከራይ
The roomer told the landlady that his room was cold. ተከራዩ ፡ ክፍሉ ፡ ቀዝቃዛ ፡ መሆኑን ፡ ለባለቤቷ ፡ ነገራት

**roomful**
*A roomful of people were at the doctor's office when I arrived. እኔ ፡ ስደርስ ፡ ሐኪሙ ፡ ቢሮ ፡ ውስጥ ፡ ሰው ፡ ግጥም ፡ ብሎ ፡ ነበር

**roommate**
We were roommates in college. ኮሌጅ ፡ ሆነን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ እንኖር ፡ ነበር

**roomy** ሰፋ ፡ ያለ
We have a roomy apartment. ሰፋ ፡ ያለ ፡ አፓርትማ ፡ አለን

**roost** [ወፎች ፡ ሌሊት ፡ የሚያርፉበት ፡ የዛፍ ፡ ቅርንጫፍ]

**rooster** አውራ ፡ ዶሮ
The rooster crows every morning. አውራ ፡ ዶሮ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ይጮኻል

**root** (vt.) አስቀረ
Fear rooted him to the spot. ፍርሃት ፡ እነበረበት ፡ አስቀረው

**root** (vi.)
1. ሥር ፡ ሰደደ. Some plants root more quickly than others. አንዳንድ ፡ ዕፀዋት ፡ ከሌሎች ፡ ይልቅ ፡ ቶሎ ፡ ሥር ፡ ይሰዳሉ
2. አነፈነፈ. Pigs root in the muddy ground for their food. አሳማዎች ፡ በረግረግ ፡ ውስጥ ፡ ምግብ ፡ ፍለጋ ፡ ያነፈንፋሉ

**root around** መሬቱን ፡ ጫረ
The hog rooted around for waste. አሳማው ፡ ቆሻሻ ፡ ፍለጋ ፡ መሬቱን ፡ ጫረ

**root out**
1. አስወጣ. They rooted out all dissident elements in the party. ተቃዋሚዎቹን ፡ በሙሉ ፡ ከፖለቲካው ፡ ቡድን ፡ አስወጧቸው
2. አጠፋ. We must root out illiteracy. ድንቁርናን ፡ ማጥፋት ፡ አለብን

**root through** በረበረ
She rooted through the closet looking for her old shoes. አሮጌ ፡ ጫማዋን ፡ ለመፈለግ ፡ ቁም ፡ ሣጥኑን ፡ በረበረች

**root up** ነቃቀለ I መነቃቀለ
The pigs rooted up the garden. አሳማ ፡ አትክልቱን ፡ ነቃቀለው ፡ (መነቃቀለው)

**be rooted** ሥር ፡ ሰደደ
Christianity is deeply rooted in Ethiopia. ክርስትና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ ሥር ፡ ሰዷል
*Good manners were rooted in him like second nature. መልካም ፡ ጠባይ ፡ አብሮት ፡ የተፈጠረ ፡ ይመስላል

**be rooted to** ከው ፡ ብሎ ፡ ቀረ
He was rooted to the spot by fear. በፍርሃት ፡ አለበት ፡ ከው ፡ ብሎ ፡ ቀረ

**root** (n.)
1. ሥር. The roots of this tree are very deep. የዚህ ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ በጣም ፡ ጥልቅ ፡ ነው
The root of the tooth is decayed. ጥርሱ ፡ ከሥሩ ፡ በሰብሷል
2. ምንጭ. Money is the root of all evil. ገንዘብ ፡ የክፋት ፡ ሁሉ ፡ ምንጭ ፡ ነው
3. መነሻ. Let's get at the root of the matter! ወደ ፡ ነገሩ ፡ መነሻ ፡ እንሂድ
4. እናት. "Go" is the root of "going". «ሄደ» ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የ«መሄድ» ፡ እናት ፡ ነው

**take root** ሥር ፡ ሰደደ
How can you tell whether the tree has taken root? ዛፉ ፡ ሥር ፡ መስደድ ፡ አለመስደዱን ፡ እንዴት ፡ ታውቃለህ?

**rope** (v.) በገመድ ፡ ጠለፈ
The cowboy roped the steer. እረኛው ፡ ኮርማውን ፡ በገመድ ፡ ጠለፈው

**rope off** በገመድ ፡ አጠረ
The police roped off the street for the parade. ፖሊሶች ፡ መንገዱን ፡ ለሰልፉ ፡ በገመድ ፡ አጠሩ

**rope** (n.)
1. ገመድ. He was leading the calf by a rope. ጥጃውን ፡ በገመድ ፡ ይጐትት ፡ ነበር
2. ድሪ. A rope of jewels hung around her neck. ያልማዝ ፡ ድሪ ፡ አንገቷ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሏል

**be at the end of one's rope** የሚያደርገው ፡ ጠፋው
With all savings gone and bills piling up, she was at the end of her rope. ያጠራቀመችው ፡ ስላለቀና ፡ ዕዳም ፡ እየበዛባት ፡ ስለሄደ ፡ የምታደርገው ፡ ጠፋት

**know all the ropes**
He knows all the ropes. መውጫ ፡ መግቢያውን ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል
[See also 'lead']

**rosary** መቍጠሪያ
She is saying her rosary now. መቍጠሪያዋን ፡ እየቈጠረች ፡ ናት

**rose, see rise**

**rose** ጽጌረዳ
The rose smells good. ጽጌረዳ ፡ ጥሩ ፡ ሽታ ፡ አለው

**roster** መዝገብ
Is my name on the roster? ስሜ ፡ መዝገቡ ፡ ላይ ፡ አለ?

**rostrum** መድረክ
The speaker descended from the rostrum. ተናጋሪው ፡ ከመድረኩ ፡ ላይ ፡ ወረደ

**rosy**
1. ጽጌረዳ ፡ የሚመስል. Her rosy cheeks indicate that she is healthy. ጽጌረዳ ፡ የሚመስሉት ፡ ጉንጮቿ ፡ ጤነኛ ፡ መሆኗን ፡ ያመለክታሉ
2. ጥሩ. His rosy future was cut short by severe illness. ጥሩ ፡ ዕድሉ ፡ በሕመሙ ፡ ምክንያት ፡ ተቀጨ

**rot** (rotted), vt. አበሰበሰ
Don't let oil get on the tire because oil rots rubber. ዘይት ፡ ጎማን ፡ ስለሚያበሰብስ ፡ እንዳይነካው ፡ ተጠንቀቅ

**rot** (vi.) በሰበሰ
The fruit is rotting on the tree. ፍሬው ፡ ዛፉ ፡ ላይ ፡ በሰበሰ

**rot** (n.)
*Rot has affected this part of the tree. የዛፉ ፡ ይኸኛው ፡ ወገን ፡ በስብሷል

**rotary**
*The rotary motion of the wheel throws off drops of water. ጎማው ፡ ሲሽከረከር ፡ ውኃ ፡ ይረጫል

**rotate** (vt.) እየለዋወጠ ፡ ዘራ
Farmers rotate crops. ገበሬዎች ፡ ዘር ፡ እየለዋወጡ ፡ ይዘራሉ

**rotate** (vi.)
1. ዞረ. The earth rotates around the sun. መሬት ፡ በፀሐይ ፡ ዙሪያ ፡ ትዞራለች
2. ተለዋወጠ. The presidency of the club rotates every year. የክበቡ ፡ ፕሬዚዳንትነት ፡ በየዓመቱ ፡ ይለዋወጣል

**rotation** ተራ
Chairmanship in the club is by rotation. እዚህ ፡ ክበብ ፡ ውስጥ ፡ ሊቀ ፡ መንበርነት ፡ በተራ ፡ ነው
*What is the rotation time of the earth? መሬት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለመሽከርከር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይወስድባታል ?
*Crop rotation improves the soil. ሰብል ፡ ሲለዋወጥ ፡ መሬት ፡ ያፋፋል

**rote, by** ~ በቃል
He learns poetry by rote. ግጥምን ፡ በቃል ፡ ያጠናል

**rotten**
1. የበሰበሰ. These rotten eggs smell bad. እነዚህ ፡ የበሰበሱ ፡ እንቁላሎች ፡ ይገማሉ
2. የተበላሸ. The rotten administration of the school improved. የተበላሸው ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አስተዳደር ፡ ተሻሻለ

**be rotten** በሰበሰ
The beams of the bridge are rotten through and through. የድልድዩ ፡ አግዳሚዎች ፡ ጨርሰው ፡ በስብሰዋል

**rotting** የተላ
The stink of rotting meat pervaded the air. የተላው ፡ ሥጋ ፡ ሽታ ፡ አየሩን ፡ ዐጠነው

**rotund** ወፍራም
A large, rotund man came to see you. አንድ ፡ ትልቅ ፡ ወፍራም ፡ ሰው ፡ ሊጠይቅህ ፡ መጣ

**rough** (v.), **rough it** በችግር ፡ ኖረ
The travelers had to rough it when they got into the jungle. መንገደኞቹ ፡ እጫካው ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በችግር ፡ መኖር ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው

**rough up** ደበደበ
The gangsters roughed up their victim. ወሮበሎቹ ፡ የያዙትን ፡ ሰውዬ ፡ ደበደቡት

**rough** (adj.)
1. ሻካራ. The rough fur of a camel makes it unsuitable for clothing. የግመል ፡ ቆዳ ፡ ሻካራ ፡ በመሆኑ ፡ ለልብስ ፡ አይሆንም
2. ያልተላገ. The bench is made of rough planks. መቀመጫው ፡ የተሠራው ፡ ካልተላገ ፡ ሳንቃ ፡ ነው
3. ኰረኰንች ፤ ወጣ ፡ ገባ ፡ ያለ. Don't drive this small car over rough roads! ይችን ፡ ትንሽ ፡ መኪና ፡ ኰረኰንች ፡ (ወጣ ፡ ገባ ፡ ያለ) ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ አትንዳት
4. ወፍራም. This fruit has a rough skin. ይህ ፡ ፍሬ ፡ ወፍራም ፡ ልጣጭ ፡ አለው
5. ከባድ. She isn't used to such rough work. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ አለመደችም
6. ጐርናና. He has a rough voice. ጐርናና ፡ ድምፅ ፡ አለው
7. በጣም ፡ አስጨናቂ. We had a rough time when we took the exam. ፈተናውን ፡ ስንፈተን ፡ ያሳለፍነው ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ አስጨናቂ ፡ ነበር
8. ጠቅላላ. This will give you a rough idea. ይህ ፡ ጠቅላላ ፡ ሐሳብ ፡ ይሰጥሃል
9. ባለጌ ፤ የብልግና. His kind act balances his rough manner. የደግነት ፡ ሥራው ፡ ባለጌ ፡ ጠባዩን ፡ ይሸፍንለታል
The student was punished for using rough language. ተማሪው ፡ የብልግና ፡ ቃል ፡ በመናገሩ ፡ ተቀጣ
10. ረብሻ ፡ የበዛበት. Rough play resulted in two players getting broken legs. ጨዋታው ፡ ረብሻ ፡ የበዛበት ፡ ስለነበር ፡ ሁለት ፡ ተጫዋቾች ፡ እግራቸውን ፡ ተሰበሩ
11. ምቾት ፡ የጐደለ(ው). The book describes the rough life of the pioneers. መጽሐፉ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ሰፋሪዎች ፡ ኑሮ ፡ ምቾት ፡ የጐደለው ፡ እንደነበር ፡ ይገልጻል
12. (= adv.) ከሞላ ፡ ጐደል. This is a rough sketch of his book. ይህ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ የሱ ፡ መጽሐፍ ፡ አስተዋጽኦ ፡ ነው

**rough behavior** (= one of rough behavior) **አመለ ፡ መጥፎ**
The child is not liked because of his rough behavior. ልጁ ፡ የማይወደደው ፡ አመለ ፡ መጥፎ ፡ ስለሆነ ፡ ነው

**rough life, rough times** ችግር ፤ የችግር ፡ ጊዜ
He leads a rough life. በችግር ፡ ይኖራል
There are rough times ahead. ወደ ፡ ፊት ፡ የችግር ፡ ጊዜ ፡ አለ

**rough weather** ያየሩ ፡ መበላሸት
Rough weather kept the planes from leaving. ያየሩ ፡ መበላሸት ፡ አውሮፕላኖቹ ፡ እንዳይነሡ ፡ አገዳቸው

**be rough**
1. (= active) አሻከረ. +Why are your hands rough? እጅህን ፡ ምን ፡ አሻከረው ?
2. ተናወጠ. The water is pretty rough today. ባሕሩ ፡ ዛሬ ፡ ተናውጧል

**have a rough flight** በጣም ፡ ነቀነቀ
The plane had a rough flight in the storm. በኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ ውስጥ ፡ አውሮፕላኑ ፡ በጣም ፡ ይነቀንቅ ፡ ነበር

## roughen አሻከረ
The wind roughened his skin. ነፋስ ፡ ቆዳውን ፡ አሻከረው

## roughly
1. በኀይለ ፡ ቃል. He spoke roughly to his wife. ሚስቱን ፡ በኀይለ ፡ ቃል ፡ ተናገራት
2. በግምት. Can you tell me roughly how much it will be? ስንት ፡ እንደሚሆን ፡ በግምት ፡ ልትነግረኝ ፡ ትችላለህ ?

**treat roughly** አጕሳቈለ
He treats his wife roughly. ሚስቱን ፡ ያጕሳቍላታል
[See also 'handle']

## round (v.)
1. ክብ ፡ አደረገ. The carpenter rounded the corners of the table. አናጢው ፡ የጠረጴዛውን ፡ ጠርዝ ፡ ክብ ፡ አደረገው
2. አሞጠሞጠ. He rounded his lips and whistled. አፉን ፡ አሞጥሙጦ ፡ አፏጨ
3. ዞረ. When the train rounded the curb, it blew the whistle. ባቡሩ ፡ መጠምዘዣውን ፡ ሲዞር ፡ ጥሩምባ ፡ ነፋ
4. አድበለበለ. Age rounded her figure. እርጅና ፡ ቅርጿን ፡ አድበለበለው

**round off** አስተካከለ
Round off the edges a little! ጠርዙን ፡ ትንሽ ፡ አስተካክለው

**round out** አሟላ(ለት)
The new stamp rounded out his collection. አዲሱ ፡ ቴምብር ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የሰበሰበውን ፡ አሟላለት

**round up** ሰበሰበ
The leader rounded up the tourists, and herded them back on the bus. አስጐብኚው ፡ ቱሪስቶቹን ፡ ሰብስቦ ፡ ወደ ፡ አውቶቡሱ ፡ ውስጥ ፡ አስገባቸው

## round (n.) ዙር
He was knocked out in the first round. በመጀመሪያው ፡ ዙር ፡ ወደቀ

**a round of drinks**
He paid for a round of drinks. ሁሉንም ፡ ሰው ፡ አንዳንድ ፡ ጋበዘ

**make the rounds**
1. እየተዘዋወረ ፡ ጠበቀ. The watchman makes his rounds of the building. ዘበኛው ፡ ሕንጻውን ፡ እየተዘዋወረ ፡ ይጠብቃል
2. እየዞረ ፡ በሽተኞቹን ፡ ጐበኘ. The doctor is making the rounds. ሐኪሙ ፡ እየዞረ ፡ በሽተኞቹን ፡ በመጐብኘት ፡ ላይ ፡ ነው
3. ክልል ፡ ቃኘ. The police officer made his rounds. የፖሊሱ ፡ መኰንን ፡ ክልሉን ፡ ቃኘ
*The book is making the rounds. መጽሐፉን ፡ ሁሉም ፡ ይቀባበለዋል

**round** (adj.)
1. ሙሉ ፡ ቀራቢ ፤ ሙሉ ፡ የተጠጋጋ. Five hundred is a round number for 498. ለ፬፻፺፰ ፡ ሙሉው ፡ ቀራቢ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻ ፡ ነው
Leave out the fractions and give me the round number. ክፍልፋዮቹን ፡ ትተህ ፡ ሙሉ ፡ የተጠጋጋውን ፡ ቁጥር ፡ ንገረኝ
2. ሙሉ. A round dozen eggs were in the basket. አንድ ፡ ደርዘን ፡ ሙሉ ፡ እንቁላል ፡ ቅርጫት ፡ ውስጥ ፡ ነበር
3. ድቡልቡል. It was round like a ball. እንደ ፡ ኳስ ፡ ድቡልቡል ፡ ነበር
4. ክብ. They have a round table in the dining room. ምግብ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ክብ ፡ ጠረጴዛ ፡ አላቸው
5. ከፍ ፡ ያለ. He paid a round price for the house. ለቤቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ከፈለ
*The polka is a round dance. ፖልካ ፡ እየዞሩ ፡ የሚደንሱት ፡ ዳንስ ፡ ነው

**in good round terms** በግልጽ
The boy's father scolded him in good round terms. የልጁ ፡ አባት ፡ በግልጽ ፡ ወቀሰው

**in round figures** በግምት ፡ - - - ያህል
In round figures, there were two hundred

people present. በግምት ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ያህል ፡ ነበሩ

**round** (adv.) በሙሉ
He works the whole year round. ዓመቱን ፡ በሙሉ ፡ ይሠራል
*The tree measures 50 inches round. የዛፉ ፡ ዙሪያ ፡ አምሳ ፡ ኢንች ፡ ይሆናል

**come round** እሺ ፡ አለ
He will come round if you keep pressing him. ከገፋፋኸው ፡ እሺ ፡ ይላል

**fall round one** ባካባቢው ፡ አረፈ
Bullets fell round him, but he was not hurt. ብዙ ፡ ጥይት ፡ ባካባቢው ፡ ቢያርፍም ፡ አልተመታም

**go round**
1. ዞሮ ፡ ሄደ. We went round by the store to get to his house. ቤቱ ፡ ለመድረስ ፡ በመደብሩ ፡ በኩል ፡ ዞረን ፡ ሄድን
2. ነፈሰ. A report is going round that the school will be closed. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ይዘጋል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ይነፍሳል

**look round and round** ዞር ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ ተመለከተ
He looked round and round, but could not discover where the noise was coming from. ዞር ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ ተመለከተ ፤ ሆኖም ፡ ድምፁ ፡ ከየት ፡ እንደሚመጣ ፡ ለማወቅ ፡ አልቻለም
[See also 'year']

## roundabout
1. ዘወርዋራ. He tried to explain in a roundabout way why he was not able to come. ለመምጣት ፡ ያልቻለበትን ፡ ምክንያት ፡ በዘወርዋራ ፡ መንገድ ፡ ለመግለጽ ፡ ሞከረ
2. የዙሪያ. They took a roundabout way to get there. እዚያ ፡ ለመድረስ ፡ በዙሪያ ፡ መንገድ ፡ ሄዱ

**in a roundabout way** የስሚ ፡ ስሚ
I heard the news in a roundabout way. ነገሩን ፡ የስሚ ፡ ስሚ ፡ ሰማሁት

## roundly በጣም
He was roundly scolded. በጣም ፡ ተወቀሰ

## round-trip ደርሶ ፡ መልስ
He bought a round-trip ticket. ደርሶ ፡ መልስ ፡ ቲኬት ፡ ገዛ
[See also 'ticket']

## roundup (n.)
*The roundup is watched by many people. እረኞቹ ፡ ከብቶቹን ፡ ሲመልሱ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር

## rouse
1. አነቃ. The noise failed to rouse him. ጩኸቱ ፡ ሊያነቃው ፡ አልቻለም
2. ስሜት ፡ ቀሰቀሰ. The speaker tried to rouse the audience. ተናጋሪው ፡ የአድማጮቹን ፡ ስሜት ፡ ሊቀሰቅስ ፡ ሞከረ

## rout (v.) ድል ፡ አድርጎ ፡ በታተነ
Our troops routed the enemy. ጦራችን ፡ ጠላትን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ በታተነው

**rout out of bed** ቀሰቀሰ
The farmer routed his sons out of bed at five o'clock. ገበሬው ፡ ልጆቹን ፡ ከንጋቱ ፡ በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ቀሰቀሳቸው

## rout (n.) ቅጥ ፡ የሌለው ፡ ሽሽት
The enemy's retreat turned into a rout. የጠላት ፡ ማፈግፈግ ፡ ቅጥ ፡ የሌለው ፡ ሽሽት ፡ ሆነ

## route (v.)
1. አስኬደ. They had to route the plane through Dire Dawa because the Addis Ababa airport was closed due to the fog. የአዲስ ፡ አበባው ፡ አውሮፕላን ፡ ማቢያ ፡ በጉም ፡ በመሸፈኑ ፡ አውሮፕላኑን ፡ በድሬዳዋ ፡ በኩል ፡ ማስኬድ ፡ ነበረባቸው
2. እንዲሄድ ፡ አደረገ. The travel bureau routed us by way of the Grand Canyon on our trip West. ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ስንሄድ ፡ የማመላለሻው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በግራንድ ፡ ካንዮን ፡ በኩል ፡ እንድንሄድ ፡ አደረገን

## route (n.) መንገድ
Which route did you take? በየትኛው ፡ መንገድ ፡ ሄድክ ?
[See also 'devious']

## routine ልማድ
Getting up and going to bed are parts of your daily routine. መተኛትና ፡ መነሣት ፡ በየቀኑ ፡ ከምታደርጋቸው ፡ ልማዶች ፡ መካከል ፡ ናቸው
*The routine of preparing breakfast bores her. ነጋ ፡ ጠባ ፡ ቁርስ ፡ ማዘጋጀት ፡ ይሰለቻታል
*Year in, year out, the same routine. ከዓመት ፡ እስከ ፡ ዓመት ፡ ያው ፡ ይደጋገማል

## rove ተዘዋወረ
He loves to rove over the fields and through the woods. በየሜዳውና ፡ በየጫካው ፡ ውስጥ ፡ መዘዋወር ፡ ይወዳል

**(one's) eyes roved** በዓይኑ ፡ ቃኘ
Looking for a familiar face at the party, his eyes roved over the many guests. የሚያውቀው ፡ ሰው ፡ እንዳለ ፡ በመፈለግ ፡ በዓይኑ ፡ በግብዣው ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ እንግዶች ፡ ቃኛቸው

**row** (vt.) ቀዘፈ
Can you row a boat? ጀልባ ፡ መቅዘፍ ፡ ትችላለህ ?

**row across** በጀልባ ፡ አቋረጠ
We rowed across the lake. ሐይቁን ፡ በጀልባ ፡ አቋረጥን

**row one across** እየቀዘፈ ፡ አሻገረ
I will row you across the lake. ሐይቁን ፡ እየቀዘፍኩ ፡ አሻግርሃለሁ

**row**, n. (rhymes with 'low')
1. ተርታ. The children were sitting in a row. ልጆቹ ፡ በተርታ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር
2. መደዳ. The row of houses near the factory burned down last night. ትላንትና ፡ ማታ ፡ ፋብሪካው ፡ አጠገብ ፡ የነበሩት ፡ መደዳ ፡ ቤቶች ፡ ተቃጠሉ
3. ረድፍ. There are three rows of seats in this room. እዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ ረድፍ ፡ መቀመጫዎች ፡ አሉ

**in a row** አከታትሎ
He won three times in a row. ሦስቴ ፡ አከታትሎ ፡ አሸነፈ

**row**, n. (rhymes with 'how')
1. ጫጫታ. I can't study with all this row going on outside my window. መስኮቴ ፡ አጠገብ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ጫጫታ ፡ እያለ ፡ ላጠና ፡ አልችልም
2. እምባጓሮ. He got into a row with the guard. ከዘበኛው ፡ ጋር ፡ እምባጓሮ ፡ ገጠመ

**make a row** ተንጫጫ
My neighbors made a terrible row last night. ጎረቤቶቼ ፡ ትላንት ፡ ማታ ፡ ክፉኛ ፡ ተንጫጩ

**rowdy** የብልግና
Rowdy behavior will be punished. የብልግና ፡ ጠባይ ፡ ያስቀጣል

**royal**
1. ንጉሣዊ. The English royal family lives in seclusion. የእንግሊዝ ፡ ንጉሣውያን ፡ ቤተሰቦች ፡ በገለልተኝነት ፡ ይኖራሉ
2. የንጉሥ. The crown and the scepter are royal insignias. ዘውድና ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ የንጉሥ ፡ አርማ ፡ ናቸው
3. ግርማ ፡ ያለው. The lion is a royal beast. አንበሳ ፡ ግርማ ፡ ያለው ፡ አውሬ ፡ ነው
4. ከፍ ፡ ያለ. He received a royal welcome. ከፍ ፡ ያለ ፡ አቀባበል ፡ ተደረገለት

**His Royal Highness** ልዑል
His Royal Highness, Prince John, arrives Tuesday. ልዑል ፡ ጆን ፡ ማክሰኞ ፡ ይገባሉ

**royalty**
1. ንጉሥነት. The crown is an attribute of royalty. ዘውድ ፡ የንጉሥነት ፡ መለዮ ፡ ነው
2. ንጉሣውያን ፡ ቤተ ፡ ሰብ. The play was performed in the presence of royalty. ቲያትሩ ፡ ንጉሣውያን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በተገኙበት ፡ ታየ
3. የደራሲ ፡ ዋጋ. He gets a royalty of 10% for his book. ለመጽሐፉ ፡ ከመቶ ፡ ዐሥር ፡ የደራሲ ፡ ዋጋ ፡ ያገኛል

**rub** (rubbed), vt.
1. አሸ. Rub his back with alcohol! ጀርባውን ፡ በአልኮል ፡ እሸው
2. አሻሸ. He rubbed his hands to keep warm. ለማሞቅ ፡ እጁን ፡ አሻሸ
3. ወለወለ. Keep rubbing it until it shines. እስኪያብረቀርቅ ፡ ድረስ ፡ ወልውለው
4. ላጠ. These shoes rub my heel. ይህ ፡ ጫማ ፡ ተረከዜን ፡ ይልጠኛል
How did you rub the skin off your knee? ጉልበትህን ፡ ምን ፡ ላጠው ?

**rub** (vi.)
1. ታከከ. The cat rubbed against my leg. ድመቷ ፡ እግሬ ፡ ላይ ፡ ታከከች
2. ተፈጋፈገ. What is the tire rubbing against? ጎማው ፡ ከምን ፡ ጋር ፡ ይፈጋፈጋል ?

**rub it in** እየደጋገመ ፡ አወራ
I know you're a better player than I, but you needn't rub it in. ከኔ ፡ የተሻልክ ፡ ተጫዋች ፡ መሆንህን ፡ አውቃለሁ ፡ ግን ፡ እየደጋገምክ ፡ ማውራት ፡ አያሻም

**rub off** ፈገፈገ
After rubbing off the dirt, he saw that it was an old coin. ቆሻሻውን ፡ ከፈገፈገ ፡ በኋላ ፡ አሮጌ ፡ ገንዘብ ፡ መሆኑን ፡ ተገነዘበ

**rub off on one**
*French manners seem to have rubbed off on him while he was in Paris. ፓሪስ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ የፈረንሳይ ፡ ባህል ፡ ሸው ፡ ያለበት ፡ ይመስላል

**rub out** ሰረዘ
You forgot to rub out the price. ዋጋውን ፡ መሰረዝ ፡ ረሳህ

**rub over** ጠረገ
The maid rubs a cloth over the mirror. ገረዲቱ ፡ መስታወቱን ፡ በጨርቅ ፡ ትጠርጋለች

**rub raw** ፈተገ
The bridle rubbed the horse's cheek raw. ልጓሙ ፡ የፈረሱን ፡ አገጭ ፡ ፈተገው

**rub the wrong way**
*He tries to be friendly, but somehow whatever

he says rubs me the wrong way. ለመወዳጀት ፡ ይሞክራል ፡ ሆኖም ፡ ንግግሩ ፡ ሰውን ፡ ይጐንጣል

**rubber**
1. ላስቲክ. The tire is made of rubber. ጎማው ፡ የተሠራው ፡ ከላስቲክ ፡ ነው
2. ላጲስ. I erased it with a rubber. በላጲስ ፡ አጠፋሁት

**rubbers**
የጎማ ፡ ጫማ. It is best to wear rubbers in rainy weather. በክረምት ፡ የጎማ ፡ ጫማ ፡ ማድረግ ፡ ጥሩ ፡ ነው

**rubber band** ላስቲክ
The papers are held together by a rubber band. ወረቀቶቹ ፡ በላስቲክ ፡ ታስረዋል

**rubber stamp** ማኅተም
I have a rubber stamp with my name and address on it. ስሜና ፡ አድራሻዬ ፡ ያለበት ፡ ማኅተም ፡ አለኝ

**rubbish** ጥራጊ
The men didn't collect the rubbish today. ሰዎቹ ፡ ዛሬ ፡ ጥራጊ ፡ አላነሡም

**be rubbish** አይረባም
This book is rubbish. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ አይረባም

**lot of rubbish**
*Gossip is often a lot of rubbish. ለወሬ ፡ የለው ፡ ፍሬ

**rubble** ፍርስራሽ
The rubble of the damaged building blocked the street. የሕንጻው ፡ ፍርስራሽ ፡ መንገዱን ፡ ዘጋው

**turn to rubble**
1. አመድ ፡ አደረገ. The bombs turned the building to rubble. ቦምቡ ፡ ቤቱን ፡ አመድ ፡ አደረገው
2. አፈራረሰ. The wreckers turned the building to rubble. የሕንጻ ፡ ማፍረሻ ፡ መኪናዎቹ ፡ ሕንጻውን ፡ አፈራረሱት

**rudder** መቅዘፊያ
They guided the boat by means of a rudder. ጀልባውን ፡ በመቅዘፊያ ፡ መሩት

**rude**
1. ባለጌ. The rude student was expelled from school. ባለጌው ፡ ልጅ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ተባረረ
2. እንደነገሩ ፡ የተሠራ. He plows the field with a rude wooden plow. ማሳውን ፡ የሚያርሰው ፡ እንደነገሩ ፡ በተሠራ ፡ የዕንጨት ፡ ማረሻ ፡ ነው

**be rude** ከበድ ፡ አለ
Life is rude to farmers who have few tools. በቂ ፡ መሣሪያ ፡ ለሌላቸው ፡ ገበሬዎች ፡ ኑሮ ፡ ከበድ ፡ ይላል

**have a rude shock** ደነገጠ
John had a rude shock when the other boys poured a pail of water on him. ጆን ፡ ልጆቹ ፡ አንድ ፡ ባልዲ ፡ ውኃ ፡ ባፈሰሱበት ፡ ጊዜ ፡ ደነገጠ

**rudely** በኀይለ ፡ ቃል
He was provoked to answer rudely. በኀይለ ፡ ቃል ፡ እንዲመልስ ፡ ሁኔታው ፡ አስገደደው

**rudeness** ብልግና
His rudeness is inexcusable. ብልግናው ፡ የማይታለፍ ፡ ነው

**rudiment**
*This animal has the rudiment of a tail. ይህ ፡ እንስሳ ፡ ለምልክት ፡ ያህል ፡ ጭራ ፡ አለው

**rudiments**
1. ላይ ፡ ላዩን. He knows only the rudiments of Amharic grammar. ያማርኛ ፡ ሰዋስውን ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ብቻ ፡ ያውቃል
2. መሠረታዊ ፡ ደንቦች. We are making efforts to teach the local people the rudiments of sanitation. ያገሩን ፡ ሰዎች ፡ የጽዳት ፡ ጥበቃ ፡ መሠረታዊ ፡ ደንቦችን ፡ ለማስተማር ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነን

**rudimentary** መጠነኛ
I have only a rudimentary knowledge of mechanics. ስለ ፡ መካኒክ ፡ መጠነኛ ፡ ዕውቀት ፡ አለኝ

**rue**
1. አዘነ. He rued his angry words. በቁጣ ፡ በመናገሩ ፡ አዘነ
2. ረገመ. You'll rue the day you insulted me. እኔን ፡ የሰደብክበትን ፡ ቀን ፡ ትረግማለህ

**rueful** የጸጸት
She gave me a rueful look when she found out I was right. ልክ ፡ መሆኔን ፡ ስታውቅ ፡ በጸጸት ፡ ዓይን ፡ ተመለከተችኝ
*She was a rueful sight. ታሳዝን ፡ ነበር

**ruffian** ወሮበላ
A gang of ruffians attacked a policeman. ወሮበሎች ፡ አንድ ፡ ፖሊስ ፡ ደበደቡ

**ruffle** (v.)
1. አንቀሳቀሰ. The lake was placid; not a breeze ruffled its surface. ምንም ፡ የሚያንቀሳቅሰው ፡ ነፋስ ፡ ስላልነበረ ፡ ሐይቁ ፡ ፍጹም ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ነበር

2. በታተነ. She ruffled his hair. ጸጉሩን ፡ በታተነ ችበት

3. ኩፍ ፡ አደረገ. The hen ruffled her feathers at the sight of the dog. ዶሮዋ ፡ ውሻውን ፡ ሲታይ ፡ ላባዋን ፡ ኩፍ ፡ አደረገች

4. ቅር ፡ አሰኘ. Our late arrival ruffled our hostess. ዘግይተን ፡ መድረሳችን ፡ ጋባዣችንን ፡ ቅር ፡ አሰኛት

5. አናወጸ. The insult failed to ruffle his composure. ስድቡ ፡ እርጋታውን ፡ አላናወጸውም

**ruffle** (n.) ዘርፍ
The skirt has a row of ruffles near the hem. ቀሚሱ ፡ ጠርዙ ፡ ላይ ፡ ዘርፍ ፡ አለው

**rug** ስጋጃ
The rug is wearing out. ስጋጃው ፡ ወደ ፡ ማርጀቱ ፡ ነው

**rugged**

1. ወጣ ፡ ገባ. The countryside is very rugged. ገጠሩ ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ ነው

2. ጠንካራ. Pioneers were rugged people. የመጀመሪያዎቹ ፡ ሰፋሪዎች ፡ ጠንካራ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ

3. የመከራ. He leads a rugged life. ኑሮው ፡ የመከራ ፡ ነው

4. አስቸጋሪ. Rugged weather allows only the hardiest people to survive. ባስቸጋሪ ፡ ያየር ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ለመኖር ፡ የሚችሉ ፡ ጠንካራ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**ruin** (v.)

1. አጠፋ. The frost will ruin the crop. ውርጩ ፡ ሰብሉን ፡ ያጠፋዋል
Gambling ruined him. ቁማር ፡ አጠፋው

2. ጐዳ. He is ruining his health. ጤናውን ፡ ይጐዳል
The heavy taxes ruined the merchant. ከፍተኛ ፡ ታክስ ፡ ነጋዴውን ፡ ጐዳ

3. አበላሸ. They ruined their clothes by playing in the mud. ጭቃ ፡ ውስጥ ፡ ሲጫወቱ ፡ ልብሳቸውን ፡ አበላሹት
The heavy trucks have ruined the road. ከባድ ፡ መኪና ፡ መንገዱን ፡ አበላሸው

4. አከሰረ. The bad management of that business nearly ruined it. የዚያ ፡ ንግድ ፡ መጥፎ ፡ አመራር ፡ ለጥቂት ፡ አክስሮት ፡ ነበር

**be ruined**

1. ችግር ፡ ላይ ፡ ወደቀ. They were ruined by the war. በጦርነቱ ፡ ምክንያት ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ወደቁ

2. ተበላሸ. His new suit is completely ruined. አዲሱ ፡ ልብሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ተበላሽቷል

3. ጐደፈ. His good name was ruined by one careless act. ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ዝንጋታ ፡ ጥሩ ፡ ስሙ ፡ ጐደፈ

**ruin** (n.)

1. ጉዳት. The ruin of property caused by the earthquake was enormous. በመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ምክንያት ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ከፍተኛ ፡ ነበር

2. ጥፋት. War breeds misery and ruin. ጦርነት ፡ ችግርና ፡ ጥፋትን ፡ ያስከትላል

**ruins** ፍራሽ
They discovered the ruins of an old temple. ያንድ ፡ የጥንት ፡ መቅደስ ፡ ፍራሽ ፡ አገኙ

**be a ruin** ፈራረሰ
The bombed church was a ruin. በቦምብ ፡ የተመታው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፈራረሰ

**be in ruins** ፈረሰ
The city is in ruins. ከተማው ፡ ፈርሷል

**be one's ruin** አጠፋ
Gambling was his ruin. ቁማር ፡ አጠፋው

**fall in ruins** ፈራረሰ
The palace has fallen in ruins. ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ፈራረሰ

**go to ruin** ፈራረሰ
The house had gone to ruin from neglect. በቸልታ ፡ ምክንያት ፡ ቤቱ ፡ ፈራረሰ

**lie in ruins** እንደፈራረሰ ፡ ቆየ
The towns lay in ruins for years after the war. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ከተማዎቹ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ እንደፈራረሱ ፡ ቆዩ
[See also 'lapse']

**ruinous**

1. ጥፋት ፡ የሚያደርስ. Ruinous floods occurred. ጥፋት ፡ የሚያደርስ ፡ ጐርፍ ፡ ጐረፈ

2. ጐጂ. His expenditures proved ruinous. ወጪው ፡ ጐጂ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

**be in a ruinous state**
The house is in a ruinous state. ቤቱ ፡ በመፍረስ ፡ ላይ ፡ ነው

**rule** (vt.)

1. ገዛ. They wanted to rule the entire world. ዓለምን ፡ በሙሉ ፡ ለመግዛት ፡ ፈለጉ

2. አስተዳደረ. The patriarch of the family rules with an iron hand. ባለቤቱ ፡ ቤተሰቡን ፡ በጥብቅ ፡ ያስተዳድራል

3. ፈረደ. The judge ruled that Parker must pay the damages. ዳኛው ፡ ፓርከር ፡ ያጠፋውን ፡ መክፈል ፡ አለበት ፡ ሲሉ ፡ ፈረዱ

4. አሠመረ. He used a ruler to rule the paper. ወረቀቱን ፡ በማሥመሪያ ፡ አሠመረ
5. ገታ. You should learn how to rule your temper. ንዴትህን ፡ መግታት ፡ መልመድ ፡ አለብህ

**rule** (vi.)
*He rules over a great empire. ግዛቱ ፡ ሰፊ ፡ ነው

**rule against** ፈረደበት
The judge ruled against them. ዳኛው ፡ ፈረደባቸው

**(be) ruled by** ተመራ
Don't be ruled by your dislike of him! ለሱ ፡ ባለህ ፡ ጥላቻ ፡ አትመራ

**rule (on)** አጸደቀ
The court ruled on the genuineness of the will. ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የኑዛዜውን ፡ እውነተኛነት ፡ አጸደቀ

**rule out**
*This doesn't rule out other possibilities. ይህን ፡ ማለት ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ የለም ፡ ማለት ፡ አይደለም

**rule out of order**
*The chairman ruled the motion out of order. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ ከሥርዓት ፡ ውጪ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ሰረዘው

**rule** (n.)
1. ደንብ. You must stick to the rules. ደንቡን ፡ መከተል ፡ አለብህ
2. ሕግ. Did you study the rules of grammar? የሰዋስውን ፡ ሕጎች ፡ ተምረሃል ?
3. የተለመደ. Fair weather is the rule in May. በግንቦት ፡ ወር ፡ ደኅና ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፡ የተለመደ ፡ ነው
4. አገዛዝ. This country was never under foreign rule. ይህ ፡ አገር ፡ በውጭ ፡ አገዛዝ ፡ ሥር ፡ ወድቆ ፡ አያውቅም

**against the rule** ክልክል
It is against the rules to smoke in class. ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ማጤስ ፡ ክልክል ፡ ነው

**as a rule**
1. ዘወትር. As a rule, I go to school by car. ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዘወትር ፡ በመኪና ፡ እሄዳለሁ
2. ፍጹም. As a rule, I don't drink. ፍጹም ፡ አልጠጣም

**(be the) exception to the rule** መደበኛውን ፡ ሕግ ፡ የማይከተል ፡ ነው
In Amharic, the subject placed after the verb is the exception to the rule. ባማርኛ ፡ ባለቤት ፡ ግስን ፡ ተከትሎ ፡ መጻፍ ፡ መደበኛውን ፡ ሕግ ፡ የማይከተል ፡ ነው

**no exception to the rule**
*There will be no exception to the rule that college applicants must have high school diplomas. ኮሌጅ ፡ ለመግባት ፡ የሚያምለክቱ ፡ ሁሉ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ እንዲኖራቸው ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚለው ፡ ደንብ ፡ የማይሻር ፡ ነው
[See also 'breach, thumb']

**ruler**
1. ገዢ. He has been an absolute ruler. ፈላጭ ፡ ቆራጭ ፡ ገዢ ፡ ነበር
2. ማሥመሪያ. The ruler is too short. ማሥመሪያው ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ ነው

**ruling** (n.) ውሳኔ
The ruling of the court was published in the paper. የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ በጋዜጣ ፡ ተገለጸ

**ruling** (adj.)
1. የገዢዎች. The ruling classes are few in number. የገዢዎቹ ፡ ወገን ፡ ቁጥሩ ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ ነው
2. በሥልጣን ፡ ላይ ፡ ያለ. The ruling party occupies all the government positions. በሥልጣን ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ፓርቲ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ ይይዛል
3. ዋና. Rest was the ruling factor in his recovery from the illness. ከበሽታው ፡ ለመዳን ፡ ዕረፍት ፡ ዋናው ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነበር
*The ruling sentiment of the town is in favor of the new mayor. ይበልጡ ፡ የከተማው ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝብ ፡ አዲሱን ፡ ከንቲባ ፡ ደጋፊ ፡ ነው

**rumble** (v.) አጕረመረመ
I heard the thunder rumbling in the distance. ነጐድጓድ ፡ ከሩቅ ፡ ሲያጕረመርም ፡ ሰማሁ

**rumble along** እየተንገጫገጨ ፡ ተጓዘ
The train rumbled along over the tracks. ባቡሩ ፡ በሐዲዱ ፡ ላይ ፡ እየተንገጫገጨ ፡ ተጓዘ

**rumble out** በማጕተምተም ፡ ሰነዘረ
He rumbled out a few remarks. ጥቂት ፡ አስተያየቶች ፡ በማጕተምተም ፡ ሰነዘረ

**rumble** (n.) ድምፅ
We could hear the rumble of the thunder in the distance. የነጐድጓዱን ፡ ድምፅ ፡ ከሩቅ ፡ እንሰማለን

**ruminate**
1. አመነዠከ. The cows ruminate quietly in their stalls. ላሞቹ ፡ ከበረት ፡ ሆነው ፡ በጸጥታ ፡ ያመነዥካሉ

2. አሰላሰለ. He ruminated over the events of the day. በዕለቱ ፡ ስለተደረጉት ፡ ነገሮች ፡ አሰላሰለ

**rummage** በረበረ
He rummaged through his drawers looking for a tie clasp. የከራቫት ፡ መያዣ ፡ ለመፈለግ ፡ መሳቢያዎችን ፡ በረበረ

**rumor** (v.), **it is rumored** እየተባለ ፡ ይወራል
It is rumored that our office will be transferred to a new site. መሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ይዛወራል ፡ እየተባለ ፡ ይወራል

**rumor** (n.) ወሬ ፤ ጭምጭምታ
He spread the rumor that the President was dead. ፕሬዚዳንቱ ፡ ሞቷል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ነዛ
The rumor is abroad that school will close. ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንደሚዘጋ ፡ ጭምጭምታ ፡ ይነፍሳል

**rumor has it** እየተባለ ፡ ይወራል
Rumor has it that the prime minister will visit Somalia. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሶማሊያን ፡ ይጐበኛሉ ፡ እየተባለ ፡ ይወራል

**rump** ታፋ
The horse was branded on the rump. ፈረሱ ፡ ታፋው ፡ ላይ ፡ ተተኩሷል

**rumple** አጨማደደ
He rumpled his suit by sleeping in it. ልብሱን ፡ ለብሶት ፡ ስለተኛ ፡ አጨማደደው

**rumpus** ሁካታ
Why the rumpus? Better be quiet! ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሁካታ ፡ ምንድነው ? ጸጥ ፡ በሉ

**run** (ran), vt.
1. አስተዳደረ. Who runs his house now that his wife is dead? ሚስቱ ፡ ከሞተች ፡ ወዲህ ፡ ቤቱን ፡ ማን ፡ ያስተዳድርለታል ?
2. አካሄደ. He has been running the business for three years. ንግዱን ፡ ለሦስት ፡ ዓመት ፡ ያካሂድ ፡ ነበር
3. አስገባ. He is running his horse in the derby. ፈረሱን ፡ እሽቅድድም ፡ ውስጥ ፡ ያስገባል
4. ለቀቀ(በት). Run some hot water into the tub! ገንዳውን ፡ ጥቂት ፡ ሙቅ ፡ ውኃ ፡ ልቀቅበት
5. አቀረበ. How many candidates will your party run? የፖለቲካ ፡ ቡድናችሁ ፡ ስንት ፡ እጩዎች ፡ ያቀርባል ?
6. እንዴት ፡ እንደሚሠራ ፡ ዐወቀ. Can you run a washing machine? የልብስ ፡ ማጠቢያ ፡ መኪና ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠራ ፡ ታውቃለህ ?
7. አጋጨ. He ran the car into a tree. መኪናውን ፡ ከዛፍ ፡ ጋር ፡ አጋጨው
8. ዘረጋ. They ran the cable along the new road. ባዲሱ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ የኮረንቲ ፡ ሽቦ ፡ ዘረጉ
9. አወጣ. All the newspapers ran the story. ጋዜጦቹ ፡ ሁሉ ፡ ወሬውን ፡ አወጡት
10. አቀረረ. My eyes ran tears. ዓይኖቼ ፡ እንባ ፡ አቀረሩ

**run** (vi.)
1. ሮጠ. Don't run so fast! እንደዚህ ፡ በፍጥነት ፡ አትሩጥ
He ran for the doctor, but it was too late; the child was already dead. ሐኪሙን ፡ ለመጥራት ፡ ሮጠ ፤ ግን ፡ ሕፃኑ ፡ ገና ፡ ዱሮ ፡ ሞቷል
2. ሄደ. The train was running 60 m.p.h. ባቡሩ ፡ በሰዓት ፡ ስልሳ ፡ ማይል ፡ ይሄድ ፡ ነበር
3. ተመላለሰ. The bus runs every hour. አውቶቡሱ ፡ በየሰዓቱ ፡ ይመላለሳል
The thought kept running through my mind. ነገሩ ፡ በሐሳቤ ፡ ውስጥ ፡ ይመላለስ ፡ ነበር
4. ገባ. This river runs into the Indian Ocean. ይህ ፡ ወንዝ ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ይገባል
5. ደረሰ. This road runs to the river. ይህ ፡ መንገድ ፡ እወንዙ ፡ ይደርሳል
6. ሠራ. The machine doesn't run properly. መኪናው ፡ በደንብ ፡ አይሠራም
Does your watch run well? ሰዓትህ ፡ ልክ ፡ ትሠራለች ?
7. አለፈ. The road runs right by my house. መንገዱ ፡ ልክ ፡ በቤቴ ፡ በኩል ፡ ያልፋል
8. ተቈጠረ. The casualties ran into the thousands. የተጐዳው ፡ ሰው ፡ በሺ ፡ ይቈጠር ፡ ነበር
9. ተዘረዘረ. Her stocking ran. የእግር ፡ ሹራቧ ፡ ተዘርዝሯል
10. ለቀቀ. The color ran when the dress was washed. ቀሚሱ ፡ ሲታጠብ ፡ ቀለሙ ፡ ለቀቀ
11. ታየ. How many weeks has this play been running? ይህ ፡ ቴያትር ፡ መታየት ፡ ከጀመረ ፡ ስንት ፡ ሳምንት ፡ ሆነው ?
12. ተወዳደረ. Who is running for mayor? ለከንቲባነት ፡ የሚወዳደረው ፡ ማነው ?
13. ተጋጨ. The car ran into a tree. መኪናው ፡ ከዛፍ ፡ ጋር ፡ ተጋጨ
14. ቀለጠ. A whisper ran through the crowd. በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ሹክሹክታው ፡ ቀለጠ
15. ነው. My lease runs two years. ኮንትራቱ ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ነው
16. በጥድፊያ ፡ ጨረሰ. The student ran carelessly through his homework. ተማሪው ፡ እንደነገሩ ፡ በጥድፊያ ፡ የቤት ፡ ሥራውን ፡ ጨረሰ

17. አለ. That is how the story runs. ታሪኩ ፡ እንዲህ ፡ ይላል
*My contract has only six months to run. ኮንትራቴ ፡ ሊያልቅ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ቀርቶታል
*A blood disease runs in their family. ከዘር ፡ የመጣ ፡ በሽታ ፡ አለባቸው
*The child's nose runs. ልጁ ፡ ንፍጣም ፡ ነው
*The disease ran its course. በሽታው ፡ እንዲሁ ፡ ተወው

**run about** ተሯሯጠ ፤ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሮጠ
He ran about looking for an exit. መውጫ ፡ ፍለጋ ፡ ተሯሯጠ
The child was running about aimlessly. ልጁ ፡ ያላንዳች ፡ ዓላማ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይሮጥ ፡ ነበር

**run across**
1. አቋረጠ. This road runs across the desert. ይህ ፡ መንገድ ፡ በረሃውን ፡ ያቋርጣል
2. አጋጠመ(ው). +Maybe I'll run across him someday. ምናልባት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ያጋጥመኝ ፡ ይሆናል

**run after** በሩጫ ፡ ተከታተለ
I ran after him, but I couldn't catch him. በሩጫ ፡ ብከታተለውም ፡ ልደርስበት ፡ አልቻልኩም

**run against**
1. ተቃረነ. His beliefs ran against mine. እምነቱ ፡ የኔን ፡ እምነት ፡ ይቃረናል
2. ገጨ. +He ran his head against the door in the dark. በጨለማ ፡ በሩ ፡ ራሱን ፡ ገጨው
3. አጋጠመ(ው). +He ran against strong opposition, but won the election. ኀይለኛ ፡ ተወዳዳሪ ፡ ቢያጋጥመውም ፡ በምርጫው ፡ አሸነፈ

**run (along)**
1. ሄደ. I have to run along now. አሁን ፡ መሄድ ፡ አለብኝ
2. ተከትሎ ፡ ሄደ. The road runs along the river. መንገዱ ፡ ወንዙን ፡ ተከትሎ ፡ ይሄዳል
3. በ --- ዙሪያ ፡ ቆመ. Shelves run along the walls. በግድግዳው ፡ ዙሪያ ፡ መደርደሪያዎች ፡ ቆመዋል

**run around**
1. ዙሪያውን ፡ ተደረደረ. The shelves ran around the room. መደርደሪያዎቹ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ዙሪያውን ፡ ተደርድረው ፡ ነበር
2. ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ አለ ፤ ተዘዋወረ. You shouldn't run around in your bare feet. በባዶ ፡ እግርህ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ማለት ፡ (መዘዋወር) ፡ አይገባህም
3. ፈነጨ. The colt runs around in the fields. የፈረሷ ፡ ውርንጭላ ፡ ሜዳ ፡ ውስጥ ፡ ትፈነጫለች
4. ተንከራተተ. Why have you been running around again? የምትንከራተተው ፡ ለምን ፡ ነበር ?

**run away**
1. ሸሸ. When the thief saw us, he ran away. ሌባው ፡ ሲያየን ፡ ሸሸ
2. ኰበለለ. I ran away from home when I was young. ልጅ ፡ ሆኜ ፡ ከቤት ፡ ኰበለልኩ

**run away with** ይዞ ፡ ጠፋ
The maid ran away with the lady's jewels. ገረዲቱ ፡ የእመቤቲቷን ፡ ጌጣ ፡ ጌጥ ፡ ይዛ ፡ ጠፋች
*His enthusiasm ran away with him. የጋለ ፡ ስሜቱ ፡ የማስተዋል ፡ ችሎታውን ፡ አቀዘቀዘበት

**run down** (vt.)
1. አድኖ ፡ ያዘ. He ran down the criminal. ወንጀለኛውን ፡ አድኖ ፡ ያዘው
2. ነቀፈ. He maliciously ran down his best friend. የቅርብ ፡ ወዳጁን ፡ በተንኰል ፡ ነቀፈው
3. ጠያይቆ ፡ ደረሰ(በት). I ran down the location of his new house. አዲሱን ፡ ቤቱን ፡ ጠያይቄ ፡ ደረስኩበት
4. ኮለል ፡ አለ. Tears ran down her face. እንባ ፡ ጉንጯ ፡ ላይ ፡ ኮለል ፡ አለ

**run down** (vi.)
1. አለቀ. The battery has run down and needs a charge. ባትሪው ፡ ስላለቀ ፡ መሞላት ፡ አለበት
2. ቆመ. My watch ran down. ሰዓቴ ፡ ቆማለች

**run (someone) down behind his back** አማ
He runs his friends down behind their backs. ጓደኞቹን ፡ ያማል

**(be) run down** (= act.) ዳጠ
+He was run down by a truck. ካሚዮን ፡ ዳጠው

**run (one's) eyes over** ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ተመለከተ
He ran his eyes over the column of figures. ቁጥሮቹን ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ተመለከታቸው

**run first** አንደኛ ፡ ሆነ
Our horse ran first in the race. ፈረሳችን ፡ በእሽቅድምድሙ ፡ አንደኛ ፡ ሆነ

**run for it** ሸሸ
You had better run for it before anyone else arrives. ማንም ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ብትሸሽ ፡ ይሻላል

**run for your life!** ሩጥ
Run for your life, a hyena is coming! ሩጥ ፤ ጅብ ፡ መጥቶልሃል

**run high**
*Food prices are running high. ምግብ ፡ ተወዷል

**run in** ጨመረ
I ran in some footnotes in my essay. በድርሰቴ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ ማስረጃዎች ፡ ጨመርኩ

**run into**
1. ገባ. He ran into debt trying to perfect his invention. የፈለሰፈውን ፡ ነገር ፡ ለማሻሻል ፡ ብድር ፡ ገባ
His yearly income runs into five figures. ያመት ፡ ገቢው ፡ ዐሥር ፡ ሺ ፡ ቤት ፡ ገብቷል
2. ድንገት ፡ አገኘ. I just ran into Henry on the street, and he told me to tell you hello. ሄንሪን ፡ መንገድ ፡ ድንገት ፡ አግኝቼው ፡ ሰላም ፡ በልልኝ ፡ ብሎኛል
3. ገጨ. Some jackass ran into my parked car. አንድ ፡ ደደብ ፡ የቆመች ፡ መኪናዬን ፡ ገጫት
4. አስከተለ. That will run into a lot of expense. ይህ ፡ ብዙ ፡ ወጪ ፡ ያስከትላል

**run off** (vt.) አባዛ
Run off a hundred copies on the mimeograph! መቶ ፡ ቅጂዎች ፡ በሚሚዮግራፉ ፡ አባዥልኝ

**run off** (vi.)
1. ሮጠ. The man ran off at the sight of the police. ሰውዬው ፡ ፖሊሱን ፡ ሲያይ ፡ ሮጠ
2. እየተንቈረቈረ ፡ ወረደ. The roof is steep, so the rain will run off easily. ጣራው ፡ ያጋደለ ፡ ስለሆነ ፡ የዝናብ ፡ ውኃ ፡ እየተንቈረቈረ ፡ ይወርዳል

**run off with** ይዞ ፡ ጠፋ
He ran off with the club's funds. የክበቡን ፡ ገንዘብ ፡ ይዞ ፡ ጠፋ

**run on for hours** ሳያቋርጥ ፡ አወራ
He will run on for hours if you don't stop him. ካላቆምከው ፡ ሳያቋርጥ ፡ ያወራል

**run out** (vt.) አወጣ
They ran him out of town. ከከተማው ፡ አወጡት

**run out** (vi.)
1. ሮጦ ፡ ወጣ. He ran out of the house. ከቤቱ ፡ ሮጦ ፡ ወጣ
2. አለቀ. When does the lease run out? ኮንትራቱ ፡ የሚያልቀው ፡ መቼ ፡ ነው ?
Time is running out. ጊዜው ፡ ሊያልቅ ፡ ነው

**run out of**
1. ጨረሰ. I ran out of money. ገንዘብ ፡ ጨረስኩ
2. አለቀ(በት). +We ran out of gas halfway to town. የከተማውን ፡ መንገድ ፡ ስናጋምስ ፡ ቤንዚን ፡ አለቀብን

**run over** (vt.)
1. ጻጠ. I felt remorse having run over the dog. ውሻውን ፡ ስለዳጥኩት ፡ ጸጸት ፡ ተሰማኝ
2. አንድ ፡ ጊዜ ፡ አነበበ. He ran over his notes before taking the test. ፈተናውን ፡ ከመፈተኑ ፡ በፊት ፡ የጻፈውን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አነበበ
3. ከ --- በላይ ፡ አወጣ. The department has run over its budget again. እንደገና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ከተመደበለት ፡ ባጀት ፡ በላይ ፡ አወጣ

**run over** (vi.)
1. ሮጥ ፡ አለ. Run over to Mrs. Smith's house and borrow a cup of sugar! ወደ ፡ ሚስስ ፡ ስሚዝ ፡ ቤት ፡ ሮጥ ፡ በልና ፡ አንድ ፡ ሲኒ ፡ ስኳር ፡ ተበድረህ ፡ ና
2. ሞልቶ ፡ ፈሰሰ. Watch out that the bathtub doesn't run over! የመታጠቢያው ፡ ገንዳ ፡ ሞልቶ ፡ እንዳይፈስ ፡ ተጠንቀቅ

**run (the) risk**
*He ran the risk of losing all his money. በገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ ፈርዶ ፡ ገባበት

**run (through)**
1. ጨረሰ. I ran through the money in one day. ገንዘቡን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ጨረስኩት
2. ከጻር ፡ እስከ ፡ ጻር ፡ ተገኘ. The idea of world peace runs through the whole novel. በልብ ፡ ወለዱ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የዓለም ፡ ሰላም ፡ ሐሳብ ፡ ከጻር ፡ እስከ ፡ ጻር ፡ ይገኛል
3. ተመለከከተ. He ran through the mail at breakfast. ቁርስ ፡ ሲበላ ፡ ደብዳቤዎቹን ፡ ተመለከከተ
4. ለራሱ ፡ አንዴ ፡ አነበበ. Run through the sentences before you dictate them. በቃል ፡ ከማጻፍህ ፡ በፊት ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮቹን ፡ ለራስህ ፡ አንዴ ፡ አንብባቸው

**run to** ደረሰ
That will run to one hundred dollars. ዋጋው ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ይደርሳል

**run up** (vt.)
1. እንዲከመርበት ፡ አደረገ. He ran up a high bill at the hotel. የሆቴሉ ፡ ሒሳብ ፡ እንዲከመርበት ፡ አደረገ
2. ወጣ. The cat ran up the tree. ድመቷ ፡ ዛፉን ፡ ወጣች

**run up** (vi.) ደረሰ
The price of coal runs up to $80 a ton. ያንድ ፡ ቶን ፡ ከሰል ፡ ዋጋ ፡ እስከ ፡ ሰማንያ ፡ ብር ፡ ይደርሳል

**run up (against)** አጋጠመው.+
+He ran up against resistance to acceptance of our plan. እቅዳችንን ፡ የማይቀበል ፡ ሰው ፡ አጋጠመው

**run wild, let ~** ልቅ ፡ ተወ
She lets the children run wild. ልጆቹን ፡ ልቅ ፡ ትተዋቸዋለች

**let run free** ለቀቀ
He took the harness off, and let the horse run free in the field. ፈረሱን ፡ ፈቶ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ለቀቀው

[See also 'afoul, course, errand, fever, loose, low, madly, past, rampant, short, snag, wild']

**run** (n.)

1, መንገድ. How many hours run is Djibouti from Addis Ababa by rail? ከአዲስ ፡ አበባ ፡ እስከ ፡ ጅቡቲ ፡ በባቡር ፡ የስንት ፡ ሰዓት ፡ መንገድ ፡ ነው ?
2. ጋጋታ. After the President's speech, there was a run on the banks to draw out money. ከፕሬዚዳንቱ ፡ ንግግር ፡ በኋላ ፡ ገንዘብ ፡ ከባንክ ፡ ለማውጣት ፡ ጋጋታ ፡ ነበር

**be on the run** ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ተሯሯጠ
I have been on the run since I got up. ከተነሣሁ ፡ ጀምሬ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እሯሯጣለሁ

**(be) given the run of**
*The guests were given the run of the house. እንግዶቹ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ልባቸው ፡ እንዲሆኑ ፡ ተፈቀደላቸው

**have a run**
1. ተዘረዘረ. +You have a run in your stocking. የእግር ፡ ሹራብሽ ፡ ተዘርዝሯል
2. ታየ. The movie had a long run of six months. ፊልሙ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**have (someone) on the run** አሳደደ
We have the enemy on the run now. ጠላትን ፡ በማሳደድ ፡ ላይ ፡ ነን

**in the long run**
1. የኋላ ፡ ኋላ. In the long run, you'll get tired of that. የኋላ ፡ ኋላ ፡ ይሰለችሃል
2. ለዘለቄታው. It is an economy in the long run to buy good quality cloth. ጥሩ ፡ ጨርቅን ፡ መግዛት ፡ ለዘለቄታው ፡ ገንዘብን ፡ ይቈጥባል

**runaway** ያመለጠ
A runaway horse caused this damage. ይህንን ፡ ጥፋት ፡ ያደረሰው ፡ ያመለጠ ፡ ፈረስ ፡ ነው
*A shortage of supplies caused runaway prices. የእቃዎች ፡ ማነስ ፡ ዋጋውን ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ እንዲል ፡ አደረገው

**rundown** (n.)
*Give me a rundown of the news! ወሬውን ፡ ባጭሩ ፡ ንገረኝ

**run-down** (adj.) የተጐሳቈለ
She looks terribly run-down. በጣም ፡ የተጐሳቈለች ፡ ትመስላለች

**be run-down** በደንብ ፡ አልተያዘም
The house is run-down. ቤቱ ፡ በደንብ ፡ አልተያዘም

**feel run-down** ድካም ፡ ተሰማ(ው)
I feel run-down because I work too hard. እጅግ ፡ ብዙ ፡ ስለምሠራ ፡ ድካም ፡ ይሰማኛል

**rung** መወጣጫ
The rung of the ladder is broken. የመሰላሉ ፡ መወጣጫ ፡ ተሰብሯል

**run-in**
*I had a run-in with the boss last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ካለቃዬ ፡ ጋር ፡ ተጨቃጨቅሁ

**runner**
1. ሯጭ. The runner arrived out of breath. ሯጩ ፡ ትንፋሽ ፡ አጥሮት ፡ ደረሰ
2. ቀጭን ፡ ምንጣፍ. The corridor is covered by a runner. መተላለፊያው ፡ ቀጭን ፡ ምንጣፍ ፡ ለብሷል

**runner-up** [በሩጫ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ውድድር ፡ ሁለተኛ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ቡድን]

**running** (n.)
1. ሩጫ. Running is good exercise. ሩጫ ፡ ጥሩ ፡ የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ነው
2. አስተዳደር. He has no say in running the company. በኩባንያው ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ሥልጣን ፡ የለውም

**be in the running** ተወዳዳሪ ፡ ነው
He is still in the running for President even though he lost the first election. በመጀመሪያው ፡ ምርጫ ፡ ቢሸነፍም ፡ አሁንም ፡ ለፕሬዚዳንትነት ፡ ተወዳዳሪ ፡ ነው

**running** (adj.)
1. መሬት ፡ ላይ ፡ የሚሳብ. Running vines keep the soil from being eroded. መሬት ፡ ላይ ፡ የሚሳብ ፡ ሐረግ ፡ አፈሩ ፡ እንዳይሸረሸር ፡ ይይዘዋል
2. ያለማቋረጥ. His running commentary helped us to understand the game. በጨዋታው ፡ ጊዜ ፡ ያለማቋረጥ ፡ የሰጠው ፡ ሐተታ ፡ ግጥሚያውን ፡ መረዳት ፡ አስቻለን
*The running time of the bus is two hours. አውቶቡሱ ፡ ከመነሻው ፡ እስከ ፡ መድረሻው ፡ ለመጓዝ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ይወስድበታል
*The child's nose is running. ልጁ ፡ ንፍጥ ፡ ይወርደዋል

**running**, adv. (= adj.) ተከታታይ
He slept badly for three nights running. ለሦስት ፡ ተከታታይ ፡ ሌሊቶች ፡ መጥፎ ፡ እንቅልፍ ፡ ተኛ
*You left the engine running. ሞተሩን ፡ ሳታጠፋ ፡ ተውከው

**running mate** ምክትል ፡ ለመሆን ፡ የሚወዳደር
The President's running mate is an obscure
country lawyer. የፕሬዚዳንቱ ፡ ምክትል ፡ ለመ
ሆን ፡ የሚወዳደረው ፡ ያልታወቀ ፡ የገጠር ፡ ጠ
በቃ ፡ ነው

**running water**
1. የቧምቧ ፡ ውኃ. Every room has running water.
እያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ የቧምቧ ፡ ውኃ ፡ አለው
2. ወራጅ ፡ ውኃ. The running water made
a pleasant sound. ወራጁ ፡ ውኃ ፡ ደስ ፡ የሚል ፡
ድምፅ ፡ አሰማ

**runoff** [እኩል ፡ የሆኑ ፡ ተወዳዳሪዎችን ፡ ለመለየ ፡
የሚደረግ ፡ የመጨረሻ ፡ ውድድር]

**run-of-the-mill** ረጋ ፡ ሠራሽ
Run-of-the-mill paintings have very little value.
ረጋ ፡ ሠራሽ ፡ ሥዕሎች ፡ ዋጋቸው ፡ በጣም ፡ ጥ
ቂት ፡ ነው

**runway** የአውሮፕላን ፡ መንደርደሪያ
The runway is made of concrete. የአውሮፕላኑ ፡
መንደርደሪያ ፡ የተሠራው ፡ በሲሚንቶ ፡ ነው

**rupture** (v.) ቈረጠ
He ruptured a blood vessel. የደም ፡ ሥሩን ፡ ቈ
ረጠ

**rupture oneself** ቡአ ፡ ወረደው ። ቡቃ ፡ ወረደው
He ruptured himself carrying that heavy load.
ያንን ፡ ከባድ ፡ ሸክም ፡ ስለተሸከመ ፡ ቡአ ፡ (ቡቃ) ፡
ወረደው

**be ruptured** ፈነዳ
The pipeline was ruptured by high pressure.
ቧምቧው ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ግፊት ፡ ም
ክንያት ፡ ፈነዳ

**rupture** (n.)
*The rupture of the pipeline was caused by
high air pressure. ቧምቧው ፡ የፈነዳው ፡ ከከፍተ
ኛ ፡ ያየር ፡ ግፊት ፡ የተነሣ ፡ ነበር

**rural** የገጠር
They are filming rural life in Ethiopia. የኢትዮጵ
ያን ፡ የገጠር ፡ ኑሮ ፡ ፊልም ፡ ያነሣሉ

**rural areas** ገጠር
The rural areas need electricity. ገጠሩ ፡ ኮረንቲ ፡
ያስፈልገዋል

**ruse** ዘዴ
The enemy had to resort to a ruse to get the
troops to leave their camp. ወታደሮቹ ፡ ሰፍራ
ቸውን ፡ እንዲለቁ ፡ ለማድረግ ፡ ጠላት ፡ በዘዴ ፡
መጠቀም ፡ ግድ ፡ ነበረበት

**rush** (vt.)
1. አጣደፈ. Don't rush me! I can't work fast.
አታጣድፈኝ ። ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ መሥራት ፡ አልችልም
2. በፍጥነት ፡ ላከ. We rushed more troops to
the front. ወደ ፡ ጦሩ ፡ ግንባር ፡ ተጨማሪ ፡ ወ
ታደሮች ፡ በፍጥነት ፡ ላክን
3. ያኄውኑ ፡ አጠቃ. The troops rushed the fort.
ወታደሮቹ ፡ ምሽጉን ፡ ያኄውኑ ፡ አጠቁት
4. አቻኰለ. He rushed the job. ሥራውን ፡ አቻ
ኰለው
5. በፍጥነት ፡ ወሰደ. Rush him to the hospital!
ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ በፍጥነት ፡ ውሰዱት !

**rush** (vi.)
1. ቸኰለ. Don't rush! We have plenty of time.
አትቸኵል ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አለን
Don't rush to conclusions! ለመፍረድ ፡ አትቸ
ኵል
2. በችኰላ ፡ ሄደ. They rushed to the bank.
ወደ ፡ ባንኩ ፡ በችኰላ ፡ ሄዱ
3. ሮጦ ፡ ገባ. The courageous boy rushed into
the burning building to rescue the child.
ደፋሩ ፡ ልጅ ፡ ሕፃኑን ፡ ለማትረፍ ፡ የተቀጣጠ
ለው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሮጦ ፡ ገባ

**rush at** ተንደርድሮ ፡ መጣ(በት) ። ሮጦ ፡ መጣ(በት)
He rushed at me. ተንደርድሮ ፡ መጣብኝ
The angry dog rushed at him, but he held his
ground. ክፉው ፡ ውሻ ፡ ሮጦ ፡ ቢመጣበትም ፡
አልተነቃነቀም

**rush into** በደንብ ፡ ሳያስብበት ፡ ጀመረ
They rushed into the new project. አዲሱን ፡ ፕ
ሮጂ ፡ በደንብ ፡ ሳያስቡበት ፡ ጀመሩት

**rush out** ተንጋግቶ ፡ ወጣ
The children rushed out of school. ልጆቹ ፡ ከ
ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተንጋግተው ፡ ወጡ

**rush past**
The river rushed past. ወንዙ ፡ ተኸርጐደጐዶ ፡
ወረደ

**rush through** በችኰላ + verb
They rushed the bill through. የሕጉን ፡ ረቂ
ቅ ፡ በችኰላ ፡ አጸደቁት

**rush** (n.)
1. ጨፌ. Rushes grow in swampy ground.
ጨፌ ፡ የሚበቅለው ፡ ረግረግ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው
2. የሚያስቸኵል ፡ ነገር ። ጥድፊያ. There's no
rush about it. ምንም ፡ የሚያስቸኵል ፡ ነገር ፡
የለም
What is the rush? Wait a minute! ጥድፊያው ፣
ምንድን ፡ ነው ? ትንሽ ፡ ቆይ
3. ግርግር. Let us wait till the rush is over.
ግርግሩ ፡ እስኪያልፍ ፡ እንቆይ

4. ሽሚያ. There was a rush for raincoats. ለዝናብ ፡ ልብስ ፡ ሽሚያ ፡ ነበር
5. ጋጋታ. I don't like the rush of city life. የከተማን ፡ ኑሮ ፡ ጋጋታ ፡ አልወድም
*The rush of the flood swept everything before it. ጐርፉ ፡ እፊቱ ፡ ያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ ጠራረገው
**be in a rush** ቸኰለ
I am in a terrible rush. በጣም ፡ ቸኵያለሁ
**rush** (adj.) የሚያስቸኵል
Can you do a rush job for me? አንድ ፡ የሚያስቸኵል ፡ ሥራ ፡ ልትሠራልኝ ፡ ትችላለህ ?

**rush hour** መኪና ፡ የሚበዛበት ፡ ጊዜ
This narrow street is a bottleneck during rush hour. መኪና ፡ በሚበዛበት ፡ ጊዜ ፡ ይህች ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡ ጭንቅንቅ ፡ ትፈጥራለች
*The rush hour starts at five o'clock. በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ትራፊክ ፡ ይበዛል

**Russia** ሩሲያ ፤ መስኮብ

**Russian**
1. መስኮብኛ. Do you know Russian? መስኮብኛ ፡ ታውቃለህ ?
2. መስኮብ. Are there many Russians in Ethiopia? ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ መስኮቦች ፡ አሉ ?

**rust** (vt.) አዛገ
Damp weather rusts iron. እርጥብ ፡ አየር ፡ ብረትን ፡ ያዝጋል
**rust** (vi.) ዛገ
Oil the machine, or it will rust. መኪናውን ፡ ዘይት ፡ ቀባው ፤ አለበለዚያ ፡ ይዝጋል
**let rust** (= vi.) ዛገ
+Don't let your mind rust during vacation; read a lot! በዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ አእምሮህ ፡ እንዳይዝግ ፡ ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ አንብብ

**rust** (n.) ዝገት
Before you paint the fence, scrape off the rust! አጥሩን ፡ ቀለም ፡ ከመቀባትህ ፡ በፊት ፡ ዝገቱን ፡ ፋቀው

**rustic**
1. ያገር ፡ ቤት. He likes rustic furniture. ያገር ፡ ቤት ፡ እቃ ፡ ይወዳል
2. የባላገርነት. His rustic manners were noticed by everybody. የባላገርነት ፡ ጠባዩ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ ታወቀ

**rustle** (vt.)
1. አንኰሻኰሸ. A mouse was rustling some old papers. አይጥ ፡ አሮጌ ፡ ወረቀቶችን ፡ ያንኰሻኵሽ ፡ ነበር
2. ዘረፈ. The bandit rustled some cattle. ሽፍታው ፡ ጥቂት ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ ዘረፈ
3. ለቀመ. He went out to rustle some wood. ጭራሮ ፡ ለመልቀም ፡ ሄደ
**rustle** (vi.)
1. ተንሿሿ. Her long skirt rustles on the grass. ረጅሙ ፡ ቀሚሷ ፡ ሣሩ ፡ ውስጥ ፡ ሲጐተት ፡ ይንሿሿል
2. (= tr.) አንኰሻኰሸ. +Leaves rustled in the breeze. ለዘብ ፡ ያለው ፡ ነፋስ ፡ ቅጠሎቹን ፡ አንኰሻኰሻቸው

**rusty** የዛገ
He scratched his hand on a rusty nail. እጁን ፡ የዛገ ፡ ምስማር ፡ ቧጠጠው
*I'm afraid my Amharic is a little rusty. አማርኛዬ ፡ ጥቂት ፡ ሳይበላሽ ፡ አልቀረም

**rut** (rutted), vt. ትልም ፡ አበጀ
The wagons rutted the plains. ሰረገላዎቹ ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ ትልም ፡ አበጁ
**rut** (vi.) ስሪያ ፡ ያዘ
The bulls are rutting; better stay away from them! ኮርማዎቹ ፡ ስሪያ ፡ ይዘዋልና ፡ ከነርሱ ፡ ብትርቅ ፡ ይሻላል
**be rutted** (= act.) የመኪና ፡ ጎማ ፡ ቈፋፈረ
The road was deeply rutted. መንገዱን ፡ የመኪና ፡ ጎማ ፡ ቈፋፍሮታል

**rut** (n.), **get into a ~** ያንኑ ፡ መደጋገሙ ፡ ሰለቸ(ው)
We've gotten into a rut; let's do something new! ያንኑ ፡ መደጋገሙ ፡ ሰለቸን ፤ አዲስ ፡ ነገር ፡ እንሥራ
**get stuck in a rut**
*The wheel got stuck in a rut. የመኪናው ፡ ጎማ ፡ መኪናዎች ፡ በሄዱበት ፡ ቦይ ፡ ውስጥ ፡ ገባ

**(be) ruthless** ጨከነ
The dictator was ruthless in his treatment of rebels. አምባገነኑ ፡ በዐመፀኞች ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ ይጨክን ፡ ነበር

**ruthlessly** ያለ ፡ ምሕረት ፤ በጭካኔ
All bandits were ruthlessly stamped out. ሽፍቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ ምሕረት ፡ (በጭካኔ) ፡ ተደመሰሱ

**ruthlessness** ጨካኝነት
His ruthlessness made him feared by all. ጨካኝነቱ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ እንዲፈራ ፡ አደረገው

**rye** አጃ
Rye is used for making bread. አጃ ፡ ለዳቦ ፡ ይሆናል

## S

**Sabbath** ሰንበት ፤ ቅዳሜ
The Jews keep the Sabbath. አይሁዳውያን ፡ ሰንበትን ፡ (ቅዳሜን) ፡ ያከብራሉ

**Sabbatical leave** [በየሰባት ፡ ዓመቱ ፡ ለዩኒቨርሲቲ ፡ መምህራን ፡ የሚሰጥ ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ]

**sabotage** (v.) በስውር ፡ አፈረሰ
The enemy tried to sabotage the bridge. ጠላት ፡ ድልድዩን ፡ በስውር ፡ ለማፍረስ ፡ ሞከረ

**saber** ሻምላ
The soldier girded on the saber. ወታደሩ ፡ ሻምላ ፡ ታጥቋል

**sacerdotal** የቤተ ፡ ክርስቲያን
Sacerdotal garments are kept in a special room. የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አልባሳት ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣሉ

**sack** (v.)
1. በጆንያ ፡ ከተተ. The farmers sacked the grain. ገበሬዎቹ ፡ እህሉን ፡ በጆንያ ፡ ከተቱ
2. በዘበዘ. The enemy troops sacked the town. የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ከተማውን ፡ በዘበዙት

**sack** (n.) ጆንያ
I want a sack of potatoes. አንድ ፡ ጆንያ ፡ ድንች ፡ እፈልጋለሁ

**sacraments** የቁርባን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት
The sacraments are administered by priests. የቁርባንን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጽሙ ፡ ቀሳውስት ፡ ናቸው

**sacramental** መንፈሳዊ
A sacramental obligation for a priest is keeping secret the confessions told him. የቄስ ፡ መንፈሳዊ ፡ ግዴታው ፡ የተነገረውን ፡ ኑዛዜ ፡ በምስጢር ፡ መጠበቅ ፡ ነው

**sacramental wine** ዘቢብ
They use sacramental wine for the church service. ዘቢቡን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎት ፡ ይጠቀሙበታል

**sacred**
1. የተቀደሰ. Prayer is a sacred duty. ጸሎት ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባር ፡ ነው
2. ቅዱስ ፡ የሚባል ፡ ነገር. Nothing is sacred to him. በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ቅዱስ ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ የለም
3. የክብር. The sacred memory of a dead hero is commemorated by this monument. የሞተው ፡ አርበኛ ፡ የክብር ፡ መታሰቢያ ፡ በዚህ ፡ ሐውልት ፡ ሲታወስ ፡ ይኖራል

**sacred promise** ቃል ፡ ኪዳን
Her sacred promise never to remarry was soon broken. ዳግመኛ ፡ ፈጽሞ ፡ ላታገባ ፡ የገባችው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቶሎ ፡ ፈረሰ

**sacrifice** (v.) መሥዋዕት ፡ አቀረበ ፤ ሠዋ
They sacrificed an ox to propitiate the rain god. የዝናምን ፡ አምላክ ፡ ለመማጸን ፡ በሬ ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡለት
She sacrificed her leisure time to work for the hospital. የዕረፍት ፡ ጊዜዋን ፡ ለሆስፒታሉ ፡ አገልግሎት ፡ ሠዋች

**sacrifice one's life** ራሱን ፡ በደለ
She sacrificed her life for him. ለሱ ፡ ብላ ፡ ራሷን ፡ በደለች

**sacrifice oneself** ራሱን ፡ መሥዋዕት ፡ አደረገ
The fatherland requires each man to sacrifice himself, if need be. አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ አገር ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ መሥዋዕት ፡ እንዲያደርግ ፡ ትጠይቃለች

**sacrifice** (n.) መሥዋዕት
The ancient Hebrews killed animals as sacrifice to God. የጥንት ፡ አይሁዶች ፡ እንስሳትን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር

**at a sacrifice** በኪሳራ
He will sell his house at a sacrifice because he needs the money. ገንዘብ ፡ ስለሚፈልግ ፡ ቤቱን ፡ በኪሳራ ፡ ይሸጣል

**give in sacrifice** ሠዋ
He gave his life in sacrifice for his country. ሕይወቱን ፡ ለአገሩ ፡ ሠዋ

**make a sacrifice** (n.) ብዙ ፡ ደከመ
He made a sacrifice to send his son to school. ልጁን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለማስገባት ፡ ብዙ ፡ ደከመ

**sacrilege**
1. የረከሰ ፡ ተግባር. Wrecking an altar is a sacrilege. ታቦትን ፡ ማበላሸት ፡ የረከሰ ፡ ተግባር ፡ ነው

2. ማራከስ. To use God's name for profane things is a sacrilege. የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በ
ከንቱ ፡ ማንሣት ፡ ማራከስ ፡ ነው

**sacrilegious** የተቀደሱ ፡ ነገሮችን ፡ የሚያረክስ
A sacrilegious person used the chalice for drinking beer. የተቀደሱ ፡ ነገሮችን ፡ የሚያረክ
ስ ፡ ሰው ፡ ጽዋውን ፡ ጠላ ፡ ጠጣበት

**sad** አሳዛኝ
He cried when he heard the sad news. አሳዛኙ
ን ፡ ዜና ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ አለቀሰ

**be sad** አዘነ
He is sad since he lost his wallet. ቦርሳው ፡ ስ
ለጠፋበት ፡ አዝኗል

**feel sad** ሐዘን ፡ ተሰማ
You feel sad if your best friend goes away. ጥሩ ፡ ጓደኛ ፡ ሲለይ ፡ ሐዘን ፡ ይሰማል

**have a sad face**
He has a sad face. ፊቱ ፡ ላይ ፡ ሐዘን ፡ ይታይ
በታል

**look sad**
Why does he look so sad? ለምን ፡ እንደዚህ ፡ ያዘነ ፡ ይመስላል ?

**sadden** አሳዘነ
His death saddens all who knew him. የርሱ ፡ መሞት ፡ የሚያውቁትን ፡ ሁሉ ፡ ያሳዝናል

**saddle** (v.)
1. ጫነ. Do you know how to saddle a horse? ፈረስ ፡ መጫን ፡ ታውቃለህ ?
2. አሸከመ. His wife saddled him with debts. ሚስቱ ፡ ዕዳ ፡ አሸከመችው

**be saddled with** ብቻውን ፡ ይዞ ፡ ተጨነቀ
He is saddled with a big house that he does not need. አንድ ፡ ትልቅ ፡ የማያስፈልገው ፡ ቤ
ት ፡ ብቻውን ፡ ይዞ ፡ ይጨነቃል

**saddle** (n.) ኮርቻ
The saddle fell off the horse. ኮርቻው ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወደቀ

**put the saddle on** ጫነ
He put the saddle on the horse. ፈረሱን ፡ ኮርቻ ፡ ጫነ

**without a saddle** ሌጣ
Can you ride a horse without a saddle? ሌጣ ፡ ፈረስ ፡ ልትጋልብ ፡ ትችላለህ ?

**saddlebag** በኮርቻ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ከረጢት
He carried his provisions in his saddlebag. ሥንቁን ፡ ሁሉ ፡ በኮርቻው ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ከረጢት ፡ ውስጥ ፡ ያዘ

**saddler** ኮርቻ ፡ ሠሪ
The saddler sells saddles every week. ኮርቻ ፡ ሠሪው ፡ በየሳምንቱ ፡ ኮርቻ ፡ ይሸጣል

**sadness** ሐዘን
Sadness has overcome him since his mother's death. እናቱ ፡ ከሞቱ ፡ ጀምሮ ፡ ሐዘን ፡ ተጭኖታል

**safe** (n.) ካዝና
We keep our safe in the office. ካዝናችንን ፡ የ
ምናስቀምጠው ፡ ቢሮ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**safe** (adj.)
1. ደኅና. Find a safe hiding place! ደኅና ፡ መደበ
ቂያ ፡ ቦታ ፡ ፈልግ
2. ሰላም. This neighborhood isn't quite safe. ይህ ፡ ሰፈር ፡ እጅግም ፡ ሰላም ፡ አይደለም
3. ጥንቁቅ. A safe driver does not speed. ጥንቁቅ ፡ ነጂ ፡ በፍጥነት ፡ አይነዳም
4. የሚያስተማምን. He is a safe guide; you can go with him anywhere. የሚያስተማምን ፡ መ
ሪ ፡ ስለሆነ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ የትም ፡ ልትሄድ ፡ ትችላለህ
5. አደጋን ፡ የማያስከትል. Is 60 m.p.h. a safe speed on this road? በዚህ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በ
ሰዓት ፡ ስልሳ ፡ ማይል ፡ መንዳት ፡ አደጋን ፡ የ
ማያስከትል ፡ ፍጥነት ፡ ነው ?
6. (= adv.) በደኅና. He came home safe after the war. ከጦርነቱ ፡ በደኅና ፡ ተመለሰ
7. (= adv.) ያላንዳች ፡ አደጋ. He piloted the aircraft to a safe landing. አውሮፕላኑን ፡ ያላን
ዳች ፡ አደጋ ፡ አሳረፈው

**be safe**
1. ደኅና ፡ ነው. Thank God she's safe! ተመስገን ፡ ጌታዬ ፡ ደኅና ፡ ነች
2. አያሰጋም. A tight boat is absolutely safe. ውኃ ፡ የማያስገባ ፡ ጀልባ ፡ በፍጹም ፡ አያሰጋም
3. ራሱን ፡ ከደጋ ፡ ጠበቀ. Use care to be safe in crossing streets! ራስህን ፡ ካደጋ ፡ ለመጠበቅ ፡ መ
ንገዶችን ፡ ስታቋርጥ ፡ ተገቢ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ አለብህ
4. ጉዳት ፡ አላስከተለም. Are these toys safe for small children? እነዚህ ፡ መጫወቻዎች ፡ ለሕ
ፃናት ፡ ጉዳት ፡ አያስከትሉም ?
5. በደንብ ፡ ተጠበቀ. The thief is safe in prison. ሌባው ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በደንብ ፡ ይጠበቃል

**safe and sound** ምንም ፡ ሳይነካው ፡ በደኅና
He is back safe and sound. ምንም ፡ ሳይነካው ፡ በደኅና ፡ ተመልሷል

**feel safe** ስጋት ፡ አላደረበትም
We feel safe with the dog in the house. በቤት ፡ ውስጥ ፡ ውሻ ፡ ሲኖር ፡ ስጋት ፡ አያድርብንም

**to be on the safe side** ለማረጋገጥ ፡ ያህል
To be on the safe side, let us ask him again. ለማረጋገጥ ፡ ያህል ፡ እንደገና ፡ እንጠይቀው

**safe conduct** የይለፍ ፡ ወረቀት
He gave the soldier a safe conduct to get him through our lines. ሰፈራችን ፡ ለመድረስ ፡ እንዲችል ፡ ለወታደሩ ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ ሰጠው

**safeguard** (v.) ጠበቀ(ለት)
Food laws safeguard your health. ምግብን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሕጎች ፡ ጤንነትህን ፡ ይጠብቁልሃል

**safeguard** (n.) መከላከያ
Keeping clean is a safeguard against disease. ራስን ፡ በንጽሕና ፡ መጠበቅ ፡ የበሽታ ፡ መከላከያ ፡ ነው

**safely**
1. በደኅና. They arrived safely. በደኅና ፡ ደረሱ
2. ያለ ፡ ፍርሃት. In the present posture of public affairs, it is difficult to invest money safely. ባሁኑ ፡ የሕዝብ ፡ ሁኔታ ፡ ገንዘብን ፡ ያለ ፡ ፍርሃት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ከባድ ፡ ነው

**safety**
1. ደኅንነት. This is for your own safety. ይህ ፡ ላንተው ፡ ደኅንነት ፡ ነው
2. ከአደጋ ፡ የሚድንበት ፡ ስፍራ. First, the children were brought to safety. መጀመሪያ ፡ ልጆቹን ፡ ከአደጋ ፡ ወደሚድኑበት ፡ ስፍራ ፡ ወሰዷቸው
*A bank assures safety for your money. ባንክ ፡ ገንዘብህ ፡ እንዳይጠፋ ፡ ይጠብቅልሃል

**to safety** ራሱን ፡ ለማዳን ፡ ሲል
He dashed to safety. ራሱን ፡ ለማዳን ፡ ሲል ፡ ተፈተለከ

**safety belt** ከአደጋ ፡ የመከላከያ ፡ ቀበቶ
A safety belt helps protect passengers in case of a crash. ከአደጋ ፡ የመከላከያ ፡ ቀበቶ ፡ ተሳፋሪዎች ፡ በግጭት ፡ ጊዜ ፡ እንዳይጐዱ ፡ ይረዳል

**safety pin** መርፌ ፡ ቁልፍ
He held his torn shirt together with a safety pin. የተቀደደውን ፡ ሸሚዙን ፡ በመርፌ ፡ ቁልፍ ፡ አያይዞታል

**sag** (sagged)
1. ረባዳ ፡ ነው. The road sags in the middle. መንገዱ ፡ መሀከሉ ፡ ላይ ፡ ረባዳ ፡ ነው
2. ዘመመ. The wall sags. ግድግዳው ፡ ዘሟል
3. ረገበ. The bed sagged from much use. ከማርጀቱ ፡ የተነሣ ፡ አልጋው ፡ ረገበ
*Our courage sagged. ሐሞታችን ፡ ፈሰሰ

**sagacious** ብልህ
A sagacious ruler is loved by his people. ብልህ ፡ ገዢ ፡ በሕዝቡ ፡ ይወደዳል

**sagacity** ብልህ ፡ መሆን
He showed sagacity in the way he answered your question. ለጥያቄህ ፡ በሰጠው ፡ መልስ ፡ ብልህ ፡ መሆኑ ፡ ይታወቃል

**sage** (n.) ዐዋቂ ፡ ሰው
He asked the sage a riddle about the sphinx. ዐዋቂውን ፡ ሰው ፡ የስፊንክስን ፡ ምስጢር ፡ ጠየቀው

**sage** (adj.)
1. ብልህ. He is a sage adviser, and you should listen to his advice. ብልህ ፡ መካሪ ፡ ስለሆነ ፡ ምክሩን ፡ ማዳመጥ ፡ አለብህ
2. የብልህ. This was a sage reply. ይህ ፡ የብልህ ፡ መልስ ፡ ነበር

**said,** see **say**

**sail** (v.)
1. ተጓዘ. The ship sailed when the storm abated. ማዕበሉ ፡ ሲቀንስ ፡ መርከቡ ፡ ተጓዘ
2. በመርከብ ፡ ተነሣ. Weather permitting, we sail on Monday. አየሩ ፡ ከተስማማን ፡ ሰኞ ፡ በመርከብ ፡ እንነሣለን
3. ተንገዋበበ. A hawk sails in the sky. ጭልፊት ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ታንገዋብባለች

**sail** (n.) የመርከብ ፡ ሸራ
The wind tore the sail. ነፋሱ ፡ የመርከቡን ፡ ሸራ ፡ ቀደደው

**sailboat** በነፋስ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ጀልባ
Sailboats were crossing the lake. በነፋስ ፡ የሚንቀሳቀሱት ፡ ጀልባዎች ፡ ሐይቁን ፡ ያቋርጡ ፡ ነበር

**sailing, go ~** በነፋስ ፡ በሚንቀሳቀስ ፡ ጀልባ ፡ ተንሸራሸረ
We go sailing every Sunday. እሑድ ፡ እሑድ ፡ በነፋስ ፡ በሚንቀሳቀስ ፡ ጀልባ ፡ እንሸራሸራለን

**sailor** መርከበኛ
How many sailors are on the ship? መርከቡ ፡ ላይ ፡ ስንት ፡ መርከበኞች ፡ አሉ ?

**saint** ቅዱስ (fem. ቅድስት)
Saint Mary and Saint Peter each have their own holiday. ቅድስት ፡ ማርያምና ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ የየራሳቸው ፡ ክብረ ፡ በዓል ፡ አላቸው

**patron saint**
1. ታቦት. Who is your patron saint? ታቦትህ ፡ ማን ፡ ነው ?

2. ፍጡነ ፡ ረድኤት. Ethiopia's patron saint is St. George. የኢትዮጵያ ፡ ፍጡነ ፡ ረድኤት ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ነው

**saintly** በቅድስና ፡ የሚኖር
The saintly man is revered by all. በቅድስና ፡ የሚኖረው ፡ ሰው ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የተከበረ ፡ ነው

**sake, for the ~ of, for one's ~** ለ - - ሲል ፤ ለ - - ብሎ
The soldier fights for the sake of his country. ወታደሩ ፡ ላገሩ ፡ ሲል ፡ ይዋጋል
I did it for the sake of peace. ለሰላም ፡ ብዬ ፡ አደረግሁት
I don't want you to go to any trouble for my sake. ለኔ ፡ ብለህ ፡ ምንም ፡ እንድትቸገር ፡ አልፈልግም
[See also 'heaven, simplicity']

**salad** ሰላጣ
Do you like salad? ሰላጣ ፡ ትወዳለህ ?

**salaried** ቋሚ
The salaried employees of the company will get pensions. የኩባንያው ፡ ቋሚ ፡ ሠራተኞች ፡ የጡረታ ፡ አበል ፡ ያገኛሉ
*The lowest salaried position pays $600.00 a month. ለዝቅተኛው ፡ ቦታ ፡ በወር ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ደሞዝ ፡ ይሰጣል

**salary** ደሞዝ
How can you manage on that salary? ያች ፡ ደሞዝህ ፡ እንዴት ፡ ትበቃሃለች ?

**sale**
1. መሸጥ. The sale of alcohol to minors is prohibited. አካለ ፡ መጠን ፡ ላልደረሱ ፡ አልኮል ፡ መሸጥ ፡ ክልክል ፡ ነው
2. የማጣሪያ ፡ ሽያጭ ፡ ጊዜ. I got it for half price at a sale. በማጣሪያ ፡ ሽያጭ ፡ ጊዜ ፡ በግማሽ ፡ ዋጋ ፡ ገዛሁት

**sales** ሽያጭ
Sales of cotton goods have doubled this year. የጨርቃ ፡ ጨርቅ ፡ ሽያጭ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ዕጥፍ ፡ ሆኗል

**be for sale** ይሸጣል
Our neighbor's house is for sale. የጎረቤታችን ፡ ቤት ፡ ይሸጣል

**have a sale** በቅናሽ ፡ ሸጠ
This store is having a sale on suits these days. ይህ ፡ መደብር ፡ ሰሞኑን ፡ ልብስ ፡ በቅናሽ ፡ ይሸጣል
[See also 'clearance']

**salesclerk** አሻሻጭ
The salesclerk is friendly. አሻሻጩ ፡ ሰው ፡ ወዳጅ ፡ ነው

**salesman** አሻሻጭ ፤ ሻጭ
The salesman gave her a demonstration of the sewing machine. አሻሻጩ ፡ (ሻጩ) ፡ የስፌት ፡ መኪናው ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠራ ፡ አሳያት

**salient** (n.)
*The enemy salient was cut off by our attack. ወደፊት ፡ ገፍቶ ፡ የገባውን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ በማጥቃት ፡ ወታደሮቻችን ፡ ከዋናው ፡ ጦር ፡ ለዩት

**salient** (adj.) ጎላ ፡ ብሎ ፡ የሚታይ
The salient feature of her face is her broad nose. ከፊቷ ፡ ጎላ ፡ ብሎ ፡ የሚታየው ፡ ሰፊ ፡ አፍንጫዋ ፡ ነው

**salient point** ፍሬ ፡ ነገር
He wrote down the salient points of the plan. የፕላኑን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ጻፈ

**saliva** ለሀጭ ፤ ምራቅ
Saliva was running down the baby's chin. የሕፃኑ ፡ ለሀጭ ፡ በአገጩ ፡ ላይ ፡ ይዝረከረክ ፡ ነበር
He spoiled my book with his saliva. መጽሐፌን ፡ በምራቅ ፡ አበላሸው

**sally** (sallied), v. ገሰገሰ
We sallied forth at dawn toward the enemy's lines. በንጋት ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ገሰገስን

**sally** (n.), **make a ~** ገሰገሰ
The troops made a sally toward the enemy's lines. ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ግንባር ፡ ገሰገሱ

**salon** የእንግዳ ፡ መቀበያ ፡ ክፍል
The salon is covered with carpets. የእንግዳ ፡ መቀበያው ፡ ክፍል ፡ ስጋጃ ፡ ተነጥፎበት ፡ ነበር

**saloon** መጠጥ ፡ ቤት
There were many men in the saloon. በመጠጡ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ

**salt** (v.) ጨው ፡ ጨመረ
Did you salt the soup? ሾርባው ፡ ውስጥ ፡ ጨው ፡ ጨምረህበታል ?

**salt** (n.) ጨው
May I have the salt please? ጨውን ፡ ታቀብለኝ

**salt** (adj.) ጨው ፡ ያለበት
Crabs are found only in salt water. ሸርጣን ፡ ጨው ፡ ባለበት ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ይገኛል

**salt bar** አሞሌ ፡ ጨው
In previous days, they used salt bars as

currency. በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ በአሞሌ ፡ ጨው ፡ ይገበያዩ ፡ ነበር
[See also 'grain']

**saltwater** (adj.) የባሕር
This is a saltwater fish. ይህ ፡ የባሕር ፡ ዓሣ ፡ ነው

**salty** ጨውማ
Soap does not lather well in salty water. ሳሙና ፡ በጨውማ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ አረፋ ፡ አይወጣውም

**be salty** ጨው ፡ በዛበት
This fish is salty. ይህ ፡ ዓሣ ፡ ጨው ፡ በዝቶበታል

**have a salty taste** ጨው ፡ ጨው ፡ አለ
This bread has a salty taste. ዳቦው ፡ ጨው ፡ ጨው ፡ ይላል

**salubrious** ለጤንነት ፡ የሚስማማ
A salubrious climate will restore him to health. ለጤንነት ፡ የሚስማማ ፡ አየር ፡ ያድነዋል

**be salubrious** ጤና ፡ ሰጠ
The climate in the highland is salubrious. የደጋው ፡ የአየር ፡ ሁኔታ ፡ ጤና ፡ ይሰጣል

**salutary**
1. ለጤና ፡ ጥሩ ፤ ለጤንነት ፡ የሚስማማ. The exercise was salutary. ጅምናስቲኩ ፡ ለጤና ፡ ጥሩ ፡ ነበር
Walking is a salutary exercise. በእግር ፡ መሄድ ፡ ለጤንነት ፡ የሚስማማ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ነው
2. ጠቃሚ. The teacher gave the boy salutary advice. አስተማሪው ፡ ለልጁ ፡ ጠቃሚ ፡ ምክር ፡ ሰጠ

**salutation** ሰላምታ
He raised his hat in salutation. ባርኔጣውን ፡ አንሥቶ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠኝ
Give my salutations to your wife! ለባለቤትህ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርብልኝ

**salute** (v.) ሰላምታ ፡ ሰጠ
The soldiers saluted the Emperor. ወታደሮቹ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጡ
*Shouts of welcome saluted their ears. እንኳን ፡ ደኅና ፡ መጣችሁ ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ሰሙ

**salute the flag, salute the colors** ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ በማክበር ፡ ሰቀለ
We salute the flag every day at school. ትምህርት ፡ ቤት ፡ በየቀኑ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ በማክበር ፡ እንሰቅላለን
Every morning the students salute the colors. ጧት ፡ ጧት ፡ ተማሪዎቹ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማውን ፡ በማክበር ፡ ይሰቅላሉ

**salute** (n.)
1. ሰላምታ. He gave the flag a salute. ለሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠ
2. የደስታ ፡ መግለጫ ፡ መድፍ. A salute of twenty-one guns was fired on the birth of the prince. ልዑሉ ፡ ሲወለድ ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ ሃያ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መድፍ ፡ ተተኰሰ

**salvage**
1. መልሶ ፡ አውጥቶ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ አዋለ. He salvaged most of the merchandise that had fallen into the river. ወንዙ ፡ ውስጥ ፡ የወደቀውን ፡ አብዛኛውን ፡ እቃ ፡ መልሶ ፡ አውጥቶ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ አዋለ
2. አዳነ. The boat sank, but they salvaged the cargo. መርከቧ ፡ ሰጠመች ፡ የጫነችውን ፡ እቃ ፡ ግን ፡ አዳኑ

**salvage** (n.) ውራጅን ፡ መሰብሰብ
Salvage is a profitable business. ውራጅን ፡ መሰብሰብ ፡ የሚያዋጣ ፡ ንግድ ፡ ነው

**salvation**
1. ድኅነት. Salvation can be obtained only through Jesus Christ. ድኅነት ፡ የሚገኘው ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማመን ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ለሕይወቱ ፡ መትረፍ ፡ ምክንያት. Her care was my salvation when I was sick. በታመምኩ ፡ ጊዜ ፡ እርሷ ፡ እኔን ፡ ማስታመሟ ፡ ለሕይወቴ ፡ መትረፍ ፡ ምክንያት ፡ ነበር

**find salvation** ጽድቅን ፡ ሻ
He mortified his body in order to find salvation. ጽድቅን ፡ በመሻት ፡ ሰውነቱን ፡ አጕሳቈለ

**salve** (n.)
1. ቅባት. Put some salve on your burn! የተቃጠለው ፡ ሰውነትህ ፡ ላይ ፡ ቅባት ፡ አድርግበት
2. ማጽናኛ. The kind words were salve to his hurt feelings. ደግ ፡ አነጋገሩ ፡ ለተጐዳው ፡ስሜቱ ፡ ማጽናኛ ፡ ሆነው

**same, the** ~ (pron., subject, object)
1. ያው. That is all the same to me. ለኔ ፡ ሁሉም ፡ ያው ፡ ነው
2. ያንኑ. He said exactly the same. ልክ ፡ ያንኑ ፡ ተናገረ
3. እሱኑ. John wants coffee, and I will have the same. ጆን ፡ ቡና ፡ ይፈልጋል ፤ እኔም ፡ እሱኑ ፡ ልጠጣ
4. አንድ ፡ ዓይነት. All people do not feel the same about what's going on today. አሁን ፡ ስለ ሚደረገው ፡ ነገር ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ስሜት ፡ የላቸውም

**the same** (adj.)
1. ያው. The same man called three times. ያው ፡ ሰውዬ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ደውሎ ፡ ነበር
2. አንድ. Boys and girls can swim in the same pool together. ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ባንድ ፡ የመዋኛ ፡ ስፍራ ፡ አብረው ፡ ሊዋኙ ፡ ይችላሉ
We lived in the same house for fifty years. አንድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ ኖርን
3. ራሱ. He is the same man who spoke to me. ያነጋገረኝ ፡ ሰው ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ነው
*We came back the same way we went. በሄድንበት ፡ መንገድ ፡ ተመልሰን ፡ መጣን
*We are the same age. በዕድሜ ፡ በዚያው ፡ ነን

**the same to you** ላንተም ፡ እንዲሁ
Have a nice holiday! The same to you! መልካም ፡ በዓል ፡ ይሁንልህ! ላንተም ፡ እንዲሁ

**it comes to the same thing** ያው ፡ ነው
Pay by check or cash; it comes to the same thing. በቼክ ፡ ወይም ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ብትከፍል ፡ ያው ፡ ነው

**in the same** ከዚያው
Put the book back in the same place you found it! መጽሐፉን ፡ ከዚያው ፡ ካገኘህበት ፡ ቦታ ፡ መልሰው

**on the same day**
I can be back on the same day. ውሎ ፡ ገባ ፡ ልመለስ ፡ እችላለሁ

**the very same** ያንኑ
You made the very same mistake again. ያንኑ ፡ ስሕተት ፡ እንደገና ፡ ደገምከው
[See also 'about, all, just, much, one, time']

## sample (v.) ቀመሰ
We sampled the cake and found it very good. ኬኩን ፡ ቀመስነው ፤ ጥሩ ፡ ነው

## sample (n.)
1. ናሙና ፤ ላሙና. Do you have a sample of the material with you? የጨርቁን ፡ ናሙና ፡ ይዘሃል ?
2. ምልክት. Pushing people aside to get on a bus is a sample of his bad manners. አውቶቡስ ፡ ለመሳፈር ፡ ሰውን ፡ መግፋት ፡ የመጥፎ ፡ ጠባዩ ፡ ምልክት ፡ ነው

**sample** (adj.) የናሙና
Give me a sample page of the book. የመጽሐፉን ፡ አንድ ፡ ናሙና ፡ ገጽ ፡ ስጠኝ

## sanatorium የሕሙማንና ፡ የድኩማን ፡ ማረፊያ ፡ ቤት
His brother stayed five months in a sanatorium. ወንድሙ ፡ ላምስት ፡ ወር ፡ በሕሙማንና ፡ በድኩማን ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ ቆየ

## sanctify (sanctified)
1. ባረከ. The priest sanctified their marriage in a beautiful ceremony. ቄሱ ፡ ጋብቻቸውን ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ባረከላቸው
2. ቅዱስ ፡ አደረገ. A life of sacrifice had sanctified him. ሕይወቱን ፡ መሠዋቱ ፡ ቅዱስ ፡ አደረገው

**be sanctified** (= active) ደገፈ
+This practice is sanctified by custom. ይህን ፡ አሠራር ፡ ባህል ፡ ይደግፈዋል

## sanction (v.)
1. ፈቀደ. The government does not sanction the sale of opium. መንግሥት ፡ የኦፒዩምን ፡ መሸጥ ፡ አይፈቅድም
2. ደገፈ. Would you sanction flogging for minor crimes? ላነስተኛ ፡ ወንጀሎች ፡ ግርፋትን ፡ ትደግፋለህ ?

## sanction (n.) ፈቃድ
This book was translated without the sanction of the author. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ያለ ፡ ደራሲው ፡ ፈቃድ ፡ ተተረጎመ

**sanctions** የኢኮኖሚ ፡ ጭቈና
We ought to impose sanctions on South Africa. በደቡብ ፡ አፍሪካ ፡ ላይ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ጭቈና ፡ ማድረግ ፡ ይገባናል

## sanctity
1. ክብር. The sanctity of the church was broken by shouts and screams. የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ክብር ፡ በጩኸትና ፡ በልቅሶ ፡ ተደፈረ
2. ቅዱስነት. The sanctity of marriage laws means nothing to him. የጋብቻ ፡ ሕጎች ፡ ለሱ ፡ ቅዱስነት ፡ የላቸውም

## sanctuary (sanctuaries)
1. መቅደስ. Because of the holiness of the sanctuary, only priests may enter it. መቅደስ ፡ የተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ስለሆነ ፡ ሊገቡ ፡ የሚፈቀድላቸው ፡ ቄሶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው
2. ጥገኝነት. He sought sanctuary in a neighboring country. ባንድ ፡ የጐረቤት ፡ አገር ፡ ጥገኝነት ፡ ጠየቀ

## sand (v.) አሸዋ ፡ አፈሰሰ
The Highway Authorities sanded the roads. የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ አሸዋ ፡ አፈሰሱ

**sand down** ፈገፈገ
Sand the wood down with sandpaper! በብርጭቆ ፡ ወረቀት ፡ ዕንጨቱን ፡ ፈግፍገው !

**sand** (n.) አሸዋ
Sand blew in my eyes. አሸዋ ፡ ዓይኔ ፡ ውስጥ ፡ ገባ

**sandal** የነጠላ ፡ ጫማ
The strap on my sandal broke. የነጠላ ፡ ጫማዬ ፡ ማሰሪያ ፡ ተበጠሰ

**sandbank** የአሸዋ ፡ ክምር
There was a sandbank by the side of the road. በመንገዱ ፡ ዳር ፡ የአሸዋ ፡ ክምር ፡ ነበር

**sandpaper** የብርጭቆ ፡ ወረቀት
Sand the wood down with sandpaper! በብርጭቆ ፡ ወረቀት ፡ ዕንጨቱን ፡ ፈግፍገው

**sandstorm** አሸዋማ ፡ ውሽንፍር
They got lost in a sandstorm. አሸዋማ ፡ ውሽንፍር ፡ ውስጥ ፡ ጠፉ

**sandwich** ሳንድዊች
I want a meat sandwich. የሥጋ ፡ ሳንድዊች ፡ እፈልጋለሁ

**sandy** አሸዋማ
The lake shores are sandy. የባሕሩ ፡ ጠረፍ ፡ አሸዋማ ፡ ነው

**sane** ጤነኛ
A sane man does not take unnecessary risks. ጤነኛ ፡ ሰው ፡ በሚሠራው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ዓይኑን ፡ ጨፍኖ ፡ አይገባም
*He has a sane approach to the problem. ጉዳዩን ፡ በማስተዋል ፡ ተከታተለው

**sang**, see **sing**

**sanguine, ~ disposition** ተስፋ ፡ ያለመቍረጥ ፡ መንፈስ
His sanguine disposition prompted him to accept the job. ተስፋ ፡ ያለመቍረጥ ፡ መንፈሱ ፡ ሥራውን ፡ እንዲቀበል ፡ ገፋፋው
*His sanguine complexion shows that he has good health. የደሙ ፡ ጥራት ፡ መልካም ፡ ጤንነት ፡ እንዳለው ፡ ያሳያል

**sanitary**
1. ንጹሕ. Food should be kept in a sanitary place. ምግብ ፡ ንጹሕ ፡ በሆነ ፡ ቦታ ፡ መቀመጥ ፡ አለበት
2. የጤና ፡ አጠባበቅ. The government imposed new sanitary laws. መንግሥት ፡ አዲስ ፡ የጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ሕግ ፡ አወጣ

**sanitation**
1. የጽዳት ፡ ጥበቃ. We are making efforts to teach the local people the rudiments of sanitation. ያገሩን ፡ ሰዎች ፡ የጽዳት ፡ ጥበቃ ፡ መሠረታዊ ፡ ደንቦች ፡ ለማስተማር ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነን
2. ንጽሕና. Rubbish removal is necessary for sanitation. ቆሻሻን ፡ ማንሣት ፡ ለንጽሕና ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**sanity** አእምሮ
He lost his sanity when his family was killed before his eyes. ቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ እፊቱ ፡ ሲገደሉ ፡ አእምሮውን ፡ ሳተ

**sank**, see **sink**

**sap** (sapped) ሸረሸረ
The flood waters sapped the wall of the canal. የውኃው ፡ መጥለቅለቅ ፡ የቦዩን ፡ ግንብ ፡ ሸረሸረው
**sap one's strength (energy)** አደከመ
The extreme heat sapped his strength. ኀይለኛ ፡ ሙቀት ፡ አደከመው
A bad cold sapped his energy. ኀይለኛ ፡ ጉንፋን ፡ አደከመው

**sap** (n.) ወተት
Euphorbia produces sap. ቁልቋል ፡ ወተት ፡ ይወጣዋል

**sapper** ሰርሳሪ
Enemy sappers undermined our fortification. የጠላት ፡ ሰርሳሪዎች ፡ ምሽጋችንን ፡ ቦረቦሩት

**sapphire** ዕንቁ ፡ ሳንፔር
The ring is decorated with a sapphire. ቀለበቱ ፡ በዕንቁ ፡ ሳንፔር ፡ ያጌጠ ፡ ነው

**sarcasm** አሽሙር
His sarcasm lost him friends. አሽሙሩ ፡ ጓደኛ ፡ አሳጣው

**sash**
1. ድግ. He wore a sash around his waist. ድጉን ፡ በወገቡ ፡ ላይ ፡ ዐጠቀ
2. ክፈፍ. The sash of the window is made of wood. የመስኮቱ ፡ ክፈፍ ፡ በዕንጨት ፡ የተሠራ ፡ ነው

**sat**, see **sit**

**Satan** ሰይጣን
Satan is trying to snare our souls. ሰይጣን ፡ ነፍሳችንን ፡ ወጥመድ ፡ ሊያገባ ፡ ይሞክራል

**satchel** ቦርሳ
He carries his books in an old satchel. መጽሐፎቹን ፡ ባሮጌ ፡ ቦርሳ ፡ ይይዛል

**sate** **አጠገበ**
No amount of food will sate him. ምንም ፡ ያህል ፡ ምግብ ፡ አያጠግበውም

**satellite**
1. ተዘዋዋሪ ፡ የሰማይ ፡ አካል. Each planet may have one or two satellites. እያንዳንዱ ፡ ዓለም ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ተዘዋዋሪ ፡ የሰማይ ፡ አካል ፡ ይኖረዋል
2. ሰው ፡ ሠራሽ ፡ መንኰራኵር. The satellite circles the earth every eighty minutes. ሰው ፡ ሠራሽ ፡ መንኰራኵር ፡ በየሰማንያው ፡ ደቂቃ ፡ ምድርን ፡ ትዞራለች

**satellite states** **ጭፍሮች ፡ አገሮች**
The satellite states always vote with their leader. ጭፍሮቹ ፡ አገሮች ፡ ሁልጊዜ ፡ መሪያቸውን ፡ አገር ፡ ተከትለው ፡ ድምፅ ፡ ይሰጣሉ

**(be) satiable** **ረካ**
His appetite is easily satiable. ከረኀቡ ፡ በቀላሉ ፡ ይረካል

**satiate** **አጠገበ**
The meal failed to satiate him. ምግቡ ፡ ሳያጠግበው ፡ ቀረ

**satiety** **ጥጋብ**
Satiety induces heavy sleep. ጥጋብ ፡ ከባድ ፡ እንቅልፍ ፡ ያስወስዳል

**reach satiety** **ጠገበ**
I have eaten so much that I have reached satiety. ብዙ ፡ ስለበላሁ ፡ ጠገብኩ

**satin** **አጥላስ**
The Emperor's robe is made of satin. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ካባ ፡ ከአጥላስ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**satire** **ምጸታዊ ፡ ትችት**
His satire of city life was appreciated by all. የከተማ ፡ ኑሮ ፡ ምጸታዊ ፡ ትችቱ ፡ በሁሉም ፡ ተደነቀ

**satirically** **በምጸት**
I spoke satirically; I didn't mean what I said to be taken literally. የተናገርኩት ፡ በምጸት ፡ ስለሆነ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ እንዲተረጐም ፡ አልፈልግም

**satisfaction** **ደስታ**
It gives me great satisfaction to hear that. ይህንን ፡ መስማት ፡ ትልቅ ፡ ደስታ ፡ ይሰጠኛል
*Give satisfaction, or you will lose your job. ሥራህን ፡ በሚገባ ፡ ሥራ ፣ ያለበለዚያ ፡ ከሥራ ፡ ትወጣለህ

**demand satisfaction** **እንዲክሰው ፡ ጠየቀ**
The angry customer demanded satisfaction, because the shopowner sold him cheap merchandise. የተናደደው ፡ ገዢ ፡ ባለሱቁ ፡ መናኛ ፡ እቃ ፡ ስለሸጠለት ፡ እንዲክሰው ፡ ጠየቀ

**satisfactorily** **በሚያስደስት ፡ አኳኋን ፤ በመልካም ፡ ሁኔታ**
He answered the question satisfactorily. ጥያቄውን ፡ በሚያስደስት ፡ አኳኋን ፡ መለሰ ፡ (or, ለጥያቄው ፡ አጥጋቢ ፡ መልስ ፡ ሰጠ)
His speech came off satisfactorily. ንግግሩ ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ ተዋጣለት

**satisfactory**
1. ደኅና. His condition is satisfactory. ሁኔታው ፡ ደኅና ፡ ነው
2. በቂ. We want satisfactory reasons why you failed to help us. ለምን ፡ እንዳልረዳኸን ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ እንፈልጋለን
3. አጥጋቢ. By and large, the results were satisfactory. በጠቅላላው ፡ ውጤቱ ፡ አጥጋቢ ፡ ነበር

**be satisfactory** **አስደሰተ**
A compromise is never fully satisfactory to both parties. ከኔ ፡ ይቅር ፡ ከኔ ፡ ይቅር ፡ የሚል ፡ ስምምነት ፡ ለሁለቱም ፡ ወገን ፡ አያስደስትም

**(be) satisfied**
1. አምኖ ፡ ተቀበለ. The teacher was satisfied that John's statement was true. አስተማሪው ፡ የዮሐንስ ፡ የተናገረው ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ አምኖ ፡ ተቀበለ
2. ረካ. My needs are easily satisfied. ፍላጎቴ ፡ በቀላሉ ፡ ይረካል

**be satisfied with**
1. ደስ ፡ አለ(ው). +I am not satisfied with my new apartment. አዲሱ ፡ አፓርተማዬ ፡ ደስ ፡ አላለኝም
2. በ - - - ተደሰተ. Otherwise, I am satisfied with his work. በተረፈ ፡ በሱ ፡ ሥራ ፡ ተደስቻለሁ

**satisfy** (satisfied)
1. አስደሰተ. You can't satisfy everybody. ሁሉን ፡ ልታስደስት ፡ አትችልም
2. አጠገበ ፤ አስረዳ. Your answer didn't satisfy me. መልስህ ፡ አላጠገበኝም
We satisfied the police that we had nothing to do with the accident. ባደጋው ፡ ምንም ፡ የማያገባን ፡ መሆኑን ፡ ለፖሊሶች ፡ አስረዳን
3. አስታገሠ(ለት) ፤ አረካ(ለት). A sandwich satisfied his hunger. አንድ ፡ ሳንድዊች ፡ ረኀቡን ፡ አስታገሠለት ፡ (አረካለት)

**satisfy the claims** **ካሳ ፡ ከፈለ**
He satisfied all claims for the damage he had

caused by the accident. ባደጋው ፡ ምክንያት ፡ ላደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ሁሉ ፡ ካሳ ፡ ከፈለ

**saturate**
1. አበሰበሰ. The rain saturated my clothing. ዝናብ ፡ ልብሴን ፡ አበሰበሰው
2. ሞላ. +They saturated the market with leopards' hides. ገበያውን ፡ የነብር ፡ ቆዳ ፡ ሞልቶት ፡ ነበር

**be saturated** ተበከለ
The ground is saturated with oil. መሬቱ ፡ በዘይት ፡ ተበክሏል

**Saturday** ቅዳሜ
We don't work on Saturday. ቅዳሜ ፡ አንሠራም

**sauce**
1. ስጎ. Put some sauce on your spaghetti! ፓስታህ ፡ ላይ ፡ ስጎ ፡ ጨምርበት
2. ማጣፈጫ. Do you have chocolate sauce? ከቸኰላታ ፡ የተቀመመ ፡ ማጣፈጫ ፡ አለህ?

**saucepan** [ረጅም ፡ እጀታ ፡ ያለው ፡ ብረት ፡ ድስት]

**saucer** ማስቀመጫ
He put the cup on the saucer. ሲኒውን ፡ ማስቀመጫው ፡ ላይ ፡ አስቀመጠው

**saunter** ተንሸራሸረ
People saunter through the park on a summer evening. በበጋ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ሰዎች ፡ በመናፈሻው ፡ ውስጥ ፡ ይንሸራሸራሉ

**sausage** ቋሊማ
He likes sausage for breakfast. ለቁርስ ፡ ቋሊማ ፡ ይወዳል

**savage** (n.) አረመኔ ፣ ያልሠለጠነ ፡ ሰው
Savages attacked and killed him. አረመኔዎች ፡ (ያልሠለጠኑ ፡ ሰዎች) ፡ ደብድበው ፡ ገደሉት

**savage** (adj.)
1. ኀይለኛ. We couldn't withstand the savage attack. ኀይለኛውን ፡ ውጊያ ፡ ለመቋቋም ፡ አልቻልንም
2. ቁጡ. The savage lion killed the tourist. ቁጡው ፡ አንበሳ ፡ አገር ፡ ጐብኚውን ፡ ገደለው
3. ጨካኝ ፤ አረመኔ. Savage outlaws burned the church and massacred the monks. ጨካኞች ፡ (አረመኔዎች) ፡ ሽፍቶች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ አቃጥለው ፡ መነኰሳቱን ፡ ገደሏቸው

**savagery**
1. አውሬነት. The savagery of lions makes them feared. ያንበሶች ፡ አውሬነት ፡ እንዲፈሩ ፡ ያደርጋቸዋል
2. ጭካኔ. The savagery of the bandits was very shocking. የሽፍቶቹ ፡ ጭካኔ ፡ በጣም ፡ የሚያስቅቅ ፡ ነበር

**savannah** [የሰንበሌጥ ፡ ምድር]

**save** (vt.)
1. አዳነ. He saved her life. ሕይወቷን ፡ አዳነ
Christ saved humanity. ክርስቶስ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ አዳነ
The woman saved her jewels from the fire. ሴትዮዋ ፡ ጌጣ ፡ ጌጧን ፡ ከእሳት ፡ አዳነች
2. አጠራቀመ. Did you save any money? ትንሽ ፡ ገንዘብ ፡ አጠራቅመሃል?
3. አስቀመጠ. Why do you save these old papers? እነዚህን ፡ አሮጌ ፡ ጋዜጦች ፡ ለምን ፡ ታስቀምጣቸዋለህ?
4. ቈጠበ. Save your strength; we have a long trip tomorrow. ጉልበትህን ፡ ቈጥብ ፤ ነገ ፡ ረጅም ፡ ጉዞ ፡ አለብን
Traveling by plane saves many hours. በአውሮፕላን ፡ መጓዝ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይቈጥባል
5. ያዘ. Please save a seat for me! ቦታ ፡ ያዝልኝ
6. ከመድከም ፡ አዳነ. The large print saves my eyes. ጉልሁ ፡ ፊደል ፡ ዓይኔን ፡ ከመድከም ፡ ያድነዋል

**save** (vi.) ገንዘብ ፡ ቈጠበ
She tries to save in every way she can. በተቻለት ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ ለመቈጠብ ፡ ትሞክራለች

**save face** ከውርደት ፡ ዳነ
He saved face by telling everyone he really wanted to do it. በእርግጥ ፡ ሊያደርገው ፡ እንደፈለገ ፡ በማስመሰሉ ፡ ከውርደት ፡ ዳነ

**save the situation** ነገሩ ፡ እንዳይባባስ ፡ አደረገ
When an offensive remark was made, the hostess saved the situation by diverting everyone's attention. የሚያስቀይም ፡ አስተያየት ፡ በተሰነዘረ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤቷ ፡ ወሬውን ፡ በመለወጥ ፡ ነገሩ ፡ እንዳይባባስ ፡ አደረገች
[See also 'skin']

**save** (prep.) ከ - - - በስተቀር
All save him approved the plan. ከሱ ፡ በስተቀር ፡ ሁሉም ፡ እቅዱን ፡ ደገፈ

**saving** (n.)
1. ማዳን. The saving of lives is a meritorious action. የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ማዳን ፡ ዝና ፡ የሚያተርፍ ፡ ተግባር ፡ ነው
2. ትርፍ. A saving of $20 was obtained by using wire instead of rope. በገመድ ፡ ፈንታ ፡ በሽቦ ፡ በመጠቀም ፡ ሀያ ፡ ብር ፡ ትርፍ ፡ አገኘ
3. (= to save) መቈጠብ. It will mean a saving of two hours to take this shortcut. በዚህ ፡ አቋራ-

ጭ ፡ መንገድ ፡ መሄድ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ለመቈጠብ ፡
ያስችላል

**savings** ያጠራቀመ ፤ ተቀማጭ ፡ ገንዘብ
He has used up all his savings. ያጠራቀመውን ፡
ሁሉ ፡ ጨርሶታል
A large bill from the doctor made a hole in
my savings. ለዶክተሩ ፡ የከፈልኩት ፡ ብዙ ፡ ገን
ዘብ ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘቤን ፡ አመነመነብኝ

**saving** (adj.)
1. ቈጣቢ. He has a saving wife. ቈጣቢ ፡ ሚስት ፡
አለው
2. ጥሩ. His only saving trait is a sense of
humor. ከጠባዩ ፡ ሁሉ ፡ ጥሩው ፡ ነገር ፡ ቀልደኛነቱ ፡
ብቻ ፡ ነው

**saving** (prep.) ከ - - - በስተቀር
I like them all, saving this one. ከዚህ ፡ በስተቀ
ር ፡ ሁሉንም ፡ እወዳለሁ

**savings account** ተቀማጭ ፡ ገንዘብ
Interest will accrue on my savings account.
እባንክ ፡ ያለኝ ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘብ ፡ ወለዱ ፡ ይ
ጨምራል

**Savior** መድኀኒታችን
The Savior will one day return to earth.
መድኀኒታችን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ይመ
ለሳል

**savor** (v.) ቀምሶ ፡ ወደደ
He savored the soup. ሾርባውን ፡ ቀምሶ ፡ ወደደው

**savor of**
1. የ - - - መልክ ፡ ታየ(በት). The plot savors of
treason. አድማው ፡ የክሕደት ፡ መልክ ፡ ይታይበታል
2. (repeated noun) + አለ. That sauce savors
of lemon. ያ ፡ ማጣፈጫ ፡ ሎሚ ፡ ሎሚ ፡ ይላል

**savor** (n.)
1. ጣዕም. The savor of this soup makes me
think of Italy. የዚህ ፡ ሾርባ ፡ ጣዕም ፡ የኢጣልያ
ንን ፡ አገር ፡ ያስታውሰኛል
2. መንፈስ. There is a savor of conceit in
everything he says. የሚለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የእብ
ሪት ፡ መንፈስ ፡ አለበት

**(be) savory** ጣፈጠ
The meat is savory. ሥጋው ፡ ይጣፍጣል

**saw,** see **see**

**saw** (v.)
1. በመጋዝ ፡ ቈረጠ. He sawed the branch off the
tree. ቅርንጫፉን ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ በመጋዝ ፡ ቈረጠው
2. መገዘ. Can you saw straight? ቀጥ ፡ አድርገህ ፡
መመገዝ ፡ ትችላለህ?

**saw** (n.) መጋዝ
Where did you buy this saw? ይህንን ፡ መጋዝ ፡
ከየት ፡ ገዛኸው?

**say** (said), v. አለ
What did you say? ምን ፡ አልክ?
*What does this sign say? ይህ ፡ ምልክት ፡ ምን ፡
ማለት ፡ ነው?
*What do you say to a walk? በእግራችን ፡ ብን
ንሸራሸርስ?
*I'll meet you, say, in an hour. ባንድ ፡ ሰዓት ፡
ውስጥ ፡ አገኝሃለሁ
*I won't say no to a glass of beer. አንድ ፡ ቢራ ፡
ብትለኝ ፡ አልጠላም
*She left the room without saying a word.
ቃልም ፡ ሳትተነፍስ ፡ ከክፍሉ ፡ ወጥታ ፡ ሄደች

**I'd say** እንደሚመስለኝ
He is, I'd say, forty. እኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ አር
ባ ፡ ዓመት ፡ ይሆነዋል

**(he) is said to be** ይባላል
He is said to be rich. ሀብታም ፡ ነው ፡ ይባላል

**that is to say** ማለት
Three weeks from tomorrow, that is to say
May 10th, we will leave this town. የነገ ፡ ሦስት ፡
ሳምንት ፤ ማለት ፡ ግንቦት ፡ ዐሥር ፤ ይህችን ፡ ከ
ተማ ፡ እንለቃለን

**to say nothing of** አይነሣ
It takes a lot of time, to say nothing of the
expense. የወጪው ፡ ነገር ፡ አይነሣ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡
ይፈጃል
[See also 'blessing, prayer, mean']

**say** (n.) ሥልጣን
He has no say in running the company.
በኩባንያው ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ሥልጣን ፡ የ
ለውም

**saying** ምሳሌ
That's a very common saying. ያ ፡ የተለመደ ፡
ምሳሌ ፡ ነው

**it goes without saying**
*It goes without saying that the Chinese will
be displeased. ቻይናዎች ፡ እንደሚከፉ ፡ ሳይታለ
ም ፡ የተፈታ ፡ ነው

**there is no saying** አይታወቅም
There is no saying when this war will end.
ይህ ፡ ጦርነት ፡ መቼ ፡ እንደሚቆም ፡ አይታወቅም

**scab** ቅርፊት
Don't pick the scab off your wound! የቁስልህን ፡
ቅርፊት ፡ አትላጠው

**scaffold** መወጣጫ
The scaffold has been built around the house for the painters to work on. ለቀለም ፡ ቀቢዎች ፡ ተብሎ ፡ መወጣጫ ፡ በቤቱ ፡ ዙሪያ ፡ ተሠርቷል

**scald**
1. በፈላ ፡ ውኃ ፡ አለቀለቀ. Scald the dishes before drying them! ከመወልወልህ ፡ በፊት ፡ ሳሕኖቹን ፡ በፈላ ፡ ውኃ ፡ አለቅልቃቸው
2. አቃጠለ. A pot of boiling water overturned and scalded the baby. የፈላ ፡ ውኃ ፡ ፈሶ ፡ ሕፃኑን ፡ አቃጠለው
3. አፈላ. Scald the milk before drinking it! ከመጠጣትህ ፡ በፊት ፡ ወተቱን ፡ አፍላው

**scale** (vt.)
1. ፋቀ. Scale the fish before you cook it! ዓሣውን ፡ ከመጥበስሽ ፡ በፊት ፡ ፋቂው
2. ወጣ. They are going to scale Mt. Everest. የኤቨረስትን ፡ ተራራ ፡ ሊወጡ ፡ ነው
3. አስተካከለ. Try to scale your spending to your income. ወጪህን ፡ ከገቢህ ፡ ጋር ፡ ለማስተካከል ፡ ሞክር

**scale** (vi.) እየተቀረፈ ፡ ወደቀ
The paint is scaling off the house. ቀለሙ ፡ ከቤቱ ፡ ላይ ፡ እየተቀረፈ ፡ ይወድቃል

**scale down** ዝቅ ፡ አደረገ
He scaled down his request for funds. የገንዘብ ፡ ጥያቄውን ፡ ዝቅ ፡ አደረገው

**scale** (n.)
1. መለኪያ. The ruler has one scale in centimeters and another in inches. ማሥመሪያው ፡ የሳንቲሜትርና ፡ የኢንች ፡ መለኪያ ፡ አለው
2. መመዘኛ. This map is on the scale of 5 inches to 1 mile. ይህ ፡ ካርታ ፡ መመዘኛው ፡ አምስት ፡ ኢንች ፡ ላንድ ፡ ማይል ፡ ነው
3. ደረጃ. He is high on the social scale. በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደረጃ ፡ አለው
4. ቅርፊት. Remove the scales from the fish! የዓሣውን ፡ ቅርፊት ፡ ላጠው

**scales** ሚዛን
Put the meat on the scales! ሥጋውን ፡ ሚዛኑ ፡ ላይ ፡ አድርገው

**on a large scale** በሰፊው
They are preparing for war on a large scale. ለጦርነት ፡ በሰፊው ፡ በመዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ናቸው

**on a small scale** እንደነገሩ
They are only dealing with the problem on a small scale. ጉዳዩን ፡ የተመለከቱት ፡ እንደነገሩ ፡ ነው

**wage scales** የሠራተኞች ፡ የቀን ፡ አበል
Wage scales are lower here than in New York. የሠራተኞች ፡ የቀን ፡ አበል ፡ ከኒው ፡ ዮርክ ፡ ይልቅ ፡ እዚህ ፡ አነስ ፡ ይላል

**scalp** (v.) አናት ፡ ገሸለጠ
The Indians scalped the settlers. ህንዶች ፡ አዲሶቹን ፡ ሰፋሪዎች ፡ አናታቸውን ፡ ይገሽልጧቸው ፡ ነበር

**scalp** (n.) አናት
The sun hit my scalp. ፀሐይ ፡ አናት ፡ አናቴን ፡ አለኝ

**scalpel** የኦፔራሲዮን ፡ ማድረጊያ ፡ ስለት ፤ የስለት ፡ ቢላዋ
The doctor laid the burned flesh bare with his scalpel. ዶክተሩ ፡ የተቃጠለውን ፡ ሥጋ ፡ በኦፔራሲዮን ፡ ማድረጊያ ፡ ስለት ፡ (በስለት ፡ ቢላዋ) ፡ ገፈፈው

**scamper, ~ away** ፈትለክ ፡ አለ
The mice scampered away when the cat came. ድመቷ ፡ ብቅ ፡ ስትል ፡ አይጧ ፡ ፈትለክ ፡ አለች

**scan** (scanned)
1. በችኰላ ፡ መልከት ፡ መልከት ፡ አደረገ. He scanned the newspapers for pictures of his children. የልጆቹን ፡ ፎቶግራፍ ፡ ፍለጋ ፡ ጋዜጣውን ፡ በችኰላ ፡ መልከት ፡ መልከት ፡ አደረገው
2. በዓይኑ ፡ ቃኘ. The general scanned the battlefield. ጄኔራሉ ፡ የጦር ፡ ሜዳውን ፡ በዓይኑ ፡ ቃኘ

**scan one's face** ትኩር ፡ ብሎ ፡ ተመለከተ
His mother scanned his face to see if he was telling the truth. እውነት ፡ መናገሩን ፡ ለማረጋገጥ ፡ እናትየዋ ፡ ትኩር ፡ ብላ ፡ ተመለከተችው

**scandal**
1. አሳፋሪ ፡ ነገር ፤ አሳፋሪ. The newspapers gave the scandal an airing. ጋዜጣዎች ፡ የተደረገውን ፡ አሳፋሪ ፡ ነገር ፡ ለሕዝብ ፡ ነዙት
The slums in the city are a scandal. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ቆሻሻ ፡ ሰፈር ፡ አሳፋሪ ፡ ነው
2. ነውር. Years ago, it was a scandal for a woman to wear lipstick. ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ሴቶች ፡ የከንፈር ፡ ቀለም ፡ ሲቀቡ ፡ እንደ ፡ ነውር ፡ ይቈጠር ፡ ነበር
3. አሉባልታ. She loves a bit of scandal. አሉባልታ ፡ ትወዳለች
4. መጥፎ ፡ ድርጊት. The mayor is mixed up in the scandal. በመጥፎ ፡ ድርጊት ፡ ውስጥ ፡ ከንቲባው ፡ ይገኝበታል

**scandalize** አስቀየመ
She scandalized her mother by smoking cigarettes. ሲጃራ ፡ በማጨስ ፡ እናቷን ፡ አስቀየመች

**scandalous** አሳፋሪ
His scandalous behavior angered everyone. አሳፋሪ ፡ ተግባሩ ፡ ሁሉን ፡ አስቆጣ

**scant**
1. አነስ ፡ ያለ. We have a scant supply of food. ሥንቃችን ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ ነው
2. ብርቅ. Rainfall is scant in the desert. በምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ ዝናም ፡ ብርቅ ፡ ነው

**scant hour** ካንድ ፡ ሰዓት ፡ ያነሰ ፡ ጊዜ
You have a scant hour in which to pack. እቃህን ፡ ለመክተት ፡ ካንድ ፡ ሰዓት ፡ ያነሰ ፡ ጊዜ ፡ አለህ

**(be) scant of** አጠረ(ው)
+She was scant of breath. ትንፋሽ ፡ አጥሯት ፡ ነበር

**scanty**
1. ትንሽ. Drought caused a scanty harvest. በድርቁ ፡ ምክንያት ፡ የተሰበሰበው ፡ ሰብል ፡ ትንሽ ፡ ነበር
2. በጣም ፡ አጭር. The dancers wore scanty costumes. ደናሾቹ ፡ የለበሱት ፡ ልብስ ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ ነበር
3. (= noun) ማነስ. The scanty rainfall is causing a water shortage. የዝናብ ፡ ማነስ ፡ የውኃ ፡ እጥረት ፡ አደረሰ

**scapegoat**
*The director served as a scapegoat for the employees' wrath. የሠራተኞቹን ፡ ስሜት ፡ ለማብረድ ፡ ሲባል ፡ ወቀሳው ፡ ሁሉ ፡ በዲሬክተሩ ፡ ላይ ፡ ሆነ

**scar** (scarred), vt. (= vi) ተቀርጾ ፡ ቀረ
The tragedy had scarred his mind. አሰቃቂው ፡ ነገር ፡ አእምሮው ፡ ላይ ፡ ተቀርጾ ፡ ቀረ
*Several wounds scarred his face. ፊቱ ፡ ጠባሳ ፡ ብቻ ፡ ነው

**be scarred**
1. ተበጫጨረ. His face was scarred from many fights. ከብዙ ፡ አምባጓሮ ፡ የተነሣ ፡ ፊቱ ፡ ተበጫጭሯል
2. ተጠቀጠቀ. His face was scarred by smallpox. ፊቱ ፡ በፈንጣጣ ፡ ተጠቅጥቆ ፡ ነበር

**scar** (n.) ጠባሳ
He has a scar on his right cheek. ቀኝ ፡ ጉንጩ ፡ ላይ ፡ ጠባሳ ፡ አለው

**scarce** ብርቅ
Cultivated land is scarce in the desert. የታረሰ ፡ መሬት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ ብርቅ ፡ ነው

**be scarce**
1. ጠፋ. During the war, sugar was scarce and had to be rationed. በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ስኳር ፡ ጠፍቶ ፡ ስለነበረ ፡ እየተመጠነ ፡ መከፋፈል ፡ ነበረበት
2. ተወደደ. Food has become scarce. ምግብ ፡ ተወዷል
3. የለም. Roads are scarce in some parts of Ethiopia. ባንዳንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ ጐዳናዎች ፡ የሉም
4. በብዛት ፡ አይገኝም. Good cooks are scarce. ጥሩ ፡ ወጥ ፡ ቤቶች ፡ በብዛት ፡ አይገኙም

**scarcely**
1. በችግር. He spoke in a scarcely audible voice. በችግር ፡ በሚሰማ ፡ ድምፅ ፡ ተናገረ
2. እምብዛም + (negative verb). I scarcely knew him. እምብዛም ፡ አላውቀውም ፡ ነበር
3. እንኳ + (negative verb). It is scarcely two days since he came. ከመጣ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ እንኳ ፡ አልሆነውም
*He can scarcely have said that. እንዲህ ፡ ይላል ፡ ብዬ ፡ አላምንም

**scarcity** እጥረት
The scarcity of food was caused by drought. የምግብ ፡ እጥረት ፡ የመጣው ፡ በድርቅ ፡ ምክንያት ፡ ነው

**scare** (vt.) አስደነገጠ
He scared the dog by shouting at it. ጮኾ ፡ ውሻውን ፡ አስደነገጠው

**scare** (vi.) ተደናገጠ
I scare easily. በቀላሉ ፡ እደናገጣለሁ

**scare away** አስደንግጦ ፡ አባረረ
The dog scared the thief away. ውሻው ፡ ሌባውን ፡ አስደንግጦ ፡ አባረረው

**be scared** ፈራ
He is scared to talk to the boss. አለቃውን ፡ ማናገር ፡ ይፈራል

**scare** (n.) ፍርሃት
Because of her scare she put on all the lights. በፍርሃቷ ፡ የተነሣ ፡ የቤቱን ፡ መብራት ፡ በሙሉ ፡ አበራች
*The war scare sent prices of food up. ጦርነቱ ፡ ሊነሣ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ስጋት ፡ የምግብን ፡ ዋጋ ፡ ሰማይ ፡ አደረሰው

**give a scare** አስደነገጠ
You gave me an awful scare. በጣም ፡ አስደነገጥ ከኝ

**scarecrow** [አሮጌ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ በእርሻ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ የቆመ ፡ አዕዋፍ ፡ እህል ፡ እንዳይበሉ ፡ ማስፈራሪያ ፡ ዕንጨት]

**scarf** ያንገት ፡ ፎጣ
Put that scarf around your neck! ያንን ፡ ያንገት ፡ ፎጣ ፡ አንገትህ ፡ ላይ ፡ ጠምጥመው

**scarlet** ደማቅ ፡ ቀይ
The Chinese like the color of scarlet. ቻይናዎች ፡ ደማቅ ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ይወዳሉ

**scary** የሚያስፈራ
I like scary movies. የሚያስፈራ ፡ ፊልም ፡ እወዳለሁ

**scatter** (vt.)
1. በታተነ. The police scattered the crowds. ፖሊሶቹ ፡ የተሰበሰበውን ፡ ሕዝብ ፡ በታተኑት
2. በተነ. He scattered ashes on the slippery sidewalk. የሚያዳልጠው ፡ የእግር ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ አመድ ፡ በተነ
The farmer scattered corn for the chickens. ገበሬው ፡ ለዶሮቹ ፡ በቆሎ ፡ በተነ
3. ነሰነሰ. They scattered straw on the floor. ወለሉ ፡ ላይ ፡ ገለባ ፡ ነሰነሱ

**scatter** (vi.) ተበታተነ
The crowd scattered when the police arrived. ፖሊሶቹ ፡ ሲመጡ ፡ ሕዝቡ ፡ ተበታተነ

**scatterbrain** ቀልበ ፡ ቢስ
She is a scatterbrain, and cannot be relied on for serious matters. ቀልበ ፡ ቢስ ፡ ስለሆነች ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሚጣልባት ፡ አይደለችም

**scattered** (adj.)
1. የተበታተነ. He must consolidate scattered land holdings. የተበታተነውን ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ማጠቃለል ፡ አለበት
2. አልፎ ፡ አልፎ ፡ የወደቀ. Scattered boulders blocked the road. አልፎ ፡ አልፎ ፡ የወደቁ ፡ ቋጥኞች ፡ መንገዱን ፡ ዘጉት
3. (= adv.) ተበታትኖ. A scattered population of hunters inhabits the south. በደቡብ ፡ በኩል ፡ አዳኞች ፡ ሕዝብ ፡ ተበታትነው ፡ ይኖራሉ

**be scattered** ተበታተነ
The books were scattered all over the floor. መጽሐፎቹ ፡ በወለሉ ፡ ላይ ፡ ተበታትነው ፡ ነበር

**scavenger** ጥንብ ፡ አንሺ
Hyenas are scavengers. ጅቦች ፡ ጥንብ ፡ አንሺዎች ፡ ናቸው

**scene**
1. ስፍራ. Maqdala was the scene of battle in 1868. መቅደላ ፡ በ፲፰፻፷ ዓ. ም. የጦርነት ፡ ስፍራ ፡ ነበር
2. ቦታ. Being seen at the scene of the crime does not constitute guilt. ወንጀሉ ፡ ከተፈጸመበት ፡ ቦታ ፡ መታየት ፡ ከወንጀል ፡ አይቈጠርም
3. ሁኔታ. Distressing scenes occurred during the earthquake. መሬቱ ፡ በተንቀጠቀጠ ፡ ጊዜ ፡ የደረሰው ፡ ሁኔታ ፡ አሳዛኝ ፡ ነበር
4. ትዕይንት. That is in the third scene of the second act. ይህ ፡ የሚገኘው ፡ በሦስተኛው ፡ ትዕይንት ፡ በሁለተኛው ፡ ገቢር ፡ ነው
5. የቲያትር ፡ ትርእይት. The scene represents a city street. የቲያትሩ ፡ ትርእይት ፡ የከተማ ፡ መንገድን ፡ ያመለክታል
*The scene of the novel is laid in Ethiopia after the Italian invasion. ታሪኩ ፡ የተመሠረተው ፡ ከኢጣልያን ፡ ወረራ ፡ በኋላ ፡ በነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነው
*He wanted to return the insult, but bit his lip in order to avoid a scene. መልሶ ፡ ሊሳደብ ፡ ፈልጎ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ የባሰ ፡ ጠብ ፡ እንዳይነሣ ፡ በማለት ፡ ትዕግሥት ፡ አደረገ

**behind the scenes** በስውር
Who knows what is going on behind the scenes in the administration? ባስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ በስውር ፡ የሚካሄደውን ፡ ማን ፡ ያውቃል?

**make a scene** ተንጫነጨ
He told his wife not to make a scene because he was late. ስለዘገየ ፡ እንዳትነጫነጭ ፡ ለሚስቱ ፡ ነገራት
*The child kicked and screamed and made such a scene that his mother was ashamed of him. ሕፃኑ ፡ እናትየዋ ፡ እስክታፍርበት ፡ ድረስ ፡ እየተወራጨ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር

**scenery**
1. ትርእይት. We did not have time to look at the scenery. ትርእይቱን ፡ ለማየት ፡ ጊዜ ፡ አልነበረንም
2. የቲያትር ፡ ትርእይት. The scenery pictures a garden in the moonlight. የቲያትሩ ፡ ትርእይት ፡ ጨረቃ ፡ የፈነጠቀችበት ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ ያሳያል

**scenic** ውብ
The view from this mountaintop is very scenic. ከዚህ ፡ ተራራ ፡ የሚታየው ፡ ትርእይት ፡ በጣም ፡ ውብ ፡ ነው

**scent** (v.)
1. የ---ጠረን ፡ አሸተተ. The dog scented the fox. ውሻው ፡ የቀበሮውን ፡ ጠረን ፡ አሸተተ
2. ተሰማ(ው). +I scent a trick in his offer. ባቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ ተንኰል ፡ እንዳለበት ፡ ይሰማኛል
*The roses scent the air. የጽጌ ፡ ረዳ ፡ አበባ ፡ መዓዛ ፡ አየሩን ፡ ያውደዋል

**scent about** አነፈነፈ
The dog scented about until he found the trail. ውሻው ፡ ዱካውን ፡ እስኪያገኝ ፡ አነፈነፈ

**scent** (n.)
1. የማሽተት ፡ ችሎታ. Our dog has a keen scent. ውሻችን ፡ ከፍተኛ ፡ የማሽተት ፡ ችሎታ ፡ አለው
2. ሽቶ. She uses too much scent. በጣም ፡ ብዙ ፡ ሽቶ ፡ ትቀባለች
3. መዓዛ. Roses have a delightful scent. የጽጌ ፡ ረዳ ፡ አበባ ፡ የሚያስደስት ፡ መዓዛ ፡ አለው
4. ጠረን. The dogs followed the fox by scent. ውሾቹ ፡ ቀበሮውን ፡ በጠረን ፡ ተከተሉት

**scepter** በትረ ፡ መንግሥት
The king holds a scepter in his right hand. ንጉሡ ፡ በቀኝ ፡ እጃቸው ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ ይዘዋል

**sceptic** ተጠራጣሪ
Only a sceptic would doubt his sincerity. ቅንነቱን ፡ የማያምን ፡ ተጠራጣሪ ፡ ብቻ ፡ ነው

**sceptical** ተጠራጣሪ
Too much reasoning makes you sceptical. ብዙ ፡ መመራመር ፡ ተጠራጣሪ ፡ ያደርጋል

**be sceptical** ተጠራጠረ
I was sceptical when he said he earned $1,000 a week. በሳምንት ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ አገኛለሁ ፡ ሲል ፡ ተጠራጠርኩት

**schedule** (v.) ወሰነ
He scheduled the meeting for today. ስብሰባውን ፡ ለዛሬ ፡ ወሰነው

**be scheduled**
1. ተቀጠረ. The meeting is scheduled for tomorrow. ስብሰባው ፡ ለነገ ፡ ተቀጥሯል
2. ታቀደ. The publication of this book is scheduled for next month. በሚመጣው ፡ ወር ፡ መጽሐፉ ፡ ሊታተም ፡ ታቅዷል

**schedule** (n.)
1. ዝርዝር. A schedule of prices is posted on the wall. የዋጋው ፡ ዝርዝር ፡ ግድግዳው ፡ ላይ ፡ ተለጥፏል
2. ሰንጠረዥ. A schedule of duties was posted in the customs house. የቀረጥ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ጉምሩክ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተለጥፏል
3. ፕሮግራም. Did you make out a work schedule? የሥራ ፡ ፕሮግራም ፡ አወጣህ ?
4. የተወሰነ ፡ ሰዓት. The train arrived on schedule. ባቡሩ ፡ በተወሰነው ፡ ሰዓት ፡ ገባ
5. መነሻና ፡ መድረሻ ፡ የሚገልጽ ፡ ፕሮግራም. Give me a plane schedule! የአይሮፕላን ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ የሚገልጽ ፡ ፕሮግራም ፡ ስጠኝ

**schematic, ~ drawing** ንድፍ
A schematic drawing shows the arrangement of the rooms and corridors. ንድፍ ፡ የክፍሎቹን ፡ የመተላለፊያዎቹን ፡ አቀማመጥ ፡ ያሳያል

**scheme** (v.)
1. ዶለተ. They schemed to oust their boss. አለቃቸውን ፡ ለማስወጣት ፡ ዶለቱ
2. ዘዴ ፡ ፈጠረ. He is always scheming to get out of working. ሥራ ፡ እንዳይሠራ ፡ ሁልጊዜ ፡ ዘዴ ፡ ይፈጥራል

**scheme** (n.)
1. መላ. He thought up a scheme to cheat the government. መንግሥቱን ፡ ለማጭበርበር ፡ መላ ፡ ፈጠረ
2. የሐሳብ ፡ ረቂቅ. The scheme was rejected by the minister. የሐሳቡን ፡ ረቂቅ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አል ተቀበሉትም
3. ዘዴ ፤ እቅድ. The boys devised a scheme for earning money during vacation. በዕረፍት ፡ ጊዜያቸው ፡ ልጆቹ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያገኙበትን ፡ ዘዴ ፡ ፈጠሩ
He has chimerical schemes for getting rich. ሀብታም ፡ ለመሆን ፡ የማይደረስበት ፡ እቅድ ፡ አለው
4. ድልድል. The color scheme of the room is blue and gold. የክፍሉ ፡ የቀለም ፡ ድልድል ፡ ሰማያዊና ፡ ወርቃማ ፡ ነው

**schism** መከፋፈል
The schism in the church caused a series of wars. የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ መከፋፈል ፡ ተከታታይ ፡ ጦርነቶችን ፡ አስነሣ

**scholar** ሊቅ
He is a scholar of Amharic. ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ሊቅ ፡ ነው

**scholarly**
1. የምሁር. He presented a very scholarly lecture. ከፍተኛ ፡ የምሁር ፡ ንግግር ፡ አደረገ
2. ጠልቆ ፡ የተማረ. He is a scholarly newspaperman. ጠልቆ ፡ የተማረ ፡ ጋዜጠኛ ፡ ነው

**scholarship**
1. ሊቅነት. He is famous for his scholarship. በሊቅነቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው
2. የነጻ ፡ ትምህርት ፡ ዕድል ፤ የነጻ ፡ ትምህርት ፤ እስኮለርሽፕ. I got a scholarship to Harvard. ሀርቫርድ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ውስጥ ፡ ለመማር ፡ የነጻ ፡ ትምህርት ፡ ዕድል ፡ አገኘሁ
His elation is due to having received a scholarship. ፍንደቃው ፡ የነጻ ፡ ትምህርት ፡ (እስኮለርሽፕ) ፡ ስላገኘ ፡ ነው

**scholastic**
1. የትምህርት. His scholastic record is bad. የትምህርቱ ፡ ውጤት ፡ መጥፎ ፡ ነው
2. (= adv.) በትምህርት ፡ በኩል. Our school has a high scholastic standing. ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ በትምህርት ፡ በኩል ፡ ስሙ ፡ ጥሩ ፡ ነው

**school**
1. ትምህርት ፡ ቤት ፤ ተማሪ ፡ ቤት. He goes to school every day. በየቀኑ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ (ተማሪ ፡ ቤት) ፡ ይሄዳል
2. ትምህርት. We start school in September. በመስከረም ፡ ትምህርት ፡ እንጀምራለን
3. የትምህርት ፡ ቤት ፡ ልጆች. The entire school will go to the football game. የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ልጆች ፡ በሙሉ ፡ የእግር ፡ ኳስ ፡ ጨዋታውን ፡ ለማየት ፡ ይሄዳሉ

**leave school** ትምህርት ፡ አቆመ
When did your brother leave school? ወንድምህ ፡ ትምህርት ፡ ያቆመው ፡ መቼ ፡ ነው ?

**put in school** ትምህርት ፡ ቤት ፡ አስገባ
He put his oldest boy in school. ትልቁን ፡ ልጁን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አስገባው

**send to school** አስተማረ
The law obliges parents to send their children to school. ሕጉ ፡ ወላጆች ፡ ልጆቻቸውን ፡ እንዲያስተምሩ ፡ ያስገድዳል

**(be) schooled** ተማረ
He was schooled in the old methods. የተማረው ፡ በጥንት ፡ ዘዴ ፡ ነው

**schooling**
1. ትምህርት. His schooling is not adequate. ትምህርቱ ፡ አጥጋቢ ፡ አይደለም
2. ማስተማር. Backward children need a special kind of schooling. በአእምሮ ፡ የደከሙ ፡ ልጆች ፡ የተለየ ፡ የማስተማር ፡ ዘዴ ፡ ያስፈልጋቸዋል

**schoolmate** የትምህርት ፡ ቤት ፡ ጓደኛ
My schoolmates have all grown up. የትምህርት ፡ ቤት ፡ ጓደኞቼ ፡ ሁሉ ፡ አደገዋል

**school year** የትምህርት ፡ ዓመት
The school year has nine months. የትምህርት ፡ ዓመት ፡ ዘጠኝ ፡ ወሮች ፡ አሉት

**science** ሥነ ፡ ፍጥረት
He is more interested in science than in art. እሱ ፡ ከሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ይልቅ ፡ ለኪነ ፡ ጥበብ ፡ ይበልጥ ፡ ዝንባሌ ፡ አለው

**scientific**
1. ሳይንስ ፡ ነክ ፡ የሆነ ፤ የሳይንስ. This store sells scientific books. እዚህ ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ ሳይንስ ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ (የሳይንስ) ፡ መጽሐፎች ፡ ይሸጣሉ
2. ዘመናዊ. He uses scientific methods in farming. በዘመናዊ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ ይጠቀማል

**scientist** የሳይንስ ፡ ሊቅ
There is a gathering of scientists in the next room. እሚቀጥለው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ ስብሰባ ፡ አለ

**scintillate** አንጸባረቀ
The diamonds scintillated in the light. አልማዙ ፡ በብርሃን ፡ ውስጥ ፡ አንጸባረቀ
*His speech scintillates with humor. በንግግሩ ፡ ላይ ፡ ቀልድ ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ ያደርጋል

**scissors** መቀስ
The scissors are not sharp. ይህ ፡ መቀስ ፡ ደንዟል

**scoff** አሾፈ(በት)
He scoffs at her foolish fears. ከመሬት ፡ ተነሥታ ፡ ስለምትፈራ ፡ ያሾፍባታል

**scold** ገሠጸ ፤ ወቀሰ
He scolded his child for being lazy. ልጁ ፡ ሰነፍ ፡ ስለሆነ ፡ ገሠጸው
He scolded me a bit, and that was the end of it. ትንሽ ፡ ወቀሰኝና ፡ በዚያው ፡ አለቀ

**scolding** ቁጣ
The child listened to the scolding in passive silence. ልጁ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ቁጣውን ፡ ተቀበለ

**scoop** ማሰ
The children scoop holes in the sand. ልጆቹ ፡ አሸዋው ፡ ውስጥ ፡ ጉድጓድ ፡ ይምሳሉ

**scoop out** ፍሬ ፡ አወጣ
You have to scoop out a gourd before you can dry it. ከማድረቅህ ፡ በፊት ፡ የቅሉን ፡ ፍሬ ፡ ማውጣት ፡ አለብህ

**scoop up** ዛቀ
He scooped up sand and put it in a bucket. አሸዋውን ፡ ዝቆ ፡ ባልዲው ፡ ውስጥ ፡ ጨመረው

**scoop,** n. [ሱኳር ፤ ዱቄት ፤ ወዘተ ፡ ለማፈስ ፡ የሚያገለግል ፡ ትንሽ ፡ አካፋ ፡ ቢጤ]

**scope** ክልል
Very hard words are not within the scope of a child's understanding. በጣም ፡ ከባድ ፡ ቃላት ፡ በሕፃናት ፡ አስተሳሰብ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ አይደሉም
*The scope of his travels includes Europe and America. እስከ ፡ አውሮፓና ፡ እስከ ፡ አሜሪካ ፡ ሄዷል
*This work gives me little scope for my abilities. ይህ ፡ ሥራ ፡ ችሎታዬን ፡ በሥራ ፡ ለማዋል ፡ የሚሰጠኝ ፡ ዕድል ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው
*Football gives scope for quick thinking. የእግር ፡ ኳስ ፡ አንጐልን ፡ ቶሎ ፡ እንዲያስብ ፡ ያደርገዋል

**be outside the scope of** አልተመለከተም
Your problem is outside the scope of this committee. ያንተ ፡ ጉዳይ ፡ ይህን ፡ ደርግ ፡ አይመለከትም

**scorch**
1. አቃጠለ. The hot iron scorched his shirt. የጋለው ፡ ካውያ ፡ ሸሚዙን ፡ አቃጠለው
2. አደረቀ. The hot sunshine scorched the grass. የፀሐዩ ፡ ሐሩር ፡ ሣሩን ፡ አደረቀው

**be scorched** አረረ
The food was scorched in the pan. ምግቡ ፡ በመጥበሻው ፡ ላይ ፡ አረረ

**taste scorched** ያረረ ፡ ያረረ ፡ አለ
The cake tastes scorched. ብስኩቱ ፡ ያረረ ፡ ያረረ ፡ ይላል

**use a scorched earth policy** የሚጠቀመውን ፡ ሁሉ ፡ አቃጠለ
The Russians used a scorched earth policy against the Germans in the Second World War. መስኮቦች ፡ በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ለጀርመኖች ፡ የሚጠቅማቸውን ፡ ሁሉ ፡ አቃጠሉ

**score** (v.)
1. አገባ. Who scored that goal? ያንን ፡ ግብ ፡ ማን ፡ አገባ ?
2. ቈጠረ. The teacher appointed me to score for both sides. አስተማሪው ፡ ለሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ እንድቈጥር ፡ መረጠኝ
3. ማርክ ፡ ሰጠ. The teacher asked me to score the test. አስተማሪው ፡ ለፈተናው ፡ ማርክ ፡ እንድሰጥ ፡ ጠየቀኝ

**be scored** ምልክት ፡ ተደረገበት
Mistakes are scored in red ink. ስሕተቶች ፡ በቀይ ፡ ቀለም ፡ ምልክት ፡ ተደርጎባቸዋል

**score a point** ዕድል ፡ አገኘ
He scored a point when he brought up the company's deficit. ኩባንያው ፡ መክሰሩን ፡ በጠቀሰ ፡ ጊዜ ፡ ዕድል ፡ አገኘ

**score a success** (= passive) ተሳካ
+He scored a success with his plan. እቅዱ ፡ ተሳካ

**score** (n.)
1. ግብ. You can equal my score easily. የኔን ፡ ግብ ፡ በቀላሉ ፡ ልትደርስበት ፡ ትችላለህ
2. ውጤት. This was a respectable score for an amateur player. ለአማተር ፡ ተጫዋች ፡ ውጤቱ ፡ ደኅና ፡ ነው
3. ነጥብ. The score is 9 to 3 in favor of our school. ነጥቡ ፡ ፱ ለ፫ ሲሆን ፡ ያሸነፈው ፡ የኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ነው
4. ጠባሳ. The thief's back shows scores made by the whip. የሌባው ፡ ጀርባ ፡ የግርፋቱን ፡ ጠባሳ ፡ ያሳያል
5. ስልት. She was studying the score of the piece she was learning to play. ለመጫወት ፡ ትማረው ፡ የነበረውን ፡ ስልት ፡ ታጠና ፡ ነበር
6. ሃያ. A score or more were present at the party. በግብዣው ፡ ላይ ፡ ከሃያ ፡ የሚበልጡ ፡ ሰዎች ፡ ተገኝተው ፡ ነበር

**scores of** ብዙ
There were scores of people in the street. መንገዱ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ

**keep score** ቈጠረ
Keep score for us while we play. እኛ ፡ ስንጫወት ፡ ቍጠርልን

**on that score** ስለሱ
You need not worry on that score. ስለሱ ፡ መጨነቅ ፡ የለብህም

**scorn** (v.)
1. አንቋሸሸ(በት). He scorned my abilities. ችሎታዬን ፡ አንቋሸሸብኝ
2. እንደ ፡ ወራዳ ፡ ተግባር ፡ ቈጠረ. He scorns to use intrigue to get what he wants. የፈለገውን ፡ ለማግኘት ፡ በተንኰል ፡ መሥራትን ፡ እንደ ፡ ወራዳ ፡ ተግባር ፡ ይቈጥረዋል
*The judge scorned to take a bribe. ዳኛው ፡ ጉቦ ፡ ይጠላል

**scorn** (n.) ንቀት
The monks' scorn for wealth is well known. የመነኰሴዎች ፡ ለሀብት ፡ ንቀት ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ነው

**feel scorn** ናቀ
Most students feel scorn for those who cheat. አብዛኞቹ ፡ ተማሪዎች ፡ የሚያጭበረብሩትን ፡ ይንቋቸዋል

**pour scorn** የስድብ ፡ መዓት ፡ አወረደ(በት)
They poured scorn on their rivals. በተወዳዳሪዎቻቸው ፡ ላይ ፡ የስድብ ፡ መዓት ፡ አወረዱባቸው

**scornful** የንቀት
His scornful face showed that my plan will not be accepted. የንቀት ፡ አስተያየቱ ፡ ሐሳቤ ፡ ተቀባይነትን ፡ የማያገኝ ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል

**scornfully**
*He laughed scornfully. የንቀት ፡ አሣሣቅ ፡ ሣቀ

**scorpion** ጊንጥ

**scoundrel** ወሮበላ
He acts like a scoundrel. አድራጎቱ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ወሮበላ ፡ ነው

**scour**
1. ፈቀፈቀ. She scoured the pot to remove the soot. ጥላሸቱን ፡ ከማሰሮው ፡ ለማስለቀቅ ፡ ማሰሮውን ፡ ፈቀፈቀችው
2. ፋቀ. Moving the furniture across the floor scours the paint. ወለሉ ፡ ላይ ፡ እቃውን ፡ መጎተት ፡ ቀለሙን ፡ ይፍቃል
3. አሰሰ. Men scoured the town for the lost child. ሰዎች ፡ የጠፋውን ፡ ልጅ ፡ ለማግኘት ፡ ከተማውን ፡ አሰሱ
4. አወጣ. The stream had scoured a channel. ወንዙ ፡ ቦይ ፡ አወጣ

**scourge** (v.) መታ
A plague scourged the country. ወረርሽኝ ፡ አገሩን ፡ መታው

**scourge** (n.) መቅሠፍት
War is the scourge of mankind. ጦርነት ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ መቅሠፍት ፡ ነው

**scout** (v.) ቃኘ
Our squad scouted the area. ቡድናችን ፡ ቀበሌውን ፡ ቃኘ

**scout out** ሰለለ
We are going to scout out their position. ያሉበትን ፡ ቦታ ፡ ልንሰልል ፡ መሄዳችን ፡ ነው

**scout** (n.)
1. እስካውት. The scout got lost in the woods. እስካውቱ ፡ ጫካው ፡ ውስጥ ፡ ጠፋ
2. አሳሽ. We sent scouts into the enemy territory. ወደ ፡ ጠላት ፡ ግዛት ፡ አሳሾች ፡ ላክን

**scowl** የግንባር ፡ መቋጠር
A scowl showed he was displeased. የግንባሩ ፡ መቋጠር ፡ አለመደሰቱን ፡ አሳየ

**scramble** (v.) ተሻማ
The boys scrambled to pick up the money. ገንዘቡን ፡ ለመልቀም ፡ ልጆቹ ፡ ተሻሙ

**scramble through** እንደምንም ፡ ጥሶ ፡ አለፈ
The boys scrambled through the underbrush. ልጆቹ ፡ ቁጥቋጦውን ፡ እንደምንም ፡ ጥሰው ፡ አለፉት

**scramble up** እየተንደፋደፈ ፡ ሄደ
The rat scrambled up the side of the road. አይጢ ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ እየተንደፋደፈች ፡ ሄደች

**scramble** (n.)
1. ሽሚያ. There was a scramble for power after the President died. ፕሬዚዳንቱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የሥልጣን ፡ ሽሚያ ፡ ነበር
2. መውደቅ ፡ መነሣት. It was a long scramble through bushes to the top of the hill. ከኰረብታው ፡ ጫፍ ፡ ለመድረስ ፡ በቁጥቋጦው ፡ ውስጥ ፡ መውደቅ ፡ መነሣት ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ነበር

**scrambled eggs** የተፈረፈረ ፡ እንቁላል
I like scrambled eggs for breakfast. ለቁርስ ፡ የተፈረፈረ ፡ እንቁላል ፡ እወዳለሁ

**scrap** (scrapped), vt.
1. ጣለ. They scrapped their old machinery and imported the latest equipment. ያረጀውን ፡ መሣሪያ ፡ ጥለው ፡ በቅርቡ ፡ የተሠራውን ፡ መሣሪያ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ አስመጡ
2. ተወ. He scrapped his bad habits. መጥፎ ፡ ልማዱን ፡ ተወ

**scrap** (vi.) ተተናኰለ
Those two dogs are always scrapping. እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ውሾች ፡ ሁልጊዜ ፡ ይተናኰላሉ

**scrap** (n.)
1. ብጫቂ. That's only a scrap of paper. ብጫቂ ፡ ወረቀት ፡ ነው
2. ቁራጭ. The famished dogs were fighting over a scrap of meat. የተራቡት ፡ ውሾች ፡ በአንዲት ፡ ቁራጭ ፡ ሥጋ ፡ ላይ ፡ ተናከሱ
3. ቁርጥራጭ ፡ ብረታ ፡ ብረት 1 ቁርጥራጭ. A man comes around collecting scrap. ቁርጥራጭ ፡ ብረታ ፡ ብረት ፡ የሚሰበስብ ፡ ሰው ፡ ይመጣል

The roof was made from scraps of old metal drums. ጣሪያው ፡ የተሠራው ፡ ካሮጌ ፡ በርሜል ፡ ቁርጥራጭ ፡ ነው

*She read aloud scraps from the letter. ከደብዳቤው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ጮክ ፡ ብላ ፡ አነበበች

**scraps** ፍርፋሪ

Give the scraps to the dog! ፍርፋሪውን ፡ ለውሻው ፡ ስጠው

**scrapbook** [ፎቶግራፎች ፡ የጋዜጣ ፡ ቁራጮችና ፡ የመሳሰሉት ፡ የሚለጠፉበት ፡ ልሙጥ ፡ ወረቀት ፡ ያለበት ፡ መዝገብ]

**scrape** (v.)

1. ፋቀ. The fence scraped the side of my car. አጥሩ ፡ የመኪናውን ፡ ጐን ፡ ፋቀብኝ
2. ፋቀ ፤ አሸ. Don't scrape your feet on the floor! እግሮችህን ፡ በወለሉ ፡ ላይ ፡ አትፋቅ ፡ (አትሽ)
3. ላጠ. He scraped his Adam's apple on his collar. ማንቁርቱን ፡ በኮሌታው ፡ ላጠ

**scrape against** ከ -- ጋር ፡ ተማታ

The branches scrape against the window when the wind blows. ነፋሱ ፡ ሲነፍስ ፡ የዛፉ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ከመስኮቱ ፡ ጋር ፡ ይማታሉ

**scrape along, just ~** እንደምንም ፡ ከረመ

That family just scrapes alongs and never asks for charity. እነዚያ ፡ ቤተሰቦች ፡ እንደምንም ፡ ይከርማሉ ፡ እንጂ ፡ ፈጽሞ ፡ እርዳታ ፡ አይጠይቁም

**scrape by** እንደምንም ፡ ከረመ

We'll scrape by on the money we saved up. በቈጠብነው ፡ ገንዘብ ፡ እንደምንም ፡ እንከርማለን

**scrape off** ፋቀ

Scrape the paint off first! መጀመሪያ ፡ ቀለሙን ፡ ፋቅ

**scrape together** ከዚያም ፡ ከዚህም ፡ አጠራቀመ

I have scraped a few dollars together for the holiday. ለበዓሉ ፡ ጥቂት ፡ ብር ፡ ከዚያም ፡ ከዚህም ፡ አጠራቅሜያለሁ

**scrape up** ለቃቅሞ ፡ በላ

The hungry boy scraped up the last crumbs from his plate. የተራበው ፡ ልጅ ፡ ሳሕኑ ፡ ላይ ፡ የተረፈውን ፡ ፍርፋሪ ፡ ለቃቅሞ ፡ በላ

**barely scrape through** እንደምንም ፡ ብሎ ፡ አለፈ

He barely scraped through the examination. ፈተናውን ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ አለፈው

**scrape** (n.) ሲጢጥ ፡ ማድረግ

The scrape of her fingernail on the glass irritates me. ጥፍሯን ፡ መስተዋት ፡ ላይ ፡ ሲጢጥ ፡ ማድረጓ ፡ ይሰቀጥጠኛል

**get into a scrape** በገዛ ፡ እጁ ፡ ዕዳ ፡ ገባ

The boys got into a scrape by stealing a car. ልጆቹ ፡ መኪና ፡ ሰርቀው ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ ዕዳ ፡ ገቡ

**scraper**

1. መፈቅፈቂያ. I need a scraper to remove the paint. ቀለም ፡ ለማስለቀቅ ፡ መፈቅፈቂያ ፡ ያስፈልገኛል
2. ማስተካከያ ፡ መኪና. The road scraper overturned. የመንገዱ ፡ ማስተካከያ ፡ መኪና ፡ ተገለበጠ

**scratch** (vt.)

1. ፋቀ. Who scratched the paint? ቀለሙን ፡ ማን ፡ ፋቀው ?
2. ቧጠጠ. The cat scratched him. ድመቷ ፡ ቧጠጠችው
3. አከከ. Stop scratching yourself! ሰውነትህን ፡ ማከክ ፡ ተው
4. ጫረ. He scratched a match on the wall. ግድግዳው ፡ ላይ ፡ ክብሪት ፡ ጫረ
5. ቧጨረ. Thorns scratched his legs. እሾህ ፡ እግሩን ፡ ቧጨረው
6. ነጨ. Scratching one's face at a funeral is an extinct custom. ሰው ፡ ሲሞት ፡ ፊትን ፡ መንጨት ፡ የቀረ ፡ ልማድ ፡ ነው

**scratch** (vi.)

1. ጫረ. The pen scratches when he writes. ሲጽፍ ፡ ብዕሩ ፡ ይጭራል
2. አከከ. That dog is always scratching. ያ ፡ ውሻ ፡ ሁልጊዜ ፡ እንዳከከ ፡ ነው

**be scratched** ተሰረዘ

Two horses were scratched from the race. ሁለት ፡ ፈረሶች ፡ ከውድድሩ ፡ ተሰረዙ

**scratch out** ሰረዘ

Scratch out the last sentence! የመጨረሻውን ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ሰርዘው

**merely scratch** (ብቻ) ፡ ነካክቶ ፡ አለፈ

The lecturer merely scratched the surface of the subject. ተናጋሪው ፡ አርእስተ ፡ ነገሩን ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ብቻ ፡ ነካክቶ ፡ አለፈ

**scratch** (n.) ቧጭር

There was a long scratch on her hand. እጇ ፡ ላይ ፡ ረጅም ፡ ቧጭር ፡ ነበር

**start from scratch** ሀ ፡ ብሎ ፡ ጀመረ

After the fire, he had to start from scratch. ከእሳቱ ፡ አደጋ ፡ በኋላ ፡ ሀ ፡ ብሎ ፡ መጀመር ፡ ነበረበት

**scratch paper** ማስታወሻ ፡ ወረቀት

Please give me scratch paper! እባክ ፡ ማስታወሻ ፡ ወረቀት ፡ ስጠኝ

**scratchy**
1. የሚጭር. Don't write with that scratchy pen! በዚያ ፡ በሚጭር ፡ ብዕር ፡ አትጻፍ
2. የሚኮሰኩስ. The scratchy sweater irritated my skin. የሚኮሰኩሰው ፡ ሹራብ ፡ ቆዳዬን ፡ አስቆጣው

**scrawl** ጫጫረ
He scrawled a few words on a card to his wife. በካርዱ ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ ቃሎች ፡ ለሚስቱ ፡ ጫጫረ

**scream** (v.) ጮኸ
The child screamed with fright. ልጁ ፡ ፈርቶ ፡ ጮኸ

**scream for**
*In ancient Rome, the rabble screamed for bread. በጥንታዊት ፡ ሮም ፡ ሕዝቡ ፡ እህል ፡ ለማግኘት ፡ አቤት ፡ ይል ፡ ነበር

**scream** (n.) ጩኸት
I thought I heard a scream. ጩኸት ፡ የሰማሁ ፡ መሰለኝ

**screech** ሲጢጥ ፡ አለ
The wheels screeched when the car stopped. መኪናው ፡ ሲቆም ፡ ጎማው ፡ ሲጢጥ ፡ አለ

**screen** (v.)
1. ከለለ ፤ ጋረደ. The trees screen their house from public view. ዛፎቹ ፡ ቤታቸውን ፡ እንዳይታይ ፡ ይከልሉታል ፡ (ይጋርዱታል)
2. በባለ ፡ ወንፊት ፡ ሽቦ ፡ ጋረደ. We have screened our porch to keep off flies. ዝንቦችን ፡ ለመከላከል ፡ በረንዳውን ፡ በባለ ፡ ወንፊት ፡ ሽቦ ፡ ጋረድነው
3. መረጠ. We screened the candidates for the job very carefully. ለሥራው ፡ የቀረቡትን ፡ ሰዎች ፡ በጥንቃቄ ፡ መረጥናቸው

**be screened off** በመጋረጃ ፡ ተከፈለ
One corner of the house was screened off. የቤቱ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ በመጋረጃ ፡ ተከፍሏል

**screen** (n.)
1. የሽቦ ፡ ወንፊት. Put a screen in the window to keep the insects out. ትንኞች ፡ እንዳይገቡ ፡ መስኮቱ ፡ ላይ ፡ የሽቦ ፡ ወንፊት ፡ አድርግበት
2. ፊልም. He looks older on the screen. ፊልሙ ፡ ላይ ፡ ያረጀ ፡ ይመስላል
*A screen of trees hides our house from the road. ዛፎቹ ፡ ቤታችንን ፡ ከመንገዱ ፡ ይጋርዱታል

**screening** ማጣራት
The screening of the candidates took two hours. የእጩዎቹ ፡ ማጣራት ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ፈጀ

**screw** (v.) በቅርንፉድ ፡ ምስማር ፡ አያያዘ
The carpenter screwed the bookshelves to the wall. አናጢው ፡ የመጽሐፍ ፡ መደርደሪያውን ፡ ከግድግዳው ፡ ጋር ፡ በቅርንፉድ ፡ ምስማር ፡ አያያዘ

**screw** (n.) የቅርንፉድ ፡ ምስማር ፤ ቡሎን
Can you loosen this screw? የቅርንፉዱን ፡ ምስማር ፡ (ቡሎንን) ፡ ልታላላው ፡ ትችላለህ ?

**screwdriver** (የ)ጠመንጃ ፡ መፍቻ
He unscrewed the lock with a screwdriver. ቁልፉን ፡ በጠመንጃ ፡ መፍቻ ፡ አወለቀው

**scribble, ~ on** ሞነጫጨረ
The baby scribbled on the wall with a pencil. ሕፃኑ ፡ ግድግዳውን ፡ በእርሳስ ፡ ሞነጫጨረ

**be scribbled up** ተሞነጫጨረ
The wall is all scribbled up. ግድግዳው ፡ ተሞነጫጭሯል

**scribe** ቁም ፡ ጸሐፊ
The scribe wrote down the royal decrees. ቁም ፡ ጸሐፊው ፡ የንጉሡን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጻፈ.

**scrimp** ጥርሱን ፡ ነክሶ ፡ ገንዘብ ፡ ቈጠበ
Many parents have to scrimp to keep their children in school. ልጆቻቸውን ፡ ለማስተማር ፡ ብዙ ፡ ወላጆች ፡ ጥርሳቸውን ፡ ነክሰው ፡ ገንዘብ ፡ መቈጠብ ፡ አለባቸው

**script** ፊደል
Amharic script is different from Arabic. የአማርኛ ፡ ፊደል ፡ ከዐረብኛ ፡ ፊደል ፡ ይለያል

**Scriptures** መጽሐፍ ፡ ቅዱስ
The Scriptures were written originally in Hebrew. መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ መጀመሪያ ፡ የተጻፈው ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ነበር
[See also 'divine']

**scrofula** ያንገት ፡ ነቀርሳ
He has a bad case of scrofula. ክፉ ፡ ያንገት ፡ ነቀርሳ ፡ ይዞታል

**scroll** የተሸበለለ ፡ ብራና
The names of those soldiers who were killed in war were written on a scroll. በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ የሞቱት ፡ የወታደሮች ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ በተሸበለለ ፡ ብራና ፡ ላይ ፡ ተጽፏል

**scrotum** ቈለጥ
The scrotum was cut and the testicles removed. ቈለጡ ፡ ተቈርጦ ፡ ፍሬዎቹ ፡ ወጡ

**scrub** (scrubbed), v.
1. አሸ. The maid scrubbed the clothes to

make them clean. ገረዷ ፡ ልብሱ ፡ እንዲጸዳ ፡ አሸችው

2. ጠረገ. Scrub the soot off the pot! ጥላቱን ፡ ከድስቱ ፡ ላይ ፡ ጥረገው

3. ፈተገ. Scrubbing pans is a chore for her. መጥበሻዎችን ፡ መፈተግ ፡ ለሷ ፡ የሚሰለች ፡ ሥራ ፡ ነው

4. ፈገፈገ. She scrubbed the pots with sand to make them clean. ማሰሮውን ፡ ለማጽዳት ፡ በአሸዋ ፡ ፈገፈገችው

**scrub** (n.) ዳዋ
Only scrub grows on the ground where Theodore's palace stood. የቴዎድሮስ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተሠርቶ ፡ እነበረበት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ዳዋ ፡ በቅሎበታል

**scrubby** ቀጫጫ
The scrubby trees on the hot lowlands show that rainfall is lacking. በሞቃቱ ፡ ረባዳ ፡ ስፍራ ፡ የሚገኙት ፡ ቀጫጫ ፡ ዛፎች ፡ ዝናብ ፡ እንዳልጣለ ፡ ያመለክታሉ

**scruples** ከኅሊናው ፡ የሚመነጭ ፡ ጥርጣሬ
No scruples ever hold him back from prompt action. ፈጣን ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠት ፡ ከኅሊናው ፡ የሚመነጭ ፡ ጥርጣሬ ፡ አያግደውም

**have scruples**

1. አሳፈረ. Have you no scruples about borrowing money from a girl friend? ከሴት ፡ ወዳጅ ፡ ገንዘብ ፡ መበደር ፡ አያሳፍርህም ?

2. ቅር ፡ አሰኘ. He has no scruples about taking bribes. ጉቦ ፡ መብላት ፡ ቅር ፡ አያሰኘውም

**scrupulous**

1. ጥንቁቅ. He is very scrupulous in all his business dealings. በንግድ ፡ ሥራው ፡ በጣም ፡ ጥንቁቅ ፡ ነው

2. ከፍ ፡ ያለ. A soldier must pay scrupulous attention to orders. ወታደር ፡ የሚሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማክበር ፡ አለበት

**scrutinize** በጥንቃቄ ፡ መረመረ
He scrutinized the list to see if his name was on it. ስሙ ፡ እንዳለ ፡ ለማየት ፡ ዝርዝሩን ፡ በጥንቃቄ ፡ መረመረ

**scrutiny**
*Will your work bear close scrutiny? ሥራህ ፡ ቢመረመር ፡ እንከን ፡ የማይገኝበት ፡ ይመስልሃል ?

**scuff** (= passive) ተላጠ
He scuffed his new shoes. አዲሱ ፡ ጫማው ፡ ተላጠ

**scuffle** (v.) ታገለ
The two boys fell as they scuffled. ሁለቱ ፡ ልጆች ፡ ሲታገሉ ፡ ወደቁ

**scuffle** (n.) ግብግብ
There was a scuffle between the police and a group of drunks. በፖሊስና ፡ በሰካራሞች ፡ መካከል ፡ ግብግብ ፡ ነበር

**scull** መቅዘፊያ
He rows the boat with a scull. ከጀልባው ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ጀልባውን ፡ በመቅዘፊያ ፡ ይቀዝፋል

**sculptor** ቅርጽ ፡ አውጪ ፤ ሐውልት ፡ ሠሪ ፤ የቀረጸ
Sculptors are creative artists. ቅርጽ ፡ አውጪዎች ፡ የፈጠራ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ አርቲስቶች ፡ ናቸው
The sculptor was awarded the first prize. ሐውልት ፡ ሠሪው ፡ ያንደኛነትን ፡ ሽልማት ፡ አገኘ
The sculptor of this statue is now dead. ይህን ፡ ሐውልት ፡ የቀረጸው ፡ ሞቷል

**sculpture** ቅርጽ
There are many pieces of sculpture in the park. በመናፈሻው ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ቅርጻ ፡ ቅርጾች ፡ ይገኛሉ

**scum**

1. ስልባቦት. Scum always forms on heated milk. ወተት ፡ ሲፈላ ፡ ሁልጊዜ ፡ ስልባቦት ፡ ይይዛል

2. ቆሻሻ. Remove the scum from the water! ከውኃው ፡ ላይ ፡ ቆሻሻውን ፡ ግፈፈው

3. ልክስክስ ፡ ሰዎች. The saloon was filled with the scum of the town. ቡና ፡ ቤቱ ፡ በልክስክስ ፡ የከተማ ፡ ሰዎች ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር

**green scum** አረንጓዴ
Green scum floated on the pond. አረንጓዴው ፡ በኩሬው ፡ ላይ ፡ ተንሳፈፈ

**scurrilous** የብልግና
Her scurrilous language shocked me. የብልግና ፡ አነጋገሯ ፡ አስቀቀኝ

**scurry** (scurried), ~ **about** ተሯሯጠ
We could hear the mice scurrying about in the walls. አይጦቹ ፡ በግድግዳው ፡ ውስጥ ፡ ሲሯሯጡ ፡ እንሰማ ፡ ነበር

**sent scurrying** አስሮጠ
The rain sent everyone scurrying for shelter. ዝናቡ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ መጠለያ ፡ ቦታ ፡ አስሮጠው

**scuttle off** ተፈተለከ
The dog scuttled off into the woods. ውሻው ፡ ወደ ፡ ጫካ ፡ ተፈተለከ

**scythe** [ረጅም ፡ ጠማማ ፡ ስለትና ፡ እጀታ ፡ ያለው ፡ ማጭድ]

**sea**
1. ባሕር. How far are we from the sea? ከባሕሩ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ርቀናል ?
2. ሞገድ. A high sea swept over the ship's deck. ከፍተኛ ፡ ሞገድ ፡ የመርከቡን ፡ ወለል ፡ አጥለቀለቀው

**seafaring** በባሕር ፡ ላይ ፡ የሚጓዝ
Sailors are seafaring men. መርከበኞች ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ የሚጓዙ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው

**seal** (v.)
1. አሸገ (ታሸገ). The police sealed all the drawers pending an investigation. ፖሊሱ ፡ ምርመራ ፡ እስኪደረግ ፡ ድረስ ፡ መሳቢያዎቹን ፡ ሁሉ ፡ አሸጋቸው
Have you sealed the letter yet? ደብዳቤውን ፡ ገና ፡ አላሸግኸውም ?
The honey is sealed in tins and shipped abroad. ማር ፡ በጣሳ ፡ እየታሸገ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ይላካል
2. ማኅተም ፡ አኖረ. The judge sealed the deed. ዳኛው ፡ ስመ ፡ ርስቱ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ማኅተም ፡ አኖረ
3. በጭቃ ፡ ደፈነ. They sealed the chinks between the logs. ከግንዶቹ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ በጭቃ ፡ ደፈኑት
4. ወሰነ. The judge's words sealed the prisoner's fate. የዳኛው ፡ ቃል ፡ የእስረኛውን ፡ ዕድል ፡ ወሰነ
5. ያዘ. Her promise sealed her lips. በገባችው ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ አፏን ፡ ያዘች

**be sealed** ማኅተም ፡ አደረገ(በት)
+The treaty was signed and sealed by both governments. ሁለቱም ፡ መንግሥታት ፡ ውሉን ፡ ፈርመው ፡ ማኅተም ፡ አደረጉበት

**seal (the) bargain**
They sealed the bargain. በገበያው ፡ ተስማሙ

**seal** (n.)
1. [የባሕር ፡ እንስሳ ፡ ዓይነት].
2. ማኅተም. The papers bear the official seal. ወረቀቶቹ ፡ የመንግሥት ፡ ማኅተም ፡ አለባቸው
3. ቴምብር. These are Christmas seals. እነዚህ ፡ የገና ፡ ቴምብሮች ፡ ናቸው
4. ምልክት. Their handshake was a seal of friendship. እጃቸውን ፡ መጨባበጣቸው ፡ የጓደኝነት ፡ ምልክት ፡ ነበር

**seal of secrecy** ምስጢር
They kept their correspondence under the seal of secrecy. የተጻጻፉትን ፡ በምስጢር ፡ ያዙት

**sea level** የባሕር ፡ ወለል
It is impossible to lower the sea level. የባሕርን ፡ ወለል ፡ ዝቅ ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም

**above sea level** ከባሕር ፡ በላይ
The mountain is 15,000 feet above sea level. ተራራው ፡ ከባሕር ፡ በላይ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ጫማ ፡ ከፍታ ፡ አለው

**below sea level** ከባሕር ፡ በታች
This place is 300 feet below sea level. ይህ ፡ ቦታ ፡ ከፍታው ፡ ከባሕር ፡ በታች ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ጫማ ፡ ነው

**seam** (v.)
1. አጨማደደ. Wind and weather had seamed the old seaman's face. ብርድና ፡ ነፋስ ፡ የሽማግሌውን ፡ መርከበኛ ፡ ፊት ፡ አጨማደውታል
2. ሰፋ. The seamstress seamed the dress. ልብስ ፡ ሰፊዋ ፡ ቀሚሱን ፡ ሰፋች

**be seamed with wrinkles** ተጨማደደ
The old woman's face was seamed with wrinkles. የአሮጊቷ ፡ ፊት ፡ ተጨማዶ ፡ ነበር

**seam** (n.)
1. ስፌት ፤ ዘርፍ. The seam on my coat is coming loose. የኮቴ ፡ ስፌት ፡ እየለቀቀ ፡ ነው
She ripped out the seams of the dress. የልብሱን ፡ ዘርፍ ፡ ቈረጠችው
2. መጋጠሚያ. The welder left a crooked seam when he welded these plates together. በያጁ ፡ እነዚህን ፡ የብረት ፡ ሳሕኖች ፡ ሲበይድ ፡ መጋጠሚያውን ፡ አዛንፎታል
The seams of the boat must be filled in if they leak. የጀልባው ፡ መጋጠሚያ ፡ ካፈሰሰ ፡ መደፈን ፡ አለበት
3. ጠባሳ. The sword cut had left a seam in his face. ጐራዴው ፡ የቈረጠው ፡ ጠባሳ ፡ ፊቱ ፡ ላይ ፡ አለ

**seaman** መርከበኛ
The seamen meet here between voyages. መርከበኞቹ ፡ ሲያርፉ ፡ እዚህ ፡ ይገናኛሉ

**seamstress** ልብስ ፡ ሰፊ
The seamstress will make you a dress. ልብስ ፡ ሰፊዋ ፡ ቀሚስ ፡ ትሰፋልሻለች

**seamy** ደስ ፡ የማያሰኝ
A policeman sees much of the seamy side of life. ፖሊስ ፡ ደስ ፡ የማያሰኝ ፡ ኑሮ ፡ ያያል

**sear**
1. ጠበሰ. The hot iron seared his flesh. የጋለው ፡ ካውያ ፡ ቆዳውን ፡ ጠበሰው
2. አደረቀ. A hot summer has seared the crops this year. የበጋው ፡ ሙቀት ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ እህሉን ፡ አደረቀ

**search** (v.)
1. ፈተሸ. The customs officials searched us. የጉምሩክ ፡ ሠራተኞች ፡ ፈተሹን
2. በረበረ. I've searched the whole house for the lost papers. የጠፋውን ፡ ወረቀት ፡ ለማግኘት ፡ ቤቱን ፡ እንድም ፡ ሳይቀረኝ ፡ በርብሬያለሁ
*I've searched everywhere for a good apartment. ጥሩ ፡ ቤት ፡ ለማግኘት ፡ ያልደረስኩበት ፡ ቦታ ፡ የለም

**search for** ፈለገ
We searched for him everywhere. እሱን ፡ በያለበት ፡ ፈለግነው

**search (one's) memory** ቢያስብ ፡ ቢያስብ
I searched my memory, but could not remember his name. ባስብ ፡ ባስብ ፡[ስሙን]፡ ማስታወስ ፡ አቃተኝ

**search out** ፈልጎ ፡ አገኘ
He searched out an old friend in the crowd. ከተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ የዱሮ ፡ ጓደኛውን ፡ ፈልጎ ፡ አገኘ

**search** (n.)
1. ፍተሻ. The police made a thorough search. ፖሊሶቹ ፡ ጥብቅ ፡ ፍተሻ ፡ አደረጉ
*An intensive search turned up the missing key. በጥንቃቄ ፡ ስለተፈለገ ፡ ቁልፉ ፡ ተገኘ

**in search of** ሲፈልግ ፤ noun + ፍለጋ
In search of knowledge, one comes across many strange things. ዕውቀትን ፡ ሲፈልጉ ፡ ብዙ ፡ እንግዳ ፡ ነገሮች ፡ ያጋጥማሉ
The dog nosed the grass in search of a trail. ውሻው ፡ መንገድ ፡ ፍለጋ ፡ ሣሩን ፡ አነፈነፈ

**make a search** ፈለገ
They made a search for the missing plane. የጠፋውን ፡ አውሮፕላን ፡ ፈለጉ

**search** (adj.) የፈላጊዎች
A search party set out to find the missing boy. የጠፋውን ፡ ልጅ ፡ ለመፈለግ ፡ የፈላጊዎች ፡ ጓድ ፡ ተሰማራ

**searching**
*The policeman gave him a searching look. ፖሊሱ ፡ ከእግር ፡ እስከ ፡ ራሱ ፡ ተመለከተው

**searchlight** ባውዛ
The searchlight spotted a plane flying in the clouds. ባውዛው ፡ በደመናው ፡ ውስጥ ፡ የሚበረውን ፡ አውሮፕላን ፡ አሳየ

**search warrant** የፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍተሻ ፡ ማዘዣ
The police must have a search warrant to enter the house. ፖሊሱ ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍተሻ ፡ ማዘዣ ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈልጋል

**seashore** የባሕር ፡ ዳር
The shells were piled on the seashore. ዛጐል ፡ እባሕሩ ፡ ዳር ፡ ተከምሯል

**seasick, get ~**
The baby got seasick. ሕፃኑ ፡ በባሕሩ ፡ ጉዞ ፡ ምክንያት ፡ አስመለሰው

**seaside** የባሕር ፡ ዳርቻ
The seaside is the best location for our factory. የባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ፋብሪካችንን ፡ ለማቋቋም ፡ ከሁሉ ፡ የተሻለ ፡ ስፍራ ፡ ነው

**season** (v.) አጣፈጠ
What did you season the meat with? ሥጋውን ፡ በምን ፡ አጣፈጥከው ?
The speaker seasoned his speech with humor. ተናጋሪው ፡ ቀልድ ፡ በመጨመር ፡ ንግግሩን ፡ አጣፈጠው

**season** (n.)
1. ወራት. What season comes after spring? ከጸደይ ፡ የሚቀጥለው ፡ የትኛው ፡ ወራት ፡ ነው ?
When does the hunting season start? ያደን ፡ ወራት ፡ የሚጀመረው ፡ መቼ ፡ ነው ?
2. ያመት ፡ ወራት. The cycle of the seasons cannot be changed. ያመቱ ፡ ወራት ፡ ዓውድ ፡ ሊለወጥ ፡ አይችልም

**be in season** ደረሰ
Corn is in season in late summer. ወደ ፡ በጋው ፡ ማለቂያ ፡ በቆሎ ፡ ይደርሳል

**be out of season** ጊዜው ፡ አይደለም
Fresh fruit is out of season in the winter. ትኩስ ፡ ፍራፍሬዎች ፡ ክረምት ፡ ጊዜያቸው ፡ አይደለም
[See 'dead, rainy']

**(be) seasonable** ጊዜው ፡ ነው
In Ethiopia, rainy weather is seasonable in

August. በኢትዮጵያ ፡ በነሐሴ ፡ ክረምት ፡ ጊዜው ፡ ነው

**seasonal**
1. ወርኀዊ. The seasonal rains of Ethiopia are divided into a big rainy season and a small one. የኢትዮጵያ ፡ ወርኀዊ ፡ ዝናቦች ፡ ዋና ፡ የክረምት ፡ ጊዜና ፡ መለስተኛ ፡ ተብለው ፡ ይከፈላሉ
2. የጊዜ. The factory geared its production to seasonal demands. ፋብሪካው ፡ የሚያወጣቸውን ፡ ነገሮች ፡ ከጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ አስማማ

**be seasonal** ቀዋሚ ፡ አይደለም
Fruit picking is a seasonal occupation. ፍራፍሬ ፡ ለቀማ ፡ ቀዋሚ ፡ ሥራ ፡ አይደለም

**seasoned** ልምድ ፡ ያለው
Seasoned troops are manning the hill posts. ልምድ ፡ ያላቸው ፡ ወታደሮች ፡ ኮረብታዎቹ ፡ ላይ ፡ መሽገዋል

**seasoned traveler** መንገድ ፡ የለመደ ፡ ሰው
A seasoned traveler does not mind discomfort. መንገድ ፡ የለመደ ፡ ሰው ፡ ለምቾት ፡ ግድ ፡ የለውም

**be seasoned**
1. ተቀመመ. This is a highly seasoned dish. ይህ ፡ ምግብ ፡ በጣም ፡ ተቀምሟል
2. ከው ፡ ብሎ ፡ ደረቀ. The wood was seasoned. ዕንጨቱ ፡ ከው ፡ ብሎ ፡ ደርቋል
3. ደረቀ. After wood is seasoned it serves for building. ዕንጨት ፡ ከደረቀ ፡ በኋላ ፡ ለቤት ፡ መሥሪያ ፡ ያገለግላል

**seasoning** ቅመም
Pepper and salt are common seasonings. በርበሬና ፡ ጨው ፡ በጣም ፡ የተለመዱ ፡ ቅመሞች ፡ ናቸው

**seat** (v.)
1. አስቀመጠ. He seated the children in the front row. ልጆቹን ፡ በመጀመሪያው ፡ ረድፍ ፡ አስቀመጣቸው
2. ያዘ. The theater seats five hundred people. ቲያትር ፡ ቤቱ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ሰው ፡ ይይዛል
+How many people can you seat in your living room? የእንግዳ ፡ ክፍልህ ፡ ስንት ፡ ሰው ፡ ይይዛል ?
3. (= take a seat) መቀመጫ ፡ ያዘ. +I second the motion to seat the delegate. መልእክተኛው ፡ መቀመጫውን ፡ እንዲይዝ ፡ የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ እደግፋለሁ

**seat oneself** ተቀመጠ
He seated himself in a comfortable chair. በምቹ ፡ ወምበር ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ

**be seated!**
Please be seated! በእግዚአብሔር ፡ ተቀመጡ

**seat** (n.)
1. ወምበር ፤ መቀመጫ. This seat is taken. ይህ ፡ ወምበር ፡ ተይዟል
Bring me a seat! መቀመጫ ፡ አምጣልኝ
2. ቦታ. I have four seats for "Hamlet". ሀምሌትን ፡ ለማየት ፡ አራት ፡ ቦታ ፡ ይዤያለሁ
3. ስፍራ. He took his habitual seat at the table. ገበታው ፡ ላይ ፡ እተለመደው ፡ ስፍራ ፡ ተቀመጠ
*Addis Ababa is the seat of government. ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሚገኙት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**have a seat, take a seat** ተቀመጠ
Please have a seat! ተቀመጥ ፡ እንጂ

**take a back seat** ከኀላፊነት ፡ ገሸሽ ፡ አለ
He took a back seat in the conduct of the business. በንግዱ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ላይ ፡ ከኀላፊነት ፡ ገሸሽ ፡ አለ

**seat belt** ያደጋ ፡ ቀበቶ
Put on your seat belt, please! ያደጋውን ፡ ቀበቶ ፡ እንድታስሩ ፡ ትለመናላችሁ

**seating** አቀማመጥ
Seating at the banquet was done in order of precedence. በእራት ፡ ግብዣው ፡ ላይ ፡ አቀማመጥ ፡ በማዕረግ ፡ ነበር

**seating room** መቀመጫ
We have seating room for thirty in our classroom. በክፍላችን ፡ ውስጥ ፡ ለሠላሳ ፡ ልጆች ፡ የሚበቃ ፡ መቀመጫ ፡ አለን

**seaweed** [በባሕር ፡ ውስጥ ፡ የሚበቅሉ ፡ ዕፀዋት]

**secede** ተገነጠለ
Katanga tried to secede from the Congo. ካታንጋ ፡ ከኮንጎ ፡ ለመገንጠል ፡ ሞከረች

**secession** መገንጠል
The secession of Katanga was announced in the paper. የካታንጋ ፡ መገንጠል ፡ በጋዜጣ ፡ ተገልጾ ፡ ነበር

**seclude** ጋረደ
The dense forest secluded the cabin. ጥቅጥቅ ፡ ያለው ፡ ጫካ ፡ ጎጆውን ፡ ጋረደው

**seclude oneself** ራሱን ፡ አገለለ
She secluded herself from public view. ራሷን ፡ ከደባባይ ፡ አገለለች

**secluded** (adj.)
1. የብቸኝነት. He leads a secluded life. የብቸኝነት ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል
2. ፈንጠር ፡ ያለ. A secluded cottage is furnished to each newlywed couple. ለያንዳንዱ ፡ አዲስ ፡ ሙሽራ ፡ ፈንጠር ፡ ያለ ፡ ጎጆ ፡ ተሰጠው
3. ወጣ ፡ ያለ. He lives in a secluded spot. ወጣ ፡ ካለ ፡ ስፍራ ፡ ይኖራል
4. ገለልተኛ. He lives in a secluded mountain retreat. በተራራ ፡ ላይ ፡ ባንድ ፡ ገለልተኛ ፡ ስፍራ ፡ ይኖራል

**seclusion** ገለልተኛነት
He sought seclusion in his study. በጥናት ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ በገለልተኛነት ፡ ቆየ
The English royal family lives in seclusion. የእንግሊዝ ፡ ንጉሣውያን ፡ ቤተሰቦች ፡ በገለልተኛነት ፡ ይኖራሉ
*His seclusion lasted more than forty years. ከአርባ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ ለብቻው ፡ ኖረ

**in seclusion** ከሕዝብ ፡ ተገልሎ
She has lived in seclusion since her husband died. ባሏ ፡ ከሞተ ፡ ጀምሮ ፡ ከሕዝብ ፡ ተገልላ ፡ ኖራለች

**second** (v.) ደገፈ
I second the motion to seat the delegate. መልእክተኛው ፡ መቀመጫውን ፡ እንዲይዝ ፡ የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ እደግፋለሁ
He seconded his son's desire to become an actor. ልጁ ፡ ተዋናይ ፡ ለመሆን ፡ ያለውን ፡ ምኞት ፡ ደገፈ

**second** (n.) ሴኮንድ
He ran a hundred yards in ten seconds. በዐሥር ፡ ሴኮንድ ፡ መቶ ፡ ያርድ ፡ ሮጠ

**seconds** እንከን ፡ ያለበት
Those stockings are seconds. እነዚህ ፡ የግር ፡ ሹራቦች ፡ እንከን ፡ ያለባቸው ፡ ናቸው

**a second** አንዳፍታ
Wait a second! አንዳፍታ ፡ ቆይ

**in just a second** አሁኑኑ
I'll be finished in just a second. አሁኑኑ ፡ እጨርሳለሁ

**only a second** ምንም ፡ ጊዜ + negative verb.
It takes only a second to phone. ቴሌፎን ፡ ለመደወል ፡ ምንም ፡ ጊዜ ፡ አይወስድ
[See also 'split']

**second** (adj.)
1. ሁለተኛ. This hotel is second–rate. ይህ ፡ ሆቴል ፡ ደረጃው ፡ ሁለተኛ ፡ ነው
The second person singular has a masculine and a feminine. በሰዋስው ፡ ሁለተኛ ፡ መደብ ፡ ተባዕታይና ፡ አንስታይ ፡ አለው
2. የሁለተኛነት. He got second prize for the high jump. በከፍታ ፡ ዝላይ ፡ ውድድር ፡ የሁለተኛነት ፡ ሽልማት ፡ አገኘ
3. ዳግማዊ. George the Second was once king of England. ድሮ ፡ ዳግማዊ ፡ ጆርጅ ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ነበሩ
He thinks he is a second Shakespeare. ዳግማዊ ፡ ሼክስፒር ፡ ነኝ ፡ ባይ ፡ ነው
4. (= adv.) ቀጥሎ. He was the second to arrive. ቀጥሎ ፡ የመጣው ፡ እሱ ፡ ነበር

**second best** ሁለተኛ
He came out second best in the fight. በግጥሚያው ፡ ሁለተኛ ፡ ሆነ

**second in command** ምክትል ፡ አዛዥ
In our company, he was second in command. በሻምበላችን ፡ ውስጥ ፡ ምክትል ፡ አዛዥ ፡ ነበር

**second nature**
*Swimming is second nature to him. ዋና ፡ አብሮት ፡ የተወለደ ፡ ነው

**be second to none** የሚወዳደር ፡ የለም
This hotel is second to none. ይህን ፡ ሆቴል ፡ የሚወዳደር ፡ የለም

**every second** በየሁለት
I have my hair cut every second week. በየሁለት ፡ ሳምንት ፡ ጸጉሬን ፡ አስተካክላለሁ

**get (one's) second wind** እንዴ ፡ ተነፈሰ
He got his second wind and kept on running. እንዴ ፡ ተንፍሶ ፡ ሩጫውን ፡ ቀጠለ

**in the second place** ሁለተኛ ፡ ደግሞ
In the first place, I have no time; and in the second place, I don't want to go anyway. መጀመሪያ ፡ ነገር ፡ ጊዜ ፡ የለኝም ፤ ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ ቢሆንም ፡ ለመሄድ ፡ አልፈልግም

**play second fiddle to** ተገዢ ፡ ነው
He plays second fiddle to his wife. የሚስቱ ፡ ተገዢ ፡ ነው
[See also 'hand, thought']

**secondarily**
*He is first a nationalist, and only secondarily a Christian. ከክርስትና ፡ እምነቱ ፡ ይልቅ ፡ ብሔራዊ ፡ ስሜቱን ፡ ያጠነክራል

**secondary** ዋና ፡ ምንጭ ፡ ያልሆነ
He uses secondary sources for his research paper. ለምርምር ፡ ድርሰቱ ፡ ዋና ፡ ምንጭ ፡ ባልሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ ይጠቀማል

**be secondary** እስኪዚሁ ፡ ተፈላጊ ፡ አይደለም
These matters are secondary. እነዚሁ ፡ ጉዳዮች ፡ እስኪዚሁ ፡ ተፈላጊዎች ፡ አይደሉም

**be secondary to**
*Reading fast is secondary to reading well. ፈጥኖ ፡ ማንበብ ፡ በደንብ ፡ የማንበብን ፡ ያህል ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም

**of secondary interest** አነስተኛ
This is a matter of secondary interest. ይህ ፡ ጉዳይ ፡ አነስተኛ ፡ ነው

**secondary school**
1. ሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት. There are several secondary schools in Addis Ababa. አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ አሉ
2. የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት. Secondary school is harder than primary. የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ካንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ይከብዳል

**second-class** መለስተኛ
He stays in a second-class hotel. መለስተኛ ፡ ሆቴል ፡ ውስጥ ፡ ያርፋል

**second-hand** (adj., adv.)
1. አሮጌ. He bought the book second-hand. አሮጌ ፡ መጽሐፍ ፡ ገዛ
2. ያገለገለ. I bought a second-hand car. ያገለገለች ፡ መኪና ፡ ገዛሁ
3. ከሰው. I only know that story second-hand. ታሪኩን ፡ የሰማሁት ፡ ከሰው ፡ ነው

**secondly** ሁለተኛ ፡ ደግሞ
In the first place, I have no time; and secondly, I don't want to go anyway. መጀመሪያ ፡ ነገር ፡ ጊዜ ፡ የለኝም ፤ ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ ቢሆንም ፡ መሄድ ፡ አልፈልግም

**second-rate** መለስተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያለው
There are many second-rate hotels in this city. እዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ መለስተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያላቸው ፡ ብዙ ፡ ሆቴሎች ፡ አሉ

**secrecy** ምስጢር
He does his work in secrecy. ሥራውን ፡ የሚሠራው ፡ በምስጢር ፡ ነው
*I am relying on your secrecy in this matter. ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ለማንም ፡ አትናገርም ፡ ብዬ ፡ እምነት ፡ ጥዬብሃለሁ
[See also 'seal, veil']

**secret**
1. ምስጢር. The secret is out. ምስጢሩ ፡ ባከኗል
Can you keep a secret? ምስጢር ፡ ትቋጥራለህ ?
Let me in on the secret. ምስጢሩን ፡ አካፍለኝ
2. ምስጢራዊ ፡ ሰነድ. His sale of secrets was a clear-cut example of treachery. ምስጢራዊ ፡ ሰነዶችን ፡ መሸጡ ፡ ለከዳተኝነት ፡ በቂ ፡ ምሳሌ ፡ ነበር
3. መንሾ. What is the secret of his success? ለዕድሉ ፡ መቃናት ፡ መንሾው ፡ ምን ፡ ይሆን ?

**give away a secret** ምስጢር ፡ አወጣ
I would die first rather than give away a secret. ምስጢር ፡ ከማወጣ ፡ አስቀድሜ ፡ ብሞት ፡ ይሻለኛል

**make no secret of** አልደበቀም
He makes no secret of his hatred for them. ለነሱ ፡ ያለውን ፡ ጥላቻ ፡ አይደብቅም

**secret** (adj.)
1. የተሰወረ. They have a secret plan. የተሰወረ ፡ እቅድ ፡ አላቸው
2. ስውር. The children have a secret hiding place. ልጆቹ ፡ ስውር ፡ የመደበቂያ ፡ ቦታ ፡ አላቸው
3. የምስጢር. This coat has two secret pockets. ይህ ፡ ኮት ፡ ሁለት ፡ የምስጢር ፡ ኪስ ፡ አለው
4. ምስጢራዊ. He was able to decipher the secret message. ምስጢራዊ ፡ መልእክቱን ፡ ለመፍታት ፡ ቻለ

**secret agent** ሰላይ
The secret agent was expelled from the country. ሰላዩ ፡ ካገር ፡ እንዲወጣ ፡ ተደረገ

**secretariat** ጽሕፈት ፡ ቤት
The United Nations secretariat will inform you. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ጉዳዩን ፡ ይገልጽልሃል

**secretary** (secretaries) ጸሐፊ
She is my secretary. ጸሐፊዬ ፡ ናት
*Who was elected secretary? ለጸሐፊነት ፡ ማን ፡ ተመረጠ ?

**private secretary** ልዩ ፡ ጸሐፊ
Who is the private secretary of the Emperor? የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ልዩ ፡ ጸሐፊ ፡ ማን ፡ ነው ?

**Secretary-General** ዋና ፡ ጸሐፊ
The Secretary-General does not want to be re-elected. ዋና ፡ ጸሐፊው ፡ እንደገና ፡ መመረጥ ፡ አይፈልግም

**secrete**
1. ወጣ(ው). +The cow's udder secretes milk. የላሚቷ ፡ ጡት ፡ ወተት ፡ ይወጣዋል
2. አወጣ. Flowers secrete nectar. አበቦች ፡ ያበባ ፡ ማር ፡ ያወጣሉ

3. ደበቀ. He secreted a book in his coat. ኮቱ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ደበቀ

**secretive** ምስጢራዊ
Their actions are rather secretive, so they may be up to something. ተግባራቸው ፡ በጣም ፡ ምስጢራዊ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ የሚሠሩት ፡ ተንኰል ፡ አለ

**secretly** በድብቅ
They met secretly. በድብቅ ፡ ተገናኙ

**secret service** ነጭ ፡ ለባሾች ፤ የጸጥታ ፡ ክፍል
In Greece, the secret service uncovered a dangerous plot. በግሪክ ፡ አገር ፡ ነጭ ፡ ለባሾች ፡ (የጸጥታ ፡ ክፍል) ፡ አደገኛ ፡ የሆነ ፡ አድማ ፡ አገኙ

**sect**
1. ወገን. The Protestant church has various sects. የፕሮቴስታንት ፡ ሃይማኖት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወገኖች ፡ አሉት
2. እምነት. This sect adheres to the eternal principles of the church. ይህ ፡ እምነት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማ ፡ ይከተላል

**sectarian**
1. የሃይማኖት. Sectarian disputes keep Lebanon from being fully united. የሃይማኖት ፡ ጭቅጭቅ ፡ ለሊባኖስ ፡ አንድነት ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆኗል
2. የወገን. Sectarian disputes divided the country. የወገን ፡ ጠብ ፡ አገሪቱን ፡ ከፋፈላት

**section** (v.) ከፋፈለ
He skillfully sectioned the orange. ብርቱካኑን ፡ በቅልጥፍና ፡ ከፋፈለው

**section** (n.)
1. ክፍል. You'll find it in chapter one, section three. አንደኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በሦስተኛው ፡ ክፍል ፡ ታገኘዋለህ
The medial section is 15 cm. wide. የመሀከለኛው ፡ ክፍል ፡ ስፋት ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ሳንቲሜትር ፡ ነው
2. ሰፈር. He lives in one of the nicest sections of the town. በከተማው ፡ ጥሩ ፡ ከሆኑት ፡ ሰፈሮች ፡ አንዱ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል
3. ፍልቃቂ. The sections of an orange were spread out to dry. የብርቱካን ፡ ፍልቃቂዎች ፡ እንዲደርቁ ፡ ተሰጥተዋል
*His section of the family estate was larger than his brother's. ከወንድሙ ፡ ይልቅ ፡ ለሱ ፡ ከቤተሰቡ ፡ የደረሰው ፡ የርስት ፡ ውርስ ፡ ይበልጥ ፡ ነበር

**sector** የጦር ፡ ይዞታ
Our sector is under heavy attack. የጦራችን ፡ ይዞታ ፡ በጣም ፡ በመጠቃት ፡ ላይ ፡ ነው
*The private sector is expected to create new business. የግል ፡ ንግድ ፡ ያላቸው ፡ ወገኖች ፡ አዲስ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ያቋቁማሉ ፡ ተብሎ ፡ ይጠበቃል

**secular**
1. ዓለማዊ. Secular organizations run many schools. ዓለማዊ ፡ ማኅበሮች ፡ ብዙ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ያካሄዳሉ
Priests prefer religious music to secular music. ቄሶች ፡ ከዓለማዊ ፡ መዝሙር ፡ ይልቅ ፡ ሃይማኖታዊ ፡ መዝሙር ፡ ይወዳሉ
2. የሕዝብ. Secular courts had no jurisdiction over priests at that time. በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሕዝብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በቄሶች ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ አልነበራቸውም
3. ሥጋዊ. Secular education is now more common than religious education. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ይልቅ ፡ ሥጋዊ ፡ ትምህርት ፡ በጣም ፡ ተስፋፍቷል
4. በሕዝብ ፡ መካከል ፡ የሚኖር ፡ ቄስ. The secular clergy minister to the needs of the town folks. በሕዝብ ፡ መካከል ፡ የሚኖሩት ፡ ቀሳውስት ፡ የከተማ ፡ ነዋሪዎችን ፡ ያገለግላሉ

**secularize** (= pass.) በመንግሥት ፡ ሥር ፡ ተዳደረ
+The President decided to secularize education. ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በመንግሥት ፡ ሥር ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ወሰነ

**secure** (v.)
1. በደንብ ፡ ዘጋ. Secure all doors and windows before you leave! ከመሄድህ ፡ በፊት ፡ መስኮቶቹንና ፡ በሮቹን ፡ ሁሉ ፡ በደንብ ፡ ዝጋ
2. ተከላከለ. Secure your house against burglars! ቤትህን ፡ ከሌቦች ፡ ተከላከል
They secured the villages from floods by building a dam. ግድብ ፡ በመሥራት ፡ መንደሮቹን ፡ ከጐርፍ ፡ ተከላከሉ
3. አጥብቆ ፡ አሰረ. Secure the boats to the dock! ጀልባዎቹን ፡ በወደቡ ፡ ላይ ፡ አጥብቀህ ፡ እሰር
4. ያዘ. Can you secure me two seats to the concert? ለሙዚቃው ፡ ትርኢት ፡ ሁለት ፡ መቀመጫዎች ፡ ልትይዝልኝ ፡ ትችላለህ ?
5. አስከበረ. The Constitution secures freedom of religion. ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የሃይማኖት ፡ ነጻነትን ፡ ያስከብራል
6. አገኘ. We secured the reading list from the librarian. የሚነበቡትን ፡ መጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ ከዐቃቤ ፡ መጻሕፍቱ ፡ አገኘን

7. በዋስትና ፡ ጠበቀ(ተጠበቀ). Every loan was secured by bonds. ማንኛቸውም ፡ ብድር ፡ በቦንድ ፡ ዋስትና ፡ የተጠበቀ ፡ ነበር
*He gave a mortgage to secure the loan. ብድሩን ፡ የሚመልስ ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጫ ፡ መያዣ ፡ ሰጠ

**secure** (adj.)
1. ሰላማዊ. Everyone lives a secure life now. አሁን ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል
2. ስጋት ፡ የሌለበት. He hoped for a secure old age. ስጋት ፡ የሌለበት ፡ የእርጅና ፡ ጊዜ ፡ ተመኘ
3. የማያሰጋ. This is a secure hiding place. ይህ ፡ የማያሰጋ ፡ መደበቂያ ፡ ቦታ ፡ ነው
4. ጽኑ. A secure foundation kept the earthquake from destroying the building. ጽኑ ፡ የሆነው ፡ መሠረት ፡ ሕንጻውን ፡ በመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ እንዳይወድቅ ፡ አደረገው
5. ጠንካራ. The boards of this bridge do not look secure. የዚህ ፡ ድልድይ ፡ ሳንቃዎች ፡ ጠንካራ ፡ አይመስሉም
6. ኪሳራ ፡ የማያደርስ. Land in a growing city is a secure investment. በመስፋፋት ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ መሬት ፡ መግዛት ፡ ኪሳራ ፡ የማያደርስ ፡ ግዢ ፡ ነው

**be secure**
1. ጠበቀ. Are the prisoners' fetters secure? የእስረኞቹ ፡ ሰንሰለቶች ፡ ጠብቀዋል ?
2. በእጁ ፡ ነው. Our victory is secure. ድሉ ፡ በእጃችን ፡ ነው

**feel secure**
1. እንደልቡ ፡ ሆነ. She felt secure because her parents were home. ወላጆቿ ፡ እቤት ፡ ስለሆኑ ፡ እንደልቧ ፡ ሆነች
2. ያለ ፡ ስጋት ፡ ኖረ. In time of war, nobody feels secure. በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ስጋት ፡ የሚኖር ፡ የለም

**keep secure** ጠበቀ
Keep the prisoner secure within the camp! እስረኛውን ፡ በሰፈሩ ፡ ውስጥ ፡ ጠብቀው

**remain secure** ጸንቶ ፡ ቆየ
He remained secure in his faith despite persecution. ቢያሳድዱት ፡ እንኳ ፡ በእምነቱ ፡ ጸንቶ ፡ ቆየ

**secured** (adj.) የተረጋገጠ
His future is secured. የወደፊት ፡ ኑሮው ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው

**security** (securities)
1. መያዣ. I had to leave my watch as a security. ሰዓቱን ፡ መያዣ ፡ መስጠት ፡ ነበረብኝ
2. ዋስትና. Insurance is a security against loss. ኢንሹራንስ ፡ ለሚጠፋ ፡ ሀብት ፡ ዋስትና ፡ ነው
3. መከላከያ. Is there any security from bombs? የቦምብ ፡ መከላከያ ፡ አለ ?
4. ጸጥታ. The police must maintain public security. ፖሊስ ፡ የሕዝብን ፡ ጸጥታ ፡ ማስከበር ፡ አለበት
5. ጥበቃ. The watchman was hired for security. ዘበኛው ፡ ለጥበቃ ፡ ተቀጠረ
6. ደኅንነት. She enjoys the cozy security of her room. በክፍሏ ፡ ውስጥ ፡ የሚሰማት ፡ ፍጹም ፡ ደኅንነት ፡ ያስደስታታል
*The insurance policy gave the widow security. ኢንሹራንሱ ፡ ባሏ ፡ የሞተባትን ፡ ሴትዮ ፡ ከገንዘብ ፡ ችግር ፡ አዳናት

**collective security** የጋራ ፡ ጸጥታ
Collective security will assure world peace. የጋራ ፡ ጸጥታ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሰላም ፡ እንዲኖር ፡ ያደርጋል

**in security** ያለ ፡ ስጋት
You may cross the street in security when a policeman holds up his hand. ፖሊስ ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሲያነሣ ፡ ያለ ፡ ስጋት ፡ መንገዱን ፡ ለማቋረጥ ፡ ይቻላል
[See also 'pledge, tenure']

**Security Council** የጸጥታ ፡ ምክር ፡ ቤት
The Security Council refused to vote on it. የጸጥታው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በነገሩ ፡ ላይ ፡ ድምፅ ፡ አልሰጥበትም ፡ አለ

**security forces** ጸጥታ ፡ አስከባሪዎች
The security forces maintained law and order. ጸጥታ ፡ አስከባሪዎቹ ፡ ሕግን ፡ አስከበሩ

**sedate** ረጋ ፡ ያለ
She is very sedate for a child and would rather read than play. ልጅ ፡ ብትሆንም ፡ ረጋ ፡ ያለች ፡ ናት ፤ ከመጫወት ፡ ይልቅ ፡ ማንበብ ፡ ትመርጣለች

**sedative** የሚያስተኛ ፡ ኪኒን
He took a sedative, so that he could sleep. እንቅልፍ ፡ እንዲወስደው ፡ የሚያስተኛ ፡ ኪኒን ፡ ዋጠ

**sedentary**
1. ሰፍሮ ፡ የሚኖር. The sedentary tribes are being attacked by nomads. ሰፍረው ፡ የሚኖሩትን ፡ ነገዶች ፡ ዘላኖቹ ፡ አጠቋቸው
2. መቀመጥ ፡ የሚያበዛ. Sedentary people get little physical exercise. መቀመጥ ፡ የሚያበዙ ፡ ሰዎች ፡ የሚያደርጉት ፡ የሰውነት ፡ እንቅስቃሴ ፡ ጥቂት ፡ ነው

*Bookkeeping is a sedentary job. የሒሳብ ፡ አ
ያያዝ ፡ ሥራ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚሠራ ፡ ነው

**sediment** ደለል
The ground was covered with sediment after the flood. መሬቱ ፡ ከውኃው ፡ መጥለቅለቅ ፡ በ
ኋላ ፡ ደለል ፡ ለብሶ ፡ ነበር

**sedition** ሕዝብን ፡ [በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ማነሣሣት
Sedition is punishable by death. ሕዝብን ፡ በመ
ንግሥት ፡ ላይ ፡ ማነሣሣት ፡ በሞት ፡ ያስቀጣል

**seditious** ሕዝብን ፡ የሚያነሣሣ
He was imprisoned because of his seditious speech. ሕዝብን ፡ የሚያነሣሣ ፡ ንግግር ፡ በማ
ድረጉ ፡ ታሰረ

**seduce**
1. አባበለ. They seduced him with a bribe to lose the game. በጨዋታው ፡ እንዲሸነፍ ፡ በ
ገንዘብ ፡ አባበሉት
2. አሳሳተ. He seduced her with promises of marriage. አገባሻለሁ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ በመግባት ፡
አሳሳታት

**seduce from** ቸል ፡ እንዲል ፡ አደረገው
An agent seduced him from his duty. አንድ ፡ የ
ውጭ ፡ ሰላይ ፡ ሥራውን ፡ ቸል ፡ እንዲል ፡ አ
ደረገው

**see** (saw), vt.
1. አየ. I would like to see the town. ከተማውን ፡
ለማየት ፡ እፈልጋለሁ
I looked back, but saw nothing. ዞር ፡ ብዬ ፡ ተመ
ለከትኩ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አላየሁም
He didn't see the question my way. ጥያቄውን ፡
በኔ ፡ መንገድ ፡ አላየውም
2. ተረዳ. You will see that it is not true by and by. እውነት ፡ ያለመሆኑን ፡ እያደረ ፡ ትረዳለህ
3. ጠየቀ. I went to see a friend. ጓደኛ ፡ ልጠ
ይቅ ፡ ሄድኩ
See what he wants. ምን ፡ እንደሚፈልግ ፡ ጠ
ይቀው
4. ሞከረ. See what you can do for him.
ልታደርግለት ፡ የምትችለው ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ሞክር
5. ሸኘ. I'll see you to the door. በሩ ፡ ድረስ ፡
ልሸኝህ
6. አሰበ. I can't see him as chairman of the committee. ለደርጉ ፡ ሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ይገባ
ል ፡ ብዬ ፡ አላስብም
7. ገባ(ው). +Do you see the point? የምለው ፡ ገ
ባህ ?
+Do you see now what I mean? ምን ፡ ማለቴ ፡
እንደሆነ ፡ ገባህ ?
8. መሰለ(ው). +I don't see any use in learning Persian. የፋርስ ፡ ቋንቋ ፡ መማር ፡ ምንም ፡ ጥ
ቅም ፡ ያለው ፡ አይመስለኝም
+I don't see it that way at all. እኔ ፡ ፈጽሞ ፡ እ
ንደዚህ ፡ አይመስለኝም
+The way I see it, the President must have made a mistake. እኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡
ሳይሳሳት ፡ አልቀረም
9. አማከረ. Why don't you see a lawyer? ለም
ን ፡ ጠበቃ ፡ አታማክርም ?
10. መስሎ ፡ ታየው. He sees no advantage in buying the land. መሬቱን ፡ መግዛቱ ፡ ምንም ፡
ጥቅም ፡ ያለው ፡ መስሎ ፡ አልታየውም
*He has seen better days. ጥሩ ፡ ኑሮ ፡ አይቷል

**see** (vi.) አየ
If you don't believe me, go and see for yourself.
ካላመንከኝ ፡ አንተው ፡ ራስህ ፡ ሂደህ ፡ እየው
Will you do it? I will see. ታደርገዋለህ ? እስቲ ፡
አያለሁ

**see about** ሞከረ
He said he would see about getting the license plates. የመኪናውን ፡ ታርጋ ፡ ለማግኘት ፡ እሞክ
ራለሁ ፡ አለ

**see after** ጠበቀ
Would you please see after my plants while I'm away? እኔ ፡ እስክመለስ ፡ ተክሎቼን ፡ ል
ትጠብቅልኝ ፡ ትችላለህ ?

**see (one) home** እቤት ፡ አደረሰ
After the dance, may I see you home? ዳንሱ ፡ ሲ
ያልቅ ፡ እቤትሽ ፡ ላድርስሽ ?

**see off** ሸኘ
I went to the airport to see them off. እነሱን ፡
ለመሸኘት ፡ አውሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ ሄድኩ

**see oneself**
*I can't see myself allowing people to cheat me.
ሰው ፡ ሲያታልለኝ ፡ ማየት ፡ አልፈልግም

**see things** ቃዠ
He must be seeing things the way he talks.
እንዳነጋገሩ ፡ ከሆነ ፡ ይቃዣል

**see through**
1. ከግብ ፡ አደረሰ. We must see the difficult situation through. አስቸጋሪውን ፡ ሁኔታ ፡ ከግብ ፡
ማድረስ ፡ አለብን
2. ደረሰ(በት). He saw through the trick. ተንኰ
ሉን ፡ ደረሰበት
*He was afraid the workers might make a mistake, so he stayed to see the job through.
ሠራተኞቹ ፡ ይሳሳታሉ ፡ ብሎ ፡ ስለሰጋ ፡ ሥራው ፡
እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ቆየ

**see (one) through**
*You'll have a hard time, but perseverance will see you through. በጣም ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ያጋጥምሃል ፤ ከበረታህ ፡ ግን ፡ ታልፈዋለህ

**see through one** ብልጠቱን ፡ ዐወቀበት
Anyone can see through him. ማንም ፡ ሰው ፡ ብልጠቱን ፡ ሊያውቅበት ፡ ይችላል

**see to it**
1. አደረገ. He saw to it that every guest had plenty to eat and drink. እንግዶቹ ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ አደረገ
2. አረጋገጠ. I will see to it that everything is ready. ሁሉም ፡ ነገር ፡ እንዲዘጋጅ ፡ አረጋግጣለሁ
3. እንድ + (imperfect). See to it that you are on time! በሰዓቱ ፡ እንድትገኝ
Please see to it that this letter is mailed today. ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ ዛሬውኑ ፡ እንዲላክ

**see (one's) way clear** ታየ(ው)
I can't see my way clear to lending you $100. ላንተ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ማበደሩ ፡ አይታየኝም

**as far as I can see** እኔ ፡ እንደሚታየኝ
As far as I can see, the situation isn't that bad. እኔ ፡ እንደሚታየኝ ፡ ሁኔታው ፡ እስከዚህ ፡ መጥፎ ፡ አይደለም

**let me see** ቆይ ፡ እስቲ
Let me see, where does he live? ቆይ ፡ እስቲ ፤ የት ፡ ነበር ፡ የሚኖረው ?

**refuse to see**
She refused to see us. አልቀበላችሁም ፡ አለች
[See also 'action, eye, fit, light, red, star, there']

**seed** (v.)
1. ዘራ. When did you seed the lawn? የግቢውን ፡ መስክ ፡ የዘራኸው ፡ መቼ ፡ ነው ?
2. ፍሬ ፡ አወጣ. She seeded the raisins. ከዘቢቡ ፡ ውስጥ ፡ ፍሬውን ፡ አወጣች

**seed** (n.)
1. ዘር. Put the seeds in the ground! ዘሮቹን ፡ ዝሩ፡ቸው
The Jews are the seed of Abraham. አይሁዶች ፡ የአብርሃም ፡ ዘሮች ፡ ናቸው
2. ፍሬ. The oil seeds are crushed by a large press. የዘይት ፡ ፍሬዎች ፡ ባንድ ፡ ትልቅ ፡ መጭመቂያ ፡ ይጨመቃሉ

**seed grain** ዘር
The farmers have very little seed grain this year. ዘንድሮ ፡ ገበሬዎች ፡ ያላቸው ፡ ዘር ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ነው

**seedling** ቡቃያ
The seedlings must be protected from frost. ቡቃያዎች ፡ ከውርጭ ፡ መጠበቅ ፡ አለባቸው

**seedy**
*A pomegranate is a seedy fruit. ሮማን ፡ ውስጡ ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ አለው

**seeing** (n.) ዓይን
His seeing is poor due to a bad diet. የተሟላ ፡ ምግብ ፡ ካለማግኘቱ ፡ የተነሣ ፡ ዓይኑ ፡ ደክሟል

**seek** (sought)
1. ፈለገ. We sought shelter from the rain. ከዝናቡ ፡ የምንጠለልበት ፡ ስፍራ ፡ ፈለግን
They sought to kill him. ሊገድሉት ፡ ፈለጉ
2. ለማግኘት ፡ ፈለገ. He sought wealth by engaging in smuggling. በኮንትሮባንድ ፡ ሥራ ፡ ሀብት ፡ ለማግኘት ፡ ፈለገ
3. ጠየቀ. He sought aid for his injured friend. ለተጐዳው ፡ ጓደኛው ፡ እርዳታ ፡ ጠየቀ
4. ሞከረ. He sought to explain it by means of an allegory. በምሳሌ ፡ አድርጎ ፡ ለመግለጽ ፡ ሞከረ
[See also 'refuge, vengeance']

**seem**
1. መሰለ. He seems bored. የሰለቸው ፡ ይመስላል
It would seem that he overstayed his leave. እርሱ ፡ የተሰጠውን ፡ የፈቃድ ፡ ጊዜ ፡ ያሳለፈ ፡ ይመስላል
2. መሰለ(ው). I shall act as it seems best. ጥሩ ፡ የመሰለኝን ፡ እሠራለሁ
I seem to be interrupting your conversation. ንግግራችሁን ፡ አቋረጥኩ ፡ መሰለኝ
That seems peculiar to me. ለኔ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ይመስለኛል
I can't seem to stop smoking. ሲጋራ ፡ የምተው ፡ አይመስለኝም
3. ታየ. Things are not always as they seem. ማንኛቸውም ፡ ነገር ፡ እንደሚታየው ፡ አይደለም

**seeming**
*In spite of his seeming friendship, he offered me no help. ወዳጅ ፡ ቢመስልም ፡ ምንም ፡ እርዳታ ፡ አላደረገልኝም
*His being born abroad was a seeming advantage when he entered the diplomatic service. ውጭ ፡ አገር ፡ መወለዱ ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ አባል ፡ ሲሆን ፡ የሚረዳው ፡ መስሎ ፡ ታይቶ ፡ ነበር

**seemingly**
1. ይመስላል. Seemingly, he has his servants do all the work. ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ አሽከሮቹን ፡ የሚያሠራቸው ፡ ይመስላል

2. ለዓይን - - - ይመስላል. This hill is, seemingly, the highest. ለዓይን ፡ ይህ ፡ ኮረብታ ፡ ከፍተኛ ው ፡ ይመስላል

**seemly** ተገቢ
It is seemly to wear black at a funeral. ቀብር ፡ ላይ ፡ ጥቁር ፡ ልብስ ፡ መልበስ ፡ ተገቢ ፡ ነው

**be seemly** ተገባ
It isn't seemly to praise oneself. ራስን ፡ ማ መስገን ፡ አይገባም

**seep** ገባ
The water seeped through his shoe. ጫማው ፡ ውስጥ ፡ ውኃ ፡ ገባ

**seepage** የዘለቀ ፡ ውኃ
Seepage from the sewer has polluted the river. ከቆሻሻ ፡ መውረጃው ፡ የዘለቀው ፡ ውኃ ፡ ወንዙን ፡ በክሎታል

**seer** ትንቢተኛ
The seer foretold a long war. ትንቢተኛው ፡ ረ ጅም ፡ ጦርነት ፡ እንደሚነሣ ፡ ተነበየ

**seesaw** (v.)
1. ሚዛን ፡ ተጫወተ. Children love to seesaw in the playground. ልጆች ፡ በጨዋታው ፡ ሜ ዳ ፡ ላይ ፡ ሚዛን ፡ መጫወት ፡ ይወዳሉ
2. አወላወለ. He seesawed between the two alternatives. እርሱ ፡ በሁለት ፡ አማራጭ ፡ መሀ ል ፡ አወላወለ

**seesaw** (n.) ሚዛን
The children played on the seesaw. ልጆቹ ፡ ሚ ዛን ፡ ተጫወቱ

**seethe**
1. ጨሰ. Outwardly he was calm, but inwardly he was seething with rage. ላይ ፡ ላዩን ፡ የረጋ ፡ ነው ፤ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ግን ፡ በንዴት ፡ ጨሶ ፡ ነበር
2. ተፋፋመ. Many countries seethe with discontent. ብዙ ፡ አገሮች ፡ በሕዝባዊ ፡ ቅሬታ ፡ ተፋፍመዋል
3. አረፋ ፡ አወጣ. Water seethed under the falls. ውኃው ፡ በፏፏቴው ፡ ሥር ፡ አረፋ ፡ አወጣ

**seething** አረፋ ፡ የሞላበት
The seething waters overturned the light boat. አረፋ ፡ የሞላበት ፡ ውኃ ፡ ትንሿን ፡ ጀልባ ፡ እየ ገላበጠ ፡ ይዟት ፡ ሄደ

**segment**
1. ክፋይ. He ate a segment of an orange. እርሱ ፡ ያንድ ፡ ብርቱካን ፡ ክፋይ ፡ በላ
2. የአካል ፡ ክፍል. The segments of an earthworm are very tiny. የቅምቡርስ ፡ የአካል ፡ ክፍሎ ች ፡ ጥቃቅኖች ፡ ናቸው

**be divided into segments** ተከፋፈለ
Bamboo is divided into segments by the joints. ቀርቀሃ ፡ ባንጓ ፡ ባንጓ ፡ የተከፋፈለ ፡ ነው

**(be) segmented** ተከፋፈለ
The body of the caterpillar is segmented. ያባ ፡ ጨጓሬ ፡ አካል ፡ የተከፋፈለ ፡ ነው

**segregate**
1. ለብቻ ፡ አደረገ. The prison segregated the hardened criminals. እስር ፡ ቤቱ ፡ የቆዩትን ፡ ወ ንጀለኞች ፡ ለብቻ ፡ አደረጋቸው
2. ገለልተኛ ፡ ቦታ ፡ አስተኛ. The doctor segregated the sick child. ሐኪሙ ፡ የታመመውን ፡ ልጅ ፡ ገለልተኛ ፡ ቦታ ፡ አስተኛው
3. ለየብቻ ፡ መደበ. Our school segregates the sexes in order to promote discipline. ሥርዓትን ፡ ለማስከበር ፡ ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ወንዶችን ና ፡ ሴቶችን ፡ ለየብቻ ፡ ይመድባል

**be segregated** ተለየ
The women were segregated from the men during the prayers. በጸሎቱ ፡ ጊዜ ፡ ሴቶቹ ፡ ከወንዶቹ ፡ ተለይተው ፡ ነበር

**segregation** ገለል ፡ ማድረግ
Segregation of those having infectious diseases is necessary. በጀርም ፡ የሚይዝ ፡ በሽታ ፡ ያላቸ ውን ፡ ገለል ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**seize**
1. ያዘ (ተያዘ). She seized his arm. ክንዱን ፡ ያዘ ችው
He seized her around the middle. ወገቧን ፡ አቅ ፎ ፡ ያዛት
His goods were seized for payment of his debt. እቃው ፡ ለዕዳው ፡ መክፈያ ፡ ተይዞበት ፡ ነበር
2. ጨብጦ ፡ ያዘ. He seized the rope with both his hands. ገመዱን ፡ በሁለቱም ፡ እጁ ፡ ጨብጦ ፡ ያዘ
3. ተረዳ. He was quick to seize the suggestion. የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ ፈጥኖ ፡ ተረዳ
*She will seize upon any excuse. ማንኛቸውም ፡ ምክንያት ፡ ይሆናታል

**seize by the collar** አንገትን ፡ አንቆ ፡ ያዘው
The policeman seized the thief by the collar. ፖሊሱ ፡ ሌባውን ፡ አንገቱን ፡ አንቆ ፡ ያዘው

**seize on** ያዘ
The drowning man seized on the rope. ሊሰም ጥ ፡ የነበረው ፡ ሰውዬ ፡ ገመዱን ፡ ያዘ

**seize the opportunity** አጋጣሚ ፡ ተጠቀመበት
If I don't seize this opportunity, it may be too late. ይህን ፡ አጋጣሚ ፡ ካልተጠቀምኩበት ፡ ያመልጠኝ ፡ ይሆናል

**seizure** መያዝ
The seizure of two robbers was reported in the paper. የሁለት ፡ ቀማኞች ፡ መያዝ ፡ በጋዜጣው ፡ ተገለጸ

**seizure of coughing**
*He had a sudden seizure of coughing. ድንገት ፡ ያስለው ፡ ጀመር

**seldom**
1. እምብዛም + (negative verb). This plant seldom grows in the desert. ይህ ፡ ዕፅ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ እምብዛም ፡ አይበቅልም
2. ብዙ ፡ ጊዜ + (negative verb). I've seldom seen such large oranges. እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ትልልቅ ፡ ብርቱካኖች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አላየሁም

**select** (v.) መረጠ
Have you selected any book yet? እስካሁን ፡ የመረጥከው ፡ መጽሐፍ ፡ አለ ?

**select** (adj.)
1. የተመረጠ. The film was shown to a select audience. ፊልሙ ፡ የታየው ፡ ለተመረጡ ፡ ተመልካቾች ፡ ነው
2. ምርጥ. They read select passages from his book. ከርሱ ፡ መጽሐፍ ፡ ምርጥ ፡ ምንባቦችን ፡ አነበቡ
*This is a select club. ይህ ፡ ክበብ ፡ ለተወሰኑ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ነው

**selection** ምርጫ
Selection of candidates requires careful screening. የእጩዎች ፡ ምርጫ ፡ በጥንቃቄ ፡ ማጣራት ፡ አለበት
*He read some selections of early English poetry. የጥንት ፡ እንግሊዝኛ ፡ ግጥሞችን ፡ መርጦ ፡ አነበበ

**big selection of** በያይነቱ ፡ ብዙ
We have a big selection of shirts. በያይነቱ ፡ ብዙ ፡ ሸሚዞች ፡ አሉን
[See also 'wide']

**selective** መራጭ
He is a selective reader. መራጭ ፡ አንባቢ ፡ ነው

**self** ራስ
It is a good thing to think more of others and less of self. ስለ ፡ ሌሎች ፡ በለጥ ፡ ስለ ፡ ራስ ፡ አነስ ፡ አድርጎ ፡ ማሰብ ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ነው

**his whole self**
*His whole self revolted at the idea. ሐሳቡን ፡ ያልተቀበለው ፡ በመላው ፡ መንፈሱ ፡ ነው

**self-assurance** በራሱ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ መተማመን
The ease of his manner shows his self-assurance. ረጋ ፡ ያለው ፡ አኳኋኑ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መተማመን ፡ ያሳያል

**self-centered** ራሱን ፡ ወዳድ
He is too self-centered to be good company. በጣም ፡ ራሱን ፡ ወዳድ ፡ ስለሆነ ፡ ጥሩ ፡ ጓደኛ ፡ አይሆንም

**self-confidence** በራሱ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ እምነት
His self-confidence was shaken by his failure to get a scholarship. የነጻ ፡ ትምህርት ፡ ሳያገኝ ፡ መቅረቱ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ እምነት ፡ ቀነሰበት

**self-confident**
He is very self-confident. በራሱ ፡ በጣም ፡ የሚተማመን ፡ ሰው ፡ ነው

**(be) self-conscious** አፈረ ፡ አለ
She was self-conscious at her first dance. በመጀመሪያ ፡ ዳንሷ ፡ ላይ ፡ አፈር ፡ ብላ ፡ ነበር

**self-control** ራሱን ፡ የመቈጣጠር ፡ ኀይል
He shows a lot of self-control. ራሱን ፡ በጣም ፡ የመቈጣጠር ፡ ኀይል ፡ አለው

**self-defense**
*He killed him in self-defense. ባልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይነት ፡ ገደለው

**self-determination** የራሱን ፡ ዕድል ፡ በራሱ ፡ መወሰን
The country demanded the right of self-determination. አገሪቱ ፡ የራሷን ፡ ዕድል ፡ በራሷ ፡ የመወሰን ፡ መብት ፡ ጠየቀች

**self-educated**
He is a self-educated man. ራሱን ፡ በራሱ ፡ ያስተማረ ፡ ሰው ፡ ነው

**self-employed** በግል ፡ ሥራ ፡ የሚተዳደር
He is self-employed and can take a vacation whenever he likes. በግል ፡ ሥራ ፡ የሚተዳደር ፡ ስለሆነ ፡ በፈቀደው ፡ ጊዜ ፡ ዕረፍት ፡ ሊወስድ ፡ ይችላል

**self-evident** ራሱ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ
It is self-evident that this was an accident. ይህ ፡ በስሕተት ፡ የተደረገ ፡ ለመሆኑ ፡ ራሱ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ነው

**self-explanatory** ራሱ ፡ ግልጽ
The matter is self-explanatory. ነገሩ ፡ ራሱ ፡ ግልጽ ፡ ነው

**self-interest** የግል ፡ ጥቅም
His motive is self-interest, not love of humanity. ዋናው ፡ ዓላማው ፡ የግል ፡ ጥቅሙ ፡ እንጂ ፡ ሰብአዊ ፡ ርኅራኄ ፡ አይደለም

**selfish** ራሱን ፡ ወዳድ ፤ ለኔ ፡ ብቻ ፡ የሚል
That selfish girl looks out for herself exclusively. ራሷን ፡ ወዳድ ፡ ልጃገረድ ፡ ለራሷ ፡ ብቻ ፡ ታስባለች
I hate people who are selfish. ለኔ ፡ ብቻ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ አልወድም

**selfishness** ራሱን ፡ መውደድ
Selfishness is an incitement to crime. ራሱን ፡ መውደድ ፡ ወንጀልን ፡ ወደ ፡ መፈጸም ፡ ይገፋፋል

**self-made**
*He is a self-made man. በራሱ ፡ ጥረት ፡ የከበረ ፡ ሰው ፡ ነው

**self-possessed, remain ~** ራሱን ፡ ለመቈጣጠር ፡ ቻለ
She remained self-possessed despite the misfortune that befell her. መከራ ፡ ቢደርስባትም ፡ ራሷን ፡ ለመቈጣጠር ፡ ቻለች

**self-preservation** ራስን ፡ ለማዳን
If it comes to self-preservation, murder may easily be committed. ራስን ፡ ለማዳን ፡ ሲያውቁ ፡ የግድያ ፡ ወንጀል ፡ በቀላሉ ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል

**self-reliance** በራሱ ፡ ሐሳብ ፡ የመመካት ፡ ችሎታ
His self-reliance enabled him to survive when he was lost in the desert. በራሱ ፡ ሐሳብ ፡ የመመካት ፡ ችሎታው ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በጠፋ ፡ ጊዜ ፡ እንዲድን ፡ ረዳው

**self-respect, have ~** ራሱን ፡ አከበረ
He has too much self-respect to tell a lie. ራሱን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ስለሚያከብር ፡ ውሸት ፡ መናገር ፡ አይሆንለትም

**self-restraint** ራስን ፡ መግዛት
Self-restraint is necessary for priests. ለቄሶች ፡ ራስን ፡ መግዛት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**self-sacrificing**
*His wife is too self-sacrificing for her own good. ሚስቱ ፡ ለሌሎች ፡ ጥቅም ፡ ስትል ፡ ራሷን ፡ ትጐዳለች

**self-service**
*There is only self-service in this cafeteria. እዚህ ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ምግቡን ፡ መውሰድ ፡ ያለበት ፡ ተመጋቢው ፡ ራሱ ፡ ነው

**self-sufficient**
He's quite self-sufficient. ራሱን ፡ የቻለ ፡ ሰው ፡ ነው

**self-supporting**
Are you self-supporting? ራስክን ፡ የቻልክ ፡ ሰው ፡ ነህ ?

**self-willed**
She is very self-willed. በራሷ ፡ ሐሳብ ፡ የምትመራ ፡ ነች

**sell** (sold), vt.
1. ሸጠ. This store sells radios. ይህ ፡ መደብር ፡ ሬዲዮ ፡ ይሸጣል
2. እንዲሸጥ ፡ ረዳ. Television sells many products. ቴሌቪዥን ፡ ብዙ ፡ እቃዎች ፡ እንዲሸጡ ፡ ይረዳል
3. አነሣ(ለት). It's not the price, but the quality that sells our goods. ገበያችንን ፡ የሚያነሣልን ፡ የዋጋው ፡ መርከስ ፡ ሳይሆን ፡ የእቃው ፡ ተመራጭነት ፡ ነው
*He couldn't sell his idea to the administration. አስተዳደሩ ፡ ሐሳቡን ፡ እንዲቀበለው ፡ ማሳመን ፡ ተሳነው

**sell** (vi.) ተሸጠ
This suit sells for thirty dollars. ይህ ፡ ልብስ ፡ በሠላሳ ፡ ብር ፡ ይሸጣል

**sell out**
1. ሸጠ. He sold out his share and retired. ድርሻውን ፡ ከሸጠ ፡ በኋላ ፡ ሥራውን ፡ አቆመ
2. ከድቶ ፡ አደረ. During the Second World War, some Frenchmen sold out to the Germans. በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ አንዳንድ ፡ ፈረንሳዮች ፡ ከድተው ፡ ለጀርመን ፡ አድረው ፡ ነበር

**be sold on** ሐሳቡን ፡ አመነበት
Are Ethiopian farmers sold on forming cooperatives? ኢትዮጵያውያን ፡ ገበሬዎች ፡ የመረዳጃ ፡ ማኅበሮችን ፡ በማቋቋም ፡ ሐሳብ ፡ አምነውበታል ?

**be sold out** ሸጦ ፡ ጨረሰ ፤ ሸቀጡ ፡ አለቀበት
Sorry, we're all sold out. አዝናለሁ ፤ ሸጠን ፡ ጨርሰናል ፡ (ሸቀጡ ፡ አልቆብናል)

**seller** ሻጭ
The seller must not defraud the buyer. ሻጭ ፡ ገዢን ፡ ማጭበርበር ፡ የለበትም

**best seller** በገበያ ፡ ዋና ፡ ተፈላጊ
This book is a best seller. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በገበያ ፡ ዋና ፡ ተፈላጊ ፡ ነው
[See also 'ticket']

**sellout**
*The play was a sellout. የጨዋታው ፡ ቲኬቶች ፡ ተሸጠው ፡ አልቀዋል
*Czechoslovakia considered the Munich Pact a sellout of her interests. የሙኒክን ፡ ስምምነት ፡ ቼኮስሎቫኪያ ፡ የራሷን ፡ ጥቅም ፡ የሚያስቀር ፡ አድርጋ ፡ ቈጠረችው

**semblance**
*The party lost all semblance of order. ግብዣው ፡ ቅጥ ፡ የሌለው ፡ ነበር
*His story had the semblance of truth, but was really false. ታሪኩ ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ እውነት ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ ውሸት ፡ ነው

**semester** ወቅት ፤ የትምህርት ፡ ዘመን ፡ አጋማሽ
The school year has two semesters. የትምህርቱ ፡ ዓመት ፡ ሁለት ፡ ወቅት ፡ (የትምህርት ፡ ዘመን ፡ አጋማሽ) ፡ አለው

**semiannual** (= adv.) በየመንፈቁ
He pays me a semiannual visit. በየመንፈቁ ፡ እየመጣ ፡ ይጠይቀኛል

**semicircle** የክበብ ፡ አጋማሽ
He drew a semicircle in the sand. በአሸዋው ፡ ላይ ፡ የክበብ ፡ አጋማሽ ፡ ሠራ

**semicolon** ነጠላ ፡ ሰረዝ
Put a semicolon before 'nevertheless'. የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ከሚለው ፡ ቃል ፡ በፊት ፡ ነጠላ ፡ ሰረዝ ፡ አድርግበት

**semifinals** የማጣሪያ ፡ ግጥሚያዎች
The semifinals will be held next week. የማጣሪያ ፡ ግጥሚያዎቹ ፡ በሚቀጥለው ፡ ሳምንት ፡ ይደረጋሉ

**seminar** ትምህርታዊ ፡ ጉባኤ
He attended a seminar in economics. በሀብት ፡ ምጣኔ ፡ ትምህርታዊ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ተካፍሏል

**seminary** መንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት
Priests get their education in a seminary. ቄሶች ፡ በመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይሠለጥናሉ

**semiofficial** በከፊል ፡ ኦፊሴላዊ
The report is semiofficial. ሪፖርቱ ፡ በከፊል ፡ ኦፊሴላዊ ፡ ነው

**Semite** ሴማዊ
The Semites inhabited Arabia. ሴማውያን ፡ ዓረብ ፡ አገር ፡ ይኖሩ ፡ ነበር

**Semitic** የሴም
Geez is a Semitic language. ግዕዝ ፡ የሴም ፡ ቋንቋ ፡ ነው

**semitropical** መካከለኛ ፡ ሞቃት
Florida has a semitropical climate. ፍሎሪዳ ፡ መካከለኛ ፡ ሞቃት ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፡ አላት

**semiweekly** (n.)
*They publish a semiweekly paper. በሳምንት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ እየታተመ ፡ የሚወጣ ፡ መጽሔት ፡ አላቸው

**senate** የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት
The senate passed the bill. የሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ አጸደቀው

**senator** የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባል
An American senator visited Ethiopia. አንድ ፡ የአሜሪካን ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባል ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጐበኘ

**send** (sent)
1. ላከ. Where can I send a telegram? ቴሌግራም ፡ ከየት ፡ መላክ ፡ እችላለሁ ?
2. አቀረበ. He sends his regards. ሰላምታ ፡ ያቀርባል
3. እንዲሄድ ፡ አዘዘ. The President sent troops to Africa. ፕሬዚዳንቱ ፡ ወታደሮች ፡ ወደ ፡ አፍሪካ ፡ እንዲሄዱ ፡ አዘዘ
4. ተፋ. The volcano sent clouds of smoke into the air. እሳተ ፡ ገሞራው ፡ ጢስ ፡ በብዛት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተፋ

**send around**
*Please send these papers around! እነዚህን ፡ ወረቀቶች ፡ በየክፍሉ ፡ እንዲዞሩ ፡ አድርግ

**send away for** አስመጣ
When we lived in the country, we had to send away for many things we needed. ገጠር ፡ በነበርንበት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ የሚያስፈልጉንን ፡ ነገሮች ፡ ማስመጣት ፡ ነበረብን

**send (him) away!** ሂድ ፡ በለው
Send him away! I don't need anything. ሂድ ፡ በለው ፤ ምንም ፡ የሚያስፈልገኝ ፡ ነገር ፡ የለም

**send back** መልሶ ፡ ላከ
Don't forget to send the book back! መጽሐፉን ፡ መልሰህ ፡ መላክ ፡ እንዳትረሳ

**send for**
1. ጠራ. Have you sent for the doctor? ሐኪም ፡ ጠርተሃል ?

2. አስወስዶ. Please keep my books until I send for them. እባክህን ፡ መጽሐፎቼን ፡ እስክ ስወስዳቸው ፡ ድረስ ፡ አንተ ፡ ጋ ፡ አቆይልኝ

**send forth** ላከ
Jesus sent his disciples forth into the world. ኢየሱስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሮቹን ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ላካቸው

**send forth leaves** ለመለመ
The tree sent forth its leaves. ዛፉ ፡ ለመለመ

**send in**
1. አቀረበ. The public sent in many complaints about the program. ሕዝቡ ፡ ስለ ፡ ፕሮግራሙ ፡ ብዙ ፡ ስሞታዎች ፡ አቀረበ
2. አስገባ. Send him in! The boss can see him. አስገባው ፤ አለቃው ፡ ሊያነጋግረው ፡ ይችላል

**send off**
1. ላከ. When did he send the package off? ጥቅሉን ፡ መቼ ፡ ላከው ?
2. ሸኘ. A large crowd went to the airport to send him off. ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አውሮፕላን ፡ ማቢያ ፡ ተገኝቶ ፡ ሸኘው

**send out**
1. ላከ. We sent our son out into the field to look for the lost cow. የጠፋችውን ፡ ላም ፡ እንዲፈልግ ፡ ልጃችንን ፡ ወደ ፡ መስክ ፡ ላክን
2. ለአጣቢ ፡ ሰጠ. We send our laundry out. ልብሳችንን ፡ ለአጣቢ ፡ እንሰጣለን
3. ፈነጠቀ. The sun sends out light and heat. ፀሐይ ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀት ፡ ትፈነጥቃለች

**send out for** አዘዘ
We sent out for some coffee. ቡና ፡ አዘናል
[See also 'bed, school, scurry, temper, word']

## (be) senile ጃጀ
He has become quite senile, and you can't rely on him. ስለጃጀ ፡ እምነት ፡ ልትጥልበት ፡ አትችልም

## senior (n.) ያራተኛ ፡ ዓመት ፡ ተማሪ
He is a senior in college. በኮሌጅ ፡ ያራተኛ ፡ ዓመት ፡ ተማሪ ፡ ነው

**be (one's) senior** በለጠ
Jim is his brother's senior by ten years. ጂም ፡ ወንድሙን ፡ በዐሥር ፡ ዓመት ፡ ይበልጠዋል

**senior** (adj.) የበላይነት ፡ ያለው
Who is the senior partner in the business? በንግዱ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ የበላይነት ፡ ያለው ፡ ሽርካ ፡ የትኛው ፡ ነው ?

## seniority
1. ያገልግሎት ፡ ዘመን. Promotion of officers is by seniority. የመኰንኖች ፡ የማዕረግ ፡ እድገት ፡ በገልግሎት ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው
2. መብለጥ. John felt that two years' seniority gave him the right to advise his brother. ጆን ፡ ከወንድሙ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ መብለጡ ፡ ወንድሙን ፡ ለመምከር ፡ የሚያስችለው ፡ መሆኑን ፡ ገመተ

## sensation
1. ስሜት. A sensation of hearing is caused in deaf persons by this drug. በዚህ ፡ መድኃኒት ፡ ደንቆሮ ፡ ሰዎች ፡ የማዳመጥ ፡ ስሜት ፡ እንዲኖራቸው ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል
2. የሕዝብ ፡ ስሜት. His speech created a sensation. ንግግሩ ፡ የሕዝቡን ፡ ስሜት ፡ ቀሰቀሰ
3. ልዩ ፡ ስሜት. President Johnson's announcement that he would not run for reelection created a sensation. የፕሬዚዳንት ፡ ጆንሰን ፡ እንደገና ፡ ለውድድር ፡ አልገባም ፡ ብሎ ፡ ማስታወቅ ፡ ልዩ ፡ ስሜት ፡ ፈጠረ

**have a dizzy sensation** በጣም ፡ አዞረው
I had a dizzy sensation when I got up this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ ስነሣ ፡ በጣም ፡ አዞረኝ

**lose sensation in** ደነዘዘ
+I lost all sensation in my leg. እግሬ ፡ በፍጹም ፡ ደንዝዟል

## sensational
1. ስሜት ፡ የሚቀሰቅስ. His sensational novel about the nobility was soon banned. ስለ ፡ መኳንንት ፡ የተጻፈው ፡ ስሜት ፡ የሚቀሰቅስ ፡ መጽሐፉ ፡ ያኔውኑ ፡ ተከለከለ
2. የወጣለት. He is a sensational football player. የወጣለት ፡ የእግር ፡ ኳስ ፡ ተጫዋች ፡ ነው

## sense (v.)
1. ተሰማ(ው). +He sensed that there was someone standing behind him. ከኋላው ፡ ሰው ፡ መኖሩ ፡ ተሰማው
2. ተረዳ(ው). +He quickly sensed the gravity of the situation. የሁኔታውን ፡ አስጊነት ፡ ወዲያው ፡ ተረዳው

## sense (n.)
1. ስሜት. Dogs have an acute sense of smell. ውሾች ፡ ኀይለኛ ፡ የማሽተት ፡ ስሜት ፡ አላቸው
2. ሕዋስ (pl. ሕዋሳት). Does man have five or six senses? የሰው ፡ ሕዋሳት ፡ አምስት ፡ ናቸው ፡ ስድስት ?
3. ችሎታ. He has an uncanny sense of hearing. በጣም ፡ ረቂቅ ፡ የሆነ ፡ የመስማት ፡ ችሎታ ፡ አለው
4. ትርጉም. The sense of the word is not clear. የቃሉ ፡ ትርጉም ፡ ግልጽ ፡ አይደለም

That doesn't make sense. ያ ፡ ምንም ፡ ትርጉም ፡ አይሰጥም
5. ጠቅላላ ፡ መንፈስ. The sense of the assembly was clear even before the vote. ድምፅ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ እንኳ ፡ የጉባኤው ፡ ጠቅላላ ፡ መንፈስ ፡ ግልጽ ፡ ነበር
*Duty well done brings a sense of pleasure. በሚገባ ፡ የተከናወነ ፡ ተግባር ፡ ደስ ፡ ያሰኛል
*The snake frightened her out of her senses. እባቡ ፡ ብርክ ፡ አስያዛት

**come to your senses!** አትበድ
Come to your senses! You can't go to America on only $50. አትበድ ፤ ኀምሳ ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ ይዘህ ፡ አሜሪካን ፡ አገር ፡ ለመሄድ ፡ አትችልም

**common sense** የተፈጥሮ ፡ ዕውቀት
Common sense would have prevented the accident. የተፈጥሮ ፡ ዕውቀት ፡ አደጋውን ፡ ለማስቀረት ፡ ይችል ፡ ነበር

**(have the) good sense** ጥሩ ፡ አደረገ
He had the good sense not to mix in their business. ሥራቸው ፡ ውስጥ ፡ አለመግባቱ ፡ ጥሩ ፡ አድርጓል

**have sense enough** አሰበ
I hope he has sense enough to take a taxi. አስቦ ፡ በታክሲ ፡ እንደሚሄድ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ

**in a sense** ባንድ ፡ በኩል
That's true, in a sense. ባንድ ፡ በኩል ፡ እውነት ፡ ነው

**in every sense of the word** በየትኛውም ፡ አንጻር
He is a gentleman in every sense of the word. በየትኛውም ፡ አንጻር ፡ እሱ ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ነው

**(a) lot of sense** ብዙ ፡ ቁም ፡ ነገር
There's a lot of sense in what he says. በሚናገረው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አለበት

**make sense of** ገባ(ው)
Can you make sense of what this author says? ደራሲው ፡ የሚለው ፡ ነገር ፡ ይገባሃል ?

**(not) make sense** የማይመስል ፡ ነገር ፡ ነው
That doesn't make sense — a boy of two stealing money. የሁለት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ገንዘብ ፡ ይሰርቃል ፡ ማለት ፡ የማይመስል ፡ ነገር ፡ ነው

**no sense in**
There's no sense in doing that. ይህንን ፡ መሥራቱ ፡ ዋጋም ፡ የለው

**(be) out of one's senses** አእምሮውን ፡ ሳተ
I must have been out of my senses. አእምሮዬን ፡ ስቼ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነዋ

**(a man in his) right senses** ጤነኛ ፡ ሰው
A man in his right senses wouldn't do that. ጤነኛ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ አይሠራም

**talk sense**
Now you're talking sense! አሁን ፡ ገና ፡ የሚመስል ፡ ነገር ፡ ተናገርክ
[See also 'honor, humor']

**senseless** (adj.) የማይረባ
Your senseless argument does not convince me. የማይረባ ፡ ክርክርህ ፡ ሐሳቤን ፡ አያስለውጠኝም

**senseless** (adv.) ነፍሱን ፡ ስቶ
She lay senseless on the floor. ነፍሷን ፡ ስታ ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ተዘረረች

**be senseless** ሞኝነት ፡ ነው
It would be senseless to go out in this rain. በዚህ ፡ በዝናብ ፡ መሄድ ፡ ሞኝነት ፡ ነው

**knock one senseless** ነፍሱን ፡ አሳተ
A hard blow on the head knocked him senseless. ራሱ ፡ ላይ ፡ የመታው ፡ ዱላ ፡ ነፍሱን ፡ አሳተው

**sensibility**
1. ስሜት. She has an unusual sensibility for colors. ለቀለማት ፡ ያልተለመደ ፡ ስሜት ፡ አላት
2. የስሜት ፡ ኀይል. Some drugs lessen a person's sensibilities. አንዳንድ ፡ መድኃኒቶች ፡ የሰውን ፡ የስሜት ፡ ኀይል ፡ ይቀንሳሉ
*That remark wounded her sensibilities. ትችቱ ፡ ቅር ፡ አሰኛት

**sensible**
1. አስተዋይ. She's a very sensible woman. በጣም ፡ አስተዋይ ፡ ሴት ፡ ነች
2. የሚስማማ. Try to wear more sensible clothing in this heat. ለዚህ ፡ ሙቀት ፡ የሚስማማ ፡ ልብስ ፡ ልበስ
3. ጠቃሚ. My friend gave me very sensible advice. ጓደኛዬ ፡ ጠቃሚ ፡ ምክር ፡ ሰጠኝ
4. ጥሩ ፡ መስሎ ፡ የታየ. The only sensible course for me was to go home. ጥሩ ፡ መስሎ ፡ የታየኝ ፡ ዘዴ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ ብቻ ፡ ነበር
*That was sensible of you. ጥሩ ፡ አድርገሃል

**be sensible of** ተሰማ(ው)
+I am sensible of your kindness. ደግነትህ ፡ ይሰማኛል

**sensitive** ቁጡ
She has a sensitive skin. ቆዳዋ ፡ ቁጡ ፡ ነው

**be sensitive** አዘነ
He was very sensitive about his failure in life. ኑሮው ፡ ስላልተሳካለት ፡ በጣም ፡ አዝኗል

**be sensitive to**
1. ተሰማ(ው). A dog's ears are sensitive to high tones we cannot hear. እኛ ፡ ልንሰማው ፡ የማንችለውን ፡ ከፍተኛ ፡ ድምፅ ፡ የውሻ ፡ ጆሮ ፡ ይሰማዋል
2. ቶሎ ፡ ተሰማ(ው). +I'm sensitive to cold. ብርድ ፡ ቶሎ ፡ ይሰማኛል
+He's very sensitive to criticism. ነቀፌታ ፡ ቶሎ ፡ ይሰማዋል

**sensual** የሥጋ
He is given to sensual but not intellectual pleasures. የአእምሮውን ፡ ሳይሆን ፡ የሥጋ ፡ ፍላጎቱን ፡ ለማርካት ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ነው

**sensuous** ሕዋሳትን ፡ የሚያነሣሣ
This sensuous music appeals to women. ይህ ፡ ሕዋሳትን ፡ የሚያነሣሣ ፡ ሙዚቃ ፡ ሴቶችን ፡ ይማርካል

**sent,** see **send**

**sentence** (v.) ፈረደ(በት)
The judge sentenced him to five years imprisonment. ዳኛው ፡ ያምስት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ፈረደበት

**sentence** (n.)
1. ዓረፍተ ፡ ነገር. The verb comes at the end of the Amharic sentence. ባማርኛ ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ግሱ ፡ የሚመጣው ፡ መጨረሻው ፡ ላይ ፡ ነው
2. ፍርድ. The sentence of the court was three years' imprisonment. የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርድ ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ነበር
3. ቅጣት. She got off with a light sentence. በቀላል ፡ ቅጣት ፡ ተገላገለች

**death sentence** የሞት ፡ ፍርድ
The Emperor commuted his death sentence to life imprisonment. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሞት ፡ ፍርዱን ፡ ወደ ፡ ዕድሜ ፡ ይፍታህ ፡ አሻሻሉለት

**pronounce sentence** ፈረደ ፤ ፍርድ ፡ ሰጠ
The judge has already pronounced sentence. ዳኛው ፡ ገና ፡ ዱሮ ፡ ፈርዷል ፡ (ፍርድ ፡ ሰጥቷል)

**serve (one's) sentence** ታሰረ
He served his sentence at the state prison. የታሰረው ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ነበር

**sentiment**
1. ስሜት. Should sentiment be controlled by reason? ስሜት ፡ ባስተሳሰብ ፡ ይገታ ?
2. አስተያየት. We must find out the sentiment of the people. የሕዝቡን ፡ አስተያየት ፡ ማወቅ ፡ አለብን
3. ይሉኝታ. There is no place for sentiment in business. በንግድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ይሉኝታ ፡ የለም

**sentimental**
1. ስሜት ፡ የሚነካ. He reads sentimental poetry. ስሜት ፡ የሚነካ ፡ ግጥም ፡ ያነባል
2. ቡቡ. He is so sentimental that sad stories bring tears to his eyes. በጣም ፡ ቡቡ ፡ ስለሆነ ፡ አሳዛኝ ፡ ታሪኮች ፡ እንባ ፡ ያመጡበታል

**for sentimental reasons** ለግል ፡ ስሜቱ
I'll save this picture for sentimental reasons. ይህንን ፡ ሥዕል ፡ ለግል ፡ ስሜቴ ፡ አስቀምጠዋለሁ

**sentinel**
1. ዘብ. A sentinel stands outside the military camp. በጦሩ ፡ ሰፈር ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ዘብ ፡ ቆሟል
2. ክብር ፡ ዘበኛ. A sentinel stands outside the palace gates. አንድ ፡ ክብር ፡ ዘበኛ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በር ፡ ላይ ፡ ቆሟል

**sentry** (sentries) ዘብ
The sentry wouldn't let me pass. ዘቡ ፡ አላስገባ ፡ አለኝ

**stand sentry** ጠበቀ
We stood sentry over the sleeper. የተኛውን ፡ ሰውዬ ፡ ጠበቅነው

**separate** (vt.)
1. ገላገለ. I could hardly separate those two. እነዚህን ፡ ሁለቱን ፡ መገላገል ፡ በጣም ፡ አዳግቶኝ ፡ ነበር
2. ከፈለ. Separate the group into five sections! ጓዱን ፡ አምስት ፡ ቦታ ፡ ክፈለው

**separate** (vi.) ተለያየ
We talked until midnight and then separated. እስከ ፡ እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ስንጫወት ፡ ቆይተን ፡ ተለያየን

**be separated** ተለያየ
My parents are separated. ወላጆቼ ፡ ተለያይተዋል

**separate** (adj.) የተለየ
The garage is separate from the house. ጋራዡ ፡ ከቤቱ ፡ የተለየ ፡ ነው
The President has powers separate from those of Congress. ፕሬዚዳንቱ ፡ ከምክር ፡ ቤቱ ፡ የተለየ ፡ ሥልጣን ፡ አለው
*Could we have separate rooms? ለየራሳችን ፡ አንዳንድ ፡ ክፍል ፡ ልናገኝ ፡ እንችላለን ?

**separately** ለየብቻ ፤ ለየብቻው
Let's question each child separately! እያንዳንዱን ፡ ልጅ ፡ ለየብቻ ፡ እንጠይቀው

Can you buy each volume separately? እያንዳን
ዱን ፡ ቅጽ ፡ ለየብቻው ፡ መግዛት ፡ ይቻላል ?

**separation** መለየት ፤ መለያየት
Separation from his friends makes him sad.
ከጓደኞቹ ፡ መለየት ፡ ያሳዝነዋል
After a separation of twenty years, he scarcely
recognized his family. ከሃያ ፡ ዓመት ፡ መለያየት ፡
በኋላ ፡ ቤተሰቡን ፡ ማወቅ ፡ አቃተው

**September** መስከረም

**sepulcher** መቃብር
He is buried in a white marble sepulcher.
የተቀበረው ፡ ነጭ ፡ እብነ ፡ በረድ ፡ መቃብር ፡ ው
ስጥ ፡ ነው

**sequel** ተከታታይ
He wants to read the sequel to this story.
የዚህን ፡ ታሪክ ፡ ተከታታይ ፡ ለማንበብ ፡ ይፈልጋል

**be the sequel of** አስከተለ
+Famine has often been the sequel of war.
አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጦርነት ፡ ረኃብን ፡ ያስከትላል

**come as a sequel** አስከተለ
+Floods come as a sequel to heavy rains.
ከባድ ፡ ዝናም ፡ የውኃ ፡ መጥለቅለቅን ፡ ያስከትላል

**sequence**
1. ተከታታይነት. The sequence of events shows
that war was definitely planned. የድርጊቶች ፡ ተ
ከታታይነት ፡ ጦርነት ፡ በእርግጥ ፡ የታቀደ ፡ እን
ደነበረ ፡ ያሳያል
2. ተራ. Arrange the names in alphabetical
sequence! ስሞቹን ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ አስቀምጣቸው
*Put these items in their proper sequence!
እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ እንደ ፡ ቅደም ፡ ተከተላቸው ፡
አስገባ

**touch off a sequence of** አስከተለ
The fight touched off a sequence of events
which ended in bloodshed. ያምባጓሮው ፡ መዘ
ዝ ፡ ትልቅ ፡ የደም ፡ መፋሰስ ፡ አስከተለ

**sequester**
1. ወረሰ. The government sequestered enemy
property. መንግሥት ፡ የጠላትን ፡ ንብረት ፡ ወ
ረሰ
2. ዘረፈ. The soldiers sequestered food from
the people they conquered. ወታደሮቹ ፡ ካሸነፉ
ዋቸው ፡ ሰዎች ፡ ምግብ ፡ ዘረፉ

**sequester oneself** ተገልሎ ፡ ተቀመጠ
He sequestered himself in a lonely cabin.
ብቻውን ፡ በቆመ ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ ተገልሎ ፡ ተቀመጠ

**sequestered** (adj.)
1. የተከለለ. Madmen have to live in a
sequestered place. ያበዱ ፡ ሰዎች ፡ በተከለለ ፡ ቦ
ታ ፡ መኖር ፡ አለባቸው
2. (=adv.) ከሰው ፡ ተለይቶ. He leads a seques-
tered life. ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ ይኖራል

**sequestration**
*Sequestration of enemy goods took place
when the war broke out. ጦርነቱ ፡ በተነሣ ፡ ጊ
ዜ ፡ የጠላት ፡ እቃዎች ፡ ተወረሱ

**serene**
1. የጠራ. The serene sky had not a cloud in it.
የጠራው ፡ ሰማይ ፡ አንድም ፡ ደመና ፡ አልነበረበትም
2. ጸጥ ፡ ያለ. The serene sea gave no hint of
the approaching storm. ጸጥ ፡ ያለው ፡ ባሕር ፡ የ
መጣውን ፡ ማዕበል ፡ የሚያስታውቅ ፡ ምልክት ፡ አላ
ሳየም
*Pictures of Our Lady Mary show her with
a serene look on her face. የእመቤታችን ፡ የቅ
ድስት ፡ ማርያም ፡ ሥዕሎች ፡ ፊቷ ፡ በእርጋታ ፡
እንደተሞላ ፡ ያሳያሉ

**serenity** የመንፈስ ፡ እርጋታ
The noise did not disturb her serenity. ድምፁ ፡
የመንፈሷን ፡ እርጋታ ፡ አላወከውም

**serf** ገባር
The serfs were freed by order of the king.
ገባሮቹ ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ነጻ ፡ ወጡ

**sergeant** የኀምሳ ፡ አለቃ
The sergeant is in command of our platoon.
የኀምሳ ፡ አለቃው ፡ የኛን ፡ ጭፍራ ፡ ያዛል

**serial** (n.) ተከታታይ ፡ ታሪክ
The serial on the adventures of Tom Sawyer
was very popular. የቶም ፡ ሶየር ፡ የጀብዱ ፡ ሥ
ራዎች ፡ ተከታታይ ፡ ታሪክ ፡ በጣም ፡ የተወደደ ፡
ነበር

**serial** (adj.), ~ **number** የመለያ ፡ ቁጥር
We have to copy the serial numbers of the
money. የገንዘቡን ፡ የመለያ ፡ ቁጥር ፡ መገልበ
ጥ ፡ አለብን

**in serial form** በተከታታይ
The newspaper is printing the story in serial
form. ጋዜጣው ፡ ታሪኩን ፡ በተከታታይ ፡ በማውጣ
ት ፡ ላይ ፡ ነው

**in serial order** በቅደም ፡ ተከተል
List the numbers in serial order! ቁጥሮችን ፡ በ
ቅደም ፡ ተከተል ፡ ጻፋቸው

**series** ተራ

He wrote down the names of the students in an alphabetical series. የተማሪዎቹን ፡ ስም ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ ጻፈ

**series of**

1. ተከታታይ. Pliny the Younger wrote a series of biographies. ታናሹ ፡ ፕሊኒ ፡ ተከታታይ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኮች ፡ ጽፏል

2. (= adv.) በተከታታይ. He's going to give a series of five lectures. በተከታታይ ፡ አምስት ፡ ንግግር ፡ ሊያደርግ ፡ ነው

**serious**

1. ኰስታራ. He is a serious boy. ኰስታራ ፡ ልጅ ፡ ነው

2. ምራቁን ፡ የዋጠ ፡ ሰው. He is evidently serious as he has studied the subject several years. ትምህርቱን ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ያጠናው ፡ ስለሆነ ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ ምራቁን ፡ የዋጠ ፡ ሰው ፡ ነው

3. ትጉህ. This student is not serious; he just fools around. ይህ ፡ ተማሪ ፡ ትጉህ ፡ አይደለም ። እንዲያው ፡ ይንቀዋለላል

4. አሳሳቢ. The international situation is serious. የዓለም ፡ ሁኔታ ፡ አሳሳቢ ፡ ነው

5. አስጊ. The badly injured man was in serious condition. ክፉኛ ፡ የተጐዳው ፡ ሰው ፡ በአስጊ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነበር

6. ከባድ. That's a serious mistake. ያ ፡ ከባድ ፡ ስሕተት ፡ ነው

7. ከፍ ፡ ያለ. Serious difficulties may arise from the application of this law. ይህንን ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል

He has a serious interest in literature. በሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ፍላጎት ፡ አለው

8. ጠለቅ ፡ ያለ. I read only serious books. ጠለቅ ፡ ያሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ብቻ ፡ አነባለሁ

**be serious about** የምሩን ፡ ነው

Is he serious about wanting to help? ልርዳ ፡ ማለቱ ፡ የምሩን ፡ ነው ?

**have a serious manner** ኰስታራ ፡ ነው

That young man has a serious manner for his age. ያ ፡ ወጣት ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ዕድሜው ፡ ኰስታራ ፡ ነው

**seriously**

1. በጠና. She is seriously ill. በጠና ፡ ታማለች

2. በጣም. My belief in him was seriously shaken. በሱ ፡ ላይ ፡ ያለኝ ፡ እምነት ፡ በጣም ፡ ተቀንሷል

3. የምር. Don't take it so seriously! የምር ፡ አታድርገው

4. ከልብ. I'm seriously considering getting married. ለማግባት ፡ ከልብ ፡ በማሰብ ፡ ላይ ፡ ነኝ

**take seriously**

1. እንደ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ቈጠረ. I am indisposed to take his request seriously. ጥያቄውን ፡ እንደ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ለመቍጠር ፡ ዝንባሌ ፡ የለኝም

2. አጥብቆ ፡ ያዘ. She took the duties of motherhood seriously. የናትነቱን ፡ ተግባር ፡ አጥብቃ ፡ ያዘች

**seriousness**

1. አሳሳቢነት. We mustn't misjudge the seriousness of the situation. የሁኔታውን ፡ አሳሳቢነት ፡ ዝቅ ፡ አድርገን ፡ መገመት ፡ የለብንም

2. ከባድነት. He will be punished according to the seriousness of the crime. እንደ ፡ ወንጀሉ ፡ ከባድነት ፡ ይቀጣል

**sermon**

1. ስብከት. Our minister gave a good sermon on Sunday. እሑድ ፡ ለት ፡ የኛ ፡ ቄስ ፡ ጥሩ ፡ ስብከት ፡ አደረጉ

2. ምክር. After the guests left, the boy got a sermon on good manners from his father. እንግዶቹ ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ አባትዬው ፡ ለልጁ ፡ ስለ ፡ መልካም ፡ ሥርዓት ፡ ምክር ፡ ሰጠው

**serpent** እባብ

The serpent bit the boy. ልጁን ፡ እባብ ፡ ነደፈው

**serum** መድኃኒት

The serum for this disease is being sent to all the hospitals. የዚህ ፡ በሽታ ፡ መድኃኒት ፡ በየሐኪም ፡ ቤቱ ፡ እየተላከ ፡ ነው

**servant**

1. አሽከር. He engaged servants for three months. ለሦስት ፡ ወር ፡ አሽከር ፡ ቀጠረ

2. አገልጋይ. The judge should not forget that he is the servant of the people. ዳኛው ፡ የሕዝብ ፡ አገልጋይ ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ የለበትም

I am your humble servant. ቅን ፡ አገልጋይዎ ፡ ነኝ

**civil servant** የመንግሥት ፡ ሠራተኛ

Civil servants got a raise. የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የደሞዝ ፡ ጭማሪ ፡ አገኙ

**serve** (vt.)

1. አገለገለ. He served his country well. አገሩን ፡ በደንብ ፡ አገልግሏል

He served God as a humble priest. ተራ ፡ ቄስ ፡ ሆኖ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገለገለ

The old car served me all summer. አሮጌው ፡ መኪና ፡ በጋውን ፡ በሙሉ ፡ አገለገለኝ

He served the cause of peace. ለሰላም ፡ አገለገለ
2. አቀረበ. Shall I serve the drinks now?
መጠጡን ፡ አሁን ፡ ላቅርብ ?
The waiter served us quickly. አሳላፊው ፡ ቶሎ ፡
አቀረበልን
3. ሰጠ. He served him a summons to appear in court. ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርብ ፡ መጥሪያ ፡
ሰጠው
4. በቃ. One cake serves six persons. አንድ ፡ ኬ
ክ ፡ ለስድስት ፡ ሰው ፡ ይበቃል

**serve** (vi.)
1. አገለገለ. He served on the President's committee for a while. በፕሬዚዳንቱ ፡ ደርግ ፡
ውስጥ ፡ ለትንሽ ፡ ጊዜ ፡ አገልግሏል
The soldier served three years in the army.
ወታደሩ ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ ለሦስት ፡
ዓመት ፡ አገለገለ
My brother served two terms in the senate.
ወንድሜ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡
ቤት ፡ ውስጥ ፡ አገለገለ
This serves as a bed and as a chair. ይህ ፡ አልጋ
ም ፡ መቀመጫም ፡ ሆኖ ፡ ያገለግላል
2. በላ. Come early! We are serving at six.
በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ስለምንበላ ፡ ቀደም ፡ ብለህ ፡ ና
3. ታሰረ. He served six years for the robbery.
በስርቆት ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ታሰረ
*He's serving a four-year term in prison.
አራት ፡ ዓመት ፡ ተፈርዶበት ፡ ታስሯል
*That serves you right! ይገባሃል

**be served**
1. ቀረበ. Dinner is served. እራት ፡ ቀርቧል
Roast meat is often served with potatoes.
የሥጋ ፡ ጥብስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚቀርበው ፡ ከድ
ንች ፡ ጋር ፡ ነው
2. ቀረበ(ለት). +You'll be served in a moment.
አሁን ፡ ይቀርብልሃል
3. ታደለ. Coffee will be served at the end of the meeting. ስብሰባው ፡ ሲያልቅ ፡ ቡና ፡ ይታ
ደላል
[See also 'inspiration, notice, purpose, right, sentence']

**serve** (n.) አሊጋግ
His serve is so weak that the ball hardly clears the net. አሊጋጉ ፡ በጣም ፡ ደካማ ፡ ከመሆኑ ፡ የተ
ነሣ ፡ መረቡን ፡ እንኳን ፡ አያልፍም

**service** (v.)
1. አገልግሎት ፡ ሰጠ. One electric company services the whole region. አንድ ፡ የኤሌክትሪክ ፡
ኩባንያ ፡ ለቀበሌው ፡ በሞላ ፡ አገልግሎት ፡ ይሰ
ጣል
2. መርምሮ ፡ የጐደለውን ፡ አሟላ. The mechanic serviced our automobile. ሜካኒኩ ፡ አውቶሞቢ
ላችንን ፡ መርምሮ ፡ የጐደለውን ፡ አሟላ

**be serviced** አስመረመረ
He took his car to be serviced. መኪናውን ፡ ሲ
ያስመረምር ፡ ወሰደ

**service** (n.)
1. አገልግሎት. His services to the state have been immense. ለመንግሥት ፡ የሰጠው ፡ አገልግሎ
ት ፡ ከፍተኛ ፡ ነበር
Bus service here is very poor. እዚህ ፡ የአውቶቡ
ስ ፡ አገልግሎት ፡ በጣም ፡ የተጓደለ ፡ ነው
2. ጥቅም. It's for a good service. ለጥሩ ፡ ጥቅም ፡
ነው
3. ቅዳሴ. Catholics often genuflect during the service. ካቶሊኮች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በቅዳሴ ፡
ላይ ፡ ይሰግዳሉ
4. እቃ ፤ እቃዎች. She has a silver tea service.
ከብር ፡ የተሠራ ፡ የሻይ ፡ እቃ ፡ አላት
The table was set with a beautiful silver service. ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ውብ ፡ የብር ፡ እቃዎች ፡
ተደርድረው ፡ ነበር
*The service is bad in this restaurant. እዚህ ፡ ም
ግብ ፡ ቤት ፡ ጥሩ ፡ አያስተናግዱም

**services** እርዳታ
Do you need the services of a doctor? የሐኪ
ም ፡ እርዳታ ፡ ያስፈልግሃል ?

**(be) at one's service**
*My car is at your service. መኪናዬን ፡ በፈለግክ
በት ፡ ጊዜ ፡ ልትጠቀምበት ፡ ትችላለህ

**be in service** ተቀጠረ
She is in service with Mr. Parker. ለሚስተር ፡
ፓርከር ፡ ተቀጥራለች

**be in the service** በወታደርነት ፡ አገለገለ ፤ በ
ጦር ፡ ሰራዊት ፡ ውስጥ ፡ ነበር
How long have you been in the service?
በወታደርነት ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ አገለገልክ ?
My brother was in the service during the war.
ወንድሜ ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ በጦር ፡ ሰራዊት ፡
ውስጥ ፡ ነበር

**be of service** ረዳ
Can I be of service to you? ልረዳህ ፡ እችላለሁ ?

**church service** ቅዳሴ
People go home after the church service.
ቅዳሴ ፡ ሲወጡ ፡ ሕዝቡ ፡ በየቤቱ ፡ ይሄዳል

**civil service**
*The civil service requires a high school education. በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለመ
ቀጠር ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ያስፈልጋል

**diplomatic service** የዲፕሎማቲክ ፡ አገልግሎት
Many young men want to enter the diplomatic service. ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ በዲፕሎማቲክ ፡ አገል ግሎት ፡ ውስጥ ፡ መቀጠር ፡ ይፈልጋሉ

**give good service** ደኅና ፡ አገለገለ
My old coat still gives me good service. አሮጌው ፡ ኮቴ ፡ አሁንም ፡ ደኅና ፡ ያገለግለኛል

**marriage service** ሥርዓተ ፡ ተክሊል
The marriage service was happily short. ደግነቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ተክሊሉ ፡ ቶሎ ፡ አለቀ

**memorial service** የመታሰቢያ ፡ ጸሎት
They are holding a memorial service for my father. ላባቴ ፡ የመታሰቢያ ፡ ጸሎት ፡ ያደርጋሉ

**render service** አገለገለ
He rendered faithful service to his master. ለጌታው ፡ በቅንነት ፡ አገለገለ

**take service**
1. ተቀጠረ. She took service as a maid with an elderly couple. በዕድሜ ፡ ገፋ ፡ ካሉ ፡ ባልና ፡ ሚ ስት ፡ ቤት ፡ ተቀጥራለች
2. አደረ. He took service with the governor general. ላገረ ፡ ገዢው ፡ አደረ
[See also 'included, religion']

## serviceable
He is a serviceable fellow. ጠቃሚ ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጥ ፡ ሰው ፡ ነው

**be serviceable** ሠራ
This motor is still serviceable after years of use. ይህ ፡ ሞተር ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ አገልግሎ ፡ አ ሁንም ፡ ይሠራል

## serviceman ሠራተኛ
A serviceman will come to repair the phone. ሠራተኛ ፡ ስልኩን ፡ ለማበጀት ፡ ይመጣል

## service station የቤንዚን ፡ ማደያ
There is a new service station in our village. በሰፈራችን ፡ አዲስ ፡ የቤንዚን ፡ ማደያ ፡ አለ

## servile በባርነት ፡ ላይ ፡ የወጣ
The servile laws of ancient Rome were strict. በጥንታዊት ፡ ሮም ፡ ውስጥ ፡ በባርነት ፡ ላይ ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ በጣም ፡ ጥብቅ ፡ ነበሩ
*He flattered me in a servile manner. እየተቅ ለሰለሰ ፡ አወደሰኝ

**be servile** ተመራ
An honest judge cannot be servile to public opinion. ሁነኛ ፡ ዳኛ ፡ በሕዝብ ፡ አስተያየት ፡ አይመራም

## servility አድር ፡ ባይነት
His servility fails to make people like him. አድር ፡ ባይነቱ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ አስጠልቶ ታል

## servitude ባርነት
His servitude lasted forty years. አርባ ፡ ዓመት ፡ በባርነት ፡ አገለገለ

## sesame [ጠፍጣፋ ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ የምሥራቅ ፡ ህንድ ፡ ዕፅ]

## session
1. ስብሰባ. The opening session of the General Assembly was attended by the Emperor. በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ የመክፈቻ ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ተገኝተው ፡ ነበር
2. ችሎት. The session of the court ends tomorrow. የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ችሎት ፡ ነገ ፡ ይፈጸማል
3. ክፍለ ፡ ጊዜ. One session overlapped into the next one. አንዱ ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፡ ከሚቀጥለው ፡ ጋ ር ፡ ተደራረበ

**have a session** ተነጋገረ
I had a long session with the boss about it. ስለዚያ ፡ ነገር ፡ ካለቃዬ ፡ ጋር ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ተነጋግሬያለሁ
[See also 'plenary']

## set (set), vt.
1. አስቀመጠ. Set it on the desk! ጠረጴዛው ፡ ላ ይ ፡ አስቀምጠው
2. ወሰነ. Why don't you set the time? ጊዜውን ፡ ለምን ፡ አትወስንም ?
3. ሠራ (ተሠራ). Set the table for five persons! ላምስት ፡ ሰው ፡ ገበታ ፡ ሥራ
The diamonds were set in a circle on the ring. አልማዙ ፡ ቀለበቱ ፡ ላይ ፡ በክብ ፡ ቅርጽ ፡ ተሠራ
4. አቆመ. He set a guard at the store. ሱቁ ፡ ላ ይ ፡ አንድ ፡ ዘበኛ ፡ አቆመ
5. አጌጠ. He set the crown with jewels. ዘውዱን ፡ በዕንቁ ፡ አጌጠ
6. አደረገ. He set the price at five dollars. ዋጋውን ፡ አምስት ፡ ብር ፡ አደረገው
7. ጠገነ. The doctor set the broken arm. የተሰበረውን ፡ እጁን ፡ ሐኪሙ ፡ ጠገነለት
8. እንዲደውል ፡ ሞላው. Set the clock for three! ሰዓቱ ፡ በዘጠኝ ፡ እንዲደውል ፡ ሙላው
9. አስተካከለ. He is so punctual that you could set your watch by him. በጣም ፡ ሰዓት ፡ አክባ ሪ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ በሱ ፡ ሰዓትህን ፡ ልታስ ተካክል ፡ ትችላለህ
10. አስማማ. He set the poem to an old tune. ግጥሙን ፡ ከድሮ ፡ ዜማ ፡ አስማማው
11. አስጀመረ. He set the men to work. ሰዎቹ ን ፡ ሥራ ፡ አስጀመራቸው

*Don't set a bad example! መጥፎ ፡ ምሳሌ ፡ አትሁን

*The government set a price on the criminal's head. ወንጀለኛውን ፡ እጁን ፡ ይዞ ፡ ላስረከበ ፡ መንግሥት ፡ ዋጋ ፡ እንደሚከፍል ፡ አስታወቀ

**set** (vi.)
1. ጠለቀ. The sun has already set. ፀሐይዋ ፡ ገና ፡ ድሮ ፡ ጠልቃለች
2. ደረቀ. The cement set overnight. ሲሚንቶው ፡ ባንድ ፡ ሌሊት ፡ ደረቀ
3. ጀመረ. He set to work immediately. ሥራውን ፡ ወዲያው ፡ ጀመረ

**set about** ጀመረ
I don't know how to set about this job. ይህንን ፡ ሥራ ፡ እንዴት ፡ እንደምጀምር ፡ አላውቅም

**set against** አሳደመ
The monitor set the children against the newcomer. የክፍል ፡ አለቃው ፡ ልጆቹን ፡ አዲስ ፡ በመጣው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ አሳደመ

**(be) set against** ተነጻጸረ
The advantages must be set against the disadvantages. ጥቅምና ፡ ጉዳቱ ፡ መነጻጸር ፡ አለበት

**set ahead** አስቀድሞ ፡ ሞላ
I set my watch five minutes ahead. ሰዓቴን ፡ አምስት ፡ ደቂቃ ፡ አስቀድሜ ፡ ነው ፡ የሞላኋት

**set apart**
1. አስቀመጠ. They set apart $500 as reserve. ለመጠባበቂያ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ አስቀመጡ
2. ለየ. Their dress sets them apart from other people. አለባበሳቸው ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ይለያቸዋል
3. በተለይ ፡ መደበ. Each year I set one week apart to go to the seashore. ወደ ፡ ባሕር ፡ ዳርቻ ፡ ለመሄድ ፡ በያመቱ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ በተለይ ፡ መድቤያለሁ

**set aside**
1. አስቀመጠ. He set aside part of his salary for his vacation. ለዕረፍት ፡ ጊዜው ፡ ወጪ ፡ ከደሞዙ ፡ ቀንሶ ፡ አስቀመጠ
2. መደበ. The traveler set aside $5.00 a day for contingent expenses. መንገደኛው ፡ ለድንገተኛ ፡ ወጪ ፡ በቀን ፡ አምስት ፡ ብር ፡ መደበ
3. ለይቶ ፡ አስቀመጠ. Set this aside for me! ይህን ፡ ለይተህ ፡ አስቀምጥልኝ

**set back** ወደ ፡ ኋላ ፡ መለሰ
Set back the hands of the clock one hour! ሰዓቱን ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መልሰው

**(be) set back**
1. መሰናከል ፡ ገጠመው. All our efforts at reform have been set back. ለማሻሻል ፡ ያደረግነው ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ መሰናክል ፡ ገጠመው
2. ትንሽ ፡ ገባ ፡ አለ. The house is set back from the street. ቤቱ ፡ ከመንገዱ ፡ ትንሽ ፡ ገባ ፡ ያለ ፡ ነው

**set down**
1. አወረደ. He set down his load and rested. ሸክሙን ፡ አውርዶ ፡ አረፍ ፡ አለ
2. አስቀመጠ. Set the box down gently! ሣጥኑን ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ አስቀምጠው
3. ቈጠረ. I'll set that down to ignorance. ይህን ፡ ከድንቁርና ፡ እቈጥረዋለሁ
4. አሰፈረ. He set down his thoughts on paper. አሳቡን ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ አሰፈረው

**set forth**
1. ገለጸ. He set forth his views in an article. ሐሳቡን ፡ ባንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ገለጸ
2. ጀመረ. He set forth on a long trip to Gondar on foot. በእግሩ ፡ ጐንደር ፡ ለመሄድ ፡ ረጅሙን ፡ ጉዞ ፡ ጀመረ

**set forward**
*When your plane lands in New York, set your watch forward two hours. ያለህበት ፡ አውሮፕላን ፡ ኒው ፡ ዮርክ ፡ ሲደርስ ፡ ሰዓትህን ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ በማስቀደም ፡ አስተካክለው

**set in** ጀመረ
Infection had set in. ቁስሉ ፡ መመረዝ ፡ ጀምሯል

**set (one's) mind** ሐሳቡን ፡ ቈረጠ
If he sets his mind to it, he will do it. ሐሳቡን ፡ ከቈረጠ ፡ ያደርገዋል

**set off** (vt.)
1. አስነሣ. The bomb set off a number of fires. ቦምቡ ፡ ብዙ ፡ ቃጠሎ ፡ አስነሣ
2. (= pass.) ጐልቶ ፡ ታየ. +The dark suit sets off his bright tie. ደማቁ ፡ ክራቫት ፡ በጥቁሩ ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ ጐልቶ ፡ ይታያል

**set off** (vi.) ጀመረ ፤ ለመሄድ ፡ ተነሣ
They set off on their trip with plenty of money. ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ይዘው ፡ ጉዞ ፡ ጀመሩ
We packed the mules and then set off for the lake. በቅሎዎቹን ፡ ጭነን ፡ ወደ ፡ ሐይቁ ፡ ለመሄድ ፡ ተነሣን

**set on** ለቀቀ(በት)
He set his dogs on me. ውሾቹን ፡ ለቀቀብኝ

**set out** (vt.)
1. ተከለ. He set out a row of cabbage. ተርታውን ፡ ጐመን ፡ ተከለ
2. ወሰነ. They set out the boundary of the town. የከተማውን ፡ ክልል ፡ ወሰኑ

3. ቈረጠ. He set out to break a new record. አዲስ ፡ ክብረ ፡ ወሰን ፡ ለማግኘት ፡ ቈርጧል

**set out** (vi.) ሄደ
He set out for home on Monday. ሰኞ ፡ ለ ት ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ሄደ

**set out on** ጀመረ
He set out on a long journey. ረጅም ፡ ጉዞ ፡ ጀመረ

**set (oneself) to** ቈርጦ ፡ ተነሣ
I have set myself to finish the job by May. ሥራውን ፡ በግንቦት ፡ ለመጨረስ ፡ ቈርጬ ፡ ተነሥቻለሁ

**set up**
1. አቆመ. They set up a statue in his honor. ለመታሰቢያቸው ፡ ሐውልት ፡ አቆሙላቸው
2. ተከለ(ተተከለ). The new machines have just been set up. አዲሶቹ ፡ የፋብሪካው ፡ መሣሪያዎ ች ፡ አሁን ፡ ገና ፡ ተተከሉ
The surveyor set up his instruments and began to make a survey of the land. ቀያሹ ፡ መሣሪያ ዎቹን ፡ ተክሎ ፡ መሬቱን ፡ መቀየስ ፡ ጀመረ
3. አቋቋመ. We lack the requisite capital for setting up a business. ንግድ ፡ ለማቋቋም ፡ አስፈ ላጊ ፡ ገንዘብ ፡ የለንም
4. አደረገ. We set him up as leader of the committee. የደርጉ ፡ ሰብሳቢ ፡ አደረግነው

**set (one) up in** ከፈተ(ለት)
His father set him up in business. አባቱ ፡ የንግ ድ ፡ ሥራ ፡ ከፈተለት

**be all set** ተዘጋጀ
Everything is all set. ሁሉም ፡ ነገር ፡ ተዘጋጅ ቷል

**be set for**
*I was set for an argument when I came home. ወደ ፡ ቤት ፡ ስገባ ፡ ንትርክ ፡ እንደሚጠብቀኝ ፡ ዐውቄ ፡ ነበር

**be set in one's ways**
He is set in his ways. እልኸኛ ፡ ነው

**be set (on)** ቈረጠ
The boy seems set on becoming a pilot. ልጁ ፡ አውሮፕላን ፡ ነጂ ፡ ለመሆን ፡ የቈረጠ ፡ ይመስላል
*I'm not set on getting my way. እኔ ፡ ያልኩት ፡ ይሁን ፡ ማለቴ ፡ አይደለም

**get set!** ተዘጋጅ
On your mark! Get set! Go! በመሥመርህ! ተ ዘጋጅ! ሂድ!
[See also 'clock, eye, fire, foot, free, heart, pace, right']

**set** (n.)
1. ኮምፕሌት. We have a whole set of dishes. ኮምፕሌት ፡ ሳሕን ፡ አለን
2. ሙሉ. I bought a set of tools so I can build whatever I need. ለቤቴ ፡ የሚያስፈልገኝን ፡ ሁ ሉ ፡ ለመሥራት ፡ እንድችል ፡ ሙሉ ፡ የአናጺ ፡ እቃ ፡ ገዛሁ
*There's only one stamp missing in that set. የሰበሰብኩት ፡ ቴምብር ፡ ሙሉ ፡ ሊሆን ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ይጐድለዋል
*He sold his old radio and bought a new set. አሮጌ ፡ ራድዮኑን ፡ ሸጠ ፡ አዲስ ፡ ገዛ

**set** (adj.)
1. የተወሰነ. The guard is changed at a set time. ዘቡ ፡ በተወሰነ ፡ ሰዓት ፡ ይለዋወጣል
2. ዝግጁ. They were all set. ሁሉም ፡ ዝግጁ ፡ ነበሩ

**setback** መሰናክል
We met with many setbacks in our business. በንግድ ፡ ሥራችን ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ መሰናክል ፡ አጋጠመን

**setting** የመነሻ ፡ ቦታ
The setting of the story is in a little village. የታሪኩ ፡ መነሻ ፡ ቦታ ፡ የሆነው ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ መንደር ፡ ነው
*The diamond came out of the setting of the ring. አልማዙ ፡ ከቀለበቱ ፡ ላይ ፡ ወለቀ

**place setting** የገበታ ፡ እቃ
Do we have enough place settings for everybody? ለሁሉም ፡ የሚበቃ ፡ የገበታ ፡ እቃ ፡ አለን ?

**settle** (vt.)
1. አቆመ ፤ ጨረሰ. Can you settle their argument? ክርክራቸውን ፡ ልታቆመው ፡ ትችላለህ ?
We settled the argument by dividing the property. ንብረቱን ፡ ተካፍለን ፡ ክርክራችንን ፡ ጨረስን
2. ከስምምነት ፡ ደረሰ. Instead of fighting, the two nations settled their quarrels in an amicable way. ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ በመካከላቸው ፡ ያለውን ፡ አለመግባባት ፡ ከመዋጋት ፡ ይልቅ ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ ከስምምነት ፡ ደረሱ
3. አጠናቀቀ. I must settle all my affairs before going away. ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ ጉዳዬን ፡ ሁሉ ፡ ማጠናቀቅ ፡ አለብኝ
4. መደምደሚያ ፡ አበጀ. What you said settles the argument. አንተ ፡ የተናገርከው ፡ ለጭቅጭቁ ፡ መደምደሚያ ፡ ያበጅለታል
5. አስወገደ. Both sides made reciprocal concessions in order to settle the border

problem. የወሰን ፡ ችግራቸውን ፡ ለማስወገድ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮችን ፡ ለመተው ፡ ተስማሙ

6. ፈጸመ. Let's settle this business right away! ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ አሁኑኑ ፡ እንፈጽም

7. ከፈለ. He settled all his bills before leaving town. ከተማ ፡ ከመልቀቁ ፡ በፊት ፡ ሒሳቡን ፡ ሁሉ ፡ ከፈለ

8. ከ --- አላቀቀ. This payment settles your debt. ይህ ፡ ክፍያ ፡ ከዕዳህ ፡ ያላቅቅሃል

9. አዘጋ. We must settle our accounts today. ሒሳባችንን ፡ ዛሬ ፡ ማዘጋት ፡ አለብን

10. ተነጋገረ. I have an account to settle with him. ከሱ ፡ ጋር ፡ የምነጋገረው ፡ ጉዳይ ፡ አለኝ

11. አስቀመጠ. Mr. Parker settled his family in the country. ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ ቤተሰቡን ፡ ባላገር ፡ አስቀመጠ

12. አወረሰ. He settled part of his estate on his nephew. ከርስቱ ፡ ከፊሉን ፡ ለወንድሙ ፡ ልጅ ፡ አወረሰ

13. አስታገሠ. This medicine will settle your stomach. ይህ ፡ መድኃኒት ፡ የሆድ ፡ ሕመምህን ፡ ያስታግሥልሃል

The rain settled the dust. ዝናብ ፡ አቧራውን ፡ አስታገሠ

14. አቀና. Who settled Canada? ካናዳን ፡ ያቀና ፡ ማነው?

**settle** (vi.)

1. ተቀመጠ ፤ ሰፈረ. Our uncle settled in California. አጎታችን ፡ ካሊፎርኒያ ፡ ተቀመጠ

Many Germans settled in Missouri. ብዙ ፡ ጀርመኖች ፡ ሚዙሪ ፡ ሰፈሩ

2. አረፈ. The bird settled on a branch overhead. ወፏ ፡ ከበላዩ ፡ ካለው ፡ ቅርንጫፍ ፡ ላይ ፡ አረፈች

3. ተስማማ. He settled with his creditors. ካበዳሪዎቹ ፡ ጋር ፡ ተስማማ

They settled on me as the new chairman. አዲሱ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ እኔ ፡ እንድሆን ፡ ተስማሙ

4. ሰከነ. Wait until the coffee has settled! ቡናው ፡ እስኪሰክን ፡ ድረስ ፡ ቆይ

5. አለፈ. Wait until the dust settles! አቧራው ፡ እስኪያልፍ ፡ ቆይ

6. ወደ ፡ መሬት ፡ ገባ. Our house has settled several inches since it was built. ቤታችን ፡ ከተሠራ ፡ ወዲህ ፡ ብዙ ፡ ኢንቾች ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ገብቷል

*The pain settled in his heart. ልቡ ፡ በሽተኛ ፡ ሆነ

*I have an account to settle with him. ከሱ ፡ ጋር ፡ እንተያያለን!

**settle down**

1. ቁጭ ፡ አለ. We settled down to wait until they came to get us. መጥተው ፡ እስኪወስዱን ፡ ድረስ ፡ ቁጭ ፡ ብለን ፡ ጠበቅናቸው

2. ተደላደለ. Hasn't he settled down yet? ገና ፡ አልተደላደለም?

3. የተደላደለ ፡ ኑሮ ፡ ጀመረ. He kicked about a good deal before settling down. የተደላደለ ፡ ኑሮ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ተዘዋወረ

4. ተረጋጋ. Wait till the excitement settles down. ግርግሩ ፡ እስኪረጋጋ ፡ ድረስ ፡ ቆይ

**settle for the night** አመቻችቶ ፡ አስተኛ

The nurse settled her patient for the night. ነርሷ ፡ በሽተኛውን ፡ አመቻችታ ፡ አስተኛችው

**settle (on)**

1. አለበሰ. The dust raised by the strong wind settled on the furniture. በኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ የበነነው ፡ አቧራ ፡ እቃውን ፡ አለበሰው

2. ቈረጠ. Have you settled on a time for leaving? የምትሄድበትን ፡ ጊዜ ፡ ቈረጥክ?

**settle oneself** ተቀመጠ

The nurse settled herself in an arm chair. ነርሷ ፡ ድጋፍ ፡ ባለው ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀመጠች

**be settled**

1. (= settle) ሰፈረ. The wide open spaces of the West are now settled. በምዕራብ ፡ በኩል ፡ የነበረው ፡ ሰፊ ፡ ባዶ ፡ ቦታ ፡ አሁን ፡ ሰው ፡ ሰፍሮበታል

2. ገብቶ ፡ ተደላደለ. Come and visit us in our new house when we are settled. አዲሱ ፡ ቤታችን ፡ ገብተን ፡ ስንደላደል ፡ መጥተህ ፡ ጠይቀን

3. ቆመ. The strike was settled by a compromise. አድማው ፡ በአስታራቂ ፡ ቆመ

4. አለቀ. The matter is pressing and must be settled now. ጉዳዩ ፡ አስቸኳይ ፡ ስለሆነ ፡ አሁኑኑ ፡ ማለቅ ፡ አለበት

## settlement

1. ቅኝ ፡ ግዛት. England had many settlements along the Atlantic coast. እንግሊዝ ፡ በአትላንቲክ ፡ ባሕር ፡ አካባቢ ፡ ብዙ ፡ ቅኝ ፡ ግዛቶች ፡ ነበሯት

2. መስፈሪያ ፡ ቦታ. The pioneers opened up the West to settlement. አገር ፡ አቅኚዎቹ ፡ የምዕራቡ ፡ ክፍል ፡ ሀገር ፡ መስፈሪያ ፡ ቦታ ፡ እንዲሆን ፡ መንገድ ፡ ከፈቱ

3. መንደርተኞች. The enemy fell upon the sleeping settlement. ተኝተው ፡ የነበሩትን ፡ መንደርተኞች ፡ ጠላት ፡ በድንገት ፡ አጠቃ

4. መኖሪያ. The only settlement in the wilderness is a penal colony. በበረኻው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ መኖሪያ ፡ የወንጀለኞች ፡ ብቻ ፡ ነው

5. መስማማት. They couldn't reach a settlement. መስማማት ፡ አቃታቸው
*This village is an old settlement. ይህ ፡ መንደር ፡ የቆየ ፡ ነው
*There is a new settlement on the banks of the river. በወንዙ ፡ ዳርና ፡ ዳር ፡ መስፈር ፡ ተጀምሯል
*Settlement of all the accounts the company owes will be made shortly. ኩባንያው ፡ ያለበትን ፡ ዕዳ ፡ በቅርቡ ፡ ይከፍላል

**settler**
1. ሰፋሪ. The settlers came into Kenya early in this century. ሰፋሪዎቹ ፡ ወደ ፡ ኬንያ ፡ የመጡት ፡ በዚህ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ነው
2. አዲስ፡የሰፈረ፡ሰው. The government parceled out land to settlers. መንግሥቱ ፡ አዲስ ፡ ለሰፈሩት ፡ ሰዎች ፡ መሬት ፡ ሸንሽኖ ፡ አከፋፈለ
3. መጤ. The Indians became very militant as settlers began to move west. መጤዎች ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ሲገፉ ፡ ህንዶች ፡ ለመዋጋት ፡ ቈረጡ

**setup**
1. እቅድ. The investigation spoiled the swindlers' setup. ምርመራው ፡ ያጭበርባሪዎቹን ፡ እቅድ ፡ አሰናከለባቸው
2. ሁኔታ. He explained the setup to us before we attacked. ከማጥቃታችን ፡ በፊት ፡ ሁኔታውን ፡ ገለጸልን

**seven** ሰባት
**seven o'clock** አንድ ፡ ሰዓት
We eat dinner at seven o'clock. እራት ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ እንበላለን

**seventeen** ዐሥራ ፡ ሰባት

**seventh** ሰባተኛ

**seventy** ሰባ

**sever** (vt.)
1. ቈረጠ. The knife severed his arm. ቢላዋው ፡ እጁን ፡ ቈረጠው
The sailor severed the rope with a knife. መርከበኛው ፡ ገመዱን ፡ በስንጢ ፡ ቈረጠው
2. አቋረጠ. Japan severed diplomatic relations with China before attacking her. ጃፓን ፡ ቻይናን ፡ ከማጥቃቷ ፡ በፊት ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ግንኙነት ፡ አቋረጠች
**sever** (vi.) ተበጠሰ
The rope severed, and the swing fell down. ገመዱ ፡ ተበጥሶ ፡ የጅውጅው ፡ መጫወቻው ፡ ወደቀ

**several** (pron.) አንዳንዶቹ
Several have given their consent. አንዳንዶቹ ፡ መስማማታቸውን ፡ ገልጸዋል
**several** (adj.)
1. በርከት ፡ ያሉ. Several people have told me I sing well. በርከት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ጥሩ ፡ ትዘፍናለህ ፡ ብለው ፡ ነግረውኛል
I'd like to stay here for several days. በርከት ፡ ላሉ ፡ ቀናት ፡ እዚህ ፡ መቆየት ፡ እፈልጋለሁ
2. ብዙ. Several words in this letter have been blotted out. እዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ቃላት ፡ ጠፍተዋል
3. በየ-. The boys went their several ways. ልጆቹ ፡ በየፊናቸው ፡ ሄዱ
**several of**
1. በርከት ፡ ያሉ. Several of us decided to walk home. በርከት ፡ ያልነው ፡ ቤታችን ፡ በእግራችን ፡ ለመሄድ ፡ ወሰንን
2. ብዙዎቹ. In that village, several of the houses are white. በዚያ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ብዙዎቹ ፡ ቤቶች ፡ ነጭ ፡ ናቸው

**severally** በዝርዝር
Consider these points — first severally and then collectively. እነዚህን ፡ ጉዳዮች ፡ መጀመሪያ ፡ በዝርዝር ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ በጅምላ ፡ ተመልከታቸው

**severe**
1. ኀይለኛ. The judge is very severe. ዳኛው ፡ በጣም ፡ ኀይለኛ ፡ ነው
He made a severe criticism of the new play. ስላዲሱ ፡ ቲያትር ፡ ኀይለኛ ፡ ትችት ፡ ሰጠ
It is a very severe winter. በጣም ፡ ኀይለኛ ፡ ክረምት ፡ ነው
2. ከባድ ፤ ብርቱ. The battle was severe but indecisive. ጦርነቱ ፡ ከባድ ፡ ቢሆንም ፡ ውጤቱ ፡ አልለየም
The punishment was too severe. ቅጣቱ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ (ብርቱ) ፡ ነበር
3. ጥብቅ. Students don't like a severe teacher. ተማሪዎቹ ፡ ጥብቁን ፡ መምህር ፡ አይወዱትም
4. አሰቃቂ. She complains of severe pains. ባሰቃቂ ፡ ሕመም ፡ ትማረራለች
5. ጽኑ. The judge imposed a severe sentence on the criminal. ዳኛው ፡ በወንጀለኛው ፡ ላይ ፡ ጽኑ ፡ ቅጣት ፡ ፈረደበት
6. መጥፎ. He had a severe case of pneumonia. መጥፎ ፡ የሳል ፡ በሽታ ፡ ይዞታል
7. ከፍ ፡ ያለ. The competition for the job is severe. ሥራውን ፡ ለማግኘት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ውድድር ፡ አለ
8. ጌጣ ፡ ጌጥ ፡ የሌለበት. She wore a severe

black dress. ጌጣ ፡ ጌጥ ፡ የሌለበት ፡ ጥቁር ፡ ልብስ ፡ ለበሰች

**severed** (adj.) የተቈረጠ
They found his severed head on a pole. የተቈረጠውን ፡ ራሱን ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ ተሰክቶ ፡ አገኙት

**severity**
1. ክባድነት. The severity of the pain is unbearable. የሕመሙ ፡ ክባድነት ፡ የማይቻል ፡ ነው
2. ኀይለኛነት. His pallid face shows the severity of the fever. የገረጣው ፡ ፊቱ ፡ የትኩሳቱን ፡ ኀይለኛነት ፡ ያመለክታል
*The children fear their father because of his severity. አባታቸው ፡ ጥብቅ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ልጆቹ ፡ ይፈሩታል
*I like the severity of modern architecture. ዘመናዊው ፡ የሕንጻ ፡ አሠራር ፡ ጌጣ ፡ ጌጥ ፡ ስለማይበዛበት ፡ እወደዋለሁ

**sew** (vt.) ሰፋ
She sews her own dresses. ልብሷን ፡ ራሷ ፡ ትሰፋለች

**sew** (vi.) ልብስ ፡ ሰፋ
My mother sews beautifully. እናቴ ፡ ልብስ ፡ አሳምራ ፡ ትሰፋለች

**sew on** ተከለ(ለት)
Please sew on the buttons of my coat! እስቲ ፡ ኮቴ ፡ ላይ ፡ ቁልፍ ፡ ትከልልኝ

**sew up**
1. ሰፋ. The doctor sewed up the wound. ዶክተሩ ፡ ቁስሉን ፡ ሰፋ
2. ዘመዘመ. Please sew up the torn buttonhole! የተቀደደውን ፡ የቁልፍ ፡ ቀዳዳ ፡ ዘምዝም

**(be) sewn up**
1. ተሰፋ. The sack was sewn up with thread. ጆንያው ፡ በክር ፡ ተሰፍቷል
2. ከስምምነት ፡ ተደረሰ. The deal is sewed up. በጉዳዩ ፡ ከስምምነት ፡ ተደርሷል

**sewage** ቆሻሻ ፤ ጥራጊ ፤ የቆሻሻ ፡ እጣቢ
The sewage empties into the river. ቆሻሻው ፡ (ጥራጊው) ፡ በቦይ ፡ ውስጥ ፡ አልፎ ፡ እወንዝ ፡ ይገባል
Sewage has polluted our drinking water. የቆሻሻው ፡ እጣቢ ፡ የመጠጥ ፡ ውኃችንን ፡ በክሎታል

**sewer** ፉካ
The sewers are choked with rubbish. ፉካዎቹን ፡ ቆሻሻ ፡ ደፍኗቸዋል

**sewing** ስፌት
The sewing is not too good. ስፌቱ ፡ እጅግም ፡ ጥሩ ፡ አይደለም

**sewing machine** የስፌት ፡ መኪና
I bought her a sewing machine. የስፌት ፡ መኪና ፡ ገዛሁላት

**sex**
1. ጾታ. Put down your sex on this application! እዚህ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ጾታህን ፡ ጻፍ
2. ፍትወት ፡ ሥጋ. A monk is expected to remain continent in regard to sex. መነኵሴ ፡ ፍትወት ፡ ሥጋውን ፡ እንዲገታ ፡ ይጠበቃል

**sexual, ~ relations** ፍትወት ፡ ሥጋ ፡ መፈጸም
Sexual relations with a minor is a criminal offense. ላቅመ ፡ ሔዋን ፡ ካልደረሰች ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ ፍትወት ፡ ሥጋ ፡ መፈጸም ፡ በሕግ ፡ ያስቀጣል

**shabby**
1. ቡትቷም. A shabby beggar is at the door. አንድ ፡ ቡትቷም ፡ ለማኝ ፡ ከበር ፡ ቆሟል
2. ከርፋፋ. You look shabby in those clothes. ይህ ፡ ልብስ ፡ ከርፋፋ ፡ አስመስሎሃል
3. ያለቀ. His suit looks shabby. ልብሱ ፡ ያለቀ ፡ ይመስላል
4. ነውር. It is shabby not to speak to an old friend because he is poor. ድኻ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የድሮ ፡ ጓደኛን ፡ አለማነጋገር ፡ ነውር ፡ ነው

**shack** ጎጆ
The refugees live in shacks made of tin cans. ስደተኞቹ ፡ ከታኒካ ፡ በተሠሩ ፡ ጎጆዎች ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ

**shackle** (v.) በሰንሰለት ፡ አሰረ
The policeman shackled the prisoner to a telephone pole. ፖሊሱ ፡ እስረኛውን ፡ ከስልክ ፡ ዕንጨት ፡ ጋር ፡ በሰንሰለት ፡ አሰረው

**be shackled** በካቴና ፡ ተቈራኘ
The prisoner was shackled to the guard. እስረኛው ፡ ከዘበኛው ፡ ጋር ፡ በካቴና ፡ ተቈራኝቶ ፡ ነበር

**shackle** (n.) እግር ፡ ብረት
He sawed through the shackles and escaped. እግር ፡ ብረቱን ፡ በመጋዝ ፡ ቈርጦ ፡ አመለጠ

**shade** (vt.)
1. ከለለ. He shaded his eyes with his hand. ዓይኑን ፡ በእጁ ፡ ከለለ
2. አጠላ. The trees shade the house. ዛፎች ፡ ቤቱን ፡ ያጠላሉ

**shade** (vi) እያደር ፡ ተለወጠ
The drapes shade from brown to black. መጋረጃዎቹ ፡ እያደር ፡ ከቡናማነት ፡ ወደ ፡ ጥቁርነት ፡ ይለወጣሉ

**shade** (n.)
1. ጥላ. Let's stay in the shade! ከጥላው ፡ አረ ፍ ፡ እንበል
2. የሸራ ፡ መጋረጃ. Pull down the shades of the window! የመስኮቱን ፡ ሸራ ፡ መጋረጃ ፡ አውርድ

**shade of**
*This word has many shades of meaning. ይህ ፡ ቃል ፡ ብዙ ፡ ለየትየት ፡ ያሉ ፡ ትርጉሞች ፡ አሉት

**a shade** ትንሽ
Your dress is a shade longer than your coat. ልብስሽ ፡ ከካፖርትሽ ፡ ትንሽ ፡ ረዝሞብሻል
*This red is a shade too dark. ቀዩ ፡ ቀለም ፡ ደ መቅ ፡ ያለ ፡ ነው
*We noticed a shade of anger in his voice. በድምፁ ፡ መጠነኛ ፡ ንዴት ፡ እንዳለበት ፡ ተገነ ዘብን

**in all shades of** በያይነቱ
I would like to see silks in all shades of blue. በያይነቱ ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ የሐር ፡ ጨ ርቅ ፡ ልመርጥ ፡ እፈልጋለሁ

**put in the shade** አስናቀ
His brilliance put his teacher in the shade. በብልህነቱ ፡ መምህሩን ፡ አስናቀ
[See also 'lampshade']

**shadow** (v.)
1. ጥላ ፡ ጣለ(በት). Hills shadowed the valley. ኮረብታዎች ፡ ሸለቆውን ፡ ጥላ ፡ ጥለውበታል
2. ሳይነቃበት ፡ ተከታተለው. The detectives shadowed the spy. መረጃ ፡ ሰብሳቢዎቹ ፡ ሰላዩን ፡ ሳይነቃባቸው ፡ ተከታተሉት

**be shadowed by** ጥላ ፡ አረፈ(በት)
+The grass is shadowed by a huge eucalyptus. ሣሩ ፡ ላይ ፡ የትልቁ ፡ ባሕር ፡ ዛፍ ፡ ጥላ ፡ አርፎበታል

**shadow** (n.) ጥላ
The trees cast long shadows. ዛፎቹ ፡ ረጅም ፡ ጥ ላ ፡ ይጥላሉ
*He's only the shadow of his former self. ውቃቢ ፡ ርቆታል
[See also 'doubt']

**shady** ጥላማ
It's shady over here. እዚህ ፡ ጋ ፡ ጥላማ ፡ ነው
*He's a man of shady character. ሰላቢ ፡ ነው
*The transaction seems rather shady. ንግዱ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ማጭበርበር ፡ ያለበት ፡ ይመስላል

**shaft**
1. ዘንግ. The shaft of the spear is made of wood. የጦሩ ፡ ዘንግ ፡ ከዕንጨት ፡ የተሠራ ፡ ነው
2. ጉድጓድ. He fell down a mine shaft. ማዕድኑ ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ
3. ብልጭታ. A shaft of light cut through the darkness. በጨለማው ፡ ውስጥ ፡ የብርሃን ፡ ብል ጭታ ፡ ታየ

**shaggy** የተመሰቃቀለ
The dog has a shaggy coat. የውሻው ፡ ጸጉር ፡ የተመሰቃቀለ ፡ ነው

**shake** (shook), vt.
1. አንቀጠቀጠ. The earthquake shook everything within the radius of ten miles. የምድሩ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ከዐሥር ፡ ማይል ፡ ወዲህ ፡ ያሉትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ አንቀጠቀጠ
2. አወዛወዘ. The wind shook the leaves of the tree. ነፋሱ ፡ የዛፉን ፡ ቅጠሎች ፡ አወዛወዛቸው
3. አነቃነቀ. The wind shook the window-panes. ነፋሱ ፡ መስኮቱን ፡ አነቃነቀው
4. አራገፈ. The maid shakes the rug every morning. ገረዲ ፡ ምንጣፏን ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ታራግፋለች
5. ነቀነቀ. He shook his head in disapproval. በነገሩ ፡ ባለመስማማት ፡ ራሱን ፡ ነቀነቀ
He stirred up the dregs by shaking the bottle of mead. የጠጁን ፡ ጠርሙስ ፡ በመነቅነቅ ፡ አ ምቡላውን ፡ ቀሰቀሰው
6. ጨበጠ. He shook my hand cordially. እጄን ፡ በወዳጅነት ፡ ጨበጠኝ
7. አናወጸ. Nothing can shake his confidence in himself. በራሱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ እምነት ፡ ም ንም ፡ የሚያናውጸው ፡ ነገር ፡ የለም

**shake** (vi.)
1. ተንቀጠቀጠ. He shook with fear. በፍርሃት ፡ ተ ንቀጠቀጠ
2. ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ አለ. Her voice shook with emotion. ከጥልቅ ፡ ስሜት ፡ የተነሣ ፡ ድምጿ ፡ ቁ ርጥ ፡ ቁርጥ ፡ ይል ፡ ነበር

**be shaken**
1. ደነገጠ. We were badly shaken by the news of his death. መሞቱን ፡ በሰማን ፡ ጊዜ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ደነገጥን
2. (= act.) አናጋ. The faith of the believers was shaken by the capture of the holy city. የቅድስት ፡ ከተማ ፡ መያዝ ፡ የአማኞቹን ፡ መንፈ ስ ፡ አናጋው

**shake at**
1. ወዘወዘ(በት). He shook his fist at me. እጁን ፡ ወዘወዘብኝ
2. ቃጣ(በት). He shook a stick at the thief. ሌባውን ፡ በበትር ፡ ቃጣበት

**shake badly** አሸበረ
The experience shook him badly. የደረሰበት ፡ ነገር ፡ አሸበረው

**shake down** ጠቀጠቀ
The farmer shakes down the sack of grain until it is firmly packed. እህሉ ፡ በደንብ ፡ እስኪታጨቅ ፡ ገበሬው ፡ ጆንያውን ፡ ይጠቀጥቀዋል

**shake hands**
1. ተጨባበጡ. They shook hands when they met. ሲገናኙ ፡ ተጨባበጡ
2. እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተጨባበጡ. We shook hands as a pledge of friendship. ለጓደኝነታችን ፡ ማረጋገጫ ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተጨባበጥን
3. የእጅ ፡ ሰላምታ ፡ ተለዋወጡ. The contestants shake hands before the fight begins. ተወዳዳሪዎቹ ፡ ከመጋጠማቸው ፡ በፊት ፡ የእጅ ፡ ሰላምታ ፡ ይለዋወጣሉ

**shake off** (vt).
1. ከሰውነቱ ፡ ላይ ፡ አራገፈ. The dog shook off the water. ውሻው ፡ ከሰውነቱ ፡ ላይ ፡ ውኃውን ፡ አራገፈ
2. ተላቀቀ. I can't seem to shake off this cold. ይህን ፡ ጉንፋን ፡ ልላቀቀው ፡ አልቻልኩም
*The thief shook the police off his trail. ሌባው ፡ ፖሊሱ ፡ መንገድ ፡ እንዲስት ፡ አደረገው

**shake off** (vi.) ሲራገፍ ፡ ቻለ
Sand shakes off easily from the shoes. አሸዋ ፡ ከጫማ ፡ ላይ ፡ በቀላሉ ፡ ሊራገፍ ፡ ይችላል

**shake out** አራገፈ
The maid shook out the dusty rug. ገረዲቱ ፡ አቧራ ፡ የሞላበትን ፡ ምንጣፍ ፡ አራገፈች

**shake up** አሸበረ
The threat of attack has shaken up the entire country. የውጭ ፡ አጥቂ ፡ ፍርሃት ፡ አገሪቱን ፡ በመላ ፡ አሸበረ

**shake with laughter**
She shook with laughter. በሣቅ ፡ ተንከተከተች
[See also 'loose']

**shake** (n.), **no great shakes**
*He's no great shakes as an administrator. ባስተዳዳሪነት ፡ ከቁጥር ፡ የሚገባ ፡ አይደለም

**shake-up, make a ~** አቋም ፡ ለዋወጠ
The new boss made a shake-up in our office. አዲሱ ፡ አለቃ ፡ የመሥሪያ ፡ ቤታችንን ፡ አቋም ፡ ለዋወጠው

**shaky**
1. የሚያረገርግ. Trucks couldn't use the shaky bridge. የጭነት ፡ መኪናዎች ፡ በሚያረገርገው ፡ ድልድይ ፡ ላይ ፡ ሊሄዱ ፡ አልቻሉም
2. የማይረባ. His shaky excuse for being late was not accepted. ለመዘግየቱ ፡ ያቀረበው ፡ የማይረባ ፡ ምክንያት ፡ ተቀባይ ፡ አላገኘም

**be shaky** ተወዛወዘ
The table was too shaky to use. ጠረጴዛው ፡ ስለሚወዛወዝ ፡ አያገለግልም
*We were still shaky from the explosion. በፈንጂው ፡ ምክንያት ፡ የደረሰብን ፡ ድንጋጤ ፡ እስካሁን ፡ አለቀቀንም

**shall**
1. (imperfect). I shall come with you. አብሬህ ፡ እሄዳለሁ
2. (jussive). Shall I come with you? አብሬህ ፡ ልሂድ ?

**shallow**
1. ግልብ ፤ ጥልቅ ፡ ያልሆነ. The lake is very shallow at this point. እዚህ ፡ ጋ ፡ ሐይቁ ፡ በጣም ፡ ግልብ ፡ ነው
The ship grounded in shallow water. መርከቢቱ ፡ ጥልቅ ፡ ባልሆነው ፡ ውኃ ፡ (ግልብ ፡ በሆነው ፡ ባሕር) ፡ ውስጥ ፡ መሬት ፡ ያዘች
2. ቅርብ. They deepened the shallow pool. ቅርቡን ፡ ጉድጓድ ፡ አርቀው ፡ ቆፈሩት
3. ዝርግ. This shallow dish is not good for soup. ይህ ፡ ዝርግ ፡ ሳሕን ፡ ለሾርባ ፡ አይሆንም
4. ገለባ. His writings are, on the whole, shallow. በጠቅላላው ፡ ጽሑፎቹ ፡ ገለባ ፡ ናቸው

**sham** (shammed), v.
1. አበለ. That boy is not crying; he is only shamming. ልጁ ፡ የሚያለቅሰው ፡ ሲያብል ፡ ነው
2. ምክንያት ፡ ፈጠረ. He shammed sickness so he wouldn't have to work. እንዳይሠራ ፡ ታምሚያለሁ ፡ እያለ ፡ ምክንያት ፡ ይፈጥራል
3. ዋሸ. He is not asleep; he is only shamming. እንቅልፍ ፡ አልወሰደውም ፤ ሲዋሽ ፡ ነው

**sham** (n.) የይምሰል
His anger was a sham. ቁጣው ፡ የይምሰል ፡ ነበር

**sham** (adj.)
1. ሰው ፡ ሠራሽ. She wears a string of sham pearls. ሰው ፡ ሠራሽ ፡ የዕንቁ ፡ ድሪ ፡ አድርጋለች
2. የውሸት. The soldiers fought a sham battle for practice. ወታደሮቹ ፡ ለልምምድ ፡ የውሸት ፡ ውጊያ ፡ ተዋጉ

**shamble** (v.), **~ along** እየተንቀጠቀጠ ፡ አዘገመ
The tired old man shambles along. ደካማው ፡ ሽማግሌ ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ ያዘግማል

**shambles, be a ~** ተመሰቃቀለ
The place was a shambles after the fight. ከረብሻው ፡ በኋላ ፡ ቤቱ ፡ በጣም ፡ ተመሰቃቅሎ ፡ ነበር

**leave a shambles** ምስቅልቅሉን ፡ አወጣ
The children left the room a shambles. ልጆቹ ፡ ክፍሉን ፡ ምስቅልቅሉን ፡ አወጡት

**shame** (v.) አሳፈረ
My mistake shamed me. ስሕተቱ ፡ አሳፈረኝ

**shame** (n.)
1. እፍረት. She blushed with shame. በእፍረት ፡ ፊቷ ፡ ፍም ፡ መሰለ
2. ማፈር ፤ መዋረድ. His shame was soon known to all. ማፈሩ ፡ (መዋረዱ) ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ ያኔውኑ ፡ ታውቆ ፡ ነበር
*Shame on you! ብትሞት ፡ ይሻልሃል
*To my shame, I must confess I begged for that money. ያንን ፡ ገንዘብ ፡ ለምኜ ፡ ማግኘቴን ፡ እያፈርኩ ፡ ልናዘዝ

**be a shame to** አሰደበ
He's a shame to his family. ቤተ ፡ ሰቡን ፡ ያሰድባል

**bring shame to** አዋረደ ፤ አሳፈረ
The young man's arrest brought shame to his family. የወጣቱ ፡ ሰውዬ ፡ መያዝ ፡ ቤተሰቡን ፡ አዋረደ ፡ (አሳፈረ)

**have shame** አፈረ
Haven't you any shame? አታፍርም ?

**it's a shame** ያሳፍራል
It's a shame the way he treats us. እንዴት ፡ እንደሚያደርገን ፡ ብታይ ፡ ያሳፍራል

**put to shame**
1. ዋጋ ፡ አሳጣ. His success put my efforts to shame. የሱ ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ ማግኘት ፡ የኔን ፡ ጥረት ፡ ዋጋ ፡ አሳጣው
2. አስናቀ. His careful work put all the rest of us to shame. ጥንቃቄ ፡ የተመላበት ፡ ሥራው ፡ ሁላችንንም ፡ አስናቀን

**what a shame!** ያሳዝናል
What a shame you can't come! መምጣት ፡ አለመቻልህ ፡ ያሳዝናል

**shamefaced** (adj.) በእፍረት ፡ የተዋጠ
The shamefaced boy asked the teacher's pardon for having insulted him. በእፍረት ፡ የተዋጠው ፡ ልጅ ፡ አስተማሪውን ፡ በመዝለፉ ፡ ይቅርታ ፡ ጠየቀ

**shamefaced** (adv.) በእፍረት ፡ ተገትሮ
He stood there shamefaced when his deception was discovered. ማጭበርበሩ ፡ በተነቃበት ፡ ጊዜ ፡ በእፍረት ፡ ተገትሮ ፡ ቀረ

**shameful** አሳፋሪ
His conduct is shameful. አድራጎቱ ፡ አሳፋሪ ፡ ነው

**shamefully, behave ~** አሳፋሪ ፡ ምግባር ፡ ፈጸመ
The enemy behaved shamefully when they occupied the country. ጠላት ፡ አገሪቱን ፡ በወረረ ፡ ጊዜ ፡ አሳፋሪ ፡ ምግባር ፡ ፈጸመ

**shameless** እፍረተ ፡ ቢስ
His shameless behavior shocked everyone. እፍረተ ፡ ቢስ ፡ ሥራው ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ እፍረት ፡ ላይ ፡ ጣለው

**shank** ቅልጥም
His shanks are thin. ቅልጥሞቹ ፡ ቀጭን ፡ ናቸው

**shanty** ደሳሳ ፡ ጎጆ
The beggar lives in a shanty. ለማኙ ፡ ደሳሳ ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል

**shape** (v.)
1. ቅርጽ ፡ አበጀ(ለት). He shaped the clay with his fingers. ሸክላውን ፡ በጣቶቹ ፡ ቅርጽ ፡ አበጀለት
2. አዛመደ. Many people shape their ideas to the times. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አስተሳሰባቸውን ፡ ከጊዜው ፡ ጋር ፡ ያዛምዳሉ
3. መራ. The war has shaped the events of the future in many ways. ጦርነት ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ የወደፊት ፡ ሁኔታን ፡ መርቷል
*He shaped his child's character by his own example. ልጁ ፡ እሱን ፡ መስሎ ፡ እንዲወጣ ፡ አድርጎ ፡ አሳደገው

**shape up** መልክ ፡ ያዘ
His plan is shaping up well. እቅዱ ፡ ጥሩ ፡ መልክ ፡ ይዟል

**be shaped**
1. ቅርጽ ፡ አለው. That cloud is shaped like a ship. ያ ፡ ደመና ፡ የመርከብ ፡ ቅርጽ ፡ አለው
2. እንዲስማማ ፡ ሆኖ ፡ ተሠራ. This hat is shaped to your head. ይህ ፡ ባርኔጣ ፡ ለራስህ ፡ እንዲስማማ ፡ ሆኖ ፡ ተሠርቷል

**shape** (n.)
1. ቅርጽ. This pot has the same shape as a pot I saw in Gondar. ይህ ፡ ማሰሮ ፡ በቅርጽ ፡ ጐንደር ፡ ያየሁትን ፡ ማሰሮ ፡ ይመስላል
There were clouds of different shapes in the sky. ሰማዩ ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅርጽ ፡ ያላቸው ፡ ደመናዎች ፡ ነበሩ

2. ተመስለ. The devil appeared in human shape. ሰይጣኑ ፡ በሰው ፡ ተመስሎ ፡ ታየ
3. ሁኔታ ፤ መልክ. The university's finances are in good shape. የዩኒቨርሲቲው ፡ የገንዘብ ፡ ይዞታ ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ (መልክ) ፡ ነው

**(be) in bad shape**
1. ተጫጫነ(ው). +I'm in bad shape because I didn't sleep well. በደንብ ፡ ስላልተኛሁ ፡ ተጫጭኖኛል
2. ተበላሸ. The exterior of the house is in bad shape. ቤቱ ፡ ውጭው ፡ ተበላሽቷል

**(be) in good shape**
His affairs are in good shape. ንግዱ ፡ ደኅና ፡ ይካሄድለታል

**(not be) in good shape** ጤንነት ፡ አልነበረውም
He was not in good shape, and he soon collapsed. ጤንነት ፡ ስላልነበረው ፡ ወዲያው ፡ ተዝለፍልፎ ፡ ወደቀ

**keep oneself in shape** ሰውነቱን ፡ በሚገባ ፡ ጠበቀ
The athlete exercised to keep himself in good shape. ስፖርተኛው ፡ ሰውነቱን ፡ በሚገባ ፡ ለመጠበቅ ፡ ልምምድ ፡ አደረገ

**(be) out of shape**
1. ተበላሸ. The hat is all out of shape. ባርኔጣው ፡ በፍጹም ፡ ተበላሽቷል
2. ሰውነቱን ፡ በሚገባ ፡ አልጠበቀም. He is out of shape; he can't possibly run that far. ሰውነቱን ፡ በሚገባ ፡ ስላልጠበቀ ፡ ያን ፡ ያህል ፡ ለመሮጥ ፡ አይችል ፡ ይሆናል

**take shape** መልክ ፡ ያዘ ፤ መልክ ፡ አገኘ
The incident gradually took shape in his mind so that he was able to explain it clearly. የሆነው ፡ ነገር ፡ አእምሮው ፡ ውስጥ ፡ እያደር ፡ መልክ ፡ ስለያዘ ፡ በደንብ ፡ ሊገልጸው ፡ ቻለ
His plan is taking shape. እቅዱ ፡ መልክ ፡ እያገኘ ፡ ሄዷል
[See also 'tiptop']

**shapeless** ቅጥ ፡ የሌለው
She wore a shapeless dress. ቅጥ ፡ የሌለው ፡ ልብስ ፡ ለብሳለች

**shapely** የሚያስደስት ፡ ቅርጽ ፡ ያለው
The shapely girl was crowned beauty queen. የሚያስደስት ፡ ቅርጽ ፡ ያላት ፡ ልጃገረድ ፡ የውበት ፡ ንግሥት ፡ ተባለች

**share** (vt.)
1. ተካፈለ ፤ ተከፋፈለ. The owners shared the profits with their employees. የንግዱ ፡ ባለቤቶች ፡ ትርፉን ፡ ከሠራተኞቻቸው ፡ ጋር ፡ ተካፈሉ ፡ (ተከፋፈሉ)
2. አለ(ው). The Tigreans and the Amharas share a common tradition. ትግሬዎችና ፡ አማሮች ፡ የጋራ ፡ ባህል ፡ አላቸው
*They shared a room while they were in college. ኮሌጅ ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር

**share** (vi.)
1. ድርሻውን ፡ ሠራ. Everybody shared in making the picnic. ሽርሽሩን ፡ ስናዘጋጅ ፡ ሁሉም ፡ ድርሻውን ፡ ሠርቷል
2. አዋጣ. We all shared in the gift for Almaz. ለአልማዝ ፡ ስጦታ ፡ ሁላችንም ፡ አዋጣን
*Please let me share in paying the expenses. ወጪውን ፡ ላግዛችሁ

**share among themselves** ተከፋፈሉ
They shared a cake among themselves. ኬኩን ፡ ተከፋፈሉት

**share (a) common border** ተዋሰነ
Ethiopia and Sudan share a common border. ኢትዮጵያና ፡ ሱዳን ፡ ይዋሰናሉ

**share out** አከፋፈለ
Share out this money among the men! ይህንን ፡ ገንዘብ ፡ ለሰዎቹ ፡ አከፋፍላቸው
[See also 'blame']

**share** (n.)
1. ድርሻ. Everybody has to pay his share. እያንዳንዱ ፡ ድርሻውን ፡ መክፈል ፡ አለበት
2. አክሲዮን. He owns five hundred shares in the company. በኩባንያው ፡ ውስጥ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ አክሲዮን ፡ አለው
3. የተመደበ(ለት). Do your share of the work! የተመደበልህን ፡ ሥራ ፡ ፈጽም

**take share, take a share** ተካፈለ
You're not taking much share in the conversation. በጨዋታችን ፡ ብዙም ፡ አትካፈል
He takes a share of the company's profit. የኩባንያውን ፡ ትርፍ ፡ ይካፈላል

**sharecropper** ጭሰኛ
He is a sharecropper; he doesn't own his farm. ጭሰኛ ፡ ነው ፤ መሬቱ ፡ የራሱ ፡ አይደለም

**shark** [ሌሎችን ፡ ዓሣዎች ፡ የሚበላ ፡ ትልቅ ፡ የውቅያኖስ ፡ ዓሣ]

**sharp**
1. ሹል. The pencil point is sharp. የእርሳሱ ፡ ጫፍ ፡ ሹል ፡ ነው
2. የሾለ. This box has a sharp corner. ሣጥኑ ፡ የሾለ ፡ ጠርዝ ፡ አለው

3. ስል ፤ ስለታም. Do you have a sharp knife? ስል ፡ (ስለታም) ፡ ቢላዋ ፡ አለህ ?
4. በጣም ፡ ቀጭን. I don't like her sharp voice. ድምጿ ፡ በጣም ፡ ቀጭን ፡ ስለሆነ ፡ ደስ ፡ አይለኝም
5. ኀይለኛ. I felt a sharp pain in my side. ጐኔ ፡ ላይ ፡ ኀይለኛ ፡ ውጋት ፡ ተሰማኝ
6. ድንገተኛ. There is a sharp curve in the road. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ድንገተኛ ፡ መጠምዘዣ ፡ አለ
7. ጉልህ. There is a sharp contrast between night and day. በሌትና ፡ በቀን ፡ መሀከል ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ልዩነት ፡ አለ
8. ብልህ. He is a sharp lawyer. ብልህ ፡ ጠበቃ ፡ ነው
9. እሳት. This child is sharp in arithmetic. ይህ ፡ ልጅ ፡ በቁጥር ፡ እሳት ፡ ነው
10. (= adv.) ባንዴ. There was a sharp drop in the price of corn. የእህል ፡ ዋጋ ፡ ባንዴ ፡ ወረደ
*The sentry kept a sharp watch for the enemy. ዘበኛው ፡ ነቅቶ ፡ ጠላትን ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር
*His eyesight is very sharp. ዓይኑ ፡ ጥሩ ፡ ያያል
*He spoke sharp words to her. በቁጣ ፡ ተናገራት

**sharp** (adv.) ልክ
We have to be there at five o'clock sharp. ልክ ፡ በዐሥሩ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ እዚያ ፡ መገኘት ፡ አለብን

**look sharp** ነቃ ፡ አለ
Look sharp when crossing streets! መንገዶችን ፡ ስታቋርጥ ፡ ነቃ ፡ በል
[See also 'appetite, tongue']

## sharpen
1. ሳለ. You have to sharpen the knife before cutting the meat. ሥጋውን ፡ ከመቍረጥህ ፡ በፊት ፡ ቢላዋውን ፡ መሳል ፡ አለብህ
This puzzle should sharpen your wits. ይህ ፡ የቃላት ፡ ጨዋታ ፡ አእምሮህን ፡ መሳል ፡ አለበት
2. ቀረጸ. Sharpen the pencil for me, please! እስቲ ፡ እርሳሱን ፡ ቅረጽልኝ

**sharpen the appetite** አስራበ
The walk has sharpened my appetite. መንገዱ ፡ አስራበኝ

## sharpener
1. መቅረጫ. The pencil sharpener is broken. እርሳስ ፡ መቅረጫው ፡ ተሰብሯል
2. መሳያ. The knife sharpener does not work. ቢላዋ ፡ መሳያው ፡ አይሠራም

## sharpening መሳል
This knife needs sharpening. ይህ ፡ ቢላዋ ፡ መሳል ፡ አለበት

## sharply
1. ጕልቶ. The tree is sharply defined in outline. የዛፉ ፡ ቅርጽ ፡ ጕልቶ ፡ የሚታይ ፡ ነው
2. ፈጽሞ. His actions contrasted sharply with his words. የሚያደርገውና ፡ የሚናገረው ፡ ፈጽሞ ፡ የተለያየ ፡ ነገር ፡ ነው

**speak sharply** ተቈጣ
Speak sharply to him about his tardiness! ስለ ፡ መዘግየቱ ፡ ተቈጣው

## sharpshooter አነጣጣሪ ፡ ተኳሽ
The sharpshooter brought down a mountain goat. አነጣጣሪው ፡ ተኳሽ ፡ ዋልያውን ፡ ጣለው

## shatter
1. ሰባበረ. The bullet shattered the glass. ጥይቱ ፡ መስታወቱን ፡ ሰባበረው
2. ብትንትኑን ፡ አወጣ. The impetus of the falling rock shattered the concrete. የተናደው ፡ ቋጥኝ ፡ ኀይል ፡ ሲሚንቶውን ፡ ብትንትኑን ፡ አወጣው
3. በጠበጠ. The great mental stress shattered his mind. ከባድ ፡ የአእምሮ ፡ ጭንቀት ፡ መንፈሱን ፡ በጠበጠው

**be shattered** ወደመ
Our hopes were shattered when the boss refused. አለቃችን ፡ እምቢ ፡ ሲል ፡ ተስፋችን ፡ ወደመ

## shave (vt.)
1. ላጨ. Who shaved your beard? ጢምህን ፡ ማን ፡ ላጨህ ?
2. በጣም ፡ ተጠጋ. The car shaved the corner. መኪናው ፡ ወደ ፡ መጠምዘዣው ፡ በጣም ፡ ተጠጋ

**shave** (vi.) ተላጨ
Do you shave every morning? ሁልጊዜ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ትላጫለህ ?

**shave off** ተላጨ
He shaved off his beard. ጢሙን ፡ ተላጨ

## shave (n.), give a ~ ላጨ
A sharp razor gives a good shave. ስለታም ፡ ምላጭ ፡ በደንብ ፡ ይላጫል
*That was a close shave! ለጥቂት ፡ ተረፍኩ

## shaver ጢም ፡ መላጫ
Do you have an electric shaver? የኤሌክትሪክ ፡ ጢም ፡ መላጫ ፡ አለህ ?

## shaving(s) ፍቅፋቂ
The metal shavings are collected and melted. የብረት ፡ ፍቅፋቂ ፡ ሰብስበው ፡ ያቀልጣሉ

**wood shavings** ፍቅፋቂ
The wood shavings caught fire. ፍቅፋቂው ፡ በእሳት ፡ ተያያዘ

**shaving brush** የጢም ፡ ብሩሽ
The shaving brush is gone. የጢም ፡ ብሩሹ ፡ ጠፍቷል

**shawl** ያንገት ፡ ልብስ
The girl bought a shawl in the market. ልጅቱ ፡ ገበያ ፡ ሄዳ ፡ ያንገት ፡ ልብስ ፡ ገዛች

**she**
1. እሷ ፤ እርሷ. She is upstairs. እሷ ፡ ፎቅ ፡ ላይ ፡ ነች
2. ሴት. The dog is a she. ውሻዋ ፡ ሴት ፡ ናት
Is the baby a he or a she? ሕፃኑ ፡ ወንድ ፡ ነው ፡ ሴት ?
[See also 'donkey']

**sheaf** (sheaves)
1. ነዶ. The farmer stacked the sheaves of grain. ገበሬው ፡ የእህል ፡ ነዶ ፡ ከመረ
2. ክምር. I handed her a sheaf of bills. አንድ ፡ ክምር ፡ የሒሳብ ፡ ደረሰኝ ፡ ሰጠኋት

**shear** (v.) ሸለተ
They shear wool from the sheep once a year. በጎቹን ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይሸልቷቸዋል

**shear off** ቈራረጠ
The blade of the machine can shear off large pieces of steel. የመሣሪያው ፡ ስለት ፡ ትላልቅ ፡ የዐረብ ፡ ብረት ፡ ሊቈራርጥ ፡ ይችላል

**shears** ትልቅ ፡ መቀስ
Give me shears to cut this thick paper! ይህን ፡ ወፍራም ፡ ወረቀት ፡ የምቈርጥበት ፡ ትልቅ ፡ መቀስ ፡ ስጠኝ

**sheath**
1. አፎት. Put the dagger in its sheath! ሳንጃውን ፡ አፎቱ ፡ ውስጥ ፡ ክተተው
2. ሽፋን. The caterpillar wound a silken sheath about itself. አባ ፡ ጨጓሬው ፡ የሐር ፡ ሽፋኑን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ጠመጠመ

**sheathe** ሰገባ ፡ ውስጥ ፡ ከተተ
He sheathed his sword. ጐራዴውን ፡ ሰገባው ፡ ውስጥ ፡ ከተተ

**sheaves**, see **sheaf**

**shed** (shed), vt.
1. ገፈፈ. The snake shed its skin. እባቡ ፡ ቆዳውን ፡ ገፈፈ
2. ጣለ. One kind of deer sheds its horns. ቀንዶቹን ፡ የሚጥል ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ አጋዘን ፡ አለ
3. አፈሰሰ. He shed his blood for his country. ደሙን ፡ ላገሩ ፡ አፈሰሰ
4. አወለቀ. He began to shed his clothes as the air got hotter. ሙቀቱ ፡ እየበረታ ፡ በሄደ ፡ ቍጥር ፡ ልብሱን ፡ ማውለቅ ፡ ጀመረ
5. (= intr.) ረገፈ. The trees shed their leaves. ዛፎቹ ፡ ቅጠላቸው ፡ ይረግፋል
*She shed bitter tears. አምርራ ፡ አለቀሰች
[See also 'light']

**shed** (n.) መጠለያ
Put the car in a shed! መኪናዋን ፡ መጠለያ ፡ ሥር ፡ አቁማት

**sheen** ወዝ
The sheen of the horses' coats show that they are well cared for. የፈረሶቹ ፡ ወዝ ፡ በደንብ ፡ የተያዙ ፡ መሆናቸውን ፡ ያሳያል

**have a sheen** አብረቀረቀ
That girl's hair has a sheen like gold. ያቺ ፡ ልጃገረድ ፡ እንደ ፡ ወርቅ ፡ የሚያብረቀርቅ ፡ ጸጕር ፡ አላት

**sheep** በግ
The sheep graze in the field. በጎቹ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ይግጣሉ

**sheepish** የእፍረት
Her sheepish smile showed she knew that what she said was stupid. የእፍረት ፡ ፈገግታዋ ፡ የተናገረችው ፡ የማይረባ ፡ መሆኑን ፡ እንዳወቀች ፡ አስረዳ

**have a sheepish look** አፈር ፡ አለ
He had a sheepish look when she caught him in a lie. መዋሸቱን ፡ ባወቀችበት ፡ ጊዜ ፡ አፈር ፡ አለ

**sheepskin** ከበግ ፡ ቆዳ ፡ የተሠራ
He wore a sheepskin coat. ከበግ ፡ ቆዳ ፡ የተሠራ ፡ ኮት ፡ ለብሷል

**sheer**
1. ስስ. The stockings are made of sheer silk. የእግር ፡ ሹራቦቹ ፡ ከስስ ፡ ሐር ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው
2. ፍጹም. That would be sheer madness. ይህ ፡ ፍጹም ፡ እብደት ፡ ነው
*It's a sheer drop of 2,000 feet. ሁለት ፡ ሺ ፡ ጫማ ፡ ርቀት ፡ ያለው ፡ ዐዘቅት ፡ ነው

**by sheer chance** እንዳጋጣሚ
By sheer chance, I discovered the fraud. እንዳጋጣሚ ፡ ማጭበርበሩን ፡ ደረስኩበት
[See also 'default']

**sheet** አንሶላ
Shall I change the sheets, too? አንሶላውንም ፡ ልለውጠው ?

*Throw a sheet over the bed! አልጋውን ፡ አንጥፈው

**sheets of metal** ጠፍጣፋ ፡ ብረት
The sides of a ship are made of sheets of metal. የመርከብ ፡ ጐንና ፡ ጐን ፡ ከጠፍጣፋ ፡ ብረት ፡ የተሠራ ፡ ነው
[See also 'paper, water']

**(be) sheeted** ተለበጠ
The statue is sheeted with lead. ሐውልቱ ፡ በእርሳስ ፡ ተለብጧል

**shelf** (shelves)
1. መደርደሪያ. The books are on a shelf. መጻሕፍቱ ፡ በመደርደሪያ ፡ ላይ ፡ ናቸው
2. እርከን. The house is built on a shelf of rock. ቤቱ ፡ የተሠራው ፡ በቋጥኝ ፡ እርከን ፡ ላይ ፡ ነው

**shell** (v.)
1. ፈለፈለ. She shelled the beans before she cooked them. ባቄላውን ፡ ከመቀቀሏ ፡ በፊት ፡ ፈለፈለችው
Do you want to shell the nuts? ለውዙን ፡ መፈልፈል ፡ ትፈልጋለህ ?
2. ላጠ. I have to shell the eggs. እንቁላሉን ፡ መላጥ ፡ አለብኝ
3. በመድፍ ፡ ደበደበ. The enemy attacked after shelling the town. ከተማዋን ፡ በመድፍ ፡ ከደበደበ ፡ በኋላ ፡ ጠላት ፡ አጠቃ

**shell** (n.)
1. ቅርፊት. The shell of the nut was very soft. የለውዙ ፡ ቅርፊት ፡ በጣም ፡ ለስላሳ ፡ ነበር
2. ዛጐል. We found many shells on the beach. በባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ብዙ ፡ ዛጐል ፡ አገኘን
3. ልብስ. The tortoise has a hard shell. የኤሊ ፡ ልብስ ፡ ድንጋይ ፡ ነው
4. የመድፍ ፡ ጥይት. A shell exploded near our house. ቤታችን ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ የመድፍ ፡ ጥይት ፡ ፈነዳ
5. ፍርግርግ. Only the shell of the house was left after the fire. ከቃጠሎው ፡ በኋላ ፡ የቤቱ ፡ ፍርግርግ ፡ ብቻ ፡ ቀረ

**rifle shell** ቀለሀ
We found some rifle shells on the ground. መሬት ፡ ላይ ፡ ጥቂት ፡ ቀለሀ ፡ አገኘን

**shelter** (vt.)
1. ከለለ. These trees shelter the house from wind. እነዚህ ፡ ዛፎች ፡ ቤቱን ፡ ከነፋስ ፡ ይከልሉታል
2. መጠጊያ ፡ ሰጠ. They sheltered and fed us. ምግብና ፡ መጠጊያ ፡ ሰጡን
3. አስጠጋ. The bushy land shelters small animals. ደን ፡ የለበሰው ፡ መሬት ፡ ትናንሽ ፡ እንስሳትን ፡ ያስጠጋል
4. ደበቀ. He sheltered the prisoner from the police. እስረኛውን ፡ ከፖሊስ ፡ ደበቀው
5. አኖረ. Marshy land shelters many small animals. ረግረግ ፡ መሬት ፡ ብዙ ፡ ትንንሽ ፡ እንስሳትን ፡ ያኖራል

**shelter** (vi.) ተጠለለ
The sheep sheltered from the hot sun in the shade of the haystack. በጓ ፡ ከሚያቃጥለው ፡ ፀሐይ ፡ በድርቆሽ ፡ ክምር ፡ ጥላ ፡ ተጠለለች

**shelter** (n.)
1. መጠለያ. A shelter was built at the bus stop. አውቶቡሱ ፡ መቆሚያ ፡ ላይ ፡ መጠለያ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር
Trees are a shelter from the sun. ዛፎች ፡ ከፀሐይ ፡ መጠለያ ፡ ናቸው
2. የሚጠለልበት ፡ ስፍራ. We sought shelter from the rain. ከዝናቡ ፡ የምንጠለልበት ፡ ስፍራ ፡ ፈለግን
3. ተገን. The people were told to seek shelter when there was an air raid. ያየር ፡ ወረራ ፡ ሲመጣ ፡ ሕዝቡ ፡ ተገን ፡ እንዲይዝ ፡ ተነገረው

**take shelter** ተጠለለ
We took shelter from the rain. ከዝናቡ ፡ ተጠለልን

**sheltered** (adj.)
*He leads a sheltered life. ያለ ፡ ስጋት ፡ ይኖራል

**shelve** ወደ ፡ ጐን ፡ አለ
They shelved the problem instead of solving it. ለነገሩ ፡ መፍትሔ ፡ እንደ ፡ ማግኘት ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ አሉት

**shelves**, see **shelf**

**shepherd** (v.) ጠበቀ
He will shepherd his flock. መንጋውን ፡ ይጠብቃል

**shepherd** (n.) እረኛ
The shepherd hums while guarding cattle. እረኛ ፡ ከብት ፡ ሲጠብቅ ፡ ያንጐራጉራል

**shield** (v.)
1. ጋረደ. He shielded his eyes with his hand. ዓይኖቹን ፡ በእጁ ፡ ጋረደ
2. ተከላከለ. He shielded his child from the dog. ልጁን ፡ ከውሻ ፡ ተከላከለ

**shield** (n.)
1. ጋሻ. He bought an old shield. አሮጌ ፡ ጋሻ ፡ ገዛ

2. መከላከያ. Vaccination is a shield against smallpox. ክትባት ፡ የፈንጣጣ ፡ መከላከያ ፡ ነው

**shift** (vt.)

1. ለወጠ. He shifted the gears. ማርሹን ፡ ለወጠ
2. አሳለፈ. We have to shift the meeting to Tuesday. ስብሰባውን ፡ ወደ ፡ ማክሰኞ ፡ ማሳለፍ ፡ አለብን
3. አላከከ. He tried to shift the blame to me. ጥፋቱን ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ለማላከክ ፡ ሞከረ

**shift** (vi.) አቅጣጫውን ፡ ለወጠ
The wind shifted and is now blowing from the north. ነፋሱ ፡ አቅጣጫውን ፡ ለውጦ ፡ አሁን ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ መንፈስ ፡ ጀምሯል

**shift for oneself** ራሱን ፡ ችሎ ፡ አደረ
When their father died, the children had to shift for themselves. አባታቸው ፡ ሲሞት ፡ ልጆቹ ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ ማደር ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው
[See also 'ground']

**shift** (n.)

1. መለወጫ. Where is the gear shift? የማርሹ ፡ መለወጫ ፡ የት ፡ ጋ ፡ ነው ?
2. (= to shift) መለወጥ. This will mean a shift in my plans. ይህ ፡ አቅዶን ፡ መለወጥ ፡ ይሆንብኛል
3. ተረኞች. The night shift reported. የሌሊት ፡ ተረኞች ፡ መጡ
*Our workers work in three shifts. ሠራተኞቻችን ፡ በሦስት ፡ ቅያሬ ፡ እየተፈራረቁ ፡ ይሠራሉ

**make shift**
*We will have to make shift with oil since we have no butter. ቅቤ ፡ ስለሌለን ፡ በቅቤ ፡ ፈንታ ፡ በዘይት ፡ መጠቀም ፡ አለብን

**shimmer** አንጸባረቀ
The lake shimmered in the morning light. ሐይቁ ፡ በጧት ፡ ብርሃን ፡ አንጸባረቀ

**shin** ቅልጥም
He hurt his shin. ቅልጥሙን ፡ ተጐዳ

**shinbone** ቅልጥም
My shinbone is broken. ቅልጥሜ ፡ ተሰበረ

**shine** (shone), vt.

1. ጠረገ. I have to shine my shoes. ጫማዬን ፡ መጥረግ ፡ አለብኝ
2. ወለወለ. The maid shines the silverware. ገረዲቱ ፡ ከብር ፡ የተሠሩትን ፡ የምግብ ፡ እቃዎች ፡ ትወለውላለች

**shine** (vi.)

1. አበራ. Her eyes were shining with joy. ዓይኖቿ ፡ በደስታ ፡ ያበሩ ፡ ነበር
2. ወጣ. The sun isn't shining today. ዛሬ ፡ ፀሐይዋ ፡ አልወጣችም
3. ብርሃን ፡ ሰጠ. The sun shines. ፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ትሰጣለች
*He shines in arithmetic. በሒሳብ ፡ ጐበዝ ፡ ነው
*He doesn't shine in conversation. ጨዋታ ፡ አያውቅም

**shine into the eyes** አንጸባረቀ(በት)
Wear dark glasses so the sun won't shine in your eyes. ፀሐይ ፡ እንዳያንጸባርቅብህ ፡ የፀሐይ ፡ መነጽር ፡ አድርግ

**shine the light** አበራ
Shine the light on the door while I try to find the keyhole. የቁልፉ ፡ ቀዳዳ ፡ እንዲታየኝ ፡ በሩ ፡ ላይ ፡ አብራልኝ

**shine** (n.) ማብረቅረቅ
The shine of his shoes reflects one's face. የጫማው ፡ ማብረቅረቅ ፡ ፊት ፡ ያሳያል
*The postman comes in rain or shine. ፖስተኛው ፡ ቢዘንብም ፡ ቢያበራም ፡ ይመጣል

**have a shine** አብለጨለጨ
Silk has a shine. ሐር ፡ ያብለጨልጫል

**shingle**

1. የተቈራረጠ ፡ ሳንቃ. The house is roofed with shingles. የጣሪያው ፡ ክዳን ፡ ከተቈራረጡ ፡ ሳንቃዎች ፡ የተሠራ ፡ ነው
2. የስም ፡ ሰሌዳ. The doctor hung out his shingle and sat down to wait for patients. ሐኪሙ ፡ የስሙን ፡ ሰሌዳ ፡ አንጠልጥሎ ፡ በሽተኞችን ፡ ተጠባበቀ

**shining**
*The children looked on with shining eyes. ሕፃናቱ ፡ ዓይናቸውን ፡ እያቁለጨለጩ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር

**shiny**

1. የሚያብረቀርቅ. Here is a shiny new penny! አዲስ ፡ የሚያብረቀርቅ ፡ ሳንቲም ፡ ይኸውልህ
2. ፀሐያማ. The shiny day made everyone happy. ፀሐያማው ፡ ቀን ፡ ሁሉንም ፡ አስደሰተ

**ship** (shipped), v.

1. ላከ. He boxed the books before he shipped them. መጽሐፎቹን ፡ ከመላክ ፡ በፊት ፡ በሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አስገባቸው

2. ጫነ (ተጫነ). The goods must be shipped by boat; they are too heavy to be shipped by plane. እቃው ፡ በጀልባ ፡ መጫን ፡ አለበት ፤ በአውሮ ፕላን ፡ ለመጫን ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ነው

**ship off** ላከ
He shipped his children off to camp. ልጆቹን ፡ ወደ ፡ መዝናኛ ፡ ሰፈር ፡ ላካቸው

**ship** (n.) መርከብ
When does the ship arrive? መርከቡ ፡ የሚገባ ው ፡ መቼ ፡ ነው ?

**shipment** እቃ
This shipment is designated for Ethiopia. ይህ ፡ እቃ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚሄድ ፡ ነው
*We've just received a new shipment of shoes. አዳዲስ ፡ ጫማ ፡ አሁን ፡ ገና ፡ ደረሰን
*A thousand boxes of oranges were ready for shipment. አንድ ፡ ሺ ፡ ሣጥን ፡ ብርቱካን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሊላክ ፡ ተዘጋጅቷል

**shipping** ጉዞ
Make these books up into bundles for shipping! ለጉዞ ፡ እንዲመቹ ፡ እነዚህን ፡ መጻሕፍት ፡ አን ድ ፡ ላይ ፡ እያደረግክ ፡ አሰራቸው

**shipwreck** (v.) ሰባበረ
A storm shipwrecked the vessel. ዓውሎ ፡ ነፋ ስ ፡ መርከቧን ፡ ሰባበራት

**shipwreck** (n.)
1. የመርከብ ፡ መስጠም ፤ የመርከብ ፡ አደጋ. The news of the shipwreck grieved everyone. የመርከ ቧ ፡ መስጠም ፡ ዜና ፡ ሁሉንም ፡ አሳዘነ
Only two people were saved from the shipwreck. ከመርከቡ ፡ አደጋ ፡ የተረፉ ፡ ሁለት ፡ ሰዎ ች ፡ ብቻ ፡ ነበሩ
2. መጨናገፍ. The shipwreck of his plan discouraged him. የእቅዱ ፡ መጨናገፍ ፡ ተስፋ ፡ አስቈረጠው

**shipshape** ጥሩ
Our office is in shipshape condition. መሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ በጥሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተደራጀ ፡ ነው

**shirk** ሸሸ
He shirks work all the time. ሥራ ፡ ይሸሻል ፡ (ሥራ ፡ እርሙ ፡ ነው)

**shirt** ሸሚዝ
He tore his shirt on a nail. ሸሚዙን ፡ ምስማር ፡ ቀደደበት

**shiver** (v.)
1. በርዶት ፡ ተንቀጠቀጠ. He shivers under his blanket. ብርድ ፡ ልብስ ፡ ቢለብስም ፡ በ ርዶት ፡ ይንቀጠቀጣል
2. (= trans.) አንቀጠቀጠ. +The child shivered with cold. ሕፃኑን ፡ ብርድ ፡ አንቀጠቀጠው
**make shiver** ዘገነነ(ው)
His touch makes me shiver. ሲነካኝ ፡ ይዘገንነ ኛል

**shiver** (n.), **give the shivers** ሰቀጠጠ
The sight of snakes gives me the shivers. እባብ ፡ ሳይ ፡ ይሰቀጥጠኛል

**shock** (v.)
1. አሰቀቀ. Her behavior shocks me. ምግባሯ ፡ ያሰቅቀኛል
2. አሳፈረ ፤ እፍረት ፡ ላይ ፡ ጣለ. The child's bad language shocks everyone. የልጁ ፡ የብ ልግና ፡ አነጋገር ፡ ሁሉን ፡ ያሳፍራል ፡ (እፍረ ት ፡ ላይ ፡ ይጥላል)
3. አሸበረ. Hitler's many atrocities shocked the world. የሂትለር ፡ ግፍና ፡ ጭካኔ ፡ ዓለምን ፡ አ ሸበረው
**be shocked** በጣም ፡ ደነገጠ
We were shocked by the news. ወሬውን ፡ ስንሰ ማ ፡ በጣም ፡ ደነገጥን

**shock** (n.)
1. ድንጋጤ. His respiration is irregular due to shock. ከድንጋጤ ፡ የተነሣ ፡ ትንፋሹ ፡ ቁርጥ ፡ ቁ ርጥ ፡ ይላል
2. ኀይለኛነት. The shock of the explosion was felt for miles around. የፈንጂው ፡ ኀይለኛነት ፡ ለብዙ ፡ ማይል ፡ ተሰምቶ ፡ ነበር
*The shock of the fall made him lose consciousness. ሲወድቅ ፡ መሬቱ ፡ የመታው ፡ ነፍ ሱን ፡ አሳተው
**be a shock to** አስደነገጠ
His death was a great shock to us all. የሱ ፡ ሞ ት ፡ ሁላችንንም ፡ በጣም ፡ አስደነገጠን
**earthquake shock** የመሬት ፡ መንቀጥቀጥ
Earthquake shocks occur often in Japan. የመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በጃፓን ፡ ላይ ፡ ይደርሳል
**get a shock** ኮረንቲ ፡ ሳበው
If you touch that wire, you'll get a shock. ያንን ፡ ሽቦ ፡ ከያዝክ ፡ ኮረንቲ ፡ ይስብሃል
[See also 'rude']

**shock treatment** የኮረንቲ ፡ ሕክምና
He needs shock treatment to cure his insan-

ity. ከእብደቱ ፡ ለመዳን ፡ የኮረንቲ ፡ ሕክምና ፡ ያስፈልገዋል

**shock troops** መቺ ፡ ኀይል
Shock troops swarmed over our defenses. መቺ ፡ ኀይል ፡ ምሽጋችንን ፡ ወረረው

**shoddy** መናኛ
The shoes he bought were so shoddy that they fell apart when he got them wet. የገዛው ፡ ጫማ ፡ መናኛ ፡ ስለሆነ ፡ እርጥብ ፡ ሲነካው ፡ ተበጣጠሰ

**shoe** (v.) ጫማ ፡ አስገባ
I need someone to shoe my horse. ለፈረሴ ፡ ጫማ ፡ የሚያስገባልኝ ፡ ሰው ፡ እፈልጋለሁ

**shoe** (n.) ጫማ
I need a pair of shoes. ጫማ ፡ ያስፈልገኛል
The horse lost one shoe. የፈረሱ ፡ አንዱ ፡ ጫማ ፡ ጠፍቷል

**be in someone's shoes**
*I wouldn't be in his shoes for anything. እንኳን ፡ እሱን ፡ አላደረገኝ

**fill someone's shoes** ተካ
She felt that no stepmother could ever fill her late mother's shoes. የሞተችውን ፡ እናቷን ፡ የሚተካ ፡ ምንም ፡ የእንጀራ ፡ እናት ፡ እንደሌለ ፡ ተሰማት

**shoehorn** የጫማ ፡ ማንኪያ
I need a shoehorn to put these tight shoes on. እነዚህን ፡ ጠባብ ፡ ጫማዎች ፡ የማስገባበት ፡ የጫማ ፡ ማንኪያ ፡ እፈልጋለሁ

**shoelace** የጫማ ፡ ማሰሪያ
My shoelace broke. የጫማዬ ፡ ማሰሪያ ፡ ተበጥሷል

**shoemaker** ጫማ ፡ ሰፊ
I am taking my shoes to the shoemaker. ጫማዬን ፡ ለማሠራት ፡ ወደ ፡ ጫማ ፡ ሰፊው ፡ ይዤ ፡ መሄዴ ፡ ነው

**shoe polish** የጫማ ፡ ቀለም
Buy more shoe polish for me! ተጨማሪ ፡ የጫማ ፡ ቀለም ፡ ግዛልኝ

**shoeshine**
*How much is a shoeshine? አንድ ፡ ጫማ ፡ ለማስጠረግ ፡ ስንት ፡ ይከፈላል ?

**shoeshine boy** ሊስትሮ
The shoeshine boys were quarreling. ሊስትሮዎች ፡ ይጣሉ ፡ ነበር

**shoestring** የጫማ ፡ ማሰሪያ
His shoestring broke when he tied his shoes. ጫማውን ፡ ሲያስር ፡ የጫማ ፡ ማሰሪያው ፡ ተበጠሰ

**on a shoestring**
*I went to Ethiopia on a shoestring. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስሄድ ፡ የያዝኩት ፡ ገንዘብ ፡ ትንሽ ፡ ነበር

**shone**, see **shine**

**shoo** እሽ ፡ አለ
John shooed the chickens. ጆን ፡ ዶሮቹን ፡ እሽ ፡ አለ

**shook**, see **shake**

**shoot** (shot), vt.
1. መታ. He shot the robber with a pistol. ሌባውን ፡ በሽጉጥ ፡ መታው
2. ገደለ. The hunter shot a lion. አዳኙ ፡ አንበሳ ፡ ገደለ
3. በጥይት ፡ ገደለ(ተገደለ). The collaborator was shot by the patriots. ግብረ ፡ አበሩ ፡ ባርበኞቹ ፡ እጅ ፡ በጥይት ፡ ተገደለ
4. ረሸነ. Shooting cattle without any good reason is an injustice. የቀንድ ፡ ከብቶችን ፡ ያለ ንዳች ፡ ምክንያት ፡ መረሸን ፡ ግፍ ፡ ነው
5. ሰደደ ፤ ወረወረ. He shot an arrow into the air. ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንድ ፡ ቀስት ፡ ሰደደ ፡ (ወረወረ)
6. አነሣ. I intend to shoot pictures at the parade. በሰልፉ ፡ ላይ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ለማንሣት ፡ እፈልጋለሁ
7. አስገባ. He shot six baskets in the basket game. በቅርጫት ፡ ኳስ ፡ ጨዋታው ፡ ጊዜ ፡ ስድስት ፡ ኳስ ፡ አስገባ
*He shot question after question at us. የጥያቄ ፡ መዓት ፡ አወረደብን

**shoot** (vi.)
1. ተኰሰ. Don't shoot! አትተኵስ
2. ተወረወረ. The meteor shot across the sky. ተወርዋሪው ፡ ኮከብ ፡ በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ተወረወረ
3. መጠቀ. The rocket shot upwards. ሮኬቷ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ መጠቀች

**be shot** በጥይት ፡ ተደበደበ
The renegade was captured and shot. ከዳተኛው ፡ ተይዞ ፡ በጥይት ፡ ተደበደበ

**shoot ahead** ሽው ፡ አለ
The car shot ahead and was soon out of sight. መኪናው ፡ ሽው ፡ ብሎ ፡ ላይን ፡ ጠፋ

**shoot angry glances**
They shot angry glances at us. ገላመጡን

**shoot away** ተኰሶ ፡ ጨረሰ
He shot away all his ammunition. ጥይቱን ፡ ሁሉ ፡ ተኵሶ ፡ ጨረሰ

**shoot away at each other** እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተታኰሱ
They shot away at each other, but didn't hit a thing. እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተታኰሱ ፤ ግን ፡ ማንም ፡ አልተመታም

**(be) shot away** በጥይት ፡ ተመቶ ፡ ወለቀ
The lower part of his face was shot away. በጥይት ፡ ተመቶ ፡ አገጩ ፡ ወለቀ

**shoot down**
1. ተኩሶ ፡ ጣለ ፤ ተኩሶ ፡ አወረደ. The enemy shot down three planes. ጠላት ፡ ሦስት ፡ አውሮፕላን ፡ ተኩሶ ፡ ጣለ ፡ (አወረደ)
2. ተኩሶ ፡ ገደለ. They shot him down in cold blood. በጭካኔ ፡ ተኩሰው ፡ ገደሉት

**(be) shot down** በጥይት ፡ ተመቶ ፡ ወደቀ
Four of the enemy's planes were shot down. አራት ፡ የጠላት ፡ አውሮፕላኖች ፡ በጥይት ፡ ተመተው ፡ ወደቁ

**shoot forth** አበበ
Buds shoot forth in the spring. በጸደይ ፡ ቡቃዮች ፡ ያብባሉ

**shoot out** (vt.)
1. አወጣ. The snake shot out its tongue. እባቡ ፡ ምላሱን ፡ አወጣ
2. በጥይት ፡ አጠፋ. The bandit shot out the lights. ቀማኛው ፡ መብራቱን ፡ በጥይት ፡ አጠፋው

**shoot out** (vi.) ተፈትልኮ ፡ ወጣ
The horses shot out of the barn. ፈረሶቹ ፡ ከጋጡ ፡ ተፈትልከው ፡ ወጡ

**shoot (it) out** ተታኰሱ
The two gunmen shot it out in the middle of the street. ሁለቱ ፡ ሽጉጥ ፡ የያዙ ፡ ሰዎች ፡ መንገዱ ፡ መሀል ፡ ተታኰሱ

**shoot out new leaves** አቈጠቈጠ
The plant shoots out new leaves. ዕፁ ፡ አቈጥቍጧል

**shoot past one**
The car shot past us. መኪናው ፡ ባጠገባችን ፡ ሽው ፡ ብሎ ፡ አለፈ

**shoot up** (vt.) እንዳገኘ ፡ ተኰሰ
The drunken soldier shot up the town. ሰካራሙ ፡ ወታደር ፡ ከተማው ፡ ውስጥ ፡ እንዳገኘ ፡ ተኰሰ

**shoot up** (vi.)
1. ተወረወረ. Flames shoot up from a burning house. ከተቃጠለው ፡ ቤት ፡ ነበልባል ፡ ይወረወራል
2. ሰማይ ፡ ደረሰ. Rents have shot up in the last few months. ባለፉት ፡ ጥቂት ፡ ወራት ፡ ውስጥ ፡ የቤት ፡ ኪራይ ፡ ሰማይ ፡ ደርሷል
3. ተመዘዘ ፤ ተመነደገ. He shot up after the age of ten. ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ ዕድሜው ፡ በኋላ ፡ ተመዘዘ ፡ (ተመነደገ)
[See also 'sight']

**shoot** (n.), **new ~** ለጋ ፡ ቅርንጫፍ
See the new shoots on that bush! በዚያ ፡ ቁጥቋጦ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ለጋ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ተመልከት

**bamboo shoot** ለጋ ፡ ሸምበቆ
Bamboo shoots are eaten by the Chinese. ቻይናዎች ፡ ለጋ ፡ ሸምበቆ ፡ ይበላሉ

**send out shoots** አቈጠቈጠ
The rosebushes send out shoots after being pruned. የጽጌ ፡ ረዳው ፡ ቁጥቋጦ ፡ ከተገረዘ ፡ በኋላ ፡ ያቈጠቍጣል

**shooting**
*The shooting took place in the center of town. የተታኰሱት ፡ ከተማው ፡ መኻል ፡ ነው

**be executed by shooting** በጥይት ፡ ተደበደበ
The murderer was executed by shooting. ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ በጥይት ፡ ተደበደበ

**shooting star** ተወርዋሪ ፡ ኮከብ
Did you see the shooting star? ተወርዋሪውን ፡ ኮከብ ፡ አየኸው ?

**shop** (shopped), v. ገዛ ፤ ገበየ
We shop at the market. ከገበያ ፡ እንገዛለን
We went to the market and shopped. ገበያ ፡ ሄደን ፡ ገበየን

**shop around** በየሱቅ ፡ ዞሮ ፡ አየ
I want to shop around before I buy the present. ስጦታውን ፡ ከመግዛቴ ፡ በፊት ፡ በየሱቁ ፡ ዞሬ ፡ ማየት ፡ እፈልጋለሁ

**shop** (n.)
1. ሱቅ. There are many shops on this street. በዚህ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሱቆች ፡ አሉ
2. ቤት. He works in a carpenter's shop. አናጢ ፡ ቤት ፡ ይሠራል

**closed shop** [ለማኅበርተኞች ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ የሥራ ፡ ቦታ]

**set up shop** መደብር ፡ ከፈተ
He set up shop as a dealer in books. አንድ ፡ የመጽሐፍ ፡ መደብር ፡ ከፈተ

**talk shop** ስለ ፡ ሥራቸው ፡ ተወያዩ
Teachers like to meet to talk shop. መምህራን ፡ ተገናኝተው ፡ ስለ ፡ ሥራቸው ፡ መወያየት ፡ ይወዳሉ
[See also 'repair']

**shopkeeper** ባለ ፡ ሱቅ
The shopkeepers had to pay a special tax. ባለ ፡ ሱቆቹ ፡ ልዩ ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ ነበረባቸው

**shoplifter** የሱቅ ፡ ሌባ
Shoplifters are sent to jail. የሱቅ ፡ ሌቦች ፡ ይታሰራሉ

**shopper** ገበያተኛ
The shoppers don't come till nine. ገበያተኞቹ ፡ ከሦስት ፡ ሰዓት ፡ በፊት ፡ አይመጡም

**shopping, go** ~ እቃ ፡ ሊገዛዛ ፡ መጣ ፤ ገበያ ፡ ወጣ
Last night I went shopping. ትላንትና ፡ ማታ ፡ እቃ ፡ ልገዛዛ ፡ ወጥቼ ፡ ነበር ፡ (ገበያ ፡ ወጥቼ ፡ ነበር)
She has her mind set on going shopping today. ዛሬ ፡ ገበያ ፡ በመውጣት ፡ ቈርጣ ፡ ተነሥታለች

**shopping bag** ዘምቢል
She put it in a shopping bag. ዘምቢል ፡ ውስጥ ፡ ከተተችው

**shopping center** አራዳ ፡ ሱቅ
Let's go to the shopping center! ወደ ፡ አራዳ ፡ ሱቅ ፡ ብቅ ፡ እንበል

**(be) shopworn**
This shirt is shopworn. ይህ ፡ ሸሚዝ ፡ ሱቅ ፡ ውስጥ ፡ ተንገላቷል

**shore** (v.), ~ **up** ደገፈ
They shored up the wall with wooden beams. ግድግዳውን ፡ በዕንጨት ፡ ምሰሶ ፡ ደገፉት

**shore** (n.) ዳርቻ
The shore of the lake is muddy. የሐይቁ ፡ ዳርቻ ፡ ጨቅይቷል

**shoreline** የባሕር ፡ ዳርቻ
Due to the action of the waves, the shoreline is gradually receding. ከሞገዱ ፡ የተነሣ ፡ የባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሸሽቷል

**short** (adj.)
1. አጭር. Give me a short stick! አንድ ፡ አጭር ፡ ዱላ ፡ ስጠኝ
He did his work in a short time. ሥራውን ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አከናወነ
She is very short for fourteen. ካሥራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ ናት
2. ያጠረ. She wears her dresses too short. አለ ፡ ቅጥ ፡ ያጠረ ፡ ልብስ ፡ ትለብሳለች
3. ጥቂት. He worked here for a short period. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እዚህ ፡ ይሠራ ፡ ነበር
4. (= adv.) ለጥቂት ፡ ጊዜ. He paid me a short visit. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ጐበኘኝ
*We have a short supply of food. ጥቂት ፡ ምግብ ፡ አለን

**short of** ከ - - - በቀር
They commit every crime short of murder. ነፍስ ፡ ከማጥፋት ፡ በቀር ፡ ሁሉንም ፡ ዓይነት ፡ ወንጀል ፡ ይፈጽማሉ

**(with) short quick steps** ቀብ ፡ ቀብ ፡ እያለ
She walked with short quick steps. ቀብ ፡ ቀብ ፡ እያለች ፡ ተራመደች

**(a) short time ago** ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት
I was there a short time ago. ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ እዚያ ፡ ነበርኩ

**be in short supply** በብዛት ፡ አይመጣም
These coats are in short supply. የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ኮት ፡ በብዛት ፡ አይመጣም

**be short** ጐደለ
+His accounts are short five dollars. ከሒሳቡ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ጐድሏል

**be short in** ጐደለ(በት)
+The cashier is short in his accounts. ገንዘብ ፡ ያዡ ፡ ገንዘብ ፡ ጐድሎበታል

**be short of**
1. አጠረ(ው). +This month, I am short of money. በዚህ ፡ ወር ፡ ገንዘብ ፡ አጥሮኛል
The newspaper is short of contributions. ጋዜጣው ፡ ጽሑፎች ፡ አጥረውታል
2. አቃተ(ው). +I am short of breath after that climb. ጋራውን ፡ ከወጣሁ ፡ በኋላ ፡ መተንፈስ ፡ አቃተኝ
3. አነሰ(ው). +The factory is short of manpower. ፋብሪካው ፡ ሠራተኞች ፡ ያንሱታል

**be (very) short with** በአጭር ፡ ቆጨ
He was very short with me when I tried to borrow money. ገንዘብ ፡ የመበደር ፡ ሙከራዬ ፡ በአጭር ፡ ቆጨው

**cut short**
1. አሳጠረ. You cut my hair too short. ጸጉሬን ፡ በጣም ፡ አሳጠርከብኝ
2. አቋረጠ. The chairman cut the speaker short. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ተናጋሪውን ፡ አቋረጠው
They had to cut their trip short. ጉዟቸውን ፡ ማቋረጥ ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው

**(be) cut short** ተቀጨ
The President's life was cut short by an assassin's bullet. የፕሬዚዳንቱ ፡ ሕይወት ፡ በጥይት ፡ ተቀጨ

**fall short**
1. አለቀ. Her funds fell short, and she had to wire home for help. ገንዘቧ ፡ ስላለቀ ፡ እንዲረዷት ፡ እቤት ፡ ቴሌግራም ፡ መላክ ፡ ነበረባት
2. በታች ፡ ነው ፤ አነሰ. Your work falls short of my expectations. ሥራህ ፡ ከገመትኩት ፡ በታች ፡ ነው ፡ (ያነሰ ፡ ነው)

**for short** ለማሳጠር
Robert was called Rob for short. ሮበርትን ፡ ለማሳጠር ፡ ሮብ ፡ ብለው ፡ ይጠሩታል

**in a short time** ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ
He will depart in a short time. ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይነሣል

**in short** ባጭሩ
In short, I can't. ባጭሩ ፡ አልችልም

**(be) little short of** ከ - - - እምብዛም ፡ አያንስ
Your actions are little short of treason. የሠራኸው ፡ ሥራ ፡ ከክሕደት ፡ እምብዛም ፡ አያንስ
*Our escape was little short of miraculous. ያመለጥነው ፡ በታምር ፡ ነው

**make (it) short** አሳጠረ
Speak if you must, but make it short. ካልተናገርኩ ፡ ካልክ ፡ ተናገር ፤ ግን ፡ አሳጥረው

**make short work of** ቶሎ ፡ ድል ፡ አደረገ
He made short work of the enemy. ጠላትን ፡ ቶሎ ፡ ድል ፡ አደረገ

**nothing short of**
*Nothing short of your best work will satisfy me. ከመልካም ፡ ሥራህ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ አይጥመኝም

**run short** ወደ ፡ ማለቁ ፡ ተቃረበ
Our supplies ran short at the end of the first week. ሥንቃችን ፡ በመጀመሪያው ፡ ሳምንት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ማለቁ ፡ ተቃረበ

**run short of** አለቀ
+I ran short of patience. ትዕግሥቴ ፡ አለቀ
[See also 'long, order, span, spell, stature, stop, trousers, while']

## short (n.)
*A short caused the fuse to blow. ሽቦው ፡ ስለተነካካ ፡ ባልቦላውን ፡ አቃጠለው
*There is a short in the radio. በራዲዮው ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱ ፡ ሽቦዎች ፡ ስለተነካኩ ፡ ራዲዮው ፡ ተበላሸ

## shortage
1. እጥረት. There is a terrible water shortage now. አሁን ፡ በጣም ፡ የሚያሰጋ ፡ የውኃ ፡ እጥረት ፡ አለ
Owing to a shortage of teachers, school will be let out early. በመምህራን ፡ እጥረት ፡ የተነሣ ፡ ተማሪዎች ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ይወጣሉ
2. ማለቅ. The war was lost due to a shortage of munitions. በጦርነቱ ፡ የተሸነፍነው ፡ ትጥቅና ፡ ሥንቅ ፡ በማለቁ ፡ ነው
3. ጉድለት. The bookkeeper found a shortage when he checked the accounts. ሒሳብ ፡ ያዡው ፡ ሒሳቡን ፡ ተቈጣጥሮ ፡ ጉድለት ፡ አገኘበት

## short-change መልሱን ፡ አሳነሰ(በት)
He short-changed me when I gave him a ten-dollar bill. ዐሥር ፡ ብር ፡ ሰጥቼው ፡ መልሱን ፡ አሳነሰብኝ
*A lax teacher may short-change his students. ልል ፡ መምህር ፡ የተሟላ ፡ ትምህርት ፡ አይሰጥም

## short circuit ኮንታክት
There is a short circuit in the radio. ሬድዮኑ ፡ ውስጥ ፡ ኮንታክት ፡ አለ

## shortcoming ጉድለት
The apartment has many shortcomings. ቤቱ ፡ ብዙ ፡ ጉድለት ፡ አለበት

## short cut አቋራጭ ፡ መንገድ
He knows a short cut to the city. ወደ ፡ ከተማው ፡ የሚያገባ ፡ አቋራጭ ፡ መንገድ ፡ ያውቃል

**take a short cut** አቋረጠ
You can take a short cut here. በዚህ ፡ ልታቋርጥ ፡ ትችላለህ

## shorten (vt.) አሳጠረ
Shorten the pants for me, please! እባክህን ፡ ሱሪውን ፡ አሳጥርልኝ

## (be) shorter አጠረ
The distance between the towns is shorter because of the new road. አዲሱ ፡ መንገድ ፡ ስለተሠራ ፡ በከተማዎቹ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ አጥሯል
During Christmas, the days get shorter. በገና ፡ ጊዜ ፡ ቀናት ፡ እያጠሩ ፡ ይሄዳሉ

## shorthand አጭር ፡ ጽሕፈት
Do you know shorthand? አጭር ፡ ጽሕፈት ፡ ትችላለህ ?

## (be) shorthanded ሠራተኞች ፡ አነሱ
+We are shorthanded at the office. በመሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ ሠራተኞች ፡ አንሰዋል

**(be) short-lived** ባጭር ፡ ተቀጨ
The plan was short-lived. እቅዱ ፡ ባጭር ፡ ተቀጨ

**shortly**
1. አሁን. He will be here shortly. አሁን ፡ ይመጣል
2. በቅርቡ. He is to leave for Mexico shortly. በቅርቡ ፡ ወደ ፡ ሜክሲኮ ፡ ይሄዳል

**shortly after**
1. ወዲያውኑ ፡ እንደ + (perfect). Shortly after I left, I discovered that I had no money. ወዲያውኑ ፡ እንደሄድኩ ፡ ገንዘብ ፡ እንደሌለኝ ፡ ተገነዘብኩ
2. በ + (perfect) + ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ. He became her friend shortly after they met. በተገናኙ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ወዳጇ ፡ ሆነ

**shortly before** ከ - - - ቀደም ፡ አድርጎ
Shortly before noon, I left the office. ከእኩለ ፡ ቀን ፡ ቀደም ፡ አድርጌ ፡ ከቢሮ ፡ ወጣሁ

**to put it shortly** ባጭሩ ፡ ለመናገር
To put it shortly, I can't come with you. ባጭሩ ፡ ለመናገር ፤ ካንተ ፡ ጋር ፡ አብሬ ፡ ልሄድ ፡ አልችልም
[See also 'afterwards']

**shorts** ቁምጣ
He ordered six pairs of shorts. ስድስት ፡ ቁምጣ ፡ አዘዘ

**(be) short-sighted**
1. ዓይኑ ፡ በርቀት ፡ በደንብ ፡ አላየም. I need glasses because I'm short-sighted. ዓይኔ ፡ በርቀት ፡ በደንብ ፡ ስለማያይ ፡ መነጽር ፡ ያስፈልገኛል
2. የሩቁን ፡ የሚያስብ ፡ አይደለም. The manager's policy is short-sighted. የሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ መመሪያ ፡ የሩቁን ፡ የሚያስብ ፡ አይደለም

**short-sleeved** እጅጌ ፡ ጉርድ
In the summer, I wear short-sleeved shirts. በበጋ ፡ እጅጌ ፡ ጉርድ ፡ ሸሚዝ ፡ እለብሳለሁ

**short story** አጭር ፡ ታሪክ
This short story describes the war. ይህ ፡ አጭር ፡ ታሪክ ፡ ጦርነቱን ፡ ይገልጻል

**short-tempered** ግልፍተኛ
He is short-tempered and therefore always shouts. ግልፍተኛ ፡ ስለሆነ ፡ ሁልጊዜ ፡ ይጮኻል

**short-term**
1. ያጭር ፡ ጊዜ. I can undertake only short-term projects. ያጭር ፡ ጊዜ ፡ እቅዶችን ፡ ብቻ ፡ ልፈጽም ፡ እችላለሁ
2. ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሚከፈል. I need a short-term loan. ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሚከፈል ፡ ብድር ፡ እፈልጋለሁ

**short-wave radio** ያጭር ፡ ሞገድ ፡ ራድዮ
I can get Addis Ababa on my short-wave radio. ባጭር ፡ ሞገድ ፡ ራዲዮ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ መሥመር ፡ ላገኝ ፡ እችላለሁ

**shot,** see **shoot**

**shot**
1. ተኩስ. Did you hear a shot? ተኩስ ፡ ሰማህ?
2. ተኳሽ. He is a good shot. ጥሩ ፡ ተኳሽ ፡ ነው
3. መርፌ. Are you getting shots? መርፌ ፡ እየተወጋህ ፡ ነህ ?
4. ፎቶግራፍ. Here are some shots of my children. የልጆቼ ፡ ፎቶግራፎች ፡ እነኚሁና

**big shot** ትልቅ ፡ ሰው
He thinks he is a big shot. ራሱን ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ይቈጥራል

**have (take) a shot at** ሞከረ
Let me have a shot at it! እስቲ ፡ ልሞክረው

**one-shot** ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚሆን
This is a one-shot affair. ይህ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚሆን ፡ ጉዳይ ፡ ነው
[See also 'volley']

**shotgun** ረሽ
He bought a shotgun. አንድ ፡ ረሽ ፡ ገዛ

**should**
1. ይገባዋል. He should telephone his parents. ለወላጆቹ ፡ ስልክ ፡ መደወል ፡ ይገባዋል
2. ሳ + negative imperfect + አይቀርም. The plane should be leaving at noon. አውሮፕላኑ ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ ሳይነሣ ፡ አይቀርም
3. (jussive). Should I take the money now or later? ገንዘቡን ፡ አሁን ፡ ልውሰድ ፡ ወይስ ፡ በኋላ ?

**if it should** ከ + perfect
If it should rain close the windows. ከዘነበ ፡ መስኮቱን ፡ ዝጋ

**shoulder** (v.)
1. አነገተ. He shouldered the gun. ጠመንጃውን ፡ አነገተ
2. ተቀበለ. He shouldered the responsibilities of supporting his brothers. ወንድሞቹን ፡ ለመርዳት ፡ ኀላፊነት ፡ ተቀበለ

**shoulder (one's) way through** እየተጋፋ ፡ አለፈ
He shouldered his way through the crowd. በሕዝቡ ፡ መሀከል ፡ እየተጋፋ ፡ አለፈ

**shoulder** (n.)
1. ትከሻ. The fall broke his shoulder. ወድቆ ፡ ትከሻው ፡ ተሰበረ
2. ውጭ. Don't drive on the shoulder of the road! ከመንገዱ ፡ ውጭ ፡ አትንዳ

**cry on someone's shoulder** አለቀሰ(በት)
Don't cry on my shoulder! This mess is your own fault. አታልቅስብኝ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ያንተ ፡ ጥፋት ፡ ነው

**give (someone) the cold shoulder** ፊት ፡ ነሣ
She gave me the cold shoulder when I tried to talk to her. ላነጋግራት ፡ ስሞክር ፡ ፊት ፡ ነሣችኝ

**put one's shoulders to the wheel** ጠንክሮ ፡ ሠራ
If we put our shoulders to the wheel, we'll be able to finish the job soon. ጠንክረን ፡ ከሠራን ፡ ሥራውን ፡ ቶሎ ፡ ለመጨረስ ፡ እንችላለን

**stand shoulder to shoulder**
1. ተጠጋግተው ፡ ቆሙ. During the parade, they stood shoulder to shoulder. በሰልፉ ፡ ጊዜ ፡ ተጠጋግተው ፡ ቆሙ
2. ተባበረ. We must stand shoulder to shoulder, or else the enemy will prevail against us. መተባበር ፡ አለብን ፤ አለበለዚያ ፡ ጠላት ፡ ያጠቃናል
[See also 'carry, chip, head, ride, sling']

**shoulder blade** መጋፊያ
He is so thin that his shoulder blades stick out. በጣም ፡ ቀጭን ፡ ስለሆነ ፡ መጋፊያው ፡ ወጣ ፡ ብሏል

**shout** (v.) ጮኸ
You don't have to shout. አትጩኽ

**shout down** ጮኾ ፡ ዝም ፡ አሰኘ
The crowd shouted the speaker down. የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ በተናጋሪው ፡ ላይ ፡ ጮኾ ፡ ዝም ፡ አሰኘው

**shout for help** ድረሱልኝ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ
The drowning boy shouted for help. ሊሰምጥ ፡ የነበረው ፡ ልጅ ፡ ድረሱልኝ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ

**shout (oneself) hoarse**
He shouted himself hoarse. ድምፁ ፡ እስኪዘጋ ፡ ጮኸ

**shout** (n.) ጩኸት
We heard shouts of joy. የደስታ ፡ ጩኸት ፡ ሰማን

**shouts for help** ኡኡታ
We heard shouts for help. ኡኡታ ፡ ሰማን

**shove** (vt.) ገፋ
He shoved the bookcase back into place. የመጽሐፍ ፡ መደርደሪያውን ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ገፋው

**shove** (vi.) ተጋፋ
Don't shove; wait your turn! አትጋፋ ፤ ተራህን ፡ ጠብቅ

**shove around**
Don't try to shove me around! ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አትበለኝ

**shove** (n.) ግፊያ
The shove knocked him down. ግፊያው ፡ ጣለው

**give a shove** ገፈተረ
He gave me such a shove I nearly fell. እንዴ ፡ ቢገፈትረኝ ፡ ልወድቅ ፡ ነበር

**shovel** (v.)
1. በአካፋ ፡ ዛቀ. The men shoveled the sand into a hole. ሰዎች ፡ አሸዋውን ፡ በአካፋ ፡ እየዛቁ ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ጨመሩት
2. ቈፍሮ ፡ አወጣ. We had to shovel a path through the snow. በረዶውን ፡ ቈፍረን ፡ መንገድ ፡ ማውጣት ፡ ነበረብን
3. ጐሰጐሰ. The hungry man shoveled the food into his mouth. የተራበው ፡ ሰው ፡ ምግቡን ፡ አፉ ፡ ውስጥ ፡ ጐሰጐሰው

**shovel** (n.) አካፋ
You'll need a pickax and a shovel. ዶማና ፡ አካፋ ፡ ያስፈልግሃል

**show** (vt.)
1. አሳየ. Can you show me the way to town? ወደ ፡ ከተማ ፡ የሚወስደውን ፡ መንገድ ፡ ልታሳየኝ ፡ ትችላለህ ?
The teacher showed the students how to do the problem. መምህሩ ፡ ጥያቄውን ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠሩ ፡ ለተማሪዎች ፡ አሳየ
2. ገለጸ ፤ አሳየ. The investigation didn't show a thing. ምርመራው ፡ ምንም ፡ አልገለጸም ፡ (አላሳየም)
3. አመለከተ. A thermometer shows the temperature. ተርሞሜትር ፡ የሙቀትን ፡ ልክ ፡ ያመለክታል
4. አስገባ. He showed the visitors into the room. እንግዶቹን ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አስገባቸው
5. አስረዳ. I shall show that he is wrong. መሳሳቱን ፡ አስረዳለሁ
6. (pass.) ታየ. +They pulled him from the river but he showed no signs of life. ከወንዙ ፡ ውስጥ ፡ ጐትተው ፡ አወጡት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሕይወት ፡ ምልክት ፡ አልታየበትም
What are they showing at the theater this evening? ዛሬ ፡ ማታ ፡ በቴያትር ፡ ቤቱ ፡ ምን ፡ ይታያል ?

**show** (vi.) ታየ
Only his head showed above the water. ራሱ ፡ ብቻ ፡ ከውኃው ፡ በላይ ፡ ይታይ ፡ ነበር
The food stain won't show. ልብሱ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የምግብ ፡ ጠብታ ፡ አይታይም
Anger showed in his face. ቁጣ ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**show around** አስጐበኘ ፤ አዙሮ ፡ አስጐበኘ
Shall I show you around the house? ቤቱን ፡ ላስጐብኝህ ?
The manager showed me around the plant. አስተዳዳሪው ፡ ፋብሪካውን ፡ አዙሮ ፡ አስጐበኘኝ

**show home**
He showed her home. ወደ ፡ ቤቷ ፡ ሸኛት

**show itself** ታወቀ
His anger showed itself in his face. ቁጣው ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ታወቀበት

**show off** (vt.)
1. ካበ. Some mothers like to show off their daughters. አንዳንድ ፡ እናቶች ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ይክባሉ
2. አሳየ. The parade was designed to show off all the latest weapons of war. ሰልፉ ፡ ዘመናዊ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎችን ፡ ለማሳየት ፡ የተደረገ ፡ ነበር
*Most girls like to show off fine clothes. አብዛኞቹ ፡ ልጃገረዶች ፡ ለእዩልኝ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ልብስ ፡ ይለብሳሉ

**show off** (vi.) ጉራ ፡ ነዛ
The boy was showing off in front of his girl friend. ልጁ ፡ ከንፈር ፡ ወዳጁ ፡ ፊት ፡ ጉራውን ፡ ይነዛ ፡ ነበር

**show oneself**
*He doesn't dare show himself around here. እዚህ ፡ ሰፈር ፡ ለመድረስ ፡ አይደፍርም

**show (to)** አስያዘ ፤ መራ
His job was to show the people to their seats. ሥራው ፡ ሰዎቹን ፡ መቀመጫ ፡ ማስያዝ ፡ ነበር
The usher will show you to your seats. አስተናባሪው ፡ ወደ ፡ መቀመጫችሁ ፡ ይመራችኋል

**show up** (vt.) ገለጸ
He undercut his superior's position by showing up many of his faults. ብዙ ፡ ስሕተቶቹን ፡ በመግለጽ ፡ ያለቃውን ፡ ክብር ፡ አጐደፈ

**show up** (vi.)
1. መጣ. Nobody showed up. ማንም ፡ አልመጣም
2. ታየ. Yellow shows up well against black. ብጫ ፡ በጥቁር ፡ ላይ ፡ ደምቆ ፡ ይታያል

**(it) goes to show** ያመለክታል
This goes to show that you must work harder. ይህ ፡ እንዴት ፡ ጠንክረህ ፡ መሥራት ፡ እንዳለብህ ፡ ያመለክታል
[See also the numerous nouns combined with 'show']

**show** (n.)
1. የትርኢይት ፡ ቦታ. Come with me to the flower show! ወደ ፡ አበባ ፡ ትርኢይት ፡ ቦታ ፡ አብረኸኝ ፡ ሂድ
2. ትርኢይት. When does the first show start? የመጀመሪያው ፡ ትርኢይት ፡ የሚጀመረው ፡ መቼ ፡ ነው ?
The Air Force will give a show soon. ያየር ፡ ኀይል ፡ በቅርቡ ፡ ትርኢይት ፡ ያሳያል
The jewels made a fine show. ጌጣጌጦች ፡ ጥሩ ፡ ትርኢይት ፡ ነበሩ
3. መታየት. The goods are on show now. ሸቀጣ ፡ ሸቀጦቹ ፡ አሁን ፡ በመታየት ፡ ላይ ፡ ናቸው

**(only) for show** ለይስሙላ
His kindness is only for show. ደግነቱ ፡ ለይስሙላ ፡ ነው

**put up a good show** ተጣጣረ
He put up a good show, but lost anyway. ተጣጥሮ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ አልቀናውም

**showcase** መስታወት
Put the jewels in the showcase! ዕንቁዎቹን ፡ መስታወት ፡ ውስጥ ፡ ደርድራቸው

**showdown**
*The two persons reached a showdown. ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ ይዋጣልን ፡ ተባባሉ

**shower** (vt.)
*They showered the winner with praise. አሸናፊውን ፡ ከልክ ፡ በላይ ፡ አሞገሱት
*He showered me with profuse thanks. ምስጋናውን ፡ አኅጐደጐደልኝ

**shower** (vi.) ገላ(ውን) ፡ ታጠበ
He showers at night. ማታ ፡ ማታ ፡ ገላውን ፡ ይታጠባል

**shower upon** አዘነበ(ለት)
His rich uncle showered gifts upon him. ሀብታም ፡ አጐቱ ፡ ስጦታ ፡ አዘነበለት

**shower** (n.)
1. ካፊያ. A shower settled the dust. ካፊያው ፡ አቧራውን ፡ አስታገሠ
2. ዝናም. We were caught in a heavy shower. ድንገተኛ ፡ ዝናም ፡ ያዘን

3. መጉረፍ. A shower of tears softened the judge's heart. የእንባዋ ፡ መጉረፍ ፡ የዳኛውን ፡ ልብ ፡ አራራው
4. ናዳ. A shower of abuse followed his refusal to buy the paper. ጋዜጣውን ፡ አልገዛም ፡ ማለቱ ፡ የስድብ ፡ ናዳ ፡ አወረደበት
5. የቁም ፡ መታጠቢያ. Does your new apartment have a shower? አዲስ ፡ አፓርትማህ ፡ የቁም ፡ መታጠቢያ ፡ አለው ?

**take a shower** ገላ(ውን) ፡ ታጠበ
I just have to take a shower and get dressed. ገላዬን ፡ ታጥቤ ፡ መልበስ ፡ አለብኝ

**showing** መታየት
A showing of the new models took three hours. ያዲዲሱ ፡ ሞዴል ፡ መታየት ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ፈጀ
*He made a poor showing in the race. በውድድሩ ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ አላሳየም

**show-off** ጉረኛ
He is a big show-off. ዋና ፡ ጉረኛ ፡ ነው

**showy** ብልጭልጭ
She wore a showy dress. ብልጭልጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሳለች

**shrank**, see **shrink**

**shred** ብጫቂ
The shred of cloth was hanging on the thorn bush. የልብስ ፡ ብጫቂ ፡ በሾሁ ፡ ቁጥቋጦ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ነበር
*There is not a shred of evidence that he took the money. ገንዘቡን ፡ ለመውሰዱ ፡ አንዲት ፡ መረጃ ፡ እንኳ ፡ የለም

**claw to shreds** ቧጥጦ ፡ ዘከዘከ
The kitten clawed my sweater to shreds. ድመቲቱ ፡ ሹራቤን ፡ ቧጥጣ ፡ ዘከዘከችው

**tear to shreds** በጫጨቀ
The dog tore the pants to shreds. ውሻው ፡ ሱሪውን ፡ በጫጨቀው

**shrew**
1. [አይጥ ፡ የሚመስል ፡ ትንሽ ፡ እንስሳ].
2. ነዝናዛ. He married a shrew and has suffered ever since. አንዲት ፡ ነዝናዛ ፡ ልጅ ፡ አግብቶ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ይሠቃያል

**shrewd** ብልጥ
He is a shrewd businessman. ብልጥ ፡ ነጋዴ ፡ ነው

**shriek** (v.) ጮኸ
The woman shrieked when the mouse ran out. አይጧ ፡ ሮጣ ፡ ስትወጣ ፡ ሴትዮዋ ፡ ጮኸች
The children shrieked with joy while sliding down the hillside. ልጆቹ ፡ ከኮረብታው ፡ ቁልቁለት ፡ ሲንሸራተቱ ፡ በደስታ ፡ ጮኹ

**shriek** (n.) ድምፅ
We heard the shriek of the whistle. የፊሽካ ፡ ድምፅ ፡ ሰማን

**shrill** በጣም ፡ ቀጭን
She has a shrill voice. በጣም ፡ ቀጭን ፡ ድምፅ ፡ አላት

**shrine** ቅዱስ ፡ ስፍራ
We will visit the shrine of Our Lady on Sunday. የእመቤታችንን ፡ ቅዱስ ፡ ስፍራ ፡ እሑድ ፡ እንሳለማለን

**shrink** (shrunk, or shrank), vt. አኰማተረ
Will this soap shrink woolen clothes? ይህ ፡ ሳሙና ፡ ሱፍ ፡ ልብስ ፡ ያኰማትራል ?

**shrink** (vi.) አጠረ
That shirt will shrink in the wash. ያ ፡ ሸሚዝ ፡ ሲታጠብ ፡ ያጥራል

**shrink from**
1. ሸሸ. He shrinks from a hard task. ከባድ ፡ ሥራ ፡ ይሸሻል
2. አፈገፈገ. She shrank from the dog in fear. ውሻውን ፡ ፈርታ ፡ አፈገፈገች
3. አልወደደም. A shy person shrinks from making new acquaintances. ዓይን ፡ አፋር ፡ ሰው ፡ እንግዳ ፡ ሰዎችን ፡ መተዋወቅ ፡ አይወድም

**shrivel** (vt.) አጠወለገ
The hot sun shrivels the leaves. ሞቃቱ ፡ ፀሐይ ፡ ቅጠል ፡ ያጠወልጋል

**shrivel** (vi.) ጠወለገ
The plant shriveled in the hot sun. ዕፀ ፡ ከፀሐዩ ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ጠወለገ

**shriveled** (adj.) የተጨማደደ
Tears ran down the old woman's shriveled cheeks. በባልቴቷ ፡ በተጨማደደው ፡ ጉንጮች ፡ ላይ ፡ እንባ ፡ ኮለል ፡ አለ

**shroud** (v.) ሸፈነ
Fog shrouded the airport. የአውሮፕላን ፡ ማቢያውን ፡ ጉም ፡ ሸፍኖታል

**shroud** (n.) ከፈን
A white cloth is used for making shrouds. ነጭ ፡ ጨርቅ ፡ ለከፈን ፡ ይሆናል

**wrap in a shroud** ገነዘ
They wrapped the corpse in a shroud. ሬሳውን ፡ ገነዙት

**shrub** ቁጥቋጦ
The shrub has small red berries. ቁጥቋጦው ፡ ትንንሽ ፡ ቀያይ ፡ ፍሬዎች ፡ ይዟል

**shrubbery** ቁጥቋጦ
This hill is covered with shrubbery. ይህ ፡ ኰረብታ ፡ ቁጥቋጦ ፡ ለብሷል

**shrug** (shrugged), v. ነቅንቆ ፡ ዝም ፡ አለ
He merely shrugged his shoulders in answer to our request for help. እንዲረዳን ፡ ብንጠይቀው ፡ ትከሻውን ፡ ነቅንቆ ፡ ብቻ ፡ ዝም ፡ አለ

**shrug** (n.)
*He dismissed the matter with a shrug of the shoulders. ጉዳዩን ፡ ንቆ ፡ ተወ

**shrunk,** see **shrink**

**shrunken** የተጨማደደ
I can't put on this shrunken shirt. ይህን ፡ የተጨማደደ ፡ ሸሚዝ ፡ ልለብሰው ፡ አልችልም

**shudder** (v.) ተንቀጠቀጠ
He shuddered in the chill wind. በብርድ ፡ ተንቀጠቀጠ

**make shudder** ዘገነነ
The bloody corpses made me shudder. በደም ፡ የተበከሉትን ፡ ሬሳዎች ፡ ማየት ፡ ዘገነነኝ

**shuffle**
1. አገላበጠ. He just shuffles those documents; he doesn't really read them. ሰነዶችን ፡ እንዲያው ፡ ያገላብጣል ፡ እንጂ ፡ አያነባቸውም
2. በወዘ. He shuffled the cards. ከርታውን ፡ በወዘ

**shuffle (along)** እግሮቹን ፡ እየጐተተ ፡ ተጓዘ
The old man shuffled along the street. ሽማግሌው ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ እግሮቹን ፡ እየጐተተ ፡ ተጓዘ

**shun** (shunned) ከ --- ራቀ
He shunned their company. ከነሱ ፡ ጓደኝነት ፡ ራቀ

**shunt**
1. አዘዋወረ. He shunted me from office to office. ከቢሮ ፡ ቢሮ ፡ አዘዋወረኝ
2. አወጣ. They shunted the train from the main track. ባቡሩን ፡ ከዋናው ፡ ሐዲድ ፡ አወጡት

**shut** (shut)
1. ዘጋ. Please shut the door! በሩን ፡ ዝጋው
2. ጨፈነ. He shut his eyes because the strong light hurt them. ኀይለኛው ፡ ብርሃን ፡ ስለወጋው ፡ ዓይኑን ፡ ጨፈነ

**shut down, be shut down** ሥራ ፡ አቆመ ፤ ተዘጋ
The factory shut down due to lack of raw material. ከጥሬ ፡ እቃ ፡ እጦት ፡ የተነሣ ፡ ፋብሪካው ፡ ሥራ ፡ አቆመ
Why was the factory shut down? ፋብሪካው ፡ የተዘጋው ፡ ለምን ፡ ነበር ?

**shut in** ዘጋ(በት)
When they left on a trip, they shut the dog in. ወደ ፡ መንገድ ፡ ሲሄዱ ፡ ውሻውን ፡ ዘግተውበት ፡ ሄዱ

**(remain) shut in** ቤት ፡ ዋለ
Because of his rheumatism, he remained shut in for several days. በቁርጥማቱ ፡ ምክንያት ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ ቤት ፡ ዋለ

**shut off**
1. ዘጋ. Shut off the water! ውኃውን ፡ ዝጋው
Shut off the radio! ራዲዮኑን ፡ ዝጋው
2. ቈረጠ(በት). The electric company shut off our lights. የኤሌክትሪክ ፡ ኀይል ፡ ኩባንያ ፡ መብራታችንን ፡ ቈረጠብን
3. ከለለ. These trees shut off the view. እነዚህ ፡ ዛፎች ፡ ትርእይቱን ፡ ይከልላሉ

**shut out**
1. አላስገባም. Shut out the dog! We don't want him to bring in any fleas. ውሻውን ፡ አታስገባው ፤ ቁንጫውን ፡ እንዲያራግፍብን ፡ አንፈልግም
The curtains shut out the light. መጋረጃዎቹ ፡ ብርሃን ፡ አያስገቡም
2. እንዳይገባ ፡ ከለከለው. They shut all newsmen out of the meeting. ጋዜጠኞችን ፡ ሁሉ ፡ ከስብሰባው ፡ እንዳይገቡ ፡ ከለከሏቸው

**shut out the view of** ከለለ
A dense fog shut out the view of the mountain. ጥቅጥቅ ፡ ያለው ፡ ጭጋግ ፡ ተራራውን ፡ ከለለው

**shut up** (vt.) ቈለፈ(በት)
They shut the boy up in the cellar. ልጁን ፡ ምድር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ቈለፉበት

**shut up** (vi.) ዝም ፡ አለ
When she finally shut up, the whole house was quiet. በመጨረሻው ፡ እሷ ፡ ዝም ፡ ስትል ፡ ቤቱ ፡ ጸጥ ፡ አለ
[See also 'snap, swell, swing']

**shutter** የሳንቃ ፡ መከለያ
This room has shutters instead of windows. ይህ ፡ ክፍል ፡ በመስኮት ፡ ፈንታ ፡ የሳንቃ ፡ መከለያ ፡ አለው

**shuttle** (vt.) አዘዋወረ
They shuttled John from job to job. ዮሐንስን ፡ ከሥራ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ አዘዋወሩት

**shuttle** (vi.) ተመላለሰ
The bus shuttles between the college and the main part of town. አውቶቡሱ ፡ በኮሌጁና ፡ በመሀል ፡ ከተማው ፡ መካከል ፡ ይመላለሳል

**shuttle** (n.) መወርወሪያ
The weaver broke his shuttle. ሸማኔው ፡ መወርወሪያውን ፡ ሰበረው

**shy** (shied), v. ደነበረ
The horse shied at a piece of paper lying in the street. ፈረሱ ፡ ብጣሽ ፡ ወረቀት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ አይቶ ፡ ደነበረ

**shy** (adj.)
1. ዓይናፋር. Don't be so shy! እንደዚህ ፡ ዓይናፋር ፡ አትሁን
2. ድንጉጥ. The antelope is a shy animal. ድኩላ ፡ ድንጉጥ ፡ እንስሳ ፡ ነው

**be shy** አፈረ
He was shy because it was his first day at school. በትምህርት ፡ ቤት ፡ የመጀመሪያ ፡ ቀኑ ፡ ስለሆነ ፡ አፈረ

**be shy of** አጠረ(ው)
I am a little shy of money today. ዛሬ ፡ ገንዘብ ፡ ትንሽ ፡ አጥሮኛል

**shyness** ዓይን ፡ አፋርነት
Due to her shyness, she does not make many friends. ከዓይን ፡ አፋርነቷ ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ጓደኞች ፡ አታፈራም

**siblings** ወንድማማቾችና ፡ እኅትማማቾች
There was rivalry between the siblings. በወንድማማቾቹና ፡ በእኅትማማቾቹ ፡ መካከል ፡ ፉክክር ፡ ነበረ

**sick** (n.) በሽተኛ
The sick are given the best of care. በሽተኞች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ይደረግላቸዋል

**sick** (adj.)
1. ሕመምተኛ. The sick child is better today. ሕመምተኛው ፡ ልጅ ፡ ዛሬ ፡ ተሽሎታል
2. የታመመ. The sick man had to stay in bed. የታመመው ፡ ሰውዬ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ ነበረበት
*He has a sick mind. አንጎሉ ፡ ታውኳል

**(get) sick and tired of** ቸከ(በት)
+I am getting sick and tired of it. ይህ ፡ ነገር ፡ ቸከብኝ

**be sick** ታመመ
He is sick in bed. ታሞ ፡ ተኝቷል

**be sick at** አዘነ
I am sick at having failed the exam. ፈተናውን ፡ በመውደቄ ፡ አዝኛለሁ

**be sick of** አበሳጨ(ው)
+I am sick of this weather. ይህ ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፡ አበሳጭቶኛል

**be sick with**
He is sick with the flu. ኢንፍሉዌንዛ ፡ ይዞታል

**feel sick** አመመ(ው)
Let her lie down; she feels sick. ትተኛ ፤ አሟታል

**make (one) sick**
1. አጥወለወለ. Bus rides make him sick. በአውቶቡስ ፡ ሲሄድ ፡ ያጥወለውለዋል
2. ሽቅብ ፡ ሽቅብ ፡ አሰኘ. The motion of the car made him sick. የመኪናው ፡ መንቅንቅ ፡ ሽቅብ ፡ ሽቅብ ፡ አሰኘው
3. ነደደ. It makes me sick to think of what he has done. ያደረገው ፡ ትዝ ፡ ሲለኝ ፡ ይነደኛል

**take sick** ታመመ
When did he take sick? መቼ ፡ ታመመ ?

**(be) taken sick** ታመመ
He was suddenly taken sick. በድንገት ፡ ታመመ

**sicken** (vt.)
1. አስጠላ. The odor sickened her. ሽታው ፡ አስጠላት
2. ዘገነነ. The sight of the murdered woman sickened him. የተገደለቿን ፡ ሴትዮ ፡ ማየቱ ፡ ዘገነነው

**sicken** (vi.) ታመመ
The bird sickened when kept in the cage. ወፏ ፡ ሽቦው ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለች ፡ ታመመች

**sickening** የሚያቅለሸልሽ
A sickening odor of burned flesh pervaded the room. የሚያቅለሸልሽ ፡ ያረረ ፡ ሥጋ ፡ ሽታ ፡ ክፍሉን ፡ ሞላው

**sick leave** የሕመም ፡ ፈቃድ
He applied for sick leave. የሕመም ፡ ፈቃድ ፡ እንዲሰጠው ፡ አመለከተ

**sickle** ማጭድ
The farmer mows grass with a sickle. ገበሬው ፡ ሣር ፡ በማጭድ ፡ ያጭዳል

**sickly**
1. ሰበበኛ. A sickly child is likely to get ill easily. ሰበበኛ ፡ ልጅ ፡ በቀላሉ ፡ ይታመማል
2. በሽታ ፡ የሚያመጣ. He does not like this city

because of its sickly climate. አየሩ ፡ በሽታ ፡ ስለሚያመጣ ፡ ይህንን ፡ ከተማ ፡ አይወደውም
*His face had a sickly color. ፊቱ ፡ ገርጥቷል ፡ (ከሰል ፡ መስሏል)
*I smell the sickly odor of burning animal flesh. ያረረው ፡ ሥጋ ፡ ሽታ ፡ ያቅለሸልሻል

**sickness** ሕመም ፤ በሽታ
He is absent because of sickness. የቀረው ፡ በ ሕመም ፡ ምክንያት ፡ ነው
Sickness can be eradicated by drugs. በሽታ ፡ በ መድኃኒት ፡ ሊጠፋ ፡ ይችላል

**side** (v.), ~ **with** ደገፈ
You always side with him. ሁሌ ፡ እሱን ፡ እንደደገፍክ ፡ ነው

**side against** ከተቃወሙት ፡ ወገን ፡ ነው
My friend sided against me on that matter. በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ጓደኛዬ ፡ እኔን ፡ ከተቃወሙት ፡ ወገን ፡ ነበር

**side** (n.)
1. ጐን. He felt a pain in his side. ጐኑ ፡ ላይ ፡ ውጋት ፡ ተሰማው
2. መልክ. There are two sides to the argument. ክርክሩ ፡ ሁለት ፡ መልክ ፡ አለው
3. ወገን. Both sides are ready for the contests. ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ለውድድሩ ፡ ተዘጋጅተዋል
The judges voted for our side in the debate. ዳኞቹ ፡ በክርክሩ ፡ ጊዜ ፡ ለኛ ፡ ወገን ፡ ፈረዱ
4. ገጽ. Write only on one side of the paper! በወረቀቱ ፡ ባንዱ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ጻፍ
5. ክፍል. The east side of the city is densely populated. የከተማው ፡ ምሥራቃዊ ፡ ክፍል ፡ ሕዝብ ፡ ይበዛበታል
6. ቡድን. Our side won the football game. ቡድናችን ፡ የእግር ፡ ኳስ ፡ ጨዋታውን ፡ አሸነፈ
*She's a cousin on my father's side. ያባቴ ፡ ወንድም ፡ ልጅ ፡ ናት
*He never left my side. ምን ፡ ጊዜም ፡ ከኔ ፡ ተለይቶ ፡ አያውቅም
*He studies all sides of a question before he makes a decision. ውሳኔ ፡ ከማድረጉ ፡ በፊት ፡ ነገሩን ፡ በደንብ ፡ ይመረምረዋል

**side** (adj.)
1. የጐን. My side pocket is torn. የጐን ፡ ኪሴ ፡ ተቀዷል
Please use the side door! በጐን ፡ በር ፡ ግባ
2. በዳር ፡ በኩል ፡ ያለ. The side aisle of the theater should be empty. በዳር ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ የቲያትሩ ፡ መተላለፊያ ፡ ባዶ ፡ መሆን ፡ አለበት

**side by side** ጐን ፡ ለጐን
They walked along silently side by side. ዝም ፡ ብለው ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ተራመዱ

**be on (someone's) side**
He is on our side. የኛ ፡ ደጋፊ ፡ ነው

**by (one's) side** ጐኑ
Come and sit by my side! ና ፤ ጐኔ ፡ ተቀመጥ

**by (the) side of** በ --- ዳር
I saw footprints in the mud by the side of the road. በመንገዱ ፡ ዳር ፡ ባለው ፡ ጭቃ ፡ ውስጥ ፡ ዱካ ፡ አየሁ

**on ... side of** በ --- በኩል ፤ ከ --- በስተ
On this side of the street, there are only a few houses. እዚህ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ያሉት ፡ ቤቶች ፡ ጥቂት ፡ ናቸው
He was on the left side of the street. እሱ ፡ ከመንገዱ ፡ በግራ ፡ በኩል ፡ ነበር
His house is on the right side of the road. ቤቱ ፡ ከመንገዱ ፡ በስተቀኝ ፡ ነው

**on the other side of** በ --- አሻገር
The enemy was strongly entrenched on the other side of the barrier. ጠላት ፡ በገደቡ ፡ አሻገር ፡ በደንብ ፡ መሽጎ ፡ ነበር

**on the side** ከዚህ ፡ ሌላ
He does something else on the side. ከዚህ ፡ ሌላ ፡ የሚሠራው ፡ ተጨማሪ ፡ ሥራ ፡ አለው

**take sides** አንዱን ፡ ወገን ፡ ደገፈ
It's difficult to take sides on this question. በዚህ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ አንዱን ፡ ወገን ፡ መደገፍ ፡ ያዳግታል
[See also 'far, near, opposite, other, right, safe']

**side issue, be a** ~ እንደ ፡ ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ተቈጠረ
Tuition is only a side issue in the debate on education. በትምህርት ፡ ጉዳይ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ የትምህርት ፡ ሒሳብ ፡ እንደ ፡ ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው

**sidelight** ትንሽ ፡ ፍንጭ
What you said threw a sidelight on the matter. የተናገርከው ፡ ስለ ፡ ነገሩ ፡ ትንሽ ፡ ፍንጭ ፡ ሰጠ

**side line**
*He sells ties as a side line; hardware is his main business. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ክራቫት ፡ ይሸጣል ፡ እንጂ ፡ ዋና ፡ ንግዱ ፡ ብረታ ፡ ብረት ፡ ነው
*The artist does carpentry work as a side line. ሠዓሊው ፡ አናጢነቱን ፡ እንደ ፡ ትርፍ ፡ ሥራ ፡ አድርጎ ፡ ይሠራል

**sidelong** adj. (= adv.) በጎን
He gave her a sidelong glance. በጎን ፡ ተመለከታት

**side road** ተገንጣይ ፡ መንገድ
The side road comes into the main road at a tangent. ተገንጣዩ ፡ መንገድ ፡ ከዋናው ፡ መንገድ ፡ በሰያፍ ፡ ይገናኛል

**sidestep** (sidestepped) ችላ ፡ አለ
He sidestepped all unpleasant issues. የማያስደስተውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ችላ ፡ አለው

**sidetrack, ~ from** እንድ+ negative verb + አደረገ
The incident sidetracked him from pursuing the main matter. አጋጣሚው ፡ ነገር ፡ ዋናውን ፡ ነገር ፡ እንዳይከታተል ፡ አደረገው

**sidewalk** የእግረኛ ፡ መሄጃ ፡ መንገድ ፤ የእግር ፡ መንገድ
They found a coin on the sidewalk. በእግረኛ ፡ መሄጃ ፡ መንገድ ፡ (በእግር ፡ መንገድ) ፡ ላይ ፡ ፍራንክ ፡ አገኙ

**sideways** በጎን
He looked sideways at his wife. ሚስቱን ፡ በጎን ፡ ተመለከታት
*He turned his head sideways. አንገቱን ፡ ዞር ፡ አደረገ

**siege** መከበብ ፤ መክበብ
The siege of the fortress weakened the enemy. የምሽጉ ፡ መከበብ ፡ ጠላትን ፡ አደከመው
The long siege turned into a war of attrition. ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ የተደረገው ፡ መክበብ ፡ እንደ ፡ መዳከም ፡ ጦርነት ፡ ሆነ
*A siege of illness left him broke. የረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሕመም ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ አስቀረው
*After his long siege, she agreed to marry him. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ደጅ ፡ ካስጠናችው ፡ በኋላ ፡ ልታገባው ፡ ተስማማች

**lay siege to** ከበበ
The Greeks laid siege to Troy. ግሪኮች ፡ ትሮይን ፡ ከበቡ
[See also 'raise']

**siesta**
*A siesta is always taken in the afternoon in tropical countries. በሞቃት ፡ አገሮች ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከምሳ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ይተኛሉ

**sieve** ወንፊት
Flour is sifted with a sieve. ዱቄት ፡ በወንፊት ፡ ይነፋል

**sift** (vt.)
1. ነፋ. Sift the flour before you use it! ዱቄቱን ፡ ከማቡካትሽ ፡ በፊት ፡ ንፊው
They sifted the sand in order to find the lost key. የጠፋውን ፡ መክፈቻ ፡ ለማግኘት ፡ አሸዋውን ፡ ነፉት
2. ነሰነሰ. The cook sifted a little flour over the meat. የወጥ ፡ ቤቱ ፡ ትንሽ ፡ የፉርኖ ፡ ዱቄት ፡ ሥጋው ፡ ላይ ፡ ነሰነሰ
3. መረመረ. The judge will sift the evidence and decide the case. ዳኛው ፡ መረጃውን ፡ መርምሮ ፡ ፍርዱን ፡ ይሰጣል

**sift** (vi.) እየበነነ ፡ ገባ
During the sandstorm, sand sifted through the cracks. በዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ጊዜ ፡ አሸዋ ፡ በቀዳዳው ፡ ውስጥ ፡ እየበነነ ፡ ገባ

**sifter** ወንፊት
My aunt bought 50 kilos of flour together with a sifter. አክስቴ ፡ አምሳ ፡ ኪሎ ፡ ዱቄትና ፡ አንድ ፡ ወንፊት ፡ ገዛች

**sigh** (v.)
1. ተከዘ. He sighed when he realized he was no longer young. የጐልማሳነቱ ፡ ጊዜ ፡ እንዳለፈ ፡ ሲረዳው ፡ ተከዘ
2. (= make sigh) አስቃሰተ. What are you sighing about? ምን ፡ ያስቃስትሃል ?
3. አፏጨ. The wind sighed in the treetops. ነፋሱ ፡ በዛፎቹ ፡ መሀል ፡ አፏጨ

**sigh for** ናፈቀ(ው)
She sighed for home and friends. ቤቷና ፡ ጓደኞቿ ፡ ናፈቋት

**sigh** (n.), **let out a ~** ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰ
He let out a sigh when I began to talk. እኔ ፡ መናገር ፡ ስጀምር ፡ ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰ

**utter a sigh** ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰ
She uttered a sigh when she heard the news. ወሬውን ፡ ስትሰማ ፡ ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰች
[See also 'heave']

**sight** (v.)
1. አየ. After months at sea, Columbus sighted land. ኮሎምበስ ፡ ለብዙ ፡ ወራት ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ከተጓዘ ፡ በኋላ ፡ የብስ ፡ አየ
2. ዐለመ. The hunter sighted carefully before firing the gun. አዳኙ ፡ ጥይቱን ፡ ከመተኮሱ ፡ በፊት ፡ በጥንቃቄ ፡ ዐለመ

**sight** (n.)

1. ዓይን. He nearly lost his sight in the accident. ባደጋው ፡ ዓይኑ ፡ ሊጠፋ ፡ ነበር
His sight is very poor. ዓይኑ ፡ በጣም ፡ ደካማ ፡ ነው
2. መልክ. I know him only by sight. የማውቀው ፡ በመልክ ፡ ብቻ ፡ ነው
3. ትርእይት. A great fire is an awesome sight. ቃጠሎ ፡ አስፈሪ ፡ ትርእይት ፡ ነው
4. የሚደነቅ ፡ ትርእይት. Niagara Falls is one of the sights of the world. የናያግራ ፡ ፏፏቴ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከሚደነቁት ፡ ትርእይቶች ፡ አንዱ ፡ ነው
*The dead bodies were a terrible sight. ሬሳዎቹን ፡ ማየት ፡ አሰቃቂ ፡ ነበር
*She is a sight in that ugly dress. ያንን ፡ አስጸያፊ ፡ ልብስ ፡ ስትለብስ ፡ ማስቀየሟ
*The rainbow is a glorious sight. ቀስተ ፡ ደመና ፡ ለዓይን ፡ ደስ ፡ ይላል

**sights**
1. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቦታዎች. Have you seen the sights of the town? በከተማው ፡ የሚገኙትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቦታዎች ፡ ጐበኘህ ?

**sight unseen** ሳያየው
I'll buy the house sight unseen. ቤቱን ፡ ሳላየው ፡ እገዛዋለሁ

**at first sight** ገና ፡ ሲያየው
I recognized you at first sight. ገና ፡ ሳይህ ፡ ዐወቅሁህ

**at sight** ሲያየው ፡ ወዲያው
He recognized his old friend at sight. የድሮ ፡ ጓደኛውን ፡ ሲያየው ፡ ወዲያው ፡ ዐወቀው

**at the sight of** ሲያይ
The man ran off at the sight of the police officer. ሰውዬው ፡ የፖሊስ ፡ መኰንን ፡ ሲያይ ፡ እግሬ ፡ አውጪኝ ፡ አለ

**catch sight of** አየ
As soon as he caught sight of you, he vanished. ወዲያው ፡ እንዳየህ ፡ እልም ፡ አለ

**(be) in sight** ታየ
Land is in sight. የብስ ፡ ይታያል

**(not be) in sight**
The end is not yet in sight. መጨረሻው ፡ ገና ፡ ነው

**in sight of** አጠገብ
We live in sight of the school. ትምህርት ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ እንኖራለን

**keep out of sight** ተደበቀ
Keep out of sight so they won't see you. እንዳያዩህ ፡ ተደበቅ

**on sight**
*They have orders to shoot on sight. ሲያዩት ፡ ወዲያው ፡ እንዲገድሉት ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጥቷቸዋል

**(be) out of sight** ላይን ፡ ጠፋ
The car shot ahead and was soon out of sight. መኪናው ፡ ሽው ፡ ብሎ ፡ ላይን ፡ ጠፋ
*He spends his day in the garden so as to be out of sight of his neighbors. ጐረቤቶቹ ፡ እንዳያዩት ፡ ቀኑን ፡ ባትክልት ፡ ቦታው ፡ ውስጥ ፡ ያሳልፋል

**take sight** አነጣጠረ
The hunter took sight and pulled the trigger. አዳኙ ፡ አነጣጥሮ ፡ ምላጩን ፡ ሳበ

**(be) within sight**
*The mountains are within sight of the town. ከከተማው ፡ ሆኖ ፡ ተራራዎቹን ፡ ማየት ፡ ይቻላል
[See also 'burrow, lose, recover']

**sightseeing** አገር ፡ ማየት
Let's go sightseeing! አገር ፡ ለማየት ፡ እንሂድ

**sign** (vt.)

1. ፈረመ. He forgot to sign the letter. ደብዳቤውን ፡ መፈረም ፡ ረሳ
2. ቀጠረ. The soccer club signed five new players. የእግር ፡ ኳሱ ፡ ክበብ ፡ አምስት ፡ አዲስ ፡ ተጫዋቾች ፡ ቀጠረ
3. ተፈራረመ. Sweden and Ethiopia signed a bilateral agreement. ስዊድንና ፡ ኢትዮጵያ ፡ የጋራ ፡ ውል ፡ ተፈራረሙ

**sign** (vi.)
1. ፈረመ. He signed on the dotted line. በነጠብጣቡ ፡ መሥመር ፡ ላይ ፡ ፈረመ
He signed with another team for the next season. በሚቀጥለው ፡ ወቅት ፡ ለሌላ ፡ ቡድን ፡ ለመጫወት ፡ ፈረመ
2. ምልክት ፡ አሳየ. The policeman signed for him to stop. እንዲቆም ፡ ፖሊሱ ፡ ምልክት ፡ አሳየው

**sign in** ስሙን ፡ መዘገበ
All delegates should sign in on the second floor. መልእክተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ሁለተኛው ፡ ፎቅ ፡ ላይ ፡ ስማቸውን ፡ መመዝገብ ፡ አለባቸው
*Don't forget to sign in! ስትመጣ ፡ የገባህበትን ፡ ሰዓት ፡ መጻፍ ፡ አትርሳ

**sign off** የፕሮግራሙን ፡ መፈጸም ፡ ተናገረ
The radio announcer signed off. የራዲዮ ፡ ተናጋሪው ፡ የፕሮግራሙን ፡ መፈጸም ፡ ተናገረ

**sign out**
*When you leave, do not forget to sign out. ስትሄድ ፡ የወጣህበትን ፡ ሰዓት ፡ መጻፍ ፡ አትርሳ

**sign over to** በ -- ስም ፡ አዛወረ
He signed over the business to his son. ንግዱን ፡ በልጁ ፡ ስም ፡ አዛወረ

**sign up**
1. ተቀጠረ. He signed up to work with the sugar company. ስኳር ፡ ፋብሪካ ፡ ውስጥ ፡ ለመሥራት ፡ ተቀጠረ
2. ተመዘገበ. I signed up for three courses. ሦስት ፡ ትምህርት ፡ ለመውሰድ ፡ ተመዝግቢያለሁ
[See also 'pledge']

**sign** (n.)
1. ምልክት. He gave us a sign to follow him. እንድንከተለው ፡ ምልክት ፡ አሳየን
The deaf and dumb talk by signs. ደንቆሮዎችና ፡ ድዳዎች ፡ በምልክት ፡ ይግባባሉ
Are dark clouds a sign of rain? የከበደው ፡ ደመና ፡ የዝናብ ፡ ምልክት ፡ ነው ?
2. መግለጫ. His gift was a sign of his love. ስጦታው ፡ የፍቅሩ ፡ መግለጫ ፡ ነበር
3. ፍንጭ. John's face showed no sign of his anger. የጆን ፡ ፊት ፡ ለመናደዱ ፡ ምንም ፡ ፍንጭ ፡ አልሰጠም
4. ሰሌዳ. The name of the store is on a large sign above it. የሱቁ ፡ ስም ፡ በትልቅ ፡ ሰሌዳ ፡ ተጽፎ ፡ ከበላዩ ፡ ይገኛል
5. ዱካ. The hunters found signs of deer. አዳኞቹ ፡ የአጋዘን ፡ ዱካ ፡ አገኙ

**sign of life**
*There are no signs of life about the house. በቤቱ ፡ አካባቢ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ አይመስልም
[See also 'caution, cross, external']

**signal** (v.)
1. አመለከተ. A bell signals the end of a school period. ደወሉ ፡ የትምህርት ፡ ጊዜን ፡ መፈጸም ፡ ያመለክታል
2. ምልክት ፡ አሳየ. He signaled the car to stop by raising his hand. እጁን ፡ በማንሣት ፡ መኪናው ፡ እንዲቆም ፡ ምልክት ፡ አሳየ
3. አሳወቀ. He blinked his flashlight to signal he was ready. መዘጋጀቱን ፡ ለማሳወቅ ፡ ባትሪውን ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ አደረገ
4. ጠራ. Will you signal the waiter, please? አሳላፊውን ፡ ጥራልኝ

**signal** (n.)
1. ምልክት. We agreed on a signal. ባንድ ፡ ምልክት ፡ ለመጠቀም ፡ ተስማማን
Birds flying south are a signal of coming winter. የወፎች ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ መብረር ፡ የክረምት ፡ መምጣት ፡ ምልክት ፡ ነው
2. መብራት. The traffic signal turned green. የትራፊኩ ፡ መብራት ፡ አረንጓዴ ፡ አበራ
*The arrival of the Emperor was the signal for an outburst of cheering. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሲደርሱ ፡ እልልታና ፡ ሆታ ፡ ቀለጠ

**signal** (adj.) የሚያስደንቅ
The airplane is a signal invention. አውሮፕላን ፡ የሚያስደንቅ ፡ ፍልሰፋ ፡ ነው

**signatory** (signatories)
1. ፈራሚ. The signatories of the contract are all Ethiopians. የውሉ ፡ ፈራሚዎች ፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ናቸው
2. የፈረመ ፡ አገር. All signatories of the treaty are members of the United Nations. ውሉን ፡ የፈረሙ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ አባሎች ፡ ናቸው

**signature** ፊርማ
Your signature is not legible. ፊርማህ ፡ አይነበብም

**significance**
1. ቁም ፡ ነገር. I did not then realize the significance of his words. በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የንግግሩን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አልተረዳሁትም
2. ታላቅነት. The significance of the victory was not immediately realized. የድሉ ፡ ታላቅነት ፡ ወዲያው ፡ አልታወቀም ፡ ነበር

**significant**
1. ታላቅ. Adowa was a significant victory. የአድዋ ፡ ድል ፡ ታላቅ ፡ ድል ፡ ነበር
2. ትርጉም ፡ ያዘለ. A significant wink showed me that he did not believe the speaker. ትርጉም ፡ ባዘለ ፡ የዓይን ፡ ጥቅሻ ፡ ተናጋሪውን ፡ እንደማያምን ፡ አስረድቶኛል

**be significant of** የ --- መግለጫ ፡ ነው
Smiles are significant of pleasure. ፈገግታ ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ ነው

**signify** (signified)
1. አመለከተ. His retreat signifies defeat. ማፈግፈጉ ፡ መሸነፉን ፡ ያመለክታል
2. ገለጸ. He signified his consent with a nod. ራሱን ፡ በመነቅነቅ ፡ መስማማቱን ፡ ገለጸ
*What does it signify how we dress on a picnic? በሽርሽር ፡ ጊዜ ፡ እንደምንም ፡ ብንለብስ ፡ ምን ፡ አለበት ?

**signpost** ምልክት
The signpost shows that the town is not far away. ምልክቱ ፡ ከተማው ፡ እሩቅ ፡ አለመሆኑን ፡ ያመለክታል

**silence** (v.)

1. ዝም ፡ አሰኘ. Please silence the dog! ውሻውን ፡ ዝም ፡ አሰኘው
2. ደመሰሰ. They silenced the dissent. ተቃውሞውን ፡ ደመሰሱት
3. ድምፅ ፡ አጠፋ. A drop of oil will silence that squeaking. አንድ ፡ ጠብታ ፡ ዘይት ፡ ቢደረግበት ፡ ሲጢት ፡ የሚለውን ፡ ድምፅ ፡ ያጠፋዋል
4. አፈነ. He silenced his conscience and did not speak out against the injustice. ኅሊናውን ፡ አፍኖ ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ስለሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ሳይናገር ፡ ቀረ

**silence** (n.)

1. ጸጥታ. There was profound silence in the room. በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ፍጹም ፡ ጸጥታ ፡ ነበር
They listened in silence. በጸጥታ ፡ አዳመጡ
2. ዝምታ. His silence meant he agreed. ዝምታው ፡ መስማማቱን ፡ አመለከተ
3. ዝም ፡ ማለት. His silence worries me. ዝም ፡ ማለቱ ፡ ያሳስበኛል

**in silence** ዝም ፡ ብሎ
He passed over the subject in silence. ጉዳዩን ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አለፈው

**lapse into silence** ጭጭ ፡ አለ
After a brief talk, he lapsed into silence. ካጭር ፡ ንግግር ፡ በኋላ ፡ ጭጭ ፡ አለ

**maintain silence** ጸጥ ፡ አለ
The congregation maintained silence during the sermon. በስብከቱ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ጸጥ ፡ አለ

**reduce to silence** ጸጥ ፡ አደረገ
The monitor reduced the class to silence. የክፍሉ ፡ አለቃ ፡ ክፍሉን ፡ ጸጥ ፡ አደረገው

**silent**

1. ጸጥ ፡ ያለ. I am looking for a silent place to study. ለማጥናት ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ እፈልጋለሁ
2. ጭር ፡ ያለ. We walked along the silent streets of the city at night. ሌሊት ፡ ጭር ፡ ባሉት ፡ የከተማው ፡ መንገዶች ፡ ላይ ፡ ተዘዋወርን
3. የጸጥታ. The cat walks with silent footsteps. ድመቷ ፡ በጸጥታ ፡ እርምጃ ፡ ትራመዳለች
4. ዝምተኛ. He is a silent, thoughtful boy. ዝምተኛና ፡ አስተዋይ ፡ ልጅ ፡ ነው
5. በቃል ፡ ያልተገለጸ. This was a silent command. በቃል ፡ ያልተገለጸ ፡ ትእዛዝ ፡ ነበር
6. የማይፈነዳ. There are silent volcanos in this region. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ የማይፈነዱ ፡ እሳተ ፡ ገሞራዎች ፡ አሉ

**be silent**
1. ጸጥ ፡ አለ. The shouting stopped, and all was silent. ጫጫታው ፡ ቆመና ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ጸጥ ፡ አለ
2. ምንም ፡ አልተናገረም. The stranger was silent about his youth. እንግዳው ፡ ስለ ፡ ልጅነቱ ፡ ምንም ፡ አልተናገረም
3. ምንም ፡ ነገር ፡ አላወራም. The newspapers were silent about the accident. ጋዜጣዎቹ ፡ ስለ ፡ አደጋው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አላወሩም
4. (= active) ዝም ፡ አሰኘ. Why are you so silent? ምን ፡ እንደዚህ ፡ ዝም ፡ አሰኘህ ?

**keep silent**
*Don't you know when to keep silent? ዝም ፡ ብትይስ ?

**remain silent** ዝም ፡ አለ
When he was asked to explain what he did with the money, he remained silent. ገንዘቡን ፡ ምን ፡ እንዳደረገበት ፡ እንዲገልጽ ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ አለ

**silently** ጸጥ ፡ ብሎ
They walked along silently side by side. ጸጥ ፡ ብለው ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ተራመዱ

**silent movie** ድምፅ ፡ የሌለው ፡ ፊልም
I saw Charlie Chaplin in a silent movie. ቻርሊ ፡ ቻፕሊንን ፡ ድምፅ ፡ እሌለበት ፡ ፊልም ፡ ውስጥ ፡ አየሁት

**silent partner**
*He's a silent partner. ባስተዳደሩ ፡ ውስጥ ፡ የማይገባ ፡ ሽርካ ፡ ነው

**silhouette** ጥላ
I could see the silhouette of a man reading a book. መጽሐፍ ፡ የሚያነብ ፡ ሰው ፡ ጥላ ፡ ይታየኛል

**silk** ሐር
The dress was made of silk. የሐር ፡ ቀሚስ ፡ ነው

**silken**

1. ከሐር ፡ የተሠራ. The king wore silken robes. ንጉሡ ፡ ከሐር ፡ የተሠሩ ፡ ካባዎች ፡ ለበሰ
2. ሐር ፡ የሚመስል. She has silken hair. ሐር ፡ የሚመስል ፡ ጸጉር ፡ አላት
3. የሐር. The caterpillar wound a silken sheath about itself. አባ ፡ ጨንሬው ፡ የሐር ፡ ሽፋኑን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ጠመጠመ

**silkworm** የሐር ፡ ትል
It is difficult to raise silkworms. የሐር ፡ ትል ፡ ማርባት ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ ነው

**silky** ሐር ፡ የሚመስል
A kitten has silky fur. የድመቷ ፡ ግልገል ፡ ጸጉሯ ፡ ሐር ፡ የሚመስል ፡ ነው

**sill** ደፍ
He stumbled over the door sill. የበሩ ፡ ደፍ ፡ አደናቀፈው

**window sill** መስኮት
She put a flower vase on the window sill. መስኮቱ ፡ ላይ ፡ ያበባ ፡ ማስቀመጫ ፡ አኖረች

**silliness** ጅልነት
Men don't like to talk to her because of her silliness. ከጅልነቷ ፡ የተነሣ ፡ ወንዶች ፡ ሊያነጋግሯት ፡ አይፈልጉትም

**silly**
1. ቂል. Don't be silly! The moon will not fall. ቂል ፡ አትሁን ፤ ጨረቃ ፡ አትወድቅም
2. የጅልነት. Her silly behavior offended her husband's friends. የጅልነት ፡ ሁኔታዋ ፡ የባሏን ፡ ጓደኞች ፡ ቅር ፡ አሰኘ
3. የማይረባ. Reading silly stories perverts our taste for good books. የማይረቡ ፡ ታሪኮችን ፡ ማንበብ ፡ ጥሩ ፡ መጽሐፍ ፡ ለማንበብ ፡ ያለንን ፡ ስሜት ፡ ያበላሽብናል

**silt** ደለል
The flooded fields were covered with silt. ጐርፍ ፡ ያጥለቀለቃቸው ፡ ሜዳዎች ፡ ደለል ፡ ለብሰው ፡ ነበር

**silver** (v.) ብርማ ፡ ቀለም ፡ ቀባ
Silver the mirror to make it reflect light! ብርሃን ፡ እንዲያንጸባርቅ ፡ ለማድረግ ፡ መስታወቱን ፡ ብርማ ፡ ቀለም ፡ ቀባው

**silver** (n.) ብር
This spoon is made of silver. ይህ ፡ ማንኪያ ፡ የተሠራው ፡ ከብር ፡ ነው

**silver** (adj.) የብር ፤ ከብር ፡ የተሠራ
Mother bought three silver spoons. እናቱ ፡ ሦስት ፡ የብር ፡ ማንኪያዎች ፡ ገዛች
The woman wore a silver anklet. ሴትዮዋ ፡ ከብር ፡ የተሠራ ፡ አምባር ፡ አድርጋለች

**silver-plated** የብር ፡ ቅብ
This spoon is silver-plated. ይህ ፡ ማንኪያ ፡ የብር ፡ ቅብ ፡ ነው

**table silver** ከብር ፡ የተሠራ ፡ የገበታ ፡ እቃ
A thief stole all our table silver. ከብር ፡ የተሠራ ፡ የገበታ ፡ እቃችንን ፡ በሙሉ ፡ ሌባ ፡ ሰረቀው

**silversmith** አንጥረኛ ፤ ብር ፡ አፍሳሽ
The silversmith made me a nice cross. አንጥረኛው ፡ ጥሩ ፡ መስቀል ፡ ሠራልኝ
The silversmith is a good artisan. ብር ፡ አፍሳሹ ፡ ጥሩ ፡ ባለ ፡ እጅ ፡ ነው

**silverware** የገበታ ፡ እቃ ፤ ከብር ፡ የተሠሩ ፡ የምግብ ፡ እቃዎች
His silverware has his initials on it. የገበታ ፡ እቃው ፡ የስሙ ፡ መጀመሪያ ፡ ፊደሎች ፡ ተቀርጸውበታል
The maid shines the silverware. ገረዲቱ ፡ ከብር ፡ የተሠሩትን ፡ የምግብ ፡ እቃዎች ፡ ትወለውላለች

**silvery**
1. ብር ፡ የሚመስል. The silvery moon seemed to float through the sky. ብር ፡ የምትመስለው ፡ ጨረቃ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ የምትዋልል ፡ ትመስል ፡ ነበር
2. የጠራ. I can see my reflection in the silvery water. በጠራው ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ መልኬን ፡ ማየት ፡ እችላለሁ

**similar**
1. ተመሳሳይ. My wife and I have similar tastes. ሚስቴና ፡ እኔ ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ምርጫችን ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው
2. ይህን ፡ የሚመስል. I know of a similar case. ይህንኑ ፡ የሚመስል ፡ ነገር ፡ አውቃለሁ

**be similar** ተመሳሰለ
A river and a brook are similar. ወንዝና ፡ ጅረት ፡ ይመሳሰላሉ

**similarity** (similarities) መመሳሰል
There is a cultural similarity between Japan and China. በጃፓንና ፡ በቻይና ፡ መሃከል ፡ የባህል ፡ መመሳሰል ፡ አለ
*There is no similarity between the two. ሁለቱ ፡ አይመሳሰሉም

**simile** ተነጻጻሪ
He uses similes such as 'He sang like a bird' in his poetry. « እንደ ፡ ወፍ ፡ ዘመረ » ፡ በሚል ፡ ዓይነት ፡ ተነጻጻሪ ፡ በግጥሙ ፡ ይጠቀማል

**similitude** ተመሳሳይነት
There is a degree of similitude between Japan and China. በጃፓንና ፡ በቻይና ፡ መሀከል ፡ በመጠኑ ፡ ተመሳሳይነት ፡ አለ

**simmer** (vt.)
[ከመፍላት ፡ ደረጃ ፡ ሳይደርስ ፡ አሞቀ]

**simmer** (vi.) ገነፈለ
He simmered with rage when the policeman gave him a ticket. ትራፊኩ ፡ ከርኒ ፡ ሲሰጠው ፡ በንዴት ፡ ገነፈለ

**simple**
1. ቀላል. It may sound simple to you, but

I don't understand it. ላንተ ፡ ቀላል ፡ ይመስልህ ፡ ይሆናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ አልገባኝም
2. ተራ. She wears very simple clothes. ተራ ፡ ልብስ ፡ ትለብሳለች
Hunger gives relish to simple food. ረኀብ ፡ ተራ ፡ ምግብን ፡ ተወዳጅ ፡ ያደርገዋል
3. ቀላል ፡ አካል ፡ ያለው. The amoeba is a simple animal. አሜባ ፡ ቀላል ፡ አካል ፡ ያለው ፡ እንስሳ ፡ ነው
4. የቀለለ. The anatomy of the earthworm is simple. የቅምቡርስ ፡ የሰውነት ፡ አሠራር ፡ የቀለለ ፡ ነው
5. ያልተወሳሰበ. This building has a simple design. ይህ ፡ ሕንጻ ፡ ቅርጹ ፡ ያልተወሳሰበ ፡ ነው
6. ቅን. She has a simple pleasant manner. ቅንና ፡ አስደሳች ፡ የሆነ ፡ ጠባይ ፡ አላት
7. ቂል. Are you simple enough to believe everything your neighbors tell you? ጐረቤቶችህ ፡ የነገሩህን ፡ ሁሉ ፡ ለማመን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ቂል ፡ ነህ ?

**(a) simple citizen** ማንም ፡ ዜጋ ፡ የሆነ ፡ ሰው
Even a simple citizen has the right to criticize the President. ማንም ፡ ዜጋ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ፕሬዚዳንቱን ፡ ለመንቀፍ ፡ መብት ፡ አለው

**simple people** ድኾች
His parents are simple people. ወላጆቹ ፡ ድኾች ፡ ናቸው

**simple truth** እቅጩ
My answer is the simple truth. መልሱ ፡ እቅጩ ፡ ነው

**simple-hearted** ገር
A simple-hearted man will never refuse a request for help. ገር ፡ ሰው ፡ እርዳታ ፡ ሲጠየቅ ፡ በፍጹም ፡ እምቢ ፡ አይልም

**simple-minded** ቂል
He must be simple-minded to have bought that old car. ያን ፡ አሮጌ ፡ መኪና ፡ የገዛው ፡ ቂል ፡ ቢሆን ፡ ነው

**simpleton** ጅል
Only a simpleton would believe that story. ያንን ፡ የሚያምን ፡ ጅል ፡ ብቻ ፡ ነው

**simplicity**
1. የዋህነት. His simplicity allows him to be easily fooled. የዋህነቱ ፡ በቀላሉ ፡ እንዲሞኝ ፡ ያደርገዋል
2. ቀናነት. The simplicity of your plan intrigues me, but I wonder if it would work. የእቅድህ ፡ ቀናነት ፡ ስቦኛል ፡ ግን ፡ የሚሠራ ፡ መሆኑን ፡ እጠራጠራለሁ
3. ቀላል ፡ ዘዴ. Simplicity of style makes his books easy to read. ቀላል ፡ ያጻጻፍ ፡ ዘዴው ፡ መጻሕፍቱን ፡ በቀላሉ ፡ የሚነበብ ፡ አድርጓቸዋል
*A room in a hospital should be furnished with simplicity. በሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ የበሽተኞች ፡ መኝታ ፡ ክፍል ፡ ዝባዝንኬ ፡ እንዳይበዛው ፡ ያስፈልጋል

**for the sake of simplicity** ነገሩን ፡ ለማቅለል ፡ ያህል
For the sake of simplicity, let's say that .... ነገሩን ፡ ለማቅለል ፡ ያህል ፡ እንዲህ ፡ እንበል

**simplify** (simplified) ቀላል ፡ አደረገ
You have to simplify your text for the first grade students. መጽሐፍህን ፡ ላንደኛ ፡ ክፍል ፡ ተማሪዎች ፡ ቀላል ፡ ልታደርገው ፡ ይገባል

**simply**
1. በፍጹም. That's simply impossible! ይህ ፡ በፍጹም ፡ አይሆንም
2. ብቻ. The baby did not simply cry; he yelled. ሕፃኑ ፡ ማልቀስ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ጮኸ
3. ጅል ፡ ሆኖ. If you behave simply toward him, you are bound to be rejected. በሱ ፡ ዘንድ ፡ ጅል ፡ ሆነህ ፡ ከተገኘህ ፡ መጠላትህ ፡ ነው
*The room is simply furnished. ክፍሉ ፡ ጌጣ ፡ ጌጥ ፡ አልበዛበትም
*I simply couldn't fall asleep. ምንም ፡ ልተኛ ፡ አልቻልኩም

**very simply** ቀላል ፡ በሆነ ፡ አኳኋን
The speaker presented his talk very simply. ተናጋሪው ፡ ንግግሩን ፡ ቀላል ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ አቀረበ
*Monks live very simply. መነኰሳት ፡ ቀላል ፡ ኑሮ ፡ ይኖራሉ

**simulate**
1. መሰለ. The butterfly simulates a twig. ቢራቢሮዋ ፡ ቅጠል ፡ ትመስላለች
The boss simulated anger when I was a minute late. አንድ ፡ ደቂቃ ፡ ዘግይቼ ፡ ብደርስ ፡ አለቃዬ ፡ የተቈጣ ፡ መሰለ
2. መስሎ ፡ ታየ. Mary simulated interest in the story to please her friend. ሜሪ ፡ ጓደኛዋን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ታሪኩን ፡ የወደደችው ፡ መስላ ፡ ታየች

**(be) simultaneous** አንድ ፡ ሆነ ፤ አንድ ፡ ላይ ፡ ነበር
The car crash and the bomb explosion were simultaneous. መኪናዎቹ ፡ ሲጋጩና ፡ ቦምቡ ፡ ሲፈነዳ ፡ አንድ ፡ ሆነ

Their responses were simultaneous. የመልሱት ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ነበር

**sin** (sinned), v.
1. ኀጢአት ፡ ሠራ. He sinned by abusing God's name. የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በመስደቡ ፡ ኀጢአት ፡ ሠራ
2. በደለ. Adam and Eve sinned. አዳምና ፡ ሔዋን ፡ በደሉ

**sin** (n.) ኃጢአት
God punished them for their sin. እግዚአብሔር ፡ ለሠሩት ፡ ኃጢአት ፡ ቀጣቸው
It's a sin to stay indoors on such a nice day. ይህን ፡ በመሰለ ፡ ጥሩ ፡ ቀን ፡ እቤት ፡ መዋል ፡ ኃጢአት ፡ ነው
[See also 'absolve']

**since** (conj.)
1. ከ + (perfect) + ወዲህ ፤ ከ + (perfect) + ጀምሮ. He has worked hard since he left school. ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ከወጣ ፡ ወዲህ ፡ (ጀምሮ) ፡ ጠንክሮ ፡ ይሠራል
2. ከ + (perfect). He has written home only once since he left us. ከሄደ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ጽፎልናል
3. ስለ. Since I didn't have the money, I couldn't go. ገንዘብ ፡ ስላልነበረኝ ፡ መሄድ ፡ አልቻልኩም
*How long has it been since you have been in Addis Ababa? አዲስ ፡ አበባ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ኖረሃል ?

**since** (prep.)
1. ከ --- ወዲህ. We have not seen him since Saturday. ከቅዳሜ ፡ ወዲህ ፡ አላየነውም
2. ከ --- ጀምሮ. The package has been ready since noon. ጥቅሉ ፡ ከስድስት ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ ተዘጋጅቷል
3. (= conj.) ከ + (perfect) + ጀምሮ. She hasn't been home since her marriage. ካገባች ፡ ጀምሮ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቿን ፡ አልጠየቀችም

**since** (adv.) ከዚያ ፡ ወዲህ
The town was destroyed ten years ago but has since been completely rebuilt. ከተማው ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ወድሞ ፡ ነበር ፤ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ እንደገና ፡ በደንብ ፡ ተሠርቷል

**since then** ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ
Since then, he's been a monk. ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ መንኲሷል

**ever since**
1. እስካሁን. He went to Ethiopia in 1954 and has lived there ever since. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም. ሄዶ ፡ እስካሁን ፡ እዚያው ፡ ይኖራል
2. ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ. I haven't talked to him ever since. ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ አላነጋገርኩትም
3. ከዚያ ፡ ወዲህ. He married a shrew and has suffered ever since. አንዲት ፡ ነዝናዛ ፡ ልጅ ፡ አግብቶ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ይሠቃያል
[See also 'long, when']

**sincere**
1. ቅን. He is a sincere person. ቅን ፡ ሰው ፡ ነው
2. (= adv.) ከልቡ. Are they sincere in their wish to disarm? የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እንቀንስ ፡ የሚሉት ፡ ከልባቸው ፡ ነው ?

**sincerely** ከልቡ
Do you sincerely believe it? የተናገርከውን ፡ ከልብህ ፡ ታምንበታለህ ?
*I sincerely hope you'll be able to come. ለመምጣት ፡ እንደምትችል ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ

**yours sincerely** ያንተው
He signed the letter, "yours sincerely". ደብዳቤው ፡ ላይ ፡ « ያንተው » ፡ ብሎ ፡ ፈረመበት

**sincerity**
1. ከልብ ፡ መሆን. He seems concerned about the matter, but I question his sincerity. ጉዳዩን ፡ ያሰበበት ፡ ይመስላል ፤ ከልቡ ፡ መሆኑን ፡ ግን ፡ እጠራጠራለሁ
2. ቅንነት. Only a skeptic would doubt his sincerity. ቅንነቱን ፡ የማያምን ፡ ተጠራጣሪ ፡ ብቻ ፡ ነው

**without sincerity**
*She spoke without sincerity of her desire to reform. ጠባዩን ፡ አርማለሁ ፡ ያለችው ፡ ከልቧ ፡ አልነበረም

**sinew**
1. ጅማት. The bowstring is made from the sinews of an ox. የቀስቱ ፡ መወጠሪያ ፡ የተሠራው ፡ ከበሬ ፡ ጅማት ፡ ነው
2. መሠረት. Schools are the sinews of democracy. ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የዲሞክራሲ ፡ መሠረት ፡ ናቸው
3. ምንጭ. Money, men, and materials are the sinews of war. ገንዘብ ፡ ሰዎችና ፡ ድርጅት ፡ የጦርነት ፡ ምንጮች ፡ ናቸው

**sinful**
1. ኀጢአተኛ. The sinful man repented of his deeds. ኀጢአተኛው ፡ ሰው ፡ በሥራው ፡ ተጸጸተ
2. (= noun) ኀጢአት. To kill is sinful. መግደል ፡ ኃጢአት ፡ ነው

**sinful act** ኃጢአት
Killing is a sinful act. ሰውን ፡ መግደል ፡ ኃጢአት ፡ ነው

**sinful man** ኀጢአተኛ
The sinful man repented. ኀጢአተኛው ፡ ንስሐ ፡ ገባ

**sing** (sang), vt. ዘመረ
He sang a song celebrating the Annunciation. ብስራተ ፡ ገብርኤልን ፡ ለማስታወስ ፡ መዝሙር ፡ ዘመረ

**sing** (vi.)
1. ዘፈነ. She sings well. ጥሩ ፡ ትዘፍናለች
2. ዘመረ. The birds are singing in the trees. ወፎች ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ይዘምሩ ፡ ነበር
3. እሽሩሩ ፡ አለ. Mother sang the baby to sleep. እናትዮዋ ፡ ሕፃኑ ፡ እንዲተኛ ፡ እሽሩሩ ፡ አለችው
4. አፏጨ. The teakettle sings. የሻዩ ፡ ጀበና ፡ ያፏጫል

**sing Mass** ቀደሰ
The priest sings Mass. ቄሱ ፡ ይቀድሳል

**sing of** በግጥም ፡ አወደሰ
The poet sang of heroes. ገጣሚው ፡ ጀግኖችን ፡ በግጥም ፡ አወደሰ

**sing (someone's) praise**
1. አሞገሰ. He sings the governor's praise. አገረ ፡ ገዢውን ፡ ያሞግሳል
2. ስለ --- ጉራ ፡ ነዛ. He sings his son's praises. ስለ ፡ ልጁ ፡ ጉራ ፡ ይነዛል
[See also 'hymn, lull']

**singe**
1. ለበለበ. The flames singed my hair. እሳቱ ፡ ጸጉሬን ፡ ለበለበው
The maid singed the chicken. ገረዲቱ ፡ ዶሮውን ፡ ለበለበች
2. አጕደፈ. Scandal singed the mayor's reputation. አሳፋሪ ፡ ወሬ ፡ የከንቲባውን ፡ መልካም ፡ ስም ፡ አጕደፈው

**singer** ዘፋኝ
The American singer is well known to all. አሜሪካዊው ፡ ዘፋኝ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው
Singers were present at the wedding. በሰርጉ ፡ ላይ ፡ ዘፋኞች ፡ ነበሩ

**single** (v.), ~ **out**
*The teacher singled Tom out for praise. አስተማሪው ፡ በተለይ ፡ ቶምን ፡ አመሰገነ

**single** (adj.)
1. አንድ. The soldiers walked in single file. ወታደሮቹ ፡ ባንድ ፡ መሥመር ፡ ተጓዙ
2. አንድ ፡ ብቻ. The spider hung by a single thread. ሸረሪቷ ፡ ባንድ ፡ ክር ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ተንጠልጥላለች
3. ወንደላጤ. They asked him, "Are you married or single?". ባለትዳር ፡ ነህ ፡ ወይስ ፡ ወንደላጤ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት
4. የወንደላጤ. I prefer a single bed to a double bed. ከፋሚሊ ፡ አልጋ ፡ ይልቅ ፡ የወንደላጤ ፡ አልጋ ፡ እመርጣለሁ
5. የማያወላውል. She showed single devotion to her religion. ለሃይማኖቷ ፡ የማያወላውል ፡ ፍቅር ፡ አሳየች

**single** (adv.) ብቻውን
He came to the party single. ለግብዣው ፡ ብቻውን ፡ መጣ

**be single** አላገባም
I asked her if she was single or married. አግብተሻል ፡ ወይስ ፡ አላገባሽም ፡ ብዬ ፡ ጠየቅኋት (or, ባለትዳር ፡ ነሽ ፡ ወይስ ፡ አይደለሽም ፡ ብዬ ፡ ጠየቅኋት)
I asked him if he was single or married. አግብተሃል ፡ ወይስ ፡ አላገባህም ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁት ፡ (or, ትዳር ፡ ይዘሃል ፡ ወይስ ፡ አልያዝክም ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁት)

**every single** እያንዳንዱ
I looked through every single drawer, but couldn't find it. እያንዳንዱ ፡ መሳቢያ ፡ ውስጥ ፡ ፈለግሁ ፡ ግን ፡ ላገኘው ፡ አልቻልኩም

**not a single** አንድም + negative verb
He didn't make a single mistake. አንድም ፡ ስሕተት ፡ አልሠራም

**single combat** የጨበጣ ፡ ውጊያ
The soldiers engaged in single combat. ወታደሮቹ ፡ የጨበጣ ፡ ውጊያ ፡ አደረጉ

**single-handedly** ብቻውን ፡ ሆኖ
The policeman made an arrest single-handedly. ፖሊሱ ፡ ብቻውን ፡ ሆኖ ፡ ወንጀለኛውን ፡ ያዘው

**(be) single-minded** የተወሰነ ፡ ዓላማ ፡ አለው
He is very single-minded and impossible to distract. የተወሰነ ፡ ዓላማ ፡ ስላለው ፡ ሐሳቡን ፡ ለማዛባት ፡ ያስቸግራል

**single-track**, ~ **mind** ሐሳበ ፡ ጠባብ ፡ ሰው
A single-track mind is incapable of devising a solution. ሐሳበ ፡ ጠባብ ፡ ሰው ፡ መፍትሔ ፡ ሊፈጥር ፡ አይችልም

**single-track railroad** አንድ ፡ የባቡር ፡ ሐዲድ ፡ መሥመር
A single-track railroad connects Addis Ababa

with Djibouti. አንድ ፡ የባቡር ፡ ሐዲድ ፡ መሥመር ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ ከጂቡቲ ፡ ጋር ፡ ያገናኛል

**singly**
1. አንድ ፡ ባንድ. He attacked the soldiers singly as they came through the forest. ወታደሮቹ ፡ ከጫካው ፡ ሲወጡ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ለቀማቸው
2. ብቻውን. Misfortunes never come singly. ክፉ ፡ ነገር ፡ ብቻውን ፡ አይመጣም

**singular** (n.) ነጠላ
The Amharic noun has a singular and a plural. ስም ፡ ባማርኛ ፡ ነጠላና ፡ ብዙ ፡ አለው
**singular** (adj.)
1. እንግዳ ፡ የሆነ. A very singular accident happened to me. በጣም ፡ እንግዳ ፡ የሆነ ፡ አደጋ ፡ ደረሰብኝ
2. ልዩ ፡ የሆነ. This singular specimen was caught by a fisherman in the Blue Nile. ይህ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ዓሣ ፡ በጥቁር ፡ ዓባይ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ዓሣ ፡ አጥማጅ ፡ የያዘው ፡ ነው
*He is a man of singular habits. ከሰው ፡ የማይገጥም ፡ ልማድ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው
*He is a man of singular courage. በጣም ፡ ደፋር ፡ ነው

**singularity**
1. ብርቅነት. The singularity of the dwarf's appearance attracted many people. የድንክዬው ፡ ብርቅነት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሳበ
2. መለዮ. One of the giraffe's singularities is the length of its neck. ከቀጭኔ ፡ መለዮዎች ፡ አንዱ ፡ ያንገት ፡ እርዝማኔ ፡ ነው

**sinister** ክፉ
When I inadvertently disclosed his secret, he gave me a sinister look. ተሳስቼ ፡ ምስጢሩን ፡ ባወጣ ፡ በክፉ ፡ ዓይን ፡ ተመለከተኝ
*This is a sinister beginning for starting a new business. ላዲስ ፡ ንግድ ፡ ይህ ፡ የመጥፎ ፡ ዕድል ፡ ምልክት ፡ ነው
**sinister role** ተንኰል
He played a sinister role in the minister's fall from power. ሚኒስትሩ ፡ እንዲሻር ፡ ተንኰል ፡ ሠራበት

**sink** (sunk, or sank), vt.
1. አሰጠመ. The submarine sank two ships. ሰርጓጅ ፡ መርከብ ፡ ሁለት ፡ መርከቦችን ፡ አሰመጠች
2. ቈፈረ. The men are sinking a well. ሰዎቹ ፡ ጉድጓድ ፡ ይቈፍራሉ
3. ሰካ. He sank the spade into the ground. አካፋውን ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ሰካው
4. አፈሰሰ. He sank a fortune into that business. በዚያ ፡ ንግድ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አፈሰሰ
5. አዋለ. He sank all his savings in stocks. ያጠራቀመውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ በንድ ፡ ላይ ፡ አዋለ
*She sank her voice to a whisper. አንሾካሾከች
**sink** (vi.)
1. ሰጠመ ፤ ሰመጠ. The ship sank in ten minutes. መርከቡ ፡ ባሥር ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ሰጠመ ፡ (ሰመጠ)
His foot sank in the mud. እግሩ ፡ ጭቃ ፡ ውስጥ ፡ ሰመጠ
2. ጠለቀ. The sun sinks in the west. ፀሐይ ፡ በምዕራብ ፡ ትጠልቃለች
3. ጐደለ. Due to lack of rain, the reservoirs sank. በዝናብ ፡ መታጣት ፡ ምክንያት ፡ የውኃ ፡ ማከማቻው ፡ ጐደለ
4. ዘቀጠ. The house has sunk two feet. የቤቱ ፡ መሠረት ፡ ሁለት ፡ ጫማ ፡ ዘቅጧል
5. አንገተበ ፡ ወረደ. The balloon sank to the earth. ፊኛው ፡ አንገተበ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ወረደ
6. ዝቅ ፡ አለ. The price of eggs sank during the summer. በበጋው ፡ የእንቁላል ፡ ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ አለ
7. ውኃ ፡ ሆነ. When he saw his wrecked car, his heart sank. የተሰበረውን ፡ መኪናውን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡ ውኃ ፡ ሆነ
**sink down** ተቀመጠ
He sank down on the bench and waited for the next bus. አግዳሚው ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ አውቶቡሱን ፡ ጠበቀ
**sink in**
*The teacher said it to the students four times before the words really sank in. ተማሪዎቹ ፡ ቃሉን ፡ ከመረዳታቸው ፡ በፊት ፡ መምህሩ ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ አለው
**(be) sunk in thought** በሐሳቡ ፡ ተዋጠ
He was sunk in thought, and nothing distracted him. በሐሳብ ፡ ተውጦ ፡ ስለነበር ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አልተሰማውም
**sink into one's mind** ገባ(ው)
This lesson does not sink into my mind. ይህ ፡ ትምህርት ፡ አይገባኝም
**sink to the ground** ተዝለፍልፎ ፡ ወደቀ
The soldier sank to the ground, badly wounded. ወታደሩ ፡ በኀይል ፡ ስለቈሰለ ፡ ተዝለፍልፎ ፡ ወደቀ
[See also 'heart, zero']

**sink** (n.) እቃ ፡ ማጠቢያ
The dishes are still in the sink. ሳሕኖቹ ፡ እስካሁን ፡ እቃ ፡ ማጠቢያው ፡ ውስጥ ፡ ናቸው

**sinner** ኃጥእ (pl. ኃጥአን)
According to some religions, sinners are punished in hell. አንዳንድ ፡ ሃይማኖቶች ፡ ኃጥአን ፡ ገሃነም ፡ ይገባሉ ፡ ይላሉ

**sinuous** ጠመዝማዛ
The course of the river is sinuous. ወንዙ ፡ ጠመዝማዛ ፡ ነው

**sip** (sipped) ፉት ፡ አለ
He likes to sip his tea. ሻዩን ፡ ፉት ፡ ማለት ፡ ይወዳል

**sip** (n.), **have a ~** ፉት ፡ አለ
I only had a sip of it. አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ፉት ፡ አልኩት

**siphon** (v.) በጎማ ፡ ቀዳ
He siphoned some gas out of his tank and gave it to me. ትንሽ ፡ ቤንዚን ፡ ከመኪናው ፡ በጎማ ፡ ቀድቶ ፡ ሰጠኝ

**siphon** (n.) [ካንዱ ፡ መያዣ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ መያዣ ፡ ፈሳሽ ፡ የሚያስተላልፍ ፡ ቱቦ]

**sir**
1. ጌቶች. Dinner is ready, sir. ጌቶች ፤ እራት ፡ ቀርቧል
2. ጌታዬ. Sir, I came to complain. ጌታዬ! አቤት ፡ ልል ፡ መጥቻለሁ

**sire** (v.) ወለደ
He sired a son much unlike himself. ምኑንም ፡ የማይመስል ፡ ልጅ ፡ ወለደ

**sire** (n.) አባት
The sire of this colt was a winning racer. የድንጉላው ፡ አባት ፡ በእሽቅድምድም ፡ አሸናፊ ፡ ነበር

**siren** ያደጋ ፡ ፉጨት
I heard a fire siren. የእሳት ፡ አደጋ ፡ ፉጨት ፡ ሰማሁ

**sirloin steak** ታላቅ ፡ ሥጋ
He likes sirloin steak. ታላቅ ፡ ሥጋ ፡ ይወዳል

**sisal** ቃጫ
The rope is made of sisal. ገመዱ ፡ ከቃጫ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**sister** እኅት
My sister is sick. እኅቴ ፡ ታማለች

**sister-in-law** ምራት
My sister-in-law always argues with my mother. ምራቴ ፡ ሁልጊዜ ፡ ከእናቴ ፡ ጋር ፡ ትጨቃጨቃለች

**sit** (sat), vt. አስቀመጠ
Our table sits only six people. ጠረጴዛችን ፡ ስድስት ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ያስቀምጣል
The woman sat the little boy down hard. ሴትዮዋ ፡ ልጁን ፡ በኀይል ፡ አስቀመጠችው

**sit** (vi.)
1. ተቀመጠ. We sat in the front row. በመጀመሪያው ፡ ረድፍ ፡ ተቀመጥን
2. ተቀመጠ(ለት). Who sat for the portrait that you just finished? ለዚህ ፡ አሁን ፡ ለጨረስከው ፡ ሥዕል ፡ ማን ፡ ተቀመጠልህ ?
3. አረፈ. A bird sat on the fence. አጥሩ ፡ ላይ ፡ ወፍ ፡ አርፋለች
4. አባል ፡ ነው. My brother sits in the senate. ወንድሜ ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባል ፡ ነው
5. ተሠየመ. While the court is sitting, visitors may not enter the building. ዳኞች ፡ ከተሠየሙ ፡ በኋላ ፡ ውጭ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ መግባት ፡ የለባቸውም
6. ስብሰባ ፡ ያዘ. Parliament was still sitting at 3 a.m. የፓርላማ ፡ መማክርት ፡ እስከ ፡ ሌሊቱ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ስብሰባ ፡ ይዘው ፡ ነበር

**sit around** ዝም ፡ ብሎ ፡ ተጐለተ
You won't get anywhere sitting around the house. ዝም ፡ ብለህ ፡ እቤት ፡ በመጐለት ፡ ምንም ፡ አታተርፍ

**sit back** ደገፍ ፡ ብሎ ፡ ተቀመጠ
Sit back in your chair! ወንበሩ ፡ ላይ ፡ ደገፍ ፡ ብለህ ፡ ተቀመጥ

**sit down** (vt.) አስቀመጠ
He sat the boy down and gave him a lecture. ልጁን ፡ አስቀምጦ ፡ ምክር ፡ ሰጠው

**sit down** (vi.) ተቀመጠ
Sit down, please! ተቀመጥ ፡ እስቲ

**sit in on** ተካፋይ ፡ ነበረ
I sat in on all conferences. የስብሰባው ፡ ሁሉ ፡ ተካፋይ ፡ ነበርኩ

**sit on the eggs** ታቀፈ
The mother hen hatches her eggs by sitting on them. ጫጩቶች ፡ የሚፈለፈሉት ፡ እናቲቱ ፡ ዶሮ ፡ ስትታቀፍ ፡ ነው

**sit loosely** ሰፋ(በት)
The coat sits loosely. ኮቱ ፡ ሰፍቶበታል

**sit out** ቁጭ ፡ ብሎ ፡ አሳለፈ
They sat out the storm in their little car. ዝናቡን ፡ ትንሿ ፡ መኪናቸው ፡ ውስጥ ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ አሳለፉት

**sit tight** ረጋ ፡ ብሎ ፡ ተቀመጠ ፤ ከዚህ ፡ ንቅንቅ ፡ አላለም

Sit tight! Your turn will come. ረጋ ፡ ብለህ ፡ ተቀመጥ ። ተራህ ፡ ይደርሳል
Sit tight till I come back. እስክመለስ ፡ ከዚህ ፡ ንቅንቅ ፡ እንዳትል

**sit up**
1. ቀና ፡ ብሎ ፡ ተቀመጠ. The patient tried to sit up in bed. በሽተኛው ፡ ካልጋው ፡ ላይ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ለመቀመጥ ፡ ሞከረ
2. ተቀመጠ. We sat up all night waiting for him. እሱን ፡ ስንጠብቅ ፡ ተቀምጠን ፡ አደርን

**sit up straight** ቀና ፡ ብሎ ፡ ተቀመጠ
Sit up straight; it's bad for you to slouch in your chair. ቀና ፡ ብለህ ፡ ተቀመጥ ። ተንጋዶ ፡ መቀመጥ ፡ ላንተ ፡ ጥሩ ፡ አይደለም

**sit well** ተስማማ
Your coat sits well. ኮትህ ፡ ይስማማሃል
[See also 'lunch']

**sit-down strike**
*The company is having a sit-down strike. የኩባንያው ፡ ሠራተኞች ፡ ሁሉ ፡ ኩባንያው ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠው ፡ አንነሣም ፡ በማለት ፡ አደሙ

**site**
1. ቦታ. A new hotel will be constructed on this site. እዚህ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ ሆቴል ፡ ይሠራል
2. ስፍራ. The site of the dam is fifty miles from here. ግድቡ ፡ ሊሠራ ፡ የታቀደበት ፡ ስፍራ ፡ ከዚህ ፡ ኀምሳ ፡ ማይል ፡ ይርቃል

**sitting** (n.)
*We ate with the first sitting. መጀመሪያ ፡ ከሚበላው ፡ ጓድ ፡ ጋር ፡ በላን

**in one sitting** አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ
He finished the book in one sitting. አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፉን ፡ አንብቦ ፡ ጨረሰው

**sitting room** እንግዳ ፡ ቤት
I waited for her in the sitting room. እንግዳ ፡ ቤት ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ጠበቅኋት

**situate** አቋቋመ
Where will you situate the new factory? አዲሱን ፡ ፋብሪካ ፡ የት ፡ ልታቋቁመው ፡ ነው ?

**be situated** ተገኘ
The village is situated in a valley. መንደሩ ፡ የሚገኘው ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ነው

**situation**
1. አቀማመጥ. Our house has a beautiful situation on a hill. በኰረብታው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ቤታችን ፡ ጥሩ ፡ የሆነ ፡ አቀማመጥ ፡ አለው
2. መሆን. The situation of Addis Ababa in the mountains gives it a mild climate. አዲስ ፡ አበባ ፡ በተራራዎች ፡ መካከል ፡ በመሆኗ ፡ ጥሩ ፡ አየር ፡ አላት
3. ሁኔታ. What is the situation in the Middle East now? አሁን ፡ በመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
4. ውጥንቅጥ. You got yourself out of that situation skillfully. ከዚያ ፡ ውጥንቅጥ ፡ ራስህን ፡ በዘዴ ፡ አወጣህ
5. ጊዜ. Act reasonably in all situations! በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ አድርግ
6. ሥራ. Is the situation still vacant? ሥራው ፡ አሁንም ፡ ክፍት ፡ ነው ?
[See also 'save']

**six** ስድስት
**six o'clock** ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት
We will have dinner today at six o'clock. ዛሬ ፡ እራት ፡ በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ እንበላለን

**sixteen** ዐሥራ ፡ ስድስት

**sixth** ስድስተኛ

**sixty** ስልሳ

**sizable** ጠቀም ፡ ያለ
He has a sizable income. ጠቀም ፡ ያለ ፡ ገቢ ፡ አለው

**size** (v.), ~ **up** ግምት ፡ ሰጠ
She sized him up carefully. ደኅና ፡ ግምት ፡ ሰጠችው
*How do you size up the situation? ስለ ፡ ሁኔታው ፡ ያለህ ፡ አስተያየት ፡ ምንድነው ?

**size** (n.)
1. ልክ. What size do you wear? ልክህ ፡ ስንት ፡ ነው ?
2. መጠን. Everything is arranged according to size. ሁሉም ፡ ነገር ፡ በየመጠኑ ፡ ተደርድሯል
3. ቁጥር. What size shoe do you wear? የጫማህ ፡ ቁጥር ፡ ስንት ፡ ነው ?
4. ቁመት. The boys are about the same size. ልጆቹ ፡ በቁመት ፡ እምብዛም ፡ አይተናነሱም
5. ስፋት. What is the size of this room? የዚህ ፡ ክፍል ፡ ስፋት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?
6. ትልቅነት. I was astonished at the size of the city. በከተማው ፡ ትልቅነት ፡ ተደንቄ ፡ ነበር
7. የሚያክለው. Notice the size of that spider! ያች ፡ ሸረሪት ፡ የምታክለውን ፡ ተመልከት
*What is the size of your herd? ምን ፡ ያህል ፡ ከብት ፡ አለህ ?

*This paper is too small; I need a larger size. ይህ ፡ ወረቀት ፡ ትንሽ ፡ ነው ፤ ከዚያ ፡ ተለቅ ፡ ያለ ፡ ያስፈልገኛል
[See also 'gigantic']

**sizzle** ተንቻቻ
The steak sizzled in the pan. ጥብሱ ፡ በመጥበሻው ፡ ላይ ፡ ተንቻቻ

**skate** (v.) በሚሽከረከር ፡ ጫማ ፡ ቆሞ ፡ ተንሸራተተ
He skated on the sidewalk. በእግረኞቹ ፡ መሄጃ ፡ ላይ ፡ በሚሽከረከር ፡ ጫማ ፡ ቆሞ ፡ ተንሸራተተ

**skein** ነዶ
"Hair like a skein of silk" is a trite expression. «የሐር ፡ ነዶ ፡ የሚመስል ፡ ጸጉር » ፡ የሚለው ፡ የነፈሰበት ፡ አነጋገር ፡ ነው

**skeleton** (n.)
1. ዐፅም. A man's skeleton was found in the cave. ዋሻው ፡ ውስጥ ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ዐፅም ፡ ተገኘ
2. ቋሚ. The steel skeleton of the new skyscraper rises above the town. ያዲሱ ፡ ሰማይ ፡ ጠቀስ ፡ ፎቅ ፡ የብረት ፡ ቋሚ ፡ ከሌላው ፡ ሕንጻ ፡ ሁሉ ፡ ልቆ ፡ ይታያል
*A long illness made a skeleton out of him. የረዥም ፡ ጊዜ ፡ ሕመም ፡ በአጥንቱ ፡ አስቀረው

**skeleton** (adj.) ጥቂት
Only a skeleton crew was needed while the ship was tied up at the dock. መርከቧ ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ ባለችበት ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ መርከበኞች ፡ ብቻ ፡ ያስፈልጓታል

**skeptic**, see **sceptic**

**sketch** (v.) በንድፍ ፡ አነሣ
He sketched the cat sleeping on the floor. ድመቱን ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ እንደተኛ ፡ በንድፍ ፡ አነሣው

**sketch** (n.)
1. ንድፍ. I have a sketch of Addis Ababa made in 1888. በ፲፰፻፹፰ ዓ. ም. የተሠራ ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ ንድፍ ፡ አለኝ
2. አስተዋጽኦ. This is a rough sketch of his book. ይህ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ የሱ ፡ መጽሐፍ ፡ አስተዋጽኦ ፡ ነው

**sketchy** ጥራዝ ፡ ነጠቅ
He has a rather sketchy knowledge of history. የታሪክ ፡ ዕውቀቱ ፡ ጥራዝ ፡ ነጠቅ ፡ ነው
*In his hurry, he had only a sketchy meal. ተጣድፎ ፡ ስለነበር ፡ የበላው ፡ ለቅመሻ ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ ነበር

**skid** (skidded), vi. (= vt.) አንሸራተተ
+The car skidded on the wet pavement. እርጥቡ ፡ መንገድ ፡ መኪናዋን ፡ አንሸራተታት

**skid** (n.)
*Skids are common in rainy weather. በዝናቡ ፡ ወራት ፡ መኪናዎች ፡ ይንሸራተታሉ

**skill**
1. ጥበብ. Diplomacy requires many skills. ዲፕሎማሲ ፡ ብዙ ፡ ጥበብን ፡ ይጠይቃል
Making pottery requires skill. የሸክላ ፡ ሥራ ፡ ጥበብ ፡ ይጠይቃል
2. ችሎታ. Learning a language is a question of learning new skills. አዲስ ፡ ቋንቋ ፡ መማር ፡ አዲስ ፡ ችሎታ ፡ መማር ፡ ነው
3. ጥሩ ፡ ችሎታ. The actor interpreted the part of the soldier with skill. ተዋናዩ ፡ ወታደሩን ፡ መስሎ ፡ በጥሩ ፡ ችሎታ ፡ ሠራ
4. ሙያ. Typing is a skill that requires practice. በመኪና ፡ መጻፍ ፡ ልምምድ ፡ የሚጠይቅ ፡ ሙያ ፡ ነው
5. የእጅ ፡ ሥራ. Society reclaims criminals by teaching them skills. ኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ ወንጀለኞችን ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ አስተምሮ ፡ ሰላማዊ ፡ ዜጎች ፡ ያደርጋቸዋል
6. ዘዴ. The trained teacher managed the children with skill. የሠለጠነው ፡ መምህር ፡ ተማሪዎቹን ፡ በዘዴ ፡ ያዘ

**skilled**
1. በእጅ ፡ ሥራ ፡ የሠለጠነ. He is a skilled laborer. በእጅ ፡ ሥራ ፡ የሠለጠነ ፡ ሠራተኛ ፡ ነው
2. ልዩ ፡ ሙያ ፡ የሚጠይቅ. Repairing watches is skilled work. ሰዓት ፡ ማደስ ፡ ልዩ ፡ ሙያ ፡ የሚጠይቅ ፡ ሥራ ፡ ነው
3. ዐዋቂ. A skilled surgeon can perform any operation. ዐዋቂ ፡ ሐኪም ፡ ማንኛውንም ፡ ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ሊያከናውን ፡ ይችላል

**skillet** መጥበሻ
He fried eggs in a skillet. እንቁላል ፡ በመጥበሻ ፡ ጠበሰ

**skillful**
1. ባለሙያ. It is difficult to find a skillful cook in this village. በዚህ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ባለሙያ ፡ ወጥቤት ፡ ማግኘት ፡ ከባድ ፡ ነው
2. ጥበብ ፡ ያለበት. That is a skillful piece of bricklaying. ይህ ፡ ጥበብ ፡ ያለበት ፡ ግንብ ፡ አሠራር ፡ ነው

**skillful performance** ቀልጣፋነት
Everyone admired her skillful performance on the piano. ፒያኖ ፡ ስትጫወት ፡ ባሳየችው ፡ ቀልጣፋነት ፡ ሁሉም ፡ አደነቃት

**be skillful** በደንብ ፡ ቻለ
He is very skillful in riding a bike. ቢስክሌት ፡ መንዳት ፡ በደንብ ፡ ይችላል

**skillfully**
1. በዘዴ. You got yourself out of that situation skillfully. ከዚያ ፡ ውጥንቅጥ ፡ ራስህን ፡ በ ዘዴ ፡ አወጣህ
2. በቅልጥፍና. He skillfully sectioned the orange. ብርቱካኑን ፡ በቅልጥፍና ፡ ከፋፈለው

**skim** (skimmed), vt.
1. ገፈፈ. He skimmed the cream from the milk. ከወተቱ ፡ ላይ ፡ ስልባቦቱን ፡ ገፈፈ
2. ገረፍ ፡ ገረፍ ፡ አደረገ. It took me an hour to skim the book. መጽሐፉን ፡ ገረፍ ፡ ገረፍ ፡ ለማ ድረግ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ወሰደብኝ
3. ጨረፍ ፡ አድርጎ ፡ አለፈ. The pebble I threw skimmed the water. የወረወርኩት ፡ ጠጠር ፡ ው ኃውን ፡ ጨረፍ ፡ አድርጎት ፡ አለፈ

**skim** (vi.) ዝቅ ፡ ብሎ ፡ በረረ
The bird skimmed over the water. ወፏ ፡ በውኃ ው ፡ ላይ ፡ ዝቅ ፡ ብላ ፡ በረረች

**skim through** ተመለከከተ
He skimmed through the newspaper. ጋዜጣውን ፡ ተመለከከተ

**skimp** (vt.) አሳነሰ
Don't skimp the butter in baking a cake! ኬኩን ፡ ስታዘጋጅ ፡ ቅቤ ፡ አታሳንስ

**skimp** (vi.) አንጀቱን ፡ አስሮ ፡ ገንዘብ ፡ አጠራቀመ ፤ ጥርሱን ፡ ነክሶ ፡ ገንዘብ ፡ አጠራቀመ
She had to skimp to send her son to college. ልጇን ፡ ኮሌጅ ፡ ለማስተማር ፡ አንጀቷን ፡ አስራ ፡ (ጥርሷን ፡ ነክሳ) ፡ ገንዘብ ፡ ማጠራቀም ፡ ነበረባት

**skimpy** ለስሙ ፡ ያህል
I had a skimpy meal of parched corn and water. ለስሙ ፡ ያህል ፡ በቆሎና ፡ ውኃ ፡ ተመገብሁ

**skin** (skinned), v.
1. ቆዳውን ፡ ገፈፈ. The farmer killed a cow and skinned it. ገበሬው ፡ አንዲት ፡ ላም ፡ አርዶ ፡ ቆዳዋን ፡ ገፈፈ
They punished robbers in ancient times by skinning them alive. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ሽፍቶችን ፡ በሕይወት ፡ እንዳሉ ፡ ቆዳቸውን ፡ በመግፈፍ ፡ ይቀጧቸው ፡ ነበር
2. ገሸለጠ. I skinned the knuckles of my hand. የጣቴን ፡ አንጓ ፡ ገሸለጥኩት
3. (= pass.) ተላጠ. +He fell and skinned his kneecap. ወድቆ ፡ ጉልበቱ ፡ ተላጠ

**skin** (n.)
1. ቆዳ. She has a sensitive skin. ቆዳዋ ፡ ቁጡ ፡ ነው
Cows have thick skins. የላም ፡ ቆዳ ፡ ጠንካራ ፡ ነው
2. ቅርፊት. These apples have a very thick skin. እነዚህ ፡ ቱፋዎች ፡ ወፍራም ፡ ቅርፊት ፡ አላቸው
The snake cast its skin. እባቡ ፡ ቅርፊቱን ፡ ጣለ

**by the skin of one's teeth** ላያመልጥ
We made the last train by the skin of our teeth. የመጨረሻውን ፡ ባቡሩን ፡ ላያመልጥ ፡ ደረስንበት

**get under one's skin** አናደደ
His laugh really gets under my skin. ሣቁ ፡ ያና ድደኛል

**have a thick skin** ግዴለሽ ፡ ነው
He has a thick skin; nothing offends him. ግዴለሽ ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ቅር ፡ አያሰኘውም

**save one's own skin** ራሱን ፡ ብቻ ፡ አዳነ
He saved his own skin, and let everyone else perish. ራሱን ፡ ብቻ ፡ አድኖ ፡ ሌሎቹን ፡ እንዲያ ልቁ ፡ ተዋቸው
[See also 'irritation, soak, tooth']

**skin-deep** ላይ ፡ ላዩን
Her generosity is only skin-deep. ደግነቷ ፡ ላ ይ ፡ ላዩን ፡ ነው
*Beauty is only skin-deep. ቁንጅና ፡ ብቻ ፡ አ ይበቃም

**skinny** ከሲታ ፤ ከሳሳ
The skinny girl does not eat much. ከሲታዋ ፡ (ከሳሳዋ) ፡ ልጅ ፡ ብዙም ፡ አትበላ

**skip** (skipped), vt.
1. ዘለለ. I skipped second grade. ሁለተኛን ፡ ክ ፍል ፡ ዘለልኩ
The children skip rope. ልጆቹ ፡ ገመድ ፡ ይዘላሉ
Skip the hard words! ከባድ ፡ የሆኑትን ፡ ቃላት ፡ ዝለላቸው
2. አፈናጠረ. He likes to skip flat stones across the pond. በኩሬው ፡ ላይ ፡ ጠፍጣፋ ፡ ድንጋዮ ች ፡ ማፈናጠር ፡ ይወዳል
3. ከ - - - ኰበለለ. He skipped town without paying the rent. ኪራዩን ፡ ሳይከፍል ፡ ከከተ ማ ፡ ኰበለለ

**skip** (vi.)
1. ዘለለ. He skipped over the difficult portions of the test. በፈተናው ፡ ውስጥ ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆ ነውን ፡ ክፍል ፡ ዘለለው

Answer the questions in order without skipping! ጥያቄዎቹን ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ሳትዘል ፡ መልስ
2. ቦረቀ. Lambs skip in the field. ጥቦቶቹ ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ ይቦርቃሉ

**skip out** ጠፍቶ ፡ ሄደ
He skipped out leaving his rent unpaid. ያለበትን ፡ ኪራይ ፡ ሳይከፍል ፡ ጠፍቶ ፡ ሄደ
[See also 'town']

**skipper** የመርከብ ፡ አዛዥ
The skipper of the ship is a Norwegian. የመርከቡ ፡ አዛዥ ፡ ኖርዌጂያዊ ፡ ነው

**skirmish** ቀላል ፡ ግጭት
The skirmish was not reported in the papers. ስለ ፡ ቀላሉ ፡ ግጭት ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ አል ተጻፈም

**skirt** (v.)
1. ዳር ፡ ዳሩን ፡ ሄደ. The travelers skirted the forest instead of going through it. ተጓዦቹ ፡ በጫካው ፡ ውስጥ ፡ አቋርጠው ፡ በመሄድ ፡ ፈንታ ፡ ዳር ፡ ዳሩን ፡ ሄዱ
2. በ - - - ዳር ፡ ነው. That community skirts the town. ያ ፡ ቀበሌ ፡ በከተማው ፡ ዳር ፡ ነው
3. ጠቀስ ፡ አድርጎት ፡ አለፈ. The mayor skirted the issue. ከንቲባው ፡ ነገሩን ፡ ጠቀስ ፡ አድርጎት ፡ አለፈ

**skirt** (n.) ጉርድ ፡ ቀሚስ
Her skirt was torn. ጉርድ ፡ ቀሚሷ ፡ ተቀዶ ፡ ነበር

**skirts, at the ~ of** በ - - - ዳር
The cattle fed at the skirts of the field. የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ በሜዳው ፡ ዳር ፡ ይግጡ ፡ ነበር

**skull** የራስ ፡ ቅል
His skull is broken. የራሱ ፡ ቅል ፡ ተሰብሯል

**skullcap** ቆብ
He wears a skullcap. ቆብ ፡ ያደርጋል

**skunk** ምጥማጥ
Skunks make a terrible smell when frightened. ምጥማጦች ፡ በደነገጡ ፡ ጊዜ ፡ አስጸያፊ ፡ ሽታ ፡ ይለቃሉ

**sky** (skies) ሰማይ
How does the sky look today? ዛሬ ፡ ሰማዩ ፡ ምን ፡ ይመስላል ?

**out of the clear sky** ሳይታሰብ
The news came out of the clear sky. ወሬው ፡ ሳይታሰብ ፡ ወረደ

**to the skies** ከልክ ፡ በላይ
He praised her to the skies. ከልክ ፡ በላይ ፡ አሞገሳት

**sky-high** ከፍ ፡ አድርጎ ፤ ከልክ ፡ በላይ
He praised her sky-high. ከፍ ፡ አድርጎ ፡ (ከልክ ፡ በላይ) ፡ አሞገሳት

**be sky-high** ሰማይ ፡ ነካ
Prices are sky-high these days. ሰሞኑን ፡ የእቃ ፡ ዋጋ ፡ ሰማይ ፡ ነክቷል

**skylight**
*The room was illuminated by a skylight. ክፍሉ ፡ ጣሪያው ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ መስኮት ፡ ብርሃን ፡ ያገኛል

**skyline** የሕንጻዎች ፡ ቅርጽ
You can see the skyline of Addis Ababa best at night. ያዲስ ፡ አበባን ፡ ሕንጻዎች ፡ ቅርጽ ፡ ሲመሽ ፡ በደንብ ፡ ማየት ፡ ይቻላል

**skyscraper** (የ)ሰማይ ፡ ጠቀስ ፡ ሕንጻ
The skyscraper is fourteen stories high. (የ)ሰማይ ፡ ጠቀሱ ፡ ሕንጻ ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ፎቆች ፡ አሉት

**slab** ቁራጭ
The hungry boy ate a slab of cheese as big as his hand. የራበው ፡ ልጅ ፡ እጁን ፡ የሚያህል ፡ ቁራጭ ፡ ፎርማጅ ፡ በላ

**slab of stone** ጠፍጣፋ ፡ ድንጋይ
A slab of stone covers the grave. መቃብሩ ፡ ጠፍጣፋ ፡ ድንጋይ ፡ ተከድኗል

**slack** (v.), **~ off** ችላ ፡ አለ
Don't slack off in your studies! ጥናትህን ፡ ችላ ፡ አትበለው

**slack** (adj.) ቸልተኛ
She is a slack housekeeper. ቸልተኛ ፡ ቤት ፡ ጠባቂ ፡ ናት

**be slack**
1. ላላ. The rope is slack. ገመዱ ፡ ላልቷል
2. ቀዘቀዘ ፡ አለ. Business is slack. ገበያው ፡ ቀዘቀዝ ፡ ብሏል

**become slack**
1. ተጉተተ. His work has become slack. ሥራው ፡ ተጉትቷል
2. ግድ ፡ የለሽ ፡ ሆነ. He has become very slack in his work. በሥራው ፡ በጣም ፡ ግድ ፡ የለሽ ፡ ሆኗል

**at a slack pace** በዝግታ
The horse was moving at a slack pace. ፈረሱ ፡ በዝግታ ፡ ይሄድ ፡ ነበር

**slacken** (vt.)
1. አላላ. Slacken the rope! ገመዱን ፡ አላላው
2. ችላ ፡ አለ. Don't slacken your efforts till the work is done. ሥራው ፡ እስኪከናወን ፡ ድረስ ፡ ጥረትህን ፡ ችላ ፡ አትበል

**slacken** (vi.)
1. ላላ. The wire slackened. ሽቦው ፡ ላላ
2. ተጐተተ. Work slackens on a hot day. በሞቃት ፡ ቀን ፡ ሥራው ፡ ይጐተታል
3. አነሰ. His business always slackens in the winter. ንግዱ ፡ ሁልጊዜ ፡ በክረምት ፡ ያነሰ ፡ ይሆናል
4. ጋብ ፡ አለ. The rain slackened. ዝናቡ ፡ ጋብ ፡ አለ

**slacken off** ቀነሰ
The demand for tobacco slackened off. የትምባሆ ፡ ተፈላጊነት ፡ ቀንሷል

**slacks** ሱሪ
She wears slacks. ሱሪ ፡ ትለብሳለች

**slain,** see **slay**

**slake** አረካ
He slaked his thirst with a bottle of cold water. ጥሙን ፡ ባንድ ፡ ጠርሙስ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ውኃ ፡ አረካ

**slam** (slammed), vt.
1. ደበደበ. He slammed his fist on the table. ጠረጴዛውን ፡ በቡጢ ፡ ደበደበ
2. በኀይል ፡ ዘጋ. He has been told once and again not to slam the door. በሩን ፡ በኀይል ፡ እንዳይዘጋ ፡ ተደጋግሞ ፡ ተነግሮት ፡ ነበር
3. ወረወረ. He slammed the book down on the desk. መጽሐፉን ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ወረወረው

**slam** (vi.) ተወርውሮ ፡ ተዘጋ
The door slammed. በሩ ፡ ተወርውሮ ፡ ተዘጋ

**slam** (n.)
*I heard the slam of a door. መዝጊያው ፡ ጥርቅም ፡ ብሎ ፡ ሲዘጋ ፡ ሰማሁ

**slander** (v.) አማ ፤ ስሙን ፡ አጠፋ
He slanders his friends. ባልንጀሮቹን ፡ ያማል
It has come to our knowledge that you are slandering us. ስማችንን ፡ እንደምታጠፋ ፡ ዐውቀናል

**slander** (n.) ሐሜት
Don't believe that slander! ያንን ፡ ሐሜት ፡ አትመን

**slanderous** ስም ፡ የሚያጠፋ
He uses slanderous talk. ስም ፡ የሚያጠፋ ፡ ወሬ ፡ ያወራል

**slang** የምስጢር ፡ ቋንቋ
Students have a special slang. ተማሪዎቹ ፡ ልዩ ፡ የምስጢር ፡ ቋንቋ ፡ አላቸው

**slant** (vt.) አዳላ ፤ አዛባ
This magazine slants news. ይህ ፡ መጽሔት ፡ ወሬ ፡ ሲያቀርብ ፡ ያዳላል ፡ (ያዛባል)

**slant** (vi.) አዘነበለ
His handwriting slants from right to left. ጽሕፈቱ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ያዘነበለ ፡ ነው

**slant** (n.)
1. አወራረድ. The slant of the roof is not steep enough. የጣሪያው ፡ አወራረድ ፡ በደንብ ፡ አልሆነም
2. አስተያየት. I need a new slant on this problem. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ አስተያየት ፡ እፈልጋለሁ

**slanted** (adj.) ዘንበል ፡ ያለ
The roof is slightly slanted. ጣራው ፡ ትንሽ ፡ ዘንበል ፡ ያለ ፡ ነው

**slap** (slapped), v.
1. በጥፊ ፡ መታ. I'll slap your hand if you touch it. ይህን ፡ እቃ ፡ የነካኸው ፡ እንደሆነ ፡ በጥፊ ፡ እመታሃለሁ
2. ጣል ፡ አደረገ(በት). She slapped some butter into the pan. በመጥበሻው ፡ ላይ ፡ ቅቤ ፡ ጣል ፡ አደረገችበት
3. ወረወረ. He slapped the book down on the table. መጽሐፉን ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ወረወረው

**slap down** ገራ
The monitor needs to slap down new students. የክፍል ፡ አለቃ ፡ አዲስ ፡ ገብ ፡ ተማሪዎችን ፡ መግራት ፡ ይገባዋል

**slap** (n.) ጥፊ
Everyone heard the slap, it was so loud. ጥፊው ፡ ኀይለኛ ፡ ስለነበር ፡ ሲጮኽ ፡ ለሁሉም ፡ ተሰማ

**give a slap** በጥፊ ፡ አጮለ
His brother gave him a slap when he insulted him. ቢሰድበው ፡ ወንድሙ ፡ በጥፊ ፡ አጮለው

**slash**
1. ገሸለጠ. He slashed the bark off the tree with his knife. የዛፉን ፡ ቅርፊት ፡ በጩቤው ፡ ገሸለጠው
2. ቈረጠ. The knife slipped, and he slashed his finger. ቢላዋው ፡ አምልጮት ፡ ጣቱን ፡ ቈረጠው
3. ጐመደ(በት). The council slashed the mayor's budget. ምክር ፡ ቤቱ ፡ ከንቲባው ፡ ያቀረበውን ፡ ባጀት ፡ ጐመደበት

**be slashed**
1. ቀነሰ. Prices have been slashed. የገበያው ፡ ዋ
ጋ ፡ ቀንሷል
2. (= slash) ተለተለ. +The thief's back was
slashed with a whip. ጅራፉ ፡ የሌባውን ፡ ጀርባ ፡
ተልትሎታል

**slate** (v.) ወሰነ
The government slated the election for No-
vember. መንግሥቱ ፡ ምርጫው ፡ በኅዳር ፡ እን
ዲሆን ፡ ወሰነ

**be slated** ከተመዘገቡት ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ነበር
He was slated to speak at the assembly.
በስብሰባው ፡ ላይ ፡ ለመናገር ፡ ከተመዘገቡት ፡
ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ነበር

**slate** (n.) ጥቁር ፡ ድንጋይ
Blackboards used to be made of slate. ጥቁር ፡
ድንጋይ ፡ ለጥቁር ፡ ሰሌዳ ፡ መሥሪያ ፡ ያገለግል ፡ ነበር

**with a clean slate** ሀ ፡ ብሎ
Let's start with a clean slate! ሀ ፡ ብለን ፡ እን
ጀምር

**slaughter** (v.) አረደ
We always slaughter a sheep for Easter. ለፋሲካ ፡
ሁልጊዜ ፡ በግ ፡ እናርዳለን

**slaughter** (n.) እልቂት
The Italians carried out a gruesome slaughter
on February 12. ኢጣልያኖች ፡ የካቲት ፡ ዐሥራ ፡
ሁለት ፡ አሰቃቂ ፡ እልቂት ፡ ፈጸሙ
*A slaughter of livestock takes place before
Easter. ለፋሲካ ፡ ከብት ፡ ይታረዳል

**slaughterhouse** ቄራ
He took his cattle to the slaughterhouse.
ከብቶቹን ፡ ወደ ፡ ቄራው ፡ ወሰደ

**slave** (v.)
*I've slaved enough today. ለዛሬ ፡ እስኪበቃኝ ፡
ሠርቻለሁ

**slave** (n.) ባሪያ
He treats them like slaves. እንደ ፡ ባሪያ ፡ ያያቸዋል
A drunkard is a slave of drink. ሰካራም ፡ ሰው ፡
የመጠጥ ፡ ባሪያ ፡ ነው

**slave dealer** ባሪያ ፡ ፈንጋይ
The slave dealers made large profits. ባሪያ ፡ ፈ
ንጋዮች ፡ ብዙ ፡ አተረፉ

**slave driver** ጨካኝ ፡ አሠሪ
He is such a slave driver that his employees hate
him. ጨካኝ ፡ አሠሪ ፡ ስለሆነ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ሁሉ ፡
ይጠሉታል

**slaver** ባሪያ ፡ ፈንጋይ
Slavers used to castrate boys. ባሪያ ፡ ፈንጋዮች ፡
ወንዶች ፡ ባሮችን ፡ ይሰልቧቸው ፡ ነበር

**slavery** ባርነት
Slavery has gone out of existence. ባርነት ፡ ቀ
ርቷል
He was sold into slavery. በባርነት ፡ ተሸጠ

**deliver from slavery** አርነት ፡ አወጣ
Lincoln delivered the slaves from slavery.
ሊንኮልን ፡ ባሮችን ፡ አርነት ፡ አወጣ

**slave trade** የባሪያ ፡ ንግድ
The slave trade has been suppressed. የባሪያ ፡ ን
ግድ ፡ ቀርቷል

**slave trader** ባሪያ ፡ ፈንጋይ
The slave traders used to make a lot of money.
ባሪያ ፡ ፈንጋዮች ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ያገኙ ፡ ነበር

**slavish**
1. አድካሚ. Weeding the field is slavish work.
ማረም ፡ አድካሚ ፡ ሥራ ፡ ነው
2. (= adv.) ዓይኑን ፡ ጨፍኖ. His slavish imitation
of others was noticed by everybody. ዓይኑን ፡ ጨ
ፍኖ ፡ ከሌሎች ፡ መቅዳቱ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡
ታወቀ

**slay** (slew, slain) ገደለ
The thief slew the man. ሌባ ፡ ሰውዬውን ፡ ገደ
ለው
A hunter slays wild animals. አዳኝ ፡ የዱር ፡ አ
ውሬዎችን ፡ ይገድላል

**sledge** [በበረዶ ፡ ላይ ፡ የሚንሸራተት ፡ ጋሪ]

**sledgehammer** መራጃ
He broke the rock with a sledgehammer.
ቋጥኙን ፡ በመራጃ ፡ ሰበረ

**sleek** ለስላሳ
The leopard has a sleek coat. ነብሩ ፡ ለስላሳ ፡ ጸ
ጉር ፡ አለው

**sleep** (slept), vt. አስተኛ.
This hotel sleeps three hundred guests. ይህ ፡ ሆ
ቴል ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰው ፡ ያስተኛል

**sleep** (vi.)
1. ተኛ. Babies should sleep a lot. ሕፃናት ፡ ብዙ ፡
መተኛት ፡ አለባቸው
Did you sleep well? ደኅና ፡ ተኛህ?
2. እንቅልፍ ፡ ወሰደው. Did you sleep well last
night? ትላንትና ፡ ማታ ፡ ጥሩ ፡ እንቅልፍ ፡ ወሰደህ?
*The seeds sleep in the ground all winter.
ፍሬዎቹ ፡ በክረምት ፡ ከመሬት ፡ አይወጡም

**sleep in** እዳሩ ፡ ከቤት ፡ ነው
Our maid sleeps in. ገረዳችን ፡ አዳሯ ፡ ከቤት ፡ ነው
**sleep off** በእንቅልፍ ፡ አስለፈ(ለት)
He drank a lot, and then went to bed to sleep it off. ብዙ ፡ ጠጥቶ ፡ በእንቅልፍ ፡ እንዲያልፍለት ፡ ተኛ
**sleep out** አዳሩ ፡ ከውጭ ፡ ነው
The servant eats with us, but sleeps out. ያሽከራችን ፡ ቀለብ ፡ ከቤት ፡ አዳሩ ፡ ግን ፡ ከውጭ ፡ ነው
**go to sleep** ተኛ
He goes to sleep at nine. እሱ ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ ይተኛል
**not let sleep** እንቅልፍ ፡ ነሣ
His agitation wouldn't let him sleep. የመንፈሱ ፡ መረበሽ ፡ እንቅልፍ ፡ ነሣው
**(be) put to sleep** የሚያስተኛ ፡ መርፌ ፡ ወጋት
He was put to sleep for the operation. ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ከማድረጋቸው ፡ በፊት ፡ የሚያስተኛ ፡ መርፌ ፡ ወጉት
[See also 'pillow']

**sleep** (n.) እንቅልፍ
I didn't get enough sleep last night. ትላንትና ፡ ማታ ፡ በቂ ፡ እንቅልፍ ፡ አላገኘሁም
**deep sleep** እልም ፡ ያለ ፡ እንቅልፍ
It was like awaking from a deep sleep. እልም ፡ ካለ ፡ እንቅልፍ ፡ እንደ ፡ መንቃት ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ነበር
[See also 'heavy']

**sleeping** የሚያስተኛ
The sorcerer put a sleeping potion in the man's drink. ጠንቋዩ ፡ በሰውዬው ፡ መጠጥ ፡ ውስጥ ፡ የሚያስተኛ ፡ መድኃኒት ፡ ጨመረበት

**sleeping sickness** የእንቅልፍ ፡ በሽታ
Is Ethiopia afflicted by sleeping sickness? ኢትዮጵያ ፡ በእንቅልፍ ፡ በሽታ ፡ ተመርዛለች ?

**sleepless**
*I spent a sleepless night. እንቅልፍ ፡ አጥቼ ፡ አደርኩ

**sleepy**
1. እንቅልፋም. A sleepy child will not learn much in school. እንቅልፋም ፡ ልጅ ፡ በትጋት ፡ አይማርም
2. ጭር ፡ ያለ. This is a sleepy, little mountain town. ይህ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ጭር ፡ ያለ ፡ ከተማ ፡ ነው
*He had a sleepy look in his eyes. ሲያዩት ፡ እንቅልፍ ፡ የያዘው ፡ ይመስላል
**be sleepy** እንቅልፍ ፡ እንቅልፍ ፡ አለ(ው)
I'm still sleepy. አሁንም ፡ እንቅልፍ ፡ እንቅልፍ ፡ ይለኛል

**sleet** እርጥብ ፡ በረዶ
The streets were covered with sleet. መንገዶቹ ፡ በእርጥብ ፡ በረዶ ፡ ተሸፍነው ፡ ነበር

**sleeve** እጅጌ
The sleeves are too short for me. እጅጌዎቹ ፡ በጣም ፡ አጥረውብኛል

**sleigh** [በበረዶ ፡ ላይ ፡ የሚንሸራተት ፡ ጋሪ]

**slender**
1. ሸንቃጣ. She used to be very fat but she has gotten slender. በጣም ፡ ወፍራም ፡ ነበረች ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ሸንቃጣ ፡ ሆናለች
2. ቀጭን. All girls want to be slender. ልጃገረዶች ፡ ሁሉ ፡ ቀጭን ፡ መሆን ፡ ይፈልጋሉ
The legs of the chair are slender. የወምበሩ ፡ እግር ፡ ቀጭን ፡ ነው
3. አነስተኛ. He has a slender income and cannot afford to buy an expensive coat. አነስተኛ ፡ ገቢ ፡ ስላለው ፡ ውድ ፡ ካፖርት ፡ ሊገዛ ፡ አይችልም
*There is slender hope that the burned child will live. እሳት ፡ ያቃጠለው ፡ ልጅ ፡ መትረፉን ፡ እንጃ
**long slender** አመልማሎ
Her long, slender fingers are very beautiful. አመልማሎ ፡ ጣቷ ፡ በጣም ፡ ያምራል

**slept,** see **sleep**

**slew,** see **slay**

**slice** (v.)
1. መተረ. The cook sliced the meat before it was served. ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ የወጥ ፡ ቤቷ ፡ ሥጋውን ፡ መተረች
2. ቁረጠ. They sliced the bread too thin. ዳቦውን ፡ በጣም ፡ አሳንሰው ፡ ቆረጡት
The cook sliced the onions and put them in the stew. የወጥ ፡ ቤቷ ፡ ሽንኩርቱን ፡ ቆረጠች ፡ ውና ፡ ወጡ ፡ ውስጥ ፡ ጨመረችው
**slice off**
1. ጐመደ. He sliced the man's arm off with his sword. የሰውዬውን ፡ ክንድ ፡ በጐራዴ ፡ ጐመደው
2. ቈረጠ. The butcher sliced off a piece of steak. ሥጋ ፡ ሻጩ ፡ ሙዳ ፡ ሥጋ ፡ ቈረጠ

**slice** (n.) ቁራጭ
The slice of meat fell on the ground. ቁራጭ ፡ ሥጋ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ወደቀ

*Will you have another slice of cake? ሌላ ፡ ኬክ ፡ ልቍረስልህ ?
*The slice of cake that you gave me is too small. የሰጠኸኝ ፡ ኬክ ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው

**slick** (v.), ~ **down** አስተኛ
He slicked down his hair with oil. ጸጕሩን ፡ በ ቅባት ፡ አስተኛው

**slick** (adj.)
1. ለስላሳና ፡ የሚያንጸባርቅ. The booklet commemorating the coronation is printed on slick paper. የዘውድ ፡ በዓሉን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ የታተመው ፡ መጽሔት ፡ ለስላሳና ፡ የሚያንጸባርቅ ፡ ወረቀት ፡ አለው
2. ጮሌ. He is a slick salesman and does a lot of business. ጮሌ ፡ አሻሻጭ ፡ ስለሆነ ፡ ጥሩ ፡ ገበያ ፡ አለው

**be slick** አዳለጠ
The roads are slick with wet mud. መንገዱ ፡ ጨቅይቶ ፡ ስለነበር ፡ ያዳልጣል

**slid**, see **slide**

**slide** (slid), vt.
1. አሾለከ. Slide the note under the door! ማስታወሻውን ፡ በመዝጊያው ፡ ሥር ፡ አሾልከው
2. ሹልክ ፡ አድርጎ ፡ አደረገ(ለት). He slid some money into my hand. ጥቂት ፡ ገንዘብ ፡ ሹልክ ፡ አድርጎ ፡ እጄ ፡ ውስጥ ፡ አደረገልኝ
3. ያዘ. He slid a pistol into his pocket. ኪሱ ፡ ውስጥ ፡ ሽጉጥ ፡ ያዘ

**slide** (vi.)
1. ተንሸራተተ Children slide on the ice. ልጆች ፡ በበረዶ ፡ ላይ ፡ ይንሸራተታሉ
2. ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ተደበቀ. The thief quickly slid behind the curtains. ሌባው ፡ በፍጥነት ፡ መጋረጃው ፡ ውስጥ ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ተደበቀ
3. አምልጦ ፡ ወደቀ. The wet glass slid from his hands. እርጥቡ ፡ ብርጭቆ ፡ ከእጁ ፡ አምልጦ ፡ ወደቀ

**slide by** ሳይታወቅ ፡ አለፈ
The days slid by during vacation. በዕረፍቱ ፡ ጊዜ ፡ ቀናቱ ፡ ሳይታወቅ ፡ አለፉ

**slide down**
1. ተንጠላጥሎ ፡ ወረደ. He slid down the rope to safety. በገመዱ ፡ ተንጠላጥሎ ፡ ወርዶ ፡ አመለጠ
2. ተንሸራቶ ፡ ቁልቁል ፡ ወረደ. The children like to slide down the grassy slope. ልጆቹ ፡ በሣሩ ፡ ላይ ፡ ተንሸራተው ፡ ቁልቁል ፡ መውረድ ፡ ይወዳሉ

**slide in and out easily** እንደልብ ፡ ተከፍቶ ፡ ተዘጋ ፤ እንደልብ ፡ ሊወጣና ፡ ሊገባ ፡ ቻለ
The drawer of my desk slides in and out easily. የጠረጴዛዬ ፡ መሳቢያ ፡ እንደልብ ፡ ተከፍቶ ፡ ይዘጋል ፡ (እንደልብ ፡ ሊወጣና ፡ ሊገባ ፡ ይችላል)

**slide into**
1. ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ገባ. The thief slid into the room. ሌባው ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ገባ
2. ቀስ ፡ በቀስ ፡ ያዘ. He had slid into bad habits. ቀስ ፡ በቀስ ፡ መጥፎ ፡ ልማድ ፡ ያዘ

**slide off** ተንሸራቶ ፡ ወደቀ
The book slid off my knee. መጽሐፉ ፡ ከጕልበቴ ፡ ላይ ፡ ተንሸራቶ ፡ ወደቀ

**let slide**
*Let things slide for now! እስኪ ፡ ለጊዜው ፡ ነገሩ ፡ እንደነበረ ፡ ይሁን

**slide** (n.)
1. ሸርተቴ. The children were playing on the slide. ልጆቹ ፡ ሸርተቴው ፡ ላይ ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር
2. ናዳ. The roads were obstructed by slides of rock. መንገዶቹ ፡ በድንጋይ ፡ ናዳ ፡ ተዘግተው ፡ ነበር
3. የማይንቀሳቀስ ፡ ፊልም. He gave a lecture with slides. ንግግር ፡ ያደረገው ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ፊልሞች ፡ እያሳየ ፡ ነው

**slide rule** ተንሸራታች ፡ ማሥመሪያ
Engineers use slide rules. መሀንዲሶች ፡ በተንሸራታች ፡ ማሥመሪያ ፡ ይጠቀማሉ

**slight** (v.)
1. ቅር ፡ አሰኘ. They slighted John by not inviting him. ጆንን ፡ ሳይጋብዙት ፡ በመቅረታቸው ፡ ቅር ፡ አሰኙት
2. ቁም ፡ ነገር ፡ አላለውም. This maid slights her work. ይህች ፡ ገረድ ፡ ሥራዋን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አትለውም

**slight** (n.) ችላ ፡ መባል
This slight rankled her. ችላ ፡ መባሉ ፡ ሆዷን ፡ በላት

**slight** (adj.)
1. ትንሽ. There's a slight difference. ትንሽ ፡ ልዩነት ፡ አለ
2. ቀጭን. She is a slight girl. ቀጭን ፡ ልጅ ፡ ናት
3. ቀላል. I have a slight headache. ቀላል ፡ የራስ ፡ ምታት ፡ አለብኝ
4. አነስተኛ. One slice of bread is a very slight lunch. ቁራሽ ፡ ዳቦ ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ምሳ ፡ ነው

**slighted** (adj.), **feel ~** የናቁት ፡ መሰለ(ው)
She felt slighted because no one spoke to her. ማንም ፡ ሰው ፡ ስላላነጋገራት ፡ የናቋት ፡ መሰላት

**slightest (thing)** ትንሽ ፡ ነገር
She gets mad at the slightest thing. ትንሽ ፡ ነገር ፡ ያናድዳታል

**not in the slightest** ምንም + negative verb
You didn't embarrass me in the slightest. ምንም ፡ ቅር ፡ አላሰኘሽኝም

**not the slightest**
I haven't the slightest doubt. ምንም ፡ አልጠራጠርም

**slightly**
1. ትንሽ. The patient is slightly better today. በሽተኛው ፡ ዛሬ ፡ ትንሽ ፡ ተሽሎታል
The roof is slightly slanted. ጣሪያው ፡ ትንሽ ፡ ዘንበል ፡ ያለ ፡ ነው
2. ትንሽ ፡ ትንሽ. I know him slightly. ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ አውቀዋለሁ

**slightly built** አጠር ፡ ቀጠን ፡ ያለ
My friend is a slightly built man. ጓደኛዬ ፡ አጠር ፡ ቀጠን ፡ ያለ ፡ ነው

**slim** (slimmed), v. ቀጭን ፡ አደረገ
Her new dress slims her waist. አዲሱ ፡ ልብሷ ፡ ወገቧን ፡ ቀጭን ፡ አድርጎታል

**slim down** ቀጠነ
She is too fat; she ought to slim down. በጣም ፡ ወፍራም ፡ ስለሆነች ፡ መቅጠን ፡ አለባት

**slim** (adj.)
1. ትንሽ. We have slim hopes of success. ነገሩ ፡ ይሳካልናል ፡ ብለን ፡ ትንሽ ፡ ተስፋ ፡ አለን
2. ጥቂት. We had a slim crowd at the football game. ኳስ ፡ ጨዋታውን ፡ ለማየት ፡ የመጡት ፡ ሰዎች ፡ ጥቂት ፡ ነበሩ
3. ቀጠን ፡ ያለ. She has a slim figure. ቀጠን ፡ ያለ ፡ ሰውነት ፡ አላት

**slime** ዝልግልግ ፡ ያለ ፡ ነገር
A slime has formed on the bottom of the pool. በኩሬው ፡ ውስጥ ፡ ዝልግልግ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ዘቅጧል

**slimy** ዝልግልግ ፤ ምዝልግልግ ፤ የሚያሟልጭ
I feel repulsion for slimy creatures. ዝልግልግ ፡ (ምዝልግልግ) ፡ እንስሳት ፡ ያስጸይፉኛል
Some people think snakes are slimy like fish. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ እባብ ፡ እንደ ፡ ዓሣ ፡ የሚያሟልጭ ፡ ይመስላቸዋል

**sling** (slung) በወንጭፍ ፡ ወረወረ
He was slinging stones at the birds. በወፎቹ ፡ ላይ ፡ በወንጭፍ ፡ ድንጋይ ፡ ይወረውር ፡ ነበር

**sling over the shoulder** አነገተ
The soldier slung the gun over his shoulder. ወታደሩ ፡ ጠመንጃውን ፡ አንግቷል

**sling** (n.) ወንጭፍ
He threw a stone with a sling. ድንጋይ ፡ በወንጭፍ ፡ ወረወረ
*He wore his arm in a sling. ጨርቅ ፡ ባንገቱ ፡ አሳልፎ ፡ የተሰበረውን ፡ እጁን ፡ ደግፎታል

**slink** (slunk), **~ away** ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ወጣ
After stealing the meat, the dog slunk away. ውሻው ፡ ሥጋ ፡ ይዞ ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ወጣ

**slip** (slipped), vt.
1. ሻጥ ፡ አደረገ. She slipped a note into his pocket. ኪሱ ፡ ውስጥ ፡ ወረቀት ፡ ሻጥ ፡ አደረገችለት
2. ወለቅ ፡ አደረገ. She slipped the ring from her finger. ቀለበቷን ፡ ከጣቷ ፡ ወለቅ ፡ አደረገችው
3. ፈታ. The dog has slipped his collar. ውሻው ፡ ማሰሪያውን ፡ ፈታ
4. ከተተ. He slipped the key into the lock. መክፈቻውን ፡ እቁልፉ ፡ ውስጥ ፡ ከተተ
5. አሾለከ. Slip the letter under the door! ደብዳቤውን ፡ በመዝጊያ ፡ ሥር ፡ አሾልከው

**slip** (vi.)
1. አሟለጨ. The knife slipped and cut him. ቢላዋው ፡ አሟልጮት ፡ ቈረጠው
2. ሾልኮ ፡ አመለጠ. The fish slipped through the hole in the net. ዓሣው ፡ በመረቡ ፡ ቀዳዳ ፡ ሾልኮ ፡ አመለጠ
3. አዳለጠ(ው). +He slipped on the ice and fell down. በረዶው ፡ አዳልጦት ፡ ወደቀ
4. ተንሸራተተ. The car slipped on the icy road. በረዶ ፡ ባለበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ መኪናው ፡ ተንሸራተተ
5. ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ገባ. He slipped into the room while nobody was looking. ማንም ፡ ሳያየው ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ገባ
*His memory is slipping. ነገር ፡ መርሳት ፡ ጀምሯል

**slip away** ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ወጣ
The party is too noisy; let's slip away! ፓርቲው ፡ በጣም ፡ ጋጋታ ፡ በዝቶበታል ፤ ሹልክ ፡ ብለን ፡ እንውጣ

**slip by** ሳይታወቅ ፡ አለፈ
The years slip by. ጊዜው ፡ ሳይታወቅ ፡ ያልፋል
*Don't let this opportunity slip by! ይህ ፡ አጋጣሚ ፡ ዕድል ፡ እንዳያመልጥህ

**slip down**
1. ተንሸራቶ ፡ ወረደ. He slipped down the slope. ከዳገቱ ፡ ላይ ፡ ተንሸራቶ ፡ ወረደ

2. ወረደ. She kept pulling her skirt up, but it kept slipping down. ዐሥሬ ፡ ከፍ ፡ ብታደርገው
ም ፡ እንኳ ፡ ጉርድ ፡ ቀሚሷ ፡ እየወረደ ፡ አስቸገራት

**slip in and out** ሊወጣና ፡ ሊገባ ፡ ቻለ
The drawers slip in and out easily. መሳቢያው ፡ በቀላሉ ፡ ሊወጣና ፡ ሊገባ ፡ ይችላል

**slip into**
1. ለበሰ. Wait until I slip into a coat. ኮቴን ፡ እስ
ክለብስ ፡ ጠብቀኝ
2. ቀስ ፡ በቀስ ፡ አደረበት. +He slipped into the habit of smoking. ቀስ ፡ በቀስ ፡ ለማጨስ ፡ ልም
ድ ፡ አደረበት

**slip into (someone's) hand** ሽጉጥ ፡ አደረገ(ለት)
I slipped a bill into the waiter's hand. ላሳላፊው ፡ ጉርሻ ፡ ሽጉጥ ፡ አደረግሁለት

**slip (one's) mind** ተረሳ(ው)
The name of the new boy has slipped my mind. ያዲሱ ፡ ልጅ ፡ ስም ፡ ተረስቶኛል

**slip off** (vt.) አወለቀ
Slip off your shoes! ጫማህን ፡ አውልቅ

**slip off** (vi.) ተንሸራቶ ፡ ወረደ
The blanket slipped off the bed. ብርድ ፡ ልብሱ ፡ ካልጋው ፡ ላይ ፡ ተንሸራቶ ፡ ወረደ

**slip on**
1. ጠለቅ ፡ አደረገ. Slip on your coat and come with us! ኮትህን ፡ ጠለቅ ፡ አድርግና ፡ አብረኸን ፡ ና
2. ጣቱ ፡ ላይ ፡ አጠለቀ. She slipped on a ring. ቀለበት ፡ ጣቷ ፡ ላይ ፡ አጠለቀች

**slip out**
1. ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ወጣ. He slipped out of the room while the teacher was not looking. መምህሩ ፡ ሳያየው ፡ ከክፍሉ ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ወጣ
2. አፉን ፡ አዳለጠው. I really didn't want to tell him, but it just slipped out. በውነቱ ፡ ልነግረው ፡ አልፈለግሁም ፡ ነበር ፡ ግን ፡ አፌን ፡ አዳለጠኝ
3. አምልጦ ፡ ወደቀ. It slipped out of my hand. ከእጄ ፡ አምልጦ ፡ ወደቀ
4. ተንሸራተተ. The chair slipped out from under him. ወንበሩ ፡ ከሥሩ ፡ ተንሸራተተ

**slip past one** ሳያየው ፡ ሹልክ ፡ አለ
He is very watchful, so it's hard to slip past him. ንቁ ፡ ስለሆነ ፡ ሳያይህ ፡ ሹልክ ፡ ለማለት ፡ ያስቸ
ግራል

**slip up (on)** ተሳሳተ
I slipped up badly on the second question. ሁለተኛውን ፡ ጥያቄ ፡ ክፉኛ ፡ ተሳሳትኩ

**slip** (n.)
1. ቁራጭ. He wrote it on a slip of paper. በቁራጭ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ጽፎታል
2. ውስጥ ፡ ልብስ. She had nothing on but a slip when I came in. እኔ ፡ ስገባ ፡ ከውስጥ ፡ ል
ብስ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አልለበሰችም ፡ ነበር
3. ስሕተት. He makes slips in grammar. የሰዋስው ፡ ስሕተት ፡ ያደርጋል

**slip of the tongue** አፍ ፡ ሲያዳልጥ
A slip of the tongue may reveal the truth. አፍ ፡ ሲያዳልጥ ፡ እውነቱ ፡ ድንገት ፡ ይገለጥ ፡ ይ
ሆናል

**give the slip** አታልሎ ፡ አመለጠ
The thief gave the policeman the slip. ሌባው ፡ ፖ
ሊሱን ፡ አታልሎ ፡ አመለጠ

**slipcover** ልብስ
The sofa is covered with slipcovers. ሶፋው ፡ ል
ብስ ፡ አለው

**slipper** ነጠላ ፡ ጫማ
I wear slippers around the house. ቤት ፡ ለቤት ፡ ነጠላ ፡ ጫማ ፡ አደርጋለሁ

**slippery**
1. ሙልጭልጭ ፡ ያለ. Fish are very slippery. ዓሣ ፡ በጣም ፡ ሙልጭልጭ ፡ ያለ ፡ ነው
2. የሚያዳልጥ. He scattered ashes on the slippery sidewalk. የሚያዳልጠው ፡ የእግር ፡ መ
ንገድ ፡ ላይ ፡ አመድ ፡ በተነ

**be slippery** አዳለጠ
The roads are very slippery. መንገዶቹ ፡ በጣም ፡ ያዳልጣሉ

**slipshod** በግዴለሽነት ፡ የተሠራ
I won't pay for this slipshod piece of work. ለዚህ ፡ በግዴለሽነት ፡ ለተሠራ ፡ ሥራ ፡ አልከፍልም

**slip-up** ስሕተት
There must have been a slip-up, or you wouldn't have been paid so much. ስሕተት ፡ ቢኖር ፡ ነ
ው ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ አትከፈልም ፡ ነበር

**slit** (slit), v. ከጐን ፡ ላይ ፡ ቅድ ፡ አወጣ(ለት)
The tailor slit the jacket to make a pocket. ልብስ ፡ ሰፊው ፡ ኪስ ፡ ለማውጣት ፡ ኮቱን ፡ ከ
ጐን ፡ ላይ ፡ ቅድ ፡ አወጣለት

**slit open**
1. ቀደደ. They slit open the animal's stomach and removed the intestines. የእንስሳውን ፡ ሆድ ፡ ቀደው ፡ አንጀቱን ፡ አወጡ
2. ቀዶ ፡ ከፈተ. He slit the envelope open with a knife. ፖስታውን ፡ በስንጢ ፡ ቀዶ ፡ ከፈተው

**slit** (n.) ቀዳዳ
The gun sticks out of a slit in the side of the tank. የጠመንጃው ፡ አፈ ፡ ሙዝ ፡ በታንኩ ፡ ቀ
ዳዳ ፡ ውስጥ ፡ ወጣ ፡ ብሎ ፡ ይታያል

**sliver** (n.) ቁራጭ

Only a sliver of cheese was left. አንዲት ፡ ፎርማጆ ፡ ቁራጭ ፡ ቀርታለች

**sliver of wood** ስንጥር

I have a sliver of wood in my finger. ጣቴ ፡ ውስጥ ፡ ስንጥር ፡ ገብቶብኛል

**slog** ዳከረ ፤ እየወደቀ ፡ እየተነሣ ፡ ሄደ

The soldiers slogged through the thick mud. ወታደሮቹ ፡ በማጡ ፡ ውስጥ ፡ ዳከሩ ፡ (እየወደቁ ፡ እየተነሡ ፡ ሄዱ)

**slogan** አርማ

We have to invent a slogan to impress these students. የነዚህን ፡ ተማሪዎች ፡ ስሜት ፡ ለመቀስቀስ ፡ አንድ ፡ አርማ ፡ መፍጠር ፡ አለብን

**slop** (slopped), vt. ረጨ

He slopped water on me. ውኃ ፡ ረጨብኝ

**slop** (vi.)

1. ተረጨ. The tea slopped onto the saucer. ሻዩ ፡ ሲኒ ፡ ማስቀመጫው ፡ ላይ ፡ ተረጨ

2. ተንቦጫረቀ. We slopped through the rain. በዝናቡ ፡ ውስጥ ፡ ተንቦጫረቅን

**slop** (n.) ጨምላቃ ፡ ምግብ

I won't eat that slop. ያን ፡ ጨምላቃ ፡ ምግብ ፡ አልበላም

**slope** (v.)

1. አጋደለ. The garden slopes down to the river. ያትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ወንዙ ፡ ያጋደለ ፡ ነው

Does your handwriting slope forward or backward? የእጅ ፡ ጽሕፈትህ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ያጋደለ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ወደ ፡ ኋላ ?

2. አቈለቈለ. The hill slopes gently down to the lake. ኮረብታው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ወደ ፡ ሐይቁ ፡ ያቈለቍላል

3. ዘንበል ፡ ብሎ ፡ ተሠራ. The roof slopes so that the rain will run off. ዝናቡ ፡ እንዲወርድ ፡ ጣሪያው ፡ ዘንበል ፡ ብሎ ፡ ተሠርቷል

4. ዘቅዘቅ ፡ አለ. Since the field slopes, the water drains from it. ሜዳው ፡ ዘቅዘቅ ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ ውኃ ፡ አይከትርም

**slope** (n.)

1. ቁልቁለት. Is the slope very steep? ቁልቁለቱ ፡ በጣም ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ነው ?

2. ዳገት. We tried to drive up the slope, but it was too steep. በዳገቱ ፡ ላይ ፡ ነድተን ፡ ለማለፍ ፡ ሞከርን ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ነበር

**sloping**

*She has sloping shoulders. ከትከሻዋ ፡ ጐበጥ ፡ ትላለች

**sloppy**

1. ዝርክርክ. She's very sloppy; her house is never clean. በጣም ፡ ዝርክርክ ፡ ስለሆነች ፡ ቤቷ ፡ ጸድቶ ፡ አያውቅም

2. የተጨማለቀ. His work is sloppy. ሥራው ፡ በጣም ፡ የተጨማለቀ ፡ ነው

3. የማያስደስት. The officer dressed the men down for their sloppy appearance. መኰንኑ ፡ ሰዎቹ ፡ ሁኔታቸው ፡ ስለማያስደስት ፡ ገሠጻቸው

4. የጨቀየ. You cannot walk on this sloppy sidewalk. በጨቀየው ፡ የእግር ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ልትሄድ ፡ አትችልም

5. ዝናባም. The sloppy weather prevented us from going on a picnic. ዝናባም ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፡ ሽርሽር ፡ እንዳንሄድ ፡ ከለከለን

**slosh**

We sloshed through the mud. ጭቃውን ፡ እያላቈጥን ፡ በችግር ፡ ተጓዝን

**slot** ቀዳዳ

The mailman pushed the mail through the slot in the door. ፖስታ ፡ አመላላሹ ፡ ደብዳቤያችንን ፡ በሩ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ቀዳዳ ፡ ጣለልን

**sloth** ስንፍና

His sloth keeps him from taking part in sports. ስንፍናው ፡ በስፖርት ፡ እንዳይካፈል ፡ ያደርገዋል

**slouch**

1. ተንጋዶ ፡ ተቀመጠ ፤ ተንፈላሶ ፡ ተቀመጠ. Sit up straight; it's bad for you to slouch in your chair. ቀና ፡ ብለህ ፡ ተቀመጥ ፤ ተንጋዶ ፡ (ተንፈላሶ) ፡ መቀመጥ ፡ ላንተ ፡ ጥሩ ፡ አይደለም

2. ተንቀዋለለ. He slouches around street corners all day. ቀኑን ፡ ሁሉ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ሲንቀዋለል ፡ ይውላል

**slouch along** እየተጐተተ ፡ ሄደ

The weary man slouched along. የደከመው ፡ ሰውዬ ፡ እየተጐተተ ፡ ሄደ

**slough off** ወደቀ

A scab sloughs off when new skin takes its place. አዲስ ፡ ቆዳ ፡ ከሥር ፡ ሲወጣ ፡ ቅርፊቱ ፡ ይወድቃል

**slovenly** ዝርክርክ

He has a slovenly appearance. ሁኔታው ፡ ሁሉ ፡ ዝርክርክ ፡ ነው

**slow** (v.), ~ **down** (vt.)
1. ጐተተ. Conversation tends to slow down the work. ወሬ ፡ ሥራን ፡ ይጐትታል
2. በዝግታ ፡ ነዳ. He slowed down the car when he came to a crossing. ማቋረጫው ፡ ላይ ፡ ሲደር
ስ ፡ መኪናውን ፡ በዝግታ ፡ ነዳ

**slow down** (vi.)
1. ዝግ ፡ አለ. Slow down when you come to an intersection! መስቀለኛ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ስትደር
ስ ፡ ዝግ ፡ በል
He put on the brake, and the car slowed down to a stop. ፍሬኑን ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፡ መኪናው ፡ ዝግ ፡
ብሎ ፡ ቆመ
2. ጐተት ፡ አለበት. +He's slowing down in his work. ሥራው ፡ ጐተት ፡ ብሎበታል

**slow up** ቀስ ፡ አለ
Slow up when you drive through a town! በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ስትነዳ ፡ ቀስ ፡ በል

**slow** (adj.)
1. ጐታታ. He is a slow worker. ጐታታ ፡ ሠራ
ተኛ ፡ ነው
2. ዝግ ፡ ያለ. The film was shown in slow motion. ፊልሙ ፡ የታየው ፡ ዝግ ፡ ባለ ፡ እንቅስ
ቃሴ ፡ ነው
3. ቶሎ ፡ የማይገባው. Slow children need special instruction. ቶሎ ፡ የማይገባቸው ፡ ልጆች ፡ ካ
ስተማሪያቸው ፡ ልዩ ፡ እርዳታ ፡ ያስፈልጋቸዋል
*Cook the soup over a slow fire! ሾርባውን ፡ እ
ሳት ፡ ሳታበዢ ፡ አብስይው
*He is slow to catch on. ቶሎ ፡ አይገባውም
*He is a slow learner. ትምህርት ፡ ቶሎ ፡ አይ
ገባውም
*He is a slow runner. ሲሮጥ ፡ ፍጥነት ፡ የለ
ውም

**slow** (adv.) በዝግታ
Drive slow past a school! ትምህርት ፡ ቤት ፡ አ
ጠገብ ፡ ስትደርስ ፡ በዝግታ ፡ ንዳ

**be slow**
1. ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀረ. Your watch is slow. ሰዓትህ ፡
ወደ ፡ ኋላ ፡ ይቀራል
2. ቀዘቀዘ. The market was slow. ገበያው ፡ ቀዝቅ
ዞ ፡ ነበር

**go slow** ቀስ ፡ ብሎ ፡ ሄደ
Go slow on a bumpy road! አባጣ ፡ ጎርባጣ ፡
መንገድ ፡ ላይ ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ ሂድ
[See also 'process, step']

**slower, go** ~ ዝግ ፡ አለ
Tell the driver to go slower. ነጂው ፡ ዝግ ፡ እ
ንዲል ፡ ንገረው

**slowly** በቀስታ ፤ ቀስ ፡ በቀስ
He was working slowly but surely. የሚሠራው ፡
በቀስታ ፡ (ቀስ ፡ በቀስ) ፡ ቢሆንም ፡ በደንብ ፡ ነበር
[See also 'move, progress']

**slug** (slugged), v. አወለቀ
He slugged him in the jaw with his fist. በቡጢ ፡
አገጩን ፡ አወለቀው

**slug** (n.)
1. ምት. The slug broke his jaw. ምቱ ፡ አገጩን ፡
ሰበረው
2. ክብ ፡ ቁራጭ ፡ ብረት. He put a slug in the telephone instead of a coin. በስልኩ ፡ ውስ
ጥ ፡ በሳንቲም ፡ ፈንታ ፡ ክብ ፡ ቁራጭ ፡ ብረት ፡
ከተተ

**sluggish, feel** ~ ሰውነቱ ፡ ፍስስ ፡ አለ
I feel sluggish after I eat a heavy meal. ከባድ ፡
ምግብ ፡ ከበላሁ ፡ በኋላ ፡ ሰውነቴ ፡ ፍስስ ፡ ይላል

**sluice gate** የውኃ ፡ መዝጊያ
When they irrigate the fields, they open the sluice gate and let the water out. ማሳ ፡ በሚያጠ
ጡበት ፡ ጊዜ ፡ የውኃውን ፡ መዝጊያ ፡ ከፍተው ፡
ውኃውን ፡ ይለቁታል

**slum** ቆሻሻ ፡ ሰፈር ፤ ባለ ፡ ደሳሳ ፡ ጎጆዎች ፡ ሰ
ፈር ፤ ደሳሳ ፡ መኖሪያ
The refugees live in slums now. ስደተኞቹ ፡ አሁ
ን ፡ የሚኖሩት ፡ በቆሻሻ ፡ ሰፈር ፡ ነው
He has an ambitious program for eliminating the slums. ባለ ፡ ደሳሳ ፡ ጎጆዎችን ፡ ሰፈር ፡ ለማስወ
ገድ ፡ ከፍተኛ ፡ እቅድ ፡ አለው
Slums are a reproach to a city. ደሳሳ ፡ መኖሪያ
ዎች ፡ ለከተማ ፡ አሳፋሪዎች ፡ ናቸው

**slumber** (v.)
1. ተኛ. The baby slumbered peacefully. ሕፃኑ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ተኛ
2. ሞተ. The volcano has slumbered for years. እሳተ ፡ ገሞራው ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ሞቶ ፡ ነበር

**slumber** (n.) መተኛት
Her slumber gave her badly needed rest. መተኛቷ ፡ በጣም ፡ የፈለገችውን ፡ ዕረፍት ፡ አ
ስገኘላት

**slump** (v.)
1. ቀዘቀዘ. Business slumped at the end of the war. ጦርነቱ ፡ ሲያበቃ ፡ የንግዱ ፡ ሥራ ፡ ቀዘ
ቀዘ
2. ተደፋ. He slumped to the floor with a bullet in his heart. ልቡን ፡ በጥይት ፡ ተመቶ ፡
ወለሉ ፡ ላይ ፡ ተደፋ

3. ዘፍ ፡ አለ. He slumped in his chair and cried bitterly. ወንበሩ ፡ ላይ ፡ ዘፍ ፡ ብሎ ፡ አምርሮ ፡ አለቀሰ

**slump** (n.) የንግድ ፡ ቀዝቀዝ ፡ ማለት
The slump has reduced taxes. ንግድ ፡ ቀዝቀዝ ፡ በማለቱ ፡ ግብር ፡ ተቀነሰ

**slung**, see **sling**

**slur** (slurred), v.
1. ዋጠ. Don't slur your words when you talk. ስትናገር ፡ ቃሉን ፡ አትዋጠው
2. አዋረደ. His cowardly behavior slurs the family name. የፈሪ ፡ ምግባሩ ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ ያዋርዳል

**slur (over)** አድበስብሶት ፡ አለፈ
He slurred over this point in his talk. በንግግሩ ፡ ላይ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ አድበስብሶት ፡ አለፈ

**slur** (n.), **be a ~ on** አጕደፈ
His remark was a slur on my family name. የሱ ፡ አስተያየት ፡ የቤተ ፡ ሰቤን ፡ ስም ፡ የሚያጕድፍ ፡ ነበር

**slush** በመቅለጥ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ በረዶ
It is difficult to drive through the slush. በመቅለጥ ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ በረዶ ፡ መንዳት ፡ ከባድ ፡ ነው

**sly**
1. ተንኰለኛ. He is a sly person, so be careful what you tell him. ተንኰለኛ ፡ ስለሆነ ፡ የምትነግረውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተጠንቀቅ
2. ብልጣ ፡ ብልጥ. The sly fox eluded the dog. ብልጣ ፡ ብልጥ ፡ ቀበሮ ፡ ከውሻው ፡ በዘዴ ፡ አመለጠች
3. ሌባ. The sly cat stole the meat while the cook's back was turned. ሌባዋ ፡ ድመት ፡ ገረዲቱ ፡ ዞር ፡ ስትል ፡ ሥጋውን ፡ ሰረቀች
4. ዞር ፡ ያለ. She asked sly questions. ዞር ፡ ያለ ፡ ጥያቄ ፡ ጠየቀች

**on the sly** በድብቅ
The story goes that the two meet each other on the sly. እንደሚወራው ፡ ሁለቱ ፡ የሚገናኙት ፡ በድብቅ ፡ ነው

**smack** (vt.)
1. አጮለ. The father smacked his son for talking back. ልጁ ፡ ላባቱ ፡ መልስ ፡ ስለሰጠው ፡ አጮለው
2. መጠጠ. He smacked his lips at the thought of cake. የኬክ ፡ ነገር ፡ ቢነሣ ፡ ከንፈሩን ፡ መጠጠ

**smack** (vi.) ተጋጨ
He smacked against the pole with his bike. በቢስክሌት ፡ ከዕንጨቱ ፡ ጋር ፡ ተጋጨ

**smack of** ቀመስ ፡ ነው
The speech of the elderly Englishman smacks of the old country. ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የመጣው ፡ ሽማግሌ ፡ አነጋገር ፡ የጥንቱን ፡ አነጋገር ፡ ቀመስ ፡ ነው

**smack** (n.)
1. ጩኸት. I heard the smack of a whip. የጅራፍ ፡ ጩኸት ፡ ሰማሁ
2. መንፈስ. The old sailor still had a smack of the sea about him. የድሮው ፡ መርከበኛ ፡ አሁንም ፡ የባሕር ፡ መንፈስ ፡ ይታይበታል

**have a smack of** (repeated noun) + አለ
This soup has a smack of lemon. ይህ ፡ ሾርባ ፡ ሎሚ ፡ ሎሚ ፡ ይላል

**small**
1. ትንሽ. The difference is very small. ልዩነቱ ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው
I put the pennies in a small envelope. ሳንቲሙን ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ አንቦልክ ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጥኩት
2. ረቂቅ. It's a strain to read this small print. ይህን ፡ ረቂቅ ፡ ጽሑፍ ፡ ማንበብ ፡ ዓይን ፡ ይጐዳል
3. ተራ. People both great and small mourned the President's death. ታላላቅና ፡ ተራ ፡ ሰዎች ፡ በፕሬዚዳንቱ ፡ ሞት ፡ አዘኑ
4. የማይረባ. Don't bother the teacher with that small matter now! በዚያ ፡ በማይረባ ፡ ነገር ፡ መምህሩን ፡ አሁን ፡ አታስቸግር
5. ያልደረጀ. Small farmers and small businessmen were hurt by the new tax. ያልደረጁ ፡ ገበሬዎችና ፡ ነጋዴዎች ፡ ባዲሱ ፡ ታክስ ፡ ተጐድተዋል
6. ቀላል. Only a small man would behave so badly. ይህን ፡ የሚያደርግ ፡ ቀላል ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው
7. (= n.) ዋዛ. It started as something small, but grew into a big difficulty. ነገሩ ፡ እንደዋዛ ፡ ጀምሮ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆነ

**be small** አነሰ
These shoes are too small for me. ይህ ፡ ጫማ ፡ በጣም ፡ ያንሰኛል

**be (rather) small** አነስ ፡ አለ
The room is rather small. ክፍሉ ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ ነው

**make feel small** አዋረደ
She made him feel small. አዋረደችው

**make (someone) look small** ዝቅተኛ ፡ አስመሰለ
He made me look small by donating twice as much money as I did. እኔ ፡ ከረዳሁት ፡ ገንዘብ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ በመርዳት ፡ ዝቅተኛ ፡ አስመሰለኝ
[See also 'bill, quantity, sale']

**small change** ዝርዝር
I haven't any small change. ምንም ፡ ዝርዝር ፡ የለኝም

**smaller** ከዚህ ፡ አነስ ፡ ያለ
This suit is too large. Do you have anything smaller? ይህ ፡ ልብስ ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ነው ። ከ ዚህ ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ አለህ ?

**small fry** አሜፋሬ
The ringleaders escaped and only the small fry were caught. ቀንደኞቹ ፡ ሲያመልጡ ፡ አሜ ፋሬዎቻቸው ፡ ብቻ ፡ ተያዙ

**small-minded**
*That was small-minded of him. ይህን ፡ ያደረ ገው ፡ አእምሮው ፡ ጠባብ ፡ በመሆኑ ፡ ነው

**smallpox** ፈንጣጣ
Smallpox is a serious disease. ፈንጣጣ ፡ ከፉ ፡ በሽታ ፡ ነው

**smart** (v.)
1. አቃጠለ. The alcohol smarts. አልኮሉ ፡ ያቃጥ ላል
2. ቈጠቈጠ. A bee sting smarts. ንብ ፡ ሲነድፍ ፡ ይቈጠቍጣል
The cut smarts. ቁስሉ ፡ ይቈጠቍጣል

**smart** (adj.)
1. ጐበዝ. He is a smart student. ጐበዝ ፡ ተማ ሪ ፡ ነው
2. ብልጥ. He is a smart businessman and makes a lot of money. ብልጥ ፡ ነጋዴ ፡ ስለሆነ ፡ ብ ዙ ፡ ገንዘብ ፡ ያተርፋል
3. ጥሩ. That's a smart dress. ጥሩ ፡ ልብስ ፡ ነው
4. ንቁ. He looks smart in his uniform. የደንብ ፡ ልብሱን ፡ ሲለብስ ፡ ንቁ ፡ ይመስላል
*That was very smart of you. ጥሩ ፡ ነገር ፡ ሠራህ

**at a smart pace** ቶሎ ፡ ቶሎ
They walked at a smart pace. ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ተ ራመዱ

**smash** (vt.)
1. ሰባበረ. The boys smashed the window. ልጆቹ ፡ መስኮቱን ፡ ሰባበሩት
2. ወቃ. He smashed his stick against the ground. ዱላውን ፡ ከመሬት ፡ ወቃው
3. ድምጥማጡን ፡ አጠፋ. They smashed the enemy in a furious attack. ባደረጉት ፡ ከባድ ፡ ማጥቃ ት ፡ ጠላትን ፡ ድምጥማጡን ፡ አጠፉት

**smash** (vi.) ነኰተ
The dishes smashed as they hit the ground. ሳሕኖቹ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡ ነኰቱ

**smash down** ሰበረ
They used a log as a ram to smash down the door. በሩን ፡ ለመስበር ፡ በግንድ ፡ መስበሪያ ፡ ተጠቀሙ

**smash flat** ጸመጠ
A boulder fell on the car and smashed it flat. ቋጥኝ ፡ መኪናዋ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ጸመጣት

**smash into** ከ -- ጋር ፡ በኀይል ፡ ተጋጨ
The car smashed into a wall. መኪናዋ ፡ ከግድግ ዳ ፡ ጋር ፡ በኀይል ፡ ተጋጨች

**smash open** (vt.) ሰብሮ ፡ በረገደ
He smashed open the door with an ax. መዝጊያ ውን ፡ በመጥረቢያ ፡ ሰብሮ ፡ በረገደው

**smash open** (vi.) ተሰብሮ ፡ ተከፈተ
The box fell on the ground and smashed open. ሣጥኑ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ተሰብሮ ፡ ተከፈተ

**smash to bits** አደቀቀ
In his rage, he smashed everything to bits. በንዴት ፡ ያገኘውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አደቀቀው

**smash** (n.) ግጭት
Both drivers were hurt in the smash. በግጭቱ ፡ ሁለቱም ፡ ነጂዎች ፡ ተጐዱ
*The smash of glass startled me. መስታወቱ ፡ ሲነኰት ፡ አስደነገጠኝ

**make a smash** ከፍተኛ ፡ ድምፅ ፡ አሰማ
The teapot made an awful smash when it fell. የሻይ ፡ ጀበናው ፡ ወድቆ ፡ ሲሰበር ፡ ከፍተኛ ፡ ድም ፅ ፡ አሰማ

**smashing**
*We heard a smashing noise. አንድ ፡ ነገር ፡ ሲ ሰበር ፡ ሰማን

**be a smashing success** በጣም ፡ ተሳካ
Our play was a smashing success. ቲያትራችን ፡ በጣም ፡ ተሳክቶ ፡ ነበር

**smashup** ግጭት
We saw a bad smashup on the road. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ አሰቃቂ ፡ ግጭት ፡ አየን

**smattering, have a ~ of** ሞካከረ ። አንዳ ንድ ፡ ነገር ፡ ቀሠመ
He has a smattering of Amharic. አማርኛ ፡ ይ ሞካክራል
He has a smattering of physics. ስለ ፡ ፊዚክስ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ቀሥሟል

**smear** (v.)
1. ተቀባ. He smeared his hair with butter. ራሱን ፡ ቅቤ ፡ ተቀብቷል
2. ቀባ. The baby smeared the wall with mud. ሕፃኑ ፡ ግድግዳውን ፡ ጭቃ ፡ ቀባው

3. አጠፋ. The newspaper smeared the President's reputation. ጋዜጣው ፡ የፕሬዚዳንቱን ፡ ስም ፡ አጠፋ

**be smeared**

1. ተጨማለቀ. The child's face was smeared with milk. የልጁ ፡ ፊት ፡ በወተት ፡ ተጨማልቆ ፡ ነበር

2. ተለወሰ. His face was smeared with mud. ፊቱ ፡ በጭቃ ፡ ተለውሶ ፡ ነበር

**smear** (n.)

1. ጠብታ. There are smears of paint on the wall. በግድግዳው ፡ ላይ ፡ የቀለም ፡ ጠብታዎች ፡ አሉ

2. ስም ፡ የሚያጠፋ ፡ ወሬ. The newspaper published a smear against the opposing candidate. ጋዜጣው ፡ የተቀዋሚውን ፡ እጩ ፡ ስም ፡ የሚያጠፋ ፡ ወሬ ፡ ጻፈ

**smear of dirt** ቆሻሻ

There was a smear of dirt on the cloth. ጨርቁ ፡ ላይ ፡ ቆሻሻ ፡ ነበር

**smell** (smelled, or smelt), vt.

1. አሸተተ. He smelled the meat to see if it was fresh. ሥጋው ፡ ትኩስ ፡ መሆኑን ፡ ለማወቅ ፡ አሸተተው

2. ሸተተ(ው). +Do you smell gas? ቤንዚን ፡ ይሸትሃል ?

3. ተሰማ(ው). +We smelled trouble. ችግር ፡ እንደሚመጣ ፡ ተሰማን

**smell** (vi.)

1. አሸተተ. We smell with our noses. ባፍንጫችን ፡ እናሸታለን

2. አነፈነፈ. The dog was smelling at the gate. ውሻው ፡ እውጩ ፡ በር ፡ ላይ ፡ ያነፈንፍ ፡ ነበር

3. መዓዛ ፡ አለው. The roses smell beautiful. ጽጌ ፡ ረዳዎቹ ፡ ጥሩ ፡ መዓዛ ፡ አላቸው

4. ሸተተ. The garbage can smells. የቆሻሻ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ቆርቆሮ ፡ ይሸታል

**smell of** መሰለ

The plan smells of trickery. እቅዱ ፡ የሚያታልል ፡ ይመስላል

**smell up** አቀረና

The burning rubber smelled up the room. የተቃጠለው ፡ ላስቲክ ፡ ክፍሉን ፡ አቀረናው

**smell** (n.)

1. ሽታ. Where does that unpleasant smell come from? ይህ ፡ መጥፎ ፡ ሽታ ፡ የሚመጣው ፡ ከየት ፡ ነው ?

2. ክርፋት. The fishy smell of the store nauseates me. በሱቁ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የዓሣ ፡ ክርፋት ፡ ልቤን ፡ አጥወለወለኝ

3. የማሽተት ፡ ኀይል. Smell is more acute in dogs than in men. ውሾች ፡ ከሰው ፡ የበለጠ ፡ የማሽተት ፡ ኀይል ፡ አላቸው

4. ማሽተት. Dogs have an acute sense of smell. ውሾች ፡ ኀይለኛ ፡ የማሽተት ፡ ሕዋስ ፡ አላቸው

**have an objectionable smell** ከረፋ

Wet dogs have an objectionable smell. ዝናብ ፡ የመታቸው ፡ ውሾች ፡ ይከረፋሉ

**smelly** የሚከረፋ

Chase away that smelly dog! ይህን ፡ የሚከረፋ ፡ ውሻ ፡ ወዲያ ፡ አባር

**smelt,** see **smell**

**smelt** አቀለጠ

They abstract iron from ore by smelting it. አፈር ፡ በማቅለጥ ፡ ብረት ፡ ያወጣሉ

**smile** (v.) ፈገግ ፡ አለ ፤ ሣቅ ፡ አለ

She smiled at you. ፈገግ ፡ አለችልህ

She smiled at me in a friendly way. በወዳጅነት ፡ መንገድ ፡ ሣቅ ፡ አለችልኝ

**smile** (n.) ፈገግታ

She has a charming smile. ደስ ፡ የሚል ፡ ፈገግታ ፡ አላት

[See also 'force']

**smirch**

1. አቆሸሸ. He smirched his clean shirt. ንጹሕ ፡ ሸሚዙን ፡ አቆሸሸው

2. አጠፋ. The newspaper smirched his reputation. ጋዜጣው ፡ ስሙን ፡ አጠፋው

**smirk** ፈገግ ፡ አለ

He smirked when I told him he was the smartest man I had ever known. ከማውቃቸው ፡ ሁሉ ፡ ጐበዝ ፡ ነህ ፡ ብዬ ፡ በነገርኩት ፡ ጊዜ ፡ ፈገግ ፡ አለ

**smite** (smote) መታ

She smote him on the back with a broom. በመጥረጊያ ፡ ጀርባው ፡ ላይ ፡ መታችው

**be smitten** ተነደፈ

He was smitten with love. በፍቅር ፡ ተነድፎ ፡ ነበር

**smith** ብረት ፡ ሠሪ

The smith makes iron tools for the village. ብረት ፡ ሠሪው ፡ ለመንደሩ ፡ ነዋሪዎች ፡ የብረት ፡ መሣሪያዎች ፡ ይሠራል

**smithy** የሚሠራበት ፡ ጎጆ
The smith keeps his equipment in a smithy. ብረት ፡ ሠሪው ፡ መሣሪያውን ፡ እሚሠራበት ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ ያስቀምጣል

**smock** [ሴቶች ፡ ወጥ ፡ ሲሠሩ ፡ እንዳይፈናጠቅባቸው ፡ ወይም ፡ ሠዓሊ ፡ ሥዕል ፡ ሲሠራ ፡ ቀለም ፡ እንዳይነጠባጠበው ፡ በልብስ ፡ ላይ ፡ የሚደርቡት ፡ እንደ ፡ ካፖርት ፡ ያለ ፡ የሥራ ፡ ልብስ]

**smoke** (vt.)
1. አጨሰ. I smoke a pipe. ፒፓ ፡ አጨሳለሁ
2. በጢስ ፡ ዐጠነ. People smoke fish to preserve them. ሰዎች ፡ ዓሣ ፡ እንዳይበላሽ ፡ በጢስ ፡ ያጥኑታል
3. ዐጠነ. I shall smoke my beehive tonight. ዛሬ ፡ ማታ ፡ ቀፎዬን ፡ አጥናለሁ

**smoke** (vi.)
1. አጨሰ. The students were not allowed to smoke in class. ተማሪዎቹ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ እንዲያጨሱ ፡ አልተፈቀደላቸውም
2. ጨሰ. The stove is smoking again. ምድጃው ፡ እንደገና ፡ መጨስ ፡ ጀመረ

**smoke** (n.) ጭስ ፤ ጢስ
Where is that smoke coming from? ያ ፡ ጭስ ፡ (ጢስ) ፡ የሚመጣው ፡ ከየት ፡ ነው ?

**smoker** ሲጋራ ፡ የሚያጨስ ፤ ሲጃራ ፡ አጫሽ
Smokers may harm their lungs. ሲጋራ ፡ የሚያጨሱ ፡ (ሲጃራ ፡ አጫሾቹ) ፡ ሳምባቸውን ፡ ሊጎዱ ፡ ይችላሉ

**smokestack** የጭስ ፡ ማውጫ
There are many smokestacks in this city. በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የጪስ ፡ ማውጫዎች ፡ አሉ

**smoking** ማጨስ ፤ ትምባሆ ፡ መጠጣት
No smoking. ማጨስ ፡ (ትምባሆ ፡ መጠጣት) ፡ ክልክል ፡ ነው

**smoky** ብዙ ፡ ጭስ ፡ ያለው
They made a smoky fire to keep off the bugs. ነፍሳቶቹን ፡ ለማባረር ፡ ብዙ ፡ ጭስ ፡ ያለው ፡ እሳት ፡ አነደዱ

**be smoky** ጭስ ፡ ለበሰ
The air is smoky because of the many fires. በብዙ ፡ ቃጠሎ ፡ ምክንያት ፡ ሰማዩ ፡ ጭስ ፡ ለብሷል

**smolder** ጨሰ
The fire is still smoldering. እሳቱ ፡ አሁንም ፡ ይጨሳል

**smooth** (v.)
1. አለሰለሰ. He smoothed the wood with a rasp. ዕንጨቱን ፡ በሞረድ ፡ አለሰለሰ
2. አስተካከለ. He smoothed the mortar with a trowel. ሲሚንቶውን ፡ በመለሰኛ ፡ አስተካከለው
3. አስተካከሉ ፡ አነጠፈ. The maid smoothed the sheets on the bed. ገረዲቱ ፡ አንሶላዎቹን ፡ አስተካክላ ፡ አነጠፈች
4. ከፈተ. His pleasantness smoothed the way for an agreement. መልካም ፡ ጠባዩ ፡ ለስምምነቱ ፡ መንገድ ፡ ከፈተ

**smooth away** አስወገደ
He smoothed away all objections to the plan. በእቅዱ ፡ ላይ ፡ የተሰነዘረውን ፡ ተቃውሞ ፡ ሁሉ ፡ አስወገደ

**smooth down** አበረደ
He smoothed down his father's temper. ያባቱን ፡ ንዴት ፡ አበረደ

**smooth out** አስተካከለ
Smooth out the tablecloth! የጠረጴዛውን ፡ ልብስ ፡ አስተካክለው

**smooth** (adj.)
1. ልስልስ. The stone is very smooth. ድንጋዩ ፡ በጣም ፡ ልስልስ ፡ ነው
2. ለስላሳ. The wall is smooth. ግድግዳው ፡ ለስላሳ ፡ ነው
This child has a smooth disposition. ልጁ ፡ ለስላሳ ፡ ጠባይ ፡ አለው
3. ሉጫ. His hair is smooth. ጸጉሩ ፡ ሉጫ ፡ ነው
4. የረጋ. He put in his hand and disrupted the smooth surface of the water. የረጋውን ፡ ውኃ ፡ በእጁ ፡ አምቦጫረቀው
5. (= adv.) ቀስ ፡ ብሎ. The airplane made a smooth landing. አውሮፕላኑ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ አረፈ
*The ride in this car is smooth. ይህ ፡ መኪና ፡ አይነቀንቅም

**smooth talker** አፈ ፡ ጮሌ
That salesman is a smooth talker. ያ ፡ አሻሻጭ ፡ አፈ ፡ ጮሌ ፡ ነው

**be smooth**
1. ጸጥ ፡ አለ. The sea was very smooth. ባሕሩ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ነበር
2. አልጓጐለም. Make sure the sauce is smooth! ወጡ ፡ እንዳይጓጐል ፡ ተጠንቀቅ

**have a smooth face** ጺም ፡ የለውም
This young man has a smooth face. ይህ ፡ ወጣት ፡ ሰው ፡ ጺም ፡ የለውም

**have smooth manners** በጣም ፡ ትሑት ፡ ነው
The salesman has smooth manners. አሻሻጩ ፡ በጣም ፡ ትሑት ፡ ነው

**in a smooth manner** በለዘብታ
He spoke in a smooth manner. በለዘብታ ፡ ተናገረ

**smoothly** ቀስ ፡ ብሎ ፤ ዝግ ፡ ብሎ
The plane landed smoothly. አውሮፕላኑ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ (ዝግ ፡ ብሎ) ፡ አረፈ

**go smoothly** ተሳካ
Everything went smoothly. ሁሉም ፡ ነገር ፡ ተሳካ
[See also 'ride']

**smote**, see **smite**

**smother** (vt.)
1. አፍኖ ፡ ገደለ. The thief smothered the man with a pillow. ሌባው ፡ ሰውዬውን ፡ በትራስ ፡ አፍኖ ፡ ገደለው
2. አለበሰ. The man smothered the fire with sand. ሰውዬው ፡ እሳቱን ፡ አሸዋ ፡ አለበሰው
3. አለባበሰ. He smothered his resentment. ቅሬታውን ፡ አለባበሰ

**smother** (vi.) ታፈነ
We nearly smothered in the heavy smoke. ጥቅጥቅ ፡ ባለው ፡ ጭስ ፡ ልንታፈን ፡ ምንም ፡ አልቀረን ፡ ነበር

**smother with ashes** አዳፈነ
The maid smothered the fire with ashes. ገረዲቱ ፡ እሳቱን ፡ አዳፈነችው

**be smothered** ተሸፈነ
In the fall, the grass is smothered with leaves. በበልግ ፡ ወራት ፡ ሣሩ ፡ በረገፈ ፡ የዛፍ ፡ ቅጠል ፡ ይሸፈናል

**smoulder**, see **smolder**

**smudge** (v.) አጨማለቀ
He smudged the writing with his dirty hand. ጽሑፉን ፡ በቆሻሻ ፡ እጁ ፡ አጨማለቀው

**smudge** (n.) ጉድፍ
You've got a smudge on your cheek. ጉንጭህ ፡ ላይ ፡ ጉድፍ ፡ አለ

**smug** መርካቱን ፡ የሚያሳይ
He has a smug smile. መርካቱን ፡ የሚያሳይ ፡ ፈገግታ ፡ አለው

**smuggle (into, out)**
1. በድብቅ ፡ አስገባ. They smuggle cigarettes into the country. ሲጃራ ፡ በድብቅ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ያስገባሉ
2. በድብቅ ፡ ላከ. He smuggled a letter out of the country. በድብቅ ፡ ደብዳቤ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ላከ

**smuggled** (adj.) ቀረጥ ፡ ያልተከፈለበት
The government officers confiscated the smuggled goods. የመንግሥት ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ ቀረጥ ፡ ያልተከፈለባቸውን ፡ እቃዎች ፡ ወረሱ

**smuggler** የኮንትሮባንድ ፡ ነጋዴ
The smugglers were caught with contraband on them. የኮንትሮባንድ ፡ ነጋዴዎች ፡ ያልተቀረጠበት ፡ እቃ ፡ እንደያዙ ፡ ተያዙ

**snack** መቆያ
She gave him a light snack just after coming home. ቤቱ ፡ ሲገባ ፡ ትንሽ ፡ መቆያ ፡ ሰጠችው

**snag** (snagged), v.
1. አስቸጋሪ ፡ ሆነ. +A workers' strike has snagged our plans. በሠራተኞቹ ፡ አድማ ፡ የተነሣ ፡ እቅዳችን ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆነ
2. ነጨ(በት). +He snagged his sweater on a nail. ሹራቡን ፡ ምስማር ፡ ነጨበት

**snag**, (n.) [በወንዝ ፡ ወይም ፡ በሐይቅ ፡ ውስጥ ፡ ተቸክሎ ፡ የቆመ ፡ ዛፍ ፡ ወይም ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ አለት]

**hit a snag** ተሰናከለ
Our vacation plans hit a snag when I became sick. የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ እቅዳችን ፡ እኔ ፡ ድንገት ፡ ስለታመምኩ ፡ ተሰናከለ

**run into a snag** ያላሰበው ፡ ችግር ፡ አጋጠመ(ው)
While working on Ethiopian literature, I ran into a snag on the poetry portion. የኢትዮጵያን ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ስመረምር ፡ እቅኔው ፡ ላይ ፡ ስደርስ ፡ ያላሰብኩት ፡ ችግር ፡ አጋጠመኝ

**snail** ቀንድ ፡ አውጣ
There are many snails around lakes. ቀንድ ፡ አውጣ ፡ በሐይቅ ፡ አካባቢ ፡ ይበዛል

**snake** እባብ
The snake was killed. እባቡ ፡ ተገደለ

**snap** (snapped), vt.
1. በጠሰ. He snapped the string. ገመዱን ፡ በጠሰው
2. አጮኸ. He snapped his finger. ጣቱን ፡ አጮኸ

**snap** (vi.)
1. ተበጠሰ. The rope snapped. ገመዱ ፡ ተበጠሰ
2. ተንጣጣ. This wood snaps as it burns. ይህ ፡ ዕንጨት ፡ ሲነድ ፡ ይንጣጣል

**snap at**
1. ለቀም ፡ አደረገ. The dog snapped at the child's hand. ውሻው ፡ የልጁን ፡ እጅ ፡ ለቀም ፡ አደረገው
2. በቁጣ ፡ ድምፅ ፡ ተናገረ. I don't know why he snapped at me that way. ለምን ፡ እንደዚያ ፡ በቁጣ ፡ ድምፅ ፡ እንደተናገረኝ ፡ አላውቅም
3. ባንዴ ፡ ተቀበለ. She snapped at the chance to go to Ethiopia. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመሄድ ፡ የተሰጣትን ፡ ዕድል ፡ ባንዴ ፡ ተቀበለች

**snap out**
The officer snapped out orders. መኰንኑ ፡ ትእዛዝ ፡ ድንገት ፡ በከፍተኛ ፡ ድምፅ ፡ ሰጠ

**snap shut** ድርግም ፡ ብሎ ፡ ተዘጋ
The door snapped shut. በሩ ፡ ድርግም ፡ ብሎ ፡ ተዘጋ

**snap to attention**
The soldiers snapped to attention. ወታደሮቹ ፡ በተጠንቀቅ ፡ ቆሙ

**snap up**
1. ዋጥ ፡ አደረገ. The dog snapped up the meat. ውሻው ፡ ሥጋውን ፡ ዋጥ ፡ አደረገው
2. ባንዴ ፡ ተቀበለ. We snapped up his offer at once. ያቀረበልንን ፡ ሐሳብ ፡ ባንዴ ፡ ተቀበልነው

**(be) snapped up** ተሸጠ
The cheapest articles were soon snapped up. ዋጋቸው ፡ የረከሰው ፡ እቃዎች ፡ ወዲያው ፡ ተሸጡ

**snap** (n.)
1. ድምፅ. I heard a snap when I opened the door. በሩን ፡ ስከፍት ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ
2. ቁልፍ. One of the snaps of your dress is unfastened. የቀሚስሽ ፡ አንዱ ፡ ቁልፍ ፡ አልተቈለፈም
3. (= adj.) በጣም ፡ ቀላል. The exam was a snap. ፈተናው ፡ በጣም ፡ ቀላል ፡ ነበር
*We heard the snap of the string. የተወጠረው ፡ ገመድ ፡ ጧ ፡ ብሎ ፡ ሲበጠስ ፡ ሰማን

**snap** (adj.)
*Don't make snap judgments! ለመፍረድ ፡ አትቸኵል

**snappy**
*He's a snappy dresser. ሁልጊዜ ፡ ይሽቀረቀራል
*Make it snappy! ፈጠን ፡ በል

**snapshot** ፎቶግራፍ
Take a snapshot of me! ፎቶግራፍ ፡ አንሣኝ

**snare** (v.)
1. አጠመደ. One day we snared a rabbit. አንድ ፡ ቀን ፡ ጥንቸል ፡ አጠመድን
2. ወጥመድ ፡ አገባ. Satan is trying to snare our souls. ሰይጣን ፡ ነፍሳችንን ፡ ወጥመድ ፡ ለማግባት ፡ ይሞክራል

**snare** (n.) ወጥመድ
The bird was caught in a snare. ወፏ ፡ ወጥመድ ፡ ውስጥ ፡ ገባች

**snarl** (vt.) አመሰቃቀለ
The kitten snarled the ball of wool. የድመቷ ፡ ግልገል ፡ የሱፉን ፡ ጥቅል ፡ አመሰቃቀለችው
*He snarled commands. ቆጣ ፡ ብሎ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ

**snarl** (vi.)
1. ተራመሰ. The traffic snarls in a big town. ትልቅ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ መኪና ፡ ይተራመሳል
2. ጥርሱን ፡ አገጠጠ(በት). The dog snarled when I got too close. ውሻው ፡ በጣም ፡ ስቀርበው ፡ ጥርሱን ፡ አገጠጠብኝ
3. በቁጣ ፡ ተናገረ. "Go away!" he snarled. ሂድ ፡ ወዲያ ፡ ብሎ ፡ በቁጣ ፡ ተናገረ

**snarl at** ጮኸ(በት)
Mr. Jones snarled at the noisy children. ሚስተር ፡ ጆንስ ፡ የሚንጫጩትን ፡ ሕፃናት ፡ ጮኸባቸው

**snarl** (n.) የተቈጣጠረ
Her hair is full of snarls. ጸጉሯ ፡ የተቈጣጠረ ፡ ይበዛዋል
*Traffic here is in a continuous snarl. እዚህ ፡ ሁልጊዜ ፡ የመኪና ፡ መጨናነቅ ፡ አለ

**snatch** (v.) መንጭቆ ፡ ወሰደ ፤ ነጠቀ
He snatched the letter from me. ደብዳቤውን ፡ መንጭቆ ፡ ወሰደብኝ
The thief snatched my purse and left me penniless. ሌባው ፡ ቦርሳዬን ፡ ነጥቆ ፡ ባዶ ፡ እጄን ፡ አስቀረኝ
*He snatched a bit of sleep sitting in his chair. ወንበሩ ፡ ላይ ፡ እንደተቀመጠ ፡ ጥቂት ፡ አንቀላፋ

**snatch at**
1. ሊይዝ ፡ ተፍጨረጨረ. The drowning man snatched at the rope. ሊሰጥም ፡ የነበረው ፡ ሰውዬ ፡ ገመዱን ፡ ሊይዝ ፡ ይፍጨረጨር ፡ ነበር
2. ያኔውኑ ፡ ተቀበለ. He snatched at the chance to travel. ለመጓዝ ፡ ያጋጠመውን ፡ ዕድል ፡ ያኔውኑ ፡ ተቀበለ

**snatch off** ቶሎ ፡ ብድግ ፡ አደረገ
He snatched off his hat and bowed. ባርኔጣውን ፡ ቶሎ ፡ ብድግ ፡ አድርጎ ፡ እጅ ፡ ነሣ

**snatch** (n.), **a ~ of** ጥቂቱን
I remember a snatch of the tune. ከዜማው ፡ ጥቂቱን ፡ አስታውሳለሁ

**sneak**
1. አደባ. The man sneaked about the house watching for a chance to steal the box. ሣጥኑን ፡ ለመስረቅ ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ በመጠበቅ ፡ ሰውዬው ፡ በቤቱ ፡ ዙሪያ ፡ አደባ
2. አስደበቀ(ው). +Why do you sneak instead of acting openly? ፊት ፡ ለፊት ፡ እንደመሥራት ፡ ምን ፡ ያስደብቅሃል ?

**sneak a glance at** እየሰረቀ ፡ አየ
He sneaked a glance at the pretty girl. ቆንጆዋን ፡ ልጃገረድ ፡ እየሰረቀ ፡ ያያት ፡ ነበር

**sneak in, sneak into** ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ገባ
He must have sneaked in while I wasn't looking. ሳላየው ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ገብቶ ፡ ይሆናል
He must have sneaked into the house. ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ገብቶ ፡ ይሆናል

**sneak out** ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ወጣ
He sneaked out while I wasn't looking. ሳላየው ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ወጣ

**sneaking** ያልተገለጸ
I have a sneaking ambition to become a reporter. ዜና ፡ አቅራቢ ፡ ለመሆን ፡ ያልተገለጸ ፡ ምኞት ፡ አለኝ

**have a sneaking suspicion**
I have a sneaking suspicion that he cheated. ማጭበርበሩን ፡ ልቤ ፡ ይጠረጥራል

**sneaky** ተንኰለኛ
He is a sneaky fellow. ተንኰለኛ ፡ ሰው ፡ ነው

**sneer** (v.), ~ **at**
1. በንቀት ፡ ተመለከተ. The rich girl sneered at the poor girl's clothes. ሀብታሟ ፡ ልጅ ፡ የድኻዋን ፡ ልጃገረድ ፡ ልብስ ፡ በንቀት ፡ ተመለከተች
2. አንኳሰሰ. He sneered at my efforts to learn Amharic. አማርኛ ፡ ለመማር ፡ የማደርገውን ፡ ጥረት ፡ አንኳሰሰብኝ

**sneer** (n.)
*His lip curled in a sneer. አፉን ፡ አጣመመብኝ

**sneeze** አነጠሰ
He has been sneezing all morning. ሲያነጥስ ፡ አረፈደ

**not to be sneezed at** እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አይታይም
A prize of $50 is not to be sneezed at. የኀምሳ ፡ ብር ፡ ሽልማት ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አይታይም

**snicker** በማሽሟጠጥ ፡ ሣቀ
The children snickered when they heard the story. ሕፃናቱ ፡ ታሪኩን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በማሽሟጠጥ ፡ ሣቁ

**snide**
*He made a snide remark about her. መጥፎ ፡ ስድብ ፡ ሰደባት

**sniff**
1. አነፈነፈ. The dog was sniffing along the ground. ውሻው ፡ እያነፈነፈ ፡ ይሄድ ፡ ነበር
I sniffed, but couldn't smell a thing. አነፈነፍኩ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አልሸተተኝ
2. ሳበ. He sniffed the morning air. የጧት ፡ አየር ፡ ሳበ
3. ጠረጠረ. The police sniffed a plot and broke up the meeting. ፖሊሱ ፡ አድማ ፡ መኖሩን ፡ ጠርጥሮ ፡ ስብሰባውን ፡ በተነው

**sniffle** ንፍጡን ፡ ማገ
The child is sniffling. ሕፃኑ ፡ ንፍጡን ፡ ይምጋል

**snip** (snipped), v.
1. በጠሰ. She snipped the thread. ክሩን ፡ በጠሰችው
2. ቀዶ ፡ አወጣ. She snipped the picture out of the paper. ሥዕሉን ፡ ከጋዜጣው ፡ ላይ ፡ ቀዳ ፡ አወጣችው

**snip** (n.) ቁርጥራጭ
There are snips of paper on the floor. በወለሉ ፡ ላይ ፡ የወረቀት ፡ ቁርጥራጮች ፡ አሉ

**snipe** አድፍጦ ፡ ተኰሰ
The soldier sniped at the enemy. ወታደሩ ፡ አድፍጦ ፡ ጠላት ፡ ላይ ፡ ተኰሰ

**sniper** የደፈጣ ፡ አደጋ ፡ ጣይ
We shot a sniper who had infiltrated our lines. ጦራችን ፡ ውስጥ ፡ ተሸሽጎ ፡ የገባውን ፡ የደፈጣ ፡ አደጋ ፡ ጣይ ፡ ገደልነው

**snippy** ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ ያለ
I don't like snippy answers. ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ ያለ ፡ መልስ ፡ አልወድም

**snob** ትምክሕተኛ
He is a snob, and won't talk to us common folk. ትምክሕተኛ ፡ ስለሆነ ፡ እንደኛ ፡ ካለው ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ አይነጋገርም

**snobbish** ትዕቢተኛ
Snobbish people are unpopular. ትዕቢተኞች ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ አይወደዱም

**snoop**
1. ወሬ ፡ ቀሠመ. The detective snooped around

the neighborhood. ጆሮ ፡ ጠቢው ፡ ከሰፈር ፡ ወሬ ፡ ይቀሥም ፡ ነበር
2. ጥልቅ ፡ አለ. The old woman snooped into everybody's business. አሮጊቷ ፡ በሰው ፡ ሥራ ፡ ጥልቅ ፡ አሉ

**snooze** (v.) ተኛ
The dog snoozed on the porch in the sun. ውሻው ፡ በረንዳው ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ ፀሐይ ፡ ይሞቃል

**snooze** (n.), **take a ~** ትንሽ ፡ ተኛ
I took a snooze after lunch. ምሳ ፡ በልቼ ፡ ትንሽ ፡ ተኛሁ

**snore** (v.) አኰረፈ
He snores loudly. በኀይል ፡ ያኰርፋል

**snore** (n.) ኵርፊያ
His snore shakes the rafters. ኵርፊያው ፡ ጋራ ፡ ዞሮ ፡ ይሰማል

**snort**
1. አሽካካ. When he tried to put the saddle on the horse, it snorted. ሊጭነው ፡ ሲሞክር ፡ ፈረሱ ፡ አሽካካ
2. ደነፋ. He snorted with rage. በንዴት ፡ ደነፋ

**snout** አፍንጫ
He slapped the pig over the snout. አሳማውን ፡ አፍንጫው ፡ ላይ ፡ መታው

**snow** (v.) በረዶ ፡ ጣለ
In the Alps, it snows sometimes in the summer. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በአልፐስ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ በበጋ ፡ በረዶ ፡ ይጥላል

**snow** (n.) በረዶ
Snow is white. በረዶ ፡ ነጭ ፡ ነው

**snub** (snubbed)
1. ችላ ፡ አለ. She snubbed me when I greeted her. ሰላምታ ፡ ስሰጣት ፡ ችላ ፡ አለችኝ
2. የንቀት ፡ ስሜት ፡ አሳየ. Mary snubbed some of the girls by not inviting them to her party. ሜሪ ፡ አንዳንድ ፡ ልጃገረዶችን ፡ ወደ ፡ ፓርቲው ፡ ባለመጥራት ፡ የንቀት ፡ ስሜት ፡ አሳየቻቸው

**snuff** (v.) አጠፋ
Snuff the candle when you go to bed. ስትተኛ ፡ ሻማውን ፡ አጥፋው

**snuff at** እያነፈነፈ ፡ ተከተለ
The dog snuffed at the tracks of the fox. ውሻው ፡ የቀበሮውን ፡ ዱካ ፡ እያነፈነፈ ፡ ተከተለ

**snuff up** ባፍንጫው ፡ ሳበ
He snuffs up salt and water to cure a cold. ለጉንፋን ፡ መድኃኒት ፡ እንዲሆነው ፡ ጨው ፡ አሟሙቶ ፡ ባፍንጫው ፡ ይስባል

**snuff** (n.) ሱረት
Do you take snuff? ሱረት ፡ ትስባለህ ?

**snug** ምቹ
The cabins on the boat are snug. የመርከቡ ፡ ክፍሎች ፡ ምቹ ፡ ናቸው
*The cat has found a snug corner behind the stove. ድመቷ ፡ ከምድጃው ፡ በስተጀርባ ፡ አንድ ፡ ጥግ ፡ ይዛ ፡ ተደላድላ ፡ ተኝታለች

**be snug**
1. ጠበበ ፡ አለ(በት). That coat is a little too snug. ኰቱ ፡ ትንሽ ፡ ጠበብ ፡ ብሎብሃል
2. ተመችቶ ፡ ኖረ. We are snug in our little cabin. በትንሿ ፡ ቤታችን ፡ ውስጥ ፡ ተመችቶን ፡ እንኖራለን

**snuggle, ~ in (someone's) arms** ለጥፍ ፡ አለ
The child snuggled in his mother's arms. ልጁ ፡ እናቱ ፡ ላይ ፡ ለጥፍ ፡ ብሎ ፡ ነበር

**so**
1. - ም. If I can do it, so can you. እኔ ፡ ልሠራው ፡ ከቻልኩ ፡ አንተም ፡ ትሠራዋለህ
2. እንደዚህ. Why are you so late? ምን ፡ እንደዚህ ፡ አዘገየህ ?
3. እስከዚህ. Don't be so yellow! The dog won't bite you. እስከዚህ ፡ አትፍራ ፤ ውሻው ፡ አይነክስህም
4. በጣም. My head aches so! ራሴን ፡ በጣም ፡ አሞኛል
He was so ill that we had to call a doctor. በጣም ፡ ታሞ ፡ ስለነበር ፡ ሐኪም ፡ መጥራት ፡ ነበረብን
5. -a. So you're back again! ተመልሰህ ፡ መጣህ!
So they say. ይላሉ ፡ (ይላሏ)
6. ታዲያ. So you think it's a good idea. ጥሩ ፡ ሐሳብ ፡ ነው ፡ አልክ ፡ ታዲያ
7. (= because) ስለ. The shops were closed so I couldn't get any paper. ሱቆቹ ፡ ተዘግተው ፡ ስለነበር ፡ ምንም ፡ ወረቀት ፡ ላገኝ ፡ አልቻልኩም
He failed to come on time so I hired somebody else. በሰዓቱ ፡ ሊመጣ ፡ ስላልቻለ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ቀጠርኩ
*I told you so! አላልኩህም! (ብዬሃለሁ! ፤ ነግሬሃለሁ!)
*He is not so tall as I am. የኔን ፡ ያህል ፡ አይረዝምም
*I said I would go, and so I shall. እሄዳለሁ ፡ ብያለሁ ፤ እሄዳለሁ!
*Isn't it so? አይደለም?

**so!** እህ ። ታዲያስ + verb -a
So! I caught you. እህ ፡ (ታዲያስ) ፡ ያዝኩሃ

**so as not to** እንድ + negative imperfect
I'll have everything ready so as not to keep you waiting. እንዳላስጠብቅህ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ አዘጋጅልሃለሁ

**so as to** እንድ + imperfect
I did some of the work so as to make things easier for you. እንዲቀልህ ፡ ብዬ ፡ ሥራውን ፡ ጥቂት ፡ ሠራሁልህ

**(and) so does, (and) so is** —ም ፡ እንዲሁ
Tom speaks Amharic, and so does John. ቶም ፡ አማርኛ ፡ ይናገራል ። ጆንም ፡ እንዲሁ
Wheat is a cereal, and so are barley and millet. ስንዴ ፡ እህል ፡ ነው ። ገብስና ፡ ጤፍም ፡ እንዲሁ

**so far**
1. እስከዚህ. Now that we have come so far, we might as well go to the end. እስከዚህ ፡ ከመጣን ፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ብንሄድስ ?
2. እስካሁን. So far you've been pretty lucky. እስካሁን ፡ ቀንቶሃል

**so far as** እንደ + relative imperfect
So far as I know he is still in Australia. እኔ ፡ እንደማውቀው ፡ አሁንም ፡ አውስትራልያ ፡ ነው

**so far, so good** እስካሁን ፡ ምንም ፡ አይል
How are things? So far, so good. ኑሮ ፡ እንዴት ፡ ነው? እስካሁን ፡ ምንም ፡ አይል

**(and) so it did** ሆነ
He told me it would happen, and so it did. ይሆናል ፡ እንዳለኝ ፡ ሆነ

**so it was** ይኸው ፡ እንግዲህ
So it was I became a sailor. ይኸው ፡ እንግዲህ ፡ መርከበኛ ፡ ሆንኩ

**so long** ይህን ፡ ያህል ። ይህን ፡ ያህል ፡ ጊዜ
We didn't expect him to stay so long. ይህን ፡ ያህል ፡ (ይህን ፡ ያህል ፡ ጊዜ) ፡ ይቆያል ፡ ብለን ፡ አላሰብንም ፡ ነበር

**so long!** ደኅና ፡ ሁን
So long! See you tomorrow. ደኅና ፡ ሁን ። ነገ ፡ እንገናኛለን

**so long as** (conj., prep.)
1. ከ + (perfect.). You may borrow the book so long as you keep it clean. መጽሐፉን ፡ በደንብ ፡ ከያዝከው ፡ ልትዋሰው ፡ ትችላለህ
2. እስከ + verb + ድረስ. He will stay here so long as the company needs him. ኩባንያው ፡ እስኪፈልገው ፡ ድረስ ፡ እዚህ ፡ ይቆያል

**so (one) may** እንድ + imperfect
Talk louder so I may hear you. እንድሰማህ ፡ ጮክ ፡ ብለህ ፡ ተናገር

**so much**
1. ይህን ፡ ያህል. There must have been a slip-up, or you wouldn't have paid so much. ስሕተት ፡ መኖር ፡ አለበት ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ አትከፍልም
2. ይህማ. He can't come to the picnic? So much the better for us. ለሽርሽር ፡ ሊመጣ ፡ አይችልም ። ይህማ ፡ ለኛ ፡ ጥሩ ፡ ነው

**so much as** እንኳን + negative verb
He didn't so much as give me a glass of water. አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ውኃ ፡ እንኳን ፡ አላጠጣኝም

**so much for** ይህ ፡ ይበቃዋል ። ያብቃና
So much for the first day of our journey. ለመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ጉዞዋችን ፡ ይህ ፡ ይበቃናል
So much for that. Now let's turn to the international situation! ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ እናብቃና ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ጉዳይ ፡ እንመለከት

**so much so**
*He's rich, so much so that he doesn't know how much money he has. በጣም ፡ ሀብታም ፡ ስለሆነ ፡ ገንዘቡን ፡ ቁጥሩንም ፡ አያውቅም

**so that** እንድ + imperfect
I'm telling you so that you'll know. የምነግርህ ፡ እንድታውቀው ፡ ብዬ ፡ ነው

**so what?** ታዲያ ፡ ምን ፡ ይሁን
I will not go to Harar. So what? ሐረር ፡ አልሄድም ። ታዲያ ፡ ምን ፡ ይሁን ?

**is that so?** እውነት ። ኧረ
She is sick. Is that so? ታማለች ። እውነት ? (ኧረ!)

**just so** ልክ ፡ እንደዚህ
Hold your pencil just so. እርሳሱን ፡ ልክ ፡ እንደዚህ ፡ አድርገህ ፡ ያዝ

**not so much** ብዙ ። ያን ፡ ያህል + negative verb
Not so much sugar, please. ብዙ ፡ (ያን ፡ ያህል) ፡ ስኳር ፡ አልወድም
[See also 'and, even, ever, forth, soon']

**soak** (vt.)
1. ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ዘፈዘፈ. We soak the laundry overnight. ልብሱን ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ዘፍዝፈን ፡ አሳድረነዋል
2. ዘፈዘፈ. Soak your finger in a solution of Epsom salts! የእንግሊዝ ፡ ጨው ፡ አሟሙተህ ፡ ጣትህን ፡ ዘፍዝፈው
3. አበሰበሰ. The rain soaked my clothes. ዝናቡ ፡ ልብሴን ፡ አበሰበሰው
4. አራሰ. The rain soaked the ground. ዝናቡ ፡ መሬቱን ፡ አራሰው

**soak** (vi.) ተዘፈዘፈ
The clothes soaked for two hours. ልብሱ ፡ ለሁለት ፡ ሰዓት ፡ ተዘፈዘፈ

**soak through**
1. ዘልቆ ፡ ወጣ. The blood soaked through the bandage. ደሙ ፡ ፋሻውን ፡ ዘልቆ ፡ ወጣ
2. ዘለቀ. The rain has soaked through the roof. ዝናቡ ፡ ጣሪያውን ፡ ዘለቀው

**soak up** መጠጠ
The sponge will soak up the water. ስፍንግ ፡ ውኃ ን ፡ ይመጠዋል

**soaked** (adv.) ርሶ
We came home soaked. ርሰን ፡ እቤት ፡ ገባን

**be soaked through** (= act.) ከእግር ፡ እስከ ፡ ራ ሱ ፡ አበሰበሰው
I was soaked through by the rain. ዝናቡ ፡ ከእግ ር ፡ እስከ ፡ ራሴ ፡ አበሰበሰኝ

**get soaked to the skin**
I got soaked to the skin. ብስብስ ፡ ብዬ ፡ ነበር

**soaking**
*A soaking downpour has helped the crops. ብርቱ ፡ ዝናብ ፡ ዘንቦ ፡ መሬቱን ፡ ስላጠገበው ፡ ለሰብሉ ፡ በጅቶታል

**so-and-so** እገሌ
So-and-so told so-and-so, and the secret was all over town. እገሌ ፡ ለእገሌ ፡ ሲነግር ፡ ምስጢ ሩ ፡ ከተማውን ፡ አዳረሰው

**soap** ሳሙና
I am going to get soap from the store. ሳሙና ፡ ልገዛ ፡ ወደ ፡ ሱቅ ፡ መሄዴ ፡ ነው

**bar of soap** ኪሎ ፡ ሳሙና
The girl bought a bar of soap. ልጅቷ ፡ አንድ ፡ ኪሎ ፡ ሳሙና ፡ ገዛች

**cake of soap** ሳሙና ፤ የገላ ፡ ሳሙና
I want a large cake of soap. አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሳ ሙና ፡ እፈልጋለሁ
Can I have a towel and a cake of soap? የገላ ፡ ሳሙናና ፡ ፎጣ ፡ ይገኛል ?

**soapy** ሳሙና ፡ ያለው
The child drank soapy water and retched on the floor. ሕፃኑ ፡ ሳሙና ፡ ያለው ፡ ውኃ ፡ ስለጠጣ ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ አስመለሰው

**soar**
1. ሰማይ ፡ ወጣ. Prices soared when the war broke out. ጦርነቱ ፡ ሲጀመር ፡ የእቃ ፡ ዋጋ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ
2. አንዣበበ. The hawk soars over our heads. ጭልፊቷ ፡ ከበላያችን ፡ ታንዣብባለች
3. ከፍ ፡ አለ. His ambition soared to the presidency. ምኞቱ ፡ ወደ ፡ ፕሬዚዳንትነት ፡ ከፍ ፡ አለ

**sob** (sobbed), v. ተነፋረቀ
The child sobs because his mother has gone to the market. እናቱ ፡ ገበያ ፡ ስለወጣች ፡ ልጁ ፡ ይነፋረቃል

**sob bitterly**
The child sobbed bitterly. ሕፃኑ ፡ ስቅቅ ፡ ብ ሎ ፡ አለቀሰ

**sob** (n.) ሲቃ ፤ መንሰቅሰቅ
His flow of words was interrupted by a sob. ንግግሩን ፡ ሲያወርደው ፡ ሲቃ ፡ በድንገት ፡ አቋረ ጠው
The unhappy boy gulped down a sob. የከፋው ፡ ልጅ ፡ መንሰቅሰቁን ፡ ዋጥ ፡ አደረገ

**sober** (v.) አቀዘቀዘ
The news of the accident sobered the party. ያደጋው ፡ ዜና ፡ ፓርቲውን ፡ አቀዘቀዘው

**sober up** ስካሩ ፡ በረድ ፡ አለ(ለት)
Drink some coffee to sober up! ስካርህ ፡ በረ ድ ፡ እንዲልልህ ፡ ቡና ፡ ጠጣ

**sober** (adj.)
1. ደብዘዝ ፡ ያለ. She likes sober colors. ደብዘ ዝ ፡ ያለ ፡ ቀለም ፡ ትወዳለች
2. ረጋ ፡ ያለ. The judge's sober opinion was not influenced by dislike. የዳኛው ፡ ረጋ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ በጥላቻ ፡ የተነካ ፡ አልነበረም
3. ተገቢ. Make a sober estimate of this car! ለመኪናው ፡ ተገቢ ፡ ግምት ፡ አድርግ
*From his sober expression, I feared bad news. ፊቱ ፡ ቢጠቋቁር ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ይነግረኝ ፡ ይሆ ናል ፡ ብዬ ፡ ፈራሁ
*He leads a sober, hard-working life. ጭምትና ፡ ጠንካራ ፡ ሠራተኛ ፡ ነው

**be sober**
*He is never quite sober. ሁሌ ፡ እንደሰከረ ፡ ነው

**so-called** ተብሎ ፡ የሚጠራ
This so-called butter is really margarine. ይህ ፡ ቅቤ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ በእውነቱ ፡ የዕንጨት ፡ ቅቤ ፡ ነው

**soccer** የእግር ፡ ኳስ ፡ ጨዋታ
Soccer is popular in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስ ጥ ፡ የእግር ፡ ኳስ ፡ ጨዋታ ፡ የተወደደ ፡ ነው

**sociable** ተጨዋች
He is a very sociable person, and so people always invite him to their parties. በጣም ፡ ተ ጨዋች ፡ ስለሆነ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ፓርቲያቸው ፡ ይጠሩታል
*We plan for a sociable evening. አንድ ፡ ምሽ ት ፡ ተሰብስበን ፡ ልንጫወት ፡ አቅደናል

**social**
1. ማኅበራዊ. Social conditions have changed tremendously. የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ በጣም ፡ ተለውጧል
Scholars investigate the social environments of different people. ሊቃውንት ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰዎችን ፡ ማኅበራዊ ፡ አካባቢ ፡ ይመረምራሉ
2. የኅብረተ ፡ ሰብ. Lying and cheating are social maladies. መዋሸትና ፡ ማጭበርበር ፡ የኅብረተ ፡ ሰብ ፡ በሽታዎች ፡ ናቸው
3. በኅብረት ፡ የሚኖር. Man is a social being. ሰው ፡ በኅብረት ፡ የሚኖር ፡ ፍጡር ፡ ነው
4. የመተዋወቂያ ፤ የመገናኛ. We organized a social gathering for foreign students. ለውጭ ፡ አገር ፡ ተማሪዎች ፡ የመተዋወቂያ ፡ (የመገናኛ) ፡ ስብሰባ ፡ አዘጋጀን
*A hermit is not a social person. ባሕታዊ ፡ ከሰው ፡ ተቀላቅሎ ፡ መኖር ፡ አይወድም

**of high social position** ትልቅ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሰው
She wants her daughter to marry a man of high social position. ልጇን ፡ ትልቅ ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ ለመዳር ፡ ትፈልጋለች

**socialize** የመንግሥት ፡ ሀብት ፡ አደረገ
The government socialized the railroads. መንግሥት ፡ የባቡሩን ፡ መሥመር ፡ የመንግሥት ፡ ሀብት ፡ አደረገ

**socialize with** ተጠጋ
He does not socialize with strangers. የማያውቀውን ፡ ሰው ፡ አይጠጋም

**socialism** ሶሺያሊዝም
Socialism is a form of government. ሶሺያሊዝም ፡ የአገዛዝ ፡ ዓይነት ፡ ነው

**social security** የጡረታ ፡ አበል
We need social security for the workers. ለሠራተኞቹ ፡ የጡረታ ፡ አበል ፡ ያስፈልገናል

**social studies** ኅብረ ፡ ትምህርት
All his courses are in the social studies. ትምህርቶቹ ፡ ሁሉ ፡ በኅብረ ፡ ትምህርት ፡ ውስጥ ፡ ናቸው

**social welfare** የሕዝብ ፡ በጎ ፡ አድራጎት
The government should promote social welfare organizations. መንግሥቱ ፡ የሕዝብ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቶችን ፡ ማበረታታት ፡ ይገባዋል

**social work agency** የማኅበራዊ ፡ ሥራ ፡ ድርጅት
The government organized a social work agency. መንግሥት ፡ የማኅበራዊ ፡ ሥራ ፡ ድርጅት ፡ አቋቋመ

**society** (societies), n.
1. ማኅበር. The society was founded ten years ago. ማኅበሩ ፡ የተመሠረተው ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ነው
2. ኅብረተ ፡ ሰብ. American society has undergone many changes. የአሜሪካን ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ብዙ ፡ ተለውጧል
War is a danger to society. ጦርነት ፡ ለኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ጠንቅ ፡ ነው
3. ከርሱ ፡ ጋር ፡ መዋል. I enjoy their society. ከነሱ ፡ ጋር ፡ መዋል ፡ ደስ ፡ ይለኛል
**in society** በሰው ፡ መኻል
He doesn't feel at ease in society. በሰው ፡ መኻል ፡ እንደልቡ ፡ አይሆንም

**society** (adj.) የትልቅ ፡ ቤተ ፡ ሰብ
The society wedding was in all the papers. የትልቁ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ሰርግ ፡ በየጋዜጣው ፡ ሁሉ ፡ ወጥቶ ፡ ነበር

**sociology** ሶሲዮሎጂ
I am taking sociology this semester. በዚህ ፡ ሴመስተር ፡ ሶሲዮሎጂ ፡ እማራለሁ

**sock** (n.) የእግር ፡ ሹራብ
I want three pairs of socks. ሦስት ፡ ጥንድ ፡ የእግር ፡ ሹራብ ፡ እፈልጋለሁ

**socket** መሰኪያ
Plug the lamp into the socket! መብራቱን ፡ መሰኪያው ፡ ውስጥ ፡ ሰካው

**sod,** n. [ተደድቆ ፡ የሚመጣ ፡ አፈር]

**(be) sodden**
1. በሰበሰ. My clothes were sodden with rain. ልብሴ ፡ በዝናቡ ፡ በስብሶ ፡ ነበር
2. ቃ ፡ አላለም. This bread is sodden, and I will not eat it. ዳቦው ፡ ቃ ፡ ስላላለ ፡ አልበላውም

**sofa** ሶፋ
Lie down on the sofa! ሶፋው ፡ ላይ ፡ ጋደም ፡ በል

**soft**
1. ልል. Is the ground soft? መሬቱ ፡ ልል ፡ ነው ?
2. ለስላሳ. This cushion is very soft. ይህ ፡ ትራስ ፡ በጣም ፡ ለስላሳ ፡ ነው
A soft answer turns away wrath. ለስላሳ ፡ ምላስ ፡ ቁጣን ፡ ታበርዳለች
3. ለስለስ ፡ ያለ. She sang in a soft voice. ለስለስ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ዘመረች
4. ቀዝቀዝ ፡ ያለ. A soft breeze was blowing. ቀዝቀዝ ፡ ያለ ፡ ነፋስ ፡ ይነፍስ ፡ ነበር

5. የማያደክም. He has a soft job. የማያደክም ፡ ሥራ ፡ አለው
6. ደብዛዛ. The lamp shed a soft light. የፋኖሱ ፡ ብርሃን ፡ ደብዛዛ ፡ ነው
7. ደብዘዝ ፡ ያለ. The coat is a soft gray. ኮቱ ፡ ደብዘዝ ፡ ያለ ፡ ግራጫ ፡ ነው

**be soft** ቀዝቀዝ ፡ አለ
The air is soft today. አየሩ ፡ ዛሬ ፡ ቀዝቀዝ ፡ ብሏል
*He is soft in dealing with workers. ለሠራተኛ ፡ ይመቻል

**be (get) too soft**
1. ሰውነቱ ፡ ጨርቅ ፡ (ልል) ፡ ነው. He is too soft from lack of exercise. ጅምናስቲክ ፡ ስለማይሠራ ፡ ሰውነቱ ፡ ጨርቅ ፡ (ልል) ፡ ነው
2. እንደ ፡ መቅለጥ ፡ አለ. The butter got too soft. ቅቤው ፡ እንደ ፡ መቅለጥ ፡ ብሏል

**have a soft heart** ርኅሩኅ ፡ ሆነ
She has a soft heart and cries when she sees a hungry man. ርኅሩኅ ፡ ስለሆነች ፡ የራበው ፡ ሰው ፡ ስታይ ፡ እንባ ፡ ይቀድማታል

**make soft** ዝቅ ፡ አደረገ
Our radio has an adjustment so that we can make the tone loud or soft. የራዲዮናችንን ፡ ድምፅ ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ የምናደርግበት ፡ ማስተካከያ ፡ አለው

## soft-boiled እሳት ፡ ያልገባው ፡ ቅቅል
He likes soft-boiled eggs. እሳት ፡ ያልገባው ፡ ቅቅል ፡ እንቁላል ፡ ይወዳል

## soft drinks ለስላሳ ፡ መጠጥ
He likes soft drinks, but I like hard liquor. እርሱ ፡ ለስላሳ ፡ መጠጥ ፡ ይወዳል ፤ እኔ ፡ ግን ፡ አልኮል ፡ ያለው ፡ መጠጥ ፡ እወዳለሁ

## soften
1. አለሰለሰ. The rain softened the soil. ዝናቡ ፡ መሬቱን ፡ አለስልሶታል
He softened the hide by soaking it in water. ቆዳውን ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ዘፍዝፎ ፡ አለሰለሰው
2. ለስለስ ፡ አደረገ. He softened his criticism of his rival's character. ስለ ፡ ተወዳዳሪው ፡ ጠባይ ፡ ያለውን ፡ ነቀፌታ ፡ ለስለስ ፡ አደረገው
3. አላላ. The judge softened the punishment. ዳኛው ፡ ቅጣቱን ፡ አላላው
4. አራራ. A shower of tears softened the judge's heart. የእንባዋ ፡ መጕረፍ ፡ የዳኛውን ፡ ልብ ፡ አራራው
5. ቀነሰ. The shutters softened the light. መጋረጃዎቹ ፡ ብርሃኑን ፡ ቀነሱት

**soften (the) heart** አራራ
Her tears softened his heart. እንባዋ ፡ አራራው

**soften (one's) tone** ለስለስ ፡ አድርጎ ፡ ተናገረ
When she realized how upset the child was, she softened her tone. ልጁ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደተበሳጨ ፡ በተረዳች ፡ ጊዜ ፡ ለስለስ ፡ አድርጋ ፡ ተናገረች

## soft-hearted ርኅሩኅ
She is so soft-hearted that she cries at almost anything. በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ ስለሆነች ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ባየች ፡ ቁጥር ፡ ታለቅሳለች

## softly ቀስ ፡ ብሎ ፤ በቀስታ
She speaks softly. ቀስ ፡ ብላ ፡ ትናገራለች
She walks softly so as not to waken the child. ልጁ ፡ እንዳይነቃ ፡ ቀስ ፡ ብላ ፡ ትራመዳለች
The crowd chanted softly. ሕዝቡ ፡ በቀስታ ፡ ዘመረ

## (be) soft-spoken
*He may be soft-spoken, but he is tough-minded. ሲናገር ፡ ልስልስ ፡ ይመስላል ፡ ግን ፡ ጥብቅ ፡ ሰው ፡ ነው

## (be) soggy
1. በሰበሰ. The paper was soggy because someone had spilled water on it. ሰው ፡ ውኃ ፡ አፍስሶበት ፡ ስለነበረ ፡ ወረቀቱ ፡ በስብሷል
2. ራሰ. My clothes were soggy from the rain. ልብሶቼ ፡ በዝናብ ፡ ርሰዋል
3. ጨቀየ. The ground is soggy after such a heavy rain. ኀይለኛ ፡ ዝናብ ፡ ስለጣለ ፡ መሬቱ ፡ ጨቅይቷል

## soil (vt.)
1. አቆሸሸ. You soiled your suit. ልብስህን ፡ አቆሽሸኸዋል
2. አጐደፈ. His actions have soiled the family name. አድራጎቱ ፡ የቤተ ፡ ሰቡን ፡ ስም ፡ አጐደፈ

**soil** (vi.)
*This cloth soils easily. ይህ ፡ ጨርቅ ፡ እድፍ ፡ አይችልም

## soil (n.)
1. አፈር. The soil here is very fertile. እዚህ ፡ አፈሩ ፡ በጣም ፡ ለም ፡ ነው
2. መሬት. A farmer tills the soil. ገበሬ ፡ መሬት ፡ ያርሳል
3. አገር. This is my native soil. ይህ ፡ የትውልድ ፡ አገሬ ፡ ነው
[See also 'virgin']

**sojourn** (v.) ተቀመጠ
He sojourned in Ethiopia for a time. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተቀመጠ

**sojourn** (n.) መቆየት
A brief sojourn in Ethiopia is not long enough to learn Amharic. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አጭር ፡ ጊዜ ፡ መቆየት ፡ አማርኛ ፡ ለመማር ፡ አይበቃም
*A sojourn in the desert made him quite sunburned. በረኻ ፡ ስለሰነበተ ፡ ፊቱ ፡ በፀሐይ ፡ ተቃጥሏል

**solace** (v.) ረዳ
The organization solaced the distress of the flood victims. ድርጅቱ ፡ በጐርፉ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ረዳ

**solace oneself** ራሱን ፡ አጽናና
He solaced himself with reading the Bible. መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ በማንበብ ፡ ራሱን ፡ አጽናና

**solace** (n.), **find ~** ተጽናና
The invalid finds solace in music. አካለ ፡ ስንኩሉ ፡ ሰው ፡ በሙዚቃ ፡ ይጽናናል

**give solace** አጽናና
Music gives solace to the invalid. አካለ ፡ ስንኩልን ፡ የሚያጽናና ፡ ሙዚቃ ፡ ነው

**solar** የፀሐይ
The solar system consists of the sun and nine planets. በፀሐይ ፡ ክበብ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ፀሐይና ፡ ዘጠኙ ፡ ዓለማት ፡ ናቸው

**solar year** የዐውደ ፡ ፀሐይ ፡ ዓመት
The solar year is 365 days. የዐውደ ፡ ፀሐይ ፡ ዓመት ፡ ፫፻፷፭ ቀን ፡ ነው

**sold,** see **sell**

**solder** በየደ
He will solder the broken iron post tomorrow. ሰውዬው ፡ የተሰበረውን ፡ የብረት ፡ ምሰሶ ፡ ነገ ፡ ይበይዳል

**soldier** ወታደር
The soldier was killed in action. ወታደሩ ፡ ጦር ፡ ሜዳ ፡ ወደቀ

**sole** (v.) ሶል ፡ አገባ
The shoemaker soled my shoes. ጫማ ፡ ሰፊው ፡ ለጫማዬ ፡ ሶል ፡ አገባልኝ

**sole** (n.)
1. ውስጥ ፡ እግር. I have a blister on my sole. ውስጥ ፡ እግሬ ፡ ውኃ ፡ ቋጥሯል
2. ሶል. There is a hole in the sole of my shoe. የጫማዬ ፡ ሶል ፡ ተበስቷል

**sole,** adj. (= adv.) ብቻ
He was the sole survivor of the accident. ከአደጋው ፡ የተረፈው ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ነው
*The sole cause of the accident was liquor. ያደጋው ፡ ምክንያት ፡ መጠጥ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አልነበረም

**for the sole purpose**
*He came here for the sole purpose of meeting you. እዚህ ፡ የመጣው ፡ አንተን ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ ብቻ ፡ ነው

**solely** ብቻ
We drive solely for pleasure. በመኪና ፡ የምንሄደው ፡ ለመዝናናት ፡ ብቻ ፡ ነው
He is solely responsible for it. ለሆነው ፡ ነገር ፡ ኀላፊው ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው

**solemn**
1. ክበድ ፡ ያለ. The minister spoke in a solemn voice. ሚኒስትሩ ፡ ክበድ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ተናገረ
2. ረጋ ፡ ያለ. The judge has a solemn aspect. ዳኛው ፡ ረጋ ፡ ያለ ፡ መልክ ፡ አለው
3. ሞገስ ፡ ያለው. The solemn festivals of the church were gratifying. የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሞገስ ፡ ያለው ፡ ሥርዐተ ፡ ቅዳሴ ፡ መንፈስን ፡ የሚያረካ ፡ ነበር

**have a solemn face**
1. ፊቱ ፡ ጠቈረ. The mourners had solemn faces. ሐዘንተኞቹ ፡ ፊታቸው ፡ ጠቍሮ ፡ ነበር
2. ፊቱ ፡ ኮስተር ፡ አለ. The judge had a solemn face. የዳኛው ፡ ፊት ፡ ኮስተር ፡ ብሎ ፡ ነበር

**give a solemn promise** ማለ(ለት)
He gave me his solemn promise that he would come. እመጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ማለልኝ

**solemnity** (solemnities)
1. ጸጥ ፡ ያለ ፡ መሆን. The solemnity of the funeral march was felt even by the children. የቀብሩ ፡ ጉዞ ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ በመሆኑ ፡ ልጆቹን ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ ተሰማቸው
2. ታላቅ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት. Epiphany is observed with solemnities. ጥምቀት ፡ በታላቅ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይከበራል

**solicit**
1. ጠየቀ. He is soliciting funds for a new building. ላዲስ ፡ ሕንጻ ፡ ማሠሪያ ፡ መዋጮ ፡ በመጠየቅ ፡ ላይ ፡ ነው
2. አባበለ. To solicit a judge means to offer him bribes. ዳኛን ፡ ማባበል ፡ ማለት ፡ ጉቦ ፡ መስጠት ፡ ማለት ፡ ነው

**solicitor** ጠበቃ
I must speak to my solicitor about that.

ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ከጠበቃዬ ፡ ጋር ፡ መነጋገር ፡ አለብኝ

**(be) solicitous** ተጨነቀ
Mother is solicitous about your safety. እናቴ ፡ ስላንተ ፡ ደኅንነት ፡ ትጨነቃለች

**solid** (n.) ጥጥር
Chemistry studies the action of solids and liquids. ኬሚስትሪ ፡ የጥጥሮችንና ፡ የፈሳሾችን ፡ ጠባይ ፡ ይመረምራል

**solid** (adj.)
1. ጥጥር. Chemistry teaches us about solid and liquid bodies. ኬሚስትሪ ፡ ስለ ፡ ጥጥርና ፡ ፈሳሽ ፡ አካሎች ፡ ያስተምረናል
Don't feed babies solid food! ሕፃናትን ፡ ጥጥር ፡ ምግብ ፡ አታብሏቸው
2. ጠንካራ. This chair doesn't seem very solid to me. ይህ ፡ ወንበር ፡ በጣም ፡ ጠንካራ ፡ አይመስለኝም
He is a man of solid character. መንፈሰ ፡ ጠንካራ ፡ ሰው ፡ ነው
The ground is not solid enough to build on. መሬቱ ፡ በጣም ፡ ጠንካራ ፡ ስላልሆነ ፡ ቤት ፡ ለመሥሪያ ፡ አይሆንም
3. ድፍን. The statue is made of solid gold. ሐውልቱ ፡ ከድፍን ፡ ወርቅ ፡ የተሠራ ፡ ነው
A bar of iron is solid. የብረቱ ፡ ቁራጭ ፡ ድፍን ፡ ነው
The cloth is solid blue. ልብሱ ፡ ድፍን ፡ ሰማያዊ ፡ ነው
4. ሙሉ. He talked to me for a solid hour. አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ አወራኝ
The President has the solid support of the Congress. ፕሬዚዳንቱ ፡ የአማካሪዎች ፡ ሙሉ ፡ ድጋፍ ፡ አለው
5. የሚታመንበት. He is a solid citizen. የሚታመንበት ፡ ዜጋ ፡ ነው

**solid state** በረዶነት
Water passes to a solid state when it freezes. ውኃ ፡ ሲረጋ ፡ ወደ ፡ በረዶነት ፡ ይለወጣል

**be frozen solid** በረዶ ፡ ሆነ
The lake is frozen solid. ሐይቁ ፡ በረዶ ፡ ሆኗል

**be solid** ጽኑ ፡ አንድነት ፡ አለው
The country was solid for peace. አገሪቱ ፡ ለሰላም ፡ ጽኑ ፡ አንድነት ፡ አላት

**solidarity** መተባበር ፤ አንድነት
African solidarity is necessary in present circumstances. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያፍሪካውያን ፡ መተባበር ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
The conference called for solidarity between the two nations. ጉባኤው ፡ በሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ አንድነት ፡ እንዲመሠረት ፡ ጠየቀ

**solidify** (solidified), vt.
1. ወደ ፡ በረዶ ፡ ለወጠ. Cold solidifies water. ቅዝቃዜ ፡ ውኃን ፡ ወደ ፡ በረዶ ፡ ይለውጣል
2. አጠነከረ. The agglutination of asphalt and gravel solidifies the highway. የሬንጅና ፡ የጠጠር ፡ መዋሐድ ፡ ጐዳናውን ፡ ያጠነክረዋል

**solidify** (vi.)
1. ረጋ. Butter solidifies as it cools. ቅቤ ፡ ሲቀዘቅዝ ፡ ይረጋል
2. ደረጀ. Their friendship solidifies yearly. ጓደኝነታቸው ፡ በያመቱ ፡ ይደረጃል

**solidity** (= adj.) የጠበቀ
The solidity of their friendship suffered a blow. የጠበቀ ፡ ወዳጅነታቸው ፡ ፈረሰ

**soliloquy** ለራሱ ፡ የሚናገረው
Do you know Hamlet's soliloquy "To be or not to be?" መኖር ፡ ወይም ፡ አለመኖር ፡ ብሎ ፡ ሀምሌት ፡ ለራሱ ፡ የሚናገረውን ፡ ታውቃለህ?

**solitary**
1. የብቸኝነት. A monk leads a solitary life. መነኵሴ ፡ የብቸኝነት ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል
2. ብቸኛ ፡ የሆነ. I spent last summer in a solitary village. ያለፈውን ፡ በጋ ፡ ብቸኛ ፡ በሆነች ፡ መንደር ፡ አሳለፍኩ
3. ብቸኛ. He was a solitary, unworldly man. ብቸኛና ፡ ዓለም ፡ የናቀ ፡ ሰው ፡ ነበር
4. ጭር ፡ ያለ. The house is in a solitary spot miles from a town. ቤቱ ፡ ከከተማ ፡ ለብዙ ፡ ማይል ፡ ርቆ ፡ ጭር ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ ነው
5. (= adv.) ብቻውን. A solitary rider was seen in the distance. ከሩቅ ፡ አንድ ፡ ፈረሰኛ ፡ ብቻውን ፡ ይታይ ፡ ነበር
A solitary tree grows on the mountaintop. አንድ ፡ ዛፍ ፡ ብቻውን ፡ ተራራው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ በቅሏል
[See also 'confinement']

**solitude**
1. ጭር ፡ ማለት. The solitude of this place got on his nerves. የቦታው ፡ ጭር ፡ ማለት ፡ አስጨነቀው
2. ብቸኛ ፡ መሆን. He likes company and hates solitude. ብቸኛ ፡ መሆን ፡ አይወድም ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ እንጂ
3. (= adj.) ጭር ፡ ያለ. In the solitude of the desert, one feels very much alone. ጭር ፡ ባለ ፡ በረኻ ፡ ውስጥ ፡ ሲሄዱ ፡ ብቸኝነት ፡ ይሰማል

**solo**, n. [አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ የሚዘፍነው ፡ የ ሙዚቃ ፡ ክፍል]

**solo**, adj. (= adv.) ብቻውን
He made a solo flight today. ዛሬ ፡ ብቻውን ፡ በረረ

**soluble** መልስ ፡ ሊያገኝለት ፡ የሚችል
The soluble problems are marked with a star. መልስ ፡ ሊያገኝላቸው ፡ የሚችሉት ፡ ጥያቄዎች ፡ የኮከብ ፡ ምልክት ፡ ተደርጎባቸዋል

**be soluble** ሟሟ
Sugar is soluble in water. ስኳር ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ይሟሟል

**solution**
1. መሟሟት. The solution of salt in water produces ions. የጨው ፡ በውኃ ፡ ውስጥ ፡ መሟሟት ፡ አዮን ፡ ያስገኛል
2. መፍትሔ. There is no solution to the education problem. ለትምህርት ፡ ችግር ፡ መፍትሔ ፡ አይገኝለትም
3. መሥራት. The solution of the problem took him many hours. ሒሳቡን ፡ መሥራት ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ወሰደበት

**solve**
1. ፈታ. I can't solve the riddle. እንቆቅልሹን ፡ ልፈታው ፡ አልችልም
2. ሠራ. A mathematician is needed to solve this problem. ይህንን ፡ ፕሮብሌም ፡ ለመሥራት ፡ ሒሳብ ፡ ዐዋቂ ፡ ያስፈልጋል
3. መፍትሔ ፡ አገኘ. They shelved the problem instead of solving it. ለነገሩ ፡ መፍትሔ ፡ እንደማግኘት ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ አሉት
4. ተረዳ. The footprints were a lead in solving the crime. የእግር ፡ ዱካዎች ፡ የወንጀሉን ፡ ሁኔታ ፡ ለመረዳት ፡ ፍንጭ ፡ ሆኑ

**solvent** (n.) ማሟሙያ
A solvent is needed to remove these grease spots. እነዚህን ፡ የቅባት ፡ ነጠብጣቦች ፡ ለማስለቀቅ ፡ ማሟሙያ ፡ ያስፈልጋል

**solvent** (adj.), **be ~** ዕዳውን ፡ ሊከፍል ፡ ቻለ
A bankrupt firm is not solvent. የከሰረ ፡ ድርጅት ፡ ዕዳውን ፡ ሊከፍል ፡ አይችልም

**somber** ጭልምልም ፡ ያለ
A cloudy winter day is somber. በክረምት ፡ ቀኑ ፡ ደመናማና ፡ ጭልምልም ፡ ያለ ፡ ነው

**be somber** ከበደ
It is a somber room with dark furniture. የቤት ፡ እቃው ፡ ጠቈርቈር ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ ክፍሉ ፡ ይከብዳል

**make (one) somber** ትካዜ ፡ ላይ ፡ ጣለ
His losses made him somber. ኪሳራው ፡ ትካዜ ፡ ላይ ፡ ጣለው

**wear a somber expression** ኮስተር ፡ አለ
The judge wore a somber expression when he condemned the criminal. ዳኛው ፡ በወንጀለኛው ፡ ላይ ፡ ሲፈርድ ፡ ኮስተር ፡ ብሎ ፡ ነበር

**sombre**, see **somber**

**some** (pr.) አንዳንድ ፡ ነገር
I agree with some of what you say. አንተ ፡ በምትለው ፡ ባንዳንዱ ፡ ነገር ፡ እስማማለሁ

**some** (adj.)
1. አንድ. Some man is at the door asking to see you. ሊያነጋግርህ ፡ የሚፈልግ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሩ ፡ ላይ ፡ ቆሟል
2. አንዳንድ. Some people can't stand noise. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ጫጫታ ፡ አይወዱም
3. ጥቂት. His Beatitude, Abuna Kerellos, died some years ago. ብጹዕ ፡ አቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ አረፉ
4. ትንሽ. He lent me some money. ትንሽ ፡ ገንዘብ ፡ አበደረኝ
Drink some milk! ትንሽ ፡ ወተት ፡ ጠጣ
5. በርከት ፡ ያለ. That will require some time. በርከት ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ይጠይቃል
6. (= pron.) አንዳንዱ. All work is not dull, some work is pleasant. ሁሉም ፡ ሥራ ፡ አይሰለችም ፤ አንዳንዱ ፡ ደስ ፡ ይላል
7. (= adv.) ያህል. We stayed some two or three hours. ሁለት ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ቆየን
8. (zero). Give me some matches. ክብሪት ፡ ስጠኝ

**some of**
1. ግማሾች + (suffix pronouns). Some of us are going by train and some by boat. ግማሾቻችን ፡ በባቡር ፡ ግማሾቻችን ፡ ደግሞ ፡ በጀልባ ፡ እንሄዳለን
2. አንዳንዶቹ. Some of them dropped from exhaustion. አንዳንዶቹ ፡ ደክመው ፡ ወደቁ
I saw some of the children. አንዳንዶቹን ፡ ልጆች ፡ አየሁ

**(be) some distance** ትንሽ ፡ ራቅ ፡ አለ
The railway station is some distance from the village. ባቡር ፡ ጣቢያው ፡ ከመንደሩ ፡ ትንሽ ፡ ራቅ ፡ ይላል

**some more**
*Give me some more. ትንሽ ፡ ጨምርልኝ

**some - - - or other**
*It is in some book or other on that shelf.

እዚያ ፡ መደርደሪያ ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ መጽሐፎች ፡ አንዱ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**some sort of** አንድ ፡ ዓይነት

The girl wore some sort of decoration on her dress. ልጃገረዲቱ ፡ በቀሚሷ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ጌጥ ፡ አድርጋለች

**some time ago**

1. ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት. He was here some time ago, but never came back. ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ እዚህ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ተመልሶ ፡ አልመጣም

2. ከ + perfect + ቆየ. He came here some time ago. ከመጣ ፡ ቆይቷል

**for some time** ላጭር ፡ ጊዜ ፤ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያህል

I shall be away for some time. ላጭር ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ እሄዳለሁ

The theft was not discovered for some time. ስርቆቱ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ አልታወቀም ፡ ነበር

[See also 'such']

## somebody አንድ ፡ ሰው

Somebody asked for you. አንድ ፡ ሰው ፡ ፈልጎህ ፡ ነበር

*He acts as if he were somebody since he won the prize. ሽልማቱን ፡ ካገኘ ፡ ወዲህ ፡ ኩራት ፡ ተሰምቶታል

## someday አንድ ፡ ቀን

You'll regret that someday. አንድ ፡ ቀን ፡ በዚያ ፡ ነገር ፡ ሳትጸጸት ፡ አትቀርም

## somehow

1. እንደምንም. The cattle got out of the pen somehow. ከብቶቹ ፡ ከበረታቸው ፡ እንደምንም ፡ ወጡ

2. ባልታወቀ ፡ መንገድ. The letter got lost somehow. ባልታወቀ ፡ መንገድ ፡ ደብዳቤው ፡ ጠፋ

3. ለምን ፡ እንደሆነ ፡ እንጃ. I somehow don't like the candidate. ለምን ፡ እንደሆነ ፡ እንጃ ፡ ተወዳዳሪውን ፡ አልወደውም

[See also 'other']

## someone

1. አንድ ፡ ሰው ፤ አንድ. Someone came to see you. አንድ ፡ ሰው ፡ (አንድ) ፡ ሊያይህ ፡ መጥቶ ፡ ነበር

2. ሰው. Call someone! ሰው ፡ ጥራ

3. (zero). Is there someone here who can play the piano? ፒያኖ ፡ መጫወት ፡ የሚችል ፡ አለ ?

[See also 'else, other']

## someplace

1. አንድ ፡ ቦታ. I've seen you someplace before. ከዚህ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ ተገናኝተናል

2. አንዱ ፡ ጋ. He's living someplace in Los Angeles. ሎስ ፡ አንጀለስ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ጋ ፡ ይኖራል

## somersault [መሬት ፡ ሳይነኩ ፡ መገለባበጥ]

## something

1. አንድ ፡ ነገር. I am sure I have forgotten something. እርግጠኛ ፡ ነኝ ፤ አንድ ፡ ነገር ፡ ረስቻለሁ

Give him something! አንድ ፡ ነገር ፡ ስጠው

2. ነገር. Give me something for my cold! ጉንፋኔን ፡ የሚያሽልልኝ ፡ ነገር ፡ ስጠኝ

3. ምናምን. Do you want something to drink with your meals? ከምግብህ ፡ ጋር ፡ ምናምን ፡ ለመጠጣት ፡ ትፈልጋለህ ?

4. አንድ ፡ ዓይነት. There is something strange about that house. ይህ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ አለበት

5. አንድ ፡ ፍሬ ፡ ነገር. There is something in what he says. በተናገረው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ አለበት

6. በመጠኑ. He knows something about medicine. ስለ ፡ ሕክምና ፡ በመጠኑ ፡ ያውቃል

7. ትንሽ ፡ ትንሽ. He looks something like me. ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ እኔን ፡ ይመስላል

**something like** ያህል

He left something like $10,000. ዐሥር ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ያህል ፡ ትቶ ፡ ሞተ

**something of** በመጠኑ

He is something of an expert in that field. በዚያ ፡ ሥራ ፡ በመጠኑ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው

**something or other**

1. አንዳንድ ፡ ነገሮች. Something or other reminded me of him. አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ እሱን ፡ አስታወሱኝ

2. ምናምን. Give him something or other! ምናምን ፡ ስጠው

**it's something** ትንሽ ፡ አይደለም

It's something to own property. ባለ ፡ መሬት ፡ መሆን ፡ ትንሽ ፡ አይደለም

**or something like that**

*He's a professor or something like that. የዩኒቨርሲቲ ፡ መምህር ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም

## sometime (adv.)

1. አንድ ፡ ጊዜ. I saw him sometime in May. አንድ ፡ ጊዜ ፡ በግንቦት ፡ ውስጥ ፡ አይቼው ፡ ነበር

Why don't you come to my office sometime? ለምን ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ወደ ፣ ቢሮዬ ፣ ብቅ ፣ አትልም ?
2. አንዱን ፣ ቀን. She'll be here sometime this week. በዚህ ፣ ሳምንት ፣ ውስጥ ፣ አንዱን ፣ ቀን ፣ ትመጣለች
*The trains stopped running sometime last year. ባለፈው ፣ ዓመት ፣ ውስጥ ፣ ባቡሩ ፣ መሄዝ ፣ አቆመ
*It happened sometime last March. ነገሩ ፣ የሆነው ፣ ባለፈው ፣ መጋቢት ፣ ውስጥ ፣ ነው

**sometime,** adj. (= adv.) ድሮ
He is a sometime pupil of our school. እሱ ፣ ድሮ ፣ የትምህርት ፣ ቤታችን ፣ ተማሪ ፣ ነበር

**sometimes** አንዳንድ ፣ ጊዜ ፤ አንዳንዴ
Sometimes it gets very hot here. አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ እዚህ ፣ በጣም ፣ ይሞቃል
Sometimes I wake up in the middle of the night. አንዳንዴ ፣ እኩለ ፣ ሌሊት ፣ ላይ ፣ እነቃለሁ

**sometimes ... sometimes** አንዴ --- አንዴ ፣ ደግሞ
She likes sometimes the one and sometimes the other. አንዴ ፣ አንዱን ፣ አንዴ ፣ ደግሞ ፣ ሌላውን ፣ ትወዳለች

**somewhat**
1. ትንሽ. My hat is somewhat like yours. ባርኔጣዬ ፣ ትንሽ ፣ ያንተን ፣ ይመስላል
2. (reduplicative). I feel somewhat tired. ተጫጭኖኛል
*We arrived somewhat late, I'm afraid. ዘግይተን ፣ ሳንደርስ ፣ አልቀረንም
*I was somewhat surprised to hear that. ያንን ፣ በመስማቴ ፣ ሳልገረም ፣ አልቀረሁም

**somewhat of**
*It was somewhat of a surprise to see him. እሱን ፣ ማግኘት ፣ የሚያስገርም ፣ ነገር ፣ ነበር

**somewhere**
1. አንዱ ፣ ጋ. He lost it somewhere between here and the post office. በዚህና ፣ በፖስታ ፣ ቤቱ ፣ መካከል ፣ አንዱ ፣ ጋ ፣ ነው ፣ የጣለው
2. አንድ ፣ ቦታ. I saw it somewhere, but I don't remember where. አንድ ፣ ቦታ ፣ አይቼዋለሁ ፤ የት ፣ እንደሆነ ፣ ግን ፣ ትዝ ፣ አይለኝም
*It happened somewhere in the last century. ባለፈው ፣ ዘመን ፣ ውስጥ ፣ ተደረገ

**somewhere about** ገደማ
My teacher is somewhere about forty. መምህሬ ፣ አርባ ፣ ዓመት ፣ ገደማ ፣ ናቸው

**somewhere else** ሌላ ፣ ጋ
Let's meet somewhere else! ሌላ ፣ ጋ ፣ እንገናኝ
[See also 'along, around, thereabouts']

**somnolent**
*He has a somnolent expression. የሚያንቀላፋ ፣ ይመስላል

**feel somnolent** እንቅልፍ ፣ እንቅልፍ ፣ አለ(ው)
Heavy meals make me feel somnolent. ከባድ ፣ ምግብ ፣ ስበላ ፣ እንቅልፍ ፣ እንቅልፍ ፣ ይለኛል

**son** ወንድ ፣ ልጅ
How many sons does he have? ስንት ፣ ወንዶች ፣ ልጆች ፣ አሉት ?

**song**
1. ዜማ. He knows the songs of the church. የቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ዜማዎች ፣ ያውቃል
2. ዘፈን. He sings only American songs. የሚዘፍነው ፣ የአሜሪካንን ፣ ዘፈን ፣ ብቻ ፣ ነው
3. ጩኸት. In the evening, you can hear the crickets' song. ማታ ፣ ማታ ፣ የፌንጣ ፣ ጩኸት ፣ ልትሰማ ፣ ትችላለህ

**for a song** የንጥቂያ ፣ ያህል
He bought the chair for a song. ወንበሩን ፣ የገዛው ፣ የንጥቂያ ፣ ያህል ፣ ነው

**songbird** የምትዘፍን ፣ ወፍ
He keeps a songbird in a cage. የምትዘፍን ፣ ወፍ ፣ ያሳድጋል

**son-in-law** አማች
My son-in-law left for America last month. አማቼ ፣ ባለፈው ፣ ወር ፣ ወደ ፣ አሜሪካ ፣ ሄደ

**Song of Songs** መኀልየ ፣ መኀልያን
He translated the Song of Songs into Amharic. መኀልየ ፣ መኀልያንን ፣ ወደ ፣ አማርኛ ፣ ተረጐመ

**sonorous**
1. ወፈር ፣ ያለ. The speaker has a sonorous voice. ተናጋሪው ፣ ወፈር ፣ ያለ ፣ ድምፅ ፣ አለው
2. የሚጮኽ. A sonorous church bell sounds the hours. የሚጮኸው ፣ የቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ደወል ፣ ሰዓቱን ፣ ያመለክታል

**soon**
1. ቶሎ. If you don't do it soon, it will be too late. ቶሎ ፣ ካልሠራኸው ፣ ጊዜው ፣ ያልፋል
2. በቅርቡ. We shall soon be having rain. በቅርቡ ፣ ዝናብ ፣ እናገኛለን
3. ቀድሞ. Why have you come so soon? ለምን ፣ እንደዚህ ፣ ቀድመህ ፣ መጣህ ?
*Come again soon! ብቅ ፣ እያልክ ፣ ጠይቀን

**soon after**
1. ወዲያውኑ. He came here in March, but left for Ethiopia soon after. በመጋቢት ፣ እዚህ ፣

መጥቶ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ወዲያውኑ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሄደ
2. ካለፈ. He came soon after three. ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ካለፈ ፡ መጣ

**soon be**
1. ተቃረበ. It will soon be time to leave. የመሄጃ ፡ ጊዜ ፡ ተቃርቧል
2. ሊሞላው ፡ ነው. It will soon be five years since we came to Addis Ababa. አዲስ ፡ አበባ ፡ ከመጣን ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሊሞላን ፡ ነው

**all too soon** ሳይታወቅ
Vacation ended all too soon. የዕረፍቱ ፡ ጊዜ ፡ ሳይታወቅ ፡ አለፈ

**as soon as** እንደ + perfect + ወዲያው
Let me know as soon as you get here. እዚህ ፡ እንደደረስክ ፡ ወዲያው ፡ አስታውቀኝ

**as soon ... as ...**
*The brave soldier would as soon die as yield to the enemy. ደፋር ፡ ወታደር ፡ እጁን ፡ ለጠላት ፡ ከመስጠት ፡ ይልቅ ፡ መሞትን ፡ ይመርጣል
*I would as soon go as stay. ከመቆየት ፡ መሄድ ፡ ይሻለኛል

**as soon as possible** እንደተመቸው
Come to see me as soon as possible! እንደተመቸህ ፡ መጥተህ ፡ እንገናኝ

**how soon?** ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ
How soon can you be ready? ለመዘጋጀት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይፈጅብሃል ?

**so soon**
*Must you leave so soon? ምነው ፡ ቸኰልክ ?

**too soon**
1. አሁን. It's too soon to tell what's the matter with him. ምን ፡ እንደነካው ፡ አሁን ፡ ለመናገር ፡ ያስቸግራል
2. ቸኩሎ. He came too soon. ቸኩሎ ፡ መጣ

**very soon** አሁን
He'll be here very soon. አሁን ፡ ይመጣል
[See also 'just']

## sooner ቀደም ፡ ብሎ

He'd better be here sooner than you are. ካንተ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ቢመጣ ፡ ይሻለዋል

**sooner or later**
1. የኋላ ፡ ኋላ. Sooner or later, this practice must disappear. የኋላ ፡ ኋላ ፡ ይህ ፡ ልማድ ፡ መቅረት ፡ አለበት
2. ግራም ፡ ነፈሰ ፡ ቀኝ. Sooner or later, we'll have to make up our minds. ግራም ፡ ነፈሰ ፡ ቀኝ ፡ ሐሳባችንን ፡ መቍረጥ ፡ አለብን
3. በምንም ፡ ዓይነት. It was bound to happen sooner or later. በምንም ፡ ዓይነት ፡ መሆኑ ፡ አይቀርም
4. ውሎ ፡ አድሮ. The situation in the country is bad, but it will come to a head sooner or later. ሀገሪቷ ፡ ያለችበት ፡ ሁኔታ ፡ መጥፎ ፡ ነው ፤ ውሎ ፡ አድሮ ፡ ያበጠው ፡ መፈንዳቱ ፡ አይቀርም

**sooner ... than**
*He'd sooner die than give in. ከሚሸነፍ ፡ ወዲያውኑ ፡ ቢሞት ፡ ይመርጣል

**no sooner ... than** ወዲያው ፡ እንደ + perfect
No sooner did we arrive than the telephone rang. ወዲያው ፡ እንደደረስን ፡ ስልኩ ፡ ተደወለ
*He had no sooner arrived home than he was asked to start on another trip. እቤቱ ፡ ከመግባቱ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ እንዲሄድ ፡ ተጠየቀ
*No sooner said than done. ካፉ ፡ ወጥቶ ፡ ሳያልቅ ፡ ትእዛዙን ፡ ፈጸመለት

**the sooner** ቶሎ
The sooner you come, the better. ቶሎ ፡ ብትመጣ ፡ የተሻለ ፡ ነው

## soot

1. ጥቀርሻ. The soot has blackened the ceiling. ጥቀርሻው ፡ ጣሪያውን ፡ አጥቍሮታል
2. ጥላሸት ፤ ጥላት. She scoured the pot to remove the soot. ጥላሸቱን ፡ ለማስለቀቅ ፡ ማሰሮውን ፡ ፈቀፈቀችው
Scrub the soot off the pot! ጥላቱን ፡ ከድስቱ ፡ ላይ ፡ ጥረገው

## soothe

1. አስታገሠ (ለት). The ointment soothed the itching. ቅባቱ ፡ የሚያሳክከውን ፡ አስታገሠለት
2. አረጋጋ. She soothed the frightened children by hugging them close to her. የደነገጡትን ፡ ልጆች ፡ አቅፋ ፡ በመያዝ ፡ አረጋጋቻቸው
3. አጽናና. John's sympathy soothed Mary in her grief. ሜሪ ፡ አዝና ፡ በነበረችበት ፡ ጊዜ ፡ የጆን ፡ ተካፋይነት ፡ አጽናናት

## soothing ያረካ

The babble of the stream was very soothing. የወንዙ ፡ ጉርምርምታ ፡ በጣም ፡ ያረካ ፡ ነበር
*She has a soothing voice. ድምጿ ፡ እርጋ ፡ ነው

**soothing lotion** ቀዝቀዝ ፡ የሚያደርግ ፡ መታሻ
She rubbed her skin with a soothing lotion. ገላዋን ፡ ቀዝቀዝ ፡ በሚያደርግ ፡ መታሻ ፡ አሸችው

## soothsayer ትንቢተኛ

The soothsayer foretold Caesar's death. ትንቢተኛው ፡ የቄሳርን ፡ ሞት ፡ ተነበየ

**(be) sooty** ጥላት ፡ ብቻ ፡ ሆነ
Her hands were sooty. እጇ ፡ ጥላት ፡ ብቻ ፡ ነበር

**sop** (sopped) አጥቅሶ ፡ በላ
The child sopped bread in milk. ልጁ ፡ ዳቦውን ፡ በወተት ፡ አጥቅሶ ፡ በላ

**sop up**
1. እያጠቀሰ ፡ በላ. He used bread to sop up the sauce. ዳቦውን ፡ ወጥ ፡ እያጠቀሰ ፡ በላ
2. አመጠጠ. Please sop up that water with a cloth! እስኪ ፡ ያንን ፡ ውኃ ፡ በጨርቅ ፡ አምጥጠው

**sophisticate** የተማረ
The young sophisticates banded together to form a club. የተማሩት ፡ ወጣቶች ፡ ክበብ ፡ ለማቋቋም ፡ ተሰበሰቡ

**sophomore** [በኮሌጅ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ተማሪ]

**soporific** የሚጫጫን
I can't stand this soporific climate. የሚጫጫነውን ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ አልወደውም

**sopping, be ~ wet**
He was sopping wet from the rain. ዝናቡ ፡ አበሰበሰው

**sorcerer** አስማተኛ
The sorcerer cast a spell on the young girl. አስማተኛው ፡ ልጅቷን ፡ በመተት ፡ አሰራት

**sorcery** አስማት
The merchant has been changed into a lion by sorcery. ነጋዴው ፡ በአስማት ፡ ወደ ፡ አንበሳነት ፡ ተለወጠ

**sordid**
1. ደሳሳ. The poor family lives in a sordid hut. ድኾቹ ፡ ቤተሰቦች ፡ በደሳሳ ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ
2. አስነዋሪ. The sordid quarrel of the two families was finally settled. የሁለቱ ፡ ቤተሰቦች ፡ አስነዋሪ ፡ ጠብ ፡ በመጨረሻው ፡ ተፈጸመ
3. ወራዳ. Prostitution is a sordid business. ሴተኛ ፡ አዳሪ ፡ ወራዳ ፡ ሥራ ፡ ነው

**sordid poverty**
They live in sordid poverty. በችግር ፡ ተቈራምደው ፡ ይኖራሉ

**sore** (n.) ቁስል
The sore is pretty well healed. ቁስሉ ፡ ጠገግ ፡ ብሏል

**be covered with sores** ቁስል ፡ ብቻ ፡ ነበር
The body was covered with sores. ገላው ፡ ሁሉ ፡ ቁስል ፡ ብቻ ፡ ነበር

**have a sore** ቈሰለ
+I have a sore on my palate. ላንቃዬ ፡ ቈስሏል

**sore** (adj.)
1. (= noun) ቁስል. A sore knee keeps me from kneeling. የጉልበቴ ፡ ቁስል ፡ እንዳልንበረከክ ፡ አድርጎኛል
2. የበሰበሰ. The wound looked sore and ugly. ቁስሉ ፡ የበሰበሰና ፡ የሚያስጋ ፡ መስሎ ፡ ይታይ ፡ ነበር
3. ከባድ. Your going away is a sore grief to us. መሄድህ ፡ ከባድ ፡ ሐዘን ፡ አሳደረብን
*He has a sore throat. ጉሮሮውን ፡ አሞታል
*Their defeat is a sore subject with the members of the team. የቡድኑ ፡ መሸነፍ ፡ ተጫዋቾቹን ፡ ቈርቊሯቸዋል

**be sore**
1. አመመ. Don't touch my arm! It's still sore. ክንዴን ፡ አትንካ ፤ አሁንም ፡ ያመኛል
2. ሰውነቱ ፡ ኀኰለ. He is sore because of all that exercise. ከሰውነት ፡ ማጠንከሪያው ፡ ልምምድ ፡ የተነሣ ፡ ሰውነቱ ፡ ኀኵሏል
3. ቅር ፡ አለ(ው). +He was sore that he hadn't been invited. ሳይጋበዝ ፡ በመቅረቱ ፡ ቅር ፡ ብሎት ፡ ነበር
4. በሐዘን ፡ ተነካ. Her heart was sore after the loss of her son. ከልጇ ፡ ሞት ፡ ወዲህ ፡ ልቧ ፡ በሐዘን ፡ እንደተነካ ፡ ነው

**be sore all over**
He is sore all over. መላ ፡ ሰውነቱ ፡ ኀኵሏል

**be sore with** ተቀየመ
Are you sore with me because I inadvertently told your secret? ሳላውቅ ፡ ምስጢርህን ፡ ስላወጣሁ ፡ ተቀየምከኝ ?

**get sore** ግልፍ ፡ አለ
You needn't get sore right away. ቶሎ ፡ ግልፍ ፡ አይበልህ

**(be) in sore need of** በጣም ፡ አስፈለገ(ው)
He was in sore need of help. እርዳታ ፡ በጣም ፡ አስፈልጎት ፡ ነበር

**make sore** አቈሰለ
Diarrhea made his anus sore. ተቅማጥ ፡ ፍንጢጣውን ፡ አቈሰለው

**make one's heart sore** በጣም ፡ አሳዘነ
The suffering of the poor makes her heart sore. የድኾች ፡ መሠቃየት ፡ በጣም ፡ ያሳዝናታል

**touch a sore spot**
*When you mention the battle of Adowa to an Italian, you touch a sore spot. የአድዋን ፡ ጦ

ርነት ፡ ለጣሊያን ፡ ተወላጅ ፡ ስታነሣበት ፡ ቁስ ሉን ፡ በዕንጨት ፡ እንደነካህበት ፡ ያህል ፡ ነው

**sorely** በጣም
The remark sorely hurt him. የተሰነዘረው ፡ አስተያየት ፡ በጣም ፡ አሳዝኖታል
I was sorely tempted to buy it. ልገዛው ፡ በጣም ፡ ጓጕቼ ፡ ነበር
[See also 'tempt, try']

**sorghum** ማሽላ
They grow sorghum in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ማሽላ ፡ ይበቅላል

**sorority** [የሴቶች ፡ ክበብ ፡ ወይም ፡ ማኅበር]

**sorrow** (v.) አዘነ
She sorrowed over the lost money. ስለጠፋው ፡ ገንዘብ ፡ አዘነች

**sorrow** (n.)
1. ሐዘን. She can't get over her sorrow. ሐዘኗን ፡ ልትረሳው ፡ አትችልም
2. አሳዛኝ. Bob's laziness was a sorrow to his parents. የቦብ ፡ ስንፍና ፡ ለወላጆቹ ፡ አሳዛኝ ፡ ነበር

**express sorrow** ተጸጸተ
She expressed sorrow at her mistake. በስሕተቷ ፡ ተጸጸተች

**pang of sorrow** ሐዘን
He felt a pang of sorrow on leaving his old home. የድሮ ፡ ቤቱን ፡ በመልቀቁ ፡ ሐዘን ፡ ተሰማው

**to my great sorrow** እግዚአብሔር ፡ ሲቈጣኝ
To my great sorrow, all my cattle were dead. እግዚአብሔር ፡ ሲቈጣኝ ፡ ከብቶቼ ፡ ሁሉ ፡ አለቁ

**sorrowful**
1. አሳዛኝ. Her sorrowful tale touched my heart. አሳዛኝ ፡ ታሪኳ ፡ ልቤን ፡ ነካው
A funeral is a sorrowful occasion. የቀብር ፡ ሥ ነ ፡ ሥርዓት ፡ አሳዛኝ ፡ ጊዜ ፡ ነው
2. ያዘነ. Sorrowful relatives followed the coffin. ያዘኑት ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ ሬሳውን ፡ ተከ ተሉት

**sorry** (adj.) የሚያሳዝን
The blind beggar in his ragged clothes was a sorry sight. ቡትቶ ፡ የለበሰው ፡ ዓይነ ፡ ስውሩ ፡ ለማኝ ፡ ሲያዩት ፡ የሚያሳዝን ፡ ነበር
It was a sorry day when our team lost. ቡድናች ን ፡ የተሸነፈበት ፡ ቀን ፡ የሚያሳዝን ፡ ቀን ፡ ነበር

**Sorry!** ይቅርታ
Sorry! Did I hurt you? ይቅርታ ፤ ጐዳሁህ ?

**be sorry** በጣም ፡ አዘነ ፤ አዘነ
I was sorry to part company with such a pleasant fellow. ከዚህ ፡ ደስ ፡ ከሚል ፡ ሰው ፡ ስ ለይ ፡ በጣም ፡ አዝኜ ፡ ነበር
I'm sorry to say that can't be so. ያ ፡ እንደዚህ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ ስል ፡ እያዘንኩ ፡ ነው
*If you'll say you are sorry, we'll forget the incident. አጥፍቻለሁ ፡ ካልክ ፡ ነገሩን ፡ እንረ ሳዋለን

**be sorry for** አዘነ(ለት)
I am sorry for her because her husband is a very cruel person. ባሏ ፡ ጨካኝ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ አዝንላታለሁ

**in a sorry state** ተበላሽቶ
He found his garden in a sorry state. ያትክል ቱን ፡ ቦታ ፡ ተበላሽቶ ፡ አገኘው

**sort** (v.)
1. ለያየ. They sorted the fruit according to size. ፍሬውን ፡ እንደየመጠኑ ፡ ለያዩት
2. ከፈለ. They sorted the class into three groups. ክፍሉን ፡ በሦስት ፡ ቡድን ፡ ከፈሉት
3. በየዓይነታቸው ፡ ለየ. The boy sorted the stamps. ልጁ ፡ ቴምብሮቹን ፡ በየዓይነታቸው ፡ ለየ

**sort out**
1. በየዓይነታቸው ፡ ለያየ. Sort out the oranges! ብርቱካኖቹን ፡ በየዓይነታቸው ፡ ለያይ
2. በየመልኩ ፡ አስቀመጠ. The books were all mixed up, and it took some time to sort them out. መጽሐፎቹ ፡ ተመሰቃቅለው ፡ ስለነበር ፡ በየ መልኩ ፡ ለማስቀመጥ ፡ ጊዜ ፡ ወሰደብኝ

**sort** (n.)
1. ዓይነት. I can't get along with that sort of person. ከዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ልስማማ ፡ አልችልም
What sort of work does he do? ምን ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ?
2. ሰው. He is a good sort. ደኅና ፡ ሰው ፡ ነው
3. ዓይነት ፡ ሰው. John is the sort who is always late. ጆን ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚዘገይ ፡ ዓይነት ፡ ሰ ው ፡ ነው
*He promised me all sorts of things. አደርግልሃ ለሁ ፡ ያላለኝ ፡ ነገር ፡ አልነበረም

**sort of**
1. በመጠኑ. I'm sort of glad. በመጠኑ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል
2. relative + ዓይነት. She's sort of interesting. የምታስደስት ፡ ዓይነት ፡ ናት
His conversation was sort of boring. ጨዋታው ፡ የሚያሰለች ፡ ዓይነት ፡ ነበር

**(I) sort of thought** ጠርጥሬ ፡ ነበር
I sort of thought this would happen. ይህ ፡ ነገር ፡ እንደሚሆን ፡ ጠርጥሬ ፡ ነበር

**a sort of** መሳይ
They drink a sort of coffee. ቡና ፡ መሳይ ፡ ይጠጣሉ

**of sorts** ቢጤ
He is a football player of sorts. የእግር ፡ ኳስ ፡ ተጫዋች ፡ ቢጤ ፡ ነው

**of the sort** እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር
I said nothing of the sort. እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አልወጣኝም

## sortie

1. ማጥቃት. The enemy's sortie did not damage our lines. የጠላት ፡ ማጥቃት ፡ የጦር ፡ ግንባራችንን ፡ አልጐዳውም
2. የስለላ ፡ በረራ. Our planes made several sorties over enemy territory. አውሮፕላኖቻችን ፡ በጠላት ፡ መንደር ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የስለላ ፡ በረራ ፡ አደረጉ

## so-so ምንም ፡ አይል

How do you feel today? So-so. ዛሬስ ፡ እንደምን ፡ ነህ ? ምንም ፡ አልል

## sought, see seek

## soul

1. ነፍስ. When a man dies, his soul leaves his body. ሰው ፡ ሲሞት ፡ ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ ትለያለች
2. ሐሳብ. She puts her whole soul into her work. ሐሳቧ ፡ ሁሉ ፡ ሥራዋ ፡ ላይ ፡ ነው
3. ምሳሌ. He is the soul of kindness. የደግነት ፡ ምሳሌ ፡ ነው
4. ዓይን. The leader was the soul of the expedition. መሪው ፡ የዘመቻው ፡ ዓይን ፡ ነበር

**have no soul** ስሜት ፡ አይሰጥም
His painting has no soul. ሥዕሉ ፡ ስሜት ፡ አይሰጥም

**not a soul** አንድም ፡ ሰው ፤ ማንም
There wasn't a soul to be seen. አንድም ፡ ሰው ፡ አልነበረም
Don't tell a soul! ለማንም ፡ አትንገር
[See also 'body, heart']

## sound (vt.)

1. ነፋ. He sounded the trumpet. ጥሩንባውን ፡ ነፋ
2. አሰማ. The trumpets sounded the call to arms. መለከቶቹ ፡ የጦርነት ፡ ዐዋጅ ፡ አሰሙ
3. አቀረበ. Everyone sounded his praises. ሁሉም ፡ ምስጋናውን ፡ አቀረበ
4. ጥልቀት ፡ ለካ. He sounded the lake. የሐይቁን ፡ ጥልቀት ፡ ለካ
5. ገመገመ. He sounded public opinion to find out how people felt about his plan. ሰዎች ፡ ስለ ፡ እቅዱ ፡ ምን ፡ እንደሚያስቡ ፡ ለማወቅ ፡ የሕዝቡን ፡ አስተያየት ፡ ገመገመ

*He sounded the retreat. ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲያፈገፍጉ ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ድምፅ ፡ አሰማ

**sound** (vi.)
1. ተሰማ. Running feet sound through the hall. የሚሮጥ ፡ ሰው ፡ ኮቴ ፡ ከመተላለፊያው ፡ ውስጥ ፡ ይሰማል
2. ተነፋ. The trumpets sounded for battle. መለከቶቹ ፡ ለጦርነት ፡ ተነፉ
3. ድምፅ ፡ አሰማ. The trumpets sounded as the troops advanced. ወታደሩ ፡ ወደፊት ፡ ሲገሰግስ ፡ መለከቶቹ ፡ ድምፅ ፡ አሰሙ
4. ተደወለ. At the precise moment that the doorbell sounded, the telephone rang. ልክ ፡ የበሩ ፡ ደወል ፡ ሲደወል ፡ ስልኩም ፡ ተደወለ
5. መሰለ. That sounds good to me. ጥሩ ፡ ይመስለኛል

His story sounds credible. ታሪኩ ፡ የሚታመን ፡ ይመስላል

6. ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ጠለቀ. The whale sounded. ዓሣ ፡ ነባሪው ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ጠለቀ

**sound alike** ባነባበብ ፡ አንድ ፡ ናቸው
These two words sound alike. እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ቃላት ፡ ባነባበብ ፡ አንድ ፡ ናቸው

**sound hoarse** ጐርናና ፡ ነው
His voice sounds hoarse. ድምፁ ፡ ጐርናና ፡ ነው

**sound out** አሳቡን ፡ ለማወቅ ፡ ጠየቀ
He sounded them out regarding their willingness to come along. ለመምጣት ፡ ይፈልጉ ፡ እንደሆነ ፡ አሳባቸውን ፡ ለማወቅ ፡ ጠየቀ
*We sounded out the teacher on the subject of a picnic. መምህሩ ፡ ስለ ፡ ሽርሽሩ ፡ ምን ፡ እንደሚያስብ ፡ ለማወቅ ፡ ነገሩን ፡ አነሣን
[See also 'alarm, funny, knell']

## sound (n.)

1. ድምፅ. Light travels faster than sound. ብርሃን ፡ ከድምፅ ፡ ይፈጥናል

I recognized her by the sound of her voice. በድምጿ ፡ ዐወቅኳት

2. ቃል. She didn't utter a sound. አንድም ፡ ቃል ፡ አልተነፈሰች
3. ሐሳብ. I heard the President's speech yesterday, but I did not like the sound of it. የፕሬዚዳንቱን ፡ ንግግር ፡ ትናንትና ፡ ሰማሁ ፤ ሐሳቡን ፡ ግን ፡ አልወደድኩትም

4. ሆሄ. Phonetics teaches how sounds are pronounced. የፊደል ፡ ድምፅ ፡ ጥናት ፡ ሆሄያትን ፡ እንደምን ፡ እንደምናነብ ፡ ያስተምረናል
5. [ሁለት ፡ ባሕር ፡ የሚያቈራኝ ፡ ረጅም ፡ የውኃ ፡ ሰላጤ]

**within sound of one's voice**
*I want the children to remain within sound of my voice. ልጆቹ ፡ ስጠራቸው ፡ ከሚሰሙኝ ፡ ቦታ ፡ እንዳይርቁ

**sound** (adj.)
1. ጥልቅ. He gave me sound advice. ጥልቅ ፡ ምክር ፡ ሰጠኝ
2. ጥሩ ፤ ጤነኛ. One must have a sound mind in a sound body. አንድ ፡ ሰው ፡ ጥሩ ፡ አእምሮ ፡ ከጤነኛ ፡ አካል ፡ ጋር ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል
3. ብርቱ. He has a sound constitution. ብርቱ ፡ ሰውነት ፡ አለው
4. ደኅና. The carpenter uses only sound timber. አናጢው ፡ በደኅና ፡ ዕንጨት ፡ ብቻ ፡ ይሠራል
5. ጠንካራ. If the foundation is not sound, the house will collapse. መሠረቱ ፡ ጠንካራ ፡ ካል ሆነ ፡ ቤቱ ፡ ይፈርሳል
6. ድብን ፡ ያለ. His sleep is sound, and nothing will wake him up. ድብን ፡ ያለ ፡ እንቅልፍ ፡ ስለሚወስደው ፡ ምንም ፡ አያነቃውም
7. የሚያስተማምን. He kept his money in a sound bank. ገንዘቡን ፡ በሚያስተማምን ፡ ባንክ ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጠ
8. በእውነት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ. That's a sound argument. ያ ፡ በእውነት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ አስተያየት ፡ ነው
9. (= adv.) ሙልጭ ፡ አድርጎ. The father gave the boy a sound whipping. አባትዬው ፡ ልጁን ፡ ሙልጭ ፡ አድርጎ ፡ ገረፈው

**be sound asleep**
He's sound asleep. ድብን ፡ ያለ ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዶታል
[See also 'safe']

**sounding** የጥልቀት ፡ መለኪያ
Soundings show Lake Tana is quite deep. የጥልቀት ፡ መለኪያው ፡ የጣና ፡ ሐይቅ ፡ ጥልቅ ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል

**(be) soundless** ድምፅ ፡ የለውም
A small electric motor is soundless. ትንሽ ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ሞተር ፡ ድምፅ ፡ የለውም

**soundly**
1. ሙልጭ ፡ አድርጎ. The monitor scolded us soundly. አለቃችን ፡ ሙልጭ ፡ አድርጎ ፡ ሰደበን
2. አስቦ. My brother decided soundly, and so kept out of trouble. ወንድሜ ፡ አስቦ ፡ ውሳኔ ፡ ስላደረገ ፡ ከችግር ፡ ዳነ
3. ደኅና ፡ አድርጎ. The thieves thrashed him soundly. ሌቦቹ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ደበደቡት
*He sleeps soundly. ሲተኛ ፡ ጆብ ፡ ቢወስደው ፡ አይሰማም

**soundness** ትክክለኛነት
The soundness of his idea is obvious. የሐሳቡ ፡ ትክክለኛነት ፡ ግልጽ ፡ ነው

**soundness of judgment** አስተዋይነት
People respect his soundness of judgment. ሰዎች ፡ ባስተዋይነቱ ፡ ያከብሩታል

**(be) soundproof**
Is this room soundproof? ይህ ፡ ክፍል ፡ ድምፅ ፡ አያስተላልፍም ?

**soup** ሾርባ
Do you like soup? ሾርባ ፡ ትወዳለህ ?

**sour** (vt.) አኰመጠጠ
Hot weather will sour milk. ሞቃት ፡ አየር ፡ ወተት ፡ ያኰመጥጣል

**sour** (vi.)
1. ኰመጠጠ. The milk soured overnight. ወተቱ ፡ ባንድ ፡ ሌሊት ፡ ኰመጠጠ
2. ብስጩ ፡ ሆነ. She has soured in the last months. ካለፉት ፡ ወራት ፡ ወዲህ ፡ ብስጩ ፡ ሆናለች

**sour (one's) temper** ግልፍተኛ ፡ አደረገ
Hardships have soured his temper. መከራ ፡ ግልፍተኛ ፡ አድርጎታል

**(be) sour**
1. ጐመዘዘ. This wine is too sour. ይህ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ በጣም ፡ ጐምዝዟል
2. መረረ. Most green fruit is sour. አብዛኛው ፡ ያልበሰለ ፡ ፍሬ ፡ ይመራል

**sour face**
*Despite his sour face, he is a nice person. ምንም ፡ እንኳን ፡ ፊቱን ፡ ቢጸጥር ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነው

**turn sour**
1. ኰመጠጠ. The milk turned sour in the hot weather. ከሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ወተቱ ፡ ኰመጠጠ
2. ሻከረ. Their friendship turned sour. ጓደኝነታቸው ፡ ሻክሯል

**source**
1. ምንጭ. The source of the Blue Nile is in northern Ethiopia. የጥቁር ፡ ዐባይ ፡ ምንጭ ፡ ሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ነው

This book is the source of my information. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የመረጃዬ ፡ ምንጭ ፡ ነው
2. መነሾ ፤ መነሻ. Have you found the source of the trouble? የሁከቱን ፡ መነሾ ፡ (መነሻ) ፡ ደረስክበት ?
3. ሰው. I have it from a good source. ከታመነ ፡ ሰው ፡ የሰማሁት ፡ ነው

**south** ደቡብ
The wind is coming from the south. ነፋሱ ፡ የሚነፍሰው ፡ ከደቡብ ፡ ነው

**southerly**
1. ከወደ ፡ ደቡብ ፡ የሚመጣ. A southerly breeze blows today. ዛሬ ፡ ከወደ ፡ ደቡብ ፡ የሚመጣ ፡ ነፋስ ፡ ይነፍሳል
2. ደቡባዊ. The southerly direction of the plane is indicated on this chart. የአውሮፕላኑ ፡ ደቡባዊ ፡ አቅጣጫ ፡ በዚህ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ ተመልክቷል

**southeast** ደቡብ ፡ ምሥራቅ
The southeast is inhabited by Somalis. በደቡብ ፡ ምሥራቅ ፡ የሚኖሩት ፡ ሱማሌዎች ፡ ናቸው

**southern** ደቡባዊ ፤ የደቡብ
This plant is found only in southern regions. ይህ ፡ ዕፅ ፡ የሚገኘው ፡ በደቡባዊ ፡ ክፍሎች ፡ ብቻ ፡ ነው
This house has a southern aspect. ይህ ፡ ቤት ፡ የደቡብ ፡ ቤቶችን ፡ ይመስላል

**South Pole** ደቡባዊ ፡ ዋልታ
The South Pole is covered with ice. ደቡባዊ ፡ ዋልታ ፡ በበረዶ ፡ ተሸፍኗል

**southwest** ደቡብ ፡ ምዕራብ
The southwest is inhabited by Gallas. በደቡብ ፡ ምዕራብ ፡ የሚኖሩት ፡ ጋሎች ፡ ናቸው

**souvenir** ማስታወሻ
I want to buy some souvenirs here. ከዚህ ፡ አንዳንድ ፡ ማስታወሻ ፡ ለመግዛት ፡ እፈልጋለሁ

**sovereign** (n.) ንጉሥ (pl. ነገሥታት)
The sovereigns of Ethiopia used to be crowned in Axum. የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውድ ፡ የሚደፉት ፡ አክሱም ፡ ነበር

**sovereign** (adj.)
1. ራሱን ፡ በራሱ ፡ የሚያስተዳድር. The sovereign state of Kenya signed the treaty. ራሷን ፡ በራሷ ፡ የምታስተዳድረው ፡ ኬንያ ፡ ውሉን ፡ ፈረመች
2. ከፍ ፡ ያለ. Character is of sovereign importance. መልካም ፡ ጠባይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ አለው
3. ከሁሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ. The President holds the sovereign power in the government. ፕሬዚዳንቱ ፡ ባስተዳደሩ ፡ ውስጥ ፡ ከሁሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ አለው

**sovereignty**
1. ነጻነት. Foreign bases are harmful to a country's sovereignty. ባንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የጦር ፡ ሰፈሮች ፡ ላገሪቱ ፡ ነጻነት ፡ ጠንቅ ፡ ናቸው
2. ራሱን ፡ የቻለ ፡ ነጻ ፡ መንግሥት ፡ መሆን. The sovereignty of Ethiopia is recognized by all. ኢትዮጵያ ፡ ራሷን ፡ የቻለች ፡ ነጻ ፡ መንግሥት ፡ መሆኗን ፡ ሁሉም ፡ ተቀብሎታል
3. ዋና ፡ ሥልጣን. In a monarchy, sovereignty rests with the king. በማንኛውም ፡ የንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ዋናውን ፡ ሥልጣን ፡ የሚጨብጥ ፡ ንጉሡ ፡ ራሱ ፡ ነው

**sow** (v.) ዘራ
As ye sow, so shall ye reap. የዘራኸውን ፡ ታመርታለህ
*She sowed hatred with her bitter words. ክፉ ፡ ምላሷ ፡ ጥላቻ ፡ አተረፈላት

**sow** (n.) አሳማ
The sow suckles her offspring. አሳማዋ ፡ ግልገሎቿን ፡ ታጠባለች

**spa** ጠበል
There is a spa in Ambo. አምቦ ፡ ውስጥ ፡ ጠበል ፡ አለ

**space** (v.)
*Space your words evenly when you write. ስትጽፍ ፡ በቃላት ፡ መካከል ፡ የምትተወውን ፡ ቦታ ፡ የተመጣጠነ ፡ አድርገው

**space far apart** አራርቆ + verb
She spaced the letters far apart. ፊደሎቹን ፡ አራርቃ ፡ ጻፈቻቸው
He spaced the posts far apart. ምሰሶዎቹን ፡ አራርቆ ፡ ተከላቸው

**be spaced apart** እየተራራቁ ፡ ቆመ
The soldiers are spaced a foot apart. ወታደሮቹ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጫማ ፡ እየተራራቁ ፡ ቆመዋል

**space** (n.)
1. ቦታ. You'll have to leave more space between the tables. በጠረጴዛዎቹ ፡ መካከል ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ መተው ፡ አለብህ
Is there still space for my bag? ለሻንጣዬ ፡ ቦታ ፡ ይገኛል ?
2. ባዶ ፡ ቦታ. Fill in the spaces as directed! ባዶውን ፡ ቦታ ፡ እንደታዘዝከው ፡ ሙላ

3. ጠፈር. The rocket traveled through space to the moon. ሮኬቱ ፡ ጠፈርን ፡ አቋርጦ ፡ ወደ ፡ ጨረቃ ፡ ተጓዘ
*The trees covered acres of space. ብዙ ፡ ጋሻዎ ች ፡ በዛፍ ፡ ተሸፍነዋል

**for a space of** ለ --- ያህል
The road is bad for a space of ten miles. ለዐሥር ፡ ማይል ፡ ያህል ፡ መንገዱ ፡ መጥፎ ፡ ነው

**for the space of** ሙሉ
He hasn't seen his brother for the space of ten years. ወንድሙን ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ አላየውም

**in the space of** በ --- ውስጥ
He did the work in the space of two weeks. በሁለት ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ሥራውን ፡ ጨረሰ

**spacious** ሰፊ
The room is spacious. ክፍሉ ፡ ሰፊ ፡ ነው

**spade** (v.) ቈፈረ
He spaded the garden before planting the flowers. አበባዎቹን ፡ ከመትከሉ ፡ በፊት ፡ ያት ክልቱን ፡ ቦታ ፡ ቈፈረው

**spade** (n.) አካፋ
Use a spade for leveling the ground! መሬቱን ፡ በአካፋ ፡ አስተካክል

**Spain** እስፓኛ

**span** (spanned), vt. (= vi.) ተዘረጋ
The bridge spans the river. ወንዙ ፡ ላይ ፡ ድል ድይ ፡ ተዘርግቷል
*His memory spans many decades. ብዙ ፡ ያለ ፉ ፡ ዓመታትን ፡ ማስታወስ ፡ ይችላል
*His life spanned almost all of the 19th century. የዐሥራ ፡ ዘጠነኛውን ፡ ዘመን ፡ በሙሉ ፡ ኖረው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል

**be spanned** (= trans.) ሞላ
+This post can be spanned by one's two hands. ይህን ፡ ምሰሶ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሁለት ፡ እጁ ፡ ሊ ሞላው ፡ ይችላል

**span** (n.)
1. ስንዝር. Length used to be measured in cubits and spans. ርዝመት ፡ የሚለካው ፡ በክን ድና ፡ በስንዝር ፡ ነበር
2. መጠን. The span of human life is about seventy years. የሰው ፡ ልጅ ፡ የዕድሜ ፡ መጠን ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ነው
3. ስፋት. The arch has a span of thirty feet. የቅስቱ ፡ ስፋት ፡ ሠላሳ ፡ ጫማ ፡ ነው
*The bridge crossed the river in a single span. ድልድዩ ፡ ያለ ፡ ምሰሶ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**in a short span of time** ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ
It was done in a short span of time. የተሠራው ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ነው
[See also 'spick']

**(be) spangled** አሸበረቀ
Her costume was spangled with jewels. ልብሷ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጌጥ ፡ አሸብርቆ ፡ ነበር

**spank** (v.) መታ
Spank your child if he misbehaves. ልጅህ ፡ ሲባ ልግ ፡ ምታው

**spank** (n.), **give a ~** መታ
He gave me a spank on the bottom. ከቂጤ ፡ ላይ ፡ መታኝ

**spanking, give a ~** መታ
I gave him a good spanking. እስኪበቃው ፡ መ ታሁት

**spare** (v.)
1. አቆየ. Can you spare one of these shirts for me until I can come by to get it? አንዱን ፡ ሸሚዝ ፡ ተመልሼ ፡ እስክወስደው ፡ ድረስ ፡ ልታቆ ይልኝ ፡ ትችላለህ ?
2. ምሕረት ፡ አደረገ. The victors spared the prisoners. ድል ፡ አድራጊዎቹ ፡ ለምርኮኞቻቸው ፡ ምሕረት ፡ አደረጉ
3. አተረፈ. The mother made a fervent plea to the judge to spare her son. እናቲቱ ፡ ዳኛው ፡ ል ጇን ፡ እንዲያተርፍላት ፡ ልብ ፡ በሚነካ ፡ ሁኔታ ፡ ለመነች
4. ከ -- አዳነ. He did the work himself to spare you the trouble. ከልፋት ፡ ሊያድንህ ፡ ሥራውን ፡ ራሱ ፡ አከናወነ
5. ከድካም ፡ አዳነ. We walked uphill to spare the horse. ፈረሱን ፡ ከድካም ፡ ለማዳን ፡ ዳገቱን ፡ በእግር ፡ ወጣን
6. ቈጠበ. Spare no effort to save the sinking ship! የሚሰጥመውን ፡ መርከብ ፡ ለማዳን ፡ ጥረት ህን ፡ አትቈጥብ
*Do you have a minute to spare? አንድ ፡ ደ ቂቃ ፡ የሚሆን ፡ ጊዜ ፡ አለህ ?
*Can you spare a pencil? እርሳስህን ፡ ልውሰድ ብህ ?
*We can't spare the time for a holiday now. አሁን ፡ ዕረፍት ፡ ለመውሰድ ፡ አንችልም
*How can we spare his feelings? ቅር ፡ እንዳይለ ው ፡ (እንዳይቀየም) ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻለናል ?

**spare oneself** ከ --- ራሱን ፡ አዳነ
You can spare yourself the trouble. ራስህን ፡ ከልፋት ፡ ልታድን ፡ ትችላለህ

**be spared** ተረፈ
His life was spared. ነፍሱ ፡ ተረፈች
**no one was spared** አንድም ፡ ሰው ፡ ሳይቀር ፤ አንድም ፡ ሰው ፡ አልተረፈ
No one was spared; all had to pay the tax. አንድም ፡ ሰው ፡ ሳይቀር ፡ ሁሉም ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ ነበረበት
When the epidemic broke out, no one was spared. ወረርሽኙ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ አልተረፈ

**spare** (adj.)
1. ትርፍ. What do you do in your spare time? በትርፍ ፡ ጊዜህ ፡ ምን ፡ ትሠራለህ ?
2. መጠባበቂያ. We never travel without a spare tire. መጠባበቂያ ፡ ጎማ ፡ ሳንይዝ ፡ ከቶ ፡ አንጓዝም
3. አነስተኛ. The explorers had to live on spare rations. አሳሾቹ ፡ ባነስተኛ ፡ ምግብ ፡ መኖር ፡ ነበረባቸው
*Fat people should live on a spare diet. ወፍራም ፡ ሰዎች ፡ በመጠኑ ፡ መመገብ ፡ አለባቸው
**spare parts** መለዋወጫ ፡ እቃ
Can you get spare parts for your radio? ለራዲዮንህ ፡ መለዋወጫ ፡ እቃ ፡ ታገኛለህ ?

**sparing**
*The sparing use of sugar will save you money on dentist's bills. ስኳር ፡ በልኩ ፡ ብትመገብ ፡ ለጥርስ ፡ ሐኪም ፡ የምታወጣውን ፡ ሒሳብን ፡ ይቀንስልሃል
**be sparing with** አላበዛም
She is very sparing with praise. ምስጋና ፡ አታበዛም

**sparingly** በቁጠባ
Use it sparingly! በቁጠባ ፡ ያዘው

**spark** (vt.) አስነሣ
The dictator's tyranny sparked a revolt. ያምባገነኑ ፡ የጭቈና ፡ አገዛዝ ፡ ዐመፅ ፡ አስነሣ
**spark** (vi.) ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ አለ
This old cigarette lighter only sparks. ይህ ፡ ያረጀው ፡ የሲጋራ ፡ ማቀጣጠያ ፡ ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ ብቻ ፡ ይላል

**spark** (n.)
1. ፍንጣሪ ፤ የእሳት ፡ ፍንጣሪ. The fire was started by a spark. እሳቱ ፡ የተነሣው ፡ በፍንጣሪ ፡ ነው
A spark set the house afire. የእሳት ፡ ፍንጣሪ ፡ ቤቱን ፡ አቀጣጠለው
2. ጭላንጭል. We saw a spark of light through the trees. በዛፎቹ ፡ መካከል ፡ የብርሃን ፡ ጭላንጭል ፡ አየን
When they pulled him out of the water, there was not a spark of life in him. ከውኃ ፡ ውስጥ ፡ ጐትተው ፡ ሲያወጡት ፡ ምንም ፡ የሕይወት ፡ ጭላንጭል ፡ አልነበረውም
**a spark of** በመጠኑ
He showed a spark of interest. በመጠኑ ፡ ደስታውን ፡ ገለጸ
**make sparks** ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ አለ
The broken electric wire was making sparks. የተበጠሰው ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ሽቦ ፡ ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ ይል ፡ ነበር
**not a spark** አንዲት ፡ ቅንጣት ፡ እንኳ
He hasn't a spark of generosity in him. አንዲት ፡ ቅንጣት ፡ እንኳ ፡ ደግነት ፡ የለውም
**throw off sparks** ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ አለ
The broken wire throws off sparks. የተበጠሰው ፡ የኮረንቲ ፡ ሽቦ ፡ ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ ይላል

**sparkle**
1. አንጸባረቀ. The water sparkles in the sun. ውኃው ፡ በፀሐይ ፡ ውስጥ ፡ ያንጸባርቃል
His conversation sparkles. ጨዋታው ፡ ያንጸባርቃል
2. ተብለጨለጨ. His eyes sparkled with excitement. ዐይኖቹ ፡ በደስታ ፡ ተብለጨለጩ
3. አሸበረቀ. The tree was sparkling with decorations. ዛፉ ፡ በጌጣጌጥ ፡ አሸብርቆ ፡ ነበር

**spark plug** ካንዴላ
The motor needs spark plugs. ሞተሩ ፡ ካንዴላ ፡ ያስፈልገዋል

**sparrow** ድንቢጥ
Sparrows are common all over the world. ድንቢጦች ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ይገኛሉ

**sparse**
1. ጥቂት. A sparse crowd participated in the demonstration. በሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ የተካፈሉት ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ
2. ዘርዛራ. He has a sparse beard. ዘርዛራ ፡ ጢም ፡ አለው
**(be) sparse** በየቦታው ፡ ተበታተነ
The nomad population is sparse. ዘላን ፡ ሕዝብ ፡ በየቦታው ፡ የተበታተነ ፡ ነው

**spasm**
*A muscle spasm causes pain. ጡንቻ ፡ ሲኰማተር ፡ ያማል

**spasmodic**
1. (= adv.) በኀይል ፡ እየደጋገመ. A spasmodic cough is a sign of a disease. በኀይል ፡ እየደጋገመ ፡ ሲያስል ፡ የበሽታ ፡ ምልክት ፡ ነው

2. እምብዛም. He took only spasmodic interest in his stamp collection. ቴምብር ፡ ለማጠራቀ ም ፡ ያለው ፡ ፍላጎት ፡ እምብዛም ፡ ነው

**spat,** see **spit**

**spat** (n.) ግጭት
He had a spat with his wife. ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ግጭት ፡ አድርጓል

**spate**
*There were a spate of reports that he would resign. ሥራውን ፡ በፈቃዱ ፡ ይለቃል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ይነፍስ ፡ ነበር

**spatial** የጠፈር
Spatial distance is limitless. የጠፈር ፡ ስፋት ፡ ወሰን ፡ የለውም

**spatter**
1. በሳሳ. Bullets spattered the wall. ግድግዳውን ፡ ጥይት ፡ በሳስቶታል
2. ረጨ. As the bus went by, it spattered us with mud. አውቶቡሱ ፡ ሲያልፍ ፡ ጭቃ ፡ ረጨብን
3. መታ. Rain spattered the window. ዝናብ ፡ መስኮቱን ፡ መታው

**spatula** መሰቅሰቂያ
She used a spatula to turn the eggs. እንቁላሉን ፡ በመሰቅሰቂያ ፡ አገላበጠች

**speak** (spoke) ተናገረ
Do I speak clearly enough? የምናገረው ፡ ይሰማል ?

**(it) speaks for itself**
*His work speaks for itself. ሥራው ፡ ራሱ ፡ ይመሰክርለታል

**speak (one's) mind**
1. የሚሰማውን ፡ ሁሉ ፡ ግልጽ ፡ አድርጎ ፡ ተና ገረ. He spoke his mind to the boss. የሚሰማውን ፡ ሁሉ ፡ ላለቃው ፡ ግልጽ ፡ አድርጎ ፡ ተናገረ
2. ያለውን ፡ ሐሳብ ፡ ተናገረ. He spoke his mind about the plan. ስለ ፡ እቅዱ ፡ ያለውን ፡ ሐሳብ ፡ ተናገረ

**speak of**
1. ጠቀሰ. At the time you are speaking of, he was in Spain. አሁን ፡ አንተ ፡ በጠቀስከው ፡ ጊዜ ፡ እሱ ፡ እስፓኝ ፡ ውስጥ ፡ ነበር
2. አመለከተ. Her eyes speak of suffering. ዓይኖቿ ፡ ብዙ ፡ ሥቃይ ፡ ማየቷን ፡ ያመለክታሉ

**speak out** ተናገረ
He was not afraid to speak out when it was something he believed in strongly. በጣም ፡ ያመ ነበት ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፡ መናገር ፡ አይፈራም ፡ ነበር

**speak to** አነጋገረ
May I speak to you? እንዴ ፡ ላነጋግርህ ?

**speak up** ተናገረ ፤ በድንብ ፡ ተናገረ ፤ ጮክ ፡ አለ
The children all spoke up in favor of the picnic. ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ ሽርሽር ፡ መሄድን ፡ እንደሚመርጡ ፡ ተናገሩ
When your turn comes, speak up. ተራህ ፡ ሲደርስ ፡ በደንብ ፡ ተናገር
Speak up! We can't hear you. ጮኽ ፡ በል ፤ ልንሰማህ ፡ አልቻልንም

**speak up in defense of** ለ --- ተከራከረ
He spoke up in defense of his friend. ለጓደኛው ፡ ተከራከረ

**speak well for**
*It spoke well for the boy that he apologized. የልጁ ፡ ይቅርታ ፡ መጠየቅ ፡ ጨዋነቱን ፡ ገለጸ

**(he) can speak** ተናገረ
Can you speak English? እንግሊዝኛ ፡ ትናገራለህ ?

**nothing to speak of** የሚነገርለት ፡ አይደለም
Did he accomplish anything? Nothing to speak of. ያከናወነው ፡ ነገር ፡ አለ ? የሚነገር ለት ፡ አይደለም

**so to speak** ለማለት ፡ ይቻላል
He did it partially, so to speak. በከፊል ፡ ሠራ ው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል

**to speak of** የኔ ፡ ነው ፡ የሚለው
He hasn't any money to speak of. የኔ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ገንዘብ ፡ የለውም
[See also 'favor, ill, low, praise, sharply']

**speaker** ተናጋሪ
In today's debate, the speakers came from various schools. በዛሬው ፡ ውይይት ፡ ተናጋሪዎ ቹ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የመጡ ፡ ናቸው
*He's an excellent speaker. ጥሩ ፡ ይናገራል
[See also 'fluent']

**speaking** መናገር
I prefer speaking to writing. ከመጻፍ ፡ ይልቅ ፡ መናገርን ፡ እመርጣለሁ
*May I speak to Mr. Jones? Speaking. ሚስተር ፡ ጆንስን ፡ ላነጋግር ? ጆንስ ፡ ነኝ

**speaking of** ከተናገርን ፡ ዘንድ
Speaking of weather, what is the lowest temperature in Canada? ስለ ፡ አየር ፡ ጠባይ ፡ ከተና ገርን ፡ ዘንድ ፡ የካናዳ ፡ ዝቅተኛ ፡ ሙቀት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይሆናል ?

**generally speaking** ጠቅላላው ፤ በጠቅላላ ፡ አነጋገር
Generally speaking, the villagers are friendly. ጠቅላላው ፡ መንደርተኞቹ ፡ ሰው ፡ ወዳጆች ፡ ናቸው
Generally speaking, our coldest weather comes in January. በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ በጣም ፡ ብርዳም ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ የሚመጣው ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ነው

**not be on speaking terms** አልተነጋገሩም ፤ ተኰራረፉ
They are not on speaking terms since they quarreled. ከተጣሉ ፡ ወዲህ ፡ አይነጋገሩም
Due to an old quarrel, they are not on speaking terms. የቆየ ፡ ጠብ ፡ ስላላቸው ፡ ተኰራርፈዋል

**spear** (v.) በጦር ፡ ገደለ
They spear fish for a living. ዓሣ ፡ በጦር ፡ እየገደሉ ፡ ይኖራሉ

**spear** (n.) ጦር
My spear broke. ጦሬ ፡ ተሰበረ

**spearhead** (v.) ቀደም ፡ ሆነ
The Third Division will spearhead the invasion. ሦስተኛ ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ የወረራው ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ይሆናል

**spearhead** (n.) የጦር ፡ ጫፍ
The spearhead is made of iron. የጦሩ ፡ ጫፍ ፡ የተሠራው ፡ ከብረት ፡ ነው

**special**
1. የተለየ. I am saving it for a special purpose. ያስቀመጥኩት ፡ ለተለየ ፡ ጉዳይ ፡ ነው
Today's topic is of special interest. የዛሬው ፡ ርእስ ፡ የተለየ ፡ ጠቃሚነት ፡ አለው
2. ልዩ. Surgery requires special skill. ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ልዩ ፡ ሙያ ፡ ያስፈልገዋል
Send this letter by a special messenger! ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ በልዩ ፡ መልእክት ፡ ላከው
3. የቅርብ. John is my special friend. ዮሐንስ ፡ የቅርብ ፡ ጓደኛዬ ፡ ነው

**special delivery** ልዩ ፡ መልእክት
Mail this letter special delivery! ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ በልዩ ፡ መልእክት ፡ ላከው

**specialist** ልዩ ፡ ዐዋቂ
They are calling in various specialists to discuss the economic problems. በኢኮኖሚው ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ለመወያየት ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ጠርተዋል
*He is a specialist in eye diseases. የዐይን ፡ ሐኪም ፡ ነው

**specialize (in)**
1. ልዩ ፡ ችሎታው ፡ ነው. +He specializes in treating eye diseases. ልዩ ፡ ችሎታው ፡ የዓይን ፡ ሕክምና ፡ ነው
2. ልዩ ፡ ትምህርቱ ፡ ነው. +He specializes in African history. ልዩ ፡ ትምህርቱ ፡ የአፍሪካ ፡ ታሪክ ፡ ነው

**specially** በተለይ
I came here specially to see you. እዚህ ፡ የመጣሁት ፡ በተለይ ፡ እንተን ፡ ለማየት ፡ ነው

**specialty**
1. ልዩ ፡ ትምህርት. His specialty is linguistics. ልዩ ፡ ትምህርቱ ፡ ቋንቋ ፡ ነው
2. (= adv.) በተለይ. The specialty of the shop is rare books. ሱቁ ፡ በተለይ ፡ የሚሸጠው ፡ እንደልብ ፡ የማይገኙ ፡ መጻሕፍትን ፡ ነው
*Children's diseases are his specialty. የሕፃናት ፡ ሐኪም ፡ ነው

**species** ዘር
Wheat is a species of grass. ስንዴ ፡ የሣር ፡ ዘር ፡ ነው

**specific**
1. የተወሰነ. The money is to be used for a specific purpose. ገንዘቡ ፡ ላንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ጉዳይ ፡ የሚውል ፡ ነው
2. ልዩ. He had specific orders to wait. እንዲቆይ ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጥቶታል
3. ፍቱን. This drug is a specific remedy for tuberculosis. ይህ ፡ መድኃኒት ፡ ለሳምባ ፡ ነቀርሳ ፡ ፍቱን ፡ ነው

**be specific!** ለይተህ ፡ ተናገር
Be specific! Do you want to study linguistics or literature? ለይተህ ፡ ተናገር ፤ ለማጥናት ፡ የምትፈልገው ፡ ቋንቋ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ?

**specifications** ዝርዝሮች ፡ ደንቦች
The specifications were not fulfilled, so the contract was voided. ዝርዝሮቹ ፡ ደንቦች ፡ ስላልተከበሩ ፡ ውሉ ፡ ፈረሰ
*Mary made careful specifications as to the kinds of cake for her party. ሜሪ ፡ ለፓርቲው ፡ የሚያስፈልጋትን ፡ የኬክ ፡ ዓይነት ፡ በጥንቃቄ ፡ ዘርዝራ ፡ አመለከተች

**specify** (specified)
1. ወሰነ. Mercantile law specifies how contracts must be drawn up. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ውልን ፡ እንዴት ፡ መዋዋል ፡ እንደሚገባ ፡ ይወስናል
2. በተለየ ፡ ወሰነ. He did not specify the amount needed. የተፈለገውን ፡ ልክ ፡ በተለይ ፡ አልወሰነም

3. ለይቶ ፡ አመለከተ. The contract specifies that only men may be hired. ሊቀጠሩ ፡ የሚችሉት ፡ ወንዶች ፡ ብቻ ፡ መሆናቸውን ፡ ውሉ ፡ ለይቶ ፡ ያመለክታል
4. እንደሚያስፈልግ ፡ ገለጸ. The recipe specifies honey. የምግብ ፡ መሥሪያ ፡ መምሪያው ፡ ማር ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ይገልጻል

**specimen**
1. ላሙና ፣ ናሙና. The specimens have been tagged. ናሙናዎቹ ፡ ምልክት ፡ ተደርጎባቸው ፡ ነበር
2. ምሳሌ. Give me a specimen of Amharic poetry! ላማርኛ ፡ ግጥም ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ ስጠኝ

**specious** የማይረባ
The teacher saw through John's specious excuse. አስተማሪዋ ፡ የሐንስ ፡ የሰጠውን ፡ የማይረባ ፡ ምክንያት ፡ ዐወቀችበት

**speck** ጠብታ
Can you clean the specks off the blanket? እነዚህን ፡ ጠብታዎች ፡ ከብርድ ፡ ልብሱ ፡ ልታስለቅቃቸው ፡ ትችላለህ ?
*There is a speck of dirt in my cup. ሲኒዬ ፡ ውስጥ ፡ ጉድፍ ፡ አለ

**speckle** (n.) ጠቃጠቆ
Her face is covered with speckles. ፊቷ ፡ ላይ ፡ ጠቃጠቆ ፡ አለባት

**(be) speckled with** ፈንጠቅጠቅ ፡ አለ(በት)
*The sky was speckled with stars. ሰማዩ ፡ ከዋክብት ፡ ፈንጠቅጠቅ ፡ ብለውበታል

**spectacle**
1. ግርማ. Travelers are awed by the spectacle of this mountain. መንገደኞቹ ፡ በዚህ ፡ ተራራ ፡ ግርማ ፡ ይደነቃሉ
2. (= adj.) የደመቀ. The Emperor's coronation was quite a spectacle. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ በጣም ፡ የደመቀ ፡ ነበር

**spectacles** መነጽር
He broke his spectacles. መነጽሩን ፡ ሰበረው

**spectacular** በጣም ፡ አስደናቂ
The view from the plane was spectacular. ከአውሮፕላኑ ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ ትርኢይት ፡ በጣም ፡ አስደናቂ ፡ ነበር

**spectator** ተመልካች
The spectators were not happy about the football game. ተመልካቾቹ ፡ በእግር ፡ ኳስ ፡ ጨዋታው ፡ አልተደሰቱም

**specter**
1. ስጋት. The specter of war haunts every sensible person. የጦርነት ፡ ስጋት ፡ ማንኛውንም ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ያሸብራል
2. መንፈስ. The specter of the murdered man still haunts the house. የተገደለው ፡ ሰውዬ ፡ መንፈስ ፡ አሁንም ፡ ቤቱን ፡ ይረብሻል

**speculate**
1. አስቀድሞ ፡ ገመተ. He refused to speculate about the possible winner. አሸናፊው ፡ ማን ፡ እንደሚሆን ፡ አስቀድሞ ፡ ለመገመት ፡ አልፈለገም
2. አወጣ ፡ አወረደ. We are speculating about the reason for his dismissal. ከሥራ ፡ የወጣበትን ፡ ምክንያት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ በማውጣት ፡ በማውረድ ፡ ላይ ፡ ነን
3. አሰበ. The philosopher speculates about the past and future. ፈላስፋው ፡ ስላለፈውና ፡ ስለሚመጣው ፡ ያስባል
*He is speculating in cottons. በጥጥ ፡ ንግድ ፡ አተርፋለሁ ፡ ብሎ ፡ በገንዘቡ ፡ ብዙ ፡ ጥጥ ፡ ገዝቶ ፡ ያስቀምጣል

**speculation** ግምት
His ideas of the cost were based on speculation. ዋጋውን ፡ የሚያውቀው ፡ በግምት ፡ ብቻ ፡ ነበር
**idle speculation** የሆነ ፡ ያልሆነውን ፡ ማሰብ
Don't waste your time in idle speculation! የሆነ ፡ ያልሆነውን ፡ በማሰብ ፡ ጊዜህን ፡ አታጥፋ

**sped**, see **speed**

**speech**
1. ንግግር. The chairman delivered a long speech. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ረጅም ፡ ንግግር ፡ አደረገ
2. ቋንቋ. The native speech of most Americans is English. ያብዛኞቹ ፡ አሜሪካኖች ፡ የናት ፡ ቋንቋ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ነው
3. አነጋገር. His speech showed that he is southern. ባነጋገሩ ፡ ከደቡብ ፡ የመጣ ፡ መሆኑ ፡ ያስታውቃል
4. መናገር. Man alone possesses the power of speech. የመናገር ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው
*He lost his speech after the accident. ከደጋው ፡ በኋላ ፡ አንደበቱ ፡ ተዘጋ
[See also 'articulate, cadence, figure of speech, free, poetic']

**(be) speechless**
1. መናገር ፡ አቃተ(ው) ፣ መናገር ፡ ተሳነ(ው)
I was speechless with terror. ከድንጋጤ ፡ የተነሣ ፡ መናገር ፡ አቃተኝ ፡ (ተሳነኝ)

2. መናገር ፡ አይችልም. Animals are speechless. እንስሶች ፡ መናገር ፡ አይችሉም

**speed** (sped), vt. አፋጠነ

Let's all speed the work! ሁላችንም ፡ ሥራውን ፡ እናፋጥነው

**speed** (vi.) በፍጥነት ፡ ተጓዘ

The boat sped over the water. ጀልባው ፡ በውኃው ፡ ላይ ፡ በፍጥነት ፡ ተጓዘ

**speed (along)** እየበረረ ፡ ሄደ ፤ በፍጥነት ፡ ሄደ

A car sped along the highway. አንድ ፡ መኪና ፡ ባውራ ፡ ጐዳናው ፡ ላይ ፡ እየበረረ ፡ ሄደ

The truck raised a cloud of dust as it sped along. የጭነት ፡ መኪናው ፡ በፍጥነት ፡ ሲሄድ ፡ ብዙ ፡ አቧራ ፡ አስነሣ

**speed (down)** በኀይል ፡ እየነዳ ፡ አለፈ

He sped down the street. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ በኀይል ፡ እየነዳ ፡ አለፈ

**speed up** (vt.) አፋጠነ

Can you speed things up a little? ነገሩን ፡ ትንሽ ፡ ልታፋጥነው ፡ ትችላለህ ?

*They have speeded up the bus service. የአውቶቡሶቹን ፡ ቁጥር ፡ ጨመሩ

**speed up** (vi.) በረረ

The car sped up and passed me. መኪናዋ ፡ እየበረረች ፡ ቀደመችኝ

**speed** (n.) ፍጥነት

The train was going at full speed. ባቡሩ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍጥነት ፡ ይሄድ ፡ ነበር

**at full speed**

*He drove through the town at full speed. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ እየከነፈ ፡ ነዳ

[See also 'rate']

**speeder** በከፍተኛ ፡ ፍጥነት ፡ የሚነዳ ፡ ሰው

Traffic police arrest speeders. የትራፊክ ፡ ፖሊሶች ፡ በከፍተኛ ፡ ፍጥነት ፡ የሚነዱትን ፡ ሰዎች ፡ ይይዛሉ

**speedily, come ~** ከተፍ ፡ አለ

He came speedily in answer to my call. ስጠራው ፡ ከተፍ ፡ አለ

**speeding** (n.) ከተወሰነው ፡ ፍጥነት ፡ በላይ ፡ መንዳት ፤ ከፍጥነት ፡ በላይ ፡ መንዳት

A policeman stopped me for speeding. ከተወሰነው ፡ ፍጥነት ፡ በላይ ፡ በመንዳቴ ፡ ፖሊስ ፡ አቆመኝ

He was arrested for speeding. ከፍጥነት ፡ በላይ ፡ በመንዳት ፡ ተያዘ

**speeding** (adj.) በፍጥነት ፡ የሚበር

She had enough presence of mind to remember the license plate of the speeding car. በፍጥነት ፡ የሚበረውን ፡ የመኪና ፡ ሰሌዳ ፡ ለማወቅ ፡ የሚያስችል ፡ የአእምሮ ፡ እርጋታ ፡ ነበራት

**speed limit** የተወሰነ ፡ ፍጥነት

Around hospitals, the speed limit is 20 miles per hour. በሆስፒታል ፡ አካባቢ ፡ የተወሰነው ፡ ፍጥነት ፡ በሰዓት ፡ ሃያ ፡ ማይል ፡ ነው

**speedy** ፈጣን

Yonas is a speedy runner. ዮናስ ፡ ፈጣን ፡ ሯጭ ፡ ነው

*I wish you a speedy recovery. ቶሎ ፡ እንድትድን ፡ እመኝልሃለሁ

**spell** (spelled, or spelt), vt.

1. ጻፈ. He spelled this word correctly. ይህን ፡ ቃል ፡ በትክክል ፡ ጻፈው

2. ፊደል ፡ ዘርዝሮ ፡ ተናገረ. Please spell your name! የስምህን ፡ ፊደል ፡ ዘርዝረህ ፡ ተናገር

3. አስከተለ. Laziness always spells failure. ስንፍና ፡ ሁልጊዜ ፡ መውደቅን ፡ ያስከትላል

4. አሳየ. This signal spells danger. ይህ ፡ ምልክት ፡ አደጋ ፡ መኖሩን ፡ ያሳያል

*You spelled my name wrong. ስሜን ፡ ስትጽፍ ፡ ፊደል ፡ አሳስተሃል

**spell** (vi.) በትክክል ፡ ጻፈ

Some words are hard to spell. አንዳንድ ፡ ቃላትን ፡ በትክክል ፡ መጻፍ ፡ ያስቸግራል

**spell each other** እየተፈራረቁ ፡ ሠሩ

They spelled each other doing that hard task. ከባዱን ፡ ሥራ ፡ እየተፈራረቁ ፡ ሠሩ

**spell** (n.)

1. አስማት. The spell transformed the young man into a frog. አስማት ፡ ወጣቱን ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ እንቁራሪት ፡ ለወጠው

2. መተት. She is under his spell. በመተቱ ፡ ይዟታል

*The child has spells of coughing. ልጁ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ያስለዋል

*There was a hot spell last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ለጥቂት ፡ ቀናት ፡ የገረረ ፡ ሙቀት ፡ ነበር

*The sailor's spell at the wheel was four hours. የመርከብ ፡ መምራት ፡ ተራ ፡ ሲደርሰው ፡ መርከበኛው ፡ የመርከቡን ፡ መሪ ፡ ላራት ፡ ሰዓት ፡ ያዘ

**cast a spell (on)** በመተት ፡ አሰረ ፤ ደገመ(በት)

The sorcerer cast a spell on the young girl. አስማተኛው ፡ ወጣቷን ፡ ልጃገረድ ፡ በመተት ፡ አሰራት ፡ (ደገመባት)

**(have a) fainting spell**

She had a fainting spell. አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነፍሷን ፡ ስታ ፡ ወድቃ ፡ ነበር

**for a short spell** ላጭር ፡ ጊዜ ፡ ብቻ
He worked for a short spell. ላጭር ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሠራ

**take spells** ተራ ፡ በተራ + verb
The men took spells at watching the trap. ሰዎቹ ፡ ወጥመዱን ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር
[See also 'dry']

**(be) spellbound** ተመሰጠ
The children were spellbound by the play. ልጆቹ ፡ በቲያትሩ ፡ ተመስጠው ፡ ነበር

**hold spellbound** ማረከ
The speaker held the audience spellbound. ተናጋሪው ፡ አድማጮቹን ፡ ማረካቸው

**spelling**
1. የቃላት ፡ አጻጻፍ. Nothing came of his attempt to simplify English spelling. የእንግሊዝኛ ፡ የቃላት ፡ አጻጻፍን ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ ያደረገው ፡ ሙከራ ፡ ውጤት ፡ አላገኘም
2. ሥርዓተ ፡ ሆሄያት. Teaching spelling is not within the province of a college. ሥርዓተ ፡ ሆሄያትን ፡ ማስተማር ፡ የኮሌጅ ፡ ተግባር ፡ አይደለም

**spelling error** የፊደል ፡ ስሕተት
I underlined all your spelling errors. የፊደል ፡ ስሕተቶችህን ፡ ሁሉ ፡ ከሥር ፡ አሥምሬባቸዋለሁ

**spelt,** see **spell**

**spend** (spent), vt.
1. አወጣ. The government spent a million dollars on building roads. መንግሥት ፡ መንገድ ፡ ለማሠራት ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ አወጣ
2. አሳለፈ. I'd like to spend my vacation here. የዕረፍት ፡ ጊዜዬን ፡ እዚህ ፡ ለማሳለፍ ፡ እፈልጋለሁ
He spent a year learning French. ፈረንሳይኛ ፡ በመማር ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ አሳለፈ
3. ፈጀ. I spent two years collecting material for the book. ለመጽሐፉ ፡ አስፈላጊውን ፡ ጽሑፍ ፡ በመሰብሰብ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ፈጀሁ
4. ቆየ. He spent a few days in Paris. ፓሪስ ፡ ጥቂት ፡ ቀኖች ፡ ቆየ
5. አጠፋ. She spends a lot of time on menial tasks such as washing dishes. ሳሕኖችን ፡ ማጠብ ፡ በመሳሰሉ ፡ ዝቅተኛ ፡ ሥራዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ታጠፋለች

**spend** (vi.) ገንዘብ ፡ አጠፋ
He loves to spend. ገንዘብ ፡ ማጥፋት ፡ ይወዳል

**spend all**
*He spent all his energies exercising. ጉልበቱን ፡ ሰውነቱን ፡ በማፍታታት ፡ ብቻ ፡ ጨረሰው

**spend (the) day** ዋለ
He spent the day working in the office. ቢሮ ፡ ውስጥ ፡ ሲሠራ ፡ ዋለ

**spend (one's) days**
He spent his days in Italy. የእርጅና ፡ ጊዜውን ፡ በኢጣልያ ፡ አሳለፈ

**spend (the) evening** አመሸ
We spent the evening talking. ስናወጋ ፡ አመሸን

**spend (its) force** በረደ
The storm has spent its force. ዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ በርዷል

**spend (the) night** አደረ
She spent the night at a friend's house. ጓደኛዋ ፡ ቤት ፡ አደረች
[See also 'time']

**spender, extravagant** ~ ገንዘብ ፡ አባካኝ
He is an extravagant spender and makes many debts. ገንዘብ ፡ አባካኝ ፡ ስለሆነ ፡ ብዙ ፡ ዕዳ ፡ ውስጥ ፡ ይገባል

**spending, extravagant** ~ ገንዘብ ፡ ማባከን
You have to put a curb on extravagant spending. ገንዘብ ፡ ማባከንህን ፡ መቈጣጠር ፡ አለብህ

**spendthrift** አባካኝ ፡ ሰው
The spendthrift wasted his inheritance in a short time. አባካኙ ፡ ሰው ፡ የወረሰውን ፡ ሀብት ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ አባከነው

**spent,** see **spend**

**spent** (adj.), ~ **bullet** ኀይል ፡ የሌላት ፡ ጥይት
A spent bullet fell at his feet. አንድ ፡ ኀይል ፡ የሌላት ፡ ጥይት ፡ እግሩ ፡ ሥር ፡ አረፈች

**spew** ተሰራጨ
Oil spewed all over the ground. ዘይት ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ ተሰራጨ

**sphere**
1. ክብ ፡ አካል. The sphere rolled into the corner. ክቡ ፡ አካል ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ጥግ ፡ ተንከባለለ
2. ሙያ. Father's sphere is business. የአባቴ ፡ ሙያ ፡ ንግድ ፡ ነው
*People used to say that woman's sphere was the home. ሰዎች ፡ ሴት ፡ መሥራት ፡ ያለባት ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ይሉ ፡ ነበር
*He moves in a different sphere now that he is rich. ሀብታም ፡ ስለሆነ ፡ ዛሬ ፡ ውሎው ፡ ከሌላ ፡ ጋር ፡ ነው

**outside (one's) sphere**
*This is outside my sphere. ይህ ፡ እኔን ፡ አይመለከትም

**spherical** ክብ
The earth is spherical in shape. መሬት ፡ ክብ ፡ ናት

**spice** (v.) ቅመም ፡ ጨመረ
He spiced the soup. በሾርባው ፡ ውስጥ ፡ ቅመ ም ፡ ጨመረ

**spice** (n.) ቅመም
Pepper is a spice used on food. በርበሬ ፡ ምግብ ፡ መሥሪያ ፡ ቅመም ፡ ነው
His wit added spice to the conversation. ቀልዱ ፡ ለጨዋታው ፡ ቅመም ፡ ጨመረበት

**spice** (adj.) የቅመማ ፡ ቅመም
The spice trade brought wealth to Arabia. የቅመማ ፡ ቅመም ፡ ንግድ ፡ ለዐረብ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ አመጣ

**spiced** (adj.), **be highly ~** ቅመም ፡ በዛበት
The meat is highly spiced. ሥጋው ፡ ቅመም ፡ በዝቶበታል

**(be) spick and span** በጣም ፡ ጸዳ
The house was spick and span. ቤቱ ፡ በጣም ፡ የጸዳ ፡ ነበር

**spicy** ቅመም ፡ የበዛበት
He likes spicy food. ቅመም ፡ የበዛበት ፡ ምግብ ፡ ይወዳል
*He tells spicy stories. ወሬ ፡ እየቀመመ ፡ ያወራል

**spider** ሸረሪት
The spider caught a fly. ሸረሪቷ ፡ አንድ ፡ ዝንብ ፡ ያዘች

**spiderweb** የሸረሪት ፡ ድር
The room is full of spiderwebs. ቤቱ ፡ የሸረሪት ፡ ድር ፡ ብቻ ፡ ነው

**spike** (v.)
1. በምስማር ፡ አያያዘ(ተያያዘ). The heavy boards were spiked to the beams. ትልልቆቹ ፡ ሳንቃዎች ፡ አውራጅ ፡ አግዳሚው ፡ ጋር ፡ በምስማር ፡ ተያይዘዋል
2. አከሸፈ(በት). The guard spiked the spy's attempt to escape. ዘበኛው ፡ ሰላዩ ፡ ለማምለጥ ፡ ያደረገውን ፡ሙከራ ፡ አከሸፈበት

**spike** (n.) ትልቅ ፡ ምስማር
The boards are fastened together by spikes. ሳንቃዎቹ ፡ በትልልቅ ፡ ምስማር ፡ ተያይዘዋል

**spill** (spilled, or spilt), vt.
1. አፈሰሰ. The waiter spilled soup on my dress. አሳላፊው ፡ ሾርባ ፡ ልብሴ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰብኝ
Try not to spill any sugar! ምንም ፡ ስኳር ፡ እን ዳታፈስ ፡ ተጠንቀቅ
2. ደፋ. Who spilled the milk? ወተቱን ፡ የደፋው ፡ ማነው ?

**spill** (vi.)
1. ሞልቶ ፡ ፈሰሰ. The water spilled over the dam. ውኃው ፡ ሞልቶ ፡ በግድቡ ፡ ላይ ፡ ፈሰሰ
2. ፈሰሰ. Water spilled from the pail. ከባልዲው ፡ ውስጥ ፡ ውኃ ፡ ፈሰሰ

**be spilled** ፈሰሰ
Blood was spilled in the riot. በረብሻው ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ፈሰሰ

**spilt**, see **spill**

**spin** (spun), vt.
1. ፈተለ. She spun the cotton. ጥጡን ፡ ፈተለችው
2. አሽከረከረ. The boy spun the top. ልጁ ፡ ጅ ልቦውን ፡ አሽከረከረ
3. ወረወረ. Spin a coin to see who goes. ፍራንክ ፡ ወርውርና ፡ ዕጣ ፡ የወጣበት ፡ ይሂድ
4. አወራ. The old man likes to spin stories of his youth. ሽማግሌው ፡ ሰው ፡ የወጣትነቱን ፡ ታ ሪክ ፡ ማውራት ፡ ይወዳል

**spin** (vi.) ተሽከረከረ
The top is spinning. ጅልቦው ፡ ይሽከረከራል
*His head spun from too much drink. ብዙ ፡ ስለጠጣ ፡ ምድር ፡ ሰማዩ ፡ ዞረበት

**spin around** ሽከርከር ፡ አለ
He spun around and faced me. ሽከርከር ፡ ብ ሎ ፡ ፊቱን ፡ ወደኔ ፡ አዞሮ ፡ ቆመ

**spin round** በፍጥነት ፡ ተሽከረከረ
The wheel spun round. ጎማው ፡ በፍጥነት ፡ ተሽከረከረ

**spin yarns**
*The old sailor loves to spin yarns about his life at sea. ሽማግሌው ፡ መርከበኛ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ያሳለፈውን ፡ ጊዜ ፡ በማስታወስ ፡ ወግ ፡ ማረቅ ፡ ይወዳል

**be spun evenly** ሰላላ ፡ ሞላላ ፡ የለበትም
The thread is spun evenly. ፈትሉ ፡ ሰላላ ፡ ሞላ ላ ፡ የሌለበት ፡ ነው

**send (someone) spinning to** ከ - - - ጋር ፡ አጋጨ
The blow sent him spinning to the wall. ምቱ ፡ ከግድግዳ ፡ ጋር ፡ አጋጨው

**spinach** [ተቀቅሎ ፡ የሚበላ ፡ አረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ ቅጠል]

**spinal column** አከርካሪ
His spinal column is broken. አከርካሪው ፡ ተሰ ብሯል ፡

**spindle** እንዝርት
The spindle pierced his thumb. እንዝርቱ ፡ አውራ ጣቱን ፡ ወጋው

**spine**
1. አከርካሪ. He broke his spine in the fall. ሲወድቅ ፡ አከርካሪው ፡ ተሰበረ
2. እሾክ. The cactus is covered with spines. ቁልቋሉ ፡ እሾክ ፡ ብቻ ፡ ነው

**spinster** ያላገባች ፡ ሴት
The spinster supports herself by sewing. ያላገባቿ ፡ ሴትዮ ፡ ልብስ ፡ በመስፋት ፡ ትተዳደራለች

**spiral** (v.) ተውለበለበ
The leaf spiraled to the ground. ቅጠሏ ፡ እየተውለበለበች ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ወረደች

**spiral** (n.) ጥምዝምዝ ፡ መሥመር
He drew a spiral on the blackboard. ጥምዝምዝ ፡ መሥመር ፡ በሰሌዳው ፡ ላይ ፡ ሣለ

**spiral** (adj.) ጠምዛዛ
A spiral staircase leads to the top of the tower. ጠምዛዛ ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ግንቡ ፡ ጫፍ ፡ ያወጣል

**spire** [እያደር ፡ እየሾለለ ፡ የሚሄድ ፡ የትልቅ ፡ ሕንጻ ፡ ጣሪያ ፡ ጫፍ]

**spirit** (v.), ~ **off** ማንም ፡ ሳያየው ፡ ወሰደ
The fox spirited off two chickens. ቀበሮዋ ፡ ማንም ፡ ሳያያት ፡ ሁለት ፡ ዶሮች ፡ ወሰደች

**be spirited away** በድብቅ ፡ ተወሰደ
She was spirited away in the dark of night. ሌሊት ፡ በድብቅ ፡ ተወሰደች

**spirit** (n.)
1. መንፈስ. The spirit is willing, but the flesh is weak. መንፈስ ፡ ጠንካራ ፡ ሲሆን ፡ ሥጋ ፡ ግን ፡ ደካማ ፡ ነው
The spirit of a law is more important than its words. ከቃሉ ፡ ይልቅ ፡ የሕጉ ፡ መንፈስ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
A spirit of reform marked the nineteenth century. ዐሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ምእተ ፡ ዓመት ፡ የመሻሻል ፡ መንፈስ ፡ የሰፈነበት ፡ ነው
2. ትጋት. Put a little spirit into your work! ሥራህን ፡ ትንሽ ፡ ትጋት ፡ ጨምርበት
3. የጋለ ፡ ስሜት. He answered with spirit. በጋለ ፡ ስሜት ፡ መለሰ
*They consider him a noble spirit because he is willing to help people in distress. የተቸገሩ ፡ ሰዎችን ፡ ለመርዳት ፡ ፈቃደኛ ፡ ስለሆነ ፡ ቸር ፡ መንፈስ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይገምቱታል
*That's the spirit! እንዲህ ፡ ነው !

**spirits** አልኮል
A ten percent tax will be paid on spirits. ለአልኮል ፡ ከመቶ ፡ ዐሥር ፡ ቀረጥ ፡ ይከፈላል

**(be) in good spirits** ደስ ፡ አለ(ው)
I hope you're in good spirits. ደስ ፡ እንዳለህ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ

**leading spirit** መሪ
He was one of the leading spirits of the reform. መሻሻልን ፡ ካስገኙት ፡ መሪዎች ፡ አንዱ ፡ እሱ ፡ ነበር

**(be) possessed by a spirit** ዛር ፡ ያዘው
Since the woman was possessed by a spirit, they called in a sorcerer. ሴትዮዋ ፡ ዛር ፡ ስለያዛት ፡ ጠንቋይ ፡ ጠሩላት
[See also 'evil, low, moving']

**spirited** ሞቅ ፡ ያለ
Her conversation was spirited. ጨዋታዋ ፡ ሞቅ ፡ ያለ ፡ ነበር

**spiritual**
1. መንፈሳዊ. Some people prefer a spiritual existence. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ መንፈሳዊ ፡ ኑሮን ፡ ይመርጣሉ
2. ረቂቅ. The physical world is perceived by the five senses; the spiritual world is not. ግዙፍ ፡ አካሎችን ፡ ባምስቱ ፡ ሕዋሳት ፡ ለማወቅ ፡ ስንችል ፡ ረቂቁን ፡ ግን ፡ አንችልም

**spit** (spat, or spit), vt. ተፋ
The children were spitting pumpkin seeds over the fence. ልጆቹ ፡ የዱባውን ፡ ፍሬ ፡ ባጥሩ ፡ ላይ ፡ ይተፉ ፡ ነበር
The guns were spitting fire. ጠመንጃዎቹ ፡ እሳት ፡ ይተፉ ፡ ነበር

**spit** (vi.)
1. ምራቅ ፡ ተፋ. Don't spit on the floor! ወለሉ ፡ ላይ ፡ ምራቅህን ፡ አትትፋ
2. ተፋ(በት). He spit in my face, and I became very angry. ፊቴ ፡ ላይ ፡ ስለተፋብኝ ፡ በጣም ፡ ተናደድኩ

**spit out** ተፋ
The baby spit out the food it was chewing. ሕፃኑ ፡ ያላምጥ ፡ የነበረውን ፡ ምግብ ፡ ተፋው
*Spit it out! አውጣት

**spit up** አስመለሰ
The baby spit up its dinner. ሕፃኑ ፡ የበላውን ፡ እራት ፡ አስመለሰው

**spit** (n.)
1. ለሀጭ. Wipe the spit off your chin! ለሀጭህን ፡ ከአገጭህ ፡ ላይ ፡ ጥረገው
2. [ሥጋ ፡ በእሳት ፡ ላይ ፡ ሲጠበስ ፡ የሚሰካበት ፡ ሹል ፡ የብረት ፡ ዘንግ]

**spite** (v.) አናደደ
He built a fence between his property and

mine just to spite me. እኔን ፡ ለማናደድ ፡ ሲል ፡ በኔና ፡ በሱ ፡ መሬት ፡ መካከል ፡ አጥር ፡ አጠረ

**spite** (n.)
1. ክፋት. He did it just for spite. ያደረገው ፡ ለ ክፋት ፡ ነው
2. እልህ. He built the fence out of spite. አጥሩን ፡ የተከለው ፡ ለእልህ ፡ ነው

**in spite of**
1. ብ + (imperfect) + ም. I went in spite of the rain. ቢዘንብም ፡ ከመሄድ ፡ አልቀረሁም
2. ብ + (imperfect) + ም ፡ እንኳ. In spite of his age, he still climbs mountains. ቢያረጅም ፡ እን ኳ ፡ አሁንም ፡ ተራራ ፡ ይወጣል

**spiteful** እልኸኛ
The spiteful little girl tore up her older sister's papers. እልኸኛዋ ፡ ልጃገረድ ፡ የታላቅ ፡ እኅ ቷን ፡ ወረቀቶች ፡ ቀደደች

**spittle** ለሀጭ ፤ አክታ
He wiped the spittle from the floor. ለሀጩን ፡ (አክታውን) ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ ጠረገ

**splash** (vt.)
1. ውኃ ፡ ረጨ(በት). The car splashed her dress. መኪናው ፡ ልብሷ ፡ ላይ ፡ ውኃ ፡ ረጨባት
2. (= pass.) ተፈናጠቀ. +Mud splashed our car. መኪናችን ፡ ጭቃ ፡ ተፈናጠቀበት

**splash** (vi.)
1. ተረጨ. The water splashes in all directions. ውኃው ፡ በያለበት ፡ ይረጫል
2. ተንቦራጨቀ. The baby likes to splash in his tub. ሕፃኑ ፡ በመታጠቢያው ፡ ውስጥ ፡ መንቦራ ጨቅ ፡ ይወዳል
3. ፈሰሰ. The paint splashed over the floor. ቀለሙ ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ፈሰሰ

**splash** (n.) የሚረጭ ፡ ውኃ
The splash of the cars on a rainy day is a nuisance to the pedestrians. በዝናብ ፡ ቀን ፡ መ ኪና ፡ የሚረጨው ፡ ውኃ ፡ ለእግረኞች ፡ ጠንቅ ፡ ነው
*There is a splash of mud on your face. ፊትህ ፡ ላይ ፡ ጭቃ ፡ ተረጭቶብሃል
*He jumped into the swimming pool with a splash. መዋኛው ፡ ውስጥ ፡ ዘሎ ፡ ሲገባ ፡ ውኃው ን ፡ አንቦራጨቀው

**make a big splash** ታየ(በት)
He made a big splash with his money and his new car. በገንዘቡና ፡ ባዲሱ ፡ መኪናው ፡ ታየበት

**splatter** ተረጨ
Water splattered everywhere. ውኃው ፡ በያለበት ፡ ተረጨ

**be splattered** ተፈናጠቀ
+His apparel was splattered with mud. ልብሱ ፡ ላይ ፡ ጭቃ ፡ ተፈናጥቆበት ፡ ነበር

**spleen** ጣፊያ
His spleen was removed in an operation. ጣፊያው ፡ በቀዶ ፡ ጥገና ፡ ወጣለት

**splendid** ግሩም ፤ የደመቀ
Today's ball game was splendid. የዛሬው ፡ ኳስ ፡ ጨዋታ ፡ ግሩም ፡ ነበር
The coronation of the king was a splendid pageant. የንጉሡ ፡ የዘወድ ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ ሥ ነ ፡ ሥርዓት ፡ የደመቀ ፡ ነበር

**splendor** ውበት
The splendor of the palace has to be seen to be believed. የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ውበት ፡ ለማ ድነቅ ፡ ማየት ፡ ያስፈልጋል

**of splendor** ዕጹብ ፡ ድንቅ
The palace is a thing of splendor. ቤተ ፡ መን ግሥቱ ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ የሆነ ፡ ሕንጻ ፡ ነው

**splice, ~ together** አቀጣጠለ
He spliced two cables together to make a single very long one. ሁለቱን ፡ ገመዶች ፡ አቀጣጥሎ ፡ አንድ ፡ ረጅም ፡ ገመድ ፡ ሠራ

**splint** [እግር ፡ ወይም ፡ እጅ ፡ ሲሰበር ፡ የተሰበረ ውን ፡ አጥንት ፡ እንዲጠግን ፡ የሚጠቀሙበት ፡ ከዕንጨት ፡ የተሠራ ፡ መጠገኛ]

**put in splints** በዕንጨት ፡ ጠገነ
He put his broken arm in splints. የተሰበረውን ፡ ክንዱን ፡ በዕንጨት ፡ ጠገነው

**splinter** (vt.) ሰነጠቀ
Lightning splintered the tree. ዛፉን ፡ መብረቅ ፡ ሰነጠቀው

**splinter** (vi.) ተሰነጣጠቀ
The glass splintered in the earthquake. መስታ ወቱ ፡ ከመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ የተነሣ ፡ ተሰነጣጠቀ

**splinter** (n.) ስንጥር
I have a splinter under my nail. ጥፍሬ ፡ ውስ ጥ ፡ ስንጥር ፡ ገባ

**splinter group** የተነጣዮች ፡ ጓድ
A splinter group separated from the party. የተነጣዮቹ ፡ ጓድ ፡ ከፓርቲው ፡ ተለየ

**split** (split), vt.
1. ፈለጠ. He split wood for the fire. ማገዶ ፡ ፈለጠ
2. ሰነጠቀ. The lightning split the tree from top to bottom. መብረቁ ፡ ዛፉን ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ሰነጠቀው

3. ተረተረ. The power of his blow split the wooden door. የምቱ ፡ ኀይል ፡ የዕንጨቱን ፡ መዝጊያ ፡ ተረተረው
4. ከፈለ. The enemy's conquest split the country in two. የጠላት ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ አገሪቱን ፡ እሁለት ፡ ከፈላት
5. ተካፈለ. They split the profit. ትርፉን ፡ ተካፈሉ

**split** (vi.)
1. ተሰነጠቀ. The wood split in the dry air. ዕንጨቱ ፡ ከድርቀት ፡ የተነሣ ፡ ተሰነጠቀ
2. ተከፈለ. The party has split into three groups. ፓርቲው ፡ በሦስት ፡ ተከፈለ

**split asunder** ሰነጣጠቀ
Lightning split the tree asunder. መብረቅ ፡ ዛፉን ፡ ሰነጣጠቀው

**split hairs**
*Don't split hairs; go on to the main point! ለቁንጫ ፡ መላላጫ ፡ ማውጣቱን ፡ ትተህ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ተናገር

**split up** ለየ
Split up a compound into its elements! ውሑዱን ፡ በየጥንተ ፡ ንጥሩ ፡ ለየው

**split** (n.)
1. ስንጥቅ. There is a split in this rock. በዚህ ፡ አለት ፡ ላይ ፡ ስንጥቅ ፡ አለ
2. መከፋፈል. The minister tried to heal the split in his party. ሚኒስትሩ ፡ በፓርቲው ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ መከፋፈል ፡ ለማስወገድ ፡ ሞከረ

**split** (adj.), **a ~ second** ከመቅጽበት
It took a split second to do it. ከመቅጽበት ፡ አለቀ

**splitting** የሚፈልጥ
I have a splitting headache. የሚፈልጥ ፡ የራስ ፡ ምታት ፡ ይዞኛል

**splurge**
1. አፈሰሰ. He splurged lots of money on her wedding. ለሰርጓ ፡ ብዙ ፡ ብር ፡ አፈሰሰ
2. ከሚገባው ፡ በላይ ፡ ገንዘብ ፡ አወጣ. He splurged and bought three suits. ከሚገባው ፡ በላይ ፡ ገንዘቡን ፡ አውጥቶ ፡ ሦስት ፡ ሙሉ ፡ ልብስ ፡ ገዛ

**splutter**
1. ተንቻቻ. The fat was spluttering in the frying pan. ቅባቱ ፡ መጥበሻው ፡ ላይ ፡ ይንቻቻ ፡ ነበር
2. እንትፍ ፡ እንትፍ ፡ አለ. He fell into the pool and came out spluttering. እመዋኛው ፡ ኩሬ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ እንትፍ ፡ እንትፍ ፡ ሲል ፡ ወጣ

**splutter out** ቀባጠረ
He spluttered out an excuse. ምክንያት ፡ ለመስጠት ፡ ቀባጠረ

**spoil** (vt.)
1. አበላሸ. She has spoiled all my fun. ደስታዬን ፡ ሁሉ ፡ አበላሸችብኝ
2. አሞላቀቀ. Her husband spoils her. ባሏ ፡ ያሞላቅቃታል
The mother is spoiling her child. እናትየዋ ፡ ልጇን ፡ ታሞላቅቀዋለች

**spoil** (vi.)
1. ተበላሸ. The meat will spoil. ሥጋው ፡ ይበላሻል
2. በሰበሰ. The apples are beginning to spoil. ቱፋዎቹ ፡ መበስበስ ፡ ጀምረዋል

**spoil (one's) appetite** ወስፋት ፡ ዘጋ
Don't spoil your appetite by eating sweets! ጣፋጭ ፡ ነገር ፡ በመብላት ፡ ወስፋትህን ፡ አትዝጋ

**spoil for a fight**
He is spoiling for a fight. አምባጓሮ ፡ ለማንሣት ፡ ይጋበዛል

**spoiled** (adj.) ሞልቃቃ
The spoiled child cried all day long. ሞልቃቃው ፡ ልጅ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ አለቀሰ

**spoils** የሰረቀው ፡ እቃ
The thieves divided the spoils among them. ሌቦቹ ፡ የሰረቁትን ፡ እቃ ፡ ተከፋፈሉ

**spoke** ሽቦ
Several spokes of the bicycle wheel were broken. የቢሲክሌቱ ፡ ሽቦዎች ፡ ብዙዎቹ ፡ ተሰብረዋል

**spoke,** see **speak**

**spokesman** ቃል ፡ አቀባይ
The spokesman made the announcement. ቃል ፡ አቀባዩ ፡ ማስታወቂያውን ፡ አሰማ

**sponge** (v.) በሰፍነግ ፡ ወለወለ
He sponged the car. መኪናውን ፡ በሰፍነግ ፡ ወለወለ

**sponge** (n.) ሰፍነግ
Where did you buy that sponge? ሰፍነጉን ፡ ከየት ፡ ገዛሽው ?

**sponsor** (v.)
1. ከፈለ(ለት). A rich man is sponsoring me so that I can go to college. አንድ ፡ ሀብታም ፡ ኮሌጅ ፡ እንድገባ ፡ ሊከፍልልኝ ፡ ነው
2. አካሄደ. The school is sponsoring the show. ቲያትሩን ፡ የሚያካሂደው ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ነው
3. አቀረበ. The two senators are sponsoring a bill to ban cigarette smoking. ሁለቱ ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ ሲጃራ ፡ ማጨስን ፡ የሚከለክል ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ አቅርበዋል

**sponsor** (n.)

1. ደጋፊ. We have to find a sponsor for the project. ለዚህ ፡ እቅድ ፡ ደጋፊ ፡ ማግኘት ፡ አለብን
2. ያቀረበ. The sponsor of the bill is the chairman of the committee. የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ ያቀረበው ፡ የደርጉ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ነው

**spontaneous**

1. በፈቃደኝነት ፡ የተደረገ. The demonstration was not spontaneous, but staged. ሰላማዊው ፡ ሰልፍ ፡ በፈቃደኝነት ፡ የተደረገ ፡ አልነበረም ፡ በትእዛዝ ፡ እንጂ
2. (= adv.) በድንገት. The fireman said that the fire was spontaneous. የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካዩ ፡ እሳቱ ፡ የተነሣው ፡ በድንገት ፡ ነው ፡ አለ
3. (= adv.) ባንዴ. There was a spontaneous burst of applause when the speaker finished his speech. ተናጋሪው ፡ ንግግሩን ፡ እንደጨረሰ ፡ ጭብጨባው ፡ ባንዴ ፡ ቀለጠ

**spool**

1. ጥቅል. Give me a spool of thread! አንድ ፡ ጥቅል ፡ ክር ፡ ስጠኝ
2. በከራ. Wind the thread on a spool! ክሩን ፡ በከራ ፡ ላይ ፡ አጠንጥነው

**spoon** (v.) ጨልፎ ፡ ፈሰስ ፡ አደረገ

She spooned the gravy on to the bread. ወጡን ፡ ጨልፋ ፡ ዳቦው ፡ ላይ ፡ ፈሰስ ፡ አደረገችው

**spoon** (n.) ማንኪያ ፤ ማንካ

The handle of the spoon is made of wood. የማንኪያው ፡ እጀታ ፡ ከዕንጨት ፡ የተሠራ ፡ ነው

**spoonful** ማንኪያ

A spoonful of sugar will sweeten the tea. አንድ ፡ ማንኪያ ፡ ስኳር ፡ ሻዩን ፡ ያጣፍጠዋል

**spoor** ፋና

He followed the spoor of the leopard for several miles. የነብሩን ፡ ፋና ፡ ለብዙ ፡ ማይል ፡ ተከተለ

**sporadic** (= adv.) አልፎ ፡ አልፎ

There were sporadic outbreaks of malaria in the south. በደቡብ ፡ በኩል ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ወባ ፡ ገብቶ ፡ ነበር

**sport** ስፖርት ፤ እስፖርት

Football is his favorite sport. የሚወደው ፡ ስፖርት ፡ የግር ፡ ኳስ ፡ ነው

**in sport** ለቀልድ ፡ ያህል

The man teased the child in sport. ሰውዬው ፡ ለቀልድ ፡ ያህል ፡ ልጁን ፡ አሾፈበት

**be a good sport**

*Jim was a good sport about giving up his turn. ጂም ፡ ተራውን ፡ ያሳለፈው ፡ በስፖርት ፡ መንፈስ ፡ ተመርቶ ፡ ነው

*Be a good sport and don't sulk! ፊትህ ፡ ፈታ ፡ ይበል ፤ አታኩርፍ

**be a poor sport** ጥሩ ፡ ስፖርተኛ ፡ አይደለም

He is a poor sport. If he doesn't win, he gets mad and walks off. ጥሩ ፡ ስፖርተኛ ፡ አይደለም ፤ ካላሸነፈ ፡ ተናዶ ፡ ይሄዳል

**sportsman** ስፖርተኛ ፤ እስፖርተኛ

The wealthy sportsman bought fishing and hunting equipment. ሀብታሙ ፡ ስፖርተኛ ፡ የዓሣ ፡ ማጥመጃና ፡ የአደን ፡ መሣሪያ ፡ ገዛ

**spot** (spotted)

1. ለይቶ ፡ ዐወቀ. I spotted him in the crowd. ከሕዝቡ ፡ መሃከል ፡ ለይቼ ፡ ዐወቅሁት
2. ለይቶ ፡ ደረሰ(በት). The teacher spotted every mistake. መምህሩ ፡ ስሕተቱን ፡ ሁሉ ፡ ለይቶ ፡ ደረሰበት
3. አመለከተ. The searchlight spotted a plane flying in the clouds. ባውዛው ፡ በደመናው ፡ ውስጥ ፡ የሚበረውን ፡ አውሮፕላን ፡ አመለከተ
4. አንጠባጠበ. She spotted her dress with sauce. ልብሷ ፡ ላይ ፡ ወጥ ፡ አንጠባጥባበታለች
5. አበላሸ. He spotted his reputation by lying. በመዋሸቱ ፡ ስሙን ፡ አበላሸ

**be spotted** ተንጠባጠበ

The table is spotted with ink. ጠረጴዛው ፡ ቀለም ፡ ተንጠባጥቦበታል

**spot** (n.)

1. ጠቃጠቆ. The white cloth has red spots. ነጩ ፡ ጨርቅ ፡ ቀይ ፡ ጠቃጠቆ ፡ አለበት
2. ቈሻሻ. You have a spot on your tie. ክራቫትህ ፡ ላይ ፡ ቈሻሻ ፡ አለ
3. ፍንጣቂ. There are spots of mud on your stocking. እግር ፡ ሹራብሽ ፡ የጭቃ ፡ ፍንጣቂ ፡ አለበት
4. ጠብታ. The cleaner said he couldn't get the spot off my coat. ልብስ ፡ አጣቢው ፡ ኮቴ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጠብታ ፡ ለማስለቀቅ ፡ አልቻልኩም ፡ አለ
5. ሽፍታ. Red spots are an external sign of measles. ቀያይ ፡ ሽፍታዎች ፡ የኩፍኝ ፡ ምልክቶች ፡ ናቸው
6. ምልክት. That spot on his cheek is a sore. በጉንጩ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ምልክት ፡ ቁስል ፡ ነው
7. ቦታ. I stood on the same spot for a solid hour. ካንድ ፡ ቦታ ፡ ሳልንቃነቅ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ቆምኩ

8. እንከን. His character is without a spot. ጠባዩ ፡ እንከን ፡ የለበትም

**hit the spot**
*This drink hits the spot. ይህ ፡ ልክ ፡ የምፈልገው ፡ ዓይነት ፡ መጠጥ ፡ ነው

**in spots** እልፍ ፡ እልፍ
My coat is threadbare in spots. ኮቴ ፡ እልፍ ፡ እልፍ ፡ ሳስቷል

**on the spot**
1. ወዲያውኑ. They fired him on the spot. ወዲያውኑ ፡ ከሥራ ፡ አስወጡት
2. እዚያው. I was on the spot when the plane crashed. አውሮፕላኑ ፡ ወድቆ ፡ ሲሰባበር ፡ እዚያው ፡ ነበርኩ

**put on the spot** በችግር ፡ ላይ ፡ ጣለ
The students put the teacher on the spot by publishing his letter against the director. ሥራ ፡ መሪውን ፡ በመቃወም ፡ የጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ አትሞ ፡ በማውጣት ፡ ተማሪዎቹ ፡ አስተማሪውን ፡ በችግር ፡ ላይ ፡ ጣሉት
[See also 'freeze, sore']

**spotless** ንጹሕ
The kitchen is spotless. ማድ ፡ ቤቱ ፡ ንጹሕ ፡ ነው

**be spotless**
His reputation is spotless. ዝናው ፡ እንከን ፡ አይወጣለትም

**spotlight** ባውዛ
The border guards have a large spotlight. ጠረፍ ፡ ጠባቂዎቹ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ባውዛ ፡ አላቸው

**be in the spotlight**
The President is always in the spotlight. ፕሬዚዳንቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ የሕዝብ ፡ ዓይን ፡ ያርፍበታል

**spotted** ቡራቡሬ
Young deer have spotted coats. ያጋዘን ፡ ግልገሎች ፡ ቆዳቸው ፡ ቡራቡሬ ፡ ነው

**spotty** ተለዋዋጭ
His work is spotty. ሥራው ፡ ተለዋዋጭ ፡ ነው

**be spotty** ጠቃጠቆ ፡ አለበት
His complexion is spotty. ፊቱ ፡ ጠቃጠቆ ፡ አለበት
*His attendance in class is spotty. ክፍል ፡ የሚገባው ፡ አንዳንዴ ፡ ነው

**spouse** ባለቤት
My spouse cannot come with me. ባለቤቴ ፡ አብራኝ ፡ ልትመጣ ፡ አትችልም

**spout** (vt.) ረጨ
The broken pipe was spouting water. የተሰበረው ፡ ቧምቧ ፡ ውኃ ፡ ይረጭ ፡ ነበር

**spout** (vi.) ተንቦለቦለ
Water spouted from a break in the pipe. ቧምቧው ፡ ተሰብሮ ፡ ውኃው ፡ ተንቦለቦለ

**spout up** ተረጨ
The fountain spouted up high. ምንጩ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ተረጨ

**spout** (n.)
1. ጡት. The spout of the coffeepot is broken. የጀበናው ፡ ጡት ፡ ተሰብሯል
2. አሸንዳ. Rain runs down a spout from our roof to the ground. የዝናብ ፡ ውኃ ፡ ከጣሪያችን ፡ ላይ ፡ ባሸንዳው ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ይፈሳል
*A spout of water shot up from the hole in the pipe. ውኃው ፡ ከቧምቧው ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ተረጨ

**sprain** ወለም ፡ አለ(ው)
+She sprained her ankle. ቁርጭምጭሚቷን ፡ ወለም ፡ አላት

**sprang**, see **spring**

**sprawl**
1. ተዘረጋ. He sprawled on the sofa and went to sleep. ሶፋው ፡ ላይ ፡ ተዘርግቶ ፡ እንቅልፍ ፡ ወሰደው
2. ዳኸ. The baby sprawled across the floor. ሕፃኑ ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ዳኸ
3. ተሞነጫጨረ. His handwriting sprawled across the page. ጽሕፈቱ ፡ በገጹ ፡ ሁሉ ፡ የተሞነጫጨረ ፡ ነው

**spray**
1. ውኃ ፡ አጠጣ. He's spraying the garden with a hose. ያትክልቱን ፡ ቦታ ፡ በቱቦ ፡ ውኃ ፡ በማጠጣት ፡ ላይ ፡ ነው
2. ውኃ ፡ ረጨ. The firemen sprayed the fire with a hose. የእሳት ፡ አደጋ ፡ ሠራተኞች ፡ ቃጠሎው ፡ ላይ ፡ በቧምቧ ፡ ውኃ ፡ ረጩ
3. ነፋ(በት). He sprayed the room with insecticide. ክፍሉን ፡ የቁንጫ ፡ መድኃኒት ፡ ነፋበት
4. ረፈረፈ. He sprayed the advancing troops with a machine gun. እየገፋ ፡ የመጣውን ፡ ጦር ፡ በመትረየስ ፡ ረፈረፈው

**spray** (n.) የሚረጭ ፡ ውኃ
The spray from the waterfall soaked me. ከፏፏቴው ፡ የሚረጨው ፡ ውኃ ፡ አራሰኝ

*A spray of bullets hit the tree behind which he was hiding. ተሸሽጎበት ፡ የነበረውን ፡ ዛፍ ፡ የጥይት ፡ በረዶ ፡ ወረደበት

**spread** (spread), vt.

1. ዘረጋ. The eagle spread its wings. ንስሯ ፡ ክንፎቿን ፡ ዘረጋች
2. አሰፋ. This hole is too narrow; we need something to spread it. ቀዳዳው ፡ በጣም ፡ ጠባብ ፡ ስለሆነ ፡ የምናሰፋበት ፡ ነገር ፡ ያስፈልገናል
3. ቀባ. He cut the bread in half and spread butter on it. ዳቦውን ፡ ከሁለት ፡ ቈርጦ ፡ ቅቤ ፡ ቀባው
   Spread some honey on the bread! ዳቦውን ፡ ማር ፡ ቀቢው
4. አነጠፈ. He spread a rug on the floor. አንድ ፡ ስጋጃ ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ አነጠፈ
5. አጋባ ፤ አራባ. Flies spread disease. ዝንቦች ፡ በሽታ ፡ ያጋባሉ ፡ (ያራባሉ)
6. ነዛ. He spread the rumor that the President was dead. ፕሬዚዳንቱ ፡ ሞቷል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ነዛ
7. አዛመተ. He spread the news of my divorce. የመፋታቴን ፡ ወሬ ፡ አዛመተው
8. ዐደለ. We spread the pamphets throughout the town. ጽሑፉን ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ዐደልነው
9. አሰራጨ. A model farm was set up to spread new farming methods. አዲስ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴዎችን ፡ ለማሰራጨት ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ እርሻ ፡ ተቋቋመ

**spread** (vi.)

1. ተነዛ. The news spread quickly. ወሬው ፡ ባንዴ ፡ ተነዛ
2. ተዛመተ. The fire is spreading rapidly. ቃጠሎው ፡ በፍጥነት ፡ ተዛመተ
   The sickness spread rapidly. በሽታው ፡ ቶሎ ፡ ተዛመተ
3. ተሰራጨ. Humanity has spread all over the world. የሰው ፡ ልጅ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ተሰራጭቷል
4. ተቀባ. The paint did not spread evenly. ቀለሙ ፡ ተስተካክሎ ፡ አልተቀባም

**spread abroad** ተሰራጨ
The news of his coming spread abroad. የመምጣቱ ፡ ወሬ ፡ ተሰራጨ

**spread apart** ለያየ
He spread the tables apart. ጠረጴዛዎቹን ፡ ለያያቸው

**spread cloth over** አለበሰ
Spread the cloth over the table! ጠረጴዛውን ፡ አልብሰው

**spread out** (vt.)

1. ዘረጋ. He spread out his arms to show how long the fish was. የዓሣውን ፡ ትልቅነት ፡ ለማሳየት ፡ እጁን ፡ ዘረጋ
2. አሰጣ. He spread out the cloth to dry. ጨርቁ ፡ እንዲደርቅ ፡ አሰጣው

**spread out** (vi.)

1. ወሰደ. Our trip spread out over two weeks. ጉዟችን ፡ ሁለት ፡ ሳምንት ፡ ያህል ፡ ወሰደ
2. ተንጣለለ. We saw the whole town spread out below us. ከተማው ፡ በሙሉ ፡ ከበታቻችን ፡ ተንጣሎ ፡ አየነው

**spread (over)** ወሰደ(በት)
His course of studies spreads over three years. ትምህርቱ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ይወስድበታል

**spread** (n.) መራባት ፤ መዛመት
They tried to check the spread of the disease. የበሽታውን ፡ መራባት ፡ (መዛመት) ፡ ለማገድ ፡ ሞከሩ

**spree, go an a ~** ጊዜውን ፡ በፈንጠዝያ ፡ አሳለፈ
The soldiers went on a spree when they were paid. ወታደሮቹ ፡ ደሞዛቸውን ፡ ባገኙ ፡ ጊዜ ፡ ጊዜያቸውን ፡ በፈንጠዝያ ፡ አሳለፉ

**go out on a buying spree** ገንዘቡን ፡ ዘራ
He goes out on a buying spree every payday. ደሞዝ ፡ በተከፈለ ፡ ቁጥር ፡ ገንዘቡን ፡ ይዘራል

**sprig** ቅጠል
He tore a sprig off the bush and chewed on it. ከቁጥቋጦው ፡ ላይ ፡ ቅጠል ፡ በጥሶ ፡ አኘከ

**sprightly** የሚቧርቅ
The sprightly kitten was leaping in the air trying to catch a fly. የምትቧርቀው ፡ የድመት ፡ ግልገል ፡ ዝምብ ፡ ለመያዝ ፡ ባየር ፡ ላይ ፡ ዘለለች

**spring** (sprang, sprung), v.

1. ተነሣ. All the rumors spring from one and the same source. ወሬው ፡ ሁሉ ፡ የሚነሣው ፡ ካንድ ፡ ምንጭ ፡ ነው
2. ዘሎ ፡ ተነሣ. He sprang from his seat. ከመቀመጫው ፡ ላይ ፡ ዘሎ ፡ ተነሣ
3. ወጣ. Sparks sprang from the fire. ፍንጣሪው ፡ ከእሳቱ ፡ ወጣ

**spring (at)** ዘሎ ፡ ተከመረ(በት)
The dog sprang at the thief. ውሻው ፡ ዘሎ ፡ ሌባው ፡ ላይ ፡ ተከመረበት

**spring back** ተፈናጥሮ ፡ ተመለሰ
A bent branch will spring back into its place. የዛፉን ፡ ቅርንጫፍ ፡ ስበው ፡ ሲለቁት ፡ ተፈናጥሮ ፡ ወደ ፡ ቦታው ፡ ይመለሳል

**spring (a) leak** ማፍሰስ ፣ ጀመረ
I need a new bucket; the old one has sprung a leak. አሮጌው ፣ ባልዲ ፣ ማፍሰስ ፣ ስለጀመረ ፣ አዲስ ፣ መግዛት ፣ ያስፈልገኛል

**spring out** ብቅ ፡ አለ
Flowers sprang out of the earth. አበባዎቹ ፡ ከ መሬት ፡ ብቅ ፡ አሉ

**spring to (one's) feet** ዘሎ ፡ ብድግ ፡ አለ
When the officer entered the room, the soldiers sprang to their feet. መኰንኑ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ወታደሮቹ ፡ ዘለው ፡ ብድግ ፡ አሉ

**spring up**
1. ሽው ፡ አለ. A cool breeze sprang up. ቀዝቃዛ ፡ ነፋስ ፡ ሽው ፡ አለ
2. ተሠራ. A town sprang up at that site. በዚያ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ከተማ ፡ ተሠራበት
*A doubt sprang up in her mind. ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ጥርጣሬ ፡ ገባት

**spring** (n.)
1. ጸደይ. Flowers bloom in spring. በጸደይ ፡ አበቦች ፡ ያብባሉ
2. ምንጭ. There is a spring behind our house. ከቤታችን ፡ ጀርባ ፡ ምንጭ ፡ አለ
3. ባሌስትራ. The spring of the truck is broken. የመኪናው ፡ ባሌስትራ ፡ ተሰብሯል
4. ሞላ. The spring of my watch is broken. የሰዓቴ ፡ ሞላ ፡ ተሰብሯል

**make a spring** ዘለለ
The dog made a spring toward us. ውሻው ፡ ወደኛ ፡ ዘለለ

**mineral spring** ጠበል
He went to a mineral spring to recuperate. ለማገገም ፡ ወደ ፡ ጠበል ፡ ሄደ

**springy**
*He walks with a springy step. ሲራመድ ፡ አፈስ ፡ አፈስ ፡ ይላል

**sprinkle** (vt.)
1. ውኃ ፡ አርከፈከፈ(በት). The gardener sprinkled the lawn. አትክልተኛው ፡ ያትክልቱን ፡ ቦታ ፡ ውኃ ፡ አርከፈከፈበት
2. አርከፈከፈ. The girl sprinkled water on the floor. ልጅቱ ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ውኃ ፡ አርከፈከፈች
3. ነሰነሰ(ተነሰነሰ). A powder made of sugar was sprinkled over the cake. በኬኩ ፡ ላይ ፡ የስኳር ፡ ዱቄት ፡ ተነስንሶ ፡ ነበር

**sprinkle** (vi.) አካፋ
It sprinkled this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ አካፋ

**sprinkle with**
1. አጠመቀ. The priest sprinkled the sick man with holy water. ቄሱ ፡ በሽተኛውን ፡ ጠበል ፡ አጠመቀት
2. በተነ. She sprinkled the floor with sand. ወለሉ ፡ ላይ ፡ አሸዋ ፡ በተነች

**sprinkle** (n.) ካፊያ
The sprinkle laid the dust. ካፊያው ፡ አቧራውን ፡ አስታገሠው

**sprinkling of** (= adv.) አልፎ ፡ አልፎ
There was a sprinkling of young people in the congregation. በምእመናኑ ፡ መካከል ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ልጅ ፡ እግሮች ፡ ይታዩ ፡ ነበር

**sprint** ሸመጠጠ
The runner sprinted for the goal. ሯጩ ፡ ሩጫው ፡ እሚያልቅበት ፡ ቦታ ፡ ለመድረስ ፡ ሸመጠጠ

**sprout** (vt.) አበቀለ
The rain has sprouted the beans. ዝናቡ ፡ ባቄላውን ፡ አበቀለው

**sprout** (vi.)
1. በቀለ. The beans sprouted in the rain. ዝናብ ፡ ሲያገኝ ፡ ጊዜ ፡ ባቄላው ፡ በቀለ
2. ብቅ ፡ ብቅ ፡ አለ. Gas stations sprouted along the new highway. ባዲሱ ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ የቤንዚን ፡ ማደያ ፡ ጣቢያዎች ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ አሉ

**sprout up** አደገ
How your children have sprouted up! ልጆችህ ፡ እንዴት ፡ አድገዋል !

**sprout** (n.) በቆልት
Bean sprouts cooked in oil are good to eat. በዘይት ፡ የተቀቀለ ፡ የባቄላ ፡ በቆልት ፡ ለመብል ፡ ጥሩ ፡ ነው

**sprouting grain** ቡቃያ
The frost killed the sprouting grain. ውርጩ ፡ ቡቃያውን ፡ አጠፋው

**spruce** (v.), ~ **up** ተኳኳለ
She spruced up while her boyfriend waited. እስክትኳኳል ፡ ድረስ ፡ የከንፈር ፡ ወዳጇ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ጠበቃት

**spruce** (adj.), **look** ~ (= tr.) ሸጋ ፡ አደረገ
+He looked very spruce in his new suit. አዲሱ ፡ ልብሱ ፡ ሸጋ ፡ አድርጎታል

**sprung**, see **spring**

**spry** ንቁ
The spry old lady traveled everywhere. ንቁዋ ፡ አሮጊት ፡ ወይዘሮ ፡ ብዙ ፡ ስፍራ ፡ ጐበኘች

**be spry**
*He's spry as a goat though he's nearly eighty. ሰማንያ ፡ ዓመት ፡ ቢሆነውም ፡ ሲራመድ ፡ የሚደርስበት ፡ የለም

**spume** አረፋ
Large pieces of spume were blown through the air. ብዙ ፡ አረፋ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በኖ ፡ ነበር

**spun,** see **spin**

**spur** (spurred), v.
1. ገፋፋ. The prize spurred everyone to work his hardest. ሽልማቱ ፡ ሁሉም ፡ ሰው ፡ ጠንክሮ ፡ እንዲሠራ ፡ ገፋፋው
2. ኰረኰረ. He spurred his horse. ፈረሱን ፡ ኰረኰረው

**spur** (n.) [ፈረሰኞች ፡ በጫማቸው ፡ ተረከዝ ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉት ፡ ከብረት ፡ የተሠራ ፡ መኰርኰሪያ]

**dig one's spurs into** ኰረኰረ
He dug his spurs into the horse's flank. ፈረሱን ፡ ኰረኰረው

**on the spur of the moment** አስቀድሞ ፡ ሳያስብ
He did it on the spur of the moment. አስቀድሞ ፡ ሳያስብ ፡ አደረገው

**spurious** የሐሰት
A spurious report stated that the boy had been killed by his mother. ልጁን ፡ የገደለችው ፡ እናቱ ፡ ናት ፡ የሚል ፡ የሐሰት ፡ ወሬ ፡ ተወራ

**spurn** በዘለፋ ፡ መለሰ
The judge spurned the bribe. ዳኛው ፡ ጉቦውን ፡ በዘለፋ ፡ መለሰው

**spurt** (v.)
1. ጢን ፡ አለ. Blood spurted from the cut in his arm. ከተቈረጠው ፡ ክንዱ ፡ ደም ፡ ጢን ፡ ይል ፡ ነበር
2. ተወረወረ. A jet of water spurted from the fountain. ውኃ ፡ ከምንጩ ፡ ውስጥ ፡ ተወረወረ
3. ጨመረ. Sales spurted greatly before Christmas. ከገና ፡ በፊት ፡ ገበያ ፡ በጣም ፡ ጨመረ

**spurt ahead** ፍጥነቱን ፡ በኀይል ፡ ጨመረ
When the runner behind him came close, he spurted ahead. ከኋላው ፡ ያለው ፡ ሯጭ ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ፍጥነቱን ፡ በኀይል ፡ ጨመረ

**spurt** (n.) መጣደፍ
There was a spurt of activity when the minister came into the office. ሚኒስትሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የሥራ ፡ መጣደፍ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**spurts of flame** ነበልባል
Spurts of flame appeared here and there on the building. ሕንጻው ፡ ላይ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነበልባል ፡ ታየ

**sputter** ሲፈናጠቅ ፡ ተንጫረጫረ
The fat sputters over the fire. ቅባት ፡ እሳት ፡ ላይ ፡ ሲፈናጠቅ ፡ ይንጫረጫራል

**sputter out** ቀባጠረ
He sputtered out an excuse. ምክንያት ፡ ሲሰጥ ፡ ቀባጠረ

**spy** (spied), v.
1. ሰለለ. He was sent by the enemy to spy on our camp. የጦራችንን ፡ ሰፈር ፡ ሊሰልል ፡ ከጠላት ፡ ተልኮ ፡ መጣ
2. ተከታተለ. I think he is spying on me. እኔን ፡ የሚከታተለኝ ፡ ይመስለኛል
3. ለየ. She spied a friend in the crowd. ጓደኛዋን ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ለየች

**spy out** ደረሰ(በት)
She spied out our plans. ምስጢራችንን ፡ ደረሰችበት

**spy** (spies), n. ሰላይ
The spy was caught and hanged. ሰላዩ ፡ ተይዞ ፡ ተሰቀለ

**squabble** (v.) ተነታረከ
Tom squabbles with his sister every day. ቶም ፡ በየቀኑ ፡ ከእኅቱ ፡ ጋር ፡ ይነታረካል

**squabble** (n.)
1. ንትርክ. Their squabble ruined the quiet of the house. ንትርካቸው ፡ ቤቱን ፡ ጸጥታ ፡ ነሣው
2. መነታረክ. I hate squabbles about unimportant things. በሆነ ፡ ባልሆነው ፡ መነታረክ ፡ አልወድም
3. ጭቅጭቅ. Can't you put an end to these squabbles? ይህንን ፡ ጭቅጭቅ ፡ ልታቆም ፡ አትችልም ?

**squad** ተነጣይ ፡ ጓድ
A squad was sent to reconnoiter the enemy lines. የጠላትን ፡ አቀማመጥ ፡ እንዲሰልል ፡ አንድ ፡ ተነጣይ ፡ ጓድ ፡ ተላከ
[See also 'firing"]

**squadron** እስኳድሮን
A squadron of planes flew overhead. አንድ ፡ እስኳድሮን ፡ አውሮፕላን ፡ በላያችን ፡ ላይ ፡ በሮ ፡ አለፈ

**squalid**
1. ደሳሳ. I saw a squalid hut made of old tin

cans in the village. መንደሩ ፡ ውስጥ ፡ ካርጊ ፡ ታኒካ ፡ የተሠራች ፡ ደሳሳ ፡ ጎጆ ፡ አየሁ
2. ቆሽሽ ፡ ያለ. The refugees live in squalid surroundings. ስደተኞቹ ፡ ቆሽሽ ፡ ባለ ፡ አካባቢ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ

**squalor** መቆሸሽ
The squalor of the town was frightening. የከተማው ፡ መቆሸሽ ፡ አሰቃቂ ፡ ነበር

**squander** አባከነ
He squandered his money on worthless things. በማይረባ ፡ ነገር ፡ ገንዘቡን ፡ አባከነ

**square** (vt.)
1. ማእዘን ፡ አወጣ. He squared the ends of the board. ለሳንቃው ፡ ጠርዞች ፡ ማእዘን ፡ አወጣ
2. አስተካከለ. This squares our account. ይህ ፡ ሒሳባችንን ፡ ያስተካክለዋል

**square** (vi.) ተመሳሰለ
His account does not square with mine. የሰጠው ፡ መግለጫ ፡ እኔ ፡ ከሰጠሁት ፡ ጋር ፡ አይስማማም

**square** (n.)
1. አደባባይ. Our windows look out on a large square. በመስኮታችን ፡ ትይዩ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ አደባባይ ፡ አለ
2. አራት ፡ ማእዘን. Arrange the chairs in a square! ወንበሮቹን ፡ ባራት ፡ ማእዘን ፡ ደርድር
Draw a square on this paper! በዚህ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ ሣል

**square** (adj.)
1. አራቱም ፡ ጐን ፡ እኩል ፡ የሆነ. I'd like a square box. አራቱም ፡ ጐን ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ ሣጥን ፡ እፈልጋለሁ
2. ካሬ. Our backyard is twenty square meters. ጓሮዋችን ፡ ሃያ ፡ ካሬ ፡ ሜትር ፡ ነው
3. ሐቀኛ. He will get a square deal at this shop. እዚህ ፡ ሱቅ ፡ ውስጥ ፡ እቃ ፡ በሐቀኛ ፡ ዋጋ ፡ ይሸጣል
4. የረባ. I haven't had a square meal in days. የረባ ፡ ምግብ ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ በልቼ ፡ አላውቅም
5. (= noun) ታማኝነት. He is known for his square dealings. በሚሠራው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ታማኝነቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**squash** (vt.)
1. ጨፈለቀ. She squashed the bug with her fingers. ትኋኑን ፡ በጣቷ ፡ ጨፈለቀችው
2. ደመሰሰ. The police squashed the uprising in Ireland. ፖሊሶች ፡ አይርላንድ ፡ ውስጥ ፡ ተነሥቶ ፡ የነበረውን ፡ ረብሻ ፡ ደመሰሱት

**squash** (vi.) ተጨመቀ
Grapes squash easily. ወይን ፡ በቀላሉ ፡ ይጨመቃል

**squash** (n.) ዱባ
I don't like to eat squash. ዱባ ፡ መብላት ፡ አልወድም

**squat** (squatted) ቁጢጥ ፡ አለ
He squatted on the ground and waited. መሬቱ ፡ ላይ ፡ ቁጢጥ ፡ ብሎ ፡ ቆየ

**squat,** adj. (= adv.) ቁጭ ፡ ብሎ.
I have a squat statue of Buddha. ቡድሀ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ የተቀረጸበት ፡ ሐውልት ፡ አለኝ

**squawk** ጮኸ
The parrot fell off the perch and squawked. በቀቀኑ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ጮኸ

**squeak** (v.) ሲጢጥ ፡ አለ
The rat squeaked when it got caught in the trap. አይጧ ፡ በወጥመዱ ፡ በተያዘች ፡ ጊዜ ፡ ሲጢጥ ፡ አለች

**squeak** (n.)
*I heard a squeak when the door opened. በሩ ፡ ሲከፈት ፡ ሲጢጥ ፡ ሲል ፡ ሰማሁት

**squeaking** (n.) ሲጢጥ ፡ የሚል ፡ ድምፅ
A drop of oil will silence that squeaking. አንድ ፡ ጠብታ ፡ ዘይት ፡ ቢደረግበት ፡ ሲጢጥ ፡ የሚለውን ፡ ድምፅ ፡ ያጠፋዋል

**squeaky** ሲጢጥ ፡ የሚል
The squeaky door rasps my nerves. ሲጢጥ ፡ የሚለው ፡ በር ፡ ያስቀጥጠኛል

**squeal**
1. ተንጫጫ. The children squealed with delight. ልጆቹ ፡ በደስታ ፡ ተንጫጩ።
2. ጮኸ. A pig squeals when it is slaughtered. አሳማ ፡ ሲታረድ ፡ ይጮኻል

**squeal** (n.)
*I heard the squeal of brakes. ፍሬን ፡ ሲጢጥ ፡ ሲል ፡ ሰማሁ

**(be) squeamish** አዘገነነ(ው)
+She is very squeamish and cannot stand the sight of bloody or slimy things. ደምና ፡ ሙልጭልጭ ፡ ነገር ፡ ስታይ ፡ በጣም ፡ ያዘገንናታል

**squeeze** (vt.)
1. ጨመቀ. I'll squeeze the oranges. ብርቱካኖቹን ፡ እጨምቃለሁ
2. ጨበጠ. Don't squeeze my hand so hard! እጄን ፡ በኀይል ፡ አትጨብጥ

3. ተጫነ. Don't squeeze the kitten! የድመቷን ፡ ግልገል ፡ አትጫናት
4. ጨመረ. I can't squeeze another thing into my trunk. ሌላ ፡ እቃ ፡ እሣጥኔ ፡ ውስጥ ፡ ለመጨመር ፡ አልችልም
5. እቅፍ ፡ አደረገ. She squeezed her child. ልጇን ፡ እቅፍ ፡ አደረገችው
6. አመቀ. They squeezed the people into the hall. ሕዝቡን ፡ አዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ አመቁት

**squeeze** (vi.) ተጨመቀ
Sponges squeeze easily. ሰፍነግ ፡ በቀላሉ ፡ ይጨመቃል

**squeeze from** አስተፋ
He squeezed money from the poor people. ድኾቹን ፡ ገንዘብ ፡ አስተፋቸው

**squeeze in**
*Can you squeeze in? If so, sit beside me. ተጣበህ ፡ ልትቀመጥ ፡ ትችላለህ? እንግዲያስ ፡ አጠገቤ ፡ ቁጭ ፡ በል

**squeeze out** በግድ ፡ አስከፈለ
The tax is intended to squeeze more money out of the public. ግብሩ ፡ የታቀደው ፡ ሕዝቡን ፡ በግድ ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ለማስከፈል ፡ ነው

**squeeze through** ተጣቦ ፡ አለፈ
The fat man squeezed through the narrow door. ወፍራሙ ፡ ሰውዬ ፡ በትንሹ ፡ በር ፡ ተጣቦ ፡ አለፈ
[See also 'pus']

**squelch** ወዲያውኑ ፡ ዝም ፡ አሰኘ
She squelched the quarrelsome child. ነጭናጫውን ፡ ልጅ ፡ ወዲያውኑ ፡ ዝም ፡ አሰኘችው

**squint** (v.) ዓይኑን ፡ ጨፈን ፡ አደረገ
He squints in order to see in the bright sunlight. በጠራራው ፡ ፀሐይ ፡ ውስጥ ፡ ለማየት ፡ እንዲችል ፡ ዓይኑን ፡ ጨፈን ፡ ያደርጋል

**make squint** አጨናበሰ
The bright sunlight made him squint. ኀይለኛው ፡ ፀሐይ ፡ አጨናበሰው

**squint** (n.)
*He has a squint in one eye. ሸውራራ ፡ ነው

**squirm** ተርመሰመሰ
I saw a worm squirming on the ground. ትል ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ሲርመሰመስ ፡ አየሁ

**squirm impatiently** ተቍነጠነጠ
The boy squirmed impatiently. ልጁ ፡ ተቍነጠነጠ

**squirrel** ሽኮኮ

**squirt** (vt.) ውኃ ፡ ረጨ(በት)
He squirted me with a hose. በላስቲክ ፡ ውኃ ፡ ረጨብኝ

**squirt** (vi.) ተፈናጥቆ ፡ ገባ
The lemon juice squirted in my eye. የሎሚው ፡ ውኃ ፡ ተፈናጥቆ ፡ ዓይኔ ፡ ውስጥ ፡ ገባ

**squirt** (n.) ፍንጣቂ
A squirt of water wet my shirt. የውኃ ፡ ፍንጣቂ ፡ ሸሚዜን ፡ አረጠበው

**stab** (stabbed), v.
1. ወጋ. He stabbed the man in the chest. ሰውዬውን ፡ እደረቱ ፡ ላይ ፡ ወጋው
2. ሰካ. He stabbed the knife into the man's chest. ሰንጢውን ፡ ሰውዬው ፡ ደረት ፡ ላይ ፡ ሰካው

**stab to the heart** ስሜቱን ፡ ጐዳው
The children's jeers stabbed Tom to the heart. የልጆቹ ፡ የፌዝ ፡ ሣቅ ፡ የቶምን ፡ ስሜት ፡ ጐዳው

**stab** (n.)
*He was bleeding from a stab in the chest. ደረቱን ፡ ስለተወጋ ፡ ደም ፡ ይፈሰው ፡ ነበር

**stab of pain**
*I felt a stab of pain in my side. ጐኔን ፡ ወጋኝ

**make a stab at** ሞከረ
Make a stab at an answer before giving up. ተስፋ ፡ ከመቍረጥህ ፡ በፊት ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ሞክር

**stability**
1. ጽናት. A concrete wall has more stability than a wooden fence. የሲሚንቶ ፡ ግድግዳ ፡ ከዕንጨት ፡ አጥር ፡ የበለጠ ፡ ጽናት ፡ አለው
2. ጠንካራነት. In particular, the book mentions the stability of Washington's character. መጽሐፉ ፡ በተለይ ፡ የዋሽንግተንን ፡ መንፈስ ፡ ጠንካራነት ፡ ይጠቅሳል
3. ጽኑ ፡ አቋም. The Greek government lacks stability and is expected to fall. የግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ጽኑ ፡ አቋም ፡ ስላጣ ፡ ይወድቃል ፡ ተብሎ ፡ ይጠበቃል

**stabilize**
1. ወሰነ. The government stabilized prices. መንግሥት ፡ የእቃን ፡ ዋጋ ፡ ወሰነ
2. ተቈጣጠረ. A small parachute stabilizes the fall of the paratrooper. ትንሽ ፡ ጃንጥላ ፡ ያየር ፡ ወለዱን ፡ አወራረድ ፡ ይቈጣጠራል

**stable** (n.) ጋጥ
I left my horse in the stable. ፈረሴን ፡ ጋጥ ፡ ውስጥ ፡ ተውኩት

**stable** (adj.)
1. የማይለዋወጥ. A stable currency is necessary for a balanced economy. ለተደላደለ ፡ ኤኮኖሚ ፡ የማይለዋወጥ ፡ ገንዘብ ፡ ያስፈልጋል
2. የረጋ. Many countries haven't had a stable government for years. ብዙ ፡ አገሮች ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ የረጋ ፡ መንግሥት ፡ አልነበራቸውም
3. ጽኑ. The stable foundation of this house was not affected by the earthquake. ጽኑ ፡ የሆነ ው ፡ የዚህ ፡ ቤት ፡ መሠረት ፡ በመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ አልተነካም
He has a stable personality, and you can rely on him. ጽኑ ፡ አቋም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ልትተማመንበት ፡ ትችላለህ

**stack** (v.) ከመረ
He stacked the dishes in the sink. ሳሕኖቹን ፡ ማጠቢያው ፡ ውስጥ ፡ ከመራቸው

**stack** (n.) ክምር
I had to look through a stack of newspapers for this article. ይህን ፡ ጽሑፍ ፡ ለማግኘት ፡ አንድ ፡ ክምር ፡ ጋዜጣ ፡ ማገላበጥ ፡ ነበረብኝ

**stacks** መጻሕፍት ፡ የተደረደሩበት ፡ ክፍል
Students are allowed to go to the stacks. ተማሪዎች ፡ መጻሕፍት ፡ እተደረደሩበት ፡ ክፍል ፡ ሊገቡ ፡ ይፈቀድላቸዋል

**stadium** እስታዲዮም
The game was held in the stadium. ጨዋታው ፡ የተደረገው ፡ እስታዲዮሙ ፡ ውስጥ ፡ ነበር

**staff** (n.)
1. ዘንግ. The shepherd leaned on his staff to rest. እረኛው ፡ ዘንጉ ፡ ላይ ፡ ደገፍ ፡ ብሎ ፡ እፎይ ፡ አለ
2. አባሎች. They captured a general and his entire staff. አንድ ፡ ጄኔራል ፡ ከመላው ፡ አባሎቹ ፡ ጋር ፡ ማረኩ
3. ሠራተኞች. The museum's staff is made of the director and his assistant. የቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ዲሬክተሩና ፡ ረዳቶቹ ፡ ናቸው
*Our school has a staff of fifteen teachers. ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ መምህራን ፡ አሉት

**general staff** የከፍተኛ ፡ ጦር ፡ መኰንኖች ፡ መምሪያ
The general staff does all the planning. የከፍተኛ ፡ ጦር ፡ መኰንኖች ፡ መምሪያ ፡ እቅዱን ፡ ሁሉ ፡ ያወጣል

**(be) staffed**
*The department is staffed with Ethiopians. የመምሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሠራተኞች ፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ናቸው

**stag** አጋዘን
The stag has long horns. አጋዘኑ ፡ ረጃጅም ፡ ቀንዶች ፡ አሉት

**stag party** [ወንዶች ፡ ብቻ ፡ ተካፋይ ፡ የሚሆኑበት ፡ ግብዣ]

**stage** (v.) አሳየ
They staged a play in the Haile Sellassie Theater. በቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ቲያትር ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ቲያትር ፡ አሳዩ

**stage a demonstration** ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ አደረገ
They staged a demonstration in front of the embassy. በኤምባሲው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ አደረጉ

**be staged**
*The demonstration was not spontaneous, but staged. ሰላማዊ ፡ ሰልፉ ፡ በፈቃደኝነት ፡ የተደረገ ፡ አልነበረም ፡ በትእዛዝ ፡ እንጂ
*The play was good, but poorly staged. ቲያትሩ ፡ ጥሩ ፡ ነበር ፡ አቀራረቡ ፡ ግን ፡ ጥሩ ፡ አልነበረም

**stage** (n.)
1. መድረክ. The stage was empty of actors. መድረኩ ፡ ላይ ፡ ተዋንያን ፡ አልነበሩም
2. ደረጃ. The decision depends on what stage the matter is in. ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ነገሩ ፡ ከምን ፡ ደረጃ ፡ እንደደረሰ ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል
3. የቲያትር ፡ ሙያ. She left the stage to marry. ለማግባት ፡ ብላ ፡ የቲያትር ፡ ሙያዋን ፡ ተወች
4. ቲያትር. Shakespeare wrote for the stage. ሼክስፒር ፡ ለቲያትር ፡ የሚሆን ፡ ድርሰት ፡ ጻፈ
5. ቦታ. France has been the stage of many wars. ፈረንሳይ ፡ ብዙ ፡ ጦርነት ፡ የተደረገበት ፡ ቦታ ፡ ነች

**by easy stages** አረፍ ፡ እያለ
They traveled by easy stages. አረፍ ፡ እያሉ ፡ ተጓዙ

**in stages** አንዳንድ ፡ እያለ
They completed the house by building it in stages. ቤቱን ፡ አንዳንድ ፡ እያሉ ፡ ሠርተው ፡ ጨረሱት

**stagger** (vt.)
1. አንገዳገደ. The blow staggered him. ዱላው ፡ አንገዳገደው
2. ግራ ፡ አጋባ. The loss of his fortune staggered him. ሀብቱን ፡ በማጣቱ ፡ ግራ ፡ አጋባው
3. (= pass.) ተደናገረ. The difficulty of the examination staggered him. ፈተናው ፡ ስለከበደው ፡ ተደናገረ

4. አፈራረቀ. All companies should stagger their office hours so that everyone won't get out of work at the same time. ሠራተኞች ፡ በሙሉ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዳይወጡ ፡ ኩባንያዎች ፡ ሁሉ ፡ የሥራ ፡ ሰዓታቸውን ፡ ማፈራረቅ ፡ አለባቸው

**stagger** (vi.) ተንገዳገደ
I saw him stagger out of the bar. ከመጠጥ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ እየተንገዳገደ ፡ ሲወጣ ፡ አየሁት

**be staggered** በጣም ፡ ደነገጠ
I was staggered to hear he was dead. መሞቱን ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ደነገጥኩ

**staggering**
1. የሚያንገዳግድ. He received a staggering blow. የሚያንገዳግድ ፡ ምት ፡ ተመታ
2. የሚያስደነግጥ. They heard staggering news about the battle. ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ የሚያስደነግጥ ፡ ወሬ ፡ ሰሙ

**be staggering** ራስ ፡ አዞረ
Prices are simply staggering. የእቃ ፡ ዋጋ ፡ ራስ ፡ ያዞራል

**stagnant**
1. የተኛ. The stagnant water was covered with green moss. የተኛውን ፡ ውኃ ፡ አረንጓዴ ፡ ሸፍኖታል
2. የታፈነ. The stagnant air makes me sick. የታፈነ ፡ አየር ፡ ጤና ፡ ይነሣኛል

**be stagnant** ቀዘቀዘ
During the summer, business is often stagnant. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በበጋ ፡ ንግድ ፡ ይቀዘቅዛል

**stagnate**
1. ሸተተ. The water of the pond will stagnate if no fresh water flows into it. የኩሬ ፡ ውኃ ፡ ከፈሳሽ ፡ ውኃ ፡ ካልተቀላቀለ ፡ ስለቆመ ፡ ይሸታል
2. ሳይንቀሳቀስ ፡ ኖረ. He stagnated in some remote post in the provinces. በጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሩቅ ፡ ከለ ፡ ቦታ ፡ ሳይንቀሳቀስ ፡ ኖረ

**stain** (v.)
1. አቆሸሸ. You have stained your vest. ሰደርያህን ፡ አቍሽሽኸዋል
2. አጐደፈ. His crimes stained the family's honor. የሠራቸው ፡ ወንጀሎች ፡ የቤተ ፡ ሰቡን ፡ ስም ፡ አጐደፉት

**be stained** ተበከለ
The tablecloth is all stained. የጠረጴዛው ፡ ልብስ ፡ ከዳር ፡ እስከዳር ፡ ተበክሏል

**stain** (n.)
1. ጠብታ ፤ ቆሻሻ ፤ እድፍ. The laundry could not get the food stains out of the shirt. የልብስ ፡ ንጽሕና ፡ መስጫው ፡ በሸሚዙ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ የምግብ ፡ ጠብታ ፡ ሊያስለቅቀው ፡ አልቻለም
I can't get the stain out of my dress. ቆሻሻውን ፡ ከልብሴ ፡ ላይ ፡ ማስለቀቅ ፡ አቃተኝ
The stain won't come out. እድፉ ፡ አይለቅም
2. ፍንጣቂ. His shirt was covered with stains which the sauce had left. ሸሚዙ ፡ የወጥ ፡ ፍንጣቂ ፡ ብቻ ፡ ነበር
3. እንከን. His character is without stain. ጠባዩ ፡ እንከን ፡ የለበትም
*There were bloodstains on his handkerchief. በመሐረቡ ፡ ላይ ፡ የደረቀ ፡ ደም ፡ ይታይ ፡ ነበር

**be a stain** አጐደፈ
The holocaust of the Jews is a stain in German history. የአይሁዶች ፡ እልቂት ፡ የጀርመንን ፡ ታሪክ ፡ የሚያጐድፍ ፡ ነው

**stained** (adj.) በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለም ፡ ያጌጠ
There is a large stained glass window in Africa Hall. ባፍሪካ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለም ፡ ያጌጠ ፡ የመስታወት ፡ መስኮት ፡ አለ

**stair** ደረጃ
She tripped on the top stair. የደረጃው ፡ አፋፍ ፡ አደናቀፋት

**staircase** ደረጃዎች
The staircase is covered with a rug. ደረጃዎቹ ፡ ምንጣፍ ፡ ተነጥፎባቸዋል

**stairway** ደረጃ
A circular stairway leads up to the balcony. እንደ ፡ ሐረግ ፡ የወጣው ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ሰገነት ፡ ያወጣል

**stake** (v.)
1. መወጣጫ ፡ ተከለ. Tomorrow we will stake the tomato plants. ነገ ፡ ለቲማቲሙ ፡ መወጣጫ ፡ እንተክላለን
2. ከለለ. The farmer staked a plot of ground. ገበሬው ፡ ማሳውን ፡ ከለለ

**stake a claim**
He staked a claim to the land. መሬቱ ፡ ላይ ፡ የባለቤትነት ፡ መታወቂያ ፡ ችካል ፡ ተከለበት

**stake** (n.)
1. ዕንጨት. The stakes for the fence were tipped with iron. ያጥሩ ፡ ዕንጨቶች ፡ በጫፋቸው ፡ ላይ ፡ ብረት ፡ ተሰክቶባቸዋል
2. ካስማ. Drive the stakes into the ground so that we can pitch the tent. ድንኳኑን ፡ ለመትከል ፡ እንድንችል ፡ ካስማዎቹን ፡ ቸክላቸው

3. ድርሻ. He has a stake in the business. በንግዱ ፡ ሥራ ፡ ድርሻ ፡ አለው
4. ገንዘብ. They were gambling for high stakes. ከፍ ፡ ባለ ፡ ገንዘብ ፡ ቁማር ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር

**be at stake**
1. ኪሳራ ፡ ነው. Too much is at stake for us to give up now. አሁን ፡ ነገሩን ፡ ብንተወው ፡ ኪሳራ ፡ ነው
2. አሰጋ. His life is at stake in this trial. አሁን ፡ የቀረበበት ፡ ክስ ፡ ለሕይወቱ ፡ የሚያሰጋ ው ፡ ነው

**(be) stale**
1. ደረቀ. The bread is stale. ዳቦው ፡ ደርቋል
2. ታፈነ. The air is stale. አየሩ ፡ ታፍኗል
*Their love affair is stale gossip. የመፋቀራቸው ፡ ወሬ ፡ ነፍሶበታል

**grow stale** ተዘነጋ(ው)
I haven't played the piano for years and have grown stale. ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ፒያኖ ፡ ስላል ተጫወትኩ ፡ ተዘንግቶኛል

**stalemate, reach a ~** የማይግባቡበት ፡ ደረ ጃ ፡ ላይ ፡ ደረሱ
The two countries reached a stalemate. ሁለቱም ፡ አገሮች ፡ የማይግባቡበት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ደረሱ

**stalk** (v.)
1. እያደባ ፡ ቀረበ. The cat stalked the rat. ድመቷ ፡ እያደባች ፡ ወደ ፡ አይጢ ፡ ቀረበች
2. ነጠቅ ፡ ነጠቅ ፡ እያለ ፡ ወጣ. The angry man stalked from the room. የተናደደው ፡ ሰው ፡ ነጠ ቅ ፡ ነጠቅ ፡ እያለ ፡ ከክፍሉ ፡ ወጣ
3. ፈታ. Terror stalked the city. ፍርሃት ፡ ከተማ ውን ፡ ፈታው

**stalk** (n.) አገዳ
A stalk of millet was hung over the door. የማሽላ ፡ አገዳ ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ነበር
He cut a stalk of sugar cane into six pieces. ሸንኮራው ፡ አገዳውን ፡ ስድስት ፡ ቦታ ፡ ቈረጠው

**stall** (vt.) ዛሬ ፡ ነገ ፡ እያለ ፡ አቆየ
He kept stalling his creditors because he had little cash. የነበረው ፡ ገንዘብ ፡ ትንሽ ፡ ስለነበር ፡ አበዳሪዎቹን ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ እያለ ፡ አቆያቸው

**stall** (vi.)
1. ዛሬ ፡ ነገ ፡ አለ. Stop stalling; do it right now! ዛሬ ፡ ነገ ፡ ማለቱን ፡ ትተህ ፡ አሁኑኑ ፡ ሥራው
2. ጠፋ. The motor has stalled again. ሞተሩ ፡ እ ንደገና ፡ ጠፋ

**stall** (n.)
1. በረት. The cow is in her stall. ላሟ ፡ በረት ፡ ውስጥ ፡ ነች
2. ጋጣ. He kept two mares in the stall. በጋጣው ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ባዝራ ፡ አሰረ
3. መደብር. I found this book in a little book-stall. ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ከንዲት ፡ ትንሽ ፡ የ መጽሐፍ ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ አገኘሁት

**stallion** ፈረስ
The stallion galloped in the field. ፈረሱ ፡ ሜ ዳውን ፡ በግልቢያ ፡ ዞረው

**stalwart**
1. ደኅና ፡ ሰውነት ፡ ያለው. The stalwart athletes leaped over the wall with little effort. ደኅና ፡ ሰውነት ፡ ያላቸው ፡ ስፖርተኞች ፡ አጥሩን ፡ ያ ለ ፡ ድካም ፡ ዘለሉት
2. ቈራጥ. He is a stalwart fighter for liberty. ለነጻነት ፡ የሚጋደል ፡ ቈራጥ ፡ ጠረኛ ፡ ነው

**stamina** ብርታት
He lacks the stamina needed to be a soldier. ወታደር ፡ ለመሆን ፡ የሚያስፈልገው ፡ ብርታ ት ፡ ይጐድለዋል

**stammer** (v.) ተንተባተበ
He stammered, so I couldn't understand him. ይንተባተብ ፡ ስለነበር ፡ የተናገረው ፡ ሊገባኝ ፡ አልቻልኩም

**stammering** መንተባተብ
His greatest disability is his constant stammering. የርሱ ፡ ትልቅ ፡ ጉድለቱ ፡ በየጊዜው ፡ መ ንተባተቡ ፡ ነው

**stamp** (vt.)
1. አተመ. I stamped all the documents. ሰነዶቹን ፡ ሁሉ ፡ አተምኳቸው
2. መሰከረ(ለት). His speech stamps him as an educated man. አነጋገሩ ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ መሆ ኑን ፡ ይመሰክርለታል
3. ቀረጸ(ተቀረጸ). His words were stamped on my mind. ንግግሩ ፡ በአእምሮዬ ፡ ውስጥ ፡ ተቀረጸ

**stamp** (vi.)
1. በእግሩ ፡ ረገጥ ፡ ረገጥ ፡ አደረገ. He stamped on the floor to see if it was sound. ወለሉ ፡ ጠንካ ራ ፡ መሆኑን ፡ ለማየት ፡ በእግሩ ፡ ረገጥ ፡ ረገ ጥ ፡ አድርጎ ፡ ሞከረው
2. ቆመ(በት). She stamped on a spider. ሸረሪቷ ፡ ላይ ፡ ቆመችባት

**stamp (one's) foot** መሬቱን ፡ ረገጠ
He stamped his foot in rage. በንዴት ፡ መሬቱ ን ፡ ረገጠ

**stamp out**
1. በእግሩ ፡ አጠፋ. He stamped out the fire. እሳቱን ፡ በእግሩ ፡ አጠፋው
2. ደመሰሰ(ተደመሰሰ). In Greece, all opposition was ruthlessly stamped out. ግሪክ ፡ ውስጥ ፡ ተቃዋሚዎቹ ፡ ሁሉ ፡ በጭካኔ ፡ ተደመሰሱ
3. እመር ፡ እመር ፡ እያለ ፡ ወጣ. The angry boy stamped out of the room. የተናደደው ፡ ልጅ ፡ እመር ፡ እመር ፡ እያለ ፡ ከክፍሉ ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ

**be stamped with** ተነበበ
+His face was stamped with fear. በፊቱ ፡ ላይ ፡ ፍርሃት ፡ ይነበብ ፡ ነበር

**stamp** (n.)
1. ማኅተም. I lost my stamp for putting my name on things. ስሜን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ የማትምበት ፡ ማኅተም ፡ ጠፋብኝ
2. ቴምብር. Did you put stamps on the letters? ደብዳቤዎቹ ፡ ላይ ፡ ቴምብር ፡ ለጠፍክባቸው ?
3. ምልክት. Her face bears the stamp of suffering. ፊቷ ፡ የመከራ ፡ ምልክት ፡ ይታይበታል

**stampede** [የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ በድንገት ፡ መበርገግና ፡ መፈርጠጥ]

**stanch**, see **staunch**

**stand** (stood), vt.
1. አቆመ. Stand it in the corner! ከጥግ ፡ አቁመው
2. ቻለ. Who will stand the cost? ዋጋውን ፡ ማን ፡ ይችላል ?
This suitcase will stand years of hard use. ሻንጣው ፡ መከራ ፡ ይችላል
I can't stand the pain any longer. ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ሥቃዩን ፡ አልችለውም
3. አለፈ. It has stood the test well. ፈተናውን ፡ በደኅና ፡ አልፏል
4. ታገሠ. I can't stand that fresh kid. ያንን ፡ ዐይን ፡ አውጣ ፡ ልጅ ፡ ልታገሠው ፡ አልችልም

**stand** (vi.)
1. ቆመ. They stood in line to get into the theater. ወደ ፡ ቲያትሩ ፡ ለመግባት ፡ በሰልፍ ፡ ቆሙ
2. ተነሣ. He stood when she entered the room. እሷ ፡ ስትገባ ፡ ተነሣ
3. ተደገፈ. The broom stood in a corner. መጥረጊያው ፡ እጥግ ፡ ተደግፏል
4. እንደጸና ፡ ቆየ ፤ ጸና. My orders stand until I cancel them. እኔ ፡ እስክሽራቸው ፡ ድረስ ፡ ትእዛዞቼ ፡ እንደጸኑ ፡ ይቆያሉ
I stand by my decision. ባልኩት ፡ እጸናለሁ
5. ተከራከረ. I stand on my rights. ለመብቴ ፡ እከራከራለሁ
6. ተመሠረተ. The case stands on his testimony. ጉዳዩ ፡ በሱ ፡ ምስክርነት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው
7. ቆየ. The house has stood two hundred years and will stand a century more. ቤቱ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ቆይቷል ፤ ወደፊትም ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ይቆያል
8. ነው. The amount now stands at $600. ሒሳቡ ፡ አሁን ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ነው
The house stands close by the river. ቤቱ ፡ ወንዙ ፡ አጠገብ ፡ ነው
*Where do you stand in your class? በክፍልህ ፡ ስንተኛ ፡ ነህ ?
*Tears stood in her eyes. ዓይኖቿ ፡ እንባ ፡ አቀረሩ

**stand about** ቆመ
People were standing about in small groups. ሰዎች ፡ ስብስብ ፡ ስብስብ ፡ ብለው ፡ ቆመው ፡ ነበር

**stand against** ተቋቋመ
One man stood alone against the enemy. አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ጠላትን ፡ ተቋቋመ

**stand apart**
1. ፈንጠር ፡ ብሎ ፡ ተገኘ. This house stands apart from the others. ይህ ፡ ቤት ፡ ከሌሎች ፡ ቤቶች ፡ ፈንጠር ፡ ብሎ ፡ ይገኛል
2. ተራርቀው ፡ ቆሙ. They stood three steps apart. ሦስት ፡ እርምጃ ፡ ተራርቀው ፡ ቆሙ

**stand aside** ዞር ፡ አለ(ለች)
Stand aside and let him pass! ዞር ፡ በልለትና ፡ ይለፍ

**(not) stand aside** ወደ ፡ ኋላ ፡ አላለም
He is a man who never stands aside when something needs to be done. መሠራት ፡ የሚገባው ፡ ነገር ፡ ሲኖር ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አይልም

**stand back**
1. ገባ ፡ አለ. The house stands back from the road. ቤቱ ፡ ከመንገዱ ፡ ገባ ፡ ብሎ ፡ ነው
2. ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመለሰ. The policemen ordered us to stand back. ፖሊሱ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንድንመለስ ፡ አዘዘን

**stand by**
1. ዝም ፡ አለ. How can you stand by and watch when some cruelty like that is being done? እንዲህ ፡ ያለ ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ እንዴት ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ታያለህ ?
2. ተጠባበቀ. Please stand by while I fix the radio! ራዲዮኑን ፡ እስክሠራ ፡ ተጠባበቅ
*Stand by for the latest news bulletin! በቅርቡ ፡ የደረሰውን ፡ ዜና ፡ እናሰማችኋለን

**stand by one**
1. ደገፈ. She stood by him when he was in trouble. ችግር ፡ ባጋጠመው ፡ ጊዜ ፡ ደገፈችው

2. ደረሰ(ለት). You know that I'll stand by you in case of trouble. በችግር ፡ ጊዜ ፡ እንደምደርስልህ ፡ ታውቃለህ

**stand by (one's) word** ቃሉን ፡ አላጠፈም
You can count on him to stand by his word. ቃሉን ፡ እንደማያጥፍ ፡ ልታምን ፡ ትችላለህ

**stand (a) chance** ዕድል ፡ አለው
I am afraid you don't stand a chance of getting the job. ሥራውን ፡ ለማግኘት ፡ ምንም ፡ ዕድል ፡ ያለህ ፡ አይመስለኝም

**stand corrected**
I stand corrected. ስሕተቴን ፡ አምናለሁ

**stand for**
1. ደገፈ. He stands for equality. እኩልነትን ፡ ይደግፋል
2. አመለከተ. U.S.A. stands for "United States of America". ዩ ፡ ኤስ ፡ ኤ ፡ የሚለው ፡ ዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ኦፍ ፡ አሜሪካ ፡ የሚለውን ፡ ያመለክታል
3. አልወደደም. The teacher said he would not stand for talking during class. መምህሩ ፡ በትምህርት ፡ ጊዜ ፡ ተማሪዎች ፡ ሲያወሩ ፡ አይወድም
*We admire democracy, and all it stands for. ዲሞክራሲንና ፡ ዓላማውን ፡ ሁሉ ፡ እናደንቃለን

**stand (one's) ground** እምነቱን ፡ አለወጠም
We stood our ground despite the criticism leveled against us. ምንም ፡ እንኳን ፡ ትችት ፡ ቢሰነዘርብን ፡ እምነታችንን ፡ አለወጥንም

**stand off** አልበገር ፡ አለ
Our troops stood off the attack for several hours. ወታደሮቻችን ፡ ላያሌ ፡ ሰዓቶች ፡ ያህል ፡ አጥቂዎቹን ፡ አንበገር ፡ አሉ

**stand on end** ቆመ
His hair stood on end with anger. በንዴት ፡ ጸጉሩ ፡ ቆመ

**stand out**
1. ማንም ፡ ለየው. +She stands out in a crowd. በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ማንም ፡ ይለያታል
2. የሚደርስበት ፡ የለም ፤ ማንም ፡ አያክለው. He stands out in physics. በፊዚክስ ፡ የሚደርስበት ፡ የለም ፡ (ማንም ፡ አያክለው)

**stand over** አጥብቆ ፡ ተቈጣጠረ
If I don't stand over him, he will make all kinds of foolish mistakes. አጥብቄ ፡ ካልተቈጣጠርኩት ፡ የማይረባ ፡ ስሕተቶች ፡ ያደርጋል

**stand still** አልተንቃነቀም
Stand still while I take your picture. ፎቶግራፍ ፡ ሳነሣህ ፡ አትንቃነቅ

**(it) stands to reason** ማስረጃው ፡ ያሳምናል
It stands to reason that he was already here when the bank was robbed. ባንኩ ፡ ሲዘረፍ ፡ እዚያ ፡ እንደነበረ ፡ ማስረጃው ፡ ያሳምናል

**stand trial** ለፍርድ ፡ ቀረበ
He must stand trial for his crime. ስለፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ለፍርድ ፡ መቅረብ ፡ አለበት

**stand up**
1. ተነሣ. You have to stand up when you are introduced. ከሰው ፡ ጋር ፡ ስትተዋወቅ ፡ መነሣት ፡ አለብህ
2. በረከተ. Wool stands up better than silk. ከሐር ፡ ይልቅ ፡ ሱፍ ፡ ይበረከታል
3. ተቀባይነት ፡ አገኘ. The case will never stand up in court. ጉዳዩ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ተቀባይነት ፡ አያገኝም

**(not) stand up** ዘላቂነቱ ፡ አጠራጠረ
His theory won't stand up under examination. ዕንሰ ፡ ሐሳቡ ፡ ሲመረመር ፡ ዘላቂነቱ ፡ ያጠራጥራል
*Don't bother standing up! በእግዚር ፡ ተቀመጥ

**stand up for** ደገፈ
If we don't stand up for him, nobody will. እኛ ፡ ካልደገፍነው ፡ ማንም ፡ አይደግፈውም

**stand up to**
1. እሺ ፡ አላለም. Why don't you stand up to your boss once in a while? አንዳንዴም ፡ አለቃህ ፡ የሚያዝህን ፡ ሁሉ ፡ እሺ ፡ አትበለው ?
2. ተቋቋመ. It takes backbone to stand up to such a big man. እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ለመቋቋም ፡ ቈራጥነት ፡ ይጠይቃል

**stand well** ተግባብቶ ፡ ኖረ
He stands well with his employers. ካለቆቹ ፡ ተግባብቶ ፡ ይኖራል

**stand with one** ሐሳቡን ፡ ደገፈ
I stand with you in this matter. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ሐሳብህን ፡ እደግፋለሁ
*I want to know where I stand with you. ካንተ ፡ ጋር ፡ ያለኝን ፡ ግንኙነት ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ እፈልጋለሁ

**as it stands** አሁን ፡ ባለበት ፡ ሁኔታ
You can have it as it stands for fifty dollars. አሁን ፡ ባለበት ፡ ሁኔታ ፡ በኀምሳ ፡ ብር ፡ ልትገዛ ፡ ትችላለህ

**as things stand** ባሁኑ ፡ ሁኔታ
As things stand, your prospects aren't very good. ባሁኑ ፡ ሁኔታ ፡ ያለህ ፡ ዕድል ፡ ጥሩ ፡ አይደለም

**can stand** ተቀበለ
The minister can stand criticism. ሚኒስትሩ ፡ ነቀፌታ ፡ ይቀበላሉ

**let stand** አቆመ
Don't let him stand outside! አውጭ ፡ አታቁመው
[See also 'alone, aloof, close, fast, foot, guard, hair, idle, innocent, leg, reason, respectful, shoulder, united']

**stand** (n.)
1. መደብ. They have a stand on the market. እገበያው ፡ ውስጥ ፡ መደብ ፡ አላቸው
2. ማቢያ. Is there a cab stand near here? እዚህ ፡ አካባቢ ፡ የታክሲ ፡ ማቢያ ፡ አለ ?
3. መድረክ. The general sat in the reviewing stand during the parade. ጄኔራሉ ፡ በሰልፉ ፡ ጊዜ ፡ በመመልከቻው ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ቆመ
4. ሐሳብ ፤ አቋም. He has changed his stand on this matter several times. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ሐሳብ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ለዋውጧል
He clarified his stand with a definite statement. አቋሙን ፡ በግልጽ ፡ አስረዳ

**make a stand against** ተቋቋመ
They made a stand against the enemy. ጠላታቸውን ፡ ተቋቋሙ

**take (one's) stand** ቆመ
Take your stand at the door! በመዝጊያው ፡ አጠገብ ፡ ቁም

**take (the) stand** ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀረበ
He took the stand and testified against me. ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ መሰከረብኝ

**standard**
1. ሥነ ፡ ሥርዓት. He didn't live up to the standard expected of a priest. ቄስ ፡ ሊኖረው ፡ የሚገባውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አልጠበቀም
2. አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሆነ ፡ መደበኛ ፡ ደንብ. The government sets the standards for pure food and drugs. መንግሥት ፡ ለንጹሕ ፡ ምግብና ፡ መድኃኒት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሆነ ፡ መደበኛ ፡ ደንብ ፡ ያወጣል
3. ደረጃ. Our school has high standards of teaching. የትምህርት ፡ ቤታችን ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ ከፍተኛ ፡ ነው
4. የተፈለገ ፡ ደረጃ. Your work is not up to standard. ሥራህ ፡ ከተፈለገው ፡ ደረጃ ፡ አልደረሰም
5. ሰንደቅ ፡ ዓላማ. The royal standard is flying above the palace. ንጉሣዊው ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ላይ ፡ ይውለበለባል
*You can't judge him by ordinary standards. ከማንም ፡ ጋር ፡ ልታወዳድረው ፡ አትችልም

**living standards** የኑሮ ፡ ደረጃ
Longevity is increasing because living standards are improving. የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ እየተሻሻለ ፡ በመሄዱ ፡ ዕድሜ ፡ እየጨመረ ፡ ይሄዳል

**standard** (adj.)
1. የተወሰነ. We need standard weights and measures. የተወሰነ ፡ መመዘኛና ፡ መለኪያ ፡ ያስፈልገናል
2. ዋና. His book is a standard reference work on modern history. መጽሐፉ ፡ ለዘመናዊ ፡ ታሪክ ፡ መረጃ ፡ ዋና ፡ ምንጭ ፡ ነው
*Headlights are standard equipment on all cars. የፊት ፡ መብራቶች ፡ በሁሉም ፡ መኪናዎች ፡ ላይ ፡ መኖር ፡ አለባቸው

**standardize**
1. ወሰነ (ተወሰነ). Weights and measures have been standardized to facilitate trade. ንግድ ፡ በደንብ ፡ እንዲካሄድ ፡ የመመዘኛና ፡ የመለኪያ ፡ ዓይነቶች ፡ ተወስነዋል
2. አንድ ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ ሰጠ. Radio and television have begun to standardize American speech. ሬዲዮና ፡ ቴሌቪዥን ፡ ለአሜሪካኖች ፡ ንግግር ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ መስጠት ፡ ጀምረዋል

**standard of living** የኑሮ ፡ ደረጃ
Their standard of living is lower than ours. የኑሮ ፡ ደረጃቸው ፡ ከኛ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ነው

**standard time**
Does Ethiopia have standard time? ኢትዮጵያ ፡ የግሪንዊች ፡ ሰዓት ፡ አቈጣጠር ፡ አላት ?

**stand-in**
1. እንደራሴ. The President uses a stand-in for important ceremonies. ፕሬዚዳንቱ ፡ ባንዳንድ ፡ ትልልቅ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ ላይ ፡ እንደራሴ ፡ ይልካሉ
2. ምትክ. For dangerous scenes, actors use stand-ins. አስቸጋሪ ፡ በሆኑ ፡ ባንዳንድ ፡ ትርእይቶች ፡ ውስጥ ፡ ተዋንያን ፡ በምትክ ፡ ይገለገላሉ

**standing** (n.) ደረጃ
He has a high standing in the community. በኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደረጃ ፡ አለው

**of standing** ስመ ፡ ጥር
He is a merchant of standing in the community. በኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ነጋዴ ፡ ነው

**of long standing**
1. የቆየ. It is difficult to right injustices of long standing. የቆየን ፡ በደል ፡ ለማስተካከል ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. የረጅም ፡ ጊዜ. They are friends of long standing. የረጅም ፡ ጊዜ ፡ ጓደኞች ፡ ናቸው

**standing** (adj.)
1. ቋሚ. The housewife has a standing order for a dozen eggs each day. የቤት ፡ እመቤቷ ፡

በየቀኑ ፡ አንድ ፡ ደርዘን ፡ እንቁላል ፡ እንዲመጣላት ፡ ቋሚ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥታለች
I need a standing lamp for this room. ለዚህ ፡ ክፍል ፡ ቋሚ ፡ መብራት ፡ እፈልጋለሁ
2. የረጋ. Standing water is not clean. የረጋ ፡ ውኃ ፡ ንጹሕ ፡ አይደለም

**standoffish** ሰው ፡ የማይቀርብ ፤ ሰው ፡ የማይወድ
He is hard to get to know because he is so standoffish. ሰው ፡ ስለማይቀርብ ፡ ጠባዩን ፡ ለማወቅ ፡ ያስቸግራል
His natural reserve makes people think that he is standoffish. ገለልተኛነቱ ፡ ሰው ፡ የማይወድ ፡ ያስመስለዋል

**standpoint** አቋም
What is your standpoint on the women's vote? ስለ ፡ ሴቶች ፡ ድምፅ ፡ መስጠት ፡ ያንተ ፡ አቋም ፡ ምንድነው ?

**standstill, come to a** ~ ተቋረጠ
Work came to a standstill when the workers went on strike. ሠራተኞቹ ፡ ሥራ ፡ ባቆሙ ፡ ጊዜ ፡ ሥራው ፡ ተቋረጠ

**roll to a standstill** ቀጥ ፡ አለ
The car rolled to a standstill. መኪናዋ ፡ ቀጥ ፡ አለች

**stank,** see **stink**

**staple** (v.) አያያዘ
Staple these papers together! እነዚህን ፡ ወረቀቶች ፡ አያይዛቸው

**staple** (n.)
1. ዋና ፡ ሰብል. Cotton is the staple in many southern states. ጥጥ ፡ በብዙ ፡ የደቡብ ፡ ክፍለ ፡ ሀገሮች ፡ ውስጥ ፡ ዋና ፡ ሰብል ፡ ነው
2. ዋና ፡ ምግብ. Bread is a staple of the Ethiopian diet. እንጀራ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ዋና ፡ ምግብ ፡ ነው
3. የወረቀት ፡ ማያያዣ. I need some staples for these papers. ለነዚህ ፡ ወረቀቶች ፡ ጥቂት ፡ የወረቀት ፡ ማያያዣ ፡ ያስፈልገኛል

**stapler** ወረቀት ፡ መስፊያ
My stapler is broken. ወረቀት ፡ መስፊያዬ ፡ ተሰብሯል

**star** (v.) የኮከብ ፡ ምልክት ፡ አደረገ(በት)
The teacher starred all the foreign words. መምህሩ ፡ የባዕድ ፡ ቃላት ፡ የሆኑትን ፡ ሁሉ ፡ የኮከብ ፡ ምልክት ፡ አደረገባቸው

**star** (n.)
1. ኮከብ. The sky is full of stars. ሰማዩ ፡ ኮከብ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. መሪ ፡ ተዋናይ. What is the name of the star of that film? የዚያ ፡ ፊልም ፡ መሪ ፡ ተዋናይ ፡ ስሙ ፡ ማነው ?
*It was not in our stars to win today. ለማሸነፍ ፡ ዛሬ ፡ ዕድላችን ፡ አልነበረም

**falling star** ተወርዋሪ ፡ ኮከብ
Look, a falling star! ተወርዋሪ ፡ ኮከብ ፡ ተመልከት !

**see stars** ምድር ፡ ሰማዩ ፡ ዞረበት
He saw stars when he bumped his head. በራሱ ፡ በተጋጨ ፡ ጊዜ ፡ ምድር ፡ ሰማዩ ፡ ዞረበት
[See also 'shooting star']

**starch** (v.) አሚዶ ፡ አደረገ(በት)
Did you starch the shirts? ሸሚዞቹ ፡ ላይ ፡ አሚዶ ፡ አደረግህበት ?

**starch** (n.) አሚዶ
Don't put starch in my shirt! ሸሚዜ ፡ ላይ ፡ አሚዶ ፡ አታድርግበት

**stare** (v.)
*He just stares into space. ዝም ፡ ብሎ ፡ ፈዞ ፡ ያያል
*Death stared him in the face. ከሞት ፡ አፋፍ ፡ ነበረ

**stare at** አፍጥጦ ፡ አየ ፤ ፍጥጥ ፡ ብሎ ፡ አየ
It's bad manners to stare at people. ሰውን ፡ አፍጥጦ ፡ ማየት ፡ (ፍጥጥ ፡ ብሎ ፡ ማየት) ፡ ብልግና ፡ ነው

**stare** (n.), **with a vacant** ~ ፍዝዝ ፡ ብሎ
He sat there with a vacant stare on his face. ፍዝዝ ፡ ብሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር

**stark,** adj. (= adv.) ሙሉ ፡ በሙሉ
That boy is talking stark nonsense. ልጁ ፡ የሚናገረው ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ነው
*He was stark naked. እርቃኑን ፡ ሥጋውን ፡ ነበር
*He was stark raving mad. ጨርቁን ፡ ጥሏል
*The rat lay stark in death. አይጧ ፡ ሞታ ፡ ደርቃለች

**starry**
*Her starry eyes express her happiness. ያይኖቿ ፡ ብሩህ ፡ መሆን ፡ መደሰቷን ፡ ይገልጻል

**be starry** ኮከብ ፡ ብቻ ፡ ነበር
Last night was a starry night. ትናንት ፡ ማታ ፡ ሰማዩ ፡ ኮከብ ፡ ብቻ ፡ ነበር

**start** (vt.)
1. ጀመረ. The boys started fighting. ልጆቹ ፡ መደባደብ ፡ ጀመሩ
2. አመነጨ. Who started this rumor? ይህንን ፡ ወሬ ፡ ማን ፡ አመነጨው ?
3. አቋቋመ. He decided to start a business. አንድ ፡ ንግድ ፡ ለማቋቋም ፡ ወሰነ
4. አስነሣ. He couldn't start the motor. ሞተሩን ፡ ማስነሣት ፡ አቃተው
5. ቀሰቀሰ. The dog started a rabbit from its burrow. ውሻው ፡ ጥንቸሏን ፡ ከጐሬዋ ፡ ቀሰቀሳት
6. ቀሰቀሰ(በት). The smoke started her coughing. ጭሱ ፡ ሳሏን ፡ ቀሰቀሰባት

**start** (vi.)
1. ተጀመረ. The concert has just started. የሙዚቃው ፡ ጨዋታ ፡ ገና ፡ መጀመሩ ፡ ነው
2. መሄድ ፡ ጀመረ. The train started slowly. ባቡሩ ፡ በዝግታ ፡ መሄድ ፡ ጀመረ
3. ሄደ. He started for Ethiopia last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሄደ
4. ተነሣ. How did the fire start? ቃጠሎው ፡ እንዴት ፡ ተነሣ ?
The car didn't start this morning. የመኪናው ፡ ሞተር ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ አልተነሣም
5. ድንግጥ ፡ አለ. She started when he came up behind and touched her on the shoulder. ከኋላዋ ፡ ድንገት ፡ ትከሻዋን ፡ ሲነካት ፡ ድንግጥ ፡ አለች

**start out**
1. ጀመረ. He started out to write a novel. አንድ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ መጻፍ ፡ ጀመረ
2. ለመሄድ ፡ ተነሣ. He started out on a long journey. ረጅም ፡ መንገድ ፡ ለመሄድ ፡ ተነሣ

**start up** ተፈጠረ
Lots of difficulties have started up. ብዙ ፡ ችግር ፡ ተፈጥሯል

**make (one) start** አስበረገገ
The noise made her start. ጩኸቱ ፡ አስበረገጋት

**to start with** መጀመሪያ ፡ ነገር
To start with, we haven't enough cups. መጀመሪያ ፡ ነገር ፡ በቂ ፡ ሲኒ ፡ የለንም
[See also 'fire, scratch']

**start** (n.) መጀመሪያ
He saw the race from start to finish. እሽቅድምድሙን ፡ ከመጀመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ተመለከተ

**from start to finish** ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር
I read the book from start to finish in one day. መጽሐፉን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ አነበብኩት

**get off to a start** ተነሣ
I have to get off to an early start. በጧት ፡ መነሣት ፡ አለብኝ

**give (one) a start** አስደነገጠ
The noise of the car gave me a start. የመኪናው ፡ ጩኸት ፡ አስደነገጠኝ

**head start** አቫንስ
Give me a head start! አቫንስ ፡ ስጠኝ

**starting, ~ today** ከ--- ፡ ጀምሮ
Starting today, the bus will stop here. ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ አውቶቡሱ ፡ እዚህ ፡ ይቆማል

**starting point** መነሻ ፡ ስፍራ
We haven't reached the starting point yet. መነሻው ፡ ስፍራ ፡ ገና ፡ አልደረስንም

**startle** (vt.)
1. አስደነገጠ. The noise startled me. ጩኸቱ ፡ አስደነገጠኝ
2. አደናገረ. The discord in modern music startles many people. የዘመናዊ ፡ ሙዚቃ ፡ አለመቀነባበር ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያደናግራል
3. አስገረመ. He made a discovery that startled the world. ዓለምን ፡ ያስገረመ ፡ ፍልሰፋ ፡ አደረገ

**startle** (vi.) ደነገጠ
He startled at the sound of my voice. ድምፄን ፡ ሲሰማ ፡ ደነገጠ

**be startled**
1. ደነገጠ. I was startled when my boss caught me unexpectedly while I was sitting sleeping instead of working. ያለ ፡ ሥራ ፡ ተቀምጬ ፡ ሳንቀላፋ ፡ አለቃዬ ፡ ድንገት ፡ ስለመጣብኝ ፡ ደነገጥኩ
2. ደነበረ. The mule was startled when she heard the hyena. በቅሎዋ ፡ የጅቡን ፡ ጩኸት ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ደነበረች

**startling** አስገራሚ
He made a startling discovery. አስገራሚ ፡ ነገር ፡ ፈለሰፈ
*He made a startling discovery : his wallet was gone. ቦርሳው ፡ መጥፋቱን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ደነገጠ

**starvation** ረኃብ
Starvation afflicts India from time to time. ህንድን ፡ በየጊዜው ፡ ረኀብ ፡ ያጠቃታል

**starvation diet**
He lives on a starvation diet. የሚበላው ፡ እንዳይሞት ፡ ያህል ፡ ነው

**starve** (vt.) ምግብ ፡ እንዳያገኝ ፡ አደረገ
They starved the enemy into surrendering. ጠላትን ፡ ምግብ ፡ እንዳያገኝ ፡ በማድረግ ፡ እጁን ፡ እንዲሰጥ ፡ አደረጉት

**starve** (vi.)
1. ተራበ. Thousands of people starved. ብዙ ፡ ሺ ፡ ሰዎች ፡ ተራቡ
2. ራበ(ው). +I ate little for lunch today, and now I'm starving. ለምሳ ፡ ብዙ ፡ ስላልበላሁ ፡ አሁን ፡ እርቦኛል
3. ጓጓ. During the war, I starved for news. በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ወሬ ፡ ለመስማት ፡ በጣም ፡ ጓጉቼ ፡ ነበር

**starve out**
*They wanted to starve us out. ምግብ ፡ እንዳናገኝ ፡ አግደው ፡ ካለንበት ፡ ሊያስወጡን ፡ ፈለጉ

**starve to death** በረኃብ ፡ ሞተ
He is his parents' mainstay; without him, they would starve to death. የወላጆቹ ፡ ዋና ፡ ደጋፊ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ እሱ ፡ ባይኖር ፡ በረኃብ ፡ ይሞቱ ፡ ነበር

**starving**
1. በረኃብ ፡ የሚሠቃይ ፤ ረኀብተኛ. The agency is trying to alleviate the condition of starving farmers. ድርጅቱ ፡ በረኃብ ፡ የሚሠቃዩትን ፡ (የረኀብተኞቹን) ፡ ገበሬዎች ፡ ሁኔታ ፡ ለማቃለል ፡ በመጣጣር ፡ ላይ ፡ ነው
2. የተራበ. The starving children are a piteous sight. የተራቡት ፡ ልጆች ፡ ለሚያያቸው ፡ ያሳዝናሉ

**be starving for affection** ናፈቀ(ው)
The children were starving for their mother's affection. ልጆቹ ፡ የእናታቸው ፡ ፍቅር ፡ ናፍቋቸዋል

**state** (v.)
1. ተናገረ. You just stated that you were not there. እዚያ ፡ አልነበርኩም ፡ ብለህ ፡ ይኸው ፡ አሁን ፡ ተናገርክ
2. ጠቀሰ (ተጠቀሰ). The truth is as stated above. እውነተኛው ፡ ነገር ፡ ከላይ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ነው
3. ወሰነ. Let's state a time and place for the meeting! ስብሰባ ፡ የምናደርግበትን ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ እንወስን
4. አቀረበ. The lawyer stated the case briefly. ጠበቃው ፡ ክርክሩን ፡ ባጭሩ ፡ አቀረበ
5. ገለጸ. State the facts precisely! ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ በትክክል ፡ ግለጽ

**state** (n.)
1. አገር. Ethiopia is the dominant state in the Horn of Africa. ኢትዮጵያ ፡ በአፍሪካ ፡ ቀንድ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለች ፡ አገር ፡ ናት
2. ግዛት. Texas is the largest state in the U.S.A. ቴክሳስ ፡ በአሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ ግዛቶች ፡ ሁሉ ፡ ትልቁ ፡ ነው
3. መንግሥት. The railroads are owned by the state. የባቡሩ ፡ ኩባንያ ፡ የመንግሥት ፡ ነው
4. ወግና ፡ ማዕረግ. Kings lived in great state. ነገሥታት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ወግና ፡ ማዕረግ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር
5. ይዞታ. What is the state of Ethiopian agriculture? የኢትዮጵያ ፡ ግብርና ፡ ይዞታ ፡ እንዴት ፡ ነው?
*She is in such a state today! መንፈሷ ፡ ዛሬ ፡ እንዴት ፡ ተሸብሯል !

**state of affairs** ሁኔታ
Anything is better than the present state of affairs. አሁን ፡ ካለው ፡ ሁኔታ ፡ ሌላ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ይሻላል

**(of) humble state**
He is a man of humble state. ከድኻ ፡ ቤተሰብ ፡ የተወለደ ፡ ሰው ፡ ነው

**lie in state** [ታላቅ ፡ ሰው ፡ ሲሞት ፡ ሬሳው ፡ በክብር ፡ ቦታ ፡ ሆኖ ፡ ለሰው ፡ እሚታይበት]

**occasions of state** ልዩ ፡ ልዩ ፡ የበዓል ፡ ቀናት
The regal robes are worn on occasions of state. የክብር ፡ ልብሶች ፡ የሚለበሱት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የበዓል ፡ ቀናት ፡ ነው

**persons in every state of life** ትንሽ ፡ ትልቁ ፡ ሳይቀር
Persons in every state of life attended the funeral. ትንሽ ፡ ትልቁ ፡ ሳይቀር ፡ በቀብሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ ተገኝቶ ፡ ነበር

**(be) received in state**
The Emperor was received in state. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የክብርና ፡ የወዳጅነት ፡ አቀባበል ፡ ተደረገላቸው
[See also 'natural, satellite, wild']

**stated** (adj.)
1. የተወሰነ. Registration sheets will be distributed at stated times. የመመዝገቢያ ፡ ወረቀቶች ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ይታደላሉ
2. የሰጠው. His stated motives are not in accord with his actions. የሰጣቸው ፡ ምክንያቶች ፡ ከሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ አይስማሙም

**stateless** ዜግነት ፡ የሌለው
Stateless persons may be granted passes, but not passports. ዜግነት ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ጊዜያዊ ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ እንጂ ፡ ፓስፖርት ፡ አይሰጣቸውም

**stately** ግርማ ፡ ያለው
The Emperor lives in a stately palace. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግርማ ፡ ባለው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ

**statement**
1. የሚለው. His statements are not to be trusted. እሱ ፡ የሚለውን ፡ ማመን ፡ አይቻልም
2. ቃል. We have to check on his statements. ቃሉን ፡ ማጣራት ፡ አለብን
3. መግለጫ. He made a clear statement on the accident. ስለደረሰው ፡ አደጋ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ መግለጫ ፡ ሰጠ
4. አነጋገር. That was a bold statement. የድፍረት ፡ አነጋገር ፡ ነበር
5. አባባል. Such statements are hard to prove. እንዲህ ፡ ያለውን ፡ አባባል ፡ ለማረጋገጥ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
6. የሒሳብ ፡ መግለጫ. My bank sends me a statement every month. ባንኩ ፡ በየወሩ ፡ የሒሳቤን ፡ መግለጫ ፡ ይልክልኛል
7. ዕዳውን ፡ የሚገልጽ ፡ የሒሳብ ፡ ዝርዝር. This store sends its customers monthly statements. ይህ ፡ መደብር ፡ በየወሩ ፡ ለደንበኞቹ ፡ ዕዳቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ የሒሳብ ፡ ዝርዝር ፡ ይልካል

**stateroom** ልዩ ፡ ክፍል
Reserve a stateroom for me on the train! ባቡሩ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ያዝልኝ

**statesman**
1. የፖለቲካ ፡ ሰው. Abraham Lincoln was a famous American statesman. አብርሃም ፡ ሊንከልን ፡ የታወቀ ፡ አሜሪካዊ ፡ የፖለቲካ ፡ ሰው ፡ ነበር
2. መሪ. There is a wide gap between the views of the two statesmen. በሁለቱ ፡ መሪዎች ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ ያስተያየት ፡ ልዩነት ፡ አለ
3. የሀገር ፡ መሪ. He is a veritable statesman. የታወቀ ፡ የሀገር ፡ መሪ ፡ ነው

**static** (n.) የሬዲዮን ፡ መንጫጫት
Static makes radio broadcasts hard to hear. የሬዲዮኑ ፡ መንጫጫት ፡ የሚተላለፈውን ፡ ፕሮግራም ፡ ለመስማት ፡ ያስቸግራል

**static** (adj.) የላሸቀ
A static mind produces no new ideas. የላሸቀ ፡ አእምሮ ፡ አዲስ ፡ ሐሳቦችን ፡ አያፈልቅም
*The country remained in a static condition for years. አገሪቱ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ከለችበት ፡ ሳትንቀሳቀስ ፡ ቆየች

**station** (v.) አቆመ
They stationed a guard at the gate. በሩፉ ፡ ላይ ፡ ዘበኛ ፡ አቆሙ

**be stationed** ተመደበ
The Ethiopian fleet is stationed in Massawa. የኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ ምፅዋ ፡ ተመድበዋል
Troops have been stationed at the border crossing. በወሰኑ ፡ መተላለፊያ ፡ ላይ ፡ ወታደሮች ፡ ተመድበው ፡ ነበር

**station** (n.)
1. ጣቢያ. I met him at the bus station. በአውቶቡስ ፡ ጣቢያ ፡ አገኘሁት
What stations can you get on your radio? ሬዲዮንህ ፡ ምን ፡ ምን ፡ ጣቢያ ፡ ማስተላለፍ ፡ ይችላል ?
2. የተመደበለት ፡ ስፍራ. The policeman took his station at the gate. ፖሊሱ ፡ በሩፉ ፡ ላይ ፡ የተመደበለትን ፡ ስፍራ ፡ ያዘ
*A judge is a man of high station. ዳኛ ፡ በኅብረ ፡ ሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**people in all stations of life** ትንሽ ፡ ትልቁ
People in all stations of life are represented in parliament. ትንሽ ፡ ትልቁ ፡ በፓርላማ ፡ ውስጥ ፡ እንደራሴ ፡ አለው
[See also 'service']

**(be) stationary**
1. ካለበት ፡ ሊንቀሳቀስ ፡ አይችልም. This machine is stationary. ይህ ፡ ሞተር ፡ ካለበት ፡ ሊንቀሳቀስ ፡ አይችልም
2. ቁጥሩ ፡ ሳይጨምር ፡ ቆየ. The population of the town has been stationary for ten years. የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥሩ ፡ ሳይጨምር ፡ ለዐሥር ፡ ዓመታት ፡ ቆይቷል
3. እንዳለ ፡ ቆየ. Prices were kept stationary during the war. በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ የእቃ ፡ ዋጋዎች ፡ እንዳሉ ፡ ቆዩ

**remain stationary** ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ
Though the dog rushed at him, the child remained stationary. ምንም ፡ እንኳ ፡ ውሻው ፡ እየሮጠ ፡ ቢመጣበት ፡ ልጁ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ

**stationery**
1. ጽሕፈት ፡ መሣሪያ ፡ መደብር. Go to the stationery and buy me five pencils. ወደ ፡ ጽሕፈት ፡ መሣሪያው ፡ መደብር ፡ ሂድና ፡ አምስት ፡ እርሳስ ፡ ግዛልኝ
2. የጽሕፈት ፡ መሣሪያ. I need some new stationery. አዲስ ፡ የጽሕፈት ፡ መሣሪያ ፡ እፈልጋለሁ

**statistics** ስታቲስቲክስ
The Ministry of Education issues statistics on the students every year. ትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ በያመቱ ፡ የተማሪዎች ፡ ስታቲስቲክስ ፡ ያወጣል

**statuary** ሐውልቶች
The statuary in the garden is lovely. ያትክልት ፡ ቦታው ፡ ሐውልቶች ፡ የሚያስደስቱ ፡ ናቸው

**statue** ሐውልት
The statue is made of bronze. ሐውልቱ ፡ የተሠራው ፡ ከነሐስ ፡ ነው

**stature**
1. ቁመት. He is a man of average stature. ቁመቱ ፡ መጠነኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ነው
2. ክብር. George Washington was a man of great stature among his countrymen. ጆርጅ ፡ ዋሽንግተን ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ትልቅ ፡ ክብር ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነበር

**short of stature** አጭር
He is short of stature. አጭር ፡ ነው

**status**
1. ሁኔታ. Diplomats are interested in the status of world affairs. ዲፕሎማቶች ፡ ያለምን ፡ ሁኔታ ፡ ይከታተላሉ
2. ሥልጣን. He has no official status in the government. በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ በይፋ ፡ የታወቀ ፡ ሥልጣን ፡ የላቸውም
3. ቦታ. A doctor has high status in our society. ሐኪም ፡ በኅብረ ፡ ሰባችን ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ አለው
4. ክብር. Some people feel that a big car gives them status. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ትልቅ ፡ መኪና ፡ ክብር ፡ የሚሰጣቸው ፡ ይመስላቸዋል

**status quo** ያለው ፡ ሁኔታ
This political party prefers the status quo. ይህ ፡ የፖለቲካ ፡ ቡድን ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ ይመርጣል

**statute** ደንብ
All government statutes are published in the Official Gazette. ማንኛቸውም ፡ የመንግሥት ፡ ደንቦች ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ይወጣሉ

**staunch** (adj.)
1. የልብ. He is a staunch friend. የልብ ፡ ጓደኛዬ ፡ ነው
2. (= adv.) በቈራጥነት. Our forces put up a staunch defense. ጦራችን ፡ በቈራጥነት ፡ ተከላከለ
3. (= adv.) አጥብቆ. He is a staunch supporter of reform. መሻሻልን ፡ አጥብቆ ፡ የሚደግፍ ፡ ሰው ፡ ነው

**stave** (staved, or stove), ~ **a hole** በሳ
The heavy waves stove a hole in the side of the ship. ኀይለኛው ፡ ሞገድ ፡ መርከቡን ፡ ጐኑ ፡ ላይ ፡ በሳው

**stave off** አስቀረ
He wasn't able to stave off the accident, but he slowed down in time to avoid much damage. አደጋውን ፡ ለማስቀረት ፡ ባይችልም ፡ ከባድ ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስ ፡ አደጋውን ፡ ሳይፈጽም ፡ ቀስ ፡ አለ
*The lost travelers ate birds' eggs to stave off starvation. የጠፉት ፡ መንገደኞች ፡ እንዳይርባቸው ፡ የወፍ ፡ እንቁላል ፡ በሉ

**stave** (n.)
1. [ለበርሜል ፡ መሥሪያ ፡ የሚያገለግል ፡ ጥርብ ፡ ዕንጨት]
2. በትር. The old man carried a stave in his hand. ሽማግሌው ፡ ሰው ፡ በትር ፡ ይዘዋል

**stay** (vt.)
1. አስታገሠ. He ate some bread and butter to stay his hunger. ረኃቡን ፡ ለማስታገሥ ፡ ዳቦ ፡ በቅቤ ፡ በላ
2. ዘለቀ. This horse won't stay the distance in a long race. ይህ ፡ ፈረስ ፡ ረጅም ፡ እርቀት ፡ ያለውን ፡ እሽቅድምድም ፡ አይዘልቅም
3. አዘገየ. The teacher stayed judgment till he could hear both sides. መምህሩ ፡ ሁለቱም ፡ ወገን ፡ የሚለውን ፡ እስኪሰማ ፡ ድረስ ፡ ውሳኔውን ፡ አዘገየው

**stay** (vi.)
1. ቆየ. I stayed there for a long time. እዚያ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆየሁ
2. አረፈ. Will you be staying with friends when you go to Addis Ababa? አዲስ ፡ አበባ ፡ ስትሄድ ፡ የምታርፈው ፡ ወዳጆችህ ፡ ዘንድ ፡ ነው ?
3. ተቀመጠ. She is staying with her aunt while her mother is ill. እናትዮዋ ፡ ታማ ፡ በነበረች ፡ ጊዜ ፡ አክስቷ ፡ ዘንድ ፡ ተቀምጣለች
4. ወደኋላ ፡ ቀረ. He stayed after the others left. ሌሎቹ ፡ ሲሄዱ ፡ እሱ ፡ ወደኋላ ፡ ቀረ
5. ቆመ. Stay where you are! አለህበት ፡ ቁም
6. ዋለ. Because of his age, he stays at home. ከዕድሜያቸው ፡ መግፋት ፡ የተነሣ ፡ እቤት ፡ ውለዋል

**stay after school** ከትምህርቱ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቆየ
Because he insulted the guard, the child had to stay after school. ዘበኛውን ፡ ስለሰደበ ፡ ልጁ ፡ ከትምህርት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መቆየት ፡ ነበረበት

**stay around** አልራቀም
Stay around in case we need you! ምናልባት ፡ እንፈልግህ ፡ ይሆናልና ፡ አትራቅ

**stay away**
1. ራቅ ፡ አለ. Stay away from the fire! ከእሳቱ ፡ ራቅ ፡ በል
2. ቆይቶ ፡ መጣ. You have stayed away a long time. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆይተህ ፡ መጣህ

**stay behind** ኋላ ፡ ቀረ
He stayed behind to watch television. ቴሌቪዥን ፡ ለማየት ፡ ኋላ ፡ ቀረ

**stay in**
1. ከቤት ፡ አልወጣም. The doctor told me to stay in for a few days. ሐኪሙ ፡ ለጥቂት ፡ ቀናት ፡ ከቤቴ ፡ እንዳልወጣ ፡ አዘዘኝ
2. እቤት ፡ ዋለ. We rebelled at having to stay in on so fine a day. በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አስደሳች ፡ ቀን ፡ እቤት ፡ መዋሉን ፡ አልወደድነውም

**stay (all) night** አደረ
Because of the rain, we pressed our guest to stay all night. በዝናቡ ፡ ምክንያት ፡ እንግዳውን ፡ ሰው ፡ እንዲያድሩ ፡ አጥብቀን ፡ ጠየቅናቸው

**stay out**
1. ውጭ ፡ አደረ. The cat stayed out all night. ድመቷ ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ውጭ ፡ አደረች
2. ውጭ ፡ አመሸ. Children must not stay out after dark. ልጆች ፡ ከጨለመ ፡ በኋላ ፡ ውጭ ፡ ማምሸት ፡ የለባቸውም

**stay (over)** ዋለ
Can you stay over Sunday? እሑድን ፡ ለመዋል ፡ ትችላለህ?

**stay overnight** አንድ ፡ ቀን ፡ አደረ
He stayed overnight at my house. አንድ ፡ ቀን ፡ ቤቴ ፡ አደረ

**stay put** ተቀመጠ
Stay put; I'll get it for you. እኔ ፡ አመጣልሃለሁ ፤ ተቀመጥ

**stay up**
1. አመሸ. Our children stay up until nine o'clock. ልጆቻችን ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ያመሻሉ
2. ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ጠበቀ. My wife stayed up until I got home. እቤት ፡ እስከገባ ፡ ድረስ ፡ ሚስቴ ፡ ቁጭ ፡ ብላ ፡ ጠበቀችኝ
[See also 'awake, background, bed, night, true']

**stay** (n.) ያሳለፈው ፡ ጊዜ
Our stay in the mountains was very pleasant. በተራራው ፡ ላይ ፡ ያሳለፍነው ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ አስደሳች ፡ ነበር
*The judge rejected his plea for a stay. ቀጠሮ ፡ እንዲያደረግ ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ዳኛው ፡ አልተቀበሉትም

**stay of execution**
*The governor granted a stay of execution. አገረ ፡ ገዢው ፡ የሞት ፡ ቅጣቱ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ እንዲተላለፍ ፡ አዘዘ

**make a stay** ሰነበተ
He made a short stay in Germany. በጀርመን ፡ አገር ፡ ጥቂት ፡ ሰነበተ
[See also 'bed, overnight']

**stead, in one's ~** በ --- ፈንታ
I won't go in his stead. በርሱ ፡ ፈንታ ፡ አልሄድም
**stand (one) in good stead** ብዙ ፡ ጠቀመው
This knowledge has stood him in good stead. ይህ ፡ ዕውቀት ፡ ብዙ ፡ ጠቀመው

**steadfast** ጽኑ
Their steadfast friendship was proof against slander and suspicion. ጽኑ ፡ ጓደኝነታቸው ፡ ሐሜቱንና ፡ ጥርጣሬውን ፡ ተቋቋመ
**remain steadfast** ፍንክች ፡ አልል ፡ አለ
He remained steadfast, despite all the pleading and pressure put on him. ብዙ ፡ ቢጠየቅና ፡ ቢለመንም ፡ ፍንክች ፡ አልል ፡ አለ

**steadily**
1. ያለ ፡ ፋታ. He worked steadily all day long. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ያለ ፡ ፋታ ፡ ሠራ
2. ሳያቋርጥ. The rain was falling steadily. ሳያቋርጥ ፡ ይዘንብ ፡ ነበር

**steady** (steadied), v.
1. ቀጥ ፡ አድርጎ ፡ ያዘ(ለት). Steady the ladder while I climb to the roof. ወደ ፡ ጣሪያው ፡ በምወጣበት ፡ ጊዜ ፡ መሰላሉን ፡ ቀጥ ፡ አድርገህ ፡ ያዝልኝ
2. አጽናና. His calm confidence steadied the nervous passengers. የረጋ ፡ እምነቱ ፡ የተደናገጡትን ፡ መንገደኞች ፡ አጽናናቸው

**steady** (adj.)
1. ቋሚ. I am looking for steady work. ቋሚ ፡ ሥራ ፡ እፈልጋለሁ
2. የዘወትር. He is one of our steady customers. ከዘወትር ፡ ደንበኞቻችን ፡ አንዱ ፡ ነው
3. ጥብቅ. The ladder isn't steady. መሰላሉ ፡ ጥብቅ ፡ አይደለም
4. የማይንቀጠቀጥ. Assembling a watch requires a steady hand. ሰዓት ፡ ለመገጣጠም ፡ የማይንቀጠቀጥ ፡ እጅ ፡ ያስፈልጋል
5. ተስፋ ፡ የሚጣልበት. He is a steady young man. ተስፋ ፡ የሚጣልበት ፡ ወጣት ፡ ነው
6. በትጋት ፡ የሚሠራ. A steady worker accomplishes a lot. በትጋት ፡ የሚሠራ ፡ ሠራተኛ ፡ ብዙ ፡ ያከናውናል
7. (= adv.) እያደር. He has made steady progress. እያደር ፡ ተሻሽሏል
**make steady** አስተካክሎ ፡ አቆመ
Make the table steady! ጠረጴዛውን ፡ አስተካክለህ ፡ አቁመው

**not be steady** ተንቀጠቀጠ
His hand is not steady because he drinks so much. ብዙ ፡ ስለሚጠጣ ፡ እጁ ፡ ይንቀጠቀጣል

**steak** ጥብስ
The steak sizzled in the pan. ጥብሱ ፡ በመጥበሻው ፡ ላይ ፡ ተንቻቻ

**steal** (stole) ሰረቀ
They stole all my money. ገንዘቤን ፡ በሙሉ ፡ ሰረቁኝ

**steal away** ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ሄደ
The nomads stole away in the dark. ዘላኖች ፡ በጨለማው ፡ ውስጥ ፡ ሹልክ ፡ ብለው ፡ ሄዱ

**steal (a) glance**
He stole a glance at her. ሰረቅ ፡ አድርጎ ፡ አያት

**steal (one's) heart**
The baby stole our hearts. ሕፃኗ ፡ በፍቅር ፡ መሰጠችን

**steal into** ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ገባ
He stole into the room. ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ገባ

**steal out** ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ወጣ
He stole out of the room when no one was looking. ማንም ፡ ሰው ፡ ሳያየው ፡ ከክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ወጣ

**stealth, by ~** በስውር ፡ መንገድ
He obtained the letter by stealth. ደብዳቤውን ፡ በስውር ፡ መንገድ ፡ አገኘ

**stealthily** በቀስታ
The burglar opened the window stealthily. ቤት ፡ ሰርሳሪው ፡ መስኮቱን ፡ በቀስታ ፡ ከፈተው

**stealthy, ~ approach** ማድባት
The cat's stealthy approach alarmed the birds. የድመቷ ፡ ማድባት ፡ ወፎቹን ፡ አስበረገጋቸው

**creep in a stealthy way** አደባ
The cat crept in a stealthy way to catch the bird. ድመቷ ፡ ወፏን ፡ ለመያዝ ፡ አደባች

**steam** (vt.)
1. በእንፋሎት ፡ አበሰለ. The Chinese steam certain foods. ቻይናዎች ፡ አንዳንድ ፡ ምግብ ፡ በእንፋሎት ፡ ያበስላሉ
2. ቀቀለ. The nurse steamed the instruments to kill the germs. አስታማሚዋ ፡ ነፍሳትን ፡ ለመግደል ፡ የሕክምና ፡ መሣሪያዎቹን ፡ ቀቀለቻቸው

**steam** (vi.) ፈላ
+The kettle is steaming. ማሰሮ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ውኃ ፡ በመፍላት ፡ ላይ ፡ ነው

**steam up** በተን ፡ ተሸፈነ
The window panes of the warm room steamed up. የሞቀው ፡ ክፍል ፡ የመስታወት ፡ መስኮቶች ፡ በተን ፡ ተሸፈኑ

**steam** (n.)
1. እንፋሎት. Steam condenses when it touches a cold object. እንፋሎት ፡ ቀዝቃዛ ፡ አካል ፡ ሲነካ ፡ ይጤዛል
2. የእንፋሎት ፡ ኀይል. Who first conceived the idea of using steam to drive vehicles? መኪናዎችን ፡ በእንፋሎት ፡ ኀይል ፡ መንዳትን ፡ መጀመሪያ ፡ ያሰበ ፡ ማን ፡ ነው ?
3. ጉልበት. That old man still has a lot of steam left in him. ያ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ ጉልበት ፡ አለው

**let off steam**
*Don't mind him; he's just letting off steam. ተወው ፤ ያለውን ፡ ይበል

**work off steam** ኀይሉን ፡ አበረደ
He worked off steam by hitting a punching bag. የቦክስ ፡ መለማመጃውን ፡ ከረጢት ፡ በመምታት ፡ ኀይሉን ፡ አበረደ

**steamboat** በእንፋሎት ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ጀልባ
A steamboat travels up and down the river. በእንፋሎት ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ጀልባ ፡ በወንዙ ፡ ላይ ፡ ይመላለሳል

**steam engine** በከሰል ፡ የሚሄድ ፡ ባቡር
An electric engine is faster than a steam engine. በኮረንቲ ፡ የሚሄድ ፡ ባቡር ፡ በከሰል ፡ ከሚሄደው ፡ ይፈጥናል

**steamroller** ዳምጠው
A steamroller crushed the gravel on the road. ዳምጠው ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ኰረት ፡ አደቀቀው

**steel** (v.), **~ oneself** ታጠቀ ፤ ተበራታ
The soldiers steeled themselves to withstand the attack. ወታደሮቹ ፡ ውጊያውን ፡ ለመከላከል ፡ ታጠቁ
The captive steeled himself to endure torture. ምርኮኛው ፡ ሥቃዩን ፡ ለመቋቋም ፡ ተበራታ

**steel** (n.) ብረት ፤ ዐረብ ፡ ብረት
Is this pot made of steel? ይህ ፡ ጀበና ፡ የተሠራው ፡ ከብረት ፡ (ከዐረብ ፡ ብረት) ፡ ነው ?

**nerves of steel**
He has nerves of steel. መንፈሱ ፡ ጠንካራ ፡ ነው

**steep** (v.)
1. ዘፈዘፈ. They steeped the flax in a bowl. ተልባውን ፡ ሳሕን ፡ ውስጥ ፡ ዘፈዘፉት

2. ነከረ. He steeped the tea in hot water. ሻይ ፡ ቅጠሉን ፡ የፈላ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ነከረው

**be steeped in** ጠንቅቆ ፡ ዐወቀ
This writer is steeped in the traditions of the church. ይህ ፡ ጸሐፊ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሥርዓት ፡ ጠንቅቆ ፡ ያውቃል

**steep** (adj.) ቀጥ ፡ ያለ
Be careful; the stairs are steep. ተጠንቀቅ ፤ ደረጃዎቹ ፡ ቀጥ ፡ ያሉ ፡ ናቸው
The hill is too steep for the car to drive up. ጋራው ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ ለመኪና ፡ ያዳግታል

**be steep** አጋደለ
The roof is steep, so the rain will run off easily. ጣራው ፡ ያጋደለ ፡ ስለሆነ ፡ የዝናብ ፡ ውኃ ፡ እየተንቆረቆረ ፡ ይወርዳል

**be too steep** በዛ
The price is too steep for me. ዋጋው ፡ ይበዛብኛል
[See also 'grade, pitch']

**steeple** የደወል ፡ ቤት ፡ ጣሪያ ፤ ጉልላት
The steeple of the church is covered with bronze sheets. የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የደወል ፡ ቤት ፡ ጣሪያ ፡ (ጉልላት) ፡ በነሐስ ፡ የተሸፈነ ፡ ነው

**steer** (vt.)
1. መራ. He steered the ship toward shore. መርከቡን ፡ ወደ ፡ ጠረፍ ፡ መራ
2. ቀዘፈ. Steer the boat to shore! ጀልባውን ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ዳር ፡ ቅዘፈው
3. ነዳ. He has difficulty steering the car because he is so short. አጭር ፡ ስለሆነ ፡ መኪናውን ፡ መንዳት ፡ ይቸግረዋል
4. አበቃ. The coach steers his team to victory. አሠልጣኙ ፡ ቡድኑን ፡ ለድል ፡ አበቃው

**steer** (vi.)
*This car doesn't steer easily. ይህ ፡ መኪና ፡ መሪው ፡ ጥብቅ ፡ ነው

**steer clear of** ራቀ
She steered clear of trouble. ከችግር ፡ ራቀች

**steer** (n.)
1. ሰንጋ. I will kill two steers for the wedding. ለሰርጉ ፡ ሁለት ፡ ሰንጋ ፡ እጥላለሁ
2. በሬ. Our steer is fierce. በሬያችን ፡ ኀይለኛ ፡ ነው

**steering wheel** መሪ ፤ የመኪና ፡ መሪ
The horn is in the center of the steering wheel. ጡሩምባው ፡ መሪው ፡ መኻል ፡ ላይ ፡ ነው
The steering wheel has to be fixed. የመኪናው ፡ መሪ ፡ መጠገን ፡ አለበት

**stela** ሐውልት
The Italians moved a stela from Axum to Rome. ኢጣልያኖች ፡ አንድ ፡ ሐውልት ፡ ከአክሱም ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ወሰዱዋል

**stem** (stemmed), vt.
1. አገደ. They stemmed the flood with dikes. ጐርፉን ፡ በግድብ ፡ አገዱት
2. ገታ. The President stemmed the opposition. ፕሬዚዳንቱ ፡ ተቃዋሚውን ፡ ክፍል ፡ ገታው

**stem** (vi.) መነጨ
The troubles stem from injustices of long standing. ችግሩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከቆየ ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ የመነጨ ፡ ነው

**stem** (n.)
1. ግንድ. The stem of the flower is thorny. የጽጌረዳ ፡ ግንድ ፡ እሾኻማ ፡ ነው
2. አንጓ. A leaf stem is caught in my teeth. የቅጠል ፡ አንጓ ፡ ጥርሴ ፡ ውስጥ ፡ ተሰካብኝ
3. መጨበጫ. The stem of a goblet can easily be broken. የጽዋው ፡ መጨበጫ ፡ በቀላሉ ፡ ይሰበራል

**stench** ክርፋት
The stench of the slaughterhouse was unpleasant. የቄራው ፡ ክርፋት ፡ በጣም ፡ መጥፎ ፡ ነበር

**stenography** አጭር ፡ ጽሕፈት
The secretary I hired knows stenography. የቀጠርኳት ፡ ጸሐፊ ፡ አጭር ፡ ጽሕፈት ፡ ትችላለች

**step** (stepped), vi.
1. ረገጠ. Don't step in the paint! ቀለሙን ፡ አትርገጠው
2. ገባ. I saw him step into the store. እሱቁ ፡ ውስጥ ፡ ሲገባ ፡ አየሁት
3. ቆመ. Perhaps if you step on a chair, you might be able to reach it. ወንበር ፡ ላይ ፡ ብትቆም ፡ ትደርስበት ፡ ይሆናል

**step aside!** ዞር ፡ በል
Step aside while we are moving the table! ጠረጴዛውን ፡ ልናነሣው ፡ ነውና ፡ ዞር ፡ በል

**step back** ወደ ፡ ኋላ ፡ ፈቀቅ ፡ አለ
Step back a bit! ትንሽ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ፈቀቅ ፡ በል

**step down**
1. ወረደ. He stepped down from the platform. ከመድረኩ ፡ ላይ ፡ ወረደ
2. ከሥልጣኑ ፡ ወረደ. After twenty years in office, he finally stepped down. ሃያ ፡ ዓመት ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ ቆይቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ከሥልጣኑ ፡ ወረደ

**step forward** ብቅ ፡ አለ
He asked for volunteers, but no one stepped

forward. ፈቃደኛ ፡ እንዳለ ፡ ቢጠይቅ ፡ ማንም ፡ ብቅ ፡ አላለ

**step in** በጉዳዩ ፡ ገባ
The President himself may have to step in. በጉዳዩ ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ራሳቸው ፡ ይገቡበት ፡ ይሆናል
*They just stepped in for a moment. ጎራ ፡ ብለው ፡ ወዲያው ፡ ሄዱ

**step into (one's) place** በቦታው ፡ ተተካ
He stepped into my place while I was gone. ሄጄ ፡ ሳለሁ ፡ በቦታዬ ፡ ተተካ

**step off**
1. ወረደ. He just stepped off the train. ከባቡር ፡ ገና ፡ አሁን ፡ ወረደ
2. በእግሩ ፡ ለካ. John stepped off 100 feet. ዮሐንስ ፡ በእግሩ ፡ መቶ ፡ ጫማ ፡ ለካ

**step (on)**
1. ረገጠ. He stepped on the mud. ጭቃውን ፡ ረገጠው
The child stepped on a worm. ልጁ ፡ ትሉን ፡ ረገጠው
2. ያዘ. Step on the brakes! ፍሬኑን ፡ ያዝ

**step out** ወጣ ፡ አለ
The children cut loose the minute the teacher steps out of the room. አስተማሪው ፡ ከክፍል ፡ ገና ፡ ወጣ ፡ ሲል ፡ ልጆቹ ፡ መረበሽ ፡ ይጀምራሉ
My wife and I are stepping out tonight. እኔና ፡ ባለቤቴ ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ ወጣ ፡ እንላለን

**step this way!** ወደዚህ! ፡ (በዚህ ፡ በኩል!)

**step up** (vt.)
1. አፈጠነ. We have to step up the pace a bit. እርምጃችንን ፡ ጥቂት ፡ ማፍጠን ፡ አለብን
2. አባባሰ. The Japanese move stepped up the arms race. የጃፓን ፡ እርምጃ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እሽቅድድሙን ፡ አባባሰው
3. ቀስ ፡ በቀስ ፡ ጨመረ. The factory has stepped up production. ፋብሪካው ፡ ሥርቶ ፡ የሚያወጣውን ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ጨመረ

**step up** (vi.)
1. መጣ. A strange man stepped up to me in the street. እመንገድ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የማላውቀው ፡ ሰው ፡ ወደኔ ፡ ዘንድ ፡ መጣ
2. ወጣ. The curb was so high that the child could not step up. የመንገዱ ፡ ጠርዝ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ ልጁ ፡ መውጣት ፡ አቃተው
[See also 'pedal, toe']

**step** (n.)
1. ደረጃ. The steps are carpeted. ደረጃዎቹ ፡ ምንጣፍ ፡ ተነጥፎባቸዋል
Make sure you finish step one before you go on to step two. ወደ ፡ ሁለተኛው ፡ ደረጃ ፡ ከመሸጋገርህ ፡ በፊት ፡ አንደኛውን ፡ ደረጃ ፡ መጨረስህን ፡ አረጋግጥ
2. እርምጃ. He took one step forward. አንድ ፡ እርምጃ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሄደ
They stood three steps apart. ሦስት ፡ እርምጃ ፡ ተራርቀው ፡ ቆሙ
The police took steps to enforce discipline. ፖሊስ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ ለማስከበር ፡ እርምጃ ፡ ወሰደ
3. ኮቴ. I hear steps outside. እውጭ ፡ ኮቴ ፡ ይሰማኛል
4. የሰው ፡ ዱካ. I see steps in the mud. በጭቃው ፡ ውስጥ ፡ የሰው ፡ ዱካ ፡ ይታየኛል
*The school is only a step from our house. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ደጃችን ፡ ነው

**step by step**
1. ቀስ ፡ በቀስ. We built up our business step by step. ንግዳችንን ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ አዳበርን
2. በደንብ. I followed him step by step. በደንብ ፡ ተከታትየዋለሁ

**be in step** ሄደ
They are not in step with the times. ከጊዜው ፡ ጋር ፡ አይሄዱም

**be out of step**
1. እግሩን ፡ አላገባም. He is almost always out of step while marching. ሲሰለፍ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እግሩን ፡ አያገባም
2. አልተራመደም. He is out of step with the times. ከጊዜው ፡ ጋር ፡ አይራመድም

**keep step** እኩል ፡ ተራመደ
Keep step with me! ከኔ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ተራመድ

**march in step**
Soldiers must march in step. ወታደሮች ፡ እግራቸውን ፡ አግብተው ፡ መራመድ ፡ አለባቸው

**watch (one's) step** ተጠንቀቀ
If he doesn't watch his step, he will be fired from the job. ካልተጠንቀቀ ፡ ከሥራ ፡ ይወገዳል

**watch your step!** እያየህ ፡ ርገጥ
The ground here is treacherous, so watch your step! እዚህ ፡ ጋ ፡ መሬቱ ፡ አታላይ ፡ ነውና ፡ እያየህ ፡ ርገጥ

**with slow steps** በዝግታ
He walked with slow steps. በዝግታ ፡ ተራመደ
[See also 'jaunty, measured, retrace, short']

**stepbrother** የእንጀራ ፡ አባቱ ፡ ልጅ ። የእንጀራ ፡ እናቱ ፡ ልጅ
My stepbrother is older than I am. የእንጀራ ፡ አ

ባቱ ፡ (የእንጀራ ፡ እናቱ) ፡ ልጅ ፡ ከኔ ፡ ያረጃል ፡ (ታላቂ ፡ ነው)

**stepchild** የእንጀራ ፡ ልጅ
The man gave his stepchild an education. ሰውዬው ፡ የእንጀራ ፡ ልጁን ፡ አስተማረ

**stepdaughter** የእንጀራ ፡ ልጅ
His stepdaughter is nicer to him than his own daughters. የእንጀራ ፡ ልጁ ፡ ከልጆቹ ፡ የበለጠ ፡ ታስብለታለች

**stepfather** የእንጀራ ፡ አባት
My stepfather gave me a watch. የእንጀራ ፡ አባቴ ፡ ሰዓት ፡ ሰጠኝ

**stepladder** ድጋፍ ፡ ያለው ፡ መሰላል
I need a stepladder. ድጋፍ ፡ ያለው ፡ መሰላል ፡ ያስፈልገኛል

**stepmother** የእንጀራ ፡ እናት
My stepmother is nice to me. የእንጀራ ፡ እናቴ ፡ ትወደኛለች

**steppe** አውላላ ፡ ሜዳ
The lion cubs were racing across the steppe. ያንበሳዎቹ ፡ ግልገሎች ፡ ባውላላው ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ይሯሯጡ ፡ ነበር

**stepping stone**
1. መረጋገጫ ፡ ድንጋይ. The stream can be crossed on stepping stones. ወንዙን ፡ በመረጋገጫ ፡ ድንጋይ ፡ ለመሻገር ፡ ይቻላል
2. መወጣጫ. This job is a stepping stone to the presidency. ይህ ፡ ሥራ ፡ ለፕሬዚዳንትነት ፡ መወጣጫ ፡ ነው

**stepson** የእንጀራ ፡ ልጅ
The woman treated her stepson badly. ሴትዮዋ ፡ የእንጀራ ፡ ልጇን ፡ አጕሳቁለችው

**sterile**
1. መኻን. The woman is sterile. ሴትዮዋ ፡ መኻን ፡ ነች
2. ከነፍሳት ፡ ንጹሕ. Make sure the scalpel is sterile. ቀዶ ፡ ጥገና ፡ ማድረጊያው ፡ ከነፍሳት ፡ ንጹሕ ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጥ
3. ጭንጫ. The ground is sterile; nothing will grow on it. መሬቱ ፡ ጭንጫ ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አያበቅልም

**sterilize** ከጀርም ፡ ነጻ ፡ አደረገ
The nurse sterilized the baby bottles by putting them in boiling water. አስታማሚዋ ፡ ጡጦዎቹን ፡ በፈላ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ በመክተት ፡ ከጀርም ፡ ነጻ ፡ አደረገቻቸው

**stern** (n.) ኋላ
The ship has a flag at the stern. መርከቡ ፡ ከኋላው ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ አለው

**stern** (adj.)
1. ኮስተር ፡ ያለ. He has a stern expression. ፊቱ ፡ ኮስተር ፡ ያለ ፡ ነው
2. ጥብቅ. A stern teacher is needed to keep the students under control. ተማሪዎችን ፡ ለመቈጣጠር ፡ ጥብቅ ፡ አስተማሪ ፡ ያስፈልጋል
3. ከባድ. Stern necessity decreed that he leave school to make a living. ከባድ ፡ ችግሩ ፡ ትምህርቱን ፡ ትቶ ፡ ሥራ ፡ እንዲይዝ ፡ አስገደደው

**stew** (v.) ቀቀለ
She stewed the meat seven hours. ሥጋውን ፡ ሰባት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ቀቀለችው

**stew** (n.) ወጥ
I like stew with a little butter in it. ትንሽ ፡ ቅቤ ፡ ያለበት ፡ ወጥ ፡ እወዳለሁ

**steward**
1. አስተዳዳሪ. He is the steward of that great estate. የዚያ ፡ የትልቅ ፡ ርስት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ነው
2. መጋቢ. The steward must give a yearly account. መጋቢው ፡ ያመቱን ፡ ወጪ ፡ ሒሳብ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት
3. አስተናጋጅ. The cabin steward waits on passengers. የክፍሉ ፡ አስተናጋጅ ፡ የመርከቡን ፡ ተሳፋሪዎች ፡ ያስተናግዳል

**stewardess** የአውሮፕላን ፡ አስተናጋጅ
The stewardess served breakfast. የአውሮፕላኑ ፡ አስተናጋጅ ፡ ቁርስ ፡ አቀረበች

**stick** (stuck), vt.
1. ወጋ. Something is sticking me. ምናምን ፡ ይወጋኛል
I stuck my finger with a needle. መርፌው ፡ ጣቴን ፡ ወጋኝ
Stick a fork into the potato to see if it is done. ድንቹ ፡ በስሎ ፡ እንደሆነ ፡ በሹካ ፡ ወግተህ ፡ እየው
2. ለጠፈ. He stuck a stamp on the envelope. ፖስታው ፡ ላይ ፡ ቴምብር ፡ ለጠፈ
3. ከተተ. He stuck his hands into his pockets. እጁን ፡ ኪሱ ፡ ውስጥ ፡ ከተተ
4. ያዘ. Just stick it in your pocket! ኪስህ ፡ ውስጥ ፡ ያዘው

**stick** (vi.)
1. ያዘ. This stamp doesn't stick. ይህ ፡ ቴምብር ፡ አይዝም
+The wheels stuck in the mud. ጎማዎቹን ፡ ጭቃ ፡ ያዛቸው

2. አጣበቀ. This glue sticks well. ይህ ፡ ሙጫ ፡ ደኅና ፡ ያጣብቃል

3. ነከሰ. This door sticks because it doesn't fit well. ይህ ፡ በር ፡ በደንብ ፡ ስለማይገጥም ፡ ይነክሳል

4. ተሰካ. I found a nail sticking in my tire. ጎማዬ ፡ ላይ ፡ ምስማር ፡ ተሰክቶ ፡ አገኘሁ

*Nothing sticks in his mind. ምንም ፡ ነገር ፡ ማስታወስ ፡ አይችልም

**stick around** ከዚህ ፡ አልጠፋም

Stick around till I get through! እስክጨርስ ፡ ድረስ ፡ ከዚህ ፡ አትጥፋ

**stick (by)** ከሱ ፡ አልራቀም

A good friend will stick by you in time of difficulty. ጥሩ ፡ ጓደኛ ፡ በችግር ፡ ጊዜ ፡ ካንተ ፡ አይርቅም

**stick by one another** አልተለያዩም

They vowed to stick by one another no matter what happened. ምንም ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ ላይለያዩ ፡ ተማማሉ

**stick into**

*Don't stick your nose into everything! የእርጎ ፡ ዝምብ ፡ አትሁን

**stick it out!**

*Try and stick it out a little longer! በርታ ፤ ተስፋ ፡ አትቍረጥ

**stick on** ያዘ

The stamp won't stick on. ቴምብሩ ፡ አይዝም

**stick oneself** እጁን ፡ ወጋ

I stuck myself with the needle. እጄን ፡ በመርፌ ፡ ወጋሁት

**stick (out)**, vt. አወጣ

Don't stick your head out the window! አንገትህን ፡ በመስኮት ፡ አታውጣ

*He stuck out his chest with pride. በትዕቢት ፡ ደረቱን ፡ ነፋ

**stick out** (vi.)

1. አፈነገጠ. He struck his arm on the corner of a box which stuck out into the room. ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ያፈነገጠ ፡ ሣጥን ፡ ጠርዝ ፡ ክንዱን ፡ መታው

Watch out! There's a nail sticking out. ተጠንቀቅ ፤ አንድ ፡ ያፈነገጠ ፡ ምስማር ፡ አለ

2. ወጣ ፡ አለ. The gun stuck out of a slit in the tank. ጠመንጃው ፡ ከታንኩ ፡ ውስጥ ፡ በቀዳዳ ፡ ወጣ ፡ ብሎ ፡ ነበር

*His ears stick out. ጆሮ ፡ ጋሻ ፡ ነው

**stick (to)**

1. ጸና. I stick to my opinion. በሐሳቤ ፡ እጸናለሁ

2. ጸንቶ ፡ ቆየ. He can't stick to anything. በምንም ፡ ነገር ፡ ጸንቶ ፡ ሊቆይ ፡ አይችልም

3. አልተላቀቀም. He sticks to his work until it is finished. እስኪጨርስ ፡ ድረስ ፡ ከሥራው ፡ አይላቀቅም

4. ተከተለ. You must stick to the rules. ሕጉን ፡ መከተል ፡ አለብህ

5. በነገሩ ፡ በረታ(በት). Stick to it. Don't give up now! በነገሩ ፡ በርታበት ፤ አታቋርጠው

**stick together**

Let's stick together! አንድ ፡ ላይ ፡ እንሁን

**stick up**

1. ብቅ ፡ ብሎ ፡ ታየ. The tree was sticking up in the water. ዛፉ ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ይታይ ፡ ነበር

2. ወደ ፡ ላይ ፡ ቆመ. Turn down your collar; it's sticking up. ኮሌታህን ፡ ቀልብሰው ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ ቆሟል

3. ተሰቀለ. The wheels of the overturned car were sticking up in the air. የተገለበጠው ፡ መኪና ፡ ጎማዎች ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተሰቅለው ፡ ነበር

**stick up for** ደገፈ

She always sticks up for him, even though he doesn't deserve it. የማይገባው ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ዘወትር ፡ እሱን ፡ ትደግፈዋለች

*He sticks up for his friends. ለጓደኞቹ ፡ ይሞታል

**be stuck**

1. ተጣበቀ. The two pages were stuck together. ሁለቱ ፡ ገጾች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተጣበቁ

2. ተቀረቀረ. A bone is stuck in his throat. ጉሮሮው ፡ ውስጥ ፡ አጥንት ፡ ተቀረቀረ

3. ነከሰ. The bottom drawer of the bureau is stuck. የጠረጴዛው ፡ የታችኛው ፡ መሳቢያ ፡ ነክሷል

4. ተወተፎ ፡ ቀረ. I'm afraid I'll be stuck in this place forever. እዚህ ፡ ቦታ ፡ ተወትፌ ፡ እንዳልቀር ፡ እፈራለሁ

5. (= act.) ያዘ. +The rear wheels are stuck in the mud. የኋላኛውን ፡ ጎማ ፡ ጭቃ ፡ ይዞታል

**be stuck by**

*He was stuck by the very first problem on the test. በፈተናው ፡ ገና ፡ የመጀመሪያው ፡ ፕሮብሌም ፡ አላነቃንቅ ፡ ብሎት ፡ ነበር

**get stuck**

1. ያዘ. +The car got stuck in the mud. መኪናውን ፡ ጭቃ ፡ ያዘው

2. ገብቶ ፡ ተቀረቀረ. The car got stuck in the ditch. መኪናዋ ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ ተቀረቀረች

**get stuck on** አስቸገረ ፤ አላነቃንቅ ፡ አለ

+I got stuck on that arithmetic problem. የሒሳብ ፡ ጥያቄ ፡ አስቸገረኝ ፡ (አላነቃንቅ ፡ አለኝ)

**get stuck with**
1. ሊገላገል ፡ አልቻለም. He got stuck with that car. ከዚያ ፡ መኪና ፡ ሊገላገል ፡ አልቻለም
2. ለብቻው ፡ ይዞት ፡ ቀረ. He got stuck with the job of cleaning up the mess. ዝባዝንኬውን ፡ የማጽዳቱን ፡ ሥራ ፡ ለብቻው ፡ ይዞት ፡ ቀረ
[See also 'gun, rut']

**stick** (n.) ከዘራ
The old man walks with a stick. ሽማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ የሚሄዱት ፡ በከዘራ ፡ ነው

**sticks** ባላገር
This fashion is not known in the sticks. ይህ ፡ ሞድ ፡ ባላገር ፡ አልገባም

**dry sticks** ጭራሮ
Gather some dry sticks to make a fire! እሳት ፡ ለማንደድ ፡ ጭራሮ ፡ ለቃቅም

**stickler**
*He's a stickler for perfection. ሁሉም ፡ ነገር ፡ ትክክል ፡ ካልሆነ ፡ ባይ ፡ ነው

**sticky** ዝልግልግ
The juice of the euphorbia is sticky. የቁልቋል ፡ ውኃ ፡ ዝልግልግ ፡ ነው

**be sticky** ወበቀ
It's awfully sticky today. ዛሬ ፡ በጣም ፡ ይወብቃል

**be sticky with** ተለውሰ ፡ አጣበቀ
My fingers are sticky with honey. ጣቶቼ ፡ በማር ፡ ተለውሰው ፡ ያጣብቃሉ

**have sticky fingers**
*Watch your new clerk! I am afraid he has sticky fingers. አዲሱን ፡ ጸሐፊ ፡ ደኅና ፡ አድርገህ ፡ ተከታተለው ፤ እጁ ፡ የሚጸም ፡ አይመስለኝም

**stiff**
1. ደረቅ. He always wears stiff collars. ሁልጊዜ ፡ ደረቅ ፡ ኮሌታ ፡ ያለው ፡ ሸሚዝ ፡ ይለብሳል
2. ከባድ. Was it a stiff examination? ከባድ ፡ ፈተና ፡ ነበር?
3. ጠንካራ. Library books need stiff covers. የቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መጽሐፎች ፡ ጠንካራ ፡ ሽፋኖች ፡ ያስፈልጋቸዋል
*He asked a stiff price for his house. ለቤቱ ፡ የጠየቀው ፡ ዋጋ ፡ አይቀመስም
*He made a stiff bow. ተለጥጦ ፡ እጅ ፡ ነሣ

**be stiff** ቆፈን ፡ ያዘው
My fingers are stiff with cold. ከብርድ ፡ የተነሣ ፡ ጣቶቼ ፡ ቆፈን ፡ ይዟቸዋል
*My legs are stiff. እግሮቼ ፡ አልታጠር ፡ አልዘረጋ ፡ አሉ

**feel stiff** ሰውነቱ ፡ ንኰለ
I feel stiff all over after that long walk. ከዛ ፡ ከረጅም ፡ ጉዞ ፡ በኋላ ፡ መላው ፡ ሰውነቴ ፡ ንኰኳል

**have a stiff neck**
*I have a stiff neck. አንገቴ ፡ አልዞር ፡ ብሎኛል

**stiffen** (vt.)
1. አጠነከረ. We need more troops to stiffen our resistance. ተከላካዩን ፡ ጦር ፡ ለማጠንከር ፡ ተጨማሪ ፡ ወታደሮች ፡ ያስፈልጉናል
2. አደረቀ. He stiffened his collar with starch. ኮሌታውን ፡ በአሚዶ ፡ አድርቆታል

**stiffen** (vi.) ስቅጥጥ ፡ አለ
She stiffened when I asked her personal questions. እሷን ፡ በግል ፡ የሚመለከት ፡ ጥያቄ ፡ ባቀርብላት ፡ ስቅጥጥ ፡ አለች

**stifle** (vt.)
1. ጸጥ ፡ አደረገ. The Greek government stifled the rebellion. የግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ዐመፁን ፡ ጸጥ ፡ አደረገው
2. አፍኖ ፡ ያዘ. He stifled his laughter. ሣቁን ፡ አፍኖ ፡ ያዘው
3. አፈነ. The smoke stifled the fireman. ጭሱ ፡ የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካዮቹን ፡ አፈናቸው
4. አጠፋ. We stifled the fire with sand. እሳቱን ፡ በአሸዋ ፡ አጠፋነው

**stifle** (vi.) ታፈነ
I am stifling in this closed room. እዚህ ፡ እተዘጋ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ታፈንኩ ፡ እኮ

**be stifling** አስጨነቀ
The heat was stifling. ሙቀቱ ፡ ያስጨንቅ ፡ ነበር

**stigma**
1. መጥፎ ፡ ስም. He bears the stigma of having once deserted from the army. አንዴ ፡ ከወታደርነት ፡ ከድቶ ፡ በመሸሽ ፡ መጥፎ ፡ ስም ፡ አትርፏል
2. እፍረት. He lived under the stigma of having been in prison. ታስሮ ፡ ስለነበር ፡ እፍረት ፡ ሆኖበት ፡ ኖረ

**stigmatize** ስም ፡ ሰጠ
His accident stigmatized him as a reckless driver. አደጋው ፡ ግድየለሽ ፡ ነጂ ፡ የሚል ፡ ስም ፡ ሰጠው

**still** (vt.) ዝም ፡ አሰኘ
The mother stilled the crying baby. እናትዮዋ ፡ የሚያለቅሰውን ፡ ልጅ ፡ ዝም ፡ አሰኘች

**still** (vi.) በረደ
The people prayed that the storm might still. ሰዎቹ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ እንዲበርድ ፡ ጸለዩ

**still** (n.) ማንጠሪያ
They make whiskey in this still. በዚህ ፡ ማንጠ ሪያ ፡ ዊስኪ ፡ ያወጣሉ

**in the still of the night** ጸጥ ፡ ባለው ፡ ሌሊት
In the still of the night, a cry for help was heard. ጸጥ ፡ ባለው ፡ ሌሊት ፡ ኡኡታ ፡ ተሰማ

**still** (adj.)
1. የረጋ. I like the still air of the morning. የጧትን ፡ የረጋ ፡ አየር ፡ እወዳለሁ
The water was so still that it mirrored the trees along the bank. ውኃው ፡ በጣም ፡ የረጋ ፡ ስለነበረ ፡ በዳርቻው ፡ ያሉትን ፡ የዛፎች ፡ ጥላ ፡ አሳየ
2. ጭር ፡ ያለ. On a still night, silence reigns. ጭር ፡ ባለ ፡ ሌሊት ፡ ጸጥታ ፡ ይሰፍናል

**be still**
1. ጭር ፡ አለ. The people left, and the house is still. ሰዎቹ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ስለሄዱ ፡ ቤቱ ፡ ጭር ፡ ብሏል
2. ጸጥ ፡ አለ. The lake is still today. ሐይቁ ፡ ዛሬ ፡ ጸጥ ፡ ብሏል

**hold still**
1. አልተንቀሳቀም. Hold still a minute while I take your picture. ፎቶግራፍ ፡ ሳነሣህ ፡ ላንድ ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ አትንቀሳቀስ
2. ዝም ፡ አለ. Hold still a minute! እስቲ ፡ አንዴ ፡ ዝም ፡ በል

**keep still**
1. ረግቶ ፡ ተቀመጠ. Why don't you keep still while I take your picture? ፎቶግራፍ ፡ ሳነሣህ ፡ ለምን ፡ ረግተህ ፡ አትቀመጥም ?
2. ዝም ፡ አለ. Why don't you keep still while I am talking? እኔ ፡ ስናገር ፡ ለምን ፡ ዝም ፡ አትልም ?

**stand still** አልተንቀሳቀም
Stand still for a few minutes! ለጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ አትንቀሳቀስ

**still** (adv.)
1. እስካሁን. The dishes are still in the sink. ሳሕኖቹ ፡ እስካሁን ፡ ከማጠቢያው ፡ ውስጥ ፡ ናቸው
2. አሁንም. I am still of the same opinion. ሐሳቤ ፡ አሁንም ፡ ያው ፡ ነው
Though she has new dolls, still she loves her old ones. አዳዲስ ፡ አሻንጉሊቶች ፡ ቢኖሯትም ፡ አሁንም ፡ የድሮዎቹን ፡ ትወዳለች
3. አሁንም ፡ ገና. He is still studying elementary mathematics. አሁንም ፡ ገና ፡ የጀማሪዎች ፡ ሒሳብ ፡ በማጥናት ፡ ላይ ፡ ነው
4. ቢሆንም. Still, I think you did the right thing. ቢሆንም ፡ ተገቢውን ፡ ነገር ፡ ያደረግክ ፡ ይመስለኛል
5. አርፎ. Sit still! አርፈህ ፡ ተቀመጥ
6. (zero). Tom is tall, but Mary is taller still. ቶም ፡ ረጅም ፡ ነው ፤ ግን ፡ ሜሪ ፡ ረዘም ፡ ትላለች
*It was futile, but still they fought. ከንቱ ፡ ቢሆንም ፡ ተዋጉ

**(be) stillborn** ሞቶ ፡ ተወለደ
The child was stillborn. ሕፃኑ ፡ ሞቶ ፡ ተወለደ

**stillness** ጸጥታ
The stillness of the night was disturbed only by an occasional cock's crow. የሌሊቱ ፡ ጸጥታ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ባውራ ፡ ዶሮው ፡ ጩኸት ፡ ይረበሽ ፡ ነበር

**stilt** ምርኩዝ
She walks on stilts. በምርኩዝ ፡ ትሄዳለች

**(be) stilted**
1. ግትር ፡ ነው. His manner is rather stilted. ሁናቴው ፡ ግትር ፡ ብጤ ፡ ነው
2. ለዛ ፡ የለውም. His language is stilted. ንግግሩ ፡ ለዛ ፡ የለውም

**stimulant** የሚያነቃቃ ፡ መጠጥ
Caffeine is a common stimulant. ካፌን ፡ የተለመደ ፡ የሚያነቃቃ ፡ መጠጥ ፡ ነው
*Money was his major stimulant. የገንዘብ ፡ ባሪያ ፡ ነው

**stimulate**
1. አነቃቃ. Coffee stimulates a person and helps him stay awake. ቡና ፡ ሰውን ፡ እያነቃቃ ፡ ንቁ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቆይ ፡ ያደርገዋል
2. አበረታታ. The prize stimulated him to do his best. ሽልማቱ ፡ ጠንክሮ ፡ እንዲሠራ ፡ አበረታታው
3. ቀሰቀሰ. This book has stimulated my interest. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ፍላጎቴን ፡ ቀስቅሶታል
Smells of cooking stimulate my appetite. የምግብ ፡ ሽታ ፡ የምግብ ፡ ፍላጎቴን ፡ ይቀሰቅሰዋል

**stimulating** የሚያነቃቃ
The lecture was quite stimulating. ንግግሩ ፡ በጣም ፡ የሚያነቃቃ ፡ ነበር

**stimulation**
1. ማነቃቂያ. He needs the stimulation coffee gives him to stay awake. ነቅቶ ፡ እንዲቆይ ፡ የቡና ፡ ማነቃቂያ ፡ ያስፈልገዋል
2. የሚያነቃቃ ፡ ነገር. Lazy children need some stimulation to make them work. ሰነፍ ፡ ልጆች ፡ እንዲሠሩ ፡ አንዳንድ ፡ የሚያነቃቃቸው ፡ ነገር ፡ ያስፈልጋቸዋል

**stimulus** የሚገፋፋ ፡ ነገር
Ambition is a great stimulus. ምኞት ፡ በጣም ፡ የሚገፋፋ ፡ ነገር ፡ ነው
*Under the stimulus of bright light, the pupil of the eye gets smaller. በደማቅ ፡ ብርሃን ፡ ምክንያት ፡ የዓይን ፡ ብሌን ፡ ይጠባል
*The stimulus for economic development is a desire for a better life. የተሻለ ፡ ኑሮ ፡ የመኖር ፡ ፍላጎት ፡ የኤኮኖሚን ፡ እድገት ፡ ይገፋፋል

**sting** (stung), vt.
1. ነደፈ. The bee stung his face. ንቧ ፡ ፊቱን ፡ ነደፈችው
2. ገረፈ. The cold wind stung her cheeks. ቀዝቃዛው ፡ ነፋስ ፡ ጉንጮቿን ፡ ገረፈው
3. ገፋፋ. The harsh speech stung them to action. ኀይለኛው ፡ ንግግር ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዲያደርጉ ፡ ገፋፋቸው
**sting** (vi.) አቃጠለ
Alcohol stings when put on a wound. አልኮል ፡ ቁስል ፡ ላይ ፡ ሲያደርጉት ፡ ያቃጥላል
**be stung** (= act.) በጣም ፡ ከነከነ
+He was stung by the mocking of the other children. የሌሎች ፡ ልጆች ፡ መሳለቂያ ፡ መሆኑ ፡ በጣም ፡ ከነከነው

**sting** (n.) የሚያቃጥል ፡ ቁስል
Put an ointment on the sting to take away the pain! እንዲተውህ ፡ የሚያቃጥልህን ፡ ቁስል ፡ ቅባት ፡ አድርግበት
*Her face was covered with bee stings. ፊቷን ፡ ንብ ፡ ስለነደፋት ፡ ተንደብድቧል
**feel the sting of**
*The ball team felt the sting of the defeat. የኳሱ ፡ ቡድን ፡ መሸነፉ ፡ ቈጨው

**stingy** ጨቅ ፤ ንፉግ
Don't be so stingy! You have plenty of money. እንደዚህ ፡ ጨቅ ፡ (ንፉግ) ፡ አትሁን ፤ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አለህ

**stink** (stank, or stunk) ገማ ፤ ሸተተ
That fish stinks. ያ ፡ ዓሣ ፡ ይገማል ፡ (ይሸታል)

**stink** (n.)
1. ሽታ. The stink of rotting meat pervaded the air. የገማው ፡ ሥጋ ፡ ሽታ ፡ አየሩን ፡ አወደው
2. ግማት. The stink of a dead carcass pervaded the air. የጥንቡ ፡ ግማት ፡ አየሩን ፡ ሞላው

**stint** (v.) ለገንዘብ ፡ ሠሠተ
Don't stint during your vacation! ለዕረፍት ፡ ስትሄድ ፡ ለገንዘብ ፡ አትሥሥት

**stint oneself of** ቈጥቦ + verb
The parents stinted themselves of food to give it to the children. ለልጆቹ ፡ ለማስተረፍ ፡ ሲሉ ፡ ወላጆቹ ፡ ምግቡን ፡ ቈጥበው ፡ በሉ

**stint** (n.)
*That generous man gives without stint. ያ ፡ ለጋስ ፡ ሰው ፡ እጁ ፡ እንዳመጣ ፡ ይሰጣል

**stipend** አበል
The government grants me a monthly stipend. መንግሥቱ ፡ የወር ፡ አበል ፡ ቈርጦልኛል

**stipulate** ገደብ ፡ አደረገ
He stipulated that the college use his gift for a new library. ለኮሌጁ ፡ የሰጠው ፡ ስጦታ ፡ ላዲሱ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ እንዲውል ፡ ገደብ ፡ አደረገ

**stipulation**
1. አንቀጽ ፤ የተጠቀሰ ፡ ግዴታ. The stipulations of the treaty were harsh. የውሉ ፡ አንቀጾች ፡ ጥብቅ ፡ ነበሩ
The stipulations have not been met, so the contract has been invalidated. የተጠቀሱት ፡ ግዴታዎች ፡ ስላልተፈጸሙ ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል
2. ስምምነት. According to stipulation, the work is to be finished by the end of the month. እንደ ፡ ስምምነቱ ፡ ከሆነ ፡ ሥራው ፡ በወሩ ፡ መጨረሻ ፡ ማለቅ ፡ አለበት

**stir** (stirred), vt.
1. አነሣሣ. The rebel stirred the populace to revolt. ዐመፀኛው ፡ ሕዝቡን ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ አነሣሣ
2. ቈሰቈሰ. Stir the fire! It's dying out. እሳቱን ፡ ቈስቍሰው ፤ መጥፋቱ ፡ ነው
3. አማሰለ. If you had stirred the soup, it wouldn't have burned. ሾርባውን ፡ ብታማስለው ፡ ኖሮ ፡ ባልጐረና ፡ ነበረ
4. አወዛወዘ. The wind stirred the leaves. ነፋሱ ፡ ቅጠሎቹን ፡ አወዛወዛቸው
**stir** (vi.)
He didn't even stir. ንቅንቅም ፡ አላለ
**stir oneself** ተጣደፈ ፤ ፈጠን ፡ አለ
He stirred himself to finish the work. ሥራውን ፡ ለመጨረስ ፡ ተጣደፈ
You'd better stir yourself if you want to be on time. በሰዓቱ ፡ ለመድረስ ፡ ከፈለግክ ፡ ፈጠን ፡ በል
**stir up**
1. አስነሣ ፤ አነሣሣ. Agents have been infiltrating the countryside to stir up riots. አነሣሾች ፡ ሁከት ፡ ለማስነሣት ፡ (ለማነሣሣት) ፡ በየባላገሩ ፡ ሰርገው ፡ ገብተዋል

2. ቀሰቀሰ. He stirred up the dregs by shaking the bottle of mead. የጠጁን ፡ ጠርሙስ ፡ በመነቅነቅ ፡ አምቡላውን ፡ ቀሰቀሰው

**stir** (n.)
1. ጉምጉምታ. There was a stir in the crowd when he got up to speak. ሊናገር ፡ ሲነሣ ፡ በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ጉምጉምታ ፡ ይሰማ ፡ ነበር
2. ስሜት. The coming of the queen caused a great stir. የንግሥቲቱ ፡ መምጣት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሜት ፡ ፈጠረ

**stirring** የሚያነቃቃ ፤ ስሜት ፡ የሚነካ ፤ አነሣሽ
It was a stirring speech. የሚያነቃቃ ፡ ንግግር ፡ ነበር
His speech on national unity was very stirring. ስለ ፡ ብሔራዊ ፡ አንድነት ፡ ያደረገው ፡ ንግግር ፡ ስሜት ፡ የሚነካ ፡ ነበር
Their hearts vibrated to the speaker's stirring appeal. በተናጋሪው ፡ አነሣሽ ፡ ንግግር ፡ ወኔያቸው ፡ ተቀሰቀሰ

**stirrup** እርካብ
The stirrup broke off my saddle. እርካቡ ፡ ከኮርቻው ፡ ላይ ፡ ተበጠሰ

**stitch** (v.)
1. ሰፋ. She stitched the shirt together with red thread. ሸሚዙን ፡ በቀይ ፡ ክር ፡ ሰፋችው
2. ጠቀመ. A needle serves for stitching clothes. መርፌ ፡ ለልብስ ፡ መጥቀሚያ ፡ ያገለግላል

**stitch** (n.)
1. ክር. Rip out these stitches! ክሩን ፡ ፍታው
2. ስፌት. When is the doctor going to take out the stitches? ሐኪሙ ፡ ስፌቱን ፡ መቼ ፡ ነው ፡ የሚያወጣው ?
*I haven't done a stitch of work today. ዛሬ ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ አልሠራሁም

**stitch of clothes** ብጣሽ ፡ ጨርቅ
She didn't have a stitch of clothes on. ብጣሽ ፡ ጨርቅ ፡ እንኳ ፡ ገላዋ ፡ ላይ ፡ አልነበረም

**make stitches** ሰፋ
Don't make such big stitches! እንደዚህ ፡ አራርቀህ ፡ አትስፋ

**stock** (v.)
1. ሞላ. The merchant stocked the store with new goods. ነጋዴው ፡ ሱቁን ፡ ባዲስ ፡ እቃ ፡ ሞላው
2. አረባ(በት). The government stocked the lake with fish. መንግሥት ፡ ሐይቁን ፡ ዓሣ ፡ አረባበት
3. አለ(ው). +Do you stock raincoats? የዝናብ ፡ ልብስ ፡ አላችሁ ?

**be stocked** ተሞላ
His shop is stocked with the latest goods. የሱ ፡ ሱቅ ፡ ባዳዲስ ፡ ሸቀጦች ፡ ተሞልቷል

**stock** (n.)
1. ዘር. These cattle are of a different stock. እነዚህ ፡ ከብቶች ፡ ዘራቸው ፡ የተለየ ፡ ነው
She's of Irish stock. ዘሯ ፡ አይሪሽ ፡ ነው
2. ከብት. The farm was sold with all its stock. እርሻው ፡ ከነከብቱ ፡ ተሸጠ
3. ሰደፍ. Hold the rifle by the stock! ጠመንጃውን ፡ ሰደፉ ፡ ላይ ፡ ያዘው
4. ሸቀጥ. I'll look through my stock and see if I have it. ሸቀጤን ፡ ልፈትሽና ፡ እንዳለ ፡ እያለሁ
5. አክሲዮን. He owns stocks and bonds. አክሲዮኖችና ፡ ቦንዶች ፡ አሉት
*Our stock of food is low. ያለን ፡ ምግብ ፡ አነስተኛ ፡ ነው

**be out of stock**
1. እቃውን ፡ ጨረሰው. It's out of stock, but we have reordered it. እቃውን ፡ ጨርሰናል ፤ ሆኖም ፡ እንደገና ፡ አዘናል
2. ለጊዜው ፡ አለቀ(በት). We are out of stock in this item. ይህ ፡ እቃ ፡ ለጊዜው ፡ አልቆብናል

**have in stock** አለ(ው)
+What kind of goods do you have in stock? ምን ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እቃ ፡ አለህ ?

**keep a stock of** አለ(ው)
+This store keeps a large stock of toys. ይህ ፡ መደብር ፡ ብዙ ፡ አሻንጉሊቶች ፡ አሉት

**take stock**
1. መረመረ. They are taking stock of the situation in Viet Nam right now. በሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የቬትናምን ፡ ሁኔታ ፡ በመመርመር ፡ ላይ ፡ ናቸው
2. እቃ ፡ ቈጠረ. Next week we are going to take stock to see what we have in the store. በሱቃችን ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ለማወቅ ፡ በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ እቃ ፡ እንቈጥራለን
[See also 'laughing']

**stockade** ምሽግ
The troops built a stockade of logs around their post. ወታደሮቹ ፡ በተመደቡበት ፡ ቦታ ፡ በግንድ ፡ የተሠራ ፡ ምሽግ ፡ አበጁ

**stock exchange** የገበያ ፡ ምንዛሪ
Gold shares jumped on the stock exchange. በገበያ ፡ ምንዛሪ ፡ የወርቅ ፡ አክሲዮን ፡ ዋጋ ፡ በንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወጣ

**stocking** የእግር ፡ ሹራብ
I'd like three pairs of stockings. ሦስት ፡ የእግር ፡ ሹራብ ፡ እፈልጋለሁ

**in stocking feet** በእግር ፡ ሹራብ ፡ ብቻ
She runs around the house in her stocking feet. ቤት ፡ ውስጥ ፡ በእግር ፡ ሹራብ ፡ ብቻ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ትላለች

**stockpile** አጠራቀመ
The army is stockpiling fuel for any future conflict. የጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ ምናልባት ፡ ወደፊት ፡ ለሚመጣ ፡ ግጭት ፡ ነዳጅ ፡ ያጠራቅማል

**stocky** ደልዳላ
He is a short, stocky man. አጭርና ፡ ደልዳላ ፡ ሰው ፡ ነው

**stockyard** [እንስሳት ፡ እስኪሸጡ ፡ ድረስ ፡ የሚቆዩበት ፡ ማጐሪያ]

**stoic** (= adv.) በትዕግሥት
She was a stoic throughout her illness. የሕመሟን ፡ ጊዜ ፡ በትዕግሥት ፡ አሳለፈችው

**stoke** ቈሰቈሰ
His father showed him how to stoke a fire. አባትዬው ፡ እሳቱን ፡ እንዴት ፡ እንደሚቈሰቍስ ፡ አሳየው

**stole** (n.) ያንገት ፡ ልብስ
She wore a stole around her shoulders. ትከሻዋ ፡ ላይ ፡ ያንገት ፡ ልብስ ፡ ጣል ፡ አደረገች

**stole**, see **steal**

**stolid** የረጋ
His stolid face betrays no sign of excitement. የረጋ ፡ ሁኔታው ፡ መሸበሩን ፡ አይገልጽም

**stomach** (v.) ታገሠ
I can't stomach that fellow. ያንን ፡ ሰውዬ ፡ ልታገሠው ፡ አልችልም

**stomach** (n.)
1. ሆድ. I cannot go to school because of an upset stomach. ሆዴን ፡ ስላመመኝ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ አልችልም
2. ጨጓራ. Food is digested in the stomach. ምግብ ፡ ጨጓራ ፡ ውስጥ ፡ ይፈጫል
3. ሐሞት. He has no stomach for fighting. ለመዋጋት ፡ ሐሞት ፡ የለውም

**have no stomach for** አልቻለም
She has no stomach for a quarrel. ጥል ፡ አትችልም
[See also 'turn']'

**stomach ache** (የ)ሆድ ፡ ቁርጠት
He suffers from a stomach ache. በሆድ ፡ ቁርጠት ፡ ይሠቃያል

**stone** (v.) ፍሬ ፡ አውጥቶ ፡ ጣለ
The cook stoned the peaches. የወጥ ፡ ቤቱ ፡ የኮኩን ፡ ፍሬ ፡ አውጥቶ ፡ ጣለ

**be stoned** በድንጋይ ፡ ተወገረ
Saint Stephen was stoned. ቅዱስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ በድንጋይ ፡ ተወገረ

**be stoned to death** በድንጋይ ፡ ተወገረ
In ancient times, adulteresses were stoned to death. ድሮ ፡ ያመነዘሩ ፡ ሴቶች ፡ በድንጋይ ፡ ይወገሩ ፡ ነበር

**stone** (n.)
1. ድንጋይ ፤ ደንጊያ. Who threw that stone? ያንን ፡ ድንጋይ ፡ የወረወረው ፡ ማን ፡ ነው ?
We had a beautiful stone put on his grave. የሚያምር ፡ ቅርጽ ፡ ያለው ፡ ድንጋይ ፡ መቃብሩ ፡ ላይ ፡ አኖርን
2. ፍሬ. These plums have giant stones. እነዚህ ፡ ፕላሞች ፡ ትልቅ ፡ ፍሬ ፡ አላቸው

**leave no stone unturned** የሚቻለውን ፡ ሁሉ ፡ አደረገ
We will leave no stone unturned in our efforts to find the culprit. ወንጀለኛውን ፡ ለማግኘት ፡ የሚቻለንን ፡ ሁሉ ፡ እናደርጋለን

**with one stone**
*He killed two birds with one stone. ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ነገር ፡ አከናወነ

**(be) within a stone's throw of** በአቅራቢያው ፡ አለ
We are within a stone's throw of a good market. ጥሩ ፡ የገበያ ፡ ቦታ ፡ በአቅራቢያችን ፡ አለ

**stone** (adj.) የድንጋይ
There are many stone houses in this village. በዚህ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የድንጋይ ፡ ቤቶች ፡ አሉ
[See also 'block, pile, slab, throw, volley']

**stone-blind**
He is stone-blind. ፈጽሞ ፡ ዕውር ፡ ነው

**stone-broke**
I'm stone-broke. ቀዳዳ ፡ ፍራንክ ፡ የለኝም

**stone-deaf**
He is stone-deaf. ፈጽሞ ፡ ደንቆሮ ፡ ነው

**stonehearted** ልበ ፡ ድንጋይ
He is too stonehearted to give any money to charity. በጣም ፡ ልበ ፡ ድንጋይ ፡ ስለሆነ ፡ ገንዘብ ፡ አይቸርም

**stony** ድንጋያማ
The ground is too stony to be plowed. መሬቱ ፡ ድንጋያማ ፡ ስለሆነ ፡ አይታረስም

**have a stony heart** ልበ ፡ ድንጋይ ፡ ነው
The cruel man has a stony heart. ጨካኙ ፡ ሰው ፡ ልበ ፡ ድንጋይ ፡ ነው

**stood,** see **stand**

**stooge** መሣሪያ
They claim our President is a foreign stooge. ፕሬዚዳንታችንን ፡ የውጭ ፡ መሣሪያ ፡ ነው ፡ ይሉታል

**stool** በርጩማ
Put the stool back in the kitchen! በርጩማውን ፡ እወጥ ፡ ቤት ፡ መልስህ ፡ አስቀምጥ

**stool pigeon** ጠቋሚ
The thieves were captured owing to information given by a stool pigeon. ሌቦቹ ፡ በጠቋሚ ፡ መረጃ ፡ መሠረት ፡ ተያዙ

**stoop**
1. ጐንበስ ፡ አለ. He stooped to pick up the newspaper. ጋዜጣውን ፡ ለማንሣት ፡ ጐንበስ ፡ አለ
2. ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አደረገ. He stooped to taking bribes. ጉቦ ፡ በመብላቱ ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አደረገ
3. ራሱን ፡ አዋረደ. He stooped to the vile tasks of the kitchen. ራሱን ፡ አዋርዶ ፡ ዝቅተኛ ፡ የሆኑትን ፡ የማእድ ፡ ቤት ፡ ሥራዎች ፡ ሠራ
*He is a man who would stoop to anything. ለጥቅሙ ፡ ሲል ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ የማይመለስ ፡ ሰው ፡ ነው

**stop** (stopped), vt.
1. አቆመ. Stop the car at the next crossing! በሚቀጥለው ፡ ማቋረጫ ፡ ላይ ፡ መኪናውን ፡ አቁም
This clock makes a lot of noise; please stop it! ይህ ፡ ሰዓት ፡ ብዙ ፡ ይጮኻል ፤ እስቲ ፡ አቁመው
2. አገደ. I couldn't stop him from mailing the letter. ደብዳቤውን ፡ ከመላክ ፡ ላግደው ፡ አልቻልኩም
The bank stopped the check. ባንኩ ፡ ቼኩን ፡ አገደው
3. ዝም ፡ አሰኘ. They were unable to stop the speaker. ተናጋሪውን ፡ ዝም ፡ ለማሰኘት ፡ አልቻሉም ፡ ነበር
4. ተከላከለ. The government took drastic measures to stop inflation. የገንዘብን ፡ መርከስ ፡ ለመከላከል ፡ መንግሥት ፡ ጥብቅ ፡ እርምጃ ፡ ወሰደ
5. ያዘ(በት). He stopped his wages. ደሞዙን ፡ ያዘበት
6. አስቀረ. They succeeded in stopping the revolt. ዐመፁን ፡ ለማስቀረት ፡ ቻሉ
*Please stop that noise! ዝም ፡ በል

**stop** (vi.)
1. ቆመ. The bus stops on the other side of the street. አውቶቡሱ ፡ ከመንገዱ ፡ ባሻገር ፡ ይቆማል
My watch has stopped. ሰዓቴ ፡ ቆሟል
2. አረፈ. Are you stopping at this hotel? የምታርፈው ፡ እዚህ ፡ ሆቴል ፡ ነው ?
3. ገባ. She stopped at the bank for a few minutes. ለጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ ወደ ፡ ባንክ ፡ ገባች
4. አባራ. The rain has finally stopped. ዝናቡ ፡ በመጨረሻ ፡ አባራ

**be stopped** ተቋረጠ
All communication with Asmara has been stopped by the rains. ከዝናብ ፡ የተነሣ ፡ ከአሥመራ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ሁሉ ፡ ተቋርጧል

**stop (a) leak** ደፈነ
He stopped a leak in the pipe with a rag. ቧምቧውን ፡ በጨርቅ ፡ ደፈነው

**stop off** ጐራ ፡ አለ
Let's stop off and see our friends for a moment! ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ጐራ ፡ እንበልና ፡ ጓደኞችንን ፡ ጠይቀን ፡ እንሂድ

**stop over** ጐራ ፡ አለ
Why don't you stop over at my place on the way? እግረ ፡ መንገድህን ፡ ለምን ፡ እቤቴ ፡ ጐራ ፡ አትልም ?

**stop overnight** አደረ
We stopped at the farmhouse overnight. አገበሬው ፡ ቤት ፡ አደርን

**stop short**
1. በድንገት ፡ ቆመ. The car ahead of me had stopped short. ከፊቴ ፡ የሚሄደው ፡ መኪና ፡ በድንገት ፡ ቆመ
2. ለጥቂት ፡ ዳነ. He stopped short at the edge of the cliff. ከገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ደርሶ ፡ ለጥቂት ፡ ዳነ

**stop (one) short** አቋረጠ
I stopped him short before he could say too much. ብዙ ፡ ከመናገሩ ፡ በፊት ፡ አቋረጥኩት

**stop short of** ምንም ፡ አልቀረው
He stopped short of demanding that she give him money. ገንዘቡን ፡ እንድትሰጠው ፡ ለማስገደድ ፡ ምንም ፡ አልቀረው

**stop up** (vt.) ደፈነ
He stopped up the mousehole with old newspapers. ያይጧን ፡ ጉድጓድ ፡ ባሮጌ ፡ ጋዜጣ ፡ ደፈነው

**stop up** (vi.) ተደፈነ
The drain is stopped up. የእጣቢ ፡ መውረጃው ፡ ቧምቧ ፡ ተደፍኗል

**stop** (n.)

1. ማቆሚያ. You have to get off at the next stop. እሚቀጥለው ፡ ማቆሚያ ፡ ላይ ፡ መውረድ ፡ አለብህ
2. (መኪናውን) ፡ ማቆም. His quick stop forestalled an accident. መኪናውን ፡ ቶሎ ፡ ማቆሙ ፡ ከአደጋ ፡ አዳነው
3. መግቻ. A stop for the door keeps it from banging. መዝጊያ ፡ መግቻ ፡ ከተበጀለት ፡ ግው ፡ ብሎ ፡ ከመዘጋት ፡ ያድናል

**bring to a stop** አቆመ
He brought the car to a full stop. መኪናውን ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ አቆመ

**come to a full stop** ቆመ
The car came to a full stop. መኪናው ፡ ቆመ

**full stop** አራት ፡ ነጥብ
Put a full stop at the end of every sentence! ከያንዳንዱ ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ አራት ፡ ነጥብ ፡ አድርግ

**have a stop** ቆመ
We have a ten-minute stop in Boston. ለዓሥር ፡ ደቂቃ ፡ ቦስተን ፡ እንቆማለን

**make a stop**
1. አረፈ. The plane makes two stops between Cairo and London. አውሮፕላኑ ፡ ከካይሮ ፡ ለንደን ፡ በሚጓዝበት ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ቦታ ፡ ያርፋል
2. ጐራ ፡ አለ. We made a stop at the museum. ወደ ፡ ቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ጐራ ፡ አልን

**make an overnight stop** አዳር ፡ አደረገ
He made an overnight stop in Gondar in his flight to Asmara. ወደ ፡ አሥመራ ፡ በአውሮፕላን ፡ ሲሄድ ፡ ጐንደር ፡ አዳር ፡ አደረገ

**put a stop to** አቆመ
We'll have to put a stop to that practice. ያንን ፡ ልማድ ፡ ማቆም ፡ አለብን

**stopgap**
*The measure was only a stopgap. የተወሰደው ፡ እርምጃ ፡ ነገሩን ፡ ለጊዜው ፡ ለማስታገሥ ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ ነበር

**stoplight** የትራፊክ ፡ መብራት
There was a car accident at the stoplight. ከትራፊኩ ፡ መብራት ፡ አጠገብ ፡ የመኪና ፡ አደጋ ፡ ደረሰ

**stopover, make a ~** መንገድ ፡ አረፈ
Does the plane go through to London or does it make stopovers along the way? አውሮፕላኑ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ለንደን ፡ ይበራል ፡ ወይስ ፡ መንገድ ፡ ያርፋል ?
*He made a stopover in Gondar. እግረ ፡ መንገዱን ፡ ጐንደር ፡ አርፎ ፡ ነበር

**stoppage**
*The stoppage of the pipe is probably due to mud. ቧምቧውን ፡ የዘጋው ፡ ጭቃ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም
*During the work stoppage, many workers looked for other jobs. ሥራ ፡ ባቆሙበት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሠራተኞች ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር

**stopper** ውታፍ ፤ ቡሽ
I need a stopper for the bottle. ለጠርሙሱ ፡ ውታፍ ፡ (ቡሽ) ፡ ያስፈልገኛል

**storage**
1. መጋዘን ፡ ውስጥ ፡ ማስቀመጥ. The storage of furniture is costly. የቤት ፡ እቃን ፡ መጋዘን ፡ ውስጥ ፡ ማስቀመጥ ፡ ውድ ፡ ነው
2. መጋዘን. I put my furniture in storage. የቤት ፡ እቃዎቼን ፡ እመጋዘን ፡ አስቀመጥኳቸው
3. ማጠራቀሚያ. Water storage will be helped by the dam. ግድብ ፡ ለውኃ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ያገለግላል

**put in storage** ከተተ
We put our furs in storage for the summer. ባለጸጉር ፡ ልብሳችንን ፡ ለበጋው ፡ ጊዜ ፡ ከተትነው

**store** (v.)
1. አስቀመጠ ፤ አኖረ. He stored the extra chairs in the cellar. ትርፍ ፡ ወንበሮቹን ፡ እምድር ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጠ ፡ (አኖረ)
Where shall I store the potatoes? ድንቹን ፡ የት ፡ ላስቀምጠው ?
2. አከማቸ. They stored the ammunition in a special building. ጥይቱን ፡ በልዩ ፡ ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ አከማቹ

**store up**
1. ጨመረ. I stored up a lot of energy during my vacation. በዕረፍት ፡ ጊዜዬ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጉልበት ፡ ጨመርኩ
2. አከማቸ. Some animals store up food for the rainy season. አንዳንድ ፡ እንስሳዎች ፡ ለክረምት ፡ የሚሆናቸውን ፡ ምግብ ፡ ያከማቻሉ

**store with** መላ
I stored my mind with information. አእምሮዬን ፡ በዕውቀት ፡ መላሁት

**store** (n.) ሱቅ ፤ መደብር
There are many stores on this street. በዚህ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሱቆች ፡ አሉ
The store is now completely bare of goods. መደብሩ ፡ አሁን ፡ ባዶ ፡ ነው

**store of** ብዙ
We have quite a store of food in the house. እቤታችን ፡ ብዙ ፡ ምግብ ፡ አከማችተናል

**be in store for** ለወደፊት ፡ ጠበቀው
Who knows what's in store for us? ወደፊት ፡ ምን ፡ እንደሚጠብቀን ፡ ማን ፡ ያውቃል ?

**have in store** አከማቸ
I have a lot of food in store. ብዙ ፡ ቀለብ ፡ አከማችሁ

**storehouse**
1. ግምጃ ፡ ቤት. The equipment is kept in a storehouse pending future use. ለወደፊት ፡ አገልግሎት ፡ እንዲውል ፡ መሣሪያው ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጧል
2. ጐተራ. This book is a storehouse of information. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የዕውቀት ፡ ጐተራ ፡ ነው

**storekeeper** ባለሱቅ
The storekeeper charges a moderate price. ባለሱቁ ፡ በደኅና ፡ ዋጋ ፡ ይሸጣል

**storeroom** መጋዘን
Put the potatoes and grain in the storeroom! ድንቹንና ፡ እህሉን ፡ እመጋዘን ፡ አስቀምጥ

**storied** ባለ ፡ ፎቅ
There are many three-storied houses in this city. በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ባለ ፡ ሦስት ፡ ፎቅ ፡ ቤቶች ፡ አሉ

**stork** አርኩም

**storm** (vt.) ወረረ
The troops stormed the enemy lines. ወታደሮች ፡ የጠላትን ፡ ሰፈር ፡ ወረሩ

**storm** (vi.) ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ተነሣ
It is storming outside, and we can't go to school. ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ተነሥቷል ፤ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ አንችልም

**storm (out)** ተቈናጥሮ ፡ ወጣ
He stormed out of the house. ከቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ተቈናጥሮ ፡ ወጣ

**storm** (n.)
1. ዓውሎ ፡ ነፋስ ፤ ኀይለኛ ፡ ዝናብ ፤ ማዕበል. There was a big storm last night. ትናንትና ፡ ሌሊት ፡ ኀይለኛ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ነበር
It would be madness to climb the mountain during a storm. ኀይለኛ ፡ ዝናብ ፡ ሲዘንብ ፡ ተራራ ፡ መውጣት ፡ እብደት ፡ ነው
The ship sank during the storm. መርከቢቱ ፡ በማዕበሉ ፡ ጊዜ ፡ ሰጠመች
2. መዓት. A storm of angry words greeted the speaker. ተናጋሪው ፡ የስድብ ፡ መዓት ፡ ወረደበት
3. ድምፅ. A storm of protest broke out when taxes were increased. ግብር ፡ በመጨመሩ ፡ የመቃወሚያ ፡ ድምፅ ፡ ተሰማ
*A storm of tears greeted the mother's refusal to buy her a dress. እናትየዋ ፡ ልብስ ፡ አልገዛልሽም ፡ ስላለቻት ፡ እንባዋ ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ ወረደ

**take by storm** በኀይል ፡ ወሰደ
We took the enemy positions by storm. የጠላትን ፡ ይዞታ ፡ በኀይል ፡ ወሰድን

**storm troops** አጥቂ ፡ ወታደሮች
The storm troops were beaten back with heavy losses. አጥቂ ፡ ወታደሮች ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ደርሶባቸው ፡ ተባረሩ

**stormy** የተፋፋመ
The stormy debates in parliament show that the bill is not likely to pass. በምክር ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የተደረገው ፡ የተፋፋመው ፡ ክርክር ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ሊያልፍ ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል

**stormy weather** ኀይለኛ ፡ ነፋስ
We had stormy weather all week. ሳምንቱን ፡ ሙሉ ፡ ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ይነፍስ ፡ ነበር

**story** (stories)
1. ተረት. He told the story of the cat and the mouse to his children. የድመቷንና ፡ የአይጧን ፡ ተረት ፡ ለልጆቹ ፡ ነገራቸው
2. ፎቅ. The house has five stories. ቤቱ ፡ አምስት ፡ ፎቅ ፡ አለው

**the story goes** እንደሚወራው
The story goes that the two meet each other on the sly. እንደሚወራው ፡ ሁለቱ ፡ የሚገናኙት ፡ በድብቅ ፡ ነው
[See also 'tall']

**storyteller** ተረት ፡ ተናጋሪ
The children stood around the storyteller. ሕፃናቱ ፡ ተረት ፡ ተናጋሪውን ፡ ከበው ፡ ቆሙ

**stout**
1. ወፍራም. He is a stout man and cannot walk fast. ወፍራም ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ መራመድ ፡ አይችልም
2. ጥብቅ. The fort has stout walls. ምሽጉ ፡ ጥብቅ ፡ ግድግዳዎች ፡ አሉት
3. የማይበገር. Our army put up a stout resistance. ሰራዊታችን ፡ የማይበገር ፡ መከላከል ፡ አደረገ
*He has a stout heart. ልበ ፡ ሙሉ ፡ ነው

**get stout** ወፈረ
He has gotten very stout lately. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ በጣም ፡ ወፍሯል

**stove** ምድጃ
There is a fire in the stove. ምድጃው ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ አለ

**stow**
1. አስቀመጠ. He stowed his clothes in a locker. ልብሱን ፡ ሣጥኑ ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጠው
2. ሞላ. The boys stowed supplies for the trip in the little cabin. ልጆቹ ፡ ትንሺን ፡ ጎጆ ፡ ለጉዞው ፡ በሚያስፈልጉ ፡ እቃዎች ፡ ሞሏት

**stow away** ተደብቆ ፡ ሄደ
The boy tried to stow away on a boat going to Aden. ልጁ ፡ ወደ ፡ ኤደን ፡ በሚሄደው ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ተደብቆ ፡ ለመሄድ ፡ ሞከረ

**straddle**
1. እግሩን ፡ አንፈራጦ ፡ ተቀመጠ. He straddled the fence. እግሩን ፡ አንፈራጦ ፡ አጥሩ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ
2. ግልጽ ፡ የሆነ ፡ አቋም ፡ አልወሰደም. They charged the minister with straddling the question of hiring practices. ሚኒስትሩ ፡ ስለ ፡ ሠራተኞች ፡ አቀጣጠር ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ አቋም ፡ ባለመውሰዱ ፡ ነቀፉት

**straggle** ስድ ፡ ተለቀቀ
Cows straggled along the road. ላሞቹ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ስድ ፡ ተለቀው ፡ ነበር

**straggle in one by one** እየተንጠባጠበ ፡ ገባ
The children straggled in one by one. ሕፃናቱ ፡ እየተንጠባጠቡ ፡ ገቡ

**straight** (adj.)
1. ቀጥ ፡ ያለ. Draw a straight line! ቀጥ ፡ ያለ ፡ መሥመር ፡ አሥምር
2. ቀጥተኛ. Give a straight answer to my question! ለጥያቄዬ ፡ ቀጥተኛ ፡ መልስ ፡ ስጥ
3. ዞማ. She has straight hair. ዞማ ፡ ጸጉር ፡ አላት
4. ሐቀኛ. He is perfectly straight in his business dealings. በንግድ ፡ ሥራው ፡ ሐቀኛ ፡ ነው
5. ግልጽ. He has always been straight with me. እሱ ፡ ለኔ ፡ ዘወትር ፡ ግልጽ ፡ ነው

**straight** (adv.)
1. በትክክል. He can't think straight, much less talk straight. በትክክል ፡ መናገር ፡ ቀርቶ ፡ በትክክል ፡ ማሰብም ፡ አይችል
2. በቀጥታ. Come straight to the point! በቀጥታ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ተናገር
He went straight home. በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሄደ
3. ሙሉ ፡ ሳያቋርጥ. He worked for fifteen hours straight. ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ሠራ

**straight across** ፊት ፡ ለፊት
Our house is straight across from the church. ቤታችን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ነው

**straight ahead** በቀጥታ ፡ ወደፊት
Keep straight ahead! በቀጥታ ፡ ወደፊት ፡ ሂድ!

**straight out** ፍርጥ ፡ አድርጎ ፤ በይፋ
I told him straight out that he was a liar. ውሸታም ፡ መሆኑን ፡ ፍርጥ ፡ አድርጌ ፡ (በይፋ) ፡ ነገርኩት

**straight up** ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሰማይ
The smoke rose straight up. ጭሱ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ

**be straight** ተስተካከለ
Is my hat straight? ባርኔጣዬ ፡ ተስተካክሏል ?

**be on straight** ተስተካከለ
Is my hat on straight? ባርኔጣዬ ፡ ተስተካክሏል ?

**get straight** በደንብ ፡ ገባ(ው)
+See if you can get the story straight. ታሪኩ ፡ በደንብ ፡ ገብቶህ ፡ እንደሆነ ፡ አረጋግጥ

**set straight** በደንብ ፡ አደራጀ
Set the room straight before the guests come! እንግዶቹ ፡ ከመምጣታቸው ፡ በፊት ፡ ክፍሉን ፡ በደንብ ፡ አደራጅ

**set (one) straight** አሳወቀ
I set him straight as to who was boss. ማንኛችን ፡ አለቃ ፡ እንደሆን ፡ አሳወቅሁት
[See also 'face, keep, sit']

**straighten**
1. አስተካከለ. Straighten the tablecloth! የጠረጴዛውን ፡ ልብስ ፡ አስተካክለው
2. አቃና. Can you straighten the rod? የብረት ፡ ዘንጉን ፡ ልታቃናው ፡ ትችላለህ ?
3. አዘጋጀ. The maid straightened the room. ገረዲቱ ፡ ክፍሉን ፡ አዘጋጀችው
4. አጸዳ. She straightens the drawer every week. መሳቢያውን ፡ በየሳምንቱ ፡ ታጸዳዋለች

**straighten out** (vt.) አቃና
1. አቃና. Did you straighten out everything? ሁሉንም ፡ ነገር ፡ አቃናህ ?

**straighten out** (vi.) ደኅና ፡ ሆነ
He will straighten out soon. በቅርቡ ፡ ደኅና ፡ ይሆናል

**straighten up** (vt.) በደንብ ፡ አደረገ
Will you please straighten up the room? እባክህን ፡ ክፍሉን ፡ በደንብ ፡ አድርገው

**straighten up** (vi.) ቀና ፡ አለ
He straightened up and looked at me. ቀና ፡ ብሎ ፡ አየኝ

## straightforward
1. ግልጽ. He is straightforward in all he does. በሚያደርገው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ግልጽ ፡ ነው
2. የማያወላውል. Our director has a straightforward approach to the problem. ዲሬክተራችን ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ የማያወላውል ፡ አቋም ፡ አላቸው
He answered in a straightforward manner. በማያወላውል ፡ መንገድ ፡ መለሰ

## strain (v.)
1. ወጠረ. Samson strained his chains and broke them. ሳምሶን ፡ የታሰረበትን ፡ ሰንሰለት ፡ ወጥሮ ፡ በጠሰው
2. ወለም ፡ አለ. The runner strained his leg. ሯጩ ፡ እግሩን ፡ ወለም ፡ አለው
3. አጠለለ. Did you strain the butter? ቅቤውን ፡ አጠለልሽው ?
4. አቆመ. She strained her ears to overhear the conversation. የሚያወሩትን ፡ ልትሰማ ፡ ጆሮዋን ፡ አቆመች
5. አፈዘዘ. I strained my eyes. ዓይኔን ፡ አፈዘዝኩት
6. (= be strained) ጐረነነ. +He strained his voice by shouting so loud. በጣም ፡ ስለጮኸ ፡ ድምፁ ፡ ጐረነነ
7. በመጠምዘዝ ፡ ተረጐመ. He strained the rules to suit himself. ለራሱ ፡ እንዲመች ፡ አድርጎ ፡ በመጠምዘዝ ፡ ሕጉን ፡ ተረጐመ
8. አዛብቶ ፡ ተናገረ. She strained the truth in telling that story. ታሪኩን ፡ ስታወራ ፡ እውነቱን ፡ አዛብታ ፡ ተናገረች
9. አሻከረ. Supporting the bandits will strain the relations between our two countries. ወሮበሎቹን ፡ መደገፍ ፡ የሁለቱን ፡ አገሮቻችንን ፡ ግንኙነት ፡ ያሻክራል

**strain at** ሊበጥስ ፡ ታገለ
The dog was straining at the leash. ውሻው ፡ ማሰሪያውን ፡ ሊበጥስ ፡ ይታገል ፡ ነበር

**strain every effort** ጣረ
We must strain every effort to finish on time. በሰዓቱ ፡ ለመጨረስ ፡ መጣር ፡ አለብን

**strain every muscle** ያለ ፡ የሌለውን ፡ ጉልበት ፡ ተጠቀመበት
He strained every muscle to lift the rock. ቋጥኙን ፡ ለማንሣት ፡ ያለ ፡ የሌለውን ፡ ጉልበት ፡ ተጠቀመበት

**strain (the) impurities from** አጣራ
She strained the impurities from the mead. ጠጁን ፡ አጣራችው

**strain oneself**
1. ተቀጨ. He probably strained himself lifting something heavy. ከባድ ፡ ነገር ፡ ሲያነሣ ፡ ተቀጭቶ ፡ ይሆናል
2. ራሱን ፡ አስጨነቀ. He never strains himself to finish his work on time. ሥራውን ፡ በጊዜው ፡ ለመጨረስ ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ አያስጨንቅም

## strain (n.)
1. ጭንቀት. He had a breakdown due to strain. ከጭንቀት ፡ የተነሣ ፡ የአእምሮ ፡ ሁከት ፡ ደረሰበት
He could not stand the strain of having to make serious decisions constantly. ዘወትር ፡ ከባድ ፡ የሆኑ ፡ ውሳኔዎችን ፡ ከማድረግ ፡ የተነሣ ፡ የደረሰበትን ፡ ጭንቀት ፡ ሊቋቋም ፡ አልቻለም
2. ጣጣ. Do you suffer from the strains of modern life? የጊዜው ፡ የኑሮ ፡ ጣጣ ፡ ያስቸግርሃል ?
3. ምልክት. There was a strain of sadness in his voice. ድምፁ ፡ የሐዘን ፡ ምልክት ፡ ነበረበት
*The strain of the weight on the bridge made it collapse. ድልድዩ ፡ ክብደት ፡ ስለበዛበት ፡ ተጠረመሰ
*The strain of sleepless nights made him ill. እንቅልፍ ፡ ማጣቱ ፡ በሽታ ፡ ላይ ፡ ጣለው
*There is a strain of insanity in that family. በቤተ ፡ ሰባቸው ፡ ንክነት ፡ አለ
*This is a horse of Arabian strain. ይህ ፡ የዓረብ ፡ አገር ፡ ፈረስ ፡ ነው
*It's a strain to read this small print. ይህን ፡ ረቂቅ ፡ ጽሑፍ ፡ ማንበብ ፡ ዓይን ፡ ይጐዳል
[See also 'insanity']

## strained (adj.)
1. ከንገት ፡ በላይ ፡ የሆነ. His strained laugh shows he did not understand the joke. ከንገት ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ ሣቁ ፡ ቀልዱ ፡ ያልገባው ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል
2. የሰለለ. He spoke in a strained voice. በሰለለ ፡ ድምፅ ፡ ተናገረ

**be strained** ሻከረ
At the moment, our friendship is somewhat strained. አሁን ፡ ጓደኝነታችን ፡ ትንሽ ፡ ሻክሯል
*The rope has been strained to the breaking point. ገመዱ ፡ እስኪበጠስ ፡ ተወጥሯል

## strainer ማጥለያ
She used a strainer for the tea. ሻዩን ፡ በማጥለያ ፡ አጠለለች

## strait የባሕር ፡ ወሽመጥ
Bab-el-Mandeb is a strait between Africa and Arabia. ባብ ፡ ኤልመንደብ ፡ በአፍሪካና ፡ በደቡብ ፡ ዓረብ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ የባሕር ፡ ወሽመጥ ፡ ነው

**straits** ችግር
They are in straits because their house burned down. ቤታቸው ፡ ስለተቃጠለ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ወድቀዋል

**strand** (v.) ባዶ ፡ እጁን ፡ አስቀረው
The loss of our money stranded us in Khartum. የገንዘባችን ፡ መጥፋት ፡ ካርቱም ፡ ላይ ፡ ባዶ ፡ እጃችንን ፡ አስቀረን

**strand** (n.)
1. ክር. A strand of the net was broken. የመረቡ ፡ ክር ፡ ተበጠሰ
2. ዘለላ. A strand of hair hung down in her eyes. የጸጉሯ ፡ ዘለላ ፡ ዓይኗ ፡ ላይ ፡ ወርዷል

**(be) stranded** ያለ ፡ ረዳት ፡ ቀረ
We were stranded in a foreign country. በባዕድ ፡ አገር ፡ ያለ ፡ ረዳት ፡ ቀረን
*The ship was stranded on the rocks. መርከቧ ፡ ከአለት ፡ ጋር ፡ ተጋጭታ ፡ መንቀሳቀስ ፡ አቃታት

**strange**
1. እንግዳ. He is strange to the work, but will soon learn. ለሥራው ፡ እንግዳ ፡ ነው ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ይለምደዋል
2. እንግዳ ፡ ነገር. All this is strange to me. ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለኔ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ነው
3. ያልተለመደ. His strange behavior aroused my suspicion. ያልተለመደ ፡ ጠባዩ ፡ ጥርጣሬ ፡ አሳደረብኝ
What a strange question! ምን ፡ ዓይነት ፡ ያልተለመደ ፡ ጥያቄ ፡ ነው!
4. ልዩ ፤ የተለየ. This flower gives off a strange odor. ይህ ፡ አበባ ፡ ልዩ ፡ (የተለየ) ፡ ዓይነት ፡ ሽታ ፡ ይሰጣል
*What strange clothes those foreigners are wearing! እነዚህ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ልብስ ፡ ነው ፡ የሚለብሱት ፡ እባካችሁ

**act strange**
1. እንግዳ ፡ ጠባይ ፡ ታየበት. He acts so strange lately. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ እንግዳ ፡ ጠባይ ፡ ይታይበታል
2. ያለወትሮው ፡ ሆነ. He is acting so strange, he must be in love. ያለወትሮው ፡ እንዲህ ፡ የሚሆን ፡ ነው ፡ ፍቅር ፡ ይዞት ፡ ይሆናል

**be a strange person** ጠባዩ ፡ የተለየ ፡ ነው
He is a strange person; I can't make him out at all. ጠባዩ ፡ የተለየ ፡ ስለሆነ ፡ እንዲህ ፡ ለማለት ፡ ያስቸግራል

**feel strange** ግራ ፡ ገባ(ው)
In Bombay, I felt strange. በቦምቤ ፡ ውስጥ ፡ ግራ ፡ ገባኝ

**have a strange feeling** አንድ ፡ ነገር ፡ ተሰማ(ው)
I had a strange feeling when I saw so many people in the street. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ በማየቴ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ተሰማኝ

**strangely**
*He acts strangely. ሁኔታው ፡ ሁሉ ፡ የተለየ ፡ ነው

**strangely enough** እንዲጋጣሚ
Strangely enough, I was there at the time. እንዲጋጣሚ ፡ ያኔ ፡ እዚያ ፡ ነበርኩ

**stranger**
1. እንግዳ. He is a stranger in Addis Ababa. ለአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ እንግዳ ፡ ነው
2. እንግዳ ፡ መንገደኛ. The stranger asked where he might find a place to spend the night. እንግዳው ፡ መንገደኛ ፡ ማደሪያ ፡ ቤት ፡ የት ፡ እንደሚገኝ ፡ ጠየቀ

**strangle** (vt.)
1. አንቆ ፡ ገደለ. The soldier strangled the spy. ወታደሩ ፡ ሰላዩን ፡ አንቆ ፡ ገደለው
2. አነቀ. His collar seemed to be strangling him. የሸሚዙ ፡ አንገት ፡ ያነቀው ፡ ይመስላል

**strangle,** vi. (= vt.) አነቀ
+He strangled on a piece of meat. የሥጋ ፡ ቁራጭ ፡ አነቀው

**strangle a desire (to)** አፍኖ ፡ ያዘ
She strangled a desire to laugh. ሣቋን ፡ አፍና ፡ ያዘች

**stranglehold, have a ~ on** አንቆ ፡ ያዘ
Foreign traders have a stranglehold on retail sales. የውጭ ፡ አገር ፡ ነጋዴዎች ፡ የችርቻሮውን ፡ ንግድ ፡ አንቀው ፡ ይዘዋል

**strangulation**
*Strangulation appears to be the cause of his death. የሞተው ፡ ታንቆ ፡ ይመስላል

**strap** (strapped), v. በመጫኛ ፡ አሰረ
We strapped the trunk. ሣጥኑን ፡ በመጫኛ ፡ አሰርን

**strap on**
1. አሰረ. He strapped on his watch. ሰዓቱን ፡ አሰረ
2. ታጠቀ. He strapped on his pistol. ሽጉጡን ፡ ታጠቀ

**strap** (n.)
1. ጠፍር. Put the strap around the suitcase! ሻንጣውን ፡ በጠፍር ፡ አሰረው
2. ማሰሪያ. The strap on my sandal broke. ነጠላ ፡ ጫማዬ ፡ ማሰሪያው ፡ ተበጠሰ

3. ጥብጣብ. The general wore shoulder straps. ጀኔራሉ ፡ ትከሻው ፡ ላይ ፡ ጥብጣብ ፡ አድርጓል

**iron strap** ቦንዳ

I need something to break the iron straps on this crate. ቦንዳውን ፡ ከሣጥኑ ፡ ላይ ፡ የምቈርጥበት ፡ ነገር ፡ እፈልጋለሁ

[See also 'leather, rawhide']

**strapping** ጥሩ ፡ ቁመና ፡ ያለው

He is a strapping fellow. ጥሩ ፡ ቁመና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**strata**, see **stratum**

**stratagem** የጦር ፡ ስልት

The general's stratagem was successful. የጀኔራሉ ፡ የጦር ፡ ስልት ፡ የተሳካ ፡ ነበር

*The spy got into the castle by the stratagem of dressing as a beggar. ሰላዩ ፡ እንደ ፡ ለማኝ ፡ ለብሶ ፡ ግንቡ ፡ ውስጥ ፡ ገባ

**strategic** ለጦር ፡ አቅድ ፡ ምቹ

We occupied a strategic section of the country. ለጦር ፡ አቅድ ፡ ምቹ ፡ የሆነውን ፡ ቀበሌ ፡ ያዝን

**strategic move** ዘዴ

By several strategic moves he became director of the business. በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴ ፡ የንግዱ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ሆነ

**strategy**

1. ዘዴ. The army succeeded by strategy rather than by force. ጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ በኀይል ፡ ሳይሆን ፡ በዘዴ ፡ የተሳካ ፡ ውጤት ፡ አገኘ

It took strategy to get him to come with us. ከኛ ፡ ጋር ፡ እንዲመጣ ፡ ለማድረግ ፡ ዘዴ ፡ መጠቀም ፡ ግድ ፡ ሆነብን

2. የጦር ፡ ስልት ፤ የጦር ፡ ዘዴ. He modeled his strategy on Napoleon's. የናፖሊዎንን ፡ የጦር ፡ ስልት ፡ በመከተል ፡ የጦር ፡ ዘዴውን ፡ አደራጀ

**stratify** (stratified) በደረጃ ፡ ከፋፈለ

Wealth tends to stratify certain societies. ሀብት ፡ አንዳንድ ፡ ኅብረ ፡ ሰቦችን ፡ በደረጃ ፡ ይከፋፍላል

**stratosphere** የላይኛው ፡ ጠፈር

**stratum** (strata) ድርብርብ

There is a stratum of porous rock beneath the soil. ከአፈሩ ፡ ሥር ፡ ውኃ ፡ የሚያሳልፍ ፡ የቋጥኝ ፡ ድርብርብ ፡ አለ

**straw** (n.)

1. ሣር. The house is thatched with straw. ቤቱ ፡ የሣር ፡ ክዳን ፡ ነው

2. የሣር ፡ አገዳ. I prefer to drink milk with a straw. ወተት ፡ በሣር ፡ አገዳ ፡ መጠጣት ፡ ደስ ፡ ይለኛል

**(be the) last straw** ከእንግዲህ ፡ በቃ

I warned him repeatedly not to take my books without my permission, but he has done it again! That is the last straw. መጽሐፌን ፡ ያለፈቃዴ ፡ እንዳይወስድ ፡ ደጋግሜ ፡ አስጠንቅቄው ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ደግሞ ፡ አድርጎታል ፤ ከእንግዲህ ፡ በቃ

**straw** (adj.)

1. የኬሻ. Women wear straw hats in the summer. ሴቶች ፡ በበጋ ፡ የኬሻ ፡ ባርኔጣ ፡ ያደርጋሉ

2. (የ)ሣር. I like to sleep on a straw mattress. ሣር ፡ ፍራሽ ፡ ላይ ፡ መተኛት ፡ እወዳለሁ

**strawberry** እንጆሪ

**stray** (v.)

1. ተለየ. Some sheep strayed from the flock. ጥቂት ፡ በጎች ፡ ከመንጋው ፡ ተለዩ

2. ባከነ. His thoughts strayed from the test. በፈተናው ፡ ጊዜ ፡ ሐሳቡ ፡ ይባክን ፡ ነበር

**stray from** ለቀቀ

Don't stray from the point! አርእስት ፡ አትልቀቅ

**stray off somewhere** ጠፋ

Our dog has strayed off somewhere. ውሻችን ፡ ጠፍቷል

**stray** (adj.)

1. የጠፋ ፤ ባለቤት ፡ የሌለው. She brings home every stray cat and dog she finds. የጠፋ ፡ ውሻና ፡ ድመት ፡ ስታገኝ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ይዛ ፡ መምጣት ፡ ነው

The stray cat insinuated himself into our kitchen. ባለቤት ፡ የሌለው ፡ ድመት ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ማድ ፡ ቤታችን ፡ ውስጥ ፡ ገባ

2. ልቅ ፡ የሆነ. The farmer impounded the stray cattle. ገበሬው ፡ ልቅ ፡ የሆኑትን ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ በአፈላማ ፡ ያዘ

3. ተባራሪ. He was hit by a stray bullet. በተባራሪ ፡ ጥይት ፡ ተመታ

4. (= adv.) አልፎ ፡ አልፎ. There were a few stray fishermen's huts along the beach. በባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ላይ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ጥቂት ፡ የዓሣ ፡ አጥማጆች ፡ ጎጆዎች ፡ ነበሩ

*The streets were empty except for a stray taxi or two. ካንድና ፡ ከሁለት ፡ ታክሲዎች ፡ በስተቀር ፡ መንገዱ ፡ ጭር ፡ ብሎ ፡ ነበር

**streak** (v.) ተተኰሰ

The shooting star streaked across the sky. ተወርዋሪዋ ፡ ኮከብ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ተተኰሰች

**streak** (n.) ጭረት
The streak will not come out of my shirt. ጭረቱ ፡ ከሸሚዜ ፡ አልለቅ ፡ ብሎኛል
*There is a streak of cruelty in his nature. ትንሽ ፡ ጨካኝነት ፡ አለበት

**stream** (v.)
1. ተንጠፈጠፈ. The sweat was streaming down his brow. ላቡ ፡ ከግንባሩ ፡ ይንጠፈጠፍ ፡ ነበር
2. ኰለል ፡ አለ. Tears streamed down her cheeks. እንባ ፡ በጉንጮቿ ፡ ላይ ፡ ኰለል ፡ አለ
3. ገባ. When I woke up, the sunlight was streaming through the windows. ስነሣ ፡ የፀሐዩ ፡ ጮራ ፡ በመስኮት ፡ ገብቶ ፡ ነበር
4. ጐረፈ. Crowds were streaming through the streets. ሕዝቡ ፡ በጐዳናዎቹ ፡ ላይ ፡ ይጐርፍ ፡ ነበር
+His eyes were streaming with tears. ከዓይኑ ፡ እንባ ፡ ይጐርፍ ፡ ነበር
5. ተውለበለበ. Flags streamed in the wind. ሰንደቅ ፡ ዓላማዎቹ ፡ በነፋስ ፡ ተውለበለቡ
6. ፈሰሰ. The water streamed across the floor. ውኃው ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ፈሰሰ

**stream blood** ደማ
The wound streamed blood. ቁስሉ ፡ ደማ

**stream** (n.) ወንዝ
Where can we cross the stream? ወንዙን ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ለመሻገር ፡ እንችላለን ?
*Did you see the stream of cars? መኪናዎቹ ፡ ሲጐርፉ ፡ አየህ ?

**streams of** ብዙ
Streams of people poured into the exhibition grounds. ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ኤግዚቢሽኑ ፡ ጐረፈ

**stream of light** ጨረር
A stream of light came in through the window. በመስኮቱ ፡ በኩል ፡ ጨረር ፡ ገባ

**a stream of**
1. ብዙ. He uttered a stream of profanities. ብዙ ፡ ጸያፍ ፡ ነገሮች ፡ ተናገረ
2. ነጐድጓድ. A stream of insults came from the mouth of the angry woman. የተናደደችው ፡ ሴት ፡ የስድብ ፡ ነጐድጓድ ፡ አወረደችበት

**with the stream**
*He prefers to go with the stream. ወደ ፡ ነፈሰበት ፡ መንፈስ ፡ ይወዳል
[See also 'perennial']

**streaming** ኀይለኛ
He had to walk in the streaming rain. በኀይለኛው ፡ ዝናብ ፡ ውስጥ ፡ መሄድ ፡ ነበረበት

**street** መንገድ
I met him on the street. መንገድ ፡ ላይ ፡ አገኘሁት

**one-way street** ባንድ ፡ በኩል ፡ ብቻ ፡ የሚያስኬድ ፡ መንገድ
Don't drive in there; that's a one-way street. ባንድ ፡ በኩል ፡ ብቻ ፡ የሚያስኬድ ፡ መንገድ ፡ ስለሆነ ፡ በዛ ፡ አትንዳ
[See also 'dead end, line, turn']

**streetcar** ትራም
Take the next streetcar! የሚቀጥለውን ፡ ትራም ፡ ውሰድ

**strength**
1. ኀይል. The enemy underestimated our strength. ጠላት ፡ ኀይላችንን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ገመቱ
The strength of this drug is enough to start a heart beating again. የዚህ ፡ መድኀኒት ፡ ኀይል ፡ ልብ ፡ ሲቆም ፡ እንደገና ፡ እንዲመታ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል
2. ጥንካሬ. He surpasses his classmates in strength and skill. በጥንካሬና ፡ በችሎታ ፡ ከክፍሉ ፡ ጓደኞቹ ፡ ይበልጣል
3. ጉልበት. I haven't the strength to lift this box. ይህንን ፡ ሣጥን ፡ ለማንሣት ፡ ጉልበት ፡ የለኝም
4. የጉልበት ፡ ብርታት. Because of his strength, he can lift great weights. ከጉልበቱ ፡ ብርታት ፡ የተነሣ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ ሊያነሣ ፡ ይችላል
5. ዓቅም. I had to apply all my strength. ባለኝ ፡ ዓቅም ፡ ሁሉ ፡ መሥራት ፡ ነበረብኝ
6. ብዛት. The strength of our army is now 60,000. የጦር ፡ ወታደሮቻችን ፡ ብዛት ፡ አሁን ፡ ስድሳ ፡ ሺ ፡ ነው

**bring up to strength** ከሚያስፈልገው ፡ ቁጥር ፡ አደረሰ
We must bring the police force up to strength. የፖሊስ ፡ ኀይላችንን ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ቁጥር ፡ ማድረስ ፡ አለብን

**in great strength** ኀይሉን ፡ አደርጅቶ
The enemy was there in great strength. ጠላት ፡ ኀይሉን ፡ አደርጅቶ ፡ መጥቶ ፡ ነበር

**on the strength of** በ --- ደጋፊነት
He was hired on the strength of your recommendation. በሰጠኸው ፡ አስተያየት ፡ ደጋፊነት ፡ ተቀጠረ
[See also 'exceed, lose, sap, tax']

**strengthen**
1. ጉልበት ፡ ሰጠ. Good food and rest have strength-

ened him. ጥሩ ፡ ምግብና ፡ ዕረፍት ፡ ጉልበት ፡ ሰጥቶታል
2. አጠነከረ. Iron rods strengthen concrete. የብረት ፡ ዘንግ ፡ ሲሚንቶውን ፡ ያጠነክረዋል
Reinforcements have strengthened our forces at the front. ተጨማሪው ፡ ወታደር ፡ የግንባር ፡ ጦራችንን ፡ አጠንክሮታል

**strenuous**
1. አድካሚ. Chopping wood is a strenuous task. ዕንጨት ፡ መቍረጥ ፡ አድካሚ ፡ ሥራ ፡ ነው
2. ብርቱ. He is a strenuous campaigner for adult literacy. ለጎልማሶች ፡ ትምህርት ፡ ብርቱ ፡ ተሟጋች ፡ ነው
*We had a strenuous day moving into our new house. አዲሱ ፡ ቤታችን ፡ስንገባ ፡ ሥራው ፡ በጣም ፡ አድክሞን ፡ ነበር

**stress** (v.) ደጋግሞ ፡ አሳሰበ
She stressed two things in particular. በተለይ ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ ደጋግማ ፡ አሳሰበች

**be stressed** ጠበቀ
The second syllable of this word is stressed. የዚህ ፡ ቃል ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍለ ፡ ቃል ፡ ይጠብቃል

**stress** (n.)
1. ችግር. These are times of stress. ዘመኑ ፡ የችግር ፡ ነው
2. ጭንቀት. The great mental stress shattered his mind. የአእምሮ ፡ ጭንቀት ፡ መንፈሱን ፡ በጠበጠው
*The stress in this word is on the first syllable. በዚህ ፡ ቃል ፡ ጠብቆ ፡ የሚነገረው ፡ ባንደኛው ፡ ክፍለ ፡ ቃል ፡ ነው

**be under stress** ተጨነቀ
When members of one's family are very sick, one is always under great stress. አንድ ፡ ሰው ፡ ዘመድ ፡ ሲታመምበት ፡ ይጨነቃል

**lay stress**
1. ግምት ፡ ሰጠ. This country lays great stress on education. ይህች ፡ አገር ፡ ለትምህርት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ትሰጣለች
2. አበረታታ. This school lays great stress on foreign languages. ይህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋዎችን ፡ እንዲማሩ ፡ በጣም ፡ ያበረታታል

**under the stress of** ገፋፍቶት
Under the stress of hunger, the man stole some food. ሰውዬው ፡ ረኃብ ፡ ገፋፍቶት ፡ ምግብ ፡ ሰረቀ

**stretch** (vt.)
1. ወጠረ. He stretched the violin string until it broke. የቫዮሊኑን ፡ ጭራ ፡ እስኪበጠስ ፡ ወጠረው
He stretched the hide for drying. ቆዳውን ፡ እንዲደርቅ ፡ ወጥሮታል
2. አሰፋ. Can you stretch my shoes a little bit? ጫማዬን ፡ ትንሽ ፡ ልታሰፋልኝ ፡ ትችላለህ ?
3. ዘረጋ. They stretched a rope across the path. በመንገዱ ፡ አግድም ፡ ገመድ ፡ ዘረጉ
4. አፍታታ. After working several hours, I have to get up and stretch my legs. ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ከሠራሁ ፡ በኋላ ፡ ብድግ ፡ ብዬ ፡ እግሬን ፡ ማፍታታት ፡ አለብኝ
5. መዘዘ. He stretched his neck to see over the wall. በግንቡ ፡ ላይ ፡ አሻግሮ ፡ ለማየት ፡ አንገቱን ፡ መዘዘ
6. ለቀቅ ፡ አደረገ. They will stretch the rule on admissions to allow certain students to enter. አንዳንድ ፡ ተማሪዎችን ፡ ለማስገባት ፡ ደንቡን ፡ ለቀቅ ፡ ያደርጉታል
7. ከጥቅም ፡ ላይ ፡ አዋለ. We must stretch every dollar. እያንዳንዱን ፡ ብር ፡ ከጥቅም ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ አለብን

**stretch** (vi.)
1. ተስፋፋ. The Roman empire stretched over many countries. የሮም ፡ ግዛት ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ነበር
2. ደረሰ. The realm of Ethiopia stretches from the Red Sea to the Sudan. የኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ከቀይ ፡ ባሕር ፡ እስከ ፡ ሱዳን ፡ ይደርሳል
3. ተዘረጋ. The road stretched for miles through the hills. መንገዱ ፡ በኰረብታዎቹ ፡ መሀከል ፡ ለብዙ ፡ ማይል ፡ ተዘርግቷል
4. ተሳበ. Will this material stretch? ይህ ፡ ጨርቅ ፡ ይሳባል ?
5. ተንጠራራ. I had to stretch in order to reach the top shelf. አላይኛው ፡ መደርደሪያ ፡ ለመድረስ ፡ መንጠራራት ፡ ነበረብኝ

**stretch every effort** የተቻለውን ፡ ሁሉ ፡ አደረገ
She stretched every effort to join us. ከኛ ፡ ጋር ፡ ለመሆን ፡ የተቻላትን ፡ ሁሉ ፡ አደረገች

**stretch out** (vt.) ዘረጋ
He stretched out his arms. እጁን ፡ ዘረጋ

**stretch out** (vi.)
1. ተዝናና. I'd like to stretch out a bit. ትንሽ ፡ ልዝናና ፡ እፈልጋለሁ
2. ጋደም ፡ አለ. He stretched out on the sofa. ሶፋው ፡ ላይ ፡ ጋደም ፡ አለ
3. ተንጣለለ. The wheat fields stretch out for miles. የስንዴው ፡ እርሻ ፡ ለብዙ ፡ ማይል ፡ ተንጣሏል

**stretch (one) out** ዘረረ
The blow stretched him out on the ground. ምቱ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ዘረረው

**lay stretched out** ተዘረረ
The cat lay stretched out beside the fire in contentment. ድመቲቷ ፡ ረክታ ፡ እሳቱ ፡ ዳር ፡ ተዘርራለች
[See also 'leg, length']

**stretch** (n.) መንገድ
We had to run the last stretch. የቀረነን ፡ መን ገድ ፡ በሩጫ ፡ መጨረስ ፡ ነበረብን
*The road passes through a beautiful stretch of wooded country. መንገዱ ፡ የሚያስደስቱ ፡ ዛ ፎች ፡ ባሉበት ፡ ገጠር ፡ ውስጥ ፡ ያልፋል
*A stretch of sand lay between the road and the ocean. በመንገዱና ፡ በውቅያኖሱ ፡ መካከል ፡ አሸዋ ፡ ተንጣሏል
*He spent a stretch of two years in jail. ሁለ ት ፡ ዓመት ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ አሳለፈ

**at a stretch** ሳያቋርጥ ፤ በመደዳው
He works about ten hours at a stretch. ሳያ ቋርጥ ፡ (በመደዳው) ፡ ዐሥር ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ይ ሠራል

**by no stretch of imagination**
*By no stretch of the imagination can it be considered possible. በምንም ፡ ዓይነት ፡ ይቻላል ፡ ተብሎ ፡ አይታለምም
[See also 'expansive']

**stretcher** ቃሬዛ
They carried him out on a stretcher. በቃሬዛ ፡ ተሸክመው ፡ ወሰዱት

**strew**
1. በተነ. The girls strewed flowers in the Emperor's path. ልጃገረዶቹ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሚያልፉበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ አበባ ፡ በተኑ
2. ዘራ. The farmer strewed grain over the field. ገበሬው ፡ መሬቱን ፡ እህል ፡ ዘራ

**strew about** አዝረከረከ
He strewed his clothes about. ልብሱን ፡ አዝረከ ረከ

**strew on the floor** ጐዘጐዘ
They strew rushes on the floor of the church. በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ ቄጠማ ፡ ይጐዘጕዛሉ

**be strewn** ተዝረከረከ
The street was strewn with litter. ጐዳናው ፡ ቆ ሻሻ ፡ ተዝረከርኮበታል

**be strewn about** ተበታተነ
Bits of furniture and glass were strewn about after the bomb's explosion. ከቦምቡ ፡ መፈንዳ ት ፡ በኋላ ፡ የቤት ፡ እቃዎችና ፡ የመስታወት ፡ ስባ ሪዎች ፡ ተበታትነው ፡ ነበር

**(be) stricken (with)**
1. ድንገት ፡ ተያዘ. She was stricken with polio. በፖሊዮ ፡ በሽታ ፡ ድንገት ፡ ተይዛ ፡ ነበር
2. አደረ(በት) ፤ ተሰማ(ው). +She was stricken with guilt. ጸጸት ፡ አደረባት ፡ (ተሰማት)

**be terror-stricken** በፍርሃት ፡ ተዋጠ
The children were terror-stricken during the thunderstorm. በነጐድጓዱ ፡ ጊዜ ፡ ልጆቹ ፡ በፍር ሃት ፡ ተውጠው ፡ ነበር

**strict**
1. ጥብቅ. Army discipline is always strict. የወታደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሁልጊዜ ፡ ጥብቅ ፡ ነው
I'm telling you this in strict confidence. ይህንን ፡ የማጫውትህ ፡ እንደ ፡ ጥብቅ ፡ ምስጢር ፡ አድርጌ ፡ ነው
2. የተወሰነ. I have to keep to a strict diet. የተወሰነ ፡ ምግብ ፡ መብላት ፡ አለብኝ
3. ደንበኛ. In the strict sense of the word, it means "soldier". በደንበኛው ፡ የቃሉ ፡ አባ ባል ፡ ለማለት ፡ የተፈለገው ፡ ወታደር ፡ ነው
*He told the strict truth. እቅጩን ፡ ተናገረ

**stride** (strode), v. በኀይል ፡ ተራመደ
He was striding down the road. በመንገድ ፡ ላ ይ ፡ በኀይል ፡ ይራመድ ፡ ነበር

**stride** (n.) እርምጃ
Ethiopia is making great strides in modernization. ኢትዮጵያ ፡ በዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ታላ ቅ ፡ እርምጃ ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ነች
His stride is long. እርምጃው ፡ ሰፊ ፡ ነው

**take in stride** በርጋታ ፡ ተቀበለ
We have to take difficulties in stride. ችግ ሩን ፡ በርጋታ ፡ መቀበል ፡ አለብን

**strident** ቀጭን
Her strident voice can be heard everywhere. ቀጭኑ ፡ ድምጿ ፡ ከየትም ፡ ሊሰማ ፡ ይችላል

**strife** ጠብ
Strife between the two tribes resulted in bloodshed. በሁለቱ ፡ ጐሳዎች ፡ ጠብ ፡ ደም ፡ ተ ፋሰሰ

**strike** (struck), vt.
1. መታ. He struck me on the chin. አገጩ ፡ ላ ይ ፡ መታኝ
He struck the table a heavy blow. ጠረጴዛውን ፡ በኀይል ፡ መታው

2. ከ - - - ጋር ፡ ተጋጨ. The car went to pieces when it struck the wall. ከግድግዳው ፡ ጋር ፡ በተጋጨ ፡ ጊዜ ፡ መኪናው ፡ እንክትክት ፡ አለ
3. አትሞ ፡ አወጣ. The mint strikes coins. ገንዘብ ፡ መሥሪያው ፡ ሳንቲሞች ፡ አትሞ ፡ ያወጣል
4. ጫረ. Strike a match! I can't see in the dark. ክብሪት ፡ ጫር ፣ በጨለማ ፡ ለማየት ፡ አልችልም
5. አገኘ. They struck oil in the desert. በረኻው ፡ ውስጥ ፡ ዘይት ፡ አገኙ
6. ሰረዘ. The secretary struck ten words from the minutes of the meeting. ጸሐፊው ፡ ከስብሰባው ፡ ቃለ ፡ ጉባኤ ፡ ውስጥ ፡ ዐሥር ፡ ቃላት ፡ ሰረዘ
7. ያዘ. Flu struck the whole family. ቤተሰቡን ፡ በሙላ ፡ ኢንፍሉዌንዛ ፡ ይዞታል
8. ሰደደ. The plant has struck root. ተክሉ ፡ ሥር ፡ ሰዷል
9. አሰማ. The prime minister struck a note of warning in his speech. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በንግግራቸው ፡ ውስጥ ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ቃል ፡ አሰሙ
10. ትዝ ፡ አለ(ው). She smiled as an amusing thought struck her. አንድ ፡ የሚያሥቅ ፡ ነገር ፡ ትዝ ፡ ብሏት ፡ ፈገግ ፡ አለች
11. መስሎ ፡ ታየ. The plan strikes me as silly. ይህ ፡ እቅድ ፡ የማይረባ ፡ መስሎ ፡ ይታየኛል
12. መሰለ. How does this idea strike you? ይህ ፡ ሐሳብ ፡ ምን ፡ ይመስልሃል ?
13. ከ---ደረሰ. The employer and the workmen have struck an agreement. ቀጣሪውና ፡ ሠራተኞቹ ፡ ከስምምነት ፡ ደርሰዋል
*The clock just struck ten. ሰዓቱ ፡ ገና ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ደወለ
*It strikes me that he's acting very strangely. አኳኋኑ ፡ ሁሉ ፡ ተለወጠብኝ

**strike** (vi.)
1. ወደቀ. Where did the lightning strike? መብረቁ ፡ የት ፡ ወደቀ ?
2. ተናደፈ. Some snakes make a noise before they strike. አንዳንድ ፡ እባቦች ፡ ከመናደፋቸው ፡ በፊት ፡ ድምፅ ፡ ያሰማሉ
3. አመራ. We struck northward. ወደ ፡ ሰሜን ፡ አመራን
4. አደመ ፣ ሥራ ፡ አቆመ. Why are the workers striking? ሠራተኞች ፡ ለምን ፡ አደሙ ? (ሥራ ፡ አቆሙ ?)
*You had better strike while the iron is hot. አባት ፡ ሳለህ ፡ አጊጥ ፣ ጀምበር ፡ ሳለ ፡ ሩጥ

**strike (one's) ear** ተሰማ(ው)
The sound of music struck my ear. የሙዚቃው ፡ ድምፅ ፡ ተሰማኝ

**strike (one's) eye** ታየ
The sign struck my eye right away. ምልክቱ ፡ ወዲያው ፡ ታየኝ

**strike off** ሰረዘ
The teacher struck off the names of tardy students. መምህሩ ፡ ዘግይተው ፡ የሚመጡ ፡ ተማሪዎችን ፡ ስም ፡ ሰረዘ

**strike on the idea** ሐሳብ ፡ በድንገት ፡ መጣለት
He struck on the idea of building additional classrooms. ተጨማሪ ፡ የመማሪያ ፡ ክፍል ፡ የማሠራት ፡ ሐሳብ ፡ በድንገት ፡ መጣለት

**strike out** ሰረዘ
Strike out the first paragraph! የመጀመሪያውን ፡ አንቀጽ ፡ ሰርዘው

**strike out across** አሳብሮ[*] ፡ ሄደ
He struck out across the country. በገጠሩ ፡ ውስጥ ፡ አሳብሮ ፡ ሄደ

**strike terror** አስደነገጠ ፣ አሸበረ
The lightning struck terror in her heart. መብረቁ ፡ ልቧን ፡ አሸበረው ፡ (በጣም ፡ አስደነገጣት)

**strike (through)** ሰንጥቆ ፡ ወጣ
The sun's rays struck through the fog. የፀሐዩ ፡ ጮራ ፡ ጉሙን ፡ ሰንጥቆ ፡ ወጣ

**strike up** (vt.) መሠረተ
We struck up an acquaintance while we were abroad. ውጭ ፡ አገር ፡ በነበርንበት ፡ ጊዜ ፡ ጓደኝነት ፡ መሠረትን

**strike up** (vi.) መጫወት ፡ ጀመረ
As soon as the President appeared, the band struck up. ፕሬዚዳንቱ ፡ ብቅ ፡ ሲል ፡ ወዲያው ፡ የሙዚቃው ፡ ጓድ ፡ መጫወት ፡ ጀመረ

**be struck dead**
*He was struck dead by lightning. መብረቅ ፡ መቶት ፡ ሞተ

**be struck down** ተቀጨ
He was struck down by illness at a very early age. በልጅነቱ ፡ በበሽታ ፡ ተቀጨ
[See also 'bargain, blow']

**strike** (n.)
1. የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማ. How long did the strike last? የሥራ ፡ ማቆሙ ፡ አድማ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ቆየ ?
2. መገኘት. The gold strike caused tremendous excitement. የወርቅ ፡ ማዕድን ፡ መገኘቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ አሳደረ

**air strike** የቦምብ ፡ ድብደባ
The air strike caused heavy losses. የቦምቡ ፡ ድብደባ ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ አደረሰ

**go on strike** ሥራ ፡ አቆመ
The workers went on strike in opposition to the new laws of the company. ሠራተኞቹ ፡ አዲሱን ፡ የኩባንያ ፡ ሕግ ፡ በመቃወም ፡ ሥራ ፡ አቆሙ

**make a strike against** ደበደበ
The planes made a strike against the enemy lines. አውሮፕላኖቹ ፡ የጠላትን ፡ ሰፈር ፡ ደበደቡ

**strikebreaker** የሥራ ፡ ማቆሙን ፡ ስምምነት ፡ የጣሰ
Rocks were thrown at the strikebreakers. የሥራ ፡ ማቆሙን ፡ ስምምነት ፡ በጣሱት ፡ ላይ ፡ ድንጋይ ፡ ተወረወረባቸው

**striker** ሥራ ፡ ያቆመ
The strikers were arrested. ሥራ ፡ ያቆሙት ፡ ተያዙ

**striking** (adj.) ደማቅ
She likes to wear striking colors. ደማቅ ፡ ልብስ ፡ መልበስ ፡ ትወዳለች
*The capital is within striking distance of our air force. መናገሻ ፡ ከተማው ፡ ያየር ፡ ኀይላችንን ፡ ለማጥቃት ፡ በሚችልበት ፡ ርቀት ፡ ላይ ፡ ነው
*There is a striking resemblance between the two boys. ሁለቱ ፡ ልጆች ፡ በጣም ፡ ይመሳሰላሉ

**string** (strung), v.
1. ሰካ. He strung the beads. ዶቃውን ፡ ሰካ
2. ቀነጠሰ. The maid strung the beans. ገረዲቱ ፡ ፋሶሊያውን ፡ ቀነጠሰችው
3. ዘረጋ (ተዘረጋ). A telephone wire is being strung to houses in the country. በባላገር ፡ ላሉ ፡ ቤቶች ፡ የስልክ ፡ መሥመር ፡ ተዘርግቶላቸዋል

**string (someone) along** አሞኘ
I suspected he's been stringing me along. ሳያሞኘኝ ፡ አልቀረም ፡ ብዬ ፡ እጠረጥራለሁ

**string along with** ያለውን ፡ ተከተለ
String along with me, and I'll help you. እኔ ፡ ያልኩህን ፡ ከተከተልክ ፡ እግዛሃለሁ

**string out in a line** ተሰለፈ
The students strung out in a line after the monitor. ተማሪዎቹ ፡ ካለቃቸው ፡ ኋላ ፡ ተሰለፉ

**string up** ሰቀለ
The bandits strung up the man. ሽፍቶች ፡ ሰውዬውን ፡ ሰቀሉት

**be strung out** ተራዘመ
The program was strung out too long. ፕሮግራሙ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ተራዘመ

**string** (n.)
1. ሲባጎ. This string is too short. ይህ ፡ ሲባጎ ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ ነው
2. ድሪ. She's wearing a string of pearls. አንገቷ ፡ ላይ ፡ የሉል ፡ ድሪ ፡ አጥልቃለች
3. አውታር. The string of the harp broke. የበገናው ፡ አውታር ፡ ተበጥሷል
*A string of cars was parked along the road. በመንገዱ ፡ ዳር ፡ ብዙ ፡ መኪና ፡ ተቀጣጥሎ ፡ ቆሞ ፡ ነበር

**strings** ግዴታ
The grant had a great many strings attached to it. እርዳታው ፡ ብዙ ፡ ግዴታዎችን ፡ ያዘለ ፡ ነው

**pull strings** በወገን ፡ ተጠቀመ
He pulled strings to get his nephew a good post in the government. ያጐቱን ፡ ልጅ ፡ ጥሩ ፡ ሥራ ፡ ለማስያዝ ፡ በወገን ፡ ተጠቀመ
[See also 'apron']

**stringed** (adj.) ባለ ፡ ጭራ
The violin is a stringed instrument. ቫዮሊን ፡ ባለ ፡ ጭራ ፡ መጫወቻ ፡ ነው

**stringent**
1. በጣም ፡ ጥብቅ. The rules are stringent. ደንቦቹ ፡ በጣም ፡ ጥብቅ ፡ ናቸው
2. የሚያግድ. Stringent reasons prevent me from telling you why I resigned. ሥራዬን ፡ በፈቃዴ ፡ ለምን ፡ እንደለቀቅኩ ፡ እንዳልነግርህ ፡ የሚያግደኝ ፡ ምክንያት ፡ አለኝ

**strip** (stripped), vt.
1. ላጠ. They stripped the bark off the trees. ቅርፊቱን ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ላጡት
They stripped the wallpaper from the wall. የግድግዳ ፡ ወረቀቱን ፡ ከግድግዳው ፡ ላይ ፡ ላጡት
2. ለቀመ. The boys stripped the fruit from the trees. ልጆቹ ፡ ፍሬዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ከዛፎቹ ፡ ላይ ፡ ለቀሙ

**strip** (vi.) ልብሱን ፡ አወላለቀ
The boys stripped and went swimming. ወንዶቹ ፡ ልጆች ፡ ልብሳቸውን ፡ አወላልቀው ፡ ዋኙ

**strip (one) naked** ዕርቃኑን ፡ አስቀሩት
The bandits stripped him naked. ሽፍቶቹ ፡ ዕርቃኑን ፡ አስቀሩት

**strip of**
1. ገፈፈ. They stripped the captured bandits of their weapons. የተማረኩትን ፡ ሽፍቶች ፡ መሣሪያቸውን ፡ ገፈፏቸው
2. ጠራርጎ ፡ ወሰደ. The looters stripped the stores of their contents during the riot. በብጥብጡ ፡ ጊዜ ፡ ዘራፊዎቹ ፡ ሱቅ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ እቃዎች ፡ ጠራርገው ፡ ወሰዱ

*They stripped the house of all its furniture. ቤቱን ፡ ባዶውን ፡ አስቀሩት

**strip off** አወላለቀ
He stripped off his clothes and jumped in the river. ልብሱን ፡ አወላልቆ ፡ ወንዙ ፡ ውስጥ ፡ ዘሎ ፡ ገባ
[See also 'husk']

**strip** (n.)
1. ስንጥር. Baskets are made by interlacing bamboo strips. ቅርጫት ፡ የቀርቀሃ ፡ ስንጥሮችን ፡ በማቆላለፍ ፡ ይሠራል
2. ብጣሽ. Write your name on a strip of paper! ስምህን ፡ ባንድ ፡ ብጣሽ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ጻፍ

**strip of** ትንሽ
There is a strip of garden behind the house. ከቤቱ ፡ ጓሮ ፡ ትንሽ ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ አለ
[See also 'cut, husk']

**stripe**
1. መሥመር. The tie had red and white stripes. ክራቫቱ ፡ ቀይና ፡ ነጭ ፡ መሥመር ፡ አለበት
How many stripes are on a sergeant's sleeve? የኀምሳ ፡ አለቃ ፡ የማዕረግ ፡ ምልክት ፡ ላይ ፡ ስንት ፡ መሥመር ፡ አለ ?
2. ሰንበር. The whip left red stripes on his back. ጅራፉ ፡ ጀርባው ፡ ላይ ፡ ቀያይ ፡ ሰንበሮች ፡ ጣለበት
*They gave the thief ten stripes. ሌባውን ፡ ዐሥር ፡ ጅራፍ ፡ ገረፉት

**stripe along the hem** ጥለት
The dress has a red stripe along the hem. ቀሚሱ ፡ ቀይ ፡ ጥለት ፡ አለበት

**striped** መሥመር ፡ ያለው
She is wearing a striped dress. መሥመር ፡ ያለው ፡ ልብስ ፡ ለብሳለች

**strive** (strove)
1. ጥሮ ፡ ሠራ. They strove to finish on time. በሰዓቱ ፡ ለመጨረስ ፡ ጥረው ፡ ሠሩ
2. ታገለ. We strive against disease. በሽታን ፡ ለማጥፋት ፡ እንታገላለን

**strode**, see **stride**

**stroke** (v.)
1. ደባበሰ. He stroked her arm to comfort her. ለማጽናናት ፡ ክንዷን ፡ ደባበሳት
2. ዳሰሰ. She stroked the cat. ድመቷን ፡ ዳሰሰቻት

**stroke** (n.)
1. ድምፅ. I heard the stroke of a hammer. የመዶሻ ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ
2. ምት. He felled the tree with six strokes. በስድስት ፡ ምት ፡ ዛፉን ፡ ጣለ
He drove in the nail with one stroke of the hammer. ምስማሩን ፡ ባንድ ፡ በመዶሻ ፡ ምት ፡ አስገባው
3. የደም ፡ መርጋት ፡ በሽታ. A stroke left the governor paralyzed on one side of his body. የደም ፡ መርጋት ፡ በሽታ ፡ የእንደራሴውን ፡ ግማሽ ፡ ሰውነቱን ፡ ሰላላ ፡ አደረገው
*I haven't done a stroke of work on my book in three weeks. ባለፉት ፡ ሦስት ፡ ሳምንቶች ፡ ውስጥ ፡ የምጽፈውን ፡ መጽሐፍ ፡ መለስ ፡ ብዬም ፡ አላየሁት

**stroke of luck** እንደ ፡ ዕድል
It was a stroke of luck that we got this apartment. ይህንን ፡ አፓርተማ ፡ ያገኘነው ፡ እንደ ፡ ዕድል ፡ ነው

**at one stroke** ባንዳፍታ
At one stroke, everything was changed. ሁሉም ፡ ነገር ፡ ባንዳፍታ ፡ ተለዋወጠ

**at the stroke of** ልክ
He arrived at the stroke of four. ልክ ፡ በዐሥር ፡ ሰዓት ፡ ደረሰ

**with a few strokes** ጥቂት ፡ ነካ ፡ ነካ ፡ አድርጎ
The painter completed the picture with a few strokes. ሠዓሊው ፡ ጥቂት ፡ ነካ ፡ ነካ ፡ አድርጎ ፡ ሥዕሉን ፡ ጨረሰው
[See also 'lightning']

**stroll** (v.) በእግር ፡ ተንሸራሸረ
Let's stroll through the town! ከተማው ፡ ውስጥ ፡ በእግራችን ፡ እንሸራሸር

**stroll** (n.), **take a ~** ተንሸራሸረ
I'd like to take a stroll through the town. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ልንሸራሸር ፡ እፈልጋለሁ

**stroller** [ወንበር ፡ የሚመስል ፡ የሕፃናት ፡ ጋሪ]

**strong**
1. ጠንካራ. Is this ladder strong enough? ይህ ፡ መሰላል ፡ ጠንካራ ፡ ነው ?
2. ኀይለኛ. There is a strong smell of gas. ኀይለኛ ፡ የጋዝ ፡ ሽታ ፡ አለ
A strong wind was blowing. ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ይነፍስ ፡ ነበር
3. ወፍራም. The tea is too strong. ሻዩ ፡ በጣም ፡ ወፍራም ፡ ነው
4. ለማሸነፍ ፡ ዕድል ፡ ያለው. Is he a strong candidate? ለማሸነፍ ፡ ዕድል ፡ ያለው ፡ ተወዳዳሪ ፡ ነው ?
5. ዓይነተኛ. He presented strong arguments in his favor. እሱን ፡ በመደገፍ ፡ ዓይነተኛ ፡ ነገሮች ፡ አቀረበ

6. (= adv.) ፈጽሞ. He has a strong dislike for coffee. ፈጽሞ ፡ ቡና ፡ አይወድም
*An army 50,000 strong is defending the country. ኀምሳ ፡ ሺ ፡ ጦር ፡ አገሪቱን ፡ ይጠብቃል

**strong drink** መጠጥ
He is addicted to strong drink. የመጠጥ ፡ ሱስ ፡ አለበት

**feel strong** ብርታት ፡ ተሰማ(ው)
+He feels very strong again. አሁን ፡ እንደገና ፡ በጣም ፡ ብርታት ፡ ይሰማዋል

**go strong** ጠንካራ ፡ ነው
He is ninety years old and still going strong. ዘጠና ፡ ዓመት ፡ ቢሆነውም ፡ ገና ፡ ጠንካራ ፡ ነው

**have a strong constitution** ጤነኛ ፡ ሆነ
He has a strong constitution and does not mind the cold. ጤነኛ ፡ ስለሆነ ፡ ለብርድ ፡ ግድ ፡ የለውም
[See also 'drive, point']

**stronghold** ጠንካራ ፡ ምሽግ
The troops have a stronghold in enemy territory. ወታደሮቹ ፡ በጠላት ፡ ይዞታ ፡ ውስጥ ፡ ጠንካራ ፡ ምሽግ ፡ አላቸው

**strongly**
1. አጥብቆ. I strongly advise you to go. እንድትሄድ ፡ አጥብቄ ፡ እመክርሃለሁ
2. በኀይል. The wind was blowing strongly. ነፋሱ ፡ በኀይል ፡ ይነፍስ ፡ ነበር

**strong-minded** ቈራጥ
He is a strong-minded person, and it is difficult to make him change his mind. ቈራጥ ፡ ስለሆነ ፡ ሐሳቡን ፡ እንዲለውጥ ፡ ለማድረግ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**strong-willed** ኀይለኛ ፤ መንፈሰ ፡ ጠንካራ
She is a strong-willed woman; everyone in her family obeys her. ኀይለኛ ፡ ስለሆነች ፡ ቤተሰቧ ፡ ሁሉ ፡ ይታዘዟታል
A leader must be strong-willed. መሪ ፡ መንፈሰ ፡ ጠንካራ ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ አለበት

**strophe** የግጥም ፡ አንቀጽ
The poem is divided into strophes. ግጥሙ ፡ በግጥም ፡ አንቀጾች ፡ የተከፋፈለ ፡ ነው

**strove,** see **strive**

**struck,** see **strike**

**structure** (n.)
1. አካል. The skull is a bony structure. የራስ ፡ ቅል ፡ አጥንታም ፡ አካል ፡ ነው
2. አቋም. The students study the structure of the human body. ተማሪዎቹ ፡ የሰውን ፡ አካል ፡ አቋም ፡ ያጠናሉ
The structure of the organization is explained in its constitution. የድርጅቱ ፡ አቋም ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጿል
3. ሕንጻ. What is the large structure across the street? ከመንገዱ ፡ ባሻገር ፡ ያለው ፡ ትልቅ ፡ ሕንጻ ፡ ምንድነው ?
4. ቋሚ. The structure of the building is made of iron beams. የሕንጻው ፡ ቋሚ ፡ ከብረት ፡ የተሠራ ፡ ነው

**struggle** (v.)
1. ታገለ. I have been struggling with this problem for some time. ይህን ፡ ፕሮብሌም ፡ ለመሥራት ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስታገል ፡ ነበር
She struggled to keep back her tears. እንባዋን ፡ ለማገድ ፡ ታገለች
2. ተፍጨረጨረ. The thief struggled to get loose. ሌባው ፡ ለማምለጥ ፡ ተፍጨረጨረ

**struggle** (n.) ትግል
The struggle for freedom must continue. የነጻነት ፡ ትግል ፡ መቀጠል ፡ አለበት

**strung,** see **string**

**strut** (strutted), ~ **around** ተወጣጠረ ፤ ተንጐራደደ
He strutted around to show off his new clothes. አዲሱን ፡ ልብሱን ፡ ለማሳየት ፡ሲወጣጠር ፡ ነበር
The little boy put on his father's medals and strutted around the room. ትንሹ ፡ ልጅ ፡ ያባቱን ፡ ሜዳይ ፡ አድርጎ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተንጐራደደ

**stub** (stubbed), v. ዕንቅፋት ፡ መታው
+He stubbed his toe. አውራ ፡ ጣቱን ፡ ዕንቅፋት ፡ መታው

**stub out** አጠፋ
He stubbed out his cigarette. ሲጋራውን ፡ አጠፋው

**stub** (n.)
1. ጉርድ ፤ ጉራጅ. Give me your ticket stub! የቲኬትህን ፡ ጉርድ ፡ (ጉራጅ) ፡ ስጠኝ
2. ቁራጭ. The stub of a pencil is hard to write with. በእርሳስ ፡ ቁራጭ ፡ መጻፍ ፡ ያስቸግራል

**stubble** ብር
After the wheat is reaped, only stubble is left in the field. ስንዴ ፡ ከታጨደ ፡ በኋላ ፡ እርሻው ፡ ላይ ፡ የሚቀረው ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ ነው

*The stubble of the beard makes one's face itch. ጢም ፡ ሲበቅል ፡ ፊት ፡ ያሳክካል

**stubborn**
1. ሐሳበ ፡ ግትር. He's terribly stubborn and does not change his mind. በጣም ፡ ሐሳበ ፡ ግትር ፡ ስለሆነ ፡ ሐሳቡን ፡ አይለውጥም
2. መንቻካ ፤ ጋግርታም. The stubborn child refused to wear the coat. መንቻካው ፡ (ጋግርታሙ) ፡ ልጅ ፡ ኮቱን ፡ አልለብስም ፡ አለ
3. እልኸኛ. The mother tried to bring her stubborn daughter to reason. እናቲቱ ፡ እልኸኛ ፡ ልጇን ፡ ለማባበል ፡ ሞከረች
4. ከባድ. The settlers made a stubborn effort to clear the forest. ሰፋሪዎቹ ፡ ጫካውን ፡ ለመመንጠር ፡ ከባድ ፡ ጥረት ፡ አደረጉ

**stubborness** እልኸኝነት ፤ እልህ
His stubborness discourages his parents. የሱ ፡ እልኸኝነት ፡ (እልህ) ፡ ወላጆቹን ፡ ያበሳጫቸዋል

**stubbornly** አጥብቆ
Every inch of ground was stubbornly defended. ለስንዝር ፡ መሬት ፡ እንኳን ፡ አጥብቀው ፡ ተከላከሉ

**stucco** አሸዋ ፡ ግርፍ
They live in a stucco house. አሸዋ ፡ ግርፍ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ

**stuck,** see **stick**
**be stuck** ተደነቀረ
The wagon is stuck in the mud. ጋሪው ፡ ማጥ ፡ ውስጥ ፡ ተደንቅሯል

**stuck-up** ትዕቢተኛ
She has no friends because she is so stuck-up. በጣም ፡ ትዕቢተኛ ፡ ስለሆነች ፡ ጓደኛ ፡ የላትም

**stud** (studded), vt. (= vi.) አልፎ ፡ አልፎ ፡ ተገኘ
Little islands studded the harbor. በወደቡ ፡ አካባቢ ፡ ትናንሽ ፡ ደሴቶች ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይገኛሉ
**be studded**
*The shield was studded with silver decorations. ጋሻው ፡ በብር ፡ ተሽላልሟል

**stud** (n.)
*The belt was ornamented with silver studs. ቀበቶው ፡ በብር ፡ የተለበጠ ፡ ነበር

**student** ተማሪ
The students play in the field. ተማሪዎቹ ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ ይጫወታሉ

**studied,** adj. (= adv.) ዐውቆ
He has a studied air of indifference. ዐውቆ ፡ ግድ ፡ የለሽ ፡ ይመስላል

**studio** የመሣያ ፡ ክፍል
The artist rented a studio. ሠዓሊው ፡ አንድ ፡ የመሣያ ፡ ክፍል ፡ ተከራየ

**studious**
1. ጥናት ፡ የሚወድ. He is very studious, and is almost always in the library. ጥናት ፡ በጣም ፡ ስለሚወድ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ውስጥ ፡ ይውላል
2. (= adv.) ከልብ. The clerk makes a studious effort to please customers. አሻሻጩ ፡ ደንበኞች ፡ ለማስደሰት ፡ ከልብ ፡ ይጥራል

**study** (studied), v.
1. ተማረ. He is studying Chinese. ቻይንኛ ፡ ይማራል
2. ተመለከተ. We studied the map before we started. መንገድ ፡ ከመጀመራችን ፡ በፊት ፡ ካርታውን ፡ ተመለከትን
3. መረመረ. He promised to study our problem. ችግራችንን ፡ ለመመርመር ፡ ቃል ፡ ገባ
4. አጠና. The prisoner studied ways to escape. እስረኛው ፡ የሚያመልጥበትን ፡ ዘዴ ፡ አጠና

**study** (studies), n.
1. ትምህርት. Has he finished his studies? ትምህርቱን ፡ ጨርሷል ?
2. ጽሑፍ. He has published several studies in that field. ስለዚያ ፡ ትምህርት ፡ አያሌ ፡ ጽሑፎች ፡ አቅርቧል
3. ንድፍ. The artist made several studies of his subject before he began the portrait. ሠዓሊው ፡ የሰውዬውን ፡ ሥዕል ፡ መሣል ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ንድፍ ፡ አወጣ
4. ጥናት. The city prepared a study on low-cost housing. ከተማዋ ፡ ባነስተኛ ፡ ገንዘብ ፡ ስለሚከራዩ ፡ ቤቶች ፡ ጥናት ፡ አዘጋጀች
5. የጥናት ፡ ክፍል. You will find the professor in his study. መምህሩን ፡ በጥናት ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ታገኘዋለህ
**course of study** ትምህርት
He is taking a course of study in military science. አንድ ፡ የወታደራዊ ፡ ትምህርት ፡ በመማር ፡ ላይ ፡ ነው
**study** (adj.) ያጠናን
He needs better study habits. የተሻለ ፡ ያጠናን ፡ ዘዴ ፡ ያስፈልገዋል

**stuff** (v.)
1. ወተፈ. Stuff cotton in your ears! ጆሮህን ፡ በጥጥ ፡ ወትፈው
2. አጨቀ. He stuffed so many old clothes into the bag, it almost burst. ብዙ ፡ አሮጌ ፡ ልብሶች ፡

ስላጨቀበት ፡ ሽንጣው ፡ ሲፈነዳ ፡ ምንም ፡ አል ቀረው
3. ቅመማ ፡ ቅመም ፡ ሆዱ ፡ ውስጥ ፡ ጨመረ. Stuff the chicken before you cook it! ዶሮዋን ፡ ከመ ጥበስህ ፡ በፊት ፡ ቅመማ ፡ ቅመም ፡ ሆዷ ፡ ውስጥ ፡ ጨምር
4. ጐሰጐሰ(ተጐሰጐሰ). The pillow is stuffed with feathers. ትራሱ ፡ ላባ ፡ የተጐሰጐሰበት ፡ ነው

**stuff animals** የእንስሳት ፡ ጐፍላ ፡ አዘጋጀ
He stuffs animals for the museum. ለቤተ ፡ መ ዘክሩ ፡ የእንስሳት ፡ ጐፍላ ፡ ያዘጋጃል

**stuff (one's) mouth with** ጐሰጐሰ
He stuffed his mouth with food. ምግብ ፡ ጐሰ ጐሰ

**stuff oneself** ብዙ ፡ በላ
Don't stuff yourself! ብዙ ፡ አትብላ
*He stuffed himself with food: ሆዱን ፡ ጥርቅ ም ፡ አድርጐ ፡ ሞላ

**be stuffed up** ተደፈነ
My nose is stuffed up. አፍንጫዬ ፡ ተደፍኗል

**feel stuffed** ወጠረ(ው)
After that heavy meal, I feel stuffed. ያንን ፡ ከባ ድ ፡ ምግብ ፡ በልቼ ፡ በጣም ፡ ወጥሮኛል

**stuff** (n.)
1. ጨርቅ. She bought some white stuff for curtains. ለመጋረጃ ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ ነጭ ፡ ጨርቅ ፡ ገዛች
2. እቃ. I hired three packhorses to carry my stuff. እቃዬን ፡ የምጭንባቸው ፡ ሦስት ፡ አጋሰሶ ች ፡ ተከራይቻለሁ
3. ትርኪምርኪ. Their cellar is full of stuff. ምድር ፡ ቤታቸው ፡ በትርኪምርኪ ፡ ተሞልቷል
4. ትምህርት. He really knows his stuff. ትምህርቱን ፡ በደንብ ፡ ያውቃል
5. የተፈጥሮ ፡ ስጦታ. He has the stuff of a singer in him. ዘፋኝ ፡ ለመሆን ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታ ፡ አለው
*They call this stuff beer? ይህ ፡ በነሱ ፡ ቤት ፡ ቢራ ፡ መሆኑ ፡ ነው ?

**old stuff** ቅራቅምቦ
Throw that old stuff away! ያንን ፡ ቅራቅምቦ ፡ ወዲያ ፡ ጣል

**stuffing** የተሞላበት ፡ ቅመማ ፡ ቅመም
The stuffing of the chicken is very good. ዶሮዋ ፡ የተሞላችበት ፡ ቅመማ ፡ ቅመም ፡ በጣ ም ፡ ጥሩ ፡ ነው
*The stuffing of the pillow is made of cotton. ትራሱ ፡ ውስጡ ፡ ጥጥ ፡ ነው

**stuffy**
1. ኩራተኛ. He is a rather stuffy person. ኩራተኛ ፡ ቢጤ ፡ ነው
2. ችክ ፡ ያለ. Their stuffy conversation bored us extremely. ችክ ፡ ያለው ፡ ወሬያቸው ፡ ከመ ጠን ፡ በላይ ፡ አሰለቸን
3. የታፈነ. It's a relief to get out of this stuffy hall. ከዚህ ፡ ከታፈነ ፡ አዳራሽ ፡ መውጣት ፡ ግ ልግል ፡ ነው

**be stuffy** ታፈነ
This room is stuffy; open a window and let fresh air in! ይህ ፡ ክፍል ፡ ታፍኗል ፤ መስኮቱ ን ፡ ከፈተውና ፡ ይንፈስበት

**make (one's) head feel stuffy** ራሱን ፡ ከበደ(ው)
+A cold makes my head feel stuffy. በጉንፋን ፡ ምክንያት ፡ ራሴን ፡ ከብዶኛል

**stultify** (stultified) በከንቱ ፡ አስቀረ
The drought stultified the farmer's labor. ድርቀቱ ፡ የገበሬውን ፡ ድካም ፡ በከንቱ ፡ አስቀረው

**stumble**
1. ተደናቀፈ. The drunkard stumbled and fell. ሰካራሙ ፡ ተደናቅፎ ፡ ወደቀ
2. ተንተባተበ. He forgot his speech and began to stumble. ንግግሩ ፡ ስለተረሳው ፡ መንተባተ ብ ፡ ጀመረ

**stumble along** ደፋ ፡ ቀና ፡ አለ
The tired old man stumbled along. የደከመው ፡ ሽማግሌ ፡ ደፋ ፡ ቀና ፡ አለ

**stumble off** ተንገዳገደ
The tired boy stumbled off to bed. የደከመው ፡ ልጅ ፡ እየተንገዳገደ ፡ ወደ ፡ አልጋው ፡ ሄደ

**stumble (on)** እንዳጋጣሚ ፡ አገኘ
He stumbled on a new way of making rubber. እንዳጋጣሚ ፡ ላስቲክ ፡ የሚሠራበት ፡ አዲስ ፡ ዘዴ ፡ አገኘ

**stumble (over)** አደናቀፈ
+I stumbled over a log. ግንድ ፡ አደናቀፈኝ

**stumble over (one's) words** አልፎ ፡ አልፎ ፡ ተንተባተበ
He stumbled over his words while reading the speech. ንግግሩን ፡ ሲያነብ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይንተባተብ ፡ ነበር

**stumbling block** ዕንቅፋት
The lack of money proved to be a stumbling block. የገንዘብ ፡ እጦት ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆኗል

**stump** (v.) ግራ ፡ አጋባ
Her questions stumped the expert. ጥያቄዋ ፡ ሊ ቁን ፡ ግራ ፡ አጋባው

*He is stumping the countryside for votes. ብዙ ፡ ሰው ፡ እንዲመርጠው ፡ በየባላገሩ ፡ እየዞረ ፡ ንግግር ፡ ያደርጋል

**stump (into)** ተንደርድሮ ፡ ገባ
He stumped into the house. እቤት ፡ ውስጥ ፡ ተንደርድሮ ፡ ገባ

**be stumped by** (= tr.) ቀጥ ፡ አድርጎ ፡ ያዘው
All the students were stumped by the second question. ሁለተኛው ፡ ጥያቄ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ቀጥ ፡ አድርጎ ፡ ያዛቸው

**stump** (n.)
1. ጉቶ. He sat on a stump. ጉቶ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ አለ
2. (= adj.) የተቈረጠ. The stump of his arm is not yet healed. የተቈረጠው ፡ ክንዱ ፡ ገና ፡ አልዳነም
3. (= adj.) ቈራጣ. The dog wagged the stump of its tail. ውሻው ፡ ቈራጣ ፡ ጭራውን ፡ ቈላ

**stumpy** ኩሩሩ
He is stumpy and cannot be seen from afar. ኩሩሩ ፡ ስለሆነ ፡ ከሩቅ ፡ አይታይም

**stun** (stunned)
1. ሰማይ ፡ ምድሩን ፡ አዞረ(በት). The blow stunned him. ዱላው ፡ ሰማይ ፡ ምድሩን ፡ አዞረበት
2. አስደነገጠ. The bad news stunned everyone. መጥፎው ፡ ዜና ፡ ሁሉንም ፡ አስደነገጠ

**be stunned** ክው ፡ አለ
He was stunned by the news of his father's death. ያባቱን ፡ መሞት ፡ ሲሰማ ፡ ክው ፡ አለ

**stung**, see **sting**

**stunk**, see **stink**

**stunning**
1. የሚያምር. What a stunning hat he wears! እንዴት ፡ ያለ ፡ የሚያምር ፡ ባርኔጣ ፡ አድርጓል!
2. ሰማይ ፡ ምድር ፡ የሚያዞር. The robber came up behind him and dealt him a stunning blow. ሽፍታው ፡ ከኋላው ፡ ደርሶ ፡ ሰማይ ፡ ምድር ፡ የሚያዞር ፡ ምት ፡ መታው

**stunt** (v.) አቀጨጨ
Poor soil stunted the plants. ጭንጫው ፡ መሬት ፡ ዕፀዋቱን ፡ አቀጨጫቸው

**stunt** (n.) አስደናቂ ፡ ትርእይት
The members of the circus did all sorts of stunts. የሰርከሱ ፡ አባሎች ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ አስደናቂ ፡ ትርእይት ፡ አሳዩ

**stunted** (adj.) የቀጨጨ
Stunted trees covered the hillside. የቀጨጩ ፡ ዛፎች ፡ ኮረብታውን ፡ ሸፍነውታል

**(be) stupefied**
1. ሰውነቱ ፡ ደነዘዘ. He was stupefied by drink. ሰውነቱ ፡ በመጠጥ ፡ ደንዝዟል
2. ቅዠት ፡ መሰለ(ው). He was stupefied to learn that he had the winning ticket. አሸናፊ ፡ ቲኬት ፡ የሱ ፡ መሆኑን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ቅዠት ፡ መሰለው
3. ክው ፡ ብሎ ፡ ቀረ. They were stupefied by the calamity. ባደጋው ፡ ምክንያት ፡ ክው ፡ ብለው ፡ ቀሩ

**stupefy** (stupefied)
1. አስደነበረ. The sudden attack stupefied the soldiers. ድንገተኛው ፡ ወረራ ፡ ወታደሮቹን ፡ አስደነበራቸው
2. አደነዘዘ. The heat and the noise stupefied us. ሙቀቱና ፡ ጩኸቱ ፡ አደነዘዘን

**stupendous** የሚያስደንቅ
That was a stupendous discovery. ያገኘው ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነበር

**stupid**
1. ደደብ. He is stupid and doesn't listen to what you tell him. ደደብ ፡ ስለሆነ ፡ የነገሩትን ፡ አይሰማም
2. የማይረባ. A stupid conversation about economics made me laugh. ስለ ፡ ምጣኔ ፡ ሀብት ፡ የተደረገው ፡ የማይረባ ፡ ንግግር ፡ አሣቀኝ

**stupidity** ጅልነት ፤ ደደብነት
It is plain stupidity to try to cross the desert without water. ውኃ ፡ ሳይዙ ፡ በረሃን ፡ ለማቋረጥ ፡ መሞከር ፡ ፍጹም ፡ ጅልነት ፡ ነው
Your stupidity is such as to fill me with despair. ደደብነትህ ፡ በጣም ፡ ተስፋ ፡ የሚያስቈርጠኝ ፡ ነው
*He was refused promotion because of his stupidity. ደደብ ፡ ስለሆነ ፡ የደረጃ ፡ እድገት ፡ ተከለከለ

**stupor, be in a ~**
1. ፈዘዘ. I had so little sleep that I was in a stupor all day long. ብዙ ፡ ስላልተኛሁ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ፈዝዤ ፡ ዋልኩ
2. ደነዘዘ. He was in a drunken stupor. በስካር ፡ ደንዝዟል

**sturdy**
1. ጠንካራ. That's a sturdy table. ጠረጴዛው ፡ ጠንካራ ፡ ነው
2. ጐበዝና ፡ ጤነኛ. His children are sturdy because they work hard. ጠንክረው ፡ ስለሚሠሩ ፡ ልጆቹ ፡ ጐበዞችና ፡ ጤነኞች ፡ ናቸው
3. የቈራጥነት. Their sturdy resistance blocked the enemy's advance. በቈራጥነት ፡ መከላከላቸው ፡ ጠላትን ፡ ወደፊት ፡ ከመግፋት ፡ አገደው

**stutter** (v.) ተንተባተበ
He stuttered when he tried to speak to the Emperor. ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መናገር ፡ ሲጀምር ፡ ተንተባተበ

**stutter** (n.) መንተባተብ
His stutter has gotten worse as he has gotten older. እያደገ ፡ ሲሄድ ፡ መንተባተቡ ፡ እየባሰበት ፡ ሄደ

**stuttering** መንተባተብ
Stuttering is a speech impediment. መንተባተብ ፡ ለንግግር ፡ ዕንቅፋት ፡ ነው

**style**
1. ዘዴ. What do you know about the Arab style of architecture? ስለ ፡ ዐረቦች ፡ የሕንጻ ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ ምን ፡ የምታውቀው ፡ ነገር ፡ አለ ?
He has a poor style of writing. ያጻጻፍ ፡ ዘዴው ፡ መጥፎ ፡ ነው
2. ሞድ. This dress is the latest style. ይህ ፡ ልብስ ፡ አዲስ ፡ ሞድ ፡ ነው
We sell clothes made in all sizes and styles. በየልኩና ፡ በየሞዱ ፡ የተሰፉ ፡ ልብሶች ፡ እንሸጣለን
**live in style** ተንደላቀቀ
He lives in style on his uncle's money. ባጐቱ ፡ ገንዘብ ፡ ይንደላቀቃል

**stylish** ቄንጠኛ
Her clothing is very stylish. ልብሷ ፡ በጣም ፡ ቄንጠኛ ፡ ነው

**suave** ለስላሳ ፡ ያለ
He spoke in a suave manner. ለስላሳ ፡ ባለ ፡ ሁኔታ ፡ ተናገረ

**suavity** የመንፈስ ፡ እርጋታ
His suavity was unruffled by the angry man's insult. የተናደደው ፡ ሰው ፡ ስድብ ፡ የመንፈሱን ፡ እርጋታ ፡ ሊያሳጣው ፡ አልቻለም

**subcommittee** ንኡስ ፡ ደርግ
The subcommittee meets tomorrow. ንኡስ ፡ ደርጉ ፡ ነገ ፡ ይሰበሰባል

**subconscious** ውስጠ ፡ ኅሊና
In his subconscious, he was afraid. በውስጠ ፡ ኅሊናው ፡ ፈርቶ ፡ ነበር

**subdivide** ከፋፈለ
The buyer subdivided the farm. መሬቱን ፡ የገዛው ፡ ሰው ፡ የርሻውን ፡ ቦታ ፡ ከፋፈለው

**subdue** አሸነፈ
They subdued the rebels after much fighting. ከብዙ ፡ ውጊያ ፡ በኋላ ፡ ዐመፀኞቹን ፡ አሸነፏቸው

**subdued** (adj.)
1. ደብዛዛ. The window curtains gave the rooms a subdued light. የመስኮቱ ፡ መጋረጃዎች ፡ ለክፍሉ ፡ ደብዛዛ ፡ ብርሃን ፡ ሰጡት
2. ትሕትና ፡ የተመላበት. He spoke in a subdued voice. ትሕትና ፡ በተመላበት ፡ አንደበት ፡ ተናገረ

**subheading** አርእስት
The first chapter has three subheadings. የመጀመሪያው ፡ ምዕራፍ ፡ በሦስት ፡ አርእስት ፡ ተከፋፍሏል

**subhuman**
1. ከሰብአዊ ፡ ተግባር ፡ ውጭ ፡ የሆነ. The dictator acted in a subhuman way. አምባገነኑ ፡ ከሰብአዊ ፡ ተግባር ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ አድራጎት ፡ ፈጸመ
2. ከሰው ፡ ዝቅ ፡ ያለ. A subhuman species once inhabited Kenya. በዱሮ ፡ ጊዜ ፡ ከሰው ፡ ዝቅ ፡ ያሉ ፡ እንስሳት ፡ ኬንያ ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ

**subject** (v.)
1. አስገበረ. Ancient Rome subjected most of Europe. ጥንታዊት ፡ ሮም ፡ አብዛኛውን ፡ የአውሮፓን ፡ ክፍል ፡ ስታስገብር ፡ ኖራለች
2. ሰጠ ፤ አሳልፎ ፡ ሰጠ. His weakness subjected him to diseases. ደካማነቱ ፡ ለበሽታ ፡ ሰጠው ፡ (አሳልፎ ፡ ሰጠው)
**subject to,** expressed by the አስ-stem
The enemy subjected their captives to torture. ጠላት ፡ ምርኮኞችን ፡ አሠቃየው
**be subjected to** እንድ + imperfect + ተደረገ
The suspect was subjected to thorough questioning. የተጠረጠረው ፡ ሰው ፡ በጥብቅ ፡ እንዲመረመር ፡ ተደረገ

**subject** (n.)
1. ነገር. Let's change the subject! I'm tired of talking about murder. ስለ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እናውራ ፤ ስለ ፡ ነፍስ ፡ ግዳይ ፡ ማውራት ፡ ሰልችቶኛል
2. ትምህርት. I am not familiar with that subject, not having studied psychology. የሥነ ፡ ልቡና ፡ ትምህርት ፡ ስላልተማርኩ ፡ ስለ ፡ ትምህርቱ ፡ ምንም ፡ አላውቅም
3. የትምህርት ፡ ዓይነት. The classes are arranged according to subject. ክፍሎች ፡ የተደለደሉት ፡ በትምህርት ፡ ዓይነት ፡ መሠረት ፡ ነው
4. አርእስት. The martyrdom of St. John the Baptist is the subject of a new play. የመጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ሰማዕትነት ፡ ያዲሱ ፡ ቴያትር ፡ አርእስት ፡ ነው
His hesitant speech shows that he has not studied the subject. እያመነታ ፡ የሚያደርገው ፡

ንግግሩ ፡ አርእስቱን ፡ በደንብ ፡ አለመረዳቱን ፡ ያሳያል
5. ሥሬ ፡ ነገር. I'll get back to the subject in a minute. ከትንሽ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሥሬ ፡ ነገሩ ፡ እመለሳለሁ
6. ዜጋ. He is a British subject. የእንግሊዝ ፡ ዜጋ ፡ ነው
7. ተገዥ. The people are the subjects of the king. ሕዝቡ ፡ የንጉሡ ፡ ተገዥ ፡ ነው
8. ባለቤት. The subject of the sentence is at the beginning. የዐረፍተ ፡ ነገሩ ፡ ባለቤት ፡ መጀመሪያው ፡ ላይ ፡ ነው
**subject** (adj.) ተገዥ
The subject tribes pay a tribute to the king. ተገዢዎቹ ፡ ጐሳዎች ፡ ለንጉሡ ፡ ግብር ፡ ይከፍላሉ
**be subject (to)**
1. ተገዛ. We are all subject to the law of the land. ሁላችንም ፡ በሀገሩ ፡ ሕግ ፡ እንገዛለን
2. ሊጠቃ ፡ ቻለ. The alimentary tract is subject to diseases. የሆድ ፡ የምግብ ፡ መተላለፊያ ፡ በበሽታ ፡ ሊጠቃ ፡ ይችላል
3. (= tr.) አጠቃ. +I am subject to colds. ጉንፋን ፡ ያጠቃኛል
4. ተመሠረተ. His consent is subject to your approval. እሺታው ፡ ባንተ ፡ ድጋፍ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው
*He is subject to fits of anger. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ግልፍ ፡ ይለዋል

**subjection**
1. ከቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ማድረግ. The subjection of the rebels took years. ዐመፀኞቹን ፡ ከቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ማድረግ ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ፈጀ
2. ተገዥነት. Many African countries lived in a state of subjection for many years. ብዙ ፡ የአፍሪካ ፡ አገሮች ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ በተገዥነት ፡ኖረው ፡ ነበር
**live in subjection to** ተገዢ ፡ ነበር
Women used to live in subjection to men. ሴቶች ፡ የወንዶች ፡ ተገዢዎች ፡ ነበሩ

**subjective**
*He is very subjective in his opinions. የሚያቀርበው ፡ ሐሳብ ፡ ሁሉ ፡ በግል ፡ስሜት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው

**subject matter** አርእስት
The book was conveniently arranged according to subject matter. መጽሐፉ ፡ በሚያመች ፡ ሁኔታ ፡ በየአርእስቱ ፡ ተዘጋጅቷል
*The subject matter of this book is colonialism. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የሚናገረው ፡ ስለ ፡ ቅኝ ፡ አገዛዝ ፡ ነው

**subjugate** አስገበረ
They subjugated the neighboring people. ባካባቢያቸው ፡ ያሉትን ፡ ሕዝቦች ፡ አስገበሩ

**sublet** ለሌላ ፡ አከራየ
Sublet your apartment while you're away. እስክትመለስ ፡ አፓርተማህን ፡ ለሌላ ፡ አከራየው

**sublime** ልብ ፡ የሚማርክ
The scenery was sublime. ትርእይቱ ፡ ልብ ፡ የሚማርክ ፡ ነበር

**submarine** (n.) ሰርጓጅ ፡ መርከብ
The submarine sank. ሰርጓጁ ፡ መርከብ ፡ ሰመጠች
**submarine** (adj.)
1. የባሕር ፡ ውስጥ. A French scientist is studying submarine life in the Red Sea. የፈረንሳይ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቅ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ የባሕር ፡ ውስጥ ፡ ሕይወትን ፡ በማጥናት ፡ ላይ ፡ ነው
2. በውቅያኖስ ፡ ውስጥ ፡ የተዘረጋ. A submarine cable connects Ethiopia with Europe. በውቅያኖስ ፡ ውስጥ ፡ የተዘረጋው ፡ ስልክ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከአውሮፓ ፡ ጋር ፡ ያገናኛታል

**submerge** (vt.) አሰበሰ
The rising water submerged the town. የውኃው ፡ መሙላት ፡ ከተማውን ፡ አሰበሰው
**submerge** (vi.) ጠለቀ
The crocodiles submerged beneath the water. አዞዎቹ ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ጠለቁ

**submission**
*The submission of the enemy was witnessed by a large crowd. ጠላት ፡ እጁን ፡ ሲሰጥ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተመለከተ
*He bowed in submission to the boss's order. ያለቃውን ፡ ትእዛዝ ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ተቀበለ
*Submission of applications must be completed before the 15th. ማመልከቻዎች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ወር ፡ አጋማሽ ፡ ቀርበው ፡ ማለቅ ፡ አለባቸው
**reduce to submission** እጁን ፡ እንዲሰጥ ፡ አደረገ
The army reduced the enemy to submission. የጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ ጠላት ፡ እጁን ፡ እንዲሰጥ ፡ አደረገ

**submissive**
1. ትሑት. The submissive child obeyed without question. ትሑቱ ፡ ልጅ ፡ ያለ ፡ ጥያቄ ፡ ታዘዘ
2. እሺ ፡ ባይ. She is very submissive. በጣም ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ ነች

**submit** (submitted), vt. አቀረበ
I'll submit my report on Monday. ሪፖሬን ፡ ሰኞ ፡ ለት ፡ አቀርባለሁ

**submit** (vi.)
1. ገባ. The rebels offered to submit if they were granted amnesty. ዐመፀኞቹ ፡ ምሕረት ፡ ከተደረገላቸው ፡ ለመግባት ፡ ጠይቀዋል
2. ተገዛ. We'll never submit to foreign rule. ለባዕድ ፡ ፈጽሞ ፡ አንገዛም

**submit (to)**
1. ፈጸመ. Make it clear to him that we will not submit to his demands. የሚጠይቀውን ፡ የማንፈጽም ፡ መሆናችንን ፡ ግለጽለት
2. አከበረ. The team submitted to the umpire's decision. ቡድኑ ፡ ያጫዋቹን ፡ ውሳኔ ፡ አከበረ

**submit oneself (to)** አከበረ
He submits himself to the authority of the state. የግዛቱን ፡ ሕግ ፡ ያከብራል

**subnormal** ዝቅ ፡ ያለ
The child's intelligence is subnormal, and he will need special teaching. የልጁ ፡ የአእምሮ ፡ ችሎታ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ ልዩ ፡ ትምህርት ፡ ያስፈልገዋል

**subordinate** (v.)
*A son subordinates his wishes to his father's will. ልጁ ፡ የግል ፡ ፍላጎቱን ፡ ላባቱ ፡ ሲል ፡ ይተዋል

**subordinate** (n.) የበታች
He expects loyalty from his subordinates. ከበታቾቹ ፡ ታዛዥነትን ፡ ይጠብቃል

**subordinate** (adj.) የበታች
He is still in a subordinate position. ገና ፡ የበታች ፡ ሠራተኛ ፡ ነው

**subparagraph** ንኡስ ፡ አንቀጽ
The matter is dealt with in subparagraph three. ጉዳዩ ፡ በሦስተኛው ፡ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ ተጠቅሷል

**subpoena** መጥሪያ
They issued a subpoena for the suspect to appear in court. የተጠረጠረው ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርብ ፡ መጥሪያ ፡ ጻፉለት

**subscribe** (vt.) ሊሰጥ ፡ ቃል ፡ ገባ
He subscribed much money to flood relief. በጐርፉ ፡ አደጋ ፡ ለተጐዱት ፡ እርዳታ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሊሰጥ ፡ ቃል ፡ ገብቷል ፡

**subscribe (to)**
1. በማኅበርተኝነት ፡ ገዛ. I subscribe to several periodicals. በርከት ፡ ያሉ ፡ መጽሔቶች ፡ በማኅበርተኝነት ፡ እገዛለሁ
2. ተቀበለ. I cannot subscribe to those ideas. እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ አስተያየቶች ፡ አልቀበልም
3. ፈረመ. Thousands of citizens subscribed to the petition. በሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ያቤቱታ ፡ ደብዳቤውን ፡ ፈረሙበት

**subscriber** የጋዜጣ ፡ ማኅበርተኛ
The subscribers have to pay $10 a year for the newspaper. የጋዜጣው ፡ ማኅበርተኞች ፡ በዓመት ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ መክፈል ፡ አለባቸው

**subscription**
1. የማኅበርተኝነት ፡ ጊዜ. Your subscription has expired. የማኅበርተኝነትህ ፡ ጊዜ ፡ አልቋል
2. ያዋጣው ፡ ገንዘብ. The monument was erected by public subscription. ሐውልቱ ፡ የተተከለው ፡ ሕዝብ ፡ ባዋጣው ፡ ገንዘብ ፡ ነው
*How much is a yearly subscription to the newspaper? ባመት ፡ ለጋዜጣው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ትከፍላለህ?

**subsequent** ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ የመጣ ፤ በኋላ ፡ የደረሰ
Subsequent events led him to reconsider his position. ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ የመጡት ፡ ጉዳዮች ፡ ሐሳቡን ፡ እንደገና ፡ እንዲመረምር ፡ አደረጉት
The plan seemed good, but subsequent events proved that it was not. እቅዱ ፡ ጥሩ ፡ ይመስል ፡ ነበር ፡ ግን ፡ በኋላ ፡ የደረሱት ፡ ነገሮች ፡ ጥሩ ፡ አለመሆኑን ፡ አመለከቱ

**subsequently** የኋላ ፡ ኋላ
She subsequently found out that he was already married. የኋላ ፡ ኋላ ፡ ሚስት ፡ ማግባቱን ፡ ዐወቀች

**subservient**
1. ተለማማጭ. Shopkeepers used to be subservient. ነጋዴዎች ፡ ድሮ ፡ ተለማማጮች ፡ ነበሩ
2. ተገዢ. He is subservient to his wife. ለሚስቱ ፡ ተገዢ ፡ ነው

**subside**
1. ጐደለ. The waters of the river have subsided, and you can now cross it. ወንዙ ፡ ስለጐደለ ፡ አሁን ፡ ልትሻገር ፡ ትችላለህ
2. ጸጥ ፡ አለ. The waves subsided when the wind stopped. ነፋሱ ፡ ሲቆም ፡ ሞገዱ ፡ ጸጥ ፡ አለ
3. ጋብ ፡ አለ. The storm has subsided. ኀይለኛው ፡ ዝናብ ፡ ጋብ ፡ ብሏል
4. በረድ ፡ አለ(ለት). His anger subsided. ቁጣው ፡ በረድ ፡ አለለት
5. ቀነስ ፡ አለ(ለት). Tom's fever subsided. ቶም ፡ ትኩሳቱ ፡ ቀነስ ፡ አለለት

**subsidiary** (n.) ቅርንጫፍ
This company is a subsidiary of a foreign company. ይህ ፡ ኩባንያ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ኩባንያ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ነው

**subsidiary** (adj.) የረዳትነት
He has a subsidiary role in the project. በፕሮጀ ው ፡ የረዳትነት ፡ ቦታ ፡ አለው

**subsidize** የገንዘብ ፡ እርዳታ ፡ አደረገ(ለት)
The government does not subsidize students studying abroad. ውጭ ፡ አገር ፡ ለሚማሩት ፡ ተማ ሪዎች ፡ መንግሥት ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታ ፡ አያደርግ ላቸውም

**subsidy** (subsidies) የገንዘብ ፡ እርዳታ
He receives a subsidy from the government. ከመንግሥት ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታ ፡ ያገኛል

**subsist**
1. በሕይወት ፡ ቆየ. He subsisted on a diet of beans. ባቄላ ፡ እየበላ ፡ በሕይወት ፡ ቆየ
2. ተገኘ. Ancient customs still subsist. የጥንት ፡ ልማዶች ፡ አሁንም ፡ ይገኛሉ
3. ተካሄደ. A club cannot subsist without contributions. አንድ ፡ ክበብ ፡ ከባሎች ፡ የገንዘብ ፡ መ ዋጮ ፡ ካላገኘ ፡ ሊካሄድ ፡ አይችልም

**subsistence** (n.) ኑሮ ፤ መኖሪያ
Eskimos used to depend on hunting for their subsistence. ኤስኪሞዎች ፡ ለኑሮዋቸው ፡ በአደን ፡ ይጠቀሙ ፡ ነበር
The crops in that region are adequate for marginal subsistence. በዚያ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ያለው ፡ እህል ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ ለመኖሪያ ፡ ያህል ፡ ይበቃል
*Fishermen obtain subsistence from the sea. ዓሣ ፡ አጥማጆች ፡ የሚተዳደሩት ፡ ከባሕር ፡ በሚ ያገኙት ፡ ዓሣ ፡ ነው

**subsistence** (adj.)
*They are paid subsistence wages. የሚከፈላቸ ው ፡ ለዕለት ፡ ምግብ ፡ የሚበቃቸው ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ ነው

**substance**
1. ነገር. Wood is a solid substance. ዕንጨት ፡ ጥ ጥር ፡ ነገር ፡ ነው
2. መሠረተ ፡ ሐሳብ. The movie is not changed in substance from the novel. የፊልሙ ፡ መሠረ ተ ፡ ሐሳብ ፡ ከመጽሐፉ ፡ የተለየ ፡ አይደለም
3. ፍሬ ፡ ነገር. Tell me the substance of last night's speech. የትናንትናውን ፡ ማታ ፡ ንግግ ር ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ንገረኝ

**have substance** ወፈረ
Pea soup has more substance than vegetable soup. ያተር ፡ ሾርባ ፡ ካታክልት ፡ ሾርባ ፡ ይወፍራል

**of substance** ባለጸጋ
A man of substance is usually chosen to be district commissioner. ወረዳ ፡ ገገር ፡ ሆኖ ፡ የ ሚመረጥ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ባለጸጋ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ነው

**substandard** ዝቅ ፡ ያለ
The villagers live on a substandard level. የመንደርተኞቹ ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ነው

**substantial**
1. ብዙ. He lost a substantial sum of money. ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ጠፋበት
I don't see any substantial difference. ብዙ ፡ ል ዩነት ፡ አልታየኝም
2. ምግብነት ፡ አለው. The food was plain but substantial. ምግቡ ፡ ተራ ፡ ቢሆንም ፡ ምግብነት ፡ ያለው ፡ ነበር
3. ጠንካራ. The bridge doesn't look very substantial. ድልድዩ ፡ በጣም ፡ ጠንካራ ፡ አ ይመስልም
4. የተጨበጠ. People and things are substantial; dreams and ghosts are not. ሰውና ፡ እ ቃ ፡ የተጨበጡ ፡ ሲሆኑ ፡ ሕልምና ፡ መናፍስት ፡ ግ ን ፡ አይደሉም
5. (= adv.) በመሠረቱ. The stories told by the two boys are in substantial agreement. ሁለቱ ፡ ልጆች ፡ የተናገሩት ፡ ነገር ፡ በመሠረቱ ፡ አንድ ፡ ነው
6. (= adv.) በጣም. My brother made a substantial improvement in health. የወንድሜ ፡ ጤንነት ፡ በጣም ፡ እየተሻሻለ ፡ ሄደ.ል

**not substantial** መሠረተ ፡ ቢስ
His fears turned out not to be substantial. ፍርሀቱ ፡ መሠረተ ፡ ቢስ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

**substantially** በመሠረቱ
The two are substantially alike. በመሠረቱ ፡ ሁ ለቱ ፡ ይመሳሰላሉ

**substantiate** በማስረጃ ፡ አረጋገጠ
He could not substantiate his charge. ክሱን ፡ በማስረጃ ፡ ሊያረጋግጥ ፡ አልቻለም

**be substantiated** ተረጋገጠ
Hearsay evidence is inadmissible in court because it cannot be substantiated. በስሚ ፡ ስ ሚ ፡ ምስክርነት ፡ ሊረጋገጥ ፡ ስለማይችል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አይቀበለውም

**substitute** (vt.) በ --- ፈንታ ፡ ጨመረ
The maid substituted sugar for honey in the cake. ገረዲቱ ፡ ብስኩቱ ፡ ውስጥ ፡ በስኳር ፡ ፈንታ ፡ ማር ፡ ጨመረችበት

**substitute** (vi.)
1. ተተክቶ ፡ ሠራ. He substituted for me while I was on vacation. ዕረፍት ፡ ላይ ፡ በነበርኩበት ፡ ጊዜ ፡ በኔ ፡ ቦታ ፡ ተተክቶ ፡ ሠራ

2. ተካ. Do you think sugar will substitute for honey? ስኳር ፡ ማርን ፡ የሚተካ ፡ ይመስልሃል ?

**substitute** (n.) ምትክ
If you can't be here tomorrow, send a substitute. ነገ ፡ እዚህ ፡ ለመገኘት ፡ ካልቻልክ ፡ ምትክ ፡ ላክ
I don't have a pair of pliers, but this will serve as a substitute. ጉጠት ፡ የለኝም ፤ ግን ፡ ይህም ፡ በምትኩ ፡ ያገለግላል

**be used as a substitute** በ --- ፈንታ ፡ ተሠራ(በት)
Margarine is frequently used as a substitute for butter. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በቅቤ ፡ ፈንታ ፡ የዕንጨት ፡ ቅቤ ፡ ምግብ ፡ ይሠራበታል

**subterfuge** ምክንያት ፤ ብልሃት
He used a subterfuge to get out of the assignment. ከተመደበለት ፡ ሥራ ፡ ለማምለጥ ፡ ምክንያት ፡ (ብልሃት) ፡ ፈጠረ

**subterranean** የመሬት ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ
This building has a subterranean passage. ይህ ፡ ሕንጻ ፡ የመሬት ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ መተላለፊያ ፡ አለው

**subtle**
1. ረቂቅ. There is a subtle distinction between these two colors. በነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ ቀለማት ፡ መሀከል ፡ ረቂቅ ፡ ልዩነት ፡ አለ
He has a subtle scheme to get some money from his uncle. ከአጎቱ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያገኝበት ፡ ረቂቅ ፡ ዘዴ ፡ አለው
2. የረቀቀ. He has a subtle mind. አእምሮው ፡ የረቀቀ ፡ ነው
3. ላመል ፡ የሚሰማ. Some subtle odors are hard to recognize. ላመል ፡ የሚሰማ ፡ ሽታን ፡ መለየት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
4. (= adv.) ላመል. Her subtle smile puzzled her husband. ላመል ፡ ፈገግ ፡ ማለቷ ፡ ባሏን ፡ ግራ ፡ አጋባው

**subtle observer** አስተዋይ
She is a subtle observer of slight differences in things. አስተዋይ ፡ ስለሆነች ፡ ባንዳንድ ፡ ነገር ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ጥቃቅን ፡ ልዩነት ፡ እንኳ ፡ ለይታ ፡ ለማወቅ ፡ ትችላለች

**subtract** ቀነሰ
If you subtract 6 from 9, you have 3. ከዘጠኝ ፡ ላይ ፡ ስድስት ፡ ብትቀንስ ፡ ሦስት ፡ ይቀራል

**subtraction** መቀነስ
The class is studying subtraction. ተማሪዎቹ ፡ መቀነስ ፡ በመማር ፡ ላይ ፡ ናቸው

**suburb** ከተማ ፡ ዳር
He lives in a suburb and works in the city. የሚኖረው ፡ ከተማ ፡ ዳር ፡ ሲሆን ፡ የሚሠራው ፡ ግን ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**subvention** የገንዘብ ፡ እርዳታ
He receives a subvention from the government. ከመንግሥት ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታ ፡ ያገኛል

**subversive**
1. የሚያደፈርስ. His speeches were subversive to peace and order. ንግግሮቹ ፡ ሰላምና ፡ ጸጥታን ፡ የሚያደፈርሱ ፡ ነበሩ
2. የዐመፅ. The foreign agent's subversive activities were discovered by the police. ከውጭ ፡ አገር ፡ የተላከው ፡ ሰው ፡ የዐመፅ ፡ ተግባሮች ፡ በፖሊስ ፡ ተደረሰባቸው

**subvert**
1. ገለበጠ. These ideas will end in subverting the government. እነዚህ ፡ ሐሳቦች ፡ ፍጻሜያቸው ፡ መንግሥቱን ፡ መገልበጥ ፡ ነው
2. አዛባ. The acceptance of bribes will subvert justice. ጉቦ ፡ መብላት ፡ ፍርድ ፡ ያዛባል

**subway** መሿለኪያ
Cross the street by the subway! መንገዱን ፡ በመሿለኪያው ፡ አቋርጥ

**subway train** ምድር ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ የሚጓዝ ፡ ባቡር
New York has many subway trains. ኒውዮርክ ፡ ምድር ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ የሚጓዙ ፡ ብዙ ፡ ባቡሮች ፡ አሏት

**succeed** (vt.)
1. ተተካ. Who succeeded him in office? በሱ ፡ ቦታ ፡ ማን ፡ ተተካ ?
2. ተካ. Dawn succeeded night. ንጋት ፡ ምሽትን ፡ ተካ
3. አልጋ ፡ ወረሰ. When the king died, his grandson succeeded him. ንጉሡ ፡ ሲሞት ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ አልጋውን ፡ ወረሰ

**succeed** (vi.)
1. ተሳካ ፤ ተቃና. If we all hang together, our plan will succeed. ሁላችንም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ከሆን ፡ እቅዳችን ፡ ይሳካል ፡ (ይቃናል)
2. ፍሬ ፡ ሰጠ. We must redirect our efforts as nothing we have yet done has succeeded. እስከ ፡ አሁን ፡ የሠራነው ፡ ፍሬ ፡ ስላልሰጠ ፡ ጥረታችንን ፡ በሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ ማድረግ ፡ አለብን
3. ተሳካ(ለት). +He succeeds in everything he undertakes. የሚያደርገው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይሳካለታል

4. ቻለ. He succeeded in easing the director out of his position. ዲሬክተሩን ፡ ከሥልጣን ፡ ለማስለቀቅ ፡ ቻለ
5. ከሰበው ፡ ደረሰ ፡ ከፍሬ ፡ ደረሰ. Some men succeed by trickery. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በማታለል ፡ ከሰቡት ፡ (ከፍሬ) ፡ ይደርሳሉ

**succeed to the crown** ዙፋኑን ፡ ወረሰ
The prince succeeded to the crown. ልዑሉ ፡ ዙፋኑን ፡ ወረሰ

**succeed to the throne** አልጋውን ፡ ወረሰ
His Imperial Majesty succeeded to the throne on the death of the Empress Zewditu. ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አልጋውን ፡ የወረሱት ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ ነው

## succeeding ከሉ ፡ በኋላ ፡ የመጣ
He left the imprint of his thought on all succeeding scholars. አስተሳሰቡ ፡ ከሉ ፡ በኋላ ፡ በመጡት ፡ ሊቃውንት ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ይታይ ፡ ነበር

## success
1. የዕድል ፡ መቃናት. What is the secret of his success? ለዕድሉ ፡ መቃናት ፡ ምስጢሩ ፡ ምን ፡ ይሆን ?
2. የውጤት ፡ መቃናት. She ascribed her success to hard work. የውጤቱ ፡ መቃናት ፡ በከባድ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ አለች
3. መልካም ፡ ውጤት. Your efforts will result in success. ጥረትህ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ያስገኝልሃል
4. መሳካት. Poor health may be a bar to success in life. የጤና ፡ ማጣት ፡ ለኑሮ ፡ መሳካት ፡ መሰናከል ፡ ሊሆን ፡ ይችላል
5. የሥራ ፡ መሳካት ፤ የሥራ ፡ መቃናት. A poor education can be hindrance to success. በቂ ፡ ያልሆነ ፡ ትምህርት ፡ ለሥራ ፡ መሳካት ፡ (መቃናት) ፡ ዕንቅፋት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል
6. እድገት. Hard work is a sure avenue to success. ጠንክሮ ፡ መሥራት ፡ የተረጋገጠ ፡ የእድገት ፡ በር ፡ ነው
*Congratulations on your success! ስለቀናህ ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ ያለህ !

**be a success** ተሳካ
The play wasn't much of a success. ቲያትሩ ፡ ብዙም ፡ አልተሳካ

**have success in** ተሳካ
Did you have success in training your dog? ውሻህን ፡ የማሠልጠኑ ፡ ጉዳይ ፡ ተሳካልህ ?

**make a success of**
1. አሳመረ. He made a success of the play by adding another scene. ሌላ ፡ ትርእይት ፡ ጨምሮ ፡ ቲያትሩን ፡ አሳመረው
2. የተቃና ፡ ሆነ(ለት). He made a success of manufacturing hats out of straw. የስፌት ፡ ባርኔጣ ፡ ንግዱ ፡ የተቃና ፡ ሆኖለታል

**win success** መልካም ፡ ውጤት ፡ አተረፈለት
His repeated efforts at last won success. ደግሞ ፡ ደጋግሞ ፡ ያደረገው ፡ ጥረት ፡ በመጨረሻው ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ አተረፈለት

**without success** በከንቱ
I have tried it time and again, but without success. መላልሼ ፡ ሞከርኩት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በከንቱ ፡ ነበር
[See also 'crown, score, smashing']

## successful
1. የተሳካ. A successful business will soon branch out all over the country. የተሳካ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ በቅርቡ ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ይሰራጫል
2. የሚያዋጣ. The beauty parlor is a successful business. የቁንጅና ፡ ሳሎን ፡ የሚያዋጣ ፡ ንግድ ፡ ነው

**be successful**
1. ተሳካ. The attempt to climb the mountain was successful. ተራራውን ፡ ለመውጣት ፡ የተደረገው ፡ ሙከራ ፡ ተሳካ
2. ተሳካ(ለት). +He is successful in everything he does. የሚያደርገው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይሳካለታል
3. ጥሩ ፡ ውጤትን ፡ አስገኘ. The fight against malaria was successful. ወባን ፡ ለማጥፋት ፡ የተደረገው ፡ ዘመቻ ፡ ጥሩ ፡ ውጤትን ፡ አስገኘ
4. መልካም ፡ ፍሬ ፡ አስገኘ. His endeavor to be elected was successful. ለመመረጥ ፡ መድከሙ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ አስገኘ

## successfully በሚገባ
He completed his mission successfully. መልእክቱን ፡ በሚገባ ፡ አከናወነ

## succession
*His succession to the office of prime minister was seen on television. የጠቅላይ ፡ ሚኒስትርነትን ፡ ሥልጣን ፡ ሲረከብ ፡ በቴሌቪዥን ፡ ታየ

**succession of**
1. የደረሰው ፡ ተከታታይ. A succession of accidents spoiled our automobile trip. የደረሰው ፡ ተከታታይ ፡ አደጋ ፡ የመኪና ፡ ጉዞዋችንን ፡ አበላሸብን
2. (= adv.) በተከታታይ. The army suffered a succession of defeats. ጦሩ ፡ በተከታታይ ፡ ድል ፡ ሆነ

**succession to the throne** የዘውዱ ፡ አወራረስ
His succession to the throne is secured by the constitution. የዘውዱ ፡ አወራረስ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ተረጋግጧል

**in (quick) succession** ተከታትሎ
Blows rained on him in quick succession. ቡጢው ፡ ተከታትሎ ፡ ወረደበት

**successive** ተከታታይ
The team won five successive games. ቡድኑ ፡ አምስት ፡ ተከታታይ ፡ ጨዋታዎችን ፡ አሸነፈ

**successor**
1. ተተኪ. He handed the job over to his successor. ሥራውን ፡ ለተተኪው ፡ አስረከበ
2. የሚተካ. The prime minister's successor will be named by the Emperor. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩን ፡ የሚተካውን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይሾማሉ
*Who was King George V's successor? ከንጉሥ ፡ ጆርጅ ፡ አምስተኛ ፡ ቀጥሎ ፡ ማን ፡ ነገሠ ?

**be someone's successor** በሱ ፡ ቦታ ፡ ተተካ
He designated the director to be his successor. ዲሬክተሩን ፡ በሱ ፡ ቦታ ፡ እንዲተካ ፡ ሠየመው

**succinct** አጭር ፡ ምጥን ፡ ያለ
His explanations are succinct. አገላለጹ ፡ አጭር ፡ ምጥን ፡ ያለ ፡ ነው

**succinctly** ቅልብጭ ፡ ባለ ፡ አነጋገር
He expressed himself very succinctly. ሐሳቡን ፡ ቅልብጭ ፡ ባለ ፡ አነጋገር ፡ ገለጸ

**succor** እርዳታ ፡ አደረገ
She succored the refugees. ለስደተኞቹ ፡ እርዳታ ፡ አደረገችላቸው

**(be) succulent** ብዙ ፡ ውኃ ፡ አለው
This orange is succulent. ብርቱካኑ ፡ ብዙ ፡ ውኃ ፡ አለው

**succumb** አረፈ
He succumbed after a long illness. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከታመመ ፡ በኋላ ፡ አረፈ

**succumb to temptation** (= adv.) ፍላጎቱ ፡ አሸንፎት
He succumbed to temptation and bought the car he couldn't pay for. ፍላጎቱ ፡ አሸንፎት ፡ ሊከፍለው ፡ በማይችለው ፡ ዋጋ ፡ መኪና ፡ ገዛ

**such**
1. እንደዚህ ፡ ያለ. Such statements are hard to prove. እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ አባባሎች ፡ ለማረጋገጥ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. የመሳሰሉ. The ladies took only tea and coffee and such drinks. ሴቶቹ ፡ ሻይ ፡ ቡናና ፡ የመሳሰሉትን ፡ መጠጦች ፡ ብቻ ፡ ጠጡ
3. (= adv.) አይ ፡ እንዲህ. Are you trying to get me fired? Such is not my intention. ከሥራ ፡ እንድወጣ ፡ ነው ፡ የምትሞክረው ? አይ ፡ እንዲህ ፡ አላሰብኩም
*His behavior was such that everyone disliked him. ጠባዩ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ የሚያስጠላው ፡ ዓይነት ፡ ነበር

**such a**
1. እንደዚህ ፡ ያለ. Such a good worker deserves better pay. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጥሩ ፡ ሠራተኛ ፡ የበለጠ ፡ ደሞዝ ፡ ይገባዋል
2. እንዲህ ፡ ያለ. She would never say such a thing. እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አይወጣትም
3. (= adv.) እንደዚህ. Don't be in such a hurry! እንደዚህ ፡ አትቸኩል !
4. ይህን ፡ የመሰለ. It's a sin to stay indoors on such a nice day. ይህን ፡ በመሰለ ፡ ጥሩ ፡ ቀን ፡ እቤት ፡ መዋል ፡ ኀጢአት ፡ ነው
5. ይህን ፡ መሳይ. I will give him a piece of my mind for telling such a lie. ይህን ፡ መሳይ ፡ ውሸት ፡ ስለነገረኝ ፡ ቅር ፡ እንደተሰኘሁ ፡ እገልጽለታለሁ
6. ይህን ፡ ያህል. He is not such a fool as you assume him to be. አንተ ፡ እንደምትገምተው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ቂል ፡ አይደለም
*We had such a good time at your house. እቤትህ ፡ ጥሩ ፡ ጊዜ ፡ አሳለፍን

**such a!** እንዴት ፤ እንዴት ፡ ያለ
He gave me such a fright! እንዴት ፡ አስደነገጠኝ !
He is such a liar! እንዴት ፡ ያለ ፡ ውሸታም ፡ ነው

**such a thing** የሚባል ፡ ነገር
Is there such a thing as a sea monster? የባሕር ፡ ጭራቅ ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ አለ ?

**such-and-such**
1. እከሌ. I met such-and-such. እከሌን ፡ አገኘሁት
The bank was robbed at such a time in such-and-such a town. በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በእከሌ ፡ ከተማ ፡ ባንኩ ፡ ተዘረፈ
2. ይህንና ፡ ያንን. If he says such-and-such, I will deny it. ይህንና ፡ ያንን ፡ ቢል ፡ አልቀበለውም

**such as**
1. እንደነ - - - የመሳሰሉት. Scholars such as Cerulli, Guidi, and Cohen have written extensively on Ethiopia. እንደነ ፡ ቸሩሊ ፤ ግዊዲና ፡ ኮሄን ፡ የመሳሰሉት ፡ ምሁራን ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሰፊው ፡ ጽፈዋል
2. የመሳሰሉ. Science courses such as chemistry and biology are taught in this school. ኬሚስትሪንና ፡ ባዮሎጂን ፡ የመሳሰሉ ፡ የሳይንስ ፡ ትምህርቶች ፡ በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይሰጣሉ
3. የ - - - ያህል. Take such blankets as you need. ከብርድ ፡ ልብሶቹ ፡ የምትፈልገውን ፡ ያህል ፡ ውሰድ

*Your stupidity is such as to fill me with despair. ደደብነትህ ፡ በጣም ፡ ተስፋ ፡ የሚያስ ቈርጠኝ ፡ ነው

**such as it is** እንዳለ

You can use my bicycle, such as it is. ብስክሌቴን ፡ እንዳለች ፡ ልትጠቀምባት ፡ ትችላለህ

**as such**

1. እስከዚህም. The work as such isn't difficult. ሥራውስ ፡ እስከዚህም ፡ አስቸጋሪ ፡ አይደለ

2. በዚህም. He is a brilliant scholar and is recognized as such. በጣም ፡ ጐበዝ ፡ ምሁር ፡ ነ ው ፤ በዚህም ፡ በጣም ፡ ታውቋል

*He is the mayor and as such must be consulted. ከንቲባ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ልናማክረው ፡ ይገባል

**some such**

*I think he calls himself Harrison or some such name. ሀሪሰን ፡ ወይም ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ ስ ም ፡ ይጠሩታል ፡ መሰለኝ

## suchlike ይህንን ፡ የመሳሰሉ ፡ ነገሮች

I have no time for concerts, cinemas and suchlike. ለሙዚቃ ፤ ለትርእይት ፤ ለሲኒማና ፡ ይህን ን ፡ ለመሳሰሉት ፡ ነገሮች ፡ ጊዜ ፡ የለኝም

## suck

1. ጠባ. The baby sucked its mother's breast. ሕፃኑ ፡ የናቱን ፡ ጡት ፡ ጠባ

The baby sucked the milk from his bottle. ሕፃኑ ፡ ጡጦውን ፡ ጠባ

The baby sucks its thumb. ሕፃኑ ፡ አውራ ፡ ጣ ቱን ፡ ይጠባል

2. መጠጠ. The child sucked the lemon and did not like it. ልጁ ፡ ሎሚውን ፡ መጠ ፡ ሳይወደው ፡ ቀረ

Plants suck moisture from the ground. ዕፀዋት ፡ ውኃ ፡ ከመሬት ፡ ይመጣሉ

Don't swallow the candy. Suck it! ከረሜላውን ፡ አትዋጠው ፤ ምጠጠው

3. ሳበ. He sucked air into his lungs. አየር ፡ ወ ደ ፡ ውስጥ ፡ ሳበ

**suck at** ሳበ

The old man sucked at his pipe. ሽማግሌው ፡ ፒፓውን ፡ ሳበ

**suck up** ሳበ

These plants suck up moisture from the soil. እነዚህ ፡ አትክልቶች ፡ ከመሬት ፡ ውኃ ፡ ይስባሉ

## sucker

1. አዲስ ፡ የበቀለ ፡ ቅርንጫፍ. Cut the suckers off the tree trunk! ግንዱ ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ የበቀ ሉትን ፡ ቅርንጫፎች ፡ ቍረጣቸው

2. ባለ ፡ ዕንጨት ፡ ከረሜላ. I like to eat suckers. ባለ ፡ ዕንጨት ፡ ከረሜላ ፡ መብላት ፡ እወዳለሁ

3. ተላላ. He is a sucker for phony oil stocks. ተላላ ፡ ስለሆነ ፡ የማይረቡ ፡ የዘይት ፡ አክሲዮኖች ፡ ያግበሰብሳል

## suckle (vt.) አጠባ

She suckled her child to quiet it. ልጇን ፡ አጥባ ታ ፡ ዝም ፡ አሰኘችው

**suckle** (vi.) ጠባ

They suckle three times a day. በቀን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ይጠባሉ

## suction

1. መምጠጥ. Some pumps work by suction. አንዳንድ ፡ ፖምፖች ፡ የሚሠሩት ፡ በመምጠጥ ፡ ነው

2. መሳብ. The suction of the sinking ship pulled many swimmers under the water. የሚሰጥመው ፡ መርከብ ፡ ውኃ ፡ መሳብ ፡ ብዙ ፡ ዋናተኞችን ፡ አጠለቃቸው

## sudden

1. ያልታሰበ. There was a sudden hitch in the program. ፕሮግራሙ ፡ ያልታሰበ ፡ መሰናከል ፡ ገጠመው

2. ድንገተኛ. A sudden storm came up. ድንገተኛ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ተነሣ

3. (= adv.) በድንገት. There has been a sudden change in the weather. አየሩ ፡ በድንገት ፡ ተለዋ ወጠ

**all of a sudden** በድንገት ፤ ድንገት

All of a sudden, it gets dark. በድንገት ፡ ይጨል ማል

All of a sudden, the rain came down. ዝናሙ ፡ ድ ንገት ፡ ጣለ

[See also 'ascent, turn']

## suddenly ወዲያውኑ

Suddenly, everything disappeared. ወዲያውኑ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ጠፋ

## suds አረፋ

The suds are spilling on the floor. አረፋው ፡ ወ ለሉ ፡ ላይ ፡ ፈሰሰ

## sue

1. ከሰ ፡ አቀረበ ፤ ከሰሰ. We sued for damages. ለደረሰብን ፡ ጉዳት ፡ ክስ ፡ አቀርበናል

We can't collect the rent other than by suing the tenant. ተከራዩን ፡ ካልከሰስን ፡ ኪራዩን ፡ ል ንቀበል ፡ አንችልም

2. ለመነ. Our enemy sued for peace. ጠላቶቻች ን ፡ ዕርቅ ፡ እንድናደርግ ፡ ለመኑን

**suffer** (vt.)
1. ታገሠ. How can you suffer such insolence? እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ብልግና ፡ እንዴት ፡ ትታገሠ ዋለህ ?
2. ደረሰ(በት). +They suffered heavy losses. ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ደረሰባቸው
**suffer** (vi.)
1. (= vt.) አሠቃየ. +I suffer from headaches. የራስ ፡ ምታት ፡ ያሠቃየኛል
2. ተሰማ(ው). +He suffers from fatigue, even after a short walk. ጥቂት ፡ እንኳ ፡ በእግሩ ፡ ሲ ሄድ ፡ ድካም ፡ ይሰማዋል
3. ተጻከመ. His business suffered while he was ill. ታሞ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ንግዱ ፡ ተጻከመ
4. ዋጋውን ፡ አገኘ. You'll suffer for your insolence some day! ለዚህ ፡ ስድነትህ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ዋጋህ ን ፡ ታገኛለህ
5. ዝቅ ፡ አለ. Her grades suffered when she did not study. ሳታጠና ፡ ስለቀረች ፡ ውጤቷ ፡ ዝቅ ፡ አለ
**suffer from** ችግር ፡ ደረሰ(በት)
+We suffered from a shortage of food. የምግብ ፡ እጥረት ፡ ችግር ፡ ደረሰብን
[See also 'beating, defeat, misfortune, relapse, reverse']

**sufferance** ፈቃድ
He is here by the sufferance of his parents. እዚህ ፡ ያለው ፡ በቤተሰቦቹ ፡ ፈቃድ ፡ ነው

**suffering** (n.)
1. ሥቃይ. He spoke passionately of Ethiopia's sufferings in the war. በጦርነቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላ ይ ፡ ስለደረሰው ፡ ሥቃይ ፡ ሲያወራ ፡ በጥልቅ ፡ ስሜት ፡ ነው
2. መሠቃየት. The suffering of the poor makes her heart sore. የድሆች ፡ መሠቃየት ፡ በጣም ፡ ያሳዝናታል
3. ችግር. They criticized his indifferent attitude toward the suffering of others. ስለ ፡ ሌሎች ፡ ች ግር ፡ በሚያሳየው ፡ የግድየለሽነት ፡ ሁኔታ ፡ ወቀ ሱት
4. መከራ. Suffering left its imprint on her face. መከራ ፡ ከፊቷ ፡ ይነበባል
**suffering** (adj.) በሥቃይ ፡ ላይ ፡ ያለ
He is unable to turn his back on any suffering creature. በሥቃይ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ማንኛቸውንም ፡ ፍጡር ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ማለፍ ፡ አይሆንለትም

**suffice**
1. በቃ. Three cups of coffee will suffice me. ሦስት ፡ ሲኒ ፡ ቡና ፡ ይበቃኛል
2. አጠገበ. A small amount of cake sufficed the baby. ትንሽ ፡ ኬክ ፡ ልጁን ፡ አጠገበው
*Your word will suffice. ቃልህን ፡ አምናለሁ
**suffice it to say** ማለቱ ፡ ይበቃል
Suffice it to say that the work hadn't even been started. ሥራው ፡ እንዲያውም ፡ አልተጀመ ረም ፡ ማለቱ ፡ ይበቃል

**sufficiency, ~ of** የሚበቃ
The ship has a sufficiency of provisions for a voyage of two months. መርከቢ ፡ ለሁለት ፡ ወር ፡ የሚበቃ ፡ ምግብ ፡ አላት

**sufficient** በቂ
Three dollars were not sufficient. ሦስት ፡ ብር ፡ በቂ ፡ አልነበረም
Do you have sufficient proof? በቂ ፡ ማስረጃ ፡ አለህ ?
[See also 'self-sufficient']

**suffix** ባዕድ ፡ መድረሻ
The plural is formed by suffixes. ነጠላ ፡ ቁጥር ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ ቁጥር ፡ የሚለወጠው ፡ ባዕድ ፡ መድ ረሻዎች ፡ በመጨመር ፡ ነው

**suffocate** (vt.) አፈነ
The smoke almost suffocated me. ጭሱ ፡ ሊያ ፍነኝ ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር
**suffocate** (vi.) ታፈነ
I nearly suffocated. ልታፈን ፡ ምንም ፡ አልቀ ረኝም

**suffrage** የምርጫ ፡ መብት
Suffrage was granted to women only recently. ለሴቶች ፡ የምርጫ ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ በቅ ርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**suffuse**
*A blush suffused her cheek. ጉንጯ ፡ ፍም ፡ መሰለ
**suffuse with** አዘለ
Her eyes were suffused with tears. ዓይኖቿ ፡ እ ንባ ፡ አዝለው ፡ ነበር

**sugar** ሱኳር
I drink coffee with sugar. ቡና ፡ በሱኳር ፡ እ ጠጣለሁ

**sugar cane** ሸንኮር ፡ አገዳ
Sugar cane grows in abundance in Wonji. ሸንኮር ፡ አገዳ ፡ ወንጂ ፡ በብዛት ፡ ይበቅላል

**sugary, be very ~** ሱኳር ፡ በዛበት
The cake is very sugary. ኬኩ ፡ ሱኳር ፡ በዝቶበ ታል

**suggest**
1. ሐሳብ ፡ አቀረበ. I'll suggest it at the next meeting. በሚቀጥለው ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ ሐሳቡን ፡ አቀርባለሁ
2. አመለከተ. His cruelty suggests that he is not human. ጭካኔው ፡ ሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ አለመሆኑን ፡ ያመለክታል
The look on his face suggests fear. የፊቱ ፡ ሁኔታ ፡ መፍራቱን ፡ ያመለክታል
3. አሳሰበ. The thought of summer suggests swimming and hot weather. በጋ ፡ ሲባል ፡ ዋናንና ፡ ሞቃት ፡ ያየር ፡ ሁኔታን ፡ ያሳስባል
Along the lines just noted, I suggest we start the new project. አሁን ፡ በተገለጹት ፡ ሐሳቦች ፡ መሠረት ፡ አዲስ ፡ እቅድ ፡ እንድንጀምር ፡ አሳስባለሁ
*I suggest that we go to the movies. ወደ ፡ ሲኒማ ፡ ብንሄድ ፡ አይሻልም ?
**suggests itself to** መጣ(ለት)
Another idea suggests itself to me. ሌላ ፡ ሐሳብ ፡ መጣልኝ
**are you suggesting that?** ማለትህ ፡ ነው ?
Are you suggesting that I'm worse at it than you? ካንተ ፡ እብሳለሁ ፡ ማለትህ ፡ ነው ?

**suggestion**
1. ያቀረበውን ፡ ሐሳብ. I refused to accept his suggestion. እሱ ፡ ያቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ አልተቀበልኩትም
2. አስተሳሰብ. The picnic was an excellent suggestion. ሽርሽሩ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ አስተሳሰብ ፡ ነበር
3. አሳሳቢነት. The trip was made at his suggestion. ጉዞው ፡ የተደረገው ፡ በሱ ፡ አሳሳቢነት ፡ ነበር
*The foreigner spoke Amharic with just a suggestion of his native accent. የውጭ ፡ አገሩ ፡ ሰው ፡ ያገሩ ፡ አነጋገር ፡ ላመል ፡ በሚታወቅበት ፡ ሁኔታ ፡ አማርኛ ፡ ተናገረ
**make a suggestion** ሐሳብ ፡ አቀረበ
May I make a suggestion that we adjourn? በቀጠሮ ፡ እንድንለያይ ፡ ሐሳብ ፡ አቀርባለሁ

**(be) suggestive of** አሳሰበ
His manner is suggestive of the 19th century. አኳኋኑ ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠነኛውን ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ የሚያሳስብ ፡ ነው

**suicide** ራስን ፡ መግደል
Suicide is prohibited by our religion. ራስን ፡ መግደል ፡ በሃይማኖታችን ፡ የተከለከለ ፡ ነው
**commit suicide** ራሱን ፡ ገደለ
He committed suicide in a fit of depression. ተስፋ ፡ በመቁረጥ ፡ ራሱን ፡ ገደለ

**suit** (v.)
1. አስደሰተ. It's hard to suit everybody. ሁሉንም ፡ ሰው ፡ ማስደሰት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. ተስማማ. Red doesn't suit you. ቀይ ፡ አይስማማህም
3. ተመጣጣኝ ፡ ሆነ. The punishment should suit the crime. ቅጣቱ ፡ ለወንጀሉ ፡ ተመጣጣኝ ፡ መሆን ፡ አለበት
**suit best** ተመቸ
Which day would suit you best? መቼ ፡ ይመችሃል ?
**suit oneself** ለራሱ ፡ እንዲመች ፡ አደረገ
He strained the rules to suit himself. ለራሱ ፡ እንዲመች ፡ አድርጎ ፡ በመጠምዘዝ ፡ ሕጉን ፡ ተረጎመ
**suit (one's) taste** ተስማማ
Does this color suit your taste? ይህ ፡ ቀለም ፡ ይስማማሃል ?
**suit yourself!** እንዳሰኘህ
A: Come with me! B: I'd rather not. A: Well, suit yourself! እንደኛው ፤ ከኔ ፡ ጋር ፡ ና ፤ ሁለተኛው ፤ ይቅርብኝ ፤ አንደኛው ፤ እንዳሰኘህ
**be suited**
1. ተስማማ. Is democracy suited to all nations? የዲሞክራሲ ፡ አገዛዝ ፡ ለሁሉም ፡ መንግሥታት ፡ ይስማማል ?
2. ተመጣጠነ. It's suited to the age of the children. ከልጆቹ ፡ ዕድሜ ፡ ጋር ፡ የሚመጣጠን ፡ ነው
3. ተገባ. Is she suited for this kind of work? ለዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ትገባለች ?

**suit** (n.)
1. ሙሉ ፡ ልብስ. He needs a new suit. አዲስ ፡ ሙሉ ፡ ልብስ ፡ ያስፈልገዋል
2. ክስ. Did Mr. Brown win the suit? ሚስተር ፡ ብራውን ፡ ክሱን ፡ ረታ ?
3. ማሽኮርመም. His suit was successful, and she married him. ማሽኮርመሙ ፡ ፍሬ ፡ አግኝቶለት ፡ ልታገባው ፡ ተስማማች
**bring suit** ከሰሰ
If you fail to pay us before Monday, we shall bring suit. እስከ ፡ ሰኞ ፡ ካልከፈልከን ፡ እንከስሃለን
**follow suit** ተከተለ
If he goes to war, I will follow suit. ሄዶ ፡ ከተዋጋ ፡ እከተለዋለሁ
*If you contribute a dollar, I will follow suit. አንተ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ካዋጣህ ፡ እኔም ፡ አዋጣለሁ

**suitable**
1. የሚስማማ. We couldn't find a suitable apartment. የሚስማማ ፡ አፓርትማ ፡ ልናገኝ ፡ አልቻልንም

2. ተስማሚ. Her dress was not suitable for the reception. ልብሷ ፡ ለግብዣው ፡ ተስማሚ ፡ አልነበረም

**suitably** (= adj.) ተስማሚ
She was suitably attired for the reception. ለግብዣው ፡ ተስማሚ ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ ነበር

**suitcase** ሻንጣ
He bought a new suitcase for the trip. ለጉዞው ፡ አዲስ ፡ ሻንጣ ፡ ገዛ

**suite** ተከታዮች
There were twenty people in the President's suite. የፕሬዚዳንቱ ፡ ተከታዮች ፡ ሃያ ፡ ነበሩ

**suite of rooms**
*He rented a suite of rooms. ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ የሚገናኙ ፡ ክፍሎች ፡ ተከራየ

**suitor**
1. ከሳሽ. The suitor lost his case. ከሳሹ ፡ ተረታ
2. የሚያሽኮረምም. She had many suitors, but she did not wish to marry any of them. የሚያሽኮረምሟት ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፡ ግን ፡ ማንኛውንም ፡ ልታገባ ፡ አልፈለገችም

**sulk**
1. ለንቦጭ ፡ ጣለ. Don't sulk because you can't get your way! የፈለግኸው ፡ ስላልሆነልህ ፡ ለንቦጭህን ፡ አትጣል
2. አኮረፈ. The deputy sulked when his boss rejected his suggestion. ምክትሉ ፡ አለቃው ፡ ሐሳቡን ፡ ስላልተቀበለው ፡ አኮረፈ

**sulky, get ~** አኮረፈ
He gets sulky and won't play if he can't be the leader. የቡድኑ ፡ አለቃ ፡ ካልሆነ ፡ አኩርፎ ፡ አልጫወትም ፡ ይላል

**sullen**
1. ያኮረፈ. The sullen child refused to answer my question. ያኮረፈው ፡ ልጅ ፡ ለጥያቄዬ ፡ መልስ ፡ አልሰጥ ፡ አለ
2. የከበደ. The sullen skies threatened rain. የከበደው ፡ ሰማይ ፡ ዝናብ ፡ የሚጥል ፡ ይመስላል

**look sullen** የቅሬታ ፡ መልክ ፡ አሳየ
She took her daughter with her, but she looked sullen all the time. እናትዮዋ ፡ እየያዘቻት ፡ ብትወጣም ፡ ልጅቷ ፡ ሁልጊዜ ፡ የቅሬታ ፡ መልክ ፡ አሳየች

**sully** (sullied) አጎደፈ
He sullied his family's honor by betraying his country. አገሩን ፡ በመክዳት ፡ የቤተ ፡ ሰቡን ፡ ክብር ፡ አጎደፈ

**sulphur** ድኝ
They fumigated the room by burning sulphur. ድኝ ፡ በማጨስ ፡ ክፍሉን ፡ ዐጠኑት

**(be) sultry** ከበደ
The weather is sultry in the south. በደቡብ ፡ አየሩ ፡ ይከብዳል

**sum** (summed), **~ up**
1. ደመረ. He summed up all his expenses. ወጪውን ፡ ሁሉ ፡ ደመረ
2. አጠቃለለ. And lastly, we shall sum up what we learned. በመጨረሻም ፡ የተማርነውን ፡ እናጠቃልላለን

**sum someone up** ገመተ
She quickly summed him up. ቶሎ ፡ ገመተችው

**to sum up** ባጭሩ
To sum up, he is no good at all. ባጭሩ ፡ እሱ ፡ በፍጹም ፡ ጥሩ ፡ አይደለም

**sum** (n.)
1. ገንዘብ. We paid the sum he asked for. የጠየቀውን ፡ ገንዘብ ፡ ከፈልነው
2. ጠቅላላ ፡ ድምር. The sum of the bill is $200. የሒሳቡ ፡ ጠቅላላ ፡ ድምር ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ነው
*The sum of three and five is eight. ሦስትና ፡ አምስት ፡ ሲደመር ፡ ስምንት ፡ ይሆናል

**sum of money** ገንዘብ
The sum of money he asked for was not large. የጠየቀው ፡ ገንዘብ ፡ ብዙ ፡ አልነበረም

**in sum** በጠቅላላው
In sum, he is a thief and a liar. በጠቅላላው ፡ ሌባም ፡ ውሸታምም ፡ ነው

**pay the sum of** ከፈለ
He paid the sum of $20 for the suit. ለሙሉ ፡ ልብስ ፡ ሃያ ፡ ብር ፡ ከፈለ
[See also 'lump']

**summarily** ባስቸኳይ
He was punished summarily. ባስቸኳይ ፡ ቅጣት ፡ ተፈጸመበት

**summarize** ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ባጭሩ ፡ አቀረበ
Mary was asked to summarize the book. ሜሪ ፡ የመጽሐፉን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ባጭሩ ፡ እንድታቀርብ ፡ ተጠየቀች

**summary** (summaries), n.
1. ፍሬ ፡ ነገር. A summary of the article is printed in English. የጽሑፉ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ታትሟል
2. አስተዋጽኦ. He was asked to present a

summary of the book. የመጽሐፉን ፡ አስተዋጽ ኦ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ተጠየቀ
3. ባጭሩ ፡ የተውጣጣ ፡ ፍሬ ፡ ነገር. The included summary was one page long. አብሮ ፡ የተያያዘው ፡ ባጭሩ ፡ የተውጣጣ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ ነበር

**summary** (adj.)
1. (= adv.) ላጭር ፡ ጊዜ. He was shot after a summary trial. ላጭር ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ በጥይት ፡ ተደበደበ
2. (= adv.) ባስቸኳይ. Summary action against traffic violators will be taken by the police. የትራፊክን ፡ ሕግ ፡ የሚጥሱ ፡ ሰዎች ፡ ፖሊስ ፡ ባስቸኳይ ፡ ይቀጣቸዋል

**summer** በጋ
They go to the beach in the summer. በበጋ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ዳርቻ ፡ ይሄዳሉ

**summit** አናት
The summit of the mountain is treeless. ተራራው ፡ አናት ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዛፍ ፡ የለም

**summit meeting** የመሪዎች ፡ ጉባኤ
The summit meeting will be held in Cairo. የመሪዎች ፡ ጉባኤ ፡ በካይሮ ፡ ይደረጋል

**summit of** ከፍተኛ
The summit of her ambition was to become an actress. ከፍተኛው ፡ ፍላጎቷ ፡ የሲኒማ ፡ ተጫዋች ፡ ለመሆን ፡ ነበር

**summon**
1. ጠራ. They summoned the doctor in the middle of the night. እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ላይ ፡ ሐኪሙን ፡ ጠሩት
2. በመጥሪያ ፡ አዘዘ. The court summoned him to appear before a trial. ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለፍርድ ፡ እንዲቀርብ ፡ በመጥሪያ ፡ አዘዘው
*He summoned all his courage for the task. ተግባሩን ፡ ለማከናወን ፡ ባጭር ፡ ታጥቆ ፡ ተነሣ

**summons** መጥሪያ
He received a summons for fast driving. ከተወሰነው ፡ በላይ ፡ በመንዳቱ ፡ መጥሪያ ፡ ደረሰው

**sumptuous** ታላቅ
The Emperor gave a sumptuous repast. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ታላቅ ፡ ግብር ፡ አበሉ

**sun** (sunned), ~ **oneself** ፀሐይ ፡ሞቀ
They were sunning themselves in the yard. በግቢው ፡ ውስጥ ፡ ፀሐይ ፡ ይሞቁ ፡ ነበር

**sun** (n.) ፀሐይ
The sun just went down. ፀሐይዋ ፡ የጠለቀችው ፡ አሁን ፡ ነው

**(the) noon sun** የቀትር ፡ ጊዜ
The pavement burns in the noon sun. በቀትር ፡ ጊዜ ፡ የእግር ፡ መንገዱ ፡ ይግላል

**under the sun** ከፀሐይ ፡ በታች
This is the most beautiful city under the sun. ከፀሐይ ፡ በታች ፡ ይህችን ፡ የመሰለ ፡ ውብ ፡ ከተማ ፡ የለም
[See also 'midday']

**sunbath, take a** ~
She took a sunbath. አካላቷን ፡ ፀሐይ ፡ ታስመታለች

**sunbeam** የፀሐይ ፡ ጨረር
A sunbeam penetrated the room. የፀሐይ ፡ ጨረር ፡ እቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ገባ

**sunburn** ፀሐይ ፡ ያቃጠለው
The ointment soothed my sunburn. ቅባቱ ፡ ፀሐይ ፡ ያቃጠለኝን ፡ አቀዘቀዘልኝ
*I got a bad sunburn. ፀሐዩ ፡ ክፉኛ ፡ ጠበሰኝ

**sunburned, make** ~ (= get sunburned) ፊቱ ፡ ተጠበሰ
A sojourn in the desert made him quite sunburned. በበረሃው ፡ ውስጥ ፡ በመሰንበቱ ፡ ፊቱ ፡ ተጠብሷል

**Sunday** እሑድ
I go to church on Sundays. እሑድ ፡ እሑድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስግላለሁ

**sunder** (vt.) አቋረጠ
The two governments sundered their diplomatic connections. ሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ግንኙነታቸውን ፡ አቋረጡ

**sunder** (vi.)
1. ፈረሰ. The coalition sundered after the leaders of the parties disagreed. የፓርቲዎቹ ፡ መሪዎች ፡ ሳይስማሙ ፡ ስለቀሩ ፡ ኅብረቱ ፡ ፈረሰ
2. ተጋጭቶ ፡ ተሰበረ. The ship sundered on the rocks. መርከቧ ፡ ከአለቱ ፡ ጋር ፡ ተጋጭታ ፡ ተሰበረች

**sundial** የፀሐይ ፡ መለኪያ
The sundial shows the hours. የፀሐዩ ፡ መለኪያ ፡ ሰዓት ፡ ይቈጥራል

**sundown** የፀሐይ ፡ጥልቀት
Let's watch the sundown! የፀሐይን ፡ ጥልቀት ፡ እንይ

**at sundown** ፀሐይ ፡ ስትጠልቅ ፤ ፀሐይ ፡ ዝቅ ዝቅ ፡ ስትል
They arrived to Gondar at sundown. ፀሐይ ፡ ስትጠልቅ ፡ (ዝቅዝቅ ፡ ስትል) ፡ ጎንደር ፡ ገቡ

**sundry** ልዩ ፡ ልዩ
This store sells sundry, inexpensive goods. ይህ ፡ መደብር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ርካሽ ፡ እቃዎችን ፡ ይሸጣል

**on sundry occasions** አልፎ ፡ አልፎ
I have heard it on sundry occasions. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሰምቼዋለሁ

**sunflower** ሱፍ
Sunflowers have edible seeds. የሱፍ ፡ ፍሬ ፡ ይበላል

**sung,** see **sing**

**sunglasses** የፀሐይ ፡ መነጽር
The sunlight is so bright that I need sunglasses. ፀሐይዋ ፡ ኀይለኛ ፡ ስለሆነች ፡ የፀሐይ ፡ መነጽር ፡ ያስፈልገኛል

**sunk,** see **sink**

**sunken**
1. ሰጥሞ ፡ የነበረ. A sunken ship lies in the harbor. ሰጥሞ ፡ የነበረው ፡ መርከብ ፡ በወደቡ ፡ ላይ ፡ ይገኛል
2. ውኃ ፡ የለበሰ. A sunken rock struck the bottom of the boat. ውኃ ፡ የለበሰ ፡ ቋጥኝ ፡ የጀልባዋን ፡ ሥር ፡ ገጨ
3. (= noun) መጐድጐድ. The man's sunken eyes show that he had been starving. የዓይኖቹ ፡ መጐድጐድ ፡ የተራበ ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል

**sunlight** የፀሐይ ፡ ብርሃን
The sunlight makes the room more cheerful. የፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ክፍሉን ፡ የበለጠ ፡ ያሳምረዋል
[See also 'blare']

**sunny**
1. ፀሐያማ. It was a very sunny day. በጣም ፡ ፀሐያማ ፡ ቀን ፡ ነበር
2. ፀሐይ ፡ የሚገባው. This is a cheerful, sunny room. ይህ ፡ ፀሐይ ፡ የሚገባው ፡ አስደሳች ፡ ክፍል ፡ ነው
3. የፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ያረፈበት. The artist portrayed the sunny field in brilliant colors. የፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ያረፈበትን ፡ ሜዳ ፡ ሠዓሊው ፡ በብሩህ ፡ ቀለማት ፡ ሣለው

**have a sunny disposition**
Mary has a sunny disposition. ሜሪ ፡ ዘወትር ፡ ደስ ፡ የሚላት ፡ ልጅ ፡ ናት

**be sunny** ፀሐይ ፡ ገባው
The front rooms are sunny. ከፊት ፡ ለፊት ፡ ያሉት ፡ ክፍሎች ፡ ፀሐይ ፡ ይገባቸዋል

**sunrise** የፀሐይ ፡ መውጣት
Let's watch the sunrise! እስቲ ፡ የፀሐይን ፡ መውጣት ፡ እንይ

**at sunrise** ፀሐይ ፡ ስትወጣ
The traveler arrived at sunrise. መንገደኛው ፡ ፀሐይ ፡ ስትወጣ ፡ ደረሰ

**sunset** የፀሐይ ፡ ጥልቀት ፤ የጀንበር ፡ ጥልቀት
The glory of the sunset filled his heart with a feeling of awe. የፀሐይ ፡ (የጀንበር) ፡ ጥልቀት ፡ ውበት ፡ ልቡን ፡ ባድናቆት ፡ መላው
*With the approach of sunset, it became chilly. ፀሐይ ፡ ልትጠልቅ ፡ አቅራቢያ ፡ መቀዝቀዝ ፡ ጀመረ

**by sunset** ጀንበር ፡ ስትጠልቅ
By sunset, we were all home. ጀንበር ፡ ስትጠልቅ ፡ ሁላችንም ፡ እቤት ፡ ገብተናል

**sunshade** ጥላ
She was sitting under a sunshade. ጥላ ፡ ሥር ፡ ተቀምጣ ፡ ነበር

**sunshine**
1. የፀሐይ ፡ ብርሃን. Sunshine and the singing of the birds are pleasing. የፀሐይ ፡ ብርሃንና ፡ የወፎች ፡ ዝማሬ ፡ አስደሳች ፡ ናቸው
2. የፀሐይ ፡ ሙቀት. Sunshine is necessary for babies. የፀሐይ ፡ ሙቀት ፡ ለሕፃናት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
3. ጨረር. The sunshine was strong. ጨረሩ ፡ ኀይለኛ ፡ ነበር

**sunstroke** ምች
He suffered a sunstroke. ምች ፡ መቶታል

**sup** (supped) እራት ፡ በላ
They supped on roast beef and bread. ለራት ፡ የተጠበሰ ፡ ሥጋና ፡ ዳቦ ፡ በሉ

**superb** ግሩም
The meal was superb. ምግቡ ፡ በጣም ፡ ግሩም ፡ ነበር

**(be) supercilious** ተገበዘ
He is very supercilious because he thinks he is smarter than everybody. ከማንም ፡ ይበልጥ ፡ እሚያውቅ ፡ እየመሰለው ፡ ይገበዛል

**superficial**

1. ቀላል. On closer examination, the wound turned out to be superficial. በደንብ ፡ ሲመረመር ፡ ቁስሉ ፡ ቀላል ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

2. ያልበሰለ. His superficial mind is concerned only with cars. ያልበሰለ ፡ አእምሮው ፡ የሚያስበው ፡ ስለ ፡ መኪና ፡ ብቻ ፡ ነው

3. (= adv.) እንደነገሩ. Girls used to receive only a superficial education. ድሮ ፡ ሴቶች ፡ የሚያገኙት ፡ ትምህርት ፡ እንደነገሩ ፡ ነበር

4. (= adv.) ጥቂት. Father and son have only a superficial likeness. አባትና ፡ ልጁ ፡ ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ይመሳሰላሉ

*I got a superficial wound from the rifle shot. ጥይቱ ፡ ጨረፍ ፡ ነው ፡ ያደረገኝ

**(be) superfluous** ለጊዜው ፡ የሚያስፈልግ ፡ አልሆነም

These items are superfluous, and so we can leave them behind. እነዚህ ፡ እቃዎች ፡ ለጊዜው ፡ የሚያስፈልጉን ፡ ስላልሆኑ ፡ ልንተዋቸው ፡ እንችላለን

**superintendent** ተቈጣጣሪ

The superintendent of schools came to visit us today. የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ተቈጣጣሪ ፡ ዛሬ ፡ ሊጐበኘን ፡ መጣ

**superior** (n.)

1. የበላይ. Is he your superior? እሱ ፡ የበላይህ ፡ ነው ?

2. አለቃ. The cowardly soldier was censured by his superiors. ፈሪው ፡ ወታደር ፡ ባለቆቹ ፡ ተነቀፈ

**superior** (adj.)

1. የበላይ. Soldiers salute their superior officers. ወታደሮች ፡ ለበላይ ፡ መኰንኖች ፡ ሰላምታ ፡ ይሰጣሉ

2. የላቀ. He has a superior mind. በአእምሮው ፡ የላቀ ፡ ነው

3. ምርጥ. It's of superior quality. ዓይነቱ ፡ ምርጥ ፡ ነው

4. ኀይለኛ. We attacked the enemy with superior forces. ጠላትን ፡ ኀይለኛ ፡ ጦር ፡ ይዘን ፡ አጠቃነው

**superior attitude** እብሪተኛነት

John's superior attitude lost him friends. ጆን ፡ በእብሪተኛነቱ ፡ ብዙ ፡ ጓደኞች ፡ አጣ

**superior to**

A wise man is superior to flattery. ብልህ ፡ ሰው ፡ አይደለልም

**superiority**

1. የበላይነት ፡ ስሜት. We all resented his offensive superiority. መጥፎ ፡ የበላይነት ፡ ስሜቱን ፡ ሁላችንም ፡ ጠላነው

2. መብለጥ. No one doubts the superiority of modern ways of traveling over those of olden times. የዘመናዊ ፡ ጊዜ ፡ መጓጓዣ ፡ ዘዴዎች ፡ ከድሮው ፡ ጊዜ ፡ መብለጣቸውን ፡ ማንም ፡ አይጠራጠርም

3. ጥራት. We are proud of the superiority of our product. በምንሠራው ፡ እቃ ፡ ጥራት ፡ እንኰራለን

**racial superiority**

*Racial superiority is a myth. አንዱ ፡ ዘር ፡ ከሌላው ፡ ይበልጣል ፡ የሚሉት ፡ እምነት ፡ ዘበት ፡ ነው

**superlative** (n.) አበላላጭ ፡ ደረጃ

The superlative of the adjectives has no special form in Amharic. ባማርኛ ፡ የቅጽል ፡ አበላላጭ ፡ ደረጃ ፡ የተለየ ፡ መልክ ፡ የለውም

**superlative** (adj.) ከሁሉ ፡ የበለጠ

King Solomon had superlative wisdom. ንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ብልህነት ፡ ነበረው

*He is a man of superlative courage. ለጀግንነቱ ፡ ወደርም ፡ የለው

**superman** ላዕለ ፡ ሰብ

Children like to play superman. ልጆች ፡ ላዕለ ፡ ሰብ ፡ እየሆኑ ፡ መጫወት ፡ ይወዳሉ

**supernatural** ከሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ውጭ ፡ የሆነ

He believes in spirits and other supernatural beings. በአጋንንትና ፡ በሌሎች ፡ ከሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ውጭ ፡ በሆኑ ፡ መናፍስት ፡ ያምናል

**supersede**

1. ተካ. Mr. Brown superseded Mr. Smith as principal. ሚስተር ፡ ስሚዝ ፡ የዲሬክተርነትን ፡ ሥልጣን ፡ ሲለቁ ፡ ሚስተር ፡ ብራውን ፡ ተኳቸው

2. ገለበጠ. The judge superseded the previous sentence. ዳኛው ፡ የበፊቱን ፡ ፍርድ ፡ ገለበጠ

**superstition** አጉል ፡ እምነት

The superstition that the number 13 is unlucky is believed by many people. ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ገደ ፡ ቢስ ፡ ቁጥር ፡ ነው ፡ የሚባለውን ፡ አጉል ፡ እምነት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያምኑበታል

**superstitious** በአጉል ፡ እምነት ፡ የሚያመልክ

The superstitious woman was greatly frightened when the mirror broke. በአጉል ፡ እምነት ፡ የምታመልከው ፡ ሴት ፡ መስታወቱ ፡ ቢሰበር ፡ በጣም ፡ ደነገጠች

**superstitious belief** እጉል ፡ እምነት
A superstitious belief is that a black cat is a sign of misfortune. ጥቁር ፡ ድመት ፡ ያዲጋ ፡ ምልክት ፡ ናት ፡ ማለት ፡ እጉል ፡ እምነት ፡ ነው

**supervise** ተቈጣጠረ
The overseer supervises the workers carefully. ተቈጣጣሪው ፡ ሠራተኞችን ፡ በደንብ ፡ ይቈጣጠራቸዋል

**supervision** ተቈጣጣሪነት
The house was built under the supervision of an architect. ቤቱ ፡ የተሠራው ፡ በመሀንዲስ ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ ነው

**be under supervision** ተቈጣጠሩት
They are under constant supervision. ዘወትር ፡ እንደተቈጣጠሯቸው ፡ ነው

**supervisor** ተቈጣጣሪ
The supervisor is in conference right now. ተቈጣጣሪው ፡ አሁን ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ ነው

**supper** እራት
I have been invited for supper. እራት ፡ ተጋብዣለሁ

**go without supper** ጦሙን ፡ አደረ
The poor boy had to go without supper. ምስኪኑ ፡ ልጅ ፡ ጦሙን ፡ ማደር ፡ ነበረበት

**supplant**
1. በ --- ፈንታ ፡ ተተካ. Buses have supplanted trains in most cities. በብዙ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ በባቡር ፡ ፈንታ ፡ አውቶቡስ ፡ ተተክቷል
2. የ --- ቦታ ፡ ያዘ. The secretary plotted to supplant the director. ጸሐፊው ፡ የዲሬክተሩን ፡ ቦታ ፡ ለመያዝ ፡ አሴረ

**supple** ቀልጣፋ
Though he is old, he is supple as a child. ቢያረጅም ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ ቀልጣፋ ፡ ነው

**supplement** (v.)
1. አሟላ. He supplemented the evidence by producing the gun. ጠመንጃውን ፡ በማሳየት ፡ ማስረጃውን ፡ አሟላው
2. እንደ ፡ ተጨማሪ ፡ ሆኖ ፡ ሊያገለግል ፡ ቻለ. This book supplements the one you are using. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ አንተ ፡ ለምትጠቀምበት ፡ እንደ ፡ ተጨማሪ ፡ ሆኖ ፡ ሊያገለግል ፡ ይችላል

**supplement** (n.) ማሟያ
The supplement to the dictionary has just been published. የመዝገበ ፡ ቃላቱ ፡ ማሟያ ፡ አሁን ፡ ገና ፡ ታትሞ ፡ ወጣ

**supplementary** በተጨማሪ ፡ የሚያገለግል
We have some supplementary texts. በተጨማሪ ፡ የሚያገለግሉ ፡ የመማሪያ ፡ መጻሕፍት ፡ አሉን

**suppliant** የልመና
He sent a suppliant message for help. የልመና ፡ መልእክት ፡ላከ

**supplicant** በአንክሮ ፡ የሚጸልይ
She knelt as a supplicant at the altar. በመሠዊያው ፡ ፊት ፡ በአንክሮ ፡ እንደሚጸልይ ፡ ሁሉ ፡ ተንበረከከች

**supplicate** ለመነ
They supplicated him for mercy. ምሕረት ፡ እንዲያደርግላቸው ፡ ለመኑት

**supplication** ልመና
He was unmoved by tears and supplications. ለለቅሶና ፡ ለልመና ፡ ፍንክች ፡ አላለም

**supply** (supplied), v.
1. ሰጠ. The farmer supplied shelter for the travelers. ገበሬው ፡ ለመንገደኞቹ ፡ ማረፊያ ፡ ሰጠ
2. አቀረበ. We are prepared to supply the goods you asked for. የጠየቃችኋቸውን ፡ እቃዎች ፡ ለማቅረብ ፡ ዝግጁ ፡ ነን
3. ተካ. Insurance will supply the loss. ዋስትና ፡ የጠፋውን ፡ ይተካል
4. መገበ. The function of the school is to supply children with knowledge. የትምህርት ፡ ቤት ፡ ተግባር ፡ ልጆችን ፡ ዕውቀት ፡ መመገብ ፡ ነው
5. አረካ. The library cannot supply the demand for books. መጽሐፍ ፡ ቤቱ ፡ ለመጻሕፍት ፡ ያለውን ፡ ፍላጎት ፡ ሊያረካ ፡ አይችልም
*Our bakery supplies all the big hotels. ትልልቅ ፡ ሆቴሎች ፡ ዳቦ ፡ የሚገዙት ፡ ከኛ ፡ ዳቦ ፡ መጋገሪያ ፡ ቤት ፡ ነው

**supply** (supplies), n.
1. እቃ. The supplies were lost when the boat overturned. ጀልባው ፡ ሲገለበጥ ፡ እቃው ፡ ሁሉ ፡ ጠፋ
2. የቤት ፡ ቀለብ. Supplies are running low. የቤቱ ፡ ቀለብ ፡ ወደ ፡ ማለቁ ፡ ነው
3. ትጥቅና ፡ ሥንቅ. Who furnishes supplies to the army? ለሰራዊቱ ፡ ትጥቅና ፡ ሥንቅ ፡ የሚያቀርበው ፡ ማን ፡ ነው ?
*The supply of pencils ran out. እርሳስ ፡ አልቋል
*Our school gets its supplies of books, paper, pencils, etc. from the city. ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ የሚገለገልባቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ ወረቀት ፤ እርሳስ ፡ የመሳሰሉትን ፡ ነገሮች ፡ የሚገዛው ፡ ከከተማ ፡ ነው

**supply of** ለገበያ ፡ የሚቀርብ
The supply of cars was in excess of the demand.
ለገበያ ፡ የሚቀርቡት ፡ መኪናዎች ፡ ከሚፈለገው ፡
በላይ ፡ ነበር

**big supply of** ብዙ ፡ የሚሸጡ
We still have a big supply of bicycles. አሁንም ፡
ብዙ ፡ የሚሸጡ ፡ ቢስክሌቶች ፡ አሉን
[See also 'ample, bountiful, copious, food, generous, medical, plenteous, short']

## support (v.)

1. ደገፈ. I'll support your plan. ሐሳብህን ፡ እደ
ግፋለሁ
2. ደግፎ ፡ ያዘ. Walls support the roof. ጣሪያው
ን ፡ ደግፈው ፡ የሚይዙት ፡ ግድግዳዎቹ ፡ ናቸው
3. ጦረ. He has to support his parents because they are too old to work anymore. በእርጅና ፡
ምክንያት ፡ ራሳቸውን ፡ መርዳት ፡ ስለማይችሉ ፡
ወላጆቹን ፡ መጦር ፡ አለበት
4. ረዳ. He has committed himself to supporting his mother's children. የእናቱን ፡ ልጆች ፡ ለመርዳ
ት ፡ ቃል ፡ ገብቷል
5. አስተዳደረ. The widow supports her three children. ባሏ ፡ የሞተባት ፡ ሴትዮ ፡ ሦስት ፡ ል
ጆቿን ፡ ታስተዳድራለች
6. በገንዘብ ፡ ረዳ. The government supports the national theater. መንግሥት ፡ ብሔራዊውን ፡
ቲያትር ፡ በገንዘብ ፡ ይረዳል
7. አብራራ. He was using examples to support his argument. ክርክሩን ፡ ለማብራራት ፡ ምሳሌዎ
ች ፡ ይጠቅስ ፡ ነበር
8. አጽናና. Hope supports us in trouble.
ተስፋ ፡ በችግር ፡ ጊዜ ፡ ያጽናናል
*Is this bridge strong enough to support heavy trucks? ይህ ፡ ድልድይ ፡ ከባድ ፡ መኪና ፡ ሊያል
ፍበት ፡ ይችላል ?

**support oneself** ራሱን ፡ ቻለ
I have had to support myself ever since I was fifteen. ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመቴ ፡ ጀምሮ ፡
ራሴን ፡ መቻል ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ

**be supported** ተካሄደ
The hospital is supported by voluntary contributions. ሆስፒታሉ ፡ በበጎ ፡ ፈቃድ ፡ መዋጮ ፡
ይካሄዳል
[See also 'weight']

## support (n.) ድጋፍ

The project foundered because public support was lacking. የሕዝብ ፡ ድጋፍ ፡ ስላላገኘ ፡ እቅ
ዱ ፡ ሳይሳካ ፡ ቀረ
*You can count on my support. እንደምደግፍህ ፡
አትጠራጠር

**be a support of** ደገፈ
Your evidence is a support of my theory.
ያንተ ፡ ማስረጃ ፡ የኔን ፡ ፅንስ ፡ ሐሳብ ፡ ይደግ
ፋል

**in support of** የሚደግፍ
Can you offer any evidence in support of your statement? የተናገርከውን ፡ ነገር ፡ የሚደግፍ ፡
ማስረጃ ፡ ልትሰጥ ፡ ትችላለህ ?

## suppose

1. መሰለ(ው). What do you suppose he wants?
ምን ፡ የሚፈልግ ፡ ይመስልሃል ?
2. ገመተ. I suppose that the situation is much more serious than it looks. ሁኔታው ፡ እንደም
ናየው ፡ ሳይሆን ፡ የበለጠ ፡ አሳሳቢ ፡ ነው ፡ ብ
ዬ ፡ እገምታለሁ
3. እንዳለ ፡ አመለከተ. Creation supposes a creator. ፍጥረት ፡ መኖሩ ፡ ፈጣሪ ፡ እንዳለ ፡ ያ
መለክታል

**suppose (that)** ብ + imperfect + ስ
Suppose you wait till tomorrow. እስከ ፡ ነገ ፡
ብትቆይስ ?
Just suppose you are a minister. ሚኒስትር ፡ ብ
ትሆንስ ?

**suppose we say that** እንበል
Suppose we say that economic collapse is unavoidable. የኤኮኖሚ ፡ ውድቀት ፡ የማይቀር ፡
ነው ፡ እንበል

**let's suppose** እንበል
Let's suppose that I'm right. ልክ ፡ ነኝ ፡ እንበል

## supposed (adj.) የተባለ

The supposed beggar was really a rich man.
ለማኝ ፡ ነው ፡ የተባለው ፡ ሀብታም ፡ ነበር

**is supposed to**
1. አለ(በት). The servant is supposed to clean the windows. አሽከሩ ፡ መስኮቶቹን ፡ መወልወ
ል ፡ አለበት
2. ይባላል. He is supposed to be rich. ሀብታም ፡
ነው ፡ ይባላል
3. ተብሎ ፡ ይታመናል. The tabernacle is supposed to be in the church of Axum. ጽላተ ፡ ሙ
ሴ ፡ አክሱም ፡ ውስጥ ፡ አለ ፡ ተብሎ ፡ ይታመናል

**is not supposed to** አይገባ(ውም)
+We are not supposed to play football on Monday. በሰኞ ፡ እግር ፡ ኳስ ፡ መጫወት ፡ አይገ
ባንም ፡ ነበር

## supposing ለምሳሌ ፡ ብ + imperfect

Supposing it rains, what will you do? ለምሳሌ ፡
ቢዘንብ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ ?

**supposition**

1. ምናልባት. This newspaper article is based on supposition, not on fact. ጋዜጣው ፡ ላይ ፡ የወጣው ፡ ጽሑፍ ፡ በእውነት ፡ ሳይሆን ፡ በምናልባት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው
2. የይምሰል ፤ የይሆናል. His whole explanation is only supposition. ሐተታው ፡ ሁሉ ፡ የይምሰል ፡ (የይሆናል) ፡ ነው

**suppress**

1. ደመሰሰ. The Chicago police suppressed the student riot. የቺካጎ ፡ ፖሊሶች ፡ የተማሪዎችን ፡ ረብሻ ፡ ደመሰሱ
2. አገደ. Each nation suppresses news that is not favorable to it. እያንዳንዱ ፡ አገር ፡ እሱን ፡ የሚቃወመውን ፡ ወሬ ፡ ያግዳል
3. እንዳይወጣ ፡ አገደ. The censors suppressed the essay. የሳንሱር ፡ ሠራተኞች ፡ ድርሰቱን ፡ እንዳይወጣ ፡ አገዱ
4. አፍኖ ፡ ያዘ. He suppressed a smile. ፈገግታውን ፡ አፍኖ ፡ ያዘ
5. አምቆ ፡ ያዘ. He suppresses his true feelings. እውነተኛ ፡ ስሜቱን ፡ አምቆ ፡ ይይዘዋል

**suppress by force** ጨቍኖ ፡ ያዘ
They suppressed the heresy by force. መናፍቃኑን ፡ ጨቍነው ፡ ያዟቸው

**be suppressed** ቀረ
The slave trade has been suppressed. የባሪያ ፡ ንግድ ፡ ቀርቷል

**suppression** መሸፈን
The suppression of facts is as harmful as the telling of lies. እውነትን ፡ መሸፈን ፡ የመዋሸትን ፡ ያህል ፡ ጐጂ ፡ ነው
*The suppression of the rebellion was followed by military rule. ዐመፁ ፡ ከተደመሰሰ ፡ በኋላ ፡ ሥልጣኑን ፡ ወታደር ፡ ያዘው

**suppurate** መገለ
The wound is still suppurating. ቁስሉ ፡ አሁንም ፡ ይመግላል

**supremacy** ይበልጣል ፡ የሚለው ፡ ሐሳብ
He won't acknowledge the supremacy of one nation over another. አንዱን ፡ ሕዝብ ፡ ከሌላው ፡ ይበልጣል ፡ የሚለውን ፡ ሐሳብ ፡ አይቀበልም

**supreme**

1. ከፍተኛ. Supreme authority resides with the President. ከፍተኛው ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ በፕሬዚዳንቱ ፡ እጅ ፡ ነው
2. ታላቅ. He won by a supreme effort. በታላቅ ፡ ጥረት ፡ አሸነፈ

**Supreme Being**
God is the Supreme Being. እግዚአብሔር ፡ ከፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ነው

**Supreme Court** ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት
He took the case to the Supreme Court. ነገሩን ፡ ለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ አለ

**surcharge** ተጨማሪ ፡ ዋጋ
The company made a surcharge for delivering the trunk outside the city limits. ኩባንያው ፡ ጭነቱን ፡ ከከተማ ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ ለማድረስ ፡ ተጨማሪ ፡ ዋጋ ፡ ይጠይቃል

**sure** (adj.)

1. የሚታመን. You can trust him; he is a sure messenger. ልታምነው ፡ ትችላለህ ፤ የሚታመን ፡ መልእክተኛ ፡ ነው
2. ታማኝ. A sure friend will not desert you when you are in straits. ታማኝ ፡ ጓደኛ ፡ ስትቸገር ፡ አይከዳህም
3. እርግጠኛ. He is sure to be back by nine o'clock. እስከ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ እንደሚመለስ ፡ እርግጠኛ ፡ ነው
4. የማያጠራጥር. The army moved on to a sure victory. ጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ ወደማያጠራጥር ፡ ድል ፡ አመራ
5. የተፈተነ. There is no sure remedy for cancer. ለካንሰር ፡ የተፈተነ ፡ መድኃኒት ፡ የለም
6. የተጨበጠ. I stand on sure ground when I speak about economics. ስለ ፡ ሀብት ፡ ምጣኔ ፡ ስናገር ፡ የተጨበጠ ፡ ነገር ፡ ይዤ ፡ ነው

**sure** (adv.)

1. ሙት. Sure, I'll do it. ሙት ! አደርገዋለሁ
2. በጣም. I'd sure like to see him. እሱን ፡ ለማየት ፡ በጣም ፡ ጓጒቻለሁ

**and sure enough** እውነትም
You thought it would rain, and sure enough it did. ይዘንባል ፡ ብለህ ፡ ነበር ፤ እውነትም ፡ ዘነበ

**as sure as**
*As sure as my name is John, she will fail to come on time. እሷ ፡ ባትዘገይ ፡ እኔ ፡ ዮሐንስ ፡ አይደለሁም

**be sure to** እንድ + imperfect
Be sure to come to see me tomorrow! ነገ ፡ መጥተህ ፡ እንድታነጋግረኝ
Be sure to write and give me all the news! እንግዲህ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ እንድትጽፍልኝ

Be sure not to forget your umbrella! ጃንጥላህን ፡ እንዳትረሳ ፡ ይሁን

**for sure**

1. በእርግጥ. I know it for sure. በእርግጥ ፡ አውቀዋለሁ

2. verbal noun + አለበት. Be there by five o'clock for sure! በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ እዚያ ፡ መገኘት ፡ አለብህ

**make sure**

1. ልብ ፡ አደረገ. Make sure that it doesn't happen again! እንደገና ፡ እንዳይደገም ፡ ልብ ፡ አድርግ

2. አረጋገጠ. I just wanted to make sure that everything was all right. ሁሉም ፡ ነገር ፡ ደኅና ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ነው

Make sure that the windows are closed! መስኮቶቹ ፡ መዘጋታቸውን ፡ አረጋግጥ

*Make sure you have your coat when you leave! ስትሄድ ፡ ኮትህን ፡ እንዳትረሳ

**to be sure**

*It's done to be sure; but how is it done? መሠራቱን ፡ ተሠርቷል ፤ ግን ፡ እንዴት ፡ ተሠራ ?

## surefooted

The mule is surefooted. በቅሎ ፡ አያዳልጣትም

## surely

1. በርእግጥ. He can surely do that. ያንን ፡ በእርግጥ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል

2. እንዴታ. Will you be there? Surely. እዚያ ፡ ትገኛለህ ? እንዴታ

3. በጥንቃቄ. He was working slowly but surely. ቀስ ፡ እያለ ፡ በጥንቃቄ ፡ ይሠራ ፡ ነበር

4. እንደልቡ. The goat leaped surely from rock to rock. ፍየሏ ፡ እንደልቧ ፡ ከቋጥኝ ፡ ወደ ፡ ቋጥኝ ፡ ዘለለች

*I surely thought it would be done. ሥራው ፡ ይከናወናል ፡ ብዬ ፡ ነበር

## surety (sureties)

1. ዋስ. He had to give surety that he would appear at the trial. ፍርድ ፡ ቤት ፡ እቀርባለሁ ፡ ብሎ ፡ ዋስ ፡ መጥራት ፡ ነበረበት

2. ዋስትና. The judge fixed his surety at $50. ዳኛው ፡ ለዋስትና ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ እንዲያሲዝ ፡ወሰነ

3. እርዳታ. The government gave the farmers surety for their crops. መንግሥት ፡ ገበሬዎቹ ፡ ለጠፋባቸው ፡ ሰብል ፡ እርዳታ ፡ ሰጠ

## surf ማዕበል

The surf is very high today. ማዕበሉ ፡ ዛሬ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ብሏል

## surface (vt.)

1. አለበሰ. They surfaced the road with gravel. መንገዱን ፡ ጠጠር ፡ አለበሱት

2. አነጠፈ(በት). They surfaced the road with asphalt. መንገዱን ፡ አስፋልት ፡ አነጠፉበት

**surface** (vi.) ከውኃው ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ አለ

He surfaced to get a breath of air. ለመተንፈስ ፡ ከውኃው ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ አለ

## surface (n.)

1. ገጽ. The surface of the moon is desolate. የጨረቃ ፡ ገጽ ፡ በዳ ፡ ነው

2. ውጭ. You can't tell what is inside something by looking at its surface. ያንድን ፡ ነገር ፡ ውጭውን ፡ ብቻ ፡ በማየት ፡ ውስጡ ፡ ምን ፡ እንዳለ ፡ ለማወቅ ፡ አይቻልም

3. ላይ ፡ ላዩን. The lecturer merely scratched the surface of the subject. ተናጋሪው ፡ አርእስቱ ፡ ነገሩን ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ነካክቶ ፡ አለፈ

4. ክፍል. The surface of the earth is largely covered by water. የመሬት ፡ ብዙው ፡ ክፍል ፡ በውኃ ፡ የተሸፈነ ፡ ነው

5. ስፍራ. The lines intersect on a plane surface. መሥመሮቹ ፡ በዝርግ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ይተላለፋሉ

*A breeze troubled the surface of the lake. ነፋሱ ፡ ሐይቁን ፡ አናወጸው

*Glass has a smooth surface. መስታወት ፡ ለስላሳ ፡ ነገር ፡ ነው

**on the surface**

1. ከንገት ፡ በላይ. She is all smiles on the surface, but angry within. ከንገት ፡ በላይ ፡ ትሥቃለች ፡ እንጂ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ነዳለች

2. ላይ ፡ ላዩን. His faults are all on the surface. ጉድፈቱ ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ነው

**to the surface**

*The submarine rose to the surface. ሰርጓጇ ፡ መርከብ ፡ ከውኃው ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ አለች

[See also 'scrape']

## surfeit, ~ of ከመጠን ፡ በላይ

A surfeit of food makes one sick. ከመጠን ፡ በላይ ፡ ምግብ ፡ መብላት ፡ሆድ ፡ ያሳምማል

## surge (v.)

1. እየተጋፋ ፡ ገባ. The crowd surged through the gates. ሕዝቡ ፡ በበሩ ፡ እየተጋፋ ፡ ገባ

2. ወረደ. The water surged through the canal. ውኃው ፡ በቦዩ ፡ ውስጥ ፡ ወረደ

## surge (n.) መጕረፍ

A surge of immigrants to America increased

the population tremendously. የስደተኞች ፡ መ ጉረፍ ፡ ያሜሪካንን ፡ የሕዝብ ፡ ቁጥር ፡ አበዛው
*A surge of anger rushed over him. በንዴት ፡ እንፋሎት ፡ ተዋጠ

**surgeon** ቀዳጅ ፡ ሐኪም ፤ ቀዶ ፡ ጠጋኝ ፡ ሐኪም
The surgeon's instruments must be clean. የቀዳጅ ፡ ሐኪም ፡ (የቀዶ ፡ ጠጋኝ ፡ ሐኪም) ፡ መ ሣሪያዎች ፡ ንጹሕ ፡ መሆን ፡ አለባቸው

**surgery** ቀዶ ፡ ጥገና ፤ ኦፔራሲዮን
Organic diseases can rarely be cured by surgery. የአካል ፡ ውስጥ ፡ በሽታዎች ፡ በቀዶ ፡ ጥገና ፡ (በኦፔራሲዮን) ፡ የሚድኑት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነው

**surly** ግልፍተኛ
The surly boy ignored our greeting. ግልፍተኛው ፡ ልጅ ፡ ሰላምታችንን ፡ ችላ ፡ አለው

**surmise** ጠረጠረ
He surmised that her absence was due to illness. የቀረችው ፡ ታማ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ጠረጠረ

**surmount**
1. ተወጣ. He was unable to surmount the obstacles in his way. ያጋጠሙትን ፡ ዕንቅፋቶች ፡ ሁሉ ፡ መወጣት ፡ አልቻለም
2. በከፍታ ፡ በለጠ. This mountain surmounts all peaks near it. ይህ ፡ ተራራ ፡ በከፍታ ፡ አጠገቡ ፡ ካሉት ፡ ኰረብታዎች ፡ ይበልጣል
3. ከ -- ከፍ ፡ ብሎ ፡ ተገኘ. The mountain surmounts the village. ተራራው ፡ ከመንደሩ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ይገኛል
4. ደፋ. A crown surmounted his head. ራሱ ፡ ላይ ፡ ዘውድ ፡ ደፍቷል

**surname** የመጨረሻ ፡ ስም
Smith is a common English surname. ስሚዝ ፡ በ ጣም ፡ የተለመደ ፡ የእንግሊዝ ፡ የመጨረሻ ፡ ስም ፡ ነው

**surpass** በለጠ
He surpasses his classmates in strength and skill. በጥንካሬና ፡ በችሎታ ፡ ከክፍል ፡ ጓደኞቹ ፡ ይበልጣል
The results surpassed my highest hopes. ውጤቱ ፡ ተስፋ ፡ ካደረግሁት ፡ በጣም ፡ ይበልጣል
*The glory of heaven surpasses description. የሰማይን ፡ ታላቅነት ፡ ለመግለጽ ፡ ቃል ፡ አይ ገኝለትም

**surplus**
1. ትርፍ ፡ እቃ. He was left with a large surplus. ብዙ ፡ ትርፍ ፡ እቃ ፡ በእጁ ፡ ላይ ፡ ቀርቶ ፡ ነበር
2. የተረፈ. She made drapes with the cloth and used the surplus to cover a pillow. ከጨር ቁ ፡ መጋረጃ ፡ ሠርታ ፡ የተረፈውን ፡ ለትራስ ፡ ልብስ ፡ አደረገችው
3. ከተፈለገው ፡ በላይ. Ethiopia had a large surplus of coffee last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከተፈለገው ፡ በላይ ፡ ቡና ፡ አምር ታ ፡ ነበር

**surprise** (vt.)
1. አስደነቀ. Nothing surprises me any more. ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አያስደንቀኝም
2. ሳይነግረው ፡ አስደነገጠው. I wanted to surprise you by buying the book you wanted. የፈለግኸውን ፡ መጽሐፍ ፡ ሳልነግርህ ፡ ገዝቼ ፡ ላስደንግጥህ ፡ ፈለግሁ
3. ደረሰ(በት). He surprised the burglar in the act of entering his house. ሰርሳሪ ፡ ሌባ ፡ ቤቱ ን ፡ ሰብሮ ፡ ሲገባ ፡ ደረሰበት

**be surprised**
1. አስገረመ. +I was very much surprised that he came. መምጣቱ ፡ በጣም ፡ አስገረመኝ
2. ገረመ(ው). +You'll be surprised to see how he's changed. እንዴት ፡ እንደተለወጠ ፡ ብታይ ፡ ይ ገርምሃል
3. ተደነቀ. I shouldn't be surprised if it rains this afternoon. ዛሬ ፡ ከቀትር ፡ በኋላ ፡ ቢዘን ብ ፡ አልደነቅም

**surprise** (n.)
1. ያላሰበው ፡ ነገር. I have a surprise for you. Here is the book that you always wanted. ያላሰብከውን ፡ ነገር ፡ አመጣሁልህ ፤ ሁልጊዜ ፡ የምትፈልገው ፡ መጽሐፍ ፡ ይኸውልህ
2. ያልታሰበ ፡ አስደሳች ፡ ነገር. Mother always has a surprise for the children on holidays. እናታችን ፡ በበዓል ፡ ቀናት ፡ ሁልጊዜ ፡ ለልጆቹ ፡ ያልታሰበ ፡ አስደሳች ፡ ነገር ፡ ታደርግላቸዋለች
3. የመደነቅ ፡ ስሜት. His face registered surprise. ፊቱ ፡ ላይ ፡ የመደነቅ ፡ ስሜት ፡ ይነበብ ፡ ነበር

**by surprise** ድንገት ፤ በድንገት
The news took them by surprise. ወሬውን ፡ የ ሰሙት ፡ ድንገት ፡ ነበር
The rain caught me by surprise. ዝናቡ ፡ በድን ገት ፡ ያዘኝ

**cause surprise** አስገረመ
Mention of the incident caused surprise. ነገሩን ፡ ማንሣቱ ፡ አስገረመኝ

**make jump with surprise** አስበረገገ
The knock on the door made us all jump with surprise. የመዝጊያው ፡ መንኳኳት ፡ አስበረገገን

**take by surprise** አስደነበረ
The onset of the enemy took us by surprise. የጠላት ፡ ማጥቃት ፡ አስደነበረን

**to my surprise** ይግረምህ ፡ ብሎ
To my surprise, the boy took my car. ይግረምህ ፡ ብሎ ፡ ልጁ ፡ መኪናዬን ፡ ይዞ ፡ ጠፋ

**with surprise** ደንግጦ
He was stunned with surprise when he found a $100 bill in the street. መቶ ፡ ብር ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ደንግጦ ፡ ፈዘዘ

**surprising** የሚደንቅ
The dissimilarity of the two brothers' characters is surprising. የሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ ጠባይ ፡ አለመመሳሰል ፡ የሚደንቅ ፡ ነው

**surprisingly** (= adj.) የሚያስገርም ፤ የሚያስደንቅ
It was surprisingly light for something so large. ይህን ፡ የሚያክል ፡ ነገር ፡ ይችን ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ መክበዱ ፡ በጣም ፡ የሚያስገርም ፡ ነው
He was surprisingly good, for one who studies so little. እንደሱ ፡ ብዙ ፡ ላላጠና ፡ ሰው ፤ ያገኘው ፡ ውጤት ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው

**surrender** (vt.)
1. አስረከበ. The prisoners surrendered their arms. ምርኮኞቹ ፡ ጠመንጃቸውን ፡ አስረከቡ
2. አሳልፎ ፡ ሰጠ. We shall never surrender our liberty. ነጻነታችንን ፡ ከቶ ፡ አሳልፈን ፡ አንሰጥም

**surrender** (vi.) እጁን ፡ ሰጠ
The enemy surrendered. ጠላት ፡ እጁን ፡ ሰጠ

**surrender hope** ተስፋ ፡ ቈረጠ
She never surrendered hope that her son would return. ስለ ፡ ልጇ ፡ መመለስ ፡ ተስፋ ፡ ቈርጣ ፡ አታውቅም

**surrender oneself** ተዋጠ
He surrendered himself to bitter grief. በመሪር ፡ ሐዘን ፡ ተዋጠ
[See also 'despair']

**surrender** (n.) እጅ ፡ መስጠት
The surrender of the soldiers saved them from being killed. ወታደሮቹ ፡ እጃቸውን ፡ መስጠታቸው ፡ ከመሞት ፡ አዳናቸው

**surreptitious** ስውር
The plotters held surreptitious meetings in a hotel. ሴረኞቹ ፡ በሆቴሉ ፡ ውስጥ ፡ ስውር ፡ ስብሰባ ፡ አደረጉ

**surreptitious action** ሹክክ ፡ ማለት
His surreptitious actions aroused the suspicion of the police. ሹክክ ፡ ማለቱ ፡ ፖሊሶቹን ፡ አጠራጠራቸው

**surreptitiously** በስውር
The offer to buy the house was made surreptitiously. ቤቱን ፡ ለመግዛት ፡ የቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ በስውር ፡ ነበር

**surrogate** ምትክ
We need to find a surrogate for the functions performed by the landowners. ባለ ፡ መሬቶች ፡ ለሚፈጽሟቸው ፡ ተግባሮች ፡ ምትክ ፡ መፈለግ ፡ አለብን

**surround**
1. ከበበ. The army surrounded the fort. ጦሩ ፡ ምሽጉን ፡ ከበበ
2. በ --- ዙሪያ ፡ ነበረ. A battery of microphones surrounded the mayor. በከንቲባው ፡ ዙሪያ ፡ ብዙ ፡ የድምፅ ፡ ማጉልያ ፡ ነበር
*A high fence surrounds the tennis court. የቴኒሱ ፡ ሜዳ ፡ ዙሪያውን ፡ በረጅም ፡ አጥር ፡ ታጥሯል

**surrounding** ባካባቢ ፡ ያለ
The new building will not match the surrounding architecture. አዲሱ ፡ ሕንጻ ፡ ባካባቢው ፡ ካሉት ፡ ጋር ፡ አይስማማም

**surroundings**
1. አካባቢ. The surroundings of the city attracted many visitors. የከተማው ፡ አካባቢዎች ፡ ብዙ ፡ ጐብኚዎችን ፡ ሳቡ
2. መኖሪያ. You don't see animals in their natural surroundings at a zoo. በእንስሳት ፡ መኖሪያ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ ለእንስሳቱ ፡ እንደ ፡ ተፈጥሮ ፡ መኖሪያቸው ፡ አይደለም
3. በዙሪያው ፡ ያለ ፡ ሁሉ. The book was so interesting that I was oblivious of my surroundings. መጽሐፉ ፡ በጣም ፡ አስደሳች ፡ ስለነበረ ፡ በዙሪያዬ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ረስቼ ፡ ነበር

**surveillance** መቈጣጠር
Surveillance of foreign agents is the task of the police. የውጭ ፡ አገር ፡ ሰላዮችን ፡ መቈጣጠር ፡ የፖሊስ ፡ ተግባር ፡ ነው

**keep under surveillance** ተከታተለ
The police are keeping him under surveillance. ፖሊሶች ፡ ይከታተሉታል

**survey** (v.)
1. ጠቃቀሰ. In his speech, the prime minister surveyed the international situation. በንግግራቸው ፡ ላይ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የዓለምን ፡ ሁኔታ ፡ ጠቃቀሱ

2. አጠና. The government is surveying the area which it needs for a base. መንግሥቱ ፡ ለጦር ፡ ሰፈር ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ቀበሌ ፡ በማጥናት ፡ ላይ ፡ ነው

3. ቀየሰ. Engineers are surveying the land before it is divided into lots. መሬቱ ፡ ከመሸንሸኑ ፡ በፊት ፡ መሀንዲሶች ፡ ይቀይሱታል

4. ባይኑ ፡ ቃኘ. He surveyed the countryside from the hilltop. ኰረብታው ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ባላገሩን ፡ ባይኑ ፡ ቃኘው

5. ተመለካከተ. The buyers surveyed the goods offered for sale. ገዢዎቹ ፡ ለሽያጭ ፡ የቀረበውን ፡ እቃ ፡ ተመለካከቱ

**survey** (n.)

1. ጥናት. The survey of the situation received little criticism. ስለ ፡ ሁኔታው ፡ የተደረገው ፡ ጥናት ፡ ብዙ ፡ ትችት ፡ አልደረሰበትም

2. አጭር ፡ አጠቃላይ ፡ ጥናት. The survey of East Africa was published in the newspaper. ስለ ፡ ምሥራቅ ፡ አፍሪካ ፡ የተደረገ ፡ አጭር ፡ አጠቃላይ ፡ ጥናት ፡ በጋዜጣ ፡ ወጥቶ ፡ ነበር

3. ቅየሳ. A survey showed that the northern boundary was not correct. ቅየሳው ፡ የሰሜኑ ፡ ድንበር ፡ ትክክለኛ ፡ አለመሆኑን ፡ አመለከተ

*We were pleased with our first survey of the house. ቤቱን ፡ መጀመሪያ ፡ ተመልክተነው ፡ ተደስተናል

**surveyor** ቀያሽ

The surveyor set up his instruments and began to make a survey of the land. ቀያሹ ፡ መሣሪያዎቹን ፡ ተክሎ ፡ መሬቱን ፡ መቀየስ ፡ ጀመረ

**survival**

1. መትረፍ. The survival of the strongest benefits the race. ከሁሉም ፡ ብርቱ ፡ የሆነው ፡ መትረፍ ፡ ለዘር ፡ ጠቃሚ ፡ ነው

2. ርዝራዥ. Belief in the evil eye is a survival of ancient magic. በቡዳ ፡ ማመን ፡ የጥንት ፡ አስማት ፡ ርዝራዥ ፡ ነው

**survival of life** ሕይወት

Some religions believe in the survival of life after death. አንዳንድ ፡ ሃይማኖቶች ፡ ከሞት ፡ በኋላ ፡ ሕይወት ፡ አለ ፡ ይላሉ

**survive**

1. ከ -- ተረፈ ፤ ዳነ ፤ ከ -- ዳነ. He survived the earthquake. ከመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ አደጋ ፡ ተረፈ

His self-reliance enabled him to survive when he was lost in the desert. በራሱ ፡ ሐሳብ ፡ የመመካት ፡ ችሎታው ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በጠፋ ፡ ጊዜ ፡ እንዲድን ፡ ረዳው

He counted himself lucky to have survived the crash. ካደጋው ፡ ስለዳነ ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ ዕድለኛ ፡ ቈጠረ

2. ዛሬም ፡ አለ. Books have survived from the time of the ancient Greeks. በጥንታውያን ፡ ግሪኮች ፡ ጊዜ ፡ የነበሩ ፡ መጻሕፍት ፡ ዛሬም ፡ አሉ

*She survived all her children. ልጆቿ ፡ ሁሉ ፡ ሲያልቁ ፡ እሷ ፡ ቀረች

**not survive the night** ሌሊቱን ፡ አያድርም

He is failing fast and may not survive the night. በጣም ፡ ስለተዳከመ ፡ ሌሊቱን ፡ አያድርም

**survivor**

1. የተረፈ. He was the lone survivor of the accident. ካደጋው ፡ የተረፈው ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ነበር

2. ከሞት ፡ የተረፈ. Hunger emaciated the survivors. ከሞት ፡ የተረፉትን ፡ ረኀብ ፡ አመንምኗቸዋል

**susceptibility** (susceptibilities)

*We must avoid offending their susceptibilities. የሚያስቈጣቸውን ፡ ነገር ፡ እንዳናደርግ ፡ መጠንቀቅ ፡ አለብን

**susceptible** ሆደ ፡ ባሻ

He is a susceptible child and cries for the slightest thing. ሆደ ፡ ባሻ ፡ ስለሆነ ፡ በትንሹም ፡ ነገር ፡ እንባ ፡ ይቀድመዋል

**be susceptible to**

He is susceptible to flattery. በከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ይደለላል

*She is susceptible to colds. ጉንፋን ፡ ያጠቃታል

**be susceptible of** ቻለ

Marble is susceptible of a high polish. እብነ ፡ በረድ ፡ እስኪያንጸባርቅ ፡ ድረስ ፡ ለመወልወል ፡ ይችላል

The poem is susceptible of several interpretations. ግጥሙ ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ሊተረጐም ፡ ይችላል

**make susceptible** አሳልፎ ፡ ሰጠው

A constitutional weakness makes him susceptible to colds. የሰውነቱ ፡ ደካማነት ፡ ለብርድ ፡ በሽታ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጠዋል

**suspect** (v.)

1. ጠረጠረ ፤ ተጠራጠረ. The police suspected the servant of murder. ፖሊሶቹ ፡ አሽከሩን ፡ በነፍስ ፡ ግዳይ ፡ ጠረጠሩት

I suspect his honesty. ሐቀኝነቱን ፡ እጠራጠራለሁ
2. ገመተ. She has more intelligence than we suspected she had. ከገመትነው ፡ በላይ ፡ ብል ሀ ፡ ናት
*I suspect you are correct. ትክክለኛ ፡ ትመስለ ኛለህ

**suspect** (n.) የተጠረጠረ ፡ ሰው ፤ ተጠርጣሪ ፡ ሰው
The police arrested many suspects, but failed to find the guilty person. ፖሊሶቹ ፡ ብዙ ፡ የተ ጠረጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ያዙ ፤ ጥፋተኛውን ፡ ግን ፡ ሊ ያገኙት ፡ አልቻሉም
The police tailed the suspect. ፖሊስ ፡ ተጠርጣ ሪውን ፡ ሰው ፡ ተከታተለው

**suspend**
1. አንጠለጠለ. He suspended the lamp from a hook. ፋኖሱን ፡ ከመንጠቆ ፡ ላይ ፡ አንጠለጠለው
2. አዘገየ. We shall suspend judgment until we have all the facts. ጉዳዩን ፡ እስከናጣራ ፡ ፍ ርዱን ፡ እናዘገየዋለን
3. ለጊዜው ፡ አቆመ. The bank has suspended all payments. ባንኩ ፡ ገንዘብ ፡ መስጠቱን ፡ ለጊዜው ፡ አቁሟል

**be suspended** ለጊዜው ፡ ታገደ
He was suspended from school for misbehaving. መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ ስላሳየ ፡ ከትምህ ርት ፡ ቤት ፡ ለጊዜው ፡ ታግዷል

**suspenders** ማንገቻ
He used suspenders to hold up his trousers. ሱሪውን ፡ በማንገቻ ፡ ይታጠቃል

**suspense**
*I can't stand the suspense any longer; tell me how the story ended. ልቤ ፡ ተሰቀለ ፤ የታሪ ኩን ፡ መጨረሻ ፡ ቶሎ ፡ ንገረኝ

**in suspense** ተጨንቆ
We waited in suspense for the doctor's opinion. ሐኪሙ ፡ የሚለውን ፡ ለመስማት ፡ ተጨንቀን ፡ ተጠባበቅን

**suspension**
1. ለጊዜው ፡ መወገድ. The suspension of the two students was right. የሁለቱ ፡ ተማሪዎች ፡ ከት ምህርት ፡ ቤት ፡ ለጊዜው ፡ መወገድ ፡ ትክክለ ኛ ፡ ነገር ፡ ነበር
2. መታገድ. His suspension from the police force was announced in the paper. ከፖሊስ ፡ ሰ ራዊት ፡ መታገዱ ፡ በጋዜጣ ፡ ተገለጸ

**suspension bridge** ተንቀሳቃሽ ፡ ድልድይ
A suspension bridge will be built. ተንቀሳቃሽ ፡ ድልድይ ፡ ይሠራል

**suspicion**
1. ጥርጣሬ. What aroused your suspicion? ጥርጣ ሬ ፡ ያሳደረብህ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
2. የጥርጣሬ ፡ ዓይን. The hag looked at him with suspicion. አስቀያሚዋ ፡ አሮጊት ፡ በጥር ጣሬ ፡ ዓይን ፡ ተመለከተችው
*She prepared the salad with just a suspicion of garlic. ሰላጣውን ፡ ነጭ ፡ ሽንኩርት ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ አደረገችበት

**arouse suspicion** አጠራጠረ ፤ ጥርጣሬ ፡ አሳደረ (በት)
His surreptitious actions aroused the suspicion of the police. ሹክክ ፡ ማለቱ ፡ ፖሊሶቹን ፡ አጠ ራጠራቸው ፡ (በፖሊሶች ፡ ጥርጣሬ ፡ አሳደረባቸው)

**be above suspicion** እንከን ፡ የለውም
Her conduct is above suspicion. ምግባሯ ፡ እን ከን ፡ የለውም

**have a suspicion** ጠረጠረ
He had a suspicion that he was being followed. ሰው ፡ እንደሚከታተለው ፡ ጠርጥሮ ፡ ነበር

**on suspicion of** ተጠርጥሮ
He was arrested on suspicion of murder. በነፍሰ ፡ ገዳይነት ፡ ተጠርጥሮ ፡ ተያዘ
[See also 'sneaking']

**suspicious**
1. ተጠራጣሪ. Is it human to be quarrelsome and suspicious? ጠበኛና ፡ ተጠራጣሪ ፡ መሆ ን ፡ የሰው ፡ ተፈጥሮ ፡ ነው ?
2. አጠራጣሪ. That looks suspicious to me. ያ ፡ አጠራጣሪ ፡ ይመስለኛል
3. የሚያጠራጥር. A man is hanging about the house in a suspicious manner. አንድ ፡ ሰው ፡ በቤቱ ፡ አካባቢ ፡ በሚያጠራጥር ፡ ሁኔታ ፡ ወዲ ያ ፡ ወዲህ ፡ ይላል

**make suspicious** ጥርጣሬ ፡ አሳደረበት
His mysterious behavior made the police suspicious. እንግዳ ፡ የሆነው ፡ ጠባዩ ፡ ፖሊሶ ቹን ፡ ጥርጣሬ ፡ አሳደረባቸው

**sustain**
1. ደገፈ. His diet won't sustain life very long. የሚመገበው ፡ ምግብ ፡ ሕይወትን ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚደግፍ ፡ አይደለም
The facts sustain his theory. ማስረጃው ፡ የሱን ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳብ ፡ ይደግፈዋል
2. መጽናኛ ፡ ሆነ. Hope sustained him in his misery. በመከራ ፡ ጊዜ ፡ ተስፋ ፡ መጽናኛ ፡ ሆ ነው
3. አምኖ ፡ ተቀበለ. The court sustained his claim. ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክሱን ፡ አምኖ ፡ ተቀበለው

4. ተሸከመ. The shelf could not sustain the weight of the books. መደርደሪያው ፡ መጽሐፎቹን ፡ መሸከም ፡ አይችልም
5. ደረሰ(በት). He sustained injuries in the accident. ባደጋው ፡ ጊዜ ፡ ጉዳት ፡ ደረሰበት

**sustained**, adj. (= adv.) ያለማቋረጥ
He made a sustained effort to catch up with me. ሊደርስብኝ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ጣረ

**sustenance**
1. ምግብ. He has gone for a week without sustenance. ያለ ፡ ምግብ ፡ ላንድ ፡ ሳምንት ፡ ቆየ
2. (= verbal noun) መርጃ. He gave money for the sustenance of a poor family. ድኾች ፡ ቤተሰቦችን ፡ ለመርጃ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጠ
3. የመንፈስ ፡ ጽናት. They find sustenance in praying to God. ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመጸለይ ፡ የመንፈስ ፡ ጽናት ፡ ያገኛሉ
*Fish is their only sustenance. የሚኖሩት ፡ ዓሣ ፡ ብቻ ፡ እየበሉ ፡ ነው
*There isn't much sustenance in a cucumber. የፈረንጅ ፡ ዱባ ፡ መብላት ፡ ለሕይወት ፡ ብዙ ፡ አይረዳም

**svelte** ስልክክ ፡ ያለ
This woman is very svelte. ይህች ፡ ሴት ፡ ስልክክ ፡ ያለች ፡ ናት

**swaddle** በጨርቅ ፡ ጠቀለለ
Formerly, they swaddled babies. ድሮ ፡ ሕፃናትን ፡ በጨርቅ ፡ ይጠቀልሏቸው ፡ ነበር

**swagger** ተጀነነ
The gunman swaggered into the bar. ሽጉጥ ፡ የታጠቀው ፡ ሰውዬ ፡ እየተጀነነ ፡ ቡና ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ገባ

**swallow** (vt.)
1. ዋጠ. The baby cannot swallow food. ሕፃኑ ፡ ምግብ ፡ መዋጥ ፡ አይችልም
Darkness swallowed the bandits. ሽፍቶቹን ፡ ጨለማ ፡ ዋጣቸው
2. ዋጥ ፡ አደረገ. She swallowed her displeasure and smiled. ቅሬታዋን ፡ ዋጥ ፡ አድርጋ ፡ ፈገግ ፡ አለች
3. ደመሰሰ. Expenses swallowed the profit. ወጪው ፡ ትርፉን ፡ ደመሰሰው
4. ቻይ ፡ ሆነ. He had to swallow a lot; if he hadn't, he would have been fired. በጣም ፡ ቻይ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ ባይሆንማ ፡ እስካሁን ፡ ከሥራው ፡ ወጥቶ ፡ ነበር
5. አመነ. He swallows everything he hears. የሰማውን ፡ ሁሉ ፡ ያምናል
6. ዐጠፈ. He swallowed his words. ቃሉን ፡ ዐጠፈ

**swallow** (vi.) ዋጠ
Because my throat hurts, I can't swallow. ጉሮሮዬን ፡ ስላመመኝ ፡ መዋጥ ፡ አልችልም

**swallow up** በላ
The waters of the lake swallowed him up. የሐይቁ ፡ ውኃ ፡ በላው

**(be) swallowed up** አለቀ
His income is swallowed up by debts. የሚያገኘው ፡ ገንዘብ ፡ በዕዳ ፡ ያልቃል

**swallow**, n. [የወፍ ፡ ዓይነት]

**swam**, see **swim**

**swamp** (v.)
1. ዋጠ. The big wave swamped the boat. ትልቁ ፡ ሞገድ ፡ ጀልባዋን ፡ ዋጣት
2. አጥለቀለቀ. Christmas mail swamped the post office. የልደት ፡ ጊዜ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ፖስታ ፡ ቤቱን ፡ አጥለቀለቁት

**be swamped** ተዋጠ
The rich man was swamped with letters asking for money. ባለጸጋው ፡ እርዳታ ፡ ከሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ በሚላኩ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ተውጧል
He is swamped with debts. በዕዳ ፡ ተውጧል

**be swamped with work** ሥራ ፡ ተጫነው
I was swamped with work last week. ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ሥራ ፡ ተጭኖኝ ፡ ነበር

**swamp** (n.) ረግረግ
He got infected with malaria while in the swamp. ከረግረጉ ፡ ውስጥ ፡ ሳለ ፡ በወባ ፡ ተለከፈ

**swampy** የረግረግ
Malaria is prevalent in swampy areas. በረግረግ ፡ ቦታዎች ፡ ወባ ፡ በብዛት ፡ ይገኛል

**swan** ዳክዬ
Swans are beautiful birds. ዳክዬዎች ፡ በጣም ፡ ያምራሉ

**swap** (swapped), v. ተለዋወጠ
We swapped places. ቦታ ፡ ተለዋወጥን

**swap** (n.) ልውውጥ
I got the better of him in the swap. በልውውጡ ፡ እኔ ፡ ተጠቀምኩ

**swarm** (vt.) ሞላ
People swarmed the streets. ሰዎች ፡ መንገዶቹን ፡ ሞሏቸው

**swarm** (vi.) ጕረፈ
Shoppers swarmed into the store. ገበያተኞች ፡ ወደ ፡ መደብሩ ፡ ጐረፉ

**swarm about** ወረረ
The mosquitoes swarmed about us. የወባ ፡ ትንኞች ፡ ወረሩናል

**swarm in** ግር ፡ ብሎ ፡ ገባ
The children came swarming in. ልጆቹ ፡ ግር ፡ ብለው ፡ ገቡ

**swarm with** አያሌ ፡ አለ
+The swamp is swarming with mosquitoes. ረግረጉ ፡ አያሌ ፡ የወባ ፡ ትንኞች ፡ አሉት

**swarm** (n.)
1. ጥፍራ. The queen bee led the swarm to a new hive. የንቡ ፡ አውራ ፡ ጥፍራውን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ ቀፎ ፡ መራ
2. መንጋ. They pursued him like a swarm of bees. እንደ ፡ ንብ ፡ መንጋ ፡ ወረሩት

**swarms of** ብዙ
Swarms of children were at play in the park. ብዙ ፡ ልጆች ፡ በመናፈሻው ፡ ቦታ ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር

**(be) swarthy** ጠቈረ
The sailor was swarthy from the sun. ከፀሐዩ ፡ የተነሣ ፡ መርከበኛው ፡ ጠቍሯል

**swash** ተላጋ
The waves swash against the boat. ሞገዱ ፡ ከጀልባው ፡ ጋር ፡ ይላጋል

**swat** (swatted) እሽ ፡ አለ
He swatted the flies with the flywhisk. ዝንቦቹን ፡ በጭራ ፡ እሽ ፡ አላቸው

**(be) swathed** ተጠቀለለ
His hand was swathed in a bandage. እጁ ፡ በሙሉ ፡ በፋሻ ፡ ተጠቅልሎ ፡ ነበር
*His head was swathed in a turban. ጥምጥም ፡ ጠምጥሟል

**sway** (vt.)
1. አወዛወዘ. The wind sways the grass. ነፋሱ ፡ ሣሩን ፡ ያወዛውዘዋል
2. መለሰ. Nothing can sway him after the mind is made up. አንዴ ፡ ከቈረጠ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አይመልሰውም
3. ማረከ. The speaker's words swayed the audience. ተናጋሪው ፡ ያደረገው ፡ ንግግር ፡ አድማጩን ፡ ሕዝብ ፡ ማረከው
4. ሐሳቡን ፡ ለወጠ. His threats will not sway us. ዛቻው ፡ ሐሳባችንን ፡ አይለውጠውም

**sway** (vi.)
1. ተወዛወዘ. The limber branches of the tree sway in the wind. የሚለመጡት ፡ የዛፍ ፡ ቅርንጫፎች ፡ በነፋስ ፡ ይወዛወዛሉ
She swayed in time to the music. ከሙዚቃው ፡ ጋር ፡ ተወዛወዘች
2. አጋደለ. The bus swayed to the left. አውቶቡሱ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ አጋደለ

**be swayed**
1. ተሳበ. The judge was swayed by the lawyer's argument. ዳኛው ፡ በጠበቃው ፡ ሙግት ፡ ተስቦ ፡ ነበር
2. ስሜት ፡ ተለወጠ. The masses are easily swayed. የሕዝቡ ፡ ስሜት ፡ በቀላሉ ፡ የሚለወጥ ፡ ነው

**(be) sway-backed** ወገቡ ፡ ተለመጠ
This horse is too sway-backed to ride. ፈረሱ ፡ ወገቡ ፡ በጣም ፡ የተለመጠ ፡ ስለሆነ ፡ ለኮርቻ ፡ አይሆንም

**swear** (swore, sworn), vt. አስማለ
He swore me to secrecy. ምስጢሩን ፡ እንዳላወራ ፡ አስማለኝ

**swear** (vi.)
1. ማለ. She swears she's telling the truth. እውነት ፡ የምትናገር ፡ ለመሆኗ ፡ ትምላለች
2. ተራገመ. He swore when he dropped a rock on his foot. እግሩ ፡ ላይ ፡ ድንጋይ ፡ ቢወድቅበት ፡ ተራገመ
3. ተናገረ. He swore that he would always love her. ምንጊዜም ፡ እወዳታለሁ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ
4. አመለከ. He swears by this medicine. በዚህ ፡ መድኀኒት ፡ ያመልካል
5. እርግጠኛ ፡ ነው. I could have sworn that there was someone in the next room. ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ሰው ፡ እንደነበረ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ

**swear at** ዘለፈ
The captain swore at his crew. የመርከቡ ፡ አለቃ ፡ መርከበኞቹን ፡ ዘለፋቸው

**be sworn in**
1. ሥርዓት ፡ መሐላ ፡ ፈጸመ. The President was sworn in during the ceremony. በሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ላይ ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ሥርዓት ፡ መሐላውን ፡ ፈጸመ
2. ቃለ ፡ መሐላ ፡ ሰጠ. Is the witness sworn in yet? ምስክሩ ፡ ቃለ ፡ መሐላውን ፡ ሰጥቷል ?

**sweat** (vt.)
1. አላበ(ው). The hard gallop sweated the horse. በኀይል ፡ ስለጋለበ ፡ ፈረሱ ፡ አልቦታል

2. በሥራ ፡ አስጨነቀ. That employer sweats his workers. ያ ፡ አሠሪ ፡ ሠራተኞቹን ፡ በሥራ ፡ ያስጨንቃቸዋል
*The police sweated a confession out of him. ፖሊሶቹ ፡ አስገድደው ፡ አውጣጡት

**sweat** (vi.) አላበ(ው)
+I sweated because I had to run so much. ብዙ ፡ ስለሮጥኩ ፡ አላበኝ

**sweat all over**
I am sweating all over. በላብ ፡ ተውጫለሁ

**sweat blood** ደም ፡ አስተፋው
+He sweated blood writing that exam. ፈተናው ፡ ደም ፡ አስተፋው

**make sweat** ላብ ፡ በላብ ፡ አደረገ
The long climb made him sweat. ዐቀበቱን ፡ መውጣቱ ፡ ላብ ፡ በላብ ፡ አደረገው

**sweat** (n.) ላብ
He wiped the sweat from his brow. ላቡን ፡ ከግንባሩ ፡ ላይ ፡ ጠረገ

**sweater** ሹራብ
He wears a sweater on cold days. በብርድ ፡ ቀን ፡ ሹራብ ፡ ይለብሳል
[See also 'woolen']

**sweaty** አድካሚ
Digging ditches is sweaty work. ጉድጓድ ፡ መቈፈር ፡ አድካሚ ፡ ሥራ ፡ ነው
*Sick people sometimes have sweaty hands. ሕመምተኞች ፡ አንዳንዴ ፡ እጃቸውን ፡ ያልባቸዋል

**Swede** ስዊድን
There are many Swedes in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ስዊድኖች ፡ አሉ

**Sweden** ስዊድን

**Swedish** ስዊድንኛ
We study Swedish in our school. በትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ውስጥ ፡ ስዊድንኛ ፡ እንማራለን

**sweep** (swept), vt.
1. ጠረገ. Did you sweep the bedroom? መኝታ ፡ ቤቱን ፡ ጠረግኸው ?
Your coat sweeps the ground. ካፖርትህ ፡ መሬት ፡ ይጠርጋል
2. አናወጸ. A hurricane swept the country. ዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ሀገሪቱን ፡ አናወጸት
3. አሰሰ. The police swept the area where the criminal was hiding. ፖሊሶች ፡ ወንጀለኛው ፡ የተደበቀበትን ፡ ቀበሌ ፡ አሰሱት
4. በከፍተኛ ፡ ድምፅ ፡ አሸነፈ. The candidate swept the election. ተወዳዳሪው ፡ ምርጫውን ፡ በከፍተኛ ፡ ድምፅ ፡ አሸነፈ
5. በሙሉ ፡ አጥለቀለቀ. A wave of enthusiasm swept the country. የደስታ ፡ ስሜት ፡ አገሩን ፡ በሙሉ ፡ አጥለቀለቀው

**sweep** (vi.)
1. አለፈ. A wild gale swept across the bay. ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ በባሕር ፡ ሰላጤ ፡ ላይ ፡ አለፈ
2. ነፈሰ. The wind sweeps over the valley. ነፋሱ ፡ በሸለቆው ፡ ላይ ፡ ይነፍሳል
3. ረዘመ. The shore sweeps to the south for miles. የባሕሩ ፡ ጠረፍ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ብዙ ፡ ማይል ፡ ይረዝማል
*His glance swept from right to left. ግራና ፡ ቀኝ ፡ ተመለከተ

**sweep along** ጠረገ
Her gown swept along the floor. ቀሚሷ ፡ መሬቱን ፡ ጠረገ

**sweep around** ዞሮ ፡ ታጠፈ
The road sweeps around the lake. መንገዱ ፡ ሐይቁን ፡ ዞሮ ፡ ይታጠፋል

**sweep away** ጠርጎ ፡ ወሰደ
The flood swept the bridge away. ጐርፉ ፡ ድልድዩን ፡ ጠርጎ ፡ ወሰደው

**sweep down** ፈጠን ፡ ፈጠን ፡ እያለ ፡ ተራመደ
He swept down the aisle to see the stage. መድረኩን ፡ ለማየት ፡ በመተላለፊያው ፡ መሀከል ፡ ፈጠን ፡ ፈጠን ፡ እያለ ፡ ተራመደ

**sweep off** ወሰደ
The wind swept my hat off. ባርኔጣዬን ፡ ነፋስ ፡ ወሰደው

**sweep off (one's) feet**
He swept her off her feet. በፍቅሩ ፡ ተነደፈች

**sweep out** ተቈናጥሮ ፡ ወጣ
The lady swept out of the room. ወይዘሮዋ ፡ ከክፍሉ ፡ ተቈናጥረው ፡ ወጡ

**sweep up** ጠረገ
I swept up the pieces of glass. የብርጭቆውን ፡ ስብርባሪ ፡ ጠረግሁት

**sweep** (n.)
*The mountain is beyond the sweep of our eye. የተራራው ፡ ርቀት ፡ በዓይን ፡ ሊገመገም ፡ አይችልም
*The house looks out upon a wide sweep of farming country. ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ እርሻ ፡ ተንጣሎ ፡ ይታያል

**make a clean sweep** አጣርቶ ፡ ከፈለ
He made a clean sweep of all his debts. ዕዳውን ፡ ሁሉ ፡ አጣርቶ ፡ ከፈለ

**with one sweep**
*He knocked everything off the table with one sweep of the arm. አንዴ ፡ እጁን ፡ ቢሰነዝር ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ እቃ ፡ ጠራርጎ ፡ ጣለው

**sweeper** መጥረጊያ
I need a sweeper to clean the rug. ምንጣፉን ፡ ለማጽዳት ፡ መጥረጊያ ፡ ያስፈልገኛል

**sweeping**
1. ጭልጥ ፡ ያለ. Don't make such sweeping statements! እንደዚህ ፡ ጭልጥ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ አትስጥ
2. ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ. Sweeping changes were made last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ለውጦች ፡ ተደርገዋል
*His sweeping glance took in the whole room. አንዴ ፡ ቃኘት ፡ በማድረግ ፡ ክፍሉን ፡ በሙሉ ፡ ተመለከተ

**sweepings** ጥራጊ
Put the sweepings in the trash can! ጥራጊውን ፡ ቆሻሻ ፡ መጣያው ፡ ቅርቅር ፡ ውስጥ ፡ ጣለው

**sweet(s)** ጣፋጭ ፡ ነገር ፤ ጣፋጭ ፤ ከረሜላ
I don't care much for sweets. ጣፋጭ ፡ ነገር ፡ (ጣፋጭ) ፡ እጅግም ፡ አልወድ
He has a craving for sweets. ለከረሜላ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉጉት ፡ አለው

**sweet** (adj.)
1. ስኳር ፡ የበዛበት. Do you like your tea sweet? ስኳር ፡ የበዛበት ፡ ሻይ ፡ ትወዳለህ ?
2. ደስ ፡ የሚል. She is a very sweet girl. በጣም ፡ ደስ ፡ የምትል ፡ ልጅ ፡ ናት

**sweet butter** [በጨው ፡ ያልታሸ ፡ የፈረንጅ ፡ ቅቤ]

**sweet words** የለሰለሰ ፡ አንደበት
I tried to placate the angry woman with sweet words. የተናደደችውን ፡ ሴትዮ ፡ በለሰለሰ ፡ አንደበት ፡ ለማባበል ፡ ሞከርኩ

**be sweet** ጣፈጠ
These apples are very sweet. እነዚህ ፡ ቱፋዎች ፡ በጣም ፡ ይጣፍጣሉ

**taste sweet** ጣፈጠ
This doesn't taste sweet enough. ይህ ፡ እጅግም ፡ አይጣፍጥ
[See also 'tooth']

**sweetbread** [የበግ ፡ እንጉል ፤ እንጀት ፤ ጣፊያን ፡ የመሳሰሉ ፡ ባንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ ለምግብ ፡ የሚሆኑ ፡ የአካል ፡ ክፍሎች]

**sweeten**
1. አጣፈጠ. A spoonful of sugar will sweeten the tea. አንድ ፡ ማንኪያ ፡ ስኳር ፡ ሻዩን ፡ ያጣፍጠዋል
2. አሳመረ. A friend's kindness sweetened his convalescence. የጓደኛው ፡ ደግነት ፡ የማገገሚያ ፡ ጊዜውን ፡ አሳመረለት

**sweeten with sugar** ስኳር ፡ ጨመረ
Sweeten the tea with sugar! ሻዩ ፡ ውስጥ ፡ ስኳር ፡ ጨምርበት

**sweetheart** የከንፈር ፡ ወዳጅ
She is his sweetheart. የከንፈር ፡ ወዳጁ ፡ ናት
She has a sweetheart. የከንፈር ፡ ወዳጅ ፡ አላት

**sweetness** ጣፋጭነት
Sweetness is an abstract; sugar is concrete. ጣፋጭነት ፡ የነገር ፡ ስም ፡ ነው ፤ ስኳር ፡ ግን ፡ የቁሳቁስ ፡ ስም ፡ ነው

**swell** (vt.)
1. ወጠረ. The wind swelled the sails. ነፋሱ ፡ የመርከቡን ፡ ሸራ ፡ ወጠረው
2. ሞላ. The melting snow will swell the stream. የበረዶው ፡ መቅለጥ ፡ ወንዙን ፡ ይሞላዋል

**swell** (vi.)
1. አበጠ. His knee began to swell. ጉልበቱ ፡ ያብጥ ፡ ጀመር
Wood often swells when wet. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ዕንጨት ፡ ሲረጥብ ፡ ያብጣል
2. ተነፋ. Dough swells when it rises. ሊጥ ፡ ሲቦካ ፡ ይነፋል
3. ደረጀ. Profits swelled. ትርፍ ፡ ደረጀ
4. ተሞላ. My bosom swells with joy. ልቤ ፡ በደስታ ፡ ተሞልቷል
5. አደረ(በት). Pride swelled in his heart. ኩራት ፡ በልቡ ፡ አደረበት
*Savings may swell into a fortune. ቁጠባ ፡ ባለጸጋ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል
*The sound swelled to a roar. ጫጫታው ፡ ወደ ፡ ጩኸት ፡ ተለወጠ
*His heart swelled with pride when he saw his son graduate. ልጁ ፡ ሲመረቅ ፡ ሲያይ ፡ የልብ ፡ ኩራት ፡ ተሰማው

**swell up** ተንደበደበ
His face, which the bee had stung, swelled up. ንብ ፡ የነደፈው ፡ ፊቱ ፡ ተንደበደበ

**be swollen**
1. አበጠ. My ankle is all swollen. ቁርጭምጭሚቴ ፡ በጣም ፡ አብጧል
2. ሞላ. The river was swollen from the heavy rain. ወንዙ ፡ በከባዱ ፡ ዝናም ፡ ምክንያት ፡ ሞልቶ ፡ ነበር

**be swollen shut** አበጠ
The boy's eyes were swollen shut from the beesting. ንብ ፡ ስለነደፈው ፡ የልጁ ፡ ዓይን ፡ አብጦ ፡ ነበር

**swelling** እብጠት
Has the swelling gone down? እብጠቱ ፡ ጐድሏል?

**swelter** ተጨነቀ
He sweltered in the humid heat. በወበቁ ፡ ምክን ያት ፡ ተጨንቋል

**swept,** see **sweep**

**swerve**
1. ዞር ፡ አደረገ. He swerved the car to avoid hitting a dog. ውሻውን ፡ እንዳይገጭ ፡ በማለት ፡ መኪናውን ፡ ዞር ፡ አደረገ
2. አደናቀፈ. Nothing could swerve him from his duty. ምንም ፡ ነገር ፡ ከተግባሩ ፡ ሊያደናቅ ፈው ፡ አይችልም

**swift** ፈጣን
The hawk is swift, but the eagle is swifter. ጭልፊት ፡ ፈጣን ፡ ናት ፤ ንስር ፡ ደግሞ ፡ የበለጠ ፡ ይፈጥናል

**swiftly** በፍጥነት
The police came swiftly. ፖሊሶቹ ፡ በፍጥነት ፡ ደረሱ

**swig, take a ~** ውኃ ፡ ተጐነጨ
He took a swig from the bottle. ከጠርሙሱ ፡ ውኃ ፡ ተጐነጨ

**swim** (swam)
1. ዋኘ. Fish swim. ዓሣ ፡ ይዋኛል
2. (= noun) ዋና. Do you know how to swim? ዋና ፡ ትችላለህ ?
3. (= trans.). አዞረ. My head is still swimming. ራሴን ፡ አሁንም ፡ ያዞረኛል

**swim across** በዋና ፡ አቋረጠ
He swam across the river and escaped. ወንዙን ፡ በዋና ፡ አቋርጦ ፡ አመለጠ

**swim in tears** እንባ ፡ አዘለ
Her eyes were swimming in tears. ዓይኖቿ ፡ እን ባ ፡ አዝለው ፡ ነበር

**swim with the tide** ወደነፈሰበት ፡ ነፈሰ
He swims with the tide, since he likes to be like everyone else. ሌሎችን ፡ መምሰል ፡ ስለሚ ወድ ፡ ወደነፈሰበት ፡ ይነፍሳል

**be swimming in** በዛ(በት)
+This meat was swimming in butter. ይህ ፡ ጥብ ስ ፡ ቅቤ ፡ በዝቶበታል

**swim** (n.) ዋና
His swim had tired him. ዋናው ፡ አድክሞታል

**keep in the swim** እንደጊዜው ፡ ሆነ
Despite her age, she tried to keep in the swim by visiting her former pupils. ዕድሜዋ ፡ የገፋ ፡ ቢሆንም ፤ የድሮ ፡ ተማሪዎቿን ፡ በመጐብኘት ፡ እ ንደጊዜው ፡ ለመሆን ፡ ሞከረች

**take a swim** ዋኘ
He takes a swim every morning. ሁልጊዜ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ይዋኛል

**swimmer** ዋናተኛ
He is a champion swimmer. ተወዳዳሪ ፡ የሌለ ው ፡ ዋናተኛ ፡ ነው

**swimming** ዋና
I like swimming. ዋና ፡ እወዳለሁ

**swimming pool** መዋኛ ፤ የመዋኛ ፡ ስፍራ
He jumped into the swimming pool with a splash. መዋኛው ፡ ውስጥ ፡ ተንቦራጭቆ ፡ ገባ
The school has a swimming pool. ትምህርት ፡ ቤ ቱ ፡ የመዋኛ ፡ ስፍራ ፡ አለው

**swimsuit** የዋና ፡ ልብስ
He put on his swimsuit. የዋና ፡ ልብሱን ፡ ለበሰ

**swindle** (v.) አጭበረበረ ፤ አታለለ
Honest merchants do not swindle their customers. ሐቀኛ ፡ ነጋዴዎች ፡ ደንበኞቻቸው ን ፡ አያጭበረብሩም ፡ (አያታልሉም)

**swindle (one) out of** አጭበረበረ
He swindled me out of $1,000. አንድ ፡ ሺ ፡ ብ ር ፡ አጭበረበረኝ

**swindle** (n.) ማጭበርበር
The merchant's swindle was known to the police. የነጋዴውን ፡ ማጭበርበር ፡ ፖሊሶች ፡ ደር ሰውበት ፡ ነበር

**swindler** አጭበርባሪ ፤ አታላይ
The swindler was arrested. አጭበርባሪው ፡ (አታ ላዩ) ፡ ተያዘ

**swine** አሳማ
The swine is voracious. አሳማ ፡ ሆዳም ፡ ነው

**swing** (swung), vt.
1. አወዛወዘ. She swings her arms when she walks. ስትራመድ ፡ እጇን ፡ ታወዛውዛለች
The policeman walked along swinging his stick. ፖሊሱ ፡ በትሩን ፡ እያወዛወዘ ፡ ተራመደ
2. አዞረ. He swung the club twice around his head. ዱላውን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ሁለቴ ፡ አዞረው

**swing** (vi.)
1. ተንጠለጠለ. The monkey was swinging from a branch. ዝንጀሮው ፡ ቅርንጫፉ ፡ ላይ ፡ ይንጠለጠል ፡ ነበር
2. ጅውጅው ፡ ተጫወተ. You'll fall off if you swing so high. በጎይል ፡ ጅውጅው ፡ ከተጫወትክ ፡ ትወድቃለህ
3. ተወዛወዘ. The pendulum swings in the clock. የግድግዳው ፡ ሰዓት ፡ እጀታ ፡ ይወዛወዛል
4. አቅጣጫውን ፡ ለወጠ. The wind swung to the east. ነፋሱ ፡ አቅጣጫውን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ለወጠ

**swing around** አዞረ
Swing the car around! መኪናዋን ፡ አዙራት

**swing (down)** ተዝናንቶ ፡ ተጓዘ
The soldiers were swinging down the road. ወታደሮቹ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ተዝናንተው ፡ ይጓዙ ፡ ነበር

**swing (into)** ዘሎ ፡ ተቀመጠ
He swung into the saddle. ዘሎ ፡ ፈረሱ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ

**swing open** ብርግድ ፡ ብሎ ፡ ተከፈተ
The door swung open. በሩ ፡ ብርግድ ፡ ብሎ ፡ ተከፈተ

**swing out** ወደ ፡ ውጭ ፡ ተከፈተ
The door does not swing out, but slides along grooves in the floor and ceiling. በሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አይከፈትም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በወለሉና ፡ በጣራው ፡ ባሉት ፡ በርበሮች ፡ ውስጥ ፡ ይንሸራተታል

**swing shut** በገዛ ፡ እጁ ፡ ተዘጋ
The door swung shut. በሩ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ተዘጋ

**swing** (n.) ጅውጅው ፤ የጅውጅው ፡ መጫወቻ
We have a swing in our garden. ባትክልት ፡ ቦታችን ፡ ውስጥ ፡ ጅውጅው ፡ (የጅውጅው ፡ መጫወቻ) ፡ አለን

**be in full swing** ደራ
The market is in full swing in the afternoon. ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ገበያው ፡ ይደራል

**swipe** መነተፈ
He swiped my pencil. እርሳሴን ፡ መነተፈኝ

**swirl** ተጥመለመለ
The stream swirls over the rocks. ወንዙ ፡ ባለቶች ፡ ላይ ፡ ይጥመለመላል

**swirl about**
*Dust swirled about the streets. በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ ቧይት ፡ ነበር

**make swirl** አዞረ
The noise made my head swirl. ጫጫታው ፡ ራሴን ፡ አዞረኝ

**swish** (vt.)
1. ሽውሽው ፡ አደረገ. She swished her skirt. ቀሚሷን ፡ ሽውሽው ፡ አደረገች
2. ነሰነሰ. The horse swished its tail. ፈረሱ ፡ ጭራውን ፡ ነሰነሰ

**swish** (vi.)
1. ተወነጨፈ. The whip swished through the air. ጅራፉ ፡ ባየሩ ፡ ውስጥ ፡ ተወነጨፈ
2. (= tr.) አንኰሻኰሸ. +The dead leaves swished in the wind. የደረቁትን ፡ ቅጠሎች ፡ ነፋሱ ፡ አንኰሻኰሻቸው

**Swiss** ስዊዝ

**switch** (vt.)
1. ገረፈ. She switched her child for being naughty. ልጁ ፡ ስለባለገ ፡ ገረፈችው
2. ለዋወጠ. Let's switch places! ቦታ ፡ እንለዋወጥ
3. አስተላለፈ. Let's switch the party to Friday! ፓርቲውን ፡ ለዓርብ ፡ እናስተላልፈው
4. ለወጠ. The wind switched direction. ነፋሱ ፡ አቅጣጫውን ፡ ለወጠ
5. አባረረ. The horse switched the flies with his tail. ፈረሱ ፡ በጭራው ፡ ዝንቦቹን ፡ አባረረ

**switch off** አጠፋ
Switch off the light! መብራቱን ፡ አጥፋው

**switch on** አበራ
Switch on the light! መብራቱን ፡ አብራው

**switch (one's) tail** በጭራው ፡ ተጋረፈ
The horse switched his tail to drive off the flies. ፈረሱ ፡ ዝንቦችን ፡ ለማባረር ፡ በጭራው ፡ ተጋረፈ

**be switched** ተዛወረ
The train was switched to another track. ባቡሩ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሐዲድ ፡ ተዛውሯል

**switch** (n.)
1. ማብሪያ ፡ ማጥፊያ. The switch is next to the door. ማብሪያ ፡ ማጥፊያው ፡ በሩ ፡ አጠገብ ፡ ነው
2. አርጩሜ. The switch broke when she hit him with it. ስትመታው ፡ አርጩሜው ፡ ተሰበረ
*The switch was left open and the train was derailed. ሐዲዱ ፡ ተጋጥሞ ፡ ስላልነበረ ፡ ባቡሩ ፡ ሐዲዱን ፡ ለቀቀ
*The big dog knocked a vase off the table with a switch of his tail. ትልቁ ፡ ውሻ ፡ ጅራቱን ፡ ሲያወዛውዝ ፡ ያበባ ፡ ማስቀመጫውን ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ጣለው

**be a switch** ተለወጠ
There was a switch in our plans due to bad weather. በመጥፎ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ እቅዳችን ፡ ተለወጠ

**Switzerland** የስዊዝ ፡ አገር

**swivel** ተሽከረከረ
He swiveled in his seat. ወምበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ተሽከረከረ

**swivel around** ዞር ፡ አለ
He swiveled around and faced me. ዞር ፡ ብሎ ፡ ወደኔ ፡ ተመለከተ

**swivel chair** ተሽከርካሪ ፡ ወምበር
It is necessary for a secretary to have a swivel chair. ለጸሐፊ ፡ ተሽከርካሪ ፡ ወምበር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**swollen**, see **swell**

**swollen** (adj.)
1. የሞላ. The banks could not confine the swollen river. የወንዙ ፡ ዳርቻዎች ፡ የሞላውን ፡ ውኃ ፡ ሊያግዱ ፡ አልቻሉም
2. ያበጠ. A swollen cheek spoiled the symmetry of his face. ያበጠው ፡ ጉንጩ ፡ የፊቱን ፡ ደልዳላ ፡ ቅርጽ ፡ አበላሸው

**swoon** (v.) አዞሮት ፡ ወደቀ
She swoons at the sight of blood. ደም ፡ ስታይ ፡ አዙሯት ፡ ትወድቃለች

**swoon** (n.), **in a ~** ነፍሱን ፡ ሳያውቅ
She lay in a swoon for quite some time. ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ነፍሷን ፡ ሳታውቅ ፡ ቆየች

**swoop down** ጅው ፡ ብሎ ፡ ወረደ
The eagle swooped down on its prey. ንስሩ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ምግብ ፡ አይቶ ፡ ጅው ፡ ብሎ ፡ ወረደ

**sword** ጐራዴ
People of olden times used to fight with swords. የድሮ ፡ ሰዎች ፡ በጐራዴ ፡ ይዋጉ ፡ ነበር

**swore**, see **swear**

**sworn** በመሐላ ፡ የተሰጠ
Only sworn testimony has value in court. በፍርድ ፡ ቤት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ በመሐላ ፡ የተሰጠ ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ነው
*They are sworn enemies. እሳትና ፡ ጭድ ፡ ናቸው

**swung**, see **swing**

**sycamore** ወርካ
The sycamores have shed their leaves. ወርካዎቹ ፡ ቅጠላቸው ፡ ረግፏል

**sycophant** አንፏቃቂ
I detest talebearers and sycophants. ወሬኛና ፡ አንፏቃቂ ፡ አልወድም

**syllable** ክፍለ ፡ ቃል
Accent the first syllable of this word! የዚህን ፡ ቃል ፡ የመጀመሪያውን ፡ ክፍለ ፡ ቃል ፡ አንሣ

**syllabus** ሥርዓተ ፡ ትምህርት
The syllabus is not yet ready. ሥርዓተ ፡ ትምህርቱ ፡ ገና ፡ አልተዘጋጀም

**symbol**
1. ምሳሌ. The dove is a symbol of peace. ርግብ ፡ የሰላም ፡ ምሳሌ ፡ ናት
2. ምልክት. "$" is the symbol for dollar. '$' የብር ፡ ምልክት ፡ ነው
3. አርማ. The eagle is used by some countries as a national symbol. ንስር ፡ ባንዳንድ ፡ አገሮች ፡ እንደ ፡ ብሔራዊ ፡ አርማ ፡ ሆኖ ፡ ይሠራበታል

**symbolize**
1. ምሳሌ ፡ ነው. The lion symbolizes bravery. አንበሳ ፡ የጉብዝና ፡ ምሳሌ ፡ ነው
2. መሰለ. How does this poet symbolize man's spirit? ይህ ፡ ገጣሚ ፡ የሰውን ፡ መንፈስ ፡ በምን ፡ ይመስላል ?

**symmetrical** ተመዛዛኝ
Both sides of the design must be symmetrical. በሁለቱም ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ንድፍ ፡ ተመዛዛኝ ፡ መሆን ፡ አለበት

**symmetry** ደልዳላ ፡ ቅርጽ
A swollen cheek spoiled the symmetry of his face. ያበጠው ፡ ጉንጩ ፡ የፊቱን ፡ ደልዳላ ፡ ቅርጽ ፡ አበላሸው

**sympathetic** ርኅሩኅ
Children like her because she is very sympathetic and listens to their troubles. በጣም ፡ ርኅሩኅና ፡ ችግራቸውን ፡ የምትሰማ ፡ ስለሆነች ፡ ልጆች ፡ ይወዷታል

**be sympathetic (to)**
1. ደገፈ. The audience was not sympathetic to the proposal. አዳማጩ ፡ ሕዝብ ፡ ያቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ አልደገፈውም
2. ተቀበለ. The teacher was sympathetic to the class's plan for a trip to the museum. አስተማሪው ፡ የክፍሉ ፡ ተማሪዎች ፡ ቤተ ፡ መዘክሩን ፡ ለመጐብኘት ፡ ያላቸውን ፡ እቅድ ፡ ተቀበለ

3. አዘነ(ለት). She is very sympathetic to his sorrow. በወደቀበት ፡ ሐዘን ፡ ታዝንለታለች

**sympathize, ~ with**
1. ደገፈ. My mother sympathizes with my plan to be a doctor. እናቴ ፡ ሐኪም ፡ ለመሆን ፡ ያለኝን ፡ ምኞት ፡ ትደግፋለች
2. አዘነ(ለት). The teacher sympathized with the child who hurt himself. መምህሩ ፡ ራሱን ፡ ለ
ጉዳው ፡ ልጅ ፡ አዘነለት
*I can sympathize with you; I, too, failed the exam. ሐዘንህ ፡ ሐዘኔ ፡ ነው ፤ በፈተናው ፡ እኔ
ም ፡ ወድቄያለሁ

**sympathy** (sympathies)
1. ማጽናኛ. He sent me a letter of sympathy. የማጽናኛ ፡ ደብዳቤ ፡ ላከልኝ
2. የሐዘን ፡ ተካፋይ ፡ መሆን. John's sympathy soothed Mary in her grief. ሜሪ ፡ አዝና ፡ በነ
በረችበት ፡ ጊዜ ፡ የጆን ፡ የሐዘኗ ፡ ተካፋይ ፡ መ
ሆን ፡ አጽናናት
3. መስማማት. The sympathy between the twins was so great that they always smiled or cried at the same things. በሁለቱ ፡ መንትዮች ፡ መካከ
ል ፡ ያለው ፡ መስማማት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለነበ
ረ ፡ ሲሥቁም ፡ ሆነ ፡ ሲያለቅሱ ፡ ባንድነት ፡ ነው
*I have no sympathy for her. ምንም ፡ አያሳ
ዝነኝ
*You have my sincere sympathy. ሐዘንህ ፡ ሐዘ
ኔ ፡ ነው

**be in sympathy with** ደገፈ
We are all in sympathy with your proposal. ያቀረብከውን ፡ ሐሳብ ፡ ሁላችንም ፡ እንደግፋለን

**feel sympathy** አዘነ
We feel sympathy for the flood victims. የጎርፍ ፡ አደጋ ፡ ለደረሰባቸው ፡ ሰዎች ፡ እና
ዝናለን

**out of sympathy** አዝኖ
He wept out of sympathy for my loss. ስለደረሰ
ብኝ ፡ ጉዳት ፡ አዝኖ ፡ አለቀሰ

**symphony** ሲምፎኒ
Schubert composed many symphonies. ሹበርት ፡ ብዙ ፡ ሲምፎኒዎች ፡ ደረሰ
*In autumn, the woods are a symphony in red, brown and yellow. በመፀው ፡ ወራት ፡ ጫካው ፡ በ
ኅብረ ፡ ቀለም ፡ ያጌጣል

**symposium** ጉባኤ
The symposium on trade problems meets tomorrow. በንግድ ፡ ችግሮች ፡ ላይ ፡ ለመወያየ
ት ፡ ጉባኤው ፡ ነገ ፡ ይሰበሰባል

**symptom** ምልክት
A headache is one of the symptoms of the disease. ራስ ፡ ምታት ፡ በሽታው ፡ ከሚያሳያ
ቸው ፡ ምልክቶች ፡ አንዱ ፡ ነው

**synagogue** ምኩራብ
The synagogue is open all week long. ምኩራቡ ፡ ሳምንቱን ፡ሙሉ ፡ ክፍት ፡ ነው

**synchronize** (vt.) አስተካከለ
Let's synchronize our watches! ሰዓታችንን ፡ እና
ስተካክል

**synchronize** (vi.) ተስማማ
The music and the action synchronized perfectly. ሙዚቃውና ፡ ንቅናቄው ፡ በሚገባ ፡ ተስማሙ

**syndicate** ማኅበር
The syndicate will buy the land and put up the buildings. ማኅበሩ ፡ መሬቱን ፡ ገዝቶ ፡ ሕ
ንጻ ፡ ይሠራበታል

**synonym** ተመሳሳይ
Do you know the synonym for this word? የዚህ ፡ ቃል ፡ ተመሳሳይ ፡ ምንድን ፡ ነው ?

**synopsis** መግለጫ
Read the synopsis before you begin the story. ታሪኩን ፡ ከመጀመርህ ፡ በፊት ፡ መግለጫውን ፡ አ
ንብብ

**syntax** አገባብ
Amharic syntax is very difficult. ያማርኛ ፡ አገ
ባብ ፡ በጣም ፡ ያስቸግራል

**synthesis** ያዋሐደ
His philosophy is a synthesis of old and new ideas. ፍልስፍናው ፡ የድሮውንና ፡ ዘመናዊን ፡ ሐ
ሳብ ፡ ያዋሐደ ፡ ነው

**synthetic** ሰው ፡ ሠራሽ
Synthetic rubber has reduced the price of natural rubber. ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጎማ ፡ ከተፈጥሮ ፡ የተገኘውን ፡ ጎማ ፡ ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ አድርጎታል

**syphilis** ቂጥኝ
The doctor cured him of syphilis. ሐኪሙ ፡ ቂጥኙን ፡ አዳነለት

**syringe** መርፌ
The doctor must use a clean syringe each time he gives an injection. ሐኪሙ ፡ መርፌ ፡ በወጋ ፡ ቁጥር ፡ በንጹሕ ፡ መርፌ ፡ መጠቀም ፡ አለበት

**syrup** ሹሮፕ
She sweetens her drinks with syrup. መጠጦቿን ፡ በሹሮፕ ፡ ታጣፍጣለች

**system**

1. ዘዴ. I have a better system for finding out information. መረጃ ፡ ለማግኘት ፡ የተሻለ ፡ ዘዴ ፡ አለኝ

The government decided on a new system of collecting taxes. መንግሥት ፡ አዲስ ፡ የግብር ፡ አሰባሰብ ፡ ዘዴ ፡ አወጣ

2. ሥርዓት. He works by a system, not by chance. የሚሠራው ፡ በሥርዓት ፡ እንጂ ፡ እንዳ መጣለት ፡ አይደለም

Any system of education must produce educated citizens. ማንኛውም ፡ የትምህርት ፡ ሥርዓት ፡ የተማሩ ፡ ዜጎች ፡ ማስገኘት ፡ አለበት

The people reacted against the system. ሕዝቡ ፡ ሥርዓቱን ፡ ተቃወመ

3. ሰውነት. My system can't take it. ሰውነቴ ፡ አይቀበለውም

4. አሠራር. The nervous system is very complex. የስሜት ፡ ሕዋሳት ፡ አሠራር ፡ በጣም ፡ ረቂቅ ፡ ነው

**systematic**

1. ሥርዓት ፡ ያለው. He made a systematic survey of population growth. ስለ ፡ ሕዝብ ፡ እድገት ፡ ሥርዓት ፡ ያለው ፡ ጥናት ፡ አደረገ

2. ሥርዓት ፡ ተከትሎ ፡ የሚሠራ. A systematic person can do more work than a disorganized one. ሥርዓት ፡ ተከትሎ ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ ከዝርክርክ ፡ ሰው ፡ ይልቅ ፡ ይበልጥ ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል

**systematize** ሥርዓት ፡ አወጣ

They tried to systematize the collection of taxes. ለግብር ፡ አሰባሰብ ፡ ሥራ ፡ ሥርዓት ፡ ሊያወጡለት ፡ ሞከሩ

# T

**tab** ማውጫ
Cards for dividing a filing box have tabs lettered from A to Z. የፋይል ፡ ማኖሪያ ፡ ሣጥኖችን ፡ የሚከፋፍሉት ፡ ካርዶች ፡ ከሀ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ የተጻፉባቸው ፡ ማውጫዎች ፡ አሏቸው

**keep tab on** ተቈጣጠረ
The foreman kept tab on the workers. አለቃው ፡ ሠራተኞቹን ፡ ተቈጣጠራቸው

**pick up the tab**
He picked up the tab. የሒሳቡን ፡ ወረቀት ፡ ሊከፍል ፡ ወሰደ

**tabernacle**
1. የጸሎት ፡ ቤት. The Protestants are holding services in a tabernacle. ፕሮቴስታንቶቹ ፡ በጸሎት ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ይቀድሳሉ
2. ጽላተ ፡ ሙሴ. The tabernacle is supposed to be in the church at Axum. ጽላተ ፡ ሙሴ ፡ አክሱም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ አለ ፡ ይባላል

**table** (v.) አስተላለፈ
They tabled the motion since there was not much time to discuss it. በቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ ለመወያየት ፡ ጊዜ ፡ ስላልነበረ ፡ አስተላለፉት

**table** (n.)
1. ጠረጴዛ. Put the table in the middle of the room! ጠረጴዛውን ፡ ክፍሉ ፡ መካከል ፡ አስቀምጠው
2. ሰንጠረዥ. The figures are given in the table on page 20. ቁጥሩ ፡ ገጽ ፡ ሃያ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ውስጥ ፡ ተዘርዝሯል
3. በጠረጴዛው ፡ ዙሪያ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች. The jokes amused the whole table. ቀልዱ ፡ በጠረጴዛው ፡ ዙሪያ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አሣቃቸው
4. ሰሌዳ. The Ten Commandments were written on tables of stone. ዐሠርቱ ፡ ቃላት ፡ በድንጋይ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ ነበር ፡ የተጻፉት

**money under the table** ጉቦ
She gave money under the table to get the apartment. አፓርትማውን ፡ ለማግኘት ፡ ጉቦ ፡ ሰጠች

**turn the tables** ሁኔታውን ፡ ለወጠ
Fortune turned the tables, and we won. ዕድል ፡ ሁኔታውን ፡ ለውጦት ፡ ለማሸነፍ ፡ ቻልን
[See also 'clear, content, multiplication, silver']

**tablecloth** የጠረጴዛ ፡ ልብስ
Please fold the tablecloth! የጠረጴዛውን ፡ ልብስ ፡ አጣጥፈው!

**tablespoon** የሾርባ ፡ ማንካ ፤ የሾርባ ፡ ማንኪያ
Use a tablespoon and not a teaspoon! የሻዩን ፡ ማንካ ፡ ተውና ፡ በሾርባ ፡ ማንካ ፡ ሥራ

**tablet**
1. ሰሌዳ. An inscription was found on a marble tablet. በእብነ ፡ በረድ ፡ ሰሌዳ ፡ ላይ ፡ የተቀረጸ ፡ ጽሑፍ ፡ ተገኘ
2. ደብተር. He needs a tablet for school. ለትምህርት ፡ ቤት ፡ ደብተር ፡ ያስፈልገዋል
3. እንክብል. If you have a headache, take two aspirin tablets. ራስ ፡ ምታት ፡ ካመመህ ፡ ሁለት ፡ የአስፒሪን ፡ እንክብሎች ፡ ዋጥ

**tableware** የገበታ ፡ እቃ
We keep the tableware in a drawer. የገበታውን ፡ እቃ ፡ የምናስቀምጠው ፡ መሳቢያ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**taboo** ክልክል
It is taboo in Christianity to mention God's name in vain. የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በከንቱ ፡ ማንሣት ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ክልክል ፡ ነው

**tabulate** በሰንጠረዥ ፡ ዘረዘረ
He tabulated the expenses. ወጪውን ፡ በሰንጠረዥ ፡ ዘረዘረው

**tacit** (= adv.) በዝምታ
He gave his tacit agreement. መስማማቱን ፡ በዝምታ ፡ ገለጸ

**taciturn** ዝምተኛ
The taciturn boy sits in the back row. ዝምተኛው ፡ ልጅ ፡ ከኋላ ፡ ይቀመጣል

**tack** (v.)
1. አያያዘ. Tack this note on to the report! ይህን ፡ ማስታወሻ ፡ ከሪፖርቱ ፡ ጋር ፡ አያይዘው
2. አከለ(በት). I will tack a new ending on to the story. ታሪኩን ፡ አዲስ ፡ መደምደሚያ ፡ አክልበታለሁ

**be tacked together** ተሰካካ
The boards were just tacked together. ሳንቃዎቹ ፡ ተሰካክተው ፡ ነበር

**tack** (n.) ምስማር
Tacks hold the carpet in place. ምንጣፉ ፡ እንዳ ይንሸራተት ፡ በምስማር ፡ ተመቷል

**tackle** (v.)
1. ሠራ. You tackled that math problem the wrong way. የሒሳቡን ፡ ፕሮብሌም ፡ የሠራኸው ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ነው
2. ጠልፎ ፡ ጣለ. The policeman tackled the suspect. ፖሊሱ ፡ ተጠርጣሪውን ፡ ጠልፎ ፡ ጣለው

**tackle** (n.), **fishing** ~ የዓሣ ፡ ማጥመጃ ፡ መሣሪያ
Fishing tackle has been used by fishermen for centuries. ዓሣ ፡ አጥማጆች ፡ በዓሣ ፡ ማጥመጃ ፡ መሣሪያ ፡ ብዙ ፡ ዘመናት ፡ ተገልግለዋል

**tact** ብልሃት
She lacks tact in dealing with people. ከሰው ፡ ጋር ፡ በምታደርገው ፡ ግንኙነት ፡ ብልሃት ፡ ያጥራታል

**tactful,** ~ **behavior** ዘዴኛነት
His tactful behavior was noted by all. ዘዴኛነቱ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**tactical**
*Occupying this high hill gives us a tactical advantage. ይህንን ፡ ኰረብታ ፡ መያዛችን ፡ ለጦር ፡ ስልታችን ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል

**tactics**
1. ዘዴ. His tactics were instrumental in defeating the enemy. የተጠቀመባቸው ፡ ዘዴዎች ፡ ጠላትን ፡ ለማሸነፍ ፡ ከረዱት ፡ ነገሮች ፡ ዋናዎቹ ፡ ነበሩ
The tactics he used in getting his present job were not honest. ያሁኑን ፡ ሥራውን ፡ ለማግኘት ፡ የተጠቀመባቸው ፡ ዘዴዎች ፡ ሐቀኛ ፡ አልነበሩም
2. የጦር ፡ ስልት. Tactics are studied at the military academy. በጦር ፡ አካዳሚው ፡ ውስጥ ፡ የጦር ፡ ስልት ፡ ይሰጣል

**tactless**
1. የሚያስቈጣ ፤ የሚያስቀይም. He made a tactless remark about foreigners at the International House. በውጭ ፡ አገር ፡ ተማሪዎች ፡ መሰብሰቢያ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የሚያስቈጣ ፡ (የሚያስቀይም) ፡ አስተያየት ፡ ሰነዘረ
2. ብልሃት ፡ የጐደለው. A tactless answer may be insulting. ብልሃት ፡ የጐደለው ፡ መልስ ፡ የሚያስቀይም ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

**tadpole** የእንቍራሪት ፡ ትል

**tag** (tagged), v.
1. የመለያ ፡ ምልክት ፡ አንጠለጠለ(በት). He tagged the specimens so they could be easily identified. እቃዎቹን ፡ በቀላሉ ፡ ለመለየት ፡ እንዲቻል ፡ የመለያ ፡ ምልክት ፡ አንጠለጠለባቸው
2. ያዘ (ተያዘ). The boy was tagged before he reached the goal. ልጁ ፡ እውድድሩ ፡ መጨረሻ ፡ ቦታ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ተያዘ
3. መጥሪያ ፡ ሰጠ. The policeman tagged the car for parking on the wrong side of the street. መኪናውን ፡ እማይሆን ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ስላቆመ ፡ ፖሊስ ፡ መጥሪያ ፡ ሰጠው
*The baby tags after his brother. ሕፃኑ ፡ ወንድሙ ፡ እሄደበት ፡ ይሄዳል

**tag** (n.)
1. የሚገልጽ ፡ ወረቀት. The price is on the tag. ዋጋውን ፡ የሚገልጽ ፡ ወረቀት ፡ ተለጥፎበታል
2. ሌባና ፡ ፖሊስ. The children were playing tag. ልጆቹ ፡ ሌባና ፡ ፖሊስ ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር

**tail** (v.) ተከታተለ
The detective tailed the suspect. ነጭ ፡ ለባሹ ፡ ተጠርጣሪውን ፡ ተከታተለው
*She's always tailing after her big brother. ዘወትር ፡ ከታላቅ ፡ ወንድሟ ፡ ሥር ፡ አትጠፋም

**tail** (n.) ጅራት
My dog has a short tail. የውሻዬ ፡ ጅራት ፡ አጭር ፡ ነው
*A crowd of small boys formed the tail of the procession. ብዙ ፡ ትንንሽ ፡ ልጆች ፡ ከሰልፉ ፡ ኋላ ፡ ይሄዱ ፡ ነበር

**at the tail end** ሊያልቅ ፡ ሲል
We arrived at the tail end of the first act. የመጀመሪያው ፡ ገቢር ፡ ሊያልቅ ፡ ሲል ፡ ደረስን

**turn tail** ፊቱን ፡ አዞረ
The dog turned tail and fled. ውሻው ፡ ፊቱን ፡ አዙሮ ፡ እግሬ ፡ አውጪኝ ፡ አለ
[See also 'head, switch']

**tailor** ልብስ ፡ ሰፊ
Where can I find a good tailor? ጥሩ ፡ ልብስ ፡ ሰፊ ፡ የት ፡ አገኛለሁ ?

**tailored**
1. የተሰፋ. These suits are tailored for stout men. ልብሶቹ ፡ ለደንዳና ፡ ሰዎች ፡ የተሰፉ ፡ ናቸው
2. የተሠራ. This movie is tailored for young people. ይህ ፡ ፊልም ፡ ለወጣቶች ፡ የተሠራ ፡ ነው

**tail wind** ከኋላ ፡ የሚነፍስ ፡ ነፋስ
A tail wind helps the plane fly faster. ከኋላ ፡ የ

ሚነፍስ ፡ ነፋስ ፡ አውሮፕላኑ ፡ በበለጠ ፡ ፍጥነት ፡ እንዲበር ፡ ይረዳል

**taint** (v.)

1. በከለ. One bad apple can taint a whole barrel. ሣጥኑ ፡ ውስጥ ፡ አንዷ ፡ ቱፋ ፡ ከበሰበሰች ፡ ሌላውን ፡ ሁሉ ፡ ትበክላለች
2. መረዘ. Flies sometimes taint what they touch. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ዝንቦች ፡ የሚነኩትን ፡ ነገር ፡ ይመርዛሉ

**be tainted**

1. መሽተት ፡ ጀመረ. This meat is tainted. ይህ ፡ ሥጋ ፡ መሽተት ፡ ጀመረ
2. ጐደፈ. His reputation was tainted from keeping bad company. ከመጥፎ ፡ ጓደኛ ፡ ጋር ፡ እየዋለ ፡ ስሙ ፡ ጐደፈ

**take** (took)

1. ወሰደ. Who took my ties? ክራቫቶቼን ፡ የወሰደው ፡ ማን ፡ ነው ?
He took the responsibility off my hands. ኀላፊነቱን ፡ ከኔ ፡ ላይ ፡ ወሰደ
The wound took a long time to heal. ቁስሉ ፡ እስኪሽር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወሰደ
2. ያዘ. She took the child by the hand while walking in the street. ጐዳና ፡ ላይ ፡ ሲሄዱ ፡ ልጁን ፡ እጁን ፡ ያዘችው
3. ይዞ ፡ ገባ. He took me into his office. እቢሮው ፡ ይዞኝ ፡ ገባ
4. ይዞ ፡ ሄደ. He took me on a trip. ወደ ፡ ሽርሽር ፡ ይዞኝ ፡ ሄደ
5. አደረሰ. This road takes us to the station. ይህ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ባቡር ፡ ጣቢያው ፡ ያደርሰናል
He took me home in his car. በመኪናው ፡ እቤት ፡ አደረሰኝ
Shall I take your message to her? መልእክትህን ፡ ለሷ ፡ ላድርስልህ ?
6. ሄደ. Why don't you take the bus? ለምን ፡ ባውቶቡስ ፡ አትሄድም ?
7. አገኘ. Jim took first prize. ጂም ፡ አንደኛ ፡ ሽልማት ፡ አገኘ
8. ፈጀ(በት) ፤ ፈጀ. It took the firemen two hours to put out the blaze. ቃጠሎውን ፡ ለማጥፋት ፡ የእሳት ፡ አደጋው ፡ ሠራተኞች ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ፈጀባቸው
9. ጠየቀ. Getting a job takes a lot of doing. ሥራ ፡ መፈለግ ፡ ብዙ ፡ ድካም ፡ ይጠይቃል
It takes time and patience to learn how to drive an automobile. መኪና ፡ መንዳትን ፡ መማር ፡ ጊዜና ፡ ትዕግሥት ፡ ይጠይቃል
10. አነሣ. We took many pictures. ብዙ ፡ ፎቶግራፍ ፡ አነሣን
11. ተቀበለ. We cannot take this affront. ይህንን ፡ ውርደት ፡ አንቀበለውም
12. ታገሠ. I couldn't take the noise any longer. ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ይህን ፡ ጩኸት ፡ ልታገሥ ፡ አልችልም
13. ገባ(ው). + He wouldn't take my hint. ስጠቅሰው ፡ አልገባውም
14. ሰማ. Take my advice! ምክሬን ፡ ስማ
15. ሠራ. The shot didn't take, so he has to take another. መርፌው ፡ ስላልሠራ ፡ ሌላ ፡ መርፌ ፡ መወጋት ፡ አለበት
16. ቈጠረ. He took her remarks as praise. የሰጠችውን ፡ አስተያየት ፡ ከምስጋና ፡ ቈጠረው
17. ተከታተለ. He takes his studies seriously. ትምህርቱን ፡ በትጋት ፡ ይከታተላል
18. ተማረ. He took French in school. ፈረንሳይኛ ፡ የተማረው ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ሳለ ፡ ነው
19. በላ. Why don't you take a cookie? ለምን ፡ ከብስኩቱ ፡ አትበላም ?
20. ዋጠ (ተዋጠ). The medicine is to be taken three times daily after meals. መድኃኒቱ ፡ በቀን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ከምግብ ፡ በኋላ ፡ የሚዋጥ ፡ ነው

*If you take 2 from 7, you have 5. ከሰባት ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ቢቀነስ ፡ አምስት ፡ ይቀራል
*Roses won't take in this soil. ይህ ፡ መሬት ፡ ለጽጌረዳ ፡ አይሆንም
*She takes pride in her schoolwork. ትምህርቷን ፡ ደስ ፡ ብሏት ፡ ትማራለች
*Can I take my time? ቀስ ፡ ብዬ ፡ ልሥራ ?
*He took me into his confidence. የምስጢሩ ፡ ተካፋይ ፡ አደረገኝ
* I take it you won't go to school since you are sick. ስለታመምክ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አትሄድም ፡ ልበል
* You're to come early, I take it. ቀደም ፡ ብለህ ፡ መምጣት ፡ አለብህ ፤ አይደል ?

**take after**

1. አሳደደ. He took after the thief. ሌባውን ፡ አሳደደው
2. አባረረ. He took after his ball. ኳሱን ፡ ያባርር ፡ ነበር

* He takes after his father. የወጣው ፡ ባባቱ ፡ ነው

**take along** ይዞ ፡ ሄደ
How much baggage should I take along? ምን ፡ ያህል ፡ ጓዝ ፡ ይዤ ፡ ልሂድ ?
He took his dog along. ውሻውን ፡ ይዞ ፡ ሄደ

**take along on the trip** ይዞ ፡ ተጓዘ
They took the child along on the trip. ልጁን ፡ ይዘው ፡ ተጓዙ

**take another** ጨመረ

Take another blanket, and you won't be cold. ሌላ ፡ ብርድ ፡ ልብስ ፡ ብትጨምር ፡ አይበርድህም

**take apart**

1. አለያየ. Take it apart if necessary. ካስፈለገ ፡ አለያየው

2. ፈታታ. The watchmaker took my watch apart and reassembled it. ሰዓት ፡ ሠሪው ፡ ሰዓቴን ፡ ፈታቶ ፡ ገጣጠመው

**take (someone) apart** ዞር ፡ አደረገ

He took me apart in order to tell me a secret. ምስጢር ፡ ሊነግረኝ ፡ ዞር ፡ አደረገኝ

**take away**

1. ወሰደ. Who took the chair away? ወንበሩን ፡ ማን ፡ ወሰደው ?

2. ይዞ ፡ ወሰደ. The policeman took him away. ፖሊሱ ፡ ይዞ ፡ ወሰደው

*If your mother should be taken away from you, who will take care of you? እናትህ ፡ ቢሞቱ ፡ ማን ፡ ያሳድግሃል ?

**take back**

1. መለሰ. Stores usually don't take back goods. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ባለ ፡ ሱቆች ፡ የሸጡትን ፡ እቃ ፡ አይመልሱም

The coat was defective, so she took it back to the store. ካፖርቱ ፡ ጉድለት ፡ ስላለበት ፡ ወደ ፡ መደብሩ ፡ መለሰችው

2. ሻረ. I take back what I said. ያልኩትን ፡ ሽሬያለሁ

**take (one) back to** አስታወሰ

Those stories took him back to his childhood days. ታሪኩ ፡ የልጅነት ፡ ጊዜውን ፡ አስታወሰው

**(be) taken by** ተደነቀ

We were taken by her beauty. በውበቷ ፡ ተደነቅን

**take down**

1. አወረደ. Take the picture down from the wall! ሥዕሉን ፡ ከግድግዳው ፡ ላይ ፡ አውርደው

2. ጻፈ. Take down my address! አድራሻዬን ፡ ጻፍ

**take for**

*He took me for my brother. ወንድሜን ፡ መሰልኩት

*Sorry, I took you for someone else. ይቅርታ ፤ የማውቀው ፡ ሰው ፡ መስለኸኝ ፡ ነበር

**take hold of yourself** አይዞህ

Take hold of yourself! Things are not so bad. አይዞህ ! ነገሩ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መጥፎ ፡ አይደለም

**take in**

1. አገኘ. He doesn't take in much more than a few dollars per day. በቀን ፡ የሚያገኘው ፡ ጥቂት ፡ ገንዘብ ፡ ነው

2. ወደ ፡ ቤት ፡ አገባ. Since it looked like rain, she took in the laundry. ዝናቡ ፡ የሚጥል ፡ ስለ መሰለ ፡ የተሰጡትን ፡ ልብሶች ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አገባቻቸው

3. ገባ(ው). They listened to my lecture, but I wonder how much they took in. ንግግሬን ፡ አዳምጠዋል ፤ ምን ፡ ያህል ፡ እንደገባቸው ፡ ግን ፡ እንጃ

4. አስጠበበ. Now that I've reduced, I have to take in my suit. ከሰቻለሁ ፤ እንግዲህ ፡ ልብሴን ፡ ማስጠበብ ፡ አለብኝ

5. ጐበኘ. The tourist took in all the sights. አገር ፡ ጐብኚው ፡ ሊታዩ ፡ የሚገባቸውን ፡ ስፍራዎች ፡ ሁሉ ፡ ጐበኘ

6. ጨመረ. The survey takes in all the colleges. ጥናቱ ፡ ኮሌጆችን ፡ ሁሉ ፡ ይጨምራል

**take in for the night** አሳደረ

He took him in for the night since there was no place else for him to go. ሌላ ፡ የሚያድርበት ፡ ቦታ ፡ ስላልነበረው ፡ አሳደረው

**(be) taken in by** (= trans.) አታለለ

+She wasn't taken in by his promises. የገባላትን ፡ ቃል ፡ አላታለላትም

**take it from me!** እመነኝ

You may take it from me that he's a liar. እመነኝ ፤ ውሸታም ፡ ነው

**take off** (vt.)

1. አወለቀ. I'm taking off my coat. ካፖርቴን ፡ አወልቃለሁ

Ladies are requested to take their hats off. ወይዛዝርት ፡ ባርኔጣቸውን ፡ እንዲያወልቁ ፡ ይለመናሉ

2. አወረደ. Take your feet off the table! እግርህን ፡ ከጠረጴዛው ፡ አውርድ

3. ቈረጠ. The surgeon took off her leg at the knee. ቀዳጁ ፡ ሐኪም ፡ እግሯን ፡ ከጉልበቷ ፡ ቈረጠው

4. ላጨ. Why don't you take off that mustache? ሪዝህን ፡ ለምን ፡ አትላጨውም ?

5. ነቀለ. He never took his eyes off her. ዓይኑን ፡ ከሷ ፡ ላይ ፡ ነቅሎ ፡ አያውቅም

6. ከክብደት ፡ ቀነሰ. Now that she has taken off twenty kilos, she had to buy new clothes. ከክብደቷ ፡ ሃያ ፡ ኪሎ ፡ ስለቀነሰች ፡ አዲስ ፡ ልብስ ፡ በልኳ ፡ መግዛት ፡ አለባት

**take off** (vi.) ተነሣ ፤ ሄደ

When does the plane take off? አውሮፕላኑ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ይነሣል ?

She took off for California. ወደ ፡ ካሊፎርኒያ ፡ ሄደች

**(be) taken off**
1. ተነቀለ. He was taken off the job. ከሥራው ፡ ተነቀለ
2. ተፋቀ. His name was taken off the rolls. ስሙ ፡ ከመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ተፋቀ

**take off from**
He took a day off from work. ያንድ ፡ ቀን ፡ የሥራ ፡ ፈቃድ ፡ ወሰደ

**take on**
1. አሳፈረ. The bus stopped to take on some children. አውቶቡሱ ፡ ልጆች ፡ ለማሳፈር ፡ ቆመ
2. ቀጠረ. He took on twenty more employees. ሃያ ፡ ተጨማሪ ፡ ሠራተኞች ፡ ቀጠረ
3. ጀመረ. I took on a new job yesterday. ትናንት ፡ አዲስ ፡ ሥራ ፡ ጀመርኩ
4. መሥራት ፡ ጀመረ. He has taken on a lot of extra work. ከተመደበለት ፡ ሥራ ፡ በላይ ፡ ብዙ ፡ ትርፍ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ጀምሯል
5. ጨመረ. He has taken on a lot of weight. በጣም ፡ ክብደት ፡ ጨምሯል

**take out**
1. አወጣ. Take something out of the freezer for supper! እራት ፡ እንድንሠራ ፡ እስቲ ፡ ከማቀዝቀዣው ፡ ውስጥ ፡ ምግብ ፡ አውጣ
2. አስለቀቀ. Will this take out ink stains? ይህ ፡ ነገር ፡ ቀለም ፡ ያስለቅቃል ?
3. ገዛ. He took out an insurance policy. ዋስትና ፡ ገዛ
4. ይዞ ፡ ወጣ. He has been taking her out every night for a walk. ሁልጊዜ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ነፋስ ፡ ለመቀበል ፡ ይዟት ፡ ይወጣል
5. ወጣ. Don't take your anger out on me! ቁጭትህን ፡ በኔ ፡ አትወጣ

**take over**
1. ተረከበ. He has taken over the business. የንግዱን ፡ ሥራ ፡ ተረከበ
Who has taken over the management of the factory? የፋብሪካውን ፡ አስተዳዳሪነት ፡ ማን ፡ ተረከበ ?
2. ተተካ. The doctor wanted his son to take over his practice when he got old. ሐኪሙ ፡ እሱ ፡ በሚያረጅበት ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ በሥራው ፡ እንዲተካ ፡ ፈለገ
3. ወሰደ. The government took over the airlines. ያየር ፡ መንገዱን ፡ መንግሥት ፡ ወሰደው
4. ሥልጣን ፡ ያዘ. A caretaker government took over until the elections. ምርጫ ፡ እስኪደረግ ፡ ድረስ ፡ ጊዜያዊ ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ያዘ
5. በእጁ ፡ አደረገ. In Colombia, the radical group is trying to take over the university. በኮሎምቢያ ፡ ተራማጅ ፡ ወገን ፡ ዩኒቨርሲቲውን ፡ በእጁ ፡ ለማድረግ ፡ ይሞክራል

**take to**
1. ጀመረ. This club has taken to admitting women. ይህ ፡ ክበብ ፡ ሴቶችን ፡ መቀበል ፡ ጀምሯል
2. ገባ. The young ducks took to the water. የዳክዬዋ ፡ ጫጩቶች ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ገቡ
3. ተላመደ. The baby took to the water. ሕፃኑ ፡ ውኃውን ፡ ተላመደው
*I don't take to him. ሰውዬውን ፡ ውቃቢዬም ፡ አልወደደው
*How did he take to your suggestion? ስላቀረብከው ፡ ሐሳብ ፡ ምን ፡ አለ ?

**take to the road** ዙረት ፡ ገባ
He gave up his job and took to the road. ሥራ ፡ ለቆ ፡ ዙረት ፡ ገባ

**take up**
1. ቀጠለ. He took up the story where he left off. ታሪኩን ፡ ካቆመበት ፡ ቀጠለ
2. አነሣ. He took up the meat with his fingers. ሥጋውን ፡ በጣቱ ፡ አነሣው
3. ተነጋገረ(በት). I shall take the matter up with the minister. ነገሩን ፡ ከሚኒስትሩ ፡ ጋር ፡ እነጋገርበታለሁ
4. መጠጠ. Blotting paper takes up ink. ማግጠጫ ፡ ወረቀት ፡ ቀለም ፡ ይመጣል
5. ያዘ. The desk takes up too much space. ጠረጴዛው ፡ ብዙ ፡ ቦታ ፡ ይይዛል
6. ተማረ. I think I will take up a foreign language this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ለመማር ፡ አስቤያለሁ
7. ጀመረ. He took up residence at Debre Zeit. ደብረ ፡ ዘይት ፡ መኖር ፡ ጀምሯል
8. ወሰደ(በት). Driving takes up much of my time. መኪና ፡ መንዳት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜዬን ፡ ይወስድብኛል
*I wouldn't take up with her if I were you. አንተን ፡ ብሆን ፡ አጠገቧ ፡ አልደርስም

**(be) taken up** አለፈ
Between teaching and writing, my time is completely taken up. ጊዜዬ ፡ በሙሉ ፡ በማስተማርና ፡ በመጻፍ ፡ ያልፋል

**take upon oneself**
He took it upon himself to give the orders. ኀላፊነቱን ፡ ወስዶ ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ

**(be) taken with**
He is quite taken with her. ልቡን ፡ በልታዋለች
[See also the numerous nouns connected with 'take']

**take-off** (= verbal noun) መነሣት
The plane's take-off was hindered by fog. በጉም ፡ ምክንያት ፡ አውሮፕላኑ ፡ መነሣት ፡ አልቻለም

**tale** ታሪክ
The tale was long and boring. ታሪኩ ፡ የተንዛዛ ፡ ነበር

**talebearer** ወሬኛ ፡ ሰው
The talebearer is disliked. ወሬኛ ፡ ሰው ፡ የተጠላ ፡ ነው

**talent**
1. ተሰጥዎ. Our daughter has a talent for music. ሴት ፡ ልጃችን ፡ የሙዚቃ ፡ ተሰጥዎ ፡ አላት
2. ችሎታ. The artist bequeathed his talent to his son. አርቲስቱ ፡ ችሎታውን ፡ ለልጁ ፡ አወረሰ
3. የተፈጥሮ ፡ ችሎታ. Your talents are going to waste in that job. የተፈጥሮ ፡ ችሎታህ ፡ በዚያ ፡ ሥራ ፡ በከንቱ ፡ መባከኑ ፡ ነው

**talented** ጐበዝ
A talented student will find scholarships easy to obtain. ጐበዝ ፡ ተማሪ ፡ የነጻ ፡ ትምህርት ፡ በቀላሉ ፡ ማግኘት ፡ ይችላል

**talisman** ክታብ
A talisman was hanging on a cord around his neck. ባንገቱ ፡ ክታብ ፡ አንጠልጥሎ ፡ ነበር

**talk** (v.)
1. ተነጋገረ. I heard him talking on the phone. በስልክ ፡ ሲነጋገር ፡ ሰማሁት
He talks in sign language. በእጅ ፡ ምልክት ፡ ይነጋገራል
They talk Amharic together for practice. ለልምምድ ፡ አማርኛ ፡ አብረው ፡ ይነጋገራሉ
The two companies have been talking of a merger. ሁለቱ ፡ ኩባንያዎች ፡ ለመዋሐድ ፡ በመነጋገር ፡ ላይ ፡ ነበሩ
2. አወራ. They like to talk politics. ስለ ፡ ፖለቲካ ፡ ማውራት ፡ ይወዳሉ
The whole town was talking about it. ከተማው ፡ በሙሉ ፡ የሚያወራው ፡ ስለሱ ፡ ነው
3. አወጋ. We spent the evening talking. ስናወጋ ፡ አመሸን
4. አፍ ፡ ፈታ. The baby is learning to talk. ሕፃኑ ፡ አፍ ፡ መፍታት ፡ ጀምሯል
*Now, you're talking! አሁን ፡ ገና ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ተናገርክ

**talk and talk** አውርቶ ፡ አይደክመውም
His wife just talks and talks. ሚስቱ ፡ አውርታ ፡ አይደክማትም

**talk away** እንዲሁ ፡ አወራ
He talked away all night long. ሌሊቱን ፡ እንዲሁ ፡ ሲያወራ ፡ አደረ

**talk back** መልስ ፡ ሰጠ ፤ መለሰ(ለት)
The father smacked his son for talking back. አባትየው ፡ ልጁ ፡ መልስ ፡ ስለሰጠው ፡ አጮለው
Don't talk back to your father when he is angry at you. አባትህ ፡ ሲቆጣህ ፡ አትመልስላቸው

**talk behind one's back** አማ
They are talking behind my back because they are jealous of me. ስለቀኑብኝ ፡ ያሙኛል

**talk big** ጉራ ፡ ነዛ
He talked big about his small deeds. ለፈጸማቸው ፡ ጥቃቅን ፡ ሥራዎች ፡ ጉራውን ፡ ነዛ

**talk business**
Let's talk business! የመጣሁበትን ፡ እንነጋገር

**talk down** ነገሩን ፡ ቀላል ፡ አድርጎ ፡ አቀረበ
It is not necessary to talk down to the audience; they are all educated people. አድማጮቹ ፡ ሁሉ ፡ የተማሩ ፡ ስለሆኑ ፡ ነገሩን ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አድርጎ ፡ ማቅረብ ፡ አያስፈልግም

**talk (one) into** አግባባ
Do you suppose we can talk them into coming with us? ከኛ ፡ ጋር ፡ እንዲመጡ ፡ ልናግባባቸው ፡ የምንችል ፡ ይመስልሃል ?

**talk oneself hoarse**
He talked himself hoarse. ብዙ ፡ ስለተናገረ ፡ ድምፁ ፡ ተዘጋ

**talk oneself into believing**
*He has talked himself into believing that he's sick. ሳይታመም ፡ ራሱን ፡ እንደታማሚ ፡ ይቈጥራል

**talk out** ተነጋገረ
We arrived at a compromise by talking out the problem. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ በመነጋገር ፡ ከስምምነት ፡ ደረስን

**talk (one) out of** እንዳ + negative imperfect + አባበለ
We talked him out of leaving. እንዳይሄድ ፡ አባበልነው

**talk over** አዋየ
Talk the matter over with him! ነገሩን ፡ ለሱ ፡ አዋየው

**talk to** አነጋገረ
Did you talk to him about the new job? ስለ ፡ አዲሱ ፡ ሥራ ፡ አነጋገርከው ?

**talk too much** ለፈለፈ
I dont like him; he talks too much. ስለሚለፈልፍ ፡ አልወደውም

**talk up** በግልጽ ፡ ተናገረ
If you don't talk up now, you may not get another chance. አሁን ፡ በግልጽ ፡ ካልተናገርክ ፡ ሌላ ፡ ዕድል ፡ አይኖርህ ፡ ይሆናል
*He talked up the virtues of his property. ንብረቱን ፡ ሊሸጥ ፡ ሲያስማማ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩውን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ እየጠቀሰ ፡ አሞገሰ
[See also 'sense, shop']

**talk** (n.)
1. ንግግር. His talk was much too long. ንግግሩ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ረጅም ፡ ነበር
2. ጭውውት. Their talk at lunch was desultory. የምሳ ፡ ጊዜ ፡ ጭውውታቸው ፡ የተወሰነ ፡ ዓላማ ፡ አልነበረውም
3. ወሬ. There is talk going around that they are engaged. ተጫጭተዋል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ይነፍሳል
Oh, that's just talk! እሱ ፡ እንኳ ፡ እንዲያው ፡ ወሬ ፡ ነው
There's too much talk and not enough work. ሥራው ፡ ቀርቶ ፡ ወሬ ፡ ብቻ ፡ ሆነ

**talk of the town** በከተማው ፡ የሚወራው
Her marriage is the talk of the town. በከተማው ፡ የሚወራው ፡ ስለሷ ፡ ጋብቻ ፡ ነው

**deliver a talk** አወራ
The traveler delivered a talk on his travels. ተጓዡ ፡ ስለ ፡ ጉዞው ፡ አወራ

**give a talk** ንግግር ፡ አደረገ
He gave a talk to our society. ማኅበራችን ፡ ጋብዞት ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**have a heart-to-heart talk** ልብ ፡ ለልብ ፡ ተጨዋወቱ
I had a heart-to-heart talk with him. ከርሱ ፡ ጋር ፡ ልብ ፡ ለልብ ፡ ተጨዋወትን

**have a talk with** ተነጋገረ
I had several talks with the principal about my boy. ስለ ፡ ልጄ ፡ ከዲሬክተሩ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተነጋግረናል

**talkative** ለፍላፊ
Talkative students disturb a class. ለፍላፊ ፡ ተማሪዎች ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ይበጠብጣሉ

**wax talkative**
*He waxed talkative after dinner. ወሬኛነቱ ፡ ከራት ፡ በኋላ ፡ ባሰበት

**talker**
He is a good talker. ጨዋታ ፡ ያውቃል
[See also 'smooth']

**talking of** ስለ --- ከተነሣ ፡ ዘንድ
Talking of travel, have you been to Addis Ababa? ስለ ፡ ጉዞ ፡ ከተነሣ ፡ ዘንድ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሄደህ ፡ ታውቃለህ ?

**tall** ረጅም
Have you ever seen such a tall building? ይህን ፡ የሚያህል ፡ ረጅም ፡ ሕንጻ ፡ አይተህ ፡ ታውቃለህ ?
He has a tall, thin sister. ቀጭን ፡ ረጅም ፡ እኅት ፡ አለችው

**tall story** የማይታመን ፡ ወሬ
You don't expect me to believe that tall story, do you? ያንን ፡ የማይታመን ፡ ወሬ ፡ እማምን ፡ ይመስልሃል ?

**be tall**
How tall are you? ቁመትህ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?

**grow tall** ተመዘዘ
He grew very tall in two years. በሁለት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ ተመዘዘ

**be taller** ከ --- ረዘመ
The boy is taller than his father. ልጁ ፡ ካባቱ ፡ ይረዝማል

**tally** (tallied), v. ተስማማ
Your account tallies with mine. ያንተ ፡ ሒሳብ ፡ ከኔ ፡ ሒሳብ ፡ ጋር ፡ ይስማማል

**tally up** ደመረ
Tally up the score! ነጥቡን ፡ ደምረው

**tally** (n.), **keep a ~** በዝርዝር ፡ ያዘ
Keep a tally of the money you spend. ወጪህን ፡ በዝርዝር ፡ ያዝ

**tambourine** [ባንድ ፡ ወገን ፡ ቀዳዳ ፡ የተለጠጠበት ፡ ዙሪያውን ፡ ቃጭል ፡ መሳይ ፡ የተሰካበት ፡ የሙዚቃ ፡ መጫሪያ]

**tame** (v.)
1. ለማዳ ፡ አደረገ. Lions are easy to tame. አንበሶችን ፡ በቀላሉ ፡ ለማዳ ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል
2. (= intr.) ተለማማጭ ፡ ሆነ. Harsh punishment in childhood had tamed him and broken his will. በልጅነቱ ፡ ብዙ ፡ ቅጣት ፡ ስላገኘው ፡ ተለማማጭና ፡ መንፈሰ ፡ ደካማ ፡ ሆኗል

**tame** (adj.) ለማዳ
The pigeons are so tame they eat out of your hand. እርግቦቹ ፡ በጣም ፡ ለማዳ ፡ ስለሆኑ ፡ ከእጅህ ፡ ይበላሉ

**be tame** ቀዘቀዘ
The party was tame because all the people were sleepy. ሰዎቹ ፡ ሁሉ ፡ እንቅልፍ ፡ ስለያዛቸው ፡ ፓርቲው ፡ ቀዝቅዞ ፡ ነበር

**tamed** (adj.) ለማዳ
Many tamed animals revert to a wild state when set free. ብዙ ፡ ለማዳ ፡ እንስሳዎች ፡ በተለ
ቀቁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አውሬነት ፡ ይመለሳሉ

**tamp, ~ down** ጠቀጠቀ
They tamped down the earth around the post.
በተተከለው ፡ ዕንጨት ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ አፈር ፡ ጠ
ቀጠቁት

**tamper (with)**
1. ነካካ. He tampered with the car, and now it won't run. መኪናዋን ፡ ስለነካካት ፡ አልነሣ ፡
አለች
2. ለመክፈት ፡ ታገለ. Someone has been tampering with this lock. አንድ ፡ ሰው ፡ ቁልፉን ፡ ለ
መክፈት ፡ ሳይታገል ፡ አልቀረም
3. አግባባ. The lawyer tampered with the witnesses. ጠበቃው ፡ ምስክሩን ፡ አግባባው

**tan** (tanned), vt. አለፋ
What do you use in tanning hides? ቆዳ ፡ የምታ
ለፋው ፡ በምንድን ፡ ነው ?

**tan** (vi.) ጠቈረ
His skin tans quickly. ቆዳው ፡ ቶሎ ፡ ይጠቊራል

**tan oneself**
*He was tanning himself in the sun. ቆዳውን ፡
ለማጥቈር ፡ ፀሐይ ፡ ውስጥ ፡ ይንቃቃ ፡ ነበር

**tan** (n.)
*He has a nice tan. ቆዳው ፡ በፀሐይ ፡ ጥሩ ፡ ጠቊ
ሮለታል

**tang** ኮረጥ ፡ ያለ ፡ መሆን
I disliked the tang of the sauce. ወጡ ፡ ኮረጥ ፡
ያለ ፡ መሆኑን ፡ አልወደድኩትም

**tang of** (expressed by the repetition of the noun)
I smell the tang of salt in the air. አየሩ ፡ ጨው ፡
ጨው ፡ ሸተተኝ

**tangent, at a ~** በሰያፍ
The side road comes into the main road at a tangent. ተገንጣዩ ፡ መንገድ ፡ ከዋናው ፡ መንገ
ድ ፡ በሰያፍ ፡ ይገናኛል

**go off at a tangent** በድንገት ፡ ካርእስቱ ፡
ውጭ ፡ ሆነ
While he was talking about economics, he went off at a tangent. ስለ ፡ ምጣኔ ፡ ሀብት ፡ ሲናገ
ር ፡ በድንገት ፡ ካርእስቱ ፡ ውጭ ፡ ሆነ

**tangerine** መንደሪን

**tangible** የሚታይና ፡ የሚጨበጥ
The results are tangible. ውጤቱ ፡ የሚታይና ፡
የሚጨበጥ ፡ ነገር ፡ ነው
*I was frightened for no tangible reason.
ይህ ፡ ነው ፡ በማልለው ፡ ምክንያት ፡ ደነገጥኩ

**tangle** (v.)
1. ወሳሰበ. The kitten had tangled the ball of yarn. የድመቷ ፡ ግልገል ፡ የክሩን ፡ ጥቅል ፡
ወሳሰበችው
2. ተጋጨ. I wouldn't want to tangle with him on the matter of hiring a new secretary.
አዲስ ፡ ጸሐፊ ፡ በመቅጠር ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከሱ ፡
ጋር ፡ ልጋጭ ፡ አልፈልግም

**become tangled**
1. ተወሳሰበ. The loose ends of the rope became tangled. ያልታሰሩት ፡ የገመዱ ፡ ጫፎች ፡
ተወሳሰቡ
2. (= active) ጠለፈ. +His feet became tangled in the garden hose. የውኃ ፡ ማጠጫው ፡ ጎማ ፡
እግሩን ፡ ጠለፈው

**be tangled up** ተወሳሰበ
The thread is tangled up. ክሩ ፡ ተወሳስቧል

**tangle** (n.) ጠብና ፡ ጭቅጭቅ
Her quick temper gets her into one tangle after another. ግልፍተኛ ፡ መሆኗ ፡ ጠብና ፡ ጭቅጭቅ ፡
ውስጥ ፡ ይጥላታል

**be in a tangle** ተጨናነቀ
The traffic was in a tangle. መኪናዎቹ ፡ ተጨናንቀው ፡ ነበር

**tank**
1. በርሜል. He has a tank in back of his house to store kerosene in. ነጭ ፡ ጋዝ ፡ እሚያስቀምጥበት ፡ በርሜል ፡ ከቤቱ ፡ ጓሮ ፡ አለው
2. ታንክ. A column of tanks led the attack.
የታንኮች ፡ ሰልፍ ፡ ከግንባር ፡ ሆኖ ፡ አጠቃ
3. የቤንዚን ፡ መያዣ. I had the tank of my car fixed. የመኪናዬን ፡ የቤንዚን ፡ መያዣ ፡ አሠራሁት

**tanker** ጫኝ ፡ መርከብ
Oil tankers bring petroleum to Asab. ዘይት ፡
ጫኝ ፡ መርከቦች ፡ ዘይት ፡ ወደ ፡ አሰብ ፡ ያመጣሉ

**tanned** (adj.) የለፋ
Shoes are made of tanned hide. ጫማዎች ፡ የሚ
ሠሩት ፡ ከለፋ ፡ ቆዳ ፡ ነው

**tanner** ቆዳ ፡ ፋቂ
The tanner gets paid for his work. ቆዳ ፡ ፋቂው ፡
ለሥራው ፡ ይከፈለዋል

**tannery** የቆዳ ፡ ፋብሪካ
There is a tannery in Addis Ababa. አዲስ ፡
አበባ ፡ ውስጥ ፡ የቆዳ ፡ ፋብሪካ ፡ አለ

**tantalize** አስጐመጀ
He tantalized the hungry dog by pretending to feed him. ምግብ ፡ የሚሰጠው ፡ በመምሰል ፡ የ ራበውን ፡ ውሻ ፡ አስጐመጀው

**tantalizing** የሚያስጐመጅ
The tantalizing smell of food came from the kitchen. የሚያስጐመጅ ፡ የምግብ ፡ ሽታ ፡ ከማእ ድ ፡ ቤት ፡ ሸተተኝ

**tantamount**
*His request was tantamount to a command. የጠየቀው ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ትእዛዝ ፡ አድርጎ ፡ ነው

**tantrum, have a ~** በንዴት ፡ ተቈላ
The spoiled child had a tantrum whenever she did not get her own way. ሞልቃቃዋ ፡ ልጅ ፡ ያሰኘችው ፡ ካልሆነ ፡ በንዴት ፡ ትቈላለች

**tap** (tapped), v.
1. መታ ፡ መታ ፡ አደረገ. He tapped on the window. መስኮቱን ፡ መታ ፡ መታ ፡ አደረገ
He tapped me on the shoulder. ትከሻዬን ፡ መታ ፡ መታ ፡ አደረገኝ
2. ጠልፎ ፡ በጕን ፡ ሰማ. The police are tapping the criminal's wires. ፖሊሶች ፡ የወንጀለኛውን ፡ የስልክ ፡ ግንኙነት ፡ ጠልፈው ፡ በጕን ፡ ይሰማሉ
3. ከፍቶ ፡ ቀመሰ. They tap the barrels of mead to see if the fermentation process has stopped. ጠጁ ፡ መብሰሉን ፡ ለማየት ፡ በርሚሉን ፡ ከፍተው ፡ ይቀምሱታል
4. ከፍቶ ፡ ማውጣት ፡ ጀመረ. He tapped a pool of oil. አንድ ፡ የነዳጅ ፡ ዘይት ፡ ማዕድን ፡ ከፍቶ ፡ ማ ውጣት ፡ ጀመረ

**tap (one's) foot** ወለሉን ፡ ቈረቈረ
Her impatience showed in her tapping her foot. ትዕግሥት ፡ ማጣቷ ፡ ወለሉን ፡ በመቈርቈሯ ፡ ታወቀ

**tap** (n.) ቧንቧ
Turn off the tap! ቧንቧውን ፡ ዝጋው

**tape** (v.)
1. በቴፕ ፡ ቀዳ. I taped his speech. ንግግሩን ፡ በቴፕ ፡ ቀዳሁት
2. በማጣበቂያ ፡ አያያዘ. He taped the torn paper. የተቀደደውን ፡ ወረቀት ፡ በማጣበቂያ ፡ አያያዘ

**tape** (n.)
1. የቁስል ፡ መለጠፊያ. Put a piece of tape on the cut! የተቈረጥክበት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ የቁስል ፡ መለጠፊያ ፡ አድርግበት
2. ጥብጣብ. The tape was sewn to the coat. ኮቱ ፡ ላይ ፡ ጥብጣብ ፡ ተሰፍቶበት ፡ ነበር
3. ቴፕ. She has many songs on tape. በቴፕ ፡ የተቀረጸ ፡ ብዙ ፡ ዘፈን ፡ አላት

**taper (to a point)**
*The candles are tapered to a fine point. ሻማዎቹ ፡ ወደ ፡ ጫፋቸው ፡ ላይ ፡ ቀጠን ፡ ይላሉ
*One end of the rod tapers to a point. የብረቱ ፡ ዘንግ ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ ቀጠን ፡ ይላል

**taper off** ቀስ ፡ በቀስ ፡ ወረደ
Her voice tapered off to a whisper. ድምጿ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ወደ ፡ ሹክሹክታ ፡ ወረደ

**tape recorder** ቴፕሪኮርደር
Tape recorders are quite expensive. ቴፕሪኮርደር ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ ነው

**tapestry** (tapestries) ስጋጃ
Beautiful tapestries were hung on the walls. ያጌጡ ፡ ስጋጃዎች ፡ ግድግዳው ፡ ላይ ፡ ተሰቅለው ፡ ነበር

**tapeworm** ኮሶ
He has a tapeworm. ኮሶ ፡ ተጣብቶታል

**taproot** ዋና ፡ ሥር
Dig up the taproot of the tree! የዛፉን ፡ ዋና ፡ ሥር ፡ ቈፍረህ ፡ አውጣው

**tar** (tarred), v.
1. አስፋልት ፡ አለበሰ. They just finished tarring the road. መንገዱን ፡ አስፋልት ፡ አልብሰው ፡ አ ሁን ፡ ገና ፡ ጨረሱ
2. አጐደፈ. Scandal has tarred his reputation. አሉባልታ ፡ ስሙን ፡ አጐድፎታል

**tar** (n.) ሬንጅ
The road is covered with tar. መንገዱ ፡ ሬንጅ ፡ ፈሶበት ፡ ነበር

**tardiness** መዘግየት ፤ ዘግይቶ ፡ መምጣት ፤ ዳተኝ ነት
The child fabricated a story to explain his tardiness. ልጁ ፡ ለመዘግየቱ ፡ ምክንያት ፡ ፈጠረ
His tardiness aggravates me. የሱ ፡ ዘግይቶ ፡ መምጣት ፡ (የሱ ፡ ዳተኝነት) ፡ ያበሳጨኛል

**tardy** ዘግይቶ ፡ የመጣ ፤ ዳተኛ
The tardy students ambled into the classroom. ዘግይተው ፡ የመጡት ፡ (ዳተኞቹ) ፡ ተማሪዎች ፡ እየተንጐራደዱ ፡ ወደ ፡ ክፍል ፡ ገቡ

**be tardy**
1. ዘገየ. My son was tardy. ልጄ ፡ ዘግይቷል
2. ወደ ፡ ኋላ ፡ ተጐተተ. Their progress is tardy. እርምጃቸው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተጐትቷል

**tardy arrival** ዘግይቶ ፡ መድረስ
The tardy arrival of the train made us impatient. የባቡሩ ፡ ዘግይቶ ፡ መድረስ ፡ ትዕግሥ ታችንን ፡ አስጨረሰን

**target** ዒላማ
Aim high or you'll miss the target. ከፍ ፡ አድርገህ ፡ እንጣጥር ፤ አለዚያ ፡ ዒላማውን ፡ ትስታለህ

**target of jokes** መሳለቂያ
His crazy ideas made him the target of jokes by everyone. ጅል ፡ የሆነ ፡ አስተሳሰቡ ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ መሳለቂያ ፡ አደረገው

**be the target of criticism** ብዙ ፡ ነቀፋ ፡ ጉረፈበት
The book was the target of much criticism. መጽሐፉ ፡ ብዙ ፡ ነቀፋ ፡ ጉረፈበት

**tariff**
1. ቀረጥ. A tariff has been imposed on cigarettes. በሲጋራ ፡ ላይ ፡ ቀረጥ ፡ ተጣለ
2. የሚያስከፍል. The tariff at the hotel ranges from $8 to $12 a day. ሆቴሉ ፡ ለመኝታ ፡ የሚያስከፍለው ፡ በቀን ፡ ከስምንት ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ብር ፡ ነው

**tarnish**
1. አጠቈረ. The salt tarnished the salt shaker. ጨዉ ፡ የጨው ፡ እቃውን ፡ አጠቈረው
2. አጎደፈ ፤ አበከለ. His business dealings have tarnished his reputation. የንግድ ፡ አያያዙ ፡ ስሙን ፡ አጎደፈው ፡ (አበከለው)

**tarnish** (vi.) ደበዘዘ
Silver tarnishes in this climate. ብሩ ፡ ከየሩ ፡ ሁኔታ ፡ የተነሣ ፡ ደብዝዟል

**tarry** (tarried)
1. ዘገየ. Don't tarry; mail the letter now! ሳትዘገይ ፡ ደብዳቤውን ፡ አሁኑኑ ፡ በፖስታ ፡ ላክ
2. በየቦታው ፡ ቆመ. He is always late because he tarries on his way to work. ወደ ፡ ሥራው ፡ ሲሄድ ፡ በየቦታው ፡ ስለሚቆም ፡ ሁልጊዜ ፡ ይዘገያል
3. አረፈ. He tarried at the inn till he felt strong enough to travel. ጉዞውን ፡ ለመቀጠል ፡ እስኪችል ፡ ድረስ ፡ በሆቴሉ ፡ ውስጥ ፡ አረፈ

**tart**
1. ኰምጣጣ. The fruit was tart. ፍሬው ፡ ኰምጣጣ ፡ ነበር
2. የሚያስቈጣ. He gave a tart reply. የሚያስቈጣ ፡ መልስ ፡ ሰጠ

**task** (v.) አሠራ
The farmer tasked his oxen beyond their strength. ገበሬው ፡ በሮቹን ፡ ከቅማቸው ፡ በላይ ፡ አሠራቸው

**task** (n.)
1. ሥራ. I have a hard task in front of me. አንድ ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ ይጠብቀኛል
2. ሙያ. Filing is a clerical task. መዝገብ ፡ አያያዝ ፡ የጸሐፊዎች ፡ ሙያ ፡ ነው

**take to task** ገሠጸ
He took me to task for my many absences. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስለቀረሁ ፡ ገሠጸኝ
[See also 'thankless']

**taste** (v.)
1. ቀመሰ. Taste this sauce to see if it's too sweet. ከመጠን ፡ በላይ ፡ መጣፈጡን ፡ ለማየት ፡ ይህንን ፡ ወጥ ፡ ቅመሰው
2. ቀመስ ፡ አደረገ. Just taste this coffee! ይህን ፡ ቡና ፡ ቀመስ ፡ አድርገው ፡ እስቲ
3. ለመደ. Having tasted freedom, the bird would not return to its cage. ወፏ ፡ እንደልቧ ፡ መሆን ፡ ለምዳ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጎጆዋ ፡ ልትመለስ ፡ አልፈለገችም
*I taste nuts in this cake. ይህ ፡ ኬክ ፡ ለውዝ ፡ አለበት ፡ መሰለኝ

**taste good** ጣፈጠ
The soup tastes good. ሾርባው ፡ ይጣፍጣል

**taste of** (repeated noun) + አለ
It tastes of vinegar. ኮምጣጤ ፡ ኮምጣጤ ፡ ይላል
[See also 'bitter, burn, flat, sweet']

**taste** (n.)
1. ጣዕም. This meat has a peculiar taste. ይህ ፡ ሥጋ ፡ ጣዕሙ ፡ ተበላሽቷል
2. የማጣጣም ፡ ችሎታ. Her taste is keen. የማጣጣም ፡ ችሎታዋ ፡ ከፍተኛ ፡ ነው
3. ፍላጎት. We each have our individual taste. እያንዳንዳችን ፡ የግል ፡ ፍላጎት ፡ አለን
4. ስሜት. The experience left a bad taste in my mouth. የደረሰብኝ ፡ ነገር ፡ መጥፎ ፡ ስሜት ፡ አሳድሮብኛል
*I just want a taste of it. እስቲ ፡ ልቅመሰው
*Give him a taste of his own medicine! ክፋን ፡ በክፉ ፡ መልስለት
*She has expensive taste in clothes. ውድ ፡ የሆነ ፡ ልብስ ፡ መልበስ ፡ ትወዳለች

**be in bad taste** ተገቢም ፡ አልነበረ
That remark was in bad taste. የተሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ተገቢም ፡ አልነበር

**excellent taste** ደስ ፡ የሚል ፡ አኳኋን
His house is furnished in excellent taste. ቤቱ ፡ ደስ ፡ በሚል ፡ አኳኋን ፡ የተደራጀ ፡ ነው

**give one a taste of**
This rain will give you a taste of the rainy season. ይህ ፡ ዝናብ ፡ ክረምቱ ፡ እንዴት ፡ እንደሚሆን ፡ ያመለክትሃል

**good taste** ተገቢነት
His remarks violated all canons of good taste. አስተያየቱ ፡ የተገቢነትን ፡ ደንብ ፡ ሁሉ ፡ ጣሰ

**have good taste in**
*She has good taste in clothing. አለባበስ ፡ ታውቃለች

**have (a) taste for** ወደደ
Many people have a taste for candy. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከረሜላ ፡ ይወዳሉ

**in good taste**
*She is always dressed in good taste. ምንጊዜም ፡ የምትለብሰው ፡ ያምርባታል
[See also 'medicinal, scorched, suit']

**tasteful**
*She has a talent for tasteful flower decorations. አበባ ፡ አደራደር ፡ ታውቃለች

**tastefully** አምርበት
She was tastefully dressed. አምርባት ፡ ለብሳ ፡ ነበር

**(be) tasteless** ጣዕም ፡ የለውም ፤ እህል ፡ ውኃ ፡ አይልም
The food is tasteless. ምግቡ ፡ ጣዕም ፡ የለውም ፡ (እህል ፡ ውኃ ፡ አይልም)

**tasty** ጥሩ
This restaurant serves tasty food. ይህ ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ ጥሩ ፡ ምግብ ፡ ያቀርባል

**be tasty** ጣመ
This food is very tasty. ይህ ፡ ምግብ ፡ በጣም ፡ ይጥማል

**tatter(s)** ቡትቶ
The beggar was dressed in tatters. የኔ ፡ ቢጤው ፡ ቡትቶ ፡ ለብሶ ፡ ነበር

**tattered** የተበጣጠሰ
Abject poverty is visible in the beggar's tattered clothes. ከለማኙ ፡ የተበጣጠሰ ፡ ልብስ ፡ አሰቃቂ ፡ ድኽነት ፡ እንዳለበት ፡ ይታወቃል

**tattered clothes** ቡትቶ
The child wore tattered clothes. ልጁ ፡ ቡትቶ ፡ ለብሷል

**tattle**
1. አሳበቀ. The boy tattled on his sister. ልጁ ፡ እኅቱን ፡ አሳበቀባት
2. ስሞታ ፡ አቀረበ. Children are always tattling on each other. ልጆች ፡ ሁልጊዜ ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ስሞታ ፡ ያቀርባሉ
3. ቱሽ ፡ አለ. If nobody tattles, the other team can't learn our plans. አንዱ ፡ ቱሽ ፡ ካላለ ፡ ሌላው ፡ ቡድን ፡ እቅዳችንን ፡ አያውቅብንም

**tattletale** አሳባቂ
A good father does not want his child to be a tattletale. ጥሩ ፡ አባት ፡ ልጁ ፡ አሳባቂ ፡ እንዲሆን ፡ አይፈልግም

**tattoo** (v.) ነቀሰ
I tattooed a cross on his arm. ክንዱ ፡ ላይ ፡ መስቀል ፡ ነቀስኩለት

**tattoo** (n.) ንቅሳት
He has a tattoo on his àrm. ክንዱ ፡ ላይ ፡ ንቅሳት ፡ አለው

**taught, see teach**

**taunt** (v.) ሣቀ(በት)
She taunted him for his failure. ሥራውን ፡ ለማከናወን ፡ ስላልቻለ ፡ ሣቀችበት

**taunt** (n.)
*The taunts of the crowd enraged him. ሕዝቡ ፡ ስለሣቀበት ፡ በጣም ፡ ተናደደ

**taut** የተወጠረ
A taut rope breaks easily. የተወጠረ ፡ ገመድ ፡ በቀላሉ ፡ ይበጠሳል

**tavern** መጠጥ ፡ ቤት
He spends all his money at the tavern. ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ ይጨርሳል

**tawdry** ርካሽና ፡ ብልጭልጭነት ፡ ያለው
She bought some tawdry trinkets. ጥቂት ፡ ርካሽና ፡ ብልጭልጭነት ፡ ያለው ፡ ጌጥ ፡ ገዛች

**tax** (v.) ቀረጥ ፡ አስከፈለ ፤ ቀረጥ ፡ ጣለ
The government protects industry by taxing imports. መንግሥት ፡ ያገር ፡ ውስጥ ፡ እንዱስትሪዎችን ፡ ለማዳበር ፡ ሲል ፡ ከውጭ ፡ በሚገቡ ፡ እቃዎች ፡ ላይ ፡ ቀረጥ ፡ ያስከፍላል ፡ (ይጥላል)

**be taxed** ተቀረጠ
Everybody was taxed two dollars. ሰው ፡ በሙሉ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ብር ፡ ተቀርጦ ፡ ነበር

**tax (one's) strength** አደከመ
The work taxed her strength. ሥራው ፡ አደከማት

**tax (one's) strength to the utmost** ድቅቅ ፡ አደረገ
The job taxed his strength to the utmost. ሥራው ፡ ድቅቅ ፡ አድርጎታል

**be taxing on** ጐዳ
Climbing stairs is taxing on a weak heart. ደረጃን ፡ መውጣት ፡ ደካማ ፡ ልብን ፡ ይጐዳል

**tax** (n.) ግብር ፤ ቀረጥ
Have you paid your taxes yet? ግብር ፡ ገና ፡ አልከፈልክም ?
The government imposed a new income tax. መንግሥት ፡ አዲስ ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ ጣለ

**be tax exempt** ከግብር ፡ ነጻ ፡ ነው
In the United States, a low income is tax exempt. አሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ዝቅተኛ ፡ ገቢ ፡ ከግብር ፡ ነጻ ፡ ነው

**be tax free** ቀረጥ ፡ አልተከፈለበትም
This item was tax free. ይህ ፡ እቃ ፡ ቀረጥ ፡ አልተከፈለበትም
[See also 'income, progressive']

**taxation**
1. ቀረጥ. Diplomats are granted immunity from taxation. ዲፕሎማቶች ፡ ከቀረጥ ፡ ነጻ ፡ ናቸው
2. የግብር ፡ አከፋፈል. He appraised the property for taxation. ለግብር ፡ አከፋፈል ፡ እንዲመች ፡ ንብረቱን ፡ ገመተ

**tax collector** ግብር ፡ አስገቢ
The man who collects taxes is called a tax collector. ግብር ፡ የሚሰበስበው ፡ ሰው ፡ ግብር ፡ አስገቢ ፡ ይባላል

**taxi** ታክሲ
Call a taxi! ታክሲ ፡ ጥራ

**taxpayer** ግብር ፡ ከፋይ
The taxpayers must pay more under the new tax law. ባዲሱ ፡ የግብር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ግብር ፡ ከፋዩ ፡ ተጨማሪ ፡ ግብር ፡ ይከፍላል

**tea** ሻይ
He drinks tea every morning. ጧት ፡ ጧት ፡ ሻይ ፡ ይጠጣል

**teach** (taught), vt.
1. አስተማረ. Mr. Brown teaches history. ሚስተር ፡ ብራውን ፡ ታሪክ ፡ ያስተምራሉ
How many students does he teach? ስንት ፡ ተማሪዎች ፡ ያስተምራል ?
2. ትምህርት ፡ ሆነው. That will teach you not to talk back to me. ሁለተኛ ፡ መልስ ፡ እንዳትሰጠኝ ፡ ትምህርት ፡ ይሆንሃል
The accident taught me to be careful. አደጋው ፡ ለወደፊቱ ፡ እንድጠነቀቅ ፡ ትምህርት ፡ ሆነኝ

**teach** (vi.) አስተማረ
He teaches in a girls' school. ሴቶች ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ያስተምራል

**teacher** አስተማሪ
The English teacher is ill. እንግሊዝኛ ፡ አስተማሪው ፡ ታሟል

**teaching**
1. መምህርነት ፤ አስተማሪነት. Teaching is a very interesting profession. መምህርነት ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ሙያ ፡ ነው
His work is teaching. ሥራው ፡ አስተማሪነት ፡ ነው
2. የማስተማር ፡ ዘዴ. Abnormal children require special teaching. በአእምሮዋቸው ፡ ዝቅ ፡ ያሉ ፡ ልጆች ፡ ልዩ ፡ የማስተማር ፡ ዘዴ ፡ ያስፈልጋቸዋል
3. ልማድ. Many Indian superstitions are old teachings of the tribe. ብዙው ፡ የህንዶች ፡ አጉል ፡ እምነት ፡ የወረሱት ፡ ልማድ ፡ ነው

**teacup** የሻይ ፡ ሲኒ
The teacup broke. የሻዩ ፡ ሲኒ ፡ ተሰብሯል

**teakettle** የሻይ ፡ ጀበና
Put the teakettle on! የሻዩን ፡ ጀበና ፡ ጣደው

**team** (v.), ~ **up** አንድ ፡ ተሰበሰበ
Everybody teamed up to clean the classroom after the party. ከፓርቲው ፡ በኋላ ፡ ሰዎቹ ፡ አንድ ፡ ተሰብስበው ፡ ክፍሉን ፡ አጸዱ
*We teamed up in groups of four. ባራት ፡ ባራት ፡ ሆን

**team** (n.)
1. ቡድን. Our team has won every game this year. ቡድናችን ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ሁሉንም ፡ ጨዋታ ፡ አሸንፏል
2. ጓድ. The government is sending a medical team to teach people hygiene. መንግሥት ፡ ሕዝቡን ፡ የጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ዘዴ ፡ ለማስተማር ፡ የሕክምና ፡ ጓድ ፡ በመላክ ፡ ላይ ፡ ነው
3. ጥማድ. He ploughs with a team of oxen. ባንድ ፡ ጥማድ ፡ በሬ ፡ ያርሳል

**team** (adj.) የመተባበር
Team spirit must be encouraged. ማንኛውም ፡ ቡድን ፡ ውስጥ ፡ የመተባበር ፡ መንፈስ ፡ እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል

**teamwork** ተባብሮ ፡ መሥራት
Teamwork is necessary to get many jobs done. ብዙ ፡ ሥራ ፡ ለማከናወን ፡ ተባብሮ ፡ መሥራት ፡ ያስፈልጋል
*We can succeed through good teamwork. ተባብረን ፡ ብንሠራ ፡ ተግባራችን ፡ ሊቃና ፡ ይችላል

**teapot** የሻይ ፡ ጀበና
Remove the tea leaves from the teapot! ከሻዩ ፡ ጀበና ፡ ውስጥ ፡ ሻይ ፡ ቅጠሉን ፡ ድፋው

**tear** (tore, torn), vt.
1. ቀደደ. The nail tore her coat. ምስማሩ ፡ ከጋርቷን ፡ ቀደደው
2. ነጨ. He tore his hair in a fury. በንዴት ፡ ጸጉሩን ፡ ነጨ
The hungry dog tore the meat with its teeth. የተራበው ፡ ውሻ ፡ ሥጋውን ፡ በጥርሱ ፡ ነጨ
3. ገነጠለ. The wind tore the awnings off the wall. ነፋሱ ፡ መጋረጃውን ፡ ከግድግዳው ፡ ላይ ፡ ገነጠለው
4. በጠሰ. He tore a sprig off the bush. ከቁጥቋጦው ፡ ላይ ፡ ቅጠል ፡ በጠሰ
5. ሸረከተ. +He tore his hand on a nail. እጁን ፡ ምስማር ፡ ሸረከተው

**tear** (vi.)
1. ተቀደደ. Cloth tears easily. ጨርቅ ፡ በቀላሉ ፡ ይቀደዳል
2. (= act.) ቀደደ. +Her dress tore on a nail. ቀሚሷን ፡ ምስማር ፡ ቀደደው

**be torn**
1. ተሠቃየ. He was torn by grief. በሐዘን ፡ ተሠቃየ
2. ተቦጫጨቀ. Nigeria was torn by civil war. ናይጂሪያ ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ተቦጫጭቃ ፡ ነበር

**tear down**
1. አፈረሰ. They tore down the house last year. ቤቱን ፡ ያፈረሱት ፡ ዓምና ፡ ነው
2. አውርዶ ፡ ቀዳደደ. He tore down the enemy's flag. የጠላትን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ አውርዶ ፡ ቀዳደደው

**tear down the middle** ተሸረከተ
The sheet tore down the middle when I took it off the bed. አንሶላውን ፡ ካልጋው ፡ ላይ ፡ ስጐትት ፡ ተሸረከተ

**tear (one's) heart** ከባድ ፡ ሐዘን ፡ አሳደረ
It tore his heart to leave his children. ልጆቹን ፡ መተው ፡ ከባድ ፡ ሐዘን ፡ አሳደረበት

**tear off** (vt.) ገነጠለ
Tear off the coupon! ኩፖኑን ፡ ገንጥለው

**tear off** (vi.) ተበጠሰ
The button tore off. ቁልፉ ፡ ተበጠሰ

**tear oneself away** ተላቀቀ
She could hardly tear herself away from him. ከሱ ፡ መላቀቅ ፡ ጭንቅ ፡ ሆነባት

**tear open** (vt.)
1. ቀደደ. Who tore the cigarette package open? የሲጋራውን ፡ ፓኮ ፡ ማን ፡ ቀደደው ?
2. ከፈተ. He tore open the envelope. ኤንቬሎፑን ፡ ከፈተ

**tear open** (vi.) ፈነዳ
The package fell and tore open. ጥቅሉ ፡ ወደቀና ፡ ፈነዳ

**tear out**
1. መንጭቆ ፡ ወሰደ(በት). She tore the letter out of his hand. ደብዳቤውን ፡ ከእጁ ፡ መንጭቃ ፡ ወሰደችበት
2. ገነጠለ. Who tore out this page? ይህን ፡ ገጽ ፡ ማን ፡ ገነጠለው ?

**tear to pieces**
1. ዘነታተለ. The dog tore the rug to pieces. ውሻው ፡ ምንጣፉን ፡ ዘነታተለው
2. ተቀራመተ. The dogs tore the meat to pieces. ውሾቹ ፡ ሥጋውን ፡ ተቀራመቱት

**tear up** ቀደደ
She asked him to tear up the letter after he read it. ደብዳቤውን ፡ ካነበበ ፡ በኋላ ፡ እንዲቀደው ፡ ነገረችው

**tear up by the root** ነቃቀለ
The wind tore up trees by their roots. ነፋሱ ፡ ዛፎቹን ፡ ነቃቀላቸው
[See also 'hair, portion, shred']

**tear** (rhymes with 'pear'), n. ቀዳዳ
Can this tear be mended? ይህ ፡ ቀዳዳ ፡ ሊሰፋ ፡ ይችላል ?
[See also 'wear']

**tear** (rhymes with 'fear'), n.
1. እንባ. We listened to the funeral oration in tears. በቀብሩ ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ ንግግር ፡ እንባ ፡ እያነቀን ፡ አዳመጥን
2. ለቅሶ. Tears won't help you. ለቅሶ ፡ አይጠቅምሽም

**burst into tears**
The girl burst into tears. ልጃገረዲቱ ፡ በድንገት ፡ እንባዋን ፡ አጐረፈችው

**draw tears to one's eyes** እንባውን ፡ አመጣ
The sad story drew tears to my eyes. አሳዛኙ ፡ ታሪክ ፡ እንባዬን ፡ አመጣው

**move to tears** አስለቀሰ ፤ ልቡን ፡ ነካው
The woman's lament moved the people to tears. የሴትዮዋ ፡ የሐዘን ፡ እንጉርጉሮ ፡ ሰውን ፡ አስለቀሰ
The tale of the accident moved him to tears. ያደጋው ፡ ዜና ፡ ልቡን ፡ ነካው

**(be) moved to tears** እንባው ፡ መጣ
I was moved to tears when I heard about his death. የርሱን ፡ መሞት ፡ ስሰማ ፡ እንባዬ ፡ መጣ
[See also 'swim, wet']

**tear gas** የሚያስለቅስ ፡ ጢስ
The police dispersed the rioters with tear gas. ፖሊሶቹ ፡ ረብሸኞቹን ፡ በሚያስለቅስ ፡ ጢስ ፡ አባረሩዋቸው

**tease** (v.) አሾፈ
Some boys take pleasure in teasing their sisters. አንዳንድ ፡ ልጆች ፡ በእኅቶቻቸው ፡ ማሾፍ ፡ ይወዳሉ
*The child teases for everything he sees. ልጁ ፡ ያየውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ካልሰጣችሁኝ ፡ ብሎ ፡ ችክ ፡ ይላል

**tease** (n.)
What a tease she is! በሰው ፡ ቀላጅ ፡ ናት!

**teaspoon** የሻይ ፡ ማንኪያ
Use only one teaspoon of salt! አንድ ፡ የሻይ ፡ ማንኪያ ፡ ጨው ፡ ብቻ ፡ ጨምርበት

**teat** ጡት
The farmer washes the cow's teats before milking it. ገበሬው ፡ ከማለቡ ፡ በፊት ፡ የላሚን ፡ ጡት ፡ ያጥባል

**technical** የቴክኒክ
The broadcast was cut for technical reasons. በቴክኒክ ፡ ጉድለት ፡ ምክንያት ፡ የሬዲዮ ፡ ፕሮግራሙ ፡ ተቋረጠ

**technical term** ግብራዊ ፡ ስያሜ
Do you know the technical term for the inversion of letters? ፊደላት ፡ ቦታቸውን ፡ ቀይረው ፡ ሲገቡ ፡ ግብራዊ ፡ ስያሜያቸውን ፡ ታውቃለህ ?

**technicality**
1. የረቀቀ ፡ አገላለጽ. The technicality of the book puzzled me. የመጽሐፉ ፡ የረቀቀ ፡ አገላለጽ ፡ ግራ ፡ አጋባኝ
2. ሥርዓት. The contract was canceled because of a legal technicality. ሕጋዊ ፡ ሥርዓትን ፡ በሙሉ ፡ ባለመከተሉ ፡ ውሉ ፡ ፈረሰ

**technician** ቴክኒሺያን
He is studying to be a technician. ቴክኒሺያን ፡ ለመሆን ፡ በመማር ፡ ላይ ፡ ነው

**technique**
1. ዘዴ. Mounting a horse requires a certain technique. ፈረስ ፡ ላይ ፡ መውጣት ፡ ልዩ ፡ ዘዴ ፡ ይጠይቃል
2. ችሎታ. His technique in playing the violin is admired by all. የቫዮሊን ፡ አመታቱ ፡ ችሎታው ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ የተደነቀ ፡ ነው

**(be) tedious** ሰለቸ
This work is tedious. ይህ ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ ይሰለቻል

**teem, ~ with** ተርመሰመሰ
+The ground was teeming with ants. መሬቱ ፡ ላይ ፡ ጉንዳን ፡ ይርመሰመስ ፡ ነበር
*On holidays, the beaches teem with bathers. በበዓላት ፡ ቀን ፡ የባሕር ፡ ዳርቻ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ይሆናል

**teen-ager** [በዐሥራ ፡ ሶስትና ፡ በዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ መሀከል ፡ ያለ ፡ ወጣት]

**teens, be in one's ~** ደረሰ
The children are now in their teens. ልጆቹ ፡ የደረሱ ፡ ናቸው

**teeth,** see **tooth**

**teethe** ጥርስ ፡ አወጣ
A baby dribbles when it is teething. ሕፃን ፡ ጥርስ ፡ ሲያወጣ ፡ ለሃጩ ፡ ይዝረከረካል

**teetotaler** መጠጥ ፡ የማይቀምስ ፡ ሰው
Teetotalers are trying to have liquor sales banned. መጠጥ ፡ የማይቀምሱ ፡ ሰዎች ፡ መጠጥ ፡ እንዳይሸጥ ፡ ለማድረግ ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ናቸው

**telegram** ቴሌግራም
I received a telegram from my aunt. ከአክስቴ ፡ ቴሌግራም ፡ ደረሰኝ

**telegraph** ቴሌግራም ፡ አደረገ
I must telegraph him to come. እንዲመጣ ፡ ለሱ ፡ ቴሌግራም ፡ ማድረግ ፡ አለብኝ

**telegraph office** የቴሌግራም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት
The telegraph office is closed. የቴሌግራም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተዘግቷል

**telephone** (v.) ደወለ
I'll telephone you tomorrow. ነገ ፡ እደውልልሃለሁ

**telephone** (n.) ስልክ
He does all his business by telephone. ጉዳዩን ፡ ሁሉ ፡ የሚፈጽመው ፡ በስልክ ፡ ነው

**telephone call** የስልክ ፡ ጥሪ
Long-distance telephone calls are expensive. የሩቅ ፡ መሥመር ፡ የስልክ ፡ ጥሪ ፡ ውድ ፡ ነው
*How many telephone calls do you make a day? በቀን ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ስልክ ፡ ትደውላለህ ?

**telephone directory** የስልክ ፡ ቁጥር ፡ ማውጫ
His name is in the telephone directory. ስሙ ፡ በስልክ ፡ ቁጥር ፡ ማውጫው ፡ ውስጥ ፡ አለ

**telephone number** የስልክ ፡ ቁጥር
What's your telephone number? የስልክ ፡ ቁጥርህ ፡ ስንት ፡ ነው ?

**telephone operator** ስልክኛ
The telephone operator gave me the wrong number. ስልክኛዋ ፡ የተሳሳተ ፡ ቁጥር ፡ ሰጠችኝ

## television ቴሌቪዥን
Television was recently introduced to Ethiopia. ቴሌቪዥን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገባው ፡ በቅርቡ ፡ ነው

## tell (told)
1. ነገረ. He told me to give you this letter. ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ እንድሰጥህ ፡ ነግሮኛል
You failed in the exam? I told you so. በፈተናው ፡ ወደቅህ ? ምነው ፡ ነግሬህ
2. ተናገረ. He told the story of Christ on the cross. የኢየሱስን ፡ ስቅለት ፡ ታሪክ ፡ ተናገረ
3. አለ. I can't tell the difference between these two materials. የነዚህን ፡ ሁለት ፡ እቃዎች ፡ ልዩነት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አልችልም
4. አበሰረ. The angel told Mary that she would have a son. መልአኩ ፡ ማርያምን ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ እንደምትወልድ ፡ አበሰራት
5. ገለጸ. The book tells about his early life. መጽሐፉ ፡ ስለ ፡ ልጅነት ፡ ኑሮው ፡ ይገልጻል
6. አዘዘ. Don't tell me what to do! ምን ፡ እንደማደርግ ፡ አትዘዘኝ
7. ፍሬ ፡ ሰጠ. His hard efforts are beginning to tell. ከባድ ፡ ጥረቱ ፡ ፍሬ ፡ መስጠት ፡ ጀምሯል
8. ለየ. I can't tell which house is yours. ያንተ ፡ ቤት ፡ የትኛው ፡ እንደሆነ ፡ ለመለየት ፡ አልችልም
You can tell his paintings by the brilliant colors. የርሱን ፡ ሥዕሎች ፡ በደማቅ ፡ ቀለሞች ፡ ለመለየት ፡ ትችላለህ
9. ዐወቀ. You can never tell what's going to happen. ምን ፡ እንደሚመጣ ፡ ለማወቅ ፡ አይቻልም
*That stuff is hard! You're telling me? ያ ፡ ነገር ፡ ኀይለኛ ፡ ነው ! መቼ ፡ አጣሁት ?

**tell apart**
1. ለይቶ ፡ ዐወቀ. It is difficult to tell the twins apart. መንትዮቹን ፡ ለይቶ ፡ ማወቅ ፡ ያስቸግራል
2. ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ ቻለ. How do you tell the two apart? ሁለቱን ፡ እንዴት ፡ ለይተህ ፡ ለማወቅ ፡ ትችላለህ ?

**tell of** ገለጸ
Her smile told of her joy. ፈገግታዋ ፡ መደሰቷን ፡ ገለጸ

**tell off**
*She really told him off. ልክ ፡ ልኩን ፡ ነገረችው

**tell on**
1. አሳበቀ(በት). My brother told on me. ወንድሜ ፡ አሳበቀብኝ
2. አስታወቀ(በት). This hard work is telling on him. ሥራ ፡ እንደበዛበት ፡ ያስታውቅበታል

**tell time** ሰዓት ፡ ቈጠረ
Can your little boy tell time? ትንሹ ፡ ልጅህ ፡ ሰዓት ፡ ይቈጥራል ?

**all told** በጠቅላላው
We were twenty all told. በጠቅላላው ፡ ሀያ ፡ ነበርን

**can tell** ዐወቀ
How can you tell that it's an inferior quality? ያ ፡ ዝቅተኛ ፡ ዓይነት ፡ መሆኑን ፡ እንዴት ፡ ታውቃለህ ?

**to tell the truth** በእውነቱ
To tell the truth, I don't know. በእውነቱ ፡ አንጃ

## teller ገንዘብ ፡ ከፋይ
The bank teller put the money in a safe. የባንኩ ፡ ገንዘብ ፡ ከፋይ ፡ ገንዘቡን ፡ ካዝና ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጠው

## temerity ደፋርነት
His temerity in rescuing the child was praised by all. ውኃ ፡ ሊወስደው ፡ የነበረውን ፡ ልጅ ፡ ሲያድን ፡ ያሳየው ፡ ደፋርነት ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ተደነቀ

**have the temerity** ደፈረ
He had the temerity to push a policeman. ፖሊስ ፡ ለመግፋት ፡ ደፈረ

## temper (v.)
*A judge should temper justice with mercy. አንድ ፡ ዳኛ ፡ ፍትሕንና ፡ ርኅራኄን ፡ አስተባብሮ ፡ መፍረድ ፡ አለበት

**be tempered** በእሳት ፡ ተግሎ ፡ ተቀጠቀጠ
Iron must be tempered to keep it from losing its edge. ብረት ፡ እንዳይደንዝ ፡ በእሳት ፡ ተግሎ ፡ መቀጥቀጥ ፡ አለበት

## temper (n.)
1. ጠባይ. He has an even temper. ጠባዩ ፡ የረጋ ፡ ነው
2. ንዴት. You'll have to learn to curb your temper. ንዴትህን ፡ መግታት ፡ መማር ፡ አለብህ
3. ግልፍተኛ ፡ መሆን. His temper gets in his way. ግልፍተኛ ፡ መሆኑ ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆነበት

**bad temper** የቁጣ ፡ ጠባይ
The child exhibited a bad temper at an early

age. ልጁ ፡ ገና ፡ በልጅነቱ ፡ የቁጣ ፡ ጠባይ ፡ ይታይበታል

**(be in a) bad temper** ተበሳጨ
He is in a bad temper because he had an argument with his wife. ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ተነታርኮ ፡ ስለነበር ፡ ተበሳጭቷል

**fly into a temper** በንዴት ፡ ጦፈ
When he heard the story, he flew into a temper. ወሬውን ፡ ሲሰማ ፡ በንዴት ፡ ጦፈ

**keep one's temper** ታግሦ ፡ ዝም ፡ አለ
In spite of those insults, she managed to keep her temper. ያ ፡ ሁሉ ፡ ስድብ ፡ ሲወርድባት ፡ ታግሣ ፡ ዝም ፡ አለች

**lose one's temper** ተናደደ ፤ ተቈጣ
He loses his temper easily. በቀላሉ ፡ ይናደዳል ፡ (ይቈጣል)

**quick temper** ግልፍተኛነት
His quick temper overshadows his real kindness. ግልፍተኛነቱ ፡ እውነተኛ ፡ ደግነቱን ፡ ይሸፍነዋል

**send into a temper** አናደደ
His answer sent me into a temper. መልሱ ፡ አናደደኝ
[See also 'flash, hot, sour, vicious']

## temperament ጠባይ
The two brothers have entirely different temperaments. ሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ በጠባይ ፡ አይገናኙም
*Some people are noted for their temperament. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከመሬት ፡ ተነሥተው ፡ ግልፍ ፡ ይላቸዋል

## temperamental ግልፍተኛ ፤ ኩርፍተኛ
The temperamental opera singer caused many problems for the manager. ግልፍተኛው ፡ (ኩርፍተኛው) ፡ ዘፋኝ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁን ፡ በጣም ፡ አስቸገረው

**temperamental attitude** ትክክለኛ ፡ ጠባይ
He has the temperamental attitude for the life of a monk. ለምንኵስና ፡ኑሮ ፡ የሚፈለገው ፡ ትክክለኛ ፡ ጠባይ ፡ አለው

## temperance መጠንን ፡ ማወቅ
Temperance should be applied not only to food and drink, but also to work and play. መጠንን ፡ ማወቅ ፡ በምግብና ፡ በመጠጥ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሥራና ፡ በጨዋታም ፡ መሆን ፡ አለበት
*Temperance in drink is best for you. በልክ ፡ መጠጣት ፡ ይጠቅምሃል
*Temperance in speech is a good quality for a conciliator. አስታራቂ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ረጋ ፡ ያለ ፡ ንግግር ፡ ያስፈልገዋል

## temperate
1. የረጋ. Although I was angry, I made a temperate reply. ብናደድም ፡ የረጋ ፡ መልስ ፡ ሰጠሁት
2. ራሱን ፡ የሚቈጣጠር. He is a temperate man, and never drinks too much. ራሱን ፡ የሚቈጣጠር ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ አይጠጣም

**temperate climate** ወይና ፡ ደጋ
We live in a temperate climate. የምኖርበት ፡ ቦታ ፡ ወይና ፡ ደጋ ፡ ነው

**be temperate** ለስለስ ፡ አለ
Be temperate in your language! ስትናገር ፡ ለስለስ ፡ በል

## temperature
1. ያየር ፡ ሁኔታ. In California, there is a great difference between morning and evening temperatures. በካሊፎርንያ ፡ ውስጥ ፡ በጧቱና ፡ በማታው ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ መካከል ፡ ትልቅ ፡ ልዩነት ፡ አለ
2. ትኩሳት. Did the doctor take your temperature this morning? ዛሬ ፡ ጧት ፡ ሐኪሙ ፡ ትኩሳትህን ፡ ለካቷል ?
3. ሙቀት. The temperature of the molten metal was 1,000 degrees. የቀለጠው ፡ ብረት ፡ ሙቀት ፡ ሺ ፡ ዲግሪ ፡ ነበር

**extremes of temperature**
*In Addis Ababa, there are no extremes of temperature. አዲስ ፡ አበባ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ሙቀት ፡ ወይም ፡ ቅዝቃዜ ፡ የለውም

## tempest ኀይለኛ ፡ ነፋስ
The tempest subsided, leaving leaves and broken branches in the street. ኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ መንገዱን ፡ በብዙ ፡ ቅጠሎችና ፡ ቅርንጫፎች ፡ ሞልቶ ፡ ጸጥ ፡ አለ

**tempest of laughter**
*A tempest of laughter greeted his question. ጥያቄ ፡ ሲጠይቅ ፡ ሰው ፡ በሣቅ ፡ ፈነዳ

## temple
1. ቤተ ፡ መቅደስ. On Sunday, the temple was full of people. እሑድ ፡ ዕለት ፡ ቤተ ፡ መቅደሱን ፡ ሰው ፡ ግጥም ፡ ብሎበት ፡ ነበር
2. ቅንጥ. His temples are getting grey. ቅንጥና ፡ ቅንጡ ፡ ሸብቷል ፡ (or, የራሱ ፡ ጐንና ፡ ጐን ፡ ሸብቷል)

## tempo
1. ስልት. The tempo of the music was too

fast for her to follow. የሙዚቃው ፡ ስልት ፡ በጣም ፡ ፈጣን ፡ ስለነበር ፡ ልትከተለው ፡ አልቻለችም
2. ፍጥነት. The tempo of his heartbeat increased. የልቡ ፡ ትርታ ፡ ፍጥነት ፡ ጨምሯል

**temporal** ዓለማዊ
The temporal power of the pope is limited. የጳጳሱ ፡ ዓለማዊ ፡ ሥልጣን ፡ የተወሰነ ፡ ነው

**temporarily** ለጊዜው
The barricade was placed there temporarily, not permanently. መንገድ ፡ መዝጊያው ፡ የተቀመጠው ፡ ለጊዜው ፡ እንጂ ፡ ለዘለቄታው ፡ አይደለም

**temporary** (= adv.) ለጊዜው
This is only a temporary solution. ለጊዜው ፡ እንደ ፡ መፍትሔ ፡ የሚያገለግል ፡ ነው

**tempt**
1. ገፋፋ. The warm weather tempted us to go for a swim. ሙቀቱ ፡ ለዋና ፡ እንድንሄድ ፡ ገፋፋን
2. አስጐመጀ. That candy tempts me. ከረሜላው ፡ አስጐምጅቶኛል
*He is tempting fate by driving with a bad tire. በተበላሸ ፡ ጎማ ፡ በመንዳት ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ አደጋ ፡ ይጐትታል

**be tempted**
1. ተገፋፋ. The hungry child was tempted to steal the bread. የራበው ፡ ልጅ ፡ ዳቦውን ፡ ለመስረቅ ፡ ተገፋፍቶ ፡ ነበር
2. አማረ(ው). +When he saw the money just lying on the desk, he was tempted to steal it. ገንዘቡ ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ቢያየው ፡ መስረቅ ፡ አማረው

**be sorely tempted** በጣም ፡ አማረ(ው)
+I was sorely tempted to buy it. መግዛት ፡ በጣም ፡ አምሮኝ ፡ ነበር

**temptation** ፈተና ፤ የሚፈታተን ፡ ነገር
He was powerless to resist the temptation. ፈተናውን ፡ (የሚፈታተነውን ፡ ነገር) ፡ ለመቋቋም ፡ ኀይል ፡ አጣ
*No temptation could make him be false to a friend. ምንም ፡ ነገር ፡ ቢያሳስተው ፡ ጓደኛውን ፡ አይከዳም

**be a temptation** አጓጓ
The sight of the food on the table was a temptation to the hungry child. በጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ምግብ ፡ ማየት ፡ ትንሹን ፡ ልጅ ፡ አጓጓው

**yield to temptation** ፍላጎቱ ፡ አሸነፈው
He yielded to the temptation and stole the money. ፍላጎቱ ፡ አሸንፎት ፡ ገንዘቡን ፡ ሰረቀ
[See also 'succumb']

**(be) tempting** አጓጓ
Your offer is tempting. ያቀረብክልኝ ፡ ሐሳብ ፡ ያጓጓል

**ten** ዐሥር

**ten o'clock** አራት ፡ ሰዓት
I will come at ten o'clock. ባራት ፡ ሰዓት ፡ እመጣለሁ

**tenacious**
1. ጥብቅ. His grip is tenacious and hard to shake loose. አያያዙ ፡ ጥብቅ ፡ ስለሆነ ፡ ለማላቀቅ ፡ ያስቸግራል
2. ታላቅ. Her tenacious courage kept the bandits from taking her money. በታላቅ ፡ ጉብዝናዋ ፡ ገንዘቧን ፡ ከሽፍቶች ፡ አዳነች
3. ከፍተኛ. Due to his tenacious memory, he is highly appreciated as a secretary. በከፍተኛ ፡ የማስታወስ ፡ ችሎታው ፡ በጸሓፊነቱ ፡ በጣም ፡ ይመሰገናል

**tenacity**
*The tenacity of his grip is amazing. ሲጨብጥ ፡ ጥንካሬው ፡ እንዲህ ፡ አይደለም

**tenant**
1. ተከራይ. We terminated our contract with the tenant. ከተከራዩ ፡ ጋር ፡ የነበረንን ፡ ኮንትራት ፡ ጨረስን
2. የሚኖር. Birds are tenants of the trees. ወፎች ፡ የሚኖሩት ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ነው

**tenant farmer** ጭሰኛ
The tenant farmers get a percentage of the crop. ጭሰኞቹ ፡ ከምርቱ ፡ ከፊሉ ፡ ይደርሳቸዋል

**tend** (vt.) ጠበቀ
The shepherds were tending their sheep. እረኞቹ ፡ በጎቹን ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር

**tend** (vi.)
1. ሰበር ፡ አለ. The road tends to the south here. እዚህ ፡ ጋ ፡ መንገዱ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ሰበር ፡ ይላል
2. ወደደ. He tends to eat too much. ብዙ ፡ መብላት ፡ ይወዳል
3. ዝንባሌ ፡ አለው. He tends to follow the ideas of his parents. የወላጆቹን ፡ አርአያነት ፡ የመከተል ፡ ዝንባሌ ፡ አለው
4. ጠባይ ፡ አለው. Fruit tends to decay quickly. ፍራፍሬ ፡ ቶሎ ፡ የመበስበስ ፡ ጠባይ ፡ አለው

5. ያዘ(ተያዘ). With careful tending, the soil will fructify. በጥንቃቄ ፡ ከተያዘ ፡ አፈሩ ፡ ይለማል

**tend (to)**

1. ቈሰቈሰ. Who is going to tend to the fire? እሳቱን ፡ ማን ፡ ሊቈሰቍስ ፡ ነው ?

2. ሥራ 1 ፈጸመ. Tend to your own business! ሥራህን ፡ ሥራ ፡ (ፈጽም)

3. ኀላፊ ፡ ሆነ. Who is going to tend to the preparations for the banquet? ለግብዣው ፡ ዝግጅት ፡ ኀላፊ ፡ የሚሆነው ፡ ማነው ?

**tendency** (tendencies)

1. ዝንባሌ. All governments have a tendency to increase taxes. መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ ታክስ ፡ የመጨመር ፡ ዝንባሌ ፡ አላቸው

2. ፍላጎት. Boys have a stronger tendency to fight than girls. ከሴቶች ፡ ይልቅ ፡ ወንዶች ፡ ለጥል ፡ የበለጠ ፡ ፍላጎት ፡ አላቸው

**have a tendency to**

1. ወደደ. He has a tendency to exaggerate the importance of what he does. የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ አጋኖ ፡ መናገር ፡ ይወዳል

2. እንደ + verbal noun + አለ. Wood has a tendency to swell if it gets wet. ዕንጨት ፡ ሲረጥብ ፡ እንደ ፡ መነፋት ፡ ይላል

**tendentious**

*Don't believe those tendentious reports! ይህን ፡ ሐሳባቸውን ፡ ለመደገፍ ፡ ሲል ፡ ያቀረቡትን ፡ ሪፖርት ፡ አትመነው

**tender** (v.) አቀረበ

He tendered his resignation to the prime minister. የሥራ ፡ መልቀቂያ ፡ ደብዳቤውን ፡ ለጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አቀረበ

**tender** (n.)

1. ጨረታ. We have received tenders for the new bridge. ላዲሱ ፡ ድልድይ ፡ ጨረታ ፡ ደርሶናል

2. ጥያቄ. She refused his tender of marriage. ለጋብቻ ፡ ያቀረበላትን ፡ ጥያቄ ፡ አልተቀበለችውም

**tender** (adj.)

1. ለስላሳ. The meat is very tender. ሥጋው ፡ በጣም ፡ ለስላሳ ፡ ነው

2. የለዘበ. He spoke tender words to the child. ልጁን ፡ በለዘበ ፡ አንደበት ፡ አናገረው

3. ለምለም. The leaves in spring are green and tender. በጸደይ ፡ ወራት ፡ ቅጠሎች ፡ አረንጓዴና ፡ ለምለም ፡ ይሆናሉ

4. በቀላሉ ፡ የሚቈጣ. His tender skin bruises at the slightest blow. በቀላሉ ፡ የሚቈጣ ፡ ቆዳው ፡ ትንሽ ፡ ሲመቱት ፡ ሰምበር ፡ ያወጣል

5. የጨቅላነት. Two years old is a tender age. ሁለት ፡ ዓመት ፡ የጨቅላነት ፡ ዓመት ፡ ነው

**tender manner** ለዘብታ

He handles people in a tender manner. ሰው ፡ በለዘብታ ፡ ይይዛል

**be at a tender age**

She is still at a tender age. ገና ፡ ጨቅላ ፡ ነች

**be tender** አልጠገገም

The wound is still tender. ቁስሉ ፡ ገና ፡ አልጠገገም

**have a tender heart** ገር ፡ ሆነ

She has a tender heart and would never hurt anyone. ገር ፡ ስለሆነች ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ አታስቀይምም

**make tender** አለሰለሰ

Marinate the meat to make it more tender! ሥጋውን ፡ ይበልጥ ፡ ለማለስለስ ፡ በቅመም ፡ ዘፍዝፈው

**tenderhearted** ርኅሩኅ

She is so tenderhearted that she cries whenever she sees anybody hurt. በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ ስለሆነች ፡ የተጐዳ ፡ ሰው ፡ ስታይ ፡ ያስለቅሳታል

**tenderize** በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅመማት ፡ አብስሎ ፡ አለሰለሰ

The cook tenderized a tough cut of meat. ወጥቤቱ ፡ አኘውን ፡ ሥጋ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅመማት ፡ አብስሎ ፡ አለሰለሰው

**tenderly, embrace ~** እቅፍ ፡ አደረገ

He embraced his child tenderly. ልጁን ፡ እቅፍ ፡ አደረገው

**tendon** ጅማት

The tendon in the back of his heel was cut. ከተረከዙ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ጅማት ፡ ተቈረጠ

**tenement** ቤት

The poor people live in miserable tenements. ድኾቹ ፡ ሰዎች ፡ በሚያሰቅቁ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ

**tenet** ትምህርት

Do you accept the tenets of the church? የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ትምህርት ፡ ትቀበላለህ ?

**tenfold** ዐሥር ፡ እጅ

Our output increased tenfold. ውጤታችን ፡ በዐሥር ፡ እጅ ፡ ጨመረ

**tennis** ቴኒስ

**tenor**

1. [በሙዚቃ ፡ ውስጥ ፡ ከቀጭን ፡ መለስ ፡ ከወፍራም ፡ ቀጠን ፡ ያለ ፡ የወንድ ፡ ድምፅ]

2. አዝማሚያ. The tenor of his sermon was generally in support of reform. የስብከቱ ፡ አዝማሚያ ፡ መሻሻልን ፡ የሚደግፍ ፡ ነበር
*She knew enough Amharic to get the tenor of what was being said. ምን ፡ እንደተባለ ፡ ለመገመት ፡ ያህል ፡ የሚያስችላት ፡ ያማርኛ ፡ ዕውቀት ፡ ነበራት

**tense** (n.) ጊዜያት
Nearly every language can express tense. ማንኛቸውም ፡ ቋንቋ ፡ ጊዜያትን ፡ ሊገልጽ ፡ ይችላል
[See also 'future, past']

**tense** (adj.)
1. የተወጠረ. A tense rope is likely to break. የተወጠረ ፡ ገመድ ፡ ሊበጠስ ፡ ይችላል
2. የመንፈስ ፡ ጭንቀት ፡ ያለበት. A tense person tends to smoke a lot. የመንፈስ ፡ ጭንቀት ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ማጨስ ፡ ይወዳል

**tense moment** የጭንቀት ፡ ሁኔታ
A tense moment occurred when the soldiers of the two armies faced each other. ሁለቱ ፡ ጦር ፡ ሰራዊቶች ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሲገናኙ ፡ የጭንቀት ፡ ሁኔታ ፡ ተፈጠረ

**be tense** ጭንቅ ፡ አለ
He was very tense just before he started to take the exam. ፈተና ፡ ሊፈተን ፡ ሲል ፡ ጭንቅ ፡ ብሎት ፡ ነበር

**tension**
1. መወጠር. I don't think that the rope will withstand the tension. ገመዱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መወጠር ፡ የሚችል ፡ አይመስለኝም
2. አለመግባባት. Since the quarrel over the car, there has been tension between the two brothers. በመኪናዋ ፡ ምክንያት ፡ ከተጣሉ ፡ ወዲህ ፡ በሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ መካከል ፡ አለመግባባት ፡ አለ
3. የመንፈስ ፡ ጭንቀት. A mother feels tension when her baby is sick. ልጇ ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ እናት ፡ የመንፈስ ፡ ጭንቀት ፡ ይሰማታል

**tent** ድንኳን
The students pitched a tent on the mountain. ተማሪዎቹ ፡ ተራራው ፡ ላይ ፡ ድንኳን ፡ ተከሉ

**tentative** ጊዜያዊ
This is only a tentative estimate. ይህ ፡ ጊዜያዊ ፡ ግምት ፡ ነው
My tentative plans are to visit Europe first. መጀመሪያ ፡ ጊዜያዊ ፡ እቅዴ ፡ አውሮፓን ፡ ለመጐብኘት ፡ ነው

**be tentative** በውጥን ፡ ላይ ፡ ነው
His plans are still tentative. እቅዱ ፡ ገና ፡ በውጥን ፡ ላይ ፡ ነው

**tenth**
1. ዐሥረኛ. Ruth is in tenth grade. ሩት ፡ የዐሥረኛ ፡ ክፍል ፡ ተማሪ ፡ ናት
2. ዐሥር. We get paid on the tenth of the month. ወር ፡ በገባ ፡ ባሥር ፡ እንከፈላለን

**one-tenth** አንድ ፡ ዐሥረኛ
It's not even one-tenth finished. አንድ ፡ ዐሥረኛው ፡ እንኳን ፡ አላለቀም

**tenuous**
1. ቀጭን. The tenuous web of the spider was destroyed in no time. ቀጭኑ ፡ የሸረሪት ፡ ድር ፡ባንዳፍታ ፡ ተበጣጠሰ
2. መሠረተ ፡ ቢስ. His tenuous argument was soon destroyed by his opponent. መሠረተ ፡ ቢስ ፡ ምክንያቱን ፡ ተከራካሪው ፡ ፉርሽ ፡ አደረገበት
*His hold was tenuous, and he soon slipped and fell. አጥብቆ ፡ ስላልያዘ ፡ ወዲያው ፡ አዳልጦት ፡ ወደቀ

**tenure** የሥልጣን ፡ ዘመን
In America, the length of tenure for the President is four years. በአሜሪካ ፡ የፕሬዚዳንትነት ፡ የሥልጣን ፡ ዘመን ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ነው
*Because of his tenure, the professor could not be dismissed. ለዘለቄታው ፡ የተቀጠረ ፡ ስለሆነ ፡ ፕሮፌሰሩን ፡ ከሥራ ፡ ለማስወጣት ፡ አልተቻለም

**security of tenure**
*The farmer wants security of tenure. ገበሬው ፡ መሬቱን ፡ እንዳያስለቅቁት ፡ ዋስትና ፡ ይፈልጋል
[See also 'land tenure']

**tepid** ለብ ፡ ያለ
The water is tepid. ውኃው ፡ ለብ ፡ ያለ ፡ ነው

**term**
1. ውል. He gave us very good terms when we bought the land. መሬቱን ፡ ስንገዛ ፡ ጥሩ ፡ ውል ፡ አደረገልን
2. ድርድር. He gave us easy terms on the loan. ለብድሩ ፡ ደኅና ፡ ድርድር ፡ አቀረበልን
3. የትምህርት ፡ ወቅት. Most schools have a fall term and a spring term. አብዛኛዎቹ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የበልግና ፡ የጸደይ ፡ የትምህርት ፡ ወቅት ፡ አሏቸው
4. ቃል (pl. ቃላት). Medical terms are not understood by laymen. የሕክምና ፡ ቃላትን ፡ ሕክምና ፡ ያልተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ሊረዷቸው ፡ አይችሉም
5. አነጋገር. He spoke of you in friendly terms. ስላንተ ፡ በወዳጅነት ፡ አነጋገር ፡ ተናገረ
6. ዘመን. During his long term of imprisonment, he learned several languages. በረጅም ፡ የእስራት ፡ ዘመኑ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ቋንቋዎች ፡ ተማረ

7. የሥራ ፡ ጊዜ. The President's term will end in October. የፕሬዚዳንቱ ፡ የሥራ ፡ ጊዜ ፡ በጥቅምት ፡ ያልቃል
*The victor dictates the terms to the defeated army. ድል ፡ አድራጊው ፡ ተሸናፊው ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንዳለበት ፡ ይወስናል
*We heard him refer to you in flattering terms. ስምህን ፡ በደግ ፡ ሲያነሣ ፡ ሰማነው

**(be on) bad terms** ተጣሉ
We are on bad terms because he refused to give back the money that he took from me. ገንዘቤን ፡ ወስዶ ፡ አልመልስልህ ፡ ስላለኝ ፡ ተጣልተናል

**bring to terms** አስገበረ
After a long fight, we brought the enemy to terms. ከረጅም ፡ ጊዜ ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ጠላትን ፡ አስገበርነው

**come to terms** ተስማማ
We have been trying to come to terms for months now. ከብዙ ፡ ወራት ፡ ጀምሮ ፡ ለመስማማት ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነን

**(on) equal terms** በእኩልነት ፡ ደረጃ
They meet each other on equal terms. ሲገናኙ ፡ በእኩልነት ፡ ደረጃ ፡ ይተያያሉ

**(be on) good terms** ስምም ፡ ናቸው
I am on good terms with my boss. ከለቃዬ ፡ ጋር ፡ ስምም ፡ ነኝ

**on (one's) terms** ባሰበው ፡ መሠረት
I insist on doing it on my terms. እኔ ፡ ባሰብኩት ፡ መሠረት ፡ መሠራት ፡ አለበት
[See also 'familiar, general, intimate, round, speaking, technical']

**(be) termed** ሊባል ፡ ይችላል
He might be termed handsome. መልከ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይችላል

**(be) terminable** ተቋረጠ
The contract is terminable in five years. ውሉ ፡ ባምስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ይቋረጣል

**be terminable by** ሊያቋርጥ ፡ ቻለ
+The contract was terminable by either party. ውሉን ፡ ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ አንደኛው ፡ ሊያቋርጥ ፡ ይችል ፡ ነበር

**terminal** (n.) ጣቢያ
The railway terminal is not far from here. የባቡር ፡ ጣቢያው ፡ ከዚህ ፡ ብዙ ፡ አይርቅም

**terminal** (adj.) የመጨረሻ
There is a terminal examination at the end of school. ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሲዘጋ ፡ የመጨረሻ ፡ ፈተና ፡ ይሰጣል
*His illness is terminal. በሽታው ፡ ከሞት ፡ የሚያደርስ ፡ ነው

**terminal point** መጨረሻ
The terminal point was soon reached. ወዲያውኑ ፡ ከመጨረሻው ፡ ደረስን

**terminate** (vt.) አቋረጠ
We terminated our contract with the tenant. ከተከራዩ ፡ ጋር ፡ የነበረንን ፡ ውል ፡ አቋረጥን

**terminate** (vi.)
1. አለቀ. The case terminated in a settlement. ክሱ ፡ በዕርቅ ፡ አለቀ
2. አበቃ. The regency will terminate when the king comes of age. ንጉሡ ፡ ለአካለ ፡ መጠን ፡ ሲደርስ ፡ እንደራሴነቱ ፡ ያበቃል

**be terminated** ተሰረዘ
His contract was terminated. ውሉ ፡ ተሰረዘ

**termination**
*The termination of the school year is in June. የትምህርት ፡ ጊዜው ፡ የሚያልቀው ፡ በሰኔ ፡ ነው
*The termination of the war is desired by all. ጦርነቱ ፡ እንዲያበቃ ፡ ሁሉም ፡ ይመኛል

**terminology** የተለዩ ፡ ቃላት
Do you know the terminology electricians use? የኤሌክትሪክ ፡ ሠራተኞች ፡ የሚጠቀሙባቸውን ፡ የተለዩ ፡ ቃላት ፡ ታውቃለህ ?

**terminus** ተራ
The bus terminus was crowded. የአውቶቡሱ ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነበር

**termite** ምስጥ
Termites have weakened the walls of the house. የቤቱን ፡ ግድግዳ ፡ ምስጥ ፡ በልቶታል

**terrace** (v.) ከታሪ ፡ አበጀ
The farmer terraced the mountainsides. ገበሬው ፡ የተራራውን ፡ ጥግ ፡ ከታሪ ፡ አበጀ

**terrace** (n.)
1. በረንዳ. We sat on the terrace and drank beer. በረንዳው ፡ ላይ ፡ ተቀምጠን ፡ ቢራ ፡ ጠጣን
2. ከታሪ. The terrace was so narrow that only a few plants could grow there. ከታሪው ፡ በጣም ፡ ጠባብ ፡ ስለሆነ ፡ ሊበቅሉ ፡ የሚችሉት ፡ ዕፀዋት ፡ ጥቂት ፡ ናቸው

**terrain** መሬት
The terrain was too rough even for a Land Rover to cross. መሬቱ ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ ስለሆነ ፡ በላንድ ፡ ሮቨር ፡ እንኳን ፡ ለማቋረጥ ፡ አይቻልም

**terrestrial**

1. የመሬት. The terrestrial features are obscured by clouds. የመሬቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ገጾች ፡ በደመና ፡ ተሸፍነው ፡ ነበር

2. ምድራዊ. Terrestrial pleasures earn no merit for the world to come. ምድራዊ ፡ ደስታ ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ አያስጥም

3. በየብስ ፡ ላይ ፡ የሚኖር. Cows, lions, and elephants are terrestrial animals while fish live in the sea. ላሞች ፡ አንበሶችና ፡ ዝሆኖች ፡ በየብስ ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ እንስሳት ፡ ሲሆኑ ፡ ዓሣዎች ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው

**terrible**

1. ኀይለኛ. The terrible storm killed more than two thousand persons. ኀይለኛው ፡ ማዕበል ፡ ከሁለት ፡ ሺ ፡ ሰው ፡ በላይ ፡ ገደለ
The heat is terrible during the summer. በበጋ ፡ሙቀቱ ፡ ኀይለኛ ፡ ነው

2. መጥፎ. The weather is terrible. አየሩ ፡ መጥፎ ፡ ነው

3. በጣም ፡ የሚያሰጋ. There is a terrible water shortage now. አሁን ፡ በጣም ፡ የሚያሰጋ ፡ የውኃ ፡ እጥረት ፡ አለ

**terrific**

1. ኀይለኛ. A terrific earthquake shook Japan. ኀይለኛ ፡ የመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ጃፓንን ፡ አናወጣት

2. ድንቅ. This is terrific! ይህ ፡ ድንቅ ፡ ነው

**terrify** (terrified)

1. አስደነገጠ. His glare terrifies the secretary. ግልምጫው ፡ ጸሓፊውን ፡ ያስደነግጣታል

2. አስፈራራ. They terrified the shopkeepers to make them pay money. ገንዘብ ፡ እንዲሰጧቸው ፡ ለማድረግ ፡ ባለ ፡ ሱቆቹን ፡ አስፈራሯቸው

3. (= intrans.) ፈራ. +Airplane trips terrify her. በአውሮፕላን ፡ መጓዝ ፡ ትፈራለች

**be terrified** በጣም ፡ ፈራ
The child was terrified of being left alone in that big house. በዚያ ፡ ሰፊ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ብቻውን ፡ ስለቀረ ፡ ሕፃኑ ፡ በጣም ፡ ፈራ

**territorial**

1. የግዛት. Ethiopia will defend her territorial integrity. ኢትዮጵያ ፡ የግዛት ፡ አንድነቷን ፡ ታስከብራለች

2. ብሔራዊ. A territorial army is going to be formed. ብሔራዊ ፡ ጦር ፡ ሊቋቋም ፡ ነው

**territorial waters** የባሕር ፡ ክልል
Our territorial waters extend twelve miles out from our coastline. የባሕር ፡ ክልላችን ፡ ከጠረፋችን ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ማይል ፡ ይርቃል

**territory** (territories)

1. አገር. The territory was once inhabited by pagan tribes. ባገሩ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አረመኔ ፡ ጐሳዎች ፡ ይኖሩበት ፡ ነበር

2. ግዛት. Angola is a large Portuguese territory in Africa. አንጎላ ፡ በአፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሰፊ ፡ የፖርቱጋል ፡ ግዛት ፡ ነው
The territory he rules is not large. ግዛቱ ፡ ሰፊ ፡ አይደለም

3. ክልል. The salesman's territory is outside Los Angeles. የአሻሻጩ ፡ ክልል ፡ ከሎስ ፡ አንጀለስ ፡ ውጭ ፡ ነው
*How much territory must he cover in a day? በቀን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መጓዝ ፡ አለበት ?

**terror**

1. ሽብር. The townspeople's terror is due to the fear of the plague. የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ ሽብር ፡ ወረርሽኙን ፡ በመፍራት ፡ ነው

2. በጥባጭ. This child is the terror of the neighborhood. ይህ ፡ ልጅ ፡ የሰፈሩ ፡ በጥባጭ ፡ ነው
*We were speechless with terror. ተደናግጠን ፡ መናገር ፡ አቃተን

**have a terror of** ፈራ
She has a terror of the dark. ጭለማ ፡ ትፈራለች
[See also 'strike']

**terrorist** ዐመፀኛ
The terrorists threatened to bring down the government. ዐመፀኞቹ ፡ መንግሥቱን ፡ ለመገልበጥ ፡ አስፈራሩ

**terror-stricken, leave ~** በድንጋጤ ፡ በድን ፡ አደረገ
The lightning left the children terror-stricken. መብረቁ ፡ ሕፃናቱን ፡ በድንጋጤ ፡ በድን ፡ አደረጋቸው

**terrorize** አሸበረ
The tiger terrorized the village. ነብሩ ፡ መንደሩን ፡ አሸበረ

**terse** ቁርጥ ፡ ያለ
"No" was his terse reply when I asked him to come with me. ከኔ ፡ ጋር ፡ እንዲመጣ ፡ በጠየቅሁት ፡ ጊዜ ፡ እምቢ ፡ በማለት ፡ ቁርጥ ፡ ያለ ፡ መልስ ፡ ሰጠኝ

**few and terse** እጥር ፡ ምጥን
His words were few and terse. ንግግሩ ፡ እጥር ፡ ምጥን ፡ ያለ ፡ ነበር

**test** (v.)

1. ፈተነ. The teacher tested me in arithmetic today. አስተማሪው ፡ ዛሬ ፡ ሒሳብ ፡ ፈተነኝ

Misfortune tests a person's character. ክፉ ፡ ቀን ፡ የሰውን ፡ ጠባይ ፡ ይፈትናል
He tested the boy's honesty by leaving money on the table. ገንዘብ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ በመተው ፡ የልጁን ፡ ታማኝነት ፡ ፈተነ
2. ፈተና ፡ ሰጠ. The teacher tests the students once a week. አስተማሪው ፡ በሳምንት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለተማሪዎቹ ፡ ፈተና ፡ ይሰጣል
3. አየ(ለት). The mechanic tested the brakes of my car. ሜካኒኩ ፡ የመኪናዬን ፡ ፍሬን ፡ አየልኝ
4. መረመረ. They tested his blood to see whether there was any poison in it. መርዝ ፡ እንዳለበት ፡ ለማየት ፡ ደሙን ፡ መረመሩት

**test out** ሞከረ
He tested out his theory in the laboratory. ፅንሰ ፡ ሐሳቡን ፡ በቤተ ፡ ሙከራው ፡ ውስጥ ፡ ሞከረ

**test** (n.)
1. ፈተና. You have to take a test before you get a driver's license. የመኪና ፡ መንጃ ፡ ፈቃድ ፡ ከማግኘትህ ፡ በፊት ፡ ፈተና ፡ መውሰድ ፡ አለብህ
2. ሙከራ. The atomic test was held on a small island in the ocean. በውቅያኖሱ ፡ ውስጥ ፡ በምትገኝ ፡ ትንሽ ፡ ደሴት ፡ ላይ ፡ የአውቶሚክ ፡ ሙከራ ፡ ተደረገ
3. የምርመራ ፡ ውጤት. The blood test showed that he had malaria. የደም ፡ ምርመራው ፡ ውጤት ፡ ወባ ፡ እንዳለበት ፡ አመለከተ

**test case** መፈተኛ
This accusation will be a test case for the new law. ይህ ፡ ክስ ፡ ላዲሱ ፡ ሕግ ፡ መፈተኛ ፡ ይሆናል

**put to the test** መፈተኛ ፡ ሆነ
The incident put their friendship to the test. የደረሰው ፡ ነገር ፡ ለወዳጅነታቸው ፡ መፈተኛ ፡ ሆነ

**testament** ኑዛዜ
His testament was written on parchment. ኑዛዜው ፡ የተጻፈው ፡ በብራና ፡ ላይ ፡ ነበር
[See also 'New Testament, Old Testament']

**testicle** የብልት ፡ ፍሬ
His testicle was diseased. የብልቱን ፡ ፍሬ ፡ ታሟል

**testify** (testified) መሰከረ
Have you anything further to testify? ሌላ ፡ የምትመሰክረው ፡ ነገር ፡ አለህ ?
She testified that she did not see the robbery. ስርቆቱን ፡ እንዳላየች ፡ መሰከረች

**testify to** አመለከተ
His words testify to his anger. ንግግሩ ፡ መናደዱን ፡ ያመለክታል

**testimonial** (n.) ሰዎች ፡ የሚሰጡት ፡ ምስክርነት
The advertiser has published testimonials of his product. የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ አዘጋጁው ፡ ስለ ፡ እቃው ፡ ጥሩነት ፡ ሰዎች ፡ የሚሰጡትን ፡ ምስክርነት ፡ በጽሑፍ ፡ አወጣ

**testimonial** adj. (= adv.) ስለ ፡ ክብሩ
He was given a testimonial dinner. ስለ ፡ ክብሩ ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ተደረገለት

**testimony** (testimonies)
1. ማስረጃ. You must produce testimony for your statement. ላልከው ፡ ነገር ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አለብህ
2. የምስክርነት ፡ ቃል. His testimony was declared invalid. የምስክርነት ፡ ቃሉ ፡ ውድቅ ፡ ሆነ

**be testimony of** አመለከተ
His smile is testimony of his joy. ፈገግታው ፡ መደሰቱን ፡ ያመለክታል

**in testimony of** ለመግለጽ
The pupils presented their teacher with a watch in testimony of their affection. ተማሪዎቹ ፡ ፍቅራቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ ላስተማሪያቸው ፡ የሰዓት ፡ ስጦታ ፡ አበረከቱለት

**testing** የፈተና
My brother works in the testing division. ወንድሜ ፡ በፈተና ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ይሠራል

**tether** (v.) አሰረ
He tethered the horses to a tree. ፈረሶቹን ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ አሰራቸው

**tether** (n.) የታሰረበት ፡ ገመድ
The cow broke the tether and ran off. ላሟ ፡ የታሰረችበትን ፡ ገመድ ፡ በጥሳ ፡ አመለጠች

**text**
1. ቃል. The text of the agreement was in two languages. የውሉ ፡ ቃል ፡ የተጻፈው ፡ በሁለት ፡ ቋንቋ ፡ ነበር
2. የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጥቅስ. The minister preached on the text, "Blessed are the merciful". ሰባኪው ፡ « ምሕረት ፡ የሚያደርጉ ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው » ፡ በሚል ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጥቅስ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ስብከት ፡ አደረገ
3. መጽሐፍ. You have to simplify your text for the first grade students. ላንደኛ ፡ ክፍል ፡ ተማሪዎች ፡ መጽሐፍህን ፡ ቀላል ፡ አድርገህ ፡ መጻፍ ፡ አለብህ
4. ጽሑፍ. This history contains 300 pages of text and about 50 pages of maps. ይህ ፡ ታሪ

ከ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ገጽ ፡ ጽሑፍና ፡ አምሳ ፡ ገጽ ፡ ካርታዎች ፡ አሉት

**textbook** የመማሪያ ፡ መጽሐፍ
This bookstore sells only textbooks. ይህ ፡ የመጻሕፍት ፡ መደብር ፡ የመማሪያ ፡ መጻሕፍት ፡ ብቻ ፡ ይሸጣል

**textile** ጨርቃ ፡ ጨርቅ
Textiles are now being made in Ethiopia. ጨርቃ ፡ ጨርቅ ፡ አሁን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይሠራል

**texture**
*The texture of the cloth is fine, almost like silk. ጨርቁ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ሐር ፡ ልስልስ ፡ ነው
*The texture of her skin is rough. ቆዳዋ ፡ ሻካራ ፡ ነው

**than** ከ - - -
I know you better than her. ከእሷ ፡ ይበልጥ ፡ አውቅሃለሁ
He is taller than his brother. ከወንድሙ ፡ ይረዝማል
**none other than** ከሱ ፡ በቀር
It was none other than him who took the money. ገንዘቡን ፡ ከሱ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ አልወሰደውም
[See also 'ever, every']

**thank**
1. ምስጋና ፡ አቀረበ. I haven't even thanked him yet. ገና ፡ ምስጋና ፡ እንኳን ፡ አላቀረብኩለትም
2. አመሰገነ. Thank you for the books! ስለ ፡ መጻሕፍቱ ፡ አመሰግንሃለሁ
*I can't thank you enough. ምስጋናዬ ፡ በአፍ ፡ አይነገርም
**thank God!** ተመስገን ፡ ነው
Thank God, it didn't rain today! ዛሬ ፡ አለመዝነቡ ፡ ተመስገን ፡ ነው
**thank you!** እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ
**have (one) to thank** ተወቃሹ ፡ እሱ ፡ ነው
We have him to thank for this trouble. ለዚህ ፡ ችግር ፡ ተወቃሹ ፡ እሱ ፡ ነው

**(be) thankful** ባለውለታው ፡ ነው
We are thankful to the boy for having shown us the way. ልጁ ፡ መንገድ ፡ ስላሳየን ፡ ባለውለታው ፡ ነን
*We are very thankful to you. ምስጋናችን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው

**thankless** ውለታ ፡ ቢስ
The thankless boy did almost nothing for his mother. ውለታ ፡ ቢሱ ፡ ልጅ ፡ ለእናቱ ፡ ምንም ፡ አላደረገም
**be a thankless act** አፍን ፡ ማበላሸት ፡ ነው
Giving him advice is usually a thankless act. እሱን ፡ ለምክር ፡ ማለት ፡ አፍን ፡ ማበላሸት ፡ ነው
**be a thankless task** ምስጋና ፡ የለውም
Being chairman of a committee is a thankless task. ያንድ ፡ ደርግ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ መሆን ፡ ምስጋና ፡ የለውም

**thanks** ምስጋና
The farmers rendered thanks to God for the harvest. ገበሬዎቹ ፡ ስለ ፡ ሰብሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቀረቡ
*I don't expect any thanks. ሰው ፡ ያመሰግነኛል ፡ ብዬ ፡ አላስብም
**thanks a lot!** በጣም ፡ አመሰግናለሁ
He said, "Thanks a lot!" and left. በጣም ፡ አመሰግናለሁ ፡ ብሎ ፡ ሄደ
**thanks to**
1. ዕድሜ ፡ ለሱ. Thanks to him, I was able to go to school. ዕድሜ ፡ ለሱ ፡ ለመማር ፡ በቃሁ
Thanks to your stupidity, I lost the job. ዕድሜ ፡ ላንተ ፡ ከሥራ ፡ ወጣሁ
2. በ - - ምክንያት. Thanks to good organization, the meeting was successful. በጥሩው ፡ ዝግጅት ፡ ምክንያት ፡ ስብሰባው ፡ የተሳካ ፡ ሆነ
It was thanks to him that things went so well. ነገሩ ፡ በመልካም ፡ የተከናወነው ፡ በሱ ፡ ምክንያት ፡ ነው

**thanksgiving** ምስጋና
They offered thanksgiving to God for their escape. ለማምለጥ ፡ ስለቻሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቀረቡ

**that** (adj. pron.)
1. (masc.) ያ ፤ - ዚያ; (fem.) ያች ፤ ያቺ ፤ - ዚያች. That man is good. ያ ፡ ሰው ፡ ደግ ፡ ነው
That woman is good. ያች ፡ ሴት ፡ ደግ ፡ ናት
That is John. ያ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው
There is no doubt about that. ያ ፡ አያጠራጥርም
I went to school with that boy. ከዚያ ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሄድኩ
I went to school with that girl. ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከዚያች ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ ሄድኩ
*Is that you, Mary? ሜሪ! አንቺ ፡ ነሽ ?
2. ያን ፤ ያንን (direct object). I don't like that new servant of his. ያንን ፡ አዲሱን ፡ አሽከሩን ፡ አልወደውም
3. (relative), የ + (perfect); የም (እም) + (imperfect). Who is that man that just came in? ልክ ፡ አሁን ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ?

Bring me the box that will hold the most. ብዙ ፡ እቃ ፡ ለመያዝ ፡ የሚችለውን ፡ ሣጥን ፡ አምጣልኝ

**that** (conj.)
1. እንደ + (perfect or relative imperfect). I know that he came to our house yesterday. ትላንትና ፡ ቤታችን ፡ እንደመጣ ፡ አውቃለሁ
I knew that he would come. እንደሚመጣ ፡ ዐወቅሁ
I know that he is here. እሱ ፡ እዚህ ፡ እንዳለ ፡ እውቃለሁ
2. (expressed by the verbal noun). He told me that she had arrived home. ቤቷ ፡ መድረሷን ፡ ነገረኝ
3. (direct speech). She said that she wouldn't come. አልመጣም ፡ አለች
4. እንድ + (imperfect). I will see to it that everything is ready. ሁሉም ፡ ነገር ፡ እንዲዘጋጅ ፡ አረጋግጣለሁ
He ran fast that he might not be late. እንዳይዘገይ ፡ በፍጥነት ፡ ሮጠ
5. ስለ + (verb). I'm sorry that you are ill. ስለታመምህ ፡ አዝናለሁ
*He died that we might live. ለኛ ፡ ሲል ፡ ሕይወቱን ፡ አሳለፈ

**that** (adv.) ይህን ፡ ያህል ፤ እስከዚህ
Take hold of yourself! Things aren't that bad. ረጋ ፡ በል! ነገሩ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ (እስከዚህ) ፡ መጥፎ ፡ አይደለም

**that is** ማለት
He is very fat, that is, he weighs 250 pounds. በጣም ፡ ወፍራም ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ኀምሳ ፡ ነጥር ፡ ይመዝናል
*I'll come tomorrow, that is, if it doesn't rain. ካልዘነበ ፡ ነገ ፡ እመጣለሁ

**that long** ያን ፡ ያህል
The baby cannot stay up that long. ሕፃኗ ፡ ያን ፡ ያህል ፡ ልታመሽ ፡ አትችልም

**that much** ይህን ፡ ያህል
I don't want that much milk. ይህን ፡ ያህል ፡ ወተት ፡ አልፈልግም

**that one** (masc.) ያኛው ፤ (fem.) ያች ፤ ያችኛዋ
That one is better. ያኛው ፡ ይሻላል
Shall we buy this book or that one? ይህንን ፡ መጽሐፍ ፡ እንግዛ ፡ ወይስ ፡ ያኛውን ?
That one is good. ያች ፡ ደግ ፡ ናት
That one is my sister. ያችኛዋ ፡ እኅቴ ፡ ናት

**that (man) there** ያ ፡ ሰውዬ
That man there eats a lot. ያ ፡ ሰውዬ ፡ ብዙ ፡ ይበላል

**that (woman) there** ያቺ ፡ ሴትዮ
That woman there eats a lot. ያቺ ፡ ሴትዮ ፡ ብዙ ፡ ትበላለች

**and that's that** ቁርጥ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ነግሬሃለሁ
I won't go with you, and that's that. ካንተ ፡ ጋር ፡ አልሄድም ፡ ብዬ ፡ ቁርጥ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ነግሬሃለሁ

**at that** ያኔ
And, at that, she left. እና ፡ ያኔ ፡ ሄደች

**by that much** ለጥቂት
She lost the race by that much. በእሽቅድምድሙ ፡ ለጥቂት ፡ ተሸነፈች

**everywhere that**
*I will look everywhere that I can. እሚቻለኝ ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ እፈልጋለሁ

**in that** ስለ
He cannot do the job in that he has no tools. መሣሪያ ፡ ስለሌለው ፡ ሥራውን ፡ ሊያከናውን ፡ አይችልም
*He said it was red, and in that he was right. ቀይ ፡ ነው ፡ ብሏል ፤ ልክ ፡ ነው

**oh, that ...!**
*Oh, that he were here! አዬ ፤ እሱ ፡ እዚህ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ !

**so** + (adverb) + **that** ከ --- የተነሣ ፤ ስለ
He ran so fast that he was five minutes early. በጣም ፡ ከመሮጡ ፡ የተነሣ ፡ አምስት ፡ ደቂቃ ፡ ቀድሞ ፡ ደረሰ
He left so late that he missed the train. እሱ ፡ ዘግይቶ ፡ ስለሄደ ፡ ባቡሩ ፡ አመለጠው
[See also 'all, far, way']

**thatch** (v.) ከደነ
He thatched the hut with straw. ጎጆውን ፡ ሣር ፡ ከደነ

**thatch** (n.)
1. የቤት ፡ ክዳን. The thatch is made of straw. የቤቱ ፡ ክዳን ፡ ሣር ፡ ነው
2. ሣር ፡ ክዳን ፡ ጣሪያ. Mice made their nest in the thatch. አይጦች ፡ ሣር ፡ ክዳኑ ፡ ጣሪያ ፡ ላይ ፡ ዋሻ ፡ ሠሩ

**thatched, ~ roof** የሣር ፡ ክዳን ፡ ጣሪያ
The rain leaked through the thatched roof. ዝናብ ፡ የሣር ፡ ክዳን ፡ ጣሪያችንን ፡ ዘለቀው

**thaw** (vt.) አቀለጠ
The sun at noon thaws the ice on the streets. የቀትር ፡ ፀሐይ ፡ በጐዳናዎች ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ በረዶ ፡ ያቀልጣል

**thaw** (vi.)
1. ሟሟ. The ice thawed in the warm room. በረዶው ፡ ሞቃቱ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ሟሟ
2. ሞቅ ፡ ብሎት ፡ ተጫወተ. The guests thawed when the party was under way. ፓርቲው ፡ ሲጫጫቅ ፡ እንግዶች ፡ ሁሉ ፡ ሞቅ ፡ ብሏቸው ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር
*His shyness thawed because of the teacher's kindness. አስተማሪው ፡ ደግ ፡ ስለሆነ ፡ ልጁ ፡ ዓይን ፡ አፋር ፡ መሆኑን ፡ ተወ

**thaw** (n.)
*The thaw came late this spring. በረዶው ፡ ጸደይ ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ሟሟ

**the,** masc. -u (after consonant), -w (after vowel); fem. -wa (after consonant and vowel); or -itu, -itwa
The doctor is good. ሐኪሙ ፡ ጥሩ ፡ ነው
The coffee is good. ቡናው ፡ ጥሩ ፡ ነው
The girl is pretty. ልጃገረዷ ፡ ቆንጆ ፡ ናት
For more details, see the existing grammars.

**the one** ያ (direct object ያንን)
Give me that book, the one with the case on it. ያንን ፡ መጽሐፍ ፡ አቀብለኝ ፤ ያንን ፡ ማኅደር ፡ ያለውን

**theater** የቲያትር ፡ ቤት
The theater was full. የቲያትር ፡ ቤቱ ፡ ሞልቶ ፡ ነበር

**thee** -ሀ ፤ ላንተ
Let us give Thee what is Thine. ያንተው ፡ የሆነውን ፡ እንስጥሀ ፡ (ላንተ ፡ እንስጥ)

**theft** ስርቆት
The theft was not discovered for some time. ስርቆቱ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ አልታወቀም ፡ ነበር

**their**
1. የነሱ. Their house is small. የነሱ ፡ ቤት ፡ ትንሽ ፡ ነው
2. -- (a) ቸው. They lost their dog. ውሻቸው ፡ ጠፋባቸው

**their own** የራሳቸው
It is their own house. የራሳቸው ፡ ቤት ፡ ነው

**of their own** የራሳቸው
They have a house of their own. የራሳቸው ፡ ቤት ፡ አላቸው

**theirs** የነርሱ
That dog is theirs. ያ ፡ ውሻ ፡ የነርሱ ፡ ነው

**them**
1. እነሱን. Call them! እነሱን ፡ ጥራ
2. - (a) ቸው. I saw them. አየኋቸው

**theme** መልእክት፤ አርእስት
The theme of the play is "Love conquers all". የቲያትሩ ፡ መልእክት ፡ « ፍቅር ፡ ሁሉን ፡ ያሸንፋል » ፡ የሚል ፡ ነው
The preacher amplified on the theme. ሰባኪው ፡ አርእስቱን ፡ በሚገባ ፡ ዘረዘረ

**themselves**
1. ራሳቸው. They themselves have often made that mistake. እነሱ ፡ ራሳቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያንን ፡ ስሕተት ፡ አድርገዋል
2. tä-stem. They hid themselves quickly. ቶሎ ፡ ተደበቁ

**be themselves** እንደ ፡ ወትሮዋቸው
They are not themselves today. እነሱ ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ወትሮዋቸው ፡ አይደሉም

**by themselves**
1. ራሳቸው. They did it by themselves. እነሱ ፡ ራሳቸው ፡ ሠሩት
2. ብቻቸውን. They were by themselves when I called. ስጠራቸው ፡ ብቻቸውን ፡ ነበሩ

**then** (adv.)
1. ያኔ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ. We were living in the country then. ያኔ ፡ ባላገር ፡ እንኖር ፡ ነበር
Prices were lower then. በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የእቃ ፡ ዋጋ ፡ ዝቅተኛ ፡ ነበር
2. በኋላ. First one boy was ahead in the race, and then the other. መጀመሪያ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ቀድሞ ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ሌላው ፡ ቀደመ
3. ከዚያ ፡ በኋላ. What did he do then? ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ አደረገ ?
4. እንግዲያውማ + verb + a. Then everything is settled. እንግዲያውማ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ተፈጸሚላ
5. ታዲያስ. Shall we try it then? ታዲያስ ፡ እንሞክረው ?
*If he read it, then he knows. ካነበበው ፡ ዘንድ ፡ ያውቀዋል ፡ ማለት ፡ ነው
*If he broke the window, then he should pay for it. መስኮቱን ፡ ከሰበረ ፡ መክፈል ፡ አለበት

**then** (adj.) በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበረ
The then prime minister signed the treaty. ውሉን ፡ የፈረመውት ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሥልጣን ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ናቸው

**then and there** ወዲያው
He fixed the car then and there. መኪናዋን ፡ ወዲያው ፡ ሠራት

**and then** በዚያውም
I like to swim, and then it's good exercise. ዋና ፡ እወዳለሁ ፤ በዚያውም ፡ ጥሩ ፡ የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ነው

*And then you must remember that he is only five. ገና ፡ ያምስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ መሆኑንም ፡ መርሳት ፡ የለብህም

**by then**

1. ያኔ. They were gone by then. ያኔ ፡ እነሱ ፡ ሄደዋል

2. እስከዚያ. Call Tuesday; he'll have received the books by then. ማክሰኞ ፡ ደውል ፤ እስከዚያ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ሳይደርሱት ፡ አይቀሩም

**from then on** ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ

From then on, he never came to see us. ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ብቅ ፡ ብሎም ፡ አልጠየቀንም

[See also 'but, now, since, too, what']

**thence**

1. ከዚያ. First she went to Paris, and thence to Rome. መጀመሪያ ፡ ፓሪስ ፡ ከዚያ ፤ ወደ ፡ ሮም ፡ ሄደች

2. ከዚያ ፡ ራቅ ፡ ብሎ. A few miles thence is a river. ከዚያ ፡ ጥቂት ፡ ማይል ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ወንዝ ፡ አለ

3. ከ -- ወዲህ. A few years thence, they had become good friends again. ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ወዲህ ፡ እንደገና ፡ ጥሩ ፡ ጓደኞች ፡ ሆነዋል

**thenceforth** ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ

We were thenceforth friends. ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ጓደኛሞች ፡ ነን

**theologian** የሃይማኖት ፡ ሊቅ (pl. የሃይማኖት ፡ ሊቃውንት)

Many theologians criticized the unsound doctrines. ብዙ ፡ የሃይማኖት ፡ ሊቃውንት ፡ መሠረት ፡ የሌለውን ፡ እምነት ፡ ነቀፉ

**theology** መንፈሳዊ ፡ ትምህርት

He is studying theology. የሚማረው ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ነው

**theoretical** (= adv.) በኀልዮ ፡ ብቻ ፤ በቴዎሪ ፡ ብቻ

I have a theoretical knowledge of business. የንግድን ፡ ሥራ ፡ የማውቀው ፡ በኀልዮ ፡ (በቴዎሪ) ፡ ብቻ ፡ ነው

**theoretically** በጽሑፍ ፤ በኀልዮ

Theoretically, the plan is fine. በጽሑፍ ፡ እንዳለ ፡ ስትመለከተው ፡ እቅዱ ፡ ጥሩ ፡ ነው

He knows machinery both practically and theoretically. መሣሪያዎችን ፡ በተግባርም ፡ በኀልዮም ፡ ያውቃል

**theory** (theories)

1. አስተያየት. There are several theories about the way in which the fire started. እሳቱ ፡ እንዴት ፡ እንደተነሣ ፡ የሚገልጹ ፡ ብዙ ፡ አስተያየቶች ፡ አሉ

My theory is that he is lying. በኔ ፡ አስተያየት ፡ ውሸቱን ፡ ይመስለኛል

2. ኀልዮ ፤ ቴዎሪ ፤ ፅንሰ ፡ ሐሳብ. Naval officers must understand both the theory and the practice of navigation. የባሕር ፡ መኰንኖች ፡ መርከብ ፡ መንዳትን ፡ በኀልዮም ፡ (በቴዎሪም) ፡ በሥራም ፡ ማወቅ ፡ አለባቸው

According to one scientific theory of life, the more complicated animals developed from the simple ones. አንድ ፡ የሳይንስ ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳብ ፡ እንደሚለው ፡ በጣም ፡ የረቀቀ ፡ አካል ፡ ያላቸው ፡ እንስሳት ፡ የመጡት ፡ ቀላል ፡ አካል ፡ ካላቸው ፡ እንስሳት ፡ ነው

**therapy** ሕክምና

Therapy was given to the mentally disturbed man. አእምሮው ፡ ታውኮ ፡ የነበረው ፡ ሰውዬ ፡ ሕክምና ፡ ተደረገለት

**there**

1. እዚያ. They go there because it's cheaper. እዚያ ፡ የሚሄዱት ፡ ረከስ ፡ ስለሚል ፡ ነው

Go there at once! ቶሎ ፡ እዚያ ፡ ሂድ

2. እዚያ ፡ ጋ. Put them there! እዚያ ፡ ጋ ፡ አስቀምጣቸው

3. እዚያ ፡ ላይ. He read to page 50, and there he stopped. እስከ ፡ ገጽ ፡ አምሳ ፡ አነበበና ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ አቆመ

4. እዚህ ፡ ላይ. There I disagree with you. እዚህ ፡ ላይ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ አልስማማም

5. (zero). There goes the bell! ደወሉ ፡ ተደወለ

**there!** ኤዲያ

There! See what you've done! ኤዲያ ፤ ተመልከት ፡ ምን ፡ እንዳደረግህ

**there and back** እዚያ ፡ ደርሶ ፡ ለመመለስ

How far is it there and back? እዚያ ፡ ደርሶ ፡ ለመመለስ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይርቃል ?

**there are**

1. ናቸው. There are a few good hotels in town. ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ጥሩ ፡ የሆኑ ፡ ሆቴሎች ፡ ጥቂት ፡ ናቸው

2. አሉ. There are many policemen in Los Angeles. ሎስ፡አንጀለስ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ፖሊሶች ፡ አሉ

**there he goes!** ያውና

There he goes! Catch him! ያውና ፤ ያዘው

**there is** አለ (masc.), አለች (fem.)

There is a park nearby. ባቅራቢያው ፡ የመናፈሻ ፡ ቦታ ፡ አለ

There is a woman in the room. እቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሴትዮ ፡ አለች
*Is there anything I can do? ምን ፡ ላድርግልህ ?

**there's no**
*There's no telling when he'll come. መቼ ፡ እን ደሚመጣ ፡ ለማወቅ ፡ አይቻልም

**there you are!**
1. መጣህ. There you are! I've been looking all over for you. መጣህ ። አንተን ፡ ያልፈለግሁበት ፡ ቦታ ፡ የለም
2. ይኸው. There you are! It's all done. ይኸው ። ተ ሠርቶ ፡ አልቋል
3. አለቀ. You have only to press the button and there you are! አንተ ፡ ማድረግ ፡ ያለብህ ፡ ቁ ልፉን ፡ መጫን ፡ ብቻ ፡ ነው ። አለቀ

**see there** ስማ
See there, that won't do at all. ስማ ። ይህ ፡ ፈጽ ሞ ፡ የማይሆን ፡ ነገር ፡ ነው

**you there!** ወንድም
You there! You dropped your wallet. ወን ድም ። የገንዘብ ፡ ቦርሳህን ፡ ጣልክ
[See also 'back, here, over, that, then, up']

**thereabouts, or ~**
1. ወደ. He is forty or thereabouts. ዕድሜው ፡ ወ ደ ፡ አርባው ፡ ነው
2. ወይም ፡ ወደዚያው ፡ ገደማ. He will come at six or thereabouts. በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ወ ይም ፡ ወደዚያው ፡ ገደማ ፡ ይመጣል
3. ወይም ፡ በዚያ ፡ አካባቢ. They live in Boston or thereabouts. በቦስተን ፡ ወይም ፡ በዚያ ፡ አካባቢ ፡ ይኖራሉ

**somewhere therabouts** በዚያ ፡ አካባቢ
He lives in Dessie or somewhere thereabouts. ደሴ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በዚያ ፡ አካባቢ ፡ ይኖራል

**thereafter** ከዚያ ፡ ወዲህ
He never took another bite of it thereafter. ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ምንም ፡ አልቀመሰለት

**thereby**
*He resigned, thereby losing his pension. ከሥራ ፡ በፈቃዱ ፡ ስለወጣ ፡ የጡረታ ፡ አበሉን ፡ አጣ
*She gave the dog a bone, thereby stopping his barking. ለውሻው ፡ አጥንት ፡ ሰጥታ ፡ መጮኹ ን ፡ አስተወችው
*He wished to travel and thereby study the customs of other countries. በየቦታው ፡ እየተ ዘዋወረ ፡ የሌሎችን ፡ አገሮች ፡ ልማድ ፡ ማጥና ት ፡ ተመኘ

**therefor**
*I enclose a check and request a receipt therefor. አንድ ፡ ቼክ ፡ ልኬያለሁና ፡ ደረሰኝ ፡ ይላክልኝ

**therefore**
*He missed the bus, and therefore he was late. አውቶቡስ ፡ ስላመለጠው ፡ ዘገየ

**therein**
1. እዚያ ፡ ውስጥ. You can't tell what may be therein. እዚያ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ለማወቅ ፡ አይ ቻልም
2. እዚያ ፡ ላይ. Therein you are wrong. እዚያ ፡ ላይ ፡ ተሳስተሃል

**thereof** ከሱ
When he saw the wine, he drank thereof. የወይን ፡ ጠጁን ፡ አየ ። ከሱም ፡ ጠጣለት
*He ate the green fruit and became sick thereof. ያልበሰለ ፡ ፍሬ ፡ በልቶ ፡ ሆድ ፡ ቁርጠት ፡ ለ ቀቀበት

**thereon** እዚያም ፡ ላይ
Before the window was a table. A huge book lay thereon. ከመስኮቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ጠረጴዛ ። እዚያም ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ መጽሐፍ ፡ ነበር

**thereto** ወደዚያ
The castle stands on the hill, and the road thereto is steep. ግንቡ ፡ ዳገት ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ ወደዚያ ፡ የሚወስደው ፡ መንገድ ፡ አቀበት ፡ ነው

**thereupon**
1. ያኔ. Thereupon he left the room. ያኔ ፡ ከክፍ ሉ ፡ ወጣ
2. በዚህም ፡ ምክንያት. The stolen jewels were found in his room; thereupon, he was put in jail. የተሰረቁት ፡ ዕንቁዎች ፡ በሱ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ተገኙ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ገባ

**therewith**
1. --- ም ፡ ጭምር. The lady gave him a rose and a smile therewith. ወይዘሮዋ ፡ ጽጌረዳ ፡ ሰ ጠችው ፤ ፈገግታዋንም ፡ ጭምር
2. --- ም ፡ ወዲያው. Our host said "Good-bye", and therewith we left. አስተናጋጃችን ፡ « ደኅና ፡ ሁኑ » ፡ አለን ፡ እኛም ፡ ወዲያው ፡ ሄድን

**thermometer**
1. የትኩሳት ፡ መለኪያ. The patient broke the thermometer. በሽተኛው ፡ የትኩሳት ፡ መለኪያ ውን ፡ ሰበረው
2. ተርሞሜትር. According to the thermometer, it is cold outside. በተርሞሜትሩ ፡ መሠረት ፡ ው ጪው ፡ ቀዝቃዛ ፡ ነው

**thermos** ማብረጃ
I carry water in a thermos. በማብረጃው ፡ ውኃ ፡ ይዣለሁ

**these** እነዚህ
These pills are no good. እነዚህ ፡ ኪኒኖች ፡ ጥሩ ፡ አይደሉም
I like these better. እነዚህን ፡ እመርጣለሁ
**these days** ባሁኑ ፡ ጊዜ ። አሁን
Everything is very expensive these days. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ተወዷል
Where is he working these days? አሁን ፡ የሚሠራው ፡ የት ፡ ነው ?
**one of these days** ሰሞኑን
I'll see you one of these days. ሰሞኑን ፡ እጠይቅሃለሁ

**thesis** (theses) ቴሲስ
Did he write his thesis yet? ቴሲሱን ፡ ጽፏል ?

**they** (masc. fem.)
1. እነሱ ። እነርሱ. They are my relatives. እነሱ ፡ የኔ ፡ ዘመዶች ፡ ናቸው
2. (expressed by the verb form). They went to school. ተማሪ ፡ ቤት ፡ ሄዱ.

**thick** (n.), **in the ~ of** መሀከል
He was in the thick of the fight. ድብድቡ ፡ መሀከል ፡ ነበር

**thick** (adj.)
1. ወፍራም. The soup is too thick. ሾርባው ፡ በጣም ፡ ወፍራም ፡ ነው
The castle has thick walls. የግንቡ ፡ ግድግዳ ፡ ወፍራም ፡ ነው
This board is thick. ይህ ፡ ሳንቃ ፡ ወፍራም ፡ ነው
These apples have a very thick skin. እነዚህ ፡ ቱፋዎች ፡ በጣም ፡ ወፍራም ፡ ልጣጭ ፡ አላቸው
2. ሰፊ. He drew a thick line on the blackboard. ጥቁር ፡ ሰሌዳው ፡ ላይ ፡ ሰፊ ፡ መሥመር ፡ አሠመረ
3. ዕጅብ ፡ ያለ. He has a thick beard. ጢሙ ፡ ዕጅብ ፡ ያለ ፡ ነው
4. ጥቅጥቅ ፡ ያለ. A thick forest covered the area. ቦታውን ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ጫካ ፡ ሸፍኖታል
5. ጥልቅ. The snow is thick. በረዶው ፡ ጥልቅ ፡ ነው
**thick and fast**
*The blows came thick and fast. የዱላ ፡ መዓት ፡ ወረደብኝ
**become thick** ወፈረ
The soup will become thick if you leave it on the fire for a long time. ሾርባውን ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ እሳት ፡ ላይ ፡ ብታደርገው ፡ ይወፍራል
**have a thick voice** ድምፁ ፡ ተዘጋ
She had a thick voice because of a cold. በጉንፋኑ ፡ ምክንያት ፡ ድምጿ ፡ ተዘግቷል
**(go) through thick and thin**
She went through thick and thin for him. ለሱ ፡ ስትል ፡ መከራንም ፡ ደስታንም ፡ አየች
[See also 'growth, skin']

**thicken** (vt.) አወፈረ
Thicken the soup with a little flour! ትንሽ ፡ ዱቄት ፡ ጨምረህ ፡ መረቁን ፡ አወፍረው
**thicken** (vi.)
1. ወፈረ. After boiling for a while, the soup began to thicken. ሾርባው ፡ እሳቱ ፡ ላይ ፡ ስለቆየ ፡ ወፍሯል
2. ከበደ. The fog began to thicken. ጭጋጉ ፡ እየከበደ ፡ ሄደ

**thicket** ጥሻ
There is someone hiding in that thicket. እዚያ ፡ ጥሻ ፡ ውስጥ ፡ የተደበቀ ፡ ሰው ፡ አለ

**thick-headed** ድንጋይ ፡ ራስ
He is too thick-headed to understand. ድንጋይ ፡ ራስ ፡ ነው ። አይገባውም

**thickly** ጥቅጥቅ ፡ ብሎ
Weeds grow thickly in the rich soil. አረም ፡ ጥሩ ፡ አፈር ፡ ካገኘ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ ይበቅላል
Most of Addis Ababa is a thickly settled region. ባብዛኛዎቹ ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ ክፍሎች ፡ ሕዝብ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ ይኖርባቸዋል
[See also 'populate']

**thickness** ውፍረት
It is four feet in thickness. ውፍረቱ ፡ አራት ፡ ጫማ ፡ ነው

**thick-skinned** ግዴለሽ
He is very thick-skinned, and such insults don't bother him much. ግዴለሽ ፡ ስለሆነ ፡ እንደዚያ ፡ ያለውን ፡ ስድብ ፡ ከምንም ፡ አይቆጥርም

**thief** (thieves) ሌባ
The thief stole my money. ሌባው ፡ ገንዘቤን ፡ ሰረቀኝ
[See also 'pack']

**thieves**, see **thief**

**thigh** ታፋ
I cut myself in the thigh. ታፋዬን ፡ ቈረጥኩት

**thimble** ቢዛ
The seamstress bought a thimble. ልብስ ፡ ሰፊ ዋ ፡ ቢዛ ፡ ገዛች

**thin** (thinned), vt. አከሳ
Hunger had thinned her body. ረኀብ ፡ ሰውነቷ ን ፡ አከስቶታል

**thin** (vi.)
1. ሳሳ. His hair is thinning. ጸጉሩ ፡ እየሳሳ ፡ ሄደ
2. ተቀነሰ. At last, the crowd thinned. በመጨረ ሻው ፡ ሕዝቡ ፡ እየተቀነሰ ፡ ሄደ
3. ለቀቀ. Let's wait until the fog thins! ጉሙ ፡ እ ስኪለቅ ፡ እንቆይ

**thin down** ከሳ
He has thinned down in recent years. ከቅርብ ፡ ዓመታት ፡ ወዲህ ፡ ከስቷል

**thin out**
1. አመነመነ. War and disease have thinned out the population. ጦርነትና ፡ በሽታ ፡ የሕዝቡ ን ፡ ብዛት ፡ አመንምኖታል
2. አሳሳ. The gardener thinned out the plants to help them grow better. አትክልተኛው ፡ ዕፀዋ ቱ ፡ በሚገባ ፡ እንዲያድጉ ፡ አሳሳቸው

**thin** (adj.)
1. ስስ. The paper is too thin. ወረቀቱ ፡ በጣም ፡ ስስ ፡ ነው
Thin boards are used for the ceiling. ጣሪያኑ ፡ የተሠራው ፡ ከስስ ፡ ሳንቃ ፡ ነው
2. ቀጭን. It was tied with a thin ribbon. በቀጭን ፡ ጥብጣብ ፡ ታስሮ ፡ ነበር
A thin man often eats more than a fat man. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ቀጭን ፡ ሰው ፡ ከወፍራም ፡ ሰው ፡ የበለጠ ፡ ይበላል
This sauce is too thin. ወጡ ፡ በጣም ፡ ቀጭ ን ፡ ነው
A thin voice is a handicap to a public speaker. ለሕዝብ ፡ ንግግር ፡ ለሚያደርግ ፡ ሰው ፡ ቀጭን ፡ ድምፅ ፡ ዕንቅፋት ፡ ነው
3. ጥቂት. A thin crowd was waiting for him at the airport. በአውሮፕላን ፡ ማረፊያው ፡ ጥቂት ፡ ሕዝብ ፡ ይጠብቀው ፡ ነበር
4. የማያጠግብ. He gave some thin excuse for being late. ለመዘግየቱ ፡ የማያጠግብ ፡ ምክንያት ፡ ሰጠ

**get thin** ከሳ
She got thin because of a long illness. ብዙ ፡ ጊ ዜ ፡ ስለታመመች ፡ ከስታለች

**slice thin** አሳነሰ ፡ ቈረጠ
They sliced the bread too thin. ዳቦውን ፡ በጣ ም ፡ አሳንሰው ፡ ቈረጡት

**wear thin** ሳስቶ ፡ አለቀ
This cloth has worn thin. ይህ ፡ ጨርቅ ፡ ሳ ስቶ ፡ ሊያልቅ ፡ ነው
[See also 'thick']

**thine** ያንተው
Let us give Thee what is Thine! ያንተው ፡ የሆነ ውን ፡ ላንተ ፡ እንስጥ

**thing**
1. ነገር. You shouldn't have said a thing like that. እንደዚያ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ መናገር ፡ አልነበረ ብህም
2. ሥራ. The next thing is to clean house. የሚቀጥለው ፡ ሥራ ፡ ቤቱን ፡ ማጽዳት ፡ ነው

**things**
1. ኑሮ. How are things? ኑሮ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
2. ሥራ. How are things at the office? እቢሮ ፡ ሥራ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
3. ጉዳይ. He is an expert in things Ethiopian. ኢትዮጵያን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ዐዋቂ ፡ ነው
4. ጓዝ. I packed my things and took the train. ጓዜን ፡ ጠቅልዬ ፡ ባቡር ፡ ተሳፈርኩ
5. እቃ. Put these things away! እነዚህን ፡ እቃ ዎች ፡ ወዲያ ፡ አስቀምጥ

**a thing or two** እንዳንድ ፡ ነገር
He certainly knows a thing or two about business. ስለ ፡ ንግድ ፡ ሥራ ፡ እንዳንድ ፡ ነገር ፡ ያውቃል

**among other things** በተጨማሪ
Among other things, he told me that his uncle died. በተጨማሪ ፡ አጐቱ ፡ መሞቱን ፡ ነገረኝ

**(the) first thing** ከሁሉ ፡ (ነገር) ፡ አስቀድሞ
I'll do it the first thing tomorrow morning. ነገ ፡ ጧት ፡ ከሁሉ ፡ ነገር ፡ አስቀድሜ ፡ እሠራ ዋለሁ
We'll do that first thing in the morning. እሱን ፡ ጧት ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድመን ፡ እንሠራ ዋለን

**for one thing** እንደኛ ፡ ነገር
I can't go; for one thing, I have no money. ለመሄድ ፡ አልችልም ፤ እንደኛ ፡ ነገር ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም

**not a thing**
1. አንድም ፡ ነገር + (negative verb). We haven't done a thing all week. ሳምንቱን ፡ ሙሉ ፡ አንድ ም ፡ ነገር ፡ አልሠራንም
2. አንድም ፡ ቃል + (negative verb). He didn't say a thing all week. ሳምንቱን ፡ ሙሉ ፡ አንድ ም ፡ ቃል ፡ አልወጣው

**not the first thing** ምንም ፡ ነገር + negative verb
I don't know the first thing about it. ስለሱ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አላውቅም

**of all things**
1. (ኧረ) ፡ ለመሆኑ. Well, of all things, what are you doing here? ኧረ ፡ ለመሆኑ ፡ እዚህ ፡ ምን ፡ ትሠራለህ ?
2. ካልጠፋ ፡ ነገር. Of all things, he had to take up Amharic! ካልጠፋ ፡ ነገር ፡ አማርኛ ፡ ይማር!

**poor thing** ምስኪን
Poor thing! He's been ill all winter. ምስኪን ። ክረምቱን ፡ በሙሉ ፡ ታሞ ፡ ነበር

**(it is the) real thing** የእውነት ፡ ነው
This time it is the real thing. አሁንስ ፡ የእውነት ፡ ነው

**the thing** ሞድ
Short skirts are the thing this year. አጫጭር ፡ ቀሚሶች ፡ የዚህ ፡ ዓመት ፡ ሞድ ፡ ሆነዋል

**the thing is** ዋናው ፡ ነገር
The thing is, can we get there on time? ዋናው ፡ ነገር ። እዚያ ፡ ልክ ፡ በሰዓቱ ፡ እንደርሳለን ?

**(is the) very thing for** በጣም ፡ አስፈለገው
A holiday is the very thing for you. ዕረፍት ፡ በጣም ፡ ያስፈልግሃል
[See also 'see']

**think** (thought)
1. አሰበ. I never thought to see you here. እዚህ ፡ አገኝሃለሁ ፡ ብዬ ፡ ፈጽሞ ፡ አላሰብኩም ፡ ነበር
Do animals think? እንስሳት ፡ ያስባሉ ?
He has never really learned how to think. በእውነቱ ፡ ማሰብ ፡ ፈጽሞ ፡ አይችልም
I'm only thinking of your good. ላንተው ፡ አስቤ ፡ ነው
I am thinking about going swimming this afternoon. ዛሬ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ዋና ፡ ለመሄድ ፡ አስቤያለሁ
What are you thinking about? ምን ፡ ታስባለህ ?
I've been thinking about it all afternoon. ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ በሙሉ ፡ ስለሱ ፡ ሳስብ ፡ ነበር
I'll think about it. አስብበታለሁ
He thought the lecture was interesting. ንግግሩ ፡ አስደሳች ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አሰበ
2. መሰለ(ው). Don't you think it's too warm? በጣም ፡ የሚሞቅ ፡ አይመስልህም ?
Do what you think fit. ተስማሚ ፡ የሚመስልህን ፡ አድርግ
She thinks she knows everything. ሁሉን ፡ ነገር ፡ የምታውቅ ፡ ይመስላታል
I think her charming. የምታስደስት ፡ ትመስለኛለች
3. አለ. That's what you think! ይህ ፡ አንተ ፡ የምትለው ፡ ነው

**think a lot (of)** ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ አለው
He thinks a lot of her. ስለ ፡ እርሷ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ አለው

**think better of** የተሻለ ፡ ግምት ፡ ሊያድርበት ፡ ቻለ
We think better of him since we found out the whole story. አሁን ፡ ታሪኩን ፡ አጣርተን ፡ ስላወቅን ፡ ስለሱ ፡ የተሻለ ፡ ግምት ፡ ሊያድርብን ፡ ችሏል

**think better of it**
*He considered emigrating to Australia, but thought better of it. ወደ ፡ አውስትራሊያ ፡ ለመሰደድ ፡ አስቦ ፡ ግን ፡ እንደገና ፡ ሲያስብ ፡ ተወ

**think differently** ሐሳቡን ፡ ለወጠ
Now he thinks differently. አሁን ፡ ሐሳቡን ፡ ለውጧል

**think highly (of)** ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ አለው
I think highly of him because I found out he was honest. ታማኝ ፡ መሆኑን ፡ ስላወቅሁ ፡ ስለሱ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ አለኝ

**(not) think much of**
He didn't think much of the new book. ስለ ፡ አዲሱ ፡ መጽሐፍ ፡ ያለው ፡ ግምት ፡ እምብዛም ፡ ነበር

**think nothing of** ከምንም ፡ አይቈጥረው
He thinks nothing of driving at night. ከመሸ ፡ መንዳትን ፡ ከምንም ፡ አይቈጥረው
Think nothing of it! Other people have been as much hurt as you. ከምንም ፡ አትቍጠረው ። ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ እንዳንተ ፡ ተጐድተዋል
*Think nothing of it! ኧረ ፡ ግዴለም

**think of**
1. ታወሰ(ው). +I thought of China as soon as he mentioned rice. ስለ ፡ ሩዝ ፡ ሲያነሣ ፡ ቻይና ፡ ታወሰኝ
2. ትዝ ፡ አለ(ው). +I can't think of his address right now. አሁን ፡ ለጊዜው ፡ አድራሻው ፡ ትዝ ፡ አይለኝም
*I often think of her. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከልቤ ፡ አትጠፋም

**think of that!** እስቲ ፡ ምን ፡ ይባላል
He doesn't like meat. Think of that! ሥጋ ፡ አይወድም ። እስቲ ፡ ምን ፡ ይባላል!

**think out loud**
*I was merely thinking out loud when I said that. ያንን ፡ ባልኩበት ፡ ጊዜ ፡ አስቤው ፡ የነበረ ውን ፡ ነው ፡ በድንገት ፡ የተናገርኩት

**think (it) over** አሰበ(በት)
You should think it over before you do it. ከመሥራትህ ፡ በፊት ፡ ልታስብበት ፡ ይገባል

**think through** አሰበ(በት)
Think the problem through! ጥያቄውን ፡ አስብበት

**think twice** አሰበ(በት)
Think twice before you ask her to marry you! እንድታገባት ፡ ከመጠየቅህ ፡ በፊት ፡ አስብበት

**think up**
1. አመነጨ. Who thought up that plan to get money out of the bank? ከባንክ ፡ ገንዘብን ፡ የመውሰድን ፡ ሐሳብ ፡ ያመነጨ ፡ ማነው ?
2. ፈጠረ. The boy had a nimble mind and could think up excuses for every occasion. ልጁ ፡ ንቁ ፡ አእምሮ ፡ ስለነበረው ፡ ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ ይፈጥር ፡ ነበር
3. አሰበ(በት). Try to think something up while I go to get a box. ሣጥን ፡ ይዤ ፡ እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ ነገሩን ፡ አስብበት

**be thought to be** ይባላል
They were thought to be Americans. አሜሪካውያን ፡ ናቸው ፡ ይባል ፡ ነበር

**come to think** አሰበ
How did you come to think of that? ያንን ፡ እንዴት ፡ አሰብከው ?

**lead to think** አጠራጠረ
What led you to think we didn't have it? እኛ ፡ እንደሌለን ፡ ምን ፡ አጠራጠረህ ?
[See also 'little, sort, well, would']

## thinking, to my ~ በኔ ፡ አስተያየት
He is, to my thinking, the best man we have. በኔ ፡ አስተያየት ፡ እዚህ ፡ ካሉን ፡ ሰዎች ፡ እሱ ፡ በጣም ፡ የተሻለ ፡ ነው
[See also 'fool, wishful thinking']

## third
1. ሦስተኛ. We couldn't stay for the third act. እስከ ፡ ሦስተኛው ፡ ትዕይንት ፡ ለመቆየት ፡ አልቻልንም ፡ ነበር
First it's expensive, second it's impractical, and third it's difficult to get. አንደኛ ፡ ውድ ፡ ነው ፤ ሁለተኛ ፡ ሊሠራ ፡ አይቻልም ፤ ሦስተኛ ፡ ደግሞ ፡ ለማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. ሣልሳዊ. David the Third was king long ago. ሣልሳዊ ፡ ዳዊት ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ንጉሥ ፡ ነበር

**a third** ሢሶ
A third of that will be enough. የዚ ፡ ሢሶው ፡ ይበቃል

## thirdly ሦስተኛ
Thirdly, I don't have enough money. ሦስተኛ ፤ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም

## thirst (v.), ~ for
1. ጠማ(ው). +They thirsted for blood. ደም ፡ ጠምቷቸው ፡ ነበር
The young man thirsted for knowledge. ወጣቱ ፡ ዕውቀት ፡ ጠምቶታል
2. በጣም ፡ ጓጓ. He thirsted for revenge. ለበቀል ፡ በጣም ፡ ጓጉቷል

## thirst (n.) ጥም ፤ ጥማት
I can't quench my thirst. ጥሜን ፡ (ጥማቴን) ፡ ላረካ ፡ አልችልም

**have a thirst for** ጠማ(ው)
He has a thirst for knowledge. ዕውቀት ፡ የጠማው ፡ ሰው ፡ ነው

## (be) thirsty ጠማ(ው)
I am very thirsty; give me some water, please! በጣም ፡ ጠምቶኛል ፤ ውኃ ፡ ስጠኝ

**make thirsty** ውኃ ፡ አስጠማ
A peppery meal makes me thirsty. በርበሬ ፡ የበዛበት ፡ ምግብ ፡ ውኃ ፡ ያስጠማኛል

## thirteen ዐሥራ ፡ ሦስት

## thirty ሠላሳ

## this (adj., pron.)
1. (masc.) ይህ ፤ - ዚህ; (fem.) ይህቺ ፤ ይቺ ፤ - ዚህች ፤ - ዚች. This book is for you. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ላንተ ፡ ነው
What I mean is this ... እኔ ፡ የምለው ፡ ይህ ፡ ነው
This is the picture I wanted to see. ላየው ፡ የፈለግሁት ፡ ሥዕል ፡ ይህ ፡ ነው
What do you think of this? ስለዚህ ፡ ምን ፡ ታስባለህ ?
What do you conclude from this? ከዚህ ፡ ምን ፡ ትገነዘባለህ ?
This woman came here last night. ይህቺ ፡ ሴት ፡ ትናንት ፡ ማታ ፡ እዚህ ፡ መጥታ ፡ ነበር
I went to school with this girl. ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከዚህች ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ ሄድኩ
2. እኚህ. This priest is my confessor. እኚህ ፡ ቄስ ፡ የንስሐ ፡ አባቴ ፡ ናቸው

**this big**
*It is this big. ይህን ፡ ያህላል

**this far**

1. እዚህ ፡ ድረስ. Now that we have come this far, we might as well go on. እዚህ ፡ ድረስ ፡ ከመጣን ፡ እንቀጥል

2. ይህን ፡ ያህል ፡ ርቀት. Do you always have to walk this far? ሁልጊዜ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ርቀት ፡ በእግርህ ፡ ትመላለሳለህ ?

**this one**

1. ይህ. Will you take this one or that one? መውሰድ ፡ የምትፈልገው ፡ ይህንን ፡ ነው ፡ ያንን ?

2. ይህኛው. This one is better. ይህኛው ፡ ይሻላል

**about this and that**

They talked about this and that. የባጥ ፡ የቆጡን ፡ አወሩ

[See also 'afternoon, day, evening, minute, morning, much, time, way, year']

**thistle** ኮሸሽላ

The thistle hurt her foot. ኮሸሽላው ፡ እግሯን ፡ ወጋት

**thong** ማሰሪያ

The thong of his sandal broke. የነጠላ ፡ ጫማው ፡ ማሰሪያ ፡ ተበጠሰ

**thorn** እሾህ

The bush is full of thorns. ቁጥቋጦው ፡ እሾህ ፡ ብቻ ፡ ነው

**thorny**

1. እሾሃማ. The sheep cannot eat these thorny leaves. በጎቹ ፡ ይህን ፡ እሾሃማ ፡ ቅጠል ፡ ሊበሉ ፡ አይችሉም

2. አከራካሪ. The location of the border between these two countries is a thorny question. በነዚህ ፡ ሁለት ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ድንበር ፡ አከራካሪ ፡ ነገር ፡ ነው

**thorough**

1. ጥንቁቅ. He's very thorough in everything he does. በሚያደርገው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ጥንቁቅ ፡ ነው

2. የተሟላ. He gave a thorough analysis of the political situation. ስለ ፡ ፖለቲካው ፡ ሁኔታ ፡ የተሟላ ፡ ትንተና ፡ አቀረበ

3. (= adv.) አንድ ፡ ባንድ. The police made a thorough search of the house. ፖሊሶቹ ፡ ቤቱን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ፈተሹ

4. (= adv.) አጠናቆ. A thorough knowledge of chemistry is necessary for this job. ለዚህ ፡ ሥራ ፡ የኬሚስትሪ ፡ ትምህርት ፡ አጠናቆ ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል

**thoroughbred** ዘረ ፡ መልካም

Thoroughbred horses from Arabia are highly prized. ከዐረብ ፡ አገር ፡ የሚመጡ ፡ ዘረ ፡ መልካም ፡ ፈረሶች ፡ ውድ ፡ ናቸው

**thoroughfare** ዋና ፡ ጐዳና

Churchill Avenue is one of the main thoroughfares in Addis Ababa. የቸርችል ፡ ጐዳና ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጐዳናዎች ፡ አንዱ ፡ ነው

**thoroughgoing** ፍጹም ፡ የሆነ

A thoroughgoing solution should prevent recurrence of the problem. ፍጹም ፡ የሆነ ፡ መፍትሔ ፡ ችግሩ ፡ ዳግመኛ ፡ እንዳይደርስ ፡ ይከለክላል

**thoroughly**

1. በዝርዝር. The lecturer treated his subject thoroughly. ተናጋሪው ፡ አርእስቱን ፡ በዝርዝር ፡ ተነተነ

2. በጥንቃቄ. It has been thoroughly tested. በጥንቃቄ ፡ ተፈትኗል

**those** (adj., pron.) እነዚያ

Those books belong to me. እነዚያ ፡ መጽሐፎች ፡ የኔ ፡ ናቸው

I don't want those; I want these. እነዚያን ፡ አልፈልግም ፤ የምፈልገው ፡ እነዚህን ፡ ነው

**thou** አንተ

O Lord, thou art the One who is merciful. አቤቱ ፡ ጌታዬ! መሓሪው ፡ አንተ ፡ ነህ

**though** (conj.)

1. ብ + (imperfect). Though they are poor, they are always neatly dressed. ድኾች ፡ ቢሆኑም ፡ ሁልጊዜ ፡ ንጹሕ ፡ ይለብሳሉ

2. ብ + imperfect + ቅሉ. Strange though it seems, the discovery was made back in 1777. እንግዳ ፡ ነገር ፡ ቢመስልም ፡ ቅሉ ፡ የተገኘው ፡ በ፲፯፻፸፯ ዓ. ም. ነው

*She was kind, though not as generous as her sister. እንደ ፡ እኅቷ ፡ ለጋስ ፡ ባትሆንም ፡ ደግ ፡ ነበረች

**though** (adv.) ግን

I'll do it! Not now, though. እሠራዋለሁ ፤ ግን ፡ አሁን ፡ አይደለም

**as though**

*He staggered as though he were drunk. ልክ ፡ እንደሰከረ ፡ ሰው ፡ ተንገደገደ

[See also 'even']

**thought** (v.), see **think**

**thought** (n.)
1. ሐሳብ. Write and let me have your thoughts on the matter! ጻፍና ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ያለህን ፡ ሐሳብ ፡ ግለጽልኝ
He was lost in thought. በሐሳብ ፡ ተውጦ ፡ ነበር
2. አስተሳሰብ. Greek thought has influenced Christianity and Islam. የክርስቲያንና ፡ የእስላም ፡ ሃይማኖቶች ፡ የግሪክ ፡ አስተሳሰብ ፡ ተጽዕኖ ፡ አለባቸው

**give some thought**
I'll have to give this matter some thought. ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ እንዳስብበት ፡ ያስፈልገኛል

**have second thoughts** አመነታ
He had second thoughts about taking the job. ሥራውን ፡ ለመያዝ ፡ ያመነታ ፡ ነበር

**have (a) thought** አሰበ
He has no thought for the future. ለወደፊት ፡ ኑሮው ፡ አያስብም

**on second thought** እንደገና ፡ ሲያስበው ፤ ካሰበበት ፡ በኋላ
On second thought, I won't do it. እንደገና ፡ ሳስበው ፡ (ካሰብኩበት ፡ በኋላ) ፡ አላደርገውም

**show thought** አሰበ
Show some thought for others besides yourself! አንዳንዴ ፡ ከራስህ ፡ ይልቅ ፡ ለሌሎች ፡ ትንሽ ፡ አስብ

**the very thought of it** ሲያስበው
The very thought of it makes me sick. ሳስበው ፡ ያንገፈግፈኛል
[See also 'deep, sink, train']

**thoughtful**
1. ደግ ፡ አሳቢ. A thoughtful neighbor, knowing the girl was sick, took her some food. ደግ ፡ አሳቢዋ ፡ ጐረቤት ፡ ልጃገረዲቱ ፡ መታመሟን ፡ ዐውቃ ፡ ምግብ ፡ ወሰደችላት
2. ጥልቅ. A thoughtful book will not be appreciated by a frivolous person. አስተሳሰቡ ፡ ቀላል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ጥልቅ ፡ መጽሐፍ ፡ አያደንቅም
3. አስተዋይ. He is a silent, thoughtful boy. ዝምተኛና ፡ አስተዋይ ፡ ልጅ ፡ ነው
*She has a thoughtful expression. ሐሳብ ፡ እንደገባት ፡ ፊቷ ፡ ላይ ፡ ይታወቃል

**be thoughtful** አሰበ
She is always thoughtful of her mother. ሁልጊዜ ፡ ለእናቷ ፡ ታስባለች
He was thoughtful for a while, and then replied "no". ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ካሰበ ፡ በኋላ ፡ እምቢ ፡ አለ

**it is thoughtful of**
*It is very thoughtful of you to bring me flowers. አስበህ ፡ አበባ ፡ ይዘህልኝ ፡ በመምጣትህ ፡ አመሰግንሃለሁ

**look thoughtful**
Why do you look so thoughtful? ምነው ፡ ሐሳብ ፡ የገባህ ፡ ትመስላለህ ?

**thoughtless**
1. ለሰው ፡ የማያስብ. Our thoughtless neighbors are always noisy. ለሰው ፡ የማያስቡት ፡ ጐረቤቶቻችን ፡ ሁልጊዜ ፡ ይንጫጫሉ
2. ግዴለሽ. The thoughtless driver passed the red light. ግዴለሹ ፡ ነጂ ፡ ቀዩን ፡ መብራት ፡ ጥሶ ፡ ሄደ

**thousand** ሺ

**thrall, held in ~** አገልጋዩ ፡ አደረገው
An enchantress held the prince in thrall. አስማተኛዋ ፡ ልዑሉን ፡ አገልጋይዋ ፡ አደረገችው

**thrash**
1. መታ. Stop thrashing that donkey! አህያዋን ፡ አትምታ
2. ገረፈ. He tried to cure the child's obstinacy by thrashing him. ልጁን ፡ በመግረፍ ፡ እልሁን ፡ ለማስተው ፡ ሞከረ
3. ደበደበ. The thieves thrashed him soundly. ሌቦቹ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ደበደቡት

**thrash about** ተንበጫረቀ
He thrashed about in the water. ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ተንበጫረቀ

**thrash out** አብጠርጥረው ፡ ተነጋገሩበት
Let's thrash this problem out at the meeting! ይህንን ፡ ችግር ፡ በስብሰባው ፡ ላይ ፡ አብጠርጥረን ፡ እንነጋገርበት

**thrash over** አውጥቶ ፡ አወረደ
She thrashed the matter over in her mind. ጉዳዩን ፡ በአእምሮዋ ፡ ውስጥ ፡ አውጥታ ፡ አወረደች

**thread** (v.)
1. ክር ፡ አገባ. She threaded the needle. መርፌውን ፡ ክር ፡ አገባችበት
2. ሰካ. She threaded a hundred beads. አንድ ፡ መቶ ፡ ዶቃ ፡ ሰካች

**thread one's way through** እየተሽሎከሎከ ፡ ሄደ
We threaded our way through the crowd. በሕዝቡ ፡ መሀከል ፡ እየተሽሎከሎክን ፡ ሄድን

**thread** (n.)
1. ክር. I have only black thread. ጥቁር ፡ ክር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ያለኝ

2. ቅደም ፡ ተከተል. His writing is so complicated that I lost the thread of the story. አጻጻፉ ፡ የተመሰቃቀለ ፡ ስለሆነ ፡ የታሪኩን ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ አልያዝኩትም
*His life hung by a thread. ሕይወቱ ፡ እሞት ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥላለች

**lose the thread of** አልተከታተለም
I lost the thread of the conversation. ወሬውን ፡ አልተከታተልኩትም

**threadbare** ቡትቶ ፡ የለበሰ
A threadbare beggar stood outside the church asking for alms. ቡትቶ ፡ የለበሰው ፡ ለማኝ ፡ ምጽዋት ፡ ለመጠየቅ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ደጃፍ ፡ ቆሟል

**be threadbare** ሳሳ
My coat is threadbare. ኮቴ ፡ ሳስቷል

**threat**
1. ዛቻ. His threats have failed to scare anyone. የሱን ፡ ዛቻ ፡ ከምንም ፡ የቈጠረው ፡ ሰው ፡ የለም
2. የማስፈራራት ፡ ስሜት. There was an implicit threat in his words. በንግግሩ ፡ ውስጥ ፡ ውስጣዊ ፡ የማስፈራራት ፡ ስሜት ፡ ነበረበት
3. ማስፈራሪያ. The letter carried a threat. ደብዳቤው ፡ ማስፈራሪያ ፡ ያዘለ ፡ ነው
4. ማስፈራራት. The teacher compelled obedience by the threat of punishment. መምህሩ ፡ በቅጣት ፡ በማስፈራራት ፡ ትእዛዝ ፡ አስከበረ
5. ስጋት. The threat of war was on everybody's mind. የጦርነት ፡ ስጋት ፡ በሁሉም ፡ ሰው ፡ አእምሮ ፡ ውስጥ ፡ ነበር

**launch threats** ዛተ
An angry person launches threats against his enemies. የተናደደ ፡ ሰው ፡ በጠላቶቹ ፡ ላይ ፡ ይዝታል

**make threats** ዛተ(በት)
He made threats against my life. እገድልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ዛተብኝ

**there is a threat of** ያስፈራራል
There was a threat of rain in the sky. ዝናብ ፡ ሊጥል ፡ ያስፈራራል

**utter a threat** ዛተ
He uttered a threat in Amharic. ባማርኛ ፡ ዛተ

**threaten** (vt.)
1. ዛተ(በት). He threatened to murder her. እገድልሻለሁ ፡ ብሎ ፡ ዛተባት
2. ቃጣ. Blinking one's eye when someone threatens to hit you in the face is a reflex action. አንድ ፡ ሰው ፡ ሊመታህ ፡ ሲቃጣ ፡ ዓይንን ፡ ማርገብገብ ፡ ሳይታሰብ ፡ በተፈጥሮ ፡ የሚደረግ ፡ ነው
3. አስፈራ. Political intrigue threatens to split the country. የፖለቲካው ፡ ሴራ ፡ አገሪቷን ፡ እንዳይከፋፍላት ፡ ያስፈራል
4. አስፈራራ. The turbulent mob threatened to tear down the gate. ሥርዓት ፡ የጐደለው ፡ ሕዝብ ፡ በሩን ፡ ለመስበር ፡ አስፈራራ
5. በማስፈራራት ፡ ገለጸ. He threatened to leave if he didn't get a raise. የደሞዝ ፡ ጭማሪ ፡ ካላገኘ ፡ ሥራውን ፡ የሚለቅ ፡ መሆኑን ፡ በማስፈራራት ፡ ገለጸ
6. አሰጋ. A flood threatened the city. የውኃ ፡ ሙላት ፡ ከተማውን ፡ አስግቶታል

**threaten** (vi.) ል + imperfect + ነው
A storm threatens. ኀይለኛ ፡ ዝናም ፡ ሊመጣ ፡ ነው

**threatening, it's ~** ያስፈራራል
It's threatening to rain any minute. ዝናም ፡ ሊጥል ፡ ያስፈራራል

**threatening cloud** ከባድ ፡ ደመና
Threatening clouds gathered in the east. በስተምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ከባድ ፡ ደመና ፡ ተከማችቷል

**three** ሦስት
**three o'clock** ዘጠኝ ፡ ሰዓት
I will come at three o'clock. በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ እመጣለሁ

**threefold** ሦስት ፡ ዕጥፍ
He got a threefold return on his investment. ያወጣውን ፡ ወጪ ፡ ሦስት ፡ ዕጥፍ ፡ አገኘ

**thresh** ወቃ
The farmer threshed the barley. ገበሬው ፡ ገብሱን ፡ ወቃ

**threshing floor** አውድማ
The threshing floor is made of stone. አውድማው ፡ የተሠራው ፡ ከድንጋይ ፡ ነው

**threshold** መጋቢያ
He stood on the threshold. መጋቢያው ፡ ላይ ፡ ቆመ
*He is at the threshold of a new career since he completed training as a lawyer. የጥብቅና ፡ ትምህርቱን ፡ ስለጨረሰ ፡ አሁን ፡ አዲስ ፡ኑሮ ፡ ሊጀምር ፡ ነው
*They were on the threshold of a new discovery. አዲስ ፡ ነገር ፡ ለማግኘት ፡ ምንም ፡ አልቀራቸው ፡ ነበር

**threw**, see **throw**

**thrice** ሦስቴ
He did it thrice in rapid succession. ሦስቴ ፡ እያከታተለ ፡ በፍጥነት ፡ አደረገው

**thrift** ገንዘብን ፡ በቁጠባ ፡ መያዝ
Thrift is a virtue most people lack. ገንዘብን ፡ በቁጠባ ፡ መያዝ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሚጐድላቸው ፡ ጥሩ ፡ ምግባር ፡ ነው

**thrifty** ቈጣቢ
She is a thrifty housewife. ቈጣቢ ፡ የቤት ፡ እመቤት ፡ ናት

**thrill** (vt.) መንፈስ ፡ አነቃቃ ፤ አስደነቀ
The film thrilled the audience. ፊልሙ ፡ የተመልካቾቹን ፡ መንፈስ ፡ አነቃቃ ፡ (ተመልካቾቹን ፡ አስደነቀ)

**thrill** (vi.)
1. በደስታ ፡ ስሜቱ ፡ ተነካ. The children thrilled at the sight of the parade. ልጆቹ ፡ ሰልፉን ፡ ሲያዩ ፡ በደስታ ፡ ስሜታቸው ፡ ተነካ
2. ተርገበገበ. Her voice thrilled with joy. ከደስታ ፡ የተነሣ ፡ ድምጿ ፡ ተርገበገበ

**be thrilled** በደስታ ፡ ተዋጠ
He was thrilled to find he had won in the lottery. ሎተሪ ፡ እንዳገኘ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ በደስታ ፡ ተዋጠ

**thrill** (n.) በጣም ፡ ግሩም
Seeing Ethiopia for the first time was a thrill. ኢትዮጵያን ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ማየት ፡ በጣም ፡ ግሩም ፡ ነበር
*The trip will give you the thrill of a lifetime. ጉዞው ፡ በሕይወትህ ፡ አጋጥሞህ ፡ የማያውቅ ፡ ደስታ ፡ ይሰጥሃል

**thriller** [የፍርሃት ፡ ወይም ፡ የመደሰት ፡ ስሜትን ፡ የሚያመነጭ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ፊልም]

**(be) thrilling** አስደነቀ
The history of America is a thrilling story. የአሜሪካ ፡ ታሪክ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ታሪክ ፡ ነው

**thrive** (thrived, or throve)
1. ዳበረ. A business cannot thrive without good management. በደንብ ፡ ካልተመራ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሊዳብር ፡ አይችልም
2. ፋፋ. The children are thriving. ልጆቹ ፡ ፋፍ ተዋል
3. ሊያብብ ፡ ቻለ. Flowers will not thrive without sunshine. አበቦች ፡ ፀሐይ ፡ ካላገኙ ፡ ሊያብቡ ፡ አይችሉም

**throat** ጉሮሮ
He cleared his throat and continued. ጉሮሮውን ፡ ጠረገና ፡ ቀጠለ
I have a sore throat. ጉሮሮዬን ፡ አሞኛል

**cut (the animal's) throat** አረደ
They cut the sheep's throat and then butchered it. በጉን ፡ አርደው ፡ ብልቱን ፡ አወጡ
[See also 'clear']

**throb** (throbbed) በኀይል ፡ መታ
I could feel his heart throbbing. ልቡ ፡ በኀይል ፡ ሲመታ ፡ ይሰማኛል

**throb with pain** ጠዘጠዘ
His hurt finger throbbed with pain. የቈሰለው ፡ ጣቱ ፡ ይጠዘጥዘው ፡ ነበር

**make one's heart throb**
The long climb up the hill made her heart throb. ዐቀበቱን ፡ ስትወጣ ፡ ልቧ ፡ በኀይል ፡ መታ

**throes, be in the ~ of** በጭንቀት ፡ ተያዘ
The Congo was in the throes of civil war. ኮንጎ ፡ በርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ጭንቀት ፡ ተይዛ ፡ ነበር

**death throes** ጣር
He is in his death throes. በጣር ፡ ላይ ፡ ነው

**throne** ዙፋን
The throne is covered with velvet and gold. ዙፋኑ ፡ በከፈይና ፡ በወርቅ ፡ ያጌጠ ፡ ነው

**assume the throne** ነገሠ
Haile Sellassie assumed the throne in 1931. ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ በ፲፱፻፳፫ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ነገሡ

**succeed to the throne** ዙፋኑን ፡ ወረሰ
After the death of Menelik, Empress Zawditu succeeded to the throne. አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ሲያርፉ ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዙፋኑን ፡ ወረሱ
[See also 'accession, succession']

**throng** (v.) አጥለቀለቀ
An orderly crowd thronged the street. በሥርዓት ፡ የሚጓዘው ፡ ሕዝብ ፡ መንገዱን ፡ አጥለቀለቀው

**throng** (n.)
*A throng of visitors were at the exposition. ኤክስፖዚሲዮኑ ፡ ውስጥ ፡ ተመልካቾች ፡ ግጥም ፡ ብለው ፡ ነበር

**throttle** (v.)
1. አንቆ ፡ ገደለ. The cruel boy throttled the cat. ጨካኙ ፡ ልጅ ፡ ድመቲቱን ፡ አንቆ ፡ ገደላት
2. ደመሰሰ. The dictator throttled all opposition. አምባገነኑ ፡ ተቃዋሚዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ደመሰሰ

3. አገደ. High tariffs throttle trade between countries. ከፍተኛ ፡ ቀረጥ ፡ ባገሮች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ንግድ ፡ ያግዳል

**throttle** (n.) [ወደ ፡ ሞተር ፡ የሚገባውን ፡ አየር ና ፡ ቤንዚን ፡ የሚቈጣጠር]

**through** (prep.)

1. በ---በኩል. I sent an announcement through the mail. በፖስታ ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ ማስ ታወቂያ ፡ ልኬ ፡ ነበር
2. በ--ውስጥ. We can see through the glass. በመስታወቱ ፡ ውስጥ ፡ ለማየት ፡ እንችላለን
3. በ --- ውስጥ ፡ ለውስጥ. The workers are tunneling through the mountain. ሠራተኞቹ ፡ በተራራው ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ መንገድ ፡ ይቀዳሉ
4. በ. The thief entered through the window. ሌባው ፡ የገባው ፡ በመስኮት ፡ ነው
He became rich through hard work. ጠንክሮ ፡ በመሥራቱ ፡ ሃብታም ፡ ሆነ
The crash happened through no fault of yours. ግጭቱ ፡ የደረሰው ፡ ባንተ ፡ ጥፋት ፡ አይደለም
5. በ---ምክንያት. The work was held up two weeks through his negligence. በሱ ፡ ቸልተኛ ነት ፡ ምክንያት ፡ ሥራው ፡ ሁለት ፡ ሳምንት ፡ ተወዘፈ
6. እስከ---ድረስ. We shall be in London through Saturday. እስከ ፡ ቅዳሜ ፡ ድረስ ፡ ለንደን ፡ ነን
7. (= adv.) -ን ፡ በሙሉ. He had a job through the summer. በጋውን ፡ በሙሉ ፡ ሥራ ፡ ነበረው
8. (= adv.) ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች. The soldiers marched through the town. ወታደሮቹ ፡ ከተማ ውን ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ በሰልፍ ፡ አለፉት
*He may not live through the night. ማደሩንም ፡ እንጃ

**through** (adv.)

1. -ን ፡ በሙሉ. He worked the whole night through. ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ ሲሠራ ፡ አደረ
2. በቀጥታ. Does the plane go through to London, or does it make stopovers along the way? አውሮፕላኑ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ለንደን ፡ ይ በራል ፡ ወይስ ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ ያርፋል ?
3. ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር. I read the book through. መጽሐፉን ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ አነበብኩት

**through** (adj.), ~ **street**
Is this a through street? ይህ ፡ መንገድ ፡ ወደዚ ያ ፡ ያዘልቃል ?
*This is a through train to Chicago. ይህ ፡ ባ ቡር ፡ ሳይቆም ፡ በቀጥታ ፡ እስከ ፡ ቺካጎ ፡ የሚሄ ድ ፡ ነው

**through and through**

1. ጨርሶ. The beams of the bridge are rotten through and through. የድልድዩ ፡ አውታሮች ፡ ጨርሰው ፡ በስብሰዋል
2. በጣም. He is reliable through and through. በጣም ፡ እምነት ፡ የሚጣልበት ፡ ሰው ፡ ነው
3. ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች. We were soaked through and through. ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ርሰን ፡ ነበር

**all the way through** ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር
She read the book all the way through. መጽሐ ፉን ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ አነበበችው

**be through** ጨረሰ
I'll be through work at five o'clock. ሥራዬን ፡ በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ እጨርሳለሁ

**be through with**
I am through with him. የሱ ፡ ነገር ፡ በቃኝ

**you are through!** በቃኸኝ
You're through; go and never come back! በቃኸኝ ፤ ዐይንህን ፡ ሁለተኛ ፡ እንዳላየው

**throughout** (prep.)

1. በ--ጊዜ ፡ ሁሉ. He remained abroad throughout the war. በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ውጭ ፡ አ ገር ፡ ነበር
2. በ. This hotel is famous throughout the world. ይህ ፡ ሆቴል ፡ በዓለም ፡ የታወቀ ፡ ነው
3. -ን ፡ ሙሉ. You can get those vegetables throughout the year. እነዚህ ፡ አትክልቶች ፡ ዓመቱን ፡ ሙሉ ፡ ከገበያ ፡ አይታጡም

**throughout** (adv.)

1. በሙሉ. The wooden part of the house is rotten throughout. በዕንጨት ፡ የተሠራው ፡ የ ቤቱ ፡ ወገን ፡ በሙሉ ፡ በስብሷል
2. ሙሉ ፡ በሙሉ. The jewelry is gold throughout. ጌጡ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ወርቅ ፡ ነው
3. ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር. The house is painted white throughout. ቤቱ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ነጭ ፡ ተቀብቷል

**throve**, see **thrive**

**throw** (threw, thrown)

1. ወረወረ. Let's see how far you can throw the ball! እስቲ ፡ ኳሷን ፡ የት ፡ ድረስ ፡ መወርወር ፡ እንደምትችል ፡ እንይ
2. ጣለ. The horse threw him. ፈረሱ ፡ ጣለው
3. ጣል ፡ አደረገ. She threw a piece of cloth over her shoulders. ትከሻዋ ፡ ላይ ፡ ጨርቅ ፡ መሳይ ፡ ጣ ል ፡ አደረገች
*He threw all caution to the winds. ጠንቃቃነቱ ን ፡ እርግፍ ፡ አድርጎ ፡ ተወ

**throw about**

1. ጣለ. Don't throw paper about in the park! በመናፈሻ ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ ወረቀት ፡ አትጣል

2. አባከነ. Don't throw your money about! ገንዘብህን ፡ አታባክን

**throw around** ረጨ
It was reported that he was throwing a lot of money around everywhere. ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ በየቦታው ፡ እንደሚረጭ ፡ ይወራ ፡ ነበር

**throw away**
1. ጣለ. Don't throw anything away! ምንም ፡ ነገር ፡ አትጣል
2. ወዲያ ፡ ጣለ. Throw the papers away! ወረቀቶቹን ፡ ወዲያ ፡ ጣላቸው
*He threw away the opportunity to go to college. ኮሌጅ ፡ የመማር ፡ ዕድሉን ፡ በከንቱ ፡ አሳለፈው

**(be) thrown away** ከንቱ ፡ ሆነ
My efforts were thrown away. ድካሜ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ሆነ

**throw back**
1. መልሶ ፡ ወረወረ. Throw the ball back to me! ኳሱን ፡ መልሰህ ፡ ወርውርልኝ
2. ወደ ፡ ኋላ ፡ መለሰ. We threw back the enemy. የጠላትን ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መለስነው
3. ወደ ፡ ኋላ ፡ አስቀረ. His illness threw him back a year at school. ሕመሙ ፡ ከትምህርቱ ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አስቀረው

**throw cold water on** ለማዳከም ፡ ጣረ
There would always be someone to throw cold water on our ambitions. ሁልጊዜ ፡ እቅዳችንን ፡ ለማዳከም ፡ የሚጥር ፡ አይጠፋም

**throw down** ጣላ
The watchman threw down the chair from the third floor. ዘበኛው ፡ ወንበሩን ፡ ከሦስተኛው ፡ ፎቅ ፡ ላይ ፡ ጣለው

**throw down carelessly** አዝረከረከ
Don't throw your things down so carelessly! እቃህን ፡ አታዝረክርከው

**throw (a) glance** መልከት ፡ አደረገ
He threw a glance at each car that passed him. የሚያልፉትን ፡ መኪናዎች ፡ ሁሉ ፡ መልከት ፡ ያደርጋቸው ፡ ነበር

**throw in**
1. መረቀ(ለት). The storekeeper threw in an extra pair of gloves. ባለሱቁ ፡ አንድ ፡ ጓንቲ ፡ መረቀልኝ
2. ጣል ፡ አደረገ. The chairman threw in an amusing anecdote to amuse the members. አባሎቹን ፡ ለማሣቅ ፡ ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ቀልድ ፡ ጣል ፡ አደረገ
*She threw in her lot with him. ዕድሉን ፡ ለመካፈል ፡ ወሰነች

**throw off**
1. አሳሳተ. The device was intended to throw the police off his trail. ዘዴው ፡ ፖሊሱን ፡ ከፍለጋው ፡ ለማሳሳት ፡ ነበር
2. አታለለ. The thief threw off his pursuers and made good his escape. ሌባው ፡ የሚከታተሉትን ፡ ሰዎች ፡ አታሎ ፡ አመለጠ
3. ለቀቀ. +He threw off a cold. ጉንፋን ፡ ለቆታል

**throw (one) off in** አሳሳተ
Keep quiet or you will throw me off in my calculations. ዝም ፡ በል ፤ ያለዚያ ፡ ሒሳቡን ፡ ታሳስተኛለህ

**throw on** ደረብ ፡ አደረገ
I'll just throw a coat on and come along. ካፖርቴን ፡ ደረብ ፡ አድርጌ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ልምጣ

**throw oneself at**
*She practically threw herself at him. እፍ ፡ እውጥታ ፡ ልትለምነው ፡ ምንም ፡ አልቀራት

**throw oneself (into)** ተጠመደ
He threw himself into his work. በሥራው ፡ ተጠመደ

**throw out**
1. ጣለ. I threw your old clothes out. አሮጌ ፡ ልብሶችህን ፡ ጣልኳቸው
2. ከቤት ፡ አስወጣ. She was so angry at me that she almost threw me out. በጣም ፡ ስለተናደደችብኝ ፡ ከቤት ፡ ልታስወጣኝ ፡ ነበር
3. ነፋ. He threw out his chest with pride. በኩራት ፡ ደረቱን ፡ ነፋ
4. አቀረበ. The committee threw out a few suggestions. ደርጉ ፡ አንዳንድ ፡ ሐሳቦችን ፡ አቀረበ

**throw over** ወረወረ(ለት) ፤ አቀበለ
Throw the ball over to me! ኳሱን ፡ ወርውርልኝ ፡ (አቀብለኝ)

**throw (people) together** አገናኘ
Chance has thrown us together in this place. እዚህ ፡ ቦታ ፡ ያገናኘን ፡ ዕድል ፡ ነው

**throw up** (vt.) አነሣ
He threw up his arms in despair. ተስፋ ፡ ቈርጦ ፡ እጁን ፡ አነሣ

**throw up** (vi.) አስመለሰ(ው) ፤ አስታወከ(ው)
+I throw up every time I ride on the train. በባቡር ፡ በሄድኩ ፡ ቁጥር ፡ ያስመልሰኛል ፡ (ያስታውከኛል)

**don't let it throw you** ተስፋ ፡ አትቍረጥ
Don't let that failure throw you! ጉዳዩ ፡ ስላልተቃናልህ ፡ ተስፋ ፡ አትቍረጥ
[See also 'court, doubt, glance, light, overboard, party, spark, track']

**throw** (n.), **is a stone's ~** በጣም ፡ ቅርብ ፡ ነው
His house is a stone's throw from the station. ቤቱ ፡ ለጣቢያው ፡ በጣም ፡ ቅርብ ፡ ነው

**be within a stone's throw** በአቅራቢያው ፡ አለ
We are within a stone's throw from a good market. ጥሩ ፡ የገበያ ፡ ቦታ ፡ በአቅራቢያችን ፡ አለ

**thrust** (thrust) ወጋ
He thrust a knife into his enemy's abdomen. ጠላቱን ፡ ሆዱ ፡ ላይ ፡ በጩቤ ፡ ወጋው

**thrust forward** እየተጋፋ ፡ ሄደ
She thrust forward through the crowd. በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ እየተጋፋች ፡ ሄደች

**thrust into** ከተተ
He thrust his hands into his pockets. እጁን ፡ ኪሱ ፡ ውስጥ ፡ ከተተ

**thrust into one's hand** በግድ ፡ አስጨበጠ
She thrust the money into his hand. ገንዘብ ፡ በግድ ፡ አስጨበጠችው

**thrust up to** ጠቀሰ
The mountains thrust their peaks up to the sky. ተራራዎቹ ፡ ሰማይ ፡ ይጠቅሳሉ

**thrust** (n.), **with a ~ of** ወግቶ
He killed his enemy with a thrust of his spear. ጠላቱን ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ ገደለው

**thud** (thudded), v.
*Rocks thudded to the ground after the explosion. ቦምቡ ፡ ከፈነዳ ፡ በኋላ ፡ ድንጋይ ፡ እየተፈናጠረ ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ ድው ፡ አለ

**thud** (n.)
*The stone fell with a thud. ድንጋዩ ፡ ዱብ ፡ ብሎ ፡ ወደቀ

**thumb** (v.), **~ (through)** መልከት ፡ መልከት ፡ አደረገ ፤ አገለባበጠ ፡ አየ
He thumbed the book and gave it back to me. መጽሐፉን ፡ መልከት ፡ መልከት ፡ አደረገና ፡ መልሶ ፡ ሰጠኝ
The student thumbed through the dictionary. ተማሪው ፡ መዝገበ ፡ ቃላቱን ፡ አገለባበጦ ፡ አየ

**thumb** (n.)
1. አውራ ፡ ጣት. I burned my thumb. አውራ ፡ ጣቴን ፡ አቃጠለኝ
2. ያውራ ፡ ጣት ፡ ማስገቢያ. There was a hole in the thumb of his glove. የእጅ ፡ ሹራቡ ፡ ያውራ ፡ ጣት ፡ ማስገቢያው ፡ ተበስቷል

**be a rule of thumb** በልማድ ፡ ተደረሰበት
It's just a rule of thumb, but not at all scientific. ይህ ፡ በልማድ ፡ እንጂ ፡ በሳይንስ ፡ ጥበብ ፡ የተደረሰበት ፡ አይደለም

**be under (one's) thumb**
*He's under his mother's thumb. ከእናቱ ፡ ቃል ፡ አይወጣም

**thumbtack** የወረቀት ፡ ምስማር
Go to the store and buy me thumbtacks! ወደ ፡ ሱቅ ፡ ሂድና ፡ የወረቀት ፡ ምስማር ፡ ግዛልኝ

**thump** (vt.) መታ
He thumped the table with his fist. ጠረጴዛውን ፡ በቡጢ ፡ መታ

**thump** (vi.) ከበሮ ፡ መታ
His heart thumped with excitement. ልቡ ፡ በድንጋጤ ፡ ከበሮ ፡ መታ

**thump on** አንኳኳ
He thumped on the door. በሩን ፡ አንኳኳ

**thump** (n.) ድው ፡ የሚል ፡ ድምፅ
We heard a thump as he fell. እሱ ፡ ሲወድቅ ፡ ድው ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ሰማን

**thunder** (v.)
1. አጕረመረመ. First it thundered; then it started to rain. ሰማዩ ፡ ሲያጕረመርም ፡ ቆይቶ ፡ መዝነብ ፡ ጀመረ
The guns could be heard thundering in the distance. መድፎቹ ፡ ከሩቅ ፡ ሲያጕረመርሙ ፡ ይሰማሉ
2. በኀይል ፡ ተናገረ. The preacher thundered against corruption and bribery. ሰባኪው ፡ ጉቦን ፡ በመቃወም ፡ በኀይል ፡ ተናገረ

**thunder** (n.) ነጐድጓድ
Did you hear the thunder last night? ትናንትና ፡ ማታ ፡ ነጐድጓድ ፡ ሰማህ ?
The thunder of applause drowned out the speaker's words. የጭብጨባው ፡ ነጐድጓድ ፡ የተናጋሪውን ፡ ድምፅ ፡ ዋጠው

**thunderbolt** የሰማይ ፡ መብለጭለጭ
A thunderbolt panicked the children. የሰማዩ ፡ መብለጭለጭ ፡ ልጆቹን ፡ አስደነገጣቸው

**come as a thunderbolt** መብረቅ ፡ የመታው ፡ መሰለው
The news of his death came as a thunderbolt. የሱን ፡ መሞት ፡ ስሰማ ፡ መብረቅ ፡ የመታኝ ፡ መሰለኝ

**thunderous, ~ applause** የጭብጨባ ፡ ነጐድጓድ

Thunderous applause greeted his appearance. ብቅ ፡ ሲል ፡ የጭብጨባ ፡ ነጐድጓድ ፡ ወረደ

**thunderstorm** ነጐድጓድ
During the thunderstorm, several trees were struck by lightning. በነጐድጓዱ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ዛፎችን ፡ መብረቅ ፡ መታቸው

**Thursday** ኀሙስ
The market is held on Thursday. ገበያው ፡ ኀሙስ ፡ ይውላል

**thus**
1. እንዲሁ. Do the outline thus! ንድፉን ፡ እንዲሁ ፡ ሥራ
2. እንግዲሁ. Thus, he is the only one left. እንግዲሁ ፡ የቀረው ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ነው
*He is ill and thus absent. ስለታመመ ፡ ቀረ

**thus far**
1. እዚህ ፡ ድረስ. We've come thus far; why not go on? እዚህ ፡ ድረስ ፡ ከመጣን ፡ ለምን ፡ አንቀጥልም?
2. እስከሁን. Thus far, he has done well. እስከሁን ፡ ደኅና ፡ ሠርቷል

**thwart** አጨናገፈ
The war thwarted our efforts to build up the country. አገሪቱን ፡ ለማሻሻል ፡ የምናደርገውን ፡ ጥረት ፡ ጦርነቱ ፡ አጨናገፈው

**thy** -ህ
Thy kingdom come! መንግሥትህ ፡ ትምጣ !

**thyme** ጠስኝ

**tiara** [የወርቅ ፤ የዕንቁ ፡ ወይም ፡ የአበባ ፡ ጉንጉን ፡ በራስ ፡ ላይ ፡ ለጌጥ ፡ የሚደረግ]

**tibia** የጭን ፡ ቅልጥም
The tibia is frequently broken by falls. ሰው ፡ ሲወድቅ ፡ የጭን ፡ ቅልጥም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይሰበራል

**tick** (v.) ሠራ
The machine won't tick. መሣሪያው ፡ አይሠራም
*What makes him tick? እንዲሠራ ፡ የሚገፋፋው ፡ ምንድነው ?

**tick off**
1. ምልክት ፡ አደረገ. He ticked off the names of those who were absent. ሳይመጡ ፡ በቀሩት ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ አቅጣጫ ፡ ምልክት ፡ አደረገ
2. ቈጠረ. The clock ticked off ten seconds. ሰዓቱ ፡ ዐሥር ፡ ሰከንድ ፡ ቈጠረ

**tick** (n.)
1. መዥገር. The sheep are full of ticks. በጎቹ ፡ መዥገር ፡ ብቻ ፡ ናቸው
2. ድምፅ. I could hear the tick of the clock. የሰዓቱ ፡ ድምፅ ፡ ይሰማኛል

**ticket**
1. ቲኬት. You can buy a ticket on the train. ቲኬት ፡ ባቡሩ ፡ ላይ ፡ ልትገዛ ፡ ትችላለህ
2. መጥሪያ. The policeman gave me a ticket for speeding. ከተወሰነው ፡ ፍጥነት ፡ በላይ ፡ ስለነዳሁ ፡ ትራፊኩ ፡ መጥሪያ ፡ ሰጠኝ

**ticket office** ቲኬት ፡ መሸጫ
Where is the ticket office? ቲኬት ፡ መሸጫው ፡ የት ፡ ነው ?

**ticket seller** ቲኬት ፡ ቈራጭ
The ticket seller is a girl. ቲኬት ፡ ቈራጯ ፡ ሴት ፡ ነች

**round trip ticket** ደርሶ ፡ መልስ ፡ ቲኬት
I want a round trip ticket to Harar. ሐረር ፡ ደርሶ ፡ መልስ ፡ ቲኬት ፡ እፈልጋለሁ
[See also 'one-way, return']

**tickle** (vt.)
1. ኰረኰረ. He doesn't laugh even if you tickle him. ብትኰረኵረው ፡ እንኳን ፡ አይሥቅም
2. አሣቀ. The story tickled him. ታሪኩ ፡ አሣቀው

**tickle,** vi. (= tr.) ከነከነ
+My nose tickles from the dust. አቧራው ፡ አፍንጫዬን ፡ ከነከነኝ

**be tickled** ደስ ፡ አለ(ው)
+I was tickled to hear you were coming. ትመጣለህ ፡ ማለትን ፡ ብሰማ ፡ ደስ ፡ አለኝ

**ticklish**
*That's a ticklish question. በጥንቃቄ ፡ ሊያዝ ፡ የሚገባው ፡ ችግር ፡ ነው
*Telling a girl her faults is a ticklish job. ለሴት ፡ ልጅ ፡ ጥፋቷን ፡ መንገር ፡ በዘዴ ፡ ነው

**be ticklish** ሰቀጠጠ
The bottoms of the feet are ticklish. የውስጥ ፡ እግር ፡ ይሰቀጥጣል
*Are you ticklish? ሲኰረኵሩህ ፡ አትወድም ? (ትፈራለህ ?)

**tidal wave** ማዕበል
A tidal wave destroyed a village on the shore. ማዕበሉ ፡ ከባሕሩ ፡ ዳር ፡ ያለችውን ፡ መንደር ፡ አጠፋት

**tide** (v.), ~ **over until** አደረሰ
Will five dollars tide you over until pay day? አምስት ፡ ብር ፡ ደሞዝ ፡ ታደርስሃለች ?

**tide** (n.) ማዕበል ፤ ሞገድ

Unload the ship before the tide goes out. ማዕበሉ ፡ (ሞገዱ) ፡ ከማፈግፈጉ ፡ በፊት ፡ መርከቡን ፡ አራግፍ

The tide is coming in. ማዕበሉ ፡ እየገፋ ፡ መጣ

*The tide of public opinion is against war. ያብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ አስተያየት ፡ ጦርነትን ፡ የሚቃወም ፡ ነው

**at high tide** ማዕበል ፡ ሲነሣ

At high tide, you cannot swim in the ocean. ማዕበል ፡ ሲነሣ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ መዋኘት ፡ አይቻልም

**at low tide** ባሕሩ ፡ ጸጥ ፡ ሲል

At low tide, the beach is quite wide. ባሕሩ ፡ ጸጥ ፡ ሲል ፡ የባሕሩ ፡ ዳር ፡ ይሰፋል

[See also 'swim']

**tidiness** ንጽሕና

Tidiness is an obsession with her. ንጽሕና ፡ ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የምትወደው ፡ ነገር ፡ ነው

**tidings** ወሬ

The tidings came too late. ወሬው ፡ የደረሰው ፡ ዘግይቶ ፡ ነው

**bearer of good tidings** አብሳሪ

The bearer of good tidings was rewarded by the family. ቤተሰቡ ፡ ላብሳሪው ፡ ወሮታ ፡ ከፈለው

**glad tidings** የምስራች

Have you heard the glad tidings? የምስራቹን ፡ ሰምተሃል ?

**tidy** (tidied), vt. አጸዳዳ

She tidied the room before the guests arrived. እንግዶቹ ፡ ከመምጣታቸው ፡ በፊት ፡ ክፍሉን ፡ አጸዳዳች

**tidy up** (vt.) አስተካከለ

Tidy up the clutter in your room! የክፍልህን ፡ ምስቅልቅል ፡ አስተካክል

**tidy up** (vi.) ለባበሰ

You'd better tidy up before the guests come. እንግዶቹ ፡ ከመምጣታቸው ፡ በፊት ፡ ብትለባብሺ ፡ ይሻላል

**tidy** (adj.)

1. ንጹሕ. The room is always tidy. ክፍሉ ፡ ሁልጊዜ ፡ ንጹሕ ፡ ነው

2. ብዙ. That's a tidy sum of money. ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ነው

**tie** (vt.)

1. አሰረ. He ties his necktie in a strange fashion. ክራቫቱን ፡ የሚያስረው ፡ በልዩ ፡ መንገድ ፡ ነው

I have to tie my shoelaces. ጫማዬን ፡ ልሰር

2. ቋጠረ. Tie the ends together! ጫፍና ፡ ጫፉን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ቋጥረው

3. ጠፈረ. He tied his books in a compact bundle. መጽሐፎቹን ፡ እጥቅ ፡ አድርጎ ፡ ጠፈራቸው

**tie** (vi.) ታሰረ

That paper ribbon does not tie well. የወረቀቱ ፡ ጥብጣብ ፡ ጠብቆ ፡ አይታሰርም

**be tied**

1. ታሰረ. His hands were tied behind his back. እጁን ፡ የፍጥኝ ፡ ታስሮ ፡ ነበር

2. እኩል ፡ ለኩል ፡ ተለያዩ. The teams are tied. ቡድኖቹ ፡ እኩል ፡ ለኩል ፡ ተለያዩ

**tie (one) down** አላላውስ ፡ አለ

His business ties him down. የንግዱ ፡ ሥራ ፡ አላላውስ ፡ አለው

**tie (oneself) down** ታሰረ

I don't want to tie myself down by having a wife, children, and a house to take care of. ለሚስት ፤ ለልጆችና ፡ ለቤት ፡ እያልኩ ፡ መታሰር ፡ አልፈልግም

**(be) tied down** ፋታ ፡ የለውም

I am tied down all day long. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ፋታ ፡ የለኝም

**tie in** ተያያዘ

This ties in with what I told you yesterday. ይህ ፡ ትላንት ፡ ከነገርኩህ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው

**tie on** አሰረ

Tie on another piece of string! ሲባጎ ፡ ጨምረህ ፡ እሰረው

**(be) tied to**

*He is always tied to his work. ከሥራ ፡ አይለይም

**tie up**

1. አዋለ. He tied up all his money in real estate. ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ አውሏል

2. በድን ፡ አደረገ. The strike tied up the whole city. የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማው ፡ ከተማውን ፡ በድን ፡ አደረገው

3. መሥራቱን ፡ አቆመ. +The strike tied up the factory. በሠራተኞቹ ፡ የሥራ ፡ ማቆም ፡ ምክንያት ፡ ፋብሪካው ፡ መሥራቱን ፡ አቁሟል

**(be) tied up**

1. ተያያዘ. Is his company tied up with another company? የሱ ፡ ኩባንያ ፡ ከሌላ ፡ ኩባንያ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው ?

2. ተያዘ. The telephone is tied up. ስልኩ ፡ ተይዟል

3. ጉዳይ ፡ አለበት. Are you tied up this evening?
ዛሬ ፡ ማታ ፡ ጉዳይ ፡ አለብህ ?
[See also 'hand, knot']

**tie** (n.)
1. ክራቫት. He wears loud ties. ደማቅ ፡ ክራቫቶ
ች ፡ ያስራል
2. ግንኙነት. There is a strong tie between the
two schools. በሁለቱ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ መሀ
ል ፡ የጠበቀ ፡ ግንኙነት ፡ አለ
3. ፍቅር. Family ties have kept him at home.
የቤተሰብ ፡ ፍቅር ፡ ከቤት ፡ አስሮ ፡ ይዞታል
**ties of friendship** ጓደኝነት
The quarrel cut the ties of friendship. ጠቡ ፡ ጓ
ደኝነታቸውን ፡ ቀጨው

**tiger** ነብር
A tiger's hide is expensive in our country. በገ
ራችን ፡ የነብር ፡ ቆዳ ፡ ውድ ፡ ነው

**tight** (adj.)
1. ድብን ፡ ብሎ ፡ የታሰረ | የደበነ | የከረረ. The
tight knot could not be untied. ድብን ፡ ብሎ ፡
የታሰረው ፡ (የደበነው, or የከረረው) ፡ ቋጠሮ ፡ ሊ
ፈታ ፡ አይችልም
2. የተወጠረ. A tight wire will vibrate when
struck. የተወጠረ ፡ ሽቦ ፡ ሲመታ ፡ ይርገበገባል
3. ጠባብ. He can't run because of his tight
shoes. በጠባብ ፡ ጫማው ፡ ምክንያት ፡ ሊሮጥ ፡ አ
ይችልም
4. ውኃ ፡ የማያስገባ. A tight boat is absolutely
safe. ውኃ ፡ የማያስገባ ፡ ጀልባ ፡ በፍጹም ፡ አያ
ሰጋም
5. አስጊ. A tight situation occurred when the
two enemies came to the same party. ሁለቱ ፡
ቂመኞች ፡ አንድ ፡ ፓርቲ ፡ ላይ ፡ በተገናኙ ፡ ጊ
ዜ ፡ አስጊ ፡ ሁኔታ ፡ ተፈጠረ
6. የሚያስጨንቅ. I have been in tight spots
before. ከዚህ ፡ በፊት ፡ በሚያስጨንቅ ፡ ሁኔታ ፡
ላይ ፡ ነበርኩ
*It was a tight race. እሩጫቸው ፡ እኩል ፡ ሊ
ሆን ፡ ምንም ፡ አልቀረው
**tight** (adv.)
1. በጥብቅ. Is the jar sealed tight? ማሰሮው ፡ በ
ጥብቅ ፡ ታሽጓል ?
2. አጥብቆ. Hold me tight; I think I may faint.
አጥብቀህ ፡ ያዘኝ | አዞረኝ
3. በኀይል. Shut your eyes tight! ዓይንህን ፡ በኀ
ይል ፡ ጨፍን
**be tight**
1. ጠበበ. This jacket is too tight for me.
ይህ ፡ ኮት ፡ በጣም ፡ ጠበኛል
2. በደንብ ፡ አልተያያዘም. The tiles were not tight.
ጡቡ ፡ በደንብ ፡ አልተያያዘም
3. ተወደደ. The money market is tight. ገንዘብ ፡
በጣም ፡ ተወዷል
**tight with (one's) money** ቆንቋና
He is too tight with his money to buy really
nice clothes. ቆንቋና ፡ ስለሆነ ፡ ለጥሩ ፡ ልብስ ፡ ገ
ንዘብ ፡ አያወጣም
[See also 'sit']

**tighten** አጠበቀ
Tighten the rope! ገመዱን ፡ አጥብቀው
[See also 'belt']

**tighter** ጠበቅ ፡ አድርጎ
I have to tie my shoelaces tighter. ጫማዬን ፡ ጠ
በቅ ፡ አድርጌ ፡ ማሰር ፡ አለብኝ

**tight-fisted** ጩቅ
His father is tight-fisted and does not buy him
anything. አባቱ ፡ ጩቅ ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ነገ
ር ፡ አይገዛለትም

**(be) tight-lipped** ዝግት ፡ አለ
She remained tight-lipped during the question-
ing. በምርመራው ፡ ጊዜ ፡ ዝግት ፡ ብላ ፡ ቀረች

**tile** ጡብ
The floor was covered with tiles. ወለሉ ፡ ጡ
ብ ፡ ተነጥፏል

**till** (v.) አረሰ
Farmers till the land with plows. ገበሬዎቹ ፡ የ
ሚያርሱት ፡ በማረሻ ፡ ነው

**till** (prep.) እስከ
Till now, the weather has been fine. እስካሁን ፡
አየሩ ፡ ደኅና ፡ ነው
*I won't be able to see you till next week.
ከሳምንት ፡ በፊት ፡ ላነጋግርህ ፡ አልችልም
**till** (conj.) እስከ + imperfect
Wait till I come back. እስክመለስ ፡ ጠብቅ
[See also 'when']

**tilt** (vt.)
1. አዘነበለ. If you tilt the bottle, you can get
the milk out. ጠርሙሱን ፡ ብታዘነብለው ፡ ወተ
ቱን ፡ ልትቀዳ ፡ ትችላለህ
Don't tilt your chair so far back! ወንበር ፡ ላ
ይ ፡ ተቀምጠህ ፡ እንደዚህ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አታዘ
ንብለው
2. ዘንበል ፡ አደረገ. He tilted his head to one
side. ራሱን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ዘንበል ፡ አደረገ
3. ደፋ ፡ አደረገ. He tilted his hat forward.
ባርኔጣውን ፡ ወደ ፡ ፊቱ ፡ ደፋ ፡ አደረገው

**tilt** (vi.) አጋደለ
The table tilted, and the plates slid off. ጠረጴዛው ፡ ስላጋደለ ፡ ሳሕኖቹ ፡ ተንሸራተው ፡ ወደቁ

**timber**
1. ዕንጨት. Forests supply timber for building houses. ጫካ ፡ ለቤት ፡ መሥሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ዕንጨቶችን ፡ ያስገኛል
2. ደን. He put a hundred acres of his land under timber. ከመሬቱ ፡ መቶውን ፡ ጋሻ ፡ ለደን ፡ አዋለው

**time** (v.)
1. አስተካከለ. Time the speed of the machine very carefully! የሞተሩን ፡ ፍጥነት ፡ በጥንቃቄ ፡ አስተካክለው
He timed his arrival to coincide with the President's visit. ከፕሬዚዳንቱ ፡ ጉብኝት ፡ ጋራ ፡ እንዲገጣጠምለት ፡ አድርጎ ፡ የመድረሻውን ፡ ጊዜ ፡ አስተካከለ
2. ለካ. He timed the car's speed at 110 miles per hour. የመኪናዋ ፡ ፍጥነት ፡ በሰዓት ፡ መቶ ፡ ዐሥር ፡ ማይል ፡ መሆኑን ፡ ለካ
*He timed his visit to find her at home. ልክ ፡ እቤት ፡ በምትገኝበት ፡ ሰዓት ፡ ሄደ

**time** (n.)
1. ጊዜ. This is no time to ask for money. አሁን ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ ጊዜ ፡ አይደለም
She was here several times. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እዚህ ፡ ትመጣ ፡ ነበር
What time do we eat? ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ የምን በላው ?
Time is up; hand in your exam papers! ጊዜው ፡ አልቋል ፤ የፈተናውን ፡ ወረቀት ፡ አስረክቡ
The world exists in space and time. ዓለም ፡ በቦታና ፡ በጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ተወስና ፡ የምትኖር ፡ ናት
2. ሰዓት. What time is it? ስንት ፡ ሰዓት ፡ ነው ?
Can you tell me the right time? ትክክለኛው ፡ ሰዓት ፡ ስንት ፡ እንደሆነ ፡ ልትነግረኝ ፡ ትችላለህ ?
It is time for lunch. የምሳ ፡ ሰዓት ፡ ነው
3. የዜማ ፡ ስልት. He beat time with a stick. የዜማውን ፡ ስልት ፡ በበትር ፡ ምት ፡ መራ

**times**
1. ጊዜ. Five times two equals ten. አምስት ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ዐሥር ፡ ነው
Times are getting better. ጊዜው ፡ እየተሻሻለ ፡ ይሄዳል
2. እጅ. Your share is ten times the size of mine. ድርሻህ ፡ ከኔ ፡ በዐሥር ፡ እጅ ፡ ይበልጣል

**time after time** ደጋግሞ
I have told him time after time not to do it. እንዳይሠራ ፡ ደጋግሜ ፡ ነግሬዋለሁ

**time and again** መላልሶ
I have tried it time and again, but without success. መላልሼ ፡ ሞከርኩት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በከንቱ ፡ ነበር

**(the) time before last** በቀደም
You paid for lunch the time before last. በቀደም ፡ ለምሳ ፡ ከፍለሃል

**(the) time is up** የመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ነው
The time is up tomorrow, so make sure you've handed your application in. የመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ነገ ፡ ስለሆነ ፡ ማመልከቻህን ፡ አስገባ

**against time**
*He worked against time to get out the newspaper. ጋዜጣውን ፡ በጊዜ ፡ ለማውጣት ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ሠራ

**ahead of time** ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በፊት
The building was completed ahead of time. ሕንጻው ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ተፈጸመ

**all the time**
1. በማንኛውም ፡ ጊዜ. We had good weather all the time. በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ጥሩ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ ነበረን
2. ሁልጊዜ ፤ ዘወትር. She is complaining all the time. ሁልጊዜ ፡ (ዘወትር) ፡ ታማርራለች
3. በ + relative imperfect + ጊዜ ፡ ሁሉ. All the time I was speaking, people in the back were whispering. በምናገርበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ከኋላ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ያንሾካሽኩ ፡ ነበር

**all this time** ይህን ፡ ያህል ፡ ጊዜ
Where have you been keeping yourself all this time? ይህን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ የት ፡ ጠፍተህ ፡ ከረምክ ?

**at all times** በማንኛውም ፡ ጊዜ
He is supposed to be ready at all times. በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ዝግጁ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ አለበት

**at any time** ምንጊዜም
I am ready at any time. ምንጊዜም ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ

**at one time**
1. ድሮ. I used to go mountain climbing at one time. ድሮ ፡ ተራራ ፡ እወጣ ፡ ነበር
2. ባንድ ፡ ጊዜ. He managed to hold two jobs at one time. ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ሥራ ፡ ለመያዝ ፡ ቻለ

**at that time** ያን ፡ ጊዜ ፤ ያኔ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ
At that time, he was not yet born. ያን ፡ ጊዜ ፡ (ያኔ) ፡ ገና ፡ አልተወለደም ፡ ነበር

At that time, I thought differently about it. በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ስለሱ ፡ የነበረኝ ፡ ሐሳብ ፡ ልዩ ፡ ነው

**at the same time**
1. አንድ ፡ ላይ ፤ እኩል. We got there at the same time. እዚያ ፡ የደረስነው ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ነው
They arrived at the same time. እኩል ፡ ደረሱ
2. የዚያኑ ፡ ያህል. She is entertaining, but at the same time tiresome. የምታስደስት ፡ ብትሆን ፡ የዚያኑ ፡ ያህል ፡ አሰልቺ ፡ ናት

**at times** አንዳንድ ፡ ጊዜ ፤ አንዳንዴ
At times, I am doubtful. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እጠራጠራለሁ
At times, I work fourteen hours at a stretch. አንዳንዴ ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ በመደዳው ፡ እሠራለሁ

**beat time with (one's) hands** አጨበጨበ
He beat time with his hands while the cantors sang. ደብተራዎቹ ፡ ሲዘምሩ ፡ ያጨበጭብ ፡ ነበር

**(be) behind time**
1. ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ዘገየ. The plane is ten minutes behind time. አውሮፕላኑ ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ዐሥር ፡ ደቂቃ ፡ ዘግይቷል
*He is always behind time in his payments. ምን ፡ ጊዜም ፡ በወቅቱ ፡ ከፍሎ ፡ አያውቅም

**(be) behind the times** ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀረ
This country is behind the times. ይህ ፡ ሀገር ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርቷል

**by the time**
1. ስ + (imperfect). By the time we reached home, it was already dark. ከቤት ፡ ስንደርስ ፡ ጨልሞ ፡ ነበር
2. በ + perfect + ጊዜ. The house was aflame by the time I got there. እኔ ፡ እዚያ ፡ በደረስኩ ፡ ጊዜ ፡ ቤቱ ፡ በእሳት ፡ ተቀጣጥሎ ፡ ነበር

**by this time** ይህን ፡ ጊዜ
By this time next week, we shall be in France. በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ነን

**double time** ዕጥፍ
He gets double time for working on holidays. በበዓል ፡ ቀን ፡ ሲሠራ ፡ ዕጥፍ ፡ ይከፈለዋል

**each time** በ + perfect + ቁጥር
He paused each time he could not think of the proper word. ትክክለኛውን ፡ ቃል ፡ ባጣ ፡ ቁጥር ፡ ቆም ፡ ይል ፡ ነበር

**every time** በ + perfect + ቁጥር
Every time I look at her, she seems more beautiful. ባየኋት ፡ ቁጥር ፡ ይበልጥ ፡ እየቆነጀችብኝ ፡ ትሄዳለች

**for the time being** ለጊዜው
Stay with us for the time being! ለጊዜው ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ተቀመጥ

**from time to time**
1. አልፎ ፡ አልፎ. He comes to see us from time to time. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሊጠይቀን ፡ ይመጣል
2. በየጊዜው. Starvation afflicts India from time to time. ረኃብ ፡ ህንድን ፡ በየጊዜው ፡ ያጠቃል

**gain time**
1. ቀደመ ፤ ሮጠ. Our clock gains time. ሰዓታችን ፡ ይቀድማል ፡ (ይሮጣል)
2. ጊዜ ፡ አገኘ. He hoped to gain time by putting off signing the papers for a few days more. ወረቀቶቹን ፡ መፈረሙን ፡ ለጥቂት ፡ ቀናት ፡ በማዘግየት ፡ ጊዜ ፡ ለማግኘት ፡ ተስፋ ፡ አደረገ

**give (someone) a bad (hard) time** አስቸገረ
He gave me a bad time when I went to ask him for money. ገንዘብ ፡ ልጠይቀው ፡ ብሄድ ፡ አስቸገረኝ
Don't give me such a hard time whenever I ask you to do something. አንድ ፡ ነገር ፡ ሥራ ፡ ባልኩህ ፡ ቁጥር ፡ እንደዚህ ፡ አታስቸግረኝ

**good time** መደሰት
She is only out for a good time. የምትፈልገው ፡ መደሰትን ፡ ብቻ ፡ ነው

**hard times** ችግር
War brings hard times. ጦርነት ፡ ችግር ፡ ያመጣል

**have a good time**
*Did you have a good time? ጊዜውን ፡ በደስታ ፡ አሳለፍክ ?
*I see you're having a good time. ደስ ፡ ብሎሃል ፡ ጃል !
*Have a good time! መልካም ፡ ጊዜ! (ጊዜው ፡ የደስታ ፡ ይሁንልህ!)

**have a hard time** ሲዳረቅ ፡ ዋለ ፤ ብዙ ፡ ተቸገረ
I had a hard time convincing her. እሷን ፡ አሳምን ፡ ብዬ ፡ ስዳረቅ ፡ ዋልኩ ፡ (ብዙ ፡ ተቸገርኩ)

**high time**
*It is high time that you wake up to the fact that you are failing in your studies. በትምህርት ፡ የምትወድቅ ፡ መሆንህን ፡ በጊዜ ፡ መረዳት ፡ ያስፈልግሃል

**in good time** በሰዓቱ
We arrived at the appointed spot in good time. ከተወሰነው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ በሰዓቱ ፡ ደረስን

**in no time** ከመቅጽበት ፤ ባንዳፍታ
He finished in no time. ከመቅጽበት ፡ ጨረሰ

In no time, the job was done. ሥራው ፡ በንጻፍ ታ ፡ አለቀ

**in olden times** በቀድሞ ፡ ጊዜ
In olden times, cars were unknown. በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ መኪና ፡ አልነበረም

**in time**
1. ውለው ፡ አድረው. I am sure we'll come to an agreement in time. ውለን ፡ አድረን ፡ መስ ማማታችን ፡ አይቀርም
2. በጊዜ. Will the vegetables arrive in time for supper? አትክልቱ ፡ ለራት ፡ በጊዜ ፡ ይደርሳል ?

**keep good time**
My watch keeps good time. ሰዓቴ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው

**keep time**
Keep time with the music! እንቅስቃሴህን ፡ ከሙ ዚቃው ፡ ጋር ፡ አስተካክል

**kill time** ጊዜ ፡ አሳለፈ
While I was waiting for you, I killed time counting the cars passing in front of the store. አንተን ፡ ስጠብቅህ ፡ በሱቁ ፡ አጠገብ ፡ የሚያ ልፉትን ፡ መኪናዎች ፡ በመቍጠር ፡ ጊዜዬን ፡ አሳለፍኩ

**make time** ጊዜ ፡ አተረፈ
We can make time if we take the path. በእግ ር ፡ መንገድ ፡ ብንሄድ ፡ ጊዜ ፡ እናተርፋለን

**many a time** ብዙ ፡ ጊዜ
I have seen him walking with his dog many a time. ውሻውን ፡ አስከትሎ ፡ በእግሩ ፡ ሲንሸራሸ ር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አየዋለሁ

**mark time** ሰዓቱን ፡ ቈጠረ
He's not doing anything; he's just marking time. ምንም ፡ አያደርግም ፤ ሰዓቱን ፡ ይቈጥራል

**next time** ለወደፊት
Next time come a little earlier! ለወደፊት ፡ ጥቂ ት ፡ ቀደም ፡ ብለህ ፡ ና

**on (one's) own time** በትርፍ ፡ ጊዜ
He worked out a more efficient method of sewing on his own time. በትርፍ ፡ ጊዜው ፡ የተሻ ለ ፡ የልብስ ፡ አሰፋፍ ፡ ዘዴ ፡ አወጣ

**on time**
1. በሰዓቱ. Please be on time! በሰዓቱ ፡ እንድት መጣ
2. በጊዜው. If you hold off applying for a passport, you may not be able to get one on time. የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ ለማግኘት ፡ ማመልከትን ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ ብለህ ፡ ካሳለፍክ ፡ በጊዜው ፡ ለማግኘ ት ፡ አትችል ፡ ይሆናል
3. በተወሰነው ፡ ጊዜ. They violated the contract by failing to finish on time. በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ባለመጨረሳቸው ፡ ውሉን ፡ ጣሱ
4. በየጊዜው ፡ ከፍሎ ፡ ሲጨርስ. He bought his car on time. በየጊዜው ፡ ከፍሎ ፡ ሲጨርስ ፡ እን ድ ፡ መኪና ፡ ገዛ

**(in) record time** ከሁሉ ፡ በፊት
He finished the job in record time. ሥራውን ፡ ከ ሁሉ ፡ በፊት ፡ ጨረሰ
*He ran the mile in record time. እንዱን ፡ ማ ይል ፡ ሲሮጥ ፡ ክብረ ፡ ወሰን ፡ ሰበረ

**since time immemorial** ከጥንት ፡ ጀምሮ
This land has belonged to the church since time immemorial. ይህ ፡ መሬት ፡ ከጥንት ፡ ጀ ምሮ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ነው

**spend (one's) time** ጊዜውን ፡ አሳለፈ
He is spending his time in the bar. ጊዜውን ፡ መ ጠጥ ፡ ቤት ፡ ያሳልፋል

**take time**
1. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወሰደ. She took her time getting ready. ስትበጃጅ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወሰደች
2. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፈጀ. That will take time to finish. ያንን ፡ ሥራ ፡ ለመጨረስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይፈጃል

**this time** ላሁኑ
This time I'll let you go. ላሁኑ ፡ ችላ ፡ እለዋለሁ

**(by) this time** ይህን ፡ ጊዜ
By this time next week, we shall be in France. በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ነን

**two at a time** ሁለት ፡ ሁለቱን
Hand them to me two at a time! ሁለት ፡ ሁለቱ ን ፡ አቀብለኝ
[See also the numerous expressions combined with 'time']

## time-consuming ጊዜን ፡ የሚወስድ
It is a time-consuming job to copy this book. ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ መገልበጥ ፡ ጊዜን ፡ የሚወስድ ፡ ሥራ ፡ ነው

## (be) time-honored
*This custom is time-honored. ይህ ፡ ልማድ ፡ ለ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ ስለመጣ ፡ ተከ ብሮ ፡ ይኖራል

## (be) timeless የጊዜ ፡ ወሰን ፡ የለውም
Eternity is timeless. ዘለዓለምነት ፡ የጊዜ ፡ ወሰ ን ፡ የለውም
*She seems to be timeless, she has lived so long. ዕድሜዋ ፡ በጣም ፡ ገፍቷል ፤ ሞት ፡ የረሳት ፡ መሰለኝ

**time limit** የተወሰነ ፡ ጊዜ
The time limit is one month. የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ነው

**timely**
1. ከጊዜው ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፤ ለጊዜው ፡ ተስማሚ. That's a timely topic. አርእስቱ ፡ ከጊዜው ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ ነው
The paper contained a timely article on foolish spending. ጋዜጣው ፡ ለጊዜው ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ በከንቱ ፡ ገንዘብን ፡ ስለ ፡ ማባከን ፡ ጉዳይ ፡ የሚናገር ፡ ጽሑፍ ፡ አዝሏል
2. (= adv.) በጊዜ. The timely arrival of the police stopped the quarrel. የፖሊሶች ፡ በጊዜ ፡ መድረስ ፡ ረብሻውን ፡ አቆመው

**timetable** ፕሮግራም
According to the timetable, we should be in Washington at five o'clock. በፕሮግራሙ ፡ መሠረት ፡ ዋሽንግተን ፡ በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ መድረስ ፡ አለብን

**timid**
1. ፈሪ. The timid child was afraid of the dark. ፈሪው ፡ ልጅ ፡ ጨለማ ፡ አይደፍርም
2. ድንጉጥ. Deer are timid animals. አጋዘን ፡ ድንጉጥ ፡ እንስሳ ፡ ነው

**timidity** ፍርሃት
His timidity keeps him from asking for his rights. ፍርሃት ፡ መብቱን ፡ ከማስከበር ፡ ያግደዋል

**timing** የመጠነው ፡ ጊዜ
His timing was off, and he came too late. የመጠነው ፡ ጊዜ ፡ በማለፉ ፡ ዘግይቶ ፡ ደረሰ
*The dancer's timing was perfect. የዳንሰኛዋ ፡ የሰውነት ፡ ንቅናቄ ፡ እንከን ፡ አይወጣለትም

**timorous** ፈሪ
The timorous boy hugged the corner. ፈሪው ፡ ልጅ ፡ ከጥግ ፡ ሽጉጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ

**tin** (n.) ቆርቆሮ ፤ የቆርቆሮ ፡ ማዕድን
The price of tin went up last week. የቆርቆሮ ፡ ዋጋ ፡ ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ጨመረ
The company reclaims tin from old tin cans. ኩባንያው ፡ ከሮጌ ፡ ጣሳዎች ፡ የቆርቆሮ ፡ ማዕድን ፡ ለይቶ ፡ ያወጣል

**tin** (adj.) የቆርቆሮ
My house has a tin roof. ቤቱ ፡ የቆርቆሮ ፡ ክዳን ፡ አለው

**tin can** ታኒካ ፤ ጣሳ
I saw a squalid hut made of old tin cans. ከሮጌ ፡ ታኒካ ፡ (ጣሳ) ፡ የተሠራች ፡ ደሳሳ ፡ ጎጆ ፡ አየሁ

**tinder** ማቀጣጠያ
The tinder caught fire readily. ማቀጣጠያው ፡ ወዲያው ፡ ተያያዘ

**ting** ድምፅ ፡ አሰማ
The bell tinged. ደወሉ ፡ ድምፅ ፡ አሰማ

**tinge** (v.) ላመለ ፡ አቀለመ
A drop of ink will tinge a glass of water. የቀለም ፡ ጠብታ ፡ አንድን ፡ ብርጭቆ ፡ ውኃ ፡ ላመል ፡ ያቀልመዋል
*Memories of the dead tinged the present joy with sadness. የሞቱት ፡ ሰዎች ፡ ትዝታ ፡ ደስታችውን ፡ ወደ ፡ ሐዘን ፡ ለውጥ ፡ አደረገው
*Sadness tinged the joy of our reunion. እንደገና ፡ የመገናኘታችንን ፡ ደስታ ፡ የሐዘን ፡ ደመና ፡ ጣል ፡ አደረገበት

**be tinged** ተቀላቀለ
Her admiration was tinged with envy. አድናቆቷ ፡ ከቅናት ፡ ጋር ፡ የተቀላቀለ ፡ ነበር

**tinge** (n.) ትንሽ ፡ ምልክት
There was a tinge of sadness in her voice. ድምጿ ፡ ትንሽ ፡ የሐዘን ፡ ምልክት ፡ ነበረበት

**tinge of** (expressed by a composite verb)
There is a tinge of red in her cheek. ጉንጯ ፡ ቀላ ፡ ብሏል

**tingle**
1. ፈነደቀ. The children tingled with excitement. ልጆቹ ፡ በደስታ ፡ ፈነደቁ
2. ወረረ(ው). +My foot tingles when it is asleep. ሲደነዝዘኝ ፡ እግሬን ፡ ይወረኛል

**tinker** ነካካ
Please don't tinker with my car engine! የመኪናዬን ፡ ሞተር ፡ አትነካካ

**tinkle** ተንቃጨለ
I hear bells tinkling in the distance. ደወሉ ፡ በሩቁ ፡ ሲንቃጨል ፡ ይሰማኛል

**tint** (v.) ቀባ
She tinted her hair red. ጸጉሯን ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ቀባችው

**tint** (n.) ዓይነት
There are different tints of blue. ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ አለ
*The tint of her skin is light brown. የቀይ ፡ ዳማ ፡ ናት

**tiny**
1. በጣም ፡ ትንሽ. This bell is tiny. ይህች ፡ ቃጭል ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነች
2. ጥቃቅን (pl.). The microscope reveals the existence of many tiny things. ማይክሮስኮፕ ፡ የብዙ ፡ ጥቃቅን ፡ ነገሮችን ፡ መኖር ፡ ያሳያል

**tip** (tipped), vt.
1. አጋደለ. He tipped the table, and the dishes fell off. ጠረጴዛውን ፡ ስላጋደለው ፡ ሳሕኖቹ ፡ ወደቁ
2. ጉርሻ ፡ ሰጠ. Did you tip the porter? ለተሸካሚው ፡ ጉርሻ ፡ ሰጠኸው ?

**tip** (vi.) አጋደለ
If the weights are unequal the balance will tip. የእቃዎቹ ፡ ክብደት ፡ እኩል ፡ ካልሆነ ፡ ሚዛኑ ፡ ያጋድላል

**tip (one's) hat**
*He tipped his hat to the lady. ባርኔጣውን ፡ አንሥቶ ፡ ሴትዮዋን ፡ እጅ ፡ ነሣ

**tip off**
1. ሹክ ፡ አለ. Who tipped you off that I was coming? እንደምመጣ ፡ ማን ፡ ሹክ ፡ አለህ ?
2. አመለከተ. A red light tips a driver off to a defect. መኪና ፡ ውስጥ ፡ ቀይ ፡ ሲበራ ፡ ጉድለት ፡ እንዳለ ፡ ለነጂው ፡ ማመልከቱ ፡ ነው

**tip over** (vt.) ደፋ
He tipped over his glass of water. የብርጭቆውን ፡ ውኃ ፡ ደፋው

**tip over** (vi.) ተገለበጠ
The boat tipped over. ጀልባው ፡ ተገለበጠ

**tip with** ጫፍ ፡ ላይ ፡ አደረገ(በት)
The farmer tipped the stakes with iron. ገበሬው ፡ ችካሎቹ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ብረት ፡ አደረገባቸው

**tip** (n.)
1. ጫፍ. They landed on the northern tip of the island. በደሴቱ ፡ ሰሜናዊ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ አረፉ
The tips of her fingers were cold as ice. የጣቷ ፡ ጫፍ ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ቀዝቅዞ ፡ ነበር
2. ጉርሻ. How much of a tip shall I give the waiter? ላሳላፊው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጉርሻ ፡ ልስጥ ?
3. ሹክ. He had a tip that the police followed him. ፖሊሶች ፡ እንደሚከታተሉት ፡ አንዱ ፡ ሹክ ፡ ነበረው
4. ጠቃሚ ፡ ወሬ. Let me give you a tip on the next horse race! በቅርቡ ፡ ስለሚደረገው ፡ የፈረስ ፡ እሽቅድምድም ፡ ጠቃሚ ፡ ወሬ ፡ ልንገርህ

**on the tip of my tongue** አፍ ፡ ላይ
The word was on the tip of my tongue. ቃሉ ፡ አፌ ፡ ላይ ፡ ነበር

**tipsy** ግልብጥ ፡ ግልብጥ ፡ የሚል
This tipsy boat is not safe to travel in. ይህ ፡ ግልብጥ ፡ ግልብጥ ፡ የሚል ፡ ጀልባ ፡ ለጉዞ ፡ የሚያስተማምን ፡ አይደለም

**get tipsy** ሰከረ
He gets tipsy on one bottle of beer. ባንድ ፡ ጠርሙስ ፡ ቢራ ፡ ይሰክራል

**tiptoe, on ~**
*The children came in on tiptoe. ልጆቹ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ በጣታቸው ፡ እየተራመዱ ፡ መጡ

**tiptop** አንደኛ
This hotel is tiptop. ይህ ፡ ሆቴል ፡ አንደኛ ፡ ነው

**tiptop shape** ሙሉ ፡ ጤንነት
I am in tiptop shape now. አሁን ፡ በሙሉ ፡ ጤንነት ፡ ላይ ፡ እገኛለሁ

**tire** (vt.) አደከመ
The walk tired the child. መንገዱ ፡ ልጁን ፡ አደከመው

**tire** (vi.) ደከመ
The old lady tires easily. አሮጊቷ ፡ ቶሎ ፡ ይደክማሉ

**tire of** ታከተ(ው)
She never tires of telling about her trip to Europe. ስለ ፡ አውሮፓ ፡ ጉብኝቷ ፡ ማውራት ፡ አይታክታትም

**tire out** አደከመ
The hustle and bustle of a big city tires me out. የትልቅ ፡ ከተማ ፡ ግርግር ፡ ያደክመኛል

**tire** (n.) ጎማ
Did you put air in the tires? ጎማውን ፡ ነፋት ፡ ሃል ?
[See also 'flat']

**tired** (adj.) የደከመ
The tired horse couldn't run. የደከመው ፡ ፈረስ ፡ ሊጋልብ ፡ አልቻለም

**be all tired out** በጣም ፡ ደከመ(ው)
I'm all tired out from the race. ከሩጫው ፡ ውድድር ፡ የተነሣ ፡ በጣም ፡ ደክሞኛል

**be tired** ደከመ(ው) ፤ ደከመ
I am tired today and cannot go to work. ስለደከመኝ ፡ (ስለደከምኩ) ፡ ዛሬ ፡ ሥራ ፡ ልሄድ ፡ አልችልም

**be tired of** ሰለቸ(ው)
+I am tired of doing the same thing over and over again. ያንኑ ፡ ነገር ፡ እየደጋገምኩ ፡ መሥራቱ ፡ ሰልችቶኛል

**be tired out**
1. ድካም ፡ አለ(ው). +I am tired out working all day. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ስሠራ ፡ ውዬ ፡ ድካም ፡ ብሎኛል
2. (= active) አደቀቀ. +I'm tired out from the trip. ጉዞው ፡ አድቅቆኛል

**feel tired** ድካም ፡ ተሰማ(ው)
I feel tired, and can't go to work. ድካም ፡ ስለተሰማኝ ፡ ሥራ ፡ ልሄድ ፡ አልችልም

**get tired** ደከመ(ው)
I get tired easily. ቶሎ ፡ ይደክመኛል

**look tired** ድካም ፡ ታየበት
He looks tired; he must have been sick. ድካም ፡ ይታይበታል ፤ ታሞ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም
[See also 'dead, dog, sick']

**tiredness** ድካም
I think my tiredness is caused by a poor diet. የድካሜ ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ የምግብ ፡ አለመመጣጠን ፡ ይመስለኛል

**tireless**
1. የማይታክት. A tireless worker is needed for this job. ለዚህ ፡ ሥራ ፡ የማይታክት ፡ ሠራተኛ ፡ ያስፈልጋል
2. ያልተቈጠበ. His tireless efforts finally succeeded in getting the bill through. ያልተቈጠበ ፡ ጥረቱ ፡ በመጨረሻ ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ እንዲያልፍ ፡ ለማድረግ ፡ አስቻለ

**tiresome**
1. አድካሚ. This work is tiresome. ይህ ፡ ሥራ ፡ አድካሚ ፡ ነው
2. አሰልቺ. Deliver me from such tiresome people! እንደዚህ ፡ ካሉ ፡ አሰልቺ ፡ ሰዎች ፡ ጠብቀኝ

**tissue** የአካል ፡ ቁራጭ
The doctor examined the bits of human tissue. ሐኪሙ ፡ የሰው ፡ የአካል ፡ ቁራጮች ፡ መረመረ

**tissue of lies** ሐሰት
Her story is a tissue of lies. የምታወራው ፡ ሁሉ ፡ ሐሰት ፡ ነው

**tissue paper** [ለንጽሕና ፡ ቤት ፡ ለመሐረብና ፡ ለእቃ ፡ ለመጠቅለያም ፡ የሚያገለግል ፡ ለስላሳ ፡ ወረቀት]

**tithe** ዐሥራት
Pay the tithe to the deacon! ዐሥራቱን ፡ ለዲያቆኑ ፡ አስረክብ

**title** (v.) ሰየመ
He titled his book "Remembrances of My Homeland". መጽሐፉን ፡ « የትውልድ ፡ አገሬ ፡ ትዝታዎች » ፡ ብሎ ፡ ሰየመ

**title** (n.)
1. አርእስት ፤ ስም. Do you know the title of the book? የመጽሐፉን ፡ ስም ፡ (አርእስት) ፡ ታውቃለህ ?
2. ማዕረግ. What's his title? ማዕረጉ ፡ ምንድነው?
3. የማዕረግ ፡ ስም. Protocol requires that dignitaries always be addressed by their titles. ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ በማዕረግ ፡ ስማቸው ፡ እንዲጠሩ ፡ ፕሮቶኮል ፡ ያስገድዳል
4. መብት. What title has he to the office? ሥልጣኑን ፡ ለመያዝ ፡ ምን ፡ መብት ፡ አለው ?
*Has he any title to the land? መሬቱ ፡ ይገባኛል ፡ የሚልበት ፡ ነገር ፡ አለ ?

**win the title** ሻምፒዮና ፡ ሆነ
Our team won the football title. ቡድናችን ፡ የእግር ፡ ኳስ ፡ ሻምፒዮና ፡ ሆነ

**title page** አርእስቱ ፡ በሰፈረበት ፡ ገጽ
The author's name is written on the title page. የደራሲው ፡ ስም ፡ አርእስቱ ፡ በሰፈረበት ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ተጽፏል

**title role** መሪ ፡ ቦታ
He played the title role in "Hamlet". በሀምሌት ፡ ውስጥ ፡ መሪውን ፡ ቦታ ፡ ይዞ ፡ ተጫወተ

**titular** (= adv.) ለስም ፡ ብቻ
He is titular head of the party. የሱ ፡ የፖለቲካው ፡ ቡድን ፡ መሪነት ፡ ለስም ፡ ብቻ ፡ ነው

**to**
1. ወደ. She went to Addis Ababa. ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሄደች
Take the first street to your left! ወደ ፡ ግራህ ፡ ያለውን ፡ የመጀመሪያ ፡ መንገድ ፡ ይዘህ ፡ ሂድ
2. ለ. It is ten to two. ለስምንት ፡ ዐሥር ፡ ጉዳይ ፡ ነው
To whom did you give it? ለማን ፡ ሰጠኸው ?
The score was 9 to 5. ውጤቱ ፡ ዘጠኝ ፡ ለአምስት ፡ ነበር
3. እስከ. I am home from 9 to 12 every day. ሁልጊዜ ፡ ከሦስት ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ እቤት ፡ ነኝ
4. በስተ --- በኩል. Eritrea is to the north of Addis Ababa. ኤርትራ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ በስተ ሰሜን ፡ በኩል ፡ ነው

5. ከ --- ይልቅ. I prefer walking to running. ከመሮጥ ፡ ይልቅ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ መሄድን ፡ እመርጣለሁ
6. ላይ. Please fasten the notice to the bulletin board! ማስታወቂያውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰሌዳው ፡ ላይ ፡ ለጥፈው
7. (suffix pronouns). Give the book to me! መጽሐፉን ፡ ስጠኝ
8. ል + (imperfect). I'm trying to help you. ልረዳህ ፡ እየሞከርኩ ፡ ነው
Speak to her! እሷን ፡ አነጋግራት
*There are four oranges to the pound. አራት ፡ ብርቱካን ፡ አንድ ፡ ነጥር ፡ ይመዝናል
*We danced to the music. ሙዚቃውን ፡ ተከትለን ፡ ደነስን
*To my amazement, he came to see me. መምጣቱ ፡ ገረመኝ
*I told him that you stayed out late last night. What did he say to that? ትናንትና ፡ አምሽተህ ፡ መግባትህን ፡ ነገርኩት ፤ ታዲያ ፡ ምን ፡ አለ ?

**to and fro** ወዲያ ፡ ወዲህ
He paced to and fro in his room. በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ተንጐራደደ

**toad** ጉርጥ
Toads eat flies. ጉርጥ ፡ ዝንቦችን ፡ ይበላል

**toast** (v.)
1. ጠበሰ. Shall I toast the bread? ዳቦውን ፡ ልጥበሰው ?
2. ስለ --- ጤንነት ፡ ጠጣ. Let's toast the hostess! ስለ ፡ አስተናጋጅዋ ፡ ጤንነት ፡ እንጠጣ
[See also 'drink']

**toast** (n.) የተጠበሰ ፡ ዳቦ
Put butter on my toast! የተጠበሰው ፡ ዳቦ ፡ ላይ ፡ ቅቤ ፡ አድርግልኝ
*The toast was followed by cheers. ጽዋ ፡ ከነሡ ፡ በኋላ ፡ ተጨበጨበ

**toaster** መጥበሻ
Put the bread in the toaster! ዳቦውን ፡ መጥበሻው ፡ ላይ ፡ አድርገው

**tobacco** ትምባሆ
Put more tobacco in my pipe! ፒፓዬ ፡ ውስጥ ፡ ትምባሆ ፡ ጨምርበት
He chews tobacco. ትምባሆ ፡ ይጐርሳል

**today**
1. ዛሬ. What's on the menu today? ዛሬ ፡ ምን ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ምግብ ፡ አለ ?
We are making great strides in medicine today. ዛሬ ፡ በሕክምና ፡ ረገድ ፡ ከፍተኛ ፡ እርምጃ ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ነን
2. ባሁኑ ፡ ጊዜ. Many people have television sets today. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ቴሌቪዥን ፡ አላቸው

**today's** የዛሬ
I haven't read today's paper yet. የዛሬውን ፡ ጋዜጣ ፡ ገና ፡ አላነበብኩትም

**a week ago today** የዛሬ ፡ ሳምንት + perfect
He left a week ago today. የዛሬ ፡ ሳምንት ፡ ሄደ

**a week from today** የዛሬ ፡ ሳምንት + imperfect
I will leave a week from today. የዛሬ ፡ ሳምንት ፡ እሄዳለሁ
Three weeks from today is a holiday. የዛሬ ፡ ሦስት ፡ ሳምንት ፡ በዓል ፡ ነው

**toddle** ድክ ፡ ድክ ፡ አለ
The baby toddled across the floor. ሕፃኑ ፡ በወለሉ ፡ ላይ ፡ ድክ ፡ ድክ ፡ አለ

**to-do** ትልቅ ፡ መራወጥ
What a to-do there was when the guests came early! የተጠሩት ፡ ሰዎች ፡ ከሰዓቱ ፡ በፊት ፡ በመምጣታቸው ፡ ትልቅ ፡ መራወጥ ፡ ነበር

**toe** (v.), ~ **the line**
1. መሥመር ፡ ላይ ፡ ተንበረከከ. The runners toed the starting line. ሯጮቹ ፡ መነሻው ፡ መሥመር ፡ ላይ ፡ ተንበረከኩ
2. ያሉትን ፡ ተቀበለ. You'd better toe the line when you're in the army. ወታደር ፡ ስትሆን ፡ ያሉህን ፡ መቀበል ፡ አለብህ
[See also 'head']

**toe** (n.) የእግር ፡ ጣት
My toes are frozen. የእግር ፡ ጣቶቼ ፡ በረዶ ፡ ሆነዋል
He has a hole in the toe of his sock. የእግር ፡ ሹራቡ ፡ ጣቱ ፡ ላይ ፡ ተበስቷል

**on (one's) toes** ንቁ
He is always on his toes when the boss is around. አለቃው ፡ ሲኖር ፡ ሁልጊዜ ፡ ንቁ ፡ ነው

**step on anyone's toes** አስቀየመ
I didn't mean to step on anyone's toes when I brought up the subject. ነገሩን ፡ ያነሣሁት ፡ ማንንም ፡ ለማስቀየም ፡ ብዬ ፡ አልነበረም

**step on one's toes** እግሩን ፡ ረገጠው
I stepped on her toes in the crowded elevator. አሳንሰሩ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ ስለነበር ፡ እግሯን ፡ ረገጥኳት

**toenail** የእግር ፡ ጥፍር
The doctor cut my toenail. ሐኪሙ ፡ የእግሬን ፡ ጥፍር ፡ ቈረጠልኝ

**together**

1. አብረው. They came together on the same train. ባንድ ፡ ባቡር ፡ አብረው ፡ መጡ
2. በመተባበር. Community of interests causes people to work together. ተመሳሳይ ፡ ዓላማ ፡ ሰዎችን ፡ በመተባበር ፡ እንዲሠሩ ፡ ያደርጋል
3. አንድ ፡ ላይ. Don't put them together in the same room! አንድ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አታስቀምጣቸው

All the cannons went off together. መድፎቹ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተተኰሱ

**together at the same time** ባንድ ፡ ጊዜ

All his troubles seem to come together at the same time. ችግሩ ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የወረደበት ፡ ይመስላል

**together with** ከ --- ጋር

These new facts, together with the evidence we already have, will be enough to convict him. እነዚህ ፡ አዲስ ፡ መረጃዎች ፡ በፊት ፡ ከነበረው ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ለመፍረድ ፡ ያስችሉናል

**very well together** ተግባብተው

We work very well together. ተግባብተን ፡ እንሠራለን

**toil** (v.) ለፋ

He toiled for many years at that job. ያንን ፡ ሥራ ፡ ለማከናወን ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ ለፋ

The farmer toils in the field. ገበሬው ፡ እርሻው ፡ ውስጥ ፡ ይለፋል

**toil up** በድካም ፡ ወጣ

The children toiled up the hill. ልጆቹ ፡ ተራራውን ፡ በድካም ፡ ወጡት

**toil** (n.) ብርቱ ፡ ሥራ ፤ ልፋት

Toil left his hands covered with calluses. ብርቱ ፡ ሥራ ፡ (ልፋት) ፡ እጁን ፡ አሻከረው

**toilet** ሽንት ፡ ቤት

Flush the toilet! ሽንት ፡ ቤቱን ፡ ውኃ ፡ ልቀቅበት

**toilet articles** መኳኳያ

He bought his wife some toilet articles in Paris. ለሚስቱ ፡ ከፓሪስ ፡ መኳኳያ ፡ ገዛላት

**make (one's) toilet** ተበጃጀ

She made a hurried toilet. በችኰላ ፡ ተበጃጀች

**token** (n.)

1. [ለስልክ ፡ መደወያ ፡ ወይም ፡ ለአውቶቡስ ፡ መሄጃ ፡ የሚያገለግል ፡ በሳንቲም ፡ ልክ ፡ የተሠራ ፡ ክብ ፡ ብረት].
2. ምልክት. He gave it to me as a token of his friendship. የወዳጅነቱ ፡ ምልክት ፡ ይሆነኝ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ሰጠኝ
3. ማስታወሻ. The ring was a token from my aunt. ቀለበቱ ፡ ከክስቴ ፡ የተሰጠኝ ፡ ማስታወሻ ፡ ነበር

**by the same token** በዚሁ ፡ ምክንያት

By the same token, I won't go either. በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ እኔም ፡ አልሄድም

**token,** adj. (= adv.) ለስሙ ፡ ያህል ፤ ለስሙ ፡ ትንሽ

The enemy offered only token resistance. ጠላት ፡ የተከላከለው ፡ ለስሙ ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ ነበር

He made only a token payment. ለስሙ ፡ ብቻ ፡ ትንሽ ፡ ከፈለ

**told,** see **tell**

**tolerable** የሚቻል

The pain was bad, but it was tolerable. ሕመሙ ፡ ኀይለኛ ፡ ቢሆንም ፡ የሚቻል ፡ ነበር

**be tolerable** ምንም ፡ አይል

The food is tolerable. ምግቡ ፡ ምንም ፡ አይል

**tolerance** መታገሥ

The teacher's tolerance of their bad behavior surprised us. አስተማሪው ፡ መጥፎ ፡ ጠባያቸውን ፡ መታገሡ ፡ አስደነቀን

**achieve tolerance** ተቻችሎ ፡ ኖረ

We must try to achieve tolerance in religious matters. በሃይማኖታችን ፡ ተቻችለን ፡ ለመኖር ፡ መሞከር ፡ አለብን

**tolerant** ቻይ

A tolerant person usually has breadth of mind. ቻይ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አእምሮው ፡ ሰፊ ፡ ነው

**be tolerant**

1. አልተቃወመም. This government is tolerant toward all religious beliefs. ይህ ፡ መንግሥት ፡ ማንኛውንም ፡ ሃይማኖት ፡ አይቃወምም
2. አይቶ ፡ እንዳላየ ፡ አለፈ. He is tolerant of other people's frailties. የሌሎችን ፡ ጠባይ ፡ ደካማነት ፡ አይቶ ፡ እንዳላየ ፡ ያልፋል

**tolerate**

1. አከበረ. We must tolerate other people's ideas. የሌሎች ፡ ሰዎችን ፡ አስተያየት ፡ ማክበር ፡ አለብን
2. ታገሠ. They tolerated the grouchy man only because he was their employer. ነጭናጫውን ፡ ሰው ፡ የታገሡት ፡ ቀጣሪያቸው ፡ ስለሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው

3. ተቀበለ. He is a zealot who can tolerate no religion but his own. የራሱን ፡ እንጂ ፡ የሌላን ፡ ሃይማኖት ፡ የማይቀበል ፡ ቀናኢ ፡ ነው

**not tolerate**

1. አልወደደም. She can't tolerate cats. እሷ ፡ ድመት ፡ አትወድም
2. ችላ ፡ ሊል ፡ አልቻለም. A nation at war will not tolerate treason. በጦርነት ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ሀገር ፡ ከዳተኞችን ፡ ችላ ፡ ሊል ፡ አይችልም
3. ተቃወመ. Christianity does not tolerate paganism. የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ አረመኔነትን ፡ ይቃወማል

**toll** (v.) ተደወለ
Church bells tolled. የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደወሎች ፡ ተደወሉ

**toll** (n.)
1. የኬላ ፡ ቀረጥ. You have to pay a toll on this bridge. በዚህ ፡ ድልድይ ፡ ላይ ፡ ሲያልፉ ፡ የኬላ ፡ ቀረጥ ፡ መክፈል ፡ ያስፈልጋል
2. ጉዳት. The earthquake took a heavy toll in lives and property. የመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ በሰውና ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ አደረሰ

**toll** (adj.) ቀረጥ ፡ የሚከፈልበት
We crossed the river on a toll bridge. ቀረጥ ፡ በሚከፈልባት ፡ ድልድይ ፡ ተሻገርን
*A toll call to a distant city costs at least a dollar. ሩቅ ፡ ወዳለ ፡ ከተማ ፡ ለሚደረግ ፡ ጥሪ ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ይከፈላል

**tomato** ቲማቲም

**tomb** መቃብር
He placed flowers on the tomb of an unknown soldier. ባልታወቀ ፡ ወታደር ፡ መቃብር ፡ ላይ ፡ አበባ ፡ አኖረ

**tombstone** ሐውልት ፤ የመቃብር ፡ ድንጋይ
They placed the tombstone on her grave yesterday. ትላንትና ፡ በመቃብሯ ፡ ላይ ፡ ሐውልት ፡ ሠሩላት
They engraved his name on the tombstone. በመቃብሩ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ስሙን ፡ ቀረጹ

**tome** መጽሐፍ (pl. መጻሕፍት)
He has many large tomes in his library. በቤቱ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ትልልቅ ፡ መጻሕፍት ፡ አሉት

**tomorrow** ነገ
I will be back tomorrow. ነገ ፡ እመለሳለሁ

**tomorrow's** የነገ
It will be in tomorrow's paper. በነገው ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ይወጣል

**the day after tomorrow** ተነገ ፡ ወዲያ
It will be ready the day after tomorrow. ተነገ ፡ ወዲያ ፡ ይደርሳል
[See also 'night']

**ton** ቶን
We have produced a hundred tons of cement this week. በዚህ ፡ ሳምንት ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ቶን ፡ ሲሚንቶ ፡ ሠርተን ፡ አወጣን

**tone, ~ down** (vt.) ለዘብ ፡ አደረገ
You'd better tone down some of the statements you made in your speech! በንግግርህ ፡ ላይ ፡ የጠቀስካቸውን ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ ለዘብ ፡ አድርጋቸው

**tone down** (vi.) በረድ ፡ አለ
The excitement toned down. ግርግሩ ፡ በረድ ፡ አለ

**tone in** ሠመረ
The painting tones in with the rest of the room. ሥዕሉ ፡ ከክፍሉ ፡ ጋር ፡ ይሠምራል

**tone** (n.)
1. ቃና. This instrument has a beautiful tone. ይህ ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ ፡ ጥሩ ፡ ቃና ፡ አለው
2. ድምፅ. He spoke in a low tone. ድምፁን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ተናገረ
3. ቃል. The officer spoke to the crew in an authoritative tone. መኰንኑ ፡ ሠራተኞቹን ፡ በአዛዥነት ፡ ቃል ፡ ተናገራቸው
4. የተናገረ. The doctor's tone was serious. ሐኪሙ ፡ የተናገረው ፡ ከስተር ፡ ብሎ ፡ ነበር
5. ቀለም. The picture's tone looks fine. የሥዕሉ ፡ ቀለም ፡ ደኅና ፡ ይመስላል
*Her dress has several tones of red. የቀሚሷ ፡ ቅላት ፡ የተለያየ ፡ ነው
*You mustn't speak to her in such a tone. እንዲህ ፡ አድርገህ ፡ ልትናገራት ፡ አይገባም
[See also 'soften']

**tongs** መቆንጠጫ
Use the tongs to stir the fire! እሳቱን ፡ በመቆንጠጫው ፡ ቈስቍሰው

**tongue**
1. ምላስ. Stick out your tongue! ምላስህን ፡ አውጣ
He lost his tongue. ምላሱ ፡ ታሰረ
2. ቋንቋ. The English tongue is spoken all over the world. የእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ይነገርበታል

**tongue of flame** የእሳት ፡ ነበልባል
Tongues of flame were seen leaping into the air.

የእሳት ፡ ነበልባል ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሲወጣ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**tongue of land** ቀጭን ፡ ልሳን ፡ ምድር
The house is built on a tongue of land which extends into the lake. ቤቱ ፡ የተሠራው ፡ ወደ ፡ ሐይቁ ፡ በሚገባ ፡ አንድ ፡ ቀጭን ፡ ልሳን ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ነው

**have a sharp tongue** ምላሰኛ ፡ ነው ፤ ምላሱ ፡ ጦር ፡ ሆነ
She has a sharp tongue, so don't argue with her. ምላሰኛ ፡ ስለሆነች ፡ (ምላሷ ፡ ጦር ፡ ስለሆነ) ፡ ከሷ ፡ ጋር ፡ አትከራከር

**hold (one's) tongue** ዝም ፡ አለ
Hold your tongue while I am speaking. እኔ ፡ ስናገር ፡ ዝም ፡ በል
[See also 'lapse, loose, native tongue, slip, tip']

## (be, become) tongue-tied ምላሱ ፡ ተሳሰረ
The excited witness became tongue-tied and couldn't answer. የደነገጠው ፡ ምስክር ፡ ምላሱ ፡ ስለተሳሰረ ፡ ሊመልስ ፡ አልቻለም

## tonic (n.) ቶኒክ
Get a bottle of tonic from the doctor! አንድ ፡ ጠርሙስ ፡ ቶኒክ ፡ ከዶክተሩ ፡ ዘንድ ፡ አምጣ

**act as a tonic** አበረታታ
The good news acted as a tonic for all of us. መልካሙ ፡ ዜና ፡ ሁላችንንም ፡ አበረታታን

**have a tonic effect** አነቃቃ
Swimming has a tonic effect. ዋና ፡ ያነቃቃል

## tonight ዛሬ ፡ ማታ
I am sleeping at my aunt's house tonight. ዛሬ ፡ ማታ ፡ የማድረው ፡ አክስቴ ፡ ቤት ፡ ነው

## tonsil
*The doctor removed his tonsils. ሐኪሙ ፡ ጉሮሮውን ፡ ቧጠጠለት

## tonsure, wear a ~ አናቱን ፡ ላጨ
Catholic priests and monks wear tonsures. የካቶሊክ ፡ ቄሶችና ፡ መነኵሴዎች ፡ አናታቸውን ፡ ይላጫሉ

## too
1. በጣም. These shoes are too large. ይህ ፡ ጫማ ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ ነው
He was too tired to go any further. በጣም ፡ ስለደከመው ፡ ጉዞውን ፡ መቀጠል ፡ ተሳነው
2. -ም. The child is hungry, and thirsty too. ልጁ ፡ ርቦታል ፡ ጠምቶታልም
May I come too? እኔም ፡ ልምጣ ?

**too long** ብዙ
Don't stay away too long; we have to leave in half an hour. በግማሽ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ መሄድ ፡ ስላለብን ፡ ብዙ ፡ አትቆይ

**too much**
1. ብዙ. This knife edge became blunt from cutting too much wood. ብዙ ፡ ዕንጨት ፡ ስለተቈረጠበት ፡ ይህ ፡ ቢላዋ ፡ ደነዘ
2. ያለመጠን ፤ ከመጠን ፡ በላይ. Don't expose your skin to too much sunshine! ቆዳህን ፡ ያለመጠን ፡ (ከመጠን ፡ በላይ) ፡ ፀሐይ ፡ አታስመታው

**then too** ከዚያም ፡ በላይ
Then too, we must take him into consideration. ከዚያም ፡ በላይ ፡ ስለሱ ፡ ማሰብ ፡ አለብን
[See also 'many, soon']

## took, see take

## tool መሣሪያ
Be careful of those tools! እነዚያን ፡ መሣሪያዎች ፡ በጥንቃቄ ፡ ያዛቸው
Books are tools of education. መጻሕፍት ፡ የትምህርት ፡ መሣሪያ ፡ ናቸው
The mayor is a tool of his party. ከንቲባው ፡ የፖለቲካው ፡ ቡድን ፡ መሣሪያ ፡ ነው

## toot አስጮኸ
He tooted his horn. መኪናውን ፡ ጥሩምባ ፡ አስጮኸ

## tooth (teeth) ጥርስ
His teeth are chipped. ጥርሱ ፡ ሸራፋ ፡ ነው
The saw has sharp teeth. የመጋዙ ፡ ጥርስ ፡ ስል ፡ ነው

**tooth and nail**
We fought against them tooth and nail. ከነሱ ፡ ጋር ፡ ባለን ፡ ኀይል ፡ ሁሉ ፡ ተዋጋን

**armed to the teeth**
He was armed to the teeth. ሙሉ ፡ መሣሪያ ፡ ታጥቆ ፡ ነበረ

**by the skin of (one's) teeth** ለትንሽ
He escaped by the skin of his teeth. ለትንሽ ፡ አመለጠ

**cut teeth** ጥርስ ፡ አወጣ
The baby is cutting its teeth. ሕፃኑ ፡ ጥርስ ፡ በማውጣት ፡ ላይ ፡ ነው

**set one's teeth on edge**
1. ሰቀጠጠ(ው). The sound of fingernails scraping on a blackboard sets my teeth on edge. ጥቁር ፡ ሰሌዳ ፡ በጥፍር ፡ ሲጧጥ ፡ ሲደረግ ፡ ይሰቀጥጠኛል
2. ጥርሱን ፡ አደነዘዘ. Sour fruit sets my teeth on edge. ከምጣጣ ፡ ፍሬ ፡ ጥርሴን ፡ ያደነዝዘዋል

**sweet tooth**
She has a sweet tooth. ጣፋጭ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ትወዳለች

**toothache** የጥርስ ፡ሕመም
His toothache is causing him great suffering. የጥርስ ፡ ሕመሙ ፡ ብዙ ፡ ያስጨንቀዋል

**toothbrush**
1. የጥርስ ፡ ብሩሽ. I lost my toothbrush. የጥርስ ፡ ብሩሼ ፡ ጠፋብኝ
2. መፋቂያ. What kind of toothbrush do the natives use? ያገሩ ፡ ተወላጆች ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ መፋቂያ ፡ ጥርሳቸውን ፡ ይፍቃሉ ?

**toothpaste** የጥርስ ፡ ሳሙና
I need some toothpaste. የጥርስ ፡ ሳሙና ፡ እፈልጋለሁ

**toothpick** የጥርስ ፡ መጐርጐሪያ
Give me a toothpick! የጥርስ ፡ መጐርጐሪያ ፡ ስጠኝ

**(be) toothsome** እጅ ፡ አስቈረጠመ
Her cooking is toothsome. የምታዘጋጀው ፡ ምግብ ፡ እጅ ፡ ያስቈረጥማል

**top** (topped)
1. ሸፈነ. Snow topped the mountain. የተራራውን ፡ ጫፍ ፡ በረዶ ፡ ሸፍኖታል
2. መደምደሚያ ፡ ሆነ. That tops everything! ያ ፡ የነገሩ ፡ ሁሉ ፡ መደምደሚያ ፡ ይሆናል
3. አንደኛ ፡ ወጣ. Jim topped his class. ጂም ፡ ከክፍሉ ፡ አንደኛ ፡ ወጣ
4. አስከነዳ. He tops them all at soccer. በእግር ፡ ኳስ ፡ ጨዋታ ፡ ሁሉንም ፡ ያስከነዳል
5. ከ - - - በለጠ. His story topped all the rest. የሱ ፡ ታሪክ ፡ ከሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ በለጠ
6. ከ - - - ጫፍ ፡ ላይ ፡ ደረሰ. The boy scouts topped the hill. ቦይ ፡ እስካውቶቹ ፡ ከተራራው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ደረሱ
7. ቀባ. The baker topped the cake with butter. ዳቦ ፡ ጋጋሪው ፡ ኬኩን ፡ ቅቤ ፡ ቀባው

**to top it off** ይግረምህ ፡ ብሎ
To top it off, he stole my wallet. ይግረምህ ፡ ብሎ ፡ የኪስ ፡ ቦርሳዬን ፡ ሰረቀኝ

**top** (n.)
1. ጫፍ. How far is it to the top of this mountain? የተራራው ፡ ጫፍ ፡ ርቀቱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?
2. ክዳን. The top of the bottle is missing. የጠርሙሱ ፡ ክዳን ፡ ጠፍቷል
3. ወለል. A table top is horizontal. የጠረጴዛው ፡ ወለል ፡ አግዳሚ ፡ ነው
4. ጅልቦ. He was spinning a top on the sidewalk. በእግረኛ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ጅልቦ ፡ ያሽከረክር ፡ ነበር
5. ሸራ. Put down the top of the car! የመኪናውን ፡ ሸራ ፡ ግለጠው

**top** (adj.)
1. ላይኛ. It's in the top drawer. ላይኛው ፡ መሳቢያ ፡ ውስጥ ፡ ነው
2. ከፍተኛ. This document is top secret. ይህ ፡ ሰነድ ፡ ከፍተኛ ፡ ምስጢር ፡ ይዟል
We drove at top speed all the way down here. እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍጥነት ፡ እየነዳን ፡ መጣን
*My brother is a top student. ወንድሜ ፡ ጉበዝ ፡ ከሚባሉት ፡ ተማሪዎች ፡ አንዱ ፡ ነው

**top half**
He is in the top half of his class. የክፍሉን ፡ አጋማሽ ፡ ተማሪዎች ፡ ከሚበልጡት ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ነው

**at the top of** መጀመሪያው ፡ ላይ
You will find that passage at the top of page 32. ያንን ፡ ምንባብ ፡ ገጽ ፡ ሠላሳ ፡ ሁለት ፡ መጀመሪያው ፡ ላይ ፡ ታገኘዋለህ

**at the top of one's voice**
She shouted at the top of her voice. ጉሮሮዋ ፡ እስኪሰነጠቅ ፡ (እስኪነቃ) ፡ ጮኸች

**come out on top** አንደኛ ፡ ሆነ
He came out on top in the fight. በትግል ፡ አንደኛ ፡ ሆነ

**on the top of** በ - - - መጀመሪያ ፡ ላይ
His name is on the top of the list. ስሙ ፡ በዝርዝሩ ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ነው

**on top** ከላይ
The book is lying on top. መጽሐፉ ፡ ከላይ ፡ ተቀምጧል

**on top of** አናት ፡ ላይ
The book is standing on top of the bookcase. መጽሐፉ ፡ መጽሐፍ ፡ መደርደሪያው ፡ አናት ፡ ላይ ፡ ነው

**on top of that**
1. ከ - - - በላይ. He gave me three weeks vacation, and on top of that, he also gave me a bonus. የሦስት ፡ ሳምንት ፡ ዕረፍት ፡ ከመፍቀዱም ፡ በላይ ፡ ጉርሻ ፡ ሰጠኝ
2. — ም - - ም. He asked me for $50, and on top of that, wanted to use my car. ኀምሳ ፡ ብር ፡ አበድረውም ፡ መኪናዬንም ፡ ሊወስድ ፡ ፈለገ

**to the top of** ከ - - አናት ፡ ላይ
The mason heaved the stone to the top of the

wall. ግንበኛው ፡ ደንጊያውን ፡ በስንት ፡ ችግር ፡ ከግድግዳው ፡ አናት ፡ ላይ ፡ አወጣው
[See also 'bottom, put']

**(be) top-heavy** አጋደለ
The load was top-heavy. ጭነቱ ፡ አጋድሏል
*The ministry is top-heavy with directors. ሚኒስቴሩ ፡ ከሚገባው ፡ በላይ ፡ ብዙ ፡ ዲሬክተሮች ፡ አሉት

**topic** አርእስት
War was the topic of their conversation. የንግግራቸው ፡ አርእስት ፡ ጦርነት ፡ ነበር

**topmost** ከፍ ፡ ብሎ ፡ የሚገኝ
The best apples seem to grow on the topmost branches. ምርጥ ፡ የሆኑት ፡ ቱፋዎች ፡ የሚገኙት ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ ከሚገኙት ፡ ቅርንጫፎች ፡ ላይ ፡ ይመስላል

**topography** የመሬት ፡ አቀማመጥ
The topography of the country is not sufficiently known. የሀገሪቱ ፡ የመሬት ፡ አቀማመጥ ፡ በደንብ ፡ አይታወቅም

**topple** (vt.)
1. ገነደሰ. The wind toppled the tree. ነፋሱ ፡ ዛፉን ፡ ገነደሰው
2. ዘረረ ፤ ጣለ. The wrestler toppled his opponent. ታጋዩ ፡ ተወዳዳሪውን ፡ ዘረረው ፡ (ጣለው)

**topple** (vi.) ተገለበጠ
The government set up by the rebels soon toppled. በመፀኞቹ ፡ ያቋቋሙት ፡ መንግሥት ፡ ወዲያው ፡ ተገለበጠ

**topple down** ተናደ
The pile of books toppled down. የመጽሐፉ ፡ ቁልል ፡ ተናደ

**topsoil** [ከላይ ፡ የሚገኘው ፡ ለም ፡ አፈር]

**(be) topsy-turvy** መላ ፡ ቅጡ ፡ ጠፋ
Everything was topsy-turvy. ሁሉም ፡ ነገር ፡ መላ ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቷል

**torch** ችቦ
The torch gave a flickering light. ችቦው ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ ይላል

**put to the torch** አጋየ
They put the village to the torch. መንደሩን ፡ አጋዩት

**tore,** see **tear**

**torment** (v.)
1. አሠቃየ. He tormented the cat by pulling its tail. ድመቷን ፡ ጅራቷን ፡ እየጐተተ ፡ አሠቃያት
2. አስቸገረ. That boy torments everyone with silly questions. ያ ፡ ልጅ ፡ የማይረባ ፡ ጥያቄ ፡ በመጠየቅ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ያስቸግራል

**torment** (n.) ሕመም ፤ ሥቃይ
His torment lasted until the medicine took effect. መድኀኒቱ ፡ እስኪሠራ ፡ ድረስ ፡ ሕመሙ ፡ (ሥቃዩ) ፡ ቆየበት

**be a torment** አሠቃየ
A bad burn can be a torment. ከባድ ፡ የእሳት ፡ ቃጠሎ ፡ ያሠቃያል

**be in torment** ተሠቃየ
He was in torment from an aching tooth. ጥርሱን ፡ አሞት ፡ ይሠቃይ ፡ ነበር

**suffer torments** ተሠቃየ
He suffered torments from his aching tooth. በጥርስ ፡ ሕመም ፡ ተሠቃየ

**tormentor** ያሠቃየ ፡ ሰው ፤ አሠቃይ
He was consumed with hate for his tormentors. ባሠቃዩት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጥላቻ ፡ አደረበት

**torn,** see **tear**

**tornado** ኀይለኛ ፡ ዉይት
The tornado flattened the town. ኀይለኛ ፡ ዉይት ፡ ከተማውን ፡ አፈረሰው

**torpedo** ቶርፒዶ
The torpedo sank the ship. ቶርፒዶው ፡ መርከቧን ፡ አሰጠማት

**(be) torpid** ፍዝዝ ፡ አለ
He was torpid after the heavy meal. ከባድ ፡ ምግብ ፡ በልቶ ፡ ፍዝዝ ፡ ብሏል

**torpor**
*His torpor is due to the heavy meal he just ate. ልፍስፍስ ፡ ያለው ፡ ከባድ ፡ ምግብ ፡ ስለበላ ፡ ነው

**torrent** ወራጅ ፡ ውኃ
The torrent swept away the bridge. ወራጅ ፡ ውኃ ፡ ድልድዩን ፡ ጠርጎ ፡ ይዞት ፡ ሄደ

**a torrent of** መዓት
The speaker was deluged by a torrent of questions. ተናጋሪው ፡ የጥያቄ ፡ መዓት ፡ ወረደበት

**torrential** ኀይለኛ
A torrential flood inundated the fields. ኀይለኛ ፡ ጐርፍ ፡ እርሻውን ፡ አጥለቀለቀው

**torrid** በጣም ፡ ሞቃት
The regions that are near the equator are torrid. በመሬት ፡ መቀነት ፡ አካባቢ ፡ ያሉ ፡ ቀበሌዎች ፡ በጣም ፡ ሞቃት ፡ ናቸው

**torsion**
*This wire cannot withstand torsion very well. ይህ ፡ ሽቦ ፡ እንደልብ ፡ አይጠመዘዝም

**torso**
*The torso of a young man was found in a grave. ራሱና ፡ እጅ ፡ እግሩ ፡ የተቈረጠ ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ በድን ፡ በመቃብር ፡ ውስጥ ፡ ተገኘ

**tortoise** ኤሊ
The tortoise has a hard shell. የኤሊ ፡ ልብስ ፡ ድንጋይ ፡ ነው

**tortuous**
1. ጠምዛዛ. A tortuous road leads to the top of the mountain. አንድ ፡ ጠምዛዛ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ጫፍ ፡ ያወጣል
2. ጠማማ. His reasoning is tortuous. ሐሳቡ ፡ ሁሉ ፡ ጠማማ ፡ ነው
*The river has a tortuous course. ወንዙ ፡ እየተጥመለመለ ፡ ይፈሳል

**torture** (v.) አሠቃየ
You must never torture animals. ምንጊዜም ፡ እንስሳትን ፡ ማሠቃየት ፡ አይገባም

**torture** (n.)
1. ሥቃይ. It was torture just to watch them. እነሱን ፡ መመልከት ፡ እንኳ ፡ ሥቃይ ፡ ነበር
2. የሥቃይ ፡ ቅጣት. Torture is odious to civilized people. ለሠለጠነ ፡ ሕዝብ ፡ የሥቃይ ፡ ቅጣት ፡ አስከፊ ፡ ነው

**subject (one) to torture** አሠቃየ
The police subjected him to torture. ፖሊሱ ፡ አሠቃየው

**use torture** አሠቃየ
The police used torture to extort a confession from him. ለማሳመን ፡ ፖሊሶቹ ፡ አሠቃዩት

**torturer** አሠቃይ
The torturers could not make the man recant. አሠቃዮቹ ፡ ሰውዬውን ፡ ሐሳቡን ፡ ሊያስለውጡት ፡ አልቻሉም

**toss** (vt.)
1. ጣል ፡ አደረገ(ለት). He tossed the beggar a coin. ለለማኙ ፡ ፍራንክ ፡ ጣል ፡ አደረገለት
2. አንገላታ. The waves tossed the boat. ማዕበሉ ፡ ጀልባውን ፡ አንገላታው
3. ነቀነቀ. She tossed her head in disdain. በንቀት ፡ መልክ ፡ ራሷን ፡ ነቀነቀች

**toss** (vi.) ልቡ ፡ ተገለበጠ
He tossed all night in his sleep. ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ በእንቅልፍ ፡ ልቡ ፡ ሲገለበጥ ፡ አደረ

**toss about** ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ
The balloons tossed about in the wind. ፊኛው ፡ በነፋሱ ፡ ኀይል ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ

**toss away** ወረወረ
He crumpled the paper and tossed it away. ወረቀቱን ፡ ጨባብጦ ፡ ወረወረው

**toss (a) coin** ዕጣ ፡ አወጣ
Let's toss a coin to see who pays! ማን ፡ እንደሚከፍል ፡ ዕጣ ፡ እናውጣ

**tot** ሕፃን
These clothes are for tots. እነዚህ ፡ ልብሶች ፡ ለሕፃናት ፡ ናቸው

**total** (v.)
1. ጠቅላላ ፡ ቁጥራቸው ፡ ነበረ. The visitors to the show totaled 15,000. ትርእይቱን ፡ ለማየት ፡ የመጡት ፡ ሰዎች ፡ ጠቅላላ ፡ ቁጥራቸው ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ነበር
2. በጠቅላላው ፡ ነበረ. His income totals one thousand dollars a year. ገቢው ፡ በጠቅላላው ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ነው
3. ደመረ. Total that column of figures! ያንን ፡ ቁጥር ፡ ደምር

**total up** ደመረ
Let's total up our expenses for the month! የወሩን ፡ ወጪያችንን ፡ እንደምረው

**total** (n.)
1. ድምር. Divide the total by four! ድምሩን ፡ ላራት ፡ አካፍለው
2. ጠቅላላ. Subtract ten from the total! ከጠቅላላው ፡ ዐሥር ፡ ቀንስ

**grand total** ጠቅላላ ፡ ድምር
The grand total is $215,000. ጠቅላላው ፡ ድምር ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ነው

**total** (adj.)
1. ፍጹም. The silence was total. ፍጹም ፡ ጸጥታ ፡ ነበር
2. ጠቅላላ. My total earnings for the month are two hundred dollars. ጠቅላላው ፡ የወር ፡ ገቢዬ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ነው
3. ትልቅ. We must avoid total war. ትልቅ ፡ ጦርነት ፡ እንዳይነሣ ፡ ማድረግ ፡ አለብን
*The evening was a total loss. ምሽቱ ፡ በከንቱ ፡ አለፈ

**totalitarian**
*Italy was once a totalitarian state. በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ኢጣልያ ፡ ሥልጣኑን ፡ ሁሉ ፡ በያዘ ፡ ባንድ ፡ ፓርቲ ፡ ትገዛ ፡ ነበር

**totality** ብዛት
The totality of voters amounted to ten. የመራጮች ፡ ብዛት ፡ ዐሥር ፡ ደርሷል

**totally** በፍጹም
We were totally unprepared for a surprise attack. ጠላት ፡ ላደረገው ፡ ድንገተኛ ፡ ወረራ ፡ በፍጹም ፡ አልተዘጋጀንም ፡ ነበር

**totem** [ለቤተ ፡ ሰብ ፡ ወይም ፡ ለጐሳ ፡ ወዘ. ተ. እንደ ፡ አርማ ፡ የሚያገለግል ፡ እንስሳ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፍጡር]

**totter** ተንገዳገደ
The wounded man tottered to his feet. ቍስለኛው ፡ እየተንገዳገደ ፡ ተነሣ

**touch** (vt.)
1. ነካ. Please don't touch that book! ያንን ፡ መጽሐፍ ፡ አትንካ
His head touches the ceiling. ቁመቱ ፡ ጣሪያ ፡ ይነካል
Our conversation touched many subjects. ንግግራችን ፡ ብዙ ፡ ነገሮችን ፡ የሚነካ ፡ ነበር
2. ዳሰሰ. When Jesus touched him, Lazarus came to life. ኢየሱስ ፡ በዳሰሰው ፡ ጊዜ ፡ አልአዛር ፡ ነፍስ ፡ ዘራ
3. ንክች ፡ አደረገ. He won't touch potatoes. ድንች ፡ ንክችም ፡ አያደርግ
4. ከ - - - ጋር ፡ ተወዳደረ. His car cannot touch mine for speed. በፍጥነት ፡ የሱ ፡ መኪና ፡ ከኔ ፡ መኪና ፡ ጋር ፡ አይወዳደርም
5. ተመለከተ. Our conversation doesn't touch you. ንግግራችን ፡ አንተን ፡ አይመለከትም
6. አነሣ. I didn't dare touch that subject. ያንን ፡ ጉዳይ ፡ ለማንሣት ፡ አልደፈርኩም
7. ተሰማ. Your kindness touches me. ደግነትህ ፡ ይሰማኛል

**touch** (vi.)
1. ተነካካ. The two benches touch. ሁለቱ ፡ አግዳሚ ፡ ወንበሮች ፡ ተነካክተዋል
+Our hands touched. እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተነካካን
2. ነካ. The steamer touches at all Mediterranean ports. መርከቧ ፡ በሜዲተራንያን ፡ ባሕር ፡ አካባቢ ፡ ያሉትን ፡ ወደቦች ፡ ሁሉ ፡ ትነካለች
3. ጠቀሰ. He touched on the race problem in his speech. በንግግሩ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ዘር ፡ ችግር ፡ ጠቀሰ

**be touched**
1. ተነካ. We were all touched with pity when we heard what had happened. ነገሩን ፡ ስንሰማ ፡ በሐዘን ፡ ተነካን
2. (= touch) [ልቡን] ፡ ነካው. +I was deeply touched by his kindness. ደግነቱ ፡ ልቤን ፡ ነካው
3. (= act.) መታ. +The roses were touched by the frost. ጽጌረዳዎቹን ፡ ውርጭ ፡ መታቸው

**touch down** አረፈ
The plane touched down at a small country air field. አውሮፕላኑ ፡ ባንዲት ፡ ባላገር ፡ ውስጥ ፡ በምትገኝ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ አረፈ

**touch each other** ተጋጠመ
The two estates touch each other at this point. ሁለቱም ፡ ርስቶች ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ይጋጠማሉ

**touch off** አስነሣ
His remarks touched off a violent argument. የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ኀይለኛ ፡ ክርክር ፡ አስነሣ

**touch up** አደሰ
He touched up the portrait of King Sahle Sellasie. የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴን ፡ የእጅ ፡ ሥዕል ፡ አደሰው

**can touch** ደረሰ(በት)
No one can touch him as an actor of dramatic roles. በድራማ ፡ አሠራር ፡ የሚደርስበት ፡ የለም
[See also 'sequence, sore']

**touch** (n.) የመዳሰስ ፡ ችሎታ
The blind develop a keen touch. ዓይነ ፡ ስውር ፡ የመዳሰስ ፡ ችሎታው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው
*His touch makes me shiver. ሲነካኝ ፡ ይዘገንነኛል
*I felt the touch of a hand on my arm. ክንዴን ፡ ሰው ፡ ሲነካኝ ፡ ተሰማኝ
*The work showed an expert's touch. ሥራው ፡ ዐዋቂ ፡ የሠራው ፡ መሆኑን ፡ ይገልጻል
*He added a few finishing touches to my report. ሪፖርቴን ፡ አሟልቶ ፡ ጻፈልኝ

**a touch of**
1. ላመል. The soup still needs a touch of salt. ሾርባው ፡ ጨው ፡ ላመል ፡ ያስፈልገዋል
2. ጥቂት. We had a touch of frost this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ ጥቂት ፡ ውርጭ ፡ ነበር

**at the slightest touch**
She jumped at the slightest touch. ትንሽ ፡ ነካ ፡ ሲያደርጓት ፡ በረገገች

**be in touch** ግንኙነት ፡ ነበረው
The salesmen were always in touch with headquarters. አሻሻጮቹ ፡ ሁልጊዜ ፡ ከዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ነበራቸው

**get in touch (with)**
1. ተገናኘ. Did you get in touch with him while you were in New York? ኒውዮርክ ፡ በነበርክበት ፡ ጊዜ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ተገናኝተሃል ?

2. አገኘ. I have to get in touch with him right away. አሁኑኑ ፡ እሱን ፡ ማግኘት ፡ አለብኝ

**keep in touch** ግንኙነት ፡ አደረገ
Don't forget to keep in touch with me while you're abroad. እውጭ ፡ አገር ፡ ሳለህ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ማድረግ ፡ አትርሳ

**keep (someone) in touch with** እንዲያውቅ ፡ ረዳ
The newspaper keeps you in touch with world events. ጋዜጣ ፡ የዓለምን ፡ ድርጊቶች ፡ እንድታውቅ ፡ ይረዳሃል

**(be) out of touch**
1. ምንም ፡ አያውቅ. He is out of touch with world events. ስለ ፡ ዓለም ፡ ጉዳይ ፡ ምንም ፡ አያውቅ
2. ግንኙነት ፡ አቋረጠ. He is out of touch with the rest of us. ከተቀረነው ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ አቋርጧል

**touch and go** ነፍስ ፡ ውጪ ፡ ነፍስ ፡ ግቢ
It was touch and go with him for a while, but he finally recovered. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ነፍስ ፡ ውጪ ፡ ነፍስ ፡ ግቢ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ተሽሎታል

**touched** (adj.) ወፈፌ
He seems a bit touched. ትንሽ ፡ ወፈፌ ፡ ይመስላል

**touching** (adj.) ልብ ፡ የሚነካ
It was a very touching scene. በጣም ፡ ልብ ፡ የሚነካ ፡ ትዕይንት ፡ ነበር

**touching** (prep.) ስለ
He asked many questions touching my home and school. ስለ ፡ ቤትና ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ጥያቄዎችን ፡ ጠየቀ

**touchstone**
*The touchstone of success in business is profit. ንግድ ፡ መሳካት ፡ አለመሳካቱ ፡ የሚታወቀው ፡ በሚገኘው ፡ ትርፍ ፡ ነው

**touchy** በጣም ፡ የሚያስቆጣ ። በጣም ፡ የሚነካ
The race problem is a touchy subject in America. በአሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ የቀለም ፡ ልዩነት ፡ ጉዳይ ፡ በጣም ፡ የሚያስቆጣ ፡ (የሚነካ) ፡ ነው

**tough**
1. ጠንካራ. His skin is tough. ቆዳው ፡ ጠንካራ ፡ ነው
Our soldiers are tough. ወታደሮቻችን ፡ ጠንካሮች ፡ ናቸው
2. ከባድ. That's a tough assignment. እሱ ፡ ሥራ ፡ ከባድ ፡ ነው
3. አንጀ. The meat is awfully tough. ሥጋው ፡ በጣም ፡ አንጀ ፡ ነው
4. መጥፎ. He lives in a tough neighborhood. መጥፎ ፡ ሰፈር ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል

**get tough** ጠንከር ፡ አለ(በት)
The employers got tough with their workers. አሠሪዎች ፡ በሠራተኞቻቸው ፡ ላይ ፡ ጠንከር ፡ አሉባቸው

**toughen, ~ oneself** ሰውነቱን ፡ አጠነከረ
He toughened himself by exercising. ልምምድ ፡ በማድረግ ፡ ሰውነቱን ፡ አጠነከረ

**toughen** (vi.) ጠንካራ ፡ ሆነ
The green troops toughened in combat. አዲሶቹ ፡ ወታደሮች ፡ ከውጊያ ፡ ልምምድ ፡ የተነሣ ፡ ጠንካራ ፡ ሆኑ

**tough-minded** ጥብቅ ፡ ሰው
He may be soft-spoken, but he is tough-minded. ሲናገር ፡ ልስልስ ፡ ይመስላል ፡ ግን ፡ ጥብቅ ፡ ሰው ፡ ነው

**tour** (v.)
1. ጐበኘ. The children toured the ship. ልጆቹ ፡ መርከቡን ፡ ጐበኙ
2. ዞረ. We toured Europe by bus. አውሮፓን ፡ በአውቶቡስ ፡ ዞርን

**tour** (n.) ጉብኝት
A tour of the museum was organized for the students. የቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ጉብኝት ፡ የተዘጋጀው ፡ ለተማሪዎች ፡ ነበር

**make a tour**
1. እየዞረ ፡ ጐበኘ. He made a tour through Europe and Asia. አውሮፓንና ፡ እስያን ፡ እየዞረ ፡ ጐበኘ
2. ጐበኘ. Our class made a tour of the historic battlefield. ክፍላችን ፡ ታሪካዊውን ፡ የጦርነት ፡ ሜዳ ፡ ጐበኘ

**tourist** ጐብኚ ። ጐብኚ
Many tourists come here during the summer. በበጋ ፡ ብዙ ፡ ጐብኚዎች ፡ እዚህ ፡ ይመጣሉ

**tourist office** የቱሪስት ፡ ድርጅት
The tourist office is promoting tours to Lalibela. የቱሪስት ፡ ድርጅት ፡ በላሊበላ ፡ ያገር ፡ ጉብኝትን ፡ በማዳበር ፡ ላይ ፡ ነው

**tournament** ውድድር
They are going to hold a sports tournament. የእስፖርት ፡ ውድድር ፡ ሊያደርጉ ፡ ነው

**tow** ጐትቶ ፡ አመጣ
They towed the damaged ship into the port. የተበላሸችውን ፡ መርከብ ፡ ወደ ፡ ወደቡ ፡ ጐትተው ፡ አመጧት

**tow away** ጐትቶ ፡ ወሰደ
The police towed away the wrecked cars. የተጐዱትን ፡ መኪናዎች ፡ ፖሊሶች ፡ ጐትተው ፡ ወሰዷቸው

**toward, towards**
1. ወደ. We sailed toward China. በመርከብ ፡ ወደ ፡ ቻይና ፡ አመራን
2. ወደ --- ገደማ. Toward noon, the fog lifted. ጭጋጉ ፡ ወደ ፡ እኩለ ፡ ቀን ፡ ገደማ ፡ ገፈፈ
I'll be there towards evening. ወደ ፡ ማታ ፡ ገደማ ፡ እዚያ ፡ እገኛለሁ
3. በ --- ገደማ. The fire broke out toward midnight. እሳቱ ፡ በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ ገደማ ፡ ተነሣ
4. ስለ. What is your attitude toward war? ስለ ፡ ጦርነት ፡ ምን ፡ አስተያየት ፡ አለህ ?
5. ለ. He was very nice toward me. ለኔ ፡ በጣም ፡ ደግ ፡ ነበር
Will you give something toward our new hospital? ላዲሱ ፡ ሆስፒታላችን ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ልትሰጥ ፡ ትፈቅዳለህ ?
We must save money towards the children's education. ለልጆቹ ፡ መማሪያ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ ማጠራቀም ፡ አለብን

**towel** ፎጣ
He dried himself with a towel. ሰውነቱን ፡ በፎጣ ፡ አደረቀ
There are no more paper towels. የወረቀት ፡ ፎጣ ፡ አልቋል

**tower** (v.)
1. ልቆ ፡ ታየ. Menelik towered above his contemporaries. ምኒልክ ፡ በዘመናቸው ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ልቀው ፡ ይታዩ ፡ ነበር
2. ረዘም ፡ ብሎ ፡ ታየ. The skyscrapers tower above the other buildings. ሰማይ ፡ ጠቀሶቹ ፡ ከሌሎች ፡ ሕንጻዎች ፡ ረዘም ፡ ብለው ፡ ይታያሉ

**tower** (n.) ግንብ
The castles at Gondar have round towers at the corners. የጐንደር ፡ ግንቦች ፡ በየማእዘኖቻቸው ፡ ላይ ፡ ክብ ፡ ግንቦች ፡ አሉዋቸው

**town**
1. ከተማ. What's the name of this town? ይህ ፡ ከተማ ፡ ምን ፡ ይባላል ?
2. የከተማ ፡ ሕዝብ. The whole town is having a holiday. የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ በዓል ፡ በማክበር ፡ ላይ ፡ ነው

**be out of town** ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሄደ
My boss is out of town. አለቃዬ ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ነው ፡ (ወደ ፡ ውጭ ፡ ሄደ)
*I come from out of town. ለከተማው ፡ እንግዳ ፡ ነኝ

**skip town** ከከተማ ፡ ወጣ
He skipped town without paying his debts. ዕዳውን ፡ ሳይከፍል ፡ ከከተማ ፡ ወጣ
[See also 'jump, talk']

**town hall** የከተማ ፡ አዳራሽ
The meeting was held in town hall. ስብሰባው ፡ የተደረገው ፡ በከተማው ፡ አዳራሽ ፡ ነው

**town meeting** የከተማ ፡ ስብሰባ
The town meeting was held on Sunday. የከተማው ፡ ስብሰባ ፡ እሑድ ፡ ለት ፡ ተደረገ

**townspeople** የከተማ ፡ ሰው
The fury of the hurricane frightened the townspeople. የዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ኀይል ፡ የከተማውን ፡ ሰው ፡ አስደነገጠ

**toxic**
*This chemical will cause a toxic reaction if you swallow it. ይህንን ፡ ኬሚካል ፡ መጠጣት ፡ ደምን ፡ ይመርዛል

**be toxic** መርዝነት ፡ አለው
Oleander leaves are toxic. የአልያንደር ፡ ቅጠሎች ፡ መርዝነት ፡ አላቸው

**toy** (v.) ተጫወተ
The boy just toys with his food. ልጁ ፡ በምግቡ ፡ ይጫወታል
She toyed with her beads. በዶቃዎቿ ፡ ትጫወት ፡ ነበር

**toy with the idea of** ያዝ ፡ ለቀቅ ፡ አደረገው
He toys with the idea of going abroad. ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የመሄዱን ፡ ጉዳይ ፡ ያዝ ፡ ለቀቅ ፡ ያደርገዋል

**toy** (n.) አሻንጉሊት
Children play with toys. ልጆች ፡ በአሻንጉሊት ፡ ይጫወታሉ

**trace** (v.)
1. ነደፈ. The spy traced a plan of the fort. ሰላዩ ፡ የምሽጉን ፡ አቀማመጥ ፡ ነደፈ
2. ገለበጠ. He put thin paper over the map and traced it. ካርታው ፡ ላይ ፡ ስስ ፡ ወረቀት ፡ አድርጎ ፡ ገለበጠው
3. በዱካ ፡ ተከታትሎ ፡ ደረሰ(በት). The hunter traced the deer. አዳኙ ፡ አጋዘኑ ፡ ያለበትን ፡ ቦታ ፡ በዱካው ፡ ተከታትሎ ፡ ደረሰበት

4. ዐወቀ. They couldn't trace the paternity of the child. የልጁ ፡ አባት ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ አልቻሉም

5. ፈልጎ ፡ አገኘ. I couldn't trace any letter from you dated 11 November. ኅዳር ፡ ፲፩ቀን ፡ ጻፍኩ ፡ የምትለውን ፡ ደብዳቤ ፡ ፈልጌ ፡ ላገኝ ፡ አልቻልኩም

6. ቈጠረ. He traces his family back eleven generations. ዘሩን ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ ይቈጥራል

*We traced the story to him. ወሬውን ፡ እሱ ፡ ማመንጨቱን ፡ ደረስንበት

*We traced the stream to its source. ወንዙን ፡ ተከትለን ፡ በመሄድ ፡ መነሻውን ፡ አገኘነው

**be traced to**

1. በመከታተል ፡ ተደረሰ(በት). The criminal was traced to Harar. ወንጀለኛው ፡ ሐረር ፡ መሄዱ ፡ በመከታተል ፡ ተደረሰበት

2. መነጨ. His fear of dogs can be traced back to a dreadful experience he had as a young boy. ስለ ፡ ውሻ ፡ ያደረበት ፡ ፍርሃት ፡ የመነጨው ፡ በትንሽነቱ ፡ ከደረሰበት ፡ አሰቃቂ ፡ አደጋ ፡ ነው

3. ታወቀ. His death was traced to an overdose of medicine. የሞተው ፡ መድኃኒት ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ በመውሰዱ ፡ መሆኑ ፡ ታወቀ

**trace** (n.)

1. ምልክት. Traces of poison were found in the wine. ወይኑ ፡ ውስጥ ፡ የመርዝ ፡ ምልክት ፡ ተገኝቶበታል

2. ርዝራዥ. There were traces of an old fortification on the hilltop. በኮረብታው ፡ ጫፍ ፡ ያሮጌ ፡ ምሽግ ፡ ርዝራዥ ፡ ይታይ ፡ ነበር

There are traces of an ancient civilization in Hararge. ሐረርጌ ፡ ውስጥ ፡ የጥንታዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ርዝራዦች ፡ አሉ

3. ዱካ. We saw traces of hares in the snow. በረዶው ፡ ውስጥ ፡ የጥንቸል ፡ ዱካ ፡ አየን

**a trace of**

1. ትንሽ. The cook put a trace of garlic in the stew. ወጥ ፡ ቤቱ ፡ ወጡ ፡ ውስጥ ፡ ትንሽ ፡ ነጭ ፡ ሽንኩርት ፡ ጣል ፡ አደረገበት

2. ላመል. There wasn't a trace of gray in her hair. ጸጉሯ ፡ ውስጥ ፡ ሽበት ፡ ላመልም ፡ አልነበረ

**without a trace**

*He disappeared without a trace. የሄደበት ፡ አልታወቀም

**track** (v.) አነፍንፎ ፡ አገኘ

The hounds tracked the fox. ውሾቹ ፡ ቀበሮው ፡ ያለበትን ፡ ቦታ ፡ አነፍንፈው ፡ አገኙት

*We tracked the fox to its den. የቀበሮውን ፡ ዱካ ፡ ተከትለን ፡ ጉድጓዱን ፡ ደረስንበት

**track down** ተከታትሎ ፡ ደረሰበት

The police tracked him down in California. በካሊፎርንያ ፡ መኖሩን ፡ ፖሊሶች ፡ ተከታትለው ፡ ደረሱበት

**track** (n.)

1. የእግር ፡ መንገድ. A track runs through the woods to the farm. አንድ ፡ የእግር ፡ መንገድ ፡ በጫካው ፡ ውስጥ ፡ አቋርጦ ፡ ወደ ፡ እርሻ ፡ ይወስዳል

2. መንገድ. A wagon track leads across the fields. የጋሪ ፡ መንገድ ፡ በሜዳው ፡ አቋርጦ ፡ ያልፋል

3. ኮቴ ፤ ዱካ. We followed the track of the deer. ያጋዘኑን ፡ ኮቴ ፡ (ዱካ) ፡ ተከተልን

4. መሥመር. The railroad from Addis Ababa to Djibouti has only one track. ካዲስ ፡ አበባ ፡ እስከ ፡ ጅቡቲ ፡ ያለው ፡ የባቡር ፡ ሐዲድ ፡ አንድ ፡ መሥመር ፡ ብቻ ፡ ነው

*The road showed many automobile tracks. መንገዱ ፡ ላይ ፡ መኪና ፡ የሄደበት ፡ ይታይ ፡ ነበር

*You're on the right track. ደኅና ፡ ይዘሃል

**get off the tracks** ከመሥመሩ ፡ ወጣ

She can't tell a story without getting off the track. ከመሥመሩ ፡ ሳትወጣ ፡ ታሪክ ፡ መናገር ፡ አትችልም

**keep track of**

1. ተከታተለ. They kept track of the enemy's movements by marking their positions on a map. በካርታው ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ በማድረግ ፡ የጠላትን ፡ መዘዋወር ፡ ተከታተሉ

Read the newspapers to keep track of current events! በየጊዜው ፡ ያለውን ፡ የዓለም ፡ ሁኔታ ፡ ለመከታተል ፡ ጋዜጣ ፡ አንብብ

2. በማስታወሻ ፡ አሰፈረ. Keep track of the hours you have worked! የሠራህበትን ፡ ጊዜ ፡ በማስታወሻ ፡ አስፍር

3. ተቈጣጠረ. A careful teacher keeps track of absentees. ጠንቃቃ ፡ መምህር ፡ የሚቀሩትን ፡ ተማሪዎች ፡ ይቈጣጠራል

**lose all track**

*I lost all track of time. ሰዓቱ ፡ ስንት ፡ እንደ ሆነም ፡ ጠፍቶኛል ፡ (or, የጊዜው ፡ ማለፍ ፡ በፍጹም ፡ አልተሰማኝም)

**(be) on the track of** ወደ ፡ ማግኘቱ ፡ ነው

They are on the track of a solution to the problem. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ መፍትሔ ፡ ወደ ፡ ማግኘቱ ፡ ናቸው

**(a) one-track**

She has a one-track mind. አስተሳሰቧ ፡ ባንድ ፡ አቅጣጫ ፡ ብቻ ፡ ነው

**race track** የእሽቅድምድም ፡ ሜዳ
Let's go to the race track! ወደ ፡ እሽቅድምድሙ ፡ ሜዳ ፡ እንሂድ

**throw off the track** በማሳሳት ፡ ጠፋ(በት)
The thief succeeded in throwing the police off the track. ሌባው ፡ ፖሊሶቹን ፡ በማሳሳት ፡ ጠፋ ባቸው
[See also 'railway']

**tract** ትንሽ ፡ ጽሑፍ
The missionaries hand out religious tracts to passers-by. ሚስዮናውያን ፡ ለአላፊ ፡ አግዳሚው ፡ ትንሽ ፡ ሃይማኖት ፡ ነክ ፡ ጽሑፎች ፡ ያድላሉ

**tract of land** መሬት
The government sold a large tract of land to him. መንግሥት ፡ ሰፊ ፡ መሬት ፡ ሸጠለት
A tract of desert land has little value. የበረሃ ፡ መሬት ፡ እምብዛም ፡ ዋጋ ፡ የለውም
[See also 'alimentary tract']

**traction** መወጠሪያ
The doctor put the broken leg in traction. የተሰበረውን ፡ እግሩን ፡ ሐኪሙ ፡ በመወጠሪያ ፡ አሰረለት
*The wheels lack traction in this fine sand. ጎማዎቹ ፡ በዚህ ፡ ደቃቅ ፡ አሸዋ ፡ ላይ ፡ መቈንጠጥ ፡ አይችሉም

**tractor** የእርሻ ፡ መኪና
Even though he is young, he manipulates the tractor well. ገና ፡ ወጣት ፡ ቢሆንም ፡ የእርሻ ፡ መኪናውን ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ ያንቀሳቅሰዋል

**trade** (v.)
1. ንግድ ፡ ከፈተ. Some companies trade all over the world. አንዳንድ ፡ ኩባንያዎች ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ንግድ ፡ ከፍተዋል
2. ለወጠ. I have traded my typewriter for a bicycle. የጽሕፈት ፡ መኪናዬን ፡ በቢስክሌት ፡ ለወጥኩት
3. ተለዋወጠ. Let's trade seats! ወንበር ፡ እንለዋወጥ

**trade (in)**
1. ነገደ. He trades in coffee and spices. ቡናና ፡ ቅመማ ፡ ቅመም ፡ ይነግዳል
2. ገንዘብ ፡ ጨምሮ ፡ ለወጠ. I want to trade this car in for a new one. ይህን ፡ መኪና ፡ ገንዘብ ፡ ጨምሬ ፡ ባዲስ ፡ ለመለወጥ ፡ እፈልጋለሁ

**trade** (n.)
1. ንግድ. Our trade with the Far East has fallen off. ከሩቅ ፡ ምሥራቅ ፡ ጋር ፡ ያለን ፡ ንግድ ፡ ተቀንሷል
2. የእጅ ፡ ሥራ. The boy has to learn a trade. ልጁ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ መማር ፡ አለበት
*He is a weaver by trade. ሸማኔ ፡ ነው

**make a trade** ለወጠ
The boys made an even trade of marbles for a penknife. ልጆቹ ፡ ያለምንም ፡ ጉዳት ፡ ብይ ፡ በሰንጢ ፡ ለወጡ

**trademark** የንግድ ፡ ምልክት
The trademark is registered. የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ የተመዘገበ ፡ ነው

**trader** ነጋዴ
Traders in cotton are being heavily taxed. የጥጥ ፡ ነጋዴዎች ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቀረጥ ፡ ይከፍላሉ

**tradition**
1. ባህል. In America, it is a tradition to eat turkey at Christmas. በአሜሪካ ፡ ለገና ፡ የቱርክ ፡ ዶሮ ፡ መብላት ፡ ባህል ፡ ነው
2. ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፡ ልማድ. Tradition requires young people to respect their elders. ታላላቆችን ፡ ማክበር ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፡ ልማድ ፡ ነው

**traditional**
1. የባህል. Countryfolk still know traditional dances. ያገር ፡ ቤት ፡ ሰዎች ፡ አሁንም ፡ የባህል ፡ ጨዋታን ፡ ያውቃሉ
2. (=adv.) በድሮ ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ. Traditional ways of doing things are slowly dying out. አንዳንድ ፡ ነገሮችን ፡ በድሮ ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ ፡ መሥራት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየቀረ ፡ ነው

**traffic** (trafficked), v. የንግድ ፡ ልውውጥ ፡ አደረገ
The men trafficked with the natives for ivory. ሰዎቹ ፡ የዝሆን ፡ ጥርስ ፡ ፍለጋ ፡ ከነዋሪዎቹ ፡ ጋር ፡ የንግድ ፡ ልውውጥ ፡ አደረጉ

**traffic (in)** ነገደ
The people in this village traffic in cotton. በዚህ ፡ መንደር ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ጥጥ ፡ ይነግዳሉ

**traffic** (n.)
1. ንግድ. The government regulates traffic in liquors. መንግሥት ፡ የአልኮል ፡ መጠጦችን ፡ ንግድ ፡ ይቈጣጠራል
2. የመኪናዎች ፡ እንቅስቃሴ ፤ የመኪና ፡ መዘዋወር. Police control the traffic in large cities. በታላላቅ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ የመኪናዎችን ፡ እንቅስቃሴ ፡ የሚቈጣጠሩ ፡ ፖሊሶች ፡ ናቸው
The accident hung up traffic for several hours. አደጋው ፡ የመኪናዎችን ፡ መዘዋወር ፡ ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ አውኮ ፡ ነበር

**heavy traffic** ትራፊክ ፡ የሚበዛበት ፡ መንገድ
He is blind in one eye, and cannot drive in heavy traffic. አንድ ፡ ዓይና ፡ ስለሆነ ፡ ትራፊክ ፡ በሚበዛበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ሊነዳ ፡ አይችልም

**traffic jam** የመኪና ፡ መጨናነቅ
The traffic jams in Addis Ababa are getting worse. በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ የመኪና ፡ መጨናነቅ ፡ እየባሰ ፡ ሄዷል

**traffic light** የትራፊክ ፡ መብራት
The traffic light isn't working. የትራፊኩ ፡ መብራት ፡ አይሠራም

**traffic police** የትራፊክ ፡ ፖሊስ ፤ ትራፊክ
Traffic police are arresting speeders. የትራፊክ ፡ ፖሊሶች ፡ (ትራፊኮች) ፡ በከፍተኛ ፡ ፍጥነት ፡ የሚነዱትን ፡ ሰዎች ፡ ይይዛሉ

**tragedy** (tragedies)
1. አሳዛኝ ፡ መከራ. The father's death was a tragedy to his family. ያባትዬው ፡ መሞት ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ አሳዛኝ ፡ መከራ ፡ ሆነ
2. አሳዛኝ ፡ የሆነ ፡ ቲያትር. The tragedy of King Theodore was written by an Ethiopian. አሳዛኝ ፡ የሆነው ፡ የአፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ቲያትር ፡ የተጻፈው ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ነው

**tragic** አሳዛኝ
A tragic accident happened at the corner. መታጠፊያው ፡ ላይ ፡ አሳዛኝ ፡ አደጋ ፡ ደረሰ

**trail** (vt.)
1. ተከታተለ. Somebody trailed me all the way home. አንድ ፡ ሰው ፡ እቤቴ ፡ ድረስ ፡ ተከታተለኝ The dogs trailed the rabbit. ውሾቹ ፡ ጥንቸሏን ፡ ተከታተሏት
2. ከ - - አልተለየም. The dog trailed its master constantly. ውሻው ፡ ምንጊዜም ፡ ከጌታው ፡ አልተለየም
3. በእግሩ ፡ ይዞ ፡ ገባ. He trailed dirt into the house. ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ በእግሩ ፡ ቆሻሻ ፡ ይዞ ፡ ገባ
4. ጐተተ. The bird trailed its broken wing. ወፉ ፡ ሰባራ ፡ ክንፉን ፡ ጐተተ

**trail along after** ተከትሎ ፡ መጣ
The children trailed along after us. ልጆቹ ፡ እኛን ፡ ተከትለው ፡ መጡ

**trail behind** ከ - - - ኋላ ፡ ኋላ ፡ ሄደ
The little child was trailing behind her parents. ትንሿ ፡ ልጅ ፡ ከወላጆቿ ፡ ኋላ ፡ ኋላ ፡ ትሄድ ፡ ነበር

**trail off** ቀስ ፡ እያለ ፡ ሄደ
The children trailed off to school. ልጆቹ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀስ ፡ እያሉ ፡ ሄዱ

**trail (on)** ጠረገ
Her long skirt trails on the ground. ረጅሙ ፡ ልብሷ ፡ መሬት ፡ ይጠርጋል

**trail (over)** አለበሰ
The roses were trailing over the wall. ጽጌረዳዎቹ ፡ ግንቡን ፡ አልብሰውት ፡ ነበር

**trail** (n.)
1. ፈለግ. He followed the animal's trail. የእንስሳውን ፡ ፈለግ ፡ ተከታተለ
2. የእግር ፡ መንገድ. The trail leads through the woods. የእግር ፡ መንገዱ ፡ በጫካው ፡ ያሳልፋል
3. ፋና. I am on the culprit's trail. የወንጀለኛውን ፡ ፋና ፡ ደርሼበታለሁ

**be on (one's) trail** ተከታተለ
The police are on his trail. ፖሊሶቹ ፡ ተከታትለውታል

**leave a trail of**
*The wounded tiger left a trail of blood. የቈሰለው ፡ ነብር ፡ ደሙን ፡ እያንጠባጠበ ፡ ሄደ
*The burning plane left a trail of smoke. የተቃጠለው ፡ አውሮፕላን ፡ ጢስ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ይታያል
[See also 'blaze']

**trailer** ተሳቢ
The car has a trailer attached to it. መኪናው ፡ ተሳቢ ፡ አለው

**train** (vt.)
1. አሠለጠነ. He trains circus animals. የሰርከስ ፡ እንስሳዎች ፡ ያሠለጥናል
2. አስተማረ. We must train our children to be good citizens. ልጆቻችን ፡ ጥሩ ፡ ዜጎች ፡ እንዲሆኑ ፡ ማስተማር ፡ አለብን
3. ደቀነ. The officer trained his guns on the fort. መኰንኑ ፡ መድፉን ፡ ወደ ፡ ምሽጉ ፡ ደቀነ
4. መራ. The gardener trains the vines to climb up the wall. አትክልተኛው ፡ ሐረጎቹ ፡ በግድግዳው ፡ ላይ ፡ እንዲያድጉ ፡ ይመራቸዋል

**train** (vi.) ልምምድ ፡ አደረገ
The runners trained for the races. ሯጮቹ ፡ ለሩጫው ፡ ውድድር ፡ ልምምድ ፡ አደረጉ

**train** (n.)
1. ባቡር. When does the train leave? ባቡሩ ፡ መቼ ፡ ይነሣል ?
2. መንጋ. A train of camels crossed the desert. የግመል ፡ መንጋ ፡ በረሃውን ፡ አቋረጠ

**train of thought** ሐሳብ
A knock on the door interrupted my train of thought. በሩ ፡ በድንገት ፡ ሲንኳኳ ፡ ሐሳቤ ፡ ተቋረጠ

**train wreck** የተገለበጠ ፡ ባቡር ፤ የተሰባበረ ፡ ባቡር
He observed the train wreck with detachment. የተገለበጠውን ፡ (የተሰባበረውን) ፡ ባቡር ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ተመለከተ

**trained** (adj.) የሠለጠነ
There is a shortage of trained nurses. የሠለጠኑ ፡ ነርሶች ፡ ያንሱናል

**be trained in** ተማረ
Conscripts are trained in marching before they are sent to the various units. ምልምሎች ፡ ወደየተመደቡበት ፡ ከመላካቸው ፡ በፊት ፡ ሰልፍ ፡ ይማራሉ

**trainer** አሠልጣኝ
The lion mauled his trainer. አንበሳው ፡ አሠልጣኙን ፡ አንገላታው
The army is lending us trainers. የጦር ፡ ሰራዊት ፡ አሠልጣኞች ፡ ያውሰናል

**training**
1. ትምህርት. Where did he receive his medical training? የሕክምና ፡ ትምህርቱን ፡ የተማረው ፡ የት ፡ ነው ?
It requires thorough training to be able to operate that machine. ያንን ፡ መኪና ፡ ለማንቀሳቀስ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ትምህርት ፡ ያስፈልጋል
2. ማሠልጠን. Good training of soldiers offsets numbers. ወታደሮችን ፡ በሚገባ ፡ ማሠልጠን ፡ የቁጥርን ፡ ማነስ ፡ ያሟላል

**trait** ባሕርይ
Kindness and generosity are fine traits. ደግነትና ፡ ለጋስነት ፡ መልካም ፡ ባሕሪዎች ፡ ናቸው
[See also 'ancestral']

**traitor** ከዳተኛ ፤ ከሐዲ
The traitor is punished by law. ከዳተኛ ፡ (ከሐዲ) በሕግ ፡ ይቀጣል

**tramp** (v.)
1. በእግሩ ፡ ሄደ. The hikers tramped all day. መንገደኞቹ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ በእግራቸው ፡ ሄዱ
2. በእግሩ ፡ ወጣ. The troops tramped through the mountains. ወታደሮቹ ፡ ተራራውን ፡ በእግራቸው ፡ ወጡ
3. በኀይል ፡ ተራመደ. He tramped across the room in his heavy boots. ከባድ ፡ ጫማዎቹን ፡ አድርጎ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ በኀይል ፡ ተራመደ
4. ቆመ(በት). The horse tramped on my foot. ፈረሱ ፡ እግሬ ፡ ላይ ፡ ቆመብኝ
5. ደፋ ፡ ቀና ፡ አለ. He tramped home, tired after a day's hike. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሲንሸራሸር ፡ ከዋለ ፡ በኋላ ፡ ደክሞት ፡ ደፋ ፡ ቀና ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ መጣ

**tramp on** ረጋገጠ
He tramped on the flowers. አበቦቹን ፡ ረጋገጠ

**tramp up and down** ተንጐራደደ
He tramped up and down the bus stop waiting for the bus. አውቶቡስ ፡ ጥበቃ ፡ አውቶቡስ ፡ ማቆሚያ ፡ አጠገብ ፡ ተንጐራደደ

**tramp** (n.)
1. በረንዳ ፡ አዳሪ ፤ ዱርዬ. The tramp was arraigned on a charge of stealing. በረንዳ ፡ አዳሪው ፡ (ዱርዬው) ፡ በሌብነት ፡ ተከሶ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀረበ
2. እርምጃ. I heard the tramp of soldiers. የወታደሮች ፡ እርምጃ ፡ ሰማሁ

**trample, ~ on** ረገጠ ፤ ረጋገጠ
The cows trampled on the clothes spread out for drying. ላሞቹ ፡ የተሰጣውን ፡ ልብስ ፡ ረገጡት ፡ (ረጋገጡት)

**trample down** ረጋገጠ
The sheep have trampled down the grain. በጎቹ ፡ እህሉን ፡ ረጋግጠውታል

**trance, be in a ~** ፍዝዝ ፡ አለ
He was in a trance when I came in. እኔ ፡ ስመጣ ፡ ፍዝዝ ፡ ብሎ ፡ ነበር

**tranquil** ጸጥ ፡ ያለ
The tranquil waters of the lake are pleasant to swim in. ጸጥ ፡ ያለው ፡ የሐይቅ ፡ ውኃ ፡ ለዋና ፡ ያስደስታል

**tranquil atmosphere** ጸጥታ
The tranquil atmosphere of the country makes me feel better. የባላገሩ ፡ ጸጥታ ፡ ያሽለኛል

**be tranquil** ጸጥ ፡ አለ
The spot is very tranquil now. አሁን ፡ ቦታው ፡ ጸጥ ፡ ብሏል

**tranquilize** የሚያስታግሥ ፡ መድኃኒት ፡ ሰጠ
The doctor tranquilized the frightened child so that he could examine it. የተሸበረውን ፡ ሕፃን ፡ ለመመርመር ፡ ሐኪሙ ፡ የሚያስታግሥ ፡ መድኃኒት ፡ ሰጠ

**tranquilizer** ማስታገሻ ፡ መድኃኒት
She takes tranquilizers because she is so nervous. መንፈሷ ፡ በጣም ፡ ስለሚጨነቅ ፡ ማስታገሻ ፡ መድኃኒት ፡ ትውጣለች

**tranquillity**
1. ጸጥታ. His tranquillity was disturbed by the baby's crying. የሕፃኑ ፡ ልቅሶ ፡ ጸጥታውን ፡ አወከበት
2. ሰላም. The turn of the century was a period of tranquillity. ክፍለ ፡ ዘመኑ ፡ ሲገባ ፡ ጊዜው ፡ የሰላም ፡ ነበር

**transact, ~ the deal** ተዋዋለ
The two farmers transacted the deal. ሁለቱ ፡ ገበሬዎች ፡ ተዋዋሉ

**be transacted** ተፈጸመ ፤ ተደረገ
The deal between the two farmers was transacted in the presence of witnesses. የሁለቱ ፡ ገበሬዎች ፡ ውል ፡ በምስክሮች ፡ ፊት ፡ ተፈጸመ ፡ (ተደረገ)

**transaction**
1. መገበያየት. His transactions are always honest. በሚያደርገው ፡ መገበያየት ፡ ሁልጊዜ ፡ ሐቀኛ ፡ ነው
2. ገበያ. No one questions the equity of this transaction. የዚህን ፡ ገበያ ፡ ትክክለኛነት ፡ የሚጠራጠር ፡ የለም
3. የንግድ ፡ ውል. The transaction was registered with the government. የንግዱ ፡ ውል ፡ መንግሥት ፡ ዘንድ ፡ ተመዝግቧል

**transcend**
1. ተወ. We must transcend our narrow personal interests and work for the good of our country. የየራሳችንን ፡ የግል ፡ ጥቅም ፡ ትተን ፡ ለሀገራችን ፡ ጥቅም ፡ መሥራት ፡ አለብን
2. አስናቀ. Her beauty transcends that of others. ውበቷ ፡ ሌሎችን ፡ ሁሉ ፡ ያስንቃል

**transcribe**
1. ገለበጠ. The medieval monks transcribed many ancient manuscripts. የመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ መነኰሳት ፡ ብዙ ፡ የጥንት ፡ ጽሑፎችን ፡ ገለበጡ
2. በልዩ ፡ ፊደል ፡ ጻፈ. They transcribed the Amharic letters. የአማርኛውን ፡ ቃላት ፡ በልዩ ፡ ፊደሎች ፡ ጻፏቸው

**transcription** የጻፈ
His transcription from Amharic into English is incorrect. አማርኛን ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ፊደላት ፡ የጻፈው ፡ ስሕተት ፡ ነው

**transfer** (transferred), vt.
1. አስተላለፈ. He transferred the farm to his son. እርሻውን ፡ ለልጁ ፡ አስተላለፈ
2. አዛወረ. He had the money transferred to her name. ገንዘቡን ፡ በሷ ፡ ስም ፡ አዛውሯል

**transfer** (vi.) ተዛወረ
Jim has transferred to another school. ጂም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተዛውሯል
Do I need to transfer to another bus? ወደ ፡ ሌላ ፡ አውቶቡስ ፡ መዛወር ፡ አለብኝ ?

**transfer** (n.) ዝውውር
I'm putting in for a transfer. ለዝውውር ፡ ማመልከቻ ፡ አቅርቤያለሁ
*I have asked for a transfer to the main office. ወደ ፡ ዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንዲያዛውሩኝ ፡ ጠይቄያለሁ

**transfigure** መልኩን ፡ ፍጹም ፡ ለወጠ
A new dress and hairdo transfigured her. አዲስ ፡ ልብስና ፡ አዲስ ፡ የጸጉር ፡ አሠራር ፡ መልኳን ፡ ፍጹም ፡ ለውጦታል

**be transfigured** ተለወጠ
Her face was transfigured with joy when she heard that her son was back from the war. ልጇ ፡ ከጦርነት ፡ መመለሱን ፡ ስትሰማ ፡ ፊቷ ፡ በደስታ ፡ ተለወጠ

**transfix**
1. ወጋ. The bandit transfixed him with his spear. ሽፍታው ፡ በጦር ፡ ወጋው
2. በድን ፡ አደረገ. Fear transfixed him. ፍርሃት ፡ በድን ፡ አደረገው

**transform**
1. ለወጠ. Wealth transformed his character. ሀብት ፡ ጠባዩን ፡ ለወጠው
2. (= pass.) ጠባዩ ፡ ተሻሻለ. Loving care transformed the child. በመልካም ፡ አኳኋን ፡ ስለተያዘ ፡ የልጁ ፡ ጠባይ ፡ ተሻሻለ

**transformation** መለወጥ
The transformation of Addis Ababa from a small village to a modern capital is the admiration of all. የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከትንሽ ፡ መንደር ፡ ወደ ፡ ዘመናዊ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ መለወጥ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ አድናቆትን ፡ አትርፏል

**transformer** ኮረንቲ ፡ መለዋወጫ
The transformer regulates the amount of electric current. ኮረንቲ ፡ መለዋወጫው ፡ የኮረንቲን ፡ ኃይል ፡ ይቈጣጠራል

**transfuse**
1. ቀድቶ ፡ አስተላለፈ. The doctor will transfuse the mother's blood into her sick child. ሐኪሙ ፡ የእናትዮዋን ፡ ደም ፡ ቀድቶ ፡ ለታመመው ፡ ልጇ ፡ ያስተላልፋል
2. ጨመረ(ለት). The victory transfused new courage into our team. የተገኘው ፡ ድል ፡ ለቡድናችን ፡ አዲስ ፡ ጉልበት ፡ ጨመረለት

**transfusion**
*The wounded soldier was given three transfusions in one week. የቈሰለው ፡ ወታደር ፡ ባ

ጎድ ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ደም ፡ ተሰጠው

**transgress**
1. ጣሰ. He transgressed an important rule. አንድ ፡ ከፍተኛ ፡ ሕግ ፡ ጣሰ
2. ከ - - - ውጭ ፡ ነው. His remark transgressed the limits of decency. የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ከመልካም ፡ ምግባር ፡ ውጭ ፡ ነበር
**transgress on** ደፈረ
He transgressed again on my rights. መብቴን ፡ እንደገና ፡ ደፈረ

**transgression** መጣስ
Transgressions of this law will be punished by fines. ይህን ፡ ሕግ ፡ መጣስ ፡ በገንዘብ ፡ ያስቀጣል

**transgressor** የሚጥስ
The transgressors of God's law will be damned. የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ የሚጥስ ፡ ይኰነናል

**transient**
1. ጊዜያዊ. These workers are transients. እነዚህ ፡ ጊዜያዊ ፡ ሠራተኞች ፡ ናቸው
2. ኅላፊ. Happiness is transient. ደስታ ፡ ኅላፊ ፡ ነው

**transit**
1. መሸጋገር. We are in transit toward a new society. ወደ ፡ አዲስ ፡ የኅብረ ፡ ሰብ ፡ ኑሮ ፡ በመሸጋገር ፡ ላይ ፡ ነን
2. መንገድ. The tomatoes were spoiled in transit. ቲማቲሙ ፡ የተበላሸው ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ነው
*Our transit through the various countries was uneventful. በልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ስናልፍ ፡ ምንም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ አላጋጠመንም

**transition** መሸጋገር
The transition from an agricultural society to a modern one is difficult. ከግብርና ፡ ኑሮ ፡ ወደ ፡ ዘመናዊ ፡ የከተማ ፡ ኑሮ ፡ መሸጋገር ፡ ከባድ ፡ ነው

**transitive** ተሻጋሪ
In the sentence "The teacher bought a house", "bought" is a transitive verb. « አስተማሪው ፡ ቤት ፡ ገዛ » ፡ በሚለው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ « ገዛ » ፡ ተሻጋሪ ፡ ግስ ፡ ነው

**transitory** ኅላፊ
Everything is transitory. ሁሉም ፡ ነገር ፡ ኅላፊ ፡ ነው

**translate**
1. ተረጐመ. How do you translate this? ይህን ፡ እንዴት ፡ ትተረጕመዋለህ ?
2. አቀረበ. He translated the theory of electricity into a language I could understand. የኤሌክትሪክን ፡ ፅንሰ ፡ ሐሳብ ፡ እኔ ፡ በምረዳው ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ ፡ አቀረበልኝ

**translation** ትርጉም
The translation of the Amharic text was recently published. ያማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ትርጉም ፡ በቅርብ ፡ ታትሟል

**translator** አስተርጓሚ
He is a translator for the sugar company. የስኳር ፡ ኩባንያው ፡ አስተርጓሚ ፡ ነው

**translucent** ብርሃን ፡ የሚያስተላልፍ
The window panes are translucent. የመስኮቱ ፡ መስታወቶች ፡ ብርሃን ፡ የሚያስተላልፉ ፡ ናቸው

**transmission**
1. ማሰራጨት. The transmission of ideas is necessary for development. አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ማሰራጨት ፡ ለማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ እድገት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
2. መተላለፍ. Telegraph transmission was interrupted by downed wires. የቴሌግራሙ ፡ መተላለፍ ፡ የተቋረጠው ፡ በስልኩ ፡ ሽቦ ፡ መበጠስ ፡ ምክንያት ፡ ነው
**medium for transmission** መተላለፊያ
Air is a medium for the transmission of sound. አየር ፡ የድምፅ ፡ መተላለፊያ ፡ ነው

**transmit** (transmitted) አስተላለፈ
Mosquitoes transmit malaria. የወባ ፡ ትንኞች ፡ ወባ ፡ ያስተላልፋሉ
He transmitted the information by radio. ወሬውን ፡ በሬዲዮ ፡ አስተላለፈ
**be transmitted** ተጋባ
The disease is transmitted by kissing. በሽታው ፡ የሚጋባው ፡ በመሳሳም ፡ ነው

**transmute** ለወጠ
The decline in exports transmuted the economic life of the country. ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚላከው ፡ እቃ ፡ ማነስ ፡ ያገሪቱን ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሁኔታ ፡ ለወጠው

**transparent** ግልጽ
His motives are transparent. የሚነፋፋው ፡ ሐሳብ ፡ ግልጽ ፡ ነው
*Glass is transparent. በመስታወት ፡ ውስጥ ፡ ማየት ፡ ይቻላል

**transpire** (= intr.) ወጣ
+The water which the plants transpire collects on the glass. ከዕፀዋቱ ፡ የሚወጣው ፡ ውኃ ፡ መስታወቱ ፡ ላይ ፡ ይጠራቀማል
*What transpired between the two is not known. ሁለቱ ፡ ምን ፡ እንዳደረጉ ፡ አይታወቅም

**transplant**
1. አዛውሮ ፡ ተከለ. We start the flowers indoors, and then transplant them to the garden. አበቦቹን ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ አብቅለን ፡ ወደ ፡ አትክልቱ ፡ ስፍራ ፡ አዛውረን ፡ እንተክላቸዋለን
2. አዛወረ(ለት). The doctor transplanted the heart of a young woman into the sick man's body. ሐኪሙ ፡ የልጅ ፡ እግር ፡ ሴት ፡ ልብ ፡ ለበሽተኛው ፡ ሰው ፡ አዛወረለት

**be transplanted** ተዛወረ
After the war, whole populations were transplanted to other countries. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ በሙሉ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ተዛወረ

**transport** (v.)
1. አጓጓዘ. They transported the goods by truck. እቃውን ፡ በጭነት ፡ መኪና ፡ አጓጓዙ
2. መንፈሱን ፡ ማረከ. A good play transports him. ጥሩ ፡ ቲያትር ፡ መንፈሱን ፡ ይማርከዋል

**be transported** ተዋጠ
He was transported with joy by the good news. ጥሩ ፡ ዜና ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በደስታ ፡ ተዋጠ

**transport** (n.)
1. የሚያጓጉዝ ፡ መርከብ. The troop transport is two weeks overdue. ወታደሮቹን ፡ የሚያጓጉዘው ፡ መርከብ ፡ ሁለት ፡ ሳምንት ፡ ዘግይቷል
2. (= transporting) ማጓጓዝ. Our primary concern is the transport of troops. ዋናው ፡ ሐሳባችን ፡ ወታደሮችን ፡ ማጓጓዝ ፡ ነው

**means of transport** መመላለሻ
My car is being repaired so I am without means of transport. መኪናዬ ፡ በመታደስ ፡ ላይ ፡ ስላለች ፡ መመላለሻ ፡ አጥቻለሁ

**transportation**
1. ማመላለሻ. There is no public transportation in town. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ የሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ የለም
2. መመላለሻ. The flood paralyzed transportation. ጎርፉ ፡ መመላለሻውን ፡ ዘጋው
3. መጓጓዣ. All transportation stopped during the storm. በዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ጊዜ ፡ መጓጓዣ ፡ በሙሉ ፡ ቆመ

**transpose** አለዋውጦ ፡ ጻፈ
He transposed the letters by mistake. ፊደሎቹን ፡ በስሕተት ፡ አለዋውጦ ፡ ጻፈ

**transverse** አግዳሚ
Transverse beams support the weight of the roof. አግዳሚ ፡ አውታሮች ፡ ጣሪያውን ፡ ይሸከማሉ

**trap** (trapped), v.
1. አጠመደ. He traps animals and sells their skins. የዱር ፡ አራዊትን ፡ እያጠመደ ፡ ቆዳቸውን ፡ ይሸጣል
2. አድፍጦ ፡ ያዘ. They trapped the enemy. ጠላትን ፡ አድፍጠው ፡ ያዙት
3. አስገደደ. My arguments trapped him into admitting his error. መረጃዬ ፡ ስሕተቱን ፡ እንዲያምን ፡ አስገደደው

**trap** (n.)
1. ወጥመድ. The police set a trap for the thief. ፖሊሶቹ ፡ በሌባው ፡ ላይ ፡ ወጥመድ ፡ አጠመዱበት
He set a trap for the mouse. ያይጡን ፡ ወጥመድ ፡ አጠመደ
2. የታቀደ ፡ ዘዴ. His question was a trap to make her tell the truth. ጥያቄው ፡ እውነቱን ፡ እንድታወጣ ፡ ለማድረግ ፡ የታቀደ ፡ ዘዴ ፡ ነበር

**trapdoor** መሹለኪያ ፡ በር
He escaped through a trapdoor in the floor. ወለሉ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ መሹለኪያ ፡ በር ፡ አመለጠ

**trapeze** ጅውጅው
The acrobats swung on a trapeze. የአክሮባት ፡ ተጫዋቾች ፡ በጅውጅው ፡ ላይ ፡ ተወዛወዙ

**trappings** ከነሙሉ ፡ ጌጥ
The king's horse with all its trappings was buried near his tomb. የንጉሡ ፡ ፈረስ ፡ ከነሙሉ ፡ ጌጡ ፡ መቃብሩ ፡ አጠገብ ፡ ተቀበረ

**trash**
1. ቆሻሻ. Burn the trash! ቆሻሻውን ፡ አቃጥለው!
2. የማይረባ ፡ እቃ. I wouldn't waste my money on such trash. እንዲህ ፡ ባለ ፡ በማይረባ ፡ እቃ ፡ ላይ ፡ ገንዘቤን ፡ አላባክንም

**trash man** ቆሻሻ ፡ የሚያነሣ ፡ ሰው
Bundle the newspapers for the trash man! ቆሻሻ ፡ ለሚያነሣው ፡ ሰውዬ ፡ ጋዜጣውን ፡ እሰርለት

**travel** (v.)
1. ተጓዘ. A train travels on tracks. ባቡር ፡ የሚጓዘው ፡ በሐዲድ ፡ ላይ ፡ ነው

Light and sound travel in waves. ብርሃንና ፡ ድምፅ ፡ የሚጓዙት ፡ በሞገድ ፡ ነው
2. ተከተለ. His eyes traveled after her wherever she went. በሄደችበት ፡ ሁሉ ፡ ዓይኑ ፡ ይከተላታል

**travel about** ተዘዋወረ
Migratory workers travel about from one job to another. ተዘዋዋሪ ፡ ሠራተኞች ፡ ካንድ ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ይዘዋወራሉ

**travel around** እየተዘዋወረ ፡ ጐበኘ
We traveled around England. የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ እየተዘዋወርን ፡ ጐበኘን

**travel faster** ፈጠነ
Light travels faster than sound. ብርሃን ፡ ከድምፅ ፡ ይፈጥናል

**travel (for)** ወከለ
The salesman travels for a paint firm. አሻሻጩ ፡ የቀለም ፡ ኩባንያን ፡ ይወክላል

**travel up and down** ተመላለሰ
A steamboat travels up and down the river. በእንፋሎት ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ጀልባ ፡ በወንዙ ፡ ላይ ፡ ይመላለሳል

**travel** (n.)
1. ጉዞ. Travel in winter is difficult. የክረምት ፡ ጉዞ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. መጓጓዣ. Riding on a donkey is a mode of travel. አህያ ፡ መቀመጥ ፡ የመጓጓዣ ፡ ዘዴ ፡ ነው
3. መንገድ. A driver spends most of his time in travel. ሾፌር ፡ ብዙውን ፡ ጊዜውን ፡ የሚያሳልፈው ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ነው

**traveled** (adj.)
*This is a heavily traveled road. ይህ ፡ መንገድ ፡ ተጓዥ ፡ የሚበዛበት ፡ ነው

**traveler** መንገደኛ ፤ የሚጓዝ ፡ ሰው
Travelers must show their visas at the border. መንገደኞቹ ፡ በወሰኑ ፡ ላይ ፡ የይለፍ ፡ ወረቀታቸውን ፡ ማሳየት ፡ አለባቸው
The traveler to Africa is a great adventurer. ወደ ፡ አፍሪካ ፡ የሚጓዘው ፡ ሰው ፡ ታላቅ ፡ የጀብዱ ፡ ሰው ፡ ነው
[See also 'seasoned']

**traveling** (adj.) መንገደኛ
A hostel is set up for the traveling students to stay in. ለመንገደኞች ፡ ተማሪዎች ፡ መቆያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ማረፊያ ፡ ተቋቋመ

**traverse**
1. አቋርጦ ፡ አለፈ. The road traverses the desert. መንገዱ ፡ በረኻውን ፡ አቋርጦ ፡ ያልፋል
The beams of the searchlight traverse the sky. የባውዛው ፡ ብርሃን ፡ ሰማይን ፡ አቋርጦ ፡ ያልፋል
2. አቋረጠ. A bridge traverses the stream. ድልድይ ፡ ወንዙን ፡ ያቋርጣል
3. ተሻገረ ፤ አቋረጠ. They traversed the swamp safely. ረግረጉን ፡ በደኅና ፡ ተሻገሩ ፡ (አቋረጡ)

**trawl** [ጥልቅ ፡ ባልሆነ ፡ የባሕር ፡ ክፍል ፡ በጀልባ ፡ የሚሳብ ፡ ትልቅ ፡ የዓሣ ፡ ማጥመጃ ፡ መረብ]

**tray** ዝርግ ፡ ሳሕን
She brought his supper in on a tray. እራቱን ፡ በዝርግ ፡ ሳሕን ፡ አቀረበችለት

**treacherous**
1. የማይታመን. The treacherous servant spied on his master. የማይታመነው ፡ አሽከር ፡ በጌታው ፡ ላይ ፡ ይሰልል ፡ ነበር
2. ከዳተኛ. The treacherous soldier carried reports to the enemy. ከዳተኛው ፡ ወታደር ፡ ለጠላት ፡ ሪፖርት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ
3. አታላይ. The ground here is treacherous, so watch your step. እዚህ ፡ ጋ ፡ መሬቱ ፡ አታላይ ፡ ነውና ፡ እያየህ ፡ ርገጥ

**treachery**
1. ከሐዲነት ፤ ከዳተኛነት ፤ ክሕደት. His treachery was punished by death. ስለ ፡ ከሐዲነቱ ፡ በሞት ፡ ተቀጣ
His sale of secrets is a clear-cut exampie of treachery. ምስጢራዊ ፡ ሰነዶችን ፡ መሸጡ ፡ ለከዳተኛነቱ ፡ በቂ ፡ ምሳሌ ፡ ነው
Under the guise of friendship, he plotted treachery. ወዳጅ ፡ መስሎ ፡ ክሕደትን ፡ አሰበ
2. ስብቀት. The revelation of the thieves' hiding place was due to the treachery of one of their members. የሌቦቹ ፡ መደበቂያ ፡ የታወቀው ፡ አንዱ ፡ ባልደረባቸው ፡ ባደረገው ፡ ስብቀት ፡ ነው

**tread** (trod, trodden), vt.
1. ተጓዘ. We trod the dusty road for hours. በአቧራው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ተጓዝን
2. አወጣ. The cattle have trodden a path to the pond. የቀንድ ፡ ከብቶቹ ፡ ወደ ፡ ኩሬው ፡ የሚወስድ ፡ መንገድ ፡ አውጥተዋል

**tread** (vi.)
1. ተራመደ. She treads lightly so as not to wake the baby. ልጇን ፡ ከእንቅልፉ ፡ እንዳታስነሣ ፡ ቀስ ፡ ብላ ፡ ትራመዳለች
2. ሄደ. Don't tread on the flower beds! አበቦቹ ፡ መደብ ፡ ላይ ፡ አትሂድ
3. ቆመ. Don't tread on my toes! እግሬ ፡ ላይ ፡ አትቁም

**tread (in)** ተከተለ
He's treading in his father's footsteps. ያባቱ ን ፡ አርአያ ፡ ተከተለ

**tread water** ውኃውን ፡ በእግር ፡ መታ
He kept from drowning by treading water. ከመስመጥ ፡ ሊድን ፡ የቻለው ፡ ውኃውን ፡ በእግሮቹ ፡ በመምታት ፡ ነው

**tread** (n.)
1. ኮቴ. We heard a heavy tread on the stairs. በደረጃው ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ኮቴ ፡ ሰማን
2. ጥርስ. The tread is worn off the tires. የጎማው ፡ ጥርስ ፡ ተበልቷል

**treason** ከሐዲነት ፤ ክሕደት ፤ አገርን ፡ መክዳት
Treason is punished by death. ከሐዲነት ፡ በሞት ፡ ያስቀጣል
Your actions are little short of treason. የሥራኸው ፡ ሥራ ፡ ከክሕደት ፡ እምብዛም ፡ አያንስ
In wartime, treason is punishable by death. በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ አገርን ፡ መክዳት ፡ በሞት ፡ የሚያስቀጣ ፡ ነው

**treasonable** ከክሕደት ፡ የሚቈጠር
Giving the enemy food and medicine is treasonable. የጠላት ፡ ምግብና ፡ መድኃኒት ፡ መስጠት ፡ ከክሕደት ፡ የሚቈጠር ፡ ነው

**treasure** (v.)
1. ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ተመለከተ. He treasures the years he lived with her. ከሷ ፡ ጋር ፡ የኖረበትን ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ይመለከተዋል
2. እንደ ፡ ትልቅ ፡ ሀብት ፡ ቈጠረ. I treasure the watch my father gave me. አባቴ ፡ የሰጠኝን ፡ ሰዓት ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ሀብት ፡ እቈጥረዋለሁ

**treasure** (n.) ሀብት
They unearthed a considerable treasure. ትልቅ ፡ ሀብት ፡ ከመሬት ፡ ቈፍረው ፡ አወጡ
The silver teapot was the old lady's chief treasure. ከብር ፡ የተሠራው ፡ የሻይ ፡ ጀበና ፡ የአሮጊቷ ፡ ዋና ፡ ሀብት ፡ ነበር

**treasure of** ብዙ
A treasure of old coins was uncovered in Axum. ብዙ ፡ የጥንት ፡ ገንዘቦች ፡ በአክሱም ፡ ተገኙ

**treasurer** ገንዘብ ፡ ያዥ ፤ ገንዘብ ፡ ቤት
The treasurer is elected by majority vote. ገንዘብ ፡ ያዥ ፡ (ገንዘብ ፡ ቤቱ) ፡ የተመረጠው ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ነው

**treasury**
1. ግምጃ ፡ ቤት. The treasury is empty. ግምጃ ፡ ቤቱ ፡ ባዶ ፡ ነው
2. ተቀማጭ ፡ ገንዘብ. We voted to pay for the picnic out of the club treasury. ለሽርሽሩ ፡ ከክበቡ ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ወሰን
3. ቅርስ. A treasury of art is housed in the museum. የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ቅርስ ፡ በቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣል
4. ጐተራ. The book is a treasury of information. መጽሐፉ ፡ የዕውቀት ፡ ጐተራ ፡ ነው

**treat** (v.)
1. ያዘ. You have to treat him rough. ጠበቅ ፡ አድርገህ ፡ ልትይዘው ፡ ይገባል
2. አስተናገደ. He treats his customer with civility. ደንበኞቹን ፡ በትሕትና ፡ ያስተናግዳል
3. አየ. A good administrator treats the poor and the rich equally. ጥሩ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ድኻንና ፡ ሀብታምን ፡ እኩል ፡ ያያል
He treats me like a child. እንደ ፡ ሕፃን ፡ ያየኛል
4. ቈጠረ. You shouldn't treat that warning so lightly. ማስጠንቀቂያውን ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ መቍጠር ፡ የለብህም
5. ተመለከተ. He always treats his elders with deference. ሁልጊዜም ፡ ታላላቆቹን ፡ በአክብሮት ፡ ይመለከታል
6. ተነተነ. The lecturer treated his subject thoroughly. ተናጋሪው ፡ የመነጋገሪያ ፡ አርእስቱን ፡ በሚገባ ፡ ተነተነ
7. ተነጋገረ. We treated with the enemy for peace. ከጠላት ፡ ጋር ፡ ዕርቅ ፡ የሚደረግበትን ፡ ዘዴ ፡ ተነጋገርን
8. አከመ. Dr. Parker is treating me. ዶክተር ፡ ፓርከር ፡ ያክመኛል

**treat badly** አጕሳቈለ
The woman treated her stepson badly. ሴትዮዋ ፡ የእንጀራ ፡ ልጇን ፡ አጕሳቈለችው

**treat of**
1. ነክ ፡ ሆነ. I like to read books that treat of politics. ፖለቲካ ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ መጻሕፍትን ፡ ማንበብ ፡ እወዳለሁ
2. አሰረዳ. This magazine treats of the progress of medicine. ይህ ፡ መጽሔት ፡ የሕክምና ፡ እድገትን ፡ ያስረዳል

**treat to** ጋበዘ
He is treating us to a bottle of wine. አንድ ፡ ጠርሙስ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ጋብዞናል
My brother treated me to the movie. ወንድሜ ፡ ሲኒማ ፡ ጋበዘኝ
[See also 'alike, harshly, ill']

**treat** (n.) ግብዣ
"This is my treat", he said. ይህ ፡ የኔ ፡ ግብዣ ፡ ነው ፡ አለ

**be a treat** በጣም ፡ አስደሰተ
It's a treat to read his books. እሱ ፡ የጻፋቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ ማንበብ ፡ በጣም ፡ ያስደስታል

**treatise** ድርሰት
The treatise was published in 1888. ድርሰቱ ፡ የታተመው ፡ በ፲፰፻፹፰ ዓ. ም. ነው

**treatment**
1. ሕክምና. The treatment failed to restore him to health. ሕክምናው ፡ ሊያድነው ፡ አልቻለም
2. ማስተዳደር. I dislike the high-handed treatment of his workers. ሠራተኞቹን ፡ ጨቋኝ ፡ ማስተዳደሩን ፡ አልወደድኩትም
3. አያያዝ. Is the treatment of prisoners worse than it used to be? የእስረኞቹ ፡ አያያዝ ፡ ከድሮው ፡ ብሷል ?
[See also 'harsh, medical, shock']

**treaty** (treaties)
1. ውል. The treaty was ratified by the senate. ውሉ ፡ በሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጸደቀ
2. ስምምነት. The boundaries were newly defined by the treaty. ወሰኑ ፡ እንደገና ፡ በስምምነት ፡ መሠረት ፡ ተከለለ

**treble** ሦስት ፡ ዕጥፍ
His salary is treble mine. የሱ ፡ ደሞዝ ፡ የኔን ፡ ሦስት ፡ ዕጥፍ ፡ ነው

**tree** ዛፍ
There are many trees in this park. በዚህ ፡ መናፈሻ ፡ ቦታ ፡ ብዙ ፡ ዛፍ ፡ አለ
**family tree** የዘር ፡ ግንድ
Here is the family tree of the President. የፕሬዚዳንቱ ፡ የዘር ፡ ግንድ ፡ ይኸው
[See also 'clear, grove']

**trek** (trekked), v. እያዘገመ ፡ ተጓዘ
The settlers trekked over mountains and deserts. ሰፋሪዎቹ ፡ በተራራዎቹ ፡ ላይና ፡ በምድረ ፡ በዳው ፡ ውስጥ ፡ እያዘገሙ ፡ ተጓዙ

**trek** (n.) የሄደበት ፡ መንገድ ፤ ጉዞ
Their trek is marked by cattle bones and broken wagons. የሄዱበት ፡ መንገድ ፡ የከብት ፡ አጥንትና ፡ የጋሪ ፡ ስባሪዎች ፡ ነበሩበት
It was a long trek over mountains for us. በተራራዎቹ ፡ ላይ ፡ ረዥም ፡ ጉዞ ፡ ተጓዝን

**tremble**
1. ተርገበገበ. His voice trembled when he spoke. ሲናገር ፡ ድምፁ ፡ ተርገበገበ
2. ተንቀጠቀጠ. He trembled with fear. በፍርሃት ፡ ተንቀጠቀጠ
3. ተወዛወዘ. The leaves tremble in the breeze. ቅጠሉ ፡ በነፋስ ፡ ሽውታ ፡ ይወዛወዛል
**tremble (voice)** ሲቃ ፡ ያዘው
+The speaker's voice trembled from the fervor of his love for his country. ለሀገሩ ፡ ካለው ፡ የጋለ ፡ ፍቅር ፡ የተነሣ ፡ ተናጋሪው ፡ ሲቃ ፡ ያዘው

**tremendous**
1. ትልቅ. That's a tremendous difference. ይህ ፡ ትልቅ ፡ ልዩነት ፡ ነው
2. የሚያስገርም. He traveled at a tremendous speed. በሚያስገርም ፡ ፍጥነት ፡ ተጓዘ
3. ከፍተኛ. The newspapers announced the tremendous boost in food prices. ጋዜጦች ፡ በምግብ ፡ ሸቀጥ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ የዋጋ ፡ ጭማሪ ፡ መደረጉን ፡ ገለጹ

**tremendously**
1. ያለቅጥ. The population increased tremendously. የሕዝቡ ፡ ቁጥር ፡ ያለቅጥ ፡ ጨመረ
2. በጣም. Social conditions have changed tremendously. የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ በጣም ፡ ተለውጧል

**tremor** ቀላል ፡ መንቀጥቀጥ
There was an earth tremor this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ ቀላል ፡ የመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ነበር
*There was a tremor in his voice. ድምፁ ፡ ይርገበገብ ፡ ነበር

**(be) tremulous**
1. ተርበደበደ. The young actor was tremulous before the performance. ወጣቱ ፡ ተዋናይ ፡ ጨዋታውን ፡ ከማሳየቱ ፡ በፊት ፡ ተርበደበደ
2. ተርገበገበ. The child's voice was tremulous with sobs. ልጁ ፡ ሲንሰቀሰቅ ፡ ድምፁ ፡ ይርገበገብ ፡ ነበር

**trench**
1. ቦይ. The trench was dug to lay a water pipe. ቦዩ ፡ የተቈፈረው ፡ የውኃ ፡ ቧምቧ ፡ ለመቅበር ፡ ነው
2. የመከላከያ ፡ ጉድባ. Our soldiers crossed the trenches under heavy fire. ወታደሮቻችን ፡ በኀይል ፡ እየተተኰሰባቸው ፡ የመከላከያውን ፡ ጉድባ ፡ አቋረጡ

**trenchant** ቁርጥ ፡ ያለ
His remarks were brief but trenchant. አስተያየቱ ፡ አጠር ፡ ያለ ፡ ቢሆንም ፡ ቁርጥ ፡ ያለ ፡ ነበር

**trend** (v.) አመራ
The road trends to the north. መንገዱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ያመራል

**trend downwards** ቀዘቀዘ
The market is trending downwards. ንግድ ፡ እ የቀዘቀዘ ፡ ሄዷል

**trend upwards** አደገ
The market is trending upwards. ንግድ ፡ እያደ ገ ፡ ሄዷል

**trend** (n.)
1. ዝንባሌ. The trend of public opinion is toward avoiding war. የሕዝቡ ፡ አስተያየት ፡ ዝንባሌ ፡ ጦርነትን ፡ ወደ ፡ ማስቀረት ፡ ነው
2. ሁኔታ. The trend of modern living is away from many old customs. የዘመናዊው ፡ ኑሮ ፡ ሁ ኔታ ፡ ከብዙ ፡ የድሮ ፡ ልማዶች ፡ በመራቅ ፡ ላይ ፡ ነው

**trepidation**
*He approached us with trepidation. ቢፈራ ፡ ቢቸር ፡ ተጠጋን

**be filled with trepidation** ተርበተበተ
He was filled with trepidation when he found the Emperor was about to visit him. ንጉሠ ፡ ነ ገሥቱ ፡ የሚጐበኙት ፡ መሆኑን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ተርበተበተ

**trespass** (v.) ሕግ ፡ ጥሶ ፡ አለፈ
We trespassed in the neighboring woods. ያካባቢያችንን ፡ ጫካ ፡ ሕግ ፡ ጥሰን ፡ አለፍነው

**trespass against** በደለ
"Forgive us our trespasses as we forgive those who trespass against us". በደላችንን ፡ ይቅር ፡ በ ለን ፡ እኛም ፡ የበደሉንን ፡ ይቅር ፡ እንል ፡ ዘንድ

**trespass on**
1. ያለፈቃድ ፡ ደፈረ. You were trespassing on my property. ንብረቴን ፡ ያለፈቃዴ ፡ ደፍረሃል
2. አባከነ(በት). He is trespassing on my time with problems he should take care of himself. የሱን ፡ ችግር ፡ ራሱ ፡ ሊያስወግድ ፡ ሲገባው ፡ የ ኔን ፡ ጊዜ ፡ ያባክንብኛል

**trespass** (n.) በደል
"Forgive us our trespasses". በደላችንን ፡ ይቅር ፡ በለን

**trial**
1. ፍርድ ፡ ቤት. They brought him to trial on a charge of murder. በነፍስ ፡ ገዳይነት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረቡት
When is your case coming up for trial? ያን ተ ፡ ነገር ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚታየው ፡ መ ቼ ፡ ነው ?
2. ሙከራ. I took it on trial. ለሙከራ ፡ ያህል ፡ አደረግሁት ፡

**be a trial** አስቸገረ
That boy is a trial to his teachers. ያ ፡ ልጅ ፡ መምህሮቹን ፡ ያስቸግራል

**give a trial** ሞከረ
Why don't you give the car a trial? መኪናውን ፡ ለምን ፡ አትሞክረውም ?
[See also 'stand']

**triangle** ሦስት ፡ ማእዘን
The table has the shape of a triangle. ጠረጴዛው ፡ የሦስት ፡ ማእዘን ፡ ቅርጽ ፡ አለው

**triangular** ባለ ፡ ሦስት ፡ ማእዘን
This frame is for photographs triangular in shape. ይህ ፡ የፎቶግራፍ ፡ ማስቀመጫ ፡ ባለ ፡ ሦስ ት ፡ ማእዘን ፡ ነው

**tribal** የጐሳዎች
Tribal affairs are handled by chiefs. የጐሳዎችን ፡ ጉዳዮች ፡ የሚያዩት ፡ ባላባቶቹ ፡ ናቸው

**tribalism** የጐሳ ፡ ልዩነት
The students are trying to discourage tribalism. ተማሪዎቹ ፡ የጐሳ ፡ ልዩነትን ፡ ለማስቀረት ፡ ይታ ገላሉ

**tribe** ጐሳ
The tribe has only three hundred members left. እዚህ ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ የቀሩት ፡ ሰዎች ፡ ሦስት ፡ መ ቶ ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**tribulation** መከራና ፡ ችግር
The war was a time of tribulation for us all. ጦርነቱ ፡ ለሁላችንም ፡ የመከራና ፡ የችግር ፡ ጊዜ ፡ ነበር

**tribunal** ፍርድ ፡ ቤት
He was brought before a tribunal. ፍርድ ፡ ቤ ት ፡ ቀረበ

**tribune**
1. ችሎት. The Emperor appointed a tribune of three judges. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አንድ ፡ ችሎ ት ፡ ላይ ፡ የሚቀመጡ ፡ ሦስት ፡ ዳኞች ፡ ሾሙ
2. መድረክ. The speakers addressed the meeting from the tribune. ተናጋሪዎቹ ፡ ከመድረኩ ፡ ላይ ፡ ለሕዝብ ፡ ንግግር ፡ አደረጉ

**tributary** (tributaries), n.
1. ገባር ፡ ወንዝ. The Danube has many tributaries. ዳኒዩብ ፡ ብዙ ፡ ገባር ፡ ወንዞች ፡ አሉት
2. ገባር. In olden times, a weak country was a tributary to a strong one. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ደ ካማው ፡ አገር ፡ ለኀይለኛው ፡ ገባር ፡ ነበር

**tribute**
1. ግብር. The subject people pay a tribute to the chief. ተገዥዎቹ ፡ ለባላባቱ ፡ ግብር ፡ ይከፍላሉ
2. መታሰቢያ. He wrote a poem as a tribute to his mother. ለእናቱ ፡ መታሰቢያ ፡ ግጥም ፡ ገጠመ

**pay tribute** በክብር ፡ አስታወሰ
Let us pay tribute to the memory of those who died defending their country! ለሀገራቸው ፡ ሲከላከሉ ፡ የሞቱትን ፡ በክብር ፡ እናስታውሳቸው

**trick** (v.) አታለለ
He tricked me again. እንደገና ፡ አታለለኝ

**trick (one) into**
*He tricked me into signing the petition. የአቤቱታውን ፡ ደብዳቤ ፡ ያስፈረመኝ ፡ በተንኰል ፡ ነው

**trick (one) out of** አታሎ ፡ ወሰደ(በት)
He tricked her out of her money. ገንዘቧን ፡ አታሎ ፡ ወሰደባት

**trick** (n.)
1. ተንኰል. He got the money from me by a trick. ገንዘቡን ፡ ከኔ ፡ የወሰደው ፡ በተንኰል ፡ ነው
2. ትንግርት. Watch my motions carefully and you will see how I do the trick. የማደርገውን ፡ ልብ ፡ ብለህ ፡ ተመልከትና ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ትንግርቱን ፡ እንደምሠራ ፡ ታያለህ
3. ጨዋታ. Does your dog know any tricks? ውሻህ ፡ ጨዋታ ፡ ያውቃል ?
4. ምስጢር. He knows all the tricks. ምስጢሩን ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል
5. ዘዴ. Mother certainly knows the trick of making cakes. እናታችን ፡ የኬክ ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ በደንብ ፡ ታውቃለች

**do the trick**
*A safety pin will do the trick. መርፌ ፡ ቁልፍም ፡ ይሆናል

**mean trick** ተንኰል
It's a mean trick to give a dog a piece of meat with pepper in it. በርበሬ ፡ የተነሰነሰበት ፡ ሥጋ ፡ ለውሻ ፡ መስጠት ፡ ተንኰል ፡ ነው

**play a dirty trick**
He played a dirty trick on me. ተጫወተብኝ

**play a mean trick** አታለለ
They played a mean trick on me by selling copper as gold. መዳቡን ፡ ወርቅ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በመሸጥ ፡ አታለሉኝ

**play tricks** ተጫወተ(በት)
This much is certain : he won't play tricks on us again. ሁለተኛ ፡ እንደማይጫወትብን ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው

**there's no trick** አያስቸግርም
There's no trick to taking pictures with this camera. በዚህ ፡ ካሜራ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ማንሣት ፡ አያስቸግርም
[See also 'dirty']

**trickery** ማታለል
Some men succeed by trickery. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በማታለል ፡ ካሰቡት ፡ ይደርሳሉ

**trickle** (vt.) አፈሰሰ
He trickled sand all over the rug. ምንጣፉ ፡ ላይ ፡ በሙሉ ፡ አሸዋ ፡ አፈሰሰበት

**trickle** (vi.)
1. ዱብ ፡ ዱብ ፡ አለ. Tears trickled down her cheeks. እንባዋ ፡ በጉንጮቿ ፡ ላይ ፡ ዱብ ፡ ዱብ ፡ አለ
2. ተንጠባጠበ. Water trickles from the trees. ውኃ ፡ ከዛፎቹ ፡ ላይ ፡ ይንጠባጠባል
3. ተንጠፈጠፈ. The brook trickled through the valley. ጅረቱ ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ይንጠፈጠፍ ፡ ነበር
*Rain trickles through the roof. ጣሪያው ፡ ያፈሳል

**trickle away** አንድ ፡ አንድ ፡ እያለ ፡ ተበታተነ
The crowd trickled away. ሕዝቡ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ እያለ ፡ ተበታተነ

**trickle into** እየተንጠባጠበ ፡ ገባ
The students trickled into the classroom. ተማሪዎቹ ፡ እየተንጠባጠቡ ፡ ወደ ፡ ክፍል ፡ ገቡ

**let trickle** በቀስታ ፡ አንቈረቈረ
He let the water trickle into the container. ውኃውን ፡ እመያዣው ፡ ውስጥ ፡ በቀስታ ፡ አንቈረቈረ

**trickster** አጭበርባሪ
There were many tricksters at the fair. በኤክስፖዚስዮኑ ፡ ስፍራ ፡ ብዙ ፡ አጭበርባሪዎች ፡ ነበሩ

**tricky**
1. የሚያሳስት. That's a tricky question. የሚያሳስት ፡ ጥያቄ ፡ ነው
2. ዘዴኛ. He is a tricky politician. እሱ ፡ ዘዴኛ ፡ የፖለቲካ ፡ ሰው ፡ ነው
3. ብልጥ. The fox is a tricky animal. ቀበሮ ፡ ብልጥ ፡ እንስሳ ፡ ነው

**trifle** (v.) ቀለደ
Don't trifle with serious matters! በቁም ፡ ነገር ፡ አትቀልድ
He trifled with her affections. በፍቅሯ ፡ ቀለደባት

**trifle away** በከንቱ ፡ አሳለፈ
He trifled his time away. ጊዜውን ፡ በከንቱ ፡ አሳለፈ

**to be trifled with**
*He is not a man to be trifled with. ከሱ ፡ ጋር ፡ መቀለድ ፡ አይቻልም

**trifle** (n.)
1. ቀላል ፡ ነገር. That's no trifle. ያ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አይደለም
2. አነስተኛ ፡ ነገር. The merest trifle upsets him. በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነገር ፡ ያበሳጨዋል
3. የማይረባ ፡ ነገር. Esau traded his primogeniture for a trifle. ኤሳው ፡ ብኵርናውን ፡ በማይረባ ፡ ነገር ፡ ለወጠው

**a trifle** ትንሽ
The trousers are a trifle too long. ሱሪው ፡ ትንሽ ፡ ረዘም ፡ ይላል

**only a trifle** ለስሙ ፡ ያህል ፡ ብቻ
It cost me only a trifle. የከፈልኩት ፡ ዋጋ ፡ ለስሙ ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ ነበር

**trifling, ~ matter** ቀላል ፡ ነገር
The friends treated their quarrel as only a trifling matter. ጓደኞቹ ፡ ጥላቸውን ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ቈጠሩት

**trigger** (v.) አስነሣ
The shooting triggered a bloody riot. ተኵሱ ፡ ደም ፡ የሚያፋስስ ፡ ብጥብጥ ፡ አስነሣ

**trigger** (n.) ምላጭ
He pulled the trigger, but the gun failed to go off. ምላጩን ፡ ሳበ ፡ ግን ፡ ጥይቱ ፡ ከሸፈ

**trilateral** ሦስት ፡ ማእዘን ፡ ያለው
This figure is trilateral. ይህ ፡ ቅርጽ ፡ ሦስት ፡ ማእዘን ፡ አለው

**trill** ድምፅ
The trill of a bird is sweet to hear. የወፏን ፡ ድምፅ ፡ መስማት ፡ የሚያስደስት ፡ ነው

**trim** (trimmed), v.
1. አስተካከለ. He trimmed the rough edges with a knife. ያልተስተካከለውን ፡ ጠርዝ ፡ በቢላዋ ፡ አስተካከለ
2. ቈረጠ. The gardener trimmed dead branches off the tree. አትክልተኛው ፡ የደረቁ ፡ ቅርንጫፎቹን ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ይቈርጥ ፡ ነበር
3. ከፈፈ (ተከፈፈ). The hat is trimmed with feathers. ባርኔጣው ፡ በላባ ፡ የተከፈፈ ፡ ነው
4. አጊያጌጠ. The children were trimming the Christmas tree. ልጆቹ ፡ የገናውን ፡ ዛፍ ፡ ያጊያጌጡ ፡ ነበር

**trim** (n.), **be in ~** በሚገባ ፡ ተዘጋጀ
Our team is in trim for the game. ቡድናችን ፡ ለግጥሚያው ፡ በሚገባ ፡ ተዘጋጅቷል

**be in good trim** በሚገባ ፡ ተደራጀ
When the captain visited our quarters, he said everything was in good trim. ሻምበሉ ፡ ሰፈራችንን ፡ በጐበኘ ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ በሚገባ ፡ ተደራጅቷል ፡ አለ

**be in poor trim**
*That ship is in poor trim for a voyage. ያቺ ፡ መርከብ ፡ ለጉዞ ፡ ሁኔታዋ ፡ አያመችም

**trim** (adj.) ሽክ ፡ ያለ
A trim maid appeared. ሽክ ፡ ያለች ፡ ገረድ ፡ ብቅ ፡ አለች
*She has a trim figure. ሸንቅጥ ፡ ናት
*She always keeps a trim kitchen. ማድቤቷን ፡ ሁልጊዜ ፡ በንጽሕና ፡ ትይዛለች

**trimmings**
1. ማጌጫ. Yesterday we bought the trimmings for the Christmas tree. ትናንት ፡ የገና ፡ ዛፍ ፡ ማጌጫዎች ፡ ገዛን
2. ተከታይ ፡ ምግቦች. We ate goose with all its trimmings. ዝዩ ፡ ከተከታይ ፡ ምግቦች ፡ ጋር ፡ በላን

**Trinity, Holy ~** ሥላሴዎች
He was baptized in the name of the Holy Trinity. በሥላሴዎች ፡ ስም ፡ ተጠመቀ

**trinkets** ጥቃቅን ፡ ጌጣጌጦች
He gave the natives some beads and other trinkets for helping him. የሀገሬው ፡ ሰዎች ፡ ስለረዱት ፡ ዶቃዎችንና ፡ ሌሎች ፡ ጥቃቅን ፡ ጌጣጌጦች ፡ አደረገላቸው

**trio**
1. የሦስት ፡ ሰዎች ፡ ጓድ. The Three Musketeers are a famous trio in French literature. ሦስቱ ፡ ነፍጠኞች ፡ በፈረንሳይ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የታወቀ ፡ የሦስት ፡ ሰዎች ፡ ጓድ ፡ ነው
2. ሦስት ፡ ዘፋኞች. The trio has sung in all the major capitals of the world. ሦስቱ ፡ ዘፋኞች ፡ በዓለም ፡ ትልልቅ ፡ ከተማዎች ፡ ሁሉ ፡ ዘፍነዋል

**trip** (tripped), vt.
1. አደናቀፈ. The stairs tripped him. ደረጃዎቹ ፡ አደናቀፉት
2. አደናገረ. The difficult question tripped him. ከባዱ ፡ ጥያቄ ፡ አደናገረው

**trip** (vi.)
1. ተደናቀፈ. He tripped and fell downstairs. ተደናቅፎ ፡ ከደረጃው ፡ ላይ ፡ ወደቀ

2. (= tr.) አደናቀፈ. +Don't trip on the stairs! ደረጃው ፡ እንዳያደናቅፍህ ፡ ተጠንቀቅ
3. ተሳሳተ. He tripped on that difficult question. ያንን ፡ ከባድ ፡ ጥያቄ ፡ ሲሠራ ፡ ተሳሳተ

**trip down** ሮጥ ፡ ሮጥ ፡ አለ
The children came tripping down the path to meet us. ልጆቹ ፡ በጠባቡ ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ሮጥ ፡ ሮጥ ፡ እያሉ ፡ ወደኛ ፡ መጡ

**trip (one) up**
1. አሳሳተ. The teacher tripped me up by that question. አስተማሪው ፡ በዚያ ፡ ጥያቄ ፡ አሳሳተኝ
2. አደናቀፈ. The toy on the floor tripped him up. ወለሉ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አሻንጉሊት ፡ አደናቀፈው
*The clever lawyer tripped the witness up. ብልሁ ፡ ጠበቃ ፡ ምስክሩ ፡ ቀድሞ ፡ የሰጠው ፡ ቃል ፡ ስሕተት ፡ መሆኑን ፡ አሳመነው

**trip** (n.)
1. ጉዞ. How was your trip? ጉዞህ ፡ እንዴት ፡ ነበር?
2. መንገድ. Have a pleasant trip! መልካም ፡ መንገድ ፡ ይሁንልህ

**go on a trip** ተጓዘ
The rich trader was told to take a bodyguard with him when he went on a trip. ሀብታሙ ፡ ነጋዴ ፡ በሚጓዝበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ዐጃቢ ፡ እንዲይዝ ፡ ተነገረው

**undertake a trip** ጉዞ ፡ ሄደ
I hope you're not planning to undertake that trip alone. ወደተባለው ፡ ጉዞ ፡ ብቻህን ፡ እንደማትሄድ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ
[See also 'round trip']

**tripartite**
*The tripartite treaty to defend Israel's territorial integrity has become a dead letter. ሦስቱ ፡ ሀገሮች ፡ የእስራኤልን ፡ የግዛት ፡ አንድነት ፡ ለመጠበቅ ፡ ያደረጉት ፡ ስምምነት ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ሆኗል

**tripe** ጨጓራ
The English are not very fond of eating tripe. እንግሊዞች ፡ ጨጓራ ፡ መብላት ፡ እጅግም ፡ አይወዱም

**triple** (v.) ሦስት ፡ ዕጥፍ ፡ አደረገ
My uncle tripled his money in these last five years. አጐቴ ፡ ባለፉት ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ገንዘቡን ፡ ሦስት ፡ ዕጥፍ ፡ አድርጓል

**triple** (n.) ሦስት ፡ ዕጥፍ
In that shop, you pay triple for everything you buy. ከዚያ ፡ ሱቅ ፡ ለምትገዛው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሦስት ፡ ዕጥፍ ፡ ትከፍላለህ

**triple** (adj.) ሦስት ፡ ዕጥፍ
He charged me triple price for the book. ለመጽሐፉ ፡ ሦስት ፡ ዕጥፍ ፡ ዋጋ ፡ አስከፈለኝ

**Triple Alliance** የሦስቱ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አገሮች ፡ ኅደኝነት
The Triple Alliance was ended by the First World War. የሦስቱ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አገሮች ፡ ኅደኝነት ፡ ባንደኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ፈረሰ

**triplets** ሦስት ፡ ልጆች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ
Triplets were born to a young couple recently. በቅርቡ ፡ ወጣት ፡ የሆኑ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ወለዱ

**triplicate** ሦስት ፡ ቅጅ
Send me the application in triplicate! ማመልከቻውን ፡ በሦስት ፡ ቅጅ ፡ ላክልኝ

**tripod** ባለ ፡ ሦስት ፡ እግር ፡ መቆሚያ
The camera rests on a tripod. ፎቶግራፍ ፡ ማንሻው ፡ ባለ ፡ ሦስት ፡ እግር ፡ መቆሚያ ፡ ላይ ፡ ነው

**triptych** ታጣፊ ፡ ባለ ፡ ሦስት ፡ ጽላት ፡ ሥዕል
He bought a triptych with a picture of the crucifixion. የስቅለት ፡ ሥዕል ፡ ያለበት ፡ ታጣፊ ፡ ባለ ፡ ሦስት ፡ ጽላት ፡ ሥዕል ፡ ገዛ

**trite** የነፈሰበት
"Hair like a skein of silk" is a trite expression. « የሐር ፡ ነዶ ፡ የሚመስል ፡ ጸጉር » ፡ የሚለው ፡ የነፈሰበት ፡ አነጋገር ፡ ነው

**triumph** (v.)
1. ድል ፡ አደረገ. In England, the conservatives triumphed over their opposition. በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የኮንሰርቫቲቭ ፡ የፖለቲካ ፡ ፓርቲ ፡ ተቀናቃኙን ፡ ድል ፡ አደረገ
2. ደነፋ(በት). Don't triumph over your defeated enemy! ድል ፡ በሆነው ፡ ጠላትህ ፡ ላይ ፡ አትደንፋበት

**triumph** (n.)
1. ድል. Atomic energy is a triumph of modern science. የአቶሚክ ፡ ኀይል ፡ ዘመናዊው ፡ ሳይንስ ፡ ያስገኘው ፡ ድል ፡ ነው
2. የድል ፡ በዓል. He celebrated the triumph of Ethiopia's armies. የኢትዮጵያን ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ የድል ፡ በዓል ፡ አከበረ

**in triumph** ድልን ፡ ተጐናጽፎ
He returned home in triumph. ድልን ፡ ተጐናጽፎ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመለሰ

**triumphal**
1. የድል ፡ በዓል. A triumphal march was played in honor of the victory. ድሉን ፡ ለማክበር ፡ የድል ፡ በዓል ፡ ማርሽ ፡ ተጫወቱ
2. የድል. The city erected a triumphal arch in his honor. ከተማው ፡ ስለ ፡ ክብሩ ፡ የድል ፡ ቅስት ፡ አቆመችለት

**triumphant**
1. አሸናፊ. The triumphant team was received by the crowd with cheers. አሸናፊውን ፡ ቡድን ፡ ሕዝቡ ፡ በጭብጨባ ፡ ተቀበለው
2. የድል ፡ ስሜት ፡ ያለው. The winner spoke in triumphant tones to his defeated rival. አሸናፊው ፡ የተሸነፈውን ፡ ተወዳዳሪውን ፡ የድል ፡ ስሜት ፡ ባለው ፡ አነጋገር ፡ ተናገረው

**trivet** ጉልቻ
The maid placed the trivet in proper order. ገረዲቱ ፡ ጉልቻውን ፡ አስተካከለችው

**trivial**
1. ዋጋ ፡ ቢስ. His remark was considered trivial. አስተያየቱ ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ሆኖ ፡ ተቈጠረ
2. የማይረባ. I cannot understand his belligerence about such a trivial matter. እንዲህ ፡ ባለ ፡ በማይረባ ፡ ነገር ፡ ጠብ ፡ መፈለጉ ፡ አይገባኝም
3. አነስተኛ ፡ ጉዳይ. That's too trivial to be bothered with. ያ ፡ ሊጨነቁለት ፡ የማይገባ ፡ አነስተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ነው

**triviality** የማይረባ ፡ ነገር
He concerns himself with such trivialities. በማይረባ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ሐሳቡን ፡ ያውላል

**trod,** see **tread**

**trodden,** see **tread**

**trombone** የጥሩምባ ፡ ዓይነት

**troop** (v.), ተንጋጋ
Watch out for children trooping out of school! ተማሪዎች ፡ ተንጋግተው ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ ሲወጡ ፡ ተጠንቀቅ

**troop off after** ተከትለው ፡ ባንድነት ፡ ሄዱ
The young boys trooped off after the older ones. ትንንሾቹ ፡ ልጆች ፡ ትልልቆቹን ፡ ተከትለው ፡ ባንድነት ፡ ሄዱ

**troop** (n.) ጓድ
Each time the troop left an exhibit, the leader counted noses. ጓዱ ፡ ከኤግዚቢሽኑ ፡ በወጣ ፡ ቍጥር ፡ መሪው ፡ ሰዎቹን ፡ ይቈጥር ፡ ነበር

**troop of** ብዙ ፡ - - - አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው
A troop of schoolchildren went on the picnic. ብዙ ፡ ተማሪዎች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ለሽርሽር ፡ ሄዱ

**troops** ወታደሮች ፤ ጦር
The returning troops were greeted with cheers. ከጦር ፡ የተመለሱትን ፡ ወታደሮች ፡ በእልልታ ፡ ተቀበሏቸው
After the war, the minister demobilized the troops. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ጦሩን ፡ በተነ
[See also 'shock']

**trophy** (trophies)
1. ምርኮ. He brought back some trophies from the war. ከጦርነቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምርኮ ፡ ይዞ ፡ ተመለሰ
2. ሽልማት. The African Cup is a famous trophy. የአፍሪካ ፡ ዋንጫ ፡ ትልቅ ፡ ሽልማት ፡ ነው

**get a trophy** ተሸለመ
The winner gets a gold cup as a trophy. አሸናፊው ፡ የወርቅ ፡ ዋንጫ ፡ ይሸለማል

**tropic(s)** የሐሩር ፡ አውራጃ ፤ ሞቃት ፡ አገሮች
Have you ever lived in the tropics? በሐሩር ፡ አውራጃ ፡ ኖረህ ፡ ታውቃለህ ?
Vegetation is rank in the tropics. በሞቃት ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ተክሉ ፡ ይጋሽባል

**tropical**
1. ሞቃት. Ethiopia's tropical climate is modified by the altitude. የኢትዮጵያ ፡ ሞቃት ፡ ያየር ፡ ንብረት ፡ ባገሪቱ ፡ ተራራማነት ፡ ቀዝቀዝ ፡ ይላል
A siesta is always taken in the afternoon in tropical countries. በሞቃት ፡ አገሮች ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ ከምሳ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ይተኛሉ
2. ለሙቀት ፡ የሚሆን. Wear tropical clothes during the hot weather! በሞቃት ፡ ጊዜ ፡ ለሙቀት ፡ የሚሆን ፡ ልብስ ፡ ልበስ

**trot** (trotted), vt. እያሠገረ ፡ ሄደ
The rider trotted his mule down the road. ሰውዬው ፡ በቅሎውን ፡ እያሠገረ ፡ ሄደ

**trot** (vi.)
1. እያሰመሰመ ፡ ሄደ. The horse trotted at the head of the parade. ፈረሱ ፡ በሰልፉ ፡ መጀመሪያ ፡ እያሰመሰመ ፡ ሄደ
2. ድክድክ ፡ እያለ ፡ ሄደ. The boy trotted at his mother's side. ልጁ ፡ በእናቱ ፡ ጐን ፡ ድክድክ ፡ እያለ ፡ ሄደ

**trot** (n.) ሶምሶማ
The horse's trot attracted the attention of the onlookers. የፈረሱ ፡ ሶምሶማ ፡ የተመልካቾችን ፡ ዓይን ፡ ማረከ

**move at a slow trot** ሠገረ
The mule moved at a slow trot. በቅሎው ፡ ሠገረ

**trouble** (vt.)
1. አስቸገረ. I'm sorry, but I'll have to trouble you again. አዝናለሁ ፤ እንደገና ፡ ላስቸግርህ ፡ ነው
2. አስጨነቀ. What's troubling you? የሚያስጨንቅህ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
3. አመመ(ው). +My arm has been troubling me ever since my accident. አደጋ ፡ ከደረሰብኝ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ክንዴን ፡ ያመኛል
4. አናወጸ. A breeze troubled the surface of the lake. የነፋስ ፡ ሽውታ ፡ ሐይቁን ፡ አናወጸው
*May I trouble you for a match? ክብሪት ፡ አንዱ ፡ ትሰጠኝ ?
*Don't trouble to return the pencil! እርሳሱን ፡ ባትመልሰውም ፡ ግዴለም

**trouble** (vi.) ተቸገረ
Why should I trouble to explain? He won't understand anyway. መቼም ፡ አይገባው ፤ ለምን ፡ ለማስረዳት ፡ እቸገራለሁ ?

**trouble oneself** ተቸገረ
Don't trouble yourself to wash the dishes! ሳሕኖቹን ፡ ለማጠብ ፡ አትቸገር

**be troubled** ተናወጠ
The waters are troubled. ባሕሩ ፡ ተናውጧል

**be troubled by**
1. (= act.) አስጨነቀ. +She is troubled by headaches. ራስ ፡ ምታት ፡ ያስጨንቃታል
2. (= act.) አሳሰበ. +I've been troubled by the state of his health recently. የጤንነቱ ፡ ሁናቴ ፡ በቅርቡ ፡ አሳስቦኛል

**trouble** (n.)
1. ችግር. I had a lot of trouble about it. በሱ ፡ ነገር ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ አጋጥሞኝ ፡ ነበር
The trouble is that money is needed, and I don't have it. ችግሩ ፡ ገንዘብ ፡ ማስፈለጉና ፡ እኔ ፡ የሌለኝ ፡ መሆኑ ፡ ነው
2. አለመግባባት. Trouble has developed between the two countries. በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ አለመግባባት ፡ ተፈጥሯል
3. ድካም. They remunerated him for his trouble. ለድካሙ ፡ ዋጋውን ፡ ከፈሉት

**be in trouble with**
*He is in trouble with the police. ፖሊሶች ፡ ይፈልጉታል

**get (one) in trouble** ችግር ፡ ላይ ፡ ጣለ
The child's insatiable curiosity often got him in trouble. የሕፃኑ ፡ የማይረካ ፡ የማወቅ ፡ ፍላጎት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ይጥለዋል

**get into trouble**
1. ጣጣ ፡ ውስጥ ፡ ገባ. He got into trouble selling illicit goods. የተከለከሉትን ፡ ነገሮች ፡ ሲሸጥ ፡ ጣጣ ፡ ውስጥ ፡ ገባ
2. ጥፋት ፡ ላይ ፡ ወደቀ. These children lack paternal control, and therefore get into trouble. እነዚህ ፡ ልጆች ፡ የወላጅ ፡ ቁጥጥር ፡ ስለሚጎድላቸው ፡ ጥፋት ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ

**give trouble** አስቸገረ
I am sorry to have given you so much trouble. ይህን ፡ ያህል ፡ ስላስቸገርኩህ ፡ አዝናለሁ

**go to a lot of trouble** ተጨንቆ ፡ ተጠቦ ፡ ቆየ
She went to a lot of trouble to make her guests comfortable. እንግዶቿን ፡ በደንብ ፡ ለማስተናገድ ፡ ተጨንቃ ፡ ተጠባ ፡ ቆየች

**go to any trouble** ተቸገረ
Don't go to any trouble for me! ለኔ ፡ ብለህ ፡ አትቸገር

**have trouble** አመመ(ው)
+He has stomach trouble. ሆዱን ፡ ያመዋል

**have trouble with** አስቸገረ
+I'm always having trouble with my tooth. ጥርሴ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያስቸግረኛል

**look for trouble** ጠብ ፡ ያለሽ ፡ ዳቦ ፡ አለ
When the soldiers come into town, they are always looking for trouble. ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ በመጡ ፡ ቁጥር ፡ ጠብ ፡ ያለሽ ፡ ዳቦ ፡ ይላሉ

**make trouble for** አስቸገረ
Some students usually make trouble for the teacher. አንዳንድ ፡ ተማሪዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መምህራቸውን ፡ ያስቸግራሉ

**put (one) in trouble** ችግር ፡ ላይ ፡ ጣለ
His remarks put him in trouble. የተናገረው ፡ ነገር ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ጣለው

**put oneself to trouble** ተቸገረ
Don't put yourself to any trouble! አትቸገር

**take (the) trouble** ተቸገረ
He took a lot of trouble just to please her. እሷን ፡ ለማስደሰት ፡ ሲል ፡ ብዙ ፡ ተቸገረ
[See also 'inflict']

**troubled** (adj.) የችግር
We are living in troubled times. ጊዜያችን ፡ የችግር ፡ ነው

**troublemaker** ነገረኛ
Be careful! He is a troublemaker. ተጠንቀቅ ፤ ነገረኛ ፡ ነው

**trouble-shooter** ችግር ፡ አስወጋጅ
The secretary serves as trouble-shooter for the minister. ጸሐፊው ፡ ለሚኒስትሩ ፡ እንደ ፡ ችግር ፡ አስወጋጅ ፡ ያገለግላል

**troublesome** አስቸጋሪ ፤ በጣም ፡ አስቸጋሪ
He is a troublesome child. አስቸጋሪ ፡ ልጅ ፡ ነው
That's a troublesome problem. በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ፕሮብሌም ፡ ነው

**trough**
1. ገንዳ. The horse drinks from a trough. ፈረሱ ፡ ከገንዳው ፡ ውስጥ ፡ ይጠጣል
2. ቡሆቃ ፤ ቦኻቃ. The baker used a trough for kneading dough. ዳቦ ፡ ጋጋሪው ፡ በቡሆቃ ፡ (በቦኻቃ) ፡ ቡሆ ፡ አቦካ

**troupe** ጓድ
A troupe of harp players is coming to the theater tonight. ዛሬ ፡ ማታ ፡ የበገና ፡ ተጫዋቾች ፡ ጓድ ፡ ጨዋታ ፡ ያሳያል

**trousers** ሱሪ
My father bought me a pair of new trousers. አባቴ ፡ አዲስ ፡ ሱሪ ፡ ገዙልኝ

**long trousers** ቦላሌ
He wears long trousers. ቦላሌ ፡ ይለብሳል

**pair of trousers** ሱሪ
I need a new pair of trousers.አዲስ ፡ ሱሪ ፡ ያስፈልገኛል

**short trousers** ቁምጣ
He wears short trousers. ቁምጣ ፡ ይታጠቃል

**trowel** ማንኪያ ፤ መለሰኛ
He smoothed the mortar with a trowel. ሲሚንቶውን ፡ በማንኪያ ፡ (በመለሰኛ) ፡ አስተካከለው

**truant** ቸልተኛ
The truant shepherd left his sheep. ቸልተኛው ፡ እረኛ ፡ በጎቹን ፡ ጥሎ ፡ ሄደ

**be truant from** ጥሎ ፡ ማገጠ
He is truant from school. ትምህርቱን ፡ ጥሎ ፡ ይማግጣል

**truant officer** [ተማሪዎች ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚቀሩበትን ፡ ምክንያት ፡ እየተከታተለ ፡ የሚማግጡትን ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ እንዲሄዱ ፡ የሚቈጣጠር ፡ ሹም]

**truce** ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ተኩስ ፡ ማቆም
The two sides agreed on a truce. ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ተኩስ ፡ ለማቆም ፡ ተስማሙ

**truck** (v.) በመኪና ፡ ወሰደ
They trucked the freight to the warehouse. ጭነቱን ፡ ወደ ፡ መጋዘን ፡ በመኪና ፡ ወሰዱት

**be trucked** በመኪና ፡ ተጫነ
The goods are trucked in from Djibouti. ሸቀጣ ፡ ሸቀጦች ፡ ከጂቡቲ ፡ በመኪና ፡ ተጭነው ፡ ይመጣሉ

**truck** (n.) የጭነት ፡ መኪና
The trucks unload here. የጭነት ፡ መኪናዎች ፡ እዚህ ፡ ይራገፋሉ
[See also 'convey']

**truculent** ተንኳሽ
He is a truculent child. ተንኳሽ ፡ ልጅ ፡ ነው
*He had a truculent expression on his face. ለጠብ ፡ መዘጋጀቱ ፡ ከፊቱ ፡ ላይ ፡ ይነበባል

**trudge** አዘገመ
The boy trudged through the forest to get to school. ልጁ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመድረስ ፡ በጫካው ፡ ውስጥ ፡ አዘገመ

**true**
1. እውነተኛ. You'll find him a true friend. እውነተኛ ፡ ወዳጅ ፡ ይሆንሃል
Is that story true? እውነተኛ ፡ ታሪክ ፡ ነው ?
My brother is the true heir to the property. ወንድሜ ፡ የንብረቱ ፡ እውነተኛ ፡ ወራሽ ፡ ነው
2. የተመሰከረለት. He is a true scholar. የተመሰከረለት ፡ ምሁር ፡ ነው
3. ትክክለኛ. This is a true copy of the document. ይህ ፡ የሰነዱ ፡ ትክክለኛ ፡ ግልባጭ ፡ ነው
4. ውስጣዊ. He cannot dissimulate his true feelings. ውስጣዊ ፡ ስሜቱን ፡ ሊደብቅ ፡ አይችልም
5. ንጹሕ. True gold is not easily distinguished from false gold. ንጹሕ ፡ ወርቅ ፡ ከውሸት ፡ ወርቅ ፡ በቀላሉ ፡ አይለይም

**be true to** አከበረ
He was true to his word. ቃሉን ፡ አክብሮ ፡ ነበር

**come true**
1. ተፈጸመ. Her dream came true. ምኞቷ ፡ ተፈጸመ
2. ያዘ(ለት). Did your dream ever come true? ሕልምህ ፡ ይዞልህ ፡ ያውቃል ?

**hold true**
*That does not hold true in our case. ነገሩ ፣ ለኛ ፣ ጉዳይ ፣ አይሆንም

**(be) proved true** ተረጋገጠ
His prophetic remark was proved true when the war broke out. ትንቢታዊ ፣ አስተያየቱ ፣ ጦርነቱ ፣ ሲነሣ ፣ ተረጋገጠ

**ring true** እውነት ፣ ያለበት ፣ መሰለ
His words ring true. የሚናገራቸው ፣ ቃላት ፣ እውነት ፣ ያለባቸው ፣ ይመስላሉ

**stay true** ጸንቶ ፣ ቆየ
He stayed true to his principles. በሚያምንበት ፣ ነገር ፣ ጸንቶ ፣ ቆየ

**truly** ከልብ
I am truly sorry. ከልብ ፣ አዝናለሁ

**very truly yours** ምንጊዜም ፣ ያንተው
The letter had "Very truly yours" and his signature. ደብዳቤው ፣ « ምንጊዜም ፣ ያንተው » ፣ የሚል ፣ ቃልና ፣ ፊርማው ፣ ነበረበት

**trump** (v.), ~ **up** ፈጠረ
He trumped up an excuse. ምክንያት ፣ ፈጠረ

**trump card**
*The surprise witness was his trump card. ያልታሰበው ፣ ምስክር ፣ የማምለጫ ፣ ዘዴ ፣ ነበር

**trumped-up**, adj. (= adv.) በሐሰት
A trumped-up charge of treason was made against him. በሐሰት ፣ በከሐዲነት ፣ ወንጀል ፣ ክስ ፣ ቀረበበት

**trumpet** (v.) ነዛ
She will trumpet the story all over town. ታሪኩን ፣ በከተማው ፣ ሁሉ ፣ ትነዛዋለች

**trumpet** (n.)
1. መለከት. The angel Gabriel will blow the trumpet on the Last Day. መልአኩ ፣ ገብርኤል ፣ በመጨረሻይቱ ፣ ቀን ፣ መለከት ፣ ይነፋል
2. ጥሩንባ. The trumpets are blown when the general comes to the camp. ጄኔራሉ ፣ ወደ ፣ ጦር ፣ ሰፈሩ ፣ ሲመጣ ፣ ጥሩንባ ፣ ይነፋል

**truncate**
1. ከጫፉ ፣ ቈረጠ. The farmer truncated the tree. ገበሬው ፣ ዛፉን ፣ ከጫፉ ፣ ቈረጠው
2. ቈረጠ(ተቈረጠ). The dog's tail was truncated near its body. የውሻው ፣ ጅራት ፣ ከሥሩ ፣ ተቈርጧል

**trundle** እየጐተተ ፣ ሄደ
He trundles his cart behind him wherever he goes. በሄደበት ፣ ሁሉ ፣ ተሳቢውን ፣ እየጐተተ ፣ ይሄዳል

**trunk**
1. ግንድ. The trunk of the tree is completely hollow. የዛፉ ፣ ግንድ ፣ ውስጡ ፣ ቀፎ ፣ ነው
2. ወገብ. The human body consists of three parts: head, trunk, and limbs. የሰው ፣ አካል ፣ በሦስት ፣ ይከፈላል ፤ እነሱም ፣ ራስ ፤ ወገብና ፣ እጅ ፣ እግር ፣ ናቸው
3. ኩንቢ. The elephant's trunk is long and leathery. የዝሆኑ ፣ ኩንቢ ፣ ረጅምና ፣ ቆዳማ ፣ ነው
4. ሻንጣ. Are the trunks packed? ሻንጣዎቹ ፣ ተዘጋጅተዋል ?
5. የእቃ ፣ ማስቀመጫ. The trunk of this car has room for two suitcases. የዚህ ፣ መኪና ፣ የእቃ ፣ ማስቀመጫ ፣ ሁለት ፣ ሻንጣዎች ፣ ይይዛል

**trunks** ሙታንቲዎች
These bathing trunks are too tight. እነዚህ ፣ የዋና ፣ ሙታንቲዎች ፣ በጣም ፣ ጠባብ ፣ ናቸው

**trust** (v.)
1. አመነ. We trust in God. በእግዚአብሔር ፣ እናምናለን
I trust you slept well. ጥሩ ፣ እንቅልፍ ፣ እንደወሰደህ ፣ አምናለሁ
2. ተማመነ. You shouldn't trust too much to your memory. በማስታወስ ፣ ችሎታህ ፣ ብዙ ፣ መተማመን ፣ አይገባም
3. በዱቤ ፣ ሰጠ. The storekeeper refused to trust them for another week's supply of food. ባለመደብሩ ፣ ለሌላ ፣ ሳምንት ፣ ምግብ ፣ በዱቤ ፣ አልሰጣቸውም ፣ አለ
*Can I trust the keys to him? እሱን ፣ አምኜ ፣ ቁልፉን ፣ ልሰጠው ፣ እችላለሁ ?

**trust (one) out-of-doors** ከቤት ፣ ውጭ ፣ ለቀቀ
It's unwise to trust small children out-of-doors in a big town. ልጆችን ፣ በትልልቅ ፣ ከተማዎች ፣ ውስጥ ፣ ከቤት ፣ ውጭ ፣ መልቀቅ ፣ ጥሩ ፣ አይደለም

**trust to (someone's) care** አደራ ፣ ሰጠ
They trusted the car to my care. መኪናውን ፣ ለኔ ፣ አደራ ፣ ሰጡኝ

**trust (one) with** አደራ ፣ ሰጠ
His father trusted him with the car. አባቱ ፣ መኪናውን ፣ አደራ ፣ ሰጠው

**be trusted** ማመን ፣ ተቻለ
His statements are not to be trusted. እሱ ፣ የሚለውን ፣ ማመን ፣ አይቻልም

**be trusted with** (= act.) አምኖ ፣ ሰጠ
Should young boys be trusted with automobiles? ለልጆች ፣ መኪና ፣ አምኖ ፣ መስጠት ፣ ይገባል ?

**trust** (n.)

1. እምነት. I am putting my trust in you. እምነቴን ፡ ባንተ ፡ ጥያለሁ

2. አደራ. The child was committed to his trust. ልጅቷ ፡ ለሱ ፡ አደራ ፡ ተሰጠች

I hold the property in trust for my nephew. የወንድሜን ፡ ልጅ ፡ ንብረት ፡ አደራ ፡ ተቀብያለሁ

3. መመኪያ. The Lord is our trust. ጌታ ፡ መመኪያችን ፡ ነው

4. ድርጅት. He made over the whole of his property to the national trust. ሀብቱን ፡ በሙሉ ፡ ለብሔራዊ ፡ ድርጅት ፡ አስተላለፈ

**of great trust**

*He has a position of great trust. ከፍ ፡ ያለ ፡ ኀላፊነት ፡ የሚጣልበት ፡ ሥልጣን ፡ አለው

**take on trust** አምኖ ፡ ተቀበለ

You have to take my statement on trust. የምልህን ፡ አምነህ ፡ መቀበል ፡ አለብህ

**trustee** ባለ ፡ አደራ

He is a trustee of the museum. የቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ባለ ፡ አደራ ፡ ነው

**trustful** ሁሉን ፡ አማኝ

That trustful boy will lend money to any of his friends. ያ ፡ ሁሉን ፡ አማኝ ፡ ልጅ ፡ ለማንኛውም ፡ ጓደኛው ፡ ገንዘብ ፡ ያበድራል

**trustfully** እምነት ፡ በተሞላበት ፡ መንፈስ

She looked at him trustfully. እምነት ፡ በተሞላበት ፡ መንፈስ ፡ ተመለከተችው

**trustworthy** ታማኝ

He was the Emperor's trustworthy servant. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ታማኝ ፡ አገልጋይ ፡ ነበር

**trusty** ታማኝ

The master left his money with a trusty servant. ጌትየው ፡ ገንዘቡን ፡ ታማኝ ፡ አሽከሩ ፡ ዘንድ ፡ ትቶ ፡ ሄደ

**truth**

1. እውነት. Tell the truth. Did you take the book or not? እውነቱን ፡ ተናገር ፤ መጽሐፉን ፡ ወስደሃል ፡ ወይስ ፡ አልወሰድክም ?

2. እውነተኛ ፡ ነገር. I told him the plain truth. ግልጽ ፡ ያለውን ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነገርኩት

**element of truth** እውነት

There is an element of truth in his story of the accident. ስላደጋው ፡ በሚለው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ እውነት ፡ አለበት

[See also 'bald, grain, naked, ring, simple, tell']

**truthful**

1. ሐቀኛ. He is always truthful. ምንጊዜም ፡ ሐቀኛ ፡ ነው

2. እርግጠኛ. He gave a truthful account of the accident. ስለ ፡ አደጋው ፡ እርግጠኛውን ፡ ነገር ፡ ተናገረ

**truthfully** በእውነቱ

Truthfully, I did not expect that. በእውነቱ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ አልጠበቅሁም

**truthfulness** እውነተኛነት

Truthfulness engenders confidence. እውነተኛነት ፡ እምነትን ፡ ያስከትላል

**try** (tried), v.

1. ሞከረ. Try to do better next time! ወደፊት ፡ የተሻለ ፡ ለመሥራት ፡ ሞክር

He tries to get out of all hard work. ከጠንካራ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ለመሸሽ ፡ ይሞክራል

2. አየ. Which judge is trying the case? ነገሩን ፡ የሚያየው ፡ የትኛው ፡ ዳኛ ፡ ነው ?

3. (= intr.) ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀረበ. They tried him, and he was found guilty. ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ወንጀለኛ ፡ መሆኑ ፡ ተረጋገጠበት

4. ቀመሰ. Try this candy and see if you like it! ይህን ፡ ከረሜላ ፡ ቅመሰውና ፡ እስኪ ፡ ትወደው ፡ እንደሆነ ፡ እይ

5. ተጣጣረ. Try hard and maybe you will succeed. በጣም ፡ ተጣጣር ፤ ምናልባት ፡ ይሳካልህ ፡ ይሆናል

6. ታገለ. I am trying to break myself of the habit of smoking. ሲጃራ ፡ ለመተው ፡ እታገላለሁ

7. አደከመ. Don't try your eyes by reading in a poor light! በደብዛዛ ፡ ብርሃን ፡ በማንበብ ፡ ዓይንህን ፡ አታድክም

8. አስጨረሰ. Her mistakes try my patience. የምታደርጋቸው ፡ ስሕተቶች ፡ ትዕግሥቴን ፡ ያስጨርሱኛል

**try for** ለማግኘት ፡ ሞከረ

He is trying for a scholarship. የነጻ ፡ ትምህርት ፡ ለማግኘት ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነው

**try on** ሞከረ

I'd like to try that suit on again. ያንን ፡ ልብስ ፡ እንደገና ፡ ልሞክረው ፡ እፈልጋለሁ

**try out** ሞከረ

We will try out the new car tomorrow. አዲሱን ፡ መኪና ፡ ነገ ፡ እንሞክረዋለን

**be tried**

1. ፍርድ ፡ ቤት. ፡ ቀረበ. He was tried and found guilty. ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

2. ለፍርድ ፡ ቀረበ. At the last Judgment, all mankind will be tried. በዕለተ ፡ ምጽአት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ለፍርድ ፡ ይቀርባል
3. ታየ. His case will be tried next week. የሱ ፡ ነገር ፡ በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ ይታያል
[See also 'hand, hard']

**try** (n.)
*He made it on the first try. በመጀመሪያ ፡ ሲሞክር ፡ ተሳካለት
**have a try** ሞከረ
Let's have another try! እንደገና ፡ እንሞክር

**trying**
*That child has trying ways. ያ ፡ ልጅ ፡ ሁኔታው ፡ ሰው ፡ ያበሳጫል
*I had a very trying day; everything seemed to go wrong. ቀኑ ፡ ለኔ ፡ አልሆነኝም ፤ ምንም ፡ ነገር ፡ አልቀናኝም

**tryout** የተጫዋቾች ፡ መምረጫ ፡ ውድድር
Tryouts for our football team will begin next week. የግር ፡ ኳስ ፡ ቡድናችን ፡ የተጫዋቾች ፡ መምረጫ ፡ ውድድር ፡ በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ ይጀምራል

**tub**
1. ሳፋ. She washed her clothes in a tub. ልብሷን ፡ በሳፋ ፡ ላይ ፡ አጠበች
2. ባኞ. The mother bathed the baby in the tub. እናትዮዋ ፡ ልጇን ፡ ባኞ ፡ ውስጥ ፡ አጠበችው
**be in the tub** ገላውን ፡ ታጠበ
He is in the tub and can't come to the door. ገላውን ፡ ስለሚታጠብ ፡ ብቅ ፡ ሊል ፡ አይችልም

**tube**
1. ላስቲክ. He was fed through a tube. የሚመገበው ፡ በላስቲክ ፡ ነው
2. ከመነዳሪያ. I need a new tube for my tire. ለጎማዬ ፡ አዲስ ፡ ከመነዳሪያ ፡ እፈልጋለሁ
**tube of toothpaste** ሙሉ ፡ የጥርስ ፡ ሳሙና
I need a tube of toothpaste. አንድ ፡ ሙሉ ፡ የጥርስ ፡ ሳሙና ፡ እፈልጋለሁ

**tuberculosis** የሳምባ ፡ ነቀርሳ
He played an important part in the fight against tuberculosis. የሳምባ ፡ ነቀርሳን ፡ ለመከላከል ፡ ታላቅ ፡ ተጋድሎ ፡ አድርጓል

**tuck**
1. ሸጐጠ. The bird tucked its head under its wing. ወፏ ፡ ራሷን ፡ ክንፏ ፡ ውስጥ ፡ ሸጐጠች
She tucked her purse under her arm. ቦርሳዋን ፡ ብብቷ ፡ ሥር ፡ ሸጐጠች
2. ከተተ. He tucked the letter into his pocket. ደብዳቤውን ፡ ኪሱ ፡ ውስጥ ፡ ከተተ
**tuck away** ከተተ
He tucked away the map in a pocket at the end of the book. ካርታውን ፡ ከመጽሐፉ ፡ መጨረሻ ፡ ባለው ፡ ኪስ ፡ ውስጥ ፡ ከተተ
**tuck in** ሱሪው ፡ ውስጥ ፡ አስገባ
Tuck in your shirt! ሸሚዝህን ፡ ሱሪህ ፡ ውስጥ ፡ አስገባው
**tuck in bed** አመቻችቶ ፡ አስተኛ
She tucked the child in bed. ልጁን ፡ አመቻችታ ፡ አስተኛችው
**tuck up** ሰብሰብ ፡ አደረገ
She tucked up her skirt to keep it from getting wet. ጉርድ ፡ ቀሚሷን ፡ ውኃ ፡ እንዳይነካው ፡ ሰብሰብ ፡ አደረገችው

**Tuesday** ማክሰኞ

**tuft**
*A goat has a tuft of hair on its chin. ፍየል ፡ ጺም ፡ አለው
**tuft of feathers** ጉትያ
The bird has a tuft of feathers on its head. ወፏ ፡ ራሷ ፡ ላይ ፡ ጉትያ ፡ አላት

**tug** (tugged), **~ at** ጐተተ
The child tugged at its mother's skirts. ልጁ ፡ የእናቱን ፡ ጉርድ ፡ ቀሚስ ፡ ጐተተ
**tug on** ሳበ
He tugged so hard on the rope that it broke. በጣም ፡ ስለሳበው ፡ ገመዱ ፡ ተበጠሰ

**tug** (n.), **give a ~** ሳብ ፡ አደረገ
The boy gave his sister's hair a tug. ልጁ ፡ የእኅቱን ፡ ጸጉር ፡ ሳብ ፡ አደረገ

**tugboat** ጐታች ፡ ጀልባ
A tugboat is used to dock large ships. ጐታች ፡ ጀልባ ፡ ትልልቅ ፡ መርከቦችን ፡ ወደ ፡ ወደብ ፡ ለማስገባት ፡ ያገለግላል

**tug of war** የገመድ ፡ ጉተታ ፡ ግጥሚያ
The tug of war ended when we pulled the other team across the line. የገመድ ፡ ጉተታው ፡ ግጥሚያ ፡ ሌላውን ፡ ቡድን ፡ መሥመሩን ፡ አሳልፈን ፡ በጐተትን ፡ ጊዜ ፡ አበቃ

**tuition**
1. ለትምህርት ፡ የሚከፈል. How much is tuition this quarter? በዚህ ፡ ተርም ፡ ለትምህርት ፡ የሚከፈለው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?
2. የመማሪያ ፡ ገንዘብ. Students do not pay tuition in a government school. በመንግሥት ፡ ትምህርት ፡

ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተማሪ ፡ የመማሪያ ፡ ገንዘብ ፡ አ ይከፍልም

**tumble**

1. ተገለባበጠ. The acrobats tumble on ground that has been covered with soft sand. አክሮባቶቹ ፡ ልስልስ ፡ አሸዋ ፡ በተሸፈነ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ይገለባበጣሉ
2. ተንከባለለ. The children tumbled in the grass. ልጆቹ ፡ ሣሩ ፡ ላይ ፡ ተንከባለሉ
3. ገባ. I was so tired that I undressed and tumbled into bed. በጣም ፡ ደክሞኝ ፡ ስለነበረ ፡ ልብሴን ፡ አወላልቄ ፡ አልጋ ፡ ውስጥ ፡ ገባሁ ፡
4. ዘው ፡ አለ. He tumbled into the room. ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ዘው ፡ አለ

**tumble down**

1. ወደቀ. He tumbled down from the horse. ከፈረሱ ፡ ወደቀ
2. ወደቀ፤ፈረሰ. The old house is tumbling down. አሮጌው ፡ ቤት ፡ ሊወድቅ ፡ ነው ፡ (ሊፈርስ ፡ ነው)
3. ከ - - - ተደናቅፎ ፡ ወደቀ. He tumbled down the stairs. ከደረጃው ፡ ላይ ፡ ተደናቅፎ ፡ ወደቀ

**tumble out** ዘሎ ፡ ተነሣ

He tumbled out of bed. ከአልጋው ፡ ላይ ፡ ዘሎ ፡ ተነሣ

**tumble over** እየወደቀ ፡ ተነሣ

The baby is learning to walk and is always tumbling over. ሕፃኗ ፡ መራመድ ፡ መጀመሯ ፡ ስለሆነ ፡ እየወደቀች ፡ ትነሣለች

**tumble restlessly** ተወራጨ

The sick child tumbled restlessly in his bed. በሽተኛው ፡ ልጅ ፡ አልጋው ፡ ውስጥ ፡ ተወራጨ

**tumble-down** ደሳሳ

He lives in a tumble-down, old house. ባንድ ፡ አሮጌ ፡ ደሳሳ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል

**tumbler**

1. ዋንጫ. In olden days, they used to drink mead in a tumbler. በድሮ ፡ ጊዜ ፡ ጠጅ ፡ በዋንጫ ፡ ይጠጣ ፡ ነበር
2. ብርጭቆ. The waiter brought us several tumblers of beer. አሳላፊው ፡ ብዙ ፡ ብርጭቆ ፡ ቢራ ፡ አቀረበልን
3. ተገለባባጭ. The tumbler broke his arm when he turned over in the air. ተገለባባጩ ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ ሲገለባበጥ ፡ ክንዱ ፡ ተሰበረ

**tumor**

1. እብጠት. He has a tumor of the brain. ያንጐል ፡ እብጠት ፡ በሽታ ፡ አለበት
2. ኪንታሮት. The surgeon excised the tumor with no difficulty. የቀዶ ፡ ጥገናው ፡ ሐኪም ፡ ኪንታሮቱን ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ ቈርጦ ፡ አወጣ

**tumult** ሁካታ

The meeting ended in tumult. ስብሰባው ፡ በሁካታ ፡ ተፈጸመ

**tumultuous**

1. የጋለ. He received a tumultuous welcome. የጋለ ፡ አቀባበል ፡ ተደረገለት
2. ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሚንጫጫ. The tumultuous crowd had to be quieted down by the police. ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሚንጫጫውን ፡ ሕዝብ ፡ ፖሊስ ፡ ዝም ፡ ማሰኘት ፡ ነበረበት
3. ኀይለኛ. Tumultuous waves beat upon the rock. ኀይለኛ ፡ ሞገድ ፡ ከአለቱ ፡ ጋር ፡ ይላተማል

**tune** (v.) ቃኘ

A man is tuning the piano. አንድ ፡ ሰው ፡ ፒያኖ ፡ በመቃኘት ፡ ላይ ፡ ነው

**tune in** አስተካከለ

You haven't tuned in to the station, have you? የጣቢያውን ፡ መሥመር ፡ አላስተካከልከውም ?

**tune up**

1. ጠጋገነ. The mechanic is tuning up my car. ሜካኒኩ ፡ መኪናዬን ፡ በመጠጋገን ፡ ላይ ፡ ነው
2. ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ሙዚቃውን ፡ ቃኘ. The orchestra is tuning up. ኦርኬስትራው ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ሙዚቃውን ፡ በመቃኘት ፡ ላይ ፡ ነው

**tune** (n.) ዜማ

She retained the tune, but not the words of the song. ግጥሙን ፡ ረስታዋለች ፤ የምታስታውሰው ፡ ዜማውን ፡ ብቻ ፡ ነው

**in tune** ድምፁን ፡ አስተካክሎ

He can't sing in tune. ድምፁን ፡ አስተካክሎ ፡ መዝፈን ፡ አይችልም

**(be) in tune with** አብሮ ፡ የሚራመድ ፡ ነው

He is in tune with the times. ከጊዜው ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ የሚራመድ ፡ ሰው ፡ ነው

**(be) out of tune**

1. በሚገባ ፡ አልተቃኘም. The piano is out of tune. ፒያኖው ፡ በሚገባ ፡ አልተቃኘም
2. አልሄደም. This is out of tune with the surroundings. ይህ ፡ ከአካባቢው ፡ ጋር ፡ አይሄድም

**to the tune of**

*He was fined to the tune of $3,000. ሦስት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ተቀጣ

**tunnel** (v.) መንገድ ፡ ቀደደ

The workers are tunneling through the mountain. ሠራተኞቹ ፡ በተራራው ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ መንገድ ፡ ይቀዳሉ

**tunnel under** ሰርስሮ ፡ ወጣ

The prisoner tunneled under the wall. እስረኛው ፡ ግድግዳውን ፡ ሰርስሮ ፡ ወጣ

**tunnel** (n.) መሿለኪያ ፤ ዋሻ
The tunnel goes through the mountain. መሿለኪያው ፡ (ዋሻው) ፡ ተራራውን ፡ ሰንጥቆ ፡ ያልፋል

**turban** ጥምጥም
The priest put on a turban. ቄሱ ፡ ጥምጥም ፡ ጠመጠመ

**turbid** የደፈረሰ
The turbid water shows that a flood is coming. የደፈረሰ ፡ ውኃ ፡ ጐርፍ ፡ መምጣቱን ፡ ያመለክታል

**be turbid** ደፈረሰ
The water is turbid. ውኃው ፡ ደፍርሷል

**turbulence** ሁካታ
The turbulence is due to the children's being dismissed from school early. ሁካታው ፡ የተነሣው ፡ ልጆቹ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ስለተለቀቁ ፡ ነው

**turbulent**
1. ሥርዓት ፡ የጐደለ. The turbulent mob threatened to break down the gate. ሥርዓት ፡ የጐደለው ፡ ሕዝብ ፡ በሩን ፡ ለመስበር ፡ አስፈራራ
2. የተናወጸ. The turbulent air made the plane pitch. የተናወጸው ፡ አየር ፡ አውሮፕላኑን ፡ ነቀነቀው
3. ኀይለኛ. The turbulent water swept away the bridge. ኀይለኛው ፡ ጐርፍ ፡ ድልድዩን ፡ ጠርጎ ፡ ወሰደው

**turf** ሣር
The golfer knocked out a piece of turf. የጎልፍ ፡ ተጫዋቹ ፡ ሣሩን ፡ ገንጥሎ ፡ ጣለው

**turgid**
1. ያበጠ. The turgid blood vessels indicate that an infection has occurred. ያበጠው ፡ የደም ፡ ሥር ፡ ሰውነቱ ፡ በበሽታ ፡ መመረዙን ፡ ያመለክታል
2. ከባድ. His turgid language is difficult to understand. ከባድ ፡ የሆነ ፡ አባበሉን ፡ ለመረዳት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**turkey** የቱርክ ፡ ዶሮ
Americans eat turkey on Christmas day. አሜሪካኖች ፡ የገና ፡ ዕለት ፡ የቱርክ ፡ ዶሮ ፡ ይበላሉ

**turmoil** ግርግር
There is always a lot of turmoil on the first day of school. በትምህርት ፡ መጀመሪያ ፡ ቀን ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ግርግር ፡ አለ

**be all turmoil** ጦፈ
He seemed calm, but within was all turmoil. የረጋ ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ ከውስጥ ፡ ጦፏል

**turn** (vt.)
1. አዞረ. I can't turn the key. ቁልፉን ፡ ማዞር ፡ አቃተኝ
The actor turned his back to the audience. ተዋናዩ ፡ ጀርባውን ፡ ወደ ፡ ተመልካቾቹ ፡ አዞረ
2. ገለበጠ. The student turned the page of his book. ተማሪው ፡ የመጽሐፉን ፡ ገጽ ፡ ገለበጠ
3. ገልብጦ ፡ ሰፋ(ለት). His wife turns the shirt collars when they get frayed. የሸሚዙ ፡ ኮሌታ ፡ ሲነትብ ፡ ሚስቱ ፡ ገልብጣ ፡ ትሰፋለታለች
4. ወለም ፡ አለ(ው). +It's the second time today that I have turned my ankle. ዛሬ ፡ ቁርጭምጭሚቴን ፡ ወለም ፡ ሲለኝ ፡ ይህ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜው ፡ ነው
5. ተረጐመ. Can you turn this passage into Greek? ይህንን ፡ ምንባብ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ለመተርጐም ፡ ትችላለህ ?
6. አበላሸ. The hot weather turned the milk. ሞቃቱ ፡ አየር ፡ ወተቱን ፡ አበላሸው
7. አተረፈ. He turned a thousand dollars on the deal. በንግዱ ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ አተረፈ
8. ሆነ(ው). He has turned fifty. ኀምሳ ፡ ዓመት ፡ ሆነው
*Churning turns the cream to butter. ወተት ፡ ሲናጥ ፡ ቅቤ ፡ ይወጣዋል

**turn** (vi.)
1. ዞረ. Turn to the left! ወደ ፡ ግራ ፡ ዙር
2. (= act.) አዞረ. +My head is turning. ራሴን ፡ አዞረኝ
3. መለስ ፡ አለ. The tide has turned. ሞገዱ ፡ መለስ ፡ ብሏል
4. ታጠፈ. Turn at the first corner above the school! ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ የመጀመሪያ ፡ መታጠፊያ ፡ ታጠፍ
The road turns to the north. መንገዱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ይታጠፋል
5. ተሽከረከረ. The wheels turned. ጎማው ፡ ተሽከረከረ
6. ተጠጋ. The child turned to its mother for comfort. ልጁ ፡ ለመጽናናት ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ ተጠጋ
7. አማከረ. He'd never had difficulty with his child before, and he didn't know to whom to turn. በልጁ ፡ በኩል ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ችግር ፡ ገጥሞት ፡ ስለማያውቅ ፡ አሁን ፡ ለማን ፡ እንደሚያማክር ፡ ግራ ፡ ገባው
8. ኰመጠጠ. The milk has turned. ወተቱ ፡ ኰምጥጧል
*The success of the picnic turns on the weather. የሽርሽሩ ፡ መሳካት ፡ እንዳየሩ ፡ ሁኔታ ፡ ይሆናል

**turn about** ዞረ
After swimming a mile, the boys turned about

and swam back to the shore. አንድ ፡ ማይል ፡ ከዋኙ ፡ በኋላ ፡ ልጆቹ ፡ ዞሩና ፡ ወደ ፡ ዳርቻው ፡ ተመለሱ

**turn against**
1. እንዲጠላ ፡ መከረው. She turned her children against the neighbors. ልጆቿ ፡ ጎረቤቶቻቸውን ፡ እንዲጠሉ ፡ መከረቻቸው
2. ከዳ. He turned against his friends. ጓደኞቹን ፡ ከዳ

**turn around** (vt.) አዞረ
Let's turn the table around! ጠረጴዛውን ፡ እናዙረው

**turn around** (vi.)
1. ዞር ፡ አለ. He turned around and looked at me. ዞር ፡ ብሎ ፡ ተመለከተኝ
2. ወደ ፡ ኋላ ፡ ዞረ. Turn around and see who is following you. ወደ ፡ ኋላ ፡ ዞረህ ፡ የተከተሉህ ፡ እነማን ፡ እንደሆኑ ፡ ተመልከት

**turn (one's) attention** ሐሳቡን ፡ አዋለ
Please turn your attention to something more important! ሐሳብህን ፡ ከዚህ ፡ ለተሻለ ፡ ነገር ፡ አውለው

**turn away** (vt.) መለሰ
They turned away customers since there was not enough merchandise. በቂ ፡ እቃ ፡ ስላልነበራቸው ፡ ደንበኞቻቸውን ፡ መለሱ
*The woman turned away the beggar. ሴትዮዋ ፡ ለማኙን ፡ እግዜር ፡ ይስጥህ ፡ አለችው

**turn away** (vi.) ዞር ፡ አለ
He turned away in disgust. ተከፍቶ ፡ ዞር ፡ አለ
*He turned away from me. ፊቱን ፡ አዞረብኝ

**turn back** ተመለሰ ፤ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመለሰ
Let's turn back! It looks like rain. ሳይዘንብ ፡ አይቀርምና ፡ እንመለስ
Go forward and do not turn back! ወደ ፡ ፊት ፡ ሂድ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አትመለስ

**turn (the) corner** ታጠፈ
The bus turns the corner here. አውቶቡሱ ፡ እዚህ ፡ ሲደርስ ፡ ይታጠፋል

**turn down**
1. ሳይቀበሉት ፡ ቀረ. He tried to enlist in the army, but they turned him down. በጦር ፡ ሰራዊት ፡ ውስጥ ፡ ሊቀጠር ፡ ሞከረ ፤ ግን ፡ ሳይቀበሉት ፡ ቀሩ
2. ቀለበሰ. Turn down your collar; it's sticking up. ኮሌታህን ፡ ቀልብሰው ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ ቆሟል
3. ቀነስ ፡ አደረገ ፤ ቀነሰ. Will you turn down the radio, please? የሬዲዮኑን ፡ ድምፅ ፡ ቀነስ ፡ አድርገው ፡ (ቀንሰው)
4. ቀነሰ. Turn down the lights! መብራቱን ፡ ቀንሰው
5. እምቢ ፡ አለ. When he asked her to marry him, she turned him down. እንድታገባው ፡ ሲጠይቃት ፡ እምቢ ፡ አለችው

**turn downwards** እየቀዘቀዘ ፡ ሄደ
The business level turned downwards. ንግድ ፡ እየቀዘቀዘ ፡ ሄደ

**turn in** (vt.)
1. አቀረበ. He turned in his resignation. የሥራ ፡ መልቀቂያ ፡ ደብዳቤውን ፡ አቀረበ
2. አስረከበ. He gave strict orders to the soldiers to turn in all confiscated rifles. የተወረሱትን ፡ ጠመንጃዎች ፡ እንዲያስረክቡ ፡ ለወታደሮች ፡ ጥብቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ
3. ሰጠ. Turn in your papers! ወረቀታችሁን ፡ ስጡ
4. ለወጠ. I turned in the old car for a new one. አሮጌ ፡ መኪናዬን ፡ ባዲስ ፡ መኪና ፡ ለወጥኩት

**turn in** (vi.)
1. ተኛ. We ought to turn in early tonight. ዛሬ ፡ በጊዜ ፡ መተኛት ፡ አለብን
2. ገባ. Turn in at the garage! ጋራዥ ፡ ውስጥ ፡ ግባ

**(be) turned in**
1. ገባ. The application must be turned in by the 15th. ማመልከቻው ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ መግባት ፡ አለበት
2. ቆልማማ ፡ ነው. His toes are turned in like a pigeon's. የእግሩ ፡ ጣት ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ እግር ፡ ቆልማማ ፡ ነው

**turn in the bed** ተገላበጠ
He couldn't fall asleep and turned in the bed. መተኛት ፡ አቅቶት ፡ ሲገላበጥ ፡ ነበር

**turn inside out**
1. ገለበጠ(በት). The wind turned my umbrella inside out. ነፋሱ ፡ ዣንጥላዬን ፡ ገለበጠብኝ
2. አመሰቃቀለ. The burglars turned everything inside out. ሌቦቹ ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ አመሰቃቀሉት
3. በረበረ. I turned my pockets inside out, but found no key. ኪሴን ፡ ብበረብርም ፡ መክፈቻውን ፡ አላገኘሁትም

**turn into** ሆነ
He turned into a vagabond. ወሮበላ ፡ ሆነ

**turn (one) into** ለወጠ
The witch gave the man a philter which turned him into a frog. አስማተኛዋ ፡ ወደ ፡ እንቁራሪትነት ፡ የሚለውጥ ፡ አስማት ፡ ለሰውዬው ፡ ሰጠችው

**turn off** አጠፋ
Turn off the heat; it is warm outside. ውጭ ፡ ሙቀት ፡ ስለሆነ ፡ ማሞቂያውን ፡ አጥፋው
Turn off the light when you go to bed. ስትተኛ ፡ መብራቱን ፡ አጥፋ

*Is this where we turn off the road to go to the farm? ወደ ፡ እርሻው ፡ ቦታ ፡ ለመሄድ ፡ መገንጠያው ፡ እዚህ ፡ ነው?

**(be) turned off** ጠፋ
The heat is turned off. ማሞቂያው ፡ ጠፍቷል
The electric current has been turned off. ኮረንቲው ፡ ጠፍቷል

**turn on** (vt.) አበራ
Why don't you turn on the light? መብራቱን ፡ ለምን ፡ አታበራውም ?

**turn on** (vi.) በራ
The light is faulty and will not always turn on. መብራቱ ፡ ብልሽት ፡ ስላለበት ፡ ሁልጊዜ ፡ አይበራም

**turn on and off** ብልጭ ፡ ድርግም ፡ አደረገ
He kept turning the lights on and off. መብራቱን ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ ማድረግ ፡ ቀጠለ

**turn out** (vt.)
1. ሠርቶ ፡ አወጣ. The factory turns out five hundred pairs of shoes a day. ፋብሪካው ፡ በቀን ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ጥንድ ፡ ጫማ ፡ ሠርቶ ፡ ያወጣል
2. አወጣ. He turns out a new book every year. በያመቱ ፡ አዲስ ፡ መጽሐፍ ፡ ያወጣል
3. ሠራ. She turns out good cakes. ጥሩ ፡ ኬኮች ፡ ትሠራለች
4. አፈራ. The school turned out some good scholars. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አንዳንድ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ የሆኑ ፡ ዐዋቂዎች ፡ አፍርቷል
5. አጠፋ. Turn out the light before you leave! ከመሄድህ ፡ በፊት ፡ መብራቱን ፡ አጥፋው

**turn out** (vi.)
1. ተገኘ. Things turned out better than I expected. ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ ካሰብኩት ፡ የተሻለ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ
+It turned out that I was right. እኔ ፡ ልክ ፡ ሆኜ ፡ ተገኘሁ
2. ታወቀ. It turned out that the news of the minister's visit was a hoax. የሚኒስትሩ ፡ ጉብኝት ፡ የፈጠራ ፡ ወሬ ፡ መሆኑ ፡ ታወቀ
3. ሆነ. How did the elections turn out? የምርጫው ፡ ውጤት ፡ እንዴት ፡ ሆነ?
4. ከቤቱ ፡ ወጣ ፤ ወጣ. Everyone turned out to watch the parade. ሰልፉን ፡ ለማየት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከየቤቱ ፡ ወጣ
The whole village turned out to combat the fire. መንደሩ ፡ ሁሉ ፡ እሳቱን ፡ ለመከላከል ፡ ወጣ
5. መጣ. Many people turned out for the picnic. ለሽርሽሩ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ መጣ
6. ተሳካ(ለት). Everything turned out the way they wanted it. ሁሉም ፡ ነገር ፡ እንደፈለጉት ፡ ተሳካላቸው
*His toes turn out. እግሩ ፡ ሸፋፋ ፡ ነው

**(be) turned out** አወረዱት
+He was turned out of office by the angry voters. የተናደዱት ፡ መራጮች ፡ ከሥልጣን ፡ አወረዱት

**turn out well** ተሳካ ፤ ተቃና
Contrary to my expectation, the experiment turned out well. እንዳሰብኩት ፡ ሳይሆን ፡ ሙከራው ፡ ተሳካ ፡ (ተቃና)

**turn out worse** ተበላሸሸ
Things turned out worse than I had expected. ነገሩ ፡ እኔ ፡ ካሰብኩት ፡ ተበላሸሸ

**turn over** (vt.)
1. አስተላለፈ. He turned over his business to his son. ንግዱን ፡ ለልጁ ፡ አስተላለፈ
2. አስረከበ. Turn over the equipment to the person who takes your place. መሣሪያውን ፡ ባንተ ፡ ምትክ ፡ ለሚገባው ፡ ሰው ፡ አስረክብ
3. ገለበጠ. I nearly turned over the table. ጠረጴዛውን ፡ ልገለብጠው ፡ ነበር
*He turned over a new leaf. ልብ ፡ ገዛ

**turn over** (vi.) ተገለበጠ ፤ ተገለባበጠ
Our boat almost turned over. ጀልባችን ፡ ሊገለበጥ ፡ ነበር
The tumbler broke his arm when he turned over in the air. ተገለባባጩ ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ ሲገለባበጥ ፡ ክንዱ ፡ ተሰበረ

**(be) turned over** ተረከበ
All weapons have to be turned over to the police. ማንኛውም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ለፖሊስ ፡ መረከብ ፡ አለበት

**turn over in (one's) mind** በጥብቅ ፡ አሰበ(በት)
She turned the question over in her mind. ጥያቄውን ፡ በጥብቅ ፡ አሰበችበት

**turn (one) over on his face** በሆዱ ፡ አስተኛው
Turn him over on his face and rub his back! በሆዱ ፡ አስተኛውና ፡ ጀርባውን ፡ እሸው

**turn to**
1. ሆነ. It was so cold that the water turned to ice. ከብርዱ ፡ የተነሣ ፡ ውኃው ፡ በረዶ ፡ ሆነ
2. ተመለከተ. So much for that; now let's turn to the international situation. ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ እናብቃና ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሁኔታዎችን ፡ እንመለከት
3. ተማጠነ. He turned to God for help. ለእርዳታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተማጠነ
4. አወጣ. Please turn to page ten! ገጽ ፡ ዐሥር ፡ አውጣ

**turn up** (vt.)
1. (= pass.) ተገኘ. +An intensive search turned up the missing key. በጥንቃቄ ፡ ስለተፈለገ ፡ የጠፋው ፡ መክፈቻ ፡ ተገኘ

2. ጠቀለለ. He turned up his sleeves because the air was sticky. አየሩ ፡ ስለሚወብቅ ፡ የሸሚዙን ፡ እጅጌ ፡ ጠቀለለ
3. ወጣ ፡ አደረገ. Turn up the wick of the oil lamp! የፋኖሱን ፡ ክር ፡ ወጣ ፡ አድርገው

**turn up** (vi.)
1. ጥልቅ ፡ አለ. He is always turning up where you don't want him. ሁልጊዜ ፡ ሳይጠየቅ ፡ ጥልቅ ፡ ይላል
2. ተገኘ. Maybe a job will turn up next week. በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ ምናልባት ፡ ሥራ ፡ ይገኝ ፡ ይሆናል

**turn upside down**
1. ገለበጠ. He turned the box upside down. ሣጥኑን ፡ ገለበጠው
2. ደፋቶ ፡ አስቀመጠ. He turned his cup upside down to show he didn't want any more to drink. መጠጥ ፡ ለመጨመር ፡ እንደማይፈልግ ፡ ለመግለጽ ፡ ብርጭቆውን ፡ ደፋቶ ፡ አስቀመጠው
3. በአፉ ፡ ደፋ. Turn the glasses upside down to drain them! ብርጭቆዎቹ ፡ እንዲደርቁ ፡ በአፋቸው ፡ ድፋቸው
4. ምስቅልቅሉን ፡ አወጣ. I turned the whole house upside down. ቤቱን ፡ ምስቅልቅሉን ፡ አወጣሁት

**make turn**
*The wine made his head turn. ወይኑ ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ

**(one's) stomach turns** አንገሸገሸ(ው)
My stomach turns at the thought of it. ገና ፡ ሳስበው ፡ ያንገሸግሸኛል

[See also 'back, deaf, head, heel, ill, leaf, loose, nose, outward, table, tail']

## turn (n.)
1. መጠምዘዣ. There are many turns in this road. ይህ ፡ መንገድ ፡ መጠምዘዣ ፡ ይበዛዋል
2. ጥምዝምዝ. The road is full of abrupt turns. መንገዱ ፡ ድንገተኛ ፡ ጥምዝምዝ ፡ ይበዛበታል
3. መታጠፊያ. Keep your eyes open, or we will miss the turn. እያየህ ፤ አለበለዚያ ፡ መታጠፊያውን ፡ እንስታለን
4. ተራ. Wait your turn in line! በሰልፍ ፡ ሁነህ ፡ ተራህን ፡ ጠብቅ
*The turn of the century was a period of tranquillity. ክፍለ ፡ ዘመኑ ፡ ሲገባ ፡ ጊዜው ፡ የሰላም ፡ ነበር
*Try two turns to the right, and maybe it will open. ወደ ፡ ቀኝ ፡ ሁለቴ ፡ ብታዞረው ፡ ይከፈት ፡ ይሆናል
*A few turns of the handle are needed to open it. እጀታውን ፡ ትንሽ ፡ ካዞርከው ፡ ይከፈታል

**turn of mind** አስተሳሰብ
A scholar has a serious turn of mind. ሊቅ ፡ የጠለቀ ፡ አስተሳሰብ ፡ አለው

**at every turn** በየጊዜው
We encountered difficulties at every turn. በየጊዜው ፡ ችግር ፡ ያጋጥመን ፡ ነበር

**by turns** ተራ ፡ በተራ
They did their shopping and cleaning by turns. መገብየቱንና ፡ ማጽዳቱን ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ ፈጸሙት
*They laughed and cried by turns. አንዴ ፡ ሲሥቁ ፡ አንዴ ፡ ሲያለቅሱ ፡ ነበር

**give (one) quite a turn** አስደነገጠ
You gave me quite a turn, coming up behind me like that. እንደዚያ ፡ ከኋላዬ ፡ ስትመጣ ፡ አስደነገጥከኝ

**good turn** ውለታ
One good turn deserves another. ውለታ ፡ መመለስ ፡ አለበት
He once did me a good turn. አንዴ ፡ ውለታ ፡ ውሎልኛል

**make a turn** ዞረ
Make a left turn at the next corner! በሚቀጥለው ፡ መታጠፊያ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ዙር

**out of turn** ያለ ፡ ተራ
You are talking out of turn. የምትናገረው ፡ ያለ ፡ ተራህ ፡ ነው

**take turns**
1. ተራ ፡ ጠበቀ. Take turns! Don't come all at once! ተራችሁን ፡ ጠብቁ ፤ ሁላችሁም ፡ ባር ፡ ብላችሁ ፡ አትምጡ
2. ተፈራረቀ. When he carries a load, taking turns with his companion will save him from getting tired. ሸክም ፡ ሲሸከም ፡ ከጓደኛው ፡ ጋር ፡ መፈራረቁ ፡ ከድካም ፡ ያድነዋል
*We agreed to take turns in driving. ተራ ፡ በተራ ፡ ለመንዳት ፡ ተስማማን

**take (a) turn for the worse**
My affairs took a turn for the worse. ጉዳዩ ፡ የባሰውን ፡ እየተበላሸ ፡ ሄደ

## turncoat ከዳተኛ
The turncoats did not return to their homeland after the war. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ከዳተኞቹ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ አገራቸው ፡ አልተመለሱም

## turning point አዲስ ፡ መልክ
The crisis has reached a turning point. ችግሩ ፡ አዲስ ፡ መልክ ፡ ይዟል

**be a turning point**
*The invention of the atomic bomb was the turning point in the history of the Second

World War. የአቶሚክ ፡ ቦምብ ፡ መፈልሰፍ ፡ የሁለተኛውን ፡ ያለም ፡ ጦርነት ፡ አቅጣጫ ፡ ለ ዋወጠው

**turnout**
*There was a large turnout for the play. ቲያትሩን ፡ ለማየት ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ ነበር ፡ (ቲያትሩ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ተመልካች ፡ ነበረ)

**turnover**
1. መለዋወጥ. Employers wish to reduce labor turnover. አሠሪዎች ፡ የሠራተኞችን ፡ ሥራ ፡ መለዋ ወጥ ፡ ለመቀነስ ፡ ይመኛሉ
2. ማጣራት. The store reduced prices to make a quick turnover. መደብሩ ፡ ሸቀጡን ፡ ቶሎ ፡ ለማጣራት ፡ የዋጋ ፡ ቅናሽ ፡ አደረገ
*The turnover of guests in this hotel is considerable. እዚህ ፡ ሆቴል ፡ ሂያጁና ፡ ወጪው ፡ ብዙ ፡ ነው

**turpitude** ውድቀት
He was charged with moral turpitude. በግብረ ፡ ገብ ፡ ውድቀት ፡ ተከሶ ፡ ነበር

**turret** የእንቁላል ፡ ግምብ
The castles in Gondar have turrets. የጐንደር ፡ ግምቦች ፡ የእንቁላል ፡ ግምቦች ፡ አሏቸው

**turtle** ኤሊ
A turtle has a hard shell. ኤሊ ፡ ጠንካራ ፡ የድን ጋይ ፡ ልብስ ፡ አላት

**tush** አይ ፡ ዝም ፡ በል
Tush, that's nothing to cry about. አይ ፡ ዝም ፡ በል ! አሁን ፡ ይኼ ፡ ያስለቅሳል ?

**tusk** ጥርስ
Elephants' tusks are precious. የዝሆን ፡ ጥርስ ፡ ውድ ፡ ነው

**tussle** ተጣላ
The two children tussled over the toy. ሁለቱ ፡ ልጆች ፡ ባሻንጉሊቱ ፡ ተጣሉ

**tutelage**
1. ማስተማር. Tutelage of the younger children used to be the mother's responsibility. ትንንሽ ፡ ልጆችን ፡ ማስተማር ፡ የእናቶች ፡ ኀላፊነት ፡ ነበር
2. አደራ. The orphan was placed under the tutelage of his uncle. ወላጆቹ ፡ የሞቱበት ፡ ልጅ ፡ ላጐቱ ፡ አደራ ፡ ተሰጠ

**tutor** (v.) አስተማረ
He is tutoring me in Amharic. አማርኛ ፡ ያስተም ረኛል

**tutor** (n.) አስተማሪ
I have hired a tutor for my son. ለልጄ ፡ አስተ ማሪ ፡ ቀጥሬያለሁ

**twaddle** ለፈለፈ
She twaddles endlessly. ያለማቋረጥ ፡ ትለፈልፋለች

**twang**
*He speaks with a twang. ሲናገር ፡ ይነፋነፋል

**tweed** [ዝንጉርጉር ፡ የሆነ ፡ ከለስላሳ ፡ ሱፍ ፡ የተ ሠራ]

**tweezers** ወረንጦ
Tweezers are used to pull out thorns. ወረንጦ ፡ እሾህ ፡ ለመንቀል ፡ ይጠቅማል

**twelfth** ዐሥራ ፡ ሁለተኛ

**twelve** ዐሥራ ፡ ሁለት
**twelve o'clock** ስድስት ፡ ሰዓት
I will come at twelve o'clock. በስድስት ፡ ሰዓት ፡ እመጣለሁ

**twenty** ሃያ

**twice**
1. ሁለት ፡ ጊዜ ፤ ሁለቴ. I was invited there twice. እዚያ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ (ሁለቴ) ፡ ተጋብዤ ፡ ነበር
2. ደጋግሞ. Think twice before you do it! አንድ ፡ ነገር ፡ ከመሥራትህ ፡ በፊት ፡ ደጋግመህ ፡ አስብ
**twice as long** ዕጥፍ ፡ ጊዜ
That way it will take twice as long. በዚህ ፡ ዓይነ ት ፡ ዕጥፍ ፡ ጊዜ ፡ ይፈጃል
**twice as much** ዕጥፍ
I paid twice as much for this book. ለዚህ ፡ መጽ ሐፍ ፡ ዕጥፍ ፡ ከፈልኩ
[See also 'think']

**twiddle** ተጫወተ
He was twiddling his thumbs when I came in. ስገባ ፡ በጣቱ ፡ ይጫወት ፡ ነበር
**twiddle away** በከንቱ ፡ አሳለፈ
He twiddled away the day. ቀኑን ፡ በከንቱ ፡ አሳ ለፈ

**twig**
1. ቀንበጥ. People chew the twigs of this bush. የዚህ ፡ ቁጥቋጦ ፡ ቀንበጦች ፡ ይታኘካሉ
2. ጭራሮ. They ignited the twigs to warm themselves. እንዲሞቃቸው ፡ ጭራሮውን ፡ አቀ ጣጠሉት

**twilight, at** ~ ደንገዝገዝ ፡ ሲል
Bats come out at twilight. የሌሊት ፡ ወፎች ፡ ደ ንገዝገዝ ፡ ሲል ፡ ከሉበት ፡ ይወጣሉ

**twin** (n.) መንታ
I can't tell those twins apart. እነዚያን ፡ መንታዎች ፡ ልለያቸው ፡ አልችልም

**twin** (adj.) መንታ ፤ መንትያ
He has a twin brother. መንታ ፡ ወንድም ፡ አለው
He is my twin brother. እሱ ፡ መንትያ ፡ ወንድሜ ፡ ነው

**twin-engined** ባለሁለት ፡ ሞተር
He flies a twin-engined plane. ባለሁለት ፡ ሞተር ፡ አውሮፕላን ፡ ይነዳል

**twine** (v.) ተጠመጠመ
The vine twines around the tree. የወይኑ ፡ ሐረግ ፡ በዛፉ ፡ ላይ ፡ ይጠመጠማል

**twine itself** ተጠመጠመ
The snake twined itself around the branch. እባቡ ፡ በቅርንጫፉ ፡ ላይ ፡ ተጠመጠመ

**twine** (n.) ሲባጎ
I need some more twine to tie this package. ይህንን ፡ ጥቅል ፡ ለማሰር ፡ ተጨማሪ ፡ ሲባጎ ፡ ያስፈልገኛል

**twinge**
*When I run, I feel a twinge of pain. ስሮጥ ፡ ውጋት ፡ ይሰማኛል

**twinkle**
1. ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ አለ. The stars twinkle in the night sky. ማታ ፡ ማታ ፡ ኮከቦቹ ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ ይላሉ
2. ተቍለጨለጨ. His eyes twinkled when he told me the joke. ቀልዱን ፡ ሲነግረኝ ፡ ዓይኑ ፡ ይቍለጨለጭ ፡ ነበር

**twirl** (vt.) አሽከረከረ
He twirled a stick in his fingers. ዱላውን ፡ በጣቶቹ ፡ አሽከረከረ

**twirl**, vi. (= vt.) አሽከረከረ
+The leaves twirl in the wind. ቅጠሎቹን ፡ ነፋስ ፡ ያሽከረክራቸዋል

**twist** (vt.)
1. ጠመዘዘ. You're twisting my arm. እጄን ፡ ጠመዘዝከኝ
He twisted the wire until it broke. ሽቦው ፡ እስኪበጠስ ፡ ድረስ ፡ ጠመዘዘው
2. ገመደ. He twisted the straw to make a rope. ማሰሪያ ፡ እንዲሆን ፡ ሣሩን ፡ ገመደው
3. ወሳሰበ(ተወሳሰበ). This silk is badly twisted. ይህ ፡ ሐር ፡ በጣም ፡ ተወሳስቧል
4. አዞረ. She twisted her ring on her finger. ቀለበቷን ፡ በጣቷ ፡ ላይ ፡ አዞረችው
5. (= intr.) ወለም፡ አለ(ው). +He fell and twisted his ankle. ወድቆ ፡ ቁርጭምጭሚቱን ፡ ወለም ፡ አለው
6. አዛባ. The reporter twisted the speaker's words. ጋዜጠኛው ፡ የተናጋሪውን ፡ ቃል ፡ አዛባ

**twist** (vi.)
1. ተጥመለመለ. The road twists up the hill. መንገዱ ፡ እየተጥመለመለ ፡ ኮረብታውን ፡ ይወጣል
2. ዞር ፡ አለ. She twisted in her seat to see what was happening behind her. ከኋላ ፡ ምን ፡ እንደሚደረግ ፡ ለማየት ፡ እንደተቀመጠች ፡ ዞር ፡ አለች

**be twisted** (= vt.) አኰማተረ
His face was twisted with pain. በሕመሙ ፡ ምክንያት ፡ ፊቱን ፡ አኰማተረ

**twist around**
*She twists him around her little finger. እንደልቧ ፡ ትጫወትበታለች

**twist into** ወደ - - - ተረጐመ
He twisted my compliments into an insult. ምስጋናዬን ፡ ወደ ፡ ስድብ ፡ ተረጐመው

**twist out (of)** ነጥቆ ፡ አመለጠ
The thief twisted out of the policeman's grip. ሌባው ፡ ከፖሊስ ፡ እጅ ፡ ነጥቆ ፡ አመለጠ

**twist (one's) way through** ተሽሎክሉኮ ፡ አለፈ
We twisted our way through the crowd. በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ተሽሎክልከን ፡ አለፍን

**twist** (n.) ጠምዛዛ
There are many twists in the road. መንገዱ ፡ ጠምዛዛ ፡ ይበዛዋል
*This is really the same old thing; he's just added a new twist to it. ትንሽ ፡ ለዋወጠው ፡ እንጂ ፡ ይኼ ፡ ያው ፡ የነበረ ፡ ነገር ፡ ነው

**twitch** (vt.)
1. ነሰነሰ. The horse twitched its tail. ፈረሱ ፡ ጭራውን ፡ ነሰነሰ
2. ሰብሰብ ፡ አደረገ. She twitched the curtain aside. መጋረጃውን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ሰብሰብ ፡ አደረገችው

**twitch** (vi.) ተርገበገበ
My eyelid won't stop twitching. የዓይኔ ፡ ክዳን ፡ መርገብገቡን ፡ አላቆም ፡ አለ
The child's mouth twitched as if he were about to cry. ለማልቀስ ፡ እንደፈለገ ፡ ሁሉ ፡ የልጁ ፡ ከንፈር ፡ ተርገበገበ

**twitch impatiently** ተቍነጠነጠ
She twitched impatiently in her chair. ወንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቍነጠነጠች

**twitter** ተንጫጫ
The birds twitter beneath my window in the morning. ወፎቹ ፡ ጢ.ት ፡ ጢ.ት ፡ መስኮቴ ፡ ሥር ፡ ይንጫጫሉ

**two** ሁለት
I have two books. ሁለት ፡ መጽሐፍ ፡ አለኝ
**two o'clock** ስምንት ፡ ሰዓት
I will come at two o'clock. በስምንት ፡ ሰዓት ፡ እመጣለሁ
**by twos** ሁለት ፡ እየሆኑ
The guests came by twos and threes. እንግዶቹ ፡ ሁለትና ፡ ሦስት ፡ እየሆኑ ፡ መጡ
**in twos** በሁለት
The children lined up in twos. ልጆቹ ፡ በሁለት ፡ ተሰለፉ
[See also 'kind, thing']

**two-edged** ባለሁለት ፡ ስለት
I bought a two-edged knife yesterday. ባለሁለት ፡ ስለት ፡ ቢላዋ ፡ ትላንትና ፡ ገዛሁ
*Trickery is a two-edged sword. ሰውን ፡ አታሎ ፡ በስፈሩት ፡ ቁና ፡ መስፈር ፡ አይቀርም

**two-faced** አስስት
She is two-faced, and I don't like her. እስስት ፡ ስለሆነች ፡ አልወዳትም

**twofold**, adj. (= adv.) ሁለት ፡ እጅ
He got a twofold return on his investment. በንግዱ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ አተረፈ
**twofold** (adv.) ዕጥፍ ፡ ሆኖ
He got his money back twofold. ገንዘቡ ፡ ዕጥፍ ፡ ሆኖ ፡ ተመለሰለት

**type** (v.) በመኪና ፡ ጻፈ
Will you type these letters for me, please? እነዚህን ፡ ደብዳቤዎች ፡ በመኪና ፡ ትጽፍልኝ ?

**type** (n.)
1. ዓይነት. What type of shoe do you wear? ምን ፡ ዓይነት ፡ ጫማ ፡ ነው ፡ የምታደርገው ?
He is not my type; I prefer educated people. ለኔ ፡ የሚስማማኝ ፡ ዓይነት ፡ አይደለም ፤ እኔ ፡ የምመርጠው ፡ የተማሩ ፡ ሰዎችን ፡ ነው
2. ምሳሌ. The Greek temple has been the type for many public buildings. የግሪክ ፡ መቅደስ ፡ ለብዙ ፡ የሕዝብ ፡ ሕንጻዎች ፡ እንደ ፡ ምሳሌ ፡ ሆኖ ፡ ነበር
3. ፊደሎች. The type is too small to read. ፊደሎቹ ፡ በጣም ፡ ትናንሽ ፡ ስለሆኑ ፡ ለማንበብ ፡ ያስቸግራሉ

**of this type** እንዲህ ፡ ያለ
A man of this type cannot be trusted. እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ እምነት ፡ ሊጣልበት ፡ አይችልም

**typewriter** የጽሕፈት ፡ መኪና
The typewriter is broken. የጽሕፈት ፡ መኪናው ፡ ተሰብሯል

**typhoid** ተስቦ
Typhoid is a dangerous disease. ተስቦ ፡ በጣም ፡ አደገኛ ፡ በሽታ ፡ ነው

**typhoon** ኀይለኛ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ
Many people died in the typhoon. በኀይለኛ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሞቱ

**typhus** ተስቦ
Typhus is caused by body lice. ተስቦ ፡ የሚመጣው ፡ ከሰውነት ፡ ቅማል ፡ ነው

**typical**
1. ዓይነተኛ. This is a typical example. ይህ ፡ ዓይነተኛ ፡ ምሳሌ ፡ ነው
2. የተለመደ. He gave one of his typical answers. የተለመደ ፡ መልሱን ፡ ሰጠ

**typify** (typified) ምሳሌ ፡ ነው
The Statue of Liberty typifies freedom. የነጻነት ፡ ሐውልት ፡ የነጻነት ፡ ምሳሌ ፡ ነው

**typing** በመኪና ፡ መጻፍ
Typing is a skill that requires practice. በመኪና ፡ መጻፍ ፡ ልምምድ ፡ የሚጠይቅ ፡ ሙያ ፡ ነው

**typist** ታይፒስት
The typist did not come to work today. ታይፒስቷ ፡ ዛሬ ፡ ሥራ ፡ አልገባችም

**typography** እትም
Typography makes the printed page more attractive. እትም ፡ ጽሑፉን ፡ የያዘው ፡ ገጽ ፡ በይበልጥ ፡ ያሳምራል

**tyrannical** ጨካኝ
He is a tyrannical boss. ጨካኝ ፡ አለቃ ፡ ነው

**tyrannize** በጣም ፡ ጨቈነ
The father tyrannizes his children. አባትዬው ፡ ልጆቹን ፡ በጣም ፡ ይጨቊናቸዋል

**tyranny** የጭቈና ፡ አገዛዝ
The dictator's tyranny sparked the revolt. የአምባገነኑ ፡ የጭቈና ፡ አገዛዝ ፡ ለዐመፁ ፡ ምክንያት ፡ ሆነ

**tyrant** አምባገነን
The tyrant was murdered by his servant. አምባገነኑን ፡ የገዛ ፡ አሽከሩ ፡ ገደለው

## U

**udder** ግት
The cow's udder secretes milk. የላም ፡ ግት ፡ ወተት ፡ ይወጣዋል

**ugly**
1. መልከ ፡ ክፉ. He is certainly an ugly beggar. በእውነት ፡ ይህ ፡ መልከ ፡ ክፉ ፡ ለማኝ ፡ ነው
2. አስቀያሚ. That's an ugly picture. ያ ፡ ሥዕል ፡ አስቀያሚ ፡ ነው
3. የሚያሰጋ. The wound looked sore and ugly. ቁስሉ ፡ የበሰበሰና ፡ የሚያሰጋ ፡ መስሎ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**be ugly** አስቀየመ
Telegraph wires over the streets are ugly. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ የቴሌግራም ፡ ገመዶች ፡ ያስቀይማሉ

**ulcer**
1. የቆላ ፡ ቁስል. I have an ulcer on my leg. እግሬን ፡ የቆላ ፡ ቁስል ፡ ይዞኛል
2. አልሰር. The doctor cured him of his stomach ulcer. ሐኪሙ ፡ የሆዱን ፡ አልሰር ፡ አዳነለት

**ulterior** የተሰወረ
He did it, not for friendship, but for some ulterior motive. ያደረገው ፡ ለወዳጅነት ፡ ሳይሆን ፡ ለተሰወረ ፡ ዓላማ ፡ ነው

**ultimate**, n. (= adj.) የመጨረሻ
This is the ultimate in stupidity. ይህ ፡ የመጨረሻው ፡ ጅልነት ፡ ነው

**ultimate** (adj.) የመጨረሻ
The ultimate limits of space are almost too remote to be imagined. የጠፈር ፡ የመጨረሻ ፡ ወሰን ፡ በጣም ፡ሩቅ ፡ ስለሆነ ፡ ለመገመት ፡ አይቻልም
His ultimate goal is to be a doctor. የመጨረሻ ፡ ዓላማው ፡ ሐኪም ፡ ለመሆን ፡ ነው
*The river reached its ultimate level at noon. ወንዙ ፡ ቀትር ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ አፍ ፡ ገደፉ ፡ ሞላ

**ultimately** ውሎ ፡ አድሮ
This will ultimately be a beautiful town. ውሎ ፡ አድሮ ፡ ይህ ፡ ከተማ ፡ ውብ ፡ ይሆናል

**ultimatum** የመጨረሻ ፡ ማስጠንቀቂያ
The government issued an ultimatum. መንግሥቱ ፡ የመጨረሻ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሰጠ

**ultra** (n.) ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ አስተሳሰብ ፡ ያለው
The ultras were all for beginning the war at once. ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ አስተሳሰብ ፡ ያላቸው ፡ ሁሉ ፡ ጦርነቱ ፡ አሁኑኑ ፡ እንዲጀመር ፡ ይፈልጋሉ

**ultramodern** እጅግ ፡ ዘመናዊ
This is an ultramodern structure. ይህ ፡ እጅግ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕንጻ ፡ ነው

**ululation** እልልታ
When the king came, the women welcomed him with ululations. ንጉሡ ፡ ሲመጡ ፡ ሴቶቹ ፡ በእልልታ ፡ ተቀበሏቸው

**umbilical cord** እትብት
The newborn baby's umbilical cord is cut and tied off. ገና ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ እትብቱ ፡ ተቈርጦ ፡ ተቋጠረ

**umbrage, take ~ in** አስቀየመ
+He took umbrage at the person's remark. ሰውዬው ፡ የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ አስቀየመው

**umbrella** ዣንጥላ ፤ ጃንጥላ
Where's my umbrella? It's raining. ዣንጥላዬ ፡ ዬት ፡ ነው ? ይዘንባል

**umpire** ዳኛ
The umpire eliminated a player. ዳኛው ፡ አንዱን ፡ ተጫዋች ፡ ከሜዳው ፡ ውስጥ ፡ አስወጣው

**(be) unabashed** አላፈረም
He was unabashed by defeat and continued to fight. በመሸነፉ ፡ ሳያፍር ፡ መዋጋቱን ፡ ቀጠለ

**unabated** ሳያቋርጥ
The storm raged on unabated. ኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ነፈሰ

**(be) unable** አልቻለም
I am unable to give you that information. ያንን ፡ መግለጫ ፡ ልሰጥህ ፡ አልችልም

**unabridged** ያላጠረ
The unabridged version of the book is much longer. ያላጠረው ፡ የመጽሐፉ ፡ እትም ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ነው

**(be) unacceptable** ተቀባይነት ፡ የለውም
Flagrant spelling errors are unacceptable.

ጉልህ ፣ የሆነ ፣ የቀለማት ፣ ስሕተት ፣ ተቀባይነት ፣ የለውም

**unaccompanied (by)** ሳያስከትል
The official arrived unaccompanied by his advisers. አለቃቸው ፣ አማካሪዎቹን ፣ ሳያስከትል ፣ መጣ

**(be) unaccountable**
1. ምንም ፣ ምክንያት ፣ አይኖረውም. His delay is unaccountable. ለመዘግየቱ ፣ ምንም ፣ ምክንያት ፣ አይኖረውም
2. አይጠየቅበትም. The poor fellow is unaccountable for his acts. ምስኪኑ ፣ ለድርጊቱ ፣ አይ ጠየቅበትም

**(be) unaccustomed** አለመደም
I am unaccustomed to public speaking. ሕዝብ ፣ ፊት ፣ ቆሞ ፣ ንግግር ፣ ማድረግ ፣ አለመ ድኩም

**(be) unaffected** (= act.) አልነካውም
+The Western world was unaffected by the change. የምዕብራብን ፣ ሀገሮች ፣ ለውጡ ፣ አልነ ካቸውም

**unanimity** ሙሉ ፣ ስምምነት
Unanimity was reached on the decision to expel South Africa. ደቡብ ፣ አፍሪካን ፣ ከስብሰ ባው ፣ ለማስወጣት ፣ ሙሉ ፣ ስምምነት ፣ ተደረገ

**unanimous** ሙሉ
The assembly is in unanimous agreement on the question of taxes. ጉባኤው ፣ በግብር ፣ ጉዳ ይ ፣ ላይ ፣ ሙሉ ፣ ስምምነት ፣ አድርጓል

**be unanimous** ባንድ ፣ ድምፅ ፣ ነው ፤ ባንድ ፣ ድ ምፅ ፣ ተደገፈ
They were unanimous in their decision. ውሳኔ ፣ የሰጡት ፣ ባንድ ፣ ድምፅ ፣ ነው
The concurrence of the committee was unanimous. የደርጉ ፣ ስምምነት ፣ በሙሉ ፣ ባንድ ፣ ድምፅ ፣ የተደገፈ ፣ ነበር

**unanimously** ባንድ ፣ ድምፅ ፤ በሙሉ ፣ ድምፅ
He was elected unanimously. ባንድ ፣ ድምፅ ፣ ተመረጠ
The resolution was adopted unanimously. ውሳኔው ፣ በሙሉ ፣ ድምፅ ፣ ተደገፈ

**unannounced**
*He arrived unannounced. እመጣለሁ ፣ ሳይል ፣ መጣ

**unarmed** መሣሪያ ፣ ያልያዘ
The cold-blooded criminal killed an unarmed man. አረመኔው ፣ ወንጀለኛ ፣ መሣሪያ ፣ ያልያዘ ፣ ሰው ፣ ገደለ

**unassuming**
He has an unassuming manner. ትሑት ፣ ነው

**unattended** ብቻዋን
His wife went to the concert unattended. ሚስቱ ፣ ወደ ፣ ኮንሰርቱ ፣ ብቻዋን ፣ ሄደች

**unavoidable** የማይቀር
The mistake was unavoidable. ስሕተቱ ፣ የማይ ቀር ፣ ነበር

**(be) unaware of** አልተገነዘበም
He is unaware of his failings. ጉድለቱን ፣ አይገነ ዘብም

**(be) unbalanced** ትክክል ፣ አልነበረም
The scales were unbalanced. ሚዛኑ ፣ ትክክል ፣ አልነበረም

**mentally unbalanced** ወፈፌ
He is mentally unbalanced, so they sent him to the hospital. ወፈፌ ፣ ስለሆነ ፣ ወደ ፣ ሐኪም ፣ ቤት ፣ ላኩት

**(be) unbearable** የሚቻል ፣ አይደለም ፤ የማይ ቻል ፣ ነው
The pain is unbearable. ሥቃዩ ፣ የሚቻል ፣ አይደለም
The severity of the pain is unbearable. የሕመሙ ፣ ክባድነት ፣ የማይቻል ፣ ነው

**(be) unbecoming**
1. ተገቢ ፣ አይደለም. His behavior is unbecoming for a man in his position. የሱ ፣ ምግባር ፣ በሱ ፣ ደረጃ ፣ ላለ ፣ ሰው ፣ ተገቢ ፣ አይደለም
2. አልተስማማም. Your clothes are unbecoming; they don't make you look good. ልብሱ ፣ አልተ ስማማህም ፤ ቁመናህን ፣ አላሳመረውም

**unbelief** መጠራጠር
Unbelief was clearly written on his face. መጠራጠሩ ፣ በፊቱ ፣ ላይ ፣ በግልጽ ፣ ይነበብ ፣ ነበር

**unbelievable**
1. ለማመን ፣ ያማያስቸግር. He told me an unbelievable story. ለማመን ፣ የሚያስቸግር ፣ ተረት ፣ አጫወተኝ
2. በጣም ፣ ጸያፍ. The invaders showed unbelievable license. ወራሪዎቹ ፣ በጣም ፣ ጸያፍ ፣ የሆነ ፣ ምግባር ፣ አሳዩ

**unbeliever** አረመኔ
The unbelievers were forcibly converted to Christianity. አረመኔዎቹ ፣ ክርስትና ፣ በግዴታ ፣ ተቀበሉ

**unbend** (unbent), vt. አቀና
He unbent the iron rod with his hand. የጉበጠውን ፡ የብረት ፡ ዘንግ ፡ በእጁ ፡ አቀና

**unbend** (vi.) ፈታ ፡ አለ
The judge unbent a little and smiled when the lawyer told a funny joke. ዳኛው ፡ ፈታ ፡ ብለው ፡ ጠበቃው ፡ በተናገረው ፡ ቀልድ ፡ ፈገግ ፡ አሉ

**unbending** ግትር
His unbending attitude discourages us from asking him again. ግትር ፡ ሐሳቡ ፡ ዳግመኛ ፡ እንዳንጠይቀው ፡ ያደርገናል

**unbent,** see **unbend**

**(be) unbiased** አድሎ ፡ የለበትም
His judgment is unbiased. ፍርዱ ፡ አድሎ ፡ የለበትም

**unborn** ወደፊት ፡ የሚመጣ
Generations yet unborn will hear of him. ወደፊት ፡ የሚመጣ ፡ ትውልድ ፡ ስለሱ ፡ ይሰማል

**unbroken**
1. (= adv.) ሳይሰበር. Fortunately, I found my glasses unbroken. ደግነቱ ፡ መነጽሬን ፡ ሳይሰበር ፡ አገኘሁት
2. (= adv.) ሳያቋርጥ. They did eight hours of unbroken driving. ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ሳያቋርጡ ፡ በመኪና ፡ ተጓዙ

**unburden, ~ oneself**
He unburdened himself to me. ችግሩን ፡ አዋየኝ

**(be) uncalled, ~ for** ተገቢ ፡ አይደለም ፤ ምክንያት ፡ የለውም
Your behavior is uncalled for. ጠባይህ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም
Your rudeness is uncalled for. ብልግናህ ፡ ምክንያት ፡ የሌለው ፡ ነው

**uncanny**
1. በጣም ፡ ረቂቅ. He has an uncanny sense of hearing. በጣም ፡ ረቂቅ ፡ የሆነ ፡ የመስማት ፡ ችሎታ ፡ አለው
2. እንግዳ. The empty house had an uncanny look. ወናው ፡ ቤት ፡ እንግዳ ፡ የሆነ ፡ መልክ ፡ ነበረው

**unceasing** የማያቋርጥ
The patriots' unceasing efforts were eventually rewarded. ያርበኞቹ ፡ የማያቋርጥ ፡ ድካም ፡ በመጨረሻ ፡ ዋጋ ፡ አገኘ

**uncertain** የማይታወቅ
This man has an uncertain temper. ሰውዬው ፡ የማይታወቅ ፡ ጠባይ ፡ አለው
*She's a lady of uncertain age. ዕድሜዋን ፡ ማወቅ ፡ ያስቸግራል

**be uncertain**
1. አላስተማመነም. The weather is uncertain. ያየሩ ፡ ሁኔታ ፡ አያስተማምንም
2. አልተረጋገጠም. His trip is still uncertain. የጉዞው ፡ ነገር ፡ ገና ፡ አልተረጋገጠም

**feel uncertain** አወላወለ
I felt uncertain whether I should call him. ልደውልለት ፡ አልደውልለት ፡ በማለት ፡ አወላወልኩ

**look uncertain** ግራ ፡ የገባው ፡ መሰለ
He looked uncertain as to what to do. ምን ፡ እንደሚሠራ ፡ ግራ ፡ የገባው ፡ መሰለ

**uncertainty** የማያስተማምን ፡ መሆን
The uncertainty of my position worries me. የሥራዬ ፡ ነገር ፡ የማያስተማምን ፡ መሆኑ ፡ ያሳስበኛል

**unchallenged** ተቃዋሚ ፡ የሌለበት
He is the unchallenged leader of the movement. እሱ ፡ ተቃዋሚ ፡ የሌለበት ፡ የንቅናቄው ፡ መሪ ፡ ነው

**unchangeable** የማይለወጥ
His honesty is unchangeable. ታማኝነቱ ፡ የማይለወጥ ፡ ነው

**(be) unchecked** አልተቈጣጠሩት
If the epidemic is unchecked, thousands more will be affected. በሽታውን ፡ ካልተቈጣጠሩት ፡ ሌሎች ፡ በሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ይታመማሉ

**uncircumcized** ያልተገረዘ
The uncircumcized are not allowed to participate in the ceremony. ያልተገረዙ ፡ የሥርዓቱ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆኑ ፡ አይፈቀድላቸውም

**uncivil** ብልግና ፡ የተመላበት
His uncivil letter was offensive. ብልግና ፡ የተመላበት ፡ ደብዳቤው ፡ አጸያፊ ፡ ነበር

**(be) uncivilized** ያልሠለጠነ ፡ ነው
He was offended when he called him "uncivilized". ያልሠለጠንክ ፡ ነህ ፡ ብሎ ፡ ስለሰደበው ፡ ተቀየመ

**uncle** አጎት
My uncle died before my father did. አጎቴ ፡ ካባቴ ፡ በፊት ፡ ሞተ

**unclean**
1. ቆሻሻ. He worked for a time, and his hands became unclean. ቢሠራ ፡ ቆይቶ ፡ እጁ ፡ ቆሻሻ ፡ ብቻ ፡ ሆኗል

2. ርኩስ. According to certain religions, pig's meat is unclean. አንዳንድ ፡ ሃይማኖቶች ፡ ያሳማ ፡ ሥጋ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ ይላሉ

**unclean conditions** የንጽሕና ፡ ጉድለት
The town boycotted the store because of the unclean conditions. ስለ ፡ መደብሩ ፡ ንጽሕና ፡ ጉድለት ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ ከመደብሩ፡ ላይገዛ ፡ ተስማማ

**uncomfortable** የማይመች
I had to sit in an uncomfortable position on the bus. ባውቶቡሱ ፡ ላይ ፡ በማይመች ፡ አኳኋን ፡ መቀመጥ ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ

**be uncomfortable** ምቹ ፡ አይደለም
That's an uncomfortable chair. ይህ ፡ ወንበር ፡ ምቹ ፡ አይደለም

**feel uncomfortable** አልተዝናናም
I feel uncomfortable when I talk to the general. ከጄኔራሉ ፡ ጋር ፡ ስነጋገር ፡ አልዝናናም

**make uncomfortable** አንገጫገጨ
The bumpy car ride made the passengers uncomfortable. ምቾት ፡ የሌለው ፡ የመኪና ፡ ጉዞ ፡ ተሳፋሪዎችን ፡ አንገጫገጫቸው

**(be) uncommitted** ማንን ፡ እንደሚደግፍ ፡ አልገለጸም
He is still uncommitted, so both parties are vying for his support. እሱ ፡ ገና ፡ ማንን ፡ እንደሚደግፍ ፡ ስላልገለጸ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ የሱን ፡ ድጋፍ ፡ ለማግኘት ፡ ይጥራሉ

**uncommon** ታይቶ ፡ የማይታወቅ
His uncommon intelligence is considered miraculous. ታይቶ ፡ የማይታወቅ ፡ ብልህነቱ ፡ እንደ ፡ ተአምር ፡ ተቈጠረ

**be uncommon** አይገኝም
His kind of intelligence is uncommon. እንደሱ ፡ ያለ ፡ ብልህ ፡ አይገኝም

**uncompromising**
He is of uncompromising honesty. ታማኝነቱ ፡ አያወላውልም

**unconcern** ግዴለሽነት
He was worried about his son's unconcern for school. የልጁ ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ግዴለሽነት ፡ አሳስቦት ፡ ነበር

**(be) unconcerned** ግድ ፡ የለውም
He is quite unconcerned about the war. ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ ምንም ፡ ግድ ፡ የለውም

**unconditional** (= adv.) ያለ ፡ ገደብ
They asked unconditional surrender of their enemy. ጠላቶቻቸው ፡ ያለ ፡ ገደብ ፡ እጃቸውን ፡ እንዲሰጡ ፡ ጠየቁ

**unconscious** ነፍሱን ፡ ስቶ
He lay unconscious on the ground. ነፍሱን ፡ ስቶ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ተዘረረ

**be unconscious** ነፍሱን ፡ ሳተ
He is still unconscious from a blow on the head. ራሱን ፡ ስለተመታ ፡ አሁንም ፡ ነፍሱን ፡ እንደሳተ ፡ ነው

**be unconscious of** አላስተዋለውም
He was unconscious of the real danger. እርግጠኛውን ፡ አደጋ ፡ አላስተዋለውም

**knock (one) unconscious** ነፍሱን ፡ እንዲስት ፡ አደረገው
A hard blow on the chin knocked him unconscious. አገጩ ፡ ላይ ፡ የተመታው ፡ ጠንካራ ፡ ምት ፡ ነፍሱን ፡ እንዲስት ፡ አደረገው

**unconsciously** ባለማወቅ
Everything that is done unconsciously is pardoned. ባለማወቅ ፡ የሚደረግ ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ይደረግለታል

**unconsciousness, relapse into ~** እንደገና ፡ ራሱን ፡ ሳተ
He relapsed into unconsciousness after reaching the hospital. ሆስፒታል ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ራሱን ፡ ሳተ

**unconstitutional** ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ የሚፃረር
The unconstitutional law was abrogated by the Supreme Court. ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ የሚፃረረው ፡ ሕግ ፡ በጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተሻረ

**uncontrollable**
*He had an uncontrollable impulse to laugh. ሣቁን ፡ መግታት ፡ አልቻለም

**uncouth** ስድ
He is very uncouth. Has no one taught him manners? በጣም ፡ ስድ ፡ ነው ፤ ማንም ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አላስተማረው ?

**uncover** (vt.)
1. ሽፋን ፡ አነሣ. She uncovered the dish. የሳሕኑን ፡ ሽፋን ፡ አነሣችው
2. ገለጠ. The mother uncovered the sleeping baby. እናቲቱ ፡ የተኛውን ፡ ሕፃን ፡ ገለጠችው
3. ደረሰ(በት). The police uncovered a plot. ፖሊሶች ፡ አድማውን ፡ ደረሱበት
4. አጋለጠ. The inquisition uncovered many heresies. ምርመራው ፡ ብዙ ፡ መናፍቃንን ፡ አጋለጠ

**uncover** (vi.) ባርኔጣውን ፡ አነሣ
Everybody uncovered for the passing funeral. ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለሚጓዘው ፡ ሬሳ ፡ ባርኔጣቸውን ፡ አነሡ

**uncover (one's) head** ባርኔጣውን ፡ አነሣ
The man uncovered his head as the flag passed by. ሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ በሰልፍ ፡ ሲያልፍ ፡ ሰውዬው ፡ ባርኔጣውን ፡ አነሣ

**unction** ቅብአ ፡ ቅዱስ
Unction was given by the priest to the dying person. ቄሱ ፡ ለሚያጣጥረው ፡ ሰውዬ ፡ ቅብአ ፡ ቅዱስ ፡ አደረገለት
*The man spoke with unction. ሰውዬው ፡ የሚናገረው ፡ አለዝቦ ፡ ነው

**unctuous, ~ manner** ካንገት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ለስላሳ ፡ ሁኔታ
His unctuous manner failed to dispel her suspicions. ካንገት ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ ለስላሳ ፡ ሁኔታው ፡ ጥርጣሬዋን ፡ ለማስወገድ ፡ ሳይችል ፡ ቀረ

**uncultivated** ያልታረሰ
Most of the province is uncultivated land. አብዛኛው ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ክፍል ፡ ያልታረሰ ፡ መሬት ፡ ነው

**(be) undaunted** ተስፋ ፡ አልቈረጠም
He is undaunted by failure and will open a new store. በመክሰሩ ፡ ተስፋ ፡ ሳይቈርጥ ፡ አዲስ ፡ ሱቅ ፡ ይከፍታል

**(be) undecided** አልተወሰነም
The question of moving to the country is still undecided. ወደ ፡ ገጠር ፡ የመዛወሩ ፡ ጉዳይ ፡ ገና ፡ አልተወሰነም

**undefined** ያልተከለለ
Undefined borders give rise to quarrels. ያልተከለሉ ፡ ወሰኖች ፡ ጠብ ፡ ያስነሣሉ

**undeniable** የማይካድ
The fact is undeniable; this stone is a diamond. ይህ ፡ ድንጋይ ፡ ዕንቍ ፡ መሆኑ ፡ የማይካድ ፡ ነገር ፡ ነው

**undeniably** ያለምንም ፡ ጥርጥር
He is undeniably clever. ያለምንም ፡ ጥርጥር ፡ ጐበዝ ፡ ነው

**under**
1. ከ - - - ሥር. I wore a sweater under my coat. ከኮቴ ፡ ሥር ፡ ሹራብ ፡ ለብሼያለሁ
This baggage should be placed under your seat. ይህ ፡ እቃ ፡ ከወንበርዎ ፡ ሥር ፡ መቀመጥ ፡ ይገባዋል
2. ከሥር. Put the book under it! መጽሐፉን ፡ ከሥሩ ፡ አድርገው
3. በ - - - ሥር. Slip the letter under the door! ደብዳቤውን ፡ በመዝጊያ ፡ ሥር ፡ አሾልከው
4. ከ - - - በታች. No one under the rank of captain was there. ማዕርጋቸው ፡ ከሻምበል ፡ በታች ፡ የሆኑ ፡ እዚያ ፡ አልነበሩም
Children under fifteen are not admitted. ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ ለሆኑ ፡ ሕፃናት ፡ አይፈቀድም
5. ከ - - - ባነሰ ፡ ጊዜ. Run 100 meters in under ten seconds! መቶውን ፡ ሜትር ፡ ካሥር ፡ ሰኮንድ ፡ ባነሰ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሩጥ
6. በ - - - መሠረት. Under the new law, taxes will be higher. ባዲሱ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ግብር ፡ ተጨምሯል
7. ላይ. Are you under medical treatment? ሕክምና ፡ ላይ ፡ ነህ ?
8. በ - - - ጊዜ. England under Queen Elizabeth was a prosperous country. እንግሊዝ ፡ በንግሥት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ጊዜ ፡ ሀብታም ፡ አገር ፡ ነበረች
*The book will cost under ten dollars. የመጽሐፉ ፡ ዋጋ ፡ ከዐሥር ፡ ብር ፡ ያንሳል
*He lives under an assumed name. የሚጠራው ፡ በሌላ ፡ ስም ፡ ነው
*He learned under good teachers. ጥሩ ፡ መምህራን ፡ ነበሩት
*You are under oath when you testify in court. ፍርድ ፡ ቤት ፡ የምስክርነት ፡ ቃልህን ፡ ስትሰጥ ፡ መሐላ ፡ ገብተህ ፡ ነው
*The bridge is still under water. ድልድዩ ፡ አሁንም ፡ ውኃ ፡ እንደለበሰ ፡ ነው
*The question under discussion cannot be solved soon. ውይይት ፡ የሚደረግበት ፡ ጉዳይ ፡ በቶሎ ፡ መፍትሔ ፡ አያገኝም
*He has several acres under cotton. ጥጥ ፡ የተዘራ ፡ ብዙ ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ አለው
*The same business is operating under a new name. ያው ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ስሙን ፡ ለውጦ ፡ ይሠራል

**from under** ከሥር
The chair slipped out from under him. ወንበሩ ፡ ከሥሩ ፡ ተንሸራተተ
[See also 'circumstance, obligation']

**(be) underage** ከተገቢ ፡ ዕድሜ ፡ በታች ፡ ሆነ
If you are underage you cannot vote. ከተገቢ ፡ ዕድሜ ፡ በታች ፡ ከሆንክ ፡ ድምፅ ፡ ልትሰጥ ፡ አትችልም

**underbrush** ጢሻ ፤ ቁጥቋጦ
The underbrush caught fire. ጢሻው ፡ (ቁጥቋጦው) ፡ ተያያዘ

**underclothes** የውስጥ ፡ ልብስ
Underclothes protect you from cold. የውስጥ ፡ ልብስ ፡ ከብርድ ፡ ይከላከላል

**undercover agent** ነጭ ፡ ለባሽ
The undercover agent was killed. ነጭ ፡ ለባሹ ፡ ተገደለ

**undercurrent** ሞገድ
This ocean has a strong undercurrent. ይህ ፡ ውቅያኖስ ፡ ኀይለኛ ፡ ሞገድ ፡ አለው

**undercurrent of** የተዳፈነ
There is an undercurrent of tension in our office. በመሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ ውስጥ ፡ የተዳፈነ ፡ ቅሬታ ፡ አለ

**undercut**
1. ሰበረ(በት). This store is undercutting our prices. ይህ ፡ መደብር ፡ ዋጋችንን ፡ ይሰብርብናል
2. አጐደፈ. He undercut his superior's position by showing up many of his faults. ብዙ ፡ ስሕተቶቹን ፡ በመግለጽ ፡ ያለቃውን ፡ ክብር ፡ አጐደፈ

**(be) underdeveloped** በልማት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀረ
The country is underdeveloped because it has few factories. አገሪቷ ፡ በልማት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርታለች ፤ ምክንያቱም ፡ ያሏት ፡ ፋብሪካዎች ፡ ጥቂት ፡ ስለሆኑ ፡ ነው

**underdog** ይሸነፋል ፡ የሚባል
He is the underdog in this contest. በዚህ ፡ ውድድር ፡ ላይ ፡ ይሸነፋል ፡ የሚባለው ፡ እሱ ፡ ነው

**(be) underdone** በደንብ ፡ አልበሰለም
The meat is underdone. ሥጋው ፡ በደንብ ፡ አልበሰለም

**underestimate** ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ገመተ
Don't underestimate him because he acts sort of stupid. ሞኝ ፡ ቢመስልህም ፡ እንኳ ፡ ዝቅ ፡ አድርገህ ፡ አትገምተው

**underfoot**
*The ground sinks underfoot. መሬቱ ፡ ሲረግጡት ፡ ይሰምጣል

**be underfoot** ዕንቅፋት ፡ ነው
The child is underfoot; get him out of here! ልጁ ፡ ዕንቅፋት ፡ ነውና ፡ ወዲያ ፡ ውሰደው

**undergo** (underwent)
1. ተደረገ(ለት). We underwent a thorough medical examination. ዝርዝር ፡ የጤንነት ፡ ምርመራ ፡ ተደረገልን
2. ደረሰ (በት). He underwent many hardships while he was in the army. ጦር ፡ ሰራዊት ፡ ውስጥ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ደረሰበት
[See also 'change']

**undergraduate** የኮሌጅን ፡ ትምህርት ፡ ያልጨረሰ ፡ ተማሪ
The undergraduates serve one year as teachers. የኮሌጅን ፡ ትምህርት ፡ ያልጨረሱ ፡ ተማሪዎች ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በመምህርነት ፡ ያገለግላሉ

**underground** (adj.)
1. በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ የሚሄድ. An underground passage connects the two buildings. ሁለቱ ፡ ሕንጻዎች ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ በሚሄድ ፡ መንገድ ፡ ተጋጥመዋል
2. ከመሬት ፡ በታች ፡ ያለ. The ammunition is stored in an underground magazine. ጥይቱ ፡ የተከማቸው ፡ ባንድ ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ባለ ፡ መጋዘን ፡ ውስጥ ፡ ነው
3. በድብቅ ፡ የሚሠራ ፤ ምስጢራዊ. The underground movement is divided into cells. በድብቅ ፡ የሚሠራው ፡ እንቅስቃሴ ፡ በቡድን ፡ የተከፋፈለ ፡ ነው
In Algeria, the underground revolt quickly succeeded in capturing all important installations. አልጄሪያ ፡ ውስጥ ፡ ምስጢራዊው ፡ እንቅስቃሴ ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ድርጅቶች ፡ በቶሎ ፡ ለመያዝ ፡ ቻለ

**underground** (adv.) በድብቅ
The spies worked underground. ሰላዮቹ ፡ በድብቅ ፡ ሠሩ

**underground room** የምድር ፡ ቤት
The explosives are stored in an underground room. ፈንጂዎቹ ፡ ባንድ ፡ የምድር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተከማችተዋል

**be underground** መሬት ፡ ውስጥ ፡ ተቀበረ
The telephone line is underground. የስልኩ ፡ መሥመር ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ ተቀብሯል

**go underground** ተደበቀ
The hunted criminal went underground. የሚፈለገው ፡ ወንጀለኛ ፡ ተደበቀ

**undergrowth** ቁጥቋጦ
The undergrowth is not more than six years old. ቁጥቋጦው ፡ ከስድስት ፡ ዓመት ፡ አይበልጠውም

**underhand, ~ method** ተንኰል
He used underhand methods to gain a promotion. ሹመት ፡ ለማግኘት ፡ በተንኰል ፡ ተጠቀመ

**(be) underhanded** ተንኰል ፡ አለበት
His methods are underhanded. ዘዴው ፡ ተንኰል ፡ አለበት

**underlay,** see **underlie**

**underlie** (underlay)
1. ከ --- ሥር ፡ ተገኘ. A sheet of rock underlies this soil. ከዚህ ፡ አፈር ፡ ሥር ፡ ጠፍጣፋ ፡ ቋጥኝ ፡ ይገኛል
2. ( pass.) ተመሠረተ. +Christianity underlies the attitude of most Westerners. ያብዛኞዎቹ ፡ ምዕራባውያን ፡ አቋም ፡ በክርስትና ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው

**underline**
1. ከሥር ፡ አሠመረ(በት). I underlined all your spelling errors. የፊደል ፡ ስሕተቶችህን ፡ ሁሉ ፡ ከሥር ፡ አሥምሬባቸዋለሁ
2. ጠቃሚነቱን ፡ አመለከተ. The speaker underlined his main points by repeating them. ተናጋሪው ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ በመደጋገም ፡ ጠቃሚነቱን ፡ አመለከተ

**underlying**
1. ከሥር ፡ ያለ. The underlying soil is rocky. ከሥር ፡ ያለው ፡ አፈር ፡ ድንጋያማ ፡ ነው
2. ዋና. The economic situation was the underlying cause of the war. የጦርነቱ ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ የኢኮኖሚው ፡ ሁኔታ ፡ ነበር

**undermine**
1. ሰረሰረ. The soldiers undermined the wall and went into the enemy's camp. ወታደሮቹ ፡ ግምቡን ፡ ሰርስረው ፡ ከጠላት ፡ ምሽግ ፡ ገቡ
2. ሸረሸረ. The flood undermined the house. ጐርፉ ፡ ቤቱን ፡ ሸረሸረው
3. ጠንቅ ፡ ሆነ. Severe colds have undermined my health. ኀይለኛ ፡ ጉንፋን ፡ ለጤናዬ ፡ ጠንቅ ፡ ሆኗል
4. አመነመነ(በት). He undermined his superior's position by a ruse. ተንኰል ፡ በመሥራት ፡ ያለቃውን ፡ ሥልጣን ፡ አመነመነበት

**underneath** ሥር
I found the ball underneath the bed. ኳሷን ፡ አልጋው ፡ ሥር ፡ አገኘኋት

**(be) undernourished** በደንብ ፡ አልተመገበም ፤ በቂ ፡ ምግብ ፡ አላገኘም
These children look undernourished. እነዚህ ፡ ሕፃናት ፡ በደንብ ፡ ያልተመገቡ ፡ (በቂ ፡ ምግብ ፡ ያላገኙ) ፡ ይመስላሉ

**underpaid,** see **underpay**

**underpass** መሿለኪያ
The road goes through an underpass. መንገዱ ፡ የሚያልፈው ፡ በመሿለኪያ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**underpay** (underpaid) ዝቅተኛ ፡ አበል ፡ ከፈለ
He underpays his workers. ለሠራተኞቹ ፡ ዝቅተኛ ፡ አበል ፡ ይከፍላቸዋል

**underpopulated**
This area is underpopulated. በቀበሌው ፡ ውስጥ ፡ የሚኖረው ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥሩ ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው

**underprivileged** ችግረኛ
The underprivileged children need playgrounds. ችግረኞች ፡ ልጆች ፡ የመጫወቻ ፡ ሜዳ ፡ ያስፈልጋቸዋል

**underrate** ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ገመተ
He underrates his ability to get things done. የሥራ ፡ ማከናወን ፡ ችሎታውን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ይገምተዋል

**underscore** ከሥር ፡ አሠመረ(በት)
Underscore the words you do not know! የማታውቃቸውን ፡ ቃላት ፡ ከሥር ፡ አሥምርባቸው

**Undersecretary of State** ምክትል ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር
The Undersecretary of State received the ambassador. ምክትል ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አምባሳደሩን ፡ ተቀበሉ

**undersell** (undersold) በዝቅተኛ ፡ ዋጋ ፡ ሸጠ
They are underselling us in order to bankrupt us. እኛን ፡ ለማክሰር ፡ በዝቅተኛ ፡ ዋጋ ፡ ይሸጣሉ

**undershirt** ካናቴራ
His undershirt is torn. ካናቴራው ፡ ተቀዷል

**undersigned** ፊርማው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የሚገኝ
The undersigned wishes to inform you that he is ready at any time. እኔ ፡ ፊርማዬ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የሚገኘው ፡ ምንጊዜም ፡ ዝግጁ ፡ መሆኔን ፡ እገልጻለሁ

**(be) undersized** ቀጫጫ
The child is undersized. ሕፃኑ ፡ ቀጫጫ ፡ ነው

**undersold,** see **undersell**

**understand** (understood)
1. ገባ(ው). +He couldn't even understand Amharic, let alone speak it. አማርኛ ፡ መናገር ፡ ቀርቶ ፡ አይገባውም

2. በሚገባ ፡ ተረዳ. A good teacher should understand children. ጥሩ ፡ መምህር ፡ ሕፃናትን ፡ በ ሚገባ ፡ መረዳት ፡ አለበት
3. ተረዳ. I understand from his letter that he likes his work. ከደብዳቤው ፡ እንደተረዳሁት ፡ ሥራውን ፡ ይወዳል
You don't understand what a position I am in. የኔን ፡ ችግር ፡ አልተረዳህልኝም
4. ማለትን ፡ ሰማ. I understand that you are leaving tomorrow. ነገ ፡ ትሄዳለህ ፡ ማለትን ፡ ሰማሁ
5. ቈጠረ. He understands my silence to be a refusal. ዝም ፡ ማለቴን ፡ እምቢ ፡ እንዳልኩ ፡ ይቈጥረዋል
6. ስሜቱን ፡ ተረዳ(ለት). Mary felt that no one understood her. ሜሪ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ስሜቷን ፡ እንዳልተረዳላት ፡ ተሰማት

**be given to understand** ተነገረ(ው)
We were given to understand that we'd be paid. እንደሚከፈለን ፡ ተነግሮን ፡ ነበር

**be understood** መቼስ ፡ የታወቀ ፡ ነው
It is understood that you will stay with us. ከኛ ፡ ጋር ፡ እንደምትቆይ ፡ መቼስ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**make oneself understood** ሐሳቡን ፡ ገለጸ
Can he make himself understood in Amharic? ባማርኛ ፡ ሐሳቡን ፡ ለመግለጽ ፡ ይችላል?

## (be) understandable በቂ ፡ ምክንያት ፡ አለው
His anger is quite understandable. የተቈጣበት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አለው

## understanding (n.)
1. አእምሮ. Human understanding is finite. የሰው ፡ አእምሮ ፡ ወሰን ፡ አለው
2. ብልህነት. His superior understanding makes him an excellent student. ከፍተኛ ፡ ብልህነቱ ፡ ምርጥ ፡ ተማሪ ፡ አድርጎታል
3. ዕውቀት. Reading widens our understanding. ማንበብ ፡ ዕውቀታችንን ፡ ያሰፋዋል
4. አድማጭነት. Parenthood requires patience and understanding. ወላጅ ፡ መሆን ፡ ታጋሽነትንና ፡ አድማጭነትን ፡ ይጠይቃል
*What is your understanding of the poem? ግጥሙ ፡ ምን ፡ የሚል ፡ ይመስልሃል?

**come to an understanding** ተግባባ
You and I must come to an understanding. እኔና ፡ አንተ ፡ መግባባት ፡ አለብን

**have an understanding** ተረዳ(ው)
+He has a clear understanding of the problem. ችግሩን ፡ በግልጽ ፡ ተረድቶታል

**it's my understanding** እንደተረዳሁት
It's my understanding that I am to teach every day till five. እንደተረዳሁት ፡ ሁል ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ዐሥሩ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ማስተማር ፡ አለብኝ

**on the understanding that** ተስማምቶ ፡ ስለነበረ
On the understanding that he was to come early, he came at 5 a.m. ቀደም ፡ ብሎ ፡ ለመምጣት ፡ ተስማምቶ ፡ ስለነበረ ፡ ከጧቱ ፡ በዐሥሩ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ መጣ

**reach an understanding** ተስማማ
Let's try to reach an understanding before we leave. ከመለያየታችን ፡ በፊት ፡ ለመስማማት ፡ እንሞክር

**understanding** (adj.) የሰው ፡ ችግር ፡ የሚገባው
She is a very understanding person. የሰው ፡ ችግር ፡ የሚገባት ፡ ሰው ፡ ናት

## understatement
*That is a great understatement; it's much worse than you say. ያልከው ፡ ሁኔታውን ፡ በ ጣም ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ያሳያል ፤ አንተ ፡ ካልከው ፡ በጣም ፡ ይብሳል

## understood, see understand

## undertake (undertook)
1. ጀመረ. Don't undertake what you can't finish! ለመጨረስ ፡ የማትችለውን ፡ ነገር ፡ አ ትጀምር
2. ቈርጦ ፡ ተነሣ. He undertook to finish the job by Friday. ሥራውን ፡ እስከ ፡ ዐርብ ፡ ለመ ጨረስ ፡ ቈርጦ ፡ ተነሣ
[See also 'trip']

## undertaker [በምዕራብ ፡ አገሮች ፡ ሰው ፡ ሲሞ ት ፡ አጥቦ ፤ ገንዘ ፤ ከፈን ፡ አልብሶ ፡ ለመቃብር ፡ የሚያዘጋጅ ፡ ልዩ ፡ ሥራው ፡ ይኸው ፡ የሆነ ፡ ሰው]

## undertaking
1. ውጥን. The undertaking succeeded. ውጥኑ ፡ ተሳካ
2. ድርጊት. An expedition to the North Pole is an adventurous undertaking. ወደ ፡ ሰሜናዊው ፡ ዋልታ ፡ መጓዝ ፡ ጀብዱ ፡ የበዛበት ፡ ድርጊት ፡ ነ ው

## undertone ሹክሹክታ
The two friends talked in undertones. ሁለቱ ፡ ጓ ደኛሞች ፡ በሹክሹክታ ፡ አወሩ
*There was an undertone of sadness in her gaiety. በደስታዋ ፡ የተሸፈነ ፡ ሐዘን ፡ ነበረባት

**undertook,** see **undertake**

**undertow** [በባሕር ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ማዕበል ፡ ከሚሄድበት ፡ አቅጣጫ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሄድ ፡ የባሕር ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ ማዕበል]

**(be) undervalued** ከሚገባው ፡ በታች ፡ ተገመተ
The property is undervalued so that not much tax is paid on it. ይህ ፡ ንብረት ፡ የተገመተው ፡ ከሚገባው ፡ በታች ፡ ስለሆነ ፡ ብዙ ፡ ግብር ፡ አይከፈልበትም

**underway, get ~** መንገድ ፡ ጀመረ
We got underway after considerable delay. ብዙ ፡ ከዘገየን ፡ በኋላ ፡ መንገድ ፡ ጀመርን

**underwear** ሙታንታና ፡ ካናቴራ
Change your underwear at least once a week! ሙታንታህንና ፡ ካናቴራህን ፡ ቢያንስ ፡ በሳምንት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለውጥ

**(be) underweight** ክብደቱ ፡ በጣም ፡ ዝቅ ፡ አለ
The sick boy is underweight. የታመመው ፡ ልጅ ፡ ክብደቱ ፡ በጣም ፡ ዝቅ ፡ ብሏል

**underwent,** see **undergo**

**underworld** በወንጀል ፡ ሥራ ፡ የሚኖር
The underworld was asked to identify the killer. በወንጀል ፡ ሥራ ፡ የሚኖረው ፡ ሁሉ ፡ ነፍስ ፡ ገዳዩን ፡ እንዲያወጣ ፡ ተጠየቀ

**underwrite** (underwrote) ከፈለ
The insurance company will underwrite our losses. የኢንሹራንስ ፡ ኩባንያ ፡ ለደረሰብን ፡ ጉዳት ፡ ይከፍለናል

**underwrote,** see **underwrite**

**undesirable** የማይፈለግ
The experiment led to undesirable results. ሙከራው ፡ የማይፈለጉ ፡ ውጤቶች ፡ አሳየ

**be undesirable** ተገቢ ፡ አይደለም
This behavior is undesirable. ይህ ፡ አድራጎት ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**(be) undeterred** ወደ ፡ ኋላ ፡ አላሰኘውም
+He was undeterred by my refusal. እምቢ ፡ ማለቴ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አላሰኘውም

**undeveloped, ~ land** ጠፍ ፡ መሬት
Undeveloped land is sold at a low price. ጠፍ ፡ መሬት ፡ በዝቅተኛ ፡ ዋጋ ፡ በመሸጥ ፡ ላይ ፡ ነው

**be undeveloped** አለማም
The land is still undeveloped. መሬቱ ፡ ገና ፡ አለማም

**undid,** see **undo**

**(be) undiminished** ሳይቀንስ ፡ ቀረ
Her verve is undiminished even at the end of an exhausting day. በጣም ፡ አድካሚ ፡ ከሆነ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ እንኳን ፡ ጉልበቷ ፡ ሳይቀንስ ፡ ቀረ

**undisciplined** ስድ
The undisciplined children were reprimanded. ስዶቹ ፡ ልጆች ፡ ተገሠጹ

**undo** (undid, undone)
1. ፈታ. Help me undo this knot! ይህንን ፡ ቋጠሮ ፡ ለመፍታት ፡ እግዘኝ
2. ሻረ. You can never undo the harm you've done. ያደረስከውን ፡ ጉዳት ፡ በፍጹም ፡ ልትሽረው ፡ አትችልም
3. አበላሸ. He has undone the good work of his predecessor. ከሱ ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ የሠራውን ፡ ጥሩ ፡ ሥራ ፡ አበላሸው
4. አጠፋ. His recklessness will undo him. ግደለሽነቱ ፡ ያጠፋዋል

**undoing** ውድቀት ፤ ያበላሸው
His inaction was his undoing. ለውድቀቱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ስንፍናው ፡ ነው
Drink was his undoing. ያበላሸው ፡ መጠጥ ፡ ነው

**undone** ያልጨረሰ
He was asked to finish his undone chores. ያልጨረሰውን ፡ ሥራ ፡ እንዲያጠናቅቅ ፡ ተጠየቀ

**be undone** ተፈታ
His shoelaces are undone. የጫማው ፡ ማሰሪያ ፡ ተፈቷል

**(be) undoubted** አላጠራጠረም
His abilities are undoubted. ችሎታው ፡ አያጠራጥርም

**undoubtedly** ያለጥርጥር
He is undoubtedly the best man we have. ያለጥርጥር ፡ ካሉን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ምርጥ ፡ እሱ ፡ ነው

**be undoubtedly** ሳይሆን ፡ አይቀርም
The mound that we see is undoubtedly a grave. ያ ፡ የምናየው ፡ ጉብታ ፡ መቃብር ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም

**(be) undreamed of** ካሰበው ፡ በላይ ፡ ነበረ
The results were undreamed of. ውጤቱ ፡ ካሰብነው ፡ በላይ ፡ ነበር

**undress** (vt.) ልብስ ፡ አወላለቀ
I'll undress the children and put them to bed. ልጆቹን ፡ ልብሳቸውን ፡ አወላልቄ ፡ አስተኛቸዋለሁ

**undress** (vi.) ልብስ ፡ አወለቀ
The bell rang just as I was undressing. ልብሴን ፡ ሳወልቅ ፡ ደወሉ ፡ ተደወለ

**undue**
1. ተገቢ ፡ ያልሆነ. He accepted with undue haste. ተገቢ ፡ ባልሆነ ፡ ችኰላ ፡ ተቀበለ
2. (= adv.) ከመጠን ፡ በላይ. A miser gives undue importance to money. ጩቅ ፡ ገንዘብን ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ያመልካል

**undulating** አባጣ ፡ ጐርባጣ
The terrain is undulating. መሬቱ ፡ አባጣ ፡ ጐርባጣ ፡ ነው

**unduly** ከልክ ፡ በላይ
He is unduly strict. ከልክ ፡ በላይ ፡ ጥብቅ ፡ ነው

**unearth**
1. መሬት ፡ ቈፍሮ ፡ አወጣ. They unearthed a considerable treasure. መሬት ፡ ቈፍረው ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ አወጡ
2. አገኘ. He unearthed an old diary among his books. የድሮ ፡ ማስታወሻውን ፡ መጻሕፍቱ ፡ መካከል ፡ አገኘ

**unearthly** አሰቃቂ
We heard an unearthly scream. አሰቃቂ ፡ ጩኸት ፡ ሰማን

**uneasy**
*His uneasy position is due to the hardness of the chair. ያልተመቸው ፡ ከወንበሩ ፡ ደረቅነት ፡ የተነሣ ፡ ነው

**feel uneasy**
1. ተጨነቀ. She felt uneasy when her husband was late. ባሏ ፡ ቢዘገይ ፡ ተጨነቀች
2. እንደልቡ ፡ ሊሆን ፡ አልቻለም. He felt uneasy before such a large audience. እንደዚያ ፡ ባለ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ እንደልቡ ፡ ሊሆን ፡ አልቻለም

**make feel uneasy** መዝናናት ፡ ነሣ
His gloom made everyone feel uneasy. የሱ ፡ መተከዝ ፡ ሁሉንም ፡ መዝናናት ፡ ነሣቸው

**uneducated** ያልተማረ
The uneducated cannot get good jobs. ያልተማሩ ፡ ጥሩ ፡ ሥራ ፡ ማግኘት ፡ አይችሉም

**unemployed** ሥራ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፤ ሥራ ፡ ፈት
The unemployed are very unhappy. ሥራ ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ (ሥራ ፡ ፈቶች) ፡ በጣም ፡ ይከፋቸዋል

**unemployment** የሥራ ፡ መታጣት
The unemployment is due to a lack of exports. የሥራ ፡ መታጣቱ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚላክ ፡ ንግድ ፡ በመታጣቱ ፡ ምክንያት ፡ ነው
*Unemployment is decreasing. የሥራ ፡ ፈቱ ፡ ቁጥር ፡ ዝቅ ፡ ብሏል
*His savings were a hedge against unemployment. ያጠራቀመው ፡ ከሥራ ፡ ሲወጣ ፡ መጠባበቂያ ፡ ነበር

**(be) unending** ማለቂያ ፡ አልነበረውም
The discussion was unending. ውይይቱ ፡ ማለቂያ ፡ አልነበረውም

**unequal** የማይመጣጠን
People who are unequal in age should not marry. በዕድሜ ፡ የማይመጣጠኑ ፡ ሰዎች ፡ መጋባት ፡ የለባቸውም

**unequal to** ከ --- በላይ
His strength is unequal to his task. ሥራው ፡ ከቅሙ ፡ በላይ ፡ ነው

**be unequal**
1. ብቁ ፡ አልነበረም. He was unequal to the task, and so he was replaced. ለሥራው ፡ ብቁ ፡ ስላልነበረ ፡ በስፍራው ፡ ሰው ፡ ተተካ
2. እኩል ፡ አልሆነም. If the weights are unequal, the balance will tip. የእቃዎቹ ፡ ክብደት ፡ እኩል ፡ ካልሆነ ፡ ሚዛኑ ፡ ያጋድላል

**(be) unequaled in** ተወዳዳሪ ፡ የለውም
He is unequaled in ability to solve mathematical problems. የሒሳብ ፡ ጥያቄዎችን ፡ ሲሠራ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የለውም

**unequivocal** ቁርጥ ፡ ያለ
His unequivocal refusal ended the matter. ቁርጥ ፡ ያለው ፡ እምቢታው ፡ ጉዳዩን ፡ ከፍጻሜ ፡ አደረሰው

**(be) unerring in** አልሳተም
+His aim is unerring. ዓላማውን ፡ አይስትም

**uneven** ጐደሎ
Twenty-seven and nine are uneven numbers. ሃያ ፡ ሰባትና ፡ ዘጠኝ ፡ ጐደሎ ፡ ቁጥሮች ፡ ናቸው

**be uneven**
1. ወጣ ፡ ገባ ፡ ነው. The ground here is uneven. እዚህ ፡ ጋ ፡ መሬቱ ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ ነው
2. ያልተመጣጠነ ፡ ነበር. The contest of the two boxers was uneven. ሁለቱ ፡ ቡጢኞች ፡ ያደረጉት ፡ ግጥሚያ ፡ ያልተመጣጠነ ፡ ነበር

**uneventful**
*Our transit through the various countries was uneventful. በልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ስናል ፍ ፡ ምንም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ አላጋጠ መንም

**unexpected** ያልታሰበ
Last night we had unexpected company. ትላንትና ፡ ማታ ፡ ያልታሰበ ፡ እንግዳ ፡ ነበረን

**unexpectedly** ሳይታሰብ
The news came entirely unexpectedly. ወሬው ፡ ፈጽሞ ፡ ሳይታሰብ ፡ ተሰማ

**unexplained**
*A deduction will be made for unexplained absences. ባልታወቀ ፡ ምክንያት ፡ ሲቀር ፡ ደሞ ዝ ፡ ይቀነስበታል

**unfailing** እውነተኛ
An unfailing friend will always be around in time of need. እውነተኛ ፡ ወዳጅ ፡ በችግር ፡ ጊዜ ፡ በቶሎ ፡ ይደርሳል
**be unfailing in** ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ፈጸመ
He is unfailing in his duties. ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ግዴታውን ፡ ይፈጽማል

**unfailingly** ምንጊዜም
He is unfailingly polite. ምንጊዜም ፡ ትሑት ፡ ነው

**(be) unfair** ተገቢ ፡ አይደለም
It is unfair for you to expect me to know that. ያንን ፡ ያውቃል ፡ ብለህ ፡ እኔን ፡ መገመትህ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**unfairly** ያለ ፡ አግባብ
He complains that he has been unfairly punished. ያለ ፡ አግባብ ፡ መቀጣቱን ፡ እያማረረ ፡ ተናገረ

**(be) unfaithful**
1. ታማኝ ፡ አልነበረም. He was unfaithful to his wife. ለሚስቱ ፡ ታማኝ ፡ አልነበረም
2. ትክክለኛ ፡ አልነበረም. This Bible translation is unfaithful. ይህ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ትርጉ ም ፡ ትክክለኛ ፡ አይደለም

**(be) unfaltering** ወደ ፡ ኋላ ፡ አላለም
He is unfaltering in the performance of his duty. ግዴታውን ፡ ለመፈጸም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አይልም

**unfamiliar**
1. የማያውቀው. The unfamiliar streets of the city bewildered me. የማላውቃቸው ፡ የከተማው ፡ መንገዶች ፡ ግራ ፡ አጋቡኝ
2. እንግዳ. He seems to be unfamiliar with the work he is supposed to do. ለተመደበለት ፡ ሥራ ፡ እንግዳ ፡ ይመስላል
**be unfamiliar** አይቶ ፡ አያውቅም
The place is unfamiliar to me. ይህን ፡ ቦታ ፡ አይቼውም ፡ አላውቅ

**unfasten** ፈታ
He unfastened the rope. ገመዱን ፡ ፈታ

**unfavorable**
1. ጉጂ. The judge handed down an unfavorable decision. ዳኛው ፡ ጉጂ ፡ ፍርድ ፡ ሰጠ
2. መጥፎ. I got an unfavorable report concerning his work. ስለ ፡ ሥራው ፡ መጥፎ ፡ ሪፖርት ፡ ደረሰኝ

**unfeeling** ርኅሩኅ ፡ የጐደለ(ው)
Only an unfeeling person would laugh when someone else is in serious difficulty. አንድ ፡ ሰው ፡ ከባድ ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ ሲወድቅ ፡ የሚሥ ቅ ፡ ርኅሩኅ ፡ የጐደለው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው

**unfinished** በጅምር ፡ የቀረ
I don't like unfinished business. በጅምር ፡ የቀ ረ ፡ ሥራ ፡ አልወድም
**leave unfinished** ሳይጨርስ ፡ ተወ
The workmen left the job unfinished. ሠራተኞቹ ፡ ሥራውን ፡ ሳይጨርሱ ፡ ተዉት

**(be) unfit**
1. ተገቢ ፡ አልነበረም. These officers are unfit for duty. እነዚህ ፡ መኰንኖች ፡ ለሥራ ፡ ተገ ቢ ፡ አይደሉም
2. አልተስማማም. The meat is unfit for consumption because it is full of worms. ሥጋው ፡ ትል ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ለመብል ፡ አይስማማም

**unflagging** (= adv.) ያለማቋረጥ
The unflagging efforts of the workers prevented a disaster. የሠራተኞቹ ፡ ያለማቋረጥ ፡ መድከም ፡ አደጋውን ፡ ሊከላከል ፡ ቻለ

**unflinching** የማይበገር
The officer's unflinching courage heartened his men. የመኰንኑ ፡ የማይበገር ፡ ጀግንነት ፡ ጦሩ ን ፡ አደፋፈረ

**unfold** (vt.)
1. ገለጠ. He unfolded the map and looked at it. ካርታውን ፡ ገልጦ ፡ ተመለከተው
2. ዘረጋ. He unfolded the tablecloth. የጠረጴዛ ውን ፡ ልብስ ፡ ዘረጋው
3. አስታወቀ. He unfolded his plans by degrees. ሐሳቡን ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ አስታወቀ

**unfold** (vi.) እየገፋ ፡ ሄደ
As the story unfolds, it gets more interesting. ታሪኩ ፡ እየገፋ ፡ ሲሄድ ፡ ያስደስት ፡ ጀመር

**(be) unforeseen** ያልታሰበ ፡ ነበረ
The director's departure was unforeseen. የዲሬክተሩ ፡ መሄድ ፡ ያልታሰበ ፡ ነበረ

**unforgettable** የማይረሳ
This is an unforgettable evening. ይህ ፡ የማይረሳ ፡ ምሽት ፡ ነው

**unfortunate**
1. ዕድለ ፡ ቢስ. The unfortunate child could not go to school. ዕድለ ፡ ቢሱ ፡ ልጅ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሊገባ ፡ አልቻለም
2. ተገቢ ፡ ያልሆነ. His unfortunate remark was followed by an awkward pause. ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ አስተያየቱ ፡ የሚያሳፍር ፡ ዝምታን ፡ አስከተለ
3. ቅር ፡ የሚያሰኝ. That was an unfortunate idea. ቅር ፡ የሚያሰኝ ፡ ሐሳብ ፡ ነበር

**unfortunately** ከፋቱ
Unfortunately, I came after the party was over. ከፋቱ ፡ ፓርቲው ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ መጣሁ

**(be) unfounded** መሠረት ፡ አልነበረውም
The rumor that he had resigned was unfounded. ከሥራ ፡ የመልቀቁ ፡ ጭምጭምታ ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ነበር

**unfriendly** ሰው ፡ ያለመውደድ
His unfriendly attitude discourages visitors. ሰው ፡ ያለመውደድ ፡ ጠባዩ ፡ ጐብኚዎችን ፡ ያባርራል
*He is unfriendly toward people he does not know. የማያውቃቸውን ፡ ሰዎች ፡ አይቀርብም

**unfurl, ~ in the breeze** ተውለበለበ
The flag unfurled in the breeze. ሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ ተውለበለበ

**(be) unfurnished** እቃ ፡ አልነበረበትም
The living room was unfurnished. የእንግዳ ፡ ቤቱ ፡ እቃ ፡ አልነበረበትም

**ungainly** ቀርፋፋ
The elephant is an ungainly creature. ዝሆን ፡ ቀርፋፋ ፡ ፍጥረት ፡ ነው

**ungodly**
1. ከሐዲ. The ungodly man was stoned by his neighbors. ከሐዲውን ፡ ሰው ፡ ጐረቤቶቹ ፡ በድንጋይ ፡ ወገሩት
2. ጆሮ ፡ የሚበጥስ. An ungodly noise broke out. ጆሮ ፡ የሚበጥስ ፡ ጩኸት ፡ በድንገት ፡ ተሰማ

**at this ungodly hour** በዚህ ፡ ውድቅት
What are you doing at this ungodly hour? በዚህ ፡ ውድቅት ፡ ምን ፡ ትሠራለህ?

**(be) ungraceful** ለዛ ፡ ጐደለው
She is too ungraceful to be a dancer. ዳንሰኛ ፡ ለመሆን ፡ ለዛ ፡ ይጐድላታል

**ungracious** (= n.) ርኅራኄ ፡ የጐደለው ፡ ነገር
To refuse to give him a drink of water is certainly ungracious. ውኃ ፡ አጠጡኝ ፡ ሲል ፡ መከልከሉ ፡ ርኅራኄ ፡ የጐደለው ፡ ነገር ፡ ነው

**ungrateful** ውለታ ፡ ቢስ
He is an ungrateful child. ውለታ ፡ ቢስ ፡ ልጅ ፡ ነው

**ungrounded** ምክንያት ፡ የሌለው
His ungrounded fear of airplanes keeps him from flying. ምክንያት ፡ የሌለው ፡ የአውሮፕላን ፡ ፍርሃቱ ፡ ከመብረር ፡ ያግደዋል

**be ungrounded (in)** አልሠለጠነም
He is ungrounded in the arts. በሥነ ፡ ጥበብ ፡ አልሠለጠነም

**ungrudging** ቂም ፡ በቀል ፡ የሌለበት
Ungrudging forgiveness between former enemies is unusual. በሁለት ፡ የቀድሞ ፡ ጠላቶች ፡ መካከል ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ የሌለበት ፡ ዕርቅ ፡ የተለመደ ፡ አይደለም

**(be) unguarded** አልተጠበቀም
The border is unguarded. ወሰኑ ፡ አይጠበቅም

**in an unguarded moment** ሳት ፡ ብሎት
In an unguarded moment, she gave away her secret. ሳት ፡ ብሏት ፡ ምስጢሯን ፡ አወጣች

**unguardedly**
*He spoke unguardedly of his hopes and fears. ስላለው ፡ ፍርሃትና ፡ ተስፋ ፡ ያለ ፡ የሌለውን ፡ ዘከዘከው

**unguent** ቅባት
Smear some unguent on your burn! ቁስልህን ፡ ቅባት ፡ ቀባው

**unhappily** ያሳዝናል
Unhappily, I lost my wallet. ያሳዝናል ፤ ቦርሳዬ ፡ ጠፋብኝ

**end unhappily** ሳይሳካ ፡ ቀረ
The effort to save his life ended unhappily. ሕይወቱን ፡ ለማትረፍ ፡ የተደረገው ፡ ጥረት ፡ ሳይሳካ ፡ ቀረ

**unhappy**
1. የከፋ. The unhappy boy gulped down a sob. የከፋው ፡ ልጅ ፡ መንሰቅሰቁን ፡ ዋጥ ፡ አደረገ
2. ተገቢ ፡ ያልሆነ. His choice of words was unhappy as it started the quarrel all over again. ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ አባባሉ ፡ ጠቡን ፡ እንደገና ፡ ቀሰቀሰው

**be unhappy**
1. አዘነ. He is very unhappy about his friend's departure. በጓደኛው ፡ መሄድ ፡ በጣም ፡ አዝኗል
2. ከፋ(ው). The unemployed are very unhappy. ሥራ ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ በጣም ፡ ይከፋቸዋል

**unharmed** ጉዳት ፡ ሳይደርስበት
He escaped unharmed. ጉዳት ፡ ሳይደርስበት ፡ አመለጠ

**unharmonious** ያልተቀናበረ
The unharmonious melody played by an inexperienced harp player is unpleasant. በቂ ፡ ልምምድ ፡ የሌለው ፡ በገና ፡ ተጫዋች ፡ ያቀረበው ፡ ያልተቀናበረ ፡ ዜማ ፡ አያስደስትም

**unharness** አራገፈ
He unharnessed the horse. ፈረሱን ፡ አራገፈ

**unhealthy**
1. ጤና ፡ የጐደለው. The unhealthy child was sent to the hospital. ጤና ፡ የጐደለው ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ተላከ
2. ሰውነትን ፡ የሚጐዳ. Unhealthy habits like smoking and staying up late are harmful to health. እንደ ፡ ሲጋራ ፡ ማጨስና ፡ እንደ ፡ ማምሸት ፡ ያሉ ፡ ሰውነትን ፡ የሚጐዱ ፡ ልማዶች ፡ ለጤንነት ፡ ጥሩ ፡ አይደሉም

**be unhealthy** ጤንነትን ፡ ጐዳ
The climate in this town is unhealthy. የዚህ ፡ ከተማ ፡ አየር ፡ ጤንነትን ፡ ይጐዳል

**(be) unheard of** ተሰምቶም ፡ አይታወቅ
Such a thing is unheard of. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ተሰምቶም ፡ አይታወቅ

**go unheard** ማንም ፡ አላጤነውም
My warning went unheard. የሰጠሁትን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ማንም ፡ አላጤነውም

**unheeded, go ~** ሳይደመጥ ፡ ቀረ
His advice went unheeded. የሰጠው ፡ ምክር ፡ ሳይደመጥ ፡ ቀረ

**unhesitatingly** ሳያመነታ
When he asked her to marry him, she answered, unhesitatingly, "yes". እንድታገባው ፡ በጠየቃት ፡ ጊዜ ፡ ሳታመነታ ፡ እሺ ፡ አለችው

**unhitch** ፈታ
He unhitched the wagon from the horse. ጋሪውን ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ፈታ

**unholy** የረከሰ
They have an unholy alliance to keep good men from being assigned. ጥሩ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ እንዳይመደቡ ፡ የረከሰ ፡ ማኅበር ፡ አላቸው

**unhurt** ሳይጐዳ
It's a marvel to me that he escaped unhurt. ሳይጐዳ ፡ ማምለጡ ፡ ለኔ ፡ ታምር ፡ ነው

**unification** አንድ ፡ ማድረግ
The unification of the country required many years of warfare. አገሪቱን ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ ብዙ ፡ ውጊያ ፡ ማድረግ ፡ አስፈልጎ ፡ ነበር

**uniform** (n). የደንብ ፡ ልብስ
We knew they were police by their blue uniforms. ፖሊስ ፡ መሆናቸውን ፡ በሰማያዊው ፡ የደንብ ፡ ልብሳቸው ፡ ዐወቅን
[See also 'official']

**uniform** (adj.)
1. እኩል. The sticks must be of uniform length. ዕንጨቶቹ ፡ በቁመት ፡ እኩል ፡ መሆን ፡ አለባቸው
2. አንድ ፡ ዓይነት. The two cities have uniform traffic laws. ሁለቱ ፡ ከተሞች ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የትራፊክ ፡ ሕግ ፡ አላቸው

**uniformed** የደንብ ፡ ልብስ ፡ የለበሰ
Uniformed men were guarding the gate. የደንብ ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ ሰዎች ፡ በሩን ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር

**unify** (unified) አንድ ፡ አደረገ
Theodore tried to unify Ethiopia. አጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ኢትዮጵያን ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ ሞከሩ

**(be) unilateral** ባንድ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ነበር
The decision to halt the bombing was unilateral. የቦምብ ፡ ድብደባውን ፡ ለማቆም ፡ የተወሰነው ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ነበር

**unimaginable** ለግምት ፡ የሚያስቸግር
An unimaginable distance is traveled by the new jets. አዲሶቹ ፡ ጄቶች ፡ ለግምት ፡ የሚያስቸግር ፡ ርቀት ፡ ይጓዛሉ

**unimportant** የሆነ ፡ ያልሆነው ፤ ጥቃቅን ፤ ቀላል
I hate petty squabbles about unimportant things. በሆነ ፡ ባልሆነው ፡ (በጥቃቅን ፡ ነገር ፤ በቀላል ፡ ነገር) ፡ መነታረክ ፡ አልወድም

**be unimportant** ዋጋ ፡ አልነበረውም
The matter is unimportant. ነገሩ ፡ ዋጋ ፡ የለውም

**(be) uninformed** ብዙ ፡ ነገር ፡ አላወቀም
He is uninformed, but not unintelligent. ብዙ ፡ ነገር ፡ ባያውቅም ፡ ደደብ ፡ አይደለም

**(be) uninhabited** ሰው ፡ አይኖርበትም
The desert is largely uninhabited. አብዛኛው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሰው ፡ አይኖርበትም

**(be) uninhibited**
*His behavior is uninhibited. ግድ ፡ የለሽ ፡ ጠባይ ፡ አለው

**unintelligible** የማይነበብ
Unintelligible writing is worthless. የማይነበብ ፡ ጽሑፍ ፡ ዋጋ ፡ የለውም

**(be) uninterested** ግድ ፡ የለውም
Monks are uninterested in mundane affairs. መነኵሳት ፡ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ጉዳይ ፡ ግድ ፡ የላቸውም

**(be) uninterrupted** አልተቋረጠም
His speech was uninterrupted by applause. ንግግሩ ፡ በጭብጨባ ፡ አልተቋረጠም ፡ ነበር

**union**
1. አንድነት. In union there is strength. አንድነት ፡ ኀይል ፡ ነው
2. መዋሐድ. The United States was formed by the union of thirteen states. አሜሪካ ፡ የተመሠረተችው ፡ በዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ግዛቶች ፡ መዋሐድ ፡ ነው
3. የሠራተኞች ፡ ማኅበር. The union is out on strike. የሠራተኞቹ ፡ ማኅበር ፡ አድማ ፡ ሥራ ፡ አቁሟል
*Their union was blessed with a child. ተጋብተው ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ወለዱ
*They live in perfect union. ስምም ፡ ናቸው

**Union of Soviet Socialist Republics**
የሶቪዬት ፡ ሶሺያሊስት ፡ ሬፑብሊኮች ፡ ኅብረት

**unique**
1. ተወዳዳሪ ፡ የማይገኝለት. It was a unique experience to see this old city. ይህን ፡ የጥንት ፡ ከተማ ፡ ማየት ፡ ተወዳዳሪ ፡ የማይገኝለት ፡ ዕድል ፡ ነበር
2. ድንቅ. This book is unique; there is no other like it. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፤ መሰሉ ፡ ፈጽሞ ፡ አይገኝም

**unison, in ~** ተባብረው
If we act in unison, we'll get what we want. ተባብረን ፡ ብንሠራ ፡ የፈለግነውን ፡ እናገኛለን

**unit**
1. ክፍል. The book is divided into twelve units. መጽሐፉ ፡ በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ተከፍሏል
The family is the basic unit of society. ቤተ ፡ ሰብ ፡ የኅብረተ ፡ ሰብ ፡ መሠረት ፡ ክፍል ፡ ነው
2. የጦር ፡ ክፍል. Some of the enemy units have been isolated by our forces. የጠላት ፡ ጦር ፡ አንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ በጦራችን ፡ ተነጣጥሎ ፡ ነበር
3. ጓድ. The soldiers are mopping up the scattered enemy units. የተበታተኑትን ፡ የጠላት ፡ ጓዶች ፡ ወታደሮቹ ፡ በመለቃቀም ፡ ላይ ፡ ናቸው
4. መለኪያ. A degree is a unit of temperature. ዲግሪ ፡ የሙቀት ፡ መለኪያ ፡ ነው
A foot is a unit of length. ጫማ ፡ የርዝመት ፡ መለኪያ ፡ ነው
[See also 'monetary']

**unite** (vt.) አገናኘ
The interests which unite our two countries cannot be broken. ሁለቱን ፡ አገሮቻችንን ፡ የሚያገናኙት ፡ ጥቅሞች ፡ መጥፋት ፡ አይችሉም

**unite** (vi.)
1. ተባበረ. The nations of the world need to unite to stop war. ጦርነትን ፡ ለማቆም ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ መተባበር ፡ አለባቸው
2. ተባብረው ፡ ተነሡ. Let's unite to fight poverty and disease! ድኽነትንና ፡ በሽታን ፡ ለመዋጋት ፡ ተባብረን ፡ እንነሣ
3. ባንድነት ፡ ተሰለፈ. The country unites behind its leader in wartime. በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ከመሪው ፡ ጐን ፡ ባንድነት ፡ ይሰለፋል
4. አንድ ፡ ሆነ. Fellow countrymen, now is the time to unite. ያገሬ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ! አንድ ፡ የመሆናችን ፡ ጊዜ ፡ አሁን ፡ ነው

**united** (adj.)
1. በፍቅር ፡ ተሳስሮ ፡ የቆየ. A united family is healthier than a broken one. ከፈረሰ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በፍቅር ፡ ተሳስሮ ፡ የቆየው ፡ ይሻላል
2. የተባበረ. Make a united effort to build the hospital! ሆስፒታሉን ፡ ለማሠራት ፡ የተባበረ ፡ ጥረት ፡ አድርጉ

**be united** ተባበረ
The tribes were united in their efforts to resist the invader. ጐሳዎቹ ፡ ወራሪውን ፡ ለመቋቋም ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ ተባብረው ፡ ነበር

**stand united** ባንድነት ፡ ጸና
The country stands united behind the President.

ሀገሪቱ ፡ በፕሬዚዳንቱ ፡ ሥር ፡ ባንድነት ፡ ትጸና
ለች

**United Nations** የተባበሩት ፡ መንግሥታት
The United Nations will send observers. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ታዛቢዎች ፡ ይልካል

**United States** ዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፤ የተባበሩ ፡ አሜሪካ ፡ መንግሥታት
The United States gave $100 million for aid. ዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ መቶ ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ ለእርዳታ ፡ ሰጠች

**unity** (unities) አንድነት
The unity of Nigeria was disrupted by agents. የናይጄሪያ ፡ አንድነት ፡ ባነሣሾች ፡ ተናውጦ ፡ ነበር

**in unity** ተስማምተው
They lived together in unity. ተስማምተው ፡ ባን
ድነት ፡ ኖሩ

**universal**
1. ዓለም ፡ አቀፍ. Universal peace was never achieved. ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሰላም ፡ ምንጊዜም ፡ አልተገኘ
2. በየትም ፡ ያለ. 'Honor thy father' is a universal rule. አባትህን ፡ አክብር ፡ የሚለው ፡ በየትም ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ ነው
3. (= adv.) በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ. War causes universal misery. ጦርነት ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ ያመጣል
4. (= adv.) በሁሉ ፡ ዘንድ. His conduct earned him universal respect. ምግባሩ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ክብርን ፡ አስገኘለት

**universally** በሁሉም ፡ ዘንድ
He is universally respected. እሱ ፡ በሁሉም ፡ ዘ
ንድ ፡ የተከበረ ፡ ሰው ፡ ነው

**universe** ጠፈር ፤ ዓለማት
The universe is infinite. ጠፈር ፡ (ዓለማት) ፡ መነ
ሻና ፡ መድረሻ ፡ የለውም

**university** (universities) ዩኒቨርሲቲ
There are at present 4,000 students in the university. አሁን ፡ በዩኒቨርሲቲው ፡ ውስጥ ፡ አራት ፡ ሺ ፡ ተማሪዎች ፡ አሉ

**unjust** ትክክለኛ ፡ ያልሆነ
These unjust laws should be abolished. ትክክለ
ኛ ፡ ያልሆኑት ፡ ሕጎች ፡ መሻር ፡ አለባቸው

**unkind** ክፉ
An unkind mother makes a bad child. ክፉ ፡ እ
ናት ፡ ለልጇ ፡ አመል ፡ ታወጣለታለች

**unknown** ስሙ ፡ ያልታወቀ
Hitherto, he was an unknown writer. እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ስሙ ፡ ያልታወቀ ፡ ደራሲ ፡ ነበር

**be unknown** አልታወቀም
He is unknown outside his country. ከሀገሩ ፡ ውጭ ፡ አይታወቅም

**be unknown to** አይወቀውም
+The book you speak of is unknown to me. የምትለውን ፡ መጽሐፍ ፡ አላውቀውም

**unlawful**
1. ክልክል. It is unlawful to drive over 60 mph. በሰዓት ፡ ከስልሳ ፡ ማይል ፡ በላይ ፡ መንዳት ፡ ክልክል ፡ ነው
2. ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የተደረገ. The unlawful search of the criminal's home was mentioned in the court. ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የተደረገው ፡ የወንጀለኛው ፡ ቤት ፡ ፍተሻ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ተነሥቶ ፡ ነበር
3. ሕገ ፡ ወጥ. It is unlawful to urinate in the street. መንገድ ፡ ላይ ፡ መሽናት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ነው

**unlearn** ተላቀቀ
It is hard to unlearn a bad method. ከለመዱት ፡ መጥፎ ፡ ዘዴ ፡ መላቀቁ ፡ ችግር ፡ ነው

**unleash**
1. ፈቶ ፡ ለቀቀ. He unleashed the dogs to let them run. ውሾቹ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እንዲሉ ፡ ፈቶ ፡ ለቀቃቸው
2. አመነጨ. The atom unleashes terrific forces. አቶም ፡ ታላቅ ፡ ኀይል ፡ ያመነጫል

**unleavened**
1. አፍለኛ. The bread is unleavened. ዳቦው ፡ አ
ፍለኛ ፡ ነው
2 ያልቦካ. Wafers are made from unleavened dough. ስስ ፡ ብስኩት ፡ ካልቦካ ፡ ሊጥ ፡ ይሠራል

**be unleavened** አልቦካም
The dough is unleavened. ሊጡ ፡ አልቦካም

**unless** (conj.) ከ + negative perfect
We'll come unless it rains. ካልዘነበ ፡ እንመጣለን

**unless** (= prep.) ከ - - - ሌላ
Nothing will come of it, unless it's disaster. ከጉዳ
ት ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ የሚያተርፈው ፡ ነገር ፡ የለም

**unlike**
1. የተለየ ፡ ነገር. It's unlike anything I have seen before. ከዚህ ፡ በፊት ፡ ካየሁት ፡ ሁሉ ፡ የተለየ ፡ ነገር ፡ ነው
2. በመጠን ፡ የተለያየ. They contributed unlike sums to charity. ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ በመጠን ፡ የተለያየ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጡ

3. እንደ -- ሳይሆን. Unlike yesterday, he is presentable today. እንደ ፡ ትላንትናው ፡ ሳይሆን ፡ ዛሬ ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችል ፡ ነው

**be unlike** አልተመሳሰለም
Their natures are quite unlike. ጠባያቸው ፡ ፈጽሞ ፡ አይመሳሰልም

**be unlike him** ልማዱ ፡ አይደለም
It is quite unlike him to come late. ዘግይቶ ፡ መምጣት ፡ ልማዱ ፡ አይደለም

**(be) unlikely** አጠራጠረ
It is very unlikely that it will rain right now. አሁን ፡ መዝነቡ ፡ ያጠራጥራል

**unlimited** ልክ ፡ የሌለው ፤ ድንበር ፡ የሌለው ፤ ገደብ ፡ የሌለው
This store has an unlimited amount of soap. ይህ ፡ መደብር ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ ሳሙና ፡ አለው
To human eyes, the heavens appear unlimited. ለሰው ፡ ዓይን ፡ ሰማይ ፡ ድንበር ፡ የሌለው ፡ ይመስላል
Unlimited power went to his head. ገደብ ፡ የሌለው ፡ ሥልጣን ፡ ለአእምሮው ፡ ተሰማው

**unload**
1. አራገፈ. They unloaded the ship yesterday. መርከቡን ፡ ትናንትና ፡ አራገፉ
2. አወረደ. We unloaded the trunks from the car. ሣጥኖቹን ፡ ከመኪናው ፡ ላይ ፡ አወረድን
3. ዘከዘከ. She unloaded her troubles on her mother. ችግሯን ፡ ሁሉ ፡ ለእናቷ ፡ ዘከዘከች

**unlock** ከፈተ
I lost the key and couldn't unlock the drawer. ቁልፌ ፡ ስለጠፋብኝ ፡ መሳቢያውን ፡ ልከፍተው ፡ አልቻልኩም

**unlucky**
1. ዕድለ ፡ ቢስ. He is an unlucky fellow. ዕድለ ፡ ቢስ ፡ ሰው ፡ ነው
2. ገደ ፡ ቢስ. The superstition that the number 13 is unlucky is believed by many people. ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ገደ ፡ ቢስ ፡ ቁጥር ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ አጉል ፡ እምነት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያምኑበታል

**unmanly** ከወንድነት ፡ የራቀ
He has an unmanly fear of animals. ስለ ፡ እንስሳት ፡ ከወንድነት ፡ የራቀ ፡ ፍርሃት ፡ አለው
*That was an unmanly thing to do. ወንድ ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ አልነበረም

**unmanned** ሰው ፡ የሌለበት
The Chinese reported shooting down an unmanned plane. ቻይናዎች ፡ ሰው ፡ የሌለበትን ፡ አውሮፕላን ፡ ተኩሰው ፡ ማውረዳቸውን ፡ ገለጹ

**unmannered** ባለጌ
He is an unmannered fellow. ባለጌ ፡ ሰው ፡ ነው

**unmannerly**
1. ሥርዓተ ፡ ቢስ. Unmannerly children are a nuisance. ሥርዓተ ፡ ቢስ ፡ ልጆች ፡ ያስቸግራሉ
2. ምግባረ ፡ የጐደለው. He was offended by the unmannerly guests. ምግባረ ፡ በጐደላቸው ፡ እንግዶች ፡ ተቀይሞ ፡ ነበር

**unmarried** ያላገባ
Unmarried women have a special hairdress. ያላገቡ ፡ ሴቶች ፡ የተለየ ፡ የጸጉር ፡ አሠራር ፡ አላቸው

**remain unmarried**
1. ቆሞ ፡ ቀረች. My niece remained unmarried. የእኅቴ ፡ ልጅ ፡ ቆሞ ፡ ቀረች
2. አሁንም ፡ አላገባ. My nephew remained unmarried. የእኅቴ ፡ ልጅ ፡ አሁንም ፡ አላገባ

**(be) unmasked** ተነቃ(በት)
The impostor was unmasked. አጭበርባሪው ፡ ተነቃበት

**unmentionable**
*His behavior is unmentionable. ጠባዩ ፡ ሰው ፡ የሚሰማው ፡ አይደለም

**unmerciful** ምሕረት ፡ የሌለው
He is an unmerciful judge. ምሕረት ፡ የሌለው ፡ ዳኛ ፡ ነው

**unmindful, ~ of** ሳያስተውል
He went ahead unmindful of the results. የሚያስከትለውን ፡ ነገር ፡ ሳያስተውል ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቀጠለ

**(be) unmistakable** ለማለት ፡ አላጠራጠረም
These spots are an unmistakable sign of smallpox. እነዚህ ፡ ምልክቶች ፡ የፈንጣጣ ፡ ጠባሳዎች ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ አያጠራጥርም
*His style of writing is unmistakable. ያጻጻፍ ፡ ዘዴውን ፡ ማንም ፡ ያውቀዋል

**(be) unmoved** ፍንክች ፡ አላለም
He was unmoved by tears and supplications. በልቅሶና ፡ በልመና ፡ ፍንክች ፡ አላለም

**leave unmoved** ስሜትም ፡ አልሰጠው
The story left him unmoved. ታሪኩ ፡ ስሜትም ፡ አልሰጠው

**unnatural**
1. ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሆነ. He has an unnatural desire for fame. ዝነኛ ፡ ለመሆን ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ፍላጎት ፡ አለው

2. ከተፈጥሮ ፡ ውጭ ፡ የሆነ. Green is an unnatural color for a dog. አረንጓዴ ፡ መልክ ፡ ለውሻ ፡ ከተፈጥሮ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ቀለም ፡ ነው

**be unnatural** ከሥርዐት ፡ ውጭ ፡ ነው
Marriage between an old woman and a young man is unnatural. በወጣት ፡ ወንድና ፡ ባሮጊት ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ጋብቻ ፡ ከሥርዓት ፡ ውጭ ፡ ነው

**unnecessary**
1. የማያስፈልግ. It is entirely unnecessary to explain it to me. ለኔ ፡ መግለጽ ፡ በፍጹም ፡ የማያስፈልግ ፡ ነው
2. ተፈላጊ ፡ ያልሆነ ፤ አስፈላጊ ፡ ያልሆነ. The speaker excluded the unnecessary material from the report. ተናጋሪው ፡ ከራፖሩ ፡ ውስጥ ፡ ተፈላጊ ፡ (አስፈላጊ) ፡ ያልሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ አስቀረ

**unnerve**
*The crash unnerved him. በመኪናው ፡ ግጭት ፡ የተነሣ ፡ ራሱን ፡ መቈጣጠር ፡ አቃተው

**unnoticed, go ~**
1. ማንም ፡ ሳያውቀው ፡ ተረሳ. I hope the incident will go unnoticed. ድርጊቱ ፡ ማንም ፡ ሳያውቀው ፡ ይረሳል ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ
2. ማንም ፡ አላወቀበትም. His departure went unnoticed. ሲሄድ ፡ ማንም ፡ አላወቀበትም ፡ ነበር

**unoccupied**
1. ባዶ. An unoccupied house stood by the road. መንገዱ ፡ ዳር ፡ አንድ ፡ ባዶ ፡ ቤት ፡ ነበረ
The seat was unoccupied, so he sat down. ወንበሩ ፡ ባዶ ፡ ስለነበረ ፡ ተቀመጠበት
2. ሥራ ፡ ፈት. An unoccupied person can easily get into trouble. ሥራ ፡ ፈት ፡ በቀላሉ ፡ ከችግር ፡ ላይ ፡ ሊወድቅ ፡ ይችላል

**be unoccupied** አልተያዘም
The land is unoccupied. መሬቱ ፡ አልተያዘም

**unofficial** ኦፊሲየል ፡ ያልሆነ
He received an unofficial report. ኦፊሲየል ፡ ያልሆነ ፡ መግለጫ ፡ ደረሰው

**unopposed** ካላንዳች ፡ ተቃውሞ
The army made its entry into the town unopposed. ጦሩ ፡ ካላንዳች ፡ ተቃውሞ ፡ ከተማው ፡ ውስጥ ፡ ገባ

**be unopposed** ማንም ፡ አልተወዳደረውም
He was unopposed in his race for mayor. በከንቲባነቱ ፡ ምርጫ ፡ ጊዜ ፡ ማንም ፡ አልተወዳደረውም

**unpack**
1. አጋባ. Unpack your suitcase! ሻንጣህን ፡ አጋባው
2. ከሻንጣ ፡ ውስጥ ፡ አወጣ. Unpack your clothes! ልብስህን ፡ ከሻንጣው ፡ ውስጥ ፡ አውጣ
3. አራገፈ. They unpacked the horses. ፈረሶቹን ፡ አራገፉ

**unpaid** ሳይከፍል
He left all his bills unpaid. ሒሳቡን ፡ ሁሉ ፡ ሳይከፍል ፡ ሄደ

**(be) unparalleled** ወደር ፡ የለውም
His generosity is unparalleled. ለጋስነቱ ፡ ወደር ፡ የለውም

**unpaved** ያልተነጠፈ
The unpaved street is full of holes. ያልተነጠፈው ፡ መንገድ ፡ ብዙ ፡ ትንንሽ ፡ ጉድጓዶች ፡ አሉበት

**unpleasant** መጥፎ
I have some unpleasant news for you. መጥፎ ፡ ወሬ ፡ ልንገርህ

**be unpleasant** አላስደሰተም ፤ ደስ ፡ አላለም
The unharmonious melody made by an inexperienced harp player is unpleasant. በቂ ፡ ልምምድ ፡ የሌለው ፡ በገና ፡ ተጫዋች ፡ ያቀረበው ፡ ያልተቀናበረ ፡ ዜማ ፡ አያስደስትም
A harsh voice is unpleasant to the ear. ጐርናና ፡ ድምፅ ፡ ለጆሮ ፡ ደስ ፡ አይልም

**unpopular** የተጠላ
The students picketed the embassy to protest against the unpopular policy. ተማሪዎቹ ፡ የሀገሩን ፡ የተጠላ ፡ አመራር ፡ በመንቀፍ ፡ በኤምባሲው ፡ አካባቢ ፡ በመቆም ፡ ተቃውሟቸውን ፡ ገለጹ

**be unpopular** በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ አልተወደደም ፤ ተወዳጅ ፡ አይደለም
The new tax law is unpopular. አዲሱ ፡ የታክስ ፡ ሕግ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ አልተወደደም
A haughty girl is unpopular in school. ትዕቢተኛ ፡ ልጃገረድ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተወዳጅ ፡ አይደለችም

**unprecedented** በማንም ፡ ተደርጎ ፡ የማይታወቅ
The man made an unprecedented voyage across the Atlantic on a raft. ሰውዬው ፡ በማንም ፡ ተደርጎ ፡ የማይታወቀውን ፡ አትላንቲክን ፡ በታንኳ ፡ አቋረጠ

**be unprecedented** ታይቶም ፡ አይታወቅ
His action is unprecedented. የሱ ፡ አድራጎት ፡ ታይቶም ፡ አይታወቅ

**(be) unpredictable** ይሀ ፡ ይሆናል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም
The weather is unpredictable. ያየሩ ፡ ጠባይ ፡ ይሀ ፡ ይሆናል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም

**unpremeditated** (= adv.) ሳያውቁ
For self-preservation, an unpremeditated murder may easily be committed. ራስን ፡ ለማዳን ፡ ሳያውቁ ፡ የግዳይ ፡ ወንጀል ፡ በቀላሉ ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል

**(be) unprepared** አልተዘጋጀም
He was unprepared to answer the questions. ጥያቄውን ፡ ለመመለስ ፡ አልተዘጋጀም ፡ ነበር

**unprofessional** ለሙያ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ
The Medical Association discourages unprofessional conduct among its members. የሕክምና ፡ ማኅበር ፡ አባሎቹ ፡ ለሙያ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ተግባር ፡ እንዳይፈጽሙ ፡ ይከለክላል

**(be) unprofitable** ትርፍ ፡ አጣ
The business proved unprofitable and went under. ንግዱ ፡ ትርፍ ፡ ስላጣ ፡ ከሰረ

**(be) unpronounceable** ለማንበብ ፡ አስቸገረ
Many Russian words seem unpronounceable. ብዙ ፡ የመስኮብ ፡ ቃላትን ፡ ለማንበብ ፡ ያስቸግራል

**unprovided**
*The children were left unprovided for. ልጆቹ ፡ ያለ ፡ ተገን ፡ ቀሩ

**unqualified** እዚህ ፡ ቀረሀ ፡ የማይባል
The teacher gave unqualified praise to the students' work. መምህሩ ፡ ለተማሪዎቹ ፡ ሥራ ፡ እዚህ ፡ ቀረሀ ፡ የማይባል ፡ አድናቆትን ፡ ገለጸ

**be unqualified**
1. ብቁ ፡ አይደለም. He is unqualified for the job. ለሥራው ፡ ብቁ ፡ አይደለም
2. መብት ፡ የለውም. He is unqualified to vote. ለመምረጥ ፡ መብት ፡ የለውም

**unquestionable** የማይጠረጠር
Size is sometimes an unquestionable advantage. ቁመት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የማይጠረጠር ፡ ጥቅም ፡ አለው

**be unquestionable** አያጠራጥርም
His honesty is unquestionable. ታማኝነቱ ፡ አያጠራጥርም

**unquestionably** ያለጥርጥር
The sweater is unquestionably his. ያለጥርጥር ፡ ሹራቡ ፡ የሱ ፡ ነው

**unquestioned** የማያጠራጥር
He is a man of unquestioned sincerity. እሱ ፡ የማያጠራጥር ፡ ቅንነት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**unquote**
*I am, quote, "like the sounding brass", unquote. ጥቅሱ ፡ እንደሚለው ፡ እኔ ፡ እንደሚጮኽ ፡ ነሐስ ፡ ነኝ

**unravel**
1. ተረተረ. She unraveled the knitted sleeve. በሹራብ ፡ መልክ ፡ የተሠራውን ፡ እጅጌ ፡ ተረተረችው
2. ገለጠ. They unraveled the mystery of the missing men. የጠፉትን ፡ ሰዎች ፡ ምስጢር ፡ ገለጡት

**unreal** የሕልም
She lives in an unreal world. በሕልም ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ትኖራለች

**seem unreal** እውነት ፡ አይመስልም
The situation seems unreal. ሁኔታው ፡ እውነት ፡ አይመስልም

**(be) unreasonable**
1. ከሚገባው ፡ በላይ ፡ ነው. The price for this house is unreasonable. የዚህ ፡ ቤት ፡ ዋጋ ፡ ከሚገባው ፡ በላይ ፡ ነው
2. ተገቢ ፡ አይደለም. His demands are unreasonable. ጥያቄው ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**unreliable** የማያስተማምን
His report is unreliable. የሱ ፡ ሪፖርት ፡ የማያስተማምን ፡ ነው

**unremitting** የማያቋርጥ
He made unremitting efforts to obtain the job. ሥራውን ፡ ለማግኘት ፡ የማያቋርጥ ፡ ጥረት ፡ አደረገ

**unrest** ሽብር ፤ ሁከት
The unrest in the city is caused by famine. ከተማው ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሽብር ፡ (ሁከት) ፡ በረኃብ ፡ ምክንያት ፡ ነው

**unrestricted** ያለቁጥጥር
Unrestricted immigration poses many problems. ሰዎች ፡ ያለቁጥጥር ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ሀገር ፡ መግባታቸው ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ የሚያስከትል ፡ ነው

**be unrestricted**
*Information must be unrestricted. ዜናዎችን ፡ መቆጣጠር ፡ አይገባም

**(be) unrewarded** ገንዘብ ፡ አይገኝበትም
Voluntary service is unrewarded, but not unrewarding. ነጻ ፡ አገልግሎት ፡ ገንዘብ ፡ ባይገኝበትም ፡ ምኞትን ፡ ለማሟላት ፡ ይጠቅማል

**(be) unrewarding** ምኞትን ፡ ለማሟላት ፡ ጠቀመ
Voluntary service is unrewarded, but not unrewarding. ነጻ ፡ አገልግሎት ፡ ገንዘብ ፡ ባይገኝበትም ፡ ምኞትን ፡ ለማሟላት ፡ ይጠቅማል

**unripe** ያልበሰለ
Don't eat unripe fruit! ያልበሰለ ፡ ፍሬ ፡ አትብላ

**be unripe** ብቁ ፡ አልነበረም
He was unripe for promotion. ለደረጃ ፡ እድገት ፡ ብቁ ፡ አልነበረም

**(be) unrivaled** ወደር ፡ የለውም
His ability to get things done is unrivaled. ቅልጥፍናው ፡ ወደር ፡ የለውም

**unroll** (vt.) ዘረጋ
The merchant unrolled the carpet. ነጋዴው ፡ ስጋጃውን ፡ ዘረጋ

**unroll** (vi.) ተዘረጋ
The carpet unrolled. ምንጣፉ ፡ ተዘረጋ

**unruffled** ጸጥ ፡ ያለ
The canoe slid across the unruffled lake. ጀልባዋ ፡ ጸጥ ፡ ባለው ፡ ሐይቅ ፡ ላይ ፡ ሄደች

**be unruffled** (= act.) ሊያሳጣው ፡ አልቻለም
His suavity was unruffled by the angry man's insult. የተናደደው ፡ ሰው ፡ ስድብ ፡ የመንፈሱን ፡ እርጋታ ፡ ሊያሳጣው ፡ አልቻለም

**unruly**
1. ከሥርዓት ፡ ውጭ. He disciplined the students for their unruly behavior. ተማሪዎቹን ፡ ከሥርዓት ፡ ውጭ ፡ ተግባራቸው ፡ ቀጣቸው
2. አዋኪ. Disciplinary measures will be taken against unruly students. ባዋኪ ፡ ተማሪዎች ፡ ላይ ፡ የቅጣት ፡ እርምጃዎች ፡ ይወሰዳሉ
3. የማይታዘዝ. Poor parenthood results in unruly children. መጥፎ ፡ ወላጅ ፡ የማይታዘዙ ፡ ልጆች ፡ ያፈራል

**be unruly** ከሥርዓት ፡ ውጭ ፡ ነው
The class is unruly. ተማሪዎቹ ፡ ከሥርዓት ፡ ውጭ ፡ ናቸው

**become unruly** ሥርዓት ፡ አልጠብቅ ፡ አለ
When the mob became unruly, the police began to lay on. ሕዝቡ ፡ ሥርዓት ፡ አልጠብቅ ፡ ሲል ፡ ፖሊሱ ፡ መደባደብ ፡ ጀመረ

**unsaddle** አራገፈ
Unsaddle the horse quickly! ፈረሱን ፡ ቶሎ ፡ አራግፈው

**unsafe** አደገኛ
This street is unsafe at night. ይህ ፡ ጐዳና ፡ ከመሸ ፡ አደገኛ ፡ ነው

**unsaid, be left ~** አይነገርም
Some things are better left unsaid. አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ ባይነገሩ ፡ ይሻላል

**(be) unsanitary** ንጽሕና ፡ የለውም
This kitchen is unsanitary. ይህ ፡ ወጥ ፡ ቤት ፡ ንጽሕና ፡ የለውም

**(be) unsatisfactory** አጥጋቢ ፡ አልነበረም
His work proved unsatisfactory. ሥራው ፡ አጥጋቢ ፡ ሆኖ ፡ አልተገኘም

**(be) unscrupulous** ይሉኝታ ፡ የለውም
The car dealer is unscrupulous. መኪና ፡ ሻጩ ፡ ይሉኝታ ፡ የለውም

**(be) unseasonal** ጊዜው ፡ አይደለም
Rain in January is unseasonal. በጥር ፡ ዝናም ፡ ጊዜው ፡ አይደለም

**unseat**
1. ከኮርቻው ፡ ላይ ፡ ጣለ. The bucking horse unseated him. እንጣጥ ፡ የሚለው ፡ ፈረስ ፡ ከኮርቻው ፡ ላይ ፡ ጣለው
2. ከሥልጣን ፡ አወረደ. He unseated the incumbent in the election. በምርጫው ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ከሥልጣኑ ፡ አወረደው

**(be) unseemly** ተገቢ ፡ አይደለም
It is unseemly to gossip about neighbors. ስለ ፡ ጐረቤቶች ፡ ማውራት ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**unseen** ሳይታይ
He entered unseen. ሳይታይ ፡ ገባ
*An unseen hand guided his destiny. እንዳች ፡ ነገር ፡ ዕድሉ ፡ በስውር ፡ ይመራዋል
[See also 'sight']

**unsettle** አሸበረ
The news unsettled him. ወሬው ፡ አሸበረው

**(be) unsettled**
1. ፍጻሜ ፡ አላገኘም. The matter is still unsettled. ነገሩ ፡ አሁንም ፡ ፍጻሜ ፡ አላገኘም
2. ተከፍሎ ፡ አላለቀም. Your bill is still unsettled. ያንተ ፡ ሒሳብ ፡ ተከፍሎ ፡ አላለቀም
3. ሰው ፡ አልሰፈረበትም. Some parts of the world are still unsettled. አንዳንድ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ አሁንም ፡ ገና ፡ ሰው ፡ አልሰፈረባቸውም

**be in an unsettled condition** አልተረጋጋም
The country was in an unsettled condition many months after the war. አገሪቱ ፡ ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ለብዙ ፡ ወራት ፡ አልተረጋጋችም ፡ ነበር

**unshackle** የእግር ፡ ብረት ፡ ፈታ
They unshackled the prisoners. እስረኞቹን ፡ የእግር ፡ ብረታቸውን ፡ ፈቱላቸው

**unshaken** የማይናጋ ፡ የሆነ
He still has an unshaken belief in prophecy. በትንቢት ፡ አሁንም ፡ የማይናጋ ፡ የሆነ ፡ እምነት ፡ አለው

**(be) unsightly** ለዓይን ፡ አስቀየመ
The garbage on your lawn is unsightly. ባጥር ፡ ግቢህ ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ጥራጊ ፡ ለዓይን ፡ ያስቀይማል

**unskilled**
1. ባለሙያ ፡ ያልሆነ. An unskilled worker makes little money. ባለሙያ ፡ ያልሆነ ፡ ሠራተኛ ፡ የሚያገኘው ፡ ገንዘብ ፡ አነስተኛ ፡ ነው
2. ሙያ ፡ የማይጠይቅ. Digging ditches is unskilled labor. ጉድጓድ ፡ መቈፈር ፡ ሙያ ፡ የማይጠይቅ ፡ ሥራ ፡ ነው

**unsound**
1. የታወከ. A person who is crazy has an unsound mind. እብድ ፡ ሰው ፡ የታወከ ፡ አእምሮ ፡ አለው
2. በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ የማይገኝ. An unsound business will not last. በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ የማይገኝ ፡ ንግድ ፡ አይዘልቅም
3. የማያስተማምን. We refused to sail on an unsound ship. በማያስተማምን ፡ መርከብ ፡ አን ሳፈርም ፡ አልን
4. መሠረት ፡ የሌለው. Many theologians criticized the unsound doctrine. ብዙ ፡ የሃይማኖት ፡ ሊቃውንት ፡ መሠረት ፡ የሌለውን ፡ እምነት ፡ ነቀፉ

**be unsound** የተሟላ ፡ አልነበረም
The plan was unsound, so it failed. እቅዱ ፡ የተሟላ ፡ ስላልነበረ ፡ ሳይሳካ ፡ ቀረ

**unsparing** ለነገ ፡ የማይል
His unsparing criticism was disturbing, but useful. ለነገ ፡ የማይል ፡ ነቀፋው ፡ ቢያበሳጭም ፡ ጠቃሚ ፡ ነበር

**be unsparing** ይህ ፡ ነው ፡ አይባልም
His efforts to finish college are unsparing. ኮሌጅን ፡ ለመጨረስ ፡ ያደረገው ፡ ጥረት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አይባልም

**unspeakable** ይህ ፡ ነው ፡ የማይባል
The children shouted and danced in unspeakable joy. ልጆቹ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በማይባል ፡ ደስታ ፡ ይጮኹና ፡ ይጨፍሩ ፡ ነበር

**unstable**. ተለዋዋጭ
The weather in spring is unstable. የጸደይ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ ተለዋዋጭ ፡ ነው

**be unstable** ጽኑ ፡ አይደለም
The foundation of this house is unstable. የዚህ ፡ ቤት ፡ መሠረት ፡ ጽኑ ፡ አይደለም

**(be) unsteady**
1. መሬት ፡ አልያዘም. The ladder is unsteady; you may fall. መሰላሉ ፡ መሬት ፡ ስላልያዘ ፡ ትወድቃለህ
2. ተንቀጠቀጠ. His hands are unsteady from too much drink. ከመጠጥ ፡ ብዛት ፡ እጆቹ ፡ ይንቀጠቀጣሉ

**be unsteady on (one's) legs** እግሩ ፡ አልጠነከረም
The foal was still unsteady on its legs. የፈረሱ ፡ ውርንጭላ ፡ ገና ፡ እግሩ ፡ አልጠነከረም

**unsuccessful** ያልተሳካ
He gave up after many unsuccessful attempts and hard work. የተወው ፡ ከብዙ ፡ ያልተሳካ ፡ ጥረትና ፡ ሙከራ ፡ በኋላ ፡ ነው

**be unsuccessful** አልተሳካለትም
His intentions were praiseworthy, but unsuccessful. አልተሳካለትም ፡ እንጂ ፡ ሐሳቡ ፡ ምስጋና ፡ የሚገባው ፡ ነው

**be unsuccessful in** አልሆነለትም
+He was unsuccessful in obtaining money. ገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ አልሆነለትም

**(be) unsuitable**
1. አይገባም. A bathing suit is unsuitable in the dining room. በዋና ፡ ልብስ ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ መግባት ፡ አይገባም
2. ምቹ ፡ አይደለም. The desert is unsuitable for human settlement. በረሃ ፡ ለሰው ፡ መኖሪያ ፡ ምቹ ፡ አይደለም

**make unsuitable** ተገቢ ፡ አላደረገም
His dishonesty makes him unsuitable for the treasurer's job. ታማኝ ፡ ያለመሆኑ ፡ ለገንዘብ ፡ ያዥነቱ ፡ ሥራ ፡ ተገቢ ፡ አያደርገውም

**(be) unsuited** አይስማማም
Our methods are unsuited to new conditions. ዘዴያችን ፡ ላዲስ ፡ ሁኔታ ፡ አይስማማም

**(be) unsuspected** አልተጠረጠረም
The real thief was unsuspected. እውነተኛው ፡ ሌባ ፡ አልተጠረጠረም ፡ ነበር

**unsuspecting** ያልጠረጠረ
The hunter caught the unsuspecting animal. አዳኙ ፡ ያልጠረጠረውን ፡ አውሬ ፡ በድንገት ፡ ያዘ

**untangle**
1. ፈታ. Try to untangle the yarn! ክሩን ፡ ለመፍታት ፡ ሞክር

2. ደረሰ(በት). The detective untangled the mystery after a few days. ወንጀል ፡ መርማሪው ፡ የተሰወረውን ፡ ጉዳይ ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ደረሰበት

**(be) unthinkable** ታይቶም ፡ አይታወቅ
It is unthinkable that anyone could be so cruel. አንድ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ጨካኝ ፡ሲሆን ፡ ታይቶም ፡ አይታወቅ

**(be) untidy** ንጹሕ ፡ አልነበረም
The room was untidy. ክፍሉ ፡ ንጹሕ ፡ አልነበረም

**untie** ፈታ
Can you untie this knot for me? ይህንን ፡ ቋጠሮ ፡ ልትፈታልኝ ፡ ትችላለህ ?
He untied his horse, and it wandered. ፈረሱን ፡ ፈቶ ፡ ስድ ፡ ለቀቀው

**until** (prep.) እስከ -- ድረስ ፤ እስከ
Wait until tomorrow! እስከ ፡ ነገ ፡ ቆይ ፡ (እስከ ፡ ነገ ፡ ድረስ ፡ ቆይ)
**until** (conj.)
1. እስከ + imperfect; እስከ + imperfect + ድረስ. He waited until the sun had set. ፀሐይ ፡ እስክትጠልቅ ፡ ቆየ
He worked until he was too tired to do more. እስኪደክመው ፡ ድረስ ፡ ሠራ
2. ከ + (perfect). We cannot stop war until we get rid of the causes of war. የጦርነትን ፡ መነሾዎች ፡ ካላስወገድን ፡ ጦርነትን ፡ ልናቆም ፡ አንችልም

**untimely** (= adv.) ያለ ፡ ጊዜው
His death was untimely. ያለ ፡ ጊዜው ፡ ሞተ
**be untimely** ወቅቱ ፡ አይደለም
Rain at this time of the year is untimely. በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዝናም ፡ ወቅቱ ፡ አይደለም

**(be) untiring**
*His efforts are untiring, but success still eludes him. ጥረቱን ፡ አያቋርጥም ፡ ግን ፡ አይሳካለትም

**unto** ለ
Give unto Caesar what is Caesar's. የቄሳርን ፡ ለቄሳር ፡ ስጥ

**untold**
1. ልክ ፡ የሌለው. Wars do untold harm. ጦርነት ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ ጉዳት ፡ ያደርሳል
2. (= adv.) ሳይገለጽ. He died with his story still untold. ታሪኩ ፡ ሳይገለጽ ፡ ሞተ

**untouched** ያልነካው
+We came to a little town untouched by modern life. ዘመናዊ ፡ኑሮ ፡ ያልነካው ፡ ትንሽ ፡ ከተማ ፡ ደረስን
**be untouched** ልቡን ፡ አልነካውም
+The miser was untouched by the poor man's story. ጩቁ ፡ የድኻው ፡ ሰው ፡ ታሪክ ፡ ልቡን ፡ አልነካውም
**leave untouched** አልነካውም
The cat left the milk untouched. ድመቷ ፡ ወተቱን ፡ አልነካችውም

**untoward** የማይገባ
We disliked his untoward rudeness to the stranger. በእንግዳው ፡ ላይ ፡ የፈጸመው ፡ የማይገባ ፡ብልግና ፡ አስከፋን

**(be) untrue**
1. ውሸት ፡ ነበረ. The story of his resignation is untrue. ሥራ ፡ የመልቀቁ ፡ ወሬ ፡ ውሸት ፡ ነው
2. እውነት ፡ አልነበረም. His representation of her part in the accident was untrue. እሷ ፡ ባደጋው ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆኗ ፡ የሰጠው ፡ መግለጫ ፡ እውነት ፡ አልነበረም
**be untrue to** አልጠበቀም
She was untrue to her promise. ቃሏን ፡ አልጠበቀችም

**untruth** ውሸት
What you say is an untruth. የምትለው ፡ ውሸት ፡ ነው

**untruthful** ሐሰተኛ
Don't believe him; he is untruthful. አትመነው ፤ ሐሰተኛ ፡ ነው

**unused**
1. ክፍት. The unused space will be occupied by another building later on. ክፍቱ ፡ ቦታ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ሕንጻ ፡ ይሠራበታል
2. ያልተጠቀመበት. His mother returned the unused dishes to the store. እናቱ ፡ ያልተጠቀመችባቸው ፡ ሳሕኖች ፡ ለመደብሩ ፡ መለሰች
**be unused to** አለመደም
He is unused to traveling. መንገድ ፡ መሄድ ፡ አለመደም

**unusual**
1. ያልተለመደ. This is an unusual happening. ይህ ፡ ያልተለመደ ፡ ሁኔታ ፡ ነው
2. ልዩ ፡ የሆነ. The book's unusual title intrigues me. የመጽሐፉ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ አርእስት ፡ ይማርከኛል

**unusually** ከመጠን ፡ በላይ
He is unusually tall for his age. እንደ ፡ ዕድሜው ፡ ከሆነ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ረጅም ፡ ነው
*He is unusually well-informed. ከሰው ፡ የበለጠ ፡ ያውቃል

**unveil** (vt.) ገለጠ
The artist unveiled his monument. አርቲስቱ ፡ ሐውልቱን ፡ ገለጠ

**unveil** (vi.) ዓይኑ ፡ እርግቧን ፡ ገለጠች
The princess unveiled. ልዕልቷ ፡ ዓይኑ ፡ እርግቧን ፡ ገለጠች

**unwary** ያልተጠራጠረ
The unwary animal was easily trapped. ያልተጠራጠረው ፡ እንስሳ ፡ በቀላሉ ፡ ከወጥመድ ፡ ወደቀ

**unwelcome**
*The bees were unwelcome guests at our picnic. በሽርሽራችን ፡ ላይ ፡ ንቦቹ ፡ አወኩን

**(be) unwell** አልተሻለውም
He is still unwell and cannot come to work. አሁንም ፡ ስላልተሻለው ፡ ሥራ ፡ ሊገባ ፡ አይችልም

**feel unwell** ጤንነቱ ፡ ታወከ
He felt unwell, and so he left. ጤንነቱ ፡ ስለታወከ ፡ ሄደ

**unwholesome**
1. ለጤና ፡ጐጂ. The damp climate is unwholesome. እርጥብ ፡ አየር ፡ ለጤና ፡ ጐጂ ፡ ነው
2. መጥፎ. Unwholesome food causes bad health. መጥፎ ፡ ምግብ ፡ ጤንነትን ፡ ያበላሻል
3. የበሽተኛነት. The prisoners had an unwholesome complexion. እስረኞቹ ፡ የበሽተኛነት ፡ መልክ ፡ ይታይባቸው ፡ ነበር

**unwieldy**
*The big trunk is unwieldy. ትልቁን ፡ ሣጥን ፡ ለማንቀሳቀስ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**(be) unwilling** ፈቃደኛ ፡ አልነበረም
He is unwilling to grant my request. ጥያቄዬን ፡ ለመቀበል ፡ ፈቃደኛ ፡ አይደለም
*The taxi driver was an unwilling accomplice in the bank robbery. ታክሲ ፡ ነጂው ፡ በባንኩ ፡ ዘረፋ ፡ ሳይወድ ፡ በግድ ፡ ተባባሪ ፡ ሆነ

**unwind** (unwound)
1. ፈታታ. Unwind the rope before you use it! በገመዱ ፡ ከመጠቀምህ ፡ በፊት ፡ ፈታታው
2. ዘረጋ. He unwound the twisted wire. የተጠመዘዘውን ፡ ሽቦ ፡ ዘረጋው

**(be) unwise**
1. ሞኝነት ፡ ነው. Your decision to buy a car while you are still so deep in debt is very unwise. ይህን ፡ ያህል ፡ ዕዳ ፡ እያለብህ ፡ መኪና ፡ ለመግዛት ፡ መወሰንህ ፡ ሞኝነት ፡ ነው
2. አይገባም. In the light of his earlier behavior, it would be unwise to give him a job. የቀድሞውን ፡ ጠባዩን ፡ ስንመለከት ፡ ሥራውን ፡ ለርሱ ፡ መስጠት ፡ አይገባም

**unwittingly** ሳያውቅ
He hurt my feelings unwittingly. ሳያውቅ ፡ አስቀየመኝ

**unwonted** ያልተለመደ
His unwonted politeness surprised us. ያልተለመደው ፡ ትሕትናው ፡ አስደነቀን

**unworldly** ዓለምን ፡ የናቀ
He was a solitary, unwordly man. ብቸኛና ፡ ዓለምን ፡ የናቀ ፡ ሰው ፡ ነበር

**(be) unworthy of** ተገቢ ፡ አይደለም ፤ አይገባም
His mean thoughts are unworthy of a person who is a priest. ወራዳ ፡ አስተሳሰቡ ፡ ቄስ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ተገቢ ፡ አይደለም
Such a silly story is unworthy of belief. የዚህ ፡ ዓይነት ፡ የሞኝ ፡ ታሪክ ፡ ሊታመን ፡ አይገባም
*This remark is unworthy of a gentleman. ይህ ፡ አስተያየት ፡ ከጨዋ ፡ አፍ ፡ የሚወጣ ፡ አይደለም

**unwound**, see **unwind**

**unwrap** (unwrapped) ከፈተ
She unwrapped her birthday present. ለልደት ፡ በዓሏ ፡ የተሰጣትን ፡ ስጦታ ፡ ከፈተች

**unwritten** በጽሑፍ ፡ ያልሰፈረ
There is an unwritten law that that can't be done. ያን ፡ ማድረግ ፡ እንደማይቻል ፡ በጽሑፍ ፡ ያልሰፈረ ፡ ሕግ ፡ አለ

**unyielding** የማይበገር
The crippled man learned to walk again because of his unyielding determination. ሽባው ፡ ከማይበገረው ፡ ጥረቱ ፡ የተነሣ ፡ እንደገና ፡ ለመራመድ ፡ ቻለ

**up** (upped), v. ከፍ ፡ አደረገ
He upped his prices 10 percent. ዋጋውን ፡ በመቶ ፡ ዐሥር ፡ ከፍ ፡ አደረገው

**up** (n.), **ups and downs**
*We have certainly had our ups and downs. በእርግጥ ፡ መከራና ፡ ደስታ ፡ ተፈራርቀውብናል

**up** (adv.)
1. **ከ - - - በላይ ፡ ወጥቶ**. He lives three floors up. ከዚህ ፡ በላይ ፡ ሦስት ፡ ፎቅ ፡ ወጥቶ ፡ ይኖራል
2. **ከዚያ ፡ በላይ**. You can get a nice room for fifty dollars and up. ኀምሳ ፡ ብር ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ የከፈልክ ፡ እንደሆን ፡ ጥሩ ፡ ክፍል ፡ ታገኛለህ

**up there** እዚያ ፡ በላይ
He is up there. እዚያ ፡ እላይ ፡ ነው

**up to**
1. **ለ**. I left the matter up to him. ነገሩን ፡ ለሱ ፡ ተውኩለት
2. **የ - - ፈንታ**. It is up to us to do it. መሥራቱ ፡ የኛ ፡ ፈንታ ፡ ነው
3. **ያህል**. Because of the storm, trains were up to two hours late. በኀይለኛው ፡ ዝናም ፡ ምክንያት ፡ ባቡሮች ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ዘግይተው ፡ ደረሱ

**(be) up to** ለመሥራት ፡ አሰበ
That child is up to some mischief. ልጁ ፡ አንድ ፡ ተንኰል ፡ ለመሥራት ፡ ያስባል
*What's he up to now? አሁን ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ሊያደርግ ፡ ነው ?

**(not be) up to** ከ - - ጋራ ፡ አይወዳደርም
This new book of his isn't up to the level of the last one. ይህ ፡ አዲስ ፡ ያሳተመው ፡ መጽሐፉ ፡ ከፊተኛው ፡ ጋር ፡ አይወዳደርም

**(if it were) up to him** እንደሱ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ
If it were up to him, he wouldn't accept. እንደሱ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ባልተቀበለ ፡ ነበር

**up to now** እስካሁን
Up to now, he hasn't answered. እስካሁን ፡ መልስ ፡ አልሰጠም

**be up**
1. **ወጣ**. The sun is up. ፀሐይ ፡ ወጣች
2. **በቀለ**. The wheat is up. ስንዴው ፡ በቀለ
3. **አለቀ**. Your time is up. የተመደበልህ ፡ ጊዜ ፡ አልቋል
4. (= act.) **አወጣ**. +His hand is up. እጁን ፡ አውጥቷል
*What's up? ታዲያስ ?
*Is he up already? ከእንቅልፉ ፡ ተነሥቷል ?
*Prices are up. ኑሮ ፡ ተወዷል

**be up against** ተጋፈጠ
He is up against a formidable opponent. ከማይገፋት ፡ ባለጋራ ፡ ተጋፍጧል

**be up and about** ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ
He is now able to be up and about. አሁን ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ማለት ፡ ችሏል

**be up and around** ተነሥቶ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ
When will she be up and around? መቼ ፡ ተነሥታ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ትላለች ?

**be up for** ተወዳደረ
He is up for class president. የክፍሉ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ለመሆን ፡ ይወዳደራል

**be up late** አመሸ
I was up late last night. ትላንት ፡ አምሽቼ ፡ ነበር

**be up to** ደረሰ
Your work is not up to standard. ሥራህ ፡ ከተፈለገው ፡ ወሰን ፡ አልደረሰም

**be up to something** አንድ ፡ የሚሠራው ፡ ተንኰል ፡ አለ
Their actions are rather secretive, so they may be up to something. ተግባራቸው ፡ በጣም ፡ ምስጢራዊ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ የሚሠሩት ፡ ተንኰል ፡ አለ

**feel up to** ቻለ
Do you feel up to going out so soon after being sick? ታመህ ፡ ቆይተህ ፡ ቶሎ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ልትወጣ ፡ ትችላለህ ?
[See also 'air, par']

## upbraid ገሠጸ
The captain upbraided his men for falling asleep. ሻምበሉ ፡ ጭፍሮቹ ፡ ስለተኙ ፡ ገሠጻቸው

## upbringing አስተዳደግ
Politeness is a mark of good upbringing. ትሕትና ፡ የጥሩ ፡ አስተዳደግ ፡ ምልክት ፡ ነው
[See also 'gentle']

## update
1. **አሻሽሎ ፡ጻፈ**. The scholar updated his dictionary. ሊቁ ፡ መዝገበ ፡ ቃላቱን ፡ አሻሽሎ ፡ ጻፈው
2. **እንደጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ አስተካከለ**. They update the report every year. ሪፖርቱን ፡ በያመቱ ፡ እንደጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ ያስተካክላሉ

## upgrade በደረጃ ፡ ከፍ ፡ አደረገ
The boss upgraded all the employees. ሹሙ ፡ ሠራተኞቹን ፡ በደረጃ ፡ ከፍ ፡ አደረጋቸው

## upheaval
1. **ረብሻ ፤ ብጥብጥ**. The upheaval left many people homeless. ረብሻው ፡ (ብጥብጡ) ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ መጠጊያ ፡ አሳጣ

## upheld, see uphold

## uphill (adv.)
1. **ዳገቱን**. We walked uphill to spare the horse.

ፈረሱን ፡ ከድካም ፡ ለማዳን ፡ ዳገቱን ፡ በእግር ፡ ወጣን
2. አቀበቱን. We walked a mile uphill. አቀበቱን ፡ አንድ ፡ ማይል ፡ ተጓዝን

**uphill** (adj.)
*This was an uphill battle against illness. ይህ ፡ ብዙ ፡ ጥረት ፡ የሚያስፈልገው ፡ የበሽታ ፡ መከላከል ፡ ሥራ ፡ ነበር

**uphill road** ዳገት
It is an uphill road all the way. መንገዱ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ዳገት ፡ ነው

**uphold** (upheld)
1. አስከበረ. We must uphold the law. ሕጉን ፡ ማስከበር ፡ አለብን
2. ጠበቀ. You must uphold the honor of your family. የቤተሰብህን ፡ ስም ፡ መጠበቅ ፡ አለብህ
3. ደገፈ. The principal upheld the teacher's decision. ሥራ ፡ መሪው ፡ ያስተማሪውን ፡ ውሳኔ ፡ ደገፈ
4. ተሸከመ. Marble columns uphold the roof. የእብነ ፡ በረድ ፡ ምሰሶዎች ፡ ጣሪያውን ፡ ተሸክመውታል

**upholster** አዲስ ፡ ፍራሽና ፡ ልባስ ፡ አደረገ
Upholster this chair; it looks very shabby. ወንበሩን ፡ አዲስ ፡ ፍራሽና ፡ ልባስ ፡ አድርግለት ፤ በጣም ፡ አስቀይሟል

**upkeep**
1. በያመቱ ፡ ማደስ. The upkeep of the building costs $18,000 a year. ሕንጻውን ፡ በያመቱ ፡ ለማደስ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ይፈጃል
2. (= verbal noun) ማስጠገን. The upkeep of a car is very expensive. መኪናን ፡ ማስጠገን ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ ነው

**uplift** (v.) ቀሰቀሰ
The words of the general uplifted the troops. የጄኔራሉ ፡ ንግግር ፡ ሰራዊቱን ፡ ቀሰቀሰው

**uplift** (n.), **give an ~** ንቃት ፡ ተሰማው
+The success gave him quite an uplift. ስለተሟላለት ፡ ንቃት ፡ ተሰማው

**uplifted** (adj.) ቀና ፡ ያለ
I see trees with uplifted branches. ቀና ፡ ያሉ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ያሏቸው ፡ ዛፎች ፡ አያለሁ

**be uplifted** ተነቃቃ
His heart was uplifted by the good news. ጥሩ ፡ ነገር ፡ ሲሰማ ፡ መንፈሱ ፡ ተነቃቃ

**upon** ላይ
The book was lying upon the table. መጽሐፉ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ነበር
[See also 'word']

**upper** የላይ
His upper lip is sore. የላይ ፡ ከንፈሩ ፡ ቆስሏል
[See also 'hand']

**uppermost**
1. የመጨረሻው ፡ ከፍተኛ. The uppermost story has the most sunlight. የመጨረሻው ፡ ከፍተኛ ፡ ፎቅ ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ የፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ያገኛል
2. የመጀመሪያ. School reform is a matter of uppermost importance. ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ማሻሻል ፡ የመጀመሪያው ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው
*The thought of her was uppermost in his mind. ምን ፡ ጊዜም ፡ ከአእምሮው ፡ አትጠፋም

**upright** (adj.)
1. ቀጥ ፡ ያለ. An upright post marks the spot where the martyr was killed. ቀጥ ፡ ያለው ፡ ዕንጨት ፡ ሰማዕቱ ፡ የተገደለበትን ፡ ቦታ ፡ ያመለክታል
2. ትክክለኛ. Everyone admired the upright judge. ሁሉም ፡ ሰው ፡ ትክክለኛውን ፡ ዳኛ ፡ አደነቀ

**upright** (adv.) ቀጥ ፡ ብሎ
He stood upright. ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ

**uprising** ዐመፅ ፤ ረብሻ
The uprising in the Congo was suppressed. ኮንጎ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ ዐመፅ ፡ (ረብሻ) ፡ ተደመሰሰ

**uproar** ሁካታ
The uproar had to be quieted by police. ሁካታው ፡ በፖሊስ ፡ መረጋጋት ፡ ነበረበት

**uproot**
1. ነቃቀለ. The storm uprooted several trees. ዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ብዙ ፡ ዛፎች ፡ ነቃቀለ
2. ነቅሎ ፡ ጣለ. The wind uprooted the telephone pole. የስልኩን ፡ ዕንጨት ፡ ነፋስ ፡ ነቅሎ ፡ ጣለው
3. ካለበት ፡ እንዲሰደድ ፡ አደረገ. War uprooted many families. ጦርነት ፡ ብዙ ፡ ቤተሰቦችን ፡ ካሉበት ፡ እንዲሰደዱ ፡ አደረጋቸው

**upset** (upset), vt.
1. አበሳጨ. Nothing ever upsets him. ምንም ፡ ነገር ፡ አያበሳጨውም

2. አሸበረ. The grievous news upset the whole family. አሳዛኙ ፡ ወሬ ፡ ቤተሰቡን ፡ ሁሉ ፡ አሸበረ

3. አሳመመ. The bad apple upset his stomach. የበሰበሰው ፡ ቱፋ ፡ ሆዱን ፡ አሳመመው

4. አጨናገፈ. The rain upset our plans. ዝናቡ ፡ እቅዳችንን ፡ አጨናገፈው

5. አመሰቃቀለ. Don't upset my books! መጽሐፎቼን ፡ አታመሰቃቅልብኝ

6. ገለበጠ. The cat upset its bowl of milk. ድመቷ ፡ የወተት ፡ ሳሕኗን ፡ ገለበጠችው

7. ሳይታሰብ፡አሸነፈ. Our swimming team upset the champions. የዋና ፡ ቡድናችን ፡ ሻምፒዮናዎቹን ፡ ሳይታሰብ ፡ አሸነፈ

**upset** (vi.) ተገለበጠ
The boat upset in a heavy wind. ጀልባው ፡ በኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ምክንያት ፡ ተገለበጠ

**upset** (n.), **suffer an ~** ሳይታሰብ ፡ ተሸነፈ
The football team suffered an upset. የእግር ፡ ኳስ ፡ ቡድናችን ፡ ሳይታሰብ ፡ ተሸነፈ

**upset** (adj.), **~ stomach**
I have an upset stomach. ሆዴን ፡ አሞኛል

**be upset** ተበሳጨ
He was all upset when he found he had failed the exam. ፈተናውን ፡ መውደቁን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ተበሳጨ

**upshot** የነገሩ ፡ ፍጻሜ
The upshot of it all was that he was fired. የነገሩ ፡ ፍጻሜ ፡ የሱ ፡ ከሥራ ፡ መወገድ ፡ ነበር

**upside down** ዘቅዝቆ ፤ የዝቅዝቅ
He held the baby upside down. ልጁን፡ዘቅዝቆ፡ያዘው
The ape was hanging upside down. ጦጣዋ ፡ የዝቅዝቅ ፡ ተንጠለጠለች

**be upside down** ተዘቀዘቀ
That picture is upside down. ሥዕሉ፡ተዘቅዝቋል

**fall upside down** በአፍ ፡ ጢሙ ፡ ተደፋ
The child fell upside down. ልጁ ፡ በአፍ፡ጢሙ፡ተደፋ

**upstairs** (adj.) ፎቅ ፡ ላይ ፡ ያለ
The upstairs apartment is vacant. ፎቅ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አፓርትማ ፡ አልተያዘም

**upstairs** (adv.) ፎቅ
Go upstairs! ፎቅ ፡ ውጣ!

**upstanding** ታማኝ
He is a fine, upstanding young man. እሱ ፡ ጥሩ ፡ ታማኝ ፡ ወጣት ፡ ሰው ፡ ነው

**upstart**
*He is nothing but an upstart. ሀብት ፡ ያገኘው ፡ በቅርቡ ፡ ነው

**upstream** በወንዙ ፡ ላይ ፡ ሽቅብ
It is hard to paddle upstream. በወንዙ ፡ ላይ ፡ ሽቅብ ፡ ለመቅዘፍ ፡ ያስቸግራል

**upsurge** ከፍ ፡ ያለ ፡ እንቅስቃሴ
There was an upsurge of interest in Africa after the movie came out. ፊልሙ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ አፍሪቃ ፡ ከፍ፡ ያለ ፡ የመንፈስ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ተፈጠረ

**up-to-date** ዘመናዊ
Her clothes are up-to-date. ልብሶቿ ፡ ዘመናዊ ፡ ናቸው
She has an up-to-date kitchen. የወጥ ፡ ቤቷ ፡ ዘመናዊ ፡ ነው

**be up-to-date on** ተከታተለ
I am not up-to-date on the developments in Africa. አፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ በቅርቡ ፡ የተደረጉትን ፡ ነገሮች ፡ አልተከታተልኩም

**bring one up-to-date** ከጊዜ ፡ ጋር ፡ አስተዋወቀ
He brought me up-to-date on what had happened during my absence. እኔ ፡ በሌለሁበት ፡ ጊዜ ፡ የተደረገውን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ከጊዜው ፡ ጋር ፡ አስተዋወቀኝ

**uptown**
*Most houses are uptown; most shops are downtown. አብዛኛዎቹ ፡ የመኖሪያ ፡ ቤቶች ፡ በከተማው ፡ የመኖሪያ ፡ ዳር ፤ አብዛኛዎቹ ፡ ሱቆች ፡ ደግሞ ፡ በአራዳ ፡ ይገኛሉ

**upturn** (n.), **take an ~** ማደግ ፡ ጀመረ
As business improved, his income took an upturn. ንግድ ፡ እየተሻሻለ ፡ ሲሄድ ፡ ገቢው ፡ ማደግ ፡ ጀመረ

**upward** (adj.)

1. ወደ ፡ ላይ. The upward flight of the birds indicates that something has frightened them. ወፎቹ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ መብረራቸው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ያስደነገጣቸው ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል

2. (= adv.) እየቀጠለ. The upward trend of prices worries many people. ዋጋ ፡ እየቀጠለ ፡ መሄዱ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያሳስባል

**upward** (adv.)

1. ወደ ፡ ሰማይ. The rocket shot upward. ሮኬቷ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ መጠቀች

2. ወደ፡ላይ. He climbed upward till he reached the apple. ቱፋውን ፡ እስኪደርስበት ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወጣ

3. ከዚያም ፡ በላይ. Children of twelve years and upward must pay full fare. ዕድሜያቸው ፡ ዐሥራ ፡ ሁለትና ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ ሙሉ ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ አለባቸው
*From ten years of age upward, she has studied French. ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሲሆናት ፡ ጀምራ ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ተምራለች

**upwards** ወደ ፡ ሰማይ
He looked upwards. ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንጋጠጠ

**upwards of** ከ -- በላይ
Upwards of fifty people came. ከኀምሳ ፡ ሰው ፡ በላይ ፡ መጣ
Repairs of the car will cost upwards of $100. መኪናውን ፡ ለማሠራት ፡ ከመቶ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ ያስፈልጋል

**urban** የከተማ
Urban life is different from rural life. የከተማ ፡ ኑሮ ፡ ከገጠር ፡ ኑሮ ፡ የተለየ ፡ ነው

**urban areas** ከተማዎች
Urban areas are getting congested. ከተማዎች ፡ እየተጨናነቁ ፡ ሄደዋል

**urbane** ጨዋ
The newcomer was an urbane and charming fellow. አዲስ ፡ መጪው ፡ ጨዋና ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነበር

**urchin** ዱሪዬ ፡ ልጅ
The urchins pursued them trying to get them to buy postcards. ዱሪዬዎቹ ፡ ልጆች ፡ ካርድ ፡ እንዲገዟቸው ፡ እየተከተሉ ፡ ይነዘንዟቸዋል

**urge** (v.)
1. ለመነ. She urged us to stay longer. ትንሽ ፡ እንድንቆይ ፡ ለመነችን
2. በጥብቅ ፡ አሳሰበ ፤ አጥብቆ ፡ አሳሰበ. The preacher urged the importance of right living. ሰባኪው ፡ የትክክለኛ ፡ አኗኗርን ፡ አስፈላጊነት ፡ በጥብቅ ፡ አሳሰበ
His doctor urges a change of climate. ሐኪሙ ፡ አየር ፡ እንዲለውጥ ፡ አጥብቆ ፡ አሳስቧል
3. አጥብቆ ፡ አስገነዘበ. He urged the importance of hard work to his pupils. በርትቶ ፡ የመሥራትን ፡ ጥቅም ፡ ለተማሪዎቹ ፡ አጥብቆ ፡ አስገነዘበ
4. ገፋፋ. We urged Jim to finish college. ጂምን ፡ የኮሌጅ ፡ ትምህርት ፡ እንዲጨርስ ፡ ገፋፋነው
Hunger urged him to steal. ረኃብ ፡ እንዲሰርቅ ፡ ገፋፋው
5. አነሣሣ. He urged the workers to strike. ሠራተኞቹ ፡ ሥራ ፡ እንዲያቆሙ ፡ አነሣሣቸው

**urge on**
1. አበረታታ. The foreman urged his workmen on. ካቦው ፡ ሠራተኞቹን ፡ አበረታታቸው
2. ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ እንዲሄድ ፡ ኰረኰረ. My horse was flagging, but I urged him on. ፈረሴ ፡ ተዳክሞ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ እንዲሄድ ፡ ኰረኰርኩት
3. እንዲበላ ፡ ገፋፋው. He urged another piece of cake on me. ሌላ ፡ ኬክ ፡ እንድበላ ፡ ገፋፋኝ
*The driver urged on his horse with a whip. ጋሪ ፡ ነጂው ፡ ፈረሱ ፡ እንዲፈጥን ፡ ገረፈው

**urge** (n.), **feel the ~**
*I felt the urge to tell him. ንገረው ፡ ንገረው ፡ አለኝ

**urgency** አስቸኳይነት
The urgency of our needs must be recognized. የሚያስፈልጉንን ፡ ነገሮች ፡ አስቸኳይነት ፡ መታወቅ ፡ አለበት
*The urgency of public opinion forced him to resign. የሕዝቡ ፡ አስተያየት ፡ በጣም ፡ ስላየለ ፡ ሥራውን ፡ እንዲለቅ ፡ ተገደደ

**urgent**
1. አስቸኳይ. I have an urgent request. አስቸኳይ ፡ ጥያቄ ፡ አለኝ
2. (= adv.) ባስቸኳይ. The earthquake victims are in urgent need of food and medicine. በመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ምክንያት ፡ የተጐዱት ፡ ሰዎች ፡ ምግብና ፡ መድኃኒት ፡ ባስቸኳይ ፡ ያስፈልጋቸዋል

**urgently** ባስቸኳይ
I spoke to him urgently about it. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ባስቸኳይ ፡ አነጋገርኩት

**urinate** ሸና
It is unlawful to urinate in the street. መንገድ ፡ ላይ ፡ መሽናት ፡ ክልክል ፡ ነው

**urine** ሽንት
The doctor examined his urine. ሐኪሙ ፡ ሽንቱን ፡ መረመረ

**urn** [እግራም ፡ እንስራ]

**us**
1. እኛን. The teacher calls us. መምህሩ ፡ እኛን ፡ ጠራ
2. ለኛ. They are going to tell us, not you. የሚነግሩት ፡ ለኛ ፡ እንጂ ፡ ላንተ ፡ አይደለም

3. — ን. Give us our daily bread! የዕለት ፡ እን
ጀራችንን ፡ ስጠን
She saw us. አየችን

**(be) usable** አገለገለ
Is this chair still usable? ይህ ፡ ወንበር ፡ አሁን
ም ፡ ያገለግላል?

**usage**
1. ልማድ. In this case, usage is the best guide. ለዚህ ፡ ዋና ፡ መመሪያ ፡ የሚሆነው ፡ ልማድ ፡ ነው
2. አገባብ. Usage determines what is good Amharic. ጥሩ ፡ አማርኛ ፡ የቱ ፡ እንደሆነ ፡ አገ
ባብ ፡ ይወስናል
*His shoes were worn out from hard usage. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚያደርገው ፡ ጫማው ፡ አልቋል

**use** (v.)
1. ተጠቀመ(በት). What toothpaste do you use? የምትጠቀምበት ፡ የጥርስ ፡ ሳሙና ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡
ነው?
Who used this book last? ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ በመጨረሻ ፡ የተጠቀመበት ፡ ማነው?
2. አዋለ. He used old boxes and bottles as containers for his food. አሮጌ ፡ ጠርሙሶችንና ፡ ሣጥኖችን ፡ ለምግብ ፡ ማስቀመጫ ፡ አዋለ
3. ጨመረ. She uses a lot of onion in her salads. ሰላጣው ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሽንኩርት ፡ ትጨምራለች
4. ሰጠ. May I use your name as a reference? በአስረጅነት ፡ ስምህን ፡ ልስጥ?
5. አደረገ. We'll use this room as a bedroom. ይህን ፡ ክፍል ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ እናደርገዋለን
*How much electricity did we use last week? ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ መብራት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ቈ
ጠረ?

**use badly** አጕላላ
The foreman used his workers badly. ካቦው ፡ ሠራተኞቹን ፡ አጕላላቸው

**use up** ጨረሰ
I have used up all my money. ገንዘቤን ፡ በሙሉ ፡ ጨርሻለሁ

**use** (n.)
1. ጥቅም. This tool has many uses. ይህ ፡ መሣ
ሪያ ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ አለው
2. አገልግሎት. Artificial light cannot compare with daylight for general use. ለጠቅላላ ፡ አገል
ግሎት ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ብርሃን ፡ ከፀሐይ ፡ ጋር ፡ አይወዳደርም
English makes widespread use of verbs and prepositions. በእንግሊዝኛ ፡ ግስና ፡ መስተዋድድ ፡ ያላቸው ፡ አገልግሎት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው
*He lost the use of his hand. እጁ ፡ አይሠራለትም

**be in use**
1. አገለገለ. Huts and similar habitations were in use in ancient times. ጥንት ፡ ጎጆዎችና ፡ እነሱንም ፡ የመሳሰሉት ፡ ለመኖሪያ ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር
2. ተሠራ(በት). This mill is still in use. ይህ ፡ ወፍ
ጮ ፡ ቤት ፡ አሁንም ፡ ይሠራበታል
*The telephone is in use in Ethiopia. በኢትዮጵ
ያ ፡ ውስጥ ፡ የስልክ ፡ አገልግሎት ፡ አለ

**be no longer in use** መዋሉ ፡ ቀረ
The sword is no longer in use as a weapon in war. ጐራዴ ፡ ለጦር ፡ መሣሪያ ፡ መዋሉ ፡ ቀርቷል

**be of use** ጠቀመ
Will that be of any use to you? ያ ፡ ይጠቅም
ሃል?

**come into use** ተለመደ
Living in apartments is just coming into use in Addis Ababa. አዲስ ፡ አበባ ፡ አፓርትማ ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ አሁን ፡ ገና ፡ እየተለመደ ፡ ሄደ

**go out of use** ቀረ
The custom of chaining the creditor to the debtor has gone out of use. አበዳሪና ፡ ተበዳሪን ፡ የማቈራኘት ፡ ልማድ ፡ ቀርቷል

**have no use for**
1. አልወደደም. He had no use for that sort of thing. ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ አይወድም
2. አላስፈለገ(ውም). +I have no use for two books on the same subject. ስለ ፡ አንድ ፡ ጉዳይ ፡ የሚናገሩ ፡ ሁለት ፡ መጻሕፍት ፡ አያስፈልጉኝም

**have the use of**
*May I have the use of your car? መኪናህን ፡ ልታውሰኝ ፡ ትችላለህ?

**it's no use**
1. ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ. It's no use; we've got to do it. ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ሥራውን ፡ ማከናወን ፡ አለብን
2. ዋጋ ፡ የለውም. It's no use hurrying. መጣደ
ፍ ፡ ዋጋ ፡ የለውም

**make use of** ተጠቀመ(በት)
He made good use of the opportunity. ያጋ
ጠመውን ፡ ዕድል ፡ በደንብ ፡ ተጠቀመበት
*Please don't make any use of this information! የነገርኩህን ፡ በልብህ ፡ ያዘው

**put to use** ጥቅም ፡ ላይ ፡ አዋለ
He put his learning to use when he returned from abroad. ከውጭ ፡ አገር ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ትምህርቱን ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ አዋለ

**what's the use of**
*What's the use of your worrying? ብትጨነቅ ፡ ምን ፡ ታተርፋለህ?
[See also 'consign, external']

**used** (adj.)
1. የሠራ. I bought a used car. አንድ ፡ የሠራች ፡ መኪና ፡ ገዛሁ
2. ያገለገለ. The store sells used books. መደብሩ ፡ ያገለገሉ ፡ መጽሐፎች ፡ ይሸጣል

**used to** (imperfect) + ነበር
I used to live here. እዚህ ፡ እኖር ፡ ነበር

**be used**
1. ተያዘ. The telephone is being used. ስልኩ ፡ ተይዟል
2. አገለገለ. Mineral oil is used in cars. የነዳጅ ፡ ዘይት ፡ ለመኪና ፡ ያገለግላል

**be used to** ለመደ
She's used to getting up at seven o'clock. ከጧቱ ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ መነሣት ፡ ለምዳለች

**be (all) used up** አለቀ
The money is all used up. ገንዘቡ ፡ አልቋል

**get one used to** አስለመደ
I've got my children used to putting their things away. ልጆቼ ፡ እቃቸውን ፡ በደንብ ፡ ማስቀመጥን ፡ አስለምጃቸዋለሁ

**useful** ጠቃሚ
I have found this book very useful. ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ጠቃሚ ፡ ሆኖ ፡ አግኝቼዋለሁ

**be useful** ጠቀመ
This book is useful for another purpose. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ለሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ይጠቅማል

**make oneself useful** ረዳ
She makes herself useful around the house. እቤት ፡ ውስጥ ፡ ትረዳለች

**usefulness** ጠቃሚነት
I have grave doubts about the usefulness of his plan. ስለ ፡ እቅዱ ፡ ጠቃሚነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥርጣሬ ፡ አድሮብኛል
[See also 'outlive']

**useless**
1. ከንቱ. It's useless to try to convince him. እሱን ፡ ለማግባባት ፡ መሞከር ፡ ከንቱ ፡ ነው
2. ጥቅም ፡ ቢስ. This thing is useless. ይህ ፡ ነገር ፡ ጥቅም ፡ ቢስ ፡ ነው
3. ዋጋ ፡ ቢስ. Earthly possessions are useless in heaven. ምድራዊ ፡ ንብረቶች ፡ በሰማይ ፡ ቤት ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ናቸው
4. የማይረባ. The new secretary proved to be useless. አዲሱ ፡ ጸሐፊ ፡ የማይረባ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ

**be useless** አልጠቀመም ፤ ጥቅም ፡ የለውም ፤ ዋጋ ፡ የለውም
This map is useless to me. ይህ ፡ ካርታ ፡ ምንም ፡ አይጠቅመኝም
It's useless to fight anymore. ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ መዋጋት ፡ ጥቅም ፡ (ዋጋ) ፡ የለውም

**user** በ --- የሚጠቀም ፡ ሰው
There are more telephone users in the U.S. than elsewhere. ከየትም ፡ አገር ፡ ይልቅ ፡ በቴሌፎን ፡ የሚጠቀሙ ፡ ሰዎች ፡ በአሜሪካ ፡ ይበዛሉ

**usher** (v.) መራ
He ushered me to my seat. መቀመጫ ፡ ወዳለበት ፡ መራኝ

**usher in** ይዞ ፡ ደረሰ
The new year ushered in a period of prosperity. አዲሱ ፡ ዓመት ፡ ብልጽግና ፡ ይዞ ፡ ደረሰ

**usher** (n.) አስተናባሪ
The usher will show you to your seats. አስተናባሪው ፡ ወደ ፡ መቀመጫችሁ ፡ ይመራችኋል

**usual**
1. የተለመደ. Our usual hours are from 8 to 3. የተለመደው ፡ የሥራ ፡ ሰዓታችን ፡ ከሁለት ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ነው
2. የተለመደ ፡ ጊዜ. School might close a week earlier than usual. ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከተለመደው ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ይዘጋ ፡ ይሆናል

**as usual**
1. እንደተለመደው. It's raining as usual. እንደተለመደው ፡ ይዘንባል
2. እንደ ፡ ወትሮው. The bus was terribly crowded, as usual. አውቶቡሱ ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ ተጨናንቆ ፡ ነበር

**usually** አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፤ ባዘቦቱ
I usually visit them twice a week. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በሳምንት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ እጠይቃቸዋለሁ
This suit usually sells for thirty dollars. ይህ ፡ ልብስ ፡ ባዘቦቱ ፡ በሠላሳ ፡ ብር ፡ ይሸጣል

**usufruct** አላባ ፡ ገለባ
The usufruct of the property amounts to several hundred dollars. ከንብረቱ ፡ የሚገኘው ፡ አላባ ፡ ገለባ ፡ ብዙ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ነው

**usurp** አላግባብ ፡ ያዘ
The pretender usurped the throne. ሐሰተኛው ፡ ወራሽ ፡ ነኝ ፡ ባዩ ፡ አልጋውን ፡ አላግባብ ፡ ያዘው

**usurper** ያላግባብ ፡ ዙፋኑን ፡ የያዘ ፡ ሰው
The usurper was later crowned king. ያላግባብ ፡ ዙፋኑን ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ በኋላ ፡ በንጉሥነት ፡ ዘውድ ፡ ጫነ

**usurer** አራጣ ፡ አበዳሪ
The usurer got rich from poor people. አራጣ ፡ አበዳሪ ፡ ድኾችን ፡ በመንጠቅ ፡ ሀብታም ፡ ሆነ

**usury** በአራጣ ፡ ማበደር
The church condemns usury. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በአራጣ ፡ ማበደርን ፡ ታወግዛለች

**utensil** እቃ
Kitchen utensils are now made of aluminum. ዛሬ ፡ የወጥ ፡ ቤት ፡ እቃዎች ፡ የሚሠሩት ፡ በአሉሚኒየም ፡ ነው

**uterus** ማሕፀን
The foetus grows inside the uterus. ፅንስ ፡ የሚያድገው ፡ በማሕፀን ፡ ውስጥ ፡ ነው

**(be) utilitarian** ለተፈላጊው ፡ ተግባር ፡ ነው
The design of this building is utilitarian, not aesthetic. ሕንጻው ፡ የተሠራው ፡ ለተፈላጊው ፡ ተግባር ፡ እንጂ ፡ ለጌጥ ፡ አይደለም

**utility** (utilities)
1. ጠቃሚነት. The utility of this machine is questionable. የዚህ ፡ መሣሪያ ፡ ጠቃሚነት ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው
2. መገልገያ. The public utilities must be in government hands only. የሕዝብ ፡ መገልገያዎች ፡ ሁሉ ፡ በመንግሥት ፡ እጅ ፡ መሆን ፡ አለባቸው

**utilize** ተጠቀመ
He utilized all his talents to achieve success. ሥራው ፡ እንዲሳካለት ፡ ባለው ፡ ችሎታ ፡ ሁሉ ፡ ተጠቀመ

**utmost** (n.) የተቻለውን ፡ ያህል
He did his utmost to finish the assignment. የተሰጠውን ፡ ሥራ ፡ ለመጨረስ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ሠራ

**to the utmost** እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ
He enjoyed himself to the utmost. እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ ተደሰተ

**utmost** (adj.)
1. ከፍተኛ. He was in the utmost delight at having received the prize. ሽልማቱን ፡ ስለተቀበለ ፡ ከፍተኛ ፡ ደስታ ፡ ተሰምቶታል
2. ከሁሉም ፡ የባሰ. He is in the utmost danger right now. አሁን ፡ ከሁሉም ፡ በባሰ ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ነው
3. መጨረሻ. He walked to the utmost end of the cliff. እስከ ፡ ገደሉ ፡ መጨረሻው ፡ ጫፍ ፡ ድረስ ፡ ሄደ

**of the utmost importance**
The matter is of the utmost importance. ነገሩ ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ ነው
[See also 'tax']

**utopian**
*His idea of a state is utopian. በሱ ፡ ሐሳብ ፡ መንግሥት ፡ ሲባል ፡ ፍጹም ፡ መሆን ፡ አለበት

**utter** (v.)
1. አሰማ. She uttered a dolorous cry. አሳዛኝ ፡ ልቅሶ ፡ አሰማች
2. ተነፈሰ. I couldn't utter a single word. አንዲት ፡ ቃል ፡ እንኳ ፡ ለመተንፈስ ፡ አልቻልኩም
[See also 'oath, sigh, threat']

**utter** (adj.) ፍጹም
They lived in utter misery. በፍጹም ፡ ድኽነት ፡ ይኖሩ ፡ ነበረ
*Things are in a state of utter confusion. ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ምስቅልቅሉ ፡ ወጥቷል

**utterance**
1. የተናገረው ፡ ቃል. He wrote down every utterance of the witness. ምስክሩ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ጻፈ
2. አነጋገር. Her utterance was hoarse. አነጋገሯ ፡ ጉርናና ፡ ነበር

**give utterance to** ገለጸ
He gave utterance to his feelings. ስሜቱን ፡ ገለጸ

**utterly** ፈጽሞ
The police are utterly without a clue in the case. ፖሊሶቹ ፡ ስለ ፡ ነገሩ ፡ ፈጽሞ ፡ ፍንጭ ፡ የላቸውም
*I am utterly exhausted. ሙትት ፡ ብያለሁ

**uttermost** የሚቻለውን ፡ ሁሉ
He did his uttermost to win the prize. ሽልማቱን ፡ ለማግኘት ፡ የሚቻለውን ፡ ሁሉ ፡ አደረገ

**uvula** እንጥል
His uvula is swollen. እንጥል ፡ ወርዶታል

# V

**vacancy** (vacancies)
1. ክፍት ፡ ቦታ. The vacancy in our office was filled by a young college graduate. በመሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ የነበረው ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ ከኮሌጅ ፡ በተመረቀ ፡ ባንድ ፡ ወጣት ፡ ተይዟል
2. ያልተያዘ ፡ ክፍል. Is there a vacancy in this hotel? እዚህ ፡ ሆቴል ፡ ውስጥ ፡ ያልተያዘ ፡ ክፍል ፡ አለ ?
3. ባዶ ፡ ስፍራ. There was a vacancy in the parking lot. መኪናው ፡ ማቆሚያ ፡ ቦታ ፡ ባዶ ፡ ስፍራ ፡ ነበር

**vacant**
1. ባዶ. A vacant chair is left at the table in honor of the late president. ስለሞቱት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ክብር ፡ በግብዣው ፡ ላይ ፡ ባዶ ፡ ወንበር ፡ ተተወ
2. ክፍት. A position in our office is vacant. በመሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ አንድ ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ አለ

**be vacant**
1. አልተያዘም. The upstairs apartment is vacant. ፎቅ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አፓርትማ ፡ አልተያዘም
2. ተለቀቀ. The apartment has been vacant for a week. አፓርትማው ፡ ከተለቀቀ ፡ አንድ ፡ ሳምንቱ ፡ ነው
[See also 'stare']

**vacate** ለቀቀ
When are you going to vacate the apartment? አፓርትማውን ፡ የምትለቀው ፡ መቼ ፡ ነው ?

**vacation** (v.) የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ አሳለፈ
We vacationed in the mountains. የዕረፍት ፡ ጊዜያችንን ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ አሳለፍን

**vacation** (n.) የዕረፍት ፡ ጊዜ
The children are looking forward to their vacation. ልጆቹ ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜያቸውን ፡ በጉጉት ፡ ይጠባበቃሉ

**vaccinate** ከተበ
They vaccinated us against smallpox. ፈንጣጣ ፡ ከተቡን

**vaccination** ክትባት
My vaccination left a large scar. ክትባቱ ፡ ትልቅ ፡ ጠባሳ ፡ ሆነብኝ

**vaccine**
1. የክትባት ፡ መድኃኒት. There is not enough vaccine at present. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሚበቃ ፡ የክትባት ፡ መድኃኒት ፡ የለም
2. ክትባት. Vaccines help to combat disease. ክትባት ፡ በሽታን ፡ ለመከላከል ፡ ይረዳል

**vacillate**
1. ዋዠቀ. He vacillates between hope and fear. በተስፋና ፡ በፍርሃት ፡ መሀከል ፡ ይዋዥቃል
2. አወላወለ. He vacillated until we lost all interest in his opinion. አስተሳሰቡ ፡ ችላ ፡ እስኪያሰኘን ፡ ድረስ ፡ አወላወለ

**vacuum** አየር ፡ የሌለበት ፡ ባዶ ፡ ስፍራ
You cannot breathe in a vacuum. አየር ፡ በሌለበት ፡ ባዶ ፡ ስፍራ ፡ ለመተንፈስ ፡ አትችልም

**vagabond** (n.) ወሮበላ
The police arrested the vagabond for stealing. ፖሊሱ ፡ ወሮበላውን ፡ በሌብነት ፡ ያዘው

**vagabond** (adj.) የዘላን
There are people who lead a vagabond life. የዘላን ፡ ኑሮ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ አሉ

**vagary** (vagaries) እንግዳ ፡ ጠባይ
She was puzzled by the vagaries of her husband's conduct. በባሏ ፡ እንግዳ ፡ ጠባይ ፡ ግራ ፡ ገብቷት ፡ ነበር

**vagina** እምስ

**vagrant** (n.) ቀፋፊ
Vagrants come to our house to beg for food. ቀፋፊዎች ፡ ምግብ ፡ ለመና ፡ ወደ ፡ ቤታችን ፡ ይመጣሉ

**vagrant** (adj.) የቀፈፋ
He leads a vagrant life. የቀፈፋ ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል

**vague**
1. ግልጽ ፡ ያልሆነ. He gave me a vague answer. ግልጽ ፡ ያልሆነ ፡ መልስ ፡ ሰጠኝ
2. (= adv.) ድብዝዝ ፡ ብሎ. In a fog, everything looks vague. በጭጋግ ፡ ውስጥ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ድብዝዝ ፡ ብሎ ፡ ይታያል

**vaguely**
1. ትንሽ ፡ ትንሽ. I remember him vaguely. ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ አስታውሰዋለሁ

2. ግልጽ ፡ ባልሆነ ፡ አነጋገር. He spoke vaguely about his future plans. ስለ ፡ ወደፊት ፡ እቅዱ ፡ ግልጽ ፡ ባልሆነ ፡ አነጋገር ፡ ተናገረ

**vaguest**
*I haven't the vaguest idea what they want. የሚፈልጉትን ፡ ነገር ፡ በፍጹም ፡ አላውቅም

**vain**
1. ግብዝ. He is terribly vain and spends much time in front of the mirror. ግብዝ ፡ ስለሆነ ፡ መስታወት ፡ በማየት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያጠፋል
2. ዋጋ ፡ ቢስ. His threats are vain. ዛቻው ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ነው
3. (= adv.) በከንቱ. I made vain attempts to reach him by telephone. በስልክ ፡ ላነጋግረው ፡ በከንቱ ፡ ደከምኩ

**be vain** ኵራ ፤ በጣም ፡ ታበየ
She is vain because she knows she is beautiful. ቆንጆ ፡ መሆኗን ፡ ስለምታውቅ ፡ ትኰራለች
She is vain about her beauty. በውበቷ ፡ በጣም ፡ ትታበያለች

**in vain** በከንቱ
Do not take the name of God in vain! የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በከንቱ ፡ አታንሣ
The doctor tried in vain to save the boy's life. ሐኪሙ ፡ የልጁን ፡ሕይወት ፡ ለማዳን ፡ በከንቱ ፡ ደከመ

**valedictorian** በምረቃው ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ ላይ ፡ ንግግር ፡ አድራጊ
The valedictorian urged the graduates to work hard. በምረቃው ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ ላይ ፡ ንግግር ፡ አድራጊው ፡ ምሩቆቹ ፡ ጠንክረው ፡ እንዲሠሩ ፡ መከሩቸው

**valedictory** የመሰነባበቻ
He gave the valedictory speech at the graduation. በምረቃው ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ ላይ ፡ የመሰነባበቻ ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**valet** አሽከር
His valet was very faithful to him. አሽከሩ ፡ ለሱ ፡ በጣም ፡ ታማኝ ፡ ነበር

**valiant**
1. በጣም ፡ ጀግና. He was a valiant warrior. በጣም ፡ ጀግና ፡ የሆነ ፡ ጦረኛ ፡ ነበር
2. የጀግንነት. His valiant deeds are sung by minstrels even now. የሱን ፡ የጀግንነት ፡ ሙያዎች ፡ አዝማሪዎች ፡ አሁንም ፡ ያነሣሉ

**valid**
1. ሕጋዊ. His valid will left all his property to his wife. ንብረቱን ፡ ሁሉ ፡ በሕጋዊ ፡ ኑዛዜ ፡ ለሚስቱ ፡ ተወ
2. ተገቢ. Illness is a valid excuse for being absent from school. ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመቅረት ፡ ሕመም ፡ ተገቢ ፡ ምክንያት ፡ ነው

**be valid** አገለገለ
Your passport is still valid. ፓስፖርትህ ፡ አሁንም ፡ ያገለግላል

**validate**
1. አረጋገጠ. A witness to the accident validated my story. አደጋው ፡ ቦታ ፡ የነበረ ፡ ምስክር ፡ እኔ ፡ የተናገርኩትን ፡ አረጋገጠ
2. አጸደቀ. The Ministry of Interior validated my passport. ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የይለፍ ፡ ወረቀቱን ፡ አጸደቀልኝ

**validity** መሠረት
The argument lacks validity. ክርክሩ ፡ መሠረት ፡ የለውም
*The validity of the passport is for three years. ይህ ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ የሚያገለግለው ፡ ለሦስት ፡ ዓመት ፡ ነው

**valise** ሻንጣ
I packed two shirts and some socks in my valise. ሁለት ፡ ሸሚዞችና ፡ ጥቂት ፡ የእግር ፡ ሹራቦች ፡ ሻንጣዬ ፡ ውስጥ ፡ ከተትኩ

**valley** ሸለቆ
The valley was flooded. ሸለቆውን ፡ ጐርፍ ፡ አጥለቀለቀው

**valor**
1. ጀግንነት. Everybody praises his valor. ሁሉም ፡ ሰው ፡ ጀግንነቱን ፡ ያደንቃል
2. ጀብዱ. The warriors performed prodigies of valor. ጦረኞቹ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ ጀብዱ ፡ ፈጸሙ

**valuable**
1. ዋጋ ፡ ያለው ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለው. Many valuable articles were stolen. ብዙ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ እቃዎች ፡ ተሰረቁ
That's a valuable ring. ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ቀለበት ፡ ነው
2. ጠቃሚ. Valuable information may be obtained from personal diaries. ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ መረጃ ፡ ከግል ፡ ማስታወሻዎች ፡ ለማግኘት ፡ ይቻላል
A valuable friend is one who stands by one in need. ጠቃሚ ፡ ጓደኛ ፡ ማለት ፡ በችግር ፡ ጊዜ ፡ የሚደርስ ፡ ነው

**make more valuable** ዋጋ ፡ ጨመረ(ለት)
The exactitude of the work makes it more valuable. የሥራው ፡ ረቂቅነት ፡ ዋጋ ፡ ይጨምርለታል

**make valuable** ዋጋውን ፡ ከፍ ፡ አደረገ
The rarity of diamonds makes them valuable. የአልማዞች ፡ ብርቅ ፡ መሆን ፡ ዋጋቸውን ፡ ከፍ ፡ ያደርገዋል

**valuables** ውድ ፡ እቃዎች
May I leave my valuables in your care? ውድ ፡ የሆኑትን ፡ እቃዎቼን ፡ ላንተ ፡ አደራ ፡ ልተው ?

**valuation**
1. ግምት. It's unwise to accept a person's valuation of himself. አንድ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ የሚሰጠውን ፡ ግምት ፡ መቀበል ፡ ጥሩ ፡ አይደለም
2. ዋጋውን ፡ ማስገመት. We took the jewels to a jeweler for valuation. ዋጋቸውን ፡ ለማስገመት ፡ ጌጣ ፡ ጌጦቹን ፡ ወደ ፡ አንጥረኛው ፡ ወሰድን

**value** (v.)
1. ገመተ. What do you value your house at? ቤትህን ፡ ስንት ፡ ትገምተዋለህ ?
2. ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ሰጠ. I value his friendship very highly. ለጓደኝነቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ እሰጠዋለሁ
*Do you value her as a secretary? ጥሩ ፡ ጸሐፊ ፡ ትመስልሃለች ?

**value above** ከ -- ይልቅ ፡ አበለጠ
I value health above wealth. ከሀብት ፡ ይልቅ ፡ ጤንነትን ፡ አበልጣለሁ

**value** (n.)
1. ዋጋ. I don't attach any value to his opinion. ላስተያየቱ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ አልሰጠውም
The value of the dollar has lessened these last 20 years. ባለፉት ፡ ሃያ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የብር ፡ ዋጋ ፡ ቀንሷል
New buildings appreciate the value of the land. አዳዲስ ፡ ሕንጻዎች ፡ የመሬትን ፡ ዋጋ ፡ ያስወድዳሉ
2. ጥቅም. The value of education is apparent to the wise. የትምህርትን ፡ ጥቅም ፡ ብልህ ፡ ሰው ፡ ያውቀዋል
The value of true friendship is realized in time of need. የታማኝ ፡ ጓደኛ ፡ ጥቅም ፡ የሚታወቀው ፡ በችግር ፡ ጊዜ ፡ ነው

**be of value** ጠቃሚ ፡ ነበር ፤ ጠቀመ
His report was of value to the governor. ሪፖርቱ ፡ ለገዢው ፡ ጠቃሚ ፡ ነበር
That is of little value to me. እምብዛም ፡ አይጠቅመኝም

**moral values** ሞራል
The future of a nation depends on its moral values. ያንድ ፡ አገር ፡ የወደፊት ፡ ዕድል ፡ ባላት ፡ ሞራል ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው
[See also 'depreciate']

**valve** መቈጣጠሪያ
He turned the valve and let the gas out of the tank. መቈጣጠሪያውን ፡ ከፍቶ ፡ ቤንዚን ፡ ከበርሚሉ ፡ ውስጥ ፡ ቀዳ

**van**
1. የጭነት ፡ መኪና. The furniture was transported in a van. የቤቱ ፡ እቃ ፡ የተጓጓዘው ፡ ባንድ ፡ የጭነት ፡ መኪና ፡ ነው
2. የፊት ፡ አዝማቾች. The army's van was under attack. የፊት ፡ አዝማቾቹን ፡ ጠላት ፡ አጠቃቸው

**vandal** አጥፊ
Vandals invaded the school at night and wrecked it. አጥፊዎች ፡ በማታ ፡ መጥተው ፡ ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ሰባበሩት

**vandalism**
*I am insured against vandalism. ንብረቴን ፡ ከሚያጠፉ ፡ ለመከላከል ፡ ዋስትና ፡ ገብቻለሁ

**vane, weather ~** የነፋስ ፡ አቅጣጫ ፡ ማሳያ
There is a weather vane on the top of the roof. በጣሪያው ፡ ላይ ፡ የነፋስ ፡ አቅጣጫ ፡ ማሳያ ፡ አለ

**vanguard** አዝማች ፡ ጦር
They cut off the vanguard from the main body of the troops. አዝማቹን ፡ ጦር ፡ ከዋናው ፡ ጦር ፡ ነጠሉት

**vanish**
1. ጠፋ. He ran away from me and suddenly vanished from sight. ሮጦ ፡ በድንገት ፡ ከፊቴ ፡ ጠፋ
2. እልም ፡ አለ. As soon as he caught sight of you, he vanished. ወዲያው ፡ እንዳየህ ፡ እልም ፡ አለ

**vanity** (vanities)
1. ግብዝነት. His vanity detracts from his merit. ግብዝነቱ ፡ መልካም ፡ ጠባዩን ፡ ይቀንሳል
2. እብሪት. Her vanity repels all those who know her. እብሪቷ ፡ የሚያውቃትን ፡ ሁሉ ፡ ከሷ ፡ እንዲሸሹ ፡ ያደርገዋል
3. ከንቱነት. Don't be misled by the vanities of life! በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከንቱነት ፡ አትታለሉ

**vanquish** ድል ፡ መታ
Our army vanquished the enemy. ጦራችን ፡ ጠላትን ፡ ድል ፡ መታ

**vantage, ~ point**
*He watched the troop movements from a vantage point on a high hill. የሰራዊቱን ፡ እንቅስቃሴ ፡ ከሚያመቸው ፡ ከፍተኛ ፡ ኰረብታ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ተመለከተ

**give a point of vantage** ምቹ ፡ ሆነ(ለት)
Capturing the hill gave our troops a point of vantage. የወታደሮቻችን ፡ ኰረብታውን ፡ መማረክ ፡ ምቹ ፡ ሆነላቸው

**vapor** እንፋሎት
The vapor coming from the boiling water made everything damp. ከሚፈላው ፡ ውኃ ፡ የሚወጣው ፡ እንፋሎት ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ አረጠበው

**vaporize** ተነነ
Boiling water vaporizes fast. የሚፈላ ፡ ውኃ ፡ በቶሎ ፡ ይተናል

**variable** ተለዋዋጭ
Her variable moods puzzle everyone. ተለዋዋጭ ፡ ጠባይዋ ፡ ሁሉንም ፡ ግራ ፡ አጋብቷል

**be variable**
1. ሊለዋወጥ ፡ ቻለ. These curtain rods are of variable length. የዚህ ፡ መጋረጃ ፡ ማንጠልጠያ ፡ ብረቶች ፡ ርዝመታቸው ፡ ሊለዋወጥ ፡ ይችላል
2. (= act.) አቅጣጫውን ፡ ለወጠ. At this time of year, winds are variable. በዚህ ፡ ወራት ፡ ነፋሱ ፡ አቅጣጫውን ፡ ይለውጣል

**variance** መለዋወጥ
A variance of temperature is responsible for the change in the color of the leaves. የቅጠሎቹ ፡ ቀለም ፡ ሊለዋወጥ ፡ የቻለው ፡ ከሙቀቱ ፡ መለዋወጥ ፡ የተነሣ ፡ ነው
*There is a large variance in our opinions of him. ስለሱ ፡ ያለን ፡ አስተያየት ፡ በጣም ፡ የተለያየ ፡ ነው

**be at variance**
1. ተለያየ. The two reports are at variance, and I can't tell which is right. ሁለቱ ፡ ሪፖርቶች ፡ የተለያዩ ፡ ስለሆኑ ፡ የትኛው ፡ ትክክል ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ተቸግሬያለሁ
2. አልተስማማም. The secretary was at variance with his superior. ጸሐፊው ፡ ካለቃው ፡ ጋር ፡ አልተስማማም

**variant** (n.) የተለያየ ፡ መልክ
Variants of this word occur in all the languages. ይህ ፡ ቃል ፡ በተለያየ ፡ መልክ ፡ በሁሉም ፡ ቋንቋ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል

**variant** (adj.) የተለያየ
There are variant spellings for certain words in English. ላንዳንድ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቃላት ፡ የተለያየ ፡ አጻጻፍ ፡ አለ

**variation** ልዩነት
The variations in the value of the world's currencies are posted in the exchange. በዓለም ፡ ያሉ ፡ ገንዘቦች ፡ የዋጋ ፡ ልዩነት ፡ በገንዘብ ፡ መመንዘሪያው ፡ ቦታ ፡ ተለጥፏል
The variation in temperature is not very great. ባየሩ ፡ መሞቅና ፡ መቀዝቀዝ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ አይደለም

**varied**
1. የተለያየ. The town has houses of varied appearance. ከተማው ፡ የተለያየ ፡ መልክ ፡ ያላቸው ፡ ቤቶች ፡ አሉት
2. ልዩ ፡ ልዩ. He has a varied collection of pictures. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ሥዕሎች ፡ ሰብስቧል

**variegated** ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ ያለው
We will use variegated marble. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ ባላቸው ፡ እብነ ፡ በረዶች ፡ እንሠራለን

**variety** (varieties)
1. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት. I like variety in my meals. የሚቀርብልኝ ፡ ምግብ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ እንዲሆን ፡ እፈልጋለሁ
2. ዓይነት. How many varieties of fruit grow in your orchard? አትክልትህ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ስንት ፡ ዓይነት ፡ ፍሬዎች ፡ ይበቅላሉ ?
3. ለውጥ. Variety is the spice of life. ለውጥ ፡ ለሕይወት ፡ ማጣፈጫ ፡ ነው

**variety of** ልዩ ፡ ልዩ
His action was prompted by a variety of reasons. አድራጎቱን ፡ እንዲፈጽም ፡ የገፋፉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ናቸው

**wide variety of** ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት
This store has a wide variety of shirts. ይህ ፡ መደብር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ሸሚዞች ፡ አሉት

**various**
1. ልዩ ፡ ልዩ. The table was decorated with various kinds of flowers. ጠረጴዛው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አበቦች ፡ አጊጦ ፡ ነበር
2. ብዙ. Various people have said so. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ እንደሱ ፡ ብለዋል

**at various times** አልፎ ፡ አልፎ
He came in at various times to see how I was coming along. አልፎ ፡ አልፎ ፡ እየመጣ ፡ ሥራውን ፡ እንዴት ፡ እንደምሠራ ፡ ተመለከተ

**varnish** በዘይት ፡ ወለወለ
The carpenter varnished the furniture. አናጢው ፡ የቤቱን ፡ እቃ ፡ በዘይት ፡ ወለወለ

**vary** (vt.) ለዋወጠ
The driver can vary the speed of an automobile. ነጂው ፡ የመኪናውን ፡ ፍጥነት ፡ ሊለዋውጥ ፡ ይችላል

**vary** (vi.)
1. ተለያየ. The size varies in each case. መጠኑ ፡ እንደ ፡ ዓይነቱ ፡ ይለያያል
2. ተለዋወጠ. The weather varies from day to day. ያየሩ ፡ ሁኔታ ፡ በየቀኑ ፡ ይለዋወጣል

**vase**
1. [ጌጣ ፡ ጌጥ ፡ የበዛበት ፡ ከመስታወት ፡ ወይም ፡ ከሸክላ ፡ የተሠራ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለአበባ ፡ ማስቀመጫ ፡ የሚሆን ፡ እቃ].
2. ያበባ ፡ ማስቀመጫ. The vase has flowers in it now. ያበባ ፡ ማስቀመጫው ፡ አሁን ፡ አበባ ፡ አለበት

**vassal** ሎሌ
In the Middle Ages, the vassal had to render service to his lord. በመካከለኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ሎሌ ፡ ጌታውን ፡ ማገልገል ፡ ነበረበት

**vast**
1. በጣም ፡ ብዙ. The war cost vast sums of money. ጦርነቱ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ፈጀ
2. አውላላ. This vast plain extends all the way to the ocean. ይህ ፡ አውላላ ፡ ሜዳ ፡ እስከ ፡ ውቅያኖስ ፡ ይደርሳል
3. በጣም ፡ ሰፊ. The Sahara is a vast desert. ሰሐራ ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ነው

**of vast importance** ከፍተኛ
This is a matter of vast importance. ይህ ፡ ከፍተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ነው
[See also 'dimension']

**vault** (v.) ዘለለ
He vaulted over the fence and ran off. በአጥሩ ፡ ላይ ፡ ዘሎ ፡ ሮጠ

**vault** (n.)
1. ባለ ፡ ቀስት ፡ ጣሪያ. The vault in the hall is made of brick. አዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ባለ ፡ ቀስት ፡ ጣሪያ ፡ የተሠራው ፡ ከጡብ ፡ ነው
2. [የከበሩ ፡ እቃዎች ፡ የሚቀመጥበት ፡ ባንክ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ክፍል]

**veal** የጥጃ ፡ ሥጋ
I like veal cooked in butter. በቅቤ ፡ የተሠራ ፡ የጥጃ ፡ ሥጋ ፡ እወዳለሁ

**veer** አቅጣጫውን ፡ ለወጠ
The wind has veered to the north. ነፋሱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ አቅጣጫውን ፡ ለውጧል
*Public opinion is veering toward peace. ሕዝቡ ፡ ሐሳቡን ፡ ወደ ፡ ሰላም ፡ በመመለስ ፡ ላይ ፡ ነው

**vegetable** (n.) አትክልት ፤ ቅጠላ ፡ ቅጠል
I don't like to eat vegetables. አትክልት ፡ (ቅጠላ ፡ ቅጠል) ፡ መብላት ፡ አልወድም

**vegetable** (adj.) ያትክልት
I like vegetable soup. ያትክልት ፡ ሾርባ ፡ እወዳለሁ

**vegetable oil** የምግብ ፡ ዘይት
Vegetable oil is used in cooking, and motor oil in cars. የምግብ ፡ ዘይት ፡ ለምግብ ፤ የነዳጅ ፡ ዘይት ፡ ደግሞ ፡ ለመኪና ፡ ያገለግላል

**vegetarian** አትክልት ፡ ብቻ ፡ የሚበላ
Generally, Indians are vegetarians. በጠቅላላው ፡ ህንዶች ፡ የሚበሉት ፡ አትክልት ፡ ብቻ ፡ ነው

**vegetate** ኑሮው ፡ እንጉል ፡ ሆነ
He has been vegetating for the last five years. ካለፉት ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ጀምሮ ፡ ኑሮው ፡ እንጉል ፡ ሆነ

**vegetation** ሣር ፡ ቅጠል
The vegetation is very green after the rains. ከዝናቡ ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ ሣር ፡ ቅጠሉ ፡ ለምልሟል
[See also 'exuberant']

**vehemence**
1. ኀይለኛነት. The vehemence of his attack broke down the door. የምቱ ፡ ኀይለኛነት ፡ መዝጊያውን ፡ ሰበረው
2. ኀይል. They argued with vehemence. በኀይል ፡ ተከራከሩ

**vehement**
1. ኀይለኛ. A vehement wind is blowing today. ዛሬ ፡ ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ይነፍሳል
2. ከባድ. Such vehement aspersions cannot be ignored. እንዲህ ፡ ያለ ፡ ከባድ ፡ ሐሜት ፡ የሚታለፍ ፡ አይደለም

**vehemently** በኀይል
He spoke vehemently against the plan. እቅዱን ፡ በኀይል ፡ በመቃወም ፡ ተናገረ

**vehicle**
1. ተሽከርካሪ. All vehicles must have licenses. ተሽከርካሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ፈቃድ ፡ ሊኖራቸው ፡ ይገባል
2. ምቹ ፡ መሣሪያ. Art may be used as a vehicle for propaganda. ኪነ ፡ ጥበብ ፡ ለፕሮፓጋንዳ ፡ ምቹ ፡ መሣሪያ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

*He uses poetry as the vehicle for his ideas. ሐሳቡን ፡ የሚገልጸው ፡ በግጥም ፡ ነው

**veil** (v.)
1. በዓይነ ፡ እርግብ ፡ ሸፈነ. An Arab woman veils her face. የዐረብ ፡ ሴት ፡ ፊቷን ፡ በዓይነ ፡ እርግብ ፡ ትሸፍናለች
2. ሸፈነ. Fog veiled the shore. ጭጋግ ፡ የባሕሩን ፡ ዳርቻ ፡ ሸፍኖታል

**veil in secrecy** ደባበቀ
The spy veiled his plans in secrecy. ሰላዩ ፡ እቅዱን ፡ ደባበቀው

**veil** (n.) ዓይነ ፡ እርግብ
A white veil covered her face. ፊቷ ፡ በነጭ ፡ ዓይነ ፡ እርግብ ፡ ተሸፍኗል

**veiled** (adj.)
1. ስም ፡ ለበስ. He expressed his opinions in veiled language. አስተያየቱን ፡ በስም ፡ ለበስ ፡ አነጋገር ፡ ገለጸ
2. (= adv.) በአሽሙር. He spoke a veiled insult to me. በአሽሙር ፡ ሰደበኝ
[See also 'insult']

**vein**
1. የደም ፡ ሥር. He cut his vein. የደም ፡ ሥሩን ፡ ቈረጠ
2. ስሜት. There is a vein of cruelty in him. የጨካኝነት ፡ ስሜት ፡ አለበት

**in a merry vein** እየቀለደ
She spoke in a merry vein of her misadventure. ስለደረሰባት ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ እየቀለደች ፡ ተናገረች

**vellum** ብራና
Vellum is used as writing material. ብራና ፡ ለመጻፊያ ፡ ያገለግላል

**velocity** ፍጥነት
The rocket's velocity exceeds 18,000 miles per hour. የሮኬት ፡ ፍጥነት ፡ በሰዓት ፡ ከዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ሺ ፡ ማይል ፡ በላይ ፡ ነው

**velvet** አጥላስ
The Emperor's cloak is made of purple velvet. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ካባ ፡ የተሠራው ፡ ከሐምራዊ ፡ አጥላስ ፡ ነው

**venal** ጉቦ ፡ የሚበላ
A venal judge should be punished. ጉቦ ፡ የሚበላ ፡ ዳኛ ፡ መቀጣት ፡ አለበት

**vendetta** የደም ፡ መበቀል
The vendetta between the two main clans of the village has caused many deaths. በመንደሩ ፡ ከሚገኙት ፡ ሁለት ፡ ዋና ፡ ጐሳዎች ፡ መሀከል ፡ የተፈጠረው ፡ የደም ፡ መበቀል ፡ ለብዙ ፡ ሕይወት ፡ መጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ሆኗል

**vendor** ሻጭ
Vendors of cigarettes must pay a tax. ሲጋራ ፡ ሻጮች ፡ ቀረጥ ፡ መክፈል ፡ አለባቸው

**veneer**
1. ሽፋን ፤ ኮምፐንሳቶ. There was a veneer of fine wood on the table. ጠረጴዛው ፡ በስስ ፡ ዕንጨት ፡ ሽፋን ፡ (ኮምፐንሳቶ) ፡ ተለብዶ ፡ ነበር
2. ሽፋን. Beneath the veneer of Western civilization, the spirit of Islam is readily apparent. ከምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሽፋን ፡ ሥር ፡ የእስላም ፡ መንፈስ ፡ ጐልቶ ፡ ይታያል

**venerable**
1. የተቀደሰ. Venerable customs like kissing the church should be continued. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሳምን ፡ የመሳሰሉ ፡ የተቀደሱ ፡ ልማዶች ፡ መቅረት ፡ አይገባቸውም
2. ብጹዕ (pl. ብጹዓን). The venerable members of the clergy will hold a meeting today. ብጹዓን ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ አባሎች ፡ ዛሬ ፡ ስብሰባ ፡ ያደርጋሉ
3. አረጋዊ. The venerable appearance of the old man made everyone think that he was a saint. የሽማግሌው ፡ አረጋዊ ፡ ቁመና ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንዲያምን ፡ አደረገው

**venerate** በታላቅ ፡ አክብሮት ፡ ተመለከተ
The students venerated their director. ተማሪዎቹ ፡ ዲሬክተራቸውን ፡ በታላቅ ፡ አክብሮት ፡ ተመለከቱት

**be venerated** ተከበረ
The memory of St. Takla Haymanot is still venerated in Ethiopia. የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ስም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይከበራል

**veneration** ማክበር
Veneration of saints is a feature of some religions. አንዳንድ ፡ ሃይማኖቶች ፡ ቅዱሳንን ፡ ማክበር ፡ ዋና ፡ መለያቸው ፡ ነው

**venereal** ያባለ ፡ ዘር
Venereal diseases can be controlled by medicine. ያባለ ፡ ዘርን ፡ በሽታ ፡ በመድኃኒት ፡ ለመከላከል ፡ ይቻላል

**vengeance** ቂም ፡ በቀል
The man killed his boss in vengeance. ሰውዬው ፡ አለቃውን ፡ በቂም ፡ በቀል ፡ ገደለው

**brood vengeance**
*For years he brooded vengeance. ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ የቂም ፡ በቀል ፡ ሐሳብ ፡ በአእምሮው ፡ ውስጥ ፡ ነበር

**seek vengeance** ተበቀለ
He seeks vengeance for his brother's murder. የወንድሙን ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ ይፈልጋል

**take vengeance on** ተበቀለ
He decided to take vengeance on his enemy. ጠላቱን ፡ ለመበቀል ፡ ቈረጠ

**vengeful** (= adv.) በደም ፡ በቀል ፡ ተነሣሥቶ
The vengeful father slew his son's murderer with a sword. በደም ፡ በቀል ፡ ተነሣሥቶ ፡ አባትየው ፡ የልጁን ፡ ገዳይ ፡ በጐራዴ ፡ ገደለው

**venial** ቀላል
Venial sins are forgiven by the Lord. ቀላል ፡ ኃጢአቶችን ፡ ጌታ ፡ ይቅር ፡ ይላል

**venom**
1. መርዝ. The snake's venom caused his arm to swell. የእባቡ ፡ መርዝ ፡ እጁን ፡ አሳበጠው
2. (= adj.) መርዘኛ. Her enemies fear the venom of her tongue. ጠላቶቿ ፡ መርዘኛ ፡ ምላሷን ፡ ይፈራሉ

**venomous** መርዘኛ
She has a venomous tongue. ምላሷ ፡ መርዘኛ ፡ ነው

**venomously**
*She spoke to him so venomously that his blood ran cold. መርዘኛ ፡ ንግግር ፡ በተናገረችው ፡ ጊዜ ፡ ክው ፡ አለ

**vent** (v.) ተወጣ
He vented his wrath on the hapless child. ንዴቱን ፡ በምስኪኑ ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ተወጣ

**vent** (n.) የጢስ ፡ ማውጫ ፤ የነፋስ ፡ ማስገቢያ
The vent is blocked, and it doesn't let smoke through. የጢስ ፡ ማውጫው ፡ ስለተደፈነ ፡ ጢስ ፡ አያሳልፍም
The vent helps cool the inside of the car. የነፋስ ፡ ማስገቢያው ፡ መኪናውን ፡ ለማቀዝቀዝ ፡ ይረዳል

**find vent**
1. ወጣ(ለት). Her anger found vent in tears. ቁጣዋ ፡ በእንባ ፡ ወጣላት
2. ሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለ. +His energy found vent in hard work. ኀይሉን ፡ በከባድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለው

**give vent to** ወጣ(ለት)
+She gave vent to her feelings with a burst of tears. አምርራ ፡ በማልቀስ ፡ ስሜቷ ፡ ወጣላት

**ventilate** አናፈሰ
Open the window to ventilate the room! ክፍሉን ፡ ለማናፈስ ፡ መስኮቱን ፡ ክፈት

**be ventilated**
*The plans for the new park were ventilated in the newspapers. ስለ ፡ አዲሱ ፡ መናፈሻ ፡ ቦታ ፡ እቅድ ፡ በጋዜጦች ፡ ሰፊ ፡ ውይይት ፡ ተደረገ

**ventilation**
*The ventilation in this room is defective. ይህ ፡ ክፍል ፡ አየር ፡ በደንብ ፡ አይገባውም

**ventilator** የነፋስ ፡ መግቢያ
The kitchen has a ventilator over the stove. ማድ ፡ ቤቱ ፡ ከምድጃው ፡ በላይ ፡ የነፋስ ፡ መግቢያ ፡ አለው

**ventriloquist** [ድምፁ ፡ ከሌላ ፡ ስፍራ ፡ የሚመጣ ፡ በማስመሰል ፡ ሊናገር ፡ የሚችል ፡ አጫዋች]

**venture** (vt.) አደጋ ፡ ላይ ፡ ጣለ
He ventured his life to save his friend from drowning. ጓደኛውን ፡ ከመስመጥ ፡ ለማዳን ፡ የገዛ ፡ ሕይወቱን ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ጣለ

**venture** (vi.) ደፈረ
Don't venture too near the edge of the cliff! ወደ ፡ ገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ደፍረህ ፡ አትጠጋ

**venture the opinion** በድፍረት ፡ ተናገረ
He ventured the opinion that the speaker was right. ተናጋሪው ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኑን ፡ በድፍረት ፡ ተናገረ

**venture** (n.) ሙከራ
It was a dangerous venture. አደገኛ ፡ ሙከራ ፡ ነበር

**business venture** የንግድ ፡ ሥራ
He invested all his money in a business venture. ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ አዋለ

**venturesome**
1. ደፋር. The venturesome boy was rescued from the beasts. ደፋሩን ፡ ልጅ ፡ ከአውሬ ፡ አዳኑት
2. አደጋ ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችል. The venturesome experiment was completely successful. አደጋ ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችለው ፡ ሙከራ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ተሳካ

**veracious** የሚታመን
He gave a veracious report of life in Ethiopia. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ኑሮ ፡ የሚታመን ፡ መግለጫ ፡ ሰጠ

**veracity** ትክክለኛነት
His veracity cannot be relied on. የሱ ፡ ትክክለኛነት ፡ አያስተማምንም

**veranda** በረንዳ
We sit on the veranda in the evening and smoke. ማታ ፡ ማታ ፡ በረንዳው ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብለን ፡ ሲጋራ ፡ እናጨሳለን

**verb** ግስ
The Amharic verb has many tenses. ያማርኛ ፡ ግስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜያት ፡ አለው

**verbal**
1. የቃል. We made a verbal agreement. የቃል ፡ ስምምነት ፡ አደረግን
2. የቃል ፡ በቃል. This is a verbal translation of the proverbs. ይህ ፡ የምሳሌዎቹ ፡ የቃል ፡ በቃል ፡ ትርጉም ፡ ነው
3. የቃላት ፡ አገባብ. The author's verbal skill is remarkable. የደራሲው ፡ የቃላት ፡ አገባብ ፡ ችሎታ ፡ የሚደነቅ ፡ ነው

**be only verbal** ከንገት ፡ በላይ ፡ ነበር
The thief's penitence was only verbal. የሌባው ፡ መጸጸት ፡ ከንገት ፡ በላይ ፡ ነበር

**verbally**
1. በቃል. He told me verbally that my case would be heard soon. ጉዳዩ ፡ በቶሎ ፡ እንደሚታይልኝ ፡ በቃል ፡ ነግሮኛል
2. በንግግር. The dumb boy could not reply verbally, but used signs. ድዳው ፡ ልጅ ፡ በንግግር ፡ ለመመለስ ፡ ስላልቻለ ፡ በምልክት ፡ አሳየ

**verbatim** ቃል ፡ በቃል
He reported the speech verbatim. ንግግሩን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ አቀረበ

**(be) verbose** ብዙ ፡ ተናገረ
He is so verbose it's hard to remember what he said. ብዙ ፡ ስለሚናገር ፡ ምን ፡ እንዳለ ፡ ለማስታወስ ፡ ያዳግታል

**(be) verdant**
1. ለምለም ፡ ሆነ. The grass is verdant because of the rain. በዝናቡ ፡ ምክንያት ፡ ሣሩ ፡ ለምለም ፡ ሆኗል
2. አረንጓዴ ፡ ለበሰ. The fields are verdant because of the rain. በዝናቡ ፡ ምክንያት ፡ መስኩ ፡ አረንጓዴ ፡ ለብሷል

**verdict** ፍርድ
The verdict cleared the accused men. ፍርዱ ፡ ተከሳሾቹን ፡ ነጻ ፡ ለቀቃቸው
*The verdict was guilty of murder. በነፍስ ፡ ግዳይ ፡ ወንጀል ፡ ተፈረደበት
[See also 'return']

**verge** (v.), ~ **on** ለ + imperfect + ምንም ፡ አልቀረው
His conversation verges on nonsense. ጨዋታው ፡ እርባን ፡ የለሽ ፡ ሊባል ፡ ምንም ፡ አልቀረው

**verge toward**
*He is a tall man, verging toward obesity. ቦርጫምነት ፡ የሚቃጣው ፡ ረጅም ፡ ሰው ፡ ነው

**verge** (n.), **on the ~ of**
1. በ --- አፋፍ ፡ ላይ. The world is on the verge of war. ዓለም ፡ በጦርነት ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ነች
2. --- ዳር. The house is on the verge of the woods. ቤቱ ፡ ጫካው ፡ ዳር ፡ ነው

**be on the verge of** ለ + imperfect + ምንም ፡ አልቀረው
I was on the verge of telling him. ልነግረው ፡ ምንም ፡ አልቀረኝ

**verifiable** ሊረጋገጥ ፡ የሚችል
This is verifiable evidence. ይህ ፡ ሊረጋገጥ ፡ የሚችል ፡ ማስረጃ ፡ ነው

**verification** ማረጋገጫ
I need verification of your statement. ለተናገርከው ፡ ነገር ፡ ማረጋገጫ ፡ እፈልጋለሁ

**verify** (verified)
1. አረጋገጠ. I can verify his statements about Ethiopia. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ለማረጋገጥ ፡ እችላለሁ
2. ትክክል ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጠ. Will you please verify these figures? እነዚህ ፡ ቁጥሮች ፡ ትክክል ፡ መሆናቸውን ፡ ታረጋግጥልኝ ?

**verily** እውነት
Verily I say to you: The transgressor of God's law will be damned. እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ የሚጥስ ፡ ይኰነናል

**veritable** የታወቀ
He is a veritable statesman. የታወቀ ፡ የሀገር ፡ መሪ ፡ ነው
*His garden is a veritable paradise. ያትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ገነት ፡ ይመስላል

**verity** እውነተኛነት
Everyone doubted the verity of his statement. ሁሉም ፡ ሰው ፡ እሱ ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ እውነተኛነት ፡ ተጠራጠረ

**vermin** ተባይ
The house is overrun with vermin. ቤቱ ፡ በተባይ ፡ ተወሯል

**vernacular**
1. ሁልጊዜ ፡ የሚነገርበት ፡ ቋንቋ. The speech was written in the vernacular and not the classical form of the language. ንግግሩ ፡ የተጻፈው ፡ ሁልጊዜ ፡ በሚነገርበት ፡ ቋንቋ ፡ እንጂ ፡ በሚጻፍበት ፡ ቋንቋ ፡ አልነበረም
2. አነጋገር. Only actors understand the vernacular of the stage. የመድረኩን ፡ አነጋገር ፡ የሚያውቁ ፡ ተዋናዮች ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**versatile** ሁሉ ፡ ገብ ፡ የሆነ
The versatile actor can play any role. ሁሉ ፡ ገብ ፡ የሆነው ፡ ተዋናይ ፡ ማንኛውንም ፡ ክፍል ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል

**verse** (v.), ~ **oneself in** ለመደ
He versed himself in French during his stay in France. ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ በኖረበት ፡ ጊዜ ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ለመደ

**be versed (in)** ዐወቀ
He is well versed in foreign affairs. ስለ ፡ ውጭ ፡ ጉዳይ ፡ አጣርቶ ፡ ያውቃል

**verse** (n.)
1. ግጥም. The play is written in verse. ቲያትሩ ፡ የተጻፈው ፡ በግጥም ፡ ነው
2. ቤት. Let's sing only the first verse! የመጀመሪያውን ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ እንዘምር
[See also 'chapter']

**versify** (versified) ግጥም ፡ ጻፈ
He can versify on almost any subject. በማንኛውም ፡ አርእስት ፡ ግጥም ፡ ሊጽፍ ፡ ይችላል

**version**
1. ሐተታ. I heard another version of the accident. ስለ ፡ አደጋው ፡ ሌላ ፡ ሐተታ ፡ ሰማሁ
2. ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ቅጂ. There are two versions of this text. ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በሁለት ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ቅጂ ፡ ይገኛል
3. ትርጉም. The English version of the Bible is accurate. የመጽሐፍ ፡ ቅዱሱ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ትርጉም ፡ ትክክለኛ ፡ ነው
4. እትም. This is an abridged version of "David Copperfield". ይህ ፡ ያጠረ ፡ የዴቪድ ፡ ኮፐርፊልድ ፡ እትም ፡ ነው

**versus**
*Freedom versus slavery is a political problem. የባርነትና ፡ የነጻነት ፡ ጉዳይ ፡ የፖለቲካ ፡ ችግር ፡ ነው
*The football game of the Congo versus Ethiopia was televised. የኢትዮጵያና ፡ የኮንጎ ፡ የእግር ፡ ኳስ ፡ ጨዋታ ፡ በቴሌቪዥን ፡ ታየ

**vertebra** (vertebrae, or vertebras) አከርካሪ
The vertebrae of a huge skeleton were unearthed yesterday. ያንድ ፡ ትልቅ ፡ ዐጽም ፡ አከርካሪ ፡ ትላንትና ፡ ተቈፍሮ ፡ ወጣ

**vertex** የመጨረሻ ፡ ከፍታ
The vertex of the rocket's flight was twenty-five miles. የሮኬቱ ፡ በረራ ፡ የመጨረሻ ፡ ከፍታ ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ ነበር

**vertical** ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ቀጥ ፡ ያለ
Draw a vertical line! ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ መሥመር ፡ አሥምር

**verve** ጉልበት
Her verve is undiminished even at the end of an exhausting day. በጣም ፡ አድካሚ ፡ ከሆነ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ እንኳን ፡ ጉልበቷ ፡ ሳይቀንስ ፡ ቀረ

**very** በጣም
The bank is not very far from here. ባንኩ ፡ ከዚህ ፡ በጣም ፡ አይርቅም
It's very cold today. ዛሬ ፡ በጣም ፡ ይበርዳል

**very much** በጣም
He likes her very much. በጣም ፡ ይወዳታል

**at the very end** ልክ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ
He came at the very end. ልክ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ መጣ

**the very**
1. ልክ. This is the very thing I want. ይህ ፡ ልክ ፡ የምፈልገው ፡ ነገር ፡ ነው
She left the very next day. ልክ ፡ በነጋታው ፡ ሄደች
2. ራሱ. This is the very hat I lost. ይህ ፡ ራሱ ፡ እኔ ፡ የጣልኩት ፡ ባርኔጣ ፡ ነው
3. እነዚያው. The very people who used to love her hate her now. እነዚያው ፡ ይወዷት ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ አሁን ፡ ጠልተዋታል

**the very best** ምርጥ
This cloth is of the very best quality. ይህ ፡ ጨርቅ ፡ ዓይነቱ ፡ ምርጥ ፡ ነው

**the very first**
*He was the very first to arrive at the party. ወደ ፡ ፓርቲው ፡ ሲመጣ ፡ ማንም ፡ አልቀደመው

**the very moment** እንደ + perfect + ወዲያውኑ
I started the very moment I got your message. መልእክትህ ፡ እንደደረሰኝ ፡ ወዲያውኑ ፡ መንገድ ፡ ጀመርኩ

**(at) the very moment** ልክ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ
At the very moment, the telephone rang. ልክ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ስልኩ ፡ ተደወለ

**to this very day** እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ
I haven't been able to learn the truth to this very day. እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ እውነቱን ፡ ለ ማወቅ ፡ አልቻልኩም
[See also 'same, soon, thought, well']

**vesper** የምሽት ፡ ጸሎት
The priest performs a vesper every day. ቄሱ ፡ ሁል ፡ ቀን ፡ የምሽት ፡ ጸሎት ፡ ያደርሳል

**vessel**
1. መርከብ. The vessel sank in deep water. መርከቡ ፡ ጥልቅ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ሰመጠ
2. እቃ. The thirsty people caught the rain in all kinds of vessels. የተጠሙት ፡ ሰዎች ፡ የዝናቡ ን ፡ ውኃ ፡ በተገኘው ፡ እቃ ፡ አጠራቀሙ
3. የወጥ ፡ ቤት ፡ እቃ. I bought some vessels at the market. አንዳንድ ፡ የወጥ ፡ ቤት ፡ እቃ ፡ ከገ በያ ፡ ገዛሁ
[See also 'blood vessel']

**vest** (v.), ~ **with** ሰጠ
The church vests its bishops with certain powers. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለጳጳሳቷ ፡ አንዳንድ ፡ ሥልጣኖች ፡ ትሰጣለች

**vest** (n.) ሰደርያ
You have stained your vest. ሰደርያህን ፡ አቆሽ ሸሽዋል

**vested** (adj.) የታቦት ፡ ልብስ ፡ የለበሰ
The vested priest stood before the altar. የታቦት ፡ ልብስ ፡ የለበሰው ፡ ቄስ ፡ መሠዊያው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ቆመ

**be vested in** በ -- ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው
The management of the hospital is vested in a board of trustees. ሆስፒታሉ ፡ የሚተዳደረው ፡ በባለ ፡ አደራዎቹ ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው

**be vested with** ተሰጠ
He was vested with the power to hire and fire. ለመቅጠርም ፡ ለማስወጣትም ፡ የሚያስችል ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠው

**have a vested interest** እሱን ፡ የሚነካ ፡ ጥቅም ፡ አለው
The church has a vested interest in maintaining its schools. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ ቤቶቿ ን ፡ ለመጠበቅ ፡ እሷን ፡ የሚነካ ፡ ጥቅም ፡ አላት

**vestibule** መተላለፊያ
The vestibule is carpeted with a soft rug. መተላለፊያው ፡ ለስላሳ ፡ ምንጣፍ ፡ ተነጥፎበታል

**vestige**
1. ፍርስራሽ. Vestiges of the ancient wall still stand. የቀድሞው ፡ ግንብ ፡ ፍርስራሾች ፡ አሁ ንም ፡ ቆመዋል
2. ጭላንጭል. Not a vestige of hope is left. የተስፋ ፡ ጭላንጭል ፡ እንኳ ፡ አልቀረም
*Not a vestige of the original paint was to be seen. የመጀመሪያው ፡ ቀለም ፡ ፈጽሞ ፡ አይታይ ም ፡ ነበር

**vestment** ልብስ
The vestments of the clergy are very colorful. የካህናቱ ፡ ልብስ ፡ የደመቀ ፡ ነው

**vestry** (vestries) እቃ ፡ ቤት
The church valuables are kept in the vestry. ውድ ፡ የሆኑት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እቃዎች ፡ እቃ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣሉ

**veteran**
1. በጦርነት ፡ ያገለገለ ፡ ሰው ፤ ከዘመቻ ፡ የተመለሰ. Veterans have preference in getting government jobs. በጦርነት ፡ ያገለገሉ ፡ ሰዎች ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ ቅድሚያ ፡ ይሰጣቸዋል
The veterans have special privileges. ከዘመቻ ፡ የተመለሱ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ አላቸው
2. በ --- ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የቆየ. Only a veteran farmer can grow crops in this rocky soil. እዚህ ፡ ድንጋያማ ፡ አፈር ፡ ላይ ፡ እህል ፡ ለመዝራት ፡ የሚችል ፡ በግብርና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የቆየ ፡ ገበሬ ፡ ብቻ ፡ ነው
*He is a veteran of the Korean campaign. ኮሪያ ፡ ዘምቶ ፡ የተመለሰ ፡ ነው

**veterinarian** የእንስሳት ፡ ሐኪም
The veterinarian will vaccinate our livestock. የእንስሳት ፡ ሐኪም ፡ ከብቶቻችንን ፡ ይከትብልናል

**veterinary** የእንስሳት ፡ ሕክምና
Veterinary training can be obtained in Ethiopia now. የእንስሳት ፡ ሕክምና ፡ ትምህርት ፡ አሁን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ መሰጠት ፡ ተጀምሯል

**veto** የማገጃ ፡ ድምፅ
This is the tenth veto they have given. ይህ ፡ እ ነሱ ፡ የሰጡት ፡ ዐሥረኛው ፡ የማገጃ ፡ ድምፅ ፡ ነው

**vex** አበሳጨ
My friend vexed me by being late. ጓደኛዬ ፡ በመ ዘግየቱ ፡ አበሳጨኝ

**be vexed** ተናደደ
She was vexed to find the baby had spilled the syrup. ሕፃኑ ፡ ሹሮፑን ፡ ማፍሰሱን ፡ ባወቀች ፡ ጊዜ ፡ ተናደደች

**vexation**

1. ብስጭት. Rain on Saturday was a vexation to the children. ቅዳሜ ፡ ቀን ፡ ዝናም ፡ መጣሉ ፡ ልጆቹን ፡ ብስጭት ፡ ላይ ፡ ጣላቸው

2. መበሳጨት. His face showed his vexation at the delay. በመዘግየቱ ፡ ምክንያት ፡ መበሳጨቱ ፡ ፊቱ ፡ ላይ ፡ ታየ

**vexatious** ብስጩ

His vexatious character succeeds in making everyone hate him. ብስጩ ፡ ጠባዩ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ያስጠላዋል

**(be) vexing** አበሳጨ

It is vexing to find that someone has taken your pen when you need it most. ብዕር ፡ በጣም ፡ ሲያስፈልግህ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሲወስደው ፡ ያበሳጫል

**via** በ -- በኩል

We went via Harar to Djibouti. በሐረር ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ጅቡቲ ፡ ሄድን

**viable**

1. ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የሚችል. A viable plan is needed to promote agriculture. እርሻን ፡ ለማስፋፋት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የሚችል ፡ እቅድ ፡ ያስፈልጋል

2. ሊያድግ ፡ የሚችል. The only viable plant for dry areas is the cactus. በደረቅ ፡ ስፍራዎች ፡ ሊያድግ ፡ የሚችል ፡ ዕፅ ፡ ቁልቋል ፡ ብቻ ፡ ነው

**viaduct** [መንገዶችን ፡ ለማገናኘት ፡ የሚረዳ ፡ በሸለቆ ፡ ላይ ፡ የሚሄድ ፡ ድልድይ]

**vibrant**

1. የሚያስተጋባ. Her vibrant voice thrilled the audience. የሚያስተጋባ ፡ ድምጿ ፡ አድማጮችን ፡ አስደነቀ

2. ንቁ. She is a vibrant young lady. ንቁ ፡ ወጣት ፡ ወይዘሮ ፡ ነች

**vibrate**

1. አስተጋባ. The hall vibrated with their cheers. በደስታ ፡ ከመጮኻቸው ፡ የተነሣ ፡ አዳራሹ ፡ አስተጋባ

2. ተርገበገበ. A guitar string vibrates when plucked. የጊታር ፡ ክር ፡ ሲመታ ፡ ይርገበገባል

3. ተንቀጠቀጠ. The house vibrates when heavy trucks pass by. ትልልቅ ፡ የጭነት ፡ መኪናዎች ፡ ሲያልፉ ፡ ቤቱ ፡ ይንቀጠቀጣል

4. ተቀሰቀሰ. Their hearts vibrated to the speaker's stirring appeal. በተናጋሪው ፡ አነሣሽ ፡ ንግግር ፡ ወኔያቸው ፡ ተቀሰቀሰ

**vibration** መንገጫገጭ

The vibrations of the window could be heard in the street. የመስኮቱ ፡ መንገጫገጭ ፡ እስከ ፡ መንገዱ ፡ ድረስ ፡ ይሰማ ፡ ነበር

**vicar** ገበዝ

The vicar is in charge of repairing the village church. ገበዙ ፡ የመንደሩን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለማደስ ፡ ኀላፊነት ፡ አለበት

**vicarious** የወኪልነት

Vicarious authority rests with the deputy during the minister's absence. ሚኒስትሩ ፡ በሌለበት ፡ ጊዜ ፡ ምክትሉ ፡ የወኪልነት ፡ ሥልጣን ፡ ይኖረዋል

*I get a vicarious thrill from reading about the adventures of others. የሌሎችን ፡ ጀብዱ ፡ ሳነብ ፡ ልክ ፡ እኔ ፡ ያለሁበት ፡ ይመስለኛል

**vice** መጥፎ ፡ ምግባር ፤ መጥፎ ፡ አመል

Gluttony and drunkenness have been called carnal vices. ሆዳምነትና ፡ ጠጭነት ፡ የሥጋ ፡ መጥፎ ፡ ምግባሮች ፡ ይባላሉ

Smoking is my only vice; drinking is his. የኔ ፡ መጥፎ ፡ አመል ፡ ማጨስ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ የሱ ፡ ደግሞ ፡ መጠጥ ፡ ነው

**vice-** ምክትል

The vice-president died last week. ምክትል ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ ሞተ

**vice versa**

*We gossip about them and vice versa. እኛ ፡ ስለነሱ ፡ ስናወራ ፡ እነሱ ፡ ደግሞ ፡ ስለኛ ፡ ያወራሉ

**vicinity**

1. አካባቢ. He knows many people in Addis Ababa and its vicinity. በአዲስ ፡ አበባና ፡ ባካባቢው ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ያውቃል

2. ቅርብነት. He was troubled by the vicinity of the factory. በፋብሪካው ፡ ቅርብነት ፡ ተቸግሮ ፡ ነበር

**be in close vicinity** ተቀራረበ

The theaters are in close vicinity. ቲያትር ፡ ቤቶቹ ፡ የተቀራረቡ ፡ ናቸው

**in the vicinity** በዚያ ፡ አካባቢ

There are good restaurants in the vicinity. በዚያ ፡ አካባቢ ፡ ጥሩ ፡ ምግብ ፡ ቤቶች ፡ አሉ

**in the vicinity of** በ — አካባቢ

There are two stores in the vicinity of our house. በቤታችን ፡ አካባቢ ፡ ሁለት ፡ መደብሮች ፡ አሉ

**vicious**

1. አረመኔ. The vicious criminal escaped from prison. አረመኔ ፡ ወንጀለኛ ፡ ከወህኒ ፡ ቤት ፡ አመለጠ
2. ተናካሽ. The dog is vicious. ውሻው ፡ ተናካሽ ፡ ነው
3. በተንኰል ፡ የተሞላ. The criminal led a vicious life. ወንጀለኛው ፡ በተንኰል ፡ የተሞላ ፡ ኑሮ ፡ ኖረ
4. የተንኰል. A vicious rumor about his sanity was spread by his enemies. ጠላቶቹ ፡ ስለ ፡ አእምሮው ፡ ጤንነት ፡ የተንኰል ፡ ወሬ ፡ ነዙ
5. የተዛባ. This argument contains vicious reasoning. ይህ ፡ ክርክር ፡ የተዛባ ፡ አስተሳሰብ ፡ አለበት

**vicious temper**
He has a vicious temper. በጣም ፡ ግልፍተኛ ፡ ነው

**vicious circle**
*The problem is caught in a vicious circle. ችግሩ ፡ ዙሪያ ፡ ጥምጥም ፡ ስለሆነ ፡ መውጫ ፡ መንገድ ፡ የለውም

**vicissitudes**
*The vicissitudes of life left marks on his face. የኑሮ ፡ ውጣ ፡ ውረድ ፡ በዝቶበት ፡ እንደነበረ ፡ ፊቱ ፡ ያመለክታል

**victim**

1. የሞተ. The victims of the earthquake were buried in a mass grave. በመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ምክንያት ፡ የሞቱት ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ መቃብር ፡ ውስጥ ፡ ተቀበሩ
2. የተጐዳ. There was an appalling number of victims after the earthquake. ከመሬት ፡ መንቀጥቀጡ ፡ በኋላ ፡ የሚያሳዝኑ ፡ ብዙ ፡ የተጐዱ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ
3. በጠላት ፡ እጅ ፡ የወደቀ. The aggressor was Italy; the victim, Ethiopia. ጠብ ፡ አጫሪዋ ፡ ኢጣሊያን ፡ ስትሆን ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ የወደቀችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነበረች
4. የ -- እርዳታ ፡ የደረሰ(በት) ፤ በ --- ጉዳት ፡ የደረሰ(በት). The flood victims received assurances of government aid. የውኃ ፡ መጥለቅለቅ ፡ አደጋ ፡ የደረሰባቸው ፡ ሰዎች ፡ ከመንግሥት ፡ እርዳታ ፡ እንደሚደርሳቸው ፡ ተረጋገጠላቸው

The organization solaced the distress of the flood victims. ድርጅቱ ፡ በጐርፉ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ረዳ

*Victims of diseases such as typhus and yellow fever must be kept away from healthy people. ተስቦንና ፡ ቢጫ ፡ ወባን ፡ የመሳሰሉ ፡ በሽታዎች ፡ የያዟቸው ፡ ሰዎች ፡ ከጤነኞች ፡ ተገልለው ፡ መቀመጥ ፡ አለባቸው

*He was the victim of a swindle. ባታላይ ፡ እጅ ፡ ወደቀ

*He was the victim of the dictator's rage. አምባገነኑ ፡ በንዴት ፡ ገደለው

**fall victim to** ተማረከ
He fell victim to her charm. በውበቷ ፡ ተማረከ

**robbery victim** የተዘረፈ ፡ ሰው
The robbery victim gave a detailed account of the robbery to the police. የተዘረፈው ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ዘረፋው ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ለፖሊሶች ፡ ነገረ

**victor** አሸናፊ
The victors paraded through the town. አሸናፊዎቹ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ በሰልፍ ፡ አለፉ

**victorious** አሸናፊ
If we are to be victorious, we must fight harder. አሸናፊዎች ፡ ለመሆን ፡ ከፈለግን ፡ ጠንክረን ፡ መዋጋት ፡ አለብን

**be victorious** አሸነፈ
Our side was victorious in the war. በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ የኛ ፡ ወገን ፡ አሸነፈ

**victory** (victories)

1. ድል. The victory was celebrated with dancing and feasting. ድሉ ፡ በጭፈራና ፡ በፈንጠዝያ ፡ ተከበረ
2. ድል ፡ መምታት. There was exultation over the army's victory. ጦሩ ፡ ድል ፡ በመምታቱ ፡ ፈንጠዝያ ፡ ሆነ

**victuals** ምግብ
The victuals offered us by the villagers were hard to digest. በመንደሩ ፡ ሰዎች ፡ የቀረበልን ፡ ምግብ ፡ አልንሸራሸር ፡ አለን

**vie** ተወዳደረ ፤ ጣረ
The two people vied with each other for the job. ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ ሥራውን ፡ ለማግኘት ፡ ተወዳደሩ
He is still uncommitted, so both parties are vying for his support. እሱ ፡ ገና ፡ ማንን ፡ እንደሚደግፍ ፡ ስላልገለጸ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ የሱን ፡ ድጋፍ ፡ ለማግኘት ፡ ይጥራሉ

**view** (v.)

1. ተመለከተ. They viewed the scene with pleasure. ትዕይንቱን ፡ በደስታ ፡ ተመለከቱ
The teachers did not view with favor the plan of changing the teaching hours. የማስተማሪያ ፡ ጊዜዎችን ፡ ለመለወጥ ፡ የታቀደውን ፡ ሐሳብ ፡ አስተማሪዎቹ ፡ በደግ ፡ አልተመለከቱትም
2. መረመረ. They viewed each idea separately. እያንዳንዱን ፡ ሐሳብ ፡ ለየብቻው ፡ መረመሩት

**view** (n.)

1. ትዕይንት. The view from the mountaintop is breathtaking. ከተራራው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ ትዕይንት ፡ ልብ ፡ ያጠፋል
2. ሥዕል. He showed me views of the falls. የፏፏቴዎቹን ፡ ሥዕል ፡ አሳየኝ
3. ማየት. It was my first view of the ocean. ውቅያኖሱን ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ማየቴ ፡ ነበር
4. ፊት. He disappeared from my view. ከፊቴ ፡ ጠፋ
5. ዓይን. The clouds came down, and the hilltops passed from our view. ደመናው ፡ የኰረብታውን ፡ ጫፍ ፡ ከዓይናችን ፡ ሰወረው
6. አስተያየት. Our views differ. አስተያየታችን ፡ ይለያያል
My father-in-law takes a dim view of my business activities. አማቴ ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ሥራዬ ፡ ዝቅተኛ ፡ አስተያየት ፡ አላቸው
The facts will help you to get a clear view of the situation. እውነተኞቹ ፡ ነገሮች ፡ ስለ ፡ ሁኔታው ፡ ግልጽ ፡ አስተያየት ፡ እንዲኖርህ ፡ ይረዱሃል
7. ሁኔታ. This book will give you a general view of the war. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታ ፡ ይገልጽልሃል
8. ዓላማ. He had a view of making more money. ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ዓላማ ፡ ነበረው

**come into view** ለዓይን ፡ ታየ
The ship finally came into view. በመጨረሻው ፡ መርከቡ ፡ ለዓይን ፡ ታየ

**hold (the) view** አስተያየት ፡ አለው
He holds the view that the plan won't work. እቅዱ ፡ አይሠራም ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ አለው

**in view**
*She went over the material with the scholarship examination in view. ለነጻ ፡ ትምህርት ፡ መፈተኗን ፡ መሠረት ፡ አድርጋ ፡ ትምህርቱን ፡ ከለሰችው

**in view of**
1. ሲታይ. In view of his record, I don't think he should be hired. የሕይወት ፡ ታሪኩ ፡ ሲታይ ፡ መቀጠር ፡ የሚገባው ፡ አይመስለኝም
2. ከ - - ጋር ፡ ሲመዛዘን. His vitality is amazing in view of his age. ጥንካሬው ፡ ከዕድሜው ፡ ጋር ፡ ሲመዛዘን ፡ በጣም ፡ ያስደንቃል

**keep in view** አስታወሰ
Keep the teacher's advice in view as you try to improve your work. ሥራህን ፡ ለማሻሻል ፡ በምትሞክርበት ፡ ጊዜ ፡ የመምህርህን ፡ ምክር ፡ አስታውስ

**(be) on view** ለሕዝብ ፡ ክፍት ፡ ነው
The exhibit is on view from 9 A.M. to 5 P.M. ኤግዚቢሽኑ ፡ ከጧቱ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ለሕዝብ ፡ ክፍት ፡ ነው

**with a view to**
*He is buying land in Harar with a view to opening a store there. ወደፊት ፡ መደብር ፡ ለመክፈት ፡ በማሰብ ፡ አሁን ፡ ሐረር ፡ ውስጥ ፡ መሬት ፡ ይገዛል
[See also 'conceal, dim, liberal, shut']

**viewpoint** አስተያየት
His viewpoint is different from mine. አስተያየቱ ፡ ከኔ ፡ የተለየ ፡ ነው

**vigil**
1. ንቅቶ ፡ መጠባበቅ. The nurse's vigil by the patient's bed lasted all night. አስታማሚዋ ፡ ንቅታ ፡ በመጠባበቅ ፡ ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ በሽተኛው ፡ አልጋ ፡ አጠገብ ፡ አደረች
2. ዋዜማ. The vigil of Christmas was kept in the church by a small group of priests. የልደት ፡ ዋዜማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ በጥቂት ፡ ቄሶች ፡ ተከበረ

**keep a vigil** ተጠባበቀ
The worried parents kept a vigil at the bedside of their sick child. በጣም ፡ የተጨነቁት ፡ ወላጆች ፡ ከታመመው ፡ ልጃቸው ፡ ጐን ፡ ሆነው ፡ ይጠባበቁታል

**vigilance** ንቃት
Through his vigilance, we avoided a trap. በሱ ፡ ንቃት ፡ ምክንያት ፡ ከመያዝ ፡ ዳን

**vigilant** ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ ንቁ
We must be vigilant if we are to prevent agents from entering our country. የውጭ ፡ አገር ፡ አነፍናፊዎች ፡ ሀገራችን ፡ እንዳይገቡ ፡ ከፈለግን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ንቁ ፡ መሆን ፡ አለብን

**vigor** ብርታት ፤ ወኔ
Age has not diminished his vigor. በዕድሜው ፡ መግፋቱ ፡ ብርታቱን ፡ አልቀነሰውም
He has the vigor of youth. የወጣት ፡ ወኔ ፡ አለው

**with vigor**
1. በርትቶ. He tackled the job with vigor. ሥራውን ፡ በርትቶ ፡ ሠራ
2. አጥብቆ. The principal argued with vigor that the new school should have a library. ሥራ ፡ መሪው ፡ አዲሱ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ እንዲኖረው ፡ አጥብቆ ፡ ተከራከረ

**vigorous**
1. ብርቱ. The old man is still vigorous and lively. ሽማግሌው ፡ አሁንም ፡ ብርቱና ፡ ንቁ ፡ ነው
2. ኀይለኛ. Doctors wage a vigorous war against diseases. ሐኪሞች ፡ በሽታን ፡ ለማጥፋት ፡ ኀይለኛ ፡ ተጋድሎ ፡ ያደርጋሉ

**vigorously** በብርታት
They fought vigorously to keep from being driven out of their post. ይዞታቸውን ፡ እንዳይለቁ ፡ በብርታት ፡ ተዋጉ

**vile**
1. ግም. Where is that vile smell coming from? ያ ፡ ግም ፡ ሽታ ፡ የሚመጣው ፡ ከየት ፡ ነው ?
2. መጥፎ. Your vile behavior has sickened us all. መጥፎ ፡ ጠባይህ ፡ ሁላችንንም ፡ አስቀይሞናል
3. የብልግና. The criminal used vile language. ወንጀለኛው ፡ የብልግና ፡ ንግግር ፡ ተናገረ
4. ዝቅተኛ. He stooped to the vile tasks of the kitchen. እራሱን ፡ አዋርዶ ፡ ዝቅተኛ ፡ የሆኑትን ፡ የማእድ ፡ ቤት ፡ ሥራዎች ፡ ሠራ

**vilify** (vilified) ስም ፡ አጐደፈ
He vilified his opponent in a public speech. በንግግሩ ፡ ላይ ፡ የተቃዋሚውን ፡ ስም ፡ አጐደፈ

**villa** ቪላ
He owns a villa on the edge of town. ከተማው ፡ ዳር ፡ አንድ ፡ ቪላ ፡ አለው

**village** መንደር
The village has no electricity. መንደሩ ፡ የኤሌክትሪክ ፡ መብራት ፡ የለውም
The whole village went to receive the governor. መንደሩ ፡ በሙሉ ፡ ገዢውን ፡ ሊቀበል ፡ ሄደ
[See also 'people']

**villager** መንደርተኛ
All the villagers went to the market. መንደርተኛው ፡ ሁሉ ፡ ገበያ ፡ ሄዷል

**villain** ተንኰለኛ
The villain aimed a murderous blow at the hero's back. ተንኰለኛው ፡ ጀግናውን ፡ ጀርባው ፡ ላይ ፡ መቶ ፡ ሊገድል ፡ የሚችለው ፡ ምት ፡ ሰነዘረ

**villainy** ክፉነት
His villainy has made him known as the greatest scoundrel in history. ክፉነቱ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የታወቀ ፡ ወሮበላ ፡ አድርጎታል

**vindicate**
1. ነጻ ፡ አወጣ. The committee vindicated him of charges of bribery. ጉቦ ፡ በልቷል ፡ በማለት ፡ ከቀረበበት ፡ ክስ ፡ ደርጉ ፡ ነጻ ፡ አወጣው
2. ደገፈ. A special committee vindicated his plans. የሱን ፡ እቅድ ፡ ልዩ ፡ ደርግ ፡ ደገፈ
3. አረጋገጠ. His brave acts vindicated their faith in him. የጀግንነት ፡ ሥራዎቹ ፡ ሰዎቹ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ እምነት ፡ አረጋገጡ
The heir vindicated his claim to the fortune. ወራሹ ፡ ሀብቱ ፡ ይገባኛል ፡ ባይነቱን ፡ አረጋገጠ

**vindictive**
1. ቂመኛ. She is vindictive and will retaliate if you offend her in any way. ቂመኛ ፡ ስለሆነች ፡ ከነካሃት ፡ ብድሯን ፡ ትመልሳለች
2. የበቀል. Vindictive punishment is no inducement to reform. የበቀል ፡ ቅጣት ፡ ለመሻሻል ፡ ምክንያት ፡ አይሆንም

**vine**
1. ሐረግ. Monkeys swing from vines hanging from the trees. ዝንጀሮዎች ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ በሚገኙ ፡ ሐረጎች ፡ ላይ ፡ ይንጠለጠላሉ
2. ወይን. Since the vine has many leaves, it serves for shade. ወይኑ ፡ ብዙ ፡ ቅጠል ፡ ስላለው ፡ ለጥላ ፡ ያገለግላል

**vinegar** ኮምጣጤ
Vinegar is used in cooking. ኮምጣጤ ፡ ለማብሰያ ፡ ያገለግላል

**vineyard** የወይን ፡ ተክል
His vineyard was damaged by the rain. የወይኑን ፡ ተክል ፡ ዝናብ ፡ አበላሽቶታል

**vintage** የተጠመቀበት ፡ ዓመት
The vintage of wine determines its price. የወይን ፡ ጠጅን ፡ ዋጋ ፡ የሚወስነው ፡ የተጠመቀበት ፡ ዓመት ፡ ነው

**of ancient vintage** የድሮ
He drives a car of ancient vintage. የድሮ ፡ መኪና ፡ ይነዳል

**violate**
1. ጣሰ. That's not the first time he's violated the law. ሕጉን ፡ ሲጥስ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜው ፡ አይደለም
2. አረከሰ. The bandits violated the shrine. ሽፍቶቹ ፡ የተቀደሰውን ፡ ስፍራ ፡ አረከሱት
3. አደፈረሰ. The loud music violated the silence. የሙዚቃው ፡ ጩኸት ፡ ጸጥታውን ፡ አደፈረሰው

**violation** ሕግን ፡ መጣስ
Violations will be severely punished. ሕግን ፡ መጣስ ፡ በጥብቅ ፡ ያስቀጣል

**violator** ያፈረሰ
The violators of this regulation were all fined

$100. ይህንን ፡ ደንብ ፡ ያፈረሱት ፡ ሁሉ ፡ መቶ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ተቀጡ

**violence**

1. ሁከት ፤ ብጥብጥ. Violence broke out in the streets when the assassination of the general became known. የጄኔራሉ ፡ መገደል ፡ እንደታወቀ ፡ በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ (ብጥብጥ) ፡ ተነሣ
2. ኀይል. He slammed the door with violence. መዝጊያውን ፡ በኀይል ፡ ዘጋው
3. ኀይለኛነት. The violence of the waves frightened everyone. የሞገዱ ፡ ኀይለኛነት ፡ ሁሉንም ፡ አስደነገጠ
The violence of his rage astonished everyone. የቁጣው ፡ ኀይለኛነት ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አስገረመ

**do violence to**

1. ተፃረረ. It would do violence to her principles to work on Sunday. በእሑድ ፡ መሥራት ፡ እምነቷን ፡ የሚፃረር ፡ ነው
2. አጠፋ(በት). The deer did violence to his garden by tramping through it. አጋዘኑ ፡ አትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ረጋግጦ ፡ አጠፋበት

**violent**

1. ኀይለኛ. We had a violent argument. ኀይለኛ ፡ ክርክር ፡ ተከራከርን
A violent blow sent him reeling into the street. በኀይለኛው ፡ ምት ፡ ምክንያት ፡ ተንገዳገደ ፡ መንገድ ፡ ውስጥ ፡ ገባ
His violent language betrayed how upset he was. ኀይለኛ ፡ አነጋገሩ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ተበሳጭቶ ፡ እንደነበር ፡ ገለጸ
2. ቁጡ. He is a very violent person. በጣም ፡ ቁጡ ፡ ሰው ፡ ነው

**die a violent death**

Lumumba died a violent death. ሉሙምባ ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ ተገደለ

**violin** ቫዮሊን

Play me a song on the violin! ቫዮሊን ፡ ተጫወትልኝ

**viper** እፉኝት

The viper bit her, and she died in agony. እፉኝት ፡ ነድፏት ፡ በአሰቃቂ ፡ ሁኔታ ፡ ሞተች

**virgin** (n.) ክብርና ፡ ያላት

In some countries, only virgins wear white for a wedding. ባንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ለሰርግ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ የሚለብሱ ፡ ክብርና ፡ ያላቸው ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**virgin forest** ሳይነካ ፡ የኖረ ፡ ጫካ

The virgin forest was soon cut down. ሳይነካ ፡ የኖረው ፡ ጫካ ፡ ባንዴ ፡ ተመነጠረ

**Virgin Mary** ድንግል ፡ ማርያም

Catholics worship the Virgin Mary. ካቶሊኮች ፡ በድንግል ፡ ማርያም ፡ ያምናሉ

**virgin soil** ድንግል ፡ መሬት

The virgin soil was put to the plow. ድንግሉ ፡ መሬት ፡ ታረሰ

**virginity** ክብርና

She was punished by her father when she lost her virginity. ክብርናዋን ፡ ስላስወሰደች ፡ አባቷ ፡ ገረፏት

**virile** ጀግና

He is very virile, but his brother is effeminate. እሱ ፡ በጣም ፡ ጀግና ፡ ነው ፤ ወንድሙ ፡ ግን ፡ ሴታ ፡ ሴት ፡ ነው

**virtual** (= adv.) ልክ ፡ እንደ

This is a virtual state of war. ይህ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ጦርነት ፡ ይዞታ ፡ ነው
*He is the virtual president, though his title is secretary. ስሙ ፡ ጸሐፊ ፡ ቢሆንም ፡ የፕሬዚዳንቱን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራው ፡ እሱ ፡ ነው

**virtually** ልክ ፡ እንደ

He is virtually prime minister since the latter is so ill. ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በጣም ፡ ስለታመመ ፡ እሱ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ነው

**virtue**

1. ጥሩነት. Our climate has the virtue of never being too hot or too cold. ያገራችን ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፡ ጥሩነት ፡ በጣም ፡ ቀዝቃዛ ፡ ወይም ፡ በጣም ፡ ሞቃት ፡ ያለመሆኑ ፡ ነው
2. ጸጋ. Leadership is not a common virtue. መሪነት ፡ ሁሉ ፡ የሚያገኘው ፡ ጸጋ ፡ አይደለም
3. ባሕርይ. Generosity is his greatest virtue. ደግነት ፡ ዋነኛው ፡ ባሕርዩ ፡ ነው
4. የመልካም ፡ ምግባር ፡ ጸጋ. Patience is a virtue. ትዕግሥት ፡ የመልካም ፡ ምግባር ፡ ጸጋ ፡ ነው
5. ደግነት. The priest extolled the virtues of the deceased. ቄሱ ፡ የሟቹን ፡ ደግነት ፡ እያነሡ ፡ በማሞገስ ፡ ተናገሩ
6. ጥቅም. Your plan has certain virtues. እቅድህ ፡ አንዳንድ ፡ ጥቅሞች ፡ አሉበት
*Have you faith in the virtue of these herbs to heal your illness? ይህ ፡ ሥራሥር ፡ ሊያድነኝ ፡ ይችላል ፡ ብለህ ፡ ታምናለህ ?

**by virtue of** በ

By virtue of his long military service, he claimed a pension. ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ በወታደርነት ፡ በማገልገሉ ፡ የጡረታ ፡ አበል ፡ እንዲከፈለው ፡ ጠየቀ

**of virtue** ጨዋ
She is a woman of virtue. ጨዋ ፡ ሴት ፡ ናት

**virtuous** ደግ ፡ አድራጊ
The divine kingdom is the reward of the virtuous in many religions. ለብዙ ፡ ሃይማኖት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መግባት ፡ የደግ ፡ አድራጊዎች ፡ ዋጋ ፡ ነው

**virtuous character** ጨዋነት
Her virtuous character has earned her the respect of all. ጨዋነቷ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ አስከብሯታል

**remain virtuous** ንጽሕናዋን ፡ ጠብቃ ፡ ቆየች
His fiancée remained virtuous while he was in prison. ታስሮ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ እጮኛው ፡ ንጽሕናዋን ፡ ጠብቃ ፡ ቆየች

**virulent**
1. የሚገድል. Typhus is a virulent disease. ተስቦ ፡ የሚገድል ፡ በሽታ ፡ ነው
2. የመረረ. They showed their virulent hostility by poisoning the travelers' mounts. የመንገደኞቹን ፡ የከርቻ ፡ ከብቶች ፡ መርዝ ፡ በማብላት ፡ ያላቸውን ፡ የመረረ ፡ ጥላቻ ፡ አሳዩ

**virus** ቫይረስ
The disease is caused by a virus. በሽታው ፡ የሚመጣው ፡ ከቫይረስ ፡ ነው

**visa** ቪዛ
I have a visa in my passport. በይለፍ ፡ ወረቀቴ ፡ ውስጥ ፡ ቪዛ ፡ አለኝ

**visibility**
*The visibility is poor because of fog. ከጭጋጉ ፡ የተነሣ ፡ በደንብ ፡ አይታይም
*Fog reduced the visibility to 500 feet. ጭጋጉ ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡ ጫማ ፡ የበለጠ ፡ አያሳይም

**visible**
1. የታወቀ. He has no visible income. የታወቀ ፡ ገቢ ፡ የለውም
2. (= adv.) በጉልህ. There is a visible increase in crime this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ ወንጀል ፡ በጉልህ ፡ ጨምሯል

**be visible** ታየ
The mountains are not visible in the fog. ተራራዎቹ ፡ ከጭጋግ ፡ የተነሣ ፡ አይታዩም

**visibly** በግልጽ
After the hike, the boys were visibly weary. ከሽርሽሩ ፡ በኋላ ፡ ልጆቹ ፡ መድከማቸው ፡ በግልጽ ፡ ይታወቅ ፡ ነበር

**vision**
1. ዓይን. His vision is getting poor. ዓይኑ ፡ እየደከመ ፡ ሄደ
2. የማየት ፡ ችሎታ. She wears glasses to improve her vision. የማየት ፡ ችሎታዋን ፡ ለማሻሻል ፡ መነጽር ፡ ታደርጋለች
3. አስተያየት. He is a man of great vision. ጥልቅ ፡ አስተያየት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው

**have visions of** አለመ
The beggar had visions of great wealth. ለማኙ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሀብት ፡ ለማግኘት ፡ ያልም ፡ ነበር

**visionary** (visionaries), n.
*Most great scientists have been visionaries. አብዛኛዎቹ ፡ ታላላቅ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ የወደፊቱን ፡ በሐሳብ ፡ የማየት ፡ ችሎታ ፡ ነበራቸው

**visionary** (adj.) የሕልም ፡ እንጀራ ፡ የሆነ
His visionary scheme called for building a canal from the Blue Nile to the Awash. የሕልም ፡ እንጀራ ፡ የሆነው ፡ እቅዱ ፡ ከዐባይ ፡ እስከ ፡ አዋሽ ፡ ቦይ ፡ ለመቅደድ ፡ ነበር

**visit** (v.)
1. ጠየቀ. He wanted to visit you. ሊጠይቅህ ፡ ፈለገ
2. ጐበኘ. Have you visited our museum yet? ቤተ ፡ መዘክራችንን ፡ ገና ፡ አልጐበኘህም ?
3. ተሳለመ. We will visit the shrine of Our Lady on Sunday. የእመቤታችንን ፡ ቅዱስ ፡ ስፍራ ፡ እሑድ ፡ እንሳለማለን

**be visited by** ደረሰ(በት)
The poor old man was visited by many troubles. ድኻው ፡ ሽማግሌ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ደረሰበት

**visit** (n.)
*That was an unexpected visit. ሳናስበው ፡ መጣህ
*His visit gives me great pleasure. ስለጠየቀኝ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለኝ
*How much does the doctor charge for a visit? ሐኪሙ ፡ እቤትህ ፡ ድረስ ፡ ቢመጣ ፡ ስንት ፡ ያስከፍላል ?

**pay a visit** ጠየቀ
I must pay my sick friend a visit. የታመመውን ፡ ጓደኛዬን ፡ መጠየቅ ፡ አለብኝ

**visiting** (adj.) እንግዳ
The reporter interviewed the visiting diplomat. ዜና ፡ አጠናቃሪው ፡ ለእንግዳው ፡ ዲፕሎማት ፡ የቃል ፡ መጠየቅ ፡ አቀረበ

**visitor**
1. እንግዳ. We are having visitors tonight. ዛሬ ፡ ማታ ፡ እንግዶች ፡ ይመጡብናል

2. ባለ ፡ ጉዳይ. He couldn't see any visitors because he was busy. ሥራ ፡ ስለበዛበት ፡ ባለ ፡ ጉዳዮችን ፡ ሊያነጋግር ፡ አልቻለም
3. ያገር ፡ ጐብኚ. The town is astir with visitors. ከተማይቱ ፡ ባገር ፡ ጐብኚዎች ፡ ተሟሙቃለች

**visor** [ፊትን ፡ ለመሸፈን ፡ የሚያገለግል ፡ የራስ ፡ ቁር ፡ ክፍል]

**vista**
*The opening between the two rows of trees afforded a vista of the lake. ግራና ፡ ቀኝ ፡ ባሉት ፡ ዛፎች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ገላጣ ፡ ሐይቁን ፡ ለማየት ፡ ያስችላል

**visual**
1. የማያ. The eye is a visual organ. ዓይን ፡ የማያ ፡ አካል ፡ ነው
2. የሚታይ. The eye changes shape when it fixes on a visual object. ዓይን ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ሲያርፍ ፡ ቅርጹ ፡ ይለወጣል

**visualize** በዓይነ ፡ ኅሊና ፡ አየ
He tried to visualize how people lived in ancient times. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡ እንዴት ፡ ይኖሩ ፡ እንደነበር ፡ በዓይነ ፡ ኅሊናው ፡ ለማየት ፡ ሞከረ

**vital**
1. በጣም ፡ አስፈላጊ ፤ እጅግ ፡ አስፈላጊ. A strong army is vital to the defense of a nation. ለሀገር ፡ መከላከል ፡ ጠንካራ ፡ ጦር ፡ በጣም ፡ (እጅግ) ፡ አስፈላጊ ፡ ነው
2. ንቁ. What a vital boy he is! እንዴት ፡ ያለ ፡ ንቁ ፡ ልጅ ፡ ነው!
*His vital wound cost him his life. በጽኑ ፡ ስለቆሰለ ፡ ሞተ

**(be a) vital blow to** አደከመ
The new invention was a vital blow to the old industry. አዲሱ ፡ ፍልሰፋ ፡ የጥንቱን ፡ ኢንዱስትሪው ፡ የሚያደክም ፡ ነበር

**vital force** ለመኖር ፡ ያለው ፡ ፍላጎት
The vital force keeps us from committing suicide. ለመኖር ፡ ያለን ፡ ፍላጎት ፡ ራሳችንን ፡ ከመግደል ፡ ያግደናል

**vital function**
Eating is a vital function. መብላት ፡ ለሕይወት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**(of) vital importance** እጅግ ፡ አስፈላጊ
It's of vital importance to me that I reach the airport on time. አውሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ በሰዓቱ ፡ መድረስ ፡ እጅግ ፡ አስፈላጊዩ ፡ ነው

**vitality** ጥንካሬ
His vitality is amazing in view of his age. ከዕድሜው ፡ ጋራ ፡ ሲመዛዘን ፡ ጥንካሬው ፡ በጣም ፡ ያስደንቃል

**vital statistics**
*Does the Ethiopian government publish vital statistics? የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ በሽታዎች ፡ የተለከፈውን ፡ የተወለደውንና ፡ የሞተውን ፡ ሰው ፡ ልክ ፡ የሚገልጽ ፡ እስታትስቲክ ፡ ያወጣል ?

**vitamin** ቪታሚን
Vitamins are necessary for the body. ቪታሚን ፡ ለሰውነት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**vitiate**
1. አበላሸ. Bad company has vitiated his character. መጥፎ ፡ ጓደኛ ፡ ጠባዩን ፡ አበላሽቶታል
2. (= intr.) ዋጋ ፡ቢስ ፡ ሆነ. The errors in marking vitiated the ballot. የድምፅ ፡ መስጫው ፡ ወረቀት ፡ ምልክት ፡ ሲደረግበት ፡ ስለተሳሳተ ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ሆነ

**vituperate** የስድብ ፡ ናዳ ፡ አወረደ(በት)
His wife vituperates him for almost anything. ሚስቱ ፡ ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ የስድብ ፡ ናዳ ፡ ታወርድበታለች

**vituperative** ስድ
Her vituperative manner of speaking offends everyone who hears her. ስድ ፡ አነጋገሯ ፡ የሚሰማትን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያስቀይማል

**vivacious** ፎለፎል
She is so vivacious, everyone wants to invite her to his party. በጣም ፡ ፎለፎል ፡ ስለሆነች ፡ ሁሉም ፡ ሰው ፡ ፓርቲ ፡ ሊጋብዛት ፡ ይፈልጋል

**vivacity** ጨዋተኛነት
His vivacity gets him invited to all the parties. በጨዋተኛነቱ ፡ በየፓርቲው ፡ ይጠራል

**vivid**
1. ጉልህ. He gave a vivid description of the massacre. ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ መፈጀት ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ገለጻ ፡ አደረገ
2. ደማቅ. These flowers are a vivid yellow. እነዚህ ፡ አበቦች ፡ ደማቅ ፡ ቢጫ ፡ ናቸው
3. (= adv.) በግልጽ. I had a vivid memory of the fire. ቃጠሎውን ፡ በግልጽ ፡ አስታውሳለሁ
4. (= adv.) ጉልቶ. I have a vivid recollection of that horrible day. ያ ፡ ክፉ ፡ ቀን ፡ ጉልቶ ፡ ይታየኛል

**vividly** በግልጽ
She remembers the accident vividly. አደጋውን ፡ በግልጽ ፡ ታስታውሳለች

**vivify** (vivified) ሕይወት ፡ ሰጠ
Her presence vivifies any gathering she attends. የሷ ፡ መገኘት ፡ ለማንኛቸውም ፡ ስብሰባ ፡ ሕይወት ፡ ይሰጠዋል

**vocabulary** (vocabularies)
1. መዝገበ ፡ ቃላት. He published an Amharic-English vocabulary. የአማርኛና ፡ የእንግሊዝኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ አወጣ
2. ቃላት. The farmer has a limited vocabulary. ገበሬው ፡ የሚያውቃቸው ፡ ቃላት ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው

**vocal**
1. ድምፅ ፡ ያለው. Men are vocal beings. ሰዎች ፡ ድምፅ ፡ ያላቸው ፡ ፍጡሮች ፡ ናቸው
2. ከድምፅ ፡ መስጠት ፡ ጋር ፡ የተያያዘ. The tongue is a vocal organ. ምላስ ፡ ከድምፅ ፡ መስጠት ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ አካል ፡ ነው
3. (= adv.) በቃል. The farmers expressed their vocal support for the project. ገበሬዎቹ ፡ እቅዱን ፡ መደገፋቸውን ፡ በቃል ፡ ገለጹ

**be vocal** ስሜቱን ፡ በግልጽ ፡ ተናገረ
She was vocal in the fight for women's rights. ስለ ፡ ሴቶች ፡ መብት ፡ በሚደረገው ፡ ትግል ፡ ላይ ፡ ስሜቷን ፡ በግልጽ ፡ ተናገረች

**vocal cords** የድምፅ ፡ አውታሮች
The vocal cords produce sound. የድምፅ ፡ አውታሮች ፡ ድምፅ ፡ ይሰጣሉ

**vocation**
1. ሥራ. His vocation is nursing the sick. ሥራው ፡ በሽተኛን ፡ ማስታመም ፡ ነው
2. ችሎታ. He has no vocation for teaching, but he would make a good policeman. የማስተማር ፡ ችሎታ ፡ ያንሰዋል ፤ ግን ፡ ጥሩ ፡ ፖሊስ ፡ ይወጣዋል

**vocational school** የሙያ ፡ ትምህርት ፡ ቤት
The town needs a vocational school. ከተማው ፡ የሙያ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ያስፈልገዋል

**vociferous**
1. የሚንጫጫ. The vociferous crowd shouted the speaker down. የሚንጫጫው ፡ ሕዝብ ፡ ተናጋሪውን ፡ በጩኸት ፡ ዝም ፡ አሰኘ
2. (= adv.) በጩኸት. The vociferous arguments could be heard all over. በጩኸት ፡ የሚያደርጉት ፡ ክርክር ፡ በአካባቢው ፡ ሁሉ ፡ ይሰማ ፡ ነበር

**vogue, in ~** ፋሺን
Long skirts were in vogue many years ago. ከብዙ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ረጅም ፡ ቀሚስ ፡ ፋሺን ፡ ነበር

**voice** (v.)
1. ሰነዘረ. Everyone voiced his opinion. እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሐሳቡን ፡ ሰነዘረ
2. አሰማ. The workers voiced protest about the increased cost of living. ሠራተኞቹ ፡ ስለ ፡ ኑሮ ፡ ውድነት ፡ ተቃውሟቸውን ፡ አሰሙ

**voice** (n.) ድምፅ
She lost her voice because of a sore throat. ጉሮሮዋ ፡ ስለቈሰለ ፡ ድም፟ ፡ ተዘጋ
The singer has a good voice. ዘፋኙ ፡ ጥሩ ፡ ድምፅ ፡ አለው
Each voter has a voice in the government. እያንዳንዱ ፡ መራጭ ፡ በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ድምፅ ፡ አለው

**give voice to** ገለጸ
They gave voice to their joy. ደስታቸውን ፡ ገለጹ

**have no voice in** አላዘዘ(በትም)
I have no voice in how my money is spent. ገንዘቤን ፡ አላዝበትም

**with one voice** ባንድ ፡ ድምፅ
They chose him with one voice. ባንድ ፡ ድምፅ ፡ መረጡት
[See also 'raise, sound, thick, top']

**(be) voiced** ድምፅ ፡ አለው
The English vowels are voiced. የእንግሊዝኛ ፡ አናባቢዎች ፡ ድምፅ ፡ አላቸው

**void** (v.) አፈረሰ
Failure to abide by the terms will void the agreement. በውሉ ፡ መሠረት ፡ ያለመፈጸም ፡ ስምምነቱን ፡ ያፈርሰዋል

**be voided** ፈረሰ
The specifications were not fulfilled, so the contract was voided. ዝርዝሮቹ ፡ ደንቦች ፡ ስላልተከበሩ ፡ ውሉ ፡ ፈረሰ

**void** (n.)
1. ባዶ ፡ ስፍራ. Space is an immense void. ጠፈር ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ ባዶ ፡ ስፍራ ፡ ነው
2. የተጓደለ. When the singer failed to appear, the other singers tried to fill the void by singing songs. ዘፋኙ ፡ በመቅረቱ ፡ ሌሎቹ ፡ ዘፋኞች ፡ በመዝፈን ፡ የተጓደለውን ፡ ለማሟላት ፡ ሞከሩ

**leave a void** (= pass.) ጉድለት ፡ ተሰማ
Tom's departure left a void in our club. በቶም ፡ መውጣት ፡ በክበባችን ፡ ጉድለት ፡ ተሰማ

**void** (adj.)
1. ዋጋ ፡ ቢስ. The agreement was void because it hadn't been signed. ያልተፈረመበት ፡ ስለነበር ፡ ውሉ ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ሆነ
2. የማይጸና. The will was declared void by the court. ኑዛዜው ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የማይጸና ፡ ነው ፡ ተባለ

**be void** አይሠራም
The passport is void now. የይለፍ ፡ ወረቀቱ ፡ አሁን ፡ አይሠራም

**be void of** የለውም
His heart is void of kindness. ልቡ ፡ ርኅራኄ ፡ የለውም

**be void of interest**
The subject is void of interest for me. ነገሩ ፡ ምንም ፡ ስሜት ፡ አይሰጠኝም
[See also 'null']

**volatile**
1. ተለዋዋጭ. He is very volatile, so it's hard to know how he will act when we meet him. በጣም ፡ ተለዋዋጭ ፡ ስለሆነ ፡ ስናገኘው ፡ እንዴት ፡ እንደሚሆን ፡ ለማወቅ ፡ ያዳግታል
2. በቀላሉ ፡ የሚተን. Alcohol is a volatile liquid. አልኮል ፡ በቀላሉ ፡ የሚተን ፡ ፈሳሽ ፡ ነው

**volcanic** የእሳተ ፡ ገሞራ.
The volcanic eruption destroyed much property. የእሳተ ፡ ገሞራው ፡ መፈንዳት ፡ ብዙ ፡ ንብረት ፡ አጠፋ

**volcanic rock** እሳተ ፡ ገሞራ ፡ የተፋው ፡ ድንጋይ
The field is covered with pieces of volcanic rock. እሳተ ፡ ገሞራ ፡ የተፋው ፡ ድንጋይ ፡ ሜዳውን ፡ አለበሰው

**volcano** እሳተ ፡ ገሞራ
There are volcanos in some parts of Ethiopia. ባንዳንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ እሳተ ፡ ገሞራ ፡ አለ

**volition** ፈቃድ
He did it of his own volition. ያደረገው ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ ነው

**volley, ~ of shots** እሩምታ ፡ ተኩስ
The volley of shots failed to hit anyone. እሩምታው ፡ ተኩስ ፡ ማንንም ፡ ሳይመታ ፡ ቀረ

**volley of stones** የድንጋይ ፡ መዓት
The boys threw a volley of stones at the hyena. ልጆቹ ፡ በጅቡ ፡ ላይ ፡ የድንጋይ ፡ መዓት ፡ አወረዱበት

**volleyball** የመረብ ፡ ኳስ ፡ ጨዋታ
Volleyball is popular in Ethiopia. የመረብ ፡ ኳስ ፡ ጨዋታ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተወዳጅ ፡ ነው

**volt** ቮልት
One volt is sufficient to power this electric motor. ይህንን ፡ የኮረንቲ ፡ ሞተር ፡ ለማንቀሳቀስ ፡ አንድ ፡ ቮልት ፡ ይበቃል

**voluble** ለፍላፊ
His voluble mother annoys all his friends with her constant chatter. ለፍላፊ ፡ እናቱ ፡ ያለማቋረጥ ፡ በመናገር ፡ ጓደኞቹን ፡ ታስቀይማለች

**volume**
1. መጽሐፍ. You may borrow three volumes at a time. ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ መጽሐፍ ፡ ልትዋስ ፡ ትችላለህ
2. ቅጽ. The book was published in two volumes. መጽሐፉ ፡ በሁለት ፡ ቅጽ ፡ ታተመ
3. ይዞታ. A liter is a measure of volume. ሊትር ፡ የይዞታ ፡ መስፈሪያ ፡ ነው
4. ድምፅ. Lower the volume of your radio! የራዲዮንህን ፡ ድምፅ ፡ ቀንሰው
5. መጠን. The factory had a large volume of sales. ፋብሪካው ፡ መጠኑ ፡ የበዛ ፡ የሽያጭ ፡ እቃ ፡ ነበረው

**voluminous**
1. ግዙፍ. She has a voluminous body. ግዙፍ ፡ ሰውነት ፡ አላት'
2. ከፍተኛ. The factory has a voluminous output. ፋብሪካው ፡ መጠኑ ፡ ከፍተኛ ፡ የሆነ ፡ ውጤት ፡ አለው
3. ሰፊ ፤ በጣም ፡ ሰፊ. He submitted a voluminous report on the riot. ስለ ፡ ሁከቱ ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ መግለጫ ፡ ሰጠ
A voluminous cloak covered him from top to toe. በጣም ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ ካባ ፡ ከራሱ ፡ እስከ ፡ እግሩ ፡ አለበሰው
4. ብዙ ፡ የሚጽፍ. Dickens was a voluminous author. ዲከንስ ፡ ብዙ ፡ የሚጽፍ ፡ ደራሲ ፡ ነበር

**voluntarily** በገዛ ፡ ፈቃድ
He went voluntarily and gave himself up to the police. በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ እጁን ፡ ለፖሊስ ፡ ሰጠ

**voluntary**
1. (= adv.) በገዛ ፡ ፈቃዱ. His enlistment was voluntary. ለወታደርነት ፡ የተመዘገበው ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ ነው
2. በፍላጎት ፡ የሚደረግ. Speaking and walking are voluntary. መናገርና ፡ መራመድ ፡ በፍላጎት ፡ የሚደረጉ ፡ ናቸው
3. በበጎ ፡ ፈቃድ ፡ የሚደረግ. The hospital is supported by voluntary contributions. ሆስፒታሉ ፡ በበጎ ፡ ፈቃድ ፡ በሚደረግ ፡ መዋጮ ፡ ይካሄዳል

4. ፈቃደኛ ፡ የሆነ. He engaged only voluntary workers. ፈቃደኛ ፡ የሆኑትን ፡ ሠራተኞች ፡ ብቻ ፡ ሥራ ፡ አስያዘ

**volunteer** (vt.) ሳይጠየቅ ፡ ተናገረ
He volunteered the information that the rebels were hiding nearby. ዐመፀኞቹ ፡ ባካባቢው ፡ መደበቃቸውን ፡ ሳይጠየቅ ፡ ተናገረ

**volunteer** (vi.) ፈቃደኛ ፡ ሆነ
Who will volunteer for this job? ለዚህ ፡ ሥራ ፡ ፈቃደኛ ፡ ማነው ?

**volunteer** (n.)
1. ፈቃደኛ. Can you get some volunteers to do it? ይህንን ፡ ሊሠሩ ፡ የሚችሉ ፡ ፈቃደኞች ፡ ልታገኝ ፡ ትችላለህ ?
2. ወዶ ፡ ዘማች. His company is made up for the most part of volunteers. የሱ ፡ ሻምበል ፡ አብዛኞቹ ፡ ወዶ ፡ ዘማቾች ፡ ናቸው

**(be) voluptuous** የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ስሜትን ፡ ቀሰቀሰ
She is very voluptuous, and men are always following her around. የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ስሜትን ፡ ስለምትቀሰቅስ ፡ ወንዶች ፡ ሁልጊዜ ፡ ይከተሏታል

**vomit** (v.)
1. አስታወከ. The baby vomited. ሕፃኑ ፡ አስታወከ
2. ተፋ. The cannon vomited smoke and fire. መድፉ ፡ ጭስና ፡ እሳት ፡ ተፋ

**voracious** የማይጠግብ
He is a voracious reader and takes out several books a week from the library. የማይጠግብ ፡ አንባቢ ፡ ስለሆነ ፡ በየሳምንቱ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ከመጻሕፍት ፡ ቤት ፡ ይዋሳል
*He is a voracious eater. መሶብ ፡ አርግፍ ፡ ነው

**voraciously** ተስገብግቦ
The hungry child ate voraciously. የተራበው ፡ ልጅ ፡ ተስገብግቦ ፡ በላ

**vote** (v.)
1. ድምፅ ፡ ሰጠ. I couldn't vote the last time. ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ድምፅ ፡ ልሰጥ ፡ አልቻልኩም
Vote by show of hands! እጃችሁን ፡ በማንሣት ፡ ድምፅ ፡ ስጡ
2. ደገፈ. Parliament voted a large sum of money for education. የሕግ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ለትምህርት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲወጣ ፡ ደገፈ
3. አስታወቀ. The children voted the picnic a great success. ልጆቹ ፡ ሽርሽሩ ፡ በጣም ፡ ተሳክቶ ፡ ነበር ፡ ሲሉ ፡ አስታወቁ

**vote down** በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ጣለ
The Senate voted down the new tax. የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አዲሱን ፡ ታክስ ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ጣለው

**(be) voted down** ድጋፉ ፡ አጣ
The proposal was voted down. የቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ድጋፉ ፡ አጣ

**vote for** መረጠ
For whom did you vote? ማንን ፡ መረጥክ ?

**vote** (n.)
1. ድምፅ. The motion was put to a vote. ሐሳቡ ፡ ድምፅ ፡ እንዲሰጥበት ፡ ተደረገ
The vote was 300 to 250. ድምፁ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ለሁለት ፡ መቶ ፡ ኀምሳ ፡ ነበር
2. የምርጫ ፡ ድምፅ. More than a million votes were cast. ከንድ ፡ ሚልዮን ፡ በላይ ፡ የምርጫ ፡ ድምፅ ፡ ተሰጥቷል
3. የመራጭነት ፡ መብት. The new constitution gave the vote to women. አዲሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለሴቶችም ፡ የመራጭነት ፡ መብት ፡ ሰጠ
*He was elected by a majority of two thousand votes. የተመረጠው ፡ በሁለት ፡ ሺ ፡ ሰው ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ነው
*A heavy vote is expected for the office of mayor. ከንቲባ ፡ ለመምረጥ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ድምፅ ፡ እንደሚሰጥ ፡ ይጠበቃል

**cast votes** ድምፅ ፡ ሰጠ
They cast their votes for him to be President. ፕሬዚዳንት ፡ እንዲሆን ፡ ለሱ ፡ ድምፃቸውን ፡ ሰጡ

**have a vote** ሊመርጥ ፡ ቻለ
Minors have no vote. ላካለ ፡ መጠን ፡ ያልደረሱ ፡ ሊመርጡ ፡ አይችሉም
[See also 'majority']

**voter**
1. ድምፅ ፡ ሰጪ. Voters stood in lines at the polling places. ድምፅ ፡ ሰጪዎች ፡ በድምፅ ፡ መስጫ ፡ ጣቢያዎች ፡ ተሰልፈው ፡ ቆሙ
2. መራጭ. The totality of voters amounted to ten. የመራጮች ፡ ብዛት ፡ በጠቅላላው ፡ ዐሥር ፡ ነበር

**voting** (n.) ምርጫ
Voting is done by districts. ምርጫ ፡ የተደረገው ፡ በቀበሌ ፡ ነው

**voting** (adj.) የምርጫ
They zoned the city into five voting districts. ከተማውን ፡ ባምስት ፡ የምርጫ ፡ ጣቢያ ፡ ከፈሉት

**votive offering** የስለት ፡ እቃ
The votive offerings are in the church. የስለት ፡ እቃዎች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ

**vouch**
1. ተዋሰ. The mayor vouched for the farmer. ከንቲባው ፡ ለገበሬው ፡ ተዋሰ
2. መሰከረ. I can vouch for his honesty. የሱን ፡ ሐቀኛነት ፡ ልመሰክር ፡ እችላለሁ
3. ኀላፊ ፡ ሆነ. I will vouch for his attendance. ለሱ ፡ መምጣት ፡ ኀላፊ ፡ እሆናለሁ

**voucher** ደረሰኝ
We must have a voucher before we will reimburse you. ያወጣኸውን ፡ እንድንመልስልህ ፡ ደረሰኝ ፡ አቅርብ

**vouchsafe** ፈቀደ
He did not vouchsafe an answer. መልስ ፡ መስጠት ፡ አልፈቀደም

**vow** (v.)
1. ማለ. He vowed not to do it again. ሁለተኛ ፡ እንዳያደርገው ፡ ማለ
2. ተሳለ. He vowed to give St. George a cross if his sores were cured. ቁስሉ ፡ የዳነለት ፡ እንደሆነ ፡ ለጊዮርጊስ ፡ መስቀል ፡ ለማግባት ፡ ተሳለ
3. ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገባ. He vowed to love her always. ምን ፡ ጊዜም ፡ ሊወዳት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገባ

**vow** (n.)
1. መሐላ. His vow was soon broken. መሐላው ፡ ቶሎ ፡ ፈረሰ
2. ቃለ ፡ መሐላ. The archbishop released the priest from his vows. ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቄሱን ፡ ከቃለ ፡ መሐላው ፡ ፈቱት
3. ስለት. I made a vow to St. Gabriel to fast for two days. ለቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ለመጾም ፡ ስለት ፡ አደረግሁ ፡ (or, ተሳልኩ)
4. ቃል ፡ ኪዳን. A man and a woman make marital vows when they marry. ወንድና ፡ ሴት ፡ ሲጋቡ ፡ የጋብቻ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይፈጽማሉ

**make a vow**
1. ማለ. Monks must make a vow of chastity and poverty. መነኰሳት ፡ በድንግልናና ፡ በድኽነት ፡ እንኖራለን ፡ ብለው ፡ መማል ፡ አለባቸው
2. ተሳለ. I made a vow to St. Gabriel to fast for two days. ለቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ለመጾም ፡ ተሳልኩ

**vowel** የድምፅ ፡ አናባቢ
There are seven vowels in Amharic. በአማርኛ ፡ ሰባት ፡ የድምፅ ፡ አናባቢ ፡ አሉ

**voyage** (v.) ተጓዘ
Columbus voyaged on unknown seas. ኮሎምበስ ፡ ባልታወቁ ፡ ባሕሮች ፡ ላይ ፡ ተጓዘ

**voyage** (n.) ጉዞ
This is the ship's maiden voyage. ይህ ፡ የመርከቢ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጉዞ ፡ ነው
Bon voyage! መልካም ፡ ጉዞ

**voyage around the world** ዓለምን ፡ መዞር
His voyage around the world made him famous. ዓለምን ፡ መዞሩ ፡ ዝነኛ ፡ አደረገው

**vulgar**
1. ባለጌ. He is too vulgar for polite society. በጣም ፡ ባለጌ ፡ ስለሆነ ፡ ከጨዋ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ሊኖር ፡ አይችልም
Her language is vulgar. ስትናገር ፡ ባለጌ ፡ ናት
2. ተራ. The vulgar language differs from the language of the court. ተራ ፡ አነጋገር ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ አነጋገር ፡ ይለያል

**vulgarity** ስድነት
Her vulgarity makes her undesirable as a wife. ስድነቷ ፡ ለሚስትነት ፡ የማትፈለግ ፡ ያደርጋታል

**vulnerable** ሊጐዳ ፡ የሚችልበት
Achilles' only vulnerable spot was his heel. አኪሊስ ፡ ሊጐዳ ፡ የሚችልበት ፡ ቦታ ፡ ተረከዙ ፡ ብቻ ፡ ነበር

**be vulnerable to**
1. አልወደደም. A vain person is vulnerable to criticism. ግብዝ ፡ ሰው ፡ ነቀፌታ ፡ አይወድም
2. (= act.) አጠቃ. +Most people are vulnerable to ridicule. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ቀልድ ፡ ያጠቃቸዋል
3. (= act.) ያዘ. +Some people are vulnerable to a certain disease. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ አንዳንድ ፡ በሽታ ፡ በቀላሉ ፡ ይይዛቸዋል

**vulture** ጥንብ ፡ አንሣ
The vultures eat carrion. ጥንብ ፡ አንሣ ፡ የሞተ ፡ ከብት ፡ ይበላል

# W

**waddle** እየተንደረከከ ፡ ሄደ
A fat man waddled across the street. አንድ ፡ ወፍራም ፡ ሰው ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ እየተንደረከከ ፡ ሄደ

**wade**
1. እየወደቀ ፡ እየተነሣ ፡ ሄደ. We had to wade through the mud. እየወደቅን ፡ እየተነሣን ፡ በጭቃው ፡ ውስጥ ፡ ሄድን
2. እየተንቦጫረቀ ፡ ሄደ. They had to wade through the flooded streets. መንገዶቹን ፡ ጉርፍ ፡ ስላጥለቀለቃቸው ፡ ሰዎች ፡ በውኃ ፡ ውስጥ ፡ እየተንቦጫረቁ ፡ መሄድ ፡ ነበረባቸው

**wadi** [በክረምት ፡ ጊዜ ፡ የሚሞላ ፡ ደረቅ ፡ ወንዝ]

**wafer** ስስ ፡ ብስኩት
Wafers are made from unleavened dough. ስስ ፡ ብስኩት ፡ ካልቦካ ፡ ሊጥ ፡ ይሠራል

**wag** (wagged) ቈላ
The dog wagged its tail. ውሻው ፡ ጭራውን ፡ ቈላ

**wage** (v.), **~ a campaign** ዘመቻ ፡ አደረገ
The government waged a campaign against mosquitoes. መንግሥት ፡ የወባ ፡ ትንኞችን ፡ ለማጥፋት ፡ ዘመቻ ፡ አደረገ

**wage war** ጦር ፡ አነሣ
Their pledge not to wage war was not believed by anyone. ጦር ፡ አናነሣም ፡ ሲሉ ፡ ቃል ፡ ቢገቡም ፡ ማንም ፡ አላመናቸውም

**wage** (n.), **wages** ደሞዝ
His wages are $70 a week. ደሞዙ ፡ በሳምንት ፡ ሰባ ፡ ብር ፡ ነው
[See also 'scale']

**wager** (v.) ተወራረደ
They are going to wager on the horse race. በፈረስ ፡ እሽቅድድሙ ፡ ላይ ፡ ሊወራረዱ ፡ ነው

**wager** (n.) ውርርድ
He made a wager at the race track. በሩጫው ፡ ውድድር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ውርርድ ፡ አደረገ

**waggle** ወዘወዘ
The man waggled his finger at the boy. ሰውዬው ፡ በልጁ ፡ ላይ ፡ ጣቱን ፡ ወዘወዘ

**wagon** ጋሪ ፤ ሰረገላ
The wagon is stuck in the mud. ጋሪው ፡ ማጥ ፡ ውስጥ ፡ ተደንቅሯል
The wagon was drawn by two horses. ሰረገላው ፡ በሁለት ፡ ፈረሶች ፡ ይሳብ ፡ ነበር

**wail** (v.)
1. አለቀሰ. The baby was wailing all night. ሕፃኑ ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር
2. እዬዬ ፡ እያለ ፡ አለቀሰ. She wailed over her misfortune. በመከራዋ ፡ እዬዬ ፡ እያለች ፡ አለቀሰች
3. አፏጨ. The wind wailed in the trees. ነፋሱ ፡ በዛፎቹ ፡ መካከል ፡ አፏጨ

**wail** (n.) ልቅሶ
The wail of the baby woke me up. የሕፃኑ ፡ ልቅሶ ፡ ቀሰቀሰኝ
*We could hear the wail of a siren. ደወሉ ፡ ሲሬኙ ፡ ሰማን

**waist** ወገብ
She has a slim waist. ወገቧ ፡ ቀጭን ፡ ነው

**wait** (v.)
1. ጠበቀ. Have you been waiting long? ስትጠብቅ ፡ ብዙ ፡ ቆየህ ?
I'll wait for you until five o'clock. እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ እጠብቅሃለሁ
They waited their turn. ተራቸውን ፡ ጠበቁ
2. ቆየ. Wait and see! ቆይ ፡ እስቲ
Let it wait until next week! እስከሚቀጥለው ፡ ሳምንት ፡ ይቆይ

**wait around** እዚህ ፡ ቆየ
Please wait around for an hour! ላንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ እዚህ ፡ ብትቆይ
*Wait around a while! ከዚህ ፡ አትራቅ ፡ (እስቲ ፡ ቆየት ፡ በል)

**wait on**
1. አስተናገደ. She waited on customers all day long. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ደንበኞችን ፡ ስታስተናግድ ፡ ዋለች
2. ታዘዘ. Will you please wait on me now? አሁን ፡ እኔን ፡ ልትታዘዘኝ ፡ ትችላለህ ?
3. የሚፈልገውን ፡ አቀረበ. We asked the waitress to wait on us. ሠራተኛዋ ፡ የምንፈልገውን ፡ እንድታቀርብልን ፡ ጠየቅናት

**can hardly wait ቸኰለ**
I can hardly wait to see him! እሱን ፡ ለማየት ፡ ቸኵያለሁ

**keep one waiting አስጠበቀ**
His wife never keeps him waiting for dinner. ሚስቱ ፡ ምንጊዜም ፡ እራት ፡ አታስጠብቀውም

**wait** (n.) መጠበቅ
We have an hour's wait before the train gets in. ባቡሩ ፡ ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ መጠበቅ ፡ አለብን

**have a long wait ብዙ ፡ ጠበቀ**
He had a long wait at the dentist's. በጥርስ ፡ ሐኪሙ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ጠበቀ

**lie in wait for አድፍጦ ፡ ጠበቀ**
The robbers were lying in wait for us. ቀማኞቹ ፡ አድፍጠው ፡ ይጠብቁን ፡ ነበር

**waiter አሳላፊ**
My husband is a waiter. ባለቤቴ ፡ አሳላፊ ፡ ነው
Waiter, please bring me the coffee! አሳላፊ ፤ ቡና ፡ ታመጣልኝ

**waiting, lady in ~ ደንገጡር**
My sister is a lady in waiting to the queen. እኅቴ ፡ የንግሥቲቱ ፡ ደንገጡር ፡ ነች

**waiting list ማቆያ ፡ መዝገብ**
The applicant was put on a waiting list. አመልካቹ ፡ ማቆያ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ተጻፈ

**waiting room ማረፊያ ፡ ክፍል**
How many patients are there in the waiting room? እማረፊያው ፡ ክፍል ፡ ስንት ፡ ሕመምተኞች ፡ አሉ ?
Is there a waiting room at the station? እጣቢያው ፡ ማረፊያ ፡ ክፍል ፡ አለ ?

**waitress አሳላፊ ፤ ሠራተኛ**
His sister is a waitress. እኅቱ ፡ አሳላፊ ፡ ናት
We asked the waitress to wait on us. ሠራተኛዋ ፡ የምንፈልገውን ፡ እንድታቀርብልን ፡ ጠየቅናት

**waive**
1. አስቀረ. The university waived the tuition fee for him. ዩኒቨርሲቲው ፡ መክፈል ፡ የነበረበትን ፡ የመማሪያ ፡ ገንዘብ ፡ አስቀረለት
2. ለሌላ ፡ ጊዜ ፡ አስተላለፈ. The parliament waived the question of taxes. ምክር ፡ ቤቱ ፡ የታክሱን ፡ ጉዳይ ፡ ለሌላ ፡ ጊዜ ፡ አስተላለፈው

**waiver**
*He received a waiver for his school fees. የትምህርት ፡ ቤት ፡ ሒሳብ ፤ እንዳይከፍል ፤ ቀደረገ

**wake** (woke, or waked), vt.
1. አስነሣ ፤ ቀሰቀሰ. Please wake me at seven o'clock! ባንድ ፡ ሰዓት ፡ አስነሣኝ ፡ (ቀስቅሰኝ)
2. ቀሰቀሰ(በት). His cruelty woke our anger. የሱ ፡ ጭካኔ ፡ ንዴታችንን ፡ ቀሰቀሰብን

**wake** (vi.) ነቃ
I usually wake at 6 o'clock. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የምነቃው ፡ በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ነው
*Whether you are waking or dreaming you always think of her. በውንህም ፡ ሆነ ፡ በሕልምህ ፡ እሷኑ ፡ ታስባለህ

**wake up** (vt.)
1. አስነሣ. Wake him up early! በጧት ፡ አስነሣው
2. አነቃቃ. He needs some interest to wake him up. እንዲያነቃቃው ፡ ሐሳቡን ፡ የሚማርክ ፡ ነገር ፡ ያስፈልገዋል

**wake up** (vi.)
1. ነቃ. I didn't wake up until eight this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ አልነቃሁም ፡ ነበር
2. ተነሣ. He woke up with a start. ባኖ ፡ ተነሣ

**wake up to the fact ተረዳ**
It's high time you wake up to the fact that you are failing in your studies. በትምህርት ፡ የምትወድቅ ፡ መሆንህን ፡ በጊዜ ፡ መረዳት ፡ ያስፈልግሃል

**wake** (n.)
*The storm left wreckage in its wake. ኀይለኛው ፡ ነፋስ ፡ ብዙ ፡ ፍርስራሽ ፡ ትቶ ፡ አለፈ

**hold a wake**
*After he died, they held a wake for him. ከሞተ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ሌሊት ፡ አስክሬኑ ፡ አጠገብ ፡ አደሩ

**in the wake of የ - - እግር ፡ ተከትለው**
Traders came in the wake of the explorers. ነጋዴዎቹ ፡ ያገር ፡ መርማሪዎች ፡ እግር ፡ ተከትለው ፡ መጡ

**wakeful ንቁ**
The wakeful guards caught the robbers. ንቁዎቹ ፡ ዘበኞች ፡ ሌቦቹን ፡ ያዟቸው
*The baby spent a wakeful night. ልጁ ፡ እንቅልፍ ፡ አጥቶ ፡ አደረ

**waken ቀሰቀሰ**
The noise wakened the child. ጫጫታው ፡ ሕፃኑን ፡ ቀሰቀሰው

**walk** (vt.)
1. አንሸራሸረ. He walks his dog every morning. ውሻውን ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ያንሸራሽረዋል
2. ሸኘ. I'll walk you home. እቤትህ ፡ ድረስ ፡ እሸኝሃለሁ

**walk** (vi.)
1. በእግር ፡ ሄደ. Shall we walk or take the bus? በእግራችን ፡ እንሂድ ፡ ወይንስ ፡ ባውቶቡስ ?
Can the baby walk yet? ሕፃኑ ፡ ገና ፡ በእግሩ ፡ መሄድ ፡ አልጀመረም ?
2. ተንሸራሸረ. I like to walk in the park. መናፈሻው ፡ ውስጥ ፡ መንሸራሸር ፡ እወዳለሁ
3. ቀስ ፡ ብሎ ፡ ሄደ. Walk, do not run, to the nearest exit! ወደሚቀጥለው ፡ መውጫ ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ ሂድ ፤ አትሩጥ

**walk about** ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ
The mother hen walked about followed by her brood. እናቲቱ ፡ ዶሮ ፡ ጫጩቶቿ ፡ ተከትለዋት ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ትል ፡ ነበር

**walk across**
1. በእግር ፡ ተሻገረ. Let's walk across the bridge! ድልድዩን ፡ በእግር ፡ እንሻገር
2. በእግር ፡ አቋረጠ. We walked across the fields. ሜዳውን ፡ በእግራችን ፡ አቋረጥን

**walk around** በእግር ፡ ተዘዋወረ
We walked around to see the town. ከተማውን ፡ ለማየት ፡ በእግር ፡ ተዘዋወርን

**walk back and forth** ተንጐራደደ
He walked back and forth across the room. እክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተንጐራደደ

**walk (down)**
1. ወረደ. He fell while walking down the stairs. ደረጃውን ፡ ሲወርድ ፡ ወደቀ
2. ሄደ. I was walking down the street. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ እሄድ ፡ ነበር

**walk in** ገባ
They were gossiping about me when I walked in. ስገባ ፡ ስለኔ ፡ ያወሩ ፡ ነበር

**walk off** ሄደ
If he doesn't win, he gets mad and walks off. ካላሸነፈ ፡ ተናዶ ፡ ይሄዳል

**walk off with** ይዞ ፡ ሄደ
Someone walked off with my umbrella. አንድ ፡ ሰው ፡ ጃንጥላዬን ፡ ይዞ ፡ ሄደ

**walk out**
1. ወጥቶ ፡ ሄደ. She walked out of the room. ከክፍሉ ፡ ወጥታ ፡ ሄደች
2. ተነሥቶ ፡ ወጣ. He affronted me by walking out in the middle of the speech. በንግግሬ ፡ መሀል ፡ ተነሥቶ ፡ በመውጣት ፡ አዋረደኝ

**walk out of** ጥሎ ፡ ወጣ
The delegation walked out of the meeting. መልእክተኞቹ ፡ ስብሰባውን ፡ ጥለው ፡ ወጡ

**walk out on** ጥሎ ፡ ሄደ
Our maid walked out on us. ገረዳችን ፡ ጥላን ፡ ሄደች

**walk up**
1. ወጣ. He can't walk up the stairs. ደረጃውን ፡ ሊወጣ ፡ አይችልም
2. ተጠጋ. A stranger walked up to me and asked me the time. አንድ ፡ የማላውቀው ፡ ሰው ፡ ወደኔ ፡ ተጠግቶ ፡ ሰዓት ፡ ጠየቀኝ
*Let's walk up the street! በእግራችን ፡ እንሂድ

**walk up and down**
1. ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ተመላለሰ. He was walking up and down the station platform. በባቡር ፡ ጣቢያው ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይመላለስ ፡ ነበር
2. ወጣና ፡ ወረደ. He was walking up and down the stairs all day long. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ደረጃውን ፡ ሲወጣና ፡ ሲወርድ ፡ ዋለ
[See also 'past']

**walk** (n.)
1. ሽርሽር. Did you have a nice walk? ሽርሽሩ ፡ ጥሩ ፡ ነበር ?
The two friends went for a walk. ሁለቱ ፡ ጓደኞች ፡ ለሽርሽር ፡ ወጣ ፡ አሉ
2. አረማመድ. You can recognize him by his walk. ባረማመዱ ፡ ልታውቀው ፡ ትችላለህ
3. በእግር ፡ መንገድ. The station is a ten-minute walk from my house. ከቤቴ ፡ ጣቢያው ፡ ድረስ ፡ በእግር ፡ የዐሥር ፡ ደቂቃ ፡ መንገድ ፡ ነው
4. የእግር ፡ መንገድ. The park has gravel walks. የመናፈሻው ፡ ቦታ ፡ ጠጠር ፡ የተነጠፈባቸው ፡ የእግር ፡ መንገዶች ፡ አሉት
*It's a long walk to the store. መደብሩ ፡ በእግር ፡ ብዙ ፡ ያስኬዳል

**walks of life** ኑሮ
A doctor and a mechanic are in different walks of life. ሐኪምና ፡ ሜካኒክ ፡ ኑሮዋቸው ፡ ለየቅል ፡ ነው

**from all walks of life** እገሌ ፡ ከእገሌ ፡ ሳይባል ፡ ሁሉም ፤ ትልቅ ፡ ትንሹ ፡ ሳይቀር
Men from all walks of life rallied to the cause. እገሌ ፡ ከእገሌ ፡ ሳይባል ፡ ሁሉም ፡ (ትልቅ ፡ ትንሹ ፡ ሳይቀር) ፡ ዓላማውን ፡ ደገፈ

**take a walk** ተንሸራሸረ
Would you like to take a walk? ልትንሸራሸር ፡ ትፈልጋለህ ?

**walking stick** ምርኩዝ
The old man uses a walking stick to get about. ሽማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ የሚለው ፡ በምርኩዝ ፡ ነው

**walkout** የሠራተኞች ፡ ሥራ ፡ ማቆም
The walkout halted the factory's production. የሠራተኞች ፡ ሥራ ፡ ማቆም ፡ ፋብሪካውን ፡ እቃ ፡ ከመሥራት ፡ አገደው

**wall** (v.), ~ **off** በግድግዳ ፡ ከፈለ
They walled off the unused room. የማይጠቀሙበትን ፡ ክፍል ፡ በግድግዳ ፡ ከፈሉት

**be walled up** በግንብ ፡ ተደፈነ
The doors and windows were walled up so that no one could get in. ማንም ፡ እንዳይገባ ፡ መስኮቶቹና ፡ በሮቹ ፡ በግንብ ፡ ተደፈኑ

**wall** (n.)
1. ግድግዳ. Hang the picture on this wall! ሥዕሉን ፡ እዚህኛው ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ ስቀለው
2. ግምብ ፤ ግንብ. He built a low stone wall around his house. ከቤቱ ፡ ዙሪያ ፡ አጠር ፡ ያለ ፡ የድንጋይ ፡ ግንብ ፡ (ግምብ) ፡ ገነባ
Cities used to be surrounded by high walls. ከተማዎች ፡ በረጃጅም ፡ ግንቦች ፡ ይከበቡ ፡ ነበር
[See also 'hole, hug']

**walled** (adj.) በግንብ ፡ የታጠረ
Harar is a walled city. ሐረር ፡ በግንብ ፡ የታጠረ ፡ ከተማ ፡ ነው

**be walled** ዙሪያውን ፡ በግንብ ፡ ታጠረ
The garden is walled. ያትክልቱ ፡ ስፍራ ፡ ዙሪያውን ፡ በግንብ ፡ ታጥሯል

**wallet** ቦርሳ
I had three dollars in my wallet. ቦርሳዬ ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ ብር ፡ ነበረኝ

**wallop** (v.) በኀይል ፡ መታ
He walloped the thief on the chin. ሌባውን ፡ አገጩ ፡ ላይ ፡ በኀይል ፡ መታው

**wallop** (n.)
*The wallop knocked him down. በኀይል ፡ ተመቶ ፡ ወደቀ

**give a wallop on** አወለቀ
He gave him a wallop on the chin. አገጩን ፡ አወለቀው

**wallow** ተንደባለለ
Donkeys often wallow in the dust. አህዮች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አቧራ ፡ ላይ ፡ ይንደባለላሉ

**wallpaper** የግድግዳ ፡ ወረቀት
The wallpaper is quite pretty. የግድግዳው ፡ ወረቀት ፡ በጣም ፡ ያምራል

**walnut** [የለውዝ ፡ ዓይነት]

**wan** የድካም
The sick boy gave the doctor a wan smile. በሽተኛው ፡ ልጅ ፡ ለሐኪሙ ፡ የድካም ፡ ፈገግታ ፡ አሳየው

**look wan** የገረጣ ፡ መሰለ
Her face looked wan after her long illness. ከረጅም ፡ ሕመም ፡ በኋላ ፡ ፊቷ ፡ የገረጣ ፡ መሰለ

**wander**
1. ተንቀዋለለ ፤ ተዘዋወረ. He wanders around the town. ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ይንቀዋለላል
He came on a cabin while wandering through the woods. ጫካው ፡ ውስጥ ፡ ሲዘዋወር ፡ አንዲት ፡ ጎጆ ፡ አገኘ
2. ተንከራተተ. His gaze wandered about the room. ዓይኑ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተንከራተተ
*His mind is wandering; try to get his attention again! ልቡ ፡ እዚህ ፡ አይደለም ፤ እስቲ ፡ ሐሳቡን ፡ ለመመለስ ፡ ሞክር

**wander away**
1. ጠፋ(በት). Some of my sheep have wandered away. ከበጎቼ ፡ ጥቂቶቹ ፡ ጠፍተውብኛል
2. ወጣ. She wanders away from her subject when she talks. ስትናገር ፡ ከአርእስቷ ፡ ትወጣለች

**wander from** እየለቀቀ ፡ ሄደ
The speaker wandered from the subject. ተናጋሪው ፡ አርእስቱን ፡ እየለቀቀ ፡ ሄደ

**wander in** ጐራ ፡ አለ
Harry wandered in to see me this morning. ሃሪ ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ ሊጠይቀኝ ፡ ጐራ ፡ አለ

**wander off** ተንከራተተ
The dog wandered off and got lost. ውሻው ፡ ሲንከራተት ፡ ጠፋ

**let wander** ስድ ፡ ለቀቀ
He untied his horse and let it wander. ፈረሱን ፡ ፈቶ ፡ ስድ ፡ ለቀቀው

**make wander** አቃወሰ
Fever made his mind wander. ትኩሳት ፡ አእምሮውን ፡ አቃወሰው

**wanderer** ዘዋሪ
The wanderer found no country in which he could make his home. ዘዋሪው ፡ የሚኖርበት ፡ አገር ፡ አላገኘም

**wane** (v.)
1. ጠፋ. The moon waxes and wanes once a month. ጨረቃ ፡ የምትወጣውና ፡ የምትጠፋው ፡ በየወሩ ፡ አንዴ ፡ ነው
2. እየደከመ ፡ ሄደ. His strength waned during his long illness. ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ታሞ ፡ ስለነበር ፡ ጉልበቱ ፡ እየደከመ ፡ ሄደ

3. ተዳከመ. Many great empires have waned. ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ግዛቶች ፡ ተዳክመዋል

**wane** (n.), **be on the ~**
1. ሊጠፋ ፡ ነው. The moon is on the wane. ጨረቃዋ ፡ ልትጠፋ ፡ ነው
2. እየተዳከመ ፡ ነው. Their power is on the wane. ኀይላቸው ፡ እየተዳከመ ፡ ነው

**wangle**
*He wangled a job in the company's newspaper. ኩባንያው ፡ በሚያወጣው ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ የተቀጠረው ፡ በዘዴ ፡ ነው

**want** (v.)
1. ፈለገ. I want to go swimming. ዋና ፡ ለመሄድ ፡ እፈልጋለሁ
Your mother wants you. እናትህ ፡ ትፈልግሃለች
2. ወደደ. He did it of necessity, not because he wanted it. ወዶ ፡ ሳይሆን ፡ የግድ ፡ ስለሆነበት ፡ ነው ፡ የሠራው
3. አለ. How much do you want for these three dresses? እነዚህን ፡ ሦስት ፡ ልብሶች ፡ ስንት ፡ ትላቸዋለህ ?
4. አለ(በት). +Your coat wants mending. ኮትህ ፡ መጠቀም ፡ አለበት
5. አስፈለገ(ው). +Plants want water. ዕፀዋት ፡ ውኃ ፡ ያስፈልጋቸዋል
6. ጐደለ. The fund for a new church wants only a few hundred dollars of the sum required. ላዲስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተሰበሰበው ፡ ገንዘብ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ገንዘብ ፡ ጥቂት ፡ ይጐድላል
My friend plays football well, but he wants confidence. ጓደኛዬ ፡ የእግር ፡ ኳስ ፡ ጥሩ ፡ ይጫወታል ። ግን ፡ በራሱ ፡ መተማመን ፡ ይጐድለዋል
7. አነሰ(ው). +This soup wants a little salt. ይህ ፡ ሾርባ ፡ ጥቂት ፡ ጨው ፡ ያንሰዋል

**let someone want** እንዲቸገር ፡ አደረገ
It's not right to let children want when you have plenty of money. አንተ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ እያለህ ፡ ልጆችህ ፡ እንዲቸገሩ ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም
*We must not let our parents want in their old age. ወላጆቻችን ፡ ሲያረጁ ፡ እንዳይቸገሩ ፡ መርዳት ፡ አለብን

**want** (n.)
1. ፍላጎት. My wants are very modest. ፍላጎቴ ፡ መጠነኛ ፡ ነው
2. የሚፈልገው. We can supply all your wants. የምትፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ እናገኝልሃለን
3. እጦት. The earthquake victims are suffering from want of medical supplies. በመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ምክንያት ፡ አደጋ ፡ የደረሰባቸው ፡ ሰዎች ፡ በሕክምና ፡ እጦት ፡ ምክንያት ፡ ይሠቃያሉ
4. ችግር. The old soldier is now in want. ሽማግሌው ፡ ወታደር ፡ አሁን ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ወድቋል

**from want** ስላጣ
From want of water, the plants died. አትክልቶቹ ፡ ውኃ ፡ ስላጡ ፡ ደረቁ

**wanted**, adj. (= verb.) ይፈለጋል
The advertisement reads: "Wanted, cook for a small family". ማስታወቂያው ፡ « ለአነስተኛ ፡ ቤተሰብ ፡ ወጥ ፡ ቤት ፡ ይፈለጋል » ፡ ይላል

**be wanted** ተፈለገ
He is wanted by the police. በፖሊሶች ፡ ይፈለጋል
Excuse me, I am wanted on the phone. ይቅርታ ፡ አድርግልኝ ። በስልክ ፡ ተፈልጌያለሁ

**(be) wanting** ጠፋ
A few pages of this book are wanting. የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ጥቂት ፡ ገጾች ፡ ጠፍተዋል

**be wanting in** ብቁ ፡ አልነበረም
+He was wanting in ability. ችሎታው ፡ ብቁ ፡ አልነበረም

**be found wanting** ብቁ ፡ ሆኖ ፡ አልተገኘም
He was tried out on that job, but was found wanting. በሥራው ፡ ላይ ፡ ተሞክሮ ፡ ነበር ። ግን ፡ ብቁ ፡ ሆኖ ፡ አልተገኘም

**have (something) wanting** ጐደለው
The machine had some of its parts wanting. መኪናው ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ ይጐድሉታል

**wanton**
1. ልክስክስ. A wanton woman makes a poor wife. ልክስክስ ፡ ሴት ፡ ጥሩ ፡ ሚስት ፡ አይወጣትም
Her wanton behavior drew everyone's criticism. ልክስክስ ፡ ጠባይዋ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ አስነቀፋት
2. ይህ ፡ ነው ፡ የማይባል. That bad boy hurts animals from wanton cruelty. ይህ ፡ ነው ፡ ከማይባል ፡ ጭካኔው ፡ የተነሣ ፡ ያ ፡ መጥፎ ፡ ልጅ ፡ እንስሳትን ፡ ያሠቃያል
3. (= adv.) ፈጽሞ. His wanton disregard of the law is very surprising. ሕጉን ፡ ፈጽሞ ፡ ችላ ፡ ማለቱ ፡ በጣም ፡ ያስደንቃል

**war** (warred), v. ተዋጋ
Germany warred against France. ጀርመን ፡ ከፈረንሳይ ፡ ጋር ፡ ተዋጋች

**war** (n.)
1. ጦርነት. Where were you during the last war? ባለፈው ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የት ፡ ነበርክ ?
We are at war. በጦርነት ፡ ላይ ፡ ነን

Italy declared war on our country. ኢጣሊያ ፡ ባገራችን ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ ዐውጇ ፡ ነበር
2. ተጋድሎ. Doctors carry on a war against disease. ሐኪሞች ፡ በሽታን ፡ ለማጥፋት ፡ ተጋድሎ ፡ ያደርጋሉ

**go to war with each other** ጦርነት ፡ ገጠመ
The two countries are not going to war with each other. ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ጦርነት ፡ አይገጥሙም

**make war on** ወጋ
Napoleon made war on Russia. ናፖሊዮን ፡ መስኮብን ፡ ወጋ
[See also 'civil war, prisoner, wage']

**warble** ተንጫጫ
The birds were warbling in the tree. ወፎቹ ፡ ዛፉ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ይንጫጩ ፡ ነበር

**war cry** ቀረርቶ
The war cries of the enemy failed to shake us. የጠላት ፡ ቀረርቶ ፡ ሊያሸብረን ፡ አልቻለም

**ward** (v.), ~ **off** ተከላከለ ፤ ተጠበቀ
He wore a charm around the neck to ward off the evil eye. ከሰው ፡ ዓይን ፡ ለመከላከል ፡ (ለመጠበቅ) ፡ አንገቱ ፡ ላይ ፡ ክታብ ፡ አሰረ

**ward** (n.)
1. ተራ ፡ ክፍል. The patient was put in the ward because all the private rooms were taken. የግል ፡ ክፍሎች ፡ ሁሉ ፡ ተይዘው ፡ ስለነበር ፡ በሽተኛውን ፡ ተራ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ አስተኙት
2. በሞግዚትነት ፡ የሚተዳደር. Since he stole the money from his ward, he has became an outcast. በሞግዚትነቱ ፡ ከሚተዳደረው ፡ ገንዘብ ፡ ከሰረቀ ፡ ወዲህ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አያስጠጋውም
*His ward is his nephew. በሞግዚትነት ፡ የሚያሳድገው ፡ የወንድሙን ፡ ልጅ ፡ ነው

**be the ward of** በ - - - ጥበቃ ፡ ሥር ፡ ነው
An orphan is the ward of the court. እናት ፡ አባት ፡ የሌለው ፡ ልጅ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ጥበቃ ፡ ሥር ፡ ነው

**warden**
1. ተቈጣጣሪ. The air-raid warden sounded the alarm. ያየር ፡ ማጥቂያው ፡ ተቈጣጣሪ ፡ ያደጋ ፡ መስጫውን ፡ ጩኸት ፡ አሰማ
2. የወህኒ ፡ ቤት ፡ አለቃ. The warden is in charge of this prison. የወህኒ ፡ ቤቱ ፡ አለቃ ፡ ለዚህ ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ኀላፊ ፡ ነው

**wardrobe**
1. ቁም ፡ ሣጥን. What are your shoes doing in my wardrobe? ጫማህ ፡ ቁም ፡ ሣጥኔ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ይሠራል ?
2. የተሟላ ፡ ልብስ. She bought herself a new wardrobe. ለራሷ ፡ አዲስ ፡ የተሟላ ፡ ልብስ ፡ ገዛች

**ware** እቃ
I bought some iron ware when I traveled in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ በሄድኩ ፡ ጊዜ ፡ የብረት ፡ እቃዎች ፡ ገዛሁ
The peddler sold his wares from door to door. ሱቅ ፡ በደረቴው ፡ እቃዎችን ፡ ከቤት ፡ ቤት ፡ እያዞረ ፡ ሸጠ
[See also 'bawl']

**warehouse**
1. መጋዘን. The furniture is still in the warehouse. የቤት ፡ እቃዎቹ ፡ አሁንም ፡ መጋዘን ፡ ውስጥ ፡ ናቸው
2. ግምጃ ፡ ቤት. The warehouse was infested with ants. ግምጃ ፡ ቤቱ ፡ በጉንዳን ፡ ተወረረ
3. እቃ ፡ ቤት. Military supplies are in the warehouse. የጦር ፡ ትጥቆቹ ፡ እቃ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ናቸው

**warfare**
1. ጦርነት. Warfare in the Middle Ages was much less cruel than warfare today. በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ የነበረው ፡ ጦርነት ፡ ከዛሬው ፡ ጦርነት ፡ ያነሰ ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ነበረበት
2. የጦር ፡ ስልት. The general is skilled in modern warfare. ጄኔራሉ ፡ በዘመናዊ ፡ የጦር ፡ ስልት ፡ የሠለጠነ ፡ ነው
3. ውጊያ ፡ ማድረግ. The unification of the country required many years of warfare. አገሪቱን ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ ብዙ ፡ ውጊያ ፡ ማድረግ ፡ አስፈልጎ ፡ ነበር

**warily** በጥንቃቄ
The soldiers climbed warily up the dangerous path. ወታደሮቹ ፡ አደገኛውን ፡ የእግር ፡ መንገድ ፡ ተከትለው ፡ በጥንቃቄ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወጡ

**warlike**
1. ውጊያ ፡ የሚወድ. These warlike people are constantly raiding the villages. እነዚህ ፡ ውጊያ ፡ የሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ መንደሮቹን ፡ ደጋግመው ፡ ያጠቃሉ
2. የጦር ፡ ስሜት ፡ ያዘለ. His warlike speech increased the ill feeling between the two countries. የጦር ፡ ስሜት ፡ ያዘለው ፡ ንግግሩ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ ጥላቻ ፡ አባባሰው
3. የጦር. They are imbued with a warlike spirit. በጦር ፡ መንፈስ ፡ ተውጠዋል

**warm** (vt.)
1. አሞቀ. Mother warmed the milk. እናቱ ፡ ወተቱን ፡ አሞቀችው
2. ቀሰቀሰ. The thought of seeing the family again warmed her heart. ቤተሰቧን ፡ የማየቱ ፡ ሐሳብ ፡ ልቧን ፡ ቀሰቀሰው
**warm** (vi.) ሞቀ
The bread warmed in the oven. ዳቦው ፡ ምጣድ ፡ ላይ ፡ ሞቀ
*The speaker warmed to his subject. ስለ ፡ አር እስቱ ፡ የተናጋሪው ፡ ስሜት ፡ እየጋለ ፡ ሄደ
**warm oneself** ሞቀ
They ignited the twigs to warm themselves. ለመሞቅ ፡ ጭራሮውን ፡ አቀጣጠሉ
**warm oneself by (in)** ሞቀ
Come in and warm yourself by the fire! ግባና ፡ እሳት ፡ ሙቅ
He is warming himself in the sun. ፀሐይ ፡ ይሞቃል
**warm up** (vt.) አሞቀ
Please, warm up the soup for me! ሾርባውን ፡ አሙቅልኝ ፡ እስቲ
**warm up** (vi.) ደመቀ
The party warmed up, and all had a good time. ፓርቲው ፡ ስለደመቀ ፡ ሁሉም ፡ ተደስተው ፡ ነበር

**warm** (adj.)
1. ትኩስ. The roast is still warm. ጥብሱ ፡ አሁንም ፡ ትኩስ ፡ ነው
2. የፈላ. I drink warm milk at bedtime. ሌተኛ ፡ ስል ፡ የፈላ ፡ ወተት ፡ እጠጣለሁ
3. ሞቃት. Hawaii has a warm climate. ሀዋዪ ፡ ሞቃት ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፡ አላት
4. ሙቀት ፡ የሚሰጥ ፤ የሚሞቅ. Put your warm clothes on; it is cold outside. ውጪው ፡ ስለሚበርድ ፡ ሙቀት ፡ የሚሰጥህን ፡ ልብስ ፡ ልበስ
We wear warm clothes in winter. በክረምት ፡ የሚሞቅ ፡ ልብስ ፡ እንለብሳለን
5. የጋለ. They gave us a warm welcome. የጋለ ፡ አቀባበል ፡ አደረጉልን
6. የልብ. He is a warm friend. የልብ ፡ ጓደኛዬ ፡ ነው
7. ሙቀት ፡ የሚያሳስብ. Yellow and red are warm colors. ቢጫና ፡ ቀይ ፡ ሙቀትን ፡ የሚያሳስቡ ፡ ቀለሞች ፡ ናቸው
**warm weather** ሙቀት
The warm weather is uncomfortable. ሙቀቱ ፡ የማያመች ፡ ነው
**be warm**
1. ሞቀ. It is very warm today. ዛሬ ፡ በጣም ፡ ይሞቃል
2. ሞቀ(ው). Are you warm enough? በደንብ ፡ ሞቆሃል ?
**keep warm** (vt.) አሞቀ
Shall I keep the dinner warm? ምግቡን ፡ ላሙቀው ?
**keep warm** (vi.)
1. ሰውነት ፡ አሟሟቀ. Exercise to keep warm! ሰውነትህን ፡ ለማሟሟቅ ፡ ጅምናስቲክ ፡ ሥራ
2. ሞቀ(ው) ፤ አሞቀ. They huddled together to keep warm. እንዲሞቃቸው ፡ እፍግፍግ ፡ ብለው ፡ ተቀመጡ
He rubbed his hands to keep warm. ለማሞቅ ፡ እጁን ፡ አሻሸ
**make warm** (= intr.) ሞቀ
+The fire made us warm. እሳት ፡ ሞቅን
[See also 'glow']

**warmest** ሙቀት ፡ የሚሰጥ
Put your warmest clothes on; it's very cold outside. ውጭው ፡ በጣም ፡ ስለሚበርድ ፡ ሙቀት ፡ የሚሰጥህን ፡ ልብስ ፡ ልበስ

**warm-hearted** ሰው ፡ ወዳድ
He is a warm-hearted fellow. ሰው ፡ ወዳድ ፡ ነው

**warmly**
1. ከልብ. He thanked me warmly for getting him a job. ሥራ ፡ ስላገኘሁለት ፡ ከልብ ፡ አመሰገነኝ
2. በጋለ ፡ ስሜት. He pressed my hand warmly. እጄን ፡ በጋለ ፡ ስሜት ፡ ጨበጠው

**warmonger** ጦር ፡ ፈላጊ
The warmonger urged his country to fight. ጦር ፡ ፈላጊው ፡ አገሩቱ ፡ እንድትዋጋ ፡ አደፋፈረ

**warmth**
1. የጋለ ፡ ስሜት. He spoke with warmth of the beauty of the mountains. ስለ ፡ ተራራዎቹ ፡ ውበት ፡ በጋለ ፡ ስሜት ፡ ተናገረ
2. (= adj.) ልባዊ. The warmth of our hostess's welcome made us feel at ease. የባለቤቷ ፡ ልባዊ ፡ መስተንግዶ ፡ እንድንዝናና ፡ አደረገን
*Come sit in the warmth of the open fire! ናና ፡ እሳቱ ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጠህ ፡ ሙቅ

**warn**
1. አስጠነቀቀ ፤ መከረ. The mother warned her child not to swim in the river near the house. እናትዮዋ ፡ ልጇ ፡ እቤታቸው ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ወንዝ ፡ ውስጥ ፡ እንዳይዋኝ ፡ አስጠነቀቀችው ፡ (መከረችው)

2. አስታወቀ. The driver signaled to warn me that he would turn. ባለመኪናው ፡ የሚታጠፍ ፡ መሆኑን ፡ ሊያስታውቀኝ ፡ ምልክት ፡ ሰጠ

**warning**
1. ማስጠንቀቂያ. Let that be a warning to you! ይህ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ይሁንህ
He was deaf to warning of danger. ስለ ፡ አደጋ ፡ የሚሰጠውን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ አልሰማም
2. ምልክት. Pain in the body is a warning of trouble. አካል ፡ ውጋት ፡ ሲሰማው ፡ የሕመም ፡ ምልክት ፡ ነው
**without warning** ሳይታሰብ
The enemy attacked without warning. ጠላት ፡ ሳይታሰብ ፡ አጠቃ

**warp** (vt.)
1. ወጣ ፡ ገባ ፡ አደረገ. The dampness has warped the boards. እርጥበቱ ፡ ሳንቃውን ፡ ወጣ ፡ ገባ ፡ አደረገው
2. አበላሸ. Bad companions had warped his character. አጉል ፡ ጓደኞች ፡ ጠባዩን ፡ አበላሹት
**warp** (vi.) ተዛባ
This old floor has warped. ይህ ፡ አሮጌ ፡ ጣውላ ፡ ተዛብቷል

**warp** (n.) ድር
The warp and the woof make up the fabric of the cloth. ልብስ ፡ የሚሆነው ፡ ድርና ፡ ማግ ፡ ነው

**warrant** (v.)
1. አረጋገጠ. The storekeeper warranted the quality of the radio. ባለመደብሩ ፡ የሬዲዮኑን ፡ ጥሩነት ፡ አረጋገጠ
I warrant that he will come. እንደሚመጣ ፡ አረጋግጣለሁ
2. በቂ ፡ ምክንያት ፡ ነው. That doesn't warrant your interference. ያ ፡ ጣልቃ ፡ ለመግባትህ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አይሆንም
3. ምክንያት ፡ ተገኘ(ለት). Nothing can warrant such rudeness. ለዚህ ፡ ዓይነት ፡ ብልግና ፡ ምክንያት ፡ አይገኝለትም
4. ተገባ(ው). +Her good work warrants our praise. መልካም ፡ ሥራዋ ፡ ምሥጋና ፡ ይገባዋል
**be warranted** ዋስትና ፡ አለው
This radio is warranted. ይህ ፡ ሬዲዮ ፡ ዋስትና ፡ አለው

**warrant** (n.)
1. የፍርድ ፡ ቤት ፡ ማዘዣ ፤ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ወረቀት. I have a warrant for his arrest. እንዲያዝ ፡ የሚል ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ማዘዣ ፡ አለኝ
The police must have a search warrant to enter the house. ፖሊሱ ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ለመፈተሽ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ወረቀት ፡ መያዝ ፡ አለበት
2. ማረጋገጫ. His wealth is no warrant of happiness. ሀብቱ ፡ የደስታ ፡ ማረጋገጫ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም
3. በቂ ፡ ምክንያት. He has no warrant for such a belief. ለዚህ ፡ ዓይነት ፡ እምነት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የለውም

**warranty** (warranties) ዋስትና
The warranty is for one year only. ዋስትናው ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ነው

**warrior** ዘማች ፤ ጦረኛ
Warriors used spears in the old days. ዘማቾች ፡ ድሮ ፡ የሚዋጉት ፡ በጦር ፡ ነበር
Our ancestors were warriors. ቅድመ ፡ አያቶቻችን ፡ ጦረኞች ፡ ነበሩ

**warship** የጦር ፡ መርከብ
The warship is completely constructed of steel. የጦር ፡ መርከቡ ፡ በሙሉ ፡ የተሠራው ፡ ከዐረብ ፡ ብረት ፡ ነው

**war song** ሽለላ
The minstrels sing war songs. አዝማሪዎቹ ፡ ሽለላ ፡ ያሰማሉ

**wart** ኪንታሮት
His hand was covered with warts. ኪንታሮት ፡ እጁን ፡ ወሮታል

**wary**
1. ጠንቃቃ. The wary patrol escaped the enemy's ambush. ጠንቃቃ ፡ የሆነው ፡ ቃኚ ፡ ጓድ ፡ ከጠላት ፡ ደፈጣ ፡ አመለጠ
2. (= adv.) በጥንቃቄ. He gave wary answers to all the stranger's questions. ለእንግዳው ፡ ሰው ፡ ጥያቄዎች ፡ ሁሉ ፡ በጥንቃቄ ፡ መልስ ፡ ሰጠ
**be wary** በጥርጣሬ ፡ ዓይን ፡ ተመለከተ
He was wary of the contract since he suspected some deceit. ማታለል ፡ አለበት ፡ ብሎ ፡ ስላሰበ ፡ የቀረበለትን ፡ ውል ፡ በጥርጣሬ ፡ ዓይን ፡ ተመለከተ

**(he) was** ነበር ፤ ነበረ
He was in school today. እሱ ፡ ዛሬ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ነበር ፡ (ነበረ)

**wash** (vt.)
1. አጠበ. Who's going to wash the dishes? ሳሕኑን ፡ ማን ፡ ሊያጥብ ፡ ነው ?

She washes her clothes twice a month. ልብሷን ፡ በወር ፡ ሁለቴ ፡ ታጥባለች
2. ታጠበ. Wash your face before dinner! ከእራት ፡ በፊት ፡ ፊትህን ፡ ታጠብ
He washed his hands before eating dinner. እራት ፡ ከመብላቱ ፡ በፊት ፡ እጁን ፡ ታጠበ
3. አወጣ. The river washed a new channel after the heavy rain. ከኀይለኛው ፡ ዝናብ ፡ በኋላ ፡ ወንዙ ፡ አዲስ ፡ መንገድ ፡ አወጣ

**wash** (vi.)
1. ልብስ ፡ አጠበ. Mother usually washes on Tuesday. እናታችን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ልብስ ፡ የምታጥበው ፡ ማክሰኞ ፡ ነው
2. ታጠበ. You should always wash before eating. ከመብላትህ ፡ በፊት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ መታጠብ ፡ አለብህ
Does this material wash? ይህ ፡ ጨርቅ ፡ ይታጠባል ?

**wash away**
1. ወሰደ. Last spring the flood washed away the dam. ባለፈው ፡ ጸደይ ፡ ጐርፉ ፡ ግድቡን ፡ ወሰደው
2. አጥለቀለቀ. It was his hard luck that the flood washed away his land. ጐርፉ ፡ የሱን ፡ መሬት ፡ ማጥለቅለቁ ፡ መጥፎ ፡ አጋጣሚ ፡ ነው

**(be) washed away** ሙልጭ ፡ ብሎ ፡ ታጠበ
Her makeup was washed away by the rain. ፊቷን ፡ የተቀባባችው ፡ በዝናብ ፡ ሙልጭ ፡ ብሎ ፡ ታጠበ

**wash down** ዋጠ
He washed down the pill with a glass of water. ኪኒኑን ፡ ባንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ውኃ ፡ ዋጠ

**wash off** ታጠበ
The dust washed off in the rain. አቧራው ፡ በዝናብ ፡ ታጠበ

**wash out** (vt.) አፈረሰ
The flood washed out the road. የውኃው ፡ መጥለቅለቅ ፡ መንገዱን ፡ አፈረሰው

**wash out** (vi.) ቢያጥቡት ፡ ለቀቀ
The stain won't wash out. ጠብታው ፡ ቢያጥቡት ፡ አይለቅም

**(be) washed out** ውኃ ፡ ወሰደው
+The bridge was washed out. ድልድዩን ፡ ውኃ ፡ ወሰደው

**(look) washed out** የለቀቀ ፡ ይመስላል
The color looks washed out. ቀለሙ ፡ የለቀቀ ፡ ይመስላል

**wash up** ታጠበ
I'd like to wash up before dinner. ከእራት ፡ በፊት ፡ ልታጠብ ፡ እፈልጋለሁ
[See also 'clean, hand']

**wash** (n.)
1. የታጠበ ፡ ልብስ. She was hanging out the wash when I came. ስመጣ ፡ የታጠበ ፡ ልብስ ፡ ታሰጣ ፡ ነበር
2. የሚታጠብ ፡ ልብስ. The wash hasn't been taken yet to the laundry. የሚታጠበው ፡ ልብስ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ንጽሕና ፡ መስጫ ፡ ቤት ፡ አልተወሰደም
3. መታጠብ. Your car needs a wash. መኪናህ ፡ መታጠብ ፡ ያስፈልጋታል

**(be) washable** ይታጠባል
Cotton is washable. ከጥጥ ፡ የተሠራ ፡ ልብስ ፡ ይታጠባል

**washing machine** የማጠቢያ ፡ መኪና
The washing machine broke down again. የማጠቢያው ፡ መኪና ፡ እንደገና ፡ ተበላሸ

**wasp** ተርብ
The wasp has a powerful sting. ተርብ ፡ ሲናደፍ ፡ ኀይለኛ ፡ ነው

**wasp nest** የተርብ ፡ እንጀራ
The boy found a wasp nest. ልጁ ፡ የተርብ ፡ እንጀራ ፡ አገኘ

**waste** (vt.)
1. አጠፋ. He wastes a lot of time talking. በወሬ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያጠፋል
Don't waste so much money! ይህን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ አታጥፋ
2. አወደመ. Swarms of locusts wasted the fields. ያንበጣ ፡ መንጋ ፡ እርሻውን ፡ አወደመ
3. አበላሸ. She wasted her chance for an education. ለትምህርት ፡ የነበራትን ፡ ዕድል ፡ አበላሸች
4. አባከነ. A busy man does not waste his time. ሥራ ፡ የሚበዛበት ፡ ሰው ፡ ጊዜውን ፡ አያባክንም
5. አደከመ. The disease wasted him for months. በሽታው ፡ ለብዙ ፡ ወራት ፡ አደከመው
*Don't waste your breath! አፍህን ፡ አታጥፋ

**waste** (vi). አለቀ
Our supplies slowly wasted. ቀለባችን ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ አለቀ

**waste away** መነመነ
In her old age, she wasted away. በእርጅና ፡ ዘመኗ ፡ መነመነች

**(be) wasted away** አለቀ
The soil was wasted away by erosion. አፈሩ ፡ እየተሸረሸረ ፡ አለቀ

**waste** (n.)
1. ማጥፋት. It's a waste of time and energy. ጊዜና ፡ ጉልበት ፡ ማጥፋት ፡ ነው

2. ቆሻሻ. The waste from the factory was dumped in the stream. ከፋብሪካው ፡ ውስጥ ፡ የሚመጣው ፡ ቆሻሻ ፡ እወንዙ ፡ ውስጥ ፡ ፈሰሰ

*It's just plain waste to have college graduates serve as waiters. ከኮሌጅ ፡ የተመረቁት ፡ እንደ ፡ አሳላፊ ፡ ሆነው ፡ መሥራታቸው ፡ አይጠቅምም

**go to waste**

1. በከንቱ ፡ ባከነ. Your talents are going to waste in that job. የተፈጥሮ ፡ ችሎታህ ፡ በዚያ ፡ ሥራ ፡ በከንቱ ፡ መባከኑ ፡ ነው

2. በከንቱ ፡ ቀረ. His training went to waste. ትምህርቱ ፡ በከንቱ ፡ ቀረ

3. ባከነ. She hates to see good food go to waste. መልካም ፡ ምግብ ፡ ሲባክን ፡ ማየት ፡ አትወድም

**let go to waste** አባከነ

A good cook doesn't let anything go to waste. ጥሩ ፡ ወጥቤት ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አያባክንም

**waste** (adj.), **lay ~** አፈረሰ

The storm has laid waste the entire area. ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ አካባቢውን ፡ በሙሉ ፡ አፈረሰው

**be laid waste**

1. ተደመሰሰ. German cities were laid waste by bombing. የጀርመን ፡ ከተሞች ፡ በቦምብ ፡ ተደምስሰው ፡ ነበር

2. ምድረ ፡ በዳ ፡ ሆነ. The whole region was laid waste by the storm. ባውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ምክንያት ፡ ቀበሌው ፡ በሞላ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሆነ

**wastebasket** ቆሻሻ ፡ መጣያ ፡ ቅርጫት

Put it in the wastebasket! ቆሻሻ ፡ መጣያው ፡ ቅርጫት ፡ ውስጥ ፡ ጣለው

**wasteful** አባካኝ

He is very wasteful as far as money is concerned. በገንዘብ ፡ ረገድ ፡ በጣም ፡ አባካኝ ፡ ነው

**wasteland** ጠፍ ፡ መሬት

Nothing can be grown in this wasteland. እዚህ ፡ ጠፍ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ለማብቀል ፡ አይቻልም

**wastepaper** ቁሻሻ ፡ ወረቀት

The wastepaper caught fire. ቁሻሻው ፡ ወረቀት ፡ በእሳት ፡ ተያያዘ

**wastepaper basket** የቆሻሻ ፡ ወረቀት ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ቅርጫት

The wastepaper basket is full; take it out and empty it! የቆሻሻ ፡ ወረቀት ፡ ማጠራቀሚያው ፡ ቅርጫት ፡ ስለሞላ ፡ አውጥተህ ፡ ድፋው

*My plan wound up in the wastepaper basket. እቅዴ ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ ቀረ

**wastrel** አባካኝ ፡ ሰው

The wastrel lost his patrimony by foolish spending. አባካኙ ፡ ሰው ፡ የወረሰውን ፡ ገንዘብ ፡ በማይረባ ፡ እያጠፋ ፡ ጨረሰው

**watch** (vt.)

1. ተመለከተ. I've been watching him for some time. ስመለከተው ፡ ቆይቼ ፡ ነበር

2. አየ. Today we watched a wrestling match. ዛሬ ፡ የትግል ፡ ውድድር ፡ አየን

3. ዝም ፡ ብሎ ፡ ተመለከተ. I get nervous when you watch me. ስሠራ ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ስትመለከተኝ ፡ እጨነቃለሁ

4. ታዘበ. Pull yourself together; people are watching you. ራስህን ፡ ተቈጣጠረው ፤ ሰው ፡ ይታዘብሃል

5. ዝም ፡ ብሎ ፡ አየ. The lost traveler watched his supply of food dwindle. የጠፋው ፡ መንገደኛ ፡ ሥንቁ ፡ እየመነመነ ፡ ሲሄድ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አየ

6. ተከታተለ. I have watched his career with interest. ሥራውን ፡ በአድናቆት ፡ ተከታተልኩት

7. ጠበቀ. Who is going to watch the children? ልጆቹን ፡ ማን ፡ ይጠብቃቸዋል ?

The shepherd watched his flock. እረኛው ፡ መንጋውን ፡ ጠበቀ

*Watch your step! በጥንቃቄ ፡ ተራመድ

*Watch your tongue; the boss is around. ምላስህን ፡ ሰብስብ ፤ አለቃችን ፡ መጥቷል

**watch** (vi.)

1. ተጠባበቀ. There is a policeman watching outside the house. ከቤቱ ፡ ውጭ ፡ አንድ ፡ ፖሊስ ፡ ይጠባበቃል

2. ተጠነቀቀ. Watch that you don't drop the plate! ሳሕኑን ፡ እንዳትጥል ፡ ተጠንቀቅ

**watch for** እንዳለ ፡ እንደሌለ ፡ አየ

The doctor told her to watch for symptoms of measles. ሐኪሙ ፡ የኩፍኝ ፡ በሽታ ፡ ምልክቶች ፡ እንዳሉና ፡ እንደሌሉ ፡ እንድታይ ፡ ነገራት

**watch out** ተጠነቀቀ

Watch out when you cross the street! መንገድ ፡ ስታቋርጥ ፡ ተጠንቀቅ

**watch out for**

1. ተጠነቀቀ ፤ ጠንቀቅ ፡ አለ(በት). Watch out for the broken stairs! የተሰበረውን ፡ ደረጃ ፡ ተጠንቀቅ

Watch out for the curves in the road! በጐዳናው ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ መጠምዘገሮች ፡ ጠንቀቅ ፡ በሉባቸው

2. ፈለገ. I'll be watching out for you at the station. እጣቢያው ፡ እፈልግሃለሁ

**watch (over)** አገደ
The goatherd watches over the goats. እረኛው ፡ ፍየሎችን ፡ ያግዳል
[See also 'sharp, step']

**watch** (n.)
1. ሰዓት. By my watch, it's five. በኔ ፡ ሰዓት ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ነው
2. ዘብ. The watch is relieved every four hours. ዘቡ ፡ በየአራት ፡ ሰዓት ፡ ይለዋወጣል

**be on the watch for** ተጠነቀቀ
Be on the watch for automobiles when you cross the street! መንገድ ፡ ስታቋርጥ ፡ መኪና ፡ ተጠንቀቅ

**keep watch over** ጠበቀ
They kept watch over the sick child. የታመመው ን ፡ ልጅ ፡ ይጠብቁት ፡ ነበር
Two policemen were assigned to keep watch over the factory. ፋብሪካውን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ሁለ ት ፡ ፖሊሶች ፡ ተመደቡ

**watchdog** ውሻ
The watchdog barks whenever strangers are near. እንግዶች ፡ ሰዎች ፡ በተጠጉ ፡ ቁጥር ፡ ውሻው ፡ ይጮኻል

**watchful**
1. ንቁቶ ፡ የሚጠብቅ. The watchful dog caught the thief. ንቁቶ ፡ የሚጠብቀው ፡ ውሻ ፡ ሌባው ን ፡ ያዘው
2. ንቁ. He is very watchful, so it's hard to slip past him. ንቁ ፡ ስለሆነ ፡ ሳያይሁ ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ እሱን ፡ ማለፍ ፡ ያስቸግራል

**be watchful for** ተጠነቀቀ
You should always be watchful for cars when you cross the street. መንገዱን ፡ ስታቋርጥ ፡ ሁል ጊዜ ፡ መኪና ፡ መጠንቀቅ ፡ አለብህ

**watching** (verbal noun) መከታተል
That fellow needs close watching; he may be a smuggler. ያንን ፡ ሰው ፡ በጥብቅ ፡ መከታተል ፡ ያስ ፈልጋል ፤ ባልተቀረጠበት ፡ የሚነግድ ፡ ይሆናል

**watchmaker** ሰዓት ፡ ሠራተኛ ፤ ሰዓት ፡ ሠሪ
The watchmaker couldn't fix my watch. ሰዓት ፡ ሠራተኛው ፡ (ሠሪው) ፡ ሰዓቴን ፡ መሥራ ት ፡ አልቻለም

**watchman** ዘበኛ
They hired a new watchman. አዲስ ፡ ዘበኛ ፡ ቀጠሩ

**watchtower** የዘብ ፡ ግምብ
Watchtowers are placed at the corners of the compound. በግቢው ፡ ማእዘን ፡ ላይ ፡ የዘብ ፡ ግምብ ች ፡ ተሠርተዋል

**watchword** የይለፍ ፡ ቃል
The watchword is, "Be prepared"! የይለፉ ፡ ቃ ል ፡ « ተዘጋጅ » ፡ ነው

**water** (v.)
1. ውኃ ፡ አጠጣ. I water the flowers every day. አበባውን ፡ በየቀኑ ፡ ውኃ ፡ አጠጣለሁ
Did you water the horses today? ዛሬ ፡ ፈረሶቹ ን ፡ ውኃ ፡ አጠጥተሃል ?
2. አጠጣ. This river waters a large valley. ይህ ፡ ወንዝ ፡ ትልቅ ፡ ሸለቆ ፡ ያጠጣል
*It is forbidden to water milk. ወተት ፡ ውስጥ ፡ ውኃ ፡ መቀላቀል ፡ የተከለከለ ፡ ነው

**be watered**
1. (= act.) ውኃ ፡ ጠጣ. Have the horses been watered yet? ፈረሶቹ ፡ ገና ፡ ውኃ ፡ አልጠጡም ?
2. (= act.) ውኃ ፡ አገኘ. Our valley is well watered by rivers. ሸለቆዋችን ፡ ከወንዞች ፡ ውኃ ፡ በሚገባ ፡ ያገኛል

**water down** አለሰለሰ
The committee watered down our report. ደርጉ ፡ ሪፖርታችንን ፡ አለሰለሰው

**make water** አስለቀሰ
The smoke made my eyes water. ጭሱ ፡ ዓይ ኔን ፡ አስለቀሰኝ

**make (someone's) mouth water** ምራቅ ፡ አስ ዋጠ
The cake makes my mouth water. ብስኩቱ ፡ ምራቄን ፡ አስዋጠኝ

**water** (n.) ውኃ
Please give me a glass of water! እስቲ ፡ አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ውኃ ፡ ስጠኝ

**be in hot water** ተጣላ
He is always in hot water with his parents. ሁልጊዜ ፡ ከወላጆቹ ፡ ጋር ፡ እንደተጣላ ፡ ነው

**by water** በመርከብ
Do you like to travel by water? በመርከብ ፡ መ ጓዝ ፡ ትወዳለህ ?

**get into hot water** ችግር ፡ ውስጥ ፡ ገባ
He got into hot water by taking off from work too often. ከሥራ ፡ ላይ ፡ አዘውትሮ ፡ በመቅረቱ ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ ገባ

**hold water** ዋጋ ፡ ያለው ፡ መሰለ
His theory doesn't hold water. ዕንሱ ፡ ሐሳቡ ፡ ዋ ጋ ፡ ያለው ፡ አይመስልም

**keep (one's) head above water**
*Even though they are frugal, they are just able

to keep their heads above water. ገንዘብ ፡ ቈጣቢ ፡ ቢሆኑም ፡ ከዕለት ፡ ጉርሻቸው ፡ የሚተርፍ ፡ የላቸውም

**make water** ሸና

The little boy went outside to make water. ትንሹ ፡ ልጅ ፡ ሊሸና ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጣ

**sheet of water** ውኃ

The ground was covered with a sheet of water. መሬቱን ፡ ውኃ ፡ አልብሶት ፡ ነበር

**(be) under water** በውኃ ፡ ተጥለቀለቀ

The fields were under water after the heavy rains. ከከባዱ ፡ ዝናም ፡ በኋላ ፡ ሜዳው ፡ በውኃ ፡ ተጥለቅልቆ ፡ ነበር

[See also 'condense, deep, drink, flowing, fresh, hot, repellent, resistant, running water, territorial, throw, tread, wring']

**water closet** ሽንት ፡ ቤት

Where is the water closet? ሽንት ፡ ቤቱ ፡ የት ፡ ነው ?

**waterfall** ፏፏቴ

The Chisisat is Ethiopia's most famous waterfall. ጭስሳት ፡ በኢትዮጵያ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ፏፏቴ ፡ ነው

**watermelon** ሐብሐብ

Do you like watermelon? ሐብሐብ ፡ ትወዳለህ ?

**(be) waterproof** ውኃ ፡ አይዘልቀውም

Is this coat waterproof? ይህ ፡ ኮት ፡ ውኃ ፡ አይዘልቀውም ?

**make waterproof**

*The farmers smear hides with pitch to make them waterproof. ገበሬዎች ፡ ቆዳው ፡ ውኃ ፡ እንዳይዘልቀው ፡ ሙጫ ፡ ይቀቡታል

**(be) watertight**

1. ውኃ ፡ አያፈስም. Is this bag completely watertight? ይህ ፡ ስልቻ ፡ በፍጹም ፡ ውኃ ፡ አያፈስም ?
2. ውኃ ፡ አይዘልቀውም. +This box is watertight. ይህንን ፡ ሣጥን ፡ ውኃ ፡ አይዘልቀውም

**make watertight**

*Boats are calked to make them watertight. ጀልባዎች ፡ ውኃ ፡ እንዳይገባቸው ፡ በቅጥራን ፡ ይመረጋሉ

**watery** እንባ ፡ ያዘለ

He looked at me with watery eyes. እንባ ፡ ባዘሉ ፡ ዓይኖቹ ፡ ተመለከተኝ

**be watery** ውኃ ፡ ውኃ ፡ አለ

This soup is watery. ሾርባው ፡ ውኃ ፡ ውኃ ፡ ይላል

**wave** (vt.)

1. አርገበገበ. Somebody was waving a handkerchief. አንድ ፡ ሰው ፡ መሐረብ ፡ ያርገበግብ ፡ ነበር
2. አውለበለበ. Wave your hand! እጅህን ፡ አውለብልብ!

The wind waved the blades of grass. ነፋሱ ፡ የሣሩን ፡ ቅጠል ፡ አውለበለበው

3. አወዛወዘ. The students cheered with abandon waving their arms. ተማሪዎቹ ፡ እጃቸውን ፡ በማወዛወዝ ፡ በጋለ ፡ ስሜት ፡ ደስታቸውን ፡ ገለጹ
4. የእጅ ፡ ምልክት ፡ ሰጠ. The policeman waved the speeding driver to the side of the road. ፖሊሱ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍጥነት ፡ ይነዳ ፡ ለነበረው ፡ ሰው ፡ የእጅ ፡ ምልክት ፡ በመስጠት ፡ መንገዱ ፡ ዳር ፡ እንዲያቆም ፡ አደረገው

**wave** (vi.)

1. ተውለበለበ. The flags were waving in the breeze. ሰንደቅ ፡ ዓላማዎቹ ፡ በነፋስ ፡ ይውለበለቡ ፡ ነበር
2. እጁን ፡ አውለበለበ ፤ እጁን ፡ አወዛወዘ ፤ እጁን ፡ አርገበገበ. The crowd waved as he drove past. እሱ ፡ በመኪና ፡ ሲያልፍ ፡ ሕዝቡ ፡ እጁን ፡ አውለበለበ ፡ (አወዛወዘ)

She looked back and saw her mother waving to her. ዞር ፡ ብትል ፡ እናቷ ፡ እጇን ፡ ስታርገበግብ ፡ ተመለከተች

*Her hair waves beautifully. የጸጉሯ ፡ ደረጃ ፡ ያምራል

**wave away** እንዳይቀርብ ፡ በእጁ ፡ ምልክት ፡ ሰጠው

He waved us away from the scene of the accident. አደጋው ፡ ከደረሰበት ፡ ቦታ ፡ እንዳንቀርብ ፡ በእጁ ፡ ምልክት ፡ ሰጠን

**be waved** ደረጃ ፡ አበጀ

Her hair is waved. ጸጉሯ ፡ ደረጃ ፡ ያበጀ ፡ ነው

**wave** (n.)

1. ሞገድ. A wave of water swept over the beach. የውኃ ፡ ሞገድ ፡ የባሕሩን ፡ ጠረፍ ፡ አጠበው
2. ስሜት. A wave of enthusiasm swept the country. የደስታ ፡ ስሜት ፡ አገሩን ፡ በሙሉ ፡ አጥለቀለቀው

*Her hair has a natural wave. ጸጉሯ ፡ በተፈጥሮ ፡ ደረጃ ፡ አበጅቷል

**crime wave**

*The police are battling a crime wave. ፖሊሶች ፡ በፍጥነት ፡ እየጨመሩ ፡ የሚሄዱትን ፡ ወንጀሎች ፡ በመከላከል ፡ ላይ ፡ ናቸው

**heat wave** ሞቃት ፡ ነፋስ

The heat wave has made temperatures extremely high. ሞቃቱ ፡ ነፋስ ፡ ሙቀቱን ፡ ከልክ ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ አደረገው

**in waves**
*The infantry attacked in waves. እግረኛ ፡ ወታደሮች ፡ በረድፍ ፡ ሆነው ፡ ደጋግመው ፡ አጠቁ

**waver**
1. አወላወለ. He never wavered in his decision to study law. ሕግ ፡ ለማጥናት ፡ ባደረገው ፡ ውሳኔ ፡ አወላውሎ ፡ አያውቅም
2. አመነታ. He is very resolute and does not waver in a difficult situation. በጣም ፡ ቈራጥ ፡ ስለሆነ ፡ በችግር ፡ ጊዜ ፡ አያመነታም
3. አቅማማ. When I asked him to come along, he wavered a moment before saying no. አብሮን ፡ እንዲሄድ ፡ ስጠይቀው ፡ እምቢ ፡ ከማለቱ ፡ በፊት ፡ ትንሽ ፡ አቅማማ
4. ተርገበገበ. His voice wavered. ድምፁ ፡ ተርገበገበ
The candlelight wavered. የሻማው ፡ ብርሃን ፡ ተርገበገበ

**wax** (vt.) ሰም ፡ ቀባ
She has waxed the floor again. ወለሉን ፡ እንደገና ፡ ሰም ፡ ቀብታዋለች
**wax** (vi.) ወጣ
The moon waxes and wanes once a month. ጨረቃ ፡ የምትወጣውና ፡ የምትጠፋው ፡ በወር ፡ አንዴ ፡ ነው
[See also 'angry, talkative']

**wax** (n.) ሰም
The candle is made of wax. ሻማው ፡ የተሠራው ፡ ከሰም ፡ ነው

**waxy** ሰም ፡ መሳይ
This flower has waxy petals. ይህ ፡ አበባ ፡ ሰም ፡ መሳይ ፡ የተቀባ ፡ ቅጠል ፡ አለው

**way**
1. መንገድ. Is this the right way to town? ወደ ፡ ከተማ ፡ የሚወስደው ፡ ትክክለኛው ፡ መንገድ ፡ ይህ ፡ ነው ?
Are you going my way? መንገዳችን ፡ አንድ ፡ ነው ?
There are different ways of doing things. ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ለመሥራት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገዶች ፡ አሉ
In many ways he is like his father. በብዙ ፡ መንገድ ፡ እሱ ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ ነው
2. ፈና. The boys went their several ways. ልጆቹ ፡ በየፈናቸው ፡ ሄዱ
3. ዘዴ. Doctors are using new ways of preventing disease. ሐኪሞች ፡ በሽታ ፡ ለመከላከያ ፡ ባዲስ ፡ ዘዴዎች ፡ ይጠቀማሉ
4. ሁኔታ. That sick man is in a bad way. ያ ፡ በሽተኛ ፡ ሰው ፡ መጥፎ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነው
She smiled to me in a friendly way. በወዳጅነት ፡ ሁኔታ ፡ ሣቅ ፡ አለችልኝ
5. ልማድ. That's just his way. ልማዱ ፡ ነው
Ethiopia has assimilated Western ways. ኢትዮጵያ ፡ የምዕራብን ፡ ልማዶች ፡ ቀሥማለች
6. (noun of manner). I don't like the way he dresses. አለባበሱ ፡ ደስ ፡ አይለኝም
He copies his mother's way of talking. አነጋገሩ ፡ የናቱን ፡ አነጋገር ፡ ይመስላል
7. መልክ. He said that by way of apology. ያንን ፡ ያለው ፡ ይቅርታ ፡ በመለመን ፡ መልክ ፡ ነው
*I paid my own way through college. ኮሌጅ ፡ የተማርኩት ፡ በራሴ ፡ ገንዘብ ፡ ነው
*This is the wrong way to shell peas. አተር ፡ እንዲህ ፡ አይፈለፈልም
*It's disgraceful the way he drinks. ጠጪነቱ ፡ በጣም ፡ ያሳፍራል

**ways** አኗኗር
The stranger conformed his ways to ours. እንግዳው ፡ ሰው ፡ አኗኗሩን ፡ ከኛ ፡ አኗኗር ፡ ጋር ፡ አስማማ

**ways and means** ዘዴ
We have to find ways and means of carrying out our plan. እቅዳችንን ፡ ከግብ ፡ የምናደርስበት ፡ ዘዴ ፡ ያስፈልገናል

**way around here**
Do you know your way around here? የዚህን ፡ አካባቢ ፡ መግቢያ ፡ መውጫውን ፡ ታውቃለህ ?

**way of life** አኗኗር
There is much difference between the Chinese way of life and ours. በቻይኖችና ፡ በኛ ፡ አኗኗር ፡ መሀከል ፡ ትልቅ ፡ ልዩነት ፡ አለ

**(be) way off**
*His figures are way off. ሒሳብ ፡ ሲያደርግ ፡ በጣም ፡ ተሳስቷል

**way out**
1. መውጫ ፡ መንገድ. I don't see any other way out. ምንም ፡ ሌላ ፡ መውጫ ፡ መንገድ ፡ አይታየኝም
2. መውጫ. Which is the way out? መውጫው ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ?
3. ሩቅ ፡ ብሎ. They have a farm way out in the wilds. ሩቅ ፡ ብሎ ፡ ከዱር ፡ ውስጥ ፡ እርሻ ፡ አላቸው

**by the way** ለመሆኑ ፤ በነገራችን ፡ ላይ
By the way, have you ever studied Amharic? ለመሆኑ ፤ አማርኛ ፡ ተምረሀ ፡ ታውቃለህ ?

By the way, I met a friend of yours yesterday. በነገራችን ፡ ላይ ፤ ጓደኛህን ፡ ትናንትና ፡ አገኘሁት

**by way of** በ --- በኩል
We sent the letter by way of the American embassy. ደብዳቤውን ፡ ባሜሪካን ፡ ኤምባሲ ፡ በኩል ፡ ላክነው
Are you going by way of Harar? የምትሄደው ፡ በሐረር ፡ በኩል ፡ ነው ?

**come (one's) way** አጋጠመ(ው)
A bit of good fortune came my way. መልካም ፡ ዕድል ፡ አጋጠመኝ

**get one's way**
*He is happy when he gets his way. ፍላጎቱ ፡ ሲሟላለት ፡ ደስ ፡ ይለዋል

**give way**
1. ገለል ፡ አለ. The crowd gave way to let the procession pass. ሰልፈኛው ፡ እንዲያልፍ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ገለል ፡ አለ
2. አፈገፈገ. The troops had to give way before the assault. ጠላት ፡ ስላጠቃ ፡ ወታደሮቹ ፡ ማፈግፈግ ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው
3. ተደረመሰ ፤ ተናደ. The bridge gave way in the flood. ድልድዩ ፡ በውኃው ፡ መጥለቅለቅ ፡ ምክንያት ፡ ተደረመሰ ፡ (ተናደ)
4. ተበጠሰ. The rope gave way, and he fell. ገመዱ ፡ ተበጠሰና ፡ እሱ ፡ ወደቀ
5. ተስፋ ፡ ቈረጠ. He gave way when he saw he could not change her mind. ሐሳቧን ፡ ሊያስለውጣት ፡ አለመቻሉን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ተስፋውን ፡ ቈረጠ
6. አለቀ. His patience finally gave way, and words of anger erupted from him. በመጨረሻ ፡ ትዕግሥቱ ፡ አልቆ ፡ የቁጣ ፡ ቃላት ፡ ያሰማ ፡ ነበር

**give way!** ዞር ፡ በል
Give way or the mule will step on you! ዞር ፡ በል ፤ አለበለዚያ ፡ በቅሎዋ ፡ ትረግጥሃለች

**go out of (one's) way**
1. በጣም ፡ ተቸገረ. He went out of his way to be nice to his guests. ለእንግዶቹ ፡ ብሎ ፡ በጣም ፡ ተቸገረ
2. ከመንገዱ ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ. They went out of the way in order to see the ancient church. የጥንቱን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለማየት ፡ ከመንገዳቸው ፡ ወጥተው ፡ ሄዱ

**have it both ways**
*You can't have it both ways; choose one or another! ሁለት ፡ ወዶ ፡ አይሆንም ፤ አንዱን ፡ መምረጥ ፡ አለብህ

**have (one's) way**
*She is determined to have her own way. እንደፈለገችው ፡ ለመሥራት ፡ ቈርጣለች
*He insists on having his own way. እኔ ፡ ያልኩት ፡ ካልሆነ ፡ ይላል
*Have it your own way! እንደልብህ ፡ ይሁን!

**in a way** ባንድ ፡ በኩል
In a way, he is right. ባንድ ፡ በኩል ፡ ልክ ፡ ነው

**in no way**
1. በምንም + (negative verb). This is in no way better than what you had before. ይህ ፡ በፊት ፡ ከነበረህ ፡ በምንም ፡ አይሻልም
2. በምንም ፡ ዓይነት + (negative verb). They are in no way similar. በምንም ፡ ዓይነት ፡ አይመሳሰሉም

**(be) in the way** መንገድ ፡ ላይ ፡ መሰናከል ፡ ሆነ
The children's bicycles are always in the way. የልጆቹ ፡ ቢስኪሌቶች ፡ ሁልጊዜ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ መሰናክል ፡ ይሆናሉ

**in the way of**
*What have you got in the way of radios? ምን ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ሬዲዮ ፡ አላችሁ ?

**(be) in (someone's) way** ችግር ፡ አጋጠመው
He might have succeeded in his ambition, had not circumstances been in his way. ችግር ፡ ባያጋጥመው ፡ ኖሮ ፡ ፍላጎቱን ፡ ለመፈጸም ፡ ይችል ፡ ነበር

**make (one's) way**
1. አለፈ. You will have to make your way through this crowd anyhow. እንደምንም ፡ ብለህ ፡ በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ማለፍ ፡ አለብህ
2. መንገድ ፡ ቀጠለ. He made his way along the river road. በወንዙ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ

**make way for**
1. አሳለፈ. Make way for the doctor! ሐኪሙን ፡ አሳልፈው
2. መንገድ ፡ ለቀቀ. Make way for the parade! ለሰልፈኛው ፡ መንገድ ፡ ልቀቁ
3. ቦታውን ፡ ሰጠ. He resigned to make way for a younger man. ወጣት ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ቦታውን ፡ ለመስጠት ፡ ሥራውን ፡ ለቀቀ
4. ለ --- ሲል. They leveled the trees to make way for the new highway. ላዲሱ ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ ሲሉ ፡ ዛፎቹን ፡ ቈረጧቸው

**no way**
*That's no way to light the fire. እሳት ፡ የሚነደው ፡ እንደሱ ፡ አይደለም

**on (one's) way** እግረ ፡ መንገዱን
Please pick up the newspaper on your way! እግረ ፡ መንገድህን ፡ ጋዜጣውን ፡ አምጣልኝ

**on the way back** ሲመለስ
On the way back, he passed through Djibouti. ሲመለስ ፡ በጅቡቲ ፡ በኩል ፡ አለፈ

**one way or another** በዚህም ፡ ሆነ ፡ በዚያ ፤ ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ
The work must be finished, one way or another. በዚህም ፡ ሆነ ፡ በዚያ ፡ ሥራው ፡ መከናወን ፡ አለበት
It hardly matters one way or another. ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ እጅግም ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም

**out of the way** የማይገባ
He has done nothing out of the way yet, but the police are watching to see if he does. እስካሁን ፡ የማይገባ ፡ ሥራ ፡ አልሠራም ፤ ፖሊሶች ፡ ግን ፡ ይሠራ ፡ እንደሆነ ፡ በማለት ፡ ይጠብቁታል

**(be somewhat) out of the way** ከመንገድ ፡ ወጣ ፡ አለ
This place is somewhat out of the way. ይህ ፡ ቦታ ፡ ከመንገድ ፡ ወጣ ፡ ያለ ፡ ነው

**(have something) out of the way** ጨረሰ
At last, we have that lawsuit out of the way. በመጨረሻ ፡ ያንን ፡ ሙግት ፡ ጨረስን

**(be) out of (one's) way**
*I hope this isn't out of your way. ከመንገድህ ፡ እንደማያወጣህ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ

**pave the way** መንገድ ፡ ጠረገ(ለት)
He paved the way for my request. ለጥያቄዬ ፡ መንገድ ፡ ጠረገልኝ

**that way**
1. እንደዚያ. I didn't mean it that way. እንደዚያ ፡ ማለቴ ፡ አልነበረም
2. በዚያ ፡ በኩል. Go that way! በዚያ ፡ በኩል ፡ ሂድ

**that's no way** ተገቢ ፡ አይደለም
That's no way to treat people. ሰውን ፡ እንደዚህ ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም

**this way**
1. በዚህ ፡ በኩል. This way in, please! በዚህ ፡ በኩል ፡ ይግቡ
2. ወደዚህ. Everyone face this way! ሁላችሁም ፡ ወደዚህ ፡ ተመልከቱ

**this way or that way** ይሄም ፡ ያም
You can go this way or that way. ይሄም ፡ ያም ፡ ያስኬድሃል

**to my way of thinking** እንደኔ ፡ አስተሳሰብ
To my way of thinking, that's proof enough that he is guilty. እንደኔ ፡ አስተሳሰብ ፡ ለጥፋቱ ፡ ያ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ነው

**(be) under way** ተጀመረ
A play was under way when we entered the auditorium. አዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ስንገባ ፡ ቲያትሩ ፡ ተጀምሮ ፡ ነበር

**which way?**
1. በየት ፡ በኩል. Which way shall we go? በየት ፡ በኩል ፡ እንሂድ ?
2. በየትኛው ፡ መንገድ. Which way shall we do it? በየትኛው ፡ መንገድ ፡ እንሥራው ?
[See also the numerous expressions combined with 'way']

**wayfarer** መንገደኛ
The wayfarers were attacked and robbed. መንገደኞቹ ፡ ተደብድበው ፡ ተዘረፉ

**waylay** አድፍጦ ፡ ዘረፈ
The robbers waylaid us on the way home. ወደ ፡ ቤታችን ፡ ስንሄድ ፡ ቀማኞቹ ፡ አድፍጠው ፡ ዘረፉን

**wayside, by the ~** መንገድ ፡ ዳር
We ate lunch by the wayside. ምሳ ፡ የበላነው ፡ መንገድ ፡ ዳር ፡ ነው

**wayward** አስቸጋሪ
She tried to correct her wayward child. አስቸጋሪ ፡ ልጇን ፡ ልትቈጣጠረው ፡ ሞከረች

**wayward mood** ግርምቢጥነት
In a wayward mood, he ran away from home. በግርምቢጥነት ፡ ቤቱን ፡ ለቆ ፡ ኰበለለ

**we** እኛ, or verbal marker
We will come later. እኛ ፡ በኋላ ፡ እንመጣለን ፡ (or በኋላ ፡ እንመጣለን)

**weak**
1. ደካማ. He is a weak person and cannot work hard. ደካማ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ብዙ ፡ ለመሥራት ፡ አይችልም
A child is too weak to run very fast. ልጅ ፡ በጣም ፡ ደካማ ፡ ስለሆነ ፡ በጣም ፡ በፍጥነት ፡ ለመሮጥ ፡ አይችልም
Their defense was weak. መከላከያቸው ፡ ደካማ ፡ ነበር
His weak character allows everyone to dominate him. ደካማ ፡ መንፈሱ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲጫነው ፡ ያደርገዋል
He is weak in arithmetic. በቁጥር ፡ ደካማ ፡ ነው
2. የደከመ. His weak eyes do not allow him to read much. የደከሙት ፡ ዓይኖቹ ፡ ብዙ ፡ እያስነበቡትም
3. ቀጭን. Weak tea has less flavor than strong tea. ቀጭን ፡ ሻይ ፡ ከወፍራም ፡ ሻይ ፡ ያነሰ ፡ ጣዕም ፡ አለው
Weak coffee tastes bad. ቀጭን ፡ ቡና ፡ መጥፎ ፡ ጣዕም ፡ አለው

**get weak** ደከመ
I get weak when I work hard. ከባድ ፡ ሥራ ፡ ስ ሠራ ፡ እደከማለሁ

**weaken** (vt.)
1. አደከመ. I took Epsom salt and it weakened me. የእንግሊዝ ፡ ጨው ፡ ጠጥቼ ፡ አደከመኝ
2. አዳከመ(በት). Defeat weakened his will to fight. መሸነፍ ፡ ለመዋጋት ፡ የነበረውን ፡ ወኔ ፡ አዳከመበት
3. አደቀቀ. Illness weakened him terribly. በሽታ ፡ አድቅቆታል
4. አቀጠነ. You can weaken tea by adding water. ውኃ ፡ በመጨመር ፡ ሻዩን ፡ ልታቀጥን ፡ ትችላለህ

**weaken** (vi.) ተዳከመ
We have almost reached the top of the mountain; let's not weaken now! ተራራው ፡ ጫፍ ፡ ልንደርስ ፡ ነው ፣ አሁን ፡ እንዳከም

**weakling**
1. ደካማ ፡ ሕፃን. In ancient Greece weaklings were left to die of exposure. በጥንታዊት ፡ ግሪክ ፡ ደካማ ፡ ሕፃናት ፡ ከሐሩርና ፡ ከቍር ፡ የተነሣ ፡ እንዲሞቱ ፡ ይጣሉ ፡ ነበር
2. ልፍስፍስ ፡ ሰው. The army will not accept weaklings. ጦር ፡ ሰራዊት ፡ ልፍስፍስ ፡ ሰዎችን ፡ አይቀበልም

**weakness**
1. የአካል ፡ ድካም. He suffered weakness after the accident. ካደጋው ፡ በኋላ ፡ የአካል ፡ ድካም ፡ ደረሰበት
2. ጉድለት. The weakness resulting from the accident made it impossible for him to play football. ካደጋው ፡ የተነሣ ፡ በደረሰበት ፡ ጉድለት ፡ ምክንያት ፡ የእግር ፡ ኳስ ፡ መጫወት ፡ አቅቶታል
Putting things off is her weakness. የሷ ፡ ጉድለት ፡ ሥራ ፡ መወዘፏ ፡ ነው
3. መድከም. The weakness of old age will afflict us all. በእርጅና ፡ ምክንያት ፡ መድከም ፡ ለሁላችንም ፡ የማይቀር ፡ ነው

**have a weakness for** ለ -- ነፍሱ ፡ ወጣ
He has a weakness for French pastry. ለፈረንሳይ ፡ ጣፋጭ ፡ ምግቦች ፡ ነፍሱ ፡ ይወጣል

**wealth**
1. ሀብት. His wealth makes us envious. የሱ ፡ ሀብት ፡ ያስቀናናል
2. መጠን. His wealth of general information is amazing. ያለው ፡ የጠቅላላ ፡ ዕውቀት ፡ መጠን ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው

**wealth of** ብዙ
He has a wealth of ideas about how to solve my problems. ለችግሬ ፡ መፍትሔ ፡ ለማግኘት ፡ ብዙ ፡ ሐሳብ ፡ አለው

**have a wealth of** ሞላ(በት)
This book has a wealth of illustrations. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ሥዕል ፡ ሞልቶበታል

**wealthy** ሀብታም ፣ ባለጸጋ ፣ ከበርቴ
He married a wealthy woman. ሀብታም ፡ (ባለጸጋ ፣ ከበርቴ) ፡ ሴት ፡ አገባ

**make wealthy** አበለጸገ
The affluence of minerals made the country wealthy. የማዕድን ፡ በገፍ ፡ መኖር ፡ ሀገሪቱን ፡ አበለጸጋት

**wean** ጡት ፡ አስጣለች
She weaned her child when it was one year old. አንድ ፡ ዓመት ፡ ሲሞላው ፡ ልጇን ፡ ጡት ፡ አስጣለችው

**be weaned** ጡት ፡ ተወ
Babies don't like to be weaned. ሕፃናት ፡ ጡት ፡ መተው ፡ አይወዱም

**weapon** የጦር ፡ መሣሪያ
All weapons have to be turned over to the police. የጦር ፡ መሣሪያዎችን ፡ ሁሉ ፡ ለፖሊስ ፡ ማስረከብ ፡ ያስፈልጋል

**wear** (wore, worn), vt.
1. ለበሰ. He wears clothes of poor quality. መናኛ ፡ ልብስ ፡ ይለብሳል
2. አደረገ. He never wears a hat. ፈጽሞ ፡ ባርኔጣ ፡ አያደርግም
He wears a ring on his finger. እጣቱ ፡ ላይ ፡ ቀለበት ፡ ያደርጋል
3. አሳደገ. He wears a beard. ጺሙን ፡ ያሳድጋል
4. ሰካ. She wore her class pin. የክፍሏን ፡ አርማ ፡ ሰክታለች
5. ታጠቀ. Do you wear a belt? ቀበቶ ፡ ትታጠቃለህ ?
6. ጫነ. Haile Sellassie has worn the crown since 1930. ከ፲፱፻፳፫ ዓ. ም. ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘውድ ፡ እንደጫኑ ፡ ነው
7. አሰረ. He wore a charm around his neck. አንገቱ ፡ ላይ ፡ ክታብ ፡ አስሯል

**wear** (vi.)
1. ለበሰ. What did she wear? ምን ፡ ለበሰች ?
2. በረከተ. This coat has worn well. ይህ ፡ ኮት ፡ ደኅና ፡ በርክቷል
*The house wore an air of sadness. በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የሐዘን ፡ ስሜት ፡ ነበር

*She used to wear her hair long. ጸጉሯን ፡ በረጅሙ ፡ ትለቀው ፡ ነበር

**be worn, look worn**
1. ተበላ. The stones were worn by the constant flow of water. ሳያቋርጥ ፡ በሚፈሰው ፡ ውኃ ፡ ድንጋዮቹ ፡ ተበልተዋል
2. አረጀ. My coat is pretty worn. ኮቴ ፡ በጣም ፡ አርጅቷል
3. ያለቀ ፡ መሰለ. The rug doesn't look worn at all. ምንጣፉ ፡ በፍጹም ፡ ያለቀ ፡ አይመስልም

**wear around the neck** አጠለቀ
She wore a golden chain around her neck. ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ ሐብል ፡ አጥልቃ ፡ ነበር

**wear away** (vt.)
1. ሸረሸረ. The action of water wore away the rocks. የውኃው ፡ ኀይል ፡ አለቶቹን ፡ ሸረሸራቸው
The water is wearing away the river bank. ውኃው ፡ የወንዙን ፡ ገረገምብ ፡ እየሸረሸረ ፡ ነው
2. ጨረሰ. The rough streets have worn away the soles of my shoes. ኮረኮንቻው ፡ መንገድ ፡ ጫማዬን ፡ ጨረሰው

**wear away** (vi.) ተበላ
A horny covering keeps the wood from wearing away. የቀንድ ፡ ሽፋን ፡ ዕንጨቱ ፡ እንዳይበላ ፡ ይከላከላል

**wear down**
1. አሸነፈ. Our attacks finally wore down the enemy's resistance. በመጨረሻም ፡ የኛ ፡ ማጥቃት ፡ የጠላትን ፡ መቋቋም ፡ አሸነፈ
2. እሺ ፡ አሰኘ. He is trying to wear me down by asking me over and over again. እየደጋገመ ፡ በመጠየቅ ፡ እኔን ፡ እሺ ፡ ለማሰኘት ፡ ይሞክራል

**(be) worn down** ተበላ
These heels are worn down. እነዚህ ፡ የጫማ ፡ ተረከዞች ፡ ተበልተዋል

**wear off**
1. ለቀቀ. The paint will soon wear off. ቀለሙ ፡ ብዙም ፡ ሳይቆይ ፡ ይለቃል
2. አለፈ. The novelty will soon wear off. ብርቅነቱ ፡ ቶሎ ፡ ያልፋል
3. በረድ ፡ አለ. Wait till the excitement wears off! ግርግሩ ፡ በረድ ፡ እስኪል ፡ ቆይ

**wear on** አለፈ
Time wears on, day by day. ጊዜ ፡ በነጋ ፡ በጠባ ፡ ያልፋል
*Everybody got more inebriated as the evening wore on. እየመሸ ፡ ሲሄድ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሞቅታው ፡ ባሰበት

**wear oneself out**
Just don't wear yourself out! ራስህን ፡ አታድክም

**wear out** (vt.) ጨረሰ
He wears out his shoes very fast. ጫማውን ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ይጨርሳል

**wear out** (vi.) አለቀ
This kind of clothing wears out quickly. የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ልብስ ፡ ቶሎ ፡ ያልቃል

**(be) worn out**
1. አለቀ. His patience was worn out. ትዕግሥቱ ፡ አለቀ
The tires are all worn out. ጎማዎቹ ፡ በሙሉ ፡ አልቀዋል
2. በጣም ፡ ደከመ(ው). I am worn out from all this work. ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ የተነሣ ፡ በጣም ፡ ደክሞኛል

**wear through** ጨረሰ
I've worn my shoes through. ጫማዬን ፡ ጨርሻለሁ
[See also 'makeup, thin']

**wear** (n.)
1. ልብስ. They carry only men's wear. የሚሸጡት ፡ የወንድ ፡ ልብስ ፡ ብቻ ፡ ነው
2. ማለቅ. As for wear, you needn't worry; it will last a long time. ስለ ፡ ማለቁ ፡ አትጨነቅ ፤ በጣም ፡ ይበረክታል
The rug shows wear. ምንጣፉ ፡ ማለቅ ፡ ጀምሯል
*There is still much wear in these shoes. ይህ ፡ ጫማ ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ ያገለግላል

**wear and tear**
*Wear and tear on the house must be paid for by the tenant. ከገልግሎት ፡ የተነሣ ፡ በቤቱ ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ ብልሽት ፡ የሚከፍለው ፡ ተከራዩ ፡ መሆን ፡ አለበት

**for everyday wear** የሰርክ
This suit is for everyday wear. ይህ ፡ ልብስ ፡ የሰርክ ፡ ነው

**wearily** በድካም ፡ መልክ
The old man walked slowly and wearily along the road. ሽማግሌው ፡ በዝግታና ፡ በድካም ፡ መልክ ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ተራመደ

**weariness**
*After walking all day, I was overcome by weariness. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ስሄድ ፡ ውዬ ፡ በጣም ፡ ደከመኝ

**wearing** አድካሚ
It was a wearing journey to Harar. ወደ ፡ ሐረር ፡ መጓዝ ፡ አድካሚ ፡ ነበር
Teaching is wearing work. ማስተማር ፡ አድካሚ ፡ ሥራ ፡ ነው

**wearing apparel** ልብስ
That store deals in wearing apparel. ያ ፡ መደብር ፡ ልብስ ፡ ይሸጣል

**wearisome** አሰልቺ
His wearisome speeches always make me go to sleep. አሰልቺ ፡ ንግግሩ ፡ ሁልጊዜ ፡ እንቅልፍ ፡ ያስመጣብኛል

**weary** (wearied), v.
1. አሰለቸ. He wearies me with his constant requests. አሁንም ፡ አሁንም ፡ በመለመን ፡ አሰልችቶኛል
2. አደከመ. Going uphill wearies me. አቀበት ፡ መውጣት ፡ ያደክመኛል

**weary** (adj.)
1. የዛለ. I soaked my weary feet in cold water. የዛለውን ፡ እግሬን ፡ ቀዝቃዛ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ዘፈዘፍኩት
2. የደከመ. The weary soldier was plodding along the side of the road. የደከመው ፡ ወታደር ፡ የመንገዱን ፡ ዳር ፡ ይዞ ፡ ያዘግም ፡ ነበር
3. አድካሚ. The traveler walked many weary miles. መንገደኛው ፡ ብዙ ፡ አድካሚ ፡ ማይል ፡ ተጓዘ

**be weary, get weary** ድክም ፡ አለ(ው) ፤ ደከመ
+I get very weary at times. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ድክም ፡ ይለኛል
I am very weary after work. ከሥራ ፡ በኋላ ፡ በጣም ፡ ደከምኩ

**be weary of** ሰለቸ(ው)
+I'm weary of your complaints. ስሞታህ ፡ ሰልችቶኛል

**weather** (vt.)
1. ሸራረፈ. Wind weathers rocks. ነፋስ ፡ ቋጥኞችን ፡ ይሸራርፋል
2. ሊቋቋም ፡ ቻለ. The government weathered another economic crisis. መንግሥቱ ፡ ሌላ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ችግር ፡ ሊቋቋም ፡ ቻለ
3. ተቋቁሞ ፡ በደኅና ፡ ዘለቀ. The ship weathered the storm. መርከቧ ፡ ማዕበሉን ፡ ተቋቁማ ፡ በደኅና ፡ ዘለቀች

**weather** (vi.) ተፈረካከሰ
Stone weathers and becomes soil. ድንጋይ ፡ ተፈረካክሶ ፡ አፈር ፡ ይሆናል

**weather** (n.) ያየር ፡ ሁኔታ ፤ አየር
The weather is exceptional for June. እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ያየር ፡ ሁኔታ ፡ በሰኔ ፡ የተለመደ ፡ አይደለም
How is the weather? አየሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ?

**feel under the weather**
*I feel a little under the weather. ድኅንነት ፡ አይሰማኝም

**in wet weather** በዝናብ ፡ ጊዜ
He stays indoors in wet weather. በዝናብ ፡ ጊዜ ፡ ከቤት ፡ አይወጣም
[See also 'bad, clear, rainy, rough, stormy, vane, warm']

**(be) weatherbeaten** ተጎሳቈለ
The woman's face was weatherbeaten from years of hard outdoor work. ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ከባድ ፡ የውጭ ፡ ሥራ ፡ ከመሥራቷ ፡ የተነሣ ፡ የሴትዮዋ ፡ መልክ ፡ ተጎሳቍሏል

**weatherman** [ያየሩን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስረዳ ፡ ሰው]

**weave** (wove, or weaved)
1. ሠራ. He weaves good woolen cloth for export. ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚላክ ፡ ጥሩ ፡ የሱፍ ፡ ጨርቅ ፡ ይሠራል
The woman wove a straw mat. ሴትዮዋ ፡ የሣር ፡ ሰሌን ፡ ሠራች
2. አደራ. The spider weaves a web. ሸረሪቷ ፡ ድር ፡ ታደራለች
3. ሰካካ. She wove flowers into her hair. እራሷ ፡ ላይ ፡ አበባ ፡ ሰካካች
4. አቀናበረ. The author wove an exciting tale of pirates. ደራሲው ፡ የባሕር ፡ ሽፍቶችን ፡ አስደናቂ ፡ ታሪክ ፡ አቀናበረ

**weave (one's) way** ተሽሎክሉኮ ፡ አለፈ
The boy weaved his way through the crowd. ልጁ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ተሽሎክሉኮ ፡ አለፈ

**weaver** ሸማኔ
The weaver weaves two dresses a week. ሸማኔው ፡ በሳምንት ፡ ሁለት ፡ ቀሚስ ፡ ይሠራል

**(be) weaving** እየተንገዳገደ ፡ ሄደ
The drunk was weaving down the sidewalk. ሰካራሙ ፡ በእግረኛው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ እየተንገዳገደ ፡ ይሄዳል

**web** ድር
The spider's web is in the corner. የሸረሪት ፡ ድር ፡ ከግድግዳው ፡ መጋጠሚያ ፡ ላይ ፡ አለ

**web of lies** የተበተበ ፡ ውሸት
His web of lies was finally found out. የተበተበው ፡ ውሸት ፡ በመጨረሻ ፡ ተገለጸ

**wed** (wedded, or wed) አጣመረ
The goldsmith weds skill and art to make beautiful jewelry. ወርቅ ፡ ሠሪው ፡ ጥበብና ፡ ዕውቀትን ፡ አጣምሮ ፡ ጥሩ ፡ ጌጥ ፡ ይሠራል

**be wed** ተጋባ
They were wed in our church. በቤተ ፡ ክርስቲያ ናችን ፡ ተጋቡ

**be wedded** ተዋሐደ
Science and art are wedded in this project. ሳይንስና ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ በዚህ ፡ እቅድ ፡ ውስጥ ፡ ተዋሕደዋል

## wedding
1. ሰርግ. Two hundred people were invited to the wedding. ለሰርጉ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰው ፡ ተጠራ
2. የሰርግ ፡ (የጋብቻ) ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት. At the end of the wedding, the priest gave his benediction. በሰርጉ ፡ (በጋብቻው) ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ፍጻሜ ፡ ላይ ፡ ቄሱ ፡ ቡራኬ ፡ ሰጠ

**wedding banquet** ሰርግ
One and all came to the wedding banquet. ማንም ፡ ሳይቀር ፡ በሰርግ ፡ ላይ ፡ ተገኘ

**wedding feast** ሰርግ
A minstrel will play songs at our wedding feast. ሰርጋችን ፡ ላይ ፡ አዝማሪ ፡ ይዘፍንልናል

**wedding guest** ለሰርግ ፡ የተጋበዘ ፡ ሰው
The wedding guests came in large numbers. ለሰርጉ ፡ የተጋበዙት ፡ ሰዎች ፡ በብዛት ፡ መጡ

## wedge (v.), ~ oneself በጭንቅ ፡ ሾለከ
He wedged himself through the narrow window. በጠባቡ ፡ መስኮት ፡ ውስጥ ፡ በጭንቅ ፡ ሾለከ

**be wedged**
1. ተቀረቀረ. His foot was wedged between two rocks. እግሩ ፡ በሁለት ፡ ድንጋይ ፡ መካከል ፡ ተቀረቀረ
2. ታጨቀ. Ten people were wedged into the car. ዐሥር ፡ ሰዎች ፡ መኪናው ፡ ውስጥ ፡ ታጭቀው ፡ ነበር

## wedge (n.) ሽብልቅ
The rock was split by using wedges. ድንጋዩ ፡ በሽብልቅ ፡ ተፈለጠ

## wedlock
*The child was born in wedlock. ልጁ ፡ የተወለደው ፡ በሕግ ፡ ከተጋቡ ፡ ወላጆች ፡ ነው
*The child was born out of wedlock. ሕፃኑ ፡ ከሕግ ፡ ጋብቻ ፡ የተወለደ ፡ አይደለም

## Wednesday ሮብ ፤ ረቡዕ

## weed (v.) አረመ ፤ አረም ፡ ነቀለ
I have to weed the garden. አትክልቱን ፡ ማረም ፡ (አረም ፡ መንቀል) ፡ አለብኝ

**weed out** መርጦ ፡ አስወጣ
The teacher weeded out the students of bad character. መምህሩ ፡ ጠባየ ፡ መጥፎ ፡ የሆኑትን ፡ ተማሪዎች ፡ መርጦ ፡ አስወጣቸው

## weed (n.) አረም
The whole garden is full of weeds. አትክልቱን ፡ አረም ፡ ውጦታል

**kill the weeds** አረም ፡ አረመ
Every year we kill the weeds that overgrow the path. የእግር ፡ መንገዱን ፡ የሚሸፍነውን ፡ አረም ፡ በየመቱ ፡ እናርማለን

## week ሳምንት
I will be back in three weeks. በሦስት ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ እመለሳለሁ

**week after week** በየሳምንቱ
I find myself doing the same thing week after week. በየሳምንቱ ፡ ያንኑ ፡ አንዱን ፡ ነገር ፡ እሠራለሁ

**a week ago** ከሳምንት ፡ በፊት
He came a week ago. የመጣው ፡ ከሳምንት ፡ በፊት ፡ ነበር

**a week from now** ከሳምንት ፡ በኋላ
A week from now we'll have an exam. ከሳምንት ፡ በኋላ ፡ ፈተና ፡ ይኖረናል

**by the week** በየሳምንቱ
They pay their employees by the week. ለሠራተኞቻቸው ፡ በየሳምንቱ ፡ ይከፍሏቸዋል
[See also 'today']

## weekday የሥራ ፡ ቀን
You may visit me any weekday. በማንኛውም ፡ የሥራ ፡ ቀን ፡ ልትጠይቀኝ ፡ ትችላለህ

**weekdays** ከሰኞ ፡ እስከ ፡ ዓርብ
The store is open weekdays. ሱቁ ፡ ከሰኞ ፡ እስከ ፡ ዓርብ ፡ ክፍት ፡ ነው

## weekend
1. የሳምንት ፡ መጨረሻ. This weekend we start our vacation. በዚህ ፡ ሳምንት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜያችንን ፡ እንጀምራለን
2. እሑድና ፡ ቅዳሜ. Try to catch up in your work by working weekends! እሑድና ፡ ቅዳሜ ፡ በመሥራት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረህበትን ፡ ለማሟላት ፡ ሞክር

## weekly (weeklies), n. ሳምንታዊ ፡ መጽሔት
He publishes a weekly. ሳምንታዊ ፡ መጽሔት ፡ ያሳትማል

**weekly** (adj.)
1. ሳምንታዊ. Is your weekly report ready? ሳምንታዊ ፡ ሪፖርትህን ፡ አዘጋጅተሃል ?

2. (= adv.) በሳምንት. His weekly wage is $80. በሳምንት ፡ የሚያገኘው ፡ ሰማንያ ፡ ብር ፡ ነው
3. (= adv.) በየሳምንቱ. She writes a weekly letter to her parents. ለወላጆቿ ፡ በየሳምንቱ ፡ ደብዳቤ ፡ ትጽፋለች

**weep** (wept) አለቀሰ
Don't weep! I'll get you another doll. አታልቅሺ ፤ ሌላ ፡ አሻንጉሊት ፡ አመጣልሻለሁ

**weft** ማግ
The weft broke and the weaver had to begin anew. ማጉ ፡ ስለተበጠሰ ፡ ሸማኔው ፡ እንደገና ፡ መጀመር ፡ ነበረበት

**weigh** (vt.)
1. መዘነ. Please weigh this package for me! እስቲ ፡ ይህንን ፡ ጥቅል ፡ መዝንልኝ
2. አመዛዘነ. He weighs his words before speaking. ከመናገሩ ፡ በፊት ፡ የሚናገረውን ፡ ያመዛዝናል
3. መረጠ. It was an important message, and he was weighing his words. በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ መልእክት ፡ ስለነበረ ፡ ቃላቱን ፡ ይመርጥ ፡ ነበር

**weigh** (vi.) መዘነ
This piece of meat weighs four pounds. ይህ ፡ ሥጋ ፡ አራት ፡ ኪሎ ፡ ይመዝናል
He weighs a lot. ብዙ ፡ ይመዝናል

**weigh against each other** አነጻጸረ
We must weigh these plans against each other. እነዚህን ፡ እቅዶች ፡ ማነጻጸር ፡ አለብን

**weigh down** ወደታች ፡ አጐበጠ
The fruit weighed the branches down. የፍሬዎቹ ፡ ክብደት ፡ ቅርንጫፎቹን ፡ ወደታች ፡ አጉብጧቸዋል

**(be) weighed down**
*He is weighed down with worry. ሐሳብ ፡ ተጭኖታል

**weigh in one's favor** አስመሰገነ
His good behavior weighs in his favor. መልካም ፡ ጠባዩ ፡ ያስመሰግነዋል

**weigh on one** ከበደው
The responsibility weighs heavily on me. ኀላፊነቱ ፡ በጣም ፡ ከብዶኛል

**weigh on one's mind** ሐሳብ ፡ አሳደረበት
The theft weighs on his mind. ስርቆቱ ፡ ሐሳብ ፡ አሳድሮበታል

**weigh oneself** ተመዘነ
I weighed myself once a week. በሳምንት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተመዘንኩ

**weigh out** መዘነ
The grocer weighed out the flour and butter for us. የምግብ ፡ ሸቀጣ ፡ ሸቀጥ ፡ ሻጩ ፡ ዱቄትና ፡ ቅቤ ፡ መዘነልን

**weigh with one** ዋጋ ፡ አልሰጠውም
+His opinion doesn't weigh with me at all. ለሱ ፡ አስተያየት ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ አልሰጠውም
[See also 'heavily']

**weight** (v.), **be weighted down with** ብዙ ፡ ተሸከመ
He was weighted down with packages. ብዙ ፡ ጥቅሎች ፡ ተሸክሞ ፡ ነበር

**weight** (n.)
1. ክብደት. My weight is 160 lbs. ክብደቴ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ነጥር ፡ ነው
Did you put down the weight of the package? የጥቅሉን ፡ ክብደት ፡ መዘገብከው ?
2. የሚዛን ፡ ድንጋይ ፤ መመዘኛ. The weights are under the scale. የሚዛኑ ፡ ድንጋዮች ፡ እሚዛኑ ፡ ሥር ፡ ናቸው
We need standard weights and measures. የተወሰነ ፡ መመዘኛና ፡ መለኪያ ፡ ያስፈልገናል
3. ሚዛን. Can you guess my weight? ሚዛኔን ፡ ልትገምት ፡ ትችላለህ ?
4. ዋጋ. Don't attach too much weight to what he says! ለሚናገረው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ዋጋ ፡ አትስጠው
5. ሐሳብ. That's a great weight off my mind. ትልቅ ፡ ሐሳብ ፡ ወረደልኝ
*The weight of the responsibility bears heavily on me. ኀላፊነቱ ፡ በጣም ፡ ከብዶኛል

**lose weight** ክብደት ፡ ቀነሰ
When I was sick I lost a lot of weight. ታምሜ ፡ ሳለሁ ፡ ብዙ ፡ ክብደት ፡ ቀነስኩ

**put on weight**
He is putting on weight. ክብደቱ ፡ እየጨመረ ፡ ነው

**receive the weight of** ተሸከመ
These pillars receive the full weight of the roof. እነዚህ ፡ ምሰሶዎች ፡ ጣሪያውን ፡ በሙሉ ፡ ይሸከማሉ

**support the weight of** ተሸከመ
The pillars support the weight of the roof. ምሰሶ ፡ ጣሪያ ፡ ይሸከማል
[See also 'carry']

**weighty**
1. አሳሳቢ. The problem was too weighty for discussion to be put off. ችግሩ ፡ አሳሳቢ ፡ ስለነበረ ፡ ውይይቱን ፡ ለሌላ ፡ ጊዜ ፡ ለማስተላለፍ ፡ አልተቻለም

2. አጥጋቢ. The speaker presented weighty arguments in favor of accepting the plan. ተናጋሪው ፡ እቅዱ ፡ ተቀባይነት ፡ እንዲያገኝ ፡ አጥጋቢ ፡ ማስረጃ ፡ አቀረበ
3. ከባድ. The old President could no longer deal with the weighty cares of state. ሽማግሌው ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከባድ ፡ የሆኑትን ፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ ሊያከናውን ፡ አልቻለም
A weighty object broke the board it rested on. ከባዱ ፡ ነገር ፡ ያረፈበትን ፡ ሳንቃ ፡ ሰበረው

**weird** እንግዳ
Something made a weird noise. አንድ ፡ ነገር ፡ እንግዳ ፡ ድምፅ ፡ አሰማ

**weird looking** ልዩ ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ ያለው
I saw a weird looking person in the crowd. በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ አየሁ

**welcome** (v.) ተቀበለ ፤ በደስታ ፡ ተቀበለ
He welcomed her with open arms. በደስታ ፡ ተቀበላት
He would welcome the opportunity to go abroad. ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ለመሄድ ፡ የተሰጠውን ፡ ዕድል ፡ በደስታ ፡ ይቀበላል

**welcome home** በደስታ ፡ ተቀበለው
They welcomed their son home when he returned from America. ልጃቸው ፡ ከአሜሪካ ፡ ሲመለስ ፡ በደስታ ፡ ተቀበሉት

**be welcomed** ተቀበሉት
+We were welcomed with open arms. እጃቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ተቀበሉን

**welcome** (n.) አቀባበል
They gave us a warm welcome. የጋለ ፡ አቀባበል ፡ አደረጉልን
*You will always have a welcome here. ምንጊዜም ፡ ብትመጣ ፡ በደስታ ፡ እንቀበልሃለን
*The chairman preceded his statement with a welcome to the audience. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ከንግግሩ ፡ አስቀድሞ ፡ አዳማጮቹን ፡ እንኳን ፡ ደኅና ፡ መጣችሁ ፡ አለ

**welcome** (adj.)
1. በደስታ ፡ የሚቀበሉት. A welcome guest is one who brings happiness with him. በደስታ ፡ የሚቀበሉት ፡ እንግዳ ፡ ደስታን ፡ ይዞ ፡ የሚመጣ ፡ ነው
2. የሚያስደስት. That's the most welcome news I have heard in months. በስንት ፡ ወሬ ፡ የሰማሁት ፡ የሚያስደስት ፡ ወሬ ፡ ነው

**welcome home!** እንኳን ፡ ደኅና ፡ ገባህ!

**be welcome** በደስታ ፡ ተቀበለው
+You're always welcome here. እዚህ ፡ ምንጊዜም ፡ በደስታ ፡ እንቀበልሃለን

**be welcome to** ቻለ
You are welcome to use our library. በመጻሕፍት ፡ ቤታችን ፡ ልትጠቀም ፡ ትችላለህ
You are welcome to borrow my bicycle. ከፈለግህ ፡ ብስክሌቴን ፡ ልትዋስ ፡ ትችላለህ

**you are welcome!** አብሮ ፡ ይስጠን
When the beggar said "Thank you", the man replied saying "You are welcome!" ለማኙ ፡ « እግዚር ፡ ይስጥልኝ » ፡ ቢል ፡ ሰውዬው ፡ « አብሮ ፡ ይስጠን » ፡ አለ

**weld** በየደ
The plumber welded the broken pipe. ቧምቧ ፡ ሠራተኛው ፡ የተሰበረውን ፡ ቧምቧ ፡ በየደ

**weld into a (strong) team** አስተሳሰረ
Working together for a month welded them into a strong team. ላንድ ፡ ወር ፡ አብረው ፡ መሥራታቸው ፡ አስተሳሰራቸው

**welder** በያጅ
The welder left a crooked seam when he welded these plates together. በያጁ ፡ እነዚህን ፡ የብረት ፡ ሳሕኖች ፡ ሲበይድ ፡ መጋጠሚያውን ፡ አዛንፎታል

**welfare**
1. ደኅንነት. The welfare of the nation is the President's chief concern. የሀገሪቱ ፡ ደኅንነት ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የሚያስብበት ፡ ጉዳይ ፡ ነው
2. በጎ ፡ አድራጎት. The family has been living on welfare since last year. ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ከዓምና ፡ ጀምሮ ፡ በበጎ ፡ አድራጎት ፡ ይኖራል

**well** (v.) መነጨ
Water welled from the ground. ውኃ ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡ መነጨ

**well up**
*Tears welled up in her eyes. ዓይኖቿ ፡ እንባ ፡ አቀረሩ

**well** (n.)
1. የውኃ ፡ ጉድጓድ. The villagers dug a well. መንደርተኞቹ ፡ የውኃ ፡ ጉድጓድ ፡ ቈፈሩ
2. ጉድጓድ. Are there oil wells in Ethiopia? ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የዘይት ፡ ጉድጓዶች ፡ አሉ ?
3. ምንጭ. The encyclopedia is a well of information. ዓውደ ፡ ጥበብ ፡ የዕውቀት ፡ ምንጭ ፡ ነው

**well** (adv., adj.)
1. ደኅና. He did well to leave the house before it rained. ከመዝነቡ ፡ በፊት ፡ ከቤት ፡ መውጣቱ ፡ ደኅና ፡ አድርጓል
He lives well on a rather small salary. ደሞዙ ፡ አነስተኛ ፡ ቢሆንም ፡ ደኅና ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል
Well, just as you say. ደኅና ። እንዳልከ ፡ ይሁን
2. ጥሩ ፡ ነገር. He spoke well of me to the director. ለዲሬክተሩ ፡ ስለኔ ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ተናገረ
3. ጥሩ. It was well for you that no one saw you. ማንም ፡ ሰው ፡ ሳያይህ ፡ መቅረቱ ፡ ላንተ ፡ ጥሩ ፡ ነው
Well spoken! I couldn't have said it better myself. ጥሩ ፡ ተናገርሃል! እኔም ፡ ራሴ ፡ ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ለመናገር ፡ አልችልም ፡ ነበር
4. ብዙ. He is well advanced in his studies. በትምህርቱ ፡ ብዙ ፡ ተራምዷል
5. ታዲያ. You don't drink coffee. Well, what would you like? ቡና ፡ አትጠጣም ። ታዲያ ፡ ምን ፡ ትፈልጋለህ ?
6. እፎይ. Well, here we are at last! እፎይ ። ይኸው ፡ በመጨረሻ ፡ ደረስን
7. መቼም. Well, there is nothing we can do about it. መቼም ፡ ስለሱ ፡ ምንም ፡ ልናደርገው ፡ የምንችለው ፡ ነገር ፡ የለም
8. እና. Well, as I was saying, he comes from an old family. እና ፡ እንዳልኩት ፡ ከትልቅ ፡ ቤተሰብ ፡ ይወለዳል

**well done!** ጎሽ
Well done! You're a good boy. ጎሽ ። ጥሩ ፡ ልጅ ፡ ነህ

**well over**
1. ከ --- የበለጠ. The exhibition brought in well over a thousand dollars. ኤግዚቢሽኑ ፡ ካንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ የበለጠ ፡ ገንዘብ ፡ አስገኘ
2. ከ -- በላይ. There were well over a thousand people there. ካንድ ፡ ሺ ፡ በላይ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ተገኝቶ ፡ ነበር

**as well as**
1. -ም ፡ --- ም. He gave me money as well as advice. ገንዘብም ፡ ምክርም ፡ ሰጠኝ
2. -- ና ፡ እንዲሁም. He knows German as well as several other languages. ጀርመንኛና ፡ እንዲሁም ፡ አያሌ ፡ ቋንቋዎች ፡ ያውቃል
3. እንዲሁም. Britain as well as France gave aid to certain African countries. እንግሊዝ ፡ እንዲሁም ፡ ፈረንሳይ ፡ ላንዳንድ ፡ የአፍሪካ ፡ አገሮች ፡ እርዳታ ፡ ሰጡ

**as well as I** የኔን ፡ ያህል
He speaks German as well as I do. ጀርመንኛ ፡ የኔን ፡ ያህል ፡ ይናገራል

**be very well** ተስማማ(ው)
We are very well where we are. ያለንበት ፡ ተስማምቶናል

**be well** ተሻለ(ው) ። ዳነ
He is now well and fit for work. አሁን ፡ ተሽሎታል ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል
The child is gaining and will soon be well. የታመመው ፡ ልጅ ፡ እየተሻለው ፡ ስለሄደ ፡ በቅርቡ ፡ ይድናል

**be well again** ዳነ
You will soon be well again and be able to go to work. ቶሎ ፡ ድነህ ፡ ሥራ ፡ ለመግባት ፡ ትችላለህ

**be well off** ሀብታም ፡ ሆነ
He is well off and can afford to buy whatever he wants. ሀብታም ፡ ስለሆነ ፡ የፈለገውን ፡ ለመግዛት ፡ ይችላል

**be well on in years**
He is well on in years. በዕድሜው ፡ ገፋ ፡ ያለ ፡ ነው

**be well past**
He is well past forty. ዕድሜው ፡ ከአርባ ፡ ዓመት ፡ በለጥ ፡ ይላል

**be well situated** ደኅና ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው
The house is well situated — far enough from the road so it isn't too noisy. ቤቱ ፡ ደኅና ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው ። ከመንገዱ ፡ ራቅ ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ ጫጫታ ፡ የለበትም

**be well up**
*His name is well up in the list. ስሙ ፡ ወደ ፡ መጀመሪያው ፡ ገደማ ፡ ነው

**do very well** ጥሩ ፡ ተካሄደ
The new business is doing very well. አዲሱ ፡ ንግድ ፡ ጥሩ ፡ ይካሄዳል

**do well**
1. ተሻለ(ው). The patient is doing very well after the operation. ከቀዶ ፡ ጥገናው ፡ በኋላ ፡ በሽተኛው ፡ በጣም ፡ ተሻለው
2. ደኅና ፡ ነው. Mother and child are doing well. እናቲቱና ፡ ሕፃኑ ፡ ደኅና ፡ ናቸው

**do well by** በሚገባ ፡ ያዘው
He has done well by his children. ልጆቹን ፡ ሁሉ ፡ በሚገባ ፡ ይዟቸዋል

**fairly well** ደኅና ፡ አድርጎ
He treated his son fairly well. ልጁን ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ያዘው

**get on well** ተስማማ
The three of us get on very well. ሦስታችን ፡ በጣም ፡ እንስማማለን

**get well (again)** ተሻለ(ው) ፤ ዳነ
Will he get well soon? በቅርቡ ፡ ይሻለው ፡ ይሆን ?
I'll do the job for you, but first I must get well again. ሥራውን ፡ እሠራልሃለሁ ፤ ግን ፡ መጀመሪያ ፡ ልዳን

**go well together** ተስማሙ
Do these colors go well together? እነዚህ ፡ ቀለሞች ፡ ይስማማሉ ?

**go well with** ሠመረ
All has gone well with our plans. ላቅዳችን ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ሠምሯል

**how well ?** እንዴት
How well is he doing in school? በትምህርቱ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
How well do you know him? ዕውቂያችሁ ፡ እንዴት ፡ ነው ?

**it's just as well**
*It's just as well I didn't lend him the money. ለሱ ፡ ገንዘብ ፡ አለማበደሬ ፡ ደግ ፡ አድርጌያለሁ

**look well** አማረ(በት)
You look well. Were you on vacation? አምሮብሃል ፤ ዕረፍት ፡ ላይ ፡ ነበርክ ?
Doesn't this hat look well on me? ይህ ፡ ባርኔጣ ፡ አያምርብኝም ?

**(he) may as well**
We may as well begin at once. ቶሎ ፡ ብንጀምርም ፡ ያው ፡ ነው

**(he) might as well** ብ + imperfect + ይሻለዋል
You might as well stop working; it won't get you anywhere. ሥራውን ፡ ብታቆም ፡ ይሻልሃል ፤ ምንም ፡ አይጠቅምህ

**think well of**
He thinks well of me. ስለኔ ፡ ጥሩ ፡ አስተያየት ፡ አለው

**very well**
1. ደኅና ፡ አድርጎ. He did it very well. ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ሠራው
2. እሺ. Very well doctor, I will give up smoking. እሺ ፡ ዶክተር ፤ ሲጋራ ፡ ማጨስ ፡ አቆማለሁ
3. መቼም. I can't very well refuse to help him. መቼም ፡ አልረዳህም ፡ ልለው ፡ አልችልም
*He couldn't very well refuse to come. አልመጣም ፡ ሊል ፡ አይችልም ፡ ነበር

**very well then** እንግዲያውስ ፡ ደኅና ፡ ነው
Very well then, we'll talk it over tomorrow. እንግዲያውስ ፡ ደኅና ፡ ነው ፤ ነገ ፡ እንነጋገርበታለን

**(he) would do well** ብ + imperfect + ይሻለዋል
You would do well to say nothing about what happened. የተደረገውን ፡ ነገር ፡ ባታነሣ ፡ ይሻልሃል

[See also 'enough, fare, full, get along, mean, mix, perfectly, stand, turn out']

## (be) well-advised
*She would be well-advised to follow the instructions. መምሪያዎቹን ፡ ብትከተል ፡ ይሻላታል

## well-balanced
1. የተመዛዘነ. He has a well-balanced outlook on life. ስለ ፡ ሕይወት ፡ ያለው ፡ አስተያየት ፡ የተመዛዘነ ፡ ነው
2. ረጋ ፡ ያለ. He is a well-balanced person, and nothing upsets him. ረጋ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አያበሳጨውም
3. በደንብ ፡ የተመጣጠነ. Eat a well-balanced meal! በደንብ ፡ የተመጣጠነ ፡ ምግብ ፡ ብላ

## well-behaved ጨዋ
She is a well-behaved child. ጨዋ ፡ ልጅ ፡ ናት

## well-being ደኅንነት
He worked for the well-being of the nation. ለሀገሪቱ ፡ ደኅንነት ፡ ሠራ
He felt a sense of well-being. የደኅንነት ፡ ስሜት ፡ ተሰማው

## wellborn
1. ጨዋ. A lowly person may often be more polite than a wellborn person. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዝቅተኛ ፡ ሰው ፡ ከጨዋ ፡ ልጅ ፡ ይልቅ ፡ ትሑት ፡ ይሆን ፡ ይሆናል
2. የሀብታም ፡ ልጅ. Since school is very expensive, only the wellborn can attend it. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ ስለሆነ ፡ ከሀብታም ፡ ልጆች ፡ በስተቀር ፡ የሚገባበት ፡ የለም

## well-bred ጨዋ
Our host was a well-bred gentleman. አስተናጋጃችን ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ነበር

## well-disposed
He is well-disposed toward me. በጥሩ ፡ ዓይን ፡ ይመለከተኛል

## well-done
1. በደንብ ፡ የበሰለ. I like well-done meat. በደንብ ፡ የበሰለ ፡ ሥጋ ፡ እወዳለሁ
2. መልካም. One feels happy after a well-done job. ከመልካም ፡ ሥራ ፡ በኋላ ፡ ደስ ፡ ይለዋል

## well-founded መሠረት ፡ ያለው
His suspicion was well-founded. ጥርጣሬው ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ ነበር

**(be) well-grounded** ጠለቅ ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ አለው
He is well-grounded in the sciences. በሳይንስ ፡ ትምህርት ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ አለው

**well-informed**
*He's unusually well informed for one so young. በዚህ ፡ ዕድሜው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ አለው

**well-intentioned** ቅን
He is well-intentioned, but clumsy. ቅን ፡ ነው ፡ ግን ፡ ቅልጥፍና ፡ ይጐድለዋል

**well-known** የታወቀ ፤ በጣም ፡ የታወቀ
"Look before you leap" is a well-known precept. ከመዝለልህ ፡ በፊት ፡ ተመልከት ፡ የሚለው ፡ የታወቀ ፡ መመሪያ ፡ ነው
He is well-known as a famous architect. በሕንጻ ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ነው

**well-mannered** ጨዋ
The well-mannered boy always remembers to say "thank you" when something is done for him. ጨዋ ፡ የሆነ ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሲያደርጉለት ፡ « አመሰግናለሁ » ፡ ማለትን ፡ አይረሳም

**well-meaning** ልበ ፡ ቅን
She is well-meaning, but she does a lot of harm. ልበ ፡ ቅን ፡ ብትሆንም ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ታደርሳለች

**(be) well-meant** በጥሩ ፡ መንፈስ ፡ ነው
His remark was well-meant, but insulting all the same. አስተያየት ፡ የሰጠው ፡ በጥሩ ፡ መንፈስ ፡ ቢሆንም ፡ ስድብ ፡ መሆኑ ፡ አልቀረም

**well-nigh** በጣም
It's well-nigh impossible to get him to come on time. በጊዜ ፡ እንዲመጣ ፡ ለማድረግ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**well-off** ሀብታም
He is well-off and can afford to buy whatever he wants. ሀብታም ፡ ስለሆነ ፡ የፈለገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለመግዛት ፡ ይችላል

**(be) well-read** በሰፊው ፡ አነበበ
He is well-read in Ethiopian history. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ በሰፊው ፡ አንብቧል

**well-thought out** በደንብ ፡ የታሰበበት
It seems to be a well-thought out plan. በደንብ ፡ የታሰበበት ፡ እቅድ ፡ ይመስላል

**(be) well-timed** በጥሩ ፡ ጊዜ ፡ ተደረገ ፤ በተገቢ ፡ ጊዜ ፡ ነበር
The conference was well-timed. ጉባኤው ፡ በጥሩ ፡ ጊዜ ፡ ተደረገ
Your remark was well-timed. አስተያየት ፡ የሰጠኸው ፡ በተገቢው ፡ ጊዜ ፡ ነበር

**well-to-do** ባለጸጋ ፤ ሀብታም
His parents are well-to-do. ወላጆቹ ፡ ባለጸጎች ፡ (ሀብታሞች) ፡ ናቸው

**well-versed** የተራቀቀ
He is well-versed in Amharic literature. ባማርኛ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ የተራቀቀ ፡ ነው

**welter** (v.) ተንደባለለ
The pigs weltered in the mud. አሳሞቹ ፡ ጭቃው ፡ ውስጥ ፡ ይንደባለሉ ፡ ነበር

**welter** (n.)
*All we saw was a welter of bodies. ያየነው ፡ የሚፍጨረጨር ፡ ሰውነት ፡ ብቻ ፡ ነበር

**went,** see **go**

**wept,** see **weep**

**west** (n.) ምዕራብ
The wind comes from the west. ነፋሱ ፡ ከምዕራብ ፡ በኩል ፡ ይነፍሳል

**west of** ከ --- በስተምዕራብ
Our house is west of the railroad tracks. ቤታችን ፡ ከባቡሩ ፡ ሐዲድ ፡ በስተምዕራብ ፡ ነው

**west** (adj.) የምዕራብ
The west wind blows only at certain times of the year. የምዕራብ ፡ ነፋስ ፡ የሚነፍሰው ፡ ከመት ፡ ውስጥ ፡ በተወሰነ ፡ ወቅት ፡ ብቻ ፡ ነው

**west-bound** ወደ ፡ ምዕራብ ፡ የሚጓዝ
He left on the west-bound train. ወደ ፡ ምዕራብ ፡ በሚጓዘው ፡ ባቡር ፡ ሄደ

**westerly**
1. ከምዕራብ ፡ የሚነፍስ. A westerly breeze carried the boat out on the Red Sea. ከምዕራብ ፡ የሚነፍሰው ፡ ለዘብ ፡ ያለ ፡ ነፋስ ፡ ጀልባዋን ፡ ወደ ፡ ቀይ ፡ ባሕር ፡ ገፍቶ ፡ ወሰዳት
2. የምዕራብ. The river runs in a westerly direction. ወንዙ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ አቅጣጫ ፡ ይፈሳል

**western** ከምዕራብ ፡ የሚነፍስ
The western wind is strong today. ከምዕራብ ፡ የሚነፍሰው ፡ ነፋስ ፡ ዛሬ ፡ ኀይለኛ ፡ ነው

**Western world** የምዕራብ ፡ አገሮች
The Western world was unaffected by the change. በለውጡ ፡ የምዕራብ ፡ አገሮች ፡ አልተነኩም

**westerner** ፈረንጅ
There are many westerners in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ፈረንጆች ፡ አሉ

**westernization** የምዕራባውያን ፡ መንፈስ
Westernization has affected many countries in Africa. ብዙዎቹ ፡ የአፍሪካ ፡ ሀገሮች ፡ የምዕ ራባውያን ፡ መንፈስ ፡ ገብቶባቸዋል

**westernize** የምዕራባውያንን ፡ መንገድ ፡ ተከተለ
The Arabs are trying hard to westernize. ዐረቦች ፡ የምዕራባውያንን ፡ መንገድ ፡ ለመከተል ፡ በጣም ፡ ይጥራሉ

**westward** ወደ ፡ ምዕራብ
He walked westward. ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ሄደ

'**wet** (wetted, or wet), v.
1. ውኃ ፡ ነከረ. Wet the cloth before you wipe off the window! መስኮቱን ፡ ከመወልወልህ ፡ በ ፊት ፡ ጨርቁን ፡ ውኃ ፡ ንከረው
2. አረጠበ. He wet his hands, but did not wash them. እጁን ፡ አረጠበ ፡ እንጂ ፡ አልታጠበም
3. ሸና. The baby wet its bed again. ሕፃኑ ፡ እን ደገና ፡ አልጋው ፡ ላይ ፡ ሸና

**wet** (adj.)
1. እርጥብ. Don't touch wet paint! እርጥብ ፡ ቀ ለም ፡ አትንካ
2. ዝናብ ፡ የመታው. Wet dogs have an objectionable smell. ዝናብ ፡ የመታቸው ፡ ውሾች ፡ ይ ከረፋሉ
3. (= noun) የዝናም ፡ ጊዜ. We had a wet January. ያለፈው ፡ ጥር ፡ የዝናም ፡ ጊዜ ፡ ነበር
4. የቦካ. The wheelbarrow was full of wet cement. ኩርኩሩ ፡ በቦካ ፡ ሲሚንቶ ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር

**be wet** ራሰ ፤ በሰበሰ
His shirt was wet with perspiration. ሸሚዙ ፡ በላብ ፡ በሰብሶ ፡ (ርሶ) ፡ ነበር

**be wet with tears**
1. በእንባ ፡ ራሰ. Her cheeks were wet with tears. ጉንጮቿ ፡ በእንባ ፡ ርሰው ፡ ነበር
2. እንባ ፡ አዘለ. His eyes were wet with tears. ዓይኖቹ ፡ እንባ ፡ አዝለዋል

**get wet**
1. በሰበሰ. I got wet through and through. ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ በሰብሻለሁ
2. ረጠበ. My clothes got wet from my sweat. ልብሴ ፡ በላብ ፡ ረጥቧል
[See also 'weather']

**wet nurse** አያጠባች ፡ የምታሳድግ ፡ ሞግዚት
The woman had to hire a wet nurse for her baby. ሴትዮዋ ፡ ልጇን ፡ አያጠባች ፡ የምታሳድግ ፡ ሞግዚት ፡ መቅጠር ፡ ነበረባት

**whack** አጮለ
He whacked his child for being impudent. ስለ ፡ ብልግናው ፡ ልጁን ፡ አጮለው

**whale** ዓሣ ፡ ነባሪ
The ocean is the habitat of the whale. ውቅያኖ ስ ፡ የዓሣ ፡ ነባሪ ፡ መኖሪያ ፡ ነው

**wharf** የወደብ ፡ መድረክ
The boxes were piled up on the wharf. ሣጥኖቹ ፡ የወደቡ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ተቆልለዋል

**what ?**
1. ምን. What would you like for supper? ለራት ፡ ምን ፡ ትፈልጋለህ ?
2. ምን ፡ ዓይነት. What's the color of the gloves? የእጅ ፡ ሹራቡ ፡ ቀለም ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ? What is that bird? ያቺ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ወፍ ፡ ናት ?
3. ምንድን. What is this tool for? የዚህ ፡ መሣሪ ያ ፡ አገልግሎት ፡ ምንድን ፡ ነው ?
4. ስንት. What time is it? ስንት ፡ ሰዓት ፡ ነው ? *Do you know what train we're supposed to take? በስንት ፡ ሰዓት ፡ ባቡር ፡ እንደምንሄድ ፡ ታ ውቃለህ ?

**what**
1. የ (with perfect); የም (with imperfect). That's just what I wanted to avoid. ልክ ፡ ይህን ን ፡ ነው ፡ እንዲደርስ ፡ ያልፈለግሁት
Give me what books you have on the subject! ስለ ፡ አርእስቱ ፡ ነገሩ ፡ ያለህን ፡ መጽሐፍ ፡ ስጠኝ
What little he said was full of wisdom. የተናገረ ው ፡ ትንሹ ፡ ነገር ፡ በጥበብ ፡ የተሞላ ፡ ነበር
What he says is not important. የሚለው ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ አይደለም
Borrow what books you need! የምትፈልገውን ፡ መጽሐፍ ፡ ያህል ፡ ተዋስ
Give me what paper you don't need! የማትፈልገ ውን ፡ ወረቀት ፡ ሁሉ ፡ ስጠኝ
2. ምን ፡ እንደም + (imperfect). I haven't the slightest idea what he wants. ምን ፡ እንደሚፈል ግ ፡ በፍጹም ፡ ለማወቅ ፡ አልቻልኩም
3. ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደም + (imperfect). I know what cookies you like. ምን ፡ ዓይነት ፡ ብስኩቶ ች ፡ እንደምትወድ ፡ አውቃለሁ

**what!**
1. እንዴ. What! You are late again? እንዴ ፤ አ ሁንም ፡ ዘገየህ ?
2. ምንኛ. What a pity! ምንኛ ፡ ያሳዝናል! What few friends I have! ምንኛ ፡ ጥቂት ፡ ጓደኞች ፡ አሉኝ

3. እንዴት + (relative imperfect). What a strange coincidence! እንዴት ፡ የሚያስገርም ፡ አጋጣሚ ፡ ነው !
What beautiful flowers you have in your garden! ባትክልት ፡ ቦታህ ፡ እንዴት ፡ የሚያምሩ ፡ አበቦች ፡ አሉህ !

**what about?**
1. - ስ. What about your date? ቀጠሮህስ ?
2. ከምን ፡ ደረሰ. What about that job you applied for? የጠየቅኸው ፡ ሥራ ፡ ከምን ፡ ደረሰ ?

**what ever? ምን**
What ever happened to her? I haven't seen her for years. ምን ፡ አገኛት ? ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ አላየኋትም

**what for? ለምን**
What is this thing used for? ይህ ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ ያገለግላል ?
*What did you say that for? እሱን ፡ ያልክበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድነው ?

**what if ብ** + imperfect + ስ
What if your friends don't get here at all? ጓደኞችህ ፡ እዚህ ፡ ሳይመጡ ፡ ቢቀሩስ ?
What if it rains when we're on the picnic? በሽርሽር ፡ ላይ ፡ ሆነን ፡ ቢዘንብስ ?

**what is it like? እንዴት ፡ ነው**
What is the weather like this morning? ዛሬ ፡ ጧት ፡ ያየሩ ፡ ጠባይ ፡ እንዴት ፡ ነው ?

**what's more ከዚህም ፡ በላይ ። ከዚህም ፡ ሌላ**
(And) what's more, he is very efficient. ከዚህም ፡ በላይ ፡ በጣም ፡ ቀልጣፋ ፡ ነው
What's more, I don't believe him. ከዚህም ፡ ሌላ ፡ እርሱን ፡ አላምነውም

**what of it? ታዲያ ፡ ምን ፡ ይደረጋል ?**
He didn't get there in time, but what of it? በጊዜው ፡ አልደረሰም ። ታዲያ ፡ ምን ፡ ይደረጋል ?

**what then? ታዲያ ፡ ምን ፡ ይደረግ ?**
If he doesn't come, what then? ካልመጣ ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ ይደረግ ?

**what with**
*What with songs and games, the hours flew by. ስንዘፍንና ፡ ስንጫወት ፡ ሰዓቱ ፡ ቶሎ ፡ አለፈ

**what with all ይህ ፡ ሁሉ**
What with all I have to do, I can't be bothered with such silly things. ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ እያለብኝ ፡ እንደዚህ ፡ ባለው ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ለመቸገር ፡ አልፈልግም

**and what have you የመሳሰሉ**
He likes magazines, books, and what have you. መጽሔቶች ፡ መጻሕፍትና ፡ የመሳሰሉትን ፡ ይወዳል

**and what not ሌላም ፡ ነገር**
I have underwear and dresses and what not in that closet. ሣጥኑ ፡ ውስጥ ፡ የውስጥ ፡ ልብስ ። ቀሚስና ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ አለኝ
[See also 'degree, else, extent']

## whatever? ምንድን
Whatever made you do that? ይህን ፡ እንድታደርግ ፡ ያስገደደህ ፡ ምንድን ፡ ነው ?

**whatever** (pron., adj.)
1. ምንም. I have no money whatever. ምንም ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም
There can be no doubt whatever about it. ስለሱ ፡ ምንም ፡ ጥርጣሬ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም
2. ማንኛውም. Whatever nonsense the newspaper prints, he believes. ጋዜጣው ፡ ላይ ፡ የሚጻፈውን ፡ ማንኛውንም ፡ የማይረባ ፡ ነገር ፡ ያምናል
3. ምንም ፡ ነገር. Whatever you do, don't hurry! ምንም ፡ ነገር ፡ ስትሠራ ፡ አትቸኩል
4. የ + (verb). Do whatever you want. የፈለግኸውን ፡ ሥራ
5. እንደ + (verb). How much do I owe you? Whatever you say. እኔ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ አለህ ? አንተ ፡ እንዳልከ
6. (by repetition of the verb). Whatever others may say, you are right. ሌሎች ፡ ያሉትን ፡ ቢሉ ፡ አንተ ፡ ልክ ፡ ነህ
Whatever he does, is all right with me. የሚሠራውን ፡ ቢሠራ ፡ በኔ ፡ በኩል ፡ ግድ ፡ የለኝም

**whatever happens የሆነ ፡ ቢሆን**
Keep calm whatever happens. የሆነ ፡ ቢሆን ፡ ረጋ ፡ በል

**any person whatever ማንም ፡ ሰው**
Any person whatever can tell you the way. ማንም ፡ ሰው ፡ መንገዱን ፡ ሊነግርህ ፡ ይችላል

## what's-his-name ማነው ፡ ስሙ
Old what's-his-name was looking for you. ሽማግሌው ፡ ማነው ፡ ስሙ ፡ ይፈልግህ ፡ ነበር

## whatsoever, no ~ ምንም + negative verb
I have no money whatsoever. ምንም ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም
I have no doubt whatsoever. ምንም ፡ ጥርጣሬ ፡ የለኝም

## wheat ስንዴ
The wheat is ripe. ስንዴው ፡ ደርሷል

## wheedle ተለማመጠ
The children wheedled their mother into letting them go to the picnic. ሽርሽር ፡ ለመሄ

ድ ፡ እንድትፈቅድላቸው ፡ ልጆቹ ፡ እናታቸውን ፡ ተለማመጡ

**wheel** (vt.) አሽከረከረ
The boy wheeled a cart. ልጁ ፡ ጋሪውን ፡ አሽከረከረ

**wheel** (vi.) ፊቱን ፡ አዞረ
The man wheeled to face me. ሰውዬው ፡ ሊያየኝ ፡ ፊቱን ፡ አዞረ

**wheel about** አዞረ
The rider wheeled his horse about. ጋላቢው ፡ ፈረሱን ፡ አዞረ

**wheel** (n.)
1. ጎማ ፤ መንኰራኵር. The wheels of the overturned car were sticking up in the air. የተገለበጠው ፡ መኪና ፡ ጎማዎች ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተሰቅለው ፡ ነበር
Many trucks have six wheels. ብዙ ፡ የጭነት ፡ መኪናዎች ፡ ስድስት ፡ መንኰራኵር ፡ አሉዋቸው
2. መሪ. She sat at the wheel waiting for him to get in the car. መሪው ፡ ዘንድ ፡ ተቀምጣ ፡ እሱ ፡ መኪናው ፡ ውስጥ ፡ እስኪገባ ፡ ጠበቀች

**wheelbarrow** ኩርኩር
The wheelbarrow was full of wet cement. ኩርኩሩ ፡ በቦካ ፡ ሲሚንቶ ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር

**wheelchair** ተሽከርካሪ ፡ ወንበር
Since the car accident, he has to move about in a wheelchair. የመኪና ፡ አደጋ ፡ ከደረሰበት ፡ ወዲህ ፡ በተሽከርካሪ ፡ ወንበር ፡ መሄድ ፡ ግድ ፡ ሆነበት

**wheeze** አቃተተ
The old man wheezed and coughed. ሽማግሌው ፡ እያቃተተ ፡ ሳለ

**whelp**
1. ቡችላ. The whelps were crying for the bitch. ቡችሎቹ ፡ ለእናታቸው ፡ ይጮኹ ፡ ነበር
2. ግልገል. The coat was made of the hide of wolf whelps. ኮቱ ፡ የተሠራው ፡ ከተኩላ ፡ ግልገሎች ፡ ቆዳ ፡ ነበር

**when ?** መቼ
When can I see you again? ዳግመኛ ፡ መቼ ፡ አገኝሃለሁ ?

**when**
1. ከ + (perfect). How can we finish when you don't help. አንተ ፡ ካልረዳኸን ፡ እንዴት ፡ ልንጨርስ ፡ እንችላለን ?
2. ስ + (imperfect). The rooster crowed when the sun rose. ፀሐይዋ ፡ ስትወጣ ፡ አውራ ፡ ዶሮው ፡ ጮኸ
You'd scarcely gone when he came. እሱ ፡ ሲመጣ ፡ ገና ፡ እግርህ ፡ መውጣቱ ፡ ነበር
How can I help them when they won't listen to me? አንሰማህም ፡ ሲሉኝ ፡ እንዴት ፡ ልረዳቸው ፡ እችላለሁ?
3. ብ + imperfect + ም. We have only three books when we need five. አምስት ፡ መጽሐፍ ፡ ቢያስፈልጉንም ፡ ያሉን ፡ ሦስት ፡ ብቻ ፡ ናቸው
4. ምን ፡ ጊዜ ፡ እንደ + (relative imperfect). They told us when to eat. ምን ፡ ጊዜ ፡ እንደምንበላ ፡ ነገሩን
*There are times when I enjoy being alone. ብቻዬን ፡ መሆን ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ፡ ጊዜ ፡ አለ
*Sunday is the day when I can sleep late. እሑድ ፡ አርፍጄ ፡ ልተኛ ፡ የምችልበት ፡ ቀን ፡ ነው

**since when ?** ከመቼ ፡ ጀምሮ
Since when has he been missing? የጠፋው ፡ ከመቼ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ?

**till when ?** እስከመቼ
Till when can you stay? እስከመቼ ፡ ልትቆይ ፡ ትችላለህ ?

**whence, from ~ ?** ከየት
Do you know from whence she came? ከየት ፡ እንደመጣች ፡ ታውቃለህ ?
*Let him return to the country from whence he came. ወደ ፡ መጣበት ፡ አገር ፡ ይመለስ

**whenever ?** ምን ፡ ጊዜ
Whenever did he find time to write? ለመጻፍ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ አገኘ ?

**whenever** በ + perfect + ቁጥር ፡ (ጊዜ)
Come to see us whenever you have time. ጊዜ ፡ ባገኘህ ፡ ቁጥር ፡ ጠይቀን
I'll discuss it with you whenever you come. በመጣህ ፡ ጊዜ ፡ እንነጋገርበታለን

**where ?**
1. የት. Where are you going? የት ፡ ትሄዳለህ ?
Where is the nearest hotel? ቀረብ ፡ ያለው ፡ ሆቴል ፡ የት ፡ ነው ?
2. ወዴት. Where did he go next? ቀጥሎ ፡ ወዴት ፡ ሄደ ?
3. ከዬት. Where did you get the story? ወሬውን ፡ ከዬት ፡ አገኘኸው ?
*Where is he at fault? ጥፋቱ ፡ ከምን ፡ ላይ ፡ ነው ?

**where** (relative verb) + በት
She wants to live in a country where it never snows. በረዶ ፡ ፍጹም ፡ በማይጥልበት ፡ ሀገር ፡ ለመኖር ፡ ትፈልጋለች
This is the house where I used to live. እኖርበት ፡ የነበረው ፡ ቤት ፡ ይህ ፡ ነው

They will be sent where they are needed most. በጣም ፡ ወደሚፈለጉበት ፡ ቦታ ፡ ይላካሉ
Where there is no rain, farming is difficult. ዝናብ ፡ በሌለበት ፡ ሀገር ፡ ግብርና ፡ በጣም ፡ ያዳግታል
I will go where you go. እሄድክበት ፡ እሄዳለሁ

**where ... from ? ከዬት**
Where does this chair come from? ይህ ፡ ወንበር ፡ ከየት ፡ መጣ ?
*Where does your friend come from? ጓደኛህ ፡ የየት ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ነው ?
[See also 'else']

**whereabouts**
1. የት. Whereabouts are we? የት ፡ ነን ?
2. የት ፡ እንዳለ. Can you tell me his whereabouts? የት ፡ እንዳለ ፡ ልትነግረኝ ፡ ትችላለህ ?

**whereas**
*He is fat, whereas she is thin. እሱ ፡ ወፍራም ፡ ሲሆን ፡ እሷ ፡ ግን ፡ ቀጭን ፡ ናት

**whereby** (relative verb) + በት
He devised a plan whereby he might escape. ሊያመልጥ ፡ የሚችልበትን ፡ ዘዴ ፡ ፈጠረ

**wherefore ? ለምን**
Wherefore did you leave? ለምን ፡ ሄድክ ?

**wherein ? የት ፡ ላይ**
Wherein am I mistaken? ስሕተቴ ፡ የት ፡ ላይ ፡ ነው ?

**wherein** (relative verb) + በት
The book wherein he read the story belongs to me. ታሪኩን ፡ ያነበበበት ፡ መጽሐፍ ፡ የኔ ፡ ነው

**whereof**
*These are the things whereof I spoke. ያልኩህ ፡ ነገሮች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው

**whereon** (relative verb) + በት
The rock whereon he stood is not far from here. የቆመበት ፡ አለት ፡ ከዚህ ፡ ሩቅ ፡ አይደለም

**whereupon ? በምን ፡ ላይ**
Whereupon does he base his argument? ክርክሩን ፡ የመሠረተው ፡ በምን ፡ ላይ ፡ ነው ?

**whereupon በዚያን ፡ ጊዜም**
He ended his speech, whereupon everyone applauded. ንግግሩን ፡ ጨረሰ ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አጨበጨበ

**wherever የትም ፡ ብ** + imperfect
Wherever you are, don't forget to write me! የትም ፡ ብትሆን ፡ ለኔ ፡ ደብዳቤ ፡ መጻፍ ፡ አትርሳ
Wherever you go in this part of the country, you'll find good roads. በዚህ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ የትም ፡ ብትሄድ ፡ ጥሩ ፡ መንገድ ፡ ታገኛለህ
*His eyes traveled after her wherever she went. በሄደችበት ፡ ሁሉ ፡ ዓይኑ ፡ ይከተላታል

**whet** (whetted) ሳለ
The farmer whets his ax before chopping wood. ዕንጨት ፡ ከመቍረጡ ፡ በፊት ፡ ገበሬው ፡ መጥረቢያውን ፡ ይስላል

**whet (one's) appetite ወስፋቱን ፡ ከፈተ(ለት)**
Exercise whets his appetite. ጅምናስቲክ ፡ ወስፋቱን ፡ ይከፍትለታል

**whether** (imperfect) + እንደሆነ
I don't know whether she will be able to come. እሷ ፡ መምጣት ፡ ትችል ፡ እንደሆን ፡ አላውቅም
I don't know whether we'll be on time for the bus. አውቶቡሱን ፡ ለማግኘት ፡ በጊዜ ፡ እንደርስ ፡ እንደሆነ ፡ አላውቅም
*Does it make a difference to you whether I come. ? ብመጣ ፡ ባልመጣ ፡ ላንተ ፡ ልዩነት ፡ ያመጣል ?
*I'd like to know whether he's coming. መምጣት ፡ መቅረቱን ፡ ለማወቅ ፡ እፈልጋለሁ

**whether ... or**
*I don't know whether to accept or refuse. እሺ ፡ ወይም ፡ እምቢ ፡ ማለት ፡ እንዳለብኝ ፡ አላውቅም
*The question was whether to take the children to the funeral or leave them at home. ጥያቄው ፡ ልጆቹን ፡ ወደ ፡ ሥርዓተ ፡ ቀብሩ ፡ ይዞ ፡ መሄድ ፡ ወይም ፡ መተው ፡ ነበር

**whether ... or not**
*The race is beginning whether you are ready or not. ብትዘጋጅም ፡ ባትዘጋጅም ፡ እሽቅድምድሙ ፡ ይጀመራል
*He doesn't know whether the people there were armed or not. እዚያ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ መያዝ ፡ አለመያዛቸውን ፡ አያውቅም ፡ ነበር

**whetstone መሳያ**
He sharpens his knife on a whetstone. ቢላዋውን ፡ በመሳያ ፡ ይስላል

**whey አጓት**
Children like to drink whey. ልጆች ፡ አጓት ፡ መጠጣት ፡ ይወዳሉ

**which ? የትኛው**
Which is taller, the table or the desk? ከጠረጴዛውና ፡ ከዴስኩ ፡ የትኛው ፡ ይረዝማል ?

Which foreign language have you studied? ያጠናኸው ፡ የትኛውን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ነው ?

**which**

1. የትኛው ፡ እንደ + (relative imperfect). I know which I like best. የትኛውን ፡ ይበልጥ ፡ እንደም ፈልግ ፡ እኔ ፡ አውቃለሁ

Here are three boxes. Choose which one you like best. ሦስት ፡ ሣጥኖች ፡ እዚህ ፡ አሉ ፤ የት ኛውን ፡ ይበልጥ ፡ እንደምትወድ ፡ ምረጥ

2. (relative verb). Where are the books which I brought? ያመጣኋቸው ፡ መጽሐፎች ፡ የት ፡ አሉ ?

The hat (which) I wanted is sold. የፈለግሁት ፡ ባርኔጣ ፡ ተሸጧል

Read the book which looks most interesting. የሚያስደስት ፡ መስሎ ፡ የሚታይህን ፡ መጽሐፍ ፡ አንብብ

**which is which**

*The twins are so much alike, I never know which is which. መንትዮቹ ፡ በጣም ፡ ስለሚ መሳሰሉ ፡ ልለያቸው ፡ ፍጹም ፡ አልችልም

**which one?** የትኛው

Which one is the right one? ትክክለኛው ፡ የት ኛው ፡ ነው ?

**which one of?** ማንኛ + suffix pronouns

Which one of you wants to go with me? ማንኛችሁ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ መሄድ ፡ ትፈልጋላችሁ ?

**which one of** የትኛው ፡ እንደ + relative imperfect

Tell me which one of them is better. የትኛው ፡ እንደሚሻል ፡ ንገረኝ

**at which time?** በስንት ፡ ሰዓት

At which time will he come? At two or at five? በስንት ፡ ሰዓት ፡ ነው ፡ የሚመጣው ? በስምንት ፡ ወይስ ፡ በዐሥራ ፡ አንድ ?

**at which time** ያኔ

Don't call until 2, at which time I will be sure to be there. እስከ ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ አ ትደውል ፤ ያኔ ፡ ግን ፡ እርግጠኛ ፡ እዚያ ፡ እገኛለሁ

[See also 'way']

**whichever**

1. (relative verb). Take whichever seat you want. እፈለግኸው ፡ መቀመጫ ፡ ላይ ፡ ተቀመጥ

2. የትኛው(ንም) ፡ ብ + (imperfect). Whichever you choose, I'll buy it. የትኛውንም ፡ ብትመር ጥ ፡ እገዛዋለሁ

*Choose whichever desk you like! ደስ ፡ ያለህ ን ፡ ጠረጴዛ ፡ ምረጥ

*It's all the same whichever day you come. በፈለግኸው ፡ ቀን ፡ ብትመጣ ፡ ያው ፡ ነው

**whichever of**

*Whichever of you comes in first wins the prize. ከመካከላችሁ ፡ መጀመሪያ ፡ የደረሰ ፡ ሽልማቱን ፡ ያገኛል

**from whichever direction** ከየትም ፡ በኩል

From whichever direction he comes, we'll be ready for him. ከየትም ፡ በኩል ፡ ቢመጣ ፡ ተዘጋጅተን ፡ እንጠብቀዋለን

**whiff** ብናኝ

A whiff of smoke blew in his face. የጢስ ፡ ብ ናኝ ፡ ፊቱ ፡ ላይ ፡ በነነ

**while** (v.), ~ **away** አሳለፈ

I am whiling away my time playing tennis. ጊዜዬን ፡ የማሳልፈው ፡ ቴኒስ ፡ በመጫወት ፡ ነው

**while** (conj.)

1. ስ + imperfect, or እለ. Jane was dressed in brown while Mary was dressed in blue. ጄን ፡ የለበሰችው ፡ ቡና ፡ ዓይነት ፡ ልብስ ፡ ሲሆ ን ፡ የሜሪ ፡ ግን ፡ ሰማያዊ ፡ ነበር

Some people live in luxury while others starve. አንዳንዶቹ ፡ በቅንጦት ፡ ሲኖሩ ፡ ሌሎቹ ፡ ይራባሉ

I want to come while the library is still open. ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ክፍቱን ፡ ሳለ ፡ ልመጣ ፡ እ ፈልጋለሁ

2. ብ + imperfect + ም. While I like the color of the hat, I do not like its shape. የባርኔጣውን ፡ ቀለም ፡ ብወድም ፡ ቅርጹን ፡ አልወደድኩትም

While she is not pretty, she has much charm. ቆንጆ ፡ ባትሆንም ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ አላት

3. በ + verb + ጊዜ. While I was speaking, he said nothing. እኔ ፡ በምናገርበት ፡ ጊዜ ፡ እ ሱ ፡ ምንም ፡ አልተናገረም

While in India he studied music. ሀንድ ፡ ሀገር ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ሙዚቃ ፡ አጠና

4. ግን. John is tall while his parents are short. ቶም ፡ ረጅም ፡ ነው ፤ ወላጆቹ ፡ ግን ፡ አጭሮች ፡ ናቸው

*I want to arrive while it's still light. ሳይጨል ም ፡ ልደርስ ፡ እፈልጋለሁ

**while** (n.)

**a little while** ትንሽ

Wait a little while! ትንሽ ፡ ቆይ

**a long while** ለረጅም ፡ ጊዜ ፤ ብዙ

He kept us waiting a long while. ለረጅም ፡ ጊ ዜ ፡ አስጠበቀን

I waited a long while for you. ብዙ ፡ ጠበቅሁህ

**a while** ትንሽ

You'll have to wait a while. ትንሽ ፡ መቆየት ፡ አለብህ

**a while ago** ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት
He left a while ago. ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ሄደ

**all this while** ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ
Where have you been all this while? ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ የት ፡ ነበርክ ?

**for a long while** ለብዙ ፡ ጊዜ
I haven't seen him for a long while. ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ አላየሁትም

**for a while**
1. **ለጊዜው**. We are short of funds and cannot buy anything for a while. ገንዘብ ፡ ስላጠረን ፡ ለጊዜው ፡ ምንም ፡ ልንገዛ ፡ አንችልም
2. **ለጥቂት ፡ ጊዜ**. He has to give up all physical activity for a while. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውንም ፡ አካላዊ ፡ እንቅስቃሴ ፡ መተው ፡ አለበት

**in a little while** ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ
I'll be back in a little while. ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ እመለሳለሁ

**(a) short while ago** ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት
He was here a short while ago. ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ እዚህ ፡ ነበረ

**worth (one's) while, make it ~**
1. **ዋጋውን ፡ በሚገባ ፡ ከፈለ ፤ ዋጋውን ፡ ከፈለ**. If you'll paint my house, I'll make it worth your while. ቤቴን ፡ ቀለም ፡ ብትቀባልኝ ፡ ዋጋህን ፡ በሚገባ ፡ እከፍልሃለሁ
He'll make it worth your while to wait. ብትቆይ ፡ ዋጋህን ፡ ይከፍልሃል
2. **ለድካሙ ፡ በሚገባ ፡ ከፈለው**. I will do it if he makes it worth my while. ለድካሜ ፡ በሚገባ ፡ ከከፈለኝ ፡ እሠራዋለሁ
[See also 'every, great, once']

**whim** ድንገት ፡ ደራሽ ፡ ፍላጎት
Her whim for African studies won't last long. ስለ ፡ አፍሪካ ፡ ለማጥናት ፡ ያላት ፡ ድንገት ፡ ደራሽ ፡ ፍላጎት ፡ ዘላቂ ፡ አይደለም

**on a whim** በድንገት ፡ ተነሣሥቶ
She went to Ethiopia on a whim. በድንገት ፡ ተነሣሥታ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሄደች

**whimper**
1. **ተነጫነጨ**. The little boy whimpered when he couldn't find his mother. ትንሹ ፡ ልጅ ፡ እናቱን ፡ ባጣ ፡ ጊዜ ፡ ተነጫነጨ
2. **አጕረመረመ**. The dog whimpered in fear of the fox. ውሻው ፡ ቀበሮውን ፡ በመፍራት ፡ አጕረመረመ

**whimsical** ጉደኛ
The English are rather whimsical at times. እንግሊዞች ፡ አንዳንዴ ፡ ጉደኞች ፡ ናቸው

**whimsy** ጉደኛነት
Lewis Carrol's whimsy is well known from his stories about Alice. የሉዊስ ፡ ካሮል ፡ ጉደኛነት ፡ ስለ ፡ አሊስ ፡ በጻፋቸው ፡ ተረቶች ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ነው

**whine** (v.)
1. **ተነጫነጨ**. The child was whining because his mother refused to give him candy. እናቱ ፡ ከረሜላ ፡ ስለከለከለችው ፡ ልጁ ፡ ይነጫነጭ ፡ ነበር
2. **አለቀሰ**. The dog whined outside the door. ውሻው ፡ ከመዝጊያው ፡ ውጭ ፡ ሆኖ ፡ አለቀሰ

**whine** (n.)
1. **ቀጭን ፡ ድምፅ**. The jet plane makes a high-pitched whine. ጄት ፡ አውሮፕላን ፡ ከፍተኛ ፡ የሆነ ፡ ቀጭን ፡ ድምፅ ፡ ያሰማል
2. **መነጫነጭ**. The child's whine annoyed me greatly. የልጁ ፡ መነጫነጭ ፡ በጣም ፡ አበሳጨኝ

**whip** (whipped), vt.
1. **ገረፈ**. He whipped the horse mercilessly. ፈረሱን ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ ገረፈው
2. **በኀይል ፡ አወዛወዘ**. The wind was whipping the branches of the trees. ነፋሱ ፡ የዛፎቹን ፡ ቅርንጫፎች ፡ በኀይል ፡ ያወዛውዝ ፡ ነበር
3. **መታ**. The cook whipped the eggs. ወጥ ፡ ቤቷ ፡ እንቁላሉን ፡ መታችው

**whip** (vi.) ተውለበለበ
The flag whipped in the breeze. ሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ ለዘብ ፡ ባለው ፡ ነፋስ ፡ ውስጥ ፡ ተውለበለበ

**whip off** በድንገት ፡ አነሣ
He whipped off his hat. ባርኔጣውን ፡ በድንገት ፡ አነሣ

**whip up**
1. **ፈጠረ**. He tried to whip up enthusiasm for his plan. ስለ ፡ እቅዱ ፡ መሳካት ፡ የጋለ ፡ ስሜት ፡ ለመፍጠር ፡ ፈለገ
2. **አነሣሣ**. The speaker whipped up the crowd. ተናጋሪው ፡ ሕዝቡን ፡ አነሣሣው

**whip** (n.) ጅራፍ
The whip is made of leather. ጅራፉ ፡ የተሠራው ፡ ከቆዳ ፡ ነው

**whipping, give a ~** ገረፈ
The mother gave the child a whipping. እናቲቱ ፡ ልጁን ፡ ገረፈችው

**whirl**
1. **ተሽከረከረ**. The world whirls on its axis. ዓለም ፡ በዘንጓ ፡ ላይ ፡ ትሽከረከራለች

The dancers whirled around the room. ዳናሾቹ ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተሽከረከሩ
2. (= active) አሽከረከረ. +The leaves whirled in the wind. ነፋሱ ፡ ቅጠሉን ፡ አሽከረከረው
3. (= active) አዞረ. +My head is whirling. ራሴን ፡ ያዞረኛል

**whirl about** (vt.) እያሽከረከረ ፡ ወሰደ
The wind whirled the dead leaves about. ነፋሱ ፡ የረገፉትን ፡ ቅጠሎች ፡ እያሽከረከረ ፡ ወሰዳቸው

**whirl about** (vi.)
*He whirled about and faced me. በፍጥነት ፡ ወደኔ ፡ ዞረ

**whirl around** ተሽከረከረ
He whirled around like a top. እንደ ፡ እንዝርት ፡ ተሽከረከረ

**whirl around to face one** በፍጥነት ፡ ወደሱ ፡ ዞረ
He whirled around to face me when I came in. እቤት ፡ ውስጥ ፡ ስገባ ፡ በፍጥነት ፡ ወደኔ ፡ ዞረ

**whirlpool** አዙሪት
The swimmer was caught in a whirlpool. ዋናተኛው ፡ ባዙሪት ፡ ተያዘ

**whirlwind** ዐውሎ ፡ ነፋስ
The whirlwind destroyed the village. ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ መንደሩን ፡ አፈረሰው

**whisk** (vt.)
1. በፍጥነት ፡ አነሣ. The servants whisked the dirty dishes from the table. የተበላባቸውን ፡ ሳሕኖች ፡ አሽከሮቹ ፡ በፍጥነት ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ አነሡ
2. ጠራረገ. She whisked the crumbs from the table. ፍርፋሪውን ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ጠራረገች

**whisk** (vi.) ጥልቅ ፡ አለ
The mouse whisked into its hole. አይጧ ፡ ጉድጓዷ ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ አለች

**whisk away** አባረረ
The horse whisked the flies away with its tail. ፈረሱ ፡ ዝንቦቹን ፡ በጭራው ፡ አባረረ

**whisk off** አጣድፎ ፡ ወሰደ
The police whisked him off to jail. ፖሊሶቹ ፡ አጣድፈው ፡ ወደ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ወሰዱት

**whisk** (n.) ብሩሽ
We brushed our coats with a whisk. ኮታችንን ፡ በብሩሽ ፡ ጠረግን
[See also 'fly whisk']

**whisker(s)** ሪዝ
The cat's whisker was pulled out. የድመቷ ፡ ሪዝ ፡ ተነቀለ
He has black whiskers. ጥቁር ፡ ሪዝ ፡ አለው

**whisper** (v.)
1. ሹክ ፡ አለ ፤ አንሾካሾከ. She whispered it in my ear. በጆሮዬ ፡ ሹክ ፡ አለችኝ
You may whisper in the library, but do not talk out loud. ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ውስጥ ፡ ልታንሾካሹኩ ፡ ትችላላችሁ ፡ ግን ፡ ድምፃችሁን ፡ ከፍ ፡ አድርጋችሁ ፡ አትነጋገሩ
2. አፏጨ. The wind whispers in the trees. ነፋሱ ፡ በዛፎቹ ፡ መሀከል ፡ ያፏጫል
3. (= active) አንኰሻኰሸ. +The leaves whispered in the wind. ነፋሱ ፡ ቅጠሎቹን ፡ አንኰሻኰሻቸው

**it is whispered** ጭምጭምታ ፡ ነፈሰ
It is whispered that his business is failing. ንግዱ ፡ እየወደቀ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ጭምጭምታ ፡ ይነፍሳል

**whisper** (n.) ሹክሹክታ
A whisper ran through the crowd. በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ሹክሹክታ ፡ ተሰፋፋ
We spoke in whispers because it was late. ውድቅት ፡ ስለነበረ ፡ በሹክሹክታ ፡ ተነጋገርን

**whistle** (v.)
1. አፏጨ. Who's whistling outside? ከውጭ ፡ የሚያፏጨው ፡ ማነው ?
We could hear the bullets whistling past us. ጥይቶቹ ፡ እያፏጩ ፡ ባጠገባችን ፡ ሲያልፉ ፡ እንሰማ ፡ ነበር
2. ፊሽካ ፡ ነፋ. The policeman whistled us to stop. ፖሊሱ ፡ እንድንቆም ፡ ፊሽካ ፡ ነፋ

**whistle** (n.)
1. ፊሽካ. He signaled to us with his whistle. በፊሽካው ፡ ምልክት ፡ ሰጠን
2. ድምፅ. We heard the whistle of a steam engine. የከሰል ፡ ባቡር ፡ ድምፅ ፡ ሰማን

**whit** ቅንጣት
There was not one whit of truth in his statement. በንግግሩ ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ ቅንጣት ፡ እንኳ ፡ እውነት ፡ አልነበረበትም

**white** (n.) ነጭ ፡ ክፍል
The white of the eyes becomes yellow when one has jaundice. አንድ ፡ ሰው ፡ የወፍ ፡ በሽታ ፡ ሲይዘው ፡ የዓይኑ ፡ ነጭ ፡ ክፍል ፡ ቢጫ ፡ ይሆናል

**white of egg** ዞፍ
The white of the egg is used to make glue. ዞፍ ፡ ሙጫ ፡ ለመሥራት ፡ ያገለግላል

**be dressed in white**
He is dressed in white. ነጭ ፡ በነጭ ፡ ለብሶ ፡ ነበር

**wear white** ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለበሰ
The bride wore white. ሙሽራይቱ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሳለች

**white** (adj.) ነጭ
She wore a white dress. ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሳለች

**white hair** የሸበተ ፡ ጸጉር
Grandmother has white hair. ሴት ፡ አያታችን ፡ የሸበተ ፡ ጸጉር ፡ አላት

**white man** ነጭ
The white man settled in South Africa in 1690. በ፲፮፻፹፪ ዓ. ም. ነጮች ፡ ደቡብ ፡ አፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ ሰፈሩ

**white people** ፈረንጆች
There are many white people in Ethiopia. ብዙ ፡ ፈረንጆች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አሉ

**be white** ነጣ
Since the clothes were thoroughly washed, they were white. ልብሱ ፡ በደንብ ፡ ስለታጠበ ፡ ነጣ

**go white** ገረጣ
Her face went white. ፊቷ ፡ ገረጣ

**turn white**
1. ሸበተ. His hair turned white. ጸጉሩ ፡ ሸበተ
2. ወደ ፡ ነጭነት ፡ ተለወጠ. The green cloth turned white from the sunlight. ከፀሐዩ ፡ ብርሃን ፡ የተነሣ ፡ አረንጓዴው ፡ ልብስ ፡ ወደ ፡ ነጭነት ፡ ተለወጠ

**white-collar employee** የቢሮ ፡ ሠራተኛ
White-collar employees get paid more than laborers. የቢሮ ፡ ሠራተኞች ፡ ከቀን ፡ ሠራተኞች ፡ የበለጠ ፡ ይከፈላቸዋል

**whiten** (vt.) አነጣ
Water from the faucet whitens clothes. የቧንቧ ፡ ውኃ ፡ ልብስ ፡ ያነጣል

**whiten** (vi.) ነጣ
Animal bones were whitening in the sun. ከፀሐይ ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ የእንስሳቱ ፡ አጥንቶች ፡ ነጥተዋል

**whiteness** ንጣት
Her black hair accentuated the whiteness of her skin. ጥቁር ፡ ጸጉሯ ፡ የቆዳዋን ፡ ንጣት ፡ አጐላው

**white paper** አቋሙን ፡ የሚገልጽ ፡ መግለጫ
The government issued a white paper on the border problem. ስለ ፡ ድንበሩ ፡ ችግር ፡ መንግሥቱ ፡ አቋሙን ፡ የሚገልጽ ፡ መግለጫ ፡ አወጣ

**whitewash** (v.)
1. ኖራ ፡ ቀባ. How long will it take you to whitewash the garage? ጋራዡን ፡ ኖራ ፡ ለመቀባት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይፈጅብሃል ?
2. ተግባር ፡ ሸፋፈነ. The commission tried to whitewash the corrupt judge. ኮሚሲዮኑ ፡ የብልሹውን ፡ ዳኛ ፡ ተግባር ፡ ለመሸፋፈን ፡ ሞከረ

**whitewash** (n.) ኖራ
The whitewash is peeling off the walls. ኖራው ፡ ከግድግዳው ፡ ላይ ፡ መቀረፍ ፡ ጀምሯል

**whither** ወዴት
Whither are you going? ወዴት ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ነህ ?

**whittle** በቢላዋ ፡ ፋቀ
The boy was whittling on a stick. ልጁ ፡ ዱላ ፡ በቢላዋ ፡ ይፍቅ ፡ ነበር

**whittle down** ቀነጣጠበ
They are trying to whittle down our salaries. ደሞዛችንን ፡ ለመቀነጣጠብ ፡ ይሞክራሉ

**whiz** (whizzed), ~ **by** ሽው ፡ ብሎ ፡ አለፈ
The car whizzed by in a cloud of dust. መኪናው ፡ በአቧራው ፡ ውስጥ ፡ ሽው ፡ ብሎ ፡ አለፈ

**who ?** ማን (sg.); እነማን (pl.) ፤ ማን ፡ ማን
The president is coming. Who? ፕሬዚዳንቱ ፡ እየመጡ ፡ ናቸው ፤ ማን ?
Who was the first man to settle in this wilderness? በዚህ ፡ ጠፍ ፡ በረኻ ፡ መጀመሪያ ፡ ማን ፡ ማን ፡ ሰፈረ ?
Who are those men? እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ እነማን ፡ ናቸው ?
I don't know who he is. ማን ፡ እንደሆነ ፡ አላውቅም

**who** (relative) የ + perfect; የም + imperfect
This is the man who rode with me. ይህ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ የተጓዘው ፡ ሰውዬ ፡ ነው
We saw the men who were working in the fields. እርሻው ፡ መካከል ፡ ይሠሩ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ አየን
Who is not for us is against us. እኛን ፡ የማይደግፍ ፡ ተቃዋሚያችን ፡ ነው

**whoever ?** ማን + gerundive + ያውቃል
Whoever heard of such a thing? እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ማን ፡ ሰምቶ ፡ ያውቃል ?

**whoever**
1. የ + (perfect). Whoever wants it may have it. የፈለገ ፡ ሊወስደው ፡ ይችላል
2. የ + perfect + ማንም ፡ ሰው ፡ ይሁን. Whoever told you that is lying. የነገረህ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ይሁን ፡ ውሸቱን ፡ ነው
3. የም + imperfect + ማንኛውም ፡ ሰው. Whoever wants the pencil may have it. እርሳሱን ፡ የሚፈልግ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሊወስድ ፡ ይችላል

**whoever it may be** ማንም ፡ ቢሆን
Don't open the door, whoever it may be. ማንም ፡ ቢሆን ፡ በሩን ፡ እንዳትከፍት

**whole** (n.)
1. ሙሉ. Three thirds make a whole. ሦስት ፡ ሢሶ ፡ አንድ ፡ ሙሉ ፡ ይሆናል
2. ሙሉ ፡ አገር. The fifty separate states form a whole. አምሳዎቹ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ግዛቶች ፡ አንድ ፡ ሙሉ ፡ አገር ፡ ይሆናሉ

**whole** (adj.)
1. ሙሉ. I waited for a whole hour. አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ጠበቅሁ
I intend to stay a whole week. አንድ ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ ለመቆየት ፡ አስቤያለሁ
2. (= adv.) በሙሉ. Can you eat a whole fish? አንድ ፡ ዓሣ ፡ በሙሉ ፡ ለመብላት ፡ ትችላለህ ?
I didn't see him the whole evening. ምሽቱን ፡ በሙሉ ፡ አላየሁትም
The whole village came to receive him. መንደሩ ፡ በሙሉ ፡ እሱን ፡ ለመቀበል ፡ መጣ
3. ደኅና. There isn't a whole plate in the house. ደኅና ፡ ሳሕን ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ አይገኝም
4. (= adv.) እንዳለ. Put whole carrots in the stew! ካሮቱን ፡ እንዳለ ፡ ወጡ ፡ ውስጥ ፡ ጨምሬው
5. (= adv.) እንዳለ ፡ ባንዴ. Snakes swallow their prey whole. እባብ ፡ የያዘውን ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ባንዴ ፡ ይውጣል
*Not one dish was left whole when the shelf broke. መደርደሪያው ፡ በተሰበረ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሳሕን ፡ እንኳን ፡ አልቀረም

**be whole** አልተሰበረም
The cup fell, but it's still whole. ሲኒው ፡ ቢወድቅም ፡ አልተሰበረም

**on the whole** በጠቅላላው
On the whole, I agree with you. በጠቅላላው ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ እስማማለሁ

**taken as a whole** በጠቅላላው ፡ ሲታይ
Taken as a whole, the problem is unsolvable. በጠቅላላው ፡ ሲታይ ፡ ለነገሩ ፡ መፍትሔ ፡ ማግኘት ፡ አይቻልም

**the whole of** በሙሉ
The whole of my money was stolen. ገንዘቤ ፡ በሙሉ ፡ ተሰረቀብኝ
[See also 'lot']

**wholehearted** ከልብ ፡ የመነጨ
The soldiers were given a wholehearted welcome. ወታደሮቹ ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ አቀባበል ፡ ተደረገላቸው

**wholeheartedly** በሙሉ ፡ ልብ
He did it wholeheartedly. በሙሉ ፡ ልብ ፡ ሠራው

**wholesale** (adj.)
1. በጅምላ ፡ የሚሸጡበት. He has a good position with a wholesale house. በጅምላ ፡ የሚሸጡበት ፡ መደብር ፡ ጥሩ ፡ ሥራ ፡ አለው
2. (= adv.) በጅምላ. What's the wholesale price? ዋጋው ፡ በጅምላ ፡ ስንት ፡ ነው ?
3. እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ. Wholesale destruction was caused by the fire bombs. የእሳት ፡ ቦምቡ ፡ ፈንድቶ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ አደረሰ

**wholesale** (adv.) በጅምላ
They sell only wholesale. የሚሸጡት ፡ በጅምላ ፡ ብቻ ፡ ነው

**wholesome**
1. ለጤና ፡ የሚስማማ. This region has a wholesome climate. ይህ ፡ ቀበሌ ፡ ለጤና ፡ የሚስማማ ፡ ያየር ፡ ንብረት ፡ አለው
2. ግብረ ፡ ገብነት ፡ ያልጐደለው. She reads only wholesome books. ግብረ ፡ ገብነት ፡ ያልጐደላቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ብቻ ፡ ታነባለች
*She has a wholesome face. መልኳ ፡ ጤናዋ ፡ የተሟላ ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል

**be wholesome** ለሰውነት ፡ ጥሩ ፡ ነው
This food is wholesome, so eat it! ይህ ፡ ምግብ ፡ ለሰውነት ፡ ጥሩ ፡ ስለሆነ ፡ ብላ

**wholly**
1. ሙሉ ፡ በሙሉ. I wholly agree with you. ካንተ ፡ ጋር ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ እስማማለሁ
2. እስከነአካቴው. Few men are wholly bad. እስከነአካቴው ፡ መጥፎ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ጥቂት ፡ ናቸው

**whom ?** ማንን
Whom do you want? ማንን ፡ ትፈልጋለህ ?

**whom,** expressed by a relative clause
The man whom you see there is my teacher. ያ ፡ የምታየው ፡ ሰውዬ ፡ መምህሬ ፡ ነው

**to whom ?** ለማን
To whom did you give it? ለማን ፡ ሰጠኸው ?

**to whom,** expressed by a relative clause
The boy to whom I spoke is my cousin. ያነጋገርኩት ፡ ልጅ ፡ የአጐቴ ፡ (የአክስቴ) ፡ ልጅ ፡ ነው

**whoop** ጩኸት
When he sighted land, the sailor let out a whoop of joy. የብስ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ መርከበኛው ፡ የደስታ ፡ ጩኸት ፡ ለቀቀ

**whooping cough** ትክትክ
Children have whooping cough quite often. ልጆች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ትክትክ ፡ ይይዛቸዋል

**whore** ሴተኛ ፡ አዳሪ
It is forbidden for whores to be near schools. ሴተኛ ፡ አዳሪዎች ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ አካባቢ ፡ እንዳይገኙ ፡ ተከልክለዋል

**whose ?** የማን
Whose watch is this? ይህ ፡ የማን ፡ ሰዓት ፡ ነው ?
Tell me whose is best. የማን ፡ እንደሚበልጥ ፡ ንገረኝ

**whose** (relative clause)
The house whose windows are broken is for sale. መስኮቱ ፡ የተሰበረው ፡ ቤት ፡ የሚሸጥ ፡ ነው

**whosoever,** expressed by a relative clause
Whosoever seeks shall find. የሚፈልግ ፡ ያገኛል

**why ?**
1. ለምን. You said I should do it. Why? መሥራት ፡ አለብህ ፡ ትለኛለህ ፤ ለምን ?
Why was he late? ለምን ፡ ዘገየ ?
2. ለምን ፡ እንደ + (verb). Do you know why he was late? ለምን ፡ እንደዘገየ ፡ ታውቃለህ ?
There are good reasons why he left. ለምን ፡ እንደሄደ ፡ ጥሩ ፡ ምክንያት ፡ አለው
The reason why he did it is not known. ለምን ፡ ይህን ፡ እንዳደረገ ፡ ምክንያቱ ፡ አልታወቀም

**why !** እንዴ
Why, it's quite easy! እንዴ! ይህማ ፡ ቀላል ፡ ነው

**why not ?**
Why not go tomorrow ? ምን ፡ አለበት ፤ ነገ ፡ ብንሄድ ?

**why ! why !** ኧረግ
Why! Why! The cage is empty! ኧረግ! ወጥመዱ ፡ ባዶ ፡ ነው

**that's why** ስለዚህ
That's why I didn't call you. ስለዚህ ፡ ነው ፡ ያልጠራሁህ

**wick** ክር
Turn up the wick of the oil lamp! የፋኖሱን ፡ ክር ፡ ወጣ ፡ አድርገው
Don't pull the wick from the candle! የሻማውን ፡ ክር ፡ አትምዘዘው

**wicked**
1. ክፉ. He is a wicked man. እሱ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ነው
A wicked blow on the head rendered him unconscious. ራሱ ፡ ላይ ፡ የተመታው ፡ ክፉ ፡ ምት ፡ሕይወቱን ፡ አሳተው
2. ግፍ. Tormenting that poor cat is wicked. ያቺን ፡ ምስኪን ፡ ድመት ፡ ማሠቃየት ፡ ግፍ ፡ ነው
3. የጭካኔ. The wicked deeds of Herod are still remembered. የሄሮድስ ፡ የጭካኔ ፡ ተግባሮች ፡ አሁንም ፡ ይታወሳሉ
4. እርጉም. The wicked witch gave the child a baleful glance. እርጉሟ ፡ አስማተኛ ፡ ልጁን ፡ በክፉ ፡ ዓይን ፡ ተመለከተችው

**wickedness** ክፋት
His wickedness brought the condemnation of the world upon him. ክፋቱ ፡ የመላውን ፡ ዓለም ፡ ውግዘት ፡ አወረደበት

**wicker** ቀርቀሀ
The basket for storing corn is made of wicker. የበቆሎ ፡ ማከማቻው ፡ ቅርጫት ፡ የተሠራው ፡ ከቀርቀሀ ፡ ነው

**wickerwork** ስፌት
She is skilled in wickerwork. በስፌት ፡ የታወቀች ፡ ናት

**wide**
1. ሰፊ. This road is very wide. ይህ ፡ መንገድ ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ ነው
A trip around the world gives wide experience. ዓለምን ፡ መዞር ፡ ሰፊ ፡ ዕውቀት ፡ ይሰጣል
2. (= noun) ስፋት. The window is five feet wide. የመስኮቱ ፡ ስፋት ፡ አምስት ፡ ጫማ ፡ ነው
Is the coat wide enough for you? የኮቱ ፡ ስፋት ፡ በቂህ ፡ ነው ?
3. የራቀ. The shot was wide of the mark. ተኩሱ ፡ ከዒላማው ፡ የራቀ ፡ ነበር

**wide selection** ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት
We have a wide selection of shoes. ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ጫማዎች ፡ አሉን

**with wide eyes** ዓይኑን ፡ አፍጥጦ
The child stared with wide eyes. ልጁ ፡ ዓይኑን ፡ አፍጥጦ ፡ ተመለከተ
[See also 'distribution, far, open, variety']

**wide-awake** ንቁ
He is a wide-awake boy with many interests. ብዙ ፡ ምኞት ፡ ያለው ፡ ንቁ ፡ ልጅ ፡ ነው

**be wide-awake** በፍጹም ፡ ነቃ
I was wide-awake when the sun rose. ፀሐይ ፡ ስትወጣ ፡ በፍጹም ፡ ነቅቼ ፡ ነበር

**widely**
1. በጣም. They differ widely in opinions. በአስተያየት ፡ በጣም ፡ ይለያያሉ
2. በሰፊው. His merits have been widely recognized. መልካም ፡ ሥራው ፡ በሰፊው ፡ ታውቆለታል

**widen** (vt.) አሰፋ
They're going to widen the street. መንገዱን ፡ ሊያሰፉት ፡ ነው
Reading widens our horizons. ማንበብ ፡ ዕውቀታችንን ፡ ያሰፋዋል

**widen** (vi.) ሰፋ
The river will widen next rainy season. በሚመጣው ፡ ክረምት ፡ ወንዙ ፡ ይሰፋል

**wider** ሰፋ ፡ ያለ
Leave a wider margin on the left side! በግራ ፡ በኩል ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ኅዳግ ፡ ተው

**widespread**
1. ሰፊ. The invention found widespread acceptance. አዲስ ፡ የተፈለሰፈው ፡ ነገር ፡ ሰፊ ፡ ተቀባይነት ፡ አገኘ
2. ሰፋ ፡ ያለ. There is widespread damage from the forest fire. ከጫካው ፡ ቃጠሎ ፡ የተነሣ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ ደርሷል
3. በሰፊው ፡ የተለመደ. Adoration of the Virgin Mary is widespread in Ethiopia. ድንግል ፡ ማርያምን ፡ ማክበር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ የተለመደ ፡ ነው
4. የተዛመተ. It is a widespread belief that black cats bring bad luck. ጥቁር ፡ ድመቶች ፡ መጥፎ ፡ ዕድል ፡ ያመጣሉ ፡ የሚል ፡ የተዛመተ ፡ እምነት ፡ አለ
*The bird's widespread wings are a sign it will attack. የወፏ ፡ ክንፍ ፡ በጣም ፡ መዘርጋቱ ፡ የምታጠቃ ፡ መሆኗን ፡ ያመለክታል

**be widespread**
1. በብዛት ፡ ተገኘ. Sorghum is widespread in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ማሽላ ፡ በብዛት ፡ ይገኛል
2. ተሰራጨ. How widespread is this view? ይህ ፡ አስተያየት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ተሰራጭቷል ?
3. በሰፊው ፡ አለ. Discrimination is widespread in South Africa. ደቡብ ፡ አፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ የቀለም ፡ ልዩነት ፡ በሰፊው ፡ አለ
4. ተስፋፋ. The cult of Apollo was widespread. የአፖሎ ፡ አምልኮ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ነበር

**widow** ባሏ ፡ የሞተባት ፡ ሴት
The widow has six children. ባሏ ፡ የሞተባት ፡ ሴትዮ ፡ ስድስት ፡ ልጆች ፡ አሏት

**widower** ሚስቱ ፡ የሞተችበት ፡ ሰው
A widower needs a housekeeper. ሚስቱ ፡ የሞተችበት ፡ ሰው ፡ ቀላቢት ፡ ያስፈልገዋል

**width**
1. ስፋት. The width of this room is twelve feet. የዚህ ፡ ክፍል ፡ ስፋት ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ጫማ ፡ ነው
The room is nine feet in width. የክፍሉ ፡ ስፋት ፡ አራት ፡ ጫማ ፡ ነው
2. ይህን ፡ ያህል ፡ የሚሰፋ. I need two widths of this material. ከዚህ ፡ ጨርቅ ፡ ሁለት ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የሚሰፋ ፡ እፈልጋለሁ

**wield** ተጠቀመ(በት)
The soldiers wield the sword with great skill. ወታደሮቹ ፡ ጐራዴያቸውን ፡ በረቀቀ ፡ ዘዴ ፡ ይጠቀሙበታል
He wields a great amount of power. ሥልጣኑን ፡ በኀይል ፡ ይጠቀምበታል

**wife** (wives)
1. ሚስት. The wife is in charge of the house. ሚስት ፡ የቤት ፡ ኀላፊ ፡ ናት
2. ባለቤት. My wife is in the hospital. ባለቤቴ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ነች
*He made her his wife. አገባት

**take a wife** ሚስት ፡ አገባ
Why don't you take a wife? ለምን ፡ ሚስት ፡ አታገባም ?

**wig** ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጸጉር
Women like to wear wigs now. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሴቶች ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጸጉር ፡ ማድረግ ፡ ይወዳሉ

**wiggle**
1. ተጥመለመለ. The worm wiggles on the hook. ትሉ ፡ በመንጠቆው ፡ ላይ ፡ ይጥመለመላል
2. ተቍነጠነጠ. The child wiggles in his chair. ሕፃኑ ፡ ወምበሩ ፡ ላይ ፡ ይቍነጠነጣል

**wild**
1. ባለጌ. The children are too wild. ልጆቹ ፡ በጣም ፡ ባለጌዎች ፡ ናቸው
2. አረመኔ. He is reading about the wild tribes of ancient times. ስለ ፡ ጥንት ፡ አረመኔ ፡ ጐሳዎች ፡ እያነበበ ፡ ነው
3. የጫካ. The wild men's genitals were covered by a cloth strip. የጫካ ፡ ሰዎቹ ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ በጨርቅ ፡ ቁራጭ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር
4. ወፍ ፡ ዘራሽ. The wild flowers blossom at the end of the rainy season. ወፍ ፡ ዘራሽ ፡ አበቦች ፡ ክረምት ፡ ሲወጣ ፡ ያብባሉ
5. ሰው ፡ ያልሰፈረበት. Wild land affords refuge for game. ሰው ፡ ያልሰፈረበት ፡ መሬት ፡ ላውሬዎች ፡ መጠጊያ ፡ ይሆናል
6. ያልተገራ. Your children are too wild; they scratched my furniture while playing. ልጆችህ ፡ ያልተገሩ ፡ ናቸው ፤ ሲጫወቱ ፡ የቤት ፡ እቃዬን ፡ አበላሹብኝ

7. የሜዳ ፤ ያልተገራ. There are many wild horses in this region. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ብዙ ፡ የሜዳ ፡ ፈረሶች ፡ አሉ
We loosed the wild horse. ያልተገራውን ፡ ፈረስ ፡ ለቀቅነው
8. የማይጨበጥ. He has a wild plan for getting rich. ሀብታም ፡ ለመሆን ፡ የማይጨበጥ ፡ እቅድ ፡ አለው
9. ከእውነት ፡ የራቀ. He made so many wild allegations that no one will believe him. ብዙ ፡ ከእውነት ፡ የራቁ ፡ ነገሮች ፡ ደረሱ ፡ ስለሚል ፡ ማንም ፡ አያምነውም
10. ታላቅ. The audience received the speech with wild applause. አዳማጮቹ ፡ ለንግግሩ ፡ ታላቅ ፡ ጭብጨባ ፡ አደረጉ

**wilds** ዱር
They have a farm way out in the wilds. ራቅ ፡ ብለው ፡ ከዱር ፡ ውስጥ ፡ እርሻ ፡ አላቸው

**wild region** በረሃ
Airplanes now fly over the wild regions of the Far North. ራቅ ፡ ብለው ፡ ሰሜን ፡ በሚገኙት ፡ በረሃዎች ፡ ላይ ፡ አሁን ፡ አውሮፕላኖች ፡ ይበራሉ

**wild state** አውሬነት
Many tamed animals revert to a wild state when set free. ብዙ ፡ ለማዳ ፡ እንስሳዎች ፡ በተለቀቁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አውሬነት ፡ ይመለሳሉ

**be wild about** ነፍሱ ፡ እስኪወጣ ፡ ወደደ
My boy is wild about ice cream. ልጄ ፡ አይስክሬም ፡ ነፍሱ ፡ እስኪወጣ ፡ ይወዳል

**make a wild guess** ዓይኑን ፡ ጨፍኖ ፡ ገመተ
I'll make a wild guess: your car cost $2,500. ዓይኔን ፡ ጨፍኜ ፡ ልገምት ፤ መኪናህ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ታወጣለች

**run wild** አውሬ ፡ ሆነ
The dog ran wild after its master died. ጌታው ፡ ከሞተበት ፡ በኋላ ፡ ውሻው ፡ አውሬ ፡ ሆነ

**(allow to) run wild** ስድ ፡ ለቀቀ
They allow their children to run wild. ልጆቻቸውን ፡ ስድ ፡ ይለቋቸዋል
[See also 'animal, beast']

**wilderness**
1. በረሃ ፤ ጠፍ ፡ በረሃ. The only settlement in the wilderness was a penal colony. በበረሃው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ መኖሪያ ፡ የወንጀለኞች ፡ ብቻ ፡ ነበር
Who was the first man to settle in this wilderness? በዚህ ፡ ጠፍ ፡ በረሃ ፡ መጀመሪያ ፡ ማን ፡ ማን ፡ ሰፈረ ?
2. ጫካ. The boy scouts cleared a path through the wilderness. እስካውቶቹ ፡ ጫካውን ፡ መንጥረው ፡ መንገድ ፡ አበጁ

**wildfire** ሰደድ ፡ እሳት
The wildfire destroyed many trees before it was put out. ሰደድ ፡ እሳቱ ፡ ከመጥፋቱ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ዛፎች ፡ አወደመ
The news spread like wildfire. ወሬው ፡ እንደ ፡ ሰደድ ፡ እሳት ፡ ተሰራጨ

**wildlife** የዱር ፡ አራዊት
There is abundant wildlife in these forests. በዚህ ፡ ደን ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ አሉ

**wile** ብልሃት
The witch by her wiles persuaded the boy to go with her. አስማተኛዋ ፡ በብልሀቷ ፡ አግባብታ ፡ ልጁ ፡ ከሷ ፡ ጋር ፡ እንዲሄድ ፡ አደረገችው

**will** (v.)
1. ተናዘዘ. He willed all his property to the city. ያለውን ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ ለከተማው ፡ ተናዘዘ
2. ቈረጠ. She willed to keep awake. ነቅታ ፡ ለመቆየት ፡ ቈረጠች
*Fate has willed it otherwise. ዕድል ፡ አይሁን ፡ ብሎታል

**will** (vi.) ተመኘ
We cannot always do as we will. ሁልጊዜ ፡ እንደምንመኘው ፡ አናደርግም

**will** (auxiliary)
1. (imperfect). I will come when I am ready. ሲመቸኝ ፡ እመጣለሁ
2. (simple imperfect). Will you open the door? መዝጊያውን ፡ ትከፍት ?
3. አለ(በት). You will do it at once! አሁኑኑ ፡ መፈጸም ፡ አለብህ
4. ቻለ. This jar will hold three liters. ይህ ፡ ማሰሮ ፡ ሦስት ፡ ሊትር ፡ ሊይዝ ፡ ይችላል

**will have** ፈለገ
Ask him if he will have some cake. ጥቂት ፡ ኬክ ፡ ይፈልግ ፡ እንደሆነ ፡ ጠይቀው

**will** (n.)
1. ኑዛዜ. They read his will and found that he had disinherited everybody. ኑዛዜውን ፡ ካነበቡ ፡ በኋላ ፡ ለቤተሰቦቹ ፡ ምንም ፡ አለማውረሱን ፡ ተረዱ
2. ፍላጎት. If the patient has a will to live, he will recover. በሽተኛው ፡ የመኖር ፡ ፍላጎት ፡ ካለው ፡ ይድናል
3. መንፈስ. He has no will of his own; his wife makes all the decisions. በራሱ ፡ መንፈስ ፡ አይመራም ፤ የምታዝዘው ፡ ሚስቱ ፡ ናት

4. ሙሉ ፡ ልብ. He went at his work with a will. ሥራውን ፡ በሙሉ ፡ ልብ ፡ ጀመረ
5. ፈቃድ. Thy will be done. ፈቃድህ ፡ ይፈጸም
I did it of my own free will. ያደረግሁት ፡ በገዛ ፡ ፈቃዴ ፡ ነው
6. ፈቃደኛነት. I will include an extra payment to show good will. በጎ ፡ ፈቃደኛነቴን ፡ ለማሳየት ፡ ትርፍ ፡ እከፍላለሁ
7. ውዴታ. He was named chairman against his will. ያለ ፡ ውዴታው ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ተመረጠ
8. ስሜት. A friendly smile generates good will. የወዳጅነት ፡ ፈገግታ ፡ መልካም ፡ ስሜትን ፡ ያተርፋል
*Where there's a will, there's a way. ቈራጥና ፡ ጨካኝ ፡ መውጫ ፡ አያጣም

**at will** እንደልቡ ፤ በፈቃዱ
They come and go at will. እንደልባቸው ፡ (በፈቃዳቸው) ፡ ይመላለሳሉ

**good will** ጥሩ; **ill will** መጥፎ
Most men feel good will toward their friends and ill will toward their enemies. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ለወዳጆቻቸው ፡ ጥሩ ፤ ለጠላቶቻቸው ፡ ደግሞ ፡ መጥፎ ፡ ይመኛሉ

**leave a will** ተናዘዘ
He died without leaving a will. ሳይናዘዝ ፡ ሞተ
[See also 'force, free']

## willful
1. ሐሳበ ፡ ግትር. She is very willful, and so it's hard to control her. ሐሳበ ፡ ግትር ፡ ስለሆነች ፡ እሷን ፡ መቈጣጠር ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. ችኮ. The willful boy will not obey. ችኮው ፡ ልጅ ፡ አይታዘዝም
3. (= adv.) ሆን ፡ ብሎ. His willful lies only create more dissension. ሆን ፡ ብሎ ፡ የሚዋሸው ፡ የበለጠ ፡ ቅሬታ ፡ ያስከትላል

## willing ፍቃደኛ ፤ ፈቃደኛ
I'm willing to try anything. ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ለመሞከር ፡ ፍቃደኛ ፡ (ፈቃደኛ) ፡ ነኝ
[See also 'perfectly']

## willingly
1. በፍቃድ. She came willingly, so why is she complaining to us now? በፍቃዷ ፡ ነው ፡ የመጣችው ፤ አሁን ፡ ምን ፡ ትነጫነጭብኛለች ?
2. በፈቃደኝነት. He did not impose his advice on me, but I listened to him willingly. ምክሩን ፡ እንድቀበል ፡ አላስገደደኝም ፤ ግን ፡ በፈቃደኝነት ፡ አዳመጥኩት

## willingness
*He sounded them out regarding their willingness to come along. ለመምጣት ፡ ይፈልጉ ፡ እንደሆነ ፡ አሳባቸውን ፡ ለማወቅ ፡ ጠየቀ

## will power ቈራጥነት
It takes will power to give up smoking. ሲጋራ ፡ ማጤስን ፡ መተው ፡ ቈራጥነትን ፡ ይጠይቃል

## willy-nilly በውድም ፡ ሆነ ፡ በግድ
Willy-nilly he will pay what he owes. በውድም ፡ ሆነ ፡ በግድ ፡ ያለበትን ፡ ይከፍላል

## wilt
1. ጠወለገ. The flowers will wilt if they are not in water. አበቦቹ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ካልሆኑ ፡ ይጠወልጋሉ
2. ጉልበቱ ፡ ፈሰሰ. We wilted under the tropical sun. ሐሩሩ ፡ ፀሐይ ፡ ውስጥ ፡ ጉልበታችን ፡ ፈሰሰ

## win (won)
1. አሸነፈ. We won the battle. ጦርነቱን ፡ አሸነፍን
Which team do you think will win? የትኛው ፡ ቡድን ፡ የሚያሸንፍ ፡ ይመስልሃል ?
2. ረታ. He won his case in court. ሙግቱን ፡ ረታ
3. አገኘ. Win a prize by making the highest score! ከፍተኛውን ፡ ነጥብ ፡ በማግኘት ፡ ሽልማት ፡ አግኝ
4. ወጣ(ለት). We are in luck; our chance in the lottery won. ታድለናል ፤ የሎተሪ ፡ ዕጣ ፡ ወጣልን
5. አፈራ. She won new friends. አዲስ ፡ ጓደኞች ፡ አፈራች
6. አተረፈ. He won renown as a courageous fighter. ጀግና ፡ ተዋጊ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ዝና ፡ አተረፈ
7. ማረከ. The speaker soon won his audience. ተናጋሪው ፡ ወዲያውኑ ፡ አድማጮቹን ፡ ማረከ
8. ደረሰ. The climbers won the top of the hill. ተራራ ፡ ወጪዎቹ ፡ ኮረብታው ፡ ጫፍ ፡ ደረሱ

**win (one's) heart** ልብ ፡ ማረከ
His childlike frankness wins the heart of everybody. እንደ ፡ ሕፃን ፡ የዋህ ፡ መሆኑ ፡ የማንኛቸውንም ፡ ሰው ፡ ልብ ፡ ይማርካል

**win (someone over) to one's side** ወደሱ ፡ ሳበው ፤ አግባባ
The power of his argument won many to his side. የክርክሩ ፡ ብርቱነት ፡ ብዙዎቹን ፡ ወደሱ ፡ ሳባቸው
I have won him over to our side. በኛ ፡ በኩል ፡ እንዲሆን ፡ አግባብቼዋለሁ
[See also 'favor, recognition, respect, success, title']

**wince** ተሸመቀቀ
I winced when he hit my hand. እጄን ፡ ሲመታኝ ፡ ተሸመቀቅሁ

**wind** (wound), vt.
1. ጠመጠመ. Wind it around my finger! ጣቴ ፡ ላይ ፡ ጠምጥመው
2. አጠነጠነ. She wound the thread on the spindle. ክሩን ፡ እንዝርቱ ፡ ላይ ፡ አጠነጠነች
3. ሞላ. I forgot to wind my watch. ሰዓቴን ፡ መሙላት ፡ ረሳሁ
*She winds him around her little finger. እጇ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**wind** (vi.)
1. ተጠማዞ ፡ አለፈ. The road winds through the mountains. መንገዱ ፡ በተራሮቹ ፡ መሃል ፡ ተጠማዞ ፡ ያልፋል
2. ተጠማዘዘ. A lazy stream winds through the meadow. ዝግተኛው ፡ ምንጭ ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ይጠማዘዛል

**wind on the spool** አዳወረ
Wind the thread on a spool! ክሩን ፡ አዳውረው

**wind up** (vt.)
1. አጠነጠነ. Will you help me wind up this yarn? ይህን ፡ የሱፍ ፡ ክር ፡ እንዳጠነጥን ፡ አግዘኝ
2. ደመደመ. He wound up his speech with an appeal to everyone's patriotism. የሁሉንም ፡ የሀገር ፡ ፍቅር ፡ ስሜት ፡ በመቀስቀስ ፡ ንግግሩን ፡ ደመደመ
3. አጠናቀቀ. They gave him two weeks' time in which to wind up his affairs. ጉዳዩን ፡ የሚያጠናቅቅበት ፡ የሁለት ፡ ሳምንት ፡ ጊዜ ፡ ሰጡት

**wind up** (vi.) አበቃ
The meeting will wind up before dark. ስብሰባው ፡ ከመምሸቱ ፡ በፊት ፡ ያበቃል
*My plan wound up in the wastepaper basket. እቅዴ ፡ መጨረሻው ፡ ከንቱ ፡ ሆነ

**(be) wound up** ጭንቅ ፡ አለው
He is so wound up, he can't relax or stop talking. ጭንቅ ፡ ስላለው ፡ ሊዝናና ፡ ወይም ፡ ዝም ፡ ሊል ፡ አልቻለም

**wind (one's) way through** እየተጠማዘዘ ፡ ሄደ
We wound our way through the narrow streets. በጠባቦቹ ፡ መንገዶች ፡ ላይ ፡ እየተጠማዘዝን ፡ ሄድን

**wind (its) way to** እየተጥመዘመዘ ፡ ከ - - - ገባ
The river winds its way to the sea. ወንዙ ፡ እየተጥመዘመዘ ፡ ከባሕር ፡ ይገባል

**wind, be winded** ትንፋሹ ፡ ተቋረጠ ፤ ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰ
The fat man was winded by walking up the steep hill. ቀጥ ፡ ያለውን ፡ ኮረብታ ፡ በመውጣቱ ፡ ወፍራሙ ፡ ሰው ፡ ትንፋሹ ፡ ተቋረጠ ፡ (ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰ)

**wind** (n.)
1. ነፋስ. There was a violent wind last night. ባለፈው ፡ ሌሊት ፡ ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ነበር
2. ትንፋሽ. He regained his wind after a short rest. ጥቂት ፡ ካረፈ ፡ በኋላ ፡ ትንፋሹ ፡ መለስ ፡ አለ

**(the) wind blows** ነፈሰ
How the wind is blowing today! ዛሬ ፡ ምንኛ ፡ ይነፍሳል!
*We won't act until we see how the wind blows. ሁኔታው ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ሳናውቅ ፡ ምንም ፡ አናደርግም

**break wind** ፈሳ
Don't break wind in public! በሰው ፡ መሃል ፡ አትፍሳ

**get wind of**
1. ዐወቀ. Don't let mother get wind of our plans to give her a gift! ስጦታ ፡ ልናበረክትላት ፡ ያለንን ፡ እቅድ ፡ እናታችን ፡ እንድታውቅ ፡ አታድርግ
2. ጭምጭምታ ፡ ሰማ. I got wind of the cabinet reshuffle yesterday. የሚኒስትሮች ፡ መለዋወጥ ፡ ይደረጋል ፡ የሚል ፡ ጭምጭምታ ፡ ትናንት ፡ ሰማሁ

**in the wind**
*There is something in the wind. አንድ ፡ ነገር ፡ ሊሆን ፡ ነው
[See also 'second']

**windbreak** ከነፋስ ፡ መከላከያ
The boys pitched their tent next to the stone wall, so that it would serve as a windbreak. ከነፋስ ፡ መከላከያ ፡ እንዲሆናቸው ፡ ልጆቹ ፡ ድንኳናቸውን ፡ ድንጋይ ፡ ግድግዳ ፡ ሥር ፡ ተከሉ

**windfall**
*He received a windfall of $200,000. እግዜር ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ጣለለት

**winding** ጠምዛዛ
High speed on a winding road is dangerous. በጠምዛዛ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍጥነት ፡ መንዳት ፡ አደገኛ ፡ ነው

**wind instrument** [በነፋስ ፡ የሚሠራ ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ]

**windmill** የነፋስ ፡ ወፍጮ
Windmills are animated by the wind. የነፋስ ፡ ወፍጮዎች ፡ የሚንቀሳቀሱት ፡ በነፋስ ፡ ኀይል ፡ ነው

**window** መስኮት
This room has two windows. ይህ ፡ ክፍል ፡ ሁለት ፡ መስኮት ፡ አለው
[See also 'sill']

**windowpane** የመስኮት ፡ መስታወት
The windowpane was cracked. የመስኮቱ ፡ መስታወት ፡ ተሰንጥቋል

**windowshopping, go ~**
She likes to go windowshopping. ባትገዛም ፡ እቃዎቹን ፡ መመልከት ፡ ትወዳለች

**windpipe** [ከአፍ ፡ ወደ ፡ ሳምባ ፡ የነፋስ ፡ መተላለፊያ]

**windshield** የመኪና ፡ የፊት ፡ መስታወት
The windshield is tinted green. የመኪናው ፡ የፊት ፡ መስታወት ፡ ትንሽ ፡ አረንጓዴነት ፡ አለው

**windshield wiper** የመኪና ፡ የዝናብ ፡ መጥረጊያ
The windshield wiper does not work. የመኪናው ፡ የዝናብ ፡ መጥረጊያ ፡ ተበላሽቷል

**windstorm** ኀይለኛ ፡ ነፋስ
The windstorm destroyed the roof. ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ጣራውን ፡ አፈረሰው

**wind vane** [የነፋስን ፡ አቅጣጫ ፡ የሚያሳይ ፡ መሣሪያ]

**windy**
1. ነፋሻ. It was very windy yesterday. ትላንትና ፡ በጣም ፡ ነፋሻ ፡ ነበር
2. ነፋስ ፡ የሚበዛበት. March is a windy month. መጋቢት ፡ ነፋስ ፡ የሚበዛበት ፡ ወር ፡ ነው
3. ገለባ. His windy talk impresses no one. ገለባ ፡ ንግግሩ ፡ ለማንም ፡ ስሜት ፡ አይሰጥም

**wine** ወይን ፡ ጠጅ
I like to drink wine. ወይን ፡ ጠጅ ፡ መጠጣት ፡ እወዳለሁ

**wing** (v.)
1. ወረወረ. The soldier winged his arrow at the target. ወታደሩ ፡ ቀስቱን ፡ ወደ ፡ ዒላማው ፡ ወረወረ
2. ጨረፍ ፡ አድርጎት ፡ አለፈ. He is not badly hurt; the bullet only winged him. በጣም ፡ አልተጐዳም ፤ ጥይቱ ፡ ጨረፍ ፡ አድርጎት ፡ ነው ፡ ያለፈው

**wing (one's) way** በረረ
The bird winged its way to the south. ወፏ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ በረረች

**wing** (n.) ክንፍ
The pigeon broke its wing. የእርግቧ ፡ ክንፍ ፡ ተሰበረ
The office is in the west wing of the building. ቢሮው ፡ ሕንጻው ፡ ውስጥ ፡ በስተምዕራብ ፡ ከሚገኘው ፡ ክንፍ ፡ ነው

**on the wing** ሲበር
It's hard to shoot a bird on the wing. ወፍ ፡ ስትበር ፡ ተኩሶ ፡ ለመግደል ፡ ያስቸግራል

**take under one's wing** ተንከባከበ
The teacher took the new student under his wing. አስተማሪው ፡ አዲሱን ፡ ተማሪ ፡ ተንከባከበው

**take wing** በረረ
The birds took wing at our approach. ስንጠጋቸው ፡ ወፎቹ ፡ በረሩ

**wink** (vt.) ጠቀሰ
He winked his eye to indicate he was not serious. ሲቀልድ ፡ መሆኑን ፡ ለማመልከት ፡ በዓይኑ ፡ ጠቀሰ

**wink** (vi.)
1. ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ አለ. We could see the lights of the city winking in the distance. የከተማው ፡ መብራት ፡ ከሩቁ ፡ ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ ሲል ፡ ይታየናል
2. ብልጭ ፡ ድርግም ፡ አለ. The lights of a passing ship winked. የሚያልፈው ፡ መርከብ ፡ መብራት ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ አለ
The stars winked. ከከቦቹ ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ አሉ
3. በዓይኑ ፡ ጠቀስ ፡ አደረገ. She winked as she passed. ስታልፍ ፡ በዓይኗ ፡ ጠቀስ ፡ አደረገች

**wink at it** አይቶ ፡ እንዳላየ ፡ ሆነ
Mother knows that we help ourselves to cookies now and then, but she winks at it. እናታችን ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብስኩቱን ፡ እንደምንበላ ፡ ታውቃለች ፡ ግን ፡ አይታ ፡ እንዳላየች ፡ ትሆናለች

**wink** (n.) ጥቅሻ
She gave me a knowing wink. ያልኩት ፡ የገባት ፡ መሆኗን ፡ በጥቅሻ ፡ ገለጸችልኝ
*I didn't sleep a wink last night. ትናንትና ፡ ማታ ፡ ባይኔ ፡ እንቅልፍ ፡ ሳይዞር ፡ አደርኩ

**in a wink** ባንድ ፡ አፍታ
I'll be there in a wink. ባንድ ፡ አፍታ ፡ እዚያ ፡ እገኛለሁ

**winner** አሸናፊ
The winner will get a gold cup. አሸናፊው ፡ የወርቅ ፡ ዋንጫ ፡ ያገኛል

**winning**

1. **አሸናፊ**. The winning team is given a large silver cup. **ላሸናፊው ፡ ቡድን ፡ ትልቅ ፡ የብር ፡ ዋንጫ ፡ ተሰጠ**
2. **የሚማርክ**. She has a winning smile. **የሚማርክ ፡ ፈገግታ ፡ አላት**

**winnow**

1. **አዘራ**. The farmers winnow the grain after they thresh it. **ገበሬዎቹ ፡ እህሉን ፡ ከወቁ ፡ በኋላ ፡ ያዘሩታል**
2. **ለየ**. You have to winnow truth from his statement. **ከሰጠው ፡ አስተያየት ፡ እውነቱን ፡ መለየት ፡ አለብህ**

**winsome ቆንጆ**

She is rather winsome, don't you think? **ቆንጆ ፡ ነች ፡ አይመስልህም ?**

**winter ክረምት**

The European and the Ethiopian winters are not the same. **የፈረንጅና ፡ ያበሻ ፡ ክረምት ፡ አንድ ፡ አይደለም**

**wipe**

1. **ወለወለ**. I'll wash the dishes if you wipe them. **አንተ ፡ ሳሕኖቹን ፡ ከወለወልካቸው ፡ እኔ ፡ አጥባቸዋለሁ**
Wipe the table after you remove the dishes! **ሳሕኖቹን ፡ ካነሣሣህ ፡ በኋላ ፡ ጠረጴዛውን ፡ ወልውለው**
2. **ጠረገ**. He wiped the spittle from the floor. **አክታውን ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ ጠረገ**
We wipe our shoes on the mat. **ጫማችንን ፡ ሰሌኑ ፡ ላይ ፡ እንጠርጋለን**
Wipe your nose with this handkerchief! **በዚህ ፡ መሐረብ ፡ አፍንጫህን ፡ ጥረግ**
*Wipe that smile off your face! **አትገልፍጥ**

**wipe away ጠረገ(ለት)**

She wiped her child's tears away. **የልጇን ፡ እንባ ፡ ጠረገችለት**

**wipe off ጠረገ**

First let me wipe off the dust of the table! **መጀመሪያ ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ አቧራውን ፡ ልጥረገው**

**wipe out**

1. **አወደመ**. The earthquake wiped out the whole town. **የመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ከተማውን ፡ በሙሉ ፡ አወደመው**
2. **አጠፋ**. An all-out effort is needed to wipe out illiteracy. **መሀይምነትን ፡ ለማጥፋት ፡ ሰፊ ፡ ጥረት ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል**

**wipe up ጠረገ**

Wipe up the spilled milk with a rag! **የፈሰሰውን ፡ ወተት ፡ በጨርቅ ፡ ጥረገው**

**wire** (v.)

1. **በሽቦ ፡ አሰረ**. He wired the two pieces together. **ሁለቱን ፡ ቁራጮች ፡ በሽቦ ፡ አሰረ**
2. **ቴሌግራም ፡ አደረገ(ለት)**. He wired me to meet him at the railway station. **ባቡር ፡ ጣቢያ ፡ እንድጠብቀው ፡ ቴሌግራም ፡ አደረገልኝ**

**be wired**

Is the house wired? **ቤቱ ፡ ሲሠራ ፡ የኮረንቲ ፡ ገመድ ፡ ግድግዳው ፡ ውስጥ ፡ ተቀብሯል ?**

**wire** (n.)

1. **ሽቦ**. The wire isn't strong enough. **ሽቦው ፡ በጣም ፡ ጠንካራ ፡ አይደለም**
The broken electric wire was making sparks. **የተበጠሰው ፡ የኮረንቲ ፡ ሽቦ ፡ ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ ይል ፡ ነበር**
2. **ቴሌግራም**. Send him a wire! **ቴሌግራም ፡ አድርግለት**

**live wire የኮረንቲ ፡ ሽቦ**

Don't touch that live wire without rubber gloves! **ያለ ፡ ላስቲክ ፡ ጓንት ፡ ያንን ፡ የኮረንቲ ፡ ሽቦ ፡ አትንካ**

**pull wires አማላጅ ፡ ላከ**

He pulled wires to get his son transferred to Washington. **ልጁ ፡ ወደ ፡ ዋሽንግተን ፡ እንዲዛወርለት ፡ አማላጅ ፡ ላከ**
[See also 'barbed']

**wireless set ሬዲዮን**

The wireless set is broken. **ሬዲዮኑ ፡ ተሰብሯል**

**wisdom**

1. **ጠቢብነት ፤ ጥበብ**. His wisdom is known throughout the world. **ጠቢብነቱ ፡ (ጥበቡ) ፡ በዓለም ፡ የታወቀ ፡ ነው**
2. **ጥልቅነት**. I challenge the wisdom of his decision. **የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ጥልቅነት ፡ እጠራጠራለሁ**
*Some old men possess a lot of wisdom. **አንዳንድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ በጣም ፡ ብልሆች ፡ ናቸው**

**wisdom tooth በመጨረሻ ፡ የሚበቅል ፡ የመንጋጋ ፡ ጥርስ**

The dentist pulled out his wisdom teeth. **የጥርስ ፡ ሐኪሙ ፡ በመጨረሻ ፡ የሚበቅለውን ፡ የመንጋጋ ፡ ጥርሱን ፡ አወለቀለት**

**wise**

1. **ጠቢብ ፤ ብልህ**. He is very intelligent, but

not very wise. የመማር ፡ ችሎታው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ግን ፡ ብልህ ፡ (ጠቢብ) ፡ አይደለም
2. በጣም ፡ ዐዋቂ. He is a wise man. በጣም ፡ ዐ ዋቂ ፡ ሰው ፡ ነው
3. ጥሩ. You have made a very wise decision. ጥሩ ፡ ውሳኔ ፡ አድርገሃል

**-wise** በ --- በኩል
Moneywise he is doing well. በገንዘብ ፡ በኩል ፡ ጥሩ ፡ ይዟል

**wisely** ጥሩ
He wisely decided not to fight the truck driver. ከጭነት ፡ መኪና ፡ ነጂው ፡ ጋር ፡ ላለመደባደብ ፡ መምረጡ ፡ ጥሩ ፡ አድርጓል

**wiser**
*I was no wiser after reading that article. ያንን ፡ ጽሑፍ ፡ አንብቤ ፡ ምንም ፡ አላተረፍኩ

**wish** (v.)
1. ተመኘ. I wish that I could be there. እዚያ ፡ ብሆን ፡ እመኛለሁ
You may get whatever you wish. የምትመኘው ን ፡ ሁሉ ፡ ልታገኝ ፡ ትችላለህ
I wouldn't wish that awful job on my worst enemy. ያን ፡ አስጠሊ ፡ ሥራ ፡ ለከፋ ፡ ጠላቴም ፡ አልመኘው
2. ተመኘ(ለት). We wished him luck on his trip. መልካም ፡ ጉዞ ፡ እንዲሆንለት ፡ ተመኘንለት
I wish you a Merry Christmas. መልካም ፡ የገና ፡ በዓል ፡ እመኝልሃለሁ
3. ፈለገ. Do you wish to go home? ወደ ፡ ቤት ፡ ለመሄድ ፡ ትፈልጋለህ ?

**wish for** ተመኘ
What do you wish for most? ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ የምትመኘው ፡ ምንድነው ?

**(could) wish for**
*He has everything a woman could wish for. ሴት ፡ ከወንድ ፡ ልትመኘው ፡ የምትፈልገው ፡ ሁሉ ፡ አለው

**I wish...** ምነው ፡ በ + perfect
I wish I knew where I put my glasses! መነጽሬ ን ፡ የጣልኩበትን ፡ ምነው ፡ ባወቅኩ

**I wish I could**
*I wish I could tell you the whole story. ታሪ ኩን ፡ በሙሉ ፡ ብነግርህ ፡ ደስ ፡ ይለኝ ፡ ነበር
[See also 'farewell']

**wish** (n.) ምኞት
My wish is easily satisfied. ምኞቴ ፡ በቀላሉ ፡ ይረካል
I send you my best wishes. መልካም ፡ ምኞቴ ን ፡ እገልጽልሃለሁ

*He has no wish to go. ለመሄድ ፡ ፈቃደኛ ፡ አይ ደለም

**wishful, ~ thinking** የሕልም ፡ እንጀራ
It is wishful thinking to feel that you will get a scholarship with your low grades. በዚህ ፡ ዝ ቅተኛ ፡ ውጤትህ ፡ ነጻ ፡ ትምህርት ፡ አገኛለሁ ፡ ማለት ፡ የሕልም ፡ እንጀራ ፡ ነው

**wishy-washy** ወላዋይ
She is wishy-washy, so you can't depend on her. ወላዋይ ፡ ስለሆነች ፡ ልትተማመንባት ፡ አትችልም

**wistful** የመጓጓት
Though she refused, her wistful expression showed that she really wanted it. እምቢ ፡ ብት ል ፡ እንኳ ፡ የመጓጓት ፡ አስተያየቷ ፡ በእርግጥ ፡ መፈለጓን ፡ አመለከተ

**wistfully** በጉጉት
The small child looked wistfully at the plate of cookies. ሕፃኑ ፡ ብስኩት ፡ ያለበትን ፡ ሳሕን ፡ በጉጉት ፡ ተመለከተ

**wit**
1. ቀልድ. What I like about him especially is his wit. ከሁሉም ፡ ነገሩ ፡ የምወደው ፡ ቀልዱ ን ፡ ነው
2. ቀልደኛነት. That was a representative example of his wit. የቀልደኛነቱ ፡ ዓይነተኛ ፡ ምሳሌ ፡ ይህ ፡ ነው
3. ወግ. His speech glittered with wit. ንግግሩ ፡ በወግ ፡ የደመቀ ፡ ነበር
4. የማሰብ ፡ ችሎታ. That poor man hasn't wit enough to earn a living. ያ ፡ ምስኪን ፡ ሠርቶ ፡ ለመብላት ፡ እንኳን ፡ የማሰብ ፡ ችሎታ ፡ የለውም

**wits** አእምሮ
People with quick wits learn easily. ንቁ ፡ አእም ሮ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በቀላሉ ፡ ይማራሉ

**at one's wit's end**
*I'm at my wit's end with this problem. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የሚቻለኝን ፡ ሁሉ ፡ አድርጌ ፡ አቅቶኛል

**(be) out of one's wits** ግራ ፡ ገባው
He was out of his wits with fear. በፍርሃት ፡ ግ ራ ፡ ገብቶት ፡ ነበር
*The snake scared her out of her wits. እባቡ ፡ አስደንግጧት ፡ ያለችበትን ፡ አታውቅም ፡ ነበር

**witch**
1. ጠንቋይ ፤ አስማተኛ. In olden days, people believed in witches. ድሮ ፡ ሰዎች ፡ በጠንቋይ ፡ ያምኑ ፡ ነበር

The witch gave the man a philter which turned him into a frog. አስማተኛዋ ፡ ወደ ፡ እንቁራሪትነት ፡ የሚለውጥ ፡ መድኃኒት ፡ በሰውዬው ፡ ላይ ፡ አደረገችበት
2. ዛር. She frightened the child because she looked like a witch. ዛር ፡ ስለምትመስል ፡ ልጁን ፡ አስደነገጠችው

**witchcraft** ጥንቆላ
They still use witchcraft for curing diseases. በሽታን ፡ ለማዳን ፡ አሁንም ፡ በጥንቆላ ፡ ይጠቀማሉ

**witch doctor** ጠንቋይ
The witch doctor can cure your wound. ጠንቋዩ ፡ ቁስልህን ፡ ሊያድንህ ፡ ይችላል

**with**
1. ከ --- ጋር. I'll have lunch with him today. ዛሬ ፡ ምሳዬን ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ እበላለሁ
Don't argue with him! ከሱ ፡ ጋር ፡ አትከራከር
I won't have anything to do with her. ከሷ ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ጉዳይ ፡ የለኝም
2. በ. Write your name with a pencil! ስምህን ፡ በእርሳስ ፡ ጻፍ
She met him with a smile. በፈገግታ ፡ ተቀበለችው
He has been with this company for years. በዚህ ፡ ኩባንያ ፡ ውስጥ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ አገልግሏል
He was trembling with fear. በፍርሃት ፡ ይንቀጠቀጥ ፡ ነበር
He did it with pleasure. በደስታ ፡ አደረገው
He shook with cold. በብርድ ፡ ይንቀጠቀጥ ፡ ነበር
We are pleased with the house. በቤቱ ፡ ተደስተናል
3. በ --- አማካይነት. The circus clown keeps his equilibrium with a pole. የሰርከሱ ፡ ተዋናይ ፡ ሚዛኑን ፡ በዘንግ ፡ አማካይነት ፡ ይጠብቃል
4. በ -- ዘንድ. His behavior will discredit him with the public. ምግባሩ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ያስገምተዋል
5. በበኩል. It's all right with me. በበኩሌ ፡ ግድ ፡ የለኝም
6. ከ --- የተነሣ. The boards of the floor were cracked with age. የወለሉ ፡ ሳንቃዎች ፡ ከማርጀታቸው ፡ የተነሣ ፡ ተሰነጣጥቀዋል
7. ለ --- አደራ. He left the dog with his sister when he went away. ሲሄድ ፡ ውሻውን ፡ ለእኅቱ ፡ አደራ ፡ ሰጠ
8. (gerundive). With all the work he's done, he still isn't finished. ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሠርቶ ፡ ገና ፡ አልጨረሰም
9. ስ + (imperfect). With the approach of sunset, it became chilly. የፀሐይ ፡ መጥለቂያ ፡ ሲቃረብ ፡ መቀዝቀዝ ፡ ጀመረ
With the coming of spring, the birds returned. ጸደይ ፡ ሲደርስ ፡ ወፎቹ ፡ ተመለሱ
10. ባለ + (noun). I want a coat with two pockets. ባለሁለት ፡ ኪስ ፡ ኮት ፡ እፈልጋለሁ
*With all her faults, I love her still. ብዙ ፡ ጉድለት ፡ ቢኖርባትም ፡ እንኳ ፡ አሁንም ፡ እወዳታለሁ
*With him, it's all a matter of money. ከገንዘብ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ አያውቅም
*With that remark, he left. እንደዚያ ፡ ብሎ ፡ ሄደ
*The English fought with the Germans against France. እንግሊዝና ፡ ጀርመን ፡ ፈረንሳይን ፡ ወጉ
*Do you want sugar with your tea? ሻይህ ፡ ውስጥ ፡ ስኳር ፡ እንዲጨመርልህ ፡ ትፈልጋለህ ?
*Are you with me or against me? ደጋፊዬ ፡ ነህ ፡ ወይስ ፡ ተቃዋሚዬ ?

**be with one**
*I shall be with you in a few minutes. ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በኋላ ፡ አነጋግርሃለሁ

**have (something) with one** ያዘው
I don't have the book with me. መጽሐፉን ፡ አልያዝኩትም

**take (something) with one** ይዞ ፡ ሄደ
He took the book with him. መጽሐፉን ፡ ይዞ ፡ ሄደ
[See also 'what']

**withdraw** (withdrew), vt.
1. አነሣ. I withdraw the motion. ያቀረብኩትን ፡ ሐሳብ ፡ አነሣለሁ
2. አስወጣ. He withdrew his child from school. ልጁን ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ አስወጣ
3. አወጣ. I withdrew $10 from the bank. ከባንክ ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ አወጣሁ
4. ሰረዘ. He withdrew the charge, and the man was released from jail. ክሱን ፡ ስለሰረዘ ፡ ሰውዬው ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ ተለቀቀ
5. አሸሸ. She withdrew her hand from the hot iron. እጇን ፡ ከጋለው ፡ ካውያ ፡ አሸሸች
6. (= intr.) ተጸጸተ. He withdrew his unkind words. በተናገረው ፡ መጥፎ ፡ ቃል ፡ ተጸጸተ

**withdraw** (vi.)
1. ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈገ. The troops withdrew under heavy fire. ወታደሮቹ ፡ ከባድ ፡ ተኩስ ፡ ስለ ወረደባቸው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈጉ
2. ወደ ፡ ሌላ ፡ ክፍል ፡ ሄደ. After dinner, the ladies withdrew. ከራት ፡ በኋላ ፡ ሴቶቹ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ክፍል ፡ ሄዱ

3. ተገለለ. He withdrew from society. ከኅብረተ፡ ሰብ ፡ ተገለለ
[See also 'circulation']

**withdrawal** መውጣት
The withdrawal of troops marked the end of the war. የወታደሮቹ ፡ መውጣት ፡ የጦርነቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ

**make a withdrawal** ገንዘብ ፡ አወጣ
After making a withdrawal from the bank, he bought a ticket. ከባንክ ፡ ገንዘብ ፡ አውጥቶ ፡ ቲኬት ፡ ገዛ

**withdrawn** የገለልተኝነት
He has a withdrawn manner. የገለልተኝነት ፡ ጠባይ ፡ አለው

**withdrew,** see **withdraw**

**withheld,** see **withhold**

**wither** (vt.) አጨማደደ
Age has withered the old lady's face. እርጅና ፡ ያሮጊቷን ፡ ፊት ፡ አጨማዶታል

**wither** (vi.)
1. ጠወለገ. The plants withered in the hot sun. በፀሐይ ፡ ምክንያት ፡ አትክልቶቹ ፡ ጠወለጉ
2. መነመነ. Her hopes withered when she saw the stern expression on his face. ፊቱን ፡ ሲያጠቍር ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ተስፋዋ ፡ ሁሉ ፡ መነመነ

**withhold** (witheld)
1. ከመግለጽ ፡ ተቈጠበ. He withheld his consent until I agreed to make a down payment. የመጀመሪያ ፡ ክፍያ ፡ ለመክፈል ፡ እስክስማማ ፡ ፈቃደኛነቱን ፡ ከመግለጽ ፡ ተቈጠበ
2. ያዘ. He withheld payment until the damaged goods were replaced. የተበላሹት ፡ እቃዎች ፡ እስኪተኩ ፡ ድረስ ፡ ክፍያውን ፡ ያዘ
3. አገለለ. The captain withholds his men from attack. ሻምበሉ ፡ ወታደሮቹን ፡ ከውጊያ ፡ ያገላቸዋል
4. ገታ. He withheld his anger. ንዴቱን ፡ ገታ

**be withheld** ተነፈገ
Freedom is a right which cannot be withheld. ነጻነት ፡ ሊነፈግ ፡ የማይቻል ፡ መብት ፡ ነው

**within** (prep.)
1. በ --- ውስጥ. I expect an answer within three days. በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ መልስ ፡ እጠባበቃለሁ
Speeding is forbidden within the city limits. በከተማው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ከተወሰነ ፡ ፍጥነት ፡ በላይ ፡ መንዳት ፡ ክልክል ፡ ነው
2. በ -- ተራርቆ. The letters came within a few days of each other. ደብዳቤዎቹ ፡ በጥቂት ፡ ቀናት ፡ ተራርቀው ፡ ደረሱ
3. (= adv.) ራቅ ፡ ብሎ. We live within a mile of the station. ከጣቢያው ፡ አንድ ፡ ማይል ፡ ራቅ ፡ ብለን ፡ እንኖራለን
4. (= adv.) በማይበልጥ ፡ ርቀት. They live within a mile of the school. ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አንድ ፡ ማይል ፡ በማይበልጥ ፡ ርቀት ፡ ይኖራሉ
*We're within walking distance of the theater. ቤታችን ፡ ከቲያትሩ ፡ ቤት ፡ የሚያስኬዳው ፡ ጥቂት ፡ ነው

**within** (adv.) ከውስጥ
They will decorate your house within and without. ቤትህን ፡ ከውስጥም ፡ ከውጭም ፡ ያጌጡታል
He seemed calm, but within all was turmoil. የረጋ ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ ከውስጥ ፡ ጦፏል
*It is warm outside, but cold within. ደጁ ፡ ሞቃት ፤ ቤቱ ፡ ግን ፡ ብርድ ፡ ነው
[See also 'hearing, limit, memory, reach']

**without** (prep.)
1. ከ -- ውጭ. Soldiers are camped within and without the city walls. ወታደሮች ፡ ከከተማው ፡ አጥር ፡ ውስጥም ፡ ውጭም ፡ ሰፍረዋል
2. ያለ. Can I get in without a ticket? ያለ ፡ ቲኬት ፡ መግባት ፡ እችላለሁ ?
He was dismissed without reason. ያለ ፡ ምክንያት ፡ አስወጡት
You will have to do without luxuries. ያለቅንጦት ፡ ለመኖር ፡ መቻል ፡ አለብህ
3. ሰ + (negative imperfect). She left the room without saying a word. ምንም ፡ ሳትናገር ፡ ከቤት ፡ ወጣች
She went out without a hat. ባርኔጣ ፡ ሳታደርግ ፡ ከቤት ፡ ወጣች
Please bill me without delay! ሳትዘገይ ፡ ሒሳቡን ፡ ላክልኝ
*It is true without any doubt. ምንም ፡ ጥርጥር ፡ የሌለበት ፡ እውነት ፡ ነው

**without** (adv.)
1. ከውጭ. The wind howled without, but within the house it was quiet and warm. ከውጭ ፡ ነፋሱ ፡ ያጕረመርም ፡ ነበር ፤ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ጸጥ ፡ ያለና ፡ የሞቀ ፡ ነበር
2. ከውጭ ፡ በኩል. The curtains are white without and green within. መጋረጃው ፡ ከውጭ ፡ በኩል ፡ ነጭ ፡ ከውስጥ ፡ ደግሞ ፡ አረንጓዴ ፡ ነው
[See also 'delay, reservation, reserve']

**withstand** (withstood)
1. ቻለ. They withstood the heat of the desert. የበረኻውን ፡ ሙቀት ፡ ቻሉት
2. ሊገታ ፡ ቻለ. They withstood all temptations to leave the job. ሥራውን ፡ ለመልቀቅ ፡ የነበ ራቸውን ፡ ፍላጎት ፡ ሊገቱት ፡ ቻሉ
3. ተቋቋመ. Their durable friendship withstood many a heated argument. ጽኑ ፡ የሆነ ፡ ጓደኝነ ታቸው ፡ ብዙ ፡ የተፋፋመ ፡ ክርክርን ፡ ተቋቍ ሟል
4. ተከላከለ. The soldiers steeled themselves to withstand the attack. ወታደሮቹ ፡ ውጊያውን ፡ ለመከላከል ፡ ታጠቁ

**withstood,** see **withstand**

**witless** (= adv.) በማይገባ ፡ አኳኋን
He made some witless remark to the minister and got fired for it. በማይገባ ፡ አኳኋን ፡ ሚኒስት ሩን ፡ ስለተናገረው ፡ ከሥራው ፡ ተወገደ

**witness** (v.) አየ
Did you witness the accident? አደጋው ፡ ሲደር ስ ፡ አይተሃል ?

**witness** (n.)
1. ምስክር. The witnesses haven't been examined yet. ምስክሮቹ ፡ ገና ፡ አልተጠየቁም
2. ማስረጃ. This receipt is witness that the bill was paid. ደረሰኙ ፡ ሒሳቡ ፡ ለመከፈሉ ፡ ማ ስረጃ ፡ ነው

**bear witness against** መሰከረበት
He saw me hitting the man and bore witness against me. ሰውዬውን ፡ ስደበድብ ፡ አይቶኝ ፡ ስለነበረ ፡ መሰከረብኝ

**bear witness to**
1. መሰከረ ፤ መሰከረ(ለት). Her tears bear witness to her sadness. እንባዋ ፡ ማዘኗን ፡ ይመሰክራል
I will bear witness to his character. ስለጠባዩ ፡ እመሰክርለታለሁ
2. ምስክር ፡ ሆነ. She bore witness to his crimes. ለወንጀሉ ፡ ምስክር ፡ ሆነች

**give witness on behalf of** ለ --- መሰከረ(ለት)
He gave witness on behalf of the accused. ለተከሳሹ ፡ መሰከረለት

**wittingly** ሆን ፡ ብሎ
He wittingly offended the judge. ዳኛውን ፡ ሆ ን ፡ ብሎ ፡ አናደደው

**witty** ቀልደኛ
They always laugh when he is around because he is so witty. በጣም ፡ ቀልደኛ ፡ ስለሆነ ፡ እሱ ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ይሥቃሉ

**wives,** see **wife**

**wizard**
1. ጠንቋይ. The wizard cast a spell on the young woman. ጠንቋዩ ፡ በወጣቷ ፡ ሴት ፡ ላይ ፡ አስማት ፡ አደረገባት
2. እሳት. He is a wizard at solving math problems. ሒሳብ ፡ ሲሠራ ፡ እሳት ፡ ነው

**wizened** የተሸበሸበ
He kissed his old mother's wizened cheeks. የአሮጊት ፡ እናቱን ፡ የተሸበሸቡ ፡ ጉንጮች ፡ ሳመ

**wobble**
1. ተውተረተረ. The baby wobbled a little and fell down. ሕፃኑ ፡ ትንሽ ፡ ተውተርትሮ ፡ ወደቀ
2. ተንቀጠቀጠ. The steering wheel wobbles. የመ ኪናው ፡ መሪ ፡ ይንቀጠቀጣል

**wobbly, feel** ~
1. ተብረከረከ. My legs feel wobbly because I was sick in bed so long. ታምሜ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልጋ ፡ ስለሰነበትኩ ፡ እግሬ ፡ ይብረከረካል
2. ዋገርቀ. The chair feels wobbly; don't sit in it! ወንበሩ ፡ የሚዋዥቅ ፡ ስለሆነ ፡ አትቀመጥበት

**woe** ሐዘን
They expressed their woe in loud cries. ሐዘናቸ ውን ፡ በእሪታ ፡ ገለጹ

**woe to!** ወዮለት
Woe to those who break the law! ሕግን ፡ የሚ ጥሱ ፡ ወዮላቸው

**woeful**
1. አሳዛኝ. She cried upon hearing the woeful tale. አሳዛኙን ፡ ወሬ ፡ ስትሰማ ፡ አለቀሰች
2. ፍጹም. His woeful ignorance kept him from getting the job. ፍጹም ፡ ድንቁርናው ፡ ሥራውን ፡ ከማግኘት ፡ አገደው

**woke,** see **wake**

**wolf** (wolves) ተኩላ
The wolves attacked the hunters. ተኩላዎች ፡ አዳኞቹን ፡ አጠቋቸው

**wolves,** see **wolf**

**woman** (women) ሴት
The woman goes to the market. ሴትዮዋ ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ትወጣለች
A woman doctor will examine your wife. ሚስትህን ፡ ሴት ፡ ሐኪም ፡ ትመረምራታለች
[See also 'aged, old, young']

**womanhood**
1. የሴትነት ፣ ባሕርይ. Her womanhood was highly regarded by all. የሴትነት ፣ ባሕርይዋ ፣ በሁሉ ፣ ዘንድ ፣ የተደነቀ ፣ ነው
2. ሴቶች. Joan of Arc was an honor to womanhood. ጆን ፣ ኦፍ ፣ አርክ ፣ የሴቶች ፣ ክብር ፣ ነበረች
3. ሴት. She is undoubtedly the cream of womanhood. ያለጥርጥር ፣ የሴት ፣ ቁንጮ ፣ ነች

**grow to womanhood** ትልቅ ፣ ሴት ፣ ሆነች
The little girl we knew has grown to womanhood. የምናውቃት ፣ ትንሽ ፣ ልጅ ፣ ትልቅ ፣ ሴት ፣ ሆናለች

**womanish** እንደ ፣ ሴት
He has a womanish way of speaking. አነጋገሩ ፣ እንደ ፣ ሴት ፣ ነው

**womankind** ሴቶች
Womankind has the responsibility of rearing children. ሴቶች ፣ ልጆች ፣ የማሳደግ ፣ ኀላፊነት ፣ አለባቸው

**womanly**
1. የሴቶች ፣ ባሕርይ ፣ የሆነ. She has much womanly sympathy for those who need help. እርዳታ ፣ ለሚያስፈልጋቸው ፣ ሁሉ ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ የሴቶች ፣ ባሕርይ ፣ የሆነ ፣ ርኅራኄ ፣ አላት
2. የሴትነት ፣ ባሕርይ ፣ ያላት. Mother is a womanly person. እናታችን ፣ የሴትነት ፣ ባሕርይ ፣ ያላት ፣ ሰው ፣ ነች

**womb** ማሕፀን
It is questionable whether the child in the womb has a soul. በማሕፀን ፣ ውስጥ ፣ ያለ ፣ ፅንስ ፣ ነፍስ ፣ ያለው ፣ ወይም ፣ የሌለው ፣ መሆኑ ፣ አጠራጣሪ ፣ ነው

**women**, see **woman**

**womenfolk** ሴቶች
The womenfolk do all the preparing of meals here. እዚህ ፣ ምግብ ፣ የሚያዘጋጁት ፣ ሴቶች ፣ ናቸው

**won**, see **win**

**wonder** (v.)
1. ተደነቀ. I shouldn't wonder if it were true. እውነት ፣ ቢሆን ፣ አልደነቅም
2. አስገረመ(ው). +I don't wonder at her refusing to marry him. አላገባውም ፣ ማለቷ ፣ አያስገርመኝም
3. ተጠራጠረ. I often wonder whether it's right. ልክ ፣ መሆን ፣ አለመሆኑን ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ እጠራጠራለሁ
4. ብሎ ፣ አሰበ. They wondered what was in the package. ጥቅሉ ፣ ውስጥ ፣ ያለው ፣ ምን ፣ ይሆን ፣ ብለው ፣ አሰቡ
*I wonder what time it is. ስንት ፣ ሰዓት ፣ ይሆን ?
*I wonder what he'll do now. አሁን ፣ ምን ፣ ያደርግ ፣ ይሆን ?

**wonder** (n.)
1. አስገራሚ ፣ ነገር ፤ አስደናቂ ፣ ነገር. Television is one of the wonders of modern science. ዘመናዊ ፣ ሳይንስ ፣ ከፈጠራቸው ፣ አስገራሚ ፣ ነገሮች ፣ (አስደናቂ ፣ ነገሮች) ፣ ውስጥ ፣ አንዱ ፣ ቴሌቪዥን ፣ ነው
2. አድናቆት. We gazed in wonder at the pyramids. ፒራሚዶቹን ፣ አተኩረን ፣ በአድናቆት ፣ ተመለከትን
3. (= adj.) አስደናቂ. It's a wonder that you got here at all. እዚህ ፣ መድረስህ ፣ አስደናቂ ፣ ነው

**and small wonder** (noun) + አያስደንቅም
He failed his exam and small wonder. በፈተና ፣ መውደቁ ፣ አያስደንቅም

**be filled with wonder** ተደነቀ
The shepherds were filled with wonder by the vision. እረኞቹም ፣ በታያቸው ፣ ተአምር ፣ ተደነቁ
**no wonder** (noun) + አያስደንቅም ፤ (noun) + አያስገርምም
No wonder it's cold, the window is open. መብረዱ ፣ አያስደንቅም ፤ መስኮቱ ፣ ክፍት ፣ ነው
He was taken ill and no wonder; he's been working 16 hours a day for years. መታመሙ ፣ አያስገርምም ፤ ለብዙ ፣ ዓመት ፣ በቀን ፣ ዐሥራ ፣ ስድስት ፣ ሰዓት ፣ ይሠራ ፣ ነበር

**work wonders**
1. ግሩም ፣ ሆነ. His plan worked wonders. እቅዱ ፣ ግሩም ፣ ሆነ
2. ፍቱን ፣ ሆነ. This medicine works wonders for cold. ይህ ፣ መድኃኒት ፣ ለጉንፋን ፣ ፍቱን ፣ ነው

**wonderful**
1. ግሩም. The dinner was wonderful. እራቱ ፣ ግሩም ፣ ነበር
She is a wonderful cook. ግሩም ፣ ወጥቤት ፣ ነች
2. አስደናቂ. The traveler had wonderful adventures. መንገደኛው ፣ አስደናቂ ፣ ጀብዱ ፣ ፈጸመ

**wonderfully** በሚያስደንቅ ፣ አኳኋን
The woodwork is wonderfully carved. ከዕንጨት ፣ የተሠራው ፣ ነገር ፣ በሚያስደንቅ ፣ አኳኋን ፣ ተቀርጿል

**wondrous** የሚያስደንቅ
It is a wondrous sight. ለዓይን ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው

**wont** (n). ልማድ
He rose late, as was his wont. እንደ ፡ ልማዱ ፡ አርፍዶ ፡ ተነሣ
*He went to bed much earlier than was his wont. አለወትሮው ፡ በጊዜ ፡ ተኛ

**be wont to** የ --- ልማድ ፡ አለው ፤ ልማዱ ፡ ነው
He is wont to read the paper at breakfast. በቊርስ ፡ ላይ ፡ ጋዜጣ ፡ የማንበብ ፡ ልማድ ፡ አለው
He was wont to agree. መስማማት ፡ ልማዱ ፡ ነበር

**won't,** negative imperfect
I won't do it unless you pay me. ካልከፈልከኝ ፡ በስተቀር ፡ አልሠራውም

**woo**
1. ሊያባብል ፡ ሞከረ. He wooed her by giving her gifts. ገጸ ፡ በረከት ፡ በመስጠት ፡ ሊያባብላት ፡ ሞከረ
2. ሊያግባባ ፡ ሞከረ. The politician wooed his audience with promises. የፖለቲካ ፡ ዐዋቂው ፡ ተስፋ ፡ በመስጠት ፡ አድማጮቹን ፡ ሊያግባባቸው ፡ ሞከረ
3. ፈለገ. He wooed fame. ዝና ፡ ፈለገ

**wood** ዕንጨት
What kind of wood is it? ምን ፡ ዓይነት ፡ ዕንጨት ፡ ነው ?

**woods** ጫካ
Is there a path through the woods? በጫካው ፡ ውስጥ ፡ የእግር ፡ መንገድ ፡ አለ ?

**beat the woods** አውሬዎቹን ፡ ቀሰቀሰ
The servant began to beat the woods for game. አሽከርዩው ፡ ለአደን ፡ አውሬዎቹን ፡ መቀስቀስ ፡ ጀመረ
[See also 'pulp, shaving, sliver']

**wooded**
1. ጫካ ፡ የለበሰ. The wooded valleys and hills of Illubabor are quite beautiful. በኢሉባቦር ፡ የሚገኙ ፡ ጫካ ፡ የለበሱት ፡ ኮረብታዎችና ፡ ሸለቆዎች ፡ በጣም ፡ ውብ ፡ ናቸው
2. ጫካማ. We drove through wooded country on our way home. ወደ ፡ ቤታችን ፡ ስንመለስ ፡ ጫካማ ፡ አገር ፡ አቋረጥን

**wooden** የዕንጨት
The pan has a wooden handle. መጥበሻው ፡ የዕንጨት ፡ እጀታ ፡ አለው

**woodpile** የተከመረ ፡ ማገዶ
There is a woodpile in back of the house. ጓሮ ፡ የተከመረ ፡ ማገዶ ፡ አለ

**woodwork** ከዕንጨት ፡ የተሠራ ፡ ነገር
The woodwork is wonderfully carved. ከዕንጨት ፡ የተሠራው ፡ ነገር ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ ተቀርጿል

**woody** ዛፍ ፡ የለበሰ
The woody hillside prevents the rain from washing away the soil. ዛፍ ፡ የለበሰው ፡ የኮረብታው ፡ ጐን ፡ ዝናብ ፡ አፈሩን ፡ እንዳያጥበው ፡ ይከላከላል

**become woody** እንደ ፡ ዕንጨት ፡ ጠጠረ
Radishes become woody when they get old. ቀይ ፡ ሥር ፡ ሲቆይ ፡ እንደ ፡ ዕንጨት ፡ ይጠጥራል

**woof** ማግ
The warp and the woof make up the fabric of the cloth. ልብስ ፡ የሚሆነው ፡ ድርና ፡ ማግ ፡ ነው

**wool** ሱፍ
The blanket is made of pure wool. ብርድ ፡ ልብሱ ፡ የተሠራው ፡ ከንጹሕ ፡ ሱፍ ፡ ነው

**woolen** ከሱፍ ፡ የተሠራ
He bought a woolen tie. ከሱፍ ፡ የተሠራ ፡ ክራቫት ፡ ገዛ

**woolen sweater** ሱፍ ፡ ሹራብ
I bought a woolen sweater. ሱፍ ፡ ሹራብ ፡ ገዛሁ

**woolens** ሱፍ ፡ ልብስ
You must wear woolens in the winter. በክረምት ፡ ሱፍ ፡ ልብስ ፡ መልበስ ፡ አለብህ

**word** (v.)
1. አቀረበ. You had better word your suggestion more politely. ሐሳብህን ፡ በበለጠ ፡ ትሕትና ፡ ብታቀርብ ፡ ይሻላል
2. ጻፈ. He worded his message clearly. መልእክቱን ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ጻፈ
*How do you want to word the telegram? የቴሌግራሙ ፡ ቃል ፡ እንዴት ፡ እንዲሆን ፡ ትፈልጋለህ ?

**word** (n.)
1. ቃል (pl. ቃላት). We have to learn fifty new words for tomorrow. ለነገ ፡ ሌላ ፡ ኀምሳ ፡ አዳዲስ ፡ ቃላት ፡ ማጥናት ፡ አለብን
2. ነገር. Have you had any word from your son lately? ከልጅህ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የሰማኸው ፡ ነገር ፡ አለ ?

3. መልእክት. Leave word for me at the office if you can't come. ልትመጣ ፡ ካልቻልክ ፡ እቢሮዬ ፡ መልእክት ፡ ተውልኝ
4. ትእዛዝ. Father's word is law. ያባታችን ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው
5. አነጋገር. He is honest in word and deed. ባነጋገሩም ፡ ሆነ ፡ ባድራጎቱ ፡ ሐቀኛ ፡ ነው
6. ወሬ. No word has come from the battle front. ከጦሩ ፡ ግንባር ፡ ምንም ፡ ወሬ ፡ አልደረሰም
He is not given to words. ወሬ ፡ አይወድም

**word for word** ቃል ፡ በቃል
Don't translate word for word! ቃል ፡ በቃል ፡ አትተርጕም

**be as good as one's word** እንዳለ ፡ አደረሰ
She said she would finish the dress today, and was as good as her word. ልብሱን ፡ ዛሬ ፡ እጨርሳለሁ ፡ ብላ ፡ እንዳለችው ፡ አደረሰች

**by word of mouth** በቃል
The story was transmitted by word of mouth. ታሪኩ ፡ የተላለፈው ፡ በቃል ፡ ነው

**exchange words**
They exchanged bitter words. ክፉ ፡ ቃል ፡ ተነጋገሩ

**give (one's) word** ቃል ፡ ገባ
He gave his word that he would finish the job. ሥራውን ፡ እንደሚጨርስ ፡ ቃል ፡ ገባ

**give (one's) word of honor** ቃል ፡ ገባ(ለት) ። የመሐላ ፡ ቃል ፡ ሰጠ
I give you my word of honor that I will return. እንደምመለስ ፡ ቃል ፡ እገባልሃለሁ
He gave his word of honor not to lie. ላይዋሽ ፡ የመሐላ ፡ ቃሉን ፡ ሰጠ

**have a word with** ተነጋገረ
They had words with me about the matter. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ተነጋግረው ፡ ነበር
*May I have a word with you? እንዳፍታ ፡ ላነጋግርህ ?

**have words**
They had words yesterday. ትናንት ፡ ተሰዳድበው ፡ ነበር

**in a word** ባጭሩ
In a word, no. ባጭሩ ። አይሆንም

**in so many words** ቁርጥ ፡ አድርጎ
In so many words he told me to leave at once. ያኔውኑ ፡ እንድሄድ ፡ ቁርጥ ፡ አድርጎ ፡ ነገረኝ

**keep (one's) word** ቃሉን ፡ አከበረ
The boy kept his word. ልጁ ፡ ቃሉን ፡ አከበረ

**last word**
*This book is the last word on the subject. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የመጨረሻው ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያለው ፡ ነው
*She had the last word as always. እንደወትሮው ፡ እሷ ፡ እንዳለችው ፡ ሆነ

**leave word** ምልክት ፡ ተወ
He left word that he would be back soon. ቶሎ ፡ እመለሳለሁ ፡ ብሎ ፡ ምልክት ፡ ትቷል

**make (one) eat his words**
*They told him he would never succeed at anything, but he made them eat their words. ምንጊዜም ፡ አይሳካልህም ፡ ብለው ፡ ነግረውት ፡ ካሰበበት ፡ ደርሶ ፡ አሳፈራቸው

**mark my words!** ምን ፡ አለ ፡ በለኝ
Mark my words! He will be a great man someday. ምን ፡ አለ ፡ በለኝ ። አንድ ፡ ቀን ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ይሆናል

**my word!** ይገርማል
My word! Your children have certainly grown. ይገርማል! ልጆችህ ፡ በእውነት ፡ ትልልቅ ፡ ሆነዋል

**of few words** ብዙ ፡ የማይናገር
He is a man of few words but of profound thoughts. ብዙ ፡ የማይናገር ፡ ግን ፡ ሐሳበ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ነው

**put in a good word for one**
I'll put in a good word for you with the minister. በሚኒስትሩ ፡ ፊት ፡ ስላንተ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ እናገርልሃለሁ

**send word** ላከ(በት)
Please send me word of your safe arrival! ደኅና ፡ መድረስህን ፡ ላክብኝ

**take my word!** እመነኝ
Take my word for it, he's a liar. እመነኝ ። ውሸታም ፡ ነው

**upon my word** ሙት ። እምላለሁ
Upon my word, this is the worst mess I've ever seen. ሙት ። ይህ ፡ አይቼ ፡ የማላውቀው ፡ ዓይነት ፡ ብልሽት ፡ ነው
Upon my word, I never said it. እምላለሁ ። ይህንን ፡ አላልኩም
[See also 'breathe, fail, hard, mark, measured, mince, play, polite, sense, sharp']

## wording

1. አጻጻፍ. The wording of this letter is not clear. የዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ አጻጻፍ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም
The wording of the treaty is very difficult to understand. የስምምነቱን ፡ አጻጻፍ ፡ እንብቦ ፡ ለመረዳት ፡ ያስቸግራል

2. ቃላትን ፡ መምረጥ. Careful wording helps you make clear to others what you really mean. ቃላትን ፡ በጥንቃቄ ፡ መምረጥ ፡ ለማለት ፡ የምትፈልገውን ፡ ለሌሎች ፡ በግልጽ ፡ ለማስረዳት ፡ ይረዳሃል

**wordy** የተንዛዛ
His wordy explanations confuse people more than they explain anything. የተንዛዛ ፡ ማስረጃው ፡ ጉዳዩን ፡ ከማብራራት ፡ ይልቅ ፡ ሰዎችን ፡ ያደናግራል

**wore**, see **wear**

**work** (vt.)
1. አሠራ. He works his employees very hard. ሠራተኞቹን ፡ በኀይል ፡ ያሠራቸዋል
2. ሠራ. Do you know how to work an adding machine? በሒሳብ ፡ መኪና ፡ መሥራት ፡ ታውቃለህ ?
He worked the clay into a vase. ከጭቃ ፡ የአበባ ፡ ማስቀመጫ ፡ ሠራ
3. አዳበረ. The farmers worked the soil. ገበሬዎቹ ፡ መሬቱን ፡ አዳበሩት

**work** (vi.)
1. ሠራ. I work from eight to five. ከሁለት ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ እሠራለሁ
The mechanic is just now working on your car. ሜካኒኩ ፡ አሁን ፡ ያንተን ፡ መኪና ፡ መሥራት ፡ ይዟል
The elevator doesn't work. ሊፍቱ ፡ አይሠራም
He is working his way through college. እየሠራ ፡ የኮሌጅ ፡ ትምህርት ፡ ይማራል
2. ተጽዕኖ ፡ አለው. His music works on the mind of the listener. ሙዚቃው ፡ ባድማጩ ፡ አእምሮ ፡ ላይ ፡ ተጽዕኖ ፡ አለው

**work away** ያለማቋረጥ ፡ ሠራ
He worked away until the job was done. ሥራው ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ሠራ

**work for** ጣረ
Doctors work for the preservation of our health. ሐኪሞች ፡ ጤናችንን ፡ ለመጠበቅ ፡ ይጥራሉ

**work hard** በጣም ፡ ጣረ
They worked hard for peace. ለሰላም ፡ በጣም ፡ ጣሩ

**work in** ሥራውን ፡ ተለማመደ
Give him a chance to work in! ሥራውን ፡ እንዲለማመድ ፡ ዕድል ፡ ስጠው

**work (one) in** አስገባ
The dentist was very busy, but said he would be able to work me in late in the afternoon. የጥርስ ፡ ሐኪሙ ፡ በጣም ፡ ሥራ ፡ በዝቶበታል ፤ ሆኖም ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ እንደምንም ፡ ብዬ ፡ አስገባሃለሁ ፡ ብሎኛል

**work off**
*Work off your anger by taking a walk! ንዴትህ ፡ እንዲበርድልህ ፡ ተንሸራሸር

**work on** አግባባ
We are working on him to give us the day off. ቀኑን ፡ ዕረፍት ፡ እንዲሰጠን ፡ ለማድረግ ፡ እሱን ፡ እያግባባን ፡ ነው

**work out** (vt.)
1. ሠራ. I can work out these math problems. እነዚህን ፡ የሒሳብ ፡ ጥያቄዎች ፡ ልሠራ ፡ እችላለሁ
2. ፈጠረ. They're working out a new method for irrigating the land. መሬቱን ፡ በመስኖ ፡ ለማጠጣት ፡ አዲስ ፡ ዘዴ ፡ በመፍጠር ፡ ላይ ፡ ናቸው

**work out** (vi.)
1. ሠራ. How do you think this idea would work out? ይህ ፡ ሐሳብ ፡ እንዴት ፡ የሚሠራ ፡ ይመስልሃል ?
2. ደረሰ. How did things work out? ነገሩ ፡ ከምን ፡ ደረሰ ?
3. ተቃና(ለት). Their marriage just didn't work out. ጋብቻቸው ፡ ምንም ፡ አልተቃናላቸውም
4. ተሳካ(ለት). His plan did not work out. እቅዱ ፡ አልተሳካለትም
5. ተዋጣ. The new secretary did not work out. አዲሷ ፡ ጸሐፊ ፡ አልተዋጣችም

**(be) worked out** ተተነተነ
The plan is well worked out. እቅዱ ፡ በደንብ ፡ ተተንትኗል

**work over** አጠና
For my history class I worked over 20 volumes of Roman history. ለታሪክ ፡ ትምህርቴ ፡ ስለ ፡ ሮም ፡ ታሪክ ፡ ሀያ ፡ መጻሕፍት ፡ አጠናሁ

**work (oneself) too hard**
He works himself too hard. ራሱን ፡ በሥራ ፡ ያደክማል

**work up** ቀስ ፡ በቀስ ፡ አደገ
He worked up to a better job. ቀስ ፡ በቀስ ፡ ወደ ፡ ተሻለ ፡ ሥራ ፡ አደገ
*I'll have to work up an appetite. ሊያስርበኝ ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ ማድረግ ፡ አለብኝ

**work (one's) way through** ጥሶ ፡ አለፈ
I have to work my way through the crowd. በተሰበሰበው ፡ሕዝብ ፡ መሀከል ፡ ጥሼ ፡ ማለፍ ፡ አለብኝ
[See also 'feverishly, rage, steam']

**work** (n.)
1. ሥራ. The work isn't interesting. ሥራው ፡ አያስደስትም

His work is teaching. ሥራው ፡ አስተማሪነት ፡ ነው
Don't phone him at work! በሥራው ፡ ላይ ፡ እ ያለ ፡ አትደውልለት
2. ጽሑፍ. Hamlet is Shakespeare's best-known work. በጣም ፡ የታወቀው ፡ የሼክስፒር ፡ ጽሑፍ ፡ ሀምሌት ፡ ነው
3. ሥዕል. The artist considers that picture to be his greatest work. ሠዓሊው ፡ ከሠራቸው ፡ ሥዕሎች ፡ ሁሉ ፡ ለዚያ ፡ ሥዕል ፡ ከፍተኛ ፡ ግም ት ፡ ይሰጠዋል
*He put in one hour's work before breakfast. ከቁርስ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሠራ

**works**
1. ሥራዎች. New public works are being planned. አዲስ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚሆኑ ፡ ሥራዎ ች ፡ ታቅደዋል
All works of art should be protected against damage. የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ከጉዳ ት ፡ መጠበቅ ፡ አለባቸው
2. መጻሕፍት. Have you read all of Shakespeare's works? የሼክስፒርን ፡ መጻሕፍት ፡ በሞ ላ ፡ አንብበሃል ?
3. ፋብሪካ. The iron works is shut down. የብረት ፡ ፋብሪካው ፡ ተዘግቷል

**hard work** ልፋት
After years of hard work, he finally arrived. ከብዙ ፡ ዓመት ፡ ልፋት ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ተሳካለት

**(be) out of work** ሥራ ፡ ፈታ
He has been out of work since the factory closed. ፋብሪካው ፡ ከተዘጋ ፡ ጀምሮ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፈታ ፡ ነው

**(it) takes a lot of work** ብዙ ፡ ደከመ
It took a lot of work to convince him that we were right. ልክ ፡ መሆናችንን ፡ እሱን ፡ ለማሳ መን ፡ ብዙ ፡ ደከምን

**work** (adj.) የሥራ
Wear your work clothes when you come. ስትመጣ ፡ የሥራ ፡ ልብስህን ፡ ልበስ
[See also 'respite, short, swamp']

## workable
*This machine is in workable condition. ይህ ፡ መኪና ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል

## workday የሥራ ፡ ቀን
On a workday I must get up early. በሥራ ፡ ቀ ን ፡ በጧት ፡ መነሣት ፡ አለብኝ

## worker ሠራተኛ
There are two hundred workers in this factory. እዚህ ፡ ፋብሪካ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሠራተ ኞች ፡ አሉ

## working (n.)
*Do you understand the working of this machine? ይህ ፡ መኪና ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠራ ፡ ይገባሃል ?

**working** (adj.)
1. ሠራተኛ. The working girls have formed a club. ሠራተኞቹ ፡ ልጃገረዶች ፡ ክበብ ፡ አቋቋሙ
The working class is large in number. ሠራተኛ ው ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥሩ ፡ ከፍተኛ ፡ ነው
2. የሥራ. His working clothes were soiled with mud. የሥራ ፡ ልብሶቹ ፡ በጭቃ ፡ ተበክለ ዋል
May I call you during working hours? በሥራ ፡ ሰዓት ፡ ልደውልልህ ?

**working order, keep in good ~** በሚገባ ፡ ያዘ; **put in ~** እንዲሠራ ፡ አደረገ
Keep the car in good working order! መኪና ዋን ፡ በሚገባ ፡ ያዝ
Put the machine in working order! መሣሪያውን ፡ እንዲሠራ ፡ አድርገው

## working man ሠራተኛ
A working man needs some kind of insurance. ሠራተኛ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ዋስትና ፡ ያስፈልገዋል

## workman (workmen) ሠራተኛ
The workmen are on strike. ሠራተኞቹ ፡ አድ ማ ፡ ላይ ፡ ናቸው

## workmanship አሠራር
We admired the workmanship of the churches of Lalibela. የላሊበላን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ አሠ ራር ፡ አደነቅን

## workout የሰውነት ፡ ልምምድ
He had a good workout running in the field before breakfast. ከቁርስ ፡ በፊት ፡ሜዳው ፡ ላ ይ ፡ በመሮጥ ፡ ጥሩ ፡ የሰውነት ፡ ልምምድ ፡ አገኘ

**give a workout** ሞከሮ ፡ አየ
The mechanic gave the car a thorough workout after repairing it. ሜካኒኩ ፡ መኪናውን ፡ ከሠ ራ ፡ በኋላ ፡ በሚገባ ፡ ሞክሮ ፡ አየ

## workshop የመሣሪያ ፡ ቦታ
The workshop has all the machinery needed for car repairs. የመሣሪያው ፡ ቦታ ፡ ለመ ኪና ፡ ጥገና ፡ የሚያስፈልጉት ፡ መሣሪያዎች ፡ ሁ ሉ ፡ አሉት

## world (n.)
1. ዓለም. If you are good in this world, you'll be rewarded in the next. በዚህ ፡ ዓለም ፡ ደግ ፡ ሥ ራ ፡ ከሠራህ ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ዋጋህን ፡ ታ ገኛለህ

He has traveled all over the world. ዓለምን ፡ በ ሙሉ ፡ ዞሯል
She retired from the world to enter a convent. ዓለምን ፡ ንቃ ፡ ገዳም ፡ ገባች
2. ሰዎች. The world of sport was grieved by his death. የሱ ፡ መሞት ፡ የእስፖርት ፡ ሰዎች ን ፡ ሁሉ ፡ አሳዘነ
All the world is interested in space travel. ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በጠፈር ፡ ጉዞ ፡ ይደሰታሉ
*The business world was surprised by the devaluation. በገንዘቡ ፡ ዋጋ ፡ መቀነስ ፡ በንግ ድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ሁሉ ፡ ተሸበሩ
*The plant world is dependent on sunlight. የዕፀዋት ፡ ሕይወት ፡ በፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ላይ ፡ የተ መሠረተ ፡ ነው

**(a) world of**
*My holiday did me a world of good. ዕረፍቴ ፡ በጣም ፡ አድርጎ ፡ ጠቀመኝ
*Your visit did me a world of good. ጉብኝትህ ፡ ትልቅ ፡ ደስታ ፡ አተረፈልኝ

**(be) brought into the world** ተወለደ
He was brought into the world by a midwife. ባዋላጅ ፡ እርዳታ ፡ ተወለደ

**for the world** ምንም ፡ ቢሆን
I wouldn't hurt her feelings for the world. ምንም ፡ ቢሆን ፡ እሷን ፡ አላስቀይማትም

**in the world** ኧረ ፡ ለመሆኑ
Who in the world is he? ኧረ ፡ እሱ ፡ ለመሆኑ ፡ ማነው ?
*Where in the world have you been? የት ፡ ጠ ፋህ ?

**(be) out of this world** ታይቶ ፡ አይታወቅም
This food is out of this world. ይህ ፡ ምግብ ፡ ታ ይቶ ፡ አይታወቅም

**think the world of** ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ አለው
My father thinks the world of you. አባቴ ፡ ላን ተ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ አለው

**world** (adj.)
*We don't have a world language as yet. እስከሁን ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ የሚግባባበት ፡ አንድ ፡ ቋንቋ ፡ የለንም
[See also 'western']

## worldly ዓለማዊ
He is attached to worldly pleasures. ዓለማዊ ፡ ደ ስታን ፡ ይወዳል

## world powers ኃያላን ፡ መንግሥታት
Russia and the U.S. are world powers. አሜሪካ ና ፡ ሩሲያ ፡ ኃያላን ፡ መንግሥታት ፡ ናቸው

## worldwide
1. በመላው ፡ ዓለም ፡ የታወቀ. The association is worldwide. ማኅበሩ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የታወ ቀ ፡ ነው
2. ዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሆነ. They set up a worldwide organization of Ethiopian studies. ዓለም፡ አቀፍ ፡ የሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ ማኅበር ፡ አቋቋሙ

## worm ትል
The worm was crawling on the ground. ትሉ ፡ እመሬቱ ፡ ላይ ፡ እየተሳበ ፡ ይሄድ ፡ ነበር

## (be) worm-eaten
1. ነቀዘ. The wood is worm-eaten. ዕንጨቱ ፡ ነቅዟል
2. ትል ፡ በላው. The apple is worm-eaten. ቱፋ ው ፡ ትል ፡ የበላው ፡ ነው

## wormy የነቀዘ
The wormy wood broke, and the house collapsed. የነቀዘው ፡ ዕንጨት ፡ ተሰብሮ ፡ ቤቱ ፡ ተደረመሰ

## worn, see wear

## worn (adj.) ያለቀ
A beggar in a worn, tattered coat is at the door. ያለቀና ፡ የተበጣጠሰ ፡ ካፖርት ፡ የለበሰ ፡ ለማኝ ፡ እደጅ ፡ ቆሟል

**be worn down** ተበላ
The stone steps were worn down by many feet. የድንጋዩ ፡ ደረጃዎች ፡ ከእግር ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ተበልተው ፡ ነበር

## worn-out ያለቀ
Throw away this worn-out pair of shoes! እነዚህን ፡ ያለቁ ፡ ጫማዎች ፡ ጣላቸው

**be worn-out** ደከመ
He looks worn-out. የደከመው ፡ ይመስላል

## worried (adj.) የተጨነቀ
The worried mother cried until her child was found. የተጨነቀችው ፡ እናት ፡ ልጇ ፡ እስኪተገ ኘ ፡ ድረስ ፡ ታለቅስ ፡ ነበር
*He has a worried look. ሐሳብ ፡ የገባው ፡ ይመ ስላል

## worrisome
1. የተጨነቀ. The worrisome parents are constantly calling the police to find their child. የተጨነቁት ፡ ወላጆች ፡ ፖሊስ ፡ ልጃቸውን ፡ እንዲፈልግላቸው ፡ አሁንም ፡ አሁንም ፡ ይደውሉ ፡ ነበር

2. የመጨነቅ. His worrisome behavior irritates me. የመጨነቅ ፡ ጠባዩ ፡ ያበሳጨኛል

**worry** (worried), vt.

1. አስቸገረ. She was always worrying her husband for more money. ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ሁልጊዜ ፡ በመጠየቅ ፡ ባሏን ፡ አስቸገረችው
He worried me with foolish questions. ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ጥያቄዎች ፡ እየጠየቀ ፡ አስቸገረኝ
2. አሳሰበ. The future doesn't worry him. የወደፊቱ ፡ ምንም ፡ አያሳስበውም

**worry** (vi.) አሰበ ፤ ተጨነቀ
Don't worry! He will come soon. አታስብ ፤ ቶሎ ፡ ይመጣል
He is a very fearful person; he is always worrying about something. እሱ ፡ በጣም ፡ ፈሪ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ሁልጊዜ ፡ ይጨነቃል

**worry about** ተጨነቀ(በት)
You have nothing to worry about. ምንም ፡ የምትጨነቅበት ፡ ነገር ፡ የለም

**be worried** ሐሳብ ፡ ያዘው
I'm worried because I haven't heard from him in a week. ላንድ ፡ ሳምንት ፡ የሱን ፡ ወሬ ፡ ስላልሰማሁ ፡ ሐሳብ ፡ ይዞኛል

**worry** (worries), n. ሐሳብ ፤ ስጋት
Worry made his hair grey prematurely. ሐሳብ ፡ ያለጊዜው ፡ አሸበተው
Her face clouded with worry. ፊቷ ፡ በሐሳብ ፡ ጠቆረ
She got sick from worry. ከስጋት ፡ የተነሣ ፡ ታመመች

**give worry** አስጨነቀ
Her son gave her a great deal of worry. ልጇ ፡ ብዙ ፡ አስጨነቃት

**worse** የባሰ
First reports were bad, but worse soon followed. የመጀመሪያዎቹ ፡ መግለጫዎች ፡ መጥፎ ፡ ነበሩ ፤ ወዲያውኑ ፡ ደግሞ ፡ የባሱ ፡ ተከተሉ
Your work is bad, but mine is much worse. ሥራህ ፡ መጥፎ ፡ ነው ፤ የኔ ፡ ደግሞ ፡ በጣም ፡ የባሰ ፡ ነው

**worse than ever** ከምን ፡ ጊዜውም ፡ የባሰ
It's raining worse than ever. ከምን ፡ ጊዜውም ፡ የባሰ ፡ ዝናብ ፡ እየጣለ ፡ ነው

**be worse**
1. ባሰ(በት). The sick man seems worse today. የታመመው ፡ ሰውዬ ፡ ዛሬ ፡ የባሰበት ፡ ይመስላል
2. ከፋ. The actuality is worse than you suspect. እርግጡ ፡ አንተ ፡ ከምትጠረጥረው ፡ ይከፋል

**be worse off** እንዲያውም ፡ ባሰ(በት)
He is even worse off now because he has a broken leg. አሁን ፡ እግሩ ፡ ስለተሰበረ ፡ እንዲያውም ፡ ብሶበታል

**change for the worse** ባሰ(በት)
The weather changed for the worse. ያየሩ ፡ ጠባይ ፡ ባሰበት

**feel worse** ባሰ(በት)
He is feeling worse this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ ብሶበታል

**get worse**
1. ተበላሸ. The nation got better materially but worse spiritually. አገሪቱ ፡ በሀብት ፡ ስትሻሻል ፡ በመንፈሳዊ ፡ ረገድ ፡ ግን ፡ እየተበላሸች ፡ ሄደች
2. ጸና(በት). As the months went on, his illness got worse. ጊዜው ፡ እየገፋ ፡ ሲሄድ ፡ በሽታው ፡ እየጸናበት ፡ ሄደ

**get worse and worse** እየባሰ ፡ ሄደ
Her condition is getting worse and worse. ሁኔታዋ ፡ እየባሰ ፡ ሄደ

**grow worse and worse** እየባሰ ፡ ሄደ
The storm grew worse and worse. ዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ እየባሰ ፡ ሄደ

**make things worse** ነገሩን ፡ አባሰ
You are only making things worse by arguing. ክርክርህ ፡ ነገሩን ፡ ያብሰዋል

**none the worse**
*I like a man none the worse for being candid. እውነቱን ፡ ስለተናገረ ፡ አንድን ፡ ሰው ፡ አልጠላውም

**be none the worse** ምንም ፡ አልጎዳውም
He is none the worse for having been imprisoned all year. ዓመቱን ፡ በሙሉ ፡ መታሰሩ ፡ ምንም ፡ አልጎዳው
[See also 'bad, turn out']

**worsen** (vt.) አባሰ(በት)
Smoking will worsen your cough. ማጨስ ፡ ሳልህን ፡ ያብስብሃል

**worsen** (vi.) ባሰ
The patient's condition continues to worsen. የበሽተኛው ፡ ሁኔታ ፡ እየባሰ ፡ ሄደ

**worship** (worshiped, or worshipped), v.
1. አመለከ. They worship gods. ባማልክት ፡ ያመልካሉ
A miser worships money. ጩቅ ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ያመልካል
2. ሰገደ. The Israelites were punished for worshipping graven images. እስራኤላውያን ፡ ለተቀረጹ ፡ ምስሎች ፡ በመስገዳቸው ፡ ተቀጥተው ፡ ነበር

3. አስቀደሰ. Where do you worship? የምታስቀድሰው ፡ የት ፡ ነው ?
4. በጣም ፡ ወደደ. She worships her mother. እናቷን ፡ በጣም ፡ ትወዳለች

**worship** (n.)
1. ማምለክ. The worship of God is fostered by many religions. ብዙ ፡ ሃይማኖቶች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማምለክን ፡ ይደግፋሉ
2. ከፍተኛ ፡ ክብር ፡ መስጠት. Hero worship is common among young men. ለጀግና ፡ ከፍተኛ ፡ ክብር ፡ መስጠት ፡ በወጣቶች ፡ ዘንድ ፡ የተለመደ ፡ ነው

**place of worship** የመጸለያ ፡ ቦታ
Places of worship should never be closed. የመጸለያ ፡ ቦታዎች ፡ ፈጽሞ ፡ መዘጋት ፡ የለባቸውም
[See also 'divine, house ']

**worshipper** ምእመን (pl. ምእመናን)
The worshippers gathered at the shrine. ምእመናኑ ፡ በቅዱስ ፡ ቦታ ፡ ተሰበሰቡ

**worst** (n.) የባሰ
But wait, I haven't told you the worst. ኧረ ፡ ቆይ ፤ ገና ፡ የባሰውን ፡ አልነገርኩህም
The destruction of Kara Qore by an earthquake was the worst in recent times. የካራ ፡ ቆሬ ፡ በመሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ምክንያት ፡ መጥፋት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ከደረሱት ፡ ጥፋቶች ፡ ሁሉ ፡ የባሰ ፡ ነበር
*He got the worst of the argument. በክርክሩ ፡ ተሸነፈ

**worst** (adj.)
1. ከ -- ሁሉ ፡ በጣም ፡ የከፋ. It's the worst accident I can remember. ከማስታውሰው ፡ አደጋ ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የከፋ ፡ ነው
2. ከፉ. I wouldn't wish that awful job on my worst enemy. ያን ፡ አስጠሊ ፡ ሥራ ፡ ለከፉ ፡ ጠላቴም ፡ አልመኘው
*I got the worst piece. ለኔ ፡ መጥፎው ፡ ደረሰኝ

**worst** (adv.)
*He acts worst when he is tired. በደከመ ፡ ጊዜ ፡ ከምንጊዜም ፡ የባሰ ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ይሠራል

**at worst** ግፋ ፡ ቢል
At worst, the storm may last a week. ግፋ ፡ ቢል ፡ ዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ቢቆይ ፡ ነው

**be worst off** ባሰ(በት)
Of the three, he is worst off. ከሦስቱ ፡ እሱ ፡ የባሰበት ፡ ነው

**for the worst**
I am prepared for the worst. ከሁሉ ፡ የከፋ ፡ ነገር ፡ ቢመጣም ፡ ተዘጋጅቻለሁ

**if worst comes to worst** የባሰ ፡ ቢብስ
If worst comes to worst, we can always sell our property. የባሰ ፡ ቢብስ ፡ ምንጊዜም ፡ ንብረታችንን ፡ ልንሸጥ ፡ እንችላለን

**(be) worsted** ተሸነፈ
He was badly worsted in the fight. በጥሉ ፡ ላይ ፡ ክፉኛ ፡ ተሸነፈ

**worth** (n.)
1. ምንነት ፤ ዋጋ. You can't tell a man's worth by the color of his skin. የሰውን ፡ ምንነት ፡ በቆዳው ፡ ቀለም ፡ ልታውቅ ፡ አትችልም
The intrinsic worth of a man cannot be measured by his wealth. የሰው ፡ ልጅ ፡ እውነተኛ ፡ ዋጋው ፡ በሀብቱ ፡ መጠን ፡ ሊመዘን ፡ አይችልም
2. ጥቅም. We should read books of real worth. እውነተኛ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጡ ፡ መጻሕፍት ፡ ማንበብ ፡ አለብን
3. ግምት. What is it worth to you? ምን ፡ ግምት ፡ ትሰጠዋለህ ?
*I know his worth as a friend. ለጓደኝነት ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ አውቀዋለሁ

**worth of**
*Give me fifty cents' worth of salt. የኀምሳ ፡ ሳንቲም ፡ ጨው ፡ ስጠኝ

**worth** (adj.) የሚገባ
This is a movie worth seeing. ይህ ፡ ሊታይ ፡ የሚገባው ፡ ፊልም ፡ ነው
The matter isn't worth mentioning. ነገሩ ፡ መጠቀስ ፡ የሚገባው ፡ አይደለም

**be worth**
1. አወጣ. I paid 300 dollars for it, but it's worth more now. የከፈልኩት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ነው ፤ አሁን ፡ ግን ፡ ይበልጥ ፡ ያወጣል
That horse is worth five hundred dollars. ያ ፡ ፈረስ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ያወጣል
2. አለው. He is worth a million dollars. አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ አለው
3. ይገባል. It's worth the trouble. ቢጨነቁለት ፡ ይገባል
4. ዋጋ ፡ አለው. The frame itself is worth more than the picture. ከሥዕሉ ፡ ይልቅ ፡ ክፈፉ ፡ ብቻውን ፡ የበለጠ ፡ ዋጋ ፡ አለው
5. ጠቀመ. Is the book worth reading? መጽሐፉን ፡ ቢያነቡት ፡ ይጠቅማል?
*It isn't worth the effort. የጥረቱን ፡ ያህል ፡ አይሆንም

**for what it is worth** እንዳለ
I pass the news on to you for what it is worth. ወሬውን ፡ እንዳለ ፡ ላንተ ፡ አስተላልፍልሃለሁ

**(one's) money's worth**
*We certainly got our money's worth from our car. በእርግጥ ፡ ለመኪናችን ፡ ያወጣንበትን ፡ ያህል ፡ አገልግሎት ፡ አገኘን
[See also 'while']

**worthless** ዋጋ ፡ ቢስ ፤ የማይረባ
He squandered his money on worthless things. ለዋጋ ፡ ቢስ ፡ (ለማይረባ) ፡ እቃ ፡ ገንዘቡን ፡ አባከነ

**be worthless** ዋጋ ፡ የለውም
This money is worthless because it is counterfeit. ይህ ፡ የሐሰት ፡ ገንዘብ ፡ ስለሆነ ፡ ዋጋ ፡ የለውም

**worthwhile** የሚረባ
A worthwhile book is more valuable than many films. የሚረባ ፡ መጽሐፍ ፡ ከብዙ ፡ ፊልም ፡ የበለጠ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው

**be worthwhile** ዋጋ ፡ አለው ፤ ጠቀመ
Does your job seem worthwhile? ሥራህ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ይመስልሃል ?
The question has narrowed down to this: is it worthwhile or not? ጉዳዩ ፡ በዚህ ፡ ተወስኗል ፤ ዋጋ ፡ አለው ፡ ወይስ ፡ የለውም ?
Is it worthwhile retreading the tire? ጎማውን ፡ ማሳደስ ፡ ይጠቅማል ?

**be hardly worthwhile** ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ነው
All this fussing about such a small matter is hardly worthwhile. ስለዚህ ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መቸገር ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ነው

**worthy**
1. ዋጋ ፡ ያለው. This is for a worthy cause. ይህ ፡ ዋጋ ፡ ላለው ፡ ዓላማ ፡ ነው
2. እርዳታ ፡ የሚያስፈልገው. She helps only the worthy poor. እርዳታ ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ድኾች ፡ ብቻ ፡ ትረዳለች

**worthy of** የሚገባ
His courage was worthy of high praise. ጀግንነቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ምስጋና ፡ የሚገባው ፡ ነው

**make (one) worthy** ብቁ ፡ አደረገ
His rectitude makes him worthy to be a judge. ታማኝነቱ ፡ ለዳኝነት ፡ ብቁ ፡ አደረገው
[See also 'note, notice']

**would**
1. imperfect (affirmative, negative). He said he would come in ten minutes. በዐሥር ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ እመጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ነበር
I thought that would happen. ይህ ፡ ይደርሳል ፡ ብዬ ፡ አስቤ ፡ ነበር
He would never take the job. ምንም ፡ ቢሆን ፡ ሥራውን ፡ አይቀበልም
2. simple imperfect + ነበር. The children would play for hours in the park. ልጆቹ ፡ በመናፈሻው ፡ ቦታ ፡ ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር
He would have helped if you had asked him. ጠይቀኸው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይረዳህ ፡ ነበር
*Please, would you hand me that book. ያንን ፡ መጽሐፍ ፡ ታቀብለኝ

**would like** ይፈልግ ፡ ነበር; (negative) አይፈልግም
I would like to go with you, but I can't. ካንተ ፡ ጋር ፡ ለመሄድ ፡ እፈልግ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ አልችልም
I wouldn't like anyone to steal my bike. ቢስኪሌቴን ፡ ማንም ፡ እንዲሰርቀኝ ፡ አልፈልግም

**would rather**
*Would you rather go to the theater? ወደ ፡ ቲያትሩ ፡ ብትሄድ ፡ ይሻል ፡ ይሆን ?
*We would rather live in the country. ባላገር ፡ ብንኖር ፡ ይሻለናል

**would that**
*Would that I had bought the farm when it was so cheap! ምነው ፡ ርካሽ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ የእርሻውን ፡ መሬት ፡ በገዛሁ ፡ ኖሮ

**would-be** ወደፊት ፡ ለመሆን ፡ የሚመኝ
Several would-be actors came to the theater. አንዳንድ ፡ ወደፊት ፡ ተዋናይ ፡ ለመሆን ፡ የሚመኙ ፡ ወደ ፡ ቲያትሩ ፡ መጡ

**wound**, see **wind**

**wound** (v.)
1. አቈሰለ. The hunter wounded the animal with one shot. አዳኙ ፡ እንስሳውን ፡ ባንድ ፡ ጥይት ፡ አቈሰለው
2. ስሜቱን ፡ ጐዳ. His cruel words wounded him. መጥፎ ፡ ንግግሩ ፡ ስሜቱን ፡ ጐዳው

**wound** (n.) ቊስል
It will be a couple of months before the wound in his leg is healed. የእግሩ ፡ ቊስል ፡ እስኪድን ፡ ድረስ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ይፈጃል

**be a wound to** አጐደፈ(በት)
The loss of his job was a wound to his pride. ሥራውን ፡ ማጣቱ ፡ ክብሩን ፡ አጐደፈበት

**wounded** (adj.) የቈሰለ
An annuity is paid to all wounded patriots. ለቈሰሉት ፡ አርበኞች ፡ ሁሉ ፡ አበል ፡ ይከፈላቸዋል

**wounded man** ቊስለኛ
The wounded man soon died. ቊስለኛው ፡ ወዲያውኑ ፡ ሞተ

**be wounded** ቈሰለ
Several men were wounded in the brawl. በጥሉ ፡ ጊዜ ፡ አያሌ ፡ ሰዎች ፡ ቈሰሉ

**wove**, see **weave**

**wrang**, see **wring**

**wrangle** ተጨቃጨቀ
The children are always wrangling about something. ሕፃናቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንደተጨቃጨቁ ፡ ነው

**wrap** (wrapped)
1. ጠቀለለ. She wrapped the baby in a blanket. ሕፃኑን ፡ በብርድ ፡ ልብስ ፡ ጠቀለለችው
Please wrap the gift! ስጦታውን ፡ ትጠቀልለው
2. ጠመጠመ. She wrapped a scarf around her head. ራሷ ፡ ላይ ፡ ያንገት ፡ ፎጣ ፡ ጠመጠመች
**be wrapped** ተሸፈነ
The incident is wrapped in mystery. ጉዳዩ ፡ ባልታወቀ ፡ ምስጢር ፡ የተሸፈነ ፡ ነው
**wrap around one** አለበሰ
She wrapped a blanket around the baby. ሕፃኑን ፡ ብርድ ፡ ልብስ ፡ አለበሰችው
**wrap oneself in**
1. ለበሰ. Wrap yourself in a blanket while I dry your clothes. ልብስህን ፡ እስካደርቅልህ ፡ ድረስ ፡ ብርድ ፡ ልብስ ፡ ልበስ
2. ደረበ. She wrapped herself in a shawl. ያንገት ፡ ልብስ ፡ ደረበች
**wrap up** ጠቀለለ
Shall I wrap it (up) for you? ልጠቅልልህ ?
**(be) wrapped up**
*She's wrapped up in her children. ሐሳቧ ፡ ልጆቿ ፡ ናቸው
**(be all) wrapped up** ተዋጠ
He is all wrapped up in his work. በሥራው ፡ ተውጧል
[See also 'shroud']

**wrap(s)** ተደራቢ
Scarfs, coats, and furs are wraps. ፎጣ ፤ ካፖርትና ፡ ባለ ፡ ጸጉር ፡ ልብስ ፡ ተደራቢዎች ፡ ናቸው

**wrapper** መጠቅለያ
The newspaper is mailed in a paper wrapper. ጋዜጣው ፡ በወረቀት ፡ መጠቅለያ ፡ ተደርጎ ፡ ተላከ

**wrapping** ሽፋን
Can you get the wrapping off? ሽፋኑን ፡ ልታነሣው ፡ ትችላለህ ?

**wrapping paper** መጠቅለያ ፡ ወረቀት
I need more wrapping paper for the package. ለጥቅሉ ፡ ተጨማሪ ፡ መጠቅለያ ፡ ወረቀት ፡ እፈልጋለሁ

**wrath** ቁጣ
A soft answer turns away wrath. የለሰለሰች ፡ ምላስ ፡ ቁጣን ፡ ታበርዳለች
**be full of wrath** በጣም ፡ ተናደደ
She was full of wrath against the landlord. በቤቱ ፡ ጌታ ፡ በጣም ፡ ተናዳ ፡ ነበር

**wreath** የአበባ ፡ ጉንጉን
He placed a wreath on the grave. በመቃብሩ ፡ ላይ ፡ የአበባ ፡ ጉንጉን ፡ አስቀመጠ

**wreathe** ጐነጐነ
The children wreathed flowers to put on the soldier's grave. ልጆቹ ፡ በወታደሩ ፡ መቃብር ፡ ላይ ፡ ለማኖር ፡ አበባ ፡ ጐነጐኑ
**be wreathed in** ተሞላ
His face was wreathed in smiles. ፊቱ ፡ በፈገግታ ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር

**wreck** (v.)
1. እንክትክት ፡ አደረገ. A tree fell on my car and wrecked it. ዛፍ ፡ መኪናዬ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ እንክትክት ፡ አደረጋት
2. አመድ ፡ አደረገው. The crash wrecked the car. ግጭቱ ፡ መኪናዋን ፡ አመድ ፡ አደረጋት
3. አፈራረሰ. The explosion wrecked the whole plant. ፈንጂው ፡ ፋብሪካውን ፡ በሙሉ ፡ አፈራረሰው
4. አፈረሰ. Wrecking an altar is a sacrilege. ታቦት ፡ ማፍረስ ፡ የረከሰ ፡ ተግባር ፡ ነው
5. ሰባበረ. He was so nervous that he all but wrecked the machine. ከመርበትበቱ ፡ የተነሣ ፡ መኪናዋን ፡ ሊሰባብራት ፡ ምንም ፡ አልቀረው
6. ጐዳ. Poor habits can wreck one's health. መጥፎ ፡ ልማድ ፡ የሰውን ፡ ጤንነት ፡ ይጐዳል
7. አጉል ፡ አደረገ. The rain wrecked our plans for the picnic. ዝናቡ ፡ ለሽርሽር ፡ ያለንን ፡ እቅድ ፡ አጉል ፡ አደረገብን
8. አበላሸ. His extravagance wrecked his business. ገንዘብ ፡ ማባከኑ ፡ ጉዳዩን ፡ አበላሸው
**be wrecked** እንክትክቱ ፡ ወጣ
The car was completely wrecked. መኪናዋ ፡ በፍጹም ፡ እንክትክቷ ፡ ወጣ

**wreck** (n.)
1. ፍርስራሽ. The bodies are still buried in the wreck. ሬሳዎቹ ፡ ገና ፡ ፍርስራሹ ፡ ውስጥ ፡ እንደተቀበሩ ፡ ናቸው

2. አደጋ. Were any killed in the wreck? በአደጋው ፡ የሞቱ ፡ ነበሩ ?
3. በግጭት ፡ የተሰባበረ ፡ ነገር. She averted her eyes from the wreck. በግጭቱ ፡ ከተሰባበረው ፡ ነገር ፡ ዓይኗን ፡ ዞር ፡ አደረገች
4. (የመርከብ) ፡ አሰባበር. I heard an authentic account of the wreck given by one of the ship's officers. ስለ ፡ መርከቡ ፡ አሰባበር ፡ ከመርከቡ ፡ መኰንኖች ፡ አንዱ ፡ የሰጠውን ፡ የሚታመን ፡ መግለጫ ፡ ሰማሁ
5. ጤና ፡ ያጣ ፡ ሰው. He is a wreck from overwork. ከመጠን ፡ በላይ ፡ ከመሥራት ፡ የተነሣ ፡ ጤና ፡ ያጣ ፡ ሰው ፡ ነው

**wreck of** የተሰባበረ
The wrecks of three ships were cast upon the shore by the waves. ሦስት ፡ የተሰባበሩ ፡ መርከቦች ፡ በሞገድ ፡ ባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ተወርውረዋል

**be a nervous wreck** ናላው ፡ ዞረ
After taking care of his children for awhile, I am a nervous wreck. ልጆቹን ፡ ስጠብቅለት ፡ ቆይቼ ፡ ናላዬ ፡ ዞረ

**cause the wreck** (= be wrecked) ወደመ
+Heavy rains caused the wreck of crops. አዝመራው ፡ በከባድ ፡ ዝናም ፡ ምክንያት ፡ ወደመ
[See also 'train']

**wreckage** ባደጋ ፡ የተጨረመተ
He was pinned under the wreckage of his car. ባደጋው ፡ ከተጨረመተው ፡ መኪና ፡ ሥር ፡ ተቀርቅሮ ፡ ነበር

**wrecked** (adj.) የተሰበረ ፤ የተጐዳ
The wrecked cars were towed away by the police. የተሰበሩትን ፡ (የተጐዱትን) ፡ መኪናዎች ፡ ፖሊሶች ፡ ጐትተው ፡ ወሰዷቸው

**wrench** (vt.)
1. መንጥቆ ፡ ወሰደ. He wrenched the book from my hands. መጽሐፉን ፡ ከእጄ ፡ መንጥቆ ፡ ወሰደ
2. (= vi.) ወለቀ. +I wrenched my shoulder trying to push my car. መኪናዬን ፡ እገፋለሁ ፡ ብዬ ፡ ትከሻዬ ፡ ወለቀ
3. (= vi.) ወለም ፡ አለው. +She wrenched her knee when she fell. በወደቀች ፡ ጊዜ ፡ ጉልበቷ ፡ ወለም ፡ አላት

**wrench off** በኀይል ፡ ጠምዝዞ ፡ ሰበረ
He wrenched the knob off when he was trying to open the door. መዝጊያውን ፡ ለመክፈት ፡ ሲሞክር ፡ እጀታውን ፡ በኀይል ፡ ጠምዝዞ ፡ ሰበረው

**wrench** (n.) ኪያቢ
I need a wrench to tighten this bolt. ብሎኑን ፡ ለማጥበቅ ፡ ኪያቢ ፡ ያስፈልገኛል

**wrest**
1. በጉልበት ፡ ነጠቀ. He wrested the knife from the crazy man. ሰንጢውን ፡ ከእብዱ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ በጉልበት ፡ ነጠቀ
2. በኀይል ፡ ነጠቀ. The army wrested power from the dictator. ሰራዊቱ ፡ የአምባገነኑን ፡ ሥልጣን ፡ በኀይል ፡ ነጠቀው

**wrest a living** ጥሮ ፡ ግሮ ፡ ኖረ
The farmer wrests a living from the soil. ገበሬው ፡ በእርሻ ፡ ጥሮ ፡ ግሮ ፡ ይኖራል

**wrestle** ታገለ
He wrestled with the thief, but the thief broke loose. ሌባውን ፡ ታግሎት ፡ ነበር ፤ ግን ፡ አመለጠው
I've been wrestling with this problem for hours. ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ከዚህ ፡ ጥያቄ ፡ ጋር ፡ ስታገል ፡ ነበር

**wrestler** ታጋይ ፤ ትግለኛ
The wrestler grappled with his opponent. ታጋዩ ፡ ከተቃዋሚው ፡ ጋር ፡ ተናነቀ
The champion wrestler seems invincible. ሻምፒዮኑ ፡ ትግለኛ ፡ የማይበገር ፡ ይመስላል

**wrestling** ትግል
I like to watch wrestling. ትግል ፡ መመልከት ፡ እወዳለሁ

**wrestling match** የትግል ፡ ግጥሚያ
Today we watched a wrestling match. ዛሬ ፡ የትግል ፡ ግጥሚያ ፡ አየን

**wretch**
1. ምስኪን. The wretch was begging for bread by the roadside. ምስኪኑ ፡ መንገድ ፡ ዳር ፡ ሆኖ ፡ ዳቦ ፡ ይለምን ፡ ነበር
2. እርጉም. Some wretch stole my books. አንድ ፡ እርጉም ፡ መጽሐፎቼን ፡ ሰረቀ

**wretched**
1. ጨቋኝ. The wretched tyrant reduced the prosperous city to a poor village. ጨቋኙ ፡ ገዥ ፡ የበለጸገችውን ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ድኽነት ፡ አወረዳት
2. ምስኪን. The wretched people were begging for food. ምስኪኖቹ ፡ ሰዎች ፡ ምግብ ፡ ይለምኑ ፡ ነበር
3. መጥፎ. A wretched meal of boiled potatoes was all I received. ያገኘሁት ፡ ምግብ ፡ መጥፎ ፡ የተቀቀለ ፡ ድንች ፡ ብቻ ፡ ነው

**feel wretched** ደኅንነት ፡ አይሰማውም
I still feel wretched even though I got off the plane some hours ago. ከአውሮፕላን ፡ ከወረድኩ ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ሰዓት ፡ ቢሆንም ፡ አሁንም ፡ ደኅንነት ፡ አይሰማኝም

**wriggle**
1. ተቅነጠነጠ. The little children wriggled in their seats from boredom. ትንንሾቹ ፡ ልጆች ፡ ከመሰልቸት ፡ የተነሣ ፡ መቀመጫቸው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ተቅነጠነጡ
2. ተጥመለመለ. The worm wriggled on the hook. ትሉ ፡ መንጠቆው ፡ ላይ ፡ ይጥመለመል ፡ ነበር

**wriggle out**
1. ተጥመልምሎ ፡ ወጣ. The worm wriggled out of my hand when I tried to put it on the hook. መንጠቆው ፡ ላይ ፡ ልሰካው ፡ በሞከርኩ ፡ ጊዜ ፡ ትሉ ፡ ከእጄ ፡ ውስጥ ፡ ተጥመልምሎ ፡ ወጣ
2. በዘዴ ፡ አመለጠ. That boy can wriggle out of any difficulty. ያ ፡ ልጅ ፡ ከማንኛውም ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ በዘዴ ፡ ሊያመልጥ ፡ ይችላል

**wring** (wrang, wrung)
1. አሸሸ. He stood there crying and wringing his hands. እዚያው ፡ ቆሞ ፡ እጁን ፡ እያሸሸ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር
2. ጠመዘዘ. Wring the clothes before you hang them up! ልብሶቹን ፡ ከማስጣትህ ፡ በፊት ፡ ጠምዝዛቸው
3. አጥብቆ ፡ ጨበጠ. He wrung his old friend's hand in joy at seeing him. የድሮ ፡ ጓደኛውን ፡ በማየቱ ፡ ተደስቶ ፡ እጁን ፡ አጥብቆ ፡ ጨበጠ
4. አስተፋ. The beggar could wring money from a miser with his sad story. አሳዛኝ ፡ ታሪክ ፡ በመንገር ፡ ለማኝ ፡ ከጩቅ ፡ ገንዘብ ፡ ሊያስተፋ ፡ ይችላል
*The police wrung a confession out of him. ፖሊሶች ፡ በማስገደድ ፡ አሳመኑት

**wring (one's) heart** ልቡን ፡ በኀይል ፡ ነካ
Her sad story wrung our hearts. አሳዛኝ ፡ ታሪኩ ፡ ልባችንን ፡ በኀይል ፡ ነካው

**wring out** ጠመዘዘ
Wring out your wet shirt! እርጥቡን ፡ ሸሚዝህን ፡ ጠምዝዘው

**wring water from** ጨመቀ
The maid wrung water from the wet towel. ገረዷ ፡ እርጥቡን ፡ ፎጣ ፡ ጨመቀችው

**wrinkle** (vt.)
1. አጨማደደ. Rain wrinkles clothing. ዝናብ ፡ ልብስ ፡ ያጨማዳል
2. አኰማተረ. He wrinkled his forehead. ግንባሩን ፡ አኰማተረ

**wrinkle** (vi.) ተጨማደደ
This silk wrinkles easily. ይህ ፡ ሐር ፡ በቀላሉ ፡ ይጨማደዳል

**be wrinkled** ቆዳው ፡ ተሸበሸበ
The aged man was wrinkled and bent. ሽማግሌው ፡ ቆዳቸው ፡ ከመሸብሸቡም ፡ በላይ ፡ ጉብጠዋል
[See also 'seam']

**wrinkle** (n.)
1. ሽብሽብ. There was dirt in the wrinkles of her forehead. በግንባሯ ፡ ሽብሽብ ፡ ውስጥ ፡ ጉድፍ ፡ ነበር
2. የተጨማደደ. She ironed out the wrinkles in her dress. የተጨማደደውን ፡ ልብሷን ፡ በተኩስ ፡ አስተካከለችው

**be full of wrinkles** ተጨማደደ
Her face is full of wrinkles. ፊቷ ፡ ተጨማዷል
[See also 'seam']

**wrist** የእጅ ፡ አንጓ
I dislocated my wrist when trying to lift the heavy box. ከባዱን ፡ ሣጥን ፡ አነሣለሁ ፡ ብዬ ፡ የእጄን ፡ አንጓ ፡ ወለም ፡ አለኝ

**wrist watch** የእጅ ፡ ሰዓት
Buy me a wrist watch! የእጅ ፡ ሰዓት ፡ ግዛልኝ

**writ** ማዘዣ
A writ from the judge ordered the man's release from jail. የዳኛው ፡ ማዘዣ ፡ ሰውዬው ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ እንዲለቀቅ ፡ አዘዘ

**write** (wrote), vt.
1. ጻፈ. Write me a letter! ደብዳቤ ፡ ጻፍልኝ
2. ደረሰ. Dickens wrote novels. ዲክንስ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪኮችን ፡ ደረሰ
Mozart wrote symphonies. ሞዛርት ፡ ሲምፎኒ ፡ ሙዚቃ ፡ ደረሰ

**write** (vi.)
1. ጻፈ. He writes with a pen. በብዕር ፡ ይጽፋል
This pen doesn't write. ይህ ፡ ብዕር ፡ አይጽፍም
2. ጽሑፍ ፡ አቀረበ. He writes for the newspaper. ለጋዜጣው ፡ ጽሑፍ ፡ ያቀርባል

**be written**
1. ተጻፈ. The letter was written in Greek. ደብዳቤው ፡ በግሪክ ፡ ተጻፈ
2. ተነበበ. Joy was written all over her face. ደስታ ፡ በፊቷ ፡ ላይ ፡ ይነበብ ፡ ነበር

**write down** ጻፈ
Write down that telephone number before you forget it! ያንን ፡ የስልክ ፡ ቁጥር ፡ ሳትረሳው ፡ ጻፈው

**write off**
*He wrote it off as something bought on the installment plan which would never be paid for. በዱቤ ፡ የሸጠውን ፡ እንደማይከፈለው ፡ ያህል ፡ ቈጠረው

**(be) written off** ዋጋ ፡ ተከፍሎ ፡ አለቀ
The new equipment was written off in three years. ያዲሱ ፡ እቃ ፡ ዋጋ ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ተከፍሎ ፡ አለቀ

**write out** ጻፈ
Please write out that check for me before I go. እስቲ ፡ ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ ቼኩን ፡ ጻፍልኝ

**(be) written up** ተጻፈ
His adventures were written up in the papers. የደረሰበት ፡ ነገር ፡ በጋዜጣዎች ፡ ተጻፈ

**writer** ደራሲ
My son wants to become a writer. ልጄ ፡ ደራሲ ፡ ለመሆን ፡ ይፈልጋል

**write-up** የተጻፈ ፡ ሐተታ
The write-up of his activities covered a whole page. ስለሱ ፡ ሥራዎች ፡ የተጻፈው ፡ ሐተታ ፡ አንድ ፡ ሙሉ ፡ ገጽ ፡ ወሰደ

**writhe**
1. ተጥመለመለ. The snake writhed along the branch. እባቡ ፡ ቅርንጫፉ ፡ ላይ ፡ እየተጥመለመለ ፡ ሄደ
2. ተንፈራፈረ. The wounded man writhed in pain. የቈሰለው ፡ ሰው ፡ በሥቃይ ፡ ተንፈራፈረ

**writing**
1. መጻፍ. I don't get around to writing. ለመጻፍ ፡ ጊዜ ፡ የለኝም
2. ጽሕፈት. I can't read his writing. የሱን ፡ ጽሕፈት ፡ ለማንበብ ፡ አልችልም
He is busy with his writing. ጽሕፈት ፡ ይዞ ፡ ይጣደፋል
3. ጽሑፍ. You had better put your agreement in writing. ስምምነታችሁን ፡ በጽሑፍ ፡ ብታሰፍሩት ፡ ይሻላል
The writings of this author are translated into several languages. የዚህ ፡ ደራሲ ፡ ጽሑፎች ፡ በብዙ ፡ ቋንቋዎች ፡ ተተርጕመዋል

**writing material** መጻፊያ
Vellum is used as writing material. ብራና ፡ ለመጻፊያ ፡ ያገለግላል

**wrong** (v.) በደለ (ተበደለ)
He wronged me when he said I had stolen it. ሰርቀሃል ፡ ስላለኝ ፡ በድሎኛል
He felt wronged. የተበደለ ፡ መሆኑ ፡ ተሰማው

**wrong** (n.)
1. ስሕተት. Can't you differentiate between right and wrong? ትክክለኛውን ፡ ከስሕተት ፡ ለመለየት ፡ አትችልም ?
2. በደል. The wrong she had suffered made her bitter. የደረሰባት ፡ በደል ፡ በጣም ፡ አማረራት
3. ጥፋት. I have done no wrong, officer. I was going only five miles an hour. ጌታዬ ፤ ምንም ፡ ጥፋት ፡ አላደረግሁም ፤ እነዳ ፡ የነበረው ፡ በሰዓት ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ ብቻ ፡ ነበር

**wrong** (adj.)
1. የተሳሳተ. He caught himself before he said the wrong thing. የተሳሳተ ፡ ነገር ፡ ከመናገሩ ፡ በፊት ፡ ራሱን ፡ ገታ
She dialed the wrong number. የተሳሳተ ፡ ቁጥር ፡ ደወለች
2. ስሕተት ፡ የሆነ. He had six wrong answers on the test. በፈተናው ፡ ላይ ፡ ስድስት ፡ ስሕተት ፡ የሆኑ ፡ መልሶች ፡ ሰጠ
3. የማይስማማ. Red is the wrong color for her. ቀይ ፡ ለሷ ፡ የማይስማማት ፡ ቀለም ፡ ነው
4. የሌላ ፡ ሰው. In a moment of abstraction, he grabbed the wrong hat. በሐሳብ ፡ ተውጦ ፡ ሳለ ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ባርኔጣ ፡ ወሰደ
5. የማይሆን. The policeman tagged the car for parking on the wrong side of the street. መኪናውን ፡ እማይሆን ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ስላቆመ ፡ ፖሊሱ ፡ መጥሪያ ፡ ሰጠው
6. ሌላ. Without my glasses, I blundered into the wrong room. መነጽሬን ፡ ሳላደርግ ፡ ቀርቼ ፡ በስሕተት ፡ ሌላ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ገባሁ
7. (= noun) ኀጢአት. Killing is wrong. መግደል ፡ ኀጢአት ፡ ነው
8. (= noun) ብልሽት. What's wrong with the car? መኪናው ፡ ምን ፡ ብልሽት ፡ ደረሰበት ?
9. (= noun) ያልሆነ ፡ ነገር. I sensed right away that something was wrong. ያልሆነ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ወዲያውኑ ፡ ተሰማኝ
10. (= noun) ስሕተት. The answer is wrong anyway you look at it. በየትኛውም ፡ አንጻር ፡ ብትመለከተው ፡ መልሱ ፡ ስሕተት ፡ ነው

**be wrong**
1. ተሳሳተ. I am afraid you are wrong. የተሳሳትክ ፡ ይመስለኛል
2. ተበላሸ. The clock is wrong. ሰዓቱ ፡ ተበላሽቷል

**be wrong with**
*Something is wrong with the telephone. ስልኩ ፡ የተበላሸ ፡ ነገር ፡ አያጣም
*Is anything wrong with you? የሆንከው ፡ ነገር ፡ አለ ?

**do a wrong** በደለ
You do an honest man a wrong to call him a liar. ሐቀኛውን ፡ ሰው ፡ ዋሾ ፡ ብትለው ፡ ትበድለዋለህ

**do something wrong**
1. አሳሳተ. You did it wrong again. አሁንም ፡ አሳሳትክ
2. አሳስቶ ፡ ሠራ. I showed you how to do it, but you did it wrong again. እንዴት ፡ እንደምትሠራው ፡ አሳይቼህ ፡ ነበር ። ግን ፡ እንደገና ፡ አሳስተህ ፡ ሠራህ

**do wrong** አጠፋ
I have done no wrong. ምንም ፡ አላጠፋሁም

**get wrong**
Don't get me wrong! የምለው ፡ ይግባህ

**go wrong**
1. ተበላሸ. He went wrong as a result of associating with criminals. ከወንጀለኞቹ ፡ ጋር ፡ ከመወዳጀቱ ፡ የተነሣ ፡ ተበላሸ
2. አልቀናውም. I had a very trying day; everything seemed to go wrong. ቀኑ ፡ ለኔ ፡ አልሆነኝም ። ምንም ፡ ነገር ፡ አልቀናኝ
*Everything went wrong today. ዛሬ ፡ የተማታ ፡ ቀን ፡ ነው (or, ዛሬ ፡ ግራ ፡ የገባው ፡ ቀን ፡ ነው)

**go (the) wrong way** መንገዱን ፡ ተሳሳተ
You're going the wrong way; turn around! መንገዱን ፡ ተሳስተሃል ። ተመለስ

**(be) in the wrong** ተሳሳተ
He admitted that he was in the wrong. መሳሳቱን ፡ አመነ

**turn out to be wrong** ሳይዝለት ፡ ቀረ
His forecast turned out to be wrong. ትንቢቱ ፡ ሳይዝለት ፡ ቀረ

**(in the) wrong direction** አላቅጣጫ
You're heading in the wrong direction. አላቅጣጫው ፡ ነው ፡ የምትሄደው
[See also 'rub']

**wrongdoer** ጥፋተኛ
Wrongdoers will be punished. ጥፋተኞች ፡ ይቀጣሉ

**wrongdoing** መጥፎ ፡ ተግባር ፡ መፈጸም
The thief was guilty of wrongdoing. ሌባው ፡ መጥፎ ፡ ተግባር ፡ በመፈጸሙ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነበር

**wrongly** ተሳስቶ
He wrongly assumed that I was an Ethiopian. ተሳስቶ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አድርጎ ፡ ገመተኝ
[See also 'rightly']

**wrote**, see **write**

**wrought** የተሠራ
Beautifully wrought furniture is expensive. አምሮ ፡ የተሠራ ፡ የቤት ፡ እቃ ፡ ውድ ፡ ነው

**be wrought** ተሠራ
The gate was wrought with great skill. መዝጊያው ፡ በታላቅ ፡ ጥበብ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**(be) wrought-up** ተበሳጨ
He was wrought-up over his bills. በሚከፍለው ፡ ሒሳብ ፡ ተበሳጨ

**wrung**, see **wring**

**wry**
*She made a wry face to show her disgust. መጸየፏን ፡ ለመግለጽ ፡ ፊቷን ፡ ኮሶ ፡ አስመሰለች

## X

**xenophobia** [የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎችን ፡ የመጥላት ፡ ስሜት]

# Y

**yacht** [ለሽርሽር ፡ ወይም ፡ ለእሽቅድምድም ፡ የሚያገለግል ፡ ጀልባ]

**yam** የስኳር ፡ ድንች
Some people eat roasted yams and pork. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የተጠበሰ ፡ የስኳር ፡ ድንችና ፡ የአሳማ ፡ ሥጋ ፡ ይበላሉ

**yank** ጉተት ፡ ጉተት ፡ አደረገ
He yanked the rope. ገመዱን ፡ ጉተት ፡ ጉተት ፡ አደረገው

**yank out** በድንገት ፡ ነቀለ
The dentist yanked out the aching tooth. የጥርስ ፡ ሐኪሙ ፡ የበሽተኛውን ፡ ጥርስ ፡ በድንገት ፡ ነቀለው

**yap** (yapped) አለዘነ
The dog is yapping. ውሻው ፡ ያለዝናል

**yard**
1. አጥር ፡ ግቢ. The house has a yard for the children to play in. ቤቱ ፡ ለልጆቹ ፡ መጫወቻ ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ አለው
2. ቦታ. The chicken yard is bare of grass. የዶሮዎቹ ፡ ቦታ ፡ ሣር ፡ የለበትም
3. ያርድ. The yard is 3 ft. long. አንድ ፡ ያርድ ፡ ሦስት ፡ ጫማ ፡ ይረዝማል
[See also 'lumber yard']

**yardstick** ያርድ
He measured the cloth with a yardstick. ጨርቁን ፡ በያርድ ፡ ለካ

**yarn**
1. ሱፍ ፡ ክር. I need some yarn to knit a sweater. ሹራብ ፡ ለመሥራት ፡ ሱፍ ፡ ክር ፡ ያስፈልገኛል
2. እየፈጠረ ፡ የሚያወራ ፡ ታሪክ. The sailors' yarns are very interesting. መርከበኞቹ ፡ እየፈጠሩ ፡ የሚያወሩቸው ፡ ታሪኮች ፡ በጣም ፡ ያስደስታሉ
[See also 'spin']

**yawn** (v.)
1. አዛጋ. He yawned to show that he was sleepy. እንቅልፍ ፡ እንቅልፍ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ለማሳየት ፡ አዛጋ
2. አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ታየ. The canyon yawned beneath our feet. ገደሉ ፡ ከበታቻችን ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**year** ዓመት
Will he come back next year? በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ይመለሳል ?

**years** ዕድሜ
He is old for his years. በዚሁ ፡ ዕድሜው ፡ አርጅቷል

**year after year** በያመቱ
He visits his relatives year after year. ዘመዶቹን ፡ በያመቱ ፡ ይጠይቃል

**years ago** ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት
That happened years ago. ያ ፡ የሆነው ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ነው

**year before last** አቻምና
The year before last it was very dry. አቻምና ፡ በጣም ፡ ደረቅ ፡ ነበር

**year by year** በያመቱ
Grain exports increase year by year. ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚላክ ፡ እህል ፡ በያመቱ ፡ ይጨምራል

**year in, year out** ከዓመት ፡ ዓመት
Year in, year out, the same routine. ከዓመት ፡ ዓመት ፡ ያው ፡ ይደጋገማል

**Year of Grace** ዓመተ ፡ ምሕረት
The Year of Grace means the Ethiopian year. ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ማለት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዘመን ፡ አቈጣጠር ፡ ማለት ፡ ነው

**academic year** የትምህርት ፡ ዓመት
The academic year is nine months long. የትምህርቱ ፡ ዓመት ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ነው

**all year round** ዓመቱን ፡ በሙሉ
They live in the country all year round. ዓመቱን ፡ በሙሉ ፡ የሚኖሩት ፡ ባላገር ፡ ነው

**for years** ለብዙ ፡ ዓመታት ፤ ብዙ ፡ ዓመታት
I haven't seen him for years. ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ አላየሁትም
We lived there for years. እዚያ ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ኖርን

**in years** ለብዙ ፡ ዓመታት
I haven't seen him in years. ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ አላየሁትም

**last year** ዓምና
Last year I was in 6th grade. ዓምና ፡ ስድስተኛ ፡ ክፍል ፡ ነበርኩ

**the year round** ከዓመት ፡ ዓመት
These birds are resident here the year round. እነዚህ ፡ ወፎች ፡ ከዓመት ፡ ዓመት ፡ እዚህ ፡ ይኖራሉ

**this year** በዚህ ፡ ዓመት ፤ ዘንድሮ
There was much rain this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ (ዘንድሮ) ፡ ብዙ ፡ ዝናብ ፡ ነበር
[See also 'early, get on, half, lean, leap year, mature, over, well']

**yearbook** ዓመታዊ ፡ መጽሔት
A yearbook lists all the companies in the country. ዓመታዊው ፡ መጽሔት ፡ ባገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ኩባንያዎች ፡ ሁሉ ፡ ይዘረዝራል

**yearling** አንድ ፡ ዓመት ፡ የሞላው
Yearling calves are sold at a high price. አንድ ፡ ዓመት ፡ የሞላቸው ፡ ጥጃዎች ፡ በከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ይሸጣሉ

**yearlong** ከዓመት ፡ ዓመት ፡ የሚቆይ
There are few yearlong religious observances. ከዓመት ፡ ዓመት ፡ የሚቆዩ ፡ ጥቂት ፡ የሃይማኖት ፡ በዓላት ፡ አሉ

**yearly** (adj.)
1. የዓመት. His yearly income is $10,000. የዓመት ፡ ገቢው ፡ ዐሥር ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ነው
Last month I took my yearly vacation. ባለፈው ፡ ወር ፡ የዓመት ፡ ፈቃዴን ፡ ወሰድኩ
2. (= adv.) በያመቱ. My uncle pays us a yearly visit. አጐቴ ፡ በያመቱ ፡ ይጠይቀናል
He sent me his yearly greetings. በያመቱ ፡ የሚልክልኝን ፡ የመልካም ፡ ምኞት ፡ መግለጫ ፡ ላከልኝ
3. (= adv.) ባንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ. The earth makes a yearly revolution around the sun. መሬት ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ፀሐይን ፡ ትዞራለች

**yearly** (adv.)
1. በዓመት. How much money does he make yearly? በዓመት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ ያገኛል ?
2. በያመቱ. This company sends out calendars to its customers yearly. ይህ ፡ ኩባንያ ፡ ለደንበኞቹ ፡ በያመቱ ፡ የቀን ፡ መቍጠሪያ ፡ ያድላል

**yearn**
1. ናፈቀ ፤ ጓጓ. I yearn to return home again. ወደ ፡ ቤት ፡ ለመመለስ ፡ ናፍቆያለሁ ፡ (ጓጉቻለሁ)
2. ራራ. Her heart yearned for the starving children. ለተራቡት ፡ ልጆች ፡ ልቧ ፡ ራራ

**yearning** ናፍቆት
His yearning for his country is well described in the book. ስለ ፡ አገሩ ፡ ያለው ፡ ናፍቆት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በደንብ ፡ ተገልጿል

**yeast** እርሾ
She prepared the yeast for baking bread. ዳቦውን ፡ ለመጋገር ፡ እርሾ ፡ አዘጋጀች

**yell** (v.) ጮኸ
We heard someone yelling for help. አንድ ፡ ሰው ፡ ለርዳታ ፡ ሲጮኽ ፡ ሰማን
He yelled with pain. ስላመመው ፡ ጮኸ

**yell for help** ኡ ፡ ኡ ፡ አለ
He yelled for help in vain. ኡ ፡ ኡ ፡ ያለው ፡ በከንቱ ፡ ነበር

**yell** (n.) ጩኸት
He let out a yell when he stepped on a thorn. እሾህ ፡ ሲወጋው ፡ ጩኸቱን ፡ ለቀቀ

**give a loud yell** ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ጮኸ
The lusty baby gave a loud yell as soon as he became hungry. የፋፋው ፡ ሕፃን ፡ ወዲያው ፡ እንደራበው ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ጮኸ

**yellow** (v.) ብጫ ፡ ሆነ
Paper yellows with age. ወረቀት ፡ ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ ብጫ ፡ ይሆናል

**yellow** (adj.) ብጫ ፤ ቢጫ
The cover of the book is yellow. የመጽሐፉ ፡ ልባስ ፡ ብጫ ፡ (ቢጫ) ፡ ነው

**be yellow** ፈራ
Don't be so yellow! That dog won't bite you. እስከዚህ ፡ አትፍራ ፤ ውሻው ፡ አይነክስህም

**yellow fever** ብጫ ፡ ወባ
I had yellow fever. ብጫ ፡ ወባ ፡ ይዞኛል

**yelp** አለቀሰ
The dog yelped with pain. ከሥቃይ ፡ የተነሣ ፡ ውሻው ፡ አለቀሰ

**yes**
1. እዎ ፤ አዎን. Can you read this? Yes. ይህን ፡ ልታነብ ፡ ትችላለህ ? እዎ ፡ (አዎን)
2. እሺ. Yes sir, I'll do it right away. እሺ ፡ ጌታዬ ፤ አሁኑኑ ፡ እሠራዋለሁ
Come here at once! Yes sir! ወዲህ ፡ ና ፡ ቶሎ! እሺ
He said "yes" when I asked him. ብጠይቀው ፡ እሺ ፡ አለ

**yesterday** ትላንትና ፤ ትናንትና ፤ ትናንት ፤ ትላንት
Yesterday it rained. ትላንት ፡ ዘነበ

**the day before yesterday** ከትናንትና ፡ ወዲያ
You came the day before yesterday. የመጣኸው ፡ ከትናንትና ፡ ወዲያ ፡ ነበር
[See also 'late']

**yet** (adv.)
1. ገና. You'll drive me crazy yet. አንተ ፡ ገና ፡ ታሳብደኛለህ
There is much work yet to be done. ገና ፡ ብዙ ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ አለ
Did you see the new play yet? አዲሱን ፡ ቲያትር ፡ ገና ፡ አላየኸውም ?
Haven't you read the book yet? መጽሐፉን ፡ ገና ፡ አላነበብከውም ?
It was not yet dark. ገና ፡ አልጨለመም ፡ ነበር
2. አሁን. Don't go yet! አሁን ፡ አትሂድ
We can't leave just yet. አሁን ፡ ልንሄድ ፡ አንችልም
3. አሁንም. Be thankful you are yet alive. አሁንም ፡ በሕይወት ፡ በመገኘትህ ፡ እግዚርን ፡ አመስግን
4. ወደፊት. I may yet get rich. ወደፊት ፡ እበለጽግ ፡ ይሆናል
5. ሆኖም. The story was strange, yet true. ወሬው ፡ እንግዳ ፡ ነበር ፤ ሆኖም ፡ እውነተኛ ፡ ነው
6. እንዲያውም. The king spoke yet more harshly. ንጉሡ ፡ እንዲያውም ፡ በቁጣ ፡ ተናገሩ

**yet** (conj.) ነገር ፡ ግን
He didn't want to go, yet he had to. ለመሄድ ፡ አልፈለገም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ግድ ፡ ሆነበት

**and yet** ሆኖም
And yet you can't help liking him. ሆኖም ፡ እሱን ፡ መውደድህ ፡ አይቀርም

**as yet** እስካሁን ፤ እስካሁን ፡ ድረስ
As yet, we have made no plans. እስካሁን ፡ (እስካሁን ፡ ድረስ) ፡ ምንም ፡ አላቀድንም

**not yet**
1. ገና + (affirmative verb). It's not yet time to go. የመሄጃው ፡ ሰዓት ፡ ገና ፡ ነው
Are you finished? Not yet. ጨርሰሃል ? ገና ፡ ነው
2. ገና + (negative verb). Haven't you seen him yet? ገና ፡ አላገኘኸውም ?
I'm not yet done. ገና ፡ አልጨረስኩም

**yield** (vt.)
1. አስገኘ. His business doesn't yield much profit. ሥራው ፡ ብዙ ፡ ትርፍ ፡ አያስገኝም
The money yields interest. ገንዘቡ ፡ ወለድ ፡ ያስገኛል
2. አፈራ. These trees yield fruit. እነዚህ ፡ ዛፎች ፡ ፍሬ ፡ ያፈራሉ
3. ለቀቀ. The enemy yielded the city. ጠላት ፡ ከተማዋን ፡ ለቀቀ

**yield** (vi.)
1. ተረታ. I'll yield on this point. እዚህ ፡ ላይ ፡ እረታለሁ
2. እጅ ፡ ሰጠ. The enemy yielded to our soldiers. ጠላት ፡ ለወታደሮቻችን ፡ እጁን ፡ ሰጠ

**yield (one's) consent** ተስማማ
Her father yielded his consent to the plan. አባቷ ፡ በእቅዱ ፡ ተስማማ

**yield ground** አፈገፈገ
The troops had to yield ground to the enemy. ወታደሮቹ ፡ ለጠላት ፡ ማፈግፈግ ፡ ነበረባቸው

**yield to** ተቀበለ
The father yielded to his request. አባትዬው ፡ ልመናውን ፡ ተቀበለው
*He yielded to curiosity and opened the letter addressed to his father. ጉጉት ፡ ገፋፍቶት ፡ ላባቱ ፡ የተጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ ከፈተው
*They will yield only to force. የሚያሸንፋቸው ፡ በኀይል ፡ ብቻ ፡ ነው
*The door yielded to his touch. በሩን ፡ ገና ፡ ሲነካው ፡ ተከፈተ
[See also 'temptation']

**yield** (n.) ምርት
The yield this year is much greater than it was last year. የዘንድሮው ፡ ምርት ፡ ከዓምናው ፡ በጣም ፡ ይበልጣል

**(be) yielding** ትሙክ ፡ ትሙክ ፡ አለ
It was soft and yielding to the touch. ሲዳሰስ ፡ ለስላሳና ፡ ትሙክ ፡ ትሙክ ፡ የሚል ፡ ነበር

**have a yielding nature** እሺ ፡ ባይ ፡ ነው
She has a yielding nature with her children. ለልጆቿ ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ ናት

**yogurt** እርጎ
Some people like to eat yogurt. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ እርጎ ፡ መጠጣት ፡ ይወዳሉ

**yoke** (v.) ጠመደ
The farmer yoked his oxen. ገበሬው ፡ በሬዎቹን ፡ ጠመደ

**be yoked** ተሳሰረ
They are yoked in marriage. በጋብቻ ፡ ተሳስረዋል

**yoke** (n.) ቀንበር
The oxen were strong and broke the yoke. በሬዎቹ ፡ ኀይለኞች ፡ ስለሆኑ ፡ ቀንበሩን ፡ ሰበሩት
The enemy's yoke was broken by our patriots. የጠላት ፡ ቀንበር ፡ ባርበኞቻችን ፡ ነኰተ

The people were under the yoke of a dictator. ሕዝቡ ፡ በአምባገነን ፡ ቀንበር ፡ ሥር ፡ ነበር

**yoke of oxen** የተጠመዱ ፡ ጥንድ ፡ በሬዎች
The plow was drawn by the yoke of oxen. ሞፈሩ ፡ የሚጎተተው ፡ በተጠመዱ ፡ በጥንድ ፡ በሬዎች ፡ ነበር

**have a yoke on the neck** ተጠመደ
The oxen do not like to have a yoke on their necks. በሬዎቹ ፡ መጠመድ ፡ አይወዱም

**yolk** የእንቁላል ፡ አስኳል
The yolk of the egg is yellow. የእንቁላል ፡ አስኳል ፡ ብጫ ፡ ነው

**yonder** adj. (= adv.) እዚያ ፡ ማዶ
There is still snow on yonder mountain. እዚያ ፡ ማዶ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ አሁንም ፡ በረዶ ፡ አለ

**yonder** (adv.) እዚያ
Look yonder! እዚያ ፡ ተመልከት

**over yonder** እዚያ ፡ ማዶ
The house is over yonder. ቤቱ ፡ እዚያ ፡ ማዶ ፡ ነው

**you** (subject)
1. አንተ (masc. sg.), አንቺ (fem. sg.), እናንተ (pl. com.), እርስዎ (resp.)
You (masc. sg.) are a good student. አንተ ፡ ጎበዝ ፡ ተማሪ ፡ ነህ
You (fem. sg.) are a good student. አንቺ ፡ ጎበዝ ፡ ተማሪ ፡ ነሽ ፡
You are good students. እናንተ ፡ ጎበዝ ፡ ተማሪዎች ፡ ናችሁ
You (resp.) are a good teacher. እርስዎ ፡ ጎበዝ ፡ አስተማሪ ፡ ነዎት
2. ሰው. When you have been ill, your face is sometimes pale. ሰው ፡ ሲታመም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱ ፡ ይገረጣል
3. (plural). The days pass quickly when you are busy. ሥራ ፡ ሲይዙ ፡ ቀኑ ፡ ቶሎ ፡ ያልፋል

**you** (direct object) -ህ (masc. sg.), -ሽ (fem. sg.), -aችሁ (pl. com.), -ዎ, -ዎት (resp.)
Yesterday I saw you (sg. masc.). ትናንት ፡ አየሁህ
Yesterday I saw you (sg. fem.). ትናንት ፡ አየሁሽ
Yesterday I saw you (pl.). ትናንት ፡ አየኋችሁ
Yesterday I saw you (resp.). ትናንት ፡ አየሁዎ ፡ (አየሁዎት)

**young** (n.)
1. ልጅ. The cat fought to defend its young. ድመቲቱ ፡ ልጆቿን ፡ ተከላከለች
2. ግልገል. Some animals will fight to protect their young. ብዙ ፡ እንስሳት ፡ ግልገሎቻቸውን ፡ ከፋ ፡ እንዳያገኛቸው ፡ ይከላከላሉ
3. ወጣት ፤ ወጣቶች. This is a game for young and old. ይህ ፡ ለወጣትም ፡ ለሽማግሌም ፡ የሚሆን ፡ ጨዋታ ፡ ነው
The educated young of today have different ideas. የዛሬ ፡ ጊዜ ፡ የተማሩ ፡ ወጣቶች ፡ የተለየ ፡ አስተሳሰብ ፡ አላቸው

**young** (adj.)
1. ልጅ. She looks very young for her age. ለዕድሜዋ ፡ በጣም ፡ ልጅ ፡ ትመስላለች
2. ወጣት. She is very young for her age. ለዕድሜዋ ፡ ገና ፡ ወጣት ፡ ናት
The young lawyer lacked assurance. ወጣቱ ፡ ጠበቃ ፡ በራሱ ፡ የመተማመን ፡ ጠባይ ፡ ይጎድለዋል
3. (= adv.) እንደ ፡ ሕፃን. John is young for his years. ጆን ፡ በዚህ ፡ ዕድሜው ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ነው
4. ታዳጊ. Kenya is a young nation. ኬንያ ፡ ታዳጊ ፡ አገር ፡ ነች
There are many young trees in this park. እዚህ ፡ መናፈሻ ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ታዳጊ ፡ ዛፎች ፡ አሉ

**young** (adv.) እንደ ፡ ወጣት
She acts young for her years. ከዕድሜዋ ፡ ጋር ፡ ሲተያይ ፡ የምትሠራው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ወጣት ፡ ነው

**young child** ሕፃን ፡ ልጅ
A young child needs motherly love. ሕፃን ፡ ልጅ ፡ የእናት ፡ ፍቅር ፡ ይፈልጋል

**young couple** ወጣት ፡ የሆኑ ፡ ባልና ፡ ሚስት
Triplets were born to a young couple recently. በቅርቡ ፡ ወጣት ፡ የሆኑ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ሦስት ፡ መንታ ፡ ወለዱ

**young man** ወጣት
Who is that young man? ያ ፡ ወጣት ፡ ማን ፡ ነው ?

**young man!** ወንድም
Listen to me, young man! ወንድም ፤ አዳምጠኝ!

**young people**
1. ወጣቶች. The young people had a lot of fun. ወጣቶቹ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ነበር
2. ልጅ ፡ እግሮች. There was a sprinkling of young people in the congregation. በምእመናኑ ፡ መካከል ፡ ልጅ ፡ እግሮች ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይታዩ ፡ ነበር

**young woman** ልጅ ፡ እግር ፡ ሴት
A young woman came to see me. ልጅ ፡ እግር ፡ ሴት ፡ ልትጠይቀኝ ፡ መጣች

**(the) night is yet young** ገና ፡ አልመሸም
Please stay! The night is yet young. ቆይ ፡ እባክህ ፤ ገና ፡ አልመሸም

**with young** ግልገል ፡ ያላት
A wild animal with young is dangerous. ግልገል ፡ ያላት ፡ አውሬ ፡ አደገኛ ፡ ናት

**younger**
1. ታናሽ. My younger brother was killed in the war. ታናሽ ፡ ወንድሜ ፡ ጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞተ
2. ትንሽ. Pliny the Younger wrote a series of biographies. ትንሹ ፡ ፕሊኒ ፡ ተከታታይ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኮች ፡ ጽፏል
3. የመጨረሻ. The younger son has pretentions to the estate. የመጨረሻው ፡ ልጅ ፡ መሬቱ ፡ ይገባኛል ፡ ባይ ፡ ነው

**youngish** ልጅ
He looks youngish for his age. ለዚህ ፡ ዕድሜው ፡ ልጅ ፡ ይመስላል

**youngster** ወጣት
The youngsters stood around in the schoolyard. ወጣቶቹ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ዙሪያውን ፡ ቆሙ

**your**
1. -ህ ፤ ያንተ (masc. sg.). Your clothes are dirty, my boy. ልብስህ ፡ (ያንተ ፡ ልብስ) ፡ ቆሽሿል ፡ ልጄ
2. -ሽ ፤ ያንቺ (fem. sg.). Your dress is torn, my girl. ልብስሽ ፡ (ያንቺ ፡ ልብስ) ፡ ተቀዷል ፡ ልጄ
3. -aችሁ ፤ የናንተ (pl. com.). Put your books away, children! ልጆች ፤ መጽሐፎቻችሁን ፡ (የናንተን ፡ መጽሐፎች) ፡ አስቀምጡ
4. -ዎ ፤ የርስዎ (resp.). Is this your book, sir? ይህ ፡ መጽሐፍዎ ፡ (የርስዎ ፡ መጽሐፍ) ፡ ነው ፡ ጌታዬ?

**yours**
1. ያንተ (masc. sg.). The book is yours, my boy. መጽሐፉ ፡ ያንተ ፡ ነው ፤ ልጄ
2. ያንቺ (fem. sg.). The chair is yours, my girl. ወንበሩ ፡ ያንቺ ፡ ነው ፤ ልጄ
3. የናንተ (pl. com.). These books are yours, boys. ልጆች ፤ እነዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ የናንተ ፡ ናቸው
4. የርስዎ (resp.). The book is yours, sir. መጽሐፉ ፡ የርስዎ ፡ ነው ፤ ጌታዬ

**yourself**
1. (subject) አንተ ፡ ራስህ (sg. masc.), አንቺ ፡ ራስሽ (sg. fem.), እናንተ ፡ ራሳችሁ (pl. com.), እርስዎ ፡ ራስዎ (resp.).
You yourself said so. አንተ ፡ ራስህ ፡ ነህ ፡ እንዲዚያ ፡ ያልከው
2. አንተው (sg. masc.), አንቺው (sg. fem.), እናንተው (pl. com.), እርስዎው (resp.).
Did you knit these gloves yourself? ይህንን ፡ የእጅ ፡ ሹራብ ፡ የጠለፍሽው ፡ አንቺው ፡ ነሽ?
3. (object) ራስህን (sg. masc.), ራስሽን (sg. fem.), ራሳችሁን (pl. com.), ራስዎን (resp.).
Ask yourself what you really want. በእርግጥ ፡ ምን ፡ እንደምትፈልግ ፡ ራስህን ፡ ጠይቅ
*Can you identify yourself? ማን ፡ እንደሆንክ ፡ ልትነግረን ፡ ትችላለህ ?

**feel like yourself** (masc. sg.) እንደወትሮህ ፡ ትሆናለህ
Now that your cold is better, you'll feel like yourself again. አሁን ፡ ጉንፋንህ ፡ የተሻለህ ፡ ስለሆነ ፡ እንደገና ፡ እንደወትሮህ ፡ ትሆናለህ

**youth** (n.)
1. ወጣት. As a youth, he showed no promise. ወጣት ፡ ሳለ ፡ ምንም ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልበት ፡ መልክ ፡ አላሳየም ፡ ነበር
He has the vigor of youth. የወጣት ፡ ወኔ ፡ አለው
2. ወጣቶች. There is a club for the youth in our town. በከተማችን ፡ ውስጥ ፡ የወጣቶች ፡ ክበብ ፡ አለ
3. ልጅነት ፤ የወጣትነት ፡ ዘመን. He had to work hard in his youth. በልጅነቱ ፡ ጠንክሮ ፡ መሥራት ፡ ነበረበት
He mourned his misspent youth. በባከነው ፡ የወጣትነት ፡ ዘመኑ ፡ ተጸጸተ
4. ልጅ ፡ መሆን. His youth was an obstacle to his success. ልጅ ፡ መሆኑ ፡ ለዕድሉ ፡ መቃናት ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆነበት

**youth** (adj.) የወጣቶች
The youth movement in Europe was started in the beginning of the 20th century. በአውሮፓ ፡ የወጣቶች ፡ ንቅናቄ ፡ የተጀመረው ፡ በሃያኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መጀመሪያ ፡ ነው
[See also 'bloom']

**youthful**
1. የወጣትነት. She still has a youthful appearance. አሁንም ፡ የወጣትነት ፡ መልክ ፡ ይታይባታል
2. ወጣት. He still looks youthful. አሁንም ፡ ወጣት ፡ ይመስላል

# Z

**zeal** ቅንአት
His zeal for the faith brough him the martyr's crown. በእምነቱ ፡ የነበረው ፡ ቅንአት ፡ የሰማዕትነትን ፡ ዘውድ ፡ አቀዳጀው

**zealot** ቀናኢ
He is a zealot who can tolerate no religion but his own. የራሱን ፡ እንጂ ፡ የሌላን ፡ ሃይማኖት ፡ መኖር ፡ የማይፈልግ ፡ ቀናኢ ፡ ነው

**zealous** ቀናኢ
Abuna Petros was a zealous patriot. አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቀናኢ ፡ አርበኛ ፡ ነበሩ

**zebra** የሜዳ ፡ አህያ
Hunting zebras is not permitted. የሜዳ ፡ አህያ ፡ ማደን ፡ አይፈቀድም

**zebu** በሬ
The Ethiopian zebu has a hump. የኢትዮጵያ ፡ በሬ ፡ ሻኛ ፡ አለው

**zenith**
1. የሰማይ ፡ እምብርት. The stars that are near the zenith sparkle. ከሰማዩ ፡ እምብርት ፡ አጠገብ ፡ ያሉት ፡ ከዋክብት ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ ይላሉ
2. ከፍተኛ ፡ ደረጃ. Rome reached the zenith of its power in 225 A.D. በ፪፻፳፭ ዓ. ም. ሮም ፡ የኀይሏን ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ደረሰች

**zephyr** በጣም ፡ ለዘብ ፡ ያለ ፡ ነፋስ
A zephyr ruffled her hair. በጣም ፡ ለዘብ ፡ ያለ ፡ ነፋስ ፡ ጸጉሯን ፡ አመሳቀለው

**zero** (v.), ~ **in** አነጣጠረ
They zeroed in their cannons on the church. መድፋቸውን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ላይ ፡ አነጣጠሩ

**zero** (zeros, or zeroes), n. ዜሮ
Two minus two is zero. ከሁለት ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ሲነሣ ፡ ዜሮ ፡ ይቀራል
There are three zeros in 1,000. በ 1,000 ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ ዜሮ ፡ አለ

**zero** (adj.) የዜሮ
At zero hour the attack will begin. በዜሮ ፡ ሰዓት ፡ ጥቃቱ ፡ ይጀምራል

**sink to zero** ከንቱ ፡ ሆነ
My hopes of getting a new car sank to zero. አዲስ ፡ መኪና ፡ ለመግዛት ፡ የነበረኝ ፡ ተስፋ ፡ ከንቱ ፡ ሆነ

**zest**
1. ድምቀት. Your presence will add zest to the party. ያንተ ፡ መኖር ፡ ለግብዣው ፡ ድምቀት ፡ ይጨምርለታል
2. ወዝ. He added zest to the discussion by making good suggestions. ጥሩ ፡ ሐሳቦችን ፡ በማቅረብ ፡ ለውይይቱ ፡ ወዝ ፡ ሰጠው
3. የደስታ ፡ መንፈስ. He works with zest. በደስታ ፡ መንፈስ ፡ ይሠራል
*He ate with zest. ጥርቅም ፡ አድርጎ ፡ በላ

**have zest** ተደሰተ
He has zest for life. በኑሮ ፡ ይደሰታል

**zigzag** (zigzagged), v. የተጠማዘዘ ፡ መሥመር ፡ ሠራ
Lightning zigzagged across the sky. ብልጭልጭታው ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ የተጠማዘዘ ፡ መሥመር ፡ ሠራ

**zigzag down** እየተጠማዘዘ ፡ ወረደ
The road zigzagged down the side of the mountain. መንገዱ ፡ በተራራው ፡ ሥር ፡ እየተጠማዘዘ ፡ ወረደ

**zigzag** (n.) የተጠማዘዘ ፡ ቅርጽ
The border of the picture is formed by a zigzag. የሥዕሉ ፡ ጠርዝ ፡ የተጠማዘዘ ፡ ቅርጽ ፡ አለው

**in zigzag** እየተጠማዘዘ
He ran in a zigzag to avoid being shot. ተኵሶ ፡ እንዳይመታው ፡ እየተጠማዘዘ ፡ ሮጠ

**zinc** ዚንክ
Roofing tin is plated with zinc. የቤት ፡ ክዳን ፡ ቆርቆሮ ፡ ዚንክ ፡ ይቀባል

**zip** (zipped) ተፈተለከ
He zipped through the town. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ተፈተለከ

**zip past one** ባጠገቡ ፡ እያፏጨ ፡ አለፈ
Bullets zipped past me. ጥይት ፡ ባጠገቤ ፡ እያፏጨ ፡ አለፈ

**zip through** በቶሎ ፡ ጨረሰ
He zipped through the lesson. ጥናቱን ፡ በቶሎ ፡ ጨረሰ

**zip up** ዚፑን ፡ ሳበ(ለት) ፤ ዚፐር ፡ ዘጋ
Please zip me up! እስቲ ፡ ዚፑን ፡ ሳብልኝ
He zipped up his coat before going out. ከቤት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የኮቱን ፡ ዚፐር ፡ ዘጋው

**zipper** ዚፐር
The zipper on my jacket is broken. የጃኬቴ ፡ ዚፐር ፡ ተበላሽቷል

**zither** [ከሠላሳ ፡ እስከ ፡ አርባ ፡ ክሮች ፡ ያሉት ፡ በጣት ፡ የሚመታ ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ]

**zodiac** [በሐሳብ ፡ እኩል ፡ በሆኑ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ የተከፈለ ፡ የሰማይ ፡ መቀነት]

**zone** (v.)
1. ከፈለ. They zoned the city into five voting districts. ከተማውን ፡ ባምስት ፡ የምርጫ ፡ ወረዳ ፡ ከፈሉት
2. ከለለ. They zoned the east of the city as a residential area. የከተማውን ፡ የምሥራቅ ፡ ክፍል ፡ የመኖሪያ ፡ ሰፈር ፡ አድርገው ፡ ከልለዋል

**zone** (n.)
1. ክልል. This is a 25 mph. traffic zone. ይህ ፡ ከሃያ ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ በላይ ፡ የማይነዳበት ፡ ክልል ፡ ነው
2. የግዛት ፡ ክልል. The Russians would not let anyone in their zone. ሩሲያውያን ፡ በግዛት ፡ ክልላቸው ፡ ውስጥ ፡ ማንንም ፡ አያስገቡም
3. ክበብ. In the frigid zone, plants cannot grow. በዓለም ፡ የበረዶ ፡ ክበብ ፡ ዕፀዋት ፡ አይበቅሉም

**border zone** የድንበር ፡ ክልል
No one is allowed in the border zone without a pass. በድንበሩ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ያለፈቃድ ፡ መግባት ፡ ለማንም ፡ አይፈቀድም

**zoo** የእንስሳት ፡ ማኖሪያ ፤ የአራዊት ፡ መጠበቂያ
The lions in the zoo are roaring. በእንስሳት ፡ ማኖሪያ ፡ (በአራዊት ፡ መጠበቂያ) ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ አንበሶች ፡ ያገሣሉ

**zoology** ዙኦሎጂ
Zoology teaches us about animal life. ዙኦሎጂ ፡ ስለ ፡ እንስሳት ፡ ሕይወት ፡ ያስተምራል

**zoom** እያጕረመረመ ፡ በረረ
The airplane zoomed through the air. አውሮፕላኑ ፡ እያጕረመረመ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ በረረ

**zoom past one** ሽው ፡ ብሎ ፡ አለፈ
The cars zoomed past me. መኪናዎቹ ፡ ሽው ፡ ብለው ፡ አለፉኝ

**zoom up** በድንገት ፡ መጠቀ
The airplane zoomed up. አውሮፕላኑ ፡ በድንገት ፡ መጠቀ